https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ስልጣን የሰራተኛ ቅነሳ ጉዳይን በሚመለከት ስለሚነሳ ክርክር /የኬኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ ሰራተኛ ማህበር እና የኬኬ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ/.....1
2. በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍርድ ቤቱ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ /ጳውሎስ ሩምቾ እና ጫልቱ መርዳሳ/..... 9
3. በስነ-ሥርዓት ህጉ የጊዜ ገደብን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎች ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ተፈፃሚ ስለማድረጉ (ጋዲሴ ኢረጌ እና ወርቅ አንጥፉ በቀለ) 12
4. ተገቢው ዳኝነት ክፍያ ሳይፈጸም በፍ/ቤት በቀጠለ ክርክር ስለሚፈፀም ስርዓት (ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የነገው ሰው ትምህርት አክስዮን ማህበር)..... 17
5. በመጓጓዝ ላይ የነበሩ ዕቃዎች በጉዳት በሰው ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን የግጭት አደጋ ለማስወገድ በተወሰደ ርምጃ የደረሰ የመኪና መገልበጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ስላለመሆኑ (የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና እነ ኮሜት ትራንስፖርት ድርጅት)..... 24
6. በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍርድ ቤቱ የሕግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ /የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና በሮኒ አቲክፖ/..... 31
7. አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ባቀረበው ክስ ወካዩን ወክሎ መከራከር ስላለመቻሉ (ማህሌት ገ/ስላሴ እና እነ መንግሥቱ ኃብቴ) 41
8. ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት (ውርጌሣ ታደሰ እና እነ መለሰ ተካ) 47
9. በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍርድ ቤቱ በህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ /ዶ/ር ዳንኤል አለሙ እና እነ ሮማን ወርቅ የማነብርሃን/ 55
10. ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የከሣሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት (ሼህ ኢትዮጵያ አ/ማ እና አስቴር ብርሃነስላሴ) 60

https://t.me/ethiopianlegalbrief

11. በህግ የተደነገገው የውል አፃፃፍ /ፎርም/ የተሰጠ ደንብ አለመፈጸም ስለማያስከትለው ውጤት /የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ሶስና አስፋው/ 66
12. በአንዳንድ ውሎች የተመለከተ የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለመቀነስ ፍርድ ቤት ስላለው ስልጣን /አስቱር አርአያ እና ግርማ ወዳጆ/ 75

Daniel fikadu law office
0913158507

Daniel fikadu law office
0913158507

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 18180

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኬ.ኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ የሰራተኞች ማህበር
መልስ ሰጪ፡- የኬ.ኬ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ

ስለ ስራ ክርክር- የስራ ክርክር ችሎቶች ሰልጣን - የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሰልጣን /የሰራተኞች ቅነሳ ጉዳይ በሚመለከት የሚነሳ የስራ ክርክር ስማየት/ -የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 138/1/፣ 147

አመልካች በሰራተኛ ማህበራችን አማካኝነት የተወሰደብን የቅነሳ እርምጃ ህገ ወጥ በመሆኑ የተቋረጠብን ክፍያ ተሰጥቶን ወደ ስራችን እንመለስ በማለት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያቀረቡትን ጥያቄ ቦርዱ በመቀበል የተደረገው ቅነሳ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 28 እና 29 ድንጋጌዎችን የሚጥስ በመሆኑ አመልካቾች ወደ ስራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ከስልጣኑ ውጭ የሰጠው ነው በሚል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለሻረው የቀረበ አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ ፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የመዳኘት ስልጣን የተሰጠው የወል የስራ ክርክር ጉዳዮችን የሚመለከቱ ክርክሮችን ሲሆን የስራ ክርክር ችሎቶች ደግሞ የግል የስራ ክርክሮችን እንዲዳኙ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡
2. ህጉ የስራ ክርክር ጉዳዮችን የወል ወይም የግል ብሎ ለመለየት የተከራካሪ ሰራተኞችን ቁጥር እንደ መስፈርት መውሰድ እንዳለበት አያመላክትም፡፡
3. ከአጠቃላይ የህጉ መንፈስ እና ድንጋጌዎች በመነሳት አንድ የስራ ክርክር ጉዳይ የወል ነው የሚባለው ጉዳዩ በጋራ የሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊ ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሲሆን አንድን የስራ ክርክር ጉዳይ የግል የሥራ ክርክር ጉዳይ የሚያደርገው ደግሞ ጉዳዩ ከግል አልፎ በጋራ መብት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የሌለ እንደሆነ ነው፡፡
4. የሰራተኛ ቅነሳ ጉዳይ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው በመሆኑ የወል የስራ ክርክር ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩን የማየት ስልጣንም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ነው፡፡
5. የአሰሪና ሰራተኛ ፍ/ቤት ቦርዱ የህግ ስህተት ፈጽሟል ብሎ ሲያምን ጉዳዩን ከመመሪያ ጋር ወደ ቦርዱ ከመመለስ አልፎ የቦርዱ ውሳኔ መሻር አይችልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኬኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መ/ስ/ማ /56/ ሰዎች ወኪል ሰይድ ሀሚድ ቀረበ

ተጠሪ፡- የኬኬ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገቡ የተያዘው ክርክር ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የተጀመረ ነው፡፡ ጉዳዩ አሠሪ የሆነው የአሁን ተጠሪ ሠራተኛ በሆኑት በአሁን አመልካቾች ላይ የወሰደውን የቅነሣ እርምጃ የሚመለከት ነው፡፡

አመልካቾች በሠራተኛ ማኅበራቸው አማካኝነት የተወሰደብን የቅነሣ እርምጃ ሕገ ወጥ በመሆኑ የተቋረጠብን ክፍያ ተሰጥቶን ወደ ሥራችን እንመለስ ሲሉ በተጠሪው ላይ ክስ መስርተዋል፡፡ ተጠሪም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የቅነሣውን ተገቢነት ይገልጻል የሚለውን መልስ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት ቦርድ ደግሞ የተደረገው ቅነሣ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 28 እና 29ን የሚጥስ በመሆኑ አመልካቾቹ በአንቀጽ 42/2/ መሠረት ወደ ሥራቸው ሊመለሱ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ከዚህ ውሣኔ ላይ በተጠሪ አማካኝነት በመ/ቁ.30769 ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ቦርዱ ይህን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ክፍ ሲል የተጠቀሰውን የቦርዱን ውሣኔ ጥቅምት 25/1997 ዓ.ም ሽሮታል፡፡

በመቀጠል አመልካቾች ይህ የፍ/ቤቱ ውሣኔ የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 147/2ን እና 154/2ን የሚጥስ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነውና ይሻርልን በማለት አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም የቀረበው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም የሚልበትን ምክንያት የሚዘረዝር መልስ አቅርቦ ተከራክሯል።

ይህም ችሎት ክርክሩን ሊያስነሣ በቻለው አወዛጋቢ የህግ ነጥብ ላይ ብቻ በማተኮር መገዝቡን መርምሯል። በዋነኛነት ሊፈቱ የሚገባቸው የነገሩ ጭብጦችም፡-

1ኛ. የሠራተኛ ቅነሣን አስመልክቶ የቀረበውን የህን ክርክር የመዳኘት ሥልጣን የማነው? የፍርድ ቤት ነው? ወይስ የቦርድ?

2ኛ. ፍ/ቤት በቦርድ የተሰጠን ውሣኔ ለመሻር ሥልጣን አለው? የሚሉት መሆናቸውን ተገንዝቧል።

ለመጀመሪያው ነጥብ ምላሽ የማግኘቱ ጉዳይ ስለ ሠራተኛ ቅነሣ፣ ስለ ቦርድ እና ስለ ፍርድ ቤት ሥልጣን የሚገልጹትን የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎችን ተመስርቶ ጭብጡን መመርመርን ይጠይቃል። ቦርድ ሊቀርቡ የሚገባቸው ጉዳዮች ፍ/ቤት ሊቀርቡ ከሚገባቸው የሚለዩበትን ምክንያት መረዳትን ይፈልጋል። በዚህ ረገድ ግንዛቤ እንድናገኝ የሚያደርገን ደግሞ ስለ ቦርድ ሥልጣን የሚደነግገው የአዋጅ ቁ.147/1/ እና ስለ ፍ/ቤት ስልጣን የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 138/2/ ይሆናል።

ስለ ቦርድ ሥልጣን ከተደነገገበት የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 147/1/ ውስጥ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሚኖረው በንዑስ አንቀጽ /1/ /ሀ/ ላይ ቦርዱ በአንቀጽ 142/1/ ላይ የተመለከቱትን የሥራ ክርክሮች የመዳኘት እና ተከራካሪዎቹን የማስታረቅ ሥልጣን አለው በሚል የተመለከተው የሕጉ ክፍል ነው። እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች ተጣምረው ሲነበቡ ቦርዱ በአንቀጽ 142/1/ ስር በተዘረዘሩትና በሌሎች የወል የሥራ ክርክሮች ላይ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን እንደተሰጠው መገንዘብ ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ በአዋ አንቀጽ 138/1/ የተዘረዘሩትንና መሰል የግል የሥራ ክርክሮችን የመዳኘት ሥልጣን ለፍ/ቤት መስጠቱን ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል።

የወል የሥራ ክርክሮች ለቦርድ፤ የግል የሥራ ክርክሮች ደግሞ ለፍ/ቤት የሚቀርቡ ናቸው ማለት ብቻውን ግን ሁለቱ ተቋማት በዚህ ረገድ ያላቸውን የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል በግልጽ እንድንለየው የሚያደርገን አይደለም። ይልቁንም የወል የሥራ ክርክር ማለት ምን ማለት ነው? የግል የሥራ ክርክር ማለትስ ምን ሊሆን ይገባል? የሥራ ክርክሮችን በምንና እንዴት የወል ወይም የግል የሥራ ክርክር ብለን ልንመድባቸው እንችላለን? የሚሉና ሌሎችንም መሰል ጥያቄዎችን እንድናነሣ የሚያደርገን ነው። ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠታችን ደግሞ የሚቀርቡ የሥራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ክርክሮችን ከየትኛው እንደምንፈርጃቸው የሚያመለክተንና በዚህ ተጨባጭ ጉዳይ ለተያዘውም የመጀመሪያ ጭብጥ መፍቻ እንድናገኝለት የሚረዳን ነው።

ስለ የወል እና የግል የሥራ ክርክር አይነቶች

የአዋጅ ቁ.42/85 ለወልም ሆነ የግል የሥራ ክርክር የሰጠው ትርጓሜ የለም። የሥራ ክርክር በዚህ አዋጅ የተተረጎመ ቢሆንም ትርጓሜው የወልና የግል የሥራ ክርክርን እንድንለይ የሚያስችለን አይደለም። ስለሆነም በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት በግርድፉ ለማስቀመጥ ሌላ መለኪያ እንድናበጅ የሚጠይቀን ነው።

እንደሚታወቀው ከአሠሪ ጋር የሚደረግ የሥራ ክርክር በሠራተኞች ማኅበር ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሠራተኞች ወይም በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚካሄድ ነው። የወል የሚለው ቃል አገላለጽ የጋራ የሆነ ጉዳይ መኖሩን ለማመልከት ያህል የሚበቃ መሆኑም እርግጥ ነው። ይሁን እንጂ የወሉን ከግል ለመለየት የተከራካሪዎቹን ሠራተኞች ቁጥር እንደመለያ መስፈርት መውሰድ እንደምንችል የሚጠቁመን የሕግ ድንጋጌ የለም። ይህ ደግሞ ሕጉ ሁለቱን ክርክሮች ለመለየት የፈለገበትን ሌላ መንገድ እንድንፈትሽ ያደርገናል። ለዚህም ሁለቱ የክርክር አይነቶች በምሣሌነት በተናጥል የተዘረዘሩበትን የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 142/1/ን እና 138/1/ን መሠረት ማድረጉ አሣማኝነት ያለው መደምደሚያ ላይ እንድንደርስ ይጠቅመናል።

አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 142/1/

ሀ. ስለደመወዝና ሌሎች ጥቅሞች አወሳሰን፣

ለ. አዲስ የሥራ ሁኔታዎችን ስለመመስረት፤

ሐ. የሕብረት ስምምነት ስለመዋዋል፣ ስለማሻሻል፣ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና ስለሚፈርስበት፣

መ. አዋጁን፣ የሕብረት ስምምነት ወይም የሥራ ደንብ ድንጋጌዎችን በሚመለከት የሚነሣ የትርጉም ክርክር፣

ሠ. ስለሠራተኛ አቀጣጠርና እድገት አሰጣጥ ሥርዓት፣

ረ. አጠቃላይ ሠራተኞችንና የድርጅቱን ሕልውና የሚነኩ ጉዳዮች፣

ሰ. ዕድገት ዝውውር እና ሥልጠናን በሚመለከት አሠሪው በሚወስዳቸው እርምጃዎች ምክንያት የሚቀርቡ ክሶች፣

ሸ. የሠራተኞች ቅነሣ እና የመሳሰሉት የሥራ ክርክሮች የወል የሥራ ክርክሮች መሆናቸውን ደንግጓል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደዚሁም አብዛኛዎቹ የድንጋጌው ከፍሎች በውጤታቸው የሁሉንም ሠራተኞች መብትና ጥቅም የሚመለከቱ ጉዳዮችን ያቀፉ መሆናቸውን በግልጽ አመላክተውናል። ለምሣሌነት በንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/፣ /ለ/፣ /ሐ/፣ /ሠ/፣ /ረ/ እና /ሸ/ የተጠቀሱትን የሥራ ክርክር አይነቶች መመልከት ይቻላል። እነዚህ የድንጋጌው አብዛኛው ንዑስ አንቀጾች ክርክሩ የወል ለመባል የጋራ የሆነን የሠራተኞቹን መብትና ጥቅም የሚመለከት ሲሆን እንደሚገባ በግልጽ ካሣዩን ደግሞ በቀሪዎቹ ንዑስ አንቀጾች ላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም በድንጋጌው ያልተካተቱትን ተመሳሳይ የሥራ ክርክሮችን የወልነት ፀባይ ከሠራተኞቹ የጋራ መብትና ጥቅም ጋር ካለው ግንኙነት አኳያ ልንመዝነው የሚገባን ይሆናል። ስለሆነም ጥያቄው የደመወዝም ሆነ የሥልጠና፣ የሕግ ትርጉም ነክም ሆነ ወይም ሌላ የወል የሚሰኘው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሊሆን ይገባዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 138/1/

ሀ. ከሥራ ማስወጣትን ጨምሮ ሌሎች የዲሲፕሊን እርምጃዎችን የሚመለከቱ ክሶች፣

ለ. የሥራ ውል መቋረጥ ወይም መሰረዝን የሚመለከቱ ክሶች፣

ሐ. የሥራ ሰዓትን፤ የተከፋይ ሂሳብን፤ ፈቃድንና እረፍትን የሚመለከቱ ክሶች፣

መ. የቅጥር ማስረጃ ሠርቲፊኬት መስጠትን የሚመለከቱ ክሶች፣

ሠ. የጉዳት ካሣን የሚመለከቱ ክሶች እና

ረ. በአዋጁ መሠረት የሚቀርብ ማንኛውም የወንጀልና ደንብ መተላፍ እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች የግል የሥራ ክርክሮች መሆናቸው ተደንግጓል። የዚህ ድንጋጌ ይዘት ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ድንጋጌ የጋራ የሆነን የሠራተኞች ጉዳይ እንደሚያጠቃልል የሚገልጽ አይደለም። ስለሆነም ሥራ ክርክሩ በእነዚህ በተዘረዘሩትም ሆነ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ ሲቀርብ ከግል አልፎ በጋራ መብት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ያለመኖሩ ጉዳይ ክርክሩን የወል ሳይሆን የግል የሥራ ክርክር እንዲሆን ያደርገዋል።

እንግዲህ አንድ የሥራ ክርክር በአንድ ወይም በብዙ ሠራተኞች መቅረቡ ጉዳዩ የወል ወይም የግል የሥራ ክርክር መሆኑን የሚያረጋግጥልን አይደለም። ይልቁንም ክርክሩ የወል መሆኑን የሚያሳየን ውጤቱ ከግል አልፎ የሠራተኞቹን የጋራ መብትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ጥቅም የሚነካ የመሆኑ ጉዳይ ሲሆን ክርክሩ የግል ነው የምንለው ደግሞ ውጤቱ በተከራካሪው ሠራተኛ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ ስናገኘው ነው።

ወደ ጭብጣችን ስንመለስ አመልካቾች ተጠሪው የቅነሣ እርምጃ ለመወሰድ የሚያስችል ምክንያት የለውም፤ ቅነሣውም በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 29 የተመለከተውን ቅደም ተከተል ያከበረ አይደለም በሚል አይነት መሟገታቸውን ያሳየናል። እንደሚታወቀው የሠራተኞች ቅነሣ መላውን የድርጅቱን ሠራተኞች ከግምት በማስገባት በሕግ አግባብ ሊከናወን የሚገባ ተግባር ነው። ቅነሣው ህግን ተመስርቶ አለመደረጉን አሳያለሁ በሚል ሁኔታ የሚቀርብ አቤቱታም በውጤቱ ሁሉንም ሠራተኞች የሚመለከት መሆኑ የሚታመን ነው። የአመልካቾች ክርክር ደግሞ በዚህ መልኩ የቀረበ መሆኑ ከፍ ሲል ተመልክቷል። ስለሆነም ጉዳይ የወል እንጂ የግል የሥራ ክርክር የሚሰኝበት ምክንያት አይኖርም። ክርክሩን የመዳኘቱ ሥልጣንም በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 142/1/ /ሸ/ መሠረት የቦርድ እንጂ የፍ/ቤት አይሆንም።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠ መሆኑን ምክንያት በማድረግ የቅነሣውን ህጋዊነት የመመርመር ሥልጣን የፍ/ቤት ነው ሲል ወስኗል። ይሁን እንጂ ከፍ ሲል እንደተገለፀው አንድ የሥራ ክርክር በቦርድ ወይም የግል የሥራ ክርክር መሆኑ እንጂ የሥራ ውሉ የመቋረጥ ወይም ያለመቋረጡ ጉዳይ አይደለም። ስለሆነም ፍ/ቤቱ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው ምክንያትም ከሕጉ ጋር የሚጣጣም አልሆነም።

በሁለተኛው ደረጃ የተያዘው ጭብጥም አግባብነት ከአለው የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 154/2/ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል። በዚህ ድንጋጌ የቦርድ ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበትና የሕግ ስህተቱም የውሣኔውን ውጤት አዛብቶት የተገኘ እንደሆነ ይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ከዝርዝርና ከአጠቃላይ መመሪያ ጋር ለመጨረሻ ውሣኔ ወደ ቦርድ እንደሚመልሰው፤ ነገር ግን የቦርዱን ውሣኔ ለመሻርም ሆነ ለማሻሻል እንደማይችል ተደንግጓል።

በእርግጥ በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቦርዱን ውሣኔ እራሱ መሻሩ የውሣኔ አሰጣጡ ከተጠቀሰው ሕግ ጋር አለመጣጣሙን ያሳያል። ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ የቦርዱን ውሣኔ የሕግ ስህተት ለማረም እንዲችል በዚሁ ሕግ ሰፊ ሥልጣን ተሰጥቶታል። ውሣኔውን በይግባኝ ሊሽረውም ሆነ ሊያሻሽለው ባይችልም የሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ስህተቱ ታርሞ በጉዳዩ እንደገና ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ክርክሩን ወደ ቦርድ እንዲመልሰው ሕጉ በግልጽ ፈቅዶለታል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቦርዱን ውሣኔ እራሱ ለመሻር ሥልጣን የሌለው በመሆኑ የፍርድ አሰጣጡ ከተጠቀሰው ህግ አግባብ ሊቃና የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1ኛ. ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው የሠራተኛ ቅነሣ የወል የሥራ ክርክር በመሆኑ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የቦርድ እንጂ የፍርድ ቤት ሊሆን አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡

2ኛ. ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ተገንዝቦ ወደ ክርክሩ በመግባትና በቦርዱ የተሰጠው ፍርድ ከሕግ አኳያ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን በመመርመር ጉዳዩ ከመመሪያ ጋር ወደ ቦርድ ሊመለስ የሚገባው መሆን አለመሆኑ ረገድ ውሣኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለትም ተወስኗል፡፡

3ኛ. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ማየት እንዲቀጥል ያስችለው ዘንድም ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343/1/ መሠረት ተመልሶለታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 15493

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አበዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ጳውሎስ ሩምኾ

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ

የውል ግዴታዎች መቅረት - ስለ ይርጋ - የውልን ጉዳይ ስለሚመለከት ማስረጃ- ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥሩ የህሊና ግምቶች - የፍትሐብሔር ህግ ቁጥሮች 1845፣ 2024

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው የጥብቅና አበል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 /ለ/ መሠረት እንደተከፈለ ስለሚቆጠር የሥር ተከሣሾች በአመልካች የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ሌሎች ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ

ውሳኔ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

1. የሐሊና ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ደንብ ድንጋጌዎች የተለዩ ናቸው፡፡
2. በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 በተደነገገው የሕግ ግምት ተጠቃሚ ያልሆነ ወገን /ተከሣሽ/ ከፍያውን በከፊል መክፈሉ ግምቱን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025 /1/ መሠረት ቀሪ አያደርግም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም

የመ/ቁ.15493

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ጳውሎስ ሩምኾ

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ

ፍርድ

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው የጥብቅና አበል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ለ/ መሠረት እንደተከፈለ ስለሚቆጠር የሥር ተከሣሾች በአመልካች የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ሌሎች ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በመሻሩ ነው፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመወሰኑ መልስ ሰጪም በጉዳዩ ላይ ያላትን የጽሁፍ መልስ አቅርባለች፡፡

አመልካች የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል የሚለው /1/ ከጥብቅና አበሉ ውስጥ የመጨረሻ ክፍያ የተፈፀመው ሰኔ 1990 ዓ.መ በመሆኑ ክስ እስከቀረበበት ታህሣሥ 18 ቀን 1992 ዓ.ም በፍትሐብሄር ሕግ ቁ.2024 /ለ/ የተጠቀሰው የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ አላለፈም /2/ መልስ ሰጪዎች ከፊል ዕዳውን በመፈፀማቸው ዕዳውን እንዳመኑ ስለሚቆጠር በ2024 የተቀመጠው የህግ ግምት በ2025/1/ መሠረት ቀሪ ሆኖአል፡፡ /3/ የጥብቅና ውሉ በጽሁፍ የተደረገ በመሆኑ የይርጋ ጊዜው መታሰብ ያለበት በ10 ዓመት እንጂ በ2024 መሠረት በሁለት ዓመት አይደለም የሚሉትንና ሌሎችንም ተመሳሳይ ክርክሮች በማቅረብ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ እንዲፀናላት ጠይቃለች፡፡

አመልካች በመልስ ሰጪ ላይ ጥር 1 ቀን 1992 ዓ.ም ክስ የመሰረተው ጥቅምት 7 ቀን 1988 ዓ.ም በአመልካችና በመልስ ሰጪ መካከል የተመሰረተውን የጥብቅና አገልገሎት ውል መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት ተዋዋዮቹ በውላቸው ላይ ለጥብቅና ውሉ ምክንያት የሆነው ቤት መልስ ሰጪ እጅ በገባ በሁለት ወር የጥብቅና ክፍያ መጠናቀቅ እንዳለበት ስለሚገልጽና ቤቱ ሕዳር 1988 መልስ ሰጪ እጅ የገባ በመሆኑ ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ክስ በቀረበበት ጊዜ ከሁለት ዓመት በላይ ስለሆነው በ2024 መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል ብሏል፡፡

ለዚህ ለሰበር ለቀረበው ጉዳይ ምክንያት የሆነው ዕዳ መከፈል ከነበረበት ሁለት ዓመት በላይ እንደሆነው በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጦአል፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት በሁለት ዓመት ውስጥ ያልተከፈለ ዕዳ እንደተከፈለ እንደሚቆጠር በዚህ ሰበር ችሎት በመ.ቁ.17068 ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ የጥብቅና አበል ክፍያን የሚመለከተው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/ለ/ም አንዱ የድንጋጌው አካል በመሆኑ በተጠቀሰው ትርጓሜ መሠረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው፡፡ ስለዚህ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ የፈፀመው የህግ ስህተት የለም፡፡ አመልካች የሕግ ግምትና የይርጋ ህግን በማመሳሰል ጉዳዩ በፍ.ብ.ሕ.ቁ.1845 እንዲታይለት ቢጠይቅም የተያዘው ጉዳይ የክፍያ ግምት እንጂ የይርጋ ጉዳይ ባለመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም፡፡ የክፍያ ግምት ውሉ በጽሁፍ የተደረገ ሲሆን ተፈጻሚ አይሆንም የሚል ህግ ባለመኖሩ አመልካች ውላችን በጽሁፍ ስለሰፈረ 2024/ለ/ ተፈጻሚ ሊሆንብኝ አይገባም ያለው ተቀባይነት የለውም፡፡ መልሰ ሰጪ በከፊል የጥብቅና አበል መክፈላቸውም ቢሆን አሁን ክስ የቀረበበትን ቀሪውን የጥብቅና አበል ማመናቸውን አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የሕጉን ግምት ተፈጻሚነት በ2025/1/ መሠረት ቀሪ ለማድረግ በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ በመሆኑም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበት ብር 71,000 /ሰባ አንድ ሺህ/ ሁለት ዓመት ካለፈው በኋላ የተጠየቀ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024/ለ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ መሻሩ ሕጉን በትክክል ተፈፃሚ ማድረጉን እንጂ የህግ ስህተት መፈፀሙን አያመለክትም፡፡

ው ሳ

ውሣኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁ.00253 በ20/7/96 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 17361

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጋዲሴ ኢርጌ
መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ወርቅአንጥፉ በቀለ

በከሣሽነት ወይም ተከሣሽነት በሙግት ተካፋይ ሰለመሆን - ሰለተከራካሪ ወገን መሞትና ሰለክሱ ያለመቋረጥ - ሰለ ጊዜ አወሳሰንና አቆጣጠር- የፍትሐበሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 49 - ሰለ ግዴታዎች መቅረት - ሰለ ይርጋ - የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1856

አመልካች ከስር ከሳሽ የነበረችውን ወ/ሮ ብሪቱ ብሩን ተክታ ለመከራከር ያቀረበችው ጥያቄ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 49 የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ጥያቄዋን ውድቅ በማድረጉ እና የፊደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ባለመቀበሉ መልስ ሰጭ ባነሳችው ክርክር ፍርድ ቤቶቹ ክሱን ውድቅ በማድረጋቸው የቀረበ አቤቱታ

<u>ው ሳ ኔ፡-</u> የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ጸንቷል፡፡

1. በሥረ ነገር /Substantive/ ህጎች የተደነገጉ የይርጋ ደንቦች በሥነ ሥርዓት ሕጎች ከተደነገጉት የጊዜ ገደቦች የተለዩ ናቸው፡፡
2. በስነ ስርዓት ህጎች በግልጽ የሰፈረን ጊዜ ሳይጠብቅ የሚቀርብን ጥያቄ ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ/ቁ. 17361

ሐምሌ 25 ቀን 1997 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጋዲሴ ኢርጌ
መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ወርቅአነጥፉ በቀለ

ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የተመለከቱ የሥነሥርዓት ደንቦች አፈጻጸምን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ ሊቀርብ የበቃው አመልካች ከስር ከሣሽ የነበረችውን ወ/ሮ ብሪቱ ብሩን ተክታ ለመከራከር ያቀረበችው ጥያቄ የሥር ፍርድ ቤት በፍትሀብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 49 የተጠቀሰውን የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ መሆኑን በመግለጽ ጥያቄዋን ውድቅ በማድረጉ ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ ዋነኛ የቅሬታ ነጥብም ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 49(2) የተጠቀሰውን የጊዜ ገደብ ማንም ተከራካሪ ወገን ሳያነሳው ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሣሽነት ተፈጻሚ ማድረጉ ሕጉ ይርጋን በማስመልከት ያስቀመጠውን ሥርዓት የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ ይሻልኝ የሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ ጉዳዩ በሰበር እንዲታይ በመወሰኑ መልስ ሰጪ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡ የመልሱ መሠረታዋ ይዘት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ምንም የሕግ ስህተት ሰለሌለበት ሊፀና ይገባዋል የሚል ነው፡፡ አመልካቿ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡ ይዘቱ ከሰበር ማመልከቻው የተለየ አይደለም፡፡

በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱተ በሥረ ነገር ሕጎች /Substantive Laws/ የተደነገጉ የይርጋ ደነቦች በሥነሥርዓት ሐጎች ከተደነገጉት የጊዜ ገደቦች ጋር ተመሳሳይ ናቸው ወይስ አይደሉም? በሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ የሚገኙትን የጊዜ ገደቦች ፍርድ ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት ተፈጻሚነታቸውን ሊከታተሉ ይችላሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ወይስ እንደሥረነገር የይርጋ ህግ በተከራካሪ ወገን ካልተነሱ እንደተተው ይቆጠራል የሚሉትን የሕግ ነጥቦች የማያስነሳ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ መረዳት እንደቻልነው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ቀደም ብላ ክስ መስርታ የነበረችውን ወ/ሮ ብሪቱ ብሩን ተክታ የፍትሐብሄር ክሱን በወራሽነት እንድትቀጥል ያቀረበችውን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ጥያቄው የቀረበው የፍትሀብሄር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 49 እንደሚያዘው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አልቀረበም በማለት ነው፡፡

የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 49(1) ከሣሽ ሲሞቱ የክሱ መብት ለሌላ የሚተላለፍ የሆነ እንደሆነ የሟቹ ንብረት አስተዳዳሪ ተተክቶ ክሱን ሊቀጥል እንደሚችል የሚፈቅድ ሲሆን የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት #ክሱን ለመቀጠል መብት አለን የሚሉት ወገኖች ዋናው ከሣሽ ወይም ከሣሾች በሞቱ በአንድ ዓመት ውስጥ ክሱን ለመቀጠል እንዲፈቀድላቸው ሳያመለክቱ የቀሩ እንደሆነ የተጀመረው ክርክር ውድቅ ይሆናል; በማለት ይደነግጋል፡፡

የፍትሀብሔር ሥነሥርዓት ሕግ የሙግትን ሂደት ለመከታተል የሚያስችሉ የተለያዩ የጊዜ ገደቦችን አስቀምጧል፡፡ ይኸው ሕግ ያስቀመጣቸውን የጊዜ ገደቦች አፈጻጸም በሚመለከትም በሥነሥርዓት ሕጉ ምዕራፍ ሰባት በርካታ ድንጋጌዎችን አስፍሮአል፡፡ የሕጉ ቁጥር 192 #በአንድ ክርክር ላይ መፈፀም ወይም መደረግ የሚገባው ነገር ሲኖርና ይህም የሚፈፀምበት ጊዜ በሕግ ያልተወሰነ ሲሆን የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የሚተየውን ጊዜ ይወስናል; በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሙግት ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት በሕግ በተቀመጠው አሊያም ፍርድ ቤቱ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን የሚጠበቅባቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ የዚሁ ሕግ ቁጥር 195 #በዚህ ሕግ በቁጥር 196 የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ነገር እንዲፈፀም ከተወሰነው ጊዜ በኋላ ቢፈፀምም እንዳልተፈፀመ ሆኖ ይቆጠራል; በማለት በተወሰነ የጊዜ ገደብ መፈፀም ያለባቸው ተግባራት ሕጉ ወይም ፍ/ቤቱ ባስቀመጠው ጊዜ ውስጥ ከተከናወኑ ብቻ ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ የሥነ ሥርዓት ሕጎች ዋነኛ ዓላማ ለፍ/ቤት የሚቀርቡ ክርክሮች ባነሰ ወጪ በተቀላጠፈና ፍትሃዊ በሆነ ሥርዓት እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በሥነሥርዓት ህጎች የሰፈሩ የጊዜ ገደባች አፈጻጸም በአንድ ጉዳይ ካሉት ተከራካሪዎች ባሻገር የሌሎች ተከራካሪዎች ጥቅም፣ በፍርድ ቤት መኖር

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ያለበትን የሙግት አመራርና አጠቃላይ የሀብትና የጊዜ አጠቃቀምን የሚመለከቱ ናቸው። የጊዜ ገደቦች አለመከበር ለመዘግየት፣ ለጉዳዮች መከማቸትና መጨናነቅ ምክንያትም ስለሚሆን የሚጎዳው በአንድ ሙግት የሚሳተፉትን ብቻ ሳይሆን የሌሎች የፍርድ ቤት ተጠቃሚዎች መብትና ጥቅምም ይነካል። ይህ ሁኔታ እንዳይፈጠር የሙግት ሂደት ሥርዓት እንዲይዝ ማድረግ ደግሞ ከተከራካሪዎችም የሚጠበቅ ቢሆንም በዋናነት ግን የፍርድ ቤቱ ሃላፊነት ነው። ይህን ሃላፊነት እንዲወጣ ከሚያደርጉት መንገዶች አንዱ ደግሞ በሠነ ሥርዓት ሕጉ የሰፈሩት የጊዜ ገደቦች በአግባቡ መፈፀማቸውን መከታተልና ያልተፈፀሙ ሆነው ሲገኙ ደግሞ ህጉ እንደሚያዘው ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ መውሰድ ነው።

በሥነሥርዓት ሕጉ የሰፈሩ ጊዜን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ይርጋን አስመልክቶ በፈትሀብሄር ሕግ ቁጥር 1856/2/ ከሰፈረውና የይርጋ ጉዳይ በተከራካሪዎች ካልተነሣ በፍርድ ቤት አይነሳም ከሚለው ሕግ የተለየ ነው። በፍትሐብሔር ሕግ የሰፈረው የይግርጋ ሕግ ዋነኛ ዓላማ የተዋዋዮችን ጥቅም መጠበቅ ነው። የዚህ መብት ተጠቃሚ የሆነ ተከሣሽ ይርጋውን ካላነሣም የሚጎዳው እሱ ብቻ ነው። ስለሆነም ተዋዋይ ወገን የተወውን መብት ፍርድ ቤት በራሱ አነሣሽነት እንዲያነሣው አይፈቀድም። በሥነሥርዓት ሕጉ የተቀመጡ የጊዜ ገደቦች መከበር አለመከበራቸውን ግን ፍርድ ቤቱ የመከታተል ሃላፊነት አለበት። በተከራካሪ ወገን ባይነሣ እንኳን በሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 195 እንደተደነገገው ጊዜው ካለፈ በኋላ የተከናወነው ነገር ሁሉ እንዳልተፈፀመ ሆኖ ስለሚቆጠር የሥነሥርዓት የጊዜ ገደቦች ተሟጋቾችን ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱንም ጭምር የሚመለከቱ ናቸው። በመሆኑም በሥነሥርዓት ሕጉ በግልጽ የሰፈረው የጊዜ ገደብ ካለኝ በኋላ የሚቀርብን ማንኛውንም ጉዳይ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረጉ ትክክለኛው አካሄድ ነው።

አሁን በቀረበልን ጉዳይ የአሁኗ አመልካች ጥያቄዋን ለፍርድ ቤቱ ያቀረበችው የቀድሞዋ ተከራካሪ የወ/ሮ ብሪቱ ብሩ ወራሽ መሆንዋን ካረጋገጠች ከ3 ዓመት በኋላ ነው። ከመዝገቡ ለመረዳት እንደተቻለው የወራሽነት ውሣኔ ያገኘችው ሐምሌ 15/91 ሲሆን ለፍርድ በቱ ጥያቄዋን ያቀረበችው ደግሞ ጥር 20/1994 ነው። ይህም የሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 49 ያስቀመጠው የአንድ አመት የጊዜ ገደብ ማለፉን የሚያረጋግጥ ነው። በሕግ የሰፈረውን ጊዜ ገደብ ያልጠበቀ ነገር የተሟጋችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ተቃውሞ ሳየጠብቅ ፍርድ ቤቱ ራሱ ውድቅ ማድረጉ ደግሞ ትክክለኛ የጉዳይ አመራር እንጂ ስህተት መፈፀሙን የሚያመለክት አይደለም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 20576 ግንቦት 1 ቀን 1975 የሰጠው ውሣኔ እና ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 22451 ሐምሌ 21 ቀን 1996 የሰጠው ውሣኔ ፀንተዋል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 17352

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አበዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር
መልስ ሰጭ፡- የነገው ሰው ትምህርት አ/ማ

ሰዳኝነት ስለሚከፈል ገንዘብ - ክስን ስርዓት ውጭ ስለሚቀርብ ክስ /የግሳኝ/ - የፍትሐበሐር ሥነሥርዓት ሀግ ቁጥሮች 215፣ 320/2/፣ 207፣ 211/2/

አመልካች ከስር ፍ/ቤት በመ/ሰጭ እንዲከፍለው የጠየቀው ወለድ በመ/ሰጭ ሊከፈለው የማገባ ቢሆንም አመልካች ክሱን ሲያቀርብ ለወለድ ጥያቄው የዳኝነት ክፍያ ያልከፈለ በመሆኑ ወለድን በሚመለከት ያቀረበው ጠያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመወሰኑና ከዚህ አንፃር የቀረበውን መስቀለኛ ይገባኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤተ ውድቅ ስላደረገው የቀረበው አቤቱታ

ው ሳ ኔ፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ የወለድ ክፍያን በሚመለከት የሰጧቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፡፡

1. አንድ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የስነ ስርዓት ስህተት የፈጸመ እነደሆነ ከተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ሲቀርብለት ወይም በራሱ አነሳሽነት ስህተቱን ማረም አለበት፡፡
2. የስነ ስርዓት ስህተት ፈጽሞ እንደሆነ ጥያቄው ለፍ/ቤቱ ሳየቀርብ ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ/ቁ. 17352
ሐምሌ 28 ቀን 1997 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አበዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/የግል ማኅበር
መልስ ሰጭ፡- የነገው ሰው ትምህርት አ/ማ

ፍ ር ድ

የሰበር ችሎቱ በዚህ መዝገብ የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮአል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው ወለድ በስር ተከሣሽ ሊከፍል የሚገባው ቢሆንም ከሣሹ ክሱን ሲያቀርብ ከነሐሴ 16/91 ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ጥቅምት 27 ቀን 1994 ድረስ ያለውን ወለድ አስቦ ዳኝነት ስላልከፈለበት በዚህ ጊዜ ውስጥ የቀረበውን የወለድ ሂሣብ ፈ/ቤቱ አልተቀበለውም በማለት በመወሰኑ ነው፡፡ ጉዳዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መስቀለኛ ይግባኝ ቢያቀርብም ተቀባይነት ባለማግኘቱ ጉዳዩ ለሰበር ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር በመቅረቡ መልስ ሰጪ መልሱን፣ አመልካች ደግሞ የመልስ መልሱን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር ማመልከቻ በተከሣሽ እንዲከፈል የተጠየቀው ብር 562,966.74 /ምስት መቶ ስልሣ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሣ ስድስት ከሰባ አራት ሣንቲም/ የወለድ ሂሣብ ዳኝነት አልተከፈለበትም ተብሎ መታለፉ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያሳያል የሚል ሲሆን መልስ ሰጪ በበኩሉ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልበትን ምክንያት ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠየቀው ወለድ ዳኝነት ያልተከፈለበት መሆኑ፣ በሌላው ጉዳይ የተከፈለ የዳኝነት ያልተከፈለበት መሆኑ፣ በሌላው ጉዳይ የተከፈለ የዳኝነተ ሂሣብ ለወለድ ጥያቄው ይያዝልኝ ማለት የማይቻል መሆኑ፣ በሰበር በቀረበው ጥያቄ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው ጥቅምት 5 ቀን 97 ሲሆን በዚህም ላይ የቀረበ የሰበር አቤቱታ አለመኖሩ፣ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበበት ጉዳይ በመስቀለኛ ይግባኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀርቦ ውድቅ የተደረገው በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቦ ዘመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የሰበር ችሎቱ በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ አንድ ተሟጋች መክፈል የሚገባውን የዳኝነት ሂሣብ ገቢ ሳያደርግ ክርክሩ እንደቀጠለ ፍ/ቤቱ የተገነዘበ እንደሆነ መፈፀም ያለበት ሕጋዊ ሥርዓት ምንድነው? የሚለውን ጭብጥ የማያስነሣ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

የሕግ ትርጉም ወደሚያሰፈልገው ዋናው ጉዳይ ከመሄዱ በፊት ፍርድ ቤቱ መልስ ሰጪ በመልሱ ላይ ያቀረባቸውን ነጥቦች ተመልክቷል፡፡

መልስ ሰጪው በስር ፍርድ ቤት የሂሣብ ይቀናነስልኝ ጥያቄ ስላልተነሣ ለሌላ ጉዳይ የተከፈለው ዳኝነት ለወለዱ ይጣጣልኝ የሚለው ጠያቂ በሰበር ሊታይ አይገባውም ብሏል፡፡ ለፍርድ ቤት የሚከፈል ዳኝነት በአጠቃላይ ከሣሽ በሚጠይቀው ዳኝነት የሚታሰብ እንጂ ለእያንዳንዷ ርዕስ እየተለየ የሚጠየቅ ባለመሆኑ ክርክሩ የሚያስኬድ አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ገቢ መሆን ያለበትን ሂሣብ የሚመለከት እንጂ በሁለቱ መካከል ያለውን ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከት ባለመሆኑ በአንዱ ወገን መነሣት አለመነሣቱ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡

ከዚህ ሌላ በአመልካች የቀረበው የሰበር ማመልከቻ የመጨረሻ ውሣኔ ያልተሰጠበት መሆኑን በመጥቀስ ጥያቄው ውድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡ ሆኖም ለሰበር ችሎት የቀረበው ጥያቄ በመስቀለኛ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን ከፍርድ ቤቱ ማጎደር ለመገንዘብ ተሰናል፡፡ ስለዚህ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ አይደለም ሊባል አይችልም፡፡ የአሁኑ መልስ ሰጪ ይግባኝ ጠይቄ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ አግኝቻለሁ የሚለውም አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበበትና ክክስ በፊት ያለውን የወለድ ሂሣብ የሚመለከት ሳይሆን ከውሣኔ በኋላ ያለውን ሂሣብ የሚመለከት መሆኑ #ተገቢው ዳኝነት ተከፍሉበት ሣይጠየቅ ወይም ወደፊት ይከፈልበት ሳይባል ክስ <u>ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ ዋናው ገንዘብ ተከፍሎ አለቀ ድረስ</u> ወለድ ታስቦ ይከፈልበት በሚል መወሰኑ ትክክል ነው የምንለው አይደለም; ከሚለው መልስ ሰጪው ራሱ በመልሱ ካካተተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የውሣኔ ክፍል መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ሁለት የተለያዩ ጥያቄዎችንና ውሣኔዎችን በማምታታት ይኸው አሁን ለሰበር የቀረበው ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ አይደለም በማለት የቀረበው ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ አይደለም በማለት የቀረበው አስተያየት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስ ይህ ችሎት የሕግ ትርጉም ያስፈልገዋል ብሎ የያዘው የሕግ ነጥብ የዳኝነት መክፈል የነበረበት ባለጉዳይ ሂሣቡን እንዳልከፈለ ፍ/ቤቱ ሲረጋገጥ ሊሰጥ የሚገባው ውሣኔ ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ አሁን በቀረበልን ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የጠየቀው የወለድ ሂሣብ ለአመልካች መከፈል ያለበት ስለመሆኑ በፍርዱ ተቀብዘለአል፡፡ ፍርድ ቤቱ ክነሐሴ 16/91 እስከ ጥቅምት 27/1994 ድረስ ያለውን የወለድ ሂሣብ ብር 562,966.74 ውድቅ ያደረገው ከሣሹ ወለድ አስበው ዳኝነት አልከፈሉበትም በማለት ነው፡፡

ማንኛውም ለፍርድ ቤት ክስ የሚያቀርብ ሰው በሕጉ በተተመነው መሠረት የዳኝነት መክፈል እንዳለበት በሥነሥርዓት ሕጉ ቁጥር 215/1/ የተመለከተ ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ጉዳይ ሕጉ በሚያዘው መሠረት ከመቀጠሉ በፊት የሚመለከተው የፍርድ ቤቱ ክፍል ይህ አስተዳደራዊ የሆነ ተግባር መከናወኑን ማረጋገጥ ይጠበቀበታል፡፡ በሌላ በኩል በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት በሕጉ መሠረት የዳኝነት መክፈል የነበረበት ተከራካሪ ወገን ይህን ተግባር ሳይፈጽም ቢቀር ሕጉ ያሰቀመጠው መፍትሄ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሙግት ሂደት የሚፈፀሙ ጉድለቶችን ለማረም የተለያዩ መፍትሄዎችን አስቀምጧል፡፡ በዋናነትና በተለምዶ በብዛት ሥራ ላይ የሚውለው ጉዳዮችን ለይግባኝ ፍ/ቤት እያቀረቡ ስህተቶች እንዲታረሙ መጠየቅ ነው፡፡ ይህ የመፍትሄ አቅጣጫ አነድ በሙግት ሂደት የተፈፀመን ስህተት ስህተቱን ፈፀመ ለተባለው ፍርድ ቤት ሳይሆን በእርከን የበላዩ ለሆነው ሌላ ፍርድ ቤት በማቅረብ የሚከናወን ሲሆን በሥነሥርዓት ሕግ ቁ. 320 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች መሠረት የሚሰተናገድ ነው፡፡

በሙግት ሂደት የሚከሰቱ ስህተቶችን ለማረም ግን ይግባኝ አንዱ ምናልባትም የመጨረሻው አማራጭ እንጂ ብቸኛው አማራጭ አለመሆኑን ከሕጉ አደረጃጀት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ የሥነሥርዓት ሕግ ስህተቶችን ወደ የግባኝ ፍርድ ቤት መውሰድ ብቻ ሳይሆን ጉዳዩን ስህተቱን ፈፀመ ለተባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚቻልበትን ሥርዓት አስቀምጡል፡፡ ከፍትህብሄር ሥነ ሥርዓት ሐግ ቁ.320/2/ መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ፍርድ ቤት የገዛ ትዕዛዙን ለማሻሻል፣ ለማረም ወይም እንደገና ለማጣራት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ከሆነ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው ይኸው ቅድመ ሁኔታ ከተሟላ ብቻ መሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ አግባብነት ያለው የሕጉ ክፍል እንዲህ ይላል በተሰጠው ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚቻል ቢሆንመ እንኳ ፍርድ ወይም ትዕዛዝ የሰጠው ፍርድ ቤት በዚህ ህግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ፍርዱን ለማረም ለማሻሻል ወይም እንደገና ለማጣራት የማችል ከሆነ ይኸው ሥርዓት አስቀድሞ ሳይፈፀም ይገባኙን ማቅረብ አይፈቀድም፡፡

ይህ ድንጋጌ አንድ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ራሱ መልሶ የሚያይበት ሥርዓት መኖሩንና ቀዳሚው የመፍትሄ አቅጣጫ ማንኛውንም ጉዳይ ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መውሰድ ሳይሆን ጉዳዩን ለያዘው ፍርድ ቤት ለራሱ በማቅረብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሠራ የተባለው ስህተት እንዲታረም መጠየቅ መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይህ አሠራር የይግባኝ ፍርድ ቤቶችን መጨናነቅ የሚቀንስ ከመሆኑ ባሻገር ተከራካሪ ወገኖች በአቅራቢያቸው ላለውና ጉዳዩን ለሚያውቀው ፍርድ ቤት ጥያቄያቸውን አቅርበው የተቀላጠፈ መፍትሄ የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች፣ ጉዳዮች ባነሳ ጊዜና ወጪ እንዲስተናገዱ ዕድል የሚሰጥ አሠራር ነው፡፡

በሥነሥርዓት ሕጉ መሠረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍርድ ቤት በዚህ ሁኔታ መልሶ ቀድሞ ያያቸውን ጉዳዮች የሚያስተናግድባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም /ለምሣሌ አንቀጽ 6፣ 74፣ 78፣ 358/ አሁን ከቀረበልን ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነትና ተፈጻሚነት ያለው ግን በሥነሥርዓት ህጉ አንቀጽ 207 ላይ የሠፈረው መሠረተ ሃሣብ ነው፡፡ የዚሁ ሕግ ሙሉ ክፍል የሚከተለው ነው፡፡

በህግ ተለይቶ ካልተደነገገ ወይም ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም ልዩ ተዕዛዝ ካልሰጠ በቀር በዚህ ሕግ የተመለከቱትን ውሣኔዎች ወይም በውሣኔዎቹ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ባለመፈፀም ከሥነሥርዓት ውጭ የሆነ ክስ ሲቀርብ ወይም በክሱ ውስጥ ደንብ ውጭ የሆኑ ተግባር ሲፈፀም፣ ከተከራካሪዎቹ ወገኖች አንዱ ባመለከተ ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ ሥልጣን ይህ ከሥነሥርዓት ውጪ የቀረበው ክስ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲሠረዝ ወይም ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በዚህም ምክንያት ስለሚደርሰው ኪሣራና ስለሌላውም ወጭ ተስማሚ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ይሠጣል፡፡

የዚሁ ሕግ የእንግሊዝኛ ቅጂ እንዲህ ይነበባል፡፡

207 Principle

Unless otherwise expressly provided by law of directed by the court, where irregularities arise from noncompliance with any provision of this code or regulation made there under the court, many of its own motion or on the application of either party, set aside such proceedings either party, set aside such proceedings either wholly or in part as irregular, or amend them or make, on such term as it thinks fit, such other order as may be appropriate.

ከዚሁ የሥነ ሥርዓት ህግ መንደርደሪያ መርህ መረዳት እንደሚቻለው በማንኛውም ፍ/ቤት በሚካሄድ ክርክር ሥነሥርዓቱን ያልተከተለ ክስ የቀረበ እንደሆነ ወይም በክሱ ሂደት ሕጉ ያስቀመጣቸው የሥነሥርዓት ደንቦች በአግባቡ ያልተፈፀሙ እንደሆነ ፍርድ ቤት ሥርዓቱ ከሚያዘው ውጪ የተሠራውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ ይህም የሚከሣወነው በተከራካሪዎች አመልካችነት ብቻ ሳይሆን በፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መርህና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደንብ መሠረት በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች በሚያካሂዱት የዳኝነት ሥራ የሥነሥርዓቱን ደንብ ያልተከተለ ክንውን በራሳቸውም ሆነ በአስተዳደር ክፍሉ መፈፀሙን ሲያውቁ ወይም ሲደርሱበት ስህተቱን እንዲያርሙ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በፍርድ ቤቶች አካባቢ የሚታየው የተለመደው አሠራር ዳኛ የሰጠውን ትዕዛዝ መቀየር አይችልም፣ መቀየር የሚችለው የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ብቻ ነው የሚል ቢሆንም ይህ በተለምዶ የዳበረው አሠራር የሥነሥርዓቱ ሕጉ ያስፈረደውን ከላይ የተጠቀሰውን መሠረታዊ መርህ የሚጻረር ነው፡፡ ሥነ ሠርዓት ነክ የሆነን ጉዳይ የሚመለከት እስከሆነ ድረስ ባለጉዳዮች ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መሄድ ሳያስፈልጋቸው ስህተቱን ለፈፀመው ፍርድ ቤት ማመልከት ይፈቀድላቸዋል፣ ዳኞችም እርግጥም ስህተት መሠራቱን ካመኑበት ስህተቱን የማረም ሥልጣንም አላቸው፡፡ /የሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁ.209/

ወደያዝነው ዋናው ጭብጥ ስንመለስ የከፍተኛ ፍ/ቤት ወለድን አስመልክቶ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ወለድ ሊከፈለው አይገባም በሚል ምክንያት ሳየሆን ለፍርድ ቤት ገቢ መሆን የነበረበትን የዳኝነት ሂሣብ አልከፈለም በማለት ነው፡፡ በሥነሥርዓት ሕጉ ቁጥር 215/1/ እንደተደነገገው ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ክሶች ሁሉ ዳኝነት ካልተከፈለባቸው በቀር ተቀባይነት አያገኙም፡፡ ስለዚህ የዳኝነት ሂማብ ለፍርድ ቤት ገቢ ማድረግ በክስ ሂደት መከናወን ያለበት ተግባር ነው፡፡ የዳኝነት ክፍያ መጠናቀቅ ያለበት ክሱ ሲቀርብ እንደሆነ ከድነጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ይህን ሥራ እንዲያከናውኑ የተመደቡ የሚመለከታቸው የፍርድ ቤቱ ክፍሎች ይህ ህጉ የሚጠይቀውን ሥርዓት መከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ማከናወን ያለበት ይህ ተግባር ሳይከናወን ቀርቶ ክሱ ለፍርድ ቤት /ለዳኛ/ ቢቀርብ ክሱ ከሥነ ሥርዓት ውጪ የቀረበ /procedurally irregular/ ይሆናል፡፡ በፍትሐብሄር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 207 እንደተደነገገው የሥነሥርዓት ሕጉን ወይም በሱ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን በመጣስ የቀረበን ከሥነሥርዓት ውጪ የተፈፀመን ተግባር የማቃናት ሃላፊነት ለፍ/ቤቱ የተሰጠ በመሆኑ የሥነሥርዓት ግድፈት የተፈፀመ መሆኑ ሲታወቅ በዚህ መሠረት መከናወን ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት ያልተከፈለ የዳኝነት ክፍያ ካለ የክሱን ሂደት አስመልክቶ የተፈፀመ የሥነ ሥርዓት ግድፈት መኖሩን ስለሚያመለክት ዳኞች በተጠቀሰው ሕግ መሠረት ግድፈቱን በማስተካከል ያልተከፈለ ሂሣብ ካለ ተሰልቶ እንዲከፈል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በያዝነውም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማድረግ የነበረበት ይህንን ነው፡፡ አመልካች ወለድ እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡ ይኸው የአመልካች ጥያቄ በሕግ ተቀባይነት ያለው መሆኑንም ፍ/ቤቱ ተቀብሎታል፡፡ በመሆኑም ያልተከፈለ ሂሣብ ካለ በሥነሥርዓት ሕጉ ቁጥር 207 መሠረት ማስከፈል ሲገባው ይህን አልፎ የቀረበውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስ በዚህ ምክንያት ውድቅ ማድረጉ ሕጉ ያስቀመጠውን የሙግት አመራር የተከተለ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህ ፍርድ ቤት አልተቀበለውም፡፡

የፍተሀብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 211/2/ #ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በተባለበት ጉዳይ ላይ የተፈፀመውን ማንኛውንም የሥነ ሥርዓት ጉድለት በራሱ አስተያየት ሊያርም ይችላል; በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የሰበር ችሎት የዳኝነትን አከፋፈል አስመልክቶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፈፀመውን የሥነ ሥርዓት ጉድለት ማቃናት እንዳለበት አምኖአል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ከ16/12/91 እስከ ጥቅምት 27/1994 ዓ.ም ያለውን የወለድ ክፍያ በሚመለከት በመዝገብ ቁ.11641 የሰጠውን ውሣኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15574 የሰጠውን ውሣኔ ሽሯል፡፡
2. መልስ ሰጪ ከ16/12/91 እስከ 27/2/94 ላለው ጊዜ በዋናው ገንዘብ ላይ 9% ወለድ ይከፈል፡፡
3. በዚሁ በተፈረደው የወለድ መጠን ያልተከፈለ የዳኝነት ገንዘብ አመልካቹ ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ ገቢ ያድርግ፡፡ የውሣኔው ገልባጭ የሚሰጠው የዳኝነቱን ገንዘብ ገቢ ማድረጉ ከተረጋገጠ በኋላ ነው ተብሏል፡፡
4. መልስ ሰጪ በዚህ ፍርድ ቤት ውሣኔ አመልካች ለዚህ ፍርድ ቤት ገቢ ያደረገውን የዳኝነት ሂሣብ ይተካለት፣ ሌላው በዚህ ፍርድ ቤት ያለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሣኔያቸው ላይ ለውጥ መደረጉን እንዲያውቁት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ለጠቅላይ ፍ/ቤት የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ይላክ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 14605

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አበዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት
መልስ ሰጪዎች፡- 1. ኮሜት ትራንስዓርት ድርጅት
2. ሸበሌ ትራንስፖርት ድርጅት
3. በክልቻ ትራንስፖርት ድርጅት
4. ወይራ ትራንስፖርት ድርጅት
5. አዲስ ሜካኒካል ድርጅት
6. አቶ ዮሐንስ ተሰፋ

ስለ ማንገዝ ስራ - የአንዥር ኃላፊነት - የተመዘገቡ ንዞች ወይም ዕቃዎች የጠፉ ወይም ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን - በተለያዩ ምክንያቶች ኪኃላፊነት መዳን የንግድ ህግ ቁጥሮች 590፣ 591፣ ውል - ውልን ስላለመፈጸም- ከዐቅም በላይ የሆነ ነይል - የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 1792

አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ከ1ኛ-5ኛ በተጠቀሱት ተጠሪዎች መኪና አቅራቢነት ነጭ ጋዝ ናፍታ አሰጭኖ ከአሰብ ወደ ባህር ዳር በሚንገዝበት ወቅት መኪናው ተገልብጦ ዋጋው ብር 51,089.78 /ሃምሳ አንድ ሺህ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከሰባ ሰምንት ሳንቲም/ የሆነ ነዳጅ ስለፈሰሰ ይህንኑ ዋጋ ብር 51,089.78 /ሃምሳ አንድ ሺህ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከሰባ ሰምንት ሳንቲም/ ከ1-5 ያሉት ተጠሪዎ እንዲሁም የመኪናው ባለንብረት 6ኛ ተጠሪ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉት ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ነዳጁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የፈሰሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በመሆኑ ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ውሳኔ በመስጠቱና ውሳኔውን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ው ሳ ኔ፡- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. አንድ አንገሸር በከፊል ወይም በሙሉ ዕቃዎች ወይም የተመዘገቡ ንዞች ወይም ጉዳት ሲያገኛቸዉ ወይም የማስረከቢያ ጊዜው ቢዘገይ በኃላፊነት የሚጠቅ ሲሆን ከዚህ ኃላፊነት የሚነው ዕቃው የጠፋው ወይም ጉዳት የደረሰው ወይም የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በተቀባዩ ጥፋት ሲሆን ነው፡፡
2. ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል የሚባለው ባለእዳው /አንገፍ/ በቅድሚያ በምንም መልኩ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይቻል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡
3. ወደ መኪና ሮጦ የገባን ሰው ለማዳን በተወሰደ ርምጃ ምክንያት በመንገዝ ላይ የነበረ ዕቃ ላይ የደረሰ ጉዳት ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ተከስቷል የሚባል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አበዱልቃድር መሐመድ

አቶ መስፍን እቁበዮናስ

ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት

ተጠሪዎች፡- 1. ኮሜት ትራንስዓርት ድርጅት

2. ሸበሌ ትራንስፖርት ድርጅት

3. በክልቻ ትራንስፖርት ድርጅት

4. ወይራ ትራንስፖርት ድርጅት

5. አዲስ ሜካኒካል ድርጅት

6. አቶ ዮሐንስ ተሰፋ

ፍርድ

ለአሁን አቤቱታ መነሻ የሆነው ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጳጉሜ 3/1992 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች በዚያ ፍ/ቤት ከ1ኛ-5ኛ ድረስ ባሉት ተጠሪዎች መኪና አቅራቢነት አመልካች 34993 ሊትር ነጭ ጋዝ ናፍታ አስጭኖ ከአሰብ ወደ ባህርዳር በሚጓጓዝበት ወቅት መኪናው በመገልበጡ የተጫነው ነዳጅ በሙሉ ስለፈሰሰ የፈሰሰውን ነዳጅ ዋጋ ብር 51089.78 /ሃምሳ አንድ ሺህ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሰባ ስምንት ሳንቲም/ ከነወለዱ አምስቱም ተጠሪዎች እንዲከፍሉ፡፡ 6ኛውም ተጠሪ የመኪናው ባለንብረት ስለሆነ በአንድነት እና በነጠላ በክሱ የተመለከተውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ጠይቋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አቀራክሮ ነዳጁ የፈሰሰው ከአቅም በላይ በሆነ ከፍተኛ ሃይል ስለሆነ ተጠሪዎቹ በሙሉ ለክሱ ሃላፊ አይደሉም በማለተ የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የስር ፍርድ ቤቱን ውሳዐነ አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ላይ ሲሆን የአመልካተ ቅሬታ በአጭሩ ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች #ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታን; ሲተረጉሙ የህግ ስህተት ፈጽመዋል የሚል ነው ተጠሪዎችም ለቀረበው አቤቱታ መልስ አቅርበዋል፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በአንድነት በ17/10/96 በተጻፈ መልስ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ በክሱ ይተካልን፣ ይህ ቢታለፍ ነዳጁ የፈሰሰው ከተባለም የቀድሞ የኢትዮጵያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን ከአመልካች ጋር የማንገባ ውል ስላልፈጸመ ለጥፋቱ ሃላፊ አንሆንም፣ በተመሳሳይ ጉዳይ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን የግለሰብ ተሽከርካሪዎች ለሚፈጽሙት ጥፋት ሃላፊነት እንደሌለበት በመ/ቁ/9678 እና በመ/ቁ 6979 በሰበር ችሎት ውሳኔ ተሰጥቷል የሚል ነው፡፡

6ኛ ተጠሪ በበኩሉ በ9/6/97 በተጻፈ መልስ ነደጁ የፈሰሰው ከፈቅም በላይ በሆነ መክንያት ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ አንዲጸናለት ጥቅቋል፡፡

አመልካችም በመልስ መልሱ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻርለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ከፍ ሲል የተገለጸው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ያቀረበው ክስ ውድቅ የተደረገው አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል ነው፡፡ በመሆኑም፣

1. አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው? ወይስ አይደለም?
2. ካልሆነ ተጠሪዎች ለክሱ ሃላፊ ሊሆኑ ይገባልን? የሚሉት ነጥቦች መታየት አለባቸው፡፡

<u>የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ</u>

አንድ አንሻር በከፊል ወይም በሙሉ እቃዎች ወይም የተመዘገቡ ንገሮች ሲጠፉ ወይም ጉዳት ሲያገኛቸው ወይም የማስረከቢያው ጊዜ ቢዘገይ በሃላፊነት እንደሚጠየቅ የግን ህጉ ቁጥር 590 ሲያመለክት አንገቦ ከዚህ ሀላፊነት የሚድነው ደግሞ የጠፋው ወይም ጉዳት የደረሰው ወይም የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በእቃው ውሳጣዊ ጉድለት ምክንያት ወይም በላኪና በተቀባዩ ጥፋት ምክንያት ሲሆን እንደሆነ የን/ህ/ቁ 591 ያመለክታል፡፡

በመሆኑም አንድ አንሻር የሚያንጉዘው እቃ የጠፋ ወይም ጉዳት የደረሰበት ከሆነ ከሃላፊነት ለመዳን እቃው የጠፋው ወይም የተጎዳው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መሆኑን ወይም ከራሱ ከእቃው ጉድለት መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ከምክንያቶቹ ውስጥም ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ የሚለው በመሆኑ ችሎቱም ይህ ሁኔታ ተከስቷል የሚባለው መቼ ነው የሚባለውን ከህጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡

በንግድ ህጉ ውስጥ "ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተመለከተ ነገር ስለሌለ ትርጉሙን ለማወቅ ወደ ፍ/ብ/ህጉ በተለይም ደግሞ ስለውሎች በጠቅላላው ወደሚመለከቱት ድንጋጌዎች ማምራቱ የግድ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረትም የፍ/ህ/ቁ 1792ን ስንመለከት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ወይም የለም የሚባለው መቼ እንደሆነ ያሳያል፡፡

የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ሀይል ደርሷል የሚባለው ባለእዳ ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍጹም መሰናክል በሆነ አይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመ ጊዜ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ከንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለእዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈጻጸም ከባድ የሆነ ወጪ በባለዕዳው የሚደርስበት ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት መመልከት ይቻላል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው ባለእዳው በቅድሚያ በምንም መልኩ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይችል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለእዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገምት ወይም ሊያስብ እና ጥንቃቄ ሊያደርግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገተኛ ደራሽ ነገር ቢሆን እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት ማየት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሊባል የሚችለው ፈጽሞውኑ ሊቋቋሙት ወይም ሊቆጣጠሩት የማይቻል ወይም ማንኛውም ጠንቃቃ ሰው ሊገምተው እና ሊያስበው የማይቻለው ሁኔታ ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1793 የተዘረዘሩት ምክንያቶችም ይህንኑ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይም ስናመራ የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪዎችን ከኃላፊነት ነጻ ያደረጓቸው ነዳጁ የፈሰሰው ወደ መኪናው ሮጦ የገባን ሰው ለማዳን በተወሰደ እርምጃ ስለሆነ ከአቅም በላይ በሆነ ድንገተኛ ደራሽ አደጋ ነው በማለት ነው፡፡ ነገር ግን አንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የመኪና አሽከርካሪ መኪያ በሚያሽከረክርበት ወቅት በመንገዱ ድንገት ሰው ሊገባበት እንደሚችል፣ የተለያዩ የመጋጨት ወይም የመገልበጥ አደጋ ሊያጋጥመው እንደሚችል ቀደም ብሎ ሊገምት ወይም ሊያስብ የሚችለው ነገር ነው። የመኪና አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ጊዜ በመንገዱ ላይ ድንገት ሰው ሊገባ ወይም ድንገተኛ አደጋ ሊያጋጥም ይችላል ብሎ ፈጽሞ አያስብም ተብሎ አይገመትም። በመሆኑም 6ኛ ተጠሪ መኪናውን ሲያሽከረክር ድንገት ሰው ሮጦ ወደ መንገዱ መግባቱ ብቻ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ መኖሩን አያሳይም። ስለዚህም የስር ፍ/ቤቶች ለነዳጁ መፍሰስ ምክንያት የሆነውን አደጋ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ትርጉም የህግ ስህተት ያለበት ነው።

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከፍ ሲል እንደተገለጸው አንድ አጓዥ በከፊል ወይም በሙሉ እቃዎች ወይም የተመዘገቡ ንዞች ሲጠፉ ወይም ጉዳት ሲያገኛቸው በኃላፊነት ይጠየቃል። ከኃላፊነቱ ነጻ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንደኛው ደግሞ አደጋው ወይም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መሆኑ ነው። በተያዘው ጉዳይ 6ኛ ተጠሪ አጓዥ መሆኑ ክርክር አልተነሳበትም። ከላይ እንደተገለጸው ደግሞ አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንየት አይደለም። ስለዚህም 6ኛ ተጠሪ ለጉዳቱ በን/ህ/ቁ 590 መሠረት ኃላፊ ነው። ከ1ኛ-5ኛ ያሉትን ተጠሪዎችን ኃላፊነት ስንመለከት ተጠሪዎቹ አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው የማይባል ከሆነ የፈረሰው የኢትዮጵያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን እቃውን ለማጓጓዝ ከአመልካች ጋር ያደረገው ውል ስለሌለ ኃላፊነት የለብንም ሲሉ ተከራክረዋል። ይሁን አንጂ በስር ፍ/ቤት የፈረሰው ድርጅት የእቃ ላኪ ኮሚሲዮን እቃ አጓዡ ያለበት መብት እና ግዴታ ያለበት በመሆኑ (የፍ/ህ/ቁ. 2252 (3)) ተጠሪዎቹ ለደረሰው ጉዳት በአንድነት አና በነጠላ ኃላፊ ሊሆኑ ይገባል።

ከ1ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በተጨማሪ ያነሱት ክርክር በተመሳሳይ ጉዳት ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን የግለሰብ ተሽከርካሪዎች ለሚፈጽሙት ጥፋት ኃላፊነት እንደሌለበት ቀደም ሲል ተወስኗል የሚል ሲሆን እንደዚህ አይነት ውሳኔ ተሰጥቶ እንኳን ቢሆን በተያዘው ጉዳይ ተመሳሳይ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ይሆንም።

በመጨረሻም እነዚሁ ተጠሪዎች ወደ አክስዮንነት የተቀየርን ስለሆነ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ተተክቶ ይከራከር ሲሉ የጠየቁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ቢሆንም ቦርዱ በኃላፊነታቸው መጠን እዳቸውን የመክፈል ግዴታ ካለበት በአፈጻጸም ጊዜ እንዲተካ ሊጠይቁ የሚችሉ በመሆኑ ጥያቄያቸው በዚሁ ታልፏል፡፡

ውሣኔ

- ተጠሪዎች በአንድነት እና በነጠላ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ በመቶ ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈሉ፡፡
- አመልካች በክርክሩ ወቅት ለደረሰበት ወጪ እና ኪሣራ ዝርዝሩን በስር ፍ/ቤት አቅርቦ ያስወስን፡፡
- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 349/87 በ3/13/92 ዓ.ም. እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 2317/93 በ14/3/96 ዓ.ም. የሰጧቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 17068

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት

መልስ ሰጪ፡- ሚ/ር ቢሮኒ አቲክፖ

ውል የግዴታዎች መቅረት - ስለ ይርጋ - የውልን ጉዳይ ስለሚመለከት ማስረጃ - ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥሩ የህሊና ግምቶች- የፍትሐብሔር ህግ ቁጥሮች 1856፣ 2024፡- ስለ አቤቱታ -ሀጋዊ ስለሆኑ ግምቶች - የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 89

አመልካች በስር ፍ/ቤት መ/ሰጪ ያልከፈለው የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍለው በመጠየቅ ባቀረበው ክስ መ/ሰጪ ሳይቀርብና ኪራዩ ተከፍሏል የሚል ክርክር ሳይነስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024 መሰረት ከሁለት አመት በላይ የሆነው የኪራይ ገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል በሚል የአመልካችን ክስ በከፊል ውድቅ ስላደረገውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን ስላጸናው የቀረበ አቤቱታ

<u>ውሳኔ</u>፡- የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ጸንቷል፡፡

1. የሕሊና ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ደንብ ድንጋጌዎች የተለዩ ናቸው፡፡
2. የቀረበላቸው ፍሬ ነገር በህግ ግምት ከተሸፈነ ተከሳሽ ፍሬ ነገሩን ካደም አልካደ ፍ/ቤቶች የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ/ቁ. 17068
ሐምሌ 19 ቀን 1997

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት
መልስ ሰጪ፡- ሚ/ር ቢሮኒ አቲክፖ (ባለቤት)

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር ማመልከቻ መነሻ የሆነው የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ክስ ካቀረበበት ገንዘብ መካከል ከሁለት ዓመት በላይ የሆነው ሂሣብ ተከሣሽ በፍ.ብ.ሕግ ቁጥር 2024 መሠረት እንደከፈለ ስለሚቆጠር ከሁለት ዓመት በላይ የሆነውን ሂሣብ በሚመለከት ከሣሽ ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት በመወሰናቸው እና ሌሎችንም ክስ የቀተበባቸው ሂሣቦች ውድቅ በማድረጋቸው ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም የቀረበው ይግባኝ ተቀባይነት በማጣቱ የሰበር ማመልከቻ አቅርቧል፡፡ የሰበር ማመልከቻው ይዘት በርካታ ነጥቦችን ያካተተ ሲሆን ዋና ዋና ነጥቦቹ የቤቱ ኪራይ በአሜሪካን ዶላር ሊከፈለን ሲገባ ታልፎብናል፣ የውሃ ፍጆታና የአገልግሎት ሂሣብ ውድቅ ተደርጎብናል፣ ከሁለት ዓመት በላይ የሆነውን ሂሣብ አስመልክቶ ክሱ ውድቅ መሆኑ አግባብ አይደለም፣ የተወሰነልን ወጪና ኪሣራም ካወጣነው ወጪ በታች በመሆኑ ትክክለ አይደለም የሚል ነው፡፡

አመልካች ካቀረባቸው ነጥቦች መካከል በሰበር ሊታይ ይገባል የተባለው የሕግ ነጥብ የሥር ፍርድ ቤቶች ተከሣሽ ክሱን ለመከላከል ባልቀረበበት ሁኔታ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 ላይ በሰፈረው የሕሊና ግምት መሠረት ከሁለት ዓመት በላይ የሆነው የኪራይ ክፍያ እንደፈከፈለ ይቆጠራል በማለት የአመልካቹን ክስ በከፊል ውድቅ ማድረጋቸው አግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረባቸው ሌሎች የቅሬታ ነጥቦች መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖሩን የሚያመለክቱ ስላልሆኑ ይህ ችሎት በነዚህ ቅሬታዎች ላይ ውሣኔ መስጠት አላስፈለገውም፡፡

የሕሊና ግምቱን በሚመለከት አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚለው፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሀ. "በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1856(2) ዳኞች በገዛ ስልጣናቸው የይርጋ ደንብን መከላከያ በራሳቸው አነሳሽነት ክሱ በይርጋ ውድቅ ነው በማለታቸው፣

ለ. ተከሣሹ ለቀረበበት ክስ መልስ ለመስጠት ካለመፈለጉም በላይ እዳውን አልካደም፣

ሐ. የሕሊና ግምት ይወሰድልኝ ማስረጃ ማቅረብ አልችልም ጠፍቶብኛል ስለዚህ የሕግ ግምት ይወሰድልኝ በማለት ተከሣሹ ሳይከራከር፣

መ. የይርጋ ክርክር የሚያነሳው ወገን ግዴታውን አለመውጣቱን ሳይክድ የተጣለበት ግዴታ ግን በይርጋ ቀሪ ስለሚሆን ከኃላፊነት ነፃ ነኝ አልጠየቅም የሚል ክርክር ሲያቀርብ ነው" የሚሉ የክርክር ነጥቦችን በማቅረብ ነው።

መልስ ሰጭ መልስ ካለው ይዞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ቢሰጥም ለዚሁ በተያዘው ቀጠሮ አልቀረበም፣ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በሰበር እንዲታይ በተያዘው የሕግ ነጥብ ላይ የቀረበ የመልስ ሰጭ መልስ የለም።

ይኸው ችሎት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መነሻ በማድረግ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የሰፈረው የሕግ ግምት ተከሣሹ ቀርቦ ፅዳውን ባልካደበት ወይም ጭራሽ ባልቀረበበት ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል አይሆንም በሚለው የሕግ ጉዳይ ትርጉም መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።

ወደ ዋናው ነጥጥ ከመግባቱ በፊት አመልካች ያቀረባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች የህሊና ግምትን ከማመለከተው የሕግ ነጥብ ጋር ያላቸውን አግባብነት መርምሯል።

አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የሰፈረው የሕግ ግምት ይርጋን ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች ጋር አንድ እንደሆኑ በመቁጠር ፍርድ ቤት የሕሊናውን ግምት በራሱ አነሳሽነት ሊያነሳው አይገባም የሚል የሕግ ክርክር አቅርቧል። ሆኖም በፍትሐብሔር ሕጉ የሰፈረው የህሊና ግምት በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 1845 (ወይም በሌሎች በርካታ አንቀጾች) ከሰፈረው የይርጋ ደንብ የተለየ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ይህን መከራከሪያ የሚቀበለው አይደለም። የይርጋ ደንብ አንድ ክስ በፍርድ ቤቱ ቀርቦ በስረ ነገር እንዳይታይ የሚከለክል ሲሆን የሕሊና ግምት (በ2024 የሰፈረው የመከፈል ግምትን ጨምሮ) በሌላ በኩል የማስረዳት ሸክምን ከአንድ ወገን ወደ ሌላው የማስተላለፍ ውጤት ብቻ ያለው በመሆኑ ከሣሽ ያቀረበውን ክስ ይዘት መርምሮ ውሣኔ መስጠትን የሚከለክል አይደለም። በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ የሰፈረውን ይርጋ ተከሣሹ ወገን ካላነሳው ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሳ እንደማይችል በፍትሐብሔር

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሕግ ቁ.1856 የተጠቀሰ ቢሆንም ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው ለይርጋ ድንጋጌዎች እንጂ በሕግ ግምት የማስረዳት ሸክም ከአንድ ተሟጋች ወደ ሌላው በሚዘዋወርባቸው ሁኔታዎች አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ድርጅት ይርጋን (Period of limitation) ከሕግ ግምት (Presumptions) ጋር በማመሳሰል ለይርጋ ተፈፃሚ የሚሆነው ሕግ ለህግ ግምትም ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል በማለት ያቀረበው ክርክር የህጉን መንፈስ፣ ዓላማና ግልጽ ይዘት ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

ቀጥሎ መታየት ያለበትና በዚህ መዝገብ የህግ ትርጉም የሚሰጠው ዋነኛው ነጥብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የሰፈረው የሕግ ግምት ተፈፃሚ የሚሆነው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? የሚል ሲሆን ተከሣሽ ቀርቦ የቀረበበትን ክስ ባልካደበት ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የሚለው ነጥብም ከዚሁ ተያይዞ የሚነሳ ነው፡፡

የሕግ ግምት አፈፃፀም የስረነገር (Substantive) ሕግ እና የስነ ሥርዓት (Procedural) ህግ ገጽታዎች ያሉት ሲሆን ከላይ የተነሱትን ነጥቦች በአግባቡ ለመመለስ የኢትዮጵያ ሕግ በሁለቱም ረገድ ያለውን ዝርዝር ድንጋጌ መመልከትና መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በኢትዮጵያ የስሪነገር ሕጎች በርካታ የሕግ ግምቶች ያሉ ሲሆን አሁን ከቀረበልን ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 2024 የሰፈረው ግምት ነው፡፡ ይህ የግህ ግምት ስለ ውሎች ማስረጃ በሚመለከተው ክፍል የሚገኝ ሲሆን በውል የሚጠየቅ ገንዘብ እንደተከፈለ ከሚያስቆጥሩ የሕሊና ግምቶች አንዱ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ዕዳው እንዲከፈል ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈሉ የቀሩ በአንቀጹ ተዘርዝረው የተቀመጡትን ዕዳዎች እንደተከፈሉ ይቆጠራል፡፡ በዚህ ግምት ከሚሸፈኑ ዕዳዎች መካከል ለቤት ኪራል የሚከፈል ዕዳ አንዱ ነው፡፡ (ቁ.2024/መ)

የሕግ ግምቶች መሠረታዊ ውጤት የማስረዳት ሸክምን ከአንዱ ወገን ወደሌላው እንዲሻገር ማድረግ ቢሆንም የማስረዳት ሸክሙ የዞረበት ወገን የሕግ ግምቱን ማፍረስ የሚችልበት የሕግ ሁኔታ ይለያያል፡፡ አንዳንድ የህግ ግምቶች የግምቱ ተጠቃሚ ያልሆነው ወገን ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ በማቅረብ የሚያፈርሳቸው ሲሆኑ (Reputable Presumption) ሌሎች የሕግ ግምቶች ደግሞ ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በማቅረብማፍረስን የማይፈቅዱ (Irrefutable Presumption) ናቸው። የፍትሐብሔር ሕጉ ከ2020 — 2024 ያሰፈራቸውን የህግ ግምቶች ለማፍረስ ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ ከሕጉ አንቀጽ 2026(1) ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል። ይኸው ድንጋጌ "ከዚህ በላይ ባሉት ቁጥሮች ላይ ለተገለጠው የሕሊና ግምት መቃወሚያ የሚሆን ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ለመቀበል አይቻልም" በማለት በሕጉ የሰፈሩትን ግምቶች ለማፍረስ አንደኛው ወገን ማንኛውንም ዓይነት ማስርጃ ማቅረብ እንደማይፈቅሉለት በመርህ ደረጃ በግልጽ አስፍሯል። ይህ አጠቃላይ መርህ ቢኖርም አንዱ ወገን ይህን አስገዳጅ የህግ ግምት ማፍረስ የሚችለው ሌላው ወገን መሀላ እንዲፈጽምለት በመጠየቅ ብቻ ነው። በዚህ መልክ ሌላው ወገን መሃላ እንዲወርድለት በመጠየቅ የማስረዳት ሸክሙን በመወጣት የሚሻ ወገን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 83 በሚያዘው መሠረት ይህን ማስረጃውን ክሱን በሚያቀርብበት ወቅት እንዲጠቅስ ይጠበቅበታል።

በውል ሕግ የሰፈሩት እነዚህ ድንጋጌዎች የስረ ነገር ሕግ ክፍሎች በመሆናቸው ፍርድ ቤቶች ሊከተሉዋቸው የሚገባ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች ናቸው። እነዚህ ድንጋጌዎች የማስረጃን አቅራረብ የሚመለከቱ ከመሆናቸው በስተቀር እንደማንኛውም ሌላ የውል ሕግ ድንጋጌዎች በባለጉዳዮች ቢጠቀሱም ባይጠቀሱም ፍርድ ቤቱ አግባብነት ባለበት ሁኔታ ሁሉ ተፈፃሚ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ድንጋጌዎች ናቸው። በመሠረቱ ወደ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ባለጉዳዮች ለጉዳያቸው አግባብነት ያለውን ፍሬነገርና የሚጠይቁትን ዳኝነት ከመግለጽ አልፈው በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን ወይም የማይሆነውን ድንጋጌ እንዲጠቅሱ አይጠበቅባቸውም። በመሆኑም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የተጠቀሰውን የሕግ ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያበቃ ፍሬ ነገር የቀረበለት መሆኑን የተረዳ ፍ/ቤት በዚሁ ድንጋጌ መሠረት የሚሸፈነውን ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ የመቁጠር ግዴታ አለበት።

የሕግ ግምቶችን አስመልክቶ በፍትሐብሔር ሕጉ የሰፈረው ይህ መሠረተ ሃሣብ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉም በተመሣሣይ መንገድ ተደንግጎ የምናገኘው ነው። በዚሁ ሕግ መሠረት ማንኛውም ተከሣሽ በመርህ ደረጃ ለፍርድ ቤቱ በሚያቀርበው መልስ ክስ የቀረበበትን ነገር በግልጽና በዝርዝር ማስተባበል ይጠበቅበታል። በክስ አቤቱታ ላይ የቀረበ ማንኛውም ነገር በግልጽ ካልተካደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
እንደታመነ ሊቆጠር እንደሚችልም ይደነግጋል። ይህ አባባል አጠቃላይ የፍትሐብሔር መደበኛ ሙግት አካሄድን የሚመለከት ቢሆንም ተከሣሹ የሕግ ግምት ተጠቃሚ ሲሆን በግምቱ የሚሸፈነውን ፍሬ ነገር በሚመለከት ይህ ግዴታ እንደሚወርድለት የሕጉ አንቀጽ 89 በግልጽ ያስቀምጣል። ይህ ድንጋጌ "አስቀድሞ በአንደኛው ወገን አቤቱታ ወይም ሙግት በግልጽ የተካደ ጉዳይ ካልሆነ በቀር አንዱ ወገን ተከራካሪ ህጋዊ በሆነ ግምት የሚደገፍበትን ነገር ወይም ሌላው ወገን ማስረጃ እንዲያቀርብ ተገቢ የሆነበትን ጉዳይ ሌላው ወገን በአቤቱታው ውስጥ መጥቀስ አይገባውም" በማለት የሕግ ግምት ተጠቃሚ የሆነ ተሟጋች በሚያቀርበው መልስ በህግ ግምት የተሸፈነውን ፍሬ ነገር በግልጽ የመካድ ግዴታ እንደሌለበት ያመለክታል። በመሆኑም አንድ ተከሣሽ በሕግ ግምት የተሸፈነውን ፍሬ ነገር በማስመልከት በመልኩ በግልጽና በዝርዝር መካድ አይጠበቅበትም። በመሆኑም በህግ ግምት የተሸፈነን ጉዳይ በማስመልከት ማንኛውም ፍርድ ቤት ቢሆን ተከሣሹ በግልጽ ስላልካደ እንዳመነ ይቆጠራል በማለት ፍርድ ሊሰጥ አይችልም። ይህ መሰረተ ሃሣብ በፍትሐብሔር ሕጉ ካለው መሠረተ ሃሣብ ጋር ተመሳሳይ እና የሚጣጣም ነው።

የሕግ ግምትን አስመልክቶ ያለው የሕግ ማዕቀፍ ይህ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ውሣኔ ይህንኑ መሠረት ያደረገ መሆን ይጠበቅበታል። ተከሣሹ የሕግ ግምት ተጠቃሚ በሚሆንበት ወቅት የሚከተሉት ሂደትና የሚሰጡት ውሣኔም በሌሎች በመደበኛ የሙግት ሂደት ከሚተከሉዋቸው የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ደንቦች የተለዩ መሆናቸው የማይቀር ነው።

በመሆኑም የቀረበላቸው ፍሬ ነገር በህግ ግምት እስከተሸፈነ ድረስ ፍርድ ቤቶች ተከሣሽ ካደም አልካደ የሕግ ግምቱን ተፈፃሚ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ተከሣሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲቀጥል መደረጉም አስገዳጅ በሆኑት የሕግ አንቀጾች አፈጻጸም ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም። ተከሳሹ ፍርድ ቤት ቢቀርብም በግልጽ እንዲክድ የማይገደደውን ፍሬ ነገር ጉዳዩ እርሱ በሌለበት በመቀጠሉ እንዳመነ የሚቆጠርበት በቂ ሕግ ምክንያት የለም።

አሁን በቀረበልን ጉዳይ ክስ በቀረበበት የኪራይ ክፍያ በከፊል መጠየቅ ከነበረበት ከሁለት ዓመት በላይ የሆነው ስለመሆኑ ከከሣሽ ክስ መረዳት ይቻላል። ይህ ከሆነ ደግሞ ተከሣሽ ባያነሳውም ወይም በሌለበት ቢታይም በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 2024 ስር ያለውን የሕግ ግምት ተፈፃሚ በማድረግ ዕዳው እንደተከፈለ መቁጠር ተገቢ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሥር ፍርድ ቤቶችም ያደረጉት ይህንኑ ነው። ስለዚህ ፍርድ ቤቶቹ ህጉን በትክክል ተፈፃሚ ያደረጉ ስለሆነ ውሣኔው የሚነቀፍ አይደለም።

ውሣኔ

1. የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ፀንተዋል።
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ

የሀሣብ ልዩነት

በአብዛኛው ድምጽ በተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 የተመለከተውም ሆነ ሌሎች የሕሊና ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ደንብ የተለዩ መሆናቸው የተገለፀ ሲሆን እኛም ይህን የምንቀበለው ነው። የሕግ ግምት የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት የማስረዳት ሸክምን በግምቱ ተጠቃሚ ከሆነው ወገን ወደ አልሆነው ተከራካሪ ማሻገር ብቻ መሆኑንም የምናምንበት ነው።

ይሁን እንጂ ፍርድ ቤት አንድን ሕግ ተመስርቶ ፍርድ ለማስፈር የቀረበለት ወይም የያዘው የፍሬ ነገር ክርክር ከተጠቃሹ ሕግ ጋር ግንኙነት ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል። ፍ/ቤቱ ሕጉን መሠረት አድርጎ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊትም ሕጉ ለክርክሩ አግባብነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል።

እኛም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 የተመለከተው የሕሊና ግምት ከተያዘው ክርክር ጋር ያለውን አግባብነት መርምረናል። አብዛኛው ድምጽ እዳ እንዲከፍል የተጠየቀው ተከሣሽ ቀርቦ እዳውን ባይክድም ወይም ጭራሹን ባይቀርብም ፍ/ቤት ይህን ድንጋጌ ተመስርቶ በሕሊና ግምቱ ተጠቃሚ ሊያደርገውና እዳው እንደተከፈለ ሊቆጠርለት ይገባል ሲል ለድንጋጌው በሰጠው ትርጓሜ እና በደረሰበት መደምደሚያ ግን ባለመስማማት እንደሚከተለው በሐሳብ ተለይተናል።

እንደሚታወቀው በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ እዳ እንደተከፈለ ይቆጠር ዘንድ ሕግ ግምት የወሰደበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 ማስረጃ ስለማቅረብ ግዴታና ስለአቀባበሉ በተዘረዘረበት የፍ/ብ/ሕግ ምዕራፍ ሰባት ክፍል አንድ ስር የሚገኝ ነው። በዚህ ምዕራፍ ስር ያለ የሕሊና ግምት ልክ እንደ ጽሑፍ፣ ምስክር፣ የእምነት ቃል ወይም መሐላ ሁሉ አንድ የማስረጃ አይነት ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2002 ላይ መገንዘብ የሚቻል ነው። ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እዳው እንደተከፈለ መቆጠሩን ቀሪ ማድረግ እንደሚቻል የሚደነግገው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025 ደግሞ እነዚህ የሕሊና ግምቶች እራሣቸው ማስረጃዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መሆናቸውን ግልጽ የሚያደርግልን ነው፡፡ ስለሆነም የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024ን ጨምሮ በዚህ ምዕራፍ ክፍል ሶስት ውስጥ የተደነገጉት ተጠያቂው ገንዘብ እንደተከፈለ የሚያስቆጥሩ የሕሊና ግምቶች በሙሉ እንደ አንድ የክርክር ማስረጃ የሚወሰዱ እንጂ ሕግ በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ የሕሊና ግምት የወሰደባቸው ናቸው ሊሰኙ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ለአንድ ውሣኔ መሠረት የመሆናቸውም ጉዳይ ከዚህ የሕጉ መንፈስና አላማ ጋር እየተዛመደ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ይህንንም ግልጽ ለማድረግ ጉዳዩን የፍትሐብሔር ሙግት ከሚመራበት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች አኳያ ማየቱ አስፈላጊ ነው፡፡

አንድ ክስ የቀረበበት ተከሣሽ የተከሰሰበትን ነገር በግልጽ መካድ እንደሚገባውና ይህን ካላደረገ ደግሞ ክሱን እንደአመነ ሊቆጠር እንደሚገባው በፍ/ብ/ሕ/ቁ.83፣ 334/1/መ/ እና 235 ላይ ተመልክቷል፡፡ እንበልና የሁለት ዓመት ጊዜ ያለፈው የኪራይ ሂሣብ እንዲከፍል ክስ የቀረበበት ተከሣሽ ቀርቦ አለመክፈሉን /እዳውን/ ቢያምን ወይም በግልጽ ባይክድ ፍ/ቤቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242ን ተመስርቶ በእምነቱ መሰረት ፍርድ ሊሰጥ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 ወደ ተጠቀሰው የሕሊና ግምት ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ አየታይም፡፡ የያዘውም ፍሬ ነገር የዚህን ስረ ነገር ሕግ ተፈፃሚነት የሚጠይቀው አይሆንም፡፡

በሌላ በኪል ደግሞ ይኸን የኪራይ ሂሣብ እንዲከፍል ክስ የቀረበበት ተከሣሽ ከፍያለሁ ቢልና የቀረበበትን ክስ ቢክድ ፍ/ቤቱ 1ኛ/ ተከሣሹ እዳውን ሊከፍል የሚገባው ስለመሆን፣ አለመሆኑ ጭብጥ ሊይዝ 2ኛ/ በተሹ ቢጠቀስም ባየጠቀስም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024ን ሊመሠረትና ተከሣሹን በሐሊና ግምት ማስረጀው ተጠቃሚ እንዲሆን ሊያደርገው ይገባዋል፡፡ በሕሊና ግምት ተጠቃሚው ተከሣሽ ሌላ ማናቸውንም አይነት ማስረጃ ከማቅረብ ግዴታ ነፃ የሚወጣ ሲሆን ከማሹ ግን ይህ የሕሊና ግምት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2026/2/ መሠረት በመሐላ ብቻ እንዲፈርስለት ለመጠየቅ ይችላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ሁለት ዓመት ያለፈው የኪራይ ሒሣብ እንዲከፍል ክስ የቀረበበት ተከሣሽ ቀርቦ መልስ የሰጠ ወይም መከራከሪያውን ያሰማ አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ አግባብነት ካላቸው የፍ/ብ/ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ሲታይ ተከሣሹ እዳውን አለመክፈሉን ወይም ክሱን ማመኑን የሚያሳየን እንጂ በምንም መለኪያ ክሱን ክዷል ወደሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርሰን የሚተል አይሆንም፡፡ ፍ/ቤቱም በፍሬ ነገርም ሆነ በሐጉ ረገድ ልዩነት የተፈጠረበት ክርክር ቀርቦለታል የሚያሰኝ ባለመሆኑም ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሊያሳርፍበት የሚገባ ጭብጥ ለመያዝ አይችልም፡፡ ይልቁንም ተከሣሹ የመከላከያ መልስ አላቀረበምና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.246 መሠረት በጉዳዩ ጭብጥ እንዲይዝበት የሚገደድበት አይሆንም፡፡ ይህ ደግሞ ተከሣሹ ክሱን እንዳመነ ተቆጥሮ በእምነቱ መሠረት ፍርድ ሊሰጥበት እንደሚገባ የሚያመለክተን ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የእምነት መነሻ ተደርጐ ፍርድ ሲሰጥ ደግሞ ወደ ሕሊና ግምት ማስረጃው መሄዱ አላስፈላጊ ነው፡፡ በውጤቱም ተከሣሹ በሐሊና ግምት ማስረጃው ተጠቃሚ መሆን እንደማይገባውና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024ም እዳው ባልተካደ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ተከሣሹ ቀርባ መልስ /መለሳከያ/ ባቀረበ ጊዜም በፍ/ቤት አነሳሽነት ለውሣኔ መሠረት ሊሆን እንደማይችል የሚያረጋግጥልን ነው፡፡

በተጨማሪም አብዛኛው ድምጽ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.89ን በመጥቀስና ይህ ድንጋጌ የሕሊና ግምቱ ተጠቃሚ የሆነው ወገን የፍሬ ነገር ክርክር የማቅረብ ግዴታውን የሚያስቀርለት ነው በማለት ድንጋጌው ከስረ ነገር ሕጉ ጋር ይጣጣማል የሚል ማጠቃለያ ላይ መድረሱን ተረድተናል፡፡ እኛም ምንም እንኳን የዚህ ድንጋጌ የአማርኛ ቅጅ በጣም ግልጽ ሆኖ ባናገኘውም ከእንግሊዘኛው ቅጂ ጋር በአንድነት ሲታይ አንደኛ ድንጋጌው በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ የተደረገ የሕግ ግምትን እሳቤ አድርጐ የተደነገገ መሆኑን፤ ሁለተኛ የግራ ቀኙን ተሟጋቾች በክርክር ውስጥ መኖር የማጠይቅ መሆኑን፤ እንዲሁም ሶስተኛ አንደኛውን ወገን ተከራካሪ ባይከራከርበትም በሕግ ግምቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ጉዳዩ በሌላው ወገን ያልተካደ ይሆን ዘንድ የሚፈልግ መሆኑን ለመረዳት ያህል ግን የሚበቃ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እነዚህ ሕጉ የሚፈለጋቸው መስፈርቶች ደግሞ እንደ ማስማረጃ ከሚቆጠረው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 ጋርም ሆነ በጉዳዩ ከተያዘው ፍሬ ነገር ጋር የተያያዙ አይደሉም፡፡ ስለሆነም በእኛ እምነት ይህ ድንጋጌ ከመሠረቱም ከዚህ ጉዳይ ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡

እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024ን ጭምር በስረ ነገር ሕጉ ምዕራፍ 7 ክፍል 3 ስር እንደተከፈሉ ይቆጠሩ ዘንድ የሕሊና ግምት የተወሰደባቸውን እዳዎች አስመልክቶ ክስ ሲቀርብ ሙግቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የተመለከተውን መደበኛ የሙግት ሥርዓት ተከትሎ የሚከናወን እንጂ የተለየ ደንብ ሊከተል የሚገባው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተከሣሹ ቀርቦ እዳውን /ክሱን/ በመካድ እስከአልተከራከረም በሕሊና ግምቱ ተጠቃሚ ሊደረግና ከእዳው ነፃ ሊሆን አይገባውም፡፡ ይልቁንም የሕሊና ግምቱ ለፍርድ መሠረት ሊደረግ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለምና ክሱን በማሰረጃ አስደግፎ ያቀረበው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ከሣሽ (አመልካች) ከሱን በመሰረትክበት ጊዜ ያልተከፈለህ ስለመሆኑ በመሐላ እንዲረጋገጥልህ አልጠየቅክም በሚል ምክንያት እዳው አይከፈልህም ሊባል የሚገባው ሆኖ አላገኘውም፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች ስማችን በ2ኛ እና በ4ኛ ተራ የተጠቀሰው ዳኞች የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ፍርድ ተሽሮ አመልካቹ የጠየቀው የቤት ኪራይ እንዲከፈለው ሊወሰን ሲገባ መጽናቱ ተገቢ ሆኖ ስላላገኘነው ፍርድ ሊሻር ይገባው ነበር ስንል በሐሣብ ተለይተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 14974

ዳኞች፡- **አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ**
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ት ማህሌት ገ/ስላሴ

መልስ ሰጪ፡- 1. አቶ መንግሥቱ ኃብ
2. አቶ ዮሴፍ ገ/ሥላሴ

ስለ እንደራሴነት - ከገዛ ራስ ጋር ስለሚደረግ ውል ፍጹም ስለሆነ እንደራሴነት - ጥብቅ የሆነ ቅን ልቡና- የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 2188፣2189፣2209፡- በክሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን - ስለ ወኪሎች - ስለ ባለጉዳዩ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ መቅረት- ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ስለማንሳት የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ህግ ቁጥሮች 57፣78

2ኛ መ/ሰጭ የአመልካች ወኪል ሆኖ ከ1ኛ መ/ሰጭ ጋር በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ በአመልካች ወኪልነቱ 2ኛ መ/ሰጭ መልስ ሰጥቶ ጉዳዩ ውሳኔ እንዲነሳ ያቀረበችውን ጥያቄ የም/ሽ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ወኪልሽ መልስ ሰጥቷል በሚል ውድቅ በማድረጉና ጉዳዩን በይግባኝ ያለው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ በማድረጋቸው የቀረበ አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ፡- የም/ሽ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የኦሮሚያ ሰበር ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

1. አንድ ተወካይ ፍጹም ታማኝ መሆን ያለበት ሲሆን በወካዩ ጥቅምና በራሱ ጥቅም መካከል ግጭት ባለበት ጊዜ ለወካዩ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
2. አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ባቀረበው ክስ ወካዩን ወክሎ መከራከር አይችልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበየሱስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ት ማህሌት ገ/ስላሴ
ተጠሪ፡- 1. አቶ መንግሥቱ ኃብ
2. አቶ ዮሴፍ ገ/ሥላሴ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ብይን የተሰጠው በም/ሽ/ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በአሁኑ ተጠሪዎች የአሁኗን አመልካች ጨምሮ ሶስት ሰዎች ላይ ክስ መስርተው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የአሁኗ አመልካች በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ ልግባ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 78 መሠረት ታመለክታለች፡፡ ፍርድ ቤቱም የአመልካች አቤቱታ ለአሁኖቹ ተጠሪዎች እንዲደርሳቸው አድርጐ ተጠሪዎቹም በክርክሩ ወቅት ለአመልካቿ ወኪል መጥሪያ ደርሶ መልስ የሰጠች ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተቃውመዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የም/ሽ/ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ህዳር 17/1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 78 መሠረት አንድ ሰው ክርክሩ ውስጥ ገብቶ መከራከር የሚችለው በሌለበት እና ሳይከራከር ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ወይም ብይን ሲሰጥ ነው፡፡ አመልካች ግን በተወካይዋ በኩል መጥሪያ ደርሷት መልስ ሰጥታ የተከራከረች በመሆኑና ውክልናው የተነሳ ለመሆኑም የቀረበ ነገር ስለሌለ አቤቱታዋ ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ በይግባኝ ያየው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ውሳኔ ስህተት የሌውም በማለት ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት የዘጋው ሲሆን የዚሁ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለውም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ብይን ላይ ሲሆን የአመልካችዋ ዋና ቅሬታም፣ 2ኛ ተጠሪ ራሱ ክስ አቅራቢ እራሱ መልስ ሰጪ ሆኖ ያቀረበው ክርክር ከህጉ መንፈስ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች ለቀረበው አቤቱታ መልስ እንዲሰጡ ተጠርተው ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ ከመዝገቡ የስር 2ኛ ከሳሽ (የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ) የአመለካች (የስር 3ኛ ተከሳሽ) ወኪል በመሠረተው ክስም በአመልካች ስም መከላከያ መልስ መስጠቱን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አንድ ተወካይ በወካይ ላይ በመሠረተው ክስ በወካዩ ስም መልስ ሊያቀርብ ይችላል ወይ? አቅርቦስ ከሆነ ክርክሩ ወካዩ እንዳቀረበው ሊቆጠር ይችላል ወይ? የሚሉ ነጥቦች የህግ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

አንድ ባለጉዳይ ፍ/ቤት መቅረብ የማይፈቅድ ከሆነ ነገሩን ለማስረዳት፣ ለመከራከር፣ ለሚጠይቀው ሁሉ በቂ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰው በዋናው ባለጉዳይ ተተክቶ በነገረ-ፈጅነት፣ በወኪልነት፣ በጠበቃነት ሊከራከር እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 57 ስር ተገልጿል፡፡ በመሆኑም አንድ ባለጉዳይ በሚከሰስበት ሆነ በሚከስበት ጉዳይ ፍ/ቤት መቅረብ ካልፈለገ ወይም ካልቻለ እሱን በመወከል እንዲከራከር ለሌላ ሰው ውክልና መስጠት የሚችል ሲሆን ይህም ውክልና የሚሰጠው ስለውክልና የሚመለከቱትን የፍ/ብ ሔር ህጉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ወኪል የውክልናውን ስራ የሚፈጽምበት ጊዜ እነዚህን የህጉን ድንጋጌዎች በመከተል ይሆናል፡፡ ወኪሉም ከተሰጠው የውክልና ስልጣን ክልል ሳይወጣ በህጉ መሠረት የሚፈጽሟቸው ተግባራት ወካዩ ራሱ እንደሚፈጽማቸው ተደርገው ይቆጠራሉ (የፍ/ህ/ቁ 2189 (1))፡፡ በመሆኑም አንድ ወኪል ስለሌላው ሰው ሆኖ በፍ/ቤት ክርክር እንዲቀርብ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሠረት የሚያቀርበው ክርክር ባለጉዳዩ እንዳቀረበው ተደርጐ ይቆጠራል፡፡ ይህ አጠቃላይ መርህ ሲሆን አንድ ሰው ስለሌላ ሰው ሆኖ ክርክር እንዲያቀርብ የውክልና ስልጣን ተሰጥቶት እንኳን ቢሆን ወኪሉ ራሱ ወካዩን በከሰሰበት ጉዳይ ግን በወካዩ ስም ክርክር ሊያቀርብ ይችላል ወይ? የሚለው ነጥብ ውክልናን ከሚመለከቱት አጠቃላይ የህጉ ድንጋጌዎች እና ከህጉ አላማ ጋር አገናዝቦ ማየቱ ተገቢ ነው፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውክልና ማለት ተወካይ የሆነ ሰው ወካዩ ለሆነው ሌላ ሰው እንደራሴ ሆኖ አንድ ወይም ብዙ ህጋዊ ስራዎች በወካዩ ስም ለማከናወን የሚገባበት ውል ነው፡፡ (ፍ/ህ/ቁ 2198)፡፡ በመሆኑም አንድ ተወካይ የውክልና ስራ በሚፈጽምበት ጊዜ የወካዩን ህጋዊ ሁኔታዎችን የመለወጥ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ይሕም በመሆኑ ተወካዩ ለወካዩ ፍጹም ታማኝ የመሆን እና የወካዩን ጥቅም ሙሉ ለሙሉ የማስጠበቅ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ስለሆነም ተወካዩ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ቅድሚያ ሊሰጥ የሚገባው የወካዩን ጥቅም ብቻ በመሆኑ የጥቅም ግጭት ባለበት ሁኔታ ተወካዩ በስራው አፈጻጸም ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የጥቅም ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ አንድ ተወካይ ከራሱ ጥቅም ይልቅ የወካዩን ጥቅም ሊያስቀድም ይችላል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ስለዚህም ተወካዩ የራሱን ጥቅም የሚመለከት ጉዳይ ሲያጋጥመው ሁኔታውን ለወካዩ ሳያሳውቅና ወካዩ ሳይስማማ ስራውን እንዳይፈጽም ይከላከላል፡፡ ስለወኪልነት የተደነገጉትን የፍ/ብሔር ድንጋጌዎች ስንመለከትም ተወካዩ ከወካዩ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ጥብቅ የሆነ ቅን ልቦና ሊኖረው እንደሚገባ እና የውክልና ስልጣኑን የሚያስቀሩ ምክንያቶች እንዳለበት (የፍ/ብ/ህ/ቁ 2208)፣ ተወካዩ ስራውን የሚፈጽመው በተለይ ለወካዩ ጥቅም ሊሰጥ የሚችል መንገድ ብቻ መሆን እንዳለበት (ፍ/ብ/ህ/ቁ 2209(1))፣ እንዲሁም ተወካዩ በራሱ ስም ከወካዩ ጋር የሚያደርገው ውል ወካዩ ካላጸደቀው በቀር ሊፈርስ እንደሚችል (የፍ/ህ/ቁ 2188) መደንገጋቸው ተወካዩ ለወካዩ ፍጹም ታማኝ መሆን እንዳለበት እና ለወካዩ ጥቅም ብቻ መስራት እንዳለበት፣ የጥቅም ግጭት ባለበት ጊዜ ሁሉ ሁኔታውን ለወካዩ የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንድ ተወካይ የጥቅም ግጭት ባለበት ጊዜ ለወካዩ ሳያሳውቅ የሚየከናውነውን ስራ ወካዩ ሊቃወመው የሚችል መሆኑን እና በዚህ ሁኔታ የተከናወነው ስራም ወካዩ ካላፀደቀው በቀር ወካዩ ራሱ እንደፈጸመው ሊቆጠር እንደማይገባ ከውክልና ግንኙነት አጠቃላይ ዓላማ እና ከፍ/ብ/ህጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በአመልካች (በስር 3ኛ ተከሳሽ) ላይ የመሰረተው ክስ በወኪሉ እና በተወካዩ መሃከል ግልጽ የጥቅም ግጭተ ፈጥሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ራሱ ከሳሽ ሆኖ የቀረበበትን ጉዳይ ለአመልካች የገለፀላት መሆኑ እና አመልካቿም ተጠሪው የቀረበውን መልስ የተስማማችበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ አመልካቿ እንዲያውም ወኪሏ የሰጠውን መልስ ተቃውማዋለች፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ ራሱ በመሠረተው ክስ ለአመልካች ሳያሳውቅ ያቀረበው መከላከያ መልስ ስለወኪልነት የተመለከቱትን መርሆች እና የህጉን ድንጋጌዎች የሚቃረን በመሆኑ አመልካች በወኪሏ በኩል ክርክር አቅርባለች ማለት አይቻልም፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች በወኪሏ በኩል መልስ ሰጥታ የተከራከረች በመሆኑ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ ልግባ በማለት ልትጠይቅ አይገባም ተብሎ የተሰጠው ብይን የህግ ስህተት አለበት፡፡

<u>ውሳኔ</u>

- አመልካች በሌለችበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ ገብታ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የመሰለውን ይወስን፡፡
- የም/ሽ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ-13/95 በ17/3/95 ዓ.ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 464/95 በ20/6/95 ዓ.ም፣ የኦሮሚያ ፍ/ቤት በመ/ቁ 532/95 በ3/5/96 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 14184

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ውርጌሳ ታደሰ

መልስ ሰጪ፡- አቶ መለሰ ተካ አቶ ፍሬሰንበት አዝማች
አቶ በቀለ ዴልኬራ አቶ አለሙ ደልሊቦ
አቶ ከተማ ኢብሣ አቶ ወ/ሰማያት ዲማ
አቶ ፍቃዱ ራህመቶ አቶ አማረ ተሰማ
አቶ ኤፌሶን መጋቢ

በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት በሙግት ተወካይ ለመሆን ስለ ባለጉዳዩ /ከሳሽ/ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ መቅረብ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር ቁጥሮች 73

አመልካች ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ዕለት በችሎቱ ባለመገኘታቸው ምክንያት ያቀረቡትን ክስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍትሐብሐር ሥነ/ሥርዓት ሕግ ቁጥር 73 መሠረት በመዝጋቱ እና ይህንኑ ትዕዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት በአብላጫ ድምጽ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ው ሳ ኔ፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጣቸው ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡

1. ክስ ያቀረበ ሰው ክሱ የሚዘጋበት ክርክሩን እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ያልቀረበ እንደሆነ ነው፡፡
2. ከተከሣሹ መልስ ለመቀበል የሚያዝ ቀጠሮ ተከሣሹ እንጂ ሕጉ እንደሚያዘው ጉዳዮ የሚሰማበት ቀጠሮ አይደለም
3. መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሳሽ ባይቀርብ ፍ/ቤቱ የተከሳሹን መልስ ተቀብሎ ጉዳዮን ለተከታዩ ክንውን ማዘጋጀት እንጅ ክሱን መዝጋት የለበትም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም
የመ/ቁ. 14184

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ውርጌሳ ታደሰ ጠበቃ ህይሉ አግዘው
መልስ ሰጪ፡- አቶ መለሰ ተካ አቶ ፍሬሰንበት አዝማች
አቶ በቀለ ዴልኬራ አቶ አለሙ ደልሊቦ
አቶ ከተማ ኢብሣ አቶ ወ/ሰማያት ዲማ ዐ/ሕግ አልቀረቡም
አቶ ፍቃዱ ራህመቶ አቶ አማረ ተሰማ
አቶ ኤፈሶን መጋቢ

ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የህግ ነጥብ አንድ ጉዳይ በይግባኝ ፍ/ቤት በሚታይበት ወቅት ከተከራካሪዎቹ የአንዱ መቅረት የሚያስከትለው በሕጉ የተደነገገ ውጤት ምንድነው? የሚል ነው፡፡ ለዚሁ የሕግ ነጥብ መነሣት ምክንያት የሆነው ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ዕለት በችሎት ባለመገኘታቸው ምክንያት አመልካቾችን በሚመለከት ቀርቦ የነበረውን ይግባኝ በፍትሀብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ.73 መሠረት በመዝጋቱ ነው፡፡ አመልካች መዝገቡ ተመልሶ እንዲከፈት ጥያቄ ቢያቀርብም ለባለጉዳዩ መቅረትም ሆነ ለጠበቃው መቅረት የቀረበው ምክንያት በቂ ስላልሆነ የተዘጋው ይግባኝ አይከፈትም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፣ ጉዳዩ በይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም የቀረበ ቢሆንም የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ በድምጽ ብልጫ ፀንቷል፡፡

አመልካች ጠበቃ የሰበር አቤቱታ በመቅረቡና ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ መልስ ሰጪ እንዲቀርቡ ታዞ በጉዳዩ መልስ ቀርቦአል፡፡ የመልስ መልስም እንደዚሁ ቀርቦ ከማኅደሩ ጋር ተያይዞአል፡፡

የሰበር ችሎት በዚሁ የቀረበው የሰበር ማመልከቻ መነሻነት መታየት ያለበት ትልቁ የሕግ ትርጉም አንድ ፍርድ ቤት በይግባኝ ደረጃ ይግባኝ ባይ አልቀረበም በማለት የይግባኝ መዝገቡን ለመዝጋት የሚችለው መቼ ነው? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፍትሐብሔር የሙግት ሂደት የሚመራው በፍትሀብሔር ሥነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሥርዓት ሕግ ጥያቄ መመለስ የሚኖርበት ሕጉ የሚያስቀምጠው ሥርዓት መሠረት ብቻ መሆን ይገባዋል፡፡ የአንዱ ወይም የሌላው ተከራካሪ ፍርድ ቤት በያዘው ቀነ ቀጠሮ አለመገኘት የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለው ነጥብም መሠረታዊ ከሆነ ከመክሰስ መብትና ክስ ከመከላከል መብት ጋር እጅጉን የተያያዘ በመሆኑ መስተናገድ የሚኖረበት ሕጉ የሚያስቀምጠው መስፈርት መሠረት ብቻ መሆን የኖረበታል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በከፊል ውድቅ የደረገው የፍትሀብሔር ሥነ ሥርዐት ሕጉን ቁጥር 73 በመጥቀስ ስለሆነ የትዕዛዙን ትክክል መሆን አለመሆ ለመመርመር በዚህ ቁጥር የሰፈረው ድንጋጌ ስለተከራካሪዎች መቅረብና አለመቅረብ የሚደነግጉትን ተዛማጅ ቁጥሮች መመልከት ያስፈልጋል፣ በቁጥር 73 የሰፈረው ድንጋጌ

> ባንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንሲማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነና ተከሣሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሣሹ በሌለበት ቢሆን የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡ ከሣሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን በመዝጋት ያሰናብተዋል፡፡

በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ ይዘት ለመገንዘብ እንደሚቻለው ክስ ያቀረበ ሰው ክሱ የሚዘጋበት የተከሣሽን መልስ ለመቀበል ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ በያዘበት ቀን ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ሳይሆን ክርክሩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ቀነ ቀጠሮ ያልቀረቡ እንደሆነ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በመሠረቱ ማንም ሰው ክስ ሊያጣ ወይም በከፊል ሊቀርበት የሚገባው ሕግ በግልጽ ለይቶ ባሰፈረው ምክንያት ብቻ ነው፡፡ አንድን ጉዳይ ለማየት የተሰየመ ፍ/ቤት የተለያዩ ክንዋኔዎችን ለመፈፀም በርካታ ቀጠሮዎች እንደሚሰጥ የታወቀ ነው፡፡ ክስ ያቀረበ ሰው በሁሉም ቀጠሮዎች እንዲገኝ የሚጠበቅበት ቢሆንም በተያዘው ቀጠሮ ባለመገኘቱ ምክንያት ያቀረበው ክስ ሊዘጋበት የሚችለው ግን ሕጉ ለይቶና ዘርዝሮ ባስቀመጣቸው ምክንያቶችና አጋጣሚዎች ብቻ ነው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች በቅጡ ለመንዘብ የፍትሐብሐር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን የከሣሽና/ወይም የተከሣሽ አለመቅረብ (non appearance of parties) አስመልክቶ ያስቀመጠውን ሥርዓት ከአጠቃላይ የሙግት ሂደት ጋር አገናዝቦ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ እንደተጠቀሰው በዚህ መዝገብ የሕግ ትርጉም የሚሻው ትልቁ ጥያቄ አንድ ከሣሽ ወይም ይግባኝ ባይ በቀነ ቀጠሮ አልቀረብክም ተብሎ ክሱ /ይግባኙ/ የሚዘጋበት መቼ ነው? የሚለው ነው። ከሕጉ ቁጥሮች 69፣70፣73 ለመገንዘብ እንደሚቻለው ሕጉ በተከራካሪ ወገኖች አለመቅረብ ምክንያት አንድ መዝገብ እንዲዘጋ ወይም ተከሣሹ በሌለበት የነገሩ መሰማት እንዲቀጥል ትዕዛዝ የሚሰጠው ከሣሽ ወይም ተከሣሹ ወይም ሁለቱም ጉዳዩ እንዲሰማ በተቀጠረው ቀን ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ነው። ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የሚሉትን በቅደም ተከተል እንመልከት።

69(1) ነገሩን ለማየት ፍርድ ቤቱ በወሰነው ቀነ ቀጠሮ ከሣሽ ተከሣሾች ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው ተሟልተው መቅረብ አለባቸው። የተከራካሪ ወገኖች መቅረብ እንደተረጋገጠም ክርክሩ መሰማት ይጀምራል።

70 የተከሣሽ ያለመቅረብ
<u>ክርክሩ እንዲሰማ</u> በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ከሣሽ ቀርቦ ተከሣሹ ያልቀረበ አንደሆነ ለጉዳዩ ውሣኔ የሚሰጠው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሥርዓት ነው።

73 ባንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነና ተከሣሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሣሹ በሌለበትም ቢሆን ፍርድ ቤቱ ተከሣሹ በሙሉ ወይም በከፊል ላመነው ጉዳይ የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ይችላል። በከፊል ላመነው ጉዳይ የፍርድ ውሣኔ ለመስጠት ይችላል። ተከሣሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን በመዝጋት ያሰናብተዋል።

አንድን ጉዳይ አይቶ ውሣኔ ለመወሰን በርካታ ቀጠሮዎችን ፍርድ ቤት እንደሚሰጥ የሚታወቅ ሲሆን ከነዚህ በርካታ ቀጠሮዎች መካከል በአንዱ ወይም በሌላኛው ወይም በሁለቱም አለመቅረብ ምክንያት ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሠረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው የባለጉዳዮቹ መቅረት የተከሰተው ጉዳይ ለመሰማት በተቀጠረበት ቀን እንደሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ ጉዳዩ ለመስማት ቀጠሮ የተያዘበት ቀን ከሌሎች ቀጠሮዎች በተለየ ሁኔታ እንዲታይ ሕግ አውጪው መፈለጉ ግልጽ ነው። በተለምዶ ብዙ ፍርድ ቤቶች መልስ ለመቀበል ከሣሽ ወይም ተከሣሽ ወምይ ሁለቱም ያልቀረቡ እንደሆነ ፍርድ ቤቶቹ እነዚህን ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በመጥቀስ ጉዳዩ እንዲዘጋ ወይም ተከሣሹ በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ የሚሰጡ ቢሆንም የድንጋጌዎቹ ይዘት ይህን አሠራር የሚደግፍ አይደለም፡፡ መልስ ለመቀበል የሚያዝ ቀጠሮ ተከሣሹ የጽሁፍ መልሱን ለማቅረብ እንዲችል የሚያዝ ቀጠሮ እንጂ ሕጉ እንደሚያዘው ጉዳዩ የሚሰማበት ቀን ቀጠሮ አይደለም፡፡ በመሆኑም መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሹ ሳይቀርብ ቢቀር ጉዳዩ ለማሰማት በተቀጠረበት ቀን ሳይቀርብ ቀረ ተብሎ መዝገቡ ሊዘጋበት የሚችልበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ በመሠረቱ መልስ ለመቀበል ቀጠሮ የሚያዘው በአንድ ጉዳይ ክስ የተመሠረተበት ሰው በጉዳዩ ላይ የቀረበበትን ክስ ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ ሃሣቡን በጽሁፍ እንዲያቀርብ ማስረጃም ካለው የማሰረጃውን ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ እንዲያቀርብ ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ከከሣሹ የሚጠበቅ ክንዋኔ የለም፡፡ ከሣሹ ሳይቀርብ ቀረ እንኳን ቢባል በፍርድ ቤቱ የሥራ ሂደት ላይ የሚያስከትለው መስተጓጐል ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሹ ባይቀርብ የተከሣሹን መልስ ተቀብሎ ለተከታዩ ክንውን ጉዳዩን ከማዘጋጀት አልፎ መዝገቡን ለመርዝጋት በቂ ምክንያት የለም፣ የመዝገብ መዘጋትን ያህል ትልቅ እርምጃ በአንድ ተከሣሽ ላይ ለመውሰድ ቢያንስ በከሣሹ በኩል መፈፀም የነበረበት ነገር ግን ሳይፈፀም የቀረ በህግ የተደገፈ በቂ ምክንያት መኖር አለበት፡፡ የተከሣሽን የጽሁፍ መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ መዝገቡ እንደሚዘጋ የሚገልጽ ድንጋጌ በሥነ ሥርዓት ህጋችን የትኛውም ክፍል አይገኝም፡፡ የህግ ድጋፍ በሌለበት ሁኔታ የአንድን ተከሣሽ ክስ መዝጋት ደግሞ አግባብ አይሆንም ተከሣሹ ባለመቅረቡ ምክንያት ክሱ እንዲዘጋ ህጉ የሚያዘው ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ከሣሹ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ኑው፡፡ ከሕጉ አደረጃጀትም መገንዘብ እንደሚቻለው ክሱ የሚሰማው የክስና የመከላከያ ጽሁፎች (ከቁጥር 222-240 የፍትብሔር ሥነሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት) ልውውጥ ከተከናወነ በኋላ ነው፡፡ የጽሁፉን ልውውጥ የሚመለከተው የሕጉ ክፍል "ስለክስና ስለመከላከያ ጽሁፍ" በሚል ርዕስ ራሱን የቻለ አንድ ክፍል ሲሆን በዚህ የጽሁፍ ልውውጥ በኋላ የሚከተለው ክንውን ደግሞ "ክስን ስለመስማት" በሚል ርዕስ ራሱን በቻለ ሌላ ምዕራፍ የምናገኘው ነው፡፡ (241-273) ከዚህ የህጉ አደረጃጀት የጽሁፍ መልስ የሚቀርብበት ቀን ቀጠሮ በመርህ ደረጃ የክሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መሰማት ከሚከናወንበት ቀነ ቀጠሮ የተለየ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ከህጉ አደረጃጀት ባሻገር የክስ መሰማትን የሚመለከተው የሙግት ሂደት በሁለት የተከፈለ ሲሆን ሁለቱም የከሣሽና የተከሣሽን መገኘት የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ የመጀመሪያ ክስ የከሣሽና የተከሣሽን መገኘት የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ የመጀመሪያ ክስ ሊከፈት የሚፈፀመውን ሥነ ሥርዓት (First hearing) ለአብነት መመልከት ይቻላል፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 24(1) መሠረት ክሱ መሰማት በሚጀምርበት ቀን ፍርድ ቤቱ የባለጉዳዮቹን ማንነት ካረጋገጠ በኋላ ክሱንና መልሱን እንደሚያነብና ተከሣሹ መልሱ ላይ የካደውን ነገር ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ በቃል እንደሚጠይቀው ይገልጻል፡፡ የዚሁ ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ ወይም ስለሱ ሆኖ የቀረበውን ሰው ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ጉዳዮች ወይም ሌሎች ነገሮች አብራርቶ ለማስረዳት ጠቃሚና ተገቢ መስሎ በገመተው ዘዴ የቃል ጥያቄ በማቅረብ ፍርድ ቤቱ ሊመረምራቸው እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከሣሽ ወይም ተከሣሹ እንዲብራራለት የሚፈልገው ጉዳይ ካለ በፍርድ ቤቱ በኩል እንዲጠየቅለት ማድረግ እንደሚችልም በዚሁ ድንጋጌ ላይ በግልጽ ሰፍሯል፡፡

ይህ የሚያስገነዝበው የመሰማት ሂደት የከሣሽና የተከሣሽ መገኘት የግድ የሚል ተሟጋቾቹም ጭምር የሚሣተፉበት ሂደት መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሂደት ፍርድ ቤቱ ባለጉዳዩችንም ጭምር በማነጋገር ጉዳዩን ለዋናው የሙግት ደረጃ የሚያዘጋጅበት በመሆኑ በከሣሹና የተከሣሹ (ወይም የወኪሎቻቸው) መገኘት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከሁለቱ የአንዱ አለመገኘት ለሂደቱ መስተጓጎል የሚኖረው ተጽእኖም ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ከሌሎች ቀጠሮዎች ይበልጥ ባለጉዳዩች ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ባይቀርቡ የሚከተለው ውጤት ከሌላው የበለጠ ጠንካራ መሆኑ አስፈላጊ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ምዕራፍ 2 (ከቁጥር 241 - 273) ያሉት ሁሉም ድንጋጌዎች የተሟጋቾች አለመገኘት የሚያስከትለውን ውጤት ከመሰማት ሂደት ጋር አያይዘው የሚያቀርቡትም በከፊል በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ለማንኛውም የመሰማት ቀነ ቀጠሮ የተከሣሽን የጽሁፍ መልስ ለመቀበል የሚሰጠው ቀነ ቀጠሮ የተለየ ነው፡፡ በመሆኑም ክርክሩ የሚሰማበት ወቅት ተፈጻሚ እንዲሆኑ የተደነገጉትን ደንቦች የተለየ ባህርይና ዓላማ ባለው መልስ የመቀበል ቀነ ቀጠሮ ተፈጻሚ ማድረግ አግባብነት የለውም፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ቁጥሮች 69፣70 እና 73 ሥር ያሉት ድንጋጌዎች ለመልስ በተቀጠረበት ቀን ተፈጻሚ ካልሆኑ ከሣሹ ወይም ተከሣሹ ወይም ሁለቱም ሳይቀርቡ የቀረ እንደሆነ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የትኞቹ ናቸው የሚል ጥያቄ መነሣቱ የማይቀር ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 67፣70፣73 እና ሌሎች ተዛማጅ ድንጋጌዎች ከተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁለቱም ጉዳዩ ለመሰማት (hearing) በተቀጠረበት ቀን ያልቀረቡ እንደሆነ ብቻ ተፈጻሚ ስለሚሆኑ ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ (እንደነገሩ ሁኔታ ይግባኝ ባይ) ወይም ተከሣሹ (የይግባኝ መልስ ሰጪ) ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ለሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የሚሆን ሌላ የህግ ድጋፍ መኖር ይኖርበታል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ከ192 እስከ 199 ባሉት ቁጥሮች ፍርድ ቤት እንዲፈፀሙ ያዘዛቸው ጉዳዮች ሳይፈፀሙ ሲቀሩ ስለሚሰጡ ትዕዛዞች የተለያዩ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ በቁጥር 199 ሥር ያለው ድንጋጌ አሁን ለያዝነው ጉዳይ በተለይ አግባብነት ያለው ነው፡፡ ቁጥር 199(1) ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት የሆነ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ ያልተፈፀመ ቢሆንም እንኳ ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ በዚያው ቀነ ቀጠሮ የመሰለውን ውሣኔ ለመስጠት ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር (2) ደግሞ ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው በተከራካሪዎቹ ወገኖች ጉድለት ያልሆነ እንደሆነ ግን ፈርድ ቤቱ ሌላ ቀጠሮ ይሰጣል ይላል፡፡

አንድ ጉዳይ የተከሣሽን መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ያልቀረቡ እንደሆነ (እንደነገሩ ሁኔታ ይግባኝ ባይ ወይም መልስ ሰጪ) ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መስጠት የሚገባቸው በዚህ ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡ ከድንጋጌው ንኡስ አንቀጽ አንድ ለማየት እንደሚቻለው ለቀጠሮ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም በቀረ ቁጥር መዝገብ የሚዘጋበት ሁኔታ እንደሌለ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ትዕዛዝ የሚሰጠው አንድ ጉዳይ እንዲፈጽም የታዘዘው ወገን ያን የታዘዘውን ጉዳይ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መልሱን እንዲያቀርብ የታዘዘ ተከሣሽ ይህን ክንውን ሳይፈጽም ቢቀር ፍርድ ቤቱ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመለሰውን ይወስናል፡፡ ከሣሹ ከመልስ በተቀጠረበት ቀን ባይቀርብ ግን ከሣሹ እንዲፈጽመው የታዘዘው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ነገር ስለሌለ ቀጣዩን ክንውን አስመልክቶ ትዕዛዝ ከመስጠት ውጪ የከሣሹን መዝገብ መዝጋት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የተከሣሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሹ ያልቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የተከሣሹን የጽሁፍ መልስ ከማህደሩ ጋር አያይዞ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ወስኖ ለዚሁ አስፈላጊ ትዕዛዞችን መስጠት አለበት እንጂ መዝገቡን መዝጋት የለበትም፡፡ ከላይ ተደጋግሞ እንደተገለፀው መዝገብ የሚዘጋው ከሣሹ ጉዳዩን ለመስማት በፍርድ ቤት ቀጠሮ በተያዘበት ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበ እንደሆነ ነው፡፡

የተከራካሪዎች መቅረብን አስመልክቶ በሰፊው ማየት የስፈለግን በያዝነው ጉዳይ ከፍተኛው ፍ/ቤት የይግባኝ ባይን መዝገብ የዘጋው መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ይግባኝ ባዩ አልቀረበም በማለት የፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.73ን በመጥቀሱ ነው፡፡ ከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው የአሁኑ አመልካች ፍርድ ቤት ሳይቀርብ የቀረውን ጉዳዩን ለማሰማት በተያዘ ቀጠሮ አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ለመዝጋት ምክንያት አድርጐ የጠቀሰው የሕግ አንቀጽ የሰጠውን ትዕዛዝ ፈጽሞ የሚደግፍ አይደለም፡፡ መልስ ለመቀበል በተያዘው ቀጠሮ ከይግባኝ ባይ የሚጠበቅ ክንውን ስላልነበረም ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን መልስ ተቀብሎ ቀጣዩን ቀጠሮ (ክንውን) በማስመልከት ትዕዛዝ ከሚሰጥ በስተቀር በተከሣሹ ላይ የፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 199ን መሠረት በማድረግ የሚሰጠው ትዕዛዝ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም ከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ የዘጋው እንዲፈጽም ትዕዛዝ ተሰጥቶት ሳይፈጽመው የቀረ ክንውን ሳይኖርና መዝገብ እንዲዘጋ ሕግ ያስቀመጠውን ሥርዓት ሳይከተል በመሆኑ ይህ ፍርድ ቤት አልተቀበለውም፡፡ መዝገቡን መልሶ ላለመክፈት የሰጠው ምክንያት ስህተት ባይሆንም ፍርድ ቤት የሠራውንና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስተካከል ሲገባው ያለፈውን ግድፈት በሥ.ሥ.ሕ.ቁ 207 እና 211(2) መሠረት ማቀናት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቷል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

(1) ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ.04000 ጥር 21 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.11523 ጥቅምት 6 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

(2) ከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ እንዲከፈት አድርጐ ካቆመበት እንዲቀጥል ታዟል፡፡

(3) ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 14047

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡-- ዶ/ር ዳንኤል አለሙ

መልስ ሰጪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሮማነወርቅ የማነብርሃን

2. ወ/ሮ በቀለች ወረደ

3. ወ/ሮ ምስለአበባ ውቤ

ውል - የግዴታ ዎች መቅረት - ሰለ ይርጋ - የውልን ጉዳይ ስለሚመለከት ማስረጃ-ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥሩ የህልና ግምቶች - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1856፣2024

አመልካች ታህሳስ 1 ቀን 1981 ዓ.ም ከመ/ሰጭዎች ጋር ባደረጉት የጥብቅና ውል መሠረት ለሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ብር 46000(አርባ ስድስት ሺህ) እንዲከፈላቸው በ1988 ዓ.ም ያቀረቡትን ክስ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክሱ ክፍያው መጠየቅ ከነበረበት ጊዜ ሁለት ዓመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024(ለ) መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በሚል ውድቅ ስላደረውና ውሣኔውን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስላጸና የቀረበ አቤቱታ፣

ውሣኔ፡- የሰበር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ጸንቷል።

1. በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024 በተደነገገው የሕግ ግምት ተጠቃሚ ያልሆነ ወገን (ከሣሽ) ክፍያው እንዳልተፈጸመ የማስረዳት ሸክም ያለበት ሲሆን ይኸን ሸክሙን መወጣት የሚችለው መሃላ በማውረድ ብቻ ነው።
2. የሕሊና ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ደንብ ድንጋጌዎች የተለዩ ናቸው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፣- ዶ/ር ዳንኤል አለሙ

መልስ ሰጪዎች፡-1ኛ. ወ/ሮ ሮማነወርቅ የማነብርሃን በክርክሩ አልቀረቡም
2ኛ. ወ/ሮ በቀለች ወረደ
3ኛ. ወ/ሮ ምስለአበባ ውቤ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሣኔ

አመልካች ለሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባፀናው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የሰጠው አመልካች መልስ ሰጭዎች በፍርድ ቤት ያላቸውን የተለያዩ ጉዳዮች በተለየዩ መዝገቦች እነሱን ወክዬ እንድከራከር ወክለውኛል፣ የጥብቅና ውሉም ታህሳስ 1 ቀን 1981 ተፈርሟል፣ በውሉ መሠረት ለፈፀምኩት የጥብቅና አገልግሎት በአጠቃላይ ብር 46.000 (አርባ ስድስት ሺህ) ይከፈለኝ በማለት ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ መልስ ሰጭዎች ለክሱ በሰጡት መልስ ውሉ የተፈፀመው በ1981 ሲሆን ክሱ ግን የቀረበው በ1988 ነው፣ ይሄውም የተጠቀሰውን ክፍያ ሳንጠየቅ ሁለት ዓመት ያለፈ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024(ለ) መሠረት ክፍያው እንደተፈፀመ ይቆጠራል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ሌሎች ክርክሮችንም አንስተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም መልስ ሰጭዎች ክፍያውን በጽሁፍ አላመኑም፣ ክሱ ከሁለት አመት ገደቡ በኋላ በመቅረቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024(ለ) መሠረት የህሊና ግምት እንዳይወሰድ መልስ ሰጭዎች የመሃላ ቃል እንዲሰጡ አልጠየቁም በመሆኑም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024(ለ) መሠረት ክፍያው መፈፀሙን የህሊና ግምት ወስዷል፡፡ በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህንኑ ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በተሰጠው ውሣኔ ላይ ሲሆን ይዘቱም ሲጠቃለል አመልካች የጥብቅና አገልግሎት የሰጠሁት በተለያዩ መዝገቦች ሲሆን የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄውም እንደየችሎቱ የክርክር ሂደት ጉዳዮች ተጠቃልለው ውሣኔ ሲያገኙ መቅረብ የሚገባው በመሆኑ ጥያቄው በዚሁ መሠረት ቀርቧል፡፡ መልስ ሰጭዎች የጥብቅና ውሉ መፈፀሙን አልካዱም፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 ሊፈርስ የሚችል የህሊና ግምት የያዘ ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2025 እና ተከታታዮቹ የሕሊና ግምቱ እንዳይወሰድ (ለማፍረስ) ያቀረብኩትን ክርክር ፍ/ቤቱ ሊመለከትልኝ ይገባ ነበር፣ ስለሆነም የሰበር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለፈፀመበት እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መልስ ሰጭዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ የጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ባለመቅረባቸው ፍርድ ቤቱ በአመልካች በኩል የቀረበውን ማመልከቻ ብቻ መሠረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በቀረበው ጉዳይ በሰበር መታየት ያለበት ነጥብ የሥር ፍርድ ቤቶች በፍ.ብ.ሕ.ቁ 2024 የሰፈረውን የሕሊና ግምት አመልካች በመሠረተው ክስ ተፈፃሚ ያደረጉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ1981 ዓ.ም ከመልስ ሰጪዎች ጋር በመሰረትነው የጥብቅና ውል መነሻነት ላበረከትኩት አገልግሎት ብር 46.000 (አርባ ስድስት ሺህ) ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡ ክሱ ይዘት ለመመልከት እንደሚቻለው አመልካች ከመልስ ሰሊዎች የሚፈልጉት ክፍያ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ነው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት መልስ ሰጪዎች ከውሉ የሚመነጨውን የክፍያ ግዴታቸውን አልተወጡም በሚል ነው፡፡ የጥብቅና አበል መከፈል አለመከፈሉ አከራካሪ በሆነ ጊዜ የማስረዳት ሸክሙ የማን ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 (ለ) ከሁለት ዓመት በላይ የሆነውን የጥብቅና ክፍያ በሚመለከት የሕሊና ግምት በማስቀመጥ በውል የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን እንደከፈለ ይቆጠራል በማለት የሕግ ግምት ተጠቃሚ ያደርገዋል፡፡ በሌላ በኩልም በሕጉ 2026(1) ይህን የሕሊና ግምት ማፍረስ እንደማይቻልና የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ አልተከፈለኝም የሚል ወገን ያለው ብቸኛ ግምቱን የማፍረሻ አማራጭ መሃላ እንዲወርድለት መጠየቅ ብቻ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡

በዚህ መሠረት መከፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ወይም ክፍያውን ያልጠየቀ ተዋዋይ በውሉ መሠረት የሚገባውን ክፍያ እንዳገኘ የሚገመትበት ብቻ ሳይሆን ክፍያው እንዳልተከፈለው የሚያስረዳው የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓትም ሌላ ፍሬ ነገርን ለማስረዳት ከሚከተለው ሥርዓት የተለየ ይሆናል፡፡ በመደበኛ የሙግት ሂደት የማስረዳት ሸክም ያለበት ወገን እንዲያስረዳ የሚጠበቅበትን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ብዙም የሕግ ገደብ የለበትም፡፡ ፍሬ ነገሩን ያስረዳልኛል የሚለውን ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ ይችላል፡፡ የጽሁፍ፣ የሰው ወይም የአካባቢ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ሸክሙን ሊወጣ ይችላል፡፡ በፍትሐብሄር ሕጉ 2024 የሚሸፈን ፍሬ ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜ ግን የማስረዳት ሸክሙ ከአንዱ ወገን (ከተከሣሽ) ወደ ሌላው (ወደከሣሽ) ከመዛወሩ በተጨማሪ የማስረዳት ሸክሙን መወጣት የሚቻልበት የማስረጃ አይነትም ውሱን ነው፡፡ በ2026 መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የማስረዳት ሸክም የተሸጋገረበት ከሣሽ ይህን የማሰረዳት ሸክሙን መወጣት የሚችለው መሣላ በማውረድ ብቻ ነው። ሌላ የትኛውም ዓይነት ማስረጃ ቢሆን የሕሊናውን ግምት ሊያፈርሰው አይችልም።

በዚህ ህግ የሰፈረው የህሊና ግምት ከይርጋ ሕግ ጋር የሚያያዝ አይደለም። በ2024 የሰፈረው የሕሊና ግምት የማስረዳት ሸክም ከተከሣሽ ወደከሣሽ ያዞራል፣ የማስረዳት ሸክም የዞረበት ከሣሽ የሚያስረዳበትን መንገድ ይደነግጋል። በሆኑም በጊዜ ማለፍ ምክንያት ክሱ እንዲቋረጥ አያደርግም። የይርጋ ሕግ በሌላ በኩል በጊዜ ማለፍ ምክንያት የመከሰስ መብትን ስለሚያስቀር ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የማስረዳት ሸክም ያለበት ወገን ማነው? የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል አልተወጣም? ወዘተ- - ጥያቄዎችን በማንሣት ወደ ጉዳዩ ፍሬ ነገር ሊገባ አይችልም። በመሆኑም የይርጋው ጊዜ በፍ.ብ.ሕ ቁ.1845 መሠረት 10 ዓመት የሆነ ጉዳይ በዚሁ ሕግ 2024 በተደነገገው የሕሊና ግምት መሠረት ሊስተናገድ ይችላል። የይርጋ ጊዜው ያላለፈን ጉዳይ በሕጉ ቁጥር 2024 መሠረት እንደተከፈለ መቁጠር እርስ በርሱ የሚጋጭ ነገር ማከናወን አይደለም።

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች ላቀረበው ክስ ምክንያት የሆነው ውል የተመሠረተው በ1981 ዓ.ም መሆኑን ግራ ቀኙ ተስማምተውበታል። የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሣሾች የሕጉ ግምት ተጠቃሚዎች ናቸው ያለው የተጠየቀው ክፍያ በ1981 ዓ.ም መከፈል የነበረበት ነው በማለት ነው። ለዚሁ መነሻ ያደረገው ተጨማሪ ፍሬ ነገር አመልካች ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ መከፈል ነበረበት በተባለው መጠን ላይ ወለድ መጠየቁ ነው። አመልካች በሌላ በኩል ክፍያው መከፈል የነበረበት ጊዜ ውሉ የተፈፀመበት 1981 ዓ.ም ሳይሆን ጉዳዩ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች የሚታይ በመሆኑ ውሣኔ የተሰጠበት ጊዜ መሆን ነበረበት ብሏል። ሆኖም ውሣኔ የተሰጠው መቼ እንደሆነ ለሰበር አቤቱታ ባቀረበው ማመልከቻ ላይ አልገለፀም። ሕጉ ከሚያዘው ከ2 ዓመት በታች መሆኑን ለማሣየት ክሱ ከቀረበበት ከ1988 ዓ.ም በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የተወሰነ መሆኑን ማስረዳት ሲኖርበት በዚህ ረገድ የቀረበ ነገር የለም። በመሆኑም ውሉ የተፈረመበትና በከሣሽ መከፈል ከነበረበት ተብሎ ለወለድ ስሌት መሠረት የሆነውን 1981 ዓ.ም መነሻ መደረጉ የሚነቀፍ አይደለም። ክሱ በ1988 ዓ.ም የቀረበ እንደመሆኑ ተከሣሾቹ የፍ.ብ.ሕ.ቁ 2024(ለ) "ለጠቀቆች፣ ለውል አዋዋዮች ለሌሎችም የሕግ አማካሪዎች በሙያ ሥራቸው ወይም በሹመት ሥራቸው ላደረጉት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
አገልግሎት የሚከፈል ዕዳ» ዕዳው መከፈል ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለው የሕግ ግምት ተጠቃሚ ናቸው መባሉ በአግባቡ ነው።

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሕግን ግምት ተፈጻሚ ከማድረግ አልፎ አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚል ውሣኔ ባለመስጠቱ እንደአመልካች አባባል በፍ.ብ.ሕ.ቁ 1845 የሰፈረውን የይርጋ ሕግ አለቦታው ተጠቅሞበታል ሊባል አይችልም። በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ በፍ.ብ.ሕ. 2024(ለ)ን መሠረት አድርጐ ውድቅ ማድረጉም ሆነ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 337 መሠረት ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚያመለክት አይደለም።

መልስ ሰጪዎች የሕግ ግምት ተጠቃሚ እስከሆኑ ድረስ፣ የውሉን መኖሩን አለመካዳቸው፣ በውሉ መሠረት ለመክፈል መስማማታቸውና ማመናቸው፣ ውሉ ፈርሷል ብለው አለመከራከራቸው ወዘተ... የሙግቱን ውጤት የሚቀይረው አይደለም። ውሉ አለ እንኳን ቢባል ዞሮ ዞሮ ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን እንደተከፈለ መቆጠሩ የሚቀር አይደለም። ይህ ሊቀር የሚችለው መሃላ እንዲወርድ ተጠይቆ እንደሆነና መሃላው የከሣሽን ክስ ያረጋገጠ እንደሆነ ነው። ይህ ስለመሆኑ ከሰበር ማመልከቻውም ሆነ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገቡ የተገነዘብነው ነገር የለም። በመሆኑም አመልካች ያቀረበው የሰበር ማመልከቻ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም።

ውሣኔ

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመቁ.5095 የካቲት 11 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፀንቷል። ይጻፍ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 15835

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካቶች፡- ሼል ኢትዮጵያ አ/ማ
መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ

በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን

- ስለ ባለ ጉደዩ ፍ/ቤት ሣይቀርብ መቅረት - የተከሣሽ ያለመቅረብ- ጉዳዩ ለመልስ በተቀጠረ ዕለት የተከሣሽ መልስ አለማቅረብ- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥሮች 70፣233

የአሁኑ መልስ ሰጪ በከፍተኛው ፍ/ቤት በአመልካች ላይ በመሠረቱት ክስ የአሁን አመልካችን መልስ ለመቀበል በተያዘው ቀጠሮ ቀርቦ መልስ ባለማቅረቡ ፍ/ቤቱ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ መ/ሰጭ ክሱን በማሻሻላቸው የተሻሻለው ክስ እንደ አዲስ ክስ መቆር ስላለበት መልስ ልስጥበት በማለት አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውድቅ ስላደረገውና ይህንኑ ትእዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ስላጸናው የቀረበ አቤቱታ፣

<u>ው ሣ ኔ ፡-</u> የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጧቸው ትእዛዞች ተሽረዋል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. ተከሣሽ ከክሱ አስወጥቶ /Ex-parte/ ጉዳዩ መታየቱ የሚቀጥለው ተከሣሹ ጉዳዩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ችሎት ያልቀረበ እንደሆነ ነው፡፡
2. ጉዳዩ የተከሣሽን መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ተከሣሽ ያልቀረበ እንደሆነ መልሱን በጽሁፍ ከማቅረብ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጥቅሞች ይቀረቡታል እንጂ በቀጣዩ ሂደት ከመሳተፍ አይከለከልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 29 ቀን 1997

የመ/ቁ 15835

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካቶች፡- ሼል ኢትዮጵያ አክስዮን ማህበር

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ

ፍ ር ድ

በዚህ መሠረት ለቀረበው ክርክር መነሻ የሆነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና የጠቅላይ ፍ/ቤት የተቀበለው ትዕዛዝ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር ማመልከቻ ያቀረበ ሲሆን ጉዳዩ በሰበር መታየት ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ መልስ ሰጪም ቀርቦ በጉዳዩ ላይ የጽሁፍ ክርክሩን አቅርቦአል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ከፍተኛ ፍ/ቤት የከሣሽ ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ መስጠቱን አውቆ ለተሻሻለው ክስ መልስ እንዲያቀርብ ሲጠይቅ ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 73 መሠረት ጉዳዩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ የተወሰነ መሆኑን በመግለጽ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ በማድረጉ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የጣሰ አሠራር ነው በማለት በሰበር እንዲስተካከልለት አመልክቷል፡፡ የአመልካች ዋና ክርክር የተሻሻለው ክስ እንደ አዲስ ክስ መቆጠር ስላለበት ቀደም ብሎ ክርክሩ በሌለበት እንዲታይ የተወሰነ ቢሆንም ለተሻሻለው ክስ መልስ የመስጠት መብቱ ሊቀርበት አይገባም የሚል ነው፡፡ መልስ ሰጪ በዚህ ጉዳይ ላይ መለሱን በጽሁፍ በማቅረብ የክሱ መሻሻል ቀደም ሲል የተሰጡትን ትእዛዞች የሚሽር ባለመሆኑ አመልካች ለተሻሻለው ክስ መልስ ለማቅረብ ያቀረበው ጥያቄ በሁለቱም ፍቤቶች ውድቅ መደረጉ የሕግ ስህተት መኖሩን አያሳይም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካች መልስ ለማቅረብ በተቀጠረበት ቀን መልሱን ይዞ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ መታዘዙን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ተገንዝቧል፣ በተሻሻለው ክስ መልስ ሊያቀርብ አይገባም የሚል ትእዛዝ የተሰጠውም ቀደም ብሎ የተሰጠውን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ እንደሆነ ተረድቷል፡፡ በዚህም መሠት ጉዳዩን በአግባቡ ለማስተናገድ የአሁኑ አመልካች መልስ እንዲያቀርብ በተቀጠረበት ዕለት መለሱን ይዞ ባለመቅረቡ የሚከተለው ሕጋዊ ውጤት ምንድነው? የሚለውንና ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ነጥቦች መመርመር ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

አንድ ተከሣሽ ጉዳዩ ለመልስ በተቀጠረበት ዕለት መልሱን ይዞ ካልቀረበ ክርክሩ በሌለበት የሚሰማ መሆኑ ፍርድ ቤቱ በሚልክለት መጥሪያ ላይ እንደሚገልጽለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 233 ላይ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቀ 70 ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ከሣሽ ቀርቦ ተከሣሽ ያልቀረበ እንደሆነ ተከሣሹ ያልቀረበው የተላከለት መጥሪያ ደርሶት ከሆነ ተከሣሹ በሌለበት የነገሩ መሰማት እንደሚቀጥል ይደነግጋል፡፡ አነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች ሁለት በተለያዩ ጊዜ የሚከናወኑ የሙግት ደረጃዎችን የሚመለከቱ ቢሆኑም የተከሣሽን መቅረት አስመልክቶ የሚያስከትሉት ውጤት ተመሳሳይ ይመስላል፡፡ የጽሁፍ መልሱን ሳያቀርብ የቀረ ተከሣሽ በ233 መሠረት በሌለበት ጉዳዩ እንደሚሰማ ጉዳዩ ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ያልቀረበ ተከሣሽም በተመሳሳይ ሁኔታ ጉዳዩ በሌለበት እንደሚሰማ በቁጥር 70(ሀ) መሠረት ትእዛዝ የሚሰጥበት ይመስላል፡፡ የሁለቱም ድንጋጌዎች የአማርኛ ቅጂ ለመልስ በተቀጠረበት ቀን መቅረትና ጉዳዩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን መቅረት አንድ አይነት ውጤት ያላቸው እንደሆነ የሚገልጹ ቢሆኑም የሁለቱም የእንግሊዝኛ ቅጂዎች ግን የተለየ ጽንሰ ሃሳብ የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡

የእንግሊዝኛ የ70(ሀ) የእንግሊዝኛ ድንጋጌ ስለ Ex-part ሲናገር የ233 ግን የሚደነግገው ስለ default proceeding ነው፡፡ሁለቱም የተለያየ ይዘት የተለያየ ውጤት ያላቸው ናቸው፡፡

የ70(ሀ) የእንግሊዝኛ ቅጂ

> 70 where the plaintiff appears and defendant does not appear when the suit is called on for hearing (a) if it is proved that the summons was duly served, the suit shall be heard ex-parte

በማለት ሲደነግግ አግባብነት ያለው የ233 ክፈል ደግሞ

> …. The court shall cause… requiring him to appear with his statement of defense to be fixed in the summons and informing him that the case wile be proceeded withnotwithstanding that he does not appear or that he appears without his statement of defense. **በማለት ይደነግጋል፡፡**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁለቱን የአንግሊዝኛ ቅጂዎች በማነጻጸር ለመገንዘብ እንደሚቻለው ለመልስ በተቀጠረ ቀን ተከሣሽ መልሱን ይዞ ባይቀርብ የሚከተለው ውጤት ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ባይገኝ ከሚከተለው ውጤት ጋር አንድ አይነት አይደለም፡፡ የ233 ድንጋጌ መለሱን ባያቀርብም የጉዳዩ መሰማት እንደሚቀጥል (default proceeding) ከሚይሳይ በቀር ተከሣሽ ክርክር እንዲወጣ የሚያደርግበት ሥርዓት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በ70(ሀ) ስር ያለው ድንጋጌ ጉዳዩ ለመሰማት በተቀጠረበት ቀን የቀረ ተከሣሽ ጉዳዩ አሉ በሌለበት መቀጠል(default proceeding) ብቻ ሳይሆን ክርክሩ እንዲወጣ (ex-part) እንደሚደረግ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይህም በአማርኛ ቅጂ ላይ ያለው አገላለጽ በእንግሊዝኛው ላይ ያለውን ሃሳብ በትክክል አለማስተላለፉን ያመለክታል፡፡

የትርጉም ልዩነት ሲኖር የአማርኛውን ቅጂ በመውሰድ ዕልባት መስጠት ይቻላል በማለት ጉዳዩ ማጠቃለል አንዱ አማራጭ ነው፡፡ ሆኖም ይህ አማራጭ አሁን በያዝነው ጉዳይ በግልጽ የሚታየውን የትርጉም ስህተት እንዲቀጥል የሚያደርግ በመሆኑ ትክክለኛ አማራጭ ነው አንልም፡፡ ይልቁም የተከሰተውን የትርጉም ልዩነት ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማ እንዲሁም ተከሣሽ በቀረበበት ክስ የመደመጥ መብትን ይበልጥ ሊያስከብር በሚችል ሁኔታ መተርጉም በበለጠ የፍትህ አስተዳደርን ዓላማ በበለጠ ስለሚያሳካ የአንግሊዝኛው ቅጂ መከተሉን መርጠናል፡፡

በዚህም መሠረት አንድ ተከሣሽ ክስ እንዲወጣ መደረግ ያለበት ጉዳዩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ እንጂ መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ካልቀረበ መሆን የለበትም፡፡ ይህ አተረጓጎም ተከሣሹ መልስ ለመቀበል በተያዘ ቀጠሮ ሳይቀርብ ቢቀር ፍርድ ቤቱ ምን ያደርጋል የሚል ጥያቄ ማስከተሉ የሚቀር አይደለም፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ፍርድ ቤት የሰጠው ቀጠሮ ሳይከበር ቢቀር ፍርድ ቤቱ ምን ያደርጋል ከሚል ሌላ ጥያቄ ጋር ተያይዞ መመለስ ያለበት ነው፡፡

በሙግት ሂደት ፍርድ ቤት የተለያዩ ጉዳዮች መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ቀጠሮዎችን ይሰጣል ሆኖም ፍ/ቤቱ የሰጠው ቀጠሮ በአንዱ ወይም በሌላው ተሟጋች በተሰተጓጎለ ቁጥር ለመስተጓጎሉ ምክንያት የሆነው ወገን ክርክክ እንዲወጣ (Ex-parte) አይደረግም፡፡ የቀጠሮው አለመከበር ቀጠሮ ከተሰጠበት ምክንያት ተነጥሎ የሚታይ ባለመሆኑ በየጉዳዩ የተለያየ ትዕዛዝ የሚሰ ቢሆንም መሠረታዊው የጉዳዩ ሂደት የሚስተናገደው በሥነ ሥርዓት ሕግ ምዕራፍ 7 በሚገኙት መርሆዎችና ድንጋጌዎች መሠረት መሆን አለበት፡፡ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 194 እንደተገለፀው በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን ያለበት ድርጊት በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ካልተከናወነ ዋጋ እንደሌለው የገልጻል፡፡ በዚህም መሠረት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መልሱን እንዲያቀርብ የታዘዘ ተከሣሽ መልሱን ከማቅረብ ጋር ተያየዘው የሚነሱ ጥቅሞች ይቀሩበታል፡፡ በቀጣዩ ሂደት ከመሳተፍ አይከለክልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አሁን አመልካች በተሻሻለው ክስ ላይ መልስ መስጠት አትችልም የተባለው ቀደም ብሎ ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን መለሱን ይዞ አለመቅረቡን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ጉዳዩ ለመልስ በተቀጠረ ቀን ተከሣሹ መልሱን ሳያቀርብ ቢቀር የጽሁፍ መልስና የማስረጃ ዝርዝር የማቅረብ ዕድሉን ከሚያጣ በቀር ከክርክሩ ውጪ እንዲሆን መታዘዝ አልነበረበትም፡፡ በዚህም ምክንያት አንድን ተከሣሽ ሕጉ ከሚፈቅደው ሁኔታ ውጪ ከክርክር ውጪ ማድረግ በጉዳዩ ላይ የሥነ ሥርዓት ግድፈት መፈጸሙን ያመለክታል፡፡ ክሱ እንዲሻሻል ትእዛዝ ሲሰጥ ተከሣሽ መልስ ማቅረብ አትችልም የተባለው ከዚህ ሥነ ሥርዓት ግድፈት ጋር በተያያዘ ምክንያት ነው፡፡ አመልካቹ ከክርክሩ መውጣት ሳይኖርበት አውጥቶ ለተሻሻለው ክስ መለስ አታቀርብም መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሥነ ሥርዓት ግድፈት መፈጸሙን በማመን ይህን ግድፈት ማስተካከል ሲገባው አልፎታል፡፡ በመሆኑም የሰበር ችሎት የተፈፀመውን የሥነ ሥርዓት ግድፈት በፍ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 211 ስር በተደነገገው መሠረት ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ውሣኔ

1. የአሁን አመልካች በከፈተኛ ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ከክርክር ውጪ የተደረገው በአግባቡ ስላልሆነ ወደ ክርክሩ ይግባ፡፡
2. ለተሻሻለው ክስ መልስ ማቅረብ እንዲችል በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሻሻለው ክስ ግልባጭ ይሰጠው፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 15992

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት
መልስ ሰጪ፡- ወ/ት ሶስና አስፋው

ውል- ስለውል አፃፃፍ/ ፎርም/- ስለ ውል አፃፃፍ ነፃነት- ስለ ውል አጻጻፍ /ፎርም/ የተሰጠ ደንብ አለመፈጸም የሚያስከትለው ውጤት - የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ስለሚመለከቱ ውሎች፣- የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ስለሚመለከቱ ውሎች በስምምነት ስለሚሆን ያጻጻፍ አይነት - የግዴታዎች ቀሪ መሆን - ስለ ይርጋ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1719፣1720/1/ 1723፣ 1726 ፣1727፣ 1845

በአመልካችና በመልስ ሰጭ መካከል የተደረገው የኪራይ ውል በሁለት ምክንያት ያልተረጋገጠ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1726/1/ እና 1727/1/ መሠረት የውል ረቂቅ እንጅ አስገደጅነት የለውም፣ አመልካች ከጠየቀው ኪራይ ውስጥ እስከ 8/2/89 ያለው መጠየቅ ከሚችልበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት አመት ያለፈው በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. በኢትዮጵያ የውል ህግ ውል አመሰራረት ደንቦች መሰረት በህግ ወይም በተዋዋዮች በራሳቸው የተለየ ፎርም ካልተፈለገ በቀር ለውል መመስረት በሁለት ተዋዋዮች መካከል የስምምነት መኖር ብቻ በቂ ነው፡፡
2. የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የሚደረግ ውል ባለቤትነትን /ownership/፣ የአላባ ጥቅምን /usufruct/፣ መያዣን /mortgage/ ወይም ሌላ አገልግሎትን /servitude/ ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የተደረገ ካልሆነ በቀር የግል በህግ በተመለከተው አጻጻፍ /ፎርም/ መከናወን የለበትም፡፡ የኪራይ ውል ከነዚህ ውሎች ውጭ በመሆኑ ከተዋዋዮች ስምምነት ካልሆነ በቀር በህጉ የተለየ አጻጻፍ /ፎርም/ የሚጠይቁት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይሆኑበትም፡፡
3. የህግ ግምት ድንጋጌዎች ከይርጋ ድንጋጌዎች የተለዩ ናቸው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብድልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት
መልስ ሰጪ፡- ወ/ት ሶስና አስፋው

በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ መርምሮ ችሎቱ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለሰበር ለቀረበው ጉዳይ መነሻ የሆነው ውሣኔ የተሰጠው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የውሣኔውም ይዘት የቤት ኪራይ ውል በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተረጋገጠ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1727/2/ እና 1726/1/ መሠረት የውል ረቂቅ እንጂ አስገዳጅነት አይኖረውም፣ በመሆኑም ከሣሽ ማስረጃዬ ነው ብሎ ያቀረበው ሰነድ ይህንን ስለማያሟላና በአመልካችና በተጠሪ መካከል የኪራይ ውል አለ ሊባል ስለማይችል ከሣሹ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት የአሁን መልስ ሰጭ ከ23/5/70 ዓ.ም እስከ 30/1/91 ዓ.ም ያልተከፈለ የኪራይ ሂሣብ ብር 65,790.67 እና ወለድ ብር 168,785.90 በድምሩ ብር 234,576.57 እንድትከፍል ያቀረበውን ክስ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም የሚል ነው፡፡ ይኸው ፍ/ቤት ተከሣሽ ያቀረበችውን ይርጋን የሚመለከት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ከሣሽ ከጠየቀው ክፍያ ውስጥ እስከ 8/2/89 ዓ.ም ድረስ ያለው በይርጋ ይታገዳል በማለት ቀደም ሲል በ23/10/92 ዓ.ም ብይን ሰጥቷል፡፡

ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ይህን ውሣኔ በመቃወም ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለሰበር ችሎቱ የሰበር ማመልከቻ አቅርቧል፡፡

የሰበር ችሎት በዚህ የክርክር ሂደት

1ኛ. ይርጋን አስመልክቶ በሰጠው ትዕዛዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2ኛ. የኪራይ ውል በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተደረገ አይፀናም በማለት የሰጠው ውሣኔ የህግ ትርጉም የሚያስነሱ በመሆናቸው ጉዳዩ በሰበር ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፤ በዚህም መሠረት መልስ ሰጪ መልሱን፣ አመልካች ደግሞ የመልስ መልሱን እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡

የሰበር ችሎቱ በቀረበለት ጉዳይ የህግ ትርጉም የሚሹትን ነጥቦች ከፍሬ ነገር ጉዳዮች በመለየት ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት፣

1ኛ. የሚፀና የኪራይ ውል ለመመስረት መሟላት ያለበት የህግ መስፈርት ምንድን ነው?

2ኛ. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የተመለከተውን የሕግ ግምት ክስን በይርጋ ከሚያግደው ድንጋጌ /1845/ ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? የሚሉትን የሕግ ነጥቦች መርምሮአል፡፡

<u>የሚፀና የኪራይ ውል ለመመስረት ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት በተመለተ፤</u>

ከላይ እንደተገለፀው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ ያቀረበውን ክስ ውድቅ ያደረገው በከሣሽ በኩል የቀረበው ሰነድ በሁለት ምስክሮች አልተፈረመም በማለት ነው፡፡

የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1719/1/ በጠቅላላው ሥርዓት በሁለቱ ወገን ተዋዋዮች በማናቸውም ሁኔታ የተደረገ ስምምነት ውል ለማድረግ በቂ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ በግልጽ ለመገንዘብ እንደሚቻለው በሁለት ተዋዋዮች መካከል በህግ የሚፀና ሕጋዊ ውጤት ያለው ውል ለመመስረት በሁለቱም መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ነው፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ የውል ሕግ የውል አመሰራረት መሠረታዊ መርህ በህግ ወይም በተዋዋዮች በራሳቸው የተለየ ፎርም ካልተፈለገ በስተቀር ለውል መመስረት በሁለቱ ተዋዋዮች መካከል የስምምነት መኖር ብቻ በቂ ነው የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ውል ህጉ ያስቀመጠውን የፎርም መስፈርት አያሟላም ተብሎ ውድቅ ሊደረግ የሚችለው ይህን ውል የሚመለከት በግልጽ የተቀመጠና የተለየ የአጻጻፍ ሥርዓት /ፎርም/ መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ህጉ የተለየ ጽሁፍ የሚጠይቅ በሆነ ጊዜ ይኸው ሥርዓት እስካልተሟላ ድረስ ውሉ እንደረቂቅ ከሚቆጠር በቀር በተዋዋዮች መካከል የሚፀናና አስገዳጅነት ያለው ህጋዊ ግንኙነት ሊመሰረት አይችልም (1720(1))፡፡ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት የሆነው ይኸው የሕግ ድንጋጌ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ ነው፡፡ ሆኖም ይህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሕጉ የተለየ ፎርም የግድ የሚልባቸው ውሎች ብቻ ነው። በመሆኑም መጀመሪያ መታየት ያለበት ነጥብ የኢትዮጵያ ህግ ቤትን አስመልክቶ የሚደረግ የኪራይ ውል በተለየ ፎርም እንዲከናወን ይጠይቃል ወይስ አይጠይቅም የሚለው ነው?

ስለ ውል አጻጻፍ /ፎርም/ የሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕግ ክፍል /አንቀጽ 1719-1730/ የኪራይ ውል የተለየ ፎርም መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ ድንጋጌ የለውም። በፍርድ ቤቱ በቀጥታ ባይጠቀስም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው ድንጋጌ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ስለሚመለከቱ ውሎች የሚደነግገው አንቀጽ 1723 ነው። ሆኖም ይህም አንቀጽ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረጉ ውሎች የተለየ ፎርም እንዲኖራቸው የሚጠይቅ ቢሆንም የኪራይ ውልን ግን የሚያጠቃልል አይደለም። ከሕጉ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው በዚሁ ድንጋጌ መሠረት የተለየ ፎርም እንዲከተሉ የሚፈለጉት ውሎች የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ሁሉም ውሎች ሳይሆኑ በድንጋጌው ውስጥ ተለይተው የተቀመጡ ውሱን የውል ዓይነቶች ናቸው። አግባብነት ያለው የቁጥር 1723 ድንጋጌ ይዘት የሚከተለው ነው።

1723/1/ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለቤትነት ወይም ባንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የአላባ ጥቅም መብት ወይም የመያዣ ወይም የሌላ አገልግሎት መብት ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉት ውሎች ሁሉ በጽሁፍና በማገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል የማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ፊት መሆን አለባቸው።

ከዚህ ድንጋጌ በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግ ውል በተለየ ፎርም እንዲፈፀም ግድ የሚሆነው ውሉ

1. ባለቤትነትን /ownership/
2. የአላባ ጥቅምን /usufruct/
3. መያዣን /mortgage/ ወይም
4. ሌላ አገልግሎትን (servitude) ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የተደረገ

እንደሆነ ብቻ ነው። አንድ ውል የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከትም ቢሆን ከእነዚህ ውሎች በአንዱ ውስጥ የሚካተት እስካልሆነ ድረስ በተለየ ፎርም መከናወን የለበትም። ከእነዚህ ውሎች በአንዱም ውስጥ ከማይካተቱና በዚህም ምክንያት የተለየ ፎርም ከማያስፈልጋቸው ውሎች መካከል የኪራይ ውል አንዱ ነው። የኪራይ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የባለቤትነት መተላለፍን የሚመለከት አይደለም። የአላባ ጥቅምን፣ መያዣን ወይም ሌላ አገልግሎት /servitude/ ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረግም አይደለም። በመሆኑም የተለየ ፎርም የሚጠይቀው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ የቤት ኪራይን ለሚመለከቱ ውሎች አግባብነት የለውም።

በሌላ በኩል ሕጉ ከሚያስቀመጠው አስገዳጅ ፎርም ውጪ ተዋዋይ ወገኖች የውላቸው አፈፃፀም ልዩ በሆነ አጻጻፍ ሥርዓት ሊወሰኑት እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1719/3/ ይደነግጋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ተዋዋዮቹ ሕጉ የማያስገድደውን ፎርም ለመፈፀም የተስማሙ እንደሆነ ውሉ ፍጹም የሚሆነው የተስማሙበትን የውላቸውን አፈጻጸም ሞልተው ሲዋዋሉ ብቻ እንደሆነ የሕጉ ቁጥር 1721 ይደነግጋል። በዚህ ህግ መሠረት የፎርሙን ዓይነትና ይዘት የሚወስኑት ተዋዋዮቹ ራሳቸው በመሆናቸው ሊከተሉ ስለፈለጉት ፎርም በመካከላቸው ግልጽ የሆነ ስምምነት መኖር ይገባዋል። በቁጥር 1719 እንደተገለፀው በመርህ ደረጃ ውል ለመዋዋል የስምምነት መኖር ብቻ በቂ በመሆኑ ውሉ እንዲፀና ተዋዋዮቹ እንዲፈፀም የፈለጉት ተጨማሪ ፎርማሊቲ ምን እንደሆነ ማወቅ የሚቻለው ተዋዋዮቹ ባደረጉት ውል ብቻ ነው። ስለዚህ የፎርሙን አይነት የምስክሮቹን ብዛት፣ ስለመመዝገብ አስፈላጊነት፣ አዋዋይ ፊት ስለመቅረብ ወዘተ ተዋዋዮቹ በፍላጎት የጨመሩት ፎርም ስለመኖሩ በተዋዋዮቹ መካከል ከተደረገው ስምምነት መገንዘብ መቻል አለበት።

ተዋዋዮቹ ውላቸውን በጽሁፍ ካሰፈሩ የጽሁፉን ፎርማሊቲ እንደፈለጉ መገመት ቢቻልም ይህ በጽሁፍ የሰፈረው ስምምነት በምስክሮች እንዲረጋገጥ ወይም እንዲመዘገብ፣ ወይም አዋዋይ ፊት እንዲቀርብ መፈለጋቸውን የሚያሳይ አይሆንም። በጽሁፍ ከመሆኑ በተጨማሪ ሌሎቹም ፎርማሊቲዎች እንዲሟሉ መፈለጋቸው በጽሁፉ በራሱ ወይም በሌላ መልክ ስምምነት መኖሩን የሚያሳይ ነገር መኖር አለበት።

በመሆኑም ተዋዋዮች በጽሁፍ መዋዋላቸውን ብቻ መሠረት በማድረግ ውሉ በምስክሮች ካልተረጋገጠ አይፀናም ማለት ተዋዋዮቹ ያልፈለጉትንና ያልተስማሙበትን ፎርም ከፍላጎታቸው ውጪ እንዲጫንባቸው ማድረግ ስለሚሆን ትክክለኛና ሕጉን የተከተለ አተረጓጎም አይደለም። ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተረጋገጠ አይፀናም የሚለው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1727/2/ ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው ውሉ በጽሁፍ እንዲሆን ግዴታ የተጣለ እንደሆነ ወይም ተዋዋዮቹ በስምምነት በሁለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ምስክር ፊት እንዲረጋገጥ ሲፈልጉ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ውጪ ተዋዋዮች የፈረሙትን ሰነድ በመካከላቸው የውል ግንኙነት ለመመሥረት በቂና ብቸኛ ፎርሙ አድርገው ከተቀበሉት ፍርድ ቤቶች ፍላጎታቸውን ከማስፈፀም ውጪ ሌላ ተጨማሪ ፎርም ሊጠይቁ አይገባም፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት ኪራይን የሚመለከተው የፍትሐብሔር ህጉ ሌላው ክፍልም ቤትም የሚመለከት የኪራይ ውል የተለየ ፎርም እንዲከተል የሚያስገድድ ድንጋጌ የለውም፡፡ /ቁጥር 2896-3018/፡፡ ይልቁንም የዚሁ ክፍል አካል የሆነው አንቀጽ 2898 የሚደነግገው የኪራይ ውልን ለማረጋገጥ ስለሚያስፈልገው የማስረጃ አይነት እንጂ የሚፀና የኪራይ ውል ለመመሥረት መኖር ስለሚገባው ጽሁፍ /ፎርም/ አይደለም፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 “ቢሆንም የኪራዩ ውል የመከናወኑን ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ይህ ውል መኖሩን ምስክሮች በማቅረብ ወይም በግምት አስተያየት ለማስረዳት ይቻላል” በማለት ስለሚደነግግ የኪራይ ውል መኖሩን ለማረጋገጥ ምስክሮች ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ ያመለክታል፡፡ ይህም ቀድሞውኑ የሚፀና የኪራይ ውል ለመመስረት የተለየ ፎርም መኖር አስፈላጊ አለመሆኑን ይበልጥ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ህጉ የማይጠይቀውን የፎርም መስፈርት መሠረት በማድረግ አመልካች ያቀረበው ሰነድ ረቂቅ እንጂ የሚፀና ውል አይደለም ማለቱ የውል ህጉን በተሣሣተ መንገድ መተርጎሙን የሚያመለክት ነው፡፡ ከላይ እንደተብራራው የኪራይ ውል ልዩ ፎርም የሚጠይቅ ባለመሆኑ በአመልካች በኩል ቀረበ የተባለው ሰነድ በሁለት ምስክር አለመፈረሙ ብቻውን ውል የለም ወደሚል መደምደሚያ የሚወስድ አይደለም፡፡

የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2898/1/ የኪራይ ውልን ለማስረዳት የጽሁፍ ማስረጃ እንደሚጠይቅ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ለማስረጃነት የሚፈለገው ጽሁፍ ለውሉ መጽናት (validity) ከሚፈለገው ጽሁፍ ጋር ተመሳሳይ ፎርማሊቲ እንዲኖረው ሕጉ አይጠይቅም፡፡ በመሆኑም ለማስረጃነት የሚፈለግ ሰነድ የግድ በሁለት ምስክሮች መፈረም አለበት ሊባል አይችልም፡፡ ለማስረጃነት የሚፈለግ ሰነድ ያስረዳል የተባለውን ፍሬነገር ለማረጋገጥ የሚያስችል ተአማኒነት እስከአገኘ ድረስ ፍርድ ቤቱ የግድ በምስክሮች ፊት አልተፈረመም ወይም ለውል መጽናት የሚፈለጉትን ሌሎች መስፈርቶች አላሟላም በማለት ዋጋ እንዲያጣ ለማድረግ የሚያስችለው የህግ ድጋፍ የለውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለዚህ 1ኛ. የኪራይ ውል በጽሁፍ መሆን እንዳለበት የሚያስገድድ ህግ ስለሌለ 2ኛ.ተዋዋዮች በጽሁፍ መዋዋላቸው ብቻውን ምስክርም እንዲኖር መፈለጋቸውን ስለማያሳይ፣

3ኛ.ለማስረጃነት የሚፈለግ ሰነድ የግድ በምስክር መረጋገጥ ስለሌለበት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውንና ማስረጃዬ ነው ያለውን የውል ሰነድ የፍትሐብሔር ሕጉን አንቀጽ 1720/1/ እና 1727/2/ በመጥቀስ ረቂቅ እንጂ አስገዳጅነት ያለው ውል አይደለም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አተረጓጎም በመሆኑ ይህ ፍርድ ቤት አልተቀበለውም፡፡

<u>በሕግ ግምትና በይርጋ ድንጋጌዎች መካከል ያለው ግንኙነት በተመለተ</u>

ከዚህ ሌላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ሲመለከት አመልካች ከጠየቀው ክፍያ እስከ 8/2/89 ዓ.ም ድረስ ያለውን በይርጋ ታግዷል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህም ረገድ ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሕግ 2024 የተቀመጠውን የሕግ ግምት (presumption of payment) የተለየ ይዘትና ዓላማ ካለው የይርጋ ሕግ (Period of limitation) ጋር በማምታታት መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያመለክታል፡፡

የይርጋ ሕግ አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ፍሬ ነገር መመርመር ሳያስፈልገው አንድን ክስ ውድቅ የሚያደርግበት ሥርዓት ሲሆን የሕግ ግምት ግን ጉዳዩ ፍርድ ቤት ቀርቦ በተከራካሪዎች መካከል የቀረበው ማስረጃ ሲመዘን ተፈጻሚ የሚሆን ደንብ ነው፡፡ በመሆኑም አልፎ አልፎ የውጤት መመሳሰል የሚያጋጥም ቢሆንም የሕግ ግምትን ተፈጻሚ ለማድረግ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ፍሬ ነገርና አግባብነት ያለውን ሕግ እንዲመረምር የግድ የሚል ሲሆን ይርጋ ግን ጊዜውን በመቁጠር ብቻ ክሱ በፍሬ ነገር ደረጃ እንዳይሰማ የሚያደርግ ሥርዓት ነው፡፡

የፍትሐብሔር ሕጉ ከ2020-2024 ባሉት ድንጋጌዎች የተለያዩ የህግ ግምቶች አስቀምጧል፡፡ እነዚህ የሕግ ግምቶችን እንደብዙዎቹ የህግ ግምቶች አንድ ክስ ለችሎት ቀርቦ በሚታይበት ወቅት የማስረዳት ሸክም ያለበት ማነው? በሕግ የሰፈረውን ግምት ማፍረስ የሚቻለው እንዴት ነው? ወ.ዘ.ተ. የሚሉትን ማስረጃን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንጂ አንድ ጉዳይ በጊዜ ማለፍ ምክንያት ክስ እንዳይቀርብበት የሚከለክሉ የይርጋ ደንቦች አይደሉም፡፡ በመሆኑም ሁለት ዓመት ያለፈው ዕዳ እንደተከፈለ የሚቆጥረው አንቀጽ 2024 ሁለት ዓመት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ካለፈው በጉዳዩ ላይ የሚቀርበውን ክስ በይርጋ የማገድ ውጤት የለውም፡፡ አንድ ክስ በይርጋ ይቋረጣል ወይስ አይቋረጥም የሚለውን በሚመለከት /ተከሣሹ በ2024 በተቀመጠው ድንጋጌ ተጠቃሚ በሆነባቸው ጉዳዮችም ጭምር/ ተፈጻሚ የሚሆነው የውልን ግንኙነት የሚመለከተው አጠቃላይ የይርጋ ሕግ ነው፡፡ አጠቃላይ የይርጋ ገደብ ደግሞ በ1845 ሥር እንደተደነገገው 10 ዓመት ነው፡፡ በዚህ መሠረት አንደ ክስ በይርጋ የሚታገደው ክሱ ከመቅረቡ ከአስር ዓመት በላይ ሲሆን እንጂ ሁለት ዓመት የሞላው እንደሆነ አይደለም፡፡ ከሁለት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች ባለው ጊዜ ውስጥ የሚገኘውና በክሱ የተጠቃለለው ክፍያ በቁጥር 2024 በተቀመጠው የሕግ ግምት የሚሸፈን በመሆኑ ከሣሹ የማስረዳት ሸክሙን መወጣት አለመወጣቱን በመመርመር ፍርድ ቤቱ በፍሬ ነገሩ ውሣኔ የሚሰጥበት እንጂ ከወዲሁ በይርጋ ታግዷል በማለት ወደ ሥረ ነገሩ ሳይገባ ክክርክር ውጪ የሚያደርገው አይደለም፡፡

በመሆኑም በዚህም ረገድ ፍርድ ቤቱ ክስ የቀረበበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ እስከ 8/2/89 ዓ.ም ድረስ ያለው ሂሣብ በይርጋ ይታገዳል ማለቱ ትክክል አይደለም፡፡ ክሱ የቀረበው በ4/2/91 ዓ.ም በመሆኑ በይርጋ የሚታገደው ከ4/2/81 ዓ.ም በፊት ያለው ሂሣብ ብቻ ነው፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.3993 በ9/10/95 እና ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.23335 የሰጧቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡
2. ፍ/ቤቱ ፍሬ ነገሩን መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ወደ ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይመለስ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ 17191

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

ወ/ት መስፍን አቁበ ዮናስ

አመልካች፡- አስቴር አርአያ

መልስ ሰጭ፡- አቶ ግርማ ወዳጆ

ውል - የውል ጉዳይ አወሳሰን - ስለ ውሎች ውጤት ውለን በመተርጎም ሰበብ ደኞች አንድ ውል ሊፈጥሩ ስላለመቻላቸው - ስለ አንዳንድ ውሎች የተጻፉ ለዩ ለዩ ደንቦች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1711፣1731፣1676/2/፣2635፣2640፣2646

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካከ ባቀረበችው ክስ በጠየቀችው መሠረት ተጠሪ አመልካች ከከፈለው ብር 35,000/ ሰላሣ አምስት ሺህ/ በተጨማሪ በፍርዱ ከተገኘው ጥቅም 20% ብር 124,188.59 /አንድ መቶ ሃያ አራት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ ለአመልካች እንዲከፍል ሲወስን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ አመልካች ለሰጠችው አገለግሎት ካገኘችው መደበኛ ክፍያ በተጨማሪ በፍርድ ከሚገኘው ጥቅም 20% ታስቦ እንዲከፈላት በውል የተደረገው ቃል በፍትህ ሆነ በርትዕ የሚደገፍ አይደለም በሚል የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ውሳኔ፤- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

1. ህግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች ውጭ ተዋዋይ ወገኖች የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደፈለጋቸው የመወሰን መብት ያላቸው ሲሆን በዚህ መሰረት የሚደረጉ የውል ስምምነቶች በተዋዋይ ወገኖች መካከል እንደ ህግ ሆነው ይቆጠራሉ፡፡
2. ሆኖም ልዩ የዕውቀት ያላቸውን የስራ ውሎች የሚያደርጉ ተዋዋዮች ስምምነት ላይ የደረሰባቸው የስራ ዋጋዎች ከመጠን በላይ መሆናቸው ግልፅ በሆነ ጊዜና ለሙያ ስራ ተግባሩም ክብር ተቃራኒ ሆኖ በተገኘ ጊዜ መጠኑን ዳኞች በመሰላቸው ሊቀንሱት ይችላሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ሰበር ችሎት

የመ/ቁ17191
ሐምሌ 29 ቀን 1997

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበ ዮናስ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስተር አርአያ

ተጠሪ፡- አቶ ግርማ ወዳጆ

መዝገቡን መርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በሰበር ችሎቱ ለቀረበው ጉዳይ መነሻ የሆነው ክስ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ በሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ሥራ የካቲት 3 ቀን 1987 በተደረገው የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ውል መሠረት በማድረግ ተጠሪ ለአመልካች ከከፈለው ብር 35,000 (ሠላሣ አምስት ሺህ ብር) በተጨማሪ "ከፍርዱ ከሚገኝ ጥቅም 20% ሊከፍል የተስማሙበትን ብር 520,000 (አምስት መቶ ሃያ ሺህ ብር) አመልካች በክሱ ምክንያት ካወጣው ወጭና የጠበቃ አበል ጋር ይከፈል በማለት ክስ መስርቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን አከራክሮ የአሁኑ ተጠሪ «ጥቅም» አላገኘሁም በሚል በሙያ አገልግሎት ውሉ የተስማማበትን ክፍያ አልከፍልም ማለቱ አግባብ አለመሆኑን ገልጾ፣ የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ግምት መሠረት በማድረግ 124,188.59 (አንድ መቶ ሃያ ራት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ ሣንቲም) የዳኝነቱንና የጠበቃ አበሉን ጨምሮ ይከፈል በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ፣ አንድ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ሙያተኛ ለአገልግሎቱ እንዲከፈለው ከተወሰነለት መደበኛ የክፍያ በተጨማሪ «ከፍርድ ከሚገኘው ጥቅም» ታስቦ እንዳከፈለው የሚደረግ የውል ቃል በርትዕም ሆነ በፍትህ የሚደገፍ አይደለም በማለት የሥር ፍቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች በሰበር እንዲታይላት ያቀረበችው ማመልከቻ የሕግ ትርጉም የሚያስነሱ ነጥቦች ያሉት መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀር ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ተጠሪ መልሷን አመልካች ደግሞ የመልስ መልሱን እንዲያቀርቡ ተደርጐ ክርክሩ አብቅቷል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ በዋናነት የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጭብጥ የእውቀት ጠባይ ያላቸው የሥራ ውሎችን አስመልክቶ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ስምምነት በተደረሰባቸው የክፍያ መጠኖች ላይ አለመግባባቶች ሲነሱ የዳኞች ሚና ምን ይሆናል? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ማንኛውም ውል በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ ላይ ተመስርቶ የማደረግ ስምምነት ነው፡፡ ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች ውጭ ተዋዋይ ወገኖች የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት ያላቸው መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1711 ያሰገነዝባበናል፡፡ ውሉን ለመዋዋል ሕጉ በሰጠው ነፃነት መሠረት የሚደረገው የውል ስምምነቶች በግራ ቀኝ ተዋዋይ ወገኖች መካከል መብትና ግዴታዎች የሚጥሉ በመሆናቸው ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ እንደ ሕግ ሆነው የሚያገለግሉ መሆናቸውን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1731 መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የአሁኗ አመልካችና ተጠሪ የካቲት 3 ቀን 1987 ዓ.ም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ውል ያደረጉ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በዚህ ውል ስምምነት መሠረት ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ ተይዞብኛል የሚለውን ቤት በማስመለስ ረገድ የአሁኗ አመልካች ለምታበረክተው ሙያዊ የጥብቅና አገልግሎት ብር 35,000 (ሠላሣ አምስት ሺህ ብር) ለመክፈልና ከፍርዱ ከሚገኘው ጥቅም 20% ለመክፈል የተስማሙ መሆኑን ከሥር መዝገቡ ተረድተናል፡፡ በዚህ የውል ስምምነት ቤት የተመለሰለት የአሁኑ ተጠሪ ብር 35,000 (ሠላሣ አምስት ሺህ) ለአመልካች የከፈለ ቢሆንም ከፍርድ ከሚገኘው ጥቅም ለመክፈል የተስማሙበትን 20% እንዲከፍል ክስ በቀረበበት ጊዜ «ጥቅም» አላገኘሁም በሚል ሲከራከር የቆየ ቢሆንም ጉዳዩን የመረመረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሉን መሠት በማድረግ የንብረቱን ግምት አስልቶ ተጠሪ ብር 124,188.59 (አንድ መቶ ሃያ ራት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ ሣንቲም) እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከፍ ሲል የገለጽነውን የውል ሕግ መሠረታዊ መርህ የሆነውን "በፍቃደኝነት ወዶ መዋዋልን" መሠረት አድርጐ ውሣኔ የሰጠ ቢሆንም

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የዚህ መርህ አፈጻጸም በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ አግባብ ካላቸው ልዩ ድንጋጌዎች ጋር እንዴት መገናዘብ እንደሚገባው ሳይመረምር ከውሣኔ እንደደረሰ ለመገንዘብ ችለናል።

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ በግራቀኙ መካከል በሕጋዊ መንገድና በፈቃደኛነት የተቋቋመን ግልጽ ውል ትርጉምንና ርትዕን ምክንያት በማድረግ የፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1711፣1714(2) እና 1733 ከሚደነግጉት ውጭ እና በወቅቱ በሥራ ላይ ያልነበረን ደንብ ዋቢ በማደረግ «ከፍርድ የሚገኘውን ጥቅም» ለሙያዊ አገልግሎት በሚደረግ ስምምነት ውስጥ ሊጠየቅ አይገባም በማለት ተዋዋይ ወገኖች በስምምነት ያስቀመጡትን ግልጽ የውል ቃል ያለምንም የዉል ማፍረሻ ምክንያት ውድቅ እንዲሆን ማድረጉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል።

ከፍ ብለን ለማሳየት እንደሞከርነው የየትኛውም ሕጋዊ ውል መሠረቱ በፈቃድ መስጠት ላይ የተመሠረተ ስምምነት መሆኑ አያከራክርም። ተዋዋይ ወገኖች ሕጉ በሰጣቸው ነፃነት ተጠቅመው ንብረትነትን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ለማቋቋም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ስምምነት ማድረግ እንደሚችሉ ይታወቃል። ይህ በጠቅላላ ክፍሉ የተነገረው የውል መሠታዊ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህን ጠቅላላ ደንቦች የሚለውጡ ወይም የሚያሟሉ ስለ አንዳንድ ውሎች የተጻፉ ልዩ የሆኑ ደንቦች ካሉ በፍትሐብሔር ሕግ 5ኛ መጽሐፍ እና በንግድ ሕጉ የሚመለከቱ ስለመሆኑ የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1776(2) ያስገነዝባል።

በዚህም መሠረት አሁን ግራቀኙ እየተከራከሩበት ያለው ሙያዊ የዕውቀት ሥራ የሚመለከት ውል በፍትሐብሔር ሕጉ 5ኛ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት ሌሎች መካከል አንደኛ እንደሆነ እንገነዘባለን። ልዩ የእውቀት ጠባይ ያላቸው የሥራ ውሎች ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2632 እና በሚቀጥሉት ቁጥሮች ውስጥ በተመለከቱ ድንጋጌዎች የሚመሩ ናቸው። እነዚህ የውል አይነቶች ልዩ ዕውቀትን የሚመለከቱ በመሆናቸው የተለየ ስምምነት ከሌለ በቀር የእውቀት ሥራውን የተዋዋለው ሰው ግዴታዎቹን ራሱ መፈፀም እንደሚጠበቅበት ከሕጉ ቁጥር 2636(1) መገንዘብ ይቻላል።

ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ፈቅዶ የመዋዋል መርህን ተጠቅመው እነዚህን አይነት መሰል ውሎች መዋዋል ቢችሉም በነዚህ ልዩ ውሎች መሠረት ስምምነት ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የተደረሱባቸው የሥራ ዋጋዎች ከመጠን በላይ መሆናቸው ግልጽ በሆነ ጊዜ እና ለሙያ ሥራ ተግባሩም ክብር ተቃራኒ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የሥራ ዋጋ መጠኑን ዳኞች በመሰላቸው ሊቀንሱት እንደሚችሉ ተደንግጓል። የዚህ ሕግ አይነተኛ ዓላማ የተለየ እውቀት በሚሻው ጉዳይ ዙሪያ አማራጭ የሌለውን ወይም አማራጩ በእጅጉ ሊጠብበት የሚችለውን ተዋዋይ ወገን የሙያውን ተግባር ከሚያከናውነውና ልዩ እውቀት ካለው ሙያተኛ ተዋዋይ ወገን ጋር ውልን ፈቅዶ በመዋዋል ረገድ የሚኖረውን ቦታ (position) በተቻለ መጠን ለማቀራረብ እንደሆነ ይገመታል። በዚህ ረገድ በአብነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ጉዳዮች መካከል ከቀዳጅ ሀኪሞች፣ ከጥርስ ሐኪሞች ወይም ከአእምሮ በሽታ ሐኪሞች እና ሰዎችን ከማከም ኪነጥበብ ጋር ተያይዘው የሙያቸውን ተግባር የሚያከናውኑ ሰዎች ከበሽተኞቻቸው ወይም ከወኪሎቻቸው ጋር ባደረጉዋቸው ውሎች መነሻነት ስምምነት የተደረሰባቸው የሥራ ዋጋዎች ከመጠን በላይ ሆነው በተገኙ ጊዜ እና ሕይወትን መታደግን ዋንኛ ሙያዊ መርህ አድርጎ ከተነሣው የዋጋውን መጠን ሊያሻሽሉት እንደሚችሉ የፍት.ሕግ ቁጥር 2640 እና 2646 ይደነግጋሉ።

በያዝነው ጉዳይ ግራቀኙ የልዩ ዕውቀት ፀባይ ያለው አገለግሎት ሥራ ውል ያደረጉ መሆኑ ይታመናል። ንብረቱ የተወሰደበት የአሁኑ ተጠሪ ለሚሰጠው ሙያዊ አገልግሎት በውሉ የተመለከተውን ብር 35,000 እና በፍርድ ከሚገኘው ጥቅም 20% ለመስጠት ተስመቶ የነበረ መሆኑን ይህ ችሎት በሚገባ ተገንዝቧል። ይህ ስምምነት ውልን ፈቅዶ በመዋዋል መርህ ላይ ተመስርቶ የተደረገ ውል አይደለም ለማለት እንኳን የሚያስችል ነገር ባይኖርም ከፍ ብለን ከላይ ሕጉ ሊጠብቃቸው ከተነሳው ዓላማ አኳያ ጉዳዩን በጥልቀት ስንመረምረው የአሁኗ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ለሰጠችው ሙያዊ አገልግሎት 35,000 (ሰላሣ አምስት ሺህ) የተከፈላቸው መሆኑ ታውቋል። ይህ ክፍያ ከንብረቱ ግምት አኳያ በመቶኛ ሲሰላ 17% ይሆናል። አሁን አመልካች በተጨማሪ እንዲከፈላት እየጠየቀች ያለችው 20% ከቀድሞ ክፍያ ጋር ሲደመር የጠቅላላ ቤቱን ግምት 37% መሆኑ ታውቋል። የተጠየቀው የገንዘብ መጠን ደግሞ ከንብረቱ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በተለምዶ ለአገልግሎቱ ከሚጠየቀው ክፍያ ጋር ሲታይ እጅግ በጣም የተጋነነና ለሙያውም ሥራ ክብር ቢሆን ተቃራኒ የሆነ መሆኑን አምነንበታል።

በመሆኑም ስምምነት የተደረሰበት የሥራ ዋጋ መጠን የበዛ እና ለሙያ ሥራ ክብርም ተቃራኒ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ዳኞች መጠኑን እንዲቀንሱ ሕጉ የሰጣቸውን ሥልጣን በመጠቀም የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች የንብረቱን ግምት ማለትም የብር 620,942.98

https://t.me/ethiopianlegalbrief
(ስድስት መቶ ሃያ ሺህ ዘጠሀን መቶ አርባ ሁለት ብር ከዘጠና ስምንት ሣንቲም) 10% (አሥር በመቶ) የሆነውን ገንዘብ እንዲከፍል ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ቀደም ሲል በውሉ መሠረት የወሰደው ብር 35,000 ከክፍያው ገንዘብ ላይ ተቀናሽ ሊሆን የሚገባ መሆኑን አምነንበታል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- ተጠሪ ብር 27,094.30 (ሃያ ሰባት ሺህ ዘጠና አራት ብር ከሠላሣ ሣንቲም) ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ይከፈል፣
- የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፣
- የፊደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሐምሌ 8 ቀን 1996 ዓ.ም በፍ/ብ/ይ/ቁ 14821 የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

ቅፅ 2

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ህዳር 1998 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማውጫ

1. የሰበር መ/ቁ 13223/ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አስፋው አበበ/ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ባቀረቡትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማናቸውም አይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪ እንዲቀርብለት በመስጠት ስላለበት ትዕዛዝ/.....1
2. የሰበር መ/ቁ. 14414/ የጊምቢ አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ/ በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ከመ/ቤቱ ጋር ባለው ስራ ክርክር የአዋጅ ቁ.42/85 ተፈፃሚ ስላለመሆኑ..... 10
3. የሰበር መ/ቁ 15270 /የአስር አለቃ ተሻገር አስታጥቁ እና አቶ አዊስ አው አበዲ/ በከተማ ቦታ ላይ ስለሚኖር መብት/ 19
4. የሰበር መ/ቁ 15410 /አቶ ተሾመ ጅፋር እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን/ አጠቃላይ የአሰራን የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ስርዓትን ሳይሆን የግል ጥቅምን መሠረት አድርጐ የሚቀርብን የደመወዝ ጭማሪ ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክሮች ችሎት ስለመሆኑ/ 27
5. /የሰበር መ/ቁ 16273 /የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገንታ ገምአ/ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠርኩ እንደሆንኩ ብቻ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ እና የግል ጥቅምን መሠረት አድርጐ የሚቀርብን የጥቅማጥቅም ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ/ 33
6. የሰበር መ/ቁ 16624 (ወ/ት እጅጋየሁ ተሾመ እና የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ/ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6/1 መሠረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት ስለመሆኑ) 53
7. የሰበር መ/ቁ 16720 ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ እና የመካከለኛው አዋሽ፣ አበባ፣ ተንዳሆ፣ የሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅቶች/ በከፊል የፍርድ ባለመብት የሆነ ሰው ባለመብት የሆነበት የፍርድ ክፍል እንዲፈጸምለት የአፈፃፀም ክስ ካቀረበ በኃላ በመጀመሪያ ፍርድ ባለዕዳ የሆነበት ፍርድ በይግባኝ አሸሮ የፍርድ ባለዕዳ የሆነበትን ፍርድ በይግባኝ አሸሮ የፍርድ ባለመብት ሲሆን አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ቀደም ሲል የተከፈተውን የአፈፃፀም መዝገብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቢዘጋም እንኳን ማንቀሳቀስ ስለመቻሉ እና በአፈፃፀም ደረጃ ወለድ የሚከፈለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ከተወሰነ ስለመሆኑ/.....60

8. የሰበር መ/ቁ . 16896 ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና የኢሉባቦር ዞን ትምህርት መምሪያ/ የተዋዋዮች በውሉ አለመግባባት ሲፈጠር ጉዳዩን በገላጋይ ዳኞች እንዲታይ ከተስማሙ ፍርድ ቤቱ ይህን ስምምነት ማስፈጸም ያለበት ስለመሆኑ/.....75
9. የሰበር መ/ቁ 17077 /ዝቋላ ስቱል ሮሊንግ ሚል እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ/ የዕዳ መክፈያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ባለገንዘቡ ለባለዕዳው የሚያደርገው የዕዳ ክፍያ ጊዜ ማራዘም ዋሱን ከዋስትናው ነፃ የሚያደርገው ስላለመሆኑ/.....83
10. የሰበር መ/ቁ 17189 /የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት እና አቶ ንጉሴ ዘለቀ/ በአሰሪ "ገንዘብ" ላይ ሰራተኛው ያደረሰው ጉዳት በአሰሪው "ንብረት" የደረሰ ጉዳት ስለመሆኑ እና ሰራተኛ የስራ ውል ተቋርጦ ስራ ያልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ/.....91
11. የሰበር መ/ቁ. 17429/ ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ እና አቶ ተስፋዬ ከበደ/ በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ኑዛዜው መነበቡን የሚያመለክት ከሆነ በግልጽ "ተነቧል" የሚል ቃል አለመኖሩ ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርግ ስላለመሆኑ 108
12. የሰበር መ/ቁ 17533/የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና ሙሉ አብርሃ/ የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሠረት የጉምሩክ ስነ ስርአት የልተፈጸመበት ዕቃ ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ በማድረግ ወይም ዴክላራሲዮን ባመስጠቱ በዕቃው ባለቤት ላይ በሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ስላለመሆኑ/.....116
13. የሰበር መ/ቁ 17712 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት እና የወ/ሮ ሳዲያ እስማኤል ወራሾች/ - /በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት ስላለመኖሩ/ 132
14. የሰበር መ/ቁ 18307 /ንብ ትራንስፖርት አ.ማ እና አቶ ተገኑ መሸሻ/ በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ የሆነ የሰራተኛ ከአሰሪው ጋር ያለው የስራ ክርክር በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎት መስጠትን ስለማመለከቱ ውሎች ክፍል የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ሲሆን የስራ ውሉ ተቋርጦ የስራ መሪው ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ/ 141

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ 13223

ጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

5. አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

መልስ ሰጭ፡- አቶ አስፋው አበበ

ስለ ፍርድና ስለትዕዛዝ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ጉዳይ ውጭ ጭብጡን ለውጦ ውሳኔ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ስለሚሰጥበት ሁኔታ፡- የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 182/2/፣ 342፣345/1/ለ/

መልስ ሰጭ የጎንደር ስጋ ፋብሪካ ገንዘብ የሆነ ብር 486,312.00 የባንኩን አሰራር በመጣስ ለአምጭው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሰላ ቅርንጫፍ በኩል እንዲከፈለው በማድረግ በፈጸመው ድርጊት ከስራ ተሰናብቶ የወንጀል ጉዳዩ በሂደት ላይ የነበረ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ/ሰጭ ወደ ስራ እንዲመለስ የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ እየታየ እያለ መ/ሰጭ በፈጸመው ድርጊት በወንጀል ተጠያቂ ተደርጎ ብር 500.00 የተቀጣ ቢሆንም ይኸው ክርክር የቀረበለት ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች የወንጀል መዝገቡን በማስረጃነት አላቀረበም በሚል ክርክሩን ውድቅ ስላደረገው የቀረበ አቤቱታ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ፡- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያሻሻለው ውሳኔዎቹ ተሽረዋል፡፡

1. ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ባይቀርብለትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማንኛውም አይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪነት እንዲቀርብ ማድረግ አለበት፡፡
2. ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት ከያዘው ጭብጥ ውጭ ጭብጡን ለውጦ ፍርድ መስጠት ይችላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - መንበረ አድማሱ ቀረበች

ተጠሪ፡- አቶ አስፋው አበበ - ቀረበ

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ የሥራ ውሌን ከሕግ ውጭ አቋርጦታልና ውዝፍ ደመወዜን ከፍሎ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ሲል በአሁን አመልካች ላይ ክስ መስርቷል፡፡ አመልካቹም ለሥራ ውሉ መቋረጥ ምክንያት የሆነው ተጠሪው ሐሰተኛ ማሕተምና ፊርማ የያዘ የማዘዣ ደብዳቤ ለባንኩ ቀርቦ ሳለ የበኩሉን ማጣሪያ ባለማድረግ የጎንደር ስጋ ፋብሪካ ገንዘብ የሆነው ብር 486,312.00 ለአምጪው በአሰላ ንግድ ባንክ አማካኝነት እንዲከፈል ማድረጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መሆኑን በመዘርዘር ባንኩ ኪሣራ ላይ እንዲወድቅ አድርጓልና የሥራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ መቋረጡ ተገቢ ነው ሲል መልሱን ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የደብዳቤው ማህተምና ፊርማ ትክክለኛነት የሥራ ድርሻው በሆነ ሌላ ሰው የተረጋገጠ መሆኑን፣ ተጠሪ ይህን የመስራት ኃላፊነትም ሆነ ግዴታ የሌለበት መሆኑን፣ በባንኩ መመሪያም መሰረት ሰነዱን ከተጠራጠረ ገንዘቡን ከመክፈሉ በፊት አውጪውን ማማከር ያለበት ከፋዩ የአሰላ ባንክ እንጂ ተጠሪው የሚገኝበት የባንኩ የመስቀል አደባባይ ቅርንጫፍ አለመሆኑን በመግለጽ የተጠሪው የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነውና የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ውሣኔው እስከተሰጠበት እለት ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ተከፈሎት ወደ ሥራው ሊመለስ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካቹ ይግባኝ ተጠሪው ደግሞ መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተከራከሩ ሲሆን የከፍተኛ ፍ/ቤትም ተጠሪ የሦስት ወር ደመወዝ ብቻ ተከፍሎት ወደ ሥራ ይመለስ ሲል የስር ፍርዱን አሻሽሎታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በመቀጠል አመልካች ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ ተጠሪም መልሱን ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ይህም ችሎት ከቀረበለት ክርክር በመነሳት በጉዳዩ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ተጠሪ ፈጽሞታል በተባለው ተግባር በወንጀል ጥፋተኛ ተሰኝቷል? ወይስ አልተሰኝም? የሥራ ውሉስ መቋረጥ በሕግ የተደገፈ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

#በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና በጥፋቱም ምክንያት ለያዘው ሥራ ብቁ ሆኖ አለመገኘት; የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ምክንያት መሆኑ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/ቀ/ ላይ ተደንግጋል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ፍሬ ነገር ስንመለስ አመልካች ተጠሪው በፈፀመው ጥፋት በመ.ቁ. 4176/88 በወንጀል ተከስሶ የጥፋተኝነት ውሣኔ ተሰጥቶበት ብር 500.00 ተቀጥቷል ሲል ተከራክሯል፡፡ ይህ ክርክር የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ አመልካቹ በተጠቀሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
አይነት ይከራከር እንጂ የወንጀሉን መዝገብ በማስረጃነት ሊያቀርብ አልቻለም በሚል ክርክሩን ውድቅ ማድረጉን በውሣኔው አመልክቷል፡፡

በመሰረቱ አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በእራሱ አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውም አይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪነት ይቀርብለት ዘንድ ማዘዝ እንዲችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.345 ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ እንዲሁም አንድ ፍ/ቤት ለውሣኔው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በእራሱ አነሳሽነትም ሆነ በተከራካሪዎቹ ጠያቂነት በሌላ ፍ/ቤት የሚገኝ ሰነድ፣ የጽሁፍ ማስረጃ ወይም ፍርድ የተሰጠበት መዝገብ እንዲቀርብለት ማዘዝ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.145/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት በአደረገው ምክንያት ሳይገደብ ጉዳዩን እራሱ በተረዳው አይነት ጭብጥ ለውጦ ፍርድ ሊሰጥ እንደሚችል ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 እና 182/2/ ላይ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከሁሉ በላይ እንደተመለከተው ይህን ጉዳይ በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪው በወንጀል ተከስሶ የተቀጣ ስለመሆኑ ክርክሩ በአመልካች ቀርቦለታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ክርክሩን ከአዋጅ ቁ. 42/85 አኳያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሊመረምረው እና ውሣኔውንም ለመስጠት ተጠሪው በወንጀሉ ጉዳይ የተሰጠበትን የጥፋተኛነት ውሣኔ ይዘት አለያም ጉዳዩ ከሥራ ውሉ መቋረጥ ጋር ያለውን ተያያዥነት እንዲያየው ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ በአመልካች ቁጥሩ የተጠቀሰለትን የወንጀል መዝገብ ከሚገኝበት ፍ/ቤት በእራሱ አነሳሽነት ጭምር ሊያስቀርበው ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ ይህንን አላደረገም፡፡ ይልቁንም ተጠሪው በወንጀል ስለመቀጣቱ ክርክሩ ቢቀርብም መዝገቡ በማስረጃነት ሊቀርብ አልቻለም ሲል ነጥቡን አልፎታል፡፡ በወንጀሉ ጉዳይ የተሰጠው ውሣኔ የሥራ ክርክሩን ጉዳይ ለመወሰን የግድ አስፈላጊ መሆኑ እየታየም ፍ/ቤቱ በወንጀሉ ክስ የተሰጠውን ፍርድ በእራሱ አነሳሽነት አስቀርቦ አለማየቱ የክርክሩን አመራር ከላይ በተጠቀሱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች አለማስደገፉንና በውጤቱም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል ግን ይህ ችሎት ተጠሪው ግብረ አበር በመሆን ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ መጠኑ ከላይ የተጠቀሰው የፋብሪካው ገንዘብ በአሰላ ቅርንጫፍ አማካኝነት ለሌላው ተከሣሽ እንዲከፈል አድርጓል

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በሚል ከሌሎች ተከሣሾች ጋር በከባድ አታላይነት ወንጀል በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሶ ፍ/ቤቱ ተጠሪውን በወ/መ/ሕ/ቁ. 412/1/ መሠረት ጥፋተኛ በማድረግ ብር 500.00 የቀጣው መሆኑን እና ይህም ፍርድ በተጠሪው አማካኝነት ይግባኝ በቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 3885 መጽናቱን አረጋግጧል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካቹ በመ.ቁ. 6928 ፍርዱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል ያቀረበውን አቤቱታ በአለመቀበል መዝገቡን የዘጋው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ይህ በወንጀሉ ጉዳይ የተሰጠው ፍርድ ተጠሪው ጥፋተኛ መሰኘቱን ብቻ ሳይሆን ጥፋተኛ የተሰኘው ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ፈጽሞታል በተባለ ወንጀል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የተረጋገጠበት ጥፋትም በስራው ለመቀጠል ብቃት የሌለው መሆኑን ለማሳየት የሚበቃ ነው፡፡ እንደውም የሥራ ውል መቋረጥ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/ቀ/ መደገፉን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም አቤቱታው በቀረበበት ውሣኔ ተጠሪው የሦስት ወር ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራ እንዲመለስ መወሰኑ የሕግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1ኛ. የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው ሕጋዊ በሆነ ምክንያት በመሆኑ ወደ ሥራ ሊመለስ አይገባም፡፡

2ኛ. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 21/88፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ በመ.ቁ. 6222 ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች ፡- የጊምቢ ከተማ አስተዳዳር ጽህፈት ቤት

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ

ስለ አዋጅ ቁ. 42/85 ተፈጻሚነት - የአሰሪና ሰራተኛ ትርጓሜ - የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 2/1/፣3/2/ /ሠ/

መ/ሰጭ የአዋጅ ቁ.42/85ን መሠረት በማድረግ አመልካች ይሽንኑ ሕግ ተላልፎ ከስራዬ ያገደኝ በመሆኑ ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት በጊምቢ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበችውን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ መ/ሰጭ ከስራ ከታገደችከት ቀን ጀምሮ ያለው ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ እንድትመለስ አለዚያ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 39፣40 እና 43 የተመለከተው ክፍያ (የስንብትና የካሣ ክፍያ) ተከፍሏት እንድትሰናበት ፍ/ቤቱ በመወሰኑና

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ውሣኔውንም የምዕራብ ወለጋ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ችሎት በማጽናታቸው የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሣኔ

የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት፣ የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የጊምቢ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. አንድ ክርክር በአዋጅ ቁ.42/85 አግባብ የሚዳኘው በአዋጁ እንደተሰጠው ትርጓሜ አንድ ወገን ተከራካሪ አሰሪ ሌላው ወገን ተከራካሪ ደግሞ ሰራተኛ የሚባሉ ከሆነ ነው፡፡
2. በአዋጅ "አሰሪ" ተብሎ ለሚጠራ "ድርጅት" የተሰጠው ትርጓሜ የሕዝብ አስተዳደር ስራ የሚያከናውኑ አካላት "ድርጅት" ሊባሉ እንደማይችሉ በግልጽ ያመለክታል፡፡
3. በአዋጁ ትርጓሜ "አሰሪ" ተብሎ ከማይጠራ "ድርጅት" ጋር የስራ ውል ያለው ሠራተኛ በአዋጁ ትርጓሜ "ሠራተኛ" ሊባል አይችልም፡፡
4. አንድ በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሠራተኛ በመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር አዋጅ አለመሸፈኑ በራሱ በአዋጅ ቁ.42/85 የሚሸፈን አያደርገውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 14414

ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፡- የጊምቢ ከተማ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት - አላዛር ኢተፋ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ- አልቀረበችም፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ የጊምቢ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ የአዋጅ ቁ. 42/85ን መሠረት በማድረግ የአሁኑ አመልካች ይሽን ሕግ ተላልፎ ከስራዬ አግዶኛልና ኪሣራዬን ከፍሎ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ ስትል ባቀረበችው ክስ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሥራ ከታገደችበት እለት ጀምሮ ያለው ደመወዝዋ እንዲከፈላት እና ወደ ሥራዋ እንድትመለስ አለዚያ በአዋጁ አንቀጽ 39፣40 እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief
43 የተመለከተው ክፍያ (የስንብትና የካሣ ክፍያ) እንዲሰጣት እና እንድትሰናበት ወስኗል፡፡

የወለጋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ውሣኔ ያፀናው ሲሆን በመቀጠል ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በዚህ ጉዳይ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የመጨረሻ ፍርድ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመም በማለት በአመልካች የቀረበለትን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህም ችሎት አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡለትን ክርክር መርምሯል፡፡

ሊፈታ የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ የተከራካሪዎቹ ግንኙነት በአዋጅ ቁ. 42/85 ይሸፈናል? ወይስ አይሸፈንም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 2/1/ መሠረት አንድ አካል አሠሪ ለመሰኘት በአዋጁ አግባብ ሰራተኛን ቀጥሮ የሚያሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሊሆን ይገባዋል፡፡ ድርጅት የሚባለው ደግሞ የንግድ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽን ወይም ሌላ ሕጋዊያን ተግባራትን ለማከናወን የተመሠረተ ተቋም መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2/2/ ላይ ተተርጉሟል። ይኸ ለጅርጅት የተሰጠው ትርጓሜ የሕዝብ አስተዳደር ሥራ የሚያከናውኑ አካላት ድርጅት ሊባሉ እንደማይችሉ በግልጽ ያመላክታል። በሌላም በኩል የመንግሥት አስተዳደር ሰራተኞች በልዩ ሕግ ከሚተዳደሩ ሌሎች ሠራተኞች ውስጥ የተመደቡ መሆናቸው እና ከአሰሪያቸው ጋር ባላቸው ግንኙነት የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ እንደማይሆን በአንቀጽ 3/2/ሠ/ ላይ ተጠቅሷል።

አመልካች የሕዝብ አገልግሎት ሥራ የሚያካሂድ የመንግሥት ተቋም መሆኑን ከስያሜው እንኳ መገንዘብ ይቻላል። በተጠሪ የቀረበውም ክርክር አመልካች ድርጅት ነው በሚል እና ይህንንም በማስረዳት ላይ የተመሠረተ አይደለም። ክርክሩ ተጠሪ በመንግሥት ሠራተኝነት የታቀፈች አይደለችም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስም ሠራተኞቹ በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ የታቀፉ አልነበሩም ተጠሪ ክስ ከመሠረተች በኋላ የወጣው የኦሮሚያ ክልል የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ ቁ. 61/94ም ወደ ኋላ ሄዶ ስለማይሰራ ግንኙነታችን በአዋጅ ቁ. 42/85 የሚሸፈን ነው የሚል ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ችሎት እምነት የአንድ ሙግት ይዘት በአዋጅ ቁ. 42/85 አግባብ የሚዳኝ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ በአዋጁ እንደተሰጠው ትርጓሜ አንዱን ወገን ተከራካሪ አሰሪ ሌላው ወገን ተከራካሪ ደግሞ ሰራተኛ ሊሰኙ ይገባል፡፡ ከአዋጁ አግባብ ቀጣሪው አሰሪ ተቀጣሪው ደግሞ ሠራተኛ ሊባሉና ሁለቱም በድንጋጌው የተቀመጠውን የትርጓሜ መስፈርት እንዲያሟሉ ያስፈልጋል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው አሰሪው አመልካች የሕዝብ አስተዳደር ሥራ የሚያካሂድ የመንግሥት መ/ቤት በመሆኑ ድርጅት ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ አመልካቹ አሰሪ ድርጅት ባለመሆኑም ተጠሪዋ በአዋጁ አሰሪ ከተባለ አካል ጋር የሥራ ውል ግንኙነት ያላት ሠራተኛ ናት ልትባል የምትችል አይደለችም፡፡ ይህ ደግሞ ሁለቱም በአዋጁ የተቀመጠውን ትርጓሜ አለማሟላታቸውን የሚያመላክት ነው፡፡

በእርግጥ ተጠሪ በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ ያልታቀፈች ሠራተኛ መሆንዋን በመግለጽ መከራከርዋን ተገንዝበናል፡፡ ይህም አዋጁ ተፈፃሚ የማይሆነው በአዋጁ አንቀጽ 3/2/ሠ/ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በልዩ ሕግ ለሚተዳደሩ የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞች እንጂ ለእኔ በልዩ አዋጁ ላልታቀፍኩት አይደለም በሚል ዓይነት መሟገቷን ያመላክታል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ እንደምትከራከረው በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጁ የታቀፈች አይደለችም ሊባል የሚችል አይነት ቢሆን እንኳን አለመታቀፏ ብቻውን እርሷን በአዋጅ ቁ. 42/85 መሠረት ሠራተኛ፣ አመልካቹን ደግሞ ድርጅት ሊያሰኛቸው የሚችል አይደለምና ግንኙነታቸው በተጠቀሰው አዋጅ የሚሸፈን ነው የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርሰን አይሆንም፡፡ አመልካች ድርጅት፣ ተጠሪ ደግሞ የድርጅት ሠራተኛ መሆናቸው በአልተረጋገጠበት ሁኔታ አዋጅ ቁ. 42/85 ለክርክራቸው ተገቢነት ሊኖረው የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ አይኖርም፡፡ እንዲሁም ተጠሪ አለኝ የምትለውን የመብት ጥያቄ ለግንኙነታቸው ተፈፃሚ ሊሆን ከሚገባው ሕግ አካያ አቃንታ ልታቀርብ ከሚገባት በቀር የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎችን ለመብቷ መጠየቂያ ልታደርግ አትችልም፡፡ በዚህ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች የተቀጠሰውን አዋጅ ተመስርተው የሰጡትን ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ፍርድ ይህ ችሎት አልተቀበለውም፡፡

ው ሣ ኔ

የጊምቢ ወረዳ ፍ/ቤት የምዕራብ ወለጋ ከፍተኛ ፍ/ቤት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና በመ/ቁ. 01235 የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በአዋጅ ቁ.42/85 መሠረት አይተው የሰጡት ከፍ ሲል የተመለከተው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 15270

ጥቅምት 28 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የፓ አለቃ ተሻገር አስታጥቁ

መልስ ሰጭ፡- አቶ አዊስ አው አብዲ

በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን - ከሣሽ የመሆን ችሎታ - ፍርድ ቤቱ የክስ አቤቱታው ተቀባይነት እንደሌለው ስለሚወስንበት ሁኔታ/በክሱ አቤቱታ ላይ የተገለጸው ነገር የማያስከስስ ሆኖ ሲገኝ፡- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33/2/፣ 231/1/ሀ/ - የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ.47/67

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኘውን ቦታ የከተማው አስተዳደር በ1982 ለአመልካች የሰጠው በ1945 ዓ.ም. ቦታው ለመ/ሰጭ አባት ተሰጥቶት እያለ በመሆኑ ለመ/ሰጭ አባት የተሰጠው የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሳይሰረዝ ሌላ ካርታ ለአመልካች መስጠቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የጅጅጋ ዞን ወረዳ ፍ/ቤት በመወሰኑና ውሣኔውም በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡<u>ውሣኔ</u>

የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት፣የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጧቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡

1. የከተማ ቦታ በአዋጅ ቁ. 47/67 መሠረት የመንግስት በመሆኑ በግለሰቦች በርስትነት የሚያዝ አይደለም፡፡
2. በከተማ ቦታ ላይ ያለን መብት አስመልክቶ ክስ ማቅረብ የሚቻለው ከአዋጅ ቁጥር 47/67 መውጣት በኋላ የመንግስት አካል በሰጠው የይዞታ ወይም የመጠቀም መብት መሠረት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 28 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፦ መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጉስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

አመልካች፦ የአስር አለቃ ተሻገር አስታጥቁ

ተጠሪ፦ አቶ አዊል አው አብዲ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘ ነው የተባለን የከተማ ቦታ ለማስመለስ በሚል በሶማሌ ብ/ክ/መ/በጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት የተጀመረን ክርክር የሚመለከት ነው። ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በጉልበትና በሕገወጥ መንገድ የያዘብኝን ቦታ ይልቀቅልኝ በማለት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የተከሣሽን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የመከላከያ ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ተከሣሽ ክስ የቀረበበትን ቦታ ለከሣሽ ይልቀቅ በማለት ወስኖአል። በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አጽንቶአል። የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም እንደዚሁ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለውም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎአል። የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ማለትም የሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.05/1/8/96 በ15/5/96 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው።

አቤቱታው በዚህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተገቢውን ሕጋዊ ሥነ-ስርዓት ተከትለው መወሰን አለመወሰናቸውን ለመመርመር ሲባል ነው። በዚህ መሠረትም ጉዳዩን ከስር መሠረቱ አንስተን መርምረናል። ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ማየት እንደቻልነው ተጠሪ ክስ ሊመሰርት የቻለው አባቱ የተወልኝን የአፈር ቤትና የውሃ ጉድጓድ ያለበትን በጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኘውን ቦታ ተከሣሽ (የአሁኑ አመልካች) በጉልበትና በሕገወጥ መንገድ ይዞብኛል በማለት ነው። መብቱን ያረጋግጥልኛል በማለት ያቀረበው ማስረጃ በ1945 ዓ.ም ለአባቱ ተሰጥቶ ነበር የሚለው የቦታ ይዞታማረጋገጫ ካርታ ብቻ ነው። አመልካች ደግሞ ቦታው በላዩ ላይ ምንም ዓይነት ቤትም ሆነ ንብረት ያልነበረበትና በማንም ሰው ያልተያዘ መሆኑ ተረጋግጦ በ1982 ዓ.ም በከተማው አስተዳደር የተሰጠው መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

፣ በሰሙ የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው መሆኑን እና በላዩም ላይ ቤት ሰርቶበት ግብርም እየከፈለበት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮአል። በዚህ ረገድም ማስረጃዎችን አቅርቦአል። የጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤትም ቦታው ለከሣሽ (ለአሁኑ ተጠሪ) ሊለቀቅ ይገባል በማለት የወሰነው አመልካች (የስር ተከሣሽ) ያቀረባቸው ማስረጃዎች ቦታው በሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሰጠው መሆኑን አያረጋግጡም በሚል ሳይሆን፣ በ1945 ዓ.ም ለከሣሽ አባት የተሰጠው የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሣይሰረዝ ሌላ ካርታ ለተከሣሽ መሰጠቱ ሕገወጥ ነው። የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል።

እንደምንመለከተው ለክርክሩ መንስዔ የሆነው ቦታ በከተማ አስተዳደር ክልል የሚገኝ ማለትም የከተማ ቦታ ነው። ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ በአመልካች ይዞታ ስር የቆየና በላዩም ላይ አመልካች ቤት የሰራበት እንደሆነም ተረጋግጦአል። በሌላ በኩል ደግሞ ቦታው ለአመልካች ከመሰጠቱ በፊት ማለትም ከ1982 ዓ.ም በፊትም ቢሆን በተጠሪው አባትም ሆነ በተጠሪው ይዞታ ስር እንዳልነበረ፤ ይልቁንም የጦር ሰፈር አካል እንደነበረ በተጠሪው የክስ ማመልከቻ ቁምር መገለፁን ነው የተገንዘብነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ.47/67 ከታወጀበት ቀን (1967) ጀምሮ የከተማ ቦታ በግለሰቦች በርስትነት የሚያዝ አይደለም። ግለሰቦች በከተማ ቦታ ላይ የመጠቀም ወይም የይዞታ መብት ሊኖራቸው የሚችለው በሚመለከተው የመንግሥት አካል በሕጋዊ መንገድ ሲሰጣቸው ነው። በያዝነው ጉዳይ እንደምናየውም አከራካሪው ቦታ ከፍ ሲል በጠቀስነው አዋጅ ቁ.47/67 መሠረት የመንግሥት ንብረት የሆነው ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ነው በመሆኑም ሊያዝበት የሚችለው መንግሥት ነው። በዚህ መሠረትም ባዶ መሆኑ እና በማንም ሰው አለመያዙ ተረጋግጦ ለአመልካች ተሰጥቶአል። በ1945 ዓ.ም ለተጠሪ አባት ተሰጥቶ የነበረው ካርታም ከ1967ቱ አዋጅ ወዲህ ለተጠሪው አባትም ሆነ ለተጠሪው የሚሰጠው መብት የለም። ከሁሉ በላይ ደግሞ ቦታው በተጠሪው አባትም ሆነ በተጠሪው ይዞታ ስር የነበረ ለመሆኑ ወይም በእነሱ ይዞታ ስር እያለ ለአመልካች የተሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስላልቀረበ ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚችልበት ምክንያት እንኳን አልነበረውም። እኛ እንዳየነው ተጠሪ ክሱን የመሠረተው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 33(2) የግድ በሚለው መሠረት ክስ በመሠረተበት ቦታ ላይ መብት ያለው መሆኑን ከጅምሩ (ከመሠረቱ) ሳያረጋግጥ ነው። በመሆኑም የወረዳው ፍ/ቤት ክሱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 33(2) እና 231(1)(ሀ) መሠረት ከጅምሩ መሠረዝ ነበረበት። ይህን መሠረታዊ የሥነ - ሥርዓት አካሄድ ባለመከተል ተጠሪን ከሕግ አግባብ ውጪ ባለመብት እንዲሆን በመወሰኑም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሞአል።

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበባቸው በሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም በጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔዎች ተሽረዋል።
2. ወጪና ኪሣራን በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች ይቻቻሉ።

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 15410

ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፡- አቶ ተሾመ ጅፋር

መልስ ሰጭ፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

ስለሥራ ክርክር - የሥራ ክርክር ችሎቶች ስልጣን - የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን - የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 147

አመልካች የደመወዝ ጭማሪ ክፍያ ይፈጸምልኝ በማለት ለአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክስ ቢያቀርብም ቦርዱ ጉዳዩ በቦርዱ ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ በአፈጻጸም የሚጠየቅ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደመወዝ ጭማሪን አስመልክቶ የተሰጠ ውሣኔ የለም በማለት ሽሮ የደመወዝ ጭማሪውን ጉዳይ የማየት ሥልጣን የቦርዱ ነው ከሚል እምነት በመነሳት ጉዳዩን አይቶ እንዲወስን ለቦርዱ ሲመልስለት ቦርዱ በበኩሉ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ወሰነ፡፡ በቦርዱ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢቀርብም

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ፍርድ የሰጠሁበት በመሆኑ እንደገና ላየው የምችልበት ሥርዓት የለም በማለት ውድቅ ስላደረገው የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሣኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወላኝ ቦርድ የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡

1. የአሰሪ አጠቃላይ የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ሥርዓት ሕገ ወጥ ነው በሚል የሚቀርብን ስክ የማየት ሥልጣን የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወላኝ ቦርድ ነው፡፡
2. የግል ጥቅምን መሠረት አድርጎ የሚቀርብን የደመወዝ ጭማሪ ክስ የማየት ስልጣን የሥራ ክርክር ችሎት ነው፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም.

የመ.ቁ. 15410

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፡- አቶ ተሾመ ጅፋር - ቀረበ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ግርማ ማርቆስ ቀረበ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው የአመልካች እና የተጠሪ ክርክር የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪው የተጠቀሰውን ክፍያ ይክፈለኝ ሲል ከአሰሪ እና ሠራተኛ ቦርድ ዘንድ ክስ ይመሰርታል፡፡ ቦርዱም በሁለቱ መካከል በነበረ ክርክር አስቀድሞ የተሰጠ ፍርድ እንደነበር ጠቁሞ ይህም ጥያቄ አብሮ ፍርድ እንዳገኘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሚቆጠር ነውና በአፈፃፀም እንጂ በክስ ሊጠየቅ የሚገባው አይደለም በማለት ይወስናል፡፡

ከዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የደመወዝ ጭማሪን አስመልክቶ የተሰጠ ፍርድ ስለሌለ ጥያቄው በክስ እንጂ በአፈፃፀም ሊጠየቅ አይገባም በማለት የቦርዱን ውሣኔ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ እንደዚሁም ቦርዱ የደመወዝ ጭማሪውን ክርክር አይቶ ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን መልሶለታል፡፡ ጉዳዩን ወደ ቦርድ የመለሰውም ይህን ክርክር የመዳኘት ስልጣን ያለው ቦርድ እንጂ ፍ/ቤት አይደለም በሚል እምነት መሆኑን በውሣኔው አመላክቷል፡፡

በመቀጠል ጥያቄው በቀጥታ ክስ አይነት ለአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ቀርቦለታል፡፡ ቦርዱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ አስቀድሜ ፍርድ የሰጠሁበት ጉዳይ ስለሆነ ደግሜ ላየው የምችልበት ሥርዓት የለም በማለት በአሁን አመልካች የቀረበለትን ይግባኝ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ይህም ችሎት በግራ ቀኙ የቀረበለትን ክርክር መርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥም ቦርድ ይህን የደመወዝ ጭማሪ ክርክር ለመዳኘት ሥልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአመልካች የደመወዝ ጭማሪ ይገባኛል ክርክር ተጠሪው በዚህ ረገድ የወሰደው አጠቃላይ እርምጃ የሠራተኞችን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ነው የሚል ይዘት ያለው አይደለም፡፡ አለያም የተጠሪው የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ሕገ ወጥ ነውና ሊሰተካከል ይገባዋል በሚል አይነት የቀረበ አይደለም፡፡ ይልቁንም ክርክሩ የግል ጥቅምን ወይም መብትን ከማስከበር አኳያ የቀረበ መሆኑን በግልጽ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ይህም ይህ ችሎት በመ.ቁ. 18180 ለግል እና ለወል የሥራ ክርክር አይነቶች ከሰጠው ትርጉም አኳያ ሲታይ የግል እንጂ የወል የሥራ ክርክር የሚሰኝ አይደለም፡፡ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣንም የፍ/ቤት እንጂ የአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ አይሆንም፡፡

ስለሆነም ቦርዱ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም የሚል ውሣኔ መስጠቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ወደ ቦርድ ሲመልሰው ክርክሩን የመዳኘት ሥልጣን ያለው ቦርድ ነው በሚል እምነት እንጂ ይህን ነጥብ በጭብጥነት ይዞ ፍርድ ያልሰጠበት መሆኑን ከውሣኔው መገንዘብ ስለሚቻል ቦርዱ የሥልጣኑን ጥያቄ በጭብጥነት ይዞ ፍርድ መስጠቱ ጉዳዩን እንዲዳኝ ከመለሰለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርድ ጋር አይጣጣምም ወይም ይቃረናል ሊያሰኘው የሚችል አይሆንም፡፡ እንዲሁም ለሁለተኛ ጊዜ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና እንዲይ የሚፈቅድልኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሥርዓት የለም ሲል የሰጠው ምክንያት የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ ባይታይም ይግባኙን ውድቅ በማድረጉ ግን የፈፀመው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የለም፡፡

ው ሣ ኔ

የአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ.ቁ.14/01/93 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ በመ.ቁ. 21501 የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም.

የመ/ቁ.16273

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

ተጠሪ፡- አቶ ገንታ ገምአ

የስራ ክርክር - የክስ ምክንያት መኖር -(በቋሚ ልሁን ጥያቄ ላይ) የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን (የቋሚነት ጥያቄንና የግል የጥቅማጥቅምን አወሳሰን በተመለከተ)- የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 9፣10፣138 142 ፡- ክሳሽ ስለመሆን ችሎታ፡- የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 33

አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ቋሚ ሠራተኛ እንዲሆንና ጥቅማ ጥቅምም እንዲሠጠው በማለት ስለወሰኑ የቀረበ አቤቱታ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ፡- የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠጡት ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡

1. አንድ ሠራተኛ ከውሉና ከሕግ አንጻር ጉደለብኝ የሚለው መብት ካለ ከሚጠይቅ በቀር ቋሚ ልሁን በሚል የሚያቀርበው ጥያቄ የክስ ምክንያት /Cause of action/ የለውም፡፡
2. የጥቅማ ጥቅም ክፍያን በተመለከተ ይህ ጥቅም ቀረብኝ የሚል ሠራተኛ የሚያቀርበው ክስ የዛን ሠራተኛ ጉዳይ ብቻ የሚመለከት በመሆኑ እንደግል የሥራ ክርክር የሚቆጠር እንጂ የወል የሥራ ክርክር አይደለም፡፡ ስለሆነም የጥቅማጥቅም ይከፈለኝ ጥያቄ የግል ክርክር በመሆኑ ለአሰሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ቀርቦ የሚስተናገድ አይሆንም፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

ተጠሪ፡- አቶ ገንታ ገምአ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ፍርድ

አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ሚያዚያ 21/96 ዓ.ም. በመ/ቁ. 303/02/94 በሰጠው ውሣኔ እና የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን በማፅናት በመ/ቁ. 30835 ሰኔ 16/96 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለአቤቱታው መነሻ ምክንያት የሆነው የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ያቀረበው ክስ ሲሆን፣ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በድርጅቱ ውስጥ በጥበቃ ሥራ ተቀጥሬ በመሥራት ላይ የምገኝ ስለሆነና ሥራውም ዘላቂነት ያለው ሆኖ ሣለ የቋሚ ሠራተኛነት መብቴ ሊጠበቅልኝ ባለመቻሉ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9 መሠረት ቋሚ ሠራተኛ እንድሆን፣ ለቋሚ ሠራተኞችም የሚሰጠው ጥቅማጥቅም ክሱን ካቀረብኩበት ጊዜ ጀምሮ እንዲሰጠኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ፡- ተጠሪው የሻምበል ባሻ የውትድርና ማዕረግ ያለው በጡረታ ላይ የሚገኝ እንደሆነ ጠቅሶ በወቅቱ ለተፈጠረ የፀጥታ ችግር ምክንያት ችግሩ እስኪወገድ ድረስ ጥበቃውን ለማጠናከር የቀድሞ ወታደሮችን ቀጥሮ ለመመደብ እንዲችል ኮርፖሬሽኑ ለበላይ አካል ጥያቄ አቅርቦ በተፈቀደለት መሠረት ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ እንጂ በቋሚነት በሥራ ላይ ሊቀጥል የሚችል አለመሆኑን፤ የጥቅማ ጥቅም ጥያቄውም በህብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስምምነቱ ለተወሰነ ጊዜ ለተቀጠረ ሠራተኛ ተፈፃሚ የሚሆን አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ቦርዱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ከሣሽ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 10 መሠረት የተቀጠረ መሆኑን ተከሳሽ በተጨባጭ በማስረጃ አስደግፎ ያላስረዳ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9 መሠረት ከሣሽ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ነው፡፡ ጥቅማጥቅምን በተመለከተም በህብረት ስምምነቱ መሠረት ውሣኔው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ወደፊት እየታሰበ ሊሰጠው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ይግባኙ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ይህ አቤቱታ ሊቀርብ ችሏል፡፡

በዚሁ መሠረት ቦርዱም ሆነ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ነው ሲል ውሣኔው እንዲታረምለት አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን፣ ተጠሪውም ቀርቦ መልሱን በመስጠት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ስህተት ስለሌለበት ውሣኔው ፀንቶ ልሰናበት በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህም ችሎት ከክርክሩ በመነሳት ጉዳዩ ምን የክስ ምክንያት /cause of action/ ቦርድስ ይህን ጉዳይ ለማየት የሚያስችለው ሕጋዊ ሥልጣን አለው ወይ? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ከሥር ውሣኔና አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርመሮታል፡፡

የክስ ምክንያት /cause of action/ አለ ወይም የለም የሚለውን ከማየታችን በፊት የዚህን ቃል ፅንሰ ሃሣብ ማየቱና መረደቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለ ክስ ምክንያት /cause of action/ ፅንስ ሀሳብ በ1958 ዓ.ም. በወጣው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ውስጥ መካተቱን ከሕጉ አንቀጽ 29፣80/2/፣ 224/2/፣ 23/1//ሀ/ ... ወዘተ መረዳት የሚቻል ሲሆን ለቃሉ የሰጠው ትርጉም ግን የለም፡፡

በመሠረቱ ማንም ሰው በህግ ችሎታ ኖሮት በሌላ ሰው ላይ ማናቸውንም ክስ ለማቅርብ እንዲችል አስቀድሞ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሠረተበት ነገር ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑ መረጋገጥ እንደሚገባው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33 ይደነግጋል፡፡ በዚህም ከሣሽ ከተከሣሽ ላይ ሊፈፀም የሚችል መብት አለኝ ብሎ ለማለት አስቀድሞ ለመብቱ መገኘት መነሻ የሆነውን ነገር በማረጋገጥ የተጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ከሣሹ በሕግ መብት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሕጉ አንቀፅ 80(2) ላይም መረዳት የሚቻለው የክስ ምክንያት ሲባል አንድ ሰው አንድን ነገር ከአንድ ሰው ላይ ለማግኘት ፍ/ቤቱ እንዲወስንለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው የፍሮ ነገር ሁኔታ ሲሆን፣ ይህም ፍሬ ነገር ዳኝነት ለማግኘት የሚያስችል መሆን ያለበት መሆኑን ነው።

ሮበርት አለን ሴድለር "Ethiopian civil procedure" በሚል ርዕስ ባዘጋጁት መጽሀፍ ላይ "የክስ ምክንያት" አለ ብሎ ለመወሰን የሚቻለው በክሱ ላይ የቀረበው ነገር ቢረጋገጥ ከሣሹ የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ሕግ ይፈቅደሉታል ወይ? ለሚለው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ መስጠት ሲቻል እንደሆነ ገልፀዋል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በግራ ቀኙ መካከል በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ውል ግንኙነት መኖሩ አልተካደም። ተጠሪው በሥር ያቀረበው ክስ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀፅ 9 መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ልቆጠር ይገባል በማለት ሲሆን፣ ከዚሁ የቋሚ ልሁን ጥያቄው ጋር በተጓዳኝ ያቀረበው ለሌሎች ቋሚ ሠራተኞች የተሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅማጥቅም ለእኔም ይሰጠኝ የሚል ነው። የአሁኑ ተጠሪ ለቦርዱ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት ያለው መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እነዚህን ጥያቄዎቹን ለያይቶ ማየት ያስፈልጋል። ተጠሪው ቋሚ ልሁን ሲል ያቀረበው ዋነኛው ጥያቄ ከአመልካች ጋር አድርጎት የነበረው ውል ባሕርይ እንዲተረጎምለት የጠየቀበት ሲሆን፣ ለሌሎች ሰራተኞች የተጠሰው ጥቅማ ጥቅም ለኔም ይሰጠኝ የሚለው ጥያቄ ደግሞ በውሉ መሠረት ሊያገኝ የሚገባውን ነገር ግን ቀረብኝ ያለውን ጥቅም ለማስከበር የቀረበ ጥያቄ ነው። የመጀመሪያው የውሉ ባሕርይ እንዲገለጽለት ከመጠየቅ የዘለለ ጥቅም የሌለው ሲሆን ሁለተኛው ግን ውሉ አልተከበረምና ውሉን የጣሰው ወገን የውሉን ቃለ እንዲያከብር እንዲደረግለት የሚጠይቅ ነው።

በመካከላቸው የሥራ ውል የተፈፀመ ስለመሆኑ ግራ ቀኙ የተቀበሉበት ጉዳይ ነው። የሥራ ውል የራሱ ልዩ ባሕሪያት ያሉት ቢሆንም ከአጠቃላይ ውሎች ጋር የሚጋራቸው በርካታ ባሕሪያት እንዳሉትም መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ከእነዚህ አንዱና ዋነኛው ውል ከተፈፀመ በኋላ ይኸው ውል በተዋዋዮች መካከል የአስገዳጅነት ባሕርይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው መሆኑ ነው፡፡ ተዋዋዮቹ በውሉ የሚገደዱት በመርህ ደረጃ ሁለቱም ስምምነት ላይ ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ በመሆኑም ተዋዋይ ወገኖች ከውል የሚመነጭ መብት ለማግኘት የፍርድ ቤት ውሣኔ የግድ አያስፈልጋቸውም፡፡ ውሎች የፍርድ ቤቶች ይሁንታ ሳያስፈልጋቸው በአንዱ ወይም በሌላው ተዋዋይ ወገን ላይ መብትና ግዴታ የሚጥሉ በመሆናቸው ተዋዋዮች ወደ ፍርድ ቤቶች ሊመጡ የሚገባው በውሉ መሠረት አልተፈፀመም የሚሉት ነገር ካለ ብቻ ወይም ውሉ ሕጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ምክንያቶች እንዲፈርስላቸው የፈለጉ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በተዋዋዮቹ መካከል ያለው የውል ዓይነት እንዲነገር ወይም ውሉ እንዲፀድቅ ለፍርድ ቤቶች ጥያቄ ሊቀርብ አይገባም፡፡

ይህ አጠቃላይ የውሎች መሠረት ሃሣብ በሥራ ውልም ላይ ተፈጻሚነት አለው፡፡ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 9 የሰፈረው መሠረት ሃሣብ በመርህ ደረጃ አንድ ሰራተኛ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ የሚገመት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የአዲሱ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9 ድንጋጌም ተመሣሣይ ይዘት ያለው ነው፡፡ ማንኛውም በአዋጁ የሚሸፈን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠራተኛ የዚህ የህግ ግምት ተጠቃሚ ነው፡፡ ይህ የሕግ ግምት የሕግ ውጤት እንደመሆኑ የፍርድ ቤት ችሮታ ሳያስፈልገው ውሉ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ የሚሰራ የሕግ ግምት ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሠራተኛ ከውሉና ከዚህ ሕግ ግምት አንጻር ጎደለብኝ የሚለው ነገር ካለ ከሚጠይቅ በቀር ቋሚ ነህ ልባል የሚል ጥያቄ ሊያቀርብ አይገባውም፡፡ በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የተፈፀመው ውል በሕጉ ግምት የሚሸፈን ሳይሆን አዋጁ በአንቀጽ 10/በአዲሱም አዋጁ አንቀጽ 10/ የሚሸፈን ነው የሚል ክርክር ሊነሳ እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ይህም ቢሆን ሊነሣ የሚችለው ሠራተኛው ቀረብኝ የሚለው ጥቅም ወይም በአሰሪው ከሕጉና ከውሉ ውጪ ተፈፀመ የሚለውን በደል ማሳየት ሲችል ነው፡፡ በመሆኑም በኔና በአሰሪዬ መካከል ያለው የሥራ ውል ጊዜያዊ ሳይሆን ቋሚ ነው ተብሎ የተርጎምልኝ የሚለው ክስ የክስ ምክንያት ያለው ባለመሆኑ በቦርድም ይሁን በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሊስተናገድ የሚገባው አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቋሚ ልሁን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚለው ጥያቄ የአንድን ሠራተኛ የውል ግንኙነት እንጂ አጠቃላይ የሥራ ሁኔታውን የሚመለከት ባለመሆኑ የግል የሥራ ክርክር እንጂ

የወል የሥራ ክርክር አይደለም በመሆኑም ጉዳዩ የክስ ምክንያት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ ለአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚቀርብም ጉዳይ አይደለም፡፡ ቦርዱ ሥልጣን ያለው የወል የሥራ ክርክሮችን ለመመልከት እንጂ የግል የሥራ ክርክር ለመዳኘት አይደለም፡፡ በመሆኑም በሁለቱም ተደራራቢ ምክንያቶች ቦርዱ የቀረበለትን ይህን የመጀመሪያ ጥያቄ ማስተናገዱ አግባብ አይደለም፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ሠራተኛው ለሌሎች ሠራተኞች የተሰጠው ጥቅም ለኔም ይጠበቅልኝ የሚል ጥያቄ አያይዞ ያቀረበ በመሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን ማስተናገዱ የሚያመጣው ለውጥ መኖር አለመኖሩ ቀጥሎ የምንመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ይህ ጥያቄ አስፈሪው የውሉን ወይም የሕጉን ወይም የሁለቱን ድንጋጌ በመጣረር መብቴን ተጋፍቷል የሚል እንደምታ ያለው በመሆኑ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ውሉ የተጣሰበት ወገን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መፍትሄ ፍለጋ ወደሚመለከተው አካል ከሶ መቅረቡ ተገቢ ነው። ውል ወይም ሕግ ተጥሶ የአንድ ወገን መብት የተጓደለ ከሆነ መብቱን ለማስጠበቅ ክስ ማቅረብ ትክክለኛ አሠራር ነው። ጥቅም ተጓደለብኝ የሚል ሰራተኛ በሕጉ አንቀጽ 9 መሠረት ቋሚ ነው የሚል የህግ ግምት ተጠቃሚ ስለሆነ ቋሚ መሆኑን ማስረዳት አያስፈልገውም። ሠራተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እስካቀረበ ድረስ ጉዳዩን የሚያየው አካል ቋል እንደሆነ ግምት መውሰድ ይገባዋል፣ ቋሚ እንዳልሆነ ማስረዳት የሌላኛው ወገን ኃላፊነት ነው።

ነገር ግን ይህ ጥቅም ቀረብኝ የሚል ሠራተኛ የሚያቀርበው ክስ የዛን ሠራተኛ ጉዳይ ብቻ የሚመለከት በመሆኑ በሕጉ አንቀጽ 138 መሠረት እንደግል የሥራ ክርክር የሚቆጠር እንጂ የወል የሥራ ክርክር አይደለም። ስለዚህ ከዚህ ጥያቄ የሚቀርበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ባይባልም ለቦርዱ ቀርቦ የሚስተናገድ ነጥብ ግን አይደለም። የወል የሥራ ክርክር ከግል የሥራ ክርክር የሚለየው በምንድነው የሚለው የሕግ ነጥብ ላይ ይህ ፍ/ቤት በመዝግብ ቁ.18180 በሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም. ውሣኔ የሰጠበት በመሆኑ አሁን በዝርዝር

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መድገሙ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ዋናው ነጥብ አንድ ሠራተኛ እሱን ብቻ የሚመለከትና የሌሎችን ሠራተኞች የሥራ ሁኔታ የማይመለከት ክስ ያቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ የግሉ የሥራ ክርክር እንጂ የወል የሥራ ክርክር ሆኖ ሊታይ አይገባውም፡፡ የወል የሥራ ክርክር ካልሆነ ደግሞ ለቦርዱ ቀርቦ ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባ አይሆንም፡፡ በአዋጃ ቁ. 42/85 አንቀጽ 1382 መሠረት በአዲሱም አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 138 የግል ሥራ ክርክርን የማየት ሥልጣን ያለው መደበኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህም ረገድ ቦርድ የሄደበት አቅጣጫ ሕጉ ካስቀመጠው ሥርዓት ውጪ ነው፡፡ በመሆኑም ለሌሎች ሠራተኞች የተሰጠ ጥቅማ ጥቅም ለኔ አልተጠበቀልኝም የሚለውን አጠቃላይ ክስ ቦርዱ የተመለከተው ከስልጣኑ ውጪ በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው፡፡

ለማጠቃለል ቋሚ ሰራተኛ እንደሆንኩ ይወሰንልኝ የሚለው ክስ የክስ ምክንያት የሌለው በመሆኑና የግል ጉዳይም በመሆኑ፣ የጥቅማ ጥቅም ጥያቄውም የግል ክርክር በመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ቀርበው መታየታቸው የጉዳዩ አመራር የህጉን ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ያልተከተለ በመሆኑ ትክክለኛውን የሕግ ትርጉም ተከትሎ እንዲሄድ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ውሣኔ

1. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሚያዝያ 21/96 ዓ.ም. በቁጥር 303/02/94 የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 30835 ሰኔ 16/96 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት በድምጽ ብልጫ ተሽረዋል፡፡
2. ውሣኔዎቻቸው የተሻሩ መሆናቸውን እንዲያውቁት የፍርዱና የውሣኔው ቅጂ ይተላለፍላቸው፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሐሳብ ልዩነት

አብዛኛው ድምጽ በተጠሪ የቀረበው አንድም የስራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል መሆኑ ተረጋግጦ ይወሰንልኝ ሌላም የሚገባኝን ጥቅማ ጥቅም እንዳገኝ ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚለው የክስ ነጥብ የውል የስራ ክርክር ሊሰኝ የሚችል ስለአልሆነ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አይደለም ሲል በሰጠው የውሣኔ ክፍል እኔም የምስማማበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሥራ ቅጥር ውሌ ላልተወሰነ ጊዜ እንደሆነ ይወሰንልኝ በሚል አይነት የቀረበው የተጠሪ አቤቱታ « የክስ ምክንያት» የለውምና በፍርድ ቤት ጭምር ሊስተናገድ የሚገባው አይደለም በሚል ዋነኛ ምክንያት ውድቅ በመደረጉ ባለመስማማት እንደሚከተለው በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

አንድ ከሣሽ ክስ በመሰረተበት ነገር ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑን በማሳየት በሕግ አግባብ ዳኝነት ይሰጥለት ዘንድ መጠየቅ ይችላል፡፡ ይህን ከ ላይ በአብዛኛው ድምፅ በተሰጠው ውሣኔ ውስጥ ከተጠቀሱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ላይ ጭምር መረዳት ይቻላል፡፡ ክሱ ጥቅም ወይም መብት የተጠየቀበት መሆኑን ለማሳየት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የቻለ እስከሆነ ድረስ ደግሞ ጉዳዩ የክስ ምክንያት ያለው ነው ለመሰኘት ይበቃል።

በስራ ክርክር ጉዳይ በሚቀርቡ ክሶች እንዲጠየቅ የሚፈለገው ዳኝነትም ከዚህ አጠቃላይ መርህ በተለየ ሁኔታ እንዲታይ የሚያስገድድ ሕግ የለም። ስለሆነም አንድ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ክስ ደመወዝ፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የሥራ ስንብት ክፍያ ወዘተ... ሊከፈለኝ ይገባል በሚል አይነት የጥቅም ጥያቄን መሠረት አድርጐ ሊቀርብ ይችላል። አለዚያም እድገት ይሰጠኝ፣ ዝውውር ላገኝ ይገባል፣ የተወሰደብኝ የዲሲፒሊን እርምጃ ተገቢ አይደለም ወዘተ... የሚሉ የመብት ጥያቄዎችን ብቻ መሠረት አድርጎ ሊቀርብ ይችላል። እነዚህ ከብዙ በጥቂቱ የተጠቀሱት የክፍያ ወይም የመብት ይረጋገጥልኝ ጥያቄዎች ለሥራ ክርክር ጉዳይ በተናጥልም ሆነ በጥምር የክስ ምክንያቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ከአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 138፣142፣162 ወዘተ ... መንፈስም መገንዘብ ይቻላል።

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የሥራ ቅጥሩ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰንለት በአቀረበው ክስ ጠይቋል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በተጨማሪም ይገባኛል የሚላቸው ጥቅሞች መኖራቸውን እና አመልካቹ ጥቅሞቹን የከለከለውም ቅጥሩ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑን ስለአልተቀበለለት መሆኑን በክሱ አመላክቷል፡፡ የክሱም አቀራረብ የሥራ ውሉ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ነው ቢሰኝ ያጣቸው ጥቅሞች ያለ ሌላ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ እንደሚከበሩለት ያስገነዝባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቹ የተጠሪ የሥራ ውል የተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑን እና ጥቅሞቹ ያለተሰጡትም ቅጥሩ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ባለመሆኑ ምክንያት መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡

ይህ የክርክራቸው ይዘት አመልካች እና ተጠሪ በመካከላቸው የነበረውን የሥራ ውል በየራሳቸው እንደሚጠቅማቸው የተረጎሙት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ይህም ግራ ቀኙ በተጠሪ የሥራ ውል ሁኔታ ላይ ማለትም የተጠሪ የሥራ ውል የተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ነው? ወይስ አይደለም? በሚለው ፍሬ ነገር ላይ ልዩነት እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ ይህ ልዩነታቸው ሊፈታ የሚችለው በፍርድ እንደመሆኑም ጉዳይ ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ሊቀርብ እና የሥራ ውሉ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10 ወይም 9 የሚሸፈን መሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለመሆኑ ተጣርቶ ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል። በእርግጥ በዚህ አይነት የሚቀርቡና የሥራ ውላችን ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ይረጋገጥልን በሚል መልኩ የሚመሰረቱ ክሶች በቀጥታ የጥቅም ጥያቄን የያዙ ክሶች አለመሆናቸው ግልጽ ነው። ነገር ግን የሥራ ቅጥር ውሌ በአሰሪው ከሕግ ውጭ የተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል እንደሆነ ተወስዶብኛልና ሊታረምልኝ ይገባል የሚል ይዘት ያላቸው እንደመሆናቸው መሠረታቸው የመብት ጥያቄ መሆኑ አከራካሪ ሊሆን የሚይገባው ነው። በዚህም ምክንያት ይህን መሰሉ ጥያቄ በአንድ ክስ ውስጥ ለብቻው ቀርቦ ዳኝነት ቢጠየቅበት እንኳን ክሱ የክስ ምክንያት የለውም የሚሰኝበት በሕግ የተደገፈ ምክንያት አይኖርም። ጉዳዩ የእራሱ የሆነ የክስ ምክንያት ያለው በመሆኑም ጭብጥ ሆኖና ከአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 9 እና 10 ጋር ተገናዝቦ ውሣኔ ሊሰጥበት ይገባል። ይህ ይሆን ዘንድ ክሱ ከሳሹ ቀረብኝ የሚባልን ጥቅም በሚጠይቅ መልኩ የቀረበ እንዲሆን አያስፈልግም። ይልቁንም የቀረበው ክስ ቀረብኝ የሚባልን ጥቅም ብቻ ጠቅሶ የቀረበ ቢሆን እንኳን የጥቅም ይገባኛል ጥያቄው ውሣኔ ከማግኘቱ አስቀድሞ ቅጥሩ የተወሰነ ወይም ያልተወሰነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ጊዜ የመሆኑ ነገር ከሕጉ አግባብ ታይቶ ምላሽ ያገኝ ዘንድ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ ይኖራል። ይህ ሁኔታ ሊያጋጥም እና የሥራ ውሉ የሚሸፈነው በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 9 ነው? ወይስ 10? የሚል ክርክር ሊነሳ እንደሚችልም በአብዛኛው ድምፅ ጭምር መታመኑን ከውሣኔው መገንዘብ ይቻላል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ የሥራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ይረጋገጥልኝ በሚል አይነት የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት የለውም የሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የሚገባ አይሆንም። ምክንያቱም የክስ ምክንያት ያላቸውም የሚባሉ ክሶች በይዘታቸው ተከሣሹ ክሱ በተመሰረተበት ጉዳይ ላይ የውልም ሆነ የሕግ ኃላፊነት እንደአለበት የሚያመለክቱ አይደሉም። እንዲህ ያሉ ክሶች ከመሰረቱም ክሱ ተከሣሹ ላይ ሊመሰረት የቻለበትን ሕጋዊ ምክንያት ለማሳየት የሚበቁም አይደሉም። ጉዳዩ ተከሣሹን የማይመለከተው መሆኑ ግልፅ ከመሆኑ የተነሳም ወደ ክርክሩ ፍሬ ነገር መግባቱ አስፈላጊ አይሆንም። የሥራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ተረጋግጣ ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚል ምክንያት ይዘው የሚመሰረቱ ክሶች ግን አሰሪ የሆነው ተከሣሽ ቅጥሩ የተወሰነ ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሥራ ውል መሆኑን እስከአሳስረዳ ድረስ የሥራ ውሉን ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ያደረገው ዘንድ የሕግ ኃላፊነት እንዳለበት የሚያመላክቱ ናቸው በተጨማሪም በዚህ መዝገብ የተያዘውን ክርክር ጨምሮ በሌሎች በርካታ መሰል ሙግቶችም ውስጥ ተከታይ ጥቅሞችን ያለክርክር ለማስገኘት የሚበቃን የመብት ጥያቄ መሰረት አድርገው የሚመሰረቱ ናቸው፡፡ ስለሆነም የክስ ምክንያት የላቸውም የሚባሉ አይሆኑም፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የዚህ መዝገብ ተከራካሪዎች ልዩነት የቅጥሩን የቆይታ ጊዜ ብቻ የሚመለከት ነው፡፡ በጥቅሞቹ አከፋፈል ጉዳይ ላይ ስምምነት እንጂ ልዩነት እንደሌላቸው ግልፅ ነው፡፡ የተጠሪ የሥራ ውል በሕግ አግባብ ተመዝኖ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ቢረጋገጥ ተጠሪው ጥቅሞቹን ሊያገኛቸው እንደሚችል በአመልካቹ ጭምር የታመነ መሆኑን ክርክሩ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተጠሪ የሥራ ውል የተወሰነ ወይም ያልተወሰነ ጊዜ ውል መሆኑ በፍርድ ሳይረጋገጥ ተጠሪው ጥቅሞቹን ያገኛል ወይም አያገኝም የሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ እንደማይችል የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው የሥራ ቅጥሩ ሁኔታ አስቀድሞ ሳይፈታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የጥቅም ጥያቄው ጉዳይ ምላሽ ሊያገኝ እንደማይችል እየታወቀም የክሱ ዋና ክፍል የሆነው የሥራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ተረጋገጦ ይወሰንልኝ የሚለው የተጠሪ አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም መባሉ ሕጋዊ አሳማኝነት የሌለው ነው።

በእኔ እምነት የሥራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መሆኑ ይወሰንልኝ በሚል አይነት የሚቀርቡ ክሶች ምንም እንኳን የወል የሥራ ክርክር ባለመሆናቸው ምክንያት በአሰሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሊታዩ የማይችሉ ቢሆኑም የግል የሥራ ክርክር አይነቶች በመሆናቸው በፍርድ ቤት ሊዳኙ የሚገባቸው ናቸው። ስለሆነም እነዚህ ጥያቄዎች የክስ ምክንያት የላቸውምና የትኛውም የዳኝነት አካል ዘንድ ሊቀርቡ አይችሉም በሚል በአብዛኛው ድምፅ በተሰጠው የውሣኔ ምክንያት ባለመስማማት ስሜ በሦስተኛ ተራ የተጠቀሰው ዳኛ በሐሳብ ተለይቻለሁ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 16624

ጥቅምት 18 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- ወ/ት እጅጋየሁ ተሾመ

መልስ ሰጭ፡- የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ

ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ፍርድ ወይም ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ለሰጠው ፍርድ ቤት ስለሚቀርብ አቤቱታ - የፍትሐብሔር ስነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 6/1/

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት ውሳኔውን የሰጠው ሀሰተኛ የኑዛዜ ሰነድን መሰረት አድርጎ በመሆኑ ዳኝነት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረበችውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ጥያቄው የቀረበው አመልካች ይግባኝ ካቀረበች በኋላ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ በመስጠቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/1/ መሠረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት መሆን አለበት፡፡
2. በውሳኔው ላይ ይግባኝ ከቀረበ የይግባኙ መዝገብ ቢዘጋም ዳኝነት እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 18 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ወ/ት እጅጋየሁ ተሾመ ጠበቃው ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ ቀርባለች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

ይህ መዝገብ ተከፍቶ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኗ አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 መሠረት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በሚል የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ሐምሌ 19 ቀን 1996 ዓ.ም. ተጽፎ እንዲቀርብ ባደረገችው ማመልከቻ መነሻ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመዝገቡ ለመመልከት እንደተቻለው ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሚቹ ወታደር በቀለ መኩሪያ ሚያዝያ 8 ቀን 1989 ዓ.ም. አድርጓል በተባለው ኑዛዜ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ታህሣስ 17 ቀን 1994 ዓ.ም. ባቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ላይ የተመለከተው ፊርማ ተመርመሮ የተናዛዡ አለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ውድቅ በማድረግ ወስኖ ከቆየ በኋላ የኑዛዜው ተጠቃሚ ነኝ የምትለው የአሁኗ አመልካች ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም. በተባራ ማመልከቻ ፍ/ቤቱ ለሰጠው ውሣኔ መሠረት የሆነው ለፖሊስ ቴክኒክ ምርመራ ተልኮ እንዲመረመር የተደረገው የኑዛዜ ሰነድ ከፍ/ቤቱ መዝገብ ጋር የተያያዘው ትክክለኛው ሰነድ ሣይሆን በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል በሚል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/1/ መሠረት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ ባቀረበችው አቤቱታ ላይ የአሁኗ ተጠሪ መልስ እንድትሰጥበት ካደረገ በኋላ ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም. በሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/1/ መሠረት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው የይግባኝ ቅሬታ ከመቅረቡ በፊት ነው። በቀረበው ጉዳይ ግን አመልካች ቀድሞ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ለይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰሚ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባለች፡፡ የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ ከቆየች በኋላ ይግባኙን በማቋረጥ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6 መሠረት ዳኝነት ይታይልኝ የሚል ጥያቄ ልታቀርብ አትችልም በሚል ምክንያት ሣይቀበላት ቀርቷል፡፡

አመልካች የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.6/4/ ዳኝነት እንደገና ሊታይ ይገባል አይገባም በሚል ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለማለት አይቻልም ስለሚል ፍ/ቤቱ የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚለውን በቀጥታ ለሰበር ችሎት ልታቀርብ ችላለች፡፡

በአመልካች በኩል የቀረበው አቤቱታ ከተመረመረ በኋላ እንደገና ዳኝነት ይታይልኝ ጥያቄ ተቀባይነት ያጣው በሕጉ አግባብ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያስፈልገዋል ተብሎ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ማመለከቻውም ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ደርሷት ቀርባ በጽሁፍ መልስ ሰጥታበት ተከራክራለች፡፡

ይህ ችሎት በበኩሉ ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ አይገባም የተባለው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6/1/ ማናቸውም ሰው ፍርዱን ወይም ውሣኔውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ለሰጠው ፍ/ቤት እንደገና ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችለው በተሰጠው ፍርድ ወይም ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት እንደሆነ ያስረዳል፡፡ በቀረበው ጉዳይ የአሁኗ አመልካች ፍ/ቤቱ አስቀድሞ በሰጠው ውሣኔ ላይ ለከፍተኛው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ በፍ/ቤቱ ለምርመራ እያለ ሲቀጥር መቆየቱ ተረጋግጧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የይግባኙን መዝገብ አስቀርቦ በተመለከተበት ጊዜ ሁሉ ይግባኙ በእንጥልጥል ላይ ነበር፡፡ አመልካች ይግባኙን አዘግቻለሁ የምትለው ፍ/ቤቱ የይግባኙን መዝገብ በማስቀረብ ለምርመራ ተበሎ መቀጠሩን በማረጋገጥ ከመለሰው በኋላ ነው፡፡ አመልካች ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ አቅርባለች አላቀረበችም የሚለው ጥያቄ ተነስቶ ማቅረቧ ከተረጋገጠ በኋላ ይግባኙን ለሚሰማው ፍ/ቤት መዝገቡ እንዲዘጋላት ጠይቃ አዘግታ መቅረቧ የይግባኝ ቅሬታ አላቀረበችም ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ አመልካች ይግባኝ ማቅረቧ ከተረጋገጠ ከላይ በተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት እንደገና ዳኝነት ይታይልኝ በሚል የምታቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
አይኖረውም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት ቀደም ሲል በተሰጠው ውሣኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ቀርቦበታል በሚል ምክንያት እንደገና ዳኝነት ሊታይ አይችልም በሚል በሰጠው ብይን ተፈጽሟል የሚባል የሕግ ስህተት የለም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ በፍ/መ/ቁ.3324, ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 16720

ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ተገኔ ጌታነህ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ት አበራሽ ጉቱ

መልስ ሰጭ፡- 1. የመካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት

2. አቦቦ እርሻ ልማት ድርጅት

3. ተንዳሆ እርሻ ልማት ድርጅት

4. የሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት

ፍርድ እንዲፈጸም ስለማቀርብ ማመልከቻና ስለ አፈፃፀሙ ስነስርዓት - ለፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት - ጉድለት ያለበት የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለማሰጥበት ስርዓት፡- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 378፣ 384፣ 385/1/

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ/ሰጭዎች ለአመልካች ብር 167,831.94 እንዲከፍሉ፤ አመልካች በበኩላቸው ለመ/ሰጭዎች ብር 17,183.94 እንዲከፍሉ፤ ከሰጠው ውሳኔ አመልካች ለመ/ሰጪ ብር 17,182.50 እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመለወጥ የተጠቀሰውን ገንዘብ/ብር 17,182.50/ መ/ሰጭዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ በመወሰኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ከመስጠቱ ቀደም ብሎ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሲሰጥ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ የተወሰነውን እና በጠቅላይ ፍ/ቤቱ በኋላ የተሻሻለውን ብር 17,182.50 ቀንሰው ቀሪውን ገንዘብ ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ የተሰጠው ትእዛዝ እንዲስተካከልና በዋናው ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈል ትዕዛዝ እንዲሰጥ በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ አመልካች የጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሳኔ ባለማያያዙ በውሳኔው መሠረት ትእዛዝ ሂሳብ ሲሰራ ይችል ስላልነበርና በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፍል የተሰጠ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ውሣኔ ባለመኖሩ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ ትክክል ነው በሚል ውድቅ በማድረጉና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ውሳኔውን በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ውሳኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

1. በአንድ ውሣኔ ላይ በከፊል ባለመብት የሆነ ተከራካሪ ወገን ባለመብት የሆነበት የውሳኔ ክፍል እንዲፈጽም ማመልከቻ ከማቅረብ የሚከለክለው ነገር የለም፡፡
2. የአፈፃፀም ማመልከቻው የቀረበለት ፍ/ቤትም ውሳኔው ካልታገደ በቀር አፈጻጸሙን ሊቀጥል ይገባዋል፡፡
3. ከፊል ባለመብት የሆነ ተከራካሪ ወገን ከፊል ባለመብት የሆነበት የውሳኔ ክፍል እንዲፈጸምለት የአፈፃፀም መዝገብ ከፍቶ ከፊል ባለዕዳ በሆነበት የውሳኔ ክፍል ይግባኝ ካቀረበና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ባዩን የሚጠቅም ውሳኔ ከሰጠ ባለመብቱ አዲስ የአፈጻጸም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው፤ ሌላ የአፈጻጸም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ የቀድሞው የአፈጻጸም መዝገብ እንዲንቀሳቀስ እና የተሻሻለው ውሳኔ እንዲፈጸምለት ለማድረግ ይችላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. የመጀመሪያው የአፈጻጸም ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ ተፈጽሞ ያለቀ ቢሆንም እንኳን የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው በቀድሞው የአፈጻጸም መዝገብ ላይ እንዳይቀጥል የሚከለክል ምክንያት የለም፡፡

5. የአፈጻጸም መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ የቀረበው ጥያቄ ትክክል ያልሆነ ህግ ተጠቅሶ የቀረበ ቢሆንም እንኳን ማመልከቻው እንዲስተካከል ፍ/ቤቱ ያዛል ወይም ፍ/ቤቱ ራሱ አግባብነት ያለውን ህግ መሰረት አድርጎ ጥያቄውን ይመረምራል እንጅ ማመልከቻውን ውድቅ ማድረግ አይገባም፡፡

6. በአፈጻጸም ደረጃ ወለድ እንዲከፈል ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት የሚችለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ውሳኔ ከተሰጠ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መ/ቁ. 16720

ጥቅምት 22 ቀን 1998

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ተገኔ ጌታነህ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሒሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ ወኪል ሚደቅሳ ጉቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. የመካከለኛ አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት - አልቀረቡም፡፡

2. አቦቦ እርሻ ልማት ድርጅት አልቀረቡም፡፡

3. ተንዳሆ እርሻ ልማት አልቀረቡም፡፡

4. የሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት - አልቀረቡም፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች ለፊ/መ/ደ/ፍ/ቤት በ7/7/93 ጽፈው ያቀረቡትን የአፈፃፀም ማመልከቻ መሠረት በማድረግ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለሥር ፍ/ቤት በዓታት አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የአሁኑዎቹ ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 167831.94 /አንድ መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከዘጠና አራት ሳንቲም/ እንዲከፍሉ ሲወስንባቸው በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ለተጠሪዎች ብር 17182.50 /አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ብር ከሀምሳ ሳንቲም/ እንዲከፍሉ ወስኖባቸዋል፡፡ ሆኖም አመልካች ለተጠሪዎቹ እንዲከፍሉ የተወሰነውን ገንዘብ በተመለከተ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ውሣኔው የተሻረ በመሆኑ ቀደም ሲል ፍ/ቤቱ የአፈፃፀም ትእዛዝ ሲሰጥ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ የተወሰነውን ብር 17182.50 ቀንሶ ቀሪውን ገንዘብ ብቻ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የሰጠውን ትእዛዝ እንዲያስተካክል እና እንዲሁም በዋናው ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈል ትእዛዝ እንዲሰጥ አመልክተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ ለአፈፃፀም መሠረት በሆነው በመ/ቁ 639/82 ሐምሌ 30 ቀን 1983 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀም የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲቀርብ አመልካች የጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሣኔ ከመዝገቡ ጋር ስላላያያዙ ፍ/ቤቱ የአፈፃፀም ትእዛዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሰጠው በዚሁ ውሣኔ መሠረት ሲሆን ትእዛዝ በተሰጠበት ወቅት ፍ/ቤቱ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ ሂሣቡን ሊሰራ ስለማይችል የሰጠው ትእዛዝ ትክክለኛ ስለሆነ የሚታረም አይደለም፣ በተፈረደው ገንዘብ ላይም ወለድ እንዲከፈል የተሰጠ ውሣኔ ስለሌለ የወለድ ይከፈለኝ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም የፌ/መ/ደ/ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታም የጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪዎች ብር 17182.50 እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሣኔ በመሻር ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ የሰጠውን ውሣኔ የሥር ፍ/ቤት እንዲፈፀም ትእዛዝ አለመስጠቱ የተሰጠውን ውሣኔ የሚለውጥ ወይም የሚሽር ስለሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘብ እንዲከፈለኝ እና በዋናው ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈለኝ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ተጠሪዎችም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ደርሷቸው በሰጡት መልስ ቀደም ሲል አመልካች በመ/ቁ 639/82 ሐምሌ 30/1983 በተሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው በውሣኔው መሠረት ተፈጽሞ ጉዳዩ አብቅቷል፡፡ በወቅቱ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ከአፈፃፀም ማመልከቻው ጋር አያይዘው አላቀረቡም፡፡ ስለዚህ አዲስ አፈፃፀም መዝገብ ከሚከፍቱ በቀር የጠቅላይ ፍ/ቤቱን ውሣኔ መሠረት አድርገው የቀድሞ አፈፃፀም ችእዛዝ እንዲስተካከል ያቀረቡት ጥያቄ ሥነ-ሥርዓትን ያልተከተለ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

ከላይ የተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን በዚህም ጉዳይ ሊታይ የሚገባው ነጥብ አንድ ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርብ ማመልከቻን የአቀራረብ አና የአፈፃፀም ሥርዓት ነው፡፡

አንድ የአፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት የሚጀምረው የተፈረደለት ሰው /የፍርድ ባለመብት/ በፍርዱ መሠረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ማመልከቻ ለፍ/ቤቱ ሲያቀርብ ነው /የሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378/1/ ይመለከታል/፡፡ በመሆኑም አንድ የአፈፃፀም ማመልከቻ ከማቅረቡ በፊት የተፈረደ ፍርድ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ እንዲፈፀም በሚቀርበው የፍርድ ውሣኔ ደግሞ ከሳሽ ከጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ ውስጥ ከፊሉ ተወስኖለት ከፊሉ ውድቅ የሚደረግበት ወይም በከፊል አንደኛው ተከራካሪ ወገን በከፊል ደግሞ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ባለመብት ሊሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በመሆኑም በከፊል ባለመብት የሆነው ወገን ወይም ከፊል የዳኝነት ጥያቄው ውድቅ የተደረገበት ወገን በተወሰነበት ጉዳይ ወይም ውድቅ በተደረገበት የዳኝነት ጥያቄ ላይ ይግባኝ ጠይቆ በተፈረደለት መጠን ብቻ የአፈፃፀም ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ሲያገኝ ባለመብቱ አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው አዲስ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅር ብቻ የቀድሞውን የአፈፃፀም መዝገብ ከማንቀሳቀስ የሚከለክለው ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይ የሚለው በዚህ ጉዳይ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሠረቱ የአፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት ዓላማው በአንድ ውሣኔ ወይም ትእዛዝ ባለመብት የሆነውን ሰው ውሣኔው ወይም ትእዛዙ ያስገኘለት መብት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ በመሆኑ አንድ ፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ውሣኔ እስከቀረበለት ድረስ ውሣኔው እንዲፈፀም ተገቢውን ትእዛዝ መስጠት ይገባዋል፡፡ በመሆኑም በአንድ ውሣኔ ላይ ከፊል ባለመብት የሆነ ተከራካሪ ወገን ባለመብት የሆነበት የውሣኔ ክፍል ሊፈፀም የሚችል እስከሆነ ድረስ ይኸው የውሣኔ ክፍል እንዲፈፀም ማመልከቻ ከማቅረብ የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ የአፈፃፀም ማመልከቻ የቀረበለት ፍ/ቤትም፣ ውሣኔው ካልታገደ በቀር አፈፃፀሙ ሊያቆም ስለማይችል /የሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 332 ይመለከቷል/፣ አፈፃፀሙን ሊቀጥል ይገባዋል፡፡ ይግባኝ የተባለበት ከፊል የውሣኔው ክፍል ግን ሊፈፀም የሚችለው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ የመሻር፣ የመለወጥ፣ ወይም የማሻሻል ስልጣን አለውና ነው፡፡ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ባዩን የሚጠቅም ውሣኔ ከሰጠ ባለመብቱ፣ አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሳያስፈልገው፣ ሌላ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ የቀድሞ የአፈፃፀም መዝገብ እንዲንቀሳቀስ እና ውሣኔው እንዲፈፀምለት ለማድረግ ይችላል። የመጀመሪያው የአፈፃፀም ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ ተፈጽሞ ያለቀ ቢሆንም እንኳን የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በቀድሞው መዝገብ ላይ እንዳይቀጥል የሚከለክል ነገር የለም። የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 378/3/ረ/ እና ቁጥር 384ም አንድ የአፈፃፀም ማመልከቻ ከቀረበ በኋላ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በተለያየ ጊዜ ሌላ ማመልከቻ እየቀረበ ነገሩን ለማንቀሳቀስ እንደሚቻል ማመልከታቸው ባለመብቱ አዲስ መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በቀድሞ መዝገብ እንዲፈፀም ማድረግ የሚቻል መሆኑን ያስገነዝባሉ። የዚህም አላማ በአንድ ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በአንድ መዝገብ ተጠቃሎ እንዲፈጸም ለማድረግ ነው። ስለዚህም በከፊል የውሣኔው ክፍል ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ያቀረበ ወገን ይግባኝ ያለበት ጉዳይ እስኪወሰን ሳይጠብቅ የፍርድ ባለመብት የሆነበት ጉዳይ ብቻ እንዲፈፀም ሊያመለክት ይችላል። ይግባኝ ያለበት ጉዳይ ከተወሰነለት ደግሞ አዲስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ሌላ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ የቀድሞውን መዝገብ አንቀሳቅሶ በይግባኝ የተወሰነለትን ፍርድ ሊያስፈጽም ይችላል፡፡

ከዚህ በመነሳት ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በመ/ቁ. 639/82 በ30/11/83 የከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ተጠሪዎች ለአመልካች 163529 ብር እና የዳኝነቱን ገንዘብ እንዲከፍሉ ሲወስን አመልካች ደግሞ ለተጠሪዎች 17182.50 ብር ከነዳኝነቱ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 657/84 በ26/9/84 በዋለው ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በመለወጥ 17182.50 ብር ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በመሆኑም አመልካች በከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲከፈላቸው ከተወሰነላቸው ብር 163529 በተጨማሪ ብር 17182.50 እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡

ነገር ግን አመልካች የመጀመሪያ የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርቡ እንዲፈጸምላቸው የጠየቁት በመ/ቁ. 639/82 የተሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ በወቅቱ የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፈጸም የቀረበ ጥያቄ አልነበረም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
እንዲፈፀም የሰጠው ትእዛዝ ትክክል ነበር፡፡ ነገር ግን አመልካች ይግባኝ ለጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው አስወስነዋል፡፡ በመሆኑም አዲስ መዝገብ መክፈት ሳያስፈልጋቸው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈጸምላቸው ሌላ የአፈፃፀም ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ ጉዳዩ እንዲንቀሳቀስላቸው መጠየቃቸው የሥ/ሥ/ሕጉ የሚፈቅድላቸው ነው፡፡ በእርግጥ አመልካች ማመልከቻውን ሲያቀርቡ የጠየቁት የአፈፃፀም ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320 እና 208 መሠረት እንዲያስተካክል በመሆኑ ለጥያቄአቸው መሠረት ያደረጓቸው የሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው ቢሆንም አንድ ባለጉዳይ አቤቱታውን ለፍ/ቤቱ ሲያቀርብ ሕግ የመጥቀስ ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ አመልካች የተሳሳተ የሕግ አንቀጽ በመጥቀሳቸው ብቻ አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ አይገባም፡፡ የቀረበለትን ማመልከቻ አግባብነት ካለው የሕጉ ድንጋጌ ጋር መመርመር ተገቢውን መፈፀም የፍ/ቤቱ ኃላፊነት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ የአፈፃፀም ማመልከቻው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት አልቀረበም የሚልበት ምክንያት ካለው እንኳን አቤቱታው ተስተካክሎ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል /የሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 385/1/ ይመለከታል/፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
አመልካች በይግባኝ ፍ/ቤት የተሰጣቸውን ፍርድ ለፌ/መ/ደ ፍ/ቤት ስላቀረቡ ፍ/ቤቱ ውሣኔው መሠጠቱን አውቋል፡፡ ስለዚህም በውሣኔው መሠረት እንዲፈፀምላቸው ተገቢውን ትእዛዝ ከመስጠት ፋንታ አመልካቹ የተጠቀሱት የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ በመሣሣቱ ብቻ አቤቱታውን ውድቅ በማድረጉ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

ሌላው አመልካች የጠየቁት በተፈረደው ዋና ገንዘብ ላይ ወለድ እንዲከፈላቸው ነው፡፡ በርግጥ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378/3/ሰ/ የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲቀርብ በፍርዱ መሠረት የሚጠየቀው የገንዘብ ልክ ከነወለዱ እንዲገለጽ ያዛል፡፡ ነገር ግን ይህ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ በዋናው ውሣኔ ላይ ወለድ እንዲከፈል የተሰጠ ውሣኔ ካለ ይኸው ወለድ ተሰልቶ ትክክለኛው አሀዝ በአፈፃፀም በማመልከቻው እንዲገለጽ የሚያዝ እንጂ ውሣኔ ያልተሰጠበትን የወለድ ክፍያ የአፈፃፀም ፍ/ቤቱ እንዲያስከፍል ስልጣን የሚሰጠው አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንድ የአፈፃፀም ፍ/ቤት በውሣኔው መሠረት ከማስፈፀም አልፎ ውሣኔ ያልተሠጠበትን ጉዳይ እንዲፈፀም የማድረግ ስልጣን የለውም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ በሰጡት ውሣኔ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 103/90 በመጋቢት 20 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 8076 በግንቦት 17 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች ብር 17182.50 /አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ብር ከሃምሣ ሳንቲም/ እና የዳኝነቱን ብር 671.00 /ስድስት መቶ ሰባ አንድ/ በድምሩ 17853.50 /አስራ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሣ ሦስት ብር ከሃምሣ ሳንቲም/ ለአመልካች ይክፈሉ፡፡
3. አመልካች በጠየቁት የገንዘብ መጠን ብር 17182.50 /አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ብር ከሃምሣ ሳንቲም/ ወለድ ሊከፈላቸው አይገባም፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡ - ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

መልስ ሰጪ፡ - የኢሊባቦር ዞን ትምህርት መምሪያ

ውል - የውል ጉዳይ አወሳሰን - የውሎች ውጤት፡ -

የፍትሐብሔር ሕግ 1711፣ 1731/1/

አመልካችና መ/ሰጪ በገቡት ውል አንቀጽ 24 ግራ ቀኙ እርስ በእርሳቸው ካልተስማሙ አንዱ ወገን በሕግ ወይም በሽምግልና መጠየቅ ይችላል በሚለው ድንጋጌ ክርክሩ በሽምግልና ብቻ ይታያል ተብሎ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም በማለት አመልካች ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጎ የኢሉባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ውሣኔ በመስጠቱና ውሣኔው በበላይ ፍ/ቤቶች በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

<u>ውሣኔ</u> የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸውና ከአለአከላቸው ነገሮች በቀር የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት አላቸው፡፡
2. በህግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው፡፡
3. የተጠቀሰው የውሉ ድንጋጌ አለመግባባቶች ከተነሱ ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት የሚደረግ መሆኑን ይህ ካልተቻለ ጉዳዩ በገላጋይ ዳኝነት የሚታይ መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ፍ/ቤት ይህንኑ ተፈፃሚ ማድረግ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 16 ቀን 1998

የመ/ቁ. 16896

ዳኞች፦ 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፦ ዘምዘም ጎላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ ወርቅዬ አባይነህ ቀረበ።

መልስ ሰጭ፦ የኢሊባቡር ዞን ትምህርት መምሪያ - ቀረበ

ፍርድ

ለሰበር ችሎቱ ለቀረበው ጉዳይ መነሻ የሆነው ክስ የተጀመረው በኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ መልስ ሰጭ የአሁኑ አመልካችንና ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ በተባለ ድርጅት ላይ ውልን መሠረት አድርጉ በአጠቃላይ 184.559.26/አንድ መቶ ሰማንያ አራት ሺ አምስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ብር ከሃያ ስድስት ሣንቲም/ እንዲከፈለው በመሠረተው ክስ ነው። የአሁኑ መልስ ሰጭ በበኩሉ በውሉ መሠረት ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት ከሚታይ በስተቀር በዚህ ፍ/ቤት እንዲቀረብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የተደረገው አላግባብ መሆኑን ገልጾ በመቃወም መልስ ከመሰጠቱ በተጨማሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15803 ገላጋይ ለመምረጥ እንዲቻል ክስ ያቀረበ መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥቷል። የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ መልስ ሰጭ ብር 31.111.40/ሰለሣ አንድ ሺ አንድ መቶ አስራ አንድ ብር ከአርባ ሣንቲም/ እንዲከፍልና ክርክሩ ላስከተለው ወጭና ኪሣራ በቁጥር 300/ሦስት መቶ ብር/ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ በበላይ ፍ/ቤቶች ፀንቷል።

የአሁኑ አመልካች በሰበር እንዲታይለት ባቀረበው አቤቱታ ላይ ግራ ቀኞችን ባደረግነው ውል መሠረት አለመግባባቶች ከተነሱ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት የሚታይ መሆኑ እየታወቀ የሥር ፍ/ቤት ይሄን አልፎ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረበው ማመልከቻ የሕግ ትርጉም የሚያስነሣ ነጥብ ያለው መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጉ የመ/ሰጭን መልስና የአመልካችን የመልስ መልስ አድምጧል።

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል። በግራቀኝ ተዋዋይ ወገኞች መካከል አለመግባባቶች ሲነሱ በውላቸው መሠረት በግልግል ዳኝነት ይታያል የተባለው የውል ቃል ታልፎ ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት እንዲታይ መደረጉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ በዋንኛነት መመርመርና መወሰን ያለበት ጉዳይ እንደሆነ ተመልክተናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከጉዳዩ አጠቃላይ ሁኔታ እንደተረዳነው በአሁኑ አመልካች በመልስ ሰጭው መካከል ቀኑ በግልጽ ባልተመለከተ የውል ሰነድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ ለማድረግ ውል የተደረገ መሆኑ ታውቋል። ለሥራው ማስጀመሪያ የሚሆን ቅድመ ክፍያ የአሁኑ አመልካች ከመ/ሰጭ ላይ ከተቀበለ በኋላ በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት በስምምነት መጨረስ ባለመቻላቸው የአሁኑ አመልካች መልስ ሰጭ በዞኑ ፍ/ቤት ክስ ከመመስረቱ በፊት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ገላጋይ ዳኛ ለማስመረጥ ክስ የመሠረተ መሆኑን ታውቋል። በተጨማሪ የዞኑ ፍ/ቤት አሁን የቀረበውን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን ገልጾ የተከራከረ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ተቃውሞውን በብይን ውድቅ በማድረግ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ የሰጠ መሆኑ ታውቋል። የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት «በውሉ አንቀጽ 24 መሠረት ግራቀኙ እርስ በእርሣቸው ካልተስማሙ አንዱ ወገን በሕግ ወይም በሽምግልና መጠየቅ ይችላል።» ይላል እንጂ ጉዳዩ በሽምግልና ብቻ ይታያል ተብሎ የተቀመጠ ግዴታ ስለሌለ ተቃውሞውን አልተቀበልነውም የሚል መሆኑን ፍ/ቤቱ በ9/1/95 ከሰጠው ብይን ለመገንዘብ ችለናል። ይህ ችሎት በግራ ቀኙ መካከል

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የተደረገውን የውሉን አንቀጽ 24 እንደመረመረው ተዋዋይ ወገኖች በመካከል አለመግባባቶች ከተነሱ ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት የሚደረግ መሆኑን፣ ይህ ካልተቻለ ጉዳዩ በገላጋይ ዳኝነት የሚዳኝ ስለመሆኑ በሚገባ ተገንዝቧል።

ይህ ሁኔታ በግልጽ ሰፍሮ እያለና በሌላ ፍ/ቤትም አስቀድሞ ክስ የቀረበለት መሆኑ ለዞኑ ፍ/ቤት የተገለፀለት ቢሆንም ፍ/ቤቱ ለመቀበል ሣይፈቅድ ቀርቷል። እንደሚታወቀው ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1711 በግልጽ ተመልክቷል። የሕጉን አግባብ ተከትለው የተቋቀሙት ውሎች ደግሞ ባቋቋሚቸው ሰዎች ላይ መብትና ግዴታን ስለሚጥሉ እንደሕግ ሆነው የሚያገለግሉ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1731(1) ይደነግጋል። የሥር ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካችና መልስ ሰጭ መካከል የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ ለመስራት ቡተደረገው ውል በአንቀጽ 24 ላይ አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት የሚታዩ ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቶ እያለ ፍ/ቤቱ የውሉን አንቀጽ እርሱ በመሰለው ብቻ ተርጉሞ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መሰጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

- የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.06203 በ10/10/96 የሰጠው ው ሣ ኔ ተሽሯል፤

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 17077

ጥቅምት 14 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጐስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡ - ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል

መልስ ሰጪ፡ - አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ

ውል፡ - ስለዋስትና - በዋናው ባለዕዳ ግዴታ ላይ ስለሚደረግ መለዋወጥ (ዋስን ሣያስፈቅድ ባለገንዘቡ ለባለእዳው የመክፈያ ጊዜ የማራዘሙ ውጤት)፡ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1928(1)

አመልካች የእዳ መክፈያ ጊዜውን ዋስ የሆነውን መልስ ሰጭን ሳያስፈቅድ ያራዘመ በመሆኑ መልስ ሰጪ (ዋስ) ከገባው ግዴታ ነፃ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ውሣኔ፡ - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀናው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1928 (2) ዓላማ ከውሉ መፈፀም በኋላ በባለገንዘቡና በባለእዳው መካከል የዋሱን ግዴታዎች የሚያባብሱ አዲስ ስምምነቶች እንዳይደረጉና ዋሱን ለተጨማሪ ጉዳት እንዳይዳርጉት ለመጠበቅ ነው፡፡
2. የመፈፀሚያ ጊዜ የተያዘላቸውና ዋስትና የተገባላቸው ግዴታዎች የግዴታ መፈፀሚያ ጊዜያቸው ሲጠናቀቅ ዋስ ላልተፈፀመው ግዴታ ተጠያቂ እንደሚሆን ሁሉ ከግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ በኋላ ባለገንዘቡ በራሱ ፈቃድ በችሮታ መልክ የሚያደርገው የክፍያ ጊዜ ማሻሻያ ሆነ ሌሎች እርምጃዎች ዋስትና ከተገባለት ከቀድሞ ግዴታ ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ለበሰለው እዳ ከመጠየቅ አይድንም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡ - ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል - አቶ ፍቅሬ ሞያ ቀረቡ

መልስ ሰጪ፡ - አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ጠበቃ መኮንን ሽፈራው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር ማመልከቻ መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የአሁኑ አመልካች የእዳ መክፈያ ጊዜውን ዋስ የሆነውን የአሁኑን ተጠሪ ሳያስፈቅድ ያራዘመ በመሆኑ ዋሱ ከገባው ግዴታ ነጻ ነው ብለው ውሣኔ በማስተላለፋቸው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ፤ ተጠሪ ስለደንበኛው በመሆን አውጥቼው ለበረው የብረት ግገር ጨረታ የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ አመልካችን ተጠቃሚ በማድረግ የሰጠ ስለሆነ የተጠሪ ደንበኛ የሆነው ድርጅት በጨረታ አሸናፊነቱ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና በ10 ቀናት በማቅረብ ውሉን እንዲፈርም ቢጠየቅ ይህን ባለመፈፀሙ የቢድ ቦንድ ዋጋውን ተጠሪ እንዲከፍለው ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ የተለያዩ ነጥቦች ያካተተ መልስ የሰጠ ሲሆን በዋነኛነት ከሳች የተከሳሽ ደንበኛ ማሸነፉን ገልጾ ደብዳቤ ሲጽፍለት ከጨረታ ቅድመ ሁኔታና ከተከሣሽ ፈቃድ ውጭ የፊርማውን ቀን በ10 ቀናት አራዝሟል፡፡ በዚህም ሳያበቃ ለተጨማሪ 5 የሥራ ቀናት እንዲራዘም አድርጓል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ያለተከሳሽ ፈቃድ የግዴታ ጊዜውን በማራዘሙ ከተጠያቂነት ነጻ ነኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም አመልካች የተጠሪ ደንበኛ ጨረታ ያሸነፈ መሆኑን በመግለጽ ጥር 6 ቀን 1994 ዓ.ም. በቁጥር ዝስሮሚ/200/07/94 በተጻፈ ደብዳቤ ውሉን በመፈረም የመልካም ሥራ አፈጻጸሙን በአሥር ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ፣ ይህ ሳይሆን ቀርቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማደርስ ጉዳት ተከሣሽ በገባው ግዴታ መሠረት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ለተከሣሽ ደንበኛ በጻፈው ደብዳቤ ገልጿል፡፡ የአሁኑ አመልካች በመቀጠል ጥር 21 ቀን 1994 ዓ.ም ቁጥር 2 ዩኤስኦ ኤም/200/05/94 በሆነ ደብዳቤ የተባለውን ጊዜ በ5 ቀናት ያራዘመ መሆኑን ለተከሣሽ ደንበኛ ገልጾ ጽፏል፡፡ እነዚህ ደብዳቤዎች የተጠሪ ደንበኛ ውል እንዲዋዋልና ዋስትናውን እንዲያቀርብ የተሰጠውን 10 ቀናት ያለ ዋሱ ፈቃድ ማራዘማቸውን የሚያስረዱ በመሆናቸው በሕ.ቁ.1928/2/ መሠረት ዋስ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ከገባው ግዴታ ነጻ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ይግባኙ ውድቅ ሆኖ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡

አመልካች በሰበር እንዲታይለት ያቀረበው ማመልከቻ ይህንን ነጥብ የሚመለከት በመሆኑና የሕግ ትርጉም የሚያስነሳ ነጥብ ያለው መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጐ የተጠሪ መልስና የአመልካች የመልስ መልስ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል። በዚህ ጉዳይ የሕግ ትርጉም የማያስፈልገው ነጥብ፣ በዋስትና ውል የተመለተን የአንድ ግዴታ መፈፀሚያ ጊዜ፣ የመፈፀሚያ ጊዜ ካበቃ በኋላ ባለገንዘቡ የዋሱን ፈቃድ ሳይጠይቅ በራሱ ችሮታ ተጨማሪ የማስፈፀሚያ ጊዜ ለባለዕዳው ሰጥቶ ቢገኝ ድርጊቱ ዋሱን ከተጠያቂነት ነፃ ያደርገዋል ወይስ አያደርገውም? የሚለው ይሆናል።

እንደሚታወቀው ለአንድ ግዴታ አፈጻጸም ዋስ የሚሆን ሰው ባለዕዳ እንዲፈጽም የሚጠየቀውን ግዴታ በተስማማበት ሁኔታ ወይም ጊዜ ያልፈፀመ እንደሆነ ይህንኑ ግዴታ ለባለገንዘቡ ለመፈፀም የሚገደድ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1920 ላይ ተደንግጓል። ግዴታውን እንዲፈጽም የሚጠራ ማንኛውም ዋስ ከውሉ መፈፀም በኋላ በባለገንዘቡና ባለዕዳው መካከል የእርሱን ግዴታዎች ያባባሱ አዲስ ስምምነቶችን በማንሳት ግዴታውን ላለመፈፀም መከራከሪያ ሊያደርጋቸው የሚችል መሆኑን ቁጥር 1928/1/ ያስገነዝባል። በዚህ አንቀጽ በተለይ በንዑስ ቁጥር 2 የዋሱ ፈቃድ ሳይኖር በባለገንዘቡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሚደረግ የመክፈያ ጊዜ ማራዘሚያ ተግባር ዋሱን ከነጭራሹ ከተጠያቂነት ነጻ የሚያደርገው መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የተጠሪ ደንበኛ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትናውን እንዲያቀርብና ውል እንዲዋዋል አመልካች ደብዳቤ መጻፉ ተረጋግጧል፡፡ ዋሱን ጨምሮ ግዴታ የገቡበት የግዴታ መፈፀሚያው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ አመልካች ሌላ ተጨማሪ ቀናት የሰጠ ደብዳቤ መጻፉ ታውቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አመልካች በራሱ ፈቃድ ያደረገው የተጨማሪ ጊዜ ችሮታ የእኔን ዋስትና ቀሪ ያደርገዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት በዋንኛነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ፣ የአሁኑ አመልካች የግዴታ መፈፀሚያ ጊዜውን ካለዋሱ ፈቃድ አራዝሟል የተባለው መቼ ነው? የሚለው ይሆናል፡፡ ከጉዳዩ በግልጽ መረዳት እንደተቻለው የአሁኑ አመልካች ጥር 6 ቀን 1994 ዓ.ም የተጠሪ ደንበኛ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ የመልካም ሥራ አፈጻጸም እንዲያቀርብና ውል እንዲዋዋል ሲገለጽለት ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚደርስ ጉዳት የአሁኑ ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ገልጿል፡፡ ከሕጉና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ ደብዳቤ መንፈስ መረዳት የሚቻለው ነገር ከተባለው 10ኛ ቀን በኋላ ማለትም ከግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ ማብቂያ በኋላ ባለዕዳው የተመለከቱትን ግዴታዎች ፈጽሞ ካልተገኘ ዋሱ በባለዕዳው እግር ተተክቶ ግዴታውን መፈፀም እንደሚገባው ነው፡፡ በአንጻሩ ከዋሱ ፈቃድ ውጭ ከግዴታ መፈፀሚያ ማብቂያ ጊዜያት በፊት በዋናው ባለዕዳ ግዴታ ላይ የሚደረግ ለውጥ ዋሱን ነጻ የሚያወጣው መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1928/2/ ያስገነዝባል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ዓይነተኛ አላማ ከፍ ብለን ለመግለጽ እንደሞከርነው ከውሉ መፈፀም በኋላ በባለገንዘቡና ባለዕዳው መካከል የዋሱን ግዴታዎች የሚያባብሱ አዲስ ስምምነቶች እንዳይደረጉና ዋሱን ለተጨማሪ ጉዳት እንዳይዳርጉት ለመጠበቅ ነው፡፡

በዚህ መሠረት ጊዜ የተያዘላቸውና ዋስትና የተገባላቸው ግዴታዎች የግዴታ መፈፀማያ ጊዜያቸው ሲጠናቀቅ ዋስ ለግዴታው ተጠያቂ እንደሚሆን ሁሉ ከግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ በኋላ ባለገንዘቡ በራሱ ፈቃድ በችሮታ መልክ የሚያደርገው የክፍያ ጊዜያት ማሻሻያም ሆነ ሌሎች እርምጃዎች ዋስትና ከተገባለት ከቀድሞ ግዴታ ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይገናኝ በመሆኑ ለበሰለው እዳ ከመጠየቅ የሚያድን አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ሕጉ ሊጠብቀው ከተነሳው ዓላማ በመውጣት የአሁኑ አመለካች የግዴታ መፈፀሚያ ጊዜው ያለፈበትን ግዴታ ከዋሱ ፈቃድ ውጪ አራዝሞአል በማለት ዋሱ ከተጠያቂነት ነጻ እንዲሆን የተከተለው አካሄድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም ግዴታ የተገባባቸው መፈፀሚያ ጊዜያት ከተጠናቀቁ በኋላ ባለገንዘቡ ለዋናው ባለዕዳ የሚሰጣቸው የችሮታ መፈፀሚያ ጊዜያትም ሆኑ ሌሎች እርምጃዎች ዋሱ ግዴታ የገባበትን የቀድሞውን ግዴታ መፈፀሚያ ጊዜያት ማራዘሚያ ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም በማለት ይህን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ውሣኔ

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት የቢድ ቦንድ ዋጋ ብር 239,600 (ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ብር) ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ይከፈል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- የዳኝነቱን በታሪፉ መሠረት የጠበቃ አበል 10% ለአመልካች ይክፈል
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 17189

ጥቅምት 17 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

4. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡ - የሽቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት

መልስ ሰጪ፡ - አቶ ንጉሴ ዘለቀ

የስራ ግንኙነትን ስለማቋረጥ - በአሰሪ አነሳሽነት የሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ - ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ስለማቋረጥ - ስለ ደመወዝ - ስራ ላልተሰራበት ጊዜ ክፍያ ስለሚደረግበት ሁኔታ፡ -

የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 27/1/በ፣ 53/1/፣54 መልስ ሰጪ የአመልካች ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ሆኖ በማሰራበት ወቅት በስሩ የሚገኘውን ገንዘብ ያዥ በተገቢው ሁኔታ ባለመቆጣጠሩ የአሰሪው ድርጅት ገንዘብ እንዲመዘበር ምክንያት በመሆኑ መ/ሰጪ ከስራ የተሰናበተው በአዋጁ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27(1) (በ) መሠረት በአግባቡ ነው በሚል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መ/ሰጪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለስ ውሣኔ በመስጠቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሣኔ፡ - የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡

1. “ገንዘብ” አንድ ግዙፍነት ያለው ተንቀሣቃሽ “ንብረት” ነው፡፡
2. በአሰሪ “ገንዘብ” ላይ የደረሰ ጉዳት በአሰሪ “ንብረት” ላይ የደረሰ ጉዳት ነው፡፡
3. የአዋጅ ቁ.42/85 ድንጋጌዎች የስራ ውል በአሰሪው አነሳሽነት በተቋረጠበትና የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው የሚል ውሣኔ በሚሰጥበት ወቅት ሠራተኛው ያልሰራበትን ጊዜ ደመወዝ እንዲያገኝ የሚፈቅዱ አይደሉም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ.ቁ. 17189

ጥቅምት 17 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብድልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ንጉሤ ዘለቀ - አልቀረበም

ፍ ር ድ

ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ክስ መስርቶ የሥራ ውሌን ከሕግ ውጭ ስላቋረጠው ውዝፍ ደመወዜን ከፍሎ ወደ ሥራ እንደመልሰኝ ይወሰንልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ይህ ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራ ቀኙ በጉዳዩ ያቀረቡለትን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ እና የአመልካችን ኦዲተር በምስክርነት ከሰማ በኋላ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበተው በአመልካቹ ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ጉዳት በማድረሱ ምክንያት ስለሆነ ስንብቱ በሕብረት ስምምነቱ እና በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/1//በ/ የተደገፈ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ይህ ውሣኔ ይግባኝ በቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሸሮ ተጠሪ የሦስት ወር ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራው እንዲመለስ እንዲሁም ብር 100.00 ወጭና ኪሣራ እንዲከፈለው ተወስኗል፡፡

አመልካች ተጠሪው ወደ ሥራ ሊመለስም ሆነ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም በማለት አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ ተጠሪው ደግሞ በሰጠው መልስ ውዝፍ ደመወዙን የማላገኝበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ወደ ሥራ መመለስን አስመልክቶ ስለቀረበው አቤቱታ የሰጠው መልስ ግን አለመኖሩን ማመልከቻው ያስረዳል፡፡

ይህም ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በክርክሩ ሊፈቱ የሚገባቸው ጭብጦችም የተጠሪ የሥራ ውል መቋረጥ በሕግ የተደገፈ ነው? ወይስ አይደለም? ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው መወሰኑስ የሕግ መሠረት አለው የሚሉት መሆናቸውንም ተገንዝቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቹ የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው በቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅነቱ የየእለቱ ገቢ ተሰብስቦ ባንክ መግባቱን ማረጋገጥ ሲገባው በጊዜው ገንዘብ ያዥ የነበረው አቶ ስለሺ ታደለ ባዘጋጀው የገንዘብ እና የባንክ መዝገብ ላይ በመፈረም ወይም ሳይፈርም በመተው ጉድለት እንዲፈጽም ረድቶታል በሚል ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡ በየቀኑ ከሽያጭ የተሰበሰበውን ገንዘብ የመቆጣጠር ጉድለት ቢገኝ ገንዘብ ያገቡን መተማመኛ አስፈርሞ በመመሪያው መሠረት እርምጃ የመውሰድ እንዲሁም ገንዘቡ ባንክ ገቢ መደረጉን የማረጋገጥ ጉዳይ በሥራ መዘርዝሩ ላይ የተጠቀሰ የተጠሪ የሥራ ድርሻ መሆኑም በሥር ውሣኔ ተመልክቷል፡፡

ተጠሪ ይህ ኃላፊነት እንዳለበት አልካደም፡፡ የሚከራከረው ገንዘብ ያገቡ እ.ኤ.አ. በሰኔ ወር 1999 ላደረሰው ጉድለት እርሱም ቢሆን ከሥራ አልተሰናበተም ይልቁንም በዚህ ጥፋቱ በተግሳፅ ታልፏል፡፡ ሌሎች ጉድለቶች ተገኝተዋል በተባለበት ጊዜ ደግሞ እኔ እረፍት ላይ የነበርኩ በመሆኑ አይመለከተኝም በሚል አይነት መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በመሰረቱ ገንዘብ ያዥው እ.ኤ.አ. በሰኔ ወር 1999 አጉድሏል የተባለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ብር 6,221.93 ሲሆን በዚህ ጊዜ ተጠሪው በሥራ ላይ የነበረ መሆኑ አላከራከረም፡፡ እንዲሁም ተጠሪው ገንዘብ ያዥው በዚህ ጥፋቱ በተግሳጽ ብቻ ታልፏል በሚል በቀር እርሱ በዕለቱ ጉድለቱን በማግኘትና በመመሪያው መሠረት ተገቢውን በማድረግ የሥራ ድርሻውን በአግባቡ የተወጣ መሆኑን አላስረዳም፡፡ እንደውም በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪው ያለበትን የሥራ ግዴታ ተወጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ገንዘብ ያዡ በዚህ ድርጊት በተግሳጽ ታልፏል ማለቱም የእርሱን ኃላፊነትና ግዴታ የሚያስቀርለት አይሆንም፡፡

እንግዲህ ክርክሩን አስቀድሞ የዳኘው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከፍ ሲል ከተጠቀሰው አግባብ በማየት ድርጊቱ ተጠሪው በአመልካች ላይ ጉዳት ማድረሱን ለማረጋገጥ ይበቃል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ በዚህም ምክንያት ሌሎች በተጠሪው ተፈጽመዋል ወደተባሉ ጥፋቶች መሄድ እንደማያስፈልግ በውሣኔው ጠቅሶታል፡፡ በሌላ በኩል ግን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ እንደተፈፀመ የተረጋገጠው ከላይ የተጠቀሰው የገንዘብ ጉድለት ተጠሪውን ከሥራ ለማሰናበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሚበቃ መሆን አለመሆኑን አልመዘነም፡፡ በተጠሪ ተፈጽመዋል ወደተባሉ ሌሎች ጥፋቶች ዘልቆ መፈጸም አለመፈጸማቸውንም ለማጣራት አልሞከረም፡፡ ለፍርዱ መሠረት ያደረገው ገንዘብ ያቸኮው ገንዘብ ባጎደለበት ጊዜ ተጠሪው ሥራ ላይ ስላልነበረ ወደ ሥራ ሲመለስ አልተቆጣጠርክም ተብሎ መሰናበቱ ትክክል አይደለም የሚለውን ምክንያት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ፍ/ቤቱ በአመልካች የተነሱትን የክርክር ነጥቦች በሙሉ ቃኝቶ ፍሬ ነገሩን በማጥራት ፍርድ አለመስጠቱን የሚያመላክት ነው፡፡ እንዲሁም የሥር ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ፍሬ ነገር የደረሰበትን መደምደሚያ አሳማኝ ምክንያት ላይ ሳይመሰረት የለወጠው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ወደ ሕጉ ስንመለስ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/1/ ስር ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ሊያቋርጡ የሚችሉ ምክንያቶች የተዘረዘሩ ሲሆን ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሚኖረው በአሰሪው ንብረት ወይም ከሥራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኛነት ጉዳት ማድረስ የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ እንደሚያቋርጥ የሚደነግገው አንቀጽ 27/1//በ/ መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ችሎቱ አምኖበታል፡፡ ችሎቱ እዚህ እምነት ላይ የደረሰው ጉዳዩን ከፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1126 እና 1127 ጋር አገናዝቦ በማየትና # ገንዘብ ; አንዱ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ # ንብረት ; መሆኑን በመቀበል ነው፡፡ በተጨማሪም አንድ ሠራተኛ በአሰሪው የተሰጠውን ኃላፊነት ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት አንድን ነገረ በማድረግም ይሁን ባለማድረግ ሳይወጣው ቢቀርና በዚህ ድርጊቱ ሌላው ሰው በአሰሪው ገንዘብ ላይ በቀጥታ ጉዳት እንደያደርስ ተባብሮ ቢገኝ እራሱ በአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት እንደደረሰ ሊቆጠር ይገባዋል የሚል ትርጓሜ ለተጠቀሰው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27/1//በ/ በመስጠቱ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪው ሥራ ላይ በነበረበት ወቅት ገንዘብ ያዥው ያደረሰውን የገንዘብ ጉድለት መቆጣጠር ሲገባው አልተቆጣጠረም፡፡ ይህ ደግሞ ቢያንስ በከባድ ቸልተኝነት በአመልካች ንብረት ላይ ቀጥተኛ ባልሆነ ሁኔታ ጉዳት ማድረሱን ያረጋግጣል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥራ ውሉን መቋረጥ ሕገ ወጥ በማድረግ ተጠሪ ወደ ሥራ እንደመለስ መወሰኑ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ጋር ያልተጣጣመ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀጥሎ ተጠሪ ከሥራ ከተሰናበተ ጊዜ ጀምሮ ያለው ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው ሕጉ ይፈቅዳል ወይስ አይፈቅድም የሚለውን ነጥብ እናያለን፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የሦስት ወር ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው ተወስኗል፡፡ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል የታዘዘው ሥራ ያልተሠራው በሠራተኛው ጉድለት ባልሆነ ምክንያት ነው በማለትና የአዋጁን አንቀጽ 54/2/ መሠረት በማድረግ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህም ውሣኔ በአንቀጽ 54/2/ ላይ የሠፈረው ድንጋጌ አባባልና መንፈስ የሚመለከተው የሥራ ውሉ ተቋርጦ የቆየን ሠራተኛ ነው ወይስ ከዚህ የተለየ አኳኋን ያለውን ሠራተኛ ነው የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ይህንኑ ለመረዳት ለዚህ አንቀጽ መሠረት የሆኑትን የ53/1/ እና የ54/1/ን ድንጋጌዎች መመልከት ያስፈልጋል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 53/1/ ደመወዝ ማለት # አንድ ሠራተኛ በሥራ ውሉ መሠረት ለሚያከናውነው ሥራ የሚከፍለው መደበኛ ክፍያ ; ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 54/1/ም እንደዚሁ በአዋጁ ወይም አግባብ ባለው ሕግ በተለየ አኳኋን ካልተወሰነ ደመወዝ የሚከፈለው ለተሠራ ሥራ ብቻ መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከነዚህ ሁለት የተያያዙ የሕግ ድንጋጌዎች የደመወዝን ምንነት እና የአከፋፈል ሁኔታ መገንዘብ ይቻላል። በአንድ በኩል አንድ ሠራተኛ ደመወዝ የሚከፈለው ከውል የመነጨ ግዴታውን መፈፀም ሲችል እንደሆነ እናያለን። የሠራተኛ እና የአሠሪ ግንኙነት የሚመነጨው ሁለቱም ወገን ከሚገቡት ውል ነው። ይኸው ውል እንደማንኛውም ሌላ ውል ለሁለቱም ወገን መብት ያመነጫል ግዴታንም ይጥላል። ከነዚህ ተያያዥ መብትና ግዴታዎች አንዱ ሠራተኛው በውል ለማከናወን ቃል የገባውን ሥራ የማከናወን በተሠራው ሥራ መጠን ደግሞ በውሉ በተጠቀሰው ጊዜና መጠን ደመወዝ የማግኘት መብትና ግዴታ ነው። በዚህ መሠረት አሠሪው ከሠራተኛው ግልጋሎት ያገኛል። ባገኘው ግልጋሎት መጠንም በውሉ የተጠቀሰውን ደመወዝ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል። በመርህ ደረጃ እነዚህ መብትና ግዴታዎች ከውል የሚመነጩ አንዱ ያለሌላው ሊታሰቡ የማይችሉ የአንድ ሕጋዊ ግንኙነት ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ስለዚህ ሥራ ሳይሠራ ደመወዝ ሊከፈል አይችልም። ደመወዝ ሳይከፈል ደግሞ ሥራ ሊከናወን አይችልም። ይህ አጠቃላይ አባባል ከውል ሕግ መሠረተ ሃሳብ ጋር የሚጣጣም ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ አጠቃላይ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕጉ ሠራተኛው ሥራ ባይሠራም ደመወዝ ሊከፈለው የሚችልበትን ሁኔታ በተለየ አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት በአዋጁ አንቀጽ 54/2/ ከሁለት ሁኔታዎች አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ ሠራተኛው ሥራ ባይሠራም አሠሪው ደመወዝ የመክፈል ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች አንደኛ ሠራተኛው ዝንጉ ሆኖ እያለ አሠሪው ለሥራው አስፈላጊ የሆነውን መሣሪያና ጥሬ እቃ ሳያቀርብለት የቀረ እንደሆነ ወይም ሁለተኛ ሠራተኛው ሥራ ሳይሠራ የዋለው በራሱ ጉድለት ባልሆነ ምክንያት እንደሆነ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት የተለዩ ሁኔታዎች ከሥራ ውልም ሆነ ከአጠቃላይ የውል መሠረታዊ መርሆዎችና ድንጋጌዎች ጋር ተያይዘው መተርጎም ይኖርባቸዋል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የሚመነጨው ከሥራ ውሉ ነው፡፡ የአሠሪ ደመወዝ የመክፈል ግዴታም የሚመነጨው እንዲሁ ከሥራ ውሉ ነው፡፡ በሌላ በኩል የሥራ ውል ቢኖርም ደመወዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሚከፈለው ለተሠራ ሥራ ብቻ በመሆኑ ሠራተኛው ሥራ ሳይሠራ ደመወዝ እንዲከፈለው ሊጠይቅ አይችልም፡፡ ሠራተኛው በርሱ በኩል ያለውን የመሥራት ግዴታ ሳይወጣ አሠሪው ደመወዝ የመክፈል ግዴታውን እንዲፈጽም ሊጠይቅ የሚችለው ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ምክንያቶቹ አንዱ መኖሩን በማስረዳት ነው፡፡ ስለዚህ በአዋጁ አንቀጽ 54/2/ ያሉት ሁለት መስፈርቶች ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉት በአሠሪና በሠራተኛ መካከል ያለው የሥራ ውል ፀንቶ በሚቆይበትና ሠራተኛው በሥራ ገበታው በሚገኝበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የሥራ ውል በሌለበት ወይም የነበረ የሥራ ውል በተቋረጠበት ሁኔታ የአዋጁ አንቀጽ 54/2/ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

የሥራ ውል በሁለቱም ወገን ሊከበር እንደሚገባና ሊቋረጥ የሚችለውም በሕጉ በሰፈሩ ምክንያቶች ብቻ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ አሠራ በአዋጁ አንቀጽ 27 የተጠቀሱ ሁኔታዎች ተሟልተዋል ብሎ ሲያምን ያለማስጠንቀቂያ፣ በአንቀጽ 28 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልቷል ብሎ ሲያምን ደግሞ ሕጉን ተከትሎ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል ሕጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የሥራ ውልን ለማቋረጥ አሠሪው ክስ መመስረት ሳያስፈልገው የተናጠል እርምጃ የመውሰድ ሕጋዊ መብት አለው፡፡ አሠሪው በዚህ ረገድ የሰጠው ውሣኔ የሥራ ክርክርን መርምሮ የመወሰን ሥልጣን ባለው አካል ታይቶ እስካልተሻረ ድረስ በሁለቱም ወገን የነበረውን የሥራ ግንኙነት ቀሪ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

አሠሪው የሥራ ውሉን ያቋረጠው ሕግ በማይቀበለው ምክንያት የሆነ እንደሆነ ሠራተኛው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ወደአለው አካል ማቅረብ መብት አለው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት አካል አሠሪው የወሰደው ውሣኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን በመመርመር ውሣኔ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ቀድሞውኑ አሠሪው የሥራ ውሉን ያቋረጠው በሕጉ መሠረት አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ከደረሰ ለሠራተኛው የሚሰጠው መፍትሔ /remedy/ ሕጉ የሥራ ውል አለአግባብ ባቋረጠ አሠሪ ተፈፃሚ እንዲሆን የፈቀደውን መፍትሔ ብቻ ነው፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 43 የሥራውል አለአግባብ ወይም ሕገወጥ በሆነ ሁኔታ ሲቋረጥ ለሠራተኛው የሚሰጠው መብት በአማራጭ ወደ ሥራ መመለስ ወይም እነደነገሩ ሁኔታ የካሣ ክፍያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የማግኘት መብት ብቻ ነው። ሠራተኛ ወደ ሥራ እንዲመለስ ከማድረግ በተጨማሪ ሠራተኛው ሥራው ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈለው የሚያዝ የሕግ አንቀጽ የለም። በመሆኑም አለአግባብ ከሥራ የተሰናበተ ሠራተኛ ወደ ሥራ እንዲመለስ ከማድረግ በተጨማሪ ሥራ ላይ ላልነበረበት ጊዜ ደመወዙ እንዲከፈለው ማድረግ ሕጉ አይፈቅድም። ከላይ እንደተገለፀው በመሠረቱ መክፈልም ከተቻለ ደመወዝ የሚከፈለው የሥራ ውል ላለው ሠራተኛ ነው። የሥራ ውሉ የተቋረጠው ሕገወጥ በሆነ መንገድ ነው ቢባል እንኳ የሥራ ውሉ ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እንዲቀጥል ከማድረግ አልፎ ውሣኔው ወደ ኋላ ተመልሶ አሠሪው የሰጠውን ውሣኔ እንዳልተሰጠ መቁጠርና የሥራ ውል እንዳልተቋረጠ በማሰብ ሠራተኛው ሳይሠራ የቀረው በርሱ ጥፋት ባልሆነ ምክንያት ነው ማለት የሚቻል አይደለም። ሠራተኛው በአሠሪው ውሣኔ ከሥራ እንዲሰናበት ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ሠራተኛው በፍርድ ወደ ሥራ እንዲመለስ በተወሰነበት ጊዜ መካከል የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት አለ ሊባል አይችልም። ለዚህ ጊዜ ደመወዝ እንዲከፈል ማዘዝም አይቻልም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ ፍርድ ቤቱ አመልካች ውዝፍ ደመወዝ ይከፈል በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት በአላቸው የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎች ትክክለኛ ትርጉም ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ እያንዳንዱ ባለጉዳይ የሚያቀርበውን የሕግ ክርክር መርምሮ ውሣኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ ተከሣሹ ወገን በሕግ ነጥብ ላይ መልስ ሰጥቶ ባይገኝ ደግሞ የሕግ ጉዳይ የቀረበለት ፍ/ቤት በእራሱ አነሳሽነት በጉዳዩ ጭብጥ ይዞ ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ይጠበቅበታል፡፡ ውዝፍ ደመወዝ መከፈል አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ነጥብ የሕግ ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን ፍርድ ቤት ከተከሳሹ ወገን የቀረበለት ክርክር ያልነበረ ቢሆን እንኳ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥበት ያስፈልጋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የተጠሪ የሥራ ውል መቋረጥ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 27/1//በ/ የተደገፈ ስለሆነ ወደ ሥራ ሊመለስ አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡
2. እንዲሁም ይህ ችሎት አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎች በመተርጎም ሕጉ አንድ የሥራ ውል በአሰሪው አነሳሽነት በተቋረጠበትም ሆነ የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በሚል ውሣኔ በሚሰጥበት ሁኔታ ሠራተኛው ያልሰራበትን ጊዜ ደመወዝ እንዲያገኝ የሚፈቅድ አይደለም የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 16329 ሐምሌ 16 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተጠሪ የሦስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡ ይኸው ይፃፍ፡፡

የሐሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 5 ላይ የተመለከተው ዳኛ በዚህ ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ ለፈፀመው ተግባር የሥራ ውሉ እንዲቋረጥ በማለት በአብላጫው ድምፅ በተሰጠው መደምደሚያ የምስማማ ቢሆንም፣ አብላጫው ድምፅ ተጠሪ ፈፀመ ለተባለው ተግባር ለውሣኔው ዋቢ አድርጐ የጠቀሰው አንቀጽ 27/1/ /በ/ በተጠሪ ተፈፀመ ከተባለው ድርጊት ጋር ግንኙነት የሌለው በመሆኑ በዚህ የህግ ድንጋጌ ሊሸፈን ባልተገባው ነበር እላለሁ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪ የሥራ ውል በአሰሪው እንዲቋረጥ የተደረገው ተጠሪ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በሚሠራበት ቅርንጫፍ በሥሩ የሚገኘውን ገንዘብ ያዥ በተገቢው ሁኔታ ባለመቆጣጠሩ የአሠሪው ድርጅት ገንዘብ እንዲመዘበር ምክንያት ሆኖአል በሚል ነው፡፡ አብላጫው ድምፅ ይህ አይነቱ ድርጊት በአዋጁ አንቀጽ 27/1/ /በ/ ሥር ይጠቃለላል በማለት መደምደምያ ላይ ደርሷል፡፡ ምንም እንኳን በዚህ አንቀጽ #ንብረት; የሚለው ቃል አገላለጽ #ገንዘብን; የሚያጠቃልል መሆኑን ብስማማበትም በዚህ ጉዳይ ተመዝብሯል ወይም ሌላ ሰው ጥቅም እንዲውል ተደርጓል የተባለን የአሠሪ ገንዘብ ሆነ ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት በአሠሪ ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስን በሚመለከተው አንቀጽ ሥር ይጠቃለላል ብሎ ማለት አግባብ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

በአብላጫው ድምፅ የተጠቀሰው የሕግ አንቀጽ የአሰሪውን ንብረቶች በተለይ በማምረት ተግባር ውስጥ ቀጥተኛ ግንኙነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሚኖራቸውን ንብረቶች ሆነ ተብሎ ወይም በሚያስቀጣ ቸልተኝነት ከሚፈፀሙ የጉዳት ተግባሮች ለመጠበቅ የተደነገገ ድንጋጌ እንጂ የሥራ ተግባርን በመጣስ /Neglect of Duty/ የሚፈፀሙ መሰል የገንዘብ ብክነቶችን የሚሸፍን አይደለም በማለት በመደምደሚያ ሃሣቡ ተስማምቼ በሕጉ አተረጓጐም ላይ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 17429

ጥቅምት 21 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ተገኔ ጌታነህ

4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡ - ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ

መልስ ሰጪ፡ - አቶ ተስፋዬ ከበደ

የኑዛዜዎች ፎርምና ማስረጃ - በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ

ፎርም፡ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881

አቶ ከበደ ዳዲ በግልጽ ባደረጉት ኑዛዜ ሰነድ ላይ የኑዛዜ ዝርዝር የአራት ሸማግሌዎች/ምስክሮች/ ስም ከተፃፈ በኋላ እኛ ከዚህ በላይ ስማችን የተጠቀሰው ሸማግሌዎች በትክክለኛ አዕምሮአቸው ሆነው ሲናዘዝ ሰጥተናል ተብሎ የተጠቀሰ ቢሆንም እና ከተናዛዡና ከአራቱ ምስክሮች ፊርማ ቀጥሎ ደግሞ ይህንኑ ቃል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመስማታችን በፊርማችን እናረጋግጣለን የሚል ቢሆንም ኑዛዜው በተናዛዡና በአራቱም ምስክሮች ፊት ስለመነበቡ በግልጽ ያልተባለ በመሆኑ ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል ውሣኔ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰጠቱና ውሣኔውን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሣኔ

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀናው ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡

1. ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ሲናዘዙ ሰምተናል፤ አይተናል ተብሎ የተገለጸው የኑዛዜውን መነበብ የሚያመለክት ነው፡፡
2. ኑዛዜው ተነቧል የሚል ቃል በግልጽ አለመስፈሩ ብቻ ኑዛዜውን በምስክሮቹና በተናዛዥ ፊት አልተነበበም በማለት ኑዛዜውን ፈራሽ ለማድረግ በቂ ምክንያት አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 21 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ተገኔ ጌታነህ

ወ/ሮ ሆሣዕና ነጋሽ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ከበደ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኗ አመልካች በሥር ፍ/ቤት የሚች ባለቤቴ አቶ ከበደ ዳዲ የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሠጠኝ ብላ አመልክታ ተጠሪ በተቀዋሚነት ቀርቦ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የአባቴ /የሚች/ አይደለም፣ ኑዛዜው እንዲሻር እኔም ሌላ መዝገብ ያስከፈትሁ ስለሆነ መዝገቦቹ በአንድነት ታይተው ይወሰንልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሁለቱን መዛግብት መርምሮ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበ ይህም ሥርዓት መፈፀሙንና የተፃፈበትን ቀን የማያመለክት ካልሆነ ፈራሽ ነው፣ በኑዛዜው ሠነድ ላይ ኑዛዜው በተናዛዡና በአራቱም ምስክሮች ፊት ስለመነበቡ በግልጽ ያልተፃፈ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 881/2/ መሠረት ፈራሽ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሣኔ አፅንቷል፡፡ አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ፍሬ ሃሣብ የኑዛዜው ፅሁፍ መነበቡን ኑዛዜው የሚያሣይ ሆኖ ሣለ ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን፣ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤቶች የተፈፀመ የሕግ ስህተት ስለሌለ ፍርዱ ይፅናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡

በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ ኑዛዜው በፍ/ሕ/ቁ. 881/2/ መሠረት የተደረገ አይደለም መባሉ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

ጳጉሜ 5 ቀን 1990 ዓ.ም. በተፃፈው የአቶ ከበደ ዳዲ ኑዛዜ ላይ የኑዛዜው ዝርዝርና የአራት ሸማግሌዎች /ምስክሮች/ ስም ከተፃፈ በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
#እኛ ከዚህ በላይ ስማችን የተጠቀሰው ሸማግሌዎች በትክክለኛ አዕምሮዋቸው ሆነው ሲናዘዙ ሰምተናል፤አይተናል; ተብሎ ተጠቅሷል። ከተናዛዡና ከአራቱ ምስክሮች ፊርማ ቀጥሎ ደግሞ #ይህንኑ ቃል ለመስማታችን በፊርማችን እናረጋግጣለን ; ይላል።

የፍ/ሕ/ቁ.881/2/ #ኑዛዜው በተናዛዡና አራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበና ይኸም ሥርዓት /ፎርማሊቲ/ መፈፀሙንና የተፃፈበትንም ቀን የሚያመለክት ካልሆነ በቀር ፈራሽ ነው; በማለት ሲደነግግ የፍ/ሕግ ቁጥር 881/3/ ደግሞ #ተናዛዡና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም የአውራ ጣት ምልክታቸውን ካላደረጉበት በቀር ፈራሽ ነው; ይላል።

እነዚህ ሁለት ንዑሳን አንቀጾች አንድ ኑዛዜ አራት ነገሮችን ማለትም ኑዛዜው የተደረገበትን ቀን፣ በአራት ምስክሮች ፊት መደረጉን፣ ኑዛዜው በተናዛዡና በምስክሮች መፈረሙንና መነበቡን ማሣየት እንዳለበት ይደነግጋሉ፤ ከፍ ሲል ከኑዛዜው ፅሁፍ ላይ ወስደን ካሠፈርነው መረዳት የተቻለው ኑዛዜው ጳጉሜ 3 ቀን 1990 በሚል ቀን የተፃፈበት፣ የአራት ምስክሮች ስም ያለበት፣ ምስክሮቹና ተናዛዡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የፈረሙበት መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሌላም በኑዛዜው ላይ #ሲናዘዙ ሠምተናል፣ አይተናል; ተብሎ መገለፁም የኑዛዜውን መነበብ የሚያመለክት ነው፡፡ ሕጉ የኑዛዜውን መነበብ አስፈላጊነት ያስቀመጠው በሚነበብበት ወቅት ሟች/ተናዛዥ የተናገረው በትክክል በፅሁፍ መስፈሩን እንዲረዳና የተናዛዡ ፈቃድ መሟላቱን ማረጋገጥ እንዲቻል ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው የኑዛዜው ክፍል #ሲናዘዙ ሠምተናል፣ አይተናል; በሚል የሠፈረው ምስክሮች ያዩትና የሰሙት ኑዛዜው ሲደረግና የተፃፈው ኑዛዜ ሲነበብ ነው ተብሎ መገመት ይኖርበታል፡፡

የሥር ፍ/ቤቶች ኑዛዜውን ለማፍረስ የሚያበቃ የሕግ መሠረት በሌለበት በኑዛዜው ፅሁፍ ላይ ኑዛዜው #ተነቧል; የሚል ቃል ባለመኖሩ ብቻ ኑዛዜው በምስክሮችና በተናዛዡ ፊት ስለመነበቡ አልተፃፈም በማለት ፈራሽ ማድረጋቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 71/93፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.03644 የሠጧቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኑዛዜው በፍ/ሕ/ቁ. 881 በተደነገገው መሠረት የተከናወነ በመሆኑ የፀና ነው ብለናል፤ ይፃፍ፤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

184

<u>የሃሳብ ልዩነት</u>

ስሜ በተራ ቁጥር አራት የተጠቀሰው ዳኛ አብዛኛው ድምፅ የኑዛዜውን ሕጋዊነት በማረጋገጥ በሰጠው ውሣኔ የማልስማማ በመሆኑ የሃሳብ ልዩነቴን እንደሚከተለው አሰፍራለሁ፡፡

ከሦስቱ ዓይነት ኑዛዜዎች አንዱ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ነው፡፡ /የፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 880/ሀ/፡፡ ይህ አይነት ኑዛዜ ለማፅናት በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት መነበብና ይኸም ስርዓት መፈፀምን ማመልከት ይኖርበታል፡፡ /የፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 881/2/፡፡ ኑዛዜ የሚቹ ጥብቅ የሆነ ራሱ የሚፈፅመው ሥራ ነው፡፡ /የፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 857/1/ የማንበብ ሥርዓት አስፈላጊ የሆነው በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡ እየተናገረ ማናቸውም ሌላ ሰው ሊፅፈው ስለሚችል በሌላ ሰው የተፃፈው ቃል በትክክል የሚች ቃል መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ምስክሮቹ ኑዛዜ የተፃፈበትን ቋንቋ ለማወቅና የተፃፈውን ለመስማት ወይም ለማንበብ ራሳቸው ችሎታ ያላቸው መሆንም አለባቸው፡፡ /የፍ/ብ/ሕግቁ.837/

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ይህም ድንጋጌ በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ የመነበብ ስርዓት አስፈላጊና መነበቡም በትክክል በማያጠራጥር ሁኔታ መፈፀም ያለበት መሆኑን ያመላክታል፡፡

ወደ ጉዳዩ ስንመጣ አብዛኛው ድምፅ ኑዛዜው ተነቧል የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው የአቶ ከበደ ኑዛዜ የአራቱን ምስክሮች ስም ከጠቀሰ በኋላ #ሲናዘዝ ሰምተናል አይተናል; እንዲሁም ከተናዛዡና ከምስክሮች ፊርማ ቀጥሎ ደግሞ ይህንኑ ቃል ለመሰማታችን #በፊርማችን እናረጋግጣለን; የሚሉ ቃላቶች በመስፈራቸው ነው፡፡ በእኔ እምነት ምስክሮቹ ሰምተናል አይተናል የሚሉት ሟች ኑዛዜውን በመስጠት ላይ እያለ የተናገረውን ሊሆን ስለሚችል እነዚህ ቃላቶች በርግጠኝነት መነበብን አያመለክቱም ከነዚህ ቃላቶች ሕጉ እንዲፈፀም የሚፈለገውን የማንበብ ሥርዓት መፈፀም አለመፈፀም በትክክል ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ተፈፅሟል ለማለትም ያዳግታል፡፡ ይህ ሕጉ በግልፅ እንዲፈፀም የሚፈልገው ስርዓት መፈፀም ሳይረጋገጥ ደግሞ ኑዛዜው ሊፀና አይገባም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሚሸርበት ምክንያት ስለሌለ ሊፀና ይገባል ስል በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡ - የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን

መልስ ሰጪ፡ - አቶ ሙሉ አብርሃ

ስለዲክራሲዮን አሰጣጥ - የመጋዘን ኪራይ ስለሚታሰብበት ጊዜ፡ - የጉምሩክ ባለስልጣን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 60/1989 ዓ.ም.፣ አንቀጽ 2/18/፣ 43/1/ /ሀ/

አመልካች ከውጭ ያስመጣሁትን እቃ የጉምሩክ ስርአት አልተፈጸመበትም በሚል በመጋዘን በማቆየት ያስከፈለኝን የመጋዘን ኪራይ እና ዲክላራሲዮን ባለመስጠቱ እቃውን ለመሸጥ እንዳይቻል በማድረግ በመጋዘን በማስቀመጥ ለኪራይ እንዳወጣ ያደረገኝን ወጪ እንዲተካልኝ በማለት መ/ሰጪ ያቀረቡትን ክስ በመቀበል መ/ሰጪ በጠየቁት ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ፡ - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሠረት ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ ላደረገው እዳ ያስከፈለውን የመጋዘን ኪራይ የሚመለስበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡
2. የጉምሩክ ባለሥልጣን ዴክላራሲዮን መስጠት የሚችለው በህጉ መሠረት የጉምሩክ ስነ ስርአት ለተፈጸመበት እቃ ብቻ ነው፡፡ የጉምሩክ ስነ ስርአት ላልተፈጸመበት እቃ ዴክላራሲዮን ባለመስጠቱ በእቃው ባለቤት ለሚደርስ ጉዳት የጉምሩክ ባለስልጣን አይጠየቅም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡ - የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ኃ/መለኮት አበበ ቀርቧል፡፡

መልስ ሰጪ፡ - አቶ ሙሉ አብርሃ ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ መዝገብ ተከፍቶ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ አመልካች ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ ጉዳዮን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተመሣሣይ መንገድ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መሆኑን በመግለጽ ጥቅምጽ 29 ቀን 1997 ዓ.ም ተጽፎ እንዲቀርብ ባደረገው አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

በአሁኑ ተጠሪ ከሣሽነት የተጀመረውን ክርክር በመጀመሪያው በፍ/መ/ቁ.34187 ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ ከውጭ አገር በሕጋዊ መንገድ በማስመጣት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባሁትን 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት ተከሣሹ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ያለአግባብ ይዞ በማቆየት ለመጋዘን ኪራይ ያስከፈለኝ ብር 11.793.10በ ተመላሽ እንዲያደርግልኝ፣ ተከሣሽ በመጨረሻ እቃውን ሲለቅ አብሮ መስጠት የሚገባውን ዲክላራሲዮን ለመስጠት ፈቃደኛ ሣይሆን በመቅረቱና በዚሁ ምክንያት እቃውን በሀገር ውስጥ ለገበያ በማቅረብ ለመሸጥ ባለመቻሌ ለመጋዘን ኪራይ ያወጣሁትን ብር 96.600 እንዲከፍለኝ፣ የእቃውን ዲክላራሲዮንም እንዲሰጠኝ በሚል ባቀረበው ክስ ላይ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን መልስ እንዲሰጥበት አድርጐ ካከራከረ በኋላ ሰኔ 14 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መርምሮ በሰጠው ውሣኔ ተከሣሹ ከጉምሩክ ሕግ ጋር በተያያዘ ያነሣቸውን ክርክሮች ውድቅ በማድረግ ክስ የቀረበበትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘብ ብር 112.069.95 ከሕጋዊ ወለድ እና ክርክሩ ካስከተላቸው ልዩ ልዩ ወጪዎች ጭምር ለከሣሹ እንዲከፍል፣ የእቃውን ዲክላራሲዮንም ተከሣሹ እንዲበትን ወስኗል።

የአሁኑ አመልካች ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.32978 የይግባኝ አቤቱታ ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም. በሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 መሠረት ይግባኙን ሠርዞበታል።

ቀጥሎም በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል። አመልካች የአሁን ተጠሪ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት የከፈለው ኪራይ በሕጉ ሊመለስለት አይችልም። የጉምሩክ ባለሥልጣን እቃው በመጋዘን ለሚቆይበት ጊዜ ኪራይ የማስከፈል ስልጣን አለው። እቃው ተይዞ ሊቆይ የቻለው በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ አንድ ካርቶን የያዘው አንድ ፓኬት የፎቶ ኮፒ ወረቀት ነው ተብሎ ቢገለጽም ሲፈተሽ አንዱ ካርቶን 5 ፓኬት የያዘ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ተጠሪው ከውጭ አገር ያስመጣው 1600 ካርቶን በአጠቃላይ 6400 ተጨማሪ ፓኬቶች የያዘ መሆኑ በተደረገው ፍተሻና ምርመራ ስለተረጋገጠ እቃውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመያዝ ሥልጣን አለው፡፡ በእቃው ላይ ተገቢው ቀረጥ ሣይከፈልበት አመልካች ዲክላራሲዮን ለመስጠት አይገደድም፡፡ ተጠሪው እቃውን ከተረከበ በኋላ ለመጋዘን ኪራይ ከፍያለው የሚለውን ገንዘብ የምከፍልበት ምክንያት የለም ባይ መሆኑን በጽሁፍ እንዲቀርብ ያደረገው ማመልከቻ ያስረዳል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው ተብሎ በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻ ለተጠሪው እንዲደርሰው ተደርጐ የካቲት 7 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ በተጠሪው በኩል የቀረበው ክርክር፡ -

ተጠሪ የእቃውን መጠንና ብዛት በተመለከተ የሰጠው መግለጫ ትክክለኛ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር በአሁኑ አመልካች የተካደ ፍሬ ነገር ስላልሆነ ለሰበር ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪው ስለዕቃው ብዛት አሳስቶ አቅርቧል በሚል የገለፀው ተቀባይነት የለውም፡፡ የቅድመ ጭነት ምርመራ እንዲያደርግ ኃላፊነትና ሥልጣን የተሰጠው ኤስ.ጂ.ኤስ ኩባንያ ሪፖርት ሲያደርግ በዕቃው ብዛትም ሆነ ክብደት ረገድ ስህተት በማድረግ በቀረጥና ታክስ ታሪፍ አመዳደብ ላይ በመንግሥት ገቢና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅም ላይ ላስከተለው ጉዳትም ሆነ ጥፋት ራሱ ኩባንያው ኃላፊነት ወስዶ ሊከፍል የሚገባው እንጂ እቃ አስመጪው የሚጠየቅበት ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪው የፈፀመው ጥፋትም ሆነ ስህተት እንደሌለ ታምኗል፡፡ አመልካችም በተጠሪው በኩል የተፈፀመ ጥፋት እንደሌለ እያወቀ እቃው በጉምሩክ መጋዘን እንዲራገፍ በማድረግ ሲጠየቅ ባለማስረከብ በመጋዘን እንዲቆይ ያደረገው ያለአግባብ ነው፡፡ ዲክላራሲዮኑንም የመስጠት ግዴታ አለበት የሚል ይዘት ያለው ሲሆን አመልካች በበኩሉ በተጠሪው በኩል የተሰጠው መልስ ተቀባይነት የለውም የሚልባቸውን ምክንየቶች በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

ይህ ችሎት በበኩሉ በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት በተያዘው ጉዳይ ከሕጉ አኳያ ሊመረመሩ የሚገባቸውን የክርክር ነጥቦች፡ -

1ኛ/ እቃ አስመጪው ከውጭ አገር ወደ አገር ያስገባው እቃ በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ እንዲከፍል የተደረገው ኪራይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይመለስልኝ ብሎ የሚጠይቅበት የሕግ ምክንያት አለ ወይንስ የለም? የጉምሩክ ባለሥልጣንስ እቃው በመጋዘን ለቆየበት ጊዜ ያስከፈለውን ኪራይ ሊመልስ ይገባል የሚባልበት ምክንያት ይኖራል?

2ኛ/ የጉምሩክ ባለሥልጣን እቃ አስመጪው ከውጭ አገር ወደ አገር ያስገባው እቃ ብዛት በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ ተገልጾ ከቀረበው መጠን በላይ በሚል እና ከቀረጥና ታክስ ጋር በተያያዘ ምክንያት ዲክላራሲዮን አልሰጥም ብሎ መከልከል ይችላል አይችልም?

3ኛ/ የአሁኑ ተጠሪ እቃውን ከተረከበኩ በኋላ ዲክላራሲዮን ባለማግኘቴ የተነሣ ሊሸጥ ባለመቻሉ ሌላ መጋዘን ተከራይቼ ለማቆየት አውጥቻለሁ የሚለውን ገንዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉምሩክ ባለሥልጣን ለመክፈል ይገደዳል አይገደድም? የሚሉት መሆናቸውን ከመዝገቡ ለመገንዘብ ተችሏል።

በቅድሚያ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ ተከፍሏል የተባለው ኪራይ ሊመለስ ይገባል አይገባም የሚለው ክርክር ሲመረመር ከሣሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ከውጭ አገር ወደ አገር ያስገባው 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ በባለሥልጣኑ እንዲከፍል የተጠየቀውን ኪራይ ብር 11,793.10 ከፍሎ እቃውን በመረከብ ወስዶ ከቆየ በኋላ ይህንኑ ገንዘብ ሊመልስልኝ ይገባል ብሎ ሊከሰው የቻለው እቃው ወደ አገር እንደገባ እንዲያስረክብ ሲጠየቅ የዕቃው ብዛት በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ ተገልጾ ከቀረበው በላይ ሆኖ ተገኝቷል በሚል ሣቢያ እቃውን ይዞ በመጋዘን በማራገፍ እንዲቆይ ያደረገው ያለአግባብ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን የክሱ ፍሬ ነገር ያስረዳል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕጉ በኩል ያለው ሲታይ የጉምሩክ ባለሥልጣንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 43/ሀ/ ላይ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባ እቃ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተፈጽሞበት እስኪወጣ ድረስ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ ኪራይ የሚከፈልበት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ኪራዩም የሚከፈለው ለባለመጋዘኑ የጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በዚሁ ሕግ መሠረት እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ ኪራይ መክፈል የሚገባው መሆኑን አውቆ የተጠየቀውን ኪራይ ከፍሎ እቃውን አውጥቷል፡፡ ተጠሪው የጉምሩክ ባለሥልጣን እቃውን በመጋዘን ያቆየው ያለአግባብ ነው በሚል የሚያቀርበውን የክርክር ምክንያት በተመለከተም የጉምሩክ ባለሥልጣን ተጠሪው ወደ አገር ያስመጣው 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት በቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት ላይ እያንዳንዱ ካርቶን በውስጡ አንድ ፓኬት እንደያዘ ተደርጐ የቀረበለት ቢሆንም ሲፈተሽ እያንዳንዱ ካርቶን 5 ፓኬት የያዘ መሆኑን ሊያረጋግጥ በመቻሉ በሕጉ መሠረት ሊከፈልበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በተያያዘ ምክንያት ይዞ ያቆየ ሆኖ የሚታይ እንጂ ከሕጉ ውጪ ፈጽሟል የሚባል ነገር የለም፡፡ የእጥፍ እጥፍ ሆኖ የተገኘው እቃ በህገወጥ መንገድ የገባ ነው ተብሎ ባይታይ እንኳን የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ሣይፈጽምበት ከጉምሩክ መጋዘን ሊወጣ አይችልም፡፡ ተጠሪው ይኸው የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ሣይፈፀም የጉምሩክ ባለሥልጣን ወዲያው እቃውን እንዲያስረክብ ሲጠየቅ ማስረከብ ነበረበት፣ በጉምሩክ መጋዘንም ማቆየት አልነበረበትም በማለት የማያቀርበው ክርክር በሕግ ተቀባይነት የለውም፡፡ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ የከፈለው ኪራይ ይመለስልኝ ብሎ የሚጠይቅበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ መሠረት የተከፈለውን የመጋዘን ኪራይ የሚመልስበት ምክንያት የለም፡፡ የፊደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለእቃው ብዛት የተሣሣተ መረጃ የሰጠው የቅድመ ጭነት ምርመራ አድራጊው ኤል.ጂ.ኤስ የተባለው ኩባንያ ስለሆነ አቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ የተከፈለው የኪራይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘብ ሊመለስለት ይገባል በሚል የወሰነው የጉምሩክ ሕግን ያገናዘበ አይደለም፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን ለመስጠት ይገደዳል አይገደድም የሚለውን ጭብጥ በተመለተም የአሁኑ አመልካች እቃውን የሚመለከት ዲክላራሲዮን ለሰጠው አይገባም በማለት አጥብቆ የሚከራከረው በእቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥ ተሟልቶ ሣይከፈል ዲክላራሲዮን ሊሰጠው አይችልም በሚል ምክንያት ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ቀረጡ ተሟልቶ ባይከፈልም የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን አልሰጥም ብሎ ሊከለከል አይችልም፣ በእቃው ብዛት አገላለጽ ላይ ስህተት የፈፀመው የቅድመ ጭነት ምርመራ ያደረገው ኤስ.ጂ.ኤስ የተባለው ኩባንያ በመሆኑ በቀረጥና ታክስ ጉዳይ በኃላፊነት መጠየቅ ያለበት ይኸው ድርጅት ነው ባይ ነው፡፡

በተጠቀሰው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 2/18/ ላይ እንደተመለከተው “የጉምሩክ ዲክላራሲዮን” ማለት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ፣ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተላላፊ እቃዎች ዝርዝር የሚገለጽበትና የጉምሩክ ሥነ ሥርአት የሚፈፀምበት በባለሥልጣኑ የሚዘጋጅ ቅጽ ሲሆን ከዚህ የሕግ አገላለጽ ዲክላራሲዮን በዋናነት የጉምሩክ ሥነ ሥርአት የሚፈፀምበት ሰነድ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት መፈፀም የሚለውም ሲታይ በቀረጥና ታክስ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣንም ዲክላራሲዮን አዘጋጅቶ ሊሰጥ የሚችለው በሕጉ መሠረት ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዲከፈልበት ተደርጐ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ለፈፀመበት እቃ ነው፡፡ በሕጉ አግባብ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ላልተፈፀመበት እቃ ግን የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን እንዲሰጥ ሕጉ አይፈቅድም፡፡ እቃ አስመጪው በበኩሉ ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገባ የተፈቀደለትን እቃ አይነት፣ ብዛትና ክብደት በትክክል ገልጾ ለባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በማቅረብ በታሪፍ መሠረት ተወስኖ የማጠየቀውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል የጉምሩክ ሥነ ሥርአት እንዲፈፀምበት ላላደረገው እቃ ዲክላራሲዮን ይሰጠኝ ብሎ የመጠየቅ መብት ሊኖረው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይችልም፡፡ በቀረበው ጉዳይ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ ከውጭ አገር ወደ አገር ባስገባው እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ተሟልቶ ያልተከፈለ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በቅድመ ጭነት ምርመራው ሪፖርት ላይ የአሁኑ ተጠሪ ከውጭ አገር ወደ አገር የሚያስገባው 1600 ካርቶን የፎቶ ኮፒ ወረቀት እያንዳንዱ ካርቶን አንድ ፓኬት የፎቶ ኮፒ ወረቀት የያዘ መሆኑ ተገልጾ ለጉምሩክ ባለሥልጣን የተላከ ቢሆንም ወደ አገር ውስጥ ከገባ በኋላ ሲፈተሽ አንዱ ካርቶን አምስት ፓኬት የያዘ ሆኖ መገኘቱም ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪው ይህንኑ እያመነና በክርክሩም ሂደት በልዩነቱ ላይ ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ ብር 49.024.78 መኖሩን እየገለጸ ስህተቱን የፈፀመው የቅድመ ጭነት ምርመራ ያደረገው ኤስ.ጂ.ኤስ የተባለው ኩባንያ ስለሆነ ቀረጥና ታክስ ተሟልቶ ባይከፈልም የጉምሩክ ባለሥልጣን ዲክላራሲዮን ሊሰጠኝ ይገባል በሚል ያቀረበው ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የለውም፡፡ የአሁኑ አመልካች የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ላልተፈፀመበት እቃ ለተጠሪው ዲክላራሲዮን መስጠት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
አለበት በሚል የተሰጠው ውሣኔም ሕጉን መሠረት የደረገ ስላልሆነ የሚሰረዝ ነው።።

በመጨረሻም የአሁኑ ተጠሪ እቃውን ከተረከበ በኋላ ዲክላራሲዮን ባለማግኘቱ ምክንያት መጋዘን ተከራይቶ እቃውን ለማቆየት አወጣሁ የሚለውን ገንዘብ አመልካች ለመክፈል ይገደዳል አይገደድም የሚለው ሲመረመር ከላይ እንደተገለጸው የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ መሠረት የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን ለመስጠት የማይገደድ ሆኖ ስለተገኘ አስመጪው እቃውን ካስወጣ በኋላ ዲክላራሲዮን ባለማግኘቱ ምክንያት ለመጋዘን ኪራይ አውጥቻለሁ የሚለውን ብር 96,600 የጉምሩክ ባለሥልጣን የሚከፍልበት የሕግ ምክንያት የለም።።

ሲጠቃለል አንድ እቃ በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ በሕጉ መሠረት የተከፈለ ኪራይ አይመለስም።።

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ መሠረት የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን ለመስጠት አይገደድም፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣን የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት በሕግ የሚጠየቀው ኪሣራ የለም፡፡

በዚህ ጉዳይ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ለቆየበት ጊዜ በሕጉ መሠረት የተከፈለውን ኪራይ የጉምሩክ ባለሥልጣን ለአሁኑ ተጠሪ እንዲመለስለት፣ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ተሟልቶ ላልተፈፀመበት እቃ ዲክላራሲዮን እንዲሰጥ ዲክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት የተጠየቀውን ኪሣራ እንዲከፍል በሚል በተሰጠው ውሣኔም የሕግ ስህተት ተፈጽሟል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በፍ/መ/ቁ.3417፣ በ14/10/96 ዓ.ም.

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሰጠው ውሣኔም ሆነ ጉዳዩራ በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 32978፣ በ16/2/97 ዓ.ም. ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በሚል የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡ - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት

መልስ ሰጪ፡ - የወ/ሮ ሳድያ እስማኤል ወራሾች

ስለባለሀብትነት ማስረጃ - የባለሀብትነት የርስት የምስክር ወረቀት - ተቃራኒ ማስረጃ፡ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1195/1/፣ 1196/1

መልስ ሰጪ በስር ፍ/ቤት በቀረበባቸው ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 5፣ ቀበሌ 09 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 797 እና 798 የሆኑትን የንግድ ቤቶች ለስር ከሣሽ እንዲያስረክቡ ከተወሰነባቸው በኋላ አመልካች በክርክሩ ገብቶ ፍ/ቤቱ ውሣኔውን እንዲሽር ያቀረበውን ጥያቄ ንብረቶቹ ለመወረሳቸው ማስረጃ አልቀረበም በሚል ውድቅ በማድረጉና የተሰጠውንም ብይን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ፡ - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ብይን በአብላጫ ድምፅ ተሽሯል፡፡

1. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል ለአንድ ሰው የተሰጠ የባለሀብትነትን የምስክር ወረቀት ማስረጃ የተሰጠው ሰው የዚሁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
2. ማስረጃው የተሰጠው ከደንብ ውጭ በሆነ አሰራር መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ከፍ/ብ/ሀ/ቁ.1195 የተመለከተው የሕሊና ግምት ፈራሽ ይሆናል፡፡
3. በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት አይኖርም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 16 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡ - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ዘመድኩን ቀረበ

ተጠሪ፡ - የወ/ሮ ሳድያ እስማኤል ወራሾች እነ ወ/ሮ ሣባህ አብዶ/

ወራሽ አህመድ አብዶ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በሰበር ችሎቱ ለቀረበው ክስ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፊ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በስር በመቃወም አመልካች በመሆን የሥር ፍ/ቤት ታህሣሥ 6 ቀን 1995 ዓ.ም. በዋለው ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሰጠው ውሣኔ ላይ የተቃውሞ አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ ይዘቱም ተቃውሞ በቀረበበት ፍርድ ተከሣሽ የሆኑት አቶ አማን መሐመድ ከመቃወም አመልካች በውል ተከራይተው የሚነግድበትን በወ.5 ቀበሌ 9 የቤት ቁ. 797 እና 798 የሆኑትን ንግድ ቤቶች ተቃውሞ በቀረበበት ፍርድ ከሣሽ የሆኑት ወ/ሮ ሳዲያ የግል ንብረቶች ናቸው በሚል ተከሣሽ ቤቶቹን ለቀው ለከሣሽ እንዲያስረክቡ እንዲሁም ከየካቲት 7 ቀን 1994 ጀምሮ ያለውን ኪራይ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ በመስጠቱ ነው፡፡ በመቃወም አመልካች ቤቶቹ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሱ ላለፉት 28 አመታት ለአቶ አማን መሐመድ አከራይቶ ሲጠቀም መቆየቱንና ለከሣሽ ተሰጥቶ የነበረው ቁጥር 5127386 የሆነ የባለቤትነት ደብተር በአ/አበባ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የቤቶች ጉዳይ መምሪያ የተሰረዘ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮ የቆየ ቢሆንም ፍ/ቤቶቹ ስለ መወረሳቸው የሚያረጋግጥ የመረካከቢያ ቅጽ አልቀረበም በማለት የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ አድርጐታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ በፊ/ከ/ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረ ቢሆንም በተመሣሣይ ሁኔታ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች በሰበር አቤቱታው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በተሰረዘና ተቀባይነት በሌለው ማስረጃ ላይ ተንተርሶ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብሎ ያቀረበው ማመልከቻ የሕግ ትርጉም የሚያስነሳ ነጥብ ያለው መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የተጠሪ መልስና የአመልካች የመልስ መልስ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነጥብ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የተሰጠ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት በተሰረዘ ጊዜ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለው ነው፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1195 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል ለአንድ ሰው የተሰጠ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ማስረጃ ለተሰጠው ሰው ለዚሁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት እንደሆነ እንደሚያስቆጥረው ተመልክቷል፡፡ በአንባሩ ማስረጃው የተሰጠው ከደንብ ውጭ በሆነ አሰራር መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ከፍ ብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍትሐብሔር ቁጥር 1195 ላይ የተመለከተው የሕሊና ግምት ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1196/1/ ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ በሕግ አግባብ ሥልጣን ተሰጥቶት ይህን መሰሉን የባለሀብትነት ማስረጃ የሚሰጠው ክፍል ቁጥር 5127386 የሆነውን የባለቤትነት ደብተር የሰረዘው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት ደግሞ የሚገኝ የባለሀብትነት መብት አይኖርም፡፡ የተጠሪ ወራሾችም አውራሻቸው ያልነበራቸውን መብት ሊወርሱ አይችሉም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከፍ ሲል በተጠቀሱት የሕግ ቁጥሮች መሠረት የባለሀብትነት የምስክረ ወረቀቱ የተሰረዘ መሆኑን የተረዳው ቢሆንም የባለቤትነት ደብተሩ መሰረዝ ለአሁኑ አመልካች የሚሰጠው መብት የለም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ይህን ፍርድ በድምጽ ብልጫ ሰጥተዋል፡፡

ውሣኔ

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጥቅምት 10 ቀን 1997 ዓ.ም. በመ/ቁ. 15563 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሒሳብ ልዩነት

በአንድ ክርክር ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ለመግባት የሚችል እና በክርክሩ ሳይካፈልበት የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ሰው ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት መቃወሚያ ሊያቀርብበት እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 ላይ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አግባብ አንድ አመልካች ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በነበረው ክርክር ተካፋይ ሊደረግ ይገባው ነበር፤ አሊያም ሳይሟገትበት የተሰጠው ፍርድ የእርሱን መብት የሚጎዳ ሆኖ ተገኝቷል ይሰኝለት ዘንድ ለአቤቱታው የአቀረበው ማስረጃ ይህንኑ የሚያረጋግጠለት እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በወረዳ 5 ቀበሌ 19 ውስጥ የሚገኙትን ቁጥር 797 እና 798 የሆኑ የንግድ ቤቶች የተጠሪዎች አውራሽ እንድትረከብ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ መብቴን የሚጎዳው ነውና ገብቼ ተከራክሬ ፍርዱን እንዳሸር

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ይፈቀድልኝ ሲል ይህን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 በመጥቀስ አቤቱታው ለተጠቀሰው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ በቤቶቹ ላይ መብት አለኝ የሚለው ደግሞ በመንግሥት የተወረሱ ናቸው በሚል መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ቤቶቹ በመንግሥት የተወረሱ መሆናቸውን የማያሳይለት ማስረጃ አላቀረበም፡፡ የአቀረበው ሙግትም ይህ ማስረጃ አለኝ ወይም ነበረኝ በሚል አይነት ፍሬ ነገር ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ በሌላም በኩል ንብረቱ ባለቤት የሌለው ጠፍ የሆነ ንብረት ነው የሚል ክርክርና ማስረጃ የሌለው በመሆኑ ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1194 አግባብ ሊታይና የቤቶቹ ባለቤት መንግሥት ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ለተጠሪዎች አውራሽ ተሰጥቶ የነበረው የባለቤትነት ደብተር ተሰርዟል ማለቱ ብቻውንም ለእርሱ መብት የሚሰጠውና አቤቱታውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 አግባብ እንዲስተናገድለት ለማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡

በኔ እምነት የስር ፍርድ ቤቶች ወደ ዋናው ጉዳይ ተመልሰው ክርክሩን እንደገና መመርመር ሳያስፈልጋቸው አመልካቹን ወደ ክርክሩ ለመግባት የሚያስችልህ መብት መኖሩን አላስረዳህም በሚል ከወዲሁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄውን ውድቅ በማድረጋቸው የፈፀሙት የሕግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ውሣኔያቸው ሊፀና የሚገባው ነው በማለት ስሜ በሦስተኛ ተራ የተጠቀሰው ዳኛ አብዛኛው ድምጽ በተሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

5. አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡ - ንብ ትራንስፖርት አ.ማ

መልስ ሰጪ፡ - አቶ ተገኑ መሸሻ

የሰራዎች አገልግሎት መስጠትን የሚመለከቱ ውሎች ለሰራተኛው ስለማገባው የደመወዝ መብት ስራ ላልተሰራባቸው ቀናት ደመወዝ ስላለማግኘት - ስለ ስራ አለመኖር /በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ ስለሆነ ሰራተኛ/፡ - የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2534፣ 2540፣ 2541/1/

መልስ ሰጪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በቴክኒክ ዋና ክፍል ኃላፊ ሆኜ ስሰራ ከስራ ከመሰናበቴ በፊት ታግጄ በቆየሁበት ከታህሣሥ 23 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
1994 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሰኔ 5 ቀን 1995 ዓ.ም. ድረስ ያለው ደመወዜ እንዲከፈለኝ በማለት በፊዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበውን ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ መ/ሰጪ የጠየቀው ገንዘብ እንዲከፈለው ውሣኔ በመስጠቱና ውሣኔውም በፊዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ውሣኔ፡ - የፊዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፊዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. በድርጅት ሥራ መሪና በድርጅቱ መካከል ያለ የስራ ክርክር የሚዳኘው በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎትን መስጠት ስለማመለከቱ ውሎች ከቁጥር 2512 እና ተከታታዮቹ በተደነገጉት ህጐች መሠረት ነው፡፡
2. የስራ መሪ ደመወዝ ለተሰራ ስራ ብቻ የሚከፈል እንጂ ላልተሰራ ስራ የሚከፈል አይደለም፡፡
3. የስራ መሪው አንድም የስራ አገልግሎት ባይሰጥም እንኳን ይኸው ሁኔታ አሰሪው ስራ ሳይሰጠው በመቅረቱ ወይም እንዳይሰራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በመከልከሉ የተነሳ እንደሆነ ደመወዙን ለማግኘት መብት የለው ውሉ ባልታገደበት ወይም ባልተቋረጠበት ጊዜ ሠራተኛው /የስራ መሪው/ ስራ ላይ ሆኖ ነገር ግን አሰሪው ሥራ ሳይሰጠው ወይም እንዳይሰራ በከለከለው ጊዜ እንጂ ሠራተኛው ከስራና ከደመወዝ ታግዶ የስራ አገልግሎት ላልሰጠባቸው ጊዜያት አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 25 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

4. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

5. አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡ - ንብ ትራንስፖርት አ.ማ

መልስ ሰጪ፡ - አቶ ተገኑ መሸሻ

ለዚህ የሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሣሽ ሲሆን አመልካቹ ተከሣሽ ነበር፡፡

የተሰጠው የሥራ ክስ በድርጅቱ ውስጥ የቴክኒክ ዋና ክፍል ሀላፊ ሆኜ ስሠራ ከታህሣሥ 23/94 ዓ.ም. ጀምሮ ከሥራ ታግጄ ከቆየሁ በኋላ ሰኔ 5/95 የተፃፈ የስንብት ደብዳቤ ተሠጥቶኛል ስለዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ከታገድኩበት ጊዜ አንስቶ እስከተሠናበትኩበት ጊዜ ድረስ ያለው የ17 ወር ከ15 ቀን የተጣራ ደመወዜ 23.500 (ሃያ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ወጪና ኪሣራ ተጨምሮ ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሽ ማለትም ተጠሪው ቀርቦ የይርጋ መቃወሚያ አንስቶ በብይን ውድቅ የተደረገበት ቢሆንም ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከሣሽ ከሥራ የተሠናበተው ድርጅቱን የሚጐዳ ተግባር የፈፀመ መሆኑን በመግለጽ ሥራ ላልሠራበት ጊዜ ደመወዜ ሊከፈለው እንደማይገባ ይከፈለው ቢባል እንኳ ከ3 ወር ደመወዝ ሊበልጥ እንደማይችል በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ከሣሽ የሥራ መሪ እንደመሆኑ በፍ/ህጉ ላይ የሥራ መሪን ከሥራ ስለማገድ የተደነገገ ድንጋጌ የለም፣ በድርጅቱ የውስጥ ደንብ ስለመኖሩና በውስጥ ደንቡ መሠረት ስለማገዱ አላስረዳም በመልስ የዘረዘራቸውን ተግባራት ከሣሽ ፈጽመዋል ቢባል እንኳ ከሥራና ከደመወዝ ለማገድ በቂ ምክንያቶች አይደሉም በፍ/ሕ/ቁጥር 2574/1 ሠራተኛው አገልግሎት ባይሰጥም ይህ የሆነው በአሠሪው ምክንያት ከሆነ ደመወዝ የመክፈል ግዴታ አለበት፣ የ3 ወር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደመወዝ ብቻ ሊከፈላቸው ይገባል የሚለው የተከሣሽ ክርክር በፍ/ሕ/ቁጥር 2574/2/ የተመለከተው የ3 ወር ደመወዝ ክፍያ የሥራ ውሉ ለተቋረጠበት እንጂ የሥራ ውሉ ለታገደበት ጊዜ የሚመለከት አይደለም በማለት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቹ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙ ተሠርዞበታል፡፡

አመልካቹ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ይታረምልኝ ሲል በ14/5/97 የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የአቤቱታው ፍሬ ቃል ተጠሪው በ5/10/95 እና በ5/2/95 ተጽፎ የተሰጣቸው ደብዳቤ የሥራ ስንብት ሣይሆን የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት በአግባቡ አልመረመረም፡፡

አመልካች ተጠሪን ከሥራ ለማገድ ምክንያት ያደረገው በድርጅቱ ሥራና ገንዘብ ላይ በተለያዩ ጊዜያት ጉዳት ማድረሣቸውን የሚያመለክቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ናቸው፡፡ ፍ/ቤቱ የፍ/ሕ/ቁጥር 2575 ስለ ሥራ ውል መቋረጥ እንጂ ስለ ሥራ ውል ማገድ የሚመለከት አይደለም ያለው ያለአግባብ ነው፣ ተጠሪው በእገዳ ላይ ለቆዩበት ጊዜ ሥራ እንዳይሠሩ የከለከላቸው ድርጅቱ ነው ተብሎ ደመወዙ ይከፈለው መባሉ ስህተት ነው ምክንያቱም የፍ/ሕ/ቁጥር 2540 ሥራ ላልተሠራባቸው ቀኖች ሠራተኛው ደመወዝ ለማግኘት መብት የለውም የሚለውን የሚቃረን ነው፡፡ የፍ/ህግ ቁጥር 2574/2/ ከ3 ወር የማይበልጥ ክፍያ እንዲከፈል የደነገገው የሥራ ውል ሲቋረጥ ብቻ ነው ተብሎ የተሰጠው ትርጉም ስህተት ነው በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ስለሆነ ውሣኔዎቹ ተሽረው ወጪና ኪሣራ ተከፍሎን እንሠናበት የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ ማመልከቻው ለተጠሪው ደርሶ ሚያዝያ 19/1997 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አይገልጽም፣ የ6 ወር የጊዜ ገደብ የከሣሽን የጥቅም ጥያቄ በይርጋ አያግደውም፣ ተጠሪው በጥፊት ተከስሼ አላውቅም፣ ባልተቀጣሁበት ጉዳይ ጥፋት ነው ተብሎ ለሠበር አቤቱታ መቅረቡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ያለአግባብ ነው፣ ተጠሪ በ5/10/95 እና በ5/2/95 የተፃፈው የሥራ የምስክር ወረቀት እንጂ የሥራ ስንብት ደብዳቤ አይደለም ያሉት የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ የህግ ስህተት መሆኑን አያመለክትም፣ አመልካች መ/ቤት ከሥራና ከደመወዝ ያለበቂ ምክንያት አግደውና አሰናብተው ስለአጉላሉኝ በደሉ ታይቶ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ሳይሆን የፍሬ ነገር ክርክር ነው፣ በፍ/ሕግ ቁጥር 2540 ሥራ ላልሠራባቸው ቀኖች ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም ለተባለው ተጠቃሹ ህግ ሠራተኛው ሥራውን በራሱ ፍላጐት ሣይሠራ ሲቀር እንጂ አሠሪው ሥራ ሲከለክለው የሚጠቀስ አይደለም፣ የፍ/ሕግ ቁጥር 2574/2/ ለኪሣራ እንጂ ውዝፍ ደመወዝን የሚመለከት አይደለም፣ ከዚህ ጉዳይ ጋርም ግንኙነት የለውም ስለሆነም ጥያቄው ከበቂ ኪሣራ ጋር ተሠርዞ እንድሠናበት በማለት ሲከራከር አመልካቹ አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የቀረበው ክርክር ከፍ ብሎ በዝርዝር የተመለከተው ሲሆን፣ በኛ በኩል ተጠሪው ከሥራ ታግዶ ለቆየበት ጊዜ ደመወዙ ይከፈለው መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን አግባብ ካላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጐች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ተጠሪው በአመልካቹ ድርጅት ውስጥ የሥራ መሪ ሆኖ ሲሠራ የነበረ በመሆኑ የአመልካችና የተጠሪው የሥራ ክርክር የሚዳኘው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 16 የሥራ አገልግሎትን መስጠት ስለሚመለከቱ ውሎች ከቁጥር 2512 እና ተከታታይዎቹ በተደነገጉት ሕጐች መሠረት ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሠሪን የሥራ ውል ስለማቋረጥ እንጂ አሠሪን ከሥራ ስለማገድ በፍ/ብሔር ሕጉ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም ካለ በኋላ በፍ/ሕግ ቁጥር 2541/1/ መሠረት አመልካቹ ተጠሪውን ከሥራና ከደመወዝ አግዶ ለቆመባቸው ወራቶች ደመወዙን ይክፈለው ሲል ወስኗል፡፡

በመሠረቱ ከፍ/ሕግ ቁጥር 2534 ድንጋጌ በግልጽ መረዳት የሚቻለው ደመወዝ ለተሠራ ሥራ ብቻ የሚከፈል እንጂ ላልተሠራ ሥራ የሚከፈል አይደለም፡፡

የፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2540 ይህንኑ የሕጉን መርህ በመከተል ሥራ ላልተሠራባቸው ጊዜያት ወይም ቀናት ሠራተኛው ደመወዝ ለማግኘት መብት የለውም በማለት ግልጽ ድንጋጌ አስፍሮ ይገኛል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ይሁንና የፍ/ሕግ ቁጥር 2541/1/ ሠራተኛው አንድም የሥራ አገልግሎት ባይሠጥም እንኳን ይኸው ሁኔታ አሠሪው የሥራ ሣይሠጠው በመቅረቡ ወይም እንዳይሠራ በመከልከሉ የተነሣ የሆነ እንደሆነ ደመወዙን ለማግኘት መብት አለው ሲል ሠራተኛው የሥራ ውሉ ባልታገደበት ወይም ባልተቋረጠበት ጊዜ ሥራ ላይ ሆኖ ነገር ግን አሠሪው ሥራ ሣይሠጠው ወይም እንዳይሠራ በከለከለው ጊዜ የሚያገለግል እንጂ ሠራተኛው ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ የሥራ አገልግሎት ላልሠጣባቸው ጊዜያት ደመወዝ እንዲከፈለው የሚፈቅድ ድንጋጌ አይደለም፡፡

ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ብቻ ብለው በተመለከቱት የፍ/ብሄር ድንጋጌዎች አተረጓጐም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊሻሩ ይገባል ብለናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 34240 በ5/5/97 የሠጠው ውሣኔ እና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 1119 በ1-2-97 የሠጠው ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት የተሻሩ ስለሆነ የውሣኔው ግልባጭ

ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረሳቸው መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

ቅፅ 3

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
የካቲት 1998 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማውጫ

1. የስራ ውሉ በህገ ወጥ መንገድ የተቋረጠ የስራ መሪ ስለሚያገኘው መፍትሔ የመ/ቁ 15815/ (አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ሰለሞን አበበ/ 1
2. የስራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል የሚቀርብ ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ - የመ/ቁ. 17483 (የኦሮሚያ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን እና ወ/ሮ ሮማን ደምሴ) 6
3. ስራ ክርክር የይርጋ ጊዜ የመ/ቁ 16648 (የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ አንለይ ያየህ) 10
4. ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ስለማድረግ - የመ/ቁ 11924 (የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት ትዕግሥት ወርቁ 30
5. አንድ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት እረፍት ቀናት በገንዘብ ተቀይሮ ስለሚከፈልበት የህግ አግባብ የመ/ቁ. 14057 (የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ጌታሁን ኃይሉ) 41
6. በመኪና ግጭት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት ካሳ ለማግኘት የመኪናው ባለቤት ጥፋት እንዳለበት ማስረዳት የማይኖርበት ስለመሆኑ - የመ/ቁ 16270 (አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ መሐሪ መታ) 49
7. በህግ ወጥ መንገድ የስራ ውል የተቋረጠ ሰራተኛ ወደ ስራ እንዲመለስ ስለሚወሰንበት የህግ አግባብ የመ/ቁ. 18581 /በአዲስ አበባ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጥበቃ እና ሲ/ር ቀቡላ ከድር/ 55
8. የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነ ጊዜ የመ/ቁ 15631 (እነ የሻረግ መንግሥት እና እማሆይ የሻረግ ፈረደ)..... 64
9. ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ ተዋዋዮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚወስነው በውሉ መሠረት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ስለመሆኑ የመ/ቁ. 15551 (ዩናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ እና የኢትዮጵያ ሞተርና መሐንዲስነት ኩባንያ) 79
10. ከውል ውጭ በደረሰ ጉዳት ካሣ በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ መቅረብ ስለሚኖርበት ጊዜ የመ/ቁ. 16062

https://t.me/ethiopianlegalbrief

11. ፍርድ ቤት በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርን የመሰረዝ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የመ/ቁ. 14554 (ወ/ሮ ጽጌ አጥናፉ እና ባላምባራስ ውቤ ሽበሽ) 81
12. ንብረት በሐራጅ ስለሚሸጥበት የህግ አግባብ የመ/ቁ. 15672 (አቶ ታደለ ገለቻ እና አቶ ውድመጣስ ኑሮ) 87
13. የመጥሪያ አደራረስ አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተናገድበት መንገድ የመ/ቁ 16301 (ተገኝ እንግዳ እና አስናቀች ኪዳኔ) 90
14. ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳዩ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ስለመሆኑ የመ/ቁ 10797 (ሸክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እና እነ ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም) 93
15. በጨረታ ለገዛው ንብረት ገገር ዋጋውን ሳይከፍል ወይም ግዳታውን ሳይፈጽም ከቀረ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ስነ ስርአት የመ/ቁ 18199 (ዶ/ር ምናሴ እሸቱ እና እነ ግርማ አያና) ... 98
16. የመንግሥት ሰራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ የሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መስራቱ ስለሚኖረው ውጤት የመ/ቁ 16378 (የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ እና የቤ/ጉ/ክ/መ ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን) 101
17. የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ የመ/ቁ. 18342 (የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እና እነ አቶ ብርሃኑ ህሩይ) 106
18. ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ህጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ የመ/ቁ 14699 (የኢንጂነር ወርቁ መኮንን ወራሾች እና የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች መምሪያ) 111

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ.ቁ. 15815

ታህሣሥ 10 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

አቶ መስፍን እቁበየሱስ

አመልካች፦ አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት- ቃሲም ፈጂስ ቀረበ

ተጠሪ፦ አቶ ሰለሞን አበቡ- አልቀረበም

የስራ ክርክር - ስለ ማኔጅመንት አባል የሆነ ሰው የስራ ስንብት፣

ስለ ስራ ስንብት እና መመለስ፣ የካሳ ክፍያ እና ማስጠንቀቂያ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2570፣ 2573፣ 2574፣ 2571

የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪን አመልካች ከስራ ያባረረው ህጉን ተከትሎ ባለመሆኑ የተቋረጠበት ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎት ወደ ስራ ሊመለስ ይገባል በማለት በአርሲ ዞን ከፍ/ቤት የተሠጠውን ውሳኔ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>፦ የአርሲ ዞን ከፍ/ቤት የሰጠውና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያጸናዉ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡

1ኛ. በስራ አመራር ላይ ያሉ አባላት የስራ ውላቸው ቢቋረጥ የሚያገኙት መፍትሔ በአሠሪ ሠራተኛ አዋጅ የሚሸፈኑ ሠራተኞች ከሚያገኙት መፍትሔ የተለየ ነው፡፡

2ኛ. በአመራር ላይ ያለው ሠው ያለበቂ ምክንያት ያለማስጠንቀቂያ ቢባረር የሶስት ወር ደመወዝ ካሳ ይሠጠዋል እንጂ ወደ ስራ ሊመለስ አይችልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሣሥ 10 ቀን 1998 ዓ.ም
የመ.ቁ. 15815

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፦ አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት- ቃሲም ፈጂስ ቀረበ
ተጠሪ፦ አቶ ሰለሞን አበቡ- አልቀረበም

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ክርክር የተጀመረው በኦሮሚያ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው። ክሱን የመሠረተው ተጠሪው ሲሆን አቤቱታውም በአሜሩ አመልካች በ1989 ዓ.ም የወጣውን የማኔጅመንት መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37(1) በመተላለፍ ከስራ ያሰናበተኝ በመሆኑ የቀረብኝ ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎኝ ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው። ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ግራ ቀ□ን በጉዳዩ ከአከራከረ በኋላ የተጠሪ የስራ ስንብት ደንቡን ተከትሎ ያልተፈፀመ ስለሆነ የተቋረጠበት ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎት ወደ ስራ ሊመለስ ይገባል በማለት ወስኗል። ይህ ውሣኔም ጉዳዩን በይግባኝ ባየው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፀንቷል።

በመቀጠል አቤቱታ የቀረበለት ይህ ችሎትም የግራ ቀፅን ክርክር መርምሯል።

አንድ የማኔጅመንት አባል የሆነ ሰው ከሥራ ቢሰናበት ስንብቱ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት ወደ ስራ እንዲመለስ መወሰንን ሕጉ ይፈቅደዋል? ወይስ አይፈቅደውም? የሚለው ነጥብ በጉዳዩ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ መሆኑንም ተገንዝቧል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ከአስተዳደሩ ክፍል የሚፈረጅ ሰራተኛ መሆኑ አላከራከረም። ከስራ የተሰናበተውም በድርጅቱ የስራ አመራር ቦርድ በተሰጠ ውሣኔ መሆኑ በስር ውሣኔ ተመልክቷል። እንዲሁም በአስተዳደር መተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ተጠሪ ፈፅሞታል የተባለው ጥፋት አስቀድሞ በኮሚቴ ከዚያ ደግሞ በይግባኝ በስራ አመራር ቦርድ ታይቶ ውሣኔ ሊያገኝ ሲገባው ተጠሪው በቀጥታ በቦርዱ ከስራ እንዲሰናበት መወሰኑ በደንቡ የተቀመጠውን ሥርዓት የጠበቀ አይደለም በሚል ምክንያት ከፍ ሲል የተጠቀሰው ውሣኔ በስር ፍርድ ቤቶች መስጠቱን መዝገቡ ያስረዳል።

በመሠረቱ የስር ፍርድ ቤቶች ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጉት የአስተዳደር መተዳደሪያ ደንቡን መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው። ይህ የአስተዳደር መተዳደሪያ አንድ የአመራር አባል ጥፋት ፈጽሟል ቢሰኝ የጥፋቱ መፈፀም አለመፈፀም ተጣርቶ እርምጃ የሚወሰድበት ሥርዓት የተቀመጠበት ደንብ መሆኑንም ከውሣኔያቸው መንፈስ መረዳት ይቻላል። ፍርድ ቤቶቹ ተጠሪ ከስራ የተሰናበተበትን ሁኔታ ከደንቡ ጋር በማገናዘብ ስንብቱ በደንቡ የተመለከተውን ሥርዓት ያከበረ አይደለም የሚል ማጠቃለያ ላይ መድረሣቸውም ከፍ ሲል ተጠቅሷል። እንግዲህ የተጠሪ የስራ ስንብት ደንቡን የተመሠረተ መሆን አለመሆኑን ለመለየት የክርክሩን ፍሬ ነገር ማጥራት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ የዚህ ችሎት የስራ ድርሻ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ስንብቱ ደንቡን የተከተለ አይደለም ሲሉ በፍሬ ነገሩ ረገድ የደረሱበትን መደምደሚያ ይህም ችሎት ተቀብሎታል።

በሌላ በኩል ግን በአስተዳደር መተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ያልተፈፀመ የስራ ስንብት ለሰራተኛው ወደ ስራ የመመለስን መፍትሔ ሊያሰጠው የመቻል አለመቻሉ ጉዳይ የሕግ ጥያቄን የያዘ ነውና በዚህ ችሎት ሊዳኝ ይገባዋል። ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመለስ ይወስኑ እንጂ ይህንኑ እንዲወስኑ ያስቻላቸው የደንቡን አንቀጽ በውሣኔያቸው አልጠቀሱም። አሊያም ደንቡ በስሩ ከተመለከተው ስርዓት ውጭ ከስራ የተሰናበተን ሰራተኛ ወደ ስራ የመመለስ አላማ ያለው መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
አላረጋገጡም። እንዲሁም ተጠሪ የአስተዳደር መተዳደሪያ ደንቡ ከስርዓት ውጭ የተናበተ የአመራር አባል ወደ ስራ ይመለስ ዘንድ የሚፈቅድ ነው ሲል ያቀረበው ክርክር የለም። ይህ ደግሞ ፍርድ ቤቶቹ ተጠሪ ወደ ስራ ይመለስ ሲሉ ለደረሱበት መደምደሚያ በደንቡ የተፈቀደ መፍትሄን መነሻ አለማድረጋቸውን ለማመላከት ይበቃል። ፍርድ ቤቶቹ ያስደገፉት ሕግ ሣይኖር የደረሱበት ይህን ይህ ማጠቃለያም አሳማኝነት የሚጎድለው ሆኖ አግኝተነዋል።

ስለሆነም ጉዳዩ ለክርክሩ አግባብነት ከአለው የፍ/ብ/ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ሊመረመር የሚገባው መሆኑን አምነንበታል። በመሠረቱ ተጠሪ የስራ አመራር አባል በመሆኑ ከአመልካች ጋር የፈፀመው ያልተወሰነ ጊዜ የሰራ ውል ከሁለቱ በአንዳቸው የሁለት ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሊቋረጥ እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2570 እና 2571 ላይ መረዳት ይቻላል። አንድ አሰሪ የስራ ውሉን ያቋረጠበት በቂ ምክንያት ከሌለው ደግሞ ለሰራተኛው የሦስት ወር ደመወዙን የመክፈል ግዴታ እንዳለበት በዚሁ ሕግ አንቀጽ 2573 እና 2574 ላይ ተደንግጎ ይገኛል። እነዚህ ድንጋጌዎች እንደ ተጠሪ ያሉ የስራ አመራር አባላት የፈፀሟቸው የስራ ውሎች ያለበቂ ምክንያት እንኳ ሊቋረጡ እንደሚችሉ የሚያስገነዝቡ ናቸው። የስራ ውሉ መቋረጥ በአሰሪው በኩል በቂ ምክንያት ያልተሰጠበት ከሆነም ሰራተኛውን ወደ ስራ የመመለስ መፍትሄ የሚያስገኝለት ሣይሆን ካሣ ተቀብሎ ይሰናበት ዘንድ የሚፈቅዱለት ናቸው። ይህም የሚያሣየን በሥራ አመራር ላይ የሚገኙ ሰዎች የሥራ ውላቸው ቢቋረጥ የሚያገኙት ሕጋም መፍትሄ (remedy) ሌሎቹ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ የሚሸፈኑ ሰራተኞች ከሚያገኙት መፍትሄ የተለየ መሆኑን ነው። ፍርድ ቤቶች ለአንድ መብቱ ተነካ ለሚል ወገን የሚሰጡት መፍትሄ ደግሞ በሕጉ ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል። ከተጠቀሱት ሕጎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው የሥራ አመራር ላይ ያለ ሰው ሕጉ በማይፈቅደው ምክንያት እንኳን ከሥራ ቢሰናበት ፍርድ ቤት ወደ ሥራው እንዲመለስ ለማድረግ የሚያስችለው የሕግ ድጋፍ የለውም። ሕጉ የሰጠው መብት ካሳ መቀበል ብቻ ነው።

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በቦርድ ውሣኔ ከስራ መሰናበቱ እንጂ አመልካቹ የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ በመሰጠት የስራ ውሉን ያቋረጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መሆኑን አልተረጋገጠም። እንዲሁም ተጠሪው ለስንብቱ ምክንያት የተደረጉትን መስሪያ ቤቱን በቅንነት ለማገልገል ፈቃደኛ አይደለም፡ የበታች ሰራተኞችን ይንቃል ትእዛዞች አይቀበልም... ወዘተ በሚል በአመልካች የተጠቀሱትን ጥፋቶች መፈፀም አለመፈፀሙም በስር ፍርድ ቤቶች አልተረጋገጠም። በሌላ በኩል ግን የሥር ፍርድ ቤቶች የተጠሪ የስራ ስንብት የአስተዳደር መተዳደሪያ ደንቡን ተመስርቶ የተፈፀመ አይደለም የሚል ማጠቃለያ ላይ የደረሱ ሲሆን ይህም ችሎት ፍርድ ቤቶቹ በጉዳዩ ፍሬ ነገር የደረሱበትን የተጠቀሰውን ማጠቃለያ ተቀብሎታል። እነዚህ በጉዳዩ የሚታዩት ፍሬ ነገሮች ተዳምረው ሲመዘኑም አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት አልነበረውም ለማለት ያህል የሚበቁ መሆናቸውንም አምኖበታል። ይህም ተጠሪው ማስጠንቀቂያ ያልተሰጠው በመሆኑ ምክንያት የሁለት ወር ደመወዝ የስራ ስንብቱ በበቂ ምክንያት ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ደግሞ ቢበዛ የሦስት ወር ደመወዝ በካሣ መልክ እንዲያገኝ የሚያስችለው እንጂ ወደ ስራ እንዲመለስ የሚያደርገው አይደለም። ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ወደ ስራ እንዲመለስ የሰጡት ውሣኔ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የፍትሐብሔሩ ድንጋጌዎት ጋር ያልተጣጣመ ነው።

ው ሣ ኔ

1. የተጠሪ የስራ ውል መቋረጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2570(1) የተደገፈ ነውና ወደ ሥራ ሊመለስ አይገባም።
2. ይሁን እንጂ አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠበት በቂ ምክንያት ስለሌለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2573 እና 2574 መሠረት የሦስት ወር ደመወዝ በካሣ መልክ እንዲከፈለው ተወስኗል።
3. በተጨማሪም ተጠሪው የሁለት ወር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ያልተሰጠው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2570(2) እና 2571 መሠረት የሁለት ወር ደመወዙ እንዲከፈለው ተወስኗል።
4. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 38/95 የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በመ.ቁ. 2339/95/016 ግንቦት 3 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠት ውሣኔ ተሽሯል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መ/ቁ. 17483

ታህሣሥ 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፦ የኦሮሚያ ገጠር መንገች ባለሥልጣን
ተጠሪ፦ ወ/ሮ ሮማን ደምሴ

የስራ ክርክር - ይርጋ - አላግባብ ተቋርጧል የተባለን የስራ ውል ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ - የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162(1)

አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ወይ ስራዋ እንድትመለስ እና ጥቅማ ጥቅሞቹ እንዲጠበቁለት በማለት የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዓለም ገና ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሠጠውን ውሳኔ በመሻር የሠጡትን ውሳኔ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ።

<u>ው ሳ ኔ</u> ፦ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል።

1ኛ. የስራ መደብ ያልተቋረጠ ከሆነ ወደ ስራ ልመለስም ሆነ የውል አበል ክፍያ ይገባኛል የሚል ጥያቄ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162(1) ስር ከተመለከተው አጠቃላይ የይርጋ ድንጋጌ እንጂ በተለይ ከተደነገጉት ንዑስ አንቀጽ (2) እና (4) ስር የሚወድቅ አይደለም።

2ኛ. አንድ ሠራተኛ ከስራና ከደመወዝ ከዘጠና ቀን በላይ ከታገደ የስራ መቋረጡ ባይገለፅለትም መብቱን ለመጠየቅ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው የዕግድ ጊዜ ከሚያበቃበት ጊዜ አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፦ የኦሮሚያ ገጠር መንገች ባለሥልጣን - ሰላማዊት ኃይሉ ቀረበች
ተጠሪ፦ ወ/ሮ ሮማን ደምሴ - ቀረበች

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ ዓለም ገና ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ጥቅምት 19 ቀን 1995 ዓ.ም በመሠረተችው ክስ የተጀመረ ነው። የክሱም ይዘት አመልካች ከሕዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ጥር ወር 1993 ዓ.ም ድረስ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንድውል ከአስደረገ በኋላ አዲት ይደረግና ትመለሻለሽ በሚል ከስራና ከደመወዝ አግኛል። ይሁን እንጂ ከሚያዝያ 23 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ግንቦት 14 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ የአዲቱ ስራ የተከናወነ ቢሆንም ስራዬ ላይ ግን ሊመልሰኝ ፈቃደኛ አልሆነም። ስለሆነም የውሉ አበሌን ከፍሎ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው። አመልካችም ክሱ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ ስለሆነ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162/1/ መሠረት በይርጋ ይታገድልኝ የሚል መቃወሚያ እና በፍሬ ጉዳዩም አለኝ የሚለውን መልስ አቅርቦ ተከራክሯል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የተጠሪ የስራ ውል መቹ እንደተቋረጠ ባይታወቅም ክሱ የተመሠረተው ግን አዲት ተደርጎ ትመለሻለሽ ተብያለሁ ከአለችበት እለት ከጥር ወር 1993 ዓ.ም በኋላ ሁለት ዓመት ቆይቶ ማለትም ጥቅምት 19 ቀን 1995 ዓ.ም ነው እንዲሁም ተጠሪ አመልካቹ መብቱን አውቆልኛል ብትልም ለዚህ ያቀረበችው የጽሁፍ ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም ሌላ የቆጠረቻቸው የሰው ማስረጃዎችም ያላስረዱላት በመሆኑ የይርጋው አቆጣጠር ሊቋረጥ የሚችል አልሆነም ስለሆነም ክሱ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል በማለት ወስኗል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አንድ የስራ ውል የሚቋረጠው በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27(2) መሠረት አሰሪው ለሰራተኛው በሚሰጠው ጽሁፍ መሆን ሲገባው ይኸ በአመልካቹ አልተደረገም። ስለሆነም በሁለቱ መካከል የተፈፀመው የስራ ውል ስላልተቋረጠ አመልካቹ ለተጠሪዋ መሰጠቱ ከቆመበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ደመወዝዋን ከፍሉ ወደ ስራዋ ሊመልሣት ይገባል በማለት ወስኖ የስር ፍርድ ቤቱን ውሣኔ ሽሮታል።

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በውሣኔው የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት በአመልካች የቀረበለትን አቤቱታ ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል።

ይህም ችሎት በግራ ቀፅ የቀረበለትን ክርክር መርምሯል። ምላሽ የሚያስፈልገውም የጉዳዩ ነጥብ በተጠሪ የቀረበው ክስ በይርጋ ሊተገድ ይገባዋል? ወይስ አይገባውም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል። የተያዘውን ሙብጥ ለመፍታት በቅድሚያ ጉዳዩ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162 ስር ከተመለከቱት የይርጋ ደንቦች ውስጥ ከየትኛው ንዑስ አንቀጽ አግባብ ሊታይ እንደሚገባው መለየት ያስፈልጋል።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቹ ተጠሪዋ በእጅዋ ከገባው ገንዘብ ውስጥ ብር 21.595.00 አጉድላ ለግል ጥቅምዋ ማዋሏ ተረጋግጧል ቢልም ይህን ምክንያት ጠቅሶ የስራ ውሏን አለማቋረጡን አልካደም። ክርክሩ ተጠሪ በዚህ ጉዳይ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ከዋለችበት ጊዜ ጀምሮ በሕግ የስራ ውሏ ተቋርጧል ሊሰኝ ይገባዋል የሚል ነው።

ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በሁለቱ መካከል ያለው የስራ ግንኙነት በሕግ መቋረጡን ስለማያመለክት ውሉ አልተቋረጠም ሲል የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ሊነቀፍ የሚገባው አልሆነም። የስራ ውሉ ያልተቋረጠ በመሆኑም ተጠሪ ወደ ስራ ልመለስ ይገባል ስትል ያቀረበችው የክሷ ነጥብም ሆነ የውሉ አበል ክፍያ ይገባኛል ስትል ያነሣችው ጥያቄ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162(1) ስር ከተመለከተው አጠቃላይ የይርጋ ደንብ ድንጋጌ አኳያ እንጂ በተለይ ከተደነገጉት ንዑስ አንቀጽ (2) እና (4) አግባብ ሊታይ የሚገባው አይደለም።

በሌላ በኩል ተጠሪ ከስራ እና ከደመወዝ ከጎዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ታግዳ የቆየች መሆኑን አልካደችም። ይሁን እንጂ እስከ ግንቦት 14 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
1994 ዓ.ም ድረስ ሒሣብ እያስመረመርኩ ስለሆነ ስራ ላይ እንደነበርኩ ሊቆጠርልኝ ይገባል በሚል አይነት ተከራክራለች፡፡ ተጠሪ በሒሣብ ማስመርመር ተግባር ላይ መቆየቷ ግን መደበኛ ስራዋን ስታከናውን ነበር የሚያሰኛት ባለመሆኑ በዚህ ረገድ ያቀረበችው ክርክር አሣማኝነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከስራና ከደመወዝ የታገደችበት እለት ጎዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም መሆኑን ይህ ችሎት ተቀብሎታል፡፡

እንግዲህ ከፍ ሲል እንደመለከተው ተጠሪ የስራ ውሏ መቃረጥ በአመልካቹ ባይገለጽላትም ከጎዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ከስራና ከደመወዝ መታገድዋ ግን ተረጋግጧል፡፡ አንድ ሰራተኛ ከዘጠና ቀናት በላይ ከስራና ከደመወዝ ሊታገድ እንደማይችል ደግሞ ከአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 21(1) መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ሕጉ ለእግድ የፈቀደው ጊዜ እንደአበቃ ይገባኛል የምትለው ነገር በአመልካቹ ካልተደረገላት መብቷን ክስ መስርታ ትጠይቅ ዘንድ ይገባል፡፡ ክሷን የምትመሰርተውም በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162(1) መሠረት ጥያቄዋን ልታቀርብ ከምትችልበት ማለትም የእግዱ ጊዜ ከማያበቃበት ከየካቲት 14 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ማለትም እስከ የካቲት 14 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ብቻ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡

አመልካች ግን ክሷን የመሠረተችው ጥቅምት 19 ቀን 1995 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ የተጠቀሰውን የአንድ ዓመት የይርጋ ጊዜ አሳልፎ የቀረበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1ኛ. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተችው ክስ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162(1) መሠረት በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል፡፡

2ኛ. የዓለም ገና ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.63/95 ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል ሲል የሰጠው ውሣኔ ፀንቶ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ደአሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው በመ.ቁ. 02006 እና 16113 ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ እንድትመለስ የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
3. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
4. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
5. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

መልስ ሰጭዎች፡- እነ አቶ አንለይ ያየህ /27 ሰዎች/

ስለ ስራ ክርክር- የይርጋ ጊዜና የዕዳ ጥያቄ ቅድሚያ- የመብት ጥያቄ ስለሚቀርብበት የጊዜ አቆጣጠር - የይርጋ ጊዜ መቋረጥ - የይርጋ መብትን ስለመተው - ኃላፊነት የተሰጠው ባለስልጣን ስላለው ስልጣን - የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162፣ 163፣ 164፣ 165፣ 166 (በጉዳዩ የተሰጠው የህግ ትርጉም የአዋጅ ቁ.42/85ን በመሻር በወጣው አዋጅ ቁ.377/96 ድንጋጌዎችም ተፈፃሚነት አለው)

መ/ሰጭዎች በጌዶ፣ነቀምት እና ጊምቢ ባከናወነው የትራንስሚሽን መስመር መዘርጋት ስራ ለተሳተፉት ሌሎች ሰራተኞች አመልካች መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም የሰጠው የሁለት ዕርከን ጭማሪ እንዲሰጣቸው በመጠየቅ ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ባቀረቡት ክስ ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል በማለት አመልካች ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቦርድ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ በመስጠቱና ውሳኔውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሳኔ፡- የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዩ ወሳኝ ቦርድ የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 162 /3/ መሰረት የደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓትና የሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ ሊጠየቅ ይገባው ነበር ከሚሰኝበት ጊዜ ጀምሮ የስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሉ ተቋርጦ ቢሆን እንኳን ይህን ከግምት ሳያስገባ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

2. የሰራተኛው ወይም የአሰሪው ጥያቄ በተተኪዎቻቸው ወይም በወራሾቻቸው በሚቀርብበት ጊዜ በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 162/3/ እና 162/3/ በተደረጉ የይርጋ ድንጋጌዎች ይመራል፡፡
3. የሰራተኛው ወይም የአሰሪው ተተኪዎች ወይም ወራሾች የሰራተኛውን ወይም የአሰሪውን ሳይሆን የራሳቸውን መብት መሰረት በማድረግ የሚያቀርቡት ጥያቄ በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 162/3/ እና 162/4/ በተደነገጉት ሳይሆን በአንቀጽ 162/1/ በተደነገገው የይርጋ ድንጋጌ ይመራል፡፡
4. በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 164/1/ መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚቋረጠው ክሱ በአዋጅ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን በተሰጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ወይም በፍርድ ቤቶች በተቋቋሙ የስራ ክርክር ችሎቶች የቀረበ እንደሆነ ነው፡፡
5. ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ባልተሰጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ወይም በስራ ክርክር ችሎት የቀረበ ክስ በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 164/1/ መሰረት የይርጋ ጊዜን መቆጠር አያቋርጥም፡፡
6. በአዋጅ ቁ.42/85 /377/96/ አንቀጽ 164/2/ መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚቋረጠው አቤቱታው የቀረበው ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
7. ለአሰሪ የቀረበ አቤቱታ በአዋጅ ቁ.42/85 (377/96) አንቀጽ 164(2) መሰረት የይርጋ ጊዜ መቆጠርን አያቋርጥም፡፡
8. በአዋጅ ቁ.42/85 (377/96) አንቀጽ 166(1) ከፍትሐ-ብሄር ህግ ቁጥር 1793 ጋር ተገናዝቦ መታየት አለበት፡፡
9. ሰራተኛ ወይም አሰሪ በአዋጅ ቁ.42/85 (377/96) አንቀጽ 166(1) ለመጠቀም በድንጋጌው የተመለከቱት ሁኔታዎች መከሰታቸውን እና ክሱ በይርጋ የሚታገድበት ከመድረሱ በፊት ያልቀረበው በድንጋጌው ከተመለከቱት ሁኔዎች ቢያንስ በአንዱ መከሰት ምክንያት መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጥ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - አልቀረበም፡፡
ተጠሪዎች፡- እነ አቶ አንለይ ያየህ /27 ሰዎች/ - ጠበቃ ብዙአለም መርሻ ቀረበ

ፍ ር ድ

ይህ ክርክር አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ዘንድ የተጀመረ ነው፡፡ ተጠሪዎች ለቦርዱ ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረቡት ክስ ተከሣሽ /አመልካች/ በጌዶ፣ ነቀምት እና ጊምቢ በአከናወነው የትራስሚሽን መስመር መዘርጋት ሥራ ላይ በተለያየ የሥራ መደብ አገልግሎት ሰጥተናል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በዚህ ሥራ ላይ ለተሳተፉት ሠራተኞች በመሉ በመንግስት ትዕዛዝ መሠረት ከመጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. ጀምሮ የሁለት እርከን ጭማሪ ሲያደርግ እኛን ግን ከልክሎናልና ለእኛም ይህን ጭማሪ ከሞራል ካሣ እና ከወጭና ኪሣራችን ጋር ሊከፍለን ይገባል ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ የተጠየቀው የእርከን ጭማሪ ክፍያ ለሌሎች ሠራተኞች ከተፈፀመበት ከመጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት እስከ ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜ ከአስራ ሰባት ወር በላይ በመሆኑ ክሱ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/1-3/ መሠረት በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል ሲል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በአማራጭም መልሱን ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሩ የቀረበለት ቦርድም " .... የከሣሽና የተከሣሽ የሥራ ግንኙነት ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ...." በክሱ የቀረበው ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል። ወደ ጉዳዩ ፍሬ ነገር በመግባትም ከከሣሾቹ ውስጥ ከፊሎቹ ብቻ የአንድ እርከን ጭማሪ እንዲሰጣቸው እና ይኸውም ከመጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. ጀምሮ ተስተካክሎ እንዲከፈላቸው ወስኗል። ከዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ፍርዱ ጉድለት የለበትም በማለት የይግባኙን መዝገብ ዘግቶታል።

በመቀጠል አመልካች ከአስራ ሰባት ወራት በኋላ የቀረበው የተጠሪዎች ክስ በይርጋ አይታገድም በሚል በመወሰኑ ሕግ ተጥሷል፤ እንዲሁም በዋናው ጉዳይ የተሰጠው ውሣኔ የተሳሳተ ፍሬ ነገርን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ሊሻርልን ይገባል ሲል አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል። ተጠሪዎችም በጠበቃቸው አማካኝነት በአቀረቡት መልስ መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. የእርከኑ ጭማሪ እንደሚሰጥ ውሣኔው ለሠራተኞቹ ይፋ የሆነበት ቀን እንጂ ክፍያው የተፈፀመበት ቀን አይደለም። ይሁን እንጂ ሌሎቹ ሠራተኞች የካቲት 8 ቀን 1993 ዓ.ም. የእርከኑ ጭማሪ ተጠቃሚዎች መሆናቸው ሲገለጽላቸው ይህ ለተጠሪዎቹ ሳይደረግ በመቅረቱ ተጠሪዎቹ ይህን እንደአወቁ የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም. አቤቱታቸውን ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቅርበዋል። ለዚህ አቤቱታ በፅሁፍ ምላሽ ያላገኙ ስለሆነም የይርጋው ጊዜ ተቋርጧል የሚልና በጥቅሉም ፍርዱ እንዲፀና የሚጠይቅ መልስ አቅርበዋል።

ችሎቱም በዚህ ጉዳይ ሊታይ የሚገባው ነጥብ በተጠሪዎች የቀረበው ክስ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል? ወይስ አይገባውም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል።

ሕግ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው አግባብነት ላለው አካል ቀርበው የሚታዩበትን የተለያየ የጊዜ ገደብ አስቀምጦ ይገኛል። በዚህም

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ምክንያት አንድን ጉዳይ ለአንድ አካል አቅርቦ እንዲታይ ለማድረግ ጉዳዩ በሕግ የተፈቀደለትን የጊዜ ገደብ ጠብቆ የቀረበ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ በሕግ የተወሰነለትን ጊዜ አሳልፎ የቀረበ ጉዳይ ወደ ፍሬ ነገሩ ተገብቶ የመታየትን እድል ሳያገኝ ከወዲሁ ውድቅ ሊደረግ ወይም በይርጋ ሊታገድ ይችላል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በግራ ቀኙ የቀረበው ሙግት የሥራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ አግባብነት ያለው ሕግም የአዋጅ ቁጥር 42/85 ነው፡፡ ይህ የአዋጅ ቁ. 42/85 በክፍል አስር ምዕራፍ አንድ ከአንቀጽ 162 — 166 በሚገኙት ሕጎች ስር ስለ ይርጋ ደንብ ደንግጓል፡፡ የአዋጅ ቁ. 42/85ን የሻረው የአዋጅ ቁ. 377/1996ም በተመሳሳይ የሕጉ ክፍል፣ በተመሳሳይ የሕጉ ምዕራፍ እና በይዘታቸው ጭምር አንድ አይነት በሆኑ አንቀጾች ስር የይርጋ ደንብን አስቀምጧል፡፡ በእርግጥ ለዚህ ለያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የአዋጅ ቁ. 42/85 ነውና ለጭብጣችን ምላሽ ለመስጠት እንድንችል በዚህ ውሣኔያችን ውስጥ እንደአግባብነታቸው ይህ አዋጅ ያስቀመጣቸው የይርጋ ደንቦች በዋነኛነት የሚጠቀሱ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁለት ሕጎች አንድ አይነት አንቀጾች የያዙ በመሆናቸው በዚህ ውሣኔ ውስጥ ለአዋጅ ቁ. 42/85 የይርጋ ደንብ ድንጋጌዎች የሚሰጠው ትርጓሜ በአዋጅ ቁ. 377/1996 ለሚገኙትም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

የአዋጅ ቁ. 42/85 የመብት ጥያቄዎች ስለሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ በአንቀጽ 162 ላይ ደንግጓል፡፡ ከመነሻው የተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በዚህም ሆነ በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ከአልተወሰነ በስተቀር ጉዳዩን ማቅረብ ከሚቻልበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ከአልቀረበ የመብቱ ጥያቄ በይርጋ እንደሚታገድ አመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ የጉዳዩ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ጉዳዩን ለማቅረብ ከሚቻልበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡ እንዲሁም በሕግ የተለየ የጊዜ ገደብ ያልተደረሰት ጉዳይ ሁሉ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊቀርብ እንደሚገባው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በመደንገግ አጠቃላይ የሆነ የጊዜ ወሰን አስቀምጧል። በተጨማሪም ይኸው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 በንዑስ አንቀጽ /2/፣ /3/ እና /4/ ላይ ሕጉ የተለየ የይርጋ ጊዜ የወሰነላቸውን የአቤቱታ አይነቶች ለይቶ አመላክቷል።

የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 የተለየ የይርጋ ጊዜ ከወሰነላቸው የመብት ጥያቄዎች ውስጥ የመጀመሪያው የሆነው አንቀጽ 162/2/ "ሠራተኛው የሥራ ውሉ ከሕግ ውጭ ተቋርጦብኛል በማለት ወደ ሥራው ለመመለስ የሚያቀርበው ክስ ውሉ በተቋረጠ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል" በማለት ደንግጓል። በሌላ በኩልም የሥራ ውልን መቋረጥ ምክንያት አድርጎ ሠራተኛው በአሰሪው ላይ አሊያም አሰሪው በሠራተኛው ላይ የሚያነሳው የክፍያ ጥያቄ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በስድስት ወር ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ በዚሁ አንቀጽ 162/4/ ላይ ተደንግጓል። በግልጽ እንደሚታየው የመጀመሪያው ድንጋጌ የሥራ ውሉን መቋረጥ ሕጋዊነት በመቃወም ወደ ሥራዬ ልመለስ ይገባል የሚል ሠራተኛ ይህን ጥያቄውን ለማቅረብ የሦስት ወር ጊዜ ብቻ እንዳለው ያስገነዝባል። ሁለተኛው ድንጋጌ ደግሞ የሥራ ውልን መቋረጥ መነሻ አድርገው የሚቀርቡ ማናቸውም አይነት የክፊያ ጥያቄዎች በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተገደቡ መሆናቸውን ያመላክታል። በተጨማሪም ከእነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች አቤቱታ አቅራቢው የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በመብቱ መጠቀም የሚችል መሆኑን መረዳት ይቻላል።

እንደሚታወቀው ወደ ሥራ ልመለስ ይገባል የሚል ክስ በሠራተኛው በእራሱ እንጂ በተተኪዎቹ ወይም በወራሾቹ ሊመሰረት የሚችል አይደለም። ይሁን እንጂ ከሥራ ውል መቋረጥ በኋላ ሠራተኛውም ሆነ አሰሪው አንዱ ከሌላው ወገን ሊጠይቋቸው የሚችሏቸው የክፍያ አይነቶች በተተኪዎቻቸው ወይም በወራሾቻቸው ሊጠየቁ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል የሚታመን ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief
እንዲህ በሚሆን ጊዜ ተተኪዎቹ ወይም ወራሾቹ መሰረት አድርገው የሚቀርቡት የእራሳቸውን ሳይሆን የአውራሻቸውን ሠራተኛ ወይም አሰሪ መብት ነውና በይርጋው ጊዜ አቆጣጠር ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም፡፡ ስለሆነም የሠራተኛውን ወይም የአሰሪውን መብት ተክተው በወራሾቻቸው ወይም በተተኪዎቻቸው የሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎች የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ካልቀረቡ በይርጋ ሊታገዱ ይገባል፡፡

ሌላው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 የተለየ የይርጋ ጊዜ የወሰነለት የአቤቱታ አይነት በአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይኸውም " ሠራተኛው የሚያቀርበው የደመወዝ የትርፍ ሰዓትና የሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ መጠየቅ ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ..." መቅረብ እንደሚገባውና ይኸ ካልሆነ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጓል፡፡ ከድንጋጌው መረዳት እንደሚቻለው ይህን አንቀጽ ተመስርቶ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ በአሰሪውና በሠራተኛው መካከል የተፈፀመው የሥራ ውል ፀንቶ በአለበት ሁኔታ ሠራተኛው ከአሰሪው የሚጠይቀውን ክፍያ የሚመለከት እንጂ የግድ የሥራ ውሉን መቋረጥ ተከትሎ የሚነሳ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የስድስት ወሩ የይርጋ ጊዜ እንደሁኔታው ክፍያው ሊጠየቅ ይገባ ነበር የሚሰኝበትን እለት ተመስርቶ መቆጠር የሚጀምር እንጂ ውስን የመነሻ ጊዜ የተቀመጠለት አይደለም፡፡

ይኸ አንቀጽ 162/3/ ሠራተኛው አሰሪውን ደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓትና ሌሎችም ክፍያዎችን ሊጠይቅ የሚችልበትን ውስን ጊዜ ያስቀመጠ ቢሆንም የሥራ ውልን መቋረጥ ለይርጋው ጊዜ አቆጣጠር እንደመነሻ ባለመውሰዱ ከአንቀጽ/2/ እና /4/ ይለያል፡፡ ይርጋውም ሠራተኛው የተጠቀሱትን ክፍያዎች ሊጠይቅ ይገባው ነበር ከሚሰኝበት ጊዜ ይነሳና ምናልባትም የሥራ ውሉ ተቋርጦ እንኳ ቢሆን ይኸን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ እስከ ስድስት ወር ድረስ መቆጠሩ ይቀጥላል፡፡ እንዲሁም

https://t.me/ethiopianlegalbrief
እነዚህ ክፍያዎች በሠራተኛው ሳይሆን በተተኪዎቹ ወይም በወራሾቹ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ እንዲህ በሚሆን ጊዜም ጥያቄው የሠራተኛውን መብት ተመስርቶ የሚቀርብ ነውና ልክ እንደቀድሞው ሁሉ በይርጋው ጊዜ አቆጣጠር ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም፡፡ ስለሆነም ተተኪዎች ወይም ወራሾች የተጠቀሱትን ክፍያዎች ሠራተኛው ሊጠይቅ ይገባው ነበር ከሚባልበት ጊዜ አንስቶ እስከ ስድስት ወር ድረስ ካልጠየቁ በቀር ክሳቸው በይርጋ የሚታገድ ይሆናል፡፡

እንግዲህ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 መሠረት አንድ የሥራ ክርክር ጉዳይ የተለየ የይርጋ ጊዜ የተቀመጠላቸውን የመብት ጥያቄዎች የሚመለከት ከሆነ ከንዑስ አንቀጽ/2/ እስከ /4/ የተጠቀሱትን የሦስት ወይም የስድስት ወራት የጊዜ ገደብ አክብሮ የቀረበ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ሥር የማይሸፈን ከሆነ ደግሞ በንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተውና በአንባሩም ሰፊ በሆነው የአንድ ዓመት የጊዜ ወሰን ውስጥ እንዲቀርብ ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የይርጋ ጊዜ የተወሰነበት የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 ሠራተኛውና አሰሪው አንዱ ከሌላቸው የመብት ጥያቄዎችን የሚያቀርቡበትን ሁኔታ ብቻ በመጥቀስ የተደነገገ መሆኑን ከአንቀጾቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የሠራተኛው ወይም የአሰሪው ጥያቄ በተተኪዎቻቸው ወይም በወራሾቻቸው በሚቀርብበት ጊዜም የይርጋው አቆጣጠር ሊለወጥ እንደማይገባ ከላይ ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ የሠራተኛውም ሆነ የአሰሪው ተተኪዎች ወይም ወራሾች የሠራተኛውን ወይም የአሰሪውን ሳይሆን የእራሳቸውን መብት መሠረት አድርገው አንዳቸው ከሌላቸው ክፍያ ሊጠይቁ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ እንዲህ በሚሆን ጊዜ ግን የይርጋው አቆጣጠር ከአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/3/ ወይም /4/ አኳያ ሳይሆን አጠቃላይ የይርጋ ደንብ ድንጋጌ ከሆነው ከአንቀጽ 162/1/ አግባብ መታየት ይገባዋል፡፡ ስለሆነም የተጠቀሱት ሰዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በእራሳቸው መብት ላይ ተመስርተው የሚያቀርቡት ክስ በሌላ ሕግ ላይ በሌላ የይርጋ ደንብ ካልተሸፈነ በቀር በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/1/ መሠረት የመብታቸውን ጥያቄ ሊያቀርቡ ከሚችሉበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ አመት ድረስ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል።

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162 አንድ የሥራ ክርክር ጉዳይ ሊቀርብ የሚችልበትን የጊዜ ወሰን አስቀምጧል። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ጉዳይ በሕግ የተወሰነለትን የጊዜ ወሰን ጠብቆ ባይቀርብም እንኳን ሊታይ የሚችልባቸው ሦስት ሁኔታዎች እንዳሉ ደንግጓል። እነዚህም ሁኔታዎች ከአንቀጽ 164 እስከ አንቀጽ 166 ባሉት ድንጋጌዎች ላይ ተጠቅሰው የሚገኙ ሲሆን እነርሱም፡- የይርጋ ጊዜ መቋረጥ፣ የይርጋ መብትን መተው እና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጊዜው ያለፈበትን ክስ መቀበል መሆናቸው በእነዚሁ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቶ ይገኛል።

ስለ ይርጋ ጊዜ መቋረጥ

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የመጀመሪያው ሁኔታ የይርጋ ጊዜ መቋረጥን ይመለከታል። ይህ ሁኔታ የተደነገገበት የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164 የይርጋ ጊዜ፡

1. የሥራ ክርክርን ለሚወሰን ባለስልጣን ክስ ቀርቦ የመጨረሻ ውሣኔ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ፣
2. የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን በሥራ ላይ ለማዋልና ለማስፈጸም ኃላፊነት ለተሰጠው ባለስልጣን አቤቱታ ቀርቦ የመጨረሻ ውሣኔ በጽሁፍ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ፣
3. በይርጋው ጊዜ ተጠያቂ የሆነው ወገን የሌላውን መብት በጽሁፍ ሲያውቅለት ወይም በከፊል ሲፈጽምለት ሊቋረጥ እንደሚችል ደንግጓል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ አንድ ወገን ተከራካሪ በሌላው ላይ ክስ መስርቶ የመገኘቱ ጉዳይ ተጀምሮ የነበረን የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር እንደሚያቋርጠው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1851/ለ/ ላይ ተመልክቷል። ለሥራ ክርክር ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የአዋጅ ቁ. 42/85ም ከዚህ የፍትሐብሔር ሕግ ጋር በተስማማ ሁኔታ ክስ አቅርቦ የመገኘት ነገር የይርጋን ጊዜ አቆጣጠር እንደሚያቋርጥ በአንቀጽ 164/1/ ላይ ጠቅሶታል። የይርጋውን አቆጣጠር የሚያቋርጠው ክስ የተመሰረተውም የሥራ ክርክርን ከሚወስን ባለስልጣን ዘንድ ሊሆን እንደሚገባ በንዑስ አንቀጹ በግልጽ ተደንግጓል። ይሁን እንጂ ይህ ድንጋጌ የሥራ ክርክርን እንዲወስን ኃላፊነት ለተሰጠው ባለስልጣን ሲል ማንን ለማለት ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ስለማይሰጥ ይህን ነጥብ ለመፍታት ይተረጎም ዘንድ ያስፈልጋል። ከአዋጅ ቁ. 42/85 አግባብ የሥራ ክርክር የሚወስን ባለሥልጣን ሊሰኝ የሚችለው የትኛው አካል ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በቅድሚያ " ውሣኔ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማየቱ ይጠቅማል። ይህ "ውሣኔ" የሚለው ቃል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 3 ላይ አንድን ክርክር የያዘ ፍርድ ቤት "... ተከራካሪዎቹ ወገኖች ያቀረቡትን ክስና መልስ እንዲሁም ማስረጃዎቹን መርምሮ ...." የሚሰጠው ውሣኔ ማለት እንደሆነ ተተርጉሟል። ስለሆነም ጉዳዩ ከዚህ ትርጓሜ አኳያ ሲታይ አንድን አካል የሥራ ክርክርን የሚወስን ባለስልጣን ነው በሚል ለመፈረጅ ተቋሙ በሥራ ክርክር ጉዳይ ላይ ግራ ቀኝ ወገንን አከራክሮ ውሣኔ ለመስጠት በአዋጁ ስልጣን የአገኘ ሊሆን ይገባዋል። እንደሚታወቀው በአዋጁ መሰረት አንድም ፍርድ ቤቶች በስራቸው በተቋቋሙ የሥራ ክርክር ችሎቶች አማካኝነት፤ ሌላም በየክልላዊ መስተዳድሩ የተቋቋመ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በሥራ ክርክር ጉዳይ ላይ ውሣኔ ይሰጡ ዘንድ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። ይኸንንም ከአዋጁ አንቀጽ 137-140 እንዲሁም ከ147-156 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ላይ መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም እነዚህን ሁለት ዳኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሰጭ አካላት የሥራ ክርክርን ለመወሰን ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው ልንላቸው እና የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164/1/ የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ሲል አንድም ፍርድ ቤትን ሌላም የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድን ማለቱ ነው፡፡ በሚል ልንተረጉመው ይገባል፡፡

በተጨማሪም የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164/1/ የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ክስ ማቅረብ የይርጋን ጊዜ እንደሚያቋርጥ ከሚደነግግ በቅር ክሱ ክርክሩን ለመዳኘት ስልጣን ለሌለው አካል ቢቀርብ የይርጋው አቆጣጠር ምን ሊሆን እንደሚገባ አላመለከተም፡፡ ለምሳሌ ፍርድ ቤት እና የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሁለቱም የሥራ ክርክርን ለመዳኘት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ቢሆኑም ፍርድ ቤት የወል የሥራ ክርክርን፤ ቦርድ ደግሞ የግል የሥራ ክርክርን የሚመለከቱ ክሶች ይዳኙ ዘንድ በአዋጁ ስልጣን አልተሰጣቸውም፡፡ ስለሆነም እነዚህ አካላት ዘንድ የቀረበው ክስ በስልጣናቸው ሊሸፈን የማይችል የሥራ ክርክር ሆኖ ቢገኝ የይርጋው አቆጣጠር ይቋረጣል? ለሚለው ጥያቄ ድንጋጌው ግልጽ ምላሽ ስለማይሰጥ ነጥቡን ለማጥራት ይቻል ዘንድ ድንጋጌው ከሌላ ተዛማጅነት ካለው ሕግ ጋር ተገናዝቦ እንዲተረጎም ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ችሎት እምነትም ለዚህ ጉዳይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 278/3/ አግባብነት ይኖረዋል፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 278/3/ በፍርድ ቤት ፈቃድ እንደገና ስለሚቀርቡ ክሶች የይርጋ አቆጣጠር የሚደነግግ ነው፡፡ ይኸውም አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ክስ በከፊልም ሆነ በሙሉ አንስቶ ከሣሹ ክሱን እንደገና እንዲያቀርብ ሲፈቅድ የይርጋው ዘመን የመጀመሪያው ክስ እንዳልቀረበ ተቆጥሮ በአዲሱ ክስ መሰረት እንደሚታሰብ ይጠቅሳል ይኸም ሁለተኛው ክስ የቀረበው የፍርድ ቤትን ፈቃድ ተመስርቶ ቢሆንም እንኳ የቀደመው ክስ የኋለኛውን ክስ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር እንደማያቋርጠው ያስረዳናል፡፡ ሕጉ ይህን ከአልፈቀደ ደግሞ ከሣሽ ክርክሩን ለመዳኘት ከስልጣኑ ውጭ ለሆነ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ በሁለተኛ ደረጃ የመሰረተውን ክስ የይርጋ አቆጣጠር ያቋርጠዋል ማለቱ አሳማኝነት የሌለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ይሆናል። የያዝነው ጉዳይ ከዚህ ሕግ አግባብ ሲታይ ደግሞ አንድ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ክስ የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ቀርቦ መገኘቱ ብቻውን የይርጋውን ዘመን አቆጣጠር የሚያቋርጠው አይሆንም። ክሱ የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠር ያቋርጠዋል ይሰኝ ዘንድ ለፍርድ ቤት ወይም ለቦርድ መቅረቡ ብቻ ሳይሆን የቀረበው የሥራ ክርክሩን ጉዳይ ለመዳኘት በሕጉ ስልጣን ላለው አካል እንዲሆን ያስፈልጋል።

ሌላው የይርጋን ዘመን አቆጣጠር የሚያቆርጠው የአዋጅ ቁ. 42/85ን እንዲያስፈፅም ስልጣን ለተሰጠው አካል አቤቱታ አቅርቦ መገኘት መሆኑ በአንቀጽ 164/2/ ላይ ተመልክቷል። ይህ አካል የመጨረሻ ውሣኔ በጽሁፍ እስከሚሰጥ ድረስ ይርጋው ሊቋረጥ እንደሚገባም በድንጋጌው ተመልክቷል። ይሁን እንጂ አዋጁን እንዲያስፈጽም ስልጣን የተሰጠው አካል ማን ነው? በዚህ አካል የሚተላለፈው ውሣኔስ በሕጉ አግባብ ውሣኔ ሊሰኝ ይገባዋል? ለሚለው ነጥብ ምላሽ ለማግኘት ድንጋጌውን መተርጎም ይገባናል።

በቅድሚያ ሁለተኛውን ጥያቄ እናያለን። በመሰረቱ ከሕግ አግባብ "ውሣኔ" ሊባል የሚገባው ምን ዓይነት ውሣኔ እንደሆነ ከፍ ሲል ተገልጿል። "ውሣኔ" ሊሰጡ የሚችሉት የሥራ ክርክርን ለመዳኘት ስልጣን ያላቸው አካላት ብቻ መሆናቸውንም በችሎት ከተሰጠው ትርጓሜ መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም አዋጁን ለማስፈፀም ስልጣን በአለው አካል የሚሰጥ ውሣኔ የአስተዳደር ውሣኔ ሊባል ከሚችል በቀር በሕጉ አግባብ በዳኝነቱ አካል እንደተሰጠ ውሣኔ የሚቆጠር አይደለም።

ወደ መጀመሪያው ጥያቄ ስንመለስ ጉዳዩን የሠራተኛና የማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም የክልሎች የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ቢሮ በሕጉ ከተሰጠው ስልጣን አኳያ መመርመሩ ተገቢነት ይኖረዋል። ይህ ሚኒስቴር በርካታ ተግባሮችን እንዲያከናውን በአዋጅ ቁ. 42/85 ስልጣን የተሰጠው ሲሆን ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል። ከአዋጁ አንቀጽ 119 ብንጀምር ይህ ሚኒስቴር በዚህ ድንጋጌ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የማሕበራትን ምዝገባ ሊከለክል ይችላል፤ በአንቀጽ 120 እና 122 መሠረት የማሕበራትን የመመዝገቢያ የምስክር ወረቀት በመሰረዝ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ውሣኔ ሊያሳልፍ ይችላል፤ በአንቀጽ 20 መሰረት ሠራተኞን ከሥራ ለማገድ የተሰጠ ምክንያት በቂ በመሆን አለመሆኑ ጉዳይ ላይ ውሣኔ ይሰጣል፤ ከዚህ የሚኒስቴሩ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ እንደሚችል ደግሞ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 20/3/ ላይ ተመልክቷል፤ በተጨማሪም ሚኒስቴሩ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 137/2/ መሠረት ፍርድ ቤት ዘንድ ተገቢ ብዛት ያላቸው የሥራ ክርክር ችሎቶች ይቋቋሙ ዘንድ ለተገቢው አካል ጥያቄ ለማቅረብ ይችላል፤ በአሰሪውና በሠራተኛው መካከል የወል የሥራ ክርክር ሲነሳ በንቀጽ 141 መሠረት ጉዳዩን በማስማማት ለመጨረስ አስማሚ ይመድባል፤ እንደዚሁም በአንቀጽ 178 መሠረት ስለ ሥራ ሁኔታ ቁጥጥር የሚያደርጉ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎችን ይመድባል፡፡ እነዚህ ከሞላ ጎደል የተጠቀሱት በሕጉ የተፈቀዱት የሚኒስቴሩ ተግባራት ሚኒስቴሩ በአሰሪና ሠራተኛው ግንኙነት ላይ ከፍተኛ የሆነ የአፈፃፀም ኃላፊነት እንዳለበት ያረጋግጡልናል፡፡ ሌላ ከሚኒስቴሩ የተሰተካከለ የአስፈፃሚነት ኃላፊነት የተሰጠው አካል አለመኖሩንም ከአዋጁ መረዳት ይቻላል፡፡ ይልቁንም ሚኒስቴሩ በአዋጁ አንቀጽ 170/1/ ላይ ሕጉን ለማስፈፀም ይችል ዘንድ በበርካታ ጉዳዮች ላይ መመሪያ የማውጣት ስልጣን እንደተሰጠው ተመልክቷል፡፡ ይህም ሚኒስቴሩ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግን በሥራ ላይ ለማዋልና ለማስፈጸም በአዋጁ ስልጣን የተሰጠው ብቸኛ አካል መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ ለዚህ አካል /በስሩ እንዲመድባቸው ስልጣን ለተሰጠው ተቋማት ጭምር/ በአዋጁ እንዲያከናውናቸው ስልጣን በአገኘበት ተግባራት ረገድ አቤቱታ አቅርቦ መገኘትም በአንቀጽ 164/2/ መሠረት የይርጋውን ዘመን አቆጣጠር የሚያቋርጠው ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጨረሻው ለይርጋ ጊዜ መቋረጥ ምክንያት የሚሆነው በአንቀጽ 164/3/ ላይ እንደተመለከተው በይርጋው ጊዜ ማለፍ ተጠቃሚ የሆነው ወገን ያልሆነውን ወገን መብት በቃል ሳይሆን በጽሁፍ ሲያውቅለት አሊያም መብቱን በከፊል ፈጽሞለት ሲገኝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ምክንያት የይርጋውን አቆጣጠር ከሦስት ጊዜ በላይ ሊያቋርጠው እንደማይችል በዚሁ ድንጋጌ ላይ የተመለከተ ነው፡፡

በእርግጥ የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164 ሦስት አይነት የይርጋ ማቋረጫ ምክንያቶች ያስቀመጠ ቢሆንም የይርጋው መቋረጥ በይርጋ ዘመኑ አቆጣጠር ላይ ያለውን ውጤት ግን አላመለከተም፡፡ በመሆኑም የይርጋ ጊዜ መቋረጥ ምን ውጤት እንደሚያስከትል ለማወቅ አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1852/1/ን ከጉዳዩ ጋር አገናዝቦ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ይህ አንቀጽ አንድ የይርጋ ዘመን ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ "... እንደገና አዲስ የይርጋ ዘመን ..." ሊቆጠር እንደሚገባ ደንግጓል፡፡ ይህም ይርጋው ከመቋረጡ በፊት ተቆጥረው የነበሩት ቀናት እንዳለ ቀሪ እንደሚሆኑና የይርጋው ጊዜ እንደገና እንደ አዲስ ተብሎ ሊቆጠር እንደሚገባ ያስገነዝበናል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164 በተመለከቱት ሁኔታዎች ሳቢያ አንድ የይርጋ ጊዜ መቋረጡ ቢረጋገጥ ቀጣዩ የይርጋ ዘመን ይሸን ከፍ ሲል የተጠቀሰውን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1852/1/ የተመለከተውን አቆጣጠር ይከተል ዘንድ ያስፈልጋል፡፡

በመሰረቱ አንድ የሥራ ክርክር ክስ የቀረበበት ወገን ክሱ የይርጋ ጊዜው ያለፈበት ነው ሲል ቢቃወም በእርግጥ ክሱ ጊዜው ያለፈበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ የጉዳዩ ጭብጥ ሆኖ እንደሚያገ ይታመናል፡፡ ለዚህ ጭብጥ መመስረት ምክንያት የሆነው ክርክር የቀረበው በተከሣሹ በመሆኑም የይርጋውን ጊዜ ማለፍ ያስረዳ ዘንድ ይገባዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክሱን ያቀረበው ወገን የይርጋው ጊዜ ተቋርጧል የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ክርክር የሚያነሳ ቢሆን ይህን ሙግቱን በቅድሚያ ያስረዳ ዘንድ ይጠበቅበታል፡፡

በተጨማሪም የሥራ ክርክር ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤት ከሣሹ አስቀድሞ በአዋጅ ቁ. 42/85 መሠረት ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን ለተሰጠው ፍርድ ቤት ወይም የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ማቅረቡን ከአረጋገጠ በአዋጁ አንቀጽ 164/1/ መሠረት የይርጋውን ዘመን መቋረጥ ሊቀበለው ይገባል፡፡ ከተጠቀሰው የሕጉ መስፈርት ውጭ የሆኑ ምክንያቶችን ለውሣኔው መሠረት ሊያደርግ አይችልም፡፡ ለምሳሌ ያህል ክሱ ሊቀርብ የሚገባው ለሥራ ክርክር ችሎቱ ነበር በሚልና በመሳሰለ ምክንያት የይርጋውን አቆጣጠር መቋረጥ አልቀበልም ሊል አይችልም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን ለማስፈፀም ስልጣን የተሰጠው ሚኒስቴሩ ብቻ መሆኑ ከላይ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ክርክሩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ከሣሹ ለዚህ ሚኒስቴር /በስሩ ለሚመድባቸው ተቋማት ጨምሮ/በስልጣኑ ክልል አቤቱታ አቅርቦ እንደነበር ከአረጋገጠ የይርጋውን ዘመን በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164/2/ መሠረት ሊያቋርጠው ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ ለሆነ አካል አቤቱታ መቅረቡ መረጋገጡ ግን የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠር የሚያቋርጠው አይሆንም፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ከሣሽ ሠራተኛ ለአሰሪው መ/ቤት አቤቱታ አቅርቤ ውጤቱን ስጠባበቅ ነበር ሲል መከራከሩንና ይህንንም ማረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ለይርጋው ዘመን አቆጣጠር ማቋረጫ አድርጎ ሊወስድለት አይችልም፡፡

የይርጋ መብትን ስለመተው

እንደሚታወቀው በአዋጅ ቁ. 42/85 ውስጥ የተመለከተው የይርጋ ሕግ በፍሬ ነገር ሕግ /Substantive law/ ላይ እንጂ በሥነ ሥርዓት ሕግ /Procedural law/ ላይ የተቀመጠ የይርጋ ደንብ አይደለም፡፡ በፍሬ ነገር ሕግ /Substantive law/ ላይ የሚገኝ የይርጋ ደንብ ደግሞ በተከሣሹ ወገን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ሊቀርብ የሚገባው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሣሹ በመቃወሚያነት አንስቶ ከአልተከራከረበት በቀር ፍርድ ቤት በእራሱ አነሳሽነት ጉዳዩ የይርጋ ጊዜ ያለፈበት መሆን አለመሆኑን አጣርቶ እና ሕጉን ጠቅሶ ፍርድ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ስለሆነም አንድ የሥራ ክርክር ክስ የተመሰረተበት ተከሣሽ የይርጋውን ክርክር በመቀወሚያነት ካላነሳው በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 165 አግባብ በዚህ ረገድ የመከራከር መብቱን እንደተወው ይቆጠራል፡፡ በውጤቱም በሕግ የተወሰነለትን ጊዜ አሳልፎ የቀረበው ክስ በይርጋ ምክንያት ውድቅ ሳይደረግ ወደ ጉዳዩ ፍሬ ነገር ተገብቶ የመዳኘት እድልን ያገኛል፡፡

ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት

አንድ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ክስ የይርጋ ጊዜውን አሳልፎ ቢቀርብ እና ይህ የሆነው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ በውሣኔ ሰጭው አካል ቢረጋገጥ ምንም እንኳን ክሱ ጊዜው ያለፈበት ቢሆንም ሊታይ እንደሚገባ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 166 ላይ ተደንግጓል፡፡ የተጠቀሰው ምክንያት በተወገደ በአስር ቀን ውስጥ ያልቀረበ ክስ ግን ተቀባይነት እንደማያገኝ በዚሁ ድንጋጌ ላይ ተመልክቷል፡፡

በግልጽ እንደሚታየው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ አልተተረጎመም፡፡ ስለዚህም ጉዳዩን ይህን ሐሳብ ከሚተረጉመው የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1792 ጋር አገናዝቦ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1792 እንደተደነገገው

> ከዓቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ኃይል ደርሷል የሚባለው አንድ ባለዕዳ ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍጹም መሰናክል በሆነ ዓይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመው ጊዜ ነው፡፡

ጉዳዩ ከዚህ ትርጉም አኳያ ሲታይ አንድን የሥራ ክርክር ክስ ጊዜው ሊያልፍበት የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ለመፈረጅ ክሱ ቀድሞ ሊታሰብ በማይችል እና ከሣሹም ፍጽም የሆነ መሰናክል የገጠመው በመሆኑ ምክንያት ብቻ በጊዜው ሳይመሰረት መቅረቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ትርጓሜ እነዚህ ምክንያቶች ምን አይነት ምክንያቶችን ይመለከታል? የሚለውን ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀሬ ይሆናል፡፡ የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 166 ከአቅም በላይ ሊሰኙ የሚችሉ ምክንያቶችን ያላመላከተን በመሆኑም ለዚህ ጉዳይ እንደገና ወደ ፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መመለስ ያስፈልገናል፡፡ የፍትሐብሔር ሕጉ በቁጥር 1793 ላይ ከአቅም በላይ ሊሰኙ የሚችሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር አስቀምጧል፡፡ እነርሱም፡-

ሀ/ ባለዕዳው አላፊ የማይሆንበት ያልታሰቡና በሌላ ሰው ላይ የሚመጡ ድንገት ደራሽ ነገሮች፣

ለ/ ውሉ እንዳይፈጸም በመንግሥት የሚደረግ ክልከላ፣

ሐ/ እንደ መሬት መናወጽ፣ መብረቅ፣ ማዕበል ይህን የመሳሰለ ፍጥረታዊ መቅሠፍት፣

መ/ የጠላት የውጭ አገር ጦርነትና የአገር ውስጥ ጦርነት፣

ሠ/ የባለዕዳው መሞት ወይም ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ሕመም /መሆናቸው ተመልክቷል/፡፡

እንግዲህ ከሣሽ ክሱን በጊዜው ያልመሰረተበት ምክንያት ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ በተመከቱት ምክንያቶች ስር የሚሸፈን ከሆነ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ገጥሞታል የሚሰኝ ይሆናል፡፡ ዳኝነት ሰጭው አካልም ይህንን ከአረጋገጠ ጊዜው ያለፈበትን ክስ ተቀብሎ ወደ ፍሬ ጉዳዩ በመግባት ፍርድ ይሰጥበት ዘንድ ይገደዳል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 166 " ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት "ማለት ምን ማለት እንደሆነ አልተረጎመም፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ምን አይነት ሊሆኑ እንደሚገባም አላመለከተም፡፡ ነገር ግን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በይርጋ የታገደን ክስ ለመቀበል" በቂ ምክንያት" ተደርገው የሚወሰዱ ምክንያቶችን አመላክቷል። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ የሠራተኛ መታመም፣

ለ/ የሠራተኛው በትዕዛዝ ከመደበኛ የመኖሪያ ሥፍራ ውጭ መላወር

ሐ/ የሠራተኛው ከብሔራዊ ጥሪ ላይ መገኘት

እነዚህ በድንጋጌው የተመለከቱት ውስን ምክንያቶች በሠራተኛው የቀረበው ክስ በይርጋ የታገደ መሆኑ ቢታይም ተቀባይነት ያገኘለት ዘንድ የሚፈቅዱ ናቸው። እንዲሁም እነዚህ እክሎች የገጠሙት ሠራተኛ ጉዳይ በዳኝነት አካል ሳይታይለት እንዳይቀር ልዩ የሆነ ጥበቃ የማድረግን ነገር አላማ ማድረጋቸውን ከድንጋጌው መረዳት የሚቻል ነው። በእርግጥ እነዚህ ምክንያቶች በሠራተኛው ክስ ተጠቅሰው መገኘታቸው ብቻውን ጊዜው ያለፈበትን ጉዳይ ለመቀበል የሚበቃ አይሆንም። ይህን ማድረግም ከድንጋጌው አላማ ጋር የተጣጣመ መደምደሚያ ላይ እንድንደርስ አይረዳንም። ስለሆነም ሠራተኛው ጊዜው ያልፈበትን ክስ ቢያቀርብ እና ጉዳዩ ከዚህ ድንጋጌ አግባብ እንዲታይለት ቢጠይቅ መታመሙን ወይም በትዕዛዝ ከመኖሪያ ሥፍራው መላወሩን ወይም በብሔራዊ ጥሪ ላይ የነበረ መሆኑን የሚያሳይለትን ማስረጃ በማቅረብ በቅድሚያ ክርክሩን ያስረዳ ዘንድ ያስፈልጋል። ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የምክንያቱን ተገቢነት በግራ ቀኙ ከቀረበለትም ሆነ በእራሱ አነሳሽነት ከአስመጣው ማስረጃ አኳያ ሊመረምረው ይገባል ፍርድ ቤቱ ይህን ሲያደርግም እነዚህ ምክንያቶች ሠራተኛው ክሱን እንዳይመሰርት መስናክል የሆኑበትን መጠን ጭምር ከግምት እንዲያስገባ ያስፈልጋል። በውጤቱም ፍርድ ቤቱ እነዚህ ምክንያቶች ከሣሹ ክሱን ሊመሰርት በማይችልበት ደረጃ ላይ አድርሰውት ነበር ሊል የሚያምንበት ሊሆን ይገባዋል። ይህ ካልሆነ ግን ፍርድ ቤቱ በይርጋ የታገደውን ክስ ከወዲሁ ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሁን በዚህ መዝገብ ወደተያዘው ክርክር እንመለሳለን፡፡ በዚህ ውሣኔ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው ተጠሪዎች ለቦርድ አቅርበውት የነበረው ክስ ለሌሎች ሠራተኞች የተደረገው የሁለት እርከን ጭማሪ ለእኛም ሊሰጠን ይገባል የሚል ሲሆን አመልካችም ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል በማለት ተቃውሞውን አቅርቦ የተከራከረበት ነው፡፡

በመሠረቱ ይህ የተጠሪዎቹ ጥያቄ የክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ እንዲሁም የክፍያ ጥያቄው በመካከላቸው ያለው የሥራ ውል ፀንቶ በአለበት ጊዜ የተነሳ እንጂ የሥራ ውል መቋረጥን ተከትሎ የቀረበ አይደለም፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የይርጋው አቆጣጠር ጉዳይ በተለይ ከተደነገገው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/3/ አግባብ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

በዚህ የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/3/ መሠረት የተጠቀሰው የክፍያ ጥያቄ ሊጠየቅ ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ድረስ ካልተጠየቀ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው ነው፡፡ ተጠሪዎች ይህ የሁለት እርከን ጭማሪ ለሌሎች ሠራተኞች ተደርጓል የሚሉት መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. እንደነበር ከስር ውሣኔ ላይ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ክሳቸውን ለቦርድ ያቀረቡት ደግሞ ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም. መሆኑ በስር ውሣኔ የተመለከተ ነው፡፡ በዚህ ችሎት እምነት አመልካች ለሌሎቹ ሠራተኞች ጭማሪውን አድርጓል መባሉ በስር ክርክር በተጠሪዎች ጭምር የታመነበት መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. ክፍያው በተጠሪዎች ሊጠየቅ የሚገባበት ጊዜ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው ነው፡፡ የተጠሪዎቹ ክስ የቀረበው ከዚህ ጊዜ በኋላ ከአንድ ዓመት በላይ ቆይቶ በመሆኑም ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት በስድስት ወሩ ይርጋ ሊታገድ የሚገባው መሆኑ የማያከራክር ነው፡፡

በእርግጥ ተጠሪዎች የእርከን ጭማሪው ለሌሎቹ ሠራተኞች የተደረገው መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም. አይደለም፡፡ ይኸ ቀን ጭማሪ መደረጉ ለሠራተኞች ይፋ የተደረገበት ቀን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የካቲት 8 ቀን 1993 ዓ.ም. ለሌሎቹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሠራተኞች ተጠቃሚ መሆናቸው ሲፃፍላቸው ለተጠሪዎች ግን ይኸ ባለመደረጉ የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም. ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቤቱታ በማቅረባችን የይርጋው አቆጣጠር ተቋርጧል በማለት በስር ፍርድ ቤቶች ያላነሱትን ክርክር ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ በመሰረቱ ይኸ የተጠሪዎቹ ክርክር በዚህ ችሎት የቀረበ አዲስ የክርክር ነጥብ በመሆኑ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባ አልነበረም፡፡ ይኸ ቢታለፍ ደግሞ አሁንም ተጠሪዎቹ ሌሎቹ ሠራተኞች የእርከን ጭማሪው ተጠቃሚ መሆናቸው ሲፃፍላቸው ለእኛ ይህ ሳይደረግ ቀርቷል ከሚሉበት ከየካቲት 8 ቀን 1993 ዓ.ም. ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ማለትም እስከ ነሐሴ 8 ቀን 1993 ዓ.ም. ክሱን ሊመሰርቱ ሲገባ ይህን አድርገው ባለመገኘታቸው ይህም ክርክራቸው የይርጋውን ጊዜ ማለፍ የሚያረጋግጥባቸው ነው፡፡ እንዲሁም ይህ ችሎት ለአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 164/2/ ከሰጠው ትርጓሜ አግባብ የአመልካች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቤቱታ ማቅረብ አዋጁን እንዲያስፈጽም ስልጣን ለተሰጠው አካል አቤቱታ እንደማቅረብ ስለማይቆጠር ይኸ ተጠሪዎቹ ፈጽመነዋል ያሉት ድርጊትም የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠር የሚያቋርጠው ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1ኛ/ ተጠሪዎች በአመልካቹ ላይ የመሰረቱት ክስ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 162/3/ መሰረት በይርጋ ሊታገድ ይገባል፡፡

2ኛ/ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደቅደም ተከተላቸው በመ.ቁ. 171/02/93 እና በመ.ቁ.28793 የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ አድርገው የአንድ እርከን ጭማሪ ለተጠሪዎች እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን
ተጠሪ፡- ወ/ሪት ትዕግስት ወርቁ

የሥራ ውል ስለሚቆይበት ጊዜ - ላልተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የስራ ውል እና ለተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የስራ ውል - ስለ ስራ ውል መቋረጥ እና ውዝፍ ዕዳ ክፍያን በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9፣ አንቀጽ 10 እና 24

ተጠሪ ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ወደ ስራ እንድትመለስ እና የአንድ አመት ደመወዝ እና የዓመት ፈቃድ እንዲሰጣት በማለት ስለወሰኑ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ሙ ቲ ኔ</u> ፡-የአመት ፈቃድን በተመለከተ ሳይጨምር በቀሪቹ ላይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔች ተሽረዋል፡፡

1ኛ. በአንድ አሠሪ እና ሠራተኛ መካከል የተደረገ የስራ ውል ያልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል ተደርጎ ሊቆጠር ይገባል፡፡ እንዲሁም ማናቸውም የስራ ውል ጊዜ እንዲልተወሰነለት የስራ ውል ሊወሰድ ይገባል፡፡

2ኛ. ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ አንድ የሥራ ውል ውሉ መስፈርቶችን በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 10 መሠረት ያሟላ ከሆነ ሊቆይ የሚችለው ጊዜው እስከሚያልቅ ወይም ስራው እስከሚያልቅ ድረስ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን - ግርማ ማርቆስ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ትዕግስት ወርቁ - ቀረበች

ፍ ር ድ

ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ እ.ኤ.አ. ከመጋቢት 24/1997 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 22/1997 ዓ.ም ድረስ በጠቅላላ አገልግሎት ውስጥ በሚገኝ የስራ መደብ በተላላኪነት ሳገለግል ቆይቼ አለአግባብ የስራ ውሌን ስላቋረጠው ጥቅሜን ከፍሎ ወደ ስራ ይመልሰኝ፤ አሊያም የስራ ስንብት ከፍሎ ያሰናብተኝ ስትል በአሁን አመልካች ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍ/ቤት የመሰረተችው ክስ ነው፡፡ ይህም ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በጉዳዩ አከራክሮ ተጠሪ ወደ ስራ እንድትመለስ፤ የአንድ ዓመት ደመወዝ እና የዓመት ፈቃድ እንዲሰጣት ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ፍርዱ ጉድለት ያለበትም በማለት የይግባኙን መዝገብ ዘግቶታል፡፡

ይህም ችሎት ግራ ቀኙ በጉዳዩ ያቀረቡለትን ክርክር መርምሯል፡፡

በአመልካችና በመልስ ሰጭ መካከል የተደረገው የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ የተደረገ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ በጉዳዩ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነጥብ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ጭብጡን አሳማኝ በሆነ መልኩ ለመፍታት ይቻል ዘንድም በቅድሚያ የሥራ ውል ስለሚቆይበት ጊዜ የሚደነግጉትን የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 9 እና 10ን በመመስረት ነጥቡን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ አንቀጽ 9ን እንመልከት፡፡ ይህ አንቀጽ ... በአንቀጽ 10 ከተመለከቱት በቀር ማንኛውም የሥራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል በማለት ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ የስራ ውል ቆይታን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሚመለከት አንድ መሰረት አስቀምጧል፡፡ ይኸውም በአንድ አሰሪ እና ሰራተኛ መካከል የተደረገ የስራ ውል ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ተደርጎ ሊቆጠር እንደሚገባ አመልክቷል፡፡ እንዲሁም ማናቸውም የስራ ውል ጊዜ እንደአልተወሰነለት የስራ ውል ሊወሰድ ይገባው ዘንድ ሕጉ ግምት የወሰደበት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንደ አንቀጽ 9 አገላለጽ አንድ የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚያስቆጥረውን የሕግ ግምት ቀሪ አድርጎ ውሉን ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ ነው የሚል ለመፈረጅ የስራ ውሉ ከአዋጅ አንቀጽ 10 አኳያ የተደረገ መሆኑ እንዲረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ወደ ተከታዩ የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10 ስንመለስ ይህ አንቀጽ ለተወሰነ ስራ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ የስራ ውል ሊደረግባቸው የሚችልባቸውን ሁኔታዎች በመዘርዘር አስቀምጧል፡፡ ይህም በድንጋጌው የተወለከቱት መስፈርቶች የመማላታቸው ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድን የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዲቆይ በማድረግ፤ አሊያም የተወሰነ ስራ ለመስራትም ሆነ ለማሰራት ብቻ ሲባል ማድረግ በሕግ የተፈቀደ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንደዚሁም ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ የስራ ውል የሚደረገው በአንቀጹ በተመለከቱት ሁኔታዎች ብቻ መሆኑን በመጠቆም አንድን የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ በሚል ማድረግ እንደ ልዩ ሁኔታ ሊቆጠር የሚገባው ተግባር መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህ የሕጉ መንፈስም በዚህ ድንጋጌ /በአንቀጽ 10/ ሊሸፈኑ የማይችሉ የስራ ውል አይነቶች ሁሉ በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረጉ ይቆጠራሉ በሚል በተደነገገው የአዋጁ አንቀጽ 9 ይደግፋል፡፡

እንግዲህ አንድ የሰራ ውል የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ በመሆን አለመሆኑ ጉዳይ ላይ ሙግት ሲነሳ በቅድሚያ በአሰሪው እና በሰራተኛው መካከል በጽሑፍም ሆነ በቃል የተደረገውን የስራ ውል ይዘት ሰፊ ዝርዝር ከያዘው የአዋጁ አንቀጽ 10 ጋር እያገናዘቡ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም አንድ አሳማኝነት ያለው መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ሕጉ እንደዚህ ያሉ የስራ ውሎች እንዲደረጉ የፈቀደባቸውን የስራ ሁኔታዎች መለየት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ እንዲሆም የስራ ውሉ ከተጠቀሰው ድንጋጌ አግባብ የተደረገ መሆኑን የማስረዳት ሸክሙ የአሰሪው ነው? ወይስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሰራተኛው? የሚለው ጥያቄ ምላሽ መስጠትን ይጠይቃል። በአጠቃላይ ይህን የአዋጁን አንቀጽ 10 የመተረጎምን ጉዳይ የግድ ያደርገዋል።

በግልጽ እንደሚነበበው የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10፡-

1. የተወሰነ ሥራ ለመሥራት /the performance of specified piece work/
2. ለጊዜው በሥራው ቀሪ የሆነን ሠራተኛ ለመተካት /the replacement a worker who is temporally absent/:
3. የሥራ ብዛትን ለማቃለል/ in the event of abnormal pressure of work/:
4. በህይወት ወይም በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሚያስችል አጣዳፊ ስራን ለመስራት እንዲሁም በሥራ ወይም በንብረት ላይ የደረሰን ጉዳትና ብልሽት ለማደስ /urgent work, to prevent damage or disaster to life or property, to repair defects of breakdowns in works, materials, buildings or plants of the works of the undertaking/:
5. እየተቃረጠ የሚሰራን ቋሚ የአሠሪ ሥራ ለመሥራት /an irregular but permanent part of the employer/:
6. ወቅት ጠብቆ የሚሠራን ቋሚ የአሠሪ ሥራ /seasonal but permanent part of the works of the employer/:
7. ቋሚ ያልሆነ እና አንዳንዴ በሚያስፈልግ ጊዜ በቻ የሚሠራን ሥራ ለመሥራት /an occasional and not part of the permanent activity of the employer/ የተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ውል ማድረግ እንዲቻል ደንግጓል።

በዚህ ችሎት እምነት ይህ ድንጋጌ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል የሚደረግባቸውን ሶስት አይነት የሥራ ሁኔታዎች ያመላክታል። የእነዚህን የሰራ ሁኔታዎች አይነት ለመለየት ድንጋጌው ቋሚ እና ቋሚ ያልሆኑ የአሠሪ ስራዎች ሲል ለይቶ ከአስቀመጣቸው ንዑስ አንቀፆች መነሳቱ ነገሩን ግልፅ ያደርገዋል።

ቋሚ በሆነ የአሰሪ ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ለማድረግ የሚቻል መሆኑን በግልጽ የሚያሳዩን የድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
/5/ እና /6/ ናቸው፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ድንጋጌዎች የስራ ውሉ የሚደረግባቸው ቋሚ የአሰሪው ስራዎች እየተቃረጡ ወይም ወቅት ጠብቀው የሚሰሩ ሊሆኑ እንደሚገባቸው በማመልከት ተጨማሪ መስፈርቶችን አስቀምጠዋል፡፡ ይህም የድንጋጌዎቹ ይዘት ቀጣይነት በሌላቸው /በተከታታይነት በማይሰሩ/ የአሰሪው ቋሚ ሰራዎች ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ሊደረግ የሚችል መሆኑን እና እነዚህም እንደ አንድ የሥራ ሁኔታ ልንወስዳቸው እንደሚገባ ያስገነዝቡናል፡፡

ይሁን እንጂ የቀጠቀሰው የድንጋጌዎቹ መንፈስ ቋሚ በሆነና ያለማቋረጥ በተከታታይ በሚሰራ የአሰሪው ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ለማድረግ አይቻልም? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ እንደሚቻል የታመናል፡፡ የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10 ከአስቀመጣቸው ከፍ ሲል ከተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች ውስጥ ቀጣይነት በአለው የአሰሪው ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ውል ማድረግ እንደሚቻል በግልጽ የሚፈቀድ ድንጋጌ የለም፡፡ በሌላ በኩል ግን አንቀጹ ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /4/ ባሉት ንዑስ አንቀጾች የስራው አይነት ቋሚ የአሰሪው ስራ የመሆን አለመሆኑን ጉዳይ ሳያነሳ ሌሎች የተጠቀሰውን አይነት ውል ሊደረግ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች አስቀምጦ እናገኘዋልን፡፡ ስለሆነም እነዚህ ንዑስ አንቀጾች ትርጓሜ አግኝተው በአሰሪው ቋሚ ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል እንዲደረግ የሚፈቅዱ አይደለም እስከአልተባለ ድረስ ሕጉ በተጠቀሰው አይነት ሥራ ላይ የተጠቀሰውን አይነት ውል ማድረግ አይፈቅድም የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አይቻልም፡፡ ወደ ትርጓሜያቸው ስንመለስ ደግሞ ቢያንስ የተወሰነ ስራ ለመስራት ወይም ለማሰራት፤ ቀሪ የሆነን ሰራተኛ ለመተካት እና የስራ ብዛትን ለማቃለል ሲባል የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ማድረግ እንደሚቻል የሚጠቅሱት ከንዑስ ቁ./1/ እስከ /3/ ያሉት ድንጋጌዎች የአሰሪውን ቋሚ ስራ በሚያገል መልኩ የተደነገጉ ናቸው ለማለት የሚያበቁ አይደሉም፡፡ ይልቁንም ከፍ ሲል በተመለከቱት ምክንያቶች መነሻ የሚደረግ የስራ ውል በቀጣይነት ከሚሰሩ እንጂ በቀጣይነት ከማይሰሩት ስራዎች ጋር ያለው ተያያዥነት እምብዛም የሚታይ አይደለም፡፡ ስለሆነም የቅጥሩ ምክንያት በእነዚህ ንዑስ አንቀጾች የተመለከቱትን ውስን ምክንያትቶች እስከያዘ ድረስ ውሉ የተደረገበት ስራ ቀጣይነት ያለው ነውና የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ሊደረግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
አይችልም የሚል በሕግ የተደገፈ ማጠቃለያ ላይ ሊደረስ አይቻልም፡፡ በመሆኑም በተጠቀሱት ድጋጌዎች አግባብ በአሰሪው ቋሚ ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ማድረግ የሚቻል ሲሆን ይህም እንደ ሁለተኛው አይነት የስራ ሁኔታ ሊቆጠር ይገባዋል፡፡

ቋሚ ባልሆነ የአሰሪው ስራ ላይ የተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ውል ሊደረግ እንደሚችል በግልጽ የሚያሳየን ደግሞ ንዑስ አንቀጽ/7/ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ውሉ የሚደረግበት ስራ ቋሚ የአሰሪ ስራ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት የሌለው ጭምር መሆኑን ከድንጋጌው በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደ ንዑስ /7/ ግልጽ ባይሆንም በንዑስ /4/ ላይ የተመለከተው ይኸው የስራ ውል የሚደረግበት ሌላ ሁኔታም ከዚሁ ቋሚ ከአልሆነው እና ቀጣይነት ከሌለው ስራ ሊመደብ የሚገባው መሆኑን ከይዘቱ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ቋሚ ያልሆነ እና በቀጣይነት የማይከናወን የአሰሪው ስራም ውሉ እንዲደረግ ሕግ የፈቀደበት ሶስተኛው አይነት የስራ ሁኔታ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባዋል፡፡

እንግዲህ አንድ የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የስራ ውል ነው ለመሰኘት ጊዜ የተወሰነበት የመሆኑ ጉዳይ ብቻ የሚበቃ አይደለም፡፡ ውሉ በጊዜ ከመገደቡ ባሻገር በአንቀጽ 10 በተመለከቱት እና ከላይ በዝርዝር ሊታዩ ከተሞከሩት የስራ ሁኔታዎች አግባብ የተደረገ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

እንዲሁም አንድ የስራ ውል የተወሰነ ስራ ለመስራት ወይም ለማሰራት ሲባል የተደረገ ነው ለመሰኘት ለተወሰነ ስራ መደረጉን የሚያሳይ ጥቅል ሐሳብ ማስቀመጡ ብቻ የሚበቃ አይሆንም፡፡ ለተወሰነ ስራ መደረጉን ከማመልከት በተጨማሪ በአንቀጽ 10 ስር በተዘረዘሩት እና ከላይ ከተጠቀሱት የስራ ሁኔታዎች አግባብ የተደረገ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ በሚል የተደረገ አንድ የስራ ውል በአንቀጽ 10 የተመለከቱትን መስፈርቶች በአሟላ ወይም በአላሟላ ጊዜ ሁለት የተለያዩ ሕጋዊ ውጤቶችን ያስከትላል፡፡ ይኸውም አንደኛ ውሉ መስፈርቶቹን አሟልቶ ከተገኘና ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ከሆነ ጊዜው እስከሚያልቅ ብቻ የሚቆይ ሲሆን ለተወሰነ ስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የተደረገ ከሆነ ደግሞ ስራው እስከሚያልቅ ድረስ ብቻ የሚቀጥል ይሆናል። ከዚያም ውሉ በአዋጁ አንቀጽ 24 መሰረት በሕግ ይቋረጣል። ሁለተኛ ውሉ መስፈርቶቹን አሟልቶ ካልተገኘ በአዋጁ አንቀጽ 9 መሰረት በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል።

አንድ አከራካሪ የስራ ውል በአንቀጽ 10 የሚሸፈን መሆን አለመሆኑ የሚለየው ተከራከሪዎቹ ከሚያቀርቡት ማስረጃ አኳያ ተገናዝቦ ሲታይ ነው። ይህን ጉዳይ ለማስረዳት የሚቀርቡት ማስረጃ ምን አይነት ሊሆን እንደሚገባ በሕጉ ተለይቶ የተወሰነ አይደለም። ስለሆነም ሙግቱን ለማስረዳት የፅሁፍም ሆነ የቃል ማስረጃ ማቅረብ እንደሚቻል የሚተመን ነው። ይልቁንም የሚያከራክረው ቅድሚያ የማስረዳት ሸክም ያለበት ማን ነው? አሰሪው ነው? ወይስ ሰራተኛው? የሚለው ጉዳይ ሲሆን ይህም አወዛጋቢ ነጥብ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር ተገናዝቦ እንደሚከተለው ምላሽ ተሰጥቶበታል፦

1ኛ- ከፍ ሲል እንደተመለከተው አንድ ከአሰሪ ጋር የስራ ውል ያለው ሰራተኛ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ ሊቆጠር እንደሚገባ የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 9 ግምት ወስዶለታል። በዚህ የሕግ ግምት የስራ ውሌ ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ነው ሲል የሚከራከረው ሰራተኛ ተጠቃሚ በመሆኑ ይህን ክርክሩን የሚደግፍለት ማስረጃ በቅድሚያ ያቀርብ ዘንድ አይጠበቅበትም። ይልቁንም በሕግ የተወሰደለት ግምት ክርክሩን ከማስረዳቱ ግዴታው ነፃ እንዲሆን ያደርገዋል። በውጤቱም በቅድሚያ የማስረዳቱ ግዴታ የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ ነውና በአንቀጽ 10 የሚሸፈን ነው ሲል በሚከራከረው በአሰሪው ላይ ይወድቃል።

2ኛ- እንደሚታወቀው አንድ የስራ ውል በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10 የሚሸፈን ነው? ወይም አይደለም? የሚለው አከራካሪ ጭብጥ በአንድ ጉዳይ ሊመሰረት የሚችለው አንዱ ወገን ተከራካሪ የስራ ውሉ ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ነው ሲል ሌላው ደግሞ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ ነው በማለት በሚሟገቱበት ሁኔታ ነው። በአብዛኛ የመጀመሪያው አይነት ክርክር የሚቀርበው በሰራተኛው ሲሆን ሁለተኛው አይነት ክርክር ደግሞ በአሰሪው የሚቀርብ ነው። ይህም የሙግታቸው አቀራረብ ለተጠቀሰው ጭብጥ መመስረት ምክንያት የሆነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ክርክር በአሰሪው በኩል መቅረቡን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የጉዳዩ ጭብጥ እንዲሆን ያስቻለውን ክርክር ያቀረበው አሰሪው ከሆነ ደግሞ ይህን ክርክሩን በቅድሚያ ያስረዳ ዘንድ የግድ ይሆንበታል፡፡ ይህም the one who alleges in the affirmative shall prove it ከሚለው አገላለጽ ጋር የተስማማ ይሆናል፡፡ እንደዚሁም ይህን ጉዳይ ስለ ማስረጃ ማቅረብ ግዴታ እና ስለአቀባበሉ ከተደነገገበት የፍትሐ ብሔር ሕጉ ክፍል ጋር ማገናዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ የፍትሐ ብሔር ሕግ ክፍል ስር የሚገኘው አንቀጽ 2001 አንድ ግዴታ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር የሚያሳይለት ማስረጃ ማቅረብ እንደሚገባው፤ ግዴታው ፈርሷል ወይም ተቀይሯል ወይም ቀርቋል የሚል ወገን ደግሞ ይህ ተግባር መፈፀሙን የሚያሳይለትን ማስረጃ ማቅረብ እንዳለበት ደንግጓል፡፡ በያዝነው አይነት የስራ ክርክር ጉዳይ የገባውን ግዴታ ሊፈጽምልኝ ይገባል የሚል ክርክር የሚቀርበው በአሰሪው ሳይሆን በሰራተኛው ነው፡፡ ስለሆነም ከተጠቀሰው ድነጋጌ አግባብ ሰራተኛው የግዴታውን መኖር ለማስረዳት በመካከላቸው የስራ ውል ያለ መሆኑን ብቻ ማሳየቱ የሚበቃው ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን የስራ ውሉ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10 የሚሸፈን ነው በሚል የሚከራከረው አሰሪ ይህን የስራ ውሉ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር የሚወድቅ መሆኑን ያረጋግጥልኛል የሚለውን ተግባር ያስረዳ ዘንድ ይጠበቅበታል፡፡

እንግዲህ አንድ የስራ ውሉ በአንቀጽ 10 የሚሸፈን ነው ሲል አሰሪው በተከራከረ ጊዜ ሁሉ ይህንን ክርክሩን የሚደግፍለት የጽሁፍም ሆነ የሰው ማስረጃ በቅድሚያ እንዲያቀርብ ያስፈልጋል፡፡ በአሰሪው የቀረበው ማስረጃ ከተመዘነ በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ሰራተኛው ቅጥሩ በአሰሪው እንደተባለው ሳይሆን በሌላ በአንቀጽ 10 ሊሸፈን በማይችል የተለየ ሁኔታ መፈፀሙን በማስረዳት በአሰሪው የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ያስተባብል ዘንድ ይገባዋል፡፡

እንዲሁም አንድ ፍ/ቤት የተከራካሪዎች የጽሁፍም ሆነ የቃል የስራ ውል ከአንቀጽ 10 አግባብ መደረግ አለመደረጉን ሲፈትሽ አለነ የሚሉትን ማስረጃ ከፍ ሲል በተመለከተው ስርዓት ሊያስተናግድ ይገባዋል፡፡ እርሱም ይጠቅመኛል የሚለውን ሌላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ተመሳሳይ አይነት ወይም አግባብነት ያለው የአካባቢ ማስረጃ ለውሳኔው መሰረት ሊያደርግ ይችላል፡፡

በሌላም በኩል አንድ የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ መሆን አለመሆኑን የማጣራቱ ጉዳይ በአሰሪው እና በሰራተኛው መካከል የተደረገውን የስራ ውል የመተርጎምን ተግባር ይሠምራል፡፡ አከራካሪ ሆኖ የተገኘውን የስራ ውል ለመተርጎም ደግሞ ተዋዋዮቹ ውሉን ሲያደርጉ የነበራቸውን ፈቃድ መለየት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የያዘውን ጭብጥ ሲፈታ የስራ ውሉ በተደረገበት ጊዜ አሰሪውና ሰራተኛው የነበራቸው የሐሳብ አንድነት ምን እንደነበር ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ፍ/ቤቱ በአደረገው ማጣራት የስራ ውሉ የተደረገበት የተዋዋዮቹ ፈቃድ ውሉ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 10 በተመለከቱት ሁኔታዎች ላይ መፈጸሙን አረጋግጦልኛል የሚል ከሆነ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ይደርሳል፡፡ የስራ ውሉ የተደረገበት የተዋዋዮቹ ፈቃድ በተጠቀሰው አንቀጽ 10 ስር የሚወድቅ አይደለም ካለ ደግሞ ውሉን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የስራ ውል ይቆጥረዋል፡፡

ወደያዘነው ጉዳይ ስንመለስ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ ማለትም ለስድስት ወራት መቀጠሯን የሚያሳይ የፅሁፍ የስራ ውል በማስረጃነት ቀርቦለታል፡፡ ቅጥሩም ወቅታዊ ስራን ለማከናወን በሚል መፈፀሙን ውሉ በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ውሉ ጊዜ የተወሰነለት መሆኑ ብቻውን የተወሰነ ጊዜ የስራ ውል የሚያሰኘው አይሆንም፡፡ ስለሆነም ውሉ በአዋጅ 42/85 አንቀጽ 10 አግባብ የተደረገ መሆን አለመሆኑ ጭምር መታየት ይኖርበታል፡፡

ሁለቱ ወገኖች የፈፀሙት ውል ተጠሪ የተቀጠረችው ወቅታዊ ስራን ለማከናወን መሆኑን የሚጠቅስ ሲሆን አመልካቹ ደግሞ ተጠሪ የተቀጠረችው በንድ ወቅት ተከስቶ የነበረን የስራ ብዛት ለማቃለል ነው ሲል ከስር ጀምሮ መከራከሩን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይህም የአመልካቹ ክርክር /ምንም እንኳን ውሉ የቅጥሩ ምክንያት ወቅታዊ ስራን ለመስራት የተደረገ መሆኑን የሚያመላክት ቢሆንም/ ተጠሪ የተቀጠረችበት የጠቅላላ አገልገሎት ክፍል የተላላኪነት ስራ ወቅት ጠብቆ የሚሰራ ቋሚ የአሰሪው ስራ በሚል ሊፈረጅ እንደማይችል በአመልካቹ ጭምር የታመነበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንዲሁም የክርክሩ አቀራረብ ጉዳዩን ከንዑስ አንቀጽ /6/ ጋር ሳይሆን ከንዑስ /3/ ጋር አገናዝበን እንድናየው እና አመልካቹም በዚህ ረገድ ያቀረበውን ክርክር ማስረዳት አለማስረዳቱን እንድንለይ ይጠይቀናል፡፡

ከጉዳዩ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ የተቀጠረችው በቀጣይነት በሚከናወን የአሰሪው ቋሚ ስራ ላይ ነው፡፡ ተጠሪም ብትሆን የምትከራከረው ስራው ወቅት ጠብቆ የሚሰራ ነው በሚል ሳይሆን ያለማቋረጥ የሚሰራ የስራ አይነት ነው በሚል ነው፡፡ በቀጣይነት የሚሰራ የአሰሪ ቋሚ ስራ ላይ የስራ ብዛትን ለማቃለል በሚል የተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ማድረግ በንዑስ ቁ./3/ የተፈቀደ ነው፡፡ በእርግጥ የቀረበው የስራ ውል አመልካቹ እንደሚከራከረው ውሉ የተደረገው በአንድ ወቅት የተከሰተን የስራ ብዛት ለማቃለል መሆኑን በግልፅ የሚጠቅስ አይደለም፡፡ ይህ ማለት ግን ውሉ የአመልካቹን ክርክር አያስረዳለትም በሚል ከወዲሁ እንድንደመድም የሚያስችለን አይደለም፡፡ ይልቁንም በውሉ ላይ የተወለከተው የቅጥሩ ምክንያት ከዚህ ንዑስ አንቀፅ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን የማየቱን ጉዳይ አስፈላጊ የሚያደርገው ነው፡፡ ተጠሪ የተቀጠረችበት የተላላኪነት ስራ የወቅት ስራ አይደለምና በዚህ ችሎት እምነት በውሉ ላይ ወቅታዊ ስራን ለማከናወን መቀጠሯ መገለፁ በጊዜው የነበረውን የሥራ ብዛት ለማቃለል ሲባል መቀጠሯን ለማረጋገጥ ያህል የሚበቃ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቹ ላቀረበው ክርክር ውሉ እንደ በቂ የፅሁፍ ማስረጃ ሊቆጠርለት የሚገባ ነው፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ በቦታው ሌላ ቀጥሮ እኔን አለአግባብ አሰናበተኝ የሚል አጠቃላይ ይዘት ያለው ክርክር ከማቅረቧ ውጭ ስራ ለማቃለል ቀጠርኳት ማለቱ ሐሰት መሆኑን አስረዳለሁ በሚል አይነት አልተከራከረችም፡፡ በዚህ አይነት ክልሚገች እና ሙግቷንም ካላስረዳች ደግሞ የአመልካቹን ክርክር አስተባብላለች የሚያስብላት አይደለም፡፡ ተጠሪ እንደምትከራከረው በቦታው ሌላ መቀጠሩን በስር ፍ/ቤት በቆጠረቻቸው ምስክሮች እንደአስረዳች ቢወስድላት እንኳ የተቀጠረችው የስራ ብዛት ለማቃለል አለመሆኑን በማስረዳት የአመልካቹን ክርክር አስተባብላለች የሚያሰኛት አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በእርሷ ቦታ ሌላ የመቀጠሩ ጉዳይ እርሷ የተቀጠረችው ስራ ለማቃለል ሲባል አይደለም የሚል አሳማኝነት ያለው መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ የሚችል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጥቅሉም በሁለቱ መካከል የተደረገው የስራ ውል በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 10/3/ የሚሸፈን የተወሰነ ጊዜ የስራ ውል መሆኑን ይህ ችሎት ተቀብሎታል፡፡ በውሉ የተወሰነ ጊዜ ሲያልቅ ውሉ መቋረጡም በአዋጁ አንቀጽ 24/1/ የተደገፈ ነውና የስር ፍ/ቤቶች የውሉን መቋረጥ ሕገወጥ አድርገው ወደስራ እንድትመለስ መወሰናቸው ከሕጉ ያልተጣጣመ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1ኛ- በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የስራ ውል የተቋረጠበት ምክንያት ሕጋዊ እንጂ ሕገ ወጥ ባለመሆኑ አመልካች ወደ ስራ ልትመለስ አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡

2ኛ- ይህ ችሎት በመ.ቁ.17189 ለጉዳዩ አግባብነት ላላቸው የአዋጅ ቁ.42/85 ድንጋጌዎች ትርጓሜ በመስጠት ሕጉ ስራ ላልተሰራበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል የሚፈቅድ አይደለም የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ተጠሪ ያልሰራችበት ጊዜ ደመወዝ ሊከፈላት አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡

3ኛ- በመሆኑም ተጠሪ የአመት ፈቃድ እንዲሰጣት የተወሰነውን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሳይጨምር ቀሪዎቹ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.224/90፤ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ በመ.ቁ.857/93 የተሰጡት የውሳኔ ክፍሎች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ ቁ.348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 14057
ጥቅምት 30 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት
ተጠሪ፡- አቶ ጌታሁን ኃይሉ

ስራ ክርክር - የዓመት እረፍት ክፍያ - የአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 79/2/ እና /5/፣ 77/5/፣ 77/3/

የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ መስርተው የ128 ቀናት የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጣቸው የጠየቁበመጀመሪያ ያየው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የተላለፈ የዓመት እረፍት ፈቃድ ከሁለት አመት በላይ መራዘም ስለሌለበት 128 የእረፍት ቀናት ተቀንሶ አዋጁ በሥራ ላይ ከዋለበት ጀምሮ ተጠሪ እስከተሰናበቱበት ድረስ የአንድ አመት ከአሥራ ሦስት ቀናት የዓመት እረፍት ክፍያ ብቻ ይከፈል በማለት ሊወሰን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ የተጠሪ ገንዘብ (የጠየቀው የአመት እረፍት) ሳይቀነስ ሊከፈል ይገባል በማለት በመወሰኑ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሻሻለው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

1. ከሁለት አመት በላይ የተራዘሙ ፈቃዶች በገንዘብ የሚተኩ አይደሉም፡፡
2. አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የዓመት ፈቃድ ክፍያ ሁሉ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈለው አይችልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 14057

ጥቅምት 30 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሀ ወርቅነህ

ስንዱ አለሙ

ሆሳዕና ነጋሽ

አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ኃይሉ ተሰማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጌታሁን ኃይሉ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

አመልካች ለሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 15313 ህዳር 25 ቀን 1996 ዓ.ም የዓመት ዕረፍት ክፍያን በተመለከተ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ከሌሎች ክፍያዎች ጋር የተጠራቀመ የ128 ቀናት የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈለው ነው፡፡ አመልካች የዓመት ዕረፍት ክፍያን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 79 2 እና 5 መሠረት የተላለፈው የዓመት ፈቃድ የሚቀጥለው ሁለት ዓመት በላይ ሊራዘም አይችልም ተጠሪ የጠየቀው ክፍያ በሕጉ ከተሰጠው በላይ ስለሆነ ሊከፈለው አይገባም በማለት መከራከሩን የፍ/ቤቱ ውሣኔ ያሳያል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ /... የአስረና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 192/1/ሠ አዋጅ ቁጥር 64/68 የሆነውን በግልጽ የሻረው በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ አዋጅ ቁጥር 42/85 ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም የሚለው የተከሣሽ ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ ስለሆነም በአዋጅ ቁ.42/85 በአንቀጽ 79/5/ ሥር በአንቀጽ 79/1 እና /2/ የተላለፈ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ከሁለት ዓመት በላይ መራዘም እንደሌለበት የተደነገገ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የከሣሽ 128 የእረፍት ቀናት ተቀንሶ አዋጁ በስራ ላይ ከዋለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ከጥር 12/85 ጀምሮ እስከተሰናበቱበት ጊዜ እስከ ጥር 28/86 ዓ.ም ያለው ጊዜ አንድ ዓመት ከአስራ ሶስት ቀናት የአመት ዕረፍት ክፍያ ብቻ በአንቀጽ 77/3/ መሠረት እንዲከፈል የሚል ነው።

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል። ፍ/ቤቱም አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 79/5/ የዓመት ዕረፍት ከሁለት ዓመት በላይ ሊተላለፍ አይችልም ሲል ሠራተኛው ከሁለት ዓመት በላይ ያጠራቀመው የዓመት ዕረፍት ካለ አይገባውም ማለቱ አይደለም። ይልቁንም በአዋጁ በቁጥር 77/5/ ላይ ያልወሰደው የዓመት ፈቃድ በጠቅላላ ታስቦ እንዲከፈለው ተደንግጓል። በመሆኑም ተጠሪ የጠየቀው የዓመት ዕረፍት ክፍያ ሳይቀነስ እንዲከፈለው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔውን በመሻሻል ወስኗል።

አመልካች የከፍተኛ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት ፈጽሟል ሲል አቤቱታ ያቀረበው በዚህ ውሣኔ ነው። ታህሣሥ 19 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ በውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተሰርቷል ሲል የሚያቀርባቸው ክርክሮችም፣

- የተጠሪ የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈለኝ ጥያቄ ከሥራ ከመሰናበታቸው ጥር 30/86 ዓ.ም በፊት የነበረና በተለይም አዋጅ በአንቀጽ 34/4/ ከሀ-ሠ መሠረት ያልተላለፈ በመሆኑ ሊጠየቅ አይገባም።
- በአዋጅ አንቀጽ 79/2-3/ መሠረት ሠራተኛው ጠይቆ ወይም አሠሪው የሥራ ሁኔታ አስገድዶት የተላለፈ ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም በላይ በዚሁ አንቀጽ 79/5/ በግልጽ እንደተቀመጠው በሁለቱ ስምምነት የተላለፈ የዓመት ዕረፍት ቢኖር እንኳን ከሁለት አመት በላይ ሊራዘም እንደማይችል በግልጽ ሰፍሯል። ተጠሪ በአዋጁ መሰረት የተላለፈ የዓመት ዕረፍት ያላቸው ለመሆኑ ያልገለጹ ከመሆኑም በላይ አንቀጽ 79/5/ ከሁለት አመት በላይ ሊተላለፍ እንደማይችል በግልጽ የደነገገውን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለመቀበል በአዋጅ አንቀጽ 77/5/ በሙሉ በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈላቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉ ናቸው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ ታዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት ሚያዚያ 28 ቀን 1996 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ በመልሱም የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የህግ ስህተት እንደሌለበት በመግለጽ እንዲፀና ጠይቋል፡፡ አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

በዚህ ጉዳይ ተመርምሮ ሊወሰን የሚገባው ዋናው የክርክር ጭብጥ አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበትን የዓመት ዕረፍት ቀናት ሁሉ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈለው ይገባል ወይ? የሚለው ጭብጥም ይታያል፡፡

በቅድሚያ ግን አመልካች የተጠሪ የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈለኝ ጥያቄ አዋጅ ቁ. 42/85 ከመውጣቱ በፊት የነበረ መብት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 64/68 መሠረት መታየት ይገባዋል ሲል የሚያቀርበውን ክርክር ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው ግንቦት 14 ቀን 1990 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 42/85 በሥራ ላይ እያለ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 64/68 በአንቀጽ 192/ሠ/ እንደተሻረ ተገልጿል፡፡ አዋጅ ቁጥር 64/68 በኋላኛው አዋጅ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ተፈፃሚ የሚሆነው በአዋጅ ቁጥር 42/85 በቁጥር 191 እንደተደነገገው አዋጅ ቁጥር 64/68 በሥራ ላይ እያለ ክሱ መታየት ጀምሮ ቢሆን ነበር፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተሻረውን አዋጅ ቁጥር 64/68 ተፈፃሚ ለማድረግ መታየት ያለበት የኋላኛው አዋጅ ሲተካ ሥራ ላይ ሲውል ጉዳዩ በቀድሞው አዋጅ መታየት የጀመረ መሆን አለመሆኑን እንጂ መብቱ የተገኘበትን ጊዜ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ ክሱን ያቀረበው አዋጅ ቁጠር 42/85 በሥራ ላይ እያለ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚ የሚሆነው ይኸው አዋጅ ቁ.42/85 ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የአዋጁን ተፈፃሚነት በተመለከተ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በመቀጠልም አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበትን የዓመት ዕረፍት ሁሉ ያለጊዜ ገደብ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው ይችላል ወይ? የሚለውን ዋና ጭብጥ እንመለከታለን፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህን ጭብጥ ለመመርመር በቅድሚያ የዓመት ፍቃድን ምንነትና አስፈላጊነት መመልከት ተገቢ ነው። በአዋጅ ቁጥር 42/85 ከአንቀጽ 76-78 ካሉት ድንጋጌዎች የአመት ፈቃድ ለሠራተኛ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የስራ ቀናት የዕረፍት ጊዜ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በአዋጁ ቁጥር 13/4/ መሠረት ሠራተኛው ለሥራ ብቁ በሆነ የአእምሮና የአካል ሁኔታ በስራ ላይ መገኘት ይጠበቅበታል። የአመት ዕረፍት ከሚሰጥባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ሠራተኛው ይህን የሚጠበቅበትን ግዴታ ማሟላት እንዲችል ነው። በአዋጁ ስለ ዓመት ፈቃድ የሚናገረው ጠቅላላ ድንጋጌ /አንቀጽ 76/2/ በዓመት ፈቃድ ፋንታ በገንዘብ መክፈል የተከለከለ እንደሆነ ይደነግጋል። አንድ ሠራተኛ የአመት ፈቃድ ለማግኘት ያለውን መብት በማናቸውም ሁኔታ ለመተው የሚያደርገው ስምምነት ተቀባይነት እንደሌለውም የዚሁ አንቀጽ ንዑስ /1/ ይደነግጋል። ከነዚህ ድንጋጌዎች ገንዘብ የአመት ፈቃድን መተካት እንደማይችል ሠራተኛው የአመት ፈቃዱን ባልተጠቀመ ቁጥር ፍቃዱ ወደ ገንዘብ ተለውጦ መከፈል እንደሌለበትም ያመለክታል።

በሌላ በኩል በዋናነት የአመት ዕረፍት ለሠራተኛ የሚሰጠው ሳይከፋፈል ሲሆን መሰጠት ያለበትም ከእያንዳንዱ አመት የአገልግሎት ዘመን በኋላ ሳይጠራቀም ነው። /ቁጥር 77/1/ እና 78 ። ሆኖም ሠራተኛው ተከፋፍሎ እንዲሰጠው ሲጠይቅና አሠሪውም ሲስማማ ለሁለት ተከፍሎ ሊሰጠው ይችላል። /79/1/ እንዲሁም ሠራተኛው ሲጠይቅና አሰሪውም ሲስማማ በአሠሪውም በኩል የሥራ ሁኔታ ሲያስገድደው የሠራተኛውን የፈቃድ ጊዜ ሊያስተላልፍ ይችላል። /አንቀጽ 79/1/ እና /3/ የአመት ዕረፍትን ከላይ እንደተገለፀው በአሠሪና በሠራተኛው ስምምነት ማራዘም ቢቻልም ሊራዘም የሚችልበት ጊዜ ግን በሕጉ ወሰን ከሚቀጥለው ሁለት አመት በላይ ሊራዘም አይችልም። ይህ ድንጋጌ ከሁለት አመት መራዘም በኋላ ሠራተኛው ፍቃዱን የግድ መጠቀም ያለበት መሆኑን ያመለክታል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመቀጠልም ሠራተኛው በዚህ ሁኔታ ተራዝሞ ያልተጠቀመበትን ፍቃድ ሁሉ የስራ ውሉ ሲቋረጥ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው ይችላል ወይ? ወደሚለው ጭብጥ እንመለሳለን፡፡ የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈልባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች በአዋጁ በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም 1ኛው የሥራ ውሉ ለተቋረጠ ሠራተኛ ሲሆን 2ኛው ደግሞ በአንቀጽ 80 እንደተገለፀው አሠሪው በፍቃድ ላይ ያለ ሠራተኛን ጠርቶ ፈቃዱን ሳይጨርስ ስራውን እንዲቀጥል ካደረገ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ በአንቀጽ 80/2/ ሠራተኛው ያልተጠቀመበትን ማለትም የቀረውን የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተተምኖ ሊከፈለው እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

ለያዝነው ጭብጥ አግባብነት ያለው የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛን በማስመልከት ስለሚፈፀመው የአመት ዕረፍት ክፍያ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 77/5/ የስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ያልወሰደው የአመት ፈቃድ ታስቦ በገንዘብ እንደሚከፈለው ይደነግጋል፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የአመት ዕረፍት መሠረት ሃሣብ ክፍያ የሚፈፀምበት የዕረፍት ቀናት ማግኘት ቢሆንም የስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ግን እደደአላማው በዕረፍቱ ሊጠቀምበት አይችልም፡፡ በዋናነት የአመት ዕረፍት በገንዘብ እንዲተካ ሕጉ ባይፈቅድም በስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ግን በዕረፍቱ ፋንታ ገንዘብ እንዲከፈለው በህጉ ተፈቅዷል፡፡ ይህም የሆነው ከላይ እንደተገለፀው የስራ ውሉ በመቋረጡ ምክንያት ሠራተኛው በዕረፍቱ ሊጠቀምበት የማይችል በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ክፍያ የሚፈፀምባቸው የትኞቹ ፍቃዶች ናቸው የሚለውን ነጥብ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የአመት ፍቃድ ከሚቀጥለው ሁለት አመት በላይ ሊራዘም እንደማይችል በአንቀጽ 79/5/ ተደንግጓል፡፡ በአንቀጽ 76/1/ እና /2/ አንድ ሠራተኛ የአመት ፈቃዱን ለመተው ስምምነት ማድረግ እንደማይችል በአመት ፈቃድ ፈንታ ገንዘብ መክፈል የተከለከለ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ተገናዝበው ሲታዩ የአዋጅ አንቀጽ 77/5/ የሥራ ውሉ ለተቋረጠ ሠራተኛ እንዲከፈል የፈቀደው የአመት ዕረፍት ክፍያ ሠራተኛው ስራ ላይ ቢሆን ኖሮ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ፍቃዶችን እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ ይኸውም በህጉ መሠረት ሁለት አመት የተራዘሙ ወይም ሊራዘሙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የሚችሉና የደረሱ ፍቃዶችን ይጨምራል። ከዚህ ውጪ ግን ከሁለት አመት በላይ የተራዘሙ ፍቃዶች በገንዘብ የሚተኩ አይደሉም የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሰናል።

ሲጠቃለል ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት አንድ ሠራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመት የአመት ፍቃድ ክፍያ ሁሉ የጊዜ ገደብ ሳይኖረው በገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈለው አይችልም። የከፍተኛው ፍ/ቤት ሠራተኛው የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት ዕረፍት ሁሉ ያለምንም የጊዜ ወሰን ወደ ገንዘብ ተቀፋሮ9 ሊከፈለው እንደሚችል በመቁጠር የአዋጁ ቁር 42/85 አንቀጽ 77/5/ን መተርጎሙ የአመት ፈቃድ አላማንና መሠረተ ሃሣብን ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት። ሊታረም ይገባል።

በመቀጠልም የአመት ዕረፍት ሠራተኛው በግልጽ በጽሁፍ ወይም በቃል ካልጠየቀ አሰሪውም በግልጽ እንዲተላለፍ ካልፈቀደ ፍቃዱ እንደተላለፈ አይቆጠርም ወይ? የሚለውን ጭብጥ እንመለከታለን። የአዋጁን አንቀጽ 79/2/ የአመት ፈቃድ ሠራተኛው ሲጠይቅና አሰሪውም ሲስማማ ሊተላለፍ እንደሚችል ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ የአመት ፍቃድን ለማስተላለፍ የአሰሪውና የሠራተኛው ስምምነት አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል። ስምምነት በግልጽ ወይም ግልጽ ባልሆነ መንገድ ሊደረግ ይችላል። ስምምነት ከአሠራርም ሊታይ ይችላል። ሠራተኛው በስምምነት እንኳን ሊተወው የማይችል የአመት ዕረፍት በሕግ ተሰጥቶታል። ፍቃዱን መጠቀሙ መብቱም ግዴታውም ነው። አሠሪው ኘሮግራም አውጥቶ ለሠራተኛው ፍቃድ መስጠት እንዳለበት የአዋጁ ቁጥር 78/2/ ይደነግጋል። የአመት ዕረፍትን ለተወሰነ ጊዜ ማራዘም እንደሚቻል ከላይ በ1ኛው ጭብጥ ተመልክተናል። እንግዲህ ሠራተኛው ፍቃድ መውሰድ ባለበት ጊዜ ሳይወስድ ቢቀር አሰሪውም ሳይሰጠው ስራውን እንዲቀጥል ቢያደርግ ከአሠራራቸው ፍቃዱን ለማራዘም የተስማሙ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ስምምነቱም ፍቃዱ በሕግ እንዲራዘም እስከተፈቀደ ጊዜ ድረስ ብቻ እንደተደረገ ሊቆጠር ይገባል።

ሲጠቃለል ፍቃድን ለማስተላለፍ የሚደነግገው አዋጁ ድንጋጌ /አንቀጽ 79/ ፍቃድን ለማስተላለፍ አሰሪውና ሠራተኛው መስማማት ያለባቸው መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ቢያስገነዝብም ስምምነታቸው ግን ግዴታ በግልጽ መሆን እንደሚገባው የግልጽነት ፎርማሊቲን እንዲያሟላ አያስገድድም፡፡ ስምምነት መኖሩን ደግሞ ከአሠራር መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች ፍቃድ ተላልፏል ለማለት አሰሪውና ሠራተኛው የግድ በግልጽ መስማማት አለባቸው የሚለው ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. ተጠሪ ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈለው የጠየቀው የአመት ዕረፍት ቀናት ክፍያ ሁሉም ሊከፈለው አይገባም፡፡
2. ተጠሪ የ1984፣ የ1985 እና የ1996 ከስራ አስከተሰናበተበት እስከ ጥር 30 ድረስ ያለው የአመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈለው፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በስራ ክርክር መዝገብ ቁጥር 1438 ነሐሴ 16 ቀን 1994 ዓ.ም እንዲሁም የከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15313 ህዳር 25 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሠረት ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ/ቁ. 16270

ታህሣሥ 17 **ቀን** 1998 **ዓ.ም**

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጉስ ወልዱ

አቶ ዳኜ መላኩ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች .... አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት

ተጠሪ..... አቶ መሐሪ ማታ

ስለውል ውጪ ያለ ኃላፊነትን በተመለከተ ስለ ካሳ መክሰን ስለወሰን

የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066(2)፣ 2086(2)፣ 2081፣ 2090፣ 2091 2102(1) እና 2092

የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የሆነው የአሁን አመልካች መኪናው አድርሷል በተባለው የግጭት አደጋ ለተጎጂው የጉዳት እና መራል ካሳ እንዲሁም የህክምና ወጪ በድምሩ ብር 30.198 እንዲከፍለው በመወሠኑ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሠቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔውን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ

<u>ውሳኔ፡ -</u> **የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔና የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀድቋል።**

1ኛ. ከውል ውጪ ኃላፊነት በሆነ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ የደረሰው በተከሳሹ መኪና መሆኑን ከማስረዳት ውጪ በባለሀብቱ በኩል ጥፋት ስለመኖሩ ማረጋገጥ አይጠበቅበትም።

2ኛ ጥፋት ባይኖርም በኃላፊነት ተጠያቂ የሆነ ሰው ከኃላፊነት ነፃ ለመሆን ጉዳት የደረሰበትን ሠው ሌላ የወንጀል ድርጊት ለመጥቀስ አይችልም።

3ኛ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343(1) መሠረት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተመልሶ ከተላከ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያው ውሳኔ ሳይገደብ የካሳውን መጠን ሊያሻሽል ይችላል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ/ቁ. 16270

ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጉስ ወልዱ

አቶ ዳኜ መላኩ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች ...አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት ነገረፈጅ አቶ ጀማል አህመድ ቀረበ

ተጠሪ..... አቶ መሐሪ ማታ ጠበቃ አቶ ተሰማ አበበ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ተከሣሽ የሆነው የአሁኑ አመልካች መኪናው አድርሷል በተባለው የግጭት አደጋ ምክንያት ለተጉጂው ለአሁኑ ተጠሪ የጉዳት ካሣ ብር 28,800፣ የሞራል ካሣ ብር 1000 እና የህክምና ወጪ ብር 308 በጠቅላላው ብር 30,198 እንዲከፍለው መወሰኑ ነው።

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው። ከሣሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ሐምሌ 15 ቀን 1987 ዓ.ም በሞተር ሣይክል በመጓዝ ላይ እያለ ንብረትነቱ የአዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት በሆነ የሰሌዳ ቁጥር 3-00217 መኪና ተገጭቶ አንድ እግሩ በመጉዳቱ ወይም በመቆረጡ ምክንያት ከአደጋው በፊት እየሰራ ያገኝ የነበረው ገቢ መቋረጡን በመግለጽ የመኪናው ባለቤት በሕግ ባለበት ኃላፊነት መሠረት የጉዳት ካሣ ብር 58,600 እንዲከፍለው የሚጠይቅ ክስ ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ በኃላፊነቱ ጉዳይም ሆነ በካሣው መጠን ላይ ካከራከረና ማሥረጃም ከሰማ በኋላ ጉዳቱን ያደረሰው የተከሣሹ የአዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት መኪና መሆኑ ስለተረጋገጠ ለደረሰው ጉዳት በሕግ ኃላፊነት አለበት፣ ተጉጂው በተከሣሹ መኪና ባይገጭ ኖሮ እግሩ ሊቆረጥ አይችልም ነበር፣ እግሩ ከተቆረጠ ደግሞ ቀደም ሲል ሲሰራ የነበረውን ሥራ ተመልሶ ለመሥራት እንደማይችል ግልጽ ነው። በአካሉ ላይ የደረሰው ጉዳትም 50% እንደሆነ ስለተገለፀ ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት በክሱ የጠየቀውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የጉዳት ካሣ በከፊል በመቀነስ ለደረሰበት ጉዳት ብር 28,800 የሞራል ካሣ ብር 1000 እና ለህክምና ያወጣውን ወጪ ብር 308 በጠቅላላው ብር 30,198 ሊከፍለው ይገባል በማለት ወስኗል።

የአሁኑ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኃላፊነቱ ጉዳይም ሆነ የካሣውን መጠን በማስመልከት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.3144 የይግባኝ አቤቱታ ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የአሁኑ ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት አድርጉ የይግባኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በመጨረሻ ግንቦት 19 ቀን 1996 ዓ.ም መርምሮ በሰጠው ውሣኔ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሣኔ የሚታይበት ጉድለት የለም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 348(1) መሠረት አጽንቶታል።

አመልካች የክልሉ ሁለት ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ በተመሣሣይ መንገድ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሚል ምክንያት በዚህ መዝገብ ለሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመወሰኑ አመልካች በ30/10/96 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ማመልከቻ ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በጠበቃው አማካኝነት ጥቅምት 5 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል። አመልካች በበኩሉ በተጠሪው ጠበቃ በኩል በጽሑፍ የተሰጠውን መልስ ከተመለከተ በኋላ የመልስ መልስ ጽፎ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ አድርጓል።

ችሎቱም የኃላፊነቱን ጉዳይም ሆነ የካሣውን መጠን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

በቅድሚያ የአሁኑ አመልካች በተጠሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት በሕግ ኃላፊነት አለበት የለበትም? ጉዳቱ የደረሰው በተጉጂው(ተበዳዩ) በገዛ ራሱ ጥፋት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት አለ ወይንስ የለም የሚለው ሲመረመር በፍሬ ነገር ረገድ የአሁኑ ተጠሪ ሞተር ሣይክል እየነዳ በመጓዝ ላይ እያለ ሁለተኛው ተከሣሽ ሲያሽከረክረው በነበረው ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች በሆነው የሰሌዳ ቁጥር 3.00217 መኪና ገጭቶ ከነሞተር ሣይክሉ በመውደቁ ምክንያት በአንድ እግሩ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት የተቆረጠ መሆኑ ተረጋግጧል።

ካሣ የተጠየቀበት ጉዳት መነሻው የአሁኑ አመልካች መኪና ያደረሰው የግጭት አደጋ ሆኖ ከተገኘ ጉዳዩ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት የሚመለከት ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) የአንድ መኪና ወይም የአንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው አደጋውን ያደረሰው መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለመንዳት ወይም ለማንቀሣቀስ ባልተፈቀደለት ሰው ቢሆንም እንኳን መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው ላደረሰው ጉዳት አላፊ የሚሆነው ባለሀብቱ መሆኑን ይደነግጋል። የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት አጥፊ ሣይሆን ጉዳት ያደረሰው መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለሀብት በመሆኑ ብቻ ለደረሰው ጉዳት በሕግ አላፊ ይሆናል። ተጐጂው ወይም ተበዳዩ ጉዳቱ የደረሰው በተከሣሹ መኪና መሆኑን ከማሥረዳት ውጭ በባለሀብቱ በኩል ጥፋት ስለመኖሩ ማረጋገጥ አይጠበቅበትም።

በሌላም በኩል ጉዳት ያደረሰው መኪና ባለሀብት ከአላፊነት የሚድንባቸው የሕግ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ ጉዳቱ የደረሰው በተጐጂው ወይም በተበዳዩ ጥፋት ምክንያት እንደሆነ አላፊነት አያመጣም በሚል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2066(2) ላይ የተመለከተው ነው። ጉዳት ያደረሰው መኪና ባለሃብት ጉዳቱ የደረሰው በተጐጂው ጥፋት ምክንያት ነው የሚል መከላከያ ካለው የማስረዳት ሸክም የራሱ ይሆናል። በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2086(2) ላይ እንደተመለከተው የአንድ መኪና ባለሀብት ጉዳቱ የደረሰው በከፊል ወይም በሙሉ ከተበዳዩ ጥፋት የተነሣ መሆኑን ካላረጋገጠ በቀር በከፊልም ሆነ በሙሉ ከአላፊነቱ ሊድን አይችልም።

በቀረበው ጉዳይ የአሁኑ አመልካች ለደረሰው ጉዳት በተበዳዩ በኩል ጥፋት አለ በማለት የሚከራከረው በሁለት ምክንያቶች ሲሆን አንደኛው ተጠሪው የሌላ ድርጅት ሞተር ሣይክል ሰርቆ እየነዳ ሲሄድ ነው የተገጨው በሚል የቀረበ ነው። የተሰረቀን ሞተር ሣይክል ወይም ሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ በሚነዳ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ በአላፊነት አያስጠይቅም የሚል ሕግ የለም። የጉዳቱም መንስኤ ተበዳዩ የተሰረቀ ሞተር ሣይክል ይዞ መገኘቱ ወይም መንዳቱ ሣይሆን የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሾፌር መንገዱን በማጥበብ ተጠሪው የሚነዳውን ሞተር ሣይክል ሊገጨው መቻሉ ነው። በመሆኑም አመልካች ተጠሪው የተሰረቀ ሞተር ሣይክል እየነዳ ሲጓዝ ነው የተገጨው በሚል ያቀረበው ክርክር ሕጋዊ መከላከያ ሊሆን አይችልም። ሁለተኛው ሞተር ሣይክል ለመንዳት የሚያስችል መንጃ ፈቃድ የለውም የሚለው ነው። መንጃ ፈቃድ የሌለው መሆኑ ብቻ ጉዳቱ የደረሰው በእርሱ ጥፋት ነው ለማለት አያስችልም። መታየት የሚገባው ሞተር ሣይክሉን እየነዳ ሲጓዝ የፈፀመው ጥፋት ምንድነው የሚለው ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተጠሪው መንጃ ፈቃድ የሌለው መሆኑን ከሚገልጽ በቀር በሥር ክርክሩ ወቅት ተጠሪው የፈፀመው ጥፋት መኖሩን አላስረዳም። መንጃ ፈቃድ ሣይኖረው የሚያሽከረክርን ሰው በመኪና መግጨት በሕግ በአላፊነት ከመጠየቅ ሊያድን ስለማይችል አመልካች በዚህም ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም። በአጠቃላይ የአሁኑ አመልካች መኪናው ላደረሰው ጉዳት አላፊ ነው ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም።

የካሣውን መጠን በተመለከተም ተጉጂው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች መኪና በተፈፀመው ግጭት የተነሣ አንድ እግሩ የተቆረጠ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በእግሩ መቆረጥ ምክንያት ቀደም ሲል የተሰማራበትን ሥራ ለመቀጠል አልቻለም። ከአደጋው በፊት በወር ብር 120 ደመወዝ እየተከፈለው ሲሰራ የነበረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማሥረጃ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ላየው ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረቡን ከተሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ተችሏል። የአሁኑ አመልካች ይህንን የሚያፈርስ ሌላ ተቃራኒ ማሥረጃ አላቀረበም። ፍ/ቤቱም በተጠሪው በደረሰበት አደጋ ምክንያት ገቢው ሊቋረጥ መቻሉንና ጉዳቱም ዘለቂታ ያለው መሆኑን በመገንዘብና ከአደጋው በፊት በየወሩ ሲያገኝ ነበር የተባለውን ደመወዝ በመነሻነት በመጠቀም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2102(1) መሠረት የጉዳት ካሣውን ልክ በርትዕ በማመዛዘን ወስኗል። የካሣ አከፋፈልና ልክ የሚወሰነው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2090 ጀምሮ በተከታታይ በተፃፉ ድንጋጌዎች መሠረት ነው። የመጀመሪያው ቁጥር 2090(1) በመደቡ በጉዳቱ ምክንያት ተብዳዩ የሚካሠው ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ኪሣራ በመክፈል እንደሆነ የሚገልጽ ሲሆን ቁጥር 2091 ደግሞ ለደረሰው ጉዳት አላፊ መሆኑ በሕግ የታወቀው ሰው የሚከፍለው የጉዳት ካሣ አላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋራ እኩል ሆኖ መመዛዘን እንዳለበት የሚደነግግ ነው። ቀጥሎ ያለው ቁጥር 2092 ሲታይ ለወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተው ጉዳት የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ እስኪፈፀም ድረስ ሣይጠበቅ ካሣ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን ያስረዳል። ከዚህ ሌላ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2102(1) ላይ የሠፈረውን ድንጋጌም ስንመለከት ስለጉዳቱ ምን ያህል ኪሣራ እንደሚከፈል በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ዳኞች የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎችንና ተጉጂውም ያደረገውን ጥንቃቄ አመዛዝነው በመገመት የኪሣራውን ልክ በርትዕ እንዲወስኑ የሚፈቅድ ነው።

በዚህ መዝገብ በቀረበው ጉዳይ የጉዳት ካሣው መጠን ስለመብዛት አለመብዛቱ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲመረመር በተጉጂው በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመኪና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግጭት በደረሰው አደጋ ምክንያት አንድ እግሩ ሊቆረጥ መቻሉ ከአደጋው በፊት እየሰራ ሲያገኝ የነበረውን ገቢ ያስቀረበት መሆኑ ብቻ ሣይሆን ወደፊት የሚኖረውን የኢኮኖሚ እድገት እንደሚጐዳው ይገመታል። በነበረው ሥራ በመቀጠል ወይም በሌላ ሙያ በመሰማራት የራሱን የገቢ ምንጭ ሊያሻሽልና ሊያሣድግ ይችላል። በደረሰበት አደጋ የአንድ እግሩ መቆረጥ ደግሞ በዚህ የወደፊት እድሉ ላይ ሁሉ ተጽእኖ ያደርጋል።

ይህ ሁሉ ሲታይ በወቅቱ የ23 ዓመት እድሜ ነበረው የተባለው የአሁኑ ተጠሪ በዋናው መንቀሣቀሻ በእግሩ ላይ የደረሰው ከፍተኛ ጉዳት እና ይኼው ባለው የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ ያስከተለው ጉዳት ተመዛዝኖ በርትዕ ብር 28,800 ካሣ እንዲከፈለው መወሰኑ በሕጉ እይታ በዝቷል ለማለት አይቻልም። የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ቀርቦለት በነበረው ክሥ መነሻ ጉዳዩን መርምሮ የጉዳት ካሣ ብር 16.000 እንዲከፈለው ከወሰነ በኋላ በይግባኝ ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች መከላከያ መልስ እና ማሥረጃ አቅርቦ ክርክርና ማሥረጃው ከተጠናቀቀ በኋላ መወሰን አለበት ብሎ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩን ከመለሰለት በኋላ ከሣሹ የአሁኑ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91(1) መሠረት ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ ተፈቅለት በአዲስ መልክ ክርክሩ ተካሂ በመጨረሻ በሰጠው ውሣኔ የካሣውን መጠን ከፍ አድርጉ በመወሰኑ ተፈጽሚል የምንለው የሕግ ስህተት የለም። ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶ ከተላከ ፍ/ቤቱ በመጀመሪያው ውሣኔ ሣይገደብ የካሣውን መጠን ዝቅ ወይም ከፍ አድርጉ ከመወሰን የሚከለክለው ሕግ የለም።

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ በኃላፊነቱ ጉዳዩም ሆነ በካሣው መጠን አወሳሰን ረገድ ተፈጽሚል የሚባል የሕግ ስህተት አልተገኘም።

ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በይ/መ/ቁ.3144, ግንቦት 19 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል።
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 18581

ህዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
3. ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
5. አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- በአ/አ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጣቢያ

ተጠሪ፡- ሲ/ር ቀቡላ ከድር

የስራ ውል መቋረጥ፣ የካሣ፣ አስፋፊል እና የስንብት ክፍያ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 23/1/፣ 43/3/፣ 40/1/2፣44

የፊደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ብተተጠሪ እስከ 6 ወር የሚደርስ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ስራ ትመለስ በማለት ውሳኔ በመስጠቱና የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በማፅናት ሆኖም የ3 ወር ውዝፍ ደመወዝ ብቻ ይከፈላት ሲል ውሳኔ መስጠቱን ተከትሎ የቀረበ አቤቱታ

<u>ውሳኔ</u>፡- የፊደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ተሽሯል።

1. በአዋጁ የሥራ መልቀቂያ አለማቅረብ የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያት አይደለም።
2. የሠራተኛው የስራ ውል ቀጥሎ ወደ ስራ ቢመለስ በአሰሪው ድርጅት ህልውና ላይ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ሠራተኛው ህጋዊው ካሣ ተከፍሎት ከስራ ይሠናበታል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ.18581

ህዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ሆሣዕና ነጋሽ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፦ በአ/አ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጣቢያ ጠበቃ መሐመድ ሲራጅ

ተጠሪ፦ ሲ/ር ቀቡላ ከድር ቀረቡ።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 30985 ጥር 24 ቀን 1997 ዓ.ም ተጠሪ የሶስት ወር ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ ትመለስ ሲል በሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተሰርቷል በማለት ነው።

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው። ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው በአመልካች ድርጅት በነርስነት በማገልገል ላይ እያለሁ መልቀቂያ አላመጣሽም በሚል ያለአንዳች ጥፋትና ማስጠንቀቂያ የሥራ ውሌን ስላቋረጠ ደመወዜ ተከፍሎ ወደ ሥራ እንድመለስ፣ የማልመለስ ከሆነ በአንቀጽ 42(4)(ሀ)፣ በ39፣ በ38 እና በ35(1) መሠረት ሙሉ ካሣ የስንብት ክፍያ ክፍያው ለዘገየበት የ1 ወር የማስጠንቀቂያ ሁለት ወር ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት ነው።

የአሁን አመልካች በስር ፍ/ቤት ቀርቦ የበኩሉን ክርክር አድርጓል። በመልሱም ተጠሪዋን ያሰናበተው መልቀቂያ ልታመጣ ባለመቻሏ እንመልቀቂያ የሌላቸውን ባለሙያዎች እንዳይቀጠሩ ደግሞ የክልሉ ጤና ቢሮ መመሪያ እንዳወጣ፣ መልቀቂያ እንድታሚላ ማስጠንቀቂያ እንደሰጣት፣ የተጠሪ ሥራ ላይ መቆየት ደግሞ የጤና ጣቢያ የሙያ ፈቃድ ሊያስጥቅና ድርጅቱንም ሊያዘጋ በሚችል ደረጃ ላይ በመድረሱ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 26(1) መሠረት ውሉ የሚቋረጥበት ሁኔታ በመፈጠሩ ስለሆነ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል።

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም መመሪያው በአዋጅ ቁጥር 42/85 በተደነገጉት የሥራ ውል ማቋረጫ ምክንያቶች ውስጥ ሊሸፈን የማይችል የሥራ ማሰናበቻ ምክንያት አይደለም። በአዋጁም ወደፊት ሚ/ር መ/ቤት በመመሪያ የሥራ ውል ማቋረጫ ምክንያቶች ሊደነግግ ይችላል አልተባለም። መመሪያው ከአዋጁ ያነሰ ሲሆን ከአዋጁ ይጋጫል። ከአዋጁ ሣይጋጭ ሊተገበር የሚችለው መልቀቂያ ያላገኘ ሠራተኛ መልቀቂያውን እንዲያገኝና እንዲሠራ አሠሪው ትጋትና ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ መልቀቂያ ያላቸውን እንዲቀጥር ለማሳሰብ እንጂ የተቀጠሩትን ማሰናበቻ አይሆንም። ስለዚህ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ብሎ እስከ ስድስት ወር የሚደርስ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ እንድትመለስ ወስኗል።

የአሁን አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቧል። ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ወደ ሥራ መመለሱን ጥያቄ በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን በማጽናት የወሰነ ሲሆን ደመወዙን ግን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን በማሻሻል የ3 ወር ደሞዝ እንዲከፈላት ወስኗል።

አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች የሕግ ስህተት ተሰርቷል ሲል የካቲት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በመፃፍ ባቀረበው ማመልከቻ የሚያቀርባቸው ክርክሮች፤

- ተጠሪ የሥራ መልቀቂያ ማስረጃ ሣይኖራቸው በጤና ጣቢያችን መሥራታቸው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መመሪያ ተደነገገውን ክልከላ የሚቃረን በመሆኑ በድርጅታችን ላይ የተደቀነውን የመዘጋት አደጋ ለመከላከል፣ የሥራ ውላችንን ለማቋረጥ መሠረት ያደረግነውን ከአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 26(1) የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግለጽ ባልሆነ ምክንያት በዝምታ በማለፍ፣ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ደግሞ በዝምታ መታለፉን ካለማረሙም በላይ፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን መመሪያ የክልከላ ሕግ ድፍን ባለ ሁኔታ ተጠሪን አይመለከትም በማለት መመሪያውን በመጣስ ውሣኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት ስለሆነ፣ ሰበር ሰሚው ችሎት፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- አንቀጽ 26(1) በዝምታ መታለፍ የሌለበት መሆኑን፣
- የክልከላው ድንጋጌ ከአዋጅ 42/85 ጋር የማይቃረን መሆኑንና መጣስ ሌለበት መሆኑን፣ በሰበር አርሞልን የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ እንዲሽርልን
- በአዋጅ ቁጥር 42/85 ስለ ውዝፍ ደመወዝ የተወሰነ ነገር የለም እንጂ ቢኖር ኖሮ ትክክለኛ ቦታው በሕገወጥ መንገድ ውሉ ስለተቋረጠበት ሠራተኛ ልዩ ልዩ ክፍያዎች የተደነገገበት አንቀጽ 43 ሆኖ ሳለ ስለመደበኛ ደመወዝ አከፋፈል የሚደነግገውን ከውዝፍ ደመወዝ ጋር ግንኙነት የሌለውን አንቀጽ (54)ን በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤቶች ያስተላለፉት የውዝፍ ደመወዝ ውሣኔ የሕግ ትርጉም ስህተት ስላለበት ስህተቱ ታርሞ ውሣኔውን ውድቅ እንዲያደርግልን። የሚሉ ናቸው።

አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ ታዞ ተጠሪዋ መልስ እንድትሰጥ በታዘዘው መሠረት ሰኔ 3 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርባለች። ዋና ዋና ክርክሮቹም፣

- መመሪያው በይግባኝ ባይ ላይ ግዴታ የሚጥለው መልቀቂያ የሌለው የጤና ባለሙያ እንዳይቀጠር ነው። ይግባኝ ባይ መመሪያውን በመጣስ ከተጠሪ ጋር የቋሚነት የሥራ ውል ከመሠረተ በኋላ ግን የሚገዛው በመመሪያ ሣይሆን በአሠሪና ሠራተኛ በአዋጅ ቁጥር 42/85 ነው። አዋጁ የሚቃረን ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች አዋጁን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ እንደማይሆን በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 192(2) ስር ተደንግገዋል።

- ይግባኝ ባይ የአዋጁን አንቀጽ 26(1) መሠረት አድርጎ ተጠሪን ከሥራ ማሰናበቱን ጠቅሶ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች ይህንን ክርክርን በዝምታ እንዳለፉት በመጥቀስ ተከራክሯል። ይህ አንቀጽ በውስጡ የሥራ ውል ከሠራተኛው በሆነ ምክንያቶች ወይንም ከድርጅቱ ድርጅታዊ አቋም ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ባላቸው ምክንያቶች የሥራ ውል ሊቋረጥ እንደሚችል ይደነግጋል። ይሁንና እነዚህ ሁኔታዎች ምን ማለት እንደሆኑ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 27 እና 28 በግልጽ ተደንግገዋል። በዚሁ መሠረት በአንቀጽ 26(1) ከድርጅቱ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የሥራ ውል መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ካሣ ተከፍሉ የማሠናበቱ አማራጭ የሚወሰደው ከሥራ ግንኙነቱ ጠባይ የተነሣ የሥራ ግንኙነታቸው ቢቀነስ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል ሲሆን ነው። አመልካች የጤና ጥበቃ ሚ/ር መመሪያን ባለማክበር መልቀቂያ የሌላት ባለሙያ በመቅጠሩ ከክልሉ ጤና ቢሮ እርምጃ ሊወሰድበት እንደሚችል ተነግሮታል። እርምጃውም ፍቃዱን ሰርዞ ክሊኒኩን እስከማዘጋት ሊደርስ እንደሚችል ተገልጸለታል። ይህም የተጠሪ የሥራ ውል ቢቀጥል ለድርጅቱ ህልውና አስጊ ሊሆን እንደሚችል ያመላክታል። በሌላም በኩል ለድርጅቱ መዘጋት ምክንያት ልትሆን ትችላለች ከሚላት ተጠሪ ጋር የሥራ ውል እንዲቀጥል ቢደረግ ግንኙነታቸው ጤናማ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ሕጉ የሰጠውን አማራጭ በመከተል የሥራ ውሉ ተቋርጦ ካሣ ተከፍሏት እንድትሰናበት ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል።

የስንብት ክፍያን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 39(1) የሙከራ ጊዜውን የጨረሰና በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ከአሠሪው የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል። እንዲሁም የሥራ ውሉ ከሕግ ወጪ ተቋርጦ ሆኖም ለአዋጁ ቁጥር 43/1/2/3/ መሠረት ወደ ሥራው የማይመለስ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ እንደሚገባው በአዋጁ ቁጥር 43(4) ላይ ተመልክቷል። አመልካቹም የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብኝም የሚል ክርክር የለውም። በመሆኑም ተጠሪ ከላይ በተገለፀው ሕግ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ ልታገኝ ይገባል።

የማስጠንቀቂያ ክፍያን በተመለከተ የአዋጁ ቁጥር 43/4/ሀ/ እና 44 ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ አሠሪው በአንቀጽ 35 ስለማስጠንቀቂያ የተጠቀሱት ሳያሟላ ሠራተኛውን ከሥራ ካስወጣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል እንደሚገባ ያስገነዝባል። በዚህ ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ የሰጣት ለመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተመልክቷል። ተጠሪዋ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠኝም ስትል ያቀረበችውም ማስተባበያ የለም። በመሆኑም አመልካች በሕግ የተጣለበትን ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታውን የተወጣ ስለሆነ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ሊከፍል አይገባም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማዘግየት ክፍያ ጥያቄ ስንመለከት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሠራተኛው ደመወዝ ከደመወዙ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ መከፈል እንዳለባቸው የአዋጁ ቁጥር 36 ይደነግጋል። ሠራተኛው ከአሠሪው የተረከበውን ንብረት የማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማናቸውም ሂሣብ በማወራረድ የራሱ ጥፋት በሆነ ምክንያት ካዘገየ ግን ክፍያው ሊራዘም እንደሚችል ይኸው አንቀጽ ይናገራል። በቁጥር 36 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሠራተኛው መከፈል የሚገባውን ሂሣብ ያልከፈለ አሠሪ ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ ለሠራተኛው ደመወዝ እንደሚከፍለው በቁጥር 38 ተደንግጓል።

በዚህ ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ይገባታል የሚለውን ክፍያ ለመክፈል ዝግጁ እንደነበር ተጠሪ ግን ተጨማሪ ክፍያ በመፈለግ ክፍያውን ለመቀበል ፍቃደኛ እንዳልሆነች በስር ክርክሩ ገልጿል። ይህ ክርክር በተጠሪ በኩል የተስተባበለ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት አልተዘገበም። በሌላም በኩል የተጠሪ ዋና ክርክር ወደ ሥራ መመለስ ነው። የልዩ ልዩ ክፍያዎች አማራጭ በ2ኛ ደረጃ የቀረበ ነው። ከዚህም አኳያ ተጠሪ ክፍያው ተቀብሎ ለመሰናበት ፍቃደኛ እንዳልነበረች ለመገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም በነዚህ ምክንያቶች ክፍያው የዘገየው በአሠሪው ጥፋት ነው ለማለት ስለማይቻል አመልካች የመዘግየት ክፍያ መክፈል የለበትም።

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ላልተሠራበት ጊዜ ደሞዝ ሊከፈል እንደማይገባ የሰበር ችሎት በመዝ/ቁጥር 17/89 አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን አንቀጾች የተረጎመ ስለሆነ ተጠሪ ያቀረበችው የውዝፍ ደሞዝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም።

ው ሣ ኔ

1. የሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ መሆኑን በማረጋገጥ የሰጡት ውሣኔ ይህም ችሎት ተስማምቶበታል።
2. የተጠሪ ወደ ሥራ መመለስ በአመልካቹ ህልውና ላይ ችግር ሊያስከትል ስለሚችል ይህም የግራ ቀኙን ግንኙነት ጤናማ ስለማያደርገው ተጠሪዋ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 43(3) መሠረት ካሣ ተከፍሏት እንድትሰናበት ተወስኗል። እንዲሁም የስንብት ክፍያ እንዲከፈላት ተወስኗል:
3. የካሣውን መጠን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 43(4)(ሀ) መሠረት ተሰልቶ እንዲከፈላት ተወስኗል። የሥራ ስንብት ክፍያም በአዋጁ ቁጥር 40/1/እና /2/ መሠረት ተሠልቶ እንዲከፈላት ተወስኗል።
4. የፌዴራል መጀመሪያና የከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁጥር 5984 እና 30985 ተጠሪዋ ወደ ሥራ እንድትመለስ የሰጡት ውሣኔ ወደ ሥራ መመለሷ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ባለማገናዘብ በመሆኑ ውሣኔዎቹን

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር.348(1) መሠረት በድምጽ ብልጫ ተሽሯል። መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ። የውሣኔዎቹን ግልባጭ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይተላለፍ። ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት።

<u>የሐሣብ ልዩነት</u>

እኔ ስሜ በሁለተኛ ተራ የተመለከተው ዳኛ ከላይ በተመለከተው በአብዛኛው ድምጽ ፍርድ ስለአልተስማማሁ የሚከተለውን የሐሣብ ልዩነት አስፍሬያለሁ።

ሠራተኛዋ ከአሰሪዋ ጋር ባላት የሥራ ግንኙነት የተፈጠረ ችግር አለ አልተባለም፤ ችግር አለ የተባለው አሰሪዋ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር ባለው ግንኙነት ነው፤ ችግሩም አሰሪው ሠራተኛዋን ካላሰናበተ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እርምጃ ይወስድባታል የሚል ነው፤ እንደተባለው ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአሰሪው ላይ እርምጃ ሊወስድበት እርምጃውን በሕጉ መሠረት መከላከል እንጂ፣ ሚኒስቴሩ እርምጃ ሊወስድበት ይችላል ተብሎ፣ የአዋጅ አንቀጽ 43/3/ ከሚለው ውጭ ሠራተኛዋ ወደ ሥራዋ እንዳትመለስ በመወሰኑ በሃሣብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ሐጐስ ወለዱ
3. አቶ ዳኜ መላኩ
4. አቶ አሰግድ ጋሻው
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካቾች፡- 1ኛ. የሻረግ መንግሥቱ
2ኛ. ሰገዴ መንግሥቱ

ተጠሪ፡- እማሆይ የሻረግ ፈረደ

ስለ ይርጋ - የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነው ጊዜ - የይርጋ ጥያቄ በፍርድ ቤት ተቀባይነት የማይኖርበት ሁኔታ - የፍ/ብ/ህ/ቁ 10001/2/፣ 1168፣ 1845፣ 1853

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ተጠሪዋ የሚች አባታችን የአቶ መንግሥቱ ዘወልዴን ቤት ሊያስረክቡን ይገባል በማለት ያቀረቡትን ክስ መርምሮ የሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የጎንደር ወረዳ ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ያፀናውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ዉሳኔ</u>፡- በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

1. ውሎች ንብረትን በተመለተ በ1675 መሠረት የሚደረግ ስምምነት በመሆኑ በዚሁ መሠረት ትርጉም የሚሰጠው የውል ሰነድ ሳይኖር በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845ን በተመለከተ የሚሰጥ ውሳኔ የለም፡፡
2. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለዕጅ /ባለይዞታ/ የሆነ ሰው የዚሁኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ 15 ዓመት ከከፈለ ሌላ ይገባኛል የሚል ሰው እንዲሰጠው ሊጠይቀው አይችልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጐስ ወለዱ

3. ዳኜ መላኩ

4. አሰግድ ጋሻው

5. ሂሩት መለሰ

አመልካቾች፡- 1ኛ. የሻረግ መንግሥቱ

2ኛ. ሰገዴ መንግሥቱ

ተጠሪ፡- እማሆይ የሻረግ ፈረደ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 364 በይግባኝ ደረጃ ቀርቦለት በነበረው ጉዳይ ሲያከራክር ቆይቶ የካቲት 16 ቀን 1996 ዓ/ም መረምሮ የሰሜን ጐንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የአሁኑ አመልካቾች ተጠሪዋ የሟች አባታችን የአቶ መንግሥቱ ዘወልዴን ቤት ሊያስረክቡን ይገባል በማለት ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔው ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የጐንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ክሱ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 /1/2/ እና 1845 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል የወሰነው በሕጉ አግባብ ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

አመልካቾች አባታችን አቶ መንግሥቱ ዘወልዴ ከሞቱ በኋላ በውርስ ሊተላለፍልን የሚገባውን ቤት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት ተረክበን ተጠሪዋ ባይወልዱንም እናታችን ናቸው ብለን በማሰብ እንዲቀመጡበት ያደረግነውንና በአክብሮት ሣንጠይቃቸው የቆይነውን ንብረት እንዲያስረክቡን በማለት ያቀረብነው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በሚል ለሰበር አቤቱታ አቅርበዋል። አመልካቾች ንብረቱን ሣንጠይቅ የቆየነው በቤተዘመድ ግንኙነት ምክንያት ተጠሪዋን በመፍራትና በማክበር ስለሆነ ፍ/ቤቱ የይርጋውን ክርክር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853/1/ መሠረት ሊቀበለው አይገባም ባዮች ናቸው።

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ በአመልካቾች በኩል የቀረበው ማመልከቻ ለአሁኗ ተጠሪ እንዲደርሳቸው ተደርጐ ሐምሌ 18 ቀን 1996 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካቾች በበኩላቸው የመልስ መልስ ሰጥተውበት ተከራክረዋል።

በተጠሪዋ በኩል የቀረበው ክርክር ሲታይ አመለካቾች እኔን የእንጀራ እናታቸውን በማክበርም ሆነ በመፍራት መብታቸውን ሣይጠይቁ ቆይተዋል ሊባል ስለማይችል ፍ/ቤት ይርጋ አልቀበልም የሚልበት ምክንያት የለም የሚል ይዘት ያለው ነው።

ችሎቱም የአሁኑ አመልካቾች ከ1962 ዓ/ም በፊት የሞቱትን የአባታችንን ቤት ይዘው የሚገኙት የአሁኗ ተጠሪ ሊያስረክቡን ይገባል በሚል ያቀረቡት ክሥ በይርጋ ቀሪ ሆኗል አልሆነም፣ ፍ/ቤት ይርጋ አልቀበልም የሚልበት የሕግ ምክንያት አለ ወይንስ የለም የሚለውን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የጐንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካቾች ከአባታችን በውርስ ሊተላለፍልን የሚገባውን ቤት የአሁኗ ተጠሪ ምንም አይነት መብት ሣይኖራቸው ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆን ይዘው ስለሚገኙ ሊያስረክቡን ይገባል በሚል ያቀረቡትን ክስ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት በአሥር አመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ሊወሰኑ የቻሉት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም ተደርጓል የተባለውን ውል መነሻ በማድረግ ነው። ከሰነዱ እንደሚታየው ግን ቤቱን የአሁኗ ተጠሪ ለቀው ለሚቹ ለአቶ መንግሥቱ ዘውልዴ ወራሾች ማሥረከባቸው እና ሌሎችን ንብረቶችም ስለመከፋፈላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ከመገለጹ በቀር የሟቹ የአባታቸው ሚስት በቤቱ እየተጠቀመበት ይቆዩ ወይም ይኑሩበት የሚል ነገር የለውም። ከዚህ ሌላ ቤቱ በሟች ሚስት ይዞታ ሥር ቆይቶ ወደፊት በዚህ ጊዜ ለወራሾች ያስረክባሉ የሚል የውል ቃል የለውም። በሰነዱ ላይ የሰፈረው በሕግ የውል ትርጉም የሚሰጠው አይደለም። ውል ማለት ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1675 ላይ እንደተመለከተው ንብረታቸውን የሚመለከቱ ግዴታቸውን ለማቋቋም ወይም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ባላቸው ተወዳዳሪ ግንኙነት በሁለት ወይም በብዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ሥምምነት ስለሆነ በዚሁ መሠረት የውል ትርጉም የሚሰጠው ነገር ሣይኖር ውል አለ የሚል መነሻ በመያዝ ይርጋን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው ስለውሎች በጠቅላላው በሚለው የፍትሐብሔር ሕጉ ክፍል ተጽፎ የሚገኘው በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 ላይ የተመለከተው የአሥር አመት ጊዜ ነው ብሎ መወሰን ትክክል አይደለም። በአሁኑ አመልካቾች በኩል የቀረበው የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም የተፃፈው ሰነድ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ጋራ በተያያዘ የሚያስነሣው የይርጋ ጥያቄ ስለሌለ በዚህ ጉዳይ የተጠቀሰው የይርጋ ሕግ አግባብነት የለውም።

በሌላም በኩል የአሁኗ ተጠሪ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ሲከራከሩ የነበሩት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም ተፃፈ የተባለውን ሰነድ መነሻ በማድረግ ብቻ ሣይሆን ቤቱ ከ1943 ዓ/ም ጀምሮ ባለማቋረጥ ግብር እየከፈልኩበት ንብረቴ ሆኗል፣ ከሃያ ሰባት አመት በላይ በስሜ ስገብርበት ቆይቼ የቤቱ የቦታ ይዞታም ሆነ የቤቱ ባለቤትነት ሥም በሥሜ ሊሆን ችሏል በሚል ምክንያት ጭምር ሲሆን እነዚህ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሆናቸውን ከመዝገቡ ለመረዳት ተችሏል። ከእነዚህ ፍሬ ነገሮች በመነሣት በሕጉ በኩል ያለው ሲታይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168/1/ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለእጅ /ባለይዞታ/ የሆነ ሰው የዚሁኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ 15 ዓመት በሥሙ ከከፈለ የዚሁ ሀብት ባለቤት ይሆናል በሚል ደንግጐ ይገኛል። ሕጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ይርጋ አዘል ስለሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለእጅ /ባለይዞታ/ የሆነው ሰው የዚህን ንብረት ግብር ባለማቋረጥ ለ15 ዓመት በሥሙ ከከፈለ ሌላ ይገባኛል የሚል ሰው እንዲሰጠው ሊጠይቀው አይችልም፡፡ በሕጉ ለባለይዞታው መብቱ ይረጋለታል፡፡ የአሁኗ ተጠሪም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ባለይዞታ በመሆን የዚሁኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ ከ15 ዓመት በላይ በሥማቸው ሲከፍሉ ስለቆዩ በሕጉ የዚሁ ሀብት ባለቤት ሆነዋል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች አባት ከ1962 ዓ/ም በፊት የሞቱ ስለሆነ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በተጠሪዋ ይዞታ ሥር የቆየውን ቤት ከሃያ ስምንት አመት በኋላ እንዲያስረክቧቸው ያቀረቡት ክሥ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በሚል የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

አመልካቾች ክስ ሣናቀርብ የቆየነው ተጠሪዋ የሚቹ አባታችን ሚስት በመሆናቸው በመፍራትና በማክበር በመሆኑ ፍ/ቤት ይርጋውን ሊቀበለው አይገባም በሚል ያነሱትን ክርክር በተመለከተም በእርግጥ ፍ/ቤት ይርጋን አልቀበልም የሚልባቸው ምክንያቶች አሉ፡፡ እነዚህ ምክንያቶች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 የተዘረዘሩት ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ባለገንዘቡ የሚፈልገውን ያልጠየቀበት ምክንያት ባለዕዳውን የመፍራትና የማክበር ስሜት መኖር አንዱ ነው፡፡ አመልከቾች ከሃያ ስምንት አመት በላይ ተጠሪዋ ቤቱን እንዲያስረክቡን ሣንጠይቅ የቆየነው የአማታችን ሚስት ስለሆኑ እንደ እናት ስለምናያቸው የመፍራትና የማክበር ስሜት አድሮብን ነው ይበሉ እንጅ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመለካቾች አባታቸው ከሞቱ በኋላ የአባታችንን ንብረት አካፍይን ወይም አስረክቢን የሚል ጥያቄ አንስተው ሽማግሌዎች ሰብስበው የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም በተፃፈ ሰነድ በተደረገ እርቅ ንብረት መከፋፈላቸው መገለጹና በዚሁ ሰነድ አማካኝነት ቤቱን ተረክበን ነበር ማለታቸው ሲታይ ከዚህ በኋላ ሣይጠይቁ የቆዩት ተጠሪዋን በመፍራትና በማክበር ምክንያት ነው ለማለት አይቻልም በሚል ሣይቀበላቸው ቀርቷል፡፡ በአመልካቾች በኩል ተጠሪዋን የመፍራትና የማክበር ስሜት ነበረ አልነበረም ለሚለው ፍ/ቤት መፍራትም ሆነ ማክበር አልነበረም የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሰ ወደ ፍሬ ነገር ጥያቄ ስለሚያመዝን በሰበር ደረጃ ሊመረመር አይችልም፡፡ በሰበር ደረጃ ሊታይ የሚችለው የሥር ፍ/ቤት የመፍራትና የማክበር ስሜት መኖሩን አረጋግጦ ይርጋን አልቀበልም ለማለት የሚያስችል የሕግ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም በሚል ወስኖ ቢገኝ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ሕግ ቀሪ መሆኑ ቢረጋገጥም ፍ/ቤት ይርጋውን አልቀበልም የሚልበት የሕግ ምክንያት አለ በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የካቲት 8 ቀን 1962 ዓ/ም በተፃፈው ሰነድ በአመልካቾችና በአሁኗ ተጠሪ መካከል ቤቱን በሚመለከት የተደረገ የውል ስምምነት እንዳለ አድርጐ በመመልከት ይህንኑ መነሻ በመድረግ ለተነሣው የይርጋ ጥያቄ የሚመለከተው የይርጋ ሕግ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የአሥር አመት ጊዜ ነው ማለቱ የተሣሣተ ሆኖ ቢታይም ክሱ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 አንፃር ሲመረመር በይርጋ ቀሪ ከመሆን የሚድን ሆኖ ስላልተገኘ በውጤቱ ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ መወሰኑ ተቀባይነት የሚሰጠው ነዉ፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአሁኑ አመልካቾች በኩል የቀረበው ክሥ በይርጋ ቀሪ መሆኑ ስለተረጋገጠ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ደስታ ገብሩ
አቶ መስፍን ፅቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ዩናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ
ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ሞተርና መሐንዲስነት ኩባንያ

ስለ ውል መፍረስ - ህጋዊ ደንብን ያልተከተለ ውል ስለሚፈርስበት ሁኔታ እና የውል መፍረስ በተዋዋይ ወገኖች ላይ የሚያወጣው ውጤት - የፍ/ብ/ህ/ቁ 1716(1)፣ 1815፣ 1816 እና 1817

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ከፈረሠ በኋላ ገንዘቡ ለአመልካች ተመልሶ በመንግስት የተወረሰችዉ መኪና ወደ ጅቡቲ ትመለስ በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የወሰነውን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ::

<u>ው ሳ ኔ</u> :- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ጅቡቲ ትመለስ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተሸሯል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል::

-ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በሓላ ተዋዋዮች ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ የሚወሰነው በውሉ ምክንያት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ነው::::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ደስታ ገብሩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ዩናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ

ተጠሪ፡- የኢዮጵያ ሞተርና መሐንዲስነት ኩባንያ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የጀመረው የአሁን አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪው ላይ ባቀረበው ክሥ መነሻ ነው፡፡

የክሱ ፍሬ ነገር ከሣሽ ላንድክሩዘር መኪና ለመግዛት ፈልጎ ተከሣሽን የመሸጫ ዋጋ ጠይቆ ጥያቄው በተከሣሽ ተቀባይነት በማግኘቱ ተከሣሹ ባቀረበው የመኪና መሸጫ ዋጋ ተስማምተው ከሣሽ ገንዘቡን የከፈለ መሆኑን፤ ነገር ግን መኪናዋ በተከሣሽ ላይሰንስ ጉምሩክ መጋዘን ከገባች በኋላ መኪናዋ በሕገወጥ መንገድ ስለገባች ማውጣት አትችሉም ሲል ጉምሩክ ስለከለከለ ውሉ ውድቅ ሆኖ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሣሽ የአሁን ተጠሪም ቀርቦ ከተከራከረ በኋላ ፍ/ቤቱ ውሉ የተደረገው ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡት ዕቃዎች ሐምሌ 12/1988 ከወጣው ደንብ በኋላ የተደረገ ስለሆነ፤ ውሉም ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1716/1/ መሠረት ፈራሽ ነው፡፡

ውሉ ፈራሽ ነው ከተባለ ደግሞ ውጤቱ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁጥር 1815/1/ ስለሚደነግግ በክሥ አቤቱታው ላይ የተመለከተውን ብር 177,184.23 /አንድ መቶ ሰባ ሠባት ሺህ አንድ መቶ ሠማንያ አራት ብር ከሃያ ሦስት ሣንቲም/ የኢትዮጵያ ብር ወይም 26037.36 /ሃያ ስድስት ሺህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሠላሣ ሰባት ብር ከሠላሣ ስድስት ሣንቲም/ የአሜሪካን ዶላር ተከሣሽ ለከሣሽ ይክፈል፣ ዳኝነት በታሪፉ ልክ፣ የጠበቃ አበል 15% ልዩ ልዩ ወጪ 100 /አንድ መቶ ብር/ ጨምሮ ለከሣሽ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪም በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ ፍ/ቤቱ የይግባኙን ክርክር መርምሮ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል በማጽናት ነገር ግን ውሉ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ይመለሱ ሲባል ከሣሽ ለመኪናው የከፈለው ገንዘብ ይመለስለት ማለት ሲሆን፤ ተከሣሹም ከውሉ በፊት ወደነበረበት ሁኔታ የሚመለሰው በውሉ ምክንያት ከጅቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው መኪና ወደ ጅቡቲ ሲመለስለት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት አንዱን ወገን ወደነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ አድርጎ ሌላውን ወገን ባለበት ሁኔታ በመተው የሰጠውን ውሣኔ አሻሽለን ከላይ በተገለፀው ሁኔታ ወደነበረበት ይመለሱ ሲል ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ የሥር ከሣሽ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ሲያቀርብ ተከሣሹም መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቧል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ዋናውን ይግባኝ በተመለከተ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር መሠረት የለውም በማለት፤ መስቀለኛ ይግባኙም በሥር ፍ/ቤቶች ተመሣሣይ ውሣኔ የተሰጠበት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 መሠረት በይግባኝ ደረጃ ሊታይ አይችልም በማለት መዝገቡን ዘግቶ መልሶለታል፡፡

እንግዲህ የሥር ከሣሹ ማለትም የአሁን አመልካች በ25/8/96 ጽፎ ያቀረበው የሠበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መኪናዋ ወደ ጅቡቲ ትመለስ የሚለው ተጨማሪ የውሣኔ ክፍል አፈፃፀሙን የተወሣሠበ ስላደረገውና የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ማረም ሲገባው ማለፉ ሥነ ሥርዓትን የሚቃረን በመሆኑ ይህ ተሻሽሎ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ ይፀናልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የማመልከቻ ግልባጭ ለተጠሪው ደረሶ ጥር 19/1997 ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካቹ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ውሣኔ ከሰጠ በኋላ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ለከፍተኛ ፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸው በውሣኔው እንደተስማሙበት የሚቆጠር ነው ለዚህ ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን አላሣዩም፣ ውሉ ሊፈርስ ይገባዋል ሲባል ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ሁኔታ ይመለሱ መባሉም ትክክል ነው አመልካች መኪናውን አልተረከቡም ለሚሉት አስቀድሞ ያለቀለት ክርክር ስለሆነ አሁን ሊነሣ አይገባውምና አቤቱታው ተሠርዞ ተገቢው ኪሣራ ተቋርጦልን እንሠናበት በማለት የተከራከረ ሲሆን አመልካችም አቤቱታውን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ከፍ ብሎ በዝርዝር የተመለከተው ሲሆን ውሣኔ ሊያገኝ የሚገባው ጭብጥ፤ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው የመኪና ሽያጭ ውል ፈርሶ ወደነበሩበት ይመለሱ ሲባል ለአመልካቹ ገንዘቡ እንዲመለስለት ብቻ ሣይሆን ከጅቡቲ ወደብ መጥታ ጉምሩክ መጋዘን ገብታለች የተባለችውም መኪና ወደ ጅቡቲ መመለስ አለባት ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው? አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው የመኪና ሽያጭ ውል እንዲፈርስ በሥር ፍ/ቤቶች በተሠጠው ውሣኔ ላይ አቤቱታ ያልቀረበበት ስለሆነ ይህን ነጥብ መመርመሩ አስፈላጊ አይደለም፡፡ የተጠሪው ክርክር ውሉ ይፍረስ ከተባለ ውጤቱ በፍ/ሕግ ቁጥር 1815/1/ መሠረት ተዋዋዮች ወደነበሩበት ይመለሣሉ ስለሚል በዚህ ሁኔታ መመላለስ ስለአለብን የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሹ ገንዘቡን እንዲያገኝ ከተወሰነ መኪናዋም ወደጅቡቲ እንድትመለስ መወሰኑ ተገቢ ነው ሲል አመልካች በበኩሉ መኪናዋ ወደ ጅቡቲ ትመለስ ከተባለ ውሣኔው ሊፈፀም የማይችል ይሆናል ባይ ነው፡፡

አከራካሪዋ መኪና ከጅቡቲ ወደብ መጥታ ጉምሩክ መጋዘን ከገባች በኋላ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ገብታለች ተብሎ ጉምሩክ ለከሣሽ ሊሰጥ አለመቻሉንና በዚሁ ምክንያት በመንግሥት ስለመወረሷ ራሱ የሥር ተከሣሽ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ካቀረበው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡

እንግዲህ ምንም እንኳን የፍ/ሕ/ቁጥር 1815/1/ አንድ ውለታ ሲሠረዝ ወይም ሲፈርስ ተዋዋዮችን በተቻለ መጠን ውለታው ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚደነግግ ቢሆንም መኪናዋ ለመንግሥት በውርስ የገባች መሆኑ እየተረጋገጠ ወደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ጅቡቲ ትመለስ ተብሎ መወሰኑ የተሠራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ ደግሞ የፍ/ሕግ ቁጥር 1816 እና 1817 የፍ/ሕ/ቁጥር 1815 ልዩ ሁኔታ (exceptions) ሆነው መፍትሄ ይሰጣሉ፡፡

ይኸውም በተለይ ለዚህ ጉዳይ ተጠቃሽነት ያለው የፍ/ሕ/ቁጥር 1817/1/ ... የተሠራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆነ ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከፍ ያለ መሠናክል የሚያመጣ ሲሆን የተሰሩት ሥራዎች እንደረጉ ይቀራሉ ይላል፡፡

ይሁንና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ድንጋጌ በሚቃረን ሁኔታ መኪናዋ በመንግሥት መወረሱን እየተረዳ ወደ ጅቡቲ ትመለስ ሲል የሰጠው የውሣኔ ክፍል መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህን ሥህተት እንዲያርም የቀረበለትን ይግባኝ ያለመቀበሉ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 11936 ጥር 26/96 በዋለው ችሎት ዋናውን ይግባኝ በተመለከተ የሰጠው የውሣኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ ተሽሯል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 216/94 በ24/7/95 በዋለው ችሎት መኪናዋ ወደ ጅቡቲ ትመለስ በማለት የሰጠውን የውሣኔ ክፍል ብቻ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ ተሽሯል፡፡

የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁጥር 492/90 በ4/11/93 በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት በማጽናት ወስነናል፡፡ የውሣኔው ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይድረሰው መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ/ቁ.16062

ህዳር 19 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ሐጎስ ወልዱ
4. አቶ ዳኜ መላኩ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

መልስ ሰጭዎች፡- ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ

ክውል ውጭ ስለሚደርስ አላፊነት- ካሣ ስለሚጠየቅበት ክስ- ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ - የፍትሐ-ብሄር ህግ ቁጥር 2143/1/፣ 2143/2/

መልስ ሰጭ በአቶ ከበደ ኃይሉ ይሽከረከር የነበረና ንብረትነቱ የአቶ አሊ መሃመድ የሆነ ተሽከርካሪ ሰኔ 5 ቀን 1984 ዓ.ም ባለቤቴን ገጭቶ ገድሏል በማለት እርሷና ሁለት ህፃናት ልጆቿ ተቋርጦብናል የምትለውን ገንዘብ በማስላት ብር 222,000 እንዲከፈላት መስከረም 4 1992ዓ.ም ባቀረበችው ክስ አመልካች ለተሽከርካሪው በሰጠው መድን በጣልቃ ገብነት በመግባት ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143/2/ መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረበውን ክርክር የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ በመስጠቱና ውሳኔውም በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ውሳኔ፡- የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያጸናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. የፍ/ብህ/ቁ.2143 ክውል በሚደርስ አላፊነት የቀለብ ገንዘብ በመጠየቅ በሚቀርብ ክስ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. ሚስት ክውል ውጭ በባሏ ላይ በሚደርስ የሞት ጉዳት የቀለብ ጥያቄ ለማቅረብ ስትል ሚስትነቷን ለማረጋገጥ በፍርድ ቤት የምታቀርበው ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ አያቋርጥም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.16062

ህዳር 19 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነገረፈጁ አቶ አብርሃም ፀጋዬ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ አልቀረበችም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ሊሆን የቻለው የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡

ይኼው ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ.304/92 በቀረበለት ካሳ ጉዳይ ላይ የአሁኑ አመልካች በጣልቃ ገብነት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን አድርጐ ጣልቃ ገቡ በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2143/1/ መሠረት ያቀረበውን የይርጋ ክርክር በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ ግንቦት 21 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በከሣሽ በኩል የቀረበውን ክሥና በግራ ቀኙ መካከል የተደረጉትን የፍሬ ነገር ክርክሮች መርምሮ ከሣሽዋ ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ ባለቤቷ አቶ ሀ/ሚካኤል መርጊያ ንብረትነቱ የአንደኛ ተከሣሽ በሆነው የሰሌዳ ቁጥር 3-17155 መኪና ተገጭቶ በመሞቱ ምክንያት በሚስቱና በሁለቱ ህፃናት ልጆቹ ላይ በቀለብ ረገድ ለደረሰው ጉዳት የመኪናው ባለቤት አንደኛው ተከሣሽ እና መኪናውን ሲያሽከረክር አደጋውን ያደረሰው ሁለተኛው ተከሣሽ በሕግ ኃላፊ ስለሚሆኑ ካሣ ብር 60,000 ሊከፍሉ ይገባል፡፡ ጣልቃ ገብ የሆነው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በበኩሉ ግጭቱን ላደረሰው መኪና በገባው የመድን ዋስትና መጠን ካሣውን መክፈል አለበት የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጣልቃ ገብነት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የተደረገው የአሁኑ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ባለመስማማትና ክሱም በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚል ምክንያት በፍ/ይ/መ/ቁ.03564 ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ መጋቢት 14 ቀን 1996 ዓ.ም መርምሮ በሰጠው ትዕዛዝ ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 መሠረት ይግባኙን በመሠረዝ አሰናብቶታል፡፡

በዚህ መዝገብ ለሰበር አቤቱታ የቀረበውም ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ ጉዳዩን ተመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሚል ሲሆን አመልካች በተነሣው የይርጋ ክርክር ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚልበትን ምክንያት ሰኔ 11 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አብራርቶ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ ተመርምሮ የይርጋው ጥያቄ ከሕጉ አኳያ ተጣርቶ መወሰን የሚያስፈልገው ሆኖ በመታየቱ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻም ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ቀርባ መልስ እንድትሰጥበት ታዞ በ15/4/97 ዓ.ም የተፃፈ መለስ አቅርባለች፡፡ በጽሑፍ ያቀረበችው መልስ ሲታይ ተጠሪ ባለቤቱ በመኪና ተገጭቶ በመሞቱ ምክንያት በክሱ የተጠየቀው የጉዳት ካሣ እንዲከፈል ሣይሆን በቀለብና መተዳደሪያ ረገድ ታስቦ ሊከፈለን የሚገባ ገንዘብ ነው፡፡ ክሱ በጉዳት ካሣ ጥያቄ ላይ ያልተመሠረተ ከሆነ ደግሞ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143/1/ በመጥቀስ የሚያቀርበው የይርጋ ክርክር ሊኖር አይችልም፡፡ ስለዚህ ክሱ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ ሌላ በሚስትነት ጉዳይ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በክርክር ላይ ቆይቼ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠው በ07/07/90 ስለሆነ ክሥ የማቅረብ መብት ያገኘሁት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ደግሞ በ4/1/92 ያቀረብኩት ክሥ ከይርጋ ነፃ ነው የሚሉትን ክርክሮች ያቀፈ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ደግሞ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪ ክሥ ያቀረበችው አደጋው ወይም ጉዳቱ ከደረሰ ከሰባት አመት ቆይታ በኋላ ነው፡፡ የይርጋ ጊዜ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2143/2/ መሠረት ለወንጀሉ ጉዳይ የተወሰነው የይርጋ ዘመን ልክ ይሆናል ከተባለም አደጋውን ያደረሰው ሹፌር የወ/መ/ሕ/ቁ.526/1/ ተጠቅሶ ክሥ ቀርቦበት በብር 1000 የተቀጣ መሆኑ በማሥረጃ ስለተረጋገጠ ለዚህ ወንጀል የተወሰነው የይርጋ ጊዜ ሶስት አመት ብቻ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

ችሎቱም በቀረበው ጉዳይ በዋናነት ሊመረመር የሚገባው ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል አይሆንም? ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ የይርጋው ዘመን ልክ ምን ያህል ነው የሚለው የይርጋ ጥያቄ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመረዳት እንደተቻለው ከሣሽ የሆነችው የአሁኗ ተጠሪ ሁለተኛ ተከሣሽ የሆነው ከበደ ኃይሉ ንብረትነቱ የአንደኛው ተከሣሽ አሊ መሐመድ የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-17155 መኪና እያሽከረከረ ሲንዝ ሰኔ 5 ቀን 1984

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ዓ.ም ባለቤቱ አቶ ሀ/ሚካኤል መርጊያን ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ገጭቶ ገድሎታል በማለት በባለቤቷ መሞት ምክንያት እርሷ እና ሁለት ህፃናት ልጆቹ ቀርቆብናል ወይም አጥተናል የምትለውን ገንዘብ በመግለጽ አስልታ በጠቅላላው ብር 222,000 ተከሣሾች በአንድነት በነጠላ እንዲከፍሏት በ4/1/92 ዓ.ም ተጽፎ እንዲቀርብ ባደረገችው ክሥ ጠይቃለች፡፡ የአሁኑ አመልካች የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በቀጥታ የቀረበበት ክሥ ባይኖርም አደጋውን ላደረሰው መኪና የመድን ዋስትና ሰጥቷል በመባሉ ምክንያት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43/1/ መሠረት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን አመልካችም አደጋውን ላደረሰው መኪና የመድን ዋስትና በተገባለት መጠን ካሣ የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት አምኖ ክሱን በማስመልከት የበኩሉን መልስ ሲሰጥ የይርጋ ክርክር አንስቷል፡፡ በኢንሹራንስ ምክንያት ካሣ እንዲከፍል የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ከተደረገ ኢንሹራንስ ገቢው ጉዳት ደርሳብኛል ብሎ በከሰሰው ሰው ላይ ሊያቀርብ የሚችላቸውን የሕግ ክርክሮች ማቅረብ ይችላል፡፡ አመልካች ሦስተኛ ወገን ሆኖ የክርክር ተካፋይ በሆነበት ጉዳይ ክሱን በመቃወም የይርጋ ክርክር ሊያቀርብ የቻለው በዚሁ ሁኔታ በመጠቀም ነው፡፡

የቀረበውን የይርጋ ክርክር በተመለከተም ጉዳዩ ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነትን የሚመለከት ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ መሆን አለመሆኑ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143 አኳያ የሚመረመር ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለይርጋው ክርክር መነሻ ያደረገው ይኼው ከውል ከውል ውጭ ስለሚመለከት ካሣ ጉዳይ ክሥ የይርጋ ዘመን የሚወሰነውን ድንጋጌ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገር ጉዳዩ ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነት የሚመለከት መሆኑን እያረጋገጠ ተጠሪዋ በአመልካች በኩል ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መልስ ስትሰጥ ጉዳዩ ሟች በመኪና ተገጭቶ ከመሞቱ ጋር የተያያዘ ቢሆንም ክሱ የተመሠረተው በቀለብ ጥያቄ ላይ እንጅ በጉዳት ካሣ ላይ ስላልሆነ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2143 ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም በሚል ያቀረችው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ተጐጂው በመሞቱ ምክንያት ሚስት ወይም ልጆች በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2095 መሠረት በቀለብ መተዳደሪያ ረገድ የሚያቀርቡት የካሣ ጥያቄም ቢሆን ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነትን የሚመለከት እንጂ በሌላ የተለየ ግንኙነት ላይ ወይም በሌላ የሕግ ምክንያት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡

በዚሁ በተጠቀሰው የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2143 ላይ የተመለከተው የይርጋ ዘመን ሲታይ የመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር «1» ተበዳዩ ክሥ ማቅረብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችለው ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት አመት ድረስ መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት የበለጠ እንደሆነ የካሣው ጉዳይ ክሥ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት እንደሚሆን ይገልፃል፡፡

የቀረበው ጉዳይ ከዚሁ የይርጋ ድንጋጌ አንፃር ሲመረመር የአሁኗ ተጠሪ ካሣ የተጠየቀበት ጉዳት ሰኔ 5 ቀን 1984 ዓ.ም ደርሶ የካሣውን ጉዳይ ክሥ ያቀረበችው መስከረም 4 ቀን 1992 ዓ.ም መሆኑ ስለተረጋገጠ በሕጉ የመጀመሪያ ንዑስ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው ሁለት አመት የይርጋ ዘመን ያለፈው የመሆኑን ጉዳይ አከራካሪ ሊሆን አይችልም፡፡ የሚቀረው ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ በወቅቱ በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተመለከተው የይርጋ ዘመን ምን ያህል ይሆናል? በዚህ ሕግ መሠረት ቢታይ የይርጋው ዘመን አላለፈም ሊባል ይችላል አይችልም? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ አደጋ ያደረሰውን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሾፌር ሁለተኛው ተከሣሽ በዚህ ጉዳይ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት በመኪና ሰው ገጭቶ ገድሏል ተብሎ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526/1/ ተጠቅሶ በቀረበበት የወንጀል ክሥ ፍ/ቤት ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጦ በገንዘብ መቀጫ ብር 1000 እንዲቀጣ መወሰኑ ተገልጿል፡፡ ሾፌሩ በወንጀሉ ጉዳይ ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበት የሕግ አንቀጽ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526/1/ መሆኑ ከታወቀ የወንጀሉ ጉዳይ የክሥ አቀራረብ የይርጋ ዘመን ምን ያህል ጊዜ ነው የሚለውን በተመለከተ ከወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 226 በመመልከት ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ ነው ለማለት የተቻለው የይርጋ ዘመን በዚሁ በተጠቀሰው ሕግ ፊደል ሠ ላይ የተመለከተው አምሥት አመት ነው፡፡

የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ ክሱን ያቀረበችው ጉዳቱ በደረሰ በአምሥት አመት ጊዜ ሣይሆን ከሰባት አመት ቆይታ በኋላ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ሚስትነቱን እስካስወሰን ድረስ በክርክር ላይ የቆየሁት ጊዜ መታሰብ የለበትም፣ ክሥ የማቅረብ መብት ያገኘሁት ሚስትነቱን ካስወሰንኩ በኋላ ስለሆነ የይርጋው ጊዜ መታሰብ ያለበት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው በሚል ያቀረችው ክርክር በሕግ ተቀባይነት የለውም፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143/1/ ላይ እንደተመለከተው የይርጋው ጊዜ የሚቆጠረው ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ መዘግየት የጠቀሰችው ምክንያት በሕጉ ይርጋውን የሚያቋርጥ ወይም የሚያረዝም አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱ የቀረበው በወንጀሉም ጉዳይ የተወሰነው የይርጋ ዘመን ካለፈ በኋላ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡ አንድ ተከራካሪ ወገን በሕግ ይገባኛል የሚለውን መብት በሕጉ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ካልጠየቀ በሕግ ከሶ የመጠየቅ መብቱ ቀሪ ይሆናል፡፡ የአሁኗ ተጠሪም በባለቤታ መሞት ምክንያት በሕግ ይገባኛል የምትለውን ካሣ በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ክሥ አቅርባ ስላልተጠየቀች ካሣ የመጠየቅ መብታ ቀርቷል፡፡

በዚህ ምክንያት በቀረበው ጉዳይ ክሱ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በ21/9/1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔም ሆነ የኦሮሚያ ጠቅላይ በመ/ቁ.03564 - በ14/7/96 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሣኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይተላለፍ ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
4. ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዕጌ አጥናፉ

መልስ ሰጭ፡- ባለምባራስ ውቤ ሺበሺ

ተዋዋይ ወገን ሳይሆን ውል እንዲሠረዝ ስለመጠየቅ በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ፍ/ቤት የመሠረዝ ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1808/2/፣ 1198/2/

ካለ አመልካች ፈቃድ የጋራቸው የሆነውን ቤት ስም ለማዛወር አመልካች ባለቤት ተከጠሪ ጋር የፈፀመው ውል ፈራሽ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መወሰኑና የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሎ እንዲፈርስ አመልካች የጠየቁት ያለአግባብ ነው በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻሩ በመጨረሻም የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔውን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡-

<u>ውሳኔ</u>፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሠሰው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

1. ተዋዋይ ወገን ሳይሆን በተፈፀመ ውል ምክንያት መብቱ ተነክቷል በማለት ውሉ እንዲሰረዝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከህግ ውጭ ከሆነ፣ ለህሊና ተቃራኒ ወይም ለውል አፃፃፍ የተደነገገው ፎርም አልጠበቀም በሚል ምክንያት ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሚቀርብ ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም፡፡
2. የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የመሠረዝ ሥልጣን ደብተሩን የሰጠው የአስተዳደር አካል እንጅ የፍ/ቤት አይደለም፡፡
3. በአስተዳደር ክፍሉም እስካልተሰረዘ ድረስ የደብተሩ ባለቤት የቤቱ ባለንብረት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎት መ/ቁ. 14554
ቀን ታህሣሥ 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፦ 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
4. ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
5. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፦ ወ/ሮ ጽጌ አጥናፌ - ቀረበች
መልስ ሰጭ፦ ባላምባራስ ውቤ ሺበሺ - አልቀረበም
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያፀናው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት እንዲሻር ጠይቀዋል።

ጉዳዩ የተጀመረው አመልካች በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ሲሆን ይዘቱም ሲጠቃለል በዚህ መዝገብ የሌሉበት የሰር 2ኛ ተከሣሽ በሆነው ባለቤቱ በአቶ ተስፋዬ ውቤ የተመዘገበውን እና የጋራ ንብረታችን የሆነውን በወረዳ 20፣ ቀበሌ 44፣ የቤ.ቁ. 399 የሆነውን መኖሪያ ቤት የሰር 2ኛ ተከሣሽ ባለቤቱ ከአሁን መ/ሰጭ ጋር በመመሳጠር ለአሁን መ/ሰጭ (የሰር 1ኛ ተከሣሽ) ለማስተላለፍ የስምምነት ውል አድርገዋል፤ ስምምነቱ መብቱን የሚነካ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ የሚል ነው። የሰር 2ኛ ተከሣሽ ለክሱ ተቃውሞ እንደሌለው የገለፀ ሲሆን የአሁን መ/ሰጭ በበኩላቸው ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1810 መሠረት በይርጋ ይታገዳል፤ እኔ በሕይወት ያለሁ በመሆኑ ቤቱ ለሰር 2ኛ ተከሣሽ በውርስ ተላልፎአል ሊባል አይችልም፤ የቤቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር በሰር 2ኛ ተከሣሽ ስም ይገኛል ለተባለው ደብተሩ የተገኘው በህሰተኛ መንገድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መሆኑን ደብተሩ በስሜ እንዲዛወር የእርቅ ስምምነት ፈርሟል፤ በመሆኑም ቤቱ የራሴ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ይደረግ በማለት ጠይቀዋል። ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ቤቱን የአሁን አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሣሽ የጋራ ንብረት ነው፤ የስር 2ኛ ተከሣሽም የጋራ ንብረቱን ያለአሁን አመልካች ፈቃድ የማስተላለፍ አይችሉም በማለት የእርቅ ስምምነቱን ውል ፍ/ቤቱ አፍርሶታል በማለት ወሰነ። ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ የአሁን አመልካች ባቀረቡት ክስ የአሁን መ/ሰጭ ከስር 2ኛ ተከሣሽ ጋር ያደረጉት ስምምነት መብቱን ስለሚነካ ስምምነቱ ይፍረስልኝ ያሉት ያለአግባብ ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሮታል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ በምክንያቱ ባይስማማም በውጤቱ በመስማማት አጽንቶታል።

አመልካች የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠውና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባፀናው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ይዘቱም ሲጠቃለል በስር ፍ/ቤት ያቀረብኩት የእርቅ ስምምነት ይፍረስልኝ የሚል ጥያቄ ሲሆን የእርቅ ስምምነቱም ውል እንጅ ውሣኔ አይደለም፤ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በውሣኔው የጠቀሣቸው ድንጋጌዎች ከጉዳዩ ጋር የሚገናኙ አይደለም፤ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ እንዲሻር የሚል ነው። መ/ሰጭ በበኩላቸው አመልካች ያቀረቡት ክርክር የፍሬ ነገር በመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት የሚታይ አይደለም፤ በተደረገው የእርቅ ስምምነት አመልካች የሌለችበት መሆኑ ክስ መመሥረት አትችልም በማለት አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል።

በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ክርክሩን እና አቤቱታ የቀረበበትን ትእዛዝ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሮታል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም መሠረት አመልካች የእርቅ ስምምነቱን መሠረት በማድረግ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላት የክስ ምክንያት አለ? ወይስ የለም? እና ፍ/ቤት ስልጣን ባለው አካል የተሰጠን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተርን ሐሰተኛ በሆነ መንገድ የተገኘ ነው በሚል የመሠረዝ ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚሉትን ነጥቦች በጉዳዩ መመለስ ያለባቸው ሆኖ አግኝቷቸዋል።

የስር ፍ/ቤት አቤቱታ ለቀረበበት ውሣኔ መሠረት የሆነውና ውሣኔ የሰጠው አመልካች ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው። አመልካች ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት በአሁን መ/ሰጭና በስር 2ኛ ተከሣሽ መካከል የተደረገው የእርቅ ስምምነት ውል መብቴን የሚነካ በመሆኑ እንዲሻር የሚል ነው። ይሄም ለክሣቸው መሠረት ያደረጉት እሣቸው የሌሉበትንና በአሁን መ/ሰጭ እና በስር 2ኛ ተከሣሽ መካከል የተደረገውን የእርቅ ስምምነት ውል መሆኑን በግልጽ ያሣያል። በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1676(1) መሠረት ስለ ውሎች በጠቅላላ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በዚህ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ናቸው። ከእነዚህ ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808(2) መሠረት ከተዋዋይ ወገኖች ውጭ የሆነ ማንኛውም ጥቅም አለኝ የሚል ሰው ውሉ እንዲሠረዝ የሚጠይቀው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከሕግ ውጭ ከሆነ፤ ወይም ለሕሊና ተቃራኒ ወይም ለውል አፃፃፍ የተደነገገው ፎርም አልተጠበቀም በሚል ምክንያት ብቻ ነው። በዚህ ጉዳይ የእርቅ ስምምነት ውል ተብሎ የተገለፀው የተደረገበት ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የወጣበትን ስም ማዛወር ሲሆን ይህም ከሕግ ውጭ ወይም ለህሊና ተቃራኒ ነው የሚባል አይደለም። የእርቅ ስምምነት ውል ነው የተባለው ለውሉ የተደነገገው ፎርም አልተጠበቀም የሚል ክርክር ደግሞ አመልካች አላቀረቡም። እነዚህ ባልተሟሉበት ሁኔታ አመልካች የሌሉበት (ያልገቡት) ውል ይሰረዝ የሚል ክስ የሚያቀርቡበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት መጀመሪያውኑ የክስ ምክንያት የሌለ በመሆኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ.33 መሠረት አመልካች ክስ ለማቅረብ የማይችሉ ናቸው በማለት ክሱን መዝጋት ነበረበት። የፌዴራል ከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ፍ/ቤትም ይሄንን ስህተት ሣያስተካክል ያለፈው በአግባቡ አይደለም። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ይሄን ስህተት በተመሣሣይ ሁኔታ ማስተካከል ሲገባው አመልካች ባቀረበችው ክስ እንዲሰረዝ የጠየቀችው የእርቅ ስምምነት ውል ሣይሆን ውሣኔ ነው በሚል ይግባኙን ውድቅ ማድረጉን ከትእዛዙ መረዳት ይቻላል። በመሠረቱ እንዲሰርዝ የተጠየቀው ጠቅላይ ፍ/ቤቱ እንዳለው ውሣኔ ነው ቢባል እንኳን በቤቱ ላይ መብት አለኝ የሚል ወገን በአፈፃፀም ሆነ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ቤቱን በሚመለከት ክስ ሲያቀርብ አመልካች ቀርበው ከሚከላከሉበት ሁኔታ በቀር ክስ ሣይቀርብባቸው በራሣቸው ክስ በማቅረብ ውሣኔው ይሰረዝልኝ የሚል ጥያቄ የሚያቀርቡበት የሕግ አግባብ የለም። ይሄም አመልካች የእርቅ ስምምነት ውል ነው ያሉት አንዱ ጠቅላይ ፍ/ቤት ድምዳሜ ውሣኔ ነው ቢባል እንኳን አመልካች ይሰረዝልኝ የሚል ክስ ሊያቀርቡ እንደማይችሉ የሚያመለክት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክፍ ብሎ በተብራራው ምክንያት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ መሻር ሲገባው ጉዳዩን መርምሮ የስር 2ኛ ተከሣሽ ያገኘው የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር በሐሰተኛ መንገድ የተገኘ ነው፤ በዚህም ምክንያት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195(1) የተደነገገው የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር የያዘ ሰው የቤቱ ባለሀብት እንደሆነ ይቆጠራል የሚለው የህሊና ግምት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1196(ለ) መሠረት ፈራሽ ሆኗል፤ በመሆኑም የስር 2ኛ ተከሣሽ የቤቱ ባለንብረት ያልሆነ በመሆኑ የእርቅ ስምምነቱ የአመልካችን መብት አይነካም በማለት ነው የስር ፍ/ቤት ውሣኔን የሻረው። ይሄም ፍ/ቤቱ የአስተዳደር አካል (ክፍል) የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር መሠረዙን ያሣያል። በመሆኑም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196 መሠረት የአስተዳደር ክፍል የሰጠውን የባለበትነት ማስረጃ ደብተር የመሠረዝ ስልጣን እንዳለውና እንደሌለው መመርመሩ አስፈላጊ ነው። በመሠረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1196 የሚመለከተው አንድ የአስተዳደር ክፍል (አካል) የሰጠው የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር በድንጋጌው በተመለከቱት ሁኔታዎች መሆኑን ባረጋገጠ ጊዜ የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር የሚሰርዝበትን አግባብ ነው። በመሆኑም የሰጠውን የባለቤትነት ደብተር የመሠረዝ ስልጣን ደብተሩን የሰጠው የአስተዳደር አካል እንጅ የፍ/ቤት አለመሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ ቁ.1198(2) አግባብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሞምር መረዳት የሚቻል ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የአስተዳደር ክፍሉ የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር በአስተዳደር ክፍሉ እስካልተሠረዘ ድረስ የባለቤትነት ደብተር ያለው ሰው በፍ/ብ/ ሕ/ቁ.1195(1) በተደነገገው መሠረት የቤቱ ባለንብረት እንደሆነ መቆጠሩ የሚቀርበት የሕግ አግባብ አይታይም። በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ የተቸው ክርክሩ ሣይቀርብለት ትንታኔ የሰጠው በአግባቡ አይደለም በሚል እንጅ ፍ/ቤቱ የአስተዳደር አካል የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ ደብተር የመሠረዝ ስልጣን የለውም በሚል አይደለም። በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንንም በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የሚታየውን ስህተት ሣያስተባብል የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት የሰረዘው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም።

ው ሣ ኔ

1ኛ/ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ተወስኗል።

2ኛ/ እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1196 መሠረት ለአከራካሪው ቤት ከአስተዳደር አካል የሰጠውን የቤት ባለቤትነት ማስረጃ ደብተር የመሠረዝ ሥልጣን ያለው ደብተሩን የሰጠው የአስተዳደር አካል እንጂ ፍ/ቤት አይደለም በማለት ተወስኗል።

3ኛ/ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 13999 ጥር 14/1996 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ የሥነ ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ የቀረበ እንዳልሆነ ጠቅሶ የሰጠውን ትችት የሚቀበለው ቢሆንም በመጨረሻ በደረሰበት መደብደሚያ ግን ባለመስማማት ትእዛዙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ/ቁ. 348(1) መሠረት ሽሮታል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ.15672

ታህሣስ 27 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ

2. አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ

3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- አቶ ታደለ ገለቻ

ተጠሪ፡- ውድመጣስ ኑሮ

ስለ ንብረት ሽያጭ - ንብረት እንደገና በሐራጅ ስለሚሸጥበት ሁኔታ፡-
ስለ ሐራጅ አሸናፊ ክፍያ መፈፀሚያ ወቅት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 442

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ባለቤት የሆነ ንብረት በሐራጅ ተሸጦ ዕዳ እንዲከፈል በማድረግ ሁለት ተጫራቶች በተለያየ ጊዜ አሸንፈው በህጉ መሠረት በ15 ቀን ውስጥ ገቢ ስላላደረጉ ድርጅትን ባለመብቱ በንብረቱ ግምት ይረከቡት በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ውሳኔ</u>፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 442 ላይ ንብረተ ለምን ያህል ጊዜ በድጋሚ እንዲሸጥ በፍ/ቤቱ እንደሚታዘዝ ሳይደነግግም ንብረቱ ገዢ አያገኝም ወደሚል መደምደሚያ አያደርስም፡፡
2. ሁለት ጊዜ ሐራጅ ሽያጭ ወጥቶ አሸናፊዎች ካልከፈሉ ለ3ኛ ጊዜ ሐራጅ ወጥቶ ቤቱ ሊሸጥ ይገባል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- አቶ ታደለ ገለቻ - ታዬ ባንጃው ጠበቃ ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ውድመጣስ ኑሮ - አልቀረበም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

ይህ የአፈፃፀም ክርክር ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ፍትሐብሔር ቀጥታ ክስ ችሎት መጋቢት 29 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሠኘታቸው ነው፡፡

ለጉዳዩም መነሻ በሆነው በአመልካችና በተጠሪ መካከል በነበረው የአፈፃፀም ክርክር ተጠሪ (የፍርድ ባለመብት) የነበሩ ሲሆን አመልካች ደግሞ የፍርድ ባለዕዳ ነበሩ አመልካች የሚሉትም የእኔ ባለቤት ከወ/ሮ ይትዓለም ለገሠ ገዝታው ስመ ያልተዛወረ «ሠላም የህፃናት ልብስ መደብር» የተባለው ድርጅት ተሸጦ ለዕዳዬ መክፈያ እንዲውል የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ሠጥቶ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ድርጅቱን አስገምቶ ፍ/ቤቱም ድርጅቱን ለሐራጅ ጨረታ እንዲቀርብ አድርጓል ሆኖም ግን ሁለት ተጫራቾች በተለያየ ጊዜ ተጫርተው ያሸነፉ ቢሆንም ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን ገቢ ሊያደርጉ አልቻሉም በዚህም መሠረት የከ/ፍ/ቤት ቀጥታ ክስ ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 442 መሠረት ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሚሠጠው ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የተገለፀ ነገር የለም፣ ነገር ግን አፈፃፀሙ ተግባራዊ መሆን ስላለበት ላልተወሠነ ጊዜ ትዕዛዝ ሲሰጥ መቆየት የለበትም፣ በመሆኑም ንብረቱ ለሁለተኛ ጊዜ ተጫራች ባለመቅረቡ ምክንያት የባለዕዳውን ንብረት ባለገንዘቡ እንደሚረከበው ሁሉ ድርጅቱን ባለመብቱ በንብረቱ ግምት መሠረት ይረከቡት የሚል ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካችም በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሠኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ የጠየቁ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አይቶ የከ/ፍ/ቤት የሠጠው ትዕዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ለዚህ ሰበር ችሎት ይግባኛቸውን አቅርበዋል፡፡ የይግባኛቸውም መሠረታዊ ነጥብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 442 ፍ/ቤቱ ንብረቱ እንደገና እንዲሸጥ ትዕዛዝ ይሰጣል ይባል እንጅ በመነሻው ግምት የፍርድ ባለመብቱ (ተጠሪ) ይረከበዋል አይልም የሚል ሲሆን ተጠሪም በዚሁ መሠረት መልሱን ይዞ የቀረበ ሲሆን አመልካችም የበኩሉን የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ይህ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን ከተገቢው የሕግ ድንጋጌ ጋር መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ክርክሩ የቀረበበትን ድርጅት ለመሸጥ ሁለት ጊዜ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ፣ በሁለቱም ሐራጅ የሐራጁ አሸናፊዎች ሐራጁ በተደረገ በ15 ቀኖች ውስጥ የንብረቱን ዋጋ በሙሉ አልከፈሉም ተብሎ የፍርድ ባለመብቱ ማለትም ተጠሪ ንብረቱን በግምቱ እንዲረከብ መባሉ አግባብ መሆን አለመሆኑን አይቷል፡፡ በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 442 ላይ እንደተመለከተው የጨረታ አሸናፊ የሆነው ሰው በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ የንብርቱን ዋጋ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ንብረቱን እንደገና እንዲሸጥ ትዕዛዝ ይሰጣል የሚል ተመልክቷል፡፡ ምንም እንኳን እዚህ ላይ በሕጉ ውስጥ ይህ አይነት ሁኔታ የተከሠተበት ንብረት ለምን ያህል ጊዜ በድጋሚ እንዲሸጥ በፍ/ቤቱ እንደሚታዘዝ ያልተመለከተ ቢሆንም ንብረቱ ከነአካቴው ገዥ አያገኝም ወደሚል መደምደሚያ የሚያስደርስ አይሆንም፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ላይ የጨረታው አሸናፊዎች ገንዘቡን አልከፈሉም ማለት ሌላ ገዥ የለም ማለት አይደለም፡፡ በዚህም መሠረት የከ/ፍ/ቤት ክርክር የተነሣበትን ድርጅት ባለመብቱ በንብረቱ ግምት መሠረት እንዲረከቡት በማለት የሠጠው ትዕዛዝና የጠ/ፍ/ቤቱም የሠጠው ይህንኑ የሚያፀና ውሳኔ አግባብ አይደለም በማለት ሽረን ክርክር የተነሣበት ድርጅት በሐራጅ ይሸጥ ሲል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ወስኗል፡፡ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ስላለቀ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 16301

ጎዳር 2 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ሐጉስ ወልዱ

አቶ ተገኔ ጌታነህ

አቶ ዳኜ መላኩ

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፦ ተገኝ እንግዳ

ተጠሪ፦ አስናቀች ኪዳኔ

የመጥሪያን አደራረስ አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተና ገድበት ሁኔታ - በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት ተከሳሽ በሌለበት ክስ እንዲታይ የሚደረግበት ሁኔታ - የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 103፣ 105(1)

አመልካች እሱ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲታገድለትና እሱም ወደ ክርክሩ እንዲገባ እንዲፈቀድለት የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን የጠየቀ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አመልካች የሥነ-ሥርዓት ሕጉ በደነገገው መሠረት ተጣርቶ ባለመቅረቡ ክርክሩ እሱ በሌለበት መታየቱ ባግባቡ ነው ሲል በመወሠን ጥያቄውን ሳይቀበለው ቀርቷል። በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተመሣሣይ ውሣኔ በመስጠቱ የቀረበ አቤቱታ።

<u>ዉሳኔ</u>፦ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያፀናው ውሣኔ ፀንቷል።

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 103 እንደተመለከተው መጥሪያ አድራሻ (ሰጪው) መጥሪያውን ለማድረስ ያልቻለበትን ምክንያት በቃለ መሐላ አረጋግጦ መጥሪያውን ለፍርድ ቤቱ ይመልሳል። ፍርድ ቤቱም የቀረበለትን ምክንያት እንደየሁኔታው በመመዘን ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ትዕዛዝ ይሰጣል።
2. ፍርድ ቤቱ መጥሪያው እንደተመለሠለት በሕጉ በተመለከተው መሠረት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ምትክ የመጥሪያ አደራረስ ስርአት ማስተላለፉ ሕጋዊ ውጤት ያለው ይሆናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ሐጉስ ወልዱ
አቶ ተገኔ ጌታነህ
አቶ ዳኜ መላኩ
ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፦ ተገኝ እንግዳ - ቀረበ
ተጠሪ፦ አስናቀች ኪዳኔ - አልቀረበችም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

<u>ፍ ር ድ</u>

አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው የመጥሪያን አደራረስ በተመለከተ የተነሣውን ቅሬታ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ተብሎ ነው። ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው የአሁኗዋ ተጠሪ ናት። አመልካቹ በተደረገለት ጥሪ መሠረት አልቀረበም ስለተባለ ክርክሩ እሱ በሌለበት ታይቶ መወሰኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል። ከዚህ በኋላ መዝገቡ የተንቀሣቀሰው አመልካች እሱ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሣኔ እንዲታገድለትና እሱም ወደክርክሩ እንዲገባ እንዲፈቀድለት በመጠየቁ ነው። ጥያቄው የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ፣ ተከሣሽ የስነ - ሥርዓት ሕጉ በደነገገው መሠረት ተጣርቶ ባለመቅረቡ ነው ክርክሩ እሱ በሌለበት እንዲታይ የተደረገው። የሚል ምክንያት በመስጠት ሣይቀበለው ቀርቶአል። በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተመሣሣይ ውሣኔ ሰጥቶአል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ማለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 859 ሚያዝያ 5 ቀን 96 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው።

ክሱ አመለካች በሌለበት እንዲታይ የተደረገው መጀመሪያ በቀጥታ በአድራሻው በመቀጠልም በጋዜጣ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ሊቀርብ አልቻለም በሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል። መጀመሪያ በቀጥታ በአድራሻው የተላከለትን መጥሪያ ሊገኝ ባለመቻሉ መስጠት እንዳልተቻለና ወኪሉም መጥሪያውን አልቀበልም ስለማለቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 103 መሠረት በመሐላ ተረጋግጦ ለፍ/ቤቱ በመቅረቡ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 105(1) መሠረት የጋዜጣ ጥሪ እንዲተላለፍ ማዘዙኑንም ተመልክተናል። አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ትእዛዝ ተሰጡብኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ያቀረበው እነዚህን የሥነ - ሥርዓት ደንቦች በመከተል የተከናወነው ሂደት ትክክል አይደለም። መጥሪያው በደንብ እንዲደርሰኝ ሣይደረግ ነው ክርክሩ በሌለሁበት እንዲታይ የተደረገው። መጥሪያው መጥቶልኝ አልቀበልም አላልኩም። ስራዬ ሾፌርነት በመሆኑም ጋዜጣውን ማየት ይችላል ተብሎ መገመት የለበትም በማለት ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍ ሲል ከተመለከቱት ሁኔታዎች ማየት እንደሚቻለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.94(1) በተደነገገው መሠረት መጥሪያውን ለአመልካቹ ልኮአል። ሆኖም አመልካቹ በአድራሻው ተፈልጎ ባለመገኘቱ እና ሌላም መጥሪያውን መቀበል የሚችል ሰው ሊገኝ ባለመቻሉ በታቀደው ሁኔታ መጥሪያውን ማድረስ ሣይቻል ቀርቶአል። ይህን መሰል ችግር ሲያጋጥም የሥነ ሥርዓት ሕጉ መፍትሄ አስቀምጦአል። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 103 እንደተመለከተው መጥሪያ አድራሹ (ሰጭው) መጥሪያውን ለማድረስ ያልቻለበትን ምክንያት በመሐላ ቃል አረጋግጦ መጥሪያውን ለፍ/ቤቱ ይመልሳል። ፍ/ቤቱም የቀረበለትን ምክንያት እንደየሁኔታው በመመዘን ተገቢ ሆኖ ያገ–ነውን ትእዛዝ ይሰጣል። ይህም ማለት ተከሣሽ መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ ያለመሆኑ ወይም ደረሰኝ ለመስጠት እምቢተኛነቱ በመሐላ በተሰጠ ቃል ከተረጋገጠለት መጥሪያው በትክክል እንደደረሰ በመቁጠር ክርክሩ ተከሣሹ በሌለበት እንዲታይ ያደርጋል። መጥሪያው በትክክል እንደደረሰ ለመቁጠር የሚያስችል ምክንያት ካላገኘ፤ ነገር ግን የመጀመሪያው ሙከራ ተደርጎ ተቀባይ ባለመገኘቱ ምክንያት መጥሪያው መመለሱን ካመነ ደግሞ ቀጥሎ ያለውን ሌላው የመጥሪያ አሰጣጥ ሥርዓት (አማራጭ) ይጠቀማል። ይህ አማራጭም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.105 ከተመለከቱት አንዱ ይሆናል ማለት ነው።

በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መጥሪያው እንደተመለሰለት ወዲያውኑ አመልካች በሌለበት ክርክሩ እንዲታይ አላዘዘም። ተገቢ ሆኖ ያገኘው አካሄድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 105(1) ከተመለከቱት ከምትክ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓቶች አንዱን ማለትም የጋዜጣ ጥሪ ማስተላለፍ ነው። በዚህ ረገድ ተገቢ ነው ያለውን አማራጭ የመወሰን ሥልጣንም የፍ/ቤቱ ነው። በጋዜጣ የሚደረግ ጥሪ በሕጉ ከተፈቀዱት ምትክ የመጥሪያ አሰጣጥ ሥርዓቶች አንዱ በመሆኑም ሕጋዊ ውጤት ያለው ነው። የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በመጨረሻ ያቀረበውን ጥያቄ ያልተቀበሉትም በዚህ ምክንያት እና ጥሪው የተላለፈው ተገቢውን የሥርዓት ደንብ ተከትሎ መሆኑን በማረጋገጣቸው ነው። በመሆኑም በዚህ ረገድ የፈፀሙት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም።

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የሥር ፍ/ቤቶች ትእዛዞች ፀንተዋል።
2. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ/ቁ. 10797
ታህሣሥ 27 *ቀን* 1998 *ዓ.ም*

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ አሰግድ ጋሻው
4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ

መልስ ሰጭዎች፡- 1. ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም
2. አቶ ሁሴን አብደላ
3. አቶ ንጉሴ ኃይሉ

ስለ ወንጀል የተወሰነ ቅጣት-የገንዘብ ቅጣቶች - ወንጀሉ የሚያስከትላቸው ሌሎች የገንዘብ ውጤቶች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 99 - ስለፍርድ አፈፃፀም - የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 378

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 1/89 መ/ስጭዎች ለአመልካች 16,000,000 /አሥራ ስድስት ሚሊዮን/ የአሜሪካ ዶላር እንዲከፍሉ የሰጠውን ውሣኔ ለማስፈጸም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 መሠረት ያቀረበውን ማመልከቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 መሠረት ሊፈጸም የሚችል ፍርድ የለም ለማለት ፍ/ቤቱ በአብላጫ ድምፅ ውድቅ በማድረጉ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>፡-የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳይ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ እንጅ ባለሀብቱ የፍትሐብሔር ክስ አላቀረበም ወይም ፍርድ ያገኘበት ውሣኔ ለአፈፃፀም የሚያበቃ የፍትሐብሔር ፍርድ አይደለም ተብሎ ሊከለከል የሚችል አይደለም፡፡
2. ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳይ በፍርድ የተወሰነውን ገንዘብ የውሣኔው ባለመብት ሌላ ቀጥታ የፍትሐብሔር ክስ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ ሊፈጽም የሚችል ፍርድ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሣሥ 27 ቀን 1998 ዓ.ም
የሰበር መ/ቁ. 10797

ዳኞች፦ 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ አሰግድ ጋሻው
4. አቶ መስፍን ዕቁበየሱስ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፦ ሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ - ጠበቃ ተሾመ ገ/ማርያም ቀረቡ
ተጠሪዎች፦ 1. ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም - ቀርበዋል
2. አቶ ሁሴን አብደላ - አልቀረበም
3. አቶ ንጉሴ ኃይሉ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት አለበት በማለት ሥህተቱ በዚህ ችሎት ታይቶ እንዲታረም ባመለከቱት መሠረት ነው።

የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ቁጥር 1/89 በሆነ የወንጀል መዝገብ መጋቢት 5 ቀን 1992 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪዎቹ ለአመልካች በጠቅላላው 16,000.000 /አስራ ስድስት ሚሊዮን/ የአሜሪካን ላር እንዲከፍሉ ወስኗል።

የአመልካች ጠበቃ ይህንኑ ውሣኔ መሠረት በማድረግ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 መሠረት አፈፃፀሙ ቀጥሎ የተባለውን ብር ተጠሪዎች እንዲከፍሉ እንዲታዘዝለት አመልክቷል። የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ በሁለቱም ወገኖች በኩል ያሉትን ባለጉዳዮች እንዲሁም ሌሎች በጉዳዩ ያገባናል የሚሉትን ወገኖች አከራክሮ ካበቃ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 መሠረት አፈፃፀም የሚጠየቅበት ፍርድ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የበኩሉን ውሣኔ አሳልፏል። ለውሣኔውም መሠረት ካደረጋቸው ምክንያቶች መካከል፤ በአጠቃላይ ክሱ የሚያተኩረው ተፈፀመ በተባለ የወንጀል ጉዳይ ላይ እንጂ የፍትሐብሔር ይዘት እንደሌለው፣ የክሱ አቅራቢና ባለቤት ዐቃቤ ሕግ ሲሆን ጠሪዎቹ በወንጀሉ ጉዳይ ተከሣሽ ሆነው የተወሰነባቸው ከመሆኑ ውጪ ከአመልካቹ ጋር በገንዘብ ክርክር እንዳልነበራቸው እና ሌሎች ነጥቦችንም በመጥቀስ ፍርድ ቤቱ ስለ ገንዘቡ ጉዳይ ሊነሣ የቻለው ከመወረስ ሁኔታ ጋር በማያያዝ የግል ተበዳዩን መብት ለመጠበቅ እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 መሠረት የሚፈፀም አይነት ፍርድ ለመስጠት እንዳልሆነ መረዳት እንደሚቻል ገልጾ የቀረበው የአፈፃፀም ጥያቄ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል።

አቤቱታው ለሠበር ችሎት የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ነው አመልካችም በአቤቱታው፣ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ከመሠረታዊ ፍርዱ ዓላማ እና ግብ የራቀ፣ የሕግ ግድፈት የሚታይበት እንዲሁም የአመልካችን ሕጋዊ መብት ገፍፎ በፍርድ የተወሰነለትን መብት እንዲያጣ ያደረገ መሆኑን ገልጾ ውሣኔው ውድቅ እንዲደረግለት፤ በአንፃሩ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በወንጀል መ.ቁ.1/89 የአሠኖቹ ተጠሪዎች ለአመልካች የተጠቀሰውን 16,000.000 የአሜሪካን ላር እንዲመለስ በወንጀሉ ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
አጣምሮ የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 መሠረት እንዲፈፀምለት አመልክቷል።

1ኛ ተጠሪ ባቀረባቸው መልስ በአሜሩ፣ አመልካቹ በወ.መ.ሕ.ቁ. 100 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 154 መሠረት በተጠሪዎቹ ላይ በግል ተበዳይነት የፍትሐብሔር ክስ አለማቅረባቸውን፣ የፍ/ብሔር ክስ በጣምራ እንዲታይ አቤቱታ ባልቀረበበት የወንጀል ክስ የሚሰጥ ውሣኔ ደግሞ ቅጣት እንጂ የካሣ ውሣኔ ሊሆን እንደማይችል እንዲሁም አመልካቹ መብት አጉናፅፎኛል የሚሉት ፍርድ ከአፈፃፀም አቤቱታው ጋር ተያይዞ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲደርስ አለመደረጉን ገልፃ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግላት አመልክታለች።

2ኛ ተጠሪ ሁሴን አብደላ የጠ/ፍ/ቤት ወንጀል ችሎት በሌለበት የወሰነበት ስለሆነ በዚህም ችሎት አልተገኘም። 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ከ1ኛ ተጠሪ መልስ በተለየ ሁኔታ፣ የወንጀል ችሎቱ ስለ አመልካቹ ገንዘብ ሊያነሣ የቻለው ገንዘቡ በመንግሥት እንዳይወረስ ከማሰብ ጋር አያይዞ መሆኑን የፍትሐብሔር ይግባኙን የመረመረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል መዝገብ ቁ. 1/89 ላይ የተሰጠው ውሣኔ መንግሥት በተጠሪዎች ላይ የሚጠይቀውን የፍ/ብሔር ጉዳይ እንደማያጠቃልል ተገልጾ እያለ በዚህ ተመሣሣይ የወንጀል መዝገብ ውሣኔ በጉዳዩ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያላነሣን ወገን የፍ/ብሔር ጉዳይ ቄምር ያካተተ ነው ለማለት እንማያስደፍር፤ በሌላ በኩል የሰበሩ አቤቱታ ከቀረበበት አፈፃፀም ክርክርና ትእዛዝ በኋላ አመልካች በስዊዘርላንድ የፌዴራል ፍ/ቤት አስወስነው ገንዘባቸውን ወስደው ሳለ በድጋሚ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው አግባብ እንዳልሆነ ገልጾ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት ጠይቋል።

የአመልካች ጠበቃ በመልስ መልሱ አቤቱታውን አጠናክሮ የተጠሪዎችን መልስ ተችቷል። በበኩላችን መዝገቡን መርምረናል። ምላሽ ማግኘት የሚገባው ሆኖ ያገኘነው ነጥብ፣ በዚህ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 መሠረት አፈፃፀም ሊጠየቅበት የሚችል ፍርድ አለ ወይስ የለም? የሚለው ነው።

ለዚህ ጉዳይ መነሻ በሆነው የወንጀል መዝገብ ቁ.1/89 የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት መጋቢት 5 ቀን 1992 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ተጠሪዎች ለአመልካች መመለስ የሚገባቸውን 16,000.000 (አስራ ስድስት ሚሊዮን) የአሜሪካን ላር እንዲከፍሉ ፈርዷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱ የሚያተኩረው ተፈፀመ በተባለ የወንጀል ጉዳይ ላይ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የወንጀል ክሱን የመረመረውና የወሰነው በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎ መሆኑን፣ ከእነዚህ አንዱ ወንጀሉን ፈጽመዋል በተባሉት ሠዎች ላይ የእሥራትና የገንዘብ መቀጮ መወሰን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተጠሪዎች ከአመልካችና ከመንግሥት ወሰዱ የተባለውን ገንዘብ ለባለቤቶቹ እንዲመለሱ መፍረድ ነው። ከዚህ በተጨማሪም አሁን የተጠየቀው ገንዘብ የአመልካች ገንዘብ ስለመሆኑ መረጋገጡን ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል።

እንደሚታወቀው ማናቸውም ሕግ ተላላፊ በወንጀል ሥራው ያገኛቸው ገንዘብና እቃዎች ሕጋዊ ባለንብረቱ ተለይቶ በታወቀ ጊዜ ሊመለሱለት እንደሚገባ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ.99(2)ዬ ወንጀሉ የሚያስከትላቸው ሌሎች የገንዘብ ውጤቶችጦ በሚለው ክፍል የደነገገ መሆኑ ይታወቃል።

የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በወንጀል መ/ቁ. 1/89 አሁን የተጠየቀውን ገንዘብ ለባለቤቱ ሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እንዲመለስ ውሣኔ የሰጠውም ይህንኑ ሕግ መሠረት አድርጉ እንደሆነ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል። ከዚህ የሕግ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ባለንበረቱ ገንዘቡን ወይም ንብረቱን ለመረከብ አዲስ ክስና ክርክር መመስረት ሳያስፈልገው በቀጥታ መረከብ እንደሚችል ነው። አሁን የተነሳው የአፈፃፀም ጥያቄም ይህንኑ ውሣኔ መሠረት አድርጉ ተጠሪዎቹ ከላይ ተጠቀሰውን ገንዘብ እያንዳንዳቸው በየድርሻቸው መመለስ የሚገባቸውን ያህል እንዲከፍሉ እንዲታዘዝ የሚጠይቅ ነው። ይህ የአፈፃፀም ጥያቄ ክፍ ሲል በጠቀስነው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ አኳያ የገንዘቡ ወይም የንብረቱ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ከመሆኑ ውጭ ባለሀብቱ የፍትሐብሔር ክስ አላቀረበም ወይም ፍርድ ያገኘበት ውሣኔ ለአፈፃፀም የሚያበቃ የፍትሐብሔር ፍርድ አይደለም ተብሎ ሊከለከል የሚችል አይደለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማጠቃለል ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በፍርድ የተወሰነውን ገንዘብ የውሣኔው ባለመብት ሌላ ቀጥታ የፍትሐብሔር ክስ ማቅረብ ሣያስፈልገው በቀጥታ ሊፈፅም የሚቻል ፍርድ ነው በማለት ይህን ፍርድ ሰጥተናል።

በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በወንጀል መ/ቁ. 1/89 ስለገንዘቡ አመላለስ አስመልክቶ በሰጠው ውሣኔ የአሁኑ አመልካች በፍርዱ ውሣኔ በተሰጠው ምርጫ መሠረት ገንዘቡን ለማስመለስ በበኩሉ ያቀረበውን ጥያቄ መርምረን በሚከተለው መልኩ እንዲፈፀም ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. 1ኛ/ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳ ወ/ሮ ሸዲያ ናዲም የአሜሪካ ላር 9,000.000 (ዘጠኝ ሚሊዮን ላር)፤
2. 2ኛ/ ተጠሪና የፍርድ ባለዕዳ አቶ ሁሴን አብደላ የአሜሪካን ላር 6,443.447.95 (ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሦስት ሺ አራት መቶ አርባ ሰባት ላር ከዘጠና አምስት ሣንቲም)
3. 3ኛ/ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳ አቶ ንጉሣ ኃይሉ የአሜሪካን ላር 556,324.05 (አምስት መቶ ሃምሣ ስድስት ሺ ሦስት መቶ ሃያ አራት ላር ከዜሮ አምስት ሣንቲም) በጠቅላላ 16,000.000 (አሥራ ስድስት ሚሊዮን የአሜሪካን ላር) ለፍርድ ባለመብቱ ለአሁኑ አመልካች ለሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እንዲመልሱ ታዟል።

- በወ.መ.ቁ. 1/89 ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት መንግሥት ከ1ኛ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳ ከወ/ሮ ሻዲያ ናዲም ላይ የሚፈልገውን ገንዘብ ከሼህ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ አስቀድሞ እንዲወስድ ታዟል።
- የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ.5915 ህዳር 12 ቀን 1995 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348(1) መሠረት ተሽሯል፤ ይፃፍ።

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 18199

ህዳር 7 ቀን 1998 **ዓ.ም**

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጉስ ወልዱ

አቶ ዳኜ መላኩ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፦ ወ/ሮ ምናሴ እሸቱ

ተጠሪዎች፦ እነ ግርማ አያና (7 ሰዎች)

በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈፅም የቀረ ገዢ ባጋጠመ ጊዜ ንብረቱን የሚያስፈፅመው ፍርድ ቤት ሊከተሰው ስለሚገባው ሥርዓት - የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 429

የአሁኑ አመልካች ፍርድ በማስፈፀም ላይ የነበረ ፍርድ ቤት ባወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት የሐራጅ ተካፋይ በመሆንና በማሸነፍ በሐራጁ ማስታወቂያ የተመለከተውን ንብረት የገዛ፣ ቢሆንም ያሸነፈበትን የጨረታ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም በዚሁ መሠረት የፍርዱን አፈፃፀም የመራው የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በጨረታ ያሸነፈበትን ዋጋ አጠቃሎ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ይከፈል በማለት ትዕዛዝ ሊሰጥ በዚሁ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የቀረበለትም የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡ -

<u>ውሣኔ</u> ፡-የአማራ ብሐራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡

1. **በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛው ተጫራች ዋጋውን እንዲከፍል ማስገደድ እንደሚቻል በሕጉ አልተመለከተም፡፡**
2. **የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 እንደሚያመለክተው ገዢው በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል የቀረ እንደሆነ ሽያጩ እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ሌላ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ሐጉስ ወልዱ
አቶ ዳኜ መላኩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፦ ወ/ር ምናሴ እሸቱ ጠበቃ አፀደወይን ተክሌ ቀረቡ።

ተጠሪዎች፦ እነ ግርማ አያና (7 ሰዎች) - የ1ኛ ተጠሪ ወኪል ቀረቡ።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ በቀረበው የሰበር አቤቱታ የተነሣው የሕግ ጥያቄ በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል ወይም ግዴታውን ሣይፈጽም የቀረ ገዥ ባጋጠመ ጊዜ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ሥርዓት የሚመለከት ነው። አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ ፍ/ቤት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በማፅናት በፍ/ብ/ይ/መ.ቁ 192/97 ታህሣሥ 7 ቀን 97 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው።

ከመዝገቡ እንደሚታየው የአሁኑ አመልካች ፍርዱን በማስፈፀም ላይ በነበረው ፍ/ቤት በወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት የሐራጅ ተካፋይ በመሆንና በማሸነፍ በሐራጁ ማስታወቂያ የተመለከተውን ንብረት (ሆስፒታል) ገዝቶአል። ሆኖም ያሸነፈበትን የጨረታ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም። የሰጠው ምክንያትም ንብረቱን ተረክብ የተባልኩት ስወዳደር ካሰብኩት እና በሐራጅ ማስታወቂያው ላይ ከተመለከተው ውጪ ነው የሚል ነው። የፍርዱን አፈፃፀም የመራው የከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ (ተቃውሞ) አልተቀበለም። ይልቁንም አመልካች በጨረታ ያሸነፈበትን ዋጋ አጠቃሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ይክፈል በማለት ትእዛዝ ሰጥቶአል። በዚህ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጉድለት የለበትምትክክል ነው ብሎአል።

እንደምናየው ጉዳዩ በፍትሐብሔር ረገድ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው። ስለፍርድ አፈፃፀም በተመለከተ የፍትሐብሔር ሥነ - ሥርዓት ሕጉ በሰባተኛው መጽሐፍ ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን አስቀምጦአል። በፍርድ አፈፃፀም ንብረትን የመሸጥ ሥነ - ሥርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ደግሞ ከቁ.422 እስከ 431 በተለይ ተቀምጠዋል። ከእነዚህም ውስጥ አሁን ለያዝነው ጉዳይ አወሳሰን ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ቁ.429 ነው። ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያመለክተው ገዢው በጨረታ ለገዛው ንብረት ዋጋውን ሣይከፍል የቀረ እንደሆነ ሽያጩ እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ሌላ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ እንደሚደረግ ነው። በእርግጥ ንብረቱ እንደገና በሚሸጥበት ጊዜ ዋጋ የቀነሰ እንደሆነ በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛውና ዋጋውን ያልከፈለው ተጫራች ልዩነቱንና ኪሣራውን እንዲከፍል እንደሚገደድም ድንጋጌው ያመለክታል። ከዚህ ውጪ ግን በመጀመሪያው ጨረታ ንብረቱን የገዛው ተጫራች ዋጋውን እንዲከፍል ማስገደድ እንደሚችል በሕጉ አልተመለከተም። ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት በጥብቅ መከተል ያለበትም ሕጉን ብቻ ነው። በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን ሕጉ ከሚለው ውጪ አመልካች የጨረታውን ዋጋ እንዲከፍል እና ንብረቱንም በግድ እንዲረከብ ነው የታዘዘው። ስለዚህም ትእዛዙ (አቤቱታ የቀረበበት) መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል።

<u>ው ሣ ኔ ፣</u>

አቤቱታ የቀረበባቸው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 192/97 የሰጠው ትእዛዝ እና በዚህ ትእዛዝ ፀንቶ የነበረው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል።

ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸው በየራሣቸው ይቻሉ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. አቶ ዳኜ መላኩ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የ10 ዓለቃ ጌታቸው ባዩ
ተጠሪ፡- በቤ/ዝ/ክ/መ/ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ቅ/መ/ቤት

ስለ ጡረታ መብት - የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ሌላ የመንግሥት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ስለመስራት - ድንጋጌ ቁጥር 46/53 እና አዋጅ ቁጥር 209/55 አንቀጽ 30(2)

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት አንድ የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ በመንግስት መስሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝና የጡረታ አበል በጣምራ ከወሠደ የጡረታ አበሉን መመለስ አለበት በማለት የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሠጠውን ውሳኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ፡፡
ውሳኔ፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

1. አንድ የመንግስት ሠራተኛ በጡረታ ተገሎ አበሉን እየተከፈለው ከሆነ በሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ደሞዝ እና የጡረታ አበል አጣምሮ መቀበል አይቻልም፡፡

2. አንድ የመንግስት ሠራተኛ በጡረታ ተገልሎ አበሉ እየተከፈለው በሌላ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጠሮ ደመወዝ ከወሰደ ከጡረታ አበሉ ወይም ከወሰደዉ ደመወዝ በመጠን የሚያነሰዉን ይመልሳል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፦ መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

መስፍን ዕቁበየሱስ

አመልካች፦ የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ ቀረበ

ተጠሪ፦ በቤ/ዝ/ክ/መ/ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ቅ/መ/ቤት ነገረፈጅ አቶ ፈርተውሃል ኃይለጊዮርጊስ ቀረበ።

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ክርክር አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ በመንግሥት መሥሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝና የጡረታ አበል በጣምራ መውሰድ ይችላል አይችልም፣ ሁለቱን በጣምራ ወስ ከተገኘ የጡረታ አበሉን ለመመለስ ይገደዳል አይገደድም የሚለውን ጉዳይ የሚመለከት ነው።

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝና የጡረታ አበል በጣምራ ሲወስድ የቆየ መሆኑ ቢረጋገጥም ደመወዙንም ሆነ የጡረታ አበሉን የሚመልስበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት የወሰነውን የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ.348(1) መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
በመሻር ቀደም ሲል በሥራ ላይ በቆየው የጡረታ አዋጅ ቁጥር 209/55 አንቀጽ 30/2/ መሠረትም ሆነ በኋላ ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 46/1/ መሠረት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና በመንግሥት መሥሪያ ቤት በመቀጠር ደመወዝ ማግኘት ከጀመረ የጡረታ አበል እና ደመወዝ በጣምራ ሊወሰድ አይችልም፣ በሕጉ የጡረታ አበሉ ተቋርጦ ይቆያል፣ ስለዚህ 10 አለቃ ጌታቸው ባዩ ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል መመለስ ይገባዋል በማለት ወስኗል። አመልካች ከየካቲት 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ያለአግባብ ሲቀበል ቆይቷል የተባለው የጡረታ አበል በአጠቃላይ ብር 9000 ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም እንዲመልስ የወሰነው ይህንኑ ገንዘብ ነው።

የሰበር አቤቱታው በዚህ ምክንያት የቀረበ ነው። አመልካች ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል መመለስ አለበት በሚል በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ነው ለሰበር አቤቱታ ያቀረበው።

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻ ለአሁኑ ተጠሪ እንዲደርሰው ተደርጉ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በጽሑፍ መልስ ሰጥቶበት ተከራክሯል። በማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በኩል የቀረበው ክርክር ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ አንድ የጡረታ መብቱ የተከበረለት ሠራተኛ እንደገና በመንግሥት መሥሪያ ቤት ደመወዝ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ከተቀጠረ የጡረታ ሕጉ የጡረታ አበሉ ወዲያውኑ የሚቋረጥ መሆኑን ይደነግጋል። አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና በመንግሥት መሥሪያ ቤት ደመወዝ በሚያስገኝ ሥራ ላይ እንደተቀጠረ ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በማሣወቅ የጡረታ አበሉ እንዲቋረጥ ማድረግ ሲገባው ደብቆ ደመወዝና የጡረታ አበል ያለአግባብ በጣምራ ሲቀበል ቆይቷል። መሥሪያ ቤቱ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና በመንግሥት መ/ቤት ደመወዝ በሚያስገኝ ሥራ ላይ መቀጠሩን የሚያውቅበት መንገድ ሰሌለ የጡረታ አበሉን እንዲያቋርጥ ለማድረግ አይችልም። የጡረታ አበሉን ሲከፍለው የቆየው ደመወዝ ማግኘቱን እያወቀ አይደለም። አመልካች በሕግ የጡረታ አበል ስለመቋረጡ አላውቅም የሚለው መከላከያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መልስ ሊሆነው አይችልም፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/በት በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሣኔም የተፈፀመ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ሊፀና ይገባል የሚል ይዘት ያለው ነው።

ችሎቱም አንድ የመንግሠት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና ተመልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ሊቀጠር ከቻለ ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ ሊቀበል ይችላል አይችልም፤ የአሁኑ አመልካች ጡረታ ከወጣ በኋላ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ ከደመወዝ ጉን ለጉን ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል ለመመለስ ይገደዳል አይገደድም የሚለውን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

የአሁኑ አመልካች ቀደም ሲል ሲሰራ ከቆየበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከታህሣሥ 1 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ እንዲገለል ተደርጉ የተወሰነለትን የጡረታ አበል ማግኘት ከጀመረ በኋላ ከየካቲት 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዝ በሚያስገኝ ሌላ የመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ በመሥራት ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ ሲቀበል የቆየ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው። ከሣሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ተከሣሹ የአሁኑ አመልካች ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ ሲቀበል የቆየው ያለአግባብ ስለሆነ የጡረታ አበሉን ሊመልስ ይገባል በሚል የከሰሰው በታህሣሥ ወር 1994 ዓ.ም ነው። ይኸው ከተረጋገጠ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ የሚሆነው በኋላ የወጣው አዋጅ ቁጥር 345/95 ሣይሆን በወቅቱ ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ በሥራ ላይ የነበረው ድንጋጌ ቁጥር 46/53 እና ይህንኑ ድንጋጌ በከፊል በማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 209/55 ነው የተጠቀሰው ድንጋጌ አንቀጽ 30/2/ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ከተቀጠረ ከደመወዙ እና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ አለበት ይላል። ከዚህ ሕግ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ መቀበል የማይቻል መሆኑን ነው። ከሁለቱ አንዱን የመምረጥ መብት የተሰጠው ለሠራተኛው ነው። በሕግ ከተፈቀደለት የጡረታ አበል እና ተመልሶ ከተቀጠረበት የመንግሥት ሥራ ከሚያገኘው ደመወዝ የበለጠ ይጠቅመኛል የሚለውን የመምረጥ እድል በሕጉ ስለተሰጠው ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ እንደተቀጠረ በአካባቢው ላለው የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በማሣወቅ ምርጫው ምን እንደሆነ መግለጽ ይኖርበታል። የበለጠ የሚጠቅመኝ አዲሱ ደመወዝ ነው ካለ የጡረታ አበሉ እንዲቋረጥ ማድረግ አለበት። አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ እንደገና ተመልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ በሚቀጠርበት ጊዜ ራሱ ወይም ቀጣሪው መሥሪያ ቤት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ካላሣወቀ በቀር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚያውቅበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
መንገድ ስለሌለ ተከታትሎ የጡረታ አበሉን ማቋረጥ አበረበት የሚለው ከጡረታ ሕጉ አኳያ ሲታይ ተቀባይነት የለውም።

ጡረታ የወጣው ሰው ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ አዲስ ደመወዝ እና የጡረታ አበል አጣምሮ ሲቀበል የቆየ መሆኑ ከተረጋገጠ በሕጉ ምን ይደረጋል? የሚለው ሲመረመር ሕጉ ደመወዙን ወይም የጡረታ አበሉን ይመልሣል የሚል ግልጽ ድንጋጌ ባይኖረውም በሕጉ ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምሮ መቀበል አይቻልም ከተባለ አጣምሮ ሲቀበል የቆየውን በሕግ ያልተፈቀደለትን ገንዘብ የማይመልስበት ምክንያት የለም። የአሁኑ ተጠሪ አመልካች ከደመወዝ ጎን ለጉን ሲቀበል የቆየውን የጡረታ አበል እንዲመልስ ጠይቋል። ሆኖም አመልካች በወቅቱ በሕጉ በተሰጠው ከአዲሱ ደመወዝ እና የጡረታ አበል አንዱን የመምረጥ መብት ስላልተጠቀመ ሊመልስ የሚገባው ሲቀበል ከቆየው ደመወዝና የጡረታ አበል አነስተኛ ሆኖ የተገኘውን ገንዘብ ነው። በሕጉ ላይ በተገለፀው መሠረት ሊመርጥ ቢችል ኖሮ ከሁለቱ ከፍ ያለውን ገንዘብ ይመርጣል ተብሎ ይገመታል። ከተቀጠረበት ሥራ የሚያገኘው ደመወዝ ዝቅተኛ ሆኖ የጡረታ አበሉ ከፍተኛ ከሆነ የጡረታ አበሉን ትቶ ዝቅተኛ የሆነውን ደመወዝ ይመርጣል ለማለት ያስቸግራል። ፍትሐዊም የሚሆነው አጣምሮ ሲቀበል ከቆየው ደመወዝና የጡረታ አበል መካከል ዝቅተኛ የሆነውን እንዲመልስ ማድረግ ነው።

ው ሣ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሎ የአሁኑ አመልካች ከየካቲት 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ አጣምሮ ሲቀበል ከቆየው ደመወዝ እና የጡረታ አበል መካከል አነስተኛ ሆኖ የተገኘውን እንዲመልስ ወይም ለተጠሪው እንዲከፍል ተወስኗል።
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ። የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ይተላለፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. አቶ ዳኜ መላኩ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን
መልስ ሰጭዎች፡- 1ኛ- አቶ ብርሃኑ ሀሩይ
2ኛ- አቶ ከበደ ገ/ማርያም

ስለማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ - የማኅበራዊ ዋስትና ባልስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 38/1988 አንቀጽ 11/1/ ፡- ስለፍርድ ቤቶች ስልጣን -የፍትሐ ብሄር ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 4

የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት የማኅበራዊ ዋስትና ባለስልጣን በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የቀረበለት የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ስለሰጠና ውሳኔውንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስላደናው የቀረበ አቤቱታ፡፡

ውሣኔ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያጸናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. በህግ ተለይተው በአስተዳራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን የለውም፡፡

2. የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የስራ ነገር ስልጣን የላቸውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ተገኔ ጌታነህ
አቶ ዳኜ መላኩ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፦ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ነገረፈጁ አቶ ፈርተውሃል ኃ/ጊዮርጊስ ቀረበ

ተጠሪዎች፦ 1ኛ/ አቶ ብርሃኑ ሕሩይ ቀረበ
2ኛ/ አቶ ከበደ ገ/ማርያም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች የሆኑት የአሁኑ ተጠሪዎች በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረን ስናገለግል በቆየንባቸው ዓመታት ለጡረታ አበል እየተባለ ከደመወዛችን ከመቶ አራት፣ ከአሠሪው መሥሪያ ቤት ደግሞ በመቶ ስድስት እየተቀነሰ ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ገቢ ተደርጓል ያሉትን ገንዘብ የሊሲ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ወደነበረበት እንዲመልስ፣ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በበኩሉ ያለአግባብ ከከሣሾች ሂሣብ ወጪ በማድረግ ለትምህርት ቤቱ የሰጠውን ገንዘብ ወደነበረበት ሂሣብ ተመላሽ እንዲያደርግ በሚል የሰጠውን ውሣኔ ከፍተኛው ፍ/ቤት ትክክል ነው ብሎ በማጽናቱ ምክንያት የቀረበ ነው።

አመልካች በዚህ ጉዳይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልባቸው ምክንያቶች የአሁኑ ተጠሪዎች ይህንኑ ከጡረታ አበል ጋር የተያያዘውን ገንዘብ ጉዳይ በሚመለከት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ጥያቄ አቅርበው መሥሪያ ቤቱ በሕጉ መሠረት አይቶ ከወሰነ በኋላ ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አመልክተው የመጨረሻ ውሣኔ ሰጥቶበታል ጉባዔው በአዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 11(1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚሰጠው ውሣኔም የመጨረሻ ስለሆነ ከዚህ በኋላ በዚሁ ጉዳይ ለፍ/ቤት ክሥ ሊቀርብበት አይችልም። ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሠረት ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሎ መወሰን ነበረበት። ከጡረታ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተነሣውን ጥያቄ መደበኛ ፍ/ቤት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለውም። የህንን ጉዳይ በየደረጃው የተመለከቱት ፍ/ቤቶች ሕጉን በአግባቡ ሣይተረጉሙ ቀርተዋል በሚል የቀረቡ ናቸው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታው ተመርምሮ የሚጣሩ የሕግ ነጥቦች ያሉት ሆኖ በመገኘቱ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻም ለአሁኑ ተጠሪዎች ተልኮ ግንቦት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካች በበኩሉ የመልስ መልስ ሰጥቶበት ተከራክሯል።

በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ክርክር ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ አመልካች ያለአግባብ ከእኛ ሂሣብ አውጥቶ የሰጠውን ገንዘብ በሚመለከት የጡረታ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣንም ሆነ ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ክሥ አቅርበን በሥማችን ውሣኔ ስለመስጠቱ የሚያስረዳ ማሥረጃ አላቀረበም። የአገልግሎት ዘመናችን ተቀንሶብናል ወይም ያለአግባብ ዕድሜአችን ለጡረታ ሣይደርስ በጡረታ እንድንገለል ተደርጓል በሚል ያቀረብነው ክስ ስለሌለ በጡረታ ሕጉ መሠረት የሚታይ ጉዳይ የለም። አመልካች አላገባብ ከሂሣባችን አውጥቶ የሰጠውን ገንዘብ ተቀብሎ ወደነበረበት ሂሣብ እንዲያስገባ በሚል የቀረበውን ክሥ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው። የሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት አመልካቹ መሥሪያ ቤትን ጠይቆ የወሰደው ገንዘብ አላገባብ መሆኑን አምኖ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት መልሶ ገቢ ስላደረገ አመልካች አልፈጽምም የሚልበት ምክንያት የለም የሚል ይዘት ያለው ነው።

ችሎቱም የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ይፈፀምልን ያሉትን ጉዳይ ፍርድ ቤት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን መርምሯል። በአዲስ መልክ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 5 ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚፈጽማቸውን ተግባሮች እና የተሰጠውን ሥልጣን የሚዘረዝር ሲሆን በዚህ አንቀጽ ሥር ከታቀፉት ንዑስ አንቀጾች መካከል በንዑስ አንቀጽ 8 ላይ የተመለከተው ሲታይ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን አግባብ ባላቸው ሕጐች መሠረት በሚቀርቡ የማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን በግልጽ ያረጋግጣል። የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በዚሁ ሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም በሚመለከት በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው በአዋጁ አንቀጽ 11 ላይ ሥልጣን ለተሰጠው ለማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ነው። ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በሚሰጠው ውሣኔ ላይ የሚቀርቡትን ይግባኞች መርምሮ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ነው። በሕጉ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በአንድ የማህበራዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ዋስትና ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ነው ከተባለ ከዚህ በኋላ በይግባኝ ደረጃም ሆነ በክሥ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት የሚሄድበት መንገድ የለም ማለት ነው። በሕግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን ስለሌለው በሕጉ መሠረት ለአንድ አስተዳደር አካል ቀርቦ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወይም ለአስተዳደር መቅረብ የሚገባውን ጉዳይ ፍ/ቤት ሊያስተናግደም ሆነ አከራክሮ ውሣኔ ሊሰጥበት አይችልም። ለአንዳንድ የመንግሥት አስተዳደር አካላት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሰጡት ሕጉች መጠበቅና መከበር ይኖርባቸዋል። የዳኝነት አካሉ ሥልጣንም በሕግ የተወሰነ ስለሆነ ሕግ የመተርጉም ሥራው በሕግ ማቀፍ የሚመራ ነው። ስለዚህ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በሕግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ሁሉ ፍርድ ቤት አይቶ ከመወሰን ሊገደብ አይችልም የሚለው አስተሳሰብ ተቀባይነት የለውም። በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.4 ላይ በፍርድ ቤቶች እንደተገለፀው በሌላ ሕግ በግልጽ ከታገዱ በጉዳዩ ላይ አከራክሮ የመወሰን ሥልጣን የላቸውም።

የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካችን ሊከሱ የቻሉበት ምክንያት እና ባቀረቡት ክስ ይፈፀምልን በሚል ያነሱት ጥያቄ ከማህበራዊ ዋስትና ጉዳይ ጋራ ተያያዥነት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ሲመረመር በመጀመሪያ በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረው ሲሰሩ ቢቆዩባቸው አመታት ለጡረታ መዋጮ እየተባለ ከእያንዳንዳቸው ደመወዝ በወር በሙዩ አራት፣ ከአሠሪው መሥሪያ ቤት ደግሞ በሙዩ ስድስት እየተዋጣ በማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በየሥማቸው በተከፈተ ሂሣብ ገቢ ሲደረግ የቆየው ገንዘብ በኋላ ወደተዛወሩበት የሌሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት መተላለፉን ገልፀዋል።

ተጠሪዎች የአሁኑ አመልካች የጡረታ መዋጮውን ወደሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ያስተላለፈው አላገባብ ነው ይበሉ እንጅ በክሣቸው ላይ ከገለፁት ፍሬ ነገር እንደሚታየው ከጥር ወር 1989 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ እንዲገለሉ ተደርጓል። ወደ ሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት እንዲተላለፍ ተደርጓል የሚሉት ትምህርት ሚኒስቴር ሲሰሩ በነበረበት ወቅት የተዋጣው የጡረታ መዋጮ ወደ ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እንዲመለስ የሚጠይቁትም ተመልሶ በእነርሱ ሥም በተከፈተ ሂሣብ እንዲቀመጥ ለማድረግ ብቻ ሣይሆን ይኸው ታስቦ በጡረታ አበላቸው ላይ እንዲጨመር ለማድረግ ወይም በሕጉ መሠረት ይገባናል የሚሉትን መብት ለማስከበር እንጅ ለሌላ ጉዳይ ለማመቻቸት አይደለም። የምናነሣው የማህበራዊ ዋስትና መብትም ሆነ ጥቅም የለም የሚሉ ከሆነ ደግሞ የጡረታ መዋጮው ቀደም ሲል በማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በሥማቸው ተከፍቶ ወደነበረው ሂሣብ እንዲመለስ የሚጠይቁበት ምክንያት አይኖርም። የጡረታ መዋጮም በቀጥታ ከማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም ጋራ ተያይዞ የሚታይ ነው። ተጠሪዎች ወደሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ተላልፏል የሚሉት የጡረታ መዋጮ ወደ ማህበራዊ ዋስትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ባለሥልጣን እንዲመለስ ተደርጉ በሕጉ መሠረት የሚገባን የማህበራዊ ዋስትና መብትና ጥቅም አለ ካሉ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 5(8) መሠረት ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ጥያቄአቸውን አቅርበው ውሣኔ እንዲሰጥበት ማድረግ አለባቸው። ተጠሪዎች ትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረው ሲሰሩ በቆዩባቸው አመታት ተዋጥቷል የሚሉት የጡረታ መዋጮ እንዲተላለፍ ከተደረገበት የሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ወደማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ካዝና እንዲመለስ መጠየቁ ብቻ በሕጉ ትርጉም የለውም። ወደ ሊሴ ገ/ማርያም ትምህርት ቤት ተላልፋል የተባለው የጡረታ መዋጮ እንዴት ይሆናል? በጡረታ አበል ሊታሰብላቸው ይገባል አይገባም የሚለውን ጥያቄ በሕጉ የመወሰን ሥልጣን ያለው ራሱ የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እና በይግባኝ ደረጃ የሚያየው ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ እንጅ ፍርድ ቤት አይደለም።

በሌላም በኩል የአሁኑ አመልካች በክርክሩ ላይ እንደገለፀው ይኸው ጉዳይ ቀደም ሲል ለማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ቀርቦ እስከ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ ደርሶ ታይቶ ውሣኔ ከተሰጠበት እንደገና የሚታይበት የሕግ አግባብ የለም። በሕጉ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ በመሆኑ ያበቃለት ጉዳይ ይሆናል።

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤት በሥረ ነገሩ ላይ የመዳኘት ሥልጣን የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል። በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

1. ይህንን ጉዳይ በማስመልከት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 2384 ታህሣሥ 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔም ሆነ ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የወሰነው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል።
2. በክርክሩ ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።
3. የውሣኔው ግልባጭ ይተላለፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሀይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢንጂነር ወርቁ መኮንን የአመልካች ወራሾች

ተጠሪ፡- የቦሌ ክ/ከተማ ገቢዎች መምሪያ

ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ሕጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ - የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀጽ 29

አመልካች ገቢ ለመፍጠር ወጪ ያደረጉት ገንዘብ በወጪነት ሳይያዝ ግብር እንዲከፍሉበት የተወሰነ በመሆኑ ይኸው ገንዘብ በወጪነት እንዲያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤውም ወጪ ለመውጣቱ ማስረጃ የቀረበ በመሆኑ በወጪነት ሊያዝላቸው ይገባል በማለት ሲወስን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ውሳኔ ያፀናው ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን የቀረቡት ማስረጃች በግብር ሕጉ በተደነገገው መሠረት ትክክለኛ ሰነዶች ስላልሆኑ በወጭነት ሊያዙ ስለማይገባ ግብር ይከፈልባቸው በማለት ውሳኔ በመሥጠቱ የቀረበ አቤቱታ::

ዉሳኔ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል::

1. የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀጽ 29 «ትክክለኛ» ሰነዶች እንዲቀርቡ የፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ወጪች በቀጥታ ገቢን ለመፈጠር ስለመውጣታቸው በበቂ ሁኔታ ለማረጋገጥ እና ግብር ከፋዩ ሃሰተኛ ሰነድ በማቅረብ የግብር ግዴታውን እንዳይሸሽ ለመቆጣጠር እንጂ የሰነዶችን አዘገጃጀት ሥነ-ሥርዓት መሟላት አለመሟላት ለመቆጣጠር አይደለም::
2. ሰነዶቹ መ/ቤቱ እንዲሟሉ የሚፈልጋቸው ሥርዓቶች ባያማሉ እንኳ ወጪ ለመውጣቱ ሊያረጋግጡ የሚችሉ በቂ ሁኔታችን እስካሳዩ ድረስ ተቀባይነት የማያገኝ በት ሕጋዊ ምክንያት የለም::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሀይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ተገኔ ጌታነህ
4. ወ/ሮ ሆሳዕና ነጋሽ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የኢንጂነር ወርቁ መኮንን የአመልካች ወራሾች ሞግዚት ወ/ሮ ገነት ኤርሲዶ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የቦሌ ክ/ከተማ ገቢዎች መምሪያ - ነ/ፈጅ ገዛኸኝ ኢርኮ ቀረበ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሲሆን አመልካች በይግባኝ አቤቱታቸው ገቢ ለመፍጠር ወጪ ያደረጉት ገንዘብ በወጪነት ሳይያዝ ግብር እንዲከፍሉበት የተወሰነ በመሆኑ ይኸው ገንዘብ በወጪነት እንዲያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን ጉባኤውም ወጪ ለመውጣቱ ማስረጃ የቀረበ በመሆኑ በወጪነት ሊያዝላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሣኔ ያፀናው ቢሆንም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ግን ለድርጅቱ ወጥተዋል የተባሉት ወጪዎችን ለማረጋገጥ የቀረቡት ማስረጃዎች በግብር ሕጉ በተደነገገው መሠረት ትክክለኛ የሆኑ ሰነዶች ስላልሆኑ በወጪነት ሊያዙ ስለማይገባ ግብር ይከፈልባቸው በማለት ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም የቀረቡት ሰነዶች ወጪዎቹ ገቢን ለመፍጠር የወጡ ወጪዎች ለመሆናቸው ለማረጋገጥ ብቃት ያላቸው ሰነዶች በመሆናቸው በወጪዎቹ ላይ ግብር እንዲከፈል መደረጉ የህግ ስህተት ነው የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ደረሰኞቹ በግብር ሕጉ መሠረት የተሰሩ ትክክለኛ ሰነዶች ስላልሆኑ ተቀባይነት ሊያገኙ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከላይ ከተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ይህ ችሎት አመልካች ግብር እንዲከፈሉ የተሰጠው ውሣኔ የገቢ ግብርን ለማስከፈል የወጣውን አዋጅ መሠረት ያደረገ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በገቢ ግብር አዋጁ መሠረት ግብር የተጣለበትን ገቢ የሚሰበስብ ማንኛውም ሰው በአዋጁ በተመለከተው መሠረት ከጠቅላላው ገቢ ላይ ገቢውን ለመፍጠር የወጡ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ በሚገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ግብር የመክፈል ሃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም ግብር ከፋይ ገቢን ለመፍጠር ያወጣውን ወጪ ትክክለኛነት ተቀባይነት ሊያገኙ የሚገባቸው ሰነዶች በማቅረብ ወጪዎቹን የማስረዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief
ሽክም አለበት፡፡ የግብር ሰብሳቢው ባለስልጣንም የሚቀርቡለትን ሰነዶች ወጪዎች በትክክል ገቢን ለመፍጠር የወጡ ለመሆናቸው የሚያስረዱ ትክክለኛ ሰነዶች ስለመሆናቸው የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡ የቀረቡለት ሰነዶች ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሃላፊነት የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት እንደመሆኑ መጠን መ/ቤቱ የሰነዶቹን ትክክለኛነት ሊያረጋግጥ የሚገባው እንዴት ነው የሚለው በቀጣይነት መታየት ይኖርበታል፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ የወጣው ግብር ከፋዩ ግብር በተጣለበት ገቢ ላይ የሚፈለገውን ትክክለኛ ግብር እንዲከፍል ለማድረግ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀውም ግብር የሚከፈልበት ገቢ ገቢውን ለመፍጠር የወጣው ወጪ ከጠቅላላ ገቢው ላይ ከተቀነሰ በኋላ በሚገኘው ትርፍ ላይ ብቻ በመሆኑ ገቢን ለመፍጠር የወጡ ወጪዎች ሳይቀነሱ በጠቅላላው ገቢ ላይ ግብር እንዲከፈል ማድረጉ የአዋጁን አላማ የሚንድ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የቀረቡትን ሰነዶች በሙሉ መቀበሉም ግብር ሊከፈልበት የሚገባው ገቢ እንዲቀንስ የሚረዳ ስለሚሆን የሚቀርቡ ሰነዶች ትክክለኛነት በጥንቃቄ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀጽ 29 ለባለስልጣኑ የሚቀርቡ የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች ውስጥ የሚሰፍሩ ሂሳቦች ትክክለኛ በሆኑ ሰነዶች /ቫውቸሮች/ መደገፍ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ ይህ የአዋጁ ድንጋጌ ትክክለኛ ሰነዶች እንዲቀርቡ የፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ወጪዎቹ በቀጥታ ገቢን ለመፍጠር ስለመውጣታቸው በበቂ ሁኔቴ ለማረጋገጥ እና ግብር ከፋዩ ሃሰተኛ ሰነድ በማቅረብ የግብር ግዴታውን እንዳይሸሽ ለመቆጣጠር እንጂ የሰነዶቹን አዘገጃጀት ሥነ - ሥርዓት መሟላት አለመሟላቱን ለመቆጣጠር ባለመሆኑ የሰነዶቹ ይዘት ሊታይ የሚገባው ከዚሁ የአዋጁ አላማ አንፃር ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም ለመ/ቤቱ የቀረቡት ሰነዶች ወጪ ለመውጣቱ የሚያሳዩ በቂ ሁኔታዎችን እስከያዙ ድረስ መ/ቤቱ ሰነዶቹ ሲዘጋጁ ሊሟሉ ያስፈልጋል የሚላቸው ስርዓቶች /ፎርማሊቲዎች/ በሙሉ ባለመሟላታቸው ብቻ ሰነዶቹን ውድቅ ማድረግ ተገቢ አይሆንም፡፡ በእርግጥ የሥርዓቶቹ መሟላት ወጪው መውጣቱን ለማረጋገጥ የተሻሉ ማስረጃዎች ሊያደርጋቸው ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም ሰነዶቹ መ/ቤቱ እንዲሟሉ የሚፈልጋቸው ሥርዓቶች ባያሟሉ እንኳን ወጪ ለመውጣቱ ሊያረጋግጡ የሚችሉ በቂ ሁኔታዎችን እስካሳዩ ድረስ ተቀባይነት ሊያገኙ የማይችሉበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

ወደ ተያዘውም ጉዳይ ስንመለስ አመልካቹ የህንፃ ተቋራጭ ሲሆኑ ግብር የተጠየቁትም ለሚሰሩት የግንባታ ሥራ እንደሆነ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ግብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የተጣለባቸው ይህንኑ ሥራ አከናውነው ገቢ አግኝተዋል በማለት ከሆነ አመልካች ግንባታውን ማከናወናቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን የሥራ ዘርፍ ለማከናወን ደግሞ አሸዋ፣ ድንጋይ የመሳሰሉት ጥሬ እቃዎች መጠቀማቸው እንደማይቀር አከራካሪ አይሆንም፡፡ አከራካሪ ሊሆን የሚችለው ግብር የተጣለበትን የግንባታ ሥራ ለመስራት እነዚህ ጥሬ እቃዎች መገዛት አለመገዛታቸው ሳይሆን ግንባታውን ለመስራት ጥቅም ላይ የዋሉት ጥሬ እቃዎች መጠን እና ዋጋቸው ነው፡፡ አመልካች ሥራቸውን ለማከናወን ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ጥሬ እቃዎች የገዙት ከገጠር የአገሪቱ ክፍል ለመሆኑ የገለፁትን እውነታ ተጠሪ ክርክር እንዳላቀረበበት ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በገጠር የሃገሪቱ ክፍል ለሚደረግ ሽያጭ ደግሞ ማህተም ያለው ደረሰኝ ማግኘት ከባድ በመሆኑ የወጣውን ወጪ ለማረጋገጥ የቀረበው ሰነድ ነጭ ወረቀት መሆኑን አመልካቹ ገልፀዋል፡፡ ግብር ሰብሳቢው መ/ቤትም የቀረበለትን ሰነድ ውድቅ ያደረገውም ሰነዱ ማህተም ያልተደረገበት ነው በሚል ብቻ እንጂ ግብር የተጣለበትን ገቢ ለመፍጠር እነዚህ ጥሬ እቃዎች አልተገዙም ወይም ወጪው የተጋነነ ነው በማለት አለመሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ በዚህ በኩል ያቀረበው ክርክር ቢኖር ኖሮ ከፍ ሲል እንደተባለው ጉዳዩ አከራካሪ ሊሆን ይችል ነበር፡፡ በተጠሪ በኩል ግን እንደዚህ አይነት ክርክር አልቀረበም፡፡ በእቃዎቹ ዋጋና መጠን ላይ ክርክር ሳይቀርብ ወጪ መውጣቱ በተረጋገጠ ጉዳይ ላይ ሰነዱ ማህተም የለውም በሚል ብቻ ሰነዱን ውድቅ ማድረጉ ደግሞ በወጣ ወጪ ላይ ግብር እንዲከፈል የማድረግ ውጤት ስለሚኖረው አዋጁን የሚቃረን አፈፃፀም ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ ለመኪና የሰሌዳ ቁጥር ከመስጠቱ በፊት የሻንሲ ቁጥር እየተመዘገበ ጥገና ሲደረግ የነበረ በመሆኑ የቀረበው የታርጋ ቁጥሩ ያልተመዘገበበት ደረሰኝ መሆኑን መዝገብ ያመለክታል፡፡ በዚህ ደረሰኝ ላይ የሰፈረው የሻንሲ ቁጥር የአመልካች መኪና ለመሆኑ ማረጋገጡን ግብር ሰብሳቢው መ/ቤትም አይከራከርም፡፡ መታየት ያለበት ደግሞ የቀረበው ሰነድ ለአመልካች መኪና ጥገና የተደረገ መሆኑን ማረጋገጡ እንጂ የግድ የመኪናው ሰሌዳ ቁጥር መፃፉ ሊሆን አይገባም፡፡ የሻንሲ ቁጥሩም ቢሆን ከታርጋ ቁጥሩ የበለጠ መኪናው የአመልካች መኪና ለመሆኑ የማረጋገጥ ብቃት አለው፡፡ በመሆኑም ደረሰኙ ጥገና የተደረገለት መኪና የትኛው መኪና ለመሆኑ ማረጋገጥ እየቻለ የታርጋ ቁጥሩ ባለመግለጹ ብቻ ገቢን ለመፍጠር የወጣው ወጪ ላይ ግብር እንዲከፈል ማድረጉ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ለነዳጁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
የወጣውን ወጪ በተመለከተም ከዚህ የተለየ አይደለም። ነዳጅ ለመቀዳቱ በተሰጠው ደረሰኝ ላይ የተመዘገበው የመኪናው ታርጋ ቁጥር የአመልካች መኪና ታርጋ ቁጥር ላለመሆኑ የቀረበ ክርክር ሳይኖር የባለቤቱ ስም ባለመፃፉ ብቻ ሰነዱ ወድቅ ሊደረግ የሚገባበት ምክንያት የለም።

በአጠቃላይ ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ሕጉ የሚያዘው ግብር ከፋዩ የተጣለበትን ግብር የመክፈል ግዴታውን ሳይወጣ እንዳይቀር ለመቆጣጠር በመሆኑ ሰነዶቹ በበቂ ሁኔታ ወጪ መውጣቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ነገሮች ከያዙ በሰነድ አዘጋጃጀት ላይ የተለያዩ ፎርማሊቲዎች ባለመሟላታቸው ብቻ ሰነዱን ውድቅ ማድረጉ፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ውጤቱ ከግብር ሕጉ በመውጣት ግብር እንዲከፈልበት ባልተጠየቀ ገንዘብ ላይ ግብር እንዲከፈል ማድረግ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ሰነዶች የተለያዩ ስርዓቶች /ፎርማሊቲዎች/ ባለማሟላታቸው ብቻ ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት ነው።

<u>ው ሣ ኔ</u>

የጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13065 በጥር 26 ቀን 1996 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።

የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.7813 በሐምሌ 16 ቀን 1995 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በግ/ይ/መ/ቁ. ወ-17 በየካቲት 8 ቀን 1992 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል።

ግራ ቀኙ ወጪ እና ኪሣራ ይቻቻሉ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief





Noble Printing Press

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት



ቅጽ 4

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሚያዝያ 2001 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

ቅፅ 4

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

አዲስ አበባ



የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

የዳኝነት አካሉን አሰራር ግልጽነት እና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ሲባል እንዲሁም ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ወጥነት ባለው የሕግ ትርጉም ችሎቶቹ የሰጧቸውን ውሳኔዎች ከአሁን ቀደም በተለያዩ እትሞች አሳትሞ ማሰራጨቱ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ የአሁኑ እትምም በአንድ በኩል የዚሁ ሂደት ቀጣይ ክንውን ሆኖ መታየት የሚችል ሲሆን በሌላ በኩል ለእትሙ መውጣት ከፍ ሲል ከተመለከቱት ምክንያቶች ሌላ አብይ ምክንያት አለው፡፡ ይኸውም የፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ወጥነት ባለው የሕግ ትርጉም ላይ የተመሠረተ ለማድረግ ሲባል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው በሚሰጠው ውሳኔ የሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ ፍርድ ቤት ዘንድ አስገዳጅነት እንደሚኖረውና አስገዳጅ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎችን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አሳትሞ እንደሚያሰራጭ በአዋጅ ቁ.454/97 መደንገጉ ነው፡፡

በዚህ እትም የተካተቱት ውሳኔዎች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጣቸውና አስገዳጁ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎች ናቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀጣይነትም ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጣቸውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎችን በተከታታይነት አሳትሞ የሚያሰራጭ ሲሆን ዳኞች፣ ሌሎች የህግ ባለሙያዎች እንዲሁም የህግ ተማሪዎች ለአዋጁ ተፈጻሚነት የበኩላችሁን ሚና እንድትወጡ እየጠየቅኩ ለግቡ መሳካት ይጠቅማሉ የምትሏቸውን ሃሳቦች እንድለግሱን ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

ከማል በድሪ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማውጫ

አሰሪና ሠራተኛ

1. **ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ስለማደረግ የስራ ውል** /የሰ.መ.ቁ. 20885/ የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገቢሳ የማነ/
2. **የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን** /የሰ/መ/ቁ/ 15533/ የኢት/ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አዱኛ ገመዳ/
3. **ወደ ሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ** /የሰ/መ/ቁ/ 21730/ ወ/ሮ ፍሬህይወት እርቁ እና የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን/
4. **የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠር** /የሰ.መ.ቁ. 21119/ ቃሊቲ ምግብ አክሲዮን ማህበር እና ማስተዋል ጫኔ/
5. **የስራ ውልን ስለማቋረጥ** /የሰ.መ.ቁ. 21961/ አቶ ግርማ ነጋሽ እና ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር/
6. **የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ ስራ ላልተሰራበት ውዝፍ ደሞዝ የሚከፈልበት ስላለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 20457/ የኢት/ንግድ ባንክ እና ወ/ሮ አለሚቱ ሞገስ/
7. **ስለ መሠረታዊ የህግ ክርክር** /የሰ.መ.ቁ. 24153/ አቶ መንግሥቱ አባተ እና የባህር ትራንዚት ድርጅት/
8. **የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን** /የሰ.መ.ቁ. 16653/ ግዮን ሆቴሎች ድርጅት እና ወ/ሮ ስለእናት ወርቅነህ/
9. **ሰራተኛው በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 25526/ መምህር ጥላሁን አስፋው እና አዲስ ኮሌጅ/

ውል

1. **ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጉም ስላለመቻላቸው** /የሰ.መ.ቁ. 15662/ የኢት/ልማት ባንክ እና ሐጂ አብዱራህማን ቴሊሳ/
2. **ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሳሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ በሌሎች ላይ ስላለው ውጤት** /የሰ.መ.ቁ. 19081/ አቶ ዓሊ ቃሌብ አህመድ እና እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ/

3. **የኪራይ ውል በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ስለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 23320/ አቶ ገብሩ አብሌ እና እነ አቶ ሁሴን አብዱረህማን ወራሾች/
4. **ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጉም ስላለመቻላቸው** /የሰ.መ.ቁ. 14493/ የኢት/ልማት ባንክ እና አቶ ሚደቅሳ ቱለማ/
5. **የውል አብዛኛው ግዴታ በተፈፀመ ጊዜ የተወሰነ ቀሪ ገንዘብ አለመከፈሉ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሰረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሰኝ ምክንያት ስላለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 18768/ ወ/ሮ አለሚቱ አግዛቸው እና እነ ወ/ሮ ዝናሽ ሀይሌ/
6. **የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ** የሰ/መ/ቁ 21448/ ወ/ሮ ጮርፌ ወርቀነህ እና እነ ወ/ሮ አበራሽ ዱባርጌ

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ

1. **በአፈጻጸም ጉዳይ በስህተት በፍ/ባለመብት እጅ ስለገባ የከተማ መሬት ይዞታ** /የሰ.መ.ቁ. 15557/ ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁና አቶ ብርሃኑ ተሊሳ/
2. **የወጪና ኪሣራ አወሳሰን** /የሰ.መ.ቁ. 22260/ የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ/
3. **ጉድለት ያለበት ሃራጅ ቀሪ ሲደረግ ሻጭና ገዢን ወደነበሩበት ለመመለስ ስላለመቻል** /የሰ.መ.ቁ. 17984/ የጌዲዮ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት እና ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ/
4. **አንድ ፍርድ ተፈጸመ ሊባል የሚገባው ለፍርድ ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ ሲደርሰው ስለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 19205/ አቶ ሽኩር ሲራጅ እና አቶ መላት ካሳ/

ንብረት

1. **አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ሆነ የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግሥት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገወትና አስፈላጊም ከሆነ**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሸጥ የሚያደርግ ውሣኔ መሬት የመንግሥት ለማድረግ የወጣውን ሕግ የሚፃረር ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 19479/ ወ/ሮ አመለወርቅ ገለቱ ወራሾች እና እነ አቶ ቢሻው አሻሜ/

2. **የሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው በተዋዋዮች ላይ ውላቸውን በመዝገቡ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ የማይጥልባቸው ስለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 16109/ አቶ ከበደ አርጋው እና የኢት/ንግድ ባንክ/
3. **ለረጅም አመታት በመንግሥት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ያለአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 14094/ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና የአቶ ሰለሞን ወረዳ ወራሽ/

ጋብቻ

1. **ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677 መሠረት በቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈጻሚ ስለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 17937/ ወ/ሮ ድንቁ ተድላ እና እነ አቶ አባተ ጫኔ/
2. **ስለ ጋብቻ መፍረስ** /የሰ.መ.ቁ. 20938/ ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ እና ወ/ሮ ሣራ ልነጋነ/

ልጅነት ይታወቅልኝ

ልጅነትን ስለማስረዳት /የሰ.መ.ቁ. 22243/ እነ ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ እና አቶ አብርሃም ካሳ/

ውርስ

1. **ኑዛዜ ህጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል ስላለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 17058/ አቶ አንበሶ ወ/ገብርአል እና አቶ መሣይ መኮንን/
2. **የኑዛዜ እያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትና ተናዛዥም ሆነ ምስክሮች /አማኞች/ በኑዛዜው ባሰፈሩት ቃላትና ሃረጎች ሊሰጡ የሚችለውን ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 22172/ አቶ እንደሻው በቀለ እና እነ ወ/ት አይናለም ያለው/

ኢንሹራንስ

መድን ሰጪ የካሳን ክፍያ በተመለከተ በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ /የሰ.መ.ቁ. 22162/ አፍሪካ ኢንሹራንስ እና አቶ ብስራት ጎላ/

የአስተዳደር ህግ

1. **የጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚተዳደሩ ስለመሆናቸው** /የሰ.መ.ቁ. 23339/ የኢት/ጉምሩክ ባለሥልጣን እና እነ አበሮ ኢርጋኖ/
2. **ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 16195/ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ስላሴ/
3. **የጉምሩክ ባለስልጣን በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ** /የሰ.መ.ቁ. 22317/ የምስራቅ ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እና አቶ አብዱ አሉ አዩ/

ወንጀል

ጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ የጥብቅና ስራ እሰራለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል የማታለል ወንጀል ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 12025/ አቶ ምናሴ አልማውና ዓቃቤ ህግ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ ከማል በድሪ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን እቁበዮናስ
ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

ተጠሪ፡- አቶ ገቢሣ የማነ

የስራ ክርክር - ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የስራ ውል - የስራ ውል መቋረጥ - አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 9፣ 10

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ ወደ ስራ ሊመለሱ ይገባል ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9 በአንድ አሰሪና ሠራተኛ መካከል የተደረገ የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ እንደሆነ ግምት ቢወስድም አሰሪ ይህንን ግምት አንቀጽ 10 ላይ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች በማስረዳት ማፍረስ ይችላል፡፡
2. አሰሪው ከሰራተኛው ጋር በጽሁፍም ሆነ በቃል ያደረገው ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ መደረጉን የሚያሳይ ጥቅል ሃሳብ ማስቀመጡ ብቻውን ውሉ በአንቀጽ 10 መሠረት የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በቂ አይሆንም፡፡
3. በአሰሪና ሠራተኛ መካከል የተደረገውን ውል ለመተርጎም ተዋዋዮች ውሉን ባደረጉበት ጊዜ የነበራቸውን የሃሳብ አንድነት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

የሰ/መ/ቁ/ 20885
ጥር 3/1999

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
3. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ
5. ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

ተጠሪ፡- አቶ ገቢሣ የማነ

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረገን የሥራ ውል የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ከሥራ ያላግባብ ያሠናበታቸው መሆኑን በመግለጽ ወደ ሥራ እንዲመልሣቸው ክስ ያቀርባሉ፡፡ አመልካች ደግሞ ወቅታዊ ሥራ ለማከናወን ለተወሠነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኛ በመሆናቸው የተቀጠሩበት ሥራና ጊዜ ሲያበቃ መሠናበታቸው ተገቢ ነው በማለት ይከራከራል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤትም ሥንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ይወስናል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ያፀናል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሥራ ውል የተወሰነ ሥራ ለመስራት የተደረገ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ጉዳዩን ለሠበር ችሎት በማስቀረቡ ግራ ቀኙ ክርራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ውሉ የተደረገው ወቅታዊ ሥራን ለማከናወን በመሆኑ የተቀጠሩበት ሥራና ጊዜ በማለቁ መሆኑን ገልጿል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ነው ወይስ ለተወሰነ ሥራና ለተወሰነ ጊዜ ነው የሚለው ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው፡፡

የሥራ ውል ስለሚቆይበት ጊዜ የሚመለከተው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9 በአንድ አሠሪና ሠራተኛ የሚደረገው የሥራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ መሆኑን የሕግ ግምት ይወስዳል፡፡ ሆኖም ይህ የሕግ ግምት ሊፈርስ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ደግሞ በአንቀጽ 10 ሥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመልክተዋል፡፡ በመሆኑም አንድ አሠሪ ሠራተኛው የተቀጠረው ላልተወሰነ ጊዜ ሣይሆን ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ መሆኑን በማስረዳት በአንቀጽ 9 ሥር የተመለከተውን የሕግ ግምት ማፍረስ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አሠሪው ከሠራተኛው ጋር በጽሁፍም ሆነ በቃል ያደረገው ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ መደረጉን የሚያሣይ ጥቅል ሃሣብ ማስቀመጡ ብቻውን ውሉ በአንቀጽ 10 መሠረት የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በቂ አይሆንም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ውሉ በአንቀጽ 10 ሥር በተዘረዘሩት ሁኔታዎች በአግባቡ መደረጉን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በሁለቱ መሃከል የተደረገውን ውል ለመተርጎምም ተዋዋዮቹ ውሉን ባደረጉበት ወቅት የነበራቸው የሃሣብ አንድነት መመርመር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረገን የሥራ ውል በተመለከተ ይህ ችሎት የሰጠውን የሕግ ትንታኔ ከመ/ቁ 11924 መመልከት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ወቅታዊ ሥራ ለማከናወን እ.ኤ.አ. ከ14/4/2000-15/10/2000 የተቀጠሩ መሆኑን በሁለቱ መሃከል የተደረገው የጽሁፍ ውል ያመለክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የተቀጠሩት ሠልጣኞች ሥልጠና አጠናቀው እስኪወጡ የማሠልጠኛው ምግብ ቤት ምግብ አዘጋጅ ሆነው እንዲሠሩ መሆኑን በአመልካች በኩል በሥር ጀምሮ የቀረበውን ክርክር ተጠሪ በዚህ ሁኔታ አልተቀጠርኩም በማለት ክደው አልተከራከሩም፡፡ ማሠልጠኛው ወደ ኮሌጅ ያደገ በመሆኑ ሥራው ቀጣይነት ስላለው ልሰናበት አይገባም በማለት ነው የሚከራከሩት፡፡ ነገር ግን አንድ አሠሪ ሥራው ቀጣይነት ቢኖረውም እንኳን የሥራ ብዛትን ለማቃለል፣ እየተቋረጠ የሚሠራ ሥራ ወይም ቋሚ ሣይሆን አንዳንዴ የሚሠራን ሥራ ለማሠራት ሠራተኛን ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ ለመቅጠር የሚችል መሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 10 ሥር ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም አመልካች ተጠሪን የቀጠረው በወቅቱ ለነበሩት ሠልጣኞች ምግብ እንዲያዘጋጅ በመሆኑና ሠልጣኞቹ ሥልጠናውን ጨርሰው ስለወጡና ተጠሪ የተቀጠሩበት ወቅታዊ ሥራና ጊዜ ሲጠናቀቅ መሠናበታቸው ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ስለዚህም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱበት ሁኔታ ከሕግ ውጪ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ የሕግ ሥህተት ያለበት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1774 በ14/06/97 እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 37579 በ23/10/97 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በአግባቡ በመሆኑ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የሰበር መ/ቁ.15531

የካቲት 6/99 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

” አሰግድ ጋሻው

” መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ የኢት/ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን

መልስ ሰጭ፦ አቶ አዱኛ ገመዳ

የስራ ክርክር - የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን የወል የስራ ክርክር - የግል የሥራ ክርክር - የግል የስራ ክርክር - የሰ/መ/ቁ/18180

ተጠሪው ከደረጃዬ ዝቅ ተደርጌያለሁ ብለው በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያቀረቡትን ክስ ቦርዱ የማየት ስልጣን አለው ሲሉ የምዕ/ኦሮሚያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የምዕ/ኦሮሚያ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የወል የስራ ክርክር ጉዳዮችን ነው፡፡
2. አንድ የሥራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡
3. አንድ የስራ ክርክር የግል የስራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀርብ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡
4. ከደረጃዬ ዝቅ ተደርጌያለሁ ተብሎ የሚቀርብ ክስ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ.15531
የካቲት 6/99 ዓ.ም

ዳኞች፦ 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. " አሰግድ ጋሻው
3. " መስፍን ዕቁበዮናስ
4. ወ/ት ሂሩት መለሠ
5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ የኢት/ኤሌክትሪክ ኃ/ኩ/ነ/ፈጅ እመቤት ለማ ቀረበች
መልስ ሰጭ፦ አቶ አዱኛ ገመዳ ቀረበ

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድን ስልጣን የሚመለከት ነው።

በመ/ሰጭ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ክሱ የቀረበው ደረጃዬ ዝቅ ተደርጓል በሚል ነው። አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክሱን ለማየት ስልጣን አለው በማለት የተሰጠ ነው። አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት መ/ሰጭ መልሱን አቅርቧል።

ችሎቱም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የሚታዩ የስራ ክርክሮች ምን አይነቶች ናቸው የሚለውን የሕግ ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበለትን ውሣኔ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሯል።

ይህ ችሎት በመ/ቁ. 18180 አግባብነት ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎች በመተርጎም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የወል የስራ ክርክር ጉዳዮችን ነው፣ አንድ የስራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፤ በአንፃሩ አንድ የስራ ክርክር የወል ሣይሆን የግል የስራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀርብ ሆኖ ሲገኝ ነው በማለት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።

መ/ሰጭ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ደረጃዬ ዝቅ ተደርጓል በሚል ያቀረበው ክስ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የስራ ክርክር አይደለም በመሆኑም ጉዳዩን ለማየት የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ስልጣን ያለው ባለመሆኑ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

የምዕ/አሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ.ቁ. ታህሣሥ 25/1995 የሰጠው ውሣኔና አሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 00692 በ21/7/96 የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል።
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ።
መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የሰ/መ/ቁ. 21730
11/7/99

ዳኞች፦ 1. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ
4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ
5. ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች፦ ፍሬህይወት እርቁ

ተጠሪ፦ የኢት. ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

የስራ ክርክር - ህግ ወጥ የስራ ውል ማቋረጥ - ወደ ስራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ - አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43(5)

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ከስራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል ሲሉ ቢወስኑም ውዝፍ ደሞዝን በተመለከተ ሳይወስኑ በዝምታ በማለፋቸው የቀረበ አቤቱታ ነው።

ውሣኔ፡ - የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡና ውሳኔ ተሻሽሎ ተጠሪ የዘጠኝ ወር ከ23 ቀን ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈላቸውና ሌሎች ወጪና ኪሳራዎች እንደመሰለው እንዲወስን ጉዳዩ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ተወስኗል።

1. የስራ ውሉ በሕገ ወጥ መንገድ የተቋረጠና ወደ ስራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት ከስድስት ወር የማይበልጥ ደሞዝ ሊወሰንለት ይገባል።
2. ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሰራተኛው መመለስ ውሳኔ ከፀና ከአንድ አመት ያልበለጠ ውዝፍ ደሞዝ ፍርድ ቤቱ ሊወሰንለት ይገባል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 21730
11/7/99

ዳኞች፡- 1. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ
4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ
5. ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- ፍሬህይወት እርቁ

ተጠሪ፡- የኢት. ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

መዝረቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግንቦት 19 ቀን 1997 ዓ.ም. 01990 በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 16 ቀን 1997 ዓ.ም. ጽፋ ባቀረበችው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ የሥራ ውሌን ያቋረጠው በሕገወጥ መንገድ መሆኑን ተቀብለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ ድንጋጌን በመጣስ የውዝፍ ደመወዝ ጥያቄዬን በዝምታ አልፈውታል በማለት አመልክታለች፡፡ ይህ ችሎት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰኔ 9 ቀን 1998 በዋለው ችሎት አድምጧል፡፡ የአመልካች የሥራ ውል በሕገ ወጥ መንገድ መቋረጡ ከተረጋገጠና ወደ ሥራ እንዲመለስ ከተወሰነ ውዝፍ ደመወዝ ሳይወሰን ማለፉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ይህ ችሎት መርምሯል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ መሠረት የሥራ ውሉ በሕገወጥ መንገድ የተቋረጠና ወደ ሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ከስድስት ወር የሚይበልጥ ውዝፍ ደመወዝ ሊወሰንለት የሚገባ መሆኑን፣ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሠተኛው ወደ ሥራ መመለስ ውሣኔ ከፀና ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ውዝፍ ደሞዝ ፍ/ቤቱ ሊወስን እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው በሕገወጥ መንገድ ነው በማለት አመልካች ወደ ሥራ እንድትመለስ ወስነው የጠየቀችው ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈላት አለመወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

ይህ ችሎት የጉዳዩን አጠቃላይ ሁኔታ በመመርመር አመልካች ከሥራ ታግዳ በነበረችበት ጊዜ ያለው ከመጋቢት 23 ቀን 1996 እስከ ነሐሴ 20 ቀን 1996 /የ4 ወር ከ28 ቀናት ደሞዝ/ በተጨማሪ የሥራ ውሉ ከተቋረጠ ከነሐሴ 21 ቀን 1996 ጀምሮ ወደ ምድብ ሥራዋ ተመለሰች እስከተባለበት ጥር 16 ቀን 1997 ዓ.ም. ድረስ ያለው የ4 ወር ከ25 ቀን ደሞዝ እና ሌሎች ወጭና ኪሣራዎች ሊከፈል በሚገባው መጠን ላይ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ሕ/ቁ. 343/1/ እንዲመለስ ታዟል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠበር መ/ቁ. 21119
መጋቢት 18/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
" አሰግድ ጋሻው
" መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሠ
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- ቃሊቲ ምግብ አክሲዮን ማህበር

መልስ ሰጭ፡- ማስተዋል ጫኔ

የስራ ክርክር - የህመም ፈቃድ - የእረፍት ፈቃድ - የስራ ውል መቋረጥ - አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 85(2)

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ውሣኔ፡ - የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. የህመም ፈቃድ ህመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው የ12 ወር ጊዜ ውስጥ በተከታታይ ወይም በተለያዩ ጊዜያት ቢወስድም በማንኛውም ሁኔታ ከስድስት ወር አይበልጥም፡፡
2. የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠር የስራ ቀናትን ብቻ በመለየት ሳይሆን ህመሙ ከደረሰበት ቀን አንስቶ በመቁጠር በጠቅላላው ከ6 ወር መብለጥ የለበትም፡፡
3. በህመም ምክንያት 6 ወር በላይ በስራ ላይ አለመገኘት የስራ ውልን ለማቋረጥ ህጋዊ ምክንያት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠበር መ/ቁ. 21119
መጋቢት 18/99 ዓ.ም

ዳኞች፦ 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. " አሰግድ ጋሻው
3. " መስፍን ዕቁበየሱስ
4. ወ/ት ሂሩት መለሠ
5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ ቃሊቲ ምግብ አክሲዮን ማህበር ነ/ፈጅ ፈለቀ ዋቆ ቀረበ
መልስ ሰጭ፦ ማስተዋል ጫኔ ቀረበ

ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10144 የካቲት 24/97 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38753 ሐምሌ 12/97 ዓ.ም የቀረበለትን ይግባኝ በመሠረዝ በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው።

የአሁን መልስ ሰጪ በሥር ያቀረበው ክስ በየካቲት ወር 1994 ዓ.ም በድንገት በመታመሙ ለ9 ወር ያህል ህክምና ሲከታተል መቆየቱን ገልፆ፣ በህመም ምክንያት የቀረበት የሥራ ቀን ታስቦ 6 ወር በህመም ፈቃድ ቀሪው 3 ወር ደግሞ የሥራ ቀን ብቻ ተቆጥሮ በዓመት ፈቃድ ታስቦ በግል ማህደሩ ተመዝግቦ እያለ ተከሣሽ ታህሣሥ 4/95 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ያለግባብ የሥራ ውሉን በማቋረጡ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራው እንዲመለስ ያመለከተበት ነው።

ክሱ የቀረበለት የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመርና በፍ/ቤቱ ትእዛዝ መሠረትም የሰዓት መቆጣጠሪያው እንዲቀርብ ካደረገ በኋላ ከታህሣሥ 01/94 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 01/95 ዓ.ም በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ በሰዓት መቆጣጠሪያው ላይ ምልክት ተደርጉ በህመም ፈቃድ ተጠሪው የቀረበት ጊዜ ለ164 ቀናት ብቻ በመሆኑ፣ እንዲሁም ለ38 ቀናት ደግሞ የዓመት ፈቃድ እንደተሰጠው በአጠቃላይ በሕመም ምክንያት የቀረው ለ164 ቀናት ብቻ በመሆኑ 6 ወር ስላልሞላው ተከሣሽ የከሣሽን የሥራ ውል ያቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 85(2) ውጪ ስለሆነ ሕገወጥ የሥራ ውል ማቋረጥ ነው በማለት የ6 ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራው እንዲመለስ ወስኗል። ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቀርቦም ይግባኙ ተሠርዞ መዝገቡ ተዘግቷል።

ይህ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ ላይ ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለውም ተጠሪ በህመም ምክንያት ከሥራ ቀረባቸው የተባሉበትን ቀናት የሥር ፍ/ቤቱ የተከተለው ስሌት በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ነው።

ይግባኝ ከቀረበበት ፍርድ ወይም ውሣኔ ላይ መረዳት እንደተቻለው የአሁን ተጠሪ በህመም ምክንያት ከየካቲት ወር 1994 ዓ.ም ጀምሮ የሥራ ውሉ እስከተቋረጠበት ታህሣሥ ወር 1995 ዓ.ም ድረስ ከ9 ወር በላይ በሥራው ላይ ያልተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል። ፍ/ቤቱ የጊዜውን አቆጣጠር ያሰላው በሰዓት መቆጣጠሪያው ላይ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለ164 የሥራ ቀናት ከሥራ መቅረቱን ምልክት የተደረገበትን ብቻ በመውሰድ ሲሆን፣ ይህም በአዋጁ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 85(2) መሠረት የ6 ወር ጊዜ አላለፈም በማለት ነው።

የህመም ፈቃድ ጊዜን አስመልክቶ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 85(2) ላይ በግልጽ የተደነገገው ግን ሕመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው የ12 ወር ጊዜ ውስጥ በተከታታይ ወይም በተለያዩ ጊዜያት ቢወሰድም በማንኛውም ሁኔታ የህመም ፈቃድ ከ6 ወር አይበልጥም የሚል ነው ይህም የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠሩ የሥራ ቀናትን ብቻ በመለየት ሣይሆን ህመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያው ቀን አንስቶ በመቁጠር በጠቅላላው ከ6 ወር መብለጥ እንደሌለበት ሕጉ በግልጽ የደነገገው ነው።

ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቱ ከዚህ የሕግ ድንጋጌ ውጪ የ6 ወራት የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠሩ የሥራ ቀናትን ብቻ የሚመለከት እንደሆነ አድርጉ በመውሰድ በሕጉ አተረጓጐሙ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል።

ው ሣ ኔ

1. የፌዴ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10144 የካቲት 24/97 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38753 ሐምሌ 12/97 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል።
2. መልስ ሰጪው በህመም ምክንያት ከ6 ወር በላይ ሥራው ላይ ባለመገኘቱ የአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 85(2) ድንጋጌን መሠረት በማድረግ የሥራ ውሉ መቋረጡ በአግባቡ ነው ብለናል።
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።
4. የዚህ ውሣኔ ቅጅም ለሥር ፍ/ቤቶቹ ይተላለፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 21961

መጋቢት 18/99 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

” አሰግድ ጋሻው

” መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ አቶ ግርማ ነጋሽ

ተጠሪ፦ ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማ

የሰራ ክርክር - የሰራ ውል ማቋረጥ - አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)ሐ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ከስራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱ አይገባም ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ ነው።

ውሣኔ፡ - የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል።

ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት ያልተከራከሩበትንና በጭብጥ ያልተያዘን መሰረት አድርጐ ውሳኔ መስጠት መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው።

የሰ/መ/ቁ. 21961

መጋቢት 18/99 ዓ.ም

ዳኞች፦ 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ” አሰግድ ጋሻው

3. ” መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ አቶ ግርማ ነጋሽ = ጠበቃ አቶ መስፍን አዲስ ቀረበ

ተጠሪ፦ ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማ = የቀረበ የለም

ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የፌዴሬ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35171 ጥቅምት 10/98 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴሬ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16343 ጥቅምት 29/97 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በመሻር በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው።

የአሁን አመልካች በሥር ያቀረበው ክስ በተጠሪው ድርጅት ውስጥ ከጥር 21/95 ዓ.ም ጀምሮ በሹፌርነት ተቀጥሮ ሲያገለግል መቆየቱን ጠቅሶ፣ ተከሣሽ ሰኔ 8/96 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ 50 ኪ.ግ.ማዳበሪያ አጉድለሀል በሚል ውንጀላ ከሕግ ውጪ የሥራ ውሉን በማቋረጡ የአገልግሎትና ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው።

የአሁን ተጠሪም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ፦ አመልካች እንዲያስረክብ ከተሰጠው 400 ኩንታል ማዳበሪያ ውስጥ 50 ኪ.ግ.ወይም አንድ ከረጢት ማዳበሪያ አጉድሎ በሸቀጥ መረከቢያ ሠነድ ቁጥር 4191 በሆነ 399.5 ኩንታል ብቻ ማስረከቡ ስለተረጋገጠና እርሱም ስላመነ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሐ) መሠረት የሥራ ውሉ መቋረጡ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክሯል።

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤትም በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክርና ማሰረጃ መርምሮ በተከሣሽ ድርጅት የሚሠጥ ትእዛዝ መሠረት ከጅቡቲ ወደብ ከሣሽ ይዞ የመጣውን 400 ኩንታል ማዳበሪያ ሙሉ በሙሉ ግንደወየን የሚባል ቦታ I S C O ጥቁር አባይ ለተባለ ድርጅት በተረካቢዋ በወ/ሮ ቅድስት ማሞ ተረካቢነት እንዳስረከበ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን መዝግቦታል። በተከሣሽ ድርጅት የቀረበውን የሠነድ ማስረጃ በተመለከተም በከሣሽ መኪና አምባሰል የንግድ ሥ/ን/የተ/የግል ማህበር የደረሰው ማዳበሪያ 399.5 ኩንታል መሆኑን ከማስረዳት በስተቀር ከሣሽ 400 ኩንታል ማዳበሪያ ተረክቦ 399.5 ኩንታል ለአምባሰል ማስረከቡን ስለማያረጋግጥ ከሣሽን ለጉደለው 50 ኪ.ግ. ማዳበሪያ ተጠያቂ የሚያደርገው አይደለም ሲል የከሣሽ የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት ባቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ መርምሮ ክፍያው እንዲፈፀም ወስኗል።

የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ የይግባኝ ክርክሩ ከተካሄደ በኋላ ፍ/ቤቱ በመጨረሻ የሰጠው ውሣኔ የአሁን አመልካች 400

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኩንታል ማዳበሪያ ስለመረከቡና 50 ኪ.ግ.መጉደሉ አከራካሪ ባለመሆኑ፣ አመልካች በተጠሪው ትእዛዝ ለታዘዘበት ድርጅት አስረክቤያለሁ ቢልም አስረክብኩ ያለበት የሠነድ ማስረጃ ግን ስርዝ ድልዝ ያለው በመሆኑ፣ ዋናው ቅጅም የቀረበ ስላልሆነ ማስረጃው ተዓማኒነት የሌለው ነው።በዚህም መሠረት አመልካቹ የተረከበውን ማዳበሪያ ሲያስረክብ መጉደሉ አከራካሪ ባለመሆኑ አመልካች ለጉድለቱ ኃላፊ ተደርጉ የሥራ ውሉ መቋረጡ በአግባቡ ነው በማለት የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤቱን ውሣኔ ሽሮታል።

ይህ አቤቱታ የቀረበውም በመጨረሻ የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ሲሆን፣ ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለውም የፌዴራ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት ክርክር ያልተነሣበትን በማስረጃነት የቀረበን ሠነድ ተዓማኒነት የለውም ሲል የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ነው።

አመልካች በአቤቱታው ላይ እንደገለፀው ከተጠሪው በተሰጠኝ የጭነት ትእዛዝ መሠረት 400 ኩንታል ማዳበሪያ ከጅቡቲ ወደብ ተነስቼ ግንደወይኒ በመድረስ ISCO ጥቁር አባይ ለተባለው ድርጅት ቅድስት ማሞ ለተባለች ተረካቢ አስፈርሜ ሙሉ በሙሉ ስለማስረከቤ ከተከሣሽ የተሰጠኝ የጭነት ማዘዣው ያስረዳል። ይህ የጭነት ማዘዣም የራሱ የተጠሪው መሆኑን አልካደም። ተጠሪው በስር ሲከራከር የነበረውም ያቀረብኩትን የጭነት ማዘዣ ሠነድ ማስረጃ አምኖ ነው። የከፍተኛው ፍ/ቤት የጭነት ማዘዣ ሠነዱን የተቸው ተጠሪው ያልተከራከረበትንና ያልካደውን ይልቁንም ያመነውን ነጥብ ፍ/ቤቱ በራሱ አነሻሽነት ማስረጃው ተዓማኒነት የለውም ሲል የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ የሻረው የዳኝነት አሰጣጥ መርህን የሚያፋልስ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ውሣኔው ተሽሮ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤቱ ውሣኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነው።

ችሎቱም ጉዳዩ ለሠበር ይቀርባል በተባለው ነጥብ ዙሪያ የሥር ክርክርና ማስረጃውን አቤቱታ ከቀረበበት ፍርድ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል።

አመልካች ከተጠሪ በተሰጠው የጭነት ማዘዣ መሠረት ከጅቡቲ ወደብ 400 ኩንታል ማዳበሪያ ጭኖ ግንደወይኒ በተባለ ቦታ ISCO ጥቁር አባይ ለተባለ ድርጅት እንዲያስረክብ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት 400 ኩንታል ማዳበሪያውን በተባለው ቦታ አድርሶ ወ/ሮ ቅድስት ማሞ ለተባለች ተረካቢ አስፈርሞ ያለጉድለት ሙሉ በሙሉ ያስረከበበትን ማሰረጃ ማቅረቡ በሥር ፍ/ቤት ተረጋግጧል። ይህ የማስረከቢያ የሠነድ ማሰረጃም በማስረጃነት ቀርቦ ተከሣሽ (የአሁን ተጠሪ) በሠነዱ ላይ ያቀረበው ተቃውሞ ወይም ክዶ የተከራከረበት ነገር እንደሌለም የሥር ክርክሩ ያስረዳል። ኋላ ግን ንብረቱን ግንደወይን ጣቢያ ከሣሽ/የአሁን አመልካች/ እንዲያስረክብ የታዘዘው ስህተት እንደሆነ ተገልፆ እንደገና ጭነቱን ጭኖ ከአምባሰል የንገድ ሥራዎች ኃ/ይተ/የግል ማህበር እንዲወሰድ ሲታዘዝ አስቀድሞ ያስረከበውን ንብረት እንደገና ሲጭን አንድ ከረጢት ወይም 50 ኪ.ግ.ማዳበሪያ መጉደሉ መረጋገጡ በአመልካች በኩል የተፈጠረ ጉድለት ስለመሆኑ ተጠሪው ያስረዳበት ነገር የለም። በተጠሪው በኩል የቀረበው ማስረጃ የሚያሣየው አምባሰል የንግድ ሥ/ኃ/የተ/የግል ማህበር ንብረቱን ሲረከብ 399.5 ኩንታል ማዳበሪያ ለመሆኑና የመረከቢያ ሠነድ ቁጥር 4191 አንድ ከረጢት ወይም 50 ኪ.ግ. ማዳበሪያ የጉደለ መሆኑን ከሚያስረዳ በስተቀር ጉድለቱ በከሣሽ የተፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ አይደለም። በዚህም አንድ የማይካድ ነገር ቢኖር 50 ኪ.ግ ማዳበሪያ መጉደሉ ግልጽ ነው። የአሁን አመልካች ግን በመጀመሪያ አስረክብ በተባለው ቦታ ሙሉ በሙሉ ያለጉድለት 400 ኩንታል ማዳበሪያ አስፈርሞ ማስረከቡን የሚያስረዳ ማስረጃ ሲያቀርብ ማስረጃው ሀሰተኛ ነው ተብሎ

በተጠሪው የተካደ አይደለም። አስረክቦት የነበረውን ንብረት እንደገና ሲጭን ግን አንድ ከረጢት ወይም 50 ኪ.ግ ማዳበሪያ ጉደለ መባሉ በአመልካች የተፈጠረ ጉድለት መሆኑን የሚያሣይ አይደለም።

የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ለጉድለቱ አመልካችን ተጠያቂ ያደረገው አስቀድሞ ሙሉ በሙሉ ያለጉድለት አስረክብኩ ያለበትን የሠነድ ማስረጃ ተጠሪው አምኖ የተቀበለውንና ክዶ ያልተከራከረበትን እምነት የሚጣልበት ማስረጃ አይደለም በማለት ተችቶ ውድቅ ካደረገ በኋላ ጉድለት መኖሩ ብቻ መረጋገጡን መሠረት አድርጉ አመልካችን ተጠያቂ ያደርገዋል በሚል ነው። ይህ ደግሞ የግራ ቀኙን ክርክርና ሞግዚት ያላገናዘበና መሠረት ያላደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

1. የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 35171 ጥቅምት 10/98 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
2. የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16343 ጥቅምት 29/97 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል።
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ተጠሪው ለአመልካች ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) ይከፈል ብለናል።
4. የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የወጪና ኪሣራውን ጨምሮ እንዲያስፈጽም ታዟል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠበር መ/ቁ. 20457

መጋቢት 20/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

” አሰግድ ጋሻው

” መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኢት/ንግድ ባንክ

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ዓለሚቱ ሞገስ ወራሽ

የስራ ክርክር - የስራ ውል ማቋረጥ - ውዝፍ ደሞዝ ክፍያ፡፡ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 43፣ 53(1)፣ 54 የሰ/መ/ቁ. 17189

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበተችው በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ የስድስት ወር ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏት ወደ ስራ ልትመለስ ይገባል ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ውሣኔ፡ - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. በአሰሪና ሠራተኛ ክርክር አንድ ሰራተኛ በክርክር ላይ እያለ በሞት ቢለይ ወደ ስራ የመመለስ ወይም አለመመለስ ጉዳይን ማጣራቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡
2. የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ ስራ ላልተሰራበት ውዝፍ ደሞዝ የሚከፈልበት አይደለም፡፡

የሠበር መ/ቁ. 20457

መጋቢት 20/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ” አሰግድ ጋሻው

3. ” መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሰ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኢት/ንግድ ባንክ ነ/ፊጅ ዘውዱ ዓለ. ቀረበ

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ዓለሚቱ ሞገስ ወራሽ የቀረበ የለም

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የአሁን መ/ሰጭ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ የተቋረጠ ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደሥራዬ እንድመለስ በማለት ክስ በማቅረቧ፣ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10440 የካቲት 28/97 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንደከሣሽ ጥያቄ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ በመቋረጡ የ6 ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏት ወደሥራዋ ትመለስ ሲል ውሣኔ የሰጠበት ነው፡፡ የአሁን አመልካች በውሣኔው ላይ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ይግባኙ ተሠርዞበታል፡፡

አመልካች ይህን አቤቱታ ያቀረበውም በዚሁ ውሣኔ ላይ ሲሆን፣ ለሰበር ይቀርባል የተባለበት ነጥብም መልስ ሰጭዋ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራዋ ትመለስ የሚለው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ለመስማት ቀጠሮ እንደተያዘ መልስ ሰጪ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቷ ወራሾች የወራሽነት ማስረጃ ይዘው ቀርበዋል፡፡

መልስ ሰጪ ከዚህ ዓለም በሞት መለየቷ ከተረጋገጠ ደግሞ ወደ ሥራ የመመለስ አለመመለስ ጉዳዩን ማጣራቱ አስፈላጊ ስላልሆነ የክርክሩ ሂደት በዚሁ ተቋርጧል፡፡

የውዝፍ ደመወዝ ክፍያውን በተመለከተም ይህ ችሎት በመ/ቁ. 17189 አግባብነት ያለው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 53(1)፣ 54 እና 43 ድንጋጌዎችን በመተርጉም የሥራ ውሉ በተቋረጠበት ጊዜ ሥራ ላልተሠራበት ውዝፍ ደመወዝ የሚከፈልበት አይደለም ሲል አስቀድሞ ውሣኔ ሠጥቶበታል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጉዳይም የሥራ ውሉ ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ ላልተሠራበት ሥራ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10440 የካቲት 28/97 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38002 ሰኔ 22/97 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሰርዟል፡፡
2. የዚህ ውሣኔ ቅጂም ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠበር መ/ቁ. 24153
መጋቢት 26/99 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
" አብዱልቃድር መሐመድ
" አሰግድ ጋሻው
" መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሠ

አመልካች፦ አቶ መንግሥቱ አባተ
ተጠሪ፦ የባህርና ትራንዚት ድርጅት

የስራ ክርክር - የስራ ውል መቋረጥ - ያለማስጠንቀቂያ ከስራ መሰናበት -አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ተ)

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበተው በህጋዊ መንገድ ነው ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ውሣኔ፡ - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

ሀሰተኛ የተባለ የትምህርት ማስረጃ ቀርቦ አልታየም፣ የቅጥር ፎርም ላይ ተጠቀሰ የተባለ በእኔ የተሞላ አይደለም የሚለው ክርክር የማስረጃ ጥያቄ እንጂ መሠረታዊ የህግ ክርክር አይደለም፡፡

የሠበር መ/ቁ. 24153
መጋቢት 26/99 ዓ.ም

ዳኞች፦ 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. " አብዱልቃድር መሐመድ
3. " አሰግድ ጋሻው
4. " መስፍን ዕቁበዮናስ
5. ወ/ሪት ሂሩት መለሠ

አመልካች፦ አቶ መንግሥቱ አባተ ቀረበ
መልስ ሰጪ፦ የባህርና ትራንዚት ድርጅት የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

አመልካች የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19788 በ14/4/98 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔና የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 43690 በ21/7/98 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ሲል ግንቦት 24/98 ዓ.ም የተፃፈ የተሻሻለ አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ለመ/ሰጪ ደርሶ የካቲት 1/98 ዓ.ም የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡

ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው አመልካች ለቅጥር ያቀረበው የትምህርት ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑ ስለተረጋገጠ በሕ/ስምምነቱም ሆነ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ተ) መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ መሠናበቱ በአግባቡ ነው ተብሎ ውሣኔ በመሰጠቱ ነው፡፡

አመልካች በአቀረበው አቤቱታም ሀሰተኛ የተባለው የትምህርት ማስረጃ ቀርቦ አልታየም፣ የቅጥር ፎርሙ ላይ ተጠቀሰ የተባለውም በእኔ የተሞላ አይደለም የሚለው ክርክር የማስረጃ ጥያቄን የሚመለከት እንጂ መሠረታዊ የሕግ ክርክር ያለው ሆኖ ባለመገኘቱ በፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19788 በ14/4/98 የተሰጠው ውሣኔም ሆነ የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43690 በ21/7/98 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡ ግራ ቀኙ ኪሣራቸውን ለየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 16653

ቀን መጋቢት 27/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. " አሰግድ ጋሻው

3. " መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- ግዮን ሆቴሎች ድርጅት

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ስለእናት ወርቅህ

የስራ ክርክር - የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን - የወል የስራ ክርክር - የሰ/መ/ቁ/18180

ተጠሪዋ የስራ መደቡ እንዲሁም ለቦታው የተመደበው ደሞዝና ጥቅማ ጥቅሞች እንዲሰጡኝ ብለው በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያቀረቡትን ክስ ቦርዱ የማየት ስልጣን አለው ሲሉ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ውሣኔ፡ - የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የወል የስራ ክርክር ጉዳዮችን ነው፡፡
2. አንድ የሥራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡
3. አንድ የስራ ክርክር የግል የስራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀርብ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡
4. የሥራ መደቡ እንዲሁም ለቦታው የተመደበው ደሞዝና ጥቅማ ጥቅሞች እንዲሰጡኝ ተብሎ የሚቀርብ ክስ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል አይደለም፡፡

የሰበር መ.ቁ. 16653

ቀን መጋቢት 27/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. " አሰግድ ጋሻው

3. " መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- ግዮን ሆቴሎች ድርጅት ነ/ፊጅ አቶ ስለሺ ቀረበ

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ስለእናት ወርቅህ አልቀረበችም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድን ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡

መልስ ሰጪ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክሱን ያቀረበችው የሥራ መደቡ እንዲሁም ለቦታው የተመደበው ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች እንዲሰጡኝ በሚል ነው፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክሱን ለማየት ሥልጣን አለው በማለት የተሰጠ ነው፡፡ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ያቀረበው የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት መ/ሰጪ መልሷን አቅርባለች፡፡

ችሎቱም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የቀረበለትን የሥራ ክርክር ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም? የሚለውን የሕግ ነጥብ መሠረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ይህ ችሎት በመ.ቁ. 18180 አግባብነት ያላቸውን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎች በመተርጉም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የማየት ሥልጣን የተሰጠው የወል የሥራ ክርክር ጉዳዮችን መሆኑን፣ አንድ የሥራ ክርክር የወል የሥራ ክርክር ነው የሚባለውም ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የማያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን በአንፃሩም አንድ የሥራ ክርክር የወል ሣይሆን የግል የሥራ ክርክር ጉደይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሠርተኛ /ሠራተኞች/ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ ሲገኝ መሆኑን በዝርዝር የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በዚህ የሕግ ትርጉም መሠረት መልስ ሰጪ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የሥራ መደቡና ለቦታው የተመደበው ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች ይሰጡኝ በማለት ያቀረበችው ክስ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የሥራ ክርክር አይደለም፡፡ በመሆኑም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ሥልጣን ሣይኖረው ጉዳዩን አይቶ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

- የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ/ቁ. 193/02/94 ጥር 13/96 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 28606 ሐምሌ 5/96 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 25526

ሚያዝያ 16/99 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- መምህር ጥላሁን አስፋው

መልስ ሰጪ፡- አዲስ ኮሌጅ

የስራ ክርክር - ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የስራ ውል - የስራ ውል መቋረጥ - አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 9፣ 10

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት ህጋዊ በሆነ መንገድ ስለሆነ ወደ ስራ ሊመለሱ አይገባም ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ውሣኔ፡ - የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

1. የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9 በአንድ አሰሪና ሠራተኛ መካከል የተደረገ የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ እንደሆነ ግምት ቢወስድም አሰሪ ይህንን ግምት አንቀጽ 10 ላይ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች በማስረዳት ማፍረስ ይችላል፡፡
2. ሰራተኛው በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው አይሆንም፡፡

የሰ/መ/ቁ. 25526

ሚያዝያ 16/99 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- መምህር ጥላሁን አስፋው ቀረበ፡፡

መልስ ሰጪ፡- አዲስ ኮሌጅ ጠበቃ አምዴ አበበ ቀረበ

መዝገቡ ተመረምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች ሰኔ 15/98 ዓ.ም. በተፃፈ ያቀረበው አቤቱታ የፌዴ/ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 5/98 ዓ.ም. በመ/ቁ. 46514 በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበበት የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔም፡- የቅጥሩ ሁኔታ በአንድ ድርጅት ቋሚ ሥራ ላይ ቢሆንም ሠራተኛን ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ሥራ ማሠራት እንደሚቻል በፌዴ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 11924 ከተሰጠው የሕግ ትርጉም መረዳት ስለሚቻል አመልካች የተቀጠሩበት የተወሰነው ጊዜ በማለቁ ምክንያት መሰናበታቸው ሕገወጥ ነው አያሰኝም በማለት የፌዴ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሚያዝያ 4/98 ዓ.ም. በቁ. 16344 የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መነሻነትም አመልካች የተቀጠረው ለተወሰነ ጊዜ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለ ሲሆን መ/ሰጪም መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ታሕሣሥ 7/98 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡

የመልስ ሰጪ ዋና መከራከሪያ የሥራ ውሉ ለአንድ ዓመት ሆኖ የውሉ ዘመን ሲያልቅ በዚሁ ሁኔታ ውሉ እየተደረገ ሲሠሩ የቆዩ ሲሆን ግራ ቀኙ ካልፈለጉ ሊያቋርጡ ከፈለጉም ያለፈው የአገልግሎት ሂሣብ ተዘግቶ እንደገና በሌላ ውል የኮንትራት የቅጥር ውል በስምምነት እየተፈረመ ሲሠሩ የቆዩ በመሆኑ የከሣሽ አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ አመልካች በ11/01/98 በተፃፈ ማመልከቻ ብቻ የሥራ መልቀቂያ ጠይቀው የተሰናበቱ ናቸው ሲልም በተጨማሪም የተከራከረበት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጀመሪያ ደረጃ የአሁን አመልካች የሥራ መልቀቂያ ጠይቆ የተሠናበተ ነው የተባለበትን በዚህ ችሎትም አስቀርበን እንደተመለከትነው በ11/01/98 ዓ.ም. አመልካች የፃፈው ኮሌጁን በመልቀቁ ምክንያት የሥራ ልምድ ይሰጠኝ ከሚል በስተቀር ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለቅቄያለሁ በማለት ያስታወቀበት ነው ሊባል የሚችል እንዳልሆነ ተመልክተናል፡፡ የሥራ ልምድ ይፃፍልኝ ብሎ መጠየቅ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለቀቀ የሚያስብለው ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

የቅጥሩ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ለአንድ ዓመት እየተባለ ጊዜው ሲያልቅ እንደገና እየታደሰ እንደ አዲስ የሚታይ ነው፡፡ በዚህም ጊዜው ሳያልቅ ውሉን ማቋረጥ ይችላል የሚለውን ክርክር በተመለከተ ቀደም ሲል የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 11924 በሰጠው ትርጉም፡- አንድ ከአሰሪ ጋር የሥራ ውል ያለው ሠራተኛ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ ሊቆጠር እንደሚገባ የአዋጅ ቁጥር 42/85/377/96/ አንቀጽ 9 ግምት እንደሚወሰድለት፣ በዚህ የሕግ ግምት የሥራ ውሉ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ነው ሲል የሚከራከረው ሠራተኛ ተጠቃሚ በመሆኑ ይህን ክርክሩን የሚደግፍለት ማስረጃ በቅድሚያ ያቀርብ ዘንድ እንደማይጠበቅበት፣ ይልቁንም በሕግ የተወሰደለት ግምት ክርክሩን ከማስረዳቱ ግዴታው ነፃ እንዲሆን እንደሚያደርገው፣ በውጤቱም በቅድሚያ የማስረዳቱ ግዴታ የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረጉ ለውጥ በአንቀጽ 10 የሚሸፈን ነው ሲል በሚከራከረው በአሠሪው ላይ የሚወድቅ መሆኑን በዝርዝር ጠቅሶ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሠራ መቆየቱና የአመልካች የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ አመልካችን ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው አይሆንም፡፡ መ/ሰጪው ይህንን አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 10/1/ መሠረት አመልካች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ እንደሌለ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ መሆኑን ከፍርዱ ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡

ስለዚህ የቅጥር ውሉ በጊዜ የተገደበ መሆኑን ብቻ የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በማየትና የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 11924 የሰጠውን የሕግ ትርጉም በአግባቡ ባለመረዳት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 5/98 ዓ.ም. በመ/ቁ. 46514 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ሚያዝያ 4/98 ዓ.ም. በቁ. 16344 የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በማጽናት ወስነናል፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰበር መ/ቁ. 15662

መጋቢት 13 **ቀን** 1999 **ዓ.ም**

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኢት/ልማት ባንክ

ተጠሪ፡- ሀጅ አብድራህማን ቱሊሳ

የውል ክርክር - የብድር ውል - የሽያጭ ውል - በሽያጭ ምክንያት ጉድለት ያለበት ነው በማለት የሚቀርብ ክስ ይርጋ - ስለ ውል ትርጉም - በተንኮል የተፈጸመ ውል - የፍ/ብ/ሕግ ቁ.2298፣ 1733

አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የብድር ውል ፈርሶ ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ ሊመለሱ ይገባል ሲሉ የአሳባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የአሳባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ዳኞች ለመተርጎም አይችሉም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 15662

መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፦ መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ የኢት/የ ልማት ባንክ ነገረፈጅ አቶ አክሊሉ ተስፋዬ

ተጠሪ፦ ሀጅ አብድራህማን ቱሊሳ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለውሣኔ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው የአላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባፀናው ውሣኔ ቅር በመሰኘቱ ነው።

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ በልዩ ወረዳው ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ ሆኖ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ አመልካች አንድ የእህል ወፍጮ ሊተክልልኝ ሐምሌ 16 ቀን 1988 ዓ.ም ባደረግነው ስምምነት መሠረት ከሠላም ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ድርጅት ገዝቶ ካስቀመጣቸው አንዱን ተረክቤ ነበረ። ሆኖም አገልግሎት ሣይሰጥ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ችግር እየፈጠረ ባለመሥራቱ ይህንኑ ባሣውቅም መፍትሄ አላገኘሁም ከዚህም በኋላ በተበላሸው ወፍጮ ምትክ ሌላ ወፍጮ ገዝቶ ሊተካልኝ መጋቢት 25 ቀን 1992 ዓ.ም ተዋውለናል። ይሁን እንጂ ተከሣሹ ሁለቱንም ውሎች ተግባራዊ ባለማድረጉና ውሉንም ለህሊና ተቃራኒ እና ተንኮል ባለው ሁኔታ ያስፈረመኝ ስለሆነ ውሎቹ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2287፣ 2290፤ 1823፣ 1824 እና 1808 መሠረት ሊፈርሱ ይገባል የሚል ነው።

የአሁን አመልካችም ከሣሽ የተበደረው ወፍጮ ሣይሆን የብር 40,000.00 /አርባ ሺህ ብር/ የገንዘብ ብድር ስለመሆኑ በውሉ ላይ ተመልክቷል።

የወፍጮው መግዣ ገንዘብ ለአስመጭው ኩባንያ በከሣሽ ስም ወጭ ሆኖ እንደሚከፈል በተስማማው መሠረት ይኸው የብድር ገንዘብ ለአስመጭው ኩባንያ ተከፍሎላቸዋል። ከሣሽ ውሉን አውቆና ተገንዝቦ ከፈረመ በኋላ ወፍጮውን ከኩባንያው ተረክቧል። ወፍጮው የሚፈለግበትን ግልጋሎት ሊሰጥ አልቻለም በሚል ምክንያት የብድሩ ውል ይፍረስልኝ ማለታቸው ተቀባይነት የለውም፤ በብድሩ ገንዘብ የተገዛው ወፍጮ መሥራት ካልቻለ የብድር ስምምነቱ ይፈርሣል የሚልም ግዴታ አልነበረንም፤ አመልካች የፈፀማቸው የተንኮል ተግባራት ምን እንደሆነም አላብራሩም፤ በቁጥር ዋሥአ/031/2000 መጋቢት 12 ቀን 1992 ዓ.ም የተፃፈውም ደብዳቤ ከሣሽ በጠየቁት መሠረት የወፍጮ

መግዣ ብድር እንዲሰጣቸው የሚል እንጂ ምትክ ወፍጮ ለመስጠት አይደለም። ይህንንም በገዛ ፈቃዳቸው ትተውታል በማለት መልስ ሰጥቶበታል።

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ፣

በአንድ በኩል ተደርጓል የተባለው ስምምነት የከሣሽን ግልጽ የሆነ የኑሮ ልማድ ዕውቀት ማጣትን በመጠቀም እንዲሁም ተከሣሽ የመንግሥት የልማት ድርጅት በመሆኑ በውሉ ላይ የተመለከተውን ቃል እንደማያጥፍ በማመን እና ብልሽት ያለበት መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ የማይቀበለውን ግዴታ እንዲቀበል መደረጉ ሆን ተብሎ የማታለል ወይም ሁለተኛ የማግባቢያ ዘዴ በመጠቀም በተንኮል የተደረገ መሆኑን በመጥቀስ ውሉ መፍረስ እንደሚገባው በውሣኔው መሠረት ያደረገ ሲሆን፣

በሌላም በኩል ግራ ቀኙ ቀጥተኛ የወፍጮ ሽያጭ ውል ባያደርጉም በተዘዋዋሪ መንገድ የወፍጮ ብድር መሆኑን ስለሚያመለክትና በብድር የተሰጠውም ወፍጮ ጉድለት ያለበት በመሆኑ የውል ስምምነቱ ፈራሽ ነው ስለሆነም የውል ስምምነቱ ሙሉ በሙሉ ፈርሶ ውል ከመደረጉ በፊት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ በማለት ወስኗል።

በዚህ ጉዳይ ይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፈተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ፣

የብድር ገንዘቡ በእጅ የሚሰጥ ሣይሆን ለወፍጮ መግዣ ባንኩ ለአስመጭው ወጭ አድርጎ የሚከፍለው እንደሆነ ውሉ የሚናገር መሆኑን ጠቅሶ ግሸርው የተፈፀመው በማን ነው የሚለውን በሚመለከት ውሉ መልስ አይሰጥም። እንዲህም በሆነ ጊዜ ከውሉ በኋላ የነበረውን ሁኔታ በማመዛዘን የተዋዋዮቹ ሀሣብ ምን ነበር? የሚለውን መሠረት በማድረግ መታየት አለበት የብድሩ ውል ከተፈረመ በኋላ በወፍጮው ርክክብ ሰነድ ላይ ባንኩ ገዢ መሆኑና ከርክክብ በኋላ በታየው ጉድለት ሣቢያ በሻጭ ላይ ክስ መመስረቱን ስለገለፀ ገዢው ባንኩ መሆኑን ያስረዳል። ተበዳሪው ከመጀመሪያውኑ ባንኩ በብድሩ ገንዘብ ገዝቶ የሚያቀርብለት ወፍጮ እንደማይሰራ ቢያውቅ ኖሮ የብድር ውሉን ባልፈረመ ነበር የሚለውን ተንተርሶ የሥር ፍ/ቤት ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል።

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ነው። የቅሬታ ነጥቦችም፣ ለክሱ መነሻ የሆነው አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ስምምነት ይዘት የገንዘብ ብድር ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች በትርጉም ሰበብ ከውል በኋላ የነበረውን ሁኔታ ማመዛዘን ያስፈልጋል የሚለውን በመያዝ የወፍጮ ሽያጭ ስምምነት ባንክ እንደፈፀመ በመቁጠር የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ፣

ሽያጭ ተከናውኗል እንኳ ቢባል በሽያጭ ምክንያት ጉድለት ያለበት ነው በማለት የሚቀርብ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2298 በአንድ ዓመት መቅረብ ሲገባው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ ጊዜ በኋላ ክስ በማቅረቡ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ ባንኩ የማጭበርበር ተግባር ፈጽሟል በማለት መታለፉ ሕግን መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ፣

አመልካች የተንኮል ተግባር መፈፀሙ ሣይረጋገጥ የማታለል ወይም ሐሰተኛ የማግባቢያ ዘዴ በመጠቀም በተንኮል የተፈፀመ ስምምነት ነው። ተበዳሪው ወፍጮው የማይሠራ መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ የብድሩን ውል ባልፈረመ ነበር በማለት እንደ ውል ማፍረሻ ምክንያት መወሰዱ ሕጋዊ መሠረት የለውም የሚሉት ናቸው።

በዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ መልስ ሰጭ እንዲቀርብ ተደርጎ በሥር ፍ/ቤቶች በየደረጃው ያቀረባቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማጠናከር በሥር ፍ/ቤቶች የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት ዝርዝር መልስ ሰጥቶበታል። የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው ግራ ቀኙ ሐምሌ 16 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት ነው። የዚህ ስምምነት ርዕስ እንደሚያመለክተውና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በውሣኔው ላይ እንደገለፀው ስምምነቱ የገንዘብ ብድር ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም እንዲሁም የብድሩ ገንዘብ ለወፍጮ ግዢ እንደሚውልና ገንዘቡም በቀጥታ በተበዳሪው የሚከፈል ሣይሆን ለወፍጮ አስመጪው ኩባንያ ስለመሆኑ ይኸው ውል ያስረዳል። ይህ ስለመሆኑ ውሉ ግልጽ ነው። ለትርጉም በር የከፈተም አይደለም። ከየትኛው አስመጪ ኩባንያ የሚለውን በሚመለከት በውሉ ላይ በግልጽ ባይመለከትም«... የወፍጮው መግዣ ገንዘብ በአስመጪው ኩባንያ ወጭ ሆኖ ይከፈላል።» በሚል መጠቀሱ የአስመጪውን ኩባንያ ማንነት ምርጫ ለአበዳሪው የተተወ ስለመሆኑ ተበዳሪው አስቀድሞ የተስማማ፤ (መሆኑን) ፈቃድ የሰጠበት መሆኑን ከሚያመለክት በቀር የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው አይደለም። ተጠሪ ከሠላም ሙያና ቴክኒክ ማሰልጠኛ የተባለውን ወፍጮ መረከቡም ይህንኑ አባባል የሚያጠናክር ነው። ይህም የውል ይዘት ባንኩ የወፍጮ ሻጭ መሆኑን አያመለክትም። ሻጭ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለተሸጠው ነገር ጉድለት ኃላፊ ለማድረግ የሚያስችል ሕጋዊ መሠረት የለም። የሥር ፍ/ቤቶች ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጉት ተበዳሪው የተሸጠው ወፍጮ ጉድለት የሚኖርበት መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ ስምምነቱን አይፈጽምም ነበር የሚለውን በመያዝ ነው። ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለፀው የብድሩ ገንዘብ ለወፍጮ መግዣ እንደሚውልና ይህም ገንዘብ በቀጥታ ለተበዳሪው የሚከፈል ሣይሆን ወፍጮውን ለሚያቀርብ አስመጪ ኩባንያ በተበዳሪው ስም ወጭ ሆኖ እንደሚከፈል የሚያረጋግጥ በመሆኑ ውሉ ግልጽ ነው። ወፍጮውን ማን ገዛው የሚለው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተያዘው ጭብጥ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም እንጂ አለው እንኳ ቢባል ተጠሪው እንደስምምነቱ ወፍጮውን ከአስመጪው ኩባንያ መረከቡ ነው። ከተረከበው በኋላ ለሚታየው ጉድለት ንጥጥሩን ወፍጮውን ከአስረከበው ኩባንያ ጋር ከሚያደርግ በቀር በውሉ ባልተመለከተው አበዳሪውን እንደ ሻጭ በመቁጠር የተሸጠው ነገር ጉድለት ተገኝቶበታልና ለጉድለቱ እንደማካካሻ የብድር ስምምነቱ ሊፈርስ ይገባል በማለት ለመጠየቅ

የሚያስችለውን መብት አይሰጠውም። የአበዳሪን ግዴታ በሚመለከት ውሉ ግልጽ ሆኖ እያለም ወፍጮውን ማን ገዛው? የሚለውን በሚመለከት ውሉ ግልጽነት ይጉድለዋል፤ ግልጽ ካልሆነ ደግሞ ከውል በኋላ የተፈፀመውን ተግባር በመንተራስ የተዋዋዮች ሀሣብ ምን ነበረ? የሚለውን በመያዝ መተርጉም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1733 "ውሉታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ የተዋዋዮቹ ፈቃድ ምን እንደነበረ ዳኞች ለመተርጎም አይችሉም" የሚለውን ክልከላ መተላለፍ ነው።

በሌላ በኩል የፈቃድ ጉድለት አለበት በሚል እንደ ውል ማፍረሻ ምክንያት የተወሰደው ተዋዋይ በኑሮ ልማድ ዕውቀት ማነስ የተነሣና አበዳሪውም የመንግሥት ተቋም በመሆኑ ኃላፊነቱን ይወጣል የሚል እምነት በመጣል ምክንያት የተፈፀመ ውል በመሆኑ የማታለል ወይም የተንኮል ተግባር የተፈፀመ መሆኑን ያሳያል በሚል የቀረበው የፍሬ ነገር ክርክር /ማስረጃ በተባለው አኳኋን የፈቃድ ጉድለት የነበረ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አይደሉም። ተቀባይነትም የላቸውም።

በሌላ በኩል አመልካች የተሸጠውን ነገር ገዢ በእጁ ከአደረገ በኋላ ለሚያርሰው አደጋ ኃላፊነቱ በማን ላይ እንደሚወድቅና ጉድለት መኖሩ ከታወቀ ለምን ያህል ጊዜ ክስ ሊቀርብ ይገባዋል የሚለውን በመጥቀስ በአማራጭ ያቀረበው ክርክር ንብረቱን በሸጠው ወገን በኩል የሚቀርቡ መከራከሪያዎች ናቸው። ከላይ እንደተገለፀው በዚህ ጉዳይ አመልካች ሻጭ አይደለም ሻጭ ሣይሆን ያነሣው ክርክር በመሆኑ ይህንኑ የመከራከሪያ ነጥብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም።

ለማጠቃለል ያህል አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ስምምነት ግልጽና ትርጉም የማያስፈልገው መሆኑ እየታወቀ በትርጉም ሽፋን የሥር ፍ/ቤቶች አመልካችና ተጠሪ ሐምሌ 16 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉት የገንዘብ ብድር ውል ፈርሶ ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ ሊመለሱ ይገባል ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ው ሣ ኔ

የልዩ ወረዳው ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በፍ/ብ/መ/ቁ. 3195 በ18/02/96 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 26638 በ4/06/96 ዓ.ም ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በሚል የተሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል።

በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሠ
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ ዓሊ ቃሌብ አህመድ

መልስ ሰጪ፦ እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ

ይርጋ - ይርጋን የማንሳት ኃላፊነት የተከሳሽ መሆኑ - የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677፣ 1901።

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ የቀረበው ክስ በይርጋ ታግዷል ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው።

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል።

1. የይርጋ አፈፃፀም ትርጉም ሊሰጠው የሚገባው በሚቀርበው የክስ ባህሪ አንጻር ነው።
2. በመርህ ደረጃ የይርጋ ጥያቄ በተከራካሪዎች ካልተነሳ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ሊያነሳው አይችልም።
3. ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሣሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ ክሱን መዘጋት ከህጉ ጋር የሚጋጭ አይደለም።

ዳኞች፦ 1. መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አሰግድ ጋሻው
3. መስፍን ዕቁበዮናስ
4. ሂሩት መለሠ
5. ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ ዓሊ ቃሌብ አህመድ - አልቀረበም

መልስ ሰጪ፦ 1ኛ/ አቶ ሚሊዮን ተፈራ - አልቀረበም
2ኛ/ ኮሜት ትራንስፖርት - ነገረፈጅ - ላቀው ክብረት ቀረቡ
3ኛ/ ኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ - አልቀረበም

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ሦስተኛ መልስ ሰጭ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ አመልካች በ1ኛና በ2ኛ ተከሣሾች ላይ ያቀረበውን ክስ ሙምር ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት ነው በሚል ነው። መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነው አመልካች በሦስቱም መልስ ሰጪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በ2ኛ ተከሣሽ ትእዛዝ፣ በአንደኛ ተከሣሽ አሽከርካሪነት ሲንቀሣቀስ የነበረው የሦስተኛ ተከሣሽ ንብረት የሆነው መኪና በከሣሽ መኪና ላይ ጉዳት በማድረሱ ለደረሰው ጉዳት ሦስቱም ተከሣሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ተጠያቂ ናቸው ይባልልኝ የሚል ነው። አንደኛው ተከሣሽ ክሱ ደርሶት ያልቀረበ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት ሲቀጥል 2ኛና 3ኛ መልስ ሰጪዎች ግን ቀርበው ተከራክረዋል። የይርጋን ጥያቄ ያቀረበው ግን 3ኛ ተከሣሽ ብቻ ነው። 2ኛ ተከሣሽ ለክሱ መቃወሚያዎችንና መልሱን ያቀረበ ቢሆንም የይርጋ ጥያቄ ግን አላነሣም።

አመልካች ለሰበር ያቀረቡት አቤቱታ 1ኛና 2ኛ መልስ ሰጪዎች ባላነሱትና ባላቀረቡት የይርጋ ጥያቄ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚል ሲሆን 2ኛ መልስ ሰጪ 3ኛ ተከሣሽ ባቀረበው የይርጋ ጥያቄ መነሻነት የአመልካች ክስ በይርጋ መዘጋቱ አግባብ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል።

የቀረበው አቤቱታ የይርጋን ሕግ አፈፃፀም የሚመለከት ሲሆን ይህ ችሎት ትርጉም ሊሰጠው የሚገባው አመልካች ካቀረበው የክስ ባህርይ አንፃር መሆን እንዳለበት አምኖበታል። በመርህ ደረጃ የይርጋ ጥያቄ በተከራካሪዎች ካልተነሣ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሣሽነት ሊያነሣው እንደማይችል በፍትሀ ብሄር ሕጉ በግልጽ ሰፍሮ የሚገኝ ነው። በዚህ ሕግ መሠረት የይርጋን ጉዳይ የማንሣት ወይም ያለማንሣት ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ የተከሣሽ ወገን ነው። ይህ አጠቃላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረተ ሃሣብ ግን በፍትሐብሔር ሕጉ ሌሎች ክፍሎች ከተጠቀሱትና አሁን ከያዝነው ጉዳይ ጋር አግባብነት ካላቸው ሌሎች ድንጋጌዎች ጋር አብሮ መታየት ይኖርበታል።

ከላይ እንደተጠቀሰው የአሁን አመልካች በሦስቱም መልስ ሰጪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ለደረሰው ጉዳት ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ይወሰንባቸው የሚል ነው። በመሆኑም ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሣሾች ስለሚያቀርቡዋቸው መከላከያዎች ሕጉ የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል። የያዝነው ጉዳይ ከውል ውጪ የደረሰ ጉዳይን የሚመለከት ቢሆንም የውል ሕግ መሠረተ ሃሣቦችም ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በሕጉ አንቀጽ 1677 ሰፍሯል። በዚህ መሠረት ያልተነጣጠለ ኃላፊነት ያለባቸው ባለእዳዎችን የሚመለከተው የውል ሕግ ክፍል ለያዝነውም ጉዳይ ቢሆን አግባብነት አለው። የውል ሕግ አንቀጽ 1901 "ባለእዳ የሆኑት ሁሉ እዳው በሙሉ ወይም በከፊል ተከፍሏል ወይም በይርጋ ታግዷል በማለት ባለገንዘቡን ለመከራከር ይችላሉ" በማለት ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ በግልጽ እንደሰፈረው ከተከሣሾች አንዱ የይርጋ ጥያቄ ማንሣት እንደሚችል ግልጽ ነው። በመሆኑም ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሦስተኛውን ተከሣሽ የይርጋ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ክሱን መዝጋቱ ከሕጉ ጋር የሚጋጭ አይደለም። በመሆኑም በዚህ ሰበር ችሎት የሚታረም የሕግ ስህተት የለም።

ው ሣ ኔ

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 145/93 የሰጠው ውሣኔና ከፍተኛው ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 1457/97 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል።

የሰበር መ/ቁ. 23320

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

" ፍስሐ ወርቅህ

" ዓብዱልቃድር መሐመድ

" መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፦ አቶ ገብሩ አብሴ

ተጠሪዎች፦ እነ የአቶ ሁሴን አብዱራህማን ወራሾች

የኪራይ ውል - የኪራይ ውል በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ስለመሆኑ - የዳኝነት አከፋፈል።

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ለ1ኛው ተጠሪ ኪራይ ሊከፍሉ ይገባል ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው።

ውሣኔ፡ - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል።

1. ኪራይ በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ውል ነው።
2. ይዞታን ያስረክቡኝ ተብሎ ለቀረበ ክስ የቤቱ ዋጋ ተገምቶ የዳኝነት ማስከፈል ስህተት ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 23320

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፦ 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. " ፍስሐ ወርቅነህ

3. " ዓብዱልቃድር መሐመድ

4. " መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፦ አቶ ገብሩ ኦብሴ - ከጠበቃ ወንድአወክ አየለ ጋር ቀረበ

ተጠሪ፦ 1. የአቶ ሁሴን አብዳራህማን ወራሾች - ወኪል ቀረበ
2. የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት - ነገረፈጅ ቀረበ
3. የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተተኪ የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል - ነ/ፈጅ ቀረበ

ፍ ር ድ

በሥር ፍ/ቤት የአሁኖቹ አንደኛ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካችና በሁለተኛና ሦስተኛ መልስ ሰጭዎች ላይ በመሠረቱት ክስ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 22 ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 13-15 የጉንደር ቡና ቤት ያለበት ሕንፃ ምርጫ ቤታቸው መሆኑንና በአዋጅም ያልተወረሰ መሆኑ ተረጋግጦ የቤት ቁጥር 013 የጉንደር ቡና ቤትና ምድር ቤቱ ለአሁኑ 1ኛተጠሪዎች በንብረትነት መፈቀዱን ገልፀው የአሁኑ አመልካች በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቤቱን ስላላስረከቡ ከሰኔ 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ ቀደም ሲል በወር 1300 (አንድ ሺ ሦስት መቶ ብር) የነበረው የቤት ኪራይ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው አዲስ ተመን መሠረት ለባለንብረቱ በስድስት ተባዝቶ ማለትም 1300X6= 7,800 (ሰባት ሺ ስምንት መቶ ብር/ ለከሣሽ መክፈል ስላለበት ከሰኔ 1 ቀን 1986 እስከ ጥቅምት ወር 1987 የ5 ወር ሂሣብ ብር 39,000 (ሰላሣ ዘጠኝ ሺ.)ብር 1ኛ ተከሣሽ እንዲከፍል፤ ሁለተኛ ተከሣሽ ከአንደኛ ተከሣሽ ጋር ያለው ኪራይ በመቋረጡ ከሰኔ 1986 ጀምሮ ኪራይ መቀበሉን እንዲያቋርጥ እስከ ጥቅምት ወር 1987 የተቀበለውን ብር 6,500 (ስድስት ሺ አምስት መቶ) ለከሣሽ እንዲከፍል፣ ሦስተኛ ተከሣሽ ለከሣሽ የባለቤትነት ደብተር እንዲሰጥ ጠይቀዋል። የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ፣ አንደኛ ተከሣሽ (የአሁኑ አመልካች) ቀደም ሲል በወር በብር 1300 ከኪራይ ቤቶች ተከራይቶት የነበረውን ቤት ለከሣሾች እንዲያስረክቡ ለአሁኑ ሁለተኛ መልስ ሰጭ የከፈሉት የኪራይ መጠን ታሣቢ ሆኖ በአዲሱ ተመን (የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው)መሠረት የቤቱ ኪራይ በስድስት ተባዝቶ ከሰኔ 1 ቀን 1986 እስከ ጥቅምት ወር 1987 ያለው ብር 39,000(ሰላሣ ዘጠኝ ሺ.) እንዲከፍሉ፤ የአሁኑ ሁለተኛ መልስ ሰጭ ከንብረቱ መመለስ በኋላ የተቀበለውን የኪራይ ልዩነት ለከሣሾች እንዲመልስ፤ በመጨረሻም የባለቤትነት ማረጋገጫ ሠነድ የሦስተኛ ተከሣሽ የነበረውን ኃላፊነት የወሰደው ክፍል እንዲሰጣቸው ተወስኗል።

ይህ የሰበር ቅሬታ የቀረበው የአሁኑ አመልካች የካቲት 14 ቀን 1998 ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው የአሁኑ አመልካች በሰበር ቅሬታ ማመልከቻው ለአሁኑ 1ኛ ተጠሪዎች ይመለስ የተባለውን ድርጅት ከታህሣሥ 29 ቀን 1959 ጀምሮ በድርጅትነት ሲገለገሉበት የቆዩ መሆኑንና ተገቢውንም የቤት ኪራይ ያለማቋረጥ ቀደም ሲል የቤቱ ባለቤት ለነበረው አከራይ ሲከፍሉ መቆየታቸውን ገልፀው፣

የቤቱ ኪራይ በስድስት ተባዝቶ በወር 7800 ብር ሂሣብ ከሰኔ 1 ቀን 1986 ጀምሮ ያለው ለ1ኛ መልስ ሰጭዎች ይክፈሉ መባሉ ሕግና ሥርዓትን የተከተለ አይደለም፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ አወጣው የተባለውም መመሪያ ከ10 ዓመት በፊት በሥራ ላይ እንዳይውል ተብሎ የታገደና ከአዋጁ ጋር የሚቃረን ነው በማለት ነው፤ ይህ ችሎት ታህሣሥ 5 ቀን 1999 በዋለው ችሎት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል።

በዚህ ጉዳይ የአሁኑ አመልካች ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲገለገሉበት የቆየው የድርጅት ቤት ለአሁኖቹ አንደኛ ተጠሪዎች ተከለከለ በሚል ኪራዩ በስድስት ተባዝቶ ያለው ውዝፍ ይከፈል መባሉ በአግቡ መሆን አለመሆኑን ይህ ችሎት መርምሯል።

ይህ ችሎት ከጉዳዩ አጠቃላይ ሁኔታ መረዳት የቻለው ነገር ቢኖር፣ የአሁኑ አመልካች የተጠቀሰውን የድርጅት ቤት ለረጅም ዘመናት የቤቱ ባለቤት ከነበረውና ቤቱን በኪራይ ውል አከራይቷቸው ከነበረው ከ2ኛ ተጠሪ ተከራይተው የኪራይ ውሉ ፀንቶ እስከቆየበት ጊዜ ድረስ ተገቢውን የኪራይ ገንዘብ ለ2ኛ ተጠሪ ሲከፍሉ መቆየታቸው ተረጋግጧል።

የአሁኑ አመልካች የውል ግዴታቸውን በዚህ ሁኔታ ሲወጡ ከመቆየታቸው ውጭ ቤቱ ተመልሰላቸው ከተባሉት ከአሁኖቹ አንደኛ ተጠሪዎች ጋርም ያደረጉት የኪራይ ውል የሌለ መሆኑን ከሥር ክርክሩ ለመገንዘብ ተችሏል። ከሁሉም በላይ የአሁኑ አመልካች የገበያ ዋጋን ለማረጋጋት በሦስተኛ አካል ማለትም በሚኒስቴር መ/ቤት ወጣ ተብሎ በተነገረው መመሪያ ለመገዛት ወደውና ፈቅደው ስለመስማማታቸው የተረጋገጠ አንዳችም ነገር ሣይኖር የሥር ፍ/ቤት የውሉችን መሠረታዊ ጽንሰሐሣብ በሚንድ ሁኔታ የአሁኑ አመልካች በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት በሌለው አካል በተወሰነው መመሪያ መሠረት አመልካች የድርጅት ኪራዩን በስድስት ተባዝቶ ይክፈል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፤ በተጨማሪ ይዞታውን ያስረክቡኝ ተብሎ ለቀረበ ክስ የቤቱ ዋጋ ተገምቶ የዳኝነት ይክፈል መባሉ ስህተት ነው ብለናል።

ው ሣ ኔ

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጥር 26 ቀን 1996 በመ/ቁ. 02631 የአሁኑ አመልካች በአዲስ ተመን መሠረት የመረከብ ግዴታ ያለባቸውን ልዩነት ከሰኔ 1 ቀን 1986 እስከ ጥቅምት ወር 1987 ብር 39,000 (ሰላሣ ዘጠኝ ሺ.) እንዲከፍሉ በማለት የሰጠውም በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29090 በ25/4/98 ያፀናው የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፣

- የአሁኑ አመልካች ረቺ በመሆናቸው በሥር ፍ/ቤት ከፍ ብሎ በተገለፀው የመ/ቁጥር እና ቀን እንዲከፍሉ የተወሰነው የዳኝነትና የጠበቃ አበል ተሽሯል።
- የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፣
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰበር መ/ቁ. 14493

መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኢት/የ ልማት ባንክ

ተጠሪ፡- አቶ ሚደቅሣ ቱሉማ

የውል ክርክር - የብድር ውል - የሸያጭ ውል - ሰለ ውል ትርጉም - በተንኮል የተፈጸመ ውል - የፍ/ብ/ህግ ቁ. 2298፣ 1733 - የሰ. 14493

አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የብድር ውል ፈርሶ ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ ሊመለሱ ይገባል ሲሉ የአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ውሣኔ፡ - የአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ የተዋዋዮች ፍቃድ ምን እንደነበር ዳኞች ለመተርጐም አይችሉም፡፡

ሰበር መ/ቁ. 14493

መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኢት/የ ልማት ባንክ ነገረፈጅ አቶ አክሊሉ ተስፋዬ

ተጠሪ፡- አቶ ሚደቅሣ ቱሉማ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነው አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ግራ ቀኙ ሐምሌ 15 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት ይዘት የገንዘብ ብድርን የሚያመለክት ነው ወይስ የወፍጮ ሽያጭን? በሚለው ነጥብ ላይ ነው የሥር ፍ/ቤቶችም ለዚህ ጭብጥ የእራሣቸውን ትንታኔ በመስጠት በዚህ ጉዳይ አመልካች የኢት/የ ልማት ባንክ የብድሩን ገንዘብ አበዳሪ ሣልሆን የወፍጮው ሽያጭ ነው የሚለውን በመያዝና በተሸጠው ወፍጮ ለታየው ጉድለት ሻጩ ኃላፊ ነው በማለት ውል ሊፈርስ ይገባል በማለት ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን ነው፡፡

ይሁን እንጂ በአመልካች በኢት/የ ልማት ባንክ እና በሌላ ግለሰብ መካከል በተነሣው ክርክር ይኸው ጉዳይ ተነስቶ ይኸው ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መ/ቁ.15662 ለክርክሩ መነሻ የሆነው ተመሣሣይ ስምምነት ለአመልካች የብድር ገንዘብን የሰጠ መሆኑን የሚያመለክት እንጂ የወፍጮ ሽያጭ መሆኑን የማያመለክት መሆኑን ገልፆ ዳኝነት የሰጠበት በመሆኑ ይህም ጉዳይ በዚያው አንፃር ታይቶ ተፈርዷል፡፡

ው ሣ ኔ

በዚህ ጉዳይ የአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 449/91 ግንቦት 04 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠውና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ ተመልክቶ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በመ/ቁ. 2415/95 ህዳር 10 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) ተሽሯል፡፡

ይህ ጉዳይ ስላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 18768

ሚያዚያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ዓለሚቱ አግዛቸው

ተጠሪ ፡- እነ ወ/ሮ ዝናሽ ኃይሌ

የውል ክርክር - የውል መፍረስ፣ የቤት ሽያጭ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1771(1)፣ 1785(2)፣ 1789

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል አመልካች ስም እንዲዛወር ፈቃደኛ ስላልነበሩ ውሉ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ተዋዋይ ወገኖች መሰረታዊ ያልሆኑና ጥቃቅን የሆኑ ምክንያቶችን ብቻ በመስጠት ውል ማፍረስ እንዳይችሉ ዳኞች ውሉ እንዲፈርስ ሊያደርጉ የሚችሉት ውሉ ባይፈርስ ከፍ ያለ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ብቻ ነው፡፡
2. የውል አብዛኛው ግዴታ በተፈፀመ ጊዜ የተወሰነ ቀሪ ገንዘብ አለመከፈሉ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሠረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሰኝ ምክንያት አይደለም፡፡

የሰ/መ/ቁ. 18768

ሚያዚያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

2. አቶ አሰግድ ጋሻው

3. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ዓለሚቱ አግዛቸው - ወኪል አቶ አግዛቸው ገ/ሚካኤል ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- እነ ወ/ሮ ዝናሽ ኃይሌ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበው የውል መፍረስን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ በወረዳ 15 ቀበሌ 26 የሚገኘውን ቁጥር 495 የሆነውን ቤት አሁኗ አመልካች ብር 9.000/ዘጠኝ ሺህ/ ሽጠው ብር 6.000/ ስድስት ሺህ/ ከተከፈላቸው በኋላ ቀሪውን ገንዘብ አመልካች ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ውሉ ቀሪ ሆኖ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ቀሪ ገንዘባቸው ያልተከፈላቸው በውሉ ላይ የተመለከተውን ግዴታዎች ባለመወጣታቸው በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በውሉ መሠረት ስም እንዲዛወር ፈቃደኛ ያልነበሩት አመልካች ካልሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት አመልካች የገዙትን ቤት እንዲያስረክቡና ተጠሪዎች የተቀበሉትን ብር 6.000 /ስድስት ሺህ/ እንዲመልሱ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በድምፅ ብልጫ መዝገቡን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሠረት ዘግቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው። ይህ ችሎትም ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን በመመርመር አቤቱታው ለሠበር እንዲቀርብ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል። ፍ/ቤቱም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል።

የአሁን ተጠሪዎች ለአመልካች ቤት መሸጣቸውን፣ ቤቱንም ማስረከባቸውን ከተዋዋሉት ብር 9.000 /ዘጠኝ ሺህ/ ውስጥ ብር 6.000 /ስድስት ሺህ/ መቀበላቸውን አምነዋል። ውሉ እንዲፈርስ የጠየቁት ከሺያጩ ዋጋ ቀሪው ብር 3.000 /ሦስት ሺህ/ ባለመከፈሉ ነው።

ውልን ስላለመፈፀም በሚመለከተው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1771/1/ ከተዋዋዮቹ አንዱ የውሉን ግዴታ ያልፈፀመ እንደሆነ ውሉ ያልተፈፀመለት ወገን የውሉን መፍረስ ሊጠይቅ እንደሚችል ይገልፃል። እንዲሁም የዚሁ ክፍል አንቀጽ 1789 ውሉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ያልተፈፀመ ከሆነ ዳኞች በአንደኛው ወገን ጠያቂነት ውሉን ሊያስቀሩት እንደሚችሉም ተመልክቷል። በአንድ በኩል ህጉ ውል አልተፈፀመልኝም የሚለው ወገን ውሉ እንዲፈርስለት ለመጠየቅ እንዲችል መብት ሰጥቶታል በሌላ በኩል ግን ዳኞች በውሉ ላይ አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ካልሆነ በቀር ውሉ እንዳያፈርሱ ህጉ ግዴታ ይጥልባቸዋል /የፍ/ህ/ቁ.1785/2/ ይመለከቷል/። ተዋዋይ ወገኖች መሠረታዊ ባልሆኑና ጥቃቅን የሆኑ ምክንያቶችን ብቻ በመስጠት ውል ማፍረስ እንዳይችሉ ዳኞች ውሉ እንዲፈርስ ሊያደርጉ የሚችሉት ውሉ ባይፈርስ ከፍ ያለ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ብቻ ነው።

በተያዘው ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት አነስተኛ ድምጽ እንዳሠፈረው የውሉ አመዛኙ ግዴታ ተፈጽሟል። ገዥ /አመልካች/ የሸያጩን አብዛኛውን ክፍያ ፈጽመው ቤቱንም ተረክበዋል። አልተፈፀመም የሚባለው ቀሪው የብር 3,000 /ሦስት ሺህ/ ክፍያ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሠረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሠኝ ምክንያት አይደለም።

በዚህም መሠረት ቀሪው ገንዘብ አልተከፈለም በማለት ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29696 ሰኔ 4/1996 የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32497 ጥር 30/1997 በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
2. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም።
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ። መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ።

የሰ/መ/ቁ/ 21448
ሚያዚያ 30/1999

ዳኞች፡- አቶ መንበረጸሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጎርፌ ወርቅነህ
መ/ሰጭዎች፡- እነ ወ/ሮ አበራሽ ደባርጌ

የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል - የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል አፃፃፍ ፎርም - የሽያጭ ውልን ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ወይም በፍርድ ቤት ፊት ስለማድረግ - የሽያጭ ውልን በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ መመዝገብ - የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1723፣ 1727፣ 2877፣ 2878፡፡

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመልስ ሰጭዎችና በአመልካች አውራሽ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በህጉ ተቀባይነት ያለው ነው ሲል የሰጠውን ውሳኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሳኔ</u>፡- የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. **የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ውሎች በህግ ፊት የሚፀኑ እንዲሆኑ ሁለት መስፈርቶችን ሟሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመጀመሪያው መስፈርት ውሉ በፅሁፍ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ውሉ በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ፊት መከናወኑ ነው፡፡**
2. **የፍ/ብ/ህግ ቁ.1723(1) የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት ፊት እንዲደረግ የሚጠይቀው በተዋዋዮች መካከል በሕግ ፊት የሚፀና ውል እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡**
3. **የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2878 የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ምዝገባ እንዲከናወን የሚጠይቀው ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡፡**
4. **ልዩ ህግ ከአጠቃላይ ህግ ቅድሚያ ይሰጠዋል** (the special prevails over the general) **የሚለው የተለመደው የህግ አተረጓጎም ስልት ተግባራዊ የሚሆነው ሁለት የህግ ድንጋጌዎችን አንድ ላይ ተግባራዊ ማድረግ ሳይቻል ሲቀር ብቻ ነው፡፡**
5. **“ስለ ውሎች በጠቅላላው” ምዕራፍ ስር የሚገኘው የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1723 እና “ስለማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ” ስር የሚገኘው የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2877 ድንጋጌዎች መካከል ልዩነት ቢኖርም በመካከላቸው ግልፅ የሆነ ግጭት የሌለ በመሆኑና የማይንቀሳቀስ ንብረትን ባለቤትነት ለማስተላለፍ ከሌሎች ውሎች የበለጠ ጥንቃቄና ጥበቃ ስለሚሻ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሽያጭ ውልን የአፃፃፍ ፎርም በሚመለከት ገዢ ድንጋጌ መሆን ያለበት የተለየና ጥብቅ መስፈርት የሚያስቀምጠው የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1723 ነው፡፡**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ.ቁ. 21448

ዳኞች፡ - አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሃመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡ - ወ/ሮ ጉርፌ ገ/ሕይወት

መልስ ሰጪ፡ - 1) ወ/ሮ አበራሽ ዱባርጌ 2) አቶ ጌታቸው ነጋ

ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የማይንቀሳቀስ ሀብት (ቤት) ሽያጭን የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች አቅርበውት በነበረው ከወራሽነት ጋር የተያያዘ የንብረት ክፍፍል ክስ ነው፡፡ አመልካች አባታቸው አጋዝ ገ/ሕይወት ወልደየስ ከአንደኛዋ መልስ ሰጪ ጋር በጋብቻ አብረው ሲኖሩ ያፈሩትና በወረዳ 24 ቀበሌ 09 የሚገኝና ቁጥሩ 011 የሆነ ቤት የጋራ መሆኑን በመግለጽ የሚቹን የአባታቸውን ድርሻ ያካፍሉኝ የሚል ክስ ለፍርድ ቤት አቀረቡ፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠቃሹ ቤት የጋራ ነው በማለት አመልካች በቤቱ ላይ ግማሽ ባለድርሻ ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጠ፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ 2ኛ መልስ ሰጪ አቶ ጌታቸው ነጋ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ይኸው ውሳኔ የኔን ይዞታ የሚያጠቃልል በመሆኑ ውሳኔው ይለወጥልኝ በማለት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁ. 358 መሠረት የመቃወም ማመልከቻ አቀረቡ፡፡ 2ኛ መልስ ሰጪ ለዚህ ማመልከቻ መሠረት ያደረጉት በ1985 ፈፀምኩ የሚሉት የሽያጭ ውል ነው፡፡ 2ኛ መልስ ሰጪ ባቀረቡት ማመልከቻ 1ኛ መልስ ሰጪና ባለቤታቸው አጋዝ ገ/ሕይወት ወልደየስ በ23/03/85 በተፃፈ የሽያጭ ውል አንድ ጅምር ቤትና 400 ካሬ ሜትር ቦታ በብር 16,500.00 (አስራ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ብር) የሸጡላቸው መሆኑን በመግለጽ ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ እንዲለውጥ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

የአሁን አመልካች 2ኛ መልስ ሰጪ ባቀረቡት መቃወሚያ ላይ መልስ እንዲያቀርቡ ተደርገው 2ኛ መልስ ሰጪ ገዛሁ የሚሉት ቤት የቤት ቁጥር ካልተገለፀና ደብተር ከሌለው ገዝቻለሁ ሊሉ እንደማይችሉ፣ ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ በ1985 ዓ.ም ጅምር ቤት ያልነበረ መሆኑን፣ ሟች ውሉ በተፈፀመበት ወቅት በእድሜ የገፉና ሕመምተኛ ስለነበሩ ውሉ ተቀባይነት እንደሌለው፣ ተፈረመ በተባለው ውል ላይ ያለው የጣት ፊርማ የሟች አለመሆኑን፣ የፍርድ አፈጻጸም መምሪያ መሃንዲስ በ1992 ክርክር የተነሳበትን ቤት ማህደር በማስቀረብ የ2ኛ መልስ ሰጪ መሆኑን የሚያመለክት ሰነድ አለማግኘቱን መግለጹን በመዘርዘር ውሉ ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የአሁንዋ አንደኛ መልስ ሰጪ በሌላ በኩል ከባለቤታቸው ጋር በመሆን ውሳኔ ያረፈበትን ቤት በከፊል ለአሁን 2ኛ መልስ ሰጪ ሸጠው በውሉ መሠረት ለ2ኛ መልስ ሰጪ ያስረከቡ መሆናቸውን በመግለጽ ወደ ክርክሩ ቢገቡ ተቃውሞ እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት በ2ኛ መልስ ሰጪ በቀረበው የሽያጭ ውል ላይ ያለው ፊርማ የሟች የአጋዝ ገ/ሕይወት መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ጉዳዩን ለፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ክላክ በኋላ ተመርማሪው የጣት ፊርማ በውስጡ በቂ ዝርዝር ማስረጃ የለውም በማለት ለመለየት መቸገሩን እንደገለፀለት በፍርዱ መዝግቧል፡፡ ይህ ሪፖርት ከቀረበለት በኋላ በግራ ቀኙ የቀረቡትን ምስክሮች ሠምቶ በ2ኛ መልስ ሰጪ የቀረበው የሽያጭ ውል ተቀባይነት ያለው ነው በማለት ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ በከፊል አሻሽሏል፡፡

የአሁን አመልካች በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን ውድቅ አድርጐታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት የሽያጭ ውሉ ይፀናል ሲል የሰጠው ውሳኔ እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡

መልስ ሰጪዎች የአመልካች የሰበር አቤቱታ እንዲደርሳቸው ከተደረገ በኋላ በዚህ ችሎት ፊት የቃል ክርክር ተካሂዷል፡፡

በዚህ በቀረበልን ጉዳይ መፍትሄ የሚፈልገው ዋነኛ ጥያቄ የማይንቀሳቀስ ሀብት ሽያጭ ሊከተለው የሚገባው የውል አጻጻፍ ፎርም ምን ዓይነት ነው የሚለው ነው፡፡ በዚህም መሠረት ይህ ችሎት የቤት ሽያጭን በሚመለከት በኢትዮጵያ ሕግ ማዕቀፍ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ዳስሷል፡፡ የማይንቀሳቀስ ሀብትን የሚመለከቱ የአጻጻፍ ፎርም ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ሕጉ የተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ በመሆናቸው የነዚህን ድንጋጌዎች ግንኙነትና ልዩነትም ተመልክቷል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ የተሰጠው የቤት ሽያጭ ውል በጽሑፍ መሆኑን በቂ ነው ከሚል አጠቃላይ መንደርደሪያ የተነሳ መሆኑ ከውሳኔው አጠቃላይ ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሉ በእርግጥ ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም የሚለውን ጥያቄ ለማጣራት ማስረጃ እንዲቀርብ ከማድረጉ በስተቀር ውሉ በእርግጥ ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት አሟልቷል ወይስ አላሟላም የሚለውን የሕግ ነጥብ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የቤቱን ሽያጭ በሚመለከት በሁለቱ ወገኖች መካከል መስማማት ነበር ወይስ አልነበረም የሚለውን የፍሬ ነገር ጉዳይ ከማጣራት አልፎ በመካከላቸው መስማማት አለ እንኳን ቢባል ሕጉ የሚፈቅደውን ሥርአት ተከትሎ የተፈጸመ ውል ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ዋነኛ ነጥብ አልተመለከተም፡፡ ይህ የሰበር ችሎት ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ የነበረውን የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ለማስተናገድ ጣልቃ ልግባ ብሎ የጠየቀው 2ኛ መልስ ሰጪ በሕግ የሚፀና የሽያጭ ውል ነበረው ወይስ አልነበረውም የሚለው የሕግ ነጥብ ይበልጥ አግባብነት የነበረው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ይህን የሕግ ነጥብ ለመፍታት ደግሞ ውሉ ላይ የነበሩ ምስክሮችን አስቀርቦ ከመስማት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይልቅ ሕጉ የሚያስቀምጠው መስፈርት መሟላት አለመሟላቱን ማጣራት ትክክለኛው አካሄድ ነው። በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በ2ኛ መልስ ሰጪ በአንድ በኩል በ1ኛ መልስ ሰጪ እና በሚቹ ባለቤታቸው በሌላ በኩል ተፈፀመ የተባለውን የቤት ሽያጭ ውል ሕልውና ለማረጋገጥ ምስክሮችን ከመስማቱ በፊት የቀረበውን ሰነድ ሕጋዊ ጠቀሜታ መመርመር ነበረበት። በዚህ ረገድ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተከተለው አሰራር ትክክለኛ አልነበረም።

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ2ኛ መልስ ሰጪ የቀረበውን መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ቀድሞ የሰጠውን የአመልካች የወራሽነት ጥያቄ ያሻሻለው ህዳር 23 ቀን 1985 ዓ.ም ተፈፀመ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል የሚፀና ነው በማለት ነው። በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ የቤት ሽያጭ ውል የሚፀናው ምን ምን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ነው የሚለውን ጥያቄ እንመለከታለን።

ለመቃወሚያው መሠረት የሆነው የቤት ሽያጭ ውል በመሆኑ በቅድሚያ የፍትሐ ብሔር ሕጉ የቤትን የሽያጭ ውል በማስመልከት ያሰፈረውን ድንጋጌ እንመለከታለን ቀጥሎ ደግሞ በሽያጭ ህጉ ያለው መስፈርት ከአጠቃላይ የውል ሕግ ካለው መስፈርት ጋር ያለውን ግንኙነት እንመለከታለን። የቤት ሽያጭን አስመልክቶ የሚቀርቡ ክርክሮችን በአግባቡ ለማስተናገድ አግባብነት ያላቸውን የሕጉ ድንጋጌዎች እንደነገሩ ሁኔታ የአማርኛም የእንግሊዝኛም ትርጉም እንጠቅሳለን። የማይንቀሳቀስ ሀብት ሽያጭን በሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕግ ክፍል የሚገኙት አንቀጽ 2877 እና አንቀጽ 2878 እንደሚከተለው ይደነግጋሉ።

2877 የሙሉ ፎርም

የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በጽሑፍ ሳይደረግ የቀረ እንደሆነ ፈራሽ ነው።

2877 form of contract

A contract of sale of an immovable shall be of no effect unless it is made in writing.

2878 በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ስለ መግቢ

ያንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኘው በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ውጤትን ሊያስገኝ አይችልም።

2878 Registration in registers of unmovable property

The sale of immovable shall not affect third parties unless it has been registered in the registrars of immovable property in the place where the immovable sold is situate.

ከድንጋጌዎቹ ይዘት ለመገንዘብ እንደሚቻለው አንቀፅ 2877 በተዋዋዮቹ መካከል በሕግ የሚፀና ውል እንዲኖር መሟላት የሚገባውን መስፈርት የሚመለከት ሲሆን አንቀፅ 2878 በሌላ በኩል ይኸው ውል ሦስተኛ ወገኖችን በሚመለከት ውጤት እንዲኖረው መሟላት ያለበትን መስፈርት የሚመለከት ነው። በአንቀፅ 2877 መሰረት

የሚፀና ውል አለ ለማለት በሻጩና በገዢው መካከል የጽሑፍ ውል መኖሩ በቂ ነው። ይህ መስፈርት ከውል ሕግ አጠቃላይ ድንጋጌዎች ጋር ተያይዞ ሲታይ በሻጭና በገዢ መካከል የተከናወነው የሽያጭ ውል በጽሑፍ እንዲሆንና ግዴታ ያለባቸው ተዋዋዮች እንዲፈርሙበትና ሁለት ምስክሮች እንዲያረጋግጡት የሚጠይቅ ነው (አንቀጽ 1727)። በተዋዋይ ወገኖች መካከል የፀና ውል እንዲኖር የዚሁ መስፈርት መሟላት አስፈላጊነት እንደተበጠቀ ሆኖ አንቀጽ 2878 3ኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ተጨማሪ የምዝገባ ሥርአት መከናወን እንዳለበት ያስገነዝባል። ይህ የምዝገባ ሂደት መከናወን ያለበት ንብረቱ በሚገኝበት የማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ መሆኑንም ድንጋጌው ይገልጻል።

የማይንቀሳቀስ ሀብት ሽያጭን በሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕጉ ክፍል ያለው የውል አፃፃፍ ፎርምን እና ምዝገባን የሚመለከት መሰረታዊ የሕግ ማዕቀፍ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን በውል ሕግ በጠቅላላ የሚገኘው መስፈርት ግን ከዚህ የተለየ ነው። አግባብነት ያለው የሕጉ አንቀጽ 1723 ድንጋጌ የሚከተለው ይዘት ያለው ነው።

1723 የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ ውሎች

(1) የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ባለቤትነት ወይም ባንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የአላባ ጥቅም መብት ወይም የመያዣ መብት ወይም የሌላ አገልግሎት መብት ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉት ውሎች ሁሉ በጽሑፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ፊት መሆን አለባቸው።

(2) እንዲሁም የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ የክፍያ ወይም የማዛወር ስምምነቶች ሁሉ በጽሑፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ፊት መሆን አለባቸው።

1723 Contracts relating to immovable

(1) A contract creating or assigning rights in ownership or bare ownership on an immovable or an usufruct, servitude or mortgage of an immovable shall be in writing and registered with a court or notary

(2) Any contract by which an immovable is divided and any compromise relating to an immovable shall be in writing and registered with a court or notary.

ከአንቀጽ 1723 (1) ይዘት ለመገንዘብ እንደሚቻለው የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ በርካታ ውሎች በሕግ ፊት የሚፀኑ ለመሆን ሁለት መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል። የመጀመሪያው መስፈርት ውሉ በጽሑፍ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው መስፈርት ውሉ በአዋዋይ ወይም በፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት መዝገብ ፊት መከናወን ነው። እነዚህ ሁለት መስፈርቶች የማይንቀሳቀስ ሀብት ባለቤትነትን ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎችንም የሚመለከቱ ናቸው። የሽያጭ ውል የንብረት ባለቤትነት ከሚተላለፉባቸው መንገዶች አንዱ በመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ውስጥ የሚጠቃለል ነው። በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሠረት ቤትን የሚመለከት የሽያጭ ውል በህግ ፊት የፀና የሚሆነው በጽሑፍ ሲደረግ ብቻ ሳይሆን ይኸው የጽሑፍ ውል ሥልጣን በተሰጠው አዋዋይ ክፍል ወይም በፍርድ ቤት የተከናወነ ሲሆን ነው። የአንቀጽ 1723 ድንጋጌ አንቀጽ 2778 ካስቀመጠው መስፈርት የተለየ ተጨማሪ መስፈርት ያካተተ መሆኑ ድንጋጌዎቹን በማነፃፀር መገንዘብ የሚቻል ነው። የሽያጭ ሕጉን በተለይ የሚመለከተው ድንጋጌ የሚጠይቀው የውሉን በጽሑፍ መከናወን ብቻ ሲሆን የውል ሕግ በጠቅላላው ግን የጽሑፍን መስፈርት እንደ አንድ አስፈላጊ መስፈርት እንጂ እንደ ብቸኛ መስፈርት አይወስደውም። በመሆኑም በሽያጭ ሕግ የሚፀና የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ለማከናወን የሚጠየቀው መስፈርት በውል ሕግ ከሚጠየቀው መስፈርት የተለየ ነው። ይህ ልዩነት አንድ የሽያጭ ውል በሕግ ፊት የሚፀና መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ገዢው ድንጋጌ መሆን ያለበት የትኛው ነው የሚለው ጥያቄ እንዲነሳ ያደርጋል። ይህን ጥያቄ ከመመልከታችን በፊት በአንቀጽ 1723 የሰፈረው ተጨማሪ መስፈርት በአንቀጽ 2878 ከሚገኘው የምዝገባ መስፈርት ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ተመሳሳይነትና ልዩነት በአጭሩም ቢሆን መመልከት አስፈላጊ ነው። የአንቀጽ 1723 (1) የእንግሊዝኛው ትርጉም “registration” የሚለውን ቃል ከመጠቀሙ በስተቀር በሁለቱም ድንጋጌዎች መካከል ያለው ይዘት ሰፊ ልዩነት ያለው ነው። በመጀመሪያ ደረጃ አንቀጽ 2878 ምዝገባ እንዲከናወን የሚጠይቀው ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ሲሆን አንቀጽ 1723 (1) አዋዋይ ወይም ፍርድ ቤት ፊት መቅረብን የሚጠይቀው በተዋዋዮች መካከል በሕግ ፊት የሚፀና ውል እንዲኖር ለማድረግ ነው። በመሆኑም የአንቀጽ 1723 (1) መስፈርት መሟላት ወይም አለመሟላት ሦስተኛ ወገኖችን የሚመለከት ሲሆን የኋለኛው መስፈርት መሟላት አለመሟላት ግን በተዋዋዮች በራሳቸውም ላይ የውል መኖር ወይም አለመኖር ውጤት የሚያስከትል ነው። በሁለተኛ ደረጃ በአንቀጽ 1723 (1) የሚከናወነው ተግባር የሚፈፀመው አዋዋይ ወይም ፍርድ ቤት ፊት በመቅረብ ሲሆን በአንቀጽ 2878 ያለው የምዝገባ ተግባር የሚከናወነው ንብረቱ በሚገኝበት ቦታ ነው። በአንቀጽ 1723 (1) የሚከናወነው ሂደት ተዋዋዮች አዋዋይ ፊት ቀርበው መዋዋላቸውን የሚያረጋግጡበት (authentication) ሂደት ሲሆን በ2878 የሚከናወነው ምዝገባ ሌሎች ሰዎች አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት በማስመልከት የተከናወኑ ሕጋውያን ተግባራት (juridical acts) ማወቅ እንዲችሉ ተግባራቱ ንብረቱ ባለበት ማህደር እንዲያያዝ በማድረግ የሚከናወን ነው። አዋዋይ ፊት ቀርቦ የመዋዋሉ መስፈርት ውሉ በተፈፀመበት ቦታ በሚገኝ አዋዋይ/ፍርድ ቤት በመቅረብ መከናወን የሚችል ሲሆን በ2878 መሠረት የሚከናወን ምዝገባ ግን የግድ ቤቱ በሚገኝበት ቦታ ባለ መዝገብ በማስገባት የሚከናወን ነው።

ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከተው የአንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት የሽያጭ ውል በሚመለከት ገዢው ድንጋጌ የትኛው ነው የሚለውን ነው። አሁን ከቀረበልን ጉዳይ አንፃር ዋናው ጥያቄ የአንቀጽ 2877ን የጽሑፍ መስፈርት ያሟላ ሰነድ ሳይኖር 1723 (1) መሠረት አዋዋይ ወይም ፍርድ ቤት ፊት ካልተደረገ እንደሚፀና ውል ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም የሚለው ነው። በዚህ ረገድ ሰበር ሰ/መ/ቁ የሚመለከተው የሽያጭ ሕግ ድንጋጌ አንድ መስፈርት ብቻ በቂ ነው ሲል ጠቅላላ የውል ሕግ ሁለት መስፈርት አስፈላጊ ነው ስለሚል በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል ያለውን አለመጣጣም ለመፍታት የሽያጭ ሕግ ልዩ ሕግ ስለሆነ አጠቃላይ ጉዳዮችን በሚመለከተው የውል ሕግ ላይ የበላይነት ተሰጥቶት ጉዳዩ የሽያጭ ሕግ በሚያስቀምጠው መለኪያ መሠረት መዳኘት አለበት የሚለውን አማራጭ እንደ መጀመሪያ መውሰድ ይቻላል። ይህ አማራጭ የተለመደውን ልዩ ሕግ ከአጠቃላይ ሕግ ቅድሚያ ይሰጠዋል (the special prevails over the general) የሚለውን የሕግ ትርጉም መርህ የሚከተል ነው። ይህን መርህ በመከተል ጉዳዩን ካስተናገድን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ በጽሑፍ እስከተከናወነ ድረስ የጽሑፍ ውሉ አዋዋይ ፊት ወይም ፍርድ ቤት ፊት ባይቀርብም ተዋዋዮቹን በሚመለከት የፀና የሽያጭ ውል ለመመስረት በቂ ነው ወደሚለው መደምደሚያ እንደርሳለን።

በሌላ በኩል ይህ የአተረጓጎም ስልት ተግባራዊ የሚሆነው ሁለት የህግ ድንጋጌዎች የሚጋጩ ሲሆንና ሁለቱም ድንጋጌዎች አንድ ላይ ተግባራዊ ማድረግ ሳይቻል ሲቀር ብቻ ተፈፃሚነት የሚኖረው የአተረጓጎም ዘይቤ በመሆኑ ይህን ዘይቤ ለመምረጥ በቅድሚያ በሁለቱም ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ መኖሩን ማረጋገጥ ይጠይቃል። የሽያጭ ሕግ በሚፀና የሽያጭ ውል ጽሑፍ ያስፈልጋል ማለቱ፣ የውል ሕግ ለሚፀና የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ከጽሑፍ በተጨማሪ አዋዋይ ፊት መከናወኑ አስፈላጊ መሆኑን ከሚገልፀው ጋር ይጋጫል? ሁለቱንም ማጣጣምስ አይቻልም? የሕጉ አንቀጽ 2877 የሽያጭ ውል በጽሑፍ ካልሆነ በቀር አይፀናም ከማለት ሌላ በአዋዋይ ፊት መከናወን አያስፈልግም የሚል ድንጋጌ የለውም። በመሆኑም የሽያጭ ሕግ በውልም ሕግ ለተጠቀሰው የጽሑፍ አስፈላጊነት አፅንኦት ከመስጠቱ ሌላ የመረጋገጥን (authentication) አስፈላጊነት አላስቀረም በማለት የሁለቱን ድንጋጌዎች ላይ ላዩን የሚታይ ቅራኔ (apparent contradiction) ማስታረቅ ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ የፍትሐ ብሔር ሕጉን አደረጃጀት፣ ዓላማና ወጥነት ግምት ውስጥ ማስገባት አሁን ለተያዘው ጉዳይ የሚበጅ ነው። የፍትሐ ብሔር ሕጉ አደረጃጀት በተለያዩ መጽሐፎች የተከፋፈሉት ርእሰ ጉዳዮች አንድን ዓላማ የሚያሳኩ፣ ከተመሳሳይ መሠረተ ሃሳብ የሚንደረደሩና እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። ይህ አደረጃጀት ሕጎቻቸውን በኮድ መልክ በሚያደራጁ አገሮች (codified systems) የተለመደና የሕግ ሥርዓቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መገለጫ ባህርይ ነው። በመሆኑም በተለያዩ የሕጉ ክፍሎች በሚገኙ ድንጋጌዎች መካከል ቅራኔ ከማፈላለግ ይልቅ ተደጋጋፊ ሆነው የጋራ ዓላማ የሚያሳክቡትን የሕግ ትርጉም መሻት የሕግ ባለሙያዎች ሊመርጡት የሚገባ የሕግ አተረጓጎም ዘይቤ ነው። ስለዚህ ልዩ ሕግ ጠቅላላ ዓላማ ካለው ሕግ ቅድሚያ ይሰጠዋል የሚለውን ዘይቤ ተከትሎ ውሳኔ ላይ ከመድረስ በፊት በእርግጥ የማይታረቅ፣ ምክንያታዊ የሆነ፣ በላቀ የሕግ አውጪው ፍላጐት የተደገፈ ግጭት መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈጋል።

ይህ ችሎት ለማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ የውል ሕግ አንቀጽ 1723 (1) የተለየና ጥብቅ መስፈርት ያስቀመጠበት ምክንያት ለአተረጓጎሙ መነሻ መሆን ይገባዋል ከሚል መንደርደሪያ ይነሳል። የፍትሐ ብሔር ሕጉ መነሻ መሰረተ ሀሳብ በመርህ ደረጃ ለውል መመስረት የተዋዋዮች ስምምነት ብቻ በቂ ነው የሚል ሆኖ ሳለ (አንቀጽ 1719) የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በሚመለከት ግን ጠበቅ ያለ ፎርም እንዲከተሉ ይደነግጋል። የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸውን በጽሑፍ ከማስፈራቸው በተጨማሪ አዋዋይ ፊት ወይም ፍርድ ቤት ፊት ቀርበው እንዲፈጽሙ መደንገጉ ሕጉ ለማይንቀሳቀስ ንብረት ልዩ ትኩረት መስጠት መፈለጉን የሚያመለክት ነው። ይህ የሕግ አውጪው ፍላጐት የማይንቀሳቀስ ንብረት ለአንድ አገር በአጠቃላይም ሆነ ለአንድ ግለሰብ በተለይ ካለው ጠቀሜታ ጋር የተያያዘ ነው። የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለው ማህበራዊ ጠቀሜታ አንፃር ውሎቹ ስልጣን ባለው አካል እንዲረጋገጡ በመጠየቅ ረገድ የኢትዮጵያ ሕግ የተከተለው ሥርአት ከሞላ ጐደል ሁሉም የሕግ ሥርአት የተቀበለው ነው። የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በማስመልከት የሚፈፀሙ ውሎች ከሌሎች ውሎች ለየት ባለ ሁኔታ ሥልጣን በተሰጠው አካል ቀርበው እንዲረጋገጡ ማድረግ በአብዛኛቹ የሕግ ሥርዓቶች የሚፈፀም አካሄድ ነው። የማረጋገጡ (authentication) ሂደት ተዋዋዮቹ ትልቅ ጠቀሜታ ባለው ንብረት ላይ የሚፈጽሙት ውል ፈቅደው የሚፈጽሙት መሆኑን ከማረጋገጥ ባሻገር፣ የሚሸጠው ሰው ባለንብረት መሆኑን ለማጣራት፣ ውሉ የተፈፀመበትን ትክክለኛ ቀን ለማረጋገጥ እድል በመስጠት የንብረት መብትን ለመጠበቅ፣ የውሎች ዋስትና (security of legal transactions)ለማረጋገጥ ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ነው። የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1723 (1) በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚከናወኑ ዓበይት ህጋውያን ተግባራት በተለይም የባለሀብትነትን (ownership) ዓላባን (usufruct) እና የአገልግሎትን መብት (servitude) ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎች የተጠቀሰውን ፎርም እንዲከተሉ የግድ ይላል። በዚህ አንቀጽ ውስጥ ከተጠቀሱት መብቶች ባለቤትነት ከሁሉም የሰፋ መብት ነው። ባለቤትነትን ማቋቋምም ሆነ ማስተላለፍም ዓላባን ወይም የአገልግሎት መብትን ከማቋቋም የበለጠ ጠቀሜታ እና ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው እሙን ነው። ባለቤትነትን ማስተላለፍ ከሌሎች በአንቀጽ 1723 (1) ከተጠቀሱት ሕጋውያን ተግባራት የበለጠ ጥንቃቄና ጥበቃ የሚሻና የሚገባው እንደመሆኑ ሕግ አውጪው የባለቤትነት መብትን ለሚያስተላልፍ የሽያጭ ውል አላባን ወይም የአገልግሎት መብትን ለማቋቋም ከሚደረጉ ውሎች ያነሰ ጥበቃ ያደርጋል ተብሎ አይገመትም። የሕጉን አንቀጽ 2877 በተናጠል በመመልከት የሽያጭ ውል በጽሑፍ ብቻ መደረጉ በቂ ነው፣ አዋዋይ ወይም ፍርድ ቤት ፊት መከናወን አያስፈልገውም ወደሚል መደምደሚያ መድረስ ከሁሉም በላይ ጥንቃቄ

የሚያስፈልገው የባለቤትነት ማስተላለፍ ጉዳይ ልል በሆነ ፎርም እንዲከናወን ማድረግን የሚያስከትል በመሆኑ ከሕጉ አጠቃላይ ዓላማ ጋር የሚጣጣም ነው አንልም። በመሆኑም የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የሚደረጉ የሽያጭ ውሎች በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን አንቀጽ 1723 (1) በሚጠይቀው መሠረት አዋዋይ ወይም ፍርድ ቤት ፊት መከናወን ይገባቸዋል። ከላይ እንደተጠቀሰው በአንቀጽ 1723 (1) የሰፈረው የማረጋገጥ (authentication) መስፈርት ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ብቻ መከናወን ያለበት ሳይሆን ውሉ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውጤት እንዲኖረውም ጭምር መከናወን ያለበት ነው። የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት የሽያጭ ውል የአንቀጽ 1723(1)ን መስፈርት የማያሟላ ከሆነ በሕጉ አንቀጽ 1720 (1) መሠረት ውሉ እንደረቂቅ ብቻ ሆኖ ከሚቆጠር በስተቀር የሚፀና ውይ አይሆንም።

አሁን በቀረበልን ጉዳይ 2ኛ መልስ ሰጪ አለኝ የሚሉት የሽያጭ ውል በጽሑፍ መሆኑ ተገጋግጦአል። ሆኖም የሽያጭ ውሉ በአዋዋይ ፊት ያልተከናወነ በመሆኑ ውሉ መፈፀሙ ራሱ አከራካሪ ሆኖአል። ሕግ አውጪው ቤትን የሚመለከቱ መሠረታዊ ውሎች በ1723 (1) የተጠቀሱ ውሎች አዋዋይ ፊት እንዲከናወኑ የሚፈልገውም የኋላ ኋላ የሚነሱትን የዚህ አይነት አለመግባባቶች ቀድሞውኑ ለማስወገድ ነው። ውሉ በአዋዋይ ፊት ወይም በፍርድ ቤት ቀርቦ ያልተረጋገጠ መሆኑን ሲገነዘብ ፍርድ ቤቱ ውሉ እንደረቂቅ እንደመቁጠር ነበሩ የተባሉትን ምክንያቶች በመስማት በሕግ ሕልውና የሌለው ውል ተቀባይነት እንዲያገኝ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው።

የአሁን ተቃዋሚ በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1723 (1) መሠረት አዋዋይ ፊት ወይም ፍርድ ቤት የተረጋገጠ የቤት ሽያጭ ውል ባለማቅረቡ ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ ለመቃወም የሚያበቃ ህጋዊ መብት የለውም። ፍርድ ቤቱም ይህን መሠረት በማድረግ የቀረበለትን ኑዛዜ በከፊል ማሻሻሉ ትክክለኛ አይደለም። በዚህም ምክንያት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊሻር የሚገባው ነው። የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህን ስህተት ማረም ሲገባው የቀረበለትን ይግባኝ አያስቀርብም በማለት መዝጋቱ ትክክል አልነበረም።

ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09823 ሐምሌ 14 ቀን 1986 የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 33751 ሰኔ 14 ቀን 1997 የሰጠው ውሳኔ ተሽረዋል።
2. የአሁንዋ አመልካች በወረዳ 24 ቀበሌ 09 በቤት ቁጥር 011 ላይ እኩል ባለድርሻ ናቸው በማለት በ16/3/92 ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በ23/3/85

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን 2ኛ መልስ ሰጪ ፈፀምኩ በሚለው የሽያጭ ውል ምክንያት ሊሻሻል አይገባም ብለናል፡፡

የሰበር መ/ቁ 15557

መጋቢት 18 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁ

ተጠሪ፡- አቶ ብርሃኑ ተሊላ

የአፈጻጸም ክርክር - የጋራ ሀብት በፍርድ አፈጻጸም የሚከበርበትና በሐራጅ የሚሸጥበት ሁኔታ - የክተማ ቦታ ይዞታ - የባልና ሚስት የጋራ ሃብት

የአፋር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪው በአፈጻጸም ከአዋሽ ማዘጋጃ ቤት የተረከበው ቦታ የፍርድ ባለዕዳው ከነበረው ቦታ የበለጠ ቢሆንም በአፈጻጸሙ አጋጣሚ ቅድሚያ የተመራ ስለሆነ ለእሱ ሊደለደል ይገባዋል እንዲሁም በፍርድ ቤቱ ተይዞ የንብረቱ ግምት ግማሽ ገንዘብ ለተጠሪው ሊመለስ ይገባል ሲል የወሰነውን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የአፋር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የዞን 3 ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጸንቷል፡፡

ማዘጋጃ ቤት በፍርድ ቤት በታዘዘ የአፈጻጸም ጉዳይ በስህተት ቦታ ለክቶ አስረክቦኛል ግብርና የስም ማዛወሪያ ከፍዬበታለሁ የሚለው መከራከሪያ ነጥብ የቦታ ባለይዞታ ለማድረግ የሚያበቃ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 15557

መጋቢት 18 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አሰግድ ጋሻው
መስፍን ዕቁበዮናስ
ሂሩት መለሰ
ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ብርሃኑ ተሊላ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው የአፋር ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ጉዳይ በይግባኝ ተመልክቶ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 15/94 የካቲት 18 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝተው የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

ተጠሪ አቶ ብርሃኑ ተሊላ በአሁን አመልካች ባለቤት በአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴ ላይ ብር 18,794.15 አስፈርደዋል፡፡ ሆኖም ይህ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በክርክር ላይ እያለ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በሚል የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበት ንብረት የአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴ ብቻ ሳይሆን ከእኔ ከአመልካች ጋር በትዳር እያለን የተፈራ፤ የተገኘ በመሆኑ የእኔ ድርሻ ሊነካብኝ አይገባም በሚል ጣልቃ ገብታ አመልካች በመከራከሯ እንደ አቤቱታዋ ዕግድ ከተሰጠበት ንብረት ግማሹ የአመልካች መሆኑ የተጠበቀ ነው በሚል ፍርድ አርፎበታል፡፡

እንዲሁም ይኸው ንብረት በአፈፃፀም ተይዞ በብር 25,000.00 ግምት መነሻ እንዲሸጥ በተባለ ጊዜ ግማሹ የአመልካች መሆኑ ተጠብቆ ንብረቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ተደርጎ ገዥ ባለመቅረቡ ምክንያት እንደ መጨረሻ አማራጭ የፍርድ ባለመብት የአሁን ተጠሪ ከግምቱ ብር 25,000.00 የሆነበትን /የአመልካችን ግማሽ ድርሻ ብር 12,500.00/አስራ ሁለት ሺህ ከፍሎ ንብረቱን እንዲረከብ ታዟል፡፡

ተጠሪም ይህንኑ ገንዘብ በሞዴል 85 አስይዞ ቦታውንም የአዋሽ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ለክቶ አስረክቦኝ አስፈላጊውን የመንግስት ውዝፍ ግብር ከከፈልኩ በኋላ ካርታ እንዲሰጠኝ ሳመለክት እንድረከብ ከተወሰነው ቦታ ተከፍሎ ለአሁን አመልካች እንዲሰጥ ታዝዣለሁ በማለት ማዘጋጃ ቤቱ እንደ ውሳኔው ሊያስፈፅምልኝ ስላልቻለ፡-

1. በሞዴል 85 የተያዘው ገንዘብ ለአመልካች እንዳይከፈልብኝ
2. እንድረከብ ለተደረገው ንብረት ተቆርሶ ለአመልካች እንዳይሰጥብኝም የማገጃ ትዕዛዝ ለማዘጋጃ ቤቱ እንዲተላለፍልኝና
3. የፍርድ ባለዕዳው የአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴ የቦታ ይዞታ ፋይል ቀርቦ ታይቶ ንብረቱን እንድረከብ ይደረግልኝ በማለት በት/ፋ/መ/ቁ 11/94 ለዞን 3 ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤትም በዚህ ጉዳይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የአሁን ተጠሪ በአፈፃፀም ይረከብ የተባለው ይዞታ የፍርድ ባለዕዳውን የአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴን ነው፡፡ የፍርድ ባለዕዳው ይዞታ ስፋት ደግሞ 600 ካሬ ሜትር እንደሆነ በማዘጋጃ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ የፍርድ ባለመብቱ ከዚህ ወጭ የፍርድ ባለዕዳውን ወንድም የአቶ ገ/አግዚአብሔር ገ/ስላሴን 200 ካሬ ሜትር እና በትርፍነት የሚገኘውን 355 ካሬ ሜትር ጭምር በስህተት ደርቦ እንዲረከብ የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለሆነም አመልካች የባለቤቷ ወንድም በግንባር ተገኝቶ እስከሚረከብ ድረስ ይህንኑ 200 ካሬ ሜትር በአደራ እንድትይዝ በትርፍነት የሚገኘውንም 358 ካሬ ሜትር ማዘጋጃ ቤቱ በስሟ እንዲያዘዋውርላት ከዚህ በቀር ተጠሪው ሊረከብ የሚገባው የፍርድ ባለዕዳውን ይዞታ 600 ካሬ ሜትር ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የጠ/ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ በተገኙበት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በትርፍነት ተገኝቷል የተባለውን ቦታ በሚመለከት ትርፍ እስከሆነ ድረስ ማዘጋጃ ቤቱ ለፈለገው ሰው መደልደል /መስጠት/ ይችላል፡፡ሆኖም ይህንኑ ቦታ ማዘጋጃ ቤቱ በመጀመሪያ ተጠሪው /እንዲረከብ/ ለክቶ እንዲረከብ ካደረገ በኋላ ከአምስት ወር ቆይታ በኋላ ደግሞ ለአመልካች እንዲሰጥ አድርጓል፡፡አንድን ቦታ ለሁለት ሰዎች በአንድ ጊዜ መስጠት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ለማን ይሰጥ የሚለው ጉዳይ በቅድሚያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማን ተስጥቶ ነበረ ከሚለው አንፃር መታየት ስላለበት ይኸው 358 ካሬ ሜትር ቦታ ለተጠሪ ይገባል እንዲሁም በሞዴል 85 ተይዞ የነበረው ገንዘብ ለአመልካች መስጠቱ ቀርቶ ለተጠሪው ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የተባለው የቅሬታ ነጥብም ክርክር ባስነሳው ትርፍ ቦታ ላይ ከተጠሪ በፊት በቦታው ላይ የቆየሁበት በመሆኑ በመሬት ወይም በምሪት አሰጣጥ ላይ የቀዳሚነት መብት የእኔ ሆኖ እያለ ለተጠሪ ይሰጥ በማለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት መወሰኑ የህግ አግባብን የተከተለ አይደለም፡፡

እንዲሁም በሞዴል 85 የተያዘው ብር 12,500.00 የእኔ የሚስት ድርሻ ሆኖ እንዲከፈል የተወሰነው ለጠ/ፍ/ቤቱ ይግባኝ ምክንያት በሆነው የትዕዛዝ ፋይል መዝገብ በአለመሆኑ በይግባኝ መዝገቡ ላይ በዚህ አኳኋን መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈፅሟልና ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ቀርቦ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የሰጠው ውሳኔ የህግ ግድፈት የለበትም የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር መልስ ሰጥቷል፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ ከሳሽ የአመልካች ባለቤት አቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴ ደግሞ ተከሳሽ ሆነው በፍ/ብ/መ/ቁ 8/90 በከፍተኛው ፍ/ቤት በመከራከር ላይ እያሉ የአሁን አመልካች ባለቤቱ አመጣው በተባለው ዕዳ ምክንያት የእኔ የጋራ ሀብት በሆነው ቤት ላይ የዕግድ ትዕዛዝ መተላለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም ጣልቃ ገብቼ ልከራከር በማለት ባቀረበቺው ጥያቄ የክርክሩ ተካፋይ ከሆነች በኋላ የከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካች ባለቤት በሥራው ምክንያት ላጐደለው ብር 18,794.15 ባለዕዳ ነው፡፡ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ቤት አመልካች በሚስትነታቸው አብረው የሰሩት መሆኑን በማስረጃ ስላረጋገጠ ድርሻቸው ሊነካባቸው አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀም በአፈፃፀም መ/ቁ 3/93 የአፈፃፀም ክሱ ቀጥሎ በብር 25,000.00 ግምት መነሻ ይህንኑ የጋራ ቤት የሚገዛ ገዥ ባለመገኘቱ አመልካች ግማሹን መክፈል ከቻለች ቤቱን እንድታስቀር ተብሎ ቢታዘዝም ይህንን መፈፀም ባለመቻሏ ተጠሪው

ብር 12,500.00 የአመልካችን ድርሻ በሞዴል 85 አስይዞ ንብረቱን ስለዕዳው እንዲረከብ በሚል የታዘዘ ስለመሆኑ ከመዝገቡ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

ይህም ከሆነ የፍርድ ባለመብቱ የአሁን ተጠሪ ስለዕዳው ሊረከበው የሚገባው ቤትና ይዞታው ይህንኑ በአፈፃፀም ምክንያት ይሸጥ የተባለውንና በባለዕዳው በአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ነው፡፡ ይህ ቦታ እና ይዞታ ደግሞ በፊቱ 650 ሜትር ካሬ ብቻ እንጂ ከዚያ ያልዘለለ ስለመሆኑ በባለሙያ በማዘጋጃ ቤቱ ተረጋግጧል፡፡ ይህንኑ ቤት ከእነ ትክክለኛ ይዞታው ተለክቶ እንዲረከብ ማድረግ ሲገባ በዕዳ ከተያዘው ንብረት ውጭ መሰራቱ እና እንዲረከብ ጥረት መደረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘውም፡፡ የማዘጋጃ ቤቱ ይህንኑ 600 ሜትር ካሬ፣ የአቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/ስላሴን ይዞታ 200 ሜትር ካሬ እና ክርክር ያስነሳውን ትርፍ ቦታ እንድረከብ ለክቶልኛል፡፡ ግብር ና የስም ማዛወሪያ ከፍዬበታለሁ የሚለው መከራከሪያ ነጥብ የዚህ ሁሉ ቦታ ባለይዞታ ለማድረግ የሚያበቃ አይደለም፡፡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ፍርዱን በአፈፃፀም ተከሳሹ ወይም በፍርድ ባለዕዳው ንብረት ላይ ብቻ ማስፈፀም ሲገባው የማዘጋጃ ቤቱ የፈፀመውን ስህተት እንደ መነሻ በመውሰድ ይህንኑ ትርፍ ቦታ በቅድሚያ የተመራው የፍርድ ባለመብቱ የአሁን ተጠሪ ነው፡፡ ስለሆነም ለእርሱ ሊደለደል ይገባል ሲል የሰጠው ውሳኔ የአፈፃፀም ሥርዓቱን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የአመልካች ባለቤት በተከሰሰበት ጉዳይ አመልካች ጣልቃ ገብታ ተከራክራ በክሱ ምክንያት ቦታ በታገደው ንብረት ላይ ያላት ድርሻ የተጠበቀ ነው በሚል ፍርድ አርፎበታል፡፡ የጣልቃ አግባብ ሥርዓቱ ተገቢ አይደለም በሚል የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦ የታረመ ስለመሆኑም አልተመለከተም፡፡ ከዚህ በላይ በአፈፃፀም መ/ቁ 3/93 ከንብረቱ ሽያጭ ግማሹ ብር 12,500.00 የሚስት/የአመልካች ድርሻ ሆኖ በሞዴል 85 እንዲያዝ ተደርጓል፡፡ ይህ መሆኑ እየታወቀ በአፈፃፀም ምክንያት ልረከብ የሚገባው ይዞታ ምን ያህል ሊሆን ይገባል የሚለውን በሚመለከት ክስ ላይ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይኸው በአደራ ተይዞ የነበረው ገንዘብ ወጭ ሆኖ ለተጠሪው ይመለስ ሲል የሰጠው ዳኝነት ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ለምን ቢባል ይሸጥ ከተባለው ንብረት ላይ ግማሹ የአመልካች ድርሻ መሆኑ ለአፈፃፀሙ ምክንያት በሆነው በዋናው ጉዳይ በመ/ቁ 8/90 ውሳኔ ያረፈበት ከመሆኑም በላይ ጠ/ፍ/ቤቱ በይግባኝ ለተመለከተው ጉዳይ መነሻ በሆነው በመ/ቁ 11/94

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሞዴል 85 የተያዘው ገንዘብ የይዞታው መጠን ታይቶ ውሳኔ እስኪሰጠው ድረስ ይህ ገንዘብ ሳይከፈል ታግዶ ይቆይልኝ በሚል እንጂ ይመለስልኝ በሚል ዳኝነት አልተጠየቀበትም፡፡ ይህን ሳይረዳ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በሞዴል 85 የተያዘው ገንዘብ ይመለስ ሲል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡

ውሳኔ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 15/94 ታህሳስ 28 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የተሻረ ሲሆን በአንዛሩ የዞን ሦስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በት/ፋ/መ/ቁ 11/94 የካቲት 19 ቀን 1994 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ የፀና ስለሆነ፡

1. ተጠሪ ገዥ ባለመገኘቱ ምክንያት በአፈፃፀም ሊረከበው የሚገባው ንብረት የፍርድ ባለዕዳውን የአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴን እና የአመልካችን ቦታና ይዞታ ብቻ በመሆኑ በማዘጋጃ ቤቱ እንደተረጋገጠው 600 ሜትር ካሬ ብቻ ሊረከብ ይገባል፡፡
2. ይህም ይሸጥ የተባለው ቤትና ቦታ የፍርድ ባለዕዳውና የአመልካች የጋራ ሀብት መሆኑ ታይቶ ለአፈፃፀሙ መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ ዳኝነት የተሰጠበት በመሆኑና ይህም በይግባኝ ያልተሻረ ስለሆነ እንዲሁም በአፈፃፀም መዝገቡም ላይ ቢሆን ይኸው መብት የተጠበቀ በመሆኑ በሞዴል 85 ተይዞ የሚገኘው ብር 12,500.00 /አስራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ የአመልካች ድርሻ በመሆኑ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

ይህ ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የሰበር መ/ቁ. 22260
መጋቢት 20 ቀን 1999

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
” አሠግድ ጋሻው
” መስፍን እቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሠ
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡- እነ ወ/ሮ ገደሪፍ ውብሃ

የወጪና ኪሣራ ክርክር - የወጪና ኪሣራ አወሳሰን - የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 463

የአማራ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪዎች ወጪና ኪሣራ እንዲከፍል የወሰነውን በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ውሣኔ፡ - የአማራ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በከፊል ተሽሯል፡፡

1. የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 462 በክስ ምክንያት ስለሚከፈለው ማናቸውም ወጪና ኪሣራ፣ የሚከፍለውን ወገን፣ የወጪውንና የኪሣራውን ልክ፣ የሚከፈልበትን የሃብት ምንጭ፣ የአከፋፈሉን ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ትክክል መስሎ በሚገምተው ሁኔታ እንዲወስን መብት (discretion) ይሰጠዋል፡፡
2. የወጪና ኪሣራ ክፍያ አላማ ረቺው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ ተረቺ እንዲሸፍን እንጂ ተረቺውን ለመቅጣት አይደለም፡፡
3. ፍርድ ቤት የወጪና ኪሣራን መጠን ሲወስን ምክንያታዊ ባልሆነና በተጋነነ መንገድ እንዳይሆን ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡
4. የወጪና ኪሣራ ዝርዝር ባልቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤት የኪሳራውን መጠን የተጋነነ እንዳይሆን ክርክሩ የወሰደው ጊዜ፣ የክርክሩ ውስብስብነትና አስፈላጊውን ዳኝነት ለመከታተል ተገቢ ናቸው የሚላቸውን ወጪዎች አመዛዝኖ ተመጣጣኝ መጠን ያለው ኪሣራ ሊወስን ይገባል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 22260

መጋቢት 20 ቀን 1999

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. " አሠግድ ጋሻው

3. " መስፍን እቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት - ነገረፈጅ በረደድ

ተጠሪዎች፡- 1.ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ የአባ ሣሙኤል ከብት እርባታ ድርጅት ባለንብረት ጠበቃ አብዱል ተካበ

2. የወተት ሃብት ልማት ድርጅት

3. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወጪና ኪሣራ አከፋፈልን የሚመለከት ነው።

የአሁኑ አመልካች 1ኛ ተጠሪ ለሚጠቀሙበት ቦታ ብር 1,479,996.60 የቦታ ግብር እንዲከፍሉ የመሠረተውን የአፈፃፀም ክስ የሰ/ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ እንዲከፍሉ ትእዛዝ ሰጥቷል። በዚህ ውሣኔ 1ኛ ተጠሪ ቀር በመሠኘታቸው ይግባኙን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ የሻረው ሲሆን አመልካች በአሁኖቹ ተጠሪዎች ላይ ተገቢ ያልሆነ ክስ በማቅረብ ለደረሰው መጉላላትና ለተከሰተው ወጪ ኃላፊ ነው በማለት ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 2,000 (ሁለት ሺህ) ለ1ኛ ተጠሪ ደግሞ 500.00 (አምስት መቶ ብር) እና የጠበቃ አባል ክስ የቀረበበትን ብር 5% እንዲከፈል ወስኖበታል።

የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው። ይህ ችሎትም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ ሣይኖር ወጪና ኪሣራ እንዲከፈላቸው እንዲሁም ለ1ኛ ተጠሪ ብር 500 እና የጠበቃ አበል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ 5% እንዲከፈል የተሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊነት የወጪና ኪሣራ አከፋፈልን አስመልክቶ ከተቀመጡት የፍ/ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ሠምቷል።

ስለወጪና ኪሣራ የሚመለከተው የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀፅ 462 በክስ ምክንያት ስለሚከፈለው ማናቸውም ወጪና ኪሣራ የሚከፍለውን ወገን፣ የወጪውንና የኪሣራውን ልክ፣ የሚከፈልበትን የሃብት ምንጭ፣ የአከፋፈሉን ሁኔታ ፍ/ቤቱ ትክክል መስሎ በሚገምተው ሁኔታ እንዲሰጥ መብት (discretion) ይሠጠዋል። የወጪና ኪሣራ ክፍያ አላማም ረቺው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ ተረቺ እንዲሸፍን እንጂ ተረቺውን ለመቅጣት ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ የወጪና ኪሣራውን መጠን ለመወሰን መብት (discretion) ቢኖረውም ውሣኔውን በሚሠጥበት ጊዜ ይህንኑ የህጉን አላማ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

ፍ/ቤቱ ተገቢ ግምት ነው ያለውን ወጪና ኪሣራ ለመወሠን ይረዳው ዘንድም ወጪው ወይም ኪሣራው ሊከፈለው የሚገባው ወገን የወጪውን ዝርዝር እንዲያቀርብ ሊያዘው እንደሚችል የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 463(1) ያመለክታል። ዝርዝሩ ቢቀርብለትም ግን የቀረበውን ዝርዝር እንዳለ ለመቀበል ሣይገደድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 464 መሠረት መርምሮ በቂ ባልሆነ ምክንያት ከፍ ብሎ የሚታየውን በመቀነስ ወይም ተገቢ ያልሆነውን በመቀነስ ወይም ሙርሱንም በመሠረዝ መጠኑን መወሰን እንደሚገባው ይኸው የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ያመለክታል።

ከፍ ሲል የተመለከቱት የሥነ ሥርዓቱ ድንጋጌዎች በሙሉ፤ ምንም እንኳን ፍ/ቤቱ የወጪና ኪሣራውን መጠን ለመወሰን መብት (discretion) ቢኖረውም፤ መጠኑን ሲወስን ምክንያታዊ ባልሆነና በተጋነነ መንገድ እንዳይሆን ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

ከዚህ ተነስተን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የሰ/ጎንደር መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት ይግባኝ የለም ይህም በመሆኑ አመልካችን ሲሞግቱ ያወጡት ወጪም ሆነ በደረሰባቸው ኪሣራ አልነበረም። ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ሊተካላቸው የሚገባ ወጪም ሆነ ኪሣራ ስለሌለ አመልካቹ ለእያንዳቸው ብር 2.000 (ሁለት ሺህ ብር) እንዲከፍል የተሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የለውም።

በሌላ በኩል ግን 1ኛ ተጠሪ በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውሣኔ ላይ ይግባኝ አቅርበው አመልካቹን መርታታቸውን ተገንዝበናል። በመሆኑም ክርክራቸውን ለመከታተል ያወጡትን ወጪና ኪሣራ አመልካቹ ሊተካላቸው ይገባል። ነገር ግን ከፍ ሲል እንደተመለከተው የወጪና ኪሣራ ክፍያ ተከራካሪው ያወጣውን ወጪ ወይም የደረሰበትን ኪሣራ ከመተካት ያለፈ አላማ ስለሌለው የፍ/ቤቱ ውሣኔ ከወጣው ወጪ ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይገባዋል። በእርግጥ ፍ/ቤቱ ትክክለኛ ነው ያለውን ግምት ለመወሰን እንዲያመቸው የወጪና ኪሣራ ዝርዝር እንዲቀርብ ማዘዝ የሚችል ቢሆንም ዝርዝር ባልቀረበለት ጊዜም ተገቢ መጠን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው ኪሣራ በግምት ሊወሰን የሚችልበት አጋጣሚ እንዳለ ከፍ/ሥ/ሕ/ ቁ.464(3) መመልከት ይቻላል። በመሆኑም ዝርዝር ባልቀረበ ጊዜ የኪሣራው መጠን የተጋነነ እንዳይሆን ክርክሩ የወሰደው ጊዜ የክርክሩ ውስብስብነት አስፈላጊውን ዳኝነት ለመከታተል ተገቢ ናቸው የሚላቸውን ወጪዎች አመዛዝኖ ተመጣጣኝ መጠን ያለው ኪሣራ ሊወሰን ይገባል።

በተያዘው ጉዳይ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ለጠበቃ አበል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ 5% የሆነውን ከፍተኛ መጠን ያለው ኪሣራ ወይም ወጪ ሲወሰን ለኪሣራው አወሣሠን መሠረት ያደረገው ነገር ግልፅ አይደለም። በእርግጥ 1ኛ ተጠሪ በጠበቃ ክርክሩን መምራታቸው አላከራከረም። ይሁን እንጂ ጠበቃው ለሰጡት አገልግሎት ሊከፍሉ የተስማሙት የገንዘብ መጠን ስለመኖሩ የቀረበ ውል ካለመኖሩም ሌላ ጉዳዩ የቦታ ኪራይ እንዲከፈል የቀረበ የግብር ውሣኔ አፈፃፀም ክርክር እንጂ መደበኛ ክርክር አለመሆኑ ክርክሩ ውስብስብነት ያለው ነው ለማለት የሚያስችል ሆኖ አላገኘነውም። ጠበቃውም ዳኝነቱን ለመከታተል የተለየ ወጪ ሊያስወጣቸው የሚችል ነገር ስለመኖሩ መዝገቡ አያመለክትም። በአጠቃላይ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወሰነው የኪሣራ መጠን የወጪና ኪሣራ አከፋፈልን አላማ ያልተከተለና በዚህም ምክንያት እጅጉን የተጋነነ መሆኑን ተረድትናል። ይህም 1ኛ ተጠሪ ያወጡትን ወጪ ከመተካት አልፎ አመልካቹን የመቅጣትና ጠበቃውንም ያላግባብ እንዲበለፅግ የሚያደርግ ውሣኔ በመሆኑ ውሣኔው የሕግ ስህተት ያለበት ነው።

በሌላ በኩል ግን 1ኛ ተጠሪ ዋናው ባለጉዳይ በመሆናቸው ዳኝነቱን ለመከታተል ወደ ፍ/ቤት መመላለስ ያለባቸው በመሆኑም ሌሎችም አስፈላጊ ወጪዎች የሚያወጡ በመሆኑ ብር 500 (አምስት መቶ) እንዲከፈላቸው መወሰኑ ስህተት ነው ማለት አልቻልንም።

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04509 በ01/02/1998 ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 2.000 (ሁለት ሺህ) እንዲሁም ለ1ኛ ተጠሪ የጠበቃ አበል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ 5% እንዲከፈል የሰጠው የውሣኔ ክፍል ተሽሯል።
2. ለ1ኛ ተጠሪ ብር 500 (አምስት መቶ)እንዲከፈል የተሰጠው የውሣኔ ክፍል ፀንቷል።
3. 1ኛ ተጠሪ ክርክራቸውን በጠበቃ የተከታተሉ በመሆኑ የክርክሩን ርዝመትና የክርክሩን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት የጠበቃ አበል ብር 3,000 (ሦስት ሺህ) አመልካች እንዲከፍል ተወስኗል።

4. በዚህ ፍ/ቤት ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ። መዝገቡ ተዘግቷል።

የሰበር መ/ቁ. 17984

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

” ፍስሐ ወርቅነህ

” ዓብዱልቃድር መሐመድ

” አሰግድ ጋሻው

” ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ የጌዲዮ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት

ተጠሪ፦ ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ

የሐራጅ ሽያጭ - ጉድለት ያለበት ሃራጅ - ጉድለት ያለበት ሃራጅ ቀሪ ሲደረግ ሻጭና ገዥን ወደነበሩበት ስለመመለስ - የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1)ና(2)

የደቡብ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሀራጅ ሽያጩ ፈርሶ ንብረቱ ወደ ነበረበትና የግዢው ገንዘብ እንዲመለስ በመወሰኑ የቀረበ አቤቱታ ነው።

ውሣኔ፡ - የደቡብ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።

1. ንብረት በሐራጅ ከተሸጠ በኋላ የሐራጅ ሽያጩ በጉድለት ምክንያት ቀሪ እንዲሆን በተወሰነ ጊዜ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1817(1) የተደነገገውን ሊከተል ይገባል።
2. የሐራጁን ሽያጭ በማፍረስ ገዢዎችን ወደ ነበሩበት መመለስ ባልተቻለ ጊዜ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1817(2) መሠረት ለደረሰው መዛባት ኪሣራ ይከፈል ለማለት ጉዳዩ የመነጨው በፍርድ ቤት አማካይነት በተደረገ ሽያጭ በመሆኑ ይህን ድንጋጌ ተፈፃሚ ማድረግ የሚቻል አይደለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 17984

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

" ፍስሐ ወርቅነህ

" ዓብዱልቃድር መሐመድ

" አሰግድ ጋሻው

" ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ የጌዲዮ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት አልቀረበም

መልስ ሰጭ፦ ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

መዝገቡን መርምረናል እንደመረመርነውም በዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ በሁለተኛው የሐራጅ አሻሻጥ ሥርዓት አፈፃፀም ላይ ጉድለት ታይቶበታል። ስለሆነም ሁለተኛው የሐራጅ ሽያጭ ሊደረግ የሚገባው በግምቱ መነሻ ሲሆን በዚህ ግምት መነሻ ገንዘ ካልተገኘ ግምቱን መሠረት በማድረግ ከላይ ወደታች ጥሪ በማድረግ ነው በዚህ አኳኋን ይፈፀም በማለት ወስኖ ወደ ሥር ፍ/ቤት መልሶታል።

የሥር ፍ/ቤትም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ለማስፈፀም ቢታሰብ በተካሄደው ሁለተኛ ጨረታ ጊዜ አሸናፊ ናቸው የተባሉት ገዥዎች ንብረቱን ተረክበው በቦታው ላይ የሚገኘውንም ንብረት አንስተው ወስደውታል። የሚገኘው ነገር ቢኖር ባዶ ቦታ ብቻ ነው ስለሆነም እንደ ውሣኔው ለማስፈፀም እንዴት እንደሚቻል ማብራሪያ ይሰጥበት በማለት በአቀረበው ጥያቄ መነሻ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ የተሰጠው ውሣኔ ይሸጥ የተባለው ንብረት ወደ ሦስተኛ ወገኖች ማለት ወደ ገዥዎች የተላለፈ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት አይደለም፤ እነዚህ ገዥዎችም ሕግን የተላለፈ ተግባር የፈፀሙ ስለመሆኑም አልተገለፀም ስለሆነም ከዚህ በፊት ሥርዓቱን በተከተለ እኳኋን ሁለተኛ የሐራጅ ሽያጭ ሊከናወን ይገባል በማለት የተሰጠው ውሣኔ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል።

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን መልስ ሰጭ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርባለች።

የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ምንም እንኳ ይሸጥ የተባለው ንብረት በገዥዎች እጅ የገባ መሆኑ ቢረጋገጥም ይኸው ግዢ የተፈፀመበት ሐራጅ በይግባኝ እስከተሻረ ድረስ ግዢው እንዳልተደረገ ሊቆጠር ስለሚገባ ግዢው ፈርሶ ገዥዎች ንብረቱን በነበረበት ሁኔታ ሊመልሱ ይገባል፤ የገዥው ገንዘብ ለእነርሱ ይመለስ በማለት ወስኗል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የክልል ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ውሣኔ ለማስለወጥ ነው።

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል። እንደተመለከትነውም ሁለተኛ የሐራጅ ሽያጭ የተደረገበት አካሄድ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጉዳይ በይግባኝ ታይቶ ከመወሰን በፊት እንደ ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ በሁለተኛው ሐራጅ ገዢ መሆናቸው የተረጋገጠው ገዥዎች ባሸነፉበት ዋጋ መሠረት እንደ ሥርዓቱ ንብረቱን እንዲረከቡ ተደርጓል።

እንዲረከቡ ከተደረገ በኋላም በገዥነታቸው እምነት የቆዳና ሌጦ መጋዘኑንም ሆነ በወፍጮው የሚገኘውን ንብረት ነቃቅለው የወሰዱት ለመሆኑና እንደ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሊሸጥ የሚቻል ንብረት በቦታው የማይገኝ መሆኑን አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በሚገባ አረጋግጧል። እንደ ፍ/ቤቱ ማረጋገጫ ከሆነም ንብረቱን በነበረበት አኳኋን ለመመለስ የሚቻል አይደለም ይህ መሆኑን እንደተረዳ የሰበር ሰሚው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1817/1/ የተመለከተውን ድንጋጌ ሊከተል ይገባ ነበር። በዚህ ጉዳይ የሐራጅ ሽያጩን በማፍረስ ገዥዎችን ወደ ነበሩበት ቦታ መመለስ ባልተቻለ ጊዜ ከላይ እንደተመለከተው ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት ለደረሰው መዛባት ኪሣራ ይከፈል እንዳይባል ጉዳዩ የመነጨው በፍ/ቤት አማካኝነት በተደረገ ሽያጭ መሠረት በመሆኑም ይህንኑ ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚቻል ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሁኔታውን እንደነበረ ለማድረግ የማይቻል መሆኑን እየተረዳ በማይፈፀም አኳኋን የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አላገኘነውም።

ው ሣ ኔ

የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠ/ፍ/ቤት በሰበር መ/ቁ. 4867 ጥቅምት 17 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል። ይህንኑ እንዲያውቀው በክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኩል አፈፃፀሙን ይዞ ለነበረው ፍ/ቤት ይተላለፍ።

ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ መዝገቡ ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 19205

መጋቢት 25/1999

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- አቶ ሽኩር ሲራጅ

መልስ ሰጪ፡- አቶ ሙላት ካሣ

የአፈጻጸም ክርክር - ለአፈጻጸም በፍርድ ቤት የሚያገዝ ገንዘብ - ፍርድ ተፈፀመ ስለሚባልበት ጊዜ - የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 395

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳው ፍርድ ያረፈበትን ገንዘብ በፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

አንድ ፍርድ ተፈጸመ ሊባል የሚገባው ለፍርድ ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ ሲደርሰው ነው፡፡

የሰበር መ/ቁ. 19205

መጋቢት 25/1999

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- አቶ ሽኩር ሲራጅ ጠበቃ ሙላት ፈለቀ

መልስ ሰጪ፡- አቶ ሙላት ካሣ - ቀርበዋል

በዚህ መዝገብ የቀረበልንን የፀቡ አቤቱታ መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበልን ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች የፍርድ ባለመብት ሲሆን መልስ ሰጪ የፍርድ ባለእዳ ነው፡፡ የአሁን አመልካች የተፈረደለትን የገንዘብ መጠን ብር 24,227 (ሃያ አራት ሺ ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ብር) ለማስከፈል የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍቶ የአሁን መልስ ሰጭ ቤት ተሸጦ እዳው እንዲከፈል ትእዛዝ ተሰጠ፡፡ ከዚህ ትእዛዝ በኋላ የአሁን መልስ ሰጪ በፍርድ ቤት ፈቃድ ብር 20,000 በሞዴል በማስያዙ የአሁን አመልካች ገንዘቡ እንዲለቀቅለት አመለከተ፡፡ ሆኖም የአፈፀፀም መዝገቡ ጠፋ በመባሉ በፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቱ ትእዛዝ ሌላ የአፈፃፀም መዝገብ እንዲከፈት ከተደረገ በኋላ የፍርድ ባለመብቱ (የአሁን አመልካች) በሞዴል 85 የተያዘው ገንዘብ እንዲከፈለው በጠየቀው መሠረት ፍ/ቤቱ ወሎ ሆኖ እንዲከፈለው አዘዘ፡፡ ትእዛዙ የደረሰው የፋይናንስ ቢሮ በሞዴል 85 ተይዞ የነበረው ገንዘብ ፍርድ ቤቱ በ15/5/89 በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ገንዘቡን አቶ ኤልያስ አርአያ ለተባለ ሰው መክፈሉን ስለገለፀ ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት የፍርድ ባለእዳ ገንዘቡን በሞዴል 85 ካስያዘ በፍርድ ቤት እንደተቀመጠ ስለሚቆጠር የፍርድ ባለመብት ጉዳዩን ተከታትሎ ገንዘቡ ለሌላ 3ኛ ወገን እንዲከፈል ምክንያት የሆነውን አካል ጠይቆ ገንዘቡን ከሚቀበል በቀር ከፍርድ ባለእዳ ድጋሚ መጠየቅ አይችልም በማለት ወሰነ፡፡ ይህ ውሣኔ በከፍተኛ ፍ/ቤት የተሻረ ቢሆንም የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መልሶ በመሻሩ የፍርድ ባለመብት ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጠቅላይ ፍ/ቤቱ የፍትሕብሔር ችሎት የፍርድ ባለእዳ በሞዴል 85 ያስያዘውን ገንዘብ በፍትሀብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ. 395 መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት ነው የአሁን መልስ ሰጪን ይግባኝ በመቀበል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ የሻረው። የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው።

አመልካች በአቤቱታው ያቀረበው ቅሬታ በሞዴል 85 የተያዘው ገንዘብ በአመልካቹ ስም ለመሆኑ አልተረጋገጠም፣ አመልካች ያስፈረደው በመልስ ሰጪ ላይ በመሆኑ ከሦስተኛ ወገን ገንዘቡን እንዲያስመልስ መታዘዙ አግባብ አይደለም፣ ገንዘቡ ለሦስተኛ ከተከፈለ ገንዘቡን ማስመለስ ያለበት በስሙ ያስያዘው መልስ ሰጪ መሆን አለበት የሚሉት ናቸው።

መልስ ሰጪ የጽሑፍ መልሱን አቅርቧል። የመልስ ሰጪ ፍሬ ሀሣብ አመልካች ገንዘቡ በስሚ አልተያዘም ማለቱ ትክክል አይደለም፣ ገንዘቡ በሞዴል 85 በፍርድ ቤት በኩል እንዲያዝ ሲታዘዝ እዳው እንደተከፈለ ስለሚቆጠር ዳግመኛ ልጠይቅ አይገባኝም የሚሉ ናቸው።

ይህ ችሎት ጉዳዩን በስር ፍርድ ቤቶች ከተደረጉ ክርክሮች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማነፃፀር መርምሯል። መልስ የሚሻው ዋነኛ ነጥብ በሞዴል 85 ተይዞ የነበረው ገንዘብ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ቢከፈልም ለአሁን አመልካች እንደተከፈለ መቆጠሩ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው።

በመዝገቡ ለመገንዘብ እንደቻልነው የአሁኑ አመልካችን የአፈፃፀም ክስ መሠረት በማድረግ ብር 20,000 በሞዴል 85 በፋይናንስ ቢሮ እንዲያዝ መደረጉ አላከራከረም። ይህ ተይዞ የነበረው ገንዘብ ለአሁን አመልካች ሣይሆን ለሌላ ሰው በፍርድ ቤት ትእዛዝ መከፈሉም ተረጋግጦአል። የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይህ መሆኑ እየታወቀ መልስ ሰጪ እዳውን እንደከፈለ ይቆጠራል ለማት የበቃው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ.395 (1(ሀ)) ያስቀመጠውን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። የዚህ ቁጥር አግባብነት ያለው ክፍል" በፍርድ ወይም በውሣኔ መሠረት የሚከፈል ገንዘብ ሁሉ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ መከፈል አለበት። ፍርዱን እንዲያስፈጽም በታዘዘው ፍርድ ቤት በማስያዝ" በማለት ይደነግጋል። ከዚህ ድንጋጌ ለመገንዘብ የሚቻለው አንድ ሰው የተፈረደበትን ገንዘብ ለፍርድ ቤት ገቢ ለማድረግ ግዴታውን የሚወጣበት አንድ አማራጭ መንገድ መሆኑ ነው። ይህ ድንጋጌ ግን እንዲህ በተናጠል ሣይሆን ከድንጋጌው ዓላማ ጋር ተጣምሮ መታየት ይኖርበታል። ባለእዳው ገንዘቡን ለፍርድ ቤት ገቢ የሚያደርገው የፍርድ ባለመብት የሚጠይቀውን ገንዘብ እንዲያገኝ ለመርዳት ነው። የሂደቱ ዋናው ተጠቃሚ የፍርድ ባለገንዘቡ እንጂ ፍርድ ቤቱ እንደሆነ ተደርጉ ሊቆጠር አይገባውም። ለአንድ ፍርድ ባለመብት በፍርዱ መሠረት

ተፈፀመለት ሊባል የሚገባውም ለፍርድ ቤቱ ገቢ የሆነው ገንዘብ ሲደርሰው ነው። በፍርድ ቤቱ የተያዘው ገንዘብ የፍርድ ባለመብቱ የሚያገበት ገንዘብ አይደለም። ወደ ፍርድ ባለመብቱ ገቢ እንዲሆን የፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚፈልገውም የፍርድ ባለመብቱ የሚያገበት ሀብት ባለመሆኑ ነው። በመሆኑም በፍርድ ቤት ገንዘብ ገቢ በማድረግ እዳ መከፈል አንድ አማራጭ መንገድ ቢሆንም የፍርድ ባለእዳው እዳውን ጨርሷል መባል ያለበት ይህ ሂደት ተጠናቅቆ የፍርድ ባለመብቱ ገንዘቡን ሲረከብ ሊሆን ይገባል።

አሁን በቀረበልን ጉዳይ የፍርድ ባለእዳው ብር 20,000 በሞዴል 85 ማስያዙ ቢታወቅም ይኸው ገንዘብ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ለሌላ ሰው ተከፍሏል። የፍርድ ባለመብት የሆነው አመልካች ይኸው ገንዘብ እንዲከፈለው የጠየቀ ቢሆንም ገንዘቡን ይዞ የነበረው የፋይናንስ ቢሮ ገንዘቡን ለሌላ ሰው መከፈሉን በመግለፁ ሊከፈለው አልቻለም። ገንዘቡ ወሰደ የተባለው ሰው በምን ምክንያት እንደወሰደው የተገለፀ ነገር ባይኖርም በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንደተለቀቀለት ግን ከፍርድ ቤቶቹ መዝገብ ለመገንዘብ ችለናል። ይህ ገንዘብ ለአሁን መልስ ሰጪ እዳ መክፈያ ውሎ ሊሆን እንደሚችልም ይገመታል። በመሆኑም የፍርድ ባለመብቱ ገንዘቡን ባልተረከበበት ሁኔታ የፍርድ ባለእዳው እንደከፈለ መቁጠሩ አግባብ አይደለም። የፍርድ ባለእዳው ያስያዘው ገንዘብ ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት ተመልሶ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ከተከፈለ ባለእዳው ገንዘብ እንዳስያዘ ሊቆጠርም አይገባውም። ያስያዘው ገንዘብ ሣይኖር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 395(2) መሠረት ፍርዱ እንደተፈፀመ የሚቆጠርበት ምክንያት የለም።

በዚህ ምክንያት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ገንዘቡ መጀመሪያ በሞዴል 85 መያዙን ብቻ ግምት ውስጥ በማስገባት የአሁን መልስ ሰጭ እዳውን እንደከፈለ ይቆጠራል በማለት የሰጠው ውሣኔ ትክክል ስላልሆነ ሊሻር ይገባዋል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን መልስ ሰጪ ያስያዘው ገንዘብ ለሌላ ሰው መከፈሉን መሠረት በማድረግ ለብር 20,000 ተጠያቂ ነው በማለት የሰጠው ፍርድ ሊፀና የሚገባው ነው።

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ.ቁ. 17544 የካቲት 14 ቀን 1997 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08423 በ17/02/97 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል። ይፃፍ።
3. የዚሁ ውሣኔ ግልባጭ ለሁለቱም ፍርድ ቤቶች ይላክ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. ወጪና ኪሣራ መልስ ሰጪ ለአመልካቹ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) ይክፈል፣ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያስከፍል።

የሰበር መዝገብ ቁ. 19479

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረ ፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሀ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃደር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች፡- የወ/ሮ አመለወርቅ ገለቱ ወራሾች

መ/ሰጪዎች፡- እነ አቶ ቢሻው አሻሜ

ውርስ - የጋራ ሃብት - የቤት ክፍፍል - የቦታ ይዞታ መብት - የአዋጅ ቁ. 47/67

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለውርስ ክፍፍል ክርክር የቀረበበት ቤት የጋራ ነው ሆኖም የቦታ ይዞታው የግል ነው ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው።

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል።

1. አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ሆነ የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግሥት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገመትና አስፈላጊም ከሆነ እንዲሸጥ የሚያደርግ ውሣኔ መሬት የመንግሥት ለማድረግ የወጣውን ህግ የሚፃረር ነው።
2. ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎች በስር ፍርድ ቤት ክርክር ያላደረጉበትን መሠረት አድርጎ መወሰን አይችልም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁ. 19479

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች:- አቶ መንበረ ፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሀ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃደር መሐመድ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች:- የወ/ሮ አመለወርቅ ገለቱ ወራሾች -ወኪል ቀርባለች

መልስ ሰጪ:- 1ኛ. አቶ ቢሻው አሻሜ -ቀረቡ
2ኛ. አቶ አዳነ አሻሜ
3ኛ. አቶ ማነው አሻሜ } - ወኪላቸው ቀርበዋል
4ኛ. ወ/ሮ እመቤት አሻሜ

በዚህ መዝገብ የቀረበልንን ጉዳይ መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል::

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ቤትን አስመልክቶ የቀረበ የክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ነው:: የአሁን መልስ ሰጪዎች መጀመሪያ ያቀረቡት ክስ የአውራሻችን የግል ቤት በስር ተከሣሾች በአሁን አመልከቾች እጅ ስለሚገኝ ድርሻችን ብር 111,111.08 /አንድ መቶ አስራ አንድ ሺህ አንድ መቶ አስራ አንድ ብር ከዜሮ ስምንት ሣንቲም/ እንዲሰጠን በማለት ክስ አቀረቡ:: ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የአሁን መልስ ሰጪዎች ቤቱ የጋራ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ስላቀረቡ ቤቱ የግል ሳይሆን የጋራ ነው በማለት ወሰነ:: ፍርድ ቤቱ ቤቱ የጋራ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው ጥያቄ የቀረበበት ቤት ጋብቻ ከተመሰረ በኋላ እንደአዲስ ተሰርቷል በማለት ነው:: ይኸው ፍርድ ቤት ቤቱ የጋራ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ቤቱ የተሰራበት ቦታ ግን የግል ነው በማለት ከየቦታው ግምትና የቤቱ ግምት ለየብቻ በባለሙያ በፍርድ አፈፃፀም ተገምቶ ተከሣሾች የቤቱን ግምት ብቻ ግማሹን ለተከሣሽ ሰጥተው ከተከሣሽ እንዲረከቡ ይህ ካልተቻለ ተከሣሽ የቦታውን ግምት እና የቤቱን ግምት ግማሽ ለከሣሾች ሰጥተው ቤቱን እንዲያስቀሩ ይህ ካልሆነ ቤቱና ቦታው በሐራጅ ተሸጦ የቦታው ግምት በውሉ የቤቱ ግምት ግማሽ ለከሣሾች እንዲከፍል እና የቀረው የቤቱ ግምት ለተከሣሽ እንዲከፍል ታዟል በማለት ሐምሌ 8 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ወሰነ::

ይህን ውሣኔ በመቃወም ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ በአሁን አመልካቾች ቢቀርብም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 33964 ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ዘግቶታል::

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት ካለበት ይታረምልን በማለት ነው:: በአቤቱታው የተገለፁት ዋና ዋና ቅሬታዎች:-

1. ቤቱን በሚመለከት እንጂ ቤቱ የተሰራበትን ቦታ በሚመለከት ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበ አቤቱታም ሆነ በፍርድ ቤቱ የተደረገ ክርክር አልነበረም:: ክርክር ባልተደረገበት ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ መስጠቱ ሥርዓቱን የተከተለ ሂደት አይደለም::
2. ቦታው የግል ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ያደረገውን አዋጅ 47/1967 እና የሕገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚጥስ ነው፣
3. ፍርድ ቤቱ ያስቀመጠው የክፍፍል ቀመር ተጠሪዎች ከጠየቁት ውጪ የተደረገ ነው፣ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.2/3/1992 ድንጋጌዎችም ያገናዘበ አይደለም የሚል ነው::

መልስ ሰጪዎች አመልካቾች ላቀረቡት አቤቱታ ሰኔ 8 ቀን 1997 የተፃፈ መልስ አቅርበዋል:: በመልሳቸው ላይም :-

1. አዋጅ ቁጥር 47/ 67 አንቀፅ 7/1/ አዋጁ ከመፅናቱ በፊት የከተማ ቦታ ያለው ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ሌላ የመኖሪያ ቤት ከሌለው በአንቀፅ 4/1/ በተመለከተው የይዞታ መጠን በቦታው ላይ የይዞታ መብት ይኖረዋል ስለሚል የቀረበው የአመልካች ቅሬታ የሕግ መሠረት የለውም፣
2. አመልካች የከተማ ቦታ የመንግስት ብቻ ነው ቢሉም ይህን የሚደግፍ አንቀፅ አልጠቀሱም፣
3. የስር ፍ/ቤቶች የሰጡዋቸው ውሣኔዎች የቤተሰብ ሕግን ድንጋጌዎች የሚጻረሩ አይደሉም፣
4. የቤቱ ግምት የተሰላው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የቀረበውን የ275, 000 ብር/ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር/ ግምት በመንተራስ በመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል::

ይህ ችሎት በግራ ቀኙ ያለው ክርክር ዋነኛ ነጥብ ክርክር ያስነሣው ቤትና ቤቱ የተሰራበት ቦታ ለየብቻ በመመልከት ቤቱ የጋራ ነው ቦታው ግን የግል ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ የሕግ መስረት ያለው ነው ወይም አይደለም የሚለው ነው::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ ከማህደሩና ተያይዘው ከቀረቡት ሰነዶች ለመገንዘብ የቻልነው በአመልካችና በመልስ ሰጪ የነበረው ሙግት ቤትን የሚመለከት ብቻ ነው። ቤቱ ያረፈበት ቦታን የሚመለከት ሙግት በመጀመሪያ ፍርድ ቤት አልተካሄደም ስለዚህ ፍርድ ቤቱ መጨረሻ ላይ ቤቱ ያረፈበትን አስመልክቶ የሰጠው ውሣኔ ባለጉዳዩቹ ያደረጉትን ክርክር መሠረት ያደረጉ አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ የከተማ /ቦታና ትርፍ ቤት የመንግስት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ. 47/67 በከተማ ቦታ ላይ የግል ባለሀብትነት ማስቀረቱን ግንዛቤ የወሰደ ውሣኔ ሆኖ አላገኘነውም። አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ይሁን የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግስት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገመትና አስፈላጊም ከሆነ እንዲሸጥ የሚያደርገው ውሣኔ መሬት የመንግስት ለማድረግ የወጣውን ህግ የሚፃረር ነው። የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የተሰራውን ስህተት ማረም ሲገባው ይግባኙን በ337 አያስቀርብም ማለቱ አግባብ አልነበረም። በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤትም ሆነ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጡት ወሣኔ ሊለወጥ የሚገባው ነው።

ው ሣ ኔ

1. ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመልስ ሰጪዎች አውራሽ የግል ሀብት ነው የሚለው የመጀሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 01416 ሐምሌ 8 ቀን 1996 የተሰጠው ውሣኔ ተሰርዟል።
2. አከራካሪው ቤትና ቦታ በግራ ቀኙ ስምምነት ይከፋፈል ። በስምምነት መከፋፈል ካልቻለ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል ይካፈሉ።
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።

የሰበር መ/ቁ. 16109

ሚያዝያ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- አቶ ከበደ አርጋው

መልስ ሰጪ፡- እነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ - የእግድ ትዕዛዝ፣ የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ስለመጠየቅ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭን በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ማስመዝገብ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1587-1620፣ 1613፣ 1614 2878

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የማይንቀሳቀስ ሽያጭ ውል በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ እስካልተመዘገበ ድረስ በሦስተኛ ወገን ላይ ወቃወሚያ ሊሆን አይችልም ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው።

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል።

1. አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭን የሚመለከት ውል በመዝገብ የሚጻፍበት ቀንና የንብረቱ የባለቤትነት ስም የሚዛወርበት ቀን ልዩነት ሊኖረው ይችላል።
2. ውሉ በመዝገቡ እስከተፃፈ ድረስ ሶስተኛ ወገኖች የስሙን አለመዛወር መሰረት በማድረግ ሊከራከሩ እንዲችሉ ሕጉ አይፈቅድላቸውም።
3. የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2878 የሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው በተዋዋዮች ላይ ውላቸውን በመዝገቡ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ አይጥልባቸውም።
4. ሽያጭ በመዝገብ ውስጥ ማስፃፍ ማለት በሚመለከተው ማህደር ውስጥ ውሉን በማያያዝ የሚጠቃለል ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 16109

ሚያዝያ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ፍስሐ ወርቅነህ

3. አብዱልቃድር መሐመድ

4. አሰግድ ጋሻው

5. መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- አቶ ከበደ አርጋው ከጠበቃው ጋር ቀርቧል፡፡

መልስ ሰጪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ቀርቧል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚሁ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158ን በመጥቀስ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ሰኔ 20 ቀን 1994 ዓ.ም. ወረዳ 23 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥሩ 153 በሆነ ቤት ላይ የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ በመድረጉ ነው፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን የእግድ ትእዛዝ የሰጠው በአሁን መልስ ሰጪ ንግድ ባንክና በአቶ ቦጋለ ቲጋ መካከል በነበረ ክርክር ምክንያት ሲሆን ቤቱ የታገደው አቶ ቦጋለ ቲጋ በነበረባቸው የባንክ እዳ ምክንያት ነው፡፡ የአሁን አመልካች በቤቱ ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ሲጠይቁ ለማመልከቻቸው መነሻ ያደረጉት ቤቱን በ1987 ዓ.ም. ከተከሰሰ ከአቶ ቦጋለ ቲጋ የገዙት መሆኑን፣ ውሉ በውል አዋዋይ ፊት የተፈፀመ መሆኑንና የቤቱን ካርታ የተረከቡ መሆኑን ቤቱን ሲገዙ ቤቱ እዳና እገዳ ያልነበረበት መሆኑ ከየዞኑ ፋይናንስ ቢሮና ከባንክ የተጣራ መሆኑን ነው፡፡

ከፍተኛው ፍርድ ቤት የመልስ ሰጪን መቃወሚያ ከተቀበለ በኋላ የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ መልስ ሰጪ ያቀረበው ተቃውሞ በዋናነት አመልካች አደረግኩት የሚሉት የሽያጭ ውል የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 2878 በሚያዘው መሠረት በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ስላልተመዘገበ እግዱ የተሰጠው በአቶ ቦጋላ ቲጋ ስም በተመዘገበ ቤት ላይ እንጂ በአመልካች ቤት ላይ አይደለም፣ የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሰኔ 19 ቀን 1994 የተሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ተግባራዊ ያደረገው ቤቱ በአሁን አመልካች ባለመመዝገቡ ነው የሚል ነው፡፡ ጥያቄው የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤትም ቤቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ የተሰጠው በሥር ተከሣሽ በአቶ ቦጋለ ቲጋ ስም የተመዘገበ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ መሆኑን የአመልካች የሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 መሠረት በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ እስካልተመዘገበ ድረስ በ3ኛ ወገን

ላይ መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል በመግለጽ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ በሥር ተከሣሽ በአቶ ቦጋለ ቲጋ ሥም ተመዝግቦ በሚገኝ ቤት እንጂ በአሁን አመልካች በአቶ ከበደ አርጋው ስም በተመዘገበ ቤት ላይ ባለመሆኑ እግዱ የሚነሳበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አደረገ፡፡ አመልካች ይግባኝ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ከሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ትእዛዝ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው መሠረታዊ ሀሣብ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ የሚጠቃለል ነው፡፡

1. ዕግድ የተሰጠበት ቤት ግንቦት 9 ቀን 1987 ዓ.ም. በተደረገና በውልና ማስረጃ በተመዘገበ የሽያጭ ውል ለአሁን አመልካች የተሸጠ መሆኑን ይህም ውል ለሥራና ከተማ ልማት ቀርቦ ከማኅደሩ ጋር የተያያዘ መሆኑ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሐምሌ 18 ቀን 1994 ዓ.ም. በተ.ቁ. 2/በ-1277/125 በዓፈው ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ ያሳወቀ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154 መሠረት በቤቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ መስጠት ትክክል አልነበረም፡፡
2. ከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠቀሰው ቤት ለአመልካች ግንቦት 9 ቀን 87 ዓ.ም. የተሸጠ መሆኑን በመግለጽ የአ/አ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ያቀረበለትን ማረጋገጫ ወደጎን የተወው ያለአግባብ ነው፡፡
3. ቤቱ የተሸጠ መሆኑ ከሚመለከተው ክፍል ቀርቦለት እያለ አመልካች የሽያጭ ውሉን አላቀረበም ማለቱ ትክክል አይደለም፡፡
4. የሽያጭ ውሉ በውልና ማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ ለሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ቀርቦ ከማህደሩ ጋር በመያያዙ የፍ/ሕግ/ቁ. 2878 መስፈርት አልተሟላም መባሉ አግባብ አይደለም፡፡
5. የከተማ ልማት ቢሮ የፃፈው ደብዳቤ የለም፤ ዝውውሩ አለመፈፀሙ እንጂ ውሉ በማይንቀሳቀስ ንብረት አለመመዝገቡን አልገለፀም የሚሉ ናቸው፡፡

መልስ ሰጪ በጉዳዩ ላይ የጽሁፍ መልስ አቅርቧል ዋና ዋና ነጥቦቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የእግድ ትእዛዝ የተሰጠው ተጠቃሹ ቤት በአቶ ቦጋለ ቲጋ ስም የተመዘገበ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡
2. የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ፃፈ የተባለውን ደብዳቤ በማስመልከት በሥር ፍ/ቤት ክርክር ስላልተደረገ በአሁን ደረጃ ክርክር መቅረብ አይችልም፡፡
3. አመልካች አለኝ የሚሉትን የሽያጭ ውል ለከፍተኛውም ሆነ ለጠቅላይ ፍ/ቤት አለማቅረባቸው የሽያጭ ውሉ በእርግጥ አለመፈፀሙ የሚያመለክት ነው፡፡
4. ጉዳዩ የሚመለከተው የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በሥር ተከሣሽ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ በማረጋገጡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 መስፈርት ተሟልቷል ሊባል አይችልም፡፡
5. ተደረገ የተባለው የሽያጭ ውል በውልና ማስረጃ መረጋገጡም ሆነ የውሉ ቅጂ ከሚመለከተው ማኅደር ቀርቧል መባሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 በሚያዘው መሠረት ምዝገባው በአሁን አመልካች ስም መፈፀሙን የሚያመለክት አይደለም፡፡
6. ቤቱ በሥር ተከሣሽ ስም የተመዘገበ በመሆኑ እግዱ ተገቢ ነው ሊነሳም አይገባውም፡፡

አመልካቹ በመልስ ሰጪ ለቀረበው መልስ በጽሁፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ ይህ ችሎት የቀረበውን ክርክር አግባብ ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮአል፡፡ በቀረበው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ለመስጠት አመልካች ውሉን በሚመለከተው አካል የሽያጭን ውል ካስመዘገበ የቤቱ ስም ባለመዛወሩ ብቻ ባለቤትነት የለውም ሊባል ይችላል? የሚለውን ከተጓዳኝ ሌሎች ነጥቦች ጋር መመልከት ያስፈጋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት መዝገብ አስቀርበን እንተመለከትነው የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሐምሌ 18 ቀን 1994 ዓ.ም. ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በላከው ደብዳቤ ስሙ በአሁን አመልካች የተዛወረ ባይሆንም አመልካችና አቶ ቦጋለ ቲጋ የሽያጭ ውል መፈጸማቸው፣ ይኸው ውል በውልና ማስረጃ የተመዘገበ መሆኑ፣ ይኸው ውል ቤቱን በሚመለከት ማኅደር ውስጥ መያዙን ገልጿል፡፡ አግባብነት ያለው የደብዳቤው ክፍል፡-

> “ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት በመሥሪያ ቤታችን የሚገኘውን የአቶ ቦጋለ ቲጋ ማኅደር አውጥተን እንዳየነው በወረዳ 23 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥር 153 በግለሰቡ ስም የተመዘገበ ሲሆን ግለሰቡ ከላይ በተጠቀሰው ወረዳና ቀበሌ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት ግንቦት 9 ቀን 1987 በውልና ማስረጃ ምዝገባ መምሪያ ባደረጉት ውል ለአቶ ከበደ አርጋው ሸጠው ውሉ በማኅደሩ ውስጥ ተያይዞ የሚገኝ እና የስም ዝውውሩ ያልተፈፀመ መሆኑን ለተከበረው ፍ/ቤት እየገለጽን ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ይዞታውን በነበረበት ሁኔታ በማስከበሪያ መዝገብ ላይ መዝግበን ያገድን መሆኑን እንገልፃለን” የሚል ነው፡፡

ከዚህ ደብዳቤ ይዘት ለመገንዘብ እንደሚቻለው የአሁን አመልካች የሽያጭ ውሉን አዋዋይ ፊት ከመፈፀም ባሻገር የሽያጭ ውሉ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል አቅርበው ከማኅደሩ ጋር እንዲያያዝ አድርገዋል፡፡ የሽያጭ ውሉ ከማኅደሩ ጋር የተያያዘው መቼ እንደሆነ በደብዳቤው ላይ ባይገለጽም ፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት መያያዙ ግን ከደብዳቤ ይዘት መገንዘብ ይሻላል፡፡ ውሉ በውልና ማስረጃ ፊት ቀርቦ የተፈፀመውም ግንቦት 9 ቀን 1987 ዓ.ም. መሆኑም ከዚሁ ደብዳቤ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ያም ሆኖ ጉዳዩ የቀረበለት መስሪያ ቤት የስም ዝውውሩን በአመልካች ስም አላደረገም፡፡ በዚህም ምክንያት ደብዳቤው በተፃፈበት በሐምሌ 18 ቀን 1994 ዓ.ም. የቤቱ ስም የተመዘገበው በሻጩ በአቶ ቦጋለ ቲጋ እንጂ በአሁኑ አመልካች አይደለም፡፡ የከፍተኛውም ፍርድ ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው ማኅደሩ ውስጥ የሚገኘውን አጠቃላይ ይዞታ ሳይሆን ቤቱ ትአዛዙ በተሰጠበት ወቅት በማን ስም ነበር የሚለውን ነጥብ ብቻ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የጠቀሰው የፍትሐብሄር ሕግ ቁ. 2878 "ያንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኘው በማይንቀሣቀስ ሀብት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ውጤትን ሊያስገኝ አይችልም" በማለት ይደነግጋል፡፡ በመሠረቱ ይህ ድንጋጌ የሚጠይቀው የሽያጭ ውሉ በመዝገብ ውስጥ መፃፍ እንዳለበት ነው፡፡ ስለዚህ የሦስተኛ ወገኖችን በሚመለከት ተዋዋዮቹ ጥበቃ የሚያገኙት ውሉ በመዝገቡ ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡ ውሉ በመዝገብ በተፃፈበት ቀንና ስሙ ወደገዢው በተዛወረበት ቀን ልዩነት ሊያስጥም እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ የስም ዝውውር ውሉን ከማቅረብ በተጨማሪ ሌሎች ጉዳዮችን ሚሚላት የሚጠይቅ በመሆኑ ውሉ በቀረበበትና በተፃፈበት ቀን ላይጠይቁት ይችላል፡፡ ውሉ በመዝገቡ እስከተፃፈ ድረስ ግን ሦስተኛ ወገኖች የስሙን አለመዛወር መሠረት በማድረግ ሊከራከሩ እንዲችሉ ይህ ድንጋጌ አይፈቅድላቸውም፡፡ የሕጉ መሠረታዊ ዓላማ ሦስተኛ ወገኖች የማይነቀሣቀሰው ሀብት በማስመልከት የተፈፀሙ ሕጋውያን ተግባራት እንዲውቁ ማስቻል ነው፡፡ ይህ ዓላማ የሽያጭ ውሉ በመዝገቡ ውስጥ እንዲፃፍ በማድረግ ማሳካት ይችላል ከሚል መንደርደሪያ የተነሣው የፍትሐብሔር ሕጉ 2878 የሽያጭ ውሉ በሦስተኛ ወገን ላይ ውጤት እንዲኖረው በተዋዋዮቹ ላይ ውላቸውን በመዝገቡ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ አይጥልባቸውም፡፡ ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ከውሉ መመዝገብ በተጨማሪ የማይንቀሣቀሰው ንብረት ሀብትነት በገዢው ስም መዛወር አለበት የሚል ድንጋጌ የለውም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የፈፀመው የሽያጭ ውል በሦስተኛው ወገን ላይ ውጤት ይኖረዋል ወይም አየኖረውም ለማለት ማጣራት የነበረበት ውሉ በማይንቀሣቀስ ንብረት መዝገብ ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዛፍ አለመዛፉን እንጂ ስሙ በአመልካች መዛወር አለመዛወሩን መሆን አልነበረበትም፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ጉዳዩ የሚመለከተው የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በአመልካችና በአቶ ቦጋለ ቲጋ ተጠቃሹን ቤት በማስመልከት የተፈፀመው ውል በማህደሩ ውስጥ መያያዙን ለፍርድ ቤቱ አስታውቋል፡፡ ሽያጭ በመዝገብ ውስጥ መዛፍ ማለት በሚመለከተው ማህደር ውስጥ ውሉን ማያያዝ የሚያጠቃልል መሆኑ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1613 እና 1614 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከፍትሐብሔር ሕግ 1587-1620 ያሉት የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች እንደሚያመለክቱት ምዝገባ የሚከናወነው መዝጋቢው አካል የሚያቀርበውን ፎርም በመጠቀም አስፈላጊ ዝርዝር ጉዳዮችን ማህደሩ ውስጥ አንዲካተት በማድረግ ነው፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች እነዚህ ፎርሞች በሚመለከተው አካል ቀርበውለት አለመሙላቱን የሚገልጽ ነገር ለፍርድ ቤቱ አልቀረበም፡፡ ይልቁንም የሽያጩን ዝርዝር የሚያመለክት የሽያጭ ውል ለሚመለከተው አካል አቅርቦና ተቀባይነት አግኝቶ ከማህደሩ ጋር ለማያያዙ ተገልፆአል፡፡

ይህ መሆኑ ሲረዳ ፍ/ቤቱ ባንክ እንደሸጥለት ጥያቄ ያቀረበበት ቤት የአሁን አመልካች መሆኑን በመገንዘብ የእግድ ጥያቄው ውድቅ ማድረግ ነበረበት፣ በወቅቱ እግዱን ቢሰጥ እንኳን አመልካቹ እግዱ ይነሣልኝ ብሎ ሲጠይቅ ጥያቄውን ተቀብሎ የሰጠው እግድ ማንሣት ነበረበት የአመልካችና የአቶ ቦጋለን የሽያጭ ውል በሚመለከት መልስ ሰጪ ባንክ ሦስተኛ ወገን ነው፡፡ ስለዚህ የሽያጭ ውሉ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2878 አባባል በማይንቀሣቀስ ሀብት መዝገብ ሲፃፍ በባንኩ ላይ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ቤቱ አሁንም በአቶ ቦጋለ ቲጋ ስም የሚገኝ ነው በማለት የሰጠው የፍርድ ትእዛዝ የዚህን ሕግ ግልጽ ድንጋጌ የሚጥስ የአንድ ሰው ሀብት ለሌላ ሰው እዳ ማስፈጸሚያ እንዲውል የሚያደርግ በመሆኑ ትክክል አይደለም፡፡

ው ሣ ኔ

1. ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 14428 ሰኔ 19 ቀን 1994 ዓ.ም በወረዳ 23 ቀበሌ 12 በቤት ቁጥር 153 የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
2. ከላይ የተጠቀሰው ቤት አመልካች የገዙትና በማይንቀሣቀስ ሀብት ሽያጭ ውሉ እንዲመዘገብ ያደረጉ በመሆኑ በመልስ ሰጪ እና በአቶ ቦጋለ ቲጋ መካከል ለነበረው የአፈፃፀም ክስ ማስፈፀሚያ ሊሆኑ አይገባም፡፡
3. ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰውን በሚመለከት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 14428 የተሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሏል፡፡
4. መዝገቡ ስለተወሰነ ከከፍተኛ ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ ይመለስ፡፡

የሰበር መ/ቁ. 14094

ሚያዝያ 18/1999

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሠግድ ጋሻው

አቶ መስፍን እቁበዮናስ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት

ተጠሪ፡- የአቶ ሰለሞን ወረደ ወራሽ ሕፃን አብይ ክብሩ

የንብረት ክርክር - ኪራይ የተወረሰ ንብረት - ክስ የማቅረብ መብት የፍ/ብ/ሀ/ቁ/ 1195፣ አዋጅ ቁ. 47/67፣ የፍ/ብ/ስ/ሥ/ሀ/ቁ/ 33/2/

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት ለተጠሪ ሊለቅ ይገባል ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሸሯል፡፡

1. ለረጅም አመታት በመንግሥት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ያለአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሣኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት አለበት፡፡
2. አንድ ከሳሽ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሃብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑን ካላረጋገጠ ክስ እንዲያቀርብ አይፈቀድለትም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 14094

ሚያዝያ 18/1999

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አሠግድ ጋሻው

3. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

4. ወ/ት ሒሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት - ነገረፈጅ አቶ አንበርብር አባይነህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአቶ ሰለሞን ወረደ ወራሽ ሕፃን አብይ ክብሩ ሰለሞን የሚች ሚስትና ሞግዚት ወ/ሮ መሠረት ከበደ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ አውራሽ አቶ ሰለሞን ወረደ በሥር ተከሣሽ ላይ ባቀረቡት ክስ ተከሣሹ በውርስ ያገኙትን ቤት በሕገወጥ መንገድ የያዙባቸው ስለሆነ እንዲለቀቅላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተከሣሹም ቤቱን ከአመልካች የተከራየላቸው አገር መከላከያ ሚ/ር በመሆኑ ሊከሠሡ እንደማይገባ ተከራክረዋል ፍ/ቤቱም አመልካቹና የአገር መከላከያ ሚ/ር እንዲገቡ በማድረግ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተከሣሹንና የአገር መከላከያ ሚ/ርን በነፃ ከክሱ በማሰናበት ክርክር የተነሣበት ቤት የከሣሽ አባት ቤት መሆኑና ከሣሹም የሣቸው ወራሽ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች ቤቱን ለከሣሽ እንዲያስረክብና የ6 ወር ኪራይ ብር 12.000 /አስራ ሁለት ሺህ/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ መልስ ሰጪን ሣይጠራ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የቅሬታ ነጥቡም ክርክር የተነሣበትን ቤት ባለቤትነት ለማሥረዳት የቀረበው ካርታና የቤት ስራ ፈቃድ ባለቤትነትን አያስረዳም፣ በፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት ከተገቢው የመንግሥት አካል የተሰጣቸው የባለቤትነት ምስክር ወረቀት አልቀረበም፣ ከአ/ቁ. 47/67 መሠረት ከታህሣሥ 11/1967 ጀምሮ የከተማ ቤት በንብረትነት የያዘ ግለሰብ ወይም ድርጅት መብቱ በሚኒስትሩ ካልፀደቀ በቀር ንብረትነቱ አይፀናለትም የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም ቤቱ እንዲመለስም ሆነ ኪራይ እንዲከፈል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም

ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በቃል ባደረገው ማጣራት ቤቱን ያስተዳድረው የነበረው የአሁኑ አመልካች እንደሆነና የሥር ከሣሽ ቤቱን የያዙት በ1983 መሆኑን ተረድቷል፡፡ መዝገቡንም እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ የተጠሪው አውራሽ ክስ ያቀረቡት ከአባቱ በውርስ ያገኘሁትን ቤት የሥር 1ኛ ተከሣሽ ያላግባብ ስለያዙብኝ ይልቀቁልኝ፣ ኪራዩንም ይክፈሉኝ የሚል ነው፡፡ ከሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርና በዚህ ችሎትም በተደረገው ማጣራት ክርክር የተነሣበትን ቤት 1ኛ ተከሣሽ የያዙት በኪራይ መሆኑን፣ ቤቱን ያከራየውም አመልካች መሆኑን፣ ቤቱ በ1983 በሥር ከሣሽ ከመያዙ በፊት ያስተዳድረው የነበረው አመልካች መሆኑን፣ አሁንም ቤቱ በአመልካች የሚተዳደር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንግዲህ ይህ ቤት ለረኽርም አመታት በመንግሥት እጅ የነበረ ሲሆን የተጠሪ አውራሽ ቤቱ በአ/ቁ 47/67 የተፈቀደላቸው እና ባለንብረት በመሆናቸው ወይንም ደግሞ ያላግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚሉም ከሆነ ለሚመለከተው አካል ጥያቄአቸውን አቅርበው ውሣኔ አግኝተው ባለመብት ስለመሆናቸው ያስረዱት ነገር የለም፡፡ የተጠሪ አውራሽ ቤቱን በ1983 መያዛቸውን ቢገልፁም በምን ሁኔታ እንደያዙት ያቀረቡት ነገር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ቤቱ እንዲመለስላቸው ክስ ሲያቀርቡ በቤቱ ላይ ያላቸውን መብት አላረጋገጡም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ አንድ ከሣሽ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሠረተበት ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑን ካላረጋገጠ ክስ እንዲያቀርብ አይፈቀድለትም፡፡

ባመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በሥር ከሣሹ አባት ስም የቀረበውን ካርታና የቤት ሥራ ፈቃድ መሠረት አድርገው ከሣሹ ክሱን ባቀረቡ ጊዜ በቤቱ ላይ የነበራቸውን መብት ሣያረጋግጥ ቤቱን እንዲረከቡና ኪራይ እንዲከፈላቸው በመወሰኑ የሕግ ሥህተት መፈፀሙን ተረድተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 3269 ሚያዚያ 6/1995 የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21007 ታህሣሥ 19/1996 የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ አውራሽ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑን ስላላረጋገጡ ክሱ ተቀባይነት የለውም፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ ወ/ሮ ድንቁ ተድላ

ተጠሪዎች፦ እነ አቶ አባተ ጫኔ

ውርስ - ይርጋ - የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1000 አፈጻጸም - ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት መፍረስ - ጋብቻ በሞት በፈረሰ ጊዜ የግል ንብረት የሚወሰድበት ጊዜ - የውል ሀግ ድንጋጌዎች በሌሎች ግዴታዎች ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ - የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 17፣ 684፣ 1000፣ 1677፣ 1845

የአማራ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ በመስጠቱ የቀረበ አቤቱታ ነው።

ውሣኔ፡ - የአማራ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል።

1. በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1000/1/ ና /2/ ላይ የሰፈረው የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆነው አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሀብት በያዘ ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ነው።
2. ተከራካሪዎች የይርጋ ጥያቄ እስካቀረቡ ድረስ ጥያቄውን በትክክለኛው አንቀጽ መሰረት እንዲመራ ማድረጉ የፍርድ ቤት ሃላፊነት ነው።
3. ጋብቻ በአንደኛው ተገቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት ባይመለከትም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677 መሠረት በቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈጻሚ ይሆናል።

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ ወ/ሮ ድንቁ ተድላ - ጠበቃ ማሞ ስበር ቀርበዋል

መልስ ሰጪ፦ (1) አቶ አባተ ጫኔ - ወኪሉ ቀርበዋል
(2) አቶ ፍስሀ መልካሙ - ቀርበዋል

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር ጉዳይ መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ሕግን በርካታ ድንጋጌዎች የሚመለከት ሲሆን በዋናነት በሰበር ፍርድ ቤት የቀረበን የይርጋ ጥያቄ የሚያስተናግድ ነው።

የአሁን መልስ ሰጪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ አውራሻቸን ደጃዝማች ጫኔ የመረጡ ከቀድሞው ንጉሰ ነ/ሥላሴ በስጦታ ያገኙትን የግል ቤት የሚች ሚስት የሆኑት የአሁን አመልካች የሌላቸውን የወራሽነት መብት አለኝ በማለት ቤትና ቦታው አለአግባብ በስማቸው እንዲዞር ጠይቀዋል። በመሆኑም አመልካችዋ ያለአግባብ የያዙብንን የአውራሻችንን ቦታ ያስረክቡ የሚል ክበር የአሁን መልስ ሰጪዎች ያቀረቡት ክስ የቤቱን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለአሁን አመልካች በሕገወጥ መንገድ ሰጥቷል በማለት የጉንደር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን 2ኛ ተከሣሽ በማድረግ ከሰዋል።

የአሁንዋ አመልካች ሚች ደጃዝማች ጫኔ የመረጡ የሞቱት በ1978 ሲሆን ክስ የቀረበው በ1990 ዓ.ም በመሆኑ ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል በማለት የይርጋ ጥያቄ አነሱ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ዝርዝር መልስም አቀረቡ። በተነሣው የይርጋ ጥያቄ ላይ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የተለያየ ውሣኔ ሰጡ። ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ውሣኔ የሰጠው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይርጋው ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ ሰጥቷል። የይርጋውን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 1000(1) በዚሁ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው። ይኸው ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንም ያለውም በሁለት ምክንያት ነው። አንደኛው ምክንያት ድንጋጌው በወራሾች መካከል የሚነሳን ክርክር የሚመለከት እንጂ በሟች ሚስት እና በወራሾች መካከል የሚነሣ ሙግትን የሚሸፍን አይደለም የሚል ነው። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ጥያቄ የቀረበበት ቤት ርስት በመሆኑ በድንጋጌው አይታቀፍም በማለት ነው። ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይህን ምክንያት በመስጠት ቀደም ሲል የይርጋው ጥያቄ ተቀብሎ የነበረውን የጉንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሯል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ሲሆን ይዘቱ የይርጋውን ጥያቄ መታለፍን የሚመለከትና ሌሎቹንም ጠቅላይ ፍ/ቤት የጉዳዩ ፍሬ ነገር ላይ የሰጣቸውን ውሣኔዎች የሚመለከት ነው።

ይህ ችሎት የይርጋው ጥያቄ አስመልክቶ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ ትክክለኛነት ለመመልከት ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ብሎ መልስ ሰጭዎች መልስ እንዲሰጡበት አድርጓል። መልስ ሰጪዎች ባቀረቡት መልስ የይርጋ ጥያቄውን በሚመለከት ዘርዘር ያለ ክርክር አቅርበዋል። የክርክራቸው መሠረተ ሀሣብ የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1000(1) ተፈፃሚነት የሚኖረው አንድ ወራሽ ሌላውን በወራሽነት ዓቅም የውርስ ሀብት የያዘን ሰው ሲከስ ነው፣ አመልካች ንብረቱን የያዙት በሚስትነት እንጂ በወራሽነት ባለመሆኑ ድንጋጌው አግባብነት የለውም፤ ከዚህ ባሻገር በአንቀጽ 1000/2/ እንደተመለከተው አከራካሪ ንብረት ከቤተሰብ የተገኘ ንብረት በመሆኑ በሦስት ዓመቱ ይርጋ ሊታጠር አይገባውም፣ ቤቱ በአመልካች መያዙን መልስ ሰጪዎች ያወቁት በ1999 ዓ.ም ክስ ሲያቀርቡ በመሆኑ ካወቁበት ጊዜ ሲቆጠር የይርጋው ጊዜ አልፎባቸዋል ሊባል አይችልም፣ የሚል ነው።

ይህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን የይርጋ ክርክር አግባብ ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ መርምሮአል።

ችሎቱ በቅድሚያ የተመለከተው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 (1) እና (2) ተፈፃሚነትና ከአሁን ጉዳይ ጋር ያለው ተዛማጅነት ነው። ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በዚህ አንቀፅ የሰፈረው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነው አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሀብት በያዘ ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ነው የሚል ውሣኔ ሰጥቷል። በዚህ የሕጉ አተረጓጉም ይህ ፍ/ቤትም ይስማማል። የአሁን አመልካች የሟች ወራሽ ባለመሆናቸውና ንብረቱንም የያዙት በወራሽነት ስላልሆነ በዚህ ሕግ የተጠቀሰው የ3 ዓመት የይርጋ ጊዜ ወራሾች በሚያነሱት ክስ ላይ ሊጠቅማቸው አይችልም። የዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ይርጋው የሚቆምበትን የመጨረሻ ጊዜ የሚሰጥ ከሚሆን በቀር መነሻ - ሀሣቡ በአውራሾች መካከል የሚደረግን ክስ የሚመለከት በመሆኑ ይኸው ድንጋጌም ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በመሆኑም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ መልስ ሰጪዎች ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000(1) መሠረት በ3 ዓመት በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ አይደለም።

ጥያቄ ክሱን በ1000/1/ መሠረት በይርጋ አይታገድም ማለት የዚህ ዓይነት ክስ ሄራሽ ይርጋ አይመለከተውም ማለት ነው? የሚለው ነው።

የስር ከሣሾች በአሁንዋ አመልካች ያቀረቡት በይዞታቸው ያደረጉት የአባታችን ንብረት ይመልሱልን የሚል ነው። ከመዝገቡ ለመረዳት የቻልነው አመልካችና የመልስ ሰጪ አውራሽ ባልና ሚስት ሆነው ለረጅም ዓመታት አብረው ከኖሩ በኋላ የመልስ ሰጪ አውራሽ በ1978 ዓ.ም መሞታቸው ነው። አመልካችና ሟች ደጃዝማች ሜኔ የመረጡ ባልና ሚስት ከነበሩ በሁለቱም መካከል የነበረው ጋብቻ የፈረሰው በ1978 ዓ.ም ነው ማለት ነው። የፍትሐብሔር ሕጉ ጋብቻ ሲፈርስ በሁለቱም ተጋቢዎች መካከል ያለው ንብረት ሕጉ በሚያዘው መሠረት መከፋፈል እንዳለበት ይደነግጋል። እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ በጋብቻው የነበረው ንብረት መከፋፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በምን ያህል ጊዜ ነው አንድ ሰው በክፍፍሉ የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ያለአግባብ ለሌላኛው ተጋቢ ተሰጥቶብኛል ማለት የሚችለው? የሚለው ነው። ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 17 ጋብቻ በአንዱ ተጋቢ ሞት ምክንያት ሲፈርስ "ከተጋቢዎቹ እያንዳንዱ የግል ሀብቱ መሆኑን አስረድቶ የግል ድርሻ ሀብት በዓይነቱ መልሶ ለመውሰድ መብት አላቸው" በማለት በአንቀጽ 684 ደንግጓል። ይህ ድንጋጌ ጋብቻው ሲፈርስ እያንዳንዱ ተጋቢ የራሱ ንብረት መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት እንዳለበት የሚያሣይ ሲሆን ይህን ጥያቄ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት ግን አይደነግግም። ጥያቄው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት በግልጽ አለመደንገጉ ግን ይህ በይርጋ ሕግ የማይገዛ አንደኛው ወገን በፈለገ ጊዜ የሚያነሣው ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚወስድ አይደለም። በጋብቻ ጊዜ የተፈራው ሀብትም ሆነ በግል የተፈራው ሀብት ሣይከፋፈል ለረጅም ጊዜ መቆየት ያለበት አይደለም በመሆኑም የሕጉ እሳቤ የዚህ ዓይነት ጥያቄ ያለገደብ ጋብቻው ከፈረሰ ከረጅም ጊዜ በኋላም እንዲነሣ ይፈቅዳል ብሎ ማሰብ አይችልም።

ጋብቻ ልዩ ባህርይ ቢኖረውም ከሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት የሚመነጭ መብትና ግዴታም የሚጥል በመሆኑ በቤተሰብ ሕግ ግልጽ ድንጋጌ ሣይኖር ሲቀር በውል ሕግ መርሆች ወይም ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ማድረግ የውል ሕግ አንቀጽ 1677ም የሚፈቅደው ነው። ይኸው ድንጋጌ «ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም የዚህ አንቀፅ ደንቦች ይፈፀሙባቸዋል» በማለት ይደነግጋል። አሁን የያዝነው የባልና ሚስት የንብረት ክርክር የተለየ የይርጋ ጊዜ ስለሌለው በዚህ ድንጋጌ መሠረት የውል ሕግ የይርጋ ድንጋጌዎች እንዲገዛ ማድረግ ተገቢ ሆኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግኝተነዋል። የወል ሕግ ይርጋ አጠቃላይ ድንጋጌ በአንቀፅ 1845 እንደተገለፀው በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር 10 ዓመት ነው። አሁን በቀረበልን ጉዳይ ጋብቻው በሞት የፈረሰው በ1978 ዓ.ም ሲሆን የአንዱን ተግጋቢ የግል ንብረት በሕይወት ካሉት ተጋቢ ለማስለቀቅ ጥያቄ የቀረበው በ1990 ዓ.ም ነው። በመሆኑም ክሱ የቀረበው 10 ዓመት ካለፈው በኋላ በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው ነው።

ከዚህ በላይ በተገለፁ ምክንያቶች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሕጉን አንቀጽ 1000(1) እና(2) በመመልከት ብቻ ከ12 ዓመት በኋላ የቀረበውን ክስ ይርጋ አያግደውም በማለት ክሱ እንዲቀጥል በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ ትክክል አይደለም። የአሁኑ አመልካች የይርጋ ጥያቄ እስከአቀረቡ ድረስ ጥያቄውን በትክክለኛው አንቀጽ መሠረት እንዲመራ ማድረጉ ደግሞ የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ነው።

<u>ው ሣ ኔ</u>

(1) የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጥቅምት 24 ቀን 1997 በመዝገብ ቁጥር 0314 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።

(2) መልስ ሰጪዎች የካቲት 11 ቀን 1990 ዓ.ም በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ይታገዳል ብለናል።

(3) ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ።

የሰ/መ/ቁ. 20938

ሚያዝያ 11/99 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሽዋዬ ተሰማ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ሣራ ልንጋነ

ጋብቻ - የጋብቻን መፍረስ ስለማስረዳት

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ የሚች የአቶ ይልማ ወ/ሃና ሚስት ናቸው ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው።

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።

1. ጋብቻ የሚፈርሰው ህጉ ባስቀመጣቸው ውሱን ምክንያቶች ነው።
2. ጋብቻ የሚፈርስበትን ምክንያት መፍረሱን ከማስረዳት መለየት ያስፈልጋል።
3. ተጋቢዎች ምንም እንኳን ቀደም ብሎ የተፈፀመ ጋብቻ የነበራቸው ቢሆንም በመካከላቸው በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት መቀጠል አለመቻላቸውና ሁለቱ በየፊናቸው የየራሳቸውን ሕይወት መጀመራቸው እያለ ፍቺ መፈፀሙን አንደኛው ተጋቢ አላስረዳም የሚል ውሣኔ ትክክለኛ የህግ አተረጓጎም አይደለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 20938

ሚያዝያ 11/99 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ ቀርባለች፡፡

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ ሣራ ልንጋነ አልቀረበችም፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች ለሰበር ችሎት ያቀረቡት ማመልከቻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልስ ሰጪ የሚች የአቶ ይልማ ወ/ሃና ሚስት ነበሩ በማለት የሰጠው ውሣኔ እንዲሻርላቸው የሚጠይቅ ነው፡፡ አመልካች መ/ሰጪ የሚቹ የአቶ ይልማ ወ/ሃና ሚስት አይደሉም በማለት ተቃውሞ ያቀረቡት ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተቃውሞው ለዚህ ፍ/ቤት ያቀረቡት ፍ/ቤት ቀደም ሲል ግንቦት 15/95 በዋለው ችሎት መልስ ሰጪ ወ/ሮ ሣራ ልንጋነ የሚች የአቶ ይልማ ወ/ሃና ሚስት ነች በማለት በመስጠቱ ነው፡፡ ተቃውሞው የቀረበለት ፍ/ቤትም አመልካች ሚስት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርበዋል በሌላ በኩል መልስ ሰጪ ከሚቹ ጋር ጋብቻ የነበራቸው መሆኑ ስለተረጋገጠና በአመልካቹ በኩል ውላቸው መፍረሱን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ ቀደም ሲል መልስ ሰጪ የሚች ሚስት ናት በማለት የተሰጠው ውሣኔ የሚለወጥበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔው አጽንቶታል፡፡

አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማመልከቻውን አይቶ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አያስቀርብም በማለት ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ቅሬታ መልስ ሰጪ ከሚች ጋር የነበራት ጋብቻ በገዛ ፈቃዷ አፍርሳ ከሌላ ሰው ጋር ከ1977 በፊት ጀምሮ ትዳር በመመስረቷ የሚቹ ሚስት ፈት ሊባል አይገባም፣ ሚች ከአመልካች ጋብቻ የፈፀመው ሌላ ጋብቻ ስላልፈፀመ ነው፣ የመልስ መሰጪን ጋብቻ መፍረስ ያውቁ የነበሩ ምስክር ቀርበው እንዳይመሰክሩ መደረጉ እውነቱ እንዳይወጣ መደረጉን ያሳያል፡፡ አቶ ይልማ የሞቱት በ1989 ሆኖ ሣለ መልስ ሰጪ ግን በ1981 ነው የሞቱት ብላ ለፍ/ቤት ማመልከቷ ጉዳዩን የተቀነባበረና የሚስትነት ጥያቄውን ከ14 ዓመት በኋላ መቅረቡን ያስረዳል የሚል ነው፡፡

በመልስ ሰጪ የቀረበው መልስ ደግሞ መልስ ሰጪና ሚች መጋባታቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠና ጋብቻ የሚፈርስባቸው በሕግ ከሚታወቅባቸው ምክንያቶች አንዱ መኖሩ ስላልተረጋገጠ የሚችና የመልስ ሰጪ ጋብቻ ፈርሷል ሊባል አይችልም፣ የሚችና የአመልካች ጋብቻ መጀመሪያ የተፈፀመውን ጋብቻ አያስቀርም፣ መልስ ሰጪ ከሌላ ሰው ሁለት ልጆች መውለዳቸውም ሆነ የሞቱበትን ቀን 1981 ብለው መጥቀሳቸውም እንደዚሁ ሚስትታቸውን አያስቀርም፤ የሚስትነት ማረጋገጫው የተሰጠው ሚቹ በ1989 ዓ.ም. ሞተዋል በማለት በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ መሠረት የለውም፣ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሕግ ስህተት ስለሌለበት ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካላቸው ሕጎች ጋር በማያያዝ ተመልክቷል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካችም ሆነ መልስ ሰጪ ከሚች አቶ ይልማ ወ/ሃና ጋር ጋብቻ መፈፀማቸው ተረጋግጦአል፡፡ መ/ሰጪ ሚስት መሆናቸውን ለማረጋገጥ በ1966 የተጋቡበት የጋብቻ ውል በ6/6/72 የተሞላ የሕይወት ታሪክ /ሚች ይሰሩበት ከነበረው የቡና ገበያ ድርጅት ማኅደር የተገኘ/ እንዲሁም ጥር 19/1974 በጡረታ ቅጽ ላይ ሚስት ተብለው የተሞላበት ሰነድ ቀርቦአል፡፡ አመልካቹ በበኩላቸው በ1987 ዓ.ም. ከሚች ጋር መጋባታቸው ማስረጃ ቀርቦ ሚስትታቸው በሌላ ተረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ባቀረቡት መቃወሚያ መነሻነት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባደረገው ማጣራት መልስ ሰጪ ለፍርድ ቤቱ በሰጡት ቃል ሚቹና መ/ሰጪ እስከ 1985 አብረው ከኖሩ በኋላ በ1985 ዓ.ም. ተጣልተው መ/ሰጪ ወደ አዲስ አበባ መምጣታቸውን በኋላ ደግሞ ሚቹ አቶ ይልማ አመልካቿን ወ/ሮ ሸዋዬን አግብተው አጋሮ መሄዳቸውን እንደሰሙ በፍርዱ ቤቱ አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሚች ጋር የነበረው ጋብቻ በፍቺ አለመፍረሱም ገልፀዋል በቃል በተደረገው ማብራሪያ የአሁን አመልካች ስለፍቺው ያውቁ እንደሆነ ተጠይቀው ሚቹ ከመልስ ሰጪ ጋር ጋብቻ የነበረው መሆኑን ስለማናውቅ ስለፍቺው አናውቅም ብለዋል፡፡

ከዚህ መገንዘብ የቻልነው የአሁንዋ መልስ ሰጪ ምንም እንኳ ከሚቹ ጋር ቀደም ብሎ የተፈፀመ ጋብቻ የነበራቸው ቢሆንም በመካከላቸው በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት በነበረው ጋብቻ መቀጠል አለመቻላቸውንና ሁለቱ በየፊናቸው የየራሳቸው ሕይወት መጀመራቸውን ነው፡፡ የአሁን መልስ ሰጪ ጋብቻው በፍቺ ምክንያት አልፈረሰም ይባል እንጂ ለፍርድ ቤቱ የሰጡት ማረጋገጫ ጋብቻው መፍረሱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ጋብቻ የሚፈርሰው ሕጉ ባስቀመጣቸው ውሱን ምክንያት መሆኑን ይህም ፍ/ቤት ይቀበለዋል፡፡ በሌላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኩል ለጋብቻ መፍረስ ምክንያቶች የሆኑ ነገሮች መኖር አለመኖራቸውን የሚረጋግጠው እንዴት ነው የሚለው ጥያቄና ነጥብ በሁለቱም ተጋቢዎች ከነበረው ሁኔታ ጭምር መረዳት የሚችል ነው። ጋብቻ የሚፈርስበትን ምክንያት መፍረሱን ከማስረዳት መለየትም ያስፈልጋል። አሁን በቀረበልን ጉዳይ የመልስ ሰጪ መከራከሪያ ፍቺ መፈፀሙን አመልካች አላስረዳችም የሚል ነው። ነገር ግን የመልስ ሰጪና የሟች ግንኙነት ማንም ሌላ ማስረጃ ሊያስረዳ ከሚችለው ከሚገልፀው በላይ በመካከላቸው የነበረው የጋብቻ ግንኙት መፍረሱ ሁለቱም ሌላ ሕይወት ጀምረው ሟቹ የአሁንዋን አመልካች ማግባታቸውን፣ ይህንንም ጋብቻ የአሁኗን መልስ ሰጪ ያውቁ እንደነበር ያስረዳል። ይህ በመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የአሁንዋን መልስ ሰጪ ቀደም ሲል የፈፀመችውን ጋብቻ መሠረት በማድረግ ብቻ ሚስት ናት ብሎ መወሰኑ ትክክለኛ የሕግ አተረጓጎም አይደለም።

ው ሣ ኔ

የፌዴራል መጀመሪያት በመ/ቁ 4796 ሚያዝያ 18 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።

ወ/ሮ ሣራ ልንጋነ የሟች የአቶ ይልማ ወ/ሃና ሚስት አይደለችም በማለት ወስነናል፣ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።

የሰ/መ/ቁ. 22243

ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን እቁበዮናስ

ወ/ሪት ሒሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካቾች፡- እነ ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ

ተጠሪ፡- አቶ አብረሃም ካሣ

ልጅነትን ስለመካድ - አባትነትን በግምት መወሰን - በማወቅ አባትነት የሚረጋገጥበት መሰረት - የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁ/126/1/፣ 143/መ/ና/ሠ/

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሟች አቶ እንድሪስ አደም የተጠሪው ወላጅ አባት ናቸው ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው።

ውሣኔ፡ - የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል።

1. በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁ. 143 መሠረት አባትነትን በፍርድ መንገር የሚቻለው አባት ማን ነው የሚለውን ለአባትነት መነሻ የሆኑትን በአንቀጽ 125/1/ መሠረት በህግ ግምት ማወቅ ካልተቻለ ወይም በአንቀጽ 125/2/ መሠረት አባት የተባለው ሰው ልጅነትን ሳይቀበል የቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው።
2. አንድ እናት በህጋዊ ጋብቻ ውስጥ እያለች ልጅ ከተወለደ የልጁ አባት ማን ነው የሚለው ምላሽ የሚያገኘው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁ. አንቀጽ 128/1/ እና ከአንቀጽ 126 — 128 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ህግ ያስቀመጠውን ግምት መነሻ በማድረግ ነው።
3. በህጉ ግምት አባት የተባለው ሰው ህጉ ያስቀመጠውን ግምት ሊያፈርስ የሚችል ክርክር በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁ. 167 ሊያቀርብ ይችላል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 22243

ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ መስፍን እቁበዮናስ
ወ/ሪት ሒሩት መለሠ
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ
2. ወ/ሮ ሶፊያ እንድሪስ
3. አቶ ዑመር እንድሪስ
} ወ/ሮ ሃፍያ እንድሪስ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አብረሃም ካሣ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍረድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሣኔ የተሰጠው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁን አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ከዚህ በፊት ተጠሪው ለዚህ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአቶ እንድሪስ አደም ልጅ ነኝ በማለት ያስወሰነ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ሆኖም አቶ እንድሪስ አደም 1ኛ ተቃዋሚን ወ/ሮ ደሐብ ሲይድን አግብተው የኖሩ ከመሆኑ በስተቀር ሌላ ሚስትም ሆነ ልጅ የላቸውም፡፡ ስለዚህ ውሣኔው ይሻርልን የሚል አቤቱታ አቅርብዋል፡፡

የአሁን ተጠሪም በአመልካቾች በኩል የቀረበው ተቃውሞ ሕጋዊ መሠረት የለውም ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ አቶ አብርሃም ካሣ የአቶ እንድሪስ አደም ልጅ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ጋር አገናዝቦ ከተመለከተ በኋላ ሰኔ 18 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተጠሪ አቶ አብርሃም ካሣ በተወለዱ ጊዜ እናታቸው እና ሟች አቶ እንድሪስ አደም ቀጣይነት ያለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ የነበረ በመሆኑና ሟቿም ልጁን /ተጠሪን/ በማሳደግ ሂደት ሲሳተፉ የነበረ ለመሆኑ በተጠሪ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን የአመልካቾች ማስረጃ ይህንኑ አላስተባበለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143/መ/ እና /ሠ/ መሠረት አቶ እንድሪስ አደም የተጠሪው የአብርሃም ካሣ ወላጅ አባት መሆናቸው የተገመተ ስለሆነ በተቃዋሚዎች አማካይነት የቀረበውን የውሣኔ ይሰረዝልን ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ይህም ውሣኔ ጉድለት የሌለበት መሆኑን በመግለጽ የፌ/ከፍተኛው ፍ/ቤት በትዕዛዝ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ፍሬ ቃልም፡-

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 126/1/ በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ነው ተብሎ የተደነገገውን በመተው በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የነበረው ጋብቻ ሳይፈርስ ከሌላ ጋር ወዳጅነት በመፍጠር ልጅ ወልጃለሁ የሚለውን ተቀብለው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መስጠታቸው የሕግ ስህተትን ያስከተለ ነው፡፡ ለዚሁ ሕግ አንቀጽ 143/መ/ እና /ሠ/ መሠረት ፍ/ቤት አባትነትን በግምት ሊወስን የሚቻለው ከዚሁ ድንጋጌ ከፍ ብለው በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጅ አባት ያልታወቀ ወይም የተካዳ ሲሆን ብቻ መሆኑ እየታወቀ ይህ ሁሉ ታልፎ የተሰጠው ውሣኔ የቤተሰብን ሕግ የተከተለ አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪም በበኩሉ የተጠሪ እናት ባል ነበራቸው በሚል በአመልካቾች በኩል የቀረበ ክርክር የለም፤ በተጠሪ እናት እና በአቶ ካሣ መካከል ጋብቻ ነበረ እንኳ ቢባል ለረጅም ጊዜ ተለያይተው መተማመንና መረዳዳት በጠፋበት ሁኔታ ትዳር/ጋብቻ አለ ማለት አይቻልም፡፡ ትዳር አለ የሚለውን መነሻ በማድረግ የሕግ ግምት የሚወሰድ ከሆነ የተፈጥሮ አባትነት የሚያሰጥ ነው፡፡ ስለሆነም ትዳር አለ ቢባል እንኳን የተለያዩት ለረዥም ዓመት በመሆኑ ግላዊ ግንኙነቱ የጠፋ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የቤተሰብ ሕጉን ዓላማ በተቃረነ መልኩ ሕጉ መተርጎም ይገባዋል የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ነጥብ ተጠሪ የሟች የአቶ እንድሪስ አደም ልጅ መሆኑን ስለአባትነት ማወቅ /Ascertainment of paternity/ ሕጉ በደነገገው መሠረት አስረድቷል ወይስ አላስረዳም? የሚለው ነው፡፡

ይህንን ጭብጥ አስመልክቶ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት ያደረገው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 በአንቀጽ 125/3/ እና 143 /መ/ እና /ሠ/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንደሆነ ከመዝገቡ ግልባጭ ተረድተናል፡፡

ሆኖም በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 143 መሠረት አባትነትን በፍርድ መንገር የሚቻለው አባት ማነው? የሚለውን በሚመለከት ለአባትነት ማወቅ መነሻ የሆኑትን በአንቀጽ 125/1/ መሠረት በሕግ ግምት አባትነትን ማወቅ ካልተቻለ ወይም በአንቀጽ 125/2/ መሠረት አባት የተባለው ሰው ልጅነት ሳይቀበል የቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ያልታወቀ እንደሆነ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ አባትነት በፍርዱ ውሣኔ ሊታወቅ ይችላል በሚል በአንቀጽ 143 ተደንግጓል፡፡ ከአንቀጽ 143 በላይ ያሉት ድንጋጌዎች ደግሞ በሕግ ግምት ወይም በማወቅ /Acknowledgment/ መሠረት አባትነት የሚረጋገጥበትን መንገድ የሚዘረዝሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ናቸው። ይህም የሚያሳየው በአንቀጽ 125/1/ አባትነት በሕግ ግምት ሊታወቅ ከቻለ ወይም 125/2/ መሠረት በማወቅ ከተረጋገጠ ይህንን አልፎ አባትነትን በፍርድ መንገር /Ascertainment of [paternity by Judicial Declaration/ የማይቻል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

አሁን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የተፀነሰው ወይም የተወለደው የተጠሪ እናት ከሌላ ሰው ጋር በሕግ ፀንቶ በቆየ ጋብቻ ተሳስራ በነበረበት ጊዜ የነበረ ስለመሆኑ እራሳቸው የተጠሪ የሰው ማስረጃዎች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። ይህንን በማስመልከት የሰጡትን አግባብነት ያለውን ቃል ለመጥቀስ ያሕልም የተጠሪ እናት ከ1960 ዓ.ም. ጀምሮ ባል አግብተው ይኖሩ ነበረ። ባልየው በሥራ ምክንያት ወደ ክ/ሀገር በሄደበት ጊዜ ከሟች ከእንዱሪስ አደም ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፍጠራቸውን እናውቃለን። በዚህም ግንኙነት ሳቢያ ተጠሪ በ1972 ዓ.ም. ተወለደ። በ1975 ዓ.ም. የተጠሪ እናት ባል ከሄደበት የሥራ ቦታ ተመልሰው ከተጠሪ እናት ጋር መኖር ቀጠሉ። ድሮውንም ቢሆን አልተፋቱም ነበር። ተጠሪም የሚጠራው በዚሁ ሰው በባልየው ስም ነው የሚለው ይገኝበታል።

እነዚህ ፍሬ ነገሮች እስከተረጋገጡ ድረስ የተጠሪ አባት ማን የሚለውን ጥያቄ ምላሽ የሚያገኘው በአዋጅ ቁጥር 213/92 በአንቀጽ 128/1/ እና ከአንቀጽ 126-128 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ሕግ ያስቀመጠውን ግምት መነሻ በማድረግ ይሆናል። በዚህም መሠረት የተጠሪ አባት የተጠሪን እናት አግብተው የነበሩት የተጠሪ እናት ባል እንጂ ሟች አቶ እንድሪስ አደም ሊሆኑ አይችሉም።

በሕጉ ግምት አባት የተባለው ሰው በበኩሉ ሕግ ያስቀመጠውን ግምት ሊያፈርስ የሚችል ክርክር በማቅረብ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 167 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ልጁን የካዱ መሆኑን መነሻ በማድረግ የቀረበ ክርክርም አልተገኘም።

በዚህ ሁሉ ምክንያት የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት የሌላቸውን በአንቀጽ 143/መ/ እና /ሠ/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አረጋግጠናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 3753 በ18/10/96 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33498 በ25/01/98 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ ተሽሯል።
2. ሟች እንድሪስ አደም የተጠሪ የአብርሃም ለማ አባት መሆናቸው አልተረጋገም በማለት ወስነናል።
   ይህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ኪሣራና ወጭ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል። መዝገቡ ተዘግቷል።

የሰበር መ/ቁ. 17058

መጋቢት 25/1999

ዳኞች፦ **አቶ** *መንበረፀሐይ ታደሰ*

” *ፍስሐ ወርቅህ*

” *አብዱልቃድር መሐመድ*

” *መስፍን ዕቁበዮናስ*

” *ተሻገር ገ/ሥላሴ*

አመልካች፦ አቶ አንበሶ ወ/ገብርኤል

መልስ ሰጭ፦ አቶ መሣይ መኩንን

ውርስ - ኑዛዜ - የኑዛዜ መፅደቅ የሚያስከትለው ውጤት - የወራሽነት የምስክር ወረቀት ውሣኔ ስላለመሆኑ - የፍ/ብ/ሀ/ቁ/ 881፣ 884፣ 892፣ 996 — 1000፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ.5

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወራሽነት ምስክር ወረቀት መስጠት በአንድ የውርስ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ እንደተሰጠ አያስቆጥርም በሚል የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን በመወሰኑ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው።

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል።

1. የትኛውም የኑዛዜ አይነት በህግ ፊት የፀና እንዲሆን ፍርድ ቤት መጽደቅ አያስፈልገውም።
2. ኑዛዜ ህጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል አይደለም።
3. በመሠረቱ ፍርድ ቤቶች ኑዛዜ ይጽደቅልኝ በማለት የሚቀርብላቸውን ጥያቄ የሚያስተናግዱበት ምክንያት መኖር የለበትም።
4. ፍርድ ቤቶች የወራሽነት ምስክር ወረቀት የሚሰጡት ጥያቄ ያቀረበው ወገን አለኝ የሚለውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ካደረጉ በኋላ እንጂ በጉዳዩ ላይ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ህግ በሚያዘው መሠረት ከሌሎች ሰዎች ጋር ሙግት እንዲገጥም በማድረግ አይደለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 17058

መጋቢት 25/1999

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

” ፍስሐ ወርቅነህ

” አብዱልቃድር መሐመድ

” መስፍን ዕቁበየሱስ

” ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ አቶ አንበሶ ወ/ገብርኤል ጠበቃ የሸጥላ አሰፋ ቀረበ

መልስ ሰጭ፦ አቶ መሣይ መኩንን - ጠበቃ በየነ ገብሬ ጋር ቀረበ።

በዚህ መዝገብ የቀረበልንን ጉዳይ መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ሙግት የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አተረጓገምና አፈፃፀምን የሚመለከት ነው። ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን ክስ የመሠረተው የአሁን መልስ ሰጪ ሲሆኑ የክሱ ፍሬ ሃሣብ የአባቱ ብቸኛ ወራሽ እኔ በመሆኔ የአሁን አመልካች የአባቱን ንብረት በእጁ ይዞ ስለሚገኝ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው። የአሁን አመልካች ለክሱ ባቀረበው መልስ የመልስ ሰጪ አባት ኑዛዜ መተዋቸውን፣ በዚሁ ኑዛዜ ለአሁኑ መልስ ሰጪ የተሰጠው ብር ሃያ ሺህ (20,000) ብቻ መሆኑን፣ ይኸው ኑዛዜ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በቦረና ዞን በአዳላ ፍ/ቤት የፀደቀ መሆኑን መልስ ሰጪ በዚሁ ሃያት ተቃዋሚ ሆኖ አለመቅረቡ በመግለፅ መልስ አቀረበ።

ጉዳዩን የያዘው ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው በአዶላ ወረዳ ፍ/ቤት የፀደቀ መሆኑ ስለተረጋገጠ - ከሦሽ የሚያቀርበው ጥያቄ ካለ መቅረብ የነበረበት ኑዛዜውን ባፀደቀው ፍ/ቤት ነው፣ በማለት ከሦሽ ማግኘት የሚችለው በኑዛዜው እንዲያገኝ የተወሰነበትን ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) በቻ ነው ሲል ወሰነ። ከፍተኛው ፍ/ቤት እዚህ መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው ኑዛዜው በፍርድ ቤት መጽደቁና በሌላ ውሣኔ አለመሻሩን ምክንያት በማድረግ ነው።

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው የአሁን መልስ ሰጪ ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቅረቡ አመልካች መልስ እንዲሰጥበት ከተደረገበት በኋላው ሣኔው በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ተሽሯል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛውን ውሣኔ የሻረው የአሁን መልስ ሰጪ ለአዶላ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበውን ጥያቄ መሠረት በማድረግ የወራሽነት የምስክር ወረቀት መስጠቱ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ እንደሰጠ የሚያስቆጥረው አይደለም፣ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንደማንኛውም ሌላ ማስረጃ የሚታይ እንጂ በኑዛዜው ላይ ሌላ ክርክር እንዳይደረግ የሚከለክል አይደለም የሚሉና ሌሎችም ተጓዳኝ ምክንያቶች

በመስጠት ነው። ፍርድ ቤቱ የወራሽነት የምስክር ወረቀት መገኘት ሌላ የውርስ ሀብት ይገባኛል የሚል ሰው ጥያቄ ሊያስቀር አይገባውም በማለት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ ይስጥ በማለት ጉዳዩን ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት መለሰው።

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሣኔ በመቃወም ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ በኑዛዜ ወራሽ ሆኖ እያለ የጠቅላይ ፍ/ቤት ያለኑዛዜ ወራሽ እንደሆነ አድርጉ የውርስ ሀብት የመጠየቅ መብት አለው - ያለው ያለአግባብ ነው። 2ኛ ተጠሪ ኑዛዜ ሲፈስ የነበሩ በመሆናቸው እንደሕጉ በኑዛዜው ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በ15 ቀን ውስጥ ያላሰሙ በመሆናቸው ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ከተሰጠው የመቃወሚያ ጊዜ ውጪ የቀረበው አቤቱታ መቀበሉ ስህተት ነው የሚል ነው።

መልስ ሰጪ በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የጽሑፍ መልስ አቅርቧል። ዋናውና መከራከሪያዎቹ፣

1. የሰበር አቤቱታው የመጨረሻ ውሣኔ ባላረፈበት ጉዳይ የቀረበ በመሆኑ ለሰበር ሊቀርብ አይገባውም፣
2. ጉዳዩ ለከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ በመወሰኑ በሁለቱ ፍ/ቤቶች እንዲቀጥል መደረጉ አግባብ አይደለም።
3. ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩ እንደገና ታይቶ እንዲወሰን ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት መመለሱ አግባብ ነው።

የሚሉ ናቸው። አመልካቹ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል። ጉዳዩ የያዘው ይህ የሰበር ችሎት በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ ተመልክቷል ለክርክሩ አወሳሰን ቀጥሎ የተመለከቱትን ጥያቄዎች መመለስ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል።

(1) የኑዛዜ መጽደቅ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ምንድ ነው?

(2) የወራሽነት የምስክር ወረቀት ውሣኔ ፍርድ ነው ወይስ አይደለም?

የከፍተኛው ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የተነሱትን በርካታ ክርክሮች አልተመለከተም ለዚህ ምክንያት የሆነው የቀረቡት ክርክሮች መታየት ያለባቸው ኑዛዜውን ባፀደቀው በአዶላ ወረዳ ፍ/ቤት በሚገኘው መዝገብ ነው በማለት ነው። ይህ የፍርድ ቤቱ አካሄድ የኑዛዜ መጽደቅ ትርጉም ምንድነው የሚለው ጥያቄ እንዲነሣ ስለሚያደርግ ይህን መመልከቱ አስፈላጊ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሠረቱ ኑዛዜ አንድ ሰው ሊፈጽማቸው ከሚችሉ ሕጋውያን ተግባራት (Juridical acts) መካከል አንዱ ነው ማንም ሰው በሕይወቱ እያለ ከህልፈቱ በኋላ ንብረቱንም ሆነ ሌሎች ሕግ በኑዛዜ እንዲከናወኑ የሚፈቅዳቸውን ተግባራት በማስመልከት ፍላጉቱንና ፈቃዱን የሚገልፅበት ሕጋዊ ሰነዱ ነው። ኑዛዜ በሕግ ፊት የፀና የሚሆነው ሕጉ ያሰፈራቸውን መለኪያዎች አሟልቶ ሲገኝ ነው። ኑዛዜ የሚሰጥበት ሥርዓት እንደኑዛዜው ዓይነት የተለያየ ቢሆንም የትኛውም የኑዛዜ ዓይነት በሕግ ፊት የፀና እንዲሆን በፍርድ ቤት መጽደቅ አያስፈልገውም። ግልጽ ኑዛዜ በሕግ ፊት የፀና እንዲሆን መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች በሕጉ አንቀፅ 881 ተቀምጠዋል፣ ከነዚህ መካከል በፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቅ የሚል መለኪያ አይገኝበትም። በመሆኑም ግልጽ ኑዛዜ በተጠቀሰው አንቀጽ ያሉትን መስፈርቶች እስከአሟላ ድረስ በፍርድ ቤት ተጨማሪ ቡራኬና ውሣኔ ሣያስፈልገው በሕግ ተፈፃሚነትና ተቀባይነት ያለው ነው። በተናዛዡ የእጅ ጽሑፍ የሚደረግ ኑዛዜ (አንቀጽ 884) በማስመልከት ካሉት ድንጋጌዎች መመልከት የሚቻለውም ለፍርድ ቤት ቀርቦ ውሣኔ መሰጠት ከኑዛዜው ተቀባይነት ጋር ተያያዥነት ያለው ጉዳይ አለመሆኑ ነው። በተናዛዡ የእጅ ጽሑፍ የሚደረግ ኑዛዜ በ7 ዓመት ውስጥ ፍርድ ቤቱ ወይም አዋዋይ ዘንድ መቀመጥ ካልተቀመጡ ፈራሽ ነው የሚለውም ቢሆን ከኑዛዜ ውድቅ መሆን (Lapse of wills) ጋር የተያያዘ ነው። መከናወንም ያለበት ተናዛዥ በሕይወት እያለ ነው። የቃል ኑዛዜውም የተለየ አይደለም አንቀጽ 892 በመሆኑም የትኛውም የኑዛዜ ዓይነት ቢሆን በሕግ የፀና እንዲሆንና ተፈፃሚነት እንዲኖረው በየትኛውም ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቅ አስፈላጊ አይደለም። ኑዛዜ ሕግ ያስቀመጣቸውን ሌሎች መስፈርቶች እስከአሟላ ድረስ በፍርድ ቤት መጽናት አለመጽናቱ የሚጨምርለትም የሚቀንስበትም ጉዳይ የለም። ውሎች የፍርድ ቤት ውሣኔ ሣያስፈልጋው በተዋዋዮች መካከል ሕግ የመሆናቸውን ያህል ኑዛዜም ሕጉ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች እስካሟላ ድረስ በፍርድ ቤት መጽደቅ ሣያስፈልገው ተናዛዡ ከሞተበት ቀን አንስቶ ሕጋዊ አስገዳጅነት ያለው ነው። ኑዛዜው ሕጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል አይደለም ሆኖም የዚህ ዓይነት ጉዳይ የሚታየው ኑዛዜው ተቀባይነት የለውም የሚል ወገን ሲቀርብ እንጂ ባለጉዳዩ በሌለበት አንድ ሰው ኑዛዜውን አፀደቅኩ በሚለው የተናጠል ሂደት አይደለም። በመሆኑም ፍርድ ቤቶች በመሠረቱ ኑዛዜ ይጽደቅልኝ በማለት የሚቀርብላቸውን ጥያቄ የሚያስተናግዱበት ምክንያት መኖር የለበትም። በሕግ ኃይል ያለተጨማሪ መዳኘት የፀናውን ሰነድ አጽንቻለሁ ብሎ «ውሣኔ» መስጠት ትርጉም የማይሰጥ አላስፈላጊ ሂደት ነው። ይህ ሂደት አላስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር የሌሎችን መብት ሊጉዳ በሚችል መንገድም ሥራ ላይ ሊውል አይገባውም። በኑዛዜው ላይ ጥያቄ ያለው ወገን የኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ የሚለውን ወገን የሕጉን ሥርዓት በመከተል ሊሞግተው ይችላል። ኑዛዜ የማፀደቅ አላስፈላጊ ሂደት ይህን መሠረታዊ መብት የሚንድ መሆን አይገባውም። የኑዛዜ ይጽደቅልኝ ጥያቄ የሚቀርበው ተለይተው በታወቁ መልስ ሰጪዎች ላይ አይደለም። "ፍርድም" ሆነ "ውሣኔ" የሚሰጠውም በማንም ተለይቶ በሚታወቅ ሰው ላይ አይደለም። በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዳተተው የኑዛዜው ይጽደቅልኝ አቤቱታ በማስመልከት በጋዜጣ ጥሪ እንኳን ተደርጉ ቢሆን ኑዛዜው የማንን መብት እንደሚነካ ቀድሞ ስለማይታወቅ ማንኛውም ሰው የጋዜጣው ጥሪ መሠረት በማድረግ አልተከራከርክም ተብሎ ኑዛዜውን አስመልክቶ ሌላ ጥያቄ ከማንሣት ሊከለከል አይገባውም። በሥነ ሥርዓት ሕጉም ቢሆን አንድ ሰው ድጋሚ ክስ ከማንሣት የሚከለክለው በአንቀፅ 5 መሠረት ተሟጋቾቹ ቀድመው

የተከራከሩበትና የተሟገቱበት ወይም እንደተከራከሩበት የሚያስቆጥራቸው ሂደት ከነበረ ነው ከላይ እንደተመለከተው የኑዛዜ ይጽናልኝ ጥያቄ በመሠረቱ ለአመልካቹ ምንም ተጨማሪ መፍትሄ (relief) የማይሰጥ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሊያስተናግዱት የማይገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ወይም ሌላ ምክንያት "የማፅናት ውሣኔ" ተሰጥቷል። ቢባል እንኳ በክርክሩ ያልነበሩ ሰዎችን በሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 5 መሠረት ሌላ ክስ እንዳያቀርቡ ሊያግዳቸው አይገባም። በኑዛዜ ይጽደቅልኝ ክሱ ተከራካሪ ስላልነበሩ (named defendants) የተሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ እንዲያሽሩም አይጠበቅባቸውም።

ቀጥሎ የምንመለከተው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ያለውን ሕጋዊ ውጤት ነው። የወራሽነት የምስክር ወረቀት የፍትሐብሔር ሕጉን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች በመከተል የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው (አንቀጽ 996- 1002) አንቀጽ 996(1) "ወራሽ የሆነው ሰው ለሚቹ ወራሽ መሆኑና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የያመለክት የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጡት ዳኞችን ለመጠየቅ ይችላል" በማለት ይደነግጋል። 997(1) ደግሞ "የምስክር ወረቀቱ እስከተሰረከዘ ድረስ ወራሹ በተባለው የምስክር ወረቀት እንደተገለጠው ወራሽ እንደሆነ ይገመታል" በማለት ይደነግጋል። ከነዚህ ድንጋጌዎች ለመገንዘብ የሚቻለው የወራሽነት የምስክር ወረቀት አንድ ሰው ወራሽ ሆኖ የመገመትን ሁኔታ እንዲፈጠርለት የሚያደርግ ነው። ከሰሙም በግልጽ እንደሚታየው ይህ ሰነድ አንድ ሰው በሰነዱ በተጠቀሰው መጠን ወራሽነቱን የሚያስረዳ ሰርቲፊኬት ነው። ይህን ሰርቲፊኬት ለማግኘት የፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚሻ ቢሆንም መጨረሻ ላይ የሚሰጠው ሰነድ ግን አንድን ሁኔታ የሚያስረዳ ማስረጃ ነው። ከአንቀፅ 996 (2) ለመገንዘብ እንደሚቻለውም ይህ ሰርቲፊኬት የሚሰጠው ጥያቄ ያቀረበው ወገን አለኝ የሚለውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ካደረጉ በኋላ እንጂ በጉዳዩ ላይ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በሚያዘው መሠረት ከሌሎች ሰዎች ጋር ሙግት እንዲገጥም በማድረግ አይደለም። የውርስ ሰርቲፊኬት አንድ ሰው የራሱ ወራሽነት ለማስረዳት የሚወስደው ማስረጃ እንጂ ሌሎች ወራሾች አለመኖራቸውን የሚያሣይ ሰነድ አይደለም ኑዛዜ በሚኖርበት ጊዜ በተለይ በኑዛዜው የተጠቀሰው በርካታ ተጠቃሚዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ የሰርቲፊኬቱ ሁኔታም ከዚህ አንፃር መመርመር ይኖርበታል። ኑዛዜው ጠቅላላ ኑዛዜ ወይም ልዩ ኑዛዜ ሊሆን ይችላል። ኑዛዜው ጠቅላላ ኑዛዜ ከሆነ የውርሱ ሰርቲፊኬት መኖር ብቻውን ሁሉንም ንብረት ጠቅልሎ እንዲወስድ የሚያደርገው ሊሆን አይችልም። የውርስ ሰርቲፊኬት ኖረም አልኖረም የጠቅላላ ኑዛዜ ውጤት የሚታየው አግባብነት ካላቸው የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ነው። ለሰርቲፊኬቱ መነሻ በሆነው ኑዛዜ ላይ የተጠቀሱ ሌሎች ሰዎች ያሉ እንደሆነም የሰርቲፊኬቱ መሰጠት እነሱን የሚነካ ሊሆን አይችልም። በውርሱ ተነቀለ የተባሉ ሰው ካለ ሌላ ስጦታ የተሰጠው ሰው ካለ ወይም በኑዛዜው ውስጥ በሌላ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ሌላ ትእዛዝ ካለ ለአንዱ ሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተሰጠው የኑዛዜ ሰርቲፊኬት እነዚህ ሌሎች ሰዎች ኑዛዜውን አስመልክቶ ጥያቄ እንዳያነሱ ሊያደርጋቸው አይችልም። ከላይ እንደተጠቀሰው ኑዛዜ በአንድ ሰው ጠያቂነት ፀና ቢባልም ይኸው የመጽናት ጥያቄ ሌሎች በኑዛዜው ጥቅም የሚያገኙ ወይም በኑዛዜው ጥቅማቸው የተነካ ሰዎች በዚህ ኑዛዜ ላይ ያላቸውን ክርክር ሊያቀርቡ ሊፈቀድላቸው ይገባል። በአጠቃላይ አነጋገር የወራሽነት ሰርቲፊኬት በሰርቲፊኬቱ ላይ የተገለፀውን ፍሬ ነገር በሚመለከት የወራሽነት ግምት የሚፈጥር ማስረጃ ከመሆን አልፎ እንደሌሎች በፍርድ ቤት እንደሚሰጡ ፍርዶች ሊወሰዱ አይገባውም። የወራሽነት ሰርቲፊኬት እስካልተሰረዘ ድረስ የወራሽነት ግምት እንደሚፈጥር ሰርቲፊኬቱ መሰረዝ የሚችለው በፍ/ቤት መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 998 ተደንግጓል። ሆኖም የወራሽነት የምስክርነት ወረቀት ለማሰረዝ የሚደረግ ጥያቄ ኑዛዜውን በመቃወም ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር አንድ ተደርጉ ሊወሰድ አይገባውም። ኑዛዜ መቃወም የግድ የወራሽነት ሰርቲፊኬት መሠረዝ አያስከትልም። የወራሽነት ምስክር ወረቀት መሰረዝ የሚያስከትልም ቢሆን ኑዛዜውን በሌላ ምክንያት መቃወም የሚፈልግ ሰው የግድ የወራሽነት ሰርቲፊኬት በሰጠው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ መገደዱ አግባብ አይደለም።

ለማጠቃለል ለጠቅላይ ፍ/ቤት የኑዛዜ መጽናቱን በማስመልከት የሚቀርቡ ክሶች የሕግ መሠረት የሌላቸው መሆኑን የውርስ ሰርቲፊኬት ማስረጃ መሆኑን በማተት የከፍተኛውን ፍርድ ውሣኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መሥራቱን የሚያመለክት አይደለም። ይልቁንም ከፍተኛው ፍርድቤት የቀረበለትን ኑዛዜ በማስመልከት በርካታ ክርክሮች ቀርበውለት እያለ ኑዛዜው በሌላ ፍርድ ቤት የፀና ስለሆነ ክርክሮቹን ለማየት አልችልም ማለቱ አግባብ አልነበረም። ከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበው ኑዛዜ የሚቹ አይደለም፣ ኑዛዜው አፀደቀ የተባለው ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አልነበረውም፣ በኑዛዜው የተጠቀሰው ምክንያት ከውርስ ለመነቀል የሚያበቃ አይደለም፣ ኑዛዜ ነው የተባለው ሰነድ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881ን የሚያሟላ አይደለም የሚሉ ክርክሮች ቢቀርቡበትም እነዚህ ነጥቦች መነሣት ይችሉ የነበረው ኑዛዜውን ባፀናው ፍ/ቤት ቀርበው ቢሆን ነበረ በማለት አልፎላቸዋል። ከላይ በተገለፀው ምክንያት ይህ የፍርድ ቤቱ አካሄድ ትክክል አይደለም። ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በነዚህና በሌሎች በሥር ተከሣሽ በሚሉ ነጥቦች ላይ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 341(1) መሠረት መመለሱ አግባብ ነው።

<u>ው ሣ ኔ</u>

(1) ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰኔ 17 ቀን 1996 በፍ/ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 13988 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል። ይፃፍ።

(2) ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ያየራሣቸውን ይቻሉ።።።

የሰ/መ/ቁ. 22712

ሚያዚያ 9 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- አቶ እንዳሻው በቀለ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ት አይናለም ያለው

ውርስ - ኑዛዜ - የኑዛዜ አፃፃፍ ስርአት - የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 881፣

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሟች አቶ በቀለ ወልዴ የሰጡት ኑዛዜ ከተፃፈ በኋላ መነበቡን ስለማይገልጽ ፈራሽ ነው ብሎ የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው።

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።

1. የኑዛዜ ስነ ስርአት ጥብቅ መሆን ዋና አላማ ኑዛዜ የሟች ፍላጐት በትክክል የሚገልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።
2. ሰነዶች ፎርማሊቲውን ያሟሉ እንደሆነ መመርመር የሚገባቸው ከዚህ አላማ አንፃር ነው።
3. የኑዛዜ እያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትና ተናዛዥም ሆነ ምስክሮች /እማኞች/ በኑዛዜው ባሰፈሩት ቃላትና ሃረጎች ሊሰጡ የሚችለውን ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 22712

ሚያዚያ 9 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- አቶ እንዳሻው በቀለ - ጠበቃ አሰፋ ዝቅአርጋቸው ቀረቡ፡፡

መልስ ሰጭ፡- 1. ወ/ት አይናለም ያለው - አልቀረበችም፡፡

2. ወ/ት የሺ ሀረግ ሺመልስ - ቀርባለች

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበልን ጉዳይ የኑዛዜ አፃፃፍ ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚሁ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሟች አቶ በቀለ ወልዴ የሰጡት ኑዛዜ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 በሚያዘው መሠረት ኑዛዜው ከተፃፈ በኋላ መነበቡን ስለማይገልፅ ኑዛዜው ፈራሽ ብሎ በመወሰኑ ነው፡፡ ኑዛዜው ፈራሽ መሆን አለበት የሚለውን ጥያቄ ያቀረቡት የአሁን መልስ ሰጪዎች ናቸው፡፡ ተቃውሞውን ያቀረቡት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቢሆንም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡትን የኑዛዜ ይፍረስልን ተቃውሞ አልተቀበለውም ነበር፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የቀረበው የሰበር አቤቱታ ኑዛዜው የህጉን መስፈርት የሚያሟላ በመሆኑ ይፍረስ መባሉ ትክክል አይደለም የሚል ነው፡፡ መልስ ሰጪዎች በቃል ክርክር የሰጡት መልስ ደግሞ ኑዛዜው ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት እስካላሟላ ድረስ ፈራሽ ነው መባሉ አግባብ ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት አከራካሪ የሆነውን ኑዛዜ አቅርቦ ተመልክቷል፡፡ ኑዛዜው በህጉ መሠረት በአራት ምስክሮች የተፈረመ ነው፡፡ ትናዛዡ ፊርመውበታል፡፡ ይኸው ፊርማ በእርግጥ የተናዛዥ መሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ተረጋግጧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የኑዛዜው የመጨረሻው ክፍል "እኛም ከዚህ በላይ ስማችን የተጠቀሰው እማኞች ይህንን ኑዛዜ አቶ በቀለ ወልዴ በህይወትና በንፁህ አዕምሮ እያሉ እና በተስተካከለ የጤና አቋም ላይ እያሉ ሲናዘዙ ሰምተናል" ይላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ "እኔም ከዚህ በላይ የተገለፀውን የኑዛዜውን ቃል ተፈጻሚ ይሆን ዘንድ በተለመደው ፊርማዬ አረጋግጣለሁ" የሚል ዐረፍተ ነገርና ፊርማ ይገኝበታል፡፡

የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 881 ኑዛዜው በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበ ዋጋ እንደማይኖረው ይደነግጋል፡፡ ይህ ሥርዓት መፈፀሙ በኑዛዜው ላይ መገለጽ እንዳለበትም ይደነግጋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው ውድቅ ያደረገው ኑዛዜው ምስክሮች ሟቹ ቃላቸውን ሲሰጡ መስማታቸውን ቢገልጽም ኑዛዜው ከተፃፈ በኋላ መነበቡን የሚገልጽ ነገር የለውም በማለት ነው፡፡ ሆኖም ከላይ ከተጠቀሰው የኑዛዜው ክፍል መገንዘብ እንደሚቻለው ምስክሮቹ ሟቹ ሲናዘዝ መስማታቸውን ይገልፃል፡፡ ይህ የኑዛዜው አገላለጽ ሟቹ ሲናገሩ መስማታቸውን ብቻ ሳይሆን የኑዛዜው ይዘት ከንግግሩ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጣቸው እንደሚገልጽ ሆኖ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ የኑዛዜው ሂደት ተከታትለው የሟች ንግግር /ቃል/ ከኑዛዜው ይዘት ጋር ለማመሳከር እድል የነበራቸው እንደሆነ በመገመት "ሲናዘዙ ሰምተናል" የሚለው ቃል ኑዛዜው ሲፃፍ የነበረውን ሂደት በአጠቃላይ በሚገልጽ ሁኔታ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የከፍተኛው ፍ/ቤት ከተፃፈ በኋላ ኑዛዜው መነበቡን አይገልጽም የሚለው መደምደምያ ከኑዛዜው ይዘት ጋር የሚጣጣም አይደለም፡፡ ኑዛዜ ጥብቅ የሆነ ሥርዓት እንዲከተል የሚፈለግ መሆኑ ከፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 881 መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም የእያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው ግን የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትም ጭምርና ተናዛዥም ሆነ ምስክሮች /እማኞች/ በኑዛዜው ባሰፈሩት ቃላትና ሀረጐች ሊሰጡ የሚችለውንም ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የኑዛዜ ሥነ ሥርዓት ጥብቅ መሆን ዋና አላማ ኑዛዜ የሚች ፍላጐት በትክክል የሚገልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ሰነዶች ፎርማሊቲው ያሟሉ እንደሆነ መመርመር የሚገባቸውም ከዚሁ አንፃር ነው፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ ምስክሮች ኑዛዜው ሟቹ በትክክለኛ አእምሮ እያሉ ሲሰጡ መስማታቸውን ገልፀዋል፡፡ የኑዛዜ መሰጠት ሥርዓት ተናዛዥ ሲናገር ማድመጥ ብቻ ሳይሆን የተባለውን ሁሉ በጽሁፍ ማስፈርን የሚያጠቃልል ነው፡፡ በመሆኑም ይኸው አገላለጽ ምስክሮች ኑዛዜው ሲነበብ መስማታቸውን ለመግለጽ ጭምር እንደተጠቀሙበት መገንዘብ የተሻለ የኑዛዜው አተረጓጐም ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 13751 ጥቅምት 18 ቀን 1998 እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22174 ታህሣሥ 26 ቀን 1998 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 373/93 በ4/11/94 የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች ፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ

ተጠሪ ፡- አቶ ብስራት ጐላ

የኢንሹራንስ ክርክር - የኢንሹራንስ ውል - ከውል ውጪ ኃላፊነት

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ም/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቀረብኝ የሚለውን የተጣራ ገቢ በቀን ብር 250 በድምሩ ብር 28000 እንዲከፈለው የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ም/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው ተከሣሽ በሶስተኛ ወገን ላይ ጉዳት ባደረሰ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የተከራካሪዎችን መብትና ግዴታ ለመወሰን ውልንና ከውል ውጪ ያሉ ሕጐችን ተፈፃሚ ማድረግ ይችላሉ፡፡
2. በመድን ሰጪውና በተከሣሹ መካከል ያለው ግንኙነት በውል ላይ የተመሠረተ በመሆኑ መድን ሰጪው ሊገደድ የሚችልበት የካሳ መጠን በመድን ውሉ የተመለከተው ነው፡፡

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች ፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ - አልቀረበም ፡፡

መልስ ሰጪ ፡- አቶ ብስራት ጐላ -ቀርበዋል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበልን ጉዳይ የኢንሹራንስ ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡ ተያይዘው ከቀረቡት ፍርዶችና ሌሎች ሰነዶች ለመረዳት እንደቻልነው የመልስ ሰጪ መኪና በደረሰበት ግጭት ምክንያት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ ስለሆነ የመልስ ሰጪ ኢንሹራንስ ኩባንያ የነበረው ህብረት ባንክ በምትኩ አዲስ መኪና ሰጥቶታል፡፡ ህብረት ባንክ ደግሞ ሂሳቡን ከአሁን አመልካች ከአፍሪካ ኢንሹራንስ ተረክቧል፡፡ የአሁን አመልካች ክፍያውን የፈፀመው ጉዳት ያደረሰው መኪና የመድን ሽፋን ስለነበረው ነው፡፡

ይህ ሁሉ ከተፈፀመ በኋላ የአሁን መልስ ሰጪ መኪናዋ ለቆመችበት ለ112 ቀናት በቀን ብር 250 ሂሳብ ብር 28,000 ሊከፈልኝ ይገባል በማለት ጉዳቱን ባደረሰው በቢፍቱ ዲንሽ ማህበር ላይ ክስ መሠረተ፡፡ የአፍሪካ ኢንሹራንስም ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ፍ/ቤቱ ባዘዘው መሠረት በጉዳዩ ላይ ገብቶ ክርክር ቀጠለ፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ቢፍቱ ዲንሽ አ.ማ ለተቋረጠው ገቢ ኃላፊ መሆኑን በመግለፅ አፍሪካ ኢንሹራንስ ብር 28,000 /ሃያ ስምንት ሺህ ብር/ እንዲከፍል ወሰነ፤ ወጪና ኪሣራ የማቅረብ መብት የተጠበቀ ነውም አለ፤ ጉዳዩ በይግባኝ ወደሚቀጥለው ፍርድ ቤት የቀረበ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ አልተለወጠም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ማመልከቻ የቀረበው ይህን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታው መሰረተ ሃሳብ የሚከተለው ነው፡ -

1. መልስ ሰጪ በወደመችው መኪና ምትክ ሌላ አዲስ መኪና ያገኙ በመሆኑ ከመኪናው ዋጋ በላይ ተጨማሪ ካሳ መጠየቅ አይገባቸውም፡፡ አመልካች መኪናውን በማስረከብ ሂደት ተሳትፎ ስላልነበረው ጉዳትም ደርሶ ከሆነ ተጠያቂ ሊሆን አይገባውም
2. የአመልካች ግዴታ የሚመነጨው ከውል ግንኙነት በመሆኑ ፍ/ቤቱ ከውል ውጪ /Extra Contractual/ ህግን መሠረት አድርጐ ካሳ ክፈል መባሉ አግባብ አይደለም
3. መኪናዋ ሙሉ በሙሉ በመውደሟ መኪናዋ ብትኖር ኖሮ አገኝ የነበረው ጥቅም ይከፈለኝ የሚለው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፣ ክፍያ ዘግይቶም ከሆነ ወለድ ከሚጠይቅ በቀር የተቋረጠ ገቢ ሊጠይቅ አይገባም፡፡

መልስ ሰጪ ባቀረቡት የአመልካች ቅሬታዎች ላይ የሚከተለውን መልስ ሰጥቷል፡ -

1. ክሱ የቀረበው ጉዳቱ ባደረሰው በቢፍቱ ዲንሽ አ.ማ. በመሆኑ ክሱም ሆነ ውሳኔው ከውል ውጪ ሕግን መሠረት ማድረጉ አግባበ ነው
2. መኪናዋ በመውደሟ ንብረት ማጣት ብቻ ሳይሆን ከንብረቱ የሚገኝ ገቢም በመቋረጡ ኃላፊ የሆነው ወገን ካሣ እንዲከፍል መወሰኑ አገባብ ነው
3. ለመዘግየቱ ምክንያት ሌላ ሦስተኛ ወገን ቢሆንም አመልካች ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን አይችልም

ይህ ችሎት ጉዳዩን አግባበነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ መርምሮአል፡፡ ዋናው መታየት ያለበት ነጥብም አመልካች የአፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ የተጠሪ መኪና ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ በመሆንዋ የተቋረጠውን ገቢ ለመተካት በህግ ይገደዳል ወይስ አይገደድም የሚለው ነው፡፡

ከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው የመልስ ሰጪ መኪና ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ በመሆንዋ መልስ ሰጪ ከራሱ መድን ሰጪ ከነበረው ከህብረት ኢንሹራንስ ሌላ መኪና ተረክቧል፡፡መልስ ሰጪ ክስ ያቀረበው መኪናዋ በደረሰው አደጋ ምክንያት ከ11/09/96 እስከ 2/13/96 ዓ.ም.ድረስ ለ112 ቀናት በመቆምዋ ሳይገኝ የቀረበው የተጣራ ገቢ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ነው፡፡መልሰ ሰጪው ቀረብኝ የሚለው የተጣራ ገቢ በቀን ብር 250 በድምሩ 28,000 /ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት

የምሥራቅ ሀረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መልስ ሰጪ አዲሱን መኪና እስኪረከብ ድረስ የ112 ቀናት ገቢ ስለተቋረጠበት ለዚሁ ጉዳት ቢፍቱ ዲንሽ ኃላፊ ነው ካለ በኋላ አፍሪካ ኢንሹራንስ ከቢፍቱ ዲንሽ ጋር ባለው የመድን ውል መነሻነት ቀረ የተባለውን ብር 28,000 /ሃያ ስምንት ሺህ/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ለመልስ ሰጪ ክስ መነሻ የነበረው በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት በመሆኑ ጉዳዩ ከውል ውጪ ለሚደርስ ኃላፊነት አግባብ ባለው ህግ መሰረት መታየቱ አመልካች እንደሚለው ከህግ ያፈነገጠ አሰራር አይደለም፡፡ አመልካች ከቢፍቱ ዲንሽ ጋር ያለው ግንኙነት በውል ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ጉዳት ደረሰብኝ የሚል ሦስተኛ ወገንን በሚመለከት የኃላፊነቱም ሁኔታም ሆነ የግምቱ መጠን በሚመለከት የውል ህግ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል የሚለው ክርክር የሚያስኬድ አይደለም፡፡ ጉዳቱ የደረሰው በውል ግንኙነት ውስጥ ባለመሆኑ የመልስ ሰጭ ጉዳይ በውል ሕግ ብቻ ሊስተናገድ አይችልም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ኃላፊ የሚሆነው ከቢፍቱ ዲንሽ ጋር በነበረው የመድን ውል መነሻነት በመሆኑ ሊከፍል የሚገደደው የካሣ መጠን በመድን ውሉ በተመለከተው ሁኔታ ውስጥ መሆኑ የሚቀር አይደለም፡፡ በዚህ መሠረት አመልካች በምትክ የተሰጠውን የመኪና ዋጋ ለህብረት ኢንሹራንስ መተካቱ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ኢንሹራንስ ኩባንያው ከዚህ በተጨማሪ በመኪናው መውደም ምክንያት ለደረሰው ጉዳት /Consequential loss/ ተጠያቂ አይደለም፡፡ መልስ ሰጪ የደረሰው ኪሣራ በአመልካች ጥፋት ምክንያት የደረሰ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ይልቁንም መልስ ሰጪ የ112 ቀናት ሂሳብ አስልቶ ያቀረበው የመድን ሽፋን ሰጥቶት የነበረው የሕብረት ኢንሹራንስ መኪናውን ለመተካት 112 ቀናት በመውሰዱ ነው፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች አፍሪካ ኢንሹራንስ በጉዳት ምክንያት የቀረ ገቢን ለመተካት ግዴታ ስለሌለበት ጥፋት መፈፀሙ የሚያሳይ ማስረጃም ስላልቀረበ መኪናው ለቆመበት 112 ቀናት የቀረውን ገቢ ብር 28,000 /ሃያ ስምንት ሺህ/ ሊከፍል ይገባል ተብሎ መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምሥራቅ ሀረርጌ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 2073 በ13/10/97 የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.20745 በ16/2/98 የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ኡንሹራንስ ኩባንያ የተጠየቀውን የጉዳት ካሳ ብር 28,000 /ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ለመልስ ሰጪ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሠ
አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት

ተጠሪዎች፡- እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ሥላሴ

የቤት አበል ክፍያ - የተወረሰ ቤት - የጠቅላይ ሚ/ር ስልጣን - የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 74(4) - የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁ. 4/87 አንቀጽ 11/1/ - አዋጅ ቁ. 47/67 አንቀጽ 21(2)

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ቤት የተወረሰባቸው በመሆኑ አበል ሊከፈላቸው ይገባል ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ውሣኔ፡ - የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚኒስቴር መ/ቤቶችን በበላይነት የመምራትና ስራዎቻቸውንም የመቆጣጠር ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
2. ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ
2. አቶ አሰግድ ጋሻው
3. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
4. ወ/ት ሂሩት መለሠ
5. አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት - ነ/ፈጅ ሂሩት አስራት ቀረቡ፡፡

መልስ ሰጭ፡- እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ሥላሴ /6 ሠዎች/ - ጠበቃ አቶ ብስራት ሐመልማል ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

ተጠሪዎች ለዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መንግስት የግል መኖሪያ ቤቶቻቸውንና አከራይተው የነበሩትን ሌሎች ቤቶች ወርሶ እያስተዳደረ በመሆኑና ምንም ገቢ ስላልነበራቸው አበል እንዲከፈላቸው ለሥራና ከተማ ሚ/ር አመልክተው እንዲከፈላቸው የተወሰነ ቢሆንም ተጠሪ አበሉን ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከ1/12/67 - 30/8/87 ያለው ውዝፍ አበልና ወደፊት ያለው አበልም ለዘለቄታው እንዲከፍል እንዲወሠንበት ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም ውዝፍ አበሉ እንዲከፈልና ከክሱ በኋላ ያለው ግን ዳኝነት ያልተከፈለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱን ውሣኔ አፅንቷል፡፡

የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታም የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የሰጠው ውሣኔ በጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ተሽሯል፣ ተጠሪዎች እስር ቤት በነበሩበት ጊዜ መንግስት ወጪ እያደረገ ያኖራቸው በመሆኑ ተጠሪዎች ውጭ አገር ነዋሪዎች በመሆናቸው ከቤት ኪራይ በቀር ሌላ ገቢ እንደሌላቸው ሣይጣራና ሣይታወቅ የተፈቀደው አበል ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የሰጠው ውሣኔ በጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ተሽሮ እያለ የተጠራቀመው የቤት ኪራይ ይከፈል መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት አቤቱታው ለችሎቱ ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ተጠሪዎች ቤታቸው በመወረሱ ምክንያት አበል እንዲከፈላቸው ክስ ለማቅረብ የቻሉት የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር አበሉ እንደከፈላቸው የሠጠውን ውሣኔ መሠረት አድርገው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር በአ/ቁ. 47/67 አንቀጽ 21/2/ መሠረት ትርፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት የተወረሠበት ቤተሠብ ወይም ግለሠብ ከቤት ኪራይ በስተቀር ለመኖሪያ የሚሆን ሌላ ገቢ የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ በመሥራት ገቢ አስከሚያገኝ ድረስ በየወሩ ለመተዳደሪያ አበል እንዲከፈለው ሊወሰን እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ህጉ የሠጠውን ስልጣን መሠረት አድርጉ የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር ለተጠሪዎች አበል እንደከፈላቸው ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ግን ይህ ውሳኔ በጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ የተሻረ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ የተጠሪዎች ክርክር የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር በአ/ቁ 47/67 የተሰጠውን ስልጣን መሠረት አድርጎ የሠጠውን ውሣኔ የጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ለመሻር የሚያስችል ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡

ከመዝገቡ የጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ የሥራና ከተማ ልማት የሠጠውን ውሣኔ የሻረው በ29/12/87 እንደሆነ ተረድተናል፡፡ በዚህን ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት ከነሐሴ 15/1987 ጀምሮ ስራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 74/4/ ሁሉም ሚኒስቴሮች የሚገኙበትን የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚመራ፣ እንደሚያስተባብርና እንደሚወክል ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም ከነሐሴ 17/1987 ጀምሮ ስራ ላይ በነበረው የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አ/ቁ 4/87 አንቀጽ 11/1/ ሥር እያንዳንዱ ሚኒስትር፣ የሚመራውን ሚኒስቴር መ/ቤት የሚመለከቱ ሥራዎች ፕሮግራሞችና ህጎች አፈፃፀም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስቴሮች ምክር ቤት መሆኑ ተገልጿል፡፡ ከነዚህ ህጎች አኳያ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚኒስቴር መ/ቤቶችን በበላይነት የመመራትና ስራቸውንም የመቆጣጠር ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ለተጠሪዎች አበል እንዲከፈል የሠጠው ውሣኔ አግባብ ሆኖ ባለመገኘቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሣኔው መሻሩ ከስልጣኑ ውጪ ነው የሚያሠኝ አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም በአ/ቁ 47/67 ሥር የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የሚሰጠውን ውሣኔ የጠቅላይ ሚኒስቴር ሊሽር፣ ሊያሻሽል ወይም ሊለውጥ የሚያስችለው ስልጣን በግልጽ አልተመለከተም በማለት ብቻ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ያለውን አጠቃላይ ስልጣን ከግንዛቤ ባለመክተት ውሣኔው የተሻረው ስልጣን በሌለው አካል ስለሆነ ውጤት የለውም ማለታቸው የህግ ስህተት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም ምንም እንኳን አበል ለተጠሪዎች እንዲከፈል ሥልጣን የነበረው አካል ወስኖ የነበረ ቢሆንም ይኸው ውሣኔ ሥልጣን ባለው የበላይ አካል የተሻረ በመሆኑ ተጠሪዎች አበል እንዲከፈላቸው የተሰጣቸውን መብት አጥተዋል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶቹ አበሉ እንዲከፈል መወሠናቸው የህግ ስህተት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03721 በ27/05/95 እና በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18942 በ8/8/96 የተሰጡት ውሣኔዎች ተሸሯል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
3. ከሥር ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 23339

መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ከማል በድሪ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ጌታቸው ምህረቱ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኢ.ጉምሩክ ባለስልጣን

ተጠሪ፡- እነ አቶ አበሮ ኢርጋኖ

የመንግሥት ሰራተኞች የስራ ክርክር - የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት ስልጣን - የጉምሩክ ሰራተኞችን አስተዳደር በተመለከተ የገቢዎች ሚኒስትር የሚያወጣው መመሪያ - አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 6/2/ለ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት የተጠሪዎቹን ክርክር ተቀብሎ ያስተናግድ ሲል የወሰነውን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሸሯል፡፡

የጉምሩክ ሰራተኞች የመንግሥት ሰራተኞች ቢሆኑም ከሌሎች የፌዴራል መ/ቤቶች ተለይተው የሚተዳደሩት የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ እንጂ በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁ. 262/1994 አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 23339

13/7 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

4. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኢት.ጉምሩክ ባለስልጣን

ተጠሪ፡- እነ አቶ አበሮ ኢርጋኖ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፣

ፍ ር ድ፣

መዝገቡ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ አመልካች የካቲት 20 ቀን 1998 ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው። ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው የአሁኖቹ ተጠሪዎች የአመልካች ድርጅት ሠራተኞች የነበሩ መሆናቸውን ገልፀው ጊዜው ያለፈ ይግባኝ ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ለፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍ/ቤት የይግባኝ ማስፈቀጃ በማቅረባቸው ነው። የኮሚሽኑ ፍ/ቤት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካችን ሳይጠራ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ የቀረበውን አቤቱታ ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለጽ ብይን ሰጥቷል። የተሰጠው ብይን በመቃወም ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቀርቦ ፍ/ቤቱ ታህሣሥ 12 ቀን 1998 በዋለው ችሎት የፌ/ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በመሻር ይግባኙ ሊፈቀድ ይገባል አይገባም የሚለውን አከራክሮ እንዲወስን በማዘዝ ጉዳዩን ወደ አስተዳደር ፍ/ቤት መልሶታል።

የአሁኑ የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ የቀረበው በዚሁ ነጥብ ላይ ነው። የአሁኑ አመልካች በሰበር ቅሬታ ማመልከቻው ላይ እንደገለፀው፣ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 6/2/ /ለ/ መሠረት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ሠራተኞች ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚተዳደር መሆኑ እየታወቀና፣ የገቢዎች ሚኒስቴርም የባለሥልጣኑን ሠራተኞች አስተዳደር አስመልክቶ ቁ.01/22/41/3 በ23/02/98 የሠራተኞች አስተዳደር አጠቃላይ መመሪያ አውጥቶ እና በሥራ ላይ አውለው እያለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካች መ/ቤት ሠራተኞች የሥራ ክርክር በፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ይታይ ማለቱ የህግ ሥህተት ያለበት ነው ብለዋል።

ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል ተብሎ የግራ ቀኙ ክርክር ሰኔ 5 ቀን 1998 ተሰምቷል። በዚህ ጉዳይ በዋነኛነት የተያዘው ጭብጥ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ሠራተኞች

የሆኑት የተጠሪዎች ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 262/94 መስተናገድ ይገባዋል ወይስ አይገባውም? የሚለው ይሆናል። በአዋጅ ቁጥር 368/1995 በአንቀጽ 6/2/ /ለ/ መሠረት "የፌዴራል መንግስት አዋጅ ቁጥር 262/1994 ቢኖርም እንኳን የባለሥልጣኑ ሠራተኞች አስተዳደር ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።" በማለት የደነገገ መሆኑ ይታወቃል። ይህንንም ተከትሎ በገቢዎች ቦርድ የሠራተኞቹን አስተዳደር በሚመለከት መመሪያ ወጥቶ ከጥቅምት 23 ቀን 1996 ጀምሮ በሥራ ላይ መዋሉ ተረጋግጧል። ይህ በዚህ ሁኔታ ተከናውኖ እያለ የሥር ፍ/ቤት "---የባለስልጣኑን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል የሚለው ቢተረጉም ስለሠራተኞቹ አስተዳደር ነክ ጉዳዮችን የሚመለከት መመሪያ ይሆን እንደሆን እንጂ በሠራተኞቹ በኩል የሚኖረው የዳኝነት ጥያቄ የት ቦታ? በማን ይታይ? የሚለውን በመመሪያ ሊወሰን ይችላል የሚል ትርጉም ሊሰጥ አይችልም።" በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ከህጉ ዓላማና መንፈስ የራቀ ትርጉም የተሰጠበት መሆኑን ያመለክታል። የአመልካች መ/ቤት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት መሆኑ ቢታወቅም፣ ሕግ አውጭው የአመልካች መ/ቤት ከሚያከናውናቸው ተግባራት አኳያ ከሌሎቹ የፌዴራል መ/ቤቶች ተለይቶ እንዲተዳደር በአዋጅ በግልጽ አመላክቶ እያለ የሥር ፍ/ቤቱ የባለሥልጣኑ ሠራተኞች አስተዳደርን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል የሚለው የሠራተኞቹን አስተዳደር ነክ ጉዳዮች ብቻ በመመሪያው መሠረት ይታያሉ በማለት የሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል።

ው ሳ ኔ

- የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍ/ቤት የአሁኖቹን ተጠሪዎች ክርክር ተቀብሎ ያስተናግድ በማለት ታህሣሥ 12 ቀን 1998 ዓ.ም በወ/ይ/መ/ቁ. 20709 የሠጠው ውሳኔ ተሽሯል፣
- የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፣
- መዝገቡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 22317

ሚያዚያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች፡- በምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ አሊ ሳዬ

የጉምሩክ ክርክር - ኮንትሮባንድ - የተቋረጠ ጥቅም ክፍያ - አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 5 - 6 የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2010/2/

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ም/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የ393 ቀናት የተቋረጠ ገቢ ለተጠሪ እንዲከፍልና መኪናውን ወይም ዋጋውን ብር 50000 እንዲተካ የሰጠውን ውሳኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ውሣኔ፡ - የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ም/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የጉምሩክ ባለሥልጣን በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
2. የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕገ ወጥ መንገድ መገልገያ የሆኑ መጓጓዣዎችን ጭምር ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ሥር ለማቆየት ግልፅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
3. የመንግሥት መ/ቤት ባለሥልጣን ራሱ የመረመራቸውን ሰነዶች ቃላት መቃወም የሚቻለው ዳኞች በተለይ ከፈቀዱ ብቻ ነው፡፡

የሰ/መ/ቁ. 22317

ሚያዚያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

2. አቶ አሰግድ ጋሻው

3. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች፡- በምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ - ነ/ፈጅ አቶ ጉሳዩ ነጋሽ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ አሊ ሳዬ - ቀረበ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሠበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ አመልካች በ12/4/98 ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ የአሁኑ አመልካች የኮንትሮባንድ ዕቃ ሳልጭን ጭነህል በማለት መኪናዬን ከሕግ ውጭ ይዞ ስላቆመብኝ በቀን አገኘው የነበረው ገቢ ብር 250 /ሁለት መቶ ሀምሳ/ ብር በ150 ቀኖች ተባዝቶ የአሁን አመልካች ብር 37,500 /ሰላሣ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብር/ እንዲከፍለው በተጨማሪም የመኪናውን ዋጋ ብር 50,000 ወይም መኪናውን እንዲያስረክበው ጠይቋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር አድምጦ ጥር 27 ቀን 1997 በዋለው ችሎት የአሁኑ አመልካች የ393 ቀናት የተቋረጠ ገቢ ለተጠሪ እንዲከፍልና መኪናውን ወይም ዋጋውን ብር 50,000 እንዲተካ ታዟል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት መኪናው በመያዙ ምክንያት የአሁኑ ተጠሪ ጠይቆ የነበረው የተቋረጠ ገቢ የ150 ቀናት ብቻ ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤት የ393 ቀናት መወሰኑ ትክክል ባይሆንም ይግባኝ ባይ በዚህ በኩል ያቀረበው አቤቱታ ስለሌለ ታልፏል ብሎ የይግባኝ መዝገቡን ዘግቶ መልሶታል፡፡

ይህ ችሎት ሚያዚያ 2 ቀን 1998 ዓ.ም. መዝገቡ ለሰበር ይቀርባል በማለት ወስኖ ጉዳዩን ለመስማት በተያዘው ቀጠሮ ተጠሪን አግኝቶ መጥሪያውን ማድረስ ያልቻለ መሆኑን አመልካች በመግለፁ ይህ ችሎት ግንቦት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. ተጠሪ የጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ታዟል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ሰኔ 28 ቀን 1998 ሆነ በሚቀጥሉት ቀናት ባለመቅረቡ ፍ/ቤቱ በሌለበት እንዲታይ ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ የተቋረጠ ገቢ ኃላፊ ነው ለማለት መሠረት ያደረጉት ምክንያት የአሁኑ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኮንትሮባንድ ዕቃ ዝርዝር የሚያሳያ የጽሁፍ ማስረጃ ቢያቀርብም የተባሉት ዕቃዎች ከተጠሪ መኪና ላይ መያዙን አይገልጽም፤ አመልካች ለሕግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ መኪናውን ይዞ በቁጥጥር ስር ማዋሉ ደግሞ ተጠሪን ሆነ ብሎ ለመጉዳት ነው በሚል መደምደሚያ እንደነበር ይህ ችሎት ተረድቶታል፡፡ በዚህ መሠረት ይህ ችሎት የተጠሪ መኪና ለህግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ተይዟል ተብሎ የአሁኑ አመልካች በውሳኔው የተመለከተውን ገንዘብ ይከፈል መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ይህ ችሎት መርምሯል፡፡

አዋጅ ቁጥር 60/89 የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 6 ላይ የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባር በዝርዝር የተመለከተ ሲሆን በተለይ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለውን ንዑስ ቁጥር 5 ስንመለከት በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ፣ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን የተሰጠው መሆኑ ተገልጿል፡፡ አመልካች በዚህ በተሰጠው ሥልጣን ተጠቅሞ በኮንትሮባንድ ወንጀል ተግባር ይዞ በቁጥጥር ሥር ባቆየው መኪና ላይ በገቢ ዕቃ መመዘገቢያ ሞዴል ላይ የተሞላውን ዝርዝር የኮንትሮባንድ ዕቃ በሰነድ ማስረጃነት አያይዞ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት የቀረቡት የገቢ መመዘገቢያ ሞዴሎችን ሕጋዊነት የተቀበለ ቢሆንም በመቀጠል ግን ማስረጃው የዕቃዎች ዝርዝር የሚገልጽ እንጂ ዕቃው በከሳሽ መኪና ላይ መያዙን አይገልጽም ብቻ በማለት ውድቅ ማድረጉ ከማስረጃ ሕግ ዓላማና በፍ/ሕ/ቁ. 2010/2/ መሠረት በባለስልጣን ስለተረጋገጡ ሠነዶች ተቀባይነት የሚደረገውን ሕግ የሚጥስ አካሄድ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአሁን አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 58/1/ /ለ/ መሠረት በሕገወጥ መንገድ መገልገያ የሆኑ መጓጓዣዎችን ጭምር ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ሥር ለማቆየት ግልጽ ሥልጣን ተሰጥቶት እያለ የሥር ፍ/ቤት የተያዘ የኮንትሮባንድ ዕቃ ዝርዝር የቀረበ መሆኑን ተቀብሎ ከአሁኑ ተጠሪ መኪና ላይ ስለመያዙ ማስረጃ አልቀረበም በሚል የተቋረጠ ገቢ ይክፈል ብሎ ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

የአሁኑ አመልካች በሕግ አግባብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ተግባሩ ሲወጣ ይዞ ላቆየው ተሽከርካሪ የተቋረጠው ገቢ ይክፈል በማለት የምስራቅ ሐረርጌ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 271/96 በ22/04/97 እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 25132 በ15/3/98 የሰጡትን የውሳኔ ክፍሎች ሽረናል፤ የአሁኑ አመልካች መኪናውን ለተጠሪ ያስረክብ ብለን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔዎች አሻሽለን ወስነናል፤

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰበር መ/ቁ. 12025

መጋቢት 18/1999

ዳኞች፡- **አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ**

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- **አቶ ምናሴ አልማው**

መልስ ሰጪ፡- **0ቃቤ ሕግ**

የወንጀል ጉዳይ ክርክር - ማታለል - የጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ የጥብቅና ስራ እሰራለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል - የመከላከል መብት - የ1949 ወንጀለኛ መቅጫ ሀግ ቁ. 656(ሀ) ና (ለ)

አመልካች በቤንሻንጉል ጉምዝ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የህግ ስህተት ያለበት ነው በሚል የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የቤንሻንጉል ጉምዝ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ጸንቷል፡፡

1. የጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ ጉዳይ አስፈጽማለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል የማታለል ወንጀል ነው፡፡
2. የመከላከል መብት ህገ-መንግሥታዊ መብት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 12025

መጋቢት 18/1999

ዳኞች፦ 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አሰግድ ጋሻው

3. መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ሂሩት መለሠ

5. ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ አቶ ምናሴ አልማው አልቀረቡም

መልስ ሰጪ፦ 0ቃቤ ሕግ አልቀረበም

ፍ ር ድ

ይህ መዝገብ ለሰበር ችሎት የቀረበው አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሕግ ስህተት መኖሩን በሚያመለክት ሁኔታ የተሰጠ በመሆኑ ውሣኔዎቹ ይሻሩልኝ ሲል በማመልከቱ ነው።

ይህ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች እንዲሁም በዚህ ፍርድ ቤት ከተደረገው የጽሑፍ ክርክርና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕጐች ጋር በማገናዘብ መርምሮአል።

በዚህም መሠረት አመልካች የተከሰሰውና ጥፋተኛ የተባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 656(ሀ) እና (ለ)ን በመተላለፍ ሲሆን ለፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ ምክንያት የሆነው አመልካች የጥብቅና ፈቃድ ሣይኖረው የጥብቅና ፈቃድ ያለው በማስመሰል የግል ተበዳዮችን ጉዳይ አስፈጽምላችኋለሁ በማለት ብር 3830 (ሶስት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሣ) መወሰዱ በመረጋገጡ ነው። አመልካች በዚህ ችሎት ማስረጃ አልቀረበብኝም ቢልም የስር ፍርድ ቤቶች በቂ ማስረጃ ቀርቦበት የወሰኑ መሆኑን ተገንዝበናል። ይልቁንም አመልካች ቀደም

ሲል ተሰጥቶት የነበረው የጥብቅና ፈቃድ መሠረዙ ከተገለፀለት በኋላ ይህን ድርጊት መፈፀሙ በማስረጃ ተረጋግጦበታል።

በሌላ በኩል አመልካች የመከላከል መብቱ አልተጠበቀልኝም ቢልም ተደጋጋሚ እድል ተሰጥቶት የመከላከያ ማስረጃውን ሊያቀርብ አለመቻሉ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል። ተከሣሹ የመከላከል መብቱ ሕገመንግሥታዊ መብት መሆኑ ባያከራክርም ተከሣሽ በሆነበት ጉዳይ ላይ በተገቢው አሜሪ ጊዜ ውስጥ የመከላከያ ማስረጃ ካለው እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቶች ተደጋጋሚ ቀጠሮ ቢሰጡም አመልካቹ እድሉን ባለመጠቀሙ ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት ጣሱ ሊያሰኛቸው አይችልም። በመሆኑም አመልካች በስር ፍርድ ቤት የቀረበበት ክስ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት በመሆኑና የተጣለበት የሁለት ዓመት ቅጣትም ሕጉ በሚያዘው ክልል ውስጥ በመሆኑ ሂደቱም ሆነ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሣይ ሆኖ አላገኘነውም።

ው ሣ ኔ

(1) በዚህ ጉዳይ የቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተቀባይነት አላገኘም።

(2) የቤንሻጉል ጉምዝ የከፍተኛና የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief





የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች
ቅፅ 5

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

ቅፅ 5

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሚያዝያ 2001 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

ቅፅ 5

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

አዲስ አበባ



የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

ከዚህ ዕትም በፊት በነበሩ ቅፆች በርካታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች ታትመው በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶችና ለሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሠራጩ ተደርጓል፡፡ ይህም በዋናነት፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል ተብሎ በመደንገጉ ፍርድ ቤቶች የሰበር ችሎቱ የሰጠውን የሕግ ትርጉም ተከትለው እንዲሠሩ ለማስቻል ነው፡፡ በየፍርድ ቤቶች ለተመሣሣይ ጉዳዮች ይሰጥ የነበረውን የተለያዩ ወሳኔዎች በማስቀረት የፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ወጥነት እንዲኖራቸውን ተገማችም እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑም ነው፡፡

በሌላ በኩል ውሣኔዎቹ በጥራዝ መልክ መዘጋጀታቸው ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ የሕግ ተማሪዎችና ምሁራን፣ ለጠበቆችና ለህብረተሰቡ በአጠቃላይ ውሳኔዎቹን በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል የሚል እምነት አለን፡፡

ተገኔ ጌታነህ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማውጫ ገጽ

ውሎች - ውክልና 1

የሰ/መ/ቁ 17320 2
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ወ/ሮ ሸዋርካብ ተሾመ
የሰ/መ/ቁ 20890 12
የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ ዓለምነሽ ኃይሌ
የሰ/መ/ቁ 23861 17
ሊቀስዩማን አሰፋ በሻውረድና የሣህሊተ ምህረትና
ክርስቶስ ሣምራ ደብር አስተዳደር
የሰ/መ/ቁ 26399 20
አቶ ኃ/ማርያም ባዩ እና እነ አቶ ሳሙኤል ጎሳዬ
የሰ/መ/ቁ 32241 29
ወ/ሮ ካሰች ተካልኝ እና እነ አቶ ኃ/ማርያም አበበ

ውሎች - ዋስትና 34

የሰ/መ/ቁ 21355 35
አንበሳ የተከማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት እና አንበሳ
ኢንሹራንስ ኩባንያ
የሰ/መ/ቁ 25115 39
አቶ ማሞ ጎበና እና አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም
የሰ/መ/ቁ 26565 42
ግሎባል ኢንሹራንስ አ.ማ እና ንብ ትራንስፖርት አ.ማ

ውሎች - ስጦታ 48

የሰ/መ/ቁ 17742 49
እነ ወ/ሮ አበበች ታደሰ እና እነ አስር አለቃ ሲሣይ ካብትህይመር
የሰ/መ/ቁ 23921 55
ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግሥቱ እና 10 አለቃ ታደሰ ወርቁ
የሰ/መ/ቁ 32337 57
ወ/ሮ ፀሐይነሽ ይሕደጎ እና እነ ወ/ሮ ትሕሽ በርሔ

ውሎች - ብድር 64

የሰ/መ/ቁ 22891 65
ወ/ሮ ማና ኃ/ሚካኤል እና እነ አቶ ገ/ማርያም ከበደው
የሰ/መ/ቁ 31737 69
አቶ ገብሩ ገ/መስቀል እና ቂስ ገ/መድኅን ረዳ

ውሎች - ልዩ ልዩ 75

የሰ/መ/ቁ 24173 76
የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና ወ/ሮ አይዳ ሐሰን
የሰ/መ/ቁ 24574 79
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤ/መ/ፓ/ጠ/ቤ/ጽ/ቤት እና አቶ
ይትባረክ ሣህሉ
የሰ/መ/ቁ 25434 83
የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን እና ፍሬተርስ
ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ ማኅበር
የሰ/መ/ቁ 26565 88
ግሎባል ኢንሹራንስ አ.ማ እና ንብ ትራንስፖርት አ.ማ
የሰ/መ/ቁ 29369 94
በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዮት የሆለታ ግብርና ምርምር
ማዕከል እና አቶ ተመስገን አድነው
የሰ/መ/ቁ 39947 98
የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ሲሳይ ጥላሁን
የሰ/መ/ቁ 31480 ባህመድ 102
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና እና አቶ መሐመድ

ከውል ውጪ 105

የሰ/መ/ቁ 19388 106
ዘይነባ ሐሰን እና ፍሬው ተካልኝ
የሰ/መ/ቁ 21296 113
የኔዘርላንድ ልማት ድርጅት እና ውበት አድባሩ
የሰ/መ/ቁ 22509 118
አቶ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ እና ዳርጌ ሰምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 23924 121
አቢሲንያ ባንክ እና አቶ አበበ ክበደ
የሰ/መ/ቁ 24818 125
ይልቃል በእውቀቱ እና ስዩም አባዲ
የሰ/መ/ቁ 27565 128
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ደምሴ ወርቅነህ
የሰ/መ/ቁ 27623 131
ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ውባየሁ አበበ
የሰ/መ/ቁ 28612 133
የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን እና የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን
የሰ/መ/ቁ 28750 136
የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 28865 141
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ካሣ ግዛው
የሰ/መ/ቁ 30032 145
የአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ እና ወ/ሮ ምንትዋብ የኔነህ
የሰ/መ/ቁ 30442 149
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሰሜን ምዕራብ ሪጅን እና ወ/ሮ ድንቋ አመኔ
የሰ/መ/ቁ 31099 153
የተንዳሆ እርሻ ልማት አ/ማ እና ወ/ሮ ኒሻን አለማየሁ
የሰ/መ/ቁ 32144 156
ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እና ወ/ሮ አልሻ ሲራጅ
የሰ/መ/ቁ 32250 159
ወ/ሮ አስናቀች ወ/ማርያም እና እነ አቶ ከተማ ተሠማ
የሰ/መ/ቁ 33975 162
የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እና ወ/ሮ አበበች ስዩም
የሰ/መ/ቁ 34138 166
እነ ሲስተር ገነት ጌታቸው እና ወንድወሰን ኃይሉ ወልደማርያም
የሰ/መ/ቁ 34906 171
የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት እና ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቁ

የቤተሰብ ህግ 174

የሰ/መ/ቁ 21740 175
ወ/ሮ አስረስ መስፍን እና ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ
የሰ/መ/ቁ 23021 180
ወ/ሮ አበባወርቅ ጌታነህ እና ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ
የሰ/መ/ቁ 23493 185
ወ/ሮ አንማው ዘገየ እና ወ/ሮ ወርቁ መኮንን
የሰ/መ/ቁ 23632 188
ወ/ት ፀዳለ ደምሴ እና አቶ ክፍሌ ደምሴ
የሰ/መ/ቁ 24295 192
ወ/ሮ ጽጌ ድረሴ እና ወ/ሮ መሰለች ረዳ
የሰ/መ/ቁ 24625 195
ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ እና ወ/ሮ ራሕማ ዓሊ
የሰ/መ/ቁ 25005 198
መኮንን በላቸው እና ወ/ሮ አለሚቱ አደም
የሰ/መ/ቁ 25281 201
ወ/ሮ መሠረት ፍስሐ እና አቶ ቀልቤሣ አበው
የሰ/መ/ቁ 25588 204
መርዳን ሃሰን ዑመር እና መውሊድ ተኸል
የሰ/መ/ቁ 26839 208
ወ/ሮ አስካለ ለማ እና ሣህለ ሚካኤል በዛብህ
የሰ/መ/ቁ 26953 211
አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ እና ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ
የሰ/መ/ቁ 27697 215
አቶ ርዕሶም ገ/መድኅን እና ወ/ሮ አልማዝ ጊላሚካኤል
የሰ/መ/ቁ 27869 220
ፍቅርና ሠላም ኃ/የተ/የግ/ማ እና ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ አቶ ትሁት ማሞ
የሰ/መ/ቁ 29343 224
1. ወ/ሮ አምሳለ ተፈራ
2. ወ/ት ሌንሳ ኢላላ እና ወ/ት አበባ አድማሱ
የሰ/መ/ቁ 29402 231
ወ/ሮ ሐዳስ ታረቀ እና የሟአለቃ አስመላሽ ኃይለስላሴ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 30959 234
1. ወ/ሮ ተወዳጅ ገ/ሥላሴ/
2. ወ/ሮሙሉ ገ/ሥላሴ እና
1. አቶ ዘለቀ ዘውዴ
2. አቶ አንዳላር ዘውዴ
የሰ/መ/ቁ 31430 237
ወ/ሮ አዲስ አለም እና የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ
የሰ/መ/ቁ 31891 240
እነ አቶ አንለይ እንየው እና ወ/ሮ መሬም ጡሃ
የሰ/መ/ቁ 31946 244
ወ/ሮ ዘውዲቱ ጌታቸው እና ተመስገን ደሣለኝ
የሰ/መ/ቁ 32130 247
እነ እማዋይሽ ከሣ እና ወ/ሮ አስቴር አህመድ
የሰ/መ/ቁ 33126 251
ወ/ሮ የዝና ተስፋሁን እና መምህር ጥሩአየሁ እውነቱ
የሰ/መ/ቁ 33411 255
ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ እና አለቃ ኪሮስ ገብሩ
የሰ/መ/ቁ 33440 259
ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም እና አቶ ግርማ ገ/ሥላሴ
የሰ/መ/ቁ 33875 262
ወ/ሮ የሻረግ አባትኩን እና ወ/ሮ መሠረት አድማሱ
የሰ/መ/ቁ 34149 268
እነ ወ/ሮ ዘለቃሽ በቀለ እና አቶ አለሙ በቀለ
የሰ/መ/ቁ 34387 271
አቶ ከበደ ሙሐሌ እና ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ
የሰ/መ/ቁ 35376 275
አቶ ዳንኤል አሰፋ እና ወ/ሪት ሐሊን ውበቱ

የንግድ ህግ

የሰ/መ/ቁ 23389 281
የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አክ/ማኅበር እና
እነ ባህሩ አብርሃም
የሰ/መ/ቁ 25306 284
አቶ ተስፋዬ ገለቱ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 27161 288
አቶ ኤልያስ ከፈለ እና እነ አቶ ከድር አህመድ
የሰ/መ/ቁ 28923 291
የባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ አክስዮን ማሕበር እና
1. የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር
2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነገረፈጅ
አቶ አዳነ መጋቡ

በአዋጅ የተወረሱ ቤቶች 296

የሰ/መ/ቁ 22297 297
የጅማ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት ተወካይ
ቲጃኔ አባቡልጉ እና አቶ ሸዋረገድ አባድር
የሰ/መ/ቁ 23608 300
የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች
እና የአቶ ኑር በዛ ተረጋ ወራሾች
የሰ/መ/ቁ 27548 306
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና
1. ወሮ ቆጽለ መርሻ 2. ወ/ሮ ፀምረ መርሻ
የሰ/መ/ቁ 29822 310
የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ
ወ/ሮ በቀለች አማረብህ
የሰ/መ/ቁ 29860 318
ወ/ሮ አስናቀች ሲሻው እና እነ ወ/ሮ አሰለፈች ከተማ
የሰ/መ/ቁ 31490 322
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ሴራኮ እስራኤላዊያን
የሰ/መ/ቁ 31682 326
አዲስ ከተማ ክ/ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ እና
1. ዘላለም ይልማ ባልቻ
2. መሠረት ይልማ ባልቻ
3. አዳሙ ይልማ ባልቻ
የሰ/መ/ቁ 32376 330
አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ
ሸዋንግዛው
የሰ/መ/ቁ 34249 335
እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ እና እነ አቶ አለሙ ወንድሙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እርቅ ግልግል 338

የሰ/መ/ቁ 22857 339
እነ አቶ ተክሌ ደግፌ እና እነ አቶ በፍቃዱ ኃይሌ
የሰ/መ/ቁ 25912 343
የአቶ ብር ቆርቾ ወራሽ ብርቅነሽ ብሩ እና አቶ ክፍሌ ሐብደታ
የሰ/መ/ቁ 29386 346
ወ/ሮ ወለላ ተሰማ እና እማሆይ በላይነሽ መለሠ
የሰ/መ/ቁ 30536 353
ወ/ት ዓለምነሽ ዋቅቶላ እና
1. አቶ ይልቃል ጌጤ 2. ካጀ ኢ/ል ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ
የሰ/መ/ቁ 30727 356
የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አ/ማህበር እና ጄቲቲ ትሬዲንግ
ሥራ አስኪያጅ

ልዩ ልዩ 361

የሰ/መ/ቁ 20036 362
ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ
የሰ/መ/ቁ 23334 366
የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እና
1. አቶ ደበሣ ገለታ 2. አቶ ኤባ ደመራ
የሰ/መ/ቁ 25899 369
የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ስዩም ካሣ
የሰ/መ/ቁ 26480 372
የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ እና አቶ ቢንያም ዓለማየሁ
የሰ/መ/ቁ 28883 375
ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ሚስተር ኒኮላ አስ
ፓፓቻት ዚስ
የሰ/መ/ቁ 29005 378
አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እና
1. ግርማቸው ይላላ
2. አዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን
የሰ/መ/ቁ 30298 381
አቶ የሺወንድም አቡሐይ እና አቶ አየነው ማለደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሎች

ውክልና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 17320

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁዮናስ

ሐሩት መለሠ

መድንን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነገረ ፈጅ ደረጀ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1ኛ/ ዶ/ር ሻውል ገብሬ - ጠበቃ ወንድሜነህ ዳኜ

2ኛ/ ወ/ሮ ሸዋርካብ ተሾመ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 03926 ሰኔ 30 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 23780 መስከረም 26 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ጥቅምት 8 ቀን 1997 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ በሕጋዊ ጋብቻ ተጣምረው የሚኖሩ ባልና ሚስት መሆናቸውን ገልፀው በጋብቻ እያሉ በወቅቱ በነበረው አስተዳደራዊ ስያሜ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 10 ቀበሌ 22 ቁጥሩ 715/2 የሆነ ቤት በጋራ ሠርተን እኛ በቡልጋሪያ አገር በነበርንበት ጊዜ አቶ ገዛኸኝ በልሁ ይህንን ቤታችንን እንዲያስተዳድርልን እንዲሸጥልን ወክለነው ነበር፡፡ አቶ ገዛኸኝ በልሁ እኛ በሰጠነው የውክልና ማስረጃ ሌላ የውክልና ማስረጃ በማዘጋጀት ከሰጠነው የውክልና ስልጣን ውጭ ቤታችንን መያዣ በማድረግ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ/ ተበድሯል፡፡ ስለዚህ አንደኛ ተከሣሽ የሆነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሁለተኛ ተከሣሽ ለሆነው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ብድር የሰጠውና የእኛን ቤት በመያዣነት የያዘው ተበዳሪው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤቱን በመያዣነት አስይዞ ለመበደር የሚያስችለው የውክልና ሥልጣን ያለው መሆኑን ሣያረጋግጥ ነው፡፡ ሁለተኛው ተከሣሽ አቶ ገዛኸኝ በልሁ ከአንደኛው ተከሳሽ የእኛን ቤት በማስያዝ ብድር የተበደሩት የተጭበረበረ የውክልና ሰነድ አቅርበው ነው፡፡ ስለዚህ በማናውቀውና ፈቃዳችንን ያልሰጠንበትን የተጭበረበረ የውክልና ሰነድ በመቀበል አንደኛ ተከሣሽ ቤታችንን በመያዣነት መያዙ ሕጋዊ ባለመሆኑ የመያዣ ውሉ ፈርሶ በባንኩ የተያዙት የባለቤትነት ሰነዶች ተመላሽ እንዲሆኑ ውሣኔ ይስጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሣሽ የሆነው አመልካች ነገረ ፈጅ ለተጠሪዎች ወኪል ለሆነው ለአቶ ገዛኸኝ በልሁ የከሳሾችን ቤት በመያዣነት በመያዝ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ያበደርነው ከሣሾች ወኪላቸው ቤቱን አስይዞ ብድር ለመበደር የሚያስችለው የውክልና ስልጣን የሰጡት መሆኑን በወኪላቸው በኩል ከቀረቡት ማስረጃዎች አረጋግጠን ነው፡፡ ስለዚህ ከሳሾች ፈቃዳችንን ሳንሰጥ አላግባብ ቤታችን በመያዣነት ተይዟል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ እንደዚሁም ተጠሪዎች ለማስረጃነት ይጠቅመናል ያሉትን የፖሊስ የምርመራ መዝገብና የተጭበረበረ የውክልና ሰነድ በመጠቀም በወንጀል ጉዳይ ተጠርጣሪ የሆነውን የተጠሪዎቹን ወኪል የአቶ ገዛኸኝ በልሁን የምስክርነት ቃል ከሰማ በኋላ ተከሳሹ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የከሳሾችን ቤት ለማስያዝ ህጋዊ የውክልና ስልጣን ስለሌለው ለአቶ ገዛኸኝ በልሁ የከሳሾችን ቤት በመያዣነት በመያዝ ብድር የሰጠው በአግባቡ አይደለም ስለዚህ የመያዣ ውሉ ፈራሽ ነው የባለቤትነት ሰነዱን ይመልስ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንን ውሣኔ ለማስቀየር ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ነገረ ፈጅ ለዚህ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከአዲስ አበባ አስተዳደር የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በኩል በቁጥር 10760/484 የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም የተመዘገበው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ያቀረቡት የውክልና ሰነድ ትክክለኛ የውክልና ሰነድ ስለመሆኑ የአዲስ አበባ የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት መጠየቅና ማረጋገጥ ነበረበት፡፡ ሰነዱን አረጋጋጮ የመዘገበው የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ሣይጠይቅ የፖሊስን የምርመራ መዝገብ የተጠሪዎችን ፓስፖርትና የተጠሪዎች ወኪል የሆኑትን የአቶ ገዛኸኝ በልሁን ምስክርነት በመቀበል ሕጋዊ ስልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ የተሰጠውን የውክልና ሰነድ በተጭበረበረ ተግባር የተገኘ ሀሰተኛ ሰነድ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተጠሪዎች በቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ለወኪላቸው አቶ ገዛኸኝ በልሁ የሰጡት የውክልና ስልጣን ቤቱን እንደወካዮቹ ሆኖ ለማከራየት ለመሸጥ ለመለወጥና በስሙ ለማዞር የሚያስችለው የውክልና ስልጣን ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ የውክልና ማስረጃ መሠረት የተጠሪዎች ወኪል ቤቱን በመያዣነት አስይዞ ብድር ለመውሰድ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3049 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ይህንን ግልጽ የሕግ ድንጋጌ ሣያገናዝቡ ቤቱን በመያዣነት ለማስያዝ የውክልና ስልጣን ከሌለው ሰው ጋር ነው ውል የተዋዋላችሁት በማለት የመያዣ ውሉ እንዲሰረዝ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ለተወካያችን አቶ ገዛኸኝ በልሁ የሰጠነው ውክልና ቤቱን በመያዣያነት ለማስያዝና ከባንክ ብድር ለመውሰድ የሚያስችለው የውክልና ስልጣን አይደለም፡፡ ተወካያችን ለአመልካች ቤታችንን በመያዣነት ያስያዘው እኛ አገር ውስጥ በሌለንበት ፈቃዳችንን ባልሰጠንበት ሁኔታ የሐሰት መታወቂያ በማዘጋጀት ሌላ ሰው በአንደኛው ተጠሪ ስም አቅርቦ በቁጥር 10760/484 የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም የአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ የሰጠው እኛ

የማናውቀውን እና ያልፈረምንበትን በማጭበርበር ወንጀል የተገኘ ሰነድ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ሀሰተኛ የውክልና ሰነድ መሠረት ቤታችን በመያዣነት መያዙ ሕጋዊ ስላልሆነ፣ የመያዣ ውሉ ፈርሶ የቤቱን ባለቤትነት የሚያረጋግጡት ሰነዶች እንዲመለሱልን የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በአቶ ገዛኸኝ በልሁ እና በተጠሪዎቹ መካከል የተወካይና የወካይ ግንኙነት እንዳለ ተረድተናል፡፡ ተጠሪዎች ቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ተወካያቸው አቶ ገዛኸኝ በልሁ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በፊት በነበረው ስያሜ ወረዳ 10 ቀበሌ 22 ቁጥሩ 715/2 የሆነውን ቤታቸውን እንዲያስተዳድርላቸው እንዲሸጥላቸው የወከሉት መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስና ማስረጃ ያሣያል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ተወካያቸው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤታቸውን እንዲያስተዳድሩ እንዲሸጡ እንዲለውጡና ለሦስትኛ ወገን ለማስተላለፍ እንዲችሉ ቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል የውክልና ስልጣን የሰጡ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ይህም የውክልና ማስረጃ በመጀመሪያ ተጠሪዎች ለተወካያቸው የሰጡት የውክልና ማስረጃ ለመሆኑ ክርክር አልተነሣም፡፡

ተጠሪዎች አናውቀውም ብለው የሚከራከሩት የተጠሪዎች ተወካይ የሆነው አቶ ገዛኸኝ በልሁ የወካዮችን ቤት በመያዣነት በማስያዝ ገንዘብ ለመበደር እንደሚችል የሚዘረዝረው በአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በኩል ተመዝግቦ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም. አንደኛው ተጠሪ ለተወካይ አቶ ገዛኸኝ በልሁ ሰጥተውታል የተባለው የውክልና ማስረጃ ነው፡፡ ተጠሪዎች ይህ ሰነድ የተጭበረበረ ሰነድ በመሆኑ፣ ይህንን መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤታችንን በመያዣነት መያዙ ሕጋዊ ውጤት ሊሰጠው አይገባም በማለት የሚከራከሩ ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ ይህ የውክልና ሰነድ የተጭበረበረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመሆኑ ሰነዱን አረጋግጦ የሰጠው የመንግሥት አካል ያላረጋገጠውና በቂ ማስረጃ ያልቀረበበት ነው በማለት ይከራከራል። ስለዚህ ተከራካሪዎቹ የሀሣብ ልዩነት ያላቸው በዚህ በሁለተኛው የውክልና ሰነድ ትክክለኛነትና ሕጋዊነት ላይ ነው። ስለሆነም የተጠሪዎቹ ወኪል የሆነው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ሁለት የውክልና ማስረጃ እንዳለውና ማስረጃዎቹንም የውክልና ስልጣኑን ለማስረዳት የተጠቀመባቸው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል። የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪዎቹ ተወካይ አቶ ገዛኸኝ በልሁ የወካዮቹን ቤት በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ ላይ አተኩሮ የሁለቱን የውክልና ማስረጃዎች ይዘትና ሕጋዊ ውጤት አልመረመረም። በአንዳሩ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ አድርጎ የያዘው በአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በኩል የተሰጠው ሁለተኛ የውክልና ማስረጃ ትክክለኛ ማስረጃ ነው ወይስ በማጭበርበር ተግባር የተገኘ የሀሰት የውክልና ማስረጃ የሚለውን ነጥብ ነው።

አቶ ገዛኸኝ በልሁ የተጠሪዎች ወኪል መሆኑ ግራ ቀኙ ያልተካካዱበትና የታመነ ፍሬ ጉዳይ ነው። አከራካሪው ነጥብ የተወካይ የውክልና ስልጣን እስከ ምን ድረስ ነው የሚለው ሲሆን የጉዳዩም ዋና ጭብጥ ወካይ የሆኑት ተጠሪዎች ተወካይ ለሆነው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤታቸውን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው የውክልና ስልጣን ሰጥተውታል ወይስ አልሰጡትም የሚለው ነው።

ይህንን ጭብጥ ለመወሰን በተጠሪዎቹ እና በአቶ ገዛኸኝ በልሁ መካከል የወካይና የተወካይ ግንኙነት ያለ መሆኑንና ወካዮች ለተወካዩ የሰጡትን የውክልና ስልጣን ይዘትና ወሰን ያሣያሉ ተብለው የቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ተዓማኒነትና ክብደት በዝርዝር መመርመርና መመዘን ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪዎች ቡልጋሪያ በሚገኘው በኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ለተወካዩ የተሰጡት የውክልና ማስረጃ በሁለቱም ማለትም በአመልካችም ሆነ በተጠሪዎች በኩል ክርክር ያልተነሣበት ተዓማኒነት ያለው ማስረጃ ነው። ይህ ማስረጃ በይዘቱ የተጠሪዎች ተወካይ የሆነው አቶ

ገዛኸኝ በልሁ የወካዮቹን ቤት እንዲያስተዳድር፣ እንዲሸጥ እንዲለውጥና ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚችል መሆኑን በግልጽ የያዘ መሆኑን አመልካችና ተጠሪዎቹ ተማምነዋል። ተዓማኒነቱም ሆነ ይዘቱ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የተስማሙበት ተጠሪዎች ቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል አረጋግጠው ለተወካያቸው አቶ ገዛኸኝ በልሁ የሰጡት የውክልና ማስረጃ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ስንመረምረው ሁለት መሠረታዊ ባሕሪያትና ውጤት ያለው ነው። የመጀመሪያው ተጠሪዎቹ ተወካዩ ቤታቸውን እንዲያስተዳድር ጠቅላላ የውክልና ስልጣን የሰጡት መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን የውክልና ማስረጃው የተወካይ አቶ ገዛኸኝ በልሁ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2204 ድንጋጌዎች የአስተዳደር ሥራ ተብለው የተዘረዘሩትን ተግባራት እንዲያከናውን ስልጣን የሚሰጥ ነው። በዚህ መሠረት በውክልና ማስረጃው ውስጥ በዝርዝር ባይገለጹም "ቤታችንን እንዲያስተዳድር" የሚለው ቃል፣ ተወካይ የወካዮቹን ቤት የመጠበቅ የማከራየት የቤት ኪራይ የመቀበል ደረሰኝ የመስጠትና ሌሎች አስተዳደራዊ ተግባራትን እንዲያከናውን የውክልና ስልጣን የሰጡት መሆኑን የሚያመለክት ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ይኸው የውክልና ማስረጃ የተጠሪዎች ተወካይ ቤቱን ለመሸጥ የመለወጥና ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ ልዩ የውክልና ስልጣን ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ነው። የውክልና ማስረጃው ለተወካዩ ልዩ የውክልና ስልጣን የሚሰጥ ከሆነ ሕጋዊ ውጤቱ በውክልና ማስረጃው ላይ ከተፃፉት ተግባራት በተጨማሪ፣ በውክልና ማስረጃው የተገለፀውን ጉዳዮችና እንደ ጉዳዩ ክብደትና እንደ ልምድ አሰራር በውክልና ማስረጃው የተገለጹትን ጉዳዮች ተከታታይና ተመሣሣይ የሆኑ አስፈላጊ ተግባራትን የመፈፀም ስልጣንን የሚያካትት መሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል። ስለዚህ የተጠሪዎች ተወካይ ቤቱን አስመልክቶ የተሰጠው ልዩ የውክልና ስልጣን፣ በውክልና ማስረጃው በግልጽ የተመለከቱትን ጉዳዮችና በውክልና ማስረጃው ባይገለፁም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንዑስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 1 የሚሸፈኑ ጉዳዮችን የመፈፀም ችሎታ እንደሚጨምር ለመረዳት ይቻላል።

በመሆኑም የተጠሪዎቹን ቤት የመሸጥ የመለወጥና ለሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ ስልጣን በውክልና ማስረጃው ያለው የተጠሪዎች ተወካይ የተጠሪዎቹን ቤት በመያዣነት የማስያዝ ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለው ጥያቄ ከላይ ከተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አንፃር መመዘን ያለበት ሲሆን የንብረቱን ባለቤትነት ለሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ ስልጣን ያለው ሰው ከዚህ መለስ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ችሎታ እንዳለውና በተለይም ንብረቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችል ስልጣን እና ችሎታ እንዳለው "ለራሱ ዕዳ ዋስትና እንዲሆን አንዱን የማይንቀሣቀሥ ንብረትን በዕዳ መያዣነት አድርጎ ለመስጠት የሚችለው የማይንቀሣቀሰውን ንብረት ለመሸጥ ችሎታ ያለው ሰው ነው" ከሚለው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3049 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል።

በመሆኑም ተጠሪዎች ለወኪላቸው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤቱን እንዲሸጥ እንዲለወጥና ለሶስተኛ ወገን እንዲያስተላልፍ በቡልጋሪያ የኢትዮጵያ አምባሲ በኩል የሰጡት የውክልና ስልጣን ተወካያቸው ቤቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው ስልጣንና ችሎታ የሚያጎናጽፈው መሆኑንን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3049 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋሉ። በመሆኑም ለአቶ ገዛኸኝ በልሁ ተጠሪዎች በመጀመሪያ የሰጡት የውክልና ስልጣን ቤቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችል የውክልና ስልጣን ነው። ስለሆነም ተጠሪዎች ተወካያችን አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤታችን እንዲሸጥ እንዲለወጥ እንጂ በመያዣነት እንዲያስይዝ የውክልና ስልጣን አልሰጠነውም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሠረት እና ድጋፍ የለውም።

ተጠሪዎች ለተወካያቸው የሰጡት የመጀመሪያው የውክልና ማስረጃ የተጠሪዎች ተወካይ ቤቱን በመያዣነት የማስያዝ ስልጣንና ችሎታ ያለው

መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ይህም የተጠሪዎች ተወካይ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሠረት ቤቱን በመያዣነት ያስያዘና ከአመልካች ገንዘብ የተበደረ ለመሆኑ ብቃት ያለው ማስረጃ ነው። ይህ ከሆነ የተጠሪዎች ተወካይ ቤቱን በመያዣነት የማስያዝና የመበደር ስልጣን ያለው መሆኑን ለማስረዳት ታስቦ ያቀረበው ሁለተኛው የውክልና ማስረጃ ተዓማኒነት የሌለውና በሀሰት የተዘጋጀ ሰነድ ሆኖ ቢገኝ እንኳን በክርክሩ ውጤት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም። ምክንያቱም የተጠሪዎች ተወካይ ሁለተኛው ሰነድ በአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በኩል ተረጋጋጦ ሣይሰጠው በፊት ተጠሪዎች በቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል፣ ለተወካያቸው የውክልና ስልጣን ከሰጡበት ቀን ጀምሮ የተጠሪዎቹ ተወካይ አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤቱን በመያዣነት የማስያዝ ስልጣንና የሕግ ችሎታ ያለው በመሆኑ ነው። አመልካች ከተጠሪዎቹ ተወካይ ጋር የመያዣ ውል የተዋዋለው ተጠሪዎቹ የተወካያቸውን ልዩ ውክልና ከመሻራቸው በፊት በመሆኑ በአመልካቾችና በተጠሪዎቹ ተወካይ መካከል የተፈፀመው የመያዣ ውል ሕጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት ያለው ነው።

ተጠሪዎች አመልካች ከተወካያቸው ጋር የመያዣ ውል የተዋዋለው የአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በቁጥር 10760/484 የመዘገበውን ሀሰተኛ ማስረጃ እና የውክልና ሰነድ መሠረት በማድረግ በመሆኑ የመያዣ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን የተከራከሩ ቢሆንም፣ ተጠሪዎች ከዚህ የውክልና ማስረጃ በፊት ለተወካያቸው በሰጡት የውክልና ማስረጃ መሠረት ተወካይ ቤቱን በመያዣነት የማስያዝ ስልጣን አለው። ስለሆነም የተጠሪዎቹ ተወካይ ቤቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው የውክልና ስልጣን እና ችሎታ ባለው ጊዜ ከአመልካች ጋር የመያዣ ውሉን የተዋዋለ መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካቹ ውሉን ሲፈጽም አንደኛውን ወይም ሁለተኛውን ሰነድ አይቶ ከተጠሪዎች ወኪል ጋር ውል የተወዋለ መሆን አለመሆኑ መሠረታዊ ጉዳይ አይደለም። መሠረታዊው ነጥብ የተጠሪዎች ተወካይ ከአመልካች ጋር ውል ሲዋዋል ቤቱን የመሸጥ የመለወጥ ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3049 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ቤቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው ስልጣንና ችሎታ ባለው ጊዜ ውስጥ ውሉን የተዋዋሉ መሆኑ ወይም አለመሆኑ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በአመልካችና በተጠሪዎቹ ተወካይ መካከል የተደረገው የመያዣ ውል ተጠሪዎች በቡልጋሪያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል አረጋግጠው በላኩለት የውክልና ማስረጃ መሠረት የተጠሪዎች ተወካይ የወካዮቹን ቤት ለመሸጥ፣ ለመለወጥ ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3049 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ቤቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው ስልጣንና ችሎታ በነበረው ጊዜ ሆኖ እያለ ይህንን መሠረታዊ ነጥብ ሣይመረምር እና ሣይመዝን ሁለተኛ የውክልና ማስረጃ ተዓማኒነት ያለው ማስረጃ ነው ወይስ በሀሰትና በማጭበርበር የተገኘ የሚለውን ነጥብ ብቻ ነጥሎ በማየት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪዎች ተወካይ መካከል የተደረገው የመያዣ ውል ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እንደዚሁም የይግባኝ ክርክሩን በመስማት የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ያፀናው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ከላይ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያበለት ውሣኔ ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 03926 ሰኔ 30 ቀን 1995 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፣ ይፃፍ፡፡
2. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 23780 መስከረም 26 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል ይፃፍ፡፡
3. አመልካች ከተጠሪዎች ወኪል ከአቶ ገዛኸኝ በልሁ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በፊት በነበረው ስያሜ በወረዳ 19 ቀበሌ 22 የሚገኘው ቁጥሩ 715/2 የሆነውን ቤት በመያዣነት በመያዝ ብር 200,000

/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ያበደረው ብድር በሕግ ፊት አስገዳጅነት ያለው ውል ነው ብለናል፡፡ አመልካቹ ይህንኑ አውቆ በአዋጅ ቁጥር 90/1997 በተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት መሠረት ተገቢውን ይፈጽም ዘንድ የፍርድ ግልባጭ ከመሸኛ ጋር ይሰጠው፡፡

4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በአዳሪ ተሰርቶ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 20890

ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ

አክሊሉ ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዓለምነሽ ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ከሥር 2ኛ ተከሣሽ ጋር ያደረገው የብድር ውል የተጭበረበረ የውክልና ሰነድን መሠረት በማድረግ ስለሆነ አመልካች የተጠሪን ቤት መያዣ በማድረግ የሰጠው ብድር ፈራሽ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ የአሁን ተጠሪ የሆኑት በአሁን አመልካችና በሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች በሆኑት ላይ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተከሣሽ የቡሌ ሆራ ወረዳ ፍትሕ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ ሆኖ ሲሠራ ለ2ኛ ተከሣሽ የግል ቤቴን ለባንክ መያዣ ሰጥቶ ገንዘብ እንዲበደር የሚል ውክልና እኔ ሳላውቀው በተጭበረበረ ሁኔታ በመስጠት እንዲሁም 2ኛ ተከሣሽም ይህንኑ እኔ ያልሰጠሁትን ውክልና ለ3ኛ ተከሣሽ ለአሁን አመልካች በማቅረብ ገንዘብ የተበደረ ስለሆነ የብድርና የመያዣ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙ አከራክሮና የውክልና ሰነዱ ላይ ያረፈው ፊርማ የተጠሪ ስለመሆኑ በፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ

መምሪያ በኩል ተመርምሮ ውጤቱ እንዲገለጽለት ትእዛዝ ሰጥቶ መምሪያው በትእዛዙ መሠረት ሰነዱን መርምሮ ፊርማው የተጠሪ አለመሆኑን በመግለጽ ለፍ/ቤቱ ሙያዊ አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ 1ኛ ተከሣሽ የሐሰት ማስረጃ በመስጠት 2ኛ ተከሣሽ ደግሞ የሐሰት ማመልከቻ በማቅረብ የከሣሽን (ተጠሪ) ቤት ለ3ኛ ተከሣሽ (ለአመልካች) በማስያዝ ገንዘብ መበደሩ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ተሰጥቷል በተባለው ውክልና ላይ ያረፈው ፊርማ የከሣሽ አለመሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ጥቅምት 16 ቀን 1998 ዓ.ም በካርታ ቁጥር 36/81 በተመዘገበው በ210 ካ/ሜትር ቦታ ላይ በተገነባው የከሣሽ ቤት የተደረገው የመያዣና የብድር ውል ፈራሽ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪን አከራክሮ በአመልካችና በሥር 2ኛ ተከሣሽ መካከል የተደረገውን ውል ለማፍረስ የሚችል በቂና ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይ? የሚለውን ጭብጥ መሥርቶ መዝገቡን በመመርመር አመልካች ከሥር 2ኛ ተከሣሽ ጋር ውሉን የተዋዋለው ተጠሪ ለሥር 2ኛ ተከሣሽ የሰጡትን ልዩ ውክልና መሠረት በማድረግ ነው፣ የውክልና ሥልጣኑ የተፈረመው ውል ለመዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ስለሆነና ይህ ሰነድ የጽ/ቤቱ ማህተምና የባለሥልጣን ፊርማ ያለው መሆኑን ብቻ አመልካች ማረጋገጥ ከሚጠበቅበት በስተቀር ማስረጃውን ለመጠራጠርም ሆነ ስለማስረጃው ተጨማሪ ማጣራት ለማድረግ ግዴታ የሌለበት በመሆኑ በከፍተኛው ፍ/ቤት የብድሩ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተቀባይነት የለውም በማለት ሽሯል፡፡

ተጠሪም በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የካቲት 10 ቀን 1990 ዓ.ም ተሰጠ የተባለው የውክልና ማስረጃ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ክፍል ተመርምሮ በውክልና ሰነዱ ላይ የይግባኝ ባይ ፊርማ ነው ተብሎ የሠፈረው የይግባኝ ባይ (የአሁን ተጠሪ) አለመሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ የውክልና ማስረጃው ይዘትም ሲታይ ስርዝ ድልዝ ያለበትና በግልጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመጠራጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሚስተዋሉበት ሆኖ እያለ አመልካች ቤቱን በመያዣ በማድረግ ብድር ከመሰጠቱ በፊት ተገቢውን ማጣራት ሲገባው አጠራጣሪ ሆኖ የሚታየውን የውክልና ማስረጃ በመቀበል የብድር ውል ወደ መፈረም የገባው ያለአግባብ ነው በማለት በሰፊው ተችቶ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር በአመልካችና በሥር 2ኛ ተከሣሽ መካከል የተደረገው የመያዣና የብድር ውል በሕግ አግባብነት ስላልተቋቋመ ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የውክልና ውሉ ፊርማው የተጭበረበረ መሆኑ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ በመረጋገጡና ውል አዋዋይም ተጠሪ እኔ ፊት ቀርቦ አልፈረመችም በማለቱ የመያዣና የብድር ውሉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲፈርስ መወሰኑ ለሰበር ችሎት ቀርቦ መጣራት የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ከአመልካች ጋር የተደረገው የብድርና የመያዣ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ከሕጉ አኳያ አግባብነቱ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት መያዣ በማድረግ የብድር ውል የተዋዋለው ተጠሪ ለሥር 2ኛ ተከሣሽ የሰጡትን ልዩ የውክልና ሥልጣን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህ የውክልና ሥልጣን በአግባቡ የተሰጠ አይደለም ወደሚል ድምዳሜ መድረስ የቻለው በአንድ በኩል የውክልና ሰነዱ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ተመርምሮ በሰነዱ ላይ ያረፈው ፊርማ የተጠሪ አይደለም ተብሎ ስለተረጋገጠና በሌላም በኩል ተጠሪ ወረዳው ፍትሕ ጉዳይ ጽ/ቤት ቀርቦ በውክልናው ሰነድ ላይ እንዳልፈረመች ውክልናውን አስፈርሚል በተባለው ሠራተኛም ጭምር የተረጋገጠ በመሆኑና የውክልና ሰነዱም ሲታይ ስርዝ ድልዝ ያለበትና በግልጽ ለመጠራጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎች

የሚስተውሉበት ስለሆነ ቤቱን መያዣ በማድረግ ብድር ከመሰጠቱ በፊት ተገቢውን ማጣራት ማድረግ ይጠበቅበት ነበር የሚል ትችት በማስፈር ነው፡፡

በመሠረቱ በባለሥልጣን ፊት የተደረጉ ጽሁፎች በግልጽ ከሚደረጉ ጽሁፎች የሚለዩ ሲሆን በግል የሚደረጉ ጽሁፎች (non-authentic deeds) ተዋዋዮች በግል ችሎታቸው የሚያዘጋጇቸው ውልን የሚመለከቱ ሰነዶች ናቸው፡፡ በባለሥልጣን ፊት የሚደረጉት ደግሞ ለዚሁ ሥራ ተብሎ የተሰየመ ባለሥልጣን ሰነዱን የተመለከታቸውና ምስክርነቱንም የሰጠባቸው ናቸው፡፡

ሰነዱ በባለሥልጣን ተረጋግጦ እስከቀረበ ድረስ በሰነዱ መሠረት ግዴታ የሚገባው ወገን ማረጋገጥ ያለበት ፊርማውንና ማንነቱን በመመልከት ሰነዱ በባለሥልጣን ፊት መረጋገጡን ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ የሰነዱን ትክክለኛነት ሊሆን አይችልም፡፡

እዚህ ላይ ተጠሪ በሰነዱ ላይ ያረፈው ፊርማ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ተመርምሮ የተጠሪ ፊርማ እንዳልሆነ ቢረጋገጥም ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ማጣራት የሚጠበቅበት ውሉ በባለሥልጣን ፊት መደረጉንና ባለሥልጣን ምስክርነቱን የሰጠበት ስለመሆኑ እንጂ የፊርማውን ትክክለኛነት ማጣራት የሚጠበቅበት አይሆንም፡፡ ይልቁንም በመርህ ደረጃ በባለሥልጣን ፊት በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ያሉትን ፊርማዎችና የሰነዶቹን ይዘት ማስተባበል እንደማይችል ይሄውም ውሉን የሚያዋውሉት ሰዎች የሕዝብ አደራ የተቀበሉና አደራውን ወደ ጎን በማድረግ ሐሰተኛ ሰነድ ያዘጋጁ ተብሎ ስለማይገመት ነው፡፡

ስለሆነም ሰነዱ ተመርምሮ ፊርማው የተጠሪ አለመሆኑ ቢረጋገጥም ይህ ሁኔታ ሰነዱን ባፈራረመው ባለሥልጣንና ከዚሁ ባለሥልጣን ጋር ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ፈጽሟል በሚባለው ግለሰብ ላይ የክስ ምክንያት ከሚሆን በስተቀር በባለሥልጣን የተረጋገጠውን የውክልና ሰነድ አመልካች ከቶውንም ሊጠራጠር ስለማይችል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በመሻር የመያዣና የብድር ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በአመልካችና በሥር 2ኛው ተከሣሽ መካከል የተደረገው የብድርና የመያዣ ውል በተጭበረበረ ሰነድ ላይ ተመሥርቶ የተደረገ ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ይህንኑ ውሣኔ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 23861

ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ሊቀስዩማን አስፋ በሻህውረድ ወኪል ጀነነው አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የሣህሊተ ምህረትና ክርስቶስ ሳምራ ደብር አስተዳደር አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል

ፍ ር ድ

ለዚህ አቤቱታ መንስኤ የሆነው የአመልካች ወኪል ጀነነው አሰፋ የተባለው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ መስርቶ ክሱ በመታየት ላይ እያለ ፍ/ቤቱ አቶ ጀነነው አሰፋ ክሱን የመሠረተው "ከሳሽ ጀነነው አሰፋ" ብሎ ፅፉል፣እሱ ወኪል እንጂ ከሳሽ ሊሆን አይችልም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረጉና በከፍተኛው ፍ/ቤትም አያስቀርብም በመባሉ ነው፡፡

ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበው አቤቱታ መሠረተ ሃሳብም አቶ ጀነነው አሰፋ የአመልካች ወኪል በመሆኑ ክሱን የመሠረተውም አመልካችን ወክሎ እንጂ በራሱ ስላልሆነ ክሱ ውድቅ የተደረገው በማይገባ ነው በማለት ነው፡፡

አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት ባለመቅረቡ ክርክሩ በሌለበት ታይቷል፡፡

የሥር ፍ/ቤት የአመልካቹ ወኪል "ከሳሽ ጀነነው አሰፋ" በማለቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33 መሠረት ክስ ማቅረብ አይቻልም ብሏል፡፡ ፍ/ቤቱ ውሣኔ በሠጠበት በግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም በውሣኔው ላይ የመዘገበው "ከሳሽ ጀነነው አሰፋ" ብሎ ነው፡፡ በነሐሴ 2 ቀን 1995 ዓ.ም በቀረበው የክስ ማመልከቻ ላይ ግን "ከሳሽ ጀነነው አሰፋ ሊቀስዩማን አሰፋ በሻህውረድ ወኪል" ተብሎ ተዕፏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውክልና ሥልጣን ያለው ሰው በዋናው ባለመብት ስም የክስ ወይም የአቤቱታ ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚችል የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 58 ይደነግጋል። አቶ ጀነነው አሰፋ የሊቀስዩማን አሰፋ በሻህውረድ ወኪል መሆኑ በፍ/ቤቱም የተገለፀ በመሆኑ አመልካቹን ወክሎ ክስ ማቅረብ ይችላል። ክስ የመሠረተውም በውክልናው መሠረት ለመሆኑ ለየካ ምድብ ፍትሃብሄር ችሎት የፃፈው የክስ ማመልከቻ ያረጋግጣል። በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ በመጥቀስ በጉዳዩ ላይ መብት ስለሌለው ሊከስ አይችልም ማለቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም። ምክንያቱም ክስ የመሠረተው በውክልናው እንጅ ባለመብት ነኝ በማለት ስላልሆነ ነው።

ፍ/ቤቱ ውሣኔ በሰጠበት ዕለት "ከሳሽ ጀነነው አሰፋ" ብሎ ይመዘገብ አንጂ የክስ ማመልከቻው ከሳሹ (ወኪሉ) የሊቀስዩማን አሰፋ በሻህውረድ ወኪል መሆኑን ያሣያል። ወኪሉ ወኪል መሆኑን እስካሣየና እስከገለፀ ድረስ በማመልከቻው ላይ የራሱን ወይም የወካዩን ስም አስቀድሞ መፃፉም ቢሆን ወኪልነቱን ለውጦ ባለመብት የሚያደርገው አይሆንም። በክስ ማመልከቻው ላይ ባለመብት ናቸው ተብለው ዋነኛ የጉዳዩ ባለቤት ተደርገው በዝርዝሩ የተጠቀሱት የአሁን አመልካች ሊቀስዩማን አስፋ በሻህውረድ ናቸው። ይህ እየታወቀ ወኪሉ በከሳሽነት ዘንግ ሆኖ ክስ መስርቷል በሚል ክሱ ውድቅ መደረጉ ስህተት ነው።

ወኪሉ በክስ ማመልከቻው ላይ የራሱን ስም ከወካዩ አስቀድሞ መፃፉን ፍ/ቤቱ ግልፅነት ይጎለዋል እንኳን ብሎ ቢገነዘብ ይህንኑ አስተካክሎ እንዲያቀርብ ማድረግ ሲችል ክሱን ያለመቀበሉ ተገቢ ባልሆነ አሠራር ሙግት እንዲራዘምና ባለጉዳይ እንዲጉላላ ማድረግ ነው። በመሆኑም የሚከተለው ተወስኗል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33 በመጥቀስ መዝጋቱም ሆነ ከፍተኛው ፍ/ቤትም ይግባኙን መሠረዙ ተገቢ ስላልሆነ ውሣኔዎቹን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ሽረናል።
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቶ ጀነነው አሰፋ የሊቀስዩማን አሰፋ በሻህውረድ ወኪል በመሆን የመሠረተውን ክስ ተቀብሎ ግራ ቀኙን በማከራከር ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥ ታዟል። ይፃፍ። መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 26399

ጎዳር 05 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አቶ ኃ/ማርያም ባዩ - ጠበቃ አቶ ማርቆስ ወ/ስንበት ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- 1ኛ/ አቶ ሳሙኤል ጎሳዬ

2ኛ/ ወ/ሪት ፀሐይ ጎሳዬ

3ኛ/ ወ/ት መንበረ ጎሳዬ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ጠበቃ አቶ ኃይሉ

4ኛ/ ወ/ት ወይንሸት ጎሳዬ አግዘው አልቀረቡም፡፡

5ኛ/ መቅደስ ጎሳዬ

1ኛው ተጠሪ በዚህ የሰበር ክርክር እንዲቀርብ በምትክ መጥሪያ ጥሪ ተደርጎለት በጥሪው መሠረት አልቀረበም፡፡ በሌላ ወገን አመልካችነት በተመሣሣይ ጥሪው ተደርጎ አለመቅረቡን በማረጋገጥ ጉዳዩ ይኸው ተጠሪ በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ በሰበር መ/ቁ. 22556 ትዕዛዝ የተሰጠበት ስለሆነ ይህም ጉዳይ እርሱ በሌለበት እንዲሰማ ተደርጓል፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በመ/ቁ 23363 ሐምሌ 03 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ነጥብ በመደርደር አመልካች ይኸው ውሣኔ እንዲሻር በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

ከተራ ቁጥር 2 እስከ 5 ድረስ የተዘረዘሩት ተጠሪዎች በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ ሆነው በ1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርበዋል፡፡ የክሱም ፍሬ ቃል ከሚች አባታችን ከአቶ ጎሳዬ ሩጋቶ በወረዳ 05 ቀበሌ 06 የቤት ቁጥር 586 የተመዘገበውንና በውርስ የተላለፈልንን የጋራ ሀብታችንን እንዲያስተዳድርልን እና እንዲሸጥ ውክልና ሰጥተነው የነበረ ቢሆንም ውክልናው ከተሻረ በኋላ መሻሩን እያወቀ ስለሸጠው የተደረገው የሽያጭ ውል ይፍረስልን የሚል ነው፡፡

ክስ የቀረበለት ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ ጥር 03 ቀን 1994 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሽያጭ ውል እንዲፈርስ አድርጎ ተዋዋዮቹ ወገኖች ሻጭና ገዢ ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህ ውሣኔ በተሰጠበት ጉዳይ የክርክር ተካፋይ መሆን ይችል የነበረ መሆኑን በማሳየት ውሣኔው ተነስቶና የእርሱ ክርክር ተሰምቶ እንደገና ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ በዚህም አቤቱታ ላይ፡-

- ከሣሾች ካቀረቡት ክስ እና ፍ/ቤቱ ከሰጠው ውሣኔ መረዳት እንደሚቻለው ውሉ ተሰርዞ ይረከቡት የተባለው የንግድ ድርጅት እና የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ቤት የባለሃብትነትና የይዞታ ባለመብት በመሆን ይዘው የሚጠቀሙበት አቤቱታ አቅራቢ ወይም ተቃዋሚ በመሆናቸው የተሰጠው ውሣኔ መብቴን ይነካል፡፡
- እንዲሁም ተዋዋይ ወገን ያልሆኑ 3ኛ ወገኖች ከተዋዋይ ወገኖች መካከል አንዱን ብቻ በመክሰስ ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉትን ውል ለማሰረዝ የሚያስችል የሕግ መሠረት የላቸውም፡፡
- የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ለማስደገፍ የጠቀሳቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2190/2/ እና 2193/1/ ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች አይደለም፡፡
- በቁጥር 2190/1/ እና /2/ የተደነገገው በመሠረቱ በቁጥር 2191 እና በቁጥር 2193/1/ ከተደነገጉት ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ከ3ኛ ወገን ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደረገውን ውል ማፍረሱን ወካይ በግልጽ ወይም በዝምታ ለ3ኛ ወገን ባስታወቀው ጊዜ ውሉ እንዲፈርስ እንደሚቆጠር የውሉ መፍረስም ስለሚያስከትለው ውጤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1808-1818 የተደነገገው ተፈፃሚ እንደሚሆን በቁጥር 2193/1/ ሥር የተመለከተው ከሚገልጽ በስተቀር ውሉ እንዲፈርስ ወካዩ በፍ/ቤት ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ ተዋዋዮችን የክስ ተከፋይ ሲያደርግ ወይም ከተዋዋዮቹ መካከል ተወካዩን ብቻ የክሱ ተከፋይ በማድረግ ከ3ኛ ወገን ጋር የተደረገውን ውል በማፍረስና በ3ኛ ወገን እጅ የሚገኘውን ንብረት ለማስለቀቅ እንደሚያስችል የሚደነግግ አይደለም፡፡

- ተወካይ የተባለው ተከሣሽ እና ተቃዋሚው የተዋዋሉበት ንብረት ከመጋቢት 09 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምሮ ተመዝግቦ የሚገኘው በዚሁ በሻጩ ስም በመሆኑ፣
- የውክልና ሰነዱም ከአባታቸው የውርስ ሀብት ውስጥ የሚደርሳቸውን ድርሻ እንዲያስተዳድርላቸው፣ እንዲሸጥና እንዲለውጥላቸው የሚያሳይ እንጂ ክርክር ያስነሳውን ንብረት በተለይ የሚጠቀስ ባለመሆኑ፣
- ተቃዋሚው በተከሣሹ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ድርጅት ገዝተውና የንግድ ሥራው የሚከናወንበትን ቤት በስማቸው በማስመዝገብ ድርጅቱን ለሌላ ለ3ኛ ወገን በሽያጭ አስተላልፈውት የሚገኝ በመሆኑ፣
- ከሳሾች የውክልና ሥልጣኑ ቀሪ ስለመሆኑ አግባብ ባለው ማስረጃ ያላረጋገጡ በመሆኑ የሚሉትን በመጥቀስ እንደዚሁም የሕግና የፍሬ ነገር ክርክሮች ታይተው እንደገና ሊወሰንልን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ተከሳሽም የተቃዋሚውን የመከራከሪያ ነጥብ እንደሚቀበሉት ገልፀው የተሰጠው ውሣኔ እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡

በከሣሾች በኩል የቀረበው ክርክር ደግሞ ሲታይ፡-

- ምንም እንኳ ከሳሾች በተቃዋሚውና በተከሳሹ መካከል የተደረገው ውል እንዲፈርስላቸው ዳኝነት የጠየቁ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2190/2/ በተደነገገው መሠረት ውሉን የማፍረስ መብታቸው በሕግ የተሰጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር በማገናዘብና በመተርጎም ውሣኔ የመስጠት ሥልጣኑን ተጠቅሞ ይህን ሕግ የተመለከተውን ጉዳይ ተቀብሎ ወሰነ እንጂ ክርክሩ የውል ይፍረስ አይፍረስ ጉዳይ አይደለም፡፡

ስለሆነም ከሳሾች ውሉን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2190/2/ መሠረት በማፍረሳቸው ተቃዋሚው የሚኖረው መብት ውሉ እንዳይፈርስ ወይም እንዳይፀና በማለት መከራከር ሳይሆን በውሉ መፍረስ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ካለ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2193፣ 2194 እና 2195 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ በመክፈል በተለየ ክስ ዳኝነት መጠየቅ ነው፡፡

የንግድ ሥራው የሚንቀሳቀስበትን ቤት በስማቸው ማስመዝገባቸውን መነሻ በማድረግ የተከራከሩ ቢሆንም የንግድ ሥራ የሚንቀሳቀስበት ቤት የንግድ ድርጅቱ አካል መሆኑ በንግድ ሕጉ የተደነገገ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

የሽያጭ ውል የተደረገበት የንግድ ድርጅት በተከሳሽ ማለትም በተወካዩ ስም የተመዘገበ ነው የተባለውን አስመልክቶ ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃ በቤት ቁጥር 586/ሀ/ የተጠቀሰ መሆኑን የሚያስረዳ እንጂ የአባታችን ንብረት የሆነውን ቁጥር 586 የሚጠቅስ አይደለም፡፡ ይህም ንብረት በቁጥር 586/ሀ/ እና/ለ/ ተብሎ ተከፍሎ አይታወቅም፡፡

ሟሚው ለእንደራሴው የሰጠውን ሥልጣን የሚሸርበት ሁኔታ የተለየ ሥርዓት እንደሚከተል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2183 የተመለከተ በመሆኑ የውክልና ሥልጣኑ ቀሪ ስለመሆኑ በተገቢው ማስረጃ አልተረጋገጠም የሚለው መከራከሪያ ሕጋዊ መሠረት የለውም የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 360/2/ መሠረት ጉዳዩን የመረመረው ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 01927 ሰኔ 12 ቀን 1995 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተቃዋሚው ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የንግድ መደብሩን አስመልክቶ የተደረገ ውልን ለማሰረዝ ብቻ ሳይሆን የማይንቀሳቀስ ንብረት የሆነውን ቤት ጭምር ለማስለቀቅ ነው በማለት ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ አስቀድሞ ውሣኔ የሰጠበት ጉዳይ የንግድ ድርጅትን የሚመለከት ነው፡፡ የንግድ ድርጅት ሲባል ደግሞ ድርጅቱ የሚገኝበትን ቤት የመከራየት መብትንም የሚያካትት በመሆኑ ክርክር በቤቱም ላይ ተደርጓል፤ ውሳኔም በቤቱ ላይ ተሰጥቷል ለማለት አያስችልም፡፡

በሌላ በኩል ተዋዋይ ወገን ያልሆኑ ሦስተኛ ወገኖች ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉትን ውል ለማሰረዝ ከተዋዋይ ወገኖች አንዱን ብቻ ነጥለው ለመክሰስ የሚያስችላቸው የሕግ መሠረት የላቸውም በሚል የቀረበውን ጉዳይ በሚመለከት ወካዮች ከሳሾች እንደራሴው ቀሪ በሆነው ሥልጣኑ የሠራውን ሥራ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090/2/ መሠረት በተሰጣቸው መብት መሠረት መሻራቸውን ፍ/ቤቱ ከማረጋገጥ አልፎ ውል እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ የሰጠው ውሣኔ የሌለ መሆኑን ካለማገናዘብ የቀረበ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም በሌላ አገላለጽ የድርጅቱ ሽያጭ ውል የፈረሰው በፍ/ቤቱ በተሰጠው ውሣኔ ሳይሆን ከሳሾች በሕግ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡

እንደራሴው ቀሪ በሆነው ሥልጣኑ የሠራውን ሥራ ወካዩ የመሻር ሥልጣን ያለው ለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2190/2/ የተደነገገ በመሆኑ ይህንን በማድረግ በቁጥር 2191 እንደተደነገገው የ3ኛ ወገን ጥያቄ የማቅረቡ ጉዳይ እንደቅድመ ሁኔታ የሚታይ አይደለም፡፡ የ3ኛ ወገኑም ግዴታ አይደለም ስለሆነም በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክርም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

እንደዚሁም የሽያጭ ውሉ ከመፈፀሙ በፊት የወክልና ሥልጣኑ የተሻረ መሆኑን የመስቀለኛ ጥያቄ በተቃዋሚዎች አማካኝነት በቀረበላቸው ምስክሮች በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑና ይህንንም ጉዳይ በምስክር ለማስረዳት የሚከለክል ሕግ ባለመኖሩ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም በሚል ያቀረቡት

ክርክር ዋጋ ያለው አይደለም፤ የሚሉትን ምክያቶች በመንተራስ ተቃዋሚው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2195 መሠረት ኪሣራ ከሚጠይቁ በቀር በዚህ መዝገብ የተሰጠውን ውሣኔ ለማሻር የሚያበቃ ምክንያት አልተገኘም በማለት ከዚህ በፊት የሰጡትን ውሣኔ አጽድቋል፡፡

ይግባኙን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ውሣኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው ፍሬ ቃል በሥር ፍ/ቤት በተሰጠው ውሣኔ ላይ ተፈጽሟል የተባለውን የሕግ ስህተት በዝርዝር የሚገልጽ ከመሆኑ በቀር በይዘቱ በሥር ፍ/ቤት ከተነሣው ክርክር የተለየ ባለመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም ለሰበር አቤቱታው በተጠሪ በኩል የተሰጠው መልስ ከዚህ በፊት ከተደረገው ክርክርም የተለየ አይደለም፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በአንድ ውል ተዋዋይ ያልሆኑት ሦስተኛ ወገኖች አንዱን ተዋዋይ ለብቻ ለይተው ለመክሰስ የሚያስችላቸው የሕግ መሠረት ሳይኖር በዚህ አኳኋን የቀረበው ክስ ሥነ-ሥርዓታዊ አልነበረም፣ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚለውን ነጥብ እንደ አንድ የሰበር ቅሬታ አድርገው አመልካች ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ እንደተባለው የአሁን አመልካች በዚህ በተነሣው ክርክር የሙግት ተካፋይ መሆን እየተገባው ተከፋይ ሳይሆን ጉዳዩ እንዲታይ መደረጉ በአንድ ሙግት የክርክር ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች እነማን ናቸው? የሚለውን አስመልክቶ ከሚደነግገው የሕግ ክፍል አንፃር ሲታይ የክሱ አቀራረብ የሕግ ግድፈት የተፈፀመበት መሆኑን ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መሆኑ እንደታወቀ በክርክር አመራር ረገድ የተፈፀመን ጉድለት ፍርድ ከተሰጠም በኋላ ቢሆን ፍርዱን በሰጠው ፍ/ቤት እንደገና ከሚታይላቸው ሥርዓቶች ይህ አንዱ መሆኑ ተረጋግጦ አመልካች የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነበት ጉዳይ የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካ መሆኑን መነሻ በማድረግ ውሣኔው እንዳልተሰጠ ተቆጥሮ አመልካች ባለበት ክርክሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ ከመሰማት መብትም ሆነ ከሚዛናዊ የዳኝነት አካሄድ አንፃር በአመልካች ላይ የተጓደለበት ሥርዓት ከላይ በተገለፀው ሁኔታ ተስተካክሎ አመልካች አለኝ የሚለውን የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ክርክር የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የቀረበው የሰበር ቅሬታ ነጥብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካቾችን የመከራከር መብት ከጠበቀ በኋላ ከዚህ በፊት ሰጥቶት የነበረውን ውሣኔ ለማጽናት በዋነኛነት መሠረት አድርጎ የያዘው ነጥብ ለተወካይ የተሰጠው የውክልና ሥልጣን ቀሪ ከሆነ በኋላ በወካዩ ስም ሕጋዊ ተግባር ፈጽሞ ከተገኘ እና ወካዩም ይህንኑ ተግባር ካላፀደቀው ወይም ካልተቀበለው ተወካዩ የፈፀመው ውል ፈራሽ መሆኑን ሕጉ ይደነግጋል፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች መኖራቸው ከተረጋገጠ ውልን የማፍረስ መብት ለወካዩ በሕግ የተሰጠው ሥልጣን በመሆኑ በዚህ አኳኋን የተፈፀመው ውል ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን አስመልክቶ ፍ/ቤቶች ዳኝነት የመስጠት መብት የላቸውም የሚለውን ነው፡፡

ይሁን እንጂ ስለዚሁ ጉዳይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች እርስ በርሳቸው አስተሳስረን ከተመለከትናቸው ከዚህ መሰል ትርጉም የሚያደርሱ ሆነው አይታዩም፡፡

ይኸውም እንደራሴው ቀሪ በሆነው ሥልጣን መሠረት በሌላ ሰው ስም ወይም ወካይ በነበረው ሰው ስም በሠራ ጊዜ በስሙ የተሠራበት ስዉ እንደፈቃድ በስሙ የተሠራውን ሥራ ለማጽደቅ፣ ለመቀበል ወይም ለመሻር መብት አለው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2191/2/ ከተደነገገ በኋላ በዚሁ በተሰጠው መብት ተጠቅሞ አንዱን መንገድ እንዲከተል ወይም እንዲመርጥ ከእንደራሴው ጋር የተዋዋሉት ሦስተኛ ወገኖች ለማስገደድ እንደሚችሉ እና aሚው ከሦስተኛ ወገኖች በቀረበለት ጥያቄ መሠረት ወዲያውኑ ካላስታወቃቸው እንደራሴው የሠራውን ሥራ እንዳልተቀበለው ሕጉ ግምት የወሰደ ለመሆኑ ተከታይ በሆነው ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡

እንግዲህ aሚው በግልጽም ይሁን በዝምታ እንደራሴው ሥልጣኑ ቀሪ ከሆነ በኋላ የሠራውን ሥራ ያልተቀበለው መሆኑ ከተረጋገጠ የዚሁ ያለመቀበል ውጤት በቁጥር 2193 ተደንግጓል፡፡ የዚህን ድንጋጌ ይዘት ስንመለከት aሚው ይህንኑ የእንደራሴውን ሥራ ካልተቀበለው ምን ጊዜም ይኸው ውል ፈራሽ ነው የሚል አይደለም፡፡ ይልቁንም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808 እስከ 1818 ድረስ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተከትሎ የውሉ መፍረስ ወይም መሰረዝ ሊወሰን የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም እነዚህኑ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በመከተል ውሉ ሊፈርስ የማይችልበት አጋጣሚ ያለ መሆኑን የሚያሳይና ነገር ግን ውሉ የሚፈርስ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ውሉ በመፍረሱ ምክንያት በቅን ልቦና ከእንደራሴው ጋር በተዋዋሉት 3ኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ካሣ የሚጠየቅበት መንገድ የሚያመቻች ድንጋጌ ነው፡፡

ይህ ሆኖ እያለ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የaሚው ፈቃድ ያልተሰጠበት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ሕጉ በእራሱ ውሉን ፈራሽ ያደርገዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ይህንኑ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን ከማወቅ አልፎ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ነጥብ ላይ ዳኝነት የመስጠት ሥልጣን የለውም በሚል የሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ አንፃር አሁን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች የንግድ ድርጅቱን ከ1ኛ ተጠሪ ከገዛ በኋላ መልሶ ለሌላ ሦስተኛ ወገን በሽያጭ ያስተላለፈውና በእጁ የማይገኝ የመሆኑ ጉዳይ በተጠሪዎችም የተካደ ፍሬ ነገር አይደለም፡፡ እንደራሴው የውክልና ሥልጣኑ ቀሪ ከሆነ በኋላ የፈፀመው ተግባር ነው ከተባለና ይህንኑ ተግባር aሚው አልተቀበለውም ከተባለ የዚሁ የአለመቀበል ውጤት ከላይ እንደተመለከተው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808-1818 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተከትሎ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ከላይ ከተረጋገጠው ፍሬ ቃል አንፃር አግባብነት ያለው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1816 ነው፡፡ ይኸውም ግራ ቀኙ በጉዳዩ ላይ በተከራከሩበት ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አከራካሪውን ንብረት ሌላ ሦስተኛ ወገን ከአመልካች ገዝቶ በእጅ አድርጎት ይገኛል፡፡ በዚህም ድንጋጌ መሠረት በቅን ልቦና ለሆነ ሦስተኛ ወገን የተሠራው ሥራ ውጤት ጠቃሚ ከሆነ ይህ ይፍርስ አይፈርስ የሚለው ውል እንደረጋ እንዲቀር ያደረጋል የሚል በመሆኑ የዚህ ክርክር አድማስ በአመልካችና በተጠሪዎች ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን የሦስተኛ ወገኖችንም ጥቅም የሚጠብቅ ነው፡፡ ስለሆነም የዚህን 3ኛ ወገን መብት ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑት የቀና ልቦና እና የተሠራው ሥራ ውጤት ጠቃሚነት መስፈርቶች የተሟሉ ሆነው እስከተገኙ ድረስ የ3ኛውን ወገን መብት ከመጠበቅ አንፃር ይህ አከራካሪ የሆነው ውል የሚፈርስ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም የተሸጠው ንብረት በሻጩ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ነው? ወይስ አይደለም? ሻጩ በእራሱ አቋም የሠራው ሥራ ነው? ወይስ ቀሪ በሆነው በእንደራሴነቱ ሥልጣን? ወደሚሉት አከራካሪ ነጥቦች ዘልቆ መመርመር ሳያስፈልግ ከላይ በተገለፀው የሕግ ትርጓሜ አመልካች እና 1ኛ ያደጉት ውል ሊፈርስ የሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01927 ሰኔ 12 ቀን 1995 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23363 ሐምሌ 03 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች አቶ ኃ/ማርያም ባዩ እና 1ኛ ተጠሪ ሳሙኤል ጎሳዬ ጥር 24 ቀን 1993 ዓ.ም. በወረዳ 05 ቀበሌ 06 በቤት ቁጥር 586/ሀ/ በተመዘገበው ቤት ላይ ያደረጉት ውል ሊፈርስ አይገባም፤ የረጋ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 32241

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ካሣች ተካልኝ - ጠበቃ ጌታቸው ሞላ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ኃ/ማርያም አበበ - ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ትዕግሥት ዱሬሣ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን ንብረት እንዲያስተዳድር በአመልካች አማካኝነት ጥቅምት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. የውክልና ስልጣን ተሰጥቶት የነበረ ሲሆን ከዚያ በኋላም 1ኛ ተጠሪ አመልካችን አግባብቶ ቃለመሐላ ትፈጽሚያለሽ በማለት ወደ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመውሰድ አመልካች አንብቤ ምንነቱን ያልተረዳሁትን ሰነድ ሚያዝያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. እንድፈርም አድርጎኛል፡፡ ከዚያም አመልካች ያለአግባብ ለ1ኛ ተጠሪ ውክልና መስጠቴን ስገነዘብ በማግስቱ ሚያዝያ 20 ቀን 1998 ዓ.ም. ውክልናውን ሽሬያለሁ፡፡ ሆኖም ሰነዶቹ 1ኛ ተጠሪ እጅ ስለነበሩ በአራዳ ክ/ከተማ የሚገኘውን የአመልካችን ጅምር ቤትና ኒሳን የቤት መኪና ለባለቤቱ ለ2ኛ ተጠሪ እጅግ አነስተኛ በሆነ ዋጋ ሸጧል፡፡

ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ ከኑሮ አጋሩ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው የቤትና የመኪና ሽያጭ ውል ከእራሱ ጋር እንደተደረገ ስለሚቆጠር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2188

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ በሁለቱ ተጠሪዎች መካከል ሚያዝያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. የተደረገው የቤትና የመኪና ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች ክስና ማስረጃም ለተጠሪዎች ደርሶ የየበኩላቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

በዚህም መሠረት 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን ንብረቶች ለ2ኛ ተጠሪ ያስተላለፉት ከአመልካች በተሰጣቸው የውክልና ሥልጠና መሠረትና ከሥልጣናቸውም ወሰን ሳያልፉ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2189/1/ መሠረት ከሣሽ እራሳቸው እንዳደረጉት ስለሚቆጠር በዚህ ክስ ውስጥ 1ኛ ተጠሪ የተካተትኩት ያለአግባብ ስለሆነ ከክሱ ልሰናበት ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ይህንኑ መቃወሚያ መርምሮ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ውል ይፍረስልኝ የሚል ሲሆን እንዲፈርስ በተጠየቀው ውል ተዋዋይ ወገኖች ደግሞ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ስለሆኑ 1ኛ ተጠሪ አመልካችን በመወከል ውሉን ያደረጉ በመሆኑ ውሉ በማናቸውም ምክንያት የሚፈርስም ሆነ የሚቀጥል ቢሆን ውጤት የሚኖረው በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ስለሆነ 1ኛ ተጠሪ በክሱ ውስጥ የተካተቱት ያለ አግባብ ነው በማለት ከክሱ አስወጥቷል፡፡

2ኛ ተጠሪም በበኩላቸው ባቀረቡት ክርክር አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ የሚያስችል ውክልና መስጠታቸውን በማረጋገጥ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤትና መኪና ከ1ኛ ተጠሪ መግዛታቸውን ውሉ በተደረገበት ሚያዝያ 19 ቀን 1998 በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የጋብቻ ግንኙነት እንዳልነበረና ጋብቻው የተፈጸመው ከዚያ በኋላ መሆኑን ገልጸው የሽያጩ ውል ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2188 ላይ የተመለከተውን በመጥቀስ 1ኛ ተጠሪ ከባለቤቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው ውል ከእራሱ ጋር እንዳደረገው ይቆጠራል በማለት ያነሱትን ክርክር በተመለከተ በሕጉ ላይ የተደነገገው ተወካዩ

ከእራሱ ጋር ውሉን በሚያደርግ ጊዜ ሲሆን አመልካች ይፍረስልኝ በማለት የሚጠይቁት ውል ግን 1ኛ ተጠሪ አመልካችን ሻጭ እራሱን ገዢ በማድረግ ሳይሆን 2ኛ ተጠሪን ገዢ በማድረግ ስለሆነ ከእራስ ጋር የተደረገ ውል የሚያስብል ሁኔታ የለም ካለ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ጋብቻ የፈጸሙት ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ስለመሆኑ የክብር መዝገብ ኮፒ በማስረጃነት የቀረበ በመሆኑ ውሉ በተደረገበት በሚያዚያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. ሁለቱ ሰዎች ባልና ሚስት አልነበሩም፡፡ ባልና ሚስት ነበሩ ቢባል እንኳ የየራሳቸው ሰውነት /Personality/ በጋብቻው ምክንያት እንደሚጠፋና እንደ አንድ ሰው እንደሚቆጠሩ በሕግ ያልተመለከተ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል ከገዛ እራሳቸው ጋር እንደተደረገ አይቆጠርም በማለት በውሣኔው ላይ አስፍሮ በመጨረሻም አመልካች በወኪላቸው አማካይነተ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጓቸው የቤትና የመኪና ሽያጭ ውሎች በአግባቡ በተሰጠ ሥልጣን የተደረጉ በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የቤትና የመኪና ሽያጭ ውሉ አይፈርስም ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ በዚሁ መሠረት ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የጉዳዩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ የዚህን ሰበር ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ 1ኛ ተጠሪ አመልካችን በመወከል ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የቤትና የመኪና ሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባልን? ወይንስ አይገባም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ሚያዝያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. በተሰጠ የውክልና ሥልጣን በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥንም ጨምሮ ለ1ኛ ተጠሪ የውክልና ስልጣን የሰጡ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

አወዛጋቢው ነጥብ ይህ የውክልና ስልጣን ከተሰጠ በኋላ 1ኛው ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤቶችና መኪና በሽያጭ ለ2ኛ ተጠሪ ማስተላለፋቸው ከውክልና ሕግ አኳያ አግባብነቱን በተመለከተ ነው፡፡ ይህንንም የክርክር ነጥብ የግራ ቀኙ ግንኙነት በተለይ ከሚገዛው የውክልና ሕግ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

1ኛ ተጠሪ ከላይ በተመለከተው ሚያዝያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. የውክልና ሥልጣኑን ከአመልካች ከተቀበሉ በኋላ የዚያኑ ዕለት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤትና መኪና በወካዩ በአመልካች ስም ለ2ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፉ ሲሆን አመልካች ይህንን ሽያጭ የሚቃወሙት በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ መካከል የባልና ሚስት ግንኙነት ስላለ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2188/1/ አኳያ ከራስ ጋር እንደተደረገ ስለሚቆጠር ፈራሽ ነው በማለት ነው፡፡

የተጠቀሰውም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2188/1/ ድንጋጌ እንደራሴው ከእራሱ ጋር ውሉን ተዋውሎ በተገኘ ጊዜ ሺሚው ይሄው ውል እንዲፈርስ መጠየቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

ነገር ግን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንደጠቀሰው የክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ ጋብቻቸውን የፈጸሙት ሽያጩ ከተደረገ በኋላ ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. በመሆኑ በሕግ ዓይን የሽያጭ ውል በተደረገ ጊዜ በሁለቱ መካከል ጋብቻ አለ ለማለት ስለማይቻል አመልካች የጠቀሱት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2188/1/ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም እንደራሴው የውክልና ሥልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞችን የማስወገድ ግዴታ እንዳለበት /Duty to avoid conflict of interest/ ከእንደራሴውም ጋር ውሉን የፈጸመው 3ኛ ወገን የሚያውቅ

ወይንም ማወቅ የሚገባው ሆኖ በተገኘ ጊዜ በሺሚው ጥያቄ መሠረት ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ብ/ቁ. 2187/1/ ላይ ተመልክቶ ይገኛል፡፡ ክርክሩም ከዚሁ ድንጋጌ አኳያ ሲታይ የሽያጭ ውሉ በተደረገ ጊዜ ተጠሪዎች ባልና ሚስት እንዳልነበሩ የተረጋገጠ ቢሆንም ሚያዝያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. ሽያጩ ተደርጎ ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ከ10 ቀን በኋላ ጋብቻቸውን መፈጸማቸው ሲታይ ሽያጩ በተደረገ ጊዜ በሽያጭ የሚተላለፈው ንብረት በቅርብ እርቀት የእራስ ንብረት ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ውሉ የተደረገ መሆኑን አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡ እንደራሴ ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን የሺሚውን ፍላጎትና ጥቅም ብቻ መሠረት አድርጎ ግዴታውን ሳይወጣ ከቀረና የእራሱን ፍላጎትና ጥቅም መሠረት ካደረገ የጥቅም ግጭት መኖሩ የማይቀር ይሆናል፡፡ 2ኛ ተጠሪም እንደራሴው 1ኛ ተጠሪ በሚያደረገው የሽያጭ ውል የጥቅም ግጭት መኖሩን እየተገነዘቡ ውሉን ማድረጋቸው የተረጋገጠ በመሆኑ በዚሁ ሁኔታ የተፈጸመው ውል ፈራሽ ነው እንዲባል አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ከተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2187/1/ አኳያ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ውሉ ሊፈርስ አይችልም በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69247 በሐምሌ 9 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57884 በሐምሌ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. 1ኛ ተጠሪ አመልካችን በመወከል በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/08 በካርታ ቁጥር 26651 ተመዝግቦ የሚገኘውን ጅምር ቤትና የሰ/ቁ. 2-52117 ኒሳን የቤት መኪና ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል የጥቅም ግጭት /Conflict of interest/ ያለበት መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሎች ዋስትና

የሰ/መ/ቁጥር 21355

ሐምሌ 3 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት ነገረፈጅ አቶ ፈቃደ ጉደታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ ጉዳዩ በይግባኝ ተጠሪን የሚያስቀርብ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን መሠረዙ ለጉዳዩ መነሻ የሆነውን ውል ህጋዊነት በተሳሳተ መንገድ በመተርጎሙ የተነሳ በመሆኑ የተፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት ይታረምልን በሚል ነው፡፡

የነገሩም መነሻ የሁኑ አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ ሲሆን ተጠሪ ተከሣሽ ነበር፡፡ አመልካች ያቀረበውን ክስ ተጠሪ ለመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ግዴታ ገብቷል፡፡ ከአመልካች ጋር ውል ያደረገው በሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ የነበረው በገባው ግዴታ መሠረት ውሉን ሳይፈጽም ያቋረጠ በመሆኑ ተጠሪ በመልካም ሥራ አፈፃም ረገድ የገባውን ግዴታ ሊፈጽም ይገባል የሚል ነው፡፡

ተጠሪም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ክርክር ከአመልካች ጋር ውል ያደረገው ድርጅት ውል ለማድረግ የሚያስችለው ህጋዊ ሰውነት የሌለው በመሆኑ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 መሠረት ፈራሽ ነው፡፡ ውሉ ፈራሽ ከሆነም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህንኑ ውል መሠረት በማድረግ የተገባው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ስምምነትም ሊፈርስ ይገባል ስለሆነም ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንድከፍል አልገደድም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ከተመለከተ በኋላ ተጠሪ ኢንሹራንስ ኩባንያው ከአመልካች ጋር ውል ያደረገው 1ኛ ተከሣሽ ባት ማስታወቂያ አገልግሎት ችሎታ የሌለው መሆኑን እያወቀ ዋስትና የሰጠ መሆኑን እንዲያስረዳ ታዞ ይህንን አልፈፀመም፤ ይህም 1ኛው ተከሣሽ ባት ማስታወቂያ አገልግሎት ህጋዊ ሰውነት ያልነበረው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ውል ለመዋዋል ችሎታ የሌለው ሰው የፈፀመው ውልም ፈራሽ ነው፡፡ ሥራ አፈፃፀም ዋስትናው ምክንያት የሆነው ውል ፈራሽ ከሆነም፤ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1923/1/ መሠረት ዋስትናውም ቀሪ ነው፣ ወይም ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ሰሚው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን የይግባኝ መዝገብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 337 መሠረት ዘግቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም

- የቀረበው ጉዳይ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1923/2/ አንፃር መታየት ሲገባው የሥር ፍ/ቤት በወሰነው በንዑስ ቁጥር 1 የተመለከተውን መሠረት ማድረጉ፣
- ተጠሪ ከ1ኛው ተከሣሽ ከባት የማስታወቂያ አገልግሎት ጋር የመልካም ሥራ አፈፃፀም ውል ሲያደርግ ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን ማረጋገጡን እያመለከተ ይህ ግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱ፣
- ውል ከተደረገ በኋላ ህጋዊ ሰውነቱን አጥቶ ከሆነ መቼ እንዳጣ ወይም ምዝገባው መቼ እንደተሰረዘ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የዋስትና ግዴታው ፈራሽ ነው በሚል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት እንዲታረም የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህም የሰበር አቤቱታ መነሻ ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ በይዘቱም በሥር ፍ/ቤት ያደረጉትን ክርክር የሚያጠናክር ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ ከነበረው ከባት ማስታወቂያ ድርጅት ጋር የመልካም ሥር አፈፃፀም ዋስትና ውል ያደረገ መሆኑን ክዶ አልተከራከረም፡፡ ህጋዊ ሰውነት ከሌለው ወገን ጋር የመልካም ሥር አፈፃፀም ዋስትና ውል ማድረጉን መነሻ በማድረግም ውሉ ህጋዊ ውጤት እንደይኖረውም ስለማድረጉም አልተገለፀም እንዲሁም ፍሬ ነገሮች የሚያመለክቱት ተጠሪ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ውል ከባት የማስታወቂያ አገልግሎት ጋር ባደረገበት ጊዜ ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን ያውቅ የነበረ መሆኑን ነው፤ እራሱ ላደረገው ውል ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን ተቀብሎ በመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትናው ውል ምክንያት ያለበትን ግዴታ እንዲፈጽም በተጠየቀ ጊዜ ተዋዋዩ ህጋዊ ሰውነት የሌለው ወገን ነው የሚለው ክርክር ወጥነት የሌለው እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፡፡

ምናልባትም ከአመልካች ጋር ውል የፈፀመው ባት የማስተወቂያ አገልግሎት ችሎታ የለውም፡፡ ችሎታ ከሌለው ሰው ጋር ውል አድርጌያለሁ፡፡ ውል ላደርግ የቻልኩትም ውሉ በተደረገበት ጊዜ ችሎታ /ህጋዊ ሰውነት/ የሌለው መሆኑን አላውቅም ነበረ በማለት ከተከራከረ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/258/1/ መሠረት ይህንኑ የማስረዳት ግዴታው በእራሱ በተጠሪ ላይ ሊሆን ይገባል፡፡

የሥር ፍ/ቤት በዚህ መሠረት ክርክሩን መምራት ሲገባው ባት የማስታወቂያ አገልግሎት ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን አመልካች ያስረዳ፤ እንዲሁም መልስ ሰጭ ከባት ማስታወቂያ አገልግሎት ጋር ውል ባደረገበት ጊዜ የማስታወቂያ አገልግሎት ድርጅቱ ህጋዊ ሰውነት የሌለው መሆኑን እያወቀ ነው ያደረገው የሚለውን አመልካች ያስረዳ በማለት የማስረዳት ሸክሙን ወደ አመልካች ማዞሩ ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በክርክሩም ሂደት ተጠሪ ከላይ የተመለከተውን ሁኔታ አላስረዳም፡፡

ስለሆነም ባት የማስታወቂያ አገልግሎት ከአመልካች ጋር ያደረገው ውል በህግ ፊት ሊፀና የማይችል ስለመሆኑ አልተረጋገጠም እንጂ ግዴታው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይፀና ነው እንኳ ቢባል ዋሱ አመልካች አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ በውል አለመጽናት ምክንያት የሆነው ጉድለት ሳያውቀው ያደረገው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ግዴታ መሆኑን ያላስረዳ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1923/2/ መሠረት የገባው ዋስትና የፀና ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሥር ፍ/ቤቶች በሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ የነበረው ባት ማስታወቂያ አገልግሎት ድርጅት ለመክሰስ የሚያስችለው ህጋዊ ሰውነት የለውም በሚል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ የሰጡት ዳኝነት የተሻረ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገብ አንቀሳቅሶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/በ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343 መሠረት መልሰናል፡፡
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በከ/ቁ. 10894 ሚያዚያ 22 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. ፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 32599 ሰኔ 06 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር ፋይል ቁጥር 25115

ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡-መንበረፀሐይ ታደሰ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ማሞ ጉበና አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለሰበር ሊቀርብ የቻለው የሰበር አመልካች (የሥር ከሣሽ) ግንቦት 28 ቀን 1998 ዓ.ም ዕፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩ የሥር አመጣጥ አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአሁኑ የሰበር ተጠሪና (የሥር 2ኛ ተከሣሽ) በሥር 1ኛ ተከሣሽ (ጉዳያቸው በሌሉበት የታየው) ላይ ያቀረቡት ክስ ከሥር 1ኛ ተከሣሽ ለነበሩት በጥቅምት 14 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ላንድሮቨር መኪና በብር 14,000 (አሥራ አራት ሺህ) ሸጠው ከዚህ ውስጥ ብር 10,000 (አስር ሺህ) ተቀብለው ቀሪውን ብር 4,000 (አራት ሺህ) በጊዜ ባለመክፈላቸው ብር 5000 (አምስት ሺህ) አድርገው ለመክፈል ተጨማሪ ውል ማድረጋቸውንና ያሁኑ ተጠሪም ባልተነጣጠለ ሃላፊነት ዋስ በመሆናቸው ዋናውን ገንዘብ ከነወለዱ ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፍሉ የሚል ሲሆን ፍርድ ቤቱም ክስና ክርክሩን ከመረመረ በኋላ የሥር 1ኛ ተከሣሽ በቀረበው ክስ መሠረት እንዲከፍሉ፣ያሁኑ ተጠሪ ግን ተራ ዋስ በመሆናቸው በርሣቸው ላይ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፣ ውሳኔው በፌ/ከ/ፍ/ቤትም በይግባኝ ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ማመልከቻው የቀረበው የተጠሪን ዋስትና አስመልክቶ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ሲሆን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ማመልከቻውን ከመረመረ በኋላ በተጠሪ ላይ ያልተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል ተጠሪን አስቀርቦ ለማከራከር ያዘዘ ቢሆንም ተጠሪ ለመቅረብ ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው ጉዳዩን በሌሉበት እንዲታይ አሣል፡፡

በዚህም መሠረት ፍርድ ቤቱ የሰበር ማመልከቻውን ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ለመረዳት እንደተቻለው ተጠሪ ተራ ዋስ መሆናቸውንና በውሉም ስምምነት ላይ የሥር 1ኛ ተከሣሽ ገንዘቡን ሳይከፍሉ ቢቀሩ ተጠሪ ሃላፊ ሆነው ገንዘቡን እንደሚከፍሉ መገለፁን አስፍሮ በተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 መሠረት ውድቅ በማድረግ ተጠሪን በነፃ አሰናብቷል፡፡ ይህ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 እንደተመለከተው የድንጋጌው ንኡስ ቁጥር /1/ ተራ ዋስ በገባው ዋስትና መሠረት ለመክፈል የሚገደደው ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለመወጣት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ለመረዳት ችሏል፡፡ በሌላም አነጋገር ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለመወጣት በቂ አቅም (ችሎታ) ያለው እስከሆነ ድረስ ገንዘብ ጠያቂው ዋናውን ባለዕዳ ትቶ ዋሱ ገንዘቡን አንዲከፍለው ለመጠየቅ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የተራ ዋስትና ዋናው መሠረት በቅድሚያ ዋናው ባለዕዳ ከገባው ውል አኳያ ግዴታውን እንዲወጣ በመቀጠልም ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለመወጣት ካልቻለ (አቅም ከሌለው) ተራው ዋስ ገንዘቡን እንዲከፍል ለመስቻል ታስቦ በሕጉ እንዲካተት የተደረገ በመሆኑ ነው፡፡ በተያዘውም ጉዳይ አመልካች ከሥር ጀምሮ ያቀረበው ክስ መስተናገድ የነበረበት ከዚህ ድንጋጌ መንፈስ አኳያ በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ለእዳው አከፋፈል ዋናው ባለዕዳ ላይ ሃላፊነትን በማስቀመጥና ዋናው ባለዕዳ ለመክፈል አቅም የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ተራው ዋስ (ተጠሪ) እዳውን እንዲሸከም በሚያስችል መልኩ መወሰን ሲኖርበት ተጠሪ እስከናካቴው ክሱ ካስከተለው ኪሣራና ወጪ ጋር በነፃ እንዲሰናበት መደረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

አንዲያውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1931 ላይ እንደተመለከተው ዋስ የሆነ ሰው በዋናው ባለዕዳ ላይ ክስ ለማቅረብ ገንዘብ ጠያቂው ለመወሰኑ ማስጠንቀቂያ ሲደርሰው ክሱ ለሚያስከትላቸው ወጪዎችም ጭምር ሃላፊ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በፍ/ብሕ/ቁ.1939 እዳው መክፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ ዋሱ ገንዘብ ለባለዕዳው መክፈል እንደሚችል ተገልፆአል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሱት ድንጋጌዎች ዋሱ ባንድ በኩል እዳውን በመክፈል ራሱን ነፃ እንዲያደርግና በሌላም በኩል ገንዘብ ጠያቂው ክስ መሥርቶ ከዋናው ገንዘብ በላይ ክሱ ለሚያስከትላቸው ወጪዎች እንዳይዳረግ ከወዲሁ የጥንቃቄ እርምጃዎችን እንዲወሰድ ለማድረግ እንዲያስችሉት መደንገጋቸው ሲታይ ተጠሪ ተራ ዋስ በመሆኑ ብቻ ስለእዳው አከፍፈል ከላይ እንደተመለከተው የቅደም ተከተል ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ከገባው የዋስትና ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከሃላፊነት ነፃ የሚሆንበት አንዳችም የሕግ መሠረት እንደሌለ ፍርድ ቤቱ ተገንዝቧል፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 ተራ ዋስን (ተጠሪን) ሃላፊ አያደርግም በማለት ድንጋጌውን በተሳሳተ አኳኋን በመተርጎም የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.43622 ግንቦት 19 ቀን 1997 ዓ.ም ፣እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት 41054 መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም ተጠሪን በተመለከተ የሰጡት ውሣኔ ተሽ[ል፡፡
2. ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ ኪሣራና ወጪ ጋር የሥር 1ኛ ተከሣሽ ለመክፈል ካልቻሉ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፣መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 26565

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ግሎባል ኢንሹራንስ /አ.ማ/ ካሣዬ ተ/አረጋይና ተፈራ ደምሴ ጠበቆች

ቀረቡ

ተጠሪ፡- ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በመድን ውል መሠረት ለደንበኛው የከፈለው ካሣ እንዲተካለት በፌ/ከ/ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ክስ መስርቶ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ጉዳት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለሆነ ተጠሪ ካሣ ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቶ በፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይሄው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ተጠሪ ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ደንበኛ የሆነው ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በጅቡቲ በኩል ከውጭ ወደ አዲስ አበባ ለሚያስመጣው 9,600 (ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ በጉዞ ላይ ለሚደርስበት ማንኛውም አደጋ ከሣሽ የመድን ሽፋን የሰጠ ሲሆን የመድን ሽፋን ከተሰጠው 9,600 (ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ ውስጥ 3,200 (ሦስት ሺህ ሁለት መቶ) ካርቶን የአንገፍ የተከሣሽ በሆነ የጭነት መኪና ተጭኖ ከጅቡቲ ወደ አ/አበባ በመጓዝ ላይ እንዳለ ከመኪናው በተነሣ እሣት ጭነቱ በሙሉ ወድሟል በኢንሹራንስ

ፖሊሲው ላይ 9,600 (ዘጠን ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ የመድን ዋስትና የተገባው ለብር 2,066,045.66 (ሁለት ሚሊየን ስልሳ ስድስት ሺህ አርባ አምስት ከስልሳ ስድስት) ሲሆን ለወደመው 3,200 (ሦስት ሺህ ሁለት መቶ) ካርቶን እርሾ ብር 688,681.87 (ስድስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሰማኒያ አንድ ከሰማኒያ ሰባት) ስለሚሆን በዚሁ መሠረት ከሣሽ በመድን ሰጭነቱ ይህንኑ ብር 688,681.87 ለደንበኛው ለፔትራም ኃ/የተ/የ/ማኅበር የከፈለ ሲሆን ተከሣሽ ይህንን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ ገንዘቡን ከወለድ ወጭና ኪሣራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች ክስና ማስረጃ ለተጠሪ ደርሶ በሰጠው መልስ ጉዳቱ መድረሱን ሣይክድ የተከሣሽ ንብረት የሆነው ከባድ የጭነት ተሽከርካሪ በጥቅምት 6 ቀን 1996 ዓ.ም የደረሰበት የእሣት ቃጠሎ አደጋ ድንገተኛ ደራሽና ያልታሰበ የመኪናው ሾፌር ቃጠሎውን ለመከላከል ባደረገው ሙከራ ሰውነቱ እንደተቃጠለና የተሽከርካሪውም ሞተር አዲስ መሆኑን ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት አደጋ እንዳላጋጠመው አደጋው ፍፁም ሊመልሱት የማይቻል በሹፌሩም ሆነ በአካባቢው ከነበሩ ሰዎች አቅም በላይ የሆነ ከፍተኛ ኃይል /force majeaure/ ስለሆነ ከንግድ ሕግ ቁጥር 591 አኳያ ተከሣሽ ኃላፊነት ስለማይኖርበት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተከሣሽ ሲያንገዳግደው በነበረ እቃ ላይ ጉዳት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው ወይንስ አይደለም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ አይደለም የሚባል ከሆነ ተከሣሽ በከሣሽ የተጠየቀውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት ወይ? የሚሉትን ጭብጦች መሰርቶ ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በጅቡቲ የሚገኘው ኤክስፐርት በአደጋው ቦታ በመሄድ ስለአደጋው አደራረስ ባቀረበው ሪፖርት መኪናው ከነጭነቱ ሙሉ በሙሉ በእሣት መቃጠሉን እሣቱ ሊነሣ የቻለው የኤክትሪክና የመካኒክ ሲስተሙ ድክመት ስለገጠመው በኤሌክትሪክ መስመሩ ላይ ከፍተኛ ኃይል ያለው ኬብል ሥራውን ስላቋረጠና ከብረት ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለተፋጨ የኤሌክትሪክ ጭረት ተነስቶ ኃይለኛ ንፋስ በመኖሩ ተቀጣጣይ የሆኑት አካሎች በእሣት ተያይዘው እሣቱም ተስፋፍቶ ወደ ተሣቢው ስለደረሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን ሌላው በማስረጃነት የቀረበውና አሽከርካሪው ለፖሊስ በሰጠው ቃል መኪናውን ከጅቡቲ ወደ አ/አበባ እያሽከረከረ ሲጓዝ በመኪናው ጋቢና የእሣት ሽታ እንደሸተተውና የተሣቢውን ጭነት ሲመለከት እንደተቃጠለና በወቅቱም ኃይለኛ ንፋስ ስለነበር መኪናውን አቁሞ ወርዶ እሣቱን ለማጥፋት እንደሞከረ በዚህ ጥረቱም እጁን እንደተቃጠለ የእሣቱን መንስኤ በተመለከተ በመኪናው ውስጥ የኮንታክት ችግር ያስነሣ እንደሚመስለው ነገር ግን ሞተሩ አዲስ መሆኑንና ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት አደጋ እንዳላጋጠመው በመግለጽ ቃሉን እንደሰጠ ያስገነዝባል፡፡

የእቃ አጓዥ በሚያጓጉዘው ዕቃ ላይ ለሚደርስ ጥፋት ኃላፊ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 590 ላይ የተደነገገ ቢሆንም በዚሁ ሕግ ቁጥር 591 ላይ ደግሞ በእቃው ላይ ጥፋት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መሆኑን አጓዡ ካስረዳ በኃላፊነት ተጠያቂ እንደማይሆን ተመልክቷል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ተከሣሽ ባቀረበው ማስረጃ ለክሱ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት አጓዡ ሊገምተውና ሊያስቀረው በማይችል አደጋ ምክንያት መሆኑን መገንዘብ የተቻለ ስለሆነ ተከሣሽ ለተከሰሰበት የንብረት ጉዳት ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሣሽም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ሠርሧል፡፡

ከዚህ በኋላም ከሣሽ (የአሁን አመልካች) የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት አቅረቦ ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በእርሾው ላይ የደረሰው ቃጠሎ ከአቅም በላይ ምክንያት ስለመሆኑ ከሕጉ አኳያ ተመርምሮ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተመለከተውም አመልካች ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሣያገኝ የቀረው ቃጠሎው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል ነው፡፡ በመሆኑም አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተመርምሮ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነው፡፡

አንድ አጓዥ በከፊል ወይም በሙሉ እቃዎች ወይም የተመዘገቡ ዝዞች ሲጠፉ ወይም ጉዳት ሲያገኛቸው ወይም የማስረከቢያው ጊዜ ቢዘገይ በኃላፊነት እንደሚጠየቅ የንግድ ሕግ ቁጥር 590 የሚያመለክት ሲሆን አጓዡ ከዚህ ኃላፊነት የሚድነው ደግሞ ንብረቱ ሊጠፋ፣ ጉዳት ሊደርስበት ወይም ሊዘገይ የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በዕቃው ውስጣዊ ጉድለት ምክንያት ወይም በላኪና በተቀባዩ ጥፋት ምክንያት ሲሆን እንደሆነ በዚሁ የንግድ ሕግ በቁጥር 591 ላይ ተመልክቷል፡፡

የግራ ቀኙ ግንኙነትን የሚገዛው ይሄው የንግድ ሕጉ ስለሆነ ክርክሩ መታየትም ያለበት ከዚሁ የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ነው፡፡ ይሁንና በንግድ ሕጉ ውስጥ "ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተመለከተ ነገር ስለሌለ ትርጉሙን ለማወቅ ከልዩ ሕጉ ወደ ጠቅላላ ሕጉ ማለትም ወደ ፍ/ብ/ሕጉ በተለይም ደግሞ ስለውሎች በጠቅላላው ስለሚመለከቱ ድንጋጌዎች ማምራት የግድ ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረትም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ለማለት የሚቻለው መቼ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1792 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህም ድንጋጌ ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ኃይል ደርሷል የሚባለው ባለዕዳው ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍፁም መሰናክል በሆነ አይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመ ጊዜ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለዕዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈፃፀም ከባድ የሆነ ወጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በባለዕዳው የሚደርስበት ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው ባለዕዳው በምንም መልኩ በቅድሚያ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይችል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለዕዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገምት ወይም ሊያስብና ጥንቃቄ ሊያደረግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገተኛ ደራሽ ነገር ቢሆን እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪውን ከኃላፊነት ነፃ ያደረጉት የክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት በቃጠሎ ሊወድም የቻለው ተሸከርካሪው የኤሌክትሪክና የመካኒክ ሲስተሙ ድክመት ስለገጠመው በኤሌክትሪክ መስመሩ ላይ ከፍተኛ ኃይል ያለው ኬብል ስራውን ስላቋረጠ ከብረት ጋር በመፋጨቱ ምክንያት በተነሣው እሣት ስለሆነና ይህም አጓጉ ሊገምተውና ሊያስቀረው የማይችል በመሆኑ ሁኔታው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የተፈጠረ ነው በማለት ነው፡፡ በጥቅሉ ሲታይ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆን አይችልም ያሉት ከተሸከርካሪው የቴክኒክ ችግር ጋር በተያያዘ ነው፡፡

ይሁንና የተሸከርካሪው ባለቤትና አጓዥ የሆነው ተጠሪ ተሸከርካሪውን በሚገዛበት ጊዜ የቴክኒክ ደንንነቱ አስተማማኝ መሆኑን ለሥራ ከሚሰማራበት አገርም ሆነ አካባቢ የአየር ንብረት ጋር ተስማሚ መሆኑን አጣርቶ ተሸከርካሪውን መግዛት እንዳለበት የሚታመን ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጎ ግዢውን ከፈፀመ በኋላም ቢሆን ለሥራ በተሰማራበት አካባቢ ምንም ዓይነት የቴክኒክ ችግር እንዳያጋጥመው ለጉዞ ከመሰማራቱ በፊትና በጉዞ በየጊዜው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ሣያደርግ ቀርቶ ጉዳት ቢደርስ እንደሕጉ አገላለጽ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከላይ

እንደተመለከተው በተሸከርካሪው ግዢ ወቅትም ሆነ ከግዢ በኋላ ተሸከርካሪው የቴክኒክ ችግር እንዳይደርስበት አስቀድሞ ሊገምተውና ሊከላከለው ሲገባ ይህንን የመከላከልና የጥንቃቄ ዕርምጃ አስቀድሞ ሣይወስድ በመቅረቱ በጉዞ ላይ ተሸከርካሪው በደረሰበት የቴክኒክ ብልሽት ምክንያት በተነሣው ቃጠሎ የመድን ሽፋን የተገባለት ንብረት መውደሙ የተረጋገጠ ስለሆነ ሁኔታው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ሊባል ስለማይችል የሥር ፍ/ቤቶች ለንብረቱ መቃጠል ምክንያት የሆነው አደጋው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ትርጉም የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 41594 በታህሳስ 26 ቀን 1998 ዓ.ም እንደዚሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23649 በግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በተጠሪ መኪና ተጭኖ ሲጓጓዝ የነበረውና አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው እርሾ በቃጠሎ ጉዳት ሊደርስበት የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ቃጠሎው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም ተብሎ የተወሰነ ስለሆነ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የካሣ ክፍያ ጥያቄውን አስመልክቶ የያዘውን ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አኳያ መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሎች

ስጦታ

የሰ/መ/ቁ. 17742

መጋቢት 02 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ አበበች ታደሰ - ከጠበቃ ኪሮስ ገብሩ ጋር ቀረቡ፡፡

2. ህፃን እርአየ ኪሮስ

3. ህፃን ወጊሐለይ ኪሮስ

4. ህፃን ይካአሉ ኪሮስ

ተጠሪ፡- 1. አስር አለቃ ሲሣይ ካብትህይመር
2. ወ/ሮ ይመኙሻል ፈቃዱ
3. ወ/ሮ አባይነሽ ደምሴ

} ጠበቃ ዮሴፍ እሸቱ ቀረበ፡፡

4. የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ /ተተኪ መሬት አስተዳደር ባለሥልጣን/ - አልቀረበም፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የማይንቀሳቀስ ንብረት ስጦታን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካቾች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በወረዳ 17 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘውን ስፋቱ 440 ካ.ሜ. ከሆነ የቦታ ይዞታ ላይ 220 ካ.ሜ. ቀንሰው በላዩ ላይ ካለው ቁጥር 272 ቤት ጋር በስጦታ ለ1ኛ አመልካች ባለቤትና ለቀሪዎቹ አመልካቾች አባት ለአቶ ኪሮስ አለማየሁ በስጦታ ከሰጡ በኋላ ይህንኑ ቤት ከራሣቸው ቤት ጋር ቀላቅለው ለ3ኛ ተጠሪ የሸጡ በመሆኑና 4ኛ ተጠሪም ይህንኑ የሽያጭ ውል የመዘገበው ስለሆነ የሽያጩ ውል እንዲፈርስ ቤቱን የሚመለከቱ አስረጂ ሰነዶችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለአመልካቾች እንዲያስረክቡ 4ኛ ተጠሪም የቤቱን የባለቤትነት ስም በአመልካቾች ስም እንዲያዛውር ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት ስጦታ በግልጽ ኑዛዜ መልክ መደረግ ሲገባው ክርክር የተነሣበት የስጦታ ውል ግን የግልጽ ኑዛዜ ፎርምን አያሟላም የቀበሌው ፍ/ሸንጎ የስጦታ ውሉን መዝግቧል የተባለ ቢሆንም የፍ/ሸንጎ ውልን ለመመዝገብ የስልጣን ስለሌለው የስጦታ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ሲሆን የፌ/ከ/ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ ላይ የቀረበለትን ይግባኝ ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ በአጭሩ የስጦታ ውሉ በፍ/ሸንጎ ቀርቦ ተረጋግጧል ከዚህ በኋላም ውሉ ለሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር ተልኮ ከቤቱ ማህደር ጋር ተያይዟል ውሉ በቀበሌ ፍ/ሸንጎ የተረጋገጠ በመሆኑ 2 ምስክሮች በቂ ናቸው፡፡ የስጦታ ውሉ ከተደረገ ከ10 ዓመት በኋላ እንዲፈርስ ሊጠየቅ አይችልም፤ የሚል ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የስጦታ ውሉ ውድቅ የተደረገበትን የሕግ አግባብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር አድርጓል፡፡ ተጠሪዎችም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት በዚህ ጉዳይ ሊታዩ የሚገባቸው ጭብጦች፤ 1/ ሕጋዊ ውጤት ያለው የስጦታ ውል አለ? የለም? 2/ አለ ከተባለ በስጦታ በተሰጠው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ሕጋዊ ውጤት አለው? የለውም? 3/ ሕጋዊ ውጤት የለውም የሚባል ቢሆን 4ኛ ተጠሪ የቤቱን የባለቤትነት ስም በአመልካቾች ስም እንዲያዛውር ሊገደድ ይችላል? አይችልም የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በክርክራቸው የስጦታ ውል እንዳላደረጉ እና ተደርጓል ቢባል እንኳን ውሉ ሕጋዊ ፎርማሊቲን ያላሟላ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

እኛም መዝገቡን እንደመረመርነው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሰኔ 16 ቀን 1984 የተፃፈ የስጦታ ውል አድርገው ይኸው የስጦታ ውል ለፍ/ሸንጎ ቀርቦ ከተረጋገጠ በኋላ ለስራና ከተማ ልማት ሚ/ር ተልኮ ከቤቱ ማኅደር ጋር መያያዙን ተረድተናል፡፡ በተለይ 4ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ በፍ/ሸንጎ የተረጋገጠ የስጦታ ውል ቀርቦለት ከቤቱ ማኅደር ጋር ማያያዙን መግለፁ ተጠሪዎቹ የስጦታ ውሉን ማድረጋቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍ/ቤትም ተጠሪዎች የስጦታ ውሉን ማድረጋቸውን አረጋግጦ ነገር ግን በሚች አርቲስት ኪሮስ አለማየሁና በተጠሪዎቹ መሃከል የተደረገው የስጦታ ውል ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት አያሟላም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎቹ የስጦታ ውሉን አላደረግንም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ከዚህ በመቀጠል ሊታይ የሚገባው ነጥብ ደግሞ ይህ የስጦታ ውል ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት አሟልቷል? አላሟላም? የሚለው ነው፡፡ አመልካቾች በስጦታ ተሰጥቶናል የሚሉት የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ስጦታ መደረግ ያለበት ደግሞ ግልጽ ኑዛዜ በሚደረግበት አይነት መሆኑን በፍ/ሕ/ቁጥር 2443 ሥር ተመልክቷል፡፡ ግልጽ ኑዛዜም መደረግ ያለበት በ4 ምስክሮች ፊት እንደሆነና ኑዛዜውም በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ ኑዛዜው ማመልከት እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁ. 881/2/ ሥር ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን ኑዛዜው በዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው ሰው ፊት የተደረገ ከሆነ 2 ምስክር በቂ እንደሚሆን በፍ/ሕ/ቁ. 882 ሥር ተመልክቷል፡፡

ከዚህ ተነስተን ወደተያዘው ጉዳይ ስናመራ የስጦታ ውሉ በ3 ምስክሮች ፊት የተደረገ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ የአመልካቾች ክርክር ስጦታው በፍ/ሸንጎ የተረጋገጠ በመሆኑ 3 ምስክሮች በቂ ናቸው የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ የፍ/ሸንጎ ውል ለማዋዋል ስልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ፍ/ሸንጎ ውል ለማዋዋል ስልጣን አለው? የለውም የሚለው መልስ ማግኘት የሚገባው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍ ሲ.ል እንደተገለፀው የስጦታ ውሉ የተደረገው ሰኔ 16 ቀን 1984 ዓ.ም. ነው፡፡ የስጦታ ውሉም ለፍ/ሽንጎ ቀርቦ ፀድቋል የተባለው ስጦታ የተደረገላቸው አርቲስት ኪሮስ አለማየሁ ከሞቱበት ከጥቅምት 3 ቀን 1986 ዓ.ም. በፊት በየካቲት 15 ቀን 1985 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ ወቅት ስራ ላይ የነበረው ማኅበራዊ ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 37/1982 ሲሆን ይህ አዋጅ በእያንዳንዱ ቀበሌ የማኅበራዊ ፍ/ቤቶች አቋቁሟል፡፡ እነዚህ ፍ/ቤቶችም በመደበኛ ፍ/ቤቶች መልክ የተደራጁ ሆነው በተሠጣቸው የሥልጣን ወሠን ውስጥ የዳኝነት ሥራ የሚያከናውኑ በሕግ የተቋቋሙ ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ በዳኛ ፊት ወይም በውል አዋዋይ ፊት መደረግ ስላለባቸው ውሎች የሚደነግጉት የፍ/ሕጉ ድንጋጌዎች ውሉ በዳኛ ፊት መደረግ እንዳለበት ከሚገልፀው በቀር በየትኛው ፍ/ቤት በሚገኝ ዳኛ ፊት መደረግ እንዳለበት የሚያስቀምጡት የተለየ መስፈርት የለም፡፡ ወይም በሌላ ሕግ ውል ለማዋዋል ስልጣን ስላለው ዳኛ ተለይቶ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት የሚያስችል ማንኛውም ዳኛ ውል ለማዋዋል ስልጣን አለው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በማኅበራዊ ፍ/ቤት የሚያስችሉ ዳኞች ውል ለማዋዋል የሚከለክላቸው ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የስጦታ ውልም በማኅበራዊ ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 882 መሠረት 2 ምስክሮች ብቻ መኖራቸው በቂ ስለሚሆን ስጦታ ውሉ ሕጋዊ ውጤት ያለው መሆኑን ተረድተናል፡፡

ከዚህም በላይ ምንም እንኳን የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገ የስጦታ ውል የግልጽ ኑዛዜ ፎርምን ከመከተሉ በተጨማሪ በፍ/ሕ/ቁ 1723 መሠረት ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ወይም በዳኛ ፊት ሊደረግ ይገባል አይገባም የሚለው ነጥብ አከራካሪነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በተያዘው ጉዳይ ግን ውሉ በግልጽ ኑዛዜ ፎርም መሠረት ከመደረጉ በተጨማሪ በዳኛ ፊትም ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የስጦታ ውሉ ሕጋዊ ውጤት ያለው ነው፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፤ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ክርክር ያስነሣው ቤት ለአርቲስት ኪሮስ አለማየሁ ሰኔ 16 ቀን 1984 ዓ.ም. በስጦታ

የሰጡ መሆኑ ከፍ ሲ.ል ተረጋግጧል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነት በሕግ ወይም በውል ሊተላለፍ እንደሚችል በፍ/ሕ/ቁ. 1184 የተመለከተ ሲሆን ንብረቱ በውል የተላለፈ ከሆነ ይኸው ውል በማይንቀሣቀስ ንብረት መዝገብ መመዝገብ እንደሚገባው የፍ/ሕ/ቁ 1185 ተጨማሪ መስፈርት ያስቀምጣል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ቤቱ በስጦታ ውል ለስራና ከተማ ልማት ሚ/ር ቀርቦ በቤቱ ማኅደር ውስጥ ተያይዞ መቀመጡ በፍ/ሕ/ቁ 1185 የተመለከተው መስፈርት መሟላቱን ያመለክታል:: ይህም በመሆኑ ክርክር የተነሣበትና በወረዳ 17 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘው ቁጥር 272 የሆነው ቤት ሀብትነት ለሚች ኪሮስ አለማየሁ ተላልፏል ማለት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው ግን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለ3ኛ ተጠሪ የሸጡት በወረዳ 17 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 367 የሆነውን የራሣቸውን ቤትና በስጦታ የሰጡትን ቁጥር 272 ጭምር ነው:: ቁጥር 272 የሆነው ቤት ሀብትነት ደግሞ ለሌላ ሰው ያስተላለፉ በመሆኑ ይህንኑ ቤት ለሌላ ሰው በሽያጭ ሊያስተላልፉ የሚችሉበት ሕጋዊ መብት አይኖራቸውም፡፡ አንድ ውል በሕግ ፊት የሚፀናው ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ ውሉ በሚቻል ነገር ላይ የተደረገና ሊፈፀም የሚችል ሲሆን ነው /የፍ/ሕ/ቁ. 1678/ለ/ እና 1715 ይመለከቷል/:: በሌላ ሰው ንብረት ላይ የተደረገ የሽያጭ ውል ቤቱን ለገዢው ማስረከብ የማይቻል በመሆኑ ውሉ ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለሆነም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ቁጥር 272 የሆነውን ቤት ሀብትነት ለአመልካቾች ካስተላለፉ በኋላ ይህንኑ ቤት በተመለከተ ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው አይችልም፡፡

የመጨረሻውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካቾች ሀብትነቱ የተላለፈላቸውን ቤት ስመ ንብረት 4ኛ ተጠሪ በስማቸው እንዲያዛውርላቸው ጠይቀዋል፡፡ ነገር ግን የማይንቀሰቀስ ንብረት ባለቤትነት ወደ ሌላ ማዛወር በአስተዳደር መ/ቤት የሚከናወን የአስተዳዳሪው ተግባር እንጂ በፍ/ቤት ውሣኔ የሚሰጥበት ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካቾች አስፈላጊውን ሰነዶች ሁሉ አቅርበው 4ኛ ተጠሪ ስም እንዲያዛውር ጠይቀው የከለከላቸው ለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በሆኑም አመልካቹ ስም ለማዛወር የሚያስችሉትን አስፈላጊ ማስረጃና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰነዶች በማቅረብ ስም እንዲያዛውርላቸው የሚመለከተውን የአስተዳደር መ/ቤት ከሚጠይቁ በቀር ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም። በመሆኑም 4ኛ ተጠሪን በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አላገኘውም።

ው ሣ ኔ

1/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 11201 ጥቅምት 9 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24848 ጥቅምት 26 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።

2/ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ሰኔ 16ቀን 1984 ዓ.ም. ያደረጉት ስጦታ ውል ፈራሽ ሊሆን አይገባም።

3/ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችና በ3ኛ ተጠሪ መሀከል በወረዳ 17 ቀበሌ 17 ክልል በሚገኘው በ220 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ ያረፈው ቁጥር 272 በሆነው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው።

4/ 4ኛ ተጠሪ በተራ ቁ. 3 ላይ የተገለፀውን ቤት ስመ ንብረት እንዲያዛውር የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት ስለሌለው ተቀባይነት የለውም።

5/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 23921

ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስፍን እቁበዮናስ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግሥቱ ቀረቡ።

ተጠሪ፡- 10 አለቃ ታደሰ ወርቁ ቀረበ።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል።

ፍ ር ድ

ለዚህ ፍርድ ቤት ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ለተጠሪው በጥር 1989 ዓ.ም. ያደረግሁት የስጦታ ውል በማታለል የተደረገና ተጠሪውም ሊጦረኝ ሲገባ ስለማይጦረኝ ውሉ ይፍረስልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ተቀባይነት በማጣቱና ይግባኝ አቅርባም ይግባኙ በመሠረዙ ነው።

የሥር ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ያደረገው በጉድለት ምክንያት ውል እንዲሠረዝ የሚቀርብ ጥያቄ በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል፤ በማለትና ተጠሪ አመልካችን የመጦር ግዴታ በውሉ አልተሰጠውም በማለት ነው።

እኛም የስጦታ ውሉ ሊፈርስ የሚገባው መሆን ያለመሆኑን አይፈርስም ከተባለስ ተጠሪው ስጦታ ሰጪዋን አመልካችን ሊጦር ይገባል ወይንስ አይገባም የሚሉትን ነጥቦች መርምረናል።

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለተ አመልካች ለተጠሪው የስጦታ ውል ያደረገችው ጥር 27 ቀን 1989 ዓ.ም ሲሆን ይህ የስጦታ ውል እንዲፈርስ ክስ የመሠረተችው ደግሞ በግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም ነው። የፍ/ሕ/ቁ 2441/1/ ሥጦታ እንዲቀነስ ወይም እንዲሻር የሚቀርብ ጥያቄ ሥጦታው ከተደረገበት ቀን አንስቶ እስከ ሁለት ዓመት ካልቀረበ በቀር ዋጋ የሌለው እንደሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደንግጓል። አመልካች የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ክስ የመሠረተችው የስጦታ ውሉ ከተደረገ ከ7 ዓመታት በኋላ ነው።

በመሆኑም የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ የቀረበውን ክስ የሥር ፍ/ቤቶች ያለመቀበላቸው የሚነቀፍ አይደለም።

በሌላ በኩል ግን ስጦታ ተቀባይ በስጦታ ውሉ ላይ በግልጽ ያልተመለከተ እንኳን ቢሆን ሰጪው በድንነት ላይ ከወደቀ ቀለብ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁጥር 2458/1/ ላይ ተደንግጓል። የሥር ፍ/ቤት ጥያቄውን ከዚህ ሕግ አኳያ መመርመር ሲገባው ተጠሪው አመልካችን ለመጦር የውል ግዴታ የላቸውም ማለቱ ከሕጉ የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

1. የስጦታ ውሉ አይፈርስም በማለት በሥር ፍ/ቤት የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል።
2. ተጠሪ ለአመልካች ቀለብ የመስጠት የውል ግዴታ የለበትም በሚል የተሰጠው የውሣኔ ክፍል ግን ተሽሯል። አመልካች በድንነት ላይ ወድቃ የምትገኝ ከሆነ ተጠሪ ቀለብ የመክፈል ግዴታ በሕጉ የተጣለበት በመሆኑ ይህንኑ በማስረጃ አጣርቶ ተገቢውን እንዲወስን የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት ታዟል። ይፃፍ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 32337

ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

አሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ፀሐይነሽ ይሕደጎ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ትሕሽ በርሔ

2. አቶ ደሣለኝ በርሔ

3. ወ/ሮ ኤልሣ በርሔ

4. ወ/ሪት ይርጋዓለም በርሔ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል፤ ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05409 ሚያዚያ 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመዝገብ ቁጥር 19936 ግንቦት 7 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንደዚሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 20118 ሐምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይሻርልን በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው። ፍሬ ጉዳዩም ተጠሪዎች በከፍተኛው ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርበው ተከሣሽዋ የአሁን አመልካች የአባታችን የአስር አለቃ በርሄ ምሩፅ የጋራ ንብረት የሆነ ቤት የያዘች ስለሆነና እኛ ደግሞ የአባታችን ወራሽ ስለሆን እንድታካፍለን ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል። አመልካች በበኩሏ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም ሟች ቤቱን ለእኔና ለሁለት ልጆቹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 5 ቀን 1989 በውልና ማስረጃ በተመዘገበ የቁም ኑዛዜ ሰጥቶናል የሚልና ሌላውን ቤት በተመለከተ እኔ ነኝ የሰራሁት የሚል መከራከሪያ አቅርባለች፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃና ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ በውልና ማስረጃ የፀደቀው የቁም ኑዛዜ ስጦታ ሰነድ በዳኛ ፊት ወይም በአዋዋይ አካል የተደረገ አይደለም፣ ስጦታው በግልጽ ኑዛዜ በሚደረግበት ፎርም መፈፀም ያለበት በመሆኑና በሰነዱ ላይ የፈረሙት ሶስት ምስክሮች ስለሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን አያሟላም፡፡ ስለዚህ ሕጋዊ ውጤት ስለሌለው ተከሣሽ የተከሣሾችን የውርስ ድርሻ ያካፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው፤ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት ስለሌለ ይግባኙ ፍሬ የለውም በማለት ሠርዞታል፡፡ አመልካች ይኸ ትእዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ጉዳዩን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርባ ሰበር ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን የሕግ ክርክር ከሰማ በኋላ ሚች ያደረገው ሰነድ የቁም ኑዛዜ ስጦታ የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን ድርሻዩን ለሁለቱ ልጆች ሰጥቻለው ካለ በኋላ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 937 መሠረት ስጦታው እንዲፀድቅላቸው የሚል በመሆኑ ሰነዱ ኑዛዜ ነው፡፡ ሆኖም ኑዛዜው ሌሎቹን ልጆች ከውርስ የሚነቅል በመሆኑና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 937 መሠረት ሚችን በዚህ አይነት መንገድ ተወላጆቹን ከውርስ መንቀል ስለማይችል፣ የሚችን ድርሻ ሌሎች ልጆችም እኩል የመካፈል መብት አላቸው በማለት በልዩነት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡ ከተሰየሙት አምስት ዳኞች ወስጥ ሁለቱ ስጦታ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 ግልጽ ኑዛዜ በሚደረግበት አሠራር መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ክርክር የተነሣበት ሰነድ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 882 መሠረት የተፈፀመ በመሆኑ ሕጋዊ የስጦታ ሰነድ ስለሆነ

ስጦታ ከተደረገላቸው ልጆች ውጭ ያሉት የሚች ልጆች ለመጠየቅ አይችሉም በማለት በልዩነት ሀሣባቸውን አስቀምጠዋል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ባቀረባቸው የሰበር አቤቱታ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የተለያዩ መሠረታዊ የሕግ ስህተቶችን ሰርተዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውልና ማስረጃ የተረጋገጠውንና ሶስት ምስክሮች የፈረሙበትን ሰነድ ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ያልተፈረመ ስለሆነ ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲሆን፤ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ኑዛዜው፣ ሌሎቹ ልጆችን ከውርስ የሚነቅል በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የለውም የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ስጦታ ሰጭው ገና በቁም ሣሉ ያደረጉት የቁም ስጦታ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት ኑዛዜ ነው ማለታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ሰነዱ "የኑዛዜ የቁም ስጦታ" የሚል በመሆኑ ሚች ያደረገው ኑዛዜ እንጅ የቁም ስጦታ ውል አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኑዛዜው በሕግ የተቀመጡ ፎርማሊቲዎችን ስለማያሟላ ውጤት የለውም መባሉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካችና ተጠሪዎች ያቀረቡት የሕግ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ እኛም የግራ ቀኙን የመከራከሪያ ነጥቦችና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ መርመረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም

1. ሚች ያደረጉት " የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች "ስለ ስጦታ ውል" የተደነገጉት ናቸው ወይስ ስለ ኑዛዜ የተደነገጉት ናቸው? የሚለው ነጥብ
2. ሚች ያደረጉት " የቁም ኑዛዜ ስጦታ" በሕግ የተደነገገውን ሥርዓትና ፎርም ያሟላ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብና
3. ሚች ያደረጉት የቁም ኑዛዜ ስጦታ ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚለው ነጥብ በዝርዝር ማየትና መወሰን አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

የመጀመሪያው ነጥብ በተመለከተ፣ ሟች በሕይወት እያሉ ከሚመለከተው የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በመቅረብ " የቁም ኑዛዜ ስጦታ" የሚል ሰነድ የካቲት 6 ቀን 1989 ዓ.ም አድርገዋል። ይኸ ሟች የተውት ሰነድ መሠረታዊ ባህሪ፣ አመልካችና ተጠሪ ለሚያደርጉት ክርክር መነሻ ነው። ስለሆነም ሟች ባደረጉት "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ላይ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ክፍል መለየት፤ የመጀመሪያውና ቀዳሚው ጉዳይ ነው። ከዚህ አንፃር ስለ ስጦታ ውል በፍትሃብሔር ሕግ ውስጥ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ስንመለከት የኢትዮጵያ ሕግ "የስጦታ ውል" ወይም "ስጦታ" በማለት እውቅና የሚሰጠው፣ ስጦታ ሰጭው ከመሞቱ በፊት የሕግ ውጤት እንዲኖራቸው አስቦ የሰጣቸው ስጦታዎችን ነው። የብዙ አገሮች ሕግጋት ለሁለት ዓይነት ስጦታዎች ዕውቅና እና ውጤት ይሰጣሉ። እነርሱም ማለት ሟች በሕይወት እያለ ተፈፃሚ ለሚሆን ስጦታ /Donation enter vivos/ እና ሟች ከሞተ በኋላ ተፈፃሚ የሚሆን ስጦታ" Donation Martis causa በማለት ይሰይሟቸዋል። የኢትዮጵያ ሕግ ስጦታ ነው በማለት እውቅና እና ጥበቃ ለሚሰጠው ለመጀመሪያው አይነት ስጦታ ማለትም ሟች ከመሞቱ በፊት ተፈፃሚ እንዲሆን እና ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው አስቦ ለሚሰጠው ስጦታ ነው። ሟች ከሞተ በኋላ ተፈፃሚ እንዲሆን አስቦ የሚያደርገው ስጦታ፣ የኢትዮጵያ ሕግ ስጦታ ነው ብሎ እውቅና እና ጥበቃ እንደማይሰጠውና እንደዚህ አይነት ስጦታ የውርስ ሕግ የኑዛዜ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዳላቸው "ሰጭው ሲሞት ይፈፀማሉ ተብለው በተወሰኑት ስጦታዎች ላይ ስለ ኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚዎች ይሆናሉ" በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2428 በግልጽ ይደነግጋል። ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የሟች " የቁም

ኑዛዜ ስጦታ" ያደረጉት ስጦታው በሕይወት እያሉ ተፈፃሚ እንደሆን አስበው ነው ወይስ ከሞቱ በኋላ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የሚለውን ነጥብ ስንመለከት በመጀመሪያ ሟች በግልጽ "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" የሚል ርዕስ የተጠቀሙ መሆኑና "ኑዛዜ" የሚለው ቃል ስጦታው ሟች ከሞተ በኋላ ተፈፃሚ የሚሆን እንደሆነ ስለሚያመለክት፤ በሁለተኛ ደረጃ ሟች በቁም ኑዛዜ ስጦታ ያደረጉበት ቤት የባልና የሚስት የጋራ ንብረት በመሆኑና ጋብቻው በፍች ወይም በሞት ምክንያት ካልተቋረጠ በስተቀር ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ባል ወይም ሚስት ከጋራ ንብረቷ አንዱን ክፍል ለይቶ መስጠት ስለማይችልና በሶስተኛ ደረጃ ሟች ባደረጉት የቁም ኑዛዜ ስጦታ ጽሑፍና የጠቀሱት የሕግ ድንጋጌ፣ ማለትም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 967 ሟች ከሞተ በኋላ ኑዛዜው ስለሚከፈትበት ቦታ የሚደነግግ በመሆኑ ሟች ያደረገው " የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ሟች ከሞተ በኋላ፤ ተፈፃሚ እንዲሆን አስቦ ያደረገው በመሆኑ፤ በጉዳዩ ተጠቃሽ የሚሆኑትና ተፈፃሚነት ያላቸው ስለኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ናቸው።

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ በማይንቀሣቀስ ንብረት ለመስጠት የሚደረግ የስጦታ ውል በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ አስራር አይነት ካልተደረገ ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 ይደነግጋል። ሟች ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው የውልና ማስረጃ ክፍል ሶስት፤ ምስክሮች ባሉበት "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" አድርጓል። ይኸም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን ፎርም የሚያሟላ በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሰነዱ የሕጉን ፎርም አያሟላም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው። ስለሆነም ሟች ያደረጉት "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገጉትን የሕግ ፎርማሊቲዎች የሚያሟላ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሶስተኛውን ነጥብ በተመለከተ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሟች ያደረገው የቁም ኑዛዜ ስጦታ የሌሎችን ወራሾች ከውርስ መንቀል ውጤት እንዳለው በመግለጽ ውድቅ አድርጎታል። ሟች ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆች ወይም ሌሎች ወራሾች ቢኖሩትና ከነዚያ መካከል ለአንደኛው የኑዛዜ ስጦታ ቢያደርግ፣ የሌሎቹን ወራሾች ከሟች ውርስ መነቀል አያስከትልም። ይህንንም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 913 የኑዛዜው ቃል የተናዛዡን ተቃራኒ ሀሣብ የሚገልጽ ካልሆነ በቀር ከውርስ ሀብት አንድ ድርሻ ወይም አንድ ንብረትን ሟቹ ለወራሾቹ መስጠቱ ተራ የሆነ የክፍያ ደንብ እንጅ እንደ ኑዛዜ ስጦታ ነው ተብሎ አይቆጠርም በማለት ይደነግጋል። በያዝነው ጉዳይም የሟችን ልዩ ሀሣብ የቀረበው ሰነድ የማያሣይ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ሟች የውርስ ንብረት ሲደለደል ቤቱ "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ላደረጉላቸው ልጆች እንዲደርሣቸው ያላቸውን ፍላጎት ከሚገልጽ በስተቀር ከሁለቱ ልጆች የተለየ የኑዛዜ ስጦታ መስጠቱን የሚያመለክት አይደለም። ስለሆነም ቤቱን ሙሉ በሙሉ "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ላደረጉላቸው ልጆች ለማስተላለፍ የሚችል ሰነድ አይደለም።

ከዚሁ ጋር መታየት ያለበት፤ ሟች ያደረጉት የቁም ስጦታ አይደለም እንጅ ቢሆንም እንኳን ተጠሪዎች የውርሱን ንብረት የመካፈል መብታቸው እንደማይገደብ ስለ ውርስ ንብረት ክፍያ በተለይም የጋራ ወራሾች ስለሚመልሷቸው ንብረቶች የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል። ስለሆነም በውጤት ደረጃ አመልካች የሟች ድርሻ ለተጠሪዎችና ለሌሎች ወራሶቹ የማካፈል ግዴታ አለበት በማለት የትግራይ ክልል በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሚቀየር አይደለም። ነገር ግን በሕግ አተረጓጎም ወቅት የተለያዩ ስህተቶችን የፈፀሙ ሆነው አግኝተነዋል። ስለሆነም በውሣኔው ተጠቃሽ ያደረጓቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ከላይ በተገለፀው መንገድ በማስተካከል በውጤት ደረጃ ግን የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ አጽንተናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ሟች ያደረጉት " የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ተራ የክፍያ ደንብ እንጅ የተጠሪዎች የውርሱን ንብረት የመካፈል መብት የማይገድብ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪዎች የውርሱን ንብረት የማካፈል ግዴታ አለበት ብለናል።
2. ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጓቸው የሕግ ድንጋጌዎች ትርጉምና ተፈፃሚት ተሻሽሎ ውሣኔያቸው በውጤት ደረጃ የፀና መሆኑን እንዲያውቁት ይፃፍ።

ይህ ውሣኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሎች ብድር

የሰ/መ/ቁ. 22891

ኅዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡-መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ማና ኃ/ሚካኤል - ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ገ/ማርያም ከበደው - አቶ ጋይም ወ/ጊዮርጊስ

2. አቶ ገ/የሱስ ገ/ፃድቃን - ጠበቃ ኃይሉ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው 1ኛ ተጠሪ በትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባልና ሚስት የሆኑት 2ኛ ተጠሪና አመልካች ብር 53,398 (ሃምሳ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና ስምንት) ተበድረውኝ ለብድሩ አከፋፈል ቼክ የሰጡኝ ቢሆንም ገንዘቡ ያልተከፈለኝ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ከወለድ ወጭና ኪሣራ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ በብድር ከከሳሽ የወሰዱት 2ኛ ተጠሪ አቶ ገ/ኢየሱስ ገ/ፃዲቅ ብቻ ከመሆናቸውም በላይ ብድሩም ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ ያልተረጋገጠ ስለሆነ 2ኛ ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለከሳሽ እንዲከፍሉ 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ ገንዘቡን ሊከፍሉ አይገባም በማለት ውሣኔ ሰጥቶ ከሳሽ በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ተከሳሾች ባልና ሚስት በመሆን ሕይወታቸውን በንግድ ሥራ የሚመሩ አንደመሆኑ መጠን በንግድ ሕ/ቁ. 19 መሠረት አንደኛው ተጋቢ የሚገባው ዕዳ ሌላውንም ተጋቢ የሚያስገድድ በመሆኑ የከፍተኛው ፍ/ቤት በዚሁ መሠረት ሚስትንም የዕዳው ተጠያቂ ማድረግ ሲገባው ተጠያቂነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለባትም በማለት ውሣኔ መስጠቱ ከሕጉ ጋር ያልተገናዘበ ነው በማለት ይህንኑ ውሣኔ ሽሮ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ሁለቱም ተከሳሾች እንዲከፍሉ በማለት የበኩሉን ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘትም የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ክሱ በቼክ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ሰበር ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት ትዕዛዝ በመስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም በአመልካች በኩል የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች፣ ቼክ ሳትሰጥ በቼክ ተከሳ በቼኩ ላይ የተመለከተውን ዕዳ በንግድ ሕግ ቁጥር 19 መሠረት የንግድ ዕዳ ወይም አግባብ ባለው የቤተሰብ ሕግ አመልካችን የሚመለከት ዕዳ መሆኑ በማስረጃ ሳይጣራ በአመልካች ላይ መፈረዱ ለሰበር ቀርቦ መጣራት እንዳለበት በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የክርክሩ ጭብጥ 1ኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡበትን ገንዘብ አመልካች ለመክፈል ይገደዳሉ የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ የሰበር አቤቱታው ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

በቅድሚያም 1ኛ ተጠሪ በትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን ያቀረቡት በቼክ ላይ ተመስርተው ወይንስ በብድር የሚለውን ነጥብ ማየት ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ በመሆኑ ይህንኑ ተመልክተናል፡፡

1ኛ ተጠሪ በክስ ማመልከቻቸው ላይ ገንዘቡ በምን ምክንያት ለከሳሾች እንደተሰጠ ዘርዝረው ያቀረቡ እንደመሆናቸው መጠን ክሱ በቼክ ላይ ተመስርቶ እንዳልቀረበና ቼኩን እንደተራ ማስረጃ በመቁጠር ክሱን እንደመሠረቱ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተከሳሾች በኩል የሥር 2ኛ ተከሳሽ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ገንዘቡን ከከሳሽ በብድር መውሰዳቸውን ያመኑ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ግን ብድሩን ክደዋል፡፡

የብድሩ ዕዳ በሥር 1ኛ ተከሣሽ በአሁኑ አመልካች ከተካደ ደግሞ የብድሩን መኖር በተመለከተ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት

ሸክሙ የሚወድቀው በከሳሽ ላይ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ረገድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2472 ላይ እንደተለከተው የሥር ከሳሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ አግባብነት ያለውን ማስረጃ አቅርበው ብድሩን በካዱት አመልካች ላይ የብድሩን መኖር አላስረዱም፡፡ ይህንንም መሠረት አድርጎ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለመክፈል አይገደዱም በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ዕዳው ይመለከታቸዋል በማለት ውሣኔ የሰጠው ከላይ እንደተመለከተው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ነጋዴዎች ስለሆኑ ከ1ኛው ተጋቢ የሚጠየቅ የንግድ እዳ በን/ሕ/ቁ.19 መሠረት ሌላውንም ተጋቢ ስለሚመለከተው ኃላፊ ናቸው በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ክሱ የቀረበው ከላይ እንደተመለከተው በቼክ ላይ ተመስርቶ ሳይሆን በብድር ላይ ተመስርቶ ከመሆኑም በላይ ብድር መኖሩም በማስረጃ የተረጋገጠው በ1ኛው ተጋቢ ላይ ብቻ ነው፡፡ በአንድኛው ተጋቢ ብቻ በብድር መወሰዱ የተረጋገጠው ገንዘብ ከንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ የተወሰደ ብድር ነው ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ ብድሩ ለጋራ ጥቅም መዋሉ ቢረጋገጥ እንኳን የዕዳው አከፋፈል ወደ ጋራ ንብረት ወይንም ወደ ሌላው ተጋቢ የግል ንብረት የሚሄደው በፍርድ አፈጻጸም ጊዜ እንጂ የብድር ውል ባልተዋዋለው ወገን ላይ ክስ ሊመሰረትም ሆነ ፍርድ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ሊከፍሉ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ ከንግድ ሕጉ ጋር የተጣጣመ ባለመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች በዚሁ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ሲያቀርቡ ክሱ የቀረበው ከላይ እንደተመለከተው በቼክ ላይ ተመስርቶ ሳይሆን በብድር ላይ ተመስርቶ ቼኩ በተራ ማስረጃነት የቀረበ በመሆኑ ጉዳዩን በሰበር ለማየት የሚችል ሆኖ ሳለ በቼክ ላይ ተመስርቶ የቀረበ ክስ በመሆኑ በሰበር ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበል መቅረቱ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይሁንና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክልሉም ሆነ የፌዴራሉ ሰበር ችሎት የተቋቋመበት ዓላማ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተትን ማረም በመሆኑ ጉዳዩን ወደ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መመለስ ሳያስፈልግ ቀጥሎ የተመለከተው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19141 በሐምሌ 21 ቀን 1997 ዓ.ም. እንደዚሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 11571 በ ጥቅምት 30 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረተዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በግንቦት 23 ቀን 1997 ዓ.ም. ይህን ጉዳይ አስመልክቶ አመልካች ክስ በቀረበበት ጉዳይ ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም በማለት የሰጠው ውሣኔ ከሕጉ ጋር የተገናዘበ ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31737

የካቲት 27 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድነን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ገብሩ ገ/መስቀል - ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- ቄስ ገ/መድነን ረዳ - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የብድር ውልን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ከአሁን ተጠሪ ጋራ በነበረን የንግድ ግንኙነት ተጠሪ ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ/ እንዳበድራቸው በስልክ ሲጠይቁኝ ፈቃደኛ በመሆን ገንዘቡን ልኬላቸው መቀሌ ከሚገኘው ወጋገን ባንክ ፈርመው ተቀብለዋል፣ በኋላ ተጠሪ ገንዘቡን እንዲመልሱልኝ በተደጋጋሚ ብጠይቃቸውም ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆኑም፣ ስለዚህ ገንዘቡን ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲሁም የጠበቃ አበል ከነወጪና ኪሣራው ይክፈሉኝ በማለት ተጠሪ ላይ በመሠረቱት ክስ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ የተባለውን ገንዘብ መቀበሌን አልክድም፣ ነገር ግን ገንዘቡን ከአመልካች ላይ የወሰድኩት ብድር ጠይቄ ሳይሆን አመልካች ከአሁን በፊት ከእኔ በብድር የወሰዱትን ገንዘብ ለመመለስ ልከውልኝ ነው፣ የገንዘብ መላኪያ ወረቀቱም በምንም አይነት የብድር ማስረጃ ሊሆን አይችልም፣ ከብር 500 /አምስት መቶ/ በላይ በሆነ ገንዘብ የተደረገ የብድር ውል በጽሁፍ ካልተደገፈ ዋጋ አይኖረውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በመጀመሪያ የማስረዳት ሸክሙ የሚወድቀው በማን ላይ ነው? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ግራ ቀኙ ግንኙነታቸው በንግድ ላይ የተመሠረተ መሆኑን አልተካካዱም፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን ተጠሪ ገንዘቡን መቀበላቸውን አልካዱም፣ አመልካች ተጠሪ ገንዘቡን የላኩት ቀደም ሲል ለነበረባቸው ዕዳ መክፈያ መሆኑን የማስረዳት የመጀመሪያ ግዴታ የሚወድቀው ተጠሪ ላይ ነው፣ ይሁን እንጂ ተጠሪ ይህንኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የማስረጃ ዝርዝር ከመልሳቸው ጋር አላቀረቡም፣ በማስረጃ ያልተደገፈ የፍሬ ነገር ክርክር ደግሞ ዋጋ የሚሰጠው አይሆንም ካለ በኋላ ተጠሪ ገንዘቡን ከአመልካች መቀበላቸውን አምነው አመልካች ገንዘቡን የሰጧቸው በፊት ለነበረ ዕዳ መክፈያ መሆኑን አስካላረጋገጡ ድረስ ባለዕዳ ናቸው፣ በመሆኑም ተጠሪ ክሱ የቀረበበትን ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ/ ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ የባንክ ወለድ ጋር ለከሣሽ ይክፈሉ በማለት ወስነ፡፡

ተጠሪ ይህንን ውሣኔ በመቃወም ለትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ባለማግኘቱ አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ ሰበር ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር አዳምጦ በማስረጃነት የቀረበው የሐዋላ ወረቀት /ደረሰኝ/ በግራ ቀኙ መካከል የብድር ውል መኖሩን የሚያረጋጋጥ ማስረጃ አይደለም የሐዋላ ወረቀት ገንዘብ ከአንድ ባንክ ወደ ሌላው የተላከ መሆኑን ከማረጋገጥ ውጪ በሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ካልተደገፈ በቀር ገንዘቡ የተላከው በብድር መሆኑን አያስረዳም፣ ተጠሪ ገንዘቡ የተላከልኝ አመልካች ለነበረባቸው ዕዳ መክፈያ እንዲሆን ነው በማለት መመለሳቸውም ቢሆን ብድሩን አምነዋል የሚያስብላቸው አይደለም፣ በመሆኑም አመልካች ገንዘቡን የላኩት በብድር መሆኑን ተጠሪ አላመኑም ክህደት ካለ ደግሞ ብድሩ መኖሩን የማረጋገጥ /የማስረዳት/ ኃላፊነቱ የአሁን አመልካች ነው፣ ስለዚህ የብድር ውል መኖሩ በመልካች ሳይረጋገጥ ወይም በተጠሪ ሳይታመን የቀድሞው ብድር መኖሩን ተጠሪ የማስረዳት ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ ተጠሪ በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍሉ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ አመልካች ለተጠሪ ልኬላቸው የነበረውን ገንዘብ

መቀበላቸውን ተጠሪ ራሳቸው አምነውና በማስረጃም ተረጋግጦ ገንዘቡን የተቀበልኩት ለዕዳ መክፈያ ሆኖ ነው የሚል መልስ በተጠሪ ስለተገለፀ ብቻ ቀድሞውኑ አመልካች የተጠሪ ተበዳሪ መሆኔን የማስረዳት ሸክም እያለባቸው የማስረዳት ሸክሙ የአመልካች ነው አመልካች ገንዘቡን በብድር መላካቸውን አላስረዱም ተብሎ በክልሉ ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ችሎቱም የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎችና የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር አመልካች ለተጠሪ ገንዘብ ልከውላቸዋል እየተባለ በበታች ፍ/ቤት አመልካች ይህንን ገንዘብ በብድር መልክ ስለመስጠታቸው የብድር ውል አቅርበው አላስረዱም በሚል ተጠሪ የተከሰሱበትን ገንዘብ አይከፍሉም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆኑና አለመሆኑ ሊጣራ የሚገባ ነጥብ ሆኖ ስላገኘነው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ከስር ጀምረው የሚከራከሩት ገንዘቡን ለተጠሪ የላኩት ተጠሪ እንዳበድራቸው በስልክ ባቀረቡልኝ ጥያቄ መሠረት ስለሆነ ገንዘቡን ይመልሱልኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ በበኩላቸው አመልካች ገንዘቡን ሊልኩልኝ የቻሉት ቀደም ሲል ያበደርኳቸውን ገንዘብ ለመመለስ እንጂ እንዲያበድሩኝ ጠይቄ አይደለም በማለት መከራከራቸውን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ተጠሪ በአመልካች የተላከላቸውን ገንዘብ መቀበላቸውን አልካዱም፣ ገንዘቡን መቀበላቸው በማስረጃም ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ገንዘቡን የተቀበልኩት አመልካች ቀደም ሲል የነበረባቸውን ዕዳ ለመክፈል ልከውልኝ ነው የሚል ክርክር ተጠሪ ከጅምሩ ጀምሮ ማቅረባቸውን ተረድተናል፡፡ በመሠረቱ ተከራካሪ ወገኖች በመከራከሪያነት የሚያቀርቧቸውን ፍሬ ነገሮች ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም በአዎንታዊ መልኩ የተከራከረ ወገን የክርክሩን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም ይወድቅበታል፡፡ የአሁን ተጠሪ የክርክሩ መነሻ የሆነውን ገንዘብ ከመቀበሌ በፊት ለአመልካች ገንዘብ አበድሬያለሁ ቢሉም ገንዘቡ ከብር 500 (አምስት መቶ) የሚበልጥ እንደመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2472/1/ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተደነገጉትና የብድርን መኖር ማስረዳት ከሚቻልባቸው ሶስት መንገዶች በአንዱም ቢሆን የአመልካች አበዳሪ መሆናቸውን አላስረዱም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለመከራከሪያ ያቀረቡትን ይህንን ፍሬ ነገር የማስረዳት ኃላፊነታቸውን አልተወጡም፡፡ በአንፃሩ ግን አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ በብድር መስጠታቸውን ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የሕግ አንቀጽ የብድር ውልን በጽሁፍ ማስረዳት እንደሚቻል በተደነገገው መሠረት ገንዘቡን የላኩበትን የሐዋላ ወረቀት በማቅረብ አረጋግጠው ያስረዱ ስለሆነ በክሳቸው ላይ ያቀረቡትን ፍሬ ነገር የማስረዳት ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል፡፡ ስለዚህ አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ ማበደራቸውን ባስረዱበትና ተጠሪ ደግሞ እንደአባባላቸው ገንዘቡ የተላከላቸው አስቀድሞ ለነበረ ዕዳ መክፈያ መሆኑን ባላረጋገጡበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ ገንዘቡን ለአመልካች ለመመለስ አይገደዱም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ክርክር የተካሄደበትን ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ በድምጽ ብልጫ ተወስኗል፡፡
2. የትግራይ ብ/ክ/መ/ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 18404 በሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
3. የክልሉ የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03390 በ5/4/99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18102 በ12/4/99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
4. የዞኑ ከፍ/ፍ/ቤት በውሣኔው መሠረት ያስፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የልዩነት ሃሣብ

ጉዳዩ ሲጀመር አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት በብድር የወሰደውን ብር 50 ሺህ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2472/1/ መሠረት በብድር ተሰጥቷል የሚባለው ገንዘብ ከብር 500 /አምስት መቶ/ በላይ ከሆነ ይህንኑ ማስረዳት የሚቻለው በጽሁፍ በፍ/ቤት በተደረገ የዕምነት ቃል ወይንም በመሐላ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

ከሳሽ በአስረጂነት ያቀረቡት ሰነድ በባንክ አማካይነት በሐዋላ ከአዲስ አበባ ወደ መቀሌ ለተከሳሽ ብር 50 ሺህ መላካቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፡፡ የሐዋላ ሰነዱ በመካከላቸው የብድር ግንኙነት መኖሩን የማያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ ተከሣሽም በባንክ በኩል የተላከውን ገንዘብ መቀበላቸውን ቢያምኑም ነገር ግን ገንዘቡን ከተከሳሽ የተቀባበሉት ከሳሽ እንደሚሉት ከእራሳቸው በመበደራቸው ምክንያት ሳይሆን ቀደም ሲል ለከሳሽ አበድረውት ለነበረ ገንዘብ በመክፈያነት እንደተቀበሉ ገልጸው ብድሩን ክደው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የብድር ውል አለ በማለት ክስ ያቀረቡት ከሣሽ ሕጉ እንደሚጠይቀው የብድር ውል ስለመኖሩ አለማስረዳታቸውን ነው፡፡

በሌላ በኩልም በአብላጫው ድምጽ ውሣኔ ላይ ተከሣሽ ገንዘቡን መቀበላቸውን እስካመኑ ድረስ በሌላ ግንኙነት የተቀበሉት ገንዘብ ስለመሆኑ ከመከራከር በስተቀር ይህንኑ ግንኙነት በማስረጃ ያላረጋገጡ ስለሆነ ክሱ የቀረበበትን ገንዘብ ሊከፍሉ ይገባል የተባለውን በተመለከተ የብድር ውል አለ በማለት ከሳሽ ክስ እስካቀረቡ ድረስ የብድር ውል አለ የለም የሚለው በጭብጥ ተይዞ የሚፈታ ፍሬ ነገር እስከሆነ ድረስ ከማስረጃ አቀራረብ አኳያ ይህንኑ በጭብጥ ተይዞ የሚፈታውን ፍሬ ነገር ማስረዳት የሚጠበቅበት ከሣሽ መሆን እንደሚገባው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ውልን አስመልክቶ ሰለ ማስረጃ አቀራረብና አቀባበል በሚደነግገው የፍትሐብሔር ሕጉ ክፍል ሥር አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ወገን ግዴታው ስለመኖሩ ማስረዳት ይጠበቅበታል ተብሎ በቁጥር 2000/1/ ላይ የተደነገገውም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት በአብላጫ ድምጽ የተሰጠው ውሣኔ ከማስረጃ አቀራረብ መርህ አኳያ ተገቢነት ያለው ባለመሆኑ የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ ሊጸና ይገባል በማለት ስሜ በተራ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰው ዳኛ ከሥራ ባልደረቦቼ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

ውሎች

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 24173

ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ፖሊስ አገልግሎት ድርጅት - ነገረ ፈጅ አቶ ማስረሻ በለጠ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አይዳ ሐሰን - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአመልካቹ አማካይነት ወደውጪ ሃገር የተላከን ጫት ዋጋ ይከፈል ዘንድ የቀረበውን ክስ መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው አመልካች አሜሪካን አገር እንዲያደርስላት በውል ያስረከበችውን ጫት በውሉ መሠረት አለማድረሱን በመግለጽ የጫቱን ዋጋ ከነመላኪያው በጠቅላላው ብር 18,000 እንዲከፍላት እንዲወሰንላት ጠይቃለች፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ መቃወሚያዎችንና የፍሬ ነገር ነጥቦችን በማንሳት የተከራከረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ግን ክርክሩን አልተቀበለም፡፡ በመጨረሻም የጫቱን ዋጋ ከነመላኪያው እንዲከፍል ወስኖበታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 3 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተወሰነው አመልካች ገንዘቡን

እንዲከፍል የተወሰነበት በሕጉ አግባብ ነው ወይ? የሚለው ነጥብ መጣራት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እንደተገነዘብነው አመልካች ለክሱ መነሻ የሆነውን ጫት ከተጠሪ መረከቡንና በዓለም አቀፍ የፖስታ ሕብረት ስምምነት መሠረት ጥቅሉን ወደሚመለከተው /ወደተላከበት/ አገር መላኩን ገልጾአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ግዴታውን በአግባቡ መወጣቱን በመግለጽ ከኃላፊነት ነፃ እንዲሆን፤ ኃላፊ ነህ የሚባል ከሆነም መጠየቅ ያለበት በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት /እንደ ክሱ አቀራረብ/ ሳይሆን፣ በተቋቋመበት አዋጅ ቁ. 240/58 መሠረት እንደሆነ በማስመልከት ተከራክሮአል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ግን አመልካች ጫቱን ለተላከለት ሰው ስለማድረሱ አላስረዳም በማለት በፍሬ ነገር ረገድ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርገውታል፡፡ የካሣውን አወሳሰን በተመለከተ የቀረበውን ክርክርም በአዋጅ ቁ. 240/58 የተገለጸ ነገር የለም የሚል ምክንያት በመስጠት አልተቀበሉትም፡፡ አመልካች አቤቱታ ያቀረበው በፍሬ ነገር ረገድ የተሰጠውን ምክንያት ጭምር በመቃወም ሲሆን፣ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል ለማለት የቻለበት ዋናው ምክንያትም ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት የሌለው የፍትሐብሔር ሕጉን መሠረት አድርጎ የተወሰነ ነው የሚል እንደሆነ ከክርክሩ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ጫቱን በአግባቡ ወደተላከው ቦታ አድርሻለሁ በማለት ያቀረበው የፍሬ ነገር ክርክር ከማስረጃ አንፃር ተመዝኖ ውድቅ ሆኖአል፡፡ በዚህ ረገድ ያለው ክርክር የማስረጃ አመዛዘንን የሚመለከት በመሆኑ በዚህ ችሎት የሚታይ አይደለም፡፡ አመልካች ጫቱን ለተላከለት ሰው አለማድረሱን ከተረጋገጠም ቀጥሎ መታየት ያለበት የሕጉ ክርክር ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሥራ ላይ የፖስታ አገልግሎትን ሕግ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁ. 240/58 በአመልካቹ አማካይነት የተላከን ዕቃ ወይም ፖስታ ጠፍቶአል፣ ተበላሽቶአል፣ ተሰርቋል፣ ወዘተ በሚል ጥያቄ ሲቀርብ ካሣ የሚከፈልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ደንግጎአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአወሳሰኑ ሁኔታም በዝርዝር አስቀምጦአል። በዚህ ረገድ የአዋጁ አንቀጽ 50፣ 51 እና 53 እንደዚሁም 54ን በተለይ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል። የሚከፈል ካሣ ካለ መጠኑ የሚወሰነው በዓለም የፖስታ ሕብረት ስምምነት /ኮንቬንሽን/ በተወሰነው እና ከሌሎች አገሮች ጋር በሚደረጉ ልዩ ስምምነቶች መሠረት እንደሆነ በአንቀጽ 54 ተመልክቶአል። እንግዲህ ከአዋጁ አጠቃላይ መንፈስ፣ በተለይ ደግሞ ከተጠቀሱት አንቀጾች በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው ፖስታው /ዕቃው/ በመጥፋቱ፣ በመሰረቁ፣ በመበላሸቱ፣ ወዘተ ምክንያት አመልካች ካሣ እንዲከፍል የሚጠይቅ ቢሆን መጠየቅ ያለበት በአዋጁ መሠረት እንደሆነ ነው። በሌላ አነጋገር በዚህ ረገድ ካሣ የሚጠየቅበትንና መጠኑም የሚወሰንበት ራሱን የቻለ ልዩ ሕግ ተደንግጎአል ማለት ነው። በመሆኑም ይህን ሕግ በመተው ካሣው በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት እንዲከፈል መወሰን መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም ነው የሚሆነው። ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል።

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደፍ/ቤት በመ/ቁ. 06053 በነሐሴ 19 ቀን 1997 ዓ.ም. እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 01854 መጋቢት 19 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጡአቸው ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል።
2. ተጠሪ ያቀረበችው የካሣ ክፍያ ጥያቄ መታየት ያለበት በአዋጅ ቁ. 240/58 መሠረት በመሆኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን ከዚህ አዋጅ አንፃር በመመርመር ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ ይስጥ ብለናል። ይፃፍለት።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 24574

ኅዳር 11 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤ/መ/ፓ/ጠ/ቤ/ጽ/ቤት አልቀረቡም።

ተጠሪ፡- አቶ ይትባረክ ሣህሉ አልቀረቡም።

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በጅጅጋ ዞን ከፍ/ቤ/ት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በቀረበው ክስ ነሐሴ 3 ቀን 1994 ዓ.ም. በተደረገ ውል ከሣሽ ሁለት የጭነት መኪናዎችን ለ1 ዓመት እንድገለገልበት ከተከሳሽ ተከራይቹ መኪናዎቹ በሥራ ላይ እንዳሉ አንደኛው መኪና የመገልበጥ አደጋ ደርሶበት በውሉ መሠረት በዚህ መኪና መሥራት እንድችል ተከሣሽ መኪናውን አስጠግኖ ማስረከብ ሲገባው ይህንን ግዴታውን ባለፈፀሙ በጠቅላላው ብር 290,377.12 (ሁለት መቶ ዘጠና ሺ ሶስት መቶ ሰባ ሰባት ብር ካስራ ሁለት ሣንቲም) ጥቅም የተቋረጠብኝ ስለሆነ ይህንን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል።

ተከሳሽም ቀርቦ በሰጠው መልስ የውሉን መኖር አምኖ ነገር ግን መኪናው ሊገለበጥ የቻለው ከሣሽ ከክብደት በላይ በመጫኑ ምክንያት ነው ብሎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ የተከራከረ ሲሆን ከዚህም ሌላ ከሳሽ በውሉ መሠረት አለመፈጸሙን ገልጾ የመኪና ኪራይ ገንዘብ፣ መኪናውን ለማስጠገን ወጭ ተደርጓል ያለውን ገንዘብና የገደብ መቀጫ ጨምሮ በድምሩ ብር 252,246 (ሁለት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺ ሁለት መቶ አርባ ስድስት) እንዲከፈለው በመጠየቅ የተከሳሽ ከሳስነት ክስ አቅርቧል። የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበለትም የዞን ከፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ ከሳሽ በክስ ከጠየቀው ገንዘብ ብር 65,254 (ስልሳ አምስት ሺ ሁለት መቶ ሀምሳ አራት) ውድቅ አድርጎ ቀሪው ብር 225,123.12 (ሁለት መቶ ሀያ አምስት ሺ አንድ መቶ ሀያ ስድስት ብር ከአስራ ሁለት ሣንቲም) ተከሣሽ ለከሳሽ እንዲከፍል በማለት ሲወስን በተከሳሽ በኩል የቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በተመለከተ ፍ/ቤቱ በውሣኔው ምንም ሳይል አልፎታል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለሱማሌ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኙን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ የአመልካችን መኪና ተከራይቶ ሲሠራበት መኪናው ተገልብጦ ሥራ በማቆሙ ተጠሪ የቀረበትን ገቢ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ እንዲሁም የአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መታለፉ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም ይሄው ነጥብ በመሆኑ ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በውሉ ግዴታ ውስጥ ባለዕዳው የጉዳት ኪሣራ ከፋይ የሚሆነው ውሉን አሟልቶ ባለመፈጸሙ ወይንም ውሉን ከስምምነቱ ውጭ አዘግይቶ በመፈጸሙ የተነሳ በሌላው ተዋዋይ ወገን ላይ በገንዘብ ሊተመን የሚችል ኪሣራ የደረሰበት መሆኑ ሲታወቅ እንደሆነና የጉዳት ኪሣራ ክፍያ ጥያቄውም ውሉን አስገድዶ ከማስፈጸም /forced performance/ ወይንም ውሉ እንዲሰረዝ ከመጠየቅ ጋር ሊቀርብ እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1790 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው በኪራይ ከአመልካች የተረከበው መኪና በሥራ ላይ እንዳለ በመገልበጡ ምክንያት ሥራ በማቆሙ የቀረበትን ገቢ አመልካች እንዲከፍለው በመጠየቅ ነው፡፡ ግራ ቀኙ ባቋቋሙት ውል መሠረት አመልካች መኪናውን ለተጠሪ

አላስረከበም ወይንም ያስረከበው አዘግይቶ ነው የሚል ክስ በተጠሪ በኩል ባለመቅረቡ አመልካች የውል ግዴታውን አልፈፀመም ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ የውሉም ይዘት ሲታይ ተጠሪ በኪራይ በተረከባቸው መኪናዎች ላይ በአደጋ ምክንያት ጉዳት ቢደርስ ለመድን ድርጅትና ለአመልካች በወቅቱ የማሳወቅ ኃላፊነት ተጠሪ እንዳለበትና አመልካችም በበኩሉ ለደረሰው ጉዳት ተገቢው ዕርምጃ እንዲወሰድ የሚያደርግ መሆኑ ከመመልከቱ በስተቀር ጉዳት የደረሰበትን መኪና በተገቢው ጊዜ እንዲጠገን ባለማድረጉ የጉዳት ኪሣራ በተጠሪ ላይ ከደረሰ አመልካች ካሣ የሚከፍል ስለመሆኑ አልተመለከተም፡፡

ሰለሆነም የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ በሕጉ ላይ ስለ ጉዳት ኪሣራ አከፋፈል ከተቀመጠው ዓላማ ጋር የማይጣጣምና ውሉንም መሠረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች በበኩሉ በውሉ አፈጻጸም ረገድ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለጽ ብር 252,246 /ሁለት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ስድስት/ ኪሣራ እንዲከፈለው በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የመሠረተ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ዳኝነት ሳይሰጥበት አልፎታል፡፡ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሳይሰጥበት የታለፈ ጉዳይ እንደተነፈገ የሚቆጠር መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ቁ. 5/3/ ላይ የተመለከተ ቢሆንም የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ዳኝነት ከተጠየቀባቸው ነገሮች በተወሰኑት ላይ ውሣኔ ተሰጥቶ በተወሰኑ ላይ ደግሞ ውሣኔ ሳይሰጥ ቢቀር የታለፈው እንደተነፈገ እንደሚቆጠር ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ጨርሶ ያልታየ በመሆኑ እንደተነፈገ ይቆጠራል ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ሰበር ሰሚ ችሎት ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83/96-380 በሰኔ 21 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የሱማሌ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 28/98 በየካቲት 25 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች መኪና በተጠሪ እጅ እያለ በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ በተጠሪ ላይ በተቋረጠ ገቢ አመልካች የጉዳት ኪሣራ ለመክፈል የሕግም ይሁን የውል ግዴታ ስለሌለበት ሊከፈል አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. በአመልካች በኩል የቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ዳኝነት ሳይሰጥበት የታለፈ ስለሆነ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች በኩል የቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 25434

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

መድነን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን - ጥሩወረቅ ሀ/ማርያም - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ፍሬተርስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማኅበር - ጠበቃ ፍቃዱ ያሚን- ቀረበ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 00241 ሰኔ 10 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 33291 መጋቢት 18 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት በሰበር ይታረምልኝ በማለት አመልካች ሰኔ 13 ቀን 1998 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች 26 ኮንቴነሮችን በማስጫን ከተጠሪው ጋር ውል የነበረው መሆኑን ገልፆ፣ በመያዣነት ካስያዝኩት ገንዘብ ውስጥ ብር 104,190 /አንድ መቶ አራት ሺ አንድ መቶ ዘጠና/ አላግባብ ቀንሶ ስላስቀረና ከነሐሴ 3 ቀን 1990 ዓ.ም. ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፈል ይወስንልኝ በማለት አመልካች ያቀረበው ክስ ሲሆን፣ ተጠሪም በበኩሉ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ከሳሽ ኮንቴነሮቹን በወቅቱ ባለመመለሳቸው እና ከሰላሣ ቀን በላይ በማቆየቱ መክፈል ያለበት መቀጫ ስለሆነ ሊመለስለት አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የውሉ የቅጣት ድንጋጌ በክፍት ቢታለፍም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1791 ንዑስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 1 መሠረት ለደረሰው ኪሣራ ከሣሽ ካሣ መክፈል ስላለበት ቅጣቱም በቀን ብር 75 /ሰባ አምስት ብር/ መሆኑን ተከሣሹ ከሌሎች ደንበኞቹ ጋር ያደረገውን ውል በማስረጃነት ስላቀረበ ከሳሽ ቀሪ የማስያዥያ ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት የቀረበውን ጥያቄ አልተቀበልነውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የፍሬ ጉዳይ እና የሕግ ምክንያት የለም በማለት ሠርዞታል፡፡ አመልካች በውል ሰነዱ መቀጫ ለመክፈል ያልተስማማንና የመቀጫ ድንጋጌው በክፍት /ዳሽ/ የታለፈ መሆኑ እየታወቀ ፍርድ ቤቱ ከሣሽ በክስ ማመልከቻው ያልጠየቀውን ኮንቴነሮቹ በወቅቱ ባለመመለሳቸው በተከሣሽ ላይ ካሣ የመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት ጭብጡን በመቀየር የወሰነ ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪው በበኩሉ ውሉ የቅጣት ድንጋጌ ያለው መሆኑን ጠቅሶ የቅጣት መጠኑ ባለመገለፁ ብቻ አመልካች አልተስማማም ማለት ስለማይቻል ይኸም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1713 መሠረት ሊፈፀም ስለሚገባው የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስ በሰበር አቤቱታው ላይ ያቀረባቸውን ነጥቦች በማጠናከር ተከራክሯል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔና ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪው አመልካች የጠየቀውን ገንዘብ በመያዣነት ተሰጥቶት ከነበረው ገንዘብ ውስጥ በመቀነስ ያስቀረ መሆኑ አልተካደም፡፡ ተጠሪው የሚከራከረው የቀነሰኩት በውሉ መሠረት ከ30 ቀን በላይ ኮንቴነሮቹ ባለመመለሳቸው አመልካች መክፈል የሚገባውን የቅጣት ገንዘብ ነው በማለት ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል፣ ኮንቴነሮቹ በመዘግየታቸው አመልካች ቅጣት ለመክፈል የተስማሙበት መሆኑን ያረጋግጣል ወይስ አያረጋግጥም? የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1791 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት

አመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ሕጋዊ መሠረት አለው ወይስ የለውም የሚሉትን ነጥቦች ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የውሉ አንቀጽ 4 ኮንቴነሩ ወደብ ከደረሰ ከሰላሣ ቀን በኋላ፣ ኮንቴነሩ በቀን ብር _____ ለመክፈል አመልካች ግዴታ መግባቱን ያሣያል፡፡ እንግዲህ በቀን ብር ዳሽ የሚለው የውሉ አራተኛው አንቀጽ እንዴት ነው መተርጎም ያለበት የሚለው የመጀመሪያው ነጥብ ነው፡፡ ተጠሪው፣ ይህ በቀን የሚከፈለውን የብር መጠን የማይገልጽ የውሉ አንቀጽ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1713 መሞላት አለበት በማለት የሚከራከር ቢሆንም ይኼ ድንጋጌ የዚህ አይነት አከራካሪና አጠራጣሪ ጉዳይ ለመፍታት አያገለግልም፡፡ እንደዚህ አይነት አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም የውሉ ድንጋጌ መተርጎም ያለበት በውሉ አስገዳጅ የሆነውን ወገን በሚጠቀምበት ሁኔታ ሣይሆን ለውሉ ተገዳጅ የሆነውን ወገን ምቹ በሚሆንበት አኳኋን መሆን እንደሚገባው አንቀጽ 1738 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው አመልካች በየቀኑ የሚከፍለው የመቀጫ ገንዘብ መጠን የሚደነግገው የውሉ አንቀጽ አራት መተርጎም ያለበት ተጠሪውን በሚጠቅም መንገድ ሣይሆን በዚህ ድንጋጌ ተገዳጅ የሆነውን አመልካቹን በሚጠቅም መንገድ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የውሉ አንቀጽ 4 ላይ የሚታየው ክፍተት አመልካች ለተጠሪው የቅጣት ገንዘብ ለመክፈል ያልተስማማ መሆኑን የሚያሣይ እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1738 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪው መካከል የቅጣት ክፍያን አስመልክቶ ውል አለ ወይስ የለም የሚለውን ጭብጥ ከውል ድንጋጌዎች አተረጓጎም አንፃር አይቶ ሣይወስን ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለተ፣ ተጠሪው ለቀረበበት ክስ፣ የተከራከረው፣ ቀንሼ ያስቀረሁት ገንዘብ አመልካች በውላችን መሠረት ኮንቴነሮቹ ከሰላሣ ቀን በላይ ለዘገየበት በቀን ብር 75 /ሰባ አምስት ብር/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሰልቶ መከፈል ያለበት የመቀጫ ገንዘብ ነው በማለት ነው። ተጠሪው የአመልካቹ ማለትም የሥር ከሣሽ ማመልከቻ ሲደርሰው በሥር ተከሣሽ የሆነው ተጠሪው አመልካች በሰላሣ ቀን ውስጥ ኮንቴነሮቹን ባለማንሣቱ ደረሰብኝ የሚለው ኪሣራ በዝርዝር በመግለጽ አመልካች የውል ግዴታውን ባለመፈፀሙ ለደረሰበት ኪሣራ ካሣ ሊክለኝ ይገባል የሚል፣ በተከሳሽ ከሳሽነት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1/ረ/ እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥግዓት ሕግ ቁጥር 234 መሠረት አልጠየቀም። ተጠሪው አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጎች መሠረት በማድረግና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 215 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አስፈላጊውን ዳኝነት ከፍሎ፣ ጥያቄውን ሣያቀርብ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ኮንቴነሮቹን በወቅቱ ባለማንሣቱ በተጠሪው /ተከሣሽ/ ላይ ላደረሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1791 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት በራሱ አነሳሽነት የሰጠው ውሣኔ፣ ከላይ የተገለጹትን መሠረታዊ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎች በግልጽ ባላቀረቡት እና በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት አይቻልም የሚለውን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረታዊ ድንጋጌ የሚጥስ በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል።

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 00241 ሰኔ 10 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 33291 መጋቢት 18 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል። ይፃፍ።
2. ተጠሪው አመልካች ክስ የቀረበበትን ብር 104190/ አንድ መቶ አራት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና/ ከነሐሴ 3 ቀን 1990 ዓ.ም. ጀምሮ

ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለአመልካች እንዲከፍል ወስነናል። በውሣኔው መሠረት አመልካች የአፈፃፀም ክስ ካቀረበ ውሣኔውን ያስፈጽም ዘንድ ግልባጩ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ይተላለፍ።

3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ።

ይህ ፍርድ መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 26565

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ግሎባል ኢንሹራንስ /አ.ማ/ ካሣዬ ተ/አረጋይና ተፈራ ደምሴ ጠበቆች

ቀረቡ

ተጠሪ፡- ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በመድን ውል መሠረት ለደንበኛው የከፈለው ካሣ እንዲተካለት በፌ/ከ/ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ክስ መስርቶ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ጉዳት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለሆነ ተጠሪ ካሣ ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይሄው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ተጠሪ ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ደንበኛ የሆነው ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በጅቡቲ በኩል ከውጭ ወደ አዲስ አበባ ለሚያስመጣው 9,600 (ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ በጉዞ ላይ ለሚደርስበት ማንኛውም አደጋ ከሣሽ የመድን ሽፋን የሰጠ ሲሆን የመድን ሽፋን ከተሰጠው 9,600 (ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ ውስጥ 3,200 (ሦስት ሺህ ሁለት መቶ) ካርቶን የአንገፍ የተከሣሽ በሆነ የጭነት መኪና ተጭኖ ከጅቡቲ ወደ አ/አበባ በመጓዝ ላይ እንዳለ ከመኪናው በተነሣ እሣት ጭነቱ በሙሉ ወድሟል፡፡ በኢንሹራንስ

ፖሊሲው ላይ 9,600 (ዘጠን ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ የመድን ዋስትና የተገባው ለብር 2,066,045.66 (ሁለት ሚሊየን ስልሳ ስድስት ሺህ አርባ አምስት ከስልሳ ስድስት) ሲሆን ለወደመው 3,200 (ሦስት ሺህ ሁለት መቶ) ካርቶን እርሾ ብር 688,681.87 (ስድስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሰማኒያ አንድ ከሰማኒያ ሰባት) ስለሚሆን በዚሁ መሠረት ከሣሽ በመድን ሰጭነቱ ይህንኑ ብር 688,681.87 ለደንበኛው ለፔትራም ኃ/የተ/የ/ማኅበር የከፈለ ሲሆን ተከሣሽ ይህንን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ ገንዘቡን ከወለድ ወጭና ኪሣራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች ክስና ማስረጃ ለተጠሪ ደርሶ በሰጠው መልስ ጉዳቱ መድረሱን ሣይክድ የተከሣሽ ንብረት የሆነው ከባድ የጭነት ተሽከርካሪ በጥቅምት 6 ቀን 1996 ዓ.ም የደረሰበት የእሣት ቃጠሎ አደጋ ድንገተኛ ደራሽና ያልታሰበ የመኪናው ሾፌር ቃጠሎውን ለመከላከል ባደረገው ሙከራ ሰውነቱ እንደተቃጠለና የተሽከርካሪውም ሞተር አዲስ መሆኑን ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት አደጋ እንዳላጋጠመው አደጋው ፍፁም ሊመልሱት የማይቻል በሹፌሩም ሆነ በአካባቢው ከነበሩ ሰዎች አቅም በላይ የሆነ ከፍተኛ ኃይል /force majeure/ ስለሆነ ከንግድ ሕግ ቁጥር 591 አኳያ ተከሣሽ ኃላፊነት ስለማይኖርበት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተከሣሽ ሲያንገዳዘው በነበረ እቃ ላይ ጉዳት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው ወይንስ አይደለም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ አይደለም የሚባል ከሆነ ተከሣሽ በከሣሽ የተጠየቀውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት ወይ? የሚሉትን ጭብጦች መሰርቶ ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በጅቡቲ የሚገኘው ኤክስፐርት በአደጋው ቦታ በመሄድ ስለአደጋው አደራረስ ባቀረበው ሪፖርት መኪናው ከነጭነቱ ሙሉ በሙሉ በእሣት መቃጠሉንመ፣ እሣቱ ሊነሣ የቻለው የኤክትሪክና የመካኒክ ሲስተሙ ድክመት ስለገጠመው በኤሌክትሪክ መስመሩ ላይ ከፍተኛ ኃይል ያለው ኬብል ሥራውን ስላቋረጠና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከብረት ጋር ስለተፋጨ የኤሌክትሪክ ጭረት ተነስቶ ኃይለኛ ንፋስ በመኖሩ ተቀጣጣይ የሆኑት አካሎች በእሣት ተያይዘው እሣቱም ተስፋፍቶ ወደ ተሣቢው ስለደረሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን ሌላው በማስረጃነት የቀረበውና አሽከርካሪው ለፖሊስ በሰጠው ቃል መኪናውን ከጅቡቲ ወደ አ/አበባ እያሽከረከረ ሲጓዝ በመኪናው ጋቢና የእሣት ሽታ እንደሸተተውና የተሣቢውን ጭነት ሲመለከት እንደተቃጠለና በወቅቱም ኃይለኛ ንፋስ ስለነበር መኪናውን አቁሞ ወርዶ እሣቱን ለማጥፋት እንደሞከረ በዚህ ጥረቱም እጁን እንደተቃጠለ የእሣቱን መንስኤ በተመለከተ በመኪናው ውስጥ የኮንታክት ችግር ያስነሣ እንደሚመስለው ነገር ግን ሞተሩ አዲስ መሆኑንና ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት አደጋ እንዳላጋጠመው በመግለጽ ቃሉን እንደሰጠ ያስገነዝባል፡፡

የእቃ አጓዥር በሚያጓጉዘው ዕቃ ላይ ለሚደርስ ጥፋት ኃላፊ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 590 ላይ የተደነገገ ቢሆንም በዚሁ ሕግ ቁጥር 591 ላይ ደግሞ በእቃው ላይ ጥፋት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መሆኑን አጓዡ ካስረዳ በኃላፊነት ተጠያቂ እንደማይሆን ተመልክቷል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ተከሣሽ ባቀረበው ማስረጃ ለክሱ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት አጓዡ ሊገምተውና ሊያስቀረው በማይችል አደጋ ምክንያት መሆኑን መገንዘብ የተቻለ ስለሆነ ተከሣሽ ለተከሰሰበት የንብረት ጉዳት ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሣሽም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ሠርሿል፡፡

ከዚህ በኋላም ከሣሽ (የአሁን አመልካች) የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት አቅርቦ ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በእርሾው ላይ የደረሰው ቃጠሎ ከአቅም በላይ ምክንያት ስለመሆኑ ከሕጉ አኳያ ተመርምሮ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተመለከተውም አመልካች ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሣያገኝ የቀረው ቃጠሎው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል ነው፡፡ በመሆኑም አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተመርምሮ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነው፡፡

አንድ አጓዥር በከፊል ወይም በሙሉ እቃዎች ወይም የተመዘገቡ ዝዞች ሲጠፉ ወይም ጉዳት ሲያገኛቸው ወይም የማስረከቢያው ጊዜ ቢዘገይ በኃላፊነት እንደሚጠየቅ የንግድ ሕግ ቁጥር 590 የሚያመለክት ሲሆን አጓዡ ከዚህ ኃላፊነት የሚድነው ደግሞ ንብረቱ ሊጠፋ፣ ጉዳት ሊደርስበት ወይም ሊዘገይ የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በዕቃው ውስጣዊ ጉድለት ምክንያት ወይም በላኪና በተቀባዩ ጥፋት ምክንያት ሲሆን እንደሆነ በዚሁ የንግድ ሕግ በቁጥር 591 ላይ ተመልክቷል፡፡

የግራ ቀኙ ግንኙነትን የሚገዛው ይሄው የንግድ ሕጉ ስለሆነ ክርክሩ መታየትም ያለበት ከዚሁ የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ነው፡፡ ይሁንና በንግድ ሕጉ ውስጥ "ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተመለከተ ነገር ስለሌለ ትርጉሙን ለማወቅ ከልዩ ሕጉ ወደ ጠቅላላ ሕጉ ማለትም ወደ ፍ/ብ/ሕጉ በተለይም ደግሞ ስለውሎች በጠቅላላው ስለሚመለከቱ ድንጋጌዎች ማምራት የግድ ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረትም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ለማለት የሚቻለው መቼ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1792 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህም ድንጋጌ ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ኃይል ደርሷል የሚባለው ባለዕዳው ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍፁም መሰናክል በሆነ አይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመ ጊዜ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለዕዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈፃፀም ከባድ የሆነ ወጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በባለዕዳው የሚደርስበት ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው ባለዕዳው በምንም መልኩ በቅድሚያ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይችል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለዕዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገመት ወይም ሊያስብና ጥንቃቄ ሊያደረግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገተኛ ደራሽ ነገር ቢሆን እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪውን ከኃላፊነት ነፃ ያደረጉት የክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት በቃጠሎ ሊወድም የቻለው ተሽከርካሪው የኤሌክትሪክና የመካኒክ ሲስተሙ ድክመት ስለገጠመው በኤሌክትሪክ መስመሩ ላይ ከፍተኛ ኃይል ያለው ኬብል ስራውን ስላቋረጠ ከብረት ጋር በመፋጨቱ ምክንያት በተነሣው እሣት ስለሆነና ይህም አጓጉ ሊገምተውና ሊያስቀረው የማይችል በመሆኑ ሁኔታው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የተፈጠረ ነው በማለት ነው፡፡ በጥቅሉ ሲታይ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆን አይችልም ያሉት ከተሽከርካሪው የቴክኒክ ችግር ጋር በተያያዘ ነው፡፡

ይሁንና የተሽከርካሪው ባለቤትና አጓዥ የሆነው ተጠሪ ተሽከርካሪውን በሚገዛበት ጊዜ የቴክኒክ ደንንነቱ አስተማማኝ መሆኑን ለሥራ ከሚሰማራበት አገርም ሆነ አካባቢ የአየር ንብረት ጋር ተስማሚ መሆኑን አጣርቶ ተሽከርካሪውን መግዛት እንዳለበት የሚታመን ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጎ ግዢውን ከፈፀመ በኋላም ቢሆን ለሥራ በተሰማራበት አካባቢ ምንም ዓይነት የቴክኒክ ችግር እንዳያጋጥመው ለጉዞ ከመሰማራቱ በፊትና በጉዞ በየጊዜው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ሣያደርግ ቀርቶ ጉዳት ቢደርስ እንደሕጉ አገላለጽ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከላይ

እንደተመለከተው በተሽከርካሪው ግዢ ወቅትም ሆነ ከግዢ በኋላ ተሽከርካሪው የቴክኒክ ችግር እንዳይደርስበት አስቀድሞ ሊገምተውና ሊከላከለው ሲገባ ይህንን የመከላከልና የጥንቃቄ ዕርምጃ አስቀድሞ ሣይወስድ በመቅረቱ በጉዞ ላይ ተሽከርካሪው በደረሰበት የቴክኒክ ብልሽት ምክንያት በተነሣው ቃጠሎ የመድን ሽፋን የተገባለት ንብረት መውደሙ የተረጋገጠ ስለሆነ ሁኔታው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ሊባል ስለማይችል የሥር ፍ/ቤቶች ለንብረቱ መቃጠል ምክንያት የሆነው አደጋው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ትርጉም የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

6. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 41594 በታህሳስ 26 ቀን 1998 ዓ.ም እንደዚሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23649 በግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
7. በተጠሪ መኪና ተጭኖ ሲጓጓዝ የነበረውና አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው እርሾ በቃጠሎ ጉዳት ሊደርስበት የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
8. ቃጠሎው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም ተብሎ የተወሰነ ስለሆነ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የካሣ ክፍያ ጥያቄውን አስመልክቶ የያዘውን ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አኳያ መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
9. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
10. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 29369

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል ነ/ፈጅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተመስገን አድነው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተከሳሽ በከሳሽ መ/ቤት ተቀጥረው ሲሠሩ ከሳሽ መ/ቤት የሚሠራውን የምርምር ሥራ በአዳዲስ ሳይንሳዊ ዕውቀት ለማሻሻል እንዲቻል ተከሳሽ በሀረማያ ዩኒቨርስቲ በኤም-ኤሲ-ሲ ደረጃ እንዲማሩ የተደረገ ሲሆን በትምህርት ላይ በነበሩበት ጊዜም የ24 ወር ደመወዝ ብር 23,520 (ሃያ ሦስት ሺ አምስት መቶ ሃያ) ተከፍሏቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ተከሳሽ ባቀረቡት ፕሮፖዛል መሠረት ብር 54,409 (ሃምሳ አራት ሺህ አራት መቶ ዘጠኝ ብር) ከሳሽ ለዩኒቨርስቲው ከፍሎላቸዋል፡፡

ተከሳሽ ወደ ትምህርት ከመሄዳቸው በፊት ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ወደ ከሳሽ መ/ቤት ተመልሰው በትምህርት ላይ ለቆዩባቸው ለእያንዳንዱ ወር የ3 ወራት የሥራ አገልግሎት ለመስጠት ጥቅምት 13 ቀን 1993 ዓ.ም የውል ግዴታ ገብተው የነበረ ሲሆን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኃላ ግን የጀመሩትን የምርምር ሥራ ትተው ሥራቸውን በፈቃዳቸው ለቀው የሄዱ ስለሆነ እንደውሉ ተገደው እንዲፈጽሙ ተከሳሽ በውሉ መሠረት ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆኑ ከሳሽ መ/ቤት ለትምህርቱ የከፈለላቸውን በድምሩ

ብር 77,929.00 (ሰባ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጡት መልስ ከሳሽ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ የውልም ሆነ የሕግ ድጋፍ እንደሌለው በመዘርዘር ክሱ ከኪሣራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከሳሽ ባቀረበው ክስ ተከሳሹ እንደ ውሉ ተገዶ ይፈጸምልኝ በማለት የጠየቀውን በተመለከተ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1776 (1) አኳያ ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ ከሳሽ በአማራጭ የጠየቀውና ለትምህርት ተብሎ የተከፈለው ውጭ ሊተካልኝ ይገባል የሚለውም የኪሳራ ክፍያ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771(2) ድንጋጌ መሠረት ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም ወይንም እንዲፈርስ ከመጠየቅ ጋር ተያይዞ መቅረብ የሚገባው ሲሆን ከሳሽ ግን ውሉ እንዲፈርስ ባልጠየቀበት ሁኔታ ኪሳራ ሊከፍለው ስለማይችል ክሱ በአግባቡ አልቀረበም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348(1) መሠረት አጽንቷል፡፡

ይህ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች ለተጠሪ አወጣሁት የሚለው ወጭ እንዲተካለት ያቀረበው አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የሰበር አቤቱታውም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የመሠረተው ከላይ እንደተጠቀሰው ተጠሪ በውሉ በገባው ግዴታ መሠረት በከሳሽ መ/ቤት እንዲያገለግል ይህ ተቀባይነት ካላገኘ የከሳሽን መ/ቤት ያገለግላል በሚል እምነት ለትምህርት የገንዘብ ወጭ የተደረገለት ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ሊተካልኝ ይገባል በማለት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1776 ላይ እንደተመለከተው የባለዕዳው ቀጥተኛ የውል ፈጻሚነት (Specific Performance) ጥያቄ ሊመጣ የሚችለው የውሉ አፈፃፀም ለባለገንዘቡ የተለየ ጥቅም የሚሰጠው ከሆነና የባለዕዳውንም የግል ነፃነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይነካ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነና ዳኝነት የተጠየቀበትም ጉዳይ የባለዕዳውን /የተጠሪን/ የግል ነፃነት የሚነካ በመሆኑ ተጠሪ ውሱን ተገዶ እንዲፈጽም ይወሰንልን በማለት አመልካች ዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ የሚነቀፍ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩልም በአማራጭ የጠየቀው ዳኝነት ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት ማገልገል የለበትም ከተባለ ለትምህርት የወጣው ወጭ ሊተካልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤት ይህንን የዳኝነት ጥያቄ ሳይቀበለው የቀረው የኪሳራ ክፍያ ጥያቄ የሚቀርበው ለብቻው ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771 መሠረት አንድም ከውል ይፈጸምልኝ ጋር አሊያም ከውል ይፍረስልኝ ጋር እንጂ ብቻውን ስላልሆነ አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ባልጠየቀበት ሁኔታ የኪሳራ ክፍያው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

በእርግጥ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771 (1) እና (2) መሠረት የኪሳራ ክፍያ ጥያቄ ከውል ይፈጸምልኝ ወይንም ይሰረዝልኝ ጋር ተጣምሮ ሊቀርብ እንደሚችል መገንዘብ ቢቻልም በተያዘው ጉዳይ ከውሉ ባህሪይ አኳያ ተጠሪን አስገድዶ ማስፈጸም አይቻልም ከተባለ ውጤቱ የውሉን ቀሪ መሆን የሚያስከትል ስለሆነ አመልካች ደረሰብኝ የሚለው ኪሳራ ካለ ከመጠየቅ በስተቀር ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቅ የሚጠበቅበት አይሆንም፡፡

በዚሁ መሠረትም አመልካች ሊተካልኝ ይገባል የሚለው ኪሳራ በአንድ በኩል ተጠሪ በትምህርት ላይ እያለ የተከፈለውን ደመወዝና በሌላ በኩልም ለዩኒቨርስቲው ተከፍሏል ያለውን ገንዘብ ነው፡፡

ተጠሪም በሰጠው መልስ በትምህርት ላይ እያለ ደመወዝ እንደተከፈለውና ሲማርበትም ለነበረው ዩኒቨርስቲ የትምህርት ወጪ መክፈሉን ሳይክድ ገንዘቡን ለአመልካች ለመመለስ ግዴታ የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ሆኖም በግራ ቀኙ መካከል ጥቅምት 13 ቀን 1993 ዓ.ም የተፈረመውን ውል ይህ ችሎት አስቀርቦ እንደተመለከተው ተጠሪ በሥልጠና ለሚቆይበት የ24 ወራት ጊዜ አመልካች ደመወዝ እንደሚከፍለውና ለሥልጠና የሚያስፈልገውንም ወጭ አመልካች እንደሚሸፍን እንደዚሁም ከሥልጠናው በኋላ ለእያንዳንዱ ወር የሥልጠና ጊዜ ሶስት ወር ተጠሪ አመልካችን ማገልገል እንደሚጠበቅበት መስማማታቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በግራ ቀኙ በኩል የተደረገው ስምምነት ይህንን የሚመስል ከሆነ ተጠሪ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ አመልካችን ለማገልገል ፈቃደኛ ካልሆነ ኪሳራ የመክፈል ኃላፊነት እንደሚኖርበት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ነገር ግን የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ኪሳራ ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ክሱን ሳይቀበሉ መቅረታቸው ከውሉና ከሕጉ ጋር ያልተገናዘበ በመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 06098 በጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 34431 በታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች ኪሳራ የመክፈል የውልና የሕግ ኃላፊነት አለበት ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካች መክፈል በሚገባው የካሣ መጠን ላይ ግን የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያልታየ ስለሆነ በዚሁ መሠረት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መጠኑን በተመለከተ ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ አኳያ ተመልክቶ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተገዝቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 30947

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽ ኮርፖሬሽን ቀረበ

ተጠሪ፡- አቶ ሲሳይ ጥላሁን ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

በጉዳዩ ላይ ክርክር የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም በአዘጋጀው የክስ ማመልከቻ ተጠሪው ከአመልካች ጋር መጋቢት 20 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረገው የቴሌፎን ደንበኝነት ውልና ተጨማሪ ሲ.ዲ.ኤ.ም.ኤ ደብልዩ.ኤል.ኤል ውል መሰረት እንዲጠቀምበት በተሰጠው ቁጥር 2512569 በሆነ ስልክ መስመር በግንቦት 1997 ዓ.ም ላገኘው አገልግሎት መክፈል የሚገባውን ብር 85,032 (ሰማንያ አምስት ሺ ሰላሳ ሁለት) የአገልግሎት ሒሳብ አለመክፈሉን በዚህ ምክንያትም ድርጅቱ አገልግሎቱን ማቋረጡን ገልጾ ተጠሪ ይህንን ሒሳብ እንዲከፍል እንዲወሰንበት ሲል ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪውም ታህሳስ 3 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ በክሱ ቁጥሩ የተጠቀሰውን ስልክ በውል መረከቡን አምኖ በክሱ የተጠቀሰው ክፍያ እንዲከፍል ምንም አይነት ጥሪም ሆነ ማስታወቂያ እንዳልደረሰው ስልኩንም ከ18 ቀን ባልበለጠ ጊዜ እንደተጠቀመበትና ክፍያው የተጋነነ መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ውድቅ እንዲደረግለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከውላቸው ጋር በማገናዘብ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ከሳሽ ያቀረበው የውል ሰነድ አንቀጽ 11 የሚከፈለው ገንዘብና

የሚከፈልበት ጊዜ ተጠቅሶ ለተከራዩ እንደሚቀርብ ስለሚደነግግ ከሣሽ ይህን ማስታወቂያ ወይም ጥሪ ሳያቀርብለት እንዲከፍለው ክስ ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም፡፡ በውሉ በስልኩ የተገለገለው ደንበኛ ማስታወቂያው በጊዜው ሳይደርሰው ቢቀር ደግሞ በመጠየቅያው ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ እንዳይከፍል እንደሚያግደው ተብሎ የተደነገገውም ለተከሳሹ መብት የሚሰጥ እንጂ ተከሳሹ ማስታወቂያ ሳይደርሰው እንዲከፍል ግዴታ የሚጥልበት አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጐታል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/337 መሰረት በመሰረዝ መዝገቡን ዘግቶ መልሶታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በመቃወም ሲሆን ቅሬታውም ተጠሪው ከተሰጠው በራሪ ወረቀትና በ1997 ዓ.ም ነፃ የመረጃ ማዕከል አማካኝነት የተጠቀመበትን የአልግሎት ሒሳብ ስለሚያውቅ እንደዚሁም የውሉ አንቀጽ 11 ማስታወቂያ በማይሰጣቸው ሁኔታዎች ደንበኞች መክፈል የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች በግልጽ ባስቀመጡበት ሁኔታ ማስጠንቀቂያ የመስጠት አስፈላጊነት እንደዋና ምክንያት ሊቆጠር አይችልም፡፡ ተጠሪው አገልግሎት ማግኘቱን አምኗል፡፡ ክርክሩ የተጠየቀው ሒሳብ የተጋነነ ነው የሚል ነው፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሒሳቡ የተጋነነ መሆን ያለመሆኑን ተጣርቶ ክፍያው እንዲፈፀም መወሰን ሲገባው በውሉ አንቀጽ 11 ደንበኛው ማስታወቂያ ባይደርሰውም ክፍያውን ከመፈፀም አይድንም ተብሎ የተደነገገውን ያለአግባብ በመተርጐም ክሱን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያሳያል፡፡ ፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ መሰረዙ በአግባቡ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ መጀመሪያ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት እንደገና አከራክሮ የቀረበውን ክስ ከማስረጃው ይዘትና ከሕግ አኳያ መርምሮ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ተብሎ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪው ቀርበው መልስ ባለመስጠታቸው ክርክሩ በሌሉበት እንዲታይ ታዟል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስልክ ክፍያውን እንዲፈጽሙ ጥሪ ስላልተደረገላቸው ወይም ማስጠንቀቂያ ስላልተሰጣቸው ክፍያውን ሊፈጽሙ አይገባም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪው ስልኩን ሊገለገሉበት ከአመልካች ጋር ውል መስርተው ማስገባታቸውንና በዚሁ ስልክ መጠቀም መጀመራቸውን አልካዱም፡፡ የስልክ አገልግሎት ክፍያ እንድከፍል ጥሪ አልተደረልኝም ማስታወቂያም አልደረሰኝም ማለታቸው ደግሞ ሒሳቡ ተመርምሮ ክፍያው ሲታወቅ እከፍላለሁ የሚል ሐሳብ ያላቸው መሆኑን እንጂ ማስታወቂያ ስላልደረሰኝ ክፍያውን አልከፍልም፣ እንድከፍልም ሕጉ አያስገድደኝ ማለታቸው ያለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የስልክ አገልግሎት ክፍያ በየወሩ የሚከናወን እንደመሆኑ መጠን ተጠሪው ክፍያውን በወቅቱ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡ በውላቸው አንቀጽ 11 ስር የተደነገገውም ተጠሪው የክፍያ ማስታወቂያ ሣይደርሳቸውም የአገልግሎት ክፍያውን መክፈል እንደማይጠበቅባቸው የሚያሳይ እንጅ ተጠሪው ካልፈለጉ ላለመክፈል የሚችሉበት ምክንያት የሚሳጣቸው አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ክሱን ተቀብሎ ግራ ቀኙን በክፍያ መጠኑ አከራክሮ ተገቢውን መወሰን ሲገባው ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ የአመልካች የስልክ አገልግሎት ክፍያን የመሰብሰብ መብት የሚከለክል በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከ/ፍ/ቤትም ይግባኙን መሰረዙ አግባብ አይደለም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 56323 የካቲት 16 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና ፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46451 የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና በአገልግሎት ክፍያ መጠኑ ላይ ያለው ክርክርም አጣርቶ ተገቢውን ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ እንዲቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 31480

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሠ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኢት/ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ወንድምአገኝ ቶሎሣ ቀረበ

ተጠሪ ፡- አቶ መሐመድ ባህሙድ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመዋዋል ችሎታን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ለአቅመ አዳም ላልደረሰው ልጁ ለወጣት አህመድ መሐመድ ሞግዚትና አሳዳሪ ሆኜ የተሾምኩ ሲሆን ንብረትነቱ የልጁ የሆነውንና ግምቱ ብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ የሆነውን ቤት እኔን ሞግዚቱን ሳያስፈቅዱ አመልካች ባንክና አቶ ሐሰን የተባሉት ግለሰብ ላደረጉት የብድር ውል መያዣ እንዲሆን ልጁን የዋስትና ግዴታ አስገብተው ከማስፈረማቸውም በላይ በቤቱ ላይ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዢ ስላልተገኘ ባንኩ ቤቱን ተረክቦ በወር ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ እያከራየው ይገኛል፤ ስለዚህ ባንኩ ያለአግባብ የያዘውን ቤትና የኪራዩን ሂሳብ እንዲመልስ ይወሰንልኝ በማለት በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ የቤቱ ባለቤት የሆነው አህመድ መሐመድ ለአቅመ አዳም የደረሰ ነው፣ ለአካለመጠን አልደረሰም ቢባል እንኳን ክሱ በይርጋ የታገደ ነው፣ አህመድ መሐመድ አሜሪካን አገር እየኖረ ባለበት ወቅት ተጠሪ የእሱ ሞግዚትና አሳዳሪ ነኝ በማለት ያለአግባብ ያገኙትን ማስረጃ

ተቃውመን ጉዳዩ በሂደት ላይ ይገኛል፣ ባንኩ ውሉን ያደረገው ችሎታ ካለው ሰው ጋር መሆኑ እንዲረጋገጥ ፍ/ቤቱ ግለሰቡን በአካል አስቀርቦ ይመልከትልን፣ ውሉ ቤቱ በሚገኝበት ዲክሲስ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የተመዘገበና የፀና ውል ነው፣ የቤቱ ግምት ብር 9,000 /ዘጠኝ ሺህ ብር/ ሲሆን በወር ከብር 15 /አስራ አምስት ብር/ በላይ የሚከራይ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ አህመድ መሐመድ በሞግዚት ስር የሚገኝ የ16 ዓመት ልጅ መሆኑ በፍ/ቤት ስለተረጋገጠ ልጁ የመዋዋል ችሎታ ሳይኖረው ከባንኩ ጋር የተረገው ውል በህግ ፊት ዋጋ የለውም፣ አመልካች የልጁ ዕድሜ 20 ዓመት ነው በአካልም ቀርቦ ይታይ ከማለት ውጪ ይህንን የሚደግፍ ማስረጃ አላቀረበም፣ ስለዚህ ውሉ ውድቅ ነው፣ አመልካች ለተጠሪ ቤቱን ይመልስ እንዲሁም ቤቱን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ መልሶ እስከሚያስረክብበት ጊዜ ያለውን የቤቱን ኪራይ በወር ብር 100 /አንድ መቶ ብር/ ሂሳብ ታስቦ ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ቅሬታውን ባለመቀበል ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ የመያዣ ውሉ የተፈረመው በ1988 ዓ.ም ስለሆነ ተጠሪ ያቀረቡት የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ በይርጋ የታገደ ነው፣ በስር ፍ/ቤት ግለሰቡ በአካል ቀርቦ ይታይልን ዕድሜውም ይመርመርልን በማለት ያቀረብነው መከራከሪያ የታለፈው ያለአግባብ ስለሆነ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካለው ህግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የበታች ፍ/ቤት የመያዣ ውሉ ይፈርሳል ብሎ የወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የመያዣ /የዋስትና/ ውል በአመልካችና በአቶ አህመድ መሐመድ መካከል የተፈረመው ሚያዝያ 5 ቀን 1988 ዓ.ም መሆኑንና ተጠሪ ለ16 ዓመቱ ልጃቸው ለአህመድ መሐመድ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ሆነው የተሾሙት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 04027 ሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑን ተገንዝበናል። በመሆኑም አቶ አህመድ መሐመድ በ1997 ዓ.ም 16 ዓመት ታዳጊ ከነበረ አከራካሪውን ውል ከአመልካች ጋር ባደረገበት ወቅት /በ1988 ዓ.ም/ የሰባት /7/ ዓመት ህፃን ነበረ ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ባንክ ከአንድ የሰባት /7/ ዓመት ልጅ ጋር የዋስትና /የመያዣ/ ውል አድርጓል ለማለት የማይቻል ነው። በመሆኑም ከላይ የተገለፀው እውነታ ተገናዝቦ ሲታይ አቶ አህመድ መሐመድ ውሉን ከአመልካች ጋር ያደረገው ችሎታ ሳይኖረው ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም። ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ልጁ ችሎታ ሳይኖረው የፈረመው ውል ፈራሽ ይሁንልኝ በማለት ተጠሪ ያቀረቡትን ጥያቄ ተቀብሎ ውሉ ፈራሽ ነው፣ አመልካች ለተጠሪ ቤቱንና የኪራይ ገንዘቡን ይመልስ ሲል የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 07730 ግንቦት 18 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 42931 ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል። ይፃፍ።
2. አቶ አህመድ መሐመድ ክርክር የተነሳበትን ውል ከአመልካች ጋር ያደረገው ችሎታ እያለው ስለሆነ ውሉ አይፈርስም፣ ቤቱንና የኪራይ ገንዘቡንም አመልካች ለተጠሪ እንዲመልስ አይገደድም በማለት ተወስኗል።
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ።
4. መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ዙ/ዘ

ከውል ውጪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 19338

መጋቢት 2 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ዘይነባ ሐሰን

ተጠሪ፡- ፍሬው ተካልኝ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአሁን አመልካች በምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ በመሆን በተጠሪ ላይ የሚከተለውን ክስ አቅርበዋል፡፡ ተከሣሽ ባደረሰብኝ ድብደባ ምክንያት ቀኝ ዓይኔ የጠፋ ሲሆን ተከሣሹም በወንጀል ተከሶ ተቀጥቷል፡፡ በአይኔ ላይ የደረሰውን ጉዳት በሕክምና ለመከታተል ከሚረዳኝ አንድ ሰው ጋር በመሆን ወደ አዲስ አበባ ለሕክምና ስንመላለስ ለትራንስፖርት ብር 2950.90 (ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ሃምሣ ብር ከዘጠና ሣንቲም) ለሆስፒታልና ለመድኃኒት ክፍያ ብር 363.16 (ሶስት መቶ ስልሣ ሶስት ብር ከአሥራ ስድስት ሣንቲም)፣ ለሰው ሠራሽ ዓይን ማስተከያና ለመነጽር ብር 415.00 (አራት መቶ አሥራ አምስት)፣ አ.አበባ ከተማ ለቆየንበት መቶ ሠላሳ አምስት ቀናት ለምግብ፣ ለአልጋና ለታክሲ በቀን ብር ስልሳ ብር ሒሳብ በድምሩ ብር 8100 (ስምንት ሺ አንድ መቶ) እንዲሁም የሞራል ካሳ ብር 1000 ይከፈለኝ በማለት ጠይቃለች፡፡ በተጨማሪም ዓይኔ ሲጠፋ 10ኛ ክፍል የደረስኩና ዕድሜዬም 20 ዓመት የነበረ ሲሆን በጉዳቱ ምክንያት ትምህርቴን በማቋረጤ የመንግሥት ሠራተኛ የመሆን

ፍላጐቱ እውን ሊሆን ባለመቻሉ ዓይኔ ባይታወር ኖሮ በትንሹ በወር ብር መቶ ሃያ መቀጠር እችል የነበረ ሲሆን በመንግሥት ሥራ ላይም እስከ 55 ዓመት እድሜ ብሠራ 35 ዓመት በሥራ ላይ እቆይ የነበረ በመሆኑ ይህም ሲሰላ 120x12x35= ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ) ይሆናል፡፡ ስለሆነም በአጠቃላይ ብር 52,830.56 (አምሳ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም) ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሽ ደርሶ በካሳ መጠኑ ላይ ብቻ ክርክሩን መሠረት በማድረግ የካሳ ክፍያው ጥያቄ በጣም የተጋነነ ከመሆኑም በላይ የማስረጃም ድጋፍ የሌለው ስለሆነ በነጻ ልሰናበት ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የምእራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ከቀረበው ማስረጃ ጋር አገናዝቦ መርምሮ ከሳሽ በደረሰባት ድብደባ ምክንያት አንድ ዓይኗን ያጣች ስለሆነና አንድ ዓይን ያለው ሰው ሁለት ዓይን ካለው ሰው ጋር እኩል የመሥራት ችሎታ እንደማይኖረው ይታመናል ካለ በኋላ ጉዳቱ ሲደርስ ከሳሽ አድሜዋ 27 ዓመት የነበረ ሲሆን ጉዳቱ ባይደርስባት ኖሮ በቀን ብር 4 ሂሳብ በወር ብር 120 በዓመት ብር 1440.00 እንደምታገኝ መረዳት ይቻላል፡፡ ከሳሽ እስከ 50 ዓመት ድረስ ትኖራለች ተብሎ ስለሚገመት በአጠቃላይ ብር 41,760.00 ገቢ ታገኝ ነበር፡፡ ይሁንና በደረሰባት ጉዳት ምክንያት 40%(አርባ በመቶ) የመስራት አቅሟ የቀነሰ ስለሆነ ይህም ሲሰላ ብር 16,800.57(አስራ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ብር ከሃምሳ ሰባት ሳንቲም) ስለሚሆን የሞራል ካሳ ብር 1000 (አንድ ሺህ) ጨምሮ በድምሩ ብር 17,800.57 (አስራ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ብር ከሃምሣ ሰባት ሣንቲም) ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል እንደዚሁም ለመድኃኒት መግዣ ብር 363.05 ለመነጽር ብር 415.40 ለትራንስፖርት ብር 1060.30(አንድ ሺ ስልሳ ከሠላሳ) በአዲስ አበባ ቆይታ የአልጋ የምግብና የታክሲ ከሳሽንና ረዳቷን ጨምሮ ብር 1740.00(አንድ ሺ ሰባት መቶ አርባ) በአጠቃላይ ብር 21,378.92 (ሃያ አንድ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከዘጠና ሁለት ሳንቲም) ተከሳሽ ለከሳሽ ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/377 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበለትም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ የአሁን አመልካች በአንድ ዓይኗ መጥፋት ምክንያት ሠርታ ገቢ ለማግኘት የሚከለክላት ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የወደፊት ጉዳት ካሳ ሊከፈላት ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2090(1) አኳያ ተገቢ አይደለም በማለት በዚህ ረገድ የተወሰነውን የካሳ ክፍያ በመሻር ሕክምናውን ለመከታተል ተጠሪ ያወጣችው ወጭና የሞራል ካሳን በተመለከተ እንዲከፈላት የተወሰነውን አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በአመልካች ላይ አንድ ዓይን የመጥፋት የአካል ጉዳት የደረሰባት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሠርታ ለመኖር የሚከለክላት ነገር የለም በሚል የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበታች ፍ/ቤቶች ካሳ እንዲከፈላት የተሰጠውን ውሳኔ የመሻሩ አግባብነት ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ በፈጸመው ድብደባ ምክንያት የአመልካች የቀኝ ዓይን የጠፋ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

በአመልካች ላይ የደረሰው ጉዳት የአካል ጉዳት እንደመሆኑ መጠን አመልካች ማስረዳት የሚጠበቅባት ጉዳት የደረሰባት መሆኑን ጉዳቱን ባደረሰው የተጠሪ ድርጊትና በተገኘው ውጤት መካከል ቅርብና ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት /cause and effect relationship/ መኖሩን ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2067 መሠረት ኃላፊነቱ በጥፋት ላይ ያልተመሠረተ ጥብቅ /Strict/ ስለሆነ የጉዳት አድራሹን የአእምሮ ሁኔታ /State of mind/ ማስረዳት አይጠበቅባትም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም በዚሁ ላይ

ተመሥርተው የኃላፊነት ውሳኔ የሰጡ ከመሆኑም በላይ ኃላፊነቱ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻው የጉዳዩ ጭብጥ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ኃላፊ ነው ከተባለ ካሳ ለመክፈል ይገደዳልን? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በቅድሚያም ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2090(1)፣ 2091 እና 2092 ድንጋጌዎችን መረዳት እንደሚያስፈልግ ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡

በዚህም መሰረት የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ቀጥሎ የተመለከተው ይዘት አላቸው፡፡

2090 የኪሣራ አከፋፈል

(1) በመደቡ በጉዳቱ ምክንያት ተበዳዩ የሚካሰው ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ካሣ በመክፈል ነው፡፡

2091 የኪሣራው ልክ

ለደረሰው ጉዳት አላፊ መሆኑ በሕግ የታወቀው ሰው የሚከፍለው የጉዳት ካሣ ኃላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን አለበት፡፡

2092 ለወደፊት ሊደርስ ስለሚችል ጉዳት

ለወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተው ጉዳት የተረጋገጠ ሲሆን አስኪፈፀም ሳይጠብቅ ካሳ ሊከፈለው ይገባል፡፡

የብዙ አገራት ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ሕጎች ሁለት ግቦችን ማለትም ጉዳቱን የመካስ /Insurace goal/ እና የጥፋት ባህሪን የመግራት /Deterrence goal/ ተብለው የሚታወቁትን መርሆች መሠረት በማድረግ የተቀረጹ ሲሆን የኢትዮጵያ ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ሕግም ይህንኑ ዓላማ አካቶ እንደተቀረጸ በሕጉ ላይ ማብራሪያ የጻፉት ፕሮፌሰር ጆርጅ ቼቺኖቪች /The Ethiopian law of compensation for damages/ በሚለው ማብራሪያቸው ላይ አንጸባርቀውታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ በተጠቀሱት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2092 መርሆች መሠረት ካሳና ጉዳት እኩል መሆን እንዳለበት ይህ ማለትም በመርህ ደረጃ ተጎጂው ከጉዳቱ አትራፊ መሆን እንደማይገባውና ከደረሰበትም ጉዳት በታች መካስ እንደሌለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተግባርና በተጨባጭ ሲታይ የጉዳት መጠኑ በፍርድ ቤቱ የሚወሰን ቢሆንም ጉዳዩ የሕግ ጥያቄ ብቻ ባለመሆኑ ውስብስብነት ያለው ከመሆኑም ሌላ ሕጉ በተጨባጭ የደረሰ ጉዳት ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትም የተረጋገጠ ሲሆን እንዲካስ ስለሚፈቅድ ወደፊት ስለሚሆን ነገር እርግጠኛ መሆን ስለማይቻል በካሳ አወሳሰን ረገድ ስሌትን የማዛነፍ ውጤት ያስከትላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተየያዘም በካሳ አወሳሰን ረገድ ከንብረት ጉዳት ይልቅ አተማመኑ የበለጠ ውስብስብ የሚሆነው የደረሰው ጉዳት የአካል ጉዳት በሚሆን ጊዜ ነው፡፡ በእርግጥ በጉዳቱ ምክንያት የተከፈለ ወጪ፣ ለመድኃኒት መግዣ እንደዚሁም ለሰው ሠራሽ የአካል ምትክና ተጎጂው ወደ ሆስፒታል የተመላለሰበት ወጪ የጉዳት ካሳው አካል ስለሆነና በቀላሉም በማስረጃ የሚረጋገጥ በመሆኑ በአወሳሰን ረገድ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ ነገር ግን ጉዳቱ የዘላቂነት ባህሪይ ሲኖረውና የተጎጂው የመሥራት አቅም በሙሉ ወይንም በከፊል ሲጓደል በጉዳት ካሳው አተማመን ረገድ አስቸጋሪ ሁኔታ መፈጠሩ አይቀርም፡፡

ስለሆነም ካሳ ከደረሰው ጉዳት ጋር አኩል ሆኖ መመዛዘን አለበት ሲባል መታየት የሚገባው በአጠቃላይ በተጎጂው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ የመሥራት ኃይል ቅነሳ /General utility/ አንጻር እንጂ ከጉዳቱ በፊት ሲሠራው የነበረውን ሥራ ላለመሥራት ጉዳቱ ያስከተለውን ልዩ ጫናና የቅነሳ መጠን /special utility/ ግምት ውስጥ በማስገባት አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በተጨባጩ ዓለም ሲታይ እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ሥራ ለመሥራት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ እንደ ሰው ለመኖር የተለያየ ፋይዳና ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ነው፡፡

በእኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች ላይ የደረሰው ጉዳት የአንድ ዓይን መጥፋት ሲሆን ይህም ጉዳት ዘላቂ ከፊል ስንኩልነት /Permanent partial disablement/ ተብሎ የሚመደብ ነው፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ለአመልካች የወደፊት ጉዳት ካሳ ሊከፈላት አይገባም ያለው አንድ ዓይኗን ያጣች ቢሆንም ወደፊት ሥራ ሠርታ ገቢ ከማግኘት ጉዳቱ አይከለክላትም በማለት ነው፡፡

ነገር ግን ጉዳት መድረሱ በተጨባጭ እስከተረጋገጠ ድረስ ለተጎጂው ካሳ አይከፈለውም ማለት ከላይ የተመለከተውንና ጉዳትን የመካስና የጥፋት ባህሪን የመግራት የሕጉን ዓላማንና ግብ የሚጻረር ነው፡፡ አመልካች በደረሰባት የአንድ ዓይን መጥፋት ምክንያት ሙሉ ለሙሉ የመሥራት ችሎታዋን አጥታለች ባይባልም ከላይ እንደተመለከተው ካሳ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን አለበት ሲባል ከአጠቃላይ የመሥራት ኃይል ቅነሳ ጋር ተገናዝቦ እንጂ ከልዩ የመሥራት ኃይል ቅነሳ ጋር ተገናዝቦ ባለመሆኑ አመልካች አንድ ዓይኗን ማጣቷ በወደፊት ሕይወቷ የገቢ መጠን መቀነስ ባያስከትልም እንኳን በአጠቃላይ እንደ ሰው ለመኖር በእያንዳንዱ የእለት ሕይወቷና እንቅስቃሴ ላይ ጉዳት /Punitive damage/ መድረሱ ምክንያታዊ እርግጠኛነት /Reasonable Certainty/ ያለው በመሆኑ ከአጠቀላይ የሕጉ ዓላማም ሆነ ከቁጥር 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች አንጻር ካሳን መወሰን አግባብነት ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳት የደረሰበት ወገን የደረሰበትን ጉዳት ልክና ጉዳት አድራሹ ካሳ በመክፈል ረገድ ያለበትን ግዴታ ማስረዳት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2141 ላይ የተመለከተ ቢሆንም ተጎጂው ጉዳት የደረሰበት መሆኑን አረጋግጦ ነገር ግን የካሳውን መጠን ለመገመት አስቸጋሪ ሁኔታ በሚያጋጥም ጊዜ በቁጥር 2102 መሠረት ዳኞች የካሳውን መጠን በርትዕ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ ይህም ጉዳት የደረሰበት ሰው የካሳውን መጠን በማስረዳት ረገድ ያለበትን ሸክም በመጠኑም ቢሆን እንደሚያቀልለት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለልም አመልካች ጉዳት የደረሰባት ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ጉዳቱም በወደፊት ሕይወቷ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኛነት ያለው ስለመሆኑም የተረጋገጠ በመሆኑ ሊወሰን የሚገባውም የካሳ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2102 መሰረት በርትእ መወሰን የግድ የሚል በመሆኑ በዚሁ መሠረትም የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የካሳውን መጠን በርትእ መወሰኑ በይግባኝ የተመለከተውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሳኔ ማጽናቱ አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይህንኑ ውሳኔ በመሻር ለአመልካች የወደፊት ካሳ ሊከፈል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 04500 ጥር 9 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍ/ቤት በመ.ቁ. 210/93 በሚያዝያ 16 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.2444/95/1 በነዳር 8 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 21296

ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍሰሐ ወርቅነህ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኔዘርላንድ ልማት ድርጅት አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ውበት አድባሩ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ክስ ባቀረበበት ጉዳይ አመልካች ኃላፊ ነው በማለት ካሣ እንዲከፍል ውሣኔ በመስጠታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በሞግዚቱ አማካይነት በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካችና በሥር 1ኛ ተከሣሽ ላይ ባቀረበው ክስ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነውን መኪና 1ኛ ተከሣሽ ሲያሽከረክር ተሳፍሬ በመንገዝ ላይ ሳለሁ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት የአካል ጉዳት የደረሰብኝ ስለሆነ የሞራል ካሣን ጨምሮ ብር 31ሺህ ተከሣሾች እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የሥር 2ኛ ተከሣሽ የአሁን አመልካችም በሰጠው መልስ በኃላፊነትና በካሣ መጠኑ ላይ ክርክር ያቀረበ ሲሆን በኃላፊነት ረገድ ባቀረበው ክርክር ከሣሽ በመኪናው ተሳፍሮ ሲጓዝ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት ጉዳቱ የደረሰ መሆኑን አምኖ ነገር ግን ከሣሽ የተሳፈረው ገንዘብ ከፍሎ ሳይሆን በነፃ ለምኖ ስለሆነ ኃላፊነት የለብኝም ብሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1ኛ ተከሣሽም የመኪናው ባለንብረት 2ኛ ተከሣሽ ስለሆነ በኃላፊነት ተጠያቂ ልሆን አልችልም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ማስረጃ ከሰማ በኋላ 2ኛ ተከሣሽን በከሣሽ ላይ ጉዳቱ የደረሰው በነፃ ተሳፍሮ በመንዝ ላይ እንዳለ ነው ቢልም ያቀረባቸው ምስክሮች ይህንን ካለማስረዳታቸውም በላይ አስረድተው የነበረ ቢሆን እንኳን 2ኛ ተከሣሽ በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆን የማይችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2081(2) ላይ እንደመለከተው መኪናው የተሰረቀበት መሆኑን ባስረዳ ጊዜ ብቻ ስለሆነ ሁለቱም ተከሣሾች ኃላፊ ናቸው በማለት በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከርክሮ ኃላፊነትን በተመለከተ ይግባኝ ባይ /የአሁን አመልካች/ መ/ሰጭው በመኪናው ተሳፍሮ የተንዘው ገንዘብ ሳይከፍል በነፃ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2089(1)መሠረት ኃላፊነት የለብኝም የሚል ክርክር ቢያቀርብም የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት መ/ሰጭም የይግባኝ ባይን መኪና እራሱ ይዞ በሚገለገልበት ጊዜ ጉዳት ደርሶ በሚገኝበት ጊዜ እንጂ መኪናዋ በይ/ባይ ቁጥጥር ሥር እያለች መ/ሰጪው ዋጋ ሳይከፍል ስለተንዘ ብቻ ተፈፃሚነት አይኖረውም በማለት በዚህ ረገድ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ አድርጎ የካሣ መጠኑንም በተመለከተ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የደረሰውን ጉዳት መሠረት ያደረገ ስለሆነ ይግባኙ ተቀባይነት የለውም ብሎ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት በአመልካች መኪና በነፃ ሲንዝ ከሆነ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2089(1) አኳያ አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን ጠርቷል፡፡ ሆኖም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ተጠሪ ባለመቅረቡ የአመልካችን የቃል ክርክር ብቻ ችሎቱ አዳምጧል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ክስ በቀረበበት ጉዳይ አመልካች ኃላፊ ነው መባሉ በአግባቡ ነው አይደለም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ተጠሪ ተሳፍሮበታል የተባለው መኪና ባለንብረት እንደመሆኑ መጠን የሚኖርበት ኃላፊነት ጥብቅ /strict/ ስለሆነ ተጠሪ ማስረዳት የሚጠበቅበት አመልካች የዚሁ ተሽከርካሪ ባለቤት መሆኑንና በዚሁ ንብረትም ሲንዝ ጉዳቱ የደረሰ መሆኑን ብቻ ሲሆን በዚሁ መሠረትም ተጠሪ በማስረጃ አረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩልም ጥፋት ሳይኖር ለሚደርስ ኃላፊነት ሕጉ ሦስት መከላከያዎችን ያስቀመጠ ሲሆን እነዚህም የተጎጂው ጥፋት፣ የውል ግንኙነት መኖርና ጥቅም የሌለው ግንኙነት /disinterested parties/ መሆናቸውን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2069፣ 2071፣ 2086፣ 2088፣ እና 2089 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ አንቀጽ በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ባቀረበው ክርክር ተጠሪ በመኪናው ላይ የተሳፈረው ገንዘብ ከፍሎ ሳይሆን በነፃ መሆኑን ገልጾ ይህንን ፍሬ ነገር ያስረዱልኛል ያላቸውን ሁለት ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ እነዚህ ሁለት ምስክሮች የሰጡት የተሟላ የምስክርነት ቃል ዋናው የፍ/ቤቱ መዝገብ ወይንም ምስክርነት ቃላቸው ተገልብጦ ባለመቅረቡ ምክንያት ዝርዝር ቃላቸውን መገንዘብ ባይቻልም ፍ/ቤቱ ከሰጠው ውሣኔ ላይ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ገንዘብ ከፍሎ በመንዝ ላይ የነበረ አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በይ/ባይ መኪና የተሳፈረው ጥቅም ሳይኖር መሆኑን ይህ ችሎት ለመገንዘብ ችሏል፡፡

ግንኙነቱ ጥቅም የሌለው በሆነ ጊዜ ደግሞ ጉዳት የደረሰበት ወገን ከውል ውጭ ኃላፊነት ድንጋጌዎችን ጠቅሶ ለመከርከርና ካሣ ለመጠየቅ እንደማይችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2089 (1) ላይ ተመልክቷል፡፡ ባለሀብቱም ሆነ የንብረቱ ጠባቂ ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉት ጥፋት ከፈፀሙ ብቻ እንደሆነ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር (2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጎጂው ከውል ውጭ ኃላፊነትን ድንጋጌ ጠቅሶ ካሣ መጠየቅ የሚችለው አደጋው የደረሰው በባለቤቱ ወይም በጠባቂው ጥፋት መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ሲሆን የባለቤቱ ወይም የጠባቂው ኃላፊነት የሚመሰረተው በቁጥር 2084(1) ወይንም 2082(1) ድንጋጌ ሳይሆን በጥፋት ላይ የተመሠረተ ኃላፊነትን በሚመለከት በቁጥር 2028 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከዚህም አኳያ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ማስረጃ ሲታይ አመልካች የተሽከርካሪው ባለንብረት መሆኑን በዚህ ተሽከርካሪም ተሳፍሮ ሲጓዝ መንገድ ላይ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ነው፡፡ ይህ ማስረጃ በጥፋት ላይ ላልተመሰረተ ኃላፊነት በቂ ቢሆንም ጉዳቱ የደረሰው በንብረቱ ባለቤት ወይንም በጠባቂው ጥፋት መሆኑን ግን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡

ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2089(2) አኳያ ሳይመለከት አመልካች ኃላፊ ነው ማለቱ በአግባቡ ካለመሆኑም በላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከዚህ ድንጋጌ ጋር አያይዞ መርምሮ በቁጥር 2089 (1) አነጋገር መሠረት ባለሀብቱ ወይም ጠባቂው አንድ ጥቅም ሳያገኝ በእንስሳው፣ በሕንፃው ወይም "በሌላ ነገር" ይገለገል የነበረው ተብሎ ከተዘረዘረው "በሌላ ነገር" የሚለው ቃል ተሽከርካሪን የሚያጠቃልል ስለመሆኑ አስራሪ እንደሆነ በውሣኔው ላይ አስፍሮ፣ ያጠቃልላል ቢባል እንኳን ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት የአመልካች መኪናን እራሱ ይዞ በመገልገል ላይ ሳይሆን የመኪናዋ ሹፌር መኪናዋን ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ እያለ ስለሆነ ድንጋጌው ተፈፃሚነት የለውም በማለት ያሰፈረው ውሣኔ አግባብነት የለውም፡፡ ይሁንና በቁጥር 2089 (1) ሥር ከተዘረዘረው ላይ "ሌላ ነገር" የሚለው ቃል ሌላ ሰው ሊገለገልበት የሚችል ተሽከርካሪን ጨምሮ ሌላ ማንኛውም ዓይነት ንብረት እንደሚያጠቃልል መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ በሕጉ ላይ መገልገል የሚለው ቃል ተጠሪ የአመልካችን መኪና እራሱ ይዞ እያሽከረከረ በሚገኝበት ጊዜ ነው የተባለውንም በተመለከተ ያለጥፋት ኃላፊነት /strict liability/ ከአንድ ንብረት ባለቤትነት ከሕንፃ፣ ከእንስሳ፣ ከተሽከርካሪና ከሌሎችም ዓይነት

ንብረቶች ሊመነጭ የሚችል እንደመሆኑ መጠን በእነዚህ ንብረቶች ላይ መገልገል እስከተቻለ ድረስ ከማንኛውም ሁኔታ ጥቅም ሳይኖር የተገለገለ ሰው ጉዳት ቢደርስበት ኃላፊነት እንደሚኖር መገንዘብ ከሚቻል በስተቀር ተጎጂው እራሱ ተሽከርካሪውን ማሽከርከር አለበት የሚለው አገላለጽ በጠባቡ የተተረጎመና በተለይም ከተሽከርካሪ ውጭ ባሉ የተለያዩ ንብረቶች ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው ስለማይችል ፍ/ቤቱ ለሕጉ የሰጠው ትርጉም የተሳሳተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሰሜን ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 60/94 ግንቦት 21 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 222/95 በግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ጥፋት መፈፀሙ ያልተረጋገጠ ስለሆነ ኃላፊ አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደመዝገብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.22509

ጥቅምት 7 ቀን 2000

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፣ አቶ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ ቀረበ

ተጠሪ፣ ዳርጌ ሰምሮ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው የአሁኑ አመልካች ታህሳስ 24 ቀን 1999 ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አሻሻሎ ባቀረበው ክስ፣ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች በሆነ የሰሌዳ ቁጥር 01-13261 አ.አ የሆነ ታክሲ በሐምሌ 5 ቀን 1991 ዓ.ም ቤልኤር አካባቢ ገጭቶ ጉዳት ያደረሰብኝ ስለሆነ የጉዳት ካሣ 20,000 (ሀያ ሺ.)፣ የሞራል ካሣ 1,000 (አንድ ሺ.)፣የተጓደለ ገቢ 123,000 በድምሩ ብር 149,820 (አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሃያ ብር) እንዲከፈለኝ የሚል ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ፣በተጠሪ ላይ የደረሰው ቀላል ጭረት ነው፡፡ ጉዳት ደረሰብኝ ለሚለው ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ተጠሪን አደጋው ደረሰ በተባለ ጊዜ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታልና የካቲት 12 ወስዶ ያሳከመ መሆኑንና ደህና ነው ተብሎ የተሰናበት መሆኑን ገልጾ የተከራከረ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል ያቀረበው ማስረጃ ጉዳት ማድረሱን ያረጋግጣል በማለት በርትዕ 15,000 (አሥራ አምስት ሺ.) የጉዳት ካሳ፣የሞራል ካሣ 1000 ጠቅላላው 16,000 (አሥራ ስድስት ሺ.) እንዲከፈል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

ይህ ችሎት ሰኔ 20 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት ለተጠሪ የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው የተወሰነው ጉዳት ያደረሰ ስለመሆኑ ተረጋግጦ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ቀርቦ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር እንዲሰማ ትዕዛዝ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ተጠሪ የጋዜጣ ጥሪ ተደርጐለት ሊቀርብ ባለመቻሉ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቶ የቀረበውን የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ በሥር ፍ/ቤት በከሳሽ በኩል ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጡ የተባሉት ምስክሮች ያረጋገጡት ነገር ሲኖር ተጠሪ በደረሰበት አደጋ የካቲት 12 ሆስፒታል እየተመላለሰ ይታከም የነበረ መሆኑን ነው፡፡ አሁን በመጨረሻ ተጠሪ ለጉዳቱ ማስረጃ አድርጐ ያቀረበው የሕክምና ማስረጃ አደጋው ደረሰ በተባለ ጊዜ ሕክምና ሲከታተልበት ከነበረው ሆስፒታል ሳይሆን ከዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል መሆኑ ታውቋል፡፡ ተጠሪ በእርግጥ ጉዳት ደርሶበት ቢሆን ኖሮ የሕክምና ማስረጃዎቹን አሟልቶ ሊያቀርብ ይገባ የነበረው ሕክምና ከተከታተለበት ሆስፒታል እንጂ ከቆይታ በኋላ ምንም የሕክምና ክትትል ካላደረገበት ሆስፒታል ሊሆን ባልተገባ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ በሥር ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት የሆነው ማስረጃ ተጠሪ ለክሱ መነሻ በሆነው መኪና ሳቢያ ጉዳት የደረሰበት ለመሆኑ የሚያስርዳ አይሆንም፡፡ ምንም እንኳን ይህ ችሎት ተጠሪ በወቅቱ ሕክምናውን ይከታተል ነበር ከተባሉባቸው ሆስፒታሎች የሕክምና ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ ያደረገው ጥረት የተፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ ያልቻለ ቢሆንም ተጠሪ በበኩ ጉዳዩን ተከታትሎ ዳር ለማድረስ ያልፈለገ መሆኑ ሲታይ ለስር ፍ/ቤት ቀርቦ ለጉዳቱ ማረጋገጫ ተደርጐ የተወሰደው የሕክምና ማስረጃ አጠራጣሪ ሊሆን እንደሚችል ይህ ችሎት ተቀብሎታል፡፡

ባጠቅላይ የሥር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የሕክምና ማስረጃ ለክሱ ምክንያት ከሆነው ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር ሳይኖር የተደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

የሥር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የሕክምና ሰርተፍኬት ለክሱ ምክንያት ከሆነው ጉዳይ ጋር ግንኙነት የለውም ብለናል፣

-የፌ/መ/ደ/ፍቤት በመ/ቁ.01187 ጥቅምት 13 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ጎዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ.26303 የሰጡዋቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፡፡

-መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

የሰበር መ/ቁ. 23924

የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቢሲንያ ባንክ - እስክንድር ጐይተኦም ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- አበበ ከበደ (አቶ) - ጠበቃ ግርማ ሃይሌ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስህተት ወደማይመለከተው የባንክ ሂሣብ የገባውና የተወሰደውን ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት አመልካች ባቀረበው ክስ መነሻነት የታየውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ለቀረበበት ክስ የመከላከያ መልስ ከመስጠቱም በተጨማሪ በበኩሉም ከሂሣቡ ያለአግባብ ወጥቶ ተወስዶአል ያለውን ገንዘብ ይከፈለው ዘንድ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቦአል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ አመልካች ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎአል፣ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ ግን የተቀበለው ሲሆን፣ በዚህ መሠረትም አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፣ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አመልካች መጋቢት 11 ቀን 1998 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በተጠሪው የባንክ ሂሣብ ውስጥ በስህተት ገባ የተባለውን ገንዘብ ተጠሪ ሊመልስ አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝብን መርምረናል።

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር በዝርዝር ተመልክተናል። ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተከፈተውን መዝገብ (ቁ. 144) አስቀርበን ተመልክተናል። በዚህ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው አመልካች ካቀረባቸው ማስረጃዎች መሃል ተጠሪ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ሲከፍት የሞላው ቁጥር 003 እንደነበር፣ እና አቶ ዮሐንስ ክፍሌ የተባሉት ደግሞ ልዩ የቁጠባ ሂሣብ ቁጥር 003 መክፈታቸውን፣ አቶ ሚካኤል ስዩም የተባለ ሰው በእነ አቶ ዮሐንስ ክፍሌ ልዩ የቁጠባ ሂሣብ ብር 29,417.00 ያስገባበት የጥሬ ገንዘብ ማስገቢያ ቅጽ እና የባንኩ ገንዘብ ያዥ ገንዘቡን ለመቀበሉ የፈረመበትና ማህተም ያደረገበት ደረሰኝ፣ ከዚህ በኋላ ተጠሪ በተለያዩ ጊዜአት ገንዘብ ወጪ አድርጎ መውሰዱን የሚያሳዩ ቼኮች እና የባንኩ ዋና ተቆጣጣሪ ለባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅና የቦርዱ ሊቀመንበር ያቀረበው ማስታወሻ እንደሚገኙ ከመዝገቡ አረጋግጠናል። ተጠሪም ባቀረበው መልስ ገንዘቡን ሊመልስ እንደማይገባ በመግለጽ የተከራከረ ቢሆንም፤ በማስረጃ ረገድ ግን የተባለውን ገንዘብ በትክክለኛ መንገድ ወደ እሱ የገባ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም። በመከላከያ ማስረጃነት የጠቀሳቸው በባንኩ ተንቀሳቃሽ ሂሣብ መክፈቱን፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው የተመዘገበ ነጋዴ መሆኑ እና ባንኩ (አመልካች) በሂሣቡ ውስጥ ብር 32,951.00 እንዳለው አረጋግጦ ጽፎለት የነበረ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው።

እንደምንመለከተው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ ብር 29,417.00 ባንክ እንዲገባ ያዘዘው አቶ ሚካኤል ስዩም በእነ አቶ ዮሐንስ ክፍሌ ስም በተከፈተው ልዩ የቁጠባ ሂሣብ እንዲገባ እንጂ በተጠሪ ስም በተከፈተው ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ውስጥ እንዲገባ አላዘዘም። በእርግጥ ይህ ገንዘብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በእነ አቶ ዮሐንስ ክፍሌ ስም በተከፈተው ልዩ ሂሣብ መግባት ሲገባው የባንኩ ሠራተኛ በፈጸመው ስህተት የተነሣ በተጠሪ ስም በተከፈተው ተንቀሳቃሽ ሂሣብ ውስጥ እንዲገባ ስለመደረጉ አመልካች በክሱ ገልጾአል። በኋላ በባንኩ ዋና ተቆጣጣሪ በተደረገው ማጣራትም ገንዘቡ በስህተት ወደማይገባው ሂሣብ ቁጥር ገብቶ መገኘቱ ታውቆአል። በመሆኑም እዚህ ላይ ሊነሳና መልስም ሊያገኝ የሚገባው ዋናው ጥያቄ አመልካች እንደክሱ ለማስረዳት አቅርቦ ካሰማው ማስረጃ ውጪ ምን የተለየ ማስረጃ እንዲያቀርብ ይጠበቅበት ነበር? የሚለው ነው። በበኩላችን እንደምናየው አመልካች የጉዳዩን አነሳስና ሂደት በትክክል የሚያሳዩ ማስረጃዎችን አቅርቦአል። ማስረጃዎቹ ሚዛን ውስጥ ገብተው ቅለታቸውና እና ክብደታቸው ሊታይ ይችል የነበረው ተጠሪ ገንዘቡ ከተባለው ወጪ በሆነ ሁኔታ ማለትም በትክክለኛ መንገድ ወደ ሂሣቡ የገባ መሆኑ የሚያሳዩ ማስረጃ አቅርቦ ቢሆን ነበር። ከክርክሩ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው እንኳንስ መከላከያ ማስረጃ ሊያቀርብ ቀርቶ ገንዘቡ ወደ ሂሣቡ ከየት በኩል እንደገባለት እንኳን ሊገልጽ አልቻለም። ይህም ማለት የማስረዳት ሸክሙን ያልተወጣው ወይም መከላከል ያልቻለው ተጠሪ ነው ማለት ነው። ሁኔታው ይህ በሆነ ጊዜም አመልካች እንደክሱ አላስረዳም ከሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የሚያስችል የሕግ ምክንያት አይኖርም። በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል።

ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 00144 ታሕሣሥ 29 ቀን 1996 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27479 ጥር 10 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል።
2. ተጠሪ ያለአግባብ የወሰደውን ብር 29,417 (ሃያ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ አስራ ሰባት ብር) ክሱ ከቀረበበት ሚያዝያ 30 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ ተከፍሎ አለቀ ድረስ 9% (ዘጠኝ በመቶ) በመጨመር ለአመልካች ይክፈል ብለናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና 23 በር ችሎት መዝገብ ሲያስከፍት የከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ተጠሪ ይተካለት ብለናል፡፡
4. አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነው ብር 3250(ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) በስህተት ወደተጠሪ ሂሣብ ገብቶአል በተባለው ብር 29,417.00 የሚጠቃለል በመሆኑ አመልካች የሚከፍልበት ምክንያት የለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጣው ቁጥር 144 የሆነው መዝገብ መደመጣበት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 24818

የካቲት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ይልቃል በእውቀቱ - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ስዩም አባዲ ወኪሉ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በመኪና አደጋ ደረሰ የተባለውን ጉዳት መሠረት በማድረግ የቀረበ የካሣ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ብ/ክ/መ/ በደቡባዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረውም የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ የአሁኑ አመልካች ንብረት በሆነው የጭነት መኪና ተሳፍሮ ሲሄድ ሳለ መኪናው በመገልበጡ አደጋው የደረሰበት መሆኑን በመግለጽ ካሣ እንዲከፈለው ክስ መስርቶአል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ኃላፊነቱንና የኃላፊነቱን መጠን በማስመልከት ክርክሩን ያሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ፣ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ በመሆኑ ብር 55370.00 /ሀምሣ አምስት ሺ ሶስት መቶ ሰባ/ ካሣ ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እና የሰበር ችሎትም ውሣኔው ትክክል ነው ብለውታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 8 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የሥር ፍ/ቤቶች አመልካችን ኃላፊ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2089 /2/ አንፃር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲታይ ያለውን አግባብነት ለመመርመር ነው። በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

ተጠሪ ካሣ የጠየቀበት ጉዳት ደረሰብኝ የሚለው በአመልካች መኪና ተሳፈሮ ሲሄድ በነበረበት ጊዜ መኪናው በመገልበጡ ነው። መኪናው ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የተመደበ ሳይሆን የደረቅ ዕቃ መጫኛ እንደሆነም አላከራከረም። በእርግጥ አመልካች በአጠቃላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ አይደለሁም በማለት የተከራከረ ሲሆን በተለይ ደግሞ የተጠሪን በመኪናው ላይ መሳፈርም ይክዳል። ተጠሪም ተሳፍሮ ሲሄድ ጉዳቱ እንደደረሰበት ከመግለጽ አልፎ በምን ሁኔታ መኪናው ላይ ሊሳፈር እንደቻለ ሊያስረዳ አልቻለም። መኪናውን ያሽከረክር ከነበረው ሹፌር ጋር ያደረገው ውል እንደነበረ በክርክሩ ላይ አላነሳም። በአጠቃላይ ገንዘብ ከፍዬ ነው የተሳፈርኩት አይልም። በመሆኑም በእርግጥም በመኪናው ተሳፍሮ ነበር። እንዲሁም በመኪናው መገልበጥ ምክንያትም ጉዳቱ ደርሶበታል ቢባልስ አመልካች ኃላፊ የሚሆንበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለው ነጥብ መመርምሩ ተገቢ ይሆናል።

እንደምንመለከተው ተጠሪ በአመልካች መኪና ላይ ተሳፍሮ መንዘሙ በመኪናው መጠቀሙን ያሳያል። በዚህ ረገድም ተጠቃሚ የሆነው ተጠሪው ብቻ ነው። የመኪናው ባለቤት /አመልካች/ ከተጠሪ ገንዘብ /የትራንስፖርት/ በመቀበል ጥቅም አላገኘም። ከዚህ የተነሣም ሁኔታው ጥቅም የሌለው ግንኙነት በሚል ከተደነገገው ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2089 አንፃር የሚታይ ይሆናል። ግንኙነቱ ጥቅም የሌለው በሆነ ጊዜ ጉዳት የደረሰበት ወገን ከውል ወጪ ኃላፊነት ድንጋጌዎችን ጠቅሶ ለመከራከርና ካሣ ለመጠየቅ እንደማይችል በንዑስ ቁ. /1/ የተመለከተ ሲሆን፣ ባለሀብቱም ሆነ ጠባቂ ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉት ጥፋት ከፈፀሙ ብቻ እንደሆነ በንኡስ ቁ. /2/ ተደንግጓል። ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተጎጂው ከውል ውጪ ኃላፊነት ድንጋጌን ጠቅሶ ካሣ መጠየቅ የሚችለው ጉዳቱ የደረሰበት በንብረቱ ባለቤት ወይም በጠባቂው ጥፋት መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው። በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካች ወይም የሹፈሩ ጥፋት ሰለመኖሩ ሊያስረዳ አልቻለም። ይልቁንም ክሱን በአመልካች ላይ የመሠረተው ባለቤትነቱን መሠረት በማድረግ ብቻ እንደሆነ ነው ከመዝገቡ ማየት የቻልነው። ስናጠቃልለው ተጠሪ ከአመልካች የጉዳት ካሣ የሚጠይቅበት የሕግ ምክንያት አለ ለማለት የሚቻል አይደለም። በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔም የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በትግራይ ብ/ክ/መ/ የደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 448/97 /00458/96/ በታሕሣሥ 6 ቀን 1998 ዓ.ም. የተሰጠው እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14674 መጋቢት 4 ቀን 1998 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል።
2. አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ አይደለም ብለናል።
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ። መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 27565

ታህሣሥ 01 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ አለማየሁ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. አቶ ደምሴ ወርቅነህ - ቀረቡ፡፡

2. ጂነሲስ ፊርምስ ኢት/ኃ/የተ/የግ/ማ - አልቀረበም፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የጀመረው በምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪና አቶ ሙሉጌታ ጌታቸው በተባሉት ላይ በመሠረተው ክስ አቶ ሙሉጌታ ጌታቸው የ2ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነችውን መኪና ሲያሽከረክር የ1ኛ ተጠሪ ታክሲን ገጭቶ ጉዳት በማድረሱ እና ታክሲዋ ከጥቅም ውጪ በመሆኗ የታክሲዋን ዋጋ ብር 80,000 (ሰማንያ ሺ.) ፣ ታክሲዋ የምታስገባው ገቢ የ211 ቀናት በቀን 100 ብር ታስቦ ብር 21,000 (ሀያ አንድ ሺ.) እና መኪናዋን ለማስጎተት የወጣው 200 ብር በድምሩ 101,300 ብር እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ መድን ድርጅት ጣልቃ እንዲገባለት በጠየቀው መሠረት አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ ስለገባና ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ታክሲዋ ከጥቅም ውጪ በመሆኗ የመኪናዋን ዋጋ 80,000 ብር የተቋረጠ ገቢ ብር 18,300 እና መኪናዋን ለማስጎተት የወጣውን ብር 200 2ኛ ተጠሪና መድን ድርጅት በመድን ሽፋኑ መሠረት እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዟል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ይህ ችሎትም መኪናው ወድሟል ተብሎ የመኪናው ዋጋ ከተከፈለ በኋላ እንደገና የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈል መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፤ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የ1ኛ ተጠሪ መኪና ንብረትነቱ የ2ኛ ተጠሪ በሆነ መኪና ተገጭቶ ሙሉ ለሙሉ መውደሙ የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት 2ኛ ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ተብሏል፡፡ በደረሰው ጉዳትም የ1ኛ ተጠሪ መኪና ሥራ ላይ ተሠማርቶ ሊያስገኝ ይችል የነበረው ገቢ ተቋርጧል፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ በመኪናው ላይ በደረሰው ጉዳት ብቻ ሣይሆን በጉዳቱ ምክንያት ለተጠሪ ገቢ ማጣትም ተጠያቂ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አንዱ ጉዳት ብቻ ተመርጦ እንዲከስ የሚደረግበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ጉዳት ሊካስ የሚገባው ከጉዳቱ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 2090 የተመለከተ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ የመኪናውን ዋጋም ሆነ የታጣውን ገቢ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ የሕግ ነጥብ ላይ የሠበር ችሎት በመ/ቁ. 12479 እና 25589 የሰጠውን ትርጉም መመልከት ይቻላል፡፡

የአሁን አመልካች ካሣውን እንዲከፍል የተወሰነው ለ2ኛ ተጠሪ የመድን ሽፋን በመስጠቱ ምክንያት ነው፡፡ አመልካችም መኪናው ወድሟል ተብሎ የመኪናው ዋጋ ከተከፈለ በድጋሚ የታጣ ገቢ እንዲከፈል መወሰኑ ሁለቴ እንዲካስ ማድረግ ነው ከማለት በቀር የታጣ ገቢ ሊከፈል የማይገባበትን ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ሌላ ክርክር አላቀረበም፡፡ በእርግጥ በሠበር ችሎት በሰጡት የመ/መልስ ላይ ለመኪናው ዋጋ በተከፈለው ገንዘብ መኪና ገዝተው በመጠቀም ገቢው እንዳይቋረጥባቸው ማድረግ ሲገባቸው ወይም የተቋረጠ ገቢን የሚተካ የመድን ዋስትና /Consequential loss policy/ በመግዛት ገቢያቸው እንዳይቋረጥባቸው ማድረግ ሲገባቸው ይህንን ሣያደርጉ የመጣባቸውን ጉዳት ሊጠይቁ አይገባም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለ2ኛ ተጠሪ በሠጠው የመድን ሽፋን ውል የታጣ ገቢ ላለመክፈል የተስማሙ ለመሆኑ ወይም ሌላ ተመሣሣይ ክርክር አላቀረቡም፡፡ ከሥር ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው የመኪናውን ዋጋና የተቋረጠ ገቢ አጣምረን ልንከፍል አይገባም የሚል በመሆኑና ይህ ደግሞ ከፍ ሲል ከተዘረዘረው ምክንያት ተቀባይነት ያለው ክርክር ባለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ማለት አልተቻለም፡፡

ው ሣ ኔ

የምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04782 በ12/7/98 የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40263 በ5/3/99 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 27623

ጎዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ -ነ/ፈጅ ተስፋዬ ምንዳገኝ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ውባየሁ አበበ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሲከፍለኝ የነበረውን የጡረታ አበል ሌላ ባል ሳላገባ አግብተሻል በሚል ምክንያት ያቋረጠ ስለሆነ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት በምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች የጡረታ አበል ክፍያውን ያቋረጠው ያለ አግባብ ስለሆነ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ በመስጠቱና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በድምጽ ብልጫ ይግባኙን በመሰረዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

ይህ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ክስ የቀረበበት ጉዳይ በፍ/ቤት ሊታይ የሚችል ስለመሆኑ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የጡረታ አበል ክፍያን በተመለከተ ይህ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 18342 ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የማኅበራዊ ዋስትና ባለሥልጣንን በአዲስ መልክ ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 5፣ 8 እና 11ን በመተርጎም የማኅበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በሕጉ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የማኅበራዊ ዋስትና መብት ጥቅምን በሚመለከት በሚሰጠው ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ለማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንደሆነ ጉባኤውም የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ መሆኑን በሕግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን እንደሌለው በመዘርዘር የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ተጠሪ ተቋርጦብኛል የሚሉት የጡረታ አበል ክፍያን በተመለከተ አቤቱታውን ማቅረብ የሚገባቸው ለማኅበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ወይንም በአሁኑ አጠራር ለማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ መሆን ያለበት ሲሆን ኤጀንሲው በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታውን ለማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ከሚያቀርብ በስተቀር ከላይ እንደተመለከተው በዚህ ጉዳይ ፍ/ቤቶች የሥረ ነገር ሥልጣን የሌላቸው በመሆኑ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ውሣኔ መስጠቱ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12570 በ22/9/98 የሰጠው ውሣኔና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09916 በ16/2/99 ዓ.ም. በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ይህን ጉዳይ በተመለከተ መደበኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 28612

የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ጋረደው ቢራቱ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን - ጥሩወርቅ ኃ/ማርያም መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

አከራካሪው ጉዳይ ከውል ውጪ የደረሰን ኃላፊነት መሠረት በማድረግ የቀረበ የካሣ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተውም ሠራተኞቹ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 12 ቀበሌ 06 ክልል የቁፋሮ ሥራ ሲያካሂዱ 200 ደንበኞችን በያዘ የስልክ ኬብል ላይ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ በደረሰው ጉዳት የተነሳም የብር 5180.62 (አምስት ሺ አንድ መቶ ሰማንያ ብር ከስልሣ ሁለት ሣንቲም) ኪሣራ ደርሶብኛል፡፡ ስለዚህ ተከሣሹ ይህን ገንዘብ ከነወጪው ይክፈለኝ በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው በማለት የወሰነ ቢሆንም፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሚከፈል ካሣ የለም በማለት መዝገቡን ዘግቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ በአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስልክ ኬብል ላይ ጉዳት ማድረሱ ተረጋግጦ ኃላፊ ነው ከተባለ በኋላ ካሣ ግን አይከፍልም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች በኬብሉ መጎዳት ምክንያት የደረሰበትን ኪሣራ አስልቶ ከነምክንያቱ በዝርዝር አቅርቧል፡፡ በኪሣራ የተጠየቀው ገንዘብ ብር 5180.62 /አምስት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ብር ከስድሳ ሁለት ሣንቲም/ ሲሆን ይህም ኬብሉን ለመጠገን ጥቅም ላይ ለዋሉ እቃዎች መግዣ እና ጥገናውን ላካሄዱ ባለሙያዎች ያወጣውን ወጪ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ማስረጃዎቹንም አይይዞ አቅርቧል፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካች ካሣ ጠያቂ እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2141 በተደነገገው መሠረት የደረሰበትን ጉዳት ልክ የሚያሳዩ ማስረጃዎች አቅርቦ ማስረዳቱን ነው፡፡ በአንፃሩ ግን ተጠሪ በክሱ የተመለከተውን ኪሣራ አለማድረሱን በማስመልከት ያቀረበው የማስተባበያ ማስረጃ የለም፡፡ በእርግጥም ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የተባለው ሰው የሚከፍለው የጉዳት ካሣ ኃላፊነትነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን እንዳለበት በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2091 ተመልክቶአል፡፡ በዚህ ድንጋጌ አባባል ጉዳቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋራ ማመዛዘን የሚቻልበት አንዱ ዋነኛው መንገድ ማስረጃ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው አመልካች የጉዳቱን ልክ የሚያሳይ ማስረጃ አቅርቦአል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው እየተባለ በሌላ በኩል ግን ላደረሰው ጉዳት ካሣ አይከፍልም የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00032 ነሐሴ 27 ቀን 95 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26756 ጎንደር 13 ቀን 99 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ብር 5180.62 /አምስት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ብር ከስድሳ ሁለት ሣንቲም/ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም በዚህ ሰበር ችሎት ከተከፈለው ዳኝነት ጋር ይክፈል ብለን ወስነናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 28750

ኅዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን - ነ/ፈጅ ዝናቡ ታደሰ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ዘውዱ ዓሊ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ በአመልካችና በሥር 1ኛ ተከሣሽ ላይ በክስ የጠየቀውን ገንዘብ ተከሳሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ሊከፍሉ ይገባል በማለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ በመስጠቱና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ይህንኑ ውሣኔ በማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አነሳስም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በአመልካችና በሥር 1ኛ ተከሣሽ ላይ ባቀረበው ክስ 1ኛ ተከሣሽ ከባንክ ጋር ባደረጉት ስምምነት ኤል-ሲ ተከፍቶላቸው ከውጭ ዕቃ እንዲገባላቸው የተደረገ ሲሆን ነገር ግን ባንኩ ሳይጽፍላቸውና ሳይወስኑ በባንኩ ስም ወይም ትዕዛዝ የመጣውን ዕቃ በሕገ ወጥ መንገድ ከጉምሩክ ወስደዋል፡፡ በመሆኑም ክስ ለቀረበበት ገንዘብ ብር 395,738.59 (ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሰባት መቶ ሰላሣ አምስት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ) ተጠያቂ ናቸው፡፡ እንዲሁም ሁለተኛ ተከሣሽ (የጉምሩክ ባለሥልጣን) በባንኩ ባለቤትነት የመጣውን ዕቃ ባለመብት ላልሆነው አንደኛ ተከሣሽ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 20/1/ እና በጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣውን የዕቃ አወጣጥ ማንዋል በመጣስ በመልቀቁ ኃላፊነት ያለበት ስለሆነ

ክስ የቀረበበትን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሾች ደርሶ የየበኩላቸውን የመከላከያ መልስ ያቀረቡ ሲሆን 2ኛ ተከሣሽ የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 20/1/ የተዘረዘሩትን ዶክመንቶች የማቅረብ ግዴታ የተጣለበት አስመጪ የተባለው ወገን ነው፡፡ አስመጪው ጉምሩክ እነዚህን ዶክመንቶች ሲጠይቀው የማቅረብ ግዴታ አለበት ማለትም ጉምሩክ እነዚህን ዶክመንቶች የማየት ግዴታ ተጥሶበታል፡፡ ወይም እነዚህን ዶክመንቶች የሚሰጡት ወገኖች ካልፈቀዱ በስተቀር ባለንብረቶቹ አይስተናገዱም ማለት አይደለም ብሏል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የገባው ዕቃ ባለቤት እኔ ነኝ በማለት የከሰሰ ቢሆንም በቀረቡት ማስረጃዎች ዶክመንቶቹ በሙሉ የሚያስረዱት የዕቃው ባለቤት 1ኛ ተከሣሽ መሆናቸውን ነው፡፡ በመሆኑም አንደኛ ተከሣሽ ዕቃው ወደ ጉምሩክ መጋዘን ሲገባ ባሉት ዶክመንቶች ቀረጥና ታክስ ከፍዬ ልስተናገድ ባሉበት ጊዜ የጉምሩክ ባለሥልጣን ይህንኑ መፍቀዱ ተገቢነት አለው በማለትና ሌሎችንም መከራከሪያዎች በማቅረብ ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ 2ኛ ተከሣሽ /አመልካች/ በ1987 ዓ.ም. በወጣው የጉምሩክ ሥራና የቁጥጥር ማንዋል መመሪያ መሠረት ዕቃዎችን ለማስረከብ የባንክ ፈቃድን የመጠየቅ ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ይህንኑ ግዴታውን በመጣስ ዕቃውን ለ1ኛ ተከሣሽ ያስረከበ ስለሆነ ብር 242,121.45 /ሁለት መቶ አርባ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ አንድ ከአርባ አምስት/ ከ1ኛ ተከሣሽ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ የሰበር ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ለእዳው ከሥር 1ኛ ተከሣሽ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ነው መባሉ ለሰበር ቀርቦ መጣራት የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከሥር 1ኛ ተከሣሽ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለመክፈል ይገደዳል ወይ ? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በባንኩ ባለቤትነት የመጣውን እቃ ባለመብት ላልሆነው አንደኛ ተከሣሽ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 20(1) እና በጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣውን የዕቃ አወጣጥ ማንዋል በመጣስ ዕቃውን የለቀቀ ስለሆነ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከ1ኛ ተከሣሽ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ሊከፍል ይገባል በማለት ነው፡፡ አመልካችም እንዲለቀቁ የተደረጉት ዕቃዎች ባለቤትነታቸው የ1ኛ ተከሣሽ እንጂ የሣሽ አይደለም በማለት ክሱን በመቃወም ተከራክሯል፡፡

ይሁንና አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ከውጭ አገር እንዲገቡ የተደረጉ ዕቃዎችን ለ1ኛ ተከሣሽ ከማስረከቡ በፊት የባንክ ፈቃድን ጨምሮ የተለያዩ ሰነዶች ተሟልተው ሲቀርቡለት ብቻ መሆኑን የአመልካችን መ/ቤት ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 እና አመልካች እራሱ ባወጣው የአዋጁ አፈፃፀም መመሪያ ላይ ተመልክቷል፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2035 መሠረት አንድ ሰው ተለይቶ የታወቀና ግልጽ የሆነ የሕግ ድንጋጌ ወይም የአስተዳደር ደንብ ከተላለፈ ጥፋት ፈጽሟል ሊባል እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በሰነድ አማካይነት መያዣ ያደረገውን ንብረት አመልካች በሕግና በመመሪያ የተጣለበትን ግዴታ በመጣስ ለሥር 1ኛ ተከሣሽ በመልቀቁ በተጠቀሰው

የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2035 መሠረት በጥፋት ላይ የተመሠረተ ከውል ውጭ ኀላፊነት እንዳለበት ይህ ሰበር ችሎት ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

በሌላ በኩልም አመልካችና የሥር 1ኛ ተከሣሽ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለተጠሪ ኃላፊ ሊሆኑ ይችላሉን? የሚለውን ነጥብ ሲታይ የአንድነትና የነጠላ ግዴታ ከውል ወይንም በቀጥታ ከሕግ ሊመነጭ የሚችል ሲሆን ግዴታው ከውልም ሆነ ከሕግ ቢመነጭም ሁልጊዜም ቢሆን እንደ አንድ ግዴታ የሚቆጠር ከመሆኑም በላይ የዚህ ዓይነት ግዴታ በሚኖርበት ጊዜም ባለገንዘቡ በሁሉም ባለእዳዎች ላይ የሚኖረው መብት ከአንድ የክስ ምክንያት /Cause of action/ እንደመነጨ በማድረግ ሕጉ ግምት የሚወስድ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1896 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ማንኛውም ከሣሽ የሆነ ወገንም ሌላው ወገን አንድ ግዴታ እንዲፈጽምለት ክስ ሲያቀርብ ተከሣሹን የሚጠይቀው በምን ዓይነት ግንኙነት እንደሆነ ለይቶ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በተጠሪና በሥር 1ኛ ተከሣሽ መካከል ሰነድን መያዣ በማድረግ በተሰጠ ብድር በውል ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የተፈጠረ ሲሆን ተጠሪም ይህንኑ በክሱ ለይቶ በመጥቀስ በውሉ ላይ ተመሥርቶ ሊከፍለኝ ይገባል የሚለውን ጠይቋል በሌላ በኩልም ተጠሪ ክሱን ሲያቀርብ 2ኛው ተከሣሽ የአሁን አመልካች በሰነድ አማካይነት መያዣ ያደረግሁትን ንብረት በሕግና በመመሪያ የተጣለበትን ግዴታ በመጣስ ለ1ኛ ተከሣሽ ለቋል በማለት ስለሆነ ኃላፊነቱም ከውል ውጭ በጥፋት ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን የሚኖርበትም ግዴታ ከውል ውጭ በፈፀመው ጥፋት ምክንያት በተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰ ከሆነ ይህንኑ ጉዳት መካስ ስለሚሆን በዚሁ መሠረት ተጠሪ ከውል ውጭ ደርሶብኛል የሚለው ጉዳት ካለ ይህንኑ አስልቶና ለይቶ በክስ መጠየቅ ሲገባው የሁለቱ ተከሣሾች ኃላፊነት ከውልና ከውል ውጭ ከተለያየ የክስ ምክንያት የመነጨ በሆነበት ሁኔታ ተጠሪ የውል ግንኙነት ካለው ከ1ኛው ተከሣሽ ከውሉ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት በክስ የሚጠይቀውን ገንዘብ ከውል ውጭ ኃላፊነት ያለበት 2ኛውም ተከሣሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/አመልካች/ በአንድነትና በነጠላ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት መጠየቁ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ከውል ውጭ በለ ግንኙነት ሆኖ አመልካችም በዚሁ መልኩ ኃላፊ መሆን እንዳለበት የተረጋገጠ ቢሆንም አመልካች በፈጸመው ጥፋት ምክንያት በተጠሪ ላይ ጉዳት ደርሶ ከሆነ ይህንኑ ጉዳት ተጠሪ አስልቶና ለይቶ ካሣ እንዲከፈለው መጠየቅ ሲገባው በዚህ መልኩ ክሱ ባልቀረበበት ሁኔታ ከተለያየ የክስ ምክንያት የመነጨውን የሁለቱን ተከሣሾች ኃላፊነት በመቀላቀል የውል ግዴታ ካለበት ከ1ኛ ተከሣሽ ጋር አመልካች በአንድነትና በነጠላ ካሣ ሊፍለኝ ይገባል በማለት ተጠሪ ያቀረበውን ክስ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተቀብሎ በዚሁ መሠረት መወሰኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ይህንኑ ማጽናቱ የሕግ ስህተት የተፈፀባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 00388 በ2/4/96 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 29113 በ5/4/99 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕግ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፈፀመው ጥፋት ከውል ውጭ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በዚህ ምክንያት ተጠሪ ደርሶብኛል የሚለው ጉዳት ተለይቶ በክስ ያልተጠየቀ ስለሆነ ከሥር 1ኛ ተከሣሽ በአንድነትና በነጠላ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 28865

ህዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጐስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ ካሣ ግዛው

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በተጠሪ በኩል ጥፋት መፈጸሙን አመልካች ያላስረዳ ሰለሆነ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት በበታች ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ አመልካች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተከሳሽ በድርጅታችን በመካኒክነት ተቀጥሮ በመሥራት ላይ እንዳለ የዋጋ ግምታቸው ብር 1178.05 (አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰባ ስምንት ብር ከአምስት ሣንቲም) የሆኑ የመኪና መለዋወጫዎችን በመኪና ላይ ለመግጠም ተረክቦ ያልገጠመ ከመሆኑም በላይ ጠፍቶብኛል በማለት ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ሳያደርግ የቀረ ስለሆነ ተከሳሽ እነዚህን የተከረባቸውን መለዋወጫ ዕቃዎች መልሶ እንዲያስረክብ ወይንም የዋጋ ግምታቸውን እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎችን መረከቡን ሳይክድ የሥራ መደቡ የተበላሹ የከሳሽ መኪናዎችን መጠገን እንደሆነና ጥገናውም የሚከናወነው በመደበኛ የሥራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰዓት እንደሆነ በሥራ መውጪያ ላይም እንደማንኛውም ሠራተኛ ተፈትሾ እንደሚወጣ ገልፆ ንብረቱ ሊጠፋ የቻለው በጥበቃ ሠራተኞች ቸልተኝነት ስለሆነ ክሱ ከበቂ ኪሳራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክሩን ከቀረበው ማስረጃ አኳያ ተመልክቶ ተከሳሽ የተረከባቸውን የመለዋወጫ እቃዎች እስከ መቼ ድረስ ተሽከርካሪዎች ላይ መግጠም እንዳለበት ወይም በምን ያህል ጊዜ ወደ ጥገና ክፍል መመለስ እንዳለበት የተመለከተ ነገር ስለሌለና ተከሳሽም የተረከባቸውን ንብረቶች ከሥራ ሰዓት ውጭ የመጠበቅ ኃላፊነት የሌለበት ከመሆኑም ሌላ ንብረቶቹን እንዲያስረክብም ሆነ የዋጋ ግምታቸውን ለመክፈል አይገደድም በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኙን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት አቤቱታውን መርመሮ ተጠሪ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎችን መከረቡና በመኪናዎች ላይም አለመገጠሙ ተረጋግጦ እያለ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል አይገባም ተብሎ መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ መጣራት እንዳለበት በማመኑ ተጠሪን ጠርቷል፡፡

ሆኖም ተጠሪ በጋዜጣ ተጠርቶ ያልቀረበ ስለሆነ በአመልካች ክርክር ላይ በመመሥረት የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ይህም ችሎት የሰበር አቤቱታውን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ ሊፈታ የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ ተጠሪ ከአመልካች የተረከባቸውን የመለዋወጫ ዕቃዎች በዓይነት ለማስረከብ ወይንም የዋጋ ግምታቸውን ለመክፈል ይገደዳል ወይስ አይገደድም የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን የመለዋወጫ ዕቃዎች ከአመልካች ላይ መረከረቡን ሳይክድ ነገር ግን ሊጠፉ የቻሉት በመ/ቤቱ የጥበቃ ሠራተኞች ጥፋት መሆኑን ገልፆ በኃላፊነት ሊጠየቅ እንደማይችል ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል አይገባም ወደሚል ድምዳሜ ለመድረስ የቻለው የተረከባቸውን የተሽከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃዎች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪዎች ላይ መግጠም እንዳለበት ወይም በምን ያህል ጊዜ ወደ ጥገና ክፍል መመለስ እንዳለበት የተመለከተ ነገር ካለመኖሩም በላይ ተጠሪ የተረከባቸውን ንብረቶች ከሥራ ሰዓት ውጭ የመጠበቅ ግዴታ ስለሌለበትና ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት የጠፉ ስለመሆኑም አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2027፣ 2029 እና 2031 መሠረት ተጠሪ ጥፋት የፈጸመ ስለመሆኑ በአመልካች ማስረጃ ስላልተረጋገጠ ኃላፊ አይሆንም በማለት ነው፡፡

ይሁንና ተጠሪ ከአመልካች ጋር በፈጠረው የሥራ ውል መነሻነት ለክሱ መነሻ የሆኑትን የተሽከርካሪ መለዋወጫዎችን ስለመረከቡ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በተጠሪም አልተካደም፡፡ ተጠሪ እነዚህን ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን የመኪና መለዋወጫዎች ከአመልካች ከተረከበ በኋላ በመኪና ላይ እስከሚገጥምበት ጊዜ ድረስ በንብረቶቹ ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት፣ ብልሽት ወይንም መጥፋት በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችል ይህ ችግር እንዳይከሰት ተጠሪ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚጠበቅበት ይታመናል፡፡ ተጠሪ ይህንን ጥንቃቄ ማድረግ ባያስፈልገው ኖሮ ቀድሞውንም ቢሆን ዕቃዎችን ፈርሞ መረከብ ባላስፈለገው ነበር፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪ ፈርሞ የተከረባቸውን እነዚህን የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች እንዳይጠፉ፣ እንዳይሰረቁም ሆነ ሌላ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚጠበቅበት በሥራ ሰዓት እንጂ ከሥራ ሰዓት ውጭ እንዳልሆነም ይታመናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖም ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት ሳይሆን ከሥራ ሰዓት ውጭ የጠፉ ስለመሆኑ የማስረዳቱ ሸክም የእራሱ የተጠሪ እንጂ የአመልካች ሊሆን የማይችል ሲሆን ተጠሪም በዚህ ረገድ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡

ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ሸክሙን ካልተወጣ ንብረቱ በእራሱ ቁጥጥር ሥር እያለ መጥፉቱን የሚያሳይና በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2027 መሠረት ቢያንስ በቸልተኝነት ጥፋት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ ንብረቶቹ ከሥራ ሰዓት ውጭ የጠፉ ስለመሆኑ ባላስረዳበት ሁኔታ የማስረዳት ሸክሙን ወደ አመልካች በማዞር ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት የጠፉ መሆኑን በማስረዳት ተጠሪ ጥፋት መፈጸሙን አላረጋገጠም በማለት ክሱን ሳይቀበል መቅረቱ እንደዚሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 39118 ህዳር 1 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 36028 ጥቅምት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ጥፋት መፈጸሙ የተረጋገጠ ስለሆነ በክስ የተጠየቀውን ብር 1178.05 (አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰባ ስምንት ከዜሮ አምስት ሣንቲም) ክስ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድ ጋር ለአመልካች እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ግልባጩ ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 30032

ታህሣሥ 1 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ ነ/ፈጅ ሰለሞን በቀለ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ምንትዋብ የኔነህ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ ክስ ባቀረቡበት የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ኃላፊ ነው በማለት ካሣ እንዲከፍል ውሣኔ በመስጠታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ባለቤቴ የነበረው ወ/ር ጌትነት ፈጠነ መስከረም 28 ቀን 1994 ዓ.ም. የተከሣሽ ንብረት በሆነው መኪና ተሳፍሮ ከባህርዳር ወደ ጎንደር በሚጓዝበት ወቅት መንገድ ላይ መኪናው ተገልብጦ ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል፡፡ ሟች በሞተበት ጊዜ ዕድሜው 38 ዓመት የነበረ ሲሆን ጡረታ ለመውጣት 17 ዓመት ይቀረው ነበር፡፡ የወር ደመወዙም ብር 460.00 የነበረ ሲሆን ይህ በ17 ሲባዛ ብር 93,840.00 ስለሚሆን የጎሊና ጉዳት ካሣ ብር 1 ሺህ ጨምሮ በድምሩ ብር 94,840.00 ካሣ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት በእራሳቸውና በሶስት ልጆች ስም ጠይቀዋል፡፡

ክሱና ማስረጃው ለተከሳሽ ደርሶም በሰጠው መልስ በተከሳሽና በሟች መካከል የነበረው ግንኙነት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት በመሆኑ ሟችም የሞተው በሥራ ላይ እያለ ስለሆነ የሟች ተተኪዎች ተጠቃሚ ሊሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2037 እና 2038 መሠረት የጡረታ አበል በመጠየቅ እንጂ ከአሰሪው ካሣ የሚጠይቁበት የሕግ ድጋፍ የለም፡፡ ይህ የሚታለፍ ቢሆን የቀረበው አቤቱታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2095 አኳያ ሲታይ የሟች ሚስትና ልጆች መጠየቅ የሚችሉት ካሣ ቀለብ ብቻ እንደሆነ የተደነገገ ሲሆን በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 12 መሠረትም ከሳሽ ቀለብ ለመጠየቅ የምትችለው ሠርታ ለመብላት አቅም የሌላት ከሆነ ብቻ ነው የሚል ክርክር አቅርቦ ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጋር የመድን ሽፋን ውል ያለው መሆኑን በማለጸ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ አመልክቷል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅትም በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እስከ ብር 10 ሺህ የመድን ሽፋን መስጠቱን አምኖ በኃላፊነትና በካሣ መጠኑ ላይ ከተከሣሽ ጋር ተመሣሣይ የሆነ ክርክር አቅርቧል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ በተከሳሽም ሆነ በጣልቃ ገቡ ኃላፊነትን አስመልክቶ የቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጎ ለደረሰው ጉዳት ተከሣሽ ኃላፊ ነው ካለ በኋላ የካሳ መጠኑን አስልቶ ቁሳዊ ጉዳት /Material damage/ ብር 24 ሺህ የሞራል ካሣ /Moral damage/ ብር 1 ሺህ እንደዚሁም ወጭና ኪሣራ ብር 1 ሺህ በድምሩ ብር 26 ሺህ ለከሳሽ ሊከፍል እንደሚገባና ከዚህ ገንዘብ ላይ ጣልቃገብ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በሰጠው የመድን ሽፋን መሠረት ብር 10 ሺህ እንዲከፍል ቀሪውን ብር 16 ሺህ ደግሞ ተከሣሽ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኙን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ለሰበር መቅረብ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ክስ በቀረበበት ነገር አመልካች ኃላፊነት አለበት? ወይንስ የለበትም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን መርምረናል፡፡

የተጠሪ ባለቤት የነበረው ሟች ሊሞት የቻለው ንብረትነቱ የአመልካች በሆነው መኪና ተሳፍሮ በመንገዝ ላይ እንዳለ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ የተያዘውን ጭብጥ በተሟላ ሁኔታ ለመፍታት እንዲቻልም ሟች የሞት አደጋ የደረሰበት በተጠሪ መ/ቤት በመሥራት ላይ እንዳለ በደረሰበት ጉዳት ነው ወይስ በሌላ መሥሪያ ቤት በመሥራት ላይ እያለ የሚለው ነጥብ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ክርክር ሟች በወቅቱ ሲሰራበት የነበረው የክልሉ ማረሚያ ቤት ከተጠሪ መ/ቤት ጋር የመዋቅር ግንኙነት እንደነበራቸውና በተጠሪ መ/ቤት ሥር እንደበረ ሲገልጽ አመልካች ደግሞ የክልሉ ማረሚያ ቤት እራሱን ችሎ የተቋቋመ ነበር በማለት ተከራክረዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ሰበር ችሎት መዝገቡን ሲመረምር ሟች ተቀጥሮ ሲሰራበት የነበረው የክልሉ ማረሚያ ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ ፍትሕ ቢሮ ማለትም ለአሁን አመልካች እንደነበረ ለመገንዘብ ችሏል፡፡ ሁለቱ መ/ቤቶች በአንድ መዋቅር ስር የተደራጁ ነበሩ ከተባለ ደግሞ ሟች በተጠሪ መኪና ሲጓዝ በመኪናው መገልበጥ ምክንያት ከሞተ በሥራ ላይ እንዳለ መሞቱን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የሞት አደጋ ቢደርስበት በመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት ካሳ እንዴት ሊከፈል እንደሚችል መረዳት እንዲቻል የአማራ ክልልን የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 74/1994ን ይህ ሰበር ችሎት አስቀርቦ የተመለከተው ሲሆን ቋሚ የሆነ የመንግሥት ሠራተኛ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት የሞተ እንደሆነ ለተተኪዎች የጡረታ አበል እንደሚከፈል በአንቀጽ 46/5/ሀ/ ላይ መደንገጉን ተገንዝቧል፡፡

ስለሆነም የተጠሪ ባለቤት በሞት የተለየው በሥራ ላይ እያለ ባጋጠመው አደጋ ምክንያት ስለሆነና በሥራ ላይ እያለ በአደጋ ምክንያት የሞት ጉዳት የደረሰበት ሰው በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተተኪዎች የጡረታ አበል ከሚከፈል በስተቀር ከዚህ አልፎ ሌላ ተጨማሪ ካሣ ሊከፈል እንደሚችል በተጠቀሰው ሕግ ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች በተረጋገጠው ፍሬ ነገር ላይ ተመሥርተው ክርክሩን ከክልሉ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ አኳያ ተመልክተው ውሣኔ መስጠት ሲገባቸው የግራ ቀኙን ግንኙነት ከሚገዛው የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ በመውጣት በፍ/ብሔር ሕጉ ከውል ውጭ ባሉ ድንጋጌዎች መሠረት ውሣኔ መስጠታቸው የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 4337 ሐምሌ 17 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10200 መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡
2. ክስ በቀረበበት ጉዳይ አመልካች ኃላፊ አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡ ስለሆነም አመልካችም ሆነ የሥር ጣልቃገቡ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለተጠሪ ካሣ ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 30442

ጎንደር 3 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሰሜን ምዕራብ ሪጅን - ሕዝቅኤል ዋዲሱ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ድንቋ አመኔ አልቀረበችም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

አከራካሪው ጉዳይ ከውል ውጪ በሆነ ኃላፊነት የተጠየቀን የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/በመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ አመልካችን የከሰሰችው ባለቤቱ እና የልጅ አባት የነበረው ሰው በአሌክትሪክ ሽቦ ተይዞ ሞቶአልና በዚህ ምክንያት በመተዳደሪያ ረገድ የቀረብኝን ገቢ ይተካልኝ በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም አመልካችን አስቀርቦ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተከሣሽ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው፡፡ በመሆኑም የተቋረጠውን ጥቅም በጠቅላላው ብር 60,800 ለከሣሽ ይክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ስህተት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበል ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. በዳፊው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በሰበር ችሎቱ ይመረመራል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ካሣውን መክፈል ያለበት እንዴት ነው የሚለው ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነጥብ ግራ ቀኝ ወገኖች ካቀረቡት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ ማረጋገጥ እንደቻልነው የተጠሪ ባል የሞተው ንብረትነቱ የአመልካች በሆነ የኤሌክትሪክ ሽቦ በመያዙ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ኃላፊነትን በተመለከተ ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡ ከኃላፊነት በመቀጠል የተነሳው ክርክር የሃላፊነቱን መጠን የሚመለከት በመሆኑ ይህን ነጥብ በተለይ በማውጣት አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በተጠሪ የክስ ማመልከቻ እንደተገለጸው እና የሥር ፍ/ቤቶችም እንደተገነዘቡት ሟች ሲሞት በ20 ዓመት እድሜ ላይ የነበረ፣ ሥራው ግብርና የሆነ እና የተለያዩ ሰብሎችን በማምረት በዓመት በአማካይ ብር 5000 (አምስት ሺ) ገቢ ያገኝ እንደነበር ነው፡፡ በመተዳደሪያ ረገድ ቀረብኝ ያለችውም ይህን በዓመት ይገኝ ነበር የተባለውን እንዳለ በማስላት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ርትዕን መሠረት በማድረግ ገቢውን ወደ ብር 3000 ዝቅ በማድረግ እና ሟች ለተጨማሪ 20 ዓመት ሊኖር ይችል ነበር የሚል ግምት በመውሰድ እንደዚሁም ብር 800 የሞራል ካሣ በማከል በድምሩ ብር 60,800 (ስልሳ ሺ ስምንት መቶ) እንዲከፈል ወስነዋል፡፡ አመልካች ይህን ካሣ ከአሠላሉም ሆነ ቀለብን በተመለከተ ከተደነገገው ሕግ አንፃር በማየት አጥብቆ ተቃውሞታል፡፡

የሞት አደጋ በደረሰ ጊዜ አንዳንድ የቅርብ ዘመዶች የሚኖራቸው መብት የሚታየው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2095 ነው፡፡ ተጠሪ ባለቤትዋ በመሞቱ ምክንያት በቀለብ ረገድ ቀረብኝ የምትለውን በገንዘብ ለማስላት በራስዋ እና በሕፃን ልጅዋ ስም ጠይቃለች፡፡ በመሆኑም የጥያቄዋ አግባብነት የሚታየው ከተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2095/1/ አንፃር ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚከፈለው ካሣ ምግብን /መተዳደሪያን/ በመስጠት እንደሚደረገው ጡረታ መልክና አይነት እንደሚሆን ሕጉ በግልጽ የሚያመለክት በመሆኑ በእርግጥ ተጠሪ ቀለብ ይቆረጥላት ዘንድ አስፈላጊ ሁኔታዎች አሉ ወይ? አመልካች ቀለብ የመስጠት

ግዴታ ያለበት ሆኖ ቢገኝ ኃላፊነቱ ለሕፃንዋ ብቻ ነው ወይንስ ለተጠሪም ጭምር? የሚሉት ነጥቦች በቅድሚያ ሊመረመሩ የሚገባቸው ናቸው፡፡

ቀለብን የመስጠት ግዴታ የሚወሰኑባቸው ሁኔታዎች በዝርዝር ተመልክተው የሚገኙት በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 807 ቀጥለው ባሉት ድንጋጌዎች ነው፡፡ ለተያዘው ጉዳይ አወሳሰን ቀጥተኛ ተገቢነት ያለው ድንጋጌ ቁ. 812 ሲሆን፣ ይህም የቀለብ መስጠት ግደታ የሚገባ ሆኖ የሚገኘው ግዴታው እንዲፈጸምለት የሚጠይቀው ሰው ሠርቶ ለመብላት የማይችል እና በችግር ላይ የወደቀ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምንመለከተው አመልካች እንደሟች ባልዋ በወጣትነት ዕድሜ ላይ የምትገኝ ከመሆንዋ በቀር ሠርታ መብላት የማትችል ወይም በቀለብ ማግኘት ረገድ በችግር ላይ እንደምትገኝ አልተገለጸም፡፡ በዚህ ሁኔታም የቀረበ ክርክር የለም፡፡ አመልካች ካሣውን የጠየቀችው ባልዋ በመሞቱ ምክንያት ብቻ በቀጥታ የሚሰጣት እንደሆነ በማመን ነው፡፡ ይህ ግን በሕጉ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ከዚህ የተነሣም በአመልካች በኩል የተጠየቀው የቀለብ ክፍያ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚኖርበት ሠርታ መብላት ለማትችለው የሟች ልጅ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ለአመልካችም ጭምር ቀለብ አስልተው መወሰናቸው ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡ አወሳሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01375 ጥቅምት 15 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 51086 ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡ በዚህም ለአመልካች ይከፈል የተባለው ካሣ አይገባትም በማለት ይህን የውሣኔው ክፍል ሽረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች ከሚች ለተወለደች ሕፃን ትዕግሥት ሰዋገኝ ጥላሁን አካለመጠን እስከደረሰች /አስራ ስምንት ዓመት እስከሞላት/ ድረስ በየወሩ ብር 100 /አንድ መቶ ብር/ በቀለብ መልክ እንዲሰጥ ወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

በዚህ ውሣኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለሥር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31099

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የተንዳሆ እርሻ ልማት አ/ማ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ኒሻን አለማየሁ፡፡ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የቀረበው አመልካች የአፋር ክልል የዱብቲ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 2057/98 መስከረም 3 ቀን 1999 ዓ.ም እና የአፋር ክልል፣ የዞን አንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0580 ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስላላቸው በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 6 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈው የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ተጠሪ ከሕፃንነት ጀምራ አሥራ አራት ዓመት እስኪሆነው ድረስ ያሳደገቻውን ሕፃን ወንድማገኝ ይልማ ግቢ ውስጥ ሲጫወት ኤሌክትሪክ ይዞት ስለሞተ፣ ሕፃኑ የእህቱ ልጅ እና ያሣደግሁት የቤተሰቡ አባል በመሆኑ በሕብረት ስምምነቱና በፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ካሣ ይከፈለኝ በማለት በአመልካች ላይ ክስ አቅርባለች፡፡ አመልካች ሕፃኑ ቤተሰብ በሚለው የሕብረት ስምምነት አይሸፈንም፡፡ ስለዚህ ካሣ መክፈል የለብንም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የዱብቲ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ ባቀረበችው ክስ መሠረት ካሣ እንዲከፍል የወሰነ ሲሆን ይህንን ውሣኔ የዞን አንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ከሕብረት ስምምነቱ ድንጋጌና ከፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ውጪ ካሣ እንድከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሏ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክራለች፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም፡-

1. አመልካች ለተጠሪ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት እንዲከፍል ይገደዳል ወይስ አይገደድም
2. አመልካች ለተጠሪ በፍታብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት የሚከፍለው ካሣ ይኖራል ወይስ አይኖርም የሚሉትን ጭብጦች አይተናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በድርጅቱ ቤት በሚኖሩ ሠራተኞች ላይ የኤክትሪክ አደጋ ቢደርስ ለንብረቱና በሠራተኛው ቤተሰብ ላይ ለሚደርስባቸው ጉዳት እና ሞት ድርጅቱ የካሣ ክፍያ የመክፈልና ሕክምና የማድረግ ግዴታ እንዳለበት የሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 29 ንኡስ አንቀጽ 13 ይደነግጋል፡፡ “ቤተሰብ” በሚለው ውስጥ የሚሸፈኑት በሌላ ሥራ ተሰማርቶ ገቢ የማያገኝ የሠራተኛው ሕጋዊ ሚስት ወይም ባል እንዲሁም እድሜቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነና በራሳቸው የማይተዳደሩ ልጆችንና የጉዲፈቻ ልጅን ይጨምራል በማለት በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 7 ተደንግጓል፡፡ ሟች የተጠሪዋ የእህቷ ልጅ እና እሷ ያሣደገችው ቢሆንም በሕግ የተቀመጠውን ሁኔታ አሟልታ በጉድፍቻ ውል መሠረት ያሳደረችው የጉድፈቻ ልጅ አይደለም፡፡ ሟች ተጠሪዋ የወለደችው ልጅ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ ባለመሆኑ የሕብረት ስምምነቱ በሰጠው ትርጓሜ የቤተሰቡ አባል ነው ተብሎ የተሸፈነ አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ተጠሪ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት አመልካች ካሣ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶችም የሕብረት ስምነቱን ድንጋጌዎች ይዘት በውል

ሣይመረምሩ አመልካች ለተጠሪው በሕብረት ስምምነቱ መሠረት ካሣ ይክፈላት በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ ስህተት አለበት፡፡

ሁለትኛውን ጭብጥ በተመለከተ ሕፃኑን ለሞት የዳረገውን ኤሌክትሪክ መስመር በአመልካች ኃላፊነት ሥር ያለ የአመልካች ንብረት ነው፡፡ ስለሆነም ለደረሰው ጉዳት አመልካች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2069 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም በሞት ምክንያት የሚከፈል የጉዳት ካሣ በቀለብ መልክ ሊሰጥ የሚችል ዳረጐት እንደሆነ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2095 ስለሚደነግግና ተጠሪ ከሟች ቀለብ ይሰፈርላት የነበረች ስላልሆነች አሁን ባለው የሕግ ማዕቀፍ ሟች በመሞቱ ምክንያት ለደረሰባት ጉዳት ካሣ የመጠየቅ መብት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2095 አይሰጣትም፡፡ ሆኖም ይህ ማለት ሟች በመሞቱ ተጠሪ የሕሊና ጉዳት አልደረሰባትም ማለት አይደለም፡፡ ተጠሪዋ ተንከባክባ ያሣደገችው ልጅ በአደጋው ምክንያት በመሞቱ የሕሊና ጉዳት ደርሶባታል፡፡ ለዚህ ለደረሰባት የሕሊና ጉዳት አመልካች ኃላፊ በመሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2116 ድንጋጌዎች መሠረት አመልካች ለተጠሪ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ የሞራል ካሣ ሊፍል ይገባዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአፋር ክልል የዱብቲ ወረዳና የዞን አንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጧቸው ውሣኔዎች ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ የሞራል ካሣ ሊከፍላት ይገባል ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ እና ኪሣራ ራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32144

መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድኀን ኪሮስ

አመልካች፡- ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልሻ ሲራጅ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጉዳት ካሣ ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው ተጠሪ ስትሆን አመልካችን የከሰሰችው ንብረቱ የሆነ መኪና ባለቤትዋን ገጭቶ በመግደሉ ለእስዋ እና ለሁለት ልጆችዋ የጉዳት ካሣ እንዲከፍላት ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት እና የሚከፍል ከሆነም በመጠኑ ረገድ ሊታዩ የሚገባቸው ነጥቦች እንዳሉ በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ክርክሩን ከመረመረ በኋላ፣ በሟች መሞት ምክንያት ተጠሪ እና ልጆቹ አጡት ያለውን ገቢ በማስላት በጠቅላላው ብር 61,275.90 ለቀብር ሥነ ሥርዓት ማስፈጸሚያ እና ለሃውልት ማሠሪያ ብር 2000 እንዲሁም የሞራል ካሣ ለእያንዳንዳቸው ብር 1000 አመልካች እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ሳይቀበለው ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተቋረጠ የተባለው

ጥቅም የተሰላበትን መንገድ እና የሞራል ካሣውን አወሳሰን በተመለከተ የቀረበው አቤቱታ መመርመር ያለባት ሆኖ በመገኘታቸው ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ነጥቦች ከሥር ጀምሮ ከቀረበው ክርክር የስር ፍ/ቤቶች ከሰጡት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ ክሱን የመሠረተችው በባለቤትዋ መሞት የተነሣ ቀረብኝ ያለችውን ጥቅም በዝርዝር በማስላት ነው፡፡ የስሌቱ መነሻ የሚች ደመወዝ እንደሆነም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም እንደዚሁ ተጠሪ በክስዋ ላይ የጠቀሰችውን የሚች ደመወዝ /ብር 895/ እንዳለ በመውሰድ ነው ስሌቱን የሠራው፡፡ በሰበር ችሎቱ ሊመረመር የሚገባ ሆኖ የተገኘው ይኸው ነው፡፡ የሚች ደመወዝ ብር 895 አይደለም የሚል ክርክር በአመልካች አልቀረበም፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበው ክርክር ከጠቅላላ /gross/ ደመወዝ ላይ የሚቀናነሱ ሕግ የሚያውቃቸው ተቀናሾች ሳይቀነሱ የጉዳት ካሣው መሰላቱ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ በበኩላችንም እንደምንገነዘበው ብር 895 /ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ብር/ የሚች ጠቅላላ /gross/ ደመወዝ እንጂ የተጣራ የወር ገቢው አይደለም፡፡ በግልጽ እንደሚታወቀው ከሠራተኛ ደመወዝ ላይ የሚቀናነሱ በሕግ የታወቁ ተቀናሾች አሉ፡፡ በመሆኑም ሠራተኛው በየወሩ የሚያገኘው ማለትም በእጁ የሚደርሰው ገቢው ከጠቅላላ ደመወዙ ያነሰ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ቀረ የተባለውን ጥቅም ያሰሉት ይህን ነገር ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ነው፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ ስህተት ተፈጽሞአል ለማለት ችለናል፡፡

ቀጥለን የተመለከትነው የሕሊና ጉዳት ካሣን በተመለከተ የተሰጠውን ውሣኔ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ለተጠሪና ሟግዚት ለሆነችላቸው ልጆች በህሊና ጉዳት ካሣ ስም እንዲከፈል የተወሰነው ብር 3000 ነው፡፡ ይህ ሊሆን የቻለውም በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2116 የተመለከተው ብር 1000 በአመልካች እና ሟግዚት በሆነችላቸው ሁለት ልጆች በየስማቸው ተይዞ እንደሚከፈል ተደርጎ ግንዛቤ በመወሰዱ ነው፡፡ በእርግጥ በሕጉ በግልጽ ከተመለከተ የህሊና ጉዳት ካሣ እንደሚከፈል በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2105 ከተቀመጠው ድንጋጌ መገንዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይቻላል። መጠኑን በሚመለከትም በማናቸውም ምክንያት ከአንድ ሺህ ብር ሊበልጥ እንደማይችል በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2116 በግልጽ ተደንግጎአል። ሕጉ የጉዳት ካሣውን በዚህ ሁኔታ ከገደበው ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ መወሰን የሚቻል አይሆንም። በመሆኑም ይህን በተመለከተ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ስህተት ያለበት ነው። ሊጠቃለል የጉዳት ካሣ አሰላልን እና የህሊና ጉዳት ካሣ አወሳሰንን በሚመለከት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05585 ግንቦት 23 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5689 ሐምሌ 9 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል።
2. በሟች ሞት ምክንያት ቀረ የተባለው ጥቅም ከጠቅላላው የሟች ደመወዝ ላይ የሚቀነሱት በሕግ የታወቁት ተቀናሾች ተቀንሰው በሚገኘው የተጣራው ገቢ መሠረት ይሰላ በማለት ወስነናል።
3. የሕሊና ጉዳት ካሣው ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ ነው ብለናል።
4. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 32250

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

መድህን ኪሮስ

ፀጋዬ አስማማው

አመልካች፡- ወ/ሮ አስናቀች ወ/ማርያም ጠበቃው ቀርቧል።

ተጠሪ፡- 1. አቶ ክተማ ተሠማ
2. አቶ ሸዋንግዛው ክተማ
ጠበቃቸው ቀርቧል።

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በተጎጂው ላይ በደረሰ የሞት አደጋ ምክንያት የሚከፈልን የካሣ አከፋፈል ሥርዓትን የሚመለከት ነው።

የአሁኗ አመልካች የአሁኑን ተጠሪዎች ጨምሮ 3 ተከሣሾች ላይ ባቀረቡት ክስ ልጃቸው ላይ በደረሰው የሞት አደጋ ኃለፊዎች ስለሆኑ ካሣ ብር 90,600 (ዘጠና ሺህ ስድስት መቶ) እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል።

ተከሣሾቹም በኃላፊነቱም ሆነ በካሣው መጠን ላይ ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በአመልካች ልጅ ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ 1ኛ ተጠሪ የመኪናው ባለቤት በመሆናቸው፣ 2ኛ ተጠሪ መኪናውን በማሽከርከር አደጋውን ያደረሡ በመሆኑ ኃላፊዎች ናቸው ካለ በኋላ የካሣውን መጠን በተመለከተ ሟች ለአመልካች በየወሩ ብር 300.00 (ሦስት መቶ) ይሰጥ ስለነበር አመልካች 85 ዓመት እስኪሞላቸው ላለው 18 ዓመት ታስቦ እንዲሁም ለቀብር ማስፈፀሚያና ለተለያዩ ወጪዎች ብር 7,077.50 (ሠባት ሺህ ሠባ ሰባት ብር ከሃምሣ ሣንቲም) በድምሩ ብር 71,877 (ሠባ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሰባት ብር) እንዲከፍሉ ወስኗል።

የአሁን ተጠሪዎች በውሣኔው ቅር በመሠኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በኃላፊነቱ እና በካሣው መጠን ላይ የተሰጠውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ ያፀና ሲሆን የአከፋፈሉን ሥርዓት በተመለከተ ግን በመተዳደሪያ ረገድ የተቋረጠ ጥቅም መከፈል ያለበት በአንድ ጊዜ ሣይሆን እንደነገሩ ሁኔታ በየጊዜው በመሆኑ ለቀብር የወጣውን ወጭ ብር 2000 እና ውሣኔ እስኪሰጥ ያለው ውዝፍ ቀለብ ብር 4,090 ተጠሪዎች በአንድነት እንዲከፍሉና ቀሪውን የጉዳት ካሣ የየዓመቱን መ/ሰጪ በሚኖሩበት አካባቢ ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም ውስጥ እንዲያስቀምጡና መልስ ሰጪ በየወሩ ብር 300 (ሦስት መቶ) በሕይወት እስካሉና 85 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ እንዲቀበሉ ሚች 85 ዓመት ሣይሞላቸው ከሞቱ ባንክ የተቀመጠው ገንዘብ ለይግባኝ ባዮች እንዲመስ በማለት አሻሽሎ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሠኝተው ይግባኙን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን በመሠረዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪዎች የየአመቱን በባንክ ወይም በሌላ ገንዘብ ተቋም እንዲቀመጥ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በማለቱ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ ሰጥተዋል፤ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ለአመልካች ልጅ መሞት ተጠሪዎች ኃላፊ መሆናቸውና የመ/ደረጃ ፍ/ቤት የወሰነው የካሣ መጠን በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የፀና በመሆኑ በዚህ መዝገብ የሚታየው የካሣው አከፋፈል ሥርዓት ብቻ ይሆናል፡፡

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ሀ/ቁ. 2095/2/ መሠረት በመተዳደሪያ ረገድ የተቋረጠ ጥቅም መከፈል ያለበት አንድ ጊዜ ሣይሆን እንደነገሩ ሁኔታ በየጊዜው መሆን እንዳለበት እና አመልካች በህይወት እስካሉና 85 እስኪሞላቸው ገንዘቡ በባንክ ወይም በሌላ ገንዘብ ተቋም ተቀምጦ አመልካች በየወሩ ብር 300 እያወጡ እንዲወስዱ የሰጠው ውሣኔ ይህ ችሎትም የሚስማማበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ ተጠሪዎች በባንክ ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም ማስቀመጥ ያለባቸው የየአመቱን የካሣ ክፍያ ብቻ እንዲሆን

መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች በሕይወት እስካሉ እና 85 ዓመት እስኪሞላቸው ካሣው በየወሩ ሊከፈላቸው እንደሚገባ ተወስኗል፡፡ በመሆኑም 85 ዓመት እስኪሞላቸውና በሕይወት እስካሉ ካሣውን በየወሩ ሊያገኙ የሚችሉበት የአከፋፈል ሥርዓት አብሮ ሊወሰን ይገባል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዳለው ተጠሪዎች የየአመቱን ካሣ ብቻ እንዲያስቀምጡ የተሰጠው ውሣኔ ግን ምናልባት ተጠሪዎች ከአመልካችዋ በፊት ቢሞቱ አመልካች ካሣውን የሚያገኙበት ሁኔታ ሊቋረጥ የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩን ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካችዋ በሕይወት እስካሉና 85 ዓመት እስኪሞላቸው በየወሩ ካሣውን ማግኘታቸው አስተማማኝ የሚሆነው ተጠሪዎች የተወሰነውን ካሣ አጠቃለው በባንክ ወይም በሌላ ገንዘብ ተቋም ሲያስቀምጡ ነው፡፡ ምናልባት አመልካችዋ ቀድመው ቢሞቱ ተጠሪዎች ገንዘቡን መልሰው መውሰድ የሚችሉበት ሁኔታ የተጠበቀ ሲሆን ተጠሪዎችም ከአመልካችዋ በፊት ቢሞቱ አመልካች ካሣው ሣይቋረጥባቸው ማግኘት ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች የየዓመቱን የካሣ መጠን ብቻ እንዲያስቀምጡ መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39178 በሰኔ 14 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች የተወሰነባቸውን ካሣ በሙሉ አመልካች በሚኖሩበት አካባቢ በሚገኝ ባንክ ወይም ገንዘብ ተቋም ያስቀምጡ፡፡ አመልካች በህይወት እስካሉና 85 ዓመት እስኪሞላቸው በየወሩ 300 (ሦስት መቶ) ብር በየወሩ እያወጡ ይውሰዱ፡፡ አመልካች ከ85 ዓመታቸው በፊት ከሞቱ ተጠሪዎች ገንዘቡን ከባንክ አውጥተው ይውሰዱ፡፡ ገንዘቡ የሚቀመጥበት ባንክ በዚህ ውሣኔ መሠረት ማስፈፀም እንዲችል የውሣኔው ግልባጭ ይተላለፍለት፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ገራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 33975

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድነን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን - አልቀረቡም፡፡

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ አበበች ስዩም - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የንብረት ጉዳት ካሣን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን መ/ሰጭ በባሌ ከተማ የሚገኘው ቤቱ ከሮቤ ወደ ሴሩ የሚሠራው መንገድ ስለወጣበት እንዲፈርስና ግምቱ ብር 17,912 /አስራ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ብር/ እንዲከፈለኝ ከተወሰነ በኋላ የአሁን አመልካች ነገ ዛሬ እያለ ስላልከፈለ የቤቱ ግምትና የጠበቃ አበል ከነወጪና ኪሣራው ይክፈለኝ በማለት በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ በመንገዱ ግንባታ ምክንያት መ/ሰጭ ቦታውን እንዲለቁ ግምት የተሠራላቸው ቢሆንም ባለንብረቷ በወቅቱ ከኢት/ንግድ ባንክ ጋራ ክርክር ስለነበራቸው ቤቱን ማንሳት ያልተቻለ ሲሆን ሌላ አማራጭ በመጠቀም ቤቱ ሳይነካ መንገዱ ተሰርቶ ተጠናቆ ርክክብ ተደርጓል፣ ስለሆነም ቤቱ በመንገድ ግንባታ ምክንያት ሳይነሳ አንድ ጊዜ ግምቱ ስለተሠራ ብቻ ይከፈለኝ በማለት መልስ ሰጪ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ የባሌ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 01 ጽ/ቤት የክርክሩ መንስኤ የሆነው ቤት በመንገዱ ግንባታ ምክንያት መነሳት አለመነሳቱን ለፍ/ቤቱ እንዲገልጽ ያዘዘ ሲሆን የቀበሌው ጽ/ቤት አከራካሪው ቤት በመንገድ ስፋት ምክንያት የተነካ

ስለሆነ በወቅቱ ግምት የተሠራለት ቢሆንም እስካሁን ድረስ አልተነሳም፣ ነገር ግን ቤቱ በፍሳሽ ቦይ ውስጥ የሚውል ስለሆነ መፍረሱ አይቀርም የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ፍ/ቤቱ በመቀጠል አመልካች ባለንብረቷ የተበደሩትን ገንዘብ ከፍለው ያጠናቀቁና ባንኩ የሚፈልግባቸው ዕዳ የሌለ መሆኑን ባንኩ ለባሌ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በፃፈው ደብዳቤ መ/ሰጭ በወቅቱ ከዕዳ ነፃ መሆናቸውና ከባንክ ጋር ክርክር ያልነበራቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቤቱ እስካሁን ያልፈረሰ ቢሆንም ወደፊት መፍረሱ እንደማይቀር ስለተረጋገጠ ቤቱ አልተነሳም የሚለው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ ስለዚህ አመልካች የንብረቱን ግምት፣ የጠበቃ አበል እንዲሁም ወጪና ኪሣራ ለመ/ሰጪ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ አቤቱታው በአጭሩ መ/ሰጭ ቤቱ ለወደፊት በኅርፍ ይነዳል የሚል ክርክር ባላቀረቡበትና ጉዳቱ የቤቱን መነሳት የሚያስከትል መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ እንዲሁም በመንገድ ዳር የማያልፍ ውሃ /ጎርፍ/ ንብረት ሳይነካ በቅያሱ ሊስተናገድ እንደሚችል ግምት ሳይወሰድ ላልተነሳና እንዲነሳ ላልተፈለገ ቤት ግምት ይከፈል ተብሎ በሥር ፍ/ቤት መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የመ/ሰጭ ቤት አልፈረሰም እየተባለ አመልካች የንብረት ካሣ ይክፈል ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው መ/ሰጭ የቤቱ ግምት ተከፍሎኝ ቤቱ እንዲነሳ ከተወሰነ በኋላ አመልካች ግምቱን አልከፈለኝም የሚል ክስ በሥር አቅርበው አመልካች ደግሞ የመ/ሰጭ ቤት ሳይነካ መንገዱ ተሠርቷል፤ ርክክቡም ተደርጓል የሚል መልስ ሰጥቶ፣ ፍ/ቤቱ የቤቱን መነሳትና አለመነሳት ሲያጣራ ቤቱ አለመነሳቱን ወደፊት ግን በቦይ ምክንያት መነሳቱ እንደማይቀር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከከተማው አስተዳደር በተገለፀለት መሠረት ቤቱ አልተነካም የሚለውን የአመልካችን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ግምቱ እንዲከፈል መወሰኑንና ይኸው ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መጽናቱን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ ጉዳይ መ/ሰጭ ካሣ እንዲከፈላቸውና ቤቱ እንዲነሳ ተወስኖ እንደነበር ከመግለጽ በስተቀር በመንገዱ ግንባታ ምክንያት ቤታቸው የተነሳ /የፈረሰ/ መሆኑን አላስረዱም፡፡ ከዚህም በላይ የከተማው አስተዳደር ቀበሌ 01 ጽ/ቤት ቤቱ ያልፈረሰ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ቤቱ እንዲነሳ ተወስኖ በነበረው መሠረት መነሳቱ ካልተረጋገጠ ደግሞ በመንገድ ግንባታ ምክንያት በመ/ሰጭ ላይ ጉዳት ደርሷል ማለት አይቻልም፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሰው የሚከፍለው ካሣ መጠን ኃላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ካደረሰው ጉዳት ጋር እኩልና ተመዛዛኝ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሠረት በሕጉ ከተደነገገው የጉዳትና የካሣ ተመዛዛኝነት አንፃር በመ/ሰጭ ላይ የደረሰ ጉዳት መኖሩ ስላልተረጋገጠ ለመ/ሰጭ ሊከፈል የሚገባ ካሣ አይኖርም፡፡

ከዚህም ባሻገር የመሬት ይዞታ ለሕዝብ ጥቅም የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀጽ 7/1/ መሠረት ካሣ የሚከፈለው የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ ለተደረገ ባለይዞታ ነው፡፡ መ/ሰጭ ግን ይዞታቸውን እንዲለቁ ታስቦ ካሣ ሊከፈላቸው የቤቱ ግምት እንደተሠራ ከመግለጽ በስተቀር ይዞታቸውን መልቀቃቸውን በማስመልከት አልተከራከሩም፡፡ ማስረጃም አላቀረቡም፡፡ ስለሆነም መ/ሰጭ ይዞታቸውን እንዲለቁ ሳይደረጉ ይዞታውን እንዲለቅ ለተደረገ ባለይዞታ ሊከፈል የሚገባው ካሣ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የደረሰ ጉዳት መኖሩ ሳይረጋገጥ አመልካች ለመ/ሰጭ ግምት ይክፈል ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 08763 የካቲት 8 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 51879 ጥቅምት 7 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. መ/ሰጭ ላይ የደረሰባቸው ጉዳት ስለሌለ በስር ፍ/ቤት አመልካች ለመ/ሰጭ ይክፈል ተብሎ የተወሰነው የቤቱ ግምት ለመ/ሰጭ ሊከፈል አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 34138

ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

አመልካቾች፡- 1. ሲስተር ገነት ጌታቸው ወኪል ጌታቸው ይማም ቀረበ

2. ሕፃን ናሆም አበበ

ተጠሪ፡- ወንድወሰን ኃይሉ ወልደማርያም ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በመኪና አደጋ ምክንያት የደረሰን የአካል ጉዳት መሠረት በማድረግ የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር አመልካቾች ከሣሾች የነበሩ ሲሆን፣ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረቱት ንብረቱ በሆነው መኪና በደረሰባቸው ጉዳት መጠን ኪሣራ እንዲከፍላቸው ነው፡፡ ከመዝገቡ ማየት እንደቻልነው አመልካቾች የተጠሪ ንብረት በሆነው መኪና ስለመጎዳታቸው አላከራከረም፡፡ ክሱን ያስተናገደው በአፋር ብ/ክ/መ/ የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ኃላፊ ነው በማለት ለ1ኛ አመልካች ብር 20,000 እንዲከፈላት ሲወስን፤ የሁለተኛ አመልካች የጉዳት መጠን ግን ገና አልታወቀም የሚል ምክንያት በመስጠት የጉዳት ኪሣራ እንዲከፈል አልወሰነም፡፡ ሕፃኑ (2ኛ አመልካች) ሕክምና ላይ ነው ያለው በማለት ተጠሪ ኃላፊነት ወስዶ ለሕክምናና ለተለያዩ ወጪዎች ይክፈል የሚል ተጨማሪ ውሣኔ መስጠቱንም ተመልክተናል፡፡ በዚህ መልክ የተሰጠው ውሣኔ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤም ጉድለት የለበትም ስለተባለ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካቾች ህዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው 1ኛ አመልካች በጉዳቱ ምክንያት ሣይከፈላት የቀረውን ደመወዝ በሚመለከት በዝምታ የመታለፉን እና ለ2ኛ አመልካች የጉዳት ካሣ ያለመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም እነዚህን ነጥቦች ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ በሁለቱም አመልካቾች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ስለመሆኑ እስካላከራከረ ድረስ አግባብ ያለው የጉዳት ካሣ እንዲከፈል መወሰኑ የግድ ነው፡፡ በዚህ መዝገብ የተነሣው የካሣ ጥያቄ መሠረት ያደረገው ከውል ውጪ የደረሰን ኃላፊነት በመሆኑ መታየት ያለበት በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13፤ በተለይም በዚሁ አንቀጽ በምዕራፍ 1 በክፍል 3 ስር ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2090(1) እና 2091 እንደተመለከተው በጉዳቱ ምክንያት ተበዳዩ የሚካሰው ለጉዳቱ ተመጣጣኝ በሆነው መጠን ነው፡፡ የጉዳት ካሣው ሲወሰን ደርሶ የተገኘውን (የታየውን) ኪሣራ በማየት ብቻ ሣይሆን፣ ለወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተውንም እግንዛቤ ውስጥ በማግባት ጭምር ሊሆን እንደሚገባ ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2092 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የብዙ አገራት ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ሕጎች ሁለት ግቦችን ማለትም ጉዳቱን የመካስ (insurance goal) እና የጥፋት ባህሪን የመግራት (deterrence goal) ተብለው የሚታወቁትን መሠረት በማድረግ የተቀረፁ ሲሆን፣ የአገራችን ሕግም እንደዚሁ ተመሣሣይ ዓላማ አካቶ እንደተቀረፀ በሕጉ ላይ ማብራሪያ የፃፉት ፕሮፌሰር ጆርጅ ቺቺ ኖቪች /The Ethiopian law of Compensation for Damage/ በሚለው የማብራሪያ መጽሐፋቸው ገልፀውታል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2091 እና 2092 በተቀመጡት መርሆዎች መሠረት ካሣና ጉዳት እኩል መሆን እንዳለበት ይህም በመርህ ደረጃ ተጎጂው ከጉዳቱ አትራፊ መሆን እንደማይገባውና ከደረሰበት ጉዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በታች መካስ እንደሌለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተግባርና በተጨባጭ ሲታይ የጉዳት መጠኑ በፍ/ቤት የሚወሰን ቢሆንም፤ ጉዳዩ የሕግ ጥያቄ ብቻ ባለመሆኑ ወስብስብነት ያለው ከመሆኑም በላይ ሕጉ በተጨባጭ የደረሰ ጉዳት ብቻ ሣይሆን ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትም የተረጋገጠ ሲሆን እንዲካስ ስለሚፈቅድ ወደፊት ስለሚሆን ነገር እርግጠኛ መሆን ስለማይቻል በካሣ አወሳሰን ረገድ ስሌትን የማዛነፍ ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በካሣ አወሳሰን ረገድ ከንብረት ጉዳት ይልቅ አተማመኑ የበለጠ ውስብስብ የሚሆነው ጉዳቱ በሰው አካል ላይ የደረሰ ሲሆን ነው፡፡ በእርግጥ በጉዳቱ ምክንያት የተከፈለ ወጪ፣ ወይም በግልጽ የሚታይ የቀረ ጥቅም ወይም ገቢ ለመድኃኒት መግዣ፣ እንደዚሁም ለሰው ሠራሽ የአካል ምትክና ተጎጂው ወደ ሆስፒታል የተመላለሰበት ወጪ የጉዳት ካሣው አካል ስለሆነና በቀላሉም በማስረጃ የሚረጋገጥ በመሆኑ በአወሳሰን ረገድ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ ነገር ግን ጉዳቱ የዘላቂነት ባህርይ ሲኖረውና የተጎጂው የመሥራት አቅም በሙሉ ወይም በከፊል ሲጓደል በጉዳት ካሣው አተማመን ረገድ አስቸጋሪ ሁኔታ መፈጠሩ አይቀርም፡፡ ስለዚህም ካሣው ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን አለበት ሲባል መታየት የሚገባው በአጠቃላይ በተጎጂው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ የመሥራት ኃይል ቅነሣ (General utility) አንፃር እንጂ ከጉዳቱ በፊት ሲሠራው የነበረውን ሥራ ላለመሥራት ጉዳቱ ያስከተለው ልዩ ጫናና የቅነሣ መጠን /special utility/ ግምት ውስጥ በማስገባት አይሆንም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በተጨባጩ ዓለም ሲታይ እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ሥራ ለመሥራት ብቻ ሣይሆን፣ በአጠቃላይ እንደሰው ለመኖር የተለያየ ፋይዳና ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በሁለቱም አመልካቾች ላይ ዘላቂ የሆነ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ በ1ኛ አመልካች ላይ የደረሰው በቀኝ እግርዋ ላይ ከባድ የስብራት ጉዳት ሲሆን፣ ይህም 18% (አሥራ ስምንት በመቶ) እንደሆነ በሐኪሞች ተረጋግጦአል፡፡ 2ኛ አመልካችም የደረሰበት ጉዳት በመቶኛ ተሰልቶ

ያልቀረበ (ገና በሕክምና ላይ በመሆኑ) ቢሆንም፤ ጉዳቱ በግልጽ የሚታይ እና ከፍተኛ እንደሆነ ሐኪሞች በሰጡት ማረጋገጫ ላይ ተመልክቶአል፡፡

ይኸውም በግራ ሰውነቱ የተወሰነው፣ በቀኝ የራስ ቅሉ የስብራት እና ጭንቅላቱ ውስጥ የመድማት ጉዳት እንደደረሰበት ከዚህ የተነሣም ለረዥም ጊዜ ራሱን ስቶ እንደቆየና አሁንም በሕክምና ላይ እንደሆነ ተገልጾአል፡፡ በመሆኑም በሁለቱም አመልካቾች ላይ ዘላቂ የሆነ ከፊል ስንኩልነት /permanent partial disablement/ ተብሎ ሊመደብ የሚችል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት 1ኛ አመልካች በርትዕ ብር 20,000 እንድትካስ የወሰኑ ቢሆንም፤ ለ2ኛ አመልካች ግን በተመሣሣይ ሁኔታ ካሣ አልወሰኑም፡፡ በበኩላችን እንደምንገነዘበው 2ኛ አመልካችም የአካል ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ርትዕን መሠረት በማድረግ ካሣ ሊከፈለው ይገባል፡፡ ሌላም መወሰን ሲገባው በዝምታ የታለፈው 1ኛ አመልካች በጉዳቱ ምክንያት በደመወዝ ረገድ ቀረብኝ ያለችው ገቢ ሲሆን፣ ይህም ጉዳቱ በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል በመሆኑ ውሣኔ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህም ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥናቸውን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በአፋር ብ/ክ/መ/የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 0574 ሐምሌ 4 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 992 ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. 1ኛ አመልካች በጉዳቱ ምክንያት በደመወዝ ረገድ ቀረብኝ የምትለው ገቢ ግራ ቀኝ ወገኖች ከሚያቀርቡት ማስረጃ አንፃር ታይቶ ይወሰን ብለናል፡፡
3. 2ኛ አመልካችም እንደ1ኛ አመልካች ዘላቂነት ያለው የአካል ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ዞኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ግምት ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማግባት እና ርትዕን መሠረት በማድረግ ተገቢ ነው የሚለውን የጉዳት ካሣ ይወስንለት ብለን ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

4. ተጠሪ ኃላፊነቱን ወስዶ ለ2ኛ አመልካች ሕክምና ተያያዥ ወጪ ይክፈል በሚል በከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በበኩላችንም ተቀብለነዋል፡፡ አልተነካም፡፡
5. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የደረሰውን ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ. 34906

ግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

መድኅን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት

ቤተልሄም ሲሣይ ቀረበች

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቁ ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሐሰት ውንጀላዎችን የያዘ ደብዳቤ በመፃፉ ስሜ ጠፍቶአልና የሕሊና (የሞራል) ጉዳት ካሣ ይከፈለኝ በማለት ተጠሪ በመሠረተችው ክሥ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ክስ የመሠረተችው ታዬ ለማ በተባለ የድሬዳዋ ሪጂን ቴሌኮሙኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ ላይ ሲሆን፣ ይህ ሰው ለክሱ በሰጠው መልስ ደብዳቤውን የፃፈው ከተጠሪ ጋር ባለው የግል ግንኙነት ሣይሆን፣ ከኮርፖሬሽኑ ሥራ ጋር በተያያዘ ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ አመልካች በክርክሩ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባለት ጠይቋል፡፡ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የሆነው በዚህ መሠረት ሲሆን አመልካች ለቀረበው ክስ የበኩሉን የመከላከያ ክርክር አቅርቧል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤት የሁሉንም ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኃላ፣ ተከሣሹን ከክሱ በማውጣት አመልካችን ኃላፊ አድርጎአል፡፡ በመቀጠልም አመልካች ብር 3000 ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን ያጸና ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም አመልካች ጥር 2 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪን በሚመለከት ለኮርፖሬሽኑ በአንድ የሥራ ኃላፊ በቀጥታ የተፃፈው ሪፖርት የስም ማጥፋት ነው በሚል አመልካች ካሣ እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ ስሜን የሚያጠፋ ውንጀላ አለበት የምትለውን ደብዳቤ የፃፈው ሰው የሷ የበላይ ዐለቃ ወይም ኃላፊ ነው፡፡ ደብዳቤው የተፃፈው ደግሞ ለቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ዋና መሥሪያ ቤት ነው፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ የምናየው በቴሌኮሙኒከሽን ኮርፖሬሽን አደረጃጀት መሠረት የሪጂን ሥራ አሥኪያጅ በስሩ ሆና የምትሠራን ሠራተኛ (ተጠሪን) በሚመለከት የበላዩ ለሆነው ለዋናው መሥሪያ ቤት ደብዳቤ በቀጥታ መፃፉን ነው፡፡ አመልካች እና ደብዳቤውን የፃፈው ሰው በፍሬ ነገር ረገድ ያቀረቡት ክርክርም እንደተመለከትነው የበታች የሥራ ኃላፊ በሥሩ የሚያስተዳድራቸውን ሠራተኞች በሚመለከት ሪፖርት በዝርዝር በማቅረቡ የሠራተኞቹን ስም አጥፍቶአል ሊባል አይችልም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ በደብዳቤዎቹ ላይ የሐሰት ውንጀላዎችን የሚያመለክቱ አገላለጾች አሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ የኔን ስም ለማጥፋት ተብሎ የገቡ ናቸው በማለት ተከራክራለች፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ደብዳቤው የተጠሪን ስም የሚያጠፋ በእውነት ላይ ያልተመሠረተ አገላለጽን የያዘ ነው በማለት ነው አመልካች ካሣ እንዲከፍል የወሰኑት፡፡ ከላይ እንተደገለፀው ለደብዳቤው መፃፍ ዋና ምክንያት ሆኖ የሚታየው የሪጂኑ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ በሥራዋ የምታሣየውን ትክክል ያልሆነ ጠባይ እና ተገቢ አይደሉም የተባሉትን ድርጊቶችዋን በሚመለከት ለበላይ ኃላፊ ለማሣወቅ (ሪፖርት ለማድረግ) በመፈለጉ ነው፡፡ በእርግጥ በደብዳቤው ውስጥ ከተጠሪ

እይታ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት የለውም ሊባል የሚችል አገላለጽ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ አይነቱ አፃፃፍ ተጠሪን ቅር የሚያሰኝ ቢሆን ደግሞ በዚያው በኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ታይቶ እልባት የሚሰጠው ነው የሚሆነው ፡፡ የሪጅኑ ሥራ አስኪያጅ ደብዳቤውን በቀጥታ የፃፈው ለበላይ መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች እንጂ ከዚህ ውጪ ላሉት ማለትም ጉዳዩ ለማይመለከታቸው ወገኖች አይደለም፡፡ ይህ በራሱ የሚያሣየው ደግሞ የደብዳቤው ዓላማ ሪፖርት ከማቅረብ ውጪ መታየት የማይችል እንደሆነ ነው፡፡ በሪፖርቱ የተገለፀው ነገር እውነት ነው አይደለም የሚለው ደግሞ የሚወስነው ሪፖርቱ በቀረበለት የበላይ ኃላፊ ነው በመሆኑም በሥራ አስኪያጁ በተፃፈው ደብዳቤ ኃላፊነትን የሚያስከትል (የፍትሐብሔር) የስም ማጥፋት ድርጊት ተፈጽሞአል የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 8329 ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 03295 ጎንደር 23 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው ካሣ የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቤተሰብ ህግ

የሰ/መ/ቁ. 21740

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ወ/ሮ አስረስ መስፍን ቀረቡ፡፡

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ ቀረቡ፡፡

መዝቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በአማ/ብሔ/ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 04313 መስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ የአሁን አመልካች ቅር በመሰኘታቸው ነው፡፡

የአሁን አመልካች ክርክሩ በተነሣበት የወረዳ ፍ/ቤት ከሳሽ ሲሆኑ ያቀረቡት አቤቱታም ባለቤቴ መ/አለቃ መኮንን ለማ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ስለሆነ ሚስትነቱ እና የልጆቹ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም በዚሁ የወረዳ ፍ/ቤት በተቃዋሚነት ቀርባ ተከራክራለች፡፡ ያነሳችውም የመከራከሪያ ነጥብ አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን ሚስት አይደለችም፡፡ ሚስት እኔ ነኝ የሚለው ነው፡፡

የወረዳው ፍ/ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ካቀረበችው የሰው ማስረጃ፣ የዕድር ሰነድ እና የማንበራዊ ፍ/ቤት ውሣኔ ጋር እገናዝቦ ከመረመረ በኋላ የአሁን አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሟች ሚስት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የአሁን መልስ ሰጭ የሟች ሚስት መሆናቸውን በሥ/ፋ/መ/ቁ. 155/95 ያስወሰኑ ቢሆንም በፍ/መ/ቁ. 148/86 ባደረጉት ክርክር ጋብቻው የፈረሰ መሆኑን ስለሚረጋገጥ የካቲት 01 ቀን 1993 ዓ.ም. ስለሚስትነት ማስረጃው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚገልፀው ውሣኔ በፍ/መ/ቁ 148/86 የካቲት 05 ቀን 1993 ዓ.ም. ጋብቻው ፈርሷል በሚል የተሰጠው ውሣኔ ይሽረዋል፡፡ ስለሆነም የአመልካችን ሚስትነት ተቀብዬ አጽድቄያለሁ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን መልስ ሰጭ የይግባኝ አቤቱታ ለከፍተኛው ፍ/ቤት በማቅረቧ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይግባኝ ባይ (የአሁን መልስ ሰጭ) የምትከራከረው የአሁን አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን ሚስት አይደለችም በሚል በመሆኑና የእርሷንም ሚስትነት አስቀድማ ያረጋገጠች በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪ ነጥብ ሆኖ መወሰድ ያለበት የአሁን አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሚች ሚስት ናት ወይስ አይደለችም የሚለው ነው፡፡ ይህንንም በሚመለከት ሚስትነትን በሁኔታ ስለማረጋገጥ የሚደነግገው ሕግ በሚጠየቀው አኳኋን አላስረዳችም፡፡ ስለሆነም መልስ ሰጭ ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት አይደለችም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ግራ ቀኙ በክልል ጠ/ፍ/ቤት ተከራክረዋል፡፡ ይህ ሁለተኛው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ መስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በተመሳሳይ መንገድ የይግባኝ ባይን (የአሁን አመልካችን) ሚስትነት ውድቅ ካደረገ በኋላ የወ/ሮ ውብነሽ ታከለን ሚስትነት ጉዳይ በሚመለከት ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ ከሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ጋር ባደረጉት ክርክር የጋብቻውን መፍረስ እና አለመፍረስ አስመልክቶ እንደገና በጉባኤ ታይቶ እንዲወሰን ተመርቶ እያለ በመካከል ሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ ጋብቻው የፈረሰው በሞት ምክንያት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ሚች በሞቱበት ጊዜ ወ/ሮ ውብነሽ ሚስት አልነበሩም ማለት አያስችልም፡፡ ስለሆነም የሚች ሚስት ናቸው የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ በሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር በይዘቱ

ከወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ ካደረጉት ክርክር የተለየ ባለመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን መልስ ሰጭ በተቃዋሚነት በጉዳዩ ቀርባ የተከራከረችው የአሁን አመልካች የሚች ሚስት አይደሉም የሚሉበትን ክርክር በማቅረብ ነው፡፡ መልስ ሰጭ ይህንኑ ክርክር ለማቅረብ የሚያስችላቸውን የእራሳቸው የሚስትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ በግራ ቀኙ መካከል በተነሳው ክርክር ለጉዳዩ ዕልባት ለመስጠት በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ነጥብ የአሁን አመልካች የሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ሊሆኑ የማይችልበትን የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር በአሁን መልስ ሰጭ በኩል ቀርቧል ወይስ አልቀረበም? በተቃዋሚ በኩል ይህን መሰል ክርክር ካልቀረበስ የአሁን አመልካች የሚች ሚስት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርበዋል ወይስ አላቀረቡም? የሚለው ነው፡፡ ከዚህ ነጥብ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከት መልስ ሰጭ ሚስት እኔ ነኝ በሚለው ላይ አትኩረው የተከራከሩ ከመሆኑ በቀር የአሁን አመልካች ሚስት ሊሆኑ ያልቻሉበትን ክርክርና ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን የመዘገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ምንም እንኳ የእርሷ ሚስትነት ከክርክሩ አካሄድ አኳያ ጥያቄ ውስጥ የገባ ባይሆንም የአሁን አመልካች የሚች የመ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ የሚለውን አቤቱታ በዚያው ደረጃ ሊያቋርጥ የሚችል ክርክርና ማስረጃ ግን አላቀረበችም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች የሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ለመሆኗ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርባለች? በሚለው ነጥብ ላይ ጉዳዩ የተወሰነ ነው፡፡ ይህንንም በሚመለከት በከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረቡት ምስክሮች ምንም እንኳ አመልካችና ሚች ባልና ሚስት ሆነው አብረው ሲኖሩ እናውቃለን በማለት ያረጋገጡ ቢሆንም ሲጋቡና የጋብቻው ሥርዓት ሲፈፀም ነበርን፤ እናውቃለን በማለት ያላስረዱ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 699/2/ እንደሚደነግገው ሚስትነትን በጋብቻ ሁኔታ አስረድተዋል ማለት አይቻልም በማለት የሰጠው ድምዳሜ ይህንን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በመተርጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 699/1/ የጋብቻ ጽሑፍ በሌለ ጊዜ ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ነው ሲል ከደነገገ በኋላ ሁለት ሰዎች የባልና ሚስትነት ሁኔታ አላቸው የሚባለው ባልና ሚስት ነን እየተባባሉ አብረው የሚኖሩ እንደሆነና ቤተዘመዶቻቸውና ሌሎችም ሰዎች በዚሁ ሁኔታ መኖራቸውን ሲያረጋግጡላቸው ነው በማለት ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በመሠረቱ ይኸው ድንጋጌ ግልጽ ነው፡፡ ሕግ ግልጽ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ደግሞ የሕግ ትርጉም ሥራ እንደማያስፈልግ የሕግ አተረጓጎም ዘዴ ያስገነዝባል፡፡ በግልጽ በሕግ በተመለከተው አኳኋን አመልካች በማስረጃ ያረጋገጠች ለመሆኑ እራሱ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ ትርጉም ሥራ እንዲገባ ምክንያት የሆነው በዚህ ድንጋጌ ቁጥር 699/2/ የተመለከተው በተለያዩ ሁኔታ ካልታየ በቀር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 708 ከተመለከተው ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት መኖር ከሚለው በምን ሊለይ ይችላል የሚለውን በመያዝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 699/2/ አለ የተባለው ግንኙነት የሚመለከት ሁኔታ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 708 የተጠቀሰውን የሚመለከት ነው የሚባል ከሆነ ይህንን የማሳየት እና የመከላከል ተግባር የሚለየው በተከራካሪ ወገን ተግባርና ግዴታ ነው፡፡ ለዚህም ነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 700/2/ የባልና ሚስትነት ሁኔታ አለመኖሩንን ለመከራከር የሚቻለው የተከራካሪዎች ዘመዶች የሆኑ ወይም ያልሆኑ አራት የመከላከያ ምስክሮችን በማስመስከር ነው የሚለውን መደንገግ ያስፈለገው፡፡

ስለሆነም አመልካች /የአሁን/ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 699/2/ ለሚደነግገው ሁኔታ የሚች የመ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ለመሆኗ በበቂ ሁኔታ ማረጋገጧ እየታወቀ ከላይ እንደተገለፀው አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በትክክል ካለመረዳት የተነሣ የሚች ሚስት መሆኗን አላረጋገጠችም በማለት ማስረጃው አግባብነት እንደሌለው ተደርጎ ሚስት አይደለችም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ናቸው፡፡ እንዲሁም ይኸው ፍርድ በውጤት ደረጃ መልስ ሰጭም የሚች ሚስት መሆናቸውን አረጋጋጭ ነው ብለናል፡፡
2. የአማ/ብ/ሕ/ክል መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 04313 በመስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት በቁጥር 01052 በሰኔ 30 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፤ ይፃፍ፤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 23021

ሐምሌ 12 ቀን 1999

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብድራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አበባወርቅ ጌታነህ - ጠበቃ አቻምየለህ ተፈሪ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የሚች አቶ አማረ ይልማ ሚስት ናቸው ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ተሽሮ ሚስት አይደሉም ተብሎ በመወሰኑ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሆኑት ባቀረቡት አቤቱታ የሚች አቶ አማረ ይልማ ሚስትነቱ ይረጋገጥልኝ በማለት አመልክተው ፍ/ቤቱም የአመልካችን ምስክሮች ሰምቶ በሰኔ 24 ቀን 1995 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አመልካች የሚች አቶ አማረ ይልማ ሚስት ናቸው በማለት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ከዚህ በኋላም የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም በሞግዚት አድራጊያቸው በወጣት ወንድወሰን አማረ ስም አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአቤቱታውም ይዘት በአመልካች ወ/ሮ አበባወርቅ ጌታነህና በሚች አቶ አማረ ይልማ የነበረው ጋብቻ የቤተዘመድ ጉባኤ በሰጠው ውሣኔ እና ፍ/ቤቱም በሐምሌ 23 ቀን 1976 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መፍረሱ የተረጋገጠ ስለሆነና አመልካቿም ከዚህ ጊዜ በኋላ ከሚች ጋር በትዳር ያልኖሩ መሆናቸው ሚች ነዋሪ ከሆኑበት ቀበሌ ለባንክ በተፃፈ ደብዳቤ የተገለጸ በመሆኑ አመልካች ሚስት ሳይሆኑ ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ሞግዚት የሆንኩለትን

የወጣት ወንድወሰን አማረን መብት የሚነካ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሣኔ ይሰረዝልኝ የሚል ነው፡፡

የተጠሪ መቃወሚያም ለአመልካች ደርሶ በሰጡት መልስ ከሚች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ ፈርሶ እንደነበር ሳይክዱ ከፍቺው በኋላ ንብረት ሳይከፋፈሉ ትዳራቸውን ቀጥለው እንደነበር ከፍቺው በኋላ በደንቡ መሠረት ጋብቻ አልተፈጸመም ቢባል እንኳ ጋብቻ መኖሩን በሁኔታ ማስረዳት እንደሚቻል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የሚፈቅድ በመሆኑ ከፍቺ በኋላም እንደ ባልና ሚስት መኖራቸውን በምስክሮች ማስረዳት ስለሚቻል ከፍቺ በኋላ ጋብቻ አልተፈጸመም በማለት በተቃዋሚ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ፍ/ቤቱ ውሣኔውን እንዲያፀናው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በግራ ቀኙ በኩል የተቆጠሩትን ምስክሮችን ከሰማ በኋላ በአመልካችና በሚች መካከል የትዳር ሁኔታ ስለመኖሩ በአመልካች ምስክሮች እንዳልተረጋገጠ በውሣኔው ላይ አስፍሮ ይልቁንም በአመልካች ልጅ በአቶ ዮናስ አማረ ጥያቄ አመልካችና ሚች አቶ አማረ ይልማ በነዋሪነት ከተመዘገቡበት ቀበሌ በሶስት ምስክሮች ተረጋግጦ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተፃፈው ደብዳቤ ሚች ከአመልካች ጋር የነበራቸው ትዳር በፍቺ ከፈረሰ በኋላ እስከ እለተሞታቸው ትዳር እንዳልነበራቸው የሚያስገነዝብ ስለሆነ ጋብቻ ስለመፈጸሙ የትዳር ሁኔታ መኖርን በማስረዳት ፍ/ቤቱ የሕግ ግምት ሊወስድ እንደሚችል በቤተሰብ ሕግ ቁጥር 97/1/ ላይ የተደነገገ ሲሆን ይህ ግምት በበቂ ማስረጃ ሊፈርስ እንደሚችል በዚሁ አንቀጽ 97/2/ ላይ ስለተመለከተና በአመልካችና በሚች መካከል የትዳር ሁኔታ ስለመኖሩ አስቀድሞ የተሰጠው ውሣኔ በበቂ ማስረጃ የተስተባበለ ስለሆነ ቀደም ሲል አመልካች የሚች ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተሰርዟል በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባይና /አመልካች/ ሚች አማረ ይልማ በ1966 ዓ.ም. ተጋብተው በ1976 ዓ.ም. ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ለአራት ወራት ተለያይተው ኖረው መልስ ሰጪ ታርቀው እንደነበርና ጋብቻው ፈርሶ ከነበረ በኋላም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንብረት ክፍፍል ተደርጎ እንዳልነበረ በአመልካች ምስክሮች ተረጋግጧል በማለት በውሣኔው ላይ አስፍሮ አመልካችና ሟች መታረቃቸው ከተረጋገጠ የሚኖረውን ውጤት በተመለከተ የተፋቱ ባልና ሚስት ግንኙነታቸውን ለማደስ ቢፈልጉ እንደገና መጋባት አለባቸው ወይንስ በእርቅ ስምምነት ወደነበሩበት ይመለሳሉ የሚለውን የቤተሰብ ሕጉ ምላሽ እንደማይሰጥና ነገር ግን በሃገራችን ባሕል መሠረት የተፋቱ ባልና ሚስት ከፍቺ በኋላ ሲታረቁ ድጋሚ ጋብቻ ሲፈጽሙ እንደማይስተዋሉና የእርቅ ስምምነቱ በእራሱ እንደ ባልና ሚስት ለመኖር ሃሣብ ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን በተመሳሳይም አመልካችና ሟች በፍቺ ከተለያዩ በኋላ መታረቃቸውን እንደ ባልና ሚስት ሆነው በጋብቻ የመኖር ውጤት ያለው መሆኑን የሚያስገነዝብ ከመሆኑም በላይ ከፍቺውም በኋላ ንብረት ያልተከፋፈሉ ስለሆነና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጋብቻ የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት ሽሯል፡፡

በዚሁ ውሣኔ ቅር የተሰኙትም የአሁን ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች ከሟች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የሟች ሚስት ነበርኩ የሚሉት አዲስ ጋብቻ ከሟች ጋር ፈጽመው ወይንም ጋብቻው ስለመፈጸሙ የትዳር ሁኔታ መኖሩን አስረዳለሁ በማለት ሳይሆን ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ታርቀን አብረን ኖረናል በማለት ስለሆነ መታረቅም ሆነ አብሮ መኖር ጋብቻን እንደመፈጸም አያስቆጥርም የሚል ትችት አስፍሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር አመልካች የሟች ሚስት አይደሉም በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ችሎቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ጋብቻው የፈረሰው በፍቺ ወይንስ በሞት የሚለው ነጥብ ለሰበር ችሎት ቀርቦ መጣራት እንደሚገባው በማጤኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ተጠሪም በበኩላቸው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ አለመሆኑን በመዘርዘር አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የሕግ ነጥብ በአመልካችና በሟች አቶ አማረ ይልማ መካከል የነበረው ጋብቻ በ1976 ዓ.ም. በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ሟች እስከሞቱበት 1995 ዓ.ም. ድረስ በመካከላቸው በድጋሚ ጋብቻ ተፈጥሯል ወይንስ አልተፈጠረም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ የሕግ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካችና ሟች አቶ አማረ ይልማ በ1966 ዓ.ም. ተጋብተው በ1976 ዓ.ም. ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም፡፡ በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ በ1976 ዓ.ም. በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ከአራት ወራት በኋላ ተመልሰው ታርቀው አብረው መኖር እንደጀመሩ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ በአመልካች ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 94 መሠረት ጋብቻ መኖሩን ማስረዳት የሚቻለው በጋብቻ የምስክር ወረቀት መሆኑ የተመለከተ ሲሆን የምስክር ወረቀቱ በሌለ ጊዜ የትዳር ሁኔታ መኖርን በማስረዳት ጋብቻ እንዳለ ማረጋገጥ እንደሚቻል በዚሁ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 96 እና 97 ላይ ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩልም የተፋቱ ባልና ሚስት በሚታረቁበት ጊዜ በድጋሚ ጋብቻ መፈጸም የሚገባቸው ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ በእርግጥ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ በድጋሚ መጋባት አዲስ ጋብቻ ከመመሥረት የተለየ ስለማይሆን ድጋሚ ጋብቻ መመሥረትን በተመለከተ በሕግ መደንገግ አስፈላጊ ሊሆን አይችልም የሚል ክርክር ሊያስነሳ እንደሚችል ቢታመንም በተያዘው ጉዳይ አመልካችና ሟች ከ10 ዓመት የጋብቻ ጊዜ በኋላ በ1976 ዓ.ም. ተፋተው ብዙም ሳይቆይ ከአራት ወራት በኋላ ሟች እስከሞቱበት 1995 ዓ.ም. ድረስ አብረው እንደኖሩ በአመልካች ምስክሮች የተነገረው ሲታይ እራሳቸውን እንደ ባልና ሚስት እንደሚቆጥሩና ንብረተሰቡም ባልና ሚስት ናቸው በማለት የተቀበላቸው መሆኑን የሚያሳይና ይህም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 96 መሠረት በመካከላቸው የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመካከላቸው የትዳር ሁኔታ መኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ ጋብቻ መፈጸሙን በአንቀጽ 97/1/ መሠረት የሕግ ግምት /Legal presumption/ መውሰድ የሚቻል ሲሆን ይህንን የሕግ ግምት ማፍረስ የሚቻለው በአንቀጽ 97/2/ መሠረት ይህንን በሚክደው ወገን አስተማማኝ ማስረጃ በሚቀርብ ጊዜ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካችና ሟች አቶ አማረ ይልማ ሲኖሩበት ከነበረው የቀበሌ አስተዳደር ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተፃፈ ደብዳቤ ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ሟች ትዳር ያልነበራቸው መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም ይህ ማስረጃ ሕጉ እንደሚጠይቀው የሕግ ግምቱን ለማፍረስ አስተማማኝ ማስረጃ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 21648 በታህሳስ 25 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32637 በሐምሌ 28 ቀን 1997 የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በአመልካች ወ/ሮ አበባወርቅ ጌታነህና በሟች አቶ አማረ ይልማ መካከል የትዳር ሁኔታ መኖሩ ስለተረጋገጠ አመልካች የሟች ሚስት ናቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 23493

ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ አንማው ዘገየ

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ወርቁ መኮንን

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ከሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ሚስት ማን ነች? የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡

ክስ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤት በዚህ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ የአሁን መልስ ሰጭ ከሟች ጋር በ1983 ዓ.ም ጋብቻ የፈፀሙት ቢሆንም በኑሮ አለመግባባት በእርሷ ክስ አቅራቢነት በወረዳው ፍ/ቤት በ1992 ዓ.ም ጋብቻው እንዲፈርስ ተደርጓል፡፡ ይህንንም እርሷ አልካደችውም፡፡ በእርሷ በኩል የቀረበው ክርክር እንደገና በመስከረም 08 ቀን 1995 ዓ.ም ታርቄያለሁ የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለማህበራዊ ዋስትና መ/ቤት የቀረበውን ማስረጃ እንደተመለከትነው በወረዳው ፍ/ቤት በተሰጠው የፍቺ ውሣኔ መሠረት ሟች ከአሁን መልስ ሰጭ ለተወለዱት ልጆች እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ የልጅ ቀለብ በወር 50.00 ሲከፍል የቆየ መሆኑን ነው፡፡ መልስ ሰጭ እንደምትለው በ1995 ዓ.ም ታርቃ ቢሆን ኖሮ ሟች ለልጆች ቀለብ ባልከፈለ ነበረ፡፡ ይህም የሚያመለክተው መስከረም 08 ቀን 1995 ዓ.ም ታርቄያለሁ ስትል ያቀረበችው ማስረጃ እምነት የሚጣልበት አለመሆኑን ነው በማለት መልስ ሰጭ የሟች ሚስት አይደለችም፤ በተቃራኒው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች የሚች ሚስት መሆኗን በበቂ ማስረጃ አስደግፋ ያስረዳች ስለሆነ ሚስት ናት በማለት ወስኗል፡፡

የይግባኝ አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም የይግባኝ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የአሁን አመልካች በደምበጫ ወረዳ ፍ/ቤት መልስ ሰጭ ደግሞ በደ/ማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት ሚስትነታቸውን አረጋግጠው አስወስነዋል፡፡ ሚስትነት ተረጋግጦ የተሰጠውን ውሣኔ አንዳቸው የአንዳቸውን አላሻሩትም፤ ውሣኔው ሕጋዊ ውጤት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ሁለቱም ሚስቶች ናቸው በማለት ከመብት በኋላ የጡረታ አበሉ ለማን ይገባል የሚለውን በሚመለከት አበል በየጊዜው ለመክፈል ከደመወዝ ተቀናሽ እየሆነ ከተጠራቀመው የሚከፈል እስከሆነ ድረስ ከሚች ጋር ረዘም ላለ ጊዜ አብራ ለቆየችው መሆን ይገበዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ መልስ ሰጭ ለ1983 ዓ.ም ጀምሮ ከሚች ጋር በትዳር የቆየች በመሆኑ የጡረታ አበሉ ለመልስ ሰጭ ይክፈል ከሚለው መደምደሚያ ደርሷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥ/ፍ/ቤት የጡረታ አበሉ ለመልስ ሰጭ ሊከፈል ይገባል ለሚለው ውሣኔው መሠረት ያደረገው ምክንያት ሕጋዊ መሠረት የለውም፤ እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኞችን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የአመልካችን ሚስትነት ለይቶ በአግባቡ ወስኖ እያለ የጠ/ፍ/ቤት ሁለታችንንም ሚስቶች ናቸው በማለት መወሰኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭም ውሣኔው ሊፀና ይገባል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ ተከራክራለች፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል እንደተመለከትነውም ሁለቱም ወገኖች በየፊናቸው የሚች ሚስት እና የልጆቻቸው ሞግዚት መሆናቸውን በተለያዩ ፍ/ቤት አረጋግጠው አስወስነዋል፡፡ ይህ ውሣኔ በይግባኝ አማካኝነት የተሻረ ለመሆኑ በግራ ቀኙ በኩል የቀረበ መከራከሪያ የለም፡፡ ይህም ሲሆን ሚስትነትን በማረጋገጥ የተሰጠው ውሣኔ ሕልውና ያለው እና ሕጋዊ ውጤትን የሚያስከትል ነው፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ ይህንኑ መሠረት አድርጎ ሁለቱም ወገኖች

አመልካችና መልስ ሰጭ የሚች ሕጋዊ ሚስቶች ናቸው ሲል የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይሁን እንጂ የጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ መገደብ ሲገባው ከዚህ አልፎ የጡረታ አበሉ ለየትኛዋ ሚስት ይገባል የሚለውን ጭብጥ ይዞ እና ይህንንም ለመለየት ከሚች ጋር ለረዥም ጊዜ በትዳር የኖረችው የትኛዋ ናት የሚለውን መሠረት አድርጎ የጡረታ አበሉ ለአሁን መልስ ሰጭ ሊከፈል ይገባል ሲል መወሰኑ በዚያው ጉዳይ ሁለቱም የሚች ሚስቶች ናቸው በሚል ከሰጠው ውሣኔ ጋር የሚጠርስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እንደቀረበለት ጥያቄ ሚስትነት በማረጋገጥ ረገድ ዳኝነት መስጠት ሲገባው ከተጠየቀው ዳኝነት ውጭ በመሄድና የሚስትነትን ውሣኔ ውጤት በሚያስቀር አኳኋን መወሰኑ ሥነ ሥርዓታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ወ/ሮ አንማው ዘገዬ እና ወ/ር ወርቁ መኰንን ሁለቱም የሚች ሚስቶች ናቸው፤ የጡረታ አበሉም ለሁለቱም ሊከፈል ይገባል ብለናል፡፡
2. የአ/ብ/አ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 07542 በየካቲት 16 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
3. የምሥ/ጎጃ/መስ/ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1039 በመስከረም 20 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ/ 23632

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ወ/ት ፀዳለ ደምሴ - ቀረበች

ተጠሪ፡- አቶ ክፍሌ ደምሴ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው የአሁኗ አመልካች የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ባቀረበችው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በቦንጋ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት የሕፃን ቢንያም ክፍሌ ወላጅ አባት ስለሆንኩ ፍ/ቤቱ ለሕፃኑ ሞግዚትና አስተዳዳሪ አድርጎ ይሹመኝ በማለት የቀረበውን አቤቱታ ፍ/ቤቱ መርምሮ የሕፃኑን ሞግዚትና አስተዳዳሪ አድርጎ ሾሞታል፡፡ የአሁኗ አመልካች በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት የአሁኑ ተጠሪ ሕፃኑን ከመውለዱ በስተቀር ምንም ዓይነት እርዳታ አላደረገም፤ ተንከባክቦም አላሳደገም በማለት የተቃውሞ አቤቱታ ያቀረበች ሲሆን ተጠሪ ሕፃኑ ከእናቱ የሚወርሰውን ሀብትና ንብረት ፍለጋ እንጂ ለሕፃኑ ጥቅም ብሎ ስላልሆነ ተጠሪ ሞግዚት እንዲሆን የተላለፈው ውሣኔ ተሽሮ በምትኩ እኔ አክስቱ ላለፉት 12 ዓመታት ተንከባክቤ ያሣደኩት ሞግዚት ሆኜ እንድሾም ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችውን መቃወሚያ የወረዳው ፍ/ቤት መርምሮ አባት ላለው ልጅ አመልካች የሞግዚትነት ጥያቄ ማቅረብ አትችልም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ሕፃኑን እስከዛሬ ድረስ ሣያሣድግ አሁን እናቱ ስትሞት ላሣድግ ማለቱ ሀብትና

ንብረት ፍለጋ ሊሆን እንደሚችል ለመገመት የሚያዳግት ቢሆንም የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/96 አንቀጽ 235/1 ከወላጆቹ አንዱ በሞት የተለየው ሕፃን በሕይወት ያለው ወላጅ ሞግዚትና አስተዳዳሪ እንደሚሆንለት ስለሚደነግግ የወረዳው ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው በማለት መልስ ሰጭን አስቀረቦ ሣያከራክር በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የለም በማለት የአሁኗን አመልካች አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የሰበር ቅሬታ ማመልከቻው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት መጋቢት 6 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዚህ ጉዳይ የሕፃን ቢንያም ክፍሌ አክስት የሆነችው የአሁኗ አመልካች ሞግዚት ለመሆን ያቀረበችውን ጥያቄ የሥር ፍ/ቤቱ ውድቅ ያደረገበትን የሕግ አግባብ ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ መልስ ሰጭም መጥሪያ ደርሶት መልሱን ባለማቅረቡ የጽሁፍ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

ይህ ችሎት የሰበር ቅሬታ ማመልከቻውን ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36 ስለ ሕፃናት መብት ደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ ሁሉ የመንግሥታዊ ወይም የበጎ አድራጎት ተቋማት እንዲሁም ፍርድ ቤቶችና የአስተዳደር ባለሥልጣናት ወይም የሕግ አውጭው አካላት የሕፃናትን ደህንነት በቀዳምትነት እንዲያስቡ በአስገዳጅነት ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው የአለም አቀፍ ስምምነቶች መካከል የሕፃናትን መብት በሚመለከት 1984 ዓ.ም የፀደቀውና በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 9(4) መሠረት የሀገሪቱ የሕግ አካል የሆነው የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1) መሠረት ፍርድ ቤቶችም ሆኑ ሌሎች አካላት ሕፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውሣኔ ሲሰጡ የሕፃናቱን ጥቅምና ደህንነት በዋነኛነት መመልከት እንደሚገባቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመልክቷል፡፡ እንደሚታወቀው የልጆቻቸው መብትና ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ከወላጆቻቸው የበለጠ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ሰው ሊኖር ስለማይችል ሕግ አውጭው በመርህ ደረጃ የተቀበለው በመሆኑ በሕይወት ያለው አባት ወይም እናት የሕፃን ልጁ ሞግዚት እና አስተዳዳሪ አድርጎ የመሾሙ አሠራር አገራችንን ጨምሮ የበርካታ አገራት ተሞክሮ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሠረት በፌዴራልም ሆነ በክልል የቤተሰብ ሕጎች ውስጥ ወላጆች ለሕፃናት ልጆቻቸው ሞግዚትና አስተዳዳሪ ስለመሆናቸው በግልጽ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ያሉ ቢሆንም እነዚህ ድንጋጌዎች ተፈፃሚት የሚኖራቸው ሞግዚት ወይም አስተዳዳሪ የተባለው ወላጅ በሕገ መንግሥቱ እንደተመለከተው ለሕፃኑ ጥቅምና ደህንነት እስከሠሩ ጊዜ ድረስ ብቻ እንደሆነ ሊስተዋል የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አነጋጋገር በአባት ወይም በእናት የሞግዚትነት ሽፋን የሕፃናትን መብትና ደህንነት የሚጎዱ ወይም ሊጎዱ የሚችሉ ሥራዎች ሁሉ በዳኞች ቀሪ እና ፈራሽ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ በሕጉ የተለያዩ ክፍሎች መገኘቱ ይህንኑ የሕፃኑን መብትና ጥቅም በዋነኛነት ለማስከበር የተደነገገ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች ሕፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሲመረምሩ ከዝርዝር ሕጎቹ በተጨማሪ በሕገመንግሥት አንቀጽ 36(2) በአስገዳጅነት የተቀመጠውን የሕፃናትን ደህንነት ከግምት ውስጥ ያስገባ ውሣኔ ላይ እንዲደርሱ የግድ ይላል፡፡ ይህን በመተላለፍ የሚሰጡ ማናቸውም ውሣኔዎችና ልማዳዊ አሠራሮች የሕገ መንግሥቱን ኃይለቃል የሚቃረኑ ስለሚሆኑ ፈራሽነታቸው የማያጠራጥር ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስናመራ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሕፃን ቢንያም ክፍሌን ሞግዚትነት አስመልክቶ የቀረበላቸውን ጉዳይ ሲመረምሩ ከሕጎቹ ግልጽ ድንጋጌዎች ባሻገር ሕገመንግሥቱ ያስቀመጠውን የሕፃኑን ደህንነትና ጥቅም የማስከበር መርህ ተግባራዊ ማድረግ ሲገባቸው በተለይ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ደረጃ የሞግዚትነት ጥያቄ ያነሣው ሕፃኑ ልጅ « ከእናቱ በውርስ ከሚያገኘው ንብረትና ሀብት ላይ ተካፋይ ለመሆን አስቦ ስለመሆኑ» የከፍተኛው ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ ገልጾ ሕፃኑን ከመውለድ ውጭ ከአስር ዓመታት በላይ ዞር

ብሎ ያላየውን፣ ያልተንከባከበውን፣ ያላሣደገውን እንዲሁም ፍላጎቱን እንኳን ያልጠየቁትን ሕፃን በሰላምና በእንክብካቤ ካደገበት ቤት አስወጥቶ በአሁኑ ተጠሪ ሞግዚትነት ሥር ይተዳደር ተብሎ የተደረሰበት መደምደሚያ የሕፃኑን ደህንነትና ጥቅም ያላገናዘበ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ከሕጎቹ ግልጽ ቃላት ባሻገር የሕጎቹን አላማና መንፈስ በቅጡ ሣያጤኑ የአንቀጾቹን ግርድፍ ቃላት ብቻ በመውሰድ ሕገመንግሥቱን በሚጋፋና የሕፃኑን መብትና ደህንነት በሚጎዳ አኳኋን የሰጡት የሞግዚትነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ከፋ ዞን የቦንጋ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 29/98 እንዲሁም የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በየካቲት 21 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ. 01001 በተጨማሪ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ.14275 የሰጡዋቸው ውሣኔዎችና ትእዛዞች ተሽረዋል፣
- የአሁኗ አመልካች ወ/ሪት ፀዳለ ደምሴ የሕፃን ቢንያም ክፍሌ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ሆና ሕፃኑ ከሚኖርበት ወላጅ እናቱ ከወ/ሮ ፋንታዬ ኃ/ሚካኤል የሚያገኘውን ማናቸውም የውርስ ሀብት ተረክባ ሕፃኑን በመልካም አስተዳደግና ደህንነት ተንከባክባ እንድታሣድገው ተሾማለች፡፡
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 24295

መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ደስታ ገብሩ

ሒሩት መለሠ

መድሕን ኪሮስ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ጽጌ ድረሴ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ መሰለች ረዳ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የንብረት ይገባኛል ጥያቄን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ስትሆን፣ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው ከሚች ባለቤትዋ ጋር አፈራሁት ያለችውን ንብረት እንድታስረክባት ነው፡፡ አመልካችም ለቀረበባት ክስ መልስ ሰጥታለች፡፡ ፍ/ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ ተከሳሽ ክስ የቀረበባቸውን ንብረቶች /መኖሪያ ቤት እና ልዩ ልዩ የቤት ቁሳቁሶች/ ለከሳሽ ታስረክብ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተመሳሳይ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ሚያዝያ 9 ቀን 1998 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ከሚች ባለቤትዋ ጋር አፈራሁት የምትለውን ንብረት በሙሉ መጠየቅ ስለመቻል አለመቻልዋ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ተጠሪ የንብረት ይገባኛል ጥያቄ ያነሳችው የሚች ሚስት መሆንዋንና በዚህ መሠረትም ንብረቱ በጋራ ያፈራችው እንደሆነ በመግለጽ ነው፡፡ አመልካችም ተጠሪ የሚች ሚስት አይደለችም ወይም በተባለው ንብረት ላይ የጋራ መብት የላትም የሚል ክርክር አላነሳችም፡፡ አመልካች ያነሳችው አንድ መቃወሚያ ሲሆን፣ ይህም የቤቱ ግምት ተጋኖአል የሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃወሚያውን በመቀበል ቤቱን በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል እንዲገመት አድርጐአል፡፡ በዚህ መሠረትም ቤቱና በዝርዝር የተገለጹት የቤት ዕቃዎች እንዳሉ ለተጠሪ እንዲሰጡ ወስኗል፡፡

እንደምንመለከተው ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ቤት እና የቤት ዕቃዎች የባልና ሚስት የጋራ ሃብቶች ናቸው፡፡ በንብረቶቹ ላይ ባልና ሚስቱ ያላቸው መብት እኩል አይደለም የሚል ክርክር አልተነሳም፡፡ በባልና ሚስቱ መካከል የነበረው ጋብቻ በባልየው ሞት ምክንያት ፈርሶአል፡፡ ጋብቻ ሲፈርስ በንብረት ክፍፍል ላይ የራሱ የሆነ ውጤት እንደሚኖረው በቤተሰብ ሕጉ ተመልክቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች በግልጽ ተለይተው የታወቁ ናቸው፡፡ አንደኛው ተጋቢ ከሌላኛው ተጋቢ ወገን የበለጠ ወይም ያነሰ መብት አለው የሚል ክርክርም አልተነሳም፡፡ ተጠሪ በንብረቶቹ ላይ እኩል የሆነ /የጋራ/ መብት እንዳላት ከመግለጽ አልፋ ከድርሻዋ በላይ የምትወስድበት ምክንያት እንዳላት አላስረዳችም፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 90 እንደተደነገገው የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተጠሪ መጠየቅ ያለባት ወይም ልታገኝ የሚገባት የንብረቶቹን ግማሽ ብቻ ነው፡፡ ግማሹ የሚች ባለቤትዋ ድርሻ በመሆኑ ይህንኑም ጠቅልላ የምትወስድበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍ/ቤቶችም ይህን በሕግ የተመለከተውን የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ሥርዓት ባለመከተል ውሣኔ መስጠታቸው ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00676 መጋቢት 30 ቀን 1997 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38807 መጋቢት 22 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተጠሪ መውሰድ ያለባት ድርሻዋ ማለትም የቤቱ እና የቤት እቃዎቹ ግማሽ ነው ብለናል፡፡ በዚህ መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈፀም ለስር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 24625

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ራሕማ ዓሊ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

አቤቱታው የንብረት ይገባኛል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተችው ተከሣሽ የሚች ባለቤቱ ማሩ ሱሌይማን ንብረት የሆነ ቤት ይዛ ስለምትገኝ የእኔንና ከሚች የወለድኩትን ልጄን ድርሻ ታካፍለን በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ከሣሽና ተከሣሽ የሚች ሚስቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የቤቱን ግማሽ ሁለቱ ይካፈሉ፡፡ ግማሹን ደግሞ ለልጁ ይሁን በማለት ሲወስን፣ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤት ግን ቤቱ የተገዛው ሚች እና ተጠሪ ባፈሩት ገንዘብ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት አመልካች ከቤቱ ልትካፈል አይገባም ሲል ወስኖአል፡፡ የመጨረሻውን ይግባኝ የሰማው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አከራካሪው ቤት አመልካችና ማሩ ሱሌይማን በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ የተገዛ ሆኖ ሳለ፣ አመልካችና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማሩ ሱሌይማን አብረው አልኖሩም፣ ቤቱ የተገዛበት ገንዘብም ማሩ ሱሌይማን ከተጠሪ ጋር በነበረበት ጊዜ የተገኘ ነው በሚል ምክንያት አመልካች ከቤቱ ድርሻ የላትም የመባሉን አግባብነት መርምሮ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንኑ ነጥብ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አከራካሪው ቤት የተሠራው በአመልካች እና በሟች ማሩ ሱሌይማን መካከል ተመሥርቶ የነበረው ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ በተጋቢዎቹ መካከል የተመሠረተው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ወቅት የተገኘ ንብረት የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ነው ተብሎ የሕግ ግምት እንደሚወሰድበት በሕግ ተደንግጓል፡፡ ይህ የሕግ ግምት ቀሪ ማድረግ የሚቻለው አንደኛው ተጋቢ ንብረቱ የግል ሃብቱ እንደሆነ ካስረዳ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው አከራካሪው ቤት የሟች የግል ንብረት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ቤቱ የሟች የግል ንብረት መሆኑ በሕግ አግባብ ካልተረጋገጠ እና ከፍ ሲል የተጠሰቀውን የሕግ ግምት ቀሪ የሚያደርግ የተለየ ሁኔታ እስከሌለ ድረስ አመልካች በቤቱ ላይ መብት የላትም ለማለት የሚቻልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር አመልካችን ከንብረቱ አንዳትካፈል ማድረግ ደግሞ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአማራ ብ/ክ/መ/የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07983 ታሕሣሥ 22 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05615 መጋቢት 7 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. በአማራ ብ/ክ/መ/ የደባርቅ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡ በመሆኑም የንብረቱ ክፍፍል በዚሁ ወረዳ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ይፈጸም ብለናል፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 25005

ጎዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- መኮንን በላቸው ቀርበ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አለሚቱ አደም ቀረበች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሳውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች በየበኩላቸው ያቀረቡት የንብረት ጥያቄ እና በዚህ ረገድ ያነሱት የመከራከሪያ ነጥብ በዝርዝር ታይተዋል፡፡ ክርክር ከተደረገባቸው ንብረቶች መካከል ዋነኛው በወረዳ 19 ቀበሌ 55 ክልል ውስጥ ይገኛል የተባለው በቁጥር 318 የሚታወቀው መኖሪያ ቤት ነው፡፡ በተደረገው ክርክር ተጠሪ የዚህን ቤት ብቸኛ ባለቤት እንደሆነች የገለጸች ስትሆን፣ አመልካች ደግሞ ቤቱ ጋብቻው ጸንቶ በነበረበት ጊዜ የተሠራ /የተፈራ/ የጋራ ንብረት ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ የዚህን ፍ/ቤት ውሣኔ በይግባኝ የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ ቤቱ ከጋብቻው በፊት ተጀምሮ የነበረ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት የተጠሪ የግል ሃብት መሆን አለበት፡፡ አመልካች ለቤቱ ያወጣው ገንዘብ ታስቦ ይመለስለት በማለት ወስነዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን ቅሬታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡

አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ለቤቱ ስራ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረጉ በዝርዝር ተገልጾ ሳለ የጋራ ባለሃብት ሊሆን አይችልም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

መዝገቡን በአጠቃላይ መርምረን እንደተገነዘብነው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ያረፈበት መሬት ጋብቻው ከመፈጸሙ በፊት ተጠሪ በማኅበር ከተመሩች በኋላ የቤት ስራው መስከረም 29 ቀን 1979 ዓ.ም. መጀመሩን፣ ጋብቻው ታሕሣሥ 26 ቀን 79 ዓ.ም. በመፈጸሙን፣ ቤቱ ሥራው አልቆ ለማኅበሩ አባላት የተከፋፈለው በጥቅምት ወር 1980 ዓ.ም. መሆኑን፣ ቤቱ ተስፋፍቶ የተሠራውና ቤትም የሆነው ጋብቻው ከተፈፀመ በኋላ እንደሆነ፣ ለቤቱ ማሠሪያ ከባንክ በብድር ገንዘብ የወሰደችው ተጠሪ ብትሆንም፣ ከ1981 ዓ.ም. ጀምሮ ጋብቻው በፍቺ እስከፈረሰበት 93 ዓ.ም. ድረስ በአመልካች በኩል ሲከፈል መቆየቱን የስር ፍ/ቤቶች በማስረጃ አረጋግጠዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቶቹ በፍሬ ነገር ረገድ ይህን ቢያረጋግጡም የቤቱ ስራ የተጀመረው ከጋብቻው በፊት ማለትም መስከረም 29 ቀን 1979 ዓ.ም. /ሦስት ወር የማይመዝን ጊዜ/ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ የተጠሪ የግል ሃብት ነው የሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው አከራካሪው ቤት በእርግጥም ቤት የሆነው አመልካች እና ተጠሪ ጋብቻቸውን ከፈጸሙ በኋላ እንደሆነ የሥር ፍ/ቤቶች በቀረበላቸው ማስረጃ በሚገባ አረጋግጠዋል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ለቤቱ መሥሪያ በሚል ከባንክ በብድር የተወሰደውን ገንዘብ ሲከፈል የቆየው በአመልካች በኩል እንደሆነ እና ይህም የሆነው ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ የባልና ሚስት የጋራ ሃብት የሚባለው ባልና ሚስቱ ከግል ንብረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኘውን ገቢዎች ሁሉ እንደሚያጠቃልል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕ/አዋጅ ቁ. 213/92/ አንቀጽ 62/1/ ተመልክቶአል፡፡ አንደኛው ተጋቢ ሃብቱ የግሉ ስለመሆኑ ካላስረዳም ንብረቱ በአንደኛው ተጋቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስም ብቻ የተመዘገበም ቢሆን የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት ነው ተብሎ በሕግ አንደሚገመት በዚሁ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 63/1/ ተደንግጎአል፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አከራካሪው ቤት ያረፈበት ቦታ /መሬት/ ከጋብቻው በፊት ተጠሪ በማንበር የተመራችው ከመሆኑ እና ጋብቻው ሊፈጸም ጥቂት ጊዜ ሲቀረው ሥራው ከመጀመሩ በስተቀር በተጠሪ የግል ጥረት እና ሃብት ብቻ የተገነባ ነው የሚባል አይደለም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ጋብቻው በተፈጸመበት ጊዜ ወይም ከዚያ በፊት ቤቱ የተጠሪ የግል ሃብት ነው ተብሎ በጋብቻ ውል ተለይቶ አልተመለከተም፡፡ እንደምንመለከተው እንግዲህ ቤቱ በማንኛውም መለኪያ የተጠሪ የግል ሃብት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በዚህ ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 2141 ታሕሣሥ 7 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 36010 ሚያዝያ 18 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ ተሻሽለዋል፡፡
2. አከራካሪው ቤት የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት ነው፡፡ ሁለቱም እኩል የመካፈል መብት አላቸው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለስር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 25281

ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ መሠረት ፍስሐ ቀርባለች፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ቀልቤሣ አበው ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 6 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩ የስር አመጣጥ አመልካች የስር ከሣሽ በመሆን በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ጋብቻ መሥርተው ሲኖሩ ከየካቲት 1 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱንና የጋራ ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ ባመለከቱት መሠረት የንብረት ዝርዝር አቅርበው ከዚህ ዝርዝር ውስጥ በጋራ የሠሩትን ቤት እንዲካፈሉና ተጠሪ ቤቱን አከራይተው ስለሚጠቀሙና ኪራዩም በወር ብር 350 (ሦስት መቶ ሃምሳ) ስለሆነ የ10 ዓመት ኪራይ ብር 36000 (ሰላሳ ስድስት ሺ) አመልካች ስላገኙ ቤቱ ተገምቶ የግምቱን ግማሽ በመክፈል ልጆቹን እንዳሳድግበት በማለት ጠይቀዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ቤቱ የተሠራበትን ቦታ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ከመተሣሰራቸው በፊት ያገኙት ስለሆነ አመልካች የቦታው ይዞታ ተካፋይ የሚሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ ሆኖም ቤቱ የተሰራው ግራ ቀኙ ጋብቻ ከመሠረቱ በኋላ ስለሆነ በባለሙያ ተገምቶ የቤቱን ግማሽ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈሉ፡፡ የኪራይ ገቢን በተመለከተ አመልካች በማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስደግፈው ባለማቅረባቸው ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል። ይህ ውሣኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ፀንቷል።

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መነሻነት ሲሆን ይህ ፍርድ ቤት አቤቱታውን መርምሮ መልስ ሰጪን ካስቀረበ በኋላ ግራ ቀኙን አከራክሯል። ክርክሩንም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል። በዚህም መሠረት የስር ፍርድ ቤት ያለአመልካች ስምምነት የቤቱን ግምት አጋማሽ ከተጠሪ ይቀበሉ በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ይህ ፍርድ ቤት እንደሚከተለው መርምሯል።

አመልካች የቤቱን ግምት ግማሽ ተቀብለው እንዲወጡ የተወሰነውን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተጠሪ የቦታውን ይዞታ ያገኙት ከአመልካች ጋር በጋብቻ ከመተሳሰራቸው በፊት በመሆኑ በዚህ ይዞታ ላይ አመልካች ተካፋይ የሚሆኑበት ምንም ምክንያት የለም የሚል መሆኑን ተረድተናል። ከፍርድ ቤቱ ውሣኔ ለመረዳት የተቻለው ቤትና ቦታውን ነጣጥሎ ማየቱን ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይህን ለማድረግ ያስቻለውን ድንጋጌ አልጠቀሰም። በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1131 ላይ እንደተመለከተው በአመልካችና በተጠሪ መካከል ቤቱን በተመለከተ የጋራ ባለሀብትነት መብት በፍርድ ቤቱ ውሣኔ የተመሠረተ ከመሆኑ አኳያ አመልካች በቤቱ ላይ ያገኙት የጋራ ባለሀብትነት መብት የመሬቱ ይዞታንም ስለሚያጠቃልል መብታቸው በይዞታውም ላይ የተዘረጋ ይሆናል። ምክንያቱም በዚህ ድንጋጌ መሠረት በቤት ላይ የተገኙ መብቶች እንደ አንድ ሙሉ ክፍል መሬቱንም እንደሚያጠቃልሉና በተከታዩ አንቀጽ 1132 ላይ እንደተመለከተው ቤቱም የመሬቱ አንድ አቋም ሆኖ የሚቆጠር በመሆኑ ነው። በተጨማሪም ከላይ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1131 መሠረት የቤቱ የጋራ ባለሀብትነትና ቤቱ የቆመበት መሬት የተጠሪ የግል ባለይዞታነት በተመለከተ ግራ ቀኙ አስቀድሞ ያደረጉት ውል ባለመኖሩ ይህ በሌለበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከጋብቻው በፊት የመሬቱ ባለይዞታ ነበር በማለት መወሰናቸው አግባብ ካለመሆኑም በላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተትም ነው።

በሌላም በኩል የጋራ ሀብትን ለማከፋፈል አመቺ በማይሆንበት ጊዜ ግራ ቀኙ ንብረቱን አንዳቸው እንዲያስቀሩ መስማማት እንደሚቻል፣ ለመስማማት ያልተቻለ ቢሆን ግን ንብረቱ ተሸጦ ገንዘቡን እንደሚከፋፈሉ፣ በንብረቱ አሻሻጥ ካልተስማሙ ደግሞ ንብረቱ በአንደኛው ጠያቂነት በጨረታ እንደሚሸጥ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 92 በግልጽ ደንግጓል። ከዚህ ውጪ ተከራካሪ ወገኖች በንብረቱ አከፋፈል ካልተስማሙ በስተቀር ፍርድ ቤቶች በራሳቸው ተነሣሽነት ንብረቱን ለአንደኛው ተከራካሪ ወገን እንዲሰጥ የማድረግ ሥልጣን እንደሌላቸው ከድንጋጌው ለመረዳት ተችሏል። ከዚህ አኳያ የሥር ፍርድ ቤቶች ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ቤቱ ለአንዳችን ብቻ ይገባል በማለት እየተከራከሩ ባሉበት ሁኔታ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስቀር በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 33271 የካቲት 10 ቀን 1997 ዓ.ም. እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 38782 መጋቢት 27 ቀን 1998 ዓ.ም. ቤቱ ለተጠሪ ይገባል በማለት የሰጧቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፤ ይፃፍ።
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ቤቱን በዓይነት መካፈል የሚችሉ ከሆነ እንዲካፈሉ፣ መካፈል የማይችሉ ከሆነ አንዱ ለሌላው ግምቱን ሰጥቶ ቤቱን እንዲያስቀር፣ በዚህ ካልተሰማሙ ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እንዲካፈሉ ያደርግ ዘንድ ታዟል፤ ይፃፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 25588

የካቲት 6 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- መርየን ሃሰን ዑመር - ቀረበች

ተጠሪ፡- መውሊድ ተኸል እስማን - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የባልና ሚስት የግልና የጋራ ሀብትን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ተጠሪው የወሰደብኝን የግሌ የሆነውን አንድ ክፍል ቤት፣ ቀደም ሲል የሰጠሁትን 96 ፍየሎች እና በመካከላችን አለመግባባት ከመፈጠሩ በፊት ከቤቱ ውስጥ አስቀምጬው የወሰደብኝን ብር 5900 ይመልስልኝ በማለት በሶማሌ ክልል ደገሐቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካችና ተጠሪ በትዳር ተሳስረን የቆየን ቢሆንም የየግላችን የሆነ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት የለንም፣ ስለተባሉት ፍየሎችና ስለገንዘቡ አንድም የማውቀው ነገር የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ሕጋዊ የትዳር ትስስር እንዳላቸው ገልፆ በክሱ ላይ የተጠቀሰው አንድ ክፍል ቤት የአሁን አመልካች የግል ንብረት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፣ 96ቱን ፍየሎች አመልካች ለተጠሪ የሰጧቸው መሆኑን በምስክሮች አስረድተዋል፣ ብር 5900 ተጠሪ ከአመልካች መውሰዳቸው ግን አልተረጋገጠም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ክሱ ሊቀርብ የሚገባው ለሸሪአ ፍ/ቤት ነው፣ ቤቱን የሠራሁት እኔ መሆኔን በምስክሮች አረጋጫለሁ፣ ካርታውንም በአመልካች ስም እንዲመዘገብ ያደረግኩት በቅን ልቦና መሆኑን እያረጋገጥኩ ፍ/ቤቱ አይገባህም ሲል የወሰነብኝ ያለአግባብ ነው በማለት ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን የአሁን አመልካችም ከተጠሪ ጋር በትዳር ተሳስረን ስንኖር በጋራ ያፈራነው አንድም ንብረት ስለሌለ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና እና ይግባኙ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ቤቱ የተሠራው አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑ በምስክሮች ስለተረጋገጠ ካርታው በአመልካች ስም መመዝገቡ ብቻ ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት መሆኑን እያረጋግጥም ስለዚህ ቤቱ የሁለቱ የጋራ ሀብት ነው፣ ፍየሎቹን አመልካች ለተጠሪ ሠርቶ እንዲጠቀም ብለው የሰጧቸው መሆኑ ስለተረጋገጠና አመልካችም ክዶ ስላልተከራከረ እንዳመነ ተቆጥሮ የፍየሎቹን ዋጋ ብር 14400 /አሥራ አራት ሺህ አራት መቶ ብር/ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈል በማለት ወሰነ፡፡

የአሁን ተጠሪ በውሣኔው ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ ንብረቶቹን ያፈራነው በጋራ ስለሆነ የስር ፍ/ቤት የፍየሎቹን ዋጋ ተጠሪ ይክፈል በማለት የወሰነው ያለአግባብ ነው በማለት ቅሬታቸውን የገለፁ ሲሆን አመልካችም የስር ክርክራቸውን በመድገም መልስ ሰጥተዋል፡፡ ችሎቱ በመ/ቁ. M/G/14/98 በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. በስር ፍ/ቤት የተፈፀመ የሕግ ስህተት ስለሌለ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ፀንቷል በማለት ወሰነ፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ የአሁን ተጠሪ ለሰበር ችሎቱ በድጋሚ አቤቱታ በማቅረባቸው ችሎቱ ጉዳዩን በሌላ ጊዜ በድጋሚ በማየት በዚያው መዝገብ በግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. ሌላ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ችሎቱ በሁለተኛው ውሣኔ የስር ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው ጉዳይ የቤተሰብ ጉዳይ መሆኑን ሲገነዘቡ ጉዳዩ በሸሪአ ፍ/ቤት እልባት እንዲያገኝ ማድረግ ሲገባቸው ይህንን አላደረጉም፣ የሰበር ችሎቱም በስር ፍ/ቤቶች የተፈፀመውን ይህንን ስህተት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለማጤን በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፣ ስለዚህ ጉዳዩ ወደ ደገሐቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

ይህንን ውሣኔ በመቃወም የአሁን አመልካች በሰኔ 20 ቀን 1998 ዓ.ም. የተፃፈ አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የክልሉ ሰበር ችሎት ለሁለተኛ ጊዜ በሰጠው ውሣኔ በፍርድ ሊወሰን የሚችልን ማንኛውምንም ጉዳይ ለፍ/ቤት የማቅረብና ውሣኔ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብቴን በሚጥስ መልኩ ጉዳዩ በሸሪአ ፍ/ቤት ሊታይ ይገባል በማለት የወሰነ ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አጽድቄዋለሁ ያለውን ውሣኔ በሌላ ቀን ችሎት ሽሬዋለሁና ክርክሩ በሸሪአ ፍ/ቤት ይታይ ብሎ የወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው የክልሉ ሰበር ችሎት በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ ራሱ ደግሞ በማየት በግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. ሌላ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በመሠረቱ አንድ ፍ/ቤት አንድ ጊዜ አይቶ ውሣኔ ያሳረፈበትን ጉዳይ በድጋሚ ሊያይም ሆነ ሊወስን በመርሕ ደረጃ የማይችል ሲሆን ነገር ግን በሕግ ላይ በተቀመጡ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ በድጋሚ ጉዳዩን ሊመለከተው ይችላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን የስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ጉዳዩ በድጋሚ ይታይልኝ ብለው ስላመለከቱ ብቻ ጉዳዩን እንደገና አይቶ ሁለተኛ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አንድ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው መሆንና አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት እንጂ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች የስር ፍ/ቤት ሁለተኛ ውሣኔ መስጠቱ ስህተት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሶማሌ ብ/ክ/መ/ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ M/G/14/98 በግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. ለሁለተኛ ጊዜ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የሶማሌ ብ/ክ/መ/ ሰበር ሰሚ ችሎ 206 ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 05/1/210/97 ዓ.ም. በጎዳር 17 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት በመ/ቁ. M/G/14/98 በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 26839

ጎዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስካለ ለማ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ሣህለ ሚካኤል በዛብህ - ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ በንብረት ክፍፍል ላይ ያደረጉት ክርክር ታይቶ በተሰጠው ውሣኔ ላይ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ተጠሪ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በ82 ካ.ሜ. ላይ የተሠራ ቪላ ቤት ከጋብቻ በፊት የተሰራ የግላቸው መሆኑንና ሌሎችን ንብረቶች ዘርዝረው በማቅረብ ለመካፈል ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ደግሞ የግል ቤቱን ሽጬ ባገኘሁት ገንዘብ ቤቱን ከማኅበሩ ተረክበን አፍርሰን አሁን ያለውን ይዘት እንዲኖረው አድርገን ስለሰራነው የግሉ አይደለም፤ እዳው ከጋብቻ በኋላ ነው የተከፈለው እንዲሁም ከሌሎቹ ንብረቶቹ ውስጥ በውርስ ያገኘኋቸው የግል ንብረቶቼ ይገኙበታል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ከጋብቻ በኋላ ተሰሩ የተባሉት ስራዎች ተገምተው ብር 82,293 (ሰማኒያ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት) ስለሆኑ የዚህን ዋጋ ግማሽ ተጠሪ ለአመልካች ከፍለው ቤቱን ያስቀሩ በማለትና በሌሎቹም ንብረቶች የክፍፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር ውሣኔን አጽንቶታል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ ግምት ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ ሂደት እንደተረዳነው ተጠሪ ግምት ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ የተወሰነው ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተገኘ የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት ነው፡፡ በመሆኑም ክርክር የተነሳበት ቤት የተጋቢዎቹ የጋራ ንብረት ነው ወይስ የተጠሪ የግል ሃብት የሚለው ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁጥር 57 ያመለክታል፡፡ አንድ ንብረት ከግል እና ከጋራ ሃብት ተቀላቅሎ የተገኘ ከሆነ ግን ንብረቱ የጋራ ወይም የግል ተብሎ እንደሚቆጠር የሕጉ ድንጋጌ በግልጽ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ ድንጋጌውን ከአላማው አኳያ መተርጎም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከጋብቻ በፊት የነበረ ንብረት የጋራ እንዳይሆን የተፈለገበት ምክንያት ጋብቻ ንብረት ለማግኘት በሚል ሃሣብ ብቻ እንዳይቋቋምና እንዳይፈርስ ለመከላከል ሲባል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ምንም ንብረት ያልነበረው ሰው ንብረት ያለውን ሰው በማግባት ጋብቻ ሲፈርስ ያላፈራውን ንብረት የሚካፈልበት ሁኔታ ማመቻቸት ለፍትሕ እና ለሕሊና ተቃራኒ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ነገር ግን ለአንድ ንብረት መገኘት ተጋቢዎቹ ያደረጉት አስተዋጽኦ ተመርምሮ እንደነገሩ ሁኔታ የግል ወይም የጋራ ሊባል ይገባል፡፡ ይህንንም ለመወሰን በንጽጽር ሲታይ አብዛኛው መዋጮ የተደረገው ከግል ነው ወይስ ከጋራ የሚለውን ከግምት ማስገባቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ንብረቱ በአብዛኛው ከጋራ ሃብት መዋጮ የተገኘ ከሆነና የግል ንብረቱ ትንሽ ከሆነ ንብረቱ የጋራ ሆኖ መቆጠሩ ፍትሐዊ ይሆናል፡፡ የንብረቱ የተወሰነ ክፍል ከጋብቻ በፊት ተገኝቶ እንኳን ቢሆን አነስተኛ የሆነው ድርሻ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከግል ሃብት ከንብረቱ ላይ በመቀላቀሉ ብቻ ንብረቱ የግል እንዲሆን ማድረጉ ፍትሐዊ አይሆንም፡፡

ከዚህ ተነስተን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በእርግጥ ቤቱ የተጀመረው ከጋብቻ በፊት ቢሆንም ቤቱ ተሠርቶ የተጠናቀቀው ከጋብቻ በኋላ እና ለቤቱ መስሪያ የተወሰደው ብድርም ከጋብቻ በኋላ መከፈሉን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህን ካረጋገጠ በኋላ ከጋብቻ በፊት የተሠራው ሥራ ምን ያሕል እንደሆነ ሳያጣራ እንዲሁም ከጋብቻ በኋላ የተሰራውንም ቢሆንም በገበያ ዋጋ ሳይሆን የመሃንዲስ ግምት ብቻ በማስቀረብ የዚህን ግምት ግማሽ ብቻ አመልካች ለተጠሪ ከፍለው እንዲያስቀሩ መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ቤቱ ተጀምሮ ከማለቁ በፊት ጋብቻው እንደተፈፀመና የተጠናቀቀውም ከጋብቻ በኋላ መሆኑን፣ ለቤቱ መስሪያ የተወሰደው ብድርም ቢሆን ከጋብቻ በኋላ መከፈሉ አብዛኛው ወጪ ከጋራ ሃብት የወጣ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በእርግጥ በንብረቱ ላይ የተቀላቀለውን የግል ሃብት በተቀላቀለው መጠን የግሉ የሆነው ተጋቢ ሊወስድ ይገባል፡፡ ይህም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁጥር 86/1/ ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር የሚስማማ ነው፡፡ በመሆኑም ቤቱ የተጀመረው ከጋብቻ በፊት በመሆኑ ብቻ ቤቱ የተጠሪ የግል ሃብት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 913 በግንቦት 29 ቀን 1996 ዓ.ም ክርክር የተነሳበትን ቤት በተመለከተ የሰጠው የውሣኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡
2. የክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሃብት ነው፡፡
3. ከጋብቻ በፊት የተሠራው ሥራ ተገምቶ ግምቱ ለተጠሪ ይከፈል፡፡ ቤቱን ከተቻለ ግራ ቀኙ በዓይነት ይካፈሉ፣ ካልተቻለ አንዱ ለአንዱ የቤቱን የገበያ ዋጋ ግምት ከፍሎ ያስቀር፣ በዚህ የማይስማሙ ከሆነ ቤቱ ተገምቶ በሃራጅ ተሸጦ የሽያጩን ገንዘብ እኩል ይካፈሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 26953

ጎንደር 13 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አብዱራሂም አህመድ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ - ቀረቡ፡፡

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልከቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በአመልካች ጠያቂነት የቀረበ የሰበር ጉዳይ ነው፡፡

በወረዳው ፍ/ቤት የአሁን መልስ ሰጭ ከሣሽ ነበሩ፡፡ ያቀረቡትም አቤቱታ ከመልስ ሰጪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን መነሻ በማድረግ የንብረት ክፍፍል ይደረግልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካችም በተከሳሽነት ቀርቦ ያካፍለኝ ስትል ከጠየቀቸው ንብረት መካከል በእጁ የሚገኘው ቤት በወንድሜ ገንዘብ የተገዛ በመሆኑ የእኔና የእርሷም አይደለም፡፡ እንዲያውም በእርሷ እጅ የጋራ ንብረት የሆነ ቤት የሚገኝ ስለሆነ ልታካፍለኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም ይህ በእኔ እጅ ይገኛል በተባለው ቤት ላይ የአሁን አመልካች እንዳችም መብት የለውም፡፡ በግል ልጄ የደም ዋጋ የተሠራ ነው የሚል ክርክር አቅርባለች፡፡

የወረዳው ፍ/ቤትም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ሁለት ቤት በሁለቱም እጅ እንደሚገኝ እና አንደኛው ቤት በዋጋ ከሌላው ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይበልጥ ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በእጃቸው ያለው ቤት ድርሻቸው ሊሆን ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤትም በይግባኝ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይህንኑ ውሣኔ በማጽናት አሰናብቷቸዋል፡፡ ለዚህ ውሣኔ የአሁን መልስ ሰጭ ቅር ተሰኝታ የይግባኝ አቤታዋን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርባለች፡፡

ጉዳዩን በሁለተኛ ደረጃ ይግባኝ የሰማው ይኸው ጠቅላይ ፍ/ቤት ሁለቱንም ወገኖች ካከራከረ በኋላ ምንም እንኳ የአሁን አመልካች በእኔ እጅ የሚገኘው ቤት በወንድሜ ገንዘብ የተሰራ እንጂ የጋራ ሀብት አይደለም በማለት የተከራከረ ቢሆንም፣ ይህ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ስለሆነም የቤቱን ግምት ድርሻውን ብር 1000.00 እንዲከፍላት፤ በአሁን መልስ ሰጭ ልጅ ሞት ምክንያት በተገኘ የደም ዋጋ ገንዘብ የተሠራ ነው የተባለው ቤት የጋራ ሀብት ነው የሚል ከሆነ ዳኝነት ሲጠይቅ የሚታይ እንጂ ለማካካሻ ምክንያት ሊሆን አይችልም በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክርም በይዘቱ በሥር ፍ/ቤት ከቀረበው የተለየ አይደለም፡፡ እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በአመልካች እጅ ያለው ቤት በትዳር እያሉ የተሠራ ስለመሆኑ ክርክር ያስነሳ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች በመከራከሪያ ነጥብነት ያቀረበው በእጁ ያለው ቤት በወንድሙ ገንዘብ የተገዛ ስለሆነ የእኔም የእርሷም አይደለም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ንብረቱ በእጁ የሚገኝና የሚገለገሉበት መሆኑ ክርክር አላስነሳም፡፡ ይህም ከሆነ በትዳር እያሉ የተገኘ ማናቸውም ሀብት የጋራ እንደሚሆን ሕጉ ግምት ወስዷል፡፡ ይህንን ግምት የማፍረስ ግዴታ የተከራካሪው ወገን ነው፡፡ ተከሪ ገንዘብ የተገዛ ነው ሲል በአባ

ይም የአሁን አመልካች በወንድሜ ያቀረበው ክርክር እንጂ በማስረጃ አስደግፎ አላስረዳም፡፡ ማስረጃ አለው አንኳ ቢባል ይኸው ንብረት ከወንድሙ በስጦታ ለግሉ ተብሎ የተሰጠ መሆኑን ሊያመለክት ይገባል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት በአግባቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አለ የተባለውን ቤት በሚመለከት መልስ ሰጭ በግል ልጄ ሞት ምክንያት በተሰጠ የደም ካሣ ዋጋ የተሰራ ስለሆነ የግል ሀብቴ ሆኖ ይቀጥላል አለች እንጂ አባባሉን የሚደግፍ የሕግ ክርክር አላቀረበችም፡፡ ይልቁንም የካሣ ክፍያው ምክንያት ምንም ይሁን ምን የካሣ ክፍያ አግኝታለች፡፡ በዚህም የካሣ ክፍያ ቤቱ የተሰራ ለመሆኑ አልካደችም፡፡ የካሣ ክፍያ ደግሞ ገቢ ነው፡፡ በትዳር እያሉ የተገኘ ገቢ እስከሆነ ድረስ ከላይ በተሰጠው የሕግ ምክንያት የጋራ ነው፡፡ የግሏ ለመሆኑ በተለየም መንገድ ቢሆንም የማያስረዳ የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አላቀረበችም፡፡ ስለሆነም ይህም በመልስ ሰጭ እጅ የሚገኘው ቤት የጋራ ሀብት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ንብረቱ የጋራ ነው የሚል ክርክር አመልካች ክስ አቅርቦ እራሱን በቻለ አካኋን ዳኝነት ከመጠየቅ በቀር በማካካሻነት ሊከራከርበት አይችልም በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ቢሆን ይህ ቤት የመልስ ሰጭ የግል ሀብቷ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ አልደረሰም፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ የፍቺ ተከታይ የሆነ የንብረት ክፍፍል ነው፡፡ ምንም እንኳ መነሻ የሆነውን የንብረት ጥያቄ የአሁን አመልካች ታቅርብ እንጂ አመልካችም በእርሱ በኩል የሚቀርብ የንብረት ክፍያ ጥያቄ ካለ በመልስ ሰጭ እጅ የሚገኘውን ንብረት በመዘርዘር ድርሻ ክፍያውን ለመጠየቅ የሚከለክለው የክርክር አቀራረብ ሥርዓት የለም፡፡ የንብረት ማጣራት እና የንብረት ክፍፍል ጥያቄው የፍቺ ውሣኔን ተከትሎ የሚመጣ እንደመሆኑ ሌላኛው ወገን በተከሣሽ ከሳሽነት ተሰይሞ ተገቢውን ዳኝነት ከፍሎ ሊጠይቅ ይገባዋል የሚያሰኝም አይደለም፡፡ ስለሆነም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ የአመልካችን ክርክር አስመልክቶ ዳኝነት ሲጠየቅ የሚታይ እንጂ በቀረበው ጉዳይ የሚስተናገድ አይደለም ሲል በክርክሩ ዳኝነት ሳይሰጥበት ማለፉ በክርክር አቀራረብ ሥርዓት ረገድ መሠረታ

ሀተት መፈፀሙን አረጋግጠናል፡፡ ይኸው ነጥብም ቢሆን በግራ ቀኙ ተገቢው ክርክር የተደረገበት እና ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በመልስ ሰጭ እጅ የሚገኘው ንብረት በሕጉ ግምት የጋራ በመሆኑ እና የሁለቱንም ቤቶች ዋጋ በንጽጽር ተመልክቶ በየእጃቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው ቤት ድርሻቸው መሆኑን በመግለጽ የወረዳው ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ በአግባብ ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 01/98 በሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የተሻረ ሲሆን የወረዳው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01837 ሰኔ 01 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቤት 7978 በሐምሌ 19 ቀን 1997 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በአመልካች እና በመልስ ሰጭ እጅ የሚገኙት ቤቶች ሁለቱም የጋራቸው ስለሆነ በየእጃቸው ያለው ድርሻቸው ነው፤ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 27697

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ርዕሶም ገ/መድኅን - ጠበቃ አበበ ኃይሌ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ጊላሚካኤል - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ተሸጧል የተባለን መኪና ዋጋው ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የሽያጩን ገንዘብ ግማሹን አመልካች ለተጠሪ ይክፈሉ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ሲሉ ተጠሪ ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ተጠሪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ከቤት በወጣሁ ጊዜ የግል አልባሳቶቼን ይገፎ ስላልወጣሁ አመልካች እነዚህን አልባሳቶቼን እንዲሰጠኝ፣ የሠ/ቁ 3-38794 የሆነው መኪና ከጋብቻ በኋላ የተገዛና የጋራ ንብረት ስለሆነ የመኪናውን ዋጋ ግማሽ ድርሻዬን እንዲሰጠኝ እንደዚሁም በጋብቻ ወቅት ያፈራናቸው የቤት ዕቃዎች ተቆጥረው የሚገኙ ስለሆነ ግማሽ ድርሻዬን እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ የነበሩት የአሁን አመልካች በበኩላቸው በሰጡት መልስ አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸውን የፈጸሙት ግንቦት 27 ቀን 1987 ዓ.ም. እንደነበረና ጋብቻቸውን በፈጸሙ ጊዜም ተጠሪ ከጋብቻ በፊት የነበራቸው አንድ መኪና እና አንድ ቤት በጋብቻ ውስ የግላቸው ሆኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደተመዘገበና የቀድሞው መኪና ተሸጦም አቤቱታ የቀረበበትን የሠ/ቁ 3-38794 መኪና ተጠሪ እንደገዙና ይህም መኪና በመካከላቸው ክርክር ከመጀመሩ በፊት በመስከረም 8 ቀን 1991 ዓ.ም በተፃፈ ውል እንደተሸጠና ገንዘቡም ለምን ጥቅም እንደዋለ በመዘርዘር በአጠቃላይም ተጠሪ ለአመልካች የሚያካፍሉት ምንም ንብረት እንደሌለ በመጥቀስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የንብረት ክርክሩ በዚሁ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ አመልካች የጠየቋቸው የግል አልባሳትና የቤት ቁሳቁሶችን በተመለከተ ተጠሪ ክደው ያልተከራከሩ ስለሆነ የግል አልባሳቶቻቸውን እንዲያስረክቧቸው የቤቱ ቁሳቁሶቹንም ከተቻለ በዓይነት እንዲከፋፈሉ ካልተቻለም ተገምተው በግምቱ መሠረት እንዲከፋፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

መኪናውን በተመለከተ ከጋብቻ በፊት ተጠሪ የነበራቸው መኪና በጋብቻ ውሉ የግል ተደርጎ የነበረ ቢሆንም ይህንኑ መኪና በጋብቻ ጊዜ ሸጠው ሌላ መኪና ሲገዙ ይዤው መኪና የግል ሀብታቸው እንዲሆን በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 58/2/ መሠረት ተጠሪ በፍ/ቤት ያላስመዘገቡ ስለሆነ በአንቀጽ 62/2/ መሠረትም የጋራ ሀብት ስለሚሆን መኪናው ተሸጧል የተባለበትን ብር 240 ሺህ ግማሹን ብር 120 ሺህ ከነወለዱ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

የሥር ተጠሪ የአሁን አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤትም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ መ/ሰጭ ከቤት በወጣሁ ጊዜ የግል አልባሳቶቼን ይገፎ ስላልወጣሁ ይግባኝ ባይ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በይ/ባይ በግልጽ ያልተካደ ስለሆነ የግል አልባሳቶቻውን ሊያስረክብ ይገባል ሊወሰንም ይ/ባይ ለመልስ ሰጪ ሊያስረክቡት የሚገባ ምንም ንብረ ለ በግልጽ ከመካዳቸውም በላይ በዚህ ረገድ መ/ሰጭ የቆጠሩት ማስረጃ ይ/ባይ የመሃላ ቃላቸውን እንዲያወርዱ በመጠየቅ ሲሆን በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ይ/ባይ የመሐላ ቃላቸውን

እንዲያወርዱ ባለመደረጉ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መሐላ እንዲያወርዱ ተደርጎ መ/ሰጭ የግል አልባሳታቸውን ጥለው እንዳልሄዱ ያረጋገጡ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ይ/ባይ የመ/ሰጭን የግል አልባሳቶችን ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት ሽሯል፡፡

የሠ/ቁ. 3-38794 የሆነውን መኪና በተመለከተ ይግባኝ ባይ የሚያቀርቡት ክርክር መኪናው የተሸጠው ግራ ቀኙ ከመፋታታቸው ከ11 ወራት በፊት አካባቢ በመሆኑ ከፊሉ ገንዘብ በጋራ ለጋራ ችግራቸው እንዳዋሉትና በቀሪው ገንዘብም ብዛት ያለው ወርቅ ገዝተው በመ/ሰጭ አክስት ቤት ማስቀመጣቸውን ቢሆንም ይህንን ለማስረዳት ያቀረቧቸው ምስክሮች ቀርበው እንደተሰሙት ይግባኝ ባይና መ/ሰጭ ተጣልተው በሽማግሌዎች ፊት እርቅ በፈጸሙበት ጊዜ የተገዛበትን ዋጋና ግራሙን የማያውቁት ወርቅ በመ/ሰጭ አክስት ቤት ሲያስቀምጡ ማየታቸውን እንጂ ለመ/ሰጭ አክስት በአደራ ተሰጥቷል የተባለው ወርቅ በመኪናው ሽያጭ ገቢ የተገዛ ስለመሆኑ ካለመሆኑም በላይ ወርቁ የመ/ሰጭ አክስት ቤት ስለመቀመጡም ቢሆን በምስክርነት ማቅረብ ይገባቸው የነበረው የመ/ሰጭ አክስትን ነበር የሚል ትችት በውሣኔው ላይ አስፍሮ የመኪናው ሽያጭ ገንዘብ ለግራ ቀኙ ጥቅም መዋሉን ይግባኝ ባይ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ አላቀረቡም በማለት ይግባኙን ባለመቀበል የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካችና ተጠሪ በፍቺ ከመለያየታቸው በፊት በአንድነት እየኖሩ ተሸጠ የተባለው መኪና የሽያጭ ገንዘብ ለግራ ቀኙ መጠቀሚያ ስለመዋሉ በማስረጃ አልተረጋገጠም ተብሎ የሽያጩን ገንዘብ ግማሹን አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ተጠሪ ባሉባት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙ ል፡፡ የሰበር አቤቱታውም ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸውን የፈጸሙት ግንቦት 27 ቀን 1987 ዓ.ም. እንደሆነ ይሄው ጋብቻቸው በፍቺ የፈረሰው ደግሞ ኅዳር 7 ቀን 1992 ዓ.ም. እንደሆነና እንደዚሁም ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነው የሠ/ቁ. 3-38794 የሆነው መኪና የተሸጠው መስከረም 1 ቀን 1991 ዓ.ም. መሆኑ እነዚህ ፍሬነገሮች ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

የተጠቀሰው መኪና ጋብቻው በፍቺ ከመፍረሱ 1 ዓመት በፊት ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ መሸጡና ጋብቻው በፍቺ በፈረሰ ጊዜ የመኪናው ሽያጭ ገንዘብ በመሉ ወይንም በከፊል አመልካች እጅ እንደሚገኝ በማስረጃ ካልተረጋገጠ ጠቅላላ የመኪና ሽያጭ ገንዘቡ በጋብቻ ጊዜ ለጋራ የትዳር ጥቅም እንደዋለ የባልና ሚስትን ሃብት ስለማጣራት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ከተደነገገው ከቁጥር 85-93 ካሉት ድንጋጌዎች አንጻር የሕግ ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡

የዚህ የሕግ ግምት ተጠቃሚ የሆነ ወገንም ንብረቱ በጋብቻ ጊዜ የተሸጠ መሆኑን ካስረዳ በቂ ሲሆን ሌላው ወገን ደግሞ ጋብቻው በፍቺ በፈረሰ ጊዜ ከንብረቱ የሽያጭ ገንዘብ በመሉ ወይንም በከፊል የሚገኝ መሆኑን ካስረዳ የሽያጩ ገንዘብ በጋብቻ ጊዜ ለጋራ ጥቅም ውሏል የሚለውን የሕግ ግምት እንዳፈረሰ ይቆጠራል፡፡

አመልካች ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነው መኪና በጋብቻ ጊዜ የተሸጠ መሆኑን በማስረዳት የሽያጩ ገንዘብ ለጋራ የትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕጉ በወሰደው ግምት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩልም ተጠሪ ጋብቻው በፈረሰ ጊዜ የመኪናው ሽያጭ ገንዘብ በመሉ ወይንም በከፊል በአመልካች እጅ እንደሚገኝ ያላስረዱ በመሆኑ የሕግ ግምቱን ማፍረስ አልቻሉም፡፡

በፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ይ/ባይ ከመኪናው ሽያጭ ገንዘብ ላይ ብር 115,000 /አንድ መቶ አሥራ አምስት ሺህ/ የሚያወጣ ወርቅ ለመ/ሰጭ ገዘቹ ወርቁም መ/ሰ

ቤት እንዲቀመጥ የተደረገ ስለመሆኑ የሚያውቁልኝ ምስክሮች እን ... .ሼ እነዚህ ምስክሮች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሊሰማልኝ ሲገባ አልተሰሙልኝም የሚል ክርክር በማቅረባቸው

ፍ/ቤቱ እነዚህን ምስክሮች አስቀርቦ ቢሰማም ወርቅ ተገዝቷል የሚለው የይግባኝ ባይ ክርክር ለትዳር ጥቅም ውሏል በሚለው የሕግ ግምት ውስጥ የሚጠቃለል ሆኖ ሳለ ማስረጃ መስማት ሳያስፈልገው በሕግ ግምቱ ላይ ተመስርቶ ውሣኔ መስጠት ሲገባው የይግባኝ ባይን የተሳሳተ የክርክር መስመር ተከትሎ ማስረጃ በመስማት ከመኪናው የሽያጭ ገንዘብ ላይ ይ/ባይ ለመ/ሰጭ ወርቅ ስለመግዛታቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የመኪናውን ሽያጭ ገንዘብ ግማሹን ይግባኝ ባይ ለመ/ሰጭ እንዲከፍሉ ውሣኔ መስጠቱ እንደዚሁም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ይህንኑ የሕግ ግምት ሳያገናዝብ ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06189 በሚያዝያ 28 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20828 በጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሠ/ቁ. 3-38794 የሆነው መኪና አመልካች የሸጡት በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ ጸንቶ ባለበት ጊዜ ስለሆነና ገንዘቡም ለጋራ የትዳር ጥቅም እንደዋለ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች አኳያ የሕግ ግምት ስለሚወሰድና ተጠሪም ይህንኑ የሕግ ግምት ያላፈረሱ ስለሆነ የሽያጩን ግማሽ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 27869

ጎዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጐስ ወልዱ

መስፍን እቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አመልካች ፡- ፍቅርና ሠላም ኃ/የተ/የግ/ማ - ጠ/ተፈራ ሙሉጌታ ቀረበ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ ቀረቡ

2. አቶ ትሁት ማሞ ጠ/ደረጀ ወርቁ ቀረበ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡

በተጠሪዎች መሐከል የነበረው ጋብቻ በ10/03/95 ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍል ክርክሩ ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ የአሁኑ አመልካች የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ናቸው የተባሉት የአ/አበባና በደ/ዘይት ከተማ የሚገኙት ቤቶች 2ኛ ተጠሪ ለማህበሩ በአይነት መዋጮ የሰጡት በመሆኑ ቤቶቹ የማህበሮቹ ናቸው በማለት ተቃውሞ አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ 2ኛ ተጠሪ የትኛውን ቤት ለማሕበሩ እንዳዋጡ የሚያሳይ የቤት6 አድራሻና ቁጥር በግልጽ በመመሥረቻ ፅሁፉ ላይ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም በሕጉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ማስተላለፍን የተመለከተው የመመዝገብ ተግባር አልተፈፀመም፤ የቤቱን የባለቤትነት ምስክር ወረቀት አቅርቦ ቤቱ የኩባንያው መሆኑን አላስረዳም በማለት ተቃውሞውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም ቤቱ ለኩባንያው በመዋጮ ተሰጥቷል ወይ የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲል መልስ ሰጪ እንዲቀርቡ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በፁሑፍ እና በቃል አሰምተዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አመልካች ክርክር የተነሳበት ቤት ለማህበሩ በመዋጮ ተሰጥቷል የሚለው 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለማህበር መስጠታቸው በማሕበሩ መመሥረቻ ጽሁፍ ላይ ተመልክቷል፡፡ የማሕበሩ መመሥረቻ ጽሁፍም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ተመዝግቧል በማለት አመልካች ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የተከራከረው በመመስረቻ ጽሁፍ ላይ በመዋጮ ተሰጠ የተባለው ቤት አድራሻውን ቁጥሩ በግልጽ ያልተጠቀሰና የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሌላ 3ኛ ወገን ለማስተላለፍ በህጉ የተመለከተው የምዝገባ ስርዐት ያልተሟላ ነው በማለት ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ በማህበሩ ተዋጣ ሲባል እኔ አልተስማማሁም በማለት ነው፡፡

በአንድ የንግድ ማህበር ውስጥ የአክስዮን ባለድርሻ ለመሆን አባላቱ ድርሻቸውን በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት ሊያዋጡ ይገባል፡፡ ኃ/ የተወሰነ የግል ማህበር ሲቋቋም በሚዘጋጀው የመመስረቻ ጽሑፍም እያንዳንዱ ማህበርተኛ ያስገባው የመዋጮ የገንዘብ ልክና በዓይነት ያገባው የመዋጮ ግምት ሊገለጽ እንደሚገባ በንግድ ህጉ ቁጥር 517/ሠ/አና/ረ/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ በንግድ ህጉ ላይ በዓይነት የተዋጣው ንብረት በምን አይነት ዝርዝር ሁኔታ መመስረቻ ጽሁፉ ላይ ሊገለጽ እንደሚገባ በግልጽ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን የተዋጣው የንብረት አይነት በማያሻማ ሁኔታ ለመለየት በሚያስችል መልኩ ሊገለጽ ይገባል፡፡ ንብረቱን በትክክል ለመለየት ወይም ለማወቅ የሚያስችል ሁኔታ ካለ ግን የተለያዩ ዝርዝር ነገሮች አልተገለፀም በሚል ብቻ መዋጮ አልተደረገም ማለት ተገቢ አይሆንም፡፡

በተያዘው ጉዳይ 2ኛ ተጠሪ የኩባንያው 27% አክስዮን ባለድርሻ የሆኑት በዓይነት ባዋጡት መዋጮ መሠረት ነው፡፡ ከዚህም መዋጮ አንዱ በአ/አበባ የሚገኘውና ክርክር የተነሳበት ቤት መሆኑን አመልካች ይገልፃል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የቤቱ አድራሻና ቁጥር ተለይቶ ያልተጠቀሰ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ በመዋጮ የተሰጠው ክርክር የተነሳበት ቤት ነው ሊባይ አይችልም ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ እኛም እንዳየነው በመመስረቻ ጽሁፍ ላይ አ/አበባ የሚገኘው ቤት በወዋጮ የተሰጠ መሆኑ ከመገለፁ በቀር የቤቱ አድራሻና ቁጥር ተለይቶ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ ያዋጡት የቱን ቤት ነው የሚለው ሊመለስ ይገባል 2ኛ ተጠሪ በመዋጮ የተሰጠው አ/አበባ የሚገኘው ቤት ክርክር የተደረገበት ሳይሆን ሌላ ቤት ነው፣ በአ/አበባ ውስጥ ከአንድ ቤት በላይ አለኝ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የለም፡፡ አንድ ውል ግልጽ ባልሆነ ጊዜ ደግሞ ሊተረጐም የሚገባው የተዋዋዮቹ ሐሳብ ምን እንደነበረ በመፈለግ ጭምር እንደሆነ የፍ/ህ/ቁ. 1733 ያመለክታል፡፡ 2ኛ ተጠሪም በአ/አበባ ያላቸው አንድ ቤት ብቻ ከሆነ ለኩባንያው በዓይነት ለማዋጣት ያሰቡት ይህንኑ ቤት ነው ተብሎ ነው ሊተገበም የሚገባው 2ኛ ተጠሪ ያዋጡት ሌላ ቤት እንደሆነ ክርክር ሳያቀርቡ የቤቱ አድራሻና ቁጥር ተለይቶ ባለመገለፁ ብቻ በግልጽ የተሰጠ መዋጮ የለም በማለት የቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡

ከዚህ ሌላ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለን መብት ለማስተላለፍ የባለቤትነት ስም የማዛወር ሥርዓት አልተፈፀመም የሚል ነው፡፡ ከመዝገቡ የመመስረቻ ጽሑፍ በውልና ማስረጃ መዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ እና በሚመለከተው የኢንቬስትመንት ባለሥልጣን ዘንድ ቀርቦ እንደተመዘገበ ተረድተናል፡፡ የቤቱ ሥም በኩባንያው ተዛውሮ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ውስጥ አለመመዝገቡ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ እንዳይሆን ከሚከለክላቸው በቀር ንብረቱ በዓይነት በመዋጮ መሠጠቱን ውጤት አያሳጣውም፡፡ ይህንንም ከፍ/ሕ/ቁ. 2878 መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ንብረቱ የጋራ ሃብት በመሆኑ ያለእሳቸው ፈቃድ ለ3ኛ ወገን ሊተላለፍ እንደማይችል ተከራክረዋል፡፡ በእርግጥ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሆነ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሀብትነትን ወይም ሌላ መብት ለ3ኛ ሰው ለማስተላለፍ የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት

ማስፈለጉ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 68/1/ ሥር የተመለከተ ሲሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢም ውሉ እንዲፈርስ ለፍ/ቤት ጥያቄ በማቅረብ ውሉ እንዲፈርስ ማድረግ ይችላል፡፡ (የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 69/1/) ውሉ የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሳይኖር በመደረጉ ብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ሳይሆን ይልቁንም ውጤት እንዳይኖረው አንደኛው ተጋቢ ለፍ/ቤት ጥያቄ በማቅረብ ማስፈረስ ያስፈልገዋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ይኸው 2ኛ ተጠሪ ከማህበሩ ሌላዋ የአክስዮን ባለድርሻ ጋር ያደረጉት ስምምነት እንዲያፈርስላቸው ለፍ/ቤት ጥያቄ አቅርበው አላስፈረሱም፡፡ በመሆኑም ውሉን ሲዋዋሉ ስለማላውቅ ቤቱ ለማህበሩ በመዋጮ ሊሰጥ የማይገባው የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በአጠቃላይ ክርክር የተነሳበትን ቤት 2ኛ ተጠሪ በአመልካች ማህበር በአይነት ያዋጡት በመሆኑ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በሚል የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለው ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 9392 በ10/01/1998 በወረዳ 17 ቀበሌ 21 ቁጥር 432 የሆነው ቤት 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች ማህበር በአይነት ያዋጡት የማህበሩ ቤት አይደለም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ከፍ ሲል ቁጥሩና አድራሻው የተጠቀሰው ቤት ለአመልካች በዓይነት የተዋጣ ንብረት ነው፡፡
3. ቤቱን በተመለከተ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በማጽናት በመ/ቁ. 42402 ህዳር 21/1999 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 29343

ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ አምሳለ ተፈራ

2. ወ/ት ሌንሳ ኢላላ ጠበቃ ተስፋዬ ዘውዴ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ት አበባ አድማሱ ጠበቃ ጥጋቡ ጌጤ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ 1ኛ ከሳሽና ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ በጋብቻ ሥርዓት ግዴታ ውስጥ እያሉ 2ኛዋን ከሳሽ ወልደዋል፡፡ ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ የካቲት 29 ቀን 1995 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሲሆን ተከሳሽ የሟች ልጅ ናቸው፡፡ ሟች እና 1ኛ ከሳሽ ታህሣሥ 18 ቀን 1962 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተጋብተው በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 09 ቁጥር 836 በሆነ መኖሪያ ቤት እየኖሩ በካርታ ቁጥር 31619 አቶ አክሊሉ አጥላባቸው ከተባሉ ግለሰብ የገዙትን መኖሪያ ቤት እያከራዩ ለትዳር ጥቅም አውለዋል፡፡ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ለመንግስት ያደረገው አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲታወጅ ባልና ሚስቱ ተነጋግረው ለዚህ ክስ ምክንያት የሆነውን በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 09 ቁጥር 836 የሆነውን ቤት በጋራ ሀብትነት መርጠው የኪራይ ገቢ ይሰበስቡበት የነበረውን ከላይ የተገለፀውን መኖሪያ ቤት በትርፍነት ለመንግሥት አስረክበዋል፡፡

የ1ኛዋ ከሳሽ እና የሟች የጋራ ሀብት የሆነውን እንዲሁም የ2ኛዋ ከሳሽ የውርስ ድርሻ የተቋቋመበትን መኖሪያ ቤት ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ በሞት

ከተለዩበት ከየካቲት 29 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ተከሳሽዋ በይዞታቸው ሥር አድርገው በወሰኗቸው ግለሰቦች አማካይነት እያከራዩ በኪራዩ ገቢ እስካሁን በብቸኝነት ይጠቀሙበታል፡፡ ይሄው ቤት በአነስተኛው በወር ብር 3.500 ሊከራይ የሚችል ሲሆን ሟች ሕይወታቸው ካለፈበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ በብቸኝነት በመሰብሰብ ያለአግባብ የበለፀጉ ስለሆነ የ2 ዓመት ከ5 ወር ገቢው ብር 101.500 /አንድ መቶ አንድ ሺህ አምስት መቶ/ ስለሚሆን የ1ኛ ከሳሽ ድርሻ ብር 50.750 የ2ኛ ከሳሽ ብር 25.375 ተከሳሽ እንዲከፍሉና ቤቱም በሐራጅ ተሸጦ እንድንከፋፈል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሾች ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ ደርሶ በሰጡት መልስ 1ኛ ከሳሽ ከሟች ጋር በጋብቻ ተቆራኝተው በነበረ ጊዜ በካርታ ቁጥር 31619 የተመዘገበውን ቤት ከአቶ አክሊሉ አጥላባቸው ገዝተው ለጋብቻ ጥቅም ሲያውሉት እንደነበር ያቀረቡት ከሀቅ ያፈነገጠ ነው፡፡ የተጠቀሰው ቦታና ቤት አቶ ኢላላ ኢብሳና አቶ ለማ ኢብሳ በጋር ገዝተውት የነበረ ሲሆን አቶ ኢላላ ኢብሳ በመሬቱና በቤቱ ላይ በግላቸው ሙሉ መብት አልነበራቸውም፡፡ ቤቱ በጋራ ሐብትነት ተመርጦ ነው በማለት ከሳሾች በክሳቸው የጠቀሱትም ሐሰት ነው፡፡ ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ ለመንግስት ያስረከቡትን ቤት ከአቶ ለማ ኢብሳ ጋር የጋራ ስለነበር የግሌ ነው ብሎ ለመምረጥ የሚያስችል መብት ስላልነበራቸው ቤትና መሬቱን ከማስረከብ በስተቀር ምንም ማድረግ የማይችሉ ስለነበርና ቤቱም ተከፍሎ ባላለቀ የባንክ ብድር ዕዳ ተይዞ የነበረ በመሆኑ በእነዚህ ምክንያቶች ቤትና ቦታውን መንግሥት በትርፍነት ወረሰው እንጂ ባልና ሚስቱ መክረው አላስረከቡትም፡፡

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09 የሚገኘውና መለያ ቁጥሩ 836 የሆነው መኖሪያ ቤት ሟች እና 1ኛ ከሳሽ ጋብቻ ከፈፀሙበት ታህሣሥ 18 ቀን 1962 ዓ.ም በፊት በ1957 ዓ.ም የተሠራና በጋብቻ ወቅትም የጋራ እንዲሆን የፈቀዱበት ውል የሌለ ስለሆነ የሟች የአቶ ኢላላ ኢብሳ የግል ንብረት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቶ ለማ ኢብሳ ለረጅም ዘመን የሚች ወኪል በመሆን ንብረታቸውን ያስተዳድርላቸው የነበረ ሲሆን ሚች ሲሞቱ ተከሳሽ አሜሪካን አገር እኖር ስለነበር የሚችን ቤት እኔ አልተረከብኩም፤ አላከራየሁም፡፡ አቶ ለማ ኢብሳን የወከልኩት ለወደፊቱ በውርስም ሆነ በሌላ ምክንያት ለማገኘው ንብረት ወኪል እንዲሆነኝ እንጂ የሚችን ቤት እንዲያስተዳድርልኝ አልወከልኩም በማለት ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን ከሰማ በኋላ የክርክሩ መሠረት የሆነው ቤት የሚች አቶ ኢላላ ኢብሳና የ1ኛ ከሳሽ የጋራ ሐብት ነው ወይንስ አይደለም?

ተከሳሽ ይህንኑ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት በወኪላቸው አማካይነት ይዘውታል ወይ? ቤቱን በተመለከተ የተጠየቀውን ገንዘብ ተከሳሽ ለመክፈል ይገደዳሉን? የሚሉትን ጭብጦች መሥርቶ ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 09 ክልል የሚገኘው የመ/ቁጥር 836 የሆነው ቤት ሚችና 1ኛ ከሳሽ ከመጋባታቸው በፊት በ1957 ዓ.ም የተሠራና በሚች አቶ ኢላላ ኢብሳ ስም የተመዘገበ ስለመሆኑ በተከሳሽ በኩል ማስረጃ የቀረበ ከመሆኑም በላይ ከሳሾችም በክርክር ወቅት ይህንን ያላስተባበሉ ሲሆን ሚች አቶ ኢላላ ኢብሳና 1ኛ ከሳሽ ይህን ከጋብቻ በፊት የተሠራውን ቤት የጋራ የጋብቻ ንብረት ያደረጉበት የጋብቻ የውል ሰነድ የለም፡፡

1ኛ ከሳሽ ክስ የቀረበበት ቤት የጋራ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡት ሌላ የመከላከያ ነጥብ ሚች አቶ ኢላላ ኢብሳና 1ኛ ከሳሽ በጋብቻቸው ወቅት ያፈሩትን በካርታ ቁጥር 31619 የሚታወቀው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 11/1/ መሠረት ለመንግስት አስወርሰው /አስረክበው/ ለአሁኑ ክርክር መሠረት የሆነውን ቤት በስምምነት መርጠው ያስቀሩት ቤቱ በአዋጁ መሠረት የጋራ ንብረት ሆኗል የሚል ነው፡፡ ነገር ግን የአዋጁ ድንጋጌ ሲታይ ቤተሰብ ወይንም ግለሰብ አንድ ቤት እንደሚፈቀድለት እንጂ ይህ አንድ ቤት ከንብረት ሕግ አንፃር የማን

ንብረት ነው የሚለውን አይመልስም፡፡ በአጠቃላይ ከሳሽ ቤቱን በስምምነት መርጠን ይበሉ እንጂ የግል ንብረት የሆነውን የጋራ ንብረት ለማድረግ በሕግ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ በማቅረብ ያላስረዱ ስለሆነ 1ኛ ከሳሽ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

የኪራይ ክፍያን አስመልክቶ በክስ የተጠየቀውን በተመለከተም ተከሳሽ አከራይተው ሲጠቀሙ የነበረ ስለመሆኑ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ ጥያቄው በአግባቡ አልቀረበም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

በመጨረሻም 2ኛ ከሳሽ በቤቱ ላይ የውርስ ድርሻ ያላቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ 2ኛ ከሳሽና ተከሳሽ የሚስማሙ ከሆነ ቤቱ ተገምቶ አንዱ ለሌላው የግምቱን ግማሽ በመክፈል ቤቱን እንዲያስቀረው በዚህ መልኩ ስምምነት ካልተገኘ ቤቱ ተገምቶ በሐራጅ ተሸጦ የሽያጩን ውጤት ገንዘብ እኩል እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሳሾች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 08 ክልል የሚገኘውና ቁጥር 836 የሆነው ቤት የ1ኛ አመልካችና የሚች አቶ ኢላላ ኢብሳ የጋራ ሀብት ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

ሚች አቶ ኢላላ ኢብሳና 1ኛ አመልካች የተጋቡት ታህሳስ 18 ቀን 1962 ዓ.ም ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ደግሞ ሁለቱ ከመጋባታቸው በፊት በ1957 ዓ.ም በሚች አቶ ኢላላ ኢብሳ የተሠራ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና 1ኛ አመልካች በጋብቻ ተሳስረው እያለ በካርታ ቁጥር 31619 በአቶ አክሊሉ አጥላባቸው ስም የተመዘገበውን ቤት ገዝተው አከራይተው ሲጠቀሙ ቆይተው የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ሀብት የሚያደርገው አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲታወጅ ይህንኑ በጋብቻ ጊዜ የገዙትን ቤት በትርፍነት ለመንግስት አስረክበዋል፡፡ በሌላ በኩልም ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በባንክ ብድር ተሠርቶ የነበረ ስለሆነ ብድሩ በጋብቻ ጊዜ ተከፍሎ የተጠናቀቀ ከመሆኑም በላይ ባልና ሚስቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 11/1/ መሠረት እንደ አንድ ቤተሰብ መቆጠር እንዳለባቸው ሕጉ ስለሚያስገድድ ምርጫቸው መሆኑን አሳውቀው መንግስት በትርፍነት እንዳይወርሰው በማድረግ የጋራ ሀብት አድርገውታል በማለት ነው፡፡

ተጠሪም በበኩላቸው በካርታ ቁጥር 31619 የተመዘገበውን ቤት 1ኛ አመልካችና ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ ስለመግዛታቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካለማቅረባቸውም በላይ ቤቱን ከአቶ አክሊሉ አጥላባቸው ላይ ታህሳስ 16 ቀን 1965 ዓ.ም በተደረገ ውል የገዙት ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና አቶ ለማ ኢብሳ ናቸው፡፡ ከአቶ አክሊሉ አጥላባቸው ላይ የተገዛው ቤት በአንድ በኩል የ1ኛ አመልካችና የአቶ ኢላላ ኢብሳ በሌላ በኩል የአቶ ለማ ኢብሳ ንብረት የነበረ ሲሆን ይህን ቤት በትርፍነት ለመንግስት አስረክበዋል ቢባል እንኳ በሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ ስም የተመዘገበውንና ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ግን የጋራ ንብረት ስለመደረጉ በአመልካቾች ማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በካርታ ቁጥር 31619 የተመዘገበው ቤት ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና 1ኛ አመልካች በጋብቻ ተሳስረው በነበረ ጊዜ የተገዛ ስለመሆኑ ተጠሪ አምነው ነገር ግን የተገዛው 1ኛ አመልካች ከሟች ባለቤታቸው ጋር በመሆን ሳይሆን ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና አቶ ለማ ኢብሳ የገዙት ነው በማለት ክርክር ቢያቀርቡም የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ሀብት

ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ይህንኑ ቤት ለመንግስት በትርፍነት ያስረከቡት 1ኛ አመልካችና ሟች ባለቤታቸው እንደነበሩ በአስረጂነት የቀረበው የመረካከቢያ ቅጽ የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ ቤቱን በትርፍነት ያስረከቡት ሟች ብቻ ናቸው ቢባል እንኳን ይህ ሁኔታ የአቶ ለማ ኢብሳን የጋራ ባለሀብትነት ሊያረጋግጥ የማይችል በመሆኑ ይህ ችሎት በካርታ ቁጥር 31619 የተመዘገበው የ1ኛ አመልካችና የሟች ባለቤታቸው የነበረ መሆኑን ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

በሌላ በኩልም አንድ ሰው ወይንም አንድ ቤተሰብ ከአንድ መኖሪያ ቤት በላይ በባለቤትነት መያዝ እንደማይችል በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 11/1/ ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህ አዋጅ በወጣበት ጊዜ 1ኛ አመልካችና ሟች ባለቤታቸው አቶ ኢላላ ኢብሳ በጋብቻ ተሳስረው ይኖሩ የነበረ እንደመሆኑ መጠን ከአዋጁ አኳያ እንደ አንድ ቤተሰብ መቆጠራቸው ስለማይቀር በጋብቻ ጊዜ ካፈሩት ቤትና ከጋብቻ በፊት ከተሠራውና የሟች የግል ንብረት ከነበረው ቤት መካከል አንዱን መርጠው በትርፍነት ለመንግሥት ማስረከብ ግድ ስለሚሆን በዚሁ መሠረት በጋብቻ ጊዜ ያፈሩትን ቤት መርጠው ማስረከባቸው ሌላውን በሟች ስም ተመዝግቦ የሚገኘውንና ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት የጋራ ማድረጋቸውን እንደሚያስገነዝብ መረዳት አያዳግትም፡፡

በእርግጥ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍርዱ ላይ እንዳሰፈረው ከተጋቢዎች መሀል አንዱ የግሉ የሆነውን ቤት የጋብቻው የጋራ ንብረት ማድረግ ቢፈልግ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የቤተሰብ ሕግ መሠረት የዚህ ዓይነት ስምምነት ወይንም የጋብቻ ውል ሊኖር እንደሚገባ መደንገጉን መገንዘብ ቢቻልም 1ኛ አመልካችም ሟች ባለቤታቸው በጋብቻ ጊዜ ያፈሩትን ቤት በትርፍነት ለመንግሥት ‹ 229 › እስከተረጋገጠ ድረስ የሟች የግል ንብረት የነበረውንና ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ከአዋጁ መንፈስ አኳያ ያለምንም ሌላ ተጨማሪ ስምምነት ይህ ሁኔታ በእራሱ ቤቱን የጋራ ማድረጋቸውን ስለሚያስገነዝብ የሥር ፍ/ቤቶች ለክሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት የሆነው ይሄው ቤት የ1ኛ አመልካችና የሚች ባለቤታቸው አይደለም በማለት የሰጡት ውሣኔ ከአዋጁ ጋር ያልተጣጣመና የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41151 በታህሳስ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 09 ክልል ቁጥር 836 የሆነው ቤት የ1ኛ አመልካችና የሚች ባለቤታቸው አቶ ኢላላ ኢብሳ የጋራ ንብረት አይደለም ማለቱ እደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23027 በየካቲት 9 ቀን 1999 ዓ.ም የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 09 ክልል የሚገኘው የቤት ቁጥር 836 የሆነው ቤት የ1ኛ አመልካችና የሚች ባለቤታቸው አቶ ኢላላ ኢብሳ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ከላይ የተጠቀሰውና የ1ኛ አመልካችና የሚች አቶ ኢላላ ኢብሳ ቤት ተገምቶ በ1ኛ አመልካችና የሚች ወራሾች በሆኑት 2ኛ አመልካችና በተጠሪ መካከል ስምምነት ከተገኘ አንዱ ለሌላው የግምቱን ግማሽ በመክፈል ቤቱን እንዲያስቀረው ተወስኗል፡፡ በዚህ መልኩ መስማማት ካልቻሉ ቤቱ ተገምቶ በሐራጅ እንዲሸጥና የሽያጩን ገንዘብ ግማሹን 1ኛ አመልካች እንዲወስዱ ግማሹን ደግሞ 2ኛ አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

የሰበር መ.ቁ. 29402

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሐዳስ ታረቀ ቀረበች

ተጠሪ፡- የ፱አለቃ አስመላሽ ኃይለሥላሴ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሣውን የንብረት ክፍፍል የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በማህበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን በዚህ ወቅት በተደረገው ክርክር ባልና ሚስቱ በጋራ ያፈሩት ቤት እንዳለ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት ነው በማለት ፍ/ቤቱ በአንድ በኩል የወሰነ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ቤቱ የተሠራበት ቦታ የተጠሪ የግል ሀብቱ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ቦታው ለክፍፍል አይቀርብም፤ የተጠሪ የግሉ ሆኖ ይኑር በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበላቸው የበላይ ፍ/ቤቶችም ውሣኔው ስህተት የለበትም ብለዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ አመልካች መጋቢት 7 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ቤቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ከተባለ ቦታው ግን የተጠሪ የግል ንብረት ይሁን ተብሎ የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከቀረበው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ.47/67 ከታወጀመበት ጊዜ ጀምሮ እና በአሁኑም ጊዜ የከተማ ቦታ በግለሰቦች በርስትነት የሚያዝ አይደለም፡፡ የቦታው (መሬቱ) ባለቤት መንግሥት በመሆኑ ግለሰቦች በቦታው ላይ የመጠቀም መብት ነው የሚኖራቸው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ይህን ቦታ ወይም መሬት የእዚህኛው ወይም የዚያኛው የግል ንብረት ነው ብሎ መወሰን የማይቻል እንደሆነ ነው፡፡ በእርግጥ በቦታው ላይ የተሠራው ቤት የአንዱ ወይም የሌላው የግል ንብረት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቤት የሚሠራው በመሬት ላይ እንደመሆኑ ቤትን ካረፈበት መሬት (ቦታ) ለይቶ (ነጥሎ) ማየት አይቻልም፡፡ በአንድ በተወሰነው መሬት (ቦታ) ላይ ቤት የሠሩ ሰዎችም በቦታው ላይ የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል ወይም እንዳላቸው ይገመታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ እንደምንመለከተው አመልካች እና ተጠሪ ንብረትነቱ የመንግሥት በሆነው ቦታ (መሬት) ላይ የጋራ ቤት ሠርተው ሲኖሩ ቆይተዋል፡፡ በዚህ መሠረትም ቤቱ እኩል የጋራቸው ነው እስከተባለ ድረስ በቦታው (ቤቱ ባረፈበት መሬት) ላይ ባላቸው የመጠቀም መብት ልዩነት መፍጠር አይቻልም፡፡ ከፍ ሲል እንዳመለከትነውም ቤቱ ካረፈበት መሬት (ቦታ) ተነጥሎ የሚታይ ባለመሆኑ ወይም ከመሬቱ ውጪ ሊታይ ስለማይችል አመልካች ቤቱ ካረፈበት መሬት በመለስ ባለው ብቻ ነው የጋራ ባለሃብት የምትሆነው ብሎ መደምደም ትክክል አይደለም፤ ትርጉምም አየኖረውም፡፡ በሌላ አነጋገር በዚህ ድምዳሜ መሠረት አመልካች በቤቱ ላይ የእኩል መብት አላት ተብሎ ተወስኖአል ለማለት አይቻልም፡፡ ከዚህ የተነሣም አመልካች የጋራ መብት ያላት በቦታው (በመሬቱ) ላይ ባረፈው ሕንፃ (ቤት) ላይ ብቻ ነው በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በማህበራዊ ፍ/ቤት፣በመቀጠልም በወረዳ ፍ/ቤት እና በመጨረሻም በትግራይ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 18601 የካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች ያለምንም ልዩነት ማለትም ቤቱ ባረፈበት መሬት ላይ ያለውን የመጠቀም መብት ጨምሮ የቤቱ እኩል ባለሀብት ናት ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀም ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 30959

ታህሣሥ 01 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካቾች፡- 1. ወሮ ተወዳጅ ገ/ሥላሴ - ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ሙሉ ገ/ሥላሴ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ዘለቀ ዘውዴ

2. አቶ አንዳላፍር ዘውዴ

ጠ/ወንድወሠን ተ/ማርያም ቀረበ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች የሟች ሌ/ኮ ገ/ስላሴ በሻህ ልጆች ለመሆናቸው እንዲረጋገጥላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ፍ/ቤቱ ተመልክቶ ልጅነታቸውን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካቾች የሟች ልጆች አለመሆናቸውን ተጠሪዎች ተቃውመው ወደ ክርክሩ ገብተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ አይቶ በአመልካቾች እና በሟች መካከል የልጅነት ሁኔታ መኖሩ ተረጋግጧል በማለት ቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ ተጠሪዎች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በአመልካቾችና በሟች መካከል የልጅነት ሁኔታ የለም ሲል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡ በዚሁ ውሣኔ ላይ አመልካቾች ለፌ/ጠቅላይ

ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኛቸው ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም አመልካቾች የሟች ልጆች አይደሉም መባሉ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ ላይ አመልካቾች የሟች ሌ/ኮ ገ/ስላሴ በሻህ ልጆች ለመሆናቸው የልጅነት ሁኔታ መኖሩ ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሠጣቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን ተረድተናል፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ አመልካቾች የሟች ልጆች አለመሆናቸውን ተቃውመው ተከራክረዋል፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 154 እና ተከታዮቹ ሥር ልጅነት የሚረጋገጥባቸው መንገዶች ተዘርዝረዋል፡፡ ልጅነት የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ፣ የልደት ምስክር ወረቀት ከሌለ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ የልጅነት ሁኔታ ከሌለ ደግሞ ተወላጅነትን በማስረዳት ማረጋገጥ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ከነዚህ ሁኔታዎች ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ልጅነት የሚታወቅበት ሁኔታ ነው፡፡ በቤተሰብ ሕጉ ቁጥር 156 አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው በማኅበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህ ሁኔታ መኖሩን ማስረዳት ከተቻለ ፍ/ቤቱ ልጁ ነው ሲል የሕግ ግምት እንደሚወስድና ይህንን ግምት ግን ልጅ ነው የተባለው ሰው ሊሆን እንደማይችል በማስረዳት ማፍረስ እንደሚችል የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 157 ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ስንመለከት ሟች አመልካቾችን እንደ ልጆቻቸው ያሳድጓቸው እንደነበር ትምህርት ቤትም አባት በመሆን እንዳስመዘገቧቸው፣ በመረዳጃ እድር ቅጽ ውስጥ ልጆች ብለው እንዳስመዘገቧቸው፣ በሠፈርም በት/ቤትም የሟች ልጆች ሆነው እንደሚታወቁ ተገንዝበናል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የልጅነት ሁኔታ የለም ያለው አመልካቾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጋብቻ ውስጥ ወይም ከጋብቻ ውጪ መወለዳቸው አልተገለፀም፣ ሚች አመልካቾች የሚች ልጆች እንዳልሆኑ ገልፀው የተውት ኑዛዜ አመልካቾች እንዲፀድቅ መጠየቃቸው ልጆች አለመሆናቸውን ያመኑ መሆኑን ያሣያል በማለት ነው፡፡ ነገር ግን የልጅነት ሁኔታን ለማረጋገጥ ልጁ በማኅበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት መሆኑን ከማረጋገጥ ባለፈ ልጁ በጋብቻ ውስጥ ወይም ከጋብቻ ውጪ የተወለደ ለመሆኑ ማስረዳት አስፈላጊ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሕጉ የማይጠይቀውን ተጨማሪ ሁኔታ አመልካቾች አላስረዱም በሚል የተሠጠው ውሣኔ አግባብነት የለውም፡፡

ሌላው ሚች በተውት ኑዛዜ ላይ አመልካቾች ልጆች አለመሆናቸውን መግለፃቸው በራሱ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማፍረስ የሚያበቃ አይደለም፡፡ የልጅነት ሁኔታ አለመኖሩን ለማስረዳት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 157/2/ መሠረት ልጅ የተባለው ሰው ልጅ ሊሆን እንደማይችል ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ኑዛዜውን አመልካቾቹ እንዲፀድቅ መጠየቃቸው አመልካቾች የሚች ልጆች አይደሉም ወደሚለው መደምደሚያ አያደርስም፡፡

በአጠቃላይ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠው ፍሬ ነገር አመልካቾች የልጅነት ሁኔታ ያላቸው መሆኑን እያሳየ ሕጉ የማይጠይቀውን ተጨማሪ ሁኔታ አመልካቾች አላስረዱም በማለት የልጅነት ሁኔታ የለም በሚል የተሠጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 4487 በሐምሌ 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 26992 በሚያዝያ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20534 በጥር 22 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 31430

ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች ፡- ወ/ሮ አዲስ አለም አከለ ቀርባለች፡፡

ተጠሪ ፡- የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ ተወካይ ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሳውን የንብረት /ገንዘብ/ ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው አመልካች እና ተጠሪ የንብረት ክፍፍል ያደረጉ ሲሆን፣ ከዚህ ክፍፍል በኋላ ሊስማሙ ያልቻሉት ተጠሪ በብሩንዲ በሰላም ማስከበር ተግባር ላይ ተሰማርቶ ለነበረበት ጊዜ በድጐማ መልክ ተከፍሎታል በተባለው ገንዘብ ክፍፍል ላይ ነው፡፡ አመልካች ይህ ገንዘብ የተገኘው ጋብቻው ከመፍረሱ በፊት /ፀንቶ በነበረበት ጊዜ/ እስከሆነ ድረስ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው በማለት ስትከራከር፤ ተጠሪ ደግሞ ገንዘቡ ከደመወዝ የተለየና በድጐማ መልክ የተሰጠኝ በመሆኑ የግሌ ነው፡፡ ከባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሚደመር አይደለም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የወረዳ ፍ/ቤት እና ይግባኙን የሰማው የከፍተኛ ፍ/ቤት ገንዘቡ የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት ነው በማለት የወሰኑ ሲሆን፣ ለመጨረሻ ጊዜ ይግባኙን የሰማው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ግን የተጠሪን ክርክር በመቀጠል ገንዘቡ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት የሚባል አይደለም፡፡ ለክፍፍል አይቀርብም በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሰኔ 21 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በድጐማ መልክ ተገኘ የተባለው ገንዘብ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የማይሆንበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪው ገንዘብ በድጐማ መልክ ለተጠሪ የተከፈለው ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ነጥብም ከዚህ ፍሬ ነገር የሚነሳ ሆኖ መወሰን ያለበት ደግሞ አግባብ ባለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት ነው፡፡ በዚህ ረገድ አግባብ ያለው የቤተሰብ ሕግ የአማራ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ. 79/95 አንቀጽ 73 እንደሆነ በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተመልክቶአል፡፡ ባልና ሚስት ተጋብተው አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ሠርተው፣ ጥረው፣ ግረው የሚያገኙዋቸው ንብረቶች የጋራ ሀብቶቻቸው እንደሆኑ በተጠቀሰው አንቀጽ 73/1/ እና /2/ በግልጽ ስለመመልከቱም በፍ/ቤቶቹ ውሣኔ ተገልጾአል፡፡ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ሕጉ እንዲህ አይልም የሚል ምክንያት አልሰጠም፡፡ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው ነጥብ ገንዘቡ ባልና ሚስቱ በመረዳዳትና በመተጋገዝ በጋራ ያፈሩት ነው ሊባል አይችልም የሚል ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ሕጉ ግልጽ ነው፡፡ ሕጉ ለጋራ ንብረት መሠረት ይሆን ዘንድ በዋነኛነት ያስቀመጠው በጋብቻው ጊዜ /ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ/ መገኘቱን ነው፡፡ ባልና ሚስቱ በጋብቻ ተሳስረው ባሉበት ጊዜ የሚገኘው ንብረት በሁለቱም የጋራ መተጋገዝ እንደተገኘ መቆጠር እንዳለበት ሕጉ ወስኗል፡፡ ባልና ሚስቱ በተለያየ ቦታ የመገኘታቸው ጉዳይ እግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ ባል በአንድ ቦታ፤ ሚስት ደግሞ በሌላ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ ቢኖሩ እንኳ ሕጉ የሚገምተው ሁለቱም ለትዳራቸው እኩል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብሎ ነው፡፡ በመሆኑም ንብረቱ በሕጉ ተቀባይነት ባለው አግባብ የአንዱ ተጋቢ ወገን የግል ሃብት መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ በጋብቻው ወቅት የተገኘው ንብረት ሁሉ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው የሚሆነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየውም ተጠሪ በድጐማ ተሰጠኝ የሚለው ገንዘብ የጋራ ሀብት የማይሆንበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ የተነሳም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 1046/98 ግንቦት 14 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ለተጠሪ በድጐማ መልክ ተከፈለ የተባለው ገንዘብ በባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሚካተት በመሆኑ አመልካች እና ተጠሪ እኩል ይካፈሉት ብለን ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይበለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31891

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካቾች፡- እነ አቶ አንለይ እንየው (7 ሰዎች) ጠበቃ ፍቅሩ ታደሰ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መሬም ጡሃ ጠበቃ ውቤ ጓዴ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ የሚች አቶ ይሃ ይብሬ ሚስትና አካለመጠን ያላደረሱ ሁለት ልጆች ሞግዚትና አስተዳዳሪ ናቸው በማለት ፍ/ቤቱ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የአሁን አመልካቾች እህት የነበሩት ወ/ሮ ጥሩዬ እንየው የተባሉት ቀርበው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት ባቀረቡት መቃወሚያ በሚች አቶ ይሃ ይብሬና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በእስልምና ኃይማኖት ሥርዓት መሠረት ፈርሷል፡፡ ተጠሪ ከሚች የወለዷቸውን ሁለት ልጆች ጥለው ወደ ውጭ አገር ከሄዱ ጊዜ ጀምሮ ልጆቹን በእናትነት አሳድገውም ሆነ ተንከባክበው አያውቁም፤ ልጆቹን ያሳደግኩት አመልካች ነኝ፡፡ ተጠሪ የሚች ሚስት ሳይሆኑ በሐሰተኛ ምስክር አማካይነት የተሰጣቸው የሚስትነት ማስረጃና በሚያሳድጓቸው ልጆች ስም የተሰጣቸው የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ማስረጃ ያለአግባብ ስለሆነ እንዲመልሱ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ለተጠሪ ደርሶ በበኩላቸው በሰጡት መልስ አመልካች በተጠሪና በሚች አቶ ይሃ ይብሬ መካከል ጋብቻ መኖሩን ሳይክዱ በመቃወሚያነት ያቀረቡት ምክንያት ተጠሪ ከኢትዮጵያ ውጭ ለ12 ዓመት ያህል ከኖሩ በኋላ አሁን የተመለሱት አቶ ይሃ ይብሬ ከሞቱ በኋላ ነው ከሚል

በስተቀር ከሚች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በሕግ አግባብ የፈረሰ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በሌላ በኩል ሚችና ተጠሪ በባልና ሚስትነት አብረው እየኖሩ 2 ልጆችን ወልደዋል፡፡ ተጠሪ ለወለዷቸው ልጆች ሞግዚት ልሁን ብለው መጠየቃቸውና ሞግዚትነታቸው በፍ/ቤት ማሳወቃቸው ጥፋተኛ አያደርጋቸውም፡፡ ስለዚህ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በተጠሪና በሚች መካከል የነበረው ጋብቻ ከ12 ዓመት በፊት ፈርሷል ቢሉም በፍ/ቤት ውሳኔ ስለመፍረሱ ያቀረቡት ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ለ12 ዓመት ተለያይተው መኖራቸው ብቻ በራሱ ጋብቻውን ሊያፈርሰው የማይችል በመሆኑ አቤቱታው በአግባቡ ያልቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል የሰጠው ውሳኔ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአመልካች ወራሾች በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሮ መወሰን ተገቢ መሆኑን በማመኑ በዚሁ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በተጠሪና በሚች አቶ ይሃ ይብሬ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ አልፈረሰም ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ አግባብነት አለውን? የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ጭብጥ አኳያም የሰበር አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረውም በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች በተጠሪና በሚች አቶ ይሃ ይብሬ መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሷል በማለት ያቀረቡትን ክርክር ፍ/ቤቱ ሳይቀበለው የቀረው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረዳት የሚቻለው በፍ/ቤት የተሰጠን ውሳኔ በማቅረብ እንጂ በምስክር ፍቺን ማስረዳት ስለማይቻል አመልካች ፍቺውን በምስክር ላስረዳ ያሉት በአግባቡ ባለመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

ሆኖም ግን ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14290 በሰጠው ውሳኔ በባልና ሚስት መካከል ያለ ጋብቻ በፍ/ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ ፈርሷል ባይባልም የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረጅም ጊዜ መኖር በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መሥርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በሕጋዊ መንገድ ተቋርጧል ሊባል ይችላል በማለት የሕግ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች የጋብቻ መፍረስ ከፍርድ ውሳኔ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሊረጋገጥ አይችልም በማለት የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከዚሁ አኳያም በዚህ ጉዳይ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ተጠሪና ሟች አቶ ይሃ ይብሬ ለ12 ዓመታት ተለያይተው እንደኖሩ በዚህ ጊዜም ተጠሪ በውጭ አገር በመኖር ላይ እንዳሉ ሌላ ባል አግብተው አንደነበር አመልካች ተከራክረው ይህንኑ ክርክራቸውን በምስክር ለማስረዳት መጠየቃቸውን ይህ ችሎት ከመገንዘቡም በላይ ተጠሪ በውጭ አገር በነበሩ ጊዜም ሟች አቶ ይሃ ይብሬና አመልካች ጋብቻ የፈጸሙ ስለመሆናቸውም ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በተጠሪና በሟች መካከል የነበረው ጋብቻ ይህ ሰበር ችሎት አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳይ ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ተቋርጧል ወይንስ አልተቋረጠም የሚለውን ለመወሰን ከፍ ብሎ በአመልካች የተጠቀሰው ፍሬ ነገር ማለትም ተጠሪና ሟች አቶ ይሃ ይብሬ ለ12 ዓመታት ተለያይተው ስለመኖራቸው በዚህም ጊዜ ውስጥ የባልና የሚስት ዓይነት ግንኙነት ያልነበራቸው ስለመሆኑና ተጠሪም በውጭ አገር በነበሩ ጊዜ ሌላ ባል ስለማግባታቸው በአጠቃላይ በዚህ ጊዜ ውስጥ ምንም ዓይነት የባልና ሚስት ግንኙነት ያልነበራቸው ስለመሆኑ ሊያስረዱ የሚችሉት አመልካች የቆጠሯቸው ምስክሮች ተሰምተው ለጉዳዩ እልባት ሊሰጠው ይገባ እንደነበር ይህ ችሎት ለመረዳት ችሏል፡፡

ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ የቆጠሯቸው ምስክሮች ሳይሰሙ ጋብቻው በፍርድ ውሳኔ ስላልፈረሰ የጸና ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08924 መጋቢት 8 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38179 ሚያዝያ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ በፍርዱ ላይ በተመለከተው መሰረት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 31946

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘውዲቱ ጌታቸው ቀርባለች

ተጠሪ፡- ተመስገን ደሣለኝ ቀርቧል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጋብቻ ውልን የሚመለከት ነው፡፡

የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የቀጠለውን የንብረት ክፍፍል በተመለከተ አመልካች ጥያቄያቸውን ለጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍ/ቤት አቅርበዋል ተጠሪም በመሃከላችን የጋብቻ ውል አለ በዚህም መሠረት አመልካችን ያገባኋት በአመት 120.00 /መቶ ሃያ/ ብር ልከፍላት ልብስ ከዛው ከደሞዟ ሊታሰብ የሕክምና ወጪ ልሸፍን እንጂ በእኩል ባለመብት እንድትሆን አልተስማማሁም በማለት አመልካች ንብረት ለመካፈል ያቀረቡትን ጥያቄ ተቃውመዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ወረዳ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ የጋብቻ ውሉ ሕጋዊ አይደለም በማለት አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ተቀብሎ ንብረቶቹን የግራ ቀኙን የጋራ ስለሆኑ እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በውሣኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምዕ/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ የወረዳ ፍ/ቤቱ ውሣኔ ስህተት የለውም በማለት የይግባኝ ቅሬታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ በመቀጠል ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሁለተኛ ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ግራ ቀኙ የንብረት ግንኙነታቸውን በተመለከተ ተጠሪ ለአመልካች በወር ከሚያገኘው ገቢ ውስጥ ለዓመት ብር 120.00 (መቶ ሃያ) ሊከፍላት ከዚህ ውጪ ሌላ ንብረት ግንኙነት እንደማይኖር መስማማታቸው ሕጉን አይቃረንም በማለት ተጠሪ አመልካች

ሳትገባ የሠራውን ሆነ ከገባች ወዲህ ታድሷል የተባለውን ቤት እንድትካፈል መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ አመልካች ቤቱን ልትካፈል አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ ባደረጉት የጋብቻ ውል ላይ ተጠሪ ለአመልካች በዓመት ብር 120.00 (መቶ ሃያ) ሊከፍላትና ከዚህ ውጪ ሌላ የንብረት ግንኙነት እንደማይኖር መስማማታቸው ሕግን አይቃረንም መባሉን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በማድረጉ ተጠሪ ቀርበው መልሣቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው ግራ ቀኙ ባልና ሚስት መሆናቸው ያልተካደ ጉዳይ ነው፡፡ አከራካሪው ነጥብ የንብረት ክፍፍል ነው፡፡ አመልካች በጋብቻ ጊዜ የተገኘ ንብረት የግል እስካልተባለ የጋራ ነው ሲሉ የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ተጋቢዎቹ የንብረት ግንኙነታቸውን በተመለከተ ሊስማሙ ስለሚችሉ በዚሁ መሠረት የተስማሙና የጋብቻ ውሉም ሕግን የሚቃረን ባለመሆኑ የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ስህተት የለውም ብለዋል፡፡

የአ/ብ/ክ/መ የቤተሰብ ሕግ ልክ እንደ የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ተጋቢዎቹ የንብረት ግንኙነታቸውን አስመልክቶ ሊስማሙ እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የንብረት ግንኙነታቸውን በመሰላቸው መንገድ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ስምምነቱን በሚወስኑበት ጊዜ መሠረታዊ የእኩልነት መብትን በሚጥስ መልክ ሊፈፀም አይገባውም፡፡ በሕገ- መንግሥቱ አንቀፅ 34(1) ሴቶች በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ግዜ እኩል መብት እንዳላቸው ያመለከተ ሲሆን አንቀጽ 35/2/ም ቢሆን ሴቶች በጋብቻ ከወንዶች ጋራ እኩል መብት እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም በጋብቻ ዘመን በተፈራ ንብረት ላይ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እኩል መብት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ ባደረጉት የጋብቻ ውል ተጠሪ ለአመልካች በዓመት ብር 120.00

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚከፍላትና ከዚህ ውጭ አመልካች በጋራ ንብረታቸው ላይ ምንም ዓይነት መብት እንዳይኖራት ያደረጉት ስምምነት ከላይ የተጠቀሰውን የሕገመንግሥቱን የእኩልነት መብት ድንጋጌን የሚፃረር ነው።ማንኛውም ሕግ ወይንም ልማዳዊ አሠራር ከሕገመንግሥቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት እንደሌለው በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ላይ ተመልክቷል።

ከዚህም ሌላ አንድ የውል ግዴታ በሕግ አግባብነት ባልተቋቋመ ጊዜ በዚህ ውል መሠረት እንዲፈጽም ጥያቄ የቀረበለት ወገን ውሉ የማይረጋ ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ይህንን ውል አልፈጽምም ማለት እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1809 የተመለከተ ሲሆን አመልካችም ከተጠሪ ጋር የተደረገው ውል ሕግን የሚፃረር ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የተከራከሩ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ስምምነት መሠረት ሊገደዱ የማይገባ ሆኖ ሣለ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመሻር የአመልካችን የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11110 ሐምሌ 3 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ከላይ እንደተጠቀሰው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል።
2. አመልካችና ተጠሪ ንብረት ሊካፈሉ ይገባል ተብሎ በጃቢ ጣህናን ወረዳ ፍ/ቤት በ14.4.99 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የምዕራብ ጎጃም ዞን ከ/ፍ/ቤት ይግባኙ አያስቀርብም በማለት በጥር 9 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል።
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ።
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 32130

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

መድነን ኪሮስ

አሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- እነ እማዋይሽ ካሣ /6 ሰዎች/ ቀርበዋል።

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስቴር አህመድ - ጠበቃው ቀርቧል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ አባትነት እንዲታወቅ የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው።

ተጠሪ በሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ እናታቸው በአመልካቾች ቤት በሠራተኛነት ተቀጥረው ሲሠሩ ከሟች አህመድ ይማም ጋር ከጋብቻ ውጪ በነበራቸው ግንኙነት የተወለዱ መሆኑና ሟችም ልጅነታቸውን ተቀብለው ሲረዱዋቸውና ሲንከባከቧቸው የነበረ በመሆኑ አባትነታቸው እንዲታወቅላቸው አመልክተዋል። አመልካቾችም ሟች ከእነርሱ በቀር ሌላ ልጅ የሌላቸው መሆኑን ተከራክረዋል። ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙራ ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ያቀረቡት ማስረጃ ልጅነታቸውን ለማወቅ የሚበቃ አይደለም በማለት ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርጓል። ተጠሪ በውሣኔው ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኙን ያየው ፍ/ቤት የቀረበው ማስረጃ ሟች ተጠሪን በመንከባከብና በማስተማሩ ወይም በማሣደጉ ላይ እንደ አባት የተሣተፈ ለመሆኑ የሚያረጋግጥና ተጠሪ በሟች ስም ተመዝግበው በስሙ ትጠራ እንደነበር ተረጋግጧል በማለት ተጠሪ ከሟች አህመድ ይማም የተወለደች ልጅ ናት በማለት ወስኗል።

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው። የአመልካቾች ቅሬታ በአጭሩ በአ/ብ/ክመ/ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 154/ሠ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት አንድን ሰው አባት ብሎ ለመወሰን ልጁን ለማስተማርና ለማሣደግ የሚያስፈልገውን እንክብካቤ ማድረጉና ይህ እንክብካቤ እና እርዳታ የተደረገው ተንከባካቢው ከወላጅነት ስሜት በመነጫ አኳኋን አባት ነኝ ከሚል እምነት የተነሣ መሆኑ መረጋገጥ ያስፈልገዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ሚች በርህራሄ እና ከሃይማኖታዊ ሥርዓት አፈፃፀም የተነሳ ተጠሪን ከመርዳት ውጪ ልጇ ናት ብሎ የረዳበት ጊዜ እንደሌለ ተረጋግጦ እያለ አባት ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ትርጉም ተጠሪ የሚች አህመድ ይማም ልጅ መሆኗ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት መረጋገጡን ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በማለቱ ተጠሪ ቀርበው መልስ ሠጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም ሚች ተጠሪን እየተንከባከቡ ያሣደጉት በበጎ አድራጎት መንፈስ ሳይሆን የወለዷት ልጅ መሆንዋን በመግለጽ እንደሆነና ገንዘብ ይልኩላት የነበረውም በአባትነት መንፈስ መሆኑ ስለተረጋገጠ ውሣኔው ስህተት የለውም ብለዋል፡፡

ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የተጠሪ ጥያቄ ሚች አቶ አህመድ ይማም አባታቸው መሆናቸው እንዲረጋገጥ የቀረበ ነው፡፡ የአ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሚች የተጠሪ አባት ናቸው የሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 154/ሐ/ እና 154/ሠ/ መሠረት ሚች ተጠሪን በማሣደግ እንደአባት ተሣትፈዋል በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው አንቀጽ 154/ሠ/ አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ በማስተማር ወይም በማሣደጉ ላይ እንደ አባት በመሆን የተሣተፈ እንደሆነ አባት ተብሎ በፍርድ ሊወሰን ይችላል፡፡ ይህ የክልሉ ድንጋጌ ከፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ምንም ልዩነት የሌለው መሆኑንም ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ አባት ነው ለመባል ሊረጋገጥ የሚገባው ፍሬ ነገር ምንድነው የሚለውን ማየቱ ጠቃሚ ነው? ድንጌጋው በግልጽ እንደሚያመለክተው አንድን ሰው አባት ነው

ለማሠኘት ይኸው ሰው ልጁን ሲንከባከብ ሲያስተምር ወይም በማሣደጉ ሂደት ሲሣተፍ የነበረ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ነገር ግን እንክብካቤውንና እርዳታውን ማድረጉ በራሱ ሰውየውን አባት አያሠኘውም፡፡ ምክንያቱም ይህ እንክብካቤና እርዳታ ከርህራሔ እና ከሰብአዊነት ስሜት በመነጨም ሊደረግ የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ ግለሰቡ አባት ነው ወደሚለው መደምደሚያ ለመድረስ ይህ እንክብካቤና እርዳታ አባት ነኝ ከሚል እምነትና ስሜት የመነጨና እንደ አባት በመሆን የተደረገ መሆኑም ጭምር ሊረጋገጥ ይገባዋል፡፡ ከዚህም በላይ እንክብካቤውን ሲያደረግ የነበረው ሰው ከእናትየው ጋር ልጅ ለመውለድ የሚያስችል ግንኙነት የነበራቸው መሆኑም ሊረጋገጥ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም ከቀረበው ማስረጃ በእናትየውና አባት ነህ በሚባለው ሰው መሃከል ልጁን ለመሳድ የሚያስችል ግንኙነት ሊኖር ይችላል የሚል እምነት የሚያሳድር ቅርበት መኖሩ እንዲሁም አባት ነህ የተባለው ሰው እርዳታውንና እንክብካቤውን ያደረገው እንደ አባት በመሆን መሆኑ ካልተረጋገጠ እርዳታ በማድረጉ ብቻ አባት ነው ወደሚለው መደምደሚያ መሄዱ የሕጉን አላማ የተከተለ አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ስንመለከት የተጠሪ እናት ከሚች እናትና አባት ቤት ተቀጥራ ስትሠራ ከሚች መውለዷን ሚች የነገራቸው መሆኑንና ሚች እንዳንዴ ገንዘብና ልብስ ይረዳት የነበረ መሆኑን በሚኒስትሪና በማትሪክ ካርዶች በሚች ስም ትጠራ የነበረ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህም ፍሬ ነገር ሚች ተጠሪ ልጇ ናት ብሎ ነግሮናል እንዲሁም አንዳንዴ ገንዘብ ይሰጣት ነበር ልብስም ያሠፋላት ነበር ከማለት ውጪ ይህንኑ እርዳታ አባት ነኝ በሚል እምነትና ስሜት ይፈጽሙ እንደነበር በሚችና በተጠሪ እናት መሀከል ተጠሪ ልትወለድ የሚያስችል ቅርበት የነበረው ግንኙነት መኖሩን አያረጋግጥም፡፡ በመሆኑም ሚች ተጠሪን አንዳንዴ መርዳታቸው ብቻ አባት ናቸው፡፡ ወደሚለው መደምደሚያ አያደርስም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ በትምህርት ቤት በሚች ስም መጠራታቸው ወይም መመዝገባቸው ብቻ ሚች የተጠሪ አባት ናቸው አያሰኝም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ የአ/ብ/ክ/መ/ ሚች አህመድ ይማም የተጠሪ አባት ናቸው በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1050/98 ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07151 በሐምሌ 26 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 33126

ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ የዝና ተስፋሁን ቀረበች

ተጠሪ፡- መምህር ጥሩአየሁ እውነቱ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጋብቻ አለ ወይስ የለም በሚል ጭብጥ ላይ ተመሥርቶ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ስትሆን በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተችው ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሳስረን ለ25 ዓመት ኖረናል፣ በዚህ ጊዜም አምስት ልጆች ወልደናል፣ ተከሣሽ ግን በመካከላችን የተመሠረተውን የጋብቻ ግንኙነት እንደሌለ በመቁጠር ግዴታውን ሊወጣ ስላልቻል ፍ/ቤቱ ተከሣሽን አስቀርቦ በመጠየቅ ተገቢው ውሣኔ ይሰጠኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በአንድ በኩል ከአመልካች ጋር በአንድ ቤት ለ25 ዓመት ያክል አብረው መኖራቸው እና በዚህ ጊዜ ውስጥ አምስት ልጆች መውለዳቸውን ሲያምን፤ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በሠራተኛነት የቀጠራት እንጂ ሚስቱ እንዳልሆነች፣ በመሃከላቸው የተመሠረተ ጋብቻም እንደሌለ በመግለጽ ክዶ ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በኋላም ፍ/ቤቱ በሁለቱም በኩል የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተመሠረተ ጋብቻ የለም፡፡ ባልና ሚስት አይደሉም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበላቸው የበላይ ፍ/ቤቶችም ውሣኔውን አጽንተዋል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው።

እኛም አመልካች መስከረም 12 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራት ግንኙነት የባልና ሚስት ሁኔታን አያሣይም የመባሉንና አመልካች በ2ኛ ደረጃ ያነሣችው ከጋብቻ ውጪ አብሮ የመኖርን መነሻ ያደረገ ክርክርም እንደዚሁ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ነው። በዚህ መሠረትም እነዚህን ነጥቦች ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና የተሰጡትን ውሣኔዎች በዝርዝር ተመልክተናል። አመልካች በወረዳ ፍ/ቤት ክስ የመሠረተችው የተጠሪ ሚስት ነኝ፤ በመሃከላችን የጋብቻ ግንኙነት አለ በማለት ቢሆንም፤ ሚስት አይደለሽም በማለት ፍ/ቤቱ ከወሰነ በኋላ ከጋብቻ ውጪ አብሮ መኖርን መሠረት ያደረገ የንብረት ክፍፍል ውሣኔ እንዲሰጥላት ጭምር በመከራከር ዋነኛ ጉዳዩን በይግባኝ የሰሙት ፍ/ቤቶችም በዚህ ነጥብ ጭምር ውሣኔ መስጠታቸውን ለመገንዘብ ችለናል። ሌላው ከተሰጡት ውሣኔዎች መገንዘብ የቻልነው ፍ/ቤቶቹ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የጋብቻ ግንኙነት የለም ለማለት የቻሉት ክርክሩን ከቀረቡላቸው ማስረጃዎች ጋር አገናዝበው ከመረመሩና ካመዛዘኑ በኋላ እንደሆነ ነው።

በመሆኑም ፍ/ቤቶቹ በማስረጃ አመዛዘን ረገድ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት የምንችልበት ምክንያት ስለሌለ ጋብቻን በሚመለከት አመልካች ያቀረበችውን አቤቱታ አልተቀበልንም።

ጋብቻ አለ ወይስ የለም የሚለውን ነጥብ በተመለከተ የቀረበውን ክርክር በዚህ ሁኔታ ካለፍን ቀጥለን የምንመለከተው ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር ነው። ከላይ እንደተገለፀው አመልካች እና ተጠሪ በአንድ ቤት ለ25 (ሃያ አምስት)

ዓመት ያክል አብረው ከመኖራቸውም በላይ፤ በዚህ ጊዜም አምስት ልጆችን ወልደዋል። ተጠሪም ይህን በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠውን ሃቅ የሚቀበል ቢሆንም፤ በሌላ በኩል ግን ከአሠሪና ሠራተኛ ያለፈ ግንኙነት የለንም በማለት ተከራክሮአል። ይህም ሆኖ ግን እሱ እንደሚለው በሠራተኛነትም ደመወዝ እየከፈላት ስለመቆየቱ አላስረዳም፤ በዚህ መልክም አልተከራከረም። ክርክሩን በይግባኝ ሰምቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ሲሆን፣ አመልካች የተጠሪ የቤት ሠራተኛ ናት ብሎ አልደመደመም። ውሣኔውን የሰጠው የአመልካች ምስክሮች ጋብቻ ስለመፈፀሙ አላስረዱም፤ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት ሆነው አብረው ስለመኖራቸውም በማስረጃ አልተረጋገጠም ማለት እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል።

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ በሰማው በደብረማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በአመልካች ተቆጥረው ከተሰሙት ምስክሮች አንዱ የአመልካች እና የተጠሪ ትልቁ ልጅ እንደሆነና እሱም በሰጠው ምስክርነት አባትና እናቱ ባልና ሚስት ናቸው ብሎ እንደሚያምን ማስረዳቱን ከወረዳው ፍ/ቤት ውሣኔ ተመልክተናል። እንደምንመለከተው ተጠሪ አመልካችን ከሃያ አምስት ዓመት በፊት በቤት ሠራተኛነት ቀጥሬያታለሁ ቢልም፤ ለሃያ አምስት ዓመት ያክል አብረው የኖሩት ግን እሱ ከሚለው በእጅጉ በተለየ ሁኔታ ነው። አብረው ለብዙ ዓመታት መኖራቸው ብቻ ሣይሆን አምስት ልጆች ወልደው በጋራ ሲያሣድጉም የመቆየታቸው ሁኔታ ሲታይ በጋብቻ ተሣስረው ከሚኖሩት ወንድና ሴት ተለይተው የሚታዩ አይመስሉም። ትልቁ ልጃቸው እንደባልና ሚስት አድርጎ የሚያያቸው መሆኑን ለፍ/ቤቱ ያስረዳውም ከዚህ በመነሣት እንደሆነ መገመቱ የሚያስቸግር አይደለም። በበኩላችን እንደምናየው የአመልካች እና የተጠሪ አብሮ የመኖር ሁኔታ በፌዴራሉ መንግሥት የቤተሰብ ሕግም ሆነ በአማራ ብ/ክ/መ/ የቤተሰብ ሕግ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን በተመለከተ የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚገባ የሚያሟላ ነው። ሲጠቃለል በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የጋብቻ ግንኙነት አለ ለማለት ባይቻለም፤ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት በመሆን አብረው መኖራቸው ግን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ በመሆኑም ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የሚያሣይ ሁኔታ በሚል በስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ትክክል አይደለም፡፡ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 09277 ሐምሌ 9 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች እና ተጠሪ ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደባልና ሚስት ሆነው አብረው ኖረዋል ብለን ወስነናል፡፡ ይህ በንብረት ግንኙነታቸው በኩል የሚኖረው ውጤት በክልሉ ሕግ ጉዳዩ በተጀመረበት ወረዳ ፍ/ቤት ቀጥሎ ይታይ ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 33411

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድነን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አለቃ ኪሮስ ገብሩ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የአፈፃፃም ክርክር ሲሆን፣ በዋናው ጉዳይ ግራ ቀኙ ጋብቻቸውን በስምምነት ለማፍረስ ተዋውለው ስምምነታቸውን በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. በት/ብ/ክ/መ/ ሕንጣሎ ዋጅራት ወረዳ ጣቢያ ደጀን ማ/ፍ/ቤት በውሣኔ እንዲያፀድቀው አድርገዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች ተጠሪው በስምምነቱ መሠረት የጋራ ንብረት ክፍፍሉን ሊፈጽሙ ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል በሚያዝያ 2 ቀን 1999 ዓ.ም. በት/ብ/ክ/መ/ ኢንጣሎ ወረዳ ጣቢያ ደጀን ማ/ፍ/ቤት የጋራ ያሏቸውን ንብረቶች በመዘርዘር ያካፍሉኝ ሲሉ በተጠሪው ላይ የአፈፃፀም ክስ መሥርተዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ /የሥር የአፈፃፀም ተከሣሽ/ በሚያዝያ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ የአሁን አመልካች በክሣቸው የዘረዘሯቸውን የጋራ ንብረቶች ለማካፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልፀው በክሱ ከተዘረዘሩት ንብረቶች መካከል የወፍጮ ድርጅት ያካፍለኝ ለተባለው ፀጋዬ ገብሩ ከተባሉት ግለሰብ በ10,000 ብር የገዛነው ቢሆንም ስመ ንብረቱ ያልተዛወረ የግር ውሉም ያልፀድቀ በመሆኑ ላካፍላት አልችልም ስለዚህ ወይ ባለቤትነት ስም እስኪዛወር ትጠብቅ ወይ የግር ገንዘቡን ግማሽ ብር 5000 (አምስት ሺህ) ትውሰድ ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአፈፃፀም ክርክሩ የቀረበለት የጣብያ ደጀን ማ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ጉዳት መርምሮ በግንቦት 11 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ፣ ቀደም ሲል ቀርቦ በፀደቀው የፍቺ ስምምነት መሠረት በጣብያ ደጀን ዓዲኾሎ የሚገኘው የወፍጮ ድርጅት የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት መሆኑ መግለጽ የሠፈረ እና ይህንኑ ድርጅት እኩል ለመካፈል የተስማሙ በመሆኑ ግራ ቀኙ የወፍጮ ድርጅቱን ከነ ሙሉ መሣሪያዎቹ እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

የጣብያ ደጀን ማ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኙት የአሁን ተጠሪ ቅሬታቸውን ለህንጣሎ ወረዳ ፍ/ቤት በይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤት ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ በመቀጠል ተጠሪ ቅሬታቸውን ለት/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡

የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የተጠሪን አቤቱታ ተቀብሎ አመልካችን በማስቀረብ ግራ ቀኙን ያከራከረ ሲሆን በነሐሴ 4 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የክርክሩ መነሻ የሆነው መፍጮ በአሁን ተጠሪ ወንድም በአቶ ፀጋዬ ገብሩ ስም እንደሚታወቅ የአሁን አመልካች አልካዱም፡፡ ንብረትነቱ በአሁን ተጠሪ ስም እንደተላለፈም የቀረበ ማስረጃ የለም፣ በመሆኑም ለዚህ ወፍጮ ግዢ ገንዘብ እንደተከፈለ እንጂ ውል ተፈጽሞ ወደ ስማቸው እንደተላለፈ እስካልተደረጋጠ የጋራ ተብሎ ወደ ተከራካሪዎቹ የትዳር ንብረት ክፍፍል ሊገባ አይችልም በሚል ግራ ቀኙ ለወፍጮ ግዢ የተከፈለውን ብር 10,000 የጋራ በመሆኑ ገንዘቡን እኩል ይካፈሉት ሲል የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

ይህ መዝገብ ለዚህ ችሎት የቀረበውም የት/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪው ለአመልካች ወፍጮ የተገዛበትን ዋጋ ብር 10,000 ያካፈሏቸው ሲል የሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አመልካች በጥቅምት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ መሠረት ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ሲጠቃለል በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. ባደረግነውና በፍ/ቤት በፀደቀው የፍቺ ስምምነት የወፍጮ ድርጅቱን እኩል ለመካፈል በግልጽ ተስማምተን፣ የስመ

አለመዛወር የንብረት ክፍፍሉን ተግባራዊነት የሚያግድ ሆኖ ሣለ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ከተከራካሪዎች ባልቀረቡለት ጥያቄ የግዢ ውሉ እንደሚፈርስ አድርጎ ለግዢ የተከፈለውን ገንዘብ እንድንካፈል መወሰኑ አላግባብ በመሆኑ ይሻር የሚል ነው፡፡

ይህም ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ የክርክሩ ምክንያት የሆነው ወፍጮ ድርጅት ባልና ሚስቱ /አመልካችና ተጠሪ/ ቢገዙትም በስማቸው አልዞረም በሚል የጋራ ሀብት አይደለም ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙን በጽሑፍ አከራክሯል፡፡ እኛም የግራ ቀኙን ክርክርና የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ተጋቢዎቹ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን የወፍጮ ድርጅት በተመለከተ በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. ተደርጎ በፍ/ቤት በፀደቀው የፍቺ ስምምነታቸው ላይ ክፍፍሉን አስመልክቶ በግልጽ ፈቃዳቸውን ሰጥተው ተስማምተዋል፡፡ ይህን ስምምነት ግራ ቀኙ ያልካዱት በሌላ ስምምነት ያልቀየሩት ወይም ያላሻሻሉት እና በፍ/ቤትም የፀደቀ ከመሆኑ አንፃር ይህ ስምምነት በግራ ቀኙ መልካም ፈቃድ እስካልተሻረ ድረስ ተጋቢዎቹ በስምምነቱ ቃል የማይገደዱበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በሌላ በኩል በማንኛውም የክርክር ደረጃ ቀርቦ በአከራካሪው ንብረት ላይ መብት አለኝ፤ የጋራ ሀብት ተብሎ ለግራ ቀኙ ሊካፈል አይገባም በሚል በ3ኛ ወገን የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ተጠሪው አከራካሪ የሆነው ንብረት በ3ኛ ወገን ስም የሚገኝ ነው ይበሉ እንጂ የተጠቀሰውን 3ኛ ወገን ወክለው ስለ ንብረቱ ለመከራከር መብት ያላቸው መሆኑን አላመለከቱም፣ እንዲሁም ንብረቱ በእጅ አይገኝም በሚል ክደው ያቀረቡት መከራከሪያ የለም፡፡ የወፍጮ ድርጅቱ ክፍፍል ላይ ያጋጠመ እክል ለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በፍቺ ስምምነቱ መሠረት አይፈፀምም መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 373/2/ የአፈፃፀም ፍ/ቤት በዋናው ፍርድ የታዘዘውን ከመፈፀም ውጪ ባለቀው ጉዳይ እንደ አዲስ ማከራከር እንደማይኖርበት በግልጽ ተደንግጎ እያለ የት/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ከፍቺ ስምመነቱ ቃልና ስምምነቱን ካፀደቀው ውሣኔ ይዘት ውጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወፍጮ ድርጅቱ የግራ ቀኙ የጋራ ሃብት አይደለም፤ ለግዢው ለ3ኛ ወገን የተከፈለውን ብር 10,000 ተጠሪው ለአመልካች እኩሌታውን ይክፈሏቸው ሲል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የክርክሩ ምክንያት የሆነው በት/ብ/ክ/መ/ በጣቢያ ደጀን አዲኽሎ የሚገኘው የወፍጮ ድርጅት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት በመሆኑ በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም ባደረጉት ስምምነት መሠረት ክፍፍሉ ይፈፀም፡፡

2/ የወፍጮ ድርጅቱን በስምምነት ማካፈል ካልተቻለ የወፍጮ ድርጅቱ ተገምቶ አንደኛው ወገን የግምቱን ግማሽ ገንዘብ ከፍሎ ድርጅቱን ለራሱ ያስቀር፡፡

3/ አንደኛው ወገን የግምቱን ግማሽ ለሌላኛው ከፍሎ ድርጅቱን ማስቀረት ካልቻለ የወፍጮ ድርጅቱ በሐራጅ ተሸጦ ግራ ቀኙ የሽያጩን ገንዘብ እኩል ይካፈሉ፡፡

4/ የት/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20701 በነሐሴ 4 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

5/ ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 33440

ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድነን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም - ጠበቃ ሰለሞን ገ/ሚካኤል

ተጠሪ፡- አቶ ግርማ ገብረስላሴ - ጠበቃ አያሌው ካሕሳይን

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በቅድሚያ የአሁን ተጠሪ የሚች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅ ነኝ በማለት የወራሽነት ማስረጃ ካገኙ በኋላ የአሁን አመልካች እዚሁ ፍ/ቤት ቀርበው ሚች እህቴ ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅ ሳትወልድ የሞተችና ከተጠሪውም ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና የሌላቸው ስለሆነ ተጠሪ የሚች ወራሽ ነው ተብሎ በዚህ መዝገብ የተሰጠው ማስረጃ ሊሰረዝ ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ልጅነትን በተመለከተ የከተማ ነክ ፍ/ቤት ለመወሰን በሕግ ሥልጣን ያልተሰጠው ስለሆነ ተጠሪ የሚች የወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅነትን በተመለከተ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ውሣኔ በተገኘ ጊዜ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ልጅነት የልደት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ማስረዳት እንደሚቻል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 154 ላይ የተመለከተ ሲሆን ከዚህ ድንጋጌ ማንኛውም ፍ/ቤት የሕግ ግምት በመውሰድ ልጅነትን ማረጋገጥ የሚችል በመሆኑ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት አቤቱታው ይቅረብ ሊባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችለውም የልደት የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ አመልካች ልጅ መሆኑን በሁኔታና በሰው ምስክር ለማስረዳት በጠየቀ ጊዜ ነው ካለ በኋላ ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪ የሚች የወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅ ስለመሆኑ በልደት የምስክር ወረቀት የተረጋገጠ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት የይግባኝ ባይ ልጅነት በቅድሚያ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ሊረጋገጥ ይገባል በማለት አቤቱታውን ሳይቀበል መቅረቱ በአግባቡ ስላልሆነ ይግባኝ ባይ የሚች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅ ከሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ስለሚሆን መ/ሰጭ ሊወርሱ ስለማይችሉ በመ/ቁ. 5205/98 ጎዳር 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ወራሽ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተሠርዟል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው ለከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በተጠሪ ልጅነት ላይ ተመስርቶ የቀረበውን ክርክር የከተማ ነክ ይ/ሰሚ ፍ/ቤት ተመልክቶ ውሣኔ መስጠቱ በሕግ በተሰጠው ሥልጣን ሥር የሚሸፈን ስለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የሰበር አቤቱታውም ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በውሣኔው ላይ እንዳሰፈረው ልጅነት የሚረጋገጥበት ዋናው ማስረጃ የልደት ምስክር ወረቀት እንደሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 154 ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህ ማለት ግን የልደት ምስክር ወረቀት ክርክር ሊነሳበት የማይችል ሙሉ እምነት ሊጣልበት የሚችል /Conclusive/ ማስረጃ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ አመልካችም ተጠሪ የሚች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅ መሆኔን ያረጋግጥልኛል በማለት ያቀረቡት የልደት ምስክር ወረቀት በተጭበረበረ መንገድ የተገኘ

ከመሆኑም በላይ ሚች በሕይወት ዘመናቸው ልጅ አልወለዱም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በተጠሪ ልጅነት ላይ በዚህ መልኩ ክርክር የተነሳበት ከሆነም የተጠሪ ልጅነት ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ክርክር ተደርጎበት ውሣኔ የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

በዚሁ መሠረትም የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር የተነሳበት የተጠሪ ልጅነት ጉዳይ በቅድሚያ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ዕልባት ሊሰጠው ይገባል ማለቱ አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግን የልደት ምስክር ወረቀቱ በማስረጃ ሊስተባበል እንደማይችል በመቁጠር የተጠሪ ልጅነት ጉዳይ ከዚህ በኋላ ክርክር ሊደረግበት አይችልም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ መሻሩ እንደዚሁም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይህንን ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03902 በሰኔ 19 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 04714 በሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 4979/97 በታህሳስ 4 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ብይን ጸንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 33875

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

ዓለ. መሐመድ

መድነን ኪሮስ

አመልካች፡- ወ/ሮ የሻረግ አባትኩን ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መሠረት አድማሱ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁንዋ ተጠሪ የአቶ ኪዳነወርቅ ብርቁ ሚስት ስለመሆናቸው መጋቢት 16 ቀን 1996 ዓ.ም. በመ/ቁ. 12185 በዚሁ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ቁራ ምድብ 1ኛ ፍትሐብሔር ችሎት የተወሰነላቸው ሲሆን የአሁንዋ አመልካች የሚች አቶ ኪዳነወርቅ ብርቁ ሚስት እኔ ነኝ፤ ወ/ሮ መሠረት አድማሱ የሚች ሠራተኛ እንጂ ሚስት አልነበሩም በማለት ተቃውመዋል፡፡

ተቃውሞው የቀረበለት ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ወ/ሮ መሠረት አድማሱ አቅርበው ያሰሙዋቸው ምስክሮች አቶ ኪዳነወርቅ ብርቁ ድግስ ደግሰው ለተጠሪው ሕዝብ ወ/ሮ መሠረት አድማሱ ሚስቴ ናት፤ ከእንግዲህ ባልና ሚስት ነን ብለው መናገራቸውንና ከዚያም በኋላ አብረው በመኖር ልጆች መውለዳቸውን ያስረዱ በመሆኑና ተቃዋሚዋ ያሰሙዋቸው ምስክሮች ደግሞ የሰጡት ምስክርነት ይህን የሚያፈርስ ባለመሆኑ ተቃውሞው ተቀባይነት የለውም በማለት ቀደም ብሎ የተሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360/2/ መሠረት አጽንቷል፡፡

የአሁንዋ አመልካች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የወ/ሮ መሠረት አድማሱ ምስክሮች ሚች ድግስ ደግሰው ባልና ሚስት ነን ብለው ተናግረዋል ብለው ቢያስረዱም ይህ አባባል በጽሁፍ በሽማግሌዎች ፊት እስካልተደረገ ጊዜ ድረስ ተደረገ የተባለው ጋብቻ በባሕላዊ ጋብቻ ሥር አይወድቅም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የወ/ሮ መሠረት አድማሱን ሚስትነት የወሰነው ጋብቻው በሰርተፍኬት ወይም በትዳር ሁኔታ ሳይረጋገጥ ነው በማለት ውሳኔውን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

የአሁንዋ ተጠሪ ደግሞ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ጠቅላይ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ ይግባኝ ባይዋ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያሰሙዋቸው ምስክሮች ሚች ድግስ ደግሰው ሰው ጠርተው በሕዝብ ፊት ከእንግዲህ ከወ/ሮ መሠረት አድማሱ ጋር ባልና ሚስት ነን በማለት በመናገር የጋብቻውን መመሥረት ያበሰሩና አብረው በመኖርም ልጆች መውለዳቸውን ያስረዱ በመሆኑ የጋብቻው መኖር በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 97/1/ መሠረት በሁኔታ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በመልስ ሰጭ ማስረጃ በአንቀጽ 97/2/ መሠረት አልተስተባበለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ለባሕላዊ ጋብቻ የሰጠው ትርጉምም የተሳሳተ ነው በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በመሻር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁንዋ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች በአቤቱታቸው ያካተቱት ቅሬታም ተጠሪ የሚች ሠራተኛ እንጂ ሚስት አይደሉም፡፡ ሕጋዊ ሚስት እኔው ነኝ፡፡ የተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት በሚችና በተጠሪ መካከል ባሕላዊ ጋብቻ ስለመመስረቱ አያስረዳም፡፡ ወቅቱ በ1976 ዓ.ም. ቦታውም አዲስ አበባ በመሆኑ በዚህ ጊዜ የሚፈፀም ባሕላዊ ጋብቻ በሽማግሌዎች ፊትና በጽሁፍ ሰፍሮ የግራ ቀኙንና የሽማግሌዎችን ፊርማ ባረፈበት ሁኔታ መሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነበረበት፡፡ በሚችና በተጠሪዋ መካከል ተደረገ የተባለው ጋብቻ ይህን የሚያሚላ አይደለም፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የመልስ ሰጭ ምስክሮች በድግስ ወቅት ሚች ሚስቴ ናት ሲሉ ሰምተናል በማለት የሰጡትን ምስክርነት ብቻ መነሻ በማድረግ የእኔ ምስክሮች ተጠሪዋ ሚስት ሳይሆኑ የሚች ሠራተኛ ናቸው ደመወዝም ይቀበሉ ነበር በማለት ያስረዱትን ባለመቀበል ተጠሪዋ የሚች ሚስት ስለመሆናቸው በሁኔታ ተረጋግጧል በማለት የሰጡት ውሣኔ በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 4 እና 97/2/ የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪዋ ባሰሙዋቸው ምስክሮች ከሚች ጋር በባሕላዊ ሥነ ሥርዓት ጋብቻ የፈፀሙ ስለመሆኑ አላስረዱም እንጂ ፍ/ቤቱ አስረድተዋል እንኳን ቢል ተጠሪዋ ከ1977 ዓ.ም. እስከ 1980 ዓ.ም. ድረስ የሚች ኪዳነወርቅ ብርቁ የጽዳት ሠራተኛ እንደነበሩ የሚያሳይ ማስረጃ መቅረቡ እንዲሁም ሚች ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ጥር ወር 1994 ዓ.ም. ሲሆን ተጠሪዋ ከ1980 ዓ.ም. ጀምሮ ከሚች በመለየት አቶ ሽፈራው መንክር የተባሉትን ሰው አግብተው ሁለት ልጆች ወልደዋል፡፡ ከዚህ ሁኔታም ተጠሪዋ ከሚች ተለያይተው ሚች ከዚህ ዓለም እስከተለዩበት ጊዜ ድረስ የየራሳቸውን ኑሮ ይኖሩ የነበረ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ባለበት ተጠሪዋ የሚች ሚስት ናቸው መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እና ፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሮ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እንዲፀና እንዲወስንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዋ ደግሞ በሰጡት መልስ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሚስትነቴን ያረጋገጠልኝ ጥቅምት 15 ቀን 1976 ዓ.ም. ዘመድ ጠርተን ድግስ ደግሰንና ጋብዘን ከዚህ በኋላ ባልና ሚስት ነን ተጋብተናል በማለት መጋባታችንን በማሳወቅ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት መፈፀማችንን ከዚህ በኋላም ባልና ሚስት ሆነን ልጅ መውለዳችንን በማስረጃ በመረጋገጡ ነው፡፡ አመልካች በወቅቱ ተጠሪ የሚች ባለቤት አይደለችም ሠራተኛው ናት ከማለት በስተቀር በማስረጃ ያረጋገጥኩትን የጋብቻ ሁኔታ ስላለመኖሩ አላስረዱም፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱን ውሣኔ የሻረው ባሕላዊ ጋብቻን በሽማግሌና በፊርማ ሥነ ሥርዓት መከናወን አለበት የሚል በጣም ጠባብ ትርጉም በመስጠት ነው፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ትርጉም ሲሸር ሕጉ በአማራጭ ያስቀመጣቸውን ሁኔታዎች ከግምት ያስገባ አይደለም፡፡ ከዚህም አልፎ በጽሑፍና በውል አባት ሽማግሌ ፊት መደረግ አለበት የሚለው ድምዳሜ የአ/አበባ ከተማ ማኅበረሰብ ሊወክል የሚችል ባሕላዊ አመራር ነው ብሎ ለመደምደም በቂ መነሻ አይሆንም በማለት ያስቀመጠው ትንታኔ የሕጉን መንፈስ በትክክል የሚገለጽ በመሆኑ ውሣኔው አንዳችም የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተጠሪ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በተጨማሪ ተጠሪ ከሚች ጋር የተዋወቅነውና የትዳር ጥያቄም ቀርቦልኝ የተጋባነው ሚች በሚያንቀሳቅሱት የባሕል ሕክምና ድርጅት ውስጥ በረዳት ሐኪምነት ተቀጥራ በነበረበት ወቅት ስለመሆኑ አልክድም ብለዋል፡፡ ሆኖም ከሚች ጋር ከተጋባን በኋላ ተለያይተን ኖረን አናውቅም፡፡ ሚች ከመሞታቸው በፊት ተለያይተው ተጠሪዋ ሌላ ባል አግብታ ነበር የተባለው በስር ፍ/ቤት ያልቀረበና በማስረጃም ያልተረጋገጠ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከሚች ባለቤቱ የወለድኩትን ልጅ ያሳደግነውና በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 19 ቀበሌ 49 ክልል የቤት ቁጥር 008 እና 009 የሆነውን ድርጅትና የመኖሪያ ቤት ያፈራነው በጋራ ነው፡፡ በሰበር መ/ቁ. 20938 የተሰጠው ውሣኔም አሁን ከቀረበው ክርክር ጋር ተዛማጅነትና ተመሣሣይነት የለውም፡፡

በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ምንም የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ውሣኔው እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ከመዝገቡ ጋር አያይዘዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ ተጠሪዋ የጋብቻ ሁኔታን አረጋግጠዋል ወይስ አላረጋገጡም? አመልካችስ የጋብቻ ሁኔታውን አስተባብለዋል ወይስ አላስተባበሉም? የሚሉት ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ግራ ቀኙ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባካሄዱት ክርክር የተጠሪ ምስክሮች ያስረዱት ሚችና ተጠሪዋ ድግስ ደግሰው ሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠርተው ሚች ከዛሬ ጀምሮ ከተጠሪዋ ጋር ባልና ሚስት ሆነዋል ብለው ማሳወቃቸውን ከዚያም በኋላ ልጅ ወልደው አብረው የኖሩ መሆናቸውን ነው። ይህ ዓይነቱ ማስረጃ ደግሞ ጋብቻው በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 4 መሠረት በባሕላዊ ሁኔታ የተፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። በአንፃሩ የአሁንዋ አመልካች ያሰሙዋቸው ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ተጠሪዋ የሚች ሠራተኛ መሆናቸውንና ከሚች ጋር ስለመጋባታቸው ግን የሚያውቁ መሆናቸውን ነው ያስረዱት። መጀመሪያ ተጋብተው ግን ደግሞ ሚች ከመሞታቸው በፊት የተፋቱ ስለመሆኑም እንዲመሰክሩ አልተጠየቁም። እነሱም ይህን አስመልክተው ያሉት ነገር የለም። ይህ የአመልካች ምስክሮች ምስክርነት ደግሞ ተጠሪዋ ከሚች ጋር የትዳር ጋብቻ ያላቸው መሆኑን በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 97/1/ ያስረዱትን የሚያስተባብል አይደለም። ይህን መሠረት በማድረግ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪዋና በሚች መካከል ጋብቻ ነበር በማለት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት አልነበረም።

የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም በሰጠው ውሣኔ በአሁንዋ ተጠሪና በሚች መካከል ባሕላዊ ጋብቻ ስለመመስረቱ በማስረጃ ተረጋግጧል። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚፈፀም ባሕላዊ ጋብቻ በሸማግሌ ፊት በጽሑፍና በፊርማ ነው የሚከናወነው በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መንደርደሪያ የሆነውን የሕግ ትርጉምም ተቀባይነት የለውም ሲል በውሣኔው ላይ ያሰፈረውን ትንታኔ ስንመለከትም ውሣኔውና ለውሣኔው መሠረት ተደርጎ የተወሰደው ትንታኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም። ምክንያቱም ተጠሪዋ ከሚች ጋር ፈፀምኩት የሚሉትን ባሕላዊ ጋብቻ ስለመመሥረቱ ለማስረዳት የሚጠበቅባቸው የአመሠራረቱን ሁኔታ ማስረዳት ነው። በምስክሮቻቸው ያስረዱትም ጋብቻውን ለሌሎች ለማሳወቅ ታስቦ ድግስ መዘጋጀቱንና ሰዎች መጠራታቸውን የተጠሩት ሰዎች ከተገኙ በኋላ ሚች ከእንዲህ ከወ/ሮ መሠረት አድማሱ ጋር ባልና ሚስት ሆነናል ዕወቁልን በማለት የተናገሩ መሆናቸውን ከዚያም በመቀጠል ባልና ሚስት ሆነው አብረው መኖራቸውንና ልጅም መውለዳቸውን ነው። ይህ ዓይነቱ ጋብቻ ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥም የሚፈፀም ነው። በዚህ

ሁኔታ ባሕላዊ ጋብቻ እንዳይፈፀምም የሚከለክል ምክንያት የለም። ተጋቢዎች ከፈለጉ ጋብቻውን በጽሑፍ በመፈራረምም ሊያደርጉት ይችላሉ። ከፈለጉ ደግሞ በቃል ለማኅበረሰቡ እወቁልን ብለው በመናገር ሊመሰርቱት ይችላሉ።

በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ምንም ዓይነት የሕግ ስህተት ያለበት ባለመሆኑ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26737 ጥቅምት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል። ይፃፍ።
2. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አበለት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34149

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ዘለቃሽ በቀለ ወርቁ መንገሻ ጠበቃ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አለሙ በቀለ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው የአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 5947 ኅዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ሊታረም ይገባዋል በማለት አመልካች ኅዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪው ጠጅነሽ በቀለ ጋር ጥቅምት 1 ቀን 1994 ዓ.ም በሕጋዊ ጋብቻ ተጋብተን ስንኖር ዋጋዬ አለሙ የተባለች ልጅ ወልደናል፡፡ አሁን ልጅቱን እንዳሣድግ ብጠይቃቸው ተከሳሾች እንቢ ስላሉኝ ልጄን ተረክቤ እንዳሣድግ ይደረግልኝ በማለት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበ ሲሆን አመልካቾች በተከሳሽነት ቀርበው የሕጻኗ ስም አዳነች በቀለ አንደሆነና እናቷ በሞት ስትለይ ግልጽ ኑዛዜ የተወች በመሆኑ ሕፃኗም የከሳሽ ልጅ ስላልሆነች ክሱ እንዲሰረዝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካቾች የሚች ወ/ሮ ጠጅነሽ በቀለ እህቶች መሆናቸውን በመግለጽ እናንተ የከሳሽን አባትነት ለመቃወም መብት የላችሁም በማለት ሕፃኗን ለተጠሪው እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ

ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሃብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ዘግቶታል፡፡ አመልካቾች ከሚች ጋር በሕጋዊ ጋብቻ ለመኖሩና ልጅቷም በጋብቻው ወቅት ወይም ጋብቻ ከፈረሰ ከሶስት መቶ ቀን በፊት የተወለደች መሆኑን የሚያስረዳ እንዲሁም ፣ ሕፃኗ የበቀለ አበበ ልጅ ለመሆኗ እኛ ማስረጃ አቅርበን እያለ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 147 በመጥቀስ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ይታረምልኝ በማለት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪው መጥሪያው ደርሶት ያልቀረበ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ብይን ተሰጥቷል፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ጉዳይ አባትነትን በመካድ የቀረበ ክስ ባለመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የጠቀሳቸው የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች አግባብነት የላቸውም፡፡ ተጠሪው ልጄ ናት የሚላት ዋጋዬ ዓለሙ ሚች ጠጅነሽ በቀለ ጋር በጋብቻ በነበሩበት ወቅት የተወለደች መሆኑን ገልጿል፡፡ ተጠሪው ልጄን ያስረክበኝ ብሎ ለመጠየቅ በመጀመሪያ ከልጅቱ እናት ወ/ሮ ጠጅነሽ በቀለ ጋር በጋብቻ ተጣምረው ይኖሩ እንደነበር፣ በጋብቻ እየኖሩ እያለ ልጅቱ የተወለደተች መሆኑን በማስረጃ የማስረዳትና የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው እነዚህን ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ያስረዱልኛል ብሎ የቆጠራቸውን ምስክሮች አልሰማም፡፡ ተጠሪው የልጅቱ አባት መሆኑን በማስረጃ ካላስረዳ የልጅቱ አክስት የሆኑ ተጠሪዎች ማንም አባት ነኝ ብሎ ለመጣ ሰው ልጅቱን አሳልፈው እንዲሰጡ የሚያስገድዳቸው የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ የልጅቱ አባት ያልሆነ ሰው አባቷ ነኝ ብሎ ሲቀርብም የልጅቱ አባት አይደለም፣ ስለዚህ በአግባቡ አያሳድጋትም የሚለውን ምክንያት አንስተው እንዳይከራከሩ የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 147 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 አይገድባቸውም፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሣይሰማ ተጠሪው የሕፃኗ አባት ስለሆነ አስረክቡ በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠው ውሣኔና የጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ውሣኔው የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 5947 ህዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ አመልካች ለራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 34387

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ከበደ ሙሐ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 51375 ግንቦት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 32029 ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ በሕጋዊ ጋብቻ ተሣሥረው ለበርካታ ዓመታት በባልና ሚስትነት የኖሩ ሲሆን፣ ጋብቻቸውን በፍች አፍርሰዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የጋራ ንብረታቸውን ለመካፈል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጋራ ንብረት ዝርዝር አቅርበው ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ተጠሪ እስከ ጥር 29 ቀን 1998 ዓ.ም. አመልካች የተቀበሉት የጡረታ አበል ታስቦ እንዲከፈለኝ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ጥያቄ ማቅረባቸው ነው፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ የጡረታ አበል ይሰጠኝ ጥያቄ የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት በከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው፣ ፍርድ ቤቱ በይግባኝ አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች የሚያገኙት የጡረታ አበል የጋራ ንብረት ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት የጡረታና ማኅበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ከግንቦት ወር 1999 ጀምሮ ግማሽ የጡረታ አበል ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኙን የሰማው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለም በማለት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ አመልካች አሁን የማገኘው አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ብር የጡረታ ገንዘብ ወታደር ቤት እያለሁ በአይኔ ላይ ጉዳት ደርሶብኝ በቦርድ በመውጣቴ የማገኘው ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት የባልና የሚስት የጋራ ሀብት ነው በማለት ተጠሪዋ ግማሹን እንድትወስድ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪዋ በበኩሏ የጡረታ አበሉ በትዳራችን ጊዜ የተጠራቀመ በመሆኑ ግማሹን እንድወስድ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለች ተከራክራለች፡፡

በሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር ግራ ቀኙ የሚያነሱት የመከራከሪያ ነጥብ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪዋ ከግንቦት 1999 ጀምሮ ግማሽ የጡረታ አበል ልታገኝ ይገባታል በማለት የሰጠው ውሣኔ ሕግን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ አይተናል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔውን በሚሰጥበት ወቅት የተከተለውን ሥርዓት ስንመረምረው፣ ተጠሪ የጡረታ አበል፣ ታስቦ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡት እስከ ጥር 29 ቀን 1998 ዓ.ም. አመልካች የወሰዱትን የጡረታ አበል መሆኑን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሣነው በግልጽ አስፍሮታል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ የጠየቁትን ጋብቻቸው ከመፍረሱ በፊት ተለያይተው እያለ አመልካች ተቀብለው የተጠቀሙበት የጡረታ አበል ታስቦ እንዲሰጣቸው እንጂ ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ አመልካች ከሚያገኙት የጡረታ አበል ግማሹን እንዲወስንላቸው በሥር ፍርድ ቤት አልጠየቁም፡፡ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያላቀረቡትንና በሥር ያልተከራከሩበትን አዲስ ነገር በይግባኝ ደረጃ ለማንሣትና ለመጠየቅ

እንደማይችሉ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 328 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በሥር ያልጠየቁትና ያልተከራከሩትን ጉዳይ በማንሣት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከግንቦት ወር 1999 ዓ.ም. ጀምሮ አመልካች ከሚያገኙት ጡረታ ግማሹን ሊከፍላት ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የሚያገኙት የጡረታ አበል፣ የመንግሥት ሠራተኛ በነበሩበት ሠዓት ከደመወዛቸው ተቆርጦ የተጠራቀመ ነው የሚለው አባባል መሠረታዊ ስህተት ያለበትና የጡረታ አበሉ መንግሥት በኩል ተቀማጭ የሚሆን ገንዘብ ያለ በመሆኑ ለአንድ ሠራተኛም የጡረታ አበል የሚከፈለው እድሜው በገፋበትና ጉልበቱ በደከመበት ጊዜ መጦሪያ የሚሆነውና ለመኖር የሚያስፈልገውን ወጭ በከፊልም ቢሆን በመሸፈንና ለማኅበራዊ ደህንነቱ ዋስትና ለመስጠት መንግሥት ካለው የማኅበራዊ ደህንነትና ዋስትና ፖሊሲ የመነጨ በመሆኑ እንደማንኛውም ገቢ የጋራ ንብረት ነው የሚባል አይደለም፡፡ የአንድ ሰው የጡረታ አበል በማናቸውም መልኩ በዕዳ ሊያዝ ወይም ሊታገድና ሊቀነስ እንደማይችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 404/ሠ/ በግልጽ የሚደነግግ ሲሆን የከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን በመተላለፍ አመልካች የሚከፈለው የጡረታ አበል ግማሹ አየተቆረጠ ለተጠሪ እንዲከፈል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 32029 ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 51375 ግንቦት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማሻሻል የወሰናቸው ሌሎች ጉዳዮች የፀኑ ሲሆን የጡረታ አበልን አስመልክቶ የሰጠው ውሣኔ ብቻ ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራን በተመለከተ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. አመልካች ከሚያገኘው የጡረታ አበል ተጠሪ ግማሹ ይሰጠኝ ካለ የመጠየቅና የመካፈል መብት የላትም በማለት ወስነናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 35376

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ዳንኤል አሰፋ ቀርቧል፡፡

2. ሕፃን አልአዛር አሰፋ ወኪል ቀርቧል

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ሒሊን ውበቱ ቀርባለች

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሣሽ በመሆን፣ አውራሽ እናቱ ወ/ሮ ስንቁ አስፋው ከአቶ አሠፋ መለሰ ጋር ተጋብተው ሲኖሩ በጋራ ያፈሩት በወ/19 ቀ/55 የሚገኝ ቁጥሩ 223 ቤት እና በውስጡ የሚገኙ የአውራሼ የግልና የጋራ ንብረቶችን የአሁኑ 1ኛ አመልካች አላግባብ ለብቻው ይዞ እየተጠቀመ በመሆኑ የድርሻዬን ያካፍለኝ ቤቱንም በማከራየት ያገኘውን ጥቅም ያካፍለኝ ስትል ታህሣሥ 21 ቀን 1995 ዓ.ም ጽፋ ባቀረበችው ክስ መነሻነት ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፈቀደለት መሠረት ወደ ክርክሩ የገባው 2ኛ አመልካች ከ1ኛው አመልካች ጋር በተመሣሣይ መከራከሪያዎች ለክሱ መልስ የሰጡ ሲሆን የመልሣቸውም ይዘት የተጠቀሰውን ቤት አቶ አሠፋ መለሰ ሥራው ተጠናቅቆ የተረከቡት ከተጠሪዋ አውራሽ ጋር ከመጋባታቸው በፊት ጥር 8 ቀን 1981 ዓ.ም ሲሆን ከተጠሪ አውራሽ ጋር ጋብቻ የፈፀሙት ግንቦት 11 ቀን 1983 ዓ.ም በመሆኑ ይህ ቤት የአቶ አሰፋ መለሰ የግል ቤት እንጂ ተጠሪዋን የውርስ ጥያቄ ለማቅረብ መብት የሚሰጥ የጋራ ሀብት አይደለም የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዋ ለቀረበው መልስ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የመልስ መልሱም ይዘት ይህ ቤት የተሠራው በባንክ ብድር በመሆኑ ብድሩ በትዳር ወቅት ከአቶ አሠፋ መለሰ ደሞዝ ለባንክ ሲከፈል ቆይቶ እዳው ተከፍሎ ሣይጠናቀቅ አቶ አሠፋ መለሰ በመሞታቸው መ/ቤታቸው በገባላቸው የሕይወት ኢንሹራንስ መሠረት ተከፋዩ ገንዘብ ለእዳው መክፈያ ውሎ እዳው ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ ተጠናቋል፡፡ ስለዚህ ቤቱ የጋራ ንብረት ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የካቲት 18 ቀን 1996 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ፣ ከጋብቻ በፊት /ከግንቦት 11/1983 ዓ.ም/ ለቤቱ መሥሪያ የከፈሉት የአቶ አሠፋ መለሰ የግል ንብረታቸው ሲሆን ከዚህ ቀን በኋላ ላለው በተከፈለው መጠን ግን ቤቱ የሁለቱም የሚቾች የጋራ ሀብት በመሆኑ ሁለቱ በግልና በጋራ በከፈሉት ገንዘብ ስሌት መሠረት ቤቱ የግልና የጋራ ሐብታቸው ነው፣ ስለዚህ ቤቱን በዚህ የድርሻ ስሌት መሠረት ግራ ቀኙ ይከፋፈሉት በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኙት የአሁን አመልካቾች ቅሬታቸውን በይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ጥቅምት 17 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ደሞዝ የባልና ሚስት የጋራ ሐብት ከመሆኑ አንፃር ሚቾ አቶ አሠፋ መለሰ የሚያገኙትን ደሞዝ ለቤት ውስጥ ፍጆታ ማዋል ሲገባቸው ይህንን ሣያደርጉ ከጋብቻ በፊት አስቀድሞ በይዞታቸው ውስጥ ያደረጉትንና የግል ንብረታቸው ለሆነው ቤታቸው እዳ መክፈያ ደሞዛቸውን በማዋላቸው ምክንያት በከፈሉት ልክ ግማሹ ተሠልቶ የጋራ ሐብት ተካፋይ ለሆኑት ወ/ሮ ስንቂ አስፋው ወራሽ /የአሁን ተጠሪ/ እንዲከፈል በማለት ወስኗል፡፡

ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በማቅረባቸው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት አመልካቾቹን አስጠርቶ ግራ ቀኙን አከራክሮ ካበቃ በኋላ ጎዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ደግሞ፣

የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 63 የግል ነው ተብሎ ያልተለየ ንብረት እንኳን የጋራ እንደሆነ እንደሚገመት እየደነገገ በዚህ ጉዳይ ግን የቤቱ እዳ በአብዛኛው ባልና ሚስቱ በጋብቻው ወቅት የጋራቸው በሆነው ደሞዝ መከፈሉ እየተረጋገጠ ብድሩ ከጋብቻ በፊት በመገኘቱ ብቻና ከ2 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የመ/ሰጭ /የአሁን አመልካቾች/ አባት ከደሞዛቸው ስለከፈሉ ቤቱ የግላቸው ነው መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

የዚህ መዝገብ መከፈት ምክንያት የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ጥር 26 ቀን 2000 ዓ.ም አመልካቾች ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ መሠረት ነው፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የአመልካቾችን አቤተታ ተመልክቶ፣ በዚህ ጉዳይ የአመልካቾቹ አባት የሠሩት ቤት እዳው ተከፍሎ ያለቀው ከተጠሪዋ እናት ጋር በጋብቻ ላይ እያሉ ነው በሚል ተጠሪ የእናቷን ድርሻ የቤቱን ግማሽ ልታገኝ ይገባል ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አሳሂደዋል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ቤቱ የጋራ ነው ሲል ለመወሰን የቻለው ቤቱ የተሠራው ከባንክ በተገኘ ብድር በመሆኑ እዳው ሲከፈል የነበረው ከአመልካች አባት ደሞዝ በመሆኑ እና ይህ ደሞዝ የጋራ ገንዘብ በመሆኑ ቤቱ የተሠራው የጋራቸው በሆነው ደሞዝ ነው በሚል መንደርደሪያ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ በመሠረቱ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 57 ባል ወይም ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ወቅት በየግል የነበሯቸው ንብረቶች የግል ሆነው ይቀራሉ ሲል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ጉዳይ የተጠሪ አውራሽ እናት እና የአመልካች አባት ጋብቻቸውን የፈፀሙት ግንቦት 11 ቀን 1983 ዓ.ም ሲሆን የአመልካቾች አባት የቤቱ ግንባታ ተጠናቆ የተረከቡት ጥር 8 ቀን 1981 ዓ.ም ለመሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ አቶ አሰፋ መለሰ ከጋብቻው አስቀድሞ የቤቱ ባለሀብት የሆኑ ሲሆን በወቅቱ ቤቱ የተሠራበት የባንክ እዳ መኖሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለሐብትነታቸውን አያስቀረውም፡፡ በሌላ አነጋገር አቶ አሠፋ መለሰ ባለዕዳነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የቤቱ ባለሐብት ሆነዋል ማለት ነው፡፡ በአንዣሩ ደግሞ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62/1 ባልና ሚስቱ በጋብቻ ወቅት ከግል ጥረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሐብት እንደሚሆኑ ያመለክታል፡፡ ከዚህ አኳያ ከጋብቻ በኋላ ለባንክ እዳ መክፈያ ሲውል የቆየው የአቶ አሠፋ መለሰ ደመወዝ የባልና ሚስቱ የጋራ ገንዘብ ለመሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 70/1/ መሠረት ደግሞ ከባል ወይም ከሚስት የሚጠየቅ ዕዳ በተቀዳሚነት ከባለእዳው ተጋቢ የግል ሐብት መክፈል እንደሚባው ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ የአመልካቾቹ አባት ለግል ቤታቸው ማሠሪያ ከባንክ የተከፈለ የግል እዳቸውን ለመወጣት የጋራ ገንዘብ ከሆነው ከደሞዛቸው ክፍያ መፈፀማቸውን ተገንዝበናል፡፡ የአመልካቾች አባት ይህንን መፈፀማቸው በተጠሪዋ እናት የጋራ ባለገንዘብነት መብት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጥቅማቸውንም የሚቀንስ ተግባር በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ የአመልካቾች አባት የተጠሪዋ እናት ባጡት ጥቅም ልክ ሊክሷቸው ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የይግባኝ ችሎት ሣያነሣው ያለፈው ግራ ቀኙን ግን ያከራከረ ነጥብ አቶ አሠፋ መለሰ ሲሞቱ መ/ቤታቸው በገባላቸው የሕይወት ኢንሹራንስ መሠረት በኢትዮጵያ መድን ድርጅት ተከፋይ የሆነው ለባንክ እዳ መክፈያ የዋለውን ገንዘብ አስመልክቶ የተነሣው ክርክር ነው፡፡ በመሠረቱ የህይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚን አስመልክቶ በተደነገገው የን/ሕ/ቁ. 701/2/ሀ/ ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም እንኳ የኢንሹራንስ ውሉን የፈረመው ሰው ባል ወይም ሚስት ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚ ተብለው እንደሚቆጠሩ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ አቶ አሠፋ መለሰ ሲሞቱ ተከፋይ ከሆነው የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ የተጠሪዋ እናት ግማሽ ተጠቃሚ ለመሆናቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ገንዘብ ደግሞ ለባንክ እዳ ክፍያ የዋለ ሰለመሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ የኢንሹራንስ ገንዘብም ለአቶ አሠፋ መለሰ የግል እዳ መክፈያ መሆኑ የወ/ሮ

ስንቂ አስፋውን ጥቅም የጎዳ በመሆኑ የዚህ ገንዘብ ግማሽ የወ/ሮ ስንቂ ድርሻ በመሆኑ ሊመለስላቸው ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የግል ዕዳው በጋራ ገንዘቡ መከፈሉ የግል የሆነውን ሐብት የጋራ ንብረት ያደርገዋል የሚል ድንጋጌ ባለመኖሩ ሊተካ የሚገባው የወ/ሮ ስንቂ አስፋው ድርሻ የሆነው በጋብቻ ውስጥ ማሉ ከአቶ አሰፋ መለሰ ደሞዝ ተከፋይ የሆነው ገንዘብ እና የኢንሹራንስ ገንዘብ ግማሽ ብቻ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የወ/ሮ ስንቂ አስፋው ወራሽ የሆኑት ተጠሪዋ ብቻ ሣይሆኑ በዚህ መዝገብ 2ኛ አመልካች የሆነው ሕፃን አልዓዛር አስፋውም ጭምር በመሆኑ ለወ/ሮ ስንቂ አስፋው ድርሻ ውስጥ ተጠሪዋ ሊያገኙ የሚገባው ግማሹን ብቻ መሆኑ ሊሠመርበት ይገባል፡፡ ይህም ማለት በጋብቻ ወቅት ከአቶ አሰፋ ደሞዝ ለቤቱ እዳ ለባንክ የተከፈለው ገንዘብ እና የመድን ድርጅት ዕዳውን ለመጨረስ የከፈለው የሕይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ ተደምሮ የድምሩ አራተኛ እጅ /25%/ ለተጠሪዋ ተከፍሎ አራተኛው እጅ ደግሞ /25%/ ለ2ኛው አመልካች ሊከፈል ይገባል ብለን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 8460 የካቲት 18 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27682 ጎዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው ብለናል፡፡ ስለዚህ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ ተጠሪዋ በጋብቻው ወቅት ከአቶ አሰፋ መለሰ ደሞዝ ለቤቱ ዕዳ ለባንክ የተከፈለው ገንዘብ እና የመድን ድርጅት እዳውን ለመጨረስ የከፈለው የሕይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ ተደምሮ የድምሩ አንድ አራተኛ /25%/ ይከፈላቸው፡፡ አከራካሪው በወዳ 19 ቀበሌ 55 የሚገኘው ቁጥሩ 223 የሆነው ቤት ግን የአቶ አሠፋ መለሰ የግል ሐብት ነው ብለን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3/ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29899 ጥቅምት 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

4/ ከዚህ ችሎት ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

5/ ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪ በየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ. 23389

ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አክ/ማኅበር - ጠበቃ ኃይሉ አስምር ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- እነ ባህሩ አብርሃም /12 ሰዎች/ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ/ቁ 08449 ላይ በታህሣሥ 27 ቀን 1997 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 37119 ላይ በሕዳር 27 ቀን 1998 ለዋለው ችሎት ብይኑን በማፅናቱ አመልካች የካቲት 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ባቀረበው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች የተፈፀመው የሕግ ስህተት እንዲታረም በመጠየቁ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ የማኅበሩ አባላት በአስተዳዳሪዎች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ ምን እንደሚመስል ለማጣራት ሲል ቅሬታው ለተጠሪዎች ደርሶ ታህሣሥ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ቀርበው በጠበቃቸው አማካይነት የቃል ክርክር አድርጓል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ክስ ሲመሰርቱ ተጠሪዎች የአክስዮን ማኅበር አስተዳዳሪዎች ሆነው ከደንብ ውጪ በአክስዮን ማኅበሩ ከተሰራው ሕንፃ ውስጥ የግንባር ሱቆችን በተደረገው ግልጽ ያልሆነ ስብሰባ ያሳለፉት ውሣኔና የወሰዱት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስተዳደራዊ ውሣኔ ከደንቡ ውጪ ስለሆነ እንዲታገድና እንዲፈርስ የሚል አቤቱታ አቅርበው ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ተጠሪዎችን እንደማይመለከትና እንደማያስከስሳቸው፣ ያስከስሳቸዋል ቢባልም እንኳ በን/ህ/ቁጥር 365/1/ መሠረት በተጠሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚቻለው ማኅበሩ እንጂ አመልካቾች ሊሆኑ እንደማይችሉ በመቃወማቸው ፍ/ቤቱም ክርክራቸውን በመስማት አመልካቾች በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 ሥር የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ሳያሟሉ በተጠሪዎች ላይ ክስ መመሥረት አይችሉም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

በዚህ ችሎትም የታየው መሠረታዊ ጉዳይ አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ በቀጥታ ክስ መመሥረት ይችላሉ ወይ የሚለው የሕግ ጥያቄ ነው፡፡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 364 እስከ 367 በተደነገገው መሠረት የአክስዮን ማኅበር አስተዳዳሪዎች ሀላፊነት ለአክስዮን ማኅበሩ አበዳሪዎች፣ ለአክሲዮን ማኅበሩ ባለድርሻ አባላት ወይም ለሦስተኛ ወገን ሊሆን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ላይ ተጠሪዎች የአመልካቾችን መብት በሚጎዳ መልኩ የሰሩ ስለሆነ ሃላፊነት አለባቸው፣ የሰሩትም ሥራ ሊፈርስ ይገባል የሚል ክስ የቀረበባቸው መሆኑ በሥር ፍ/ቤት መዝገብ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የበታች ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ለማድረግ መሠረት ያደረገው የሕግ አንቀጽ የንግድ ሕጉ ቁጥር 365 ቅድመ ሁኔታዎች አልተሟሉም የሚል ነው፡፡ ሆኖም በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የተመለከተው ማኅበሩ አስተዳዳሪዎችን ለመክሰስ ሲፈልግ ሊያሟላ የሚገባውን ቅድመ ሁኔታዎች እንጂ የተወሰኑ የአክሲዮን ማኅበሩ ባለድርሻዎች የሚያቀርቡትን ክስ አያጠቃልልም፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው አስተዳዳሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚችሉ ወገኖች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በንግድ ሕጉ ለየብቻ የተደነገጉ ስለሆነ እነዚህን ለይቶ በአግባቡ ማየት የግድ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት አሁን በተያዘው ጉዳይ ላይ አመልካቾች የሚሉት በተጠሪዎች የተፈፀመው ተግባር መብታቸውን የሚጎዳ በመሆኑ አስተዳደሪዎችን /ተጠሪዎች/ በቀጥታ መክሰስ

የበታች ፍ/ቤት አንቀጽ 365ን መሠረት አድርጎ መከልከሉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

እኛም ይህንን ሁኔታ ከላይ እንደተመለከተው የተጠያቂነት መሠረቱ ለየብቻ መታየት እንዳለበት የሕጉን ዓላማና መንፈስ መሠረት አድርገን አጽንተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካቾች የአክስዮን ባለድርሻ አባላት በመሆናቸው የአባልነት መብታቸውን በሚጎዳ መልኩ አስተዳዳሪዎች /የአሁን ተጠሪዎች/ መሥራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ ቀጥታ መክሰስ እንደሚችሉ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 367 ይፈቅድላቸዋል፡፡

በመሆኑም አመልካቾች የሚጠበቅባቸው በተጠሪዎች ሥራ አመራርና የውሣኔ እርምጃ ተጎጂ መሆናቸውን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 367 መሠረት ማረጋገጥ እንጂ የበታች ፍ/ቤት እንደተመለከተው በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አይጠበቅባቸውም፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 365 የተወሰኑ የአክስዮን ማኅበሩ አባላት በአስተዳዳሪዎች ላይ የሚያቀርቡትን ክስ የሚመለከት ስላልሆነ የሥር ፍ/ቤት ተገቢ ያልሆነውን የሕግ አንቀጽ መሠረት አድርጎ የአመልካቾችን ክስ መዝጋቱ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08449 የሰጠው ብይን እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37119 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 341/1/ መሠረት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ተመልሶ የፍሬ ነገር ክርክር ውሣኔ እንዲያገኝ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 25306

ጎንደር 12 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን እቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ ገለቴ - ጠበቃ በፀሎት መኮንን ቀረበ፡፡

መልስ ሰጪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፊጅ ታሪኳ ላዕከ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 4 ቀን 1995 ዓ.ም. በአሁኑ መልስ ሰጭ እና በሥር ጣልቃ ገብ በነበሩት በአቶ ሃይደር ከቢር እና በፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት ላይ መስርቶት የነበረው ክስ፣ በመልስ ሰጭ ባንክ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ በሂሣብ ቁጥር 1011 ከነበረው የተንቀሳቃሽ ሂሣቤ ውስጥ ሳይፈረድብኝና በአፈፃፀምም ሳልገደድ ባንኩ ከፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት ታዝዤ ከፍያለሁ በማለት ብር 135,912.08 /አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ብር ከዜሮ ስምንት ሳንቲም/ ወጭ በማድረግ ከፍሏል፡፡ በመጨረሻም ከፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠ የክፍያ ትዕዛዝ የሌለ መሆኑና ባንኩ የከፈለው በተጭበረበረ ሰነድ መሆኑን ገልጨ ያለአግባብ የከፈለውን ገንዘብ ወደ ሂሣቤ እንዲያስገባልኝ ብጠይቅ እምቢተኛ በመሆኑ፣ የሥራ ግዴታውን ባለመወጣት የከፈለውን ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከወለዱና ከወጭና ኪሣራ ጋር እንዲከፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ መልስ ሰጭ በበኩሉ በሰጠው መልስ፣ ክፍያ የፈፀመባቸው ትዕዛዞች የመጡት ከፍርድ ቤት መሆኑንና ማኅተሞቹም ትክክለኛ መሆናቸውን አምኖ የከፈለ መሆኑን ገልፆ ፊርማው የዳኛው ስለመሆኑ የማረጋገጥ ግዴታ የሌለበት መሆን በመግለጽ መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ባንኩ ሐሰተኛ

ነው ተብሎ ሊታወቅ በማይችል የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የከፈለ በመሆኑ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ምክንያት የለም በማለት በነፃ አሰናብቶታል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡

ይህ ችሎት በጥቅምት 30 ቀን 1999 በዋለው ችሎት ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ እንዲሁም የቃል ክርክሩን አሰምቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ በዋነኛነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባው የሕግ ጥያቄ፣ የአሁኑ መልስ ሰጭ በአደራ ተቀብሎ ያስቀመጠውንና ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ብር 135,912.08 ለሌላ ግለሰብ ከፍሎ በመገኘቱ ገንዘቡን ለመመለስ በኃላፊነት አይጠየቅም መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን መመርመር ይሆናል፡፡

በመሠረቱ በአሁኑ አመልካችና በመልስ ሰጭው መካከል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1779 እና በሚቀጥሉት አንቀጾች እንዲሁም ከተያዘው ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ አግባብነት ባለው በንግዱ ሕግ ቁጥር 896 እስከ 902 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት የአደራ ውል ስምምነት ያለ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ የውል ግንኙነት ተቃራኒ የሆነ ስምምነት ከሌለ በቀር አደራ ተቀባዩ ባንክ በተጠየቀ ጊዜ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑ ሳይቀር በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ አስፈላጊ ለሆኑ ስራዎቹ እንዲገለገልበት መብት የሚያገኝ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 896 በግልጽ ደንግጓል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ ተቃራኒ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ አደራ አስቀማጩ በአደራ ተቀባዩ ዘንድ ያስቀመጠውን ገንዘብ በማንኛውም ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ሊያዝበት የሚችል መብት ያለው ስለመሆኑም በዚሁ ንግድ ሕግ ቁ. 898/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአሁኑ መልስ ሰጭ በአደራ የተቀበለውን የአመልካችን ገንዘብ አደራ አስቀማጩ ወይም በሕግ አግባብ ሥልጣን የተሰጠው ክፍል ሳያዘው ገንዘቡን አሳልፎ ለሌላ ከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ለክፍያውም ምክንያቱ የማጭበርበር ተግባር ድርጊት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አቶ ሐይደር ከዲር በተባለ ሰው ተፈፀመ በተባለው የማጭበርበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተግባር የተጭበረበረው የአሁኑ መልስ ሰጪ ባንክ እንጂ የአሁኑ አመልካች አይደለም፡፡ የአሁኑ መልስ ሰጭ ተጭበርብሮ ከሆነ ያጭበረበረውን ሰው በሕግ አግባብ ከሶ ከሚጠይቅ በቀር ተቃራኒ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ የተቀበለውን የአደራ ገንዘብ አደራ አስቀማጩ በተጠየቀ ጊዜ የማይመልስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የማጭበርበር ተግባሩ ሕጋዊ ስርዓቱን ባልተከተለ የፍርድ ቤት ማንተም መሆኑ የአደራ ተቀባዩን ባንክ ኃላፊነትም አይቀንሰውም፡፡ በመጨረሻ በዚህ የማጭበርበር ተግባር ሊጎዳ የሚችል ክፍል ቢኖር በቀጥታ የማጭበርበር ተግባሩ ሰለባ የሆነው መልስ ሰጪ ባንክ እንጂ በምትኩ ያልተጭበረበረው አደራ አስቀማጭ ሊሆን የሚችልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡

በአጠቃላይ ተቃራኒ ስምምነት በሌለ ጊዜ የአደራ ገንዘብ እንደተጠየቀ የሚከፈል ገንዘብ ነው፡፡ አደራ ተቀባዩ ተጭበርብሬ ነው በማለት የሚያነሳው መቃወሚያ ገንዘቡ እንዲከፈል በተጠየ ጊዜ ከመክፈል የሚያግደው አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአደራ ተቀባይና በአደራ አስቀማጩ መካከል የተደረገ ተቃራኒ ስምምነት መኖሩን ሳያረጋግጥ “መልስ ሰጪ ሐሰተኛ ነው ተብሎ ሊታወቅ በማይችል የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የከፈለ በመሆኑ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ምክንያት የለም” በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሐምሌ 30 ቀን 1996 በመ/ቁ. 29968 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት መጋቢት 25 ቀን 1998 ዓ.ም. በመ/ቁ. 33810 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- መልስ ሰጭ ባንክ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 135,912.08 /አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ብር ከዜሮ ስምንት ሣንቲም/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል፤

- አመልካች ለዳኝነት የከፈለውን ገንዘብ መልስ ሰጪ ይተካ፤ የጠበቃ አበል 10% ይክፈል፤ ኪሣራ በቁርጥ ብር 2000 /ሁለት ሺህ/ ለአመልካች ይክፈል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 27161

ኅዳር 12 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን እቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አቶ ኤልያስ ከፈለ - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- እነ አቶ ከድር አህመድ /4 ሰዎች/ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ጥቅምት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ መሰረት ነው፡፡

የጉዳዩን የሥር አመጣጥ የአሁን ተጠሪዎች በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ በቂርቆስ ክ/ከተማ የሚገኘውን የንግድ ቤት ለኑሮአቸው መቋቋሚያ ተፈቅዶላቸው መንቀሳቀሻ ገንዘብ በማጣት ላሁኑ አመልካች ቦታውን ለ4 ዓመት ማከራየታቸውን፣ ውሉ ከተደረገ በኋላ ቦታው የተሰጣቸው ለዘለቄታው ሣይሆን ለ3 ዓመት ብቻ መሆኑን መገንዘባቸውንና በቦታው ላይ ከብረታ ብረት ወርክሾፕ በስተቀር ሌላ ሥራ መሥራት እንደማይችሉ፣ ከዚህ ውጭ ሠርተው ከተገኙ የሊዝ ውሉ የሚሠረዝ መሆኑ በአስተዳደር አካል የተነገራቸው መሆኑን፣ አመልካች ግን ከሊዝ ውሉ ውጭ እየሠሩ ስለሚገኙ በውሉ ለመቀጠል አስቸጋሪ ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ ከክ/ከተማው ጋር ባረደረጉትም ውል ለሌላ ሶስተኛ ወገን ቦታውን አሣልፎ መስጠት የተከለከለ በመሆኑ ባጠቃላይ ውሉ የተሣሣተ ውል ነው ተብሎ እንዲሠረዝ የሚል ነው፡፡ አመልካችም መልስ እንዲሰጡ በተታዘዙበት እለት ባለመቅረባቸው በጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ ከዚህ በኋላ ግራ ቀኙ የቃል ክርክር እንዲያቀርቡ ተደርጎ ፍርድ

ቤቱ አመልካችና ተጠሪዎች ያደረጉት ውል ከሊዝ ውሉ ጋር የማይጣጣም ነው በማለት ውሉን ሠርዞ ግራ ቀኙ ወደየነበሩበት እንዲመለሱ ሲወሰን የከፍተኛው ፍርድ ቤትም በይግባኝ ውሣኔውን አጽንቷል፡፡ አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መነሻነት ሲሆን ፍ/ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ መልስ ሰጪን በማስቀረብ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ክርክራቸውንም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል ከሕዳር 6 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ ለአራት ዓመት ማለትም አስከ ኅዳር 6 ወይም 7 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ የሚዘልቅ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተረድቷል፡፡

በሌላም በኩል ተጠሪዎች ከቂርቆስ ክ/ከተማ ጋር ያደረጉት የሊዝ ውል ለሶስት ዓመታት የሚዘልቅ መሆኑን ተጠሪዎች በክሣቸው ላይ ገልፀዋል ተጠሪዎች ካቀረቡት ክስ በመነሣት ፍርድ ቤቱ ለመገንዘብ የቻለው ጉዳይ በክርክር ሒደት ላይ እያለ የሊዝ ውሉ የጊዜ ገደብ ያበቃ መሆኑን ነው፡፡ የሊዙ የጊዜ ገደብ ካለቀ ደግሞ ተጠሪዎች የነበራቸውን የክስ መሠረት ያጡ ለመሆኑ አጠያያቂነት የለውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 ላይ እንደተመለከተው ክሱ በማንኛውም ደረጃ ባለ ጊዜ የክሱ መሠረት ማክተሙን ፍርድ ቤቱ ከተረዳ ክሱን እንደሚሠርዝ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪዎች ለሶስት ዓመት ከክፍለ ከተማው ጋር ያደረጉት ውል ማብቃቱ የተረጋገጠ ስለሆነና በዚህም ሣቢያ በቦታው ላይ ምንም አይነት መብት ስለሌላቸው፣ በሌላም በኩል አመልካችም በውሉ ከተመለከተው የአራት ዓመት ጊዜ በላይ በቦታው የተጠቀመ ስለሆነ ግራ ቀኙን መብት በሌላቸው ጉዳይ እየተከራከሩ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በመገንዘቡ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ማየት ሣያስፈልግ የሰበር አቤቱታውን ሠርዘናል በተመሣሣይ ሁኔታም ተጠሪዎችን ተጠቃሚ ያደረገው የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔም ከላይ በተመለከተው ምክንያት ከአንግዲህ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

- የሰበር አቤቱታው ተሰርሏል፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና በዚህ ጉዳይ የተጀመረው የአፈፃፀም መዝገብ እንዲዘጋ ታዟል፡፡
- ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁጥር 28923

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማሕበር አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር አልቀረቡም

2ኛ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነገረፈጅ አቶ አዳነ መጋቡ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የአማራ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአማራ ብሔራዊ ክልል የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ፍሬ ጉዳዩም አንደኛ ተጠሪ የአማራ ብሔራዊ ክልል ባወጣው ደንብ መሠረት በ1988 ዓ.ም የቦታ ኪራይ ብር 497,943.54 /አራት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ ሦስት ብር ከሀምሣ አራት ሣንቲም/ እንዲከፍል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ያልከፈለ በመሆኑ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት በአመልካች ላይ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካችም ይህ ዕዳ የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደነበርና ወደ ባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማሕበር ከመቀየሩ በፊት የነበረ ስለሆነ፣ ሁለተኛው ባለዕዳ፣ ሦስተኛ ወገን ተከራካሪ፣ /ተከሣሽ/ ሆኖ ጣልቃ እንዲገባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጠየቁት መሠረት ፍ/ቤቱ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስና አመልካቹና ሁለተኛው ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ የቦታውን ዋና ግብር 454,511.99 /አራት መቶ ሀምሣ አራት ሺ አምስት መቶ አሥራ አንድ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ ሁለተኛ ተጠሪ ብር 56,159.44 /ሀምሣ ስድስት ሺ አንድ መቶ ሀምሣ ዘጠኝ ብር ከአርባ አራት ሣንቲም/ ብቻ እንዲከፍል ቀሪውን ዕዳ አመልካች እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በክሱ ተከሳሽ የሆነው የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማሕበር የተመሰረተው 1992 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ ፋብሪካው ወደ አክስዮን ማሕበርነት ከመለወጡ በፊት የነበረው ዕዳ እኛን የሚመለከት ባለመሆኑና ሁለተኛው ተጠሪ ይህንን ዕዳ የመክፈል ግዴታ በአዋጅ ቁጥር 182/1992 የተጣለበት ሆኖ እያለ አክስዮን ማሕበሩ ዕዳውን እንዲከፍል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበትና አክስዮን ማህበሩን ለኪሣራ የሚዳርግ በመሆኑ በሰበር ይታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ ወደ አክስዮን ማሕበሩ የሚተላለፉና የማይተላለፉ ዕዳዎችን የመወሰን ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መከፈል ያለበት ዕዳ ነው በማለት ያሣወቀን 56,159.44 /ሃምሣ ስድስት ሺ አንድ መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር ከአርባ አራት ሣንቲም/ በመሆኑ ከዚህ ውጭ ያለውን ዕዳ አመልካች መክፈል ይገባዋል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በበኩሉ ዕዳው መከፈል ያለበት ዕዳ መሆኑን ሁለተኛ ተጠሪና አመልካች እንዳልካዱ ገልፆ በሁለቱ መካከል በሚደረገው ክርክር የከተማው አስተዳደር ማግኘት የሚባውን ክፍያ ሣያገኝ ጉዳዩ እየተንተተ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ታይቶ ዕዳውን ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና የአመልካችና ተጠሪዎች በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ያለበት ዕዳና አጠቃላይ እሴቱ እና መንቀሳቀሻ ካፒታሉ ተለይቶ የባህርዳር ጨርቃጨቅ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር ተብሎ በአዲስ መልክ በአክስዮን ማህበርነት ከመደራጀቱ በፊት ለአንደኛ ተጠሪ መክፈል የሚገባውን የቦታ ግብር ዕዳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው መንግሥት አመልካች ድርጅት ወደ አክስዮን ማህበር ከመቀየሩ በፊት የነበሩበትን ዕዳዎች በኃላፊነት የሚረከብ አንድ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ ምክንያት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራ ቦርድን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና በመወሰን ሕግ ያወጣ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 208/1992 መግቢያ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የባለአደራ ቦርዱ መሠረታዊ ዓላማም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደግል ይዞታ በሚዛወርበት ወይም ወደ አክስዮን ማህበር በሚለወጥበት ወይም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት ወደ አክስዮን ማህበሩ ወይም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ የማይተላለፉ ሂሣቦችን መሰብሰብ ዕዳዎችን መረከብና ከዚሁ ጋር የተያያዙ የፍርድ ቤት ጉዳዮችን መከታተል እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የባለአደራ ቦርዱ ወደ አክስዮን ማህበርነት የተቀየሩ ወደ ግል የተዛወሩ ወይም ለቀድሞ ባለቤታቸው የተመለሱ የመንግሥት የልማት ድርጅት ዕዳዎችን ለመንግሥት እያቀረበ እንዲከፈሉ የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ/ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መዝገብ የባህርዳር ከተማ አስተዳደር የጠየቀው የመሬት ኪራይ የባህርዳር ጨርቀጨርቅ ፋብሪካ ወደ አክስዮን ማህበርነት ከመቀየሩ ከአራት ዓመት በፊት የነበረና የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የመንግሥት የልማት ድርጅት በነበረበት 1988 ዓ.ም መክፈል የሚባው ዕዳ ነው፡፡ አሁን ያለው የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር 1992 ዓ.ም ህጋዊ ሰውነት ያገኘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድርጅት በመሆኑ ከጅምሩ በፈረሰውና ወደ አክስዮን ማህበርነት በተቀየረው የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ስም ያቀረበውን ክስ በኃላፊነት ይዞ መከራከር የሚገባው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ ዕዳውን ላለመክፈል የሚያቀርበው ምክንያት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አላሳወቀኝም የሚል ነው፡፡ ሆኖም የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ወደ አክስዮን ማህበርነት ሲቀየር በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያልታወቀና ውሣኔ ያልተሰጠበት ዕዳ ሁሉ ወደ አክስዮን ማህበሩ ይተላለፋል የሚል ግልጽ የህግ ድንጋጌ ካለመኖሩም በላይ የዚህ አይነት የህግ አተረጓጐም አክስዮን ማህበሩን ለከፍተኛ ኪሣራ የሚዳርግና የባለአደራ ቦርዱ የተቋቋመበትን መሠረታዊ ዓላማ ጋር የሚቃረን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም ዕዳው አክስዮን ማህበሩ ከመቋቋሙ በፊት የነበረ እስከሆነ ድረስ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በወቅቱ ያላወቀውና ውሣኔ ያልሰጠበት ዕዳ በአክስዮን ማህበሩ መከፈል ይገባዋል በማለት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 07500 ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ የፍርዱ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
2. የአማራ ክልል የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03792 ሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ የፍርዱ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
3. ሁለተኛው ተጠሪ ብር 454,511.99 /አራት መቶ ሀምሣ አራት ሺ አምስት መቶ አሥራ አንድ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ እና የከፍተኛው ፍርደ ቤት ውሣኔ ከሰጠበት ከሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም

ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት /9%/ ህጋዊ ወለድ ለአንደኛው ተጠሪ ይክፈል ብለናል፡፡

4. አመልካችና ተጠሪዎች ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዋጅ የተወረሱ ቤቶች

የሰ/መ/ቁ. 22297

ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የጅማ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት ተወካይ ቲጃኔ አባቡልጉ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሸዋረገድ አባድር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በወረዳው ፍ/ቤት ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት በጠየቀው ዳኝነት መነሻ አድርጎ ያቀረበው ምክንያት እናቴ በካርታ ቁጥር 928 1392 ካሬ ሜትር በሆነው ቦታ ላይ የቤት ቁጥር 156 የሆነ ቤት አላቸው የእናቴ ወራሽ መሆኔን አረጋግጫለሁ ሆኖም ተከሣሽ የአሁን አመልካች ለሌላ ግለሰብ ስለሸጠብኝ ሁከት ተፈጥሮብኛል የሚለውን ነው፡፡

አመልካችም ይህ በካርታ ቁጥር 928 የተመዘገበው ካርታ የተሰጠው በ1954 ዓ.ም. ነው፡፡ የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ባደረገው አዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ይህ ክስ የቀረበበት ንብረት የተወረሰ ነው፤ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር የወረዳ ፍ/ቤትም በውርስ አግኝቼ የእራሴ ሆኗል በማለት ከሳሽ ይከራከር እንጂ ይህ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ንብረቱ በአዋጅ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

47/67 የተወረሰ ስለሆነ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ወስኗል። ይህም ውሣኔ በከፍተኛው ፍ/ቤት ፀንቷል።

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በይግባኝ ካከራከረ በኋላ የአሁን አመልካች ተወርሷል ይበል እንጂ ስለመወረሱ ማስረጃ አላቀረበም። ንብረቱ በከሳሽ በአሁን ተጠሪ ስም መሆኑን አልካደም የወራሽነት ማስረጃ ቀርቦ እያለ የሥር ፍ/ቤት መልስ ሰጭ የባለቤትነት ማስረጃ የለውም ማለቱ ተገቢ አይደለም ስለሆነም ካርታ እና ፕላን ያለውን ንብረት በሊዝ መሸጡ ተገቢ አይደለም በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል።

የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይኸው የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት አመልካችን አሰናብቷል።

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልን ይገባል በማለት ነው።

ግራ ቀኙም በዚህ ሰበር ችሎት የቃል ክርክር አድርገዋል።

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል። እንደተመለከትነውም ተጠሪ ሁከት ተፈጠረበት በተባለው ንብረት መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን ለማሣየት መሠረት ያደረገው ወራሽ ነኝ በማለት ነው። ንብረቱም የአውራሽ የእናቴ ነው ለማለት ያበቃው በካርታ ቁጥር 928 የተመዘገበውን ካርታ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ካርታ በ1954 ዓ.ም. የተሰጠ ነው በማለት አመልካች ላቀረበው ክርክር ማስተባበያ አላቀረበበትም። ክዶም አልተከራከረም። አመልካች ይህ የንብረቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ሲሆን ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ ግን ተወርሷል በማለት ይህንኑ ሕግ መሠረት አድርጎ ለቀረበው ክርክር ተጠሪ አልተወረሰም በማለት ተከራክሯል። የቤቱ ካርታ የተሰጠበት ጊዜ እና አዋጁ የወጣበት ጊዜ እንደ መነሻ ፍሬ ነገር በመያዝ ንብረቱ የተወረሰ መሆኑን የግምት መነሻ በመስጠት አመልካች ያስረዳ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ይህ ንብረት ያልተወረሰ መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ ማስረጃ

በማቅረብ አላረጋገጠም። ይልቁንም በቃል በተደረገው ክርክር አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲወጣ እኔ እስር ቤት ነበርኩኝ፤ የደርግ መንግሥት በአምባገነንነት በቀበሌ አማካኝነት ለሌሎች ሰዎች በኪራይ ተሰጠብኝ የሚለውን መግለጽ ንብረቱ በእርግጥም የተወረሰ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ስለሆነም ንብረቱ ተወርሷል ወይስ አልተወረሰም የሚለውን ነጥብ በሚመለከት ማን ክርክሩን መጀመርና ማስረዳት እንዳለበት የሚያመለክተውን ድንጋጌ ባለመከተል እና ይህም ሥርዓት ቢዛነፍም እንኳ ከግራ ቀኙ ማን የተሻለ ማስረጃ አቅርቧል የሚለውን ነጥብ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ው ሣ ኔ

1. አመልካች ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የፈፀመው ሁከት የለም ብለናል።
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22312 በሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መ/ቁ. 32640 በህዳር 21 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 348 /1/ መሠረት ተሽሯል።
3. የወረዳው ፍ/ቤት በ/መ/ቁ 532/96 በጥቅምት 18 ቀን 1997 ዓ.ም. እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 05349 በታህሣሥ 21 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 23608

ጎንደር 3 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ

ኤጂንሲ ነ/ፈጁ መስፍን በሻህ

ተጠሪ፡- የአቶ ኑር በዛ ተረጋ ወራሾች

ጠበቃ ስንታየሁ ባህሩ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የአሁን ተጠሪዎች አውራሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻነት ሲሆን የክሱም ይዘት ባጭሩ በወረዳ 18 ቀበሌ 34 ክልል ቁጥራቸው ከ001 -007 የሆኑት ቤቶች ያለአግባብ በመንግሥት የተወሰዱ መሆናቸው ታምኖበት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በኩል እንዲመለስልኝ ተወስኖ በዚሁ ውሣኔ መሠረት ቤቶቹን እንድረከብ ታህሣሥ 3 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ለተከሣሽ (ለአሁን አመልካች) አመልክቼ እንዳለሁ በጎንደር ወር 1991 ዓ.ም አካባቢ በቤቶቹ ውስጥ የነበሩት ተከራዮችን ሲለቁ ከሣሽ ቤቶችን የተረከብኩኝ ቢሆንም ያቀረብኩት አቤቱታ አስቀድሞ ቤቶቹ ሊመለሱልኝ እንደሚገባ ታምኖበት በተወሰነልኝ መሠረት እንዲመለሱልኝ የሚል ሆኖ ሳለ አቤቱታዬን በትክክል ባለመረዳት ለቤቶቹ የቤት ባለቤትነት መብት እንዲሰጠኝ እንዳመለከትኩኝ ቆጥሮ የሚመለሱት ቤቶች በሙሉ ሣይሆን በከፊል ብቻ ነው በማለት በመወሰኑ ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ ይግባኝ ያቀረብኩ

ቢሆንም ቦርዱ የኤጀንሲውን ውሣኔ በመሻር መዝገቡን የዘጋ ስለሆነ የኤጀንሲውም ሆነ የቦርዱ ውሣኔ ከሥልጣናቸው ውጭ ስለሆነ በፍርድ ሊሰረዝልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

የከሣሽ ክስና ማስረጃ ለተከሣሽ (ለአሁን አመልካች) ደርሶ በሰጠው መልስ ከሣሽ በክስ አቤቱታቸው በጠቀሷቸው ቤቶች ትርፍነታቸው ተረጋግጦ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የተወረሱ ንብረቶች ናቸው በመሆኑም በመጀመሪያ የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅ በመቀጠልም የኤጀንሲው ሥራ አመራር ቦርድ ይህን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን እንደሌለው በማለጽ የመጨረሻ ውሣኔ በመስጠት መዝገቡ እንዲዘጋ ወስኗል፡፡ በአዋጁ ቁጥር 110/87 መሠረት ተከሣሽ የሚሰጣቸውን ውሣኔዎች በፍ/ቤት እንደገና ሊታዩ /Review/ እንደሚችሉ የተደነገገ ድንጋጌ ስለሌለ ፍ/ቤቱ ይህንን አቤቱታ ተቀብሎ የማየት ሥልጣን የለውም፡፡ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም ሙሉ መልስ በመስጠት ክሱ ከበቂ ኪሣራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ በተከሣሽ በኩል የፍ/ቤቱን ሥልጣን አስመልክቶ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ አ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት በአንቀጽ 79(1) ላይ የዳኝነት ሥልጣን የፍ/ቤቶች ብቻ እንደሆነ በአንቀጽ 37(1) ላይ ደግሞ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ (Justieable matter) ለፍ/ቤት የማቅረብና ውሣኔ የማግኘት መብት እንዳለው የተደነገገ ከመሆኑም በላይ በአስተዳደር አካላት የተሰጡ ውሣኔዎችን ፍ/ቤቶች እንደገና ለማየት ተፈጥሯዊ /inherent/ የሆነ ሥልጣን ያላቸው ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ተብሎ በተከሣሽ በኩል የቀረበው መቃወሚያ በአግባቡ የቀረበ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ግራ ቀኙ ያደረጉትን ክርክር መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀጽ 4(1) እና አንቀጽ 3(2) መሠረትና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ቁጥር 001/88 አንቀጽ 3(1) እና (2) መሠረት ከአዋጁ ቁጥር 47/67 ውጭ የተወሰዱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረቶች ይመለሱልኝ የሚሉ አቤቱታዎችን እንደዚሁም ከአዋጅ ውጭ በተወረሰ ንብረት ላይ አዋጅ ቁጥር 110/87 ከመጽናቱ በፊት በሌላ አካል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠ ቢሆንም ይህ ውሣኔ እንደገና እንዲመረመር አቤቱታ ሲቀርብ ኤጂንሲው ከዚያም ቦርዱ የማየት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሆኖም በአዋጁና በመመሪያው መሠረት ከእነርሱ በፊት ሌላ የአስተዳደር ባለሥልጣን ከአዋጁ ወጭ የተወረሱ ናቸው የተባሉ ንብረቶች ላይ የሰጠውን የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ ኤጀንሲውም ሆነ ቦርዱ በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉት አቤቱታ ሲቀርብላቸው እንጂ በገዛ ፈቃዳቸውና በእራሣቸው ጊዜ አይደለም በማለት በውሣኔው ላይ አስፍሮ፤ በተያዘው ጉዳይ የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅና የሥራ አመራር ቦርድ ከላይ የተጠቀሱትን የአዋጁንና የመመሪያውን ድንጋጌዎች ጥሰው ከሥልጣናቸው በማለፍ ከሣሽ ቤቶቹን ለመረከብ በተወሰነልኝ መሠረት ርክክቡ ይፈፀምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ያለአግባብ የተወረሱ ቤቶች ይመለስልኝ በማለት አዲስ አቤቱታ ያቀረቡ በማስመሰል ውሣኔ የሰጡ ስለሆነ የኤጂንሲው ሥ/አስኪያጅም ሆነ ቦርዱ ከሥልጣናቸው ውጭ ውሣኔ ስለሰጡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2121 መሠረት ተሰርዟል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን አስመልክቶ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሣይቀበለው የቀረው በአግባቡ እንደሆነና በዚህ ረገድ የቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ነው ካለ በኋላ በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድም ኤጀንሲውም ሆነ የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የሰጡት ውሣኔ ከአዋጁም ሆነ ከመመሪያው አኳያ ሲታይ ከሥልጣናቸው ውጭ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔው ሊሰረዝ እንደሚገባ የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ እንዳልሆነ ነገር ግን የኤጂንሲው ሥራ አስኪያጁ ውሣኔ በቦርዱ ተሽሮ ባለበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ በድጋሚ የኤጀንሲውን

ሥራ አስኪያጅ ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ አይደለም በማለት በዚህ መልኩ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻል አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የፕራይቬታይዜሽን ኤጂንሲ የሰጠው ውሣኔ እንደገና ለማየት ፍ/ቤቶች ተፈጥሯዊ /inherent/ ስልጣን አላቸው በማለት ኤጀንሲው የሰጠውን ውሣኔ የሥር ፍ/ቤቶች በድጋሚ አይተው ውሣኔ መስጠታቸው አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባ በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታውም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የተጠሪዎች አውራሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት /Relief/ ኤጂንሲውም ሆነ ቦርዱ የቀረበላቸው አቤቱታ ከአዋጁ ውጭ የተወሰደ ቤት እንዲመለስልኝ ይወሰንልኝ የሚል ባልሆነበት ሁኔታ ከተጠየቀው ውጭ ሌላ ጭብጥ በመያዝ ውሣኔ የሰጡ ስለሆነ ይሄው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ነው፡፡

ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰዱ ንብረቶች በወጣው አዋጁ ቁጥር 110/87 አንቀጽ 4(1) እና (2) መሠረት ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን የባለቤትነት ሁኔታ የማጣራትና የመወሰን ሥልጣን ለአመልካች የተሰጠ ሲሆን የባለቤትነትን ጥያቄ በሚመለከት ኤጀንሲው በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታውን ለኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ ማቅረብ እንደሚችል በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 5/3/ ላይ ተመልክቷል፡፡

በእርግጥ የተጠሪዎች አውራሽ ታህሣሥ 3 ቀን 1988 ዓ.ም ለአመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ከአወጁ ውጭ የተወሰዱ ስለሆነ ይመለስልኝ በማለት ሣይሆን የቤቶቹ ባለቤትነቱ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አማካይነት ተረጋግጦ ተወስኖልኝ ርክክቡ የዘገየ ስለሆነ ቤቶቹን እንድረከብ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪዎች አውራሽ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች እንዲመለሱልኝ በሌላ አካል ተወስኖልኛል የሚሉ ከሆነ ቀድሞውንም ቢሆን ቤቶቹን ለመረከብ አቤቱታ ማቅረብ የነበረባቸው ለፍ/ቤት እንጂ ለኤጀንሲው አልነበረም፡፡

በሌላ በኩልም ለኤጀንሲው የቀረበው አቤቱታ ይዘቱ ምንም እንኳን የቤቶቹን ርክክብ የሚመለከት ቢሆንም ኤጀንሲው የተቋቋመው ከአዋጁ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶች የባለቤትነት ሁኔታ አጣርቶ ለመወሰን እስከሆነ ድረስ የእነዚህንም ቤቶች የባለቤትነት ሁኔታ ከአዋጁ አኳያ መርምሮ ውሣኔ ቢሰጥ ከሥልጣኑ ውጭ በማለፍ ውሣኔ ሰጥቷል ወደሚል ድምዳሜ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ይልቁንም ኤጀንሲው የተቋቋመበትን አ/ቁ/110/87 ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ቁጥር 001/88 መሠረት አዋጅ ቁ. 110/87 ከመውጣት በፊት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 ውጭ በተወሰደ ንብረት ላይ በሌላ አስተዳደራዊ አካል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ ተሰጥቶ ባለበት ሁኔታም የውሣኔው አግባብነት እንዲመረመር አቤቱታ ሲቀርብ ኤጀንሲውም ሆነ ቦርዱ መርምረው ውሣኔ መስጠት እንደሚችሉ የተመለከተ እንደመሆኑ መጠን የተጠሪዎች አውራሽ በዚህ መልኩ ያቀረቡትን አቤቱታ ኤጀንሲውም ሆነ ቦርዱ መርምረው ውሣኔ መስጠታቸው ከስልጣናቸው ውጭ ነው ሊባል አይችልም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 37/1/ ላይ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡

ከዚህ የሕገመንግሥቱ ድንጋጌ በግልጽ መገንዘብ የሚችለው ፍ/ቤቶች አንድን አቤቱታ ተቀብለው ውሣኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉደይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ ነው፡፡

የተያዘውም ጉዳይ በተጠቀሰው አ/ቁጥር 110/87 መሠረት የዳኝነት ሥልጣኑ በግልጽ ለሌላ አካል ማለትም ለአመልካች የተሰጠ ስለሆነና ኤጀንሲውም በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን ለኤጀንሲው የሥራ

አመራር ቦርድ ማቅረብ እንደሚችልና የቦርዱም ውሣኔ የመጨረሻና አሳሪ /Final and binding/ እንደሆነ በአዋጁ ላይ ስለተመለከተ አቤቱታው ይህንን ሥርዓት ካለፈ በኋላ በኤጀንሲውም ሆነ በቦርዱ የተሰጠው ውሣኔ ከሥልጣን ውጭ ስለሆነ ውሣኔው ሊሰረዝ ይገባል የሚለው የተጠሪዎች አቤቱታ በአንድ በኩል በዚህ መልኩ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ቤት በድጋሚ ለማየት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ /legal frame work/ በሌለበት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ በሌላም በኩል የፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በእኛ አገር ሁኔታ ከሕግ የመነጨ እንጂ ተፈጥሯዊ /inherent/ ባልሆነበት ሁኔታ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የፍ/ቤቱን ሥልጣን አስመልክቶ በቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተመስርቶ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት መመለስ ሲገባው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሣያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 48/93 በመጋቢት 16 ቀን 1994 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 13021 በታህሣሥ 5 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/ለ/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት አቤቱታ የፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 27548

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ሐሩት መለሠ

መድነን ኪሮስ

ዓለ. መሐመድ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፊጅ አሰፋ መኮንን

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ቆጽለ መርሻ

2. ወ/ሮ ፀምረ መርሻ ሻለቃ ገ/መስቀል እንደሻው

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ክርክር የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪዎች ከሣሽ በመሆን በአሁን አመልካችና በስር 2ኛ ተከሣሽ በነበረው በአቶ ከበደ ዋጋሪ ላይ በሐምሌ 12 ቀን 1993 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ክስ፣ በቀድሞው ወረዳ 15 ቀበሌ 28 የቤ/ቁ 360 የሚገኝ በአውራሻችን ስም ቁጥር 14354 የሆነ ካርታ ያለው እና ቁጥር 15/31948 የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የተሠጠበትን ቤት የአሁኑ አመልካች ለ2ኛው ተከሣሽ እያከራየ በመጠቀም ላይ በመሆኑ ተከሣሾቹ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡን እና የአሁን አመልካች ከ2ኛ ተከሣሽ የተቀበለውን ኪራይ የመጠየቅ መብታችን ተጠብቆ ይወሠንልን ሲሉ ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች በታህሣሥ 9 ቀን 1994 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ ለቤቱ ተከራይ /ለስር 2ኛ ተከሣሽ/ ቤቱን እንዲለቅ ደብዳቤ ጽፈን ለማስረከብ በሂደት ላይ ሣለን የወረዳ 15 ቀበሌ 28 መ/ጽ/ቤት በዓፈው ደብዳቤ መሠረት በተደረገው ማጣራት የቤቱ ባለንብረት የነበሩት አቶ መርሻ ሀ/ማርያም በትርፍነት ያስረከቡት በመሆኑ የደብተሩ አግባብነት ተመርምሮ ውጤቱ ካልተገለፀልን በቀር ለማስረከብ አለመቻላችንን ለስራና ከተማ ልማት ቢሮ ጽፈን የደብተሩን መሠረዝ በመጠባበቅ ላይ ነን ስለዚህ ከበቂ ኪሣራ ጋር መዝገቡ ይዘጋልን ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር 2ኛ ተከሣሽም የበኩሉን መልስ ሰጥቷል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም በሰኔ 3 ቀን 1997 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ተከሣሾች ገና ለገና የደብተሩን ጽኑነት እያጣራን ነው ከማለት ውጭ ደብተሩ ዋጋ የሌለው እንደሆነ ወይም የተሠረዘ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረቡም በሌላ በኩል ከሣሾች በ1986 ዓ.ም. በተሠጣቸው የባለቤትነት ደብተርና በቤቱ ላይ ያላቸውን የባለቤትነት መብት ከተከሣሾች ይልቅ በተሻለ ሁኔታ ያስረዱ ስለሆነ ተከሣሾች ለከሣሾች ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል ብሎ የወሰነ ሲሆን የከሣሾቹን የኪራይ ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04279 በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች በግንቦት 29 ቀን 1999 ዓ.ም. አሻሽለው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የስር ከሣሾች የአሁን ተጠሪዎች በወራሽነት ይገባናል የሚሉት ቤት በአ/ቁ. 47/67 አንቀጽ 13/1/ እና /2/ መሠረት በትርፍነት በመንግሥት ተወርሶ በአመልካች እስከ አሁን ድረስ የሚተዳደር መሆኑን እና በቁጥር 15/31948 ተመዝግቦ የተሠጠው የቤት ባለቤትነት ደብተር ሕግን የሚቃረን መሆኑን በበቂ ሁኔታ አስረድተን እያለ የስር ፍ/ቤቶች ቤቱን ለተጠሪዎች አስረክቡ ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል ሲሉ አቤት ብለዋል፡፡ ይህም ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ተወርሷል እየተባለ ቤቱን ለተጠሪዎች አስረክብ መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት መዝገቡን ለሠበር ችሎት በማስቀረብ ተጠሪዎቹ የጽሁፍ መልሣቸውን እንዲሠጡ አድርጓል፡፡ አመልካቹም ለተጠሪዎች መልስ የመልስ መልሱን አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ይህም ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሠረቱ አግባብ ካለው አካል /አስተዳደር ክፍል/ የተጠሰ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ባለደብተሩ የማይንቀሣቀሰው ንብረት ባለሐብት ለመሆኑ የሕሊና ግምት የሚያስወስድ ለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195/1/ ላይ እንደመርህ ተደንግጎ ይገኛል። ሆኖም ይህ ደብተር የተሰጠው ከደንብ ውጪ በሆነ አሰራር መሆኑን የሚረጋገጥበት ሁኔተ ካለ ይህ የህሊና ግምት ፈራሽ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196/1/ ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል በተያዘው ጉዳይ ላይም የየካ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የክርክሩ መንስኤ በሆነው ቤት ላይ በሚያዝያ 14 ቀን 1986 ዓ.ም. ለተጠሪዎች የከተማ ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር መስጠቱ ታውቋል። የሆነው ሆኖ ይኸው የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ለተጠሪዎች ሰጥቷቸው የነበረው ቁጥር 15/31948 የሆነው የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የተሠጠው አለአግባብ እና በአዋጅ በተወረሰ የመንግሥት ቤት ላይ መሆኑን አረጋግጦ በቁጥር የሳ10/30/78841/99 በተፃፈ ደብዳቤ የተጠሪዎቹ የባለቤትነት መብት ከግንቦት 9 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ቀሪ መሆኑን ለተጠሪዎች ጭምር ማሣወቁን ለመገንዘብ ተችሏል። በመሆኑም አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ቤቱን ለማስረከብ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የሚመለከታቸው አካላት ተጠሪዎች የያዙት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አጠራጣሪ በመሆኑ አግባብነቱ በመጣራት ላይ መሆኑ በተገለፀለት መሠረት ቤቱን ለተጠሪዎቹ ለማስረከብ እንደማይችል ገልፆ እየተከራከረ የስር ፍ/ቤቶች በደብተሩ ላይ የተያዘውን የምርመራ ውጤት ሣይጠብቁ ወይም ደግሞ ደብተሩን የሰጠውን አካል ማብራሪያ ሣይጠይቅ በደፈናው ደብተር አልተሠረዘም በሚል ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲመልስ ውሣኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

1/ የስር ፍ/ቤቶች አጠራጣሪ በሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ላይ ተመርኩዘው አመልካች በወረዳ 15 ቀበሌ 28 የቤት ቁ. 360 የሚገኘው ቤት ለተጠሪዎች ይመለስ ሲሉ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል። ይፃፍ።

2/ አመልካች ክርክር የተነሣበትን ቤት ለመመለስ አይገደድም ብለናል።

3/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04279 በሰኔ 3 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።

4/ የፌ/ክ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41022 በጥቅምት 24 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 29822

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

መድነን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተደደር ጽ/ቤት ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- እነ ወ/ሮ በቀለች አማረብህ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሾች ወ/ሮ በቀለች አማረብህ፣ አቶ በላይነህ ወንድ አፍራሽ በራሳቸውና በሞግዚት አድራጊዎቻቸው ስም፣ ተከሣሾች ደግሞ የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ፣ አቶ ገብሬ ኃይሌ እና የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት ናቸው፡፡ የክሱ አመጣጥ በተመለከተም ከሣሾች ሐምሌ 20 ቀን 1993 ዓ.ም. በተፃፈ የክስ ማመልከቻ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 6 ቀበሌ 02 ቁጥር 159-160 የሆነውን የግል መኖሪያ ቤት የአንደኛ ከሣሽ እና የአቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ የግል ቤት ሲሆን ቤቱን አቶ ወንድአፍራሽ በትርፍነት ያላስረከቡት እና በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 11 መሠረት ለአንድ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ የተፈቀደ ነው፡፡ ቤቱ እንደተወረሰ በማስመሰል ቁጥር 159 በሚል በቀበሌ ቢመዘገብም በአግባቡ ተጣርቶ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ተሰቶት በእጃችን ይገኛል፡፡ አቶ ወንድአፍራሽ በመሞታቸውም የ1ኛ ከሣሽ ሚስትነት እና የሌሎቹ ከሣሾች ወራሽነት ተረጋግጧል፡፡ በአዋጁ መሠረት የተፈቀደልንን መብት ሶስተኛ ተከሣሽ ሊያስረክበን ሲገባ ለሁለተኛ ተከሣሽ አከራይቶት እየኖሩበት ይገኛሉ፡፡ ሁለተኛ ተከሣሽ ከሣሾችን ለመጉዳት ተነሳስተው ቁጥሩ 159 በሆነው ቤት ላይ የተሰጠው ደብተር እንዲመለስ የሚል ደብዳቤ አጽፈዋል፡፡ አንደኛ ተከሣሽም

ይህንን የቀላጤ ደብዳቤ በጥቅምት 23 ቀን 1985 ዓ.ም. ጽፏል፡፡ አንደኛ ተከሣሽ እንደ ይግባኝ ሰሚ ሆኖ የሰጠው ደብተር በቀላጤ መሻር አይችልም፡፡ ትዕዛዙም ደብተሩ መሠረዙን አይገልጽም፡፡ ስለዚህ ትዕዛዙ ሕገወጥ ነው፡፡ በሌላ በኩል በትዕዛዙ ላይ ስማቸው የተገለፀው አቶ ሽዋአለም ሃ/ማርያም የቤት ቁጥር 159 ባለቤት ስላልሆኑ እና ለማስረከብም የተሰጣቸው ውክልና ስለሌለ ትዕዛዙ ሕጋዊነት የለውም፡፡ ስለዚህ ደብተሩ እንዲመለስ በቀላጤ ያለአግባብ የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲሰረዝ እና ወጪና ኪሣራ እንዲከፈለን እንዲወሰንልን በማለት ክስ መስርተዋል፡፡

አንደኛ ተከሣሽ በታህሣሥ 10 ቀን 1994 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ ከሳሾች ቁጥሩ 159 የሆነው ቤት ባለቤት አልነበሩም፤ አይደሉምም፡፡ ቤቱ የተወረሰው ከአቶ ሽዋዓለም ኃይለማርያም ነው፡፡ ከሣሾች ያስረከቡት እና የተወረሰባቸው ቤት አይደለም፡፡ ደብተር የወሰዱትም ያለአግባብ ነው፡፡ ደብተሩን የወሰዱት ያለአግባብ መሆኑ በተደረሰበት ጊዜም ተመላሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አንደኛ ተከሣሽ በአዋጅ ቁጥር 41/85 አንቀጽ 8፣ በአዋጅ ቁጥር 7/86 አንቀጽ 32/1/ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት በከተማው ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ቤቶችን የመቆጣጠር ሥልጣን አለው፡፡ በዚህ ሥልጣኑ መሠረት የሰጠው ማስረጃ ከደንብ ውጪ ሆኖ ሲገኝ ፈራሽ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196 ላይ ተደንግጓል፡፡ ደብተሩ እንዲመለስ ማስገደድም ይችላል፡፡ ይህንን ማድረጉም ሕጋዊ መሆኑን ከሚያመለክት በስተቀር ክስ እንዲቀርብበት የሚያደርግ አይደለም፡፡ ስለዚህ ጥያቄው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ሁለተኛ ተከሣሽም በታህሣሥ 10 ቀን 1994 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ ከሣሽ ያለአግባብ የቤት ባለቤትነት ደብተር ያወጡ መሆኑን በመረዳት አንደኛ ተከሣሽ ደብተሩ እንዲመለስ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ከሣሾች የራሳቸው ባልሆነ ንብረት አሳስተው የወሰዱት ደብተር ውድቅ እንዲሆን የተወሰነ በመሆኑ የመክሰስ መብት የላቸውም፡፡ ይህ ከታለፈ ደግሞ ተከሣሽ ቤቱን ከአቶ ሽዋለም ሃ/ማርያም ተከራይቼ ስጠቀም አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲታወጅ በአዋጁ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኪራይ ፎርም ሞልቼ ኪራዩን ለመንግሥት እየከፈልኩኝ ሳለ አውራሻችን የሚሉዋቸው አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ በማሳሳት የቤት ባለቤትነት ደብተር ማውጣታቸውን በመስማቴ ባደረግኩት ጥቆማ ቤታቸው አለመሆኑ ተረጋግጦ ደብተሩ ተሰርዟል፡፡ ስለዚህ ክሱ ውድቅ ሊሆን የሚጋባው ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሶስተኛ ተከሣሽ ደግሞ በየካቲት 21 ቀን 1994 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ በአዋጅ ቁጥር 87/89 መሠረት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው የከተማ ነክ ፍ/ቤት ነው፡፡ ቤቱ መንግሥት የያዘው ትርፍ ቤት በመሆኑና የሚያስረክብ ሰውም በመታጣቱ ምክንያት ነው፡፡ ቤቱ ትርፍ መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻለውም በጊዜው በምን ሁኔታ ላይ እንደነበረ በመመልከት ነው፡፡ በወቅቱ ቤቱን በሚመለከት የተገኘው ሰነድ ቅጽ ዐዐዐ ሲሆን የቤቱ ባለቤት ማለት አከራይ የነበሩት አቶ ሸዋለም ሃ/ማርያም መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ከሣሾች ቁጥሩ 160 የሆነውን ቤት አያያዛቸው አጠያያቂ ሆኖ ሳለ በትርፍነት መንግሥት በወረሰው ቤት ላይ /ቁጥር 159/ የባለቤትነት ደብተር ሲያወጡ ተጣርቶ ደብተሩ እንዲመለስ ተወስኖባቸዋል፡፡ ከሣሾች የእነሱ ባልሆነ ቤት ላይ ደብተር ሊያወጡ እና ባለቤት ነን ሊሉ አይችሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

በሌላ በኩል አንደኛ ተከሣሽ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ በተከሣሽ ከሣሽነት ክሱም ቁጥሩ 159 የሆነው ቤት በትርፍነት ተወርሶ አቶ ሸዋለም ሃ/ማርያም ያስረከቡት መሆኑ ታውቆ የወሰዱትን ደብተር እንዲመልሱ በከሣሾች አውራሽ ላይ የተወሰነ ቢሆንም ስላልመለሱ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩን እንዲመልሱ ይወስንልን በማለት ጠይቋል፡፡

ከሣሾች ደግሞ ለቀረበባቸው የተከሳሽ ከሣሽነት ክስ በሰጡት መልስ አቶ ሸዋለም ሃ/ማርያም በወቅቱ የቤቱ ተከራይ እንጂ ባለቤት ስላለሆኑ ቤት ለማስረከብ ወይም ለማስወረስ የሚያስችል መብት የላቸውም፡፡ የተከሣሽ ከሣሽ ደብተሩ እንዲመለስ በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ስለሌለው ጥያቄው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ቤቱ በትርፍነት በቅጽ ዐዐዐ ላይ ከመመዝገቡ በስተቀር የተወረሰ ለመሆኑ የሚያሳይ በቅጽ ዐዐ3 የተሞላ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ቤቱ ቀደም ብሎ የአቶ ይፍሩ አማረብህ መሆኑንና አቶ ወንዳፍራሽ ገመዳ እንደገዙት አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመዉጣቱ በፊት ቤቱን አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ ያከራዩት እንደነበር ቤቱ በአዋጁ መሠረት ያለወመረሱን አቶ ሸዋለም ሃ/ማርያም ተከራይ እንጂ የቤቱ ባለቤት ያለመሆናቸውን ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም ቤቱ የተወረሰ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ በተከሳሾች ያልቀረበ ስለሆነ ተከሣሾች ቤቱን ለከሣሾች እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

የተከሳሽ ከሣሽ ያቀረበውን ክስም ውድቅ አድርጎታል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ ተመልክቶ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አመልካች በሆነው የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት የቀረበው አቤቱታም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ቤቱ የተጠሪዎች አይደለም ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው የከተማ ነክ ፍ/ቤት ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹ ክሱን ያዩት ሥልጣን ሳይኖራቸው ነው፡፡ በወረዳ 6 ቀበሌ 02 የሚገኘው ቁጥሩ 159 የሆነውን ቤት ያስረከቡት አቶ ሸዋለም ሃ/ማርያም ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ተወርሷል፡፡ አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ በቤቱ ላይ የቤት ባለቤትነት ደብተር ያወጡት በሌላቸው መብትና ከደንብ ውጭ ነው፡፡ የባለቤትነት ደብተሩ የተወሰደው ከደንብ ውጪ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196/1/ መሠረት በአስተዳደራዊ ውሣኔ ተሰርዟል፡፡ የቤት ባለቤትነት ደብተሩ በዚህ ሁኔታ መሠረዙም በአግባቡ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክሱ የቤት ባለቤትነት ደብተሩን እንድንመልስ የተሰጠው ትዕዛዝ ይሻርልኝ የሚል ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቶች ተከሣሾች ቤቱን ለከሣሾች እንዲያስረክቡ በማለት የሰጡት ውሣኔ ክስ ያልቀረበበትን ጭብጥ በመያዝ በመሆኑ ውሣኔው ሥነ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባው በመሆኑ ውሣኔው እንዲሻርልኝ ሲል አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች ደግሞ በሰጡት መልስ አመልካች በሥር ፍ/ቤት በማስረጃነት ያቀረበው ሰነድ የቤቶቹ መመዝገቢያ ቅጽ የሆነው ቅጽ ዐዐዐ እንጂ ቤቱ የተወረሰ ለመሆኑ የሚያሳይ ቅጽ ዐዐ3 አይደለም፡፡ ቤቱ የግል መሆኑ ታውቆ የቤት ባለቤትነት ደብተር ተሰጥቷል፡፡ ክርክሩ የግል ቤት የተመለከተ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ሥልጣኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ ክሱም የቀረበው የቤት ባለቤትነት ደብተሩን እንድንመልስ የተሰጠውን ትዕዛዝ ለማሰረዝና ቤቱን ለማስለቀቅ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሚነቀፍበት አንዳችም የሕግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ውሣኔው ፀንቶ ልንሰናበት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ በወረዳ 6 ቀበሌ ዐ2 የሚገኘውን ቁጥሩ 159 የሆነውን ቤት በሚመለከት የወሰዱት የቤት ባለቤትነት ደብተር እንዲመልሱ በማለት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ቤት ውሣኔ መሻር የሚገባው ነው ወይስ አይደለም? ቤቱ ለተጠሪዎች ሊመለስላቸው ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳው ቤት የአውራሻቸው የአቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ መሆኑን ለማስረዳት የሞከሩት በሰው ማስረጃ ሲሆን ያቀረቡዋቸው ምስክሮችም አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ቤቱን ከአቶ ይፍሩ አማረብህ የገዙት መሆኑን ነው የገለጹት፡፡ ሌሎች ሁለት ምስክሮች ደግሞ የገለጹት ቤቱ አቶ ሽዋለም ሃ/ማርያም በኪራይ ይኖሩበት እንደነበሩ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ተጠሪዎች ቤቱ የአውራሻቸው ስለመሆኑ የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡

አመልካች ደግሞ ቤቱን በትርፍነት ያስመዘገቡትና ለመንግሥት ያስረከቡት አቶ ሽዋአለም ሃ/ማርያም በመሆናቸው ቤቱ የአቶ ወንድአፍራሽ

ገመዳ አይደለም በማለት ይህን እንዲያስረዱለት ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የሆነው ቅጽ ዐዐዐ ቤቱ የአቶ ሽዋለም ሃ/ማርያም መሆኑን ነው የሚገልፀው፡፡

በሌላ በኩል የተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ ሌሎች ቤቶቻቸውን በትርፍነት ሲያስመዘግቡ መርጠው ከውርስ ያስቀሩት ቁጥሩ 160 የሆነውን ቤት ስለመሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በትርፍነት አስመዝግበው ለመንግሥት ያስረከቡዋቸው ቤቶች ቁጥር 149፣ 150፣ 151፣ 161፣ እና 162 ሲሆኑ ቁጥሩ 159 የሆነው ክርክር ያስነሳው ቤት ደግሞ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ሌላ ሰው የተከራየው ኪራይ ቀመስ ሆኖ መቆየቱንና አዋጁ ከወጣ በኋላም በኪራይ ቤትነት የቀጠለ ስለመሆኑ ክርክሩ ያስረዳል፡፡ የተጠሪዎች አውራሽ ሌሎቹ ቤቶቻቸውን በትርፍነት ሲያስረክቡ ቁጥሩ 159 የሆኑውን ቤት መርጠው ያስቀሩት ስለመሆኑ ወይም ደግሞ በትርፍነት ለመንግሥት ያስረከቡት መሆኑን የሚልጽ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች ለመገንዘብ የሚቻለውም የተጠሪዎች አውራሽ ቤቱን በምርጫ ያላስቀሩት ወይም ደግሞ በትርፍነት ለመንግሥት ያላስረከብኩት በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት ያልነበራቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የከተማ ትርፍ ቤትና ቦታ የመንግሥት በሆነበት ጊዜ የተጠሪዎች አውራሽ ቤቱን በምርጫ ሳያስቀሩት ወይም ደግሞ በትርፍነት ሳያስመዘግቡትና ለመንግሥት ሳያስረክቡት በአቶ ሽዋለም ሃ/ማርያም አማካኝነት በትርፍነት ተመዝግቦ መንግሥት ተረክቦት በባለቤትነት ሲያስተዳድረው ለአመታት ከቆየ በኋላ በምርጫ ካስቀሩት ቁጥሩ 160 ከሆነው ቤት ጋር በማያያዝ የቤት ባለቤትነት ደብተር ያወጡበት የቤት ባለቤትነት መብት ሳይኖራቸው መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ባጋጠመበት ጊዜ የአስተዳደር ክፍሉ ቀደም ሲል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት የሰጠውን የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196/ሀ/ መሠረት ለማስመለስና ለመሰረዝ እንደሚችል በሕግ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ ተጠሪዎች የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቤት ባለቤትነት ደብተሩ እንዲመለስ በማለት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ቤት እንዲሻርልን በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የባለቤትነት ደብተሩ ለአስተዳደር ክፍሉ መመለስ የለበትም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ የተጠሪዎች አውራሽ ቤቱን በምርጫ ከውርስ ያስቀሩት ወይም ደግሞ በትርፍነት የተመዘገበና መንግሥት የልወረሰው መሆኑን ባላስረዱበት ይልቁንም ቤቱን በትርፍነት ያስመዘገቡትና ለመንግሥት ያስረከቡት አቶ የሸዋአለም ሃ/ማርያም መሆናቸው በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ቤቱ የተጠሪዎች አውራሽ በመሆኑ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች የሚያስረክቡበት ምክንያት የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ ስንመለከትም ተጠሪዎች የአስተዳደር ክፍሉ የቤት ባለቤትነት ደብተሩን እንድንመልስ የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሰረዝልን በማለት ያቀረቡትን ክስ መነሻ በማድረግ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲመልስ በማለት ፍ/ቤቶቹ መወሰናቸው በአግባቡ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ቤቱን የመረከብ ጥያቄ በተጠሪዎች ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አልቀረበም፡፡ በጭብጥነትም ተይዞ ግራ ቀኙ አልተከራከሩበትም፡፡ ዳኝነት ባልተከፈለበት፣ በክሱ በግልጽ ባልተጠየቀና በጭብጥነት ተይዞም ግራ ቀኙ ባልተከራከሩበት ነጥብ ላይ ውሣኔ መስጠት ስለማይቻልም የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04258 የካቲት 17 ቀን 1998 ዓ.ም. የፌ/ከ/ፍ/ቤት ደግሞ በመ/ቁ. 46860 የካቲት 21 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ቀደም ብሎ የወጣው የቤት ባለቤትነት ደብተር የተሰጠው ከደንብ ውጪ ሆኖ ካገኘው ደብተሩን

የማስመለስና የመሰረዝ ስልጣን ያለው በመሆኑና ተጠሪዎች በዚህ ጉዳይ ቅሬታ ካላቸው ደረጃውን ተከትለው በአስተዳደር ክፍሉ እንዲጣራላቸው ከሚያደርጉ በስተቀር ደብተሩን እንዲመልሱ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ቤት ውሣኔ የሚሻርበት ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡

3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን እንዲችሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 29860

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

መድህን ኪሮስ

ዓለ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስናቀች ሲሻው ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ አሰለፈች ከተማ ቀረቡ

2. ወ/ሮ የሺመቤት አየነው ቀረቡ

3. ወ/ሮ ደብረወርቅ አየነው

4. ወ/ሮ ብዙየ አየነው

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 32110 ግንቦት 9 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 22931 ጥር 21 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ሚያዝያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በመጠየቃቸው ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይ በዚህ መዝገብ ተጠሪ የሆኑት ሰዎች አንደኛ ተጠሪ የሚች ፊታውራሪ አየነው ገብረመድህን ሚስት ከሁለተኛ እስከ ሶስተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች ደግሞ ልጆች መሆናቸውን በመግለጽ ሚች ፊታውራሪ አየነው ገብረመድህን ለወ/ሮ ወለተኪዳን በህይወት እስካሉ ድረስ ብቻ እንዲኖሩበት መስከረም 22 ቀን 1960 ዓ.ም ባደረጉት የስጦታ ውል በወረዳ 11 ቀበሌ 2 የቤት ቁጥር 631 የሆነውን ቤት ሰጥተዋቸው ነበር፡፡ ወ/ሮ ወለተኪዳን በህይወት በመኖራቸው በዚሁ ቤት

ውስጥ ሲኖሩ ቆይተው የሞቱ ስለሆነ ቤቱን ያስረክቡን ብለው አመልካችን በመክሰሳቸው ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር የሰማው የሥር ፍርድ ቤት ለተጠሪዎች ቤቱን ማስረከብ አለባችሁ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይግባኝ ብለው በፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኙ ከተሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሮታል፡፡ ተጠሪዎች ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች በዚህ ፍርድ ቤት ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ አዋጅ ቁጥር 47/67 እና የፍትሐብሔር ህጉ የንብረት ድንጋጌዎችና እና የይርጋ ድንጋጌዎችን ስላላቸው ተፈፃሚነት የቃልና የጽሑፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ወ/ሮ ወለተኪዳን ቤቱን ከያዙት በኋላ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ንብረት ለማድረግ አዋጅ ቁጥር 47/1967 ታውጇል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/3/ሀ/ መሠረት ትርፍ ቤት ማለት አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ለመኖሪያ ከሚያስፈልገው ወይም ከያዘው አንድ መኖሪያ ቤት ውጪ ያለ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሚች ፊታውራሪ አየነው ለወ/ሮ ወለተኪዳን በቤቱ የመጠቀም መብት ብቻ በውል ያስተላለፉ በመሆናቸው አዋጁ ሲታወጅ በወረዳ 11 ቀበሌ 2 የቤት ቁጥር 631 እና በወረዳ 11 ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 634 ባለቤት እንደሆኑ ከህጉ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሚች ፊታውራሪ አየነው የቤት ቁጥር 634 በምርጫ ይዘዋል፡፡ ይህ ከሆነ ወ/ሮ ወለተ ኪዳን ይኖሩበት የነበረው ቁጥሩ 631 የሆነው ቤት በአዋጁ አንቀጽ 2/3/ሀ/ መሠረት ትርፍ ቤት ነበር፡፡ ፊታውራሪ አየነው ይህንን የመጠቀም መብት ለወ/ሮ ወለተኪዳን በውል ያስተላለፉትን ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አዋጁ በታወጀ በሰላሣ ቀን ውስጥ ማስመዝገብና ማሣወቅ ሲገባቸው በዚህ የህግ ድንጋጌ መሠረት ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡ ሆኖም ፊታውራሪ አየነው ቤቱን በአዋጁ አንቀጽ 13 ንዑስ 2

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት አለማግኘቃቸው የቤቱ ባለቤት ይዘው ለመቆየት የሚያስችላቸው አይደለም፡፡ ምክንያቱም በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማዘጋጃ ቤት ወይም በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ ትርፍ ቤት ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ የመንግስት ንብረት እንደሆነ በግልጽ ስለሚደነግግ ነው፡፡ በመሆኑም የቤት ቁጥር 631 አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ ትርፍ ቤት የነበረ በመሆኑ ከነሐሴ 1 ቀን 1967 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመንግስት ንብረት ሆኗል፡፡ ስለሆነም ፊታውራሪ አየነው ከነሐሴ 1 ቀን 1967 ዓ.ም ጀምሮ በፊት በነበረው ስያሜ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 11 ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 631 ላይ የነበራቸው የባለቤትነት መብት በህግ ተቋርጧል፡፡ ይህ ከሆነ የተጠሪዎቹ መብት በሚች ፊታውራሪ አየነው መሞት ምክንያት የማይቋረጡ መብትና ግዴታዎች ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ይህም በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሚች ፊታውራሪ አየነው ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ የባለቤትነት መብት የሌላቸውና በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ መንግስት የዞረ ስለሆነ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ ወ/ሮ ወለተኪዳን ከያዙት ከሠላሳ ዓመት በኋላ የይገባኛል ጥያቄ የማቅረብ መብት የላቸውም የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንፃር በመመልከት ተጠሪዎችን በቤቱ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችላችሁ በቂ ምክንያት የለም ብለው ማሰናበት ሲገባቸው ጉዳዩን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1168 አንፃር ብቻ በመመልከት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የቤቱ ባለቤት ሆነዋል ወይስ አልሆኑም የሚለውን ነጥብ የወሰኑት የቤቱ ባለቤት ፊታውራሪ አየነው እንደሆኑ በመቁጠር ነው፡፡ ነገር ግን ከነሐሴ 1 ቀን 1967 ዓ.ም. ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የባለቤትነት መብታቸው በህግ ለመንግስት የተላለፈ በመሆኑ በፍርሐብሔር ህግ ቁጥር 1168 መሠረት ወ/ሮ ወለተኪዳን የቤቱ ባለቤት

መሆን አይችሉም የሚለውን መከራከሪያ ለማንሳትና አመልካችን ለመሚገት የሚችለው የሚመለከተው የመንግስት አካል እንጂ ተጠሪዎች አይደሉም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የክርክሩን መሠረታዊ ጭብጥ ወደ ጐን በመተውና የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን ለመንግስት ለማድረግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 47/1967 ድንጋጌዎች ሳያገናዘቡ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 32110 ግንቦት 9 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 22931 ጥር 21 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 32110 ህዳር 1 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31490

ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

መድህን ኪሮስ

ዓለ መሐመድ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- ሴርኮ እስራኤላዊያን - ጠበቃ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ ከሣሽ በመሆን በአመልካቹ ላይ ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ.ም ያቀረበው ክስ፣ የአሁን አመልካች ቤቱን ያለሕግ አግባብ ይዞ በመቆየቱ ከመጋቢት 9 ቀን 1971 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 9 ቀን 1994 ዓ.ም ላለው ጊዜ ያጣሁትን ጥቅም እና የደረሰብኝን ጉዳት ብር 363,931/ሦስት መቶ ስልሳ ሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ አንድ/ ከወጪና ኪሣራ ጋር ይክፈለኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ቀርቦ በሰጠው መልስ የተለያዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያቀረበ ሲሆን ከመቃወሚያዎቹም አንዱ በአዋጅ ቁ.193/92 አንቀጽ 2/3/ መሰረት ከአዋጅ ውጭ የተወረሱ ቤቶች በመንግስት እጅ በቆዩበት ጊዜ ለታጣ ገቢ ክፍያ መጠየቅ ስለማይቻል ክሱ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የቀረበውን መቃወሚያ ከግንዛቤ በማስገባት በሰጠው ውሣኔ ቤቱ በመንግስት እጅ የቆየው ከአዋጅ ውጭ ተወስዶ በመሆኑ አዋጅ ቁ.193/92 በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ስለዚህ ወደ ፍሬ ጉዳይ

ክርክሩ መግባት ሣያስፈልግ የተጠሪውን ክስ ውድቅ አድርጌዋለሁ በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ተጠሪው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አሰምተዋል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤትም አመልካችን አስቀርቦ ግራ ቀኙን በማከራከር መዝገቡን መርምሮ በሰጠው ውሣኔ የክፍያው ጥያቄ ከዋጅ ቁ. 193/92 አኳያ ተቀባይነት የለውም ተብሎ በስር ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ቢቀርብም የዚህ አይነቱ መቃወሚያ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 244 ስር ያልተሸፈነና የፍሬ ጉዳይ ክርክር ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ እስከሰጠበት ድረስ በቁጥር 341 መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት የሚመልሰው ሆኖ አልተገኘም፣ በሌላ በኩል አመልካቹ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ፍ/ቤቱ ብይን ሣይሰጥ በዚሁ ነጥብ ላይ ተመስርቶ በሰጠው ፍርድ አመልካቹን ረቺ ቢያደረግም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ባለመስጠቱ አመልካች መስቀለኛ ይግባኝ ያላቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በራሱ አስተያየት ሊመለከተው የሚችል ሆኖ አልተገኘም በሚል አመልካቹ አላግባብ ለበለፀገበት ብር 62,970 /ስልሣ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ/ ከተለያዩ ወጪና ኪሣራ ጭምር ለተጠሪው እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካቹ ይግባኙቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ፈጽመዋል በማለት አመልካቹ ለዚህ ችሎት ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ይህም ችሎት የአመልካቹን አቤቱታ መሰረት በማድረግ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ካቀረባቸው የመልስ መቃወሚያዎች ውስጥ አንዱ ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ ውድቅ ቢደረግለትም መስቀለኛ ይግባኝ ካላቀረበ በስተቀር በቀሪዎቹ ነጥቦች ላይ የቀረበው ክርክር ሊታይለት አይገባም የመባሉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብነት ለማጣራት ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙን አከራክሯል። መዝገቡንም አግባበነት ካላቸው ህጐች አንፃር መርምረናል።

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ለቀረበበት ክስ በስር ፍ/ቤት ቀርቦ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ያላቸውን አምስት ነጥቦችን እና መቃወሚያዎቹ ቢታለፉ በሚል ደግሞ ለክሱ ዝርዝር መልሱን አቅርቧል። የመ/ደ/ፍ/ቤቱም በሰጠው ውሣኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከተባሉት ነጥቦች አንዱን መርምሮ፣ ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክር መግባት ሣያስፈልግ ክሱን ውድቅ አድርጌዋልሁ በማለት ወስኗል። ይህ ከሆነ ደግሞ ፍ/ቤቱ አመልካቹ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሲል ያቀረበውን ነጥብ እንደመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነቱ ተቀብሎ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አግባብ ቀሪ መቃወሚያዎችንና የፍሬ ጉዳይ ክርክሮችን ሣይመረምር ክሱን ውድቅ ማድረጉን ለመገንዘብ ተችሏል። በማንኛውም ቀመር የክሱ ውድቅ መደረግ አመልካችን ተጠቃሚ ወይም ረቺ የሚያደርግ እንደመሆኑ አመልካቹ ቀሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች እና የፍሬ ጉዳይ ክርክሮች ሊመረመሩ ይገባ ነበር ሲል ይግባኝ እንዲል የሚጠበቅበት አይሆንም።

በሌላ በኩል ደግሞ የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካቹ ይግባኝ ሊጠይቅ ሲችል አልጠየቀም በሚል የአመልካች መቃወሚያ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አይደለም ለዚህ ጉዳይም አግባብነት የለውም በማለት አመልካቹ ሌሎቹን መከራከሪያዎች እንዳመነ ያህል ሌሎቹን መቃወሚያዎችና የፍሬ ነገር ክርክሮች ሣይመረመር ውሣኔ መስጠቱ የአመልካቹን ፍትህ የማግኘት መብት በእጅጉ የሚያጣብብ ሆኖ ተገኝቷል። በእርግጥ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የቀረበው መቃወሚያ ከፍ/ብ/ስ/ህ/ቁ. 244 አንፃር አግባብነት የለውም ማለቱ የሚነቀፍ ባይሆንም፣ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ለማድረግ የተከተለው አካሄድ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት ሲያገኝ በሚፈፀመው አግባብ ከመሆኑ አንፃር ሌሎች በፍ/ቤቱ ያልተመረመሩ መቃወሚያዎችና መከራከሪያዎች መኖራቸው ግልጽ ነው። ይህ በሆነበት ሁኔታ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ መቃወሚያው በማንኛውም ምክንያት ውድቅ ሲደረግ እንደሚፈፀመው ሁሉ

በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341 መሰረት ቀሪ መቃወሚያዎችንና መከራከሪያዎችን መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን ወደ ስር ፍ/ቤት ሊመልሰው ሲገባ አመልካቹ ይግባኝ አልጠየቁምና ቀሪ መከራከራያዎቻቸው አይታዩም ሲል ውሣኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል። የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም ሲል ይግባኙን መሰረዙ በተመሣሣይ ሁኔታ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1) የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39329 ሚያዝያ 14 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ብይን ውድቅ መደረጉን ተገንዝቦ የቀሩትን መቃወሚያዎችና መከራከሪያዎች መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341 መሰረት ይመለስለት ብለናል።
2) የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40110 በግንቦት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል። ይፃፍ።
3) የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27255 መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል። ይፃፍ።
4) ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ። መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31682

መጋቢት 12 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሐሩት መለሠ

መድህን ኪሮስ

ዓለ. መሐመድ

አመልካች፡- አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ

ተጠሪዎች፡- 1. ዘላለም ይልማ ባልቻ

2. መሠረት ይልማ ባልቻ

3. አዳሙ ይልማ ባልቻ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የዚህ ክርክር መነሻ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከወረዳ 5 ቀበሌ 23 አስተዳደር እና አቶ ፈይሣ ቦንሣ ከተባሉት ግለሰብ ጋር ባደረጉት ክርክር በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ቁጥራቸው 308 እና 309 የሆኑትን ቤቶች በአ/ቁ. 47/67 መሠረት መወረሣቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ቤቶቹ ለተጠሪዎቹ ይመለሱ ሲል የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ይህ ተከራካሪ ባልሆንኩበት የተሠጠው ውሣኔ እንዲነሣ ሲሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358ን ጠቅሰው በመቃወም ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልክተዋል፡፡ አመልካቹ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሐምሌ 17 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፈው ያቀረቡት ማመልከቻ ይዘት ሲጠቃለል ቁጥሩ 309 የሆነው ቤት በአ/ቁ. 47/67 መሠረት በትርፍነት የተወረሠ ሲሆን አመልካቹ በአ/ቁ/2/1995 አንቀጽ 46/1/ መሠረት ቤቱን እንዲያስተዳድር ስልጣን ተሠጥቶታል በመሆኑም ተጠሪዎች /የስር ከሣሾች/ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ባላቀረቡበት ሁኔታ ቤቱን እንዲረከቡ የተሰጠው ውሣኔ መብቴን የሚጎዳ በመሆኑ ሊነሣ ይገባዋል የሚል ነው፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የአመልካቹን ተቃውሞ እና የተጠሪዎቹን መልስ መርምሮ

በጥቅምት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ. 21594 በሰጠው ፍርድ በመቃወም አመልካች ቁጥሩ 309 የሆነውን ቤት ለማስተዳደር መብት ያለው መሆኑን ያላስረዳ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በጥር 15 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ሊነሣ የሚገባ ሆኖ አላገኘውም ሲል ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኙት አመልካች አቤቱታቸውን በይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካቹም የስር ፍ/ቤቶች ተቃውሞውን ውድቅ ማድረጋቸው አ/ቁ. 47/67ን በሚገባ ያልመረመረና ያላገናዘበ በመሆኑ ቁጥር 309 የሆነው ቤት ለተጠሪዎች እንዲመለስ የተሠጠው ውሣኔ በውሣኔ እንዲሻር ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሐምሌ 2 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ጠይቀዋል፡፡ ይህም ችሎት የአመልካቹን የሠበር አቤቱታ መርምሮ ክርክር የተነሣበት ቤት በአ/ቁ 47/67 መሠረት ለመወረሱ ማስረጃ አልቀረበም በሚል ቤቱ ለተጠሪዎች እንዲመለስ መወሰኑ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲል ተጠሪዎችን አስቀርቧል፡፡ የሰበር ተጠሪዎችም ለአመልካች አቤቱታ በሐምሌ 30 ቀን 1993 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቹም አቤቱታውን በመልስ መልሱ አጠናክሮ ቀርቧል፡፡

ይህም ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና የሥር ፍ/ቤት ውሣኔዎችን በጥሞና መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም ከሁሉ አስቀድሞ ምላሽ የሚሻው ጭብጥ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቀድሞውንስ ቢሆን በዚህ ጉዳይ የቀረበለትን ክስ ተቀብሎ የማከራከር ስልጣን ነበረው ወይ? የሚለውን ነጥብ መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በወረዳ 5 ቀበሌ 23 አስተዳደር ጽ/ቤት እና በአቶ ፈይሣ ቦንሣ ላይ ያቀረቡት ክስ ተከሣሾቹ በአ/ቁ. 47/67 ያልተወሰነበትን ቁጥራቸው 308 እና 309 የሆኑት ቤቶች አላግባብ ስለያዙብን ለቀው እንዲያስረክቡን የሚል ነበር፡፡ የአሁኑ የሰበር አመልካችም ሆነ በስር ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረው የቀድሞው ወረዳ 5 ቀበሌ 23 ጽ/ቤት ለክርክሩ መንስኤ የሆኑት ቤቶች በአ/ቁ. 47/67 ተወርሰው የሚያስተዳድሯቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆናቸውን በመግለጽ ተከራክረው የነበረ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ቤቶቹ ስለመወረሣቸው የሚያረጋግጥ ተገቢው ቅጽ አልቀረበም በሚል ቤቶቹ ለአሁን ተጠሪዎች እንዲመለስ በማለት ወስኗል፡፡ በመሠረቱ አዋጅ ቁጥር 47/67ን መነሻ አድርጎ አላግባብ የምርጫ ቤቱ ተወስዷል በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን አዋጁን ለማስፈጸም ለተቋቋመው የሚኒስቴር መ/ቤት በኩል እየተመረመሩ ተገቢውን ውሣኔ ማግኘት ያለባቸው ስለመሆኑ በአዋጁ ተመልክቷል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የምርጫ ቤቱን በቀላጤ፣ በቃል ትዕዛዝ ወይም በመመሪያ ከሕግ ውጭ ተወሰደብኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ለኢትዮጵያ ፕሪይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርበው መወሰን እንደሚገባቸው በሕጉ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ክፍሎች የሚሰጡ የባለቤትነት ማስረጃዎችን መሠረት አድርገው በሚቀርቡ የባለሃብትነት ጥያቄዎች ላይ ፍ/ቤቶች እንደነገሩ ሁኔታ ስልጣን ከሚኖራቸው በቀር ተወርሰዋል ተብለው በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሠረት አድርገው ፍ/ቤቶች የቤቱን መወረስና አለመወረስ ለማረጋገጥ ማስረጃዎች መርምረው የሚደርሱባቸው መደምደሚያዎች ለፍ/ቤቶች በሕግ ያልተሰጣቸው ስልጣን ከመሆኑም ባሻገር የአስፈፃሚ አካላቱን ስልጣንና ተግባር በግልጽ የሚቃረን ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ክርክር በተነሣባቸው ቤቶች ላይ ከአስፈፃሚ አካላቱ የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ባላቀረቡበት ሁኔታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች በአ/ቁ. 47/67 መሠረት ትርፍ ናቸው ተብለው ለመወረሣቸው መቅረብ ይገባው የነበረው ቅጽ 003 በወረዳ 5 ቀበሌ 23 ጽ/ቤትም ሆነ በአሁኑ አመልካች አልቀረበም በሚል ቤቶቹ አልተወረሱም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች አግባብ ካላቸው አስፈፃሚ አካላት የባለቤትነት ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ በሕግ ባልተሰጠው ስልጣን ቤቶቹ በአ/ቁ. 47/67 ተወርሠዋል ወይስ አልተወረሱም የሚለውን ነጥብ መርምሮ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡
2. ይህ ውሣኔ ተጠሪዎች በቤቶቹ ላይ አለን የሚሉትን መብት አግባብ ላለው አካል አቅርበው ከመጠየቅ አያግዳቸውም፡፡
3. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በጥር 15 ቀን 1998 ዓ.ም. በመ/ቁ 21594 የሰጠው ውሣኔ የቤት ቁጥር 309 በተመለከተ ብቻ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በጥቅምት 13 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ 21594 ቁጥር 309ን በተመለከተ ብቻ የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
5. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ. 50128 ቁጥር 309ን በተመለከተ ብቻ የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32376

ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃደር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት አልቀረቡም

ተጠሪ- እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሸዋንግዛው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪዎች በአመልካችና በሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት ክስ ከወላጅ አባታችን በውርስ የተላለፈልንን በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቀበሌ 10 ክልል የሚገኝ ቤታችንን 1ኛ ተከሳሽ ከአዋጅ 47/67 ውጭ ያለአግባብ በመያዝ ለ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በመከራየት ላይ ስለሚገኝ ይህንኑ ያለ አግባብ ይዘው የሚገኙትን ቤታችንን ለቀው እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ቀርቦ በሰጠው መልስ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች በአዋጅ 47/67 መሰረት የተወረሱ ወይንም ያልተወረሱ ለመሆናቸው የሚጠቁም ማስረጃ በ1983 ዓ.ም በመዘረፉ ምክንያት ማቅረብ አልቻልንም፡፡ በአሁኑ ሰአት ይህ ክስ መመስረቱ አግባብነት የሌውና ተከራዮችን የሚጐዳ ነው፡፡ ጉዳዩም መታየት ያለበት በፍ/ቤት ሳይሆን በÝራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በኩል ስለሆነ መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችም በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ ከሳሾች ቁጥራቸው 204(1) እና 204/2/ የሆኑት ቤቶች ሊመለሱልን ይገባል በማለት

ቀደም ሲል ለወረዳ 27 ፍ/ቤት ክስ አቅረበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ Ýራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ በድጋሚ ለፍ/ቤቱ ክሱ መቅረቡ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 አኳያ ተቀባይነት ስለሌለው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩ አስቀድሞ ውሳኔ ያገኘ ነው ተብሎ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የወረዳ 27 ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ Ýራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ከማለት በስተቀር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን ተመልክቶ ውሳኔ ያልሰጠ በመሆኑ ክርክሩ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 ሥር ስለማይወድቅ በዚህ ረገድ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አግባብነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ከዚህም ሌላ 1ኛ ተከሳሽ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ሳይሆን የኢትዮጵያ Ýራይቬታይዜሽን ነው በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ አስመልክቶም በአዋጅ 110/87 መሰረት ለኤጀንሲው ሥልጣን የተሰጠው በቃል ትእዛዝ፣ በቀላጤ ወይንም በመመሪያ አንድ ንብረት ተወስዶ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ ስለተመለከተና ከሳሾች በዚህ መንገድ ቤቱ ተወስዶብኛል ያላሉ ስለሆነ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡

ከዚህ በኋላም በፍሬ ጉዳይ ረገድ የተደረገውን ክርክር ከማስረጃው ጋር አገናዝቦ መርምሮ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች የተወረሱ ስለመሆናቸው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ 1ኛ ተከሳሽ ከ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል በማቋረጥ ለከሳሾች ቤቱቹን እንዲያስረክቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመከተው የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 ሊጠቅስ የሚገባው አንድ የክስ ምክንያት በተከራካሪ ወገኖች ወይም ከእነዚህ ወገኖች ጥቅም የሚያገኙ 3ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገኖች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ በተመሳሳይ የክስ ምክንያት ክስ በሚቀርብበት ጊዜ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የቀድሞ ወረዳ 27 ፍ/ቤት የቤት ይለቀቅልኝ ክርክሩን ለማየት ሥልጣን ያለው ሌላ አካል ስለሆነ ጉዳዩን አላስተናግድም በማለት በብይን መዝገቡን በመዝጋቱ በቀረበው የክስ ምክንያት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ካለመስጠቱም በላይ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/ረ/ መሰረት የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የከተማው አስተዳደር ከያዛቸው ቤቶች ጋር የሚቀርቡ ክሶችን ለማከራከር የሥረ ነገር ስልጣን ያለው በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ ባለመቀበል ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የሰበር አቤቱታ ቀርቦለት መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅርቱ ተጠሪዎች ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የሰበር አቤቱታውም ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ነክ መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበው ከአዋጅ ውጭ የተወሰደን ንብረት ባለቤትነት አጣርቶ ለመመለስ በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሰረት ሥልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ ኢራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው በማለት ሲሆን ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን ሳይቀበለው የቀረው ለኤጀንሲው ሥልጣን የተሰጠው ንብረቱ በቃል ትእዛዝ በመመሪያ ወይንም በቀላጤ ተወስዶ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ

በአዋጁ ላይ ስለተመለከተና ከሳሾች በዚህ መንገድ ክስ የቀረበበት ቤት ተወሰደብን ያላሉ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ሥልጣን አለው በማለት ነው፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤት የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን አለው ያለው የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት እንዳለው ክስ የቀረበበት ቤት በቀላጤ፣ በመመሪያ ወይንም በቃል ትእዛዝ ተወስዷል ስላልተባለ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው በማለት ሳይሆን የከተማው አስተዳደር ከያዛቸው ቤቶች ጋር የሚቀርቡ ክሶችን ለማከራከር የሥረ ነገር ሥልጣን ያለው የአ/አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 ላይ የተመለከተ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ሥልጣን አለው በሚል ነው፡፡

ይሁንና ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በቀላጤ፣ በቃል ትእዛዝ ወይንም በመመሪያ ተወስዶብናል ያላሉ በመሆኑ በአ/ቁ. 110/87 መሰረት ጉዳዩ በኢትዮጵያ ኢራይቬታይዜሽን በኩል የሚታይ አይደለም መባሉ ተገቢነት የነበረው ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/ረ/ ስር ለከተማ ነክ ፍ/ቤት ሥልጣን የተሰጠው የአ/አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ጉዳዮችን በተመለከተ ስለሆነና ይህም ባለቤትነቱ የከተማው አስተዳዳር ስለመሆኑ ክርክር ሳይኖርበት ከባለቤትነት በመለስ የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ እንደሆነ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በተያው ጉዳይ ተጠሪዎች ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት በውርስ የተላለፈልን የግል ቤታችን ነው በማለት ባለቤተነትን የመፋለም ክስ /petitory action/ ያቀረቡ በመሆኑና በቤቱ ባለቤትነት ላይም ክርክር እስከቀረበበት ድረስ ከተጠቀሰው የአዋጁ ድንጋጌ አኳያ የከተማ ነክ ፍ/ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን ሊኖረው የማይችል በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የከተማ ነክ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው በማለት ተመልክተው ውሳኔ መስጠታቸው ለአዋጁ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት እንደሆነ መረዳት የተቻለ ስለሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአ.አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00148 በታህሣሥ 24 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሰኔ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03006 በጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 04058 በግንቦት 8 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአ.አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዘገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 34249

በሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ - ወራሽ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- እነ አቶ አለሙ ወንድሙ - ጠበቃ አቢይ ወርቁ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በአመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ በወረዳ 7 ቀበሌ 32 ቁጥር 074 የሆነውን ቤት ከአዋጅ 47/67 በፊት የሰራነው ሲሆን በአዋጁም አልተወረሰም፡፡ በዚሁ ቤት በስማችን የንግድ ፈቃድ አውጥተን በኃይለስላሴ ጊዜ ተከሣሾችን በግል ድርጅታችን እንዲሰሩ አስጠግተናቸው ነገር ግን እንዲለቁ ተጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆኑ እንዲለቁ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሾችም ቀርበው ክስ የቀረበበት ቤት በአዋጁ ተወርሶ የአከራይ ተከራይ ግንኙነታችን ተቋርጧል፡፡ ኪራይም ለቤቱ ባለቤት ለቀበሌው አስተዳደር እየከፈልን ስለሆነ ከሣሾች ቤቱ ይለቀቅልን በማለት ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትን የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር የቀረበበትን ቤት ማኅደር አስቀርቦ በመመልከት ቤቱ የተወረሰ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ተከሳሾች ይህንኑ ክስ የቀረበበትን ቤት ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በኋላም ጉዳዩ በይግባኝና በሰበር ለከተማው ፍ/ቤት ቀርቦ ቤቱ ሊመለስ ይገባል ተብሎ በበታች ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ይህ ችሎት በቅድሚያ የተመለከተው የክርክሩን አመራር በተመለከተ ነው፡፡

የሥር ከሳሾች የአሁን ተጠሪዎች ዳኝነት የጠየቁት የግል የሆነ ቤታችን በሥር ተከሳሾች በአሁን አመልካቾች ያለአግባብ የተያዘብን ስለሆነ እንዲመለስልን ይወሰንልን በማለት ነው፡፡

ተከሳሾችም በበኩላቸው ቤቱ በመንግሥት በመወረሱ ምክንያት ከከሣሾች ጋር የነበራቸው የኪራይ ውል ተቋርጦ ከቤቱ ባለቤት ከቀበሌው አስተዳደር ጋር የኪራይ ውል በመዋዋል ኪራይ እንደሚከፍሉ ገልፀው ክሱ ሊሰረዝ ይገባዋል ብለዋል፡፡

ከሳሾች በአንድ በኩል የቤቱ ባለቤት ነን የሚሉ ከሆነና በሌላ በኩልም ቤቱ በአዋጅ በመንግሥት ተወርሷል ከተባለ ክርክሩ ባለቤትነትን የመፋለም /Petitory action/ ስለሚሆን ቤቱን በውርስ ይዞ በማስተዳደር ላይ ይገኛል የተባለው የቀበሌው አስተዳደር ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ ወገን /Indispensable Party/ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ወገን በሌለበት የሚሰጥ ውሣኔ መብቱን፣ ጥቅሙን ሊነካ እንደሚችል ስለሚታመን ነው፡፡ ይህ ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ወገን በከሳሾች በኩል በተከሳሽነት እንዲጣመር ባይደረግም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 40/2/ ላይ ለፍርድ ቤቱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ማድረግ ነበረበት፡፡

ስለሆነም በየደረጃው ባሉ የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ እልባት የተሰጠው ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ የሆነው የቀበሌው አስተዳደር የክርክሩ ተካፋይ ባልሆነበት ሁኔታ ስለሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደ/ፍ/ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና ሰበር ችሎት በዚህ ጉዳይ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የሚመለከተው የቀበሌ አስተዳደር ለጉዳዩ እጅግ አስፈላጊ ወገን /indispensable party/ ስለሆነ የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ይህንኑ ወገን ወደ ክርክሩ በማስገባት አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ክሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እርቅ ግልግል

የሰ/መ/ቁ. 22857

ታህሣሥ 15 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- እነ አቶ ተክሌ ደግፌ /2 ሰዎች/ የ2ኛ አመልካች ወራሽ ቀረበ፡፡

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ በፍቃዱ ኃይሌ /2 ሰዎች/ - ጠ/ዳንኤል ቀረበ፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት የፍርድ ባለመብቶች ሲሆኑ 1ኛ አመልካች ደግሞ የፍርድ ባለእዳ ነበሩ፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተያዘው አፈፃፀም የፍርድ ባለዕደ የሆኑት የአሁኑ 1ኛ አመልካች ቤት የፍርድ ባለመብቶቹ እንዲረከቡት የተሰጠውን ትዕዛዝ የአሁኑ 2ኛ አመልካች ተቃውመው ቀርበዋል፡፡ 2ኛ አመልካች ቤቱን ከውሣኔ በኋላ የገዙት መሆኑን ገልፀው አፈፃፀሙ እንዲቋረጥ ጠይቀዋል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ 2ኛ አመልካች ቤቱን የገዙት ከውሣኔ በኋላ ከመሆኑም ሌላ የሽያጩን ውል ያደረጉት ከፍ/ባለዕዳው ጋር እንጂ ከፍርድ ባለመብቶች ጋር ባለመሆኑ ጥያቄያቸው ተቀባይነት የለውም በማለት አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ላይ አመልካቾች ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል ሠርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች በቅሬታቸው ላይ ነሐሴ 13 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ የእርቅ ስምምነት፣ 2ኛ አመልካች በ1ኛ አመልካች ስም ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) ለ1ኛ ተጠሪ በራሣቸውና በ2ኛዋ ተጠሪ ስም ፈርመው ገንዘብ ተቀብለው ታርቀው በዚሁ እርቅ ስምምነት መሠረት አፈፃፀሙ እንዲቋረጥ ለፍ/ቤቱ የቀረበውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄ ፍ/ቤቱ ያለምንም ምክንያት ውድቅ በማድረግ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ማድረጉ ስህተት ነው በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩ በእርቅ ማለቁ ለፍ/ቤት ቀርቦ እያለ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል መደረጉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪዎች ቀርበው መልሣቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ በመልሳቸውም 1ኛ ተጠሪ ስምምነቱን የፈረሙት በሸማግሌዎች ከፍተኛ ተጽኖ እና ጫና እንጂ በነፃ ፈቃዳቸው ካለመሆኑም በላይ ከ2ኛ ተጠሪ የተሰጣቸው ውክልና ሣይኖር በመሆኑ በፍርዱ መሠረት እንዲፈጽሙ መደረጉ ስህተት የለውም ብለዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት በ1ኛ አመልካችና በተጠሪዎች መካከል በነበረው ክርክር ተጠሪዎች የ1ኛ አመልካችን ቤት እንዲረከቡ ተወስኖላቸው እንደነበር፣ ከውሣኔው በኋላ 1ኛ አመልካች ይህንኑ ቤት ለ2ኛ አመልካች መሸጣቸውን፣ ተጠሪዎች ይህንን ቤት ለመረከብ በአፈፃፀም ላይ እያሉ ደግሞ አመልካቾችና ተጠሪዎች ነሐሴ 13 ቀን 1996 በተደረገ የዕርቅ ስምምነት ጉዳያቸውን ለመጨረስ መስማማታቸውን ተረድተናል፡፡

ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት በፍ/ቤት የጀመሩትን ክርክር በፍርድ ሂደት ከመቋጨት ይልቅ በእርቅ ስምምነት ለመጨረስ ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ ክርክሩ በማናቸውም ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በፍ/ቤት ወይም ከፍ/ቤት ውጪ በዕርቅ ወይም በግልግል ጉዳያቸውን ጨርሠው በፍ/ቤት የጀመሩትን ክርክር ለማቋረጥ እንደሚችሉም ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 274/1/ እና 275/1/ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍ/ቤቱም ይህን የዕርቅ ስምምነት በጽሁፍ ሲቀርብለት ዕርቁ ለሕግ ወይም ለሞራል የማይቃረን መሆኑን እስካረጋገጠ ድረስ ስምምነቱን ተቀብሎ በፍርድ ቤት የተያዘውን ጉዳይ ማቋረጥ እንደሚገባው ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277/1/ ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ በራሣቸውና በ2ኛ ተጠሪ ባለቤታቸው ስም ሆነው የእርቁን ስምምነት መፈረማቸውን አልካዱም፡፡ የሚያነሱት ክርክር

ስምምነቱን በተጽኖ ነው የፈረምኩት ከ2ኛ ተጠሪም የተሠጠኝ የውክልና ስልጣን አልነበረም የሚል ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ ውሉን ከነፃ ፍላጎታቸው ውጪ በሆነ ሁኔታ እንደፈረሙ ይግለፁ እንጂ በዚህ ሁኔታ ለመፈረማቸው ያስረዱት ነገር ካለመኖሩም ሌላ ውሉ እንዲሠረዝላቸው አላደረጉም፡፡ በመሆኑም በዚህም ምክንያት በስምምነቱ መሠረት ሊፈፀም አይገባም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ከአመልካቾች አቤቱታ 1ኛ አመልካች ከተጠሪዎች በወሰዱት ብድር ምክንያት እዳው ካልተከፈለ ለዕዳው በመያዣ የተያዘው ቤት ተጠሪዎች እንዲረከቡት መወሰኑን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን ተጠሪዎች ቤቱን በመያዣ የያዙበት እዳ ተከፍሏቸው ቤቱን ለመልቀቅ ተስማምተዋል፡፡ ነሐሴ 13 ቀን 1996 ዓ.ም. ግራ ቀኙ ካደረጉት ስምምነትም ተጠሪዎች ይህ ስምምነት ከመደረጉ በፊት የወሰዱት ገንዘብ ስላነሣቸው ተጨማሪ ገንዘብ እንዲሠጣቸው ያቀረቡትን ጥያቄ አመልካቾች ተስማምተውበት ተጨማሪ ገንዘብ ለተጠሪዎች መክፈሉን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ቤቱን በመያዣ የያዙበት ዕዳ ከተከፈላቸው በኋላ በድጋሚ ቤቱን ለመረከብ አፈፃፀሙ ሊቀጥል ይገባል በማለት የቀረቡት ክርክር ከቅን ልቦና ውጪ ከመሆኑም በላይ ለአንድ ዕዳ ሁለት ጊዜ ክፍያ እንዲፈፀምላቸውና አላግባብ እንዲበለጽጉ የሚያደርግ ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ቢሆን ግራ ቀኙ ያቀረቡት ለእርቅ ስምምነት ለሕግ ወይም ለሞራል ተቃራኒ መሆን አለመሆኑን መርምሮ ካልሆነ እርቁን በመመዝገብ አፈፃፀሙን ማቋረጥ ሲገባው በውሣኔው መሠረት ቤቱን ተጠራዎች እንዲረከቡ ትዕዛዝ መስጠቱ የእርቅ ስምምነት ጉዳይን ስለመጨረስ የሚደነግጉትን የሥነ ስርዓት ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ በመ/ቁ 05393 ጎዳር 7 ቀን 1998 ዓ.ም. የሠጠው ትዕዛዝ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43087 በታህሳሥ 11 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ ነሐሴ 13 ቀን 1996 ዓ.ም. ያደረጉት ስምምነት ሕግና ሞራልን የማይቃረን በመሆኑ በእርቁ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 277 የተመዘገበ በመሆኑ የተጀመረው አፈፃፀም ተቋርጦ በዕርቁ መሠረት እንዲፈጸም ታዟል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 25912

ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

መድኅን ኪሮስ

ዓለ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የአቶ ብሩ ቆርቾ ወራሽ ብርቅነሽ ብሩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ክፍሌ ሐብደታ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00808 ጳጉሜ 4 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26283 ሰኔ 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪው አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 25 ቀበሌ 01 ቁጥሩ 292 የሆነውን ቤት ብር 4500 /አራት ሺ አምስት መቶ ብር/ የሸጡልኝ ስለሆነ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ጉዳዩ ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም ባደረጉት ዕርቅና ግልግል ያለቀ ስለሆነ ቤቱን ያስረክቡኝ የሚለው ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ አመልካች ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም በተስማሙት መሠረት የተቀበሉትን የቤቱን ዋጋ ብር 760 /ሰባት መቶ ስልሣ ብር/ እና የገደብ መቀጫ ብር 2000 /ሁለት ሺ ብር/ ለተጠሪ አሟልተው ያልከፈሉ ስለሆነ በቤት ሽያጭ ውሉ መሰረት ቤቱን እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከፍተኛው ፍርድ ቤትም በይግባኝ የሚያስቀርብ ነጥብ የለውም በማለት ዘግቶታል። አመልካች ይኸ ውሣኔ ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረግነውን ስምምነት ወደ ጐን በመተው የተወሰነ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪው በበኩል አመልካቹ በዕርቁ ውል መሰረት ያልፈፀመ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረነዋል። መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካችና ተጠሪው ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም የግልግል ውል ያደረጉ መሆኑ አልተካደም። አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የግልግል ስምምነት አመልካች ከተጠሪው የተቀበለውን ብር 760 /ሰባት መቶ ስልሣ ብር/ እና የቤት ሽያጭ ውሉ በመቅረቱ መቀጫ ብር 2000 /ሁለት ሺ ብር/ ሲከፍል ተጠሪው ደግሞ አመልካች ቤቱን ያስረክበኝ የሚለውን ክስ ለመተው የተስማሙ መሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሣያል።

ይህ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የተደረገው የግልግል ስምምነት በመጀመሪያ የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል የማስቀረት ውጤት እንደሚኖረው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3308 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል። ይህም በመሆኑ ተጠሪው እና አመልካች ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረጉት የግልግል ስምምነት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3312 ድንጋጌዎች መሠረት እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር በመሆኑ ይኸው በግልግል ውላቸው ላይ የተስማሙበት ጉዳይ ማለትም አመልካች በስምምነታቸው መሠረት ብር 2760 / ሁለት ሺ ሰባት መቶ ስልሣ ብር/ እንዲከፍል ከሚጠይቁ በስተቀር ቤቱን ሸጦልኛልና ያስረክበኝ በማለት በግልግል ውል ቀሪ የሆነውን ጉዳይ የማንቀሣቀስ እና የመጠየቅ መብት የላቸውም። ስለሆነም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በቤት ሽያጭ ውሉ መሰረት ቤቱን ለተጠሪው እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተገለፁትን የሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል።

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00808 ጳግሜ 4 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል። ይፃፍ።
2. የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26283 ሰኔ 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል ይፃፍ።
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል።

ይህ ፍርድ ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 29386

የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ወለላ ተሰማ - ጠበቃ ሽፈራው አመኑ

ተጠሪ፡- እማሆይ በላይነሽ መለሠ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት አቤቱታ ሟች ልጇ እመቤት ለገሠ ከሟች አባቷ አቶ ለገሠ ቢነግዴ በውርስ ማግኘት የሚገባትን ንብረት ተጠሪ ይዘው ስለሚገኙ በዓይነት እንዲያካፍሉኝ የማያካፍሉኝ ከሆነም ንብረቶቹ ተሸጠው ድርሻ ገንዘቤን እንዲሰጡኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም የአሁን አመልካች ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱት ክርክርም የሟች እመቤት ለገሠ አውራሽ አቶ ለገሠ ቢነግዴ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ከ27 ዓመት በፊት በመሆኑ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ መሠረት በይርጋ የሚታገድ ነው፡፡ ሟች እመቤት ለገሠ በሕይወት በነበረችበት ጊዜ የሟች አባቷን የአቶ ለገሠ ቢነግዴን የውርስ ንብረት ክፍፍልን በሚመለከት በስምምነት ለመካፈል ባቀረበችው ጥያቄ መሠረት ሽማግሌዎች ንብረት ለይተውና አጣርተው ድርሻዋን ወስዳለች፡፡ በዚህ ዓይነት በግልግል ያለቀ ጉዳይ ይግባኝ ሳይኖረው የመጨረሻ ፍርድ ሆኖ እንደሚቆጠር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3312/1/ ላይ የተመለከተ በመሆኑ በሟች እመቤት ለገሠና በተከሣሽ መካከል የነበረው የንብረት ክፍፍል በስምምነት የመጨረሻ ውሣኔ

ያገኘና ያለቀለት ጉዳይ በመሆኑ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 244/2/ረ/ መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች የወራሽነት መብታቸውን ያረጋገጡት ሰኔ 22 ቀን 1991 ዓ.ም. ሲሆን ልጃቸው እመቤት ለገሠ የሞተችው ጥር 16 ቀን 1991 ዓ.ም. ነው፡፡ መብት በተረጋገጠበትና ክስ በቀረበበት ጊዜ መካከል 3 ዓመት ያልሞላ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ መሠረት አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በአግባቡ የቀረበ አይደለም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩ አስቀድሞ በግልግል አልቋል ተብሎ የቀረበውን መቃወሚያ በተመለከተም መስከረም 3 ቀን 1984 ዓ.ም. ከተደረገው የዘመድ ዳኞች ውሣኔ ጋር አቶ ተሾመ ተሰማ የሚች እመቤት ለገሠ ወኪል ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስላልተያያዘ ውክልናው በአግባቡ ተሰጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1080/1/ መሠረት ከወራሾች አንዱ ሳይኖር የቀረ ወይም በሚገባ ወኪል ያላዳረገ እንደሆነ የንብረት ክፍፍሉን ዳኞች ካላፀደቁት በቀር ፈራሽ እንደሆነ የተመለከተ ስለሆነ ጉዳዩ አስቀድሞ በግልግል ዕልባት አግኝቷል ተብሎ የቀረበውም መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን ከሰጠ በኋላ በሟች አቶ ለገሠ ቢነግዴ ወራሽና በባለቤታቸው መካከል ይገኛል የተባለን የጋራ ንብረት ለይተውና አከፋፍለው ውጤቱን በሪፖርት መልክ ለፍ/ቤቱ እንዲገልጹ በማለት ውርስ አጣሪ ሾሞ አጣሪውም የማጣራቱን ሥራ አጠናቀው ሪፖርቱን ለፍ/ቤቱ አቅርበው ፍ/ቤቱም የውርስ አጣሪው ሪፖርት ለሕግም ሆነ ለሞራል ተቃራኒ ያልሆነ ስለሆነ ተቀባይነት አለው በማለት ይህንኑ በመዝገቡ ላይ አስፍሯል፡፡

የሥር ተጠሪ ፍ/ቤቱ በሰጠው ብይንና ትዕዛዝ ላይ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤትን ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመወቃም ሲሆን ይህ የሰበር ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል፤ ጉዳዩም አስቀድሞ በግልግል ዕልባት አግኝቷል በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በበታች ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ወይስ አልሆነም ሲሆን አልሆነም የሚባል ቢሆን ጉዳዩ አስቀድሞ በግልግል ዕልባት አግኝቷል? አላገኘም? የሚለው በመሆኑ በዚህ መሠረት አቤቱታው ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ የአሁን አመልካች ክሱ በ3 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ክርክር ያቀረቡት በፍ/ብሕ/ቁ. 1000/1/ የተመለከተውን በመጥቀስ ነው፡፡

ችሎቱም በቅድሚያ የተመለከተው የፍ/ብሕ/ቁ. 1000/1/ ተፈፃሚነት ከዚህ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ ላይ የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት አንድ ወራሽ የሆነ ሰው የውርስ ሀብትን በያዘ በሌላ ወራሽ ላይ ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ እንደሆነ በመ/ቁጥር 17937 በመጥቀስ ይህ ሰበር ችሎት የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአሁን አመልካች የሚች እመቤት ለገሠም ሆነ የአቶ ለገሠ ዲነግዴ ወራሽ ባለመሆናቸውና ንብረቱንም የያዙት በወራሽነት ስላልሆነ በተጠቀሰው ሕግ ላይ የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ለጉዳዩ አግባብነት አይኖረውም፡፡

ይህ ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለት ግን አቤቱታው ጭራሽ የይርጋ ጊዜ የለውም ማለት ስላልሆነ የይርጋ ክርክሩ ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር መታየት የሚገባው ነው፡፡

የሚች እመቤት ለገሠ አባት የነበሩት ሚች ለገሠ ዲነግዴና የአሁን አመልካች ባልና ሚስት እንደነበሩ፣ በመካከላቸው የነበረውም ጋብቻ በአቶ ለገሠ ዲነግዴ ሞት ምክንያት በነሐሴ ወር 1967 ዓ.ም. እንዲፈርስ ሚች እመቤት ለገሠም ግንቦት 25 ቀን 1969 ዓ.ም. የሚች አባታቸው ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው ነገር ግን የንብረት ክፍፍል ሳይደረግ በጥር ወር 1991 ዓ.ም. ሚች እመቤት ለገሠ እንደሞቱ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

ከባልና ከሚስት በአንዳቸው ሞት ምክንያት ጋብቻ በሚፈርስበት ጊዜ ከተጋቢዎቹ እያንዳንዱ የግል ሀብቱ መሆኑን አስረድቶ የእራሱን ድርሻ የመውሰድ መብት እንዳለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 684 ላይ ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ ይህ ድንጋጌ ጥያቄው በምን ያህል ጊዜ መቅረብ እንዳለበት ባይደነግግም በጋብቻ ጊዜ የተፈራ የግልም ሆነ የጋራ ንብረት ሳይከፋፈል ለረጅም ጊዜ ቆይቶ ጥያቄውን ከረጅም ጊዜ በኋላ ለማቅረብ የሕጉ ዓላማ ሊሆን አይችልም፡፡ ግንኙነቱን የሚገዛው የቤተሰብ ሕጉ የይርጋ ድንጋጌን በዚህ ረገድ ካላካተተ ወደ ሌሎች ድንጋጌዎች መሄድ ግድ ስለሚል በዚሁ መሠረትም ሲታይ ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆንም የጠቅላላ የውል ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዳላቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ ላይ የተመለከተ ሲሆን የውል ሕግ ደግሞ ዋናው የይርጋ ደንብ በቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ መቃወሚያ ያቀረቡት የሚች እመቤት ለገሠ አባት አቶ ለገሠ ዲነግዴ ከሞቱበት ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ጊዜ በመቁጠር ነው፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ክስ ያቀረቡት በአቶ ለገሠ ዲነግዴ እግር ተተክተው ሳይሆን በሚች ልጃቸው በእመቤት ለገሠ እግር በመተካት እንደመሆኑ መጠን ሚች እመቤት ለገሠ ደግሞ የሞቱት ጥር 16 ቀን 1991 ዓ.ም. ሆኖ የልጁ ድርሻ ንብረት ይገባኛል በማለት ክስ ያቀረቡት ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት በ1994 ዓ.ም. ስለሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ከውጤት አኳያ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ከተባለም ቀጥሎ መታየት የሚገባው ጭብጥ ክርክሩ አስቀድሞ በግልግል ዕልባት አግኝቷል ወይስ አላገኘም የሚለው ጭብጥ ነው፡፡

በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ሟች እመቤት ለገሠ በሕይወት እያሉ ከአመልካች ጋር በዘመድ ዳኞች አማካይነት መስከረም 3 ቀን 1984 ዓ.ም. የንብረት ክፍፍል አድርገው ድርሻቸውን የወሰዱ ስለሆነ በግልግል ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበው ክስ በአግባቡ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 244/2/ረ/ ላይ የተመለከተውን በመጥቀስ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት መቃወሚያውን ሳይቀበለው የቀረው በአስረጂነት ከቀረበው የሽምግልና ዳኞች ውሣኔ መገንዘብ የሚቻለው ክፍፍሉ የተደረገው የሟች ወኪል ናቸው በተባሉት በአቶ ተሾመ ተሰማ አማካይነት እንደሆነ ሲሆን ነገር ግን አቶ ተሾመ ተሰማ የሟች ወኪል ናቸው ተብሎ በውሣኔው ላይ ከመጠቀሱ በስተቀር ከውሣኔው ጋር የውክልና ሥልጣኑ አልተያያዘም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1080/1/ መሠረት ከወራሾች አንዱ ሳይኖር የቀረ ወይም በሚገባ ወኪል ያላደረገ እንደሆነ የንብረት ክፍያውን ዳኞች ካላፀደቁት በስተቀር ፊራሽ እንደሆነ የተመለከተ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ የተደረገውም የንብረት ክፍፍል ፍ/ቤት ቀርቦ ያልፀደቀ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

የውርስ ሀብት ክፍፍልን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1079 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከተው በዚህም ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት እንዳለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 689/2/ የተመለከተ ቢሆንም በቁጥር 1080/1/ ድንጋጌ መሠረት ከወራሾች አንዱ ባልተገኘበት ወይም በሚገባ ባልተወከለበት የተደረገን የንብረት ክፍፍል ዳኞች ካላፀደቁት በስተቀር ፈራሽ ነው ሊባል የሚችለው በዚሁ እንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /2/ ሥር እንደተመለከተው በሌለበት ክፍያው የተፈጸመበት

ወራሽ በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት እንደሆነ የተመለከተ ከመሆኑም በላይ የዚህ ዓይነቱንም ጥያቄ ወራሹ ማቅረብ የሚችለው የንብረት ክፍፍል በሌለበት መደረጉን ባወቀ በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሆነና ነገር ግን ሟች ከሞተ 10 ዓመት ያለፈለው ከሆነ በማናቸውም ምክንያት ጥያቄውን ማቅረብ እንደማይቻል በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /3/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ አውራሽ መስከረም 3 ቀን ተደርጓል የተባለው የንብረት ክፍፍል በሌለሁበት ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል በማለት ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት አቤቱታ አቅርበው ክፍፍሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ያልተወሰነ ከመሆኑም በላይ ተጠሪም ክስ የመሠረቱት ከሟች ልጂ በውርስ የተላለፈልኝ ንብረት ይገባኛል በማለት እንጂ ክፍፍሉ እንዲፈርስ ዳኝነት ያልጠየቁ በመሆኑ በዚህ ሁኔታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክፍፍሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ብይን እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይህንኑ ብይን በማጽናት የሰጠው ፍርድ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች በኩል ጉዳዩ አስቀድሞ በግልግል አልቋል ተብሎ የቀረበውን የመጀመያ ደረጃ መቃሚያ በመ/ቁ. 00202 በሚያዝያ 21 ቀን 1995 ዓ.ም ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ብይንና ከዚህም በኋላ በዚሁ መዝገብ ውርስ አጣሪ እንዲቋቋምና የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ በግንቦት 14 ቀን 1995 ዓ.ም. እና በሐምሌ 7 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጣቸው ትዕዛዞች እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34902 በጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ አውራሽ መካከል በግልግል ዳኞች አማካይነት መስከረም 3 ቀን 1984 ዓ.ም. የንብረት ክፍፍል መደረጉ የተረጋገጠ ስለሆነ ተጠሪ ድርሻ ንብረቱ ይገባኛል በማለት ያቀረቡት ክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 244/2/ረ/ መሠረት ተቀባይነት የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 30536

መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ደስታ ገብሩ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ት ዓለምነሽ ዋቅቶላ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. አቶ ይልቃል ጌጤ አልቀረቡም፡፡

2. ካጀ ኢ/ል ኃ/የ/የ/ኩባንያ አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የ2ኛ ተጠሪ የሆነውን መኪና 1ኛ ተጠሪ ሲያሽከረክር ጉዳት የደረሰብኝ ስለሆነ ካሣ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃ ለተከሣሾች እንዲደርስና መልስ እንዲሰጡበት ታዞ 2ኛ ተከሣሽ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከሳሽና 2ኛ ተከሣሽ ባደረጉት ስምምነት ከሳሽ በደረሰባቸው የአካል ጉዳት ብር 30 ሺህ ከአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ለመቀበል በተስማሙት መሠረት ገንዘቡን ከኩባንያው የተቀበሉ ስለሆነ ክስ ያቀረቡት በዕርቅ ባለቀ ጉዳይ ስለሆነ ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ውድቅ ሊያደርገው ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚህ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ ከሳሽና 2ኛ ተከሣሽ ጉዳዩን በዕርቅ መጨረሳቸውን የቀረበው ማስረጃ ስለሚያረጋግጥ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት በብይን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ከሣሽ በዚሁ ብይን ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ በእርቅ ያለቀ ነው ተብሎ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተጠሪዎች ባሉበት ለሰበር ችሎት ቀርቦ መጣራት የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪዎችን ጠርቷል፡፡ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ በአድራሻው ባለመገኘቱ በጋዜጣ ተጠርቶ ስላልቀረበ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ግን ቀርቦ የበኩሉን የጽሁፉን የቃል ክርክር አቅርቧል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱ በብይን ተቀባይነት የለውም ወደሚል መደምደሚያ ለመድረስ የቻለው አመልካች የካቲት 29 ቀን 1997 ዓ.ም. ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት ውል ለደረሰባቸው ቋሚ የአካል ጉዳት ካሳ የሚሆን ብር 30 ሺህ የተቀበሉ ስለሆነና ከዚህ በላይ 2ኛ ተጠሪንም ሆነ መድን ሰጭውን አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያን ላለመጠየቅ ስምምነት ላይ የደረሱ በመሆኑ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ አስቀድሞ በስምምነት ዕልባት አግኝቷል በማለት ነው፡፡

ይሁንና የካቲት 29 ቀን 1997 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለው ውል ይዘት ሲታይ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ 2ኛ ተጠሪን በመወከል በካሣ አከፋፈሉ ረገድ ከመልካች ጋር ውሉን እንደተዋዋሉ መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ በስር ፍ/ቤትም ሆነ ለዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ሲከራከሩ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ 2ኛ ተጠሪን በመወከል ይህንኑ ውል ከአመልካች ጋር እንደተዋዋለና በውሉ ላይ የተጠቀሰውንም ብር 30 ሺህ ኢንሹራንስ ኩባንያው ለአመልካች መክፈሉ የተረጋገጠ ስለሆነ ኢንሹራንስ ኩባንያው 2ኛ ተጠሪን በመወከል ከአመልካች ጋር ውሉን መዋዋል የሚችለው ለ2ኛ ተጠሪ በሰጠው የመድን ሽፋን ልክ እንጂ ከዚያ በላይ ሊሆን ስለማይችል የጉዳት አድራሹ መኪና ባለንብረት 2ኛ

ተጠሪ ከብር 30 ሺህ በላይ የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ አስመልክቶ የቀረበበት ክስ በዕርቅ አልቋል ሊባል ስለማይችል የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በአጠቃላይ በዕርቅ አልቋል በማለት ክሱን ሳይቀበል መቅረቱ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተግኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12463 በታህሳስ 12 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ብይን እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 41413 በየካቲት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ያለው ክርክር በዕርቅ አልቋል ለማለት ስለማይቻል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 30727

ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

አልማው ወሌ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አ/ማኅበር ነ/ፈጅ ወንድአንተ ነጋሽ

ተጠሪ ፡- ጄቲቲ ትሬዲንግ ሥራ አስኪያጅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ግራ ቀኞችን ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረግነው ውል ከሳሽ ጋር 10 ኢንች የማይዝግ የብረት ቧንቧ ለማቅረብ ስምምነት የተደረሰ ቢሆንም ተከሳሽ ውሉን በማፍረሱ ያለመግባባት በመፈጠሩ ምክንያት ችግሩን ለመፍታት ከሳሽ የበኩሉን ጥረት ቢያደርግም በተከሳሽ በኩል አዎንታዊ ምላሽ ባለመገኘቱ በውሉ አንቀጽ 10/4/ /2/ መሠረት ጉዳዩን በግልግል ለማየት ተጠሪ የግልግል ዳኛ በ10 ቀን ውስጥ መርጦ እንዲያሳውቀን በጽሁፍ ያሳወቅነው ቢሆንም ፈቃደኛ ያልሆነ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በተከሳሽ ምትክ በሕግና በውላችን መሠረት የግልግል ዳኛ እንዲመርጥልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ አቤቱታም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ በሕግም ሆነ በኩባንያው የመመስረቻ ጽሁፍ፤ በመተዳደሪያ ደንቡ እንደዚሁም በሥነ ሥርዓትና በፍ/ብሔር ሕጉ የተቀመጠው የችሎታ መስፈርት ለተጠሪው

ወይንም ለእንደራሴው አልተሰጠም ብለዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ተከሳሽ የግልግል ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በእራሳቸው የግል ችሎታ ሳይሆን በሌሎች የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰዎች ስም የሆነ እንደሆነ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ እንዲስማሙ የሚያስችላቸው ልዩ የውክልና ስልት እንዲኖራቸው ይገባል ያሉ ሲሆን አመልካች ወደ ግልግል ዳኝነት እንግባ የሚልበት ጉዳይ በግልግል ስምምነቱ አይሸፈንም እንጂ የሚሸፈን ነው ቢባል እንኳ ወደ ግልግል ዳኝነት ከመግባቱ በፊት በእራሳቸው በተዋዋዮች ድርድር ተጀምሮ በሂደት ላይ ያለው ስምምነት ገና ያልተጠናቀቀ ስለሆነና ይህንንም ለማድረግ ውሉ ስለሚያስገድድ በዚህ ሁኔታ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተገቢነት ያለውን የክርክሩን ጭብጥ ከያዘ በኋላ ተጠሪ የአክሲዮን ማኅበር ሲሆን ተጠሪና አመልካች ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተዋዋሉት መሠረት ያለመግባባቶችን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት ተደርጐ ካልተቻለ የግልግል ዳኛ በመምረጥ ጉዳዩ እንደሚታይ የተስማሙ ስለሆነ አክሲዮን ማኅበር ያለመግባባቶችን በግልግል ለመፍታት እንደማይችል የሚያመለክት የሕግ ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ጉዳዩን በግልግል መጨረስ አልችልም በማለት ያቀረበው ክርክር አግባብነት የሌለው ነው ካለ በኋላ የተፈጠረውን ያለመግባባት በውሉ መሠረት በስምምነት ለመፍታት ከሳሽ /አመልካች/ ተገቢውን ጥረት ስለማድረጉ ካቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ግራ ቀኙ ያለመግባባታቸውን በስምምነት መጨረስ ስላልቻሉ ጉዳያቸው በግልግል ዳኛ አማካይነት መታየት ስላለበት የየበኩላቸውን የግልግል ዳኛ መርጠው ይቅረቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሥር ተከሳሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግልግል ዳኛ እንዲታይ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ አግባብነቱ ተጠሪ ባለበት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የዚህን ችሎች ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጥሯል የተባለው አለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ሊታይ ይችላል ወይንስ አይችልም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን መርምረናል፡፡

በቅድሚያም አመልካች ምን ዓይነት የሕግ ሰውነት (legal personality) እንዳለው መመልከት ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ሲታይ አመልካች የአክሲዮን ማኅበር እንደሆነ ከክርክሩና ከቀረበው ማስረጃ ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን ይህንንም የሕግ ሰውነት ማግኘት የቻለው አስቀድሞ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደነበረና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/91 መሠረት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጅት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አንድን የልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማኅበርነት እንዲለወጥ ማድረግ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 5/1/ ላይ የተመለከተ በመሆኑ በዚሁ መሠረት አመልካች ወደ አክሲዮን ማኅበርነት የተቀየረ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ መልኩ የሚቋቋሙና በንግድ ሕጉ መሠረት የሚቋቋሙ የአክስዮን ማኅበራት በአክሲዮን ባለቤትነት በሥልጣንና በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ አንድ ዓይነት እንዳልሆኑ ከተጠቀሰው አዋጅ መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ የንግድ ሕግ ቁጥር 307/1/፣ 311፣ 312/1/ለ/፣ 315፣ 347/1/ እና 349 ከመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማኅበርነት በተለወጡት ላይ ተፈፃሚነት እንደሌላቸው ነገር ግን ሌሎች የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በአዋጁ ላይ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት የአክሲዮን ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊኖረው እንደሚችል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 348/3/ ላይ የተመለከተ ሲሆን በተያዘውም

ጉዳይ አመልካች አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ያለው ስለመሆኑ በአክሲዮን ማኅበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የተመለከተ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩልም የአመልካች አክሲዮን ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12 ሥር የተዘረዘሩ ሲሆን ተጠሪም በዚሁ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12/2/ ሥር ዋና ሥራ አስኪያጁ የኩባንያውን የዕለት ተዕለት ሥራ ያከናውናል ተብሎ የተመለከተው ከሌሎች ወገኖች ጋር ውል መዋዋልን በውሉ አፈፃፀም ረገድ ያለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩን በግልግል ለማየት መስማማት እንደሚችልም ስለሚያስገነዝብ በዚሁ መሠረት ውሉ የተፈረመ ስለሆነ ጉዳዩ በግልግል እንዲታይ መወሰኑ አግባብነት አለው በማለት ተከራክሯል፡፡

ይሁንና ዋናው ሥራ አስኪያጅ የኩባንያውን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ያከናውናል ተብሎ ሥልጣንና ተግባሩን በሚዘረዝረው የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም አክሲዮን ማኅበሩ ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ ሲታይ ሙሉ በሙሉ በንግድ ሕጉ መሠረት ያልተቋቋመ ስለሆነና ዋናው ሥራ አስኪያጁ ኩባንያውን በመወከል ውል የመዋዋል ሥልጣን እንዳለው መገንዘብ ቢቻልም ከዚህ አልፎ በውሉ አፈፃፀም ረገድ ያለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩ በግልግል ዳኛ አማካይነት ዕልባት እንዲያገኝ ለመስማማት እንደሚችል ሥልጣን ያልተሰጠው መሆኑን መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት መታየት ይችላል በማለት የሰጡት ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 146/91 እና ከማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ጋር ያልተጣጣመ በመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 59068 በየካቲት 17 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 46254 በየካቲት 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች ከተቋቋመበት ሕግ አካያና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ዋናው ሥራ አስኪያጅ በውል አፈፃፀም ረገድ የሚፈጠርን ያለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ዕልባት እንዲያገኝ ለመስማማት ሥልጣን ያልተሰጠው ስለሆነ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጥሯል የተባለው ያለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ሊታይ አይችልም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 20036

ግንቦት 16 ቀን 1998

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

· ምህረቱ

መለሱ እቁበዮናስ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ሊከፈል የማይገባው የጡረታ አበል ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረተው ክስ ተጠሪ የሚች ባለቤታቸውን የወ/ር ተፈራ አድማሱን ጡረታ እየተቀበሉ ሌላ ባል በማግባታቸውና፤ የሚች ባላቸውን ጡረታ አበል እየበሉ ሌላ ባል ያገቡ የጡረታ አበል እንደሚቋረጥባቸው ሕጉ ግልፅ ሆኖ ሣለ፤ ይህንኑ በመቃረን ተጠሪ ሌላ ባል አግብተውም የሚችን ጡረታ ለ 13 አመታት ስለተቀበሉ በድምሩ ብር 7593.75 ይክፈሉ በማለት ጠይቋል፡፡

ተጠሪም ቀርበው ከ13 ዓመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው፣ ሌላ ባል አላገባሁም ከጋብቻ ውጪ በነበረን ግንኙነት 2 ልጆች ወልጃለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም ክስ የቀረበበት የይመለስልኝ ጥያቄ በየጊዜው (በየወሩ) የሚከፈልና ለመጨረሻም ጊዜ ክፍያው የተደረገው በ ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ሲሆን ክስ የተመሠረተው በሰኔ 5 ቀን 1995 ዓ.ም በመሆኑ የይርጋው ጊዜ አላለፈም፣ ነገር ግን ተጠሪ ሌላ ባል ያገቡ ለመሆናቸው አላስረዳም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚህ ውሣኔ ላይ የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡

የአሁኑ አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በግራ ቀኙ መሃከል ጋብቻ መኖር አለመኖሩን ለመመርመር ሲል አቤቱታው

ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡

አመልካች ክስ የመሠረተው መክፈል የማይገባኝን የጡረታ አበል የከፈልኩ ስለሆነ ይመለስልኝ በሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብሔር ሕጉ ያለአግባብ ስለመበልፀግ ከሚናገረው ምዕራፍ ውስጥ የማይገባውን ስለመካፈል በሚለው ክፍል ሥር የሚወድቅ ነው፡፡ አንድ ሠው ሊከፍል የማይገባውን ነገር ከከፈለ እንዲመልስለት የመጠየቅ መብት እንዳለው የፍ/ህ/ቁ 2164 (1) ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በጡረታ ሕጉ በባልዋ መሞት ምክንያት ጡረታ የምታገኝ ሴት ሌላ ባል ባገባች ጊዜ የሚች ባሏ ጡረታ አበል መቋረጥ ያለበት ለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ የተጠሪ የመጀመሪያ ክርክር ክስ የቀረበበት ጉዳይ 10 አመት ስላለፈው በ10 አመት ይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡

የማይገባውን ስለ መክፈል የሚለው ክፍል የሚገኘው ከውል ውጪ ስለሚደርስ ሃላፊነትና ያለግባብ ስለመበልፀግ በሚናገረው አንቀፅ ሥር ነው፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በዚሁ አንቀፅ ተካቶ የሚገኘው የይርጋ ጊዜ ይሆናል፡፡ የፍ/ህ/ቁ 2143(1) ተበዳይ ክስ ማቅረብ የሚችለው ጉዳቱ ከደረሠ ጊዜ ጀምሮ እስከ 2 ዓመት ድረስ ነው፡፡ አመልካች መክፈል የማይገባውን ነገር መክፈል የጀመረው ከህዳር ከህዳር 1 ቀን 1981 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ክፍያ ያቋረጠው ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ክስ ከቀረበበት ሰኔ 10 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ወደኋላ ያለው የሁለት አመት ጊዜ ብቻ በይርጋ ቀሪ የማይሆን ሲሆን ከዚህ ጊዜ በፊት የነበረው የአመልካች ጥያቄ ግን በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

ሌላው የተጠሪ ክርክር ከአቶ ገብሩ አሰፋ ጋር ጋብቻ የለንም፡፡ ከጋብቻ ውጪ ባለ ግንኙነት ነው ልጆች የወለድኩት የሚል ነው፡፡

ከፍ/ቤቱ መዝገብ ተጠሪ አቶ ገብሩ አሰፋ ባላቸው መሆናቸውን በቀበሌ ቅፅ ላይ ሞልተው አረጋግጠዋል፡፡ አቶ ገብሩ አሠፋም ቢሆኑ በሚሠሩበት መ/ቤት በሞሉት የሕይወት ታሪክ ቅፅ ላይ ተጠሪ ሚስታቸው መሆናቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አረጋግጠዋል። ከዚህም በላይ ተጠሪ ከጋብቻ ውጪ ነው ይበሉ እንጂ እንደ ባልና ሚስት በመሆን አንድ ላይ ይኖሩ እንደነበር አልካዱም።

በተሻሻለው የቤተሠብ ሕግ አንቀፅ 95 ላይ ጋብቻ መኖሩን ለማረጋገጥ ሊቀርብ የሚገባው የጋብቻ ምስክር ወረቀት መሆኑን ያመለክታል። ይህ ማስረጃ በሌላ ጊዜ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 95 እንደተመለከተው የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ጋብቻን ማስረዳት ይቻላል። የትዳር ሁኔታ አለ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ራሳቸውን እንደ ባልና ሚስት የሚቆጥሩና የሚኖሩ እንዲሁም ማሕበረሰቡና ቤተዘመዶቻቸው እንደባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሆነው ሲገኙ ነው ተብሎ በአንቀጽ 96 ስር ተጠቅሷል ። ይህን ሁኔታ ማስረዳት ከተቻለ ፍ/ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሊል የሕግ ግምት እንደሚወስድም አንቀጽ 97 ያመለክታል። ሕጉ የጋብቻ ሁኔታ የሚረጋገጥበትን ማስረጃ አይነት ለይቶ ያላመለከተ በመሆኑም ማንኛውም ማስረጃ ሊቀርብ የሚችል መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተጠሪና በአቶ ገብሩ አሰፋ መሃከል ጋብቻ መኖሩን የጋብቻ (የትዳር) ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት ማስረጃዎቹን አቅርቧል። ተጠሪ አቶ ገብሩ ባላቸው ለመሆናቸው በቀበሌ ፎርም ላይ ሞልተው ማረጋገጣቸውን እንዲሁም አቶ ገብሩም ቢሆኑ በሚሠሩበት መ/ቤት በሞሉት የሕይወት ታሪክ ቅፅ ተጠሪዋ ሚስታቸው መሆናቸውን አረጋግጠው መሙላታቸውን ከመዝገቡ ተረድተናል። ይህም ተጠሪና አቶ ገብሩ እራሣቸውን እንደባልና ሚስት እየቆጠሩ የሚኖሩ መሆኑን ማህበረሰቡም በዚሁ መልኩ የተቀበላቸው መሆኑን ያመለክታል። ነገር ግን የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የአቶ ገብሩ ሚስት ለመሆናቸው የጋብቻ ሠርትፍኬት አልቀረበም ወይም ሠርተፊኬቱ መጥፋቱ አልተረጋገጠም በማለት በሁለቱ መሃከል ትዳር የለም በማለት የደረሠበት መደምደሚያ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የቤተሠብ ህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው።

ው ሣ ኔ

1. ተጠሪ ከሰኔ 10 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ሰኔ 10 ቀን 1995 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የወሰዱትን የሚች ባለቤታቸውን የጡረታ አበል ለአመልካች ይመልሱ።
2. ከሰኔ 10 ቀን 1993 ዓ.ም በፊት አመልካች ለተጠሪ የከፈለው የጡረታ አበል እንዲመለስ ያቀረበው ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኗል።
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ። መዝገቡ ተዘግቷል። ለመ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገብ ቁጥር 23334

ሕዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሀይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ - ነ/ፊጅ ፍሬው ማሞ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ደባሣ ገለታ - ቀረቡ

2. አቶ ኤባ ደመራ

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጀመረው በምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ባቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ በሥራ ምክንያት እጁ ገብቶ የነበረውን ስንዴና የስንዴ ዱቄት ለራሱ ጥቅም ስላዋለ ግምቱን 89,750 (ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ) ይክፈል 2ኛ ተጠሪ እስከ ብር 10,000 (አሥር ሺህ) ለሚደርስ ገንዘብ ዋስ ስለሆኑ ገንዘቡን ይክፈሉ በማለት ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎቹ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌለበት የታየ ሲሆን ፍ/ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ተጠሪ 16.5 ኩንታል የስንዴ ዱቄት ማጉደሉን በፊርማው ስላረጋገጠ ለመተካት ይገደዳል፡፡ 558.5 ኩንታል ስንዴ ለማጉደሉ ግን የፈረመው መተማመኛ ስለሌለ አይጠየቅም በማለት ማጉደሉ የተረጋገጠውን 16.5 ኩንታል የስንዴ ዱቄት እንዲተካ፣ 2ኛ ተጠሪ ግን ተጠያቂ አይደሉም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም 1ኛ ተጠሪ ለ558.5 ኩንታል ስንዴ ጉድለት ተጠያቂ አይሆንም የተባለበትን የሕግ አግባብ ለመመርምር አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ እንዲታይ

አድርጓል፡፡ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ላይ የምንጠይቀው ዳኝነት የለም በማለቱ ለአቤቱታው መልስ የሰጡት 1ኛ ተጠሪ ብቻ ናቸው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ነሐሴ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በተጻፈ መልስ 558.5 ኩንታል ስንዴ የጎደለዉ በእርሳቸው ጥፋት ባልሆነ ምክንያት መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው ምርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች 1ኛ ተጠሪ 558.5 ኩንታል ስንዴ አጉድለዋል በሚል ክስ ቀርቧል፡፡ ክሱንም ለማስረዳት 1ኛ ተጠሪ የፈረሙበትን መተማመኛ አቅርቧል፡፡ በዚህ መተማመኛ 1ኛ ተጠሪ ስንዴው በጉድለት መገኘቱን አረጋግጠው ፈርመዋል፡፡ ከዚህም በላይ በዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስ ጉድለት መኖሩን አምነዋል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ለተገኘው ጉድለት ተጠሪ ጎላፊ አይሆኑም ያሉት በመተማመኛው ላይ ስንዴው የጎደለበት ምክንያቶች የተቀመጡና እነዚህም ጉድለቱ በተጠሪ ጥፋት የተከሰተ መሆኑን አያሳዩም በማለት ነው፡፡

እንግዲህ አመልካች 558.5 ኩንታል ስንዴ አጉድለዋል በማለት ክስ ሲመሰረት ጉድለቱ መኖሩን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት ጉድለቱን የሚያሳይና 1ኛ ተጠሪ የፈረሙበት መተማመኛ አቅርቧል፡፡ ይህ ከሆነ ጉድለቱ በ1ኛ ተጠሪ ጥፋት አለመከሰቱን የማስረዳት ሸክም የማነው የሚለው ጥያቄ ይነሣል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው በመተማመኛው ላይ ስንዴው ሊጎድል የቻለበትን ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ዘርዝረው አስቀምጠዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን ምክንያቶች መዘርዘሩ ብቻ ከተጠያቂነት ሊያድናቸው አይችልም ምንም እንኳን ተጠሪው በስር ፍ/ቤት ያልተከራከሩ ቢሆንም ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ ጉድለቱን አምነዋል፡፡ ጉድለቱን አምነው በመተማመኛው ላይ ባመለከቷቸው ምክንያቶች ክሱ አይመለከተኝም የሚሉ ከሆነ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም መወጣት እንዳለባቸው ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 258(1) መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ተጠርተው ባለመቅረባቸው ከሀላፊነት ነፃ የሚያደርጋቸውን የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አቅርበው ክሱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልተከላከሉም በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣ አዲስ ነገር ደግሞ በሰበር ደረጃ ሊነሣ አይችልም፡፡

በመሆኑም ጉድለቱ መኖሩ ከተረጋገጠና ይህ ጉድለት በተጠሪው ጥፋት ያልተከሠተ መሆኑን ተጠሪው ካላስረዱ ከሀላፊነት ነፃ የሚሆኑበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የጉድለቱ ምክንያቶች በሙተማመኛው ላይ ተገልፀዋል በሚል ብቻ ተጠሪ ከተጠያቂነት ነፃ መሆናቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ አጎደሉ ለተባሉት የስንዴ ዱቄትና ስንዴ በክሱ ላይ የተመለከተውን ዋጋ ተቃውመው ያቀረቡት ክርክር ሳይኖር የሥር ፍ/ቤቶች የአንድ ኩንታል የስንዴ ዱቄት ዋጋ አልተገለፀም በሚል 1ኛ ተጠሪ የስንዴ ዱቄቱን በአይነት እንዲመልሱ የሠጡት ውሳኔ አግባብ አይደለም፡፡

ው ሳ ኔ

1) የምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ/ቁ00468 በጥር 25 ቀን 1996 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 07116 በታህሳስ 11 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2) 1ኛ ተጠሪ ለጎደለው 16.5 ኩንታል የስንዴ ዱቄት እና 558.5 ኩንታል ስንዴ ተጠያቂ ስለሆኑ ክስ የቀረበበትን 89,750.50 (ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር ከሃምሳ ሣንቲም) ይክፈሉ፡፡ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ሕጋዊ ወለድ ጨምረው ይክፈሉ፡፡
3) ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግጓል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 25899

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
መስፍን ዕቁበዮናስ
መድነን ኪሮስ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የማነበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ምንዳገኝ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ር ስዩም ካሣ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የጀመረው በኦ/ብ/ክ/መ/ የአሩሲ ዞን ከ/ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪው ላይ ሰኔ 11 ቀን 1994 ዓ.ም. ባቀረበው ክስ ሲሆን ይዘቱም ተጠሪው ጡረታ ወጥተው ጡረታ አበል እየተከፈላቸው ከሕግ ውጪ በመንግሥት መ/ቤት /የአሠላ ማዘጋጃ ቤት/ ተቀጥረው ደሞዝም እያገኙ በመሆኑ ከሰኔ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1988 ዓ.ም. ድረስ እና ከመስከረም 1 ቀን 1989 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 30 ቀን 1993 ዓ.ም. ድረስ የተከፈላቸውን የ72 ወራት የጡረታ አበል ድምር ብር 6604.50 /ስድስት ሺ ስድስት መቶ አራት ብር ከሃምሣ/ ከወለድ ጋራ እንዲመልሱ ይወሰን የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩላቸው በሰጡት መልስ እኔ የቀን ሠራተኛ እንጂ ቋሚ ሠራተኛ አይደለሁም፣ ከ1993 ዓ.ም. ወዲህ ግን በደሞዝ ስለተቀጠርኩ ደመወዝን መርጬ የጡረታ አበል ትቻለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአሰላ ከተማ አስተዳደር የተጠሪን ቅጥር በተመለከተ አስተያየቱን እንዲሰጥ አዞ አስተዳደሩ በዓፈው ደብዳቤ ተጠሪው ከግንቦት 15 ቀን 1987 ዓ.ም. አንስቶ እስከ ጥር 30 ቀን 1995 ዓ.ም. ድረስ የኮንትራት ሠራተኛ መሆኑን ከየካቲት 1 ቀን 1995 ዓ.ም. ጀምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግን ተጠሪ ቋሚ ደሞዝተኛ መሆኑን በመግለጹ ፍ/ቤቱ ሰኔ 15 ቀን 1997 በሰጠው ውሣኔ በአ/ቁ. 345/95 አንቀጽ 46/1/ እና /2/ መሠረት የጡረታ አበል መውሰድ የማይችለው በቋሚነት የሚሠራ ሠራተኛ ሲሆን ተጠሪው ግን በክሱ በተጠቀሰው ወቅት የኮንትራት ሠራተኛ የነበሩ በመሆኑ ክሱ አግባብነት የለውም ሲል ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአርሲ ዞን ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ቅሬታውን በይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት አቤቱታውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ መዝገብ ለዚህ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለውም አመልካች ሐምሌ 4 ቀን 1998 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው የአ/ቁ. 209/55 እና የአ/ቁ 345/95ን ድንጋጌዎች የሚፃረር በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለታቸው ነው፡፡

እኛም የአመልካችን አቤቱታ ተመልክተን በዚህ ጉዳይ ተጠሪ የጡረታ ተጠቃሚ ሆኖ በመንግሥት ሥራ በኮንትራት የተቀጠረ እንጂ በቋሚነት የተቀጠረ ባለመሆኑ የጡረታ አበልና ደሞዝ አጣምሮ ተቀብሏል በመሆኑም የጡረታ አበሉን ይመልስ በሚል አመልካች ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርበን ግራ ቀኙ የቃል ክርክራቸውን አካሂደዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ የአርሲ ዞን ከ/ፍ/ቤት የቀረበለትን ክስ ውድቅ ለማድረግ መሠረት ያደረገው የአ/ቁ. 345/95 አንቀጽ 46/1/2/ የጡረታ አበል ሊቀበል የማይችለው በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሠራተኛ እንጂ በኮንትራት ተቀጥሮ የሚያገለግል ሠራተኛን አይመለከትም በሚል ነው፡፡ በመሠረቱ በዚህ ጉዳይ ክስ የተመሠረተው ሰኔ 11 ቀን 1994 ዓ.ም. በመሆኑ አ/ቁ. 345/95 ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፡፡ ከዚህ ይልቅ ክስ በተመሠረተበት ወቅት በሥራ ላይ የነበረው እና ለጉዳዩም አግባብነት ያለው አ/ቁ. 209/55 መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የአ/ቁ. 209/55 አንቀጽ 30/2/ ደግሞ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ

ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደመዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ከተቀጠረ ከደሞዙ እና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ እንደሚኖርበት በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሥራው ደሞዝ የሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ መሆኑን እንጂ የቅጥሩ ሁኔታ በጊዜያዊነት ይሁን በቋሚነት የሚል መስፈርት ከግምት ውስጥ አያስገባም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በዚህ ጉዳይ የስር ፍ/ቤት አ/ቁ 345/95ን አጣቅሶ በጊዜያዊና ቋሚ ሠራተኛ መካከል ልዩነትን መፍጠሩ በአ/ቁ. 209/55 ላይ ያልተካተተ ነጥብ ከመሆኑ አንፃር ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ የተቀጠሩት በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት በክሱ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የጡረታ አበል ለመቀበላቸው እስካልተካደ ድረስ ከደሞዛቸው በተጨማሪ የወሰዱትን የጡረታ አበል የማይመልሱበት ምክንያት አይኖርም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአ/ብ/ክ/መ/ የአርሲ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01713 ሰኔ 15 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይህንን ውሣኔ በመ/ቁ. 32888 ሚያዝያ 10 ቀን 1998 ዓ.ም. በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ስለዚህ ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰውን አላግባብ የወሰዱትን የ72 ወራት የጡረታ አበል ብር 6604.50 /ስድስት ሺህ ስድስት መቶ አራት ብር ከሃምሣ ሣንቲም/ ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ.26480

ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ ቢንያም ዓለማየሁ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ ተጠሪ በጥር 12 ቀን 1995 ዓ.ም በሥር ፍ/ቤት መሥርቶት በነበር ክስ፣ከታህሣሥ 22 ቀን 1984 ዓ.ም ጀምሮ በሌክቸረር 3 ማዕረግ በመነሻ ደሞዝ ብር 850 እተየከፈለው ሲያገለግል መቆየቱን ገልጾ፣በወቅቱ ማግኘት የሚገባውን እድገትና የደሞዝ ጭማሪ እንዳያገኝ በርካታ አስተዳደራዊ በደሎች የደረሱበት መሆኑን፤ ከ1989 ዓ.ም--1991 ዓ.ም አለአግባብ ከሥራ መታገዱን፣ በድጋሚ ከ1992 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም ከሥራ መታገዱን በመጨረሻም በቂ ምክንያት ሣይኖር ከሥራ መባረሩን ገልጾ ወደሥራው እንዲመለስ፣ ማግኘት የነበረበት የደረጃ እድገትና የደሞዝ ጭማሪ በአግባቡ ተሰልቶ እንዲከፈለው፤ ከዚሁ ጋር ውዝፍ ደሞዙ ጭምር ብር 157,935 እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካች በነገረፈጁ አማካኝነት በሰጠው መልስ፣ የአሁኑ ተጠሪ ከሥራ የታገደውም ቀጥሎም የተሰናበተው በዲሲፕሊን ጥፋት መሆኑን፤ ጥፋቱም በኮሌጁ የዲስፕሊን ኮሚቴ እና በማኔጅሜንቱ በአግባቡ የተሰጠ ውሣኔ መሆኑን ተረድቶ ቦርዱ ውሣኔውን ያፀደቀ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን የሚመራው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች መልስ ሰጭን ከሥራ ያገደውና ያሰናበተው አለአግባብ ስለሆነ ወደ ሥራው እንዲመለስው፣ በተጨማሪ ከ1988 ዓ.ም

ጀምሮ መልስ ሰጭ ከሥራ እስከተሰናበተ ጊዜ ድረስ ሣይከፈል የቀረውን ደሞዝና የቤት ኪራይ አበል ብር 32,765 /ሰላሣ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ስልሣ አምስት ብር/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ቅሬታ ላይ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ነሐሴ 3 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙ መልስ እና የመ/መልስ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

በዚህ ጉዳይ በሰበር ችሎቱ በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ጉዳይ፣ በአመልካችና በመልስ ሰጭው መካከል ተደርጎ ነበር የተባለው የውል ግንኙነት የሚመራው በየትኛው ሕግ ነው? የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው ለመወሰን ሥልጣን የነበራቸው መሆኑን አለመሆኑን? ነው፡፡ ይህ ችሎት በዚሁ ጉዳይ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የከፍተኛ ትምህር ተቋማት መምህራን ቅጥር፣ አስተዳደርና የዲሲፕሊን አወሳሰን ማንዋሎችንና የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅን ለማቋቋም የወጣውን ደንብ አግባብ ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

በመሠረቱ የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የተቋቋመው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 12/1991 መሠረት ነው፡፡ በዚሁ ደንብ በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የኮሌጁ አካዳሚክ ሠራተኞች ስለሚቀጠሩበትና ስለሚተዳደሩበት ሁኔታ ተገቢውን ለመወሰን እንዲችል ለኮሌጁ ቦርድ ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከነሐሴ ወር 1993 ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው የኮሌጁ መተዳደሪያ ዝርዝር ደንብ ወይም «ሌጂስሌሽን» በሥራ ላይ ውሎ ሙሉ ተፈፃሚነት የነበረው ስለመሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱም በዚህ ደንብ በክፍል አምስት ውስጥ ስለአካዳሚክ ባልደረቦች ምደባና ዕድገት፣ ስለዲሲፕሊን ጥፋቶችን አካሄድና የውሣኔ አሰጣጥ ሥርዓቶች በሰፊው ተደንግጓል፡፡ በዚሁ ክፍል በአንቀጽ 5.4.7 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው በአካዳሚክ ባልደረባ ላይ የሚሰጡ የዲሲፕሊን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኮሚቴ የመጨረሻ ውሣኔዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በዲኑ ወይም በቦርዱ በሚሰጡ የመጨረሻ ውሣኔዎች መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በተጠሪ ላይ ተወሰዱ የተባሉት አስተዳደራዊ ውሣኔዎች ከፍ ሲል የተመለከተው የአካዔዱ ሥነ ሥርዓት ተከትለው የተወሰዱ መሆኑ ታውቋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት አስተዳደራዊ አካዔዳቸውን ተከትለው የተሰጡ የመጨረሻ የዲሲፕሊን ውሣኔዎችን እንደገና መርምሮ ለመወሰን የሚያስችለው የሕግ ሥልጣን ስለመኖሩ በውሣኔው ሣያመለክት የአሁኑ አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያገደውና ያሰናበተው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን? እንዲሁም የአሁኑ ተጠሪ ማግኘት የሚገባውን ደሞዝና የደረጃ እድገት የተነፈገው በተገቢው መንገድ ነው ወይስ አይደለም? የሚልና ሌሎች ጭብጦችን ይዞ የደረሰበት መደምደሚያ ሕግ አውጪው ለትምህርት ተቋማት የሰጠውን ተቋማዊ ነፃነት በጽኑ የሚፃረር ከመሆኑ በተጨማሪ የዳኝነት አካላቱ በሕግ ተለይቶ ባልተሰጣቸው ተግባር ያከናወኑት ተግባር በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ታህሣሥ 27 ቀን 1996 ዓ.ም በመ/ቁጥር 66879 እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት ሐምሌ 6 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ. 29061 የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ ያገኘውን ጉዳይ እንደገና አይተው ለመወሰን የሚያስችላቸው ሥልጣን ሣይኖር የሰጡዋቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፣
- የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፣
- መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 28883

ነዳር 26 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማኅበር - ጠበቃ ብስራት ሐመልማል ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ሚስተር ኒኮላ አስ ፓፓቻት ዚስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፣

ፍ ር ድ፣

በዚህ ጉዳይ የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረው ክስ፣ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ሆቴል ለተገለገለበት ክፍያ የሰጣቸው የክፍያ ማዘዣዎች በባንክ ተቀባይነት በማጣታቸው ብር 85,467.24 /ሰማኒያ አምስት ሺ አራት መቶ ስልሣ ሰባት ብር ከሃያ አራት ሳንቲም/ ይክፈል የሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በበኩሉ ተከሳሽ የውጭ አገር ዜጋ ስለመሆኑም በ28/5/99 ቃለ መሐላ አቅርቧል፡፡ በዚህ መሠረት የውጭ አገር ዜጋ የክርክሩ ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ ግልጽ ነገር /Foreign Elements/ እንደሚኖር ይታመናል፤ ይህም የግለሰብ ዓለምአቀፍ ሕግን /Private International law/ የሚያስነሳ ይሆናል በአዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 11/2/ሀ/ መሠረት ደግሞ እንዲህ አይነት ጉዳዮችን ለማየት ስልጣኑ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለሆነ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ቀርቦለት የነበረውም የፌ/ከፍ/ቤት ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡

የሰበር ቅሬታ ማመልከቻው የቀረበው በዚህ ነጥብ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎት የካቲት 12 ቀን 1999 በሰጠው ትዕዛዝ የውጭ አገር ዜጋ ተከራካሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሆነበት ጉዳይ ላይ የግለሰብ አለምአቀፍ ሕግ ጥያቄ ይነሳል በሚል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ታዞ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን መልስ እና የመልስ መልስ እንዲሁም ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. በችሎት የተደረገው የቃል ክርክር አድምጧል፡፡

በመሠረቱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11/2/ሀ/ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ /ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው/ የሚመለከቱ ጉዳዮች በሚኖሩ ጊዜ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሔር የዳኝነት ሥልጣን እንደሚኖረው ተመልክቷል፡፡ አዋጁ የፍርድ ቤቱን ስልጣን በዚህ መልክ የደነገገው አንድም፣ ወደፊት በሥራ፣ ላይ የሚውለው የአገሪቱ የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግ በሕግ አውጪው አካል ፀድቆ በስራ ላይ ሲውል በዚህ ዙሪያ የሚነሱ የሕግ ክርክሮችን የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን አይቶ እንዲወስን አሊያም አሁን ባለው ሁኔታ ለኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ለዳኝነት በቀረበ አንድ ጉዳይ ላይ ከተከራከሪ ወገኖች አንዱ የኢትዮጵያ ሕግ ከአመልካቹ አገር ሕግ ወይም ከሌላ አገር ሕግ ጋር ይጋጫል ወይም ይቃረናል በማለት በኢትዮጵያ ሕግ እንዳይዳኝ ወይም በራሱ ወይም በሌላ አገር ሕግ ጉዳዩ እንዲታይና እንዲወሰንለት ሲያመለክት ወይም በሌላ አነጋገር ለዳኝነት የቀረበው ጉዳይ በባሕሪው ከአንድ በላይ የሆኑ የሕግ ስርዓቶችን ለጉዳዩ አወሳሰን የሚጋብዝና የየትኛው ሥርዓት ሕግ ተመራጭ ሊሆን ይገባል የሚለው ክርክር ሲነሳ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን አይቶ እንዲወስን ከመደረጉ ውጭ በማናቸውም ሁኔታ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ የውጪ አገር ዜጋ በሆነበት ጊዜ ሁሉ በተከራካሪ ወገን ጥያቄ ባይነሳም ክርክሩ የፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው ጥያቄ ያስነሳል ብሎ ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

- አመልካች በተጠሪ ላይ በር 85,467.24 እንዲከፍለው ያቀረበውን ክስ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የማየት ስልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በጥር 30 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ 82621 እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የካቲት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ. 52718 የሰጡዋቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፣
- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 343/1/ ተመልሶለታል፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁጥር 29005

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ሠልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡- 1. ግርማቸው ይላላ ቀረበ፡፡

2. አዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የግንባታ ፈቃድ እና ካርታ ይሰጠኝ በሚል 1ኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪው ክስ የመሠረተው በ2ኛው ተጠሪ ላይ ነበር፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በሁለቱ መካከል የተሰማውን ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ 2ኛ ተጠሪ የተጠየቀውን የግንባታ ፈቃድ እና ካርታ ለ1ኛ ተጠሪ ይስጥ በማለት ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የአሁኑ አመልካች ክርክሩ የእኔን መብት የሚነካ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 358 መሠረት መቃወሚያ ያቀረበው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን የተመለከተ ቢሆንም፤ በመጨረሻ ግን ተቃዋሚው /የአሁኑ አመልካች/ ተጠሪነቱ ለ2ኛ ተጠሪ በመሆኑ ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር ተካፋይ አልነበረም የሚባል አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 14 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ፣ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች በአቃቂ ክፍለ ከተማ ስር የተደራጀ አስፈፃሚ አካል ነው፡፡ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 10/2/ እንደተመለከተው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያሉት ክፍለ ከተሞች የየራሳቸው ምክር ቤት፣ ዋና አስፈፃሚ እና ቋሚ ኮሚቴ ኖሯቸው የተደራጁ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አካላት ናቸው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 30 እንደተደነገገውም ክፍለ ከተሞች ባልተማከለ የስልጣን ክፍፍል መርህ በተሰጠው የቦታ ክልል ማዘጋጃ ቤት በመሆንና ከከተማው ማዕከል ጋር በመቀናጀት ይሰራሉ፤ በሥራቸው የሚገኙትን ቀበሌዎችም ያስተዳድራሉ፡፡ በአጠቃላይ በአዋጁ አንቀጽ 10 በተመለከተው አይነት የከተማው አስተዳደር የስልጣን አካላት የተደራጁ ሲሆን፣ ከነዚህ አንዱ ክፍለ ከተማ ነው፡፡ ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ የሚቻለው እያንዳንዱ ክፍለ ከተማ የራሱ የሕግ ሰውነት ያለው እና በሕግ በተሰጠው የስልጣን ክልል ውስጥ በራሱ ኃላፊነት የሚንቀሳቀስ እንደሆነ ነው፡፡

በዚህ መዝገብ በሁለተኛ ተጠሪነት የተመዘገበው አካል ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ ክፍለ ከተሞች ካርታ እና የግንባታ ፈቃድ የመስጠት ስልጣንና ተግባር በቻርተሩ እና ቻርተሩን መሠረት በማድረግ በወጡት የከተማው አስተዳደር አዋጆች እንደተሰጣቸው አረጋግጦአል፡፡ በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካወጣቸው አዋጆች አንዱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍለ ከተማዎችና የቀበሌዎች አስተዳደር ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁ. 1/95ን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁ. 18/97 ሲሆን፣ ይህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ በክፍለ ከተማው ውስጥ ያለውን ቦታ የማስተዳደር ስልጣን የክፍለ ከተማው እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ቦታ ማስተዳደር ደግሞ ለአሁኑ ክርክር መነሻ የሆነውንም እንደሚያጠቃልል በአዋጁ አንቀጽ 2 ተመልክቶአል፡፡ አመልካች በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር መነሻነት ውሣኔ የተሰጠበት ጉዳይ እኔን የሚመለከት ነው በማለት መቃወሚያ ያቀረበውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ነገሩን አጠቃለን ስንመለከተው አመልካች የራሱ የሆነ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይም በሱ የስልጣን ክልል ውስጥ የሚከናወን ነው፡፡ በመሆኑም አያገባህም የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች እነዚህን ሁኔታዎች ባለማገናዘባቸው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48511 ሚያዝያ 11 ቀን 1998 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47682 ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ጉዳዩ እሱን በቀጥታ የሚመለከት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ያቀረበው መቃወሚያ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተቀብሎ ክርክሩን በመስማት ይወስን ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 30298

ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ የሺወንድም አቡሐይ

ተጠሪ፡- አቶ አየነው ማለደ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በተጠሪ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የመጥፋት ውሣኔ ሲሰረዝ አመልካች ለ3ኛ ወገን በሽያጭ አስተላልፈውታል የተባለውን ቤት ለተጠሪ ሊመለሱ ይገባል የሚሉት በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ሲሉ አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ ለሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በአመልካች ጠያቂነት ቀደም ሲል በወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በተሰጠው የመጥፋት ውሣኔ የተነሣ መሆኑን ገልፀው የግል ንብረቱ የሆነውና የዋጋ ግምቱም ብር 50.000 (ሃምሣ ሺህ) የሆነው ቤት አመልካች ለ3ኛ ወገን በሽያጭ ያስተላለፈው ስለሆነ እንዲመለስ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ቀርበው በሰጡት መልስ ተጠሪ ከእናቱ ጋር ጋብቻ መሥርቶ እያለ እናቱን ጥሎ በመጥፋቱ በሽተኛ ስለነበረች እሷን ለማሣከም ገንዘብ በማስፈለጉ ቤቱ የተሸጠ ሲሆን የሸያጩ ዋጋም በከሣሽ እንደተጠቀሰው ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ/ ሣይሆን ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ ነው በማለት ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ከቀረበው ማስረጃ አኳያ መርምሮ ተከሣሽ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት የከሣሽና የእናቱ የጋራ ሀብት ነው የሚል ክርክር ቢያቀርብም ከጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የቀረበው የስነድ ማስረጃና እንደዚሁም በከሣሽ በኩል የቀረቡት ምስክሮች በሰጡት ቃል ከሣሽ ከተከሣሽ እናት ጋር ጋብቻ ከመመሥረታቸው በፊት የሠሩት ቤት እንደሆነ ስለሚያረጋግጥ ተከሣሽ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ ጠፍቷል የተባለ ሰው ከመጣ ጠፍቷል መባሉ ተሠርዞ ወደ ሌላ ሰው ተላለፎ የሚገኝ ንብረትም ሊመለስለት እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171(1) ላይ የተመለከተ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ለከሣሽ ሊመለስ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ተጠሪ ጠፍተዋል በማለት የመጥፋት ውሣኔ ካገኙ በኋላ ወራሽነታቸውን አረጋግጠው የተጠሪን ቤት ለ3ኛ ወገን መሸጣቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ሲመለሱ ሊመለስላቸው የሚገባው የቤቱ ሽያጭ ዋጋ ወይንስ ቤቱ እራሱ የሚለው ነጥብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171 አኳያ አቤቱታው ለሰበር ቀረቦ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በተጠሪ ላይ የመጥፋት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሽያጭ ወደ 3ኛ ወገን እንደተላለፈ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

የመጥፋት ውሣኔን ውጤት ቀሪ ከሚያደርጉ ምክንያቶች /effects of termination of absence/ ጠፍቷል የተባለው ሰው መመለስ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171 ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረትም ጠፋ የተባለው ሰው

በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹን በሚገኙበት አካኋን መልሶ የመረከብ እንደዚሁም የተሸጡትን ንብረቶች ዋጋ የማግኘት መብት እንዳለው በግልጽ ተመልክቷል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው ቤት መሸጡ ከተረጋገጠ ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ አኳያ ተጠሪ ሊረከቡ የሚገባቸው የተሸጠውን ቤት ሣይሆን የሽያጩን ዋጋ ነው ማለት ነው፡፡ የሽያጩን ዋጋ በተመለከተም አመልካች በብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ መሸጡን ሲገልፁ ተጠሪ ዋጋው ብር 50.000 (ሃምሣ ሺህ) እንደሆነ ከመግለጽ በስተቀር በዚህ ዋጋ የተሸጠ መሆኑን ማስረጃ አቅርበው አልተከራከሩም፡፡

ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች በሽያጭ የተላለፈው ቤት ለተጠሪ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 15240 በጥር 28 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ለአመልካች ይገባል ማለቱ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11660 በመጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም ይግባኙን ባለመቀበል የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በብር 25.000 (ሃያ አምስት ሺህ) ስለመሸጡ የተረጋገጠ ስለሆነ የህንኑ የሽያጭ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief





የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ቅፅ 6

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

ቅፅ 6

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሚያዝያ 2001 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

ቅፅ 6

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

አዲስ አበባ



የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

ከዚህ ዕትም በፊት በነበሩ ቅፆች በርካታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች ታትመው በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶችና ለሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሠራጩ ተደርጓል። ይህም በዋናነት፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል ተብሎ በመደንገጉ ፍርድ ቤቶች የሰበር ችሎቱ የሰጠውን የሕግ ትርጉም ተከትለው እንዲሠሩ ለማስቻል ነው። በየፍርድ ቤቶች ለተመሣሣይ ጉዳዮች ይሰጥ የነበረውን የተለያዩ ወሳኔዎች በማስቀረት የፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ወጥነት እንዲኖራቸውን ተገማችም እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑም ነው።

በሌላ በኩል ውሣኔዎቹ በጥራዝ መልክ መዘጋጀታቸው ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ የሕግ ተማሪዎችና ምሁራን፣ ለጠበቆችና ለህብረተሰቡ በአጠቃላይ ውሳኔዎቹን በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል የሚል እምነት አለን።

ተገኔ ጌታነህ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማውጫ ገጽ

የፍትሀብሄር ሥነ ሥርዓት 1

የሰ/መ/ቁ 08751 2
ወ/ሮ አበበች በጅጋ እና እነ ዶክተር ተስፋዬ አካሉ
የሰ/መ/ቁ 19142 11
አቶ መላኩ ማሞ እና እነ ወ/ሮ ፈለቀች ማሞ
የሰ/መ/ቁ 20262 14
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ የአቶ አሰፋ ባላንጎ ወራሾች
የሰ/መ/ቁ 20465 18
አዋሽ ኢንተርናሽናል ኩባንያ እና እነ ፀሐይ ዮሐንስ
የሰ/መ/ቁ 21270 22
የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ ወይንሸት አበራ
የሰ/መ/ቁ 22556 26
ታደሰ አብዛ እና እነ የአቶ ጎሳዬ ሩጋቶ ወራሾች
የሰ/መ/ቁ 22603 29
የድሬዳዋ ጊዜ /አሰ/ቀበሌ 20 ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ሸሪፍ አሊ
የሰ/መ/ቁ 23363 33
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ፊርሃን አህመድ
የስ/መ/ቁ 23628 37
ሶሎ ሲርካርና ኤ. ኤስ እና እነ ጌትያን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
የሰ/መ/ቁ 23692 40
አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና እነ አሊ መሐመድ
የሰ/መ/ቁ 23744 49
አቶ በቀለ በድዬ እና የወጋገን ባንክ አዋሳ ቅርንጫፍ፣ የቡሌ ሆራ ከተማ አስተዳደር ፣ አቶ ሁሴን ወልዴ
የሰ/መ/ቀ 23769 53
ኢንጂነር ጋሪ ፉፋ እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናት ኢንስቲትዩት
የሰ/መ/ቀ 24111 56
የቂርቆስ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለሥልጣን እና ወ/ሮ የዕለተወርቅ ገ/አብ

የሰ/መ/ቁ 24627 60
ዶ/ር ቤተልሄም ታደሰ እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ
የሰ/መ/ቁ 24775 64
ማታዶር አዲስ ጎማ እና ቢተው ረታ
የሰ/መ/ቁ 25026 66
ወ/ሮ ሁዳ መሐመድ እና ሀጂ አህመድ አህመዲን
የሰ/መ/ቁ 25890 72
የኢ/ት መድን ድርጅት እና እነ ዝናሽ አሰፋ
የሰ/መ/ቁ 26670 76
አዲስአለም ሲሚይ እና የኢት/ ልማት ባንክ
የሰ/መ/ቁ 27739 81
አቶ ድንቁ ገላው እና ወ/ሮ ዋለ እሸቴ
የሰ/መ/ቁ 27808 84
የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ማይገነት ብርሃኑ፣
የሰ/መ/ቁ 28522 87
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ሞያሌ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ እና እነ ወ/ሮ ወርቁ ያደቹ
የሰ/መ/ቁ 28802 91
እነ ወ/ሮ በየነች ይገዙ እና አቶ ሳሙኤል ዝቅአርጋቸው
የሰ/መ/ቁ 29738 94
የአፓርታማ 79/6 የመኖሪያ ቤት ጎብረት ሥራ ማኅበር የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልት እና ወ/ት ዘርአዳም አሰጋኸኝ
የሰ/መ/ቁ 29761 98
እነ አቶ ዳባ ደበሌ እና እነ የአቶ ደበበ ተፈራ ወረሾች
የሰ/መ/ቁ 29780 103
እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ ዓለሙ እና ወ/ሮ ከተማሽ ቸርነት
የሰ/መ/ቁ 30631 107
ወ/ሮ ዘቢዳ ሙሳ እና እነ ወ/ሮ አሻ የሱፍ ወ/ሮ ፋጡማ የሱፍ
የሰ/መ/ቁ 30704 110
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአቶ በቀለ ወ/ማርያም ወራሾች

የሰ/መ/ቁ 31490 114
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ሴርኮ አስራኤላውያን
የሰ/መ/ቁ 31547 118
አቶ ኪዳኔ ገ/ጊዮርጊስ እና ወ/ሮ አብርሃ ተስፋሁን
የሰ/መ/ቁ 31833 122
ሀጂ አብድልቃድር አህመድ እና እነ ወ/ሮ ደስታ ገ/ዮሐንስ፣
የሰ/መ/ቁ 32147 126
አቶ መሐመድ አብዲ እና አቶ አብዱራሂም አብዲ
የሰ/መ/ቁ 32376 129
አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሸዋንግዛው
የሰ/መ/ቁ 32638 134
የቂርቆስ ክ/ከተማ መሰረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና እነ አቶ ይርጋ ንጋኔ
የሰ/መ/ቁ 33606 139
የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ደጀኔ አበበ
የሰ/መ/ቁ 33824 144
የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሰረተ ልማትና የቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና የቀኛዝማች መኮንን ነጋሽ ወራሾች
የሰ/መ/ቁ 34249 152
እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ እና እነ አቶ አለሙ ወንድሙ
የሰ/መ/ቁ 34313 155
የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እና ከበደ ታደሰ
የሰ/መ/ቁ 35403 160
አቶ አብዱልነጢፍ ሙሄ እና እነ ትዕግስት በርሃ፣ደምስስ ተማም

የንብረት ህግ 164

የሰ/መ/ቁ 22008.....165
የኪራይ ቤቶች አ/ድርጅት እና አነ አቶ ኦላና ጥርቅና

የሰ/መ/ቁ 22297 170
የጅማ ከተማ የአካባቢ አስተዳደት ጽ/ቤት እና አቶ ሸዋረገድ አባድር
የሰ/መ/ቁ 22469 173
የጅጅጋ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያ እና እነ አዳነች መንግስቱ
የሰ/መ/ቁ 22719 176
የአ/አ/ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተተኪ የመሬት ልማትና አሰተዳደር እና አቶ ነጋሽ ዱባለ
የሰ/መ/ቁ 23608 179
የኢትዮጵያ ፕራይቬታይሽንናየመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጂንሲ እና የአቶ ኑር በዛ ተረጋ ወረሾች
የሰ/መ/ቁ 24269 ----------185
የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና ተክለማርያም መኮንን
የሰ/መ/ቁ 26130 188
አቶ ገ/እግዚአብሔር ከበደው እና ወ/ት ሰላማዊት ወ/ገብርኤል
የሰ/መ/ቁ 27506.....192
እነ ሣሙኤል ውብሸት እና ብዙነህ በላይነህ
የሰ/መ/ቁ 27600.....196
ሕብረት ባንክ አክሲዮን ማኅበር እና እነ አቶ ጀማል መሐመድ
የሰ/መ/ቁ 29005 200
አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እና አቶ ግርማቸው ይላላ ፣ እና አዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን
የሰ/መ/ቁ 30101 203
አቶ ገዛሽኝ አድነው እና እነ ወ/ሮ ዳሳሽ ባይነሳኝ
የሰ/መ/ቁ 30461 206
የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እና አቶ ኢሳ መሐመድ
የሰ/መ/ቁ 33499.....210
አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና እነ አቶ ዶቶሮ ደሌቦ

የሰ/መ/ቁ 33711 214
በቀድሞ ወረዳ 3 ቀበሌ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ክብርነሽ ቀደመ
የሰ/መ/ቁ 33831.....218
አቶ ሀሰን ኢብራሂም እና አቶ ኢብራሂም ይመር ሐሰን
የሰ/መ/ቁ 33924 222
ወ/ሮ ገብርኤላ ሂኮላቶማስ እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ
የሰ/መ/ቁ 34406.....225
ወ/ሮ መገርቱ ነጋሣ እና እነ ወ/ሮ ፀሃይ ልጋ

ይርጋ 229

የሰ/መ/ቁ 20295 230
አቶ ደጀኔ ለገሠ እና እነ አቶ መላኩ ጌታቸው
የሰ/መ/ቁ 25567 235
ወ/ት አይናለም አበበ እና አቶ ደገፉ ጉርሙ
የሰ/መ/ቁ 25664 239
አቶ ተገኝ ይማም እና እነ አቶ ካሣሁን ደሳለኝ
የሰ/መ/ቁ 26422 249
ወ/ሮ ስንልሽ ማዘንጊያ እና እነ አቶ ተስፋ ማዘንጊያ
የሰ/መ/ቁ 28686 251

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ግዛው መንጀታ
የሰ/መ/ቁ 28997 254
ሰለአሶሳ ዞን ግብርና እና ትምህርት መምሪያዎች የቤኒሻንጉል ጎምዝ ክልል መንግሥት ፍትህ ቢሮ፣ እና በላይ ወርቁ
የሰ/መ/ቁ 29920 257
የባህርዳር ጨ/ጨ/አ/ ማኅበር እና አቶ አመሸ ሰይድ
የሰ/መ/ቁ 31185 261
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 31217 265
ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ጫሊ ሐሰን

የሰ/መ/ቁ 31857 269
መሐመድ አብደላ እና የድሬደዋ ኢትዮ ጅቡቲ ም/ባቡር
የሰ/መ/ቁ 32013 272
ደምስ ጥበበሥላሴ እና ቴዎድሮስ ጥበበሥላሴ
የሰ/መ/ቁ 32217 275
ወ/ሮ እማዋይሽ አበራ እና ወ/ሪት እልፍነሽ ሸዋዬ
የሰ/መ/ቁ 32788 278
የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና አቶ ግርማ ተገኝ
የሰ/መ/ቁ 34011 282
እልፍነሽ አማረ እና እነ አቶ ግርማ አማረ
የሰ/መ/ቁ 31748 285
ይስማው ድረስ እና እነ ይበልጥል ፍቅር

የአስሪና ሰራተኛ ህግ 288

የሰ/መ/ቁ 18832 289
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ከበደ ቱሉ
የሰ/መ/ቁ 20416 293
አቶ ቢኒያም ገረመው እና የቻይና መንገድና ድልድይ ሥራ ድርጅት
የሰ/መ/ቁ 20670 296
የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ሰለሞን በርሄ
የሰ/መ/ቁ 21329 299
የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ በቀለ ኩምሳ
የሰ/መ/ቁ 22275 305
የኢ/ት ንግድ ባንክ እና አቶ ኃይሌ ገ/ሥላሴ
የሰ/መ/ቁ 25317 310
ጥቁር አባይ ትራንስፖርት እና ደሳለኝ አብርሃ
የሰ/መ/ቁ 25511 313
የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ አብራራው ከፍያለው
የሰ/መ/ቁ 25765 317
ኃይለሚካኤል ይህደጎ እና ግርማ አየለ
የሰ/መ/ቁ 26077 320
አቶ አይናለም ባይሌ እና የኢት/ንግድ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 27704 323
ድራጋዶስ ጄ እና ፒ የመንገድ ሥራ ድርጅት እና አብዲ ሁሴን
የሰ/መ/ቁ 27959 325
የኢት/ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ አሊ መሐመድ አሊ
የሰ/መ/ቁ 29692 327
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ከበደ
የሰ/መ/ቁ 29740 331
አቶ ስሜነህ ተክሉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 29866 336
ቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን እና ወርቅነህ ምህረቱ
የሰ/መ/ቁ 29949 340
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ዋሲሁን አዳነ
የሰ/መ/ቁ 30956 344
የወረዳ 5 አጠቃላይ ነጋዴዎች ማኅበር እና አቶ በድሉ ጫላ
የሰ/መ/ቁ 31402 348
የኢትዮጵያ አገር አቋርጭ ከፍተኛ አውቶብስ የግል ባለንብረቶች ማኅበር እና አቶ አያሌው ይርጉ
የሰ/መ/ቁ 32545 351
አቶ ግርማ ሽፈራው እና የክርስቲያን በጎ አድራጎት ልማት ድርጅት
የሰ/መ/ቁ 33314 355
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ወልዴ
የሰ/መ/ቁ 33513 361
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ዘውዴ ተናኘ
የሰ/መ/ቁ 34585 364
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ደረጀ ወልደኪዳን
የሰ/መ/ቁ 35440 367
ዋልያ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ድርጅት እና ብርሃኔ አሊማ
የሰ/መ/ቁ 29415 370
ዎተር አክሽን እና ይልማ አሰፋ
የሰ/መ/ቁ 32822 374
ጂ.ሰቨን የንግድና ኢንዱስትሪ የመኸር ቃጫ ውጤቶች ፋብሪካ እና መኮንን አበራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 32229 377
መሪጌታ ልሣነወርቅ በዛብህ እና ጠቅላይ ቤ/ክህነት ጽ/ቤት
የሰ/መ/ቁ 29419 381
ሬቫ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር እና እነ እንዳለ ታደሰ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍትሀብሄር
ሥነ ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 08751

ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ አበበች በጅጋ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ
2. ሲ/ር አየሁብዙ ይመኑ } ጠበቃ ደሳለኝ ዓለሙ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ችሎቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፌዴራል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች አመልካችና ተጠሪዎች ግንቦት 13 ቀን 1979 ዓ.ም. ያደረጉት የመያዣ ውል ግንቦት 21 ቀን 1979 ዓ.ም. በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል አልተተካም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔውን በመሻር በግራ ቀኙ መካከል ተደርጎ የነበረው የመያዣ ውል ቀጥሎ በተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ተተክቷል በማለት ጥቅምት 12 ቀን 1996 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበን ሠነድ መሠረት በማድረግ ስለሆነ የቀድሞው ውሣኔ እንዲሰረዝ ይወሰንልን በማለት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 6 መሠረት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ የአሁን ተጠሪዎች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩ ሲጀመር ከሣሾች የነበሩ ሲሆን በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ግንቦት 13 ቀን 1979 ዓ.ም. በተፈረመ የቤት መያዣ ውል ብር 60,000 /ስልሳ ሺህ/ ከተከሳሽ ከአሁን አመልካች ተበድረናል፡፡ ለብድሩ አፈፃፀምም በመያዣነት የአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 24 ቀበሌ 13 ክልል የሚገኘውን የቤ.ቁ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1099 የሆነውን ባለ አንድ ፎቅ ከነካርታው ለተከሣሽ አስረክበናል፡፡ የመያዣ ውሉ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ለ10 ዓመት ጸንቶ የሚቆይ ሲሆን የውሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ ተከሳሽ የብድሩን ገንዘብ ተቀብለው ቤቱን ለማስከረብ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ገንዘቡን ተቀብለው ቤቱን እንዲያስረክቡ ኪራይም እንዲከፍሉ ይወስንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የተጠሪዎች ክስ ለአመልካች ደርሶም በሰጡት መልስ ግንቦት 13 ቀን 1979 ዓ.ም. የመያዣ ውል ማድረጋቸውን ሳይክዱ ነገር ግን ግንቦት 21 ቀን 1979 ዓ.ም. በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የመያዣ ውሉ የተተካ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጽሁፍ ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በቃል አከራክሮ ከሳሾች በአንድ በኩል የመያዣ ውሉ ሳይፈርስ የሽያጭ ውል ሊደረግ እንደማይችል ተደርጓል ቢባል እንኳን ሥርዓቱ ያልተሟላ እንደሆነና በሰነዱ ላይ ያረፈውንም ፊርማ ክደው በመከራከራቸው ግንቦት 21 ቀን 1979 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለውን ውልና የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞችን ዋናውን ኮፒ ተከሣሽ እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሠጥቶ ማቅረብ ያልቻሉ ሲሆን ከዚያም ፍ/ቤቱ የፊርማ ማስመርመሩ ሂደት ይቀጥል የነበረው የመያዣ ውሉን የተካው የቤት ሽያጭ ውል በአግባቡ ተቋቁሟል የሚባል ከሆነ ነው ካለ በኋላ ነባሩ ውል በአዲስ ውል ተተክቷል ወይንስ አልተተካም የሚለውን ጭብጥ መስርቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1828 መሠረት መተካት አለ ለማለት የሚቻለው ነባሩ ግዴታ በግልጽ በአዲስ ግዴታ የተተካ ስለመሆኑ በሚገለጽበት ጊዜ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

ነገር ግን ግንቦት 21 ቀን 1979 ዓ.ም. በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ከላይ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1828 መሠረት የቀድሞው የመያዣ ውል ቀሪ ስለመደረጉና በሽያጩ ውል የተተካ ስለመሆኑ ያልተገለጸ ስለሆነ የመያዣ ውሉ በሽያጭ ውል ተተክቷል ለማለት አይቻልም ካለ በኋላ የመያዣ ውሉ በሽያጭ ውሉ አልተተካም የሚባል ከሆነ ከሣሾች ባቀረቡት የመያዣ ውል መሠረት ለመፈጸም ይገደዳሉ በማለት በውሣኔው ላይ

አስፍሮ ከሳሾች የተበደሩትን ብር 60,000 (ስልሳ ሺህ) ለተከሣሽ እንዲከፍሉና ተከሣሽም በመያዣ የያዙትን ቤት ለከሳሾች እንዲያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅሬታ ያደረባቸውም ተከሣሽ የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ በማጽናት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

ከዚህ በኋላም ተከሣሽ ለሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው የመያዣ ውሉ በሽያጭ ውል አልተተካም ተብሎ መወሰኑ እንደዚሁም የቤት ሽያጭ ውሉ ኮፒ ተቀባይነት ሳያገኝ የመቅረቱ አግባብነት ሊጣራ እንደሚገባ በመታመኑ አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን በማከራከር የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1826 እና 1828 ድንጋጌዎች መሠረት ተዋዋይ ወገኖች ቀድሞ የነበራቸውን ግዴታ በአዲስ ለመተካት እንዲቻል የመጀመሪያውን ግዴታ በማያጠራጥር አኳኋን የሚያስቀር ፈቃድ ሊኖር እንደሚገባ የሚደነግጉ ሲሆን በምትክ ውሉ ላይ የቀድሞውን ውል ቀሪ ስለማድረግ በግልጽ ማስቀመጥ እንደሚገባ አይገልጽም፡፡ በአንፃሩ ግን አዲሱ ግዴታ የመጀመሪያውን ግዴታ በማያጠራጥር አኳኋን የሚያስቀር መሆን እንደሚገባው የሚደነግግ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይም የነበረው የቀድሞው ግዴታ የመያዣ ውል ሲሆን አዲሱ ግዴታ ደግሞ የሽያጭ ውል እንደመሆኑ መጠን ይህም ቀድሞ የነበረውን ግዴታ በማያጠራጥር ሁኔታ የተካው መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት የሕግ አተረጓጎም ሲታይ በምትክ ውል ላይ የቀድሞው ውል ቀሪ ስለመደረጉ ስላልተጠቀሰ የመያዣ ውሉ በሽያጭ ውል አልተተካም ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ተሽሯል በማለት ጥቅምት 12 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ይህ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላም ተጠሪዎች ታህሣሥ 4 ቀን 1998 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ ውሣኔ የተሰጠው በሐሰት ተዘጋጅቶ በቀረበ ማስረጃ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመስርቶ መሆኑን በመግልጽ ውሣኔው እንዲሰረዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 6 መሠረት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአቤቱታውም ይዘት ተጠቃሎ ሲታይ አመልካች ግንቦት 13 ቀን 1979 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለው የመያዣ ውል ግንቦት 21 ቀን 1979 ዓ.ም. በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ተተክቷል ቢሉም በማስረጃነት ያቀረቡት ኮፒ የሽያጭ ውል በከፍተኛ ጥንቃቄ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይኽውም የኢትዮጵያ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ኮፒ ሰነድ ሊመረምር እንደማይችል አመልካች ስለሚያውቁ ለፍ/ቤቱ ያቀረቡት ፎቶ ኮፒውን ብቻ ነው፡፡ ይህም ሰነድ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡ ክርክሩ ሲካሄድ ሰነዱ በሐሰት የተዘጋጀና ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ በሰነዱ ላይ እንደፈረሙ ተደርጎ በማስመሰል የተፈረመ እንጂ የእሳቸው ፊርማ አለመሆኑን ጠቅሰን የተከራከርን ከመሆኑም በላይ ዋናው ካልቀረበ ፎቶ ኮፒው ሰነድ ብቻውን ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ እንደማይችልም መቃወሚያ ቀርቦበት ነበር፡፡

በወቅቱ ሰነዱ በፖሊስ በኩል እንዲመረመር ጥረት አድርገን ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ ጥረታቸውን በመቀጠል በአሜሪካን አገር በዊስትቸስተር ኢሎኖስ በሚገኝ የአሜሪካን የኮሌጅ ፎረንሲክ መማሪያዎች ብሔራዊ የሰነዶች መርማሪያዎች ማኅበር እንዲመረመር በማድረጋቸው ክርክር ያስነሳው ሰነድ በዶ/ር ተስፋዬ አካሉ ያልተፈረመ እንደሆነ እ.ኤ.አ. ታህሣሥ 1 ቀን 2005 ሊረጋገጥ ችሏል፡፡

ይህ ማስረጃ በሐሰት የተዘጋጀ መሆኑ ቀደም ብሎ ቢታወቅና ቢገለጽ ኖሮ ፍ/ቤቱ ውሣኔውን ሊሰጥ እንደማይችል የሚታመን በመሆኑ ጥቅምት 12 ቀን 1996 ዓ.ም. በሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ ይሰረዝልን የሚል ነው፡፡

በአስረጂነትም ግንቦት 21 ቀን 1979 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ከሌሎች ማመሳከሪያ ሰነዶች ጋር በአሜሪካን አገር በሚገኝ የአሜሪካን የኮሌጅ ፎረንሲክ መርማሪዎች ብሔራዊ የሰነዶች መማሪያዎች ማኅበር በኩል ተመርምሮ ሰነዱ የተጭበረበረ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች ያቀረቡት አቤቱታ ለአመልካች ደርሶም ጥር 22 ቀን 1998 ዓ.ም. የተፃፈ 3 ገጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የአመልካች መልስ ይዘት ጠቅለል ተደርጎ ሲታይም በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ተጠሪዎች ያነሱት ክርክር የመያዣ ውሉ ሳይፈርስ የሽያጭ ውል ተደርጓል ለማለት አይቻልም፡፡ ተደርጓል ቢባል እንኳን ፊርማው ያልተሟላ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ሊቀበለው አይገባም፡፡ ይህም ቢሆን ውሉን ተቀብለን ፊርማውን መካዳችን አይደለም ፊርማውም ሊመረመር አይገባውም በማለት ውሉን ሳይክዱ በመከራከራቸው የሥር ፍ/ቤትና ሰበር ችሎት አምነውበት በሰነዱ ላይ ውሣኔ የሰጡበት ስለሆነ በዚያው ነገር ላይ ሁለተኛ ክስ ማቅረባቸው ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 አኳያ በአግባቡ አይደለም፡፡

አቤቱታው ተቀባይነት አለው ቢባል እንኳን የቀረበው ሕጉ ባስቀመጠው የ1 ወር ጊዜ ሳይሆን ሰበር ችሎት ውሣኔ ከሰጠ ከ2 ዓመት በኋላ ስለሆነ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ተመርማሪና ማመሳከሪያ ሰነዱ ወደ ውጭ ሄዶ እንዲመረመር መደረጉ አግባብ ካለመሆኑም በላይ ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት ሰነዶቹ በማያጠራጥር ሁኔታ ከታወቀ የመንግሥት መ/ቤት እንዲቀርብ ሳይደረግና በጥንቃቄም ለመርማሪው ክፍል ሳይልክ ተጠሪዎች ባሉበትና በቅርብ በሚያደርጉት ክትትል ብቻ በዘፈቀደ የሚከናወን ባለመሆኑ በዚሁ ማስረጃ ላይ ተመስርተው የቀድሞው ፍርድ እንዲሰረዝ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም አቤቱታው ሕጉ ባስቀመጠው የ1 ወር ጊዜ እንደቀረበ በመግለጽና የአመልካችን መልስ በመተቸት የመልስ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን በቃል አከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላም ሰበር ችሎቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ እንደሚገባ በማመኑ በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ማስረጃ ለአመልካች ደርሶ ሙሉ ክርክራቸውን እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሠጥቶ ሐምሌ 23

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀን 1999 ዓ.ም. የተፃፈና ከቀድሞው መልስ ያልተለየ 2 ገጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም፡-

- አቤቱታው በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቧል አልቀረበም
- በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቧል ከተባለ ቀደም ሲል ጥቅምት 12 ቀን 1996 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል ወይንስ አይገባም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ አቤቱታውን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተም ፍርድ እንደገና ይታይልኝ የሚል ማመልከቻ ለአቤቱታው መሠረት የሆነው ማስረጃ ከተገኘበት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 6/2/ ላይ የተመለከተ ሲሆን ማስረጃው የሚገኝበትን ጊዜ በተመለከተ የይርጋ ዘመን የሌለ በመሆኑ ፍርዱ እንደገና ይታይልኝ የሚለው ማመልከቻ ማስረጃው እንደተገኘ በማንኛውም ጊዜ መቅረብ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የተጠሪዎች ጠበቃ ማስረጃው የተጭበረበረ ስለመሆኑ አሜሪካን አገር በሚገኙት 1ኛ ተጠሪ አማካይነት ጎዳር 22 ቀን 1998 ዓ.ም. ታውቋል በማለት ታህሣሥ 4 ቀን 1998 ዓ.ም. አቤቱታውን ያቀረቡ ሲሆን ያቀረቡትም ማስረጃ ለአቤቱታው መሠረት ነው የሚሉት ሰነድ ጎዳር 22 ቀን 1998 ዓ.ም. አሜሪካን አገር በሚገኝ የሰነድ ምርመራ ባለሙያ አማካይነት የተመረመረ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

የአመልካች ጠበቃ አቤቱታው የቀረበው የሰበር ችሎት ውሣኔ ከሰጠ ከ2 ዓመት በኋላ ነው ቢሉም ከላይ እንደተጠቀሰው ማስረጃው የሚገኝበት ጊዜን በተመለከተ የይርጋ ዘመን በሕጉ ላይ ያልተመለከተ ከመሆኑም በላይ ተጠሪዎች ለአቤቱታው መሠረት ነው የሚሉት ማስረጃ በተገኘ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ አቤቱታው ያልቀረበ ስለመሆኑ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ አላስተባበሉም፡፡

ስለሆነም የአመልካች ጠበቃ አቤቱታው በ1 ወር ጊዜ ውስጥ አልቀረበም በማለት ያቀረቡት ክርክር የማስረጃ ድጋፍ የሌለው ስለሆነ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

አቤቱታው በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ከቀረበ ጥቅምት 12 ቀን 1996 ዓ.ም. በዚህ ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለውን ሁለተኛ ጭብጥ በተመለከተም በመርህ ደረጃ አንድ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በዚያው ሥረ ነገርና ጭብጥ ላይ ተመስርቶ በተመሣሣይ ተከራካሪ ወገኖች መካከል ድጋሚ ዳኝነት ሊታይ እንደማይችል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 ላይ የተደነገገ ሲሆን ከፍርድ በኋላ አዲስ ማስረጃ በተገኘ ጊዜ ግን ፍርድ እንደገና ሊታይ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 6 ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህም የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ /exception to the general rule/ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 6 መሠረት አንድ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የተሰጠውን ፍርድ ሊያስለውጥ የሚችል አዲስ ማስረጃ በአንድ ተከራካሪ ወገን መገኘት ብቻውን ፍርዱ እንደገና እንዲታይ የማያበቃ ሲሆን ፍርዱን እንደገና ለማየት ማስረጃው በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሰነድን፣ ሐሰተኛ የምስክርነት ቃልን፣ መደለያን ወይንም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሠረት ያደረገ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ በሕጉ ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አዲስ የተገኘው ማስረጃ የውሣኔውን መሠረታዊ ይዘት የሚነካ /Substantially affects the merit of the case/ መሆን አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ ክርክሩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣኑ ሲመለከተው በነበረው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የተጠሪዎች ዋናው የክርክር መስመር ግንቦት 13 ቀን 1979 ዓ.ም. የተደረገው የመያዣ ውል ግንቦት 21 ቀን 1979 ዓ.ም. ተደርጓል በተባለ የሽያጭ ውል አልተተካም የሚል የነበረ ሲሆን በአማራጭም የሽያጭ ውሉ አልተደረገም በማለት ፊርማውንም ክደው ተከራክረዋል፡፡

ፊርማውም የተካደ በመሆኑም አመልካች የውሉን ዋና ኮፒ /ኦርጅናል/ እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም በትዕዛዙ መሠረት ዋናው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠነድ ሳይቀርብ በመቅረቱ ሠነዱ ያልተመረመረ ሲሆን ፍ/ቤቱም የማስመርመሩ ሂደት መቀጠል የነበረበት የመያዣ ውሉን የተካው የቤት ሽያጭ ውል መተካቱ ሕጉ በሚያዘው መሠረት ተደርጓል የሚባል ከሆነ ነው ብሎ በዚሁ ጭብጥ ላይ ተመስርቶ የመያዣ ውሉ በሽያጭ ውል የተተካ ስለመሆኑ በሽያጭ ውሉ ላይ በማያጠራጥር አኳኋን ያልተገለጸ ስለሆነ መያዣው በሽያጭ አልተተካም በማለት ለጉዳዩ እልባት ሰጥቷል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት ለጉዳዩ እልባት የሰጠው በዚህ መልኩ ስለሆነ በጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ በሰበር ችሎት ክርክሩ የታየው የመያዣ ውሉ በቤት ሽያጭ ውል ተተክቷል ወይንስ አልተተካም በሚለው ላይ ተመስርቶ ነው፡፡

የሰበር ችሎት የመያዣ ውሉ በሽያጭ ውሉ ተተክቷል በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ግንቦት 21 ቀን 1979 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ኮፒ ተጠሪዎች ከላይ በተጠቀሰውና አሜሪካን አገር በሚገኝ የሰነድ ምርመራ የግል ተቋም ከሌሎች የተለያዩ ማመሳከሪያዎች ጋር ተነጻጽሮ እንዲመረመር በማስደረግ በሙያው እርግጠኝነትና ምክንያታዊ በሆነ ግምት /Reasonable degree of professional certainty/ ተመርማሪው ሠነድ የተጭበረበረና ፊርማውም የ1ኛ ተጠሪ እንዳልሆነ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ይሁንና የመያዣ ውሉ በሽያጭ ውል ተተክቷል ወይንስ አልተተካም የሚለው በዋናነት በሕግ ላይ የተመሠረተ የሕግ ጭብጥ እንጂ በማስረጃ ላይ የተመሠረተ የፍሬ ነገር ጭብጥ አይደለም፡፡ መተካት አለ ወይንስ የለም የሚለው የሕግ ጭብጥም ዕልባት የሚያገኘው ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1826 እና 1828 አኳያ በመመልከት ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም ጉዳዩን ከዚሁ አንፃር ተመልክቶ መተካት አለ በማለት አስቀድሞ ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተጠሪዎች ዳኝነት እንደገና እንዲታይ አቤቱታ ያቀረቡት ግንቦት 21 ቀን 1979 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለው የቤት ሽያጭ ውል የተጭበረበረ ነው በማለት ነው፡፡ ሆኖም ግን ከላይ እንደተመለከተው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

ክርክር ሲደረግ ሠነዱ የተጭበረበረ መሆኑን አስመልክቶ በተጠሪዎች የቀረበው ክርክር ዋናው ሰነድ ሊቀርብ ባለመቻሉ ምክንያት ፊርማ የማስመርመሩ ሂደት ተቋርጦ ክርክሩ ከመተካት አኳያ ብቻ ታይቶ ውሣኔ የተሰጠ ስለሆነና ይህም ፊርማውን ፍ/ቤቱ የተቀበለው መሆኑን ስለሚያስገነዝብ መተካት የለም በማለት ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሣኔ ተጠሪዎችን ረቺ አድርጎ የነበረ ቢሆንም በፊርማ ረገድ በቀረበው ክርክር ላይ ፍ/ቤቱ ገፍቶ በመሄድ ለጉዳዩ እልባት ሳይሰጥ በመቅረቱ ቅሬታ ካለ በዚህ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለበላይ ፍ/ቤት ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ ድጋሚ ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ የቀረበበትም የሰበር ችሎት ውሣኔ የሰጠው የመያዣ ውሉ በሽያጭ ውሉ ተተክቷል ወይንስ አልተተካም በሚለው ጭብጥ ላይ ብቻ ተመስርቶ ስለሆነ የሽያጩ ውል የተጭበረበረ ነው ቢባል እንኳን በዚህ ላይ ተመስርቶ ውሣኔ ያልሰጠ በመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት ቀደም ሲል የመያዣ ውሉ በሽያጭ ውል ተተክቷል በማለት የሰጠው ውሣኔ ፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 6 መሠረት ተጠሪዎች ባቀረቡት አቤቱታ ሊሰረዝ የሚገባው /Set aside/ አይደለም ብለን አቤቱታውን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በችሎቱ ትዕዛዝ እንዲቀርብ የተደረገው የፖሊስ የምርመራ መዝገብ በመጣበት አኳኋን ይመለስ ብለናል፡፡

ተጨማሪ ትዕዛዝ

ይህ ችሎት መጋቢት 17 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ በዚህ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.19142

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ጌታቸው ምህረቱ

አሰግድ ጋሻው

ሒሩት መለሰ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አቶ መላኩ ማሞ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ፈለቀች ማሞ (3 ሰዎች)

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው በመጀመሪያ ደረጃ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ የተሰጠ ውሳኔ ላይ ከሥረ-ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ የማቅረብ መብትን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

ጉዳዩ የጀመረው በሰ/ሸዋ መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ ከአክስታቸው በውርስ የተላለፈላቸውን ቤት የአሁኑ አመልካች ለብቻው ይዞ ሊያካፍላቸው ፈቃደኛ ባለመሆኑ ቤቱን እንዲያካፍላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካቹ በሰጡት መልስ የኑዛዜ ወራሽነታቸውን ቀደም ሲል በወረዳ ፍ/ቤት አረጋግጠው የጨረሱ በመሆኑ ድጋሚ ክስ ሊቀርብ እንደማይገባው ክሱም ቢሆን በይርጋ የሚቋረጥ እንደሆነና የቤቱ ግምትም የተጋነነ መሆኑን በመግለጽ ተከራክርዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ኑዛዜው በሕጉ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አያሟላም፤ ክሱም በይርጋ አይቋረጥም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎ ቤቱ በባለሙያ እንዲገመት ትእዛዝ ሰጥቶ ውጤቱን ለመጠባበቅ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ብይን ላይ አመልካች ለአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ መልስ ሰጪዎችን ሳይጠራ የይግባኝ ቅሬታውን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 377 መሰረት ዘግቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ኑዛዜው መፍረሱ እና የይርጋው መቃወሚያም ውድቅ መደረጉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅረበዋል፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን ምርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪዎች ላቀረቡት ክስ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያዎቹን ውድቅ በማድረግ ቤቱ እንዲገመት ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ በሥረ-ነገሩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ገና አልሰጠም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320(3) መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ ሲሰጥ ከሥረ-ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ማለት እንደማይፈቀድ እና ይግባኝ ማለት የሚቻለው የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ አመልካች ባቀረቡት የመጀመሪያ መቃወሚያ ላይ ፍ/ቤቱ የመሰለውን ብይን ከሰጠ በኋላ በሥረ-ነገሩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያልሰጠ በመሆኑ ከፍ ሲል በተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት በብይኑ ላይ ይግባኝ ሊቀርብበት አይችልም፡፡ አመልካች በዚህ ብይን ላይ ያላቸውን ቅሬታ ይግባኝ ሊያቀርቡበት የሚችሉት ፍ/ቤቱ በሥረ-ነገሩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም የመጨረሻ ውሳኔ ሳይሰጥ የቀረበው ይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ የሥነ ሥርዓት ሕጉን ያልተከተለ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሰ/ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩ ይግባኝ የማይባልበት መሆኑን ገልጾ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ፋንታ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መዝጋቱ ተገቢ አልነበረም፡፡

ው ሳ ኔ

1. በስረ-ነገሩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሳይሰጥ በመቃወሚያው ላይ ይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ ሊቀረብ አይችልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የሰ/ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 190/97 መጋቢት 06 ቀን 1997 ዓ.ም ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 በመዝጋት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁጥር 20262

ጎንደር 05 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
መስፍን ዕቁበዮናስ
አብዱራሂም አህመድ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ የምስራች - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. የአቶ አሰፋ ባላንጎ ወራሾች አዲሱ አሰፋ - ቀረቡ፡፡
2. የአቶ ታፈሰ ሃሚስ ወራሾች - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የፍርድ አፈጻጸም ክርክር በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግሥት በዳሌ ወረዳ ፍ/ቤት ቀጥሎ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ከፍርድ ባለዕዳዎች /ከተጠሪዎች/ የሚፈለገው ዕዳ ተከፍሏል በማለት የአፈፃፀም መዝገቡን በመዝጋቱ አመልካች የይግባኝ ቅሬታውን ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የዳሌ ወረዳ ፍ/ቤት አፈጻጸሙን የቀጠለው የክልል 14 ዞን ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 372 በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ስለሆነ የወረዳው ፍ/ቤት በሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ይግባኝ ባይ ቅሬታ ካደረበት የይግባኝ አቤቱታውን ማቅረብ የሚገባው አፈጻጸሙ በወረዳው ፍ/ቤት እንዲቀጥል ውክልናውን ከሰጠው ከክልል 14 ዞን ፍ/ቤት በላይ ለሚገኝ ፍ/ቤት እንጂ ለሲዳማ ዞን ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረቡ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 374 አኳያ በአግባቡ አይደለም በማለት ትዕዛዝ በመሰጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ የአሁን አመልካች በብድር የተወሰደ ገንዘብ እንዲከፈለው በዋናው ባለዕዳና በዋሶቹ ላይ በቀድሞው የኢ.ህ.ዲ.ሪ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ መስርቶ ውሣኔ ከተሰጠና አፈፃፀሙም በኋላ በተቋቋመው የክልል 14 ዞን ፍ/ቤት ቀጥሎ እንዳለ የ1ኛው የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ከፍ/ቤቱ የግዛት ሥልጣን ክልል ውጭ በዳሌ ወረዳ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን ክልል እንደሚገኝ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አፈጻጸሙ በዚህ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲቀጥል የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 372 በሚፈቅደው መሠረት የዞኑ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሠጥቶ በዚሁ ትዕዛዝ መሠረት አፈፃፀሙ በዳሌ ወረዳ ፍ/ቤት ቀጥሎ በፍርድ ባለዕዳዎች ወራሾች የሚፈለገው ዕዳ መከፈሉ ተረጋግጧል በማለት ፍ/ቤቱ የአፈጻጸሙን መዝገብ በመዝጋቱ የይግባኝ አቤቱታ ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት ይግባኙን ሳይቀበል ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ የሚችለው ለየትኛው ፍ/ቤት ነው የሚለው ነጥብ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት አልችልም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው የመቅረቱ አግባብነት ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ፍርድን እንዲያስፈጽም የታዘዘ ፍ/ቤት የሚኖረው ሥልጣን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 374/ለ/ ላይ የተመለከተ ሲሆን በዚሁ መሠረትም ፍርዱን እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍ/ቤት ስለ ፍርዱ አፈጻጸም የሚሰጠው ትዕዛዝና በትዕዛዙም ላይ ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ ያለው ሥልጣን ዋናውን ፍርድ ከወሰነው ፍ/ቤት ሥልጣን ጋር እኩል ሆኖ እንደሚቆጠር ተመልክቷል፡፡

ዋናውን ፍርድ የሰጠው ከላይ እንደተጠቀሰው የኢ.ህ.ዲ.ሪ. ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ይህንን ፍርድ እንዲያስፈጽም የታዘዘው ደግሞ የዳሌ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ትዕዛዙንም ያስተላለፈው የኢ.ህ.ዲ.ሪ. ከፍተኛ ፍ/ቤትን የተካው የክልል 14 ዞን ፍ/ቤት ነው፡፡ ዋናውን ፍርድ የፈረደው ፍ/ቤት የኢ.ህ.ዲ.ሪ. ከፍተኛ ፍ/ቤት የነበረ ቢሆንም ይህ ፍ/ቤት በሌላ ፍ/ቤት ከተተካ በኋላ የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ በክልል 14 ፍ/ቤት ከዚያም በፌዴራል ፍ/ቤት ተተክቷል፡፡

በወቅቱ ዋናውን ፍርድ የፈረደው የኢ.ህ.ዲ.ሪ. ከ/ፍ/ቤት ክስ ከቀረበበትም ሆነ ፍርድ ከተሰጠበት የገንዘብ መጠን አኳያ የነበረው የሥረ-ነገር ሥልጣን አሁን ካለው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጋር እኩል ሲሆን ይህም ማለት አሁን ባለው የፍ/ቤቶች አወቃቀር ዋናውን ፍርድ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት እንደፈረደ ይቆጠራል ማለት ነው፡፡

የዳሌ ወረዳ ፍ/ቤትም ይህንኑ የአፈጻጸም ጉዳይ ሲመለከት ዋናውን ውሣኔ እንደሰጠ ከሚቆጠረው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ጋር እኩል ሥልጣን እንደሚኖረው ከተጠቀሰው የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም በዳሌ ወረዳ ፍ/ቤት የሚሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ደረጃ እንደተሰጠ የሚቆጠር ከመሆኑም በላይ ክስ የቀረበበትም ሆነ ፍርድ ያረፈበት የገንዘብ መጠን በወረዳው ፍ/ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ የወረዳው ፍ/ቤት እኩል ሥልጣን እንዳላቸው መገንዘብ ስለሚቻል ይግባኙ መቅረብ ያለበት ከወረዳው ፍ/ቤት ቀጥሎ ለሚገኘው ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለሆነ የዞኑ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በይግባኝ ለማየት አልችልም በማለት ሳይቀበለው መቅረቱ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 3019 በመጋቢት 12 ቀን 1997 ዓ.ም. ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት አልችልም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ያለው ስለሆነ የቀረበውን ይግባኝ መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 20465

ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሃመድ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች..... አዋሽ ኢንተርናሽናል ኩባንያ ጠበቃ ጐሣዬ ጉርሙ ቀረቡ

መልስ ሰጪ..... ፀሐይ ዮሐንስ የህፃን ተመስገን ቱጂ ሞግዚትና አሳዳሪ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥረ ነገር ሥልጣንን በሚመለከት የፊዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአሁኑ መልስ ሰጭ ፀሐይ ዮሐንስ በህፃን ተመስገን ቱጂ ላይ በደረሰው የአካል ጉዳት ምክንያት በጉዳት አድራሹ እና ጉዳት ባደረሰው ንብረት ባለቤት ላይ የካሣ ጥያቄ (ክስ) አቅርበዋል፡፡ ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበውም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን በከሳሽና በተከሳሽ መካከል በተነሳው የካሣ ክርክር የአሁኑ አመልካች ጣልቃ ገብቶ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የተከራካሪ ወገኖችን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ ተከሣሾችንም ሆነ ጣልቃ ገቡን ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ጠቅሶ ለደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝን አቤቱታውን ለፊዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

የፊዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በይግባኝ የአሁን አመልካችና መልስ ሰጪን ካከራከረ በኋላ፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችለው የስረ ነገር ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ነጥብ መስርታል ይህንንም አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ለመወሰን ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚከተሉትን ምክንያቶች አስፍሯል፡፡

ይግባኝ ባይ የይግባኝ አቤቱታውን ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊያቀርብ የቻለው ይግባኝ ባዩ በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገበ ወይም የተቋቋመ የንግድ ድርጅት መሆኑን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይግባኝ ባይ በሁለት የአንድ ክልል ነዋሪዎች መካከል በተነሳ የፍትሐብሔር ክርክር ላይ ጉዳት ላደረሰው መኪና የመድን ሽፋን በመሰጠቱ የተነሳ ጉዳት አድርሷል በተባለው መኪና ባለቤት እግር ተተክቶ ጣልቃ ገብቶ ከመከራከሩ በስተቀር የራሱን መብትና ግዴታ በሚመለከት የቀረበበት ክስ አልነበረም፡፡ በስር ፍ/ቤትም የፍ/ቤቱን ሥልጣን አስመልክቶ ያነሳው ክርክር አልነበረም፡፡ ስለሆነም ክሱ የፌዴራል ጉዳይን የሚመለከት ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ ለመወሰን የሚያስችለው ስልጣን የለውም፡፡ ስለሆነ በፍ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(2) መሠረት ውሣኔውን አጽንቶን ይግባኙን ሰርዘናል በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይኸው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚልበትን ነጥብ በመንቀስ እንዲታረምለት ነው፡፡ ነጥቦቹም፡-

- ሥልጣንን አስመልክቶ በተከራካሪ ወገን ክርክር ሳይነሳ ፍ/ቤቱ በእርሱ አነሳሽነት ማንሳቱ የሥነ ሥርዓት ግድፈት መፈጸሙን ያሳያል፡፡
- የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ውሣኔ የሰጠው ክርክሩ ከያዘው የገንዘብ መጠን አንፃር በህገ-መንግሥቱ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን በመተካት ስለሆነ እንጂ ጉዳዩ የፌዴራል ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ ውሣኔ እንዲሰጥ አዋጅ ቁጥር 322/95 ስለሚከለክለው የይግባኝ አቤቱታው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረቡ ስነ-ሥርዓታዊ ሆኖ እያለ ውድቅ መደረጉ ህጉን መሰረት ያደረገ አይደለም የሚሉት ናቸው፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ክሱም ሆነ የይግባኝ አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱን፣ ይግባኙን ተመልክቶ ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችለው የሥረ -ነገር ሥልጣን የሌለው መሆኑን ከተረዳ ለሌላው ተከራካሪ ወገን ስለዚሁ ጉዳይ ክርክር ባይቀርብበትም ከፍርድ በፊት በማንኛውም ጊዜ በራሱ አነሳሽነት አንስቶ መዝገቡን መዝጋት የሚችል ስለመሆኑ በሥነ-ሥርዐት ህጉ በአንቀጽ 9፣231፣207፣211 እና 228 የተደነገገ በመሆኑ በዚህ ረገድ ይህ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበው/ በማለት የቀረበው ክርክር የህግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ 2ኛውን ነጥብ በሚመለከት በመጀመሪያ ክርክሩ የተነሣው የክልሉ ነዋሪ በሆኑ ሁለት ግለሰቦች መካከል ነው፡፡ በዚህ ክርክር አመልካች ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ተፈቅዶለታል፡፡ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በተፈቀደለት ጊዜ ጣልቃ ገቢው በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገበ ወይም የተቋቋመ የንግድ ድርጅት በመሆኑ ምክንያት ብቻ ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር እንዲወድቅ ሊያደርገው ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ አመልካች የይግባኙ ጉዳይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ ይገባዋል ለሚለው አቤቱታው መሠረት ያደረገው የከፍተኛ ፍ/ቤትን ስለማደራጀት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 322/95ን በመጥቀስ ነው፡፡ የዚህ አዋጅ ይዘት እንደሚያስረዳው ክርክር የተነሣበትን የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልልን ጨምሮ በ5ቱም ክልሎች የሚገኙ ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ቀደም ሲል በፌዴራል ጉዳይ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80/2 በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሰረት ስለከፍተኛ ፍ/ቤት ሆነው በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣናቸው ጉዳዮችን ተቀብለው ለማየትና ለማስተናገድ ተሰጥታቸው የነበረው ሥልጣን ቀሪ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ የነዚህ ክልሎች ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ባላቸው የውክልና ስልጣን ያዩትን የፌዴራል ጉዳይ በይግባኝ ተቀብለው ለማየት ያላቸውን ሥልጣን ያስቀረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ከማቅረብ የሚያግደው ምክንያት አልነበረም፡፡ እራሱ ባነሳው የክርክር መስመርም ቢሆን ይህንኑ ለመንቀስ ታስቦ እንጂ ክርክር ያስነሳው ጉዳይ በይዘቱ የፌዴራል ጉዳይ ነው ለማለት ተፈልጎ አይደለም፡፡

ስለሆነም ሥልጣንን አስመልክቶ የፌዴራል ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ተወስኖ ነገሩን ሰምቼ ለመወሰን የሚያስችለኝ ሥልጣን የለኝም በሚለው ውሣኔ መገደብ ሲገባው ከዚህ አልፎ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቶን ይግባኙን ሠርዘናል ማለቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሳ ኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ.ቁ.38232 ግንቦት 18 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡ ከዚህ በፊት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 21270

ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ ወይንሸት አበራ በሌለችበት የሚታይ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የዕግድ ይነሳልኝ ጉዳይ አስመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ ሆነው በወ/ሮ አስናቀች ቶለሣ ላይ ክስ አቅርበዋል፡፡ የዚህም ክስ ውጤት እስከታወቀ ድረስ የተከሳሽ የወ/ሮ አስናቀች የሆነው ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ታግዶ ይቆይ ዘንድ ክሱ በቀረበለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154 መሠረት የዕግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ አድርገዋል፡፡

አመልካችም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለወ/ሮ አስናቀኝ ቶለሣ በሰጠው የብድር ገንዘብ ምክንያት ይህንኑ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ንብረት አስቀድሞ በመያዣ የያዘው መሆኑንና የብድር ገንዘቡ እንደ ውሉ ባለመመለሱ፤ ተበዳሪ ዕዳውን ለመክፈል ባለመቻሏ ምክያት በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንኑ በመያዣ የተያዘውን ንብረት ለመሸጥ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ከላይ በተገለፀው አካኋን በፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት መሆኑን በመረዳቱ አስቀድሞ በመያዣ የያዘው መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመግልጽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 158 መሠረት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳለት ጠይቋል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ ንብረት በፍ/ቤት ትዕዛዝ ታገደ ማለት የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ወገን በንብረቱ ላይ መብት አግኝቷል ማለት አይደለም፡፡

የቀረበውም የዕግድ ይነሳልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት በአፈፃፀም ጊዜ ከቅድሚያ መብት ጋር ተያይዞ የሚታይ እንጂ በዚህ መዝገብ የሚስተናገድ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡

የይግባኝ አቤቱታ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤትም በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ በአጭሩ በተመለተው አኳኋን በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ይታረምልን የሚልበትን ክርክር በማቅረቡ ነው፡፡

በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 158 መሠረት ሊነሳ አይገባም የመባሉን አግባብነት መልስ ሰጭ ባለበት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና መልስ ሰጭም የበኩላቸውን ክርክር እንዲያቀርቡ ጥሪ ቢያደርግላቸውም በጥሪው መሠረት ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከሣሽ የሆነ ወገን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረትም ይሁን ወይም ደግሞ የባለመብቶችን ጥቅም ለመጉዳት ሲል ንብረቱን ለሌላ ሰው አሳልፎ ለመስጠት ያቀደ ወይም ያሰበ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ይኸው ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ለሦስተኛ ወገን ሳይተላለፍ ታግዶ እንዲቆይ የማስደረግ መብት እንዳለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154/ሀ/ እና /ለ/ ተደንግጓል፡፡

ከዚህም ድንጋጌ የምንረዳው በዚህ አኳኋን የሚሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ንብረቱ ከመታገዱ በፊት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን ያልተላለፈ ከሆነ ወይም ደግሞ በማናቸውም ምክንያት ሦስተኛ ወገኖች በንብረቱ ላይ መብት ከማግኘታቸው በፊት ሊሆን ይገባል፡፡

የዚሁ ድንጋጌ ዓላማም ከሳሽ ያቀረበው ክስ ወደ ፊት ውጤት የሚያገኝለት ከሆነ በአፈፃፀም ጊዜ ለማሸጥ ወይም በመረከብ እንደ ፍርዱ ይፈፀምለት ዘንድ የተሰጠው የሕግ ጥበቃ ነው፡፡ እንደ ሕጉ ሐሳብ የዕግድ ትዕዛዙ ውጤት ሊያገኝ የሚችለው ይኸው ንብረት በሌላ ዕዳ ምክንያት በሌላ ወገን ያልተያዘ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም ደግሞ በዚህ ንብረት ላይ መብት ያገኙ ሰዎች የሌሉ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ በዚህ ንብረት ላይ የዕግድ ትዕዛዝ በፍ/ቤት ከመስጠቱ በፊት የአሁን አመልካች በሰጠው የብድር ገንዘብ ምክንያት በመያዣ አስቀድሞ ይዞት የነበረ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

ይህም ምክንያት በፍ/ቤት የተሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ ለማስነሳት በቂ ምክንያት ሆኖ ስለሚገኝ አመልካች ዕግዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ቅሬታውን ማሰማቱ እንደታወቀ ከላይ በተገለፀው ዝርዝር ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት የሰጠውን ዕግድ ሊያነሳ ሲገባ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418ን በመጥቀስ ጥያቄው በአፈፃፀም ጊዜ ከቅድሚያ ክፍያ ጋር ተያይዞ የሚታይ እንጂ በዚህ መዝገብ የሚስተናገድ አይደለም፤ ንብረት አሳገደ ማለት በንብረቱ ላይ መብት አገኘ ማለት አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ እና እንዲሁም ባንክ በሰጠው የብድር ገንዘብ ምክንያት በመያዣ የያዘውን ንብረት ተበዳሪው ዕዳውን መክፈል በተሳነው ጊዜ በሐራጅ አሸጦ የብድሩን ገንዘብ የማስመለስ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 97/90 የተሰጠው በመሆኑና ይህ ክርክር የተነሳበት ንብረት በፍ/ቤት ትዕዛዝ ከመታገዱ በፊት ባንኩ በመያዣ ይዞት የነበረ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በሕግ በተሰጠው መብት መገልገል ይችል ዘንድም የሥር ፍ/ቤት ይህንኑ ተገንዝቦ የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ ማንሳት ሲችል ያለ ሕጋዊ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄውን ውድቅ በማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀመ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በከፍተኛ 01 ቀበሌ 06 የቤት ቁጥር 029 በሆነውና በወ/ሮ አስናቀች ተሾሣ ስም ተመዝግቦ በሚገኘው ካፍቴሪያ ላይ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገብ ቁ. 2602 በታህሣሥ 16 ቀን 1991 ዓ.ም. የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 2602 በታህሣሥ 28 ቀን 1995 የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 01359 ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 22556

ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ታደሰ አብዛ

ተጠሪዎች፡- 1. የአቶ ጎሳዬ ሩጋቶ ወርሾች

2. ሳሙኤል ጎሳዬ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከቤት ሺያጭ ውል ጋር ተያይዞ የተነሣን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ክርክሩ ውስጥ የገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ ቁ. 358 ላይ የተመሠረተ መቃወሚያ በማቅረቡ ነው፡፡ መቃወሚያ ያቀረበው ቀደም ሲል በተጠሪዎች መካከል በተካሄደው ክርክር መነሻነት ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ እንዲሻርለት እና ለክርክሩ መነሻ የሆነው ንግድ ቤት ከ2ኛ ተጠሪ ከገዛ ሰው ላይ የገዛው ንብረቱ መሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰንለት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች መቃወሚያውን አልተቀበሉትም፡፡ የሰጡት ምክንያትም አመልካች ቤቱን ሽጦልኛል ያለው (ሃይለማርያም ባዬ የተባለው) በቤቱ ላይ መብት የለውም ተብሎ ተወስኖአል፡፡ ይኸው ሰው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር አድርጎት የነበረው የቤት ሺያጭ ውልም በ1ኛ ተጠሪዎች ከሣሽነት ፈርሶአል የሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አመልካች ታሕሣሥ 27 ቀን 1998 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ አቤቱታውን ያቀረበ ሲሆን፣ተጠሪዎችም ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በጻፉት መልስ ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል ተደረጎ የነበረው ውል ሲፈርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሦስተኛ ወገኖች መብት ምን መሆን ይገባዋል? የሚለውን ነጥብ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

አመልካች ክርክሩ ውስጥ የገባው በግዥ አግኝቻለሁ የሚለውን ንግድ ቤት በተመለከተ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ ለመቃወም አንደሆነ ከላይ ተጠቅሶአል፡፡ የተባለውን ንግድ ቤት ሃይለማርያም ባዬ ከተባለ ሰው ላይ በውል ስለመገዛቱም አላከራከረም፡፡ ሃይለማርያም ባዬ ንግድ ቤቱን ከ1ኛ ተጠሪዎች ወኪል (2ኛ ተጠሪ) ጋር በተደረገው ውል ገዝቶ በራሱ ስም አድርጎት እንደነበረም በመዝገቡ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ደግሞ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች መብት ከሰጠው ሰው ላይ ንግድ ቤቱን መግዛቱን ነው፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያው ውል ማለትም በሃይለማርያም ባዬ እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው ውል ፈርሶአል ቢባል የአመልካቹ መብት የሚወሰነው እንዴት ነው? የሚለውን ነጥብ በአግባቡ ታይቶ ውሣኔ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቹን መቃወሚያ ከጅምሩ ስላላስተናገዱት ጉዳዩ በዝርዝር አልታየም፡፡ በበኩላችን አንደምንገነዘበው አመልካች ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠ ውሳኔ /ፍርድ/ መብቱን የሚነካበት መሆኑን በመግለጽ መቃወሚያ ማቅረቡ ተገቢ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች ክርክሩን በዝርዝር ሳይሰሙ ማሰናበታቸው አግባብ አይደለም፡፡ በመሆኑም በክርክሩ አመራር ረገድ መሠረታዊ ስህተት ተፈጽሞአል ለማለት ችለናል፡፡\

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01927 ሐምሌ 29 ቀን 1996 ዓ.ም፣እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.33512 ጥቅምት 7 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጡአቸው ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ ቁ.348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ ቁ.358 መሠረት ያቀረበው መቃወሚያ በሕግ አግባብ የቀረበ በመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃወሚያውን ተቀብሎ ቀጥለው ባሉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ክርክሩን እንዲሰማ፣በመጨረሻም ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ታዟል፡፡ ይፃፍስት፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 22603

ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሠግድ ጋሻው

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የድሬዳዋ ጊዜ/አስ/ ቀበሌ 20 ጽ/ቤት

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሸሪፍ አሊ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ የቀረበው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በድሬዳዋ በከፍተኛ 04 ቀበሌ 20 ክልል በካርታ ቁጥር 1732 የተመዘገበ ቦታ ላይ የሠፈረውን ቁጥር 034 የሆነ መኖሪያ ቤት አመልካች ለሥር 2ኛ ተከሣሽ በማከራየቱ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ አመልክተው ሚያዝያ 9 ቀን 1984 ዓ.ም. ቤቱን እንዲረከቡ ስለወሰነላቸው አመልካች ቤቱን የተከራዩትን ግለሰብ /የሥር 2ኛ ተከሣሽን/ አስለቅቆ እንዲያስረክባቸው ተከራዩም ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ፤ የባለቤትነት መብትን ያሣያሉ በማለት ያቀረቧቸው ማስረጃዎች እርስ በርሣቸው የተሣከሩ ናቸው፤ ከቤቱም ጋር ግንኙነት የላቸውም ስለዚህ የመክሰስ መብት የላቸውም ቤቱ በአ/ቁ 47/67 መሠረት የተወረሰ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በሰጠው ውሣኔ ቤቱ ያላግባብ የተወረሰ መሆኑ ተረጋግጦ ካልተመለሰልኝ የቤቱ ባለቤት በመሆኔ ተከሣሾች

ቤቱን ይልቀቁ የሚል በመሆኑ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ፍ/ቤቱ ስልጣን አለው፤ ቤቱ በከተማ ልማትና ቤት ኮንስትራክሽን መምሪያ እንዲመለስላቸው ስለተወሰነ ተጠሪ የቤቱ ባለቤት በመሆናቸው አመልካች የሥር 2ኛ ተከሣሽን አስለቅቆ ቤቱን እንዲያስረክባቸው 2ኛ ተከሣሽም ቤቱን ለቀው እንዲወጡ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡

የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም፤ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት በአቤቱታቸው ላይ የጠየቁት የቤት ቁጥር ካርታ 1732 ሲሆን በማስረጃ ዝርዝራቸው ያያያዙት ካርታ ቁጥር 4732 ነው፤ ግብር ለቤቱ ከፍያለሁ በማለት ያቀረቡት ደረሰኝ ለቤት ቁጥር 034 ሣይሆን ለቤት ቁጥር 185 ነው፤ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ይመለስላቸው በማለት የፃፈላቸው ደብዳቤ ላይ የተገለፀው የካርታ ቁጥር 2502 ነው? ይህ የቤት ካርታ ከጉዳዩ ጋር ምንም ግንኙነት ስለሌለው ተጠሪ ክርክር በተነሣበት ቤት ላይ መብት የላቸውም፤ ቤቱ የተወረሰ ነው፤ ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም፤ የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም በአመልካች የተነሱት የቅሬታ ነጥቦች በሰበር ችሎት ሊመረመሩ የሚገባቸው በመሆኑ አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጎ ችሎቱ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር መጋቢት 13 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አድምጧል፡፡ መዝገቡንም እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው ተጠሪ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት በሚያዝያ 9 ቀን 1984 ዓ.ም. የመለሠላቸው በመሆኑ አመልካቹ ያከራያቸውን ግለሰብ አስወጥቶ ቤቱን እንዲያስረክባቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ዋነኛ ክርክሩ በዚህ ቤት ላይ ተጠሪ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን ስላላረጋገጡ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም የሚል ነው፡፡ ለዚህ ለክርክሩ ምክንያት ያደረገው የቤቱ ባለቤት መሆናቸው ለማረጋገጥ ያቀረቧቸው ማስረጃዎች እርስ በእራሣቸው የተሣከሩ ናቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ነው። በተለይ በሰበር አቤቱታው ላይ ተጠሪዋ በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ላይ የገለጹት፣ ከማስረጃ ዝርዝሩ ጋር ያቀረቡት እና የሥራና ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ የተጠቀሰው የካርታ ቁጥሮች የተለያዩ ናቸው፣ ለቤቱ ግብር መክፈላቸውን ለማስረዳት ያቀረቡት ደረሰኝ ለቤት ቁጥር 034 ሚይሆን ለ185 መሆኑን የሚያመለክት ነው በማለት ተከራክሯል። በቃል ክርክር ወቅት ተጠሪ እነዚህ ልዩነቶች መኖራቸውን ሚይክዱ የካርታ ቁጥሩ በታይፕ ስህተት መሆኑን በግብር ደረሰኙ ላይ ደግሞ 185 ተብሎ የተጠቀሰው የቦታው ስፋት በካ.ሜ ሲሆን በስህተት ለአንድ ጊዜ በቤት ቁጥሩ ቦታ ላይ በመፃፉ መሆኑን ገልፀዋል። ይህ ችሎትም ተጠሪ አንድን ነገር ለማረጋገጥ ያቀረቧቸው ሠነዶች የተለያዩ መሆናቸውን ተገንዝቧል።

አንድ ፍርድ ቤት ከሣሽና ተከሣሽ በሚያቀርቡት ክርክር የሚያለያያቸው ሕግ ወይም ፍሬ ነገር ካለ ጭብጡን ከመሠረተ በኋላ መጀመሪያ ከቀረቡት በቀር ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ሙግት አቅርቦ መመርመር የማያስፈልገው ከሆነና በቀረበለት ማስረጃ ብቻ ውሣኔ ቢሠጥ ትክክለኛውን ፍትህ የማያጓድል ከሆነ በዚሁ ማስረጃ ውሣኔ ሊሠጥ የሚችል መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 255 ሥር ተቀምጧል። ነገር ግን የቀረቡት ማስረጃዎች በቂ ባልሆኑበት ጊዜና እነዚህን ማስረጃዎች ብቻ መሠረት አድርጎ መወሰኑ ፍትህን የሚያዛባ ከሆነ ለክርክሩ ትክክለኛ ውሣኔ ለመስጠት ይቻለው ዘንድ ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ምስክር እንዲቀርብ ሊያዝ እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ 257 ያመለክታል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስናመራ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪ የቤቱ ባለቤት ለመሆናቸው ባቀረቧቸው ማስረጃዎች ልዩነት መኖሩን ሚይክዱ የራሣቸውን መከራከሪያ አቅርበዋል። ማስረጃዎቹ ላይ የሚታየው ልዩነትም ተጠሪ በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉትን የባለቤትነት መብት አጠራጣሪ ያደርገዋል። በመሆኑም ልዩነት የሚታይባቸውን ማስረጃዎች ብቻ መሠረት አድርጎ ውሣኔ መስጠቱ ፍትህን ሊያጓድል እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። የሥር ፍ/ቤትም

ተጨማሪ ማስረጃ በማቅረብ ጥርጣሬ ያለበትን ጉዳይ አጥርቶ ሊወስን ሲገባ አልፎ በቀረቡት ማስረጃዎች ብቻ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም።

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 2438 በነሐሴ 24 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01890 በታህሣሥ 18 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለተጠሪ የተመለሰው ትክክለኛው ቤት የቱ እንደሆነ ቤቱን መለሠ የተባለውን የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን መምሪያ ወይም በአሁኑ ወቅት የዚህን አካል መብትና ግዴታ የወሰደውን ተገቢውን አካል በመጠየቅና ጉዳዩን በማስረጃ በማጣራት የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሷል።
3. መዝገቡ ተዘግቷል። ለመ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 23363

ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድነን ኪሮስ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. አቶ ፈርሃን አህመድ - ቀረቡ

2. አቶ አይድድ የሱፍ - ቀረቡ

3. አቶ አብዱልወሃብ አቲዬ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በሥር 1ኛ ተከሣሽ በመከላከያ ሚኒስቴር የምድር ጦር 103ኛ ሠራዊትና በ2ኛ ተከሣሽ አቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/ሕይወት ላይ ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የ1ኛ ተከሣሽ የሆነውን መኪና 2ኛ ተከሣሽ ሲያሽከረክር ሆድሌ በተባለ ቦታ መስመሩን ጥሎ በመውጣት የ1ኛ ከሣሽን መኪና በመግጨት ከጥቅም ውጭ ያደረገ ስለሆነ የመኪናውን ግምት ብር 219 ሺህ እንዲከፍል፣ እንደዚሁም በዚሁ ግጭት ምክንያት ከጥቅም ውጭ በሆነው ንብረትነቱ የ1ኛ ከሣሽ በሆነው መኪና የ2ኛ ከሣሽ ልጅ ተሳፍሮ ሲጓዝ የሞት አደጋ የደረሰበት ስለሆነና ሟችም ለአካለመጠን ያላደረሱ የ2 ሕፃናት ልጆች አባት ስለነበር እነዚህ 2 ሕፃናት አካለመጠን እስከሚደርሱ እነሱን ለማሳደግና ለመንከባከብ በድምሩ ብር 65,520 /ስልሣ አምስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር/ እንደዚሁም ካሣ ብር 74,000 /ሰባ አራት ብር/ በአጠቃላይ ብር 139,520 /መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሃያ/ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ሲሆን 3ኛ ከሳሽም በዚሁ ግጭት የአካል ጉዳት

እንደደረሰባቸው ዘርዝረው በድምሩ ብር 140,000 ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ሶስቱም ከሣሾች በዚህ መልኩ ክሱን ያቀረቡ ሲሆን ተከሣሾች ቀርበው ጉዳቱን አድርሷል የተባለው ተሽከርካሪ በኢትዮጵያ መድን ድርጅት በኩል የመድን ሽፋን የተገባለት መሆኑን ገልፀው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 43 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ ይግባልን በማለት አመልክተው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጣልቃ ገብቶ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳው ክርክር ከተከራካሪ ወገኖች መካከል አንደኛው የፌዴራል መንግሥት አካል በሆነ ጊዜና ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ከብር 500 ሺህ /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በላይ ከሆነ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም የሚል ነው፡፡

በፍሬ ጉዳዩ ክርክር ረገድም ጣልቃ ገብ የደንበኛው ተሽከርካሪ በ3ኛ ወገን ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ብር 100 ሺህ /አንድ መቶ ሺህ ብር/ እንደዚሁም በሰው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት የሰጠው ሽፋን እስከ ብር 30 ሺህ /ሰላሣ ሺህ ብር/ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ጉዳት በ2 ሰዎች ላይ ስለደረሰ በድምሩ ብር 60 /ስልሳ ሺህ/ ሺህ እንደዚሁም በንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት በተሰጠው የመድን ሽፋን ልክ ብር 100 ሺህ /አንድ መቶ ሺህ/ ስለሚሆን በአጠቃላይ ብር 160 ሺህ /መቶ ስልሣ ሺህ/ ጣልቃገብ ካሣ ከሚከፍል በስተቀር በክስ የተጠየቀውን በሙሉ ለመክፈል አይገደድም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍ/ቤቱን የሥረ ነገር ሥልጣን አስመልክቶ በተነሳው መቃወሚያ ላይ ብይን ሳይሰጥ በቀጥታ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የተነሣውን ክርክር መርምሮ 1ኛ ከሣሽን በተመለከተ በግጭቱ ምክንያት መኪናው ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ የሆነ ስለሆነ የመኪናውን የዋጋ ግምት ብር 217 /ሁለት መቶ አስራ ሰባት ብር/ ሺህ 2ኛ ከሣሽን በተመለከተም በአደጋው ምክንያት ልጁ ስለሞተ ብር 91,520 /ዘጠና አንድ ሺህ ብር አምስት መቶ ሃያ ብር/ እንደዚሁም 3ኛ ከሣሽን በተመለከተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለደረሰበት የአካል ጉዳት ብር 60 ሺህ /ስልሳ ሺህ ብር/ እንዲከፈለው በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ጣልቃ ገብ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ነበረው? ወይንስ አልነበረውም? ሥልጣን አለው ቢባልስ የካሳ ክፍያውን አስመልክቶ የሰጠው ውሣኔ አግባብነት አለውን? የሚለው በመሆኑ በዚሁ መሠረት አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተም የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ ለመመልከትና ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም ተብሎ መቃወሚያ የቀረበው በአንድ በኩል ጣልቃ ገብ /አመልካች/ የፌዴራል መንግሥት አካል ነው በሚልና በሌላ በኩልም የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከብር 500 ሺህ /አምስት መቶ ሺህ ብር/ የሚበልጥ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት ነው፡፡

ይሁንና የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በክልሎች ካልተቋቋመ የፌዴራል ጉዳዮችን ክልሎች መመልከት እንደሚችሉ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 78/2/ ላይ የተመለከተ ከመሆኑም በላይ የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከብር 500 ሺህ /አምስት መቶ ሺህ/ የማይበልጥ ስለሆነ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ስላለው በዚህ ረገድ የቀረበው አቤቱታ የሕግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ ችሎቱ አልተቀበለውም፡፡

አመልካች መክፈል የሚገባውን የካሣ መጠን በተመለከተም በንግድ ሕግ ቁጥር 665/2/ ላይ እንደተመለከተው የመድን ገቢው ኃላፊነት በፖሊሲው ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ሊሆን እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን አመልካችም በሰው ላይ ለሚደርስ ጉዳት እስከ ብር 30 ሺህ በ3ኛ ወገን ንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ደግሞ እስከ ብር 100 ሺህ /አንድ መቶ ሺህ/ ካሣ ለመክፈል ለሥር 1ኛ ተከሣሽ የመድን ሽፋን መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡ በዚሁ መሠረትም በአደጋው ጉዳት የደረሰው በ2 ሰዎች እንደመሆኑ መጠን ለእያንዳንዱ ተጎጂ በሽፋኑ መጠን ልክ እንደዚሁም በ3ኛ ወገንም ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት በመድን ሽፋኑ ልክ ታይቶ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ከመድን ሽፋኑ በላይ አመልካች እንዲከፍል በሥር ፍ/ቤቶች መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አመልካች በመድን ውሉ መሠረት በ1ኛ ተጠሪ ንብረት ላይ ለደረሰ ጉዳት ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ እንደዚሁም ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለደረሰው የሞትና የአካል ጉዳት ለእያንዳንዳቸው ብር 30,000 /ሠላሣ ሺህ/ በድምሩ ብር 160,000 /አንድ መቶ ስልሳ ሺህ/ የሥር 1ኛ ተከሣሽን በመተካት ይክፈል በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት አሻሽለን ወስነናል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 23628

ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን እቁበዮናስ

ብርሃኑ አመነው

ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች፡- ሶሎ ሲርካርና ኤ.ኤስ ጠበቃ ከበደ ወርቁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. ጌትያን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ-ጠበቃ ያሲን እንድሪስ

2ኛ. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነ/ፈጅ በቀለ ተፈራ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበው የአሁኑ አመልካች መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ አመልካች በሰበር ቅሬታ ማመልከቻው፣ለክብሪት ሥራ የሚያገለግለውን የመቀስ የንግድ ምልክት እ.ኤ.አ. ከ1921 ጀምሮ በቼክ ሪፑብሊክ የንግድ ምልክቶች መ/ቤት በማስመዝገብ ባለቤትነቱን አስከብሮ መቆየቱን ገልጾ በኢትዮጵያም ውስጥ ምልክቱ እንዲመዘገብለት የአሁኑን 2ተኛ ተጠሪ ጠይቆ ምዝገባው አንዲፈፀም ወስኖ በሂደት ላይ ያለ መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰው የንግድ ምልክቱ ምዝገባ ለኔ ይገባል ሲል የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ አቅርቦት የነበረውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ መሆኑን፤ሆኖም አንደኛ ተጠሪ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይ ክስ መመስረቱን፤በተከሳሽነት የቀረበው የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ብቻ በመሆኑ በክሱ የሚነሱት ጭብጦች አመልካችን በቀጥታ የሚመለከቱ በመሆናቸው በክርክሩ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር እንዲፈቀድለት ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የንግድ ሕግ ቁጥሮች 100፣107፣219፣222 እና 223 ን በመጥቀስ የአሁኑ አመልካች ኩባንያ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላልተመዘገበ

የሕግ ሰውነት የለውም፡፡ የሕግ ሰውነት ከሌለው ደግሞ ፍ/ቤት ቀርቦ ለመከራከር አይችልም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የበታች ፍ/ቤት ውሳኔን እንዳለ አፅድቆታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎት ሚያዚያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት፣የአሁኑ አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ አልተመዘገበም በሚል አቅርቦት የነበረው የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሠበር እንዲቀርብ ወስኖ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡

በመሠረቱ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አመልካች እዚህ አገር በነጋዴነት ያልተመዘገበ ስለሆነ ፍ/ቤት ቀርቦ ለመከራከር አይችልም በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ለውሳኔውም መሠረት ያደረገው የንግድ ሕግ ቁጥር 100 እና የሚቀጥሉትን አንቀጾች በመጥቀስ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የንግድ ሕግ ቁጥር 100 እና የሚቀጥሉት አንቀጾች የሚናገሩት ስለምዝገባ ቢሆንም፣የምዝገባ አስፈላጊነት በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራን ለማካሄድ በዋነኛነት መከናወን ከሚገባቸው መስፈርቶች አንዱ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የንግድ ሥራ መሥራትና የንግድ ምልክትን ማስመዝገብ የተለያዩ ተግባራት መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል፡፡ አመልካች የንግድ ምልክትን በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲመዘገብለት ጠይቆ ጉዳዩ በሂደት ያለ ስለመሆኑ የአሁኑ በሰበር 2ኛ ተጠሪ የሆነው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያረጋገጠለት ስለመሆኑ ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የአሁኑ አመልካች በውጪ አገር ሕግ ተመዝግቦ የሕግ ሰውነት ያለው ኩባንያ መሆኑ ከተረጋገጠና በዚህ ባገኘው የሕግ ሰውነት በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ ቢያነሳ ቀደም ሲል በሌላ አገር የተጎናፀፈው የሕግ ሰውነት እንደሌለ ይቆጠራል የሚያሰኝ ሊሆን አይገባም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ መሠረት የአሁኑ አመልካች በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 41 መሠረት በጉዳዩ ያገባኛል የሚልበትን ምክንያትም የመብቱን ሁኔታ በዝርዝር ገልጾ የነበረ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ከጥያቄው ጋር አግባብነት የሌላቸውን የሕግ ቁጥሮች ጠቅሶ የጣልቃ ገብነቱን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

- የፌ.መ.ደ.ፍ/ቤት በመ/ቁ.3312 በሰኔ 07 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ብይን እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.32181 በጥር 26 ቀን 1998 የሰጡዋቸው ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡
- ይህ ችሎት አመልካች በጉዳዩ ጣልቃ ገብ ሆኖ ለመከራከር የሚያስችለው መብት ያለው ወገን መሆኑን በመቀበል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ ጉዳዩን መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.343/1/ መሠረት መልሶለታል፡፡
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰበር መ.ቁ. 23692

ሐምሌ 03 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ጠበቃ አቶ ጉሳዬ ጉርሙ ቀረቡ፡፡

መልስ ሰጭዎች፡- እነ አሊ መሐመድ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የጉዳዩም መነሻ ነገር የአሁን መልስ ሰጭዎች ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ላየው ለጌዲኦ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት የጉዳት ካሣ ክስ በአራት ተከሳሾች ላይ አቅርበዋል፡፡ 1ኛው ተከሣሽ አበባ ኃ/የተ/የግል ማህበር እራሱን በሚመለከት የሕግና የፍሬ ነገር ክርክር ካቀረበ በኋላ ጉዳት አድርሷል የተባለው መኪና በሌላ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት የአሁን አመልካች አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ካሣ ለመክፈል እስከ ብር 30,000.00 የመድን ሽፋን የሰጠበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት በሦስተኛ ወገን ተከሳሽነት ገብቶ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ይታዘዝልን በማለት ጠይቋል፡፡

በዚህም መሠረት የአሁን አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ደረሰ ለተባለው ጉዳት 1ኛ ተከሳሽ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑንና በካሣው መጠንም ረገድ አለኝ የሚለውን የመከራከሪያ ነጥብ በማንሣት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከፍተኛው ፍ/ቤት ኃላፊነቱንና የካሣውን መጠን በሚመለከት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ 1ኛው ተከሣሽ ለጉዳቱ ኃላፊ ነው፤ ለዚህ ጉዳትም ሊከፍል የሚገባው የካሣ መጠን ብር 41,800.00 (አርባ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ብር) መሆኑ ተረጋግጧል ካለ በኋላ አመልካች ለሚደርሰው ጉዳት እስከ ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ ብር) ድረስ ካሣ ለመክፈል ለ1ኛ ተከሣሽ የመድን ሽፋን ስለሰጠ ይህንኑ ገንዘብ ይከፍላል፤ ቀሪውን ብር 11,800.00 (አስራ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ብር) 1ኛ ተከሣሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤትም በዚህ ቅሬታ መነሻ ጉዳዩን ተመልክቶ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የትዕዛዙ ይዘትም፡-

አመልካች አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ወደ ክርክሩ የገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 መሠረት በተከሳሹ ተጠርቶ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 መሠረት የገባ ወገን ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 40/2/ መሠረት ተከሳሽን ተክቶ ካልገባ በቀር ክሱን ካቀረበው ተጭጂ ጋር መከራከር አይችልም፡፡ ሦስተኛ ወገን ተከሳሹ መከራከር የሚችለው ወደ ክርክሩ ላልገባው ተከሳሽ ኃላፊነት አለብኝ ወይም የለብኝም በሚለው ነጥብ እንጂ ከዚህ አልፎ ተከሳሹ ለከሳሹ ኃላፊ አይሆንም፤ ከሳሹ ያቀረበው የካሣ መጠን የተጋነነ ነው በማለት ከከሳሹ ጋር ሙግት መግጠም አይችልም፡፡ ከከሳሹ ጋር በዚህ መልክ መከራከር ይችል የነበረው በንግድ ህግ ቁጥር 687/1/ እና በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት የክርክሩ መሪ በመሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 40/2/ መሠረት ተከሳሹን ሲተካ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ አልሆነም እንዲሁም አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ቀርቦ ተከሳሹ ለከሳሹ ኃላፊ ሆኖ ቢገኝ በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት ለተከሳሹ ኃላፊ እንደሚሆን አልካደም፤ አምኗል፡፡ ካልካደ እና ካመነ በተከሳሹ እና በሦስተኛ ወገን ተከሳሹ / በአመልካች/ መካከል ክርክር አይኖርም፡፡ ስለሆነም ኢንሹራንስ ኩባንያው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት እስከገባ ድረስ ተከሳሹ ለከሳሽ ኃላፊ አይሆንም፤ ይህንን ያህል የካሣ መጠን

መክፈል የለበትም በማለት ከከሳሹ ጋር በሥር ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ደረጃ መከራከር ስለማይችል የተከሳሽን ኃላፊነትና ይክፈል የተባለውን የካሣ መጠን አስመልክቶ ያቀረበውን ይግባኝ አልተቀበልነውም የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 ድንጋጌን የተፈፃሚነት ወሰን በሚመለከት የሰጠው ትርጓሜ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልን በሚል ነው፡፡

አመልካች በክርክሩ የገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 መሠረት በመሆኑ ከመልስ ሰጭዎች /በሥር ፍ/ቤት ከሳሾች/ ጋር ሊከራከር አይችልም በሚል የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት የቃል ክርክር አድርገዋል፡፡

አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ መከራከር ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው የመከራከሪያ ነጥብ በሥር ፍ/ቤት በከሳሾች ሳይነሳ ይግባኙን የሰጠው ፍ/ቤት በእራሱ አንስቶ የትዕዛዙ መሠረት ማድረጉ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 ከቁጥር 76 ጋር ተጣምሮ ሲታይ አመልካች በክርክሩ ገብቶ ከከሳሽ ጋር ያለገደብ ከመከራከር የሚያግደው አይደለም፡፡

ተከሳሽ ኃላፊ ሆኖ ቢገኝ ኢንሹራንስ ኩባንያው ለተከሳሽ እስከ ብር 30,000.00 ብቻ ኃላፊነቱን የወሰደ በመሆኑ በፍርዱ እንደተገለፀው የካሣው መጠን ከብር 30,000.00 በላይ ሆኖ ከተገኘ ለብልጫው ተከሳሽን ተክቶ ለመከራከር የሚያስችለው መብት ስለማይኖር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 40/2/ መሠረት ተክቶ ካልገባ በቀር ከከሳሽ ጋር መሟገት አይችልም የተባለው ምክንያት ህጋዊ መሠረት የለውም በማለት የሰበር አቤቱታውን አሰምቷል፡፡

መልስ ሰጭዎችም በጠበቃቸው አማካኝነት ጉዳዩ በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣ ክርክር እንደ አዲስ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተነሣ ነው ለተባለው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተከራካሪዎች ባነሱት የመከራከሪያ ነጥብ ሳይገደብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማንኛውንም በጉዳዩ አግባብ ነው ብሎ የሚያስበውን ነጥብ ጭብጥ አድርጎ ሊይዝ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182 ተደንግጓል፡፡

ፍርድ ቤቱ በፍሬ ነገርና በማስረጃ ጉዳይ ሊያከራክርና ሊዳኝ የሚችለው ከሣሽና ተከሣሽን ወይም ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 40 ንዑስ ቁጥር 2 እና 4 ወይም በቁጥር 41 መሠረት ተከራካሪ ሆነው የቀረቡትን ወገኖች ብቻ ነው፡፡ በሦስተኛው ወገን ተከሣሽነት የሚቀርበው ወገን በመሠረቱ ተከራካሪ አይደለም፡፡ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል ያለውን ክርክርና ማስረጃ አይቶና ተረድቶ ስለካሣ ድርሻው ያለውን መልስ መስጠት ይችል ዘንድ የዋናዎቹ ተከራካሪዎች ክስና የመከላከያ መልስ ከእነ ማስረጃው እንዲደርሱት ከሚደረግ በቀር የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃ እየቀረበ እንዲከራከር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 ድንጋጌ መብት አይሰጠውም፡፡ ግንኙነቱም ከከሳሽ ጋር ሳይሆን ከተከሳሽ ጋር ብቻ ሲሆን ፍ/ቤቱም በእነዚህ ሁለት ወገኖች መካከል ያለውን የመብት ማስተካከል ጉዳይ በመሰለው ሁኔታ ሊወሰን እንደሚቻል በዚሁ ህግ ቁጥር 43/3/ ላይ በግልፅ መደንገጉ ከሳሽ በቀረበው ክስ ላይ የሚያሰማው ማስረጃ አለመኖሩን በማያሻማ ሁኔታ ያመላክታል፡፡ ስለሆነም በክስ የሚገባ ሦስተኛ ወገን ለክሱ የመከራከሪያ መልስ መስጠት ይችላል የሚለው ክርክር የህግ መሠረት ያለው አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 ድንጋጌን አተረጓጎም በሚመለከት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ዳኝነት እና በዚህም ላይ ግራ ቀኙ በሰበር ያደረጉት ክርክር ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ይህንኑ ነጥብ መርምረናል፡፡

ለዚህ አከራካሪ ነጥብ መልስ መስጠት እንዲቻል በቅድሚያ የዚህኑ ድንጋጌ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 76 ድንጋጌ ይዘት በእራሱ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

> በቁጥር 43/2/ ሦስተኛው ወገን በክሱ ውስጥ እንዲገባ ፍ/ቤቱ የፈቀደ እንደሆነ የክሱ ማመልከቻ ግልባጭና ለክሱ የተሠጠው የመከላከያ መልስ እንዲደርሰው ይታዘዛል ተብሎ

ከተደነገገው “. . . በክሱ ውስጥ እንዲገባ . . .” የሚለው ሐረግ ይህ ሦስተኛ ወገን የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን መደረጉንና የክርክሩ ተካፋይ (a party to the suit) ከሆነም ስለ ጉዳዩ የሚያቀርበው ክርክር ድርሻ ወይም ካሣ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን በሚመለከት ክርክር ካለው ከተከሳሽ ጋር ክርክር ለማድረግ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ከሳሹ ያቀረበውን ክስ አስመልክቶ በኃላፊነትና በካሣ መጠን ረገድ ክርክር ማቅረብ የሚችል መሆኑን አመልካች ነው፡፡ የክሱ ማመልከቻና ለክሱ የተሰጠው የመከላከያ መልስ እንዲደርሰው የሚደረገውም የሦስተኛ ወገን ተከሳሹ ክርክር እንደአስፈላጊነቱ ከተከሳሹ ጋር ሊሆን እንደሚችልና በተካሹ እንደተገለፀው ድርሻ ወይም የካሣ ክፍያ ካለበት ደግሞ ተከሳሹ ለከሣሽ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? ካለበትስ ለደረሰው ጉደት ሊከፈል የሚገባው የካሣ መጠን ምን ያህል ነው የሚለውን በሚመለከት በተከሳሽ እግር ተተክቶ ከከሳሹ ጋር መሟገት እንዲችል ነው፡፡ በዚሁ በቁጥር 43/2/ " . . .በክሱ ውስጥ እንዳለ ይቆጠራል " የሚለውና የዚህ ግልባጭ የሆነው የእንግሊዝኛው ንባብ " . . .shall be deemed to be in the same position as a defendant" የሚለው አነጋገር ይህንኑ አባባል የሚደግፍ ነው፡፡

እንዲሁም ይህ ሦስተኛ ወገን ተከሣሽ ቀርቦ በክርክሩ ውስጥ ገብቶ እንዲከራከር ጥሪ ተደርጎለት ያልቀረበ እንደሆነ ምን ውጤት እንደሚያስከትል በሚደነግገው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 76 ላይ

> “. . . ይህ ሦስተኛ ወገን ቀርቦ በክርክሩ ውስጥ በመግባት መልስ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዞ መጥሪያው ከደረሰው በኋላ ቀርቦ <u>መልስ ሳይሰጥ ወይም አላፊ የማይሆንበትን ምክንያት በማስረዳት</u> ሳይከራከር የቀረ እንደሆነ . . .” /ሰረዝ የተጨመረ/

የሚለውን የሕግ አነጋገር

“Where a third party duly summoned to appear under Art. 43(2) fails without good cause to appear <u>for the purpose of</u>

https://t.me/ethiopianlegalbrief

disputing the plaintiff's claim against the defenders on whose behalf the summon was issued, or his own liability to the defendant, (emphasis added.)

ከሚለው የእንግሊዘኛ ግልባጭ ጋር አያይዘን ከተመለከትነው ሦስተኛው ወገን ተከሳሽ በክርክሩ ውስጥ እንዲገባ ከተፈቀደ የክርክሩ ተካፋይ ሆኖ የሚያቀርበው ክርክር ሁለት ፈርጅ ሊይዝ የሚችል መሆኑን የሚያሣይ ነው። ይኸውም 1ኛው ከተከሳሽ ጋር ሆኖ ድርሻ ክፍያ ወይም ስለተከሣሽ ሆኖ የካሣ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተቀብሎ በተከሳሽ እግር በመተካት ተከሳሽ ለከሳሽ ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን፤ ኃላፊነት አለበት እንኳ ቢባል ሊከፈል በሚገባው የካሣ መጠን ላይ ከከሳሽ ጋር ክርክር ማድረግ፤ መሟገት የሚችልበት ክርክር ሲሆን ሌላውና ሁለተኛው ደግሞ ድርሻ ወይም ካሣ ለመክፈል ለተከሳሽ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መከራከር የሚችልበት መንገድ ነው።

ስለሆነም የድንጋጌውን ይዘት ብቻ ስንመለከተው እንኳ በክርክር ውስጥ ገብቶ እንዲከራከር የተጠራ ሦስተኛ ወገን ተከሣሽ በክርክሩ ከገባ በኋላ መሟገት የሚችለው ከተከሳሽ ጋር እንጂ ከከሣሽ ጋር ለመከራከር የሚያስችለው መብት የለውም የሚለው መደምደሚያ ህጋዊ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

የሥነ ሥርዓት ድንጋጌን በሚመለከት የትርጉም ጥያቄ ከተነሣ ከሥነ ሥርዓት ህግ ዓላማ አንፃር በማየት ትክክለኛ ትርጉሙን መፈለግ የግድ ይላል።

የሥነ ሥርዓት ህግ ዓላማ ክርክርን ፍትሃዊ በሆነ፤ ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በተቀላጠፈና በአነስተኛ ወጭ እንዲቋጭ ማድረግ ነው። በክርክር ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች እነማን ናቸው? የሚለውም የዚህ ሕግ አካል በመሆኑ የክርክርን አድማስ በመወሰን ረገድ ቁልፍ ቦታ የያዘ በመሆኑ ከሳሽ ተከሳሽ ማን ነው? በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የሚጣመሩትስ እነማን ናቸው? ጣልቃ ገብነት እና የሦስተኛ ወገን

ተከሳሽነትን በሚመለከት የተቀመጡት ድንጋጌዎች ይህንኑ ዓላማ መሠረት ያደረጉ ናቸው። ከዚህ አንፃር ክርክር ያስነሣውን ድንጋጌ ምንነት እንመልከተው።

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43/1/ ". . . ሌላ ሦስተኛ ወገን ከእኔ ጋር ድርሻ ካሣውን መክፈል አለበት . . ." በሚል ይቀመጥ እንጂ ከዚህ የሕግ አነጋገር ድርሻ ካሣውን የሚለውን ሐረግ ካየነው ትርጉም የሚሰጥ መስሎ አይታይም። ለምን ቢባል ድርሻ እና ካሣ የተለያዩ ፅንሰ ሃሳቦች ናቸው። አንዱ ቃል ሌላውንም ሊተካ አይችልም። ምንጫቸውም የተለያየ ነው። በተለይም "Where a defendant claims to be entitled to contribution or indemnity from any person . . ."

ከሚለው የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዘኛ ግልባጭ ጋር ከላይ የተመለከተውን ሐረግ ከተመለከትነው "ድርሻ" እና "ካሣ" የተለያዩ ሆነው "ወይም" በሚለው ምህፃረ ቃል የተያያዙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ድርሻ (Contribution) የሚለው ቃል ለክሱ ምክንያት በሆነው ጉዳይ ከተከሳሹ ጋር የአንድነትና የነጠላ ግዴታ ያለባቸው ወገኖች ኖረው ከሳሽ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1897 መሠረት አንደኛውን ባለዕዳ ብቻ ነጥሎ በከሰሰ ጊዜ ተከሳሹ ከእኔ ጋር ድርሻውን መክፈል ያለበት ሌላ ሦስተኛው ወገን ስላለ የክርክሩ ተካፋይ ይሁንልኝ በማለት በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን በማድረግ፤እንዲሁም ካሣ (indemnity) የሚለው ቃል ደግሞ ተከሳሹ በተከሰሰበት ጉዳይ ኃላፊ የምሆን ከሆነ የሚፈረድብኝን ክፍያ እኔን ተክቶ የሚሸፍን ወገን /እንደ ኢንሹራንስ ባለ ጉዳይ/ ስለአለ ጣልቃ ገብቶ ይከራከራር በማለት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን በማድረግና የሚመለከታቸው ወገኖች በአንድ ፋይል እንደተገናኙ ጉዳዩ የሚያልቅበትን ሥርዓት በመዘርጋት ተከታይ ክስን ለማስቀረት ታስቦ የተቀመጠ ድንጋጌ መሆኑን እንረዳለን።

ይህ ባይሆን ኖሮ ድርሻ የሚከፍል ወገን እያለ ከተከሳሽ ላይ ብቻ ሊፈረድበት እርሱም በተራው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1908 እና 1909 መሠረት በብልጫ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በከፊለው መጠን በሌሎች የጋራ ባለዕዳዎች ላይ ክስ ማቅረቡ አይቀሬ ይሆናል፡፡

የካሣ ክፍያን በሚመለከትም እንደ አሁኑ ባለው ጉዳይ ሦስተኛ ወገን የሆነው ኢንሹራንስ ሰጭው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 ሆነ በንግድ ህግ ቁጥር 687 መሠረት የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ተከሣሽ በሆነው ኢንሹራንስ በገባው ሰው ላይ ብቻ ተፈርዶበት ከሆነ ኢንሹራንስ ሰጭው በሚከፍለው ካሣ ልክ ይህንኑ የካሣ ገንዘብ እንዲተካለት በንግድ ህግ ቁጥር 688 በኢንሹራንስ ሰጭው ላይ ክስ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 አስፈላጊነትም ከላይ እንደተመለከተው ተከታይ ክስ ሳይኖር በክርክርና በማስረጃ አቀራርብ ረገድ ጉዳዩን በአንድ ፍ/ቤት እንዲታይ በማድረግ ኃላፊነት ያለባቸውን እና ሊከፈል የሚገባውን የካሣ መጠን በመወሠንና በመጨረሻም የሚከፍለውን ወገን በመለየት በአጭር ጊዜ በአንስተኛ ወጭ ዕልባት እንዲያገኝ ለማድረግ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ለጉዳዩ የሰጠው ውሣኔ ይህንኑ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ዓላማ የተከተለ አይደለም እንደይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መነሻ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1896 መሠረት የአንድነትና የነጠላ ግዴታ ያለበት ባለዕዳ በሦስተኛ ወገን ተከሳሽነት ድርሻ ክፍያውን እንዲችል በተከሣሽ ጠያቂነት ቀርቦ እንዲከራከር ከተፈቀደለት ሙግቱን ከተከሳሹ ጋር ማድረግ አይችልም ወደ ሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ በመሆኑ የዚህኑ ሦስተኛ ወገን ተከሳሽ ከሳሽን በመሞገት ረገድ ከመሠረታዊ ህጉ የመነጨውን መብት የሚያስቀርና የሥነ ሥርዓት ህጉን ዓላማና መንፈስ ያልተከተለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በንግድ ህግ ቁጥር 687 መሠረት ሦስተኛ ወገን ተከሳሹ የክስ መሪ ስለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፤ የክሱ መሪ ቢሆን ኖሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40/2/ መሠረት ተከሳሽን ተክቶ በተከራከረ ነበር የሚለው ምክንያትም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳት የደረሰበት ወገን ለኃላፊነት የሚያቀርበውን የፍ/ብሔር ክስ ኢንሹራንስ ሰጭው መሪ እንዲሆን በኢንሹራንስ ውላቸው አለመገለፁ ክሱ እራሱ በሚሰጠው አመራር (direction) ሊመራ

የማይችል መሆኑን ከሚያመለክት በቀር የእራሱን ክርክር በሚመለከት ብቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት ገብቶ ለመከራከር የሚከለክለው አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት በቀረበው ጉዳይ አመልካች በሦስተኛ ወገን ተከሣሽነት በክርክሩ ቢገባም ከጠራው ከተከሣሽ ጋር ከመሟገት በቀር ተከሳሹን ተክቶ ተገዢውን /ከሣሽን/ መከራከር አይችልም ሲል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 ድንጋጌን ተርጉሞ ዳኝነት መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈፅሟል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. በሦስተኛ ወገን ተከሣሽነት በክርክሩ ጣልቃ የገባው ተከሣሹ ለከሳሹ ኃላፊነት ያለበት መሆኑንና አለመሆኑን እና ኃላፊነት አለበት እንኳ ቢባል ሊከፍል በሚገባው የካሣ መጠን ላይ አለኝ የሚለውን ክርክር በማንሳት ከከሳሹ ጋር መሟገት የሚችል በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ መዝገቡን አንቀሣቅሶ በዚህ መሠረት የይግባኝ ክርክሩን ተመልክቶ የመሰለውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት መዝገቡን መልሰናል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት በኮ.ቁ 2 38309 የካቲት 03 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ግልባጩ ይተላለፍ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 23744

ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሒም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- አቶ በቀለ በድዬ

መልስ ሰጪ፡- 1ኛ/ የወጋገን ባንክ አዋሳ ቅርንጫፍ

2ኛ/ የቡሌ ሆራ ከተማ አስተዳደር

3ኛ/ አቶ ሁሴን ወልዴ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ዳኝነት ሳይከፈልበት በነፃ ክስ ለማቅረብ እንዲፈቀድ ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/3/ የተመለከተውን ድንጋጌ አተረጓጎም የሚመለከት ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት የቦረና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ዳኝነት ሳይከፍልበት በነፃ ክስ ለማቅረብ የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ መክፈሉ በተረጋገጠ ጊዜ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት አለው በማለት አሰናብቶታል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

የጠ/ፍ/ቤትም በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/3/ መሠረት በዳኝነት ክፍያ ክርክር ላይ ይግባኝ ሊቀርብ እንደማይችል ስለሚደነግግ ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ያለውን ትዕዛዝ መስጠት በመሆኑ በእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ከተሰጠ እንጂ በትዕዛዝ ላይ ይግባኝ መጠየቅ የሚቻል ባለመሆኑ የይግባኝ አቤቱታው

የሕግ አካሄድን ጠብቆ የቀረበ አይደለም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320/3/ የተመለከተው ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማና አስፈላጊነት ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል፡፡

አንድ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ሙሉ የክርክር አካሄድን ተከትሎ የመጨረሻ ውሣኔ ለመስጠት በእያንዳንዱ የክርክር ደረጃ የሚሰጣቸው ትዕዛዞችና ብይኖች ይኖራሉ፡፡ በዚህ አኳኋን በክርክር ሂደት መካከል ትዕዛዞችና ብይኖች በመስጠት ይግባኝ እንዲቀርብ ቢፈቀድ በአንድ ጉዳይ ምክንያት በተለያየ ፍ/ቤት የተለያየ ክርክር እንዲኖር የሚጋብዝ አሠራር ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ክርክርን ፍትሃዊ በሆነ እና ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአፋጣኝ እና በአነስተኛ ወጭ መቋጨት ይገባል ለሚለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ገዥ ዓላማ ጋር የሚፃረር ነው፡፡

ለዚህም ነው ማናቸውም ፍ/ቤት ክርክሩን በሚሰማበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ ጊዜአዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ሲሰጥ ከሥረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ለማለት አይቻልም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/3/ የተደነገገው፡፡

ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸው ትዕዛዞች የትኞቹ ናቸው? የሚለውን ለማመልከት ከተዘረዘሩት የትዕዛዝ ዓይነቶች ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ የሚቀርብ ጥያቄ አንዱ የትዕዛዝ ዓይነት እንደሆነ በዚሁ ድንጋጌ ሥር ተመልክቷል፡፡

ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ በቀረበ ጥያቄ ላይ ሊሰጥ የሚችለው ትዕዛዝ እንደነገሩ ሁኔታ ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው ከሣሽ የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችለው የገንዘብ አቅም የሌለው ስለሆነ እንደ ጥያቄው የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፍል በነፃ ፋይል ከፍቶ ክሱን ለማቅረብ ይችላል የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከሣሹ ድሃ ያለመሆኑ ስለተረጋገጠ ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ ካልከፈለ በቀር በነፃ ፋይል ከፍቶ ክሱን ለማቅረብ አይችልም የሚለው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጀመሪያው አካኋን ትዕዛዝ በተሰጠ ጊዜ በዚህ ትዕዛዝ መሠረት ፋይሉ ተከፍቶ ክርክሩ የሚቀጥል ነው፡፡ የክርክሩ ውጤት የሚታወቀው ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር ማስረጃ መሠረት ነው፡፡ በመጨረሻው የክርክር ውጤት ተከሣሹ ባይስማማ ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ክሱ ዳኝነት ሳይከፈልበት በነፃ እንዲከፈት መደረጉ የሕግ ድጋፍ አልነበረውም የሚለውን እንደ አንድ የይግባኝ ምክንያት በማድረግ በውሣኔው ላይ ካለው ቅሬታ ጋር አዳምሮ ማቅረብ ይኖርበታል እንጂ ከሥረ-ነገሩ ፍርድ በፊት የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ መብት አይኖረውም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/3/ የተመለከተው ድንጋጌም በዚህ አካኋን በሚቀርበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ ክልከላ ለማድረግ ነው፡፡

በሌላ በኩል ድሀ ያለመሆንህ ተረጋግጧል፡፡ የዳኝነት ገንዘብ ካልከፈልክ በቀር ፋይል አይከፈትም ለተባለው ከሣሽ ግን ይህ ዓይነቱ ትዕዛዝ የመጨረሻ ነው፡፡ ሌላ የሚጠበቅ የሥረ-ነገር ፍርድ የለውም፡፡ ስለሆነም የዳኝት ገንዘብ ለመክፈል አቅም ሳይኖረኝ ክርክሬና ማስረጃዬ በአግባቡ ሳይታይ አቅም እንዳለኝ ተቆጥሮ የዳኝነት ገንዘብ ክፈል መባሌ ተገቢ አይደለም የሚል ከሆነ የተሰጠው ትዕዛዝ የመጨረሻ እንደመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320/1/ መሠረት የይግባኝ አቤትታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

ስለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320/3/ ... ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ የሚለውን አነጋገር ከላይ በተመለከተው መሠረት ከሁለት ማዕዘን አንፃር ሳይመለከት በደፈናው ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸው ትዕዛዞች ናቸው በሚለው ድንጋጌ ሠፍሮ የሚገኝ መሆኑን ብቻ በማየት አመልካች በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀመ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የዳኝነት ገንዘብ መክፈል አለበት ወይስ የለበትም? የሚለውን ነጥብ ከስር ፍ/ቤት የመዝገብ ግልባጭ ጋር አገናዝቦ ጉዳዩን መርምሮ ሊወሰን ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
2. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 18993 በጥር 30 ቀን 1998 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 23769

ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ኢንጅነር ጋሪ ፉፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናት ኢንስቲትዩት

ነ/ፊጅ ተሾመ አፈወርቅ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የተጠሪ መ/ቤት ሠራተኛ ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ ለሥራ የተረከቧቸውን የተለያዩ ንብረቶች አልመለሱም ተብሎ የንብረቶቹን ዋጋ ግምት እንዲከፍሉ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመወሰኑ ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ የንብረቶቹ ዓይነትና የዋጋ ግምታቸው በአባሪነት የተገለፁትን በድምሩ ብር 27,812.95 /ሃያ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሁለት ከዘጠና አምስት/ የሚያወጡ ንብረቶች ያልመለሱ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካችም በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከተጠሪ መ/ቤት በጡረታ ከተገለሉ ከሁለት ዓመት በኋላ ክሱ መቅረቡ አግባብ እንዳልሆነ ገልፀው ክስ ከቀረበባቸው ንብረቶች መካከል የተወሰኑትን እንዳስረከቡና ጉድለቱ በትክክል እንዲጣራ በኦዲተሮች በድጋሚ እንዲመረመር ይታዘዝልኝ በማለት

ተከራክረዋል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የንብረት ጉድለቱ በተጠሪ ኦዲተሮች በድጋሚ ተጣርቶ ውጤቱ እንዲቀርብለት ትእዛዝ ሰጥቶ በዚሁ መሠረት በድጋሚ ተጣርቶ አመልካች ግምቱ ብር 21,154.82 /ሃያ አንድ ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አራት ከሰማኒያ ሁለት/ የሚያወጣ የተለያየ ንብረት አላስረከቡም የሚል ሪፖርት በማቅረባቸው ፍ/ቤቱም ይህንኑ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኙ መ/ሰጭን አያስቀርብም በማለት ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ ክስ የቀረበበትን የንብረት ግምት አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ለሰበር ችሎት ቀርቦ መጣራት የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ባጠቃላይ የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን አመልካች ከተጠሪ መ/ቤት የተረከቧቸውን የተለያዩ ንብረቶች የዋጋ ግምት ለተጠሪ እንዲከፍሉ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ከህጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች በተጠሪ መ/ቤት ተቀጥረው በሚሰሩበት ጊዜ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን የተለያዩ የሥራ ማከናወኛ ቁሣቁሶችን የተረከቡት ከ1958 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1983 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑን ከቀረበው ማስረጃ መረዳት የሚቻል ሲሆን የዕቃዎቹም ዓይነት ሲታይ ኩባያ፣ጭልፋ፣ማንኪያና ሹካን የሚጨምርና በአገልግሎት መስጠት ምክንያት ከጥቅም ውጭ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ቁሣቁሶችን እንደሚያካትት መገንዘብ ተችሏል፡፡ አመልካች በተጠሪ መ/ቤት ከ1956 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ እስከተገለሉበት 1985 ዓ.ም ድረስ ተቀጥረው ሲሰሩ የነበሩ ሲሆን ለክሱ መነሻ ምክንያት የሆኑትም የተለያዩ የሥራ ማከናወኛ ቁሣቁሶች አመልካች በተጠሪ መ/ቤት ካበረከቱት የረጅም ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አገልግሎት አንፃር እነዚህ የተለያዩ የሥራ ማከናወኛ ቁሣቁሶች በአገልግሎት ብዛት ከጥቅም ውጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚታመን ነው፡፡ ዕቃዎቹ በአገልግሎት መስጠት ምክንያት ሊኖሩ እንደማይችሉ ከታመነ አመልካች ከመ/ቤቱ በጡረታ በሚገለሉ ጊዜ ሊያስረክቧቸው የማይችሉ ሲሆን የዕቃዎቹ የዋጋ ግምት እንዲከፈል መጠየቅ የሚቻለው በአገልግሎት መስጠት ምክንያት ከጥቅም ውጭ የማይሆኑ ከሆነ ነው፡፡

ስለሆነም ዕቃዎቹን በዓይነት ማስረከብ ካልተቻለ የዋጋ ግምታቸውን መጠየቅ የማይቻል ሲሆን በዚህ ሁኔታ ክስ አቅርቦ የዋጋ ግምት እንዲከፈል መጠየቅ የክስ ምክንያቱ ቀሪ በሆነ ነገር ላይ ክስ እንደመመስረት የሚቆጠር በመሆኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የዕቃዎቹን የዋጋ ግምት አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 04061 ነሐሴ 12 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 26394 ጥር 5 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያቱ ቀሪ በሆነ ነገር ላይ ስለሆነ አመልካች በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 24111

የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የቂርቆስ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ደረጀ ያኪ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የዕለተ ወርቅ ገ/አብ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ ጉዳይ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ክስ የቀረበበትን ቤት አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በማለት የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመስጠታቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በአመልካች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በወረዳ 20 ቀበሌ 29 ክልል የቤት ቁጥር 396 — 401 የሆኑትን ቤቶች መሥራቱ ተረጋግጦ የቤት ባለቤትነት ደብተር በተጠሪ ተሰጥቶኛል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ሌላ ቤት ሳይኖረኝ አለሽ በማለት የተሰጠኝ ደብተር የተሰረዘ መሆኑን በማስታወቅ እንዲመለስለት ጠይቋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አስቀድሞ በአግባቡ ተሰጥቶኝ የነበረውን የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ከሕግ ውጭ እንዲሰረዝ ውሣኔ የሰጠ ስለሆነ ይኼው ውሣኔ ይሰረዝልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

በክሣሽ በኩል የቀረበው ክስና ማስረጃ ለተተኪው የአሁን አመልካች የቂርቆስ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ደርሶ መልስ እንዲሰጥበት ትዕዛዝ ተሰጥቶ መጥሪያው ለተተኪ በአግባቡ መድረሱ ተረጋግጦ ተክሣሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ መሰጠቱን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ከዚህ በኋላም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ የአመልካችን የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር መሠረዙን በማስታወቅ የፃፈው ደብዳቤ ሕጋዊ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መስርቶ መዝገቡን መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት ተጠሪ በ1985 ዓ.ም. የቤት ባለቤትነት ደብተር ለአመልካች ከሰጠ በኋላ ለመሰረዝ የሚችለው ሕጋዊ ምክንያት ካለውና ለመሰረዝም ሥልጣኑ የሚፈቅድለት ከሆነ ብቻ ሲሆን ተጠሪ ግን ለአመልካች የተሰጠው የባለቤትነት ደብተር በአግባቡ የተሰረዘ ስለመሆኑ ቀርቦ ካለማስረዳቱም በላይ በተጠሪ በኩል በአስረጂነት የቀረበውን ሰነድ ፍ/ቤቱ እንደተመለከተው አመልካች ለተጠሪ የተሰጠውን የቤት ባለቤትነት ደብተር የሰረዘው ተጠሪ በወረዳ 1 ቀበሌ 04 ክልል የሚገኝ ሌላ ቤት ባለቤት የነበሩና ቤቱን የሸጡ ስለሆነ ደብተሩ በማጭበርበር የተሰጠ ስለሆነ ነው በሚል ምክንያት ቢሆንም ይህን አባባሉን ፍ/ቤት ቀርቦ ያላስረዳ ስለሆነ ለተጠሪ የተሰጠው የቤት ባለቤትነት ደብተር መሠረዙን በማስታወቅ አመልካች የፃፈው ደብዳቤ ሕገወጥ ስለሆነ ውድቅ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኙ መ/ሰጭን አያስቀርብም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዟል፡፡

ይህ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ አግባብነቱ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር ክርክሩም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት ከላይ እንደተመለከተው የተሰጠኝን የቤት ባለቤትነት ደብተር የሰረዘው ከሕግ ውጭ ስለሆነ ውሣኔው ሊሰረዝ ይገባል በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የፍ/ቤቱ መጥሪያ ለተከሳሽ በአግባቡ መድረሱ የተረጋገጠ ስለሆነ ጉዳዩ በሌለበት ይታያል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩን ተመልክቶ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሥር ተከሣሽ የአሁን አመልካች በሌለበት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የሰጠው ውሣኔ አግባብነቱ ከመመርመሩ በፊት ቀድሞውንም ቢሆን ለተጠሪ የተላከው መጥሪያ በአግባቡ የደረሰው ስለመሆኑ በመረጋገጡ ክርክሩ ተከሣሽ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ መሰጠቱ አግባብነት የነበረው ስለመሆኑ በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህም መሠረት ይህ ችሎት በመ/ቁ. 15835 በሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 70/ሀ/ መሠረት አንድ ተከሣሽ ከክስ እንዲወጣ /Ex. parte/ የሚደረገው የተከሣሹን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ሳይቀርብ በመቅረቱ ሳይሆን ጉዳዩን ለመስማት ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ በመዘርዘር ሰፋ ያለ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተከሣሽን ከክርክሩ ያስወጣው ጉዳዩን ለመስማት ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ሳይቀርብ በመቅረቱ ሳይሆን መልሱን ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ባለመቅረቡ ነው፡፡

የተከሳሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ተከሣሽ ሳይቀርብ ቢቀር ፍ/ቤቱ መስጠት የማገባውን ትዕዛዝ በተመለከተም ጉዳዩ መታየት የሚባው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195 ላይ እንደተመለከተው በተወሰነ የጊዜ ገደብ መከናወን ያለበት ድርጊት በዚህ የተወሰነ ጊዜ ካልተከናወነ ዋጋ እንደሌለው የተደነገገ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ተከሳሽ መልሱን ይዞ እንዲቀርብ በተያዘው ቀጠሮ ሳይቀርብ ቢቀር መልስ የማቅረብ መብቱን ከሚያጣ በስተቀር ከዚህ አልፎ በአጠቃላይ ክክርክሩ ውጭ በመሆን በቀጣዩ የክርክር ሂደት የመሳተፍ መብቱን ሊያጣ የሚችል አይሆንም፡፡

ስለሆነም የተከሣሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ተከሣሽ ባለመቅረቡ የፌዴራል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተከሣሽን በአጠቃላይ ከክርክሩ ማስወጣቱ የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. ዐዐዐ8 በግንቦት 26 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41015 በየካቲት 13 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክክርክሩ ውጭ እንዲሆን የተደረገው ያለአግባብ ስለሆነ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ጉዳዩ እንዲታይ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 24627

ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

አመልካች፡- ዶ/ር ቤተልሄም ታደሰ - ጠበቃ አሥራት አርአያ

ተጠሪ፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ሚካኤል ጌታቸው

መዝገቡ ተመርመሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ክርክር የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኗ አመልካች ከሣሽ ነበሩ፡፡ አመልካቿ በአሁኑ ተጠሪ ላይ በነሐሴ 23 ቀን 1995 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ፣ ተጠሪው ከአባቴ በውርስ የተላለፈልኝን በወረዳ 4 ቀበሌ 50 የቤት ቁ. 683 የሚገኘውን ቤት ውጭ አገር ለትምህርት በሄድኩበት ወቅት በአደራ አስተላልፌለት ስመለስ ቤቱን ሊያስረክበኝ ፈቃደኛ አልሆነም ስለዚህ ተጠሪው ቤቱን እንዲያስረክብ ያለአግባብ ያገኘውን ጥቅም እንዲመልስ ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪው /የሥር ተከሣሽ/ ቀርቦ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎቹን ያቀረበ ሲሆን እነርሱም፣ በዚህ ጉዳይ ስልጣን ያለው ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው፣ ኤጀንሲው ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ በፍ/ቤት ድጋሚ ሊታይ አይገባም፣ ቤቱ ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ እጅ ስለሚገኝ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚሉ መቃወሚያዎች አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም መቀወሚያዎቹን መርምሮ ሐምሌ 6 ቀን 1996 ዓ.ም. በሰጠው ብይን፣ በዚህ ጉዳይ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ሥራ አመራር ቦርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠበት ጉዳይ ስለሆነ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በክርክሩ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ከሰጠበት በኋላ በዚሁ ጉዳይ ላይ 2ኛ ክስ የቀረበ ስለሆነ በሚል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244/2/ለ/፣5 እና በአ/ቁ/110/87 አንቀጽ 5/3 መሠረት ክሱን ውድቅ አድርጎታል።

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሰጠው ብይን ቅር የተሠኙት የአሁኗ አመልካች ቅሬታቸውን በይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያሰሙ ቢሆንም ከ/ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤትን ብይን ምክንያቱን በመለወጥ በዚህ ጉዳይ ስልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ስልጣን እንደሌለው አውቆ ክሱን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231/1/ለ መሠረት ውድቅ ሊያደርግ ይገባው ነበር ቢልም የስር ፍ/ቤትን ብይን ከውጤት አንፃር በሚል አጽንቶታል።

ይህም መዝገብ ለዚህ ችሎት የቀረበው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጡት ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አመልካች ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር ማመልከቻ በማቅረባቸው ነው። የሰበር አቤቱታው ፍሬ ነገር ሲጠቃለል፣ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ድንጋጌ መሠረት በድጋሚ የቀረበ ነው ቢልም የቀድሞውን ውሣኔ የሰጠው ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንደ ፍ/ቤት ሊቆጠር አይገባውም፣በአ/ቁ/110/87 መሠረት ኤጀንሲው ባየው ጉዳይ በቀጥታ ለፍ/ቤት ክስ ማቅረብ አልተከለከለም በቀድሞው ጉዳይ የነበረው ጭብጥና ስረነገር ከዚህ ጉዳይ ጋር ተመሣሣይ አይደለም፣ በአዋጁ መሠረት ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በዚህ ጉዳይ ስልጣን የለውም፣ ፍ/ቤቶች ተመሣሣይ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን አላቸው የሚል ነው።

ይህ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ የስር ፍ/ቤቶች ክርክሩ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የሚታይ ነው በሚል የወሠኑት በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሁፍ መከራከሪያዎቻቸውን አቅርበዋል። እኛም የግራ ቀኙን መከራከሪያዎችና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች አገናዝበን መዝገቡን መርምረናል። እንደተመረመረውም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ፍ/ቤቶች በዚህ መዝገብ

የቀረበውን ክርክር የመዳኘት ስልጣን የላቸውም፣ ስልጣኑ ያለው ፕራይቤታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ለማለት መንደርደሪያ ያደረገው አ/ቁ/110/87'ን' ሲሆን የዚህ አዋጅ አንቀጽ 3/1/ን ጠቅሶ ከአዋጅ ውጭ የተወረሱ ንብረቶችን የባለቤትነት ሁኔታዎች እያጣራ የመወሰን ስልጣን ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የተሰጠ ስለሆነ ፍ/ቤቶች አከራክረው የመወሰን ስልጣን የላቸውም ሲል አትቷል። በመሠረቱ በአዋጁ ላይ በግልጽ እንደተደነገገው ኤጀንሲው በመመሪያ፣ በቀላጤ ወይም በቃል ትእዛዝ ከግለሰቦች ተወስደው በመንግሥት ቁጥጥር ስር የገቡ ንብረቶችን በተመለከተ የሚቀርቡ ክርክሮችን ብቻ የማየት ስልጣን እንዳለው መረዳት ይቻላል። በዚህ ጉዳይ ደግሞ አከራካሪው ንብረት በመመሪያ፣ በቀላጤ ወይም በቃል ትእዛዝ መወሰዱን የሚያመለክት ማስረጃም ሆነ የቀረበ ክርክር የለም። ይህ በሆነበት ሁኔታ አመልካች ለተጠሪው በአደራ የሠጠሁትን ቤት ሊመልስ ይገባል በሚል ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ስልጣኑ ያለው ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ማለት፣ ኤጀንሲው በሌለው ስልጣን ዳኝነት ይስጥ የሚል እንደምታ ያለው በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ መዝገብ ፍ/ቤት ስልጣን የለውም በሚል በተለየ አካሄድ የቀረበ መቃወሚያም ሆነ የሕግ ክርክር የለም፣ ፍ/ቤቶችን ይህን ጉዳይ አከራክሮ ከመወሰን የሚያግዳቸው የሕግ አግባብ አይኖርም። በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ መዝገብ የቀረበውን ክርክር አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ማለታቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም። የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በዚህ ጉዳይ ስልጣን የለውም ከተባለ ደግሞ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩ በኤጀንሲው ከዚህ ቀደም የተወሰነበት በመሆኑ ድጋሚ በፍ/ቤት ሊታይ አይችልም ማለቱም አላግባብ መሆኑን ተገንዝበናል። ምክንያቱም ኤጀንሲው በሌለው ስልጣን ውሣኔ ሰጥቶ ቢሆን እንኳ ውሣኔው በሕጉ አግባብ የተሰጠ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባውም፤ፍ/ቤቱም ውሣኔው እንዳልተሰጠ ቆጥሮ ጉዳዩን ሊያየውና ሊወስን ይገባው ነበር ብለናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1/ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.36910 በመጋቢት 15 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33322 ሐምሌ 6 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆናቸው ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በዚህ መዝገብ የቀረበውን ክርክር አይቶ የመወሰን ስልጣን የሌለው በመሆኑ ክርክሩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት በድጋሚ ቀርቧል ሊባልም ሆነ ፍ/ቤቶች ስልጣን የላቸውም ለማለት ባለመቻሉ በግራ ቀኙ ክርክር የተነሱ ሌሎች መቃወሚያዎችን እና የፍሬ ነገር መከራከሪያዎችን መርምሮ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ይመለስለት ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

4/ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ.24775

ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች- ማታዶር አዲስ ጎማ - ጠበቃ - አቶ ደረጀ ታፈሰ ወርቁ፡፡

ተጠሪ፡- ቢተው ረታ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል፡፡

ፍ ር ድ

ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካቹ ላይ ለተመሠረተው ክስ አመልካች መልስ ይዞ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ በያዘው ቀጠሮ አመልካች ቀርቦ መልስ ባለመስጠቱ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ታዟል፡፡ ፍ/ቤቱ ትዕዛዙን እንዲያነሳለት አመልካች ያቀረበውን ማመልከቻም ፍ/ቤቱ ባለመቀበሉ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ይግባኙ አያስቀርብም በመባሉ አመልካች ለዚህ ፍ/ቤት አቤቱታውን አቅርቧል፡፡

አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ ክርክሩን ለመስማት ቢጠራም ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ቀጥሏል፡፡ በዚህም አመልካች መልስ ስጥ በተባለበት ዕለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ የመታዘዙን ተገቢ መሆን ያለመሆን መርምረናል፡፡

የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 233 አንድ ተከሳሽ የመከላከያ መልሱን ፅፎ እንዲያቀርብ ታዞ መከላከያውን ለፍርድ ቤቱ ሳያቀርብ የቀረ ወይም ራሱ መከላከያ ሳይይዝ የቀረበ እንደሆነ ክርክሩ በሌለበት የሚሠማ መሆኑ በመጥሪያ ይገልፅለታል ይላል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አንድ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የሚታዘዘው መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ቀን ሲቀር ሣይሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 241 መሠረት ክርክሩ ሊሠማ በተቀጠረበት ቀን ያልቀረበ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሆነ ነው፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.241/1/ “ክሱ መሠማት በሚጀምርበት ቀን.....ቀርቦም እንደ ሆነ የመከላከያውን መልስ ለማራ ቁኙ” ፍ/ቤቱ እንደሚያነብ መጥቀሱ አንድ ተከሳሽ መልስ ባያቀርብ እንኳን ክሱ ሊሠማ በተቀጠረበት ዕለት ቀርቦ መከራከር እንደሚችል የሚያሣይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ዕለት ባለመቅረቡ ብቻ የሥነ ሥርአት ሕጉን ያላግባብ በመተርጎም በሌለበት ጉዳዩ ይታያል መባሉ መሠረታዊ የመሰማት መብቱን የገደበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች መልስ እንዲሠጥ በታዘዘበት ዕለት ባለመቅረቡ በሌለበት እንዲታይ መወሰናቸው መሠታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ውሣኔዎቹ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በሕጉ መሠረት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ተገቢውን እንዲወስን ታዟል፣ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

የሰ/መ/ቁ. 25026

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሁዳ መሐመድ - ጠበቃ አቶ ይልማ አቻሜ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ሀጂ አህመድ አህመዲን፣ ጠበቃ ደምሴ ኪዳኔ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን የተቀጠሪው፣ ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሚያዝያ 6 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ የክርክሩን ፍሬ ጉዳይ በተመለከተ፣ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በከሳሽነት ቀርባ ከተከሳሽ ጋር ታህሣሥ 8 ቀን 1991 ዓ.ም. በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል፣ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 6 ቀበሌ 02 ክልል የቤት ቁጥር 003 የሆነው ቤት በብር 650,000 /ስድስት መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ ገዝቼአለሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ብር 70,000 /ሰባ ሺህ ብር/ የመጀመሪያ ክፍያ የከፈልኩ ሲሆን የቤቱን ካርታ እና የባለቤትነት ደብተር ማረጋገጫ ተረክቤአለሁ፡፡ ተከሣሽ በውሉ መሠረት እንዲፈጽም ማስጠንቀቂያ ብሰጠው ፈቃደኛ ስላልሆነ፣ በፍርድ ተገድዶ ቤቱን እንዲያስረክብና የውል ግዴታውን እንዲፈጽም ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ ያቀረበች ሲሆን፣ ተጠሪው የከፍተኛው ፍርድ ቤት መጥሪያና ክስ ደርሶአቸው መልሳቸውን፣ ይዘው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪው ፍርድ ቤቱ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ ከሰጠ ከሶስት ወር በኋላ ወደ ክርክሩ ለመግባት እንዲፈቀድለት የጠየቀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የአመልካችን የሰነድና የጽሑፍ ማስረጃ መርምሮ ተጠሪው ታህሣሥ 8 ቀን 1991 ዓ.ም. በተደረገው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ቤቱን ከነይዞታው ለአመልካች እንዲያስረክብ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል።

ተጠሪው በዚህ ውሣኔ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረብ ውሉ ሥልጣን በተሰጠው አካልና በማይንቀሳቀስ ንብረት መመዝገቢያ መዝገብ ያልተመዘገበ በሽያጭና በግዢ እንዲሁም በምስክሮች የተፈረመበት ስላልሆነ በውል ልገደድ አይገባኝም በማለት የተከራከሩ ሲሆን መልስ ሰጭም ተጠሪው በይግባኝ ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል። የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተፈረመ ስለሆነና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እንደ ረቂቅ ሆኖ ስለሚቆጠር፣ ይግባኝ ባይ /ተጠሪው/ የሚገደድበት ውል የለም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሯል። አመልካች ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ተጠሪው በከፍተኛ ፍርድ ቤት በተከሰሰበት ጊዜ የፍርድ ቤት መጥሪያ ክስና ማስረጃ ደርሶት እያለ፣ ቀርቦ ያልተከራከረ በሥር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመቀበል የተሰጠ ውሣኔ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ግድፈት አለበት የሚልና የውል ሕግ ድንጋጌዎችን አተረጓጎም አስመልክቶ በፍርድ ቤቱ የተሰጠው ትርጉም ተገቢ አለመሆኑን የሚዘረዝር የሰበር አቤቱታ አቅርባለች። ተጠሪው በበኩሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሥር ያልታየ አዲስ ጭብጥ ይዞ ዳኝነት ሊሰጥ እንደሚችል በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ በመሆኑ የውሉን ፎርም መሟላትና አለመሟላት መርምሮ መወሰኑ ተገቢ ስለሆነ፤ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል። አመልካች የመልስ መልስ

ያቀረበች ሲሆን በሰበር አቤቱታዋ ያነሳቻቸውን ነጥቦች በማጠናከር ተከራክራለች።

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይና በሰበር በግራ ቀኙ በኩል የቀረበው የሕግ መከራከሪያ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ተጠሪው የፍርድ ቤት መጥሪያና የከሳሽ ክስና ማስረጃ ደርሶት በከፍተኛው ፍርድ ቤት ቀርቦ ያላነሳቸውን መከራከሪያዎች በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አንስቶ መከራከሪያ ማድረግ ይችላል ወይስ አይችልም? ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎች በሥር መከላከያ አድርገው ሊያነሳቸው የሚገቡ ነገር ግን በሥር ቀርበው ያላነሷቸውን ክርክሮች ራሱ በማንሣት ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ ነው አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪው አመልካች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስና ማስረጃ እንደዚሁም የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሶት በወቅቱ ቀርቦ የመከላከያ መልሱንና ማስረጃውን አላቀረበም። ተጠሪው ያለበቂ ምክንያት ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ሣይቀርብ ቀርቶ መከራከሪያውን ባለማቅረቡና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 74 በሚደነግገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማለትም በሰላሣ ቀን ውስጥ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ጥያቄ ባለማቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ ተወስኗል። ተጠሪው የከፍተኛው ፍረድ ቤት ወደ ክርክሩ እንደገባ ያልፈቀደልኝ በአግባቡ አይደለም በማለት ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ አላቀረበም። ይግባኝ ባይ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሶት ቀርቦ ባልተከራከረበት ሁኔታ፣ በሌለበት ታይቶ በተሰጠው ውሣኔ ላይ በሚያቀርበው ይግባኝ በሥር ቀርቦ በመከላከያነት ሊያቀርባቸው የሚችለውን ሁሉንም የመከራከሪያ ነጥቦች በማንሣት የይግባኝ ቅሬታው መሠረት ማድረግ እንደማይችል ከፍትሐብሔር ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 328 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል። ምክንያቱም እንኳንስ የፍርድ ቤት መጥሪያ ደርሶት የቀረበበትን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል በሕጉ መሠረት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተወሰነበት ተከራካሪ ጉዳዩ እሱ ባለበት ታይቶና ክሱ ወይም የመከላከያ መልሱና ማስረጃው ተሰምቶ የተወሰነበት ወገን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በይግባኝ ደረጃ በሥር ፍርድ ቤት ያላነሳውን አዲስ መከራከሪያ ማቅረብ እንደማይችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 328 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በሌለበት ውሣኔ የተሰጠበት ተከራካሪ በሥር ቀርቦ መከላከያ ሊያደርጋቸው የሚገባውን የመከራከሪያ ነጥቦች በይግባኝ ቅሬታው የመከራከሪያ ነጥብ አድርጎ ለማንሳት ከላይ የተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ የማይፈቅድ ሲሆን ተከራካሪው እንኳን ቢያነሣው ይግባኙን የሚያየው ፍርድ ቤት ውድቅ ሊያደርገው ይገባል፡፡

በሌለበት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው በሌለበት በተሰጠው ውሣኔ ላይ ሊያነሣቸው የሚገባው የይግባኝ ቅሬታ ነጥቦችና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀብሎ ሊመረምራቸው የሚችላቸው መከራከሪያዎች እጅግ በጣም ውስን ናቸው፡፡ ይኸውም በክርክሩ ገብቶ የመከላከያ መልስና ማስረጃውን ባያቀርብም በከሣሽ በኩል የቀረበው ክስና ማስረጃ እሱን በሕግ አግባብ ኃላፊ የማያደርግ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ፣ የከሳሽን ክስና ማስረጃ ሲመዝን በፊፀመው የጎላ ስህተት ምክንያት ፍትሐዊ ያልሆነ ውሣኔ የተወሰነበት መሆኑን የሚያረጋግጡና ማንም ተከራካሪ ወገን ባያነሣቸውም ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ሊያነሣቸው የሚገቡ መሠረታዊ የሕግ ጉዳዮች በማለፍ ውሣኔ መስጠቱን የሚያመለክቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪው ውሉ በገንዘና በሻጭ ያልተፈረመ መሆኑን በምስክሮች ፊት ያልተፈረመ መሆኑና ውሉ በሚመለከተው ስልጣን ባለው አካል አለመመዝገቡን በይግባኝ መከራከሪያ ነጥቦች አድርጎ ያቀረበ ሲሆን ይግባኙን የሰማው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎትም ተቀብሎታል፡፡ ሆኖም እነዚህ መከራከሪያ ነጥቦች ተጠሪው በተከሳሽነት ቀርቦ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያነሣቸውና ሊከራከርባቸው የሚገቡ የመከላከያ ነጥቦች ናቸው፡፡ ተጠሪው የፍርድ ቤቱ መጥሪያ፣ የአመልካች ክስና ማስረጃ ደርሶት በራሱ ቸልተኝነት ምክንያት ለሥር ፍርድ ቤት በመከራከሪያነት አላቀረባቸውም፡፡ በክርክሩ ሂደት ባለመቅረቡም ጉዳዩ በሌለበት ተሰምቶና ተመርምሮ ተወስኗል፡፡ ስለሆነም ተጠሪው እነዚህን የመከራከሪያ ነጥቦች የይግባኝ ቅሬታ አድርጎ ማቅረቡና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ

ችሎትም መከራከሪያውን ተቀብሎ ውሣኔ መስጠቱ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው በሌለበት አይቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ የተፈፀመ የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት በሌለበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሣቸው የማይፈቀድለትን የተጠሪን መከራከሪያዎች ለምን ራሱ አነሣው የሚል ይዘት ያለው በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ፣ በሕግ በልዩ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ በይግባኝ የሚደረገው ክርክር በሥር ፍርድ ቤት የተነሣና የታየ ጉዳይ የሚመለከት እደሆነና፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር ፍርድ ቤት ክርክሩን በሚመራበት ማስረጃ በሚቀበልበት ወይም በሚመዝንበት እና ውሣኔ በሚሰጥበት ወቅት የፈፀማቸውን የሕግና የፍሬ ጉዳይ ስህተቶች ለማረም እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት ያልታዩና ያልተያዙ ጭብጦች መርምሮ እንደሚወስን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚህ ድንጋጌ የተሰጠው ስልጣን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተከራካሪዎች በሥር ፍ/ቤት በመከላከያነት ሊያነሷቸው የሚችሏቸው ነገር ግን ያላነሷቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በራሱ አነሳሽነት በማንሣት ውሣኔ የመስጠትን ሁኔታ የሚጨምር አይደለም፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪው የከፍተኛው ፍርድ ቤት መጥሪያና የአመልካች ክስና ማስረጃ ደርሶት ክርክር በሚያሰማበት ወቅት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ ተወስኗል፡፡ ተጠሪው በሕጉ የተቀመጡትን ሁኔታዎች በማክበር ቀርቦ በመከላከያ መልሱ ሊያነሣቸው የሚገቡ የውሉን ፎርም የተመለከቱ የመከራከሪያ ነጥቦች በራሱ ቸልተኝነት ምክንያት ባለማቅረቡ፣ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪው መከላከያ ሊያደርጋቸው የሚገባቸውን ነጥቦች በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ ባልተከራከረበትና ባላነሣበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በይግባኝ ተቀብሎና በራሱ አነሳሽነት አንስቶ መሻሩ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 328 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

182 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች መንፈስና ዓላማ ጋር የማይጣጣም እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 19095 ሚያዝያ 6 ቀን 1998 ዓ.ም. ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 16545 ጥር 14 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሥነ ሥርዓት ሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ስላተሻረ ተጠሪው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት በውሉ የገባውን ግዴታ የመፈፀም ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 25890

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሠ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢት/መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ኃይሉ ተሰማ ቀረበ

መ/ሰጭ፡- እነ ዝናሽ አሰፋ /2ሰዎች/ - ቀረበች

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የካሣ ክፍያን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን መ/ሰጭዎች የሥር 1ኛ ተከሣሽ /አቶ መኩንን ደበበ/ ንብረትነቱ የሥር 2ኛ ተከሣሽ /የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር/ የሆነውን ተሽከርካሪ በቢሾፍቱ ከተማ ሲያሽከረክሩ አባታችንን ገጭተው የገደሉ ስለሆነና ሟች አባታችን አስተዳዳሪያችን ስለነበሩ ከቀን ገቢያቸው ከብር 22.00 /ሃያ ሁለት ብር/ ላይ 60% የሚሆነውን ለእኛ ይሰጡን ስለነበር በሟች ምክንያት ጉዳት ደርሶብናል፣ ስለዚህ ካሣ ይከፈለን በማለት በኦሮ/ብ/ክ/መ/ምስ/ሽ/ዞ/ ከፍ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ በወቅቱ ጣልቃ ገብ የነበረው የአሁን አመልካች አደጋው በደረሰበት ወቅት የሟች የቀን ገቢ ብር 22.00 አልነበረም፣ ሟች እስከ 65 ዓመታቸው ድረስ ይኖራሉ የተባለው ተቀባይነት የለውም፣በመ/ሰጭ የተጠየቀው ልዩ ልዩ ወጪ በማስረጃ አልተደገፈም፣ መ/ሰጪዎች ለአካለ መጠን የደረሱ ስለሆነ ካሣ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በኋላ በቃል ክርክር ወቅት የሥር 2ኛ ተከሣሽ ቀርቦ አደጋው የደረሰው በእኛ ተሽከርካሪ መሆኑ ባይካድም በሾፌሩ ጥፋት ምክንያት አይደለም ሲል ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም መኪናውን ሲያሽከረክር የነበረው የሥር 1ኛ ተከሣሽ /ሹፌሩ/ ጥፋተኛ መሆናቸው በትራፊክ ፖሊስ ማስረጃ ስላልተረጋገጠ ጥፋተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደሉም፣ የሥር 2ኛ ተከሣሽ ደግሞ አደጋውን ያደረሰው የእሱ ንብረት የሆነው መኪና መሆኑን ስላመነ እና የመኪናው ባለቤት ስለሆነ ተጠያቂ ነው፣የካሣ ክፍያውን በተመለከተ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2095/2/ እና 807 እስከ 825 ካሣው የሚከፈለው በቀለብ መልክ እንደሆነ ከመግለጽ ውጭ ካሣ መጠየቅ የሚችሉትን ሰዎች በእድሜ ለይቶ አላስቀመጠም፣ አባት ልጆቹን እስኪያረጁ ድረስ እንኳን ቢረዳቸው የሚከለክለው ሕግ የለም፣ ስለሆነም ጣልቃ ገብ /የኢት/መድን ድርጅት/ ለመ/ሰጭዎች ብር 21,000 /ሃያ አንድ ሺህ/ ይክፈል ሲል ወሰነ፡፡

የሥር ጣልቃ ገብ /የኢት/መድን ድርጅት/ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱ የኢት/መድን ድርጅት የደንበኛው (የአቅም ግንባታ ሚ/ር) ተወካይ ወይም ጠበቃ እስካልሆነ ድረስ ደንበኛው ከ3ኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ክርክር ጣ/ገብቶ እንዲከራከር የሚፈቅድለት ሕግ የለም፡፡ በመሆኑም የኢት/መድን ድርጅት ደንበኛውን ወክሎ ደንበኛው ሊያነሣ የሚችለውን ክርክር በማንሣት መከራከር የሚችለው ምናልባት የሚመጣውን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ ደንበኛውን ከክርክሩ አስወጥቶ ከቀረበ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ደንበኛው እየተከራከረ ሳለ አንድ ጊዜ ከደንበኛው ጋር በሌላ ጊዜ ደግሞ ከ3ኛ ወገን ጋር መከራከር የሚችልበት የሕግ አግባብ ስለሌለና ድርጅቱ ለደንበኛው ጥብቅና የመቆም መብቱ ከፖሊሲው ስለማይመነጭ እሱን የማይመለከተውን ክርክር ማቅረቡ ያለአግባብ ነው በማለት የይግባኝ ቅሬታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታው አጠቃላይ ይዘትም በጣልቃ ገብነት የመከራከር መብቱን አስመልክቶ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ሕግን የተከተለ አይደለም፤ ለአካለ መጠን ለደረሱ ሰዎች የክርክሩ መነሻ የሆነው ካሣ እንዲከፈል የተሰጠው ውሣኔም ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡ የአሁን መ/ሰጭዎች አስተዳዳሪያችን የነበሩት አባታችን

በተሽከርካሪ ተገጭተው በመሞታቸው ምክንያት የተቋረጠብን ገቢ ይከፈለን በማለት በክልሉ ምስ/ሽ/ዞ/ከፍ/ፍ/ቤት የአቅም ግንባታ ሚ/ርን ከነ ሾፌሩ ከከሰሱ በኋላ ፍ/ቤቱ ተገቢ ነው ያለውን ካሣ በወቅቱ ጣልቃ ገብ የነበረው የአሁኑ አመልካች ይክፈል በማለት ውሣኔ መስጠቱን፣ እንዲሁም አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱ አመልካች የደንበኛው ጠበቃ ስላልሆነ በጣልቃ ገብነት ቀርቦ የደንበኛውን ክርክር እያነሣ መከራከር አይችልም በማለት መወሰኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

በመሠረቱ በጣልቃ ገብ /የኢት/መድን ድርጅት/ እና በሥር 2ኛ ተከሣሽ (የአቅም ግንባታ ሚ/ር) መካከል የመድን ውል መኖሩ አላከራከረም፡፡ የአቅም ግንባታ ሚ/ር ተሽከርካሪ ጉዳት በማድረሱ ምክንያት ክስ ቀርቦ ካሣ መክፈል እንዳለበት ከተወሰነ በመድን ውሉ ላይ እስከተገለፀው መጠን ድረስ ያለውን ካሣ የመክፈል ኃላፊነቱ የአመልካች እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡ ስለሆነም የክርክሩ ውጤት በአመልካች መብት ወይም ጥቅም ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሣድር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአቅም ግንባታ ሚ/ር ተሽከርካሪ ባደረሰው ጉዳት ምክንያት የካሣ ክፍያ ጥያቄን የያዘ ክስ ሲቀርብ ጉዳዩ አመልካችን ስለሚመለከተው በክርክሩ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የኋላ ኋላ ሊመጣበት የሚችለውን ማንኛውንም ኃላፊነት ቢቻል ለማስወገድ ባይቻል ለመቀነስ የሚያስችለውን ክርክር ማቅረቡ ተገቢ ነው፡፡ በአንድ ክስ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በክርክር ላይ ባሉበት ጊዜ በጉደዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም 3ኛ ወገን ከፍርድ ውሣኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ መከራከር እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41/1/ ላይ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች የደንበኛው ጠበቃ ስላልሆነ ጣልቃ ገብቶ መከራከር አይችልም በማለት በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የኦሮ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35340 ሰኔ 1 ቀን 1998 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል። ይፃፍ።
2. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ጣ/ንብቶ የመከራከር መብት ያለው መሆኑን ተገንዝቦ በጉዳዩ ጣልቃ አስገብቶ እንዲያከራክረውና በሕጉ መሠረት እንዲወስን ብለናል።

ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ። መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 26670

ህዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አዲስዓለም ሲሣይ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢት/ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ ቀረበ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 428(2) ባለገንዘቡ ንብረት እንዲረከብ ሲታዘዝ በእዳውና በንብረቱ መሃከል ያለውን ልዩነት ባለገንዘቡ ለባለእዳው ተመላሽ ሊያደርግ ይገደዳል ወይ? የሚለውን ነጥብ የሚመለከት ነው።

ጉዳዩ የጀመረው በደቡብ ወሎ መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው። የአሁኑ አመልካች በመሠረቱት ክስ ለዳቦ ቤት ማስፋፊያ ከተጠሪ ባንክ የተበደሩትን ብር 43,259 (አርባ ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ) ባለመክፈላቸው ተጠሪ ወለድን ሁሉ በማካተት በብር 54,718.38 (ሃምሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ አሥራ ስምንት ከሰላሳ ስምንት) ክስ መሥርቶ ካስወሰነ በኋላ የተለያዩ ወጪዎችን ጨምሮ የብር 63,184.74 (ስልሳ ሦስት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ አራት ከሰባ አራት) የአፈፃፀም ክስ አቅርቧል። ይህ ገንዘብም ባለመከፈሉ የዳቦ ቤት ድርጅት፣ መኖሪያ ቤት እና የሆቴል ቤት ድርጅት ጠቅላላ ግምታቸው 121,829.67 (አንድ መቶ ሃያ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከስልሳ ሰባት) የሆኑ ንብረቶች በጨረታ ሊሸጡ ባለመቻላቸው ባንኩ በግንቦት 5 ቀን 1994 ዓ.ም በተሰጠ ትእዛዝ ተረክቧቸዋል። ስለዚህ ከቤቱ ግምት ላይ በአፈፃፀም የጠየቀው 63,184.47 (ስልሳ ሦስት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ አራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከአርባ ሰባት) እና ለኦሮሚያ ገንዘብ ጽ/ቤት ለአመልካች የከፈለው ብር 10,222.05 (አስር ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ከ አምስት) ተቀንሶ ከተረፈው ብር 48,644.93 (አርባ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ አርባ አራት ከዘጠና ሦስት) የአመልካችን ድርሻ ብር 24,322.46 (ሃያ አራት ሺህ ሦስት መቶ ሃያ ሁለት ከአርባ ስድስት) ከባንክ ወለድ ጋር እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለቀረበበት ክስ አመልካች የሚፈለግባቸው ዋና እዳ፣ ወለድና የቅጣት ወለድ፣ የኢንሹራንስና ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች እንዲሁም የሽያጭ ታክስ በድምሩ 111,607.62 (አንድ መቶ አስራ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰባት ከሥልሳ ሁለት) ሲሆን ይኸው እዳ ተቀንሶ ተራፊው ብር 10,222.05 (አስር ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ከአምስት) በአመልካች ስም በአገር ውስጥ ገቢ ለሚፈለግባቸው እዳ ገቢ የተደረገ በመሆኑ እዳቸው ተቻችሎ የቀረ ገንዘብ የለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት አመልካች ብር 54,718.38 (ሃምሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ አሥራ ስምንት ከሠላሳ ስምንት) እዳው ተከፍሎ አለቀ ድረስ ባልተከፈለው የገንዘብ መጠን ላይ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ ብር 63,184.74 (ስልሳ ሦስት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ አራት ከሰባ አራት) እንዲከፈለው የአፈፃፀም ክስ አቅርቧል የኢንሹራንሽ ክፍያ፣ ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች፣ የሽያጭ ታክስ፣ የወለድ ወለድ ከመቼ እስከ እስከመቼ ያለው እንደሆነ አልገለፀም አልተከራከረበትም፡፡ በመሆኑም የአፈፃፀም ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ቤቱን እስከተረከበበት ጊዜ ድረስ ያለውን ወለድ፣ በቤቱ ላይ የተደረገውን ጨረታ ለማስፈፀም የወጣውን ወጪ አመልካች ለተጠሪ ይክፈሉ፣ ከዚህ ውጪ ለኢንሹራንስ ለልዩ ልዩ ወጪዎች የቅጣት ወለድና የሽያጭ ታክስ ክፍያ ገንዘቡ ተቻችሏል በማለት ማስቀረት ስለማይችል ይህንን ገንዘብ ለአመልካች ተመላሽ ያድርግ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ ሕጉ በሚያዘው መሠረት ጨረታ ተካሂዶ ንብረቱን የሚገዛ ሰው ሲጠፋ ፍ/ቤቱ

በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 428(2) መሠረት ትእዛዝ ሲሰጥና ባለገንዘቡ ንብረቱን ሲረከብ የባለእዳው ንብረት ግምት ከፍተኛ ከሆነ ልዩነቱን የፍርድ ባለመብት ይመልሣል የሚል ነገር የለም በማለት የንብረቱ ግምት ልዩነት ለአመልካች እንዲመለስ የተሰጠውን ውሣኔ ሽሯል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የባለእዳውን ንብረት በጨረታ የሚገዛ ጠፍቶ ባለገንዘቡ ሲረከበው በንብረቱ ግምትና በእዳው መሃከል ያለውን ልዩነት ባለገንዘቡ ሊመልስ አይገባም ወይ? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በቃል ለችሎቱ አሰምተዋል፡፡

አንድ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ በተለይ ውሣኔው ገንዘብ እንዲከፈል የሚያዝ ከሆነ ፍርዱ ወይም ውሣኔውን የፍ/ባለእዳውን ንብረት በማስከበርና በማሸጥ ለማስፈፀም የሚቻል መሆኑን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.394(1) ያስገነዝበናል፡፡ ውሣኔውን ለማስፈፀም የሚሸጠው ወይም የሚከበረው ንብረት ግምትም በተቻለ መጠን በፍርዱ ወይም በውሣኔው ላይ ከተገለፀው የገንዘብ ልክ ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን እንደሚገባ ተከታዩ ንዑስ ቁጥር ያመለክታል፡፡ ይህም የሆነው አንድ ባለገንዘብ በአፈፃፀም ሊያገኝ የሚገባው በፍርድ የተወሰነለትን የገንዘብ መጠን ብቻ በመሆኑ ከእዳው በላይ የሚያወጣ ንብረት መሸጡ አግባብ ስለማይሆን ነው፡፡ በእርግጥ ከእዳው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት ባልተገኘ ጊዜ ከዕዳው በላይ ዋጋ ያለው ንብረት ሊሸጥ ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ግን ከሸያጩ ገንዘብ ላይ እዳው ተከፍሎ ተራፊው ለባለእዳው እንዲመለስ ሊደረግ ይገባል፡፡ ነገር ግን ንብረቱ ገዢ አጥቶ ባለገንዘቡ ሲረከበውና የንብረቱ ግምት ከእዳው በላይ ሲሆን ልዩነቱን ባለገንዘቡ ለባለእዳው ተመላሽ ሊያደርግ ይገባል ወይ? የሚለው ሊመለስ ይገባል፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 428(2) ሁለተኛ ጨረታ ወጥቶ ተጫራች ካልቀረበ ንብረቱን ባለገንዘቡ ተረክቦ እንዲይዝ ትእዛዝ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን ከማመልከት በቀር ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ጥያቄ የሚመልስ ግልጽ ነገር አላስቀመጠም፡፡ በተመሣሣይ በባንክ በመያዣ የተያዙ ንብረቶችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተመለከተ የወጣውን አዋጅ ቁ. 97/90ን ለማሻሻል የወጣው አ/ቁ.216/92 አንቀጽ 1 ባንክ ሁለት ጊዜ ጨረታ አውጥቶ ገዢ ካልተገኘ ንብረቱን ለመጀመሪያ ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሠረት እንደሚረከበው ከመደንገግ አልፎ በዋጋ ግምቱና በእዳው መሃከል ልዩነት ቢኖር ሊፈፀም የሚገባውን ነገር አያመለክትም፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አንድ ባለገንዘብ ሊያገኝ የሚገባው የእዳውን መጠን ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉም ሆነ በተጠቀሰው አዋጅ በዋጋው ግምትና በእዳው መሃከል ልዩነት ባለ ጊዜ ስለሚፈፀመው ነገር አልተገለፀም በሚል ባለገንዘቡ ከሚፈለገው እዳ መጠን በላይ የሚገመት ዋጋ ያለው ንብረት ተረክቦ ልዩነቱን እንዳይከፍል ማድረግ ለባለገንዘቡ ያላበደረውን ገንዘብ በማስከፈል አላግባብ ማበልፀግና ባለእዳውም ከእዳው በላይ እንዲከፍልና ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ ይሆናል፡፡ የሕጉ አላማም ይኼ አይደለም፡፡

በመሆኑም ባለገንዘቡ የተረከበው ንብረት ዋጋ ግምት ከእዳው በላይ ከሆነ ልዩነቱን ሊከፍል ይገባል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ ከአመልካች ላይ የሚፈልገው እዳ ባንኩ ከተረከበው ንብረት በታች መሆኑ አላከራከረም፡፡ በመሆኑም ባንኩ ልዩነቱን የመመለስ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 428(2) ላይ ይህንን አስመልክቶ በግልጽ የተመለከተ ነገር የለም በማለት ተጠሪ ልዩነቱን ሊከፍል አይገባም ብሎ የደረሰበት መደምደሚያ ስህተት ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል ሊታይ የሚገባው አመልካች አለብኝ የሚሉት እዳና ተጠሪ አለባቸው የሚለው የእዳ መጠን ልዩነት ነው፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው ተጠሪ አመልካች ላይ ያስወሰነው ብር 54,718.38 (ሃምሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ አሥራ ስምንት ከሰላሳ ስምንት) እና እዳው ተከፍሎ እስከ አለቀ ድረስ ባልተከፈለው የገንዘብ መጠን ላይ የሚታሰብ የባንክ ወለድ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ለኢንሹራንስ፣ የቅጣት ወለድ፣ የሽያጭ ታክስ ሆነ ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች እንዲከፈለው የተሰጠ ውሣኔ

የለም፡፡ በመሆኑም ከፍተኛ ፍ/ቤቱ አፈፃፀም ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ ቤቱን እስከተረከበበት ጊዜ ያለው ወለድ እና በቤቱ ላይ የወጣውን ጨረታ ለማስፈፀም የወጣው ወጪ አመልካች እንዲከፍሉና ተጠሪ ለኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች፤ ለሽያጭ ታክስ የወለድ ቅጣት ላለባቸው እዳ ቀንሻለሁ ያለው አግባብ ባለመሆኑ የአመልካች ድርሻ እንዲመለስላቸው መወሰኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የደ/ወሎ መስ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05839 ሰኔ 20 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 58/98 ሐምሌ 17 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ፋይል ቁ. 27739

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አቶ ድንቁ ገላው

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዋለ እሸቱ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መቅረብ ምክንያት የሆነው አመልካች ጽፈው ያቀረቡት ማመልከቻ ነው፡፡

የጉዳዩ የሥር አመጣጥ አመልካች ከሳሽ በመሆን በጭልጋ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ተጠሪ ቤት ሠርቼ ባዶ ቦታ ስላለኝ ግዛኝ ብለው በሽማግሌዎች አስማሚነት ቦታውን በብር 3500 (ሶስት ሺህ አምስት መቶ) ገዝቼ ቤት ሠርቼበታለሁ፣ በቤቱም የልብስ ስፌት ድርጅት አቋቁሜ እየሠራሁበት ነው፣ ሆኖም ተጠሪ ቤቱን በስሜ ስላላዛወሩልኝ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2892 መሠረት ተገደው እንዲፈጽሙ ይደረግልኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪም በበኩላቸው ውሉ በሚመለከተው አካል ቀርቦ ያልፀና ከመሆኑም በላይ በማታለልና በተንኮል የተፈፀመ በመሆኑ ሕጋዊነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የሽያጭ ውሉ ይፀድቃል፣ ውሉ ለውልና ማስረጃ ቀርቦ እንዲፀድቅና ስመ ንብረቱ ለአመልካች እንዲዛወር የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ያሁኗ ተጠሪ በውሣኔው ቅር ተሰኝተው ለሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም መሬት መሸጥ የተከለከለ በመሆኑ ውሉ ለሕግ ተቃራኒ ነው በማለት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር እና አመልካች ለቤት ማሠሪያ

ያወጡትን ወጭ በሕግ የመጠየቅ መብት በመጠበቅ ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ በአመልካች ይግባኝ ባይነት ቀርቦ ከተመረመረ በኋላ ክሱ ሙሉ የባለቤትነት መብትን ለመገልገል ለመሸጥ፣ ለመለወጥ ወይም ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ እንዲቻል የቀረበ፣ በሌላም በኩል ተጠሪ ንብረቱ ያላግባብ ከእጄ ወጥቷል በማለት ባልተከራከሩበት ከፍተኛው ፍርድ ቤት ባልተጠየቀው ጉዳይ ዳኝነት ሰጥቷል በሚል ውሣኔውን በመሻር የከፍተኛው ፍርድ ቤት ስመ ንብረቱ ሊዛወር ይገባዋል ወይስ አይገባውም በሚል ጭብጥ ላይ ብቻ ተመሥርቶ በማከራከር እንዲወስን ጉዳዩን መልሶታል የፍተኛው ፍርድ ቤትና በድጋሚ ጉዳዩን አይቶ መሬት መሸጥ ሕገወጥ መሆኑን ተችቶ ተጠሪ ተገደው ለአመልካች ሊያስተላልፉ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም እንደገና ይግባኝ ቀርቦለት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ካፀና በኋላ አመልካች ለቤቱ ማሠሪያ ያወጡትን ወጪ በተመለከተ መብታቸውን በመጠበቅ ቤቱን አፍርሰው ቁሣቁሱን ከወሰዱ በኋላ ቦታውን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት በዚህ ነጥብ ላይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በገዘምታ ያለፈውን በማሻሻል ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረቡት በዚህ መነሻ ሲሆን የአቤቱታው አንኳር ነጥብ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበለትን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ክርክራቸውንም ከሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን እንደመረመረው ገና ከጅምሩም ክሱን ለማስተናገድ የሚያስችል የክስ መሠረት እንደነበርና እንዳልነበር ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ ባዶ ቦታን የሚመለከት እንደመሆኑ የመሬት ባለቤት መንግሥት መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለና በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ከመነሻውም ፈራሽ መሆኑ እየታወቀ ወይም መታወቅ ሲኖርበት ጉዳዩ የክስ መሠረት እንዳለው ተቆጥሮ መስተናገዱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ምንም እንኳ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሕገ ወጥ ውል ሣቢያ የአመልካችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው አግባብ ቢሆንም የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረግ የነበረባቸው ጉዳዩን ከክስ መሠረት መኖርና አለመኖር አኳያ በማጤን ነበር፡፡ ምክንያቱም የክስ መሠረት ሣይኖር ጉዳዩ እንዲስተናገድ በመደረጉ አመልካችና ተጠሪ በየደረጃው በተሰጡ ውሣኔዎች አንዱ የፍርድ ባለመብት በሌላ ጊዜ ደግሞ የፍርድ ባለእዳ ለመሆን ተዳርገዋል፡፡ ለዚህም አመልካች በወረዳው ፍርድ በተደረገው ክርክር የፍርድ ባለመብት ሲሆኑ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሣኔ የፍርድ ባለእዳ መሆናቸውን መጥቀሱ ይበቃል፡፡ ሆኖም የክስ ማመልከቻው የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 231/1/ መሠረት ማመልከቻው የክስ መሠረት መኖሩን አላመለከተም በማለት ተጠሪን ሣያስቀርብ ክሱን መዝጋት ሲኖርበት ግራ ቀኙን አከራክሮ መወሰኑ ተገቢነት እንደሌለው እየታወቀ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን ነጥብ ትቶ ጉዳዩ የክስ መሠረት እንዳለው አድርጎ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሣኔው መሻሻል ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

- የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 05873 ጎንደር 11 ቀን 1999 ዓ.ም፣ እንዲሁም የሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 05220 ታህሣሥ 4 ቀን 1997 ዓ.ም በዋሉት ችሎቶች የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሎ ክሱ ከመነሻውም የክስ መሠረት የሌለው ነው ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
- በዚህ ጉዳይ ለአፈፃፀም የሚቀርብ ነገር ባለመኖሩ የጭልጋ ወረዳ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም መዝገቡን እንዲዘጋ የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 27808

የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
ተገኔ ጌታነህ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ሒሩት መለሠ
አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

ተጠሪ፡- 1. ማይገነት ብርሃኑ
2. ፍሬ ሰላም በቀለች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ አቤቱታ የቀረበው አመልካች ታህሣሥ 5 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው የሰበር ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩ የሥር አመጣጥ የአሁን ተጠሪዎች በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እነ መኮንን አስፋው ከተባሉት ጋር በነበራቸው ክርክር ምክንያት በምዕራብ ሸዋ ዞን ኤጆሬ ወረዳ አዲስ ዓለም ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 447 የሆነውን ቤትና እንዲሁም በ2243 ሜትር ካሬ ላይ የሰፈረው የሆቴል ድርጅት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ የእግድ ትዕዛዝ መሰጠቱን አመልካች ገልፆ እነዚህን ንብረቶች አመልካች በታህሣሥ 01 ቀን 1994 ዓ.ም. በተፈረመ የብድር ውል ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሣ ሺህ/ ለመኮንንና ሊሻን የእህል ንግድ ሽርክና ማኅበር ሲያበድር በመጀመሪያ ደረጃ ዋስትና መያዙን፣ ተበዳሪዎች በውሉ መሠረት ባለመክፈላቸው ባንኩ በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በመያዣ የተሰጡትን ንብረቶች በጨረታ አወዳድሮ አሸናፊ ለሆኑት ለወ/ሮ ጥሩነሽ ቴሶ ስመንብረቱ እንዲዛወር ለአዲስ ዓለም ከተማ አስተዳደር የፃፈው ደብዳቤ ከላይ ፍርድ ቤቱ ንብረቶቹ እንዳይሸጡ ባስተላለፈው እግድ ምክንያት ተቀባይነት አለማግኘቱን በመግለጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እግዱ እንዲነሣለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት እግዱን ለሰጠው ፍርድ ቤቱ አቅርቦ የአሁኑ ተጠሪዎችም እግዱ ሊሠማ አይገባውም በማለት ያቀረቡትን ተቃውሞ ከመረመረ በኋላ ፍርድ ቤቱ አመልካች በክርክሩ ወቅት ጣልቃ አለመግባቱን፣ ተጠሪዎቹ በንብረቱ ላይ ባለመብት መሆናቸው ከተወሰነ በኋላም አመልካች ተቃውሞ አለማንሣቱን ምክንያት በማድረግ እግዱ አይነሣም በማለት ወስኗል፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ውሣኔውን አጽንቷል። አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው በዚህ መነሻነት ሲሆን ይህ ፍርድ ቤት ተጠሪዎችን በማስቀረብ ግራ ቀኙን አከራክሯል። ክርክራቸውን ከሕግ ጋር በማገናዘብም መርምሯል። በዚህም መሠረት እግዱ አይነሣም ተብሎ በሥር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው ባግባቡ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው ተመልክቷል።

በዚህ ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን እግድ የሰጠው የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን እግዱንም የሰጠው ያሁን ተጠሪዎች እነ መኮንን አስፋው ከተባሉት ጋር በነበራቸው የውርስ ንብረት ክርክር ምክንያት ሆኖ እግዱም የሚቆየው ፍርድ ቤቱ ለክርክሩ እልባት እስኪሰጥ ድረስ ነው። በዚህ ክርክር አመልካች ተካፋይ አልነበረም። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 153/2/ ላይ እንደተመለከተው ከፍርድ በፊት የሚሰጥ የማገጃ ትዕዛዝ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን የእግድ ትዕዛዙ ከመስጠቱ በፊት ያገኘውን መብት እንደማይነካበት ግልጽ በሆነ መልኩ ደንግጎት ይገኛል። በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀደም ሲል ከነ አቶ መኮንን አስፋው ጋር የመያዣ ውል አድርጓል። ይህንን ውል መሠረት አድርጎም በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የመያዣ ንብረቶቹን ፍርድ ቤት መሄድ ሣያስፈልገው በቀጥታ በራሱ መሸጥ የሚችል ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ንብረቶቹ በሌሎች ወካዮች መካከል ባለው ክርክር ምክንያት በመታገዱ እግዱ እንዲነሣለት ሲጠይቅ የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ከሌሎቹ ወራሾች ጋር በነበረው ክርክር ጣልቃ አልገባም በማለት እግዱን አለማንሣታቸውና ይልቁንም በክርክሩ ተካፋይ ያልነበረ መሆኑ ከላይ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 153/2/ መሠረት ተጠቃሚ መሆን

ሲገባቸው ተጎጂ እንዲሆን ማድረጋቸውን ፍርድ ቤቱ ተረድቷል። በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የሚያስችላቸው ግልጽ ድንጋጌ እያለ እግዱን ያለ ሕጋዊ መሠረት ላለማንሣት የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. ዐዐ033 ሐምሌ 06 ቀን 1998 ዓ.ም. እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 44141 ጥቅምት 24 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጡት ትዕዛዝ ተሽሯል፤ ይፃፍ።
- የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ጉዳይ የሰጠው እግድ ተነስቷል። ይፃፍ፤
- ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ፤፤
- መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 28522

ኅዳር 3 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢት/ ንግድ ባንክ - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- 1. ሞያሌ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ ዓሊ ሺዶ ቀረበ፡፡

2. ወ/ሮ ብርቂ ያደቹ፣ ዓሊ አብዱልአዚዝ - ቀረበ፡፡

3. የሐጂ አብዱላዚዝ ካሕሣይ ወራሾች

1. አቶ አሊ አብዱላዚዝ - ቀረበ፡፡

2. ወ/ት ፋሪያ አብዱላዚዝ - ቀረበች፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በቦረና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ባቀረበው ክስ ለሐጂ አብዱላዚዝ ካሕሣይ ብድር ሲሠጥ በሞያሌ ከተማ የሚገኘውን መኖሪያና ንግድ ቤት በመያዣ የያዘ ሲሆን ይህን የመያዝ መብቱን 1ኛ ተጠሪ እንዲመዘግብ ጠይቆ ተጠሪው መያዣውን መመዝገቡን ያረጋገጠለት ቢሆንም ይህንኑ ንብረት የቦረና ዞን ፋይናንስ መምሪያ ለሚፈልገው የግብር ዕዳ በሐራጅ ለመሸጥ በሂደት ላይ እንዳለ ጣልቃ ገብቶ ቢከራከርም ባንክ ብድሩን ከመስጠቱ በፊት ይህ ንብረት በፍ/ቤት ትዕዛዝ ተከብሮ የቆየ ነው በሚል ጥያቄውን አልተቀበለም፡፡

በመሆኑም አስተዳደሩ የሙያ ግዴታውን ሣይወጣ በመቅረቱ የተነሣ ገንዘባችንን ስላሣጣን ተበዳሪው ያልመለሠውን ገንዘብ ይመልስ፣ የተበዳሪው ሚስት እና ወራሾቹ ያልተከፈለውን እዳ ይክፈሉ በማለት ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ባንኩ መያዣውን ከማስመዝገቡ በፊት በሌላ እዳ የተያዘ መሆኑን ሣያጣራ እንዲመዘገብለት ብቻ

ጠይቆ አስተዳደሩም መያዣውን ባለበት ሕጋዊ ግዴታ መሠረት በቅደም ተከተል በመመዝገቡ ኃላፊነት የለበትም የተበዳሪው ሚስትና ወራሾችን በተመለከተ ሚች ከቦረና ዞን ፋይናንስ መምሪያ ጋር ሲፋለሙ ባንኩ ተከራክሮ ስለተወሰነበት ድጋሚ አዲስ ክስ ሊያቀርብ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የቀረበለትን የይግባኝ ቅሬታ መ/ሰጪዎችን ሣይጠራ ዘግቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበው ክስ ቀደም ሲል ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ ላይ ነው በሚል ክሱ ውድቅ መደረጉንና 1ኛ ተጠሪ ከኃላፊነት ነፃ የተደረገው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበው ፍ/ቤቱ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለተ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሠረት ማንኛውም ፍ/ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ የፍርድ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ 3ኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸውም ዓይነት ሌላ ክርክር ሊቀርብባቸው አይችልም፡፡ እንግዲህ ይህ የሰነ ሥርዓት ሕጉ ተፈፃሚ እንዲሆን መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንደኛው ውሣኔ የተሠጠበትና አዲስ ክስ የቀረበበት ክርክር ሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት መሆኑ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ባንክ ቀድም ሲል ክርክር አቅርቦ የነበረው ለፋይናንስ መምሪያው ዕዳ በሃራጅ እንዲሸጥ የተባለውን ንብረት በመያዣ የያዘው በመሆኑ በንብረቱ ላይ የቀዳሚነት መብቱን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም በክርክሩ የተያዘው ሥረ ነገርና ጭብጥ ባንክ በንብረቱ ላይ የቀዳሚነት መብት አለው? የለውም? የሚለው ነው፡፡ በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ክስ ደግሞ ሚች ሃጂ አብዱላዚዝ ካሕሣይ የወሠዱትን ብድር የሚቹ ባለቤትና ወራሾቻቸው ሊከፍሉ ይገባል የሚል በመሆኑ የሚያዘው ጭብጥ ተከሣሾቹ የብድሩን ገንዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊከፍሉ ይገባል? አይገባም? የሚለው ነው። በመሆኑም የሁለቱም ክርክሮች ሥረ ነገርና የተያዘው ጭብጥ የተለያየ በመሆኑ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ነው ለማለት አይቻልም። ስለዚህ ፍ/ቤቶቹ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5ን ጠቅሰው የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው የሕግ ስህተት ነው።

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ ኃላፊ የመሆን አለመሆኑ ጉዳይ ነው። ከመዝገቡም እንዲሁም ይህ ችሎት ባደረገው የቃል ማጣሪያ ጥያቄ አመልካች በመያዣ የያዘውን ንብረት በመያዣነት እንዲመዘገብለት ለ1ኛ ተጠሪ ሲጠይቅ ተጠሪውም በዚሁ መሠረት ንብረቱ የተበዳሪው መሆኑን በማረጋገጥ መመዝገቡን ገልጿል። ባንኩ ይህ በመያዣ የያዘው ንብረት በሌላ እዳ የተያዘ ለመሆኑ 1ኛ ተጠሪ እንዲያረጋግጥለት ያቀረበው ጥያቄ ስለመኖሩም ሆነ ተጠሪው ንብረቱ ከሌላ እዳ ነፃ መሆኑን አረጋግጦ የሰጠው መልስ ስለመኖሩ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም። በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚቋቋሙ መብቶች አብዛኞቹ ንብረቱ በሚገኝበት አገር ባለው የሃብትነት መዝገብ ስለሚመዘገቡ /የፍ/ሕ/ቁ. 1567 ተከታዮቹን ይመለከታል/ 3ኛ ወገን በንብረቱ ላይ ያለውን ግዴታና እዳ እንደሚያውቅ ይገመታል አመልካቹም መያዣውን ከማስመዝገቡ በፊት በንብረቱ ላይ ያለውን ግዴታ ማጣራት ይጠበቅበታል። 1ኛ ተጠሪ ባንኩ የመያዣ ውሉን እንዲመዘግብ ሲጠይቅ መመዝገቡ ሕጋዊ ተግባሩን መወጣቱን ከሚያመላክት በቀር ኃላፊነት የሚያስከትል ስራ ሠርቷል ማለት አይቻልም። አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከአንድ በላይ ለሆነ እዳ ሊያዝ ስለሚችል በንብረቱ ላይ ቀድሞ የተመዘገበ ዕዳ ወይ ግዴታ መኖሩ ንብረቱን ለተጨማሪ እዳ ልመዘግብ አልችልም የሚልበት ምክንያት የለም።

በአጠቃላይ 1ኛ ተጠሪ የሚች ንብረት ላይ ዕዳ መኖሩን ቢያውቅም የባንክን መያዣ መመዝገቡ ኃላፊነት ሊያስከትልበት የሚችል ድርጊት ሆኖ አልተገኘም። የሥር ፍ/ቤቶችም 1ኛ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ የሕግ ስህተት አለው ለማለት አይቻልም።

ው ሣ ኔ

1. የቦረና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01107 በታህሣሥ 20 ቀን 1998 የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል።
2. 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበው ክስ በውሣኔ ባለቀ ጉዳይ ደግሞ የቀረበ ባለመሆኑ ወደ ፍሬ ነገሩ ገብቶ አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩ ለቦረና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመልሷል።
3. 1ኛ ተጠሪ በቀረበበት ክስ ኃላፊነት የለበትም።
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ለመ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 28802

ታህሣሥ 8 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ በየነች ይገዙ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሳሙኤል ዝቅአርጋቸው - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት በሐራጅ ተሸጦ ግራ ቀኙ እንደየድርሻቸው ይከፋፈሉ በማለት በበታች ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካቾች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ ከሚች አባታቸው በውርስ ተከፍሎ የሚደርሳቸውን በወረዳ 16 ቀበሌ 09 ክልል የሚገኘው ቁጥር 249 የሆነው ቤት የዋጋ ግምቱ ብር 120,000.00 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ) ሲሆን ከዚህ ላይ የከሳሽ ድርሻ 1/6ኛ ብር 20.000 /ሃያ ሺህ/ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ተከሣሾች እንዲከፍሉኝ እንደዚሁም ሚች አባቴ ከሞቱበት ጥቅምት 1992 ዓ.ም. ጀምሮ ቤቱን ተከሣሾች ይዘው ለተጠቀሙበት ብር 2,186.87(ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ስድሥት ብር ከሰማኒያ ሰባት ሳንቲም) ጨምሮ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሾች ደርሶ በሰጡት መልስ ከሳሽ የሚች አቶ ዝቅአርጋቸው ተካ ልጅ መሆኑን አምነው የቤቱን ግምት ለከሳሽ በድርሻው ልክ ለመስጠት እንደዚሁም የኪራይ ክፍያ ጥያቄውን በተመለከተም ለመክፈል

ፈቃደኛ እንደሆኑ በመግለጽ መልስ ሠጥተዋል፡፡ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም የተጠቀሰው ቤት በመሐንዲስ ተገምቶ በተገኘው ግምት ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥና የከሳሽ ድርሻም ከተጠየቀው የኪራይ ክፍያ ጋር እንዲከፈላቸው በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሾች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

ይህም ችሎት አመልካቾችና ተጠሪ የቀረቡትን ክርክር መርምሯል፡፡

ሊፈታ የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በመሐንዲስ ተገምቶ በተገኘው ግምት በሐራጅ ተሸጦ የተጠሪ ድርሻ ይከፈል ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት የተመለከተ ነው፡፡

በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ ዳኝነት የጠየቁት ከላይ እንደተመለከተው ከአባታቸው በውርስ የተላለፈው የጋራ የውርስ ቤት ግምቱ ብር 120,000 /አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር/ መሆኑን ገልጸው ከዚህ ላይ ድርሻዬ ነው የሚሉት ብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ ይክፈለኝ በማለት ነው፡፡ ተከሣሾች የአሁን አመልካቾችም በክስ በተጠየቀው መሠረት ገንዘቡን ለመስጠት ፈቃደኞች መሆናቸውን ገልጸው መልስ ሠጥተዋል፡፡

ከሣሽ ዳኝነት የጠየቁትና የተከሳሾችም መልስ ከላይ የተመለከተው ከሆነ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ዳኝነት በተጠየቀውና በታመነውም መሠረት ይህንኑ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ተከሳሾች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ መስጠት ሲገባው ከዚህ አልፎ ቤቱ በመሀንዲስ ተገምቶ በሐራጅ ተሸጦ የከሳሽ ድርሻ ይከፈላቸው በማለት ውሣኔ መስጠቱ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 182/2/ ጋር ያልተጣጣመና ባልተጠየቀ ነገር ላይ የተሰጠ ዳኝነት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ቀጥሎ የተመለከተው ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15166 በህዳር 21 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37786 በህዳር 20 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ዳኝነት በጠየቁት መሠረት ብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር አመልካቾች እንዲከፍሏቸው ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 29738

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የአፓርትማ 79/6 የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት

ተጠሪ፡- ወ/ት ዘርአዳም አሰጋኸኝ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥነ ሥርዓት ህግን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች የሕብረት ቤት ስራ ማህበር ውስጥ በአባልነቱ ከተሰሩት ቤቶች መካከል ድርሻዬ የሆነውን ቤት የስራ አስፈጻሚ አባላት የሆኑት ግለሰቦች በወቅቱ ለእኔ ባለማስረከባቸው ምክንያት በቤቱ ላይ ለታየ ጉድለት ማሟያና ማሰሪያ ብር 80,000፣ /ሰማኒያ ሺህ ብር/ ቤቱን በወቅቱ ተረክቤ ቢሆን ኖሮ በማከራየት ላገኝ እችል የነበረውን ጥቅም ብር 24,000፣ /ሃያ አራት ሺህ ብር/ እንዲሁም ሌሎች ጉዳቶች በድምሩ 320,000/ሦስት መቶ ሃያ ሺህ ብር/ ሊከፍሉኝ የገባል በማለት በፌደ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች በሰጡት መልስ ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 የሚታገድ ከመሆኑም በላይ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም? ጉዳዩ ከዚህ በፊት በውሳኔ ያለቀ ነው ወይ? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 ከውል ውጪ በሆነ ኃላፊነት ጉዳት ደረሰብኝ የሚል ወገን ክሱን ማቅረብ ያለበት ጉዳቱ በደረሰ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳለበት ስለሚደነግግና የአሁን ተጠሪ ደግሞ ክሱን ያቀረቡት ጉዳቱ ከደረሰ ከ13 ዓመት በኋላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል።

የአሁን ተጠሪ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኙ የቀረበበት ጉዳይ ከዚህ በፊት በፍርድ ቤት የታየ ስለሆነ እንደገና ዳኝነት ሊጠየቅበት ስለማይገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 ይግባኙ አያስቀርብም የሚል ብይን ሰጥቶ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል።

የአሁን ተጠሪ በዚህም ብይን ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኙን አያስቀርብም ለማለት የሰጠው ምክንያት የፌደ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ከሰጠው ብይን ጋር የሚገናኝ አይደለም፣ በአሁን ተጠሪ የቀረበውን ቅሬታ መሰረት ያደረገም አይደለም፤ ፍ/ቤቱ መዝገቡን የዘጋው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሠረት በመሆኑ ፍርዱን የሰጠው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 342 ላይ እንደተመለከተው የነገሩን ጭብጥ በመለወጥ ወይም በማሻሻል ነው ለማለት የሚቻልበት የህግ ምክንያት የለም፣ ይግባኙ አያስቀርብም ማለትም ፍርድ መስጠት ማለት አይደለም፤ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በአንድ በኩል ይግባኙ አያስቀርብም እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የይግባኝ ክርክር ሰምቶ ሊሰጥ የሚችለውን ፍርድ መስጠቱ ትክክል አይደለም፤ በአጠቃላይ ፍ/ቤቱ የተከተለው አካሄድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ ከተደነገገው የክርክር አመራር ሥነ ሥርዓት የወጣ በመሆኑ ይግባኙ የቀረበለት የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት ተሸሯል፣ የፌደ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ብይን በሰጠበት የይርጋ ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመር ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ/ውሳኔ/ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት ተመልሶለታል በማለት ወስኗል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔዎች አግባብ ካለው ህግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት በፌደ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ቀርቦለት ይግባኙን መልስ ሰጭን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሠረት የሰረዘው በመሆኑ በዚህ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ሁለተኛ ይግባኝ

ለፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ መታየቱ አግባብ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል።

መዝገቡን እንደመረመርነው የፌደ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበለትን ክስ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን ሰጥቶ የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት ደግሞ ጉዳዩን በይግባኝ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ ከዚህ በፊት በፍርድ ቤት የታየ ስለሆነና እንደገና ዳኝነት ሊጠየቅበት ስለማይገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 ይግባኙ አያስቀርብም በማለት ይግባኙን በብይን ሰርዞት በዚህ ብይን ላይ የቀረበለትን ይግባኝ የፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀብሎ በመመርመር የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን ሽሮ የመጀ/ደ/ፍ/ቤቱ ብይን በሰጠበት የይርጋ ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመር ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ/ውሳኔ/ ይስጥ በማለት ጉዳዩን ለከፍ/ፍ/ቤት የመለሰው መሆኑን ተገንዝበናል።

በመሠረቱ አንድ ፍ/ቤት ወይም ችሎት የቀረበለትን ጉዳይ መመርመር ከመጀመሩ በፊት በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆንና አለመሆኑን ማረጋገጥ የኖርበታል። የፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀብሎ በማየት ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ በመጀ/ደ/ፍ/ቤት ብይን ተሰጥቶበት ከፍ/ፍ/ቤትም በይግባኝ አይቶ ብይን የሰጠበት በመሆኑ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው። በፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁ. 25/1988 አንቀጽ 10/1/ መሠረት የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች (መሠረታዊ የሕግ ስህተት ካለባቸው) አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንጂ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት (የፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት) ይህንን የፌደ/ከፍ/ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠበትን ጉዳይ በይግባኝ አይቶ ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌደ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 24699 ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን የቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 29761

ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
መስፍን እቁበዮናስ
ሂሩት መለሰ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- 1ኛ አቶ ዳባ ደበሌ - ቀረቡ
2ኛ .. ደምሴ በዳዳ ቀረቡ
3ኛ ወ/ሮ አለሚ ተ/ፃዲቅ ቀረቡ
4ኛ .. ደግነሽ ጫሞራ ቀረቡ
5ኛ ቄስ ኤፍሬም መኮንን ቀረቡ

መልስ ሰጭ፡- የአቶ ደበበ ተፈራ ወራሾች
1ኛ ወ/ሮ ሸዋማማሽ ደበበ
2ኛ ሻ/ቃ ጌቱ ደበበ
} ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚው ችሎት በመ/ቁጥር 03678 መጋቢት 7 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭዎች ለሰበሩ አቤቱታ መነሻ በሆነው ጉዳይ ከሣሽ የነበሩ ሲሆን ክሱን በቅድሚያ ተቀብሎ ላየው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ የአውራሻችን የአቶ ደበበ ተፈራ ንብረት የሆነውን በአቃቂ ከተማ የሚገኘውን የወፍጮ ቤት ድርጅት በወቅቱ የነበሩት የቀበሌ ተመራጮች ከፋፍለው ለአምስቱም አመልካwች በመስጠታቸው እና አውራሻችን ከዚሁ ድርጅት በቀር ሌላ ያልነበራቸው መሆኑን በማረጋገጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ይኸው ንብረት እንዲመለስላቸው ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ የከተማ ልማትና የቤት ሚ/ር በቁጥር 80/ደ/2135/83 ንብረቱ እንደመለስላቸው ተወስኗል፡፡ ስለሆነም ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው በፍርድ ኃይል ሊያስረክቡን ይገባል የሚል ሲሆን ለዚህም አቤቱታቸው ማስረጃዎቻቸውን ዘረዝረው አቅርበዋል፡፡

የአሁን አመልካwችም ይኸው ንብረት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የተወረሰ በመሆኑ ለረዥም ጊዜ ከመንግሥት ተከራይተን ለመንግሥትም ኪራይ እየከፈልን የምንኖርበት ንብረት በመሆኑ ልንከሰስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ክርክር ያስነሣው ንብረት ለመልስ ሰጭዎች አውራሽ እንዲመለስላቸው የተወሰነ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ማስረጃውም በሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የተሰጠ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 31 መሠረት አዋጁን የማስፈፀም ሥልጣን የተሰጠው ለዚሁ የሥራና ቤቶች ሚ/ር በመሆኑ ንብረቱ ሊመለስላቸው ይገባል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን አመልካwች ቤቶቹ የተወረሱ ናቸው ከማለት በቀር ለመልስ ሰጭዎች እንዲመለሱ አልተወሰነም በማለት አልተከራከሩም፡፡ ያልተመለሱ ስለመሆኑም በማስረጃ አስደግፈው አላስረዱም ስለሆነም ክስ የቀረበበትን ንብረት አምስቱም አመልካwች ለመልስ ሰጭዎች ያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡

ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም በየደረጃው ላሉት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚው ችሎት ቢያቀርቡም አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በሚል መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ዳኝነት ላይ ቅር በመሰኘት ይሻርላቸው ዘንድ በዝርዝር በመጠየቃቸው ነው፡፡

የቅሬታውም ፍሬ ሀሣብ በይዘቱ በሥር ፍ/ቤቶች ከተደረገው ክርክር የተለየ አይደለም፡፡

እኛም በአመልካwች በኩል የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ለዚሁ አቤቱታ በመልስ ሰጭዎች በኩል የሰጠውን መልስ ከሥር ፍ/ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም በዚህ ጉዳይ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባውን አከራካሪ ነጥብ ይህንን አከራካሪ የሆነውን ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለማስተናገድ የሚያስችላቸው ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም የሚለው ነው፡፡

በግራ ቀኙ ከቀረበው ክርክር ይዘት እንደምንረዳው የአሁን መልስ ሰጭዎች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ እና የጠየቁት ዳኝነት የአውራሻችን ንብረት የሆነውን የወፍጮ ድርጅት በወቅቱ የቀበሌ አመራር የነበሩት ያለአግባብ ከፋፍለው ለአመልካwች የሰጡብን ስለሆነና ይህም አድራጎት ተገቢ አለመሆኑ ታውቆ ቤቱ እንዲመለስልን ሥልጣን ባለው አካል የተወሰነ ስለሆነ ንብረቱን በእጃቸው አድርገው የሚገኙት ተገልጋዮች እንዲያስረክቡን ይደረግልን የሚል ነው፡፡ አመልካwችም ይኸው ንብረት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት መንግሥት ወርሶት በቀበሌው አስተዳደር ሥር የሚተዳደርና ከቀበሌው ተከራይተን ለረዥም ዓመታት ኪራይ እየከፈልን የምንኖርበት ስለሆነ ልናስረክብ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ አንኳር ነጥብ ይህ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ክርክሩ ይህ ከሆነ ይህንን ጉዳይ የከተማው ፍ/ቤቶች የማየት ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ከደነገገው አዋጅ ከአዋጅ ቁጥር 361/95 አንፃር ሊታይ ይገባዋል፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 41 የእነዚሁ ፍ/ቤቶች የፍ/ብሔር ጉዳይ የዳኝነት ሥልጣን ተዘርዝሯል፡፡ በዚሁ ዝርዝር ላይ ያለአግባብ በመንግሥት የአስተዳደር አካላት ተወስዷል የተባለን ንብረት ለማስመለስ ሲባል የሚቀርበው የፍ/ብሔር ክርክር የከተማ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ነው በሚል የተካተተ አይደለም፡፡ ምናልባትም በአንቀጽ 41 (ሀ) ሥር በተመለከተው መሠረት ሊታይ የሚችል ነው እንዳይባል ጉዳዩ የይዞታ ባለመብቶችን የሚመለከት እንጂ የተወሰደን ንብረት ለማስመለስ የሚልን ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይጨምር ከመሆኑም በላይ ይኸው የይዞታ ባለመብትነት ከከተማው መሪ ዕላን አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የተገኘ እንደሆነ ብቻ በመሆኑ ይኸው ንዑስ ድንጋጌ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ አይገኝም፡፡ እንዲሁም ይኸው ክርክር ያስነሣው ጉዳይ በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ድንጋጌ (ረ) እንደተመለከተው «የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግሥት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮች፤» በሚለው ሥርም የሚወድቅ አይደለም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን በሚመለከተው በዚሁ ደንብ ሥር ያልተመለከተን ጉዳይ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለማስተናገድ ሥልጣን የላቸውም፡፡ ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱን ተቀብሎ ለማስተናገድ በሕግ የተሰጠው ሥልጣን የሌለው መሆኑ ከተከራካሪው ወገን በመከራከሪያ ነጥብነት ባይቀርብለትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 231(1)(ለ) በተደነገገው መሠረት በእራሱ አነሣሽነት በክሱ ላይ የተገለፀው ጉዳይ ከፍርድ ቤቱ ሥልጣን ውጭ መሆኑን በመግለጽ መዝገቡን ዘግቶ ሊያሰናብታቸው ይገባል፡፡

የአሁን መልስ ሰጭዎች ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ ተመሣሣይ ዳኝነት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቃቂ ምድብ ክስ አቅርበው በጉዳዩ ላይ ይመለከተዋል የተባለው የክፍሉ ቀበሌ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ ከተከራከረ በኋላ በመ/ቁ 311/95 ታህሣሥ 21 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው ክርክር የወፍጮ ቤት ድርጅት የተባለው ንብረት የተወረሰ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ክርክሩን ለማየት ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ እንግዲህ ከዚህ ውሣኔ በኋላ ነው የአሁን መልስ ሰጭዎች ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚሁ ጉዳይ አዲስ ዳኝነት የጠየቁት፡፡ ጉዳዩን የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ለማየት የሚያስችለው ሥልጣን ያለው ስለመሆኑም የተለየ አዲስ ጉዳይ የተካተተበትም አይደለም፡፡ በመሆኑም ከላይ እንደተመለከተው መልስ ሰጭዎች ክስ ያቀረቡት ጉዳይ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ሆኖ ባለመገኘቱ እና ክሱ የቀረበላቸውም ፍ/ቤቶች ክርክሩ በደረሰበት ደረጃም ቢሆን ይህንኑ እንደተረዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231(1) (ለ)

እንደተደነገገው ጉዳዩ ከፍ/ቤቱ ሥልጣን ውጭ ነው የሚለውን መሠረት በማድረግ መዝገቡን መዘጋት ሲገባቸው ተቀብለውና አስተናግደው በጉዳዩ ላይ ዳኝነት በመስጠታቸው በሥነ ሥርዓት ጉድለት ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን ተረድተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1.የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00870 በመጋቢት 25 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03275 ሐምሌ 27 ቀን 1998 ዓ.ም እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚው ችሎት በመ/ቁ. 03678 በመጋቢት 07 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዞች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 29780
ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
ተገኔ ጌታነህ
መስፍን ዕቁበዮናስ
አብዱራሂም አህመድ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ አለሙ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ከተማሽ ቸርነት - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/5 መሰረት በበታች ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ የአሁን አመልካቾች በተጠሪ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 9 ቀበሌ 07 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 1288 የሆነውን ቤት በውርስ ያገኙት መሆኑን ገልፀው ይህንኑ ቤት ቆልፈን እንደሄድን ተከሳሽ በሀይል በመክፈት ስለገቡበት እንዲያስረክቡንና ኪራይም እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም በሰጡት መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ባነሱት ክርክር ከሳሾች በመ.ቁ. 02330 በዚሁ ቤት የሁከት ይወገድልን ክስ መስርተው ፍ/ቤቱም ውሣኔ የሰጠ ስለሆነ በተመሳሳይ ጉዳይ ድጋሚ ክስ

መቅረቡ በአግባቡ ስላልሆነ ፍ/ቤቱ ውድቅ ሊያደርገው ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ ተከሳሽ በዚህ ጉዳይ አስቀድሞ ውሣኔ መስጠቱን ለማስረዳት ያቀረቡትን የፍ/ቤት ውሣኔ ፍ/ቤቱ እንደተመለከተው ከሳሾች ወራሽነታቸውን ገልፀው ተከሳሽ ቤቱን ትልቀቅልን በማለት ክስ መስርተው ፍ/ቤቱም ውሣኔውን ሲሰጥ ይህንኑ ጭብጥ በመከተል ተከሳሿ ቤቱን በይዞታነት የምትጠቀምበት መሆኗን ከቀበሌው አረጋግጦ ከሳሾች እንደ ክሳቸው ባለማስረዳታቸው ጥያቄያቸውን ባለመቀበል መዝገቡን እንደዘጋ መረዳት የተቻለ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/5 መሠረት በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ-ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነና ፍርድ የተሰጠበት ከሆነ ተከራካሪ ወገኖች ድጋሚ ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ ስለተደነገገ ከሳሾችም በዚህ መዝገብ ያቀረቡት ክስ አስቀድሞ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ በአግባቡ የቀረበ አይደለም በማለት ክሱን በብይን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ አመልካቾች በድጋሚ ያቀረቡት አቤቱታ አስቀድሞ ውሣኔ ያገኘ ስለመሆኑ ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ከላይ እንደተጠቀሰው ጉዳዩ አስቀድሞ ውሣኔ ያገኘ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመ/ቁ. 02330 አመልካቾች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት በወረዳ 9 ቀበሌ 07 ክልል ከወላጆቻችን በውርስ ያገኘነውና በይዞታችን አድርገን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የምንጠቀምበት የቤት ቁጥር 1288 የሆነውን ቤታችንን በቁልፍ ቆልፈነው እንዳለ እንዳንገባ፣ እንዳንወጣና እንዳንገለገልበት በማድረግ ተከሳሽ ሁከት የፈጠረችብን ስለሆነ ሁከቱ እንዲወገድና ቤታችንን ለቃ እንድትወጣ ይወሰንልን በማለት ነው፡፡

በሌላ በኩልም ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት በሆነው መዝገቡ ላይ ያቀረቡት ክስ ደግሞ ከላይ እንደተመለከተው ይህንኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪ ቁልፉን ከፍተው በመግባት በኃይል የያዙት ስለሆነ ያስረክቡን በማለት ነው፡፡

በሁለቱም መዝገቦች ላይ አመልካቾች የጠየቁት ዳኝነት /Relief/ አቤቱታ የቀረበበትን ቤት ለመረከብ ቢሆንም በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሱት ዝርዝር ፍሬ ነገር ሲታይ ግን በመጀመሪያው መዝገብ የተፈጠረው ሁከት ተወግዶ ቤቱን እንረከብ በማለት የጠየቁ እንደመሆኑ ሁከት አለ የለም የሚለው ነጥብ በቅድሚያ ተይዞ የሚፈታ ሲሆን በሌላ በኩልም በሁለተኛው መዝገብ ባቀረቡት አቤቱታ ቤቱ ያለአግባብ የተወሰደባቸው መሆኑን በመግለጽ እንዲመለስላቸው የጠየቁ በመሆኑ በዚህ መዝገብ በቅድሚያ ሊያዝ የሚችለው ፍሬ ነገር ሁከት አለ ወይንስ የለም የሚል ሳይሆን ባለቤትነት የመፋለም ክስን /petitory action/ የሚመለከት በመሆኑ በቅድሚያም ተይዞ የሚፈታው ፍሬ ነገር ይሄው ባለቤትነትን አስመልክቶ የቀረበው ክስ ስለሚሆን በሁለቱ መዝገቦች ላይ የቀረበው ክርክር በቅድሚያ የተለያየ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች አስቀድሞ ውሣኔ ባገኘ ቅድሚያ ላይ ድጋሚ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት ሁለተኛውን ክስ ሳይቀበሉ መቅረታቸው የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06644 ጎዳር 8 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26636 በመጋቢት 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ

ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካቾች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 06644 በተጠሪ ላይ ያቀረቡት አቤቱታ አስቀድሞ በመ.ቁ. 02330 ውሣኔ ካረፈበት የተለየ በመሆኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ያደረጉትን መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 341 መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 30631

ጎዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘቢዳ ሙሣ - ጠበቃ ወርቅዬ ዓባይነህ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ አሻ የሱፍ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፋጡማ የሱፍ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀረብ የቻለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የሥር 2ኛ ተከሣሽና የአሁን አመልካች ለተጠሪዎች ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ የአሁን ተጠሪዎች በአሁን አመልካችና በሥር 2ኛ ተከሣሽ በድሬዳዋ ከተማ ከፍተኛ 3 ቀበሌ 15 አስተዳደር ጽ/ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ በድሬዳዋ ከተማ ከፍተኛ 3 ቀበሌ 15 ክልል የሚገኘውና ቁጥር 722 የሆነው ቤት ከሣሾች በውርስ የተላለፈልን ባለቤት ስንሆን አባታችን በሞት ከተለየ ጊዜ ጀምሮ 2ኛ ተከሣሽ ለ1ኛ ተከሣሽ አከራይቶ ስለሚገኝ እንዲያስረክበን በተደጋጋሚ ተጠይቆ ፈቃደኛ ያልሆነ ስለሆነ በሕገወጥ መንገድ ይዘው አከራይና ተከራይ በመሆን በእጃቸው የቆየበትን ከሳሾች ስም ካዛወርንበት ጊዜ ጀምሮ የቤቱን ኪራይ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሾች ክስና ማስረጃ ለተከሳሾች ደርሶ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ለፍሬ ጉዳዩም ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተነሣው ክርክርም ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን ባለቤትነት በማጣራት የመመለስ ሥልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስልሆነ ፍ/ቤቱ ይህን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን የለውም፡፡ እንደዚሁም ጉዳዩ በፍ/ቤት መታየት የሚችል ነው ከተባለም ሥልጣኑ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሳይሆን የድሬዳዋ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው የሚል ነው፡፡

የመቃወሚያ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ ከሣሾች ክስ ያቀረቡት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት 2ኛ ተከሣሽ በሕገወጥ መንገድ ለ1ኛ ተከሣሽ እያከራየ ስለሆነ ሊለቁልን ይገባል በማለት እንጂ ስለመወረሱ ያነሱት ክርክር ስለሌለ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው፣ የድሬዳዋ ከተማ ነክ ፍ/ቤትም ይህን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት መቃወሚያውን ሳይቀበለው የቀረ ሲሆን ግራ ቀኙ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ያደረጉትን ክርክር መርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ተከሳሾች ለከሳሾች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የድሬዳዋ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሥር 1ኛ ተከሳሽም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት ለተጠሪዎች እንዲመለስ መወሰኑ አግባብነቱ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባ በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም ነጥብ ይህን ጉዳይ ለማየት የድሬዳዋ ፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሥልጣን ነበረውን? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ነጥብ በጭብጥነት ይዘን አቤቱታውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪዎች በድሬዳዋ ፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካችና በሥር 2ኛ ተከሣሽ የቀበሌው አስተዳደር ላይ ክስ የመሠረቱት በውርስ የተላለፈልንን የግል ቤት በሕገወጥ መንገድ ይዘው ስለሚገኙ ያስረክቡን በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች በክሳቸው ቤቱ በአዋጅ ሳይወረስ በሕገወጥ መንገድ ተይዞብናል የሚሉ ከሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ አነጋገር ቤቱ ከአዋጅ ውጭ ተወርሷል ማለት ነው። ከአዋጅ ውጭ ተወርሰዋል የሚባሉ ቤቶችን ደግሞ ባለቤትነታቸውን በማጣራት ውሣኔ ለመስጠት በአዋጅ ቁጥር 110/87 ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን አጀንሲ ሥልጣን ተሰጥቶታል። በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 231/1/ለ/ ላይ እንደተመለከተው ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት በክሱ ላይ የተገለጸው ጉዳይ ከሥልጣኑ ውጭ መሆኑን ሲረዳው ተከሳሹን ሳያስጠራ የክስ አቤቱታውን በመሠረዝ ክሳሹን ማሰናበት ይኖርበታል። በዚሁ መሠረት ተጠሪዎች ባቀረቡት አቤቱታ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሕገወጥ መንገድ እንደተወሰደባቸው የገለጹ ስለሆነና በሕገወጥ መንገድ ተወስዷል ከተባለም በሌላ አገላለጽ ቤቱ ከአዋጅ ውጭ ተወስዷል ማለት ስለሆነ የድሬዳዋ ፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የሥረ-ነገር ሥልጣን እንደሌለው ተገንዝቦ ከመነሻውም አቤቱታቸውን ሊሰርዝ ሲገባ አለመሰረዙ በአግባቡ ካለመሆኑም በላይ በዚህ ሁኔታ ተከሳሾችን ከጠራ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን እንደሌለው በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ ሲቀርብለት መቃወሚያውን ተቀብሎ አቤቱታውን ውድቅ ማድረግ ሲገባው ሳይቀበለው መቅረቱ እንደዚሁም ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የድሬዳዋ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት አለማረሙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

1. የድሬዳዋ ፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02230 በየካቲት 26 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የድሬዳዋ ፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02902 በሚያዝያ 29 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል።
2. የድሬዳዋ ፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም ተብሎ ተወስኗል።
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ።
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁጥር 30704

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

መድነን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፊጅ መሠረት የማነ ቀረበ።

ተጠሪ፡- 1/ የአቶ በቀለ ወ/ማርያም ወራሽ ወ/ሮ ዘለቃወርቅ በቀለ

2/ ወ/ሮ ዘውዲቱ አርጋው ከጠበቃ ከሙሉጌታ

3/ አቶ ደረጀ ዘለቀ ገብሩ ጋር ቀረቡ።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

ይህ ክርክር የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች እና ኮ/ል ወንድወሰን ሠይፉ በተባሉ ግለሰብ ላይ በመስከረም 28 ቀን 1994 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ክስ፣ የአሁኑ አመልካች ባለቤትነቱ የአውራሻችን የሚች ሙሉነሽ ወ/ማርያም የሆነው በቀድሞው ወረዳ 20 ቀበሌ 29 የቤ/ቁ. 313 የሚገኘው ቤት በአውራሻችን ተመርጦ በአዋጅ ያልተወረሰ ሲሆን የአሁን አመልካች ያለ ሕጋዊ ምክንያት ይዞ ለ2ኛው ተከሣሽ እያከራየ በመጠቀም ላይ በመሆኑ ተከሣሾቹ ቤቱን አስረክበው መስከረም 01 ቀን 1968 ዓ.ም. እስከ ጥር 08 ቀን 1994 ዓ.ም. ድረስ ያጣነውን የኪራይ ገንዘብ በወር ብር 255 ሂሣብ በአጠቃላይ 74,500 ብር /ሰባ አራት ሺህ አምስት መቶ/ እንዲከፍሉ ይወሰንልን ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል።

የአሁን አመልካች በግንቦት 02 ቀን 1994 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ቤቱ በአ/ቁ. 47/67 የተወረሰ መሆኑን ገልፆ ይህንን ቤት ይዞ ማስተዳደር ከጀመረ ከሃያ አራት ዓመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፣ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለውም የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለመሆኑን ተጠሪዎቹ /የሥር ተከሣሾች/ ያቀረቡት ማስረጃ የቦታ ካርታ ሲሆን ይህም የተጠሪዎቹ አውራሽ ቦታውን መግዛታቸውን እንጂ የግል ቤታቸው መሆኑን እንደማያሣይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቤቱ የተጠሪዎች አውራሽ ነው ቢባል እንኳን የኪራይ ገንዘቡን ለመመለስ በሕግ የተጣለበት ግዴታ አለመኖሩን በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የአመልካችን መቃወሚያዎች ውድቅ በማድረግ የቂርቆስ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤትን ዋቢ በማድረግ ቤቱ ማኅደር የሌለው መሆኑን ጠቅሶ ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡትን ማስረጃ በመመዘን ከሣሾች /የአሁን ተጠሪዎች/ አውራሻቸውን ባለቤት ሊያደርጋቸው የሚችሉ ጠቋሚ ማስረጃዎች ሲያቀርቡ አመልካች ግን በረጅም ጊዜ ቤቱን አስተዳድረዋለሁ ከማለት ውጭ ባለቤትነቱን ሊያሣይ የሚችል ማስረጃ አላቀረበም በሚል ቤቱ ለአሁን ተጠሪዎች እንዲመለስ እና የተጠየቀው የኪራይ ገንዘብ ብር 74,500 እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበበት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይህንን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር በመሠኘት ለዚህ ችሎት የሠበር ማመልከቻውን በግንቦት 16 ቀን 1994 ዓ.ም. ጽፎ አቅርቧል፡፡ የሰበር ማመልከቻውም ይዘት ሲጠቃለል የአሁን ተጠሪዎች በውርስ ይገባናል የሚሉት ቤት የአውራሻቸው የግል ቤት ለመሆኑና መርጠውት ምርጫቸው የፀደቀላቸው ለመሆኑ ማስረጃ ሣይቀርብ የግል ቤቱ ወይም ንብረቱ ነው ለማለት የሚቻለው አግባብ ካለው መንግሥታዊ አካል የባለቤትነት ደብተር በማቅረብ ሆኖ ሣለ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎቹ እንዲያስረክብ እና የቤቱን ኪራይ ብር 74,500 ከነወለዱ እንዲከፍል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚል ነው፡፡ ይህም ችሎት የአመልካቹን አቤቱታ ተመልክቶ ተጠሪን በማስቀረብ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም ከሁሉ

አስቀድሞ ምላሽ የሚሻው ጭብጥ የፌ/መ/ፍ/ቤት በተጠሪዎች የቀረበለትን ክስ መርምሮ የመወሰን ስልጣን አለው ወይ? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አመልካች የክርክሩ መንስኤ የሆነው ቤት በአ/ቁ. 47/67 ተወርሶ ሲያስተዳድረው መቆየቱን በመግለጽ የተከራከረ ቢሆንም የስር ፍ/ቤቱ ስለመወረሱ ተገቢው ማስረጃ አልቀረበም በሚል ቤቱ ለአሁን ተጠሪዎች እንዲመለስ ወስኗል፡፡ በመሠረቱ አዋጅ ቁጥር 47/67ን መነሻ አድርጎ አላግባብ የምርጫ ቤቱ ተወስዷል በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች አዋጁን ለማስፈፀም በተቋቋመው የሚኒስቴር መ/ቤት በኩል እየተመረመሩ ተገቢውን ውሣኔ ማግኘት ያለባቸው ስለመሆኑ በአዋጁ ተመልክቷል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ ምርጫ ቤቱን በቀላጤ፣ በቃል ትዕዛዝ ወይም በመመሪያ ከሕግ ውጭ ተወሰደብኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በአ/ቁ. 110/87 መሠረት ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርበው መወሰን እንደሚገባቸው በሕጉ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ክፍሎች የሚሰጡ የባለቤትነት ማስረጃዎችን መሠረት አድርገው በሚቀርቡ የባለቤትነት ጥያቄዎች ላይ ፍ/ቤቶች እንደነገሩ ሁኔታ ስልጣን ከሚኖራቸው በቀር ተወርሠዋል ተብለው በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ይመለሱልኝ እንዲሁም ውዝፍ ኪራይ ይከፈለኝ በሚል የሚቀረቡ አቤቱታዎችን መሠረት አድርገው ፍ/ቤቶች የቤቱን መወረስና አለመወረስ ለማረጋገጥ ማስረጃዎችን መርምረው የሚደርሱባቸው መደምደሚያዎች የአስፈፃሚ አካላቱን ስልጣን እና ተግባር በግልጽ የሚቃረን ከመሆኑም በተጨማሪ ለፍ/ቤቶች በሕግ ያልተሰጠ ስልጣን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአሁን ተጠሪዎች ክርክር በተነሣበት ቤት ላይ ከአስፈፃሚ አካላቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ ባላቀረቡበት ሁኔታ የአሁን ተጠሪዎችን ባለቤት ሊያደርጓቸው የሚችሉ ጠቋሚ ማስረጃዎች አቅርበዋል በሚል ለፍ/ቤቶች ባልተሠጠ የስልጣን ክልል በመግባት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሰዋል ሲል ያቀረበውን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ቤቱ ለተጠሪዎች ይመለስ ሲሉ መወሠናቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. አመልካች ክርክር የተነሣበትን ቤት ለመመለስም ሆነ ውዝፍ ኪራይ ለመክፈል አይገደድም ብለናል፡፡
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ያስነሣው በቀድሞው ወረዳ 20 ቀበሌ 29 የቤት ቁጥር 313 የሆነው ቤት በአ/ቁ/ 47/67 ተወርሷል አልተወረሰም የሚለውን ጭብጥ የመመርመር ስልጣን የለኝም ብሎ ክሱን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 231/1/ለ/ መሠረት ወድቅ ሊያደርገው ሲገባ አከራክሮ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ በመ/ቁ. 14806 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41668 በሚያዝያ 24 ቀን 1994 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31490

ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- ሴርኮ እስራኤላውያን - ጠበቃ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ ከሣሽ በመሆን በአመልካቹ ላይ ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ.ም ያቀረበው ክስ፣ የአሁን አመልካች ቤቱን ያለሕግ አግባብ ይዞ በመቆየቱ ከመጋቢት 9 ቀን 1971 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 9 ቀን 1994 ዓ.ም ላለው ጊዜ ያጣሁትን ጥቅም እና የደረሰብኝን ጉዳት ብር 363,931/ሦስት መቶ ስልሳ ሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ አንድ/ ከወጪና ኪሣራ ጋር ይክፈለኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ቀርቦ በሰጠው መልስ የተለያዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያቀረበ ሲሆን ከመቃወሚያዎቹም አንዱ በአዋጅ ቁ.193/92 አንቀጽ 2/3/ መሰረት ከአዋጅ ውጭ የተወረሱ ቤቶች በመንግስት እጅ ለቆየበት ጊዜ ለታጣ ገቢ ክፍያ መጠየቅ ስለማይቻል ክሱ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የቀረበውን መቃወሚያ ከግንዛቤ በማስገባት በሰጠው ውሣኔ ቤቱ በመንግስት እጅ የቆየው ከአዋጅ ውጭ ተወስዶ በመሆኑ አዋጅ ቁ.193/92 በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ስለዚህ ወደ ፍሬ ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሩ መግባት ሣያስፈልግ የተጠሪውን ክስ ውድቅ አድርጌዋለሁ በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ተጠሪው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አሰምተዋል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤትም አመልካችን አስቀርቦ ግራ ቀኙን በማከራከር መዝገቡን መርምሮ በሰጠው ውሣኔ የክፍያው ጥያቄ ከዋጅ ቁ. 193/92 አኳያ ተቀባይነት የለውም ተብሎ በስር ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ቢቀርብም የዚህ አይነቱ መቃወሚያ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 244 ስር ያልተሸፈነና የፍሬ ጉዳይ ክርክር ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ እስከሰጠበት ድረስ በቁጥር 341 መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት የሚመልሰው ሆኖ አልተገኘም፣ በሌላ በኩል አመልካቹ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ፍ/ቤቱ ብይን ሣይሰጥ በዚሁ ነጥብ ላይ ተመስርቶ የሰጠው ፍርድ አመልካቹን ረቺ ቢያደረግም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ባለመስጠቱ አመልካች መስቀለኛ ይግባኝ ያላቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በራሱ አስተያየት ሊመለከተው የሚችል ሆኖ አልተገኘም በሚል አመልካቹ አላግባብ ለበለፀገበት ብር 62,970 /ስልሣ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ/ ከተለያዩ ወጪና ኪሣራ ጭምር ለተጠሪው እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካቹ ይግባኛቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ፈጽመዋል በማለት አመልካቹ ለዚህ ችሎት ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ይህም ችሎት የአመልካቹን አቤቱታ መሰረት በማድረግ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ካቀረባቸው የመልስ መቃወሚያዎች ውስጥ አንዱ ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ ውድቅ ቢደረግለትም መስቀለኛ ይግባኝ ካላቀረበ በስተቀር በቀሪዎቹ ነጥቦች ላይ የቀረበው ክርክር ሊታይለት አይገባም የመባሉን

አግባብነት ለማጣራት ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ መዝገቡንም አግባበነት ካላቸው ህጐች አንፃር መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ለቀረበበት ክስ በስር ፍ/ቤት ቀርቦ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ያላቸውን አምስት ነጥቦችን እና መቃወሚያዎቹ ቢታለፉ በሚል ደግሞ ለክሱ ዝርዝር መልሱን አቅርቧል፡፡ የመ/ደ/ፍ/ቤቱም በሰጠው ውሣኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከተባሉት ነጥቦች አንዱን መርምሮ፣ ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክር መግባት ሣያስፈልግ ክሱን ውድቅ አድርጌዋለሁ በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ፍ/ቤቱ አመልካቹ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሲል ያቀረበውን ነጥብ እንደመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነቱ ተቀብሎ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አግባብ ቀሪ መቃወሚያዎችንና የፍሬ ጉዳይ ክርክሮችን ሣይመረምር ክሱን ውድቅ ማድረጉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በማንኛውም ቀመር የክሱ ውድቅ መደረግ አመልካችን ተጠቃሚ ወይም ረቺ የሚያደርግ እንደመሆኑ አመልካቹ ቀሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች እና የፍሬ ጉዳይ ክርክሮች ሊመረመሩ ይገባ ነበር ሲል ይግባኝ እንዲል የሚጠበቅበት አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካቹ ይግባኝ ሊጠይቅ ሲችል አልጠየቀም በሚል የአመልካች መቃወሚያ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አይደለም ለዚህ ጉዳይም አግባብነት የለውም በማለት አመልካቹ ሌሎቹን መከራከሪያዎች እንዳመነ ያህል ሌሎቹን መቃወሚያዎችና የፍሬ ነገር ክርክሮች ሣይመረመሩ ውሣኔ መስጠቱ የአመልካቹን ፍትህ የማግኘት መብት በእጅጉ የሚያጣብብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእርግጥ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የቀረበው መቃወሚያ ከፍ/ብ/ስ/ህ/ቁ. 244 አንፃር አግባብነት የለውም ማለቱ የሚነቀፍ ባይሆንም፣ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ለማድረግ የተከተለው አካሄድ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት ሲያገኝ በሚፈፀመው አግባብ ከመሆኑ አንፃር ሌሎች በፍ/ቤቱ ያልተመረመሩ መቃወሚያዎችና መከራከሪያዎች መኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ መቃወሚያው በማንኛውም ምክንያት ውድቅ ሲደረግ እንደሚፈፀመው ሁሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341 መሰረት ቀሪ መቃወሚያዎችንና መከራከሪያዎችን መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን ወደ ስር ፍ/ቤት ሊመልሰው ሲገባ አመልካቹ ይግባኝ አልጠየቁምና ቀሪ መከራከራያዎቻቸው አይታዩም ሲል ውሣኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም ሲል ይግባኙን መሰረዙ በተመሣሣይ ሁኔታ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1) የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39329 ሚያዝያ 14 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ብይን ውድቅ መደረጉን ተገንዝቦ የቀሩትን መቃወሚያዎችና መከራከሪያዎች መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341 መሰረት ይመለስለት ብለናል፡፡
2) የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40110 በግንቦት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3) የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27255 መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
4) ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 31547

መጋቢት 07 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሐጐስ ወልዱ
ሂሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ
ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ኪዳኔ ገ/ጊዮርጊስ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አብርሃ ተስፋሁን

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በትግራይ ክልል ደቡብ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ የአሁን አመልካችን ጨምሮ በ7 ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የሚች አባታችንና የባለቤታቸው የወ/ሮ ሮማን ቢሆን የሆነውን በመቀሌ ከተማ የሚገኘውን ቤት ከ1-6 የተጠቀሱት ተከሳሾች ያለእኔ ፈቃድ ለ7ኛ ተከሳሽ /አመልካች/ የሸጡ ስለሆነ ከሽያጩ ገንዘብ የእኔ ድርሻ ብር 9,375 ስለሚሆን ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አሁን በዚህ የሰበር ክርክር የሌለት የሥር ከ1-6 ተከሳሾች ቀርበው የይርጋ ክርክር ያነሱ ሲሆን የአሁን አመልካችም ቀርበው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በሕጋዊ መንገድ እንደገዙትና ውሉም በሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተመዘገበ መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የወረዳው ፍ/ቤት የሸያጩ ውል በሚመለከተው አካል መጽደቁን የቀረበው ማስረጃ የሚያረጋግጥ ከመሆኑን በላይ የተሸጠውም በብር 30 ሺህ እንደሆነ መገንዘብ ስለተቻለ ከዚህ ላይ የሚች ድርሻ ብር 15 ሺህ ስለሆነና ይህም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለ8 ተወላጆች ሲከፋፈል የከሳሽ ድርሻ ብር 1875 ስለሚሆን ይህንኑ ገንዘብ ከ1-6 የተጠቀሱት ተከሳሾች እንዲከፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሳሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዚያም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 337 መሠረት በሁለቱም ፍ/ቤቶች ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ሰበር ችሎቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የጋራ የሆነውን የውርስ ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ የሁሉም የጋራ ወራሾች ፈቃድ ማግኘት አስፈላጊ ሆኖ ሳለ ነገር ግን ከ1-6 የተጠቀሱት ተጠሪዎች የአመልካችን ፈቃድ ሳያገኙ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ለ7ኛ ተጠሪ በሽያጭ ማስተላለፋቸው አግባብ እንዳልሆነ በውሣኔው ላይ አስፍሮ ከ1-6 ከተጠቀሱት ተጠሪዎች ጋር ውሉ እንደፀና እንዲቆይ ነገር ግን አመልካችን በተመለከተ ውሉ እንዲፈርስና የቤቱ 1/6ኛ በአመልካች ስም እንዲመዘገብ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በክልሉ ሰበር ችሎት 7ኛ ተጠሪ የነበሩት የአሁን አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ ከቤት ሽያጩ ውል ድርሻዋ እንዲከፈላት ባቀረበችው ክስ በእሷ ድርሻ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መወሰኑ ተጠሪ ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ በማግኘቱ በዚሁ መሠረት ተጠሪን ጠርቶ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አቤቱታው ያስቀርባል የተባለበት ነጥብ ስለሆነ ከዚሁ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ጉዳዩ በወረዳ ፍ/ቤት ሲጀመር የአሁን ተጠሪ ዳኝነት የጠየቁት ከላይ እንደተመለከተው ለክርክሩ ምክንያት ከሆነው የቤት የሽያጭ ገንዘብ ላይ ድርሻዬ ይከፈለኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ዳኝነት የጠየቁት በዚህ

መልኩ ከሆነ በጭብጥነት የሚያዘውም ነጥብ በክሱ የጠየቁት ገንዘብ ሊከፈላቸው ይገባል ወይንስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ ከዚህ አልፎ የቤት ሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚለው ነጥብ ዳኝነት ያልተጠየቀበት ስለሆነ በጭብጥ የሚያዝ አይሆንም፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከተውም የወረዳው ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው ዳኝነት በተጠየቀበት ነጥብ ላይ ተመስርቶ ስለነበር ውሣኔው የሚነቀፍ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 182 ላይ እንደተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ባላመለከቱት ነገር ላይ ተመስርቶ ውሣኔ መስጠት እንደማይችል ገደብ የተደረገበት ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚለው የክርክር ነጥብ / Point of Dispute/ ስላልነበር በዚህ ላይ ተመስርቶ ጭብጥ ሊያዝ ስለማይችል በተጠየቀው ዳኝነት ላይ ተመስርቶ ለጉዳዩ ዕልባት መስጠቱ አግባብነት የነበረው ሲሆን ከዚህ በኋላም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት የክልሉ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ይግባኙን ሳይቀበሉ መቅረታቸው አግባብ ሆኖ ሳለ ነገር ግን ሰበር ችሎቱ ከአመልካች /ከአሁን ተጠሪ/ አንፃር ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ ከሙግት አመራር አኳያ አግባብነት የሌለውና የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 17478 በግንቦት 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16464 በጥቅምት 3 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 3782 በሰኔ 9 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንደዚሁም የወረዳው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02166 በሰኔ 16 ቀን 1998 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 31833

ግንቦት 14 ቀን 2000

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሀጅ አብዱልቃድር አህመድ - ጠበቃ ዘላለም ክፍሌ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ደስታ ገ/ዮሐንስ

2. አቶ ሲሳይ ገ/ዮሐንስ - ጠበቃ መሉጌታ ገብሩ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 31359 ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡ ፍሬ ጉዳዩ ተጠሪዎች የአመልካች ሚስት የነበሩት ወ/ሮ ሀዋ ገብረዮሐንስ ጥር 27 ቀን 1991 ዓ.ም. በሞት የተለዩ መሆኑን ገልፀው እህታችን ልጅ ያልነበራት ስለሆነ ሚች ወራሾች ነን፡፡ ስለዚህ ሚች እህታችን ከተከሣሽ ጋር ከመጋባታቸው በፊት የሠሩት በወረዳ 23 ቀበሌ 15 ቁጥሩ 435 የሆነውን ቤትና ሌሎች የጋራ ንብረቶችንና ጥሬ ገንዘብ እንዲያካፍለን ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ አቅርበው አመልካችም በተካሣሽነት ቀርበው ቤቱ ሚች እኔን ከማግባቷ በፊት የሠራችው ቢሆንም አፈር የነበረውን ወለል ሊሾ በማድረግ የቆርቆሮውን አጥር በግንብ በመቀየርና ቤቱን በማደስ በርካታ ወጭ ያወጣሁ ስለሆነ፣ የጋራ ንብረት ሊባልልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክር ከሰማ በኋላ፣ ቤቱ ተከሣሹ /የአሁን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች/ ሚችን ካገባ በኋላ መሠረታዊና ዓይነታዊ ለውጥ የተደረገለት በመሆኑ፣ የሚችና የተከሣሽ የጋራ ሀብት ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል። ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ የአመልካችንና የተጠሪዎችን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ቤቱ ሚች ከአመልካች ጋር ከተጋቡ በኋላ እድሳት የተደረገለት መሆኑ የሚችን የግል ንብረት ወደ ጋራ ንብረትነት ለመለወጥ ምክንያት ስለማይሆን፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቤቱ የጋራ ንብረት ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮታል።

አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይገባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል። አመልካች ይህንን በመቃወም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ እኔና ሚች ባለቤቴ ለረዥም ጊዜ አብረን ስንኖር የቀድሞውን ጭቃ ቤት በማፍረስ በብሎኬት የሠራነው በመሆኑ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው መባል ሲገባው የግል ንብረት ነው መባሉና ቤቱን ለማደስ ያወጣሽውን ውጭ አዲስ ክስ አቅርበህ ጠይቅ መባሌ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያመለከቱ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው አመልካች ለቤቱ እድሳት ያወጣውን ወጭ ክስ አቅርቦ የመጠየቅ መብቱ ተጠብቆለት እያለ የሚች እህታችን የግል ንብረት የጋራ ንብረት ነው ተብሎ እንዲወሰንለት መጠየቁ ምንም አይነት የሕግ ድጋፍ የለውም። ስለሆነም የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል። ጉዳዩን እንመረመርነው አመልካች ክርክር የተነሳበት ቤት ሚች ከእርሱ ጋር ጋብቻ ከመፈፀሟ በፊት የነበራት የግል ንብረት እንደሆነ አልካዱም። አመልካች የሚከራከሩት በፊት ሚች ሠርታው የነበረ ቤት እኔ ጋር ከተጋባን በኋላ በመጠንም ሆነ በአይነት መሠረታዊ ለውጥ የተደረገበትና እንደ አዲስ ቤት የተገነባ በመሆኑ የጋራ መሆን አለበት የሚል ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው ሚች በመጀመሪያ በሠሩት ቤት ላይ እድሳት የተደረገለት መሆኑን አምነው፣ በቤቱ ላይ የተደረገው እድሳት መሠረታዊ ለውጥ አይደለም። ስለሆነም ቤቱን እንደገና ተሰርቷል የሚያሰኝና የጋራ ንብረት የሚያደርገው ስላልሆነ፣ የሚች የግል ንብረት ነው በማለት ይከራከራሉ። ከዚህ አንፃር በቤቱ ላይ የተደረገው ለውጥ መሠረታዊና የቀድሞው ቤት በአዲስ መልክ ተሠርቷል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ፣ በግራ ቀኙ የሚቀርበውን ክርክር ለመፍታት አስፈላጊ ነው።

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ይህንን ነጥብ በጭብጥነት ይዞ ውሣኔ የሰጠበት ቢሆንም፣ ፍርድ ቤቱ በቤቱ ላይ የተደረገው የዓይነት እና የመጠን ለውጥ ምን ያህል እንደሆነ የባለሙያ ማስረጃ እንዲቀርብለት አላደረገም። ፍርድ ቤቱ በቤቱ ላይ የተደረገው እድሳት መሠረታዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን የወሰነው፤ ስለ ቤት አሠራር እና ሕንፃ ግንባታ ልዩ የሙያ ዕውቀት የሌላቸውን ምስክሮች በመስማት ነው። ስለሆነም ከዚህ አንፃር ፍርድ ቤቱ አስፈላጊውን የሙያ ምስክርነት ማስረጃ ሳይሰማ ቤቱ የጋራ ነው ብሎ የሰጠውን ውሣኔ የከፍተኛው ፍርድ ቤት መሻሩ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም። በሌላ በኩል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የመጀመሪያው ቤት ፈርሶ እንደ አዲስ ቢገነባም የሚች የግል ንብረት የነበረው ቤት በምንም መልኩ የጋራ ንብረት እንደማይሆን በመዘርዘር የሰጠው ውሣኔና በቤቱ ላይ የተደረገው ለውጥና እድሳት በዚሁ መዝገብ በባለሙያ አስጠንቶ መወሰን አየተቻለ አመልካች ለቤቱ ያወጡትን ወጭ በተመለከተ በሌላ ክስ ዘርዝረው ይጠይቁ በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ በአጭሩ ከመፍታት አንፃር ጉድለትና ስህተት ያለበት፤ ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም በቤቱ ላይ የተደረገው እድሳትና ለውጥ ምን ያሕል የመጠንና የአይነት ለውጥ እንዳመጣ፣ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 መሠረት ልዩ አዋቂ መድበው በማስጠናት መወሰን ሲገባቸው፣ ስለ ቤትና የግንባታ ሥራ ዕውቀት የሌላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምስክሮች የሰጡትን ቃል መነሻ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ውሣኔ ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 23879 ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 31359 ታህሣሥ 5 ቀን 1998 ዓ.ም. ቤቱን በተመለከተ ብቻ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 599 ሚያዝያ 18 ቀን 1996 ዓ.ም. ቤቱን በተመለተ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ የተደረገውን እድሳት ምን ያሕል ገንዘብ እንዳስወጣና በመጀመሪያው ቤት ላይ ምን ያሕል የአይነትና የመጠን ለውጥ ያደረገ መሆኑን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 መሠረት በልዩ አዋቂ በማስገመት የመሰለውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ የውሣኔው ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 32147

መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ መሐመድ አብዲ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አብዱራሂም አብዲ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በውርስ የተላለፈልኝን መሬት ተከሣሽ በጊዜያዊነት እንዲገለገልበት ሰጥቼው ለመልቀቅ ፈቃደኛ ያልሆነ ስለሆነ እንዲያስረክብ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቦታ የተከሣሽ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ በከሳሽ በኩል የቀረበው ክስ የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አክራክሮ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር ይግባኝ ባይ ክስ ባቀረበበት ቦታ ላይ መብት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃው የሚያረጋግጥ ስለሆነ መ/ሰጭ ለይግባኝ ባይ ሊመልስ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታው ለሰበር ሊቀርብ ይገባል ብሎ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቅድሚያም ችሎቱ የተመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት ያለው መሆኑን በተመለከተ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ዳኝነት የጠየቁት በውርስ የተላለፈላቸውን መሬት አመልካች በጊዜያዊነት እንዲገለገሉበት ሠጥተዋቸው ነገር ግን አመልካች መሬቱን ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጸው እንዲመልሱ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 6 መሠረት በከተማ ባለርስትና በከተማ ጭሰኛ መካከል ያለው ግንኙነት እንደፈረሰ ጭሰኛው ለከተማ ባለርስት ከሚከፍለው ኪራይና ሌላ ክፍያ እንደዚሁም ከማንኛውም አገልግሎትና ዕዳ ነፃ እንደሆነ ከመደንገጉም በላይ ማንኛውም ጭሰኛ በያዘው የከተማ ቦታ ላይ የይዞታ መብትም እንደማይኖረው ተመልክቷል፡፡

ለክሱ ምክንያት የሆነው መሬት በአዋጅ የመንግሥት መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ተጠሪ አመልካችን ለመክሰስ የማያበቃ መነሻ ምክንያት /Cause of action/ የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 231 ላይ እንደተመለከተውም ማንኛውም ፍ/ቤት የክስ አቤቱታ ሲቀርብለት ተከሣሽ የሆነው ወገን ክሱን እንዲከላከል ከመጥራቱ በፊት ከሳሹ ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መነሻ ምክንያት ያለው ስለመሆኑና ፍ/ቤቱም አቤቱታውን ተቀብሎ ለማየት ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ መመርመር ይኖርበታል፡፡

በዚህም መሠረት ተጠሪ አመልካች ሊመልስልኝ ይገባል በማለት አቤቱታ ያቀረበበት መሬት በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የመንግሥት ሀብት ስለሆነ ከመነሻው አቤቱታቸው የክስ ምክንያት እንደሌለው መገንዘብ ስለሚቻል የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1/ሀ/ መሠረት አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ማለት ሲገባው አከራክሮ

ውሣኔ መስጠቱ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የጅጅጋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ በሚያዝያ 13 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ በሰኔ 13 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32376

ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃደር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት አልቀረቡም

ተጠራ- እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሸዋንግዛው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪዎች በአመልካችና በሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት ክስ ከወላጅ አባታችን በውርስ የተላለፈልንን በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቀበሌ 10 ክልል የሚገኝ ቤታችንን 1ኛ ተከሳሽ ከአዋጅ 47/67 ውጭ ያለአግባብ በመያዝ ለ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በማከራየት ላይ ስለሚገኝ ይህንኑ ያለ አግባብ ይዘው የሚገኙትን ቤታችንን ለቀው እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ቀርቦ በሰጠው መልስ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች በአዋጅ 47/67 መሰረት የተወረሱ ወይንም ያልተወረሱ ለመሆናቸው የሚጠቁም ማስረጃ በ1983 ዓ.ም በመዘረፉ ምክንያት ማቅረብ አልቻልንም፡፡ በአሁኑ ሰአት ይህ ክስ መመስረቱ አግባብነት የሌውና ተከራዮችን የሚጐዳ ነው፡፡ ጉዳዩም መታየት ያለበት በፍ/ቤት ሳይሆን በÝራይቤታይዜሽን ኤጀንሲ በኩል ስለሆነ መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችም በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ ከሳሾች ቁጥራቸው 204(1) እና 204/2/ የሆኑት ቤቶች ሊመለሱልን ይገባል በማለት

ቀደም ሲል ለወረዳ 27 ፍ/ቤት ክስ አቅረበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ Ýራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ በድጋሚ ለፍ/ቤቱ ክሱ መቅረቡ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 አኳያ ተቀባይነት ስለሌለው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩ አስቀድሞ ውሳኔ ያገኘ ነው ተብሎ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የወረዳ 27 ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ Ýራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ከማለት በስተቀር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን ተመልክቶ ውሳኔ ያልሰጠ በመሆኑ ክርክሩ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 ሥር ስለማይወድቅ በዚህ ረገድ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አግባብነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ከዚህም ሌላ 1ኛ ተከሳሽ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ሳይሆን የኢትዮጵያ Ýራይቬታይዜሽን ነው በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ አስመልክቶም በአዋጅ 110/87 መሰረት ለኤጀንሲው ሥልጣን የተሰጠው በቃል ትእዛዝ፣ በቀላጤ ወይንም በመመሪያ አንድ ንብረት ተወስዶ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ ስለተመለከተና ከሳሾች በዚህ መንገድ ቤቱ ተወስዶብኛል ያላሉ ስለሆነ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡

ከዚህ በኋላም በፍሬ ጉዳይ ረገድ የተደረገውን ክርክር ከማስረጃው ጋር አገናዝቦ መርምሮ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች የተወረሱ ስለመሆናቸው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ 1ኛ ተከሳሽ ከ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል በማቋረጥ ለከሳሾች ቤቱቹን እንዲያስረክቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 ሊጠቅስ የሚገባው አንድ የክስ ምክንያት በተከራካሪ ወገኖች ወይም ከእነዚህ ወገኖች ጥቅም የሚያገኙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3ኛ ወገኖች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ በተመሳሳይ የክስ ምክንያት ክስ በሚቀርብበት ጊዜ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የቀድሞ ወረዳ 27 ፍ/ቤት የቤት ይለቀቅልኝ ክርክሩን ለማየት ሥልጣን ያለው ሌላ አካል ስለሆነ ጉዳዩን አላስተናግድም በማለት በብይን መዝገቡን በመዝጋቱ በቀረበው የክስ ምክንያት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ካለመስጠቱም በላይ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/ረ/ መሰረት የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የከተማው አስተዳደር ከያዛቸው ቤቶች ጋር የሚቀርቡ ክሶችን ለማከራከር የሥረ ነገር ስልጣን ያለው በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ ባለመቀበል ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የሰበር አቤቱታ ቀርቦለት መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተጠሪዎች ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የሰበር አቤቱታውም ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ነክ መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበው ከአዋጅ ውጭ የተወሰደን ንብረት ባለቤትነት አጣርቶ ለመመለስ በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሰረት ሥልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ ኢራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው በማለት ሲሆን ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን ሳይቀበለው የቀረው ለኤጀንሲው ሥልጣን የተሰጠው ንብረቱ በቃል ትእዛዝ በመመሪያ ወይንም በቀላጤ ተወስዶ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ

በአዋጁ ላይ ስለተመለከተና ከሳሾች በዚህ መንገድ ክስ የቀረበበት ቤት ተወሰደብን ያላሉ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ሥልጣን አለው በማለት ነው፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤት የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥረ ነገር ሥልጣን አለው ያለው የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት እንዳለው ክስ የቀረበበት ቤት በቀላጤ፣ በመመሪያ ወይንም በቃል ትእዛዝ ተወስዷል ስላልተባለ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው በማለት ሳይሆን የከተማው አስተዳደር ከያዛቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክሶችን ለማከራከር የሥረ ነገር ሥልጣን ያለው የአ/አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 ላይ የተመለከተ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ሥልጣን አለው በሚል ነው፡፡

ይሁንና ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በቀላጤ፣ በቃል ትእዛዝ ወይንም በመመሪያ ተወስዶብናል ያላሉ በመሆኑ በአ/ቁ. 110/87 መሰረት ጉዳዩ በኢትዮጵያ ኢራይቬታይዜሽን በኩል የሚታይ አይደለም መባሉ ተገቢነት የነበረው ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/ረ/ ስር ለከተማ ነክ ፍ/ቤት ሥልጣን የተሰጠው የአ/አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ጉዳዮችን በተመለከተ ስለሆነና ይህም ባለቤትነቱ የከተማው አስተዳዳር ስለመሆኑ ክርክር ሳይኖርበት ከባለቤትነት በመለስ የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ እንደሆነ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት በውርስ የተላለፈልን የግል ቤታችን ነው በማለት ባለቤትነትን የመፋለም ክስ /petutory action/ ያቀረቡ በመሆኑና በቤቱ ባለቤትነት ላይም ክርክር እስከቀረበበት ድረስ ከተጠቀሰው የአዋጁ ድንጋጌ አኳያ የከተማ ነክ ፍ/ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን ሊኖረው የማይችል በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የከተማ ነክ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው በማለት ተመልክተው ውሳኔ መስጠታቸው ለአዋጁ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት እንደሆነ መረዳት የተቻለ ስለሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአ.አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00148 በታህሣሥ 24 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሰኔ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03006 በጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 04058 በግንቦት 8 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአ.አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዘገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 32638

መጋቢት 12 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ሒሩት መለሠ
መድህን ኪሮስ
ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የቂርቆስ ክፍለ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት አቶ ተስፋዬ ዘመድኩን ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1ኛ/ አቶ ይርጋ ንጋኔ ቀረቡ፡፡
2ኛ/ ወ/ሮ በላይነሽ ሙሽጋ ቀረቡ፡፡
3ኛ/ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት
4ኛ/ አቶ ሰንበት ታደሰ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የተከፈተው አመልካቹ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05469 መጋቢት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝና፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54329 ሐምሌ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል በማለት ነሐሴ 16 ቀን 1999 ዓ.ም. አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡

የክርክሩን መሠረታዊ ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጠው ትዕዛዝና በአመልካችና በተጠሪዎች በኩል ለዚህ ፍርድ ቤት በጽሑፍ ከቀረበው ክርክር እንደተረዳነው አቶ ይርጋ ንጋኔና ወ/ሮ በላይነሽ መሽጋ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት እና አቶ ሰንብት ታደሰ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግል ንብረታችን የሆነውን የቤት ቁጥር 271 ያላግባብ በመያዝ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት አከራይ አቶ ስንብት ታደሰ ደግሞ ተከራይ በመሆን እየተጠቀመበት ስለሚገኙ ንብረታችንን እንዲያስረክቡን በማለት ክስ አቅርበው ሶስተኛ እና አራተኛ ተጠሪ መልስና የመከላከያ ማስረጃ ካቀረቡ በኋላ በሥር ፍ/ቤት ተከሣሾች የነበሩት ሶስተኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች ለከሳሾች ማለትም ለአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ክስ ያቀረበበትን ቤት እንዲያስረክቡ የፌዴራል የመጀመያ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች የፍርድ ባለዕዳዎች ማለትም ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪዎች እንደ ፍርዱ እንዲፈጽሙ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው የአፈፃፀም ክስ አቅርበው የፍርድ አፈፃፀሙ በሒደት ላይ እያለ አመልካች የካቲት 29 ቀን 1999 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያሉ ቤቶችን አስመልክቶ የማስተዳደርና ተገቢውን ውሣኔ የመወሰን ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 2/1995 አንቀጽ 46 መሠረት የቤቶች መሠረተ ልማት ኤጀንሲ መሆኑ እየታወቀ ኤጀንሲው በክርክሩ ውስጥ ተሣታፊ ሣይሆን በባለቤትነት የሚያስተዳድረው ቤት አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች የግል ንብረት ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተሰርዞ ወደ ክርክሩ ገብተን የመከላከያ ማስረጃችንንና መልሳችን እንድናቀርብ ይፈቀድልን በማለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሠረት የፍርድ መቃወሚያቸውን አቅርበዋል፡፡

የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻው የቀረበለት ፍርድ ቤትም አንድ ሰው የፍርድ መቃወሚያ ሊያቀርብ የሚችለው በክርክሩ ሣይካፈል ሲቀርና የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ቤቱን በቀጥታ ሲያስተዳድር የነበረው የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት በተከሣሽነት ቀርቦ የተከራከረ በመሆኑ አመልካች የተሰጠው ፍርድ እንዲነሣና ወደ ክርክሩ እንደገባ ያቀረበው ጥያቄ ተገቢ አይደለም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የቀበሌ አስተዳደርና የአዲስ አበባ ከተማ መሠረተ ልማትና የቤቶች ኤጀንሲ ሁለት የተለያዩ የሕግ ሰውነት ያላቸው የተለያየ ሥልጣንና

ሀላፊነት በማቋቋሚያ አዋጃቸው የተሰጣቸው ሆኖ እያለ፣ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት በተከሳሽነት ስለተከራከረ ፍርዱን ለመቃወም አትችሉም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንን ስህተት እንዲያርም ያቀረብነውን ይግባኝ የሰረዘው በአግባቡ ስላልሆነና የሥር ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን ሣይኖረው የወሰነብን ስለሆነ በሰበር ሊታረም ይገባዋል በማለት የጽሑፍ ክርክር ያቀረበ ሲሆን አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው የቂርቆስ ክፍለ ከተማ 02 ቀበሌ አስተዳደር በተከሣሽነት ስለተሣተፈ አመልካቹ በክርክሩ እንደተሣተፈ ይቆጠራል፡፡ የክፍለ ከተማው አስተዳደር ነገረ ፈጆች ቀበሌውን ወክለው የተከራከሩ ስለሆነ የፍርድ መቃሚያ ማመልከቻቸውን ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን አራተኛው ተጠሪ እኔ ተከራይ በመሆኔ ከክርክሩ ውጭ እንዲሆን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ፍረድ ቤት ያቀረቡት የመከራከሪያ ሃሣቦች ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች መልስና የመከላከያ ማስረጃው እንዲሰማለትና በክርክሩ ተካፋይ ሣይሆን የተሰጠው ፍርድ እንዲሠረዝለት ያቀረበውን ጥያቄ ጉዳዩን ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው በግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የተሻሻለው የአዲስ አበባ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 ቀበሌ ማለት የከተማው ሦስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን የሆነ የክፍለ ከተማ አካል እንደሆነ በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ የተደነገገ ሲሆን የቀበሌ አስተዳደር ስልጣንና ተግባርን የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 35 የቀበሌ አስተዳደር በከተማው አስተዳደር ሥር ያሉ ቤቶችን የመሸጥ የመለወጥ እና ከዚህ ጋር ተመሣሣይ ውጤት ሊያስከትሉ የሚችሉ ተግባራትን የማከናወን ስልጣንና ሀላፊነት ያለው ስለመሆኑ አይደነግግም፡፡ ቻርተሩ በአዲስ አበባ ከተማ ሥር ያሉ ቤቶችን የማስተዳደር የመሸጥና ሌሎች ውሣኔዎችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚሰጠው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በበኩሉ ይህንን ተግባር ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን የአዲስ አበባ የመሠረተ ልማትና የቤቶች ኤጀንሲን በዋጅ ቁጥር 2/1995 አቋቁሟል። ከዚህም የምንረዳው የቀበሌ አስተዳደር ለሕብረተሰቡ በቅርበት አስተዳደራዊ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ የከተማው አስተዳደር በሶስተኛ ደረጃ የሚገኝ ሲሆን በከተማዋ አስተዳደር ሥር ያሉ ቤቶችን አስመልክቶ በሃላፊነት የሚከታተለውና ተገቢውን ውሣኔ መስጠት የሚችለው የመሠረተ ልማትና የቤቶች ጉዳይ ኤጀንሲ ነው። ሁለቱ የቀበሌ አስተዳደርና ኤጀንሲው የተለያየ ባህሪ ስልጣንና ሀላፊነት እንዲሁም ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አካላት ናቸው።

አንድ ወደ ክርክር መግባት ያለበት አካል በክርክሩ ተሣታፊ ሣይሆን የተወሰነው ውሣኔ መብቱን የሚነካ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔው ከመፈፀሙ በፊት ውሣኔው እንዲነሣና ክርክሩ እርሱ ባለበት እንዲቀጥል መጠየቅ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 ይደነግጋል። አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለአንደኛና እና ሁለተኛ ተጠሪዎች እንዲመለስ ውሣኔ የሰጠበትን ቤት የማስተዳደርና በቤቱ ላይ የተሻለ መብት አለኝ የሚል ሰው ሲመጣ በሕግ አግባብ የመፋለም ስልጣንና ኃላፊነት ያለው ከቀበሌ አስተዳደር የተለየና ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው።

አመልካችና የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማዋን ለማስተዳደር አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያደራጃቸው የመንግሥት አካላት በመሆናቸው ብቻ ቀበሌው በክርክሩ በተከሳሽነት በመሣተፍ አመልካች በክርክሩ ተሣታፊ ሆኖ ማቅረብ የሚገባውን የመከላከያ መልስና ማስረጃ የማቅረብ እድል አግኝቷል ብሎ ለመደምደም አይቻልም።

በመሆኑም አመልካች በክርክሩ ውስጥ ተሣታፊ ሣይሆን አሉኝ የሚላቸውን ማስረጃዎችና ሌሎች የመከራከሪያ ሃሣቦች ሳያቀርብ የሚያስተዳድረውን ቤት ለአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪ እንዲተላለፍ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሣና ክርክሩ እሱ ባለበት እንደገና እንዲታይ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና

በፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ክርክር የተነሣበትን ቤት አስመልክቶ 05469 መጋቢት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል። ፍርድ ቤቱ አመልካች የሚያቀርበውን ማናቸውንም የሕግና የፍሬ ጉዳይ ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የመሠለውን ፍርድ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341 መሠረት ተመልሷል። ይፃፍ።
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 54329 ነሐሴ 16 ቀን 1999 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።
3. በዚህ ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ። ይህ ፍርድ ቤት መጋቢት 12 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 33606

የካቲት 20 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሠ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ደጀኔ አበበ (5ሰዎች) - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጋቢት 4 ቀን 1999 ዓ.ም በእሸት የምግብ ውጤቶችና መኖ አክሲዮን ማህበር የዱቄት ፋብሪካ ላይ ቀደም ብሎ የተሰጠው እግድ መነሳት የለበትም በማለት የሰጠውን ትእዛዝ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ ማጽናቱን በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ይህን መሠረት በማድረግ ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች በእሸት የምግብ ውጤቶችና መኖ አክሲዮን ማህበር ላይ የሒሣብ ይጣራልን ክስ አቅርበው የዚሁ አክሲዮን ማህበር ንብረት የሆነው ዱቄት ፋብሪካ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ የሚል የዕግድ ትእዛዝ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አሰጥተዋል፡፡ በበኩላችን ደግሞ ፋብሪካው ለአክሲዮን ማህበሩ ለሰጠነው የብር 14,569,000(አስራ አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ስድሣ ዘጠኝ ሺህ) ብድር በአንደኛ ደረጃ መያዣነት የያዝነው በመሆኑና ብድሩም እስካሁን ስላልተመለሰ ፋብሪካውን ሸጠን ገንዘባችንን ለማስመለስ እንድንችል እግዱ ይነሣልን በማለት ህዳር 12 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀናል፡፡

ሆኖም ጉዳዩን የያዘው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ህዳር 28 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሒሣብ ማጣራቱ ውጤት እስከሚታወቅበት ጊዜ ድረስ የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ የሚነሣበትን ሁኔታ ስላላገኘን አቤቱታውን አልተቀበልንም፣ እግዱ እንዳለ ይቀጥል ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ እንደገና ታህሣሥ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው እግድ እንዲነሣልን ብናመለክትም አሁንም ፍ/ቤቱ ራሴ የሰጠሁትን የዕግድ ትእዛዝ መልሼ የማነሣበት ምክንያት የለም በማለት ጥያቄያችንን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚሁ ጉዳይ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ብናቀርብም ይህ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤቱን ትእዛዝ በማፅናት ይግባኛችንን ሰርዞብናል፡፡

የሥር ፍ/ቤት ሒሣቡ እስኪጠራ ድረስ እግዱ አይነሣም ሲል የሰጠው ትእዛዝ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 የተሰጠውን ስልጣን እንዳይጠቀምበት ገደብ የሚጥል፣ መብት የሚነፍግ ከመሆኑም በላይ በአመልካች ባንክ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ነው ምክንያቱም የሒሣብ ማጣራቱ ሥራ እንደተመለከትነው የጊዜ ገደብ ያልተቀመጠለት በመሆኑና የብድሩ ገንዘብ ወለድ እየጨመረ የድርጅቱ ንብረትም እየተበላሸ በመሆኑ እግዱ ባለመነሣቱ ምክንያት የሚደርሰው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡

የአክሲዮን ማህበሩ ንብረት የሆነው ዱቄት ፋብሪካ የታገደው ለዕዳው ተጠያቂ በሆኑ የማህበሩ አባላት በሆኑት ሰዎች በነበረው የሒሣብ ክርክር መነሻነት ሲሆን ባንኩ የሚፈለገው ብር 22,000,000(ሃያ ሁለት ሚሊዮን) ደግሞ የማህበሩ አባላትና የአክሲዮን ማህበሩ የጋራ ዕዳ ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹ የሰጡት ትእዛዝ ደግሞ ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 98/90 የተሰጠውን በብድር የሰጠውን ገንዘብ የመሰብሰብ ሥልጣን የሚገደብና በሕዝብና መንግሥት ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ነው፡፡

በመሆኑም ሰበር ሰሚው ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ትዕዛዝ በመሻር እግዱ እንዲነሣ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎቹ (ፋብሪካው) ታህሣሥ 4 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ እሸጉ የምግብ ውጤቶችና መኖ አክሲዮን ማህበር ከአባላቱ መዋጮና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከአመልካች ባንክ በተገኘው ብድር በብር 53,000,000 የተመሠረተ የዱቄት ፋብሪካ ነው፡፡ የአክሲዮን ማህበሩ ቦርድ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ለሶስት ተከታታይ ዓመታት አባላትን ባለመጥራቱና ሪፖርትም ባለማቅረቡ የተነሣ በስር ፍ/ቤት የሒሣብ ይጣራ ክስ ተመሥርቷል፡፡ ንብረቱ እንዳይባክን ፋብሪካው ሒሣቡ ተጣርቶ እስከሚያልቅ ጊዜ ድረስ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ባቀረብነው ጥያቄ መሠረት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ ተሰጥቶልናል፡፡ አመልካችም እግዱ እንዲነሣለት አመልክቶ በፍ/ቤቱ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በዚሁ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ማለት ሲገባው አመልካቹ እንደገና ተመሣሣይ የሆነ የእግድ ይነሣልኝ ጥያቄ መጀመሪያ የእግድ ትእዛዝ ለሰጠውና እግዱ እንዲነሣ ጥያቄ ቀርቦለትም እግዱ አይነሳም ላለው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ይህ ፍ/ቤት ራሱ የሰጠውን ትእዛዝ የሚያስለውጥ ሌላ ትእዛዝ መስጠት ስለማይችል የእግድ ይነሣልን ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው፡፡ ፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ መሠረዙ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

እኛ የእግድ ትእዛዝ እንዲሰጥልን ያመለከትነው የማጣራት ሥራው እስኪያልቅ ጊዜ ድረስ ፋብሪካው ካልታገደ የሒሣቡ ጉድለትና የንብረቱ መባከን ሣይታወቅ ተሸፋፍኖ ይቀራል የሚል ስጋት ስላደረብን ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹም የሰጡዋቸው ትእዛዞች ይህን ስጋት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

የማጣራት ሥራው በአፋጣኝ ሊከናወን ያልቻለው አመልካች የዱቄት ፋብሪካውን በሮች በመበየድ አጣሪዎች እንዳይገቡ በመከላከሉ መክንያት ነው፡፡ ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው ፍ/ቤት አመልካች ብይዱን እንዲያነሣና የሒሣብ ማጣራት ሥራው እንዲቀጥል ሲል ትእዛዝ የሰጠ ቢሆንም እስካሁን የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ተግባራዊ አልሆነም፡፡

በመሆኑም አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጀመሪያ እግዱ አይነሳም በማለት በሰጠው ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ማለት ሲገባው እንደገና የእግድ ይነሣልኝ ጥያቄ ማቅረቡ አግባብ ባለመሆኑና የሥር ፍ/ቤት ደግሞ ራሴ የሰጠሁትን ትእዛዝ መልሼ ራሴ ላነሣው አልችልም ያለው በአግባቡ በመሆኑ፣ ፌ/ከ/ፍ/ቤት

የሰጠው ትእዛዝም የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ በስር ፍ/ቤቶቹ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም፡፡ ሰበር ሰሚው ችሎትም ይህን ተመልክቶ በሥር ፍ/ቤቱቹ የተሰጡትን ትክዛዞች እንዲያፀናልን ሲሉ አመልክተዋል፡፡

አመልካችም የመልስ መልሱን በማቅረብ በአቤቱታው የተጠቀሱትን ክርክሮች ለማጠናከር ሞክሯል፡፡

በበኩላችን ደግሞ በአመልካቹ የቀረበውን የዕግድ ይነሣልኝ ጥያቄ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ የዱቄት ፋብሪካው የተመሠረተው ከአመልካች ባንክ በብድር በተገኘው ገንዘብ ጭምር መሆኑን ስላመኑና ለዚህ በብድር ለተገኘው ገንዘብም ፋብሪካው በአንደኛ መያዣነት አልተመዘገበም ብለው ስላልካዱ አመልካቹ ያቀረበው የእግድ ይነሣልኝ ጥያቄ በአግባቡ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የሥር ፍ/ቤቱ መጀመሪያ የሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ደግሞ በአክሲዮን ማህበሩ አባላት መካከል የሒሣብ ይጣራልን ክስ ቀርቦ በክርክር ላይ ባሉበት ጊዜ ከአባላቱ በአንዱ ወገን ሒሣቡ ሣይጣራ ፋብሪካ እንዳይሸጥ ለመከላል እንጂ በብድር ምክንያት በመያዣነት የያዘው ባንክ ገንዘቡን ለማስመለስ በማሰብ እንዳይሸጠው ለመከልከል እንዳልሆነ ከትዕዛዙ መንፈስ ለመረዳት ችለናል፡፡

አመልካች ባንክ በዋስትና የያዘውን ንብረት በመሸጥ በብድር የሰጠውን ገንዘብ ከነወለዱ የማስመለስ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት የተሰጠው በመሆኑ በዋስትና በያዘው ፋብሪካ ላይ የተሰጠው እግድ እንዲነሣለት ጥያቄ ማቅረቡ በአግባቡ ነው፡፡ ሆኖም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የእግድ ይነሣልኝ ጥያቄው ሲቀርብለት አመልካች በአዋጁ የተሰጠውን ሥልጣን መሠረት በማድረግ መብቱን ለማስጠበቅ እንዲችል የእግድ ትእዛዙን ሊያነሣለት ሲገባ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት መሆኑን ተመልክተናል፡፡

መጀመሪያ እግዱ አይነሣም የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶ እያለ በዚሁ ትእዛዝ ይግባኝ እንደማለት ተመልሶ እንደገና አመልካች ለዚሁ እግዱ አይነሣም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላለው ፍ/ቤት እግዱ ይነሣልኝ ማለት አይችልም ተብሎ በተጠሪ የቀረበውን ክርክር ስንመለከትም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ጊዜያዊ እንደመሆኑ መጠን ከጊዜ በኋላ ከሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ ሊሻሻል፣ ሊነሣ ወይም ሊሠረዝ የሚችልበት ምክንያት ሲኖር አስቀድሞ የእግድ ትእዛዝ የሰጠው ፍ/ቤት እግዱን እንዲያነሣ ማመልከት እንደሚቻልና ፍ/ቤቱም እንደየሁኔታው እግዱን ሊያሻሽል፣ሊያነሣ ወይም ጨርሶ እንዲሰረዝ ሊያደርግ እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 የተደነገገ በመሆኑ የተጠሪዎቹ ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመጀመሪያም ይሁን በሁለተኛው ጊዜ የቀረበውን የእግድ ይነሣልኝ ጥያቄ ያለመቀበሉና የእግድ ትእዛዙን ያለማንሣቱ፣ ፌ/ከ/ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤቱን ትእዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት የቀረበለትን ይግባኝ መሠረዙ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ትእዛዞቹ መሻር ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1- የፌ/መ/ፌ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31653 መስከረም 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው የዕግድ ትእዛዝና ህዳር 28 ቀን እና መጋቢት 4 ቀን 1999 ዓ.ም እግዱ አይነሣም በማለት የሰጣቸው ትእዛዞች እንደዚሁም የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 55387 ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ እግዱም ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

2- ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 33824

ሚያዝያ 16 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

አመልካች፡- የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሠረተ ልማትና የቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- 1ኛ የቀኛዝማች መኮንን ነጋሽ ወራሾች ከጠ. ጋር ቀረቡ፡፡

2ኛ ወ/ሮ ገነት አበራ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ መስከረም 30 ቀን 1990 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ቁጥሩ 953/ለ/ የሆነው በወረዳ 5 ቀበሌ 06 ውስጥ የሚገኘው ቤት የቀኛዝማች መኮንን ነጋሽ ጋራዥ ውስጥ የሚገኝና አቶ ተስፋዬ ሃይሌ የሚባሉ የጋራዡ ሠራተኛ ሲኖሩበት የነበረ የአውራሻችን የቀኛዝማች መኮንን ነጋሽ ቤት በመሆኑ ይልቀቁልን በማለት በወ/ሮ ገነት አበራ ላይ ክስ አቅርበዋል፡፡

ተከሳሿም የካቲት 8 ቀን 1991 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የቤቱ ግምት በክሱ ላይ አልቀረበም፡፡ ዳኝነትም አልተከፈለበትም፡፡ ከሣሾች በንብረት አጣሪነት አልተሾሙም የሚሉትን ነጥቦች በመጠቃቀስ የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ ተከሳሽ በፍሬ ነገሩ ላይ ክደው ስላልተከራከሩ በክሱ የተጠቀሰውን ቤት ለከሳሾች እንዲያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም የአ/ከ/ክ/ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ ሚያዝያ 29 ቀን 1999 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሳሾች ክስ የመሰረቱበት በቀድሞ ወረዳ 5 ቀበሌ 06፣ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 10/11/12 ክልል የሚገኘው ቁጥሩ 953/ለ/ የሆነው ቤት ያረፈበት ቦታ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የተወረሰ ነው፡፡ ተከሳሽ የመንግስትን ቦታ ላይ ያለፈቃድ የንግድ ቤት ሠርተው ነበር፡፡ አስተዳደሩ ቦታውን ለማጽዳት ሲንቀሳቀስ ተከሳሽ ባለሃብትነታቸውን ለመንግስት አስተላልፈው የቤት ኪራይ እየከፈሉ በቤቱ ለመገልገል በመስማማታቸው ከአስተዳደሩ ጋር ውል ገብተው የቤት ኪራይ እየከፈሉ ይገኛሉ፡፡ የመቃወም አመልካች በመንግስት ባለቤትነት ሥር የሚገኙትን ቤቶች የማስተዳደርና የመቆጣጠር ሥልጣን አለው፡፡ ከሣሾች ክስ ባቀረቡበት ቤት ላይ ያቀረቡት ካርታ ወይም ደብተር የለም፡፡ ተከሳሽ ቤቱን ለከሳሽ እንዲያስረክቡ በማለት ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሣኔ የመቃወም አመልካችን መብት የሚጋፋ ነው፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቱ መዝገቡን ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ያስተላልፍልን እንደዚሁም ቤቱ የመቃወም አመልካች እያከራየ ኪራይ የሚሰበስብበት ስለሆነ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ ኪሣራ እንዲቆርጥልን በማለት አመልክቷል፡፡

ከሣሾች ደግሞ በግንቦት 28 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የመቃወም አመልካች ቀበሌው በከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 4156፣ 24900፣ 3931 እና 24931 በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ማልቃ ገብቶ ቤቶቹ ተወርሰዋል የሚለውን ክርክር አቅርቦ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ተወስኖበታል፡፡ ክ/ከተማው የቀበሌው የበላይ አካል ስለሆነ እንደገና ተቃዋሚ ሆኖ የሚቀርብበት ምክንያት የለም፡፡ ቤቶቹ አልተወረሱም እንጂ ተወርሰዋል የሚል ክርክርም ካለ መከራከር የሚችለው የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነው፡፡ ማስረጃዎችን በተመለከተ ቤቶቹ ተመን እንዲወጣላቸው በነሐሴ 6 ቀን 98 ዓ.ም የተፃፈ የተባለው የቤት መውረሻ ቅጽ አረጋጋጭ ቁጥር 2060/19/14/98 ተከሳሾች ከተፈረደባቸው በኋላ በ1998 ዓ.ም የተፃፈ ስለሆነ የቤት መውረስን አያስረዳም፡፡ የወ/ሮ ገነት አበራ ጉዳይ በሰበር

ያለቀለት ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ እንዲያደርግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በመቃወም አመልካች ቁጥሩ 953/ለ/ የተወረሰ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረበው ሰነድ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮ በዞን አንድ የወረዳ 6 ፋይናንስ ቢሮ ጽ/ቤት በ13/13/91 የፃፈው ሠነድ ሲሆን ሰነዱም በቤት ቁጥር 953/2/ በሆነው ቤት 2ኛ የመቃወም ተጠሪ ይሠሩበት የነበረ መሆኑን የሚገልጽ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የወረዳ 5 ቀበሌ 6 አስተዳደር ጽ/ቤት በመስከረም 03 ቀን 1992 ዓ.ም የፃፈው ሰነድ ሲሆን ይዘቱም ከላይኛው ማስረጃ ተመሳሳይ ነው፡፡ በተጨማሪ የመቃወም አመልካች በቤት ቁጥር 953/2/ ላይ የ2ኛ የመቃወም ተጠሪ የንግድና የሥራ ፈቃድ እንዳለውና ቤቱን የክልል 14 መስተዳድር ጽ/ቤት ለ2ኛ የመቃወም ተጠሪ ያከራየበትን በጥቅምት 6 ቀን 1991 ዓ.ም የተደረገ ውል ቀርቧል፡፡ ማስረጃው ሲመረመርም ማስረጃዎቹ በዚህ መዝገብ ውሣኔ ያረፈበት ቤት 2ኛ የመቃወም ተጠሪ የያዙት መሆኑን ወይም ለ2ኛ የመቃወም ተጠሪ የተከራየ መሆኑን ሊያስረዳ ከሚችል በስተቀር የቤቱ ባለቤት ማን እንደሆነ የሚያስረዳ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ትርፍ የሆኑ ቤቶች ባለቤቱ የመረጠውን ቤት ከወሰደ ወይም ካስቀረ በኋላ ትርፍ ቤቶቹን ለመንግስት የሚያስረክብበት ስርዓት መኖሩ ይታወቃል፡፡ ሆኖም የመቃወም አመልካች በክሱ የተጠቀሰው ቤት በዚሁ መልኩ በትርፍነት መንግስት የተረከበው ስለመሆኑ የሚያስረዳ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑ በመቃወም አመልካች በዚህ መዝገብ ውሣኔ ያረፈበት ቁጥር 953/2/ የተወረሰ መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ ቤቱ የተወረሰ ስለሆነ ውሣኔው ይሰረዝልኝ በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም ብሎ ክርክሩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360/2/ መሠረት ውድቅ አድርጎታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይግባኝ ቀርቦለት የሥር ፍ/ቤት ፍርድ ጉድለት አላገኘሁበትም በማለት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

የሥር የመቃወም አመልካች የአሁኑ አመልካች ለዚህ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታን ያቀረበውም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ ቅሬታውም ፍ/ቤቶቹ ክሱን በመስማት ግራ ቀኙን አከራክረው ውሣኔና ትዕዛዝ የሰጡት ክሱን የማየት ሥልጣን ሳይኖራቸው ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ የተከራዩት ቤት የተሰራው በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት በተወረሰ ባዶ የመንግስት መሬት ወይም ቦታ ላይ ሆኖ የተሠራውን ያለፈቃድ በመሆኑ መፍረስ የነበረበት ሲሆን በወቅቱ በነበረው መመሪያ መሠረት ከሚፈርስ ተጠሪዋ በኪራይ እንዲጠቀሙበት ተወስኖ ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ በኪራይ እየተጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡ ይህ ክርክር ያስነሳው ቤት 1ኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት አልተወረሰም እያሉ የሚያቀርቡት ክርክር ካቀረብነው መቃወሚያ ጋር ያልተገናዘበ ነው፡፡ የኛ ጥያቄ ቤቱ የተሰራው በአዋጁ መሠረት በተወረሰ የመንግስት ቦታ ላይ ነው የሚል እንጂ ቤቱ ራሱ በውርስ የተገኘ ነው የሚል አይደለም፡፡ አመልካች በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በባለቤትነት የሚያስተዳድረውን ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የተፈቀደላቸውና ያለአግባብ ከአዋጁ ውጪ ተወስዶብኛል የሚሉ ከሆነ ተጠሪዎች ለሚመለከተው ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ጥያቄያቸውን አቅርበው ማስወሰን ይጠበቅባቸዋል በዚሁ መሠረት ጥያቄያቸውን አቅርበው ባላስወሰኑበት ወይም የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርም ይሁን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በማቅረብ በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ሳያረጋግጡ ክስ ማቅረብ አይችሉም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ መሠረት ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው ክሱን ተቀብለው ማከራከራቸውና ከዚህም አልፈው ቤቱ የተወረሰ ስለመሆኑ የመቃወም አመልካች አላስረዳም በማለት ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪዎች እንድናስረክብ መወሰናቸው ሕጉን

ያላገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሮ ጉዳዩ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት እንዲዳኝ ተብሎ ሊወሰንልን ይገባል የሚል ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አከራካሪው ቤት አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት በቀኛዝማች መኮንን ነጋሽ የተሰራና አቶ ተስፋዬ ሀይሉ የተባሉ የድርጅቱ የሕግ ክፍል ሰራተኛ የሚጠቀሙበት ነበር፡፡ ወ/ሮ ገነት አበራም ከዚህ ሠራተኛ ጋር አብረው ይሰሩ ስለነበር ቤቱን ልቀቂ ሲባሉ አለቅም አሉ እንጂ ቤቱን ራሳቸው አልሰሩትም፡፡ አመልካች ቤቱን መንግስት ተረክቦት ኪራይ እየሰበሰበበት ነው የሚለው ከ1990 ዓ.ም በኋላ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመስማማት ነው፡፡ ቤቱ በ1967 ዓ.ም ሆነ ከዚያ ወዲህ ተወርሶ አመልካች የሚያስተዳድረው አይደለም፡፡ አመልካች በተቃዋሚነት ልግባ ብሎ እኔ የማስተዳድረው ቤት ነው ብሎ ስለመጣ ቤቱ ስለመወረሱ አስረዳ ተባለ እንጂ ቦታው ባዶ ሆኖ ቦታውን ስለመውረሱ ማስረጃ አቅርብ አልተባለም፡፡ እኛ በግቢው ውስጥ ያሉት ቤቶች ሁሉ የቀኛዝማች መኮንን ነጋሽ ንብረት መሆናቸውን አስረድተናል፡፡ የፌ/ፍ/ቤቶች ስልጣን የላቸውም ተብሎ ለማስረዳት የተጠቀሱት ሕጐችም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ስለሌላቸው ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀድቅልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈው መልስ በወረዳ 5 ቀበሌ 06 በአዲሱ አደረጃጀት ደግሞ በአ/ክ/ከተማ ቀበሌ 10/11/12 ክልል የሚገኘው ቁጥሩ 953/ለ/ የሆነው ቤት ቀደም ብሎ በሳጠራና በቆርቆሮ ከፍዬ የታይፕ የጽህፈት ሥራ ሳከናውንበት በነበረው ባዶ የመንግስት መሬት ላይ እኔ ራሴ የሰራሁት ቤት ነው፡፡ አመልካች ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት በተወረሰው ባዶ የመንግስት ቦታ ላይ የተሰራ ቤት መሆኑን ካወቁ በኋላ ቤቱን ለማፍረስ አስበው የነበረ ቢሆንም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቱ ቢፈርስ እኔንና ቤተሰቤን የሚያፈናቅል ሆኖ ስላገኙት በኪራይ እንድኖርበት ተፈቅዶልኝ እየሠራሁበት እገኛለሁ፡፡ 1ኛ ተጠሪዎች ከአቶ ተስፋዬ ሃይሉ ጋር ጥገኛ ስለነበርሽ አሁን ያለሽበትም ቤት አቶ ሃይሉ ሲሰራበት የነበረው ቤት ነው በማለት ይህን ቤት ከሌሎች ቤቶች ጋር በመደመር ክስ መሰረቱብኝ እንጂ ቤቱ አቶ ተስፋዬ ሲሰሩበት የነበረው ቤት አይደለም፡፡ እንደዚሁም 1ኛ ተጠሪዎች ቤቱ የእነሱ ስለመሆኑ የሚያስረዳ የቤት ባለቤትነት ደብተርም ይሁን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሳያቀርቡ በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት ሳይኖራቸው ነው ክስ የመሰረቱብኝ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ቤቱን እንድለቅ የወሰኑት 1ኛ ተጠሪዎች ቤቱ የእነሱ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ሳያቀርቡ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲሻርልኝ በማለት ተከራክራለች፡፡

ከዚህ በኋላም ግራ ቀኙን በቃል በማነጋገርና አንዳንድ ነጥቦች ላይ ጥያቄ በማቅረብ ተከራካሪዎቹ ተጠቃሹ ቤትና የተጠሪዎች አውራሽ ጋራዥ ያላቸውን የአቀማመጥ ግንኙነት በተመለከተ ግልጽ አድርገውልናል፡፡

በበኩላችን ደግሞ የፌ/ፍ/ቤቶች ክሱን ለማየት ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? 1ኛ ተጠሪዎች በክሱ የተጠቀሰው ቤት የአውራሻቸው የቀኛዝማች መኮንን ነጋሽ ቤት ስለመሆኑ በማረጋገጥ ነው ክስ የመሰረቱት ወይስ አይደለም? የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ቤቱ የተወረሰ መሆኑን ስላላስረዳ ቤቱን ለስር ከሣሾች /ለአሁን 1ኛ ተጠሪዎች/ እንዲያስረክብ ቀደም ብሎ የተሰጠው ፍርድ የሚሻርበት ምክንያት የለም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ክሱ የባለቤትነት ጥያቄን መሠረት በማድረግ የቀረበ እንጂ ከቤት ኪራይ ጋር በተያያዙ ሁኔታዎች መነሻነት የቀረበ ባለመሆኑ የፌ/ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያላቸው መሆኑን ተግንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች የፌ/ፍ/ቤቶች ክሱን ያዩት በሌላቸው

ሥልጣን በመሆኑ ጉዳዩ በከተማ ነክ ፍ/ቤት እንዲታይ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ 1ኛ ተጠሪዎች በክሱ የተጠቀሰው ቤት ያለአግባብ የተወረሰ ነው በማለት እንዲመለስላቸው ለፕራይቤታይዜሽን ኤጀንሲ በማቅረብ ቤቱ እንዲመለስላቸው የተወሰነላቸው ስለመሆኑ ወይም ቤቱ የራሳቸው ስለመሆኑ የሚያስረዳ የቤት ባለቤትነት ደብተር ወይም ደግሞ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያላቸው ስለመሆኑ ማስረጃ በማቅረብ አላሳዩም፡፡ ክሱን ያቀረቡት ለክሱ መነሻ በሆነው ቤት ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ሳያረጋግጡ ነው፡፡ በክርክሩ ሂደትም የባለቤትነት መብት ያላቸው ስለመሆኑ አላስረዱም፡፡ በመሆኑም ክሱ ከመጀመርያው የቀረበው መብቱ ያላቸው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 33/2/ መሠረት ውድቅ መሆን የነበረበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነት የሚረጋገጠው ከአስተዳደር ክፍል የተሰጠ የምስክር ወረቀት በማቅረብ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1195 ተደንግጓል፡፡ አዋጅ ቁጥር 47/67 ደግሞ ከታህሳስ 11 ቀን 67 ዓ.ም ጀምሮ የከተማ ቤትን በንብረትነት የያዘ ሰው መብቱ በሚኒስትሩ ካልፀደቀ በስተቀር ንብረትነቱ አይፀናለትም ይላል፡፡ የእነዚህን ሕጐች ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ስንመለከተው ደግሞ ማንኛውም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ነኝ የሚል ሰው ንብረቱ የራሱ ስለመሆኑ በአስተዳደር ክፍል ተረጋግጦ የምስክር ወረቀት ወይም ውሣኔ ካልተሰጠው በስተቀር ወይም ለአስራ አምስት ዓመት ግብር እየገበረበት በይዞታው ስር አድርጐ ካላቆየው በስተቀር የንብረቱ ባለሃብት እንደሆነ እንደማይቆጠር ለመረዳት ይቻላል፡፡ የሕጉ ድንጋጌ የሚያዘው ይህ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች ቤቱ የእኛ ነው ያስረክቡን በማለት ክስ የመሰረቱት 1ኛ ተጠሪዎች የቤቱ ባለቤትና የሃብቱም ባለመብት ስለመሆናቸው ማስረዳት ሲኖርባቸው አመልካቹ ቤቱ የተወረሰ መሆኑን ያስረዳ ማለታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአግባቡ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ እንደዚሁም ቤቱ የተሰራው በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት በተወረሰው ባዶ ቦታ ላይ ነው በማለት አመልካች እየተከራከረ እያለ ቤቱ የተገኘው በውርስ ነው በማለት እንደተከራከረ በመቁጠር ክርክሩ ቤቱ የተገኘው በውርስ ነው ወይስ አይደለም በማለት ግራ ቀኙን ማከራከራቸው ተገቢ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37819 ሕዳር 13 ቀን 1993 ዓ.ም እና በመ/ቁ. 88281 ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 59130 ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአዲስ ከ/ክ/ከተማ በቀበሌ 10/11/12 ክልል የሚገኘው ቁጥር 953/ለ/ የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት በተወረሰው ወይም በተገኘው ባዶ የመንግስት ቦታ ላይ የተሰራና አመልካች የሚያስተዳድረው የመንግስት ቤት ነው ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 34249

በሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ - ወራሽ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- እነ አቶ አለሙ ወንድሙ - ጠበቃ አቢይ ወርቁ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በአመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ በወረዳ 7 ቀበሌ 32 ቁጥር 074 የሆነውን ቤት ከአዋጅ 47/67 በፊት የሰራነው ሲሆን በአዋጁም አልተወረሰም፡፡ በዚሁ ቤት በስማችን የንግድ ፈቃድ አውጥተን በኃይለስላሴ ጊዜ ተከሣሾችን በግል ድርጅታችን እንዲሰሩ አስጠግተናቸው ነገር ግን እንዲለቁ ተጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆኑ እንዲለቁ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሾችም ቀርበው ክስ የቀረበበት ቤት በአዋጁ ተወርሶ የአከራይ ተከራይ ግንኙነታችን ተቋርጧል፡፡ ኪራይም ለቤቱ ባለቤት ለቀበሌው አስተዳደር እየከፈልን ስለሆነ ከሣሾች ቤቱ ይለቀቅልን በማለት ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር የቀረበበትን ቤት ማንደር አስቀርቦ በመመልከት ቤቱ የተወረሰ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ተከሳሾች ይህንኑ ክስ የቀረበበትን ቤት ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በኋላም ጉዳዩ በይግባኝና በሰበር ለከተማው ፍ/ቤት ቀርቦ ቤቱ ሊመለስ ይገባል ተብሎ በበታች ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ይህ ችሎት በቅድሚያ የተመለከተው የክርክሩን አመራር በተመለከተ ነው፡፡

የሥር ከሳሾች የአሁን ተጠሪዎች ዳኝነት የጠየቁት የግል የሆነ ቤታችን በሥር ተከሳሾች በአሁን አመልካቾች ያለአግባብ የተያዘብን ስለሆነ እንዲመለስልን ይወሰንልን በማለት ነው፡፡

ተከሳሾችም በበኩላቸው ቤቱ በመንግሥት በመወረሱ ምክንያት ከከሣሾች ጋር የነበራቸው የኪራይ ውል ተቋርጦ ከቤቱ ባለቤት የቀበሌው አስተዳደር ጋር የኪራይ ውል በመዋዋል ኪራይ እንደሚከፍሉ ገልፀው ክሱ ሊሰረዝ ይገባዋል ብለዋል፡፡

ከሳሾች በአንድ በኩል የቤቱ ባለቤት ነን የሚሉ ከሆነና በሌላ በኩልም ቤቱ በአዋጅ በመንግሥት ተወርሷል ከተባለ ክርክሩ ባለቤትነትን የመፋለም /Petitory action/ ስለሚሆን ቤቱን በውርስ ይዞ በማስተዳደር ላይ ይገኛል የተባለው የቀበሌው አስተዳደር ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ ወገን /Indispensable Party/ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ወገን በሌለበት የሚሰጥ ውሣኔ መብቱን፣ ጥቅሙን ሊነካ እንደሚችል ስለሚታመን ነው፡፡ ይህ ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ወገን በከሳሾች በኩል በተከሳሽነት እንዲጣመር ባይደረግም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40/2/ ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ማድረግ ነበረበት፡፡

ስለሆነም በየደረጃው ባሉ የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ እልባት የተሰጠው ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ የሆነው የቀበሌው አስተዳደር የክርክሩ ተካፋይ ባልሆነበት ሁኔታ ስለሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደ/ፍ/ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና ሰበር ችሎት በዚህ ጉዳይ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የሚመለከተው የቀበሌ አስተዳደር ለጉዳዩ እጅግ አስፈላጊ ወገን /indispensable party/ ስለሆነ የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ይህንኑ ወገን ወደ ክርክሩ በማስገባት አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ክሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34313

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ዓለ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ነገረ ፈጅ ሣሙኤል ክፍሉ

ተጠሪ፡- ከበደ ታደሰ ተወካይ ግዛው ከበደ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል የደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01253 ግንቦት 9 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25765 ህዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት ታህሣስ 7 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪው ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል የማዕድንና ኢነርጅ ቢሮ በተሰጠኝ ፈቃድ መሰረት አስቆፍሬ ያከማቸሁትን 10,850 /አስር ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ/ ሜትር ኪዩብ በአስራ ዘጠኝ መኪና አስጭኖ የተጠቀመበት በመሆኑና ቦታውን በመያዝ የወደፊት ጥቅም ያስቀረብኝ ስለሆነ ብር 488,250 /አራት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺ ሁለት መቶ ሐምሳ ብር/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት በሥር ተከሳሽ በሆነው የድራጋዶስ የመንገድ ሥራ ድርጅት ያቀረበው ክስ ሲሆን አመልካቹ ወደ ክርክሩ የገባው ቦታው ከማናቸውም ሰው የይገባኛል ጥያቄ ነፃ ነው በማለት ያስረከበኝ የኢትዮጵያ መንገድ ባለስልጣን ስለሆነ ቦታውን አስመልክቶ ለተነሳው ክርክር በሶስተኛ

ወገን ተከሳሽነት ጣልቃ እንዲገባ ተከሳሹ በማመልከቱና ክሱን ያየው ፍርድ ቤት ትእዛዝ በመስጠቱ ነው፡፡ አመልካች በሶስተኛው ወገን ተከሳሽነት ቀርቦ ክርክር የተነሣበትን ቦታ ለተከሳሹ ያስረከበው በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ሐላፊነት መሆኑንና ከሳሽም የመንግስት ሐብት ከሆነው መሬት ገረጋንቲ በማምረት የማገኘው የወደፊት ጥቅም ተቋርጦብኛል በማለት ለመክሰስ ህጋዊ መሰረት እንደሌለው ተከሳሽ ወስዷል ለተባለው ገረጋንቲ በሐላፊነት ሊጠየቅ የማይችል መሆኑን በማንሣት ተከራክሯል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ያየው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሳሹ የከሳሽን 10,400 /አስር ሺህ አራት መቶ/ ኪዩብ ሜትር ገረጋንቲ የተጠቀመ ለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት የመንገድ ስራ ድርጅቱና አመልካች የገረጋንቲው ጠቅላላ ዋጋ ብር 360,000 (ሦስት መቶ ስልሣ ሺ ብር) እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ አመልካች ይግባኝ አቅርበው የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ በማሻሻል አመልካች ከመንገድ ሥራ ድርጅቱ ጋር በጋራ ለተጣራው ብር 150,000 /አንድ መቶ ሐምሳ ሺ ብር/ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የፍርድ ቤቶች አይደለም፡፡ መሬቱንም ለመንገድ ስራ ድርጅቱ የሰጠነው በአዋጅ ቁጥር 80/1989 ድንጋጌ መሰረት ሆኖ እያለና መሬት የመንግስት መሆኑ እየታወቀ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1460-1488 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ታልፈው የተሰጠ ውሣኔ በመሆኑ በሰበር ሊታይ ይገባዋል የሚል አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው፡፡ የእኔ ክስ በገንዘቤና በድካሜ ያመረትኩትን 10,850 /አስር ሺህ ስምንት መቶ ሀምሳ/ ኪዩብ ገረጋንቲ የአመልካች ወኪል አላግባብ ወስዶ የተጠቀመበት በመሆኑ ዋጋውን ይክፈለኝ የሚል በመሆኑ በሰበር አቤቱታው አመልካች የጠቀሰው የህገ መንግስቱ ድንጋጌም ሆነ የፍታብሔር ህግ ድንጋጌች ከተያዘው ጭብጥ ጋር ግኑኝነት የላቸውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መሬቱን በሚመለከት ካልሆነ በቀር የመንገድ ሥራ ድርጅቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አላግባብ ወስዶ ጥቅም ላይ አውሎታል ለሚለው ገረጋንቲ ተጠያቂና ሐላፊ የምንሆንበት የህግ መሰረት የለም በማለት የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

በከፍተኛው ፍርድ ቤት እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኩል የተሰጠው ውሣኔና ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀ ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመረነው አመልካች የሶስተኛ ወገን ተከሳሽነት ጣልቃ ገብ ሆኖ በተከራከረበት ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ለወሰነው የገንዘብ መጠን በአንድነትና በነጠላ ሐላፊ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ህጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመረዳት እንደሚቻለው ተጠሪው በመጀመሪያ ያቀረቡት ክስ ሁለት የክስ ምክንያቶች ያሉት ነው፡፡ የመጀመሪያው በሥር ተከሳሽ የነበረው ድራጋዶስ የመንገድ ሥራ ድርጅት 10,850 /አስር ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ/ ኪዩብ ገራጋንቲ አምርቼ አስቀም Â እያለ ከእኔ ፈቃድ ውጭ አላግባብ ስለተጠቀመበት ዋጋውን እንዲከፍለኝ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ተከሳሽ ስልጣን ካለው ከኦሮሚያ የማዕድንና ኢነርጅ ቢሮ ፈቃድ አውጥቼ በእጄ አድርጌ ገረጋንቲ እያመረትኩ ከምጠቀምበት ስፍራ በመግባት የምርት ሥራዬን ስላስተጓጎለ ከቦታው አገኝ የነበረው የወደፊት ጥቅም ታስቦ ካሣ ሊከፍለኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

በሥር ተከሳሽ የሆነው የድራጋዶስ የመንገድ ሥራ ድርጅት አመልካችን በሶስተኛ ወገን ተከሳሽነት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ የጠየቀው ተጠሪው በሁለተኛ ደረጃ ላቀረበው ክስ ነው፡፡ የመንገድ ሥራ ድርጅቱ ቦታውን ገረጋንቲ እያመረትኩ እንድጠቀምበት ከማናቸውም ሰው የይገባኛል ጥያቄ ነፃ መሆኑን አረጋግጠው ያስረከቡኝ የወሊሶ ከተማ አስተዳደርና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በመሆናቸው ከየቦታው አላግባብ በመግባት የወደፊት ገቢዬን አሳጥቶኛል የሚለውን የከሳሽ ክስ አስመልክቶ እነዚህ አካላት በሶስተኛ ወገን ተከሳሽነት እንዲጠሩ አመልክቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካቹ ለተከሳሹ ቦታውን ያስረከበ መሆኑን አልካደም፡፡ አመልካች ቦታውን ለመንገድ ሥራ ድርጅት ያስረከበው በአዋጅ ቁጥር 89/1989 መሰረት መሆኑን በመጥቀስ ተክራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው በቦታው ላይ ገረጋንቲ እያመረትኩ አገኝ የነበረው የወደፊት ጥቅም ስለተቋረጠ ተከሳሽ ካሣ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ያቀረበውን ጥያቄ በማለፍ ተጠሪው ተከሳሽ አላግባብ ወስዶ ተጠቅሞበታል ያለውንና በማስረጃ ተረጋግጧል ብሎ ፍርድ ቤቱ ያመነበትን 10,400 /አስር ሺ አራት መቶ/ ኪዩብ ሜትር ጠቅላላ ዋጋ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በመሆኑም የሶስተኛ ወገን ጣልቃገብ ተከሳሽ ሐላፊነት የሚመነጨው ከተከሳሹ ሐላፊነት በመሆኑና በዚህ ጉዳይ ተከሳሽ አላግባብ ቦታውን በመያዝ የከሳሽን የወደፊት ጥቅም በማስቀረትህ ካሣ ትከፍላለህ ተብሎ ያልተወሰነበት በመሆኑ አመልካች በሐላፊነት የሚጠየቅበት ህጋዊ መሰረት የለም፡፡

ሁለተኛው የተጠሪው የክስ ምክንያት ድራጋዶስ የመንገድ ሥራ ድርጅት አላግባብ እኔ ያመረትኩትን ገረጋንቲ ተጠቅሟልና ዋጋውን ይክፈለኝ የሚለው ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ የሆነው የመንገድ ሥራ ድርጅት አመልካች በሶስተኛ ወገን ተከሳሽነት ጣልቃ ገብ እንዲሆን ያልጠየቀ ከመሆኑም በላይ የመንገድ ሥራ ድርጅቱ እራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው ሥራውን በሚያከናውንበት ስአት አላግባብ በሰው ሐብትና ንብረት ላይ ጉዳት ቢያደርስ ተጠያቂ የሚሆነው የመንገድ ሥራ ድርጅቱ እንጂ ኮንትራክት ሰጭ የሆነው አመልካች ባለመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሹ አላግባብ ለተጠቀመበት ገረጋንቲ በሶስተኛ ወገን ተከሳሽነት ከተከሳሹ ጋር የአንድነትና የነጠላ ሐላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 43 ንኡስ አንቀጽ 1 ጋር የሚጣጣም ሆኖ አላገኘውም፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶች በመጀመሪያ ተከሳሽ የሆነው የመንገድ ሥራ ድርጅት አመልካቹ እንዲያስረዳለትና በሐላፊነት እንዲጠየቅለት ባልጠየቀበት ጉዳይ እንደዚሁም በተከሳሽ በኩል ጥፋት እንኳን ቢኖር አመልካቹ በሶስተኛ ወገን ተከሳሽነት ቀርቦ ለጥፋቱ ተጠያቂ የሚሆንበት ከህግ ወይም ከውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመነጨ ግዴታ መኖሩን ሣያረጋግጡና የፍታሃብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 43 ድንጋጌዎችን በመተላለፍ መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈጽመዋል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል የደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01253 ግንቦት 9 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25765 ህዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ለተጠሪው ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር/ የመክፈል ሐላፊነት የለበትም፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኛቸው የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

የሰበር መ/ቁ. 35403

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ ዓሊ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ዓብዱልነጢፍ ሙሐ ከጠበቃው ጋር ቀርቧል

ተጠሪ፡- 1/ትዕግሥት በርሃ ወኪል - ቀረበ፡፡

2/ ደምስስ ተማም ከጠበቃው ጋር ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የተነሣው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ከጉራጌ ዞን የወልቂጤ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ግራ ቀኙ የንግድ መደብርን በተመለከተ ሲከራከሩ ቆይተው ፍ/ቤቱ አመልካቹን ረቺ የሚያደርግ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ተጠሪዎች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6'ን' መሠረት አድርገው ዳኝነት እንደገና እንዲታይ አቤቱታ በማቅረባቸው መዝገቡ ዳግመኛ ተንቀሣቅሶ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6/3/ መሠረት ለአመልካቹ መጥሪያ በተጠሪዎችና በቀበሌ በኩል ልኮለት ተጠሪዎቹ በመሐላ ቃል አስደግፈው አመልካቹ መጥሪያ ደርሶት ደረሰኝ አልሰጥም ብሏል በሚል በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ባቀረቡት አቤቱታና የጎምሽ ቀበሌ ገ/ማ/ጽ/ቤት አመልካቹ መጥሪያው ደርሶት ለመቀበሉ ደረሰኝ ለመሰጠት ፈቃደኛ አልሆነም ሲል የፃፈውን ደብዳቤ በመመርኮዝ ጉዳዩን አመልካቹ በሌለበት መርምሮ ቀደም ሲል የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪዎቹን ረቺ ያደረገ ውሣኔ በታህሣሥ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ አመልካቹ በወልቂጤ አካባቢ ከ/ፍ/ቤት መጋቢት 19 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ይዞ በመቅረብ፣ በፍ/ቤቱ ቀርቤ ያልተከራከርኩት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጥሪያ ሥላልደረሰኝ በመሆኑና ይህም በቂ ምክንያት በመሆኑ የሰጠው ውሣኔ ተነስቶ በጉዳዩ ላይ መልስ ሰጥቼበት ይወሰን ሲል ፍ/ቤቱን ጠይቋል፡፡

የወልቂጤ አካባቢ ክ/ፍ/ቤትም የአመልካቹን አቤቱታ መርምሮ ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የተጠሪዎቹን በመሐላ ቃል ተደግፎ የቀረበ አቤቱታና የቀበሌውን ደብዳቤ በማውጣት መጥሪያ አልደረሰኝም ተብሎ የቀረበው አቤቱታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78/2 ድንጋጌ መንፈስ ባሟላ መልኩ የቀረበ ባለመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በዚህ ትእዛዝ ቅር የተሠኙት አመልካች ቅሬታቸውን በየደረጃው ላሉ ፍ/ቤቶች ቢያቀርቡም የወልቂጤ አካባቢ ክ/ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ እስከ ክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሠበር ችሎት ድረስ ባሉት ፍ/ቤቶች ፀንቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተዘረዘረው ሲሆን ይህ መዝገብ ለዚህ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሠበር ችሎት ሊቀርብ የቻለውም አመልካች ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሠበር ማመልከቻ የቀበሌ ገ/ማህበሩ በቁ/027/99 በሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የፍ/ቤት መጥሪያ ለአሁን አመልካች እንዳልሰጠኝ እያረጋገጠ እና መጥሪያውን ተቀብዬ አልፈርምም ማለቱ በምስክር ሣይረጋገጥ የስር ፍ/ቤቶች መጥሪያ ደርሶት ለመከራከር ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ውሣኔው ተነስቶ መከራከሪያዬን እንዳላቀርብ መከልከላቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲሉ አቤት በማለታቸው ነው፡፡

ይህም ችሎት የአመልካቹን አቤቱታ ተመልክቶ፣የስር ፍ/ቤቶች አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78/2/ መሠረት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎቹን አስቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክራቸውን አካሂደዋል፡፡ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሠረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78/2/ ተከሣሹ መጥሪያ በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን ገልፆ ሲያመለክት እና ፍ/ቤቱም ተከሣሹ ቀርቦ መልስ ያልሰጠው በበቂ ምክንያት መሆኑን የተረዳው ሲሆን ትእዛዙን ወይም ብይኑን

በማንሣት ክርክሩ እንደገና እንዲሰማ እንደሚያደርግ ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ማንኛውም ግለሰብ ለቀረበበት ክስ መልስ የመስጠት መብት እንዳለው ይታወቃል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አንድ ፍ/ቤት የአንደኛውን ተከራካሪ መከራከሪያ ላለመስማት በተቻለው መጠን ይኸው ተከራካሪ በቀነ ቀጠሮው ያልቀረበው በቂ ባልሆነ ምክንያት መሆኑን የቀረቡለትን ማስረጃዎች በሚገባ መርምሮ ማረጋገጥ እንደሚኖርበት መገንዘብ አያዳግትም፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት አመልካቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት መጥሪያ እንዳልደረሰው ገልፆ አቤቱታ ሲያቀርብም ቀድሞ ከተጠሪዎቹ በቀረበለት በመሐላ ቃል የተደገፈ ማመልከቻ ላይ አመልካቹ መጥሪያ ተቀብሎ ደረሰኝ አልሰጥም ሲል አይተዋል ተብለው የቀረቡትን ምስክሮችም ሆነ መጥሪያው በቀበሌው በኩል ሲሰጥ የነበሩት ምስክሮች እንዲሰሙ አላደረገም፡፡ እንደውም ከዚህ በኋላ ቀደም ሲል የጎምሽ ቀበሌ ገ/ማ/አስ/ጽ/ቤት የላከውን ደብዳቤ ፃፉ የተባሉት የቀበሌው ሠራተኛ እራሣቸው በሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ሌላ ደብዳቤ ክስም ሆነ መጥሪያ ደርሶን የሰጠነው ነገር የለም ሲሉ በቀበሌው ስም የሰጡት ማረጋገጫ መኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ደግሞ አመልካቹ መጥሪያ ደርሶት ያለበቂ ምክንያት ስላለመቅረቡ ተረጋግጧል ለማለት አይቻልም፡፡ ከዚህ ይልቅ ቀበሌው ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ የሚያረጋግጠው አመልካቹ ቀርቦ ያልተከራከረው መጥሪያው ሣይደርሰው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቿ በሥር ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት ያቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባው የነበረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቹ ቀርቦ ያልተከራከረው መጥሪያ ደርሶት ነው ሲሉ በደረሱበት መደምደምያ የአመልካቹን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ መደረጉ አግባብ ባለመሆኑ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የወልቂጤ አካባቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 01871 ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝም ሆነ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 17917 ሠኔ 13 ቀን 1999 ዓ.ም እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18594 ጥር 2 ቀን 1999 ዓ.ም የከ/ፍ/ቤቱን ትእዛዝ በማጽናት የሠጧቸው ትእዛዞች ተሽረዋል፡፡ ይባፍ፡፡

2/ የወልቂጤ አካባቢ ከ/ፍ/ቤት አመልካች ቀርበው ያልተከራከሩት በበቂ ምክንያት ማለትም መጥሪያ ሣይደርሳቸው መሆኑን ተገንዝቦ ውሣኔውን በማንሣት የአመልካችን መከራከሪያዎች ተቀብሎ ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

3/ ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

4/ እግዱ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይባፍ፡፡

5/ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የንብረት ህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/22008

ሐምሌ 3 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አሰግድ ጋሻው
ሂሩት መለሰ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አ/ድርጅት አልተጠሩም

ተጠሪ፡- 1. አቶ ኦላና ጥርቅና
2. አቶ ኃይሉ ወ/ሰማያት } ጠበቃ ወንድም አገኘሁ ገ/ሥላሴ
3. ኮ/ል እስጢፋኖስ ቡሽን

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና በፌ/ከ/ፍ/ቤት ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስ በወረዳ 18 ቀበሌ 27 ክልል ቁጥር 545 የሆነውን ቤት 1ኛ ተጠሪ የግል ቤታቸው በማስመሰል በወረዳ 18 ቀበሌ 41 ክልል በሚገኝ እና ንብረትነቱ የአቶ በላይ ተወልደ ከሆነ የቤ.ቁ 035 ጋር ተለዋውጠናል በማለት ይህንኑ ሕገወጥ ውል ለከሳሽ በማቅረብ በወኪሎቻቸው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አማካይነት አመልካች ቤቱን በአደራ ለማስተዳደር ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ከሰበሰበው የቤት ኪራይ ገንዘብ ብር 20,542.20 (ሃያ ሺህ አምስት መቶ አርባ ሁለት ከሃያ) ያለአግባብ የከፈለ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ከነወለዱና ክሱ ካስከተለው ወጪ ጭምር ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወስንልኝ በማለት ጠይቆ ክሱን ያስረዳልኛል ያላቸውን ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡

የአመልካች ክስና ማስረጃ ለተጠሪዎች ደርሶም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሙሉ መልስም በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱት ክርክርም ክሱ የቀረበው ከ17 ዓመት በኃላ ስለሆነ በይርጋ ይታገዳል፣ ከሳሽ የቤቱ ባለቤት ወይም ሌላ ቤቱ ይገባኛል የሚል 3ኛ ወገን ወኪልም አይደለም፡፡ ስለዚህ መብት ሳይኖረው ያቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 33/2/ መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንደዚሁም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የ1ኛ ተጠሪ ወኪሎች ስለሆኑ በእነሱ ላይ ክስ ሊቀርብ አይገባም የሚል ሲሆን በፍሬ ጉዳይ ረገድም 1ኛ ተከሳሽ /ተጠሪ/ የእራሳቸውን ቤት አሁን ለክርክሩ መነሻ ከሆነው ቁጥር 545 ቤት ጋር ከአቶ በላይ ተወልደ ጋር የቤት ልውውጥ ውል አድርገዋል፡፡ ይህ ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል አስገዳጅና እንደ ሕግ የሚቆጠር ነው፡፡ ከሳሽም በወቅቱ ውሉን አምኖ ተቀብሎ ክፍያ የፈጸመ ስለሆነ ሕጋዊውን ውል አስመልክቶ ክርክር ሊያቀርብ አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክርክሩንም ይደግፍልናል ያሏቸውን ማስረጃዎች አቅርበዋል፡፡

ከዚህም ሌላ 1ኛ ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት አቅርበዋል፡፡ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ ቢሆንም ከዚህ ጋር በተያያዘ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበ አቤቱታ ስለሌለ ዝርዝሩን መመዝገቡ ባለማስፈለጉ ታልፏል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች ክሱ ባይርጋ ቀሪ ሆኗል እንደዚሁም አመልካች ክስ ባቀረበበት ነገር ላይ መብትና
ጥቅም የለውም በማለት ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ካደረገ በኃላ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በክሱ መካተት በተመለከተ ግን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የ1ኛ ተጠሪ ወኪሎች መሆናቸው ክርክር ያላስነሳ ስለሆነና ተወካይ ሆኖ የሚሠራ ሰው የሚሰራቸው ሕጋዊ ሥራዎች አስገዳጅነታቸው ወካዩን እንደሆነ በፍ/ሕግ ስለ እንደራሴነት የተደነገጉት ድንጋጌዎች ስለሚያስረዱ አመልካች በ2ኛ እና በ3ኛ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በአግባቡ አይደለም በማለት ክሱ አሰናብቷቸዋል፡፡

በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድም ሕጋዊ የቤት ልውውጥ ውል ነበር ወይንስ አልነበረም? ነበር ከተባለ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚሉትን ጭብጦች መስርቶ መዝገቡን መርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም መሠረት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቁጥር 545 ቤት የአቶ በላይ ተወልደ የነበረውን የ1ኛ ተጠሪ ቤት ከሆነው ቁጥር 035 ቤት ጋር የልውውጥ ውል ነሐሴ 7 ቀን 1971 ዓ.ም ተደርጓል። ይህ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1731 መሠረት በተዋዋይ ወገኖች መካከል እንደ ሕግ የሚቆጠርና አስገዳጅነት ያለው ውል ነው። በዚህ ውል መሠረት ቁጥር 545 የሆነ ቤት የ1ኛ ተጠሪ ሲሆን ቁጥር 035 ቤት ደግሞ የአቶ በላይ ተወልደ ነው። በ1ኛ ተጠሪና በአቶ በላይ ተወልደ መካከል የተደረገውን ውል አመልካች ያውቀው የነበረ ሲሆን ይህንኑ ውል መሠረት በማድረግም የ1ኛ ተጠሪ ወኪሎች ለሆኑት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ክፍያውን ፈጽሟል። ይህም 1ኛ ተጠሪ የቤ.ቁ 545 ባለቤት መሆናቸውን አመልካች ዕውቅና መስጠቱን ስለሆነ አሁን ይመለስልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል።

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኙን መርምሮ መልስ ሰጭዎችን ሳይጠራ ይግባኙን ሠርዟል፡፡

ከዚህ በኋላም የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ችሎቱም ያቀረበውን አቤቱታ መርምሮ 1ኛ ተጠሪ በለውጥ ያገኙት ቤት የህብረት አምባ መኖሪያ ቤት ነ/ሥ/ማህበር መሆኑ ተረጋግጦ ቤቱን ይዜው ማኅበር እንዲረከብ ከተወሰነ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ሲቀበሉ የቆዩትን የኪራይ ማካካሻ ገንዘብ ሊመልሱ አይገባም መባሉ ተገቢ መሆኑ ሊጣራ እንደሚገባ በመታመኑ አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ትዕዛዝ ሠጥቷል።

ሆኖም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ተጠሪዎች ስላልቀረቡ ክርክር ለማቅረብ እንዳልፈለጉ በመቁጠር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል።

አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ክስ ያቀረበው ከፍ ብሎ እንደተመለከተው 1ኛ ተጠሪ የእራሴ ነው በማለት በአደራ እንዳስተዳድርላቸው ያስረከቡኝ ቤት በፍ/ቤት ውሳኔ የእሳቸው ሳይሆን የሕብረት አምባ መኖሪያ ቤት ነ/ሥ/ማህበር መሆኑ በመረጋገጡ ቤቱን ለዚሁ ማኅበር ያስረከብኩኝ ስለሆነ በኪራይ ማካካሻነት የ1ኛ ተጠሪ ወኪሎች ለሆኑት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የከፈልኩት ብር 20,542.20 /ሃያ ሺህ አምስት መቶ አርባ ሁለት ከሃያ/ ከወለድ፣ ከወጭና ኪሣራ ጋር ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ነው።

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን ክስ በማሰናበት የክፍያ ጥያቄውን በተመለከተ አመልካች ከአቶ በላይ ተወልደ ጋር ባደረጉት የቤት ልውውጥ ውል በወረዳ 18 ቀበሌ 27 ክልል ቁጥር 545 የሆነው ቤት ባለቤት ስለሆኑና አመልካችም ይህንኑ ውል ተቀብሎ የኪራይ ማካካሻውን ለ1ኛ ተጠሪ ወኪሎች የከፈለ በመሆኑ ይመለስልኝ ሊል አይችልም በማለት ክሱን ሳይቀበል ቀርቷል።

እኛም ጉዳዩን እንደመረመርነው ምላሽ ማግኘት የሚገባቸው ጭብጦች፡-

- 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከክሱ መሰናበታቸው በአግባቡ ነው አይደለም?
- አመልካች ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ በአግባቡ ነው አይደለም? የሚሉት በመሆናቸው እነዚህን ጭብጦች በመያዝ አቤቱታውን መርምረናል።

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የ1ኛ ተጠሪ ወኪል ስለመሆናቸው ግራ ቀኙን አላከራከረም። አንድ ተወካይ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን ሥር ሆኖ የሚያከናውናቸው ማናቸውም ተግባራት የአስገዳጅነት ውጤት የሚኖራቸው በተወካዩ ላይ ሳይሆን በወካዩ ላይ እንደሆነ በውክልና ሕግጋት ሥር ከተደነገገው ከፍ.ብ.ሕ.ቁ 2199 እና ተከታታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል።

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከአመልካች ሲቀበሉ የነበሩት ከ1ኛ ተጠሪ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን ስለመሆኑም በአመልካች ታምኗል። ይህም ክፍያው እንደተፈጸመ የሚቆጠር ለተወካዮቹ ሳይሆን ለወካዩ ለ1ኛ ተጠሪ ነው።

ስለሆነም አመልካች 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የ1ኛ ተጠሪ ወኪል መሆናቸውን እየተገነዘበ ያለአግባብ ተከፍሏል የሚለው ገንዘብ እንዲመለስለት ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን የከሰሰው ያለአግባብ የቀረበውን ክስ መሰረዙና የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም።

አመልካች ያቀረበው የክፍያ ጥያቄን በተመለከተም 1ኛ ተጠሪ የቤ.ቁጥር 545 የሆነውን ቤት በለውጥ ያገኙት መሆኑን የሚያረጋግጥ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማቅረብ ቤቱን አመልካች እንዲያስተዳድርላቸውና በኪራይ ከሚሰበስበውም ገንዘብ ማካካሻው ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲከፍልላቸውና ውክልና ቢሰጡም ይሄው ቤት የ1ኛ ተጠሪ ሳይሆን የሕብረት አምባ የመኖሪያ ቤት ኀ/ሥ/ማህበር እንደሆነና አመልካችም ቤቱን ለማኅበሩ እንዳስረከበ ቤቱም በባንክ ብድር ተሰርቶ የነበረ በመሆኑ ለባንክ መክፈል የነበረበትን ዕዳ አመልካች ከቤቱ የሰበሰበውን የኪራይ ገቢ በማኅበሩ ስም ለባንክ ስለመክፈሉ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲያደርግ አመልካች አቅርቧል፡፡ የቤት ቁጥር 545 የሆነው ቤት በፍርድ ጭምር የ1ኛ ተጠሪ አለመሆኑ ከተረጋገጠ የእራሳቸው ያልሆነን ቤት አመልካች በአደራ እንዲያስተዳድርላቸው በማስረከብ የኪራይ ማካካሻ በወኪሎቻቸው አማካይነት ያለአግባብ ሲቀበሉ እንደነበር መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ይህም አመልካች መክፈል የማይገባውን ክፍያ ሲፈጽም እንደነበር የሚያሳይ ሲሆን ሊከፍል የማይገባውን የከፈለ ደግሞ እንዲመለስለት መጠየቅ እንደሚችል በፍ.ብ.ሕ.ቁ 2164 ላይ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካች ገንዘቡ ይመለስልኝ በማለት መጠየቅ አይችልም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስላለበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

ው ሳ ኔ

- አመልካች ክስ ያቀረበበት ብር 20,542.20 (ሃያ ሺህ አምስት መቶ አርባ ሁለት ከሃያ) በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድ ጋር 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
- ውሳኔው የተሻረ መሆኑ እንዲታወቅ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 22297

ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የጅማ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት ተወካይ ቲጃኔ አባቡልጉ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሸዋረገድ አባድር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በወረዳው ፍ/ቤት ክሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት በጠየቀው ዳኝነት መነሻ አድርጎ ያቀረበው ምክንያት እናቴ በካርታ ቁጥር 928 1392 ካሬ ሜትር በሆነው ቦታ ላይ የቤት ቁጥር 156 የሆነ ቤት አላቸው የእናቴ ወራሽ መሆኔን አረጋግጫለሁ ሆኖም ተከሣሽ የአሁን አመልካች ለሌላ ግለሰብ ስለሸጠብኝ ሁከት ተፈጥሮብኛል የሚለውን ነው፡፡

አመልካችም ይህ በካርታ ቁጥር 928 የተመዘገበው ካርታ የተሰጠው በ1954 ዓ.ም. ነው፡፡ የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤትን ለመንግሥት ባደረገው አዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ይህ ክስ የቀረበበት ንብረት የተወረሰ ነው፤ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር የወረዳ ፍ/ቤትም በውርስ አግኝቼ የእራሴ ሆኗል በማለት ክሳሽ ይከራከር እንጂ ይህ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ንብረቱ በአዋጅ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

47/67 የተወረሰ ስለሆነ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ወስኗል። ይህም ውሣኔ በከፍተኛው ፍ/ቤት ፀንቷል።

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በይግባኝ ካከራከረ በኋላ የአሁን አመልካች ተወርሷል ይበል እንጂ ስለመወረሱ ማስረጃ አላቀረበም። ንብረቱ በከሳሽ በአሁን ተጠሪ ስም መሆኑን አልካደም የወራሽነት ማስረጃ ቀርቦ እያለ የሥር ፍ/ቤት መልስ ሰጭ የባለቤትነት ማስረጃ የለውም ማለቱ ተገቢ አይደለም ስለሆነም ካርታ እና ፕላን ያለውን ንብረት በሊዝ መሸጡ ተገቢ አይደለም በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል።

የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይኸው የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት አመልካችን አሰናብቷል።

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልን ይገባል በማለት ነው።

ግራ ቀኙም በዚህ ሰበር ችሎት የቃል ክርክር አድርገዋል።

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል። እንደተመለከትነውም ተጠሪ ሁከት ተፈጠረበት በተባለው ንብረት መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን ለማሣየት መሠረት ያደረገው ወራሽ ነኝ በማለት ነው። ንብረቱም የአውራሽ የእናቴ ነው ለማለት ያበቃው በካርታ ቁጥር 928 የተመዘገበው ካርታ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ካርታ በ1954 ዓ.ም. የተሰጠ ነው በማለት አመልካች ላቀረበው ክርክር ማስተባበያ አላቀረበበትም። ክዶም አልተከራከረም። አመልካች ይህ የንብረቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ሲሆን ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ ግን ተወርሷል በማለት ይህንኑ ሕግ መሠረት አድርጎ ለቀረበው ክርክር ተጠሪ አልተወረሰም በማለት ተከራክሯል የቤቱ ካርታ የተሰጠበትን ጊዜ እና አዋጁ የወጣበትን ጊዜ እንደ መነሻ ፍሬ ነገር በመያዝ ንብረቱ የተወረሰ መሆኑን የግምት መነሻ በመስጠት አመልካች ያስረዳ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ይህ ንብረት ያልተወረሰ መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ የፍሬ

ነገር ክርክርም ሆነ ማስረጃ በማቅረብ አላረጋገጠም ይልቁንም በቃል በተደረገው ክርክር አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲወጣ እኔ እስር ቤት ነበርኩኝ፤ የደርግ መንግሥት በአምባገነንነት በቀበሌ አማካኝነት ለሌሎች ሰዎች በኪራይ ሰጠብኝ የሚለውን መግለፁ ንብረቱ በእርግጥም የተወረሰ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ስለሆነም ንብረቱ ተወርሷል ወይስ አልተወረሰም የሚለውን ነጥብ በሚመለከት ማን ክርክሩን መጀመርና ማስረዳት እንዳለበት የሚያመለክተውን ድንጋጌ ባለመከተል እና ይህም ሥርዓት ቢዛነፍም እንኳ ከግራ ቀኙ ማን የተሻለ ማስረጃ አቅርቧል የሚለውን ነጥብ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አመልካች ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የፈፀመው ሁከት የለም ብለናል።
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22312 በሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መ/ቁ. 32640 በህዳር 21 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 348 /1/ መሠረት ተሽሯል።
3. የወረዳው ፍ/ቤት በ/መ/ቁ 532/96 በጥቅምት 18 ቀን 1997 ዓ.ም. እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 05349 በታህሣሥ 21 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠ/መ/ቁ.22469

ሐምሌ 05 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሠግድ ጋሻው

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የጅጅጋ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክርስትያን አልቀረበም

ተጠሪ፡- እነ አዳነች መንግስቱ (7 ሰዎች) የቀረበ የለም

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የህዝብ የሆኑ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለቤትነት የሚረጋገጥበትን መንገድ የሚመለከት ነው፡፡፡

የአሁን/የአሁኗ አመልካች በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበችው ክስ ለክርክር ምክንያት የሆነውና በ06 ቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኘው 6 ክፍል ቤት ቀድሞ የቤ/ክርስትያኗ የነበረና ከአዋጅ ቁ. 47/67 በኋላ ቀበሌው ቤቱን የያዘ ቢሆንም ቤቱ አንዲመለስላት ስለተወሠነ ተጠሪዎቹ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ጠይቃለች፡፡

ተጠሪዎች በሠጡት መልስ ቤ/ክርስትያኗ የቤቱ ባለቤት ለመሆኗ ያቀረበችው የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ባለመኖሩ ክሱ ውድቅ እንዲሆን ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም ይህንኑ ክርክር ተቀብሎ አመልካች ባለቤት ለመሆኗ አላረጋገጠችም በማለት ክሷን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የህዝብ የሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነት የሚረጋገጠው እንዴት ነው የሚለውን ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ቀርቦ ለተጠሪዎች መጥሪያ ቢላክም ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌለበት አንዲታይ ታዟል፡፡

ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡ ክፍ ሲል እንደተገለፀው የአመልካች ክስ ውድቅ የተደረገው እንዲመለስላት ለጠየቀችው ቤት ባለቤትንቷን የሚያርጋግጥ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት አላቀረበችም በሚል ነው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማረጋገጥ በተገቢው አስተዳደር ክፍል ለአንድ ሰው የተሠጠው የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት ይህ ሰው የዚሁ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሃብት እንደሆነ እንደሚያስቆጥረው በፍ/ህ/ቁ 1195(1) የተመለከተ በመሆኑ አንድ ሰው የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤት መሆኑን ለማረጋገጥ ይህንኑ ምስክር ወረቀት እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን ይህ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብትነት ማረጋገጫ መንገድ የግል ሃብት የሆነውን ንብረት የሚመለከት ነው፡፡ የግል ሀብት ያልሆነው እና ለህዝብ የሚያገለግል የማይንቀሣቀስ ንብረትን በተመለከተ ህጉ የተለየ ሁኔታን አስቀምጧል፡፡ ለህዝብ የሚያገለግል የማይንቀሣቀስ ንብረት፤ እሱን የሚመለከት ግዙፍ መብቶች ከሌሉበት በቀር፤ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ውስጥ መመዝገብ እንደማያስፈልገው የፍ/ህ/ቁ 1578 ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለሃብትነት ለማረጋገጥ የግድ መዝገብ የገባ የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲቀርብ ህጉ አያዝም፡፡ በሌላ አነጋገር እነዚህን ንብረቶችን በተመለከተ ባለሀብትነት በሌላ ሁኔታ ወይም ማስረጃ ሊረጋገጥ ይችላል ማለት ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስናመራ ቤቶቹ የቤተክርስትያኗ በመሆናቸው ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ እንጂ የግል ሃብት ስላልሆኑ የንብረቶቹ ባለሃብትነት የግድ በባለቤትነት የምስክር ወረቀት መረጋገጥ የለበትም፡፡ በመሆኑም በሚቀርቡ ሌሎች ማስረጃዎች ታይቶ ሊወሠን ይችላል፡፡ በዚህ ጉዳይም ቢሆን መዝገቡ እንደሚያስረዳው ቀበሌው ራሱ በሠጠው መልስ በማዕከላዊ መንግስት ቤቱ ለአመልካች እንዲመለስ መታዘዙንና የጅጅጋ ማዘጋጃ ቤትም ቤቱን ለአመልካች አንዲያስረክብ ያዘዘ መሆኑን ገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ችሎት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የመንግስት አካላት ከፃፉት ደብዳቤ ቤቱ ለአመልካች የተመለሠ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለህዝብ አገልግሎት የሚውል እንጂ የግል ሃብት ባለመሆኑ ቤ/ክርስትያኗ ባለቤትነትን ለማረጋገጥ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት አንድታቀርብ ስለማትገደድ የሥር ፍ/ቤቶች የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አልቀረበም በማለት የሠጡት ውሣኔ የህግ ስህተት አለበት፡፡

ው ሣ ኔ

1) የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰኔ 09 ቀን 1996 ዓ.ም. የሠጠው ውሣኔና የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05/1/134/96 በጥቅምት 12 ቀን 1998 ዓ.ም. የሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2) ክርክር የቀረበበትን 6 ክፍል ቤት ተጠሪዎች ለአመልካች ያስረክቡ፡፡
3) የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ መሠረት እንዲያስፈፅም የዚህ ትዕዛዝ ግልባጭ ይድረሠው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 22719

ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የአ/አ/ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተተኪ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለሥልጣን አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ነጋሽ ዱባለ - ጠበቃ አቶ መኮንን ኪዳኔ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ መ/ቁ 35928 ላይ ታህሳስ 5 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናቱ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት አለበት እና እንዲታረም ሲል አመልካች ጥር 15 ቀን 1998 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

በአቤቱታው መሠረት ሰበር ችሎት መዝገቡን ከመረመረ በኃላ የተሰረዘው የቤት ባለቤትነት ደብተር እና ካርታ ተፈፃሚነት እንዲቀጥል ሲል የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ተጠሪ እንዲቀርብ አዞ/አዝዞ ግራ ቀኙ ክርክርራቸውን አሰምተዋል፡፡ የሰበር ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ መዝገቡን ከሥር ፍ/ቤት ክርክርና ውሳኔ አንፃር አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

የጉዳዩ መነሻ በአጭሩ ሲታይ በወረዳ 17 ቀበሌ 20 የሚገኙ በቁጥር 1304፣1305 እና 1306 ቤቶች በካርታ ቁጥር 32221 እና በቤት ባለቤትነት ደብተር ቁጥር 17/3/91 ማረጋገጫ መሠረት የተጠሪ መሆናቸው ተረጋግጦ በፍ/መ/ቁ. 503/88 እና በአፈጻጸም መ/ቁ 90/92 ተጠሪ እንዲረከብ ከተደረገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኋላ አመልካች እና የመ/ቤቱ የሥራ ሐላፊዎች / በሥር ፍ/ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች/ ይህንን የባለቤትነት ማረጋገጫ እንዲመክን በማድረጋቸወ ለዚህ ሕገወጥ ተግባራቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ እና የሰነዶቹ ትክክለኛነት ተረጋግጦ ካርታ እና ደብተሩ ተዘጋጅቶ ለተጠሪ /ለሥር ከሳሽ/ አንዲሰጥ ይወሰንልኝ ሲል ባቀረበው ክስ የሥር ፍ/ቤት ከአከራከና የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካች ድርጊት ሕገወጥ ነው በማለት የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶቹ ተፈፃሚነት እንዲቀጥል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ውሳኔ እና ለሰበር ከቀረበው ክርክር አንፃር በመሠረታዊነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ የተጠሪ /የሥር ከሳሽ/ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች በአስተዳደር አካል ከተሰረዘ ክስ ለማቅረብ የክስ ምክንያት አለን? የሚለውን የሕግ ጥያቄ አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ በመሠረቱ አመልካች መሥሪያ ቤት የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የመስጠትም ሆነ የመሰረዝ መብት በሕግ ተሰጥቶታል፡፡ ተጠሪም በሥር ፍ/ቤት እንዳረጋገጠው በቤት ቁጥር 1304፣1305 እና 1306 ላይ የተሰጠው የካርታ ቁጥር 32221 እና የቤት ባለቤትነት ደብተር ቁጥር 17/3/91 ተሰርዟል፡፡ ይህንን ያደረገው አካል በሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ሃላፊነት መሆኑ እንደተመለከተ ሆኖ ይህ አካል በሥልጣኑ በወሰነው ጉዳይ ጉድለት ካለበት መታረም የሚችለው የሥልጣን ተዋረዱን ጠብቆ ባለው የአስተዳደር አካል መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ የአሁን ተጠሪ በፍ/ቤት ክስ ለማቅረብ በመጀመሪያ በሕጉ አግባብ መሠረት ለክርክሩ መነሻ ወይም መሠረት በሆነው ሀብት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ይህ መብት ወይም ጥቅም ሊረጋገጥ የሚችለውም በምኞት ወይም በፍላጐት ብቻ ሳይሆን በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን አረጋጋጭ ማስረጃ በማቅረብ መሆን እንዳለበት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 33/2/ መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ይህ የሕግ ክርክር በሥር ፍ/ቤት የተነሳ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት አፅንኦት ሰጥቶት አልተመለከተውም፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ ላይ አመልካች የተጠሪን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች ከሰረዘ ተጠሪ አስቀድሞ በተጠቀሱት ቤቶች ላይ ባለመብት መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በእጁ ማስገባት ይኖርበታል፡፡ ይህ መሠረታዊ ማረጋገጫ ሰነድ ወይም ማስረጃ ሳይኖረው ፍ/ቤት ሰነድ እንዲሰጠው እንዲወሰንለት መጠየቅ አይቻልም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ መብትና ጥቅም የሚረጋገጠው የአስተዳደር አካላት በሚሰጡት የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች እንደሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1195/1/ ተመልክቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ አካል የተረጋገጠ ማስረጃ ሳይኖረው ለክርክሩ መነሻ በሆኑ ቤቶች ላይ መብት እንዳለው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳያቀርብ ክስ ማቅረቡ በሕግ ተቀባይነት የለውም፡፡

ስለዚህ የተጠሪ ክስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 33/2/ የተመለከተውን አሟልቶ ያልቀረበ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንን ወደ ጐን በመተው ወደ ጉዳዩ ገብተው በማከራከር አመልካች ለተጠሪ ሰጥቶ የነበረውን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች መሰረዙ አግባብ ስላልሆነ የሰነዶቹ ተፈፃሚነት እንዲቀጥል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 30467 ጥቅምት 25 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.35928 ታህሳስ 5 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ የዚህን ችሎት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዘገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 23608

ጎንደር 3 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ

ኤጂንሲ ነ/ፈጁ መስፍን በሻህ

ተጠሪ፡- የአቶ ኑር በዛ ተረጋ ወራሾች

ጠበቃ ስንታየሁ ባህሩ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የአሁን ተጠሪዎች አውራሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻነት ሲሆን የክሱም ይዘት ባጭሩ በወረዳ 18 ቀበሌ 34 ክልል ቁጥራቸው ከ001 -007 የሆኑት ቤቶች ያለአግባብ በመንግሥት የተወሰዱ መሆናቸው ታምኖበት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በኩል እንዲመለስልኝ ተወስኖ በዚሁ ውሣኔ መሠረት ቤቶቹን እንድረከብ ታህሣሥ 3 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ለከተሣሽ (ለአሁን አመልካች) አመልክቼ እንዳለሁ በጎንደር ወር 1991 ዓ.ም አካባቢ በቤቶቹ ውስጥ የነበሩት ተከራዮችን ሲለቁ ከሣሽ ቤቶችን የተረከብኩኝ ቢሆንም ያቀረብኩት አቤቱታ አስቀድሞ ቤቶቹ ሊመለሱልኝ እንደሚገባ ታምኖበት በተሰነልኝ መሠረት እንዲመለሱልኝ የሚል ሆኖ ሳለ አቤቱታዬን በትክክል ባለመረዳት ለቤቶቹ የቤት ባለቤትነት መብት እንዲሰጠኝ እንዳመለከትኩኝ ቆጥሮ የሚመለሱት ቤቶች በሙሉ ሣይሆን በከፊል ብቻ ነው በማለት በመወሰኑ ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ ይግባኝ ያቀረብኩ

ቢሆንም ቦርዱ የኤጀንሲውን ውሣኔ በመሻር መዝገቡን የዘጋ ስለሆነ የኤጀንሲውም ሆነ የቦርዱ ውሣኔ ከሥልጣናቸው ውጭ ስለሆነ በፍርድ ሊሰረዝልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

የከሣሽ ክስና ማስረጃ ለተከሣሽ (ለአሁን አመልካች) ደርሶ በሰጠው መልስ ከሣሽ በክስ አቤቱታቸው በጠቀሷቸው ቤቶች ትርፍነታቸው ተረጋግጦ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የተወረሱ ንብረቶች ናቸው በመሆኑም በመጀመሪያ የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅ በመቀጠልም የኤጀንሲው ሥራ አመራር ቦርድ ይህን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን እንደሌለው በማለጽ የመጨረሻ ውሣኔ በመስጠት መዝገቡ እንዲዘጋ ወስኗል፡፡ በአዋጁ ቁጥር 110/87 መሠረት ተከሣሽ የሚሰጣቸውን ውሣኔዎች በፍ/ቤት እንደገና ሊታዩ /Review/ እንደሚችሉ የተደነገገ ድንጋጌ ስለሌለ ፍ/ቤቱ ይህንን አቤቱታ ተቀብሎ የማየት ሥልጣን የለውም፡፡ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም ሙሉ መልስ በመስጠት ክሱ ከበቂ ኪሣራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ በተከሣሽ በኩል የፍ/ቤቱን ሥልጣን አስመልክቶ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ አ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት በአንቀጽ 79(1) ላይ የዳኝነት ሥልጣን የፍ/ቤቶች ብቻ እንደሆነ በአንቀጽ 37(1) ላይ ደግሞ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ (Justicable matter) ለፍ/ቤት የማቅረብና ውሣኔ የማግኘት መብት አለው የተደነገገ ከመሆኑም በላይ በአስተዳደር አካላት የተሰጡ ውሣኔዎችን ፍ/ቤቶች እንደገና ለማየት ተፈጥሯዊ /inherent/ የሆነ ሥልጣን ያላቸው ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ተብሎ በተከሣሽ በኩል የቀረበው መቃወሚያ በአግባቡ የቀረበ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ግራ ቀኙ ያደረጉትን ክርክር መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀጽ 4(1) እና አንቀጽ 3(2) መሠረትና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ቁጥር 001/88 አንቀጽ 3(1) እና (2) መሠረት ከአዋጁ ቁጥር 47/67 ውጭ የተወሰዱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረቶች ይመለሱልኝ የሚሉ አቤቱታዎችን እንደዚሁም ከአዋጅ ውጭ በተወረሰ ንብረት ላይ አዋጅ ቁጥር 110/87 ከመጽናቱ በፊት በሌላ አካል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠ ቢሆንም ይህ ውሣኔ እንደገና እንዲመረመር አቤቱታ ሲቀርብ ኤጂንሲው ከዚያም ቦርዱ የማየት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሆኖም በአዋጁና በመመሪያው መሠረት ከእነርሱ በፊት ሌላ የአስተዳደር ባለሥልጣን ከአዋጁ ወጭ የተወረሱ ናቸው የተባሉ ንብረቶች ላይ የሰጠውን የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ ኤጀንሲውም ሆነ ቦርዱ በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉት አቤቱታ ሲቀርብላቸው እንጂ በገዛ ፈቃዳቸውና በእራሣቸው ጊዜ አይደለም በማለት በውሣኔው ላይ አስፍሮ፤ በተያዘው ጉዳይ የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅና የሥራ አመራር ቦርድ ከላይ የተጠቀሱትን የአዋጁንና የመመሪያውን ድንጋጌዎች ጥሰው ከሥልጣናቸው በማለፍ ከሣሽ ቤቶቹን ለመረከብ በተወሰነልኝ መሠረት ርክክቡ ይፈፀምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ያለአግባብ የተወረሱ ቤቶች ይመለስልኝ በማለት አዲስ አቤቱታ ያቀረቡ በማስመሰል ውሣኔ የሰጡ ስለሆነ የኤጂንሲው ሥ/አስኪያጅም ሆነ ቦርዱ ከሥልጣናቸው ውጭ ውሣኔ ስለሰጡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2121 ??መሠረት ተሰርሧል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን አስመልክቶ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሣይቀበለው የቀረው በአግባቡ እንደሆነና በዚህ ረገድ የቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ነው ካለ በኋላ በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድም ኤጀንሲውም ሆነ የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የሰጡት ውሣኔ ከአዋጁም ሆነ ከመመሪያው አኳያ ሲታይ ከሥልጣናቸው ውጭ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔው ሊሰረዝ እንደሚገባ የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ እንዳልሆነ ነገር ግን የኤጂንሲው ሥራ አስኪያጁ ውሣኔ በቦርዱ ተሽሮ ባለበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ በድጋሚ የኤጀንሲውን

ሥራ አስኪያጅ ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ አይደለም በማለት በዚህ መልኩ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻል አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የፕራይቬታይዜሽን ኤጂንሲ የሰጠው ውሣኔ እንደገና ለማየት ፍ/ቤቶች ተፈጥሯዊ /inherent/ ስልጣን አላቸው በማለት ኤጀንሲው የሰጠውን ውሣኔ የሥር ፍ/ቤቶች በድጋሚ አይተው ውሣኔ መስጠታቸው አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባ በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታውም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የተጠሪዎች አውራሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት /Relief/ ኤጂንሲውም ሆነ ቦርዱ የቀረበላቸው አቤቱታ ከአዋጁ ውጭ የተወሰደ ቤት እንዲመለስልኝ ይወሰንልኝ የሚል ባልሆነበት ሁኔታ ከተጠየቀው ውጭ ሌላ ጭብጥ በመያዝ ውሣኔ የሰጡ ስለሆነ ይሄው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ነው፡፡

ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰዱ ንብረቶች በወጣው አዋጁ ቁጥር 110/87 አንቀጽ 4(1) እና (2) መሠረት ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን የባለቤትነት ሁኔታ የማጣራትና የማሰወሰን ሥልጣን ለአመልካች የተሰጠ ሲሆን የባለቤትነትን ጥያቄ በሚመለከት ኤጀንሲው በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታውን ለኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ ማቅረብ እንደሚችል በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 5/3/ ላይ ተመልክቷል፡፡

በእርግጥ የተጠሪዎች አውራሽ ታህሣሥ 3 ቀን 1988 ዓ.ም ለአመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ከአወጁ ውጭ የተወሰዱ ስለሆነ ይመለስልኝ በማለት ሣይሆን የቤቶቹ ባለቤትነቱ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ዓማካይነት ተረጋግጦ ተወስኖልኝ ርክክቡ የዘገየ ስለሆነ ቤቶቹን እንድረከብ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪዎች አውራሽ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች እንዲመለሱልኝ በሌላ አካል ተወስኖልኛል የሚሉ ከሆነ ቀድሞውንም ቢሆን ቤቶቹን ለመረከብ አቤቱታ ማቅረብ የነበረባቸው ለፍ/ቤት እንጂ ለኤጀንሲው አልነበረም፡፡

በሌላ በኩልም ለኤጀንሲው የቀረበው አቤቱታ ይዘቱ ምንም እንኳን የቤቶቹን ርክክብ የሚመለከት ቢሆንም ኤጀንሲው የተቋቋመው ከአዋጁ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን የባለቤትነት ሁኔታ አጣርቶ ለመወሰን እስከሆነ ድረስ የእነዚህንም ቤቶች የባለቤትነት ሁኔታ ከአዋጁ አኳያ መርምሮ ውሣኔ ቢሰጥ ከሥልጣኑ ውጭ በማለፍ ውሣኔ ሰጥቷል ወደሚል ድምዳሜ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ይልቁንም ኤጀንሲው የተቋቋመበትን አ/ቁ/110/87 ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ቁጥር 001/88 መሠረት ከአዋጅ ቁ. 110/87 መውጣት በፊት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 ውጭ በተወሰደ ንብረት ላይ በሌላ አስተዳደራዊ አካል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ ተሰጥቶ ባለበት ሁኔታም የውሣኔው አግባብነት እንዲመረመር አቤቱታ ሲቀርብ ኤጀንሲውም ሆነ ቦርዱ መርምረው ውሣኔ መስጠት እንደሚችሉ የተመለከተ እንደመሆኑ መጠን የተጠሪዎች አውራሽ በዚህ መልኩ ያቀረቡትን አቤቱታ ኤጀንሲውም ሆነ ቦርዱ መርምረው ውሣኔ መስጠታቸው ከስልጣናቸው ውጭ ነው ሊባል አይችልም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 37/1/ ላይ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡

ከዚህ የሕገመንግሥቱ ድንጋጌ በግልጽ መገንዘብ የሚችለው ፍ/ቤቶች አንድን አቤቱታ ተቀብለው ውሣኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉደይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ ነው፡፡

የተያዘውም ጉዳይ በተጠቀሰው አ/ቁጥር 110/87 መሠረት የዳኝነት ሥልጣኑ በግልጽ ለሌላ አካል ማለትም ለአመልካች የተሰጠ ስለሆነና ኤጀንሲውም በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን ለኤጀንሲው የሥራ

አመራር ቦርድ ማቅረብ እንደሚችልና የቦርዱም ውሣኔ የመጨረሻና አሰሪ /Final and binding/ እንደሆነ በአዋጁ ላይ ስለተመለከተ አቤቱታው ይህንን ሥርዓት ካለፈ በኋላ በኤጀንሲውም ሆነ በቦርዱ የተሰጠው ውሣኔ ከሥልጣን ውጭ ስለሆነ ውሣኔው ሊሰረዝ ይገባል የሚለው የተጠሪዎች አቤቱታ በአንድ በኩል በዚህ መልኩ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ቤት በድጋሚ ለማየት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ /legal frame work/ በሌለበት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ በሌላም በኩል የፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በእኛ አገር ሁኔታ ከሕግ የመነጨ እንጂ ተፈጥሯዊ /inherent/ ባልሆነበት ሁኔታ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የፍ/ቤቱን ሥልጣን አስመልክቶ በቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተመስርቶ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት መመለስ ሲገባው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሣያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 48/93 በመጋቢት 16 ቀን 1994 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 13021 በታህሣሥ 5 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/ለ/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት አቤቱታ የፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 24269

ጎዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ታረቀኝ ሞላ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ተክለማርያም መኮንን ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ ባቀረበው የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ ላይ የተመሠረተ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመመበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ የከሰሰው አዳነ ገብሩ እና ወ/ሮ ፈትለወርቅ ጌታቸው የተባሉትን ሰዎች ሲሆን፣ አመልካች ክርክሩ ውስጥ የገባው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት ላይ የተነሣው ጥያቄ ይመለከተዋል ስለተባለ ጣልቃ እንዲገባ ታዞ ነው፡፡ ተጠሪው ክስ የመሠረተውም በወረዳ 17 ቀበሌ 15 ክልል የሚገኝ ቁጥር 367/ለ/ የሆነው ቤት የግል ንብረቱ ሲሆን አዳነ ገብሩ በተባለው ተከሣሽ በውል አከራይቼው ሲጠቀምበት ቆይቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከኔ ፈቃድ ውጪ ለወ/ሮ ፈትለወርቅ ጌታቸው አከራይቶታል፡፡ ስለዚህ ተከሣሾች ኪራዩን እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስረክቡኝ ሊወስንልኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱም ከተከሣሾች እና ከጣልቃ ገቡ የቀረቡትን የመከራከሪያ ነጥቦች ከሰማ በኋላ፣ 1ኛ ተከሣሽ እና ጣልቃ ገቡ ቤቱን ለከሣሽ ያስረክቡ፣ ከመስከረም ወር 1993 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የኪራይ ገንዘብም በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ሲል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ከአሁኑ አመልካች ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት

የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡

የሰበር ችሎቱ አመልካች ሚያዝያ 4 ቀን 1998 ዓ.ም. በዓፈው ማመልከቻ የቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት የሠራው ባልተፈቀደለት የከተማ ቦታ ላይ ነው እየተባለ ቤቱን ሊረከብ ይገባል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ ቤቱን ሠርቻለሁ በሚል ለሌላ ሰው በውል አከራይቶ ከመገኘቱ በቀር በቦታው ላይ ቤት እንዲሠራ አግባብ ካለው ባለስልጣን የተፈቀደለት ወይም በቦታው የመጠቀም መብት ያገኘ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የሰጡት ማስረጃ አግኝተናል በማለት ሳይሆን፣ አመልካች ቤቱ ያረፈበት የከተማ ቦታ ለመወረሱ /የመንግሥት ንብረት ለመሆኑ/ ማስረጃ አላቀረበም የሚል ምክንያት በመስጠት እና ቤቱ በሕገ ወጥ መንገድ የተሠራ ነው ከተባለም የሚመለከተውና ሥልጣን ያለው አካል ነው ተገቢውን እርምጃ የሚወስደው የሚል ትችት በማከል ብቻ ነው፡፡

ለሁሉም ግልጽ እንደሆነው የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ. 47/67 ከታወጀ ወዲህ የከተማ ቦታ የመንግሥት ሃብት ሆኖአል፡፡ ይህ ማለት በግል የሚያዝ የከተማ ቦታ የለም ማለት ነው፡፡ ግለሰቦች በከተማ ቦታ የመጠቀም /የመያዝ/ መብት የሚኖራቸው አግባብ ባለው የመንግሥት አካል /ባለስልጣን/ ሲሰጣቸው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የምናየው ግን ተጠሪ በቦታው ላይ ይጠቀም ዘንድ /ቤቱን እንዲሠራ/ ሳይፈቀድለት ነው ቤት ሠርቼ አከራየሁ የሚል ክርክር ያቀረበው፡፡ የከተማ ቤት አሠራርና አጠቃቀምን በተመለከተ በወጣው አዋጅ ቁ. 292/78 በአንቀጽ 7/1/ እንደተደነገገው ከሚመለከተው ባለስልጣን ፈቃድ ሳይኖር የተሠራ የከተማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ሕጋዊነት አይኖረውም፡፡ ቤቱ እንዲወረስ ወይም እንዲፈርስ እንደሚደረግም ሕጉ ያመለክታል፡፡ ከዚህ አንፃር የተጠሪ ክርክር ሲታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም እነዚህን ሁኔታዎች እና ሕጉን ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20911 ታህሣሥ 22 ቀን 97 ዓ.ም. የሰጠው እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37803 መጋቢት 13 ቀን 98 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበው የቤት ልረከብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 26130

የካቲት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ገ/እግዚአብሔር ከበደው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ት ሠላዊት ወ/ገብርኤል - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ክርክር የተጀመረው በትግራይ ክልል በመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ የሚች እናቴ ወ/ሮ ድንቅነሽ ድምጹ ወራሽ ስሆን በአውራሽ ስም የተመዘገበውንና በመቀሌ ከተማ የሚገኘውን 10 ክፍል ቤት እኔ በማላውቀው ሁኔታ ተከሣሽ ይዞ በማከራየት ላይ ስለሚገኝ የ13 ወር የቤት ኪራይ በጠቅላላው ብር 35,000 /ሠላሳ አምስት ሺህ/ በመክፈል ቤቱን እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሽም ቀርበው ለክሱ በሰጡት መልስ ከሳሽ የሚች ወ/ሮ ድንቅነሽ ድምጹ ልጅ መሆኗን እንደማይክዱ ነገር ግን ከሚች ጋር በ1977 ዓ.ም. ተጋብተን አብረን ስንኖር ልጆች የወለድን ከመሆኑም በላይ ክስ የቀረበበትንም ቤት አብረን ሠርተናል፡፡ የሚያከራክረው ቤትና ቦታ ግማሹ የራሴ ሲሆን ግማሹ ደግሞ የሚች ወ/ሮ ድንቅነሽ ድምጹ ስለሆነ ከሣሽ ከሌሎች ወራሾች ጋር በመሆን ድርሻዋን ብትካፈል አልቃወምም ብለው የቤት ኪራይን በተመለከተ ቤቱ በወር ብር 2000 /ሁለት ሺህ/ ይከራይ እንደነበረ አምነው ነገር ግን ከሰኔ 29 ቀን 1995 ዓ.ም. እስከ ሕዳር 1997 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ሚች በሕይወት እያለች በጋራ የተጠቀምንበት ሲሆን ቀሪውንም ከከሳሽ ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጋራ ስለተጠቀምንበት ክሱ ያለአግባብ ስለቀረበ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ክስ ከቀረበበት ቤት መካከል 5 ክፍል ቤት የከሳሽ እናትና ተከሣሽ በ1977 ዓ.ም. ከተጋቡ በኋላ በ1994 ዓ.ም. የተሰራ መሆኑ ስለተረጋገጠ ግማሹ የተከሳሽ ሆኖ ግማሹ ደግሞ ከሳሽን ጨምሮ ወራሾች እንዲካፈሉት ቀሪው 4 ክፍል ቤት ደግሞ ከመጋባታቸው በፊት መሠራቱ ማስረጃ ስለተረጋገጠ ከሣሽና ሌሎች የሟች ወራሾች እንዲከፋፈሉት በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

እንደዚሁም ቤቱ ያረፈበትን የቦታ ይዞታ በተመለከተ የቦታው ስፋት በማዘጋጃ ቤት ደንብ መሠረት ለሁለት ለማካፈል የሚቻል ከሆነ ግማሹን ከሳሽና ሌሎች ወራሾች እንዲወሰዱ ቀሪውን ግማሽ ደግሞ ተከሣሽ እንዲወሰዱ የማዘጋጃ ቤት ደንብ ቦታውን ለሁለት ለማካፈል የማይቻል ከሆነም ቤቱና ቦታው ተሸጦ ከላይ በተመለከተው ዓይነት ወራሾችና ተከሣሽ እንዲከፋፈሉ በማለት በአብላጫ ድምጽ ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

የአነስተኛው ድምጽ ደግሞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተሰራበት ቦታ የከሳሽ እናት ወ/ሮ ድንቅነሽ ድምጹ ተከሣሽን ከማግባቸው በፊት የነበራቸው ይዞታ ስለሆነ ተከሳሽ መብት የሚኖራቸው በዚህ ቦታ ላይ ከጋብቻ በኋላ ለተሠራዉ ቤት ግማሹን በተመለከተ ስለሆነ የዚህን ቤት ግምት ይዞ እንዲሄድ ከሚወሰን በስተቀር ከጋብቻ በፊት የከሳሽ እናት ባረጋገጡት ቦታና ቤት ላይ መብት ሊኖረው አይገባም የሚል ነው፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ በአብላጫ ድምጽ የተሰጠውን የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር የአነስተኛውን ድምጽ አጽንቷል፡፡

አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ችሎቱ አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤትና የቦታ ይዞታን ክፍፍል አስመልክቶ በትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታውም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተሰራበትን ቦታ የተጠሪ እናት ወ/ሮ ድንቅነሽ ድምጹ ከአመልካች ጋር ከመጋባታቸው በፊት ይዘውት እንደነበር በዚሁ ቦታም ላይ አመልካችን ከማግባታቸው በፊት 5 ክፍል ቤት ሠርተው እንደነበር ቀሪው 4 ክፍል ቤት ደግሞ ከአመልካች ጋር ከተጋቡ በኋላ እንደተሰራ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩልም በፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግም ሆነ በአዋጅ ቁጥር 33/91 በታወጀው የትግራይ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 85 መሠረት ከጋብቻ በፊት የነበረ የባልና ሚስት ንብረት የግል ንብረት እንደሚሆን የተመለከተ ቢሆንም የከተማ ቦታን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የከተማ ቦታ በግል ባለቤትነት ሊያዝ እንደማይችል ከመደንገጉም በላይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 40/3/ ላይ መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ንብረት እንደሆነ ስለተደነገገ ግለሰቦች በመሬት ላይ የይዞታ መብት እንጂ የባለቤትነት መብት ሊኖራቸው ስለማይችል የተጠሪ እናት ቤቱ በተሰራበት ቦታ ላይ አመልካችን ከማግባታቸው በፊት የነበራቸው የይዞታ መብትም ቢሆን ከተጠሪ ጋር ከተጋቡ በኋላ በነበራቸው የቦታ ይዞታ ላይ ተጨማሪ ቤት እንዲሰራ በፈቀዱት መሠረት አራት ክፍል ተጨማሪ ቤት በጋራ ስለመስራታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ ጋብቻው በሞት ምክንያት ሲፈርስ አመልካች ከሚደርሳቸው ቤት በተጨማሪ በቦታው ላይ የይዞታ መብትም የሚገባቸው በመሆኑ በዚሁ መሠረትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቦታውን ወራሾችና አመልካች በማዘጋጃ ቤት ደንብ መሠረት እኩል ለመካፈል የሚችሉ ከሆነ እኩል እንዲካፈሉት እኩል ለማካፈል ካልተቻለም ተሸጦ ገንዘቡን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውሣኔው መሠረት እንዲካፈሉ በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ውሣኔ በመሻር በጋብቻ ጊዜ የተሰራውን ቤት የግማሹን የዋጋ ግምት አመልካች ሊወስድ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ካለመሆኑም በላይ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14635 በግንቦት 25 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11460 በጎንደር 30 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የመቀሌ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1498 በሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ.ም. በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕግ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ.ቁ. 27506

ሐምሌ 19 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

አብዱልቃድር መሐመድ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- እነ ሣሙኤል ውብሸት - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ብዙነህ በላይነህ - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀረብ የቻለው አመልካቾች ተጠሪ በይዞታችን ላይ የፈጠረው ሁከት ይወገድልን የሚል አቤቱታ ለጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ የፈጠረው ሁከት ሊወገድ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቶ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በመሻር ሁከት የለም በማለት ውሣኔ በመስጠቱ አመልካቾች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀረብ በተሰጠው ትእዛዝ ተጠሪ የአመልካቾች አቤቱታ ደርሷቸው መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካቾችም የመልስ መልስ በመስጠት አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካቾች በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኝና የምንኖርበት ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶ ቀበሌው የሚያስተዳድረውና ላለፉት 20 ዓመታት በተከራይነት ኖረንበታል፡፡ ይሁን እንጂ ተከሣሽ ይዜው ቤት የአውራሼ የሚች ወ/ሮ ተዋበች ዘርፉ ነው በማለት እኛ በሌለንበት ይህንኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከቀበሌው አስተዳደር በኪራይ የያዝነውን ቤት እየተገለገለበት ሰለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም በበኩሉ በሰጠው መልስ ለክሱ መነሻ ምክንያት የሆነው ቤት ከአክስቱ በውርስ የተላለፈለት ንብረት መሆኑን በመግለጽ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች የጅጅጋ ከተማ አስተዳደር መሆናቸውን ከሣሾችም በእነዚሁ ቤቶች በሕጋዊ መንገድ እየኖሩ እንደሆነ ከቀረበው ማስረጃ ማረጋገጥ የተቻለ ስለሆነ በተከሣሽ በኩል የተፈጠረው ሁከት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1149(3) መሠረት እንዲወገድ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ክርክሩን በይግባኝ የተመለከተውም የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች በአዋጅ ያልተወረሱ ስለመሆናቸው የሚመለከተው የቀበሌ አስተዳደር ያረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ይግባኝ ባይ (ተጠሪ) የቤቱ ባለንብረት የነበሩት ግለሰብ ወራሽ መሆናቸው ባቀረቡት ማስረጃ ስለተረጋገጠ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ በኩል የተፈጠረው ሁከት ሊወገድ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ ከጭብጡ ያፈነገጠ ነው በማለት ሽሯል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም አቤቱታው ለሰበር ቀረቦ መታየት አለበት በማለት ትእዛዝ የሰጠው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የቀበሌው አስተዳደር እያከራየ ገቢ ይሰበስብ ነበር ከተባለ በአዋጅ አልተወረሰም በሚል የተጠሪ የውርስ ሀብት ነው የመባሉን አግባብነት ለማጣራት ሲሆን ከዚሁ አኳያም አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካቾች በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረቱት ከጅጅጋ ከተማ ቀበሌ አስተዳደር በተከራይነት የምንኖርበትን ቤት ተጠሪ ወራሽ ነኝ በማለት ያለአግባብ ይዘው የሚገኙ ስለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልን በማለት ነው፡፡

ሁከት ይወገድልኝ የሚል አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን በንብረቱ ላይ የይዞታ መብት እንዳለውና በእርግጥም የሚያዝበት መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/1140 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ሁከት ተፈጥሮብናል የሚሉበትን ቤት በኪራይ ውል መነሻነት ይዘው እንደሚገኙና የይዞታ መብት እንዳላቸው በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ በማስረጃ አረጋግጠዋል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ሁከት ይወገድልን የሚል ከሆነ ክርክሩ የይዞታ መብትን /possessory action/ የሚመለከት በመሆኑ በጭብጥ ተይዞ ዕልባት ሊሰጠው የሚገባው ነጥብ ሁከት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም የሚለው ነው፡፡

ይሁንና ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክርክር ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት በውርስ የተላለፈልኝ የግል ቤቴ ሰለሆነ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት እንጂ ሁከት አልፈጠርኩም በማለት አይደለም፡፡

ተጠሪ በባለቤትነት ረገድ የሚያነሱት ክርክር ሁከት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም ተብሎ ለሚያዘው ጭብጥ ተገቢነት የሌለውና እራሱን የቻለ ባለቤትነትን የመፋለም ክስ /petitory action/ በሚመለከተው ላይ አቅርበው ከሚታይ በስተቀር ሁከት እንዲወገድ በቀረበ ክስ የባለቤትነት ክርክር ማንሣት አግባብነት አይኖረውም፡፡ ስለሆነም የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በተጠሪ በኩል ባለቤትነትን የመፋለም ክስ ባልቀረበበትና አመልካቾች ሁከት ይወገድልን በማለት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ የቤቱ ባለቤት ናቸው በማለት ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 149/97 በየካቲት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. ተጠሪ በአመልካቾች ላይ የፈፀመው ሁከት ይወገድ በማለት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመ/ቁ. 05/1/91/99 በጎዳር 2 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል። ይፃፍ።

2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ።

3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማየነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 27600
ታህሣሥ 8 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ሕብረት ባንክ አክሲዮን ማኅበር ነ/ፈጅ ንጉሴ ኪዳኔ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ጀማል መሐመድ - አልቀረበም።

2. ወ/ሮ ማይሙና ሼህ አብዱልሰመድ - አልቀረቡም።

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ የፈጠረው ሁከት ይወገድ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም ነው።

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ላይ ገንዘብ ስንበደር በካርታ ቁጥር 045/91 በተመዘገበና በ2500 ካሬ ሜትር ክልል ውስጥ የተሠራን መጋዘን ብቻ ለብድሩ አስፋፊል ዋስትና የሰጠን ሲሆን ከ2500 ካ.ሜትር ውጭ የተሠራና በዋስትና ያልተያዘ ቤት ጨምሮ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት አመልካች በሽያጭ ለ3ኛ ወገን በማስተላለፍ ላይ ስለሚገኝ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል።

ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ቀርቦ በሰጠው መልስ በዋስትና የተያዘው ይዞታ የማይነጣጠል መሆኑን፣ ውሉም መኖሪያ ቤትና መጋዘን በሚል እንዳልተከፋፈለ የተመዘገበውም ይዞታ 2500 ካ.ሜትር እንደሆነና የብድር ውሉ ሲፈረም መኖሪያ ቤቱ በጅምር እንደነበርና በኋላ የተሰራ ነው ቢባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንኳን የመያዣው አካል መሆኑ እንደማይቀር በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ለክሱ ምክንያት የሆነውና ሁከት ተፈጥሮበታል የተባለው ቤት የብድርና የመያዣ ውሉ ከተፈረመ በኋላ የተሰራ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ውሉም ሲፈረም ከሳሾች በካርታ ይዞታ ከነበራቸው 2500 ካ.ሜትር ቦታ በመጨመር በአሁኑ ጊዜ ይዞታቸው ወደ 3200 ካ.ሜ ከፍ ብሎ ቤቱም በተጨማሪ ባገኙት ቦታ ላይ ስለመሠራቱ የተረጋገጠ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3066 መሠረት ይሄው ቤት የመያዣው አካል ሊሆን ስለማይችል ተከሣሽ መያዣ ያላደረገውን ንብረት ሊሸጥ አይችልም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበል ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ሁከት ፈጥሯል? ወይንስ አልፈጠረም? የሚለው ነው፡፡

በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በተደረገው የብድርና የመያዣ ውል ለብድሩ አከፋፈል በአዳማ ከተማ ቀበሌ 16 ክልል በባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር 045/91 በተመዘገበው የሊዝ ይዞታ ላይ የሠፈረውን ንብረት 1ኛ ተጠሪ በዋስትና መስጠታቸውን ከውሉ በግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በውሉም ላይ መያዣው መጋዘንን ብቻ እንጂ ሌላ ንብረትን እንደማይመለከት አልተገለጸም፡፡

ተጠሪዎች አጥብቀው የሚከራከሩት በዋስትና የተያዘው መጋዘን አመልካች በዋስትና በያዘው 2500 ካ.ሜትር የቦታ ይዞታ ላይ የተሰራ ሲሆን ሁከት የተፈጠረበት ቤት ግን ከዚህ ይዞታ ክልል ውጭ በሚገኝ በቀሪው 800

ካ.ሜትር ይዞታችን ላይ የተሰራ ስለሆነና ይህ ይዞታ ደግሞ በመያዣው ውስጥ ያልተካተተ ስለሆነ ይህንን ቤት ጨምሮ አመልካች መሸጥ ስለማይችል ሁከቱ ሊወገድ ይገባል በማለት ነው፡፡

ይሁንና ግራ ቀኙ ባቋቋሙት የብድርና የመያዣ ውል ከላይ እንደተጠቀሰው መያዣው ተፈፃሚነት የሚኖረው በመጋዘኑ ላይ ብቻ እንደሆነ ካለመስማማታቸውም በላይ የአዳማ ከተማ ማዘጋጃ ቤትም ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፃፈው ደብዳቤ መጋዘኑም ሆነ መኖሪያ ቤቱ አመልካች ለዋስትና በያዘው በካርታ ቁጥር 045/91 ተመዝግቦ በሚገኘው 2500 ካ.ሜትር ቦታ ላይ እንደተሰራ አረጋጦ ከዚህ የካርታ ይዞታ ውጭ ተጨማሪ 784 ካ.ማትር ቦታ እንደሚገኝና ይህንኑ ቦታ በሊዝ ለማግኘት 1ኛ ተጠሪ ጠይቀው ተፈቅዶላቸው ነገር ግን ግብር ሳይከፍሉበት በአጥር ከልለውት እንደሚገኝ የገለጸ በመሆኑ ሁከት ተፈጥሮበታል የተባለው ቤት አመልካች ለዋስትና በያዘው የተጠሪዎች የካርታ ይዞታ ሥር እንደሚገኝ ተረጋግጧል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያዘም ይሄው ቤት የተሰራው የብድርና የመያዣ ውሉ ከተፈረመ በኋላ ነው ቢባል እንኳን ውሉ ሲፈረም በ2500 ካ.ሜትር ይዞታ ላይ የሰፈረን ንብረት እንደሚመለከት ስምምነት ላይ የተደረሰ ከሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3066 መሠረትም በመያዣ በተያዘ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በማሻሻልም ሆነ ሌሎች አዳዲስ የሚሠሩ ሥራዎችን መያዣው እንደሚያጠቃልልላቸው የተመለከተ ስለሆነ ይህም ቤት በመያዣው ውሉ የማይጠቃለልበት ምክንያት ስለሌለ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአንድ በኩል ቤቱ የተሰራው ተጠሪዎች አስቀድሞ ከነበራቸው የካርታ ይዞታ ውጭ ነው ማለቱ ከቀረበው ማስረጃ ጋር የማይጣጣም ከመሆኑም በላይ በሌላም በኩል ቤቱ የተሰራው ውሉ ከተፈረመ በኋላ ስለሆነ በመያዣ ውሉ አይጠቃለልም ማለቱ እርስ በርሱ የማይጣጣምና የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3066ን ያለአግባብ በመተርጎም የተሰጠ ውሣኔ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ መልኩ የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት ሳያርም የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04032 በመጋቢት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40698 በኀዳር 7 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ሁከት ተፈጥሮበታል የሚሉት ቤት አመልካች ለብድሩ አከፋፈል በዋስትና በያዘው በካርታ ቁጥር 045/91 ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ስለሆነ ይህንን ቤት ጨምሮ ለመሸጥ ስለሚችል ሁከት አልተፈጠረም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁጥር 29005

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡- 1. ግርማቸው ይላላ ቀረበ፡፡

2. አዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የግንባታ ፈቃድ እና ካርታ ይሰጠኝ በሚል 1ኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪው ክስ የመሠረተው በ2ኛው ተጠሪ ላይ ነበር፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በሁለቱ መካከል የተሰማውን ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ 2ኛ ተጠሪ የተጠየቀውን የግንባታ ፈቃድ እና ካርታ ለ1ኛ ተጠሪ ይስጥ በማለት ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የአሁኑ አመልካች ክርክሩ የእኔን መብት የሚነካ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 358 መሠረት መቃወሚያ ያቀረበው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን የተመለከተ ቢሆንም፤ በመጨረሻ ግን ተቃዋሚው /የአሁኑ አመልካች/ ተጠሪነቱ ለ2ኛ ተጠሪ በመሆኑ ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር ተካፋይ አልነበረም የሚባል አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 14 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ፣ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች በአቃቂ ክፍለ ከተማ ስር የተደራጀ አስፈፃሚ አካል ነው፡፡ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 10/2/ እንደተመለከተው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያሉት ክፍለ ከተሞች የየራሳቸው ምክር ቤት፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ቋሚ ኮሚቴ ኖሯቸው የተደራጁ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አካላት ናቸው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 30 እንደተደነገገውም ክፍለ ከተሞች ባልተማከለ የስልጣን ክፍፍል መርህ በተሰጠው የቦታ ክልል ማዘጋጃ ቤት በመሆንና ከከተማው ማዕከል ጋር በመቀናጀት ይሰራሉ፤ በሥራቸው የሚገኙትን ቀበሌዎችም ያስተዳድራሉ፡፡ በአጠቃላይ በአዋጁ አንቀጽ 10 በተመለከተው አይነት የከተማው አስተዳደር የስልጣን አካላት የተደራጁ ሲሆን፣ ከነዚህ አንዱ ክፍለ ከተማ ነው፡፡ ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ የሚቻለው እያንዳንዱ ክፍለ ከተማ የራሱ የሕግ ሰውነት ያለው እና በሕግ በተሰጠው የስልጣን ክልል ውስጥ በራሱ ኃላፊነት የሚንቀሳቀስ እንደሆነ ነው፡፡

በዚህ መዝገብ በሁለተኛ ተጠሪነት የተመዘገበው አካል ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ ክፍለ ከተሞች ካርታ እና የግንባታ ፈቃድ የመስጠት ስልጣንና ተግባር በቻርተሩ እና ቻርተሩን መሠረት በማድረግ በወጡት የከተማው አስተዳደር አዋጆች እንደተሰጣቸው አረጋግጦአል፡፡ በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካወጣቸው አዋጆች አንዱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍለ ከተማዎችና የቀበሌዎች አስተዳደር" ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁ. 1/95ን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁ. 18/97 ሲሆን፣ ይህ አዋጅ በክፍለ ከተማው ውስጥ ያለውን ቦታ የማስተዳደር ስልጣን የክፍለ ከተማው እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ቦታ ማስተዳደር ደግሞ ለአሁኑ ክርክር መነሻ

የሆነውንም እንደሚያጠቃልል በአዋጁ አንቀጽ 2 ተመልክቶአል፡፡ አመልካች በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር መነሻነት ውሣኔ የተሰጠበት ጉዳይ እኔን የሚመለከት ነው በማለት መቃወሚያ ያቀረበውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ነገሩን አጠቃለን ስንመለከተው አመልካች የራሱ የሆነ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይም በሱ የስልጣን ክልል ውስጥ የሚከናወን ነው፡፡ በመሆኑም አያገባህም የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች እነዚህን ሁኔታዎች ሳያገናዝቡ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48511 ሚያዝያ 11 ቀን 1998 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47682 ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ጉዳዩ እሱን በቀጥታ የሚመለከት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ያቀረበውን መቃወሚያ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተቀብሎ ክርክሩን በመስማት ይወስን ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 30101

ጎዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ገዛኸኝ አድነው ጠበቃ ደሴ ሙላት

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ዳሳሽ ባይነሳኝ /3 ሰዎች/ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ ጉዳይ ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የሌሎቹ ተጠሪዎች አባት የሆኑት አቶ አድነው አወቀ በልደታ ክ/ከተማ ቀበሌ 02 ክልል የቤት ቁጥር 560/ሀ/እና /ለ/ የሆኑ ቤቶች የነበራቸው ሲሆን ተከሣሽ የቤ/ቁ. 560/ለ/ የሆነውን ቤት በኃይል ገብቶ እየተጠቀመበት ስለሚገኝ ይህንኑ ቤት እንዲያስረክበን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም በሰጠው መልስ ክስ የቀረበበት የቤት ቁጥር 560/ለ/ እራሴ የሰራሁትና በስሜ የተመዘገበ ስለሆነ ክሱ ከኪሣራ ጋር ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሣሽ ለክሱ መነሻ ወደሆነው ቤት በኃይል እንዳልገባ ነገር ግን 1ኛ ተጠሪ ባለበት የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ አውራሽ የነበሩት አቶ አድነው አወቀ ፈቅደውለት ቤቱን ለመስራቱ መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1179 መሠረት ተጠሪዎች ቤቱ የተሠራበትን ዋጋ ከፍለው ቤቱን መረከብ ይችላሉ ካለ በኋላ ግምቱ መሰላት ያለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1180

በተደነገገው መሠረት መሆን ስለሚገባው ከዚሁ አኳያ የቤቱን ዋጋ ¼ኛ ከሳሾች ለተከሳሽ ከፍለው ቤቱን ይረከቡ በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ይግባኝ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኙን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ መጣራት እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ክስ የቀረበበትን ቤት ሊያስረክብ ይገባል? ወይንስ አይገባም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በፍ/ብሔር ሕጉ ስለ ንብረት በጠቅላላው በሚደነግገው ሶስተኛ መጽሐፍ ሥር በአንቀጽ 1178/1/ ባለመሬቱ በግልጽ እየተቃወመው ማንም ሰው በሌላ ሰው መሬት ላይ ሕንጻ የሠራ እንደሆነ በህንፃው ላይ አንዳችም መብት ሊኖረው እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን ባለመሬቱ ሳይቃወም በመሬቱ ላይ ሕንፃ የሠራ ሰው የዚሁ ሕንጻ ባለሀብት ሊሆን እንደሚችል ቀጥሎ በሚገኘው በቁጥር 1179/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜም ባለመሬቱ ከባለ ሕንፃው ጋር የተስማሙበትን ግምት በመክፈል ወይም በግምቱ ያልተስማማ እንደሆነ በቁጥር 1180 በተመለከተው መሠረት የሕንፃውን ግምት በመክፈል ሕንፃውን ማስለቀቅ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

ሕጉም በዚህ መልኩ የተቀረጸ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ አባትና አውራሽ የሆኑት አቶ አድነው አወቀ በነበራቸው መሬት ላይ አመልካች ቤት እንዲሰሩ ፈቅደውላቸው ቤቱን የሰሩ መሆኑን የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡

ከላይ በተቀጠሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1179/2/ መሠረት በሌላ ሰው መሬት ላይ ቤት /ሕንፃ/ የሰራ ሰው የሕንፃውን ግምት ተቀብሎ ሕንፃውን ለባለመሬቱ ለማስረከብ የሚገደደው ባለመሬቱ ሳይቃወም ሕንፃውን የሰራ በሚሆንበት ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የሰራው የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የቀሪዎቹ ተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት ሟች አቶ አድነው አወቀ ሳይቃወሙ በቀሩበት ሁኔታ ሳይሆን ይልቁንም ፈቃዳቸውን ሠጥተዋል በተባለበት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ ሕጉ በወጣበት ዘመን ግለሰቦች በመሬት ባለቤትነት ረገድ መብት የነበራቸው ቢሆንም አሁን ባለው ሁኔታ ደግሞ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት መሬት በግል ባለቤትነት መያዙ ቀርቶ የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት እንዲሆን የተደረገ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች የመሬቱ ባለቤት ስለሆኑ አመልካች በመሬቱ ላይ የሰራውን ቤት የዋጋ ግምቱን ¼ኛ ከተጠሪዎች ተቀብለው ቤቱን ያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሣኔ በዚህ ረገድ ከነበረው ሕግም ሆነ ከሕገ መንግሥታችን ጋር የተጣጣመ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05950 በሕዳር 9 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 43119 በሕዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ለተጠሪዎች ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 30461

ህዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሂሩት መለሰ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ነ/ፈጁ መስፍን ታዬ

ተጠሪ፡- አቶ ኢሳ መሐመድ ጠበቃ ከፍያለው በላቸው

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ በአመልካችና በሥር 2ኛ ተከሳሽ ላይ በኢሉባቦራ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አሸዋ አውጥቼ ለመነገድ ከዞኑ ንግድ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም መምሪያ ፈቃድ እንደዚሁም ከዞኑ የሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በመሐንዲስ ቦታው ተለክቶ ካርታ የተሰጠኝ ሲሆን ተከሳሾች ወደ ይዞታዬ ገብተው አሸዋዬን እንዳይወስዱ ብከለክላቸውም ፈቃደኛ ባለመሆን ከመጋቢት 7 ቀን 1996 እስከ መጋቢት 12 ቀን 1996 ዓ.ም. ድረስ በአራት መኪና አሸዋዬን ተመላልሰው የወሰዱብኝ ስለሆነ ጠቅላላ ዋጋውን ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ ክሱ ካስከተለው ወጭና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ክስ በማቅረባቸው ነው፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሳሽ ለክሱ ምክንያት በሆነው ቦታ ላይ የንግድ ፈቃድና ካርታ የተሰጠ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ 1ኛ ተከሳሽ /አመልካች/ አሸዋ የሚወጣበት ቦታ የእኛ ነው ከማለት በስተቀር ያቀረበው ማስረጃ ስለሌለና 2ኛ ተከሳሽም አሸዋውን መጫኑን ስላልካደ ኃላፊ ናቸው ብሎ በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍሉ በመወሰኑና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች መሠረታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረቡ ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ታዟል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም በአመልካች በኩል የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ አመልካች ክስ በቀረበበት ጉዳይ ኃላፊ ነው ተብሎ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ከአዋጅ ቁጥር 80/89 አኳያ የሰበር አቤቱታው ሊጣራ የሚገባ ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የክርክሩ ነጥብ አመልካች ለተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለመክፈል ይገደዳል ወይ የሚለው በመሆኑ ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የሥር ፍ/ቤቶች ለውሳኔያቸው መሠረት ያደረጉት ለክርክሩ መነሻ ምክንያት በሆነው የአሸዋ ማምረቻ ቦታ ላይ ለተጠሪ ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የንግድ ፈቃድና ካርታ የተሰጠ ስለሆኑና አመልካች በዚሁ የአሸዋ ማምረቻ ቦታ ባለመብት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያላቀረበ ስለሆነ ከተጠሪ ይዞታ ለተወሰደው አሸዋ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ለመክፈል ይገደዳል በማለት ነው፡፡

በሌላ በኩልም የአመልካች መ/ቤትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 80/89 አንቀጽ 6/18/ መሠረት ለአውራጎዳናዎች ግንባታና ጥገና እንደዚሁም ለመኖሪያ ለመሣሪያ ማሳረፊያና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶች ያለክፍያ በነጻ እንደሚጠቀምና በሚጠቀምበት መሬት ላይ ለሚገኙ ንብረቶች በሕግ መሠረት ካሳ እንደሚከፍል ተመልክቷል፡፡ የአመልካች መ/ቤትም የተቋቋመው አውራጎዳናዎችን ለማልማትና ለማስተዳደር እንደዚሁም በመንገዶች ሥራ ወጥነትን ለማረጋገጥና የመንገድ አውታር በተቀናጀ መልኩ የሚያድግበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር እንደሆነ በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 5 ላይ ተመልክቷል፡፡

አመልካች የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶች በነፃ መጠቀም እንደሚችል በተጠቀሰው አዋጅ የተፈቀደለት እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ አዋጅ በመጥቀስ በኢሉባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት

ክርክር ያቀረበ ቢሆንም በዝምታ የታለፈ ሲሆን በኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ ክርክር ሲደረግ ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ እንዳስፈረው በይ/ባይ የተጠቀሰው ይሄው ሕግ አሸዋና ድንጋይ ሊጠቀም የሚችል መሆኑን የሚገልጽ እንጂ በይዞታነት ለሌላ ሰው በተሰጠ የአሸዋ ማምረቻ መጠቀም አንደሚችል ስለማይገልጽ ሕጉ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይሁንና የአመልካች መ/ቤት የተቋቋመበት አጠቃላይ አላማ ለሀገርና ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም መሠረት ልማትን በመላ ሀገሪቱ ለማስፋፋት እንደመሆኑ መጠን መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶችን በነፃ መጠቀም እንደሚችል በሕግ ተፈቅዶለታል፡፡

አመልካች መሬትና ድንጋይ ነክ የሆኑ ሀብቶችን በነፃ ሲጠቀም በመሬቱ ላይ የሰፈረ ንብረት ካለ ለዚሁ ንብረት ካሳ እንደሚከፍል በተጠቀሰው አ/ቁ. 80/89 አንቀጽ 6(18) ላይ ከመመልከቱ በስተቀር ለድንጋዩም ሆነ ለአሸዋው ገንዘብ መክፈል እንዳለበት አልተመለከተም፡፡

ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው መሬትም ሆነ ድንጋይ ነክ ሀብት የተፈጥሮ ሀብት እንደመሆኑ መጠን የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት ደግሞ መንግስትና ሕዝብ እንደሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ም ሆነ በክልል ሕገ መንግስታት በግልጽ የተንጸባረቀ ስለሆነ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ረገድ መንግስትና ሕዝብ ባለቤት ከመሆናቸው አኳያ በነጻ የመጠቀም መብት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው አሸዋ የሚገኝበት ቦታ የንግድ ፈቃድና ካርታ ከሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተሰጠው ቢሆንም አሸዋ የተፈጥሮ ሀብት ከመሆኑ አኳያ በዚህ የተፈጥሮ ሀብት የባለቤትነት መብት የማይኖረው ከመሆኑም በላይ በክሱም የጠየቀው አሸዋውን ለመሰብሰብ የወጣ ወጭ ሳይሆን የአሸዋውን ዋጋ ስለሆነ ይህም የሕግ መሠረት ስለሌለው የኢሉባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የአሸዋውን ዋጋ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የኢሉባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01451 በሚያዝያ 6 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 42157 በመጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶችን በነፃ ለመጠቀም በአዋጅ ቁጥር 80/89 አንቀጽ 6/18/ ላይ የተፈቀደለት ስለሆነ ለመንገድ ሥራ ለተጠቀመበት አሸዋ ለተጠሪ ካሳ ሊከፍል አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 33499

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድነን ኪሮስ

አመልካች፡- አዋሣ እርሻ ልማት ድርጅት

ተጠሪ፡- አቶ ዶቶሮ ደሌቦ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ በመጀመሪያ የቀረበው ለአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ሊቀርብ የቻለውም የአሁኑ አመልካች ተጠሪው በአዋሳ ከተማ በታቦር ቀበሌ ክልል በሚገኘው በገኛ ካምፕ በድርጅቱ ይዞታ ሥር ካለው ቦታ እንዲኖርበት ተብሎ በጊዜያዊነት ከተሰጠው ቤት ቅጥር ግቢ ከፍሎ ሌላ ቤት ሰርቶበታል፡፡ የሰራውን ቤትና አጥር በራሱ ወጪ አፍርሶ ግቢውን ወደነበረበት ሁኔታ እንዲመልስ እንዲወሰንበት የሚል ክስ ስላቀረበ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ቤቱን እኔ በግሌ ለግል ጥቅሜ ልገለገልበት የሰራሁት ሳይሆን እንደሌሎቹ የእርሻ ልማት ሠራተኞች መኖሪያ ካምፖች ምዕመናን የአካባቢው አስተዳደር የማምለኪያ ቤት መስሪያ ቦታ እስከሚሰጥ ጊዜ ድረስ ጊዜያዊ መጠለያ ሠርተው እንዲያመልኩ ታስቦ ነው፡፡ ቤቱንም የሠሩት የአካባቢው ምዕመናን በመሆናቸው እኔ ልጠየቅበት የምችል ጉዳይ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከተመለከተ በኋላ ቤቱ ለተጠሪው /የአሁኑ ተጠሪ የሥር ተከሣሳሽ/ በድርጅቱ ከተሰጠው ቤት ግቢ ቦታ ላይ የተሰራ ስለመሆኑ በማስረጃ ቢረጋገጥም ቤቱን የሰራው ተከሣሽ /ተጠሪ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይሆን የአካባቢው ምዕመናን መሆናቸው የተጠሪው /ተከሣሽ/ ምስክሮች ስላስረዱ ቤቱ ለቤተክርስቲያንነት እንጂ ለተከሳሽ /ተጠሪ/ የግል ጥቅም ነው ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ተከሣሹ /ተጠሪው/ የሚጠየቅበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህን ከዚህ በላይ የተገለፀለውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአቤቱታው ቅሬታም ይህ ክርክር እየተካሄደበት ያለው ቤት የተሰራው ለተጠሪው ለጊዜው እንዲኖርበት ተብሎ በድርጅቱ ከተሰጠው ቤት ክልል ላይ ነው፡፡ ይህ ለፀሎት ማከናወኛ ተብሎ የተሰራው ቤት በድርጅቱ ለተጠሪው እንዲኖርበት ተብሎ በተሰጠው ቤት ቅጥር ክልል ስለመሆኑ ተጠሪው ሳይክድና በተሰሙት የግራ ቀኛችን ምስክሮችም ተነግሮ እያለ ቤቱ የተሰራው ለፀሎት ማከናወኛ እንጂ ለተከሣሹ /ተጠሪው/ ለግል ጥቅም ተብሎ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ ተጠሪውን በነፃ ማሰናበቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ በመሆኑም ተጠሪው ከድርጅቱ በጊዜያዊነት ተረክቦ በይዞታው ስር ያደረገውን ቦታ የመጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ ስላለበት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሮ ተጠሪው የሰራው ወይም የተሰራውን ቤትና አጥር አፍርሶ እንዲያነሳ ተብሎ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ እንደተመለከተው የአመልካች ይዞታ በሆነው መሬት ላይ ከሕግ ውጪ በሆነ ሁኔታ ተሰርቷል የተባለውን ቤት ተጠሪው አፍርስ ሊባል አይገባም መባሉ አግባብ መሆን አለመሆኑን መመርመር በማስፈለጉ ተጠሪው ቀርቦ መልሱን እንዲሰጥበት ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም ቤቱ ለምዕመናን የፀሎት ማከናወኛ በየወቅቱ በነበሩት የስራ ኃላፊዎች ፈቃድና እውቅና የተሰራ ሆኖ ሳለ ላንተ የግል ጥቅም አገልግሎት መስጫ ነው መባሉ ትክክል አይደለም፡፡ ድርጅቱ የሰጠኝንና ለፀሎት ማከናወኛ የምንጠቀምበት ቤት በጊዜያዊነት የምንጠቀምበት ነው፡፡ የከተማው አስተዳደር ሌላ ቦታ ይስጠንና ምትክ የፀሎት ቤት ስንሰራ ይህን የድርጅቱን ቦታ

እንለቃለን ብዬ ለድርጅቱ መልስ መስጠቴ ድርጅቱ በንፁህ ህሊና ሊመለከተው ሲገባ አሁኑኑ ቤቱን ካላፈረስክ ማለቱ አግባብ አይደለም፡፡ የፀሎት ቤት የተሰራው በዚህ ካምፕ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ካምፖች ነው፡፡ አሁን ደግሞ መስጊድም ሳይቀር እየተሰራ ነው የኛን የፀሎት ቤት እንዲፈርስ ክስ ማቅረቡም ከአድሏዊነት ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤትም ተከሣሽ በዚህ ቤት በግሉ የሚጠቀምበት ነገር ባለመኖሩ በቀረበበት ክስ ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት መወሰኑ አንዳችም የሕግ ስህተት የለበትም በመሆኑም ውሣኔ ሊፀናልኝ ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

አመልካችም የመልስ መልሱን ከመዝገቡ ጋር አያይዟል፡፡

በበኩላችን ደግሞ ተጠሪው ለጊዜው እንዲኖርበት በአመልካች በተሰጠው ቤት ቅጥር ግቢ ላይ የተሰራውን ቤት ሊያፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ክርክር ያስነሳው ቤት የተሰራው በማን እንደሆነ በግልጽ በማስረጃ ባይረጋጥም የተሰራበት ቦታ ግን የድርጅቱ ይዞታ በሆነውና ለተጠሪው ለጊዜው እንዲኖርበት ተብሎ በተሰጠው ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ስለመሆኑና ተጠሪውም በዚሁ ቤት ውስጥ ተጠቃሚ ስለመሆኑ ራሱ ለድርጅቱ በፃፈው ደብዳቤና በሌሎችም ምስክሮች የተረጋገጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይህ ቤት የተሰራው በድርጅቱ ፈቃድ ስለመሆኑም ተጠሪ አላስረዳም፡፡ እንደዚሁም ለጊዜው እንዲኖርበት በተሰጠው ቤት ቅጥር ግቢ ላይ ሌሎች ሰዎች ቤት እየሠሩ ናቸው ብሎም ለድርጅቱ በወቅቱ ሪፖርት በማቅረብ የተከላከለ ስለመሆኑም ያስረዳው ነገር የለም፡፡ ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው ተጠሪው ራሱ ፈልጎና ፈቅዶ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን በድርጅቱ በተሰጠው ቤት ቦታ ላይ የፀሎት ቤቱን የሠራ መሆኑ ነው፡፡ አመልካች ድርጅት ለጊዜው እንድትኖርበት በሰጠሀህ ቦታ ላይ ሳይፈቀድልህ ሌላ ቤት መሥራት አትችልም፤ የሰራኸውን ቤት አፍርስ ብሎ ማስጠንቀቂያ እየተሰጠው የከተማው አስተዳደር ለፀሎት ቤት መስሪያ የሚሆን ቤት እስኪሰጠን ጊዜ ይሰጠን በማለት ተጠሪው መጠየቁ አንድ ነገር ሆኖ ድርጅቱ ካልፈቀደ ተጠሪው ቤቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አላፈረስም ማለቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1178 ላይ የተደነገገውን የሚተላለፍ ድርጊት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የሥር ፍ/ቤትም ቤቱ የተሰራው ለተጠሪው ለጊዜው እንዲኖርበት ተብሎ በድርጅቱ በተሰጠው ቤት ቅጥር ግቢ መሆኑንና ቤቱን በመስራት ተግባርም ተጠሪው የተሳተፈና ቤቱንም በመጠቀም ተሳታፊ መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪው ቤቱን ሠርቶ ለግል ጥቅሙ ስለማዋሉ ማስረጃው አያስረዳም፡፡ የተሰራውን ቤት እንዲያፈርስ አይገደድም በማለት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1178/2/ መሠረት ባለሀንፃው በራሱ ኪሣራ ቤቱን አፍርሶ እንዲሄድ ማድረግ ይችላል ተብሎ ባለይዞታው ማለትም ለድርጅቱ የተሰጠውን መብት የሚጋፋ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 02133 የካቲት 29 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሸሯል፤ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪው በአዋሳ ከተማ በታቦር ቀበሌ ክልል በሚገኘው በ7ኛ ካምፕ በአመልካች ይዞታ ላይ የሠራውን ቤት ከነአጥሩ እንዲያፈርስ ተወስኗል፤ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁጥር 33711

መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
ደስታ ገብሩ
ሂሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ
ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- በቀድሞ ወረዳ 3 ቀበሌ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት ነ/ፈጅ ገ/ፃዲቅ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ ወ/ሮ ክብርነሽ ቀደመ ወኪል እመቤት ሣህለማርያም

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በአ/አ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪዎች በዚሁ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የተቀሩት ተጠሪዎች አባት በወረዳ 5 ቀበሌ 07 መስተዳድር ክልል ውስጥ ባዶ ቦታ ተከራይተው አፈር ኪራይ እየከፈሉ በቦታው ላይ ቤት ሠርተው በማከራየት ሲጠቀሙ ቆይተዋል፡፡ እሣቸው በ1968 ዓ.ም ከሞቱ በኋላም ወራሽነታችንን አረጋግጠን ለኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት የአፈር ግብር እየከፈልን በኋላም ለቀበሌው መስተዳደር በዚሁ መልክ እየከፈልን በውርስ ባገኘነው ሱቅ ስንጠቀም ቆይተናል፡፡ የቀበሌው መስተዳደር ቤቱን የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት እና የተቀሩት ተጠሪዎች አባት የሠሩት መሆኑን እያወቀ በየወሩ ብር 6,160.00 (ስድስት ሺህ አንድ መቶ ስልሣ) እንድንከፍል ውል አስፈርሞናል፡፡ በመጨረሻም ነሐሴ 1 ቀን 1993 ዓ.ም. አዲስ የኪራይ ውል ለ1 ዓመት ካልፈረማችሁ እያለን ስለሆነ ቀድሞ ስንከፍል የነበረውን ብር 55.00 የአፈር ግብር ብቻ እየከፈልን በገንዘባችን በሠራነው ቤት ኪራይ እንድንከፍል ሁከት ይወገድልን፡፡ አላግባብ ያስከፈሉንን ብር 24,844.48 (ሃያ አራት ሺህ ስምንት መቶ አርባ አራት ብር ከአርባ ስምንት ሣንቲም) ተመላሽ እንዲያደርግልን ይወስንልን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካችም ለቀረበበት ክስ መቃወሚያና በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ የሰጠ ሲሆን በበኩሉም የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቧል። በክሱም ተጠሪዎች በነበራቸው የተሻሻለ የቤት ኪራይ ውል መሠረት ብር 6,160/ስድስት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ/ እየከፈሉ ቢቆዩም ከጥር 1994 ዓ.ም. እስከ አሁን ድረስ መክፈል ስላቆሙ ውዝፍ ኪራይ ከወለድ ጋር ታስቦ ይክፈሉ። በመሃከላችን ያለው ውል ከነሐሴ 1994 ዓ.ም ስላለቀ ቤቱን ልረከብ በማለት ጠይቋል። ተጠሪዎችም ለቀረበባቸው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል።

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ቤቱን የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የቀሪዎቹ አባት የሠሩት መሆኑ ተረጋግጧል። በመሆኑም ቀድሞውኑ በግል ቤት ላይ አስተዳደሩ የኪራይ ውል መዋዋል አይገባውም ነበር። ስለዚህም ውሉ ሕገ ወጥ ነው። ውሉ ሕጋዊ ባለመሆኑ አመልካች ተጠሪዎች ኪራይ ይክፈሉ ብሎ ማስገደዱ ሁከት በመሆኑ ሁከቱ ይወገድ። ተጠሪዎች ከመስከረም 1994 ዓ.ም. እስከ ታህሳስ 1994 ዓ.ም እንዲከፍሉ የተደረገው ሕገ ወጥ በመሆኑ ይኸው ገንዘብ ይመልስ በማለት ወስኗል።

በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር ተሠኝቶ ይግባኙን ለከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ የመጀመሪያውን ውሣኔ አጽንቷል። የአ/አ ከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎትም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጐታል።

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው። ይህ ችሎትም የኪራይ ውሉ እንዲፈርስና የኪራይ ገንዘቡ እንዲመለስ የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው በሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል። ተጠሪዎችም አቤቱታው ደርሷቸው መልስ የሰጡ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል።

ከፍ ሲል እንደተገለፀው በከተማ ነክ መ/ደረጃ ፍ/ቤት ክስ የተመሠረተው ሟች አቶ ሣህለማሪያም ፈርዳ ባዶ ቦታ ተከራይተው የአፈር ኪራይ እየከፈሉ በገንዘባቸው በሠሩት ቤት ላይ አመልካች ኪራይ እንዲከፍሉ

በማድረግ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ እና ቀደም ሲል የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸው ነው። ክርክሩ ሂደት ተጠሪዎች ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል ፈጽመው በቤቱ ኪራይ እየከፈሉ ይኖሩ እንደነበር ተረድተናል። ተጠሪዎች ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆናቸውም አመልካቹ ነሐሴ 1993 ዓ.ም በአንድ ዓመት ውል እንዲፈጽሙ መጠየቁ ነው። በፍ/ሕ/ቁ 1149/1/ መሠረት ይዞታ የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተነሣበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንዲመለስ ወይም በሥላማዊ ይዞታው ላይ የተነሣው ሁከት እንዲወገድለት ክስ ለማቅረብ ይችላል። በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ቀድሞውኑ ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል ፈጽመው በቤቱ ኪራይ እየከፈሉ ረጅም ጊዜ ኖረዋል። በመሆኑም የቀድሞ ግንኙነቱ እንዲቀጥል ተጠሪዎች የኪራይ ውል እንዲፈርሙ መጠየቁ በተጠሪዎች ሥላማዊ ይዞታ ላይ ሁከት መፍጠር ነው አያሰኝም።

በሌላ በኩል ተጠሪዎች ለአመልካች የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸው ጠይቀዋል። ከመዝገቡ እንደተመለከትነው ተጠሪዎች ይህንን ጥያቄ ያቀረቡት የቤቱ ባለሃብት ነን በማለት መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል። ነገር ግን የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሃብት ለመሆን የቤቱ ባለቤትነት ምስክር ወረቀት መቅረብ አለበት። ተጠሪዎች የቤቱ ባለሃብት ለመሆናቸው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት አላቀረቡም ወይም በቤቱ ላይ በስማቸው ከ15 ዓመት በላይ ግብር እየከፈልን የቤቱ ባለሃብት ሆነናል በማለት ያቀረቡትም ክርክር የለም። በመሆኑም ተጠሪዎች የቤቱ ባለሃብት ናቸው ለማለት የሚያስችል ሁኔታ አላገኘንም፤ በዚህም ምክንያት ተጠሪዎች የቤቱ ባለቤት ስለሆኑ የከፈሉት የኪራይ ገንዘብ እንዲመለስላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የከተማ ነክ ይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት በመ/ቁ 04230 በሐምሌ 20 ቀን 1999 ዓ.ም የከተማ ነክ ይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመ/ቁ 02605 በታህሣሥ 24 ቀን 1990 ዓ.ም. እንዲሁም የአ/አ ከተማ የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 00366 ግንቦት 30 ቀን 1997 ዓ.ም የሠጡዋቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡

2. ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 33831

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ሀሰን ኢብራሂም

ተጠሪ፡- ኢብራሂም ይመር ሐሰን

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያለአግባብ የተያዘብኝ ቤት ይለቀቅልኝ በሚል አመልካች ባቀረበው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክሱን ያስተናገደው የደሴ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪን በማስቀረብ የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ሰምቷል፡፡ በመጨረሻም ከሳሽ የቤቱ ባለሀብት መሆኑን በማስረጃ አረጋግጧል በማለት ተጠሪ ቤቱን እንዲለቅና ለአመልካች እንዲያስረክብ ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ ተጠሪ በቤቱ ላይ የተሻለ መብት ስላለው ለአመልካች ሊያስረክብ አይገባም በማለት የወሰነ ሲሆን፣ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ህዳር 9 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ክርክር የተነሳበት ቀደም ሲል ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት በአመልካች ስም ስለመመዝገቡ ማስረጃ ቀርቦአል እየተባለ በቤቱ ላይ የተሻለ መብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው ተጠሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመዝገቡ ከሰፈረው የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና የስር ፍ/ቤቶች ከሰጡአቸው ውሣኔዎች ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ተመዝግቦ የሚገኘው በአመልካቿ ስም ነው፡፡ ወደኋላ ያለውን የቤቱን ታሪክ ስንመለከትም ቀደም ሲል ብርሃኔ አድማሱ፣ ጣይቱ አድማሱ እና አበበ ፋሪስ የተባሉት ሰዎች ንብረት እንደነበረ፣ እነዚህ ሰዎች ከአመልካች ብር 12,000(አስራ ሁለት ሺህ) በመበደራቸው ቤቱን ለ15 ዓመት በመያዣ ለአመልካች መስጠታቸውን በተባለው 15 ዓመት ውስጥ ገንዘቡን ካልመለሱ አመልካች ቤቱን በስሙ ለማዞር እንዲችል መስማማታቸውን አመልካችም በተባለው 15 ዓመት ውስጥ ገንዘቡ ስላልተመለሰልኝ በውላችን መሠረት ቤቱ በኔ ስም እንዲመዘገብ ይወሰንልኝ በማለት ለፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ማስወሰኑን፣ በዚህ ረገድ የተሰጠው የፍ/ቤት ውሣኔም በይግባኝ ቀርቦ አለመሻሩን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ እንግዲህ ከአመልካች አንፃር ያለው ሁኔታ ሲሆን፣ ተጠሪ ደግሞ ቤቱ እኔም ከተባሉት ሰዎች በይዞታ ተሰጥቶኛል በማለት ነው የተከራከረው፡፡ ክርክሩን በይግባኝ የሰሙት ፍ/ቤቶች በወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በመለወጥ የወሰኑትም ተጠሪ አለኝ ለሚለው የመያዣ ውል ከፍተኛ ግምት በመስጠት እና አመልካች ቤቱን በስሙ ያስመዘገበው ያለአግባብ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ክርክሩ ውስብስብነት የሌለው እጅግ ግልጽ ቀላልም ነው፡፡ አመልካችም ሆነ ተጠሪ ከቀድሞ የቤቱ ባለቤቶች ጋር የመያዣ ውል ማድረጋቸውን በተመሳሳይ ሁኔታ የገለፁ ቢሆንም፣ አመልካች ግን አንድ እርምጃ ወደፊት በመሄድ የመያዣ ውል ነው ያለውን መሠረት በማድረግ ክስ መስርቶ ቤቱ በሱ ስም እንዲመዘገብ

አስወስኖአል፡፡ ይህ ውሣኔ በማንኛውም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያልተሻረ ሲሆን፣ አመልካችም በውሣኔው መሠረት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ቤቱን በስሙ አስመዝግቦ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አግኝቶአል፡፡ ከዚህ እንግዲህ በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው በአሁኑ ደረጃ የቤቱ ባለቤት ሊባል የሚችለው አመልካች እንደሆነ ነው /በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1195 የተቀመጠው ድንጋጌ ይመለከታል/፡፡ ይግባኙን የሰሙት ፍ/ቤቶች ተጠሪ አለኝ የሚለውን የመያዣ ውል በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 3052 በተደነገገው መሠረት የተመዘገበ እና በሕግ የሚታወቅ ስለመሆኑ እንኳን ሳያረጋግጡ በቤቱ ላይ ከአመልካች የተሻለ መብት አለው ወደሚለው መደምደሚያ መድረሳቸው አግባብ አይደለም፡፡ የመያዣ ውሉ በሕግ የታወቀ ቢሆን እንኳን ተጠሪን በቀጥታ የቤቱ ባለቤት የሚያደርገው አይደለም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች ቤቱን በስሙ ያስመዘገበው በፍ/ቤት ባሰጠው ውሣኔ መሠረት በመሆኑና ይህ ውሣኔም በበላይ ፍ/ቤት ያልተሻረ በመሆኑ በአሁኑ ደረጃ የስም ዝውውሩ ትክክል አልነበረም ወደሚለው ነጥብ መግባት የሚቻልበት ምንም የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለል በሕግ በግልጽ የተረጋገጠ የባለቤትነት መብት ያለው አመልካች ሆኖ ሳለ ከዚህ ውጪ በሆነ ሁኔታ /በሕሊና ግምት ላይ በመመስረት/ ፍርድ መስጠቱ በማንኛውም መለኪያ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለዚህም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በአማራ ብ/ክ/መ/በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 15/2000 ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አከራካሪው ቤት የአመልካች ንብረት መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 13033 የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ ውሣኔው ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

ሚያዝያ 16 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

አመልካች፡- ወ/ሮ ገብርኤላ ሂኮላቶማስ - ጠ/አስቱር አርአያ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ቤዛ አስራት ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ክስ የጀመረው በፊ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁን አመልካች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ ከአባቴ በውርስ የተላለፈልኝን ቤት ተጠሪው በአደራ ተረክቦ እያስተዳደረ ቢቆይም ቤቱን እንዲያስረክበኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆኑ ቤቱን እንዲያስረክበኝና ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ የሰበሰበውን የኪራይ ገንዘብ እንዲመልስልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም፣ አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም፣ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ቤቱ የአባታቸው የግል ቤት ለመሆኑ የሚያስረዳ በህጉ መሰረት የተሰጠ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ አላቀረቡም ወይም ቤቱ ከአዋጅ ውጪ የተወረሰ ተብሎ ከሚመለከተው አካል እንዲመለስላቸው የተፈቀደ ማስረጃ አላቀረቡም በመሆኑም ክስ በተመሰረተበት ንብረት ላይ ጥቅም ወይም መብት የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ የቀረበ ነው ይህ ችሎትም አመልካች የመክሰስ መብት የላቸውም መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ ቀርቦ ክርክሩን በጽሁፍ አቅርቧል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ክስ የመሰረቱት ተጠሪ በአደራ ሲያስተዳድረው የቆየውን የአባታቸውን ቤት እንዲያስረክባቸው ነው፡፡ አንድ ከሣሽ ክስ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት ለክሱ ምክንያት በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሃብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑን ካረጋገጠ እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/ ሥር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለመረከብ ክስ በመሰረቱት ቤት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ክስ ወድቅ ያደረጉት የቤቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ ባለመቅረቡ አመልካች በንብረቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን አላረጋገጡም በማለት ነው፡፡

እኛ እንዳየነው ግን አመልካች ክስ የቀረበበት ቤት የሚች አባታቸው ቤት ለመሆኑ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ባያቀርቡም በስራና ከተማ ልማት ሚ/ር የተፃፈ ደብዳቤና የቤቱን የቦታ ካርታ አቅርበዋል በማስረጃነት የቀረበው ደብዳቤ ክርክር የተነሣበት ቤት የአመልካች አባት የነበረና እሳቸው ሲሞቱ ቤቱን ተረክቦ የነበረው የግሪክ ኤምባሲ ቤቱን ለስራና ከተማ ልማት ያስረከበ በመሆኑ ግሪክ አገር አሉ የተባሉት የሚች ልጆች ባለመብቶች መሆናቸው ከተረጋገጠ ቤቱን እንዲረከቡ የሚያሣስብ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የከተማ ቤቶችን ባለቤትነት ለመወሰን ስልጣን ያለው አካል የፃፈው ይህ ደብዳቤ ቤቱ የአመልካች አባት መሆኑን የሚጠቁም ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ደግሞ የሚች አባታቸው ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው የቀረቡ በመሆኑ በቤቱ ላይ ጥቅም ወይም መብት ያላቸው መሆኑን አላረጋገጡም ለማለት የሚያስችል

ሁኔታ አላየንም፡፡ የፍ/ህ/ቁ. 1195/1/ም ቢሆን ለአንድ ሰው የተሰጠው የቤት ባሃብትነት ምስክር ወረቀት ይህ ሰው የዚሁ ቤት ባለሃብት እንደሆነ ግምት ከሚወሰድ በቀር የቤቱ ባለሃብትነት በሌላ ሰነድ ሊረጋገጥ አይችልም የሚል እንድምታ የለውም፡፡ በእርግጥ አመልካች ቤቱን ሊረከቡ ይገባል አይገባም የሚለው ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንፃር ተመርምሮ የሚወሰን ቢሆንም አመልካች ግን ክስ በቀረበበት ቤት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን አላረጋገጡም ማለት ስለማይቻል የሥር ፍ/ቤቶች የቤቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አለመቅረቡን ብቻ መሰረት አድረገው ሌሎቹን የአመልካች ማስረጃዎች ሳያገናዝቡ አመልካች በንብረቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም ማለታቸው ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48823 በሰኔ 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31862 ህዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ክስ በተመሰረተበት ንብረት ላይ ጥቅም ወይም መብት ስላላቸው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341 መሰረት ተመልሷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34406

ሚያዚያ 07 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ መልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ መገርቱ ነጋሣ- አልቀረቡም

ተጠሪ፣ እነ ወ/ሮ ፀሃይ ልጋ አልቀረቡም

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት የቀሪዎቹ ተጠሪዎች አባት በህይወት በነበሩበት ጊዜ ክስ የቀረበበትን ቤት ለአቶ ደረጀ መንግስቱ አከራይተው የነበረ ሲሆን ተከራዩ አመልካችን ቤቱ ውስጥ አስገብተው አካባቢውን ለቀው ጠፍተዋል፡፡ አመልካችንም የግል ቤታችንን ለቀው እንዲወጡ ጠይቀን ፍቃደኛ አልሆኑም፡፡ለሚመለከተዉ ቀበሌም አመልክተን አመልካችም ቤት ሲያገኙ ለቀው የሚወጡ መሆኑን በእማኞች ፊት አረጋጠው የፈረሙ ቢሆንም ቤቱን ስላለቀቁ ቤቱን እንዲያስረክቡን፣ ያለምንም ክፍያ ከመጋቢት 26 ቀን 1991 ዓ.ም ክስ እስከቀረበበት ድረስ ስለኖሩ በወር ብር 150(አንድ መቶ ሃምሳ) ታስቦ በድምሩ ብር 11,250 (አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ) እንዲከፈሉ ይወሰንልን ብለው ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ ክስ የቀረበበት ቤት ተጠሪዎች በሚኖሩበት ቤት ይዞታ ስር የሚጠቃለል ለመሆኑ ማስረጃ አላቀረቡም፣ ቤቱ ለአቶ ደረጀ መንግስቱ የተከራየበት ማስረጃ አልቀረበም፣ ቤቱን በወረራ ይዛለች ካሉ ይህን ካወቁ 10 ዓመት በላይ ስለሆነ በይርጋ ይታገዳል፣ የደረሰባቸው የጥቅም ጉዳት ከውል ውጪ እንደመሆኑ መጠን

የኪራይ ማስከፈል ጥያቄአቸው ሁለት አመት ካለፈው በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካቀረቡ በኋላ ለፍሬ ጉዳዩ በሰጡት መልስ ቤቱን የተጠሪዎች አውራሽ አልሰሩትም ለአቶ ደረጀም አላከራዩም፣ ቤቱ የአቶ ደረጀ ሲሆን ለአመልካች አከራይተውኛል፣ ቤቱን ለማስረከብ ቃል ገብታለች የተባለው ተገድጄ የፈረምኩት ስለሆነ አልገደድበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የአመልካችን መቃወሚያዎች ውድቅ ካደረገ በኋላ አመልካች ይዘውት የሚገኘው ቤት የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የቀሪዎቹ አባት ይዞታ ስር የሚካተት መሆኑ ተረጋግጧል በማለት አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡና አመልካች ቤቱን እለቃለሁ ብለው ከፈረሙበት ጊዜ ጀምሮ በወር ብር 150.00 (መቶ ሃምሣ) እየታሰበ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ብር 11,250 (አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ) ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔውን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሣኔው የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች ከመጋቢት 26 ቀን 1991 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 19 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ ያለውን የተጠሪዎችን ቤት ያላግባብ የያዙበትን ብር 11,250(አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ) እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጐ ተጠሪዎች ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ተጠሪዎች አመልካች ቤታቸውን ያለአግባብ ስለያዙ እንዲያስረክቧቸውና በቤቱ ያለአግባብ ለተገለገሉበት ካሣ እንዲከፍሉ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ቤቱ የተጠሪዎች አለመሆኑንና ቤት እንዲለቁም ሆነ ካሣ እንዲከፍሉ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ክስ የቀረበበት ቤት የተጠሪዎች መሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን የተገነዘብን በመሆኑ አመልካች የቤቱን ባለቤትነት በተመለከተ ማስረጃ ላይ ተንተርሰው ያቀረቡትን ክርክር ይህ ችሎት አልተቀበለውም፡፡ ሌላው አመልካች ያነሱት ክርክር ቤት እንዲያስረክቡ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው የሚል ነው፡፡ አመልካችዋ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ያሉት ክሱ ሁከት ይወገድልኝ በማለት የቀረበ ስለሆነ ነው በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ተጠሪዎች ይዞታችን በሃይል ተወስዷል ወይም በይዞታችን ላይ ሁከት ተፈጥሯል በማለት ያቀረቡት ክስ የለም፡፡ ክሣቸው በኪራይ ለአቶ ደረጀ ያስረከቡትን ቤት አመልካች መብት ሣይኖራቸው ገብተው አልወጣም ብለዋልና ያስረክቡን የሚል ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች አለአግባብ የያዙትን ንብረት እንዲለቁ የቀረበ ክስ ስለሆነ የአመልካች ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም፡፡

በመጨረሻ አመልካች ያቀረቡት ክርክር የቀረበው የካሣ ጥያቄም ቢሆን በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል ነው፡፡ ክስ የቀረበበት ቤት የተጠሪዎች በመሆኑ ቤቱን ያላግባብ ይዘው ለተጠቀሙበትና ያላግባብ ለበለፀጉበት ካሣ እንዲከፍሉ ክስ ቀርቧል:: በሌላ ሰው የስራ ድካም ወይም በሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው ጥቅም ባገኘበት መጠን ለባለሃብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው ኪሣራ መክፈል እንዳለበት በፍ/ህ/ቁ. 2162 ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች በቤቱ አላግባብ በበለፀጉበት መጠን ኪሣራ እንዲከፍሉ መጠየቃቸው ህጉን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ይህ የካሣ ጥያቄ ሊቀርብ የሚገባበትን የጊዜ ገደብ በተመለከተ ክርክር ቀርቧል፡፡ ያለአግባብ ስለመበልፀግ የሚናገረው ምዕራፍ የካሣ ጥያቄ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ አይናገርም፡፡ ነገር ግን አላግባብ ስለመበልፀግና ከውል ውጪ ስለሚደርስ ሃላፊነት የሚናገሩት ድንጋጌዎች በአንድ አንቀጽ ውስጥ ተካትተው መገኘታቸው እንዲሁም ያለአግባብ መበልፀግም ከውል ውጪ የሚደርስ ሃላፊነት በመሆኑ ከውል ውጭ በሚደርስ ሃላፊነት ሥር የተመለከተው የይርጋ ዘመን በተመሣሣይ አላግባብ መበልፀግን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት ከውል ውጭ

ሃላፊነትን በተመለከተ ተበዳዩ ክስ ማቅረብ የሚችለው ካሣ የሚጠይቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ አስከ 2 አመት ድረስ መሆኑ በፍ/ህ/ቁ 2143/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቤቱን ያለማቋረጥ ለረኽም ጊዜ ይዘው እየተገለገሉበት በመሆኑ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ኋላ ላሉት ሁለት አመታት አላግባብ በቤቱ በተገለገሉበት መጠን እንዲከፈሉ የተጠየቁት ካሣ በይጋ የሚታገድ አይሆንም:: ከዛ በፊት ያሉት ግዜያት ግን በይርጋ ቀሪ የሚሆኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የ6 አመት ካሣ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13468 በሐምሌ 27 ቀን 1999 የሰጠው ውሣኔ፣ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58602 በጎንደር 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔዎች ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ክስ የቀረበበትን ቤት ያስረክቡ፡፡ ከሐምሌ 20 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 19 ቀን 1997 ዓ.ም ላለው ጊዜ ብቻ በቤቱ አላግባብ ለተጠቀሙበት በወር ብር 150.00(አንድ መቶ ሃምሣ) ታስቦ በድምሩ ብር 3,600(ሦስት ሺህ ስድስት መቶ) ለተጠሪ ይክፈሉ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይ ር ጋ

የሰ/መ/ቁ/ 20295

ሐምሌ 5 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- አቶ ደጀኔ ለገሠ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ አቶ መላኩ ጌታቸው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የውርስ ሀብት ለመረከብ በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ከሳሽ በእናታቸው በወ/ሮ የልፍኝ እጅጉ ተተክተው የወ/ሮ ያምሮት እጅጉ ወራሽ መሆናቸውን ሰኔ 30 ቀን 1996 ዓ.ም በፍ/ቤት ውሳኔ አረጋግጠዋል፡፡ የተከሳሾች አያት ወ/ሮ ታደለች አርጋው ከወ/ሮ ምንትዋብ ሙሴ ጋር በመሆን የአክስቱ የወ/ሮ ያምሮት እጅጉ ወራሽ ናቸው ተብሎ የካቲት 29 ቀን 1981 ዓ.ም በፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ መቃወሚያ አቅርቤ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም ተሰርዟል፡፡ ከዚያም ቤት ለማስለቀቅ ሚያዚያ 10 ቀን 1992 ዓ.ም በተከሳሾች እናትና በወ/ሮ ምንትዋብ ሙሴ ላይ ክስ ብመሠርትም ተከሳሾች በሞት በመለየታቸው መጥሪያ ሳይደርሳቸው ክሱ ተቋርጧል፡፡

በአጠቃላይ ተከሳሾች ከወ/ሮ ያምሮት እጅጉ የሚደርሰኝን የውርስ ሀብት ያስረክቡኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎችም በሰጡት መልስ ከሳሽ የወ/ሮ ያምሮት እጅጉ ሕጋዊ ወራሾች መሆናቸውን ያረጋገጡት ሐምሌ 14 ቀን 1986 ዓ.ም ተከሳሾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይዘውብኛል የሚሉትን ቤት ላለፋት ዘጠኝ ዓመታት ያልጠየቁ ስለሆነ ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1000 (1) መሠረት በ3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በፍሬ ጉዳዩም ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት የከሳሽ ክስ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም የሚለውን ጭብጥ መሥርቶ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክሩን መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት ከሳሽ የወ/ሮ ያምሮት እጅጉ ወራሽ መሆናቸውን ያረጋገጡት ሐምሌ 14 ቀን 1986 ዓ.ም ነው፡፡ ከዚህም በኋላም በተከሳሾች እናት ላይም ሆነ በተከሳሾች ላይ የውርስ ሀብት ይልቀቁልኝ በማለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እንዳገኙ ይቆጠራል፡፡

ይህ የይርጋ ጊዜ ሊቋረጥ ከሚችልባቸው ምክንያቶች አንዱ ክስ ቀርቦ በሆነ ጊዜ ሲሆን ከሳሽ በመ/ቁ 3311/81 የካቲት 29 ቀን 1981 ዓ.ም የተከሳሾች ወላጅ እናትና ወ/ሮ ምንትዋብ ሙሴ ወራሾች ናቸው ተብሎ የተሰጠን ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ይህ የመቃወሚያ ክርክር የወራሽነት መብት ላይ ብቻ ያነጣጠረ በመሆኑና የውርስ ንብረት

ይሰጠኝ በሚል የቀረበ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1851(ለ) መሠረት ይርጋው ተቋርጧል ለማለት አይችልም፡፡

ስለሆነም ከሳሽ የወራሽነት መብታቸውን ካረጋገጡና የውርሱ ንብረቶች በተከሳሾች መያዛቸውን ካወቁ በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ በተከሳሾች ላይ ክሱን ያላቀረቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ ቁጥር 1000(1) መሠረት በ3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተመሳሳይ ጭብጥ በመያዝ የፍ/ብ/ሕ ቁ.1000(1) ተፈፃሚነቱ አንድ የወራሽነት ማስረጃ ያለውና ነገር ግን ይህ ማስረጃው በሕግ ዓይን ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ውርሱን ወይም የውርሱን አንድ ክፍል የያዘ ከሆነ በሕጉ ዓይን

ተቀባይነት ያለው ማስረጃ የያዘው ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት የውርስ ንብረቶች እንዲመለሱለት በሚጠየቅበት ጊዜ እንደሆነ በውሳኔው ላይ አስፍሮ በተያዘው ጉዳይ ግን መ/ሰጭዎች ተጠቃሹን ንብረት የያዙት ምንም ዓይነት የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖራቸው ስለሆነ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 ሳይሆን ቁጥር 1845 ነው ካለ በኋላ ከዚሁ አካያ ሲታይም የይ/ባይ/የተጠሪ አውራሽ በ1978 ዓ.ም መሞታቸው የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪም በመብታቸው መሥራት የሚችሉት ከዚህ ጊዜ በኋላ ስለሆነ ቤት ይለቀቅልኝ በማለት ክስ የመሠረቱት ምንም እንኳን መጥሪያው ለመ/ሰጭዎች አውራሽ ያልደረሰ ቢሆንም በ1992 ዓ.ም ከ14 ዓመት በኋላ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 ላይ በተቀመጠው የ10 ዓመት ጊዜ ክሱ ያልቀረበ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ምክንያቱን ቀይሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወምና መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የመ/ሰጪዎች አውራሽ የሚች ወ/ሮ ያምሮት እጅጉ ልጅ ነኝ በማለት ያወጡትን የወራሽነት ማስረጃ አመልካች ጥር 20 ቀን 1987 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መቃወሚያ በማቅረብ እንዲሰረዝ ካደረገ፣ የወራሽነት ማስረጃ ያሰረዘበት ውሳኔ ከግምት ሳይገባ ንብረቱን ለመረከብ የጠየቀው አውራሹ ከሞቱ ከ10 ዓመት በኋላ ነው ተብሎ ክሱ በይርጋ ቀሪ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበው ክሱ በይርጋ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ አግባብነት በመዘርዘር አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን በሥር ፍ/ቤቶች በተጠሪ በኩል የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ከሕጉ አካያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ክስ ባጭሩ ከአክስቱ ከወ/ሮ ያምሮት እጅጉ በውርስ የተላለፈልኝን ቤት ይዘው የሚገኙ ስለሆነ ያስረክቡኝ በማለት ነው፡፡

ተጠሪዎች የአመልካች አክስት የሆኑት የወ/ሮ ያምሮት እጅጉን ንብረት በመውረስ ረገድ የቅድሚያ መብት እንደሌላቸው ቢረጋገጥም ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ይዘው የተገኙት ወራሽ ነን በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በመውረስ ረገድ ከአመልካች የቀደመ መብት ባይኖራቸውም ንብረቱን ይዘው የሚገኙት የመውረስ መብት ሳይኖራቸው ነው ለማለት ግን የሚያስችል አይሆንም፡፡

ተጠሪዎች ቤቱን ይዘው የሚገኙት በወራሽነት መብት ነው ከተባለ ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000(1) በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠቀሰው ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የይርጋ ክርክሩን ከቁጥር 1845 ድንጋጌ ጋር አያይዞ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ክሱ በይርጋ ተቋርጧል የሚል ውሳኔ የሰጠው ሕጉን በተገቢው ካለመተርጎም እንደሆነ ታምኖበታል፡፡በሌላ በኩልም አመልካች ተጠሪዎች የያዙትን የውርስ ንብረት ያስረክቡኝ በማለት በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱት ሰኔ 30 ቀን 1996 ዓ.ም ሲሆን የአክስታቸው ወራሽነታቸውን ያረጋገጡት ደግሞ ሐምሌ 14 ቀን 1986 ዓ.ም ነው፡፡

አመልካች ወራሽነታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1000(1) ላይ የተቀመጠው የ3 ዓመት የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት በተጠሪዎች ተይዞብኛል የሚሉት ንብረት እንዲመለስላቸው መጠየቅ ይገባቸው እንደነበር የሚታመን ከመሆኑም በላይ የተጠሪዎች አውራሽ የአመልካች አክስት ወራሽ ናቸው ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ አመልካች ለማሰረዝ አቤቱታ አቅርበው ክሱን ማቅረብ የሚችሉት ውሳኔው ከተሰረዘ በኋላ ነው ቢባል እንኳን ይሄው ውሳኔ በ1991 ዓ.ም ተሰርዞ ክሱን ግን ያቀረቡት የ3 ዓመቱ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ በ1996 ዓ.ም ስለሆነ ከተጠቀሰው የፍ.ብ.ሕ.ቁ 1000(1) አኳያ በይርጋ የማይታገድበት ምክንያት አልተገኘም፡

ው ሳ ኔ

(1) የሥር ፍ/ቤቶች የቀረበው ክስ በይርጋ ተቋርጧል በማለት የሰጡት ውሳኔ ከውጤት አኳያ በአግባቡ ሆኖ ስለተገኘ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348 (1) መሠረት ፀንቷል፡፡

(2) የፍርዱ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ

(3) ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ

(4) መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

ተጨማሪ ትዕዛዝ

በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 03/09 የቤት ቁጥር 507 የሆነው ቤት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ባለበት ሁኔታ ተከብሮ እንዲቆይ በዚህ ፍ/ቤት በግንቦት 22 ቀን 1998 ዓ.ም የተሰጠው የፅሁፍ ትዕዛዝ በዚህ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 25567

ጎዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- ወ/ት አይናለም አበበ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ደገፋ ጉርሙ - ጠበቃ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በአመልካች ሰኔ 16 ቀን 1998 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀረበ ክርክር ሲሆን ፍሬ ነገሩም ያሁኑ ተጠሪ የሥር ከሣሽ በመሆን በሥር 1ኛ በመቃወም በተጠሪ ወ/ሮ ደስታ ይመር /በዚህ መዝገብ የሌሉበት/ እና ባሁኗ አመልካች የሥር 2ኛ በመቃወም ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ሚች ወንድማቸው አቶ አበበ ጉርሙ ልጅ አለመውለዱ እየታወቀ አመልካች የሚች ልጅ ናት ተብሎ ወራሽነቱ የተረጋገጠው ባግባቡ ስላልሆነ ውሣኔው ይሻር የሚል ነው፡፡ ለክሱም 1ኛ የመቃወም ተጠሪ በርግጥ አመልካች ከኔም ሆነ ከሚች አትወለድም ልጂ ነች ብዬ ውሣኔ ያሰጠሁት ከሕፃንነቷ ጀምሮ ስላሳደኳትና እንደ ልጅ ስለምቆጥራት ነው ሲሉ አመልካችም በበኩሏ ተጠሪ ሕፃን ሆኜ ውሣኔ ሲሰጥ ቀርበው መቃወም ሲችሉ ከ21 ዓመት በኋላ መቅረባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት በየበኩላቸው መልስ ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 የሚሠራው የፈረሰ ንብረት ይገባኛል ለሚል ክርክር እንጂ ወራሽ ናት አይደለችም ለሚል ክርክር አይደለም በሚል የይርጋ

መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎ አመልካች ከሚች የማትወለድ በመሆኑ ስለ ኑዛዜ ወራሽ ልትሆን አትችልም በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ሚችና 1ኛ የመቃወም ተጠሪ በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143/ሠ/ መሠረት አመልካችን ወደ ቤት በመውሰድ፣ በማንከባከብና በማስተማር እንደ አባት በመሆን የተሣተፉ በመሆኑ አመልካች የሚች ልጅና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ነች በማለት ወስኗል፡፡

ያሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መነሻነት ሲሆን ፍርድ ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በማስቀረብ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ክርክሩንም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች ጎዳር 5 ቀን 1993 ዓ.ም. የወራሽነት ማስረጃ ካገኙ በኋላ የሚች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን በመግለጽ በቤቱ ላይ ያገኙት የጋራ ባለሀብትነት መብት /ከሥር 1ኛ የመቃወም ተጠሪ ጋር/ ተቀባይነት ያጣው ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ክርክር ባንድ በኩል የሚች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ነኝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ከ20 ዓመት በላይ ቆይተው በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉት የወራሽነት መብት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 መሠረት የሚታገድ ነው የሚል ሲሆን የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የጠቀሱት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 ተፈፃሚነት ያለው የውርስ ንብረት ይገባኛልና ይሰጠኝ ለሚል ክርክር እንጂ ወራሽ ናት አይደለምችም ለሚል ክርክር አይደለም በማለት የሰጠውን ውሣኔ እንደተመለከትነው ድንጋጌው ባግባቡ አለመፈጸሙን ተረድተናል፡፡ ያሁኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ በራሱም ሲታይ ይዘቱ ወንድሜ ልጅ አለመውለዱ እየታወቀ አመልካች በሐሰት ልጅ ነኝ ብላ የወራሽነት ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወሰደች ስለሆነ ትመልስ እንዲሁም በቤቱ ላይ ያለው የሚች ድርሻ ለኔ ይሰጠኝ የሚል ሲሆን አመልካችም በበኩሏ የሚች ልጅ መሆኗን እና ንብረቱም እንደሚገባት መከራከራቸው ክክርክሩ ትክክለኛ ገጽ ታይቷል። /ክክርክሩ ትክክለኛ ገጽ/ ይህ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ክሱን ያመኑ ይመስል ገና ከጅምሩ ድንጋጌውን አጥብቦ በመተርጎም የልጅነት ጥያቄ ቢነሣ ድንጋጌው ተፈፃሚነት የለውም ማለቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም። ይህ ድንጋጌ መገኛው አንቀጽ 999 ሆኖ እውነተኛ ወራሽ እኔ ነኝ ከሚል ጥያቄ ጀምሮ የውርስ ንብረት ያላግባብ ተወስዷልና ይመለስልኝ በማለት የሚቀርቡትን ክሶች /ጥያቄዎች/ የሚያካትት ለመሆኑ አንቀጽ 999ን መመልከቱ ይበቃል። በዚህ ረገድ አመልካች ክርክሩን ባስነሳው ቤት ላይ ከ20 ዓመት በላይ የቆየ የባለሀብትነት ድርሻ ማግኘታቸው እየተመለከትም፤ ተጠሪም ድርሻቸውን ለመጠየቅ ከሚያስችላቸው ጊዜ በላይ ቆይተው ክስ ለማቅረባቸው አመልካች ያቀረቡት የይርጋ ክርክር ተቀባይነት ያጣው ድንጋጌው በጠባቡ በሥር ፍርድ ቤት በመተረጎሙ ሳቢያ መሆኑን ይህ ፍ/ቤት ተገንዝቧል። በመሆኑም የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይርጋውን ነጥብ አልፎ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል።

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ምንም እንኳ የአመልካችን ልጅነት ተቀብሎ የሥር ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሻረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ለይርጋው ጥያቄ በቅድሚያ ምላሽ ቢሰጥ ኖሮ ወደዚህ ነጥብ መግባት የሚያስፈለገው እንዳልነበር ተገንዝበናል። ስለሆነም ክሱ በይርጋ ታግዷል ብለናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 21679 ግንቦት 23 ቀን 1988 ዓ.ም. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 03562 ጥር 19 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጧቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፤ ይፃፍ።
- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 28193 ሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፤ ይፃፍ።

- የከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁ. 28193 በመጣበት አካኋን በመሸኛ ተመልሶ ይላክ።
- መዝገቡ ተዘግቷል።
- ክሱ በይርጋ ይታገዳል ተብሏል።
- መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 25664

ግንቦት 07 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መድኅን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ተገኝ ይማም አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ካሣሁን ደሳለኝ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ነሐሴ 7 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ እህታችን ወ/ሮ ያልጋ ደሳለኝ እና አቶ ተገኝ ይማም ተጋብተው እየኖሩ ሳሉ እህታችን ጥቅምት 11 ቀን 1982 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለየች አብረው የሠሩትን ቤትና አብረው ያፈሩትን ሌላ ንብረት ለእኛው ለሟች ወራሾች ግማሹን እንዲሰጡን እንዲወሰንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ደግሞ በታህሳስ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት መልስ ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1000(2) እና 1845 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚገባው ነው፡፡ ከሟች ጋር ከግብረ ሥጋ ግንኙነት በስተቀር የጋብቻ ግንኙነት አልነበረንም፡፡ ቤቱ የግል ንብረቴ ነው፤ የሌሎቹን ንብረቶች ግምትም የተጋነነ ነው፡፡ በመሆኑም ክሱ ውድቅ ሆኖ ልሰናበት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ ክሱ በይርጋ ቀሪ አይሆንም፡፡ ተከሣሾቹ የሟችን ግማሽ ንብረት ለከሣሾች እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ ከተመለከተ በኋላ የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም ሲሆን አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ ክሱ የቀረበው ሟች ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየች ከአሥራ ሦስት ዓመት በኋላ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1000(2) እና 1845 መሠረት በይርጋ ቀሪ መሆን ያለበት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የይርጋ ክርክሬን ውድቅ በማድረግ በእኔ ላይ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔና ፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሻሩልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ ክሱ በይርጋ አይታገድም መባሉ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል አቤቱታው ያስቀርባል የሚል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች ደግሞ ባቀረቡት መልስ እህታችን ከሞተች አሥራ አምስት ዓመት ሳያልፍ ነው ክስ የመሠረትነው በመሆኑም ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1000(2) መሠረት በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ/1845 ደግሞ ተግባራዊ የሚሆነው ውልን መሠረት በማድረግ በሚቀርቡት ክርክሮች ላይ እንጂ የውርስ ክርክርን በሚመለከት አይደለም፡፡ በዚሁ ምክንያት ክሱ በይርጋ የሚታገድበት ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ ክሱን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻልነውም ከተጠሪዎቹ አንዱ የሆነው አቶ ካሣሁን ደሳለኝ በሻዕቢያ መንግሥት የተከፈተብንን ወረራ ለመመከት በመዝመቱ ምክንያት ሳይሰማ በመቅረቱ ምክንያት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔም የሚነቀፍበት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና እንዲወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን እንደመረመርነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1000(2) መሠረት የይርጋ ጥያቄ የሚነሳው ክርክሩ እየተደረገ ያለው በወራሾች መካከል ሲሆን በመሆኑና በዚህ ጉዳይ ክስ የቀረበው በወራሽ ላይ ባለመሆኑ ክሱ በዚሁ የሕግ ቁጥር መሠረት በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የለም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል ደግሞ ክርክሩ እየተካሄደ ያለው በወራሾችና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል በመሆኑ ተጠሪዎች የእህታቸውን ንብረት የያዙትን አመልካች ንብረቱን እንዲያካፍላቸው ለመጠየቅ የሚከለክላቸው ወይም በጊዜ እንዳይጠይቁ የሚያደርጋቸው ሕጋዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ክስ ሳይመሠርቱ ከአሥር ዓመት በላይ የቆዩበትን ሁኔታ ስንመለከት ጥያቄው የይርጋ ክርክር ሊያስነሣ የሚችል ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም አመልካች ያነሱትን የይርጋ መቃወሚያ አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/1677 እና 1845 አንፃር መታየት የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል። በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1677(1) እንደተመለከተው ግዴታው ከውሉ የተገኘ ባይሆንም በፍትሐብሔር ሕጉ አራተኛ መፀሐፍ በአንቀጽ 12 ሥር የተመለከቱት ስለ ውሎች በጠቅላላው የተቀመጡት ድንጋጌዎች በግዴታው ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። በእርግጥ የአንዳንድ ግዴታዎችን አመጣጥ ወይም ዓይነት በመመልከት ከተጠቀሰው አንቀጽ ሥር ከተመለከቱት ደንቦች የተለዩ ድንጋጌዎች በሕግ ተመልክቶ ከተገኘ እነዚህ በተለይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብነት እንደሚኖራቸው በተጠቀሰው ቁ.1677(2) ተመልክቷል።

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች የመሠረቱትን ክስ በተመለከተ በተለይ አግባብ ያለው የይርጋ ደንብ የለም። የግዴታውን አመጣጥ ወይም አይነት በሚመለከት አግባብ ያለው የይርጋ ደንብ ከሌለ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ1845 የተደነገገው የአሥር አመት ገደብ/ይርጋ/ ሊፈፀምበት እንደሚገባ ግልጽ ነው። ክሱ የቀረበው ሟች ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩ ከአሥራ ሦስት ዓመት በኋላ በመሆኑም በዚሁ የይርጋ ደንብ ተቋርጧል ማለት ነው። እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ የሥር ፍ/ቤቶች በይርጋ ረገድ የቀረበውን የአመልካች መቃወሚያ ውድቅ ያደረጉት ያለአግባብ ከሕጉ ውጪ ነው። ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል።

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/31726 ህዳር 1 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠውና የፌ/ከ/ቤት በመ/ቁ/34855 ግንቦት 8 ቀን 1998 ዓ.ም ያፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348(1) መሠረት ተሽሯል። ይፃፍ።
2. ተጠሪዎች በአመልካች ላይ የመሠረቱት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ወስነናል። ይፃፍ። ውሣኔው የተሰጠው በድምጽ ብልጫ ነው።
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙን ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>የልዩነት ውሣኔ</u>

እኔ በአራተኛ ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ ተጠሪዎች የሟች እህታቸው ወ/ሮ ያልጋ ደሣለኝ ከተጠሪው ጋር በጋብቻ በነበረችበት ወቅት አፍርታ የነበረውን ቤትና ሌሎች የጋራ ንብረቶች ተጠሪው እንዲያካፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1677 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት በይርጋ ስለሚታገድ ተቀባይነት የለውም የማለት በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማሁ በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ።

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ከላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የተጠሪዎች አውራሽ የሆነችው ወ/ሮ ያልጋ ደሣለኝ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችው ጥቅምት 11 ቀን 1982 ዓ.ም ነው። ተጠሪዎች አመልካች የሟችን የውርስ ንብረት እንዲያካፍላቸው ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት ነሐሴ 7 ቀን 1995 ዓ.ም ነው። ተጠሪዎች የሟች ውርስ በአመልካች እጅ መሆኑን ያወቁት በሐምሌ ወር 1993 ዓ.ም እንደሆነ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መጋቢት 7 ቀን 1996 ዓ.ም በሰጠው ብይን በግልጽ ተመልክቷል። ይሽም ሲሰላ፤ ተጠሪዎች የወራሽነት ጥያቄያውን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 መሠረት ያቀረቡት ሟች ከሞተች ከአሥራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሦስት ዓመት ከአሥር ወር ውስጥ የሚች ንብረት በአመልካች እጅ መሆኑን ካወቁበት ሁለት ዓመት እንደሆነ ያመለክታል፡፡

ከላይ የተመለከቱት ፍሬ ጉዳዮች ሲመዘኑ ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የሦስት ዓመት የይርጋ ገደብም ሆነ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው የአሥራ አምስት ዓመት የይርጋ ገደብ ከማለፉ በፊት ቢሆንም አብላጫው ድምጽ ከላይ የተገለፀውን ውሳኔ የሰጠው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚያገለግለው ክርክሩ በሚች ወራሾች መካከል በሚደረግበት ጊዜ እንጂ የሚች ወራሾች ወራሽ ካልሆነ ሰው ጋር በሚከራከሩበት ጊዜ ተጠቃሽነትም ሆነ ተፈፃሚነት የለውም የሚል የሕግ ትርጓሜ በመስጠት ነው፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1677/1/ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት በይርጋ ይታገዳል የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በእኔ በኩል ይህ አበላጫው ድምጽ በሰጠው የህግ ትርጓሜና ውሣኔ የማልስማማው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡፡

1. በሚች ወራሾች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን በመሠረታዊነት በሁለት ክፍሎ ማየትና በእነዚህም ክርክሮች ላይ ተፈፃሚነት የሚኖራቸውን፣ የይርጋ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ የሚች ያለኑዛዜ ወራሾች፣ በሚች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሾችና በሚች ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተቀባዮች መካከል በመጀመሪያ ክርክር የሚነሣው በውርስ ማጣራት ሂደት ውስጥ የውርስ አጣሪው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 971 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 972 መሠረት የሚችን የኑዛዜና ያለኑዛዜ ወራሾች እንደዚሁም የውርስ ንብረቱ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ ሲያሣውቃቸው ነው፡፡ የሚች ወራሾች የውርስ አጣሪ ሀሣቡን ከገለፀ በኋላ የሚች ኑዛዜ ነው ተብሎ በአጣሪው እውቅና የተሰጠውን የኑዛዜ ሰነድ በመቃወም ወይም አጣሪው ስለውርሱ ንብረት አከፋፈል ያቀረበውን የውሣኔ ሀሣብ በመቃወም እርስ በርሳቸው ወይም ከውርስ አጣሪው ጋር የሚራከሩበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

የሚች ወራሾች ከላይ በተገለፁት የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የውርስ አጣሪውን የውሣኔ ሀሣብ የሚቃወሙ ከሆነ ሀሣቡን የሚቃወሙበት የጊዜ ገደብና የአጣሪው ውሣኔ ፈራሽ እንዲሆን ክስ የሚያቀርቡበት የይርጋ የጊዜ ገደብ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 973 እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 974 ተደንግጓል፡፡ ሕግ አውጪው በሚች የኑዛዜና ያለ ኑዛዜ ወራሾች መካከል ውርሱ እየተጣራ ባለበት ሂደት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 973 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 974 መሠረት ይፈታል በሚል እምነት የይርጋ የጊዜ ገደቦችን አስቀምጧል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ሕግ አውጪው በሚች ውርስ አወራረስ ሥርዓት ውስጥ መሠረታዊና ቁልፍ የሥራ ሂደት አድርጐ የሚመለከተው የውርስ ማጣራት ሒደትን ሲሆን የሚችን ውርስ በአግባቡ ለማጣራት ይቻል ዘንድ አንድ መቶ ዘጠኝ የሚሆኑ ድንጋጌዎችን ማለትም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 942 እስከ ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1051 ደንግጓል፡፡ ሆኖም የሚች ውርስ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት በአግባቡ የማይጣራ በመሆኑ በሚች ወራሾች መካከል በፍርድ ቤቶች የሚካሄዱ ክርክሮች ይታያሉ፡፡ ስለሆነም በሚች ወራሾች መካከል የሚደረገው ክርክር ባህሪ በመለየት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 973 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 974 የተደነገጉት የይርጋ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በሚሆኑበት አግባብ ለሕጉ ትርጓሜ መስጠት ሲገባ በወራሾች መካከል ውርሱ በሚጣራበት ጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ ለሚነሱ ክርክሮች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ የይርጋ ገደብ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን የሚያሣይ ትርጓሜ መስጠቱ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡

2. በሁለተኛ ደረጃ በሚች ወራሾች መካከል ክርክር የሚነሣው የሚችን ውርስ የማጣራት ሂደት ከተዘጋ በኋላ በተለይም የሚች ንብረት ክፍፍል ከተደረገ በኋላ ነው፡፡ የሚች ውርስ ንብረት በወራሾች መካከል መከፈል ያለበት ሁሉም የሚች ወራሾች ወይም ወኪላቸው በተገኘበት መሆን እንዳለበትና የሚች ውርስ ክፍያ አንደኛው ወራሽ ወይም ወኪሉ በሌለበት የተፈፀመ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሆነና ክፍያውን ዳኞች ካላፀደቁት በቀር ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1080 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡

የሚች አንደኛው ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ህጋዊ ወራሾቹ በሌሉበት ወይም ወኪላቸው ባልተኘበት ሁኔታ ይልቁንም ሚች ሌላ ወራሽ እንደሌለው በመቁጠር የሚች ውርስ ሲከፈል የነበሩት የሚች ወራሾች የሚችን ንብረት ተከፋፍለው ቢወስዱ የሚች ውርስ ሲከፈል ያልነበረው ወራሽ ክፍያው ፈራሽ እንዲሆንና እሱ ባለበት እንደገና የውርስ ንብረቱ ተከፍሎ ድርሻው እንዲሰጠው መጠየቅ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1080 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ እሱ በሌለበት ሌሎች የሚች ወራሾች የሚችን ንብረት ተከፋፍለው የደረሰ የሚች ወራሽ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1080 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተደረገው የውርስ ንብረት ክፍያ እንዲፈርስና የእሱ ድርሻ እንዲሰጠው መጠየቅ የሚችልበትን የይርጋ የጊዜ ገደብ በተመለከተ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1080 ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡ ይኸውም የውርስ ክፍያ ሲከናወን ያልነበረው ወራሽ ክፍያውን ካወቀበት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ሚች ከሞተበት ቀን አንስቶ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ጥያቄው ውድቅ እንደሚሆን በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም በሚች ወራሾች መካከል የሚች ውርስ ከተዘጋ በኋላ የሚኖረው ክርክር የውርስ ሀብቱን ያካፍለኝ የሚል መሆኑና እንደዚህ አይነት ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው የሚች ውርስ ክፍያ መደረጉን ካወቀበት በአንድ ዓመት ውስጥ ወይም ሚች ከሞተበት ቀን አንስቶ ደግሞ በአሥር ዓመት ውስጥ ካልቀረበ ተቀባይነት እንደሌለው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1080 ንዑስ አንቀጽ 3 በግልጽ በሚደነግግበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 የይርጋ ድንጋጌዎች በወራሾች መካከል ለሚደረግ ክርክር ተፈፃሚነት ያላቸው ናቸው በማለት አብላጫው ድምጽ የሰጠው ትርጉም አግባኝ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

3. ከላይ በተራ ቁጥር አንድና ሁለት ለመግለጽ እንደሞከርኩት የሚች ወራሾች የሚች ውርስ በመጣራት ሒደት ላይ እያለም ሆነ የሚች ውርስ ከተዘጋና የውርስ ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ የሚያቀርቡትን ክርክር በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ማቅረብ እንደሚባቸው ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 973፣ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 974 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1080 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ተደንግጓል፡፡ እነዚህ የይርጋ የሕግ ድንጋጌዎች ባሉበት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000 በሚች ወራሾች መካከል ያለን የይርጋ የጊዜ ገደብ ለመወሰን ነው የተቀመጠው የሚለው ትርጓሜ ከመያዙ በፊት የእነዚህን ድንጋጌዎች ዓላማና የተፈፃሚነት ወሰን በትኩረት ማየት ይጠይቃል፡፡

በእኔ በኩል ከላይ የተገለፁትን የይርጋ ድንጋጌዎች ህግ አውጪው በወራሾች መካከል የሚነሳውን ክርክር ለመዳኘት አስቦ የደነገገ ሲሆን የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000 የይርጋ ድንጋጌዎች ግን የሚች ሕጋዊ ወራሽ በሆነ ሰውና የሚች ወራሽ ባልሆነ ሰው መካከል የሚችን ውርስ ንብረት አስመልክቶ የሚደረገውን ክርክር የጊዜ ገደብ ለመወሰን የደነገጋቸው ናቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ ሕግ አውጪው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ድንጋጌዎች የሚች ወራሾች ያልሆኑ ሰዎች በሚያደርጉት ክርክር ተፈፃሚነት እንዲኖረው በማሰብ የደነገገ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1002 ያሉትን ድንጋጌዎች ያስቀመጠበትን አግባብ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የእነዚህን ድንጋጌዎች ርዕስና አቀማመጥ ስንመለከት

- የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 የወራሽነት ጥያቄ /1/ መሠረቱ
- የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 /2/ ጥያቄው ለማቅረብ የተወሰነ ጊዜ
- የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1001 /3/ ውጤቱ
- የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1002/4/ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ የተደረገላቸው ሰዎች በማለት ከአንድ እስከ አራት ተከታታይ ቁጥር በመስጠት ደንግጓቸዋል፡፡ ይህንንም በማድረግ ሕግ አውጪው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 እስከ 1002 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተከታታይና ተያያዥነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላቸው በተለይም ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 እስከ ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1002 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ ለማስፈፀም የሚረዱ ዝርዝር ድንጋጌዎች መሆናቸውን የሕግ አቀራረጽ ጥበብንና የድንጋጌዎች አደረጃጀትን በመጠቀም ለማሣየት ሞክሯል፡፡

ስለሆነም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ድንጋጌዎች በራሳቸው ተነጥለው የሚቆሙና የሚተረጎሙ ሳይሆኑ ሕግ አውጪው መሠረታዊ መርህ ነው በማለት በግልጽ ካስቀመጠው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 ጋር ተያያዥነት ያላቸውና በይዘትም ሆነ በትርጓሜያቸው ከዚሁ ጋር መታየት ያለባቸው የወራሽነት ጥያቄ መሠረታዊ መርህ እንደሆኑ በግልጽ በርዕሱ ላይ በማመልከት ሕግ አውጪው የደነገገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 አንድ ሰው ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሣይኖረው ውርስን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል ብቻ በእጁ ያደረገ እንደሆነ እውነተኛው ወራሽነቱ እንዲታወቅለት እና የተወሰዱት የውርስ ንብረቶች እንዲመለስለት በዚህ ሰው ላይ የወራሽነት ጥያቄ ክስ ለማቅረብ እንደሚችል የሚደነግግ ሲሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ደግሞ እውነተኛው ወራሽ፣ ወራሽ ካልሆነው ሰው ላይ የውርስ ንብረቱ እንዲመለስለት ክስ የሚያቀርብበትን የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚደነግግ ነው፡፡

ስለሆነም በእኔ በኩል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ድንጋጌዎች የሚች እውነተኛ ወራሽ የሆነ ሰው የሚች ወራሽ ካልሆነ ማናቸውም ሰው ላይ የውርሱን ንብረት ለማስመለስ የሚያቀርበውን ክስ የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚይደነግጉ መሆናቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ አከራካሪው ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ንዑስ አንቀጽ 2 የተፈፃሚነት ወሰንና አተረጓጎም ነው፡፡ ስለሆነም የሚች ውርስ ንብረት ክፍያና ከሚች ውርስ ሊደርሰኝ የሚገባው ድርሻ አልደረሰኝም በማለት የሚች ወራሾች በሌሎቹ ውርሱን በተካፈሉት ወራሾች ላይ የሚያቀርቡት ክስ የይርጋ የጊዜ ገደብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1080 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገ

በመሆኑና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚች ወራሽ የሚች ወራሽ ካልሆነ ሰው የውርሱን ንብረት ለማስመለስ የሚያቀርበውን የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚደነግግ በመሆኑ ተጠሪዎች ያቀረቡት የወራኝነት ጥያቄ አሥራ አምስት ዓመት ያልሞላው በመሆኑ በይርጋ አይቋረጥም የሚል የሀሣብ ልዩነት አለኝ፡፡

4. ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥናቸው የውርስ ሕግ ልዩ የይርጋ ድንጋጌዎች ባሉበት ሁኔታ አብላጫው ድምጽ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845ን ለመጠቀም መሞከሩ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1845 ድንጋጌን የሚቃረን ነው፡፡ ምክንያቱም የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1845 ተፈፃሚነት የሚኖረው “ሕግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር; እንደሆነ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ በሚች ወራሾች መካከል የሚደረገውን ክርክር የይርጋ የጊዜ ገደብ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 973 የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 974 እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1080 ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡ የእነዚህን ድንጋጌዎች መሠረታዊ ዓላማና የተፈፃሚነት ወሰን በመተርጎም በሚች ወራሾች መካከል የሚነሣውን ክርክር የይርጋ የጊዜ ገደብ መወሰን በሚቻልበት ሁኔታ ሕግ አወጪው አንድ ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የውርስ ንብረት እንዲመልስለት ወራሽ ባልሆነ ሰው ላይ የሚያቀርበውን ክስ ለመዳኘት በማሰብ የደነገገውን የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1000፣ በወራሾች መካከል ባለ ክርክር ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ ነው የሚል ትርጓሜ መስጠትና በወራሾችና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረገውን ክርክር የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚደነግግ የውርስ ሕግ ድንጋጌ ስለሌለ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ተፈፃሚነት ሊኖረው ይገባል በማለት አብላጫው ድምጽ የሰጠው መደምደሚያ ከላይ ባነሣኋቸው ምክንያቶች ተገቢ ናቸው ብዬ ስለማላስብ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች በአመልካችና በተጠሪዎች ጉዳይ ተፈፃሚነት ያላቸው ናቸው፡፡ የተጠሪዎችም የወራሽነት ክስ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 26422

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፣ ወ/ሮ ስንልሽ ማዘንጊያ - ጠበቃ ቀረበ

ተጠሪ፣ እነ አቶ ተስፋ ማዘንጊያ - ቀርበዋል

መዝገቡን መርምረን የሚተለውን ፍርድ ሰጥተናል፣

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ ጉዳይ የአሁኖቹ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ጎዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ፣የአሁኗ አመልካች ግምቱ ብር 190,850 (የአንድ መቶ ዘጠና ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ) የሆነና ከአውራሻችን ከወ/ሮ የንጉሤ ማዘንጊያ የሚደርሰንን የውርስ ንብረት የያዘች ስለሆነ የውርስ ንብረት ታካፍለን የሚል ነው፡፡ የአሁን አመልካች ለክሱ ከሰጠችው መልሶች መካከል፣አሁን የተጠየቀውን የውርስ ንብረት ወራሽ መሆኔ በፍ/ቤት ተረጋግጦ ላለፉት 10 ዓመታት በእጄ የቆየ ስለሆነ ተጠሪዎች በይርጋ ቀሪ የሆነን ጉዳይ አንስተው ሊጠይቁኝ አይገባም የሚል ይገኝበታል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት የሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኗን አመልካች የይርጋ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የውርስ ንብረቱን ከሳሽና ተከሳሾች እኩል ይካፈሉ ብሏል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የቀረበለት የአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው በዚህ ላይ የቀረበ ሲሆን ፣ይህ ችሎት የካቲት 13 ቀን 1999 በዋለው ችሎት የሥር ፍ/ቤት የይርጋ ጥያቄውን ያለፈው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን

ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰኔ 26 ቀን 1999 ሰምቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት የይርጋውን ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት ዋነኛ ምክንያት የአሁኗ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን የውርስ ንብረቶች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 /2/ በሚደነግገው መሠረት ከ15 ዓመት በላይ በይዞታዋ ስር ስላላደረገች ክሱ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ አውራሽ የተባሉት ወ/ሮ የንጉሤ ማዘንጊያ መጋቢት 7 ቀን 1988 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑ ታውቋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ግንቦት 15 ቀን 1989 ዓ.ም የሚች ሕጋዊ ወራሽ መሆኗ ተረጋግጦ ንብረቱን ይዛ ስትገለገልበት ስለመቆየቷም ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ መረዳት ተችሏል፡፡ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ደግሞ በዚሁ ከተማ እየኖሩ ላለፉት 10 ዓመታት በተከሳሽ የተያዙትን የውርስ ንብረቶች ሳይጠይቁ መቆየታቸው ታውቋል፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 /1/ መሠረት ከሳሽ መብቱንና የውርስ ንብረቶች በተከሳሹ መያዛቸውን ካወቀ ሦስት ዓመት በኋላ ስለወራሽነት ጥያቄ የሚቀርበው ክስ ተቀባይነት ለማግኘት አይችልም በሚል ተደንግጓል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህን መሠረታዊ የይርጋ ሕግ ወደ ጐን በመተው ግራ ቀኙ እየተከራከሩበት ያለው የውርስ ንብረት ከዘር የወረደ ርስት እንደሆነ በመቁጠር ለጉዳዩ አግባብ ያልሆነ ሕግ ጠቅሶ የይርጋ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉ መሠታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የተጠሪዎች የውርስ ንብረት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ብለናል፣
- የአ/ብ/ክ/መ የሰሜን ጎንደር መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 15 ቀን 1998 ቁጥር 13047 በሆነ መዝገብ የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 09867 በሐምሌ 17 1998 ዓ.ም የሰጧቸው ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡
- የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፣
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 28686

ኅዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡-

መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ- ነ/ፊጅ አቶ ዓለሙ ኢብሳ

ተጠሪ፡- አቶ ግዛው መንጀታ - ጠበቃ አቶ ማርቆስ ወ/ሰንበት

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ በወረዳ 5 ቀበሌ 07 ክልል ቁጥር 1354 የሆነውን ቤት ጥቅምት 1 ቀን 1977 ዓ.ም በተፈረመ ውል ለመኖሪያ አገልግሎት ተከራይቶ የነበረ ሲሆን ያለ አከራዩ ፈቃድ ወደ ምግብ ቤት በመለወጥ የንግድ ሥራ እየሠራበት ስለሚገኝ የኪራይ ውል ተሰርዞ ቤቱን እንዲያስረክብ በማለት ጠይቆ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተከሳሽ ለመኖሪያነት የተከራዮትን ቤት ወደ ንግድ ቤት መቀየራቸውን ከሳሽ ያወቀው በ1979 ዓ.ም ሲሆን ክሱን በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ሲገባው ጊዜው ካለፈ በኋላ ያቀረበ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ውሳኔ በመስጠቱና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/337 መሠረት ይግባኙን በመሠረዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎቱም በአመልካች በኩል የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ቁብጥ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል? የሚለው በመሆኑ ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

ውል ባለመፈጸሙ ምክንያት እንዲፈጸም በመጠየቅ ወይም በውል አለመፈጸም ምክንያት የጉዳት ኪሣራ በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ ወይንም እንዲሰረዝ በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ በ10 ዓመት የጊዜ ግደብ ካልቀረበ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1845 ላይ የመለከተ ሲሆን የይርጋው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረውም ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም ውሉ የሚሰጠው መብት ከተሠራበት ቀን ጀምሮ እንደሆነ በቁጥር 1846 ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተው ለመኖሪያ ቤት የተከራየውን ቤት ወደ ንግድ ቤትነት የቀየረ ስለሆነና ይህም ውሉን መጣስ ስለሆነ ውሉ በፍርድ ተሰርዞ ቤቱን እንድረከብ ይወሰንልኝ በማለት እንደመሆኑ መጠን የውል መጣስ ተግባሩ በዚህ ቀን ተጀምሮ በዚህ ቀን ቆሟል ለማለት ከውሉ ባህሪይ አኳያ የማይቻል ከመሆኑም በላይ አሁንም እየቀጠለ ያለ ተግባር በመሆኑ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1846 መሠረት በማናቸውም ጊዜ ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ስለሚሆን ተጠሪ የመኖሪያ ቤቱን ወደ ንግድ ቤት ከቀየሩበት ጊዜ ጀምሮ 10 ዓመት በመቁጠር የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ሳይቀበለው መቅረቱና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ማጽናቱ ከውሉ ባህርይም ሆነ ከሕጉ ጋር ያልተገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ቀጥሎ የተመለከተው ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 34077 መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 46125 ጎዳር 29 ቀን 1999ዓ.ም አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሰጧቸው ውሳኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348 (1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ያልሆነ ስለሆነ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ የበኩሉን ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ 341 መሠት ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተገዝቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 28997

ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሰ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ስለአሶሳ ዞን ግብርና እና ትምህርት መምሪያዎች የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መንግሥት ፍትህ ቢሮ፣

ተጠሪ፡- - በላይ ወርቁ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ፡-

ጉዳዩ ይዞታዬ በተከሣሾች በመወሰዱ በላዩ ላይ (በመሬቱ ላይ) የነበሩትን ልዩ ልዩ ተክሎች ግምት በካሣ መልክ ይክፈለኝ በሚል ተጠሪ በመሠረተው ክስ መነሻነት የተጀመረውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቤኒሻንጉል ብ/ክ/መ በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ፍ/ቤቱ ከሣሽና ተከሣሾች ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሣሾች ብር 148,600 (መቶ አርባ ስምንት ሺ ስድስት መቶ) ለከሣሽ ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሥር ተከሣሾች ውሣኔውን በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማለታቸው ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የኃላፊነቱን መጠን ብቻ በማሻሻል ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺህ) እንዲከፈል በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የሥር ተከሣሾችን በመወከል የካቲት 9 ቀን 99 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪውን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ተከሣሾች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት የይርጋ ክርክር የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምናል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ ላቀረበው የካሣ ጥያቄ መነሻ የሆነው መሬት ተወሰደ የተባለው በ1984 ዓ.ም ሆኖ ተጠሪ የካሣ ይከፈለኝ ክሱን ለፍ/ቤት ያቀረበው ደግሞ በ1998 ዓ.ም ነው፡፡ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበውም ከውል ውጭ የደረሰን ኃላፊነት መሠረት በማድረግ የቀረበው የካሣ ክፍያ ጥያቄ በፍ/ብ/ ሕግ ቁ 2143 መሠረት በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ጉዳቱ ደረሰ የተባለበትን ጊዜ እና ክሱ የቀረበበትን ጊዜ በማስመልከት የቀረበው የፍሬ ነገር ክርክር ትክክል መሆኑን ግንዛቤ ወስደዋል፡፡ የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረጉትም ክርክሩን በማስረጃ አላስደገፉም በማለት ሳይሆን፣ ተጠሪ ክሱን ከመመስረቱ በፊት ለከተማው ማዘጋጃ ቤት ጥያቄ አቅርቦ ስለነበር የይርጋው አቆጣጠር በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1851 በተደነገገው መሠረት ተቋርጦአል የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ ከ1998 ዓ.ም ዓ.ም በፊት በየትኛውም ፍ/ቤት ክስ አልመሠረተም፡፡ ይህም ማለት በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1851(ለ) እንደተመለከተው መብቱ እንዲታወቅለት በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ካሣ ሊከፍሉኝ ይገባል ለሚላቸው ሰዎች (አካላት) አስታውቆ አልተገኘም፡፡ ተከሣሾችም ቢሆኑ እዳውን አምነው ተገኝተዋል አልተባለም፡፡ እነዚህ በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ባልተገኙበት ጊዜ በሕጉ የተቀመጠው የይርጋ አቆጣጠር ተቋርጦአል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ተጠሪ መሬቱን ወስዷል ወይም አስወስዷል ላለው የከተማው ማዘጋጃ ቤት ጥያቄ አቅርቦ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ግን የይርጋ ማቋረጫ ሁኔታ ተደርጎ በሕጉ የተቀመጠ ባለመሆኑ ተጠሪ መከራከሪያ ሊያደርገው አይችልም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህንኑ መከራከሪያ በመቀበል

መወሰናቸው ትክክል አይደለም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የቤኒሻንጉል ጉምዝ ብ/ክ/መ/የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 1359 ሐምሌ 21 ቀን 98 ዓ.ም የሰጠውና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.916 ጥር 21 ቀን 99 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበው የካሣ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ብለናል፡፡
3. ወጭና ኪሣራ ግራቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት የዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 29920

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የባህርዳር ጨ/ጨ/አ/ማኅበር - ነ/ፈጅ ኃ/የሱስ ደምሴ - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አመሸ ሰይድ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ከነበርኩበት የሥራ ደረጃ ያለአግባብ ዝቅ የተደረግሁ ስለሆነ በደረጃዬ እንድመደብ ይወሰንልኝ የሚል ክስ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በአመልካች በኩል የቀረበን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ የኋላ ክፍያ ሣይጠይቅ በጠየቀው የሥራ መደብ ተመድቦ እንዲሰራ በማለት ውሣኔ ሠጥቶ በዚህ ውሣኔ ላይ ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ቅሬታ አድሮባቸው በየበኩላቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለምዓራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ሁለቱም የይግባኝ መዝገቦች ተጣምረው እንዲታዩ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ በተመለከተ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አሻሽሎ ይ/ባይ በደረጃ 9 ከተመደበበት ቀን ጀምሮ ያለውን ክፍያ መ/ሰጭ ሊከፍለው ይገባል የሚል ውሣኔ በመስጠቱና አመልካች በበኩሉ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ምንም ሣይባል በመታለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ ቀደም ሲል ክሱን ለወረዳ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው

የአሠሪና ሠራተኛ ወሣኝ ቦርድ ነው በማለቱ ክሱን ለአሠሪና ሠራተኛ ወሣኝ ቦርድ አቅርቦ ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ተብሎ ከተወሰነ በኋላ ተጠሪ በድጋሚ ክሱን ለወረዳ ፍ/ቤት ሲያቀርብ አመልካች ያነሣው የይርጋ ክርክር ተቀባይነት ሣያገኝ መቅረቱ ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባ በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ወይንስ አልሆነም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪ ከላይ የተመለከተውን ክስ ለባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ሲያቀርብ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር የተፈፀመው በ1994 ዓ.ም ሲሆን ክሱ ግን የቀረበው በ1998 ዓ.ም ከ4 ዓመት በኋላ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የመጀመያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም ጉደዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ክርክሩ የግል የሥራ ክርክር እንጂ የወል የሥራ ክርክር ስላልሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አለው በማለት ውሣኔ የሰጠ ስለሆነ መቃወሚያው በአግባቡ አልቀረበም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሣሽ የሆነ ወገን ክሱን ለፍ/ቤት ከማቅረቡ በፊት የትኛው ፍ/ቤት ክሱን ለማየት የግዛትና የሥረ ነገር ሥልጣን እንዳለው አጣርቶ ማቅረብ እንዳለበት ይታመናል፡፡ በዚሁ መሠረትም ተጠሪ ክሱን በቅድሚያ ለባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት አቅርቦ ነበር፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ ጉደዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም ሲል ከሣሹ/ተጠሪ/ የመረጠው ይግባኝ ማለትን ሣይሆን ክሱን ለአሠሪና ሠራተኛ ወሣኝ ቦርድ ማቅረብን በመሆኑ በዚሁ መሠረት ክሱን ለቦርዱ አቅረቦ ክርክሩ ቀጥሎ መጨረሻ ጉዳዩ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ችሎቱም የዚህ ዓይነት ክርክር በወል የሥራ ክርክር ሊሸፈን ስለማይችል ቦርዱ ይህን ጉዳይ ተመልክቶ ውሣኔ የሰጠው ሥልጣን ሣይኖረው ነው በማለት የበኩሉን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በኋላ ተጠሪ ክሱን ለባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ሲያቀርብ ክሱ በይርጋ ቀሪ መሆኑን በመግለጽ አመልካች የይርጋ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ክስ የይርጋ ጊዜ ከፍተኛው 1 ዓመት እንደሆነ በአሠሪና ሠራተኛ አ/ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህ የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት ተጠሪ በቅድሚያ ክሱን ለወረዳ ፍ/ቤት አቅርቦ ነበር፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት ክሱን ሣይቀበል ሲቀር ክርክሩ የግል የሥራ ክርክር ከመሆኑ አኳያ በይግባኝ ሥነ ሥርዓት በመጠቀም ይህንኑ ውሣኔ ተጠሪ ማስለወጥ ሲገባው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ለሌለው ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክሱን ማቅረብ አልነበረበትም፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ/ቁ 15722 ግራ ቀኙን አከራክሮ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንፃር ይህንን ጉዳይ ለማየት የሥረ - ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ውሣኔ ከመስጠቱ በስተቀር አስቀድሞ ክርክሩ በተጀመረበት በባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ክርክሩ ይቀጥል በማለት ውሣኔ አልሰጠም፡፡

ስለሆነም ለባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ድጋሚ ክስ ሲቀርብ በሕጉ ላይ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ካለፈ ከ4 ዓመት በኋላ ቀርቦ ባለበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ የይርጋ መቃወሚያውን ሊቀበለው ሲገባ ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡት ይግባኝ ተጣምሮ እንደሚታይ ትእዛዝ የሰጠ ቢሆንም በተጠሪ በኩል የቀረበውን ይግባኝ መርምሮ ከመወሰኑ በስተቀር የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ ሣይመለከተው አልፎታል፡፡

ዳኝነት የተጠየቀበት ነገር ተቀባይነት ሣያገኝ የታለፈ እንደሆነ እንደተከለከለ እንደሚቆጠር በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5(3) ላይ የተመለከተ ስለሆነ

በዚህም ጉዳይ ይርጋን አስመልክቶ አመልካች ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ቅሬታ ስለታለፈ እንደተከለከለ የሚቆጠር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ሐምሌ 17 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚሁ ጉዳይ መጋቢት 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ ክሱ ያቀረበው በሕጉ ላይ የተቀመጠው ጊዜ ካለፈ በኋላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 31185

ግንቦት 12 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በመድን ውል ላይ የተመሠረተን ይርጋ የሚመለከት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁን አመልካችና በሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች ላይ ባቀረበው ክስ 1ኛ ተከሣሽ በሚያዝያ 13 ቀን 1989 ዓ.ም በተፈረመ ውል ከከሣሽ ብር 3000 ሺህ ሲበደር በ2ኛ ተከሣሽ ስም የተመዘገበች መኪና በዋስትና አስይዟል፡፡ በብድሩ ውል መሠረት 1ኛ ተከሣሽ ዕዳውን አጠናቆ ሳይከፍል በዋስትና የተያዘችው መኪና ጉዳት የደረሰባት ስለሆነና ከሣሽ በመድን ውሉ መሠረት 3ኛ ተከሣሽ ለ1ኛ ተከሣሽ ሊከፍለው የሚገባው ገንዘብ ቅድሚያ መብት ስላለው 3ኛ ተከሣሽም ለመክፈል ፈቃደኛ ሆኖ ነገር ግን ዛሬ ነገ በማለት ክፍያውን ሳይፈጽም ስለቀረ ሦስቱም ተከሣሾች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ይወስንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የሥር 3ኛ ተከሣሽ የአሁን አመልካችም ቀርቦ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ባነሣው ክርክር በዋስትና ተይዛለች የተባለችው መኪና በአደጋ ጉዳት የደረሰባት በነሐሴ 2 ቀን 1988 ዓ.ም ሲሆን ክሱ የቀረበው መስከረም 24 ቀን 1997 ዓ.ም ነው፡፡ 3ኛ ተከሣሽ ዕዳውን አምኗል የተባለው ደግሞ የካቲት 11 ቀን 1989 ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ድረስ ያለው ሲታሰብ 7 ዓመት ከ7 ወር ከ10 ቀን ነው፡፡ ይህም በንግድ ሕግ ቁጥር 674 ላይ እንደተመለከተው ጉዳቱ በደረሰ በ2 ዓመት ጊዜ ወስጥ ክሱ መቅረብ ሲገባው እንደዚሁ ተቋርጧል ቢባል ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት አመት መቅረብ ሲኖርበት በዚህ ጊዜ ውስጥ ክሱ ያልቀረበ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ስለሚሆን ፍ/ቤቱ ክሱን ውድቅ ሊያደርግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር መርምሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1852/2/ መሠረት ይርጋ ከተቋረጠ በኋላ ድጋሚ የሚኖረው የይርጋ ጊዜ 10 ዓመት እንደሆነ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑና ይህ የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜም ከመጠናቀቁ በፊት ክሱ ስለቀረበ 3ኛ ተከሣሽ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ያቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ ግራ ቀኙ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

3ኛ ተከሣሽ የአሁን አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይርጋ ከተቋረጠ በኋላ ድጋሚ የይርጋ ጊዜ የሚታሰበው አስቀድሞ በነበረው የይርጋ ጊዜ ልክ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1852 ድንጋጌ መረዳት የሚቻል እንደመሆኑ መጠን በዚህም ጉዳይ ይግባኝ ባይ ዕዳውን አምኗል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ ከሚታሰብ በስተቀር 10 አመት ሊሆን ስለማይችል ይርጋው ከተቋረጠም በኋላ በዚህ የሁለት አመት ጊዜ መልስ ሰጪ ክሱን ያላቀረበ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ አይደለም ብሎ ይህንኑ የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ ሽሮ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪም በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር በይርጋ አልተቋረጠም ሲል ዋናው ክርክር በኦሮሚያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲታይ ብሎ ጉዳዩን ወደ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት መልሷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ ጉዳዩ በንግድ ሕግ ቁጥር 674/1/ ላይ የተመለከተው የ2 ዓመት ጊዜ ተቋርጧል ከተባለ አዲሱ የይርጋ ጊዜ የሚታሰበው በንግድ ሕግ መሠረት ወይንስ በፍትሐብሔር ሕግ የሚለው ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በኢንሹራንስ ውል ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ማንኛውም ክስ ጉዳቱ በደረሰ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት የኢንሹራንስን ጉዳይ በተለይ በሚገዛው በንግድ ሕጉ በቁጥር 674/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩልም በሕጉ ላይ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ሲቋረጥ እንደ አዲስ ስለሚቆጠረው የይርጋ ጊዜ በንግድ ሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ ይህ ነጥብ በልዩ ሕጉ ማለትም በንግድ ሕጉ ካልተሸፈነ ወደ ጠቅላላ ሕግ መሄድ ከሕግ አተረጓጐም መርህ አኳያ ተቀባይነት ያለው ስለሆነ በዚሁ መሠረት ጠቅላላ ሕጉን መመልከት አግባብነት ይኖረዋል፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት የሚኖረውም ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁ/1852 ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረትም ይርጋ በተቋረጠ ጊዜ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እንደገና አዲስ የይርጋ ዘመን መቁጠር እንደሚጀምር በዚሁ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ተመልክቷል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ በግልጽ መረዳት የሚቻለው ይርጋው በተቋረጠ ጊዜ ቀድሞ የነበረው የይርጋ ጊዜ እንደ አዲስ መቁጠር የሚጀምር መሆኑን ነው፡፡

በእርግጥ በዚሁ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር /2/ ሥር ይርጋው ተቋርጦ በሚገኝበት ጊዜ የይርጋ ዘመኑ አቆጣጠር ሁልጊዜ 10 ዓመት እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይሁንና ይህ ድንጋጌ የሚገኘው ጠቅላላ የውሎች ሕግ በሚለው ክፍል ከመሆኑም በላይ ውልን አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ በ10 ዓመት ይርጋ

ቀሪ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 ላይ ስለተመለከተ ከዚሁ ከጠቅላላ ውል ጋር በተያያዘ አንድ የይርጋ ጊዜ ሲቋረጥ ሌላ አዲስ የ10 አመት የይርጋ ጊዜ ሊኖር እንደሚችል ከሚያስገነዝብ በስተቀር በልዩ ሕግ የይርጋ ጊዜው ከ10 ዓመት ዝቅ ብሎ የሚገኘው ሁሉ ተቋርጦ በሚገኝበት ወቅት አዲሱ የይርጋ ጊዜ 10 ዓመት ነው ማለት ሕግ አውጪው ለተለያዩ ክሶች የተለያየ የይርጋ ጊዜ የሰጠውን እንደመለወጥ የሚቆጠር ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ አልተቋረጠም በማለት የሰጠው ውሣኔ ለድንጋጌው ተገቢውን ትርጉም ባለመስጠት ስለሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 24495 በሚያዝያ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የይርጋ ጊዜው ከተቋረጠ በኋላ ክሱን በንግድ ሕግ ቁጥር 674/1/ ላይ እንደተመለከተው በ2 ዓመት ጊዜ ማቅረብ ሲገባው ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ስለሚሆን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚሁ መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 31217

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

በላቸው አንሺሶ

አመልካች፡- ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጫሊ ሐሰን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረው በጉራጌ ዞን ወልቂጤ ከተማ መጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ድርጅቱ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ያደረገውን የደመወዝ ጭማሪ በድምሩ ብር 4736፣ ከሐምሌ ወር 1998 ዓ.ም ጀምሮ የተደረገውን የደመወዝ ጭማሪ በድምሩ ብር 1132፣ ከሚያዝያ 1998 - ሰኔ 1998 ያልተከፈለኝ የትራንስፖርት አበል ብር 300 በድምሩ ብር 8159 ከወለድ ጭምር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ደግሞ በሰጠው መልስ ከሣሽ ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄ 6 ወር ያለፈበት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162/3/ መሠረት በይርጋ ይታገዳል፡፡ ቦነሱና ሌላው ጥቅማጥቅምን በተመለከተም ከሣሽ ክፍያው እንዲከፈላቸው የጠየቁት በሥራ ላልነበሩበት ጊዜ በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም ክሱ ውድቅ ሊሆን የሚገባው ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አንድ ሠራተኛ ለስድስት ወር የሥራ ከሆነ ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደውን ጭማሪና ቦነስ እንደሚያገኝ በሕብረት ስምምነቱ የተደነገገ በመሆኑ ድርጅቱ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ

ለከሣሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በድርጅቱ ስለቀረበው የይርጋ ጥያቄ ግን ምንም ሣይል አልፎታል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት በጉራጌ ዞን የወልቂጤ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከተመለከተ በኋላ ከሣሽ በሌሉበትና ለኮርፖሬሽኑ እድገትና ብልጽግና ያደረጉት አስተዋፅኦ ሣይኖር ሊከፈላቸው የሚገባ የደመወዝ ጭማሪም ሆነ የቦነስ ክፍያ የለም፡፡ በ1998 ዓ.ም በጀት ዓመት የተደረገው የደመወዝ ጭማሪም ሆነ የቦነስ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም፡፡ በሌላ በኩል ግን ከሣሽ ከደርጅቱ ከመሰናበታቸው በፊት በ1997 ዓ.ም ለአሥራ አንድ ወራት ያክል በድርጅቱ የሠሩ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ድርጅቱ በዚሁ ዓመት ለሌሎች ሠራተኞች የከፈለውን የደመወዝ ጭማሪና ጥቅማጥቅም ለከሣሽም እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው፡፡ በመሆኑም ድርጅቱ የ1997 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪና ቦነስ ለከሣሽ እንዲከፍል በማለት የመ/ደ/ፍ/ቤቱን ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ በአመልካች ስለቀረበው የይርጋ ክርክር ደግሞ ምንም ሣይል አልፎታል፡፡

አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህን በጉራጌ ዞን የወልቂጤ አካባቢ ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ቅሬታውም ፍ/ቤቱ የይርጋ ክርክሬን ወደጎን በመተው የ1997 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪና ቦነስ ለአሁን ተጠሪ እንድከፍል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፣ የ1997 ዓ.ም ክፍያ ተከፍሎ የተጠናቀቀው በጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም ሲሆን ክሱ ደግሞ የቀረበው ጥቅምት 21 ቀን 1999 ዓ.ም ልክ በዓመቱ ነው ክሱ የስድስት ወር ጊዜ ሣያልፍ መቅረብ ሲገባው የቀረበው በዓመቱ በመሆኑ ጥያቄው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162/3/ መሠረት በይርጋ ቀሪ መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ተጠሪው ደገሞ በሰጡት መልስ በጊዜው ክስ ላቀርብ ያልቻልኩት ያለአግባብ ተሰናብቻለሁ፡፡ ወደሥራ ልመለስ ይገባል የሚል ክስ አቅርቤ ስለነበረ ነው፡፡ ወደሥራ ከተመለስኩኝ በኋላም ክፍያው እንዲከፈለኝ በተደጋገሚ ጥያቄ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እያቀረብኩኝ ስለነበር ክሱ በይርጋ አይታገድም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ በመሆኑም ውሣኔው ሊፀናልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ ክሱ በይርጋ ቀሪ መሆን የሚገባው ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነውም የ1997 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪ የተከፈለው ጥቅምት 1998 ዓ.ም በመሆኑና ክሱ ደግሞ የቀረበው በጥቅምት ወር 1999 ዓ.ም በመሆኑ ጥያቄው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/3/ መሠረት በይርጋ ቀሪ መሆን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በወቅቱ ክስ ልመሠርት ያልቻልኩት ወደሥራ ልመለስ የሚል ክስ አቅርቤ ስለነበረ ነው በማለት ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተም ወደ ሥራ ልመለስ የሚለው ክስ የይርጋ ጊዜውን ሊያቋርጥ የሚችል ባለመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ ወደ ሥራ ከተመለስኩም ከግንቦት 15 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ እንዲከፈለኝ እጠይቅ ነበር ያሉትም ቢሆን በድርጅቱ ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘ በመሆኑ የይርጋ ጊዜውን የሚያቋርጥ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶቹ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ የ1997 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪና ቦነስ ለተጠሪው እንዲከፈል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መታረም የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የ1998 ዓ.ም እና የ1999 ዓ.ም ክፍያን በተመለከተ ደግሞ ተጠሪው መስቀለኛ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡበት ባለመሆኑ እንዲሁ መታለፍ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1- የጉራጌ ዞን የወልቂጤ ከተማ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02327 ግንቦት 15 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የወልቂጤ ከተማ መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00700 የካቲት 1 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡

2- የሥር ፍ/ቤቶች ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚገባው ነው በማለት መወሰን ሲገባቸው በቀረበው የይርጋ ጥያቄ ምንም ሣይሉ ማለፋቸውና ክፍያው እንዲፈፀም በማለት የሰጡት ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/3/ ሥር የተደነገገውን የይርጋ ሕግ የሚጋፋ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡

3- ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ እንዲቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31857

መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

አለ. መሐመድ

አመልካች፡- መሐመድ አብደላ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የድሬደዋ ኢትዮ ጅቢቲ ም/ባቡር - አልቀረበም፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው አሠሪው የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት የሚቋረጥበት የጊዜ ገደብን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ያላግባብ ከሥራ መሰናበታቸውን ጠቅሰው ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ጉዳይም ከታወቀ አንድ ወር ያለፈው በመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች ፈፀሙት የተባሉው ድርጊት ከታወቀ ከ30 ቀናት በኋላ የተወሰደው የሥራ ውል ማቋረጥ እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ መሠረት ተቀባይነት የለውም ሲል አመልካች ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱ ችግሩ መኖሩ ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ የሥራ ውሉ እስከተቋረጠበት ቀን ድረስ 30 የሥራ ቀናት ስለማያልፍ የአሠሪው መብት በይርጋ አይቋረጥም ሲል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩን ለሥር ፍ/ቤት መልሷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካችም ቅሬታ በተጠሪ ድርጅት ቅዳሜ ቀን የሥራ ቀን በመሆኑ የጊዜ ገደቡ አልፏል የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ክርክር ያስነሣው አመልካች ፈፀሙ የተባለውን ድርጊት ምክንያት በማድረግ ተጠሪ ከሥራ ለመባረር ያለው መብት በይርጋ ቀሪ ሆኗል አልሆነም የሚለው ነጥብ ነው፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ፈፀሙ የተባለው ድርጊት የታወቀው እ.ኤ.አ. በፌብሩዋሪ 26 ቀን 2005 ዓ.ም ቅዳሜ ወይም በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር የካቲት 19 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑንና አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት እ.ኤ.አ. ኤፕሪል 8 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ከዚህም በመነሣት ድርጊቱ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ የስንብት ደብዳቤው እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ያለው ቅዳሜና እሁድን እንዲሁም የበዓላትን ቀን ሳይጨምር 29 ቀን ብቻ ስለሆነ አሠሪው የስንብት እርምጃ የመውሰድ መብቱ በይርጋ አይቋረጥም ብሏል፡፡ ይህ ችሎት ለግራ ቀኙ ባደረገው የቃል ክርክር የተጠሪ ሠራተኞች በሣምንት 48 ሰዓት የሚሠሩ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በቀን 8 ሰዓት እየተሠራ በሣምንት 48 ሰዓት ሊሠራ የሚችለውም በሣምንት 6 ቀናት ሲሠራ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ መ/ቤት የሥራ ቀን ቅዳሜንም የሚጨምር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ድርጊቱ ተፈፀመ ከተባለበት እ.ኤ.አ. ፌብርዋሪ 26 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የስንብት ደብዳቤው እስከተሰጠበት እ.ኤ.አ. እስከ ኤፕሪል 8 ቀን 2005 ዓ.ም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ባረጋገጠው መሠረት አርባ ሁለት ቀናት ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 12 ቅዳሜና እሁዶች እንዲሁም አንድ የበዓል ቀን ነበር፡፡ ስለሆነም ካሉት 42 ቀናቶች ውስጥ በተጠሪ መሥሪያ ቤት የነበረው የሥራ ቀን 35 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች ፈፀሙ የተባሉት ድርጊት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ተጠሪው የሥራ ውሉን የማቋረጥ መብቱን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ እንደሚያዘው በ30 ቀናት ውስጥ ያልተጠቀመበት በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም በተጠሪ መ/ቤት ቅዳሜ ዕለት የሥራ ቀን መሆኑን ግንዛቤ ሣያስገባ የደረሰበት ውሣኔ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12181 ሐምሌ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ት በመ/ቁ. 02394 ግንቦት 8 ቀን 1999 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 32013

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድኀን ኪሮስ

አመልካች፡- ደምስ ጥበበሥላሴ - ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- ቴዎድሮስ ጥበበሥላሴ - ወኪል ቀርባለች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስን ጥያቄ መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተውም የሁለታችን አባት የሆኑት አባ ጥበበሥላሴ ካሣሁን ስለሞቱ ወራሽነቱ ተረጋግጧል፡፡ የውርስ ሀብቱ ግን ያልተከፋፈለ በመሆኑ የውርስ አጣሪ ይሾምልን በማለት ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ተከራክሯል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ክርክሩን ከመረመረ በኋላ፣ ጥያቄው በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. በዛፊው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ያነሳው የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገው በሕግ አግባብ ነው ወይ የሚለውን ነጥብ መመርመር ያለበት ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህ ነጥብ፣ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች የይርጋ መቃወሚያውን ያነሳው ተጠሪ ክሱን ያቀረበው አባታችን ከሞቱ ከስምንት ዓመት በኋላ ነው፡፡ በሌላ ሰው እጅ ያለአግባብ ተይዞ የነበረውን የውርስ ሃብት ብቻዬን ተከራክሬ በማስለቀቅ ለስምንት ዓመት ሙሉ በይዞታዬ ሥር የያዝኩት በመሆኑ አሁን አካፍል ልባል አይገባም በማለት ነው፡፡ በእርግጥም ተጠሪ ክሱን ያቀረበው በአመልካች ክርክር የተነገረው ሁሉ ከተከናወነ በኋላ ስለመሆኑም አልተካደም፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተቃውሞውን ውድቅ ያደረገው የይርጋውን ድንጋጌ የያዘው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1000 ተገቢነት የሚኖረው የውርስ ሃብቱ የተያዘው ትክክለኛ ወራሽ ባልሆነ ሰው ሲሆን ነው፡፡ አመልካች ግን /የስር ተከሣሽ/ ትክክለኛ ወራሽ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ለመመልከት ችለናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪው ጉዳይ ከውርስ ሃብት ክፍፍል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የአንድ አባት ልጆች ናቸው፡፡ እየተከራከሩ ያሉት አባታቸው በተውት የውርስ ሃብት ላይ ነው፡፡ ስለ ውርስ ወይም አወራረስን በተመለከተ ተገቢነት ያለው ሕግ በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ አምስት ሥር ያሉትን ድንጋጌዎች አጠቃሎ የያዘው የሕጉ ክፍል ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ ሥር ያሉት ከቁጥር 826 እስከ 1125 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች እንደየአግባቡ ከውርስ ጋር ተያይዘው ለሚነሱት ክርክሮች መፍቻ የሚውሉ ወይም አግባብነት ያላቸው ናቸው፡፡ የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1000ም ከነዚሁ አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም አግባብነቱ በወራሾች መካከል ለሚነሳው የይርጋ መቃወሚያ /ክርክር/ እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡ አግባብነት የማይኖረው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ካለው በተቃራኒው፣ ማለትም አንደኛው ተከራካሪ ወገን ወራሽ ባልሆነበት ጊዜ ነው፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍ/ቤቶች ለፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1000 የሰጡት ትርጉም ትክክል አይደለም ማለት ነው፡፡

ሌላው ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 974/2/ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ሟቹ ከሞቱ ከአምስት ዓመት በኋላ ስለውርስ ክፍያ አመዳደብ ወይም ድልድል በማናቸውም አስተያየት ቢሆን መቃወሚያ ማቅረብ

እንደማይቻል ያመለክታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 947 እንደተደነገገው ያለ አንዳች ፎርማሊቲ የውርስ አጣሪነት መብት አለው፡፡ በዚህ መሠረትም የውርሱ ሃብት የሆነውን ንብረት ካለበት ፈልጎና ይዞት ከነበረው ሰው አስለቅቆ በራሱ ይዞታ ስር አድርጎታል፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታም ለስምንት ዓመት ያሕል ቆይቶአል፡፡ አመልካች ንብረቱን የያዘው ለኔ የሚገባ የውርስ ሃብት ነው በሚል እንደሆነ መገመት የሚያስቸግር አይደለም፡፡ ተጠሪ ግን ይህ ንብረት ለኔም የሚገባ /የምወርሰው/ ሃብት ነው ወይም አመልካች ብቻውን ሊይዘው አይገባም የሚል ጥያቄ ሳያነሳ ለ8 /ስምንት/ ዓመት ያክል ቆይቶአል፡፡ በመሆኑም የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ ያቀረበው የውርስ ሃብት ክፍፍል ጥያቄ በአምስት ዓመቱ ይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ ሲጠቃለል የተጠሪ የውርስ ሃብት ክፍፍል ጥያቄ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1000/1/ በተመለከተው የሦስት ዓመትም ሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 974/2/ በተቀመጠው የአምስት ዓመት የጊዜ ገደብ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ ስለዚህም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20011 ግንቦት 24 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 56847 ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ /ትዕዛዝ/ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበው የውርስ ይጣራልኝ ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ብለን ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግን ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32217

ታህሣሥ 8 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታፈሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ እማዋይሽ አበራ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት እልፍነሽ ሸዋዬ - ጠበቃ ዳኜ ረዳ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በውርስ ሃብት ክፍፍል ላይ ተመስርቶ የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በትግራይ ብ/ክ/መ/በምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ስትሆን፣ ከአባትዋ በውርስ አገኘሁ ያለችውን ንብረት እንዲያካፍሉዋት በአሁንዋ አመልካችና በሌሎች ሁለት ሰዎች /እህቶችዋ/ ላይ ክስ መስርታ ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ ለክሱ ምክንያት ከሆነው ንብረት ላይ ድርሻዋን ትውሰድ ተብሎ ተወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በተሰጠው ውሣኔ ላይ ባለመስማማት ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ክርክሩ በድጋሚ ከተሰማ በኋላ በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ እንዲሻር በሚል ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎት አመልካች ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ይርጋን መሠረት በማድረግ ያቀረበችውን መቃወሚያ ውድቅ የመሆኑን

አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ በግራ ቀኝ ወገኖች ከቀረበው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ክርክሩ የውርስ ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ሆኖ ተጠሪ ያቀረበችው የድርሻዬን ይሰጠኝ ክስ የይርጋ መቃወሚያ ቀርቦበታል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በሰጡአቸው ውሣኔዎች ላይ እንደተመለከተው የተጠሪ አባት ማለትም የንብረቱ የቀድሞ ባለሃብት የሞቱት በ1976 ዓ.ም. ሲሆን፣ ተጠሪ የውርስ ንብረት ይገባኛል ክስ የመሠረተችው ደግሞ በ1996 ዓ.ም. ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹ በአመልካች በኩል የቀረበውን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረጉት ከሣሽ ክሱን ያቀረበችው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1000/2/ የተመለከተው የ15 ዓመት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡

እንደምናየው የተጠሪ አውራሽ በሞቱበት እና ክሱ በቀረበበት ጊዜ መካከል ያሉት ዓመታት ሲቆጠሩ ከ20 ዓመት በላይ አልፎአል፡፡ ወራሽ የሆነው ሰው በሌላ ሰው የተያዘበትን የውርስ ሃብት ለማስመለስ ክስ መመስረት እንደሚችል በሕጉ የተመለከተ ቢሆንም፤ /የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 999/ ክሱን የሚያቀርብበት ጊዜ ግን በሕግ ተወስኖአል፡፡ ከሣሹ መብቱንና የውርሱ ንብረቶች በተከሣሹ መያዛቸውን ካወቀ ሦስት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለወራሽነት ጥያቄ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት እንደሌለው በፍ/ብ/ብ/ሕግ ቁ. 1000/1/ ተመልክቶአል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ይመለስልኝ የምትለው የውርስ ሃብት አመልካች እንድትመልስላት ክስ የመሠረተችው በአመልካች መያዙን ካወቀች የሦስት ዓመት ጊዜ ከማለፉ በፊት ነው የሚል በፍሬ ነገር ረገድ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ ክሱን የመሠረተችው የሦስት ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ እንደሆነ ነው በሥር ፍ/ቤቶች ጭምር ግንዛቤ የተወሰደው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ በሕጉ የተመለከተው የሦስት ዓመት የጊዜ ገደብ ካለፈ ደግሞ ወደ 15 ዓመት የሚሔድበት ምክንያት የለም፡፡ በፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 1000/2/ የተመለከተው የ15 ዓመት የጊዜ ገደብ አስፈላጊ የሚሆነው በንኡስ ቁ. /1/ በተቀመጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌ መሠረት ለጉዳዩ እልባት መስጠት የማይቻል ሆኖ በተገኘ ጊዜ ነው። ሲጠቃለል ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበችው ክስ በሕጉ በተመለከተው የሦስት ዓመት የይርጋ ጊዜ ቀሪ ሆኖአል። በመሆኑም ክሱ በይርጋ ቀሪ አልሆነም በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በትግራይ ብ/ክ/መ/ በምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01155 በሕዳር 5 ቀን 1999 ዓ.ም.፣ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18017 መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም. እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 19639 ግንቦት 2 ቀን 1999 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል።
2. ተጠሪ ያቀረበችው የውርስ ንብረት ይሰጠኝ ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ብለናል።
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 32788

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድነን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ነ/ፊ ቀረበ።

ተጠሪ፡- አቶ ግርማ ተገኝ ጠበቃ ቀርበዋል።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

የጉዳዩ አመጣጥ መጀመሪያ የአሁኑ ተጠሪ ከየካቲት ወር 1994 ዓ.ም. ጀምሮ ለሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪ ስለተደረገላቸው ለእኔም ሊደረግልኝ ይገባል በማለት ግንቦት 23 ቀን 1999 ዓ.ም. በተፃፈው ማመልከቻ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ ያቀርባሉ።

የአሁኑ አመልካችም ከሥራ የተሰናበትከው በ1994 ዓ.ም. በመሆኑ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄህ በይርጋ ይቋረጣል በማለት መቃወሚያ ያቀርባል። ፍ/ቤቱም ይህን መቃወሚያ በመቀበል ክሱ በአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀጽ 162/2/ መሠረት በይርጋ የሚቋረጥ ነው ሲል ክሱን በመሠረዝ መዝገቡን ዘግቶታል።

በመቀጠልም የአሁኑ ተጠሪ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ስላቀረቡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀጽ 164/3/ መሠረት በይርጋው ተጠያቂ የሆነው ሰው ወይም ወገን የሌላውን መብት በጽሑፍ ሲያውቅለት ተብሎ በተደነገገውን መሠረት ሲታይ በሕብረት ስምምነቱና በደመወዝ ስኬል አፈፃፀም መመሪያው ሠራተኛው ከተጠያቂነት ነፃ መሆኑ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ የኋላ ቀሪ ክፍያ የሚያጠቃልል የደመወዝ ጭማሪ ሊያገኝ ይችላል ተብሎ ስለተደነገገ ይህ ድንጋጌ የይርጋውን ጊዜ ያቋርጠዋል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ክሱን በመቀበል ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን በማለት ይወስናል፡፡

የሰበር አቤቱታውም ሊቀርብ የቻለው በዚሁ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ የሰበር አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ተጠሪው ያቀረቡት የተጨማሪ ደመወዝና የጥቅማጥቅም ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ቀሪ የሚሆን በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ብንከራከርም የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን የመቃወሚያ ክርክራችንን ውድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤቱን ትዕዛዝ በመሻር ክሱ በአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀጽ 164/3/ መሠረት በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት መወሰኑ አግባብ አይደለም፡፡ ድርጅቱ ለተጠሪው ይርጋውን ለማቋረጥ የሚችል በጽሑፍ ያወቀለት መብት የለም፡፡ በሕብረት ስምምነቱና በደመወዝ ስኬል አፈፃፀም መምርያውም ይህን የሚያረጋግጥ ድንጋጌ የለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቱ ውሣኔ ተሽሮ ክሱ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው ተብሎ እንዲወስንልን የሚል ነው፡፡

ይህ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን በመመርመር የስር ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

ተጠሪም ጥር 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ በሕብረት ስምምነታችን አንቀጽ 32 እና 34 መሠረት እንዲሁም በድርጅቱ የደመወዝ ስኬል አፈፃፀም መመሪያ ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ በሚሠራበትና በ1996 ዓ.ም. በሥራ አመራር ቦርዱ በተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 6 እና በቁጥር 3.3.10 መሠረት አንድ ሠራተኛ በጥፋት ምክንያት በክርክር ላይ እያለ የደመወዝ ጭማሪ መጠየቅ እንደማይችል ነገር ግን ተጣርቶ ከጥፋቱ ሙሉ በሙሉ ነፃ መሆኑ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ የደመወዝ ጭማሪውን ያለፈ ውዝፍ ክፍያም ጭምር ማግኘት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ እኔም የተሰናበትኩት በአግባቡ ያለመሆኑን ተረጋግጦ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ ስለተወሰነልኝ ውሣኔ

ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ስድስት ወር ሳይሞላ ነው ክሱን ያቀረብኩት በመሆኑም ክሱ በይርጋ አይቋረጥም ተብሎ በፌ/ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት ባለመኖሩ ውሣኔው ይጽናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ድርጅትም የመልስ መልሱን በማቅረብ ክርክሩን ለማጠናከር ሞክሯል፡፡

በበኩላችን ደግሞ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይችላል ወይስ አይችልም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነውም ሐምሌ 1990 ዓ.ም. በወጣው የሕብረት ስምምነት በአንቀጽ 34.2.7.4 የደመወዝ ጭማሪ በሚሰጥበት ወቅት በጥፋት ምክንያት በጊዜያዊ እገዳ ላይ የሚገኝ ሠራተኛ በዚህ የሕብረት ስምምነት መሠረት የደመወዝ ጭማሪ ለማግኘት የአስተዳደር ውሣኔ የማያግደው ከሆነ ጭማሪውን ከተፈቀደበት ጊዜ ጀምሮ ያገኛል ተብሎ የተደነገገው የአስተዳደር ውሣኔው ሊያግደው ይችላል ወይስ አይችልም የሚለውን ቅድመ ሁኔታ ከተመለከቱ በኋላ የሚታይ እንጂ በቀጥታ የደመወዝ ጭማሪን ለማግኘት በሚፈቅደው መንገድ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን በድርጅቱ የደመወዝ ስኬል የአፈፃፀም መመሪያ በአንቀጽ 3.3.10 በዲስፕሊን ጉድለት ወይም በሌላ ጥፋት ምክንያት በሕብረት ስምምነት ወይም በሥራ አመራር አባላት የአስተዳደር ደንብ መሠረት በቅጣት የሪከርድ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች የሪከርድ የጊዜ ገደቡ እስኪያበቃ ድረስ የደመወዝ ጭማሪ እንዳይሰጣቸው ተከልክለው የቆዩት ሠራተኞቹ ፈፀሙት የተባለው ድርጊት ተጣርቶ ከተጠያቂነት ሙሉ በሙሉ ነፃ መሆናቸው ከተረጋገጠ ወይም የደመወዝ ጭማሪ እንዳይሰጣቸው በአስተዳደር ውሣኔ ካልተወሰነ ከተጠያቂነት ነፃ መሆናቸው ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ብቻ የኋላ ቀሪ ክፍያን የማያጠቃልል የደመወዝ ጭማሪ ሊያገኙ ይችላሉ ተብሎ ቢደነግግም ይህ ድንጋጌ የሚመለከተው ከድርጊታቸው ከተጠያቂነት ነፃ ከወጡ በኋላ በዚያው ድርጅት መሥራት የሚቀጥሉ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ ሰኔ 9 ቀን 1991 ዓ.ም. ተሻሽሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በወጣው የደመወዝ እስኬል አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 2/ለ/ ስለተደነገገና ተጠሪው ደግሞ ይህን የደመወዝ ጭማሪ ክስ ከማቅረባቸው በፊት ጥር 28 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሥራ ክር/መ/ቁ/4544 የተሰጠው ውሣኔ ተጠሪው ካሣ ተከፈሎአቸው ከድርጅቱ እንዲሰናበቱ የተወሰነ በመሆኑ ተጨማሪ ደመወዙን የሚጠይቁበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

በመሆኑም እነዚህ ተጠሪው በሰበር መልሳቸው የጠቀሱዋቸውና የሥር ፍ/ቤትም ለውሣኔው መሠረት ያደረጋቸው የሕብረት ስምምነቱና የደመዝ ስኬል አፈፃፃም መመሪያ አንቀፆች ለተጠሪው መብት የሚሰጡ ባለመሆናቸው የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜውን ለማቋረጥ ምክንያት የሚሆኑበት መንገድ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤትም በሰጠው ውሣኔ ድርጅቱ ለከሣሹ /የአሁን ተጠሪ/ መብታቸው በጽሑፍ ያወቀላቸው በመሆኑ ክሱ በአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀጽ 164/3/ መሠረት በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በመሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57049 ሐምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24175 ግንቦት 23 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል፤ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 34011

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

አመልካች፡- እልፍነሽ አማረ - ወኪል ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ግርማ አማረ - ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ አመልካች የጋራ እናተቸውን የውርስ ሀብት ይዘው ስለሚገኙ የንብረቶቹን ግማሽ 47737.50 (አርባ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሰላሳ ሰባት ከሃምሳ) እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በሰጡት መልስ የግራ ቀኙ እናት የሞቱት ግንቦት 17 ቀን 1987 ዓ.ም ስለሆነ ከሞቱ 11 ዓመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ይቋረጣል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤትም የተጠሪ ጥያቄ የበፍ/ሕ/ቁ. 1000/1/ መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከተው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥያቄው የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት በመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ 1000/1/ ተፈፃሚነት የለውም ጉዳዩ መታየት የነበረበት ከፍ/ሕ/ቁ. 1000/2/ ጋር ተገናዝቦ ነው በማለት የተጠሪ ክስ በይርጋ ስለማይታገድ የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ የውርስ ንብረት በመካፈል ከ11 ዓመት በኋላ ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ አይታገድም መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ቀርበው ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ተጠሪ ክስ የመሠረቱት ከእናታቸው በውርስ ሊተላለፍላቸው የሚገባውን ቤትና ሌሎች ንብረቶች ለመካፈል ነው፡፡ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ክስ በይርጋ አይታገድም ያለው ተጠሪ ያቀረቡት የውርስ ክፍፍል ጥያቄ የማይንቀሣቀስ ንብረትን የሚመለከት በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1000/2/ መሠረት በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም በማለት ነው፡፡ ይኸው ፍ/ቤቱ የጠቀሰው የፍትሐብሄሩ ድንጋጌ "እንደዚሁም ሟች ከሞቱበት ወይም ከሣሹ በመብቱ ለመሥራት ከቻለበት ቀን አንስቶ አሥራ አምስት ዓመት ካለፈው በኋላ፤ ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በቀር የተባለው የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸውም አስተያየት ቢሆን ተቀባይነት አያገኝም፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ አካያ በይርጋ የማይታገደው "ከዘር የወረደ ርስት" መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እዚህ ላይ ሊነሣ የሚገባው ቤት የማይንቀሣቀስ ንብረት በመሆኑ "ርስት" ነው ሊባል ይችላል አይችልም የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ በመሆኑም ርስት የሚለው ቃል በፍ/ሕጉ ውስጥ ከተካተቱ ድንጋጌዎች ምን ማለት እንደሆነ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1130 የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች የመሬት ርስቶችና ቤቶች ናቸው በማለት የስቀምጣል፡፡ ከዚህም ድንጋጌ ርስት የሚለው ቃል መሬትን የሚያመለክት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደዚሁም ስለ ንብረቶች በሚናገረው የፍ/ብሔር ሕጉ ክፍል የሚገኙት የተለያዩ ድንጋጌዎች ርስትን ከመሬት ጋር የሚያያዙ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ርስት የሚለው ቃል "1. ቤተ ዘመድ የሆነ እያረሠ የሚጠቀምበትና ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ የመሬት አጽመ ርስት 2. የግል ወይም የራስ ይዞ የሆነ ቦታ፣ መሬት" በማለት ትርጓሜ ይሠጠዋል፡፡ በመሆኑም ከተለያዩ የፍ/ሕጉ ድንጋጌዎችም ሆነ ከአማርኛው ትርጉም ርስት መሬት እንጂ ቤትን የማይመለከት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደ ፍ/ሕ/ቁ 1000/2/ ስንመጣም "... ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በቀር ..." የሚለው ሀረግ በተለይ ከፍ ሲል ከተገለፀው የአማርኛ ትርጉም ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ መሬት ከሚለው ጋር የሚጣጣም መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ከዚህ ተነስተን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የሟች ቤት ርስት ነው ወደሚለው መደምደሚያ የደረሰውና ክርክሩ በፍ/ሕ/ቁ. 1000/2/ መሠረት በይርጋ አይቋረጥም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 394/98 ጎዳር 5 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የሰሜን ሸዋ መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10940 በሐምሌ 13 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31748

የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ይስማው ድረስ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ይበልጣል ፍቅር ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን መነሻ የደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ በመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ከአባቴና እናቴ በውርስ የተላለፈልኝን ቤት ከሕግ ውጪ ይዞብኛል እና ያስረክበኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ ቤቱ በተጠሪ አባት በውል ገዝቶ በስሙም ግብር እየገበረ ከ19 ዓመት በላይ ይዞት እንደሚገኝ ገልጾአል፡፡ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለትም ተከራክሮአል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የይርጋውንም ሆነ በፍሬ ነገር ረገድ የቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የምስራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍ/ቤትም በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ የቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች በኩል የቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ግራ ቀኝ ወገኖች ከስር ጀምሮ ካደረጉት ክርክር አና የሥር ፍ/ቤቶች ከሰጡት ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች አከራካሪውን ቤት ሊይዝ የቻለው ከተጠሪ አባት ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መነሻነት ነው፡፡ የሽያጭ ውሉ የተደረገው በ1980 ዓ.ም. ሲሆን፣ ይህን ውል መሠረት በማድረግም አመልካች ቤቱን በይዞታው ስር ከማድረጉም በላይ፣ ቤቱ ለሚገኝበት ከተማ ማዘጋጃ ቤት አቅርቦ በስሙም ግብር ሲከፍል እንደቆየ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ተጠሪ የቤት ይለቀቅልኝ ክስ የመሠረተው መጋቢት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. ነው፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ቤቱን የያዘው ከተጠሪ አባት ጋር ባደረገው የሽያጭ ውል መሠረት ነው፡፡ ገንዘቡንም በወቅቱ ለተጠሪ አባት የከፈለ ስለመሆኑ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪ ቤቱ ከመሠረቱ የሱ አይደለም፡፡ የአባቱን ወራሽነት መሠረት አድርጎ ነው ክሱን የመሠረተው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች ቤቱን የያዘው ከ1980 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን፣ ተጠሪው ክስ የመሠረተው ደግሞ በ1999 ዓ.ም. ማለትም ከ19 ዓመት በኋላ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም ወደክሱ ፍሬ ነገር ከመገባቱ በፊት አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ አግባብነት ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የውል ግንኙነት የለም፡፡፡ የተጠሪ አባት በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የውል ይፍረስልኝ ክስ መስርተው ክርክሩ ከመወሰኑ በፊት በመሞታቸው ምክንያት ተጠሪ ተተክቶ የክርክሩ ተካፋይ የሆነ ሳይሆን፣ የወራሽነት መብቱን መሠረት በማድረግ በራሱ ክስ አንደ መሠረተም ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ያነሳው የይርጋ መቃወሚያ መታየት ያለበት ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1677 እና 1845 አንፃር ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕግ/ቁ.1677/1/ እንደተመለከተው ግዴታው ከውል የተገኘ ባይሆንም በፍትሐብሔር ሕጉ አራተኛ መጽሐፍ በአንቀጽ 12 ስር የተመለከቱት ስለ ውሎች በጠቅላላው የተቀመጡ ድንጋጌዎች ይፈጸሙባቸዋል፡፡ በእርግጥ የአንዳንድ ግዴታዎችን አመጣጥ ወይም አይነት በመመልከት በተቀጠሰው አንቀጽ ስር ከተመለከቱት ደንቦች የተለዩ ድንጋጌዎች በሕግ ተመልክቶ ከተገኘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እነዚህ በተለይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብነት እንደሚኖራቸው በተጠቀሰው ቁ. 1677/2/ ተመልክቶአል። ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የመሠረተውን ክስ በተመለከተ በተለይ አግባብ ያለው የይርጋ ደንብ የለም። ስለዚህም በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1845 የተደነገገው የአስር ዓመት ገደብ /ይርጋ/ ይፈጸምበታል። ክሱ የቀረበው ቤቱ በአመልካች ከተየዘ ከአሥራ ዘጠኝ ዓመት በኋላ በመሆኑም በዚሁ የይርጋ ደንብ ተቋርጧል ማለት ነው። እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ የሥር ፍ/ቤቶች በይርጋ ረገድ የቀረበውን የአመልካች መቃወሚያ ውድቅ ያደረጉት የለአግባብ ከሕጉ ውጪ ነው። ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል።

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በሁለት እጅ እነሴ ወረዳ ፍ/ቤት ሚያዝያ 12 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18003 ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ያፀናው እንዲሁም የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 13294 ሐምሌ 3 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል።
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ወስነናል።
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የአሰሪና ሰራተኛ ህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 18832

ኅዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ጌታቸው ምህረቱ

አሰግድ ጋሻው

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነገረ ፈጅ ልኡል ሰገድ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- እነ አቶ ከበደ ቱሉ /6 ሰዎች/

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በሐረሪ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪዎች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ አመልካች መስሪያ ቤት ያላግባብ ከስራ ስላሰናበታቸው ሕጉ የሚፈቅድላቸውን ክፍያዎች አመልካቹ እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉ ሠራተኞች ሲሆኑ የተቀጠሩትም ለተወሰነ ጊዜ ነው፡፡ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪዎች ለአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክስ አቅርበው ከጡረታ አበል እና ከደሞዛቸው አንዱን እንዲመርጡ ተወስኖ በዚህ መሠረት ተጠይቀው ጡረታ አበሉን በመምረጣቸው ነው፡፡ ዘላቂ የጡረታ አበል ክፍያ ያለው ሠራተኛ በአ/ቁ 88/86 እና 42/85 አንቀጽ 39 መሠረት የስንብት ክፍያ አያከፈለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም በአ/ቁ 42/85 አንቀጽ 10 መሠረት የተቀጠሩ መሆናቸውን አመልካች ስላላስረዳ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ናቸው፡፡ የጡረታ አበላቸውን ስለመምረጣቸው አላስረዳም፡፡ የጡረታ አበል ያለው ሠራተኛ ተጨማሪ ስራ እንዳይሰራ አልተከለከለም፡፡ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የተለያየ ክፍያ እንዲከፈላቸው

ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የሐረሪ ክፍተኛ ፍ/ቤት መልስ ሰጪዎችን ሳይጠራ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ይህንንም አላስተባበሉም፡፡ በእድሜ ምክንያት በጡረታ ስለተገለሉ ላልተወሰነ ጊዜ ሊቀጠሩ አይችሉም፡፡ የደንብ ልብስ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች በገንዘብ ተተምኖ እንዲከፈላቸው የሚፈቅድ ሕግ የለም የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም ተጠሪዎች የጡረታ አበላቸውን መርጠው ጡረታቸውን ወስደዋል እየተባለ ከሥራ መሰናበታቸው ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ ተጠሪዎች በአመልካች መ/ቤት የተቀጠሩት እድሜያቸው ለጡረታ በመድረሱ በጡረታ ከተገለሉ በኋላ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ጡረታ አንድ ሠራተኛ እድሜውን ሙሉ ብቃት ያለው ሠራተኛ ሆኖ እንደማይቀጥል ከእድሜው መግፋት ጋር የሥራ ውጤታማነቱ እንደሚቀንስ ስለሚታመን እድሜውን ሙሉ በተቀጠረበት ስራ ላይ እንዲቀጥል መደረጉ የአሰሪውን ጥቅም ይጎዳል ተብሎ ስለሚታመን ሠራተኛው ከስራ ተሰናብቶ አሰሪው ብቃት ያለው ሠራተኛ በቦታው እንዲተካ ለማስቻል ሠራተኛው በጡረታ የሚገለልበት ስርአት ነው፡፡ ተጠሪዎች በዚህ መልኩ የጡረታ እድሜአቸው ደርሶ በጡረታ የተገለሉ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በጡረታ የተገለለ ሰው ስራ መስራት አይችልም የሚባል ባይሆንም አንድ አሰሪ በጡረታ የተገለለን ሠራተኛ በድጋሚ ላልተወሰነ ጊዜ ቀጥሮ ያሰራል ለማለት አይቻልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪዎች ራሳቸው ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ባቀረቡት ክስ ለተወሰነ ጊዜ መቀጠራቸውን አምነው ለቋሚ ሠራተኛ የተጨመረው ደሞዝ ለእነሱም እንዲጨመርላቸውና በሌሎችም ጥያቄዎች ላይ ክስ አቅርበው የነበረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ እንግዲህ በአንድ በኩል ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጊዜ መሆኑን አምነው ሲከራከሩ የነበረ መሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ እድሜያቸው ለጡረታ ደርሶ ከስራ የተሰናበቱ መሆኑ ተዳምሮ ሲታይ አመልካች ተጠሪዎችን የቀጠረው ላልተወሰነ ጊዜ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ተጠሪዎች የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ስለሆነ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛም የተወሰነው ጊዜ ሲያበቃ ሊሰናበት እንደሚችል በአ/ቁ. 42/85 አንቀጽ 24/1/ ተመልክቷል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ የተወሰነው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የስራ ውሉ ያለበቂ ምክንያት ከተቋረጠ ግን ሠራተኛው የውሉ ጊዜ ወይም ስራ እስኪያቅ ቢቆይ ኖሮ ያገኝ የነበረውን ደሞዝ የሚያሕል ደሞዝ እንደሚከፈለው በአዋጁ አንቀጽ 43/4/ለ/ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪዎቹ ደግሞ የተሰናበቱት የውሉ ጊዜ ከማብቃቱ 15 ቀናት በፊት መሆኑን አመልካች ራሱ አምኗል፡፡ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ባደረግነው የስራ ውል ላይ በተስማማነው መሠረት በአ/ቁ. 42/85 አንቀጽ 32/2/ መሠረት የ1 ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ እችላለሁ ሲል ተከራክሯል፡፡ ነገር ግን ተፈፃሚነት ያለው አመልካች የጠቀሰው አንቀጽ ሳይሆን አንቀጽ 35/2/ ሲሆን ይህም ቢሆን አመልካቹ የተወሰነው ጊዜ ሳያልቅ ውሉን ለማቋረጥ መብት አይሰጠውም ይህ ከሆነ ሠራተኞቹ ሊከፈላቸው የሚገባው ለቀሪው 15 ቀን ማግኘት የሚገባቸውን ደሞዝ ብቻ ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሐረሪ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 171/95 በታህሣሥ 12 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተጠሪዎች የሥራ ስንብት ሕገ-ወጥ ነው በማለት የካሣ ክፍያ፤ የደንብ ልብስ በገንዘብ ተቀይሮ፤ እና ክፍያ ለዘገየበት እንዲከፈላቸው የሰጠው ውሣኔ ተሸሯል፡፡
2. በሌላ በኩል ተጠሪዎች በመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመት ያልተጠቀሙበት የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸው እና 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሠርተው ያልተከፈላቸው ቀሪ ደሞዝ እንዲከፈላቸው የሰጠው የውሣኔ ክፍል ብቻ ጸንቷል፡፡

3. አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው የ15 ቀን ደመዛቸውን ይክፈላቸው፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 20416

ታህሣሥ 08 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ቢኒያም ገረመው - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የቻይና መንገድና ድልድይ ሥራ ድርጅት

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡

አመልካች ተሻሽሎ በቀረበ የክስ ማመልከቻ ተጠሪ ከሥራ ያላግባብ ያሰናበታቸው ስለሆነ አዋጁ የሚፈቅድላቸውን ክፍያዎች እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ተጠሪ አመልካችን ከሥራ ያሰናበተው ከሕግ ውጭ በመሆኑ የስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ፣ የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተቀይሮ፣ እንዲሁም የካሣ ክፍያ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ በደቡብ ጎንደር መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም አመልካች ከስራ የተሠናበቱት በሕገ ወጥ መንገድ መሆኑን በመቀበል የሥር ፍ/ቤት ግን ክሱ እንዲሻሻል ሲያዝ በቂ ምክንያት ያልነበረው በመሆኑና የተጠየቀውን ገንዘብ ከፍ ለማድረግ ብቻ ክስ ሊሻሻል እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91 ስላልተመለከተ አመልካች ክርክሩን ሊቀጥል የሚገባው መጀመሪያ ባቀረበው የገንዘብ መጠን ነው በማለት አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ክስ የጠየቁትን የአገልግሎት ክፍያና የ2 ወር ደመወዝ ብቻ እንዲከፍላቸው ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሻሻለውን ክስ ውድቅ በማድረግ በመጀመሪያ በቀረበው ክስ መሠረት ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱተው ለሠበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ ተጠሪ ለአቤቱታው መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ ልኳል፡፡ ነገር ግን ተጠሪው መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ችሎቱ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት ውሣኔ የሠጠው የአመልካችን የተሻሻለ ክስ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግን አመልካች በመጀመሪያ ክሣቸው ላይ የጠየቁትን የገንዘብ መጠን ከፍ ለማድረግ ብቻ ክሱ እንዲሻሻል መደረጉ ተገቢ አይደለም በማለት የአመልካችን የመጀመሪያ ክስ መሠረት አድርጎ ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ ይህ ችሎትም ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የተሻሻለውን ክስ ውድቅ ለማድረግ የሕግ መሠረት ነበረው ወይ? የሚለውን ነጥብ ተመልክቷል፡፡

የመጀመሪያው ፍ/ቤት ክሱ እንዲሻሻል የፈቀደበት ምክንያት በመጀመሪያው ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ያልተመለከተ ቢሆንም ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ክሱ እንዲሻሻል የተፈቀደው አመልካች የሚጠይቋቸውን መብቶች በተብራራ ሁኔታ አሻሽለው እንዲያቀርቡ መሆኑን በውሣኔው ላይ አስፍሯል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካቹ በቀድሞ ክሣቸው ከጠየቁት ዳኝነት በተጨማሪ በሕገ-ወጥ ስራ ስንብት ምክንያት ሊከፈሏቸው የሚገባቸውን ሌሎች መብቶች አካተው ጠይቀዋል፡፡ ይህም ቀድሞ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የገንዘብ መጠን ከፍ እንዲል አድርጎታል፡፡ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤትም የተሻሻለውን ክስ ውድቅ ያደረገው በክስ ማሻሻል ሠበብ በመጀመሪያ ዳኝነት የተጠየቀበትን የገንዘብ መጠን ከፍ ማድረግ አይገባም በማለት ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91 መሠረት ክስ ሲሻሻል ዳኝነት የተጠየቀበትን የገንዘብ መጠን ከፍ ማድረግ ይቻል ወይም አይቻል እንደሆነ ተመልክተናል፡፡

በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91 መሠረት ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ተገቢ ሆኖ ካገኘው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራው ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ከሆነ ክሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሻሻልና ክርክሩ እንዲለወጥ ሊፈቀድ ይችላል፡፡ እንግዲህ አንድ ተከራካሪ ክሱን ለማሻሻል ወይም ክርክሩን ለመለወጥ ፍ/ቤትን ለመጠየቅ መብት ያለው ሲሆን ፍ/ቤቱ ግን ጥያቄውን የሚቀበለው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ክስ የቀረበበትን ጉዳይ በይበልጥ ግልጽ የሚያደርገው ወይም ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑን ሲያምን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በመጀመሪያው ክሣቸው የጠየቁት የስንብት ክፍያና የ2 ወር ደሞዝ ብቻ ነበር፡፡ ነገር ግን አንድ ሠራተኛ በሕገወጥ መንገድ ከሥራ ሲሠናበት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች የማግኘት መብት አለው፡፡ አመልካችም በሕገወጥ መንገድ ከሥራ ከተሠናበቱ ሊከፈላቸው የሚገባውን ክፍያዎች ሁሉ የማግኘት መብት ስላላቸው በመጀመሪያ ሣይጠይቁ የቀሩትን ክፍያዎች ጨምረው ክሱን ማሻሻላቸው ለትክክለኛ ፍትህ አሠጣጥ የሚረዳ በመሆኑ ክሱ መሻሻሉ ስህተት ነው ለማለት አይቻልም፡፡ በሆኑም ክስ የሚሻሻለው ጉዳዩን ለማብራራት ብቻ ሣይሆን ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በመሆኑና አመልካችም በሕገወጥ መንገድ ከተሠናበቱ ሊከፈላቸው የሚገባውን ክፍያ ሁሉ መጨመራቸውና ይህም ዳኝነት የጠየቁበትን የገንዘብ መጠን ከፍ ያደረገው ቢሆንም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ በመሆኑ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የተሻሻለውን ክስ ተቀባይነት ማሣጣቱ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደ/ጎንደር መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06764 በግንቦት 11 ቀን 1997 ዓ.ም. አመልካች ሊከፈላቸው የሚገባው በቀድሞ ክስ የጠየቁት ብቻ ነው በማለት የሠጠው ውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ሊከፈላቸው የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ የፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01511/96 በጥቅምት 17 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የመ/ቁ. 20670

ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች መንበረፀሐይ ታደሰ
ጌታቸው ምህረቱ
አሰግድ ጋሻው
ሂሩት መለሰ
አብዱረሂም አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ነገረፈጅ ግርማ ማርቆስ

ተጠሪ፡- አቶ ሰለሞን በርሄ - አልቀረቡም፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በስር ከሣሽ ነበሩ፡፡ በክሣቸውም ተጠሪ አመልካች መ/ቤት ተቀጥረው ሲያገለግሉ መ/ቤቱ ያላግባብ ስላሰናበታቸው የተለያዩ ክፍያዎች እና ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎአቸው ወደሥራቸው እንዲመለሱ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ቀርቦ ተጠሪ በጡረታ ተገለው የነበሩና ለ3 ዓመት ጥበቃን ለማጠናከር በጊዜያዊነት የተቀጠሩ በመሆናቸው የተቀጠሩበት ጊዜ ሲያበቃ መሰናበታቸው አግባብ መሆኑን ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤትም የቅጥር ውሉ ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ጊዜው ሲያበቃ መሰናበታቸው አግባብ ነው፡፡ የ3 ዓመት ቦነስ የ3 ዓመት ትርፍ ሰዓት እና በዚህ 3 ዓመት ውስጥ ለ21 የበዓል ቀናት የሰሩበት ክፍያ ግን ይከፈላቸው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለተው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የቦነስ ጥያቄው ባልሰሩበት ጊዜ የተጠየቀ ነው በሚል ይህን የውሣኔ ክፍል ብቻ ሽሮታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን የቅሬታው ነጥብ የክፍያ ጥያቄዎቹ በይርጋ የሚታገዱ ሆነው እንዲከፈል መወሰኑ እና የትርፍ ሰዓት ለመሥራታቸውም ያስረዱት ነገር ሣይኖር አመልካች አልካደም በሚል ብቻ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ የሰበር ችሎትም የይርጋው መቃወሚያ ታልፎ መወሰኑ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪ ቀርበው መልሣቸውን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ የታዘዘ ቢሆንም በትእዛዙ መሠረት ያቀረቡት መልስ ባለመኖሩ ችሎቱ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ከጠየቁት ዳኝነት ውሣኔ የተወሰነላቸው የትርፍ ሰዓት እና የበአል ቀናት የሰሩበት ክፍያ ብቻ ሲሆን አመልካች ግን ይህም ክፍያ ቢሆን በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ከስር ክሱ መረዳት እንደቻለነው ተጠሪ የጠየቁት የ3 ዓመት የትርፍ ሰዓት እና በዚሁ 3 ዓመታት ውስጥ ለ21 የበዓል ቀናት የሰሩበት ክፍያን ነው፡፡ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162(3) መሠረት ሠራተኛው የሚጠይቃቸው የደሞዝ፣ የትርፍ ሰዓት እና ሌሎች የክፍያ ጥያቄዎች ሰራተኛው ክፍያዎቹ መጠየቅ ካለባቸው ጊዜ አንስቶ እስከ 6 ወር ካልጠየቁ መብቱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ደግሞ ተጠሪ የጠየቁት ክፍያ ስራ ከጀመሩበት ከህዳር 5 ቀን 1993 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ተሰናበቱበት ህዳር 1 ቀን 1996 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ክፍያ ነው የትርፍ ሰዓትም ሆነ የበአላት ቀን ክፍያ ደግሞ ከደሞዝ ጋር አብሮ የሚከፈል በመሆኑ (የአዋጁን አንቀጽ (68(2)ይመለከታል) ተጠሪ እነዚህን ክፍያዎች መጠየቅ ያለባቸው የትርፍ ሰዓት ወይም የበአል ቀናት የሰሩበት ወር ደሞዝ ከሚከፈልበት ቀን አንስቶ እስከ 6 ወር ድረስ ብቻ ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪ በክሣቸው ካቀረቡት የክፍያ ጥያቄ ውስጥ በይርጋ ሊታገድ የማይችለው ክስ ካቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ ወደኋላ ያለው የስድስት ወር ክፍያ ብቻ ነው፡፡

በእርግጥ አመልካች የይርጋውን ክርክር ስለ ማንሣቱ በፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ግልባጭ ላይ የሚታይ ባይሆንም በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ሃተታ ላይ ግን ክርክሩ መነሣቱ ይታያል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን በዝምታ አልፎታል፡፡ ተጠሪም ቢሆኑ በዚህ ችሎት ቀርበው ክርክሩ

በስር ፍርድ ቤት አለመነሣቱን ያስተባበሉት ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ተጠሪ ትርፍ ሰዓት እና የበአል ቀናት ያለመስራታቸውን ባለማስተባበሉ የስር ፍርድ ቤቶች አቤቱታውን እንዳመነበት መቁጠራቸው የሕግ ስህተት ፈጽመዋል አያስብላቸውም፡፡ ምክንያቱም ተከሣሽ ክሱ ላይ የቀረበውን ነገር በዝርዝርና በግልጽ ያልካደው ከሆነ እንደታመነ የሚቆጠር መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 235 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡

በአጠቃላይ በይርጋ ሊታገድ የማይችለው ክስ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ ወደ ኋላ ባለው የ6 ወር ጊዜ ውስጥ ተጠሪ የሰሩበት የትርፍ ሰዓት እና የበዓል ቀናት ክፍያ ብቻ በመሆኑ አመልካች ሊከፍል የሚገደደውም ይኸንኑ ክፍያ ብቻ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የአመልካችን የይርጋ ክርክር በማለፍ የ3 ዓመት የትርፍ እና በአል ቀናት ክፍያ እንዲከፈል መወሰናቸው የሕግ ስህተት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35539 በግንቦት 30 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ክስ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ ወደ ኋላ ሲቆጠር 6 ወር ያለፈው የክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡
3. ክስ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ ወደ ኋላ በአለው የ6 ወር ጊዜ ውስጥ ተጠሪ የሰሩት የትርፍ ሰዓት እና የበዓል ቀናት ክፍያ ካለ ይኸው ታስቦ ይከፈላቸው፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 21329

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፍስሐ ወርቅነህ

ዳኜ መላኩ

ደስታ ገብሩ

አማረ አሞኜ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ አቶ በቀለ ኩምሳ

2ኛ/ አቶ ኦላኒ ግዛው

3ኛ/ አቶ ሰቦቃ መለታ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ጥያቄ ለሥራ መሪ ሊከፈል የሚገባ ውዝፍ ደመወዝ ስለመኖር አለመኖሩ የሚመለከት ነው፡፡

ከሣሾች የሆኑት የአሁኑ ተጠሪዎች በኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ተቀጥረን በየሥራ ክፍላችን በሥራ መሪነት በማገልገል ላይ እያለን ድርጅቱ ያለአግባብና ከሕግ ውጭ የሥራ ውላችንን በማቋረጥ ከሥራ እንድንሰናበት ያደረገ በመሆኑ ሥራ ካቋረጥንበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ ለእያንዳንዳችን በመክፈል ወደ ሥራ ሊመልሰን ይገባል በሚል ያቀረቡትን ክስና ክርክር በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድርጅቱ የሥራ መሪዎችን በሚመለከት ካወጣው መመሪያ ውጭ የሥራ ውላቸውን በማቋረጥ ያለአግባብ ከሥራ እንዲሰናበቱ አድርጓል በማለት ወደ ሥራ እንዲመልሣቸውና ሥራ ካቋረጡበት ጊዜ ጀምሮ ለእያንዳንዳቸው ደመወዛቸውን እንዲከፍል የወሰነ ሲሆን ተከሣሽ የሆነው የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ የቻለ

ቢሆንም ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በሚል ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም በዚህ ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች የሥራ መሪዎች ለሆኑት ለአሁን ተጠሪዎች በተለይ ውዝፍ ደመወዝ በመክፈል ወደ ሥራ እንዲመልሣቸው በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ምክንያት ነሐሴ 26 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ገልጾ አቅርቧል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ለሥራ የሚከፈል ውዝፍ ደመወዝ የመኖር አለመኖሩ ጉዳይ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመባሉ የአሁኑ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ተደርጎ ክርክሩ ተሰምቷል፡፡

በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ተጠሪዎች የሥራ ውላቸው ተቋርጦ ሣይሰሩ ለቆዩበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው የጠየቁትም ሆነ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሊከፍላቸው ይገባል ብሎ የወሰነው አሠሪው ድርጅት የሥራ መሪዎችን በሚመለከት ካወጣው የአስተዳደር መመሪያ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ ለሥራ መሪ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል የሚያዝ ሕግም ሆነ የአስተዳደር መመሪያ የለም፡፡ ደመወዝ የሚከፈለው በሥራ ውል መሠረት ለተሰራ ሥራ ነው፡፡ ተጠሪዎች የሥራ ውላቸው ተቋርጦ ተሰናብተው በነበረበት ወቅት ለድርጅቱ ያከናወኑት ሥራ ስለሌለ ሊከፈላቸው የሚገባ ደመወዝ አይኖርም፡፡ የሥራ መሪ የሥራ ውል ያለአግባብ ወይም ከሕግ ውጭ ተቋርጧል በሚል እንኳን ውዝፍ ደመወዝ ይከፈለዋል የሚል ሕግ የለም የሚል ነው፡፡

በተጠሪዎች በኩል ያለው ክርክር ደግሞ ሥራችንን በአግባቡ በማከናወንና በመፈፀም ላይ እያለን አሠሪው ድርጅት ካለው ሕግና መመሪያ ውጭ ከሥራችን በማፈናቀል እንዳንሰራ አድርጎ ላቆየበት ጊዜና ለደመወዛችን አለመከፈል ምክንያት ተጠያቂው አመልካቹ ድርጅት ስለሆነ ውዝፍ ደመወዛችንን የማይከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ ውዝፍ ደመወዝ ለሥራ መሪዎች አይከፈልም ብሎ የሚከለክል ሕግም የለም፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 54(2) ያለአግባብ የሥራ ውሉ ለተቋረጠበት ሠራተኛ የ12 ወር ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው ፍ/ቤት መወሰን እንደሚችል ስለሚያስረዳ ይኼው በትርጉም ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል። ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደስራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚታይበት የህግ ስህተት የለም በሚል የቀረበ ነው።

ችሎቱም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

በዚህም መሠረት በቀረበው ጉዳይ ከሕጉ አንፃር መወሰን የሚገባው ዋናው ነጥብ የሥራ ውሉ ተቋርጧል ተብሎ ከሥራ ተሰናብቶ ለቆየ የሥራ መሪ አሠሪው ድርጅት ውዝፍ ደመወዝ ለመክፈል የሚገደድበት የሕግ ምክንያት አለ ወይንስ የለም? ለሥራ መሪ ውዝፍ ደመወዝ ይከፈል ለማለት የሕግ መሠረቱ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

ለሰበር ችሎት አቤቱታው የቀረበበት ምክንያት የውዝፍ ደመወዝ ጥያቄን በሚመለከት ስለሆነ በዚህ መዝገብ የአሁን ተጠሪዎች ወደ ሥራ እንዲመለሱ ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን መመረመር አስፈላጊ አይደለም። መመርመር የሚገባው የውዝፍ ደመወዝ ጥያቄ ብቻ ነው።

<u>ለሥራ መሪ የሚከፈል ውዝፍ ደመወዝ መኖር አለመኖሩን በተመለከተ</u>

አንድ ተከራካሪ ወገን በሕግ ይገባኛል ብሎ የሚጠይቀው መብት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መሆን ይኖርበታል። ፍርድ ቤትም ለአንድ ተከራካሪ ወገን እንዲህ ዓይነት መብት ይገባዋል ብሎ የሚሰጠው ውሣኔ በሕጉ የሚደገፍና ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆን እንዳለበት ይታመናል። በዚህም ጉዳይ የሥራ መሪዎች ሆነው የተገኙት የአሁን ተጠሪዎች አሠሪው ድርጅት የሥራ ውላቸው ተቋርጧል ብሎ ከሥራ በማሰናበቱ ምክንያት ሣይሰሩ ለቆዩበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለን ይገባል በሚል ያቀረቡት ጥያቄና ክርክር በሕጉ በኩል ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑና የሕግ መሠረት ሊኖረው መቻል አለመቻሉ ሲመረመር በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪዎች የሥራ

መሪዎች መሆናቸው ስለተረጋገጠ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 የሚሸፈኑ አይደሉም። በዚህ ሕግ የማይሸፈን የሥራ መሪ የሚያቀርበው ወደ ሥራ የመመለስ ጥያቄም ሆነ የውዝፍ ደመወዝ ጉዳይ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በሚመለከተው ሕግ መሠረት ታይቶ የሚወሰን ባለመሆኑ ተጠሪዎች አሠሪው አካል የሥራ ውሉን ከሕግ ውጭ በማቋረጥ ላባረረው ሠራተኛ ፍርድ ቤት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት መወሰን ይችላል በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም። የተጠቀሰው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ በእንዲህ አይነቱ ጉዳይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍርድ ቤት የሥራ መሪ የሆኑት የአሁን ተጠሪዎች ፈጽመዋል የተባለው ጥፋት ወይም ታይተውባቸዋል የተባሉት የሥራ ድክመቶችና ጉድለቶች የሥራ ውላቸው ተቋርጦ ከሥራ እንዲባረሩ ለማድረግ የሚያስችሉ አይደሉም፤ አሠሪው ድርጅት የወሰደው እርምጃ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ወደ ቀድሞ ሥራቸው እንዲመልሣቸው፣ ላልሰሩበት ጊዜም ውዝፍ ደመወዛቸው ታስቦ እንዲከፈላቸው የወሰነው የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን በየካቲት ወር 1993 ዓ.ም ያወጣውን የሥራ መሪዎች የአስተዳደር መመሪያ መሠረት በማድረግ ሲሆን መመሪያው ደግሞ ሲታይ የሥራ ውሉ ያለአግባብ ተቋርጦ ከሥራ እንዲሰናበት የተደረገ የሥራ መሪ ወደ ሥራ እንዲመለስ ሲደረግ ላልሰራበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ታስቦ ይከፈለዋል አይልም። መመሪያው ለሥራ መሪ የሚከፈል ውዝፍ ደመወዝ ስለመኖሩ በግልጽ የሚያስረዳው ነገር ስለሌለ በድርጅቱ በኩል የወጣው መመሪያ የሥራ መሪን የውዝፍ ደመወዝ ጥያቄ የሚደግፍ አይደለም። የፍርድ ቤቱም ውሣኔ የአስተዳደር መመሪያውን የተመረኮዘ ነው የሚባል አይደለም።

በሌላም በኩል ጉዳዩ በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ አምስተኛ መጽሐፍ ክፍል "ስለሥራ ውል በጠቅላላው" በሚለው ሥር ከተዓፉ ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ የዚሁ ሕግ ቁጥር 2573 አሠሪው ያለበቂ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥራ ውሉን ቀሪ በማድረግ ወይም አላድስም በማለት ሠራተኛው ከሥራ እንዲሰናበት ሲያደርግ ሠራተኛው ኪሣራ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ የኪሣራውን መጠን በተመለከተም ቁጥር 2574(2) ሠራተኛው ባለፈው ሦስት ወር ከተቀበለው ደመወዝ ሊበልጥ እንደማይችል ያስረዳል፡፡

በዚህ መዝገብ በቀረበው ጉዳይ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪዎች ወደ ሥራ እንዲመለሱ ተወስኖ በሥራ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን በክርክሩ ላይ ስለገለፁ ከላይ የተጠቀሰው ከሥራ ለተሰናበተ ሠራተኛ ስለሚሰጥ ኪሣራ የሚደነግገው የፍትሐብሔር ሕግ ለዚህ ጉዳይ ሊያገለግል አይችልም፡፡ ይህ ሕግ ሠራተኛው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራው ይመለስ ብሎ ለመወሰን የሚያስችል አይደለም፡፡ ሕጉ እስከመጨረሻው ከሥራ ተሰናብቶ ለሚቀር ሠራተኛ አሠሪው ሊከፍለው ስለሚገባው ኪሣራ የሚመለከት በመሆኑ ወደሥራ ይመለሱ ለተባሉት ለአሁኑ ተጠሪዎች አሠሪው ድርጅት በዚህ ሕግ መሠረት ኪሣራ ሊከፍላቸው ይገባል ሊባል አይችልም፡፡ በአጠቃላይ ወደ ሥራ ይመለሱ የተባሉት የአሁን ተጠሪዎች የሥራ ውላቸው ተቋርጧል በሚል ምክንያት ሥራ ላይ ላልነበሩበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ይከፈላቸው ብሎ ለመወሰን የሚያስችል ሕግ አልተገኘም፡፡

የሥር ፍ/ቤት የሥራ ውላቸው ተቋርጧል ተብሎ በአሠሪው ድርጅት ሥራ ላይ ተሰማርተው ላልቆዩት የሥራ መሪዎች ላልሰሩበት ጊዜ አሠሪው ውዝፍ ደመወዝ ሊከፍላቸው ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሥራ ውሉ ተቋርጧል ተብሎ በሥራ ላይ ላልቆየ የሥራ መሪ በሕጉ ሊከፈለው ይገባል የሚባል ውዝፍ ደመወዝ እንደሌለ ስለተረጋገጠ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 44088, ሰኔ 17 ቀን 1997 ዓ.ም ውዝፍ ደመወዝን በሚመለከት የሰጠውን ውሣኔም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይኼው ጉዳይ በይግባኝ ቀርቦለት በመ/ቁ 40928, ሀምሌ 28 ቀን 1997 ዓ.ም ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በሚል የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሣኔ የሥር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ወደ ሥራ ይመለሱ በሚል የሰጠውን ውሣኔ ክፍል አይነካም፡

2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የፍርዱ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 22275

ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢት/ንግድ ባንክ - የቀረበ የለም፡፡

መልስ ሰጪ፡- አቶ ኃይሌ ገ/ሥላሴ - ቀረበ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የፌ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ሥራ ክርክር ችሎት በመ/ቁ. 16341 ግንቦት 19 ቀን 1997 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔና በይግባኝም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40290 ሕዳር 6 ቀን 1998 ዓ.ም የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በማጽናት ይግባኙ አያስቀርብም በማለቱ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ሊታረም ይገባዋል በማለት የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

የአሁኑ መ/ሰጪ በሥር በአሁን አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ፡- ህዳር 14 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ በተከሣሽ መ/ቤት በጥበቃ ሠራተኛነት በወር ብር 230 ደመወዝ እየተከፈለኝ ስሰራ ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሌን በማቋረጡ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የካሣ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ክፍያ እንዲሁም ክፍያው ለዘገየበትም ክፍያ የሥራ ምስክር ወረቀት ጨምሮ ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፈል እንዲወሰንበት የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካችም ለቀረበለት ክስ የሰጠው መልስ፡- ከሣሽ ተቀጥሮ ሲሠራ የነበረው ድርጅቱ በመያዣነት የያዛቸውን የተለያዩ ተበዳሪ ሰዎች ገንዘብ

ባለመክፈላቸው ንብረቱ እስኪሸጥ ድረስ በጥበቃ ሠራተኛነት በተለያየ ጊዜ ውል እየታደሰለት ሲሠራ የቆየና የመጨረሻ ጊዜ ውል የታደሰለትም ግንቦት 6 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 5 ቀን 1996 ዓ.ም ሲሆን፣ ከሣሽ ከሥራ ሊሠናበት የቻለው ድርጅቱ የዕዳት እና የጥበቃ ሥራን ለሌላ ድርጅት በኮንትራት ለማሠራት በመስጠቱ ነው በማለት ስንብቱ ህገወጥ ነው ሊባል ስለማይችል ከሣሽ የጠየቀው የክፍያ ጥያቄ አይገባውም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሥራውን ለሌላ ድርጅት በኮንትራት መስጠቱን የሚያሳይም ሰነድ አቅርቧል፡፡

ክሱ የቀረበለት የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በመጨረሻም፡- የከሣሽ የሥራ ውል የሚቋረጠው ነሐሴ 5 ቀን 1996 ዓ.ም ሆኖ ተከሣሽ ግን ከሣሽን ከሥራ ያሰናበተው ሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም የውሉ ጊዜ ሳያበቃ በመሆኑ ስንብቱ ህገወጥ ነው፡፡ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከህግ ውጪ ሲሆን ደግሞ የስንብት ክፍያ ሊከፈል ስለሚገባ የከሣሽ ጥያቄ ተቀባይነት አለው፡፡

የካሣ ክፍያን በተመለከተ የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ የውሉ ጊዜ ሊቆይ እስከሚችለው ጊዜ ድረስ ያለው ከሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 5 ቀን 1996 ዓ.ም ያለው ደመወዙ ሊከፈለው ይገባል፡፡

የዓመት እረፍትን በተመለከተም በአዋጁ ቁጥር 377/96 አ.79/5/ ከሁለት ዓመት በላይ ሊጠየቅ ስለማይችል የሥራ ውሉ ከመቋረጡ ሁለት ዓመት በፊት ያለው ይከፈል፡፡ የሥራ ምስክር ወረቀት ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲሰጥ በማለት መወሰኑን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

የአሁን አመልካች በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 ይግባኙ ተሠርዞበታል፡፡

ለሰበር የቀረበው አቤቱታም በዚሁ ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት እንዲታረም የሚጠይቅ ሲሆን፣ አቤቱታው ተመርምሮ የሥር ፍ/ቤት የመ/ሰጪ የሥራ ውል የተቋረጠው በህገወጥ መንገድ ነው በማለት ለመ/ሰጪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈል የተሰጠው ውሣኔ በህጉ አግባብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆን አለመሆኑን ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል፡፡

በዚህም መሠረት ግራቀኙ እንዲቀርቡ ተደርጐ የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በአመልካችና በመ/ሰጪ መካከል የሥራ ውሉ የሚቆየው እስከ ነሐሴ 5 ቀን 1996 ዓ.ም ሆኖ ከወዲሁ ሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም የመልስ ሰጪ ውል ሊቋረጥ የቻለው መልስ ሰጪ ይሠራበት የነበረው የጥበቃ ሥራና የዕዳት አገልግሎትንም ጨምሮ ለሌላ ድርጅት በኮንትራት ተሰጥቶ በማሠራት መሆኑን አመልካች ማስረጃ አቅርቦ ማስረዳቱ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተመዝግቧል፡፡

በዚህ መሠረት አመልካች የመልስ ሰጪን የሥራ ውል ሊያቋርጥ የቻለው መልስ ሰጪ ይሠራበት የነበረው የሥራ መደብ ለሌላ ድርጅት በመሰጠቱ ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠና ያልተካደ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ አሠሪው በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም፣ የድርጅቱን ምርታማነት ለማሳደግ የአሠራር ዘዬዎችን በመለወጡ ምክንያት ሠራተኛው የያዘው የሥራ መደብ ቢሠረዝ አሠሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት በህጋዊ መንገድ የሠራተኛውን የሥራ ውል ማቋረጥ እንዲችል የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 መብት ይሰጠዋል፡፡

የሥር ፍ/ቤት የመልስ ሰጪ የሥራ ውል የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው ያለው የውል ዘመኑ ከማለቁ በፊት የሥራ ውሉ መቋረጡን ምክንያት በማድረግ ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ ቢሆን አሠሪው የሥራ ውሉን ለማቋረጥ በቂና ህጋዊ የውል ማቋረጫ ምክንያት እስካለው ድረስ የውል ዘመኑ ከማለቁ በፊት ወይም የውል ዘመኑ ላልተወሰነ ጊዜ ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 35 መሠረት የማስጠንቀቂያ ጊዜ በመስጠት የሥራ ውሉን ለማቋረጥ እንደሚችል ከህጉ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡

ማስጠንቀቂያ መስጠት የሚያስፈልገውም በተለይ በዚህ ጉዳይ የውሉ ዘመን ሳያልቅ በበቂ ምክንያት የሥራ ውሉ ከወዲሁ ሊቋረጥ የሚችል ሆኖ ሲገኝ እንጂ የውሉ ዘመኑ በማለቁ የሥራ ውሉ ለሚቋረጥ ሠራተኛ ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ አይሆንም፡፡ አመልካች የውል ዘመኑ ከመድረሱ በፊት የመልስ ሰጪን የሥራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት መኖሩን እያስረዳ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ የሥራ ውሉን ማቋረጡ ግን አግባብ እንዳልሆነ ግልጽ ነው :: ይህ ማለት ግን የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው ማለት ሳይሆን ውጤቱ ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ በህጉ በተጠቀሰው በማስጠንቀቂያው ጊዜ ለሠራተኛው ሊከፈለው ይገባ የነበረውን ደመወዝ እንዲከፍለው የሚያስገድደው ብቻ ነው የሚሆነው፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት አመልካች የመልስ ሰጪን የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ በማቋረጡ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው በሚል ይህን ተከትሎ የሚከፈል ክፍያ እንዲፈፀም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለው ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የመልስ ሰጪ የሥራ ውል የተቋረጠው በህግ አግባብ በመሆኑ የስንብት ክፍያም ሆነ የውሉ ጊዜ ሊቆይ እስከሚችልበት ጊዜ ድረስ ያለው ደመወዙ በካሣ መልክ ለመልስ ሰጪ እንዲከፈለው በፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.16341 ግንቦት 19 ቀን 1997 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔም ሆነ በይግባኝ የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 40290 ህዳር 6 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የሥራ ውል ዘመኑ ከማለቁ በፊት ያለማስጠንቀቂያ የመልስ ሰጪን የሥራ ውል በማቋረጡ በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 35/1/ መሠረት በማስጠንቀቂያው ጊዜ ሊከፈለው ይገባ የነበረውን የአንድ ወር ደመወዝ አመልካች ለመልስ ሰጪው እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የዓመት እረፍት ፈቃድ ክፍያንና የሥራ ምስክር ወረቀት እንዲሰጥ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እንደተጠበቀ ነው ፀንቷል፡፡
4. የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በዚህ መልኩ ተሻሽሎ የተወሰነ በመሆኑ ይኸው ታውቆ ተገቢው ይፈፀም ዘንድ የዚህ ውሣኔ ግልባጭም ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡
5. ወጪና ኪራሣ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 25317

ጎዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ጥቁር አባይ ትራንስፖርት - ዘርኡ ኃይሉ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ደሳለኝ አብርሃ - ጠበቃ ማስረሻ በላይ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአማራ ብ/ክ/መ/ በኮምቦልቻ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረው የሥራ ውል ከሕግ ውጭ የተቋረጠበት መሆኑን በመግለጽ ወደ ስራው እንዲመለስ፤ ይህ ካልተቻለም በሕጉ መሠረት ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉትና እንዲሰናበት ይወሰንለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኋላ፤ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው፡፡ ስለዚህም ከሣሽ የጠየቀውን ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎት ይሰናበት ሲል ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል እና የተጠሪው ከውሳኔው በፊት መሞቱን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አመልካች የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ ለተቋረጠበት ተጠሪ ጥገኞች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39/2/ለ/ እና 110/3/ መሠረት ታስቦ የሥራ ስንብት ክፍያ ይሰጣቸው በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ሰኔ 8 ቀን 98 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤት ለተጠሪ ጥገኞች እንዲከፈል ያሉት ገንዘብ በሕጉ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ በገንዘቡ አሰላል ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ እኛም ይህን አቤቱታ መሠረት በማድረግ የተጠሪውን ወራሾች /ጥገኞች/ አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ክርክሩን አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ሕግ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 ነው፡፡ መወሰን ያለበት ነጥብም የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በመባሉ ምክንያት ለጥገኞቹ የሚከፈለው ክፍያ የሚሰላው እንዴት ነው? የሚለው ነው፡፡ የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሰራተኛ ሕግ ከደነገገው ውጪ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውሉ ሲቋረጥ የሥራ ስንብት እና ካሣ የሚከፈለው በአዋጁ አንቀጽ 40 መሠረት ነው፡፡ ሠራተኛው ክፍያው ሳይፈጸምለት የሞተ ከሆነ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 110/2/ ለተመለከቱት ጥገኞቹ እንደሚከፈል በአንቀጽ 39/2/ ተመልክቶአል፡፡ ሕጉ የዘረጋው አሠራር ይህን በመሰለ ሁኔታ በግልጽ የተቀመጠ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቱ የተከተለው አካሄድ ግን ከዚህ የወጣ ነው፡፡ ክፍያውን ያሰላው ሠራተኛው /ሟች/ በሥራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት እንደሞተ በመቁጠር ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በዋቢነት የጠቀሰው አንቀጽ 110/3/ የሚገኘው "በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ስለሚሰጡ ክፍያዎች" በሚለው በአዋጁ በምዕራፍ ሦስት ስር ነው፡፡ አንቀጽ 110/2/ በአንቀጽ 39/2/ የተጠቀሰውም በሥራ ውል ከሕግ ውጪ መቋረጥ የተነሳ የሚከፈለው ክፍያም በስራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች በሚሰጡት ክፍያዎች ዓይነት ይሰላል ለማለት ታስቦ ሳይሆን፣ የሟች ጥገኞች ተዘርዝረው የሚገኙት በአንቀጽ 110/2/ በመሆናቸው ነው፡፡ ስናጠቃልለው ከሕግ ውጪ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ በሞተ ጊዜ ለጥገኞቹ ክፍያ የሚፈጸመው በአዋጁ አንቀጽ 39/2/ እና 40 መሠረት እንጂ በአንቀጽ 110/3/

መሠረት እንዳልሆነ በሕጉ በግልጽ ተመልክቶ ስለሚገኝ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአማራ ብ/ክ/መ/የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08881 ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ለተጠሪ ጥገኞች የሚሰጠውን ክፍያ በተመለከተ የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ለተጠሪ ጥገኞች የሚሰጠው ክፍያ መሠላት ያለበት በአዋጁ አንቀጽ 39/2/ እና 40 መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ክርክር /የሰበር/ ምክንያት የደረሰ ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

   በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለስር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 25511

ጥቅምት 2 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነገረ ፈጁ አቶ ታምራት ታለጌታ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አብራራው ከፍያለው - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበው የሥራ ውል በሕጋዊ ምክንያት በተቋረጠ ጊዜ አሠሪው የሥራ ስንብት ክፍያ እንድከፍል በሕግ ከተደነገገው ውጪ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንዲታረም ሲል አመልካች ሰኔ 16 ቀን 1998 ዓ.ም. ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የሰበር ችሎትም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከአሠሪ /አመልካች/ ፈቃድ ውጪ ተጠሪ ከስራ ገበታው ላይ በመጥፋቱ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት ተረጋግጦ እያለ የሥራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈለው መወሰኑ በሕጉ አግባብ ስለመሆኑ ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ ቀርበው ክርክራቸውን አሰምቷል፡፡

በዚሁ መንፈስ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡ በሥር ፍ/ቤት እንደተረጋገጠው የሥራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ ከአንድ ወር በላይ በገዛ ፈቃዱ ከሥራ ገበታው ላይ በመቅረቱ ምክንያት መሆኑ በሥር ውሣኔ ተመልክቷል፡፡ ይህ መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ሕጋዊ ምክንያት አለው፡፡ የሥር ፍ/ቤትም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጋዊ ምክንያት መሆኑን ተቀብሎታል፡፡

የሥር ፍ/ቤት የሥራ ውል የተቋረጠው በተጠሪ ጥፋት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የሥራ ስንብት ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፈል ሲወስን መሠረት ያደረገው የሕግ ድንጋጌ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 40 /2/ መሆኑን በውሣኔው ተመልክቷል፡፡

አመልካች ይህ የስራ ስንብት ክፍያ ውሣኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ አይደለም እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ሲል ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ከፍተኛው ፍ/ቤት የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አጽንቷል፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት ሊታይ የተፈለገው መሠረታዊ ነጥብ የሥራ ውሉ በሕጋዊ ሁኔታ ከተቋረጠ ለሠራተኛው የሚከፈል የስራ ስንብት ክፍያ ስለመኖሩ በሕጉ የተመለከተውን ማገናዘብ አስፈላጊነት እና የሥር ፍ/ቤት አቋም አግባብነትን ነው፡፡

የሥራ ውሉ የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች በአዋጁ በዝርዝር የተመለከቱ በመሆናቸው ያንን ደግሞ መዘርዘሩ አስፈላጊ አይደለም፡፡ የሥራ ውል በተለያዩ ምክንያቶች ሲቋረጥ የሚኖረው ውጤትም እንደዚሁ በሕጉ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በተለይም ለሠራተኛው ሊጠበቁ የሚገቡ የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችና መብቶች በአዋጅ ቁ. 337/96 በምዕራፍ ሦስት በተለይም በዘርፍ አንድ፣ ሁለት እና ሦስት ተመልክተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሥራ ስንብት ክፍያን በሚመለከት የተቀመጠው ድንጋጌ አንቀጽ 39 ጠቅላላ ሁኔታን የሚዘረዝር ሲሆን ከነዚህም ዝርዝር ሁኔታዎች መረዳት የሚቻለው የሥራ ስንብት ክፍያን የማግኘት ጉዳይ የሁሉም የሥራ ውል መቋረጥ ውጤት ሳይሆን ለውስንና የተገደቡ ምክንያቶች ብቻ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ በመሠረቱ የዚህ ሕግ ድንጋጌ መንፈስ ቀደምት ከነበረው አዋጅ ቁጥር 42/85 የተለየ ይዘት ያለው መሆኑን ማጤን አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 39/1/ መሠረት “የሙከራ ጊዜውን የጨረሰና በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ ከአሠሪው የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት” እንዳለው ተደንግጓል፡፡ ይህ ሁኔታ በማናቸውም የሥራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል መቋረጥ ላይ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በአንባሩ አዋጅ ቁ. 377/96 ግን የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፈል የሚችለው የሥራ ውሉ በማናቸውም ምክንያት ለተቋረጠበት ሠራተኛ ሁሉ ሳይሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 39/1/ሀ-ረ/ እና በማሻሻያው አዋጅ ቁ 494/98 አንቀጽ 2 /ሰ-ቀ/ በተዘረዘረው ምክንያት ብቻ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ አሁን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው ተጠሪው ያለ አመልካች /አሰሪ/ ፈቃድ ከአንድ ወር ላላነሰ ጊዜ ከሥራው ገበታ በመጥፋቱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ሁኔታ መኖሩ ከተረጋገጠ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1/ለ መሠረት ተጠሪ ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉ ሊቋርጥ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የሥራ ውሉ መቋረጥ ሕጋዊ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከዚህ አንፃር የሥራ ውል በዚህ ምክንያት ሲቋረጥ ጠሥራ ስንብት ክፍያ ሊፈጸም የሚችልበት ሁኔታ ከላይ በተመለተው የአዋጁ እና የማሻሻያው ድንጋጌዎች ውስጥ የተካተተ አይደለም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የአዋጅ ቁ. 377/96ን መንፈስና ይዘት በአግባቡ ሳያጠኑት በአዋጅ 42/85 የነበረውን ይዘት በመከተል አሁን ለቀረበው ክርክር የሰጡት ውሣኔ የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሥራ ውሉ መቋረጥ ሕጋዊ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የስንብት ክፍያን በተመለከተ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 39 ከነማሻሻያው በተመለከቱት ዝርዝር ምክንያቶች ውስጥ ያልተካተተን ሁኔታ መሠረት አድርገው የስራ ስንብት ክፍያ ለተጠሪው እንዲከፈል መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በሌላ በኩል የዓመት እረፍት ክፍያን በተመለከተ በአመልካች በኩል የቀረበ አቤቱታ ስለሌለ ውሣኔውን አልመረመርነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አመልካች የሥራ ስንብት ክፍያ ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡
2. የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁ. 07868 ግንቦት 14 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ 15756 ሰኔ 8 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. በሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 25765

ጥቅምት 07 ቀን 2000

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ኃይለሚካኤል ይህደጎ

ተጠሪ፡- ግርማ አየለ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል፡፡

ፍ ር ድ

የዚህ መዝገብ ክርክር የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ ለልሰና ሥራ በአመልካች ተቀጥሬ እየሠራሁ ባለሁበት አመልካቹ ያለጥፋት የሥራ ውሴን ስላቋረጠ ወደ ሥራ ሊመልሰኝ ይገባል ይህ ካልሆነም የሥራ ስንብት፣ የካሣና ሌሎች ክፍያዎች ሊከፈለኝ ይገባል ሲል ክስ መስርቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪው በግል ሕንፃዬ ላይ ይሠራ የነበረው ጊዜያዊ ሥራ ነው፤ ሥራው በመጠናቀቁ ነው የተሠናበተው በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ተጠሪ ከሥራ የተሰናበተው ሥራው በማለቁ ምክንያት መሆኑን አመልካች አላስረዳም፤ በማለት ተጠሪ የጠየቃቸው ክፍያዎችን ሊያገኝ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሠርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝቶ ለዚህ ፍ/ቤት ያቀረበው አቤቱታ ተጠሪ የተቀጠረው ለግል ቤቱ የልሰና ሥራ ለአጭር ጊዜ ነው፤ አንድ ወር እንኳን መሥራቱን ባላስረዳበት ሁኔታ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ያለግባብ ነው ተብሎ የተወሰነብኝ ውሣኔ ሊሻር ይገባል በማለት ነው፡፡ ተጠሪ የተቀጠረው

ለተወሰነ ሥራ መሆን ያለመሆኑን ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክር ተሠምቷል፡፡

ተጠሪ ለልሠና ሥራ የተቀጠረ መሆኑ የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ላይ ተመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ የተቀጠረው አመልካች ለድርጅት ሥራው በሚያስገነባው ሕንፃ ላይ መሆኑን በውሣኔው ጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም ተጠሪው በቋሚ ሥራ አለመቀጠሩንም በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን የሥራ ውል ባሕርይ፣ ሲገለጽ ጠቅሶታል፡፡

የሥራ ውል ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሠሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሠሪው ለመሥራት የሚደረግ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 4/1/ ይደነግጋል፡፡

ተጠሪ የተቀጠረው አመልካች ያሠራ ለነበረው ቤት የልሰና ሥራ እንዲሠራ ነው፡፡ ቤቱን የመለሰን ሥራ ሲያበቃ የሥራ ውሉም ያበቃል ማለት ነው (አንቀጽ 10/1/ሀ/) ፡፡ በሁለቱ መካከል ይህ ውለታ መኖሩ እየታወቀ ሥራው በማለቁ ምክንያት ተጠሪ ስለመሠናበቱ አመልካች አላስረዳም በማለት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ከላይ በሕጉ ላይ እንደተገለፀው የሥራ ውል ለተወሰነ ሥራ ሊያደርግ እንደሚችል የተደነገገውን ያላገናዘበ ነው፡፡

በሌላ በኩል የሥራ ስንብት ክፍያና ካሣ የሚከፍለው የመከራ ጊዜውን ለጨረሰና በአዋጁ አንቀጽ 39 ሥር በተመለከቱት ምክንያቶች የሥራ ውሉ ለተቋረጠበት ሠራተኛ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ግን የተጠሪው የሥራ ውል ለተወሰነ ሥራ የተደረገና ሥራው በማለቁ ውሉ የተቋረጠ በመሆኑ የስንብትና የካሣ ክፍያ ይከፈለው መባሉ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የሥራ ውሉ የተቋረጠው ያላግባብ ነው ሲል መወሰኑና የስንብትና ካሣ ክፍያ ይሰጠው ማለቱም ሆነ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን መሠረዙ ተገቢ ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡

ተጠሪ የካሣና የስንብት ክፍያ አይገባውም ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ.26077

ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሀይ ታደሠ

አሠግድ ጋሻው

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሠ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ አይናለም ባይሌ ቀረበ

ተጠሪ፡- የኢት/ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ መንበረ አድማሱ ቀረበች

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥራ ስንብት ክፍያን ይመለከታል፡፡

አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከስራ በገዛ ፍቃዳቸው የለቀቁ መሆኑን ገልፀው በተጠሪ ድርጅት 9ኛው ህብረት ስምምነት አንቀፅ 34(2) መሠረት የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሠጠው መልስ የተጠቀሠው የህ/ስምምነት በራሱ አነሳሽነት ስራውን የለቀቀ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ እንደሚከፈለው በግልፅ አላሠፈረም፣አስፍሯል ቢባል እንኳን ህ/ስምምነቱ ከአ/ቁ. 377/96 አንቀፅ 39 ጋር ይቃረናል፡፡ ስለዚህ ተፈፃሚነት የሚኖረው ህጉ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 39 ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ስንብት መክፈያ ምክንያቶች አነስተኛ መለኪያዎች (minimum standards) ከመሆናቸው በላይ በአዋጁ አንቀፅ 377/96 አንቀፅ 134(2) መሠረት የህ/ስምምነቱ ለሠራተኛው የበለጠ ጥቅም የሚያስገኝ ሆኖ ሲገኝ ስምምነቱ ተፈፃሚ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ በአጠቃላይ 9ኛው ህ/ስምምነት በአ/ቁ 377/96 ባልተሻረበት ሁኔታ የስራ ስንብት ክፍያው ተፈፃሚ መሆን የለበትም የሚለው የተጠሪ ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ለአመልካች የሚገባቸው የሥራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ በአ/ቁ 377/96 በራሱ አነሣሽነት የሥራ ውሉን ላቋረጠ ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ አልተፈቀደም፡፡ የተጠሪ ድርጅት የህ/ስምምነት ደግሞ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው አዲሱን አዋጅ እስካልተቃረነ ድረስ ነው፡፡ በመሆኑም የህ/ስምምነቱ አንቀፅ 34(2) ተፈፃሚነት የለውም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በተጠሪ ድርጅት 9ኛው የህብረት ሥምምነት በራሱ አነሣሽነት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያለው ቢሆንም ይህ ድንጋጌ ከአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 39 ጋር ይቃረናል በማለት የአመልካች የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት መከልከሉ በአግባቡ መሆኑ ቀርቦ እንዲታይ ተደርጓል፡፡ በዚህም ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ የፁሁፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡ የፁሁፍ ክርክራቸውም በሥር ፍ/ቤቶች የተነሱትን ነጥቦች ያካተተ ነው፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ ከግራ ቀኙ ክርክር የተጠሪ ድርጅት 9ኛው ህ/ስምምነት በራሱ አነሣሽነት የስራ ውሉን ያቋረጠ ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ተረድተናል፡፡ ክርክሩ በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 39 በራሱ አነሣሽነት የሥራ ውሉን ያቋረጠ ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያልተጠበቀለት በመሆኑ የህ/ስምምነቱ አንቀፅ 34(2) ተፈፃሚነት ሊኖረው ይችላል? አይችልም? የሚለው ነው፡፡

በእርግጥ የአ/ቁ 377/96 የስራ ስንብት ክፍያ የሚከፈልባቸውን ሁኔታዎች በአንቀፅ 39(1) ሥር ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥም በራስ አነሣሽነት የስራ ውልን ማቋረጥ አልተመለከተም ነገር ግን ይህ የአዋጁ ድንጋጌ አሠሪው በድንጋጌው ሥር ከተቀመጡት ሁኔታዎች ውጪ የሥራ ውል በሚያቋርጥበት ጊዜ ለሠራተኛው የስራ ስንብት ክፍያ እንዳይከፈለው ያስቀመጠው ክልከላ የለም ፡፡ ይህ ድንጋጌ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት እንዳለው አነስተኛ መለኪያ(minimum standard) ከማስቀመጥ አልፎ

ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጪ በማናቸውም ሁኔታ የስራ ስንብት ክፍያ እንዳይፈፀም ገደብ የሚጥል አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላም ቢሆን ሠራተኛው በራሱ አነሣሽነት ስራ በሚለቅበት ጊዜም የሥራ ስንብት ክፍያ እንዲያገኝ አሠሪውና ሠራተኛው ሊስማሙ ይችላሉ፡፡ ይህ ስምምነትም አዋጁን የሚቃረን ነው ሊባል አይችልም፡፡ በመሆኑም በህ/ስምምነቱ ላይ በራሱ አነሣሽነት ሥራውን የለቀቀ የሰንበት ክፍያ ሊከፈለው ይገባል የሚለው አንቀፅ አ/ቁ 377/96ን ስለሚቃረን ተፈፃሚነት የለውም ሊባል አይችልም፡፡

በሌላ በኩል ቢሆንም በአዋጁ ከተደነገገው ይልቅ የህ/ስምምነቱ የበለጠ መብት ለሠራተኛው የሚያስገኝ ሆኖ ሲገኝ የህ/ስምምነቱ ተፈፃሚ እንደሚሆን በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 134(2) ተመልክቷል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ከአዋጁ ይልቅ ህብረት ስምምነቱ የተሻለ መብት የሚሠጥ በመሆኑ የህ/ስምምነቱ አንቀፅ 134(2) ተፈፃሚ ሊሆን የገባል፡፡

ከፍ ሲል በተገለፀው ምክንያትም አ/ቁ 377/96 አንቀፅ 39 በራሱ አነሣሽነት የስራ ውሉን ላቋረጠ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያልጠበቀለት በመሆኑ የተጠሪ ድርጅት የህ/ስምምነት አንቀፅ 34(2) ተፈፃሚ አይሆንም በሚል የአመልካች የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ የህግ ሥህተት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1) የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 44385 ሚያዚያ 17 ቀን 1998 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2) የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 16173 ጥር 05 ቀን 1998 የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 27704

ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ድራጋዶስ ጄ እና ፒ የመንገድ ሥራ ድርጅት

ተጠሪ፡- አብዲ ሁሴን - ተወካይ ደመላሽ አበበ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የአሠሪና ሠራተኛን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአማራ ብ/ክ/መ/ በሰሜን ሸዋ ዞን ቀውት ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ከሕጉ ውጪ የሥራ ውሌ ተቋርጦብኛል በሚል በአመልካች ላይ ክስ መስርቶአል፡፡ በዚህም ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራው እንዲመለስ እንዲወሰንለት ጠይቆአል፡፡ ፍ/ቤቱ ተከሣሹን በመጥራት ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ሆኖም ከሣሽ ወደ ሥራው ቢመለስ ከተከሣሽ ጋር ተስማምተው ሊሠራ ስለማይችል ውዝፍ ደመወዙ እና ሌሎች ክፍያዎች ተከፍሎት ይሰናበት በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በውሣኔው ስላልተስማማ ወደ ሰሜን ሸዋ መስተዳድር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ክርክሩ እንዲሰማ አድርጎአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል መከፈል ያለበት ውዝፍ ደመወዝ የስድስት ወር ብቻ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አመልካች ኅዳር 27 ቀን 99 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን

ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ወደ ሥራው እንዲመለስ ሳይወሰን ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ለዚህ ጉዳይ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ሕግ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በውሣኔአቸው በዋቢነት የጠቀሱት የአዋጁ አንቀጽ 43/5/ በግልጽ የሚያመለክተው ለሠራተኛው ውዝፍ ደመወዝ የሚከፈለው ሠራተኛው ወደ ሥራው ይመለስ ተብሎ ሲወሰን ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን ሠራተኛው ማለትም ተጠሪው ወደ ሥራው እንዲመለስ አልተወሰነም፡፡ በሌላ አነጋገር የሥራ ውሉ እንዲቋረጥ ተወስኖአል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው መወሰን በቀጥታ ሕጉን መቃረን ነው የሚሆነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተጠሪው ውዝፍ ደመወዝ አይከፈለውም ብለናል፡፡
3. በአማራ ብ/ክ/መ/የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10748 ኅዳር 4 ቀን 1999 ዓ.ም. እና የቀወት ወረዳ ፍ/ቤት መጋቢት 19 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጡአቸው ውሣኔዎች መሻሻላቸው ይታወቅ ዘንድ የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ይላክላቸው፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 27959

ጎንደር 03 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢት/ ፖስታ አገልግሎት ድርድት - ነ/ፈጅ ታደሰ በቀለ

ተጠሪ፡- አቶ አሊ መሐመድ አሊ - ቀረበ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረቡት ተጠሪ ስራ ላይ ላልነበሩበትና በክርክር ላይ ለነበሩበት የ5 ዓመት የአመት እረፍት እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ከሥራ አሠናብታቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ክስ መስርተው በክርክር ላይ ለነበሩበት ጊዜ ያልተሠጣቸው የአመት እረፍት እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ሁለት አመት ያለፈው የአመት እረፍት ሊሠጣቸው እንደማይገባና ስራ ላይ ላልነበሩበት ጊዜ የአመት እረፍት ሊሠጣቸው እንደማይገባ ተከራክሯል፡፡ ወረዳ ፍ/ቤቱም ተጠሪ ክርክር ላይ ለነበሩበት ጊዜ ይርጋው የሚቋረጥ በመሆኑ ከ1991 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም. ያለው የአመት እረፍት እንዲሠጣቸው በማለት ወስኗል፡፡ የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ ስራ ላይ ላልነበሩበት ጊዜ የአመት እረፍት እንዲሠጣቸው መወሰኑ አግባብ መሆን አለመሆኑን፣ነው ቢባል እንኳን 2 ዓመት ያለፈው የአመት እረፍት ሊሠጣቸው የሚገባ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሠበት ችሎት እንዲቀርብ አድርጎ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው ተጠሪ ከስራ ተሠናብተው ስለነበር ወደ ሥራ እንዲመለሱ ክስ መስርተው ተወስኖላቸው ወደ ስራ ተመልሰዋል፡፡ አሁን ክስ ያቀረቡት ከስራ ተሠናብተው ለነበሩበትና በክርክር ላይ ለነበሩበት ጊዜ ያልወሰዱት የአመት እረፍት እንዲሰጣቸው ነው፡፡

በመሠረቱ የሣምንት ወይም የአመት እረፍት የሚሠጠውም ሆነ በቀን የተወሰነ ሠዓት ብቻ እንዲሠራ ሕጉ የሚያስገድደው ሠራተኛው በሥራ የደከመ አእምሮውንና አካሉን በማሣረፍ አካላዊና አእምሯዊ ጤንነቱን በመጠበቅ የሥራ ውጤታማነቱ እንዲጨምር ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሠራተኛ የሣምንት ወይም የአመት እረፍት የማግኘት መብት ሊኖረው የሚችለው በሥራ ገበታው ላይ ተገኝቶ ሥራ ለሠራበት ጊዜ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪ የአመት እረፍት እንዲሠጠው እየጠየቀ ያለው ስራ ላይ ላልነበረበት ጊዜ በመሆኑ እና የሕጉም አላማ ይህ ባለመሆኑ የተጠሪ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የአመት እረፍት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 79/5/ የአመት ፈቃድ ከሚቀጥለው ሁለት አመት በላይ ሊተላለፍ እንደማይችል ስለሚያመለክት ሁለት አመት ያለፈው የአመት ፈቃድ ለተጠሪ እንዲሠጠው የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. የጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03144 በሚያዝያ 18 ቀን 1998 የሠጠው እንዲሁም የምስ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10075 በጎንደር 28 ቀን 1999 ዓ.ም. የሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ስራ ላይ ላልነበሩበትና በክርክር ላይ ለቆዩበት ጊዜ የአመት እረፍት ሊሠጣቸው አይገባም፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 29692

ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ዘውዱ አሊ

ተጠሪ፡- እነ አቶ አለማየሁ ከበደ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የሥራ ውል መኖሩ ስለተረጋገጠና በአመልካችም በኩል የተደረገው ስንብት ሕገወጥ ስለሆነ ካሳና የማስጠንቀቂያ ክፍያ አመልካች ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገባል በማለት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ ተጠሪዎች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች መ/ቤት በተለያየ የሥራ መደብ ተቀጥረን በመሥራት ላይ እንዳለን የተቀጠርንበትም ሥራ ቀጣይነት ያለው ሆኖ ሳለ የሥራ ውሉ ያለአግባብ የተቋረጠ ስለሆነ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎን ወደ ሥራ እንድንመለስ ይወሰንልን ይህም ካልሆነ በአማራጭ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲከፈሉን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽም በበኩሉ በሰጠው መልስ ከሳሾች ሥራው በሚኖር ጊዜ ብቻ በቀን ሂሳብ የሚሰሩ ሲሆን በቀን የሚሠሩትም ሥራ የተቋረጠ ስለሆነ ከሳሾች የቀን ሠራተኞች ስለሆኑ ወደ ሥራ ለመመለስም ሆነ የተለያዩ ክፍያዎችን መጠየቅ ስለማይችሉ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሳሾች የቀን ሠራተኛ በመሆን ሥራ ባለ ጊዜ እንደሚሰሩና ደመወዛቸውም በቀን ታስቦ በሳምንት እንደሚከፈላቸው ከዚህ ሌላ ከባንኩ የሚያገኙት ጥቅማ ጥቅምም ሆነ ግንኙነት እንደሌለ በግራ ቀኙ በኩል የቀረቡት ምስክሮች ያስረዱ ከመሆኑም በላይ በተከሳሽ በኩልም የቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ይህንኑ ስለሚያጠናክር ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 4 አኳያ በመካከላቸው የሥራ ውል እንደሌለ መገንዘብ ስለተቻለ ወደ ሥራ ለመመለስ ሆነ የተለያዩ ክፍያዎች መጠየቅ ስለማይችሉ ክሱ የቀረበው በአግባቡ አይደለም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይ/ባዮች ረዘም ላለ ጊዜ ያለማቋረጥ በይ/ባይ መ/ቤት እንደሰሩ በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ በግራ ቀኙ መካከል የሥራ ውል አለ ካለ በኋላ የሥራ ውሉም የተቋረጠው ያለአግባብ በመሆኑ መ/ሰጭ የ6 ወር ደመወዝ ካሳና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ለይግባኝ ባዮች ሊከፍላቸው ይገባል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪዎች ለተወሰነ ሥራ የተቀጠሩ ቢሆንም ስንብቱ ሕገወጥ ነው በሚል የ6 ወር ካሳና የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፈላቸው የተሰጠው ውሳኔ አግባብነቱ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በመታመኑ ተጠሪዎችን የጠራን ሲሆን ከ13ኛ ተጠሪ በስተቀር ቀሪዎቹ ቀርበው የፌዴራል ከፍተኛ /ፍ/ቤት ውሳኔ አግባብነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ይህም ችሎት በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክር መርምሯል፡፡ ምላሽ የሚያስፈልገውም የክርክሩ የሕግ ነጥብ የስራ ስንብቱ ሕገወጥ ነው? አይደለም? ሕገወጥ ነው ከተባለ የካሳና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ለተጠሪዎች ሊከፈላቸው ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቅድሚያም የግራ ቀኙን የውል ግንኙነት በተመለከተ ማንኛውም ሰው ደሞዝ እየተከፈለው በአሠሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይንም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሠሪው ለመስራት ሲስማማ በሁለቱ መካከል የሥራ ውል ግንኙነት ተመስርቷል ለማለት እንደሚቻል በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 4/1/ የተመለከተ ሲሆን ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የሚደረግ ውልም በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ተዘርዝሮ ይገኛል፡፡

በዚሁ መሠረትም አንዳንድ ጊዜ የሚሰራና ለአሠሪው ቋሚ ሥራ ያልሆነ፣ በሚያስፈልግበት ጊዜ ብቻ የሚሰራ ለተወሰነ ስራ የተደረገ የስራ ውል ሆኖ እንደሚቆጠር የተመለከተ ሲሆን ተጠሪዎችም የቀን ሠራተኛ በመሆን ሥራ ባለ ጊዜ ብቻ በአመልካች መ/ቤት ሥራ ሲሰሩ እንደነበር በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ባቀረቧቸው ምስክሮች የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ አመልካችም ይህንን ያልካዱ በመሆኑ በመካከላቸው የሥራ ውል የተመሠረተ መሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና ተጠሪዎች በአመልካች መ/ቤት የተቀጠሩት ከላይ እንደተመለከተው ሥራ ሲኖር ብቻ እንደ አስፈላጊነቱ አንዳንድ ጊዜ ለሚሰራ ሥራ በመሆኑ እና ይህም ሥራ የአመልካች መ/ቤት ቋሚ ሥራ ሆኖ እየተቋረጠ አልፎ አልፎ የሚሰራ ሥራ በመሆኑ ሥራው እንደተሰራ (እንዳለቀ) አሰሪውን ውሉን ከማቋረጥ የሚያግደው ሁኔታ አይኖርም፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረገ የሥራ ውል በውሉ የተወሰነው ጊዜ ወይም ሥራ ሲያልቅ ወይም ውሉ ሲቋረጥ ስንብቱ ሕጋዊ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 24/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው ውሉ የተደረገው የተወሰነ ስራን በሚመለከት፣ አንዳንድ ጊዜ በሚሰራና ቋሚ ባልሆነ ሥራ በመሆኑ ምክንያት በዚህ መልኩ የተደረገ የሥራ ውል ማቋረጥ ደግሞ በሕግ ስለተፈቀደ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ

ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም ስንብቱ በአግበቡ ነው ስለተባለ የክፍያ ጥያቄው የሚታይ አይሆንም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.49403 የካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሥራ ስንብቱ ሕገወጥ ስለሆነ አመልካች ለተጠሪዎች ካሳና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 21039 መስከረም 03 ቀን 1999 ዓ.ም ስንብቱ በአግባቡ ስለሆነ የክፍያ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡ ይፅፍ፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠ/መ/ቁ. 29740

ሚያዚያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሠ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ስሜነህ ተክሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነገረፈጅ አቶ ዘርዓይ ገ/ወልድ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የተቀጠረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መጋቢት 7 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲል አመልካች መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላመለከተ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ፣ አመልካች ለተጠሪው ስድስት ዓመት ከአስራ አንድ ወር ያገለገለ መሆኑን ገልፆ፣ በገፃ ፈቃዱ ሥራውን የለቀቀ መሆኑንና ተጠሪው የሥራ መልቀቂያ ሠርቲፊኬት ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ የሥራ የምስክር ወረቀት፣ የአገልግሎት ካሣ ክፍያ፣ የሰባ ቀናት የዓመት እረፍት ክፍያ፣ የሥራ መልቀቂያ ባለመስጠቱ ለደረሰብኝ የሞራልና የማቴሪያል ጉዳት ካሣ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪው በተከሣሽነት ቀርቦ አመልካች የወሰዳቸውን ብድሮች፣ መጽሐፎች እና የመሣሰሉትን ንብረቶች ሲመልሱ የሥራ አገልግሎት ማስረጃ እንደሚሰጣቸውና የጠየቋቸው የተለያዩ ክፍያዎች የሚፈለግባቸውን ሒሣብ ካወራረዱ በኋላ የሚተርፍ ካለ የሚከፈላቸው መሆኑን በመግለጽ መልስ

ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አግባብነት አላቸው የሚላቸውን የህብረት ስምምነት ድንጋጌዎችና የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 36 በመጥቀስ አመልካች ለተጠሪው ያለበትን እዳ አወራርዶ በክሱ የጠየቃቸውን ክፍያዎች መጠየቅ እንደሚችል በመግለጽ ክሱን ውድቅ አድርጎበታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የሌለ መሆኑን በመግለጽ ይግባኙን ሠርዞታል፡፡

አመልካች ተጠሪው በእኔ በኩል ያቀረብኩትን ክስ ክዶ አልተከራከረም ፡፡ ይህ ከሆነ ፍርድ ቤቱ በእምነቱ መሠረት ፍርድ መስጠት ሲገባውና ተጠሪው ከእኔ የሚፈልገውን የገንዘብ መጠን ከእኔ የይገባኛል ጥያቄ ጋር አገናዝቦ መወሰን ሲገባው በጥቅሉ ዕዳህን ስትከፍል ተከፋይ ሒሣቦችን ትጠይቃለህ በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የዳኝነት ሥራ አካሄድ፣ የፍትሐብሔር የሥነ ሥርዓት ሕግ እና የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ መስከረም 20 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች አዋጅ ቁጥር 377/1996 ከነማሻሻያው ወደኋላ ተመልሶ እንዲሠራ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች ለአስቸኳይና ድንገተኛ ብድር የወሰደው 13,171.69 (አስራ ሶስት ሺ አንድ መቶ ሰባ አንድ ብር ከስልሣ ዘጠኝ ሣንቲም) ከደመወዝ የሚታሰብ ብር 500 /አምስት መቶ ብር/፣ የአርባ ብር መጽሐፍ፣ ሁለት መቶ ብር የማስተካከያ ክፍያ፣ 2087.60 (ሁለት መቶ ሰማኒያ ሰባት ከሥልሳ) መቀጫና ተቀናሽ ግብር 1239.02 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ከዜሮ ሁለት) በድምሩ 17,291.31 (አስራ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሰላሣ አንድ ሣንቲም) ስለሚፈለግበት ዕዳውን አወራርዶ ቀሪ ሒሣብ ካለው ይጠይቅ መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በበኩሉ ብር 13,171.69 /አስራ ሶስት ሺህ አንድ መቶ ሰባ አንድ ብር ከስልሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ እና የአርባ ብር ዋጋ ያለው መጽሐፍ እዳ እንዳለብኝ አምናለሁ፡፡ ስለዚህ ይኸ ቢቻቻልልኝ አልቃወመም፡፡ሆኖም የሥር ፍርድ ቤት 6,809.68 /ስድስት ሺ ስምንት መቶ ዘጠኝ ብር ከስልሣ ስምንት ሣንቲም/ ቀሪ ተከፋይ ሒሣብ እንዳለኝ አምኖ እያለ እንዲከፈለኝ አለመወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪው እንዲከፍለው የጠየቀውን የሥራ አገልግሎት ካሣ (የሥራ ስንብት) ክፍያና የዓመት እረፍት ክፍያ እኔን አይመለከተኝም ከእኛ የሚጠይቀው ገንዘብ የለም በማለት በግልጽ ክዶ አልተከራከረም፡፡ ተጠሪው በሰበር ያነሣው የይርጋ ጊዜ መከራከሪያም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሣኔው ውስጥ ያልገለፀው በመሆኑ በሥር የተነሣ ክርክር መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ተጠሪው የይርጋ ክርክሩን በሥር አንስቶት ከሆነም ጥያቄውን ፍርድ ቤቱ ሲያልፍበት ደረጃውን ጠብቆ በይግባኝ እንዲስተካከል ያላደረገ በመሆኑ ይህ ፍርድ ቤት ሊያስተካክለው አይችልም፡፡ በመሆኑም ተጠሪው አመልካች የጠየቀውን የሥራ አገልግሎት ክፍያ እና የሰባ ቀን የዓመት እረፍት ክፍያ በግልጽ ክዶ ያልተከራከረ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 235 መሠረት እንዳመነ የሚቆጠር በመሆኑ ተጠሪው ለአመልካች አግባብነት ባለው የህብረት ስምምነትና የሕጉ ድንጋጌ መሠረት የአገልግሎት ካሣ ክፍያና የሰባ ቀን የዓመት እረፍት ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

በሌላ በኩል፣ ተጠሪው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 236 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከአመልካች የሚጠይቀው ዕዳ እንዳለ፤ ለክሱ ባቀረበው መልስ ገልጿል፡፡

ከተጠሪው ከአመልካች እፈልጋለሁ ብሎ የጠየቀው ዕዳ ውስጥ አመልካች ብር 13,171.69 /አስራ ሶስት ሺ አንድ መቶ ሰባ አንድ ብር ከስልሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ ብድርና አርባ ብር ዋጋ ያለው መጽሐፍ በአጠቃላይ 13,211.69 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ አስራ አንድ ብር ከስልሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ እንዳለበት በማመን ተከራክሯል፡፡ ተጠሪው ከዚህ በተጨማሪ ከአመልካቹ 4079.62 /አራት ሺ ሰባዘጠኝ ብር ከስልሣ ሁለት ሣንቲም/ ዕዳ እንዲቻቻልለት የጠየቀ ቢሆንም ይህንን አመልካቹ አልተቀበለውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ይኸ ገንዘብ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ዕዳ ለመሆኑ ግልፅ ውሣኔ አልሰጠበትም፡፡ ስለሆነም በዚህ ጉዳይ አመልካች ለተጠሪው መክፈል ከሚገባው የአገልግሎት ካሣና የሰባ ቀን ዓመት እረፍት ክፍያ በሕጋዊ መንገድ ሊቻቻልበት የሚችሉ ብር 13,211.69 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ብር ከስልሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ ብቻ ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 236 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሠረት በመጀመሪያ አመልካች በክሱ ከጠቀሣቸው ክፍያዎች ውስጥ ተጠሪው ሊከፍለው የሚገባውን የገንዘብ መጠን በመወሰን ከዚያ በማስከተል ደግሞ በተጠሪው በኩል ከቀረበው የመቻቻል ጥያቄና ከአመልካች የሚፈለግ ዕዳ የትኞቹ ማስረጃ የቀረበባቸውና መቻቻል እንደሚገባቸው መወሰን ነበረበት፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በዚህ መንገድ ሣይሆን በጥቅሉ አመልካች እዳውን ስላላወራረደ ያቀረበው የሥራ አገልግሎት ክፍያና ሌሎች የጥቅማጥቅም ጥያቄዎች ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ የአመልካቹ ፍትህ የማግኘት መብት የሚያጣብብ፣ ክርክሮችን ያለ ብዙ ወጭ በቀረቡበት መንገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ አጣርቶ ለመወሰን ታስቦ የተደነገገውን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 236 ድንጋጌዎችን ያልተከተለ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

1.የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም በጥቅሉ አመልካች የተጠሪውን ዕዳ ያወራርድ በማለት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አግባብነት ያላቸውን የሕብረት ስምምነትና የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ተጠሪው ለአመልካች መክፈል የሚገባውን የአገለግሎት ካሣ ክፍያና የሰባ ቀን የዓመት እረፍት ክፍያ በአግባቡ ለይቶ እንዲወስንና ከዚህ ውስጥ አመልካች ለተጠሪው መክፈል የሚገባውን ብር 13,211.69 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ አስራ አንድ ብር ከስልሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 236 መሠረት በማቻቻል ቀሪ ገንዘብ የሚኖር ከሆነ ለአመልካች እንዲከፈል እንዲያደርግ፤ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. የከፍተኛው ፍርድ ቤት መጋቢት 7 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

ይህ ፍርድ ሚያዚያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰበር መ/ቁ. 29866

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

አመልካች፡- ቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- ወርቅነህ ምህረቱ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥራ ውል የሚመሰረትበትን ሁኔታ የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ለአመልካች ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ተቀጥሬ ደመወዝ እየተከፈለኝ በጥቅምት 2 ቀን 1996 ዓ.ም በተሰጠኝ የውክልና ሥልጣን ድርጅቱን በጥብቅና ሥራ በማገልገል ላይ ሳለሁ አመልካች የስራ ውሌን ያቋረጠው ስለሆነ በአመልካች ሊከፈልኝ ይገባል ያሉትን ክፍያ በመዘርዘር በአማራ ክልል ደ/ማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ ድርጅቱ ተጠሪን በሠራተኛነት አልቀጠረም፤ ደመወዝም አልከፈለም፤ የድርጅቱ ጠበቃ የነበሩት አቶ የስጋት ንጉሴ ሥራቸውን ሲለቁ አዲስ አበባ የሚገኙትንና የድርጅቱ የህግ አማካሪ የነበሩትን አቶ ጥበቡ ጋሹ የተባሉትን ግለሰብ መጥተው ደ/ማርቆስ አካባቢ ያለውን የድርጅቱን ጉዳይ እንዲከታተሉ ስንጠይቃቸው አዲስ አበባ ያለው ጉዳይ ብዙ ስለሆነ መምጣት አልችልም - ነገር ግን እኔ ደመወዝ እየከፈልኩት የእኔን ቦታ ሸፍኖ የሚሰራ ሰው ስላገኘሁ ድርጅቱ ውክልና ብቻ ይስጠውና የጥብቅና አገልግሎት ይስጥ በማለት በጠየቁን መሰረት ለአሁን ተጠሪ የውክልና ስልጣን ሰጥተናቸው ሲያገለግሉ ከመቆየታቸው በስተቀር ከእኛ ጋር የሥራ ውል የላቸውም፤ በመሆኑም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመካከላችን የቅጥር ውል ሳይኖር ተጠሪ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል። ፍ/ቤቱም የቀረበለትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በተጠሪ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ የሚያስረዳው ተጠሪ በአመልካች መወከላቸውን ነው በተጠሪ የተቆጠሩት ምስክሮች የመሰከሩትም ተጠሪ በድርጅቱ ውስጥ ተቀጥረው መስራታቸውን እንደማያውቁ ነው፣ በአመልካች በኩል የተቆጠሩት ምስክሮች ደግሞ አመልካች የሰጠውን መልስ በሚደግፍ መልኩ መስክረዋል፣ በግራ ቀኙ የጋራ ምስክር ሆነው የተቆጠሩት አቶ ጥበቡ ጋሹ ቀርበው እኔ በስሬ ሌሎች ባለሙያዎችን እየቀጠርኩ በተመሳሳይ ሁኔታ በሌሎች ክልሎችም የሙያ ስራ ስለምሰራ ተጠሪንም በዚሁ መልክ ቀጥሬአቸው ደመወዝ እየከፈልኳቸው አመልካች በሚሰጣቸው የውክልና ሥልጣን በጥብቅና እንዲያገለግሉ ተደርጎ እኔ ከአመልካች ድርጅት ጋር ያለኝ ውል ሲቋረጥ ተጠሪ ሥራቸውን አቁመው በእጃቸው የሚገኙትን መዝገቦች እንዲያስረክቡ በነገርኳቸው መሰረት አስረክበዋል በማለት የመሰከሩ ስለሆነ አመልካች ባቀረቧቸው ማስረጃዎች ስላላስረዱ በግራ ቀኙ መካከል የሥራ ውል የለም፣ መካከላቸው የሥራ ውል ከሌለ ደግሞ ተጠሪ የሥራ ውልን መሰረት አድርገው ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ህጋዊ መብት ስለሌላቸው ያቀረቡት ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33(2) መሠረት ውድቅ ተደርጓል በማለት ወስኗል። የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምስ/ጎጃ/ዞ/ከፍ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 6 እና 7 መሠረት የሥራ ውል በጽሁፍም ሆነ ያለጽሁፍ ሊመሰረት ስለሚችል ተጠሪ ያቀረቡት የውክልና ሥልጣን ማስረጃ በግራ ቀኙ መካከል ውል መኖሩን የሚያስረዳ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ለህጉ የተሳሳተ ትርጓሜ በመስጠት ተጠሪ የጠየቋቸው ክፍያዎች አይገቧቸውም በማለት የሰጠው ውሳኔ ሚዛናዊነት የጎደለው ነው በሚል ተጠሪ የጠየቋቸው ክፍያዎች ይከፈሏቸው ሲል ወስኗል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔዎች አግባብ ካለው ህግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሥራ ውል አለ የተባለው

በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል።

መዝገቡን እንደመረመርነው የምስ/ጎጃ/ዞ/ከፍ/ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የሥራ ውል አለ ለማለት የቻለው በተጠሪ የቀረበው የውክልና ሥልጣን ማስረጃ በግራ ቀኙ መካከል በቅጥር ላይ የተመሰረተ የውል ግንኙነት እንደነበረ ያረጋግጣል በሚል መሆኑን ተገንዝበናል። በመሠረቱ በሁለት ወገኖች መካከል በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ውል በጽሁፍ ቢደረግም ባይደረግም ውጤቱ ተመሳሳይ መሆኑ የማያከራክር ነው። ይህ የሚሆነው ግን ግንኙነቱ በውል ላይ የተመሠረተ ሲሆንና ይህም በማስረጃ ሲረጋገጥ ነው።

በዚህ ጉዳይ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ተቀጥረው ደመወዝ እየተከፈላቸው የጥብቅና አገልግሎት ሲሰጡ መቆየታቸውን ለማረጋገጥ ያቀረቡት በአመልካች ተሰጥቷቸው የነበረውን የውክልና ሥልጣን ማስረጃ ሲሆን ይህ ማስረጃ የሚያረጋግጠው አመልካች በተጠሪ ተወክለው እንደነበረ እንጂ ተቀጥረው ሲያገለግሉ እንደነበረ አይደለም። በሌላ በኩል በግራ ቀኙ የጋራ ምስክር ሆነው የተቆጠሩት ግለሰብ ለአመልካች ድርጅት የጥብቅናና የህግ ማማከር አገልግሎት ሲሰጡ በነበረበት ወቅት ተጠሪን በመቅጠር ደመወዝ እየከፈሏቸው ከአመልካች በሚያገኙት የውክልና ሥልጣን ለድርጅቱ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጡ ያሰማሯቸው መሆኑንና ድርጅቱ ከእሳቸው ጋር የነበረው ግንኙነት ሲቋረጥም ተጠሪ ከድርጅቱ ጋር የነበራቸው ግንኙነትም አብሮ የተቋረጠ መሆኑን መስክረዋል። ከዚህ መረዳት ሚቻለው ተጠሪ የተቀጠሩት አመልካች ድርጅት በቀጠራቸው ግለሰብ እንጂ በአመልካች አለመሆኑ ራሳቸው ተጠሪ ባቀረቧቸው ምስክር የተመሰከረ መሆኑን ነው። በመሆኑም በግራ ቀኙ መካከል የውል ግንኙነት እንዳልነበረ ተገንዝበናል። በተጠሪና በአመልካች መካከል የውል ግንኙነት ካልነበረ ደግሞ ተጠሪ በአመልካች ላይ ከውል የመነጨ የመብት ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም። በዚህም ምክንያት ተጠሪ አገልግሎቱን ሲሰጡ የነበረው ከአመልካች ጋር በነበራቸው የውል ግንኙነት መሆኑን ባላስረዱበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የውክልና ሥልጣን ማስረጃው በግራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀኙ መካከል የውል ግንኙነት እንደነበረ ስለሚያስረዳ በተጠሪ የተጠየቁትን ክፍያዎች አመልካች መክፈል አለበት በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ደ/ማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 01741 ታህሣስ 13 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የክልሉ የምስ/ጎጃ/ዞ/ከፍ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.12681 ጥር 9 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የአመልካች ተቀጣሪ ስላልነበሩ አመልካች በተጠሪ የተጠየቀውን ክፍያ ለመክፈል አይገደድም በማለት ተወስኗል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 29949

ሐምሌ 19 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

ነ/ፈጅ አለሙ ዋሴ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ዋሲሁን አዳነ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀረብ የቻለው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቀጠርና በዚያን ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች የደረሱበት የደመወዝ ስኬል ላይ እንዲደርስ በማለት ውሣኔ በመስጠቱና በይግባኝ የተመለከተውም የክልሉ ዞን 3 ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ባለመቀበል ይህንኑ ውሣኔ በማጽናቱ አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የክርክሩ ሂደትም ባጭሩ ሲታይ በአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ መስርቶ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት የሠራበት የ65 ቀን ደመወዝና ብር 200 (ሁለት መቶ) ኪሣራ አመልካች ከፍሎት ከሥራ እንዲሰናበት በማለት ጥቅምት 24 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን በዚህ ውሣኔ መሠረት አፈፃፀም ሣይቀጥል እንደዚሁም አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ባልሆነበት ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት ተቀጥሮ እንዲሰራ ፍ/ቤቱ በተለያየ ጊዜ ውሣኔ መስጠቱን አመልካች ከሰበር አቤቱታው ጋር አያይዞ ያቀረባቸው የፍ/ቤቱ ውሣኔዎች ያስገነዝባሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም መሠረት ኅዳር 24 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ በተገኘው ክፍት የሥራ ቦታ ተቀጥሮ እንዲሰራ፣

ሐምሌ 17 ቀን 1998 ዓ.ም ደግሞ በአዋሽ በሚከፈተው የአመልካች የዲስትሪክት ቅርንጫፍ መ/ቤት በተገኘው ክፍት ቦታ ተጠሪ ተቀጥሮ እንዲሰራ

እንደዚሁም ነሐሴ 8 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአዋሽ የዲስትሪክት ጽ/ቤት በተገኘው ቦታ ተጠሪ ተቀጥሮ እንዲሰራ በማለት ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ቅርንጫፍ መ/ቤት እንዲቀጠር በማለት ፍ/ቤቱ በሰጠው ተደጋጋሚ ውሣኔ መሠረት አፈፃፀሙ ቀጥሎ ከታህሣሥ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ በአመልካች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀጠር የተደረገ ቢሆንም መቀጠር ከነበረብኝ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ መድረስ የሚገባኝ የደመወዝ ስኬል ላይ መድረስ ይገባኛል በማለት ተጠሪ ክርክር በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ይህንኑ የተጠሪን ክርክርን ተቀብሎ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቀጠርና በዚያን ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች የደረሱበት የደመወዝ ስኬል እንዲደርስ በማለት ጥር 1 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የዞን 3 ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ባለመቀበል ይህንኑ ትእዛዝ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪ ከ1990 ዓ.ም እስከ 1999 ዓ.ም በሥራ ላይ ያልነበረ መሆኑ እየታወቀ በሥራ ላይ ላልነበረበት ጊዜ ጥቅማ ጥቅምና የደረጃ ዕድገት ይከፈለው የመባሉ አግባብነት ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በመታመኑ ፍ/ቤቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ተጠሪም በበኩሉ የሰበር አቤቱታው በአግባቡ የቀረበ እንዳልሆነ በመዘርዘር የወረዳውና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ተጠሪ ሥራ ላይ ባልነበረበት ጊዜ ሊደርስበት የሚገባው የደመወዝ ስኬል ተጠብቆለት

ደመወዝ እንዲከፈለው የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ክርክር በፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት ቀጥሎ ጥቅምት 24 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሰጠው ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ለተጠሪ የ65 ቀን ደመወዝ እንደዚሁም ብር 200 (ሁለት መቶ) ኪሣራ እንዲከፍልና ተጠሪም ከሥራ እንዲሰናበት በማለት ነው፡፡

በዚህ ውሣኔ መሠረትም ተጠሪ የአፈፃፀም አቤቱታውን አቅርቦ ፍ/ቤቱ በውሣኔው መሠረት አፈፃፀሙን መቀጠል ሲገባው በተለያየ ጊዜ ፍርድ ያላረፈበትን የአፈፃፀም ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በአመልካች ቅርንጫፍ መ/ቤት ከታህሳስ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቀጠር መደረጉን ተገንዝበናል፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ የአመልካች አቤቱታ ተጠሪ ሥራ እንዲቀጠር በመደረጉ ሣይሆን የደመወዝ ስኬል ተጠብቆለት ደመወዝ ይከፈለው ተብሎ በተወሰነው ላይ በመሆኑ ይህም የአፈፃፀም ትእዛዝ ሲታይ ቀድሞውንም ቢሆን ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለስ ባልተወሰነበት ሁኔታ የተሰጠ የአፈፃፀም ትእዛዝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ፍርድ ባላረፈበት ነገር የአፈፃፀም ትእዛዝ መስጠት ደግሞ ጉልህ የሆነ የሥነ ሥርዓት ግድፈት (Serious procedural irregularity) ነው፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለስ በፍርድ ባልተወሰነበት ሁኔታ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዳለ በመቁጠር በዚያን ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ከደረሱበት የደመወዝ ስኬል እንዲደረስ ተደርጎ ደመወዝ እንዲከፈለው በማለት የተሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ ጉልህ የሆነ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ያለው ከመሆኑም በላይ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 54/1/ ላይ የተደነገገውንና ደመወዝ የሚከፈለው ለተሰራ ሥራ ነው የሚለውን የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፈንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1/89 ጥር 1 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ብይን የዞን 3 ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 0449 መጋቢት 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት እንዲቀጠር በፍርድ ውሣኔ ያላገኘ ስለሆነ ሥራ ላይ ላልነበረበት ጊዜ የደመወዝ ስኬል ሊጠበቅለትም ሆነ ደመወዝ ሊከፈለው አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድነን ኪሮስ

አመልካች፡- የወረዳ 5 አጠቃላይ ነጋዴዎች ማኅበር ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ በድሉ ጫላ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በጉዳዩ ላይ ክርክር የተጀረመው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ሰኔ 9 ቀን 1996 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረበው የክስ ማመልከቻ ከጥቅምት 19 ቀን 1992 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቅን 96 ዓ.ም. በማኅበሩ በጥበቃ አባልነትና በጥበቃ ቡድን መሪነት በወር ብር 250 ደመወዝ እየተከፈለኝ ሳገለግል የቆየሁ ሲሆን ድርጅቱ ግንቦት 30 ቀን 1996 ዓ.ም. ያለ አንዳች ጥፋትና ማስጠንቀቂያ ከሥራ በቃል አሰናብቶኛል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የስንብት፣ የካሣ፣ የማስጠንቀቂያ፣ የዓመት ዕረፍት ክፍያ እንዲሁም የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጠኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተከሣሽ ማኅበርም ሐምሌ 7 ቀን 1996 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ ከሣሽ ከሥራ በተደጋጋሚ ስለሚቀሩ፣ ትዕዛዝ ስለማያክብሩ፣ የተመደቡበትን የጥበቃ ቦታ ለቀው ስለሚሄዱ፣ በስራ ላይ አምባንሮ ስላነሱ እና የሥራ ሰዓት ስለማይቀበሉ በአዋጁ አንቀጽ 27/1/ሀ/ መሠረት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶቸው በአግባቡ የተሰናበቱ በመሆኑና ደመወዛቸውም ብር 200 እንጂ ብር 250 ባለመሆኑ ክሳቸው ተቀባይነት የለውም ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት ተክራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ካዳመጠ በኋላ ከሣሽ የተሰናበቱት በፈፀሙት ጥፋት መሠረት ስለመሆኑ በማስረጃ በመረጋገጡ የጠየቁት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም ያልወሰዱት የዓመት ዕረፍት ክፍያ ግን በደመወዛቸው መሠረት እንዲከፈላቸው የሥራ የምስክር ወረቀትም እንዲሰጣቸው ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ተመልክቶ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ከሥራ የተሰናበቱት በሕገወጥ መንገድ በመሆኑ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዛቸው እንዲከፈላቸው ወደ ሥራም እንዲመለሱ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች የሥር ተከሣሽ ያቀረበው የሰበር አቤቱታም የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ቅሬታውም ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት ለክሱ በሰጠነው መልስ በጠቀስናቸው ጥፋቶች ምክንያት መሆኑን አስረድተን እያለ የከፍተኛው ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ ነው፣ ተጠሪው ወደ ሥራ ይመለሱ፣ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝም ይከፈላቸው በማለት የሰጠው ውሣኔ ማስረጃችንን ያላገናዘበና ተጠሪው ካቀረቡት ክስ እና ዳኝነት ከጠየቁበት ጥያቄ ውጭ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በመሆኑም የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲፀና እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር ሰሚ ችሎትም ተጠሪው ወደ ሥራ ለመመለስ ክስ ሳያቀርቡ ፌ/ከ/ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ ነው፣ ተጠሪው ወደ ሥራ ይመለሱ ብሎ የመወሰነው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን መመርመር በማስፈለጉ አቤቱታው ያስቀርባል ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪው ደግሞ በሰጡት መልስ የተሰናበትኩት ያለ አንዳች ጥፋትና ያለማስጠንቀቂያ ስለመሆኑ በማስረጃዬ ያረጋገጥኩኝ በመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ ነው፣ ሠራተኛው ወደ ሥራው መመለስ አለበት፣ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝም ሊከፈለው ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ የተሰጠ እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት አይደለም፡፡ እንዲያውም

ውሣኔው ተሻሽሎ የዓመት ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለኝ ሊወሰንልኝ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የመልስ መልሱን በማቅረብ ከመዝገቡ ጋር አያይዟል፡፡

በበኩላችን ደግሞ አመልካች ተጠሪውን ያሰናበታቸው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተጠሪው ወደ ሥራ ሊመለሱ፣ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዛቸውም ሊከፈላቸው ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በቀረበው ክስ ዳኝነት የተጠየቀበትን ነጥብ መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች መሠረት በማድረግ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪው ሰኔ 9 ቀን 1996 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ማንበሩ ከስራ ያሰናበተኝ በሕገወጥ መንገድ ነው ቢሉም ማንደራቸው ሲታይ በተለያየ ጊዜ ከስራ በመቅረት፣ የተመደቡበትን የጥበቃ ቦታ ለቆ በመሄድ እና የሥራ ሰዓትን ባለማክበር የተገመገሙና ይህን ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆናቸው የሥር ፍ/ቤቶች መዝገቦች ስለሚያስረዱና እነዚህ ጥፋቶች ደግሞ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብቱ እንደሚችሉ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 የተደነገገ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪው ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁባቸው ነጥቦች የስንብት፣ የካሣ፣ እና የዓመት ዕረፍት ክፍያዎችንና የሥራ ልምድ ሰርተፊኬት ማግኘትን የተመለከቱ እንጂ ውዝፍ የወር ደመወዝ ክፍያና ወደ ሥራ የመመለስ ጥያቄን ያካተቱ አይደሉም፡፡ ስለሆነም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተጠሪው የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ በማለት የወሰነው አግባቡ ባለመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 52185 ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07722 ጥር 16 ቀን 99 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ አጽንተናል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ እንዲቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31402

ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

ደስታ ገብሩ

ሒሩት መለሠ

መስፍን እቁበዮናስ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አገር አቋራጭ ከፍተኛ አውቶብስ የግል ባለንብረቶች ማኅ/ አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አያሌው ይርጉ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን ክርክሩ ሲጀምር የአሁኑ ተጠሪ ከሣሽ አመልካቹ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ ጥቅምት 2 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ክስ፣ በአመልካቹ መ/ቤት በገንዘብ ያዥነት ተቀጥሬ ስሰራ ገንዘብ በማጉደሌ መ/ቤቱ የስራ መደቤን ቀይሮ የቀረብኝን 13,819.36 (አሥራ ሦስት ሺህ ስምንት መቶ አሥራ ዘጠኝ ከሰላሳ ስድስት) ብር እየሠራሁ በመክፈል ተስማምቼ ሣለ ድርጅቱ እድሜዬ ከ60 ዓመት በላይ በመድረሱ ከስራ ተሠናብተሀል በማለት በስምምነታችን መሠረት እዳዬን ከፍዬ ሣልጨርስ ከስራዬ ያሠናበተኝ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ ሲሉ ዳኝነት በመጠየቃቸው ነው፡፡

አመልካቹ ቀርበው መልስ የሰጡ ሲሆን ይዘቱም፡- ከሣሹ /የአሁን ተጠሪ/ በጡረታ ሕጉ እና በድርጅቱ የአስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3.1.1.10.4 መሠረት በእድሜ ገደብ ጡረታ ከወጡ በኋላ ወደ ሥራዬ ልመለስ በማለት የሚጠይቁበት የሕግ ስርዓት ስለሌለ ክሱ ውድቅ ይደረግ የሚል ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ መጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የከሣሽ ድርጅትን የአስተዳደር መመሪያ ትክክል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳልሆነ ወይም እንደሌለ ከሣሹ የሚያቀርቡት ክርክር ሣይኖር ከፍዬ ያልጨረስኩትን ገንዘብ ሣልከፍል መሠናበት የለብኝም የሚለው መከራከሪያ በድርጅቱ ውስጥ ለመቆየት ዋስትና ሊሆን አይችልም በሚል ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡

በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኙት ከሣሽ /የአሁን ተጠሪ/ ቅሬታቸውን በይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የአሁን አመልካችን በማስቀረብ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ግንቦት 28 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ተጠሪው በድርጅቱ ሲቀጠሩ በጡረታ የተገለሉ መሆኑ ታውቆ ስራቸውን ጀምረው ሲሠሩ እንደገና 60 ዓመት የጡረታ እድሜ ስለደረሰ በማለት ለሁለተኛ ጊዜ በጡረታ ማሰናበቱ ከሕጉ አግባብ ውጪ በመሆኑ ስንብቱ አላግባብ ነው፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ባይ /የአሁን ተጠሪ/ የ6 ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

ይህ የሰበር መዝገብ የቀረበው አመልካች ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የሠበር ማመልከቻ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተጠሪ የ6 ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ ይመለሱ ሲል የሰጠው ውሣኔ ከአ/ቁ. 377/96፣ ከድርጅቱ የአስተዳደር መመሪያና ከጡረታ ሕጋችን አግባብ ውጪ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለዚህ ችሎት አቤት በማለታቸው ነው፡፡

ይህ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ በዚህ ጉዳይ ተጠሪ በእድሜ ገደብ ጡረታ የወጣ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ ይመለስ መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አካሂደዋል፡፡ እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመሠረቱ በአዋጅ ቁ. 377/96 በአንቀጽ 24/3/ ላይ የሥራ ውል ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች አንዱ የሠራተኛው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት

በጡረታ ሲገለል መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የአመልካች መ/ቤት የአስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3.1.1.10.4 እና የመንግሥት ሠራተኞችን የጡረታ ጉዳይ የተመለከተው አ/ቁ. 345/95 አንቀጽ 12/1/ሐ/ የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ መውጫ እድሜ 60 ዓመት መሆኑን በግልጽ ደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪው የጡረታ እድሜያቸው መድረሱን ክደው ያልተከራከሩ ሲሆን በእነዚህ ሕጎች መሠረት ከስራቸው በጡረታ የማይገለሉበት ወይም የስራ ውላቸው የማይቋረጥበት ምክንያት አልተገኘም፡፡ ተጠሪው የቀረብኝን እዳ ሣልከፍል በጡረታ ልገለል አይገባም ቢሉም በጡረታ ቢገለሉ እንኳ እዳቸውን ከመክፈል እንደማይገደቡ ግልጽ ነው፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በውሣኔው እንዳተተው ሁሉ እዳቸውን አለመክፈላቸው በድርጅቱ ውስጥ ለመቆየት ዋስትና ሊሆናቸው አይችልም፡፡ አመልካቹም ቢሆን የጡረታ እድሜው ያለፈን ሰራተኛ ወደ ሥራ መልስ ተብሎ የሚገደድበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ያለ አንዳች የሕግ ድጋፍ ተጠሪው የ6 ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ ይመለሱ ሲል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 53867 ግንቦት 28 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች በጡረታ የተገለለ ሠራተኛን /ተጠሪን/ ወደ ሥራ የሚመልስበትም ሆነ ውዝፍ የ6 ወር ደመወዝ የሚከፍልበት የሕግ አግባብ የለም ብለን ወስነናል፡፡
3. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10819 መጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 32545

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ሽፈራው ጠበቃ ባዩ ደስታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የክርስቲያን በጎ አድራጎት ልማት ድርጅት ጠበቃ አድማሱ መዓዛ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቁራ ምድብ የሥራ ክርክር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 22417 ሚያዚያ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰኔ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ አመልካች ተጠሪው ብር 19173.70 /አስራ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሰባ ሶስት ብር ከሰባ ሣንቲም/ ፕሮቬደንት ፈንድ እንዲከፍላቸው ያቀረቡት ክስ ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረበውን ክርክር በመቀበል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ብሎ ውሣኔ በመስጠቱና የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ይህንኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ በማጽደቁ ነው፡፡

አመልካች ፕሮቪደንት ፈንድ ከሠራተኛው ደመወዝ በየወሩ በፐርሰንት እየተቀነሰ በአሰሪው የሚቀመጥና የሚጠራቀም ሠራተኛው ከሥራ ሲሰናበት የሚጠቀምበት በጡረታ መልክ የሚከማች የሠራተኛው ገንዘብ ነው፡፡ ይህ

ገንዘብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2800 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2802 የተቀመጠ በመሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1756 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ባለመብቱ ሲጠይቅ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል ስለሆነ በይርጋ ይቋረጣል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪው በበኩሉ፤ ፕሮቪደንት ፈንድ በመዝገበ ቃላት ውስጥ ያለውን ትርጓሜ በመጥቀስና ፕሮቪደንት ፈንድ የሰራተኛ ጥቅማጥቅም በሚባሉት ውስጥ፤ የሚመደብ እንደሆነ በመግለጽ እንደዚሁም ፕሮቪደንት ፈንድ ሠራተኛው 5% አሠሪው ደግሞ 15% በማዋጣት በባንክ በተከፈተ ሒሣብ እንደሚቀመጥ በመግለጽ፣በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይና በሰበር በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ከሥራ ቅጥር ውል የሚመነጩ የደመወዝ እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ጥያቄዎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለባቸው መሆኑን በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ተደንግጓል፡፡ እነዚህ ክፍያዎች በመሰረታዊነት ሰራተኛው ስራ ላይ እያለ የይገባኛል ጥያቄ ሊያቀርብ እና የመብት ጥያቄ ሊነሣ የሚችልባቸው ናቸው፡፡

ይህ ከሆነ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ፣ በባህሪው ከደመወዝ ጭማሪ፣ ከትርፍ ሰዓት እና በዓል ቀን ክፍያ የተለየ ነው፡፡ የገንዘቡም ምንጭ ቢሆን ሙሉ በሙሉ አሠሪው አይደለም፡፡ ከተጠራቀመው ገንዘብ ውስጥ፣ከሠራተኛው በየወሩ አምስት ፐርሰንት እየተቆረጠ ተቀምጧል፡፡ ዓላማውም ሠራተኛው ከሥራ ሲሰናበቱ ወይም ሥራውን በራሣቸው ፈቃድ ሲለቁ፤ እነሡና ቤተሰቦቻቸው ችግር ላይ እንዳይወድቁ፣ ለመደጎምና የማህበራዊ ደህንነትና ዋስትና ክፍያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ፕሮቪደንት ፈንድ ይከፈለኝ የሚለው ጥያቄ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/1996 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል አመልካች ገንዘቡ የአደራ ገንዘብ በመሆኑ በተጠየቀ በማናቸውም ጊዜ ሊከፈል ይገባዋል በማለት ያቀረበው ክርክር ፕሮቪደንት ፈንድ ባለባቸው መሥሪያ ቤቶች የሚተዳደሩ ሠራተኞች በሕይወት ባሉበት በማናቸውም ጊዜ ወይም የእነርሱ ወራሾች፤ መብቱን ሊጠይቁ ከሚችሉበት ቀን አንስቶ፣ ከሃያ ዓመት በኋላ፣ ከሃምሣ ዓመት በኋላ እና ከዚያም በላይ እየመጡ፣ ጥያቄ እንዲያቀርቡ እድል የሚሰጥ ነው፡፡ ይኸ ደግሞ የሚበረታታና የሕግ ጥበቃ የሚሰጠው አይደለም፡፡ ስለሆነም ፕሮቪደንት ፈንድ፤ በስንት ዓመት ውስጥ መጠየቅ እንደሚገባው የሚደነግግ ግልጽ የሕግ ድንጋጌ ባይኖርም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1677 አንቀጽ 1 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት መታየት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ፕሮቪደንት ፈንድ ባለመብቱ በአስር ዓመት ውስጥ ካልጠየቀ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለው የሥራ ውል የተቋረጠው ጥቅምት 29 ቀን 1992 ዓ.ም በመሆኑ፣ ፕሮቪደንት ፈንዱን ተጠሪ እንዲከፍለው ያቀረበው ጥያቄ አስር ዓመት አልሞላውም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቁራ ምድብ ችሎት አመልካችና ተጠሪ የሚያደርጉትን ሌሎች የፍሬ ጉዳይና የሕግ ክርክር በመስማትና ማስረጃቸውን በማመዛዘን የመሰለውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሣቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 33314

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- እነ አቶ አለማየሁ ወልደ /10 ሰዎች/ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን አመጣጡን በተመለከተ ደግሞ የአሁን ተጠሪዎች መስከረም 9 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ በብራሌ የምግብ ዘይት ፋብሪካ በዘበኝነት ተቀጥረን ስናገለግል ቆይተናል፡፡ የፋብሪካው ባለቤት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በብድር የወሰደውን ገንዘብ ሊከፍል ባለመቻሉ ፋብሪካው ለባንኩ ተላልፏል፡፡ ድርጅቱ ሚያዝያ 12 ቀን 1997 ዓ.ም በሕገወጥ መንገድ ከሥራ አሰናብቶናል፡፡ ስለሆነም የሥራ ስንብት፣ የማስጠንቀቂያ፣ ከሰኔ 1995 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 12 ቀን 1997 ያለው ያልተከፈለ ደመወዛቸው፣ የካሣ ክፍያዎችና የመጓጓዣ አበል እንደዚሁም የዓመት እረፍት ቀኖችን በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈለን የምስክር ወረቀትም እንዲሰጠን በማለት በፋብሪካውና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ ክስ መስርተዋል፡፡

1ኛ ተከሳሽ የሆነው ፋብሪካ ባለቤት በሰጡት መልስ የድርጅቱ ንብረትነት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተላልፏል፡፡ የከሳሾችንና የሌሎች ሠራተኞችን ክፍያ በተመለከተ ባንኩ ተጠይቆ አያገባችሁም ብሎናል፡፡ ከሣሾቹ እኔን የሚጠይቁበት ምክንያት ባለመኖሩ ከክሱ ልሰናበት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደግሞ በሰጠው መልስ የፋብሪካው ባለቤት ፋብሪካውን መያዣ በማድረግ ገንዘብ ተበድረው አልመለሱም፡፡ በብድር የተወሰደውን ገንዘብ ለማስመለስ ሲባል ፋብሪካውን በጨረታ ለማሸጥ ተሞክሮ የሚገዛው አልተገኘም፡፡ ፋብሪካው ገዢ ስላጣም ባንኩ ተረክቦታል፡፡ የተረከበው ግን የፋብሪካ ሥራውን ለማስቀጠል ሳይሆን ሽጦ ገንዘቡን ገቢ ለማስደረግ ነው፡፡ ፋብሪካውን ሲረከብም ባንኩ ሰራተኞችን የሚመለከት ግዴታ ጨምሮ አይደለም፡፡ ከሠራተኞቹ ጋርም ባንኩ ያደረው የሥራ ውል የለም፡፡ በመሆኑም ክሱ ስለማይመለከተው ባንኩ ከክሱ በነፃ ሊሰናበት ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ፋብሪካው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተረከበው በመሆኑ ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት የለውም፡፡ የድርጅቱ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 2ኛ ተከሳሽ የተደረገ በመሆኑ 1ኛ ተከሳሽ ተደርጐ ክስ የቀረበበት ፋብሪካ ከክሱ በነፃ እንዲሰናበት በማለት ወስኗል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ የሆነው ባንክ 1ኛ ተከሳሽ ከሆነው የፋብሪካው ባለቤት የወሰደው ቁሳቁስ ሳይሆን ድርጅት ነው፡፡ ከሣሾች ከሥራ የተሰናበቱት ፋብሪካው ወደ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከተላለፈ በኋላ በመሆኑና የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 16 የድርጅት ባለቤትነት መተላለፍ በሥራ ውሉ ላይ ለውጥ እንደማይኖረው የሚደነግግ በመሆኑ 2ኛ ተከሳሽ የሆነው ባንክ ከሣሾችን በሚመለከት የአሰሪ ግዴታዎች ሁሉ ይኖሩታል፡፡ በመሆኑም ባንኩ ተከሳሽ የተደረገው በአግባቡ ነው፡፡ የከሳሾችን ክፍያ ጥያቄዎች በሚመለከት ጥያቄዎቹን ያቀረቡት ሚያዝያ 12 ቀን 1997 ዓ.ም በሕገ ወጥ መንገድ ከሥራ ተሰናብተናል የተለያዩ ክፍያዎችንም አልተከፈለንም በሚል ነው፡፡ 2ኛ ተከሳሽ የሆነው ባንኩ የሥራ ውሉን መቋረጥ ያመነ ቢሆንም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጋዊ መንገድ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክርም ይሁን ማስረጃ የለም በመሆኑም ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ ባንኩ ለከሣሾች በክሱ የተጠቀሰው ደመወዛቸውን፣ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደዚሁ የዓመት እረፍት ሁለት ዓመት ያላለፈውን ብቻ በገንዘብ በመለወጥ እንዲከፍል የምስክር ወረቀትም እንዲሰጣቸው በማለት ወስኗል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ መሠረት በማድረግ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት አላገኘሁበትም በማለት ውሣኔውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበውም የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡዋቸው ውሣኔዎች ቅር በመሰኘት ሲሆን ቅሬታዎችም የሥር ፍ/ቤቶች 1ኛ ተከሳሽ የሆነውን ድርጅት ክሱ በነፃ ያሰናበተው በአግባቡ አይደለም፡፡ ድርጅቱ በንግድ ሕግ ቁጥር 969 መሠረት መክሰሩ አልተረጋገጠም፡፡ ድርጅቱ ወደ ባንኩ በተላለፈበት በሚያዝያ 12 ቀን1997 ዓ.ም ሠራተኞቹ በሥራ ላይ አልነበሩም፡፡ ድርጅቱ ባንኩን የተረከበው ለእዳ መክፈያነት እንጂ ሥራውን ለማካሄድ ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 16 ሥር ያለውን ግዴታ የምረከብበት ምክንያት የለም፡፡ ድርጅቱን በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 98/90 የተረከብኩት እንደማንኛውም የዋስትና የተያዘ ንብረት በመሸጥ ገንዘቤን ገቢ ለማስደረግ ነው፡፡ ከተጠሪዎች ጋር ያደረግኩት የሥራ ውል ባለመኖሩና ፋብሪካውንም የተረከብኩት ሥራውን ለማስቀጠል ባለመሆኑ የፋብሪካው ባለቤት የነበረውን ግዴታ የምሸከምበት በክሱ የተጠቀሰውን ክፍያ እንድከፍል የምገደድበት ምክንያት የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ድርጅቱን የተረከብከው የሰራተኞችንም የተለያዩ ክፍያዎች ለመክፈል ጭምር ነው በማለት በክሱ የተጠቀሱትን ክፍያዎች እንድከፍል በመወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል፡፡ በመሆኑም ውሣኔው ሊሻርልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎቹ ደግሞ በሰጡት መልስ የተሰናበትነው አመልካች ድርጅቱን ከተረከበ በኋላ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 16 የአንድ ድርጅት የባለቤትነት መብት በየትኛውም መልኩ ሲተላለፍ የሥራውን ውል የመለወጥ ወይም የማሻሻል ይዘት እንደማይኖረው ይደነግጋል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ አንዳችም የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ

ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም ውሣኔው ሊፀናልን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ያቀረበው የመልስ መልስ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ በመቀጠልም ግራ ቀኙ የቃል ክርክር አድርገው ክርክራቸውን አስመዝግበዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ አመልካች በብድር የተወሰደው ገንዘብ ባለመከፈሉ ምክንያት ለብድሩ በዋስትና ተይዞ የነበረውን ድርጅት በጨረታ የሚገዛው ካጣ በኋላ በመነሻ ዋጋው ስላስቀረው ሠራተኞችን የሚመለከት ግዴታም ከድርጅቱ ጋር ይተላለፍለታል ወይስ አይተላለፍለትም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም አመልካች ባንክ የምግብ ዘይት ፋብሪካውን በጨረታ መነሻ ዋጋው የተረከበው ጨረታ ወጥቶ የሚገዛው በማጣቱ ምክንያት እንጂ ፋብሪካው የማምረት ሥራውን ለማስቀጠል እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ፋብሪካው ባንኩ ከተረከበው ጊዜ ጀምሮ እስካሁን እየሠራ አይደለም፡፡ የባንኩ ሥራ ገንዘብንና ገንዘብ ነክ ነገሮችን ማስቀመጥ፣ ማዘዋወር፣ ማበደርና መሰብሰብ እንጂ ሌላ የንግድ ሥራ ማከናወን ባለመሆኑም ባንኩ ለወደፊቱም ቢሆን ፋብሪካውን ይሰራበታል ተብሎ አይገመትም ፡፡ ያለው እድል በአነስተኛ ዋጋም ቢሆን ፋብሪካውን እንዳለ በመሸጥ ወይም ማሽኖቹንና ህንፃውን ነቃቅሎና ከፋፍሎ በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ የሚያደርግበትን አማራጭ መውሰድ እንጂ ፋብሪካውን እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ በመውሰድ ዘይት ማምረት አይሆንም፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዘይት ፋብሪካውን የተረከበው በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት በዋስትና የተያዘውን ንብረት ተረክቦ በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ ለማድረግ እንጂ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 16 መሠረት ፋብሪካው የሕግ ሰውነት ኖሮት የባለቤትነት መብቱን ወደራሱ በማስተላለፍ ዘይት የማምረት ሥራውን ለማስቀጠልና በዚሁ ሥራ ትርፍ ለማግኘት አይደለም፡፡ ይህ ፋብሪካ ባንኩ ከተረከበው ጊዜ ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 2/2/ በትርጉም እንደተቀመጠው የድርጅቱን ተግባር ለማከናወን አላማ ይዞ በአንድ አመራር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚመራ ተቋም ሆኖ የተቋቋመ አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 16 ሥር የአንድ ድርጅት የባለቤትነት መብት ወደሌላ መተላለፍ የሥራ ውሉን የማሻሻል ውጤት አይኖረው ተብሎ የተደነገገው የባለቤትነት መብቱን ወደራሱ ያዛወረው አካል ድርጅቱን የወሰደው ሥራውን እንዳለ ለማስቀጠል ነው ተብሎ ስለሚገመት ነው፡፡ ባንኩ ግን ፋብሪካውን የተረከበው እንዳለ ሊሰራበት ሳይሆን በማናቸውም ሁኔታ ሽጦ ገንዘቡን ገቢ ለማድረግ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ነው ባንኩ ድርጅቱን ከመረከቡ በፊት አብዛኛው የፋብሪካው ሰራተኛ አስቀድሞ በፋብሪካው ባለቤት የተሰናበተው ፡፡ ተጠሪዎች ሌላው ሠራተኛ ከተሰናበተ በኋላ በጥበቃ ሥራ ላይ የቆዩትም የፋብሪካው ባለቤት ፋብሪካውን ለባንኩ እስኪያስረክቡ ብቻ እንጂ ፋብሪካው ሥራውን እንዲቀጥልና ተጠሪዎችም በተቀጠሩበት ሥራ እንዲቀጥሉ ለማድረግ አልነበረም፡፡

በመሆኑም ተጠሪዎቹ የድርጅቱ የጥበቃ ሠራተኞች ሆነው የተቀጠሩት ባንኩ ፋብሪካውን ከመረከቡ በፊት በፋብሪካው ባለቤት በመሆኑና በጥበቃ ሥራም የቀጠሉት ባንኩ ድርጅቱን እስከሚረከብ ከፋብሪካው ባለቤት ጋር በመስማማት እንጂ ከባንኩ ጋር ባደረጉት ውል ባለመሆኑ፣ እንደዚሁም ባንኩ ድርጅቱን የተረከበው ከላይ በዝርዝር እንደተገለፀው ሽጦ ገንዘቡን ገቢ ለማድረግ እንጂ የዘይት ማምረት ሥራውን ለማስቀጠል ስላልሆነ ተጠሪዎች በክሱ የጠቀሷቸውና ድርጅቱ ለባንኩ ከመተላለፉ በፊት መከፈል የነበረባቸው ክፍያዎች የፋብሪካውን ባለቤት የሚመለከቱ እንጂ አመልካችን የሚመለከቱ ግዴታዎች ባለመሆናቸው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት 1ኛ ተከሳሽ የሆነውን የፋብሪካውን ባለቤት ከክሱ በማስወጣት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በክሱ የተጠቀሱትን ክፍያዎች እንዲከፍል በማለት መወሰኑ በአግባቡ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ስለዚህ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የሰጡት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 377/96 ልዩነቶችን ያላገናዘበ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መታረም የሚገባው ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሸሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የምግብ ዘይት ፋብሪካውን በጨረታው መነሻ ዋጋ የወሰደው ፋብሪካውን በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ ለማድረግ እንጂ የፋብሪካውን ሥራ ለማስቀጠል ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 16 መሠረት ቀደም ብሎ ፋብሪካው ከተጠሪዎች ጋር ያደረገውን የሥራ ውል የሚያስቀጥልበትና ሠራተኞችን የሚመለከት ግዴታ የሚሸከምበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡
4. ቁጥሩ 20484 የሆነው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገብ ወደመጣበት ከሸኚ ደብዳቤ ጋር ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 33513

ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

ተጠሪ፡- ዘውዴ ተናኘ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ክርክር በተጀመረበት በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/በአርሲ ዞን የጢዮ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ሥራውን ሸፍኜ እየሰራሁ ባለሁበት የሥራ መደብ ላይ ሊያሳድጉኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የደረጃ እድገት ሊሰጥ ወይም ሊገኝ የሚችለው ሕግና ስርዓት መሰረት ተደርጐ በሚካሄደው ውድድር ነው፡፡ ከሳሽ ያቀረበው ጥያቄ ከዚህ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ከሳሽ በጠየቀው የሥራ መደብ ላይ እድገት ይሰጠው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ በቀጥታ ያቀረበውን የደረጃ ዕድገት ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ የመወሰኑን

አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ ክስ የመሰረተው ከፍ ያለ ደመወዝ የሚከፈልበትን የሥራ መደብ ሸፍኜ ለሰራሁበት ጊዜ ተገቢው ክፍያ ይሰጠኝ በማለት ሳይሆን፣ በቦታው ላይ በቋሚነት የደረጃ እድገት ይሰጠኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ የደረጃ እድገት ሊገኝ የሚችለው በሥራ ክርክር ችሎት ክስ በመመስረት ሳይሆን፣ በኮርፖሬሽኑ ወንቶ ባለው የህብረት ስምምነት መሰረት ክፍት የሥራ መደብ መኖሩ ሲረጋገጥና ለሁሉም ሰራተኞች የውድድር ማስታወቂያ ወጥቶ ተወዳድሮ በማሸነፍ ነው በማለት አጥብቆ ተከራክሮአል፡፡ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነውም ተጠሪ በቀጥታ ክስ ከመመስረቱ ውጪ አመልካች በገለፀው አይነት ተወዳድሮ እድገቱን ያገኘ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክርም የረገጡም ጊዜ አገልግሎቱ እና የትምህርት ማስረጃው ታይቶለት ዕድገቱ በፍ/ቤት ሊሰጠው እንደሚገባ ከመግለጽ አልፎ የተጨበጠ ነገር አላቀረበም፡፡ አንድ ሰራተኛ የደረጃ እድገት የሚያገኘው አመልካች ከገለፀው አሰራር ውጪ በሆነ ሁኔታ ነው ለማለትም አልቻለም፡፡ በእርግጥ ዕድገት በጠየቀበት ቦታ ላይ ተመድቦ ይሰራ የነበረው ሰራተኛ ባለመኖሩ የሱን ሥራ ሸፍኖ መስራቱንና የዕድገት ጥያቄውን ያቀረበውም ይህን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በክርክሩ አመልክቶአል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ለተሠራ ተጨማሪ ሥራ ክፍያ መጠየቅ እና በአንድ የሥራ መደብ ላይ በቋሚነት የደረጃ እድገት ይሰጠኝ ማለት በእጅጉ የተለያዩ ናቸው፡፡ አመልካችም በአቤቱታው እንደገለፀው ተጠሪ ተጨማሪ ሥራ ሸፍኖ ሰርቶ ከሆነ ስለምትክ ሠራተኞች አመዳደብ ኮርፖሬሽኑ ባለው መመሪያ ወይም አሠራር መሠረት ይገባኛል የሚለውን ክፍያ ከመጠየቅ አልፎ ከዕድገት አሰጣጥ ሕግና ሥርዓት ውጪ የደረጃ ዕድገት በፍ/ቤት እንዲሰጠው መጠየቁ አግባብ አይደለም ፡፡ በአሰሪና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 138 እንደተመለከተው የደረጃ እድገት ይሰጠኝ ጥያቄ ወይም ክስ በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የዳኝነት ሥልጣን ስር የሚካተት አይደለም፡፡ ይህም ማለት ተጠሪ ለወረዳ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ያቀረበው ክስ ከመሰረቱ መቅረብ የሚችል አልነበረም ማለት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ባለማየት የተጠሪን የእድገት ጥያቄ በመቀበል የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በአርሲ ዞን ጢዮ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 07193 ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 13157 ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጠው ብይን የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ በቋሚነት እንዲሰጠው የጠየቀውን የደረጃ እድገት የሚያገኝበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡

   አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሻሩ ይታወቅ ዘንድ ለስር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

የሰበር መ.ቁ. 34585

ግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

መድህን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ተስፋዬ ኬርጋ

ተጠሪ፡- ደረጀ ወልደኪዳን ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ በሆነ ሁኔታ ተቋረጠብኝ በማለት ሲሆን፣ ወደስራው እንዲመለስ፤ ይህ ካልተቻለም ተገቢ የሆኑት ክፍያዎች ተከፍለውት ይሰናበት ዘንድ እንዲወሰንለት ጠይቆአል፡፡ አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከስራ የተሰናበተው በተቀጠረበት የጥበቃ ስራ ላይ ተመድቦ በመስራት ላይ እንዳለ የሥርቆት ተግባር ሲፈጽም በመገኘቱ እንደሆነ በመግለጽ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ክርክሩን መርምሮ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ተጠሪ የሁለት ወር ደመወዙ ተከፍሎት ወደስራው ይመለስ ዘንድ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም አመልካች ታህሣሥ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ የስርቆት የሙከራ ወንጀል ፈጽሞአል ቢባልም፤ ከቀረበበት የወንጀል ክስ በነፃ ተለቆአል በሚል የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ይዘት እና ከግራ ቀኝ ወገኖቹ ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ በጥበቃ ስራ ላይ ተሰማርቶ በነበረበት ዕለት ስምንት ጆሪካን የትራንስፎርመር ዘይት ሞልቶ ሊያወጣ /ሊወስድ/ ሲል በድርጅቱ ስራ አስኪያጅ እና ሠራተኞች ስለመያዙ በማስረጃ ተረጋግጦአል፡፡ ፍ/ቤቱ በተጠሪ ላይ የተወሰደው የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃ ከሕግ ውጪ ነው ለማለት የበቃው ተጠሪ የመስረቅ ሙከራ ተግባር ለመፈፀሙ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ሣይሆን፣ የወንጀል ክስ ቀርቦበት በነፃ ተሰናብቶአል፣ ድርጊቱ ከሙከራ ያላለፈ ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ የራሱ ያልሆነውን ንብረት ሠርቆ ለመውሰድ ሲል እጅ ከፍንጅ ስለመያዙ በማስረጃ ተረጋግጦአል፡፡ ይህን መሰሉ የስርቆት ተግባር ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ከሚያሰናብቱ ምክንያቶች አንደኛው እንደሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27 ተመልክቶአል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሕጉ እንዲህ የሚል ስለመሆኑ ግንዛቤ መውሰዱን በውሣኔው ላይ ገልጾአል፡፡ በመሆኑም የተፈፀመው ድርጊት ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ ነው የተቋረጠው ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡ ሌላው በወንጀል ክሱ ተጠሪ ጥፋተኛ አልተባለም የሚለው ሲሆን፣ ይህም በፍትሐብሔር ረገድ ለቀረበው ክርክር ያለውን አግባብነት በሚገባ ማየት ያስፈልጋል፡፡ እንደሚታወቀው

የወንጀል እና የፍትሐብሔር ክርክሮች ራሣቸውን ችለው የሚታዩ ናቸው፡፡ በማስረጃ ምዘና ረገድም የየራሣቸው አካሄድ አላቸው፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው በወንጀል ጥፋተኛ ያልተባለ ሰው በፍ/ብሄር ረገድ ከቀረበበት ክስም የግድ ነፃ ይሆናል ለማለት የማይቻል እንደሆነ ነው፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ፈጽሞታል የተባለውን የስርቆት ወንጀል በእርግጥም ስለመፈፀሙ ክሱን በሰማው የስራ ክርክር ችሎት ተረጋግጦአል፡፡ ችሎቱ በራሱ ይህን ካረጋገጠ ደግሞ በወንጀል ክሱ ወደተሰጠው ውሣኔ የሚዛድበት ምክንያት የለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ የፈፀመው ድርጊት በሕጉ ብቻ ሣይሆን፣ በህበረት ስምምነቱም ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብት እንደሆነ ነው ለመገንዘብ የቻልነው፡፡ ስናጠቃልለው አመልካች ከተጠሪ ጋር አድርጎት የነበረውን የስራ ውል ያቋረጠው በሕጉ መሠረት በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.18281 ሚያዝያ 22 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 55472 ታህሣሥ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35440

ግንቦት 19 ቀን 20000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ዋልያ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ድርጅት - ምንተስኖት ተፈሪ /ነገረ ፈጅ/ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ብርሃኔ አሊማ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ እሱም ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ባቀረበው ክስ የአዋጁን አንቀጽ 29 በሚቃረን መልኩ በሠራተኛ ቅነሳ ሰበብ የሥራ ውሌ ተቋርጦብኛል እና ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከስራው የተሰናበተው ድርጅቱ በመክሰሩ የተነሣ ሠራተኞችን መቀነስ አስፈላጊ /ግዴታም/ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ ተጠሪ ድርጅቱን ለማዳን /እንዳይዘጋ ለማድረግ/ ሲባል በተደረገው የመዋቅር ለውጥ የሚመጥነው የስራ መደብ አልተገኘም፡፡ ቅነሳው የተካሄደው ሕጉን ተከትሎ የድርጅቱ ሠራተኛ ማኅበርም በተሳተፈበት ሁኔታ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዱም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ቅነሳው ሕጉን የተከተለ ነው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማለቱ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የቦርዱን ውሣኔ በመሻር

ተጠሪ ወደ ስራው እንዲመለስ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በዓፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የጠ/ፍ/ቤቱ የቦርዱን ውሣኔ የሻረበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ተጠሪን ከስራ ውጪ ያደረገው የሠራተኛ ቅነሳ ሕጉን ተከትሎ የተደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ከተደረገው ክርክር እና ቦርዱ ከሰጠው ውሣኔ እንዳየነው አመልካች ድርጅት ከ75% በላይ ኪሣራ የደረሰበት መሆኑ ተረጋግጦአል፡፡ ድርጅቱ በመክሰሩም የነበረው አማራጭ መፍረስ ቢሆንም፣ አፍርሶ ከመሄድ ይልቅ ሌላ አማራጭ ፈልጎ ሕልውናውን ማቆየት ይሻላል በሚል ሠፊ ጥረትና ጥናት ከተካሄደ በኋላ አዲስ የስራ መዋቅር በማዘጋጀት ሠራተኞቹ ባላቸው የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ መሠረት ምደባ መደረጉንም ቦርዱ አረጋግጦአል፡፡ በመጨረሻም የድርጅቱ የሠራተኛ ማኅበር በተሳተፈበት የሠራተኛ ቅነሳ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በአዲሱ የሥራ መዋቅር ለመመደብ የትምህርት ዝግጅቱ የሚፈቅድለት ሆኖ ባለመገኘቱ እንዲቀነስ መደረጉን በቦርዱ ውሣኔ ላይ ቁልጭ ብሎ መቀመጡን በበኩላችንም ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ እንግዲህ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠውን ሁኔታ በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ካለው የአዋጁ አንቀጽ 29/3/ ጋርም የሚስማማ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያመለክተው በአዋጁ አንቀጽ 28/1/ መሠረት የሠራተኞች ቅነሳ በሚደረግበት ጊዜ አሠሪው ከሠራተኞች ማኅበር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር የስራ ችሎታ ያላቸውንና ከፍተኛ የምርት ውጤት ያሳዩ ሠራተኞችን በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የሰራተኞች ቅነሳ የተደረገው በድንጋጌው የተመለከተውን ስርዓት ተከትሎ ነው። የጠ/ፍ/ቤቱ ከዚህ በተቃራኒ ስለመፈጸሙ በራሱ በኩል ያረጋገጠው የለም። አመልካች ተጠሪን በሚመጥነው የሥራ መደብ ሊመድበው ይገባል ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰውም ምንም የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት ሳይኖረው ነው። ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13933 ጥር 1 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል።
2. አመልካች ተጠሪን የቀነሰው በሕጉ መሠረት ነው ብለናል። ስለዚህም ወደስራው ይመለስ የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም ብለን ወስነናል።
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 29415

ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ዎተር አክሽን - ጠበቃ ተስፋዬ ብርሃኔ ቀረቡ።

ተጠሪ፡- ይልማ አሰፋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረውን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ ውጭ ስለሆነ ወደ ሥራው ሊመለስ ይገባል በማለት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው።

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በአመልካች ላይ በአላባ ቁሊቶ መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ በድርጅቱ ውስጥ ሕገወጥ ድርጊቶችን በመቃወሜ ከጥር 15 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ተከሣሽ ከሥራና ከደመወዝ ያገደኝ ስለሆነ ወደ ሥራ እንድመለስና ከታገድኩበት ጊዜ አንስቶ ያለው ደመወዜ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል።

የከሣሽ ክስና ማስረጃ ለተከሣሽ ደርሶ በሰጠው መልስ ከሥራና ከደመወዝ ከሣሽን ማገዱን አምኖ ይህም ሊሆን የቻለው ከሣሽ አስቀድሞ ሲሰራበት ከነበረው ፕሮጀክት ወደ ሌላ ፕሮጀክት ተዛውሮ እንዲሰራ ተወስኖ ወደተዛወረበት ፕሮጀክት በመሄድ ሥራ ለመጀመር ፈቃደኛ ባለመሆኑ ዕገዳው ትክክል ስለሆነ ወደ ሥራ ለመመለስም ሆነ ውዝፍ ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት ያቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ የተከሣሽ ድርጅት አንድን ሠራተኛ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ አዛውሮ ማሰራት እንደሚችል በድርጅቱ የአስተዳደር ማኑዋል ላይ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነ በዚሁ መሠረት ከሣሽ ወደተዛወረበት ቦታ በመሄድ ሥራ መጀመር ሲገባው አለመሄዱ አግባብነት የለውም ካለ በኋላ ከሣሽ ከተዛወረበት ጊዜ አንስቶ ለአምስት የሥራ ቀናት በሥራ ላይ ባይገኝ ያለማስጠንቀቂያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) መሠረት ተከሣሽ የሥራ ውሉን ማቋረጥ ቢችልም የሥራ ውሉ መቋረጡን በመግለጽ ለከሣሽ ያስታወቀው በሕጉ ላይ የተቀመጠው የ5 ቀን ጊዜ ሣይደርስ ስለሆነ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው ብሎ ከሣሽ ወደሥራው ተመልሶ አዲስ በተመደበበት ቦታ ሄዶ እንዲሰራ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የአላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የቀረበው አቤቱታ ከሥራ ማገድን የሚመለከት ሆኖ ሣለ የወረዳው ፍ/ቤት በዚሁ ነጥብ ላይ ተመስርቶ ውሣኔ መስጠት ሲገባው የሥራ ውል መቋረጥን አስመልክቶ ክርክር ሣይደረግበት ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

በመቀጠልም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ አከራክሮ አመልካች አዲስ ወደተመደበበት ቦታ በመሄድ ከጥር 8 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲገኝ ከተገለፀለት በኋላ ከሥራ መሰናበቱን የሚገልጽ ደብዳቤ የደረሰው ደግሞ ከጥር 5 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ስለሆነ ከጥር 8 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ በተመደበበት ሥራ ላይ ስላለመገኘቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አስቀድሞ የተደረገው የሥራ ስንብት ሕገወጥ ነው በማለት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባቸው የጉዳዩ ጭብጦች አመልካች ተጠሪን ከሥራ አግዷል ወይንስ አሰናብቷል? አሰናብቷል የሚባል ቢሆን ስንብቱ ሕጋዊ ነው ወይንስ አይደለም የሚሉት በመሆናቸው እነዚህን ጭብጦች በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተም ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ያለአግባብ ከሥራና ከደመወዝ ያገደኝ ስለሆነ ወደሥራዬ እንድመለስና ውዝፍ ደመወዝም እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካችም ተጠሪን ከሥራና ከደመወዝ ማገዱን ሣይክድ ተጠሪ ከሥራ ተሰናብቷል ባልተባለበት ሁኔታ ወደ ሥራ የመመለሱም ሆነ የክፍያ ጥያቄው ያለአግባብ ስለሆነ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይሁንና አመልካች ለተጠሪ በዓፈው ደብዳቤ ከሥራና ከደመወዝ መታገዱን እስካስታወቀ ድረስ የሥራ ውሉ መቋረጡንና የሥራ ስንብት መደረጉን የሚያስገነዝብ ከመሆኑም በላይ በአ/ቁ/377/96 አንቀጽ 27/4/ ላይ የሠራተኛው የሥራ ውል እንዲቋረጥ ከመደረጉ በፊት ሠራተኛውን ከሥራ አግዶ ለማቆየት ስለሚቻልበት ሁኔታ በንብረት ስምምነት ሊወሰን እንደሚችል የተመለከተ ስለሆነ በዚህ መልኩም የተደረገ የንብረት ስምምነት ስለመኖሩ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች በተጠሪ ላይ የፈፀመው የሥራ እገዳ ሣይሆን የሥራ ስንብት መሆኑ ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡

ተጠሪ ከሥራ መሰናበቱ ከተረጋገጠ ስንብቱ ሕጋዊ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለው 2ኛው ጭብጥ ሲታይ አመልካች ለተጠሪ በዓፈው ደብዳቤ ከጥር 8 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ ወደተዛወረበት ቦታ በመሄድ ሥራ መጀመር እንደሚገባው አስታውቆት ወደዚሁ ቦታ ሄዶ ሥራውን ያልጀመረ ከመሆኑም በላይ ከጥር 8 ቀን 1998 ዓ.ም በፊትም ቀድሞ ሲሰራበት በነበረው መ/ቤት ከጥር 5 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዳልተገኘና በአጠቃላይም ለ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ያለበቂ ምክንያት በሥራ ገበታው አለመገኘቱ የተረጋገጠ ስለሆነ ይህ ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(2)(ለ) መሠረት በአሠሪው አነሣሽነት የሥራ ውልን ለማቋረጥ የሚያበቃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመሆኑ መጠን በዚሁ መሠረትም አመልካች የሥራ ውሉን ባቋረጠበት ሁኔታ የበታች ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት ተጠሪው ወደሥራ እንዲመለስ በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአላባ ቁሊቱ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01073 በመጋቢት 29 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የደቡብ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 15679 በየካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ከሕግ ውጭ ስላልሆነ ተጠሪ ወደ ሥራ ለመመለስ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰበር መ/ቁ. 32822

ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ጂ.ሰቨን የንግድና ኢንዱስትሪ የመኸር ቃጫ ውጤቶች ፋብሪካ

ተጠሪ፡- መኰንን አበራ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት የቀረበ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ የመሰረተው የሥራ ውሌ በሕገ ወጥ መንገድ ተቋርጦብኛል በማለት ነው፡፡ ይህን ምክንያት መሰረት በማድረግም የአገልግሎት እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ እንዲከፈለው፣ እንዲሁም የስራ መፈለጊያ ክፍያ፤ክፍያ ለዘገየበት ጊዜም ክፍያ እንዲወሰንለት ጠይቆአል፡፡ ፍ/ቤቱ ተከሣሽ የነበረውን የአሁኑን አመልካች በማስቀረብ ክርክሩን ከሰማ ብኋላ ከሣሽ የዓመት እረፍት እንደወጣ ለተከሣሽ ሳያሳውቅ ያለበቂ ምክንያት ለአምስት የስራ ቀናት የቀረ በመሆኑ አመልካች የሥራ ውሉን ማቋረጡ አግባብ ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ እንደገና ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ተጠሪ ከሥራ የቀረው በቂ በሆነ ምክንያት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ ተጠሪ የጠየቃቸውን ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉትም ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ነሐሴ 22 ቀን 99 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠበትን የሕግ አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪ ለአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ከሥራ ገበታው ላይ ሳይገኝ እንደቀረ አላከራከረም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ለውሳኔአቸው መሰረት ያደረጉት ጭብጥ የተጠሪው ከሥራ መቅረት በበቂ መክንያት የተደገፈ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራ መቅረቱን ካመነ በእርግጥም በቂ ምክንያት የነበረው መሆኑን ያስረዳ ዘንድ የግድ ነው፡፡ አመልካች ከሥር ጀምሮ አጥብቆ የተከራከረው ተጠሪ ለእረፍት እንደወጣ በዚያው ከመቅረቱ ውጪ ባለበት ቦታ ሆኖ እንኳን ሊያሳውቀኝ አልቻለም በማለት ሲሆን፣ ተጠሪ ደግሞ በጉርፍ አደጋ የተጠቁትን ዘመዶቹን ለመጠየቅ ወደ ድሬዳዋ ሄጀ ነበር የሚል የመከራከሪያ ነጥብ ማንሳቱን ተመልክተናል፡፡ ይህንን የመከራከሪያ ነጥብ ግን በቃል ከመግለጽ አልፎ በየትኛውም የማስረጃ አይነት አስረዳለሁ አላለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም አባባሉን እንዳለ ከመቀበል አልፎ ያረጋገጠው ነገር የለም፡፡ ይህ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተፈጸመ ከማስረጃ ሕግ አኳያ የሚታይ ስህተት እንዳለ እንገነዘባለን፡፡ በሌላ አነጋገር ፍ/ቤቱ ውሳኔውን የሰጠው በምንም አይነት ማስረጃ ላይ ሳይመሰረት ነው ማለት ነው፡፡ አመልካች ግን ተጠሪ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1) (ለ) የተመለከተውን ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል ድርጊት ስለመፈጸሙ አስረድቶአል፡፡ ያለው እውነታ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው በሕግወጥ መንገድ ነው የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔም ከዚህ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ፡፡

1. አቤቱታ የቀረበበት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 53908 ሐምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕጉ መሰረት ነው ብለናል፡፡ ስለዚህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 24792 መጋቢት 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቶአል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32229

ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድኀን ኪሮስ

አመልካች፡- መሪጌታ ልሣነወርቅ በዛብህ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጠቅላይ ቤ/ክህነት ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ፍቅረማርያም ካሣ ቀረበ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪ ጽ/ቤት የኢጋዴን ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሆኜ በመስራት ላይ ሣለሁ ከታህሣሥ 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ የቁልቢ ነዋየ ቅድሣት ማደራጃ ዋና ፀሐፊ ሆኜ እንድሰራ ተደርጓል፣ ተጠሪው ደረጃዬን ከሥራ አስኪያጅነት ወደ ፀሐፊነት ዝቅ ማድረጉ አግባብ ስላልሆነ ወደ ሥራ አስኪያጅነት ደረጃና ደመወዝ እንድመለስ ይወስንልኝ በማለት ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች የሥራ መሪ ስለሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም፣ አመልካች ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ በቦታቸው ሌላ ሥራ አስኪያጅ መመደቡን እያወቁ ሣይቃወሙ ቆይተው አሁን ያቀረቡት ክስና የክፍያ ጥያቄ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ቦርዱም አመልካች የሥራ መሪ ስለሆኑ ቦርዱ ክሱን ተቀብሎ የማየት ሥልጣን የለውም፣ ክሱ ግን በይርጋ የታገደ ነው በማለት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

በመቀጠልም አመልካች ይህንኑ ክስ ለፌዴ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት አቅርበው ተጠሪ በሰጠው መልስ ክሱ ቀደም ሲል ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ቀርቦ ቦርዱ ውሣኔ የሰጠበት ስለሆነና ፍ/ቤቱ ደግሞ ይግባኝ ሰሚ ስላልሆነ

ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚለውንና ሌሎች መከራከሪያዎችን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ቦርዱ በዚህ ዓይነቱ ክርክር ላይ የዳኝነት ሥልጣን ሣይኖረው በክርክሩ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ ስለማይኖር ፍ/ቤቱ የቦርዱን ብይን የሚረዳው ክሱ በይርጋ ቀሪ ቢሆንም ቦርዱ ጉዳይን የማየት ሥልጣን የለውም የሚል መሆኑን ነው፣ ስለዚህ አመልካች አሁን ክሱን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ያቀረቡ ስለሆነ በዚህ ረገድ ተጠሪ የፍ/ብሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5ን በመጥቀስ ያነሣው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም በማለት ብይን ከሰጠ በኋላ ተጠሪ አመልካችን ከሥራ አስኪያጅነት ወደ ሌላ የሥራ መደብ የለወጣቸው ያለአግባብ በመሆኑ ተጠሪ አመልካችን ቀድሞ ወደነበሩበት የሥራ መደብ /ወደ ሥራ አስኪያጅነት/ በመመለስ በመደቡ የሚከፈለውን ደመወዝና አበል ሊከፍላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ቀደም ሲል ክሱ ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ቀርቦ ቦርዱ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ሲል ብይን ሰጥቶበታል፣ ብይኑ ይግባኝ ተብሎበት በፍርድ ውሣኔ አልተሻረም፣ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የቀረበለትን ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ውድቅ ማድረግ ሲገባው ይህ ያልተሻረ ብይን እያለ ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ መስጠቱ አግባብ ስላልሆነ የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል በማለት ወስነ፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘትም ባጭሩ የሥር ፍ/ቤት ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መወሰኑ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ይህ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ሥልጣን የለኝም ሲል ከወሰነ በኋላ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት በብይኑ ላይ ማስፈሩ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያቀረቡት ክስ ቀደም ሲል ውሣኔ አግኝቶ የበቃ ነው ለማለት የሚያስችል መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን የሚባው ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በመጀመሪያ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክስ አቅርበው ቦርዱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለኝም እንጂ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ሲል መበየኑን፣ በመቀጠልም አመልካች ክሱን ለፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት አቅርበው ተጠሪ ጉዳዩ ቀደም ሲል የቦርዱ ውሣኔ /ብይን/ ያረፈበት ስለሆነ ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ሊታገድ ይገባል የሚል መቃወሚያ ያቀረበ መሆኑን፣ ፍ/ቤቱ ቦርዱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን ሣይኖረው ይርጋውን አስመልክቶ ብይን መስጠት አይችልም በማለት መቃወሚያውን በብይን ውድቅ አድርጎ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱን፣ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቦርዱ ቀደም ሲል ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ሲል የሰጠው ብይን በይግባኝ ስላልተሻረ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበለትን ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ውድቅ ማድረግ ሲገባው በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ አግባብ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ የሻረው መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ መዝገብ የሚያከራክረውን ጉዳይ በየደረጃው ያዩት ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የተለያየ ሲሆን ለዚህ ልዩነት መነሻው ቦርዱ የዳኝነት ሥልጣን የለኝም ነገር ግን ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ሲል የሰጠው ብይን መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይኸውም የመጀ/ደ/ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለኝም የሚለውን የብይኑን ክፍል ይዞ ውሣኔውን ያሣረፈ ሲሆን ከፍ/ፍ/ቤት ደግሞ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው የሚለውን ክፍል በመያዝ ይርጋውን አስመልክቶ የተሰጠው ብይን ስላልተሻረ ለመ/ደ/ፍ/ቤት ክስ ሊቀርብ አይችልም በማለት ወስኗል፡፡

በመሠረቱ አንድ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ስልጣን ያለው መሆኑን ካላረጋገጠ የግራ ቀኙን ክርክር መመርመር አይጀምርም፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክሱ ለቦርድ መቅረብ ያልነበረበት መሆኑን ከተገነዘበ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን እንደሌለው በመግለጽ እዚያው ላይ

ማቆም ሲገባው በተጠሪ የቀረበውን የይርጋ ክርክር መርምሮ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል ሀሣብ በብይኑ ላይ አስፍሯል፡፡ ቦርዱ የዳኝነት ሥልጣን ከሌለው ይርጋውንም አስመልክቶ ብይን መሰጠት አይገባውም፡፡ ስለሆነም ቦርዱ በአንድ በኩል የዳኝነት ሥልጣን የለኝም እያለ በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣኑ ቢኖረው ኖሮ ሊመረምር ይገባው የነበረውን ጉዳይ በብይኑ ላይ መጥቀሱ ስለይርጋው ብይን ሰጥቷል ለማለት የሚያስችል ስላልሆነ አመልካች ለመ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 መሠረት ውድቅ የሚያደረግ አይደለም፡፡ በዚህ ምክንያት ቦርዱ ቀደም ሲል ይርጋውን በተመለከተ ብይን የሰጠ ስለሆነ ብይኑ በይግባኝ ሣይሻር ክሱ ለመጀ/ደ/ፍ/ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 52954 ሰኔ 1 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ብይኑ የተሻረ መሆኑን ተገንዝቦ በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ በመመርመር የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 29419

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ሬቫ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር - ጠበቃ ንጉሴ ገዛኸኝ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. እንዳለ ታደሰ - በሌለበት

2. ማሞ ዋቅጅራ - በሌለበት

3. ሚሊዮን ዘውዴ - በሌለበት

4. ሰይድ መሐመድ - በሌለበት

5. አባቡ ውበቱ - ቀረበ

6. ግዛው ፈይሳ - ቀረበ

7. ከፍያለው ጌታቸው - በሌለበት

8. ምስጋና አዲስ - በሌለበት

9. ገመዳ ሞገስ - በሌለበት

10. ታምራት ኃይሉ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

አከራካሪው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ከሣሾች ነበሩ፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱትም በአናጺነት ሥራ ተሰማርተን አንድንሠራ በውል ተቀጥረን

ስንሠራ የቆየን ቢሆንም፤ ሥራው ሳያልቅ ከሕግ ውጪ የሥራ ውላችን ተቋርጦብናል፡፡ ስለዚህ ወደ ስራችን እንድንመለስ፤ የማንመለስ ከሆነም ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ተገቢው ክፍያ ተከፍሎን እንሰናበት ዘንድ ይወሰንልን በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ጊዜያዊነት ላለው ሥራ አገልግሎት እንዲሰጡ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ተመድበው ቢሠሩም ደመወዝ የሚከፈላቸው በቀን እየታሰበ ነው፡፡ በመጨረሻም ስራው ስላለቀ በአዋጁ አንቀጽ 24/1/ መሠረት ተሰናብተዋል፡፡ በመሆኑም የሥራ ውላችን ሕገወጥ በሆነ መንገድ ተቋርጦአል የሚሉበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት መከራከሩን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ማረጋገጡን ገልጾ፣ በሌላ በኩል ግን ስንብቱ የተከናወነው በአዋጅ አንቀጽ 30/1/ መሠረት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት አመልካች የዓመት ዕረፍት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ እና ክፍያ በመዘግየቱ ሊከፈል የሚገባው ነው ያለውን ደመወዝ ለተጠሪዎች እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አመልካች መጋቢት 7 ቀን 1999 ዓ.ም. በዳፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቀርበው ክርክራቸውን ያሰሙት በ5ኛ፣ በ6ኛ እና በ10ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች ብቻ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ስላልቀረቡ ክርክሩ እነሱ በሌሉበት ተሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ናቸው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመዝገቡ ከቀረበው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች በኮንስትራክሽን ሥራ ዘርፍ የተሰማራ ድርጅት ሲሆን፣ ተጠሪዎችን ቀጥሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያሠራው የተወሰነ የግንባታ ሥራ ማለትም ሃያ /20/ ቤቶችን ሲሠራ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ የተቀጠሩበት ስራም የአናጺነት ስራ ነው፡፡ ቤቶች ሲገነቡ ከሚያስፈልጉት ሥራዎች አንዱ የአናጺነት ስራ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም፤ ይህ ስራ እስከ መጨረሻው ይዘልቃል ወይም ያስፈልጋል ማለት ግን አይደለም፡፡ በእርግጥ አመልካች በኮንስትራክሽን የሥራ ዘርፍ የተሰማራ የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ የኮንስትራክሽን ስራዎች እስካሉ ድረስ በዚሁ የሚቀጥል ቋሚ ድርጅት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ድርጅቱ ቋሚ ነው ከተባለ ደግሞ አብረውት የሚዘልቁ ቋሚ ሠራተኞች ማለትም በተወሰነ ሰዓት ሥራ ገብተው በተወሰነ ሰዓት የሚወጡ /መደበኛ የሥራ ሰዓት ያላቸው/ በየወሩም በፔይሮል ደመወዝ የሚከፈላቸው እንደሚኖሩት ይታወቃል፡፡ ድርጅቱ አንድ የተወሰነ የግንባታ ስራ በሚሠራበት ጊዜ በተጨማሪነት የሚቀጥራቸው ሠራተኞች ግን ግንኙነታቸው ከተቀጠሩበት የተወሰነ የግንባታ ስራ ጋር በመሆኑ በቋሚነት ከተቀጠሩት የድርጅቱ ሠራተኞች በተለየ ሁኔታ መታየት እንዳለባቸውም ሊያከራክር የሚችል /የሚገባ/ አይደለም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ሃያ ቤቶች በሚሠሩበት ወቅት የአናጺነት ሥራ እንዲሠሩ በመሆኑ ቅጥራቸው በአዋጁ አንቀጽ 10/1/ሀ/ እንደተመለከተው ለተወሰነ ሥራ ነው፡፡ ይህም ከሥራው ባሕርይ አንፃር ግልጽ ስለሆነ አመልካች የተቀጠሩት ለተወሰነ ሥራ መሆኑን አላስረዳም የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ክሱን የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንዳመለከተው የቤቶቹ ስራ ተገባዶ የነበረ ሲሆን፣ ተጠሪዎች ከሥራው እንዲሰናበቱ የተደረጉትም ያኔ ነው፡፡ ከላይ እንዳመለከትነው የአናጺነት ስራ የራሱ ባሕይር ያለው በመሆኑ ቤቶቹ ፍጹም ተጠናቀው ለመኖሪያነት ብቁ እስከሆኑ ድረስ የሚዘልቅ አይደለም፡፡ በመሆኑም የቤቶቹ ስራ ተገባዶ ነበር እስከተባለ ድረስ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት የአናጺነት ስራ አልተጠናቀቀም ወይም ቀጣይነት ነበረው ወደሚለው ድምዳሜ መድረስ የሚቻልበት ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጉት የአዋጁ አንቀጽ 30/1/ም መታየት ያለበት ከላይ በዝርዝር ከተገለጸው

የአመልካች የስራ ባሕርይ አንፃር ነው፡፡ በዚህ መሠረት ሲታይም የቤቶቹ ግንባታ እያለቀ ሲሄድ ለሚቀረው ስራ አስፈላጊ የሆኑት ሠራተኞች ብቻ ቀርተው ባለቀው ስራ ላይ ሲሠሩ የነበሩት ይሰናበታሉ /ይቀነሳሉ/ የሚል ትርጉም ነው የሚኖረው፡፡ ተጠሪዎች የተሰናበቱት የተቀጠሩበት የአናጺነት ሥራ በመጠናቀቁ በመሆኑም ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው የአዋጁ አንቀጽ 24/1/ ነው፡፡ በመጨረሻም የሥራ ውሉ በመቋረጡ ምክንያት የሚከፈሉ ክፍያዎች ካሉም መታየት ያለባቸው ከዚሁ አንፃር ነው፡፡ ሲጠቃለል ተጠሪዎች የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ነው እንደዚሁም ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ድንጋጌ የአዋጁ አንቀጽ 30/1/ ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 28432 የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 52206 የካቲት 28 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በአዋጁ አንቀጽ 24/1/ እንደተመለከተው በሕግ በተደነገገው መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief





የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች
ቅፅ 7

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

ቅፅ 7

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሚያዝያ 2001 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

ቅፅ 7

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

አዲስ አበባ



የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

ከዚህ ዕትም በፊት በነበሩ ቅፆች በርካታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች ታትመው በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶችና ለሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሠራጩ ተደርጓል። ይህም በዋናነት፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል ተብሎ በመደንገጉ ፍርድ ቤቶች የሰበር ችሎቱ የሰጠውን የሕግ ትርጉም ተከትለው እንዲሠሩ ለማስቻል ነው። በየፍርድ ቤቶች ለተመሣሣይ ጉዳዮች ይሰጥ የነበረውን የተለያዩ ወሳኔዎች በማስቀረት የፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ወጥነት እንዲኖራቸውን ተገማችም እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑም ነው።

በሌላ በኩል ውሣኔዎቹ በጥራዝ መልክ መዘጋጀታቸው ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ የሕግ ተማሪዎችና ምሁራን፣ ለጠበቆችና ለህብረተሰቡ በአጠቃላይ ውሳኔዎቹን በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል የሚል እምነት አለን።

ተገኔ ጌታነህ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማውጫ ገጽ

የውል ህግ 1

የሰ/መ/ቁ 12719.....2
ለክሰር የቱሪስትና የጉዞ ወኪል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እና ብሩኔይስ ኃ/የተ/የግ/ማ'ነበር
የሰ/መ/ቁ 20232.....9
አቶ ትዕግሥቱ ብዛ እና አቶ ይሃ ይብሬ
የሰ/መ/ቁ 20979.....14
የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ የወ/ሮ ግምጃ በሐቲ ወራሽ
የሰ/መ/ቁ 21531.....17
ኢትዮ ትሬዲንግ የንግድ ሥራ ማስፋፊያ እና የውሃ ሃብት ሚኒስቴር
የሰ/መ/ቁ 23609 21
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አሰበወርቅ ዘገየ
የሰ/መ/ቁ 30298.....26
አቶ የሺወንድም አቡሐይ እና አቶ አየነው ማለደ

የመያዣ ውል 30

የሰ/መ/ቁ 16218.....31
የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ወ/ሮ አስካለ ሁንዴ
የሰ/መ/ቁ 25863 38
የኢት/ልማት ባንክ እና የኢት/ንግድ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 29269.....42
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ዋለልኝ አያሌው
የሰ/መ/ቁ 29375.....48
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ተስፋዬ ገብረጊዮርጊስ
የሰ/መ/ቁ 33295.....51
ወ/ሪት ብርሃኔ አበበ እና እነ አቶ ማርቆስ ተርፋ

የኪራይ ውል.....58

የሰ/መ/ቁ 23024.....59
ወ/ሮ ፋጤ በሽር እና መልዓከገነት ዮሐንስ አምባው እና የኪራይ ቤቶ ኤጀንሲ
የሰ/መ/ቁ 24221 63
ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ወ/ሮ አረጋሽ አምደሚካኤል
የሰ/መ/ቁ 25938.....67
የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና የአቶ ገ/ሕይወት ከበዶም ወራሾች
የሰ/መ/ቁ 28025.....71
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ታደለ አበበ
የሰ/መ/ቁ 30894.....74
ወ/ሮ መዓዛገነት ዳኜ እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ
የሰ/መ/ቁ 31601.....80
ወ/ሮ መዓዛ ይሕደጎ እና እነ አየለ ወልዴ
የሰ/መ/ቁ 31634.....83
ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአቶ ወርቁ ሚስት ወ/ሮ ጽጌ በየነ
የሰ/መ/ቁ 31917 90
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ለምለም ገ/ትንሳኤ
የሰ/መ/ቁ 32521.....94
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ዳባ ኢጃቶ
የሰ/መ/ቁ 34456.....99
የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እና ወ/ት ደብሪቱ ወልደሃና

የሽያጭ ውል..... 103

የሰ/መ/ቁ 16455.....104
ወ/ት አዜብ ሽፈራው እና ወ/ሮ ታዮች ንጉሴ
የሰ/መ/ቁ 18380 108
አቶ ማሞ ደምሴ እና እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር
የሰ/መ/ቁ 22448 112
ኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ክፍል አ/ማህበር እና አቶ ሙሉነህ ካሳ
የሰ/መ/ቁ 22860 116
ሰንላይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ እና አቶ ካሣዬ ዘውዴ
የሰ/መ/ቁ 23331 119
ጀማል ሐሚድ እና እነ ወ/ሮ ለተሃይማኖት ተክሌ
የሰ/መ/ቁ 23895 122
ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል እና መኮንን ሉሌ
የሰ/መ/ቁ 24554 125
አቶ አይሸሹም ጋተው እና እነ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ
የሰ/መ/ቁ 24974 132
እነ አቶ ፈቃዱ ዴሬሎ እና እነ አቶ ንጉሴ ወርቁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 25165 136
አቶ እርቁ ጎዳ እና አቶ አህመድ አብዱልሐሚድ
የሰ/መ/ቁ 26996 140
አቶ በቀለ ደቦጭ እና እነ ወ/ሮ አዛለች ደሣለኝ
የሰ/መ/ቁ 27349 146
ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና ዘላቂ ግብርና ተሐድሶ ኮሚሽን
የሰ/መ/ቁ 28663 150
አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ እና ወ/ሮ አልማዝ ወልዴ
የሰ/መ/ቁ 29233 153
አቶ ሙሂዲን ፋሪስ እና አቶ ኢያሱ በዕደ ማርያም
የሰ/መ/ቁ 31223 159
ወ/ሮ ለምለም መኩሪያ እና ወ/ሮ ሙሉእመቤት ጌታሁን
የሰ/መ/ቁ 31482 163
ወ/ሮ ዓለምነሽ ወ/አገኘሁ እና አቶ አባተ ተፈሪ
የሰ/መ/ቁ 31640 166
አቶ ገረመው ግዛው እና አቶ ፈቃዱ ያደቴ
የሰ/መ/ቁ 32222 170
አቶ መሐመድ ኢብራሂም እና አቶ ታይደር ማች
የሰ/መ/ቁ 32899 174
ወ/ሮ አስካለ ማርያም ታደሰ እና አቶ ተሸመ ካሣዬ

የጠበቆች ፈቃድ 180

የሰ/መ/ቁ 25287 181
ሜድሮክ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ በዛወርቅ ሺመላስ

ውርስ 191

የሰ/መ/ቁ 23322 192
ወ/ሮ አዳነች ወርዶፋ እና እነ ወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ
የሰ/መ/ቁ 25869 197
ወ/ሮ አየለች አልታዬ እና ወ/ሮ አስናቀች አየለ
የሰ/መ/ቁ 30158 201
ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞገዚት ሐይሉ ሲሳይ እና የክ/ል እሸቱ ተስፋዬ ወራሾች
የሰ/መ/ቁ 30991 207
እማሆይ ወይንሸት አድማሱ እና እነ ወ/ሮ ክብነሽ ስዩም የሰ/መ/ቁ 32414 212
ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ እና እነ ወ/ሮ ሃሳብ ከፋይ ጌራወርቅ
የሰ/መ/ቁ 34076 217
ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ እና እነ እማሆይ ድብቅነሽ ግዛው

መድን 220

የሰ/መ/ቁ 22530 221
የቀድሞው የኢትዮጵያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን እና እነ አጂፕ ኢትዮጵያ አክሲዮን ማህበር
የሰ/መ/ቁ 24703 225
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ት ቢሮ
የሰ/መ/ቁ 24704 229
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ጤና ቢሮ
የሰ/መ/ቁ 28254 234
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና መኮንን መስፍን
የሰ/መ/ቁ 31334 239
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ

ወንጀል 246

የሰ/መ/ቁ 21411 247
የቤንሻንጉል ጉመዝ ክልል ዐ/ሕግ እና ወ/ር ሰይድ እንድሪስ ዩሱፍ
የሰ/መ/ቁ 22069 251
የአማራ ብ/ክ/መንግሥት ፍትሕ ቢሮ እና አቶ አስማማው አራጌ
የሰ/መ/ቁ 22452 255
የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና አሣምነው ገ/መስቀል
የሰ/መ/ቁ 22514 262
አቶ ኩራት ተገኘ እና ዓቃቤ ህግ
የሰ/መ/ቁ 23855 265
የጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ እና አቶ ፀጋሁን መንግሥቱ
የሰ/መ/ቁ 24278 270
ሰለሞን ሄርጃቦ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የሥ/ፀ/መ/ኮ/ዐ/ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 28952 273
የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ እና እነ ባንቲ ታኤራ
የሰ/መ/ቁ 29325 275
ኤርምያስ ካሣ ተፈራ እና ዓቃቤ ሕግ
የሰ/መ/ቁ 31731 278
የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እና ዘሪሁን ታደሰ
የሰ/መ/ቁ 31734 283
አቶ አስናቀ በቀለ እና ዓቃቤ ሕግ
የሰ/መ/ቁ 34077 287
አቶ ሰይድ ይመር እና የአማራ ክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን
የሰ/መ/ቁ 34280 292
አቶ ግርማይ ደስታ እና ዓቃቤ ሕግ
የሰ/መ/ቁ 34521 297
የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ እና ስንታየሁ ተፈራ
የሰ/መ/ቁ 35611 300
ሻለቃ ታደሰ ካሕሳይ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ

ግብር 303

የሰ/መ/ቁ 18809 304
አቶ ሚሊዮን ዑመር እና የፌደራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን

የንግድ ተቋማት 307

የሰ/መ/ቁ 19258 308
አቶ ተክሌ ዋቅጅራ እና አቶ ሾንጣ ጉቡ
የሰ/መ/ቁ 23389 314
የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኅበር እና እነ ባህሩ አብርሃም
የሰ/መ/ቁ 28923 318
የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማሕበር እና የባህር ዳር ልዩ አስተዳደር እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ

አፈጻጸም 323

የሰ/መ/ቁ 10489 324
የስራና ክተማ ልማት ሚ/ር ተተኪ መሠረተ ልማት ሚ/ር እና የቀድሞ ብሔራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግ/ማ
የሰ/መ/ቁ 18576 330
ወ/ሮ ደስታ መኮንን እና ወ/ት መሰሉ ጌታሁን
የሰ/መ/ቁ 19283..... 335
ወ/ሮ መድኃኒት ኃይሉ እና የኮንስትራክሽን ቢዝነስ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 22481 340
አቶ ክፍሌ ወልዴ እና ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር
የሰ/መ/ቁ 22930 350
ወ/ሮ ታድሬ አባተ እና ወ/ሮ ዓለም ገ/የሱስ
የሰ/መ/ቁ 23733 353
ሃፍቶም ገ/እብዝጊ እና እነ ሙሉ ካሳ
የሰ/መ/ቁ 23989 356
አቶ ደስታ ሠርዳ እና የመከተል ዞን ፍትህ መምሪያ
የሰ/መ/ቁ 25031 360
ወ/ሮ አልታየወርቅ ኃ/ማርያም እና አቶ ዓለማየሁ ገለቱ
የሰ/መ/ቁ 26553 363
የባህርዳር ልዩ ዞን ገንዘብ መምሪያ እና የኮንስትራክሽ ቢዝነስ ባንክ እና ሙክታር መሐመድ
የሰ/መ/ቁ 27574 370
ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ እና የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማኅበር
የሰ/መ/ቁ 28019 373
አቶ ብርሃኑ ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ
የሰ/መ/ቁ 28154 376
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 28362 379
አቶ መሐመድ ኑር ጀብራል እና እነ ወ/ሪት ውበት ላሊሶ
የሰ/መ/ቁ 29344 383
ወ/ሮ ዝማም ህሉፍ እና አቶ መረሣ ገ/ዩሐንስ
የሰ/መ/ቁ 29371 387
ሶፊያ መሐመድ እና እነ ኢብራሂም መሐመድ
የሰ/መ/ቁ 29653 391
አቶ ነጋ ደምሴ እና ሃምሳ አላቃ አዲሱ ደምስ
የሰ/መ/ቁ 33760 394
ሐጂ ታጁ ለገሠ እና የጎንደር ከተማ የመሀል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውል ህግ

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 12719

ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- ሉክሰር የቱሪስትና የጉዞ ወኪል ኃ/የተ/የግ/ማኅበር - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- ብሩኔይስ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር - ጠበቃ ተስፋዬ ዘውዴ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፣

ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች ኅዳር 28 ቀን 1993 ዓ.ም. ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ፣ የአሁኑ ተጠሪ ሚያዝያ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. ካቻማሌ አስ.ፒ. ኤ. ለተባለ ድርጅት የአሜሪካን ዶላር 540,000 /አምስት መቶ አርባ ሺህ/ ለመክፈል ግዴታ ገብቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ እና ካቻማሌ አስ ፒ ኤ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ባደረጉት ተጨማሪ ውል መሰረት ተጠሪ ላለበት ዕዳ ከፊል ክፍያ እንዲሆን ጠቅላላ ዋጋቸው የአሜሪካን ዶላር 452,338 /አራት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺ ሦስት መቶ ሰላሣ ስምንት/ ወይም በኢትዮጵያ ብር 3,673,000 /ሦስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ሦስት ሺህ/ የሆኑ አዲስ አበባ አምቼ ኩባንያ የቆሙ አምስት አውቶብሶችን ለአመልካች ለማስረከብ ግዴታ ገብቷል፡፡ ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት አውቶብሶቹን ለአመልካች ስላላስረከበ በፍ/ቤቱ አስገዳጅነት እንዲያስረክበውና አውቶቡሶቹን ባለመረከቡ ምክንያት አመልካች ያጣውን ጥቅም ከህጋዊ ወለዱ ጋር እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡ ተጠሪ ጥር 7 ቀን 1993 ዓ.ም. ከሰጠው መልስ መካከል፣ አመልካች ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ተፈረመ በተባለው ስምምነት ላይም ሆነ

ሚያዝያ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. በተደረገው ውል ላይ ተዋዋይ ወገን ባለመሆኑ ሠነዱን መሠረት አድርጎ የዳኝነት ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችለው መብት የለም፤ ከተገለፀው ሰነድ ላይ ስሙ የተመለከተ ቢሆንም እንደ ካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. ሆኖ አውቶቡሶቹን ሊረከብ እንጂ ርክክቡ ለከሳሹ የባለቤትነት መብት እንዲያጎናጽፍ ታስቦ የተፃፈ አይደለም፡፡ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም የተፃፈው ሰነድ እንደዋናው ውል በሁለት ምስክሮች ያልተረጋገጠ ስለሆነ የሚያጎናጽፈው መብት የለም፤ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ሰነድ ተጨማሪ ውል ሳይሆን ደብዳቤ ብቻ በመሆኑ ተጠሪ ስለዕዳው አከፋፈል አዲስ ሐሣብ አቀረበ እንጂ የገባው ግዴታ የለም የሚል ይገኝበታል፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. የተፃፈው ሰነድ አዲስ የውል ሐሣብ የያዘ ደብዳቤ እንጂ ተጨማሪ ውል ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ጥያቄውን አልተቀበለውም፡፡ ተከሣሽ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን አውቶቡሶች ለከሳሽ ሊያስክብም ሆነ ዋጋቸውን ሊተካ እንዲሁም ርክክብ ቢፈፀም ኖሮ ተሸከርካሪዎቹ ሊያስገኙ ይችሉ የነበረውን ጥቅም ተከሣሽ ለከሳሽ ሊከፍል አይገደድም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰኔ 24 ቀን 1995 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይኸን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ይህ ችሎት ታህሣሥ 30 ቀን 1996 ዓ.ም. መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ ከመዝገቡ ጋር አያይዟል፡፡ በዚህ ጉዳይ ውሣኔ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ፣ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. በአሁኑ ተጠሪና በካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. መካከል ተፈረመ የተባለው ሰነድ የዕዳ ክፍያ ተጨማሪ ስምምነት ሳይሆን አዲስ ሐሣብ የቀረበበት ደብዳቤ ስለሆነ መልስ ሰጭ በዚህ ደብዳቤ የሚገደድበት ምክንያት የለም መባሉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ችሎት አቤቱታውን በሥር ከተደረጉ ክርክሮች እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ የአሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረው ክስ፣ የአሁኑ ተጠሪ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ከካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. ጋር ተጨማሪ ውል ሲያደርግ አምስት አውቶብሶችን ለኔ ለማስረከብ ግዴታ የገባ በመሆኑ በገባው ግዴታ መሠረት ርክክቡን እንዲፈጽምልኝ፤ ርክክቡም በመዘግየቱ የቀረብኝን ጥቅም ይተካልኝ በማለት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠውም መልስ ሆነ ለሰበር ቅሬታው ጥር 27 ቀን 1996 ዓ.ም. ለዚህ ችሎት ከሰጣቸው መልሶች መካከል፣ ማያዝያ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. የተደረገው ስምምነት ተከሳሽን /የአሁን ተጠሪ/ እና ካቻማሊ ኤስ ፒ ኤን ብቻ የሚመለከት ነው፡፡ ሰኔ 30 ቀን 1991 ተፃፈ የተባለውም ሰነድ ቢሆን ተጠሪንና ካቻማሊ ኤስ ፒ ኤን ብቻ የሚመለከት ሆኖ በሰነዱ ላይ የከሳሽ /የአመልካች/ ስም መጠቀሱ በሰነዱ ላይ የተመለከቱትን አውቶቡሶች እንደካቻማሊ ኤስ ፒ ኤ ሆኖ እንዲረከብ እንጂ ከርክክቡ በኋላ የባለቤትነት መብት እንዲያገኝ ታስቦ የተዘጋጀ ባመሆኑ የሥር ከሳሽ የሆነው የአሁኑ አመልካች ተዋዋይ ወገን ያልሆነበትን ሰነድ መነሻ አድርጎ መብት ለመጠየቅ አይችልም፡፡ ሦስትኛ ወገኖች የውል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ውሉ በግልጽ ለይቶ የማመልከት ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግለጽ ሰፊ መልስ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል የአመልካች ጠበቃ በበኩሉ፣ ተዋዋይ ወገኖች በውሉ ያልነበሩ ሦስተኛ ወገኖችን የውሉ ተጠቃሚ ስለሚያደርጉበት የሕግ አግባብ፤ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. የአሁኑ ተጠሪ በራሱ አነሳሽነት ለአሁኑ በስር ባለገንዘቡ /በካቻማሌ አስ. ፒ. ኤ./ ተቀባይነት በማግኘቱ በገባው ግዴታ ለአሁኑ ተጠሪ አውቶቡሶቹን የማስረከብ ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

በበኩላችን ጉዳዩን በሚከተለው አኳኋን መርምረናል፡፡ በመሠረቱ ከውል የሚመነጭ መብትም ሆነ ግዴታ የሚመሰረተው ውሉን በፈቃዳቸውና በስምምነታቸው ባቋቋሙት ተዋዋይ ወገኖች ላይ መሆኑ አጠያያቂ

አይደለም፡፡ በውሉ መደረግ ጊዜ ተዋዋይ ወገን ያልነበሩ ሦስተኛ ወገኖች የመብቱ ተጠቃሚዎችም ሆነ የግዴታው ተጠያቂዎች ሊሆኑ እንደማይችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 1952/1/ ያስገነዝባል፡፡ ይህ አጠቃላይ መርህ Privity of contract or Relative Effect of contract በመባል የሚታወቀው የውል ሕግ አጠቃላይ መርህ ነው፡፡ ውሎች ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው የሚለው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1731 አነጋገርም ከዚህ መርህ ጋር የሚጣጣም ድንጋጌ ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ መርህ በተለየ ሁኔታ በአንድ ውል ምስረታ ጊዜ የውሉ ተካፋይ ያልነበሩ ሦስተኛ ወገኖች ወደ ውሉ ውጤት ሊገቡ የሚችሉበት አግባብ በሕጉ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የተመለከተ ስለመሆኑ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1957 እና በሚቀሉት አንቀጾች መሠረት ለሦስተኛ ወገን ጥቅም ሲባል የሚደረጉ የውል ስምምነቶች /Contract for the Benefit of third parties/፣ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2212/1/ እና 2222 መሠረት ወካይ የተባለው ተወካዩ ከሌላው ጋር ላደረገው የውል አፈፃፀም ተጠያቂ የሚሆንበት አግባብ ወይም በንግድ ሕግ ቁጥር 701/1፣ 706 መሠረት ለአንድ የተለየ ተጠቃሚ ጥቅም ሲባል የሚደረጉ የኢንሹራንስ ውሎች የዚህ አጠቃላይ የውል ሕግ መርህ ልዩነቶች /Exceptions/ ስለመሆናቸው ለአብነት ለመጥቀስ የሚቻል ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ሚያዝያ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. በተደረገ ውል የአሁኑ ተጠሪ 540,000 (አምስት መቶ አርባ ሺ) የአሜሪካን ዶላር ለካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. ለመክፈል ግዴታ የገባ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ የግዴታ ስምምነት ጥቂት ወራት በኋላ የአሁኑ ተጠሪ እራሱ ባዘጋጀው ሰነድ ቀደም ሲል የነበረበትን የገንዘብ ዕዳ መቀነሻ ይሆን ዘንድ ዋጋቸው የአሜሪካን ዶላር 462,338 የሆኑ የሻንሲ ቁጥራቸው የተጠቀሱትን አምስት አውቶቡሶች በአይነት ለአሁኑ አመልካች ለማስረከብ፣ ቀሪውንም የገንዘብ ዕዳ ለባለገንዘቡ በየወሩ በሚደረግ የክፍያ ስርዓት ለማጠናቀቅ ከባለገንዘቡ ጋር ስምምነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተደርሶ በውሉ መደረግ ጊዜ የውሉ ተካፋይ ያልነበረውን የአሁኑን አመልካች የውሉ ተጠቃሚ /Beneficiary/ አድርገው ሰይመውት የነበረ መሆኑ ታውቋል፡፡ በአሁኑ ተጠሪ እና በካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. መካከል ዕዳን በአይነት ለመቀነስ መግባባት ላይ ተደርሶ ያልነበረ ቢሆን ኖሮ የአሁኑ ተጠሪ እራሱ ባዘጋጀው ሰነድ በባዶ ሜዳ ተነስቶ የአሁኑን አመልካች የውሉ ተጠቃሚ አድርጎ ይጠቅሰው ነበር ብሎ ለማለትም ጭራሹኑ የሚቻል አልነበረም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ከሥር ባለገንዘቡ /ካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ./ ጋር ያደረገው ዋናው ውል /ሚያዝያ 21 ቀን 1991 ዓ.ም. የተደረገው/ በልዩ ሥርዓት እንዲደረግ ሕግ የሚያስገድድ በመሆኑ ከቀድሞው ውል ጋር በተዛመደ አኳኋን የተደረገው የሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም ተጨማሪ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1684 በተመለከተው አኳኋን በዝምታም ጭምር መቀበል የሚቻል የነበረ ቢሆንም ተዋዋይ ካቻማሊ ኤስ.ፒ. ኤ. በፊርማውም ጭምር አረጋግጦታል፡፡ በተጨማሪ የአሁኑ ተጠሪ ውሉ በተደረገ ማግሥት ማለትም ሐምሌ 1 ቀን 1991 ዓ.ም. ለእዳው መቀነሻ እንዲሆን ታስቦ ለአሁኑ አመልካች ለማስረከብ በተጨማሪ ውሉ ግዴታ የገባባቸው አውቶቡሶች ከማናቸውም ዕዳ ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጫ መስጠቱን ይህ ችሎት ከሥር መዝገቡ ጭምር ተረድቷል፡፡ ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት አውቶቡሶችን ለአሁኑ አመልካች ባለማስረከቡ ተዋዋይ /ካቻማሊ አስ. ፒ. ኤ./ በተከታታይ ጊዜያት ግዴታውን እንዲወጣ አሳስቦታል፡፡ ግዴታውንም የማይወጣም ከሆነ የሕግ እርምጃ ለመውሰድ የሚገደድ መሆኑን ጭምር ሲገልጽ ቆይቷል፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ የተጠሪ ጠበቃ እንደሚለው ሳይሆን የሕጉን አግባብ የተከተለ አካሄድ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 1958/2/ ያስገነዝበናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካችም ቢሆን በጠበቃው አማካኝነት ተጠሪ አውቶቡሶችን እንዲያስረክበው ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ መቆየቱን ከጉዳዩ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ሁሉ ሁኔታ በአንድነት ተደምሮ ሲታይ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. የተፈረመው ሰነድ ተጠሪ እንደሚለው አዲስ የውል ሐሣብ የቀረበበት ደብዳቤ

ሳይሆን የሕጉን ሥርዓት የተከተለና የሁሉም ወገኖች ማለትም የተዋዋዩ /የካቻማሌ አስ.ፒ.ኤ./ የተስፋ ሰጭው /የአሁኑ ተጠሪ/ እና የተጠቃሚው /የአመልካች/ ይሁንታ የነበረበት ተጨማሪ ውል መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

የሥር ፍ/ቤት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1734 መሠረት ከዋናው ውል መደረግና ከዚያ በኋላ የተዋዋይ ወገኖች የሐሣብ አንድነት ምን እንደነበረ ከፍ ብለን በገለጽነው አኳኋን መርምሮ ውሣኔ ላይ መድረስ ሲገባው ዋናው ውል ራሱ ልዩ የፎርም ስርዓት እንዲከተል ሕጉ በአስገዳጅነት የጠየቀው መስፈርት ሳይኖር ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ዋናውን ውል ተክትሎ ተዘጋጀ የተባለው ሠነድ የአፃፃፍ ስልቱ ከውል ይልቅ የደብዳቤ ቅርጽ ያለው ነው፣ ፊርማውም ቢሆን በካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. ሊሰፍር የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል በሚል በሕግ ያልተደገፈ ግምታዊ /Speculation/ እሳቤ ላይ ደርሶ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. በግራ ቀኙ የተፈረመው ሰነድ ደብዳቤ እንጂ ተጨማሪ ውል አይደለም ብሎ ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመጨረሻ የውሉ ተጠቃሚ የሆነው የአሁኑ አመልካች በካቻማሌ ኤስ. ፒ. ኤ. እና በአሁኑ ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረውን የውል ስምምነት የተቀበለው በመሆኑ በተስፋ ሰጭው ማለትም በአሁኑ ተጠሪ ላይ ውሉ የሚያስገኛቸውን መብቶች በማይመለስ አኳኋን ይዞ እንደሚቆይ እና ተስፋ ሰጭው በተዋዋዩ ማለትም በካቻማሌ ኤስ. ፒ. ኤ. ላይ ሊኖረው የሚችለውን የግል የሆኑትን መከራከሪያዎች ሰበብ በማድረግ በተጠቃሚው ላይ መቃወሚያ ሊያደርግ የማይችል ሰለመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1961 ያስገነዝባል፡፡ አጠቃላይ የሕጉ አፈፃፀም ይህ ሆኖ ሳለ የአሁኑ ተጠሪ ከግዴታው ጋር ጭራሽ ባልተገናኘ ሁኔታ ካቻማሊ ኤስ. ፒ. ኤ. ውክልናዬን ስለሰረዘ ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. የተደረገውን ስምምነት ሰርዣለሁ ብሎ ማለቱ ከተጠያቂነት አያድነውም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- አቶ ትዕግሥቱ ብዛ ቀርቧል

ተጠሪ፡- አቶ ይሃ ይብሬ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 17 ቀን 1997 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ሲሆን የጉዳዩ መነሻ አመልካች ጥቅምት 14 ቀን 1989 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ውልና ለውሉ ማረጋገጫና ማስፈፀሚያነት በዚሁ ቀን በቁጥር ኢዲ 657900 የሆነ ቼክ ብር 90,000 (ዘጠና ሺህ) የካቲት 1 ቀን 1989 ዓ.ም የሚከፈል ለተጠሪ ከሰጡ በኋላ ገንዘቡ እንዳይከፈል አግደውብኛል በማለት ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በቀረበው ክስ መሠረት በቼኩ የተመለከተውን ገንዘብ የሥር ተከሣሽ (አመልካች) እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ አፀናው፡፡

ለሰበር የቀረበው አቤቱታ አመልካች ቼኩን የሰጠው ተገዶ ያለፍቃዱና ያለፍላጐት መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የውል ህጐችን መሠረታዊ መርሆዎች በግልጽ ተጓድለው እያሉ የሥር ፍ/ቤት የቀረበውን ሠነድ ሕጋዊ እንዳልሆነ እና ውሉ ጉድለት እንደሌለበት አድርጐ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለው በመሆኑ እንዲሻርለት ጠይቋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ሰኔ 30 ቀን 1991 ዓ.ም. በተጠሪውና በካቻማሌ ኤስ. ፒ. ኤ. መካከል የአሁኑን አመልካች ተጠቃሚ በማድረግ የተፈረመው ሰነድ የዕዳ መክፈያ ተጨማሪ ስምምነት ነው ብለናል፣
2. ተጠሪ ለአሁኑ አመልካች ለማስረከብ ግዴታ የገባውን የሻንሲ ቁጥራቸው የተመለከቱትን አምስት አውቶቡሶች ለአመልካች ያስረክብ፣
3. ተጠሪ አውቶቡሶቹን ማስረከብ ካልቻለ ጠቅላላ ዋጋቸው 452,338 /አራት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሣ ስምንት/ የአሜሪካን ዶላር ወይም በአፈፃፀም ወቅት በሚኖረው የምንዛሬ ተመን መሠረት ዋጋው በብር ተሰልቶ ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚኖረው ሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል፣
4. አመልካች ወጭና ኪሣራ የማቅረብ መብቱ ተጠብቋል፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ሰበር ችሎትም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ይህንኑ ቅሬታ ለማጣራት ተጠሪ እንዲቀርብ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪው ሊቀርብ ባለመቻሉ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ሰኔ 7 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት አሟል፡፡

በዚሁ ሁኔታ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡ ከቀረበው አቤቱታና ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ አንፃር አመልካች ቼኩን የፈረምኩት ተገድጄ ነው በማለት ያቀረበው የሕግ ክርክር ውሉን ፈራሽ ያደርገዋል ወይስ አያደርገውም የሚለውን እንደሚከተለው ከውል ሕጐች መሠረታዊ መርህ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

በፍሬ ነገር ክርክር ደረጃ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንደተብራራው አመልካች ለተጠሪ የብር 90,000 (ዘጠና ሺህ) ተከፋይ ቼክ ጥቅምት 14 ቀን 1989 ዓ.ም መስጠቱን አልካደም፡፡ ሆኖም በቼኩ ክፍያ አለመፈፀም ያቀረበው መቃወሚያ ቼኩና ውሉ የተፃፈው ተጠሪ በወረዳ 5 ፖሊስ ጣቢያ አሳስሮት በእሥር ላይ ሆኖ ተገዶ የፈረመው ስለሆነ እና በዚሁ ወንጀል የፖሊስ ጣቢያው አዛዥና መርማሪ ፖሊስ በወንጀል ተከሰው በዐቃቤ ህግ ክስ የተመሠረተባቸው መሆኑን በመግለጽ ለዚህም የሰውና የሰነድ መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ በቼኩ የተመለከተውን ገንዘብ ለመክፈል እንደማይገደድ ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ይህንኑ ጉዳይ ለማጣራት አመልካች ያቀረባቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ቼኩን ለማስፈረም የኃይል ሥራ ተፈጽሟል ለማለት አይቻልም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡

በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ውስጥ እንደተመለከተው የማስገደድ ተግባር በአመልካች ላይ ስለመፈፀሙ የቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ እንዲሁም በወቅቱ የፖሊስ ጣቢያው አዛዥ በነበረው ሻ/ል ክብረት ከበደ ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 07009 ጥቅምት 11 ቀን 1998 ዓ.ም በልዩ ወ/መ/ሕግ አዋጅ ቁጥር 214/74 አንቀጽ 23-1ሀ መሠረት የተሰጠው

የጥፋተኛነት ውሣኔ ሲታይ በወቅቱ አመልካች ውሉን የተዋዋለው በአስገዳጅ ሁኔታ ሥር ሆኖ እንደነበር የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

ይህ ሁኔታ ከሕጉ አንፃር ምን ውጤት ሊኖረው ይችላል የሚለውን ለማጤን ከውል መሠረታዊ መርህ ጋር መጤን አለበት፡፡ ቼክ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ መሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር 715 የተመለከተ ነው፡፡ በእነዚህ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች የሚፈጠሩባቸውና የሚረጋገጡባቸው ናቸው፡፡ የሰነዱ አውጪ ግዴታ የሚገባበት ሲሆን የሰነዱ አምጪ /ያገር/ የመብት ወይም ጥቅም ማረጋገጫ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ይህንን ሁኔታ ለመፍጠር እንደማንኛውም ውሎች የውል ህግ መሠረታዊ ድንጋጌዎች መሟላት እንዳለባቸው የሚያከራክር አይደለም ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች መሠረት በባህሪያቸውና በዓላማቸው ልዩ ቢሆንም ተዋዋይ ወገኖች በዚህ ሰነድ መብትና ግዴታ ለመፍጠር የውል ሕግ አጠቃላይ መርሆዎችን አሟልተውና አክብረው መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከእነዚህ መሠረታዊ መርሆዎች ውስጥ አንደኛው ውሉን ለመፈፀም (ለመዋዋል) የተዋዋይ ወገኖች ፈቃደኛነትና ነፃነት መኖር አስፈላጊነት ነው፡፡ ውል በተዋዋይ ወገኖች ሙሉ ፈቃደኛነት ላይ ካልተመሠረተ በሕግ ፊት የፀና ሊሆን አይችልም በመሆኑም የውል መፈረስ ምክንያት ከሚሆኑት መሠረታዊ ነገሮች አንዱ በውል አመሠራረት ሂደት ውስጥ በአንደኛው ወገን የሚፈፀም የኃይል ወይም የማስገደድ ተግባር ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ መርህ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1679 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህንን መሠረታዊ መርህ በዝርዝር የሚያመለክተው የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1706 እና ተከታዩ የማስገደድ ተግባሩ በማን ተፈፀመ? እንዴትስ ተፈፀመ? በማን ላይ ተፈፀመ የሚሉትን ሁኔታዎች በዝርዝር አመልክቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ላይ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው አመልካች ቼኩን የፈረመው በፖሊስ ጣቢያ ታስሮ በፖሊስ ጣቢያው አዛዥ አስገዳጅነት እንደሆነ በቀረቡት ማስረጃዎች በሥር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ አይነት አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የተደረገው ውል ፈቃደኛነትና የመዋዋል ነፃነት ጉድለት ያለበት መሆኑን መገንዘብ የሚያዳግት አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ ደግሞ ውሉን ስለመፈፀም መቃወሚያ አድርጐ ማቅረብ ስለመቻሉ በንግድ ሕግ ቁጥር 841 ተመልክቷል፡፡

በዚህ የንግድ ሕግ ቁጥር 841 ድንጋጌ መሠረት የቼኩ አውጪ በአምጪው ላይ መቃወሚያ ሊያደርግ የሚችለው ቼኩን ያገኘው ቅን ልቦና በጐደለው ሁኔታ ወይም ቼኩን ሲያገኝ ከባድ ጥፋት ያደረገ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት አሁን የቀረበውን የቼክ ክፍያ ጥያቄ በተመለከተ ተጠሪው ቼኩን ከአመልካች ያገኘው ቅን ልቦና በጐደለው ሁኔታ ከመሆንም አልፎ በማስገደድ ተግባር በመሆኑ ከባድ ጥፋት መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡

ስለዚህ አንድ የኃይል ሥራ ወይም የማስገደድ ተግባር አንድ ተዋዋይ ወገን ሳይወድና ሳይፈቅድ ከፍላጐቱ ውጪ የውል ግዴታ እንዲገባ ለማስገደድ በቃላት ወይም በድርጊት የሚፈፀም ሕገ ወጥ ማስፈራት ወይም ዛቻ ወይም በአካል ላይ የሚፈፀም አድራጐት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በአመልካች ላይ የተፈፀመው የማስገደድ ተግባር እሥር እና ዛቻ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጦ እያለ የሥር ፍ/ቤት በምን ተገደደ በዱላ ወይስ በሌላ በማለት ጭብጥ በመያዝ የመገደድ ተግባር አልተፈፀመበትም በማለት የወሰደው አቋምና የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ አተረጓጐም ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ መሠረታዊ የሆነውን የፈቃደኛነትና የመዋዋል ነፃነትን የሚጋፋ ተግባር ተፈጽሞ እያለ ጉድለት የለበትም ማለት ሕግ ለተዋዋይ ወገኖች የመዋዋል ነፃነት ያደረገውን ጥበቃ በእጅጉ የሚያላላ ውሣኔ ሆኖ በመገኘቱ የሥር ተከሣሽ የአሁን አመልካች ያለፈቃዱ እና ፍላጐቱ ተገዶ በፈረመው ቼክ ክፍያ ሊገደድ አይገባም ብለናል፡፡ ስለዚህ የአመልካች መቃወሚያ በንግድ ሕጉ ቁጥር 841 እና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1679 መሠረት ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05017 ግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍቤት በመዝገብ ቁጥር 32762 መጋቢት 16 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለአመልካች በክሱ ክርክር ምክንያት ለደረሰበት ወጪና ኪሣራ በቁጥጥ ብር ሁለት ሺህ (2000) እንዲከፍለው ብለናል፡፡

መዝገቡ ዘግተን ወደመዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 20979

የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን-ነ/ፈጅ ጋሻው በርጋ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- የወ/ሮ ግምጃ በሐቲ ወራሽ ወ/ሮ ሒሩት ቢያድግልኝ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፣

ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤት አሻሽሎ ባቀረበው ክስ ለወ/ሮ ግምጃ በሐቲ ሰኔ 2 ቀን 1992 ዓ.ም በተፈረመ የቴሌፎን ደንበኛነት ውል ቁጥር 626382 የሆነ የስልክ መስመር ወራሻቸውና ወኪላቸው በሆነችው በአሁኗ ተጠሪ አማካኝነት አስገብቶ የነበረ መሆኑን ገልጾ፣ ከየካቲት ወር 1994 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ ወር 1994 ዓ.ም. ድረስ የሚፈለገውን የአገልግሎት ሂሣብ ብር 5023.36 ስላልከፈሉ የአሁኗ ተጠሪ ወራሽ በመሆኗ እንድትከፍል ጠይቋል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ የፍ/ሕ/ቁ 2023/ሀ/ በመጥቀስ የተከራከረች ሲሆን አመልካችም ክሱ በይርጋ ቀሪ እንደማይሆን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የተቀረለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በግንቦት 16 ቀን 1996 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ፣ የአሁኑ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ የተጠየቀው የስልክ አገልግሎት ሂሣብ የተጠሪ አውራሽ ከሞቱ በኋላ የቆጠረ ስለሆነ እንደ ውርስ ዕዳ የሚቆጠር አይደለም በማለት የቀረበውን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይኸው ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ይህ ችሎት መጋቢት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ቅሬታ መርምሮ መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ ከወሰነ በኋላ የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ አቀባብሏል፡፡

በበኩላችን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ የሟች ወራሽ መሆኗን አልካደችም፡፡ በአመልካች አማካኝነት የስልክ መስመሩ በገባ ጊዜ ወኪል ሆና በውሉ ለመገደድ የተስማማች መሆኗም ታውቋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአሁኗ ተጠሪ አውራሼ የምትላቸው ሰው በሞቱ ጊዜ የውሉን መቋረጥም ሆነ ውሉን ተከትሎ ከአውራሽዋ ሞት በኋላ በስልክ መስመሩ በሚጠየቅ ዕዳ ኃላፊ የማትሆን መሆኗን በመግለጽ ለአመልካች መ/ቤት አላሳወቀችም፡፡ የአሁኑ አመልካች ደግሞ በራሱ አነሳሽነት የተጠሪን አውራሽ ሞት የሚያውቅበት መንገድ የለም፡፡ በዚህ መሠረት አውራሽ የሆነ ሰው ከሞተም በኋላ ቢሆን የሚመጣን የስልክ ሂሣብ የመክፈሉ ግዴታ ውርሱን የተቀበለው ወራሽ ነኝ የሚለው ወገን መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት ዕዳው አውራሽ ከሞቱ በኋላ የቆጠረ የስልክ ሂሣብ ስለሆነ ተጠሪን አይመለከትም ብሎ ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሚያዚያ 16 ቀን 1996 ዓ.ም. በፍ/መ/ቁ. 11657 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሚያዝያ 26 ቀን 1997 ዓ.ም በመ/ቁ. 33089 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡

2. ተጠሪ ከየካቲት እስከ ሚያዝያ ወር 1994 ዓ.ም የሚፈለግባትን ሂሣብ ብር 5023.36 /አምስት ሺህ ሃያ ሦስት ከሰላሳ ስድስት/ ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ /9%/ ጋር ለአመልካች ትክፈል፡፡ የስልኩን ቀፎ ትመልስ ወይም ዋጋውን ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

238.70/ሁለት መቶ ሠላሳ ሰምንት ከሰባ/ ለአመልካች ትክፈል በማለት ተወስኗል፡፡

3. መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 21531

ጥር 30 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን እቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- ኢትዮ.ትራዲንግ የንግድ ስራ ማስፋፊያ-አቶ ብርሃኑ አስረስ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የውሃ ሃብት ሚኒስቴር - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡ ይህ ፍርድ የካቲት 29 ቀን 1999 ዓ.ም. ከተደረገው የቃል ክርክር በኋላ የፍርዱ ግልባጭ በዛሬው ቀን ተፈርሞ ወጭ ተደርጓል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ክርክር የጀመረው የአሁን አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪ ላይ በጥቅምት 20 ቀን 1995 ዓ.ም የተባፈ ክስ በመመስረታቸው ነው፡፡ የክሱም ይዘት በአጭሩ፣ ከሣሽ የተከሣሹ ደንበኛ ለሆነው በኢጣሊያ ለሚገኘው ጋዚና ትራዲንግ ለሚባለው የእቃዎች አቅራቢ ድርጅት የአገር ውስጥ ወኪል ሲሆን፣ ተከሣሹ ከዚሁ አቅራቢ ድርጅት በግዢ ወደ አገር ውስጥ ላስገባቸው ዕቃዎች የክሊራንስ ሰነዶችን በወቅቱ ለከሣሹ ባለማቅረቡ እነዚሁ አቃዎች በጅቡቲ ወደብ አላግባብ ለ15 ቀናት በመቆየታቸው ከሣሹ ለወደብ ኪራይና ለደመራኘር ብር 14,558.17 (አሥራ አራት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ስምንት ከአስራ ሰባት) ክፍያ ፈጽሜ ለተከሣሽ ያስረከብኩ በመሆኑ ተከሣሹ ይህንን ገንዘብ ሊተካልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡ ተከሣሹ መ/ቤት ለክሱ በሰጠው መልስ፣ ከሻጩ ጋራ ባደረግነው ውል መሠረት የሚጠበቅብኝን ክፍያ ሙሉ በሙሉ ፈጽሜያለሁ፣ በውሉ አንቀጽ 6

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት የኢንሹራንስ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የከሣሹ ግዴታ እንጂ የተከሣሽ አይደለም፣ በሌላ በኩል ከሣሽ ለዚህ ክፍያ የተዳረገው ተከሣሹ ሠነዶቹን በጊዜ ባለማቅረቡ ለመሆኑም በተጨባጭ ማስረጃ አላረጋገጠም ሲል ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሣኔ፣ በውሉ አንቀጽ 6 መሠረት የኢንሹራንስ የምስክር ወረቀት ለገዢው ወይም ለባንክ የማቅረብ ኃላፊነት የአቅራቢው ማለትም የከሣሽ ነው፣ ከሣሽ ለሰጠው አገልግሎት በውሉ መሠረት ተከፍሎታል፣ በውሉ አንቀጽ 17 መሠረት የዋጋ ለውጥ ካልተደረገ በቀር ለከሣሽ የሚሠጠው ዋጋ በጨረታ ያስቀመጠውን ያህል ብቻ ነው፣ በመሆኑም ከሣሽ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ግራ ቀኙ በጥር 4 ቀን 1992 ዓ.ም. ካደረጉት ውል መንፈስ ውጪ ነው ሲል የከሣሽን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ከሣሽ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26105 ኀዳር 6 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ከ/ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም ሲል ይግባኙን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት በሰኔ 22 ቀን 1997 ዓ.ም. ሠርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታም የቀረበው አመልካች መስከረም 11 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለታቸው ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው አንኳር ነጥቦች ሲጠቃለሉ አመልካቹ በውልም ሆነ በሕግ ባልተጣለብኝ ግዴታ ለወደብ ኪራይና ለዳመራኘር ክፍያ የተዳረኩት የኢንሹራንስ ሰነዶቹ በጊዜው ባለመቅረባቸው ብቻ ሣይሆን ተጠሪው እቃውን ከወደብ ለማንሣት አስፈላጊ የሆኑትን የማጓጓዣ ሰነዶችን አና ገንዘብ ሚኒስትር እቃዎቹ ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ እንደገቡ ለተጠሪው መ/ቤት የሚሰጠውን ደብዳቤ ተጠሪው በቸልተኝነት በጊዜው ሊያስረክበኝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው፤ ተጠሪው ማለትም የዕቃው ባለቤትና ገዢው በን/ሕ/ቁ 48 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2221/1/ እና /2/ የተጣለበትን ግዴታ በአግባቡ አልተወጣም፤ በሌላ በኩል የተጠሪው

ኃላፊነት ሊታይ የሚገባው ከውሉ አንፃር ብቻ ሣይሆን ከውል ውጪ የሚመነጩ ኃላፊነቶችንም ከሚመለከቱ ሕጎች አንፃር ነው፤ በመሆኑም እቃዎቹ በወደብ የዘገዩት በተጠሪው ጥፋት በመሆኑ ገንዘቡን ተጠሪ ሊተካ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ይህም የሰበር ሠሚ ችሎት የሰበር አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በማስቀረብ በግራ ቀኙ መካከል የካቲት 28 ቀን 1998 ዓ.ም. የቃል ክርክር አካሂዷል፡፡ በቃል ክርክሩ ወቅት ተጠሪ ቀርበው ያሠሟቸው መከራከሪያ ነጥቦች በአጭሩ ሲቀመጡ፡- በመጀመሪያ ደረጃ አመልካቹ የሻጩ የጋዚና ትራዲንግ ወኪል እንጂ የተጠሪ ወኪል አይደለም፤ አመልካቹ በውሉ መሠረት የኢንሹራንስ ሠነዶችን በጊዜው ባለማቅረባቸው ለተዳረጉት የወደብ ኪራይና ደመራኘር ክፍያ ተጠሪ ተጠያቂ ሊሆን አይገባም፤ በተጨማሪም አመልካች እቃዎቹ በወደብ ለ15 ቀናት ዘገዩ ይበል እንጂ ከመቼ እስከመቼ እንደዘገዩ በመረጃ አላስደገፈም፤ በመሆኑም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህም የሰበር ሰሚ ችሎት የመዝገቡንና የግራ ቀኙን ክርክር በጥሞና መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም በዚህ ጉዳይ እልባት የሚሻው ጭብጥ “አመልካች በውሉ መሠረት የኢንሹራንስ ሠነድ አላቀረበም በሚል አመልካቹ ለወደብ ኪራይና ለደመራኘር የከፈለውን ክፍያ ተጠሪ ሊተካ አይገባም ተብሎ መወሰኑ አግባብ ነው ወይ?” የሚለው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንደሚታወቀው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው የውሉን አንቀጽ 6 ሲሆን ይህም አንቀጽ የኢንሹራንስ ሠነዶቹን ማቅረብ የአመልካቹ ግዴታ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በመሠረቱ የኢንሹራንስ ዋነኛ ጠቀሜታ ኢንሹራንስ የተገባለት ዕቃ አደጋ ቢደርስበት በአደጋው ምክንያት የደረሰው ጉዳት ሣይካስ እንዳይቀር መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ከመዝገቡና ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት የሚቻለው ደግሞ እቃዎቹ ጅቡቲ ወደብ በሠላም መድረሳቸውን፣ አልፎ ተርፎም እቃዎቹ በወደብ ለ15 ቀናት ከዘገዩም በኋላ ቢሆን የኢንሹራንስ ሠነድ ባልቀረበበት ሁኔታ እቃዎቹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተጠሪው እጅ በሠላም መድረሳቸውን ነው። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው እቃዎቹን ከወደብ ለማንሣት የኢንሹራንስ ሠነዱ መቅረብ አስፈላጊ እንዳልነበረ ነው። በመሆኑም ተጠሪው እቃዎቹ በወደብ የዘገዩት አመልካቹ በውሉ መሠረት የኢንሹራንስ ሠነድ ባለማቅረቡ ነው ሲል ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የሌለው ነው። ከዚህ ይልቅ አመልካቹ ለክፍያ የተዳረጉት እቃዎቹን ከወደብ ለማንሣት አስፈላጊ የሆኑትን የማጓጓዣ ሠነዶች በተለይም የገንዘብ ሚኒስቴር ከቀረጥ ነፃ ብሎ ለተጠሪው የሚሠጠው ደብዳቤ ተጠሪው መ/ቤት ለአመልካቹ በጊዜው ለማቅረብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መሆኑ ታውቋል። በአጠቃላይ አመልካቹ ለተጠሪው ጥቅም በሌለበት ግዴታ የከፈለውን የወደብ ኪራይና የደመራዥር ክፍያ ተጠሪው ሊተካ አይገባም መባሉ አላግባብ መሆኑን ይህ ፍ/ቤት ተገንዝቧል።

ው ሣ ኔ

- ተጠሪ ለአመልካች ብር 14,558.17 /አስራ አራት ሺህ አምስት መቶ ሃምሣ ስምንት ከአስራ ሰባት/ ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ይክፈል፣
- አመልካች ለዳኝነቱ የከፈለው ገንዘብ ተጠሪ ይተካለት፤
- የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፤
- መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፤

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 23609

ታህሣሥ 15ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን እቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፊጅ ዘውዱ አሊ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አሰበወርቅ ዘገየ - አልቀረቡም

ፍ ር ድ

በሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው።

ተጠሪ ለሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች መ/ቤት የሥራ ውላቸውን ያላግባብ ስላቋረጠባቸው ውዝፍ ደሞዝ የተጠራቀመ የዓመት እረፍት፣የቦነስ ክፍያ፣ አበል፣ የእቃ ማጓጓዣ ፣የኤርፖርት ታክስ፣የካሣ ክፍያ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል።

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ከስራ የተሰናበቱት ያለአግባብ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ፣ የእረፍት ጊዜ በገንዘብ ተለውጦ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና የአገልግሎት ካሣ የ6 ወር ደመወዛቸውን እንዲከፈላቸው ወስኗል። የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ አጽንቷል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ይህ ችሎትም የአመት እረፍትና የአገልግሎት ካሣ እንዲከፈላቸው የተሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል።

ተጠሪም ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል።

አመልካች በሰበር አቤቱታው ውዝፍ ደሞዝ በተመለከተ ቀደም ሲል ከሰው ተወስኖላቸው የወሠዱ በመሆኑ በድጋሚ ሊከፈላቸው አይገባም፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የተመደቡበት የስራ ኃላፊነት ከፍተኛ እምነትን የሚጠይቅ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸው በድርጅቱ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ሊያደርሱ ስለሚችሉ በፍ/ሕ/ቁ. 2577 መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበቱ ችለዋል። ከስራ የተሰናበቱት በጥፋት ስለሆነ ካሣ ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል። ተጠሪም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ በአግባቡ ነው ሲሉ ዝርዝር መልስ ሰጥተዋል። ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል።

ተጠሪ ያለአግባብ ከሥራ ተሰናብቻለሁ በማለት ሊከፈላቸው የሚገባውን ክፍያ ዘርዝረው ክስ አቅርበዋል ከመዝገቡ እንደተረዳነውም አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ጥፋት ፈጽመዋል በሚል ቢሆንም ጥፋት መፈፀማቸውን እንዳላስረዳ የሥር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል ። ጥፋት መኖር አለመኖሩ ደግሞ የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ በዚህ ሠበር ችሎት በድጋሚ የሚታይ አይሆንም። በመሆኑም የተጠሪ የሥራ ውል ያለበቂ ምክንያት ከተቋረጠ ተጠሪ ሊያገኙ የሚገባቸው ክፍያዎች ምንድናቸው የሚለውን መመለከት ተገቢ ነው። በተለይ አመልካች ቅሬታ ያቀረበባቸው ክፍያዎች የተጠራቀመ ደመወዝ፣ የዓመት እረፍት፤ የማስጠንቀቂያና የካሣ ክፍያዎችን የሚመለከቱ በመሆናቸው እነዚህ ክፍያዎች ለተጠሪ ሊከፈሉ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ተመልክተናል። ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆናቸው የሣቸው ጉዳይ የሚታየው በፍትሐብሔር ሕጉ እንደመሆኑ የተያዘው ጉዳይ ስለሥራ ውል በፍ/ብ/ሕጉ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች አኳያ ተመርምሯል።

የካሣን ጥያቄ በተመለከተ ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ተጠሪ ጥፋት ፈጽመው ነው ቢልም ይህንን እንዳላስረዳ የሥር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል በመሆኑም የተጠሪ የሥራ ውል የተቋጠረው ከሕግ ውጪ መሆኑን ተገንዝበናል። አሠሪው ውሉን ቀሪ ለማድረግ በቂ ምክንያቶች የሌለው እንደሆነ ለሠራተኛው ተገቢ የሆነ ኪሣራ ለመክፍል እንደሚገደድ በፍ/ሕ/ቁ. 2573 ሥር ተመልክቷል። በመሆኑም

አመልካች ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በጥፋት ስለሆነ ካሣ ልከፍል አልገደድም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም።

የኪሣራውን ልክ በተመለከተ ግን ለሠራተኛው የሚከፈለው ባለፈው 3 ወር ከተቀበለው ደመወዝ ሊበልጥ እንደማይችል በፍ/ህ/ቁ. 2574(2) ሥር የተመለከተ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የ6 ወር ደመወዝ በካሣ መልክ እንዲከፈል መወሰናቸው ተገቢ አይደለም።

ሌላው የማስጠንቀቂያ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን አሠሪው ውሉን ቀሪ ለማድረግ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ መስጠት እንደሚገባው በፍ/ሕ/ቁ. 2570/2/ ሥር ተቀምጧል። የሥራ ውሉ ከአንድ አመት በላይ ቆይቶ ከሆነ ማስጠንቀቂያው ቢያንስ ከ2 ወር አስቀድሞ ሊሰጠው ይገባል (የፍ/ህ/ቁ.257(2) ይመለከታል) ። አመልካች ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ አይገባም የሚለው ስራው ልዩ ችሎታንና ከፍተኛ እምነት የሚጠይቅ ነው በማለት የፍ/ሕ/ቁ. 2577 ን መሠረት አድርጎ ሲሆን የተጠሪ የሥራ አስኪያጅነት ሥራ ግን በዚህ አንቀጽ የሚሸፈን ባለመሆኑ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም።

የተጠራቀመ ደሞዝን በተመለከተ አመልካች በሰበር አቤቱታው ለተጠሪ በባንክ ሂሣባቸው ደመወዛቸውን ገቢ ሲያደርግ ቆይቶ ደመወዝ ለተጠሪ ሊከፈል እንደማይገባ ሲረዳ ከሂሣባቸው ወጪ አድርጎ በመውሰዱ አመልካቹ የወሰደውን ገንዘብ እንዲመልስ ተጠሪ ክስ አቅርበው ስላስወሰኑበት በአፈፃፀም ገንዘቡን የተቀበሉ በመሆኑ በድጋሚ ደመወዝ ሊከፈላቸው እንደማይገባ ገልጿል። ይህ ችሎቱም መዝገቡን እንደመረመረው ተጠሪው አመልካች ወደ ሂሣባቸው ገቢ አድርጎ መልሶ የወሰደውን ገንዘብ እንዲመልስ በሌላ መዝገብ ክስ መስርተው አስወስነውበት ገንዘቡን የተቀበሉ መሆኑን፣ ይህም ገንዘብ የተጠሪ ደመወዝ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል። በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ደመወዝ እንዲመልስ በሌላ መዝገብ ተወስኖበት ከከፈለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኋላ ተጠሪ በድጋሚ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈላቸው የሚገባበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

የመጨረሻው ነጥብ የዓመት እረፍትን የሚመለከት ነው ተጠሪ የሚከራከሩት የዓመት እረፍት ካልተወሰደ ተጠራቅሞ ሠራተኛው በሚመቸው ጊዜ እንደሚወስደው ካልወሰደ ግን በገንዘብ ተቀይሮ እንደሚከፈለው እና ከ90 ቀናት በላይ እረፍቱ አይተላለፍም የሚለው ክርክር የሕግ ድጋፍ እንደሌለው ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ በወቅቱ የነበረው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እረፍት ከ90 ቀናት በላይ ሊተላለፍ እንደማይችል ይገልፃል፣ ያም ቢሆን ተጠሪ እረፍታቸውን ተጠቅመውበታል፣ አላቸው ቢባል እንኳን በፍ/ሕ/ቁ. 2562 (3) መሠረት ከ20 ቀናት በላይ ያለው እረፍት ተቀባይነት የለውም በማለት ይከራከራል የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ አልቀረበም፣ ቢቀርብም በፍ/ሕጉ ላይ ገደብ የማያስቀምጥ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም በሚል ነው፡፡ ነገር ግን የፍ/ሕጉ የዓመት እረፍት ላልተወሰነ ጊዜ እንደሚተላለፍ ያስቀመጠው ነገር ስለሌለ መመሪያው በፍ/ሕጉ ላይ ገደብ አስቀምጧል ለማለት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የብሔራዊ ባንክ መመሪያ እረፍት ከ90 ቀናት በላይ ሊተላለፍ አይችልም በማለት ያስቀመጠው ገደብ የለም በማለት በግልጽ ያቀረቡት የተቃውሞ ክርክር የለም፡፡ በፍ/ሕጉ ላይ ያልተመለከቱ ነገሮችን ደግሞ የመ/ቤቱ አስተዳደር መወሰኑ ሕገ - ወጥ ነው ለማለት አያስችልም፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ተጠሪ እረፍታቸውን በሙሉ ተጠቅመዋል ይባል እንጂ የሥር ፍ/ቤት የተጠሪን ማህደር አስቀረቦ ተጠሪ ያልወሠዱት እረፍት መኖሩን ስላረጋገጠ በዚህ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በመሆኑም ተጠሪ የተጠራቀመ የ90 ቀን ብቻ ሊሰጣቸው ሲገባ የሥር ፍ/ቤት 522 ቀናት እረፍት እንዲያገኙ መወሰኑ ስህተት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1759/87 ሐምሌ 30 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 4624 ታህሣሥ 7 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

2/ ለተጠሪ የተጠራቀመ ደመወዝ እንዲከፈል የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

3/ አመልካች ለተጠሪ የ3 ወር ደመወዝ ካሣ ክፍያ እንዲከፍላቸው ተወስኗል፡

4/ አመልካች ለተጠሪ የ2 ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ይክፈላቸው፡፡

5/ አመልካች ለተጠሪ የ90 ቀን የዓመት እረፍት በገንዘብ ቀይሮ ይክፈላቸው፡፡

6/ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 30298

ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ የሺወንድም አቡሐይ

ተጠሪ፡- አቶ አየነው ማለደ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በተጠሪ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የመጥፋት ውሣኔ ሲሰረዝ አመልካች ለ3ኛ ወገን በሽያጭ አስተላልፈውታል የተባለውን ቤት ለተጠሪ ሊመለሱ ይገባል የሚሉት በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ሲሉ አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ ለሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በአመልካች ጠያቂነት ቀደም ሲል በወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ የተሰጠው የመጥፋት ውሣኔ የተነሣ መሆኑን ገልፀው የግል ንብረቴ የሆነውና የዋጋ ግምቱም ብር 50.000 (ሃምሣ ሺህ) የሆነው ቤት አመልካች ለ3ኛ ወገን በሽያጭ ያስተላለፈው ስለሆነ እንዲመለስ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ቀርበው በሰጡት መልስ ተጠሪ ከእናቴ ጋር ጋብቻ መሥርቶ እያለ እናቴን ጥሎ በመጥፋቱ በሽተኛ ስለነበረች እሷን ለማሣከም ገንዘብ በማስፈለጉ ቤቱ የተሸጠ ሲሆን የሽያጩ ዋጋም በአሣሽ

እንደተጠቀሰው ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ/ ሣይሆን ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ ነው በማለት ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ከቀረበው ማስረጃ አኳያ መርምሮ ተከሣሽ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት የከሣሽና የእናቱ የጋራ ሀብት ነው የሚል ክርክር ቢያቀርብም ከጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የቀረበው የሰነድ ማስረጃና እንደዚሁም በከሣሽ በኩል የቀረቡት ምስክሮች በሰጡት ቃል ከሣሽ ከተከሣሽ እናት ጋር ጋብቻ ከመመሥረታቸው በፊት የሠሩት ቤት እንደሆነ ስለሚያረጋግጥ ተከሣሽ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ ጠፍቷል የተባለ ሰው ከመጣ ጠፍቷል መባሉ ተሠርዞ ወደ ሌላ ሰው ተላለፎ የሚገኝ ንብረትም ሊመለስለት እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171(1) ላይ የተመለከተ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ለከሣሽ ሊመለስ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ተጠሪ ጠፍተዋል በማለት የመጥፋት ውሣኔ ካገኙ በኋላ ወራሽነታቸውን አረጋግጠው የተጠሪን ቤት ለ3ኛ ወገን መሸጣቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ሲመለሱ ሊመለስላቸው የሚገባው የቤቱ ሽያጭ ዋጋ ወይንስ ቤቱ እራሱ የሚለው ነጥብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171 አኳያ አቤቱታው ለሰበር ቀረቦ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠሪ ላይ የመጥፋት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሽያጭ ወደ 3ኛ ወገን የተላለፈ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

የመጥፋት ውሣኔን ውጤት ቀሪ ከሚያደርጉ ምክንያቶች /effects of termination of absence/ አንዱ ጠፍቷል የተባለው ሰው መመለስ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171 ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረትም ጠፋ የተባለው ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹን በሚገኙበት አካኋን መልሶ የመረከብ እንደዚሁም የተሸጡትን ንብረቶች ዋጋ የማግኘት መብት እንዳለው በግልጽ ተመልክቷል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው ቤት መሸጡ ከተረጋገጠ ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ አኳያ ተጠሪ ሊረከቡ የሚገባቸው የተሸጠውን ቤት ሣይሆን የሽያጩን ዋጋ ነው ማለት ነው፡፡ የሽያጩን ዋጋ በተመለከተም አመልካች በብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ መሸጡን ሲገልፁ ተጠሪ ዋጋው ብር 50.000 (ሃምሣ ሺህ) እንደሆነ ከመግለጽ በስተቀር በዚህ ዋጋ የተሸጠ መሆኑን ማስረጃ አቅርበው አልተከራከሩም፡፡

ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች በሽያጭ የተላለፈው ቤት ለተጠሪ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 15240 በጥር 28 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ለአመልካች ይገባል ማለቱ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11660 በመጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም ይግባኙን ባለመቀበል የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሰለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በብር 25.000 (ሃያ አምስት ሺህ) ስለመሸጡ የተረጋገጠ ስለሆነ ይህንኑ የሽያጭ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመያዣ ውል

የሠ/መ/ቁ. 16218

መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ አስያድ ጋዲሳ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ አስካለ ሁንዴ - አልቀረቡም፡፡

2. አቶ አንቻሎ ቡራ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ጎዳር 8 ቀን 1991 ዓ.ም. በተፈረመ የገንዘብ ብድር ውል ተጠሪዎች ከአመልካች ብር 140,000 (መቶ አርባ ሺህ) ተበድረናል፡፡ ገንዘቡም ተከፍሎ የሚጠናቀቀው ጥር 22 ቀን 1992 ዓ.ም. የነበረ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ጥር 26 ቀን 1991 ዓ.ም. በተፈረመ የገንዘብ ብድር ውል ብር 90 ሺህ ተበድረናል፡፡ ሁለተኛውም የብድር ገንዘብ ተከፍሎ የሚጠናቀቀው የካቲት 26 ቀን 1995 ዓ.ም. ነበር፡፡ ሆኖም የብድሩ የመጨረሻ መክፈያ ጊዜ ሳይደርስ በሕገወጥ መንገድ የመያዣ ንብረቶቹን የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠን በዋስትና ያልተያዘውንም ንብረታችንን ጭምር በኃይል አስፈራርቶ ወስዶብናል፡፡ ስለዚህ ከሱቅ፣ ከእንጨትና ቁርስ ቤት የተቋረጠ ገቢ ብር 210,800.00 (ሁለት መቶ አሥር ሺህ ስምንት መቶ) ንብረቶቹ በሕገወጥ መንገድ በመወረሳቸው የደረሰብን ጉዳት ብር 146,890.00 (መቶ አርባ ስድስት ሺህ ስምነት መቶ ዘጠና) የተወሰደብን ቤት ቢሸጥ ብር 310,000.00 (ሦስት መቶ አስር ሺህ) ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚፈለግብን ዕዳ ከተቀነሰ በኋላ ብር 134,502.43 (መቶ ሠላሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ከአርባ ሦስት) ሊከፍለን ይገባል በማለት በአጠቃላይ ሌሎች ወጭዎችን ጨምረው ብር 492,192.43 (አራት መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ከአርባ ሦስት) ተከሣሽ እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሣሾች ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ ደርሶም በሰጠው መልስ ባንኩ ንብረቱን የተቆጣጠረው በአዋጁ ቁጥር 97/90 መሠረት ሕጋዊ ሥርዓትን ተከትሎ ስለሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 33/2/ አኳያ ከሳሾች ክስ ባቀረቡበት ነገር መብትና ጥቅም ስለሌላቸው መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድ የሰጠው መልስ ተጠቃሎ ሲታይ የብድሩ መክፈያ ጊዜ ሳይጠናቀቅ ዕርምጃ ተወስዷል በማለት ከሣሾች ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2488/1/ መሠረት ውዝፍ ዕዳው ከጠቅላላ ዕዳው 1/10 ከሆነ የመጨረሻ መክፈያ ጊዜውን ሳንጠብቅ ዕርምጃ መውሰድ እንችላለን፡፡ ከዚህም ሌላ ባንኩ የንብረት ርክክብ ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የሚመለከታቸው ተወካዮች በተገኙበት ነው በማለት ተከራክሮ ከሳሾች በጠየቁት የካሣ መጠንም ላይ ግምቱ የተጋነነ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከሣሽ በኩል የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ በጥር 26 ቀን 1991 ዓ.ም. በግራ ቀኙ መካከል በተፈረመው የብድር ውል ከሳሾች የብድሩን ገንዘብ አጠናቀው መክፈል የሚገባቸው በየካቲት 26 ቀን 1995 ዓ.ም. ሆኖ ሳለ እንደዚሁም ቀደም ብሎ በህዳር 8 ቀን 1991 ዓ.ም. ባደረጉት የብድር ውልም በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 መሠረት ተከሳሽ የ1 ወር ማስጠንቀቂያ ለከሳሾች መስጠት ሲገባው ይህን ሳያደርግ በመያዣ ያልያዘውንም የከሳሾችን ንብረት ጭምር ማሸጉ

አግባብነት የሌለው በመሆኑ ኃላፊነት አለበት ካለ በኋላ በመያዣ ከተያዘው ቤት ጋር የታሸጉት የከሳሾች ንብረት የዋጋ ግምታቸው እንዲገለጽለት ለሚመለከተው መ/ቤት ትዕዛዝ ሠጥቶ ብር 183,130.06 (አንድ መቶ ሰማኒያ ሦስት ሺህ አንድ መቶ ሠላሳ ከ ስድስት) እንደሆነ የተገለጸለት ቢሆንም በዚህ ረገድ ከሳሾች የጠየቁት ክፍያ ብር 146,890 (መቶ አርባ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና) ስለሆነ ይሄው የንብረት ዋጋ ግምት ሊከፈላቸው ይገባል ብሏል፡፡

በሌላ በኩልም የብድሩን ክፍያ በተመለከተ ከሳሾች የሚፈለገባቸው ቀሪ የብድር ገንዘብ ብር 175,497.57 (አንድ መቶ ሰባ አምስት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ሰባት ከሃምሳ ሰባት) ሲሆን ተከሳሽ የተረከበው የከሳሾች ቤት ደግሞ ብር 310,000 (ሦስት መቶ አሥር ሺህ) እንደሆነ ስለተረጋገጠ ከከሳሾች የሚፈለገው ዕዳ ከቤቱ ግምት ሲቀነስ ብር 134,502.43 (አንድ መቶ ሠላሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ከአርባ ሦስት) ስለሚመጣ ይህንንም ተከሣሽ ለከሳሾች መክፈል አለበት ብሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተከሣሽ የተረከባቸው የከሳሾች ሱቅ፣ ቁርስ ቤትና እንጨት ቤት ታሽገው በቆዩበት 138 ቀናት ከሣሾች ባቀረቡት የተጣራ ትርፍ ማስረጃ መሠረት በድምሩ ብር 210,800.00 (ሁለት መቶ አሥር ሺህ ስምንት መቶ) ተከሣሽ ለከሳሾች መክፈል አለበት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በአጠቃላይ ድምርም ብር 492,192.43 (አራት መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ከአርባ ሦስት) የጠበቃ አበል በዚሁ ልክ 10 /አስር በመቶ/ ወጭና ኪሣራ በቁርጥ ብር 200 (ሁለት መቶ) ጨምሮ ተከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ አመልካች በመያዣነት የያዛቸውን ንብረቶች በሕገወጥ መንገድ ይዟል በማለት ከላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገባል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ተጠሪዎች ባሉበት ሊታይ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች የተጠቀሰውን ገንዘብ ለተጠሪዎች እንዲከፍል መወሰኑ አግባብነት አለውን? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 216/92 በተደረገው ማሻሻያ ባንኮች ለሰጡት ብድር አከፋፈል በመያዣነት በዋስትና የተቀበሉትን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት የብድር ዕዳው እንዲከፈል በተወሰነው ጊዜ ሳይከፈል ከቀረ ከሠላሣ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የመያዣ ንብረቱን በሐራጅ ለመሸጥና ባለቤትነቱንም ለገዢው ለማዛወር ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

ከአዋጁ ድንጋጌዎችም መረዳት የሚቻለው አበዳሪው ባንክ በዋስትና የያዛቸውን ንብረቶች የብድር ገንዘቡ ካልተመለሰለት ያለማንም ጣልቃገብነት አግባብነት ያላቸውን የሕጉን ድንጋጌዎች በመከተል በሐራጅ ሸጦ ለዕዳው ክፍያ ማዋል እንደሚችል እና በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ሕጉን ባለመከተል የፈጸመው ስህተት ቢኖርና በዚህም በባለዕዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባዕዳው ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በሕጉ ላይ የተቀመጡትም ዝርዝር ድንጋጌዎች ዓላማም በአዋጁ መግቢያ /Preamble/ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ባንኮች የሚሰጧቸውን ብድሮች በተቀላጠፈ አኳኋን ለመሰብሰብ እንዲችሉ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘም አዋጁን ለማስፈጸም እንዲረዳ አመልካች የፎርክሎዠር መመሪያ ለማውጣት እንዲችል ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን

በዚሁ መሠረትም አመልካች ባወጣው የፎርክሎዠር መመሪያ ተበዳሪው በገባው የብድር ውል መሠረት ሁለት ተከታታይ ክፍያዎችን ወይም ከአጠቃላይ ብድሩ 1/10ኛ ካልከፈለ አበዳሪው ባንክ የፎርክሎዠር ውሣኔ እንደሚሰጥ ከዚህ በኋላም ተበዳሪው ከባንኩ የሚፈለግበትን ዕዳ በ30 ቀናት ውስጥ አጠቃሎ እንዲከፍል ማስጠንቀቂያ እንደሚሰጠው በዚህ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ከባለዕዳው የሚፈለገው ዕዳ ሳይከፈል ከቀረ ባንኩ የመያዣ ንብረቱን እንደሚይዝ መያዣ ሰጭው ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ካልሆነ ከሬጅስትራርና ከፖሊስ ጋር በመተባበር ንብረቱን በኃይል እንደሚይዝ ንብረቱ ከተያዘም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በባንኩ ባለሙያዎች አማካይነት እንደሚገመትና ከዚያም በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ንብረቱ በሐራጅ እንደሚሸጥ ተመልክቷል፡፡

የተያዘውም ጉዳይ ከአዋጁ ከመመሪያውና እንደዚሁም ግራ ቀኙ ካደረጉት ውል አንፃር ሲታይ ተጠሪዎች ለሁለት ተከታታይ ጊዜ የብድር ክፍያ ማቋረጣቸው የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች በአዋጁ በመመሪያውና በውሉ ባለበት ግዴታ መሠረትም የሦላሳ ቀን ማስጠንቀቂያ ለተጠሪዎች መሰጠቱ በማስረጃ መረጋገጡን ይህ ችሎት ለመገንዘብ ችሏል፡፡

አመልካች ለተጠሪዎች የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ዕዳው ሳይከፈል በመቅረቱ በመያዣ የያዘውን ንብረት የተረከበ ሲሆን ይህም ከላይ እንደተመለከተው የፎርክሎዠር መመሪያው የሚፈቅድለት ከመሆኑም በላይ ተጠሪዎችም በገቡት የውል ግዴታ ዕዳው በከፊል ወይንም በሙሉ ሳይከፈል ቢቀር የሰላሣ ቀን ማስጠንቀቂያ ከተሰጠ በኋላ ንብረቱ ሊሸጥ እንደሚችል በውል ስምምነታቸውን የሰጡ በመሆኑ የአመልካች አድራጎት በአዋጁ በመመሪያውና በውሉ የተደገፈ ስለሆነ ሕገወጥ ነው የሚያሰኝ አይሆንም፡፡

አመልካች የመያዣ ንብረቱን ለመያዝ ሲዘጋጅ ተጠሪዎች ቀርበው ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ እንዳልነበሩም በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ አመልካች የሚመለከታቸው አካላት እንዲገኙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማድረግ ንብረቱን በኃይል ለመያዝ እንደሚችል የፎርክሎዠር መመሪያው ሥልጣን የሚሰጠው ስለሆነ ተጠሪዎች በመያዣ የተያዘውን ንብረት ለአመልካች ለማስረከብና ክስ ያቀረቡባቸውንም የተለያዩ ንብረቶች ቀርበው ለመረከብ ፈቃደኛ ካልሆኑ እነዚህ ንብረቶች ተመዝግበው በንግድ መደብሮቹ ውስጥ እንዳሉ መታሸጋቸው ስለማይቀር ንብረቶቹን ከአመልካች ጠይቀው መውሰድ ከሚችሉ በስተቀር የዋጋ ግምታቸው እንዲከፈላቸው እንደዚሁም የንግድ መደብሩ በመታሸጉ ምክንያት ተቋርጦብናል የሚሉት ጥቅም እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ከእራሳቸው ተግባር የመነጨ በመሆኑና አመልካችም የአዋጁን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የፈጸመው ተግባር ባለመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካች ኃላፊ ነው ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች የተረከበው የተጠሪዎች ቤት የዋጋ ግምት ብር 310 000 /ሦስት መቶ አስር ሺህ/ እንደሆነ በተጠሪዎች በኩል የቀረበውን የዋጋ ግምት አስመልክቶ አመልካች ግምቱን በመቃወም ያልተከራከረ ስለሆነና ቤቱን ከተረከበ ጊዜ ጀምሮም ብድሩ እንደተከፈለ ሊቆጠር ስለሚችል የቤቱ ግምትና ከተጠሪዎች በቀረነት የሚፈለገው የብድር ዕዳ ተቀናንሶ በልዩነት ከአመልካች የሚፈለገውን ብር 134,502.43 /አንድ መቶ ሠላሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ብር ከአርባ ሶስት/ ለተጠሪዎች እንዲከፍል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምሥራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ በመጋቢት 22 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት የንብረቶቹን የዋጋ ግምትና የንግድ መደብሮቹ በመታሸጋቸው ምክንያት በተጠሪዎች ላይ ደርሷል የተባለን ኪሣራ በድምሩ ብር 357,690.00 /ሶስት መቶ ሀምሳ ሰባት

ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ብር/ አመልካች ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11804 በሰኔ 21 ቀን 1996 ዓ.ም. በዚህ ረገድ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ አመልካች የአዋጁን ድንጋጌዎችንም ሆነ የአፈፃፀም መምሪያውን ባልተላለፈበት ሁኔታ ስለሆነ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች የተጠሪዎችን የንግድ መደብር ተረክቦ ያሸገው አዋጁና መመሪያው የሚፈቅድለት በመሆኑ ስለሆነ በንግድ መደብሩ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ለተጠሪዎች ከሚያስረክብ በስተቀር የንብረቶቹን የዋጋ ግምትም ሆነ የተቋረጠ ገቢ ሊከፍል ስለማይገባ አይከፍልም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. አመልካች በተረከበው ቤትና በብድሩ ገንዘብ መካከል ያለውን ብር 134,502.43 /አንድ መቶ ሠላሣ አራት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ብር ከአርባ ሶስት ሳንቲም/ ለተጠሪዎች እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር እንደዚሁም የጠበቃ አበል በዚሁ ልክ 10% /አሥር በመቶ/ ጨምሮ ለተጠሪዎች ይክፈል በማለት ተወስኗል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 25863

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሠ ይርጋ

አመልካች፡- የኢት/ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ አዲስ ወልዴ

ተጠሪ፡- የኢት/ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ቀረቡ

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በመያዣ በተሠጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለን የቀዳሚነት መብት የሚመለከት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት የአፈፃፀም ባለዕዳ ከሆኑት ግለሠብ ጋር በነበረው የአፈፃፀም ክርክር አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሠረት መቃወሚያ በማቅረቡ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው አመልካች ለጎጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ በአፈፃፀም በሃራጅ እንዲሸጥ የታዘዘው ንብረት አመልካች ለአፈፃፀም ባለዕዳው ብር 118,500(አንድ መቶ አስራ ስምንት ሺህ አምስት መቶ) ሲያበድር በመያዣ የያዘው በመሆኑ መያዣውም ቀድሞ የተመዘገበ ስለሆነ በንብረቱ ላይ የቅድሚያ መብት ያለው በመሆኑ ሐራጁ እንዲሰረዝለት ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ክርክር የተነሣበትን ንብረት በመያዣ የያዘውና የቀዳሚነት መብት ያለው ተጠሪ ነው ሲል የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጓል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ሠርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ክርክር የተነሣበት ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ማን

እንደሆነ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ ያቀረቡ ሲሆን ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ ሂደት እንደተረዳነው አመልካች የሚከራከረው ክርክር የተነሣበትን የእህል መጋዘን ለሰጠው ብድር በመያዣ መያዙን እና መያዣውንም መጋቢት 6 ቀን 1988 ዓ.ም ያስመዘገበ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የአመልካች መያዣ አግባብ ባለው አካል ፊት ያልተመዘገበና በሠነዱ ላይ የሰፈረው ማህተምም በወቅቱ ሥራ ላይ ያልነበረና አጠራጣሪ መሆኑን፣ተጠሪ ግን ከአመልካች በፊት መያዣውን ሰኔ 23 ቀን 1990 ዓ.ም በማስመዝገቡ የቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑን ተከራክሯል፡፡

ይህ ችሎትም ቀዳሚ መብት ያለው ማነው የሚለውን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ እንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ለብዙ ዕዳዎች በመያዣ ሊሠጥ የሚችል መሆኑ በፍ/ህ/ቁ 3088 ሥር ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት በመያዣ ከተሰጠ በመብቱ ለመገልገል መያዣው አግባብ ባለው አካል መመዝገብ እንዳለበት የፍ/ህ/ቁ. 3052 ያስገነዝባል፡፡ ከሌሎች የመያዣ መብት ካላቸው ባለገንዘቦች በፊትም የቀዳሚነት መብት ለማግኘት መያዣውን ከሌሎቹ በፊት ቀድሞ ማስመዝገብ ይገባል (የፍ/ህ/ቁ 3081 ይመለከቷል)፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች መያዣውን ከተጠሪ በፊት ቀድሞ ማስመዝገቡን ገልጦ የቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑን ተከራክሯል፡፡ ከመዝገቡም እንዳየነው አመልካች የመያዣ ውሉን በቦረና አስተዳደር አካባቢ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ የነገሌ ከተማ አስተዳደር ፅ/ቤት የመያዣ ውሉን ተቀብሎ ማህተሙን በማኖር መመዝገቡን አረጋግጧል፡፡ አመልካች መያዣው የተመዘገበው መጋቢት 6 ቀን 1988 ዓ.ም ነው በማለት ባቀረበው ክርክር ላይ የሥር ፍ/ቤት ያለው ነገር የለም ፍ/ቤቱ የአመልካችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄ ውድቅ ያደረገው መያዣው ተመዝግቧል በተባለበት ወቅት ሠነዱ ላይ ያረፈው ማህተም አጠራጣሪ ነው በሚል ብቻ ነው። እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሠውም በወቅቱ ክልሉ የሚሠራው በኦሮሚኛ ሆኖ ይህ ማህተም እንዴት በአማሪኛ ሊሆን ቻለ ከሚል ጥርጣሬ ብቻ ነው። የማህተሙን ትክክለኛነት ወይም ሐሠተኛነት በተጨባጭ ያረጋገጠው ነገር የለም። ማህተሙ የአስተዳደር ፅ/ቤቱ አይደለም የሚባል ከሆነ ተቃራኒ ማስረጃ ሊቀርብ ይገባ ነበር። ተቃራኒ ማስረጃ ሣይቀርብና የማህተሙ ሀሰተኛ መሆን ሣይረጋገጥ በጥርጣሬ ብቻ የተደረሰበት መደምደሚያ ህጋዊ መሠረት የለውም።

እንግዲህ የማይንቀሣቀስ ንብረት መያዣ ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው መመዝገብ አስፈላጊ በመሆኑ (የፍ/ህ/ቁ 3052ን ይመለከቷል) አመልካችም ሆነ ተጠሪ መያዣቸውን በመዝጋቢው አካል አስመዝግበዋል። በአንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ብዙ ገንዘብ ጠያቂዎች የመያዣ መብት አስመዝግበው እንደሆነ ደግሞ የቀደምትነት መብታቸውን የሚሠሩበት ተራ የሚወሠነው መብታቸውን ያስመዘገቡበትን ቀን በመከተል እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ. 3081/1/ ተመልክቷል።

በተያዘው ጉዳይ አመልካች መያዣውን መጋቢት 6 ቀን 1988 ዓ.ምያስመዘገበ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ሰኔ 23 ቀን 1990 ዓ.ም ነው ያስመዘገበው:: ይህ ከሆነ ደግሞ የቀደምትነት መብት ያለው ቀድሞ መብቱን ያስመዘገበው አመልካች ነው።

በሌላ በኩል ግን አመልካች እየጠየቀ ያለው የሐራጅ ሽያጩ እንዲሠረዝ ነው። በማይንቀሣቀስ ንብረት የመያዣ መብት የተሠጠው ገንዘብ ጠያቂ ንብረቱ በሌሎች ባለገንዘቦች የተያዘ እንደሆነ ከንብረቱ ዋጋ ላይ የሚፈልገው ገንዘብ ከሌሎቹ ገንዘብ ጠያቂዎች ለርሱ በቀዳሚነት እንዲከፈለው ከመጠየቅ ያለፈ መብት የለውም (የፍ/ህ/ቁ 3059(1) ይመለከቷል) የማይንቀሣቀሠው ንብረት ክፍያቸው በደረሠ ማንኛውም

ባለገንዘቦች ሊያገና ሊሰጥ የሚችል ሲሆን የቀዳሚ መብት ያለው ባለገንዘብ ከሽያጩ ገንዘብ የርሱ እዳ በቅድሚያ እንዲከፈለው ከመጠየቅ በቀር ሽያጩ እንዳይከናወን ሊቃወም አይችልም።

በመሆኑም አመልካች ምንም እንኳን መያዣውን ከተጠሪው በፊት በማስመዝገቡ ቀዳሚ መብት ቢኖረውም ይህ መብቱ ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ የእርሱ እዳ ቀድሞ እንዲከፈለው ከማድረግ በቀር ሽያጩ እንዲሰረዝ ሊጠይቅ አይችልም።

በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት ማህተሙ አጠራጣሪ ነው በሚል ብቻ የአመልካችን ክርክር ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1) የጉጂ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 00246 ሰኔ 07 ቀን 1997 ዓ.ም የሠጠው ብይን እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 3286 ሚያዚያ 10ቀን 1998 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።

2) ክርክር የተነሣበት የመያዣ ንብረት በሐራጅ ተሸጦ ከሚገኘው ገንዘብ አመልካች የሚፈልገው እዳ ተከፍሎት ተራፊ ገንዘብ ካለ ለተጠሪ እንዲከፈል ተወስኗል።

3) መጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል። ለመ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.29269

ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አቶ ሳሙኤል ገዛኸኝ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. አቶ ዋለልኝ አያሌው ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ለመች ላቀው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሔራዊ ክልልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 07568 ታህሳስ 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት ዝርዝር ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት 2ኛ ተጠሪ ባለዕዳ ሆነው በምዕ/ጎጃ መስተዳደር ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት በአፈፃፀም መ/ቁ. 8291 በሆነው መዝገብ ላይ የአፈፃፀም ክሱ እየታየ ባለበት ጊዜ የአሁኑ አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.418 ን መሠረት በማድረግ ጣልቃ ገብቶ ተከራክሯል፡፡

ጣልቃ ለመግባት ያቀረበውም ምክንያት የፍርድ ባለመብት እንዲረከብ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የባለዕዳዋን ንብረት አስቀድሜ ያስከበርኩት ስለሆነ ቤቱን ባለመብቱ አንዲረከብና ስመ ንብረትነቱም እንዲዛወርለት የተሰጠው ትዕዛዝ ቀሪ አንዲሆንልን ይታዘዝልን የሚል ነው፡፡ በማስረጃነትም በዚሁ ንብረት ላይ የማስከበሪያ ትዕዛዝ ጥቅምት 28 ቀን 1995 ዓ.ም ያሰጠበት መሆኑንና ባለዕዳ በተባለችው በአሁን 2ኛ ተጠሪ ላይ በዋስትና

ግዴታ ምክንያት ከሶ ፍርድ ያሰጠበት መሆኑን የሚገልፅ የሰነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡

በዚሁ አቤቱታ ላይ መልስ የተሰጠበት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ከገለፀ በኋላ የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ምንም እንኳን የአሁን አመልካች በዚሁ ንብረት ላይ የማስክበሪያ ትዕዛዝ ያሰጠበት መሆኑ ቢረጋገጥም ማስከበር ብቻውን የቀዳሚነትን መብት የሚያሰጥ ሆኖ አላገኘነውም ስለሆነም የቀረበው የአፈፃፀም ክስ ይቋረጥልኝ አቤቱታ ውድቅ ነው በማለት በይኗል፡፡

በዚህም ብይን የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታ ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ታህሳስ 24 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተነሳው አከራካሪ ነጥብ ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ወገን ማን ነው? የሚለው መሆኑን ለይቶ በጭብጥነት ከያዘ በኋላ ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2ኛ ተጠሪ ላይ አስቀድሞ ክስ ያቀረበ እና አስወስኖ የአፈፃፀም ክስ ያቀረበ መሆኑ ቢረጋገጥም 1ኛ ተጠሪ አቶ ዋለልኝ አያሌው ለ2ኛዋ ተጠሪ በወ/ሮ ለመች ላቀው ብር 80,000.00/ሰማንያ ሺህ/ ብድር ሲሰጡ ይህ የብድር ገንዘብ በተባለው ጊዜ ውስጥ ባይመለስ የክርክሩ መንስኤ የሆነውን ቤት ለማስረከብ የውል ግዴታ የገቡ መሆናቸውንና እንደ ግዴታቸው የገንዘብ መክፈያ ጊዜው የብድሩን ገንዘብ መመለስ አለመቻላቸው ተረጋግጦ በሥር ፍ/ቤት ጥቅምት 10 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይኸው በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ በፍኖተ ሰላም ከተማ ቀበሌ 02 በቁጥር መ/1/1984 ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት እንዲረከቡ ተወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የአፈፃፀም ክስ ያቀረበውም ከዚሁ ንብረቱን ይረከብ የሚለው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመሆኑ እና ንግድ ባንክ በቀጥታ ክሱ ጊዜ ይኸው ንብረት ታግዶ እንዲቆይ ማስደረጉም የፍርድ ባለመብት በቤቱ ላይ ያገኘውን መብት የሚያሳጣ ሆኖ ባለመገኘቱ የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው አይደለም፡፡ እንዲሁም አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ተከብሮ የመያዙ እውነታም ንብረቱ ከመያዙ በፊት ገንዘብ እንዲከፈላቸው በባለሀብቱ ላይ ያስፈረደ ወገን በቀረበ ጊዜ የተያዘውን ንብረት ለመውሰድ እንደማይከለክል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ፍ/ቁ.403 ይደነግጋል፡፡ አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤቱን በመያዣ የያዘው ባለመሆኑም ቀድሞ ክስ ማቅረቡ ብቻውን የ1ኛ ተጠሪን የአቶ ዋለልኝ አያሌውን መብት የሚያስቀር አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች በመንተራስ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ የአመልካችም የሰበር አቤቱታ ፍሬ ቃል፡-

የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለውሳኔው የሰጠው ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.403 የተመለከተውን ድንጋጌ ትክክለኛ ትርጉም የተከተለ አይደለም፡፡

ከ1ኛ ተጠሪ ይልቅ ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ ቀድመን መብታችንን ያስጠበቅን መሆኑ እየታወቀ እና በዚህም የተነሣ በሥነ ሥርአት ህጉ የተሰጠን ዋስትና እያለ ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህም እንኳ ቢታለፍ የፍርድ ባለመብት እንደመሆናችን መጠን የባለዕዳዋ ንብረት ተሸጦ እንደየድርሻችን መከፋፈል ሲገባን ለ1ኛ ተጠሪ ብቻ እንዲሰጥ መደረጉ የህግ ድጋፍ ያለው ባለመሆኑ ይኸው ይታረምልን የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት ህግን መሠረት ያደረገ መሆኑን በመግለፅ ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን 1ኛ ተጠሪ የብድር ውልን መሠረት አድርጎ ክስ ከማቅረቡ እና ከማስወሰኑ በፊት የአሁን አመልካች በ2ኛዋ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ምክንያት ጥቅምት 28 ቀን 1995 ዓ.ም ይኸው ክርክር ያስነሳው ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ያሳገደው ለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል

የተካደ ፍሬ ነገር አይደለም፡፡ ይህም መሆኑ ከተረጋገጠ በአመልካች በኩል የተፈፀመው ተግባር በ2ኛ ተጠሪ ላይ የገንዘብ ክስ አቅርቤአለሁ፤ እንደ ክሱ ባስፈርድ ፍርዱ ውጤት ያገኝ ዘንድ የተከሳሽ ንብረት ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በማለት ተከብሮ ይቆይልኝ የሚል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3044 እንደተመለከተው ይህ የማሳገድ ተግባር ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይኸውም ፍርድ ቤቱ የሰጠው ፍርድ ተፈፃሚነት እንዲያገኝ ለማረጋገጥ አንዱ ወገን ለሌላው ወገን በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ከሚያሰጠው የማስከበሪያ ትዕዛዝ አንዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.154 መሠረት ግራ ቀኙ በክርክር ላይ እያሉ ከፍርድ በፊት በንብረት ላይ የሚሰጠው የማገጃ ትዕዛዝ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች በዚሁ መሠረት የ2ኛዋ ተጠሪ ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ተከብሮ እንዲቆይ ያስደረገ ለመሆኑ የተለየ ሆኖ ካልተገኘ አመልካች በዚሁ ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያገኘ መሆኑን አረጋጋጭ ነው፡፡ እንደ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትንተና የመያዣ መብት ሁልጊዜ ከውል ብቻ እንደሚመነጭ ተደርጎ የተሰጠው ትርጉም ስህተት ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041 እንደተደነገገው መያዣ ከውል ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ከሕግ ወይም በፍርድ ሊቋቋም ይችላል፡፡ በዚህ መሠረት አመልካች ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ የመነጨ የመያዣ ውል ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ይህ በመያዣ የተያዘውን ንብረት ገንዘብ ጠያቂ ያስያዘው እንደሆነ ከንብረቱ ዋጋ ላይ የሚጠየቀው ገንዘብ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በፊት ለእርሱ በቀዳሚነት እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3059/1/ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች የጠየቀው ዳኝነት ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ እያለ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ህግ ከሚደነግገው ውጭ በሥር ፍ/ቤት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን ያሳያል፡፡

አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተከብሮ የመያዙ እውነታ ንብረቱ ከመያዙ በፊት ገንዘብ እንዲከፈላቸው በንብረቱ ባለሀብት ላይ ያስፈረዱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገኖች በቀረቡ ጊዜ የተያዘውን ሀብት ከመውሰድ እንደማያግዳቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 403 ተደንግጓል በሚል በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ትንታኔም ተመልክተናል፡፡ በመሠረቱ የዚህ ድንጋጌ አግባብነት ከድንጋጌው ርዕስ እንደምንመለከተው የአንድ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት በእርሱ ላይ የቀረቡትን ገንዘብ ጠያቂዎች ፍላጐት የሚያሟላ ሆኖ ከተገኘ ይኸው ንብረቱ በእነዚህ ገንዘብ ጠያቂዎች መካከል እንዴት እንደሚከፋፈል የሚደነግግ እንጂ እንደ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አባባል አንደኛው ገንዘብ ጠያቂ ብቻውን ጠቅልሎ እንዲወስድ የሚያስችል አይደለም፡፡ የድንጋጌውም ተፈፃሚነት የፍርድ ባለዕዳውን ንብረት በተራ ባለገንዘቦች መካከል ማከፋፈል በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የተወሰነ እንጂ የቀዳሚ መብትነት የሚመለከት አይደለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች ከፍርድ የመነጨ የመያዣ ውል የመኖሩን እውነታ ወደ ጐን በመተው ንብረቱን በሚመለከት በንብረቱ ላይ ያስወሰነው 1ኛ ተጠሪ ነው የሚለውን ብቻ መሠረት በማድረግ ለዚሁ 1ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የቀዳሚነት መብት እንዲኖረው በማድረግ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የምዕ/ጐጃ መስ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአፈፃ/መ/ቁ.8291 በመስከረም 23 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የአማራ ብሔ/ክል/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 07568 ታህሳስ 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው በመሆኑ ይኸው በፍኖተ ሰላም ከተማ ቀበሌ 02 በ2ኛዋ ተጠሪ በወ/ሮ ለመች ላቀው ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የሆቴል ቤት ድርጅት ተሸጦ ከሽያጩ ገንዘብ የአሁን አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሚፈልገው ዕዳ በቅድሚያ

ሊውል ይገባል ብለናል፡፡ ስለሆነም አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በዚሁ ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈፅም አዘናል፡፡ ግልባጩ ይድረሰው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 29375

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ሣሙኤል ገዛኸኝ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ተስፋዬ ገብረጊዮርጊስ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የማይንቀሣቀሱ ንብረት ከመያዣ ውል ጋር በተያያዘ ሁኔታ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአማራ ብ/ክ/መ/ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪው በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው የመያዣ ውሉ በዋስትና ያላስያዝኩትን ቤት ጨምሮ ሸጦብኛል በማለት ነው፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት በጨረታ የሸጥኩት በመያዣው ውል የተመለከተውን ቤት ነው በማለት ተከራክሯአል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣ ተከሣሽ የመያዣ ውሉ ከተፈረመ በኋላ የተሠሩትን ሰርቪስ ቤቶች ጭምር የሸጠ በመሆኑ የሰርቪስ ቤቶቹ ግምት ለከሣሽ ይክፈል ሲል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም ውሣኔውን አፅንቶአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 23 ቀን 1999 ዓ.ም. በዓፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በመያዣ ውሉ

መሠረት ከያዘው ቤት ጋር ተያይዘው ለተሠሩት ሰርቪስ ቤቶች ግምት እንዲከፈል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪው ነጥብ የሚወሰነው ስለማይንቀሣቀሱ ንብረቶች መያዣ እና አፈፃፀሙን በሚመለከት በፍትሐብሔር ሕጉ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ ከሥር ጀምሮ በተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው ለአሁኑ ክርክር መነሻ የሆኑት ሰርቪስ ቤቶች የተሠሩት አመልካች በዋስትና የያዘው ቤት ባለበት (በተሠራበት) ቦታ ላይ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ማለት ከዋናው ቤት በመቀጠል ወይም በማያያዝ የተሠሩ ናቸው ማለት ነው፡፡ የማይንቀሣቀሰው ንብረት በመያዣነት ከተሰጠ በኋላ አዲስ ሥራ ወይም ማሻሻል ቢደረግ የመያዣ ውሉን አፈፃፀም በተመለከተ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 3066 ግልጽ የሆነ መልስ ሰጥቶአል፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረት መያዝ መብት የመያዣው መብት በሚመለከተው የማይንቀሣቀስ ንብረትና በዚሁ ንብረት ላይ የሚሠሩትን አዳዲስ ሥራዎች እንደሚጠቀልል ያመለክታል፡፡ ይህን ድንጋጌ ከያዝነው ክርክር ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ተጠሪ ቤቱን በመያዣነት ለአመልካች ከሰጠ በኋላ ሠራሁአቸው የሚላቸው ሰርቪስ ክፍሎች ከመያዣው ውጪ ሊታዩ እንደማይችሉ ነው መገንዘብ የምንችለው፡፡ በመሆኑም ሰርቪስ ቤቶቹ የመያዣ ውሉ በተደረገ ጊዜ ያልነበሩና ያልተገመቱ ናቸው በሚል ምክንያት አመልካች የሰርቪሶቹን ግምት እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበባቸው በአማራ ብ/ክ/መ/ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 3840 ሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው እና የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 07448 ጥር 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች የሰርቪስ ቤቱቹን ግምት የሚከፍልበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ውሣኔው ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 33295

ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

አመልካች፡- ወ/ሪት ብርሃኔ አበበ ጠበቃ ክፍሌ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ማርቆስ ተርፋ ጠበቃ ቢኒያም ተርፋ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፀሐይ መንበረ በሌሉበት ይታያል
3. አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ ነገረፈጅ ሽጋው ሰውነት
4. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በሌሉበት ይታያል፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ 04227 ሐምሌ 30 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 23888 ሰኔ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በማመልከታቸው ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ፣ ተከራካሪዎች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ካቀረቡት ክርክርና የከፍተኛ ፍርድ ቤት በትእዛዝ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች በማስቀረብ መርምሮ በውሣኔው ካሰፈረው ለመረዳት እንደሚቻለው በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 3 ቀበሌ 52 የቤት ቁጥር 154 የሆነዉን ቤታቸውን ሁለተኛ ተጠሪ በ1986 ዓ.ም ለአቶ ሽሮ ገመቹ ይሸጣሉ፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ለአቶ ሽሮ ገመቹ ከሸጡ በኋላ ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችላቸውና ቤቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመሸጥ ለመለወጥ እንዲችል፣ ሌላ ሰው መወከል የሚያስችላቸውን የውክልና ስልጣን ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ በኋላ አቶ ሽሮ ገመቹ በበኩላቸው የቤቱን ስመ ንብረት በስማቸው ሣያዛውሩ ቤቱ በሁለተኛ ተጠሪ ስም እያለ ለአንደኛ ተጠሪ አቶ ማርቆስ ተርፉ ከሸጠ በኋላ፣ ሁለተኛዋ ተጠሪ ቤቱን ስትሸጥለት ነሐሌ 18 ቀን 1987 ዓ.ም በቁጥር 21134/87 ዓ.ም በሰጠችው ውክልና ስልጣን መሰረት ሁለተኛው ተጠሪ ቤቱን እንዲሸጥና እንዲለውጥ የውክልና ስልጣን ይሰጣሉ፡፡

- አንደኛ ተጠሪ በበኩሉ የቤቱን ስመ ንብረት በስሙ ሣያዛውር ቤቱ በሁለተኛዋ ተጠሪ ስም እያለ አቶ ሽሮ ገመቹ የሰጠውን የውክልና ስልጣን በመጠቀም መስከረም 28 ቀን 1988 ዓ.ም ለአመልካች በብር 70,000 /ሰባ ሺህ ብር/ ሽጦና ውሉም በአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ተረጋግጦ የቤቱን ዋጋ ብር 70,000/ሰባ ሺ ብር/ ከአመልካች ተቀብሎ የቤቱን ካርታና ሃላን እንደዚሁም ሌሎች ማስረጃዎች ለአመልካች ያስረክባል፡፡
- ከዚህ በኋላ አንደኛው ተጠሪ መስከረም 28 ቀን 1988 ዓ.ም ለአመልካች የሸጠውን እና ስመ ንብረቱ በሁለተኛ ተጠሪ ስም ያለውን ቤት መያዣ በማድረግ፣ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ጥቅምት 26 ቀን 1988 ዓ.ም ከሶስተኛው ተጠሪ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ይወስዳል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በማቅረብ ጥቅምት 27 ቀን 1988 ዓ.ም ያስመዘግባል፡፡ አንደኛው ተጠሪ፣ የቤቱን ካርታና ሃላን ለአመልካች ያስረከበ በመሆኑ ቤቱን በመያዣነት ሲያስይዝ የቤቱ ካርታና ሃላን በእጁ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ብድሩን ከወሰደ ከሃያ አምስት ቀን በኋላ የቤቱ ካርታ ሃላንና የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጠፍቶብኛል በማለት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመልክቶ

ህዳር 21 ቀን 1988 ዓ.ም በቁጥር 33564 የሆነ የተመዘገበ ምትክ ካርታና ሃላን አውጥቷል፡፡

አመልካች የቤቱን ስመ ንብረት ለማዛወር ስትሞክር የገዛችው ቤት በመያዣነት ተይዞ በማግኘቷ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ አቅርባለች፡፡ አንደኛው ተጠሪ ቤቱን የሸጠ መሆኑን ሣይክድ ገንዘብ አልተቀበልኩም ሰነዶቹንም በማጥፋት አመልካች እንዳትጠቀም አድርጌአለሁ የሚል ክርክር ያቀረበ ሲሆን፣ ሁለትኛዋ ተጠሪ ቤቱን የሸጥኩት ለአቶ ሽሮ ገመቹ በመሆኑም እኔ ልጠየቅ አይገባኝም ብላለች፡፡ ሶስተኛ ተጠሪ፣ የተመዘገበ የመያዣ ውል ያለኝ በመሆኑ በቤቱ ላይ ቀደምት መብት ያለኝ እኔ ስለሆንኩ የቤቱ ስመ ንብረት ይዛወርልኝ በማለት አመልካች ያቀረበችው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ አራተኛው ተጠሪ በበኩሉ እኔ የምከሰስበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአመልካች ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የወሰነ ሲሆን፣ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ አመልካች በቤቱ ላይ የምታነሣው የቀዳሚነትና የባለቤትነት መብት ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህ ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የቤቱን ስመ ንብረት ለማዛወር ጠይቄ የነበረ ሲሆን በወቅቱ በመመሪያ በመታገዱ ብቻ ሣይዛወር ቀርቷል፡፡ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም፣ አንደኛ ተጠሪ በማጭበርበር ሸጦ ገንዘብ የተቀበለበት ቤት ለሶስተኛ ተጠሪ መያዣ በማድረግ ገንዘብ መበደሩ፣ ለሶስተኛው ተጠሪ የቀዳሚነት መብት የሚያስገኝለት አይሆንም፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ይባልልኝ በማለት ያመለከተች ሲሆን አንደኛ እና አራተኛ ተጠሪ በጋዜጣ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌለበት ቀጥሏል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ በቤቱ ላይ ህጋዊ የቀዳሚነት መብት ያለኝ እኔ ነኝ በማለት የፍታብሔር ህግ የመያዣ ውል፣ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ይዘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ሶስተኛ ተጠሪ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረጉት የመያዣ ውል በህግ በተደነገገው አግባብ የተመዘገበና የቀዳሚነት መብት የሚያስገኝ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች በማስቀረብ አረጋጋጦ በፍርድ ከመዘገበው ፍሬ ጉዳይ እንደተረዳነው ሶስተኛ ተጠሪ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር የመያዣ ውል ተፈራርሞ 200,000 ብር (ሁለት መቶ ሺ) ያበደረው ጥቅምት 26 ቀን 1988 ዓ.ም ሲሆን የመያዣ ውሉ በአስተዳደሩ የተመዘገበው ጥቅምት 27 ቀን 1988 ዓ.ም ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የቤቱን ስም ለማዛወር በአስተዳዳሩ ጥያቄ አቅርቤለሁ የሚል ክርክር በማቅረቧ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሁለተኛ ተጠሪ ስም ያለው የቤቱ መዝገብና ማህደር እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ የልደታ ክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በቁጥር ልደታ 114/10/4357/98 ታህሣስ 4 ቀን 1998 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ በጽ/ቤቱ በነበረው የመዋቅር ለውጥ ምክንያት ወ/ሮ ፀሐይ መንበረ ስም ተከፍቶ የነበረው ማህደር የጠፋ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መስሪያ ቤቱ ምትክ ማህደር በሶስተኛ ተጠሪ አመልካችነት መክፈቱን ገፆአል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ ተመዝግቧል የሚለው የመያዣ ውል ተመዝግቦና ተይዞ የተገኘው በአንደኛ ተጠሪ ስም ተከፍቶ በነበረውና እንደጠፋ በተረጋገጠው ማህደር ሣይሆን፣ በራሱ በሶስተኛ ተጠሪ አመልካችነት በተከፈተው ምትክ ማህደር ውስጥ ነው፡፡

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ አንደኛ ተጠሪ የቤት ሃላንና ካርታ ሣይኖረው ከሶስተኛ ተጠሪ ጋር ያደረገውን የመያዣ ውል፣ የቤቱ ባለቤት በሆነችው ሁለተኛ ተጠሪ ስም የነበረው ማህደር በሌለበት ሁኔታ አራተኛው ተጠሪ በምን መንገድ ጥቅምት 27 ቀን 1988 ዓ.ም የአንደኛ ተጠሪና የሶስተኛውን ተጠሪ መያዣ ውል መዝገበው? አመልካች በወቅቱ የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ ላለማቅረቧስ ማህደሩ በጠፋበት ሁኔታ እንዴት ለማረጋገጥ

ይቻላል የሚሉት ነጥቦች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር መታየት አለባቸው፡፡

የማይንቀሣቀስ ንብረት መያዣ በማናቸውም አይነት ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆን ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ ርስት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ማንኛውንም አይነት ውጤት እንደማያስገኝ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3052 የሚደነግግ ሲሆን የማይንቀሣቀስ ንብረትን መያዣ እንዲመዘግብ ጥያቄ የቀረበለት የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ሰራተኛ የውሉን አመዘጋገብ ሥርአት የሚፈጽመው በዚህ ህግ ስለማይንቀሣቀሱ ንብረቶች አመዘጋገብ ሥርአት በሚመለከተው አንቀጽ በተደነገገው ደንብ መሰረት መሆን እንደ ሚገባው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3053 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ይኸም የሚያሳየው የመያዣ ውል በህጉ በተቀመጠው መሰረት በአግባቡ ካልተመዘገበ ህጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡ ከዚህ አንፃር የማይነቀሳቀስ ንብረት መያዣ መመዝገብ ያለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1605 እና 1607 የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው መሆን ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ሶስተኛ ተጠሪ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረገው የመያዣ ውል እንዲመዘገብለት አስተዳደሩን ሲጠይቅ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1606 የተደነገገውን ሁኔታ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያልነበረ ሲሆን እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1607 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት መቅረብ የሚገባቸው አስረጅ ሰነዶች ባልቀረቡበት ሁኔታ ነው፡፡

ለዚህም ምክንያቱ አስተዳደሩ የመያዣ ውሉን አስመዘገብኩ በሚልበት ጥቅምት 27 ቀን 1988 ዓ.ም የቤቱ ካርታ እና ሃላን የለም፡፡ አንደኛው ተጠሪ በሐሰት ካርታና ሃላን ጠፍቷል ብሎ ምትክ ካርታ ሃላን ያወጣው ህዳር 21 ቀን 1988 ዓ.ም ነው፡፡ በሌላ በኩል በሁለተኛ ተጠሪ ስም የነበረው ማህደር በአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ተፈልጐ ሊገኝ እንዳልቻለ ታውቋል፡፡ ይኸ ከሆነ አስተዳደር መስሪያ ቤቱ ሶስተኛ ተጠሪ በፍታብሔር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህግ ቁጥር 1606 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1607 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ለመያዣ የተመዘገበው ቤት አስረጅ ሰነዶች ሳይቀርቡለት የአንደኛ ተጠሪ እና ሶስተኛ ተጠሪን ውል ብቻ በማየት ያደረገው ነው፡፡

ሶስተኛ ተጠሪ ህጋዊ የንብረት ማረጋገጫ ሰነድ በሌለበት ሁኔታ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረገው የመያዣ ውል በመያዣ ተሰጠ የተባለው ቤት ማህደርና አስረጅ ሰነድ በሌለበት ሁኔታ በአስተዳደሩ መመዝገቡ በህጋዊ መንገድ ገብታ የንብረቱን ባለቤትነት የሚያረጋግጡ ሰነዶችን በእጇ አድርጋ ንብረቱን በይዞታዋ አድርጋ እየኖረችበት ካለችው ከአመልካች የተሻለ የቀዳሚነት መብት የሚያስገኝለት አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በሽያጭ ውሉ መሰረት ንብረቱ በስሟ ለማዞር ጥያቄ ያቀረበች መሆኑን ገልፃለች፡፡ ማህደሩ የጠፋ በመሆኑ አመልካች ጥያቄውን ማቅረብ አለማቅረቧን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ሶስተኛ ተጠሪም ቢሆን በራሱ አመልካችነት ምትክ ማህደር አስከፍቶ ስለተገኘ ብቻ መያዣ ውሉ በህጉ አግባብ ተመዝግቧል ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ሶስተኛ ተጠሪ፣ ተገቢውን ትጋት በማድረግ የንብረቱ ካርታና ሃላን እንደዚሁም ሌሎች አስረጅ ሰነዶች በአንደኛ ተጠሪ ሳይቀርብለት ተዋውሎና እና የመያዣ ውሉም አስፈላጊ ከሆኑ ሰነዶች ጋር ሣይቀርብ የመያዣ ውል አስመዝግቦ መገኘቱ የቤቱን ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ በሌለበት የተፈፀመ በመሆኑ ከአመልካች የተሻለና የቀዳሚነት መብት የሚያስገኝለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ህገ ወጥና የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት መሆኑን የሚያመላክቱ ማስረጃዎች እያሉና የመያዣ ውሉ የተደረገውም ሆነ የተመዘገበው የንብረቱ ካርታና ሃላን በሌለበትና ለሚመዘግበው አካል ባልቀረበበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ ሶስተኛው ተጠሪ የቀዳሚነት መብት አለው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ብለን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ሶስተኛ ተጠሪ አመልካች መስከረም 27 ቀን 1988 ዓ.ም ገዝታ በይዞታዋ አድርጋ እየኖረችበት ባለው ቤት ላይ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የመያዣ ውል መሰረት የቀዳሚነት መብት አለኝ በማለት የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡
3. በቤቱ ላይ የቀዳሚነት መብት ያላት አመልካች ስለሆነች የቤቱ ባለቤትነት ለአመልካች ሊተላለፍ ይገባል ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኪራይ ውል

የሰ/መ/ቁ. 23024

ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ፋጤ በሽር - ጠበቃ አቶ ወልደሥላሴ ብርቱ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- መልዓከገነት ዮሐንስ አምባው - ቀረበ፡፡

ጣልቃ ገብ፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነገረ ፈጅ አቶ ዓለሙ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ክርክሩ የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ በውክልና እንዲያስተዳድሩ የተሰጣቸውን ቤት እንዲያስረክቡ የሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው ቤቱ ከከሣሽ /ተጠሪ/ ጋር አብረው ባቋቋሙት "መሠረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር" ስም ተዛውሮ ኪራይም በንግድ ድርጅቱ ስም ሲከፈል የቆየ በመሆኑ ቤቱ እንደጋራ ንብረት ከሚቆጠር በስተቀር የግል ሊሆን ስለማይችል ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ኤጀንሲም በጣልቃ ገብነት በጉዳዩ ገብቶ አመልካችና ተጠሪ በጋራ ያቋቋሙት የንግድ ድርጅት የፈረሰና ሕልውና ያከተመ በመሆኑ የቤቱ ይዞታ ሊመለስለት እንደሚገባ አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ክርክሩን መርምሮ የቤቱ ኪራይ ውል በንግድ ድርጅቱ ስም የተመዘገበ ስለሆነ አመልካችና ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት ስለሌላቸው ሊከራከሩ አይችሉም፣ ጣልቃ ገብም በክርክሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውስጥ የገባው ክርክሩን ለማስቆም ብቻ ስለሆነና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ ዓላማም ከዚህ ያለፈ ስላልሆነ የዳኝነቱን ጥያቄ በተገቢው መንገድ ከሚያቀርብ በስተቀር ይዞታው እንዲመለስልኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም "ቤቱን በኪራይ ለመያዝ ከግራ ቀኙ የተሻለ መብት ያለው ማነው" የሚል ጭብጥ መሥርቶ ተጠሪ ቀደም ሲል የንግድ ድርጅቱ ከመቋቋሙ በፊት በራሱ ስም ተከራይቶት የነበረው ቤት ከእጁ ሊወጣ የቻለው ለአመልካች በሰጠው ውክልና ምክንያት በመሆኑ፤ ከዚያ በኋላ በጋራ ያቋቋሙት ድርጅትም በመፍረሱና ውክልናውም በመሻሩ ግራ ቀኙ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1815 መሠረት ወደየነበሩበት ቦታ ሊመለሱ ይገባል፤ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ጣልቃ ገብ ባለመጠራቱ በክርክሩ አልተካፈለም፡፡

አመልካች ለዚህ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በንግድ ድርጅቱ ስም መከራየቱ እየታወቀና ድርጅቱም ከፈረሰ የድርጅቱ መልካም ስምና የተከራይ መብት የጋራ ከሚሆን ወይም የቤቱ ኪራይ ለጣልቃ ገብ ከሚመለስ በስተቀር በንግድ ሕግ በአንቀጽ 24 እና 26 መሠረት ቤቱ ለተጠሪ ሊመለስ አይገባውም የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ከተመረመረ በኋላ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክብ የተባለው በአግባቡ መሆኑን አለመሆኑን ለመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ መዝገቡ ለውሣኔ ተቀጥሮ ሲመረመር በዚህ ጉዳይ በሥር ፍርድ ቤት በጣልቃ ገብነት ተከራካሪ የነበረው የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ በጠቅላይ ፍርድ ቤት በተደረገው የይግባኝ ክርክር ተካፋይ እንዲሆን አለመጠራቱ በከፍተኛ ፍ/ቤት ያገኘውን መብት የሚያሳጣና በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 40/5/ ላይ የተደነገገውን አሠራር ያልተከተለ ሆኖ በመገኘቱ በሰበር ክርክሩ በጣልቃ ገብነት ተካፋይ እንዲሆን ተበይኗል፡፡

ፍርድ ቤቱ በአጠቃላይ በአመልካች፣ በተጠሪና በጣልቃ ገብ መካከል የተደረገውን ክርክር ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሠረቱ ክርክሩን ያስነሳው ቤት ባሁኑ ጊዜ ፈርሶ ሕልውናው ባከተመው "መሠረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር" ስም የኪራይ ውሉ ተመዝግቦ ኪራዩም በማኅበሩ ስም የሚከፈል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ለዚሁም የኪራይ ውሉ በማስረጃነት ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ይሁን እንጂ የኪራይ ውሉ በድርጅቱ ስም ከመደረጉ በፊት ቤቱ በተጠሪ ስም እንደነበር አልተካደም፡፡ ቤቱ በድርጅቱ ስም የተዛወረውም አመልካች ከተጠሪ ባገኙት ውክልና መነሻነት ለመሆኑም ግራ ቀኙ ተማምነዋል፡፡ ተጠሪ ምንም እንኳን ውክልናው በኋላ ተሽሯል የሚል ክርክር ቢኖራቸውም ቤቱ በንግድ ድርጅቱ ስም ከመዛወሩ በፊት ውክልናውን ለመሻራቸው ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡

በመሆኑም ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት በማስረጃዎች ነጥረው ከወጡት ሁለት ፍሬ ነገሮች በመነሣት የቤቱ ባለይዞታ የንግድ ማኅበሩ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የንግድ ማኅበሩ ባሁኑ ወቅት ፈርሶ ሕልውናውን አጥቷል፡፡ የንግድ ማኅበሩ መፍረሱ ከተረጋገጠ ደግሞ የቤቱ እጣ ፈንታ የሚወሰነው በማኅበርተኞቹ ስምምነት ወይም በመካከላቸው ስምምነት ከሌለ ቤቱ የግል ወይም የጋራ ይሁን በማለት እርስ በርስ በሚያስነሱት ክርክር አይደለም፡፡ ምክንያቱም የቀድሞ የንግድ ድርጅት ማኅበርተኞች በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት የላቸውም፡፡ በሌላ አነጋገር ቤቱ የማኅበርተኞቹ የካፒታል አካል ሳይሆን የጣልቃ ገብ ንብረት ነው፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ በጋራ ያቋቋሙት የንግድ ማኅበር መፍረሱ እስከተረጋገጠ ድረስ በማኅበሩ ስም ከጣልቃ ገብ ላይ በተከራዩት ቤት አንዳቸውም የተሻለ የይዞታ መብት የላቸውም በማለት የወሰነው ባግባቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ተጠቃሚው ጣልቃ ገብ የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያስተናገደው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን ጣልቃ ገብን ባለመጥራት ከአመልካችና ከተጠሪ የተሻለ መብት ያለው ማነው? የሚል ጭብጥ መስርቶ ጣልቃ ገብን የሚጎዳ ውሣኔ መስጠቱ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 40/5/ ድንጋጌን ያልተከተለ አሠራር በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

በተጨማሪም ተጠሪ በቤቱ ላይ ቀደም ሲል የንግድ ማኅበሩ ከመቋቋሙ በፊት የነበራቸው የተከራይነት መብት ከእጃቸው ሊወጣ የቻለው ለአመልካች በሰጡት ውክልና መነሻነት ነው በማለት ውክልናው የኪራይ ውሉ ወደ ድርጅቱ ስም በተዛወረበት ጊዜ የፀና እንደነበር እየተመለከተ ሕልውናው ባከተመና በሌላ ውል በተተካው በቀድሞ የኪራይ ውል ላይ ሕይወት በመዘራት ተጠሪ ቤቱን እንዲረከቡ የሰጠው ውሣኔ ምንም ዓይነት ሕጋዊ መሠረት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በሕግ ተደግፎ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ያለ ሕግ ወስኖ በመገኘቱ ሌላ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

ው ሣ ኔ

- የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 20708 ጥር 12 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20/80 ግንቦት 17 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የመዝገብ ቁጥር 24221

ህዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡-መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ- ነ/ፈጅ አበበ ጥላዬ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ አረጋሽ አምደሚካኤል- ጠበቃ ዘውዱ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ቤት ይልቀቅልኝ በማለት በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ባለማግኘቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጸሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ በሰኔ 1 ቀን 1974 ዓ.ም. በተደረገ ውል በወረዳ 21 ቀበሌ 04 ቁጥር 031/08 የሆነውን ቤት በወር ብር 212.50/ሁለት መቶ አስራ ሁለት ከሀምሳ/ ተከራይተው እያለ ውሉን በመጣስ ከአገር ሲወጡ ቤቱን ለ2ኛ ተከሳሽ አስተላልፈዋል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሽም ቤቱን በሕገወጥ መንገድ ይገለገሉበታል፡፡ ስለዚህ የኪራይ ውሉ ተሰረዞ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም ባቀረቡት የመከላከያ መልስ 1ኛ ተጠሪ ለሕክምና ከኢትዮጵያ ውጭ ሲሄዱ እስኪመለሱ ድረስ 2ኛ ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውክልና ንብረታቸውን እንዲጠብቁላቸው 2ኛ ተጠሪም ለተወሰነ ጊዜ ለሥራ ከአዲስ አበባ ውጭ ሲሄዱ 3ኛ ተጠሪ በቤቱ ውስጥ እንዳሉ ገልጻው ክሱ ከበቂ ኪሳራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገቡን መርምሮ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች የተከራዩትን ቤት ለሌላ ስለማስተላለፋቸው አመልካች በማስረጃ ያላረጋገጠ ሲሆን ተጠሪዎች ባቀረቧቸው ማስረጃዎች ግን 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪን 2ኛ ተጠሪም 3ኛ ተጠሪን ንብረት ለማስተዳደር የሚያስችል ውክልና መስጠታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ማንም ሰው ደግሞ ውክልና የመስጠት መብት ያለው ስለሆነ የኪራዩ ውል ሊሰረዝም አይችልም በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኙን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ኪራይ ውል ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ ተጠሪዎች ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ሊፈታ የሚገባው የጉዳዩ ግብጥ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ኪራይ ውል ሊሰረዝ ይገባል? ወይንስ አይገባም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ባቋቋሙት የቤት ኪራይ ውል አንቀጽ 2.5 እና 2.6 ላይ ተከራይ የተከራየውን ቤት ያለአከራይ ፈቃድ ለሌላ ወገን ቢያስተላልፍ ውሉ እንደሚሰረዝ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች አጥብቀው የሚከራከሩት 1ኛ ተጠሪ በሕክምና ምክንያት ወደ ውጭ አገር

ሲሄዱ ንብረታቸውን እንዲያስተዳድሩላቸው ለ2ኛ ተጠሪ ውክልና ሰጥተዋል፡፡ እንደዚሁም 2ኛ ተጠሪ ከአዲስ አበባ ውጭ ሲሄዱ በበኩላቸው ለ3ኛ ተጠሪ ውክልና የሰጡ በመሆኑ ድርጊቱ ውሉን የሚጻረር ባለመሆኑ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ነው፡፡

በእርግጥ ማንም ሰው ከባለቤትነት መብትም ይሁን ከይዞታ መብት በመነጨ በሚያዝበት ንብረት ላይ ውክልና የመስጠት ከሕግ የመነጨ መብት እንዳለው የሚያከራክር አይሆንም፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ እንደተባለው ለሕክምና ከኢትዮጵያ ውጭ ሲሄዱ ለ2ኛ ተጠሪ ውክልና የሰጡ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ ረዘም ላለ ጊዜ በቤቱ ውስጥ መኖራቸው ሲታይ ከዚህም አልፎ እሳቸውም በበኩላቸው 3ኛ ተጠሪን መወከላቸው እንደዚሁም ለሕክምና ወደ ውጭ አገር ሄደዋል የተባሉት 1ኛ ተጠሪ ለረጅም ጊዜ ሳይመለሱ መቅረታቸው እነዚህ ሁኔታዎች በድምሩ ሲታዩ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች በኪራይ የያዙትን ቤት ለ2ኛ ተጠሪ ማስተላለፋቸውን የሚያረጋግጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ከተረጋገጠ ደግሞ ግራ ቀኙ ባቋቋሙት የቤት ኪራይ ውል ላይ ከላይ እንደተመለከተው ተከራይ ያለአከራይ ፈቃድ በኪራይ የያዘውን ቤት ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ እንደማይችል የተሰማሙትን የሚጻረር እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የውል ይሰረዝልኝ አቤቱታም ለፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ዳኞች ውሉ እንዲሰረዝ ከመወሰናቸው በፊት የተዋዋዮችን ጥቅምና በቅን ልቦና የሚያስፈልገውን መሠረት ማጤን እንዳለባቸው እንደዚሁም ዓይነተኛ የውል መጣስ ተግባር /fundamental breach of contract/ ካልተፈጸመ ውሉ ይሰረዝ ሊሉ እንደማይችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1785 ላይ የተመለከተ እንደመሆኑ መጠን ከዚህም አንጻር ሁኔታው ሲታይ 1ኛ ተጠሪ በኪራይ የያዙትን ቤት በውክልና ሽፋን ለሌላ ማስተላለፋቸውን መገንዘብ ስለተቻለና ይህም ቅን ልቦና የጎደለው መሆኑን የሚያሳይ፣ ከአመልካች ጥቅምም አኳያ ሲታይ በአዋጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቋቋመው የመኖሪያ ቤት ችግርን የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ቤት ለተቸገሩ ሰዎች የኪራይ መብት እንዲያገኙ ማድረግ በመሆኑ በዚህም ጉዳይ ውሉ እንዲሰረዝ የጠየቀው ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት እንደሆነ የሚታመን ከመሆኑም በላይ የተከራዩ 1ኛ ተጠሪም ተግባር፣ ዓይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተግባር መሆኑን መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶቹ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 20837 በግንቦት 22 ቀን 1995 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔና የፌዴ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 22487 በጥር 16 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ሆነው ስለተገኙ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በሰኔ 1 ቀን 1974 ዓ.ም የተደረገው የቤት ኪራይ ውል በ1ኛ ተጠሪ በኩል ዓይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተግባር የተፈጸመበት ስለሆነ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 25938

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድነን ኪሮስ

ዓለ. መሐመድ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት - ነ/ፈጅ አያሌው ሊበን

ተጠሪ፡- የአቶ ገ/ሕይወት ከበዶም ወራሾች /2 ሰዎች/ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ውዝፍ የቤት ኪራይ ክፍያን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በወረዳ 15 ቀበሌ 30 የሚገኘውንና ቁጥሩ 602/10 የሆነውን ቤት በብር 1249 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ) ሐምሌ 18 ቀን 1984 ዓ.ም. በተፃፈ ውል ተከራይተው ከመስከረም ወር 1985 ዓ.ም. እስከ መጋቢት ወር 1989 ዓ.ም. ያለውን የኪራይ ሂሣብ ስላልከፈሉ ይህንኑ የኪራይ ሂሣብ፣ መቀጫ 20% እና የውሃ አገልግሎት ሂሣብ በድምሩ ብር 176,564 (አንድ መቶ ሰባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ አራት) ከነወጪና ኪሣራው ይክፈሉ በማለት ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመሠረተው ክስ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በሰጡት መልስ በማስረጃነት የቀረበው የኪራይ ውል በአመልካች ያልተፈረመና በሁለት ምስክሮች ፊት ያልተረጋገጠ ስለሆነ ፈራሽ ነው፤ የአመልካች ድርጅት የወቅቱ የደንበኞች አገልግሎት ኃላፊ በብር 510 (አምስት መቶ አስር) ሂሣብ መክራየት እንደምንችል ገልፀውልን የሂሣብ ክፍሉ ሊቀበሉን ባለመፈለጋቸው የኪራዩን ሂሣብ ብር 15,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) በአመልካች የሂሣብ ቁጥር ገቢ አድርገናል፤ ስለዚህ ልንከፍል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚገባን ተመሣሣይ ቤት ለኢትዮጵያውያን በሚከራይበት ዋጋ ተሰልቶ በባንክ የተከፈለው ገንዘብም ተቀንሶ ነው በማለት ተከራክረዋል። ፍ/ቤቱም የቀረበው የውል ሰነድ በተከራይ የተፈረመ በአከራይ ግን ያልተፈረመ በመሆኑ የውሉ ረቂቅ እንጂ ውል አይደለም፤ ሆኖም ግን ተጠሪዎች ቤቱን ያለውል በመያዝ ሲጠቀሙበት በመቆየታቸው ያለአግባብ የበለፀጉበትን ከመስከረም 1985 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 1989 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ሂሣብ ተጠሪዎች ራሳቸው ባመኑት በብር 510 (አምስት መቶ አስር) ሒሣብ ተሰልቶ ከሚመጣው ብር 28,000 (ሃያ ስምንት ሺህ) ላይ ተከሣሽ የከፈሉት ብር 15,000 (አሥራ አምስት ሺህ) ተቀንሶ የሚቀረውን ብር 12,650 (አሥራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ) ለአመልካች ይክፈሉ፤ ቅጣቱን በተመለከተም በግራ ቀኙ መካከል ውል በሌለበት ሁኔታ ተጠሪዎች ቅጣት እንዲከፍሉ አይገደዱም፤ የተጠየቀውን የውሃ ሂሣብ ግን ተጠሪዎች መክፈል እንደማይገባቸው ስላላስረዱ ብር 1,100 (አንድ ሺህ አንድ መቶ) ለአመልካች ይክፈሉ በማለት ወስኗል። የአሁን አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ቅሬታውን ባለመቀበል ውሣኔውን አጽንቶታል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው። ችሎቱም በአቤቱታው መነሻነት የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የኪራይ ውል ነው ተብሎ በአመልካች በቀረበው ሰነድ ላይ አከራዩ አልፈረመበትም ተብሎ በግራ ቀኙ መካከል የኪራይ ውል የለም በማለት የተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር አንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቷል።

መዝገቡን እንደመረመርነው የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው ውል ረቂቅ እንጂ ውል አይደለም ለማለት የበቃው በማስረጃነት ባቀረበው ሰነድ ላይ አከራይና ምስክሮች አልፈረሙበትም ከሚል

መንደርደሪያ በመነሳት መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል። በመሠረቱ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በማናቸውም ሁኔታ የተደረገ ስምምነት ውል ለማድረግ በቂ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1719/1/ ይደነግጋል። ከዚህ ድንጋጌ በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚፀና ወይም ሕጋዊ ውጤት ያለው ውል ለመመስረት በሁለቱም መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ነው። ስለዚህ ከኢትዮጵያ የውል ሕግ መሠረታዊ መርህ አንፃር በሕግ ወይም በተዋዋዮች በራሳቸው የተለየ ፎርም ካልተፈለገ በስተቀር ውልን ለመመስረት በተዋዋዮች መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ነው። በመሆኑም አንድ ውል ሕጉ ያስቀመጠውን የፎርም መስፈርት አያሟላም ተብሎ ውድቅ ሊደረግ የሚችለው ይህንን ውል የሚመለከት በግልጽ የተቀመጠና የተለየ የአፃፃፍ ሥርዓት /ፎርም/ ኖሮ ተዋዋዮች ይህንን ፎረም ሳይከተሉ ከቀሩ ወይም በተዋዋዮች ምርጫና ፍላጎት ስምምነቱ በጽሁፍ ከመሆኑ በተጨማሪ ሌሎቹንም ፎርማሊቲዎች እንዲሟሉ መፈለጋቸው በጽሁፉ በራሱ ወይም በሌላ መልክ ተገልፆ ሲረጋጥና ውሉም ይህንን በመከተል የተደረገ ካልሆነ ብቻ ነው። ስለሆነም የውልን አፃፃፍ ፎርምን የሚመለከትው የፍ/ብ/ሕግ ክፍል /አንቀጽ 1719-1930/ የኪራይ ውል የተለየ ፎርም መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ ድንጋጌ የለውም። በዚህም ምክንያት ሕጉ የኪራይ ውልን በጽሁፍ እንዲሆን የሚያዝ አስገዳጅ ድንጋጌ ባላስቀመጠበትና ተዋዋዮች ውሉ በጽሁፍ እንዲሆን የተስማሙ መሆናቸው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ውሉ የሕጉን ፎርማሊቲ ያላሟላ ስለሆነ ፈራሽ ነው ሲል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

በተጨማሪም የፍ/ብ/ሕግ በተለይ የኪራይ ውልን በሚመለከተው ልዩ ድንጋጌው በአንቀጽ 2898/3/ ላይ የኪራዩ ውል መከናወን ጀምሮ እንደሆነ የውሉን መኖር በምስክሮች ወይም በግምት አስተያየት ማስረዳት እንደሚቻል ደንግጓል። በመሆኑም ክርክር የተነሳበት የኪራይ ውል መከናወን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጀመረ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ከመሆኑ ባሻገር አመልካች የዚህን ውል መኖር በምስክር ወይም በግምት አስተያየት ከማስረዳት ይልቅ ተከራይ የፈረመበትን ማስረጃ በማቅረብ ያስረዳ ሲሆን ፍ/ቤቱ ይህ ማስረጃ ሕጉ በቂ ናቸው ከሚላቸው የማስረጃ አይነቶች የተሻለ መሆኑን ከግምት ውስጥ ባለማስገባት በግራ ቀኙ መካከል የኪራይ ውል የለም ሲል መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 04072 ሚያዝያ 29 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 32027 ሚያዝያ 14 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. በግራ ቀኙ መካከል የኪራይ ውል መኖሩን በመገንዘብ አመልካች በስር ባቀረባቸው ጥያቄዎች ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት 341/1/ መሠረት ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 28025

ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረ ፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፊጅ አያሌው ሊበን

ተጠሪ፡- አቶ ታደለ አበበ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሠረተው ክስ ተጠሪ በወረዳ 21 ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ ቁጥር 292/14 የሆነውን ቤት ተከራይተው ያልከፈሉት ውዝፍ ኪራይ እና የውሃ ክፍያ ያለባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ቤት መስራታቸው ስለተረጋገጠ የኪራይ ውሉ ፈርሶ ቤቱን እንዲያስረክቡ እና ውዝፍ ኪራይ እና የውሀ ሂሣብ እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ባልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ሊፈርስ የሚችለው አከራዩ ለተከራዩ የ2 ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሲሆን አመልካች ግን ይህን ስላላደረገ ውሉ ፈርሶ ቤቱን ለመረከብ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፣ ተጠሪ ያለባቸው ቀሪ ዕዳ ብር 442.20 (አራት መቶ አርባ ሁለት ከሃያ) ስለሆነ ይህንን ገንዘብ ለአመልካች ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የመጀመሪያውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል በሚል ነው፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች የኪራይ ውሉ እንዲፈርስለት የጠየቀው ተጠሪ ግዴታቸውን አክብረው የኪራይ ገንዘቡን ባለመክፈላቸውና ቤት የሠሩ በመሆኑ ሲሆን ቤት ባይኖራቸውም እንኳን በፍ/ህ/ቁ. 2966 መሠረት የኪራይ ውል በአንድ ወገን ብቻ ሊፈርስ እንደሚችልም ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ተጠራቅሟል የተባለውን የቤት ኪራይ አጠናቀው በመክፈላቸው እና ማስጠንቀቂያ ያልተሰጣቸው በመሆኑ እንዲሁም ግዴታቸውን መፈፀም ባይችሉ ወደ ሌላ ቤት እንዲዛወሩ ከሚደረግ በቀር ቤቱን እንዲለቁ ሊጠየቁ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የቤትን ኪራይ ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች አኳያ መርምሯል፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የተደረገው የኪራይ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ደግሞ ለተከራዩ በሚሰጥ ማስታወቂያ በማንኛውም ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል መሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2966(1) ሥር ተመልክቷል፡፡ አከራዩ በፈለገ ጊዜ ለተከራዩ ማስታወቂያ በመስጠት የኪራይ ውሉን ሊያፈርስ መብት አለው፡፡ ከፍ ሲል እንደተባለው አከራዩ ውሉን ለማፍረስ ማስታወቂያ ለተከራዩ መስጠት እንደሚያስፈልግው የተመለከተ ቢሆንም ማስታወቂያ መስጠት ግን ውሉን ለማፍረስ አስገዳጅ የሆነ ቅድመ ሁኔታ አይደለም፡፡ ተከራዩ ማስጠንቀቂያ ባለማግኘቱ የደረሰበት ጉዳት ወይ ኪሣራ ካለ ይህንኑ ከመጠየቅ በቀር ውሉ ሊፈርስ አይችልም በማለት ለመከራከር መብት አይሰጠውም፡፡

በተያዘው ጉዳይም በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የተደረገው ውል ላልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ በመሆኑ አመልካች በማንኛውም ጊዜ ማስታወቂያ ሰጥቶ ሊያቋርጠው ይችላል፡፡ ማስታወቂያ አለመስጠቱም ከፍ ሲል እንደተገለፀው በተጠሪ ላይ ኪሣራ ያደረሰ ከሆነ ተጠሪ ይህንኑ ሊጠይቁ

ከሚያስችላቸው በቀር የውሉን መፍረስ አያስቀረውም፡፡ ተጠሪውም በክሱ ቤቱን እንዲለቁ ከተጠየቁበት ጊዜ ጀምሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ እስኪሰጥበት ጊዜ ድረስ እንኳን ወደ አንድ ዓመት የሚጠጋ ጊዜ አልፏል፡፡ በመሆኑም ቤቱን ለመልቀቅ እንድችል ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስላልተሰጠኝ ልለቅ አይገባም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ የኪራይ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ በመሆኑ በማንኛውም ጊዜ አከራዩ ውሉን ማቋረጥ የሚችል ስለሆነ (የፍ/ሕ/ቁ. 2966 (1) ይመለከቷል) ተጠሪ የቤቱን ኪራይ ከፍዬ አጠናቅቄአለሁ፣ ሌላ ቤት መስራቴ ቤቱን እንድለቅ አያደርገኝም የሚለው ክርክራቸው ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ የኪራይ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የፍ/ሕ/ቁ. 2966(1) አኳያ ሲመረመር ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1ኛ/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20941 ግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ.ም የኪራይ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው የውሣኔ ክፍልና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22378 በጥቅምት 22 ቀን 1999 ዓ.ም ይህንኑ የውሣኔ ክፍል በማጽናት የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡

2ኛ/ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል በወረዳ 21 ቀበሌ 01 ቁጥር 292/14 በሆነው ቤት ላይ የተደረገው የኪራይ ውል ፈርሷል፡፡ ይህንኑ ቤት ተጠሪ ለአመልካች ያስረክቡ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 30894

ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

ደስታ ገብሩ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

አመልካች ፡- ወ/ሮ መዓዛነት ዳኜ

ተጠሪ ፡- ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ የስር ከሣሽ ነሐሴ 26 ቀን 1997 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ የአሁኑ አመልካች የስር ተከሳሽ በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 05 የሚገኘው ቁጥሩ 608 የሆነውን ቤት በማካሻነት ነው የያዝኩት፤ ኪራይ አልከፍልም ስላሉ ያልከፈሉትን ኪራይ እንዲከፍሉ ቤቱንም እንዲያስረክቡን ይወሰንል ሲል ክስ አቅርቧል፡፡

የአሁኑ አመልካች የሥር ተከሳሽ ደግሞ ጥቅምት 29 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ቤቱ በማካሻነት መንግስት የሰጠኝ በመሆኑ መንግስት የወሰደውንና በቀበሌ እጅ የሚገኘውን ቤቴን ሳይመልስልኝ በማካሻነት የያዝኩትን ቤት እንድመልስ የቀረበው ክስ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተከሳሽ ያለአግባብ የተያዘባቸው ቤት ካላቸው ከሰው ከሚጠይቁ በስተቀር የያዙትን የመንግስት ቤት ያለኪራይ ሊኖሩበት አይገባም፣ ብር 13,500 (አስራ ሦስት ሺህ አምስት መቶ) ክስ

ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀበት ጊዜ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ ይክፈሉ፣ ቤቱንም ለከሳሽ ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም ያቀረቡት አቤቱታም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ የአቤቱታው ቅሬታም የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤቶችን የመንግስት ያደረገው አዋጅ በወጣ ጊዜ በመንግስት ቤት እንዳለኝ በቅጽ 004 ተረጋግጦ አሁን የምኖርበትን የመንግስት ቤት ያለክፍያ እንድኖርበት ነሐሴ 3 ቀን 1968 ዓ.ም ተወስኗል፡፡ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴርም በማካካሻነት ቤት የተወሰደባቸው ቤቶች ብዙ ናቸው ስለተባለ እስከሚጣራ የኪራይ መካሳሱ ይቁም አሉ እንጂ በማካካሻነት ስም የያዘችውን ቤት ታስረክብ አላለም፡፡ በእኔና በመንግስት መካከል ያለው የቤት መቻቻል ውል አንደኛው ወገን ብቻ ሊያፈርሰው የሚችል አይደለም፡፡ ቀበሌና ኪራይ ቤቶች ለአሰራር እንዲያመች መንግስት ያቋቋማቸው የመንግስት መ/ቤቶች በመሆናቸው ከሳሽ ቤት ካለሽ ቀበሌን ክሰሽ፣ ጠይቂ ሊል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ መንግስት በማካካሻነት የሰጠሁሽን ቤት መልሺ ሊለኝ የሚችለው የሰጠሁት ቤቴን ሲመልስልኝ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ውዝፍ ኪራይ ክፈይ ቤቱንም ለኪራይ ቤቶች አስረክቢ በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሣኔው እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ደግሞ መስከረም 23 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የአመልካች ቤት ኪራይ እንዲካካስ ነሐሴ 3 ቀን 1968 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር በጥቅምት 19 ቀን 1978 ዓ.ም ዓ.ም በዓፈው ማሳሰቢያ ሁኔታዎች እስኪጣሩ ድረስ ማካሳሱ ለጊዜው እንዲቆም አሏል፡፡ በዚሁ መሰረት የፊተኛው ደብዳቤ የተሻረ በመሆኑ አመልካች የቤት ኪራይ መክፈል ነበረባቸው፡፡ ኪራይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ውዝፍ ኪራይ ከፍለው ቤቱን እንዲለቁልን ክስ መመስረታችን በአግባቡ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔም የሚነቀፍበት የፈፀመው የሕግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ውሣኔው እንዲፀድቅልን በማለት ተከራክሯል፡፡

በበኩላችን ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ያገኙት ለራሳቸው ቤት በማካሻነት ነው እየተባለ ባለበት ጊዜ የራሳቸው ቤት ሳይመለሰላቸው የያዙትን ቤት ለመንግስት መልሱ መባሉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም አመልካች ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ የተከራከሩት መንግስት የእኔን ቤት ሲወስድ ክርክር ያስነሳውን ቤት ያለ ኪራይ እንድኖርበት በማካሻነት ሰጥቶኛል፡፡ ይህን ቤቴን ሳይመልስልኝ የያዝሽውን ቤት ልቀቂ ሊለኝ አይችልም በማለት ነው፡፡ ክርክር ያስነሳውን ቤት አመልካች የያዙት በማካሻነት ስለመሆኑ የሚጠቁሙ ሰነዶች ከመኖራቸውም በተጨማሪ ተጠሪ ቤቱን መጀመርያ አመልካች ያገኙት በማካሻነት አይደለም በማለት ክዶ አልተከራከረም፡፡ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴርም ጥቅምት 19 ቀን 1978 ዓ.ምበፃፈው ደብዳቤ ግለሰቧ ቤቱን በማካሻነት የያዙት በብዙ ቤቶች መሆኑ ስለተደረሰበት ሁኔታውን ማጣራት አስፈልጓል፡፡ ኪራይ ቤቶች የመንግስት ቤት በማካሻነት የተሰጠበት የግለሰቧ የሆነውን ቤት ቁጥር አጣርቶ ለከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር እንዲገለጽና የማካሻ ኪራይም ለጊዜው እንዲቆም በማለት ነው ያሳሰበው፡፡ ይህ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፃፈው ደብዳቤ ግለሰቧ ማለት አመልካችዋ ክርክር ያስነሳውን ቤት በኪራይ ማካሻነት የያዙት በርግጥ በሰነዶቹ ላይ እንደተገለፀው ለመንግስት ያስረከቡት ቤት ኖሮአቸው ነው? ወይስ አይደለም? በማካሻነት የያዙት መንግስት ለወሰደባቸው ቤት ከሆነስ ለአንድ ቤት ነው ወይስ ለበርካታ ቤቶች? የሚሉትን ጥያቄዎች ማጣራት አስፈላጊ

መሆኑንና ሁኔታው ከተጣራ በኋላ ደግሞ አስፈላጊውን ውሣኔ መስጠት እንደሚገባው ነው የሚገልፀው፡፡

ሆኖም ተጠሪው መ/ቤት በሚኒስቴሩ ደብዳቤ መሠረት አመልካች በማካሻነት የመንግስትን ቤት የያዙበት መንግስት የወሰደባቸው ቤት ስለመኖርና ያለመኖሩ ማጣራት ሲገባው ይህን ሳያደርግና በርግጥም አመልካች የመንግስትን ቤት በማካሻነት ስም የያዙት ያለአግባብ መሆኑን ሳያረጋግጥ ለመንግስት የሰጠሽው ቤት ካለ ከሰሽ ጠይቂ፤ የያዝሽውን ቤቴን ግን ልቀቂ በማለት ክስ መመስረቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የተመሰረተውን ክስና የተደረገውን ክርክር ስንመለከተው ደግሞ አመልካች ቤቱን የያዝኩት በማካሻነት ነው በማለት እየተከራከሩ ባሉበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ቤቱን የያዙት በማካሻነት ነው ወይስ አይደለም? በማካሻነት የያዙት ከሆነስ መንግስት በዚሁ ክርክር ባስነሳው ቤት ማካሻነት የወሰደውን ቤት ሊመልስላቸው ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ አጣርቶ መወሰን ሲገባው የማጣራት ቅድመ ሁኔታ የሚያስቀምጠውን ሚኒስቴሩ መ/ቤት ጥቅምት 19 ቀን 1998 ዓ.ም የፃፈውን ደብዳቤ ቀደም ብሎ የተሰጠውን የማካሻነት ውሣኔ የሚሽር ነው በማለት በተሳሳተ ሁኔታ በመተርጎም ማካሻነቱ ቀሪ ሆኖአል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ተገንዝበናል፡፡ የሥር ፍ/ቤቱ በማካሻነት በያዝሽው ቤት ምትክ መንግስት የወሰደብሽ ቤት ያለው በቀበሌ እጅ ከሆነ ቀበሌውን ከሰሽ ከምትጠይቂ በስተቀር ቤቴን መንግስት ሳይሰጠኝ በማካሻነት የያዝኩትን ቤት ልለቅ አይገባም በማለት ልትከራከሪ አትችይም በማለት የሰጠው ውሣኔም ቀበሌና ኪራይ ቤቶች ሁለት የመንግስት አካላት ቢሆኑም በማካሻነት ተያዘ የተባለው ቤት ሁለቱንም የሚያቆራኛቸው በመሆኑ በአንድ ዘንግ ቆመው በጉዳዩ መከራከር የሚገባቸው መሆኑን የሥር ፍ/ቤት እንዳልተገነዘበው ለመረዳት ችለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተደረገ የተባለው መቻቻል ወይም መካካስ አመልካች ሲያከራዩት የነበረው ቤት ውስጥ የነበሩት ተከራይ ግለሰቦችን ላለማፈናቀል ሲባል ይህ ቤት በመንግስት እጅ ሆኖ እንዲቆይ መደረጉ አመልካች ኪራይ እየከፈሉ ሲኖሩበት የነበረውን የመንግስት ቤት አመልካችዋ ኪራይ ሳይከፍሉ እንዲኖሩበት በአመልካችዋና በመንግስት ፈቃድና ስምምነት የተደረገ ነው የሚመስለው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1840 መሠረት ተዋዋዮቹ አስቀድመው የመቻቻሉ ጉዳይ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈፀም በመግለጽ የወሰኑበት ሆኖ ከተገኘ ደግሞ የውሉ መሰረዝ ወይም መፍረስ ጥያቄ ሲነሳ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1815 መሠረት ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት የሚመለሱበት ሁኔታ ስለሚኖር የሥር ፍ/ቤት እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ቤቱ የተያዘው በማካካሻነት መሆን ያለመሆኑን እንደዚሁም ቤቱ በማካካሻነት የተያዘው በአንድ ቤት ወይም በብዙ ቤቶች መሆን ያለመሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል ቀበሌውን በጣልቃገብነት ክርክሩ ውስጥ አስገብቶና ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን መወሰን ሲገባው ይህን መንገድ ሳይከተል ማካካሻው ለጊዜው እንዲቆም የሚለውን የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ደብዳቤ ማካካሻነቱ ተሰርዟል እንደሚል አድርጐ በመተርጐም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መሻር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 57332 መጋቢት 13 ቀን 1998 ዓ.ም ወ/ሮ መዓዛ ገነት ዳኘ ክርክር ያስነሳውን ቤት ለኪራይ ቤቶች እንዲያስረክቡ እንደዚሁም ኪራይ ብር 13,500 (አስራ ሦስት ሺህ አምስት መቶ) እንዲከፍሉ በማለት የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 46871 ሚያዝያ 12 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡

2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሥር ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች የሆነውን ቤት በማካካሻነት በመያዝ ቤቱን እያከራየ ይገኛል የተባለው ቀበሌ በጣልቃ ገብነት ክርክሩ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ፣ ማካካሻ የተደረገላቸው የአመልካችና የመንግስት ቤቶች የትኞቹ መሆናቸውን ለመለየት እንዲቻል ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ እንዲመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31601

የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

አመልካች፡- ወ/ሮ መዓዛ ይሕደጎ - ጠበቃ ግራዝማች አወቀ አእምሮ ቀረበ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አየለ ወልዴ ቀረበ፡፡

2. ጌታቸው ሃይለማርያም ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የኪራይ ውልን መነሻ በማድረግ የቀረበ የገንዘብ ክፍያ እና ቤት ልረከብ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በማንበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችውም አመልካች ናት፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተችው በውክልና የማስተዳድረውን ቤት በኪራይ ውል ይዘው እየተገለገሉበት ቢሆንም፤ ኪራዩን ግን ሊከፍሉ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ የተጠራቀመውን ኪራይ ከፍለው ቤቱን ሊያስረክቡኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ የማንበራዊ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኝ ወገኖችን ካከራከረ በኋላ፣ ተከሣሾች የኪራዩን ገንዘብ ይክፈሉ፤ በኪራዩ መቀጠል ሁለቱ ወገኖች የማይስማሙ ከሆነም የሚፈለግባቸውን ኪራይ ከፍለው ቤቱን ለከሣሽ ያስረክቡ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ክርክሩን የሰማ ሲሆን በመጨረሻም የማንበራዊ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት ውሣኔውን ሽሯል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ይህንኑ አጽንቷል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 27 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ክሱ በቀረበ ጊዜ የኪራይ ገንዘብ የተጠየቀበትን ቤት ግምት ጭምር መቅረብ ነበረበት፡፡ ግምቱ ቢቀርብም ኖሮ ጉዳዩ ክሱን ካየው የማንበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን በላይ ይሆን ነበር በሚል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ በቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተችው በመሃከላቸው በተደረገው የኪራይ ውል መሠረት የሚፈለግባቸውን የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍሏት እና በኪራይ ይዘውት የሚገኙትን ቤትም እንዲለቁላት ነው፡፡ በመዝገቡ እንደተገለጸውም በክሱ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ብር 4800 /አራት ሺህ ስምንት መቶ/ ነው፡፡ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 50 (1) አንደተመለከተው የቀበሌ ማንበራዊ ፍ/ቤቶች ግምታቸው ከብር 5000 /አምስት ሺህ/ ያልበለጠ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮችን የማየት /የመዳኘት/ ሥልጣን አላቸው፡፡ አመልካች ክሱን ለማህበራዊ ፍ/ቤት ያቀረበችው በዚህ መሠረት ሲሆን፣ ማንበራዊ ፍ/ቤቱም ሥልጣን እንዳለው በመገንዘብ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የማንበራዊ ፍ/ቤቱ ከስልጣኑ ውጪ ጉዳዩን አይቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸው ለክሱ መነሻ የሆነው ምክንያት የኪራይ ገንዘቡ አለመከፈሉ ነው፡፡ አመልካች የከሰሰችው የኪራይ ውሉን መሠረት በማድረግ እስከሆነ ድረስ በቤቱ ላይ የንብረት ጥያቄ /የባለ ሃብትነት/ ያነሳች ይመስል በቤቱ ግምት መጠን ዳኝነት ከፍለሽ አልጠየቅሽም ወይም መጠየቅ ነበረብሽ የምትባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የተጠየቀው የኪራይ ገንዘብም በውሉ መሠረት ተሠልቶ ቀርቦ ሳለ ይግባኙን የሰማው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁ. 227 (2)ን በመጥቀስ የዓመቱን ክፍያ በ20 ተባዝቶ መቅረብ ነበረበት የሚል ትችት መስጠቱ አግባብ አይደለም፡፡ እንደምንመለከተው የኪራይ ገንዘቡ የሚከፈለው በየወሩ ሲሆን በዚህ መሠረት ባለመከፈሉ ሂሣቡ ተሰልቶ ክሱ ቀርቧል፡፡ አመልካች ከዚህ ውጪ እንድታደርግ አትጠበቅም /በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 226 የተመለከተው ድንጋጌ ተሟልቷል/፡፡ ሲጠቃለል የቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ክሱን ያስተናገደው በሕጉ የተሰጠውን ሥልጣን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ በመሆኑም ክሱን ለማየት ሥልጣን አልነበረውም ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01137 ሚያዝያ 25 ቀን 1998 ዓ.ም. የተሰጠው እና በከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03572 ሚያዝያ 3 ቀን 1999 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በቂርቆስ ክ/ከተማ የቀበሌ 06 ማኅበራዊ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 2096 ሐምሌ 22 ቀን 1996 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31634

መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ

ተጠሪዎች፡- 1. የአቶ ወርቁ ደመሣ ሚስት ወ/ሮ ጽጌ በየነ በራሳቸው እና ሞግዚት በሆኑላቸው

ሀ. ትዝታ ወርቁ

ለ. ሚካኤል ወርቁ

ሐ. ቤተልሔም ወርቁ

2. ወ/ሪት ትዕግሥት ወርቁ
3. አቶ መላኩ ወርቁ
4. አቶ ዮሴፍ ወርቁ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች በጥር 13 ቀን 1996 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ በወረዳ 7 ቀበሌ 29 የሚገኘው ቁጥር 550 /አምስት መቶ ሃምሳ ብር/ የሆነው ቤት አቶ ወርቁ ደመሳ ከኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ በወር በብር 500/አምስት መቶ/ ተከራይተዋል፡፡ ተከራይ ከሞቱ በኋላም ተከሣሾች የተከራዩን መብትና ግዴታ በመያዝና በመሸከም ተስማምተው በቤቱ መኖር ቀጥለዋል፡፡ ሆኖም ከሚያዝያ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 30 ቀን 1996 ዓ.ም. የተወዘፈውን ኪራይ እንዲከፍሉ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ሊከፍሉ ባለመቻላቸው የቤቱን ውዝፍ ኪራይ ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

51,500፣ /ሃምሳ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ወለድ ብር 32,257.45 /ሠላሳ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ሰባት ብር ከ አርባ አምስት/ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 770 /ሰባት መቶ ሰባ/ በድምሩ ብር 84,527.45 /ሰማኒያ አራት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሰባት ከአርባ አምስት/ በመክፈል ቤቱን ሊያስረክቡኝ ይገባል በማለት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የመሰረተው ክስ ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን በማከራከር ከሚያዚያ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. እስከ መስከረም 1 ቀን 1994 ዓ.ም. ድረስ መክፈል የነበረበት የቤት ኪራይ ለማስከፈለ ክሱ የቀረበው 2 ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ ኪራዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል፡፡ ከመስከረም 1 ቀን 1994 ዓ.ም. በኋላ መክፈል የነበረበት ኪራይ ደግሞ ያለመክፈሉን ተከሳሾች ስላመኑ መክፈል አለባቸው፡፡ ወለዱን በተመለከተ ደግሞ ኪራዩ ሊከፈል ያልቻለው ተከሣሾች እንክፈል ሲሉ ከሣሽ ውዝፉን ካልከፈላችሁ ሌላውን አልቀበልም በማለቱ ምክንያት መሆኑን ስለተረጋገጠ ተከሣሾች ወለዱን መክፈል አይገባቸውም፡፡ በመሆኑም ተከሣሾች ከመስከረም 1994 ዓ.ም. ጀምሮ ውሣኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የቤት ኪራይ ብር 22899/ሀያ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ዘጠኝ/ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 770/ሰባት መቶ ሰባ/ በድምሩ ብር 23,669.00/ሀያ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ/ ለከሣሽ እንዲከፍሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተከሣሾች ያልፈፀሙት ግዴታ አለመኖሩ ባለመረጋገጡ ቤቱን ለከሣሽ ሊያስረክቡ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ፍርዱ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን በመሠረዝ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች በሁለቱም ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር በመሰኘቱ ምክንያት ለዚህ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ የጠቀሳቸው ቅሬታዎችም አቶ ወርቁ ዳመሣ ከመስከረም 1985 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 30 ቀን 1987 ዓ.ም. ያለውን የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ ተከሰው ተወስኖባቸው አፈፃፀሙን እየተከታተልን እያለን በሞት ከዚህ ዓለም ተለይተዋል፡፡ የቤቱን ኪራይ

አስመልክቶ መብትና ግዴታ ያለው ሰው ካለ ማንነቱን እያጠያየቅን ቆይተናል፡፡ ኪራዩን በወቅቱ ለመሰበሰብ የልቻልነውም በዚሁ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ኪራዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል ያሉት አግባብነት የለውም፡፡ መልስ ሰጭዎች ውዝፉን ሳይከፍሉ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ኪዩን እንክፈሉ ሲሉ መጀመሪያ ውዝፉን ካልከፈላችሁ የአሁኑን ብቻ አንቀበልም ማለታችንም በአግባቡ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች መልስ ሰጭዎች ውዝፉን መክፈል የለባቸውም፡፡ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ኪራይም ያለወለድ መክፈል የለባቸውም፡፡ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ኪራይም ያወለድ መክፈል አለባቸው፡፡ ያልተወጡት ግዴታም ስለሌለ ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም በማለት የሰጡት ውሣኔ ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህ ውሣኔያቸው ልክ እንደክሳችን እንዲወስንልን የሚሉ ናቸው፡፡

መልስ ሰጭዎችም ሕዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ ከሚያዚያ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1993 ዓ.ም. ድረስ ያለው የቤት ኪራይ በወቅቱ በአቶ ወርቁ ደመሣ ተከፍሏል፡፡ አልተከፈለም ቢባልም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው፡፡ አመልካች ኪራዩን በወቅቱ እንዳንሰባሰብ የሚቹን መብትና ግዴታ ማን እንደተሸከመ ባለማወቃችን ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ነው ያለው በስር ፍ/ቤት የተነሣ ክርክር አይደለም፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔውን ማጽናቱ በአግባቡ ነው፡፡ አመልካች የኪራይ ውሉ እንዲቋረጥ የጠየቀው የውል ግዴታቸውን በውሉ አንቀጽ 4 መሠረት አልተወጡም ያለውም ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ላወጣው ማስጠንቀቂያ ኪራይ ለመክፈል ፈቃደኞች መሆናችንን ገልፀናልና፡፡ በመሆኑም የውሉ አንቀጽ 4/2/ለ/ በኛው ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔም የሕግ ስህተት የሌለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ ውሣኔያቸው ፀድቆ እንድንሰናበት ይወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው የመልስ መልስ ክርክርሩን ለማጠናከር ሞክሯል፡፡

በበኩላችን ደግሞ ተጠሪዎች ከሚያዝያ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1993 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ውዝፍ የቤት ኪራይ መክፈል አለባቸው ወይስ የለባቸውም? ከመስከረም 1994 ዓ.ም. ጀምሮ ላልከፈሉት የቤት ኪራይስ ወለድ መክፈል አለባቸው ወይስ የለባቸውም? ቤቱንስ ለአመልካች መመለስ ይገባቸዋል ወይስ አይገባቸውም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረነዋል፡፡

መዝገቡን እንደረመመርነውም አመልካች ተከራዩ በሞት ከዚህ ዓለም ከተለዩ በኋላ ኪራዩን መሰብሰብ ወይም ደግሞ ቤቱን መረከብ ሲኖርበት የሚች ወራሾች ቤቱን እየተጠቀሙበት መሆኑን እያወቀ ኪራዩን ሳይሰበስብ ከሚያዝያ 1987 ዓ.ም. እስከ ነሐሴ 1993 ዓ.ም. መቆየቱ በማናቸውም መስፈርት ከአቅም በላይ ነው ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ነጥብ ላይ የሥር ፍ/ቤቶች ኪራዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ተደርጎ መቆጠር አለበት በማለት መወሰናቸው በግባቡ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከ1994 ዓ.ም. በኋላ ያለውን የኪራይ ክፍያን ስንመለከትም ተጠሪዎች ኪራዩን እንክፈል በማለት እየደጋገሙ ሲጠይቁት ከሚያዝያ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ውዝፍ ኪራይ ካልከፈላችሁ በስተቀር ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን የቤት ኪራይ አልቀበልም እያለ ሳይቀበል ቀርቶ ሲያበቃ አመልካች በዚሁ ራሱ ሳይቀበል ባቆየው ክፍያ ወለድ መጠየቁ አግባብነት ስለሌለው አመልካቹ ወለድን አስመልክቶ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የመጨረሻውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪዎቹ አቶ ወርቁ ዳመሣ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ በየወሩ የቤቱን ኪራይ የመክፈል ግዴታ እያለባቸው ይህን ግዴታቸውን ያለመፈፀማቸውን ይልቁንም ኪራዩን እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ አመልካች ሳይጠይቅ ጠይቆ ፈቃደኝነት ካላገኘም ክስ ሳይመሰርት ሁለት ዓመት ያለፈ በመሆኑ ከ1987 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም. የነበረው የቤት ኪራይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል ማለታቸው በወቅቱ ማለት ሁለተ ዓመት ሳያልፍ እኛን በመክሰስ ገንዘብህን መሰብሰብ ነበረብህ፡፡ ይህን ባለማድረግህ መንግሥት የጣለብህን ግዴታ አልተወጣህም የሚል ትርጉም የሚሰጠው እንጂ ተጠሪዎች ኪራይ የመክፈል ግዴታቸውን ተወጥተዋል ማለት አይደለም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 /መ/ ዕዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት የተደነገገው ደግሞ ባለገንዘቡ ሁለት ዓመት ሳይሞላው ክስም መስርቶ ቢሆን ገንዘቡን በወቅቱ ተግቶ እንዲሰበስብ ለማድረግ እና ሁለት ዓመት ካለፈው በኋላ ከሶም ቢሆን ገንዘቡን ለመሰብሰብ እንደማይችል ለማስገንዘብ እንጂ ባለዕዳው ሁለት ዓመት እስከሚያልፍ ዕዳውን ሳይከፈል ቢቆይ የመክፈል ግዴታውን እንደተወጣ ለመቁጠር ወይም ለማረጋገጥ አይደለም፡፡ በተጨማሪ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ኪራይ ያልከፈሉትን ተከራዮች ኪራዩን በክስ እንዲከፍሉ ከመገደድ የሚያድናቸው እንጂ ኪራዩን የመክፈል ግዴታቸውን እንደተወጡ የማያረጋግጥላቸው እንዳልሆነ ለመረዳት ችለናል፡፡

ይህን መሠረት በማድረግ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ ስንመለከተው ከ1987 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም. የነበረው የቤት ኪራይ መጠየቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሲታይ ሁለት ዓመት ያለፈበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል፡፡ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ መክፈል የነበረበት የቤት ኪራይም በወቅቱ ሳይከፈል የቀረው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ክፍያውን አልቀበልም በማለቱ ምክንያት በመሆኑ ወለድ ሊጠየቅበት አይገባም በማለት መወሰናቸው በአግባቡ ነው፡፡ ተጠሪዎች ያልተወጡት ግዴታ የለም በማለት ቤቱን ለአመልካች ማስረከብ የለባቸውም በማለት የሰጡት ውሣኔ ደግሞ ተጠሪዎቹ በወቅቱ ያልተወጡትን በየወሩ ኪራይ የመክፈል ግዴታ እንደተወጡ የሚያረጋግጥ አና በውላቸው አንቀጽ 4 ላይ የተደነገገውን ግዴታ ያላገናዘበ፣ እንደዚሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 መንፈስንም የሳተ በመሆኑ ውሣኔያቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፊ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 36746 ሐምሌ 24 ቀን 1998 ዓም የሰጠው ፍርድና የፊ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 49555 ሚያዝያ 15 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ የሚፀናና የሚሻር ነጥብ ያለበት በመሆኑ

ሀ/ ፍርድ ቤቶቹ የቤቱን ኪራይ የተመለከተውን ክፍያ መልስ ሰጭዎች ለአመልካች ብር 23,669.00 (ሃያ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ) እንዲከፍሉ በማለት የወሰኑትን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንተናል፡፡

ለ/ በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቶቹ መልስ ሰጪዎች ቤቱን ለአመልካች ማስረከብ የለባቸውም በማለት የሰጡትን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. መልስ ሰጭዎች በፊ/መ/ደ/ፍቤት በዚህ ጉዳይ ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር የቤቱን ኪራይና ተጨማሪ እሴት ታክሱን በድምሩ ብር 23,669.00 (ሃያ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ) ለአመልካች ይክፈሉ ይባላ፡፡

3. መልስ ሰጪዎች በክሱ የተጠቀሰውን ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ ቤቱን እስካስረከቡበት ቀን ድረስም ኪራዩን ይክፈሉ ይባላ፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31917

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነገረፈጅ ድጋፌ ለገሰ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ለምለም ገ/ትንሳኤ በሌሉበት ይታያል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48841 ታህሣስ 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52647 ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ተጠሪ የንግድ ድርጅት ከሌላ ሰው ስትገዛ፣ ንግድ ይካሄድበት የነበረውን ቤት የመከራየት መብቷ ተጠብቆላታል፤ ቤቱ የአመልካች በመሆኑ በፊት የነበረው የኪራይ ተመን ተስተካክሎ ብር 2009 /ሁለት ሺ ዘጠኝ/ የተተመነ ቢሆንም ኪራዩ በዛብኝ ብላ በማመልከቷ ብር 1448 /አንድ ሺ አራት መቶ አርባ ስምንት/ እንደተደረገባት አመልካች በማመልከቻው ገልጿል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ወይም ተጠሪ በቀድሞው ኪራይ ብር 125/አንድ መቶ ሃያ አምስት/ ብቻ የከፈለች በመሆኗ ከታህሣስ ወር 1993 ዓ.ም እስከ ግንቦት 2 ቀን 1996 ዓ.ም ያለው የቤት ኪራይ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ 57,614.20 (ሃምሣ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ አስራ አራት ከሐያ) ከወጭና ኪሣራ ጋር

እንድትከፍል ይወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች ይህንን ክሱን የሚያስረዱ የጽሑፍ ማስረጃዎችንም አቅርቧል፡፡

ተጠሪ የአመልካች ክስና ማስረጃ ከፍርድ ቤቱ መጥሪያ ጋር ደርሷት መልሷን ይዛ እንድትቀርብ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ቀርባ ባለመከራከሯ፡ ጉዳዩን ተጠሪ በሌለችበት ታይቷል፡፡ ጉዳዩን ተጠሪ በሌለችበት ያየው የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ከሳሽ (አመልካች) በቀድሞ የኪራይ ተመን ከተከሳሽ (ተጠሪ) ኪራይ ሲቀበል ከቆየ በኋላ እንደገና አዲስ ተመን አውጥቻለሁ ይከፈለኝ በማለት መጠየቅ ስለማይችል ተከሳሽ የሁለት ወር ከሁለት ቀን ሂሳብ ብቻ በአዲሱ የኪራይ ተመን መሠረት ትከፍላለች በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ እና የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች ይኸ ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት አለበት፤ ተጠሪ በአዲሱ የኪራይ ዋጋ ካልተስማማች ቤቱን ለአከራዩ ማስረከብ ነበረባት፤ ይህን አላደረገችም፤ እንደዚሁም በተመሣሣይ ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 23067 የሕግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች ይህንን በመተላለፍ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ባለመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በአድራሻዋ ባለመገኘቷ በጋዜጣ ጥሪ የተደረገላት ሲሆን ያልቀረበች በመሆኑ የሰበሩ ክርክር በሌለችበት እንዲታይ ብይን ተሰጥቷል፡፡

በሥር እና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ የድርጅት ቤት ኪራይ ሲተመን ሙሉ እውቀት የነበራት መሆኑንና የኪራዩ መጠን በዝቶብኛል ብላ በማመልከቷ ኪራዩ ከሁለት ሺ ዘጠኝ ብር ወደ አንድ ሺ አራት መቶ አርባ ስምንት ብር ዝቅ እንዲል ተወስኖላታል፡፡ ተጠሪ ይህንን ለማስረዳት በአመልካች በኩል የቀረበውን ማስረጃ ቀርባ አላስተባበለችም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ባቀረበችው አቤቱታ መነሻ ተሻሽሎ በተወሰነው የቤቱ ኪራይ የማትስማማ ከሆነ፣ ቤቱን ለአከራዩ በማስረከብ ከአመልካች ጋር የነበረው የአከራይ ተከራይ ውል ማቋረጥ ነበረባት፡፡

ተጠሪ የንግድ ድርጅቱን ስትገዛ የንግድ ድርጅቱ ያለበትን ቤት የመከራየት መብት የሚተላለፍላት እንደሆነ በንግድ ሕጉ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የመከራየት መብት ስለተላለፈላት ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል አላት፡፡ ይኸም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው የኪራይ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ነው፡፡ ይህ ከሆነ አከራዩ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2966 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የኪራዩን ዋጋ እንደጨመረ አስታውቋል፡፡ ተጠሪ የታደሰው የኪራይ ውል በዝቷል በማለት አመልክታ ተሻሽሎላታል፡፡ ተጠሪ በተሻሻለው የኪራይ ውል ዋጋ ከደረሳት በኋላ በቤቱ መኖር ከቀጠለች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2968 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ውሉ እንደታደሰ የሚቆጠር ይሆናል፡፡

ይህ ከሆነ ተጠሪ በተሻሻለው የኪራይ ውል መሠረት የመክፈል ግዴታ አለባት፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በተሻሻለው የኪራይ ዋጋ መሠረት የመክፈል ግዴታ የለባትም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተጠሪ በተሻሻለው የቤት ኪራይ ዋጋ መሠረት 15% ተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የመክፈል ግዴታ አለባት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48841 ታህሣሥ 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52647 ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆኑ ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ አመልካች ክስ ያቀረበበትን የኪራይ ሂሳብ ብር 57,614.20 /ሐምሣ ሰባት ሺ ስድስት መቶ አስራ አራት ከሃያ / 18% ተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር መክፈል ይገባታል ብለን ወስነናል፡፡
3. ወጭና ኪሣራ አመልካች ራሱን ይቻል

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32521

ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሐሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድነን ኪሮስ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ አብርሃም አጥላባቸው

ተጠሪ፡- እነ ዳባ ኢጃቶ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 24 ቀበሌ 15 ክልል የሚገኘውንና ቁጥር 802/1-2-803/ 1-2 የሆነውን ቤት ለቢሮ አገልግሎት በወር ብር 1,800 (አንድ ሺ ስምንት መቶ) ለኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት አከራይቶ የነበረ ሲሆን ተከራዩ ቢሮውን ወደ ሌላ ቦታ በመቀየሩ ከታህሳስ 1988 ዓ.ም. ጀምሮ በድርጅቱ ውስጥ የነበሩ አባሎች ወደ ኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ስለተዛወሩ በቤቱ ውስጥ የነበሩት እዚያው እንዲቆዩ ስለፈለገ የኪራይ ውሉ ወደ ኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ተዛውሮ በቢሮነት እንድንጠቀምበት ይፈቀድልን በማለት የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን በደብዳቤ ጠይቆ ሲከታተል ከቆየ በኋላ ውል ሳይፈጸም አባሎቹ በቤቱ እንዲጠቀሙ አድርጓል፡፡ በዚህ መሠረት የአሁን ተከሣሾች የኪራይ ውል ሳይኖራቸው ኪራይም ሳይከፍሉ ያለከሳሽ ፈቃድ ከጥር 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ በሕገወጥ መንገድ እየተጠቀሙበት ስለሚገኝ በአጠቃላይ ያለውን ውዝፍ ኪራይ ብር 183,600.00 (አንድ መቶ ሰማኒያ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ) ወለድ ብር 113,511.35 (አንድ መቶ አሥራ ሦስት ሺህ አምስት

መቶ አሥራ አንድ ከሰላሳ) በድምሩ ብር 297,111.35 (ሁለት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ አንድ መቶ አሥራ አንድ ከሰላሳ አምስት) ከፍለው ቤቱን ለከሣሽ እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሣሽ ክስና ማስረጃ ለተከሳሾች ደርሶ መልስ እንዲሰጡ በታዘዘው መሠረት የተወሰኑት ተከሣሾች ቀርበው መልስ ሲሰጡ የተወሰኑት ደግሞ በአግባቡ ተጠርተው ባለመቅረባቸው በሌሉበት ጉዳዩ እንዲታይ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡ የቀረቡት ተከሣሾች በሰጡት መልስ ክስ የቀረበበት ቤት የከሣሽ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ከሣሽም አስተዳድሮት አያውቅም፡፡ ከሣሽ ከእኛ ጋር ውል ስላልፈጸመ በማናውቀው ውል መነሻነት የኪራይ ገንዘብ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ለክሱ መሠረት የሆነውን ውል ከሳሽ ያደረገው ከኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ጋር ሲሆን በዚህ ውል መሠረትም ተከሣሾች በቤቱ ውስጥ ሊገቡ መቻላቸውን ከሣሽ በክሱ ከመግለጹም በላይ በውሉ መሠረት ኪራይ ሊከፍል የተስማሙና ሲከፍል የቆየው ይሄው የኦሮሞ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት እንጂ ተከሣሾች አይደሉም ካለ በኋላ ውሉ ሳይታደስ ቀርቶ ቤቱ ያለ አግባብ ተይዞብኛልና ይለቀቅልኝ ወይም ውዝፍ ኪራይ ይከፈለኝ በማለት ሊጠይቅ የሚችለው በውል የተከራየውን ወገን እንጂ ተከሣሾችን አይደለም፡፡ እንደዚሁም ውሉ ስላለቀ ሊያስረክበን ይገባል ከሆነም ውሉን ለማፍረስ ውል የገባውን ወገን መክሰስ እንጂ ውሉ ባልፈረሰበት ሁኔታ ቤቱ እንዲለቀቅለት ያቀረበው ጥያቄ በአግባቡ አይደለም በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም በበኩሉ አቤቱታው ለሰበር ይቀርባል ብሎ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ተጠሪዎች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ወይንስ አይገባም? ኪራይስ ሊከፍሉ ይገባልን? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የሰበር አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤትም ሆነ በዚህ ችሎት ክርክር ሲደረግ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት ባለንብረት ስላልሆነ ቤቱ ይለቀቅልኝም ሆነ ኪራይ ይከፈለኝ ማለት አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም ግን አመልካች ክስ ያቀረበው ባለቤትነትን በመፋለም ረገድ /Petitory action/ ስላልሆነ የቤቱ ባለቤት ስለመሆኑ ማስረዳት የሚጠበቅበት አይሆንም፡፡ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ለኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት አከራይቶት እንደነበር በአስረጂነት ባቀረበው የኪራይ ውል የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪዎችም ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል ሳይኖራቸው በቤቱ ውስጥ እንደሚኖሩ በአመልካች ማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ በተጠሪዎችም አልተካደም፡፡

ከሣሽ የሆነ ወገን የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስለቀቅና ለመረከብ ክስ ባቀረበ ጊዜ በማናቸውም ምክንያትና ሁኔታ በዚሁ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሠፍረው የሚገኙትን ሁሉ አጣምሮ መክሰስ እንደሚችል ተከሣሾችን አጣምሮ ስለመክሰስ /Joinder of defendants/ በሚደነግገው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 36/4/ ላይ ተመልክቷል፡፡

ለመብትም ሆነ ለግዴታ ምንጭ ውል ወይንም ሕግ ሲሆን ተጠሪዎች ግን ከውልም ሆነ ከሕግ የመነጨ መብት ሳይኖራቸው ለክርክሩ

ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ያለአግባብ በመበልጸግ ላይ እንደሚገኙ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣኑ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለክሱ መሠረት በሆነው ቤት ላይ የውል ግንኙነት የተመሠረተው በአመልካችና በኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት መካከል እንጂ ከተጠሪዎች ጋር ስላልሆነ ቤት ይለቀቅልኝም ሆነ ኪራይ ይከፈለኝ ተብሎ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ ይሁንና በአመልካችና በተጠቀሰው የኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት መካከል በዚሁ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የኪራይ ውል እንደነበር የተረጋገጠ ቢሆንም ተከራዩ ቤቱን ለቆ ሄዷል ከተባለ የኪራይ ውሉ መቋረጡን የሚያስገነዝብ ከመሆኑም በላይ አመልካችም በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው ውሉን መሠረት በማድረግ ሳይሆን አላግባብ በልጽገዋል በማለት ስለሆነ ይህንኑ የተቋረጠ ውል መሠረት አድርጎ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሣኔ በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32793 ሚያዝያ 5 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 25411 ግንቦት 14 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ለክሱ ምክንያት በሆነው ቤት ከውልም ይሁን ከሕግ የመነጨ መብት ሳይኖራቸው እየኖሩበት ያለአግባብ የበለጸጉ ስለሆነና የበለጸጉበትም መጠን ቤቱ አስቀድሞ ሲከራይበት በነበረው ልክ ስለሆነ በዚሁ መሠረት አመልካች አስልቶ የጠየቀውን ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

183,600.00 /አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ/ ተጠሪዎች ለአመልካች በመክፈል ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡

የወለድ ክፍያ ጥያቄውን በተመለከተ በመካከላቸው የኪራይ ውል ስለሌለ ተጠሪዎች ሊከፍሉ አይገባም ብለናል፡፡

3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ 34456

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ብርሃኑ አመነው

መድሕን ኪሮስ

ፀጋዬ አስማማው

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነገረ ፈጅ ቀርቧል፡፡

መ/ሰጪ፡- ወ/ት ደብሪቱ ወልደሃና - ጠበቃዋ ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገን የቤት ኪራይ ውል የሚመለከት ነው፡፡

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ በቀድሞ ወረዳ 21 ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና የቤት ቁጥር 288/1-5 የሆነውን ቤት ለመኖሪያ አገልግሎት በወር ብር 22 (ሃያ ሁለት ብር) የኪራይ ዋጋ ለአንድ ዓመት ጊዜ በ1977 ዓ.ም ለመልስ ሰጪ አከራይቶ የነበረ መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጪ በቤቱ ከአንድ ዓመት በላይ የተገለገለች በመሆኑ የኪራይ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር በመሆኑ ውሉ አመልካች ለመልስ ሰጪ በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ፈርሷል፡፡ ስለሆነም መልስ ሰጪ ቤቱን እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ ሲል በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዮን በቅድሚያ ያስተናገደው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መልስ ሰጪ በኪራይ ምክንያት የያዘውን መኖሪያ ቤት ለአመልካች ሊያስረክብ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ መሥርቶ የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ምንም እንኳን የተደረገው የኪራይ ውል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚቆጠር ቢሆንም እና የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2966 ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ማስጠንቀቂያ በመስጠት እንዲያበቃ ለማድረግ እንደሚቻል ቢደነግግም ግራ ቀኙ ከዚህ በፊት ለተወሰነ ጊዜ (ለአንድ አመት) ባደረጉት የኪራይ ውል ላይ ውሉ የሚፈርስበትን (የሚበቃበትን) ሁኔታዎች የዘረዘሩ በመሆኑና ከእነዚህ ዝርዝር ሁኔታዎች ውስጥ መ/ሰጪ አንዱንም ያላፈረሰች በመሆኑ ወይም ደግሞ በውሉ እንደተገለፀው ቤቱ ለመንግሥት አገልግሎት ስለመፈለጉ እና ምትክ ቤት ለመስጠት የተዘጋጀ ስለመሆኑ አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ አመልካች ለመልስ ሰጪ ማስጠንቀቂያ ሰጥቼ ውሉን ያቋረጥኩ ስለሆነ ቤቱን ልረከብ ይገባል በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው የአሁኑ አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ጉዳዮን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለበት ነው በማለት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች በውሳኔያቸው ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ በመሆናቸው እንዲታረም በሚል ነው፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም የስር ፍ/ቤት አመልካች ከመልስ ሰጪ ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል አመልካች ለመልስ ሰጪ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ብቻ ማቋረጥ አይችልም፤ ውሉ ሊቋረጥ የሚችለው ቤቱ ለመንግሥት ሥራ ሲፈለግ ብቻ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል አቤቱታውን ለሰበር ችሎት በማስቀረብ የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር መርምሯል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአሁኑ መልስ ሰጪ ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን የመኖሪያ ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም የሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው በዋናነት በግራ ቀኙ መካከል ከዚህ ቀደም የተደረገ የቤት ኪራይ ውል የነበረ በመሆኑና በዚህ ውል ላይ ተከራካሪዎችቹ በመካከላቸው ያደረጉት የኪራይ ውል ቀሪ ሊሆን የሚችልባቸውን ምክንያቶች

የዘረዘሩ መሆኑንና ከእነዚህ የውል ማፍረሻ ምክንያቶች ውስጥ መልስ ሰጪ አንዱንም ያላፈረሱ መሆኑን ከግምት በማስገባት ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ግራ ቀኙ ባደረጉት ውል መሠረት ቤቱ ለመንግሥት አገልግሎት የተፈለገ ከሆነ እንኳን አመልካች ምትክ ቤት በመስጠት ብቻ መልስ ሰጪን ከቤቱ ሊያስለቅቅ እንደሚችል የተስማሙ በመሆኑ የአመልካች ቤቱን ልረከብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በሚል ነው፡፡

ይሁን እንጂ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2966 ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገን የኪራይ ውል ለማብቃት አከራዩ ተከራዩን ለማስታወቅ ወይም ተከራዩ አከራዩን ለማስታወቅ ይችላል በማለት በግልጽ ደንግጓል፡፡ በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረትም በተዋዋዮች መካከል የተደረገው የኪራይ ውል የጊዜ ገደብ ያልተበጀለት በሆነ ጊዜ ከተዋዋዮቹ አንደኛው ወገን ውሉ እንዲያበቃ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉ ፍፃሜ እንዲያገኝ ለማድረግ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ቀደም ሲል ለተወሰነ ጊዜ ያደረጉትን የኪራይ ውል መሠረት በማድረግ በውሉ የተጠቀሰው የኪራይ ጊዜ ካለቀ በኋላና የውሉ አይነት ወደ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ከተቀየረ በኋላ መልስ ሰጪ ቀደም ሲል ለተወሰነ ጊዜ በተደረገው ውል መሠረት ግዴታቸውን የፈፀሙ (ያላፈረሱ) በመሆኑ አመልካች የኪራይ ውሉን ማስጠንቀቂያ በመስጠት በቻ ለማፍረስ (ለማብቃት) አይችልም፡፡ ውሉ ሊቋረጥ የሚችልበት ብቸኛ ምክንያት ቤቱ ለመንግሥስት ሥራ ሲፈለግ ነው፡፡ ይህም ቢሆን አመልካች ለመልስ ሰጪ ምትክ ቤት ሰጥቶ ነው ውሉን ለማቋረጥ የሚችለው በመሆኑም አመልካች ማስታወቂያ ሰጥቼ ውሉን ያቋረጥኩ ስለሆነ ቤቱን ልረከብ ይገባል በሚል ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕጉን መንፈስና ዓላማ ሙሉ በሙሉ ያላገናዘበ በመሆኑ መታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዮን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ቢሆን የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በሚገባ ሳይመረምር እንዳለ ተቀብሎ ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ት እ ዛ ዝ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 11851 ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 55271 በጥቅምት 7 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአመልካችና በመ/ሰጪ መካከል የተደረገው የኪራይ ውል የፈረሰ በመሆኑ መ/ሰጪ በኪራይ ውሉ ምክንያት የያዙትን መኖሪያ ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሽያጭ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 16455

ኅዳር 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች ፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ጌታቸው ምህረቱ

አሠግድ ጋሻው

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- ወ/ት አዜብ ሽፈራው - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ታየች ንጉሴ - ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከሣሽ ሲሆኑ አመልካች ደግሞ 1ኛ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስም በወረዳ 21 ቀበሌ 24 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥር 646 የሆነውን ቤት ለአሁኗ አመልካች የሰጧት ሲሆን ቁጥር 643 እና 644 የሆኑትን ቤቶች ግን አመልካች አጠቃልዬ እገዛቸዋለሁ በማለት ተረክበው ለሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች በማከራየት እየተጠቀሙ በመሆኑ ቤቶቹን ለቀው እንዲያስረክቡኝ የቤቶቹን ኪራይም እንዲከፍሉ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኗ አመልካችም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ለፍሬ ጉዳዩም መልስ የሰጡ ሲሆን በመልሣቸው ላይ መጋቢት 2 ቀን 1985 የተደረገው የሽያጭ ውል እነዚህን ቤቶችንም የሚጠቀልል ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ካደረገ በኋላ በመ/ቁ. 2793/88 ተጠሪ የሸያጩ ውል እንዲፈርስ ባቀረቡት ክስ ፍ/ቤቱ የቤ/ቁ 643 እና 644 በተመለከተ የቀረበው ክስ ዳኝነት ያልተከፈለባቸው እና በሽያጭ ውሉ ያልተካተቱ በመሆኑ በሌላ መዝገብ በመክሰስ የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለትና የሽያጭ ውሉ ግን ሊፈርስ እንደማይገባ በሰጠው ውሣኔ ላይ ቤቶቹ

በሽያጩ ውል ላይ እንዳልተካተቱ ከተረጋገጠ አመልካች ቤቶቹን አስረክበው ኪራዩንም እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ቀደም ሲል በቀረበው ክስ አሁን ክርክር የተነሣባቸውን ቤቶች በተመለከተ ተጠሪ የዳኝነት ክፍለው እንዲጠይቁ በተሠጠው ውሣኔ ትችት ላይ ቤቶቹ በሽያጭ ውሉ አለመካተታቸው መገለፁን ምክንያት በማድረግ ብቻ አመልካች ቤቱን እንዲለቁ የወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡንም እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ክስ የመሠረቱት አመልካች ቁጥር 646 የሆነውን ቤት ሲገዙ ክርክር የተነሣባቸውን ቤቶችም አጠቃለው እገዛለሁ ብለው የተረከቡ በመሆኑ እነዚህን ቤቶች እንዲመልሱላቸው ነው፡፡ አመልካች ደግሞ መጋቢት 2 ቀን 1985 ዓ.ም. የተደረገው የሽያጭ ውል እነዚህን ቤቶች የሚያጠቃልል መሆኑን በመግለጽ ሊለቁ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ የቤ/ቁ 646ን የሸጡ መሆኑን አልካዱም፡፡ እንደውም ይህ የሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው በመ/ቁ. 2793/88 ክስ አቅርበው ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ ውሣኔ ያገኘ መሆኑን በክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አሁን በዚህ መዝገብ የተነሣው ክርክር ይህ የሽያጭ ውል ክርክር የተነሣባቸውን የቤት ቁጥር 643 እና 644ን ያጠቃልላል አያጠቃልልም? የሚለው ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የወሰነው የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ እነዚህ ሁለት ቤቶች በሽያጩ አለመካተታቸው ተረጋግጦ ተወስኗል በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ ማለት ተከራካሪዎቹ ወገኖች ያቀረቡትን ክስና መልስ እንዲሁም ማስረጃዎቹን መርምሮ ስለተከራካሪዎቹ ወገኖች መብትና ስለክሱ አወሳሰን ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሣኔ ለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ለውሣኔ ከሰጠው ትርጉም መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ፍ/ቤቱ በቀድሞ ክስ ተጠሪ ተገቢውን ዳኝነት ከፍለው ይጠይቁ ከማለት በቀር አሁን ክርክር የተነሳባቸውን ቤቶች በተመለከተ ክሱንና መልሱን እንዲሁም ማስረጃዎቹን መርምሮ ስለተጠሪም ሆነ ስለ አመልካች መብት የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡ ግራ ቀኙ ተከራክረው ውሣኔ ባልተሰጠበት ጉዳይ ደግሞ ቤቶቹ በሽያጩ ውል ላይ አልተካተቱም በሚል በውሣኔ ትችቱ ላይ መግለፁ ብቻ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መሰጠቱን አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት ክርክር ተደርጎ ውሣኔ ያልተሠጠበትን ጉዳይ እንደተሰጠበት በመቁጠር ለውሣኔው መሠረት ማድረጉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ፍ/ቤቱም ቀድሞ ውሣኔ ተሰጥቶበታል ወደሚለው መደምደሚያ በመድረሱም ግራ ቀኙ በቤቶቹ ላይ ያላቸውን ክርክርና ማስረጃ በአግባቡ ሣይመረምር ውሣኔ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡ እኛ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ መጋቢት 2 ቀን 1985 በተደረገ የሽያጭ ውል በወረዳ 21 ቀበሌ 24 የሚገኘውንና የቤት ቁጥር 646 የሆነውን ቤት መሸጣቸውን ተረድተናል፡፡ የሽያጭ ውሉን እንደተመለከትነውም በከተማ ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ቁጥር 21/08700 በስማቸው የተመዘገበውንና በፕላን ቁጥር 96/57 በቦታ ይዞታ 308 ካ.ሜ. ላይ በ56 ካ.ሜ. ቦታ ላይ የሰፈረውን ቤት አዋሳኞቹን በመጥቀስ በብር 62,000(ስልሳ ሁለት ሺ) ለአመልካች ሸጠዋል፡፡ ይህ በሽያጭ ውሉ ላይ በተገለፀው የከተማ ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ላይ ደግሞ የተጠቀሱት ቁጥር 643፣ 644 እና 646 የሆኑ ቤቶች ናቸው፡፡ የሽያጭ ውሉ እና የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩ አንድ ላይ ተገናዝበው ሲታዩም ተጠሪ ለአመልካች የሸጡት ሦስቱን ቤቶች በሙሉ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በተለይ በሽያጭ ውሉ ላይ ተጠሪ የቤ/ቁ 646ን ብቻ ለይተው እንደሸጡ የገለፁት ነገር

አለመኖሩ ሲታይም የሽያጭ ውል በባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩ ላይ የተጠቀሱትን ቤቶች በሙሉ የሚያጠቃልል መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አሁን ክርክር የተነሳባቸውን ቤቶች ለአመልካች ያስረከብኩት ወደፊት ቤቶቹን አጠቃልዬ እገዛለሁ ስላሉኝ ነው ያሉ ቢሆንም ይህ ፍሬ ነገር እውነት ለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ነገር አላገኘንም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ቤቱን የያዙት መጋቢት 2 ቀን 1985 ዓ.ም. በተደረገው የሽያጭ ውል መሠረት ገዝተው በመሆኑ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተሠጠው ውሣኔ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37/94 በሐምሌ 26 ቀን 1994 ዓ.ም እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15800 በግንቦት 23 ቀን 1996 ዓ.ም የተሰጡት ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ቤቶቹን የያዙት ገዝተው በመሆኑ ቤቶቹን ሊለቁም ሆነ ኪራዩን ሊከፍሉ አይገባም፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.18380

ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፍስሐ ወርቅነህ
ዳኜ መላኩ
ደስታ ገብሩ
አማረ አሞኜ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ማሞ ደምሴ አልቀረቡም
ተጠሪ፡- 1ኛ. አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር አልቀረቡም
2ኛ. ወ/ሮ ታየች ብርሃኑ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የሐረር አውራጃ ፍ/ቤት በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት የ2ኛ ተጠሪ ስምምነት ሳይኖርበት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 658ን በሚጻረር ሁኔታ ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ በመስጠቱና ይሄው ውሳኔ በክልሉ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በመጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ አሁን አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተደርጓል የሚሉት የቤት ሽያጭ ውል ይጽደቅልኝ በማለት ለሐረር አውራጃ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም ሰኔ 27 ቀን 1984 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሉ ፀድቋል በማለት ውሳኔ ሠጥቶ ተጠሪዎች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/358 በሚፈቅደው መሠረት ይ/ባዮች ወደ ክርክሩ

ገብተው ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ በማለት ጉዳዩን ወደ አውራጃው ፍ/ቤት መመለሱን የመዘገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡

ከዚህ በኋላም በአውራጃው ፍ/ቤት 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሕጋዊ ባልና ሚስት መሆናቸውን ገልጸው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውና በሐረር ከተማ ከፍተኛ 2 ቀበሌ 14 ክልል የሚገኘው ቁጥር 707 የሆነው ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ዘመን በጋራ መሥራታቸው፣ ሆኖም ይህንኑ ቤት 1ኛ ተጠሪ ያለ ባለቤታቸው ስምምነት ለአመልካች መሸጣቸውና ይህም የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 658ን የሚጻረር ስለሆነ የሽያጩ ውል እንዲጸድቅ አስቀድሞ በፍ/ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ መብቴን የነካ ስለሆነ ይሄው ውሳኔ ይሰረዝልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡፡

1ኛ ተጠሪም በይዘቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የሕግና የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል ብለዋል፡፡

አመልካችም በበኩላቸው አቤቱታው መሠረት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን በሌላ በኩልም ወ/ሮ ከበቡሽ በጅጋ የተባሉት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ሰኔ 17 ቀን 1984 ዓ.ም በተጻፈ ውል ከባልና ሚስቱ (ከተጠሪዎች) በመግዛት የቤቱ ካርታና ቁልፍ በእጃቸው እንደሚገኝ ገልፀው አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በዚሁ ቤት ላይ ያደረጉት ውል ሕገ ወጥ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ውድቅ ሊያደርግው ይገባል በማለት የበኩላቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለትም የአውራጃው ፍ/ቤት የተጋቢዎች የጋራ የሆነን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ የተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.658/ሀ/ ላይ የተመለከተ ስለሆነና በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች የሸጡት ያለ ባለቤታቸው (2ኛ ተጠሪ) ስምምነት ስለሆነ ይሄው ውል ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱትም የክልሉ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ይህንኑ ውሳኔ አጽንተዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ግራ ቀኙ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ይፈርሳል ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመን ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡

ይሁንና 1ኛ ተጠሪና የ2ኛ ተጠሪ ወራሾች በጋዜጣ እንዲጠሩ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በዚሁ መሠረት በጋዜጣ ቢጠሩም አልቀረቡም፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታውም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የአሁን አመልካች በሐረር አውራጃ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተደርጓል የሚሉት ውል ይጽደቅልኝ በማለት ነው፡፡

ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ማናቸውም አቤቱታ ተመርምሮ ውሳኔ (remedy) ሊሰጠው የሚችለው የቀረበው አቤቱታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችል (justicable) ሆኖ በሚገኝበት ጊዜና እንደዚሁም አቤቱታው የክስ ምክንያት ያለው ሆኖ በሚኝበት ጊዜ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ የቤት ሽያጭ ውል ይጽደቅልኝ የሚል እንደመሆኑ መጠን ማናቸውም ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1678 ላይ የተመለከቱትን የውል አመሠራረት መርሆዎች /Elements of contracts/ መሠረት አድርጎ እስከተቋቋመ ድረስ በሕግ አግባብነት ተቋቁሟል ለማለት የሚቻል ሲሆን ከዚህ አልፎ ውሉ በፍ/ቤት እንዲጸድቅ የሚያስገድድ የሕግ ማዕቀፍ የለም፡፡ በመሠረታዊ ሕጉ /substantive law/ ላይ የዚህ ዓይነቱ ግዴታ ከሌለ ደግሞ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ በመሠረታዊ ሕግ የተሰጠን

መብትና ግዴታን ማስፈጸሚያ እንጂ በእራሱ የመብትና ግዴታ ምንጭ ሊሆን አይችልም፡፡

ስለሆነም የቤት ሽያጭ ውል ይፅደቅልኝ በማለት አቤቱታ ማቅረብ ለፍ/ቤት በማይቀርብና የክስ ምክንያትም በሌለው ነገር አቤቱታ እንደማቅረብ የሚቆጠር በመሆኑ የአውራጃው ፍ/ቤት ይህንኑ አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.231 (1) (ሀ) መሠረት ተቀባይነት የለውም ማለት ሲገባው ውሳኔ መሰጠቱ እንደዚሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚሁ መሠረት ማረም ሲገባው ተጠሪዎች በተቃዋሚነት ገብተው ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ መወሰኑና ከዚህም በኋላ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታው የክስ ምክንያት የለውም ማለት ሲገባው በዚህ ሁኔታ የተሰጠውን ውሳኔ ማጽናቱ ያለአግባብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሐረር አውራጃ ፍ/ቤት ታህሳስ 30 ቀን 1985 ዓ.ም በመ.ቁ 73/84 የሰጠው ውሳኔ የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግንቦት 18 ቀን 1987 ዓ.ም በመ.ቁ.31/86 የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጎዳር 27 ቀን 1997 ዓ.ም በመ.ቁ 00001 የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽ [ል፡፡ ይጻፍ፡፡

2. አመልካች ለሐረር አውራጃ ፍ/ቤት የቤት ሽያጭ ውል ይፅደቅልኝ በማለት ያቀረቡት ለፍ/ቤት የማይቀርብና የክስ ምክንያት የሌለው ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ፍይል ቁጥር 22448

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- ኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ክፍል አ/ማህበር - ግርማ ሥላሴ ጠበቃ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሙሉነህ ካሣ ጠበቃ ቀረቡ

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ታህሣሥ 8 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መነሻ ነው፡፡

የጉዳዩ የስር አመጣጥ ተጠሪ ጥር 8 ቀን 1993 ዓ.ም ከአመልካች ጋር ባደረገው ውል 10 የመርቸዲስ ቤንዚን አክተርስ ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች በወቅቱ ዋጋቸው ለመግዛት ተስማምቶ ውሉ ሲደርግ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ሊከፍል፣መኪኖቹ ጂቡቲ ወደብ ሲደርሱ 2ኛውን ክፍያ ብር 767,236 (ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሠላሰ ስድስት) ለመክፈልና መኪኖቹን ከተረከበ በኋላ በየደረጃው ሌሎች ክፍያዎችን ለመፈፀም ተስማምቶ በዚሁ መሠረት ብር 500,000 (አምስት ሺህ) የመጀመሪያ ደረጃ ክፍያ ፈፅሞ እያለ መኪኖቹን አመልካች በወቅቱ ሊያስረክበው ባለመቻሉ የከፈለውን ገንዘብ አጠፌታ እንዲከፍለው ክስ አቅርቧል አመልካችም በበኩሉ መኪኖቹን ለማስረከብ ያልተቻለው ተጠሪ ሁለተኛውን ክፍያ ባለመክፈሉ እንደሆነ በመግለፅ ለክሱ መልስ ሰጥቷል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በርግጥም ተጠሪ በውሉ መሠረት የሚፈለግበትን ክፍያ አለመፈፀሙን በመግለፅ 2ኛውን ክፈያ ለተከሣሽ ከፍሎ መኪኖቹን እንዲረከብ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪም በዚሁ ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ የአፈፃፀም ፋይል የከፈተ ሲሆን በአፈፃፀም የጠየቀውም ሁለተኛውን ክፍያ ብር 767,236 (ሰባት ሺ ስልሳ ሰባት ሁለት መቶ ሠላሳ ስድስት) ከፍሎ መኪኖቹን እንድረከብ የሚል ነው አመልካችም በበኩሉ ተጠሪ ተረቺ እንጅ ረቺ ስላልሆነ የአፈፃፀም መዝገብ ሊከፍት አይችልም፣የፍርድ ቤቱም ውሣኔ ይህን ለማድረግ የሚያስችለው አይደለም በማለት ተከራክሯል ፍርድ ቤቱም በጥቅምት 18 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ በውሉ መሠረት የመኪናዎቹን ቀሪ ዋጋ ከፍሎ መኪናዎቹን ይረከብ በማለት በሠጠው ትዕዛዝ መሠረት አመልካች ለተጠሪ በውሉ መሠረት የመኪናዎቹን ዋጋ ብር 12,152,980.70 (አሥራ ሁለት ሚሊየን አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ከሰባ) ከፍሎ መኪኖቹን እንዲረከብ መግለጫ ቢሰጥም ተጠሪ ግን 2ኛውን ክፍያ ብር 767,236 (ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሠላሳ ስድስት) ብቻ ከፍዬ መኪናዎቹን እንድረከብ ብጠይቅም አመልካች ፈቃደኛ አልሆነም በማለት ለፍ/ቤት በማመልከቱ ፍርድ ቤቱም በጥቅምት 2 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠውን ትዕዛዝ በመሻር አመልካች ብር 767,236 (ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር) ተቀብሎ መኪኖቹን እንዲያስረክብ በግንቦት 19 ቀን 1997 ዓ.ም የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ትዕዛዝ ሰጥቷል ለፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ ውሣኔውን አፅንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ መነሻነት ሲሆን ይህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን በማስቀረብ አከራክሯል ክርክሩንም ከሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ ለቀረበው ክርክር መሠረት የሆነው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ጥር 7 ቀን 1996 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ “ከሳሽ በውሉ መሠረት 2ኛ ክፍያውን ለተከሣሽ ከፍሎ መኪናዎቹን ከሚረከብ በቀር ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም ብሎ ወስኗል” በማለት ያሠፈረው የድምዳሜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዐረፍተ ነገር ነው። ተጠሪም ዐረፍተ ነገሩ የፍርድ ባለመብት አድርጐኛል በማለት አፈፃፀም የከፈተ ሲሆን አመልካችም በበኩሉ ባንድ በኩል ተጠሪ የፍርድ ባለመብት አለመሆኑን በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ መኪኖቹን ለመረከብ የሚችለው በውሉ ላይ በተመለከተው ዋጋ መሠረት ሣይሆን አሁን ባለው የገበያ ዋጋ መሠረት ነው የሚል ነው ፍርድ ቤቱ ከላይ የተመለከተውን የመደምደሚያ ዐረፍተ ነገር ያስቀመጠው አመልካች ቀደም ሲል ለክሱ ሰጥቶት በነበረው መልስ ላይ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1757 መሠረት በቅድሚያ የበኩሉን ግዴታ ሣይወጣ አመልካች መኪናዎቹን ከጂቡቲ አስመጥቶ እንዲያስረክብ ለመጠየቅ በማለት ያቀረበውን በመቀበል የሰፈረ እንጂ ተጠሪን የፍርድ ባለመብት ለማድረግ አይደለም በሌላ አነጋገር ተጠሪ በቀብድ የከፈልኩትን ገንዘብ በአጠፊታ መመለስ ይገባዋል በማለት ባቀረበው የውል ይሰረዝልኝ ክስ ፍርድ ቤቱ ውሉ ሊሰረዝ አይገባውም ምክንያቱም ተጠሪ የበኩሉን ግዴታ አልተወጣም፣ተጠሪ መብቱን መጠየቅ የሚችለው ግዴታውን ከተወጣ በኋላ ነው በማለት ክሱን ውድቅ ከማድረግ በስተቀር ተጠሪን የፍርድ ባለመብት ማድረጉን አያመለክትም፤ይልቁንም ፍርድ ቤቱ በሥረ ነገር ክርክሩ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ለመስጠት ለውሉ መፍረስ የሚያበቃ ምክንያት አለ ወይ? በማለት ጭብጥ መያዙ ከላይ የተገለፀውን አባባል ያጠናክራል። ይህን መነሻ በማድረግ ተጠሪ በቀብድ መልክ የከፈልኩት ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት ውሉ እንዲፈርስለት ክስ አቅርቦ የሥር ፍርድ ቤትም ውሉ አይፈርስም፣ምክንያቱም ውሉ ሊፈፀም ያልቻለው በአመልካች ጥፋት አይደለም በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር በተቀበለበት ሁኔታ የአሁኑ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሆኗል ለማለት አልተቻለም። በተጨማሪም ተጠሪ ከሥር ጀምሮ ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ የፍርድ ባለመብት ሆኗል መባሉ ተገቢ ካለመሆኑም በላይ አመልካች ለክሱ ሰጥቶት በነበረው መልስ ላይ ተጠሪ 2ኛውን ክፍያ በመፈፀም መኪኖቹ ከጂቡቲ ወደብ ተነስተው ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ባለማድረጉ ለከፍተኛ

የወደብ ኪራይ ተዳርገናል በማለት ካቀረበው ክርክር አንፃር ተጠሪ የበኩሉን ግዴታ እንዳልተወጣ የሥር ፍርድ ቤት አረጋግጦ የቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረጉን ተገንዝበናል። በመሆኑም ውል ይፍረስ ተብሎ በቀረበ ክስ ላይ ውሉ መፍረስ የለበትም ተብሎ በአሁኑ አመልካች የቀረበው የክስ መከላከያ ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ ውድቅ በሆነበት ሁኔታ ክሱ ውድቅ የተደረገበት ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሆኗል መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል ምክንያቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378/1/ በተመለከተው መሠረት የፍርድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ ችሎታ ያለው ፍርድ የተፈረደለት ሰው (ወገን) ብቻ በመሆኑና በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪ ክሱ ውድቅ የተደረገበት በመሆኑ ነው።

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአፈፃፀም መ/ቁ.31336 እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20370 ህዳር 29 ቀን 1998 ዓ.ም አመልካች ያልተከፈለውን ቀሪ ገንዘብ ተቀብሎ መኪናዎቹን ያስረክብ በማለት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል ይፃፍ።
- የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በሥራ-ነገር ክርክሩ (በዋናው ጉዳይ) በተሰጠው ውሳኔ መሠረት አፈፃፀም ሊጠይቁ የሚችሉበት የህግ አግባብ የለም ብለናል።
- ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻቻሉ
- መዝገቡ ተዘግቷል።ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 22860

የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡-መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ሰንላይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ - ነ/ፈጅ ብርሃኑ ወንደሰን

ተጠሪ፡- አቶ ካሣዬ ዘውዴ - አልቀረበም፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረ ሲሆን ለተጠሪ በሁለት የዱቤ ሰነዶች የውሃ ማሞቂያ መሸጡንና ተጠሪ ግን ለገዙት ዕቃ ዋጋቸውን ስላልከፈሉ የዕቃዎቹን ዋጋ ብር 44,930 /አርባ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሣ/ ብር እንዲከፍሉ ጠይቋል፡፡ ተጠሪም ክሱን ክደው ተከራክረዋል:: ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በከሣሽና በተከሣሽ መሀከል የተደረገ የሽያጭ ውል አልቀረበም፡፡ የዱቤ ሰነዱ በፍ/ሕ/ቁ. 1685 መሠረት ተጠሪን አያስገድዳቸውም፡፡ የሽያጭ ውል ተያይዞ ባለመቅረቡም ውሉ በከሣሽና በተከሣሽ መሀከል አለ ለማለት አይቻልም ሲል የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል ሠርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አቤቱታው በአጭሩ ሲጠቃለል ሽያጩ የተደረገው በዱቤ ሰነድ /Credit invoice/ ሆኖ ግለ የዱቤ ሰነዱ ጋር የሽያጭ ውል አልተያያዘም በማለት ፍ/ቤቱ ክሱን ውድቅ ማድረጉ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም ከዱቤ ሰነዱ በተጨማሪ ሌላ የሽያጭ ውል አልቀረበም በማለት ክሱ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው ለቀረበው ክስ ምንም ዓይነት ማስረጃ ስላልቀረበ ውሣኔው ስህተት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ክስ የመሠረተው ተጠሪ በዱቤ ሽያጭ የገዙትት ውሃ ማሞቂያ ዋጋ እንዲከፍሉ ነው፡፡ አንድ ግዴታ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው ለግዴታው መኖር ማስረጃ ማቅረብ እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁ. 2001/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪው ውሃ ማሞቅያውን መግዛታቸውንና ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት ሕጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ያዘዘ ካልሆነ በቀር ግዴታው መኖሩን በጽሑፍ በምስክር፣ በሕሊና ግምት፣ በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሐላ ማስረዳት እንደሚቻል በፍ/ሕ/ቁ. 2002 ሥር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እንዲያስረዳ የሚጠበቅበት ተጠሪ በዱቤ የውሃ ማሞቂያ ገዝተው የተረከቡ መሆኑን ነው፡፡ የውሃ ማሞቂያ ሽያጭ ውል ደግሞ በተለየ ሁኔታ እንዲደረግ ወይም ውሉ ስለመደረጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ሕጉ የማያስገድድ በመሆኑ አመልካች ሽያጩ ለመከናወኑ ማንኛውንም ማስረጃ ማቅረብ ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ሽያጭ ለመደረጉ የዱቤ ሰነድ /Credit invoice/ አቅርቧል፡፡ ይህ የዱቤ ሰነድ ግራ ቀኙ ተስማምተው እስከፈረሙት ድረስ የዱቤ ሽያጭ መከናወኑን ለማስረዳት በቂ ነው፡፡ ሕጉ ይህ አይነቱ ሽያጭ በጽሁፍ እንዲሆን ስለማያዝም ከዱቤ ሰነዱ በተጨማሪ ሌላ የጽሁፍ ውል እንዲቀርብ የሚጠየቅበት ምክያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት ከዱቤ ሽያጩ ጋር የጽሁፍ ውል ባለመያያዙ ሽያጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከናውኗል ማለት አይቻልም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ ስህተት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩል ግን አመልካች ሽያጭ መከናወኑን ለማስረዳት ባቀረበው የዱቤ ሰነድ ላይ የፈረሙት አመልካችና ሌላ አብይ የተባሉ ግለሰብ እንጂ ተጠሪ አይደሉም፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ፈርመውበት ቢሆን ኖሮ የጽሁፍ ሠነድ በላዩ ላይ ስለሚገኘው የስምምነት ቃልና በላዩ ላይ ስለተፃፈው ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ይሆን ነበር /የፍ/ሕ/ቁ. 2005/1/ ይመለከቷል/:: በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪ በሰነዱ ላይ ያልፈረሙ በመሆኑ በሰነዱ ላይ ስለሠፈረው ጉዳይ ተስማምተዋል ወይም ግዴታ ገብተዋል ለማለት አይቻልም፡፡ በዚህ ችሎት በተደረገው የቃል ክርክር አመልካች ሰነዱ ላይ የፈረሙት ግለሰብ የተጠሪ ወኪል ናቸው ይበል እንጂ ይህ ክርክር ከስር ያልተነሣ አዲስ ነገር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329/1/ መሠረት ተቀባይነት የለውም፡፡

በመሆኑም አመልካች ያቀረበው ሰነድ በአመልካችና በተጠሪ መሀከል የዱቤ ሽያጭ ውል መደረጉን እና በዚህም ምክንያት ተጠሪ የእቃውን ዋጋ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን አያስረዳም፡፡ በዚህም ምክንያት ምንም እንኳን የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት ስህተት ቢሆንም ክሱን ውድቅ ማድረጉ ግን በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጋቢት 5 ቀን 1997 ዓ.ም በመ/ቁ. 11568 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38828 ኅዳር 23 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 23331

ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ጀማል ሐሚድ - ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ለተሃይማኖት ተክሌ

2. ወ/ሮ ኪሮስ ወልዱ
3. ወ/ሮ ምዕራፍ ወልዱ
4. ተመስገን ወልዱ
5. መብራቱ ወልዱ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ከሕግ ውጭ ተይዞ የሚገኘውን ቤት ይለቀቅልን በማለት ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት የተጀመረውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ መልስ የሰጠ ሲሆን፣ በዚህም አከራካሪው ቤት ከ2-5 ያሉት ተጠሪዎች እህት ከሆነችው ገዝቶ የያዘው እና ከገዛው በኋላም ለውጦ (አሻሽሎ) በመስራት እየተጠቀመበት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ ክስ የቀረበበት የወረዳ ፍ/ቤትም የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲለቅ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ በየደረጃው ይግባኝ የቀረበላቸው የበላይ ፍ/ቤቶችም ውሣኔውን አፅንተዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም አመልካች የካቲት 16 ቀን 98 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ስምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች እና ቤቱን በሸጠችለት የተጠሪዎች እህት መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ሳይፈርስ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው። በዚህ መሠረትም ይህንን ነጥብ በግራ ቀኝ ወገኖች ከቀረበው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አከራካሪው ቤት በቀበሌው ገበሬ ማህበር ውስጥ የሚገኝ ነው። ተጠሪዎች ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ክስ የመሠረቱት ሠርተነዋል በማለት ሳይሆን አባታችን መሬቱን በ1962 ዓ.ም ከሌላ ሰው ገዝቶ የቆርቆሮ ቤት ሠርቶበታል በማለት ነው። አመልካች ደግሞ ቤቱን መስከረም 13 ቀን 1984 ዓ.ም ከወ/ሮ ንግሥት ወልዱ ጋር ባደረገው የሽያጭ ውል ገዝቶና አሻሽሎ በመስራት የሚኖርበት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮአል። የሁለቱ ወገኖች ክርክር ይህን ሲመስልም በአመልካች እና በወ/ሮ ንግስት ወልዱ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ደግሞ ፈርሶአል አልተባለም። ውሉ የሕግን መስፈርት አያሟላም የሚል ክርክርም አልቀረበበትም። የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔም የተመሠረተው ውሉ ሕገወጥ ነው ወይም በማናቸው ሁኔታ ፈራሽ ሆኖአል በሚለው ላይ ሳይሆን አመልካች ቤቱን የገዛው መብት ከሌለው ሰው ነው በሚለው ላይ ነው። በበኩላችን እንደምናየው ወ/ሮ ንግስት ወልዱ (ቤቱን የሸጠችው ሰው) የተጠሪዎች እህት እንደሆነች በተጠሪዎችም ጭምር የታመነ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ወ/ሮ ንግስት የሚች ወራሽ ነች ማለት ነው። በመሆኑም ቤቱን ለመሸጥ መብት አልነበራትም ወደሚለው መደምደሚያ መድረስ የሚቻል አይደለም። በሌላም በኩል ተጠሪዎች ቤቱ የተሸጠው ያለአግባብ ነው የሚል እምነት ቢኖራቸው ውሉ ፈራሽ ነው

ይባልላቸው ዘንድ አግባብ ያለውን አካሄድ በመከተል መጠየቅ ነበረባቸው። በዚህ መልክ የተደረገ ክርክር የለም። ማስረጃም አልቀረበም። እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በቤቱ ላይ መብት የለውም ለማለት የሚቻልበት የሕግ ምክንያት የለም። በመሆኑም አመልካች ቤቱን ይልቀቅ በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

<u>ው ሣ ኔ፣</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በኦ/ብ/ክ/መ በምስራቅ ሸዋ ዞን በሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ 240/93 የካቲት 14 ቀን 93 ዓ.ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 482/93 ግንቦት 7 ቀን 95 ዓ.ም በተሰጠው እና በኦ/ብ/ክ/መ/ጠ/ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01642 ታህሳስ 4 ቀን 98 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ እንዲሁም በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 35730 የካቲት 8 ቀን 98 ዓ.ም በተሰጠው ትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ//ብ/ሥ/ሥ/ሕግ.ቁ 348(1)መሠረት ተሽሮአል።
2. አመልካች አከራካሪውን ቤት ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል።
3. ወጪና ኪሣራ ግራቀኝ ወገኖች የራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 23895

ታህሳስ 15 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል

ተጠሪ፡- መኮንን ሉሌ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በተጠሪው ላይ ክስ የመሠረተው ተጠሪ በሁለቱ መካከል በተደረገው የሽያጭ ውል መሠረት በግዢ ለተረከበው ወፍጮ መከፈል የሚገባውን ዋጋ ከነመቀጫው በጠቅላላው ብር 63,010 እንዲከፍለው ነው፡፡ ተጠሪ ለቀረበበት ክስ መልስ በመስጠት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣ በሁለቱ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ተከሣሹ በውሉ መሠረት አፍርሶታል /ቀሪ አድርጎታል/፡፡ ከዚህ በኋላም ቀደም ሲል ተደርጎ በነበረው ውል አይነት የሽያጭ ውሉ አልታደሰም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት በመልካች የቀረበውን ክስ ውድቅ አድርጎአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች መጋቢት 18 ቀን 98 ዓ.ም. በዛፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው

አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የሽያጭ ውል ከሚገዛበት ሕግ አንፃር በማየት አግባብነቱን ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የተከራካሪዎቹ ወገኖች ግንኙነት የተመሠረተው በዕቃ ሽያጭ ውል ላይ ነው፡፡ በዚህ ውል መሠረት አመልካች ወፍጮዎችን ለተጠሪ ሸጦአል፣ ተጠሪም በውሉ መሠረት ወፍጮዎቹን ተረክቦ የነበረ ሲሆን፣ ዋጋቸውን ግን አልከፈለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ወፍጮዎቹ በውሉ መሠረት ትክክለኛ ሆነው አልተኙም ወይም ጉድለት ያለባቸው ናቸው በሚል ለአመልካች ያስታወቀበት ሁኔታ የለም፡፡ ገንዘቡን እንዲከፍል በተጠየቀ ጊዜ /ሲከሰስ/ ያቀረበው መከራከሪያም የወፍጮዎቹን ትክክል አለመሆን የሚመለከት አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረጉት ውሉ እንደፈረሰ በመቁጠር እንጂ የሽያጭ ውል አፈፃፀምን በተመለከተ የተደነገገውን ሕግ መሠረት በማድረግ አይደለም፡፡

እንደምንመለከተው ጉዳዩ የዕቃ ሽያጭ ውልን የሚመለከት እንደመሆኑ የተከራካሪዎቹ ወገኖች መብትና ግዴታ መታየት ያለበት "ስለ ልዩ ውሎች" በሚል በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ አስራ አምስት ሥር ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሻጩን ግዴታ እና ገዢውም ዕቃውን እንደተረከበ ሊወስዳቸው የሚገቡ እርምጃዎች ምን እንደሆኑ ያመለክታሉ፡፡ ሻጩ በውሉ በተመለከተው መሠረት ትክክለኛውን ዕቃ ለገዢው የማስረከብ ኃላፊነት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕግ ቁ 2287 እና 2288 እንደተደነገገው ሁሉ ገዢም ዕቃው በውሉ መሠረት የተሟላ አይደለም ወይም ጉድለት ያለበት ነው የሚል እምነት ካለው በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስታወቅ ግዴታ አለበት /የፍ/ብ/ሕግ ቁ 2291፣ 2292/፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት የተረከባቸው ወፍጮዎች ጉድለት ያለባቸው ናቸው በሚል አመልካችን ያስታወቀበት ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/ሁኔታ/ የለም፡፡ ጉድለትን መሠረት በማድረግም በአመልካች ላይ ክስ አልመሠረተም ወይም የሽያጭ ውሉን ቀሪ እንዲሆን አላደረገም፡፡ በመሆኑም የሽያጭ ውሉ ፈርሶአል በማለት የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ ትክክል አይደለም፡፡ ይህን መደምደሚያ መሠረት በማድረግ የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10908 ጥቅምት 1 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34216 የካቲት 10 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ . 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 63,010.00 /ስድሳ ሦስት ሺህ አስር/ ከነዳኝነቱ እንዲሁም ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ዘጠኝ በመቶ /9%/ ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ አመልካች ዝርዝሩን አቅርቦ ያስወስን ብለናል፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 24554

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ አይሸሹም ጋተው - ጠበቃ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- እነ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ጠበቃ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን አመጣጡን በተመለከተም የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 25 ቀን 1994 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ የተከሳሾች አውራሽ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ነሐሴ 24 ቀን 1985 ዓ.ም. በተፃፈ የቤት ሽያጭ ውል ስምምነት አድርገን በወረዳ 12 ቀበሌ 11 የሚገኘው ቁጥሩ 1408 የሆነውና በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኘውን የግል ቤታቸው በብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ ሸጠውልኝ ከዚሁ ሽያጭ ገንዘብ ብር 10,000 ተቀብለው ቀሪውን ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ ስም ሲዞርልኝ ሊቀበሉ ተስማምተው በእማኞች ፊት ፈርመዋል፡፡ በዚሁ መሠረትም ውሉ እንዲፀድቅልን ለዞን 4 ወረዳ 12 ፍ/ቤት መዝገብ ክፍቹ የተከሳሾች አውራሽ ከመሞታቸው በፊት መጥሪያ ደርሶአቸው ቤቱን የሸጡ በመሆኑ ስሙ በከሣሽ ስም ቢዞር ተቃውሞ እንደሌላቸው የወረዳው ፍ/ቤት ቀርበው አመልክተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ተቃዋሚ ቢኖር እንዲቀርብ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲወጣ አዝዞ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ መጋቢት 15 ቀን 1987 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ውሉን አጽድቆ የቤቱን ባለቤትነት ስም በከሣሽ ስም እንዲዘዋወር ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ መሠረትም የሥራና ከተማ ልማት በስሜ ካርታ ሠርቶ ሰጥቶኛል፡፡ ነገር ግን ሚች የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ቤቱን ሲሸጡልኝ ስለቤቱ ርክክብ ሣይፈፀም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ባለቤት የሆንኩለትን ቤት ተከሣሶች ያለአግባብ እየተጠቀሙበት በመሆኑ መብቴን ጠብቄ ቤቱን እንዲያስረክበኝ ክስ ካቀረብኩበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ተከሣሾች የተጠቀሙበት የቤት ኪራይ ሂሣብ ተምኜ የመካስ መብቴ ይጠበቅልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተከሣሾች ከሆኑት የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ወራሾች መካከል 2ኛ ተከሣሽ ወ/ሪት ክብርወርቅ ሞገስ እና 5ኛ ተከሣሽ ወ/ሪት የምስራች ሞገስ ታህሣሥ 12 ቀን 88 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ በማቅረብ ክርክር የቀረበበት ቤት የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ እና ወ/ሮ ፋናዬ አየለ በጋብቻ ያፈሩት ስለሆነ እናታችን ወ/ሮ ፋናዬ አየለ ሳታውቅ የተደረገው የሽያጭ ውል በሕግ ፊት ተቀባይነት የለውም በማለት የተከራከሩ ሲሆን 1ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተከሣሾች በተገቢው ሁኔታ ተጠርተው ያልቀረቡ ስለሆነ ክሱ በሌሉበት እንዲታይ ፍ/ቤቱ ታህሣሥ 23 ቀን 1993 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ብይን ሰጥቷል፡፡ ጣልቃ ገብ አመልካች ወ/ሮ ፋናዬ አየለ የተከሳሽ እናት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41/1/ መሠረት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ጠይቀው ፍ/ቤቱ ፈቅዶላቸው መጋቢት 3 ቀን 1993 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ ክስ የቀረበበት ቤት የጣልቃ ገብና የሚች የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ የጋራ ሀብት ስለሆነ ከሣሽና ሚች የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል ሕጋዊ ሊሆን አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ካዳመጠ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2266 ጀምሮ በተደነገጉት መሠረት የሽያጭ ውል ተፈፀመ የሚባለው ገዢው ገንዘብ በውሉ መሠረት ሲከፍልና የገዛውን ነገር ሲረከብ ሻጭም የሸጠውን ነገር ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር ለገዢው ሲያስረክብ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ከሣሽ የሆኑት አቶ አይሸሹም ጋተው ግን ከተከሣሾች አውራሽ

ገዛሁ ያሉትን ቤት እንደውሉ አፃፃፍ አልተረከቡም፡፡ ባለመረከባቸውም ስም እንዲዛወር ክስ አቅርበው ውሉን በፍ/ቤት አስመዝግበው ቤቱን እንዲረከቡ አሁን የተያዘው ክርክር ያስነሳውን መዝገብ ከፍተዋል፡፡ ከመረከብ ጥያቄያቸው በመረዳትም ነሐሴ 24 ቀን 1985 ዓ.ም የተደረገው ውልና በፍ/ቤት ተመዝግቦ ስም እንዲዛወር ተወስኖ በስማቸው የባለቤትነት ማረጋገጫ ያገኙበት ምክንያት የሽያጩ ውል የተደረገው የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሚስት የሆኑት ወ/ሮ ፋናዬ አየለ ሳያውቁና ስምምነታቸውን ሳይገልፁ በመሆኑና የማይንቀሳቀስ ሃብቱንም በእጃቸው ከማድረጋቸውና ባለ ይዞታ ከመሆናቸው በፊት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196 ድንጋጌ መሠረት ውጤት የሚኖረው አይደለም፡፡ በመሆኑም ተከሣሾች ቤቱን ለከሣሽ የማስረከብ ግዴታ የለባቸውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ ተመልክቶ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ቅሬታውም የቤቱን ሽያጭ የሚቃወም ካለ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲቀርብ ማስታወቂያ ወጥቶ ወ/ሮ ፋናዬ አየለ ቀርበው አልተቃወሙም፡፡ የሽያጩን ገንዘብ ባለቤቴ ናቸው ከሚሉዋቸው የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ከሚካፈሉ በስተቀር በአግባቡ የተደረገውን የሽያጭ ውል ሊያፈርሱ የሚችሉበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሚስት ነኝ የሚሉት ተቃዋሚ ቤቱ በተሸጠበት ጊዜ ከባላቸው ተለይተው ወደናዝሬት በመሄድ ሌላ ባል አግብተው ይኖሩ ስለነበር በቤቱ ላይ ምንም መብት የላቸውም፡፡ ሽያጩ ከተደረገ 13 ዓመት ሆኖታል፡፡ ከአስራ ሶስት ዓመት በኋላ መጥተው የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በማለት ያቀረቡት ጥያቄም ተቀባይነት የለውም፡፡ የሽያጭ ውሉ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የፀደቀና ማረጋገጫ የተሰጠበት ነው፡፡ ሚስት መብት ነበራቸው የሚባሉም ከሆኑ የሽያጭ ውሉን የሚቃወም ካለ እንዲቀርብ ተብሎ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ሳይቀርቡ ፍ/ቤቱ የሽያጭ ውሉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካጸደቀና ማረጋገጫ ከተሰጠበት በኋላ ባቀረቡት ጥያቄ የሽያጭ ውሉን ሊያፈርስ የሚችልበት ምክንያት የለም። ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የሽያጭ ውሉ ተፈፃሚነት የለውም ተከሳሾች ቤቱን ለገዢው እንዲያስረክቡ አይገደዱም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ይሻርልኝ ቤቱንም እንዲሰጡኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው።

ተጠሪዎች ደግሞ በሰጡት መልስ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ የሸጡት ቤት የግላቸው አይደለም። የሽያጭ ውሉን በፍ/ቤት ያፀደቁትም በሐሰተኛ መንገድ ነው። የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሚስት የሆንኩት መልስ ሰጭ መፃፍ ማንበብ ስለማልችል በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ወጣ የተባለውን ማስታወቂያ አላየሁትም። ቀሪዎቻችንም ቤቱን ከአባታችን በውርስ ያገኘነው ነው። የሥር ፍ/ቤቶቹ የሽያጭ ውሉ ተቀባይነት የለውምነኽ ተከሣሾች ቤቱን ለከሣሽ ማስረከብ የለባቸውም በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት ስለሌለበት ሊፀድቅልን ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

በበኩላችን ደግሞ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ወራሾች ክርክር ያስነሳውን ቤት ለአመልካች የማያስረክቡበት ምክንያት አለ ወይስ የለም? ወ/ሮ ፋናዬ አየለ የሸያጩን ውል በመቃወም ጣልቃ መግባት የነበረባቸው በመ/ቁ. 2643 ነው ወይስ በመ/ቁ. 561/86? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

መዝገቡን እንደመረመርነው የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ወራሾች የሆኑት ተጠሪዎች የሚያቀርቡት መከራከሪያ ነጥብ ክርክር ያስነሳው ቤት የአባታችን የ50 አለቃ ሞገስ ማሞና የእናታችን ወ/ሮ ፋናዬ አየለ በመሆኑና የተሸጠውም እናታችን ሳታውቅና ስምምነቷን ሳትሰጥ ነው፣ ቤቱ የተሸጠው በአግባቡ አይደለም። እኛ ደግሞ የአባታችን ወራሾች በመሆናችን የቤቱ ግማሽ ይገባናል። በመሆኑም ቤቱን ለሥር ከሣሽ ለአሁኑ ተጠሪ ልናስረክብ አይገባም የሚል ነው። ይህን የወራሾች ክርክር ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ስንመለከተው የውርስ ንብረት ነው የሚሉት ቤት አባታቸው የ50 አለቃ

ሞገስ ጽጌ በሕይወት እያሉ በ1985 ዓ.ም. ለአመልካች የሸጡትና የሽያጭ ውሉም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2877 መሠረት በጽሑፍ የተደረገና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሠረት ደግሞ የሽያጭ ውሉ በመጋቢት 15 ቀን 1987 ዓ.ም. በፍ/ቤት የተረጋገጠና የቤት ባለቤትነቱንም ለአመልካች እንዲዛወርላቸው የተወሰነ በመሆኑ ይህ ቤት የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሃብት መሆኑ በዚያን ጊዜ ያበቃለት ሆኗል። ቤቱ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ማለት የወራሾቹ አባት የሆኑት ሰው ንብረት ካልሆነ ደግሞ ወራሾቹ ንብረትነት ጥያቄ የሚያነሱበት ምክንያት አይኖርም። እንደዚሁም ወራሾቹ ቤቱን ለአመልካች አናስረክብም ለማለት የሚያስችላቸው መብት የሌላቸው በመሆኑ ክርክራቸው ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም። ቤቱ የተሸጠው የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሚስት የሆነች እናታችን ሳታውቅና ስምምነቷን ሳትሰጥበት በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሚያቀርቡትን ክርክር በተመለከተም ይህን ክርክር መነሻ በማድረግ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሚስት የሆኑት ወ/ሮ ፋናዬ አየለ ራሳቸው በመቃወም አመልካችነት ጣልቃ ገብተው እየተከራከሩ የሚገኙ በመሆኑ ክርክሩ በወራሾቹ የሚነሳበትና የሚቀጥልበት ምክንያት የለም። በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ወራሾች ቤቱን ለአመልካች የማስረከብ ግዴታ የለባቸውም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ያለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ቤቱን ነሐሴ 24 ቀን 1985 ዓ.ም. ለአመልካች መሸጣቸውንና የሽያጭ ውሉም በጽሑፍ መደረጉን፣ ይህን የሽያጭ ውል በመያዝ ገዢና ሻጭ ሽያጩን ለማስመዝገብና የባቤትነቱን ስም ለማዛወር ፍ/ቤት ዘንድ መቅረባቸውን፣ ፍ/ቤቱም ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲጣራ ካደረገ በኋላ የመጣ ተቃዋሚ ያለመኖሩን በማረጋገጥና የግራ ቀኙን ስምምነትንም በመረዳት ውሉ እንዲፀድቅ፣ የባለቤትነት ስምም ከሻጭ ወደ ገዢ እንዲዛወር በማለት መወሰኑን በመ/ቁ. 561/86 መጋቢት 15 ቀን 1987 ዓ.ም.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ችለናል። ወ/ሮ ፋናዬ አየለ በወቅቱ በጋዜጣው ጥሪ መሠረት ወይም በሌላ መንገድ ስምተው፣ በሰሙበትና ባወቁበት ጊዜ መቃወሚያ በማቅረብና ጣልቃ በመግባት መከራከር የነበረባቸው የሽያጭ ውሉ በፀደቀበትና የቤቱ ባለቤትነት ስም ለገዢው እንዲዛወር ተብሎ በተወሰነበት የመዝገብ ቁ 561/86 በተደረገው ክርክርና በተሰጠው ውሣኔ ላይ እንጂ ቤቱን ያስረክቡን ተብሎ በቀረበው ክስ ጣልቃ ገብተው ሊከራከሩ የሚችሉበት የሕግ ምክንያት የለም። ምክንያቱም አመልካች ቤቱን አስረክቡኝ እያሉ ያሉት በፀደቀው የሽያጭ ውልና ስም እንዲዛወር ተብሎ በፍ/ቤት በሌላ መዝገብ ተወስኖ ባደረ ጉዳይ በመሆኑ ቤቱን የተመለከተ መብት የሽያጭ ውሉ በፍርድ ቤት በፀደቀበትና የባለቤትነት መብት ለገዢው እንዲዛወር ተብሎ በተወሰነበት ጊዜ የታየና ያለቀለት ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪዋ ይህ ውሣኔ በተሰጠበት የመ/ቁ. 561/86 ጣልቃ ገብተው መከራከር ነበረባቸው። ክሱ በፀደቀልኝ የሽያጭ ውልና ስም እንዲዛወርልኝ በተወሰነልኝ መሠረት ቤቱን ያስረክቡኝ የሚል እንጂ የሽያጭ ውሉ ይጽደቅልኝ የሚል ባለመሆኑ በፀደቀው የሽያጭ ውልና ስም እንዲዛወር ተብሎ አስቀድሞ በሌላ መዝገብ በፍ/ቤት ተወስኖ ባደረው ጉዳይ ጣልቃ ገብተው የሽያጭ ውሉን በዛን ጊዜ ያልተቃወሙት አመልካች በዚሁ ቤቱን ያስረክቡኝ በሚለው ክስ ላይ ጣልቃ መግባት አይችሉም።

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ቤቱን ያስረክቡኝ በማለት በአመልካች ኋላ የቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ ግራ ቀኙን ባከራከረበት ጊዜ ጣልቃ ልግባ በማለት የአሁን ተጠሪ ሲያመለክቱ ጣልቃ መግባት ያለባቸው ቀደም ብሎ የሽያጭ ውሉ ይጽደቅልኝ የባለቤትነት ስምም እንዲዛወርልኝ በማለት አመልካች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሮ ሌላው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ በሰጠበት የመ/ቁ. 561/86 እንጂ ኋላ በቀረበው በዚሁ የቤት ያስረክቡኝ ክስ አይደለም በማለት ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ሲገባ ጣልቃ እንዲገቡ በመፍቀድ አከራክሮ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የነበረው ፍ/ቤት

የሰጠውን ውሣኔ በሚሽር መልኩ የሽያጭ ውሉ በአግባቡ የተደረገ ባለመሆኑ ሊፈርስ ይገባል፤ ተከሣሾች ቤቱን የማስረከብ ግዴታ የለባቸውም በማለት የሰጠውን ውሣኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 እና 41 ጋር በማገናዘብ ስንመለከተው ውሣኔዉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም።

በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መታረም የሚገባው ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል።

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 2643 ሰኔ 3 ቀን 1995 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23795 የካቲት 1 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል።
2. የቤት ሽያጭ ውሉ በፍ/ቤት የፀደቀና የቤቱ ባለቤትነት መብትም ወደ አመልካች እንዲዞር ተብሎ የተወሰነ በመሆኑ ቤቱ የውርስ ንብረት አይደለም። የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ወራሾችም ቤቱን የመውረስ መብት የላቸውም። የ50 አለቃ ሞገስ ጽጌ ሚስትም ጣልቃ በመግባት መከራከር የነበረባቸው የሽያጭ ውሉ በፀደቀበትና የባለቤትነት ስም ለገዢው /ለአመልካች/ እንዲዛወር ተብሎ ውሣኔ በተሰጠበት ክርክር እንጂ ቤቱን ለመረከብ በቀረበው ክስ መሆን የለበትም። ተጠሪዎች በወረዳ 12 ቀበሌ 11 የሚገኘውንና ቁጥሩ 1408 የሆነውን ቤት ለአመልካች በውሉ መሠረት እንዲያስረክቡ በማለት ወስነናል። ይፃፍ።
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 24974

ታህሳስ 8 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- 1. አቶ ፈቃዱ ደሬሎ

2. ወ/ሮ ዓይናለም በሻህ } ጠበቃ መላት ፈለቀ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ንጉሴ ወርቁ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሐረገወይን ጀማነህ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በአመልካቾችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ተሰርዞ ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ በሥር ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካቾች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪዎች በአመልካቾች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በወረዳ 16 ቀበሌ 04 ክልል የቤት ቁጥር 898 የሆነውን ቤት በታህሳስ 1 ቀን 1977 ዓ.ም. በተፃፈ የሽያጭ ውል በብር 58,000 /ሃምሳ ስምንት ሺህ/ ከሣሾች ለተከሣሾች ሸጠን ውሉ በተደረገ ዕለት ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ/ የተቀበልን ሲሆን ቀሪውን 8,000 /ስምንት ሺህ/ ደግሞ በ30 ቀን ውስጥ ቤቱን አስረክበን እንደሚከፈለን በተስማማነው መሠረት ቤቱን ያስረከብን ቢሆንም ቀሪው ገንዘብ ያልተከፈለ ስለሆነ ውሉ እንዲፈርስና ወደነበርንበት እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ክሱና ማስረጃው ለተጠሪዎች ደርሶም በሰጡት መልስ የውሉን መደረግ አምነው ውሉ በተፈረመ በ30 ቀን ውስጥ ከሳሾች የሸጡትን ቤት ከእዳና ዕገዳ ነፃ አድርገው ውል ክፍል ቀርበው መሸጣቸውን በማረጋገጥ ሲፈርሙ ቀሪው ብር 8,000 (ስምንት ሺ.) እንደሚከፈላቸው በውሉ ላይ የተስማማን ቢሆንም ይህንን ግዴታ ካለመወጣታቸው በላይ በክስ ከተጠየቀው ገንዘብ ላይም ክስ ከመቅረቡ በፊት ብር 5,000 (አምስ ሺ.) ለከሳሾች የከፈልን ስለሆነ ውሉ ይፍረስል በማለት ያቀረቡት ክስ ከበቂ ኪሣራ ጋር ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተከሳሾች በቀረነት የሚፈለግባቸውን ገንዘብ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 1977 ዓ.ም. ድረስ አጠቃለው ለመክፈል በውል ግዴታ ገብተው ክፍያውን አለመፈጸማቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል ፈርሶ ወደነበሩበት ሊመለሱ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሾች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሊሰረዝ ይገባል? ወይንስ አይገባም? የሚለው በመሆኑ ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

ታህሣሥ 1 ቀን 1977 ዓ.ም. በተፃፈ ውል ግራ ቀኙ የቤት ሽያጭ ውል ማድረጋቸውንና ውሉ በተደረገ ዕለት ሻጮች የአሁን ተጠሪዎች ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ/ የተቀበሉ መሆኑን ግራ ቀኙ ተማምነውበታል፡፡ ተጠሪዎች ውሉ ይሰረዝልን በማለት በክስ የጠየቁት ቀሪው ብር 8,000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(ስምንት ሺህ) አልተከፈለንም በሚል ምክንያት ነው። በውል አፈፃፀም ሂደት ከተዋዋዮች አንዱ የውሉን ግዴታ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ሌላው ወገን እንደሁኔታው ውሉ እንዲፈጸምለት መጠየቅ እንደሚችል ይህም ካልሆነ ውሉ እንዲሰረዝ ጥያቄውን ማቅረብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1771 ላይ ተመልክቷል። የውል ይሰረዝልኝ ጥያቄ ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ዳኞች ውሉ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ውሣኔ ከመስጠታቸው በፊት የተዋዋዮችን ጥቅምና ለቅን ልቦና የሚያስፈልገውን ነገር መሠረት ማድረግ እንዳለባቸው፣ በውሉ ላይ ዓይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተግባር /fundamental breach of contract/ ካልተፈጸመ በስተቀር ዳኞች ውል ይሰረዝ ማለት እንደሌለባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1784 እና 1785 ላይ ተመልክቷል።

በተያዘው ጉዳይ በቤት ሽያጭ ውሉ መሠረት ለተጠሪዎች መከፈል ከሚገባው ገንዘብ አብዛኛውን አመልካቾች እንደከፈሉ ተረጋግጧል። ከዚህም ውሉ በአመዛኙ እንደተፈጸመ መገንዘብ ይቻላል። ውሉ ባመዛኙ መፈጸሙ ከተረጋገጠ ደግሞ ዓይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተግባር ተፈጽሟል ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ ከቅን ልቦና መለኪያ አኳያም ሲታይ ተጠሪዎች በቀሪነት የሚፈለገውን አነስተኛ ገንዘብ እንዲከፈላቸው በመጠየቅ ውሉ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ እየቻሉ እንዲሰረዝ መጠየቃቸው ተቀባይነት ያለው ምክንያት አይደለም። የሥር ፍ/ቤቶችም ቀሪው ገንዘብ ባለመከፈሉ ምክንያት የቀረበውን የውል ይሰረዝልኝ ክስ ተቀብለው ውሉ እንዲሰረዝ መወሰናቸው የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10356 ነሐሴ 16 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43067 ግንቦት 9 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል።
2. አመልካቾች መሠረታዊ የሆነ የውል መጣስ ተግባር ያልፈጸሙ ስለሆነ ከተጠሪዎች ጋር ያደረጉት ውል ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ተወሰኗል።
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ።
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 25165

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ እርቁ ጎዳ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አህመድ አብዱልሐሚድ - ባለቤታቸው ቀርበዋል

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የሠፈረውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በፌ/ከ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሣሽ የነበሩ ሲሆን በአሁን አመልካችና አሁን በክርክሩ ውስጥ በሌሉት ሌሎች ሁለት ሰዎች ላይ በጥቅምት 30 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከ2ኛዋ ተከሣሽ ከወ/ሮ ወይንሸት ካሣሁን ጋር ሚያዝያ 7 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ ስነድ የባህል ጋብቻ መሥርተን በሰኔ 3 ቀን 1992 ዓ.ም ጋብቻውን በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ያስመዘገብን ሲሆን 1ኛው ተከሣሽ አቶ ውሂብ ማዘንጊያ ከ2ኛዋ ተከሣሽ በተሰጠው የውክልና ስልጣን ስሙ በ2ኛዋ ተከሣሽ የሆነውን የጋራ ቤታችንን ያለ ከሣሽ እውቅና ለ3ኛ ተከሣሽ (ለአሁን አመልካች) በመጋቢት 5 ቀን 1994 ዓ.ም በተፈረመ ውል በብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) ሸጠው የገንዘቡን መጠን ዝቅ በማድረግ ቤቱ የተሸጠው በብር 23,000 (ሃያ ሦስት ሺህ) መሆኑን የሚገልጽ ውል በመጋቢት 12 ቀን 1994 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው ተፈራርመዋል፡፡ ቢሆንም የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው ከቅን ልቦና ውጪ በመሆኑ ውሉ ፈርሶ የባለቤትነት ስሙ በ2ኛዋ ተከሣሽ እንዲመዘገብ ይደረግልኝ ሲሉ ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡ 1ኛው ተከሣሽ ከ2ኛ ተከሣሽ በተሰጠኝ ውክልና መሠረት በፈፀምኩት ውል ልከሰስ አይገባም

የሚል መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም ረገድ ከ3ኛው ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ጋር በጋራ በሰጡት መልስ የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው በብር 23,000 (ሃያ ሦስት ሺህ) እንጂ በብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) የተደረገ ውል የለም፡፡ ጋብቻ መኖሩንም አናውቅም፣ ቤቱ የተመዘገበው በ2ኛዋ ተከሣሽ ስም ከመሆኑ ባሻገር 2ኛ ተከሣሽ ትዳር እንደሌላቸው ከሚኖሩበት ቀበሌ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከሣሽ(የአሁን ተጠሪ) ጉዳት ደርሶብኛል ካሉ 2ኛዋን ተከሣሽ ከሚጠይቁ በቀር በቅን ልቦና የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የ1ኛውን ተከሣሽ ተቃውሞ በመቀበል ከክርክሩ ያሰናበታቸው ሲሆን የአሁን አመልካች ውሉን በፈፀመበት ወቅት 2ኛዋ ተከሣሽ ትዳር እንዳላት እንደማያውቁ ክደው የተከራከሩት በተጠሪ ያልተስተባበለ በመሆኑ አመልካች በቅን ልቦና በተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል መሠረት በህጉ አግባብ የባለቤትነት መብት ያገኙበትን ንብረት ሊያጡ አይገባም ሲል የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ የአሁን ተጠሪ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24830 በህዳር 6 ቀን 1998 ዓ.ም ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግኝ አቅርበዋል፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1266 እና አ/ቁ. 213/92 አንቀጽ 68/ሀ/ነን ጠቅሶ በማይንቀሣቀስ የጋራ ንብረት ላይ ለመዋዋል የሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት ያስፈልጋል፣ ማስረጃውን የሰጠው ቀበሌም 2ኛዋ መ/ሰጭን በነዋሪነት ያስመዘገበ ከመሆኑም በላይ ስለጋብቻው መኖር አለመኖር የማስረዳት ብቃት የለውም ከዚህ እና ሁለት የተለያየ የሽያጭ ዋጋ ያላቸው ውሎች በተዋዋዮች ስምምነት ከመደረጋቸው አንፃር የውሉ አደራረግ ከመነሻው በተንኮል መሆኑን፣ በአጠቃላይ የውሉ አደራረግ ለህሊና ብቻ ሣይሆን ለህግም ተቃራኒ ነው ማለት ይቻላል በሚል ምክንያት ውሉ በአ/ቁ. 213/92 አንቀጽ 69/1/ መሠረት ሊፈርስ ይገባል ሲል የከ/ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሮታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታም የቀረበው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመ/ቁ. 22126 በግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡

ይህም ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ተመልክቶ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ የተወሰነው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር በሚል ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በመሠረቱ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ውሉን ለማፍረስ ምክንያት ያደረገው የቀበሌ ጽ/ቤት የጋብቻ መኖር አለመኖርን የማስረዳት ብቃት የለውም፣ ጋብቻን የመመዝገብ ስልጣን በተሰጠው እና የጋብቻ የምስክር ወረቀት ከሚሰጠው አካል ማስረጃ አልተጠየቀም፣ ሁለት የተለያየ የሽያጭ ዋጋ ያላቸው ውሎች መደረጋቸው የውሉ አደራረግ ከመሠረቱ የተንኮል መነሻ የነበረው ነው የሚል ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ አመልካቹ ቤቱን ሲገዙ ከቀበሌ ማስረጃ መጠየቃቸው የቀበሌ ጽ/ቤት የነዋሪዎችን አሠፋፈርና የአኗኗር ሁኔታ በተመለከተ ከማንኛውም ተቋም በተሻለ መረጃዎችን ሰብስቦ የሚመዘግብ ከመሆኑ አንፃር መረጃው አግባብነት ያለው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ቀርበው በውልና ማስረጃ ካስፀደቁት ውል በተጨማሪ በብር 160.000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) የተደረገ ሌላ ውል አለ ያሉ ሲሆን፣ ነገር ግን ህጉም ሆነ ይህ ፍ/ቤት ከግንዛቤ የሚያስገባው ያልፀደቀውን እና አመልካች የካዱትን የመንደር ውል ሣይሆን በአዋዋይ የፀደቀውንና በብር 23,000 (ሃያ ሦስት ሺህ) የተደረገውን የሽያጭ ውል ብቻ ነው፡፡ ከነዚህ ነጥቦች በመነሣት አመልካች የቤቱ ባለቤትነት በወ/ሮ ወይንሸት ካሣሁን ስም መሆኑን፣ ወ/ሮ ወይንሸትም ትዳር የሌላቸው መሆኑን በበቂ ሁኔታ አረጋግጠው የፈፀሙት የሽያጭ ውል ለሕግና ለሞራል ለቅን ልቦናም ተቃራኒ ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አለተገኘም፡፡ በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የአመልካችን የቅን ልቦና መከራከሪያ ወደጎን በመተው የሽያጭ ውሉ ይፈርሣል ሲል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ በወረዳ 16 ቀበሌ 11 የቤ.ቁ. 098 የሆነውን ቤት አስመልክቶ መጋበት 12 ቀን 1994 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል አይፈርስም ብለን ወስነናል፡፡

2/ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22126 በግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

3/ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24830 ህዳር 6 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 26996

በየካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሠ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

አለ. መሐመድ

አመልካች፡- አቶ በቀለ ደቦጭ - ጠበቃ መ/አለቃ ሽፈራው አመኑ

ተጠሪዎች፡- 1/ ወ/ሮ አዛለች ደሣለኝ
2/ ወ/ሮ አምሣለ ኃይሉ
3/ ወ/ሮ አስቴር ኃይሉ
4/ አቶ ጌድዮን ኃይሉ
5/ አቶ ፍቅሩ ኃይሉ
6/ አቶ በትሩ ኃይሉ
7/ ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ
ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ክርክር የተጀመረው በኦ/ብ/ክ/መ/የጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ከሣሾች አመልካቹ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በጥቅምት 12 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ አመልካቹ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የተቀሩት ተጠሪዎች አባት ከሆኑት ከሟች ግራዝማች ኃይሉ ወ/ፃድቅ በጥቅምት 22 ቀን 1986 ዓ.ም ባደጉት ውል ግምቱ 1,300,000.00 (አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺህ) ብር የሆነው የእንጨት መሠንጠቂያ ፋብሪካ ግማሽ በብር 650,000.00 (ስድስት መቶ ሃምሳ ሺህ) ገዝተው ከውሉ ገንዘብ ውስጥ ብር 160,000.00 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) የከፈሉ ሲሆን የቀረው ብር 490,000.00 (አራት መቶ ዘጠና ሺህ) እስከ

አሁን ድረስ ያልተከፈለ በመሆኑና አመልካቹም የሽያጭ ስምምነቱ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ የፋብሪካው ሰራ አስኪያጅ ሆኖ እየሠራ ያለ በመሆኑ ከፋብሪካው ላይ የሚፈለግ ልዩ ልዩ እዳ ከፍሎ ከሆነ ተሣስበን ቀሪውን ገንዘብ ከወለዱ ጋር እንዲከፈለን እንዲሁም ፋብሪካውን ለወደፊት በጋራ እንድንጠቀምበት እንዲወሰንልን በማለት ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ለተጠሪዎች ክስ በሰጠው መልስ ግማሽ ፋብሪካውን በብር 650,000 (ስድስት መቶ ሃምሳ ሺህ) መግዛቱ እና ቀብድ ብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) መክፈሉን ሣየስተባብል ነገር ግን በውሉ መሠረት ቀሪውን ገንዘብ ብር 490,000 (አራት መቶ ዘጠና ሺህ) ለመክፈል የሚገደደው የመንግሥስትና የግለሰብ የተለያዩ እዳዎች ተከፍለው ስመንብረቱ በስሙ ከተዛወረ በኋላ መሆኑን ሆኖም ፋብሪካው ቀድሞ በ1971 ዓ.ም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በዕዳ መያዣነት እንደያዘው በአሁኑ ሰዓትም ባንኩ በፋብሪካው ላይ የቀዳሚነት መብት አለኝ በሚል የወሰደው እና በእጁ የማይገኝ በመሆኑ ክሱ የሕግ ድጋፍ የለውም ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአሁን አመልካች የተከሣሽ ከሣሽ በመሆን በዚያው መዝገብ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ በየካቲት 5 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ እና ባለቤታቸው በዋስትና የተያዘውን ፋብሪካ ከዕዳና እገዳ ነፃ የሆነ በማስመሰል የሸጡልኝ በመሆኑ ውሉ ፈርሶ የከፈልኩትን ቀብድ ብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1885/2/ መሠረት እጥፍ አድርገው ብር 320, 000 (ሦስት መቶ ሃያ ሺህ) ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ ሲል ፍ/ቤቱን ጠይቋል፡፡

የሥር ከሣሾች ለተከሣሽ ከሣሽነት ክሱ በሰጡት መልስ በተከሣሽ ከሣሽነት የቀረበው ክርክር ከዚህ ቀደም በተመሣሣይ ጉዳይ በመ/ቁ. 19/94 ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ ድጋሚ ሊቀርብ አይችልም፣ ውሉ ተሠርዞ በቀብድ የተሰጠው ገንዘብ ይመለስ ቢባል እንኳ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810/1/ እና በቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1845 መሠረት ክሱ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ የከሣሾችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስ በተመለከተ፣ ፋብሪካው በመያዣ የተያዘ በመሆኑ የአሁን አመልካች (የሥር ተከሣሽ) እንደፍላጎቱ ስሙን ማዛወር አይችልም፣ ከሣሾቹ ከስምምነቱ በፊት በፋብሪካው ላይ ያለውን ዕዳ በመክፈል ከእዳ ነፃ አድርገው ስሙ ከተዛወረለት በኋላ ቀሪው ብር 490,000(አራት መቶ ዘጠና ሺህ) እንደሚከፈል ውሉ በግልጽ አስቀምጦ ሣለ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ውሉ ሊፈፀም ይገባል ማለት አስቸጋሪ ስለሚሆን የከሣሾቹ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፤ ያለ ሲሆን የተከሣሽ ከሣሹን ክስ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪዎች በባንክ አዳ የተያዘን ንብረት አመልካቹን (የሥር ተከሣሽን) በማሳሳት ሸጠውለት ብር 160,000(አንድ መቶ ሰልሳ ሺህ) ወስደው ቀሪውን ብር 490,000(አራት መቶ ዘጠና ሺህ) ስመንብረት በተከሣሽ ስም ካዛወሩ በኋላ ለመውሰድ ያደረጉት ስምምነት ሊፈፀም የማይቻል ስምምነት ሆኖ የተገኘ ስለሆነ ተጠሪዎች (የሥር ከሣሾች) ቅን ልቦና የሌላቸው መሆኑን በመገንዘብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1885(2) መሠረት የወሰዱትን ብር 160,000(አንድ መቶ ሰልሳ ሺህ) እጥፍ በማድረግ ብር 320,000(ሦስት መቶ ሃያ ሺህ) ከፍለው ውሉ እንዲፈርስ ሲል ወስኗል፡፡

የጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለኦ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት የቀረበ ሲሆን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በሚያዝያ 26 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የተጠሪዎችን መቃወሚያ ከግምት ውስጥ በማስገባት የአሁን አመልካች (በስር መ/ሠጭ) ቁጥሩ 19/94 በሆነ ሌላ መዝገብ በተጠሪዎቹ (በስር ይ/ባዮች) ላይ የዚህ ክርክር መነሻ በሆነው ውል መሠረት ስመንብረቱን በስሜ እንዲያዛውሩልኝ፤ በዚህ ፋብሪካ ምክንያት ያወጣሁትን ወጭ እና በድርጅቱ ላይ ያለውን ዕዳ እንዲከፍሉኝ

ሲሉ ክስ አቅርበው ተጠሪዎቹ በውሉ መሠረት የድርጅቱን ግማሽ ስመንብረት እንዲያዛውሩ እና ለድርጅቱ የወጣውን እዳ ከተለያዩ ወጪዎች ጭምር ብር 215,460.13(ሁለት መቶ አሰራ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰልሳ ከአስራ ሦስት) እንዲከፍሉት ተወስኖ እያለ አመልካች ውል ይፍረስልኝ ብሎ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በማቅረቡ ብቻ ውሉ እንዲፈርስ ተብሎ መወሰኑ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፣ ተጠሪዎቹም ግዴታቸውን እንደስምምነቱ ሣይፈጽሙ ቀሪው ገንዘብ ሊከፈለን ይገባል በማለት ያቀረቡት ቅሬታም ተቀባይነት የለውም ያለ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የአሁን አመልካች የፋብሪካው ስራ አስኪያጅ ሆኖ በሠራበት ጊዜ ከፋብሪካው የሚገኘው ገቢ በማስረጃ ተጣርቶ ተጠሪዎቹ የድርጅቱ ገቢ ይከፈለን በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ውሣኔ እንዲያኝ በማለት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሠረት ወደ ጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገቡ በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሠኙት የአሁን አመልካች ለክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታቸውን ቢያቀርቡም የኦ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤታቸውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች በመስከረም 12 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት ውሉ ፈርሶ ተጠሪዎች አመልካች የከፈሉትን ቀብድ እጥፍ አድርገው ይመልሱ ሲል የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ከድርጅቱ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ አጣርቶ የመሠለውን ይወስን ሲል መወሰኑ እና የክልሉም ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይህንን ውሣኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታቸው ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይህም ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውና አመልካች የገዙት ፋብሪካ በእዳ በባንክ የተሸጠ በመሆኑ ስም ሊዛወር ስለማይችል ውሉ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ በስር ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተሰጠው ውሣኔ እንዲሻር መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አድርገዋል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው የኦ/ጠ/ፍ/ቤት የጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤት ውሳኔ ፈርሶ ተጠሪዎቹ የተቀበሉትን ቀብድ እጥፍ አድርገው ይክፈሉ ሲል የሰጠውን ውሣኔ ለመሻር መሠረት ያደረገው አመልካቹ ከዚህ ቀደም በመ/ቁ. 19/94 ተጠሪዎቹ የፋብሪካውን ስመንብረት ያዛውሩልኝ ለፋብሪካው እዳ የተከፈለ ገንዘብ ይመለስልኝ ሲሉ ባቀረቡት ክስ በተጠሪዎች ላይ ያስወሰኑ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሠረት ዳግመኛ ክስ ሊመሠርቱ አይችሉም በሚል ነው፡፡ በመሠረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 ተፈፃሚነቱ ቀድሞ በተወሰነው ክርክር የስረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አንድ አይነት በሆነ ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን ምንም እንኳ ቀድሞ በመ/ቁ. 19/94 የቀረበው ክርክር በፋብሪካ ሽያጭ ውሉ ዙሪያ የሚያጠነጥን ቢሆንም በክሱ የተጠየቀውም ዳኝነት ይሁን አከራካሪ የነበረው ጭብጥ ከውሉ መፍረስና አለመፍረስ ጋር የተገናኘ ባለመሆኑ አመልካች ውል ይፍረስልኝ ሲሉ ያቀረቡት ክስ በድጋሚ የቀረበ ክርክር ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

አመልካቹ በተያዘው ጉዳይ ያቀረቡት ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 5 ሥር የሚካተት አይደለም ከተባለ ደግሞ የውሉን መፍረስ አግባብነት መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡ የክርክሩ መነሻ በሆነው ውል የተሸጠው ፋብሪካ በአሁኑ ሰዓት ባንክ ለእዳው ማስፈፀሚያ ያዋለው መሆኑን ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ ከተደረጉት ክርክሮች እና ከተሰጡት ውሣኔዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የውሉ ጉዳይ የሆነው ፋብሪካ በአመልካቹ ስም ሊዛወርም ሆነ አመልካች በውሉ ላይ ተመርኩዞ ሊተላለፍለት የሚችል መብት አይኖርም፡፡ በሌላ አነጋገር የዚህ ውል ጉዳይ የሆነው እንደ ፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1715 ድንጋጌ አነጋገር ሊፈፀም የማይችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የውሉ ጉዳይ ሊፈፀም የማይችል በሆነ ጊዜ ውሉ እንደሚፈረስ ይኸው ድንጋጌ ይገልፃል፡፡ አንድ ውል ሲፈርስ ደግሞ ውጤቱ የሚሆነው ተዋዋዮቹን ወደ ነበሩበት ቦታ

መመለስ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 ይደነግጋል፡፡ ይህም ችሎት የጅማ ዞን ከ/ፍ/ቤት ውሉ ይፈርሣል ሲል የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ መሆኑን የተገነዘበ ሲሆን ከፍተኛ ፍ/ቤቱ አመልካች የፈፀሙት ክፍያ ቀብድ በመሆኑ ተጠሪዎች እጥፉን ይመለሱ ሲል የሰጠውን ውሣኔ ግን በውሉ ክፍያው ቀብድ መሆኑ ካለመገለፁ አንፃር አልተቀበለነውም፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት የፋብሪካ ሽያጭ ውሉ ይፈርሣል፣ ተጠሪዎቹም አመልካች የከፈሉትን ብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) ሊመልሱ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የኦ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.22676 በሚያዝያ 26 ቀን 1998 ዓ.ም አመልካች በውሣኔ ያለቀውን ክርክር በድጋሚ ማቅረብ አይችልም ሲል ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ላይ ተመርኩዞ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2. የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎቹ የወሰዱትን ቀብድ እጥፍ አድርገው ብር 320,000 (ሦስት መቶ ሃያ ሺህ) ይክፈሉ ሲል የሰጠውን ውሣኔ አሻሽለን፣ክፍያው ቀብድ ለመሆኑ ውሉ ስለማይገለጽ ተጠሪዎች ሊመልሱ የሚገባው የወሰዱትን ብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) ነው በማለት ውሉ ይፈርሣል ሲል በመ/ቁ.02939 በሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ አጽንተነዋል፡፡

ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 27349

ታህሳስ 8 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ ኮ/ል ደነቀው

ተጠሪ፡- ዘላቂ ግብርና ተሐድሶ ኮሚሽን አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በይግባኝ ተመልክቶ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካችና በሥር 1ኛ ተከሣሽ ላይ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 1ኛ ተከሣሽ ልዩ ልዩ የቢሮ ዕቃዎችን ለመግዛት በወጣው ጨረታ ተካፋይ በመሆን ብር 468,540.00 (አራት መቶ ሺህ አምስት መቶ አርባ) የሚያወጡ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን በ120 ቀን ውስጥ ሊያቀርብ ስምምነት ተፈራርሞና 2ኛ ተከሣሽ በቀረበው የሥራ አፈፃፀም ዋስትና አሸናፊ ሆኖ ሙሉ ክፍያ የተፈፀመለት ቢሆንም በውሉ መሠረት ጊዜውን ጠብቆ አብዛኛውን ዕቃ በጥራት አሟልቶና አስተካክሎ ያላቀረበ ስለሆነ በክስ የተጠየቀውን ተከሳሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቆ ተከሳሻች ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሙሉ መልስም በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

በተከሳሾች በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተነሳው ክርክርም በውሉ አንቀጽ 8 መሠረት ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችለው ሐምሌ 12 ቀን 1991 ዓ.ም. በተፈረመው ውል አንቀጽ መሠረት በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩ ወደ አስታራቂ ኮሚቴ ሊመራ እንደሚገባውና አስታራቂ ኮሚቴውም ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ቅሬታ ቢኖር ሲሆን በቀጥታ ወደ ፍ/ቤት መሄድ ግን ውሉን የሚቃረን ስለሆነ ፍ/ቤት ሊቀበለው አይገባም የሚል ነው፡፡

የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚህ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ ግራ ቀኙ ባቋቋሙት ውል አንቀጽ 8 ላይ ተከሳሾች በጠቀሱት መልኩ ስምምነት የተደረገ ስለሆነና በሕግ አግባብነት የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋዮች ላይ አሳሪ ስለሚሆኑ በዚህ ሁኔታ የቀረበው ክስ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 244/2/ረ/መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ መ/ሰጪዎች በይ/ባይ አማካይነት በውሉ መሠረት በስምምነት ለመጨረስ በደረሰባቸው ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያ መሠረት መቅረብ ሲገባቸው ያልቀረቡ በመሆኑና ይህ ከሆነ ደግሞ በውላቸው ላይ አለመግባባት ከተከሰተ ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት በመከራከር ወይም በሚመርጧቸው አስታራቂ ኮሚቴዎች ለመፍታት መስማማታቸው ብቻውን ይግባኝ ባዮችን ወደ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከማቅረባቸው በፊት በስምምነታቸው መሠረት መጨረስ ነበረባቸው ተብሎ ጉዳያቸውን ወደ ፍ/ቤት የማቅረብ መብታቸው የሚነፈግበት ምክንያት የለም የሚል ትችት በውሣኔው ላይ አስፍሮ የሥር ፍ/ቤት ብይን በመሻር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይታይ በማለት ጉዳዩን መልሷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ጉዳዩ በፍ/ቤት መታየት አለበት ተብሎ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ ሊጣራ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ክርክሩ በፍ/ቤት ሊታይ ይችላል? ወይንስ አይችልም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን መርምረናል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ውል ማንኛውም አለመግባባት ቢፈጠር ጉዳዩን በስምምነት ለመፍታት ይህም ካልተቻለ በአስታራቂ አማካኝነት ለመጨረስና ወደ ፍ/ቤት ለመሄድ የተስማሙት በእነዚህ አማራጮች አማካይነት ጥረት አድርገው ያልተቻለ ከሆነ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ስምምነት የተደረገ መሆኑም ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ተጠሪ በዚህ የውል ቃል መሠረት ላለመግባባቱ ዕልባት ለመስጠት በማሰብ ለአመልካቾች ማሳሰቢያ ቢላክላቸውም ያልቀረቡ ስለሆነ ክሱ በቀጥታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ እንደቻለ በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡

ይሁንና የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንዳሰፈረው በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋዮች ላይ ሕግ እንደመሆናቸው መጠን ግራ ቀኙ በዚህ መልኩ ለመፈፀም ፈቃዳቸውን እስከሰጡ ድረስ በዚህ የውል ቃል የማይገደዱበት ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ ተጠሪ ጉዳዩን በውሉ መሠረት ለመጨረስ በማሰብ ለአመልካች ማሳሰቢያ ስለመላኩ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው ቢባል እንኳን ማድረግ የሚጠበቅበት በውሉ መሠረት አስታራቂ ሽማግሌዎች ተሰይመው ጉዳዩ ዕልባት እንዲያገኝ ዳኝነት መጠየቅ እንጂ በቀጥታ ክስ ማቅረቡ ውሉን የሚፃረር በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሉ ላይ ተመስርቶ ክሱን በብይን ሳይቀበል መቅረቱ የሚነቀፍ አልነበረም፡፡ ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዚህ ዓይነት ስምምነት ቢኖርም ወደ ፍ/ቤት ከመቅረብ አያግዳቸውም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን መሻሩ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ውል አለመግባባትን በአስታራቂ ወይም በዘመድ ዳኛ አማካይነት ለመጨረስ

ያደረጉት ስምምነት በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 1765 የተፈቀደ ከመሆኑም በላይ ማንኛውም ውል በሕግ አግባብ እስከተቋቋመ ድረስ በተዋዋዮች ላይ ሕግ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731/1/ ላይ የተመለከተ በመሆኑ በዚህ ሁኔታ ጉዳዩ በቀጥታ በፍ/ቤት መታየት ይችላል በማለት የሥር ፍ/ቤትን ብይን በመሻር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩ እንዲታይ ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ለፍ/ቤት በመ/ቁ. 02001 ጥቅምት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 333/93 የካቲት 27 ቀን 1995 ዓ.ም. የሰጠው ብይን ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠበር መ/ቁ. 28663

ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ወልዴ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የዚህ ጉዳይ መነሻ ተጠሪ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ቤንች ማጂ ዞን ሸካ ወረዳ ፍ/ቤት 1ኛ/ አቶ ታደሰ ገ/የሱስ 2ኛ አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ (የአሁኑ አመልካች) ላይ የውል ይፍረስልኝ ክስ በማቅረባቸው ነው፡፡ የክሱም ይዘት በአጭሩ 1ኛው ተከሣሽ የትዳር አጋሬ ሲሆን እኔ በሌለሁበት የጋራ ሀብታችን የሆነውን መኖሪያ ቤት ለ2ኛ ተከሣሽ ሚያዚያ 12 ቀን 1994 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል የሸጠለት ሲሆን እኔ ከአንድ ዓመት በኋላ ስመለስ 1ኛው ተከሣሽ በጨቤ አስፈራርቶኝ ተገድጄ በውሉ ላይ ፈርሜአለሁ፡፡ ስለዚህ ይህ በግዳጅ የተፈፀመ ውል ይፍረስልኝ ብለዋል፡፡ 1ኛው ተከሣሽ ክሱን አምኖ የተቀበለ ሲሆን፣2ኛው ተከሣሽ ግን በመልሱ ውሉን ፈቅዳ ፈርማለች ክሷን ከ2 ዓመት በላይ ቆይታ መመሥረቷ ከቅን ልቦና ውጪ መሆኑን ያሣያል ሲል ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ምስክሮችን ያዳመጠ ሲሆን ምስክሮቹም ውሉ በተፈረመበት ዕለት ባልና ሚስቱ መጨቃጨቃቸውን የቃላት ዛቻ እንደነበረ መስክረዋል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት በውሣኔው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706 አንፃር ውሉን ተገዳ መፈረሟ በመረጋገጡ እና የፍ/ህ/ቁ. 658(ሀ) በሚያዘው መሠረት በተጋቢዎቹ መሀል

ስምምነት ሣይኖር በማይንቀሣቀስ ንብረት መዋዋል ስለማይቻል ውሉ ይፈርሣል፣ 2ኛ ተከሣሽ ቤቱን ያስረክብ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በውሣኔው ቅር በመሠኘት ለቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኛቸውን ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኛቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች አቤቱታውን በመቀጠል ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም አቤቱታቸውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታም የቀረበው የወረዳው ፍ/ቤት ውሉ ይፈርሣል ሲል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታም ለሰበር እንዲቀርብ ታዞ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተካሂዷል፡፡ ይህ ችሎት በፍሬ ጉዳዩ ላይ የተነሱትን ክርክሮችና የስር ፍ/ቤት ውሣኔዎችን ምርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም በዚህ ጉዳይ መፍትሔ የሚሻው ነጥብ የቤት ሽያጭ ውሉ የተጠሪ ሙሉ ፈቃድ ያልታከለበት ነው በሚል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 658 አንፃር ውሉ ይፈርሣል መባሉ አግባብ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡

የወረዳው ፍ/ቤት ተጠሪዋ ውሉ ላይ የፈረመችው ተገድዳ በመሆኑ በውሉ ልትገደድ እንደማይገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706ን መሠረት አድርጎ ወስኗል፡፡ ከዚህም ባሻገር አመልካች ከተጠሪዋ ባለቤት ከአቶ ታደሰ ገ/የሱስ ጋር የፈፀመው የቤት ሽያጭ ውልም ቢሆን ከተጠሪዋ ፈቃድ ወጪ የተፈፀመ ነው በሚል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658ን መሠረት አድርጎ ውሉ ይፈርሣል ሲል ወስኗል፡፡ በእርግጥ በዚህ ድንጋጌ ስር የተጠቀሱትን ተግባራት ለመፈፀም የሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል እንጂ የሦስተኛ ወገን ተዋዋዮችን መብት የሚነካ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ የድንጋጌው ውጤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 686 ላይ በግልጽ ተጠቅሷል፡፡ ይኸውም አንደኛው ተጋቢ ወገን በቁጥር 658 ላይ የተጣለበትን የስልጣን ገደብ ተላልፎ የጋራ ሀብትን የሚጎዳ ተግባር ፈጽሞ ቢገኝ የጋብቻው ግንኙነት በሚቋረጥበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወቅት በካሣ ተጠያቂ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም በቁጥር 658ን የተላፈው ድንጋጌ በምንም ዓይነት አንዱ ተጋቢ ወገን ከሦስተኛ ወገን ጋር ያደረገውን ውል ለማፍረስ ምክንያት አይሆንም፡፡ በአጠቃላይ ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658 መሠረት አድርገው ውሉ ይፈርሣል ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ በአመልካች እና በአቶ ታደሰ ገ/የሱስ መካከል ሚያዝያ 12 ቀን 1994 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፀንቷል፡፡

2/ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/የቤንች ማጂ ዞን ሻላ ወረዳ ፍ/ቤት ግንቦት 3 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

3. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/የቤንች አካባቢ ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02954 ግንቦት 14 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

4. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት በመ/ቁ. 15221 ታህሳስ 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 29233

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ብርሃኑ አመነው

መድንን ኪሮስ

ፀጋዬ አስማማው

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሙሂዲን ፋሪስ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ኢያሱ በዕደ ማርያም ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>**ፍ ር ድ**</u>

የሰበር አቤቱታው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 22359 ታህሣሥ 13 ቀን 99 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ላይ የቀረበ ሲሆን ጉዳዩ ከቤት ሽያጭ ውል ጋር የተያያዘን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት የአሁን አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ የመሠረቱት ክስም በውል የገዛሁትን ቤት እንዲያስረክቡኝ እንዲሁም ዋጋውን በማካካስ በሸጥኩላቸው ጊዜ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ቅድሚያ ክፍያ ተቀብለው ሲያበቁ ቤቱን ባለመረከባቸው ለዘበኛ ብር 750.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ) ከፍያለሁ፡፡ የሸጡልኝ ቤት ባለማስረከባቸው በወር ብር 10,000 (አስር ሺህ) በማከራየት አገኝ የነበረውን የሶስት ወር ኪራይ ብር 30,000 (ሰላሳ ሺ) አሳጥተውኛል፡፡ በመሆኑም የሸጥኩላቸውን ቤት እንዲረከቡና የሸጡልኝን ቤት እንዲያስረክቡኝ፡፡ ለዘበኛ ያወጣሁትን ወጪ ብር 750.00(ሰባት መቶ ሃምሳ) እንዲከፍሉኝ፣ እንደዚሁም ቤቱን አከራይቼ አገኝ የነበረውን ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) እና እስኪያስረክቡ ድረስ በየወሩ ብር 10,000 (አስር ሺ) እንዲታሰብ እንዲከፍሉኝ እንዲወስንልኝ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ደግሞ በሰጡት መልስ ቤቶቹን ለመሻሻጥ ውል ያደረግን መሆኑ አይካድም፡፡ ሆኖም በተፈራረምነው የውል ጽሑፍ ላይ የተቀመጡትን የቤቶቹን ሰነዶች የመለዋወጥና በአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ሽያጩን የማስመዝገብና የሽያጩን የማስፈፀም ሥራዎች አልተከናወኑም፡፡ ከሣሽ የሸጡልኝ ቤት የሚመለከት ካርታም ይሁን የቤት ባለቤትነት ደብተር የላቸውም፡፡ አስፈላጊዎቹን የሸጡልኝ ቤት ሰነዶች እንዲሰጡኝ፤ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ሄደን ሽያጩን እንድናስመዘግብና ውሉ እንዲፈፀም ጠይቂያቸው ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ በመቀጠልም የተጀመረውን የቤት ሽያጭ ውል ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ማስጠንቀቂያ ጽፌላቸዋለሁ በመሆኑም ውሉ ረቂቅ እንጂ የተሟላና ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ሆኖ ልሰናበት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በሰጠው ውሣኔ ውሉ የሚፈፀምበት ምክንያት የለም፡፡ ተከሳሽ የከሻሽን ቤት ከሣሽ ደግሞ የተከሣሽን ቤትና የቤቶቹን ሰነዶች ይረካከቡ ብሏል፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በአሁኑ አመልካችና ተጠሪ መካከል የተደረገ በሕግ የሚታወቅ የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ደግሞ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ያደረግነው የቤት ሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1720/2/ መሠረት የሚፀና ውል ነው፡፡ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሠረት ፈራሽ ነው ወይም ደግሞ ውሉ ሥልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ በረቂቅነት ደረጃ የሚታይ ነው በማለት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በጽሑፍ ከተደረገ የፀና ይሆናል ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2877 የተደነገገውን የሚቃረን በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ ፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይፅናልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ ደግሞ በሰጡት መልስ በመካከላችን የተደረገው ውል ረቂቅ ነው፡፡ ውሉ የተሟላ ሊሆን ይችል የነበረው በተስማማነው መሠረት አመልካች የሸጡልኝን ቤት ሰነዶች ሲያቀርቡና የሁለቱንም ቤቶች ሰነዶች ይዘን ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በመቅረብ የሽያጩ ውል የተመዘገበ እንደሆነ ነው፡፡ አመልካች በተስማማነው መሠረት ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡ አመልካች ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) አልከፈሉኝም፡፡ የሰጡኝ ቅድሚያ ክፍያ ብር 50,000 መሆኑን በክርክራቸው ላይ ጠቅሰዋል፡፡ ከእኔም የሽያጭ ገንዘብ አልተቀበሉኝም፡፡ በበኩሌ የአመልካች ሁኔታ የተጀመረውን የቤት ሽያጭ ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሆኖ ስላላገኘሁት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2348 እና 2349 መሠረት የተጀመረውን የሽያጭ ውል ስምምነት ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡ ውሉም በተስማማነው መሠረት በፍ/ቤትም መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተመዘገበ በመሆኑ በረቂቅነት የሚታይ እንጂ የተሟላና ሊፈፀም የሚገባው ውል አይደለም፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ስር የተደነገገውን መሠረት በማድረግ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ በሕግ የሚታወቅ የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ እንዳችም የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ሊፀናልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ በሕግ የሚታወቅ የቤት ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለም? በሕግ የሚታወቅ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ከሌለስ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት ሊመለሱ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም አመልካችና ተጠሪ የቤቱን ሽያጭ አስመልክቶ የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል የሽያጩ ስምምነት በጽሑፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰፍሮ ከተፈራረሙ በኋላ የሁለቱን ቤቶች ካርታ ይዘው በውል ክፍል ቀርበው ከተፈራረሙ በኋላ ሽያጩን አስመዝግበው ለመጨረስ እንደነበር ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክርና የሥር ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ችለናል። በውል ጽሑፋቸው ባሰፈሩት ስምምነት መሠረት በውል ክፍል ቀርበው ሽያጩን እንዳያስመዘግቡ በአመልካች በኩል በስምምነት ጽሁፍ ላይ የሰፈረውን ግዴታ ያለመፈፀም ሁኔታ እንቅፋት መሆኑንም ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር ለመገንዘብ ተችሏል። እነዚህ ሁኔታዎች ተሟልተው ግራ ቀኙ ማስረጃዎቻቸውን ይዘው በመቅረብ የሽያጭ ውሉን በፍ/ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ካላስመዘገቡት ደግሞ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1720/1/ መሠረት በተቀዳሚ ውልነት ወይም በረቂቅነት ደረጃ ላይ የቀረበ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሠረት የተደረገ የተሟላ ውል ነው ለማለት የሚቻል አይሆንም። በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል በሕግ የሚታወቅ የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ የተደረገው ውል ተቀዳሚ ውል ወይም ረቂቅ ውል እንጂ ሊፈፀም የሚገባው የተሟላ ውል አይደለም ማለት በመሆኑ ፍ/ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ መሆኑን ተገንዝበናል።

በሌላ በኩል ግን ውሉ በተቀዳሚ ውልነት ወይም በረቂቅ ውልነት ደረጃ ላይ ባለበት ጊዜ በውል ስምምነት አድራጊዎቹ የተደረገ የገንዘብ ወይም የሌላ ነገር ልውውጥ ቢኖር ውሉ ሊፈፀም የሚያስችለው ደረጃ ላይ ባልደረሰበት ጊዜ የውል አድራጊዎቹ ወደነበሩበት መመለስ ተገቢ በመሆኑና በዚህ ጉዳይም አመልካች ለተጠሪ ከፈልኩ የሚሉት ብር 50,000.00(ሃምሳ ሺህ) ስላለና ተጠሪም በስር ፍ/ቤትም ይሁን በዚሁ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን ክደው የተከራከሩ ባለመሆኑ የግራ ቀኙ ወደነበሩበት መመለስ አስፈላጊነት በግልጽ ስለሚታይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የተደረገ የሚፈፀም የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት ሲወስን ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 መሠረት መወሰን ሲገባው ይህን በማለፉ

ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊሻሻል የሚባው ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22359 ታህሣሥ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል።
2. በመልካችና በተጠሪ መካከል ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ያልተሟላና በረቂቅነት ደረጃ ላይ ያለ በመሆኑ ውሉ እንዲፈፀምልኝ በማለት በመልካች የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም። ይህን አስመልክቶ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ፀንቷል። ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱና ተጠሪ በቅድሚያ ክፍያነት የተቀበሉትን ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ / ለአመልካች እንዲከፍሉ ተወስኗል። ይፃፍ። ውሣኔውን ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያስፈጽም።
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
4. መዝገቡ ተዘግቷል:: ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት።

የሀሣብ ልዩነት

እኔ በአምስተኛ ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ድምጽ በአመልካችና በተጠሪው መካከል ያለው ውል ፈርሶ፣ ሁለቱም ወደነበሩበት፣ እንዲመለሱ በሰጠው ማጠቃለያ ተስማምቼ አብላጫው ድምጽ ከዚህ ውሣኔ ለመድረስ ከሰጠው ምክንያት የተለየ ምክንያት ያለኝ በመሆኑ፣ ይህንን የልዩነት ሃሣብ ጽፌአለሁ። አንድ ተዋዋይ ወገን፣ ሌላው ወገን ውል ይፈጽምልኝ የሚል ክስ ለማቅረብ የሚችለው፣ በራስ በኩል ያለውን ግዴታ ሲፈጽም እንደሆነ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1771 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ለተጠሪው የሸጠውን ቤት፣ ካርታና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች እንዲያስረክቡ በተጠሪው ተጠይቀው የቤቱን ካርታና ኘላን እንደዚሁም ሌሎች ሰነዶችን ለማስረከብ ባለመቻላቸው ምክንያት ውሉ ያልተፈፀመ በመሆኑ አመልካች በራሳቸው በኩል፣ የገቡትን የውል ግዴታ ስላልተወጡ ተጠሪው ውል ይፈጽምልኝ በማለት ለመጠየቅ አይችሉም። እንደውም በራሳቸው በኩል የነበረውን ግዴታ የተወጡት ተጠሪ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1771 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አመልካች ውሉን እንዲፈጽም ወይም ውሉ ፈራሽ እንዲሆን መጠየቅ የሚችሉ በመሆኑ ተጠሪ አመልካች በእሳቸው በኩል ያለውን ግዴታ አልፈፀሙም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ውሉን ፈራሽ ለማድረግ በቂ ምክንያት ነው። ከዚህ ውጭ በግራ ቀኙ መካከል የተደገው ውል ረቂቅ እንጂ በሕግ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ውል አይደለም በማለት አብላጫው ድምጽ የሰጠው የሕግ ምክንያት እኔን የሚያሣምን ባለመሆኑና በአመልካችና በተጠሪው መካከል ያለው ውል፣ አመልካች የበኩሉን ግዴታ ባለመፈፀሙ ምክንያት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1771 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፈራሽ መሆን ያለበት በመሆኑ፣ አብላጫው ድምጽ በሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ በመስማማት፣ ውሉ ፈራሽ በሚሆንበት ምክንያት ላይ ያለኝን የልዩነት ሀሣብ አስፍሬያለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ
ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ለምለም መኩሪያ ቀርባለች።

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሙሉአመቤት ጌታሁን ጠበቃው ቀርቧል።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

ከመዝገቡ እንዳየነው ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውል አፈፃፀምን የሚመለከት ነው። ክርክሩ በተጀመረበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ናት። በተጠሪዋ ላይ ክስ የመሠረተችውም ቀደም ሲል በተደረገው የሽያጭ ውል መሠረት በቀሪ የሚፈለግባትን የቤቱ ዋጋ እንድትከፍላት፣ የውሉን አፈጻጸም በማዘግየትዋም በውሉ የተመለከተውን መቀጫ እንድትከፍል፤ እንደውሉ የማትፈጽም ከሆነ ደግሞ ውሉ ፈርሶ ወደየነበሩበት እንዲመለሱ እንዲወሰን በመጠየቅ ነው። ፍ/ቤቱ ተከሣሽን አስቀርቦ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ገንዘቡ የሚከፈለው ሻጭ የሆነችው ከሣሽ የቤቱን ስም በተከሣሽ ስም ስታዛውር ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ሰርዞአል። ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔውን አጽንቶአል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው።

እኛም አመልካች ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም. በዛፊችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረጉበትን አግባብ ለመመርመር ነው። በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተካሄደው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የግራ ቀኙ ወገኖች ግንኙነት የተመሠረተው በውል ላይ ነው፡፡ ይህም ሚያዝያ 28 ቀን 1996 ዓ.ም. የተደረገው /የተፈረመው/ የቤት ሽያጭ ውል ሲሆን፣ የሁለቱን ወገኖች መብትና ግዴታ በዝርዝር ይዞአል፡፡ አመልካች ቤትዋን በብር 185,000 /አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ/ ለተጠሪ ለመሸጥ መስማማትዋን፣ ውሉ በተፈረመበት ዕለትም ከዋጋው ላይ ብር 60,000 /ስድሳ ሺህ/ መቀበልዋን፣ ቀሪውን ብር 125,000 /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ/ ደግሞ ቀደም ሲል በቤቱ ላይ በፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔና ለፍርድ አፈፃፀም የተላለፈውን ትዕዛዝ አስነስታ ማስረጃውን ቤቱ ለሚገኝበት የሕብረት ሥራ ማኅበር አቅርባ በሷና በሟች ባለቤቷ ስም የተመዘገበውን ቤት በተጠሪ ስም እንዲመዘገብ ስታደርግ ወዲያውኑ እንዲከፈላት መስማማቷን ውሉ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በውሉ በተመለከተው መሠረት ቤቱን ለመግዛት መስማማቷ እና ውሉ በተፈረመበት እለት ከከፈለችው ብር 60,000 /ስልሳ ሺህ/ ሌላ በቀሪ የሚፈለግባትን ብር 125,000 /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ/ አመልካች ግዴታዋን እንደተወጣች ወዲያውኑ ለመክፈል እንደተስማማች በውሉ በግለጽ ተመልክቷል፡፡

አመልካች ወደ ክስ ያመራችው ተጠሪ እንደውሉ ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆነችም በማለት እና የበኩልዋን ግዴታ ግን እንደተወጣች በመግለጽ ነው፡፡ ከእርሷ የሚፈለገው ግዴታ ከላይ በዝርዝር የተመለከተው ሲሆን፣ በእርግጥም ይህ በሚገባ ስለመፈጸሙ በጽሑፍ እና በቃል በተደረገው ክርክር ተረጋግጧል፡፡ ቀደም ሲል በቤቱ ላይ ተሰጥቶ የነበረውን የፍርድ ቤት ውሣኔ እና ለፍርድ አፈፃፀም መመምሪያ ተላልፎ የነበረውን ትዕዛዝ አስነስታ፣ ማስረጃውንም ለሕብረት ስራ ማኅበሩ አቅርባ ተጠሪን አንድትተካ ስለማድረግዋ በዚህ ስበር ችሎት በተደረገው ክርክር ጭምር ግራ ቀኝ ወገኖች

አረጋግጠዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንደሚያመለክተው ፍ/ቤቱ በውሉ ላይ ያልተመለከተው እና ግራ ቀኝ ወገኖች በግልጽ የስምምነታቸው አካል ያላደረጉትን “የስም ማዛወር” የሚል አስተሳሰብን መሠረት በማድረግ ነው ውሣኔ የሰጠው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተፈረመው ውል ግልጽ ነው፡፡ ጠቅላላ አነጋገር የሚመስል አገላለጽ በፍጹም አይታይበትም፡፡ ውሎች ግልጽ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ ዳኞች ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው መራቅ ውሉን መተርጎም እንደማይችሉ /እንደማይገባቸው/ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1733 ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቀሪውን ገንዘብ ለመክፈል በግልጽ የተስማማችው በቤቱ ላይ የነበረው መሰናክል ተወግዶ በማኅበሩ ዘንድ አመልካችንና ሟች ባለቤትዋን ተክታ ስትመዘገብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሚገባ ተፈጽሞአል፡፡ ለነገሩ መግባት አያስፈልግም እንጂ ይኸሳ ከተባለም በማህበራት ይዞታ ስር ያሉትን ቤቶች በተመለከተ የሻጭን ስም በገዢው ስም ከመተካት ያለፈ ነገር ሊከናወን ሰለማይችል ተጠሪ በውሉ መሠረት አልተፈጸመላትም ለማለት የሚያስችል የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ ሲጠቃለልም አመልካች ግዴታዋን አልተወጣችም የሚባልበት የሕግ ምክንያት ስለሌለ የስር ፍ/ቤት በውሉ የሌለ እና አስፈላጊ ያልሆነ ተጨማሪ ግዴታ እንዳለባት በመቁጠር የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌ/መ/ደፍ/ቤት በመ/ቁ. 43844 ሰኔ 26 ቀን 1997 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41177 መጋቢት 25 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ተጠሪ በቀሪ የሚፈለግባትን የቤቱን ዋጋ ብር 125,000 /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ/ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ አለቀ ድረስ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ በመጨመር ለአመልካች ትክፈል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31482

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዓለምነሽ ወ/አገኘሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አባተ ተፈሪ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአማራ ብሄራዊ ክ/መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረብርሃን ወረዳ ከተማ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት የአፈጻጸም ክስ በደብረብረሃን ከተማ ቀበሌ 03 ክልል የሚገኘውና የቤ.ቁ. 167 የሆነውን ቤት የአፈጻጸም ተከሳሽ በብር 18,500 (አስራ ስምንት ሺህ አምስት መቶ) ሸጦልኝ ቤቱንም አስረክቦኝ ነገር ግን ባለሐብትነቱን በስሜ ባለማዛወሩ ምክንያት በዚሁ ፍ/ቤት ክስ አቅርቤበት ስም እንዲያዛውር የተወሰነ ስለሆነ በዚሁ ውሳኔ መሰረት ይፈጸምልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአፈጻጸም አቤቱታውም ለአፈጻጸም ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ደርሶ በሰጡት መልስ ለአፈጻጸም ክርክሩ ምክንያት የሆነውና በሽያጭ የተላለፈው ቤት የእራሳቸው እንዳልሆነ በመግለጽ ስም ማዛወር አልችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአፈጻጸም ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለትም የወረዳው ፍ/ቤት በሽያጭ ለአፈጻጸም ከሳሹ ተላልፏል የተባለው ቤት ባለሐብትነት በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተውን አካል ጠይቆ በአፈጻጸም ተከሳሽ ስም ሳይሆን በሌላ ግለሰብ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ በመረጋገጡ የአፈጻጸም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሳሹ ስም ይዛወርልኝ በማለት ያቀረቡት የአፈጻጸም ማመልከቻ በአግባቡ ስላለሆነ ሊፈጸም አይችልም ብሎ በሽያጩ ጊዜ የአፈጻጸም ተከሳሹ የተቀበሉትን ብር 15,000(አሰራ አምስት ሺህ) ለአፈጻጸም ከሳሹ ሊመልሱ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአፈጻጸም ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በፍርድ አፈጻጸም ወቅት አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ መሻሩ ለሰበር ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ተመርምሯል፡፡

አመልካች በደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁት ቤት ሸጦልኝ ርክክቡ የተከናወነ ቢሆንም ስም ያላዛወረልኝ ስለሆነ እንዲያዛውር ይወሰንልኝ በማለት ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ሻጩ ስም ሊያዛውሩ ይገባል በማለት ውሳኔ መስጠቱን ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል፡፡

በዚህ ውሳኔ መሰረት ይፈጸምልኝ በማለት የአፈጻጸም ከሳሽ/የአሁን አመልካች/ የአፈጻጸም ማመልከቻ ሲያቀርቡ አስቀድሞ ተከሳሹ ስም ሊያዛውሩ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በይግባኝ አስካልተሻረ ድረስ ትክክል እንደሆነ የሚገመት በመሆኑ ይህንኑ ውሳኔ ከማስፈጸም በስተቀር ውሳኔውን በአፈጻጸም በመሻር ሻጩ የሸያጩን ገንዘብ ለገዢው ሊመልስ ይገባል ተብሎ ውሳኔ መስጠቱ ሙግቱ የሚመራበትን የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩልም ለአፈጻጸም ክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ባለቤትነቱ በአፈጻጸም ተከሳሹ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ሳይሆን በሌላ 3ኛ ወገን ስም ተመዝግቦ ይግኛል ቢባል እንኳን ዋናው ክርክር ሲደረግ ይህ 3ኛ ወገን የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.41 በሚፈቅደው መሰረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ መብቱን ማስጠበቅ የሚችል ከመሆኑም በላይ ዋናው ክርክር ሲደረግ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚችልበት ሁኔታ ካልተፈጠረም በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ መብቱን የነካ ከሆነ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 በሚፈቅደው መሰረት በሌለበት የተሰጠው ፍርድ እንዲሰረዝለት ከሚጠይቅ በስተቀር ፍ/ቤቱ በእራሱ አስተያየት ሊመለከተው አይችልም፡፡

ስለሆነም ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ጉዳዩ ይመለከተኛል የሚል 3ኛ ወገን ባልቀረበበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ በእራሱ አስተያየት በሽያጭ ለአፈጻጸም ከሳሹ ተላልፏል የተባለው ቤት በ3ኛ ወገን ስም የተመዘገበ ስለሆነ አፈጻጸሙ ሊቀጥል አይችልም በማለት የሸያጩ ገንዘብ ሊመለስላቸው ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05529/99 መጋቢት 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13181 ግንቦት 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 378/99 ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በውሳኔው መሰረት እንዲያስፈጽም ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 31640

የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ገረመው ግዛው ከጠበቃ ተሾመ ደምሴ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ፈቃዱ ያደቴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ በክስ የጠየቀውን ገንዘብ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት በበታች ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ ተጠሪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ተከሣሽ የሠ.ቁ.1-07889 የሆነውን መኪና በነሐሴ 4 ቀን 1991 ዓ.ም በተፃፈ ውል በብር 34,000 (ሠላሣ አራት ሺህ) ሸጦልኝ መኪናውንም ያስረከበኝ ቢሆንም ስም ሣያዛውር በመቅረቱ ምክንያት ክስ አቅርቤበት በግንቦት 9 ቀን 1996 ዓ.ም ስም እንዲያዛውር ተወስኖበት ጉዳዩ በአፈፃፀም ላይ ይገኛል፡፡ የስም ዝውውሩን በተመለከተ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ ክርክር ላይ እያለን መኪናውን ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ትእዛዝ ከፍ/ቤቱ በመተላለፉ እስከ የካቲት 30 ቀን 1993 ዓ.ም መኪናውን ለማንቀሳቀስ ችዬ ነበር፡፡ ነገር ግን ከመጋቢት 1 ቀን 1993 ዓ.ም ይህ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ መኪናውን ማንቀሣቀስ ያልተቻለ ስለሆነና የመኪናውም የቀን ገቢ ብር 50 በ1710 ቀናት ሲባዛ በድምሩ ብር 85.500

(ሰማንያ አምስት ሺህ አምስት መቶ) ከወለድ ወጭና ኪሣራ ጋር ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የከሣሽ ክስና ማስረጃም ለተከሣሽ ደርሶ በሰጠው መልስ በመካከላቸው የመኪና ሽያጭ ውል የተደረገ መሆኑን አምነው በፍ/ቤት ትእዛዝ እስከ የካቲት 30 ቀን 1993 ዓ.ም መኪናው ከተንቀሳቀሰ ከዚያ ወዲህም ቢሆንም ለፍ/ቤት አመልክቶ ማንቀሣቀስ እየቻለ በገዛ ፈቃዱ አቁሞት ከሆነ ተከሣሽ ኃላፊ ሊሆን አይችልም፡፡ እንደዚሁም ከሣሽ መኪናውን ከተረከበ 7 ዓመት ያለፈው ስለሆነ ውሉ ጉዳት አድርሷል በውሉ አፈፃፀም ጉዳት ደርሷል ሳይባል በውሉ መሠረት ስም እንዳዛውር በተወሰነው መሠረት ስም ከማዛወር በስተቀር ሌላ ዕዳ ለመክፈል የገባሁት ግዴታ ስለሌለ ክሱ ከኪሣራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገቡን መርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው (ታክሲ) መኪና ባለቤትነቱን ተከሣሽ በሕግ ተገደው በከሣሽ ስም እንዲያዛውሩ እስከተደረገበት ግንቦት 9 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የመኪናው ባለቤትነት በተከሣሽ ስም ተመዝግቦ እንደነበር የሚታመን ሲሆን በመኪናው ላይ ቦሎ ለማስለጠፍ ደግሞ የመኪናው ባለንብረት መቅረብ እንዳለባቸውና ተሽከርካሪውን ለምርመራ ክፍሉ በማሣየት ማስመርመር እንደሚገባቸው የተረጋገጠ ሲሆን ተከሣሽ ግን ይህን ባለማድረጋቸው ተሽከርካሪው ሊንቀሣቀስ ያልቻለ በመሆኑ በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናቸው ካለ በኋላ መኪናው ያለ ሥራ የቆመበትን የ3 ዓመት ከ2 ወር ከ9 ቀን በድምሩ ብር 57.450 (አምሣሰባት ሺህ አራት መቶ ሃምሣ) ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል ይገባል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል ይገባልን? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የጉዳት ኪሣራ ጥያቄ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ ባለ ግንኙነት ላይ ተመሥርቶ ሊቀርብ የሚችል ሲሆን ከውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የጉዳት ኪሣራ ጥያቄ የሚመዘነው ውሉ በአግባቡ ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ጥያቄ አቅራቢው ሊኖረው ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጋር ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል በመኪና ሽያጭ ውል ላይ ተመሥርቶ የነበረ ግንኙነት ተቋቁሞ እንደነበር የተረጋገጠ ሲሆን በዚሁ ውል መሠረትም የመኪናው ገዢ የሆኑት የአሁን ተጠሪ ሻጩ (አመልካች) ባለቤትነቱን በስሜ ያላዛወረ ስለሆነ እንዲያዛውር ይወሰንልኝ የሚል አቤቱታ ለፍ/ቤት አቅርበው ይሄው አቤቱታም በፍ/ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ሻጭ የመኪናውን ባለሀብትነት በገዢው ስም ሊያዛውሩ ይገባል በማለት ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች ስም ማዛወር እንደሚገባቸው በፍርድ የተወሰነ ቢሆንም በውል ግዴታ ውስጥ ባለዕዳ የሆነው ወገን የጉዳት ኪሣራ ክፋይ የሚሆነው ውሉን አሟልቶ ሣይፈጽም ሲቀር ወይም ውሉን ከስምምነቱ ውጭ አዘግይቶ በመፈፀሙ የተነሣ በሌላው ተዋዋይ ወገን ላይ በገንዘብ የሚተመን ኪሣራ የደረሰ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደመሆኑ መጠን አመልካች ስም የማዛወር ኃላፊነት አለበት ተብሎ ውሣኔ የተሰጠ ቢሆንም የሽያጭ ውሉ በተደረገ ጊዜ የመኪናው ባለቤትነት የተመዘገበው በሻጭ በአሁን አመልካች ስም ሣይሆን በሌላ ግለሰብ ስም መመዝገቡን ተጠሪ ያውቅ

እንደነበር ሻጭም መኪናውን ለመሸጥ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን የነበረው ስለመሆኑ ገዢው (ተጠሪ) አረጋግጦ ግዢውን እንዳልፈፀመ መገንዘብ የተቻለ ከመሆኑም በላይ አመልካች የመኪናውን ባለሀብትነት በተጠሪ ስም ለማዛወር የበኩሉን ጥረት አድርጎ ነገር ግን በተጠሪ አለመቅረብና አለመከታተል ምክንያት የስም ዝውውሩ ተግባራዊ ሊሆን እንዳልቻለም ተረጋግጧል፡፡

የስም ዝውውሩ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው በሻጩ ቀጥተኛ የውል ፈፃሚነት (specific performance) ብቻ የሚከናወን ሣይሆን የገዥውም ድጋፍ ታክሎበት ለውጤት የሚበቃ በመሆኑ በዚሁ መሠረት የበኩሉን አስፈላጊ ድጋፍ ተጠሪ ለአመልካች በመስጠት ስም እንዲዛወር ማድረግ ሲገባው ይህንን ባልፈፀመበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብሔር ሕጉ ውልን አለመፈፀምንና የጉዳት ኪሣራ አከፋፈልን አስመልክቶ በቁጥር 1771 እና ተከታዮቹ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ጋር የተገናዘበ ባለመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11081 በጥቅምት 2 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 50188 በሰኔ 13 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ *መሠረታዊ* የሕግ ስህተት የተፈፀመበባቸው ስለሆነ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32222

የካቲት 4 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ መሐመድ ኢብራሂም ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ታይደር ማች - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በአስረጂነት ያቀረቡት ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሠረት በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ክስ የቀረበበትን ቤት ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመስጠታቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ የአሁኑ ተጠሪ በመልካች ላይ በጋምቤላ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ በጋምቤላ ከተማ ወረዳ 1 ቀበሌ 03 ክልል በስሜ ተመዝግቦ ከሚገኘው ሁለት ክፍል ቆርቆሮ ቤት አንዱን ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ይዞ ስለሚገኝ እንዲለቅ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀ ሲሆን ተከሳሽም በሰጠው መልስ ክስ የቀረበበትን ቤት ከከሣሽ ጋር በነበረን ውል መሠረት በእሱ እጅ በነበረው ይዞታ ላይ ሁለት ክፍል ቤት ሰርቼ አንዱን ክፍል ለእሱ ሌላውን ክፍል ደግሞ ለእኔ እንዲሆን የተስማማን ስለሆነ ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተከሣሽ ክስ የቀረበበት ቤት ባለመብት ስለመሆኑ ያረጋግጥልኛል በማለት ያቀረበው ውል ሥልጣን በተሰጠው መንግሥታዊ

አካል ያልፀደቀ ከመሆኑም በላይ ከሣሽ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ቤቱና ይዞታው የእራሱ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ስለሆነ ክስ የቀረበበትን ቤት ተከሣሽ ለከሣሽ ሊያስረክብ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

በተከሣሽ ይግባኝ ባይነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል መስከረም 1 ቀን 1988 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለው ውል ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀ ስላልሆነ ግዴታን ሊፈጥር አይችልም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች ውሉ ተቀባይነት ሳያገኝ የመቅረቱ አግባብነት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው ውል በሕግ አግባብ የተደረገ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ አግባብነት አለውን? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የአሁን ተጠሪ በጋምቤላ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁት ተከሣሽ ቤቱን ያለአግባብ ይዞ ስለሚገኝ እንዲመልስ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ተከሣሽ የአሁን አመልካችም ቤቱን ያለአግባብ አለመያዛቸውን ገልጸው መስከረም 1 ቀን 1988 ዓ.ም. ከከሣሽ ጋር ባደረጉት ውል መነሻነት በከሳሽ ይዞታ ላይ ተከሣሽ ሁለት ክፍል ቤት እንዲሰሩና አንዱ ለከሳሽ ሌላው ቤት ደግሞ ለተከሣሽ እንዲሆን በተስማሙት መሠረት ሁለት ክፍል ቤቱን ሠርተው አንዱን ከሳሽ እንደተረከቡና ሁለተኛውንና ክስ የቀረበበትን ቤት ደግሞ ተከሣሽ የተረከቡት መሆኑን ገልጸው ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሉ የጸና አይደለም ያለው ውል ለማዋዋል በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተደረገ ስላልሆነ ነው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚደረጉ ውሎች ውል ለማዋዋል በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ካልተደረጉ ዋጋ ሊኖራቸው እንደማይችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 እና 1720 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ መስከረም 1 ቀን 1988 ዓ.ም. ያደረጉት ውል ይዘት ሲታይ ውሉ በተደረገ ጊዜ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ያልነበረ በመሆኑ በዚህ ውል መነሻነት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ከአንዱ ወደ ሌላው ተላልፏል የሚያስብል አይደለም፡፡ ከስምምነታቸውም በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው ይዞታው የከሳሽ በሆነ ቦታ ላይ ተከሣሽ ሁለት ክፍል ቤቶችን በመስራት አንዱን ለከሳሽ በመስጠት ሌላውን ቤት ደግሞ ለእራሳቸው ለመውሰድ መስማማታቸውን ስለሆነ ይህ ስምምነት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ድንጋጌ የሚገዛ አይሆንም፡፡ ይልቁንም የማይንቀሳቀስ ንብረት መሥራትና መሸጥን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2876 ላይ እንደተመለከተው አንዱ ወገን ተዋዋይ ለሌላው ወገን ተዋዋይ አንድ ቤት አንድ የቤት ክፍል ወይም ገና የሚሰራ ሕንፃ ለመስጠት ግዴታ የሚገባበት ውል የአንድ ሕንፃ የሥራ ውል ከሚባል በስተቀር የሽያጭ ውል ሊባል እንደማይችል ስለተመለከተ የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 አኳያ መመልከታቸው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል የሕንፃ ሥራ ውል ነው ከተባለ የውሉን አመሰራረት የሚገዛው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሥራ ውልን አስመልክቶ በቁጥር 3019 እና 3020 ላይ በተመለከተው መሠረት ሲሆን ከዚህ አኳያም ውሉ የተለየ የአፃፃፍ ሥርዓትን ተከትሎ መደረግ የሚገባው ሳይሆን የሥራው መጀመሪያም ሆነ የዋጋ ክፍያ ውሉ በአግባቡ እንደተመሠረተ የሚያረጋግጥ እንደሆነ በቁጥር 3020/2/ ላይ የተደነገገ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል በሕግ አግባብ

የተቋቋመ ውል የለም በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የጋምቤላ ክልል ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00321 በጥር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. እንደዚሁም የጋምቤላ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00605 በሰኔ 22 ቀን 1997 ዓ.ም. በግራ ቀኙ መካከል የተደረገ ውል የሰጧቸው ውሳኔዎች ውል የለም በማለት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል በሕግ አግባብ የተቋቋመ ውል ያለ ስለሆነ ውሉን አስመልክቶ ባነሱት ክርክር ላይ የጋምቤላ ክልል ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 341 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32899

ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች ፡- ወ/ሮ አስካለ ማርያም ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ተሾመ ካሣዬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በመጋቢት 5 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ተከሳሽ በሱልልታ ሙሉ ወረዳ የማህበር አባል ነኝ በማለት ድርሻዬ ነው ያሉትን ቦታ በብር 18,400 (አስራ ስምንት ሺህ አራት መቶ) ሸጠውልኝ የቦታውን ካርታ አስረክበውኛል፡፡ ቦታውን አጥሬ ለመስራት ስሞክር ግን ቦታው የተገኘው በሕገወጥ መንገድ ነው በማለት የመሬት አስተዳደር ቦታውን ወርሶብኛል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ገንዘቤን እንዲመልስልኝ ይወስንልኝ የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ሌላ ቤት የገዛባቸው አቶ ኤልያስ ደምሴ የተባሉት ተከሳሽ ደግሞ በሰጡት መልስ ይህ ክስ መቅረብ የሚገባው በቤት ሥራ ማህበሩ እንጂ በእኔ ላይ አይደለም፡፡ ከሣሽ ካርታውን የተቀበሉት ከማህበሩ እጅ በመሆኑ ስለቦታው ሕጋዊነት መጠየቅ ያለባቸው ማህበሩ ነው፡፡ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ከከሳሽ አልተቀበልኩም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠና ማስረጃም ከሰማ በኋላ ተከሳሽ ገንዘቡን መቀበላቸውንና በውላቸው ደግሞ ቦታውን ለከሣሽ

ካላስረከብኩኝ ገንዘቡን እመልሳለሁ_በማለት ግዴታ መግባታቸውን በማስረጃ ስለተረጋገጠ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለከሳሽ ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

በመቀጠልም ፍ/ቤቱ የአሁኑ ተጠሪ በተከሳሽ ስም የተመዘገበው ቤት የገዛሁት በመሆኑ እግዱ ይነሳልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ደግሞ በተከሳሽ ላይ ቀደም ብሎ የወሰዱት ገንዘቤን እንዲመልሱልኝ ያስወሰንኩኝ በመሆኑና ቤቱም ተሸጦ ገንዘቤን የማስመልስበት የተከሳሹ ሃብት በመሆኑ እግዱ መነሳት የለበትም በማለት ተቃውመዋል፡፡

ፍ/ቤቱም አቶ ተሾመ ካሣዬ ገዛሁት የሚሉትን ቤት የሽያጭ ውል ስልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 መሠረት ውጤት የለውም፡፡ እግዱ በቀረበው አቤቱታ መልኩ ሊነሳ የሚችልበት ምክንያት የለም በማለት ጥያቄውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

በዚህ የእግዱ ይነሳልኝ ጥያቄ መሠረት የአሁን ተጠሪ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱም ይግባኝ ባይ ቤቱን ከአቶ ኤልያስ ደምሴ መስከረም 19 ቀን 98 ዓ.ም በተፈፀመ የሽያጭ ውል ገዝተው ስም ለማዛወር በሒደት ላይ መሆኑን ገልጾ ነው ውልና ማስረጃ የእግድ ትዕዛዙን የመዘገበው፤ ሽያጩ በክብር መዝገብ የተመዘገበው የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመመዝገብ ስልጣን ባለው አካል በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት እግዱ አይነሳም ማለቱ በአግባቡ አይደለም በማለት እግዱ እንዲነሳ ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይግባኝ ቀርቦለት ይግባኙን መሠረት በማድረግ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌ/ከ/ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ለዚህ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡትም የፌ/ከ/ፍ/ቤትና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ ቅሬታውም አቶ ኤልያስ ደምሴ ገንዘቡን ከንብረታቸው እንዲከፍሉኝ ተወስኖልኛል፡፡ አቶ ተሾመ ካሣዬ ቤቱን ገዝቸዋለሁ ቢሉም የሽያጭ ውሉ ስልጣን ባለው አካል አልተመዘገበም፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሽያጭ ውሉን ለማስመዝገብ ጥያቄ መቼ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳቀረበ ሳያጣራ ተመዝግቧል በማለት እግዱን ያነሳው በአግባቡ አይደለም፡፡ ጠ/ፍ/ቤቱም የከ/ፍ/ቤቱን ውሣኔ ማጽናቱ ተገቢ አልነበረም፡፡ ሁለቱም ፍርድ ቤቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2878 የተደነገገውን ሳያገናዝቡ የሰጡዋቸው ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ስለሆኑ ተሽረው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ሊፀናልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

ተጠሪው ደግሞ በሰጡት መልስ የሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2878 መሠረት እስከተመዘገበ ድረስ ስም ያለመዛወር የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ የሽያጭ ውሉ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ቀደም ብሎ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 16109 ሚያዝያ 12 ቀን 99 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የሽያጭ ውሉ ከመዝገቡ ጋር መያያዝ በቂ ነው ተብሏል፡፡ በመ/ቁ/ 21448 የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1123 ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡ የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠው የሽያጭ ውሉ ከተያያዘ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀናልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በቤቱ ላይ የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ በተጠሪው አመልካችነት ሊነሳ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘው የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥሩ ኮ/ቁ/ 09/3/መ/00/180/ 6904/00 በሆነው ቤት ላይ የእግድ ትዕዛዝ የሰጠው መጋቢት 29 ቀን 98 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ የእግድ ትዕዛዝ ደግሞ በኮልፌ ቀራንዮ መሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ተመዝግቧል፡፡ እግዱ በተመዘገበበት ጊዜም ቤቱ በአቶ ኤልያስ ደምሴ ስም የተመዘገበ መሆኑን እና የሽያጭ ውሉ ከማህደሩ ጋር የተያያዘ ቢሆንም የስም ማዞሩ ጉዳይ በሂደት ላይ ያለ መሆኑን የመሬት አስተዳደር ባለስልጣኑ ገልጸአል፡፡ ነገር ግን የመሬት አስተዳደር ባለስልጣኑ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል

ያለው የሽያጭ ውል መቼ ከመዝገቡ ጋር እንደተያያዘ አልገለፀም፡፡ በማስረጃነት ቀርቦ ከፍ/ቤቱ መዝገብ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የሽያጭ ውል ጽሑፍም ስንመለከተው እላዩ ላይ ክብ የውሎችና የክብር መዝገብ ማስረጃ ማህተም ከማረፉ በስተቀር ይህ ማህተም መቼ የውል ጽሑፉ ላይ እንደተደረገ አይታወቅም፡፡ በሽያጭ ውሉ ጽሑፍ ላይም ይሁን ጀርባ ያረፈ አራት ማዕዘን ማህተም የለም፡፡ የሽያጭ ውሉ በክብር መዝገብ ውስጥ የተያያዘው መቼ እንደሆነ ካልታወቀ ደግሞ የተያያዘው የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የሽያጭ ውሉ የተያያዘው የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ነው ከተባለም በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2878 የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኘው በማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ውጤትን ሊያስገኝ አይችልም ተብሎ ከተደነገገው ጋር በማዛመድ ስንመለከተው የሽያጭ ውሉ በማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ከመፃፉ በፊት የሽያጭ ውሉ መኖር ያለመኖሩ አስቀድሞ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህ በተጠሪውና በአቶ ኤልያስ ደምሴ መካከል ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1723 በፍ/ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተሰራ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ጽሑፍ በማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ የተፃፈው ሳይረጋገጥ በመሆኑ ውሉ በመልካች ላይ የሚያመጣው ለውጥ ወይም የሚያስገኘው ውጤት የለም፡፡

በተጠሪው በመከራከርያነት የተጠቀሰው ቀደም ብሎ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 16109 የሰጠውን ውሣኔ ስንመለከተውም ፍ/ቤቱ የውሉ ከማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ጋር መያያዝ በቂ ነው ያለው የሽያጭ ውሉ ግንቦት 9 ቀን 1987 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ መምርያ አዋዋይነት የተደረገ መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመመልከቱ ምክንያት በመሆኑ ጉዳዩ በዚህ መዝገብ ከሚታየው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ባለመሆኑ የተጠሪው ክርክር አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የሽያጭ ውሉን ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ የቀረበለትን የሽያጭ ውል ተቀብሎ ከማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ላይ ከማያያዝና ከመፃፍ በስተቀር የማዋዋልና የማረጋገጥ ስልጣን ስለሌለው የፌዴራል ከፍ/ፍ/ቤትና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የመሬት አስተዳደሩ ባለስልጣን የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሽያጭ ውል የመመዝገብ ስልጣን አለው፤ የሽያጭ ውሉ በዚሁ ሁኔታ የተመዘገበ በመሆኑ እግዱ መነሳት አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መታረም የሚገባው ነው፡፡

በመሆኑም አመልካች ቀደም ብለው ክርክር ባስነሰው ቤት ላይ የእግድ ትዕዛዝ ያሰጡት ከአቶ ኤልያስ ደምሴ የሚፈልጉትን ገንዘብ ለማስመለስ በመሆኑና በዚሁ መሠረትም ያስወሰኑ ስለሆነ ቤቱን በሐራጅ በማሸጥ ገንዘባቸውን የማስመለስ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡ ይህ መብታቸው ቀሪ ሊሆን ይችል የነበረው የቤቱ ባለቤትነት ከአቶ ኤልያስ ደምሴ ወደ ተጠሪ ዞሮ ቢገኝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቤቱ በአቶ ኤልያስ ደምሴ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑና በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ የተያያዘው የሽያጭ ውልም ስልጣን ባለው አካል ያልተረጋገጠ በመሆኑ ቀደም ብሎ የተሰጠው እግድ ተነስቶ የባለቤትነቱ ስም ወደ ተጠሪው እንዲዛወር ማድረግ ተጠሪው ያለአግባብ እንዲጠቀሙ አመልካች ደግሞ በፍርድ ያገኙትን መብት እንዲያጡ የሚያደርግ በመሆኑ እግዱ በተጠሪው አመልካችነት የሚነሳበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በዚሁ ምክንያትም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊሻር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 29717 ሐምሌ 17 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 50420 መጋቢት 13 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆናቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘው በካርታ ቁጥር ኮ/ቁ/09/3/ መ/00/180/6904/00 የተመዘገበው ቤት ላይ በመ/ቁ/ 32777 ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው እግድ በተጠሪው አመልካችነት ሊነሳ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ እግዱ ሊነሳ የሚችለው አመልካች ከአቶ ኤልያስ ደምሴ እንዲከፈላቸው የተወሰነላቸው ብር 18,400 ሲከፈላቸው ወይም ደግሞ ቤቱን በሐራጅ ለመሸጥ እንዲቻል አመልካች እግዱ እንዲነሳ ሲጠይቁ ነው በማለት ተወስኗል፡፡ በዚሁ መሠረትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32777 ጥቅምት 22 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን እንዲችሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ ጠ በ ቆ ች
ፈ ቃ ድ

የሰበር መ/ቁ 25287

ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አቶ መድህን ኪሮስ

አቶ በላቸው አንሺሶ

አመልካች፡- ሜድሮክ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ በዛወርቅ ሺመላሽ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የክርክሩን አመጣጥ በተመለከተ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሣሽ መጋቢት 18 ቀን 1993 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ በተከሣሽ ድርጅት ውስጥ ከግንቦት 24 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 20 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ በሕግ አገልግሎት ሃላፊነት ተቀጥሬ ያገለገልኩ ሲሆን በፌደራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥን ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92 መሠረት ለተከሳሹ አገልግሎት ለመስጠት በመቸገሬ ምክንያት ተከሣሹ ሁኔታውን እንዲያሻሽል ብጠይቅ ተከሣሹ የሥራ ውሌን አቋርጧል፡፡ የተከሳሹ ሥራ አስኪያጅ በብር 5,000 /አምስት ሺህ ብር/ ደመወዝና የመኪና አበል (በተጨማሪነት) የቀጠሩኝ ቢሆንም ይህ ክፍያ ሣይከፈለኝ የቆየ በመሆኑ የ43 ወራት የአገልግሎት ቀሪ ክፍያ ብር 76,411፣ የመኪና ማካካሻ ክፍያ ብር 43,000፣ የትራንስፖርት አበል ብር 21,500፣ እ.ኤ.አ. ህዳር 23 ቀን 1999 በተፃፈ ደብዳቤ የታመነ ብር 1,349.74፣ ዳላስ ሄጀ የተመለስኩበት የውሎ አበል ብር 5,049፣ የአውሮፕላን ትኬት ክፍያ ብር 2,607፣ የ3 ወር ያልተከፈለ አበል ብር 19,500፣ የ3 ዓመት ወለድ ብር 30,495፣ በድምሩ ብር 199,911.74

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(አንድ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ አንድ ብር ከሰባ አራት ሳንቲም) እንዲከፈለኝ ወደ ሥራም እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል።

ተከሳሽም ጥቅምት 14 ቀን 1994 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የከሣሽ የክፍያ ጥያቄዎች በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ የታገዱ ናቸው፤ ሊከፈላቸው የሚገባ ደመወዝ ላይ የተደረገ ስምምነት የለም፣ ደመወዛቸው ሲከፈላቸው እንደቆየው ነው፣ ፈርመው ሲቀበሉት በነበረው ገንዘብ ላይ ክርክር መፍጠራቸው አግባብ አይደለም፤ ዳላስ ሄደው የተመለሱበት የውሎ አበል ተከፍሏቸዋል፤ ብር 1,349.74 ሊከፈላቸው አይገባም፤ የአውሮፕላን ትኬቱን በተመለከተ ብር 2,607 ለመክፈል ፈቃደኛ ሆነን እያለ ከሣሽ ጥያቄ ባለማቅረባቸው ዕድሉ አልፏቸዋል፤ ከሣሽ የሶስት ወር ደመወዝና አበል ያሉት የመቼ እንደሆነ ያልተገለፀ ከመሆኑም ሌላ ከሣሽ እስከተሰናበቱበት ጊዜ ድረስ ያለ የሚገባቸው ደመወዝና አበል ተከፍሎአቸዋል፤ ከሣሽ የተሰናበቱት በአግባቡ ነው፤ የሚከፈላቸው ወለድም የለም በማለት ከተከራክሯል።

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካደመጠ በኋላ ከሣሽ ያቀረቡት የአውሮፕላን ትኬት፣ የውሎ አበልና የብር 1,349.74 ክፍያ መከፈል ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ሲሰላ አንድ አመት ያለፈበት እንደመሆኑ ክፍያው በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ የታገደ ነው፤ የደመወዝ ጥያቄውም እንደዚሁ ክስ ከቀረበበት ጊዜ አንድ አመት ወደኋላ በመቁጠር ሲታይ ጊዜ ያለፈበት በመሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 162(1) መሠረት በይርጋ ቀሪ መሆን የሚገባው ነው፤ በሌላ በኩል ተከሣሽ ከሣሽን ከሥራ ያሰናበተበት ምክንያት አቶ ዳንኤል ተገኑ ከፃፉት ሪፖርት በመነሳት እንጂ ሌላ ተከሣሽ አልሰራም ያሉ ስለመሆናቸው የሚያሳይ ማስረጃ ባለመገኘቱ ሥንብቱ ሕጋዊ አይደለም። በመሆኑም የተከሣሽ ወደ ሥራ መመለስ ለሥራ ግንኙነቱ የማይመች ሊሆን ስለሚችል

ከሣሽ ለከሣሽ የሥራ ስንብት፣ የሁለት ወር የማስጠንቀቂያና የስድስት ወር የካሣ ክፍያ በመክፈል ከሣሽን እንዲያሰናብት፤ ከይርጋ የተረፈውን ክፍያ በተመለከተ የከሣሽ የደመወዝ ብር 5,000 ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩና ከሣሽ የጠየቁት የሶስት ወር ክፍያም የመቼ እንደሆነ ተብራርቶ ስላልቀረበ የሶስት ወር ደመወዝ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም፤ ኃላፊዎቹ በመጻጻፍ ሒደት ላይ ስለነበሩ የከሣሽ ደመወዝ ብር 5,000 እንዲሆንላቸው ተወስኖ ሊሆን እንደሚቻል ተገንዝበናል። ልዩነቱን የይርጋ ጊዜ ከሚጀምርበት መጋቢት 21 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ እስከተሰናበቱበት ጥቅምት 20 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ያለውን የስምንት ወር ልዩነት ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል በማለት ወስኗል።

የአሁን አመልካች የፌ/መ/ደፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቧል። ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በድርድር ላይ ያለ ደመወዝ እንደተወሰነ ደመወዝ ተደርጐ ሊወሰድ አይችልም፣ የሠራተኛው ደመወዝ ብር 4,524 ነው። ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት የሠራተኛው ደመወዝ ብር 5,000 ነው ያለው በአግባቡ አይደለም። ሰራተኛው እስከተሰናበቱበት ጊዜ ድረስ ደመወዛቸውን ሲያገኙ የቆዩ በመሆናቸው የስምንት ወር የደመወዝ ልዩነት ይከፈላቸው ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔም ተቀባይነት የለውም። የስንብትና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ለሰራተኛው እንዲከፈላቸው የተባለውም በአግባቡ አይደለም። ስንብቱ ሕገወጥ በመሆኑ ድርጅቱ የስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለሰራተኛው ሊከፍላቸው እንደሚገባ ግልጽ ቢሆንም ድርጅቱ ይህን ክፍያ መፈፀሙን በስንብት ደብዳቤው ስለገለፀና ሠራተኛውም ይህ ክፍያ አልተከፈለኝም ብለው ስላልተከራከሩ ድጋሚ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ድርጅቱ በብር 4,524 የደመወዝ ሒሳብ አስልቶ ካሣ ለሰራተኛው ይክፈል በማለት በፌ/መ/ደ/ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመቀጠልም አመልካች የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለዚህ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ ቅሬታውም ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት የተቀጠሩበትን ሥራ አልሰራም በማለታቸው ነው፡፡ ተጠሪው ሥራውን አልሰራም ያሉትም ኩባንያው የጥብቅና ፈቃድ ካላወጣልኝ ወይም ደግሞ የኩባንያው ሽሪክ (ባለአክሲዮን) አድርጐ ካላስመዘገበኝ ሥራ መስራት አልችልም፡፡ ከሠራሁ በወንጀል የሚያስጠይቀኝ በመሆኑ ሁኔታው ሊመቻችልኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ እንዲህ የሚል ሐሳብ ስለማቅረባቸው ራሳቸው የፃፉት ደብዳቤ ያስረዳል፡፡ አቶ ዳንኤል ተገኑ የፃፉት ደብዳቤም ተጠሪው አልሰራም ማለታቸውን ያረጋግጣል፡፡ እንደዚሁም አቶ ዳንኤል ተገኑ በመከላከያ ምስክርነት ቆጥረናቸዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የወሰኑትም የቀረቡትን ማስረጃዎችና የተደረገውን ክርክር ባለመገንዘብና በመከላከያ ምስክርነት የቆጠርናቸውን አቶ ዳንኤል ተገኑን ምስክርነት ባለመሰማት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪው የተቀጠሩበትን ሥራ አልሰራም በማለታቸው በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 26(1) እና 28 መሠረት የተሰናበቱ ናቸው፡፡ ስንብቱ ሕጋዊ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የአዋጁን ድንጋጌ የሚፃረር በመሆኑ ውሳኔቸው መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበትና ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪው ደግሞ በሰጡት መልስ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ በመሆኑ አመልካች ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ነበረበት፡፡ ይህን አልፎ ለሰበር ችሎት አቤቱታ ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም፡፡ ድርጅቱ የጥብቅና ፈቃድ ካላስወጣልኝ ሥራ አልሰራም አላልኩም ባለአክሲዮን አድርጐ ካላስመዘገበኝ የምክር አገልግሎት አልሰጥምም አላልኩም፡፡ አመልካች አልተሰማልኝም ያሉት ምስክር የሚያውቀውን በጽሑፍ ስለገለፀ ለምን ቀርቦ አልመሰከረም አይባልም፡፡ ተፈጠረ ላልኩት ችግር መፍትሄ ሳይሰጥበት ድርጅቱ እኔን ማሰናበቱ ተገቢ

አይደለም፡፡ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ድርጅቱ ለችግሩ መፍትሄ ሳይፈልግ የተወሰደው የሥራ ስንብት እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት የወሰነው በአግባቡ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበትና በአግባቡ የተሰጠ በመሆኑ ሊፀናልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ግራ ቀኙ ያደረጉት የቃል ክርክርም በመቅረፀ ድምፅ ከተሞላው ካሴት ወደ ጽሑፍ ተመልሶ ጽሑፉ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ አመልካች ያቀረበው የመልስ መልስም እንደዚሁ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

በበኩላችን ደግሞ አመልካች ኩባንያ ተጠሪውን ያሰናበታቸው በሕገወጥ መንገድ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪው ሐምሌ 7 ቀን 1992 ዓ.ም ለአቶ ንጉሴ አበራ በፃፉት ደብዳቤ አዋጅ ቁጥር 199/92 በአንቀጽ 31 የጥብቅና አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ሰው ከፍትህ ሚኒስቴር የጥብቅና ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት ደንግጓል፣ እንደዚሁም የግል ድርጅት ወይም ኩባንያ ኃላፊ ወይም ባለአክሲዮን ወይም ሽሪክ የሆኑ ሰዎች የጥብቅና ፈቃድ ሳይኖራቸው የጥብቅና አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ በአዋጁ አንቀጽ 31(1) ሥር ተደንግጓል፣ እኔ እነዚህን መስፈርቶች ስለማላሟላ የጥብቅና አገልግሎት ብሰጥ በሕጉ እቀጣለሁ፣ የድርጅቱን ወይም የኩባንያውን ጥቅም ለማስጠበቅ በፍርድ ቤት መከራከር ሕጋዊ የውክልና ሥልጣን የተሰጠው ሰው፣ የኩባንያ ኃላፊ፣ ባለአክሲዮን ወይም ሽሪክ መሆንን ይጠይቃል፡፡ ፍ/ሚኒስቴር የጥብቅና ፈቃድ የሚሰጠው የሙሉ ሰዓት ተቀጣሪ ላልሆነ ሰው እንጂ ለሙሉ ሰዓት ተቀጣሪ አይደለም፡፡ በመሆኑም መመርያችሁን እጠብቃለሁ ማለታቸውን ተመልክተናል፡፡ የዚህ ደብዳቤ ይዘት ደግሞ የሙሉ ሰዓት ተቀጣሪ ሆኜ መስራት ብቀጥል የጥብቅና ፈቃድ ስለማይሰጠኝ የጥብቅና ፈቃድ ማግኘት አልችልም፡፡ ያለ የጥብቅና ፈቃድ ለመስራት የሚቻልበት ሌላው አማራጭ ደግሞ የኩባንያው ሐላፊ ባለአክሲዮን ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሸሪክ በመሆን ቢሆንም እኔ ባለአክሲዮን ወይም ሸሪክ ወይም ደግሞ የኩባንያው ኃላፊ ባለመሆኔ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አልችልም። ፈቃድ ሳይወጣልኝ ወይም ባለአክሲዮን ሆኜ ሳልመዘገብ የሕግ አገልግሎት ለኩባንያው ብሰጥ በወንጀል የምቀጣ በመሆኑ መፍትሄ እስከሚፈለግልኝ ጊዜ ድረስ የተቀጠርኩበትን ሥራ አላከናውንም የሚል ነው።

ተጠሪው መጋቢት 18 ቀን 1993 ዓ.ም ባዘጋጁት የክስ ማመልከቻና ታህሳስ 17 ቀን 94 ዓ.ም ባቀረቡት የመልስ መልስ የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት በቅድሚያ የጥብቅና ፈቃድ እንደሚያሻ፣ ፈቃድ ሳይኖር አገልግሎት መስጠት በወንጀል እንደሚያስጠይቅ፣ ለግል ኩባንያም ቢሆን ያለ ጥብቅና ፈቃድ አገልግሎት መስጠት የሚችሉት የድርጅት ሃላፊ ወይም ሸሪክ መሆን እንደሚያስፈልግ የጠበቆች አዋጅ ይደነግጋል፤ ላይሰንስ (የጥብቅና ፈቃድ) የማገኝበት መንገድ ሳይቀየስና ፈቃድ ሳይኖረኝ ብሰራ በወንጀል እንደምቀጣ እየታወቀ አቶ ዳንኤል ተገኑ ሆራ ሆቴል በሚመለከት የሕግ አገልግሎት እንድሰጥ ማዘዛቸው እኔን ለማስወንጀል ወይም ደግሞ የተመደበበትን ሥራ አልሰራም ብሏል በማለት እርምጃ ለማስወሰድ የታሰበ ነበር በማለት ያቀረቡት ክርክርም ኩባንያው የጥብቅና ፈቃድ ካላስወጣልኝ ወይም ደግሞ የባለአክሱዮንነት ምዝገባ ካላደረገልኝ ሥራውን አልሰራም ማለታቸውንና ሆራ ሆቴልን የተመለከተውን ሥራም ሳያከናውኑ መቅረታቸውን በማመን የተከራከሩ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነው።

አቶ ዳንኤል ተገኑ ሰኔ 7 ቀን 1993 ዓ.ም በፃፉት ደብዳቤ አቶ በዛወርቅ ሽመላሽ የሆራ ሆቴል ኮንትራትን በተመለከተ የሕግ አስተያየት እንዲሰጡ እንደነግራቸው በተሰጠኝ መመሪያ መሠረት ብነግራቸውም አዲሱ ሕግ አይፈቅድልኝም በማለት የሕግ አስተያየታቸውን ለመሰጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል በማለት የሰጡትን መግለጫ ተጠሪው በፊ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስና የመልስ መልስ ከጠቀሷቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ጋር በማገናዘብ ስንመለከተው ተጠሪው በኩባንያው የጥብቅና ፈቃድ የማገኝበት

ሁኔታ ካልተመቻቸልኝ እና ፈቃዱን ካልያዝኩኝ በስተቀር ለድርጅቱ የሕግ አገልግሎት አልሰጥም በሚል አቋማቸው መሠረት ሆራ ሆቴልን የሚመለከት የሕግ አስተያየት ሳይሰጡ የቀሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሆኖ አግኝተነዋል።

እንደዚሁም ተጠሪው ነሐሴ 9 ቀን 1992 ዓ.ም ለአቶ ንጉሴ በፃፉት ደብዳቤ ሆራ ሆቴልን የሚመለከት የሕግ አስተያየት እንድሰጥ በአቶ አልፍሬድ መመሪያ መሰጠቱን አቶ ዳንኤል ነግሮኛል እንዲህ ዓይነት የሕግ አስተያየት (ምክር) መስጠት በአዲሱ አዋጅ ሊያስጠይቅ ይችላል እያልኩኝ እየወተወትኩኝ እንደዚህ ዓይነት መመሪያ ለምን እንደተሰጠ አልገባኝም፣ አሁንም ቢሆን በቅድሚያ የጥብቅና ፈቃድ የማገኝበት መንገድ እንዲቀየስ አሳስባለሁ ማለታቸው ኩባንያው የጥብቅና ፈቃድ ስላላስወጣልኝ ሥራውን አላከናውንም በማለት የሕግ አገልግሎት ሳይሰጡ መቅረታቸውንና ለወደፊቱም ድርጅቱ ፈቃዱን ካላስወጣላቸው በስተቀር የተመደቡበትን የሕግ አገልግሎት የመስጠት ሥራ እንደማያከናውኑ የሚያስረዳ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪው በስር ፍ/ቤቶች ባደረኩት ክርክር አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ ኩባንያው ለቀጠራቸው የሕግ ባለሞያዎች የጥብቅና ፈቃድ የማስወጣት ግዴታ ያለበት መሆኑንና ይህን ግዴታውን መወጣት ሲገባው ሳይወጣ የቀረ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም። ኩባንያው ይህ ዓይነቱ ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚደነግግ ሕግ አለ ብለው አልጠቀሱም አልተከራከሩምም። ኩባንያው ሰዎችን በባለአክሲዮንነት የሚመዘግብ ከሆነም የኩባንያውን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በማድረግ ከሚጠይቁ በስተቀር ተጠሪው የሕግ አገልግሎት እንዲሰጡ ተብሎ በባለአክሱዮንነት ወይም በሸሪክነት ሊመዘግባቸው የሚገደድበት ምክንያት የለም። ተጠሪም በፃፉት ደብዳቤ በምላሌነት ጠቀሱት እንጂ ኩባንያው በባለአክሲዮንነት ወይም በሸሪክነት እንዲመዘግባቸው በግልጽ የጠየቁ ባለመሆኑ ይህን ነጥብ አመልካች በክርክሩ ውስጥ ማካተቱ ተገቢ አይደለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በላይ በተዘረዘረው ሁኔታ ተጠሪው የጥብቅና ፈቃድ በኩባንያው አማካኝነት ካልወጣልኝ በስተቀር የተመደብኩበትን የሕግ አገልግሎት የመስጠት ሥራ አላከናውንም በማለት ሥራ ማቆማቸው ራሳቸው ባደረጉት ክርክር ያመኑበትና ከግራ ቀኙ በቀረቡት የጽሑፍ ማስረጃዎች የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪው የተቀጠርኩበትን ሥራ አልሰራም አላልኩም በማለት ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስና በቃልም ባደረጉት ክርክር መግለፃቸው ተቀባይነት የለውም፡፡

ሌላው ቁምነገር ደግሞ ተጠሪው ኩባንያው የጥብቅና ፈቃድ ካላወጣልኝ የሕግ አገልግሎት ሥራ አልሰራም፣ ከሠራሁኝ በወንጀል እቀጣለሁ የሚሉት ቀደም ብለው የወሰዱትን የጥብቅና ፈቃድ ሳይመልሱና የሕግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶችም በውክልና የሕግ ባለሞያዎችን እንዳያሰሩ በአዋጅ ባልተከለከለበት ጊዜ ነው፡፡ የጥብቅና ፈቃድ እያላቸው በውክልናም መሥራት እየቻሉ ለኩባንያው የሕግ አገልግሎት ብሰጥ በወንጀል እቀጣለሁ ማለታቸውም ግልጽ አይደለም፡፡

አመልካች ለቀጠራቸው የሕግ ባለሞያዎች ከፍትህ ሚኒስቴር የጥብቅና ፈቃድ የማስወጣት ግዴታ ሳይኖርበትና ተጠሪው ለአመልካች የጥብቅና ማለትም የሕግ አገልግሎት ቢሰጡ በወንጀል የሚቀጡበት የሕግ ምክንያት በሌለበት ጊዜ ተጠሪው ድርጅቱ የጥብቅና ፈቃድ ካላስወጣልኝ በስተቀር የተቀጠርኩበትን የሕግ ምክር አገልግሎት የመስጠት ሥራ አላከናውንም የሚሉበትና አመልካች ደግሞ ተጠሪው ምንም ሥራ ሳይሰሩ ሰራተኛዬ ናቸው በማለት ደሞዝ እየከፈለ የሚቆይበት ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 13(2) ሥር የተደነገገው የአሠሪውን ትእዛዝ የመቀበል ግዴታቸውን ያልተወጡ በመሆኑ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 26(1) መሠረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ቅጥር ውሉን ለማቋረጥ ይችላል፡፡ አመልካች የሥራ ውሉን በአዋጁ አንቀጽ 26 እና 28 መሠረት ማቋረጡና ተጠሪውን ማሰናበቱም በአግባቡ ነው፡፡

በመሆኑም አመልካች ተጠሪውን ከሥራ ያሰናበታቸውን የተቀጠሩበትን የሕግ ምክር አገልግሎት የመስጠት ሥራ ለመስራት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ተጨባጭ የሥራ ትእዛዝን አልቀበልም በማለታቸው ምክንያት መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠና ተጠሪም ያመኑበት ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ ነው፣ አመልካች ለተጠሪው ካሣ ይከፈል በማለት ውሳኔ መስጠታቸው አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ፍርድ ቤቶቹ የግራ ቀኙን ክርክርና የቀረበላቸውን ማስረጃ በሚመለከት ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው የቀረበላቸው ማስረጃ የሚያስረዳውን ቁምነገር በመተውና ተጠሪው በክርክራቸው ያመኑትን ከግምት ውስጥ ባለማስገባት የተጠሪውን የግል ማህደር በማስቀረብ ተጠሪው የተቀጠሩበትን ሥራ ለማከናወን ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ከማሕደራቸው ስላላገኘን ለመስራት ፈቃደኛ ስላለመሆናቸው የሚያስረዳ ማስረጃ የለም፣ ስንብቱ ሕገወጥ ነው፣ አመልካች ለተጠሪው ካሣ ይከፈል በማለት የሰጡት ውሳኔም የአዋጅ ቁጥር 42/85 ዓላማን የሳተና ለተጠሪው የማይገባቸውን መብት ያጐናፀፈ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/08459 ህዳር 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 43679 ሚያዝያ 17 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪው ከሥራ የተሰናበቱት ድርጅቱ /ኩባንያው/ የጥብቅና ፈቃድ ካላወጣልኝ በስተቀር የተቀጠርኩበትን የሕግ ምክር አገልግሎት የመስጠት ሥራ አላከናውንም በማለታቸውና በተጨባጭም ሆራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆቴልን የተመለከተ የሕግ አስተያየት አልሰጥም በማለታቸው ምክንያት መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ስንብቱ ሕጋዊ ነው፡፡ የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ወስነናል፡፡ ፍ፡ፃ፡፡

3. ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

ው ር ስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 23322

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አቶ መድሕን ኪሮስ

አቶ ዓሊ መሐመድ

አቶ ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ አዳነች ወርዶፋ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ ወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን አመጣጡም የአሁንዋ አመልካች ህዳር 10 ቀን 97 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ የውርስ አጣሪው በ16/2/97 ዓ.ም ያቀረቡት ሪፖርት በአግባቡ የቀረበ አይደለም፡፡ አጣሪው ሊጸድቅ የማይገባውን የስጦታ ውል መነሻ በማድረግ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ በውርስ እዳነት መመዝገብ የማይገባውን እዳ መዝግበዋል፡፡ ያቀረብኳቸውን ማስረጃዎች በአግባቡ አልመረመረም፡፡ ወራሾች ሳንስማማበት የውርስ ንብረት ለወራሾች እንዲከፋፈል ወስነዋል፡፡ በመሆኑም የውርስ አጣሪው ሪፖርት መጽደቅ የለበትም በማለት አመልክተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የውርስ አጣሪው የሚች የኑዛዜና ያለኑዛዜ ወራሾች እነማን እንደሆኑ፣ የሚች የውርስ ሃብት ምን እንደሆነ ከውርሱ ሐብት ላይ ሊከፈል የሚገባውን እዳ ምንነት እና በኑዛዜ የተሰጠ ስጦታ ለተቀባዩ መክፈልን በተመለከተ የግራ ቀኙን አቤቱታና ማስረጃ መርምረው ያቀረቡት ሪፖርት የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ አመልካች አለኝ የሚሉት መብት ካላቸው ዳኝነት ከፍለው በክስ ከሚጠይቁ በስተቀር የውርስ አጣሪውን

ሪፖርት ባለማጽደቅ በዚህ መዝገብ ሊጠይቁ የሚችሉበት ሁኔታ የለም በማለት አቤቱታውን ባለመቀበል ሪፖርቱን አጽድቆታል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከአመልካች የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡትም የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ትእዛዝ በመቃወም ነው፡፡ በአቤቱታው ውስጥ የተጠቀሱት ቅሬታዎችም የውርስ አጣሪው የሚችን ሃብት በአግባቡ አላጣሩም፡፡ በሕግ መፍረስ የሚገባውን የስጦታ ውል አጽድቀዋል፡፡ የቆጠርኳቸውን ማስረጃዎች ባለመስማት መብቴን አጣብበውብኛል፡፡ ያለአግባብ የውርስ ንብረቶችን ወራሾች እንድንከፋፈል ወስነዋል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የውርስ አጣሪው ያቀረቡትን ሪፖርት እንዳያጸድቅ፣ የውርስ ማጣራቱ ሥራ እንደገና እንዲካሄድ እንዲያደርግልኝ ያቀረብኩትን ጥያቄ ባለመቀበል ሪፖርቱን ማጽደቁ በአግባቡ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ መሰረትዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ትእዛዙ ሊሻርልኝ ይገባል የሚሉ ናቸው፡፡

1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 30 ቀን 99 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የውርስ አጣሪው በኑዛዜ ስጦታው ላይ ያሉትን ምስክሮች አስቀርበው በመስማት የኑዛዜ ስጦታው የህግ ስህተት የሌለበት መሆኑን አጣርተው የአሁንዋ አመልካችንና ሌሎቹን ወራሾች በዝርዝር መዝግበው ባደረጉት ማጣራት መሰረት ሪፖርታቸውን ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ማቅረባቸው በአግባቡ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶቹ ሪፖርቱን ለማጽደቅ የሰጡት ትእዛዝም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ በመሆኑም ትእዛዙ ሊጸድቅልን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ደግሞ ሐምሌ 30 ቀን 99 ዓ.ም ጽፈው በሰጡት መልስ ውርስ አጣሪው የውርስ ንብረቱን በአግባቡ አላጣሩም የ1ኛ ተጠሪን ቤት በውርስ ንብረት ውስጥ ማካተት ሲኖርባቸው በስጦታ ያገኙት ነው በማለት መወሰናቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚች ለእኔ የሰጡኝን ቁጥሩ 432 የሆነውን ቤት በውርስ ንብረት ውስጥ ያለማካተታቸው ግን በአግባቡ ነው፡፡ በመሆኑም የውርስ አጣሪው ሪፖርት ባለበት ሁኔታ እንዲፀድቅ መደረጉ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የውርስ ንብረት አጣሪውን ሪፖርት ምንም ጉድለት አላገኘሁበትም በማለት ያፀደቀው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም የውርስ አጣሪው ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ሪፖርት ቁጥሩ 432 የሆነው ቤት አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ሚች ወ/ሮ ደጊቱ ደንጓሬ ለወ/ሮ አስለፊች ወርዶፋ በስጦታ የሰጡዋቸው በመሆኑ የውርስ ሐብት አይደለም በማለት ወስኛለሁ፣ ቁጥሩ 431 የሆነው ቤትም የወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ የኑዛዜ ድርሻ ነው፣ አመልካች ስጦታዎቹ ፈራሽ ናቸው በማለት ቢከራከሩም የሚፈርስበትን ምክንያት አልገለፁም፣ ስጦታው እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ጠይቀው ያስፈረሱበትን የፍ/ቤት ውሳኔ አላቀረቡም በማለት ያሰፈሩዋቸው ድምዳሜዎች ንብረቶቹን የማከፋፈል ዓይነት ሥራ ያከናወኑ መሆኑን እንደሚጠቁሙ ለመረዳት ችለናል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 956 እንደተደነገገው የአጣሪው ሥራ ሚቹ አንድ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግና በመጨረሻው ውርሱ የሚደርሳቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ፣ የውርሱን ሃብት ማስተዳደር፣ መክፈያቸው የደረሰውን የውርስ እዳዎች መክፈል እና ሚቹ በኑዛዜ ያደረጋቸውን ስጦታዎች መክፈልና የኑዛዜውን ቃል ለመፈፀም ማንኛቸውም ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎች ማድረግ ነው፡፡ እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት በሚያከናውንበት ጊዜ ደግሞ በኑዛዜው የውርስ ንብረት መሆናቸው ተጠቅሶ የክፍፍል ስርአትም የተቀመጠላቸውና ወራሾች በሙሉ የተስማሙባቸው ንብረቶችና መክፈያቸው የደረሰው የውርስ እዳዎች ሲኖሩ በወራሾቹ ስምምነት መሰረት ንብረቶቹን ሊያከፋፍልና እዳዎችንም ሊከፍል ይችላል፡፡

በኑዛዜው ላይ በተጠቀሱትና ባልተጠቀሱት ንብረቶች የውርስ ሃብት መሆን ያለመሆን ላይ ወራሾቹ ያልተስማሙና ክርክር ያነሱ ከሆነ ግን የአጣሪው ሥራና ሐላፊነት ወራሾች የተስማሙባቸውን ንብረቶች የውርስ ሃብት መሆናቸው መመዝገብ፡፡ ወራሾች ያልተስማሙባቸው ንብረቶችና እዳዎች ካሉ ደግሞ ማስረጃ በመስማት ማስረጃው ምን እንደሚያስረዳ ሪፖርቱ ላይ በማስፈር እንዲያጣራ ላዘዘው ፍ/ቤት ማቅረብ እንጂ ንብረት አጣሪው ይህ ንብረት የውርስ ሐብት አይደለም የሚሉ ወራሾች ቢኖሩም ማስረጃ በመስማት የውርስ ሃብት መሆኑን ስለተገነዘብኩኝ ንብረቱ የውርስ ሃብት ነው በማለት ወስኛለሁ ወይም ደግሞ ማስረጃውን እንደተመለከትኩት ንብረቱ የውርስ ሐብት ያለመሆኑን ስላረጋገጥኩኝ የውርስ ሐብት አይደለም በማለት ወስኛለሁ ለማለት የሚያስችለው ሥልጣን የለውም፡፡

በዚህ ጉዳይ የውርስ አጣሪው ያደረጉትን የማጣራት ሥራ ስንመለከተው ወራሾቹ የውርስ ሐብት ናቸው በሚሉዋቸው ሁለቱም ቤቶች ላይ ገና ከጅምሩ አንስቶ ያልተስማሙና ክርክር ያነሱ በመሆኑ አጣሪው ማስረጃ መስማታቸው በአግባቡ ነው፡፡ ሁኖም አጣሪው በወራሾች መካከል የተደረገው ክርክር ምን እንደነበረ፣ የኑዛዜ ወራሾችና የሕግ ወራሾች እነማን እንደሆኑ፣ የግራ ቀኙ ማስረጃ ምን እንደሚመልስ፣ እንዲሁም ወራሾች የተማመኑባቸውና ያልተማመኑባቸው የውርስ ንብረቶችና እዳዎቹ ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ሪፖርት ማዘጋጀት ሲኖርባቸው ከዚህ አልፈው ወራሾችን አከራክረው ማስረጃ ከሰሙ በኋላ ክርክሩንና ማስረጃውን ከሕግ ጋር በማገናዘብ ይህ ንብረት የእገሌ እንጂ የእገሌ አይደለም በማለት መወሰናቸው ከተሰጣቸው የውርስ አጣሪነት ሥልጣን በላይ በመሄድ መደበኛ ፍ/ቤት በሚያከናውነው የዳኝነት ሥራ ውስጥ መግባት መሆኑንና ይህም ተገቢ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ውርስ አጣሪው አዘጋጅተው ያቀረቡት ሪፖርት ውሳኔም ጭምር ያዘለ በመሆኑ ሪፖርቱ በቀረበለት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መጽደቁ ደግሞ በአጣሪው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተወሰነው ነገር በፍ/ቤት ተቀባይነት አግኝቶ የፀደቀ ተደርጐ ስለሚወሰድ አመልካች አዲስ ክስ አቅርበው የውርስ ድርሻቸውን ለማግኘት የሚያስችላቸውን መብት የሚያጣብብ ነው የሚሆነው፡፡ በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሪፖርቱን መርምሮ ያለበትን ጉድለት እንዲስተካከል ማድረግ ሲገባው እንዳለ ተቀብሎ ማጽደቁ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለዚህ የውርስ ንብረት አጣሪው ያቀረቡት ሪፖርት የአጣሪንና የመደበኛ ፍ/ቤትን ሥራ አጠቃሎ የያዘ በመሆኑ ሪፖርቱ በአግባቡ የተዘጋጀ ባለመሆኑና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሪፖርቱን ያፀደቀበትና የፌ/ከ/ፍ/ቤት ደግሞ የቀረበለትን ይግባኝ የሰረዘበት ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆነው ስለተገኙ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04036 ጥር 5 ቀን 97 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37777 ሐዳር 21 ቀን 98 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤት የውርስ ማጣራት ሪፖርቱን ያፀደቀው ከነጉድለቱ ጭምር በመሆኑ መጽደቅ አልነበረበትም ብለናል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት እንደገና አጣሪ ሾሞ የውርስ ማጣራቱን ሥራ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 956 መሰረት እንዲከናወን በማስደረግ ሪፖርቱ በአግባቡ የቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ በሕጉ መሰረት አስፈላጊውን እንዲፈጽም በማለት ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን እንዲችሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መለስናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ. 25869

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድነን ኪሮስ

ዓለ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ አየለች አልታዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስናቀች አየለ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሰበር የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት እና ህዳር 27 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 5436 ሚያዝያ 3 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 19 ቀን 1998 ዓ.ም ባቀረበችው አቤቱታ ስለጠየቀች ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች የሕፃን ዮናስ ወንድሙና የያሬድ ወንድሙ ወላጅ እናት እና ሞግዚት መሆኗን ገልፃ የሞግዚት አድራጊዎች ወላጅ አባት አቶ ወንድሙ ገብረየስ መጋቢት 3 ቀን 1981 ዓ.ም በሞት ተለይተዋል፡፡ ሟች አቶ ወንድሙ ከተከሣሽ /ከተጠሪ/ ጋር በባልና ሚስትነት እያሉ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 19 ቀበሌ 56 ቁጥሩ 115 የሆነ መኖሪያ ቤት ሠርተዋል፡፡ ስለዚህ የመኖሪያ ቤቱን ግምትና ቤቱን ለሱቅና ለሆቴል እያከራዩች የምታገኘው ገንዘብ ጭምር የሕፃኖቹ ወላጅ አባት የጋራ ሀብት በመሆኑና የውርስ ሀብት ክፍል እንድታካፍለኝ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ የውርስ ንብረት ክፍል ነው የተባለውን ሀብት አስመልክቶ የተለያየ ክርክርና ማስረጃ ያቀረበች ሲሆን ወ/ሮ ጥሩወርቅ ወንድሙ የተባለች ሴት በበኩሏ የሟች ወንድሙ ገብረየስ ወራሽ እና ልጅ ነኝ በማለት የወራሽነት ማስረጃዋን በማያያዝ በክርክሩ ጣልቃ ገብታለች፡፡

ፍርድ ቤቱ ቤቱና ሌሎች ንብረቶች ተገምተው እንዲቀርቡለት ትእዛዝ ሰጥቶ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ መሀዲስ የቤቱ ጠቅላላ ዋጋ ብር 19,823.47 /አስራ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ ነው በማለት አስተያየት አቅርቧል፡፡ ከዚህ በኋላ የቤቱ ግማሽ ባለቤትነት የተጠሪ፣ የቤቱ ግማሽ ባለቤትነት ደግሞ የአመልካች ሞግዚት አድራጊዎችና የወ/ሮ ጥሩወርቅ ወንድሙ መሆኑን ከዘረዘረ በኋላ ተጠሪና ወ/ሮ ጥሩወርቅ ወንድሙ፣ ለአመልካች ብር 5,551.21/አምስት ሺ አምስት መቶ ሃምሣ አንድ ብር ከሃያ አንድ ሣንቲም/ በመክፈል ቤቱን በጋራ እንዲያስቀሩ ይህንን ማድረግ ካልቻሉ በሀራጅ እንዲሸጥ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርባ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ልጆቹን ማሣደጊያ ቤት የለኝም፡፡ ንብረቱ በአይነት መካፈል እየተቻለ ተጠሪ ትጠቅልለው መባሉ ተገቢ አይደለም፣ ንብረቱም መሸጥ ካለበት መሀዲሱ ባቀረበው ግምት ሣይሆን በሀራጅ መሆን ይገባዋል፣ የዳኝነት በጋራ ክፈሉ መባሉ ተገቢ አይደለም፣ በአጠቃላይ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያመለከተች ሲሆን፤ ተጠሪ ደግሞ በበኩሏ ቤቱ አመልካችና ተጠሪ ባሉበት በመሐንዲስ የተገመተ በመሆኑ እና በአይነት ሊከፈል የማይችል በመሆኑ፤ አመልካች ያቀረበችው አቤቱታ ሕጋዊ መሠረት የለውም የሚል መልስ የሰጠች ሲሆን አመልካች የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ሟች ወንድሙ ገብረየስ እና ተጠሪ በባልና ሚስትነት ሲኖሩ በጋራ የሰሩት ቤትና የጋራ ንብረት መሆኑ አልተካደም፡፡ ሟች ወንድሙ የሞተ በመሆኑ እሱ በቤቱ ላይ ያለው የጋራ ባለቤትነት መብት ለወራሾቹ ዮናስ ወንድሙ፣ ያሬድ ወንድሙና ጥሩወርቅ ወንድሙ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይተላለፋል፡፡ ስለሆነም የቤቱ የጋራ ባለንብረቶች ሟች ወንድሙ ገብረየስ ወራሾች እና ተጠሪ ናቸው፡፡

የማይንቀሣቀስ ንብረት የጋራ ባለቤት የሆኑ ሰዎች የማይንቀሣቀሰውን ንብረት በአይነት ለመከፋፈል የሚችሉ ከሆነ በአይነት መከፋፈል እንደሚችሉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1272 የተደነገገ ሲሆን ንብረቱ በአይነት መከፋፈል የማይቻል ሲሆን ደግሞ በሀራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እንደሚከፋፈሉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1273 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ንብረቱ በአይነት ለመከፋፈል የሚችል ከሆነ የሟች ወራሾች እና ተጠሪ ንብረቱን እኩል መከፋፈልና የሟች ወራሾች ድርሻቸውን በስምምነት የሚከፋፈሉበት ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ስለሆነም ቤቱ በአይነት ለመከፋፈል የሚቻል ሲሆን አመልካችና ተጠሪ ቤቱን በአይነት እንዲካፈሉ ትእዛዝ መስጠት ሲገባቸው አላግባብ ያለፉት በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በተገለፀው መንገድ ቤቱ በአይነት ለመከፋፈል የሚችል ካልሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1273 መሠረት ግልጽ ሀራጅ ወጥቶ መሸጥ ይገባዋል፡፡ ተጠሪም ሆነች አመልካች የቤቱን ዋጋ በመክፈል የቅድሚያ ግዥ መብታቸው የሚጠበቀው ቤቱ በግልጽ ጨረታ ያወጣውን ከፍተኛ ዋጋ ገቢ ለማድረግ ዝግጁ ሆነው ሲገኙ እንጅ መሀዲሱ ገምቶ ያቀረበውን ዋጋ ገቢ በማድረግ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም አመልካችና ተጠሪ ቤቱን በግልጽ ሀራጅ በሚያወጣው ዋጋ መሠረት ለማስቀረት የሚስማሙ ከሆነ በስምምነታቸው መሠረት መፈፀም አለበት፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የማይስማሙ ከሆነ ግን ቤቱ በግልጽ ሐራጅ ተሸጦ የሚች ወራሽ የሆኑት ሶስት ልጆች ግማሹን ለሶስት እኩል እንዲካፈሉ፣ ተጠሪ ደግሞ የቤቱን ግማሽ ዋጋ እንድትወስድ መደረግ ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ባቀረበችው ክስ መሠረት በክርክሩ ፊት ሆና እያለ ከተጠሪ ጋር ዳኝነት በጋራ እንድትከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ህዳር 27 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 5436 ሚያዚያ 3 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ የሚቻል ከሆነ ቤቱንና ቦታውን በአይነት እንዲከፋፈሉ ቤቱን በአይነት ለመከፋፈል የማይችሉ ከሆነ በግልጽ ጨረታ በሀራጅ ተሸጦ ግማሹን ተጠሪ እንዲወስዱ፣ ግማሹን የሚች አቶ ወንድሙ ወራሾች ለሶስት እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስነናል፡፡
4. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ወጭ ተጠሪ ብቻዋን መሸፈን አለባት ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 30158

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካቾች፡- እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞግዚት ሐይሉ ሲሳይ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- የኮ/ል እሸቱ ተስፋዬ ወራሾች ጠበቃ ወርቅዬ አባይነህ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 83/90 መጋቢት 17 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 04711 ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 255/1999 ጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ እናቱ ወ/ሮ አበበች ጀግሬና አክስቱ በየነች ጌቶ አሁን በህይወት የሉም፡፡ እናቱና አክስቱ ከሚች እናታቸው ወ/ሮ ጀማነሽ አቡዬ በውርስ የተላለፈላቸውንና በደሴ መዝገበ ማርያም የስንዴ ግብር እየከፈሉ ይዘውት የቆዩትን በደሴ ከተማ ቀበሌ 05 ቁጥሩ 407 የሆነ ቤትና 668 ካሬ ሜትር ቦታ አቶ በዛብህ ጉሽ አላግባብ የያዘና በስሙ ያዛወረ ስለሆነ ከውርስ ንብረቱ የሚደርሰኝን ብር 6000 (ስድስት ሺህ ብር) እንዲከፍል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይወሰንልኝ በማለት የወራሽነት ክስ በማቅረቡ ነው፡፡ አመልካቾቹ በክሱ የተገለፀው ቤትና ቦታ የአቶ በዛብህ ጐሽ የግል ንብረት እንደሆነና ይኸም በደሴ ማዘጋጃ ቤት እንደተመዘገበ ገልፀው የተከራሩ ሲሆን ንብረቱ ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት ነው ቢባል እንኳን የከሳሽ(ተጠሪ) ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቾች በኩል የቀረበውን ክርክር አልፈው ተጠሪ ያቀረበውን የሰው ማስረጃ መሰረት ንብረቱ የውርስ ንብረት ስለሆነ አመልካቾች ለተጠሪ እንዲያካፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ የክለሳ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ይኸ ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት በደሴ ከተማ ቀበሌ 05 ቁጥሩ 407 የሆነው መኖሪያ ቤት ጥንት ለመገገበ ምህረት ማሪያም የስንዴ ግብር ተገብሮበት ነበር በማለት ቤተክርስቲያን በፃፈው ቀላጤ መነሻ ለሰላሣ ሁለት ዓመት በስማቸው ያለውን ንብረት አካፍሉ መባላችን መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ንብረቱ በአመልካች ባለቤትና አውራሾች በዛብሕ ጐሽ ስም ስለሆነ ተጠሪዎች ሊጠየቁ ይችላሉ የሚለው ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ንብረቱ በውርስ ከወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬ በውርስ የተላለፍ ነው፡፡ የተጠሪ እናትና አክስት ይኖሩ ነበር ተጠሪ አውራሽ እናታቸው 1989 ዓ.ም ሞተው በ1989 ዓ.ም የወራሽነት ጥያቄ ያቀረቡ ስለሆነ የይርጋ የጊዜ ገደብ አልተላለፈም፡፡ ንብረቱ የሟች ወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬ ስለሆነና ለተጠሪ እናትና አክስት በውርስ የተላለፈ በመሆኑ ተጠሪ ድርሻ መጠየቃቸው ህጋዊ ነው የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን የቃል ክርክር

ሰምቷል፡፡ ይህ ችሎት ግራ ቀኙ የአከራካሪውን ቤት ባለቤትነት አስመልክቶ ያቀረቡት ክርክር ከመታየቱ በፊት የተጠሪ ክስ በይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል ወይስ አይታገድም? የሚለውን ጭብጥ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ተጠሪ ለደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት አስቀርቦ ካሰማቸው እና ፍርድ ቤቱ በውሣኔው ላይ የምስክርነት ቃላቸው ከመዘገበው አንደኛ ምስክር ለመረዳት የሚቻለው የተጠሪ እናት እና አክስት አውራሽ ናቸው የተባሉት ወ/ሮ ጀማነሽ አቡዬ የሞቱት በ1949 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ከዚህ በኋላ የተጠሪ እናት ወ/ሮ አበበች ጀግሬና አክስታቸው ወ/ሮ በየነች ጌቶ የእናታቸው የውርስ ንብረት እንዲከፈልና ድርሻቸው በስማቸው እንዲዞር ያቀረቡት ክስ የለም፡፡ ንብረቱንም በስማቸው አላዞሩም፡፡ በተቃራኒው የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች አባት አቶ በዛብህ ጐሽ የቤቱን ስመ ንብረት በስማቸው አዛውረውና በደሴ ማዘጋጃ ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ አስመዝግበው እንደኖሩ ተረጋጋጧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪው ክስ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚታገድ አይደለም የሚል ብይን የሰጡት ንብረቱ ከዘር የወረደ ርስት ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) “ሟች ከሞተበት ወይም ተከሳሹ በመብቱ ለመምራት ከቻለበት ቀን አንስቶ አስራ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በስተቀር የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸውም አስተያየት ቢሆንም ተቀባይነት አያገኝም” በማለት ይደነግጋል፡፡

ከዚህም ድንጋጌ የምንረዳው ሟች ከሞተ ከአስራ አምስት አመት በኋላ ወይም ተከሳሹ በመብቱ ሊሰራበት ከቻለበት ቀን አንስቶ ለምሣሌ ህፃን ልጅ ወራሽ ሲሆንና ሞግዚትና አስተዳዳሪው መብቱን በአግባቡ ያልጠየቀለት ቢሆን አካለ መጠን ከደረሰበትና በመብቱ ሊሰራበት ከቻለበት ቀን አንስቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአስራ አምስት አመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ ጉዳዩ በይርጋ እንደሚታገድ በመርህ ደረጃ ይደነግጋል። ድንጋጌው ከላይ የተገለፀው የአስራ አምስት ዓመት ጊዜ ሣያልፍ የወራሽነት ጥያቄ ክስ ያላቀረበ ሰው ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ ክስ እንዲያቀርብ የሚፈቅደው በአንድ ልዩ ሁኔታ ብቻ ነው። ይኸውም ንብረቱ ከዘር የወረደ ርስት ሆኖ ሲገኝ በአስራ አምስት አመት የይርጋ ጊዜ የማይገደብ መሆኑን በልዩ ሁኔታ የደነገገ በመሆኑ ነው። ስለሆነም ተጠሪ ክስ ማቅረብ የሚችሉት ክርክር የተነሣበት ንብረት ከዘር የወረደ ርስት ከሆነ ብቻ በመሆኑ ክርክር የተነሣበት "ከዘር የወረደ ርስት" ምን አይነት ንብረትን ያጠቃልላል? በተለይም ከዘር የወረደ ርስት የሚባለው ቤትን ያጠቃልላል ወይ? የሚለውን ትርጉም መስጠት ያስፈልጋል። ስለሆነም "ርስት" የሚለውን ቃል ስንመለከት "ቤተዘመድ የሆነ እያረሰ የሚጠቀምበት ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ መሬት" ማለት እንደሆነ ከአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ለመገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) "ከዘር የወረደ ርስት" የሚለው አገላለጽ፣ ለተወላጅ በውርስ የተላለፈ መሬትን ብቻ የሚመለከት እንጂ ቤትንና ሌሎች የማይንቀሣቀሱ ንብረቶችን የሚመለከት አይደለም። መሬት የመንግስትና የህዝብ በመሆኑና አሁን ባለው ህገመንግስታዊ ሥርዓት የመሬት ባለቤት የኢትዮጵያ ብሔር በሔረሰቦችና ህዝቦች እና መንግስት እንደሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ "ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በስተቀር" የሚለው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) ድንጋጌ በአሁኑ ሰዓት የተሻረና ተፈፃሚነት የሌለው ነው።

ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ርስት የሌለ በመሆኑ ሟች ከሞተበት ወይም ተከሳሹ በመብቱ ሊሰራበት ከቻለበት ጊዜ ጀምሮ ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ የሚቀርብና በይርጋ የማይገደብ የወራሽነት ጥያቄ የለም። ስለሆነም የተጠሪ እናትና አክስት አውራሻቸው ወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬ ከሞቱበት 1949 ዓ.ም ጀምሮ የወራሽነት ክስ ያላቀረቡ በመሆናቸው ይርጋው መቆጠር ያለበት

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር የተጠሪ አውራሽ ወ/ሮ አበበች ጀግሬም ሆኑ ተጠሪ አውራሻቸው ከሞቱ ከሰላሣ ዘጠኝ አመት በኋላ ተጠሪ የወራሽነት ጥያቄ ያቀረቡ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 (2) በተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ክሳቸው ቀሪ ይሆናል። የተጠሪ እናት እቤቱ ውስጥ መኖራቸው የውረሱን ንብረት የተካፈሉና በስማቸው ያደረጉት መሆኑን አያረጋጋጥም። ስለሆነም የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤትና የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ንብረቱ ከዘር የወረደ እርስት ስለሆነ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጡት ትርጓሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት። እንደዚሁም ተጠሪው አውራሹ የሆነችው ወላጅ እናቱ የአናቷን የወ/ሮ ጀማነሽ አቦዬን ውርስ ሳትጠይቅ ያሳለፈችው ረጅም ጊዜ በተጠሪው ላይ የሚቆጠርበት መሆኑን ሣያገናዝብ ተጠሪው የይርጋ የጊዜ ገደቡ ሣያልፍ ነው ክስ የቀረበው በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም። የተጠሪ የወራሽነት ጥያቄ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) መሰረት በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ የቤቱን ባለቤትነት አስመልክቶ ያነሱትን ክርክር መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም። ስለሆነም ከላይ በተገለፀው መንገድ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) በተሣሣተ መንገድ በመተርጉም የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ የህግና የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማጽደቅ የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሄር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 255/1999 ጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል። ይፃፍ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐብሄር ይግባኝ መዘገብ ቁጥር 04711 ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 83/90 መጋቢት 17 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ የታገደ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
5. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

የሰ/መ/ቁ. 30991

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ብርሃኑ አመነው

አቶ መድሕን ኪሮስ

አቶ ዓሊ መሐመድ

አቶ ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- እማሆይ ወይንሸት አድማሱ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ክብነሽ ስዩም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን አመጣጡም የአሁኑ ተጠሪዎች ታህሳስ 30 ቀን 99 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ሚች አቶ ስዩም አየለ በወረዳ 3 ቀበሌ 53 ቁጥሩ 143 የሆነውን ቤት እኩል እንድንካፈለው ለኛና ለተከሳሾች ተናዝዘውልናል፡፡ ስለቤቱ አጠቃቀም ውርሱን በማጣራትና በመለየት ቤቱን አስከምንከፋፈል በኪራይም ይሁን በኮንትራት የሚገኘውን ገቢ እየተከፋፈልን እንድቆይ ተስማምተናል፡፡ ሆኖም ተከሳሾች ቤቱን አከራይተው ያገኙትን ገቢ ሊያካፈሉን ፈቃደኞች ባለመሆናቸው በኪራይ ያገኙትን ገንዘብ እንዲያካፍሉን፡፡ ቤቱም ተሸጦ እንድንከፋፈል ይወሰንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

የአሁን አመልካቾች (የሥር ተከሳሾች) ደግሞ ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ ያደረግነው ስምምነት ኑዛዜውን የሚተካና ወሳኝነት ያለው አይደለም ክርክር ያስነሳው ቤትም የምንኖርበት እንጅ የሚከራይ አይደለም፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ተከራይቶ በነበረበት ጊዜ የተገኘው ገቢም ብር 7560 ነው፡፡ ከዚሁ ገንዘብ የቤት ባለቤትነት ደብተር ለማስወጣት ከፍለንበታል፡፡ ቀሪውን ገንዘብ ተሳስበን ለመክፈል ዝግጁነን፡፡ የቤቱን መከፋፈል ግን የሚደረገው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኑዛዜው መሰረት ከ1ኛ ተከሳሽ የህይወት ፍፃሜ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም ከሣሾች ያቀረቡት ክስ ኑዛዜውን መሰረት ያላደረገ መሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረና ማስረጃ ከተማ በኋላ ተከሳሾች ቤቱን በማከራየት ካገኙት ገቢ ውስጥ የከሳሾች ድርሻ የሆነውን ብር 1628.50 ለከሳሾች እንዲከፍሉ፡፡ ቤቱም በሐራጅ ተሸጦ ለወራሾች እንዲከፋፈል በማለት ወስነናል፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ መሰረት በማድረግ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካቾች የሰበር አቤቱታው ያቀረቡት በሥር ፍ/ቤቶቹ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ቅሬታቸውም ሟች የተናዘዙት ክርክር ያስነሳውን ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሌሎቻችን ወራሾች ጋር በመሆን እንዲገለገሉበት፡፡ ለሌሎቻችን ወራሾች ሊከፋፈል የሚችለው እሳቸው ከዚህ ዓለም በሞት በሚለዩበት ጊዜ መሆኑን ነው፡፡ 1ኛ አመልካች በህይወት እያለ ቤቱን መሸጥና መከፋፈል አይቻልም፡፡ እንደዚሁም ወራሾች በሙሉ ተሰብስበን 1ኛ አመልካችም ጭምር ቤቱ ሳይከፋፈል ከሚያስገኘው ጥቅም እኩል እየተጠቀምን መቆየት እንዳለብን የተስማማንና የተዋዋልን በመሆኑ ተጠሪዎች ቤቱን ለመካፈል ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን ወራሾች እንዲከፋፈሉት በማለት የሰጡት ውሳኔ የአውራሻችን ኑዛዜና ከዚያም በኋላ ወራሾች ያደረግነውን ውል ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው ሊሻርልን ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ ክርክር የተነሳበት ቤት በአጠቃላይ በሐራጅ እንዲሸጥ በማለት የተሰጠው ውሳኔ የሟችን የኑዛዜ ቃል የተከተለ መሆን አለመሆኑን መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘው አቤቱታው ያስቀርባል ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎችም ሐምሌ 2 ቀን 99 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ 1ኛ አመልካች በቤቱ ላይ የጋራ መብት የላቸውም፡፡ ከኑዛዜው በኋላ ጥር 8 ቀን 1987 ዓ.ም በተፃፈው የወራሾች የጋራ የስምምነት ውል 1ኛ አመልካች ቤቱ የማይመለከታቸው መሆኑ ተወስኗል፡፡ ቤቱ የወራሾች የጋራ ንብረት በመሆኑ ተሸጦ እንድንከፋፈለው እንዲወሰንልን ክስ ማቅረባችን አግባብ ነው፡፡ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በኑዛዜ ያገኘነውን ቤት ክርክር ካስነሳው ቤት ጋራ በሐራጅ እዲሸጥ ተወሰነብን በማለት ያቀረቡት ክርክር በስር ፍ/ቤት ያላነሱት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን ወራሾች እንዲከፋፈሉት በማለት የሰጡት ውሳኔም አንዳችም የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ በመሆኑም ውሳኔው እንዲፀናልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት የመልስ መልስ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

በበኩላችን ደግሞ 1ኛ አመልካች በህይወት እያሉ ወራሾቹ ክርክር ያስነሳውን ቤት በሐራጅ ተሸጦ ሊከፋፈሉት ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም የወራሾቹ አውራሽ የሆኑት ሟች አቶ ስዩም አየለ ነሐሴ 11 ቀን 1984 ዓ.ም በሰጡት ኑዛዜ ወ/ሮ ወይንሸት አድማሱ ክርክር ባስነሳው ቤት ውስጥ ከሌሎቹ ወራሾች ጋር አብረው እንዲኖሩ የፈቀዱና እሳቸው በህይወት እያሉም ቤቱን ሸጬ ድርሻዬን እወስዳለሁ የሚል ካለ ያገዱት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተናዛዡ ወራሾችን ወይም በኑዛዜ ስጦታ የተሰጣቸውን ሰዎች ከሚደርሳቸው ሃብት ላይ በተለይ ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች አንድ አገልግሎት እንዲሰጡ ግድ እንዲሆንባቸው በኑዛዜው ለመወሰን እንደሚቻል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 920 ተደንግጓል፡፡ የአመልካቾችና የተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት አቶ ስዩም አየለ በኑዛዜያቸው ያስቀመጡት የ1ኛ አመልካች ቤቱን የመጠቀም መብትም ወራሾች እንዲፈጽሙት የሚያስገድዳቸው ነው፡፡ በኑዛዜው ግዴታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተገባላቸው 1ኛ አመልካችም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 922/1/ መሰረት የታዘዘላቸውን እንዲፈጽሙላቸው ወራሾችን ለማስገደድ ይችላሉ፡፡

ወራሾቹ ተሰብስበው በውርስ ስለተሰጣቸው ቤት አጠቃቀም ለመወሰን ጥር 8 ቀን 1987 ዓ.ም የደረሱበት ስምምነትም የአውራሹን ኑዛዜ የሚያስቀይር ይዘት ስለሌለው ተጠሪዎቹ ላቀረቡት ክስ በምክንያትነት ሊጠቀስ የሚገባው አይሆንም፡፡ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በኑዛዜ አገኘነው ያሉትን ቤት በተመለከተ ደግሞ የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ተለይቶ ክስ ያልቀረበበትና የሥር ፍ/ቤትም ይህን አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ ባለመኖሩ በግራ ቀኙ የተደገው ክርክር አግባብነት የለውም፡፡

በመሆኑም 1ኛ አመልካች በኑዛዜ የተሰጣቸውን በህይወት ዘመናቸው ክርክር ያስነሳውን ቤት የመገልገል መብት ወራሾች ሊያሳጡዋቸው የሚችሉበት ምክንያት ባለመኖሩ ተጠሪዎች የውርስ ንብረት የሆነው ቤት ተሸጦ ገንዘቡን ወራሾች እንድንከፋፈለው በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ቤቱ ተሸጦ ገንዘቡ ወራሾች እንዲከፋፈሉት የሚለው ውሳኔም የ1ኛ አመልካችን በቤቱ የመገልገል መብትና የወራሾቹን 1ኛ አመልካች በህይወት እያሉ ቤቱን ያለመሸጥ ግዴታ የጣሰና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16509 ሰኔ 3 ቀን 97 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41583 ሚያዝያ 16 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አቶ ስዩም አየለ 1ኛ አመልካች በቤቱ ውስጥ መኖር እንዳይከለከሉ፡፡ እሳቸው በህይወት እያሉ ቤቱን ሽጩ ልካፈል ማለት አይቻልም በማለት የተናዘዙ በመሆኑ በወረዳ 3 ቀበሌ

53 ክልል የሚገኘው ቁጥሩ 143 የሆነው ቤት እማሆይ ወይንሸት አድማሱ በህይወት እያሉ መሸጥ የለበትም በማለት ወስነናል፡፡ይፃፍ፡፡

3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ/ 32414

ሰኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አቶ መድሕን ኪሮስ

አቶ ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ - ከጠበቃ ዳኞቸው ተስፋዬ ጋር ቀረበች

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሃሳብ ከፋይ ጌራወርቅ ቀረበች፡፡

2. ደረጀ ጌራወርቅ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ኑዛዜን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ በተጀመረበት በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የመጀመያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁንዋ አመልካች ሟች አቶ ጌራወርቅ ህሩይ (ባለቤትዋ) አድርገውት ያለፉት ኑዛዜ መሠረት ተደርጉ የወራሽነት ማስረጃ ይሰጣት ዘንድ በመጠየቅዋ ፍ/ቤቱም ጥያቄዋን በመቀጠል የኑዛዜ ወራሽነት በማለት ማስረጃውን ሰጥቶአት ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ማስረጃው መሰጠት አልነበረበትም በማለት መቃወሚያ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ጉዳዮን በድጋሚ ያየ ሲሆን በመጨረሻም ሟች አድርገውታል የተባለውን ኑዛዜ ከፊሉን በመሻር የተወሰነውን ክፍሉን ደግሞ በማጽደቅ ወስኖአል፡፡ በዚህ ላይ ከአሁንዋ አመልካች ይግባኝ የቀረበላቸው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶችም

ውሳኔው ጉድለት የለውም ብለዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ነሐሴ 4 ቀን 1999 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ጉዳዩን ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እደተመለከተው ክርክሩ ሊነሳ የቻለው ሟች አደረገው የተባለው ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል የሚል ክስ በመቅረቡ ሳይሆን (የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 973) ኑዛዜውን መሠረት በማድረግ የወራሽነት ማስረጃ (የምስክር ወረቀት) ይሰጠኝ (የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(1)) በማለት አመልካች ጥያቄ በማቅረብዋ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርበው ክስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ከሚቀርበው ጥያቄ (አቤቱታ) የተለየ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ የተለያዩ በመሆናቸውም የተለያየ ውጤት ነው ያላቸው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(1) እንደተደነገገው ወራሽነኝ የሚል ማንኛውም ሰው የወራሽነት ምስክር ወረቀት ይሰጠው ዘንድ ለፍ/ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከመቀበሉ በፊት ጠያቂው ማስረጃዎቹን ሁሉ እንዲያቀርብ በማድረግ እና አስፈላጊ መስሎ የታየውን ዋስትና እንዲሰጥ በማስገደድ ጭምር ዋስትናውን ካገኘ በኋላ የተጠየቀውን የምስክር ወረቀት ሊሰጥ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(2) ተመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቱ የአመልካቹን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ሰጥቶት የነበረውን የወራሽነት የምስክር ወረቀት ሊሰርዘው እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 998(1) የተቀመጠው ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ እንደሚቻለው የምስክር ወረቀቱ በጠያቂው አቤቱታ መነሻነት የሚሰጥ ቢሆንም የተሰጠው ያለአግባብ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚል መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩንና መቃወሚያው ተገቢ ሆኖ ከተገኘም የምስክር ወረቀቱ የሚሰረዝ መሆኑን ነው።

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበለት ፍ/ቤት ጥያቄውን ተቀብሎ የምስክር ወረቀቱን ሰጥቶ እንደነበር እንመለከታለን። ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(1) የተመለከተውን ድንጋጌ ተከትሎ የተፈጸመ በመሆኑ ትክክል ነው። ሌላው ቀጥለን የምናየው ተጠሪዎች የተሰጠውን የወራሽነት የምስክር ወረቀት በመቃወም መቅረባቸው ሲሆን ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን መሠረት በማድረግ ለምስክር ወረቀቱ መሰጠት መሠረት የሆነውን ኑዛዜ ይዘት እና ሕጋዊነትን መርምሮአል። በመጨረሻም ኑዛዜውን በከፊል በመሻር በከፊል ደግሞ አጽድቄአለሁ ብሎአል። በበኩላችን ትክክለኛ አካሄድ ሆኖ ያላገኘነውም ይህንን ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ በሕጉ የተቀመጠውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ኑዛዜው ፈራሽ ነው እንዲባል ክስ አልቀረበለትም። የፍ/ቤቱ የዳኝነት ሥልጣን የተወሰነ በመሆኑ በሥልጣን ክልሉ ስር የሚወድቀውን የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ነው ጥያቄ የቀረበለት። ይህን ጥያቄ ተቀብሎ ሰጥቶት የነበረውን የምስክር ወረቀት ተጠሪዎች ካቀረቡለት መቃወሚያ አንጻር ሲመዝነው ተገቢ አልነበረም የሚል ድምዳሜ ከደረሰም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 998(1) በተደነገገው መሠረት መሠረዝ ነው የነበረበት። ከዚህ አልፎ ኑዛዜው ፈራሽ ይባል የሚል ክስ በቀረበ ጊዜ ሊደረግ እንደሚችለው ሁሉ ኑዛዜውን በከፊል ሽሬአለሁ ማለቱ ትክክል አይደለም። የሕግ መሠረትም የለውም። ከሁሉ በላይ ደግሞ ፍ/ቤቱ ወደ ኑዛዜው ይዘት እና ሕጋዊነት ሁኔታ ገብቶ ውሳኔ መስጠት የሚችልበት ሕጋዊ መንገድ አልነበረውም እንጂ ሕጋዊ መንገድ ነበረው ተብሎ ቢሆን ኖሮ እንኳን የደረሰበት መደምደሚያ የኑዛዜን ፎርም እና ማስረጃ ከሚመለከተው ሕግ አንፃር ሊታይ ፍጹም የተሳሳተ ነው።

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ኑዛዜ በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ እንደሆነ በፍ/ቤቱ ውሳኔ ተመልክቶአል። በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ ሊያሟላቸው የሚገቡትን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 ስር የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ እንደሆነም ፍ/ቤቱ ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ አመልክቶአል። ይህን ሁሉ ካረጋገጠ በኋላ በከፊል ሽሬዋለሁ ያለው ሟች ንብረቱ ባልሆነው ንብረት ላይ ጭምር ተናዟል በማለት እንደሆነ ከውሳኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል። በሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው በግልጽ የተደረገው ኑዛዜ በሕጉ መሠረት አልተደረገም ተብሎ ሊነቀፍ የሚችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 የተቀመጡትን መስፈርቶች ያላሟላ ሆኖ ሲገኝ ነው። የስር ፍ/ቤት ኑዛዜውን ለመንቀፍ ምክንያት ያደገው ነጥብ የኑዛዜውን ሕጋዊነት በተመለከተ አግባብነት የለውም። ተናዛዡ የእሱ ባልሆነው ንብረት ጭምር ተናዟል የሚባል ቢሆን የንብረት ክርክር ሲቀርብ እራሱን ችሎ የሚታይ ጉዳይ ነው። ፍ/ቤቱ ይህን ነጥብ በማድረግ የኑዛዜውን ሕጋዊነት (ፎርም) መንቀፍ ተገቢ አይደለም የምንለውም በዚህ ምክንያት ነው። ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች የተጠሪዎችን መቃወሚያ መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ሆኖ አግኝተነዋል።

ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር የድሬዳዋ ከተማ የመጀመያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 00113/97 የካቲት 30 ቀን 99 ዓ.ም ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ.ቁ 106/99 ግንቦት 8 ቀን 99 ዓ.ም በተሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮአል።
2. ቀደም ሲል ለአመልካች የተሰጠው የወራሽነት የምስክር ወረቀት የሚሰረዝበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 34076

ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ - ወኪል እስክንድር ወልዱ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አማሆይ ድብቅነሽ ግዛው

2. ወ/ሮ አዳነች ወልዱ ፀጋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በውርስ ንብረት ክፍፍል ላይ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ስትሆን፣ በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተችው ይዘውት ከሚገኘው የውርስ ንብረት ላይ ድርሻዋን እንዲያካፍሉአት ነው፡፡ የውርስ ንብረት የተባሉት በአዲስ አበባ እና በደሴ ከተማ የሚገኙ ሁለት ቤቶች እንደሆኑም ተገልፆአል፡፡ ክሱ የቀረበለት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ወደ ክሱ ስረ ነገር ከመግባቱ በፊት አዲስ አበባ ከተማ ይገኛል በተባለው ቤት ላይ የዳኝነት ስልጣን የለኝም፣ ማስተናገድ የምችለው ደሴ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ቤት በሚመለከት የሚቀርበውን ክስ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም የግዛት ክልል ስልጣን የለኝም ተብሎ በሚሰጥ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ አይችልም፡፡ የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ሳያስተናግድ ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም አመልካች ሕዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተወሰነው አመልካች ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበችው የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከተው ክስ በግዛት ክልል የዳኝነት ስልጣን ምክንያት አይስተናገድም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ትእዛዝ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የሟች አቶ ወልዱ ፀጋ ልጆች ሲሆኑ፣ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ የሟቹ ሚስት ናቸው፡፡ ሟች ይኖሩ የነበሩት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን እንደሆነና የሞቱትም በዚሁ ቦታ ስለመሆኑ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪዎች ሟች በኖሩበትና በሞቱበት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን በደሴ ወረዳ ፍ/ቤት የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ማቅረባቸውን ከቀረበው ክርክር ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተችው የውርስ ሃብት ነው ከተባለው ንብረት ላይ ድርሻዋን ለማግኘት ነው፡፡ በአጠቃላይ ክርክሩ የፍትሐብሔር እንደመሆኑ የሚመራው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት ነው፡፡ በግዛት ክልል ስለሚወሰን የዳኝነት ሥልጣን በተመለከተ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አንደኛ መጽሐፍ በምዕራፍ 3 ስር ካሉት ድንጋጌዎች ውስጥ በቁጥር 23 የተመለከተውም ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በውርስ ምክንያት የሚቀርብ ክስ የሚታይበትን ቦታ የሚወሰን ነው፡፡ ክሱ መቅረብ ያለበት ወይም የሚቀርበው የውርሱ ክፍያ በተጀመረበት ቦታ ለሚገኘው ፍ/ቤት እንደሆነም ያመለክታል፡፡ ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ የውርስ ሃብት የሆኑ ንብርቶች በተለያዩ ቦታዎች የመኖራቸውን ጉዳይ

ግምት ውጥስ የሚገባ አይደለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ትእዛዝ ከዚህ አንጻር ሲታይም የሕግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክ/መ/ደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16355 ሰኔ 25 ቀን 99 ዓ.ም ተሰጥቶ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1070/99 መስከረም 27 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኝ አይባልበትም የተባለው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች ያቀረበችው የውርስ ክፍፍል ክስ መታየት ያለበት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ፍ/ቤት በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክሱን በማስተናገድ በበኩሉ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ይስጥበት ብለናል፡፡ ጉዳዩ ይመለስለት፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መ ድ ን

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
3. አቶ መስፍን እቁበዮናስ
4. አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ
5. አቶ አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- የቀድሞው የኢትዮጵያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን በሕግ የተካው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነ/ፈጅ ፍቅሩ ሸዋ አማረ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ አጂሃ ኢትዮጵያ አክሲዮን ማህበር (23 ሰዎች) - ጠበቃ አጥናፉ ቦጋለ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ አንደኛ ተጠሪ የሆነው አጂሃ ኢትዮ.አክሲዮን ማህበር በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ፣የአሁኑ አመልካች ነዳጅ ለማጓጓዝ ገንዘብ እየተከፈለው የትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጥ በአጓጓዥነት የተሰጡትን የነዳጅ ውጤቶች ልማድንና የማጓጓዝ ውልን በመጣስ፣ ብቃት የሌላቸውን መኪናዎች በማሰማራትና በሾፌሮች ጥንቃቄ ጉድለት በተለያዩ ቦታዎች በደረሱ አደጋዎች የተጫነው ነዳጅ በመፍሰሱ የብር 479,273.70 /አራት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ብር ከሰባ ሳንቲም/ ኪሣራ የደረሰበት መሆኑን ገልጾ አንደኛ ተጠሪ የነበረው የአሁኑ አመልካች ከወለዱ ጭምር እንዲከፍለው ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካች በበኩሉ፣በአዋጅ ቁጥር 107/69 እንዲሁም በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 105/79 እና 49/69 መሠረት አመልካች ከተራ ቁጥር 2--23 የተዘረዘሩት ተጠሪዎች ጭነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንዲያገኙ በተራ መዝግቦ ከአስጫኝ ጋር በማገናኘት ከሁለቱም ወገኖች ማለትም ከአስጫኝና ከአጓጓዥ የተፈቀደለትን የአገልግሎት ዋጋ ከመቀበል ውጭ የእነርሱ ወኪል ያለመሆኑን፣እንዲሁም በስማቸው የተዋዋለው ውልና የተረከበውም ነዳጅ ስለሌለ በኃላፊነት ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑን፤እያንዳንዱ መኪና ላጓጓዘው ነዳጅ ኃላፊነቱ የእርሱ መሆኑን በማስረዳት ተከራክሯል፡፡ የራሱ በሆኑት 9 ተሽከርካሪዎች ለጫኑትና ደረሰ ለተባለው የነዳጅ ጉድለት ደግሞ በን.ሕ.ቁ. 591 መሠረት ከአቅም በላይ የደረሰ አደጋ ስለሆነ ሊጠየቅ የማይገባው መሆኑን በመግለጽ በሰፊው ተከራክሯል፡፡ ከተራ ቁጥር 2-23 የተዘረዘሩት የጭነት ማጓጓዣ ባለቤቶችም በበኩላቸው ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የውል ግንኙነት የሌላቸውና ከአቅም በላይ በደረሰ አደጋ ሊጠየቁ የማይገባቸው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በጉዳዩ የቀረበውን ሰፊ ክርክር መርምሮ፣ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አዋጅና የሕግ ክፍል ማስታወቂያ መሠረት በአሆኑ አመልካችና ከተራ ቁጥር 2-23 በተጠቀሱት ባለንብረቶች መካከል የባለኮሚስዮንነት የሕግ ውክልና ግንኙነት ተፈጥሯል፡፡ በን.ሕ.ቁ. 60-62 መሠረት አንደኛ መልስ ሰጭ ከሆነው አስጫኝ ጋር ውል አድርጓል፡፡ ውሉም በቀረቡት የገንዘብ መክፈያ ደረሰኞች ተረጋግጦአል፡፡ በመሆኑም በተቀሩት መልስ ሰጭዎችም ላይ ለደረሰው ጉዳት የአሁኑ አመልካች ኃላፊ ነው፡፡ በራሱ ተሽከርካሪዎች ለጫነውና ደረሰ ለተባለው ጉድለትም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ስለሌለ ከኃላፊነት ነፃ አይደለም በማለት ወስኖ የደረሰው ጉድለት ለመተመን የቀረቡት ማስረጃዎች ክብደት የሚሰጣቸው ባለመሆናቸው ሂሳቡ በባለሙያ ተሰርቶ እንዲቀርብ አዟል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ እንዳለ አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር ቅሬታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የካቲት 10 ቀን 1998 በዋለው ችሎት የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች (ከ2-23 በተጠቀሱት) ተጭኖ ሲጓጓዝ ብክነት ለደረሰበት ነዳጅ

ኃላፊ መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ በማድረግ ጉዳዩ በሚሰማበትና ከዚያ በኋላ በተያዙ ተከታታይ ቀጠሮዎች ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ታዞ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 107/69 መሠረት ለተሽከርካሪዎች የስምሪት ፈቃድ ይሰጥና በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 49/69 እና 105/79 መሠረት የተፈቀደለትን የአገልግሎት ክፍያ ይቀበል የነበረ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የራሱ በሆኑ የጭነት ተሽከርካሪዎችም የጭነት ማጓጓዝ ሥራ ይሰራ የነበረ መሆኑም አላከራከረም፡፡ የአሁኖቹ ተጠሪዎችም በአመልካች አማካኝነት በሚያገኙት ስምሪትና ጭነት ባለንብረት በሆኑባቸው የግል ተሽከርካሪዎቻቸው ከሳሽ የነበረውን የአሁኑን አንደኛ ተጠሪ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ከቦታ ወደ ቦታ ያጓጉዙ አንደነበረ አልተካደም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የንግድ ሕግ ቁጥር 60-62 ያለውን መሠረት በማድረግ በሥር ጣልቃ ገብ በነበሩት በአሁኖቹ ከ2-23 በተመለከቱት ተጠሪዎችና በአሁኑ አመልካች መካከል የባለ ኮሚስዮን የሕግ ውክልና ግንኙነት ተፈጥሯል በማለት የአሁኑ አመልካች ከከሳሽ ጋር በገባው የኮሚስዮን ወኪልነት መሠረት በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት በሙሉ ኃላፊ ነው ብሏል፡፡

በመሠረቱ በንግድ ሕግ ቁጥር 60 ላይ የተመለከተው የባለኮሚስዮንነት ትርጓሜ ማንም አበል ለማግኘት ባለኮሚስዮን ስላደረጋቸው ሰው በራሳቸው ስም ሸቀጦችን ወይም የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችን ወይም ማናቸውም እነዚህን የመሳሰሉ ዕቃዎችን ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወይም የማጓጓዝ ውል ለመዋዋል በራሳቸው ሥም ግዴታ የሚገቡ ሰዎችን ወይም የንግድ ማህበሮችን እንደሚሸፍን ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአሁኑ አመልካች በወቅቱ በነበረው ፖሊሲ መሠረት የመንገድ ትራንስፖርት ቅንጅትን ለመጠበቅ ሲባል የግል ተሽከርካሪዎች ጭነት እንዲያገኙ ሥራውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማዕከላዊነት እንዲመራና ስለአገልግሎቱ ከአስጫኝ እና ከጫኙ ክፍያ እንዲያገኝ መደረጉ ብቻውን እንደ ሕጉ አነጋገር ባለኮሚስዮን ስላደረጉት ሰዎች በራሱ ሥም የማጓጓዝ ውል ለመዋዋል ግዴታ የገባ ነው መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ በሥር ጣልቃ ገብ የነበሩት የአሁኖቹ ከ2–23 የተመለከቱት ተጠሪዎች ከአሁኑ አመልካች ጋር በሕግ የታወቀ የኮሚሽን ኤጀንት ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ ዋጋ ተከፍሏቸው በየግል ተሽከርካሪዎቻቸው ላጓጓዙትና ላደረሱት ብክነት በግል ተጠያቂ የማይሆኑበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

በሌላ በኩል የአሁኑ አመልካች የራሱ የሆኑ ዘጠኝ ተሽከርካሪዎችን የማጓጓዝ ሥራ ላይ አሰማርቶ ለደረሰው ብክነት በሥር ፍ/ቤት ኃላፊ መባሉ በተመሣሣይ ሁኔታ ከተራ ቁ. 2–23 የተመለከቱት ተጠሪዎች በን.ሕ.ቁ. 591 መሠረት ከአቅም በላይ በሆነ ሆኔታ የደረሰ አደጋ ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በየግል ንብረቶቻቸው ለባከነው ነዳጅ በየድርሻቸው ኃላፊ መባላቸው በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች የአሁኖቹን ተጠሪዎች (ከ2–23 የተመለከቱትን) ወክሎ በኮሚሽን ኤጀንትነት ከከሳሽ (1ኛ ተጠሪ) ጋር በገባው ውል መሠረት በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት በሙሉ ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፣
- አመልካች በራሱ ተሽከርካሪዎች ላደረሰው ብክነት ኃላፊ ነው መባሉ በአግባቡ ነው፣
- ከተራ ቁጥር 2–23 የተመለከቱት ተጠሪዎች በየስማቸው አንዳር በተመለከቱት የግል ተሽከርካሪዎች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው በማለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሚያዚያ 13 ቀን 1996 ዓ.ም በመ/ቁ. 03013 የሰጠውንና የፌ/ከ/ፍ/ቤት ጥቅምት 9 ቀን 1998 በመ/ቁ. 33475 የሰጠውን ትዕዛዝ አሻሽለን ወስነናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 24703

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
2. ወ/ት ሂሩት መለሰ
3. አቶ ታፈሰ ይርጋ
4. አቶ መድሕን ኪሮስ
5. አቶ ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ት ቢሮ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተጠሪ ለሚጠቀምባቸው 10 ተሽከርካሪዎች በገባው የመድን ውል መሰረት መክፈል የሚገባውን ብር 55,068.56 የአረቦን ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ እንዲከፈል ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች ክስና ማስረጃ ለተጠሪ ደርሶ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ ደርሶት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የአመልካችን ክስና ማስረጃ መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመድን ውል አለ ለማለት ስለማይቻል አመልካች ያቀረበው ማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ በግራ ቀኙ መካከል በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመድን ውል አለ ወይስ የለም? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ክስ ያቀረበው ከተጠሪ ጋር ባደረግነው የመድን ውል መሰረት ሊከፈለኝ ይገባኝ የነበረው የአረቦን ክፍያ ያልተከፈለኝ ስለሆነ ይከፈለኝ በማለት እንደመሆኑ መጠን ጉዳዩ መታየት ያለበት የግራ ቀኙን ግንኙነት በተለይ ከሚገዛው የንግድ ሕጉ አኳያ ነው፡፡

ከዚህም አንጻር ጉዳዩ ሲታይ የመድን ውል ሲመሰረት እንደማንኛውም ውል የውል አቀራረብና አቀባበል /offer and acceptance/ ሊኖር የሚገባ ሲሆን የውል አቀራረብ /offer/ የሚከናወነው መድን ገቢው በመድን ሰጭው የሚዘጋጅን መግለጫ /proposal form/ ሲሞላና ይህንኑ መግለጫም ለመድን ሰጭው ሲያስረክብ ነው፡፡ በመድን ገቢው የቀረበው የውል አቀራረብ ጥያቄ በመድን ሰጭው ተቀባይነት አግኝቷል ለማለት የሚቻለው ደግሞ በተዘጋጀው ፖሊሲ ላይ በሚፈርምበት ጊዜ /The issuance of policy/ እንደሆነ፣ ከዚህ በኋላም በሁለቱ ወገኖች መካከል የመድን ውል የተቋቀመ መሆኑንና የትኛውም ወገን ሊያቋርጠው እንደማይችል ከንግድ ሕግ ቁጥር 651፣654 እና 657 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ መ/ቤት ለሚጠቀምባቸው ተሽከርካሪዎች የመድን ውል ለመግባት እንደሚፈልግ በመግለጽ የመ/ቤቱን ማሕተም በማድረግና በኃላፊው አማካኝነት በመፈረም ለመድን ሰጭው ለአመልካች መ/ቤት ደብዳቤ ጽፏል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በተጠሪ በኩል የውል አቀራረብ /offer/ የተደረገ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች በተዘጋጀው ፖሊሲ ላይ መፈረሙ የተረጋጠ እንደመሆኑ መጠን ከላይ

ከተጠቀሱት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ በመካከላቸው የመድን ውሉ የተደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በእርግጥ በፍ/ብሄር ሕጉ በተለየ የአጻጻፍ ሥርአት መደረግ ከሚገባቸው ውሎች መካከል አንዱ የኢንሹራንስ ውል ሲሆን የዚህ ዓይነት ውሎችም በተዋዋይ ወገኖች መፈረም እንዳለባቸውና በሁለት ምስክር ፊትም መረጋገጥ እንዳለባቸው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ቁ.1725 እና 1727 ላይ የተመለከተ ቢሆንም የግራ ቀኙን ግንኙነት በተለይ የሚገዛው ልዩ ሕግ የሆነው የንግድ ሕጉ ስለሆነና በጠቅላላ ሕግና በልዩ ሕግ መካከል አለመጣጣም በሚኖርበት ጊዜ ልዩ ሕግ የበላይነት እንደሚኖረው /The special prevails over the general/ ከሕግ አተረጓጎም መርህ መገንዘብ የሚቻል እንደመሆኑ በዚሁ መሰረትም መድን ሰጭው በሚያዘጋጀው ፖሊሲ ላይ እራሱ መፈረም እንዳለበት በን/ሕ/ቁ. 657 ላይ ከመመልከቱ በስተቀር መድን ገቢው መፈረም እንደሚገባው ያልተመለከተ በመሆኑ በውል ማቅረቢያ /offer/ ሰነዱ ላይ መድን ገቢው ከፈረመና በፖሊሲው ላይ ደግሞ መድን ሰጭው ከፈረመ በሁለቱ መካከል የመድን ውል ስለመደረጉ በቂ አስረጂ እንደሆነ ከንግድ ሕጉ አኳያ መገንዘብ ስለሚቻል በሁለቱ መካከል የመድን ውል አልተቋቋመም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 528 ታህሳስ 30 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31510 የካቲት 6 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከንግድ ሕጉ አኳያ በአግባቡ የተቋቋመ የመድን ውል መኖሩ የተረጋገጠ ስለሆነና በክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠየቀውም ገንዘብ ላይ ተጠሪ ክርክር ስለሌው ይህንኑ በክስ የተጠየቀውን ብር 55,068.56 /አምሳ አምስት ሺህ ስልሳ ስምንት ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

የሰ/መ/ቁ. 24704

ነዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

አቶ ተገኔ ጌታነህ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት-ጠበቃ አቶ ኃይሉ ተሰማ-ቀረቡ

ተጠሪ፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ ጤና ቢሮ ዐ/ሕግ አቶ ተመስገን መንግሥቴ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር የመድን ዋስትና ውል ስለመኖር የሚመለከት ነው፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ክስ በአሰላ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሠረተው የአሁኑ አመልካች ሲሆን የክሱ ይዘትም ባጭሩ የተጠሪ ንብረት የሆኑ ሁለት ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን እንዲያገኙ ጥር 2 ቀን 1995 በደብዳቤ ቁጥር 2915/73/9 በጠየቀው መሠረት አመልካች ተገቢውን ማጣራት ካደረገ በኋላ የሰሌዳ ቁ. 4-28437 ቶዮታ ኮብራ የሆነው የተጠሪ መኪና እ.ኤ.አ. ከ13/3/93 ጀምሮ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የመድን ሽፋን ውል በፖሊሲ ቁጥር NK/1/MTPV/0727/03 ተሰጥቶት፣ ለዚህም አገልግሎት አረቦን ብር 11,510.00 /አሥራ አንድ ሺህ አምስት መቶ አሥር ብር/ ተጠሪ ባለመክፈሉ በፍርድ እንዲወሰንበት ሲል ክስ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም የተጠሪን የጽሑፍ እና የቃል ክርክር ካዳመጠ በኋላ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበውን የመድን ዋስትና ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለመኖር የተመለከተ ክርክር ከቀረበው የግራ ቀኝ ማስረጃ አንፃር ከመረመረ በኋላ የመድን ዋስትና ውሉ ላይ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1727/1/ የተዋዋይ ወገኖች ፊርማ መኖር እንዳለበት እና ይህም በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ ያለበት መሆኑን ሕጉ የሚያስገድድ ሆኖ እያለ በአመልካች በኩል የቀረበው ማስረጃ ይህንን እና ሌሎች የሕጉን ድንጋጌዎች ስለማያሟላ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ውል ተቋቁሟል ለማለት እጅግ አዳጋች ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል። ይህንን ውሣኔ መቃወም አመልካች ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍረድ ቤት ይግባኙ አያስቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል።

ለሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ይህንን ውሣኔ የሚቃወም ሲሆን አመልካች ያቀረባቸው የአቤቱታ ነጥቦች፣ የመድን ውል አመሠራረት የሚረጋገጠው በንግድ ሕጉ በተደነገገው እንጂ በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ አይደለም፣ ይህም ሲባል በጉዳዩ ላይ ልዩ ሕግ እያለ የጠቅላላ ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት አድርጎ የመድን ውል የለም መባሉ አግባብ አይደለም። እንዲሁም የምስክሮች ፊርማ መኖር ወሳኝና አንገብጋቢ መሆኑን የንግድ ሕጉ አያመለክትም። ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች የመድን ውል አመሠራረትን በተመለከተ የወሰዱት አቋም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም ሲል ጠይቋል።

የሰበር ችሎቱም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሠነድ ልውውጥ በሕግ የተደነገገውን የመድን ውል ፎርም አያሟላም በሚል አመልካች ያቀረበው ክስ ውድቅ የተደረገው በሕጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቦ አከራክሯል።

የተጠሪ መ/ቤት ተወካይ የክልሉ ፍ/ቢሮ በአቤቱታው ላይ ሚያዝያ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ የመድን ውል በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ካልተፈረመና በምስክሮች ካልተረጋገጠ ሕጋዊ ውጤት እንደሌለው የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1675 እና የንግድ ሕግ አንቀጽ 659/1/ ያስገነዝባል።

አመልካች የመድን ውል አለ በማለት ያቀረበው ማስረጃ የተጠሪ መ/ቤት ማኔጅመንና ፊርማ የሌለው በመሆኑ አመልካች ብቻውን ያዘጋጀው ውል ተጠሪን ስለማያስገድድ የመድን ውል ሳይኖር የመድን ውል ግዴታ የለም በማለት በሥር ፍ/ቤት ያቀረበውን ክርክር አጠናክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና ጠይቋል።

አመልካች ግንቦት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ባቀረበው የመልስ መልስ በተጠሪ የቀረበው የመድን ዋስትና ሽፋን ጥያቄ እና በአመልካች የተሰጠው የመድን ውል ፖሊሲ በጋራ ሊታዩ ይገባል በማለት አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል።

በዚህ ጉዳይ ምላሽ የሚያሻው የሕግ ነጥብ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሠነድ ልውውጥ ስለ ኢንሹራንስ ውል አፃፃፍ ፎርም የተመለከተውን ድንጋጌ አሟልቷልን? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል።

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት የሕጉን ይዘት ከመመርመራችን በፊት በፍሬ ጉዳይ ክርክሩ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ንብረትነታቸው የተጠሪ ለሆኑት ሁለት መኪኖች የመድን ሽፋን እንዲሰጠው በተጠሪ መ/ቤት ማኔጅም እና በሚመለከተው ሁለት ፊርማ መጠየቁ አመልካች ለአንደኛው መኪና የመድን ሽፋን ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ የመድን ውል ፖሊሲ ለተጠሪ መስጠቱ ነው። አከራካሪው ጉዳይ የእነዚህ ሁኔታዎች መኖር በራሱ የኢንሹራንስ ውል በአመልካች እና በተጠሪ መካከል መመሥረቱን ያረጋግጣልን? የሚለው ነው።

የመድን ውል ስለመኖሩ ለማስረዳት አመልካች ያቀረበውን ማስረጃ ከፍተኛው ፍ/ቤት ሲመረምር መሠረት ያደረገው በፍ/ብ/ሕግ ስለውሎች አጻጻፍ ፎርም የተመለከተውን ድንጋጌ ነው። በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ አጥብቆ የተከራከረው የውሎችን አመሠራረት የሚመለከቱ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌዎች ከመሆኑ የተነሣ ይመሰላል ከፍተኛው ፍ/ቤት ትኩረት የሰጠውና ለውሣኔው መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1719 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በጥቅሉ መሠረት ያደረጉት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1725/ለ/ እና 1727/2/ መሠረት የኢንሹራንስ ውሎች በጽሁፍ መደረግ እንዳለባቸው በጽሁፍ የሚደረጉትም በምስክሮች ፊት መሆን እንዳለበት ይህ ካልተፈፀመ ውሉ እንደማይፀና የሚያስገነዝቡ ናቸው የሚለውን የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የኢንሹራንስ ውል አመሠራረት እና የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1725 እና 1727 ድንጋጌዎች አፈጻጸም ወሰን እንዲሁም የንግድ ሕግ ስለ ኢንሹራንስ ውሎች የተመለከተውን ድንጋጌ ቁጥር 657 እና ተከታዮቹ በተመለከተ የሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በመዝገብ ቁጥር 23003 ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ አሁን ከተያዘው ጉዳይ እና ጭብጥ ጋር ተመሣሣይ ሆኖ ስላገኘነው ከዛው ውሣኔ አንፃር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም አሁን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የመድን ሽፋን ለአንድ ዓመት በመሆኑ የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 23003 በወሰደው አቋም መሠረት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1725 እና 1727 ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፡፡ /የሰበር መ/ቁ. 23003 ይመለከቷል/

ስለዚህ ተጠሪ የመድን ሽፋን እንዲሰጠው በጠየቀው መሠረት አመልካች ለአንድ ዓመት የሚቆይ የመድን ሽፋን በፖሊሲው ፈርሞ የሰጠው መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ እና የፖሊሲው ይዘት በንግድ ሕግ ቁጥር 654, 657 እና 658 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘት ያሟላ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት ያልተካደ በመሆኑና እነዚህ አንቀጾች በአመልካችና በተጠሪ መካከል ለአንድ ዓመት የቆየ የመድን ሽፋን መኖሩን ለማረጋገጥ በቂ ሆነው ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1725 እና 1727ን መሠረት በማድረግ በሁለቱ መካከል የመድን ውል አልተመሰረተም በማለት ተጠሪ የጠየቀውን አረቦን እንዳይከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በፓሊሲ ቁጥር NK/1/MTPV/07 27/03 በተሰጠው የመድን ፖሊሲ ውል መሠረት ለአንድ ዓመት የቆየ የመድን ውል ተመስርቷል ብለናል፡፡
2. የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 816 መጋቢት 19 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39792 የካቲት 7 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
3. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የመድን ውል መኖር ስለተወሰነ በአረቦን አከፋፈል ላይ ፍ/ቤቱ የመሠለውን ውሣኔ እንዲሰጥ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ጉዳዩ ለአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 28254

ሐምሌ 22 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ መድሕን ኪሮስ

አቶ ፀጋዬ አስማማው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አትናቦን ነጋሳ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- መኮንን መስፍን ከጠበቃ በሻዳ ገመቹ ጋር ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመድን ዋስትና ውልን መነሻ ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ተከሣሽ የመድን ዋስትና የገባለት የሠ.ቁ. 3-28204 አ.አ. የሆነ መኪናዬ በመገልበጥ ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ተከሣሽም በገባው ግዴታ መሠረት ከወደቀበት ቦታ አንስቶት በማምጣት በሪከቨሪ ክፈሉ ያስገባው ቢሆንም፤ በመጨረሻ ግን ሊያስጠግንልኝ አልቻለም፡፡ ስለዚህ በገባው የውል ግዴታ መሠረት መኪናውን አስጠግኖ እንዲያስረክበኝ ወይም የመኪናውን ሙሉ ዋጋ እንዲከፍለኝ መኪናው የንግድ መኪና በመሆኑ እና ተከሣሽም በተገቢው ጊዜ ለመጠገን ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ የተቋረጠ ጥቅም ታስቦ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ የመድን ዋስትና ውል መግባቱ ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን መኪናው የተገለበጠው በውሉ የተደረገውን ስምምነት በመጣስ ተሳቢ ሲጎትት በነበረበት ጊዜ በመሆኑ

ኃላፊነት የለብኝም፡፡ የመድን ዋስትና ውሉ የተቋረጠ ገቢ እንዳይጠየቅ የሚከለክል በመሆኑ የተቋረጠ ጥቅምን በሚመልከት የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡ በተቋረጠ ጥቅም ስም የተጠየቀው የገንዘብ መጠንም የተጋነነ ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ተከሳሽ በገባው ውል መሠረት የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ መኪናውን አስጠግኖ ወደነበረበት በመመለስ ለከሣሽ ያስረክብ፣ በገባው የውል ግዴታ መሠረት መኪናውን ለማስጠገን ፈቃደኛ ባለመሆኑ የተቋረጠውን ጥቅም ብር 56,300 ይክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ ከዚህ በኋላ መጀመሪያ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ተጠሪም በበኩሉ በተቋረጠ ጥቅም ስም የተወሰነው ገንዘብ አንሶአል በሚል መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቦአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በሁለቱም በኩል የቀረቡትን ይግባኞች መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም መኪናውን አስጠግኖ ለተጠሪ ያስረክብ፡፡ እንደዚሁም ተቋረጠውን ገቢ ብር 275,000 ይክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ኅዳር 18 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ በመደረጉም ሆነ የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፍል የተሰጠውን ውሣኔ የሕግ አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የመድን ዋስትና ውል ስለመኖሩ አላከራከረም፡፡ ዋስትና የተገባለት መኪና በስራ ላይ እንዳለ መገልበጡንና በዚህ የመገልበጥ አደጋ የተነሣም ጉዳት የደረሰበት መሆኑም አከራካሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም፡፡ አመልካች ውሉን መሠረት በማድረግ መኪናውን ከወደቀበት ቦታ አስጎትቶ በማምጣት ወደ ረከቨሪ ክፍሉ ካስገባው በኋላ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት ነው ወደ ክርክር የገባው፡፡ ክርክሩን በየደረጃቸው የሰሙት የስር ፍ/ቤቶችም አመልካች ኃላፊነት የለብኝም ለማለት በመከራከሪያነት ያነሳውን ነጥብ እግምት ውስጥ በማግባት ክርክሩን ከመምራታቸውም በላይ፣ በግራ ቀኝ ወገኖች በኩል የተቆጠሩትን ማስረጃዎችንም ሰምተዋል፡፡ በመጨረሻም ማስረጃዎቹን በማመዛዘን በተሻለ ሁኔታ ያስረዳው ተጠሪ እንደሆነ በመገንዘባቸው የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርገዋል፡፡ አመልካች የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት እንዳለበትም አረጋግጠዋል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ኃለፊነት የለብኝም ለማለት በመከራከሪያነት ያነሳው ነጥብ በግራ ቀኝ ወገኖች ከቀረበው ማስረጃ አንፃር ታይቶ እና ማስረጃውም ተመዝኖ እልባት አግኝቶአል፡፡ የሰበር ችሎት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች አግባባነት ሊመረምር የሚችለው በሕግ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት አለ ሲባል ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን አመልካች ያቀረበው አቤቱታ በማስረጃ አመዛዘን ረገድ ስህተት ተፈጽሞአል ከሚል ያለፈ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከፍ ሲል በሰጠነው ምክንያት የምንመረምረው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለትም አልቻልንም፡፡

ከዚህ በመቀጠል የመረመርነው ተጠሪ በክሱ ከጠየቀው ገንዘብ በላይ እንዲከፈለው ተወስኖለታል በማለት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ነው፡፡ ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው የክስ ማመልከቻ የተቋረጠ ጥቅም በማለት እንዲከፈለው የጠየቀው ገንዘብ ብር 130,400 /አንድ መቶ ሰላሳ ሺህ አራት መቶ ብር/ እንደነበር ከመዝገቡ አረጋግጠናል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ይህን መነሻ በማድረግ እና የመኪናው

የዓመት ገቢ ነው ያለውን መጠን እግምት ውስጥ በማግባት አስልቶ የተጠየቀው ብር 130,400 ያነሰ ገንዘብ እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ ተጠሪም በክሱ የጠየቀውን የገንዘብ መጠን ሳይለውጥ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የወሰነው ገንዘብ አንሶኛል በማለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦአል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ገንዘቡ ያንሳል ወይስ አያንስም የሚል ጭብጥ በመያዝ በእርግጥ ተጠሪ ከመኪናው በዓመት የሚያገኘው ገቢ ወይም ጥቅም ምን ያሕል እንደሆነ ለማጣራት በራሱ በኩል ማጣራቱና ማስረጃም መስማቱ ትክክል ነው፡፡ በዚህ ረገድ ፍ/ቤቱ ስህተት ፈጥሮአል ማለት የሚቻለው ተጠሪ ከጠየቀው በላይ ገንዘቡን ወደ ብር 275,000 ከፍ አድርጎ በመወሰኑ ነው፡፡ በመሆኑም ይህኛውን የውሣኔው ክፍል ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመጨረሻም የመድን ዋስትና ውሉ የተቋረጠ ጥቅም እንዳይጠይቅ ይከለክላል የሚለውን የአመልካች ክርክር ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ በውሉ ላይ ይህን መሰል ስምምነት ስለመደረጉ የተካደ አይደለም፡፡ ነገር ግን አመልካች መኪናውን አስጎትቶ ካመጣና አስጠግናለሁ በሚል እሳቤ ረከቨሪ ክፍሉ አስገብቶ ከቆየ በኋላ ለማስጠገን ፈቃደኛ አይደለሁም በማለቱ ተጠሪ ወደ ክስ እንዲያመራ አስገድዶታል፡፡ መኪናው በንግድ ስራ ላይ ተሰማርቶ የነበረ በመሆኑ በመቆሙ ምክንያት በተጠሪ ላይ ከፍተኛ ኪሣራ እንደሚደርስ የሚያከራክር አይደለም፡፡ አንድ ተዋዋይ ወገን እንደ ውሉ ሳይፈጽም ቢቀርና በዚህ ምክንያትም በሌላኛው ተዋዋይ ወገን ላይ ጉዳት ቢደርስ የመካስ ኃላፊነት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1771/2/ የተቀመጠው ድንጋጌ በግልጽ ያመለክታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች እንደ ውሉ ለመፈጸም ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ በተጠሪ ላይ ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት ሆኖአል፡፡ ከዚህ የተነሣም እንደ ውሉ ይፈጽማል የሚል ግምት ተይዞ የተቀመጠውን የውሉን አንድ አንቀጽ በመጠቀም ኪሣራውን ከመክፈል ነፃ ሊሆን የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚባል አይደለም፡፡ ስናጠቃልለው አመልካች ኃላፊነትንና የተቋረጠ ጥቅምን በተመለከተ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በሌላ በኩል በተቋረጠ ጥቅም ስም የተጠየቀውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ የተሰጠውን የውሣኔውን ክፍል ማሻሻል እንደሚገባ አምነንበታል፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00252 ሚያዝያ 11 ቀን 96 ዓ.ም. እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቁ. 31541 ጥቅምት 2 ቀን 99 ዓ.ም. የተሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች በተጠሪው መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም መኪናውን አስጠግኖ ለተጠሪ የማስረከብ እና የተቋረጠውን ጥቅም የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብለን ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ በተቋረጠ ጥቅም ወይም ገቢ ስም ሊከፈለው የሚገባ ካሣ በክሱ በግልጽ የጠየቀው ብር 130,400 /አንድ መቶ ሠላሣ ሺህ አራት መቶ ብር/ ነው ብለናል፡፡ አመልካች ይህንኑ ገንዘብ ለተጠሪ ይክፈል፡፡
4. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች አልተነኩም፡፡
5. ተጠሪ በመኪናው አለመጠገን በቀጣይ የደረሰበት ኪሣራ ካለ ክስ አቅርቦ የመጠየቅ መብቱ ይህ ውሣኔ አያስቀርበትም፡፡
6. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የደረሰውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡
8. ከፌ/ከ/ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ ቁ. 31541 ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31334

ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ታፈሰ ይርጋ
መድነን ኪሮስ
ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ኃይሉ ተሰማ

ተጠሪ፡- 1/ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ
2/ የአቶ ገብረኪዳን ገዳ ወራሾች እነ ፋሲል ገ/ኪዳን - ጠበቃ ኃ/ማርያም ኢቲቻ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የሰበር አቤታውም ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ተጠሪዎች ባቀረቡት የተከሳሽ ከሣሽነት ክስ መሠረት አመልካች የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል ተብሎ በመወሰኑ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካች በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው ክስ ከሣሽ ንብረትነቱ የአቶ ደረጀ ጉደታ ለሆነ ተሽከርካሪ በደቡብ አብይ ቅርንጫፍ አጠቃላይ የመድን ዋስትና ሰጥቶ በእንቅስቃሴ ላይ እንዳለ ንብረትነቱ በአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መኪና በመገጨቱና ከፍተኛ ጉዳት መድረሱ ለደረሰው አጠቃላይ ውድመት ከሣሽ ተገቢውን ካሣ የከፈለ ሲሆን በደረሰው አደጋ ጥፋተኛው የተከሣሽን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ግለሰብ እንደሆነ በማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተረጋግጧል፣ ይሄው አደጋውን ያደረሰው ተሽከርካሪ በኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሰሜን ምዕራብ ዓቢይ ቅርንጫፍ የመድን ዋስትና ስለነበረው በዚሁ መሠረት በ3ኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት እስከ ብር 100 ሺህ ካሣ ለመክፈል ከሣሽ ኃላፊነት ስለነበረበት ይህንን ገንዘብ በቀጥታ ጠያቂ ለሆነው ለደቡብ ዓቢይ ቅርንጫፍ እንዲከፍል ተደርጓል፡፡ ስለሆነም የተከሣሽ መኪና በሌላ የ3ኛ ወገን መኪና ላይ ባደረሰው ጉዳት በዋስትና ከተገባው የ3ኛ ወገን ኃላፊነት ጣሪያ በላይ የሆነውን ብር 369,342.00 እንዲከፍሉ ይወስንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሣሽ አቶ ገብረኪዳን ገዳ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ስለተባለ የሚች ሚስትና ወራሾች በክርክሩ እንዲተኩ ተደርጎ በሰጡት መልስ አደጋ አደረሰ የተባለው የሰ/ቁ. 3-38201 መኪና በከሣሹ የመድን ሽፋን የተሰጠው ስለሆነና ጉዳቱም የደረሰው በሁለቱም መኪናዎች ላይ በመሆኑ በዚሁ መሠረት በሁለቱም መኪናዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ መክፈል ስለሚገባው እኛን መጠየቅ አይችልም በማለት የተከራከሩ ሲሆን በሌላ በኩልም የተከሣሾች መኪና በግጭቱ መውደሙ በከሣሽ የታመነ ስለሆነ የመኪናውን የዋጋ ግምት ብር 265 ሺህ የቅሪቱን ዋጋ እና የተቋረጠ ገቢን ጨምሮ በድምሩ ብር 488 ሺህ ከሣሽ እንዲከፍል ይወስንልን በማለት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ዋናውን ክስና የተከሣሽ ከሣሽነት ክሱን መርምሮ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለተጎጂውም ሆነ ለጉዳት አድራሹ መኪና የመድን ሽፋን የሰጠ እንደመሆኑ መጠን ከንግድ ሕግ ቁጥር 663 እና 664 አኳያ ለሁለቱም ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ስላለበት ለተከሣሾች ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት ካለ በኋላ መጠኑን በተመለከተ ከሣሽ ብር 92 ሺህ ካሣ ለመክፈል መስማማቱን ከቀረበው ማስረጃ መረዳት የተቻለ ስለሆነና የመኪናውም ቅሪት ብር 250 ሺ እንደሆነ ስለተረጋገጠ ይህንን ክፍያ ለመፈጸም ከሣሽ ፈቃደኛ የነበረ ቢሆንም ያልፈጸመ በመሆኑ በድምሩ ብር

342 ሺህ በመኪናው ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ መክፈል ያለበት ስለሆነ የሚች ሚስት የሆኑት ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ግማሹን ማግኘት ስለሚገባቸው ብር 171 ሺህ እንዲከፈላቸው እንደዚሁም የተቋረጠ ገቢን በተመለከተ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ መኪናው ተጠግኖ ሥራ ቢጀምር ፈቃደኛ መሆናቸውን በ6/2/96 ዓ.ም. ባቀረቡት ማስታወሻ ለከሣሽ ያረጋገጡ ቢሆንም በዚሁ መሠረት መኪናው ተጠግኖ ያልተሰጣቸው ስለሆነ መኪናውን ለመጠገን ያስፈልጋል ተብሎ የሚገመተው የ3 ወር ጊዜ ተቀንሶ ከ6/7/96 እስከ 18/4/98 ዓ.ም. ላለው የ1 ዓመት ከ8 ወር ከ12 ቀናት የተቋረጠ ጥቅም ከሣሽ መክፈል ይገባዋል ካለ በኋላ መጠኑን በተመለከተም ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ መኪናው በቀን ብር 700 ገቢ ያስገኝ እንደነበር በመግለጽ በዚሁ ተሰልቶ ካሣ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን በመቀበል በዚሁ ስሌት መሠረት የወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ድርሻ ብር 214,200 ስለሚሆን ይህንን የተቋረጠ ገቢና ከላይ የተጠቀሰውን የመኪና ጉዳት ካሣ ጨምሮ በድምሩ ብር 385,200.00 ከሣሽ ለወ/ሮ ለተብርሃን በየነ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩልም ከሣሽ ያቀረበውን ክስ በተመለከተም ከሣሽ ለወ/ሮ ለተብርሃንም ሆነ ለአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ወራሾች ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይፈጽም ክሱን በአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ወራሾችና በወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ላይ ማቅረቡ በንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ መሠረት አግባብነት የለውም ብሎ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሥር ከሣሽ የአሁን አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ይግባኙን መርምሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በደንበኛው ላይ ለደረሰ ጉዳት የከፈለውን ገንዘብ ደንበኛውን ተክቶ የጉዳት አድራሹን ቤተሰብ በን/ሕ/ቁ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

683/3/ መጠየቅ አይችልም መባሉ፣ በተጠሪዎች መኪና የዋጋ ግምትና በተጨማሪም የተቋረጠ ገቢ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ የጉዳዩ ጭብጦች፡-

አመልካች ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረው በአግባቡ ነው አይደለም?

ለተጠሪ የመኪና ዋጋ ግምትና የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈል የተወሰነው በአግባቡ ነው አይደለም? የሚሉ ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ከላይ እንደተመለከተው ንብረትነቱ የአቶ ደረጀ ጉደታ የሆነው ተሸከርካሪ በአቶ ገ/ኪዳን ገዳ ተሸከርካሪ ግጭት ደርሶበት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ በመሆኑ ከነተሳቢው ብር 783,512.50 ካሣ የተከፈለ ስለሆነና ከዚህ ገንዘብ ላይ የመኪናው ቅሪት የተሸጠበት ዋጋና እንደዚሁም የተጠሪዎች መኪና በ3ኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ለተገባ የኃላፊነት ኢንሹራንስ /liability insurance/ የተከፈለው ሲቀነስ በቀሪነት ብር 396,342.00 ስለሚፈለግ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይወስንልኝ በማለት ነው፡፡ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ መልኩ የቀረበውን ክስ ሳይቀበለው የቀረው መድን ሰጭው በን/ሕ/ቁ. 683/3/ መሠረት በመድን ገቢው ሚስትና ልጆች ላይ የመዳረግ መብት ስለሌለው ለደንበኛው የከፈለው ገንዘብ ይተካልኝ በማለት ጥያቄ ማቅረብ አይችልም በሚል ነው፡፡

የንግድ ሕግ ቁጥር 683 ስለ ኢንሹራንስ ሰጭው በምትክነት መግባት /Substitution of insurer/ የሚመለከት ሲሆን በዚሁ መሠረትም ኢንሹራንስ ሰጭው በከፈለው ካሳ መጠን ጉዳቱ እንዲደርስ ባደረጉት 3ኛ ወገኖች ላይ ክስ ለማቅረብ ኢንሹራንስ ለገባው ሰው በተከፈለው ገንዘብ

መጠን ባሉት መብቶችና ክሶች ኢንሹራንስ ሰጭው ምትክ ሆኖ እንዲገባ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ተመልክቷል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖም ለክፋት የተደረገ ካልሆነ በስተቀር ኢንሹራንስ ሰጭው በኢንሹራንስ ገቢው ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወኪሎች ሠራተኞች ወይም ከእርሱ ጋር ዘወትር አብረው በሚኖሩት ሰዎች ላይ ኢንሹራንስ ሰጭው የመዳረግ መብት እንደሌለው በዚሁ ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ /3/ ሥር ተመልክቷል፡፡ ይህም የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ /Exception to the General Rule/ እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን ከዚህም ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ኢንሹራንስ ሰጭው የመዳረግ መብት የሚኖረው በሕጉ ላይ የተዘረዘሩት ሰዎች የመድን ሽፋን በተሰጠው የመድን ገቢው ንብረት ላይ በክፋት ጉዳት አድርሰው በሚገኙበት ጊዜ እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች የመዳረግ መብቱን መሠረት በማድረግ በክስ የጠየቀው በተጠሪዎች መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት የተከፈለው ካሣ እንዲተካለት ሳይሆን በተጠሪዎች መኪና ተገጭቶ ጉዳት የደረሰበትንና ካሣ የተከፈለበትን የአቶ ደረጀ ጉደታን መኪና በተመለከተ ስለሆነ ከላይ በተጠቀሰው የንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ መሠረትም የመዳረግ መብት የሚኖረው ይሆናል ማለት ነው፡፡ ሆኖም ግን የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ አመልካች የመዳረግ መብት የለውም በማለት ክሱን ሳይቀበል መቅረቱ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ ለድንጋጌው የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ወደ 2ኛው ጭብጥ ስናልፍም የመድን ሽፋን የተገባለት የተጠሪዎች መኪና ቅሪቱ ተገምቶ ብር 250 ሺህ እንደሆነ እንደዚሁም የጉዳት ካሣ ብር 92 ሺህ እንደሆነና በድምሩ ብር 342 ሺህ አመልካች ለተጠሪዎች መክፈል እንደሚገባው በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪዎች ባቀረቡት የተከሳሽ ከሣሽነት ክስ የዚህ ገንዘብ ግማሹ ብር 171

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሺህ ለወ/ሮ ለተብርሃን እንዲከፈል መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የተቋረጠ ገቢ በተመለከተም አመልካች የሚከራከረው ግራ ቀኞችን ባደረግነው ውል የተቋረጠ ገቢ እንደማይከፈል ተስማምተናል በማለት ሲሆን ነገር ግን አመልካች ጉዳት የደረሰበትን የተጠሪዎች መኪና ጠግኖ ለማስረከብ ስምምነቱን የገለጸ እንደመሆኑ መጠን ከውሉ አኳያ የተቋረጠ ጥቅም ለመክፈል የማይገደደው መኪናውን ለመጠገን አስፈላጊ ለሆነው ጊዜ (ማስጠገኑ ለሚወስደው ጊዜ) ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ መኪናው ሳይጠገን ለቀረበት ጊዜ በሙሉ ሊሆን አይችልም፡፡ በዚሁ መሠረትም መኪናውን ለመጠገን ያስፈልጋል የተባለው የ3 ወር ጊዜ በአእምሮ ግምት ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ በዚህ ጊዜ መኪናውን አመልካች ጠግኖ ለተጠሪዎች ካላስረከበ ደግሞ ተጠግኖ ቢሆን ኖሮ ሊያስገኝ ይችል የነበረውንና ነገር ግን ሳይከፈል የቀረውን የተቋረጠ ገቢ መክፈል ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተም መኪናው በቀን ብር 700 ገቢ ያስገባ እንደነበር ተጠሪዎች ገልጸው በዚሁ ልክ ካሣ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ሆኖም ግን ጉዳት የደረሰበት መኪና ይህን ያሕል ገቢ ያስገባ እንደነበር በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ ባለ ግንኙነት የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ወገን የደረሰበትን ኪሣራ /Damages/ በማስረጃ ማረጋገጥ እንደሚገባው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1790/1/ እና 2141 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና ጉዳት መድረሱ እስከተረጋገጠ ድረስ የነገሩን አካባቢ ሁኔታ ግምት ውስጥ በመክተት የካሣ መጠኑን ዳኞች በርትዕ መወሰን እንዲችሉ ሕጉ ሥልጣን የሰጣቸው እንደመሆኑ መጠን በተያዘውም ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች በክሥ የተጠቀውን የገንዘብ መጠን በበኩሉ አስልቶ እንዲከፈል ውሣኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሣ ኔ

1. አመልካች በዚህ ጉዳይ የመዳረግ መብት ስለሌለው በክስ የጠየቀው ገንዘብ ሊከፈለው አይገባም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ለንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ስለሆነ ይህንኑ ሽረን አመልካች የመዳረግ መብት አለው ብለናል፡፡

   ስለሆነም አመልካች በመዳረግ ከጠየቀው ብር 396,342 /ሶስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ሶስት መቶ አርባ ሁለት/ ላይ ግማሹን ብር 198,171 /አንድ መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰባ አንድ ብር/ ተጠሪ ወ/ሮ ለተብርሃን በየነ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
2. አመልካች በድምሩ ብር 385,200.00 /ሦስት መቶ ሠማንያ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ብር/ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ የተወሰነው የካሣ መጠን በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ አንዱ ከሌላው የሚፈልገው ገንዘብ ሲቻቻል አመልካች ብር 187,029.00 /አንድ መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ ሀያ ዘጠኝ ብር/ ለተጠሪ መክፈል የሚገባው ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወ ን ጀ ል

የሰበር መ/ቁ. 21411

ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ሐጐስ ወልዱ

2. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

3. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

4. አቶ አብዱራሂም አህመድ

5. አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዐ/ሕግ - ቀርቧል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሰይድ እንድሪስ ዩሱፍ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ነሐሴ 18 ቀን 1997 ዓ.ም ዕፎ ባቀረበው ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩ የሥር አመጣጥ ተጠሪ የወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1ሀ/ን በመተላለፍ መጋቢት 26 ቀን 1996 ዓ.ም ከምሽቱ 6፡00 ሰዓት ላይ በፖሊ ልዩ ወረዳ በዳንጉር ቀበሌ መክላክያ ካምፑ አካባቢ ሰውን ለመግደል አስቦና አቅዶ ሟች ማስተዋል አማርቸኩል የተባለችውን በእኔ ላይ ወንድ ደርባለች በሚል ምክንያት ቂም ይዞ በመነሳሳት በያዘው ክላሽንኮቭ ጠመንጃ ጭካኔበተሞላበት ሁኔታ በሶስት ጥይት ደብድቦ ገድሏል የሚል ክስ ቀርቦበት ድርጊቱ በማለስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ በተጠቀሰበት አንቀጽ መሠረት ጥፋተኛ ተብሎ በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፈርዷል፡፡ ተጠሪ በቅጣት ውሣኔው ላይ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በአብላጫ ድምፅ ቅጣቱን ወደ ሃያ አመት ፅኑ እስራት ዝቅ አድርጐለታል የክልሉ ዓቃቤ ሕግም በዚሁ የቅጣት ውሣኔ ቅር ተሰኝቶ ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በማስቀረብ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ክርክሩንም አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙን ያለመካዱን፣ ተጠሪ ድርጊቱን ቢያምንም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎቹን እንዲያቀርብ ማድረጉን እና ተጠሪም እንዲከላከል መብቱ ቢጠበቅለትም የመከላከያ ማስረጃ እንደሌለው መግለፁን አስፍሮ በቀረበው የዓቃቤ ሕገ ማስረጃ መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ ካሣለፈ በኋላ ዓቃቤ ሕግ ቅጣቱ በተጠሪው ላይ ከብዶ እንዲወሰንበት በመጠየቅ፣ ተጠሪም በበኩሉ ቀደም ሲል ሌላ ወንጀል አለመፈፀሙን እና ለ6 ዓመት በመከላከያ ሠራዊት አባልነት ማገልገሉን በመግለፅ ግራ ቀኙ የየበኩላቸውን የቅጣት አስተያየት ካቀረቡ በኋላ ፍርድ ቤቱ በአንድ በኩል ተጠሪ በመጥፎ አመል በቂመኝነትና በወራዳነት፣ ፍፁም በሆነ ፈቃደኝነትና ከፍተኛ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ሟችን አያ[[ጠ መግደሉ ጨካኝነቱን እንደሚያመለክት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ማገልገሉና የቀድሞ ሪከርድ የሌለበት መሆኑን መገንዘቡን ገልፆ ቅጣቱን ከማቅለል ይልቅ የወንጀል አፈፃፀሙ ቅጣቱ እንዲከብድ የሚያመዝን ሆኖ መገኘቱን በመግለፅ ተጠሪ በዕድሜ ክል ዕኑ እሥራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ባቀረበው ይግባኝ ወንጀሉን የፈፀመው የትዳር ጓደኛው የሆነችው ሟች በርሱ ላይ ሌላ ወንድ መደረቧ ለወንጀል ያነሣሣው መሆኑን እና በወቅቱም በስካር መንፈስ ራሱን ሊቆጣጠር የማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ መሆኑን፣ በተጨማሪም የስካር መንፈሱ እንደበረደለት በድርጊቱ ተፀፅቶ እጁን ለፖሊስ መስጠቱን ገልፆ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ድርጊቱን በደም ፍላትና በስካር መንፈስ ለመፈፀሙ ያቀረባቸው ምክንያቶች ቅጣቱን ለማቅለል የሚያስችሉ ቢሆኑም ተጠሪ ድርጊቱን በዚህ መሠረት ለመፈፀሙ ማስረጃ ያለማቅረቡን በመግለፅ ክርክሩን

ውድቅ አድርጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በመቀጠል 1. ተጠሪ ጥፋቱን አምኖ ለመንግሥት እጁን መስጠቱ 2. በሌላ ማስረጃ ባይረጋገጥም ሟች ሌላ ወንድ ደርባለች በማለት መጠርጠሩ ስሜቱን ሊነካና መረበሽንም የሚያስከትልበት ሆኖ መታሰቡና 3. ተጠሪ አስካሁን ባሉት ክርክሮች የወንጀል ድርጊቱን አምኖ መፀፀቱን ስለሚያመለክት በወ/መ/ሕ/ቁ. 79/1/መ/ እና /ሠ/ እንዲሁም 184/መ/ መሠረት ከመነሻው እድሜ ልክ በመፍረድ ቅጣቱን ወደ 20 አመት ዝቅ አድርጓል፡፡

በመሆኑም በተጠሪ ላይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነው የእድሜ ልክ ፅኑ እሥራት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሻሽሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅጣትን ለማቅለል ከተጠቀመባቸው ሦስት ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ማለትም ተጠሪ ድርጊቱን ከፈፀመ በኋላ እጁን ለመንግሥት መስጠቱ መፀፀቱን ያመለክታል በማለት እና እስካሁን በተካሔዱት ክርክሮችም ተጠሪ ድርጊቱን አምኖ ቅጣቱ ብቻ ይቀነስልኝ ማለቱም በተመሳሳይ ሁኔታ ፀፀትን ያመለክታል በማለት የጠቀሳቸው ምክንያቶች ተቀባይነት ያላቸው ሆነው አልተገኙም ለማለት አልተቻልም፡፡ ምክንያቱም በ1996 ዓ.ም በወጣው አዲሱ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 82/1/መ/ ላይ ወንጀለኛው ወንጀሉን ካደረሰ በኋላ በእውነት የተፀፀተ መሆኑን ለማስረዳት ጥፋቱን በመገንዘብ ራሱን ለፍትሕ አካላት ካቀረበ፣ በክስ ማመልከቻው የተገለፀውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ካመነ ቅጣቱ እንደሚቀልለት ተደንግጓል፡፡ ምንም እንኳን ተጠሪ ድርጊቱን በፈፀመበት ወቅት ተፈፃሚው ሕግ የቀድሞው የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቢሆንም ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ውሣኔ በተሰጠበት ሰኔ 13 ቀን 1997 ዓ.ም አዲሱ የወንጀል ሕግ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ በመሆኑና በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 ሥር አዲሱ ሕግ ከፀና በኋላ በሥራ ላይ ከነበረው /ከቀድሞው/ የወንጀል ሕግ ይልቅ አዲሱ ሕግ ቅጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያቀል ከሆነ በዚሁ ሕግ መሠረት ቅጣቱ እንደሚቀል የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ ድርጊቱን ከፈፀመ በኋላ እጁን ለመንግሥት መስጠቱና የቀረበበትንም ክስ ገና ከመነሻው ጀምሮ አምኖ መገኘቱ የቅጣት ማቅለያ ተጠቃሚ የሚያደርገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለዚህ ከላይ የተመለከቱት 3 ምክንያቶች ቅጣቱን ለማቅለል የሚያስችሉ በመሆናቸው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ው ሣ ኔ

- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 647 ሰኔ 13 ቀን 1997 ዓ.ም በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
- ውሳኔው መፅናቱን እንዲያውቁት የውሣኔው ግልባጭ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ለተጠሪ በየአድራሻቸው ይድረሳቸው፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ. 22069

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

አቶ ተገኔ ጌታነህ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የአማራ ብ/ክ/መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ አቶ ደረጀ ኃይሉ

ተጠሪ፡- አስማማው አራጌ - ከጠበቃ ወ/ሮ አዜብ ፋንታሁን ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበው ተጠሪው በፈጸመው የወንጀል ድርጊት በሥር ፍ/ቤት ጥፋተኛ የተባለበት የወ/መ/ህ አንቀጽ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት መለወጡ አግባብ አይደለም ሲል አመልካች ህዳር 14 ቀን 1998 ዓ.ም አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የሰበር ችሎትም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የተጠቀሰውን የሕግ አንቀጽ ለመቀየር ሕጋዊ ምክንያት የነበረው መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ግራ ቀኙን አስቀርቦ አከራክሯል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት ውሳኔ መረዳት እንደተቻለው ለከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ተጠሪ ሚችን /ሚስቱ የነበረችውን ገነት ገበዬን/ ጨካኝና ነውረኛ በሆነ አኳኋን በመግደሉ በወ/መ/ህግ አንቀጽ 522/1/ሀ/ አመልካች መስሪያ ቤት ክስ አቅርቦ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከተጠሪው የወንጀል አፈጻጸም አኳያ በተጠቀሰው የወንጀል ሕግ አንቀጽ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ በሃያ /20/ ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ፈርዶበታል፡፡ በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ በማቅረቡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የወንጀሉን አፈጻጸም መነሻ ምክንያትና ሁኔታ በመዘርዘር ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል በወ/መ/ህ አንቀጽ 523 መሠረት ጥፋተኛ በማለት በዚሁ መሠረት በአሥራ ሦስት /13/ ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ ይህ ፍርድ በመሠረቱ የሕግ ስሕተት አለው ሲል አመልካች ያቀረበው አቤቱታ የተጠሪ የወንጀል አፈጻጸም በወ/መ/ህ አንቀጽ 522/1/ሀ/ ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ሳለ ወደ 523 ለመለወጥ የሕግ መሠረት የለውም የሚል ነው፡፡

ከዚሁ አኳያ የሰበር ችሎቱ መዝገቡን መርምሯል፡፡ በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሐተታ እንደተመለከተው ሐምሌ 16 ቀን 1994 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ላይ ተጠሪና ሟች መኖሪያ ቤት ውስጥ ሆነው ተጠሪ የመኖሪያ ቤታቸውን በር ከዘጋ በኋላ ሟችን በበር መቀርቀሪያ ግንባሯን መትቷት በወደቀችበት ቦታ ሁለት እጆቿን በማሰር ብልቷ ውስጥ እጁን በማስገባት ከባድ ጉዳት እንዳደረሰባት እና በዚሁ ምክንያት ሐምሌ 23 ቀን 1994 ዓ.ም ሕይወቷ እንዳለፈ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህንን የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ የድርጊቱ አፈጻጸም የተጠሪን ጨካኝነት እና ነውረኛነት ያረጋግጣል በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ለመለወጥ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ያስቀመጠው ምክንያት “የተጠሪው ድርጊት ዘግናኝ ቢሆንም ሟችን ለመግደል አስቀድሞ ያሰበና የተዘጋጀ ለመሆኑ አልተረጋገጠም” የሚል ነው፡፡ ይህንን የጠቅላይ ፍ/ቤቱን አቋም ከወ/መ/ህግ አንቀጽ 522 ይዘት አንፃር መመርመር አግባብነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ሕግ የሀሳብ ክፍል የሚረጋገጠው ከወንጀል ድርጊት አፈጻጸም መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የተጠሪ የወንጀል አፈጻጸም በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 522/1/ሀ/ ሥር በተመለከቱት ሁኔታዎች ውስጥ እንዲወድቅ ያደረገው ድንጋጌው “አስቀድሞ ማሰብን” እንደዋነኛ ምክንያት ወይም ብቸኛ ምክንያት የተመለከተ አለመሆኑ ነው፡፡ በዚህ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ከባድ የግፍ አገዳደል ወንጀል መፈጸሙን ለማረጋገጥ ወይም ለማቋቋም የሚታዩት ሁኔታዎች በአማራጭ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች መሆናቸው እንጂ አንዱ ከሌላው ጋር በተደራራቢነት እና በጋራ የሚታዩ ጉዳዮች መሆናቸው አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም የተጠሪን የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው በመጀመሪያ በቀን የመኖሪያ ቤቱን በር በመዝጋት በሟች ጩኸት የአካባቢው ሰው ደርሶ እንዳያስጥለው ማድረጉ፣ ሟች ራሷን እንዳትከላከል በገመድ እጇን ወደ ኋላ ማሰሩ፣ እንዲሁም ሟችን በበር መቀርቀሪያ ግንባሯን መትቶ ከጣላት በኋላ ብልቷ ውስጥ እጁን በመክተት እጅግ ከፍተኛ ለሆነ ጉዳት መዳረጉ ሲታዩ ተጠሪው የድርጊቱ ውጤት ይህንን እንዲያስከትል የፈለገ መሆኑንና አስቀድሞ ማሰቡን የሚያመለክቱ ከመሆናቸውም በላይ በሚስቱ የመዋለኛ አካል ላይ የዚህ አይነት ድርጊት መፈጸሙ ነውረኛ እና ጨካኝ መሆኑን በማያጠራጥር ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው የተጠሪ የሀሳብ ሁኔታ ከድርጊቱ በመነሳት የሚገመት መሆኑ እንዳለ ሆኖ የድርጊቱ አፈጻጸም በራሱ እጅግ ጨካኝና ነውረኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህም ባሻገር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ውሳኔውን ለማሻሻል መሠረት ያደረገው ሁኔታ የተጠሪን “የስንፈተ ወሲብ” ችግር ሕብረተሰቡ ከሚያደርስበት ተፅኖ አንፃር በማየት እንደሆነ በውሳኔው ተመልክቷል፡፡ ይህም ሁኔታ የተጠሪው የተፈጥሮ ችግር ቢኖር እንኳ ጋብቻቸውን ከማፍረስ አልፎ የሟችን ሕይወት ለማጥፋቱ እንደተገቢ ምክንያት ተደርጎ መወሰዱ አግባብነት የለውም፡፡ ባጠቃላይ የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም በማስረጃ በማጣራት አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 522 /1/ ሀ ሥር የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ቅጣት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በቂ የሕግ ምክንያት ሳይኖረው መቀየሩ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 05312 ጥቅምት 6 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ጐንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር ወ/00320 በጥቅምት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔውን እንዲያውቁት ይፃፍ፡፡
4. የዞኑ ማረሚያ ቤቶች በዚህ ፍርድ መሠረት እንዲያስፈጽሙ ይፃፍ፡፡
5. መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ት ሂሩት መለሰ
አቶ ፀጋዬ አስማማው
አቶ በላቸው አንሺሶ
አቶ አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አማምነው ገ/መስቀል - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ሊቀረብ የቻለው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በከሣሽ የአሁኑ አመልካችና በተከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ መካከል የነበረውን በግፍ ሰው የመግደል እና በግፍ ሰው የመግደል ሙከራ የወንጀል ክርክር የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በወ/መ/ቁ. 258/94 ግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪን በግፍ ሰው የመግደል ወንጀል በቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበበት ድንጋጌ፣ በግፍ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ደግሞ በዓቃቤ ሕግ በኩል የተጠቀሰበትን ድንጋጌ ዝቅ በማድረግ ተራ በሆነ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል በሚያስጠይቅ ድንጋጌ ጥፋተኛ ከአደረገው በኋላ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የወሰነውን ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ይኸው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ ያደረገባቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን ዝቅ በማድረግ ቅጣቱን በተመለከተም ተጠሪን የሚያርመው ተመጣጣኝ ቅጣት የ8/ስምንት/ ዓመት ጽኑ እስራት ነው በማለት በመወሰኑ ይኸው ውሣኔ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለባቸው የሕግ አንቀጾችም ሆኑ የቅጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አወሣሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያሣያል በማለት የአሁኑ አመልካች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ስህተት የለበትም በማለት ውሣኔውን በማጽናቱ ነው፡፡

አመልካች በቁጥር 05/I/A-11/1120 በቀን 20/04/98 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የተጠሪ አድራጉት በስር ፍ/ቤት ጥፋተኛ በተባሉባቸው ድንጋጌዎች የሚሸፈን ሆኖ እያለ ውሣኔ የተሰጠበት የሕግ አንቀጽ መለወጡ አግባብነት ስለሌለው ተስተካክሎ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጉም ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መልሱን ሰጥቷል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከበታች ፍ/ቤቶች የውሣኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የም ራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ ያደረገባቸውን የህግ አንቀጾች የለወጠው በአግባቡ /በሕጉ ረገድ/ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ተጠሪ በወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ሀ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በክሱ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ሟች ባለቤቱን፤ ወ/ሮ ዝናሽ ለማ የተባለችውን ሕፃን ልጅ ወልዳ አራስ ቤት በተኛችበት ስፍራ ማካሮቭ ሽጉጥ ተኩሶባት አናቷ ላይ ሁለት ቦታ መቷት ለህልፈተ ህይወት ዳርጓታል፤ በወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 522/1/ሀ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ደግሞ በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ከሟች ዝናሽ ለማ ጋር እንዳይጣላ ሰዎች ጣልቃ ገብተው ለማለያየት ሊገላግሉ ሲሉ እናንተ ነገ ምስክሮች ትሆኑብኛላችሁ አይደል? በማለት ማካሮቭ ሽጉጡን በመተኮስ የግል ተበዳይ የሆኑትን 1ኛ/

ወ/ሪት እስከዳር ጋሻውን በሁለት ጥይት ከፊቷ ላይ መቷት አንዱ ጥይት ከአንገቷ በስተኋላ ሲወጣ አንዱ ጥይት ደግሞ ከአንገቷ ስር በሰውነቷ ውስጥ የቀረ በመሆኑ፤ 2ኛ/ ወ/ሪት መና መሐመድ በምትባለው ላይም አንድ ጥይት ተኩሶባት በመሸሸዋ ህይወቷ መትረፍ የቻለ መሆኑን በመግለጽ በግፍ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ክስ በአመልካች በኩል ቀርቦበት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪን የመከላከያ ማስረጃ የአቃቤ ሕግን ማስረጃዎች አያስተባብልም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጐ ተጠሪን በወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ሀ/፣ 522/1/ሀ/ እና 523 ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ አድርጓል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ግን በተጠሪ ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተቀበለ በኋላ አድራጉቶቹ የሚሸፈኑባቸው ድንጋጌዎች ግን የስር ፍ/ቤት የጠቀሣቸው አለመሆናቸውን በመግለጽ አግባብነት አላቸው ወደአላቸው ድንጋጌዎች ለውጦ ተጠሪን ጥፋተኛ አድርጓል፡፡ ይህ ችሎት ለሕግ አንቀጾቹ መቀየር ዋነኛ ምክንያት አድርጐ የያዘው ተጠሪ በወቅቱ በ1ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ተሰድቧል የተባለው የስድብ ዓይነት ሲታይ ለወንጀል ድርጊቶቹ ቅድመ ዝግጅት እና ማነሣሣት፣ የክፋትና የጭካኔ ስሜት በሚያሣይ ሁኔታ ሣይሆን በምስክር ድርጊት የተነሣ በንዴት፣ ስሜት ውስጥ በመግባት እራሱን መቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ሁኖ ነው የሚለውን ነጥብ ነው፡፡

በመሰረቱ የሰው ግድያ ወንጀል በወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ መሰረት አንድን ሰው የሚያስጠይቀው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በመዘጋጀት ሲፈፀም ወይም በቁጥር 81 ወይም በቁጥር 83 የተመለከቱት አክባድ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ስለመሆኑ በተጠቃሹ አንቀጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚሁ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለውም ለወንጀሉ ማቋቋሚያ የተጠቀሱት ነጥቦች “... ወይም...” በሚል ቃል ተያይዘው የተዘረዘሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆናቸውንና ምክንያቶቹም ወንጀሉን ለማቋቋም በአንድነት ተጣምረው መገኘት ሣያስፈልጋቸው በራሣቸው ቁመው የወንጀሉ ማቋቋሚያ ሊሆኑ የሚችሉ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ቅድመ ዝግጅት እና የክፋትና የጭካኔ ስሜት ተጣምረው የመገኘት ሁኔታ የወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ ድንጋጌ ብቸኛ የወንጀሉ መቋቋሚያ ነጥቦች አይደሉም፡፡ ይልቁንም በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሣቸው መቆም የሚችሉ ናቸው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ባለቤቱን ለመግደል የ1ኛዋ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ስድብ እንደምክንያት የማይወሰድ መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ያመነበት ጉዳይ ሆኖ የምስክሯ አድራጐት ግን የተጠሪን የክፋትና የጭካኔ ስሜት በሚያሣይ ሁኔታ እራሱን በማዘጋጀትና በማነሣሣት ለመሆኑ አያሣይም በሚል ተደምድሟል፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው ድምዳሜ ፍ/ቤቱ የምስክሯ አድራጐት ባለቤትን ለመግደል ምክንያት ሊሆን አይችልም ብሎ ከተነሣበት ነጥብ ጋር የሚጋጭ ነው ከመባሉ በተጨማሪ የወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሣቸው ሊቆሙ የሚችሉ መሆናቸውን ያላገናዘበ ነው፡፡ ሟች በወቅቱ ወልዳ የተኛች አራስ ከመሆኗም በተጨማሪ በወቅቱ ያደረገችው ምንም አራጐት የሌለ ሆኖ ተጠሪ ለሕልፈት የዳረጋት ግንባሯ ላይ በሁለት ጥይት በመምታት መሆኑ ሲታይ የተጠሪን የጭካኔ እና የክፋት ስሜት በግልጽ የሚያሣይ ነው፡፡ ድርጊቱ የተፈፀመው በውድቅት ሌሊት የጦር መሣሪያን በመጠቀም በወቅቱ አራስ በመሆኗ ልዩ ድጋፍ በሚያስፈልጋትና እንስት መሆኗ ሲታይም አድራጐቱ በቁጥር 81(1)(ሐ) እና (ሠ) ስር እንደተመለከተው በወ/መ/ሕ/ቁ. 522(1)(ሀ) ስር የሚሸፈን መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ተጠሪ አድራጐቱን የፈፀመው ማንነቱን ተቀብላ አብራው በመኖር ሁለት ልጅ በወለደችለት ባለቤቱ ላይ መሆኑ ከወ/መ/ሕ/ቁ. 83 አኳያ ሲታይ አክባጅ ምክንያት መኖሩን የሚያሣይና በግፍ ሰው የመግደል

አድራጐትን የሚያቋቁም ነው፡፡ በ1ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ተነገረ የተባለው ስድብ በማናቸውም መመዘኛ አራስ የሆነችን የትዳር አጋር በክፋትና በጨካኝነት መንፈስ ለሕልፈተ-ሕይወት ለመዳረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ሊባል አይችልም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በባለቤቱ ላይ የፈጸመው ግድያ ከቁጥር 81(1)(ሐ እና ሠ) እና ከቁጥር 83 ድንጋጌ አኳያ ሲታይም በግፍ መግደሉ ተረጋግጦ እያለ ለዚህ አድራጐት አግባብ ተብሎ በወ/መ/ሕ/ቁ. 523 ስር ጥፋተኛ መባሉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል በ2ኛው ክስ ለተጠቀሰው አድራጐት አግብብነት አለው የተባለው የወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 524/ለ/ ሲታይ ከምስክሯ አድራጐትና ከነባራዊው ሁኔታ አኳያ ሲመዘን ባግባቡ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አልተገኘም፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ በባለቤቱ ላይ ለፈፀመው የግድያ ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባው በወ/መ/ሕ/ቁ. 522(1)(ሀ) ሲሆን በ2ኛው ክስ በተጠቀሱት የግል ተበዳዮች ላይ ለፈፀመው አድራጐት ደግሞ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተለወጠው ድንጋጌ መሠረት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ይህ የሚያስገነዝበው ደግሞ ተጠሪ በዚህ ችሎት ጥፋተኛ የተባለው የበታች ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ውሣኔ የሰጡባቸው ድንጋጌዎች መሻሻላቸውን ነው፡፡

እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በዚህ ችሎት ጥፋተኛ በተባለባቸው ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡ በአጥፊ ላይ ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወ/መ/ሕ/ቁ. 86 ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ችሎቱም እነዚህን ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም፡፡ ተጠሪ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ፣ ብዙም ባለመማሩ የእውቀት ማነስና የመንፈስ ልልነት ያለበት መሆኑ እና የኋላ ታሪኩ ሲታይም መልካም የነበረ መሆኑ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዙለት የሚገቡ መሆኑን ከወ/መ/ሕ/ቁ. 86 እና 79(1)(ሀ) ድንጋጌዎች ተገንዝበናል፡፡ እነዚህን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያቶች መሰረት ስናደርግ ደግሞ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት የመጀመሪያው ክስ ድንጋጌ ያስቀጣው የነበረው እድሜ ልኩን ሁኖ በወ/መ/ሕ/ቁ. 184/ለ/ መሰረት መጠኑ መቅለል ያለበት መሆኑን ተገንዘብናል፡፡

ሲጠቃለልም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ባለቤቱን በመግደሉ ሊጠየቅ የሚገባው ድንጋጌ ተራ የሰው ግድያ ወንጀል በሚያስጠይቅበት ማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የተጠሪ አድራጐት በግፍ ሰው መግደል የሚሸፈንና የቅጣቱ መጠንም ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሰረትም የሚከተለው ተወስኗል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 258/94 ግንቦት 19 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 02316 የካቲት 15 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ እንዲሁም የዚሁ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 11541 ጥቅምት 07 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሰረት አሻሽለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ በ1ኛው ክስ ለተጠቀሰው ድርጊት ጥፋተኛ የተባለበትን ድንጋጌ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 113/2/ መሰረት በመለወጥ በወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ በ2ኛው ክስ ለተጠቀሰው ድርጊት በወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 524/ለ/ ስር ጥፋተኛ መባሉ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡

4. ተጠሪ ለጉዳዩ የታሰረበት ጊዜ የሚታሰብለት ሁኖ ሊቀጣ የሚገባው በ20/ሃያ/ ዓመት ጽኑ እስራት ነው ብለናል፡፡
5. ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማረሚያ ቤቱ ይፃፍ፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 22514

መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

2. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

3. አቶ ታፈሰ ይርጋ

4. አቶ ዓሊ መሐመድ

5. አቶ ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- 1ኛ/ አቶ ኩራት ተገኘ

2ኛ/ አቶ መርሻ ኩራት

ተጠሪ፡- ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ጥፋተኝነትንና ቅጣትን የተመለከተ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው ተጠሪ /ዓቃቤ ሕግ/ በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ በመሠረተው ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በአጭሩ የአሁን አመልካቾች በቂም በቀል ተነሣስተው ሰው ለመግደል በማሰብ ጌጡ ተስፋው እና ብርሌ ባላምባራስ የተባሉ የግል ተበዳዮችን ራስ ራሳቸውን በድንጋይና በዱላ ከደበደቧቸው በኋላ 1ኛ ተከሣሽ በያዘው አጭር አልቤን መሣሪያ አንድ ጥይት ተኩሶ 2ኛ የግል ተበዳይን የግራ ፊቱን በማቁሰሉ በፈፀሙት በግብረ-አበርነት ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በዓቃቤ የቀረበውን የሰውና የሕክምና ማስረጃ ሰምቶ ተከሳሾች መከላከል ሳያስፈልጋቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 141 መሠረት በነፃ ያሰናበታቸው ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዓቃቤ ሕግ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ተከሣሾች በአቃቤ ሕግ ምስክሮች የተመሰከረባቸው ስለሆነ በተመሰከረባቸው መጠን ሊከላከሉ ይገባል፣

በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የተከሣሳሾችን የመከላከያ ማስረጃ በመስማት የመሰለውን ይወስን በማለት ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት መለሰው፡፡

ጉዳዩ የተመለሰለት ፍ/ቤትም የመከላከያ ምስክሮቹን አዳምጦ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል በመከላከያ ምስክሮቹ ቃል ስላልተስተባበለ ተከሳሾች /የአሁን አመልካቾች/ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ናቸው፣ ስለሆነም እያንዳንዳቸው በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወሰነ፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ቅሬታውን ባለመቀበል ፍርዱን አጸንቶታል፡፡

የሰበር አቤታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር አመልካቾች ፈፀሙት በተባለው አስቀድሞ በማሰብ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ የተባሉት በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡

አመልካቾች የተከሰሱትም ሆነ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡት አስቀድሞ በማሰብ ወይም ምክንያት በማድረግ ሰው የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ነው፡፡ ምንም እንኳ በዓቃቤ ሕግ በምስክርነት የተቆጠሩት የግል ተበዳዮች ድርጊቱ የተፈፀመው በድንበር ግጭት ምክንያት የአሁኖቹ አመልካቾች ቂም በቀል ይዘው ነው የሚል የምስክርነት ቃል ስለመስጠታቸው በስር ፍ/ቤት የውሣኔ ሐተታ ላይ የተመለከተ ቢሆንም ይህ አባባል ከእነሱ ቃል በስተቀር በሌላ ገለልተኛ ማስረጃ ተደግፎ አለመገኘቱን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዓቃቤ ሕግ የቀረበው የሰውና የሕክምና ማስረጃ ያረጋገጠው ነገር በግል ተበዳዮች ላይ "የአጥንት ስብራት የሌለበት ቀላል እብጠትና ደም ያለው ምልክት" መሆኑ ታውቋል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ተፈፀመ የተባለው ተግባር ተራ የሆነ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ይህ ችሎት አምኖበታል፡፡ በመሆኑም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 113/2/ መሠረት አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበትን የወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 522/1/ሀ/ በመለወጥ አመልካቾች በወ/መ/ሕ/ቁ. 27/1/ እና 523 መሠረት ጥፋተኞች ናቸው ብለናል፡፡

አመልካቾች የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪከርድ የሌለባቸው መሆኑን ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በመረዳት በወ/መ/ሕ/ቁ. 86 ላይ የተደነገገውን ከግምት አስገብተን አመልካቾች እጃቸው ከተያዘ ጊዜ ጀምሮ በ5 ዓመት /አምስት ዓመት/ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በ8/11/97 በመ/ቁ. 00665 የሰጠው ውሣኔ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በ30/3/98 በመ/ቁ 07247 የፀናው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
- ውሣኔው መሻሻሉን እንዲያውቁት የውሣኔው ግልባጭ ለፍርድ ቤቶቹ ይተላለፍ፣
- ውሣኔው የተሻሻለ መሆኑን አውቆ በተሻሻለው ውሣኔ መሠረት እንዲያስፈጽም የውሣኔው ግልባጭ እስረኞቹ ለሚገኙበት ማረሚያ ቤት ይተላለፍ፣
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ.ቁ. 23855

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ ሙሉእመቤት ውብአየሁ

ተጠሪ፡- አቶ ፀጋሁን መንግሥቱ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ከመ.ቁ. 23523፣ 24021፣ 23533፣ 23532፣ 23522፣ 23527፣ 24020፣ 23531፣ 23534፣ 23530፣ 23820፣ 23710፣ 27500፣ 23529፣ እና 23528 ጋር በተመሣሣይ የሕግና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ተመስርቶ የቀረበ ስለሆነ ሁሉም መዛግብት ጎን ለጎን ተመርምረው ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በተለያዩ የወንጀል መዛግብት ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 74 የተመለከተውን በመተላለፍ ምንም ዓይነት የጉምሩክ ሥነ - ሥርዓት ሣይፈፀምበት የመንግሥት ቀረጥ ያልተከፈለበትን መኪና ይዘው የተገኙ ስለሆነ በፈፀሙት ሕገወጥ ዕቃ ይዞ መገኘት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ክስ አቅርቦ ፍ/ቤቱም በእያንዳንዱ የወንጀል መዝገብ የከሣሽን ማስረጃ ሰምቶ ተከሣሾች በየበኩላቸው ይዘው ተገኝተዋል የተባሉትን መኪናዎች በሕጉ ላይ አንደተመለከተው እያወቁ ይዘው ስለመገኘታቸው በከሣሽ ማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 141 መሠረት ተከሣሾች መከላከል ሣያስፈልጋቸው በነፃ እንዲሰናበቱ ብይን በመስጠቱና በዚሁ ብይን ላይ የቀረበው ይግባኝ በፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ተቀባይነት ሣያገኝ በመቅረቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታም ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት መኪና በግለሰብ እጅ መገኘቱ ሕገወጥ በመሆኑ የተያዙት መኪናዎች ሊወረሱ ወይንም ቀረጥና ታክስ ሊከፈልባቸው እንደሚገባ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው መደንገጉ እየታወቀ የበታች ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ ምንም ሣይሉ ማለፋቸው ከፍተኛ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ከሕጉ አኳያ ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባ በማመኑ በየመዝገቡ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ተጠሪዎችም በየበኩላቸው ያቀረቡት ክርክር ተጠቃሎ ሲታይ አመልካች የመኪናዎቹን መወረስም ሆነ የቀረጥ ክፍያን አስመልክቶ የሚያቀርበው ክርክር በወቅቱ በሥራ ላይ ከነበረው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 74 ድንጋጌ ውጪ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ ተከሣሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ባይገኝም ንብረቱ እንደሚወረስ ወይንም ቀረጥና ታክስ እንደሚከፍል አልተደነገገም፡፡ አመልካች አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት መኪና ሊወረስ ወይንም ቀረጥና ታክስ ሊከፈልበት እንደሚገባ የተደነገገ መሆኑን ገልጾ ቢከራከርም የአዋጁ ማሻሻያ ወደኋላ ተመልሶ ሊሰራ ስለማይችል አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ ያቀረበባቸው ከላይ እንደተጠቀሰው በአዋጅ ቁጥር 60/89 በአንቀጽ 74 ላይ የተመለከተውን

በመተላለፍ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመባቸውን መኪናዎች ይዘው የተገኙ ስለሆነ በፈፀሙት ወንጀል ተከሰዋል በማለት ነው፡፡

በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሣሽ የእቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊከፈል ከሚገባው ጠቅላላ የቀረጥ ሂሣብ በማያንስ የገንዘብ መቀጮና ከ3-5 ዓመት በሚደርስ እሥራት እንደሚቀጣ በድንጋጌው ላይ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆኑት መኪናዎች ተገቢው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዳልተፈፀመባቸውና ቀረጥና ታክስም ያልተከፈለባቸው መሆኑን ከማስረዳት በስተቀር በሕጉ ላይ እንደተመለከተው ተከሣሾች በይዞታቸው ሥር የሚገኙት መኪናዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዳልተፈፀመባቸው እያወቁ ይዘው ስለመገኘታቸው ባለማስረዳቱ ተከሣሾች ከቀረበባቸው የወንጀል ክስ መከላከል ሣያስፈልጋቸው በብይን በነፃ ተሰናብተዋል፡፡

አመልካች ክሱን ያቀረበው ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 74 መሠረት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመኪናው መወረስም ሆነ የገንዘብ ቅጣትና እሥራት ሊወሰን የሚችለው ተከሣሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡

በሌላ በኩልም ይሄው አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 388/95 የተሻሻለ ሲሆን በዚህ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 385/95 አንቀጽ 80(3) መሠረት በወንጀል የተከሰሰው ግለሰብ ከወንጀሉ ክስ በነፃ የተሰናበተ ቢሆንም እንኳን እቃው ወይም ማጓጓዣው የጉምሩክ ሕግን የሚፃረር ስለመሆኑ የቀረበው መረጃ አጥጋቢ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቱ ንብረቱ እንዲወረስ ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል ወይንም ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ትእዛዝ በመስጠት እቃው ወይም ማጓጓዣው ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰው እንዲመለስ እንደሚያደርግ ተመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ረገድ ተጠሪዎች የሚከራከሩት የአዋጁ ማሻሻያ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ አይችልም በማለት ነው።

በእርግጥ የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ እንደማይሰራ በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 22 እንደዚሁም በወንጀለኛ መቅጫ ሕጋችን በአንቀጽ 5 ላይ ተመልክቷል።

ይሁንና የጉምሩክ ሥነ - ሥርዓት ያልተፈፀመበት ንብረት እንዲወረስ ወይንም ቀረጥና ታክስ እንዲከፈልበት በተሻሻለው አዋጅ ላይ መካተቱ የዚህ ዓይነት ግዴታ መሠረት በቀጥታ ከግብር ሕግ የመነጨ ግዴታ እንጂ ከወንጀል ሕግ የመነጨ ኃላፊነት ባለመሆኑ የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ አይሰራም በሚለው የወንጀል ሕግ መርህ ሥር የሚሸፈን አይሆንም።

ከዚህም በተጨማሪ የተሻሻለው አዋጅ የፀናው ከጳጉሜ 1 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን አመልካች በእያንዳዱ ተጠሪ ላይ የወንጀል ክሱን የመሠረተው አዋጁ ከፀና በኋላ በተወሰኑት ላይ በ1996 ዓ.ም በተወሰኑት ላይ ደግሞ በ1997 ዓ.ም ነው። አመልካች የመሠረተው በዋናነት የወንጀል ክስ እንደመሆኑ መጠን መጥቀስ የሚጠበቅበት ወንጀል ነው የተባለው ተግባር ተፈፀመ በተባለ ጊዜ በሥራ ላይ የነበረውን ድንጋጌ እንደሆነ ይታመናል። በሌላ በኩልም የንብረቱን መወረስም ሆነ የቀረጥና የታክስ ክፍያን አስመልክቶ ተሻሽሎ በወጣው ሕግ ላይ የተመለከተው ከወንጀል ኃላፊነት ተነጥሎ መታየት የሚገባው እንደመሆኑ መጠን ከወንጀሉ ክስ ጋር ተያይዞ የቀረበ ቢሆንም ክሱ በቀረበ ጊዜ አዋጁ በሥራ ላይ እስከዋለ ድረስ በዚሁ በተሻሻለው አዋጅ መሠረት ክርክሩ እልባት እንዲያገኝ ቢደረግ ሕጉ ወደ ኋላ ተመልሶ ሠርቷል የሚያሰኝ አይሆንም። ከዚህም ከተሻሻለው ሕግ አኳያ ክርክሩ ሲታይ በተጠሪዎች እጅ የነበሩት ተሽከርካሪዎች ቀረጥ ያልተከፈለባቸው መሆናቸውን አመልካች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረባቸው ማስረጃዎች በአጥጋቢ ሁኔታ የሚያረጋግጡ እንደመሆናቸው መጠን

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚሁ በተሻሻለው አዋጅ መሠረት ለጉዳዩ ዕልባት አለመስጠታቸው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም።

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 34003፣ 52056፣ 51818፣ 33863፣ 33867፣ 33868፣ 33864፣ 34000፣ 34007፣ 34001፣ 33937፣ 34008፣ 33862፣ 33933፣ 33858፣ 33865 እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 31745፣ 31625፣ 31104፣ 31063፣ 31698፣ 31619፣ 31068፣ 31621፣31101፣3777፣31623፣ 31103፣ 31624፣ 31776፣ 42070፣ እና 45618 የሰጧቸው ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348 (1) መሠረት ተሽረዋል።
2. በተጠሪዎች ይዞታ ሥር የነበሩት ተሽከርካሪዎች አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመባቸው መሆናቸው አመልካች ባቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ተጠሪዎች ለመንግሥት መክፈል ያለበትን ቀረጥና ታክስ በመክፈል መኪናዎቹን እንዲረከቡ ቀረጥና ታክስ ካልከፈሉም መኪናዎቹ እንዲወረሱ በአዋጅ ቁ. 388/95 አንቀጽ 80 (3)(ሀ) እና (ለ) መሠረት ተወስኗል።
3. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሣኔ ከላይ በተጠቀሱት መዝገቦች ላይ ተፈፃሚነት ስላለው የውሣኔው ግልባጭ በእያንዳንዱ መዝገብ ላይ እንዲያያዝ ታዟል።
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 24278

ጎዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. ወ/ት ሒሩት መለሠ

5. አቶ ታፈሠ ይርጋ

አመልካች፡- ሰለሞን ሄርጃቦ

ተጠሪ፡- የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሥ/ፀ/መ/ኮ/ዐ/ሕግ

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የጀመረው በሃዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በመሠረተው ክስ አመልካች በሥራው አጋጣሚ እጁ የገባውን ያልተሠራበት አንድ ጥራዝ የገቢ መሠብሠቢያ ደረሰኝ በመሰወር የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት አ/ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ን በመጥቀስ ክስ አቅርቧል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ያስረዳሉ ያላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ አመልካች ክሱን እንዲከላከል በተሠጠው ብይን መሠረት መከላከያ አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካቹ በተጠቀሰበት አንቀጽ ጥፋተኛ ነው በማለት በ6 ዓመት እስራትና በ200 ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤትም በአመልካች የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ባለመቀበል የሠረዘው ሲሆን የክልሉ ሠበር ችሎትም ውሣኔው የሕግ ስህተት የለበትም ብሏል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም አመልካች ፈፀመ የተባለው ድርጊት በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ ድንጋጌ የሚሸፈን ነው ወይ? የሚለውን ለመመርመር

ሲል ተጠሪ እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል፡፡ መዝገቡንም መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው አመልካች የሶሮ ወረዳ የፋይናንስ ጽ/ቤትን ለመመርመር በሄዱበት ወቅት ንብረት ክፍሉን ሲመረምሩ በሥራቸው አጋጣሚ በእጃቸው የገባውን የገቢ ደረሠኝ ሠውረው የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ነው፡፡

በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ መሠረት የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ሊሆን የሚችለው እንዲጠብቃቸው በአደራ የተረከባቸውን ወይም በሥራው አጋጣሚና ምክንያት በእጁ የገቡትን ንብረቶች የወሠደው ወይም የሰወረው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማገኘት በማሠብ ከሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሠረት ወንጀል ተፈጽሟል ሊባል የሚችለው በሥራ አጋጣሚ በእጅ የገባው ንብረት በመጥፋቱ ብቻ ሣይሆን ንብረቱ እንዲጠፋ የተደረገው ያለአግባብ ለመበልፀግ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማስገኘት በማሠብ ጭምር ከሆነ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የአጥፊው ሃሣብ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የገቢ ደረሠኞቹን የሠወረ መሆኑ ቢረጋገጥም ሠነዱን የሠወረው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ ሆነ ብሎ የፈፀመው ድርጊት መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ይህ የሃሣብ ክፍል መኖሩ ሣይረጋገጥ ሠነዱ በመጥፋቱ ብቻ አመልካቹ በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ ሥር በተመለከተው መሠረት የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተሠጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ት ዕ ዛ ዝ

1. የሃዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. ዐዐ261 በ11/12/96 የሠጠው ውሣኔ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 7406 በ02/01/98 የሠጠው ውሣኔ እንዲሁም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 11605 በ25/05/98 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በተከሠሠበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ አይደለም፡፡
3. አመልካች ሌላ የታሠረበት ጉዳይ ከሌለ እንዲፈታ ለማረሚያ ቤቱ የመፈቻ ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ.28952

መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ - ሙሉአመቤት ውባየሁ

ተጠሪ፡- አቶ ባንቲ ታኤራ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተጠሪ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 122(2) መሰረት ካነሳ በኋላ በድጋሚ ክስ ሊያቀርብ አይችልም በማለት ድጋሚ የቀረበውን ክስ የሥር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉት በመቅረታቸው ነው፡፡

ይህ ችሎትም የቀበረውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የቀረበው የወንጀል ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 122(2) መሰረት ለጊዜው ተቋርጧል ተብሎ ከታዘዘ በኋላ አቃቤ ሕጉ ክሱን ለመቀጠል አይችልም መባሉ ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሥር ፍ/ቤቶች ክሱ ሊቀጥል አይችልም ያሉበት ምክንያት አግባብነት እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የወንጀል ክርክር በሚመራበት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥ/ሥ/ቁ. 122(2) መሠረት አንድ ክስ በከሳሽ (በዓቃቤ ሕግ) ጥያቄ እንዲነሳ ከተደረገ በኋላ ክሱን ለወደፊት ለመቀጠል የሚከለክል እንደማይሆን በዚሁ አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በንኡስ አንቀጽ 5 ላይ ተመልክቷል፡፡ የወንጀል ሕግ መርህም የሚከተለው በወንጀል የተከሰሰ ሰው በተከሰሰበት ጉዳይ ጥፋተኛ ነው ከተባለ ወይንም በነጻ ከተለቀቀ በኋላ በዚያው ጉዳይ ዳግመኛ ክስ የማይቀርብበት መሆኑን በተመለከተ ነው፡፡

ስለሆነም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረት ከሳሽ (ዓቃቤ ሕግ) ክስ ማንሳት እንደሚችልና ያነሳውንም ክስ መቀጠል እንደሚችል የተመለከተ በመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተነሳው ክስ ሊቀጥል አይችልም በማለት የዐ/ህግን ጥያቄ ሳይቀበለው መቅረቱ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43170 በ27/3/97 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 35780 ሐዳር 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች አስቀድሞ ክስ ማንሳቱ በድጋሚ ክሱን ለመቀጠል የሥነ ሥርአት ሕጉ የሚፈቅድት ስለሆነ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን ተቀብሎ ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን ተመልሶለታል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 29325

የካቲት 18 ቀን 2000ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ሐጎስ ወልዱ
4. ወ/ት ሒሩት መለሠ
5. አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ኤርምያስ ካሣ ተፈራ - ጠበቃ ስንታየሁ ባህሩ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ዓቃቤ ሕግ - ሺበሺ ይግዛው ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26583 ታህሣሥ 26 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ተሰምቶአል፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረው አመልካች የተከሰሰው የወ/መ/ሕግ ቁ.27/1/ እና 522/1/ሀ/ ድንጋጌን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም አመልካች ቀርቦ ሲጠየቅ ጥፋተኛ አይደለሁም ስላለ ፍ/ቤቱ በቅድሚያ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ በመቀጠልም አመልካች እንዲከላከል ብይን በመስጠት የአመልካችን የመከለከያ ማስረጃ ሰምቶል፡፡ በመጨረሻም አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ስላገኘው በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡ አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ነው ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበው፡፡ ፍ/ቤቱ ግን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ የወሰነው አመልካቹ በሌለበት ስለሆነ ይግባኝ ከማለቱ በፊት ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማመልከት አለበት የሚል ምክንያት በመስጠት ወደ ይግባኙ ስረ ነገር ሳይገባ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎት አቤቱታውን አስቀርቦ የሰማው አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለወንጀሉ ክስ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቶ እና የመከላከያ ማስረጃውንም አሰምቶ ተከራክሮ እያለ የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሣኔ ሲሰጥ በመገኘቱ ብቻ ጉዳዩ በሌለበት እንደታየ ተቆጥሮ ይግባኙ ሳይታይ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህንን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ትዕዛዝ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል በዝርዝር እንደተገለፀው ክርክሩ /ጉዳዩ/ ከመሠረቱ አመልካች በሌለበት የታየ አይደለም፡፡ ይልቁንም አመልካች በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ በሰጠው መልስ ክሱን ክዶ በመከራከሩ በዓቃቤ ሕግ በኩል የተቆጠሩት ማስረጃዎች እና በአመልካች በኩል የተቆጠሩት የመከላከያ ማስረጃዎች አመልካቹ ባለበት ተሰምተዋል፡፡ የክርክሩ መሰማት ሂደት በዚህ መልክ ከተካሄደም ቀጥሎ የሚሆነው በተሰማው ክስ እና ማስረጃ መሠረት የመጨረሻ ውሣኔ መስጠት ነው፡፡ ውሣኔው የሚመሠረተውም በተሰማው ክርክር እና ማስረጃ ላይ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የጥፋተኛነቱንም ሆነ የቅጣት ውሣኔውን የሰጠው አመልካች ባለበት የሰማውን ክርክር እና ማስረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ ውሣኔው በተሰጠበት ጊዜ አመልካች ፍ/ቤት አልቀረበም፡፡ ከዚህ የተነሣም ውሣኔው የተሰጠው አመልካች በሌለበት እንደሆነ በውሳኔው መግቢያ ላይ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ለተያዘው አቤቱታ አወሳሰን ሊታይ የሚገባው ነጥብ ክሱና ማስረጃው ለውሣኔ በተቀጠረ ጊዜ የቀረ ተከሣሽ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 161/1/ በተደነገገው መሠረት ጉዳዩ በሌለበት እንደተሰማ ይቆጠራል ወይ? የሚለው ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው በወንጀል የተከሰሰ ሰው ፍ/ቤት እንዲቀርብ የሚጠራው የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲያውቅ እና የሚከላከል ቢሆንም ሕጉ በሰጠው መብት እንዲጠቀም ነው፡፡ ተከሣሹ ይህ የመከላከል መብቱን ላለመጠቀም በተደረገለት ጥሪ መሠረት ሳይቀርብ ቢቀር ሕጉ ባስቀመጠው ድንጋጌ መሠረት ጉዳዩ /ክሱ/ ተከሣሹ በሌለበት ተሰምቶ ይወሰናል፡፡ እዚህ ላይ እንግዲህ ትኩረት የሚያስፈልገው ቁልፍ ነገር የተከሣሹን የመከላከል መብት ሲሆን፣ ይህም የእምነት ክህደት ቃል ከመስጠት ጀምሮ የመከላከያ ማስረጃ እስከ መስማት ድረስ ያለውን ሂደት የሚያጠቃልል ነው፡፡ በመሆኑም ተከሣሹ ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቶ እና የመከላከያ ማስረጃውን አሰምቶ ከሆነ ክሱ እሱ በሌለበት ነው የታየው ለማለት የሚቻልበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ ዓቃቤ ሕግ ለሰበር አቤቱታው የሰጠው መልስ አመልካች የተሰጠበትን ውሣኔ በመሸሽ የተደበቀ በመሆኑ በጠበቃው አማካይነት የቀረበው አቤቱታ ሊታይለት አይገባም በማለት መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡ ይሁንና ይህ ክርክር ምን ውጤት ይኖረዋል? የሚለው ይግባኙን በሚሰማው ፍ/ቤት ከሚታይ በስተቀር በዚህ ሰበር የሚስተናገድ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለል ጉዳዩ /ክሱ/ የታየው አመልካች በሌለበት ነው በሚል የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለዚህ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195 መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት አመልካች የቀረበለትን ይግባኝ እንዲቀበል፣ በመሰለው ሁኔታ ይግባኙን አይቶ የራሱን ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ እንዲሰጥ ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ 31731
የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ - ተሾመ ግርማ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ዘሪሁን ታደሰ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ አስገድዶ የመድፈር ወንጀል ፈጽሞአል በሚል ቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀረው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ዓቃቤ ሕግ በተጠሪው ላይ ክስ የመሠረተው ተከሣሽ በወ/መ/ሕግ ቁ. 590 የተመለከተውን በመተላለፍ ወ/ሪት አስማረች መርሳ የተባለችውን አስገድዶ በመድፈር ክብረ ንጽሕናዋን /ድንግልናዋን/ ገስሷል በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ተጠሪውን አስቀርቦ የእምነት ክህደት ቃል ከሰማ በኋላ፣ ዓቃቤ ሕግ ያቀረበውን የጽሑፍ እና የሰው ማስረጃ ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ዓቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አላስረዳም የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪ ተከላከል ሊባል አይገባም በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ብይን ላይ ይግባኝ የቀረበላቸው የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት እና የሰበር ችሎትም ብይኑ ጉድለት የለበትም ብለዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪው

በተከሰሰበት ወንጀል መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ ይሰናበት የተባለበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ክሱ የወንጀል እንደመሆኑ ተከሣሹ /የአሁን ተጠሪ/ የእምነት ክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ከተጠየቀ በኋላ፣ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች /ማስረጃዎች/ ተሰምተዋል፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ዓቃቤ ሕግ ያሰማው ማስረጃ የግል ተበዳይን ጨምሮ አምስት ምስክሮች እና አንድ የጽሁፍ ማስረጃን የሚጠቃልል ነው፡፡ የግል ተበዳይ በሰጠችው የምስክርነት ቃል ዓቃቤ ሕጉ በክሱ በተሰጠቀሰው ቀንና ሰዓት ተጠሪ ቡና ታፈላ ከነበረችበት ክፍል ውሃ አቀብይኝ ብሎ እንደጠራት እና አስዋም ውሃ በጀሪካን ስትወስድለት በቤቱ /በራሱ ቤት/ በር ስር ቆሞ በመጠበቅ ይዞአት ወደ መኝታ ክፍሉ በመውሰድ ፖንትዋን /የውስጥ ሱሪዋን/ በግድ አውልቆ እንደደፈራት፣ አስዋም ለጊዜው እራስዋን ስታ እንደነበር፣ ሰውነትዋ እንደደማ፣ በመቀጠልም ጩኸት እያሰማች 3ኛ እና 4ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን፣ መጥራትዋን፣ ተጠሪም ቀስ አድርጎ በማስኬድ ወደ ቤትዋ እንዳስገባት በማረጋገጥ እንደመሰከረች የከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ብይን ላይ በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ በመቀጠል የተሰማችው 2ኛዋ የዓቃቤ ሕግ ምስክርም ተጠሪ የግል ተበዳይዋን ሲደፍር አለማየትዋን በአንድ በኩል ብትገልጽም፤ በሌላ በኩል ግን በዓቃቤ ሕግ ክስ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት የግል ተበዳይ ቡና ስታፈላላቸው ቆይታ ሁለተኛውን /ከአቦል ቀጥሎ ያለውን/ አፍልታ ለማምጣት ወደኩሽና መውጣትዋን ከ30 /ሰላሣ/ ደቂቃ በኋላ ተጠሪ ድንግልናየን ወሰደብኝ እያለች እየጮኸች መምጣትዋን፣ ልብስዋን ወደ ላይ አድርጋ ስታሳያትም ደም ማየትዋን፣ የግል ተበዳይን ይዛ ወደ ተጠሪው ቤት ስትሄድ ተጠሪ እቤቱ ውስጥ ሆኖ ቆዩ ሰው እየመጣ ነው ሲል መስማትዋትን በማረጋገጥ መስክራለች ተብሎ በብይኑ ተገልጸአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌሎች 3ኛ እና 4ኛ ተብለው የተመዘገቡት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች እንደዚሁ ሰጡት የተባለው የምስክርነት ቃል እንዳየነው በዓቃቤ ሕግ ክስ በተጠቀሰው ቀን እና ሰዓት አካባቢ በተጠሪው ቤት ተቀምጠው ሳለ የግል ተበዳይ የተጠሪን ቤት ማንኳኳትዋን፣ እነሱም በሩን ከፍተው ወደ ውጪ ሲወጡ ተጠሪ አስገድዶ ስለደፈረኝ ጠይቁልኝ ማለትዋን፣ እነሱም እንጠይቅልሻለን ብለው መልስ እንደሰጡአት መናገራቸውን /መመስከራቸውን/ የሚያመለክት ነው፡፡ በ5ኛ ምስክርነት የተመዘገበው ፖሊስ ሲሆን፣ የመሰከረውም የግል ተበዳይ ተደፈረች በተባለበት ማግስት ከረፋዱ አምስት ሰዓት ላይ መደፈርዋን በመግለጽ ማመልከትዋን /አቤቱታ መቅረብዋን/ እንደሚያውቅ፣ ተጠሪም የግል ተበዳይ ምን ብላ አመለከተች ተብሎ ያኔ እንደ ጠየቀው፣ ምስክሩ ምን ብላ እንዳመለከተች ሲነግረውም ወደፊትም ክሱ የሚደርስበትን ደረጃ ትነግረኛለህ እንዳለው በመግለጽ መመስከሩ ተመዝግቦአል፡፡

በመጨረሻ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የተመለከተው ማስረጃ ከግምቢ ሆስፒታል የተሰጠውን የሃኪም ማረጋገጫ ነው፡፡ በዚሁ ማስረጃ የተገለጸው በግል ተበዳይ ላይ የክብረ ንጽሕና መድፈር ተግባር መፈጸሙን፣ ብልትዋ ወደላይ አብጦ መገኘቱን፣ እየደማም እንደነበር፣ ሁኔታው የግል ተበዳይ ተገዳ መደፈርዋን ሊያመለክት እንደሚችል ነው፡፡

እንደምንመለከተው በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ክስ እና ማስረጃ ከላይ በዝርዝር የተገለጸው ሲሆን፣ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ይህንኑ በግልጽ ከመዘገበ በኋላ፣ ዓቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አላስረዳም የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪን በነፃ ለቅቋል፡፡ በመሆኑም እዚህ ላይ ሊነሳ እና በአግባቡ ሊጤን የሚገባው ነጥብ ዓቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ከዚህ የተለየ ምን አይነት ማስረጃ እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል? የሚለው ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከተው ዓቃቤ ሕግ ክሱን የመሠረተው በወ/መ/ሕግ ቁ. 590 የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞአል በማለት

ነው፡፡ ይህ ድንጋጌም ስንመለከተው “በንጽሕና ክብር ላይ ስለሚደረግ የኃይል ተግባር” የሚል ርእስ የተሰጠው ሲሆን፣ ይዘቱም በኃይል ወይም በብርቱ ማስፈራራት ወይም በማናቸውም አመጣጥ ለመቃወም ከማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ከጣለው በኋላ ግብረ ስጋን በመሰለ ወይም ለንጽሕና ክብር ተቃራኒ በሆነ በማናቸውም ሥራ ጾታው ልዩ የሆነውን ሰው ለመገናኘት የሚያስገድድ ሰው ሕግን እንደተላለፈ ተቆጥሮ የሚቀጣ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ እንግዲህ ዓቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አስረድቶአል ወይስ አላስረዳም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያሰማውን ማስረጃ ከሕጉ ይዘት ጋር ማገናዘብ ይገባል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ዓቃቤ ሕግ ያቀረባቸው የሰው እና የጽሑፍ ማስረጃዎች በዝርዝር ይዘታቸውም ሆነ በጊዜ እና ሰዓት አጠቃቀስ ረገድ እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው፡፡ ሲጠቃለሉም በጊዜው ተፈጸመ የተባለው ድርጊት በሚገባ መፈጸሙን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ አንድ ክስን የሚሰማ ፍ/ቤት በክሱ አከራካሪ የሆኑትን ነገሮች እውነት መሆን አለመሆን ወይም ሕያው መሆን አለመሆን ማረጋገጥ የሚችለው በሚቀርብለት ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በእርግጥም የማስረጃውን ይዘት በመመርመር ክብደቱንና ቅለቱን የመመዘን ስልጣንም የፍ/ቤቱ ነው፡፡ ይሁንና ማስረጃውን በግልጽ ከመዝገቡ እና ይዘቱንም ምን እንደሚመስል እያየ ግን ማስረጃ እንዳልቀረበ አድርጎ ማለፍ ይችል ዘንድ ሕግ አይፈቅድለትም፡፡ የአንድ አከራካሪ ነገር አውነት ወይም ሕያው መሆንና አለመሆን የሚረጋገጠው በማስረጃ ነው የሚለውን መርህም መጣስ አይችልም፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ዓቃቤ ሕግ ያሰማው ማስረጃ በሕጉ የተነገረው ወንጀል ስለመፈፀሙ በግልጽ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን ይህን የመሰለውን ማስረጃ እንዳላዩ አድርገው አልፈውታል፡፡ በእኛ ግንዛቤ እና እምነት ይህ አይነቱ አካሄድ ሕግን በግልጽ የጣሰ ብቻ ሳይሆን፣ ፍትሕንም በእጅጉ የሚጎዳ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/በምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 806 ሰኔ 22 ቀን 97 ዓ.ም. ተሰጥቶ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እና የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 32806 ግንቦት 16 ቀን 98 ዓ.ም. እና በሰበር መ/ቁ. 43754 ሚያዝያ 15 ቀን 99 ዓ.ም. በሰጡአቸው ትዕዛዞች የፀናው ብይን በወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ/ቁ. 195 መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ማስረጃ የተከሰሰበት ወንጀል ስለመፈጸሙ የተመሰከረበት ስለሆነ ሊከላከል ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ክሱን የሰማው የከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ መሠረት ክርክሩን ሰምቶ ይወስን ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31734

ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሐሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ አስናቀ በቀለ - ወኪል አንቀጸ ጌታቸው

ተጠሪ፡- ዓቃቤ ሕግ - ፍቅሬ ከተማ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብ/ክ/መንግሥት በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከሰሰበት ወንጀል ዋስትና በመከልከሉና ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተውም በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች በወኪሉ አማካይነት ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 13/2/፣ አንቀጽ 14/2/ እና አንቀጽ 17/2/ የተመለከቱትን በመጥቀስ ሶስት የወንጀል ክሶችን በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን አመልካችም በዚሁ ፍ/ቤት ቀርቦ የዋስትና መብት እንዲፈቀድለት ጠይቆ ዓቃቤ ሕግ አመልካች የብዙ ሀገር ፓስፖርትና ቪዛ በእጁ ስለሚገኝ የዋስትና መብት ቢፈቀድለት ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ ይችላል ተብሎ ስለማይገመት ፍ/ቤቱ የዋስትና ጥያቄውን ሊቀበለው አይገባም የሚል ክርክር በማቅረቡ ፍ/ቤቱም ይህንኑ የዓቃቤ ሕግን ተቃውሞ ተቀብሎ ተከሳሹ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊቀርብ ይችላል ተብሎ ስለማይገመት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67/ሀ/ መሠረት ያቀረበው የዋስትና ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ብይን ሠጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተከሣሹን ይግባኝ ባለመቀበል የከፍተኛውን ፍ/ቤት ብይን አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች የዋስትና መብት የተከለከለበት ሁኔታ አግባብነት ከሕጉ አኳያ ሊጣራ እንደሚገባ በማመኑ ተጠሪን /ዐቃቤ ሕግን/ በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ አመልካች ዋስትና የመከልከሉ አግባብነትም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በመርህ ደረጃ የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸው በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 19/6/ ላይ የተመለከተ ሲሆን በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ደግሞ ፍ/ቤቱ ዋስትና ለመከልከል አንደሚችል በዚሁ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ይህም የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ /Exception to the General Rule/ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የዋስትና መብት የተከለከለው የተከሰሰበት ወንጀል የዋስትና መብት የሚከለክል ነው በሚል ሳይሆን ከላይ እንደተመለከተው በዋስ ቢለቀቅ ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም በሚል ነው፡፡ ተከሣሹ የዋስትና ግዴታውን ሊፈጽም አይችልም ተብሎ ሲገመትም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 167/ሀ/ መሠረት ዋስትና መከልከል ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም በዚህ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ መሠረት ዋስትና ለመከልከል ግምት ብቻ በቂ ቢሆንም ነገር ግን ለግምቱ በቂ መንደርደሪያ ምክንያት ሊኖር እንደሚገባ ይታመናል፡፡ አለበለዚያ “ግምት” ከሚለው ቃል አጠቃላይነትና ስፋት አኳያ በሰፊው ከተተረጎመ ሕግ አውጭው የዋስ መብት ሊከለክላቸው ያልፈለገውን ተከሣሾችም የዋስ መብት እንዲከለከሉ መንገድ የሚከፍትና ሕጉም የታቀደለትን ዓላማና ግብ እንዳይመታ በትርጉም እንዲዘጋ ስለሚያደርግ በጠባቡ መተርጎም ይኖርበታል፡፡

አመልካች የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚለውን ግምት የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለመውሰድ የቻሉት አመልካቹ የበርካታ አገር ፓስፖርትና ቪዛ ያለው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ከተከሰሰበት የወንጀል ክብደት አኳያ ለወጣ ይችላል በሚል ነው፡፡

ይሁንና አመልካች ከአንድ በላይ ፓስፖርት አለው መባሉ በእራሱ አከራካሪ ከመሆኑም በላይ የበርካታ አገሮች መግቢያ ቪዛ አለው ቢባል እንኳን ይህ ሁኔታ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚለውን ግምት ለመውሰድ በቂ መንደርደሪያ ምክንያት ሊሆን የማይችልና ድንጋጌው ከሕጉ ዓላማ ጋር ተጣጥሞ ያልተተረጎመ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩልም የአመልካች ፓስፖርትና የበርካታ አገሮች መግቢያ ቪዛ ይዞ መገኘት ግምቱን ለመውሰድ በቂ ምክንያት ነው ቢባልም ከአገር የማይወጣበትን ሁኔታ በመፍጠር የዋስትና ግዴታውን አክብሮ እንዲቀርብ የሚያደርግ ትዕዛዝ መስጠት እየተቻለ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዋስትናውን መከልከሉና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ አለማረሙ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09054 በ11/10/99 ዓ.ም. እንደዚሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 18698 በ26/10/99 ዓ.ም. አመልካችን ዋስትና በመከልከል የሰጡት ብይንና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል የብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ ዋስ እንዲጠራ ወይንም ገንዘቡን አስይዞ በዋስ ሆኖ እንዲከራከር በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ለአመልካች ዋስትና በተፈቀደለት መሠረት በእጁ የሚገኘውን ፓስፖርት በፍ/ቤቱ እንዲቆይ በማድረግ በዚሁ ልክ ዋስትና አስጠርቶ ወይንም ገንዘቡን እንዲያሲዝ አድርጎ በዋስ ሆኖ እንዲከራከር እንዲያደርግ ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 34077

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ሐጎስ ወልዱ
4. ወ/ት ሒሩት መለሠ
5. አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ሰይድ ይመር - ጠበቃ ማስረሻ በላይ

ተጠሪ፡- የአማራ ክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ በጊዜው ሥራ ላይ በነበረውና በአዋጅ ቁጥር 214/74 ተሻሽሎ በወጣው የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር 23/1/ /ሀ/ እና /ለ/ ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመጥቀስ 3 /ሦስት/ የወንጀል ክሶችን አቅርቧል፡፡

የተጠሪ ክስ ለአመልካች ደርሶም ባቀረበው የመቃወሚያ ክርክር ተከሣሽ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት ፈጸመ ከተባለ በኋላ አዲስ የወንጀል ሕግ የወጣ እንደመሆኑ መጠን ይህም አዲስ የወንጀል ሕግ ተከሣሽን የሚጠቅም ስለሆነ መከሰስ የሚገባኝ በአዲሱ የወንጀል ሕግ እንጂ በቀድሞው ሊሆን ስለማይችል ክሱ ተሻሽሎ ሊቀርብ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪም በበኩሉ ከአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 5/1/ አኳያ ክርክሩ መቀጠል የሚገባው በተሻረው ሕግ መሠረት ስለሆነ ክሱ ሊሻሻል ስለማይገባ መቃወሚያው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተከሣሽ ድርጊቱን ፈጸመ በተባለበት ጊዜ የነበረው ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሸሮ አዲስ የወንጀል ሕግ የወጣ ሲሆን በተሻረው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሙስና ወንጀል ተብሎ የተቀመጠው ድርጊት ተሸሮ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የሙስና ወንጀል ተብሎ ከአንቀጽ 407 ጀምሮ የተደነገገ ከመሆኑም በላይ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ የተደነገገው ቅጣት ከተሻረው ሕግ ቅጣት ያነሰና ተከሳሽን የሚጠቅም እንደሆነ በብይኑ ላይ አስፍሮ አዲሱ የወንጀል ሕግ ተከሳሽን የሚጠቅም እስከሆነ ድረስ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ ስለሚችል ከሳሽ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/1/ ላይ የተመለከተውን በመጥቀስ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ ይህ ድንጋጌም የዋስትና መብት ስለማይከለክል ተከሣሽ የብር 5000 /አምስት ሺህ/ ዋስትና ሲያሟላ በዋስ ሆኖ ክርክሩን እንዲቀጥል በማለት ብይን ሠጥቷል፡፡

የሥር ከሣሽ የአሁን ተጠሪ በዚሁ ብይን ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የወንጀል ሕግ ተከሳሹን የሚጠቅም ከሆነ ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሰራ መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም ነገር ግን ተፈፃሚነት የሚኖረው በጥፋተኛነትና በቅጣት ጊዜ ስለመሆኑ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቁጥር 6 ላይ የተመለከተ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የክርክሩ ሂደት ሳይጠናቀቅ ክሱ እንዲሻሻል በማዘዝ ዋስትና መፍቀዱ በአግባቡ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ብይን በመሻር መ/ሰጭው /የአሁን አመልካች/ ጉዳዩን በማረሚያ ቤት ሆኖ ሊቀጥል ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለወንጀል ሕግ ቁጥር 6 የሰጠው ትርጉም ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች የዋስትና መብት ሊፈቀድለት ይገባል? ወይንስ አይገባም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ወንጀል ፈጽሟል የተባለው አዲሱ የወንጀል ሕግ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

ወንጀሉ የተፈጸመው አዲሱ የወንጀል ሕግ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከሆነ ተከሣሹ መከሰስ የሚገባው በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 5 መሠረት በአዲሱ ሕግ ሳይሆን ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ሥራ ላይ በነበረው ሕግ መሠረት ነው፡፡

በሌላ በኩልም ተከሣሽ የሚከሰሰው በቀድሞው ሕግ መሠረት ቢሆንም የቀድሞው የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ተሸሮ የሙስና ወንጀሎችንም በተመለከተ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቁጥር 407 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ሥር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 437/97 መሠረትም በተከሣሹ ላይ ሊወሰን የሚችለው ቅጣት ከ10 ዓመት በታች ከሆነ የዋስትና መብት ሊፈቀድለት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

አመልካች የወንጀሉን ድርጊት ፈጽሟል በተባለ ጊዜ የነበረው ሕግ የተሻረ ቢሆንም መከሰስ የሚገባው ድርጊቱ በተፈጸመ ጊዜ ሥራ ላይ በነበረውና አመልካችም በሚያውቀው ሕግ መሠረት መሆን እንደሚገባው ከሕግ መርህ /Rule of legality/ አኳያ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመርህ ደረጃ የተሻረ ሕግ ተፈፃሚነት ባይኖረውም ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለ ጊዜ ተከሣሹ የሚያውቀው ይህንኑ የተሻረ ሕግ ስለሆነ ክስ መቅረብም የሚገባው ይሄው የተሻረ ሕግ ተጠቅሶ ነው፡፡ ይህም የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ /exception to the general rule/ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 5 ላይም የተንጸባረቀው ይህንኑ መሠረት አድርጎ ነው፡፡

አመልካች መከሰስ የሚገባው በቀድሞው ሕግ መሠረት ከሆነ ጥፋተኛም የሚሆነው በዚሁ የቀድሞ ሕግ መሠረት መሆኑ የማይቀር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩልም የወንጀል ሕግ በመርህ ደረጃ ወደ ኋላ ተመልሶ እንደማይሰራ ነገር ግን ተከሣሽን የሚጠቅም እስከሆነ ድረስ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ እንደሚችል በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 ላይ እና በሕገመንግስታችን አንቀጽ 22 ላይ ተመልክቷል፡፡

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል ሕግ ቁጥር 6 ላይ የተመለከተውና የወንጀል ሕግ ተከሣሹን የሚጠቅም በሆነ ጊዜ ወደ ኋላ ተመልሶ ይሰራል ተብሎ የተደነገገው ተፈፃሚነቱ በቅጣት ጊዜ እንጂ ክርክሩ በተጀመረበት ደረጃ ተፈፃሚነት ስለማይኖረው የዋስትናው ጉዳይ መታየት ያለበት ከተከሰሰበት ድንጋጌ አኳያ በመሆኑ የተከሰሰበትም ድንጋጌ የዋስትና መብት ስለማይፈቅድ አመልካቹ በእሥር ሆኖ ሊከራከር ይገባል ብሏል፡፡

በመርህ ደረጃ የተሻረ ሕግ ተፈፃሚነት የሌለው ሲሆን በተሻረ ሕግ ክስ ማቅረብ ደግሞ የመርሁ ልዩ ሁኔታ ነው፡፡ የተሻረውም ሕግ ተጠቅሶ በተከሳሹ ላይ ክስ የሚቀርበው ወንጀሉ ተሰርቷል በተባለ ጊዜ ሕጉ ሥራ ላይ ስለነበርና ተከሣሹም ያውቀዋል ተብሎ ስለሚገመትና በሚያውቀው ሕግ መሠረት መከራከር እንዳለበት የሕግ መርህ /Rule of legality/ ስለማያስገድድ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የተሻረው ሕግ የሚጠቀሰው ተከሳሹ ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት እንዲያስችለው እንጂ ከዚህ ያለፈ ውጤት የሌለውና መጨረሻም ላይ ቅጣት የሚወሰነው ሥራ ላይ ባለ ሕግ ላይ ተመስርቶ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህም ሌላ የዋስትና ጉዳይ በዋናነት የሚታየው ቅጣትን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ አመልካች የተከሰሰው የዋስትና መብት በሚከለክል ድንጋጌ ቢሆንም ድንጋጌው የሚጠቀሰው ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት ታስቦ እንደሆነ ሕጉ ይዞት የተነሳውን ዓላማ መገንዘብ ከተቻለ የዋስትናው ጉዳይ መታየት የሚገባው ሊወሰንበት ከሚችለው ቅጣት አኳያ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡

ክርክሩ እልባት ካገኘ በኋላ አመልካች የሚቀጣው በአዲሱ ሕግ መሠረት እንደሆነ ከወዲሁ በግልጽ መገንዘብ እየተቻለ ክርክሩ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በእሥር ይቆይ ማለት ሕግ አውጭው የዋስትና መብት ሊከለክላቸው ያልፈለገውን ተከሣሾች የዋስትና መብት እንደመከልከል የሚቆጠርና ሕጉም የታለመለትን ዓላማና ግብ እንዳይመታ የሚያደርግ ነው፡፡

ስለሆነም በመልካች ላይ ቅጣት ሊወሰንበት የሚችለው በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቁጥር 407/1/ ሥር ስለሚሆንና በተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ - ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 437/97 መሠረት ከ10 ዓመት በታች በሚያስቀጡ የሙስና ወንጀሎች የዋስትና መብት የተፈቀደ ስለሆነ አመልካችም ሊቀጣ የሚችለው ከ10 ዓመት በታች ስለሆነ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱ እንዲሻሻል ትዕዛዝ መሰጠቱ አግባብነት ባይኖረውም የዋስትና መብት መፍቀዱ ግን ተገቢነት ያለው ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ብይን በመሻር ለአመልካች የዋስትና መብት ሊፈቀድለት አይገባም በማለት የሰጠው ፍርድ ከላይ ከተመለከተው አኳያ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 285/99 ጥቅምት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/2/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14168 በ9/6/99 ዓ.ም. ለአመልካች የዋስትና መብት በመፍቀድ የሰጠው ብይን በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ለአመልካች ዋስትና በፈቀደው መሠረት ዋስትናውን እንዲያሟላ በማድረግ አመልካች በዋስ እንዲከራከር ታዟል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34280

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ግርማይ ደስታ - ጠበቃ ረዳኢ ባራኪ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ዓቃቤ ሕግ - ሚሊዮን ተዘራ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 19769 ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 33217 ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ዓቃቤ ሕግ ክስ አቅርቦበት፣ ፍርድ ቤቱን የግራ ቀኙን ክስና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 22ን እና ሌሎች ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ብሎ፣ አመልካች በአምስት ዓመት እስራት እንዲቀጣ ከወሰነ በኋላ፣ ቅጣቱን በሶስት ዓመት ገድቧል፡፡ ዓቃቤ ሕግ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በሌለበት ይግባኙን ከሰማ በኋላ፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቅጣቱን መገደቡ ሌሎችን ሊያስተምር የሚችል አይደለም በማለት ከፍተኛው ፍርድ ቤት

የሰጠውን የሶስት ዓመት የገደብ ውሣኔ በመሻር አመልካች አምስት ዓመት እስራቱን እንዲፈጽሙ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው፣ ችሎቱ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሚያስለውጥ ምክንያት የለም በማለት አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው፣ ይህ ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ነው፡፡ አመልካች በጠበቃቸው በኩል ባቀረቡት ማመልከቻ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን በአግባቡ ሳይገነዘቡና ሣይተረጉሙ በመሆኑ መሠረታዊ ስህተት አለበት በማለት ዝርዝር ማመልከቻ ያቀረቡ ሲሆን፣ በዓቃቤ ሕግም በኩል በሰበር ደረጃ ጥፋተኝነቱን ለማስለወጥ ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢ አለመሆኑንና የቅጣት ገደቡ መነሣቱ ተገቢ መሆኑን በመጥቀስ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ በሰበር የሚታረም አይደለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች ከቅጣት ውሣኔ አሰጣጥና ቅጣትን ስለመገደብ ከተቀመጡት የወንጀል ሕግ መርሆች አንፃር ሲታይ ቅጣትን ለማስተማሪያነት ሣይሆን በመበቀያነቱ ለመጠቀም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል በማለት የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው የሕግ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው፡-

- በሰበር ደረጃ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?
- በሥር ፍርድ ቤቶች ቅጣቱን ለመገደብና ቅጣቱን ተፈፃሚ መሆን አለበት በማለት የተለያየ ውሣኔ የሰጡበት የቅጣት ውሣኔን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለመገደብ የተደነገጉ ድንጋጌዎች በምን አይነት ሁኔታ መተርጎምና ሥራ ላይ መዋል አለባቸው የሚሉትን ነጥቦች መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ቅር በመሰኘት በመጀመሪያ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ የነበረባቸው ሲሆን ይህንን ማድረጋቸውን የፍርድ ቤቱ መዝገብ አያሣይም፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን ይግባኝ ሰምቶ በቅጣት ውሣኔው ላይ የተሰጠውን የሶስት ዓመት ገደብ በመሻሩ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በጥፋተኝነት ውሣኔው ላይ፣ የነበራቸውን ቅሬታ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ይግባኝ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ በማቅረብ እስከ ሰበር ድረስ በማምጣት መከራከር ነበረባቸው፡፡ አመልካች ይህንን ሥርዓት ተከትለው፣ በጥፋተኝነት ውሳኔው ላይ ተፈጽሟል የሚሉትን የህግ ስህተት ባላቀረቡበት ሁኔታ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔውን መገደቡ ተገቢ አይደለም ብሎ ዐቃቤ ሕግ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት የተሰጠውን ውሳኔ መሠረት አድርገው የከፍተኛ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በማለት የሰበር መከራከሪያ ነጥብ ማድረጋቸው የህግ ድጋፍ የሌለውና ሥርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ በመሆኑ፣ አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ፣ ፍርድ ቤት በአንድ ሰው ላይ የቅጣት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የቅጣት ውሳኔውን ለመገደብ እንደሚችልና የቅጣት ውሳኔው ሊገደብላቸው የሚገባው ምን መሰረታዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 192 ላይ መሰረታዊ መርሁ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቅጣት የወሰነው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔውን ከመገደብ በህግ የሚከለከልበት ሁኔታ እንዳለና ይኸም የህግ ክልከላ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 194 የተደነገገ መሆኑን ለመረዳት እንችላለን፡፡ ከዚህ አንፃር

ስንመዝነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአምስት ዓመት እስራት ቅጣት በሶስት ዓመት መገደቡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የማይጥስና በሕጉ የቅጣት ውሣኔ እንዳይገደብ የተደነገገውን ክልከላ ተላልፎ፣ የሰጠው አይደለም፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሣኔውን ሲገድብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 የተደነገገውን የሕግ ክልከላ አልተላለፈም ካልን በሁለተኛ ደረጃ የሚነሣው ጥያቄ አመልካች ቅጣቱ የተገደበለት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 የተቀመጡትን መሠረታዊ ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ በመገኘቱ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅጣቱን የገደበው አመልካቹ ከዚህ በፊት በወንጀል ያልተቀጣ በመሆኑና ቅጣቱን ተፈፃሚ ከማድረግ ይልቅ ቅጣቱን መገደቡ የተሻለ ውጤት ይኖረዋል በማለት ነው፡፡ በእርግጥ የሥር ፍርድ ቤቶች በዚህ መንገድ አይተው ባሣለፉት ቅጣትን የመገደብ ውሣኔ የይግባኝ ቅሬታ ሊቀርብበት የሚችልና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ውሳኔውን ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 መርህ አንፃር በመመዘን ሊሽረው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊያፀናው የሚችል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ካየነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአምስት ዓመቱ እስራት ቅጣት በሶስት ዓመት እንዲገደብ የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መመርመሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሣኔው በሶስት ዓመት ተገድቦ እንዲቆይ የሰጠውን ትዕዛዝ የሻረው፣ አመልካቹ የቅጣት ገደብ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውንና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 የተቀመጠውን መሠረታዊ መርህ የሚያሟላ አይደለም በማለት ሣይሆን በአመልካቹ ላይ የተወሰነው ቅጣት መገደቡ ሌሎች ተመሣሣይ ወንጀል የመሠራት ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ለማስፈራራትና አመልካችን በመቀጣጫነት በማሣየት ትምህርት ለመስጠት የማያስችል ነው በሚል ምክንያት እንደሆነ በውሣኔው ተልጿል፡፡ አመልካቹ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 የተቀመጠውን መርህ የሚያሟላበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታ ጠቅላላውን የወንጀል ሕጉን መሠረታዊ ግብ መነሻ በማድረግ ቅጣቱ መገደብ የለበትም ከሚለው መደምደሚያ ላይ መድረሱ የወንጀል ቅጣት አወሳሰንና አፈፃፀም የወንጀል ሰሪውን ልዩና ግላዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ መሆን አለበባቸው በማለት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 41 የተቀመጠውን መሠረታዊ መርህ የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም ቅጣትን መገደብን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ግምት ውስጥ በማስገባትና በሕግ የተደረገውን ክልከላ ሣይተላለፍ፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቅጣቱን በመገደብ የሰጠውን ትዕዛዝ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በመሻር የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ስለሆነም ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ አመልካች ያልፈፀመው ቀሪው፣ የእስራት ቅጣት በሶስት ዓመት ሊገደብለት ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. አመልካች ያልፈፀመው ቀሪው የእስራት ጊዜ በሶስት ዓመት የሙከራ ጊዜ የተገደበለት መሆኑን አውቆ፣ ከእስር እንዲለቅቀው አመልካች እስሩን እየፈፀመበት ላለው ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣቱን አፈፃፀም አስመልክቶ፣ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአዳሪ ሲሰራ ቆይቶ ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 34521

ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
መስፍን እቁበዮናስ
ታፈሰ ይርጋ
መድሕን ኪሮስ

አመልካች፡- የአማራ ብ/ክ/መ/ ፍትሕ ቢሮ

ተጠሪ፡- ስንታየሁ ተፈራ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ተጠሪ በሰው ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈጽሞአል በሚል የቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክሱን የሰማው የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ በቅድሚያ የተጠሪን የእምነት ክህደት ቃል ከተቀበለ በኋላ ተጠሪ ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለቱ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡትን ምስክሮች ሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪ እንዲከላከል ብይን በመስጠት የመከላከያ ምስክሮችን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ተጠሪ ወንጀሉን ላለመፈጸሙ በመከላከያው አስረድቶአል በማለት በነፃ አሰናብቶታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዓቃቤ ሕጉ ውሣኔውን በመቃወም ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ ከዚህ በኋላም ፍ/ቤቱ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ነው ብሎአል፡፡ ለጥፋቱ ይመጥናል ብሎ ባመነው መሠረትም ተጠሪ በስድስት /6/ ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም አመልካች ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በወ/መ/ሕግ ቁ. 27/1/ እና 523 የተመለከተለውን ድንጋጌ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል በሚል ጥፋተኛ የተባለውን ተጠሪ በስድስት /6/ ወር እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎአል፡፡ ጥፋተኛ የተባለበት የወ/መ/ሕግ ቁ. 523ም የሚያስቀጣው ከአምስት /5/ ዓመት በማያንስ ከሃያ /20/ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ነው፡፡ በእርግጥ ጥፋተኛ በተባለ ተከሣሽ ላይ ቅጣት ሲወሰን /ሕጉን መሠረት ያደረጉ/ የተለያዩ የማክበጃም ሆነ የማቅለያ ምክንያቶችን እግምት ውስጥ በማግባት በመሆኑ እንደ ሁኔታው ቅጣቱ ሊቀልም ሊከብድም የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የቅጣቱ መነሻ በሕጉ በግልጽ ተቀምጦአል፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ የወሰነው ቅጣት ግን ከመነሻው ወርዶ /ዝቅ ብሎ/ ስድስት ወር ሆኖአል፡፡ አከራካሪ ሆኖ የቀረበውም ፍ/ቤቱ ይህን ያሕል ዝቅ ብሎ ለመውረድ የሚያስችለው የሕግ ምክንያት ነበረው ወይ? የሚለው ነው፡፡

ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ለማቅለል ይችል ዘንድ በዋቢነት የጠቀሰው የወ/መ/ሕግ ቁ. 184/መ/ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ቁጥር 184 ቅጣትን ለማቅለል የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች በዝርዝር የያዘ ሲሆን፣ ይህም ከፍተኛው ቅጣት ማለትም ከሞት ቅጣት ነው የሚጀምረው፡፡ የሞት ፍርድን ከሃያ /20/ ዓመት እስከ እድሜ ልክ ጽኑ እስራት፣ የእድሜ ልክ እስራትን ከአስር /10/ ዓመት እስከ ሃያ /20/ በሆነ ጽኑ እስራት ማቃለል እንደሚቻል በንኡስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ የተመለከተ ሲሆን፣ የእስራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ

ብሎ በተለይ የታዘዘ ከሆነ ደግሞ ቅጣቱን ዝቅ ማድረግ የሚቻለው ከአንድ /1/ ዓመት ጀምሮ እንደሆነ በንኡስ አንቀጽ /ሐ/ ተመልክቶአል፡፡ በወ/መ/ሕግ ቁ. 107 እንደተደነገገው ጽኑ እስራት የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ዓመት እስከ 25 /ሃያ አምስት/ ዓመት ቢሆንም፤ በሕጉ ልዩ ክፍል የቅጣቱ መነሻ ከአንድ ዓመት በላይ ከፍ ብሎ ከተወሰነ ግን በሕጉ አግባብ ያላቸው የማቅለያ ምክንያቶች ካልተገኙ በቀር እንደመነሻ የሚያዘው ይኸው በልዩ ክፍል የተመለከተው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይም ቅጣቱ መወሰን ያለበት በዚህ መሠረት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የጠ/ፍ/ቤቱ እግምት ውስጥ ያስገባቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጠሪ ላይ ሊወሰን የሚችለው ቅጣት ከአንድ /1/ ዓመት በታች ሊወርድ የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ ውሣኔ በሰጠበት ጊዜ ሥራ ላይ በነበረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 179/ሐ/ እንደተመለከተውም የጽኑ እስራቱ ቅጣት መነሻ ከፍ ብሎ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ በዚህ ቅጣት ምትክ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል መነሻ ሆኖ ከተደነገገው ከአንድ ዓመት ጀምሮ የጽኑ እስራት ቅጣት ሊወሰን እንደሚቻል ነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 103/98 ኅዳር 4 ቀን 2000 ዓ.ም. የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕግ ስ/ስ/ቁ. 195/2/መ/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተጠሪ በአንድ /1/ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡ ይኸው ለሚመለከተው ማረማያ ቤት ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35611

ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሻለቃ ታደሰ ካሕሳይ - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 27428 ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ አመልካች በሰው አካል ላይ ጉዳት አድርሷል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦበት፣ ፍርድ ቤቱ የአመልካችንና የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቶ፣ በዘጠኝ ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ለመስማት ለጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. የቀጠረ ሲሆን አመልካች በዕለቱ ሣይቀርብ ቀርቷል፡፡ አመልካች በቀጠሮው ቀን ያልቀረበው የአየር ኃይል መሥሪያ ቤት በግዳጅ ላይ በመሆኑ ምክንያት መሆኑን ገልፆ ትብብር እንዲደረግለት የጠየቀ መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ካሰፈረ በኋላ፣ ይግባኝ ባይ ስላልቀረቡ ይግባኙ እንዲሰረዝ እና ይግባኝ ባይ በዋስትና

ያስያዙት ገንዘብ ገቢ እንዲሆን ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ከአቅም በላይ በሆነ የሥራ ጉዳይ ያልቀረብኩ መሆኔ፣ ፍርድ ቤቱ ማስረጃ ቀርቦለትና ማስረጃውም ደርሶት እያለ፣ በቸልተኝነት ቀጠሮ እንዳሣለፍኩ በመቁጠር ይግባኙን መሰረዙ ተገቢ አይደለም ያለ ሲሆን ዓቃቤ ሕግ በበኩሉ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የወሰነው አመልካች ባለመቅረቡ ሣይሆን የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ትክክል ሆኖ ስላገኘው ነው የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን የሰረዘው አመልካች በቀጠሮ ቀን ባለመቅረቡ ምክንያት መሆኑን በሰጠው ትዕዛዝ በግለጽ ያሰፈረው በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ ይግባኙ የተሰረዘው በአመልች አለመቅረብ ምክንያት ነው በማለት በሰበር ያቀረበው መከራከሪያ ተገቢ አይደለም፡፡ ወደ ዋናው ነገር ስንመለስ ይግባኙ የሚሰማበት ቀን ይግባኝ ባዩ ወይም ጠበቃው ካልቀረቡ ፍርድ ቤቱ ይግባኙን እንደሚሰርዘው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193/1/ የሚደነግገው፣ ይግባኝ ባይ ጉዳዩን በትጋት ካልተከታተለ እና በቸልተኝነት የተወው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ግልጽ በማድረግ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች በሥራው ባሕሪ ምክንያት ወታደራዊ ግዳጅ ላይ እንደሆነ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አሣውቋል፡፡ ይህ ከሆነ ፍርድ ቤቱ በሚቀጥለው ቀጠሮ አመልካች ራሱ ወይም ወኪል ጠበቃው እንዲቀርብ ለመጠባበቅ ቀጠሮ መስጠት እየቻለ ይህንን አሳማኝ ምክንያት ወደ ጎን በመተው ይግባኙን መሠረዙ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193/1/ን መሠረታዊ ግብና ዓላማ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በቀጠሮው ቀን የቀረው በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቦለት እያለ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 79 ድንጋጌ ውጪ አመልካች በዋስትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያስያዘው ገንዘብ፣ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት፣ በመዝገብ ቁጥር 27428 ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. የአመልካች ይግባኝ እንዲሰረዝና የዋስትናው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።
2. የከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካችንና የመልስ ሰጭን ክርክር መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ፣ ጉዳዩን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት መልሰን ልከንለታል። ይፃፍ።

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

ግ ብ ር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 18809

ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ሚሊዮን ዑመር - ጠበቃ አዳሙ ደነቀው - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- የፌደራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ነገረ ፈጅ ገ/እዛቤር ሙላቸውና ተፈራ ጥላው ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለውሳኔ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 15697 ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ተጠሪው ያለአግባብ ከግብር ህግ በተለይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ካወጣው ደንብ ቁጥር 75/1993 ውጭ የትራንስፖርት መኪና ለመንገድ ስራ ድርጅት በማከራየቱ ብቻ የሰበሰውን ገንዘብ እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው ክስ፣ ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ ግብሩ የተሰበሰበው በደንብ ቁጥር 75/1993 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 9 መሰረት ስለሆነ፣ገንዘቡ መመለስ የለበትም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች ገንዘብ እንዲመለስ የወሰነ ሲሆን፣ በዚህ ውሣኔ ተጠሪው ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርቦ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሳሳተ የሕግ ትርጓሜ ሰጥቷል፡፡ ያከራየነው መኪና እንጅ መሣሪያ ባለመሆኑ ደንብ ቁጥር 75/1993 በእኛ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ፣ ግብሩ በአግባቡ ነው የተሰበሰበው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመረነው “ኮምፒውተርን ጨምሮ ከተለያዩ መሣሪያዎች ህንፃዎች እና ሌሎች እቃዎች ኪራይ” አምስት ፐርሰንት ግብር እንደሚከፈል፡፡ ደንብ ቁጥር 75/1993 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 9 ይደነግጋል፡፡

አመልካች “መሣሪያዎች” የሚለው የትራንስፖርት መኪናን አይጨምርም የሚል ክርክር ያቀረበ ቢሆንም መኪኖቹ ለህዝብ ማመላለሻ እና ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠታቸው ቆሞ በኪራይ ለኮንስትራክሽን ድርጅቱ በመከራየታቸው በደንቡ የተመለከተውን ግብር ከመክፈል ነፃ የሚሆኑበት ሁኔታ የለም፡፡ የህግ አውጭው ሐሳብም የህዝብ ማመላለሻ መኪና ከመደበኛው ስምሪት ወጥቶ ከተከራየ ከኪራዩ ግብር ለማስከፈል እንደሆነ ከደንብ ቁጥር 75/1993 ድንጋጌዎችና ይህንን ደንብ ለማሻሻል ከወጣው ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 2/ሸ/ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ፍሬ ያለው ሆኖ ስላላገኘው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ውሣኔውን በማጽናት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ይፃፍ፡፡
3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

የ ን ግ ድ

ተ ቋ ማ ት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 19258

ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አቶ ብርሃኑ አመነው

አመልካቾች፡- 1. አቶ ተክሌ ዋቅጅራ
2. አቶ ጥላሁን ቦባስ
3. አቶ ሃቢብ መሐመድ
} ቀረቡ

መልስ ሰጭ፡- አቶ ሾንጣ ጉቡ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር አንድ አባል አገባለሁ ያለውን መዋጮ መቼና እንዴት ማግባት ያለበት መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካቾችና መልስ ሰጭዎች ጠቅላላ ግምቱ ብር 800,000 /ስምንት መቶ ሺህ ብር/ ካፒታል ያለው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሥርተዋል፡፡ የእያንዳንዳቸው መዋጮ ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ሲሆን የአሁን መልስ ሰጭ በዓይነትም ሆነ በገንዘብ አገባለሁ ካለው መዋጮ ውስጥ ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር/ ሣያስገባ ማህበሩ ሥራውን ሲያንቀሳቅስ ከቆየ በኋላ ሌሎች አባላት ይህንኑ ሊያስገባ የተስማማውን መዋጮ በገንዘብ ገቢ እንዲያደርግ ሲጠይቁት መልስ ሰጭ ይህንኑ መዋጮ ማህበሩ ከሚያስገኘው ትርፍ ገቢ በድርሻዬ

ከማገኘው እከፍላለሁ እንጂ እንደ ጥያቄያችሁ ክፍያውን ለመፈፀም ግዴታ አልገባሁም በማለቱ ምክንያት ይህ ክርክር ሊከሰት ችሏል፡፡

ይህንኑ ክርክር ያስነሣውን መዋጮ ገቢ ያደርግ ዘንድ አመልካቾች በጌዲኦ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት ክስ መሥርተው መልስ ሰጭም ከላይ የተጠቀሰውን መከራከሪያ በማቅረቡ ይኸው ፍ/ቤት ጉዩን ተመልክቶ የአሁን መልስ ሰጭ ቀሪ አክሲዮን ድርሻውን /መዋጮውን/ በዚህ ጊዜ አስገባለሁ ብሎ ግዴታ አልገባም ማስጠንቀቂያ የደረሰው መሆኑም አልተረጋገጠም፣ ስለሆነም የሚከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁን አመልካቾች ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታቸውን ለደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክለል ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረባቸው ግራ ቀኙ በጉዳዩ ላይ ክርክር አድርገዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የአሁን መልስ ሰጭ አስገባለሁ ካለው መዋጮ ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር/ አላስገባም (አልከፈለም) ሆኖም ይህንኑ ቀሪ ክፍያ ለመፈፀም ውል አድርጓል፡፡ ይህ ውልም ፈራሽ ነው አልተባለም ስለዚህ መልስ ሰጭ ገንዘቡን ሊከፍል ይገባል በማለት ዳኝነት ሰጥቶ ግራ ቀኙን አሰናብቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የአሁን መልስ ሰጭ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ በሰበር ግራ ቀኙ ተከራክረዋል፡፡ ሰበር ሰሚው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ እንደሚከተለው ወስኗል፡፡

በንግድ ሕግ ቁጥር 338/1/ አክሲዮኖች በሚገዙበት ጊዜ እጅግ ቢያንስ ከተዛፈባቸው ዋጋ አንድ ሩብ ሊከፈል እንደሚገባ ወይም በሙሉ እንደሚከፈል ተደንግጓል፡፡ ዋጋቸው በሙሉ እስኪከፈል ድረስም አክስዮኖቹ በማህበሩ ስም የሚቆዩ ናቸው ሆኖም ይህ ያልተከፈለው አክሲዮን ማህበሩ በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ቢበዛ እስከ አምስት ዓመት ድረስ በየጊዜው መከፈል እንዳለበት በዚሁ ሕግ እና ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመልክቷል፡፡ በዚህ ሕጉ ባስቀመጠው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለው የአክሲዮን ክፍያ ካልተፈፀመ ምን ውጤት እንደሚያስከትል ደግሞ በንግድ ሕግ ቁጥር 342 ሥር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ድርሻ የአክሲዮን ክፍያውን ገቢ ለማድረጉ ከተረጋገጠ በንግድ ሕግ ቁጥር 338/1/ እና 342 መሠረት

- ያልተከፈለባቸውን አክሲዮኖች ስም በማህበሩ ማቆየት፣
- በሐራጅ ማሸጥ፣
- ኪሣራ ካስከተለ መጠየቅ እንዲሁም ከጉባዔ ድምፅ እንዲታገድ ከሚድረግ

በቀር የአክሲዮን ክፍያ ገንዘብ አልከፈለም በሚል እንዲከፍል ማስገደድ ሕጋዊ መሠረት አይኖረውም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካቹ መክፈል የሚገባውን ቀሪ ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር ከሰማንያ ሣንቲም/ የአክሲዮን ክፍያ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ወስነናል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ያመለክታሉ ያላቸውን ነጥቦች አመልካች በመጥቀስ እንዲታረምለት ነው፡፡

መልስ ሰጭም በበኩሉ የሥር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ግድፈት አልተፈፀመበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

እኛም ጉደዩን ተመልክተናል እንደተመለከትነውም አመልካቾችና መልስ ሰጭ ያቋቋሙት የንግድ ማህበር የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር ስለመሆኑና ክርክር ያስነሣውን የብር 74,838.80 መዋጮ መልስ ሰጭ ለዚሁ የንግድ ማህበር ገቢ ማድረግ በሚገባው ጊዜ ያላገባ ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የተካዱ ነጥቦች አይደሉም ። እያንዳንዱ ማህበርተኛ በዓይነትም ሆነ በገንዘብ ማግባት የሚገባውን መዋጮ አጠቃሎ መክፈል ያለበት መሆኑን ከንግድ ሕግ ቁ. 516 እና 517 ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

ይኸውም ማህበሩ ተቋቁሟል የሚባለው በማህበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ ዓይነት በተዘጋጀው ግልጽ በሆነ ጽሁፍ ላይ ማህበርተኞቹ ወይም ወኪሎቻቸው የፈረሙበት እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ላይ ከሚገለፁት ነገሮች አንዱ የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ መግባቱን የመጠቀሱ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲሁም በንግድ ሕግ ቁጥር 121 ሥር የአክሲዮኖች ድርሻ መዝገብ ምን ምን ነገሮችን ማካተት እንዳለበት ከተዘረዘሩት መካከል በንዑስ ቁጥር 1(ለ) “እያንዳንዱ ማህበርተኛ ማግባት ያለበትን የመዋጮዎች ግምት” የሚለው መዋጮው ከተቋቋመም በኋላ ወደ ፊት መግባት እንደሚችል በሚገልጽ አኳኋን የተፃፈ ቢሆንም "the value of all contributions made by the members" ከሚለው የእንግሊዝኛ ግልባጭ ጋር አጠቃለን ስናየው መዋጮ አስቀድሞ መግባት ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ እነዚህም ድንጋጌዎች ማህበርተኛው አገባዋለሁ ያለውን መዋጮ ማህበሩ በተቋቋመበት ጊዜ አጠቃሎ መክፈል ያለበት መሆኑን የሚያመለክቱ እንጂ ስለ አክሲዮን ማህበር በዚሁ ሕግ ቁ. 338/1/ እንደተመለከተው ክፍያ ሣይፈፀምበት ሊቆይ የሚችል መዋጮ ሊኖር የሚይችል መሆኑን አያሣዩም ማህበርተኞቹ ማህበሩን ሲያቋቁሙ በዚህ መሠረት መፈፀም ሲገባቸው አላደረጉም ሆኖም ማህበርተኛው መዋጮውን ዘግይቶ እንዲያስገባ በማድረግ ማህበሩን መሥርተው በተገኙ ጊዜ ማህበሩ ህልውና የለውም ማለት አይደለም፡፡ ይህንን አስመልክቶም የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ይህ በጊዜው ገቢ ያልሆነው መዋጮ መቼ እና እንዴት መከፈል እንዳለበት በመመስረቻ ጽሑፍ ላይ ባይገለጽም መልስ ሰጭው ያልከፈለውና ገቢ ማድረግ ያለበት መዋጮ መኖሩን አምኖ እንደሚከፍል መተማመኛ የሰጠ ለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የህንን መተማመኛ ከሰጠ በኋላ የአሁን መልስ ሰጭ የሚያቀርበው ክርክር ይህንን ገቢ ያላደረግሁትን መዋጮ ማህበሩ ከሚያገኘው ትርፍ በአስገባሁት መዋጮ ልክ ከሚደርሰኝ ገቢ እየተሰላ በየጊዜው ልከፍል ከሚገባ በቀር በአንድ ጊዜ የመክፈል ግዴታ የለብኝም የሚል ነው፡፡ ሆኖም ከላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደተመለተው የተወሰነ ኃላፊነት ያለው ማህበር መዋጮ መክፈል ያለበት ማህበሩ ሲቋቋም እንጂ ተቋቁሞ ሥራውን ከጀመረ በኋላ ባለመሆኑና መልስ ሰጭም ያላገባውን መዋጮ እከፍላለሁ በማለት እራሱን ግዴታ ውስጥ ያስገባ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ መተማመኛ የሰጠ በመሆኑ በሂደት ማህበሩ በሚያስገኘው ገቢ ልክፈል የሚለው መከራከሪያው ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት መዋጮ ሣይከፈል ከተገኘ በባለድርሻው ስም ሣይሆን በማህበሩ ስም ተመዝግቦ ሊቆይ እንደሚችልና መከፈል በሚገባው እጅግ ቢዘገይ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለ ምን ውጤት እንደሚያስከትል በንግድ ሕግ ቁጥር 342 ተመልክቷል የሚለውን ምክንያት ይዞ መልስ ሰጭ ያላገባውን መዋጮ እንዲከፍል ማስገደድ አይቻልም በሚለው መደምደሚያው የጠ/ፍ/ቤቱን ውሣኔ ሊሽር የቻለው በንግድ ሕግ ቁጥር 338 እና 342 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው ይሁን እንጂ እነዚህ ድንጋጌዎች የአክሲዮን ማህበርን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የአክስዮን ማህበርና የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር ሁለቱም የንግድ ማህበሮች ይሁኑ እንጂ በአመሠራረታቸው በአለባቸው የኃላፊነት አድማስ፣ በሚሰማሩበት የሥራ ዘርፍ ገደብ ያለባቸው ስለመሆኑና አለመሆኑ ወዘተ ስራ ልዩነት አላቸው፡፡ ለአክስዮን ማህበር የሚሸጡት አክሲዮኖች መቼ ገቢ እንደሚሆኑና ለተወሰነ ኃላፊነት ያለው ማህበር ደግሞ መዋጮው መቼ መግባት እንዳለበት በተለያዩ አካኋን በየሚመለከታቸው ክፍሎች ተደንግገዋል መዋጮ መቼ መግባት ያለበት መሆኑን ስለአክሲዮን ማህበር የሚደነግጉትን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ማድረግ እንደሚቻልም ተጠቅሶ አልተገኘም፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የንግድ ሕግ ቁጥር 338 እና 342 አሁን ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንዳላቸው ቆጥሮ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ለውሣኔው መሠረት ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

ው ሣ ኔ

1. መልስ ሰጭ ለንግድ ማህበሩ ገቢ አደርጋለሁ ሲል መተማመኛ የሰጠበትን ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺ ስምንት መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከ80%/ ገቢ ሊያደርግ ይገባል፤ ይከፈል ብለናል፡፡
2. የጌዲኦ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 22/92 በ24/3/95 የሰጠው ውሣኔ እና የደቡ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በይ/መ/ቁ. 5648 በ26/04/97 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
3. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 3694 በ29/4/96 የሰጠውን ውሣኔ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበተ

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 23389

ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ አብዱራሂም አህመድ

አቶ ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኅበር - ጠበቃ ኃይሉ አስምር ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች፡- እነ ባህሩ አብርሃም /12 ሰዎች/ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ/ቁ 08449 ላይ በ27/4/97 በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 37119 ላይ በ27/3/98 ለዋለው ችሎት ብይኑን በማፅናቱ አመልካች የካቲት 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ባቀረበው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች የተፈፀመው የሕግ ስህተት እንዲታረም በመጠየቁ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ የማኅበሩ አባላት በአስተዳዳሪዎች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ ምን እንደሚመስል ለማጣራት ሲል ቅሬታው ለተጠሪዎች ደርሶ ታህሣሥ 19/1999 በዋለው ችሎት ቀርበው በጠበቃቸው አማካይነት የቃል ክርክር አድርጓል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ክስ ሊመሰርቱ ተጠሪዎች የአክስዮን ማኅበር

አስተዳዳሪዎች ሆነው ከደንብ ውጪ በአክስዮን ማኅበሩ ከተሰራው ሕንፃ ውስጥ የግንባር ሱቆችን በተደረገው ግልጽ ያልሆነ ስብሰባ ያላለፉት ውሣኔና የወሰዱት አስተዳደራዊ ውሣኔ ከደንቡ ውጪ ስለሆነ እንዲታገድና እንዲፈርስ የሚል አቤቱታ አቅርበው ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ተጠሪዎችን እንደማይመለከትና እንደማያስከስሳቸው፣ ያስከስሳቸዋል ቢባልም እንኳ በን/ህ/ቁጥር 365/1/ መሠረት በተጠሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚቻለው ማኅበሩ እንጂ አመልካቾች ሊሆኑ እንደማይችሉ በመቃወማቸው ፍ/ቤቱም ክርክራቸውን በመስማት አመልካቾች በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 ሥር የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ሳያሟሉ በተጠሪዎች ላይ ክስ መመሥረት አይችሉም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

በዚህ ችሎትም የታየው መሠረታዊ ጉዳይ አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ በቀጥታ ክስ መመሥረት ይችላሉ ወይ? የሚለው የሕግ ጥያቄ ነው፡፡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 364 እስከ 367 በተደነገገው መሠረት የአክስዮን ማኅበር አስተዳዳሪዎች ሀላፊነት ለአክስዮን ማኅበሩ አበዳሪዎች፣ ለአክሲዮን ማኅበሩ ባለድርሻ አባላት ወይም ለሦስተኛ ወገን ሊሆን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ላይ ተጠሪዎች የአመልካቾችን መብት በሚጎዳ መልኩ የሰሩ ስለሆነ ሃላፊነት አለባቸው፣ የሰሩትም ሥራ ሊፈርስ ይገባል የሚል ክስ የቀረበባቸው መሆኑ በሥር ፍ/ቤት መዝገብ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የበታች ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ለማድረግ መሠረት ያደረገው የሕግ አንቀጽ የንግድ ሕጉ ቁጥር 365 ቅድመ ሁኔታዎች አልተሟሉም የሚል ነው፡፡ ሆኖም በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የተመለከቱት ማኅበሩ አስተዳዳሪዎችን ለመክሰስ ሲፈልግ ሊያሟላቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎችን እንጂ የተወሰኑ የአክሲዮን ማኅበሩ ባለድርሻዎች የሚያቀርቡትን ክስ አያጠቃልልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአስተዳዳሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚችሉ ወገኖች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በንግድ ህጉ ለየብቻ የተደነገጉ ስለሆነ እነዚህን ለይቶ በአግባቡ ማየት የግድ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት አሁን በተያዘው ጉዳይ ላይ አመልካቾች የሚሉት በተጠሪዎች የተፈፀመው ተግባር መብታቸውን የሚጎዳ በመሆኑ የአስተዳደሪዎችን /በተጠሪዎች/ በቀጥታ መክሰስ የበታች ፍ/ቤት አንቀጽ 365ን መሠረት አድርጎ መክልከሉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

እኛም ይህንን ሁኔታ ከላይ እንደተመለከተው የተጠያቂነት መሠረቱ ለየብቻ መታየት እንዳለበት የሕጉን ዓላማና መንፈስ መሠረት አድርገን አጽንተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካቾች የአክስዮን ባለድርሻ አባላት በመሆናቸው አስተዳዳሪዎች /የአሁን ተጠሪዎች/ የአባልነት መብታቸውን በሚጎዳ መልኩ መሥራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ ቀጥታ መክሰስ እንደሚችሉ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 367 ይፈቅድላቸዋል፡፡

በመሆኑም አመልካቾች የሚጠበቅባቸው በተጠሪዎች የሥራ አመራርና የውሣኔ እርምጃ ተጎጂ መሆናቸውን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 367 መሠረት ማረጋገጥ እንጂ የበታች ፍ/ቤት እንደተመለከተው በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አይጠበቅባቸውም፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 365 የተወሰኑ የአክስዮን ማኅበሩ አባላት በአስተዳዳሪዎች ላይ የሚያቀርቡትን ክስ የሚመለከት ስላልሆነ የሥር ፍ/ቤት ተገቢ ያልሆነውን የሕግ አንቀጽ መሠረት አድርጎ የአመልካቾችን ክስ መዝጋቱ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05449 የሰጠው ብይን እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37119 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡

2. ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 341/1/ መሠረት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ተመልሶ የፍሬ ነገር ክርክሩ ውሣኔ እንዲያገኝ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 28923

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማሕበር አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር አልቀረቡም

2ኛ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነገረደጅ አቶ አዳነ መጋቡ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የአማራ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአማራ ብሔራዊ ክልል የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ፍሬ ጉዳዩም አንደኛ ተጠሪ የአማራ ብሔራዊ ክልል ባወጣው ደንብ መሠረት የ1988 ዓ.ም የቦታ ኪራይ ብር 497,943.54 /አራት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ ሦስት ብር ከሀምሣ አራት ሣንቲም/ እንዲከፍል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ያልከፈለ በመሆኑ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት በአመልካች ላይ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካችም ይህ ዕዳ የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደነበርና ወደ ባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማሕበር ከመቀየሩ

በፊት የነበረ ስለሆነ፣ ሁለተኛው ባለዕዳ፣ ሦስተኛ ወገን ተከራካሪ፣ /ተከሣሽ/ ሆኖ ጣልቃ እንዲገባ በጠየቁት መሠረት ፍ/ቤቱ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስና አመልካቹና ሁለተኛው ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ የቦታውን ዋና ግብር 454,511.99 /አራት መቶ ሀምሣ አራት ሺ አምስት መቶ አሥራ አንድ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ ሁለተኛ ተጠሪ ብር 56,159.44 /ሀምሣ ስድስት ሺ አንድ መቶ ሀምሣ ዘጠኝ ብር ከአርባ አራት ሣንቲም/ ብቻ እንዲከፍል ቀሪውን ዕዳ አመልካች እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በክሱ ተከሳሽ የሆነው የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማሕበር የተመሰረተው 1992 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ ፋብሪካው ወደ አክስዮን ማሕበርነት ከመለወጡ በፊት የነበረው ዕዳ እኛን የሚመለከት ባለመሆኑና ሁለተኛው ተጠሪ ይህንን ዕዳ የመክፈል ግዴታ በአዋጅ ቁጥር 182/1992 የተጣለበት ሆኖ እያለ አክስዮን ማሕበሩ ዕዳውን እንዲከፍል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበትና አክስዮን ማህበሩን ለኪሣራ የሚዳርግ በመሆኑ በሰበር ይታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ ወደ አክስዮን ማሕበሩ የሚተላለፉና የማይተላለፉ ዕዳዎችን የመወሰን ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መከፈል ያለበት ዕዳ ነው በማለት ያሣወቀን 56,159.44 /ሃምሣ ስድስት ሺ አንድ መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር ከአርባ አራት ሣንቲም/ በመሆኑ ከዚህ ውጭ ያለውን ዕዳ አመልካች መክፈል ይገባዋል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በበኩሉ ዕዳው መከፈል ያለበት ዕዳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ሁለተኛ ተጠሪና አመልካች እንዳልካዱ ገልፆ በሁለቱ መካከል በሚደረገው ክርክር የከተማው አስተዳደር ማግኘት የሚባውን ክፍያ ሣያገኝ ጉዳዩ እየተጓተተ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ታይቶ ዕዳውን ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና የአመልካችና ተጠሪዎች በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ያለበት ዕዳና አጠቅላይ አሴቱ እና መንቀሳቀሻ ካፒታሉ ተለይቶ የባህርዳ ጨርቃጨቅ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር ተብሎ በአዲስ መልክ በአክስዮን ማህበርነት ከመደራጀቱ በፊት ለአንደኛ ተጠሪ መክፈል የሚገባው የቦታ ግብር ዕዳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ብንመዝነው መንግሥት አመልካች ድርጅት ወደ አክስዮን ማህበር ከመቀየሩ በፊት የነበሩበትን ዕዳዎች በኃላፊነት የሚረከብ አንድ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ ምክንያት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራ ቦርድን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና በመወሰንና ሕግ ያወጣ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 208/1992 መግቢያ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የባለአደራ ቦርዱ መሠረታዊ ዓላማም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደግል ይዞታ በሚዛወርበት ወይም ወደ አክስዮን ማህበር በሚለወጥበት ወይም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት ወደ አክስዮን ማህበሩ ወይም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ የማይተላለፉ ሂሣቦችን መሰብሰብ ዕዳዎችን መረከብና ከዚሁ ጋር የተያያዙ የፍርድ ቤት ጉዳዮችን መከታተል እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የባለአደራ ቦርዱ ወደ አክስዮን ማህበርነት የተቀየሩ ወደ ግል የተዛወሩ ወይም ለቀድሞ ባለቤታቸው የተመለሱ የመንግሥት የልማት ድርጅት ዕዳዎችን ለመንግሥት እያቀረበ እንዲከፈሉ የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ/

ይደነግጋል፡፡ በዚህ መዝገብ የባህርዳር ከተማ አስተዳደር የጠየቀው የመሬት ኪራይ የባህርዳር ጨርቀጨርቅ ፋብሪካ ወደ አክስዮን ማህበርነት ከመቀየሩ ከአራት ዓመት በፊት የነበረና የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የመንግሥት የልማት ድርጅት በነበረበት 1988 ዓ.ም መክፈል የሚባው ዕዳ ነው፡፡ አሁን ያለው የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር 1992 ዓ.ም ህጋዊ ሰውነት ያገኘ ድርጅት በመሆኑ ከጅምሩ በፈረሰውና ወደ አክስዮን ማህበርነት በተቀየረው የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ስም ያቀረበውን ክስ በኃላፊነት ይዞ መከራከር የሚገባው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ ዕዳውን ላለመክፈል የሚያቀርበው ምክንያት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አላሳወቀኝም የሚል ነው፡፡ ሆኖም የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ወደ አክስዮን ማህበርነት ሲቀየር በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያልታወቀና ውሣኔ ያልተሰጠበት ዕዳ ሁሉ ወደ አክስዮን ማህበሩ ይተላለፋል የሚል ግልጽ የህግ ድንጋጌ ካለመኖሩም በላይ የዚህ አይነት የህግ አተረጓጎም አክስዮን ማህበሩን ለከፍተኛ ኪሣራ የሚዳርግና የባለአደራ ቦርዱ የተቋቋመበትን መሠረታዊ ዓላማ ጋር የሚቃረን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም ዕዳው አክስዮን ማህበሩ ከመቋቋሙ በፊት የነበረ እስከሆነ ድረስ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በወቅቱ ያላወቀውና ውሣኔ ያልሰጠበት ዕዳ በአክስዮን ማህበሩ መክፈል ይገባዋል በማለት የሰጠው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 07500 ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ የፍርዱ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የአማራ ክልል የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03792 ሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ የፍርዱ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
3. ሁለተኛው ተጠሪ ብር 454,511.99 /አራት መቶ ሀምሣ አራት ሺ አምስት መቶ አሥራ አንድ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ እና የከፍተኛው ፍርደ ቤት ውሣኔ ከሰጠበት ከሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት /9%/ ህጋዊ ወለድ ለአንደኛው ተጠሪ ይክፈል ብለናል፡፡
4. አመልካችና ተጠሪዎች ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

አፈጻጸም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 10489

ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር ተተኪ መሠረተ ልማት ሚ/ር ነገረ ፈጅ

አቶ ወ/ማርያም ሥዩም ቀረቡ

መልስ ሰጭ፡- የቀድሞ ብሔራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግል ማህበር

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን የአፈፃፀም ጉዳይ በሚመለከት የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5520 ህዳር 30 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌ/ከፍተኛው ፍ/ቤትም በይግባኝ ተመልክቶ ይኸው ትእዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልን በማለት ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር ብር 11,908, 734 /አስራ አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሣ አራት ብር/ ከእነ ወለዱ ለመልስ ሰጭ ለብሔራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር እንዲከፍል ህዳር 23 ቀን 1991 ዓ.ም የተሰጠውን ትእዛዝ መነሻ በማድረግ አፈፃፀሙ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲታይ ቆይቷል፡፡

ይኸው ፍ/ቤት ክፍያው እንዴት እንደሚፈፀም ግራ ቀኙ በሌሉበት ጉዳዩን ሲከታተል ከቆየ በኋላ ህዳር 30 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት ባለእዳ እዳውን እንዲከፍል የተለያየ ትዕዛዝ ሲሰጥ ቢቆይም ዕዳው አልተከፈለም ፡፡ የፍርድ ባለእዳ የሆነው የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር በአዋጅ ቁጥር 256/94 ፈርሶ መብትና ግዴታው ወደ መሠረተ ልማት ሚ/ር ተላልፏል፡፡ ተተኪው የመሠረተ ልማት ሚ/ር ባለበት ጉዳዩ በመታየት ላይ እንዳለ በጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት በቁጥር ጠ/80 -ጠ4/01/11 በ3/8/94 በተፃፈው ደብዳቤ መነሻነት የብሔራዊ መሐንዲሶች ሥራ ተቋራጭ ማህበርን የቀድሞ ባለንብረቶች ይረከቡት ዘንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ሲታይ የቆየ ቢሆንም ኮሚቴው ውጤታማ ይሆን ዘንድ የመሠረተ ልማት ሚ/ር ሥራውን መሥራት አልቻለም ፡፡

ስለዚህ አስቀድሞ በተወሰነው መሠረት ፍ/ቤቱ አፈፃፀሙን ከመቀጠል ውጭ አማራጭ አላገኘም የሚለውን ምክንያት ካሰፈረ በኋላ የኢት/ያ ብሔራዊ ባንክ የመሠረተ ልማት ሚ/ር ካለው ሂሣብ ላይ ህዳር 23 ቀን 1999 ዓ.ም በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ቀንሶ ለፍርድ ባለመብት ለአሁን መልስ ሰጭ ይክፈል የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍ/ቤቶች ከላይ በተገለፀው አኳሃን የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል፤ ይታረምልን በማለት ነው የአቤቱታው ይዘትም ተጠቃሎ ሲታይ፡፡

በአዋጅ ቁጥር 256/94 አንቀጽ 26/1/ ድንጋጌ መሠረት የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር መብትና ግዴታ ለመሠረተ ልማት ሚ/ር ይተላለፍለት እንጂ ለዕዳ መክፈያ በጀት አልተመደበለትም፡፡ የአመልካች በጀት ለደምወዝና ለስራ ማስኬጃ ብቻ ሆኖ እያለ በጀት ለዕዳ መክፈያ እንዲውል መደረጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብነት የለውም፤ የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎትና አምኖበት ለእዳው አከፋፈል በኮሚቴ አማካኝነት የንብረት ማስተላለፍ ተግባር እንዲደረግ ታዞ በዚህም መሠረት ሥራው ቀጥሎ ከ80% በላይ ኮሚቴው ሥራውን ማከናወኑ እየታወቀ የሥር ፍ/ቤት የአንድን ወገን አቤቱታ ብቻ አዳምጦ እራሱ የሰጠውን ትእዛዝ እንደይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሆኖ በመሻር ዕዳው በመደበኛ በጀት እንዲከፈል ትእዛዝ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያመለክታል የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭም ይህንኑ ቅሬታ አስመልክቶ ዝርዝር መልስ ሰጥቶበታል የመልሱም ፍሬ ቃል የሥር ፍ/ቤት ስለአፈፃፀሙ የሰጠው ዳኝነት የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚያዘው መሠረት መሆኑንና ዕዳውንም በመጨረሻ መንግሥት የሚሸከመው መሆኑን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ናቸው የሚላቸውን በመጥቀስ አስፈላጊም ከሆነ ከመንግሥት ካዝና ወጪ ሆኖ ሊከፈል እንደሚገባ አብራርቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚው ችሎትም በበጀት የሚተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤት የፍርድ ባለእዳ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔውን ለማስፈፀም ለሌላ ጉዳይ በበጀት የተያዘውን እና የሠራተኛ ደመወዝን የሚጨምረውን ገንዘብ ከባንክ ወጭ ሆኖ እንዲከፈል ማዘዝ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለውን መነሻ በማድረግ ነው ያከራከረው፡፡ ክርክሩ በሰበር ከመቅረቡ በፊትም ሆነ በኋላ ጉዳይ በሃራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ቀርቦ ግራ ቀኙ ሲደራደሩ እንደነበር ለመረዳት ተችሏል፡፡ ድርድሩ የተደረገውም በሠራተኛ ቅነሣ ጥያቄ ዕዳውን እረከባለሁ በማለት ቦርድ ኃላፊነት ሊወስድ የሚገባው የመሆኑን አግባብነት፣ በተገባው ቃል መሠረት የቦታ ርክክብ ሊፈፀም ያለመቻሉን፡

እንዲሁም ተረከቡ ያሉን መሣሪያዎች የተገመቱት ከ5 ዓመት በፊት በመሆኑ በዚያው ዋጋ ተረከቡ መባሉን ፤

የወደቁ መሣሪያዎች ተለይተው ከግምቱ ተቀናሽ መሆን የሚገባቸው መሆኑን፣

ክሱ ተሰልቶ በሚታውቀው ግምት እና እኛ በምንፈልገው ገንዘብ መካከል ያለውን ልዩነት ጊዜ ተሰጥቶን ልንከፍል የምንችልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ ሲሆን ድርድሩ ውጤት ሣያገኝ መቅረቱን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ በፊት የተጀመረው ድርድር እልባት ያገኝ ዘንድ በፍትህ ሚ/ር ሰብሣቢነት የሚመራ ኮሚቴ የተቋቋመ መሆኑንና ይህም ኮሚቴ ሥራውን በመስከረም ወር 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዚያ ወር 1999 ዓ.ም ድረስ ከመልስ ሰጭዎች ጋር ሲደራደር ከቆየ በኋላ ደርሰንበታል ባለው ስምምነት መነሻ ስለጉዳዩ በመንግሥት በኩል ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ የውሣኔ ሀሣብ ያቀረበ መሆኑን ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ከቀረበው ሪፖርት መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በአመልካችና በመልስ ሰጭ መካከል የተነሣውን የአፈፃፀም ጉዳይ የሥር የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት እንደጀመረው ከጠቅላይ ሚ/ሩ በተፃፈው ደብዳቤ መሠረት ዕልባት የሚያገኝ ከሆነ በሚል ይህ ሰበር ችሎትም የእራሱን ጥረት አድርጓል ይሁን እንጅ በተለያዩ ምክንያቶች ውጤት ሣያገኝ ቀርቷል ግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች እንደየጉዳዩ እየታየ በፍ/ቤቱ አነሳሽነት በሚቀርብላቸው ጥያቄ መሠረት ጉዳያቸውን በስምምነት መጨረስ ካልቻሉ ሕግን ባገናዘበ ሁኔታ ዳኝነት ሊያገኙ ይገባል ስለሆነም ይህ ችሎት ቀደም ሲል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለት በምክንያትነት ከያዘው ነጥብ አንፃር ጉዳዩን መርምሯል፡፡

እንደመረመርነውም የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መግባባት አፈፃፀሙ ፍፃሜ እንዲያገኝ ጥረት ቢያደርግም የፍርድ ባለእዳን የተካው የመሠረተ ልማት ሚ/ር የሚጠበቅበትን አልሰጠም በሚል እንደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጨረሻ አማራጭ የኢት/ብሔራዊ ባንክ ከመሠረተ ልማት የባንክ ሂሣብ ገንዘቡን ወጭ አድርጎ እንዲከፍል ትእዛዝ ሰጥቷል። ይህ ከባንክ ወጭ ሆኖ ለዕዳ መክፈያ ይዋል የተባለው ገንዘብ የመ/ቤቱ መደበኛ በጀት መሆኑንም መልስ ሰጭ ክዶ አልተከራከረም ። መደበኛ በጀት ለሠራተኛ ደመወዝ ፤ለመ/ቤቱ የዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ ሲባል የሚመደብ ገንዘብ አንደመሆኑ ለተጠየቀው ዕዳ ክፍያ ይዋል ቢባል የመ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ መግታት ይሆናል። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 404 ድንጋጌ ሥር በዕዳ ምክንያት በአፈፃፀም ሊያዙ አይችሉም ተብለው የተዘረዘሩትን የንብረት ዓይነቶችና መጠን አዳምረን ስናይ እነዚህ ለባለእዳው ፍፁም አስፈላጊ የሆኑና ለዕለት ጉርሱ የሚውሉ በመሆናቸው ህልውናውን ለመጠበቅ ታስቦ የተሰጠ የሕግ ጥበቃ መሆኑን እንረዳለን። አንድ የመንግሥት መ/ቤትም ለህዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ ከተዋቀረ ለመደበኛ ሥራው ሲባል የተመደበውን በጀት ለሌላ ተግባር ማለትም ለእዳ ክፍያ እንዲውል ከተደረገ በግለሰብ አቋም እንዳየነው ሁሉ የመ/ቤቱን ሕልውና የሚፈታተንና የህዝብንም ጥቅም የሚጎዳ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 404ን በማመሳሰል ሥራ ላይ የማይውልበት ምክንያት አላገኘንም።

ስለሆነም ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ ሆኖ በተያዘው ነጥብ መሠረት የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀሙ በመሠረተ ልማት ሚ/ር መደበኛ በጀት ላይ ተፈፃሚ እንዲሆን፤ ከመደበኛ በጀት ወጭ ሆኖ እንዲከፈል ሲል የሰጠው ትእዛዝ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም።

በሌላ በኩል ከዚህ ውጭ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ለአፈፃፀሙ ተስማሚ እና ተገቢ ነው የሚለውን መንገድ ተከትሎ ፍርዱን ያስፈጽም ብለናል።

ው ሣ ኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5520 ህዳር 30 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ቀሪ ሆኖ ሌላ ተስማሚ እና ተገቢ ነው የሚለውን መንገድ ተከትሎ ፍርዱን ያስፈጽም ብለናል።
2. በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5520 በኀዳር 30 ቀን 1995 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ እና የከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/ቁ. 16478 ታህሣሥ 30 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ ተሽሯል

ግልባጩ ይድረሣቸው ።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 18576

26/09/2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ወ/ሮ ደስታ መኮንን - ጠበቃ መሰለ ገ/ጊዮርጊስ

ተጠሪ፡- ወ/ት መሰሉ ጌታሁን - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪና ሌሎች 2 ሰዎች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት የፍርድ አፈፃፀም አቤቱታ የፍርድ ባለዕዳ /የአሁን አመልካች/ የአውራሻችንን ንብረት እንድታካፍለን ክስ አቅርበን ፍ/ቤቱ የውርስ አጣሪ ሾሞልን ውርሱ ተጣርቶ ሪፖርቱ ለፍ/ቤቱ የቀረበ ቢሆንም በሪፖርቱ መሠረት ንብረቱን በስምምነት ለመካፈል ያልቻልን ስለሆነ መኖሪያ ቤቱንና የንግድ ቤቶቹን በፍ/ቤቱ በኩል እንድንካፈል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የፍርድ ባለዕዳ /አመልካች/ ቀርበውም በሰጡት መልስ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ማለት የፍ/ቤቱ ውሣኔ አይደለም፡፡ የፍ/ቤቱ ውሣኔ ካልሆነ ደግሞ አፈጻጸም ሊጠየቅበት ስለማይችል አቤቱታው ከሥነ ሥርዓት ውጭ ስለቀረበ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ቀደም ሲል የውርስ አጣሪ እንዲቋቋም በታዘዘው መሠረት አጣሪው ሥራውን በሕጉ መሠረት ሠርቶ አጠናቋል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚቀረው ነገር የውርስ አጣሪው በሰራው መሠረት ሀብቱን ማከፋፈል ነው፡፡ የንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1060 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት በወራሾች ስምምነት ወይም ይህ ካልተቻለ አንደኛው ወገን በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት በፍ/ቤት ሊፈጸም ስለሚችል የፍርድ ባለዕዳ ክርክር ተቀባይነት የለውም ብሎ የውርስ ንብረቱ በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል በሐራጅ ተሸጦ ግራ ቀኙ ድርሻቸውን በሪፖርቱ መሠረት እንዲከፋፈሉ በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውርስ አጣሪ ተቋቁሞ የውርስ ንብረት ከተጣራ በኋላ አጣሪው በሚያቀርበው ሪፖርት መሠረት ንብረቱን መከፋፈል ካልተቻለ ክስ አቅርቦ ከማስወሰን በስተቀር የአጣሪው ሪፖርት ፍርድ ወይም ውሣኔ ባለመሆኑ በቀጥታ ለአፈፃፀም የሚቀርብ አይደለም ስለሆነም በዚህ መልኩ የቀረበውን ሪፖርት የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ እንዲፈጸም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት ሽሯል፡፡

የአሁን ተጠሪም በዚሁ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የውርስ ክርክር በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውርስ አጣሪ ተቋቁሞ የአጣሪው ሪፖርት ለፍ/ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱም ሪፖርቱን ተቀብሎ መዝገቡን የዘጋ ሲሆን መ/ሰጭ የአሁን አመልካች የሪፖርቱን ትክክለኛነት የማይቀበሉ ቢሆን መከራከር የነበረባቸው ፍ/ቤቱ ሪፖርቱን ተቀብሎ መዝገቡን ከመዘጋቱ በፊት ነበር፡፡ በጊዜውና በአግባቡ ሪፖርቱ ላይ ተቃውሞ ካልቀረበ ደግሞ ሪፖርቱን ግራ ቀኙ እንደተቀበሉት ስለሚጠቆጠርና ክፍፍልም የማይደረግበት ምክንያት የለም ብሎ የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የውርስ አጣሪው ሪፖርት በመ/ቁ. 428

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመመዝገቡ ብቻ ለአፈፃፀም መነሻ ሊሆን ይችላል ተብሎ መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ተመስርቶ የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላልን? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በቅድሚያም የውርስ አጣሪን ሥልጣን መመልከት ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሕጉን ድንጋጌዎች ተመልክተናል፡፡

የውርስ አጣሪ ሥልጣን መብት አለኝ ባይዎችን ወይንም ወራሾችን መወሰን፣ የሟች ኑዛዜ ካለ መፈለግና በዚህ ኑዛዜ መሠረት ተጠቃሚዎችን መወሰን፣ ውርሱን ማስተዳደር የውርሱን ተካፋይ ገንዘብ መሰብሰብና ዕዳዎችን መክፈል፣ የሟችን ንብረት ማጣራትና ማፈላለግ የኑዛዜ ስጦታዎችን መክፈል እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 944፣ 946 እና 956 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

የውርስ አጣሪው የማጣራቱን ተግባር ካከናወነ በኋላ ሪፖርቱን ለወራሾችና ለፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚጠበቅበትም በፍ/ህ ቁጥር 960 ላይ ተመልክቷል፡፡ የውርስ ማጣራቱ ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላም በአጣሪው ሪፖርት መሠረት ወራሾች የወራሽነት የምስክር ወረቀት /certificate of Succession/ ከፍ/ቤት ማግኘት እንደሚችሉም በቁጥር 996 ላይ ተደንግጓል፡፡

በሕጉ ላይ የተመለከተው የውርስ አጣሪው ሥልጣን ከላይ የተዘረዘረው ሲሆን የማጣራቱ ውጤትም እያንዳንዱ ወራሽ ከውርሱ የሚደርሰው ድርሻ ተለይቶ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ማግኘት ነው፡፡

እያንዳንዱ ወራሽ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ካገኘና በክፍፍሉ ረገድ በወራሾች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር የወራሽነት የምስክር ወረቀት ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም /Vested interest/ ከሚሰጥ በስተቀር በእራሱ ፍርድ ስላልሆነ በቀጥታ አፈፃፀም ሊጠየቅበት የሚችል አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የውርስ ማጣራቱም ሆነ የማጣራቱ ተግባር ተፈጽሞ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ማግኘት ዓለማው የእያንዳንዱን ወራሽ ድርሻውን በመለየት መብቱን ማረጋገጥ ስለሆነ በዚህ መልኩ መብት ከተረጋገጠ በኋላ በዚሁ መሠረት ወራሾች ድርሻቸውን በስምምነት መከፋፈል ካልቻሉ በድርሻቸው መጠን ዳኝነት ከፍለው ይኸው መብታቸው በፍርድ እንዲረጋገጥ ዳኝነት መጠየቅ ስለሚገባቸው ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ መልኩ ዳኝነት ሳይጠየቅ በውርስ አጣሪው ሪፖርት መሠረት እንዲፈጸም የአፈፃፀም አቤቱታ ማቅረብ ፍርድ ያላረፈበትን ነገር ለማስፈጸም እንደመጠየቅ የሚቆጠርና የሕጉን ዓላማ የሳተ ነው፡፡

ስለሆነም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ተመስርቶ የቀረበውን የአፈፃፀም አቤቱታ ተቀብሎ ማስተናገዱ ከሕጉ አኳያ አግባብ አይደለም ተብሎ በፌዴራል ከ/ፍ/ቤት መሻሩ ተገቢነት የነበረው ሆኖ ሳለ ይሄው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተሽሮ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲጸና መደረጉ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14546 በሐምሌ 2 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እንደዚሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29686 ጥቅምት 8 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33021 በጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 19283

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አብዱልቃድር መሐመድ
ተገኔ ጌታነህ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ መድኃኒት ኃይሉ - ቀረቡ፡፡
2. አቶ ጌታቸው ተሰማ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ - ነገረ ፈጅ ወይንሸት ቸርነት

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በአመልካቾች በኩል በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት በሥር ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካቾች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካቾች በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ከተከሳሽ ጋር በተደረገ የብድር ውል በአዳማ ከተማ ቀበሌ 11 ክልል በካርታ ቁጥር 7006/82 የተመዘገበውን ሆቴል መያዣ ሠጥተን ብር 295,620.00 /ሁለት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሀያ ብር/ ተበድረናል፡፡ ከተከሣሽ የተበደርነውን ገንዘብ ሥራ በማጣታችን ምክንያት መክፈል ባለመቻላችን ተከሣሹ በዋስትና የያዘውን ንብረት አስገምቶ በብር 1,607,607.00 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባት ብር/ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ለመሸጥ ጨረታ አውጥቶ የሚገዛ ስለጠፋ ድጋሚ ጨረታ አውጥቶ ያለአግባብ ከአዋጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 97/90 ውጪ መነሻ ግምቱን በጣም ዝቅ አድርገ በብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ/ ወስዶታል፡፡

ስለሆነም ተከሣሹ ልዩነቱን ብር 1,307,607.00 /አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባት ብር/ ንብረቱን ከወሰደበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሾች ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ጨረታ ወጥቶ ገዢ ስላልቀረበ ድጋሚ ጨረታ ወጥቶ ከአንድ ሌላ ተጫራች ጋር ተወዳድረን ሚያዝያ 19/1991 ዓ.ም. ተከሣሽ ጨረታውን አሸንፎ በብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ/ ሆቴሉን ገዝቷል፡፡ ተከሣሽ ሆቴሉን የገዛው በሕጋዊ መንገድ ስለሆነ ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ከቀረበው ማስረጃና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መርምሮ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 430/1/ ሥር እንደተመለከተው የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን በሚሸጥ ንብረት በጨረታ መሳተፍ የሚችለው ፍ/ቤትን አስፈቅዶ ሲሆን በዚሁ መሠረት ተከሣሽ ፍ/ቤትን አስፈቅዶ በጨረታው መሳተፍ ሲገባው ሳያስፈቅድ በጨረታው የተሳተፈ ስለሆነ ተግባሩ ሕገወጥ ነው ካለ በኋላ ተከሣሽ የከሳሾችን ሆቴል በመጀመሪያ ጨረታ ብር 1,607,607.00 መገመቱንና ይህንኑ ሆቴልም በብር 300,000.00 መግዛቱን ያመነ በመሆኑ በልዩነት በከሳሾች የደረሰውን ጉዳት ብር 1,307,607.00 /አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባት ብር/ ተከሣሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራቀኙን አከራክሮ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 216/92 አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ጨረታ ወጥቶ ገዢ ባለመገኘቱ ባንኩ ንብረቱን

ከያዘ ወይም ከወሰደ በመጀመሪያው ጨረታ ላይ በተሰጠው ግምት ያስቀረዋል የሚል ሲሆን ይግባኝ ባይ ባንክ ግን ክርክር የተነሳበትን ሆቴል እራሱ የያዘው ወይም ያስቀረው ሳይሆን በድጋሚ ጨረታ የሸጠው ስለሆነ በባለዕዳው ላይ ጉዳት አድርሷል ለማለት ስለማይቻል የሥር ፍ/ቤት ጉዳት ደርሷል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስላልሆነ ይግባኝ ባይ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል አይገባም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካቾችም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኙ ተቀባይነት የለውም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሠርዟል፡፡

ይህም ችሎት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካቾች በክስ የጠየቁትን ገንዘብ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት አለውን? የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ አቤቱታው ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነውንና በአዳማ ከተማ የሚገኘውን የሆቴል ንግድ ድርጅት ለተጠሪ መያዣ በመስጠት ብር 296,620.00 /ሁለት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ብር/ መበደራቸውን፣ ብድሩ ባለመከፈሉ ምክንያት በሀራጅ መነሻ ግምት ብር 1,607,670.00 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ብር/ የመጀመሪያ ጨረታ ወጥቶ ገዢ በመጥፋቱ በድጋሜ 2ኛ ጨረታ ወጥቶ ተጠሪና ሌላ አንድ ተጫራች ቀርበው ተጠሪ በብር 300,000.00 /ሶስት መቶ ሺህ/ የጨረታው አሸናፊ ስለመሆኑ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ግራ ቀኙን አላከራከሩም፡፡

በባንክ መያዣ የተያዙ ንብረቶችን አስመልክቶ በወጣው አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 መሠረት መያዣ ተቀባይ ዕዳው በውሉ ላይ በተመለተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጊዜ ሳይከፈለው ቢቀር ከሰላሣ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ ለመያዣ ሰጭው /ለባለዕዳው/ በመስጠት በመያዣ የያዘውን ንብረት መሸጥ እንደሚችል የተመለከተ ሲሆን በመጀመሪያ ጨረታ ንብረቱ ሳይሸጥ ቢቀር አዋጅ ቁጥር 97/90 ለማሻሻል በወጣው በአዋጅ ቁጥር 216/92 አንቀጽ 2/1/ መሠረት ድጋሚ ጨረታ ወጥቶ ገዢ ካልቀረበ ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሠረት አበዳሪው ባንክ ንብረቱን ለመውሰድና የባለቤትነት መብቱም በስሙ እንዲዛወርለት ማድረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩልም ባንክ በመያዣ የያዘውን ንብረት በሐራጅ የመሸጥ ሥልጣን በሥራ ላይ በሚያውልበት ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 394-449 ያሉትን ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚነት እንደሚኖራቸው በተቀጠሰው አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ላይ የተመለከተ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 430/1/ ላይም የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን በሐራጅ እንዲሸጥ የተወሰነውን ሀብት ለመግዛት ፍ/ቤትን ማስፈቀድ እንደሚጠበቅበት ተመልክቷል፡፡ ይሁንና የሐራጅ ሽያጭ በሚከናወንበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሱትን የሥነ - ሥርዓት ድንጋጌዎች ባንክ በሥራ ላይ የሚያውላቸው ከጉዳዩ ጋር አግባብነት በሚኖራቸው ጊዜ እንደሆነ በአዋጁ ላይ ከመመልከቱም በላይ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ባንኩ የመያዣ ንብረቱን ሲሸጥ ባለዕዳውን በመወከል የሚያደርገው ሽያጭ ሆኖ እንደሚቆጠር በአንቀጽ 5 ላይ የተመለከተ ስለሆነ ባዕዳውን ሻጭ እራሱን ደግሞ ገዢ ማድረግ ስለማይችል ተጠሪ ሽያጩ በአግባቡ ተከናውኗል በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ በመያዣ የያዘውን የሆቴል የንግድ ድርጅት ለመሸጥ የመጀመያውን ጨረታ አውጥቶ ገዢ ሳይቀርብ በመቅረቱ ድጋሚ ጨረታ ሲያወጣም ገዢ ካልቀረበ ሕጉ በጣለበት ግዴታ መሠረት በመጀመሪያው የጨረታ መነሻ ዋጋ ንብረቱን መረከብ ሲገባው እራሱ

በጨረታው መሳተፍም ሆነ አሸናፊ ሆኖ መገኘቱ ከሕጉ ያፈነገጠ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተጠሪ ንብረቱን የተረከበበት አግባብ ከአዋጁ መንፈስ ውጭ ቢሆንም 2ኛ ጨረታ ወጥቶ ገዢ በመጥፋቱ ምክንያት ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሠረት ንብረቱን እንደተረከበው ሊቆጠር የሚችል ስለሆነ ንብረቱን በተረከበበት የዋጋ ግምትና ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት መክፈል የሚገባው በመሆኑ በዚሁ መሠረት እንዲከፈል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ተጠሪ ሽያጩን ያከናወነው በግባቡ ስለሆነ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03516 በጥር 26 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18631 መጋቢት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ለአመልካቾች ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለሆነ ጸንቷል፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 22481

መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ክፍሌ ወልዴ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን፣ ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

መዝገቡ የተከፈተው አመልካች በፍርድ የተወሰነብኝን የተጠሪውን እዳ እንዲያስፈጽም፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተሰጠው የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ፣ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን ሳያከብር፣ የፈፀመውን የሀራጅ ሽያጭ የከፍተኛው ፍ/ቤት በማጽደቅ፣ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደ ይግባኙ የሚያስገባ በቂ ምክንያት የለም በማለት አላግባብ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በማጽናቱ፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተፈፀመው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላልታረመ በሰበር ይታይልኝ በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ክርክሩን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመብቱን /የተጠሪውን/ ዕዳ ለማስከፈል ይቻል ዘንድ በቡራዩ ልዩ ቀበሌ በቤት ቁጥር 1008 ተመዝግቦ የሚገኘው፣ የአመልካቹ የመናፈሻ ድርጅት በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል በሀራጅ ተሸጦ ለፍርድ ባለመብቱ እንዲከፈል የሰጠውን ትዕዛዝ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን በአግባቡ ተግባራዊ ሳያደረግ፣ ሽያጩን ፈጽሟል እና ይሰርዝ

የሚል ነው፡፡ አመልካቹ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ንብረቱን ከዋጋው በታች በሆነ ግምት፣ የሀራጅ ጨረታ ማከናወኑ፣

- የድርጅቱ ሽያጭ የተከናወነው፣ በግልጽ ጨረታ ሣይሆን፣ ሀራጅ ባይ፣ ብቸኛ ተወዳዳሪ ሆኖ ጨረታውን አሸንፏል ከተባለው ሰው ጋር ባደረገው ድርድር እንጂ በሀራጅ ደንብና ሥርዓት መሠረት ባለመሆኑ፣
- በወቅቱ በሀራጅ ጨረታው ለመወዳደር ስድስት የሚሆኑ ሰዎች ቀርበው የነበሩ ቢሆንም አላግባብ በተንኮል በጨረታው እንዳይሣተፉ በመደረጉ
- ብቸኛ ተጫራች ሆኖ በመቅረብ ንብረቱን ገዝቷል የተባለው ግለሰብ የፍርድ ባለመብት የሆነው የንግድ ድርጅት መሥራች እና ባለአክስዮን የሆኑት የአንደኛው ወንድም በመሆናቸው፣ በአጠቃላይ ሀራጁ የሕግ ስርዓትን ባላሟላ ሁኔታ፣ በተንኮልና በጥድፊያ የተፈፀመ በመሆኑ የሀራጅ ሽያጩ ፈርሶ ሌላ ጨረታ እንዲካሄድ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት፣ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያመለከቱ ሲሆን ተጠሪው በበኩላቸው የንብረቱን ግምት በተመለከተ ቀደም ብለው ያቀረቡት ተቃውሞ ስለሌለ አሁን ሊከራከሩበት አይችሉም፤
- በጨረታው የተሣተፈው አንድ ተጫራች ብቻ ቢሆንም፤ ከመነሻው ብር 5000 /አምስት ሺህ/ ጨምረው የገቡ በመሆኑ በዚህ በኩል የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም፡፡
- ጨረታውን ያሸነፉት ግለሰብ የፍርድ ባለመብት የሆነው የንግድ ድርጅት የአክሲዮን ባለድርሻ ከሆኑት የአንደኛው ወንድም ናቸው የሚለው አቤቱታም ዕውነትነት የሌለውና ቢሆንም ቢሆኑም እንኳን ጨረታውን ለማፍረስ በቂ ምክንያት ስለማይሆን የፍርድ ባለዕዳው ማመልከቻ ውድቅ ሆኖ የሀራጅ ሽያጩ እንዲፀድቅልን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክር ከሰማ በኋላ በጉዳዩ ላይ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያን ሪፖርትና መግለጫ ከሰማ በኋላ ከመጀመሪያ በሀራጅ ሂደቱ ከሥነ ሥርዓት ውጭ የሆነ ተግባር ተፈጽሟል አልተፈፀመም ተፈጽሞስ ከሆነ ተፈፀመ የተባለው ግድፈት ጨረታውን ለማፍረስ የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ወይስ አይደለም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ፣

- በጨረታው አንድ ተጫራች ብቻ ቀርቦ፣ ንብረቱ ለእሱ እንዲሸጥ መደረጉ፣ ምንም ዓይነት የሕግ ስህተት የሌለበት አሠራር በመሆኑ፤
- በጨረታው አሸናፊ ሆኖ የፍርድ ባለዕዳውን ንብረት የገዛው፣ የፔትራም ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የአክሲዮን ባለድርሻና ባለቤት ከሆኑት የአንደኛው ወንድም ነው የተባለው በፍርድ ባለዕዳው የተካደና ማስረጃ ያልቀረበበት በመሆኑና፣ ወንድም ሆነው ቢገኙ እንኳን፣ ሽያጩን ለማፍርስ በቂ ምክንያት ስለማይሆን፤
- ሽያጩ የተከናወነው በድርድር ነው የሚለው፣ ምንም እንኳን ግንቦት 3 ቀን 1997 ዓ.ም. በሀራጅ ባዩ ተዘጋጅቶ የቀረበው ሪፖርት ንብረቱ በድርድር የተሸጠ በሚመስል አገላለጽ ተጽፎ፣ የቀረበ ቢሆንም አገላለፁ፣ በወቅቱ የቀረበው ብቸኛ ተጫራች በመጀመሪያ ንብረቱን በመነሻ ዋጋው ለመግዛት እንደሚፈልግ ለሀራጅ ባዩ ከገለፀ በኋላ ሀራጅ ባዩ ከመነሻ ዋጋው ላይ የተወሰነ ዋጋ ጨምሮ እንዲገዛ ሲነግረው ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ በመጨመር ግዢውን እንደፈፀመ ለመግለጽ ታስቦ የተፃፈ መሆኑን ስለሚያሣይና ይኸም በፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 422 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ንብረቱ በግል ውል ወይም በድርድር የተሸጠ መሆኑን ስለማያመለክት እና በአጠቃላይ የሀራጅ ሽያጩ ሊፈርስ የሚችለው፤ ጨረታው እንዲፈርስ በጠየቀው ወገን መብት ላይ ጉዳት ማድረሱ ሲረጋገጥ በመሆኑና ሀራጅ የተባለውን ንብረት

ግምት ብር 438,946 /አራት መቶ ሰላሣ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስድስት ሆኖ እያለ ከግምቱ በላይ በብር 443,946 /አራት መቶ አርባ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስድስት ብር/ የተሸጠ በመሆኑና የፍርድ ባለዕዳው የንብረቱ ግምት ከሶስት ሚሊዮን በላይ ነው በማለት ያቀረበው ተቃውሞ፣ ንብረቱ ሀራጅ ከመባሉ በፊት ያልቀረበና ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የፍርድ ባለዕዳው የሀራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ያቀረቡት ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል።

አመልካች በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ተፈጽሟል የሚላቸውን ስህተቶችና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ አለበት የሚሉትን የሕግ ስህተት በመግለጽ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ የሚነቀፍበት ምክንያት እና ወደ ይግባኙ የሚያስገባ ምክንያት አለመኖሩን በመግለጽ መዝገቡን ዘግቶታል።

አመልካች ይህንን በመቃወም ለሰበር ባቀረቡት አቤቱታ፡-

- በዕለቱ ሀራጅ የተባለውን ድርጅት ለመግዛት ስድስት ሰዎች መጥተው የነበረ መሆኑንና ባልታወቀ ምክንያት ሌሎች ሰዎች ከሄዱ በኋላ አንድ ተጫራች ብቻ ነው የቀረበው ተብሎ መሸጡን አስመልክቶ ያነሳሁትን ተቃውሞ በተጠሪው በኩል ሣይካድ፣ ፍርድ ቤቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428 ንዑስ አንቀጽ 5 አላግባብ በመጥቀስና በመተርጎም የጨረታው አሸናፊ የሆነው ሰው ብቻውን መጫረቱ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ
- ድርጅቱን የገዛው ግለሰብ፣ በግልጽ ጨረታና በሀራጅ ደንብ፣ መሠረት ሣይሆን ከሀራጅ ባዩ ጋራ በዋጋ በመደራደር፣ የገዛው መሆኑን የሀራጅ ባዩ ሪፖርት እና ማብራሪያ እያስረዳ ከፍተኛው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 422 ንዑስ አንቀጽ 3 አላግባብ በመጥቀስና በመተርጎም ሽያጭ ያከናወነው የግልጽ ጨረታና የሀራጅ ደንብን ተከትሎ ነው በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ ስህተት ያለበት በመሆኑ

- ንብረቱን የገዛው ሰው የፍርድ ባለመብት የሆነው የንግድ ድርጅት ባለአክስዮን ድርሻና ባለቤት የሆኑት የአንደኛው ወንድም ነው የሚለውን መቃወሚያ በማስረጃ አልተረጋገጠም፣ ቢረጋገጥም እንኳን፣ ጨረታውን ለማፍረስ በቂ ምክንያት አይደለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ የተሣሣተ በመሆኑና በአጠቃላይ የጨረታው ሂደት የፍርድ ባለመብቱን መብት በሚጎዳ መንገድ ያልተከናወነ በመሆኑ፣ የሀራጅ ሽያጩ ይፀናል በማለት የሰጠው ትዕዛዝና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ጉዳይ የሚያስገባ በቂ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሰበር ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የተፈፀመው ስህተት እንዲታረም ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት በጽሁፍ አመልክተዋል፡፡

ሰበር ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማጣራት ካስቀረበ በኋላ፣ በጭብጡ ዙሪያ አመልካችና ተጠሪው የካቲት 29 ቀን 1998 ዓ.ም. ያደረጉትን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ በተደረገው የቃል ክርክር አመልካቾች በአብዛኛው በሰበር አቤቱታቸው የገለፁትን ነጥቦች በማብራራት ሀራጅ የተባለው ንብረት በዝቅተኛ ግምት ሀራጅ ጨረታ መቅረቡ፣ ንብረቱን የገዛው ሰው በሀራጅ ደንብና ሥርዓት መሠረት ሣይሆን በድርድር ንብረቱን መግዛቱ፣ በዕለቱ ስድስት ሰዎች ንብረቱን ለመግዛት የቀረቡ መሆኑና በማያውቁት ምክንያት ከግቢው ወጥተው ሲሄዱ እንዳገኟቸው በማብራራት የከፍተኛው ፍርድ ቤት እነዚህን መሠረታዊ ስህተቶች ለመሠራታቸው በቂ ማስረጃ እያለ የሀራጅ ሽያጩ

ይፀናል በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የተጠሪው ጠበቃ በበኩላቸው ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ድርጅት አመልካች የፍርድ ባለዕዳ መሆናቸውን በ1993 ዓ.ም. በፍርድ ያስወሰነ ቢሆንም ለሰባት ዓመት ያህል የፍርድ ባለዕዳው በተለያየ ፍርድ ቤቶች ተንኮል ያለበት ክርክር ውስጥ በመግባትና ንብረቱን በማሣገድ ፍርዱን ማስፈፀም እንዳልቻሉ የሀራጅ ሽያጩ በተከናወነበት ቀን እኔ በቦታው ያልነበርኩ ሲሆን፣ ከደንበኞቼ ለመረዳት እንደቻልኩት፣ በወቅቱ ስድስት ሰዎች በጨረታው ለማሣተፍ መጥተው የነበረ መሆኑንና ሰዎቹም መታወቂያቸውን አስይዘው እንደነበር ነገር ግን አመልካቹ ይህ ቤት ሌላ ዕዳ አለበት ብትገዙት ሌላ ጣጣ ትገባላችሁ ብለው ስላስፈራሯቸው ከገዢው በስተቀር ሌሎቹ ጥለው የሄዱ መሆኑንና የጨረታው አሸናፊ በመነሻ ዋጋው ንብረቱን ለመግዛት እየቻለ ሀራጅ ባዩ ዋጋ ጨምር ሲለው ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ የጨመረ መሆኑንና ይህም የአመልካችን መብት የሚያስጠብቅ እንጂ የሚጎዳ ባለመሆኑ፣ በአጠቃላይ የሀራጅ ሽያጩን የሚያፈርስ በቂ ምክንያት የለም በማለት ፍርድ አስፈፃሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደርግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የቀረበው የመከላከያ ሀሳብ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የፍርድ ባለዕዳው /አመልካቹ/ ንብረት ሀራጅ በሚባልበት ወቅት ስድስት ሰዎች በቦታው ተገኝተው የነበረ መሆኑንና በመጨረሻ አንደኛው ብቻ ቀርቶ ንብረቱን የገዛ መሆኑን ሁለቱም ተከራካሪዎች አልተካካዱም፡፡ አመልካቹ የመጡት ገዢዎች ምክንያቱን በማላውቀው ሁኔታ ከግቢ ሲወጡ አገኘሽቸው ያለ ሲሆን በተጠሪዎቹ በኩል የመጡት ገዢዎች የሄዱት አመልካቹ ይህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ሌላ ዕዳ አለበት ብትገዙት ጣጣ ውስጥ ትገባላችሁ በማለቱና ሁከት በመፍጠሩ ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ ቀርበው የነበሩት ስድስት ሰዎች ውስጥ በጨረታ አሸናፊ የሆነውና ብቸኛ ተጫራች ነው የተባለው ሰው ሲቀር ቀሪዎቹ ጨረታውን በአግባቡ ለመከታተል የማያመች ሁኔታ በመፈጠሩ ወይም በመኖሩ ምክንያት ጥለው እንደሄዱ ግራ ቀኙ ተማምነዋል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አንድን ንብረት በግለጽ ጨረታ ለመግዛት የተሰበሰቡ ሰዎች በተከራካሪዎቹ ወይም ከተጫራቾቹ አንደኛው በፈጠረው ሁከት ወይም በሌላ ሶስተኛ ሰው ተግባር ምክንያት ጨረታውን በመተው ሲበተኑ አንደኛው ሰው ቢቀርና ሀራጅ ባዩ ለቀረው ሰው ንብረቱን ቢሸጥ ጨረታው በአግባቡ ተፈጽሟል ማለት ይቻላል ወይ? የሚለው ነው፡፡

አንድ ንብረት ሀራጅ በሚባልበት ጊዜ በጨረታው ለሚሳተፍ ጨረታውን ለሚያስፈጽሙና ሌሎች ሰዎች የሀራጅ ሂደቱን በተረጋጋ ሁኔታ የሚከታተሉበት፣ ሰላማዊ ሁኔታ መኖሩ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ጥፋቱ በማንኛው ተከራካሪ በኩል እንደተፈፀመ ለማየት ባይቻልም በሀራጅ ጨረታውን ለመሣተፍ ከመጡት ስድስት ሰዎች ውስጥ ከአንደኛው በስተቀር ሌሎቹ በወቅቱ ለመወዳደር የሚያስችላቸው ምቹና የተረጋጋ ሁኔታ ባለመኖሩ ጨረታውን ትተው ለመሄድ እንደተገደዱ በመዝገቡ ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ያሣያል፡፡

ስለሆነም አንድን ንብረት በሀራጅ ለመግዛት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆነ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ከመጡና በጨረታውም ለመሣተፍ እንደመጡ ከገለጹ በኋላ ከተከራካሪዎቹ በአንደኛው ወይም በሌላ ሶስተኛ ወገን ወይም በአጋጣሚ በተፈጠረ አደጋና ክስተት ተደናግጠው ሌሎቹ ጥለው ሲሄዱ አንደኛው ብቻ ቢቀር ፍርድ አስፈፃሚው ንብረቱን ለመጫረት የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ እንደሆነ በመቁጠር ጨረታውን ማከናወኑ የፍርድ አስፈፃሚው በአሻሻጡ ሥርዓት ላይ

ግዙፍ የሆነ ስህተት እንዳልፈፀመ ተደርጎ መታየት የለበትም፡፡ ምክንያቱም የሀራጅ ሽያጭ በሂደቱ ለመካፈል የሚፈልጉ ሁሉም ተሣታፊዎች ለደህንነታቸው የሚያሠጋቸውና የሚያስፈራቸው ሁኔታ ሣይኖር በተረጋጋ ሁኔታ በሀራጁ ተሳትፈውና ተወዳድረው ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበው አሸናፊ የሚሆንበት የሽያጭ ሥርዓት በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ሀራጅ በሚባልበት ጊዜ በተፈጠረው ሁከት ሣይደናገጥ ወደ ኋላ የቀረው ተጫራች እንደ ብቸኛ ተጫራች በመውሰድ በፍርድ አስፈፃሚው በኩል ሽያጩ መከናወኑ በንብረቱ አሻሻጥ ላይ የሚታየው የመጀመሪያው ግዙፍ ጉድለት በመሆኑና ይህም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 455 መሠረት ሽያጩን ለማፍረስ የሚያስችሉት መሠረታዊ ምክንያቶች መሆኑ “... በአሻሻጡ ሥርዓት ላይ ግዙፍ የሆነ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ከተፈፀመና ...” ይህም በአመልካች ላይ መሠረታዊ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ ሀራጁን ለማፍረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት እንደሆነ ሕጉ ካስቀመጣቸው ድንጋጌዎች ለመረዳት እየተቻለ፣

በያዝነው ጉዳይ ንብረቱን ለመግዛት ስድስት ሰዎች ቀርበው በጨረታው ለመወዳደር እንደሚፈልጉ ገልፀውና መታወቂያቸውን ካስያዙ በኋላ በዕለቱ በተፈጠረው ምቹ ያልሆነ ሁኔታና ሁከት ሌሎቹ ሲሄዱ ወደ ኋላ የቀረውን ተጫራች እንደ ብቸኛ ተጫራች በመቁጠር የፍርድ አስፈፃሚው ሽያጭ ማከናወኑ ምንም ዓይነት ስህተት እንደሌለበት በመቁጠር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428 ንዑስ አንቀጽ 1 በመጥቀስ የሰጠው ትዕዛዝ የክርክሩን መሠረታዊ ጭብጥ የሳተና ከላይ የተነሱትን መሠረታዊ ነጥቦች ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ አመልካቹ ንብረቱ የተሸጠው በሀራጅ ሽያጭ መሠረት አይደለም በማለት የተከራከረ በመሆኑና ከፍተኛው ፍርድ ቤትም ሆነ ተጠሪው በድርድር በሚመስል ሁኔታ ዋጋው የተወሰነ መሆኑን የሚያመላክት አገላለጽ የተጠቀሙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ ንብረቱ የተሸጠው በሀራጅ ሽያጭ ሥርዓት መሠረት ነው ወይስ በድርድር የሚለው ነጥብ መታየት ይኖርበታል፡፡

አንድ ንብረት በሀራጅ ሲሸጥ፣ የዋጋው ከዜሮ ሊነሣ ወይም ንብረቱ የሚሸጥበት ዝቅተኛ ዋጋ ተገምቶ ሊካሄድ እንደሚችል ይታወቃል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ንብረቱ የሚሸጥበት ዝቅተኛ ዋጋ ተገምቶ ቀርቧል፡፡ ንብረቱን በጨረታ አሸናፊ ሆኗል የተባለው ሰው መጀመሪያ የሰጠው ዋጋ ንብረቱን በግምቱ ማለትም በብር 438,946 /አራት መቶ ሰላሣ ስምንት ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ ስድስት ብር/ ለመግዛት ነበር፡፡ ይህ ገዢ ያቀረቡት የመግዣ ዋጋ ፣ ሌሎች ተጫራቾች ቢኖሩ የተሻለ ዋጋ በማቅረብ ለማፍረስና በመጨረሻም ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበው የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ግቡን የሚፈጽምበት ሥርዓት ትክክለኛው የሀራጅ የሽያጭ ሥርዓት እንደሆነ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1688 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ንብረቱን የገዛው ሰው ብቸኛ ተጫራች ነው፡፡ ይህ ሰው ንብረቱን በመነሻ ዋጋ ለመግዛት ዋጋ ሲያቀርብ ሀራጅ ባዩ በዚህ ዋጋ ከተስማማ ሽያጩ መፈፀሙን ማሣወቅ በተጫራቹ የቀረበው ዋጋ በቂ አይደለም ብሎ ካሰበ ደግሞ ሂደቱን በማቆም ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማድረግ ሲገባው የቀረበውን ብቸኛ ተጫራች የተባለውን ሰው ንብረቱን ለመግዛት ከቀረበው ዋጋ በላይ ሀራጅ ባዩ ይህንን ያሕል ጨምረህ ውሰድ በማለት ሽያጭ መፈፀሙ ከገዢው ጋር ንብረቱ የተሸጠበትን ዋጋ በድርድር የወሰነው መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ እያለ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን እንደ ትክክለኛ የሀራጅ ሽያጭ መቀበሉ ተገቢ ባለመሆኑና ክርክር የተነሳበት ንብረት የሀራጅ ሽያጭ ሥርዓትን ተከትሎ ሣይሆን ያለ ፍርድ ቤቱ ልዩ ፈቃድ ሀራጅ ባዩ ከገዢው ጋር ባደረገው የዋጋ ድርድር የተሸጠ መሆኑን ስለሚያሣይ ይህም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 422 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የሚጥስ

መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት አፈፃፀም በመሆኑ በአጠቃላይ የሀራጅ ሽያጩ በሚፈፀምበት ጊዜ ከላይ የተገለጹት ሁለት መሠረታዊ ግዙፍ ጉድለቶች በመሆናቸውና እነዚህም ጉድለቶች በመልካቹ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የሚያደርሱ መሆናቸው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በፍርድ አስፈፃሚው የተሠራ መሠረታዊና በአመልካች ላይ ጉዳት የሚያስከትል ጉድለት የለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ይግባኙ የሚያስገባ በቂ ምክንያት የለም በማለት ይግባኙ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት እንዲሰረዝ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ከዚህ በፊት የተደረገው የሀራጅ ሽያጭ መሠረታዊ ግድፈት ያለበት በመሆኑ በዚህ ፍርድ ቤት የተሰረዘ መሆኑን አውቆ ድርጅቱ እንደገና በሀራጅ እንዲሸጥ በማድረግ አፈፃፀሙን እንዲያስቀጥል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሣኔው ግልባጭ ከመሸኛ ጋር ይላክ፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፣ መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 22930

ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሠ

መድሕን ኪሮስ

ዓለ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ታድሬ አባተ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዓለም ገ/የሱስ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ መዝገብ በአፈፃፀም ላይ የተነሣን ክርክር የተመለከተ ሲሆን የአፈፃፀም ክሱ የተመሠረተው በአ/ብ/ክ/መ የሠሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁን ተጠሪ ነበር፡፡ የአሁን ተጠሪ ክሣቸውን ያቀረቡት አሁን በክርክሩ ውስጥ በሌሉት በአሁን አመልካች የቀድሞ ባለቤት በነበሩት በመሪጌታ መዘምር ዕዑብ ላይ ነው፡፡ የአፈፃፀም ክሱም ይዘት ተከሣሹ መሪጌታ መዘምር ዕዑብ በተጠሪዋ ላይ ላደረሱት የአካል ጉዳት የሞራል ካሣ 1000 ብር የተወሰነልኝ በመሆኑ ተከሣሹ ይህን ውሣኔ በፍርድ ተገደው ይፈጽሙ የሚል ነው፡፡ የሠሜን ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤትም የአፈፃፀም ተከሣሽ ንብረት ነው በተባለው ቤት ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ትዕዛዝ የሠጠ ሲሆን በዚህ ወቅት አመልካች ተቃዋሚ ሆነው በመቅረብ ይህንን ቤት ከባለቤቱ ከመሪጌታ መዘምር ዕዑብ ጋር በፍቺ ተለያይተን በንብረት ክፍፍሉ ወቅት የእኔ ድርሻ የሆነ በመሆኑ ለአፈፃፀም ሊውል አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የሠሜን ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤትም ታህሳስ 12/98 ዓ.ም. በሠጠው ትዕዛዝ "ጣልቃ ገብና የአፈፃፀም ተከሣሽ በመጋቢት 18/95 ዓ.ም ጋብቻቸውን አፍርሰዋል፣ ይሁን እንጂ ውሣኔው የተወሰነው በሠኔ 25/96 ዓ.ም ነው፡፡

በዚህ መሠረት እዳው እንደ ጋራ እዳ ስለሚገመት አፈፃፀሙ ጣልቃ ገብ ንብረቴ ነው በምትለው ቤት ይቀጥል" ብሏል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የቀረበበት የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሠበር አቤቱታውም የቀረበው የሠሜን ጎንደር ዞ/ከ/ፍ/ቤት አፈፃፀሙ በቤቱ ላይ ይቀጥል ሲል የሠጠው ትዕዛዝም ሆነ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይህን ትዕዛዝ ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው በሚል ነው፡፡ አመልካች ጥር 29/98 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ይዘት ሲጠቃለል፣ ከውሣኔ በፊትም ይሁን በኋላ ስንለያይ በፍ/ቤት የፍቺ ውል ቀርቦ ንብረታችንን ተካፍለን ካደርን በኋላ ይህ በግሉ የተወሰነበት እዳ በግሉ ተካፍሉ ባደረው ንብረት ላይ ውሣኔ መስጠት እየተቻለ በግል በእኔ ንብረት ላይ ትዕዛዝ መስጠቱ አላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ የሠበር ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ፣ ብር 1000 እንዲከፍል የተፈረደበት ባልየው ሌላ የግል ንብረት ወይም በክፍፍል ያገኘው ንብረት አለ እየተባለ ሚስት በክፍፍል በደረሣት ወይም በግል ንብረቷ ላይ ዕዳው መፈፀም አለበት በሚል የተወሠነው በህጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት መዝገቡን ለሠበር ሊቀርብ ይገባል ሲል በየካቲት 24/98 ዓ.ም ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ መልሣቸውን በጽሁፍ ይዘው ያልቀረቡ ከመሆኑ ባሻገር የግራ ቀኙን ክርክር ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ባለመቅረባቸው ክርክር ለማቅረብ እንዳልፈለጉ በመቁጠር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ በቀረበው ጉዳይ አመልካች ከባለቤታቸው ጋር ፍቺ የፈፀሙት በመጋቢት ወር 1995 ዓ.ም ለመሆኑ በሠበር ማመልከቻቸው እና ለችሎቱም በቃል ከማስረዳታቸው ባሻገር የሠሜን ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤትም አረጋግጦ የመዘገበው ስለመሆኑ ከመዝገቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአመልካቿ ባለቤት በሠው ላይ የአካል ጉዳት በማድረሣቸው የሞራል ካሣ ብር 1000 እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው ሠኔ 25/1996 ዓ.ም ለመሆኑ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪዋ በሥር ፍ/ቤቶች ክደው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መከራከራቸውን የሚያመለክት ነገር የለም፣ በዚህ ችሎትም ቀርበው አልተከራከሩም። ይህ በሆነበት ሁኔታ ፍቺ ተፈጽሞ የንብረት ክፍፍል ከተፈፀመ በኋላ አንደኛው ተጋቢ ላመጣው እዳ ሌላኛው ተጠያቂ የሚሆንበት የህግ አግባብ የለም። ይህ በእንዲህ እያለ የሞራል ካሣ የተወሰነው በጋብቻ ውስጥ አይደለም እንጂ በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ነው ቢባል እንኳ ጋብቻው በፍቺ ከፈረሠ በኋላ ለሚጠየቅ እዳ፣ እዳው የሚመለከተው አንደኛውን ተጋቢ በሆነ ጊዜ የእዳው ክፍያ ሊጠየቅ የሚችለው ባለእዳ ከሆነው ተጋቢ ብቻ እንደሚሆን የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አ/ቁ/79/95 በአንቀጽ 104/2/ ላይ በግልጽ ተደንግጓል። በተያዘው ጉዳይ ደግሞ የተጠየቀው እዳ የአመልካቹ እና የባለቤታቸው የጋራ እዳ ወይም ደግሞ ለጋራ ጥቅማቸው ሲባል የመጣ እዳ ሣይሆን ከአመልካቿ ባለቤት የግል ተግባር የመነጨ እዳ ለመሆኑ መገንዘብ አያዳግትም። ስለሆነም ይህ እዳ አፈፃፀም የተጠየቀበት ከፍቺ በኋላ እስከሆነ ድረስ የአመልካቿ ድርሻ ለዚህ እዳ ማስፈፀሚያ የሚሆንበት ምክንያት አልተገኘም።

ው ሣ ኔ

1. የአ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 07974 በ8/5/98 የሠጠው ትዕዛዝ ተሽሯል። ይፃፍ።
2. የሠሜን ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 01772 በ12/4/98 የሠጠው ትዕዛዝ ተሽሯል። ይፃፍ።
3. የአመልካቿ ንብረት በቀድሞ ባለቤቷ ላይ ለተፈረደው የሞራል ካሣ ብር 1000 ክፍያ ማስፈፀሚያ ሊውል አይገባም ብለን ወስነናል።
4. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ። መዝገቡ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 23733

ህዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች መንበረፀሐይ ታደሠ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- 1. ሃፍቶም ገ/አብዝጊ ቀረቡ

2. ተኪኢን ገ/አብዝጊ

ተጠሪዎች፡- 1. ሙሉ ካሣ

2. ባይራይ አረጋይ

3. አዜብ አረጋይ - } ቀረቡ

4. አታክልቲ አረጋይ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የአፈፃፀም ክርክር ነው። አመልካቾች በወረዳ ፍ/ቤት ክርክር የተነሣበትን ቤት በውሣኔ መሠረት ለመከፋፈል የአፈፃፀም ክስ አቀረቡ። ፍ/ቤቱም በባለሙያ በተገመተው መሠረት አመልካቾች ድርሻቸውን እንዲቀበሉ ሲጠየቁ ፈቃደኞች አልሆኑም በማለት አፈፃፀም መዝገቡን ዘግቴአለሁ። የከፍተኛ ፍ/ቤቱም ይህ የአፈፃፀም ትዕዛዝ በግባቡ የተሠጠ ነው ሲል የይግባኝ ቅሬታውን ሰርዞታል። በተመሣሣይ ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትና ሠበር ችሎቱ የአመልካቾችን ቅሬታ ባለመቀበል መዝገቦቹን ዘግተዋል።

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው። ቅሬታውም ግምቱ አንሷል ፣ በግምቱ መሠረት እዳ ከፍለን ቤቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንድናስቀር ጠይቀን ተቀባይነት አላገኘንም ይህ ካልሆነ ደግሞ በጨረታ ተሸጦ እኩል እንካፈላለን እንጂ መበላለጥ የለብንም የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአፈፃፀም ትዕዛዝ የተሠጠው በውሣኔው መሠረት መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ የሠበር አቤቱታው ለተጠሪዎች ደርሶ ግራ ቀኙ የቃል ክርክር አሠምተዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን አንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ የፍርድ አፈፃፀምም በፍርድ የተገኘ መብት ውጤት እንዲሠጥ እና የፍርድ ባለመብቱ የተወሠነለትን ነገር አንዲያገኝ የሚከናወን ስርአት ነው፡፡ በመሆኑም በፍርድ አፈፃፀም ጊዜ ፍ/ቤቶች ሊያስፈፅሙ የሚገባው በተሠጠው ፍርድ መሠረት ነው፡፡ በእርግጥ ፍርዱን በሚያስፈጽምበት ጊዜ ፍርዱ ውጤት እንዲያገኝ አመቺ የሆነ የአፈፃፀም ስርአት ሊከተሉ ይገባል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን በአፈፃፀም ወቅት የተሰጠው ፍርድ በተለየ መልኩ ውሣኔው እንዲፈጸም ሊያደርጉ የሚያስችላቸው የህግ መሠረት የላቸውም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ላይም አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች የሠጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ውሣኔውን መሠረት ያላደረገ መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ እኛ እንደተመለከትነው በዋናው ውሣኔ አሁን ክርክር የተነሳበት ቤት ወራሾች እንዲከፋፈሉት ተወስኗል፡፡ ከወረዳ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ለማየት እንደሚቻለው ቤቱን መካፈል የሚችል ከሆነ እንዲካፈሉ፣ የማይካፈል ከሆነ ግን በባለሙያ ተገምቶ ይውሠዱ የሚል ነው፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ወይም ተጠሪዎች ግምቱን ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ የተሠጠ ውሣኔ የለም፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ ከተስማሙ ቤቱን እንዲካፈሉ መካፈል የማይችሉ ከሆነ ግን አንደኛው ወገን ግምቱን ከፍሎ እንዲያስቀር መብቱ የተጠበቀለት ባለመሆኑ ያለው አማራጭ ቤቱ

ተገምቶ በሃራጅ ተሸጦ የሸያጩን ገንዘብ በድርሻቸው መጠን መከፋፈል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ተጠሪዎች ግምቱን ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ መብታቸው ተጠብቆ የተሠጠ ውሣኔ ሣይኖር ለአመልካቾች ግምት ተከፍሏቸው ቤቱን ተጠሪዎች እንዲያስቀሩ የሠጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ስህተት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የትግራይ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት በመ/ቁ 12350 በ08/06/98 የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የህግ ስህተት የለውም በማለት የሠጠው ውሣኔ እና የሥር ፍ/ቤቶች የሠጡት የአፈፃፀም ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ክርክር የተነሣበትን ቤት ግራ ቀኙ ከተስማሙና ከተቻለ በድርሻቸው መጠን እንዲከፋፈሉ፣ በዚህ የማይስማሙ ወይም መካፈል የማይቻል ከሆነ ቤቱ ተገምቶ በሃራጅ ተሸጦ ከሸያጩ ገንዘብ ላይ ግራ ቀኙ በድርሻቸው መጠን እንዲከፋፈሉ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ በመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 23989

ታህሣሥ 17 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አቶ ደስታ ሠርዳ

ተጠሪ፡- የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ክርክር የተጀመረው በስር የአፈፃፀም ተከሣሽ በነበረው አቶ አምሣሉ ኤቢሣ ላይ ያስፈረደበትን ገንዘብ ለማስመለስ የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ የአፈ/መ/ቁ. 01378 አስከፍቶ የዚሁ የፍ/ባለእዳ የሆኑትን ሁለት የመኖሪያ ቤቶችና አንድ መጋዘን በመሐንዲስ አስገምቶ ለመተከል ዞን ከ/ፍ/ቤት በማቅረቡ፣ የአሁኑ አመልካች ከመኖሪያ ቤቶቹ መካከል በኤበች በር የሚገኘውን ግምቱ 6,340 ብር የሆነውን ቤት ቀድሞ ለእኔ በሽያጭ ስለተላለፈልኝ አፈፃፀሙ በቤቱ ላይ ሊቀጥል አይገባም ሲሉ በመቃወም በመቅረባቸው ነው፡፡ ከማመልከቻውም ጋር ቤቱን ከአፈ/ተከሣሹ ላይ ለመግዛታቸው ያስረዱልኛል ያሏቸውን ለቤቱ ሽያጭ ለወንበራ ወረዳ ማዘጋጃ ቤት በ17/2/97 በካርኒ ንምራ ቁጥር 84777 የተከፈለ ብር 140 እና የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ ቀርቦ የፀደቀ የቤት ሽያጭ ውል አያይዘዋል፡፡ የዞኑ ከ/ፍ/ቤትም የአፈ/ከሣሹ ንብረት ይጣራ ብሎ ከማመልከቱ አስቀድሞ ቤቱ የተሸጠ በመሆኑ፣ለአፈፃፀም የተያዘው በኤበች በር አካባቢ የሚገኘው መኖሪያ ቤት የተቃዋሚው ሕጋዊ ንብረት በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ ይለቀቅለት ሲል ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪም በፍ/ቤቱ ውሣኔ ቅር በመሰኘቱ ቅሬታውን ለቤ/ን/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ተዘዋዋሪ ችሎት በይግባኝ አቅርቧል፡፡ የይግባኙም ፍሬ ሀሣብ በአጭሩ፣ በተጠቀሰው ንምራ ቁጥር የተደረገው ክፍያ የንግድ ትርፍ ግብርና የቴምብር ቀረጥ የተፈፀመበት እንጂ የስም ማዛወር የተደረገበት አይደለም፣ ውሉ በዞኑ ፍትህ መምሪያ ቢፀድቅም መፅደቁ የስም ማዛወር ተግባር አይደለም፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1185 እና 2878 መሠረት የቋሚ ንብረት ሽያጭ ውል ፀድቆ ስም ዝውውር አልተፈፀመም የሚል ነው በዚሁ የይግባኝ መዝገብ ውስጥ የስር አፈፃፀም ተከሣሽ 1ኛ መ/ሰጭ የነበረ ሲሆን በመልሱም የሽያጭ ውሉን በተዋዋይነት መፈረሙንና ውሉም በፍ/መምሪያው ፀድቆ መመዝገቡን ገልፆ የስም ዝውውሩን በተመለከተ በተለያዩ ምክንያቶች በቶሎ አለመፈፀሙን አስረድቷል፡፡ በይግባኝ መዝገቡ 2ኛ መ/ሰጭ የነበረው የአሁን አመልካች በበኩሉ ቤቱን በሕጋዊ መንገድ ለመግዛቱ በበቂ ማስረጃ ያስረዳሁ በመሆኑ ይግባኙ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡

የክልሉም ወ/ፍ/ቤት ለውሣኔው መንደርደሪያ ይሆነው ዘንድ፡ ∀የሽያጭ ውል ሰነድ መቅረቡ፣ይህም ውል በፍ/መምሪያው የፀደቀ መሆኑ እና የሽያጭ ታክስ የተከፈለበት የሠነድ ማስረጃዎች መቅረባቸው ቤቱ ለ2ኛ መ/ሰጪ ተሸጧል ወይም ተዘዋውሯል ማለት እንችላለን ወይ?∀ የሚል ጭብጥ ይዞ መዝገቡን መርምሯል፡፡ በውሣኔውም አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀበትነት በውል ወይም በኑዛዜ ለማስተላለፍ ምዝገባ ወሣኝ መሆኑን፣ ንብረቱ የሚተላለፈው በሽያጭ ከሆነም ሽያጩ ተከናውኖ በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ርስት መመዝገቢያ ደብተር ተመዝግቦ ስሙ ተዘዋውሮ የምስክር ወረቀት ሊሰጠው እንደሚገባ፣ ይህም ሲሆን ሦስተኛ ወገን መብታቸውን በመንካቱ ንብረቱ አላግባብ የሚተላለፍ ከሆነ ተቃውሞ በማንሣት መከራከር እንደሚችሉ የፍ/ብ/ቁ. 1195(1)፣ 1185 እና 2878 ጠቅሶ አትቷል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ የሽያጭ ውሉ በሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመመዝገብና የማዛወር ስልጣን በተሰጠው አካል ስመርስቱ ወደ 2ኛ መ/ሰጪ ባለመዛወሩ፣ ይህ ውል በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም በማለት የዞኑ ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር አፈፃፀሙ በቤቱ ላይ ሊቀጥል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የክልሉ ወ/ፍ/ቤት በ30/5/98 ዓ.ም በመ/ቁ/ ዐ0891 የሰጠውን ውሣኔ ለማስለወጥ የቀረበ ነው፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት አቤት ያሉት ቤቱን በመተከል ዞን ለፍትህ መምሪያ በፀደቀ ሕጋዊ የሽያጭ ውል መግዛቱ በማንኛውም ወገን ያልተስተባበለ ሆኖ ሣለ፣ስመርስቱ በአመልካች ስም ባለመዘዋወሩ በቻ በቤቱ ላይ መብት የለህም ተብዬ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው በማለት ነው፡፡ ተጠሪም ለመልሣቸው የአንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤት መሆን የሚቻለው በመግዛት ብቻ ሣይሆን በፍ/ብ/ሕጉና በሌሎች የማዘጋጃ ቤት ደንቦች መሠረት በርስት መዝገብ ተመዝግቦ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በመያዝ ሊሆን ይገባል፤ ስለዚህም አመልካች በቤቱ ላይ መብት ስለሌላቸው አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡አመልካችም በጽሁፍ የመልስ መልሣቸውን አቅርበው ቅሬታቸውን አጠናክረዋል፡፡ ይህም ችሎት መዝገቡን በጥሞና መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም በዚህ ጉዳይ መፍትሔ የሚሻው አብይ ጭብጥ ክርክር የተነሣበትን ቤት አመልካች የገዙት መሆኑና ውሉም ተመዝግቦና በቤቱ ማህደር ተያይዞ እያለ፣ የባለቤትነት ስሙ በአመልካች ባለመዘዋወሩ ብቻ በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም በሚል አፈፃፀሙ ቤቱ ላይ እንዲቀጥል መደረጉ አግባብ ነው ወይ?∀ የሚለው ነው፡፡

የቤ/ጉ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2878 የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች ሽያጭ ውል ውሎችን ለማፅደቅ ስልጣን በተሰጠው አካል ከፀደቁ በኋላ ንብረቱ በሚገኝበት ስፍራ በሚገኝ ማዘጋጃ ቤት ወይም የመሬት አስተዳደር መስሪያ ቤት ርስት መዝገብ ተመዝግቦ

ሲገኝ ሦስተኛ ወገኖች በንብረቱ ላይ ለሚጠይቁት መብት መቃወሚያ ሊሆን እንደሚችል ደንግጓል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ፣ በአቶ ደስታ ሠርዳ እና በአቶ አምሣሉ ኤቢሣ መካከል በጥቅምት 17 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በኅዳር 1 ቀን 1997 ዓ.ም በመተከል ዞን ፍ/መምሪያ የፀደቀ ሲሆን የፍትህ መምሪያው የውሉን መጽደቅ አረጋግጦ ለወንበራ ወረዳ መሣጋጃ ቤት የስም ዝውውሩን እንዲፈጽምላቸው በኅዳር 1 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ መጠየቁን በዚሁም መሠረት የወረዳው ማዘጋጃ ቤት የቤት ሽያጭ ውሉን ከቤቱ ማኅደር ጋር ማያያዙ ታውቋል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሻጩ በመታሠሩ እና በማዘጋጃ ቤቱ የአሠራር ችግር ምክንያት ስመ ንብረቱ በአመልካች ስም ሊዘዋወር አልቻለም፡፡ በመሠረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 የሽያጭ ውሉ በ3ኛ ወገን ላይ ውጤት እንዲኖረው በተዋዋዮቹ ላይ ውላቸውን በመዝገቡ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ አይጥልባቸውም፡፡ ተዋዋዮች በሕግ በተጣለባቸው ግዴታ መሠረት ውሉን በሕግ አግባብ ሥልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ ፈጽመው እንዲመዘገብ ካደረጉ በኋላ ቀሪ የሚሆነውን የስም ማዛወር ተግባር ሊፈጽም የሚችለው የአስተዳደር መ/ቤቱ እንጂ ተዋዋዮች ራሣቸው ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በመሆኑም የስም ማዛወሩን ተግባር መ/ቤቱ አልፈፀመም በሚል ተዋዋች ውሉን ለ3ኛ ወገን መቃወሚያ ሊያደርጉት አይችሉም መባሉ ተገቢ አይደለም፣ ሕጉም አይደግፈውም፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የቤ/ጉ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በጥር 30 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ. ዐ0791 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ በቤ/ጉ/ብ/ክ/መ/የመተከል ዞን ከ/ፍ/ቤት በጥቅምት 15 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ/ 01378 የሰጠውን ውሣኔ አጽንተነዋል፡፡

3/ አፈፃፀሙ አመልካች በገዛው ቤት ላይ ሊቀጥል አይገባም ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 25031

ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልታየወርቅ ኃ/ማርያም - ጠበቃ አርአያ

ተጠሪ፡- አቶ ዓለማየሁ ገለቱ - ጠበቃ ጌታቸው እንግዳ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍርድ ባለመብት የአሁን ተጠሪና በፍርድ ባለዕዳው መካከል አፈፃፀም ቀጥሎ የአሁን አአመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሠረት አፈጻጸሙን በመቃወም ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለተውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ውድቅ በማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የክርክሩ ሂትም ባጭሩ ሲታይ የአሁን አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሠረት ባቀረቡት አቤቱታ አፈጻጸም እየቀጠለበት ያለው በወረዳ 25 ቀበሌ 01 ክልል የሚገኘውና በሟች አቶ አበራ ገብረስላሴ ስም የተመዘገበውን የቤ/ቁ. 650 የሆነውን ቤት ሰኔ 21 ቀን 1995 ዓ.ም. በተፃፈ ውል ከሟች ወራሾች ሕጋዊ ወኪል ከሆኑት ከፍርድ ባለእዳ ከወ/ሮ አልማዝ ከበደ ላይ በብር 140 ሺህ በመግዛት ቤቱን ተጨማሪ ገንዘብ በማውጣት ያሻሻልኩት ሲሆን የፍርድ ባመብት ከቤቱ ሽያጭ ገንዘብ ላይ ድርሻቸውን መጠየቅ ሲችሉ አመልካች

የገዙት ቤት በሐራጅ እንዲሸጥ ያቀረቡት ጥያቄ አግባብነት ስለሌለው የሐራጅ ሽያጩ ቀሪ እንዲሆን ይታዘዝልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም የፍርድ ባለመብትን ክርክር ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችና የፍርድ ባለዕዳ ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የፍርድ ባለመብት እስካልተስማሙ ድረስ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ ድርሻውን እንዲቀበሉ የማይገደዱ ከመሆኑም በላይ አመልካች በሐራጅ እንዲሸጥ በተባለው ቤት ላይ ቀዳሚ መብት የሌላቸው በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡

ይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ትዕዛዝ አጽንቶታል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ለሰበር ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ገና ከመነሻው አቤቱታቸውን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.418 መሠረት ማቅረባቸው አግባብነት ነበረውን? የሚለው ሆኖ ስለተገኘ ከዚሁ አኳያ ተመርምሯል፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ክርክር ሲያደርጉ ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነውና በወረዳ 25 ቀበሌ 01 ክልል የሚገኘው ቁጥር 650 የሆነው ቤት የፍርድ ባለመብት በነበሩት በአሁን ተጠሪና የፍርድ ባለዕዳ በነበሩት በወ/ሮ አልማዝ ከበደ መካከል ዋናው ክርክር ሲደረግ በዚሁ ቤት ላይ ፍርድ ያረፈበት መሆኑን ግራ ቀኙ ተጠይቀው አረጋግጠዋል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ፍርድ አርፎበታል ከተባለ ደግሞ ይሄው ፍርድ ሊሰረዝልኝ ይገባል የሚለው ወገን አቤቱታ ማቅረብ ያለበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት እንጂ በ418 መሠረት ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሁለቱ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች የተለያየ ዓላማና ውጤት ያላቸው ስለሆነ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሠረት አቤቱታ አቅራቢ በዋናው ፍርድ ላይ ምንም ዓይነት ክርክር የሌላውና አፈጻጸም እንዲቀጥል ትዕዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ወገን መሆን አለበት፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የፍርድ ውሣኔ እስከተሰጠ ድረስ ከላይ በተጠቀሰው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት አመልካች ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት መቃወሚያ ማቅረብ ሲገባቸው ፍርድ ባረፈበት ንብረት ላይ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሠረት አቤቱታ ማቅረባቸው ከሥነ ሥርዓት ውጭ የቀረበ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የቀረበውን አቤቱታ ከመነሻው መቀበል ያልነበረበት ቢሆንም ግራ ቀኙን አከራክሮ የሰጠው ትዕዛዝ ግን አቤቱታውን ባለመቀበል ስለሆነ ከውጤት አኳያ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11745 የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46067 ግንቦት 9 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ከውጤት አኳያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሠረት አቤቱታ ለማቅረብ አይችሉም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 26553

ሐምሌ 03 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የባህርዳር ልዩ ዞን ገንዘብ መምሪያ አልቀረበም

መልስ ሰጭዎች፡- 1. የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ ነገረፈጅ

አቶ ደመቀ ተሾመ ቀረበ

2. መክታር መሐመድ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.መ.ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 02096 ግንቦት 30 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የነገሩም መነሻ አመልካች የፍርድ ባለመብት ሆኖ በግብር እዳ ምክንያት ያስወሰነውን ገንዘብ ለማስከፈል የሁለተኛ የፍርድ ባለእዳ ንብረት የሆነው በባህርዳር ከተማ ወረዳ 02 ቀበሌ 13 በካርታ ቁጥር 9333 ተመዝግቦ የሚገኘው የመኖሪያ ቤት እንዲሸጥ አፈፃፀሙን ለያዘው ለምዕ/ጎጃም መስ/ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት ጠይቋል፡፡

ይህም ፍ/ቤት ይህ በአፈፃፀም የተመራው ንብረት በእርግጥም የሁለተኛው የፍርድ ባለመብት መሆኑ ከተረጋገጠ በሐራጅ ይሸጥ ዘንድ ተገምቶ እንዲቀርብለት የባህርዳር ከተማን ማዘጋጃ ቤት አዟል፡፡ ማዘጋጃ ቤቱም ይኸው ይገመት የተባለው ንብረት በ1ኛ መልስ ሰጭ እና በኢ/ያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንግድ ባንክ የብድር ገንዘብ ምክንያት በዋስትና የተያዘ መሆኑን ገልፆ የግምቱን ሥራ ሠርቶ ውጤቱን አስተላልፏል፡፡

በግምቱም መነሻ ጨረታ ተደርጎ ገዢው እንደታወቀ ከሽያጩ ገንዘብ የፍርድ ባለመብቱ የጠየቀው ይከፈል፤ ተራፊው ለፍርድ ባለእዳው ይመለስለት ሲል የከፍተኛው ፍ/ቤት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህ ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ የአሁን 2ኛ መልስ ሰጭ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 418 መሠረት ጨረታው እንዲፈርስ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታውም ፍሬ ቃል በሐራጅ ይሸጥ የተባለው ንብረት በእዳ ምክንያት በመያዣነት የተያዘ መሆኑ በማዘጋጃ ቤት መረጋገጡ ሲታወቅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 423/2//ለ/ መሠረት በወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ ላይ በመያዣ መያዙ መገለጽ ሲኖርበት ይኸው በሥርዓት ስላልተሟላ፤

እንዲሁም ይሸጥ የተባለው ንብረት የማይንቀሣቀስ ሀብት እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 426 መሠረት የጨረታ ማስታወቂያም ወጥቶ ለአንድ ወር ያህል መቆየት ሲገባው ይህ የቆይታ ጊዜ አልተጠበቀም ስለሆነም በአሻሻጥ ሥርዓቱ ላይ ጉድለት የተፈፀመበት ስለሆነ የሐራጅ ሽያጩ በዚሁ ሕግ በቁጥር 445 - 447 በተመለከተው መሠረት ሊሰረዝ፤ ሊፈርስ ይገባል የሚል ነው፡፡

አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤትም ጣልቃ ገብ የክርክሩ ተካፋይ ሆኖ መያዣ የተሰጠበትን የዕዳ መጠን ባልገለፀበት ሁኔታ በቁጥር 423(2)(ለ)መሠረት የመያዣ ልኩን ማወቅ ስለማይቻል በጨረታ ማስታወቂያው ላይ በመያዣ የተያዘ ንብረት መሆኑ አልተገለፀም የሚለው መከራከሪያ ነጥብ ተቀባይነት የለውም፡፡

የጨረታ ማስታወቂያው ማሟላት የሚገባውን አላሟላም ከመባሉ በቀር የሽያጩ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ተከናውኗል፡፡ የማጭበርበር ተግባር ተፈጽሞበታል አልተባለም ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 445 መሠረት የተደረገውን የጨረታ ሽያጭ ማፍረስ አይቻልም እንዲሁም

የጨረታው ሽያጭ ከፀደቀ እና ባለመብቱ በዕዳ የሚፈልገውን ገንዘብ ከወሰደ እና ተራፊው ደግሞ ለባለእዳው ከተመለሰ በኋላ ሽያጩ ይፍረስ ማለቱ የሐራጅ ገዥውን መብት የሚጎዳ በመሆኑ ጨረታው እንዲሰረዝ የቀረበውን ጥያቄ አልተቀበልነውም በማለት ወስኗል፡፡

የይግባኝ አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤት አስቀድሞ በመያዣ በተያዘ ንብረት ላይ ለሌላ እዳ ማስፈፀሚያ እንዲውል ጥያቄ ሲቀርብለት በሐራጅ ማስታወቂያው ላይ በመያዣ መያዙን ሣይገልጽና ጨረታውም በጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ማስታወቂያው ለአንድ ወር መቆየቱን ሣያረጋግጥ ጨረታው መካሄዱን በተቃውሞ አማካኝነት እንደተረዳ ጨረታው እንዲፈርስ ማድረግ ሲገባው ይህን ሣያደርግ ሽያጩ እንዲከናወን አድርጎ ገንዘቡ ለ1ኛ መልስ ሰጭ ለአሁን አመልካች እና ለአሁኑ ሁለተኛ መልስ ሰጭ እንዲከፈል ማድረጉ ሕጉን ያልተከተለ በመሆኑ ጨረታውን አፍርሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 447(5) መሠረት ገንዘቡ ለገዥ ያለ ወለድ እንዲመለስ በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ይታረምልን በማለት ነው፡፡ በአቤቱታው የተጠየቀውም ዳኝነት፣

- 1ኛ/ መልስ ሰጭ በአፈፃፀም ይሸጥ የተባለው ንብረት በሌላ ዕዳ ምክንያት ለማሸጥ የሚገመት ለመሆኑ አስቀድሞ ያውቅ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት ቀርቦ የመያዣ ልኩን ሣይገልፅ በሐራጅ ማስታወቂያው ላይ ንብረቱ በመያዣ የተያዘ መሆኑ አልተገለፀም በማለት ዘግይቶ ሊከራከርበት ስለማይቻል፡-
- የሐራጅ ማስታወቂያውን የሚቆይበትን ጊዜ አስመልክቶ የሚሸጠው ንብረት ባለበት የፍርድ ባለእዳው አንስቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚከራከርበት በቀር 1ኛ መልስ ሰጭ ሊከራከርበት አይችልም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 423(2) (ለ) እና 426 ን መሠረት አድርጎ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ይታረምልን የሚል ነው፡፡

አመልካችና 1ኛ መልስ ሰጭ በዚህ ሰበር ችሎት ባደረጉት የቃል ክርክር በሥር ፍ/ቤት ያደረጉትን ክርክር በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የአሁን መልስ ሰጭ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 415 መሠረት በአፈፃፀም ክሱ ጣልቃ ለመግባትና ጣልቃ ገብቶም የጨረታውን ሽያጭ በማስረከብ ያቀረባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ሁለት ናቸው አንደኛው የአሁን አመልካች ለዕዳ ማስፈፀሚያነት እንዲውል የመራው ንብረት በ1ኛ መልስ ሰጭ የብድር ገንዘብ ምክንያት በመያዣነት የተያዘ መሆኑን እያወቀ እንዲሸጥ ማድረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን ሌላውና ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የአሻሻጥ ሂደቱ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌውን የተከተለ አይደለም የሚል ነው፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በሚመለከት ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059(1) የተመለከተን እንደሆነ ፣

1ኛ/ መልስ ሰጭ ተበዳሪ ለሆነው ለሁለተኛው መልስ ሰጭ በሰጠው የብድር ገንዘብ ምክንያት በሐራጅ ይሸጥ የተባለውን ንብረት በመያዣ የያዘው ስለመሆኑ የተካደ አይደለም፡፡ ክርክር የተነሣውም መያዣ ሰጭው ይህንኑ በመያዣ የተያዘውን ንብረት ለሌላ ሦስተኛ ወገን በማስተላለፉ ሣይሆን ሌላ ገንዘብ ጠያቂ ለዕዳ ማስፈፀሚያነት ተሸጦ እንዲከፈለው በማስያዙ ክሱን እንዲህም ያለ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የማይንቀሣቀስ ንብረት መያዣ መጠቀምን በሚመለከተው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059(1) መሠረት ለአመልካች በቅድሚያ የመያዣ መብት የተሰጠው በመሆኑ ሌላ ገንዘብ ጠያቂ ከሆነው ከአሁኑ አመልካች ቀድሞ በብድሩ ምክንያት የሚጠይቀውን ገንዘብ

እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት የሚሰጠው ካልሆነ በቀር አስቀድሜ በመያዣ ይገዢዋለሁ በመያዣ የያዝኩት መሆኑን አመልካች እያወቀ እንዲሸጥ መጠየቅ አልበረበትም ሲል የጠየቀው ዳኝነት ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም ለምን ቢባል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3084 እንደተመለከተው ምንም እንኳ አንድ ንብረት በዕዳ ምክንያት በመያዣነት ሲያዝም ባለዕዳው የህንኑ ንብረት ለመሸጥ ለመለወጥ የሚችል በመሆኑ መያዣ የያዘው ገንዘብ ጠያቂ ያለው መብት ቢኖር ከላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059(1) መሠረት ገንዘብ በቅድሚያ የማግኘት መብት ብቻ ነው ። ከዚህም የምንረዳው በመያዣ የተያዘ ንብረት ሊሸጥ የሚችል መሆኑን ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በአንድ በኩል በአሻሻጥ ሥርዓቱ ላይ ጉድለት የተፈፀመበት ነው የሚለውን በውሣኔው መሠረት ካደረገ በኋላ በስተመጨረሻ ጨረታው ፈራሽ ነው የሸያጩ ገንዘብ ለገዢው ያለወለድ ይመለስለት በማለት መወሰኑ በውስጠ ታዋቂነት ይህንኑ ንብረት 1ኛ መልስ ሰጭ አስቀድሞ በመያዣነት ቢያዝም መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ሊሸጥ አይገባውም የሚለውን መልዕክት የያዘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የተደረገው የሐራጅ ሽያጭ ተሰርዟል በሚለው ጉዳዩን ቋጭቶ መቆሙ ከላይ በተመለከተው ምክንያት የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

በአሁን አመልካች ጠያቂነት ይኸው ይሸጥ የተባለው ንብረት ለዕዳ ማስከፈያ እንዲውል ማሸጥ ይቻል ዘንድ ተገምቶ እንዲቀርብ ሲታዘዝ በሌላ የብድር ገንዘብ ምክንያት በመያዣነት የተያዘ መሆኑን ገልፆ እንዲገምት የታዘዘው ማዘጋጃ ቤት አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አስታውቋል፡፡ እንደ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 423(2)(ለ) መፈፀም ይቻል ዘንድ ፍርድ ቤቱ በእራሱ አነሣሽነት የመያዣውን ልክ ምን ያህል እንደሆነ ማዘጋጃ ቤቱን በትእዛዝ ጠይቆ መረዳት ሲቻል 1ኛ መልስ ሰጭ የክርክሩ ተካፋይ ሆኖ የመያዣ ልኩን ባላሣወቀበት ሁኔታ በጨረታ ማስታወቂያው ላይ ይህ አልተገለፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መባሉ ተገቢነት የለውም ሲል የሰጠው ምክንያት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

እንዲሁም የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በማስታወቂያ በተገለፀ ጊዜ ማስታወቂያው ለ30 ቀናት ሣይቆይ በሐራጅ ሊሸጥ እንደማይችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 426 አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ተደንግጎ እያለ ይህ ጊዜ ሣይጠብቅ ለ16 ቀናት ብቻ ቆይቶ እንዲሸጥ መደረጉ ሥነ ሥርዓታዊ ጉድለት የተፈፀመበት መሆኑን ስለሚያመለክት በእነዚህ ሁለት ምክንያቶች የሸያጩ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ መፈፀሙን ስለተረዳን ሸያጩ እንዲፈርስ መደረጉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይሁን እንጂ የመጀመሪያው የሐራጅ ሽያጭ አሻሽጥ ሥርዓት ጉድለት ተገኝቶበት እንዲፈርስ ከተደረገ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን በሚመለከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 447(5) መሠረት ገዥ ነው ተብሎ ለነበረው ወገን የንብረቱ ዋጋ ከእነ ወለዱ ወይም እንደነገሩ አካባቢ ሁኔታ ያለወለድ ገንዘብ የተቀበለው ሰው እንዲመልስ ይደረጋል የሚለው ከመገለፀ በቀር ሌላ የተቀመጠ ውጤት የለም ፡፡ ሆኖም የሸያጩ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወይም በማጭበርበር ምክንያት እንዲፈርስ ከተደረገ የፍርድ ባለመብቱ የጠየቀውን ገንዘብ እንዲያገኝ ባለእዳውም ግዴታውን እንዲወጣ ለማድረግ ሲባል ተገቢ በሆነ መንገድ እና ከማጭበርበር ተግባር ነፃ በሆነ ሁኔታ በድጋሚ ሐራጅ ንብረቱ ሊሸጥ እንደሚችል የሚያከራክር ስላልሆነ ንብረቱ በድጋሚ ሐራጅ ሊሸጥ ይገባል ብለናል፡፡

ንብረቱ በድጋሚ ሐራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በሸያጩ ገንዘብ ላይ የቀዳሚ መብት ያለው ማን ነው? የሚለውን በሚመለከት በአመልካችና በ1ኛ መልስ ሰጭ መካከል የሚነሣውን ክርክር አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለአብነትም ያህል በአዋጅ ቁጥር 286/94 በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059 መሠረት ታይቶ ተገቢው ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በምዕ/ጎጃ መስ/ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት አማካኝነት የተደረገው የሐራጅ ሽያጭ ፈርሷል፡፡ ድጋሚ ጨረታ ይካሄድ በጨረታው ሽያጭ የሚገኘውን ገንዘብ የቀዳሚ መብት ላለው ወገን ክፍያው ይፈፀም፡፡
2. የሥር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡትን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ሽረናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 27574

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ

ተጠሪ፡- የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማህበር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአፈፃፀም የተያዘን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጀ ፍ/ቤት አመልካች የፍርድ ባለመብት፤ ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለእዳ ነበሩ፡፡ አመልካች ለአፈፃፀም ያቀረበችው ውሣኔ በሰኔ 26 ቀን 1996 ዓ.ም በሽምግልና ጉባዔ ተሰጠ የተባለው ነው፡፡ የፍርድ ባለአዳው ለአፈፃፀም ክሱ በሰጠው መልስ ለአፈፃፀም የቀረበው ውሣኔ በአስታራቂ ሽማግሌዎች የተሰጠ የድርድር ሃሣብ እንጂ በፍ/ቤት የሚፈፀም ውሣኔ አይደለም በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይህን ክርክር በመቀበል ለአፈፃፀም የቀረበው ውሣኔ ስልጣን ባልተሰጣቸው አስታራቂ ሽማግሌዎች የተሰጠ ነው፡፡ በግልግል ዳኞች እንደተሰጠ ተቆጥሮ የሚፈፀም አይደለም በማለት የአፈፃፀም ክሱን ዘግቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ስህተት የለበትም በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጎአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ህዳር 17 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪውን አስቀርበን ክርክሩን

አሰምተናል፡፡ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመር የተፈለገው ነጥብ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ለአፈፃፀም ያቀረበችው ውሣኔ በፍ/ቤት ሊፈፀም አይችልም ማለታቸው አግባብ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ፣ ከቀረበው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተመለከተው አመልካች ለአፈፃፀም ያቀረበችው ውሣኔ በ26.10.96 ዓ.ም የተሰጠው ነው፡፡ ይህ ውሣኔ ሦስት አባላት ባሉት የሽምግልና ጉባዔ የተሰጠ ነው፡፡ የሽምግልና ጉባዔው ሊቋቋም የቻለው ጉዳዩ ስለህበረት ስራ ማህበራት በወጣው አዋጅ ቁ. 147/91 መሠረት መታየት ያለበት በሽምግልና ነው ተብሎ በፍ/ቤት ቀደም ሲል በመበየኑ ምክንያት እንደሆነም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በዚህ መሠረት የሽምግልና ጉባዔው ከተቋቋመ በኋላም አመልካች በከሣሽነት፤ተጠሪ ደግሞ በተከሣሽነት ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ በመጨረሻም ጉባዔው ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የሽምግልና ጉባዔው በሰጠው ውሣኔ ላይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ ፍ/ቤቱም የሽምግልና ጉባዔውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ አመልካች የአፈፃፀም ክሱን ያቀረበችው ከዚህ በኋላ ነው፡፡

እንደምንመለከተው በፍ/ቤት ቀደም ሲል በተሰጠው ብይን መሠረት ሦስት አባላት ያሉት የሽምግልና ጉባዔ ከመቋቋሙም በላይ፤ አመልካች እና ተጠሪም የጉባዔውን ስልጣን በመቀበል ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ውሣኔውን የሰጠው የሽምግልና ጉባዔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 215(1) እንደተመለከተው በፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ውሣኔ ሊሰጥ የሚችል አካል ነው ማለት ነው፡፡ በግልግል ወይም በቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች የተሰጠ ውሣኔ የሚፈፀመው በመደበኛ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በሚፈፀምበት አይነትና ሁኔታ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 319(2) በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ግን ይህን በግልጽ የተመለከተውን ሕግ የተከተለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም፡፡ ስለዚህም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በዚህ ጉደይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 3058 ግንቦት 5 ቀን 1997 ዓ.ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39254 ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ ውሣኔው ለሰበር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 28019

ታህሣሥ 1 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ብርሃኔ ገ/እግዚአብሔር - ጠበቃ መሰለ ገ/ጊዮርጊስ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ - ጠበቃ ወንድሙ ግዛው

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የጋራ ንብረት ክፍፍልም በተመለከተ ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሲሰጥ አሁን ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነው በወረዳ 19 ቀበሌ 55 ክልል የሚገኘው ቁጥር 108 የሆነውን ቤት የገበያ ዋጋ ግምት ግማሽ የአሁን ተጠሪ ለአሁን አመልካች ሰጥተው ቤቱን እንዲያስቀሩ ተጠሪ በዚህ መልኩ የቤቱን የገበያ ዋጋ ግማሽ ለአመልካች ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ ግራ ቀኙ ተስማምተው ቤቱን በገበያ ዋጋ ሸጠው የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ገንዘብ ለሁለት እንዲካፈሉ በዚህ መልኩም ቤቱም ለመሸጥ ካልቻሉም በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ የሚል ውሣኔ ሰጥቶ በዚሁ ውሣኔ መሠረት አፈፃፀሙ ቀጥሎ ፍ/ቤቱ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ቤቱን በመሐንዲስ አማካይኝነት ገምቶ ውጤቱን እንዲልክ ትዕዛዝ ሠጥቶ የቤቱ ግምት ብር 83,596.61 እንደሆነ በመግለጽ ክፍለ ከተማው ለፍ/ቤቱ መልስ በመስጠቱ የዚህን ግምት ግማሹን ተጠሪ ለአመልካች ሰጥተው ቤቱን እንዲያስቀሩ በማለት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ሠጥቶ በዚሁ ትዕዛዝ አመልካች ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አፈፃፀሙ የቀጠለው በፍርዱ መሠረት ስለመሆኑ ለሰበር ቀርቦ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ የሚሻውም የጉዳዩ ጭብጥ አፈፃፀሙ የቀጠለው በፍርዱ መሠረት ነው ወይንስ አይደለም የሚለው ሲሆን በዚሁ ነጥብ ላይ በመመስረት አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የጋራ ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10320 መጋቢት 21 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ መሠረትም ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነው በወረዳ 19 ቀበሌ 55 ክልል የሚገኘው ቁጥር 108 የሆነው የጋራ ቤት ከላይ እንደተመለከተው የገበያ ዋጋ ግምቱን ተጠሪ ለአመልካች በመስጠቱ ቤቱን እንዲያስቀሩ ፈቃደኛ ካልሆኑም በሁለቱ የጋራ ስምምነት በገበያ ዋጋ ተሸጦ የሽያጩን ገንዘብ እኩል እንዲካፈሉ ይህም ካልተቻለ በፍርድ አፈፃፀም መመሪያ እኩል በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ሆኖም ግን አፈፃፀሙ ሲቀጥል በዚሁ ውሣኔ መሠረት መፈጸም ሲገባው የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት የሆነው ቤት በክፍለ ከተማው መሐንዲስ በኩል እንዲገመት መደረጉ ከውሣኔ ያፈነገጠ ከመሆኑም በላይ በውጤት ደረጃም ቢሆን የመሐንዲስ ግምትና የገበያ ዋጋ ልዩነት እንዳለው የሚታመን ስለሆነ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ በመ/ቁ. 10320 መጋቢት 21 ቀን 1996 ዓ.ም. ፍ/ቤቱ ከሰጠው ውሣኔ ጋር የተጣጣመ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ

ሲቀርብለት ይህንኑ ስህተት ማረም ሲገባው ይግባኙን ሳይቀበል በመቅረቱ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14724 በ23/9/98 ዓ.ም. የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 47756 በ19/3/99 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 10320 መጋቢት 21 ቀን 1996 ዓ.ም. በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በገበያ ዋጋ አስገምቶ የግምቱን ግማሽ የአሁን ተጠሪ ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ ለአሁን አመልካች ለአቶ ብርሃኔ ገ/እግዚአብሔር በመስጠት ቤቱን እንዲያስቀሩ በዚህ መልኩ ተጠሪ ካልተስማሙ ቤቱን በጋራ በገበያ ዋጋ ሸጠው ገንዘቡን እንዲከፋፈሉ ይህም ካልተቻለ ቤቱ በፍርድ አፈፃፀም መመሪያ በኩል በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲከፋፈሉ እንዲያደርግ ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 28154

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ አለሙ ኢብሳ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ የምስራች ደሳለኝ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን በፍርድ ባለመብት የአሁን ተጠሪና በፍርድ ባለእዳዎች እና አቶ ካሊድ የሱፍ /2 ሰዎች/ መካከል የነበረው የፍርድ አፈጻጸም ክርክር በሥር ፍ/ቤት ቀጥሎ በከፍተኛ 5 ቀበሌ 12 ክልል በ1ኛ የፍርድ ባለእዳ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቁጥር 1267 የሆነው መጋዘን ተሸጦ ሕዳር 3 ቀን 1969 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል በማለት በቅድሚያ መጋቢት 30 ቀን 1979 ዓ.ም ከዚያም በ15/2/97 ዓ.ም የአፈጻጸም ትእዛዝ መስጠቱን ከመዝገቡ የተረዳን ሲሆን 2ኛው የአፈጻጸም ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ በፍርድ አፈጻጸም እንዲሸጥ ትእዛዝ የተሰጠበት መጋዘን ላይ መብት ያለኝ ስለሆነ አፈጻጸሙ በዚህ መጋዘን ላይ ሊቀጥል አይገባም በማለት የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ አቅርቦ አፈጻጸሙን በጊዜው ይዞት የነበረው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃወሚያው ለፍርድ ባለመብት እንዲደርስ በማድረግ አከራክሮ መቃወሚያው በአግባቡ አልቀረበም የሚልበትን ምክንያት በዝርዝር አስፍሮ ተቀባይነት የለውም ብሎ አስቀድሞ በተሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ መሰረት ይሄው መጋዘን ተሸጦ በውሳኔው

ከፍርድ ባለእዳዎች የሚፈለገው ገንዘብ ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚሁ ትእዛዝ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ባለመቀበል ይህንኑ የሥር ፍ/ቤትን ትእዛዝ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ይህም ችሎት በቅድሚያ የተመለከተው የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሰረት አፈጻጸሙን በመቃወም ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበው አቤቱታ ለፍርድ ባለመብት ብቻ እንዲደርስ ተደርጐ የፍርድ ባለእዳዎች በዚህ ላይ ክርክራቸውን ሳያቀርቡ ትእዛዝ መስጠቱን አግባብነት በተመለከተ ነው፡፡

በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ 3ኛ ወገኖች መብት ያቋቋምን ስለሆነ በዚህ ንብረት ላይ አፈጻጸም ሊቀጥል አይገባም በማለት 3ኛ ወገኖች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 418/1/ መሰረት መቃወሚያ ሲያቀርቡ ተከራካሪ ወገኖች ይህንኑ መብት የሚቃወሙ ከሆነ ፍ/ቤቱ የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ እንደሚሰጥ ከተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 ከፍ ብሎ ከተመለከተውና ከቁጥር 419 ድንጋጌ በግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፍርድ አፈጻጸም እንዲሸጥ የተባለው መጋዘን የ1ኛ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ነው እንደተባለ በትእዛዙ ላይ የተመለከተ ሲሆን በዚህ ንብረት ላይ ተቃዋሚው የአሁን አመልካች አፈጻጸሙን በመቃወም አቤቱታ ሲያቀርብ ከላይ ከተጠቀሰው የሥነ ሥርአት ሕጉ ድንጋጌ አኳያ አቤቱታው ለፍርድ ባለመብቱና ለባለእዳዎች ደርሶ የሁሉንም ወገኖች ክርክር በመስማት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 419 መሰረት ፍ/ቤቱ ውሳኔ መስጠት ሲገባው አቤቱታው ለፍርድ ባለመብት ብቻ እንዲደርስ በማድረግ ለዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ትእዛዝ መስጠቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ጉድለት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41092 በሰኔ 22 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 41120 በታህሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሰረት ያቀረበው አቤቱታ ለፍርድ ባለአዳዎችም እንዲደርስ ተደርጐ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ትእዛዝ የቀረበው መዝገብ በመጣበት አካኋን ይመለስ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

የሰ/መ/ቁ. 28362

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች ፡- አቶ መሐመድ ኑር ጅብሪል ቀርቧል፡፡

ተጠሪ ፡- እነ ወ/ሪት ውበት ላሊሶ /3/ ሰዎች ቀርባለች፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በፍርድ አፈፃፀም ላይ የቀረበ አቤቱታ ሲሆን በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ በአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ በፍርድ ባለመብት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንደዚሁም በፍርድ ባለዕዳ 3ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው የአፈፃፀም ክርክር ቀጥሎ በአዋሳ ከተማ በከፍተኛ 1 ቀበሌ 02 ክልል የሚገኝ ቤት በሐራጅ እንዲሸጥ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተሰጥቶ እንዳለ የአሁን አመልካች በፍርድ አፈፃፀም በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የተሰጠበትን ቤት የፍርድ ባለዕዳ /3ኛ ተጠሪ/ በስማቸው ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚያረጋግጥ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት አቅርበውልኝ ቤቱን ከእሳቸው ላይ የገዛሁ ከመሆኑም በላይ ባለቤትነቱ በስሜ ተዛውሮ የሚገኝ ስለሆነ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው ውሣኔ ያለአግባብ በመሆኑን ፍ/ቤቱ ይህንኑ ትዕዛዝ ያንሳልኝ በማለት መቃወሚያ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በፍርድ አፈፃፀም በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የተሰጠበት ቤት አቤቱታ አቅራቢው ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት መሆኑን እየተገነዘበ ከፍርድ ባለዕዳ ላይ ስለመግዛቱ መገንዘብ የተቻለ ስለሆነ አቤቱታው ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አፈፃፀሙ ሊቀጥል ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚሁ ብይን ቅሬታ አድሮባቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታቸውን እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎትም የቀረበው አቤቱታ ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ብሎ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሑፍና በቃል አከራክሯል፡፡

የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ አፈፃፀም ሊቀጥል አይገባም በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት አለማግኘቱ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ጭብጥ አኳያም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም 3ኛ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት በስማቸው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከሚመለከተው መንግስታዊ ተቋም ካገኙ በኋላ ሐምሌ 1 ቀን 1995 ዓ.ም በተፃፈ ውል ለአመልካች በሽያጭ ያስተላለፉ ስለመሆኑ የሽያጭ ውሉ ከተደረገ በኋላም አመልካች እንደውሉ ይፈፀምልን በማለት በ3ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ.ቁ. 340/96 በ2/4/96 ዓ.ም 3ኛ ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ በማለት ውሣኔ መስጠቱንና በዚሁ ውሣኔ መሠረትም አፈፃፀሙ ቀጥሎ እንዳለ 1ኛ ተጠሪ አፈፃፀሙን በመቃወም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 418 መሠረት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም አከራክሮ 1ኛ ተጠሪ አቤቱታቸው በማስረጃ ያልተደገፈ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ብሎ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል በማለት ትዕዛዝ መስጠቱን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

አመልካች በ3ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት 3ኛ ተጠሪ ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ ውሣኔ ከተሰጠ ይሄው ቤት በፍርድ አፈፃፀም በኩል በሐራጅ ተሸጦ ተጠሪዎች ገንዘቡን ሊከፋፈሉ ይገባል ተብሎ የተሰጠውን ውሣኔ ተከትሎ አፈፃፀም ሲቀጥል አመልካች በዚሁ ቤት ላይ

በፍ/ቤት ውሣኔ የፍርድ ባለመብት የሆኑ በመሆኑ አፈፃፀሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል አይገባም በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ግራ ቀኙ በቤቱ ላይ ካቋቋሙት መብት አኳያ ታይቶ የአፈፃፀም ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው አመልካች በዚህ ቤት ላይ መብት የላቸውም በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ አፈፃፀሙ ይቀጥል ተብሎ በአዋሳ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የተሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝና እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስም ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት የተሰጠው ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 147/98 ታህሣሥ 13 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንደዚሁም የአዋሳ ከተማ ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01015 በ18/5/98 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 13987 ታህሣሥ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የፍርድ አፈፃፀም አመልካችና ተጠሪዎች በየበኩላቸው ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ እንዲወስን ለአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ ል ዩ ነ ት ሐ ሳ ብ

የአዋሳ ወረዳ ፍ/ቤት የፍርዱ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል በማለት በሰጠው ትዕዛዝ የይግባኝ ቅሬታ ለሲዳማ ዞን ከ/ፍ/ቤት ቀርቦ በይግባኝ ክርክሩ የአሁኑ አመልካች ተካፋይ ሳይሆኑ ተጠሪዎችን ብቻ በይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አከራክሮ 3ኛ ተጠሪ በሽያጭ ለአመልካች ያስተላለፉት ቤት ሙሉ በሙሉ የግላቸው ሳይሆን የ1ኛ እና የ2ኛ ተጠሪዎችም ድርሻ ያለበት ስለሆነ በሽያጭ ውሉ መሠረት በገዢው ስም ሊዛወር የሚችለው በድርሻቸው ልክ እንጂ የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ድርሻ ጨምሮ ስለማይሆን የወረዳው ፍ/ቤት የቤቱ ባለሃብትነት ሙሉ በሙሉ ወደ ገዢው ይዛወር በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት አሻሽሎ በ3ኛ ተጠሪ ድርሻ ብቻ ስም ይዛወር ሲል ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ ይህ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት እንዳለበት መገንዘብ ቢቻልም በይግባኝ እስካልተለወጠ ተፈፃሚነት ያለው ስለሚሆን አመልካች በአዋሳ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 147/98 አፈፃፀሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል አይገባም በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ ከከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ አኳያ ታይቶ አፈፃፀሙ ሊቀጥል ይገባል በማለት በተራ ቁ. 2 ላይ ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

የሰበር መ/ቁ. 29344

ግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሠ

መድህን ኪሮስ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዝማም ህሉፍ ወኪል ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ መረሣ ገ/ዮሐንስ ጠበቃው ቀርቧል፣፣

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በመቀሌ ዞን ማ/ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46/96 በመስከረም 4 ቀን 1992 ዓ.ም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የቦታ ሽያጭ ውል ፈርሶ ወደነበሩበት እንዲመለሱ በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ተጠሪ ቤት እና ቦታውን ለአመልካች እንዲያስረክቧቸው ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከቱት የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ትዕዛዝ ስህተት የለውም በማለት የቀረበላቸውን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ አድርገውታል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በግራ ቀኙ የተደረገው የቦታ ሽያጭ ውል ሻጭ ባለቤት ሳይሆኑ የተፈፀመ ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ሆኖ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ተወስኗል፡፡ ይህም ማለት ገዢ ገንዘባቸው እንዲመለስላቸው ቦታው ደግሞ ቦታውን ለማስተዳደር ስልጣን ላለው ማዘጋጃ ቤት እንጂ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪ አይደለም በማለት ተጠሪ ለአመልካች ቦታውን እንዲያስረክቡ የተሰጠውን ትዕዛዝ ነው፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የተሰጠው የአፈፃፀም ውሣኔ ዋናውን ውሣኔ የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው ከአመልካች ክርክር የሰበር ችሎቱ የሰጠው የአፈፃፀም ውሣኔ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠውን ፍርድ የሚለውጥ ነው፣ 3ኛ ወገኖች ክርክር ባላቀረቡበት ጉዳይ መብት እንዲያገኙ የሚደረግበት ህጋዊ መሠረት የለም የሚሉ ይገኙበታል፡፡

ይህ ችሎትም ጭብጥ የያዘው በአፈፃፀም የተሰጠው ውሣኔ ዋናውን ፍርድ መሠረት አድርጐ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ስለሆነ ዋናው ውሣኔ ምን ይላል የሚለውን ማየት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም አንድ ውሣኔ የሚያስፈጽም ፍ/ቤት በውሣኔው መሠረት ከማስፈፀም ውጪ በአፈፃፀም ጊዜ ዋናውን ፍርድ ሊለውጥ የሚችልበትን የህግ መሠረት የለውም ለአፈፃፀም ምክንያት ከሆነው ውሣኔ ላይ እንደተገነዘብነውም አመልካች ለከብት እርባታ ተብሎ በጊዜያዊነት የተሰጣቸው የመሬት ሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው ያቀረቡት ክስ እስከ ትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ከታየ በኋላ አመልካች በቦታው ላይ የባለቤትነት መብት ሳይኖራቸው ያደረጉት የሽያጭ ውል ህግን የሚፃረር በመሆኑ ውሉ እንዳልነበር ተቆጥሮ እንዲፈርስና ተዋዋይ ወገኖች የሽያጭ ውል ከማድረጋቸው በፊት ወደነበሩበት ሁኔታዎች እንዲመለሱ ተወስኗል፡፡ ከዚህ ውሣኔ እንግዲህ መገንዘብ የሚቻለው የውሣኔው ውጤት ሻጭ የሸጠው መሬት እንዲመለስለት ገዢ ደግሞ ለሻጩ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡ የሰበር ችሎቱ በዋናው ጉዳይ ላይ ከፍ ሲል የተመለከተውን ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ደግሞ በመቀጠል የመቀሌ ከተማ ቦታን የማስተዳደር ስልጣን የመቀሌ ማዘጋጃ ቤት እሲሆን እያከራከረ ያለው ቦታ

ወደፊት እንደኤት ይሁን የሚለውን ሊወስንና እርምጃ ሊወስድ የሚችለው እራሱ ስለሆነ ተከታትሎ አንድ ነገር የማድረግ መብቱ ተጠብቆለታል ብሏል፡፡ በዚህም ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ግራ ቀኙ ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ከተወሰነ በኋላ የመቀሌ ማዘጋጃ ቤትን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ያለው ነገር ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ዋናው ፍርድ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲወሠን ገዢ የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸው እና ቦታው ግን ማዘጋጃ ቤቱ እንዲረከበው ከመወሰኑ በቀር አመልካችን የፍርድ ባለመብት የሚያደርግ ውሣኔ አልተሰጠም በማለት ለደረሰበት መደምደሚያ መሠረት ያደረገው ከውሣኔው በኋላ ማዘጋጃ ቤቱ ወደፊት ቦታውን በተመለከተ ተገቢ ነው ያለውን እርምጃ እንዲወስድ የተሰጠውን ማሳሰቢያ ነው እኛ እንደተረዳነው ግን ሰበር ችሎቱ ማዘጋጃ ቤቱ ቦታውን አስመልክቶ እርምጃ እንዲወስድ ማሳሰቢያ ከመስጠቱ በቀር ቦታው በክርክሩ ተካፋይ ላልነበረው አካል እንዲመለስ የተሰጠው ውሣኔ አለመኖሩን ነው፡፡

ስለሆነም የትግራይ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው የአፈፃፀም ውሣኔ ከዋናው ውሣኔ ያፈነገጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩል ግን ይህ ችሎት ግራ ቀኙን በቃል በአነጋገረበት ወቅት ቦታው ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪዎች እጅ መሆኑንና ማዘጋጃ ቤቱም ቦታውን ለተጠሪዎች ሰጥቶ ቦታውን የሚመለከቱ ሰነዶች ለመውሰድ በዝግጅት ላይ እንዳሉ በዚህ ችሎት የዕግድ ትዕዛዝ ምክንያት መቆመን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም የቦታው ባለቤት የሆነው ማዘጋጃ ቤት ቦታውን ለተጠሪዎች አሳልፎ መስጠቱን ተረድተናል፡፡ የፍ/ባለዕዳው በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ፍርድን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመፈፀም የማይችል መሆኑን ፍ/ቤቱ ከተረዳው ደግሞ ፍርድ እንዲፈፀም ትዕዛዝ እንደማይሰጥ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 392/2/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዋናው ውሣኔ ውሉ ፈርሶ ቦታው ለአመልካች እንዲመለስ የተወሰነ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ማዘጋጃ ቤቱ ቦታውን ለተጠሪዎች የሰጠ በመሆኑ ፍርዱ ሊፈፀም የሚችል አይደለም፡፡

በዚህም ምክንያት የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት የሰጠውን ምክንያት በመቀየር ውሣኔውን አጽንተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 10962 በታህሳስ 5 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

ተ ጨ ማ ሪ ት ዕ ዛ ዝ

ይህ ችሎት ነሐሴ 14/1999 የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 29371

ታህሣሥ 1 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካቾች፡- 1. ሶፊያ መሐመድ ቀረበች፡፡
2. ከድጃ መሐመድ ቀረበች፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. ኢብራሂም መሐመድ
2. ፋጡማ መሐመድ
} ጠበቃ ዘላለም ባይህ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ መሠረቱ የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም በአፈፃፀም ደረጃ ላይ ያለ ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ለአፈፃፀሙ መሠረት የሆነው ውሣኔ የተሰጠው ተጠሪዎች ወንድማቸው በሆነው አብዱልቃድር መሐመድ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ ተጠሪዎች በአማራ ብ/ክ/መ/የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተከሣሽ ይዞት የሚገኘው ከአባታቸው የተገኘውን የውርስ ሃብት እንዲያካፍላቸው የጠየቁ ሲሆን፣ ተከሣሹም ክሱን አምኖ በመቀበሉ ንብረቱ ተከራካሪዎቹን ጨምሮ ለሰባት /7/ የሚች ልጆች እኩል ይካፈል በማለት ፍ/ቤቱ ወስኖአል፡፡ በመቀጠልም ውሣኔን በስሩ የሚገኘው ባቲ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም ተጠሪዎችንና አብዱልቃድር መሐመድን /የሥር ተከሣሽን/ ብቻ በማከራከር በባቲ ከተማ የሚገኙ አራት ቤቶች እና አንድ መኪና ለተጠሪዎች እንዲሰጡ በማለት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካቾች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና እንደዋናው ውሣኔ አባባል ይፈጸም ዘንድ እንዲታዘዝላቸው በመጠየቅ ለወረዳው ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ግን ቀደም ሲል የሰጠውን ትዕዛዝ አልለወጠም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መዝገቡ በጣም የቆየ በመሆኑና ለአፈጻጸምም ስላስቸገረ ለከፍተኛው ፍ/ቤት መቅረብ አለበት በማለት ትዕዛዝ ስለሰጠ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን መነሻ በማድረግ ጉዳዩን አይቶአል፡፡ በመጨረሻም የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በማሻሻል ንብረቱ በዋናው ውሣኔ መሠረት ሰባቱም ወራሾች እኩል ይካፈሉት በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪዎች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ የታየ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ /ትዕዛዝ/ በመሻር ቀደም ሲል በባቲ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠውን የንብረት ክፍፍል ትዕዛዝ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካቾች መጋቢት 5 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በዋናው ፍርድ ከተሰጠው ውሣኔ በተለይ ሁኔታ የተከናወነውን አፈፃፀም ተፈጽሞ ያለቀ ነው በሚል ብቻ አመልካቾች ዋናውን ፍርድ መሠረት አድርገው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪ ሆኖ የቀረበው እና በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ አፈፃፀሙ ተከናወነ የተባለው በዋናው ፍርድ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነው፡፡ በአማራ ብ/ክ/መ/የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ግልጽ ነው፡፡ በውርስ ተገኘ የተባለው ንብረት የሟች ወራሾች የሆኑት ሰባት ሰዎች እኩል ይካፈሉት የሚል ነው፡፡ ከሰባቱ ወራሾች መካከልም የአሁኖቹ

አመልካቾች ይገኛሉ፡፡ የባቲ ወረዳ ፍ/ቤት በከፍተኛው ፍ/ቤት የታዘዘውም /የተወከለው/ በዚህ መልክ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ንብረቶቹን ለወራሾች እንዲያከፋፍል ነው፡፡ እንዳየነው ግን ንብረቶቹን ለሁሉም ወራሾች እንዲከፋፈሉ አላደረገም፡፡ የተገኙት ንብረቶች እንዳሉ በቀጥታ ለተጠሪዎች ብቻ እንዲሰጡ ነው ያደረገው፡፡ ይህ አካሄድ በግልጽ የሚያሳየው አመልካቾች እና ሌሎቹ ወራሾች በውሣኔ ጭምር ያገኙትን የወራሽነት መብት እንዲያጡ መደረጋቸውን ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም አመልካቾች ትዕዛዝ እንዲታረምና እነሱም ድርሻውን እንዲያገኙ እንዲታዘዝላቸው ፍ/ቤቱን የጠየቁ ቢሆንም፣ ፍ/ቤቱ ተጨማሪ እርምጃ አልወሰደም፡፡ በእርግጥ ጉዳዩ ዋናውን ውሣኔ በሰጠው ከፍተኛ ፍ/ቤት እልባት ማግኘት አለበት በማለት የወረዳው ፍ/ቤት ለከፍተኛው ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሊያርም የቻለውም ይህን መሠረት በማድረግ ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 374/1/ ይመለከቷል/፡፡ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ትዕዛዝ የሻረው ደግሞ አፈፃፀሙ ከመጠናቀቁም በላይ፤ የትዕዛዙም አሰጣጥ ስነ-ስርዓትን የተከተለ አይደለም በማለት ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ክርክሩ እልባት ሊያገኝ የሚገባው በዚህ መልክ ሳይሆን፣ ቀደም ሲል እንዳመለከትነው በዋናው ውሣኔ መሠረት ተፈጽሞአል ወይስ አልተፈጸመም የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ነው፡፡ በዋናው ውሣኔ መሠረት የተከናወነ አፈፃፀም እንደሌለ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም እንደተገነዘበ በውሣኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ በእርግጥ እኛም እንደተገነዘብነው የከፍተኛው ፍ/ቤት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ለማረም የተከተለው አካሄድ ትክክል አልነበረም፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ ይህን አካሄድ ትክክል አይደለም በማለት የሰጠው ትችትም ስህተት ነው የምንለው አይደለም፡፡ ትክክል ሆኖ ያላገኘነው ሁለቱም ፍ/ቤቶች ዋናው ውሣኔ ሊፈጸም የሚችልበትን መንገድ አለማመቻቸታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ ደጋግመን እንደገለጽነው ዋናውን ውሣኔ መሠረት ተደርጎ የተከናወነ አፈፃፀም የለም፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ ውሣኔ እንዲፈጸም የሚቀርበው ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል እስካልተባለ ድረስ አንዱ ትዕዘዝ ተሰጥቶአልና ከዋናው ውሣኔ ውጪም ቢሆን አይነካም ብሎ ማለፍ የሚቻል /የሚገባም/ አይደለም፡፡ ይህ ዓይነቱ አካሄድ ሁለት መሠረታዊ ግድፈቶች አሉት፡፡ የመጀመሪያው እንደ ውሣኔው እንዲፈጸም የቀረበውን ጥያቄ የሕግ ምክንያት ሳይኖር ተቀባይነት እንዳ ኖረው ማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በውርስ ሃብቱ ላይ እኩል መብት ያላቸውን ወገኖች /አመልካቾችና ሌሎች ወራሾች/ ከሕግ አግባብ ውጪ ተካፋይ እንዳይሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ስናጠቃልለው አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ የአፈፃፀም ክርክር የተነሳበትን ዋናውን ውሣኔ መሠረት ያላደረገ እና ውሣኔው የሚፈጸምበትን ሁኔታ ያላሟየ በመሆኑ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 622/98 ጥር 14 ቀን 99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ዋናውን ውሣኔ /የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው/ መሠረት በማድረግ የውርሱን ሃብት አውራሾች እንዲያከፋፍል ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 29653

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሠ ይርጋ

አመልካች፡- 1. አቶ ነጋ ደምስ
2. አቶ ኃይሉ ደምስ } ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 50 አለቃ አዲሱ ደምስ - ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ነው፡፡ የአሁኖቹ አመልካቾች ከሥር አፈፃፀም ባለዕዳ ጋር ተከራክረው ካስወሰኑ በኋላ በውሣኔው መሠረት እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በውሣኔው መሠረት ለማስፈፀም የውርስ ንብረት የሆነውን ቤት በሀራጅ አሸጦ ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ ለማከፋፈል በሒደት ላይ እንዳለ የአሁኑ ተጠሪ እሣቸውም የቀኝ አዝማች ደምስ አስፋው የልጅ ልጅ መሆናቸውንና እናታቸውን ወ/ሮ ይርገዱ ደምስን ተክተው ሊወርሱ እንደሚገባ ገልፀው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ጣልቃ ገብተው ለመከራከር ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካቾች የአፈፃፀም ባለዕዳ የሆኑትን ወ/ሮ እስከዳር ደምስን ከሰው ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ በውርሱ ቤት እስከ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ሲከራከሩ ጣልቃ ገብተው ያልተከራከሩና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ለመቃወም መብት የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ የአያታቸው ፊትአውራሪ ደምስ አስፋው የልጅ ልጅ በመሆናቸው እናታቸውን ተክተው ሊወርሱ ስለሚገባ ከተሸጠው ከፊታውራሪ ደምስ አስፋው ቤት ድርሻ ገንዘቡን ሊያገኙ ይገባል በማለት የመጀመሪያውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑን ስላመነ መ/ሰጪዎቹን አስቀርቧል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነው ክርክሩ የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡ አመልካቾች የሥር የአፈፃፀም ባለዕዳዋን የአባታቸውን የፊታውራሪ ደምስ አስፋውን ቤት አስመልክተው ከሠው አስፈርደዋል፡፡

ይህ የውርስ ቤት የአመልካቾች እናት እና አባት በመሆኑ አመልካቾቹ የሁለቱንም ወላጆችቻቸው ድርሻ የፍ/ባለዕዳዋ ደግሞ የአባታቸውን ድርሻ ብቻ እንዲያገኙ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ለማከፋፈል ጉዳዩ በአፈፃፀም ደረጃ ደርሶ ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ገንዘቡ ተይዟል፡፡ እንግዲህ በዚህ ደረጃ ነው ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት መቃወሚያ ያቀረቡት፡፡ በመሠረቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው አንድን ውሣኔ ለማስፈፀም ንብረት ሲያዝ በንብረቱ ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ሰው ይህ ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር ነው፡፡ ይህ የስነ ስርዓቱ ድንጋጌም የሚመለከተው ለፍርዱ ምክንያት የሆነን ንብረት ሣይሆን ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠን ውሣኔ ለማስፈፀም የተያዘን ንብረት ነው፡፡ ንብረቱ ፍርድ ያረፈበት ከሆነ ግን መብቱ ተነክቷል የሚለው ወገን አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ውሣኔው ከመፈፀሙ በፊት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት ነው በመሆኑም

በዋናው ክርክር ገብቶ ተከራክሮ ውሣኔ ያላገኘ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ጊዜ ውሣኔ እንዲፈፀምለት ጥያቄ የሚያቀርብበት የሕግ መሠረት የለም፡፡

በተያዘው ጉዳይም ቢሆን አመልካቾች የፍ/ባለዕዳዋን ከሰው አስወስነው ውሣኔውን በማስፈፀም ላይ ይገኛሉ ተጠሪ ውሣኔው መብታቸውን የሚነካ ከሆነ ውሣኔውን በመቃወም ቀርበው እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ ማድረግ ነበረባቸው በመሆኑም በውሣኔው ያላገኙትን መብት በአፈፃፀም እንዲከበርላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ቀዳሚነት መብት የሌላቸው መሆኑን እያረጋገጠ የውርስ ንብረት እንዲካፈሉ ሲል የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የለውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10050 መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04241 በሐምሌ 13 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁጥር 33760

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1. ሐጂ ታጁ ለገሠ ቀረበ፡፡

2. መሬም መሐመድ

ተጠሪ፡- የጎንደር ከተማ የመሀል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር ነገረ ፈጅ

ፈረደ ሀይለማርያም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው የአማራ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 11731 መስከረም 6 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አመልካቾች ጎዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በአፈፃፀም የባልና የሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል በሚደረግበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ከዚህ ክርክር አንደኛ አመልካች የሆኑት ሀጂ ታጁ ለገሠ በሁለተኛ መልስ ሰጭ እና ወ/ሮ ሀዋ መሐመድ ጋር በጋብቻ ሲኖሩ የጋራ ንብረት አፍርተዋል፡፡ አንደኛው አመልካች ከወ/ሮ ሀዋ መሐመድ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍች ሲፈርስ የጋራ ንብረታቸውን እንዲካፈሉ ከተሰማሙ ባልና ሚስት ከቀበሌ በተከራዩት ቤት ላይ ያላቸው የንግድ ድርጅት ተካፍለው ኑሯቸውን እንዲመሩ ወስኗል፡፡ ይህንንና ሌሎች የጋራ ንብረቶችን ለማካፈል

ለወ/ሮ ሀዋ መሐመድ የአፈፃፀም ክሳሽነት የአፈፃፀም መዝገብ ተከፍቶ አፈፃፀሙ በሂደት ላይ እያለ ተጠሪው ቤቱ የቀበሌ 02 በመሆኑ ባልና ሚስቱ ንብረታቸው ያልሆነውን ሊካፈሉ አይገባም በማለት ለጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት መቃወሚያ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ የንግድ ድርጅቱ የባልና የሚስት የጋራ ንብረት ነው፡፡ ቤቱን አስመልክቶ የተከራይ መብት ነው ያላቸው ስለዚህ ተቃውሞው ተገቢ አይደለም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ይህንን አውቀውም ተጠሪው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ አጽንቷል፡፡

ተጠሪው ይህንን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቤቱ የቀበሌ ስለሆነ የንግድ ድርጅቱን ሽቀጥና ፅቃ ባልና ሚስቱ እንዲካፈሉ በማለት የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔዎች ሽሮአቸዋል፡፡ አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ባለቤቱ የነበረችው ወ/ሮ ሀዋ መሐመድ በእኔ ስም ከማዘጋጃ ቤት በተከራየሁት ቤት ላይ የነበራትን ድርጅት ከሌላው ንብረት ጋር ተካክሶ የተካፈለች ሲሆን በእሷ ስም ከቀበሌ በተከራየነው ቤት ያለን የንግድ ድርጅት እኔ ልትካፈል አይገባም መባሉ ተገቢ አለመሆኑና ቀበሌውም በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ የሚሆንበት ሁኔታ ስለሌለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የተጠሪ ተወካይ በበኩሉ ቤቱ የቀበሌ ቤት ሆኖ እያለ እንደባልና እንደ ሚስት የጋራ ንብረት ተቆጥሮ ይካፈሉ ቤቱን ለኢንሸስትመንት ስለሚፈለግ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥና በመዝገቡ የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን አኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአንደኛው አመልካች ሚስት በነበሩት በወ/ሮ ሀዋ መሐመድ ስም የነበረው የንግድ ድርጅት የሚካሄድበት ቤት የቀበሌ ንብረት አንደሆነና የኪራይ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከቀበሌ 02 የተያያዘ መሆኑ ክርክር አልተነሣበትም፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤትም ሆነ የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች እና ወ/ሮ ሐዋ መሐመድ የቀበሌ የሆነውን ቤት ለሁለት ተካፍለው የባለቤትነት መብት ያግኙ የሚል ትዕዛዝ አልሰጡም፡፡

በሌላ በኩል የወረዳና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የጋራ የሆነውና የተጠሪው የሆነውን ቤት በኪራይ ይዘው እየሰሩበት ያለው የንግድ ድርጅት እንዲካፈሉ መወሰኑ ተጠሪውን መብትና ጥቅም የሚነካ አይደለም፡፡ ተጠሪው ፍርድ ቤቶቹ በሰጡት ውሣኔ መሰረት የንግድ ድርጅቱ ሲከፈል የቤቱን መሰረታዊ ይዘትና ዋጋ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ያደርሣል የሚል ክርክር አላቀረበም፡፡ ድርጅቱ መከፈል የማይቻል ሲሆን አመልካቾችና ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ የንግድ ድርጅቱን እንዳለ በመሸጥ ዋጋውን እንዲካፈሉ ለማድረግ የሚያበቃ ምክንያት ከመሆኑ ውጭ ተጠሪውን ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ክርክር እንዲያቀርብ ምክንያት ሊሆን የሚችል መሰረታዊ ጉዳይ አይደለም፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የንግድ ድርጅቱ የሚከናወንበት ቤት የቀበሌ ስለሆነ ባልና ሚስቱ ንብረቱንና እቃውን ነው የመካፈል መብት ያላቸው በማለት የሰጠውን ውሣኔ አንድ የንግድ ድርጅት በንግድ መደብርነት በውስጡ አካትቶ የሚይዛቸው ነገሮች በውስጡ ከተቀመጡት ሸቀጦችና እቃዎች የማይወሰን እንደሆነ በተለይ በንግድ ህጉ አንቀጽ 127 ንኡስ አንቀጽ 2 በንግድ መደብር የንግድ ቤቱ ስም የሚነገድበት የተለያየ የንግድ ማስታወቂያ የንግድ ስራ የሚያከናውንባቸው ቤቶች የመከራየት መብት የሚያጠቃልል መሆኑን ሣያገናዝብ የተሰጠና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የንግድ ድርጅት ማካፈል ማለት የንግድ ድርጅቱን ካፒታል እና በውስጡ ያሉ እቃዎች ከመካፈል ውጭ የንግድ ድርጅቱ በሚከናወንበት ቤት ላይ ያላቸውን

የኪራይ መብት አይጨምርም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 11731 መስከረም 6 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ግልባጩ ይተላለፍ፡፡
2. የአማራ ክልል የጐንደር ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 04996 ግንቦት 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የስሜን ጐንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15566 ጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡት ወጭ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴሬሽን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



ቅጽ-8

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ - 8

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት መልዕክት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጀ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው፤ በዚህ ረገድ የሚሠጡ የሰበር ውሣኔዎችን ፍርድ ቤቱ አሣትሞ ማሠራጨት እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሠረትም እስካሁን ድረስ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው ፍርዶች ከቅጽ 1 እስከ ቅጽ 7 ድረስ በማሣተም ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲሠራጩ ተደርገዋል፡፡

እነዚህ ፍርዶች የሀገራችን ፍርድ ቤቶች የሚሠጧቸው ፍርዶች ወጥነትና ተገማችነት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ የማይናቅ ሚና እየተጫወቱ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህን ቀጣይ ለማድረግ ቅጽ 8፣ 9 እና 10 እነሆ ለሕትመት በቅተዋል፡፡

አስገዳጅ የሰበር ውሣኔዎች ሥራ ላይ ከዋሉ አጭር ጊዜያቸው ነው፤ በአንፃራዊነት የብቃትም ሆነ የልምድ ውሱንነቶች በመኖራቸው እነዚህ እጥረቶች በሰበር ፍርዶቻችን ላይ አልፎ አልፎ መንፀባረቃቸው አልቀረም፡፡ በዚህ መስክ የረጅም ዘመናት ታሪክ ያሏቸው ሀገሮችም በተመሣሣይ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው እኛም አቅማችንን በማጠናከር የእነዚህን አገሮች ተሞክሮዎች በማገናዘብና የሀገራችን የሕግ ባለሙያዎች በፍርዶቻችን ላይ የሚሠጡትን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ግብዓት በማድረግ ኃላፊነታችንን በአግባቡ ለመወጣት ጥረታችን እንደሚቀጥል በዚህ አጋጣሚ እየገለጽሁ የሕግ ትምህርት ቤቶቻችን፣ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎችና ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ለጥረታችን እውን መሆን የማይተካ ድርሻ አላቸውና ከጎናችን እንዲቆሙ ጥሪየን አስተላልፋለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ2001 ዓ.ም. የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሣኔዎች

ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት				1
1	ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2)	33945	አቶ ሣልህ ሁሴን እና ደግፌ ደርቤ	ጥቅምት 20/2001	2
2	ማንኛውም ክርክር ሊወሰን የሚገባው በቀረበው ማስረጃ እና በህጉ መሰረት ብቻ ስለመሆኑ	36848	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና መኰንን ግርማይ (ሦስት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	5
3	በክርክር ሂደት ተቃዋሚ ወገን መጠራት ያለበት ምስክር ከመሰማቱ በፊት ስለመሆኑ	35946	እነ አቶ ማማሸ ወ/ስላሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሰብለ ወንድይራድ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 27/2001	7
4	መጥሪያ ለምስክር እንዲደርስ በሚል ፍ/ቤቶች ሊልኩ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103	36479	ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ኃይሉ ወልዱ	ጥቅምት 25/2001	9
5	በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የተወሰነበት ተከራካሪ ፍ/ቤት ህጉን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78	36412	ተስፋሁን ዋኘው እና በጃክ አግሮ ኮሜርሻል ኢንተርፕራይዝ	ጥቅምት 13/2001	12
6	የቃል ክርክር ለመስማት እና የጽሁፍ መልስ ለመቀበል በሚል ፍ/ቤቶች በአንድ ቀጠሮ ሁለት ተግባራትን ለማከናወን የሚሰጡት ትዕዛዝ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ ስለመሆኑ	36380	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ታረቀኝ ገ/ዓዲቅ	ጥቅምት 18/2001	16
7	የበላይ ፍ/ቤቶች ውሣኔን ወደጉን በመተው በሥር ፍ/ቤቶች የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ	37725	እነ በቀለ ድሪብሣ (ሁለት ሰዎች) እና የምክር በሪሁን	ጥቅምት 6/2001	18
8	በግልፅ የቀረበን ክርክር በተቆጠረ ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ እንዲጣራ/እንዲነጥር/ ሣይደረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	37105	ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር እና ሰለሞን አበበ ኮከብ	ጥቅምት 25/2001	21
9	ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን አስቀርተዋል /ትተዋል/ ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢያዊ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በተረዱበት ደረጃ እርስ በርሳቸው ስምምነት ባደረጉ ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 350(1) እና (2)	37678	ድራጋዶስ ጂ ኤንድ ፒ.ጆይንት ቬንቸር እና ሳባ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር	ህዳር 18/2001	23
10	በሥር ፍ/ቤት ዳኝነት ያልተጠየቀበት ጉዳይ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ታይቶ ሊወሰን የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1), 182(2)	37762	ገወኔ ኢንተርፕራይዝ ኃ/ተ/የግ/ማህበር እና አቶ የሱፍ ይማም	ታህሣሥ 9/2001	26
11	ከሥራ ውል ጋር በተያያዘ የሚጠየቁ ክፍያዎች ሳይነጣጠሉ በአንድ ላይ መቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4), 5	38601	የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና ወ/ሮ ከድኛ ሳቢር	ታህሣሥ 14/2001	29

https://t.me/ethiopianlegalbrief

12	• ክርክር ከሚካሄድበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ መብትና ጥቅም እንዳለ የተረጋገጠ እንደሆነ በክርክር ጣልቃ ለመግባት በቂ ምክንያት ስለመሆኑ • በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ጥያቄ (ተቃውሞ) አለማቅረብ ሚስት/ባል የሆነን ወገን የጋራ ነው በሚለው ንብረት ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚያግድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41	37742	ወ/ሮ አልማዝ ጐንፌ ኦራቲ እና ወ/ሮ ፀሐይ ሊበን	ታህሣሥ 7/2001	31
13	በአንድ መንግስታዊ መዋቅር ሥር የሚገኙ ሁለት ራሳቸውን የቻሉና የህግ ሰውነት ያላቸው ተቋሞች የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቁ አካላት በመሆናቸው ብቻ እንደ አንድ መቆጠር የሌለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 አዋጅ ቁጥር 1/1995,18/1997,2/1995,4/2000	37502	የአዲስ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ህግ ጉዳዬች ቢሮ እና እነ ወ/ሮ የኃላሸት ገመዳ ቤኛ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣስ 2/2001	33
14	ፍ/ቤቶች ለክርክር ፍትሐዊነት ተገቢ ነው ብለው ሲያምኑ ማናቸውንም አይነት ማስረጃ አስቀርበው መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 145,345,327/3/	29861	ወ/ሮ ህጽአት ፍስሐጽዬን እና እነ ወ/ሮ አልማዝ ተረፈ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 14/2001	36
15	የክርክር ዋነኛ ጭብጥ በሆነ ጉዳይ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሣኔ ፍ/ቤት በድጋሚ "ስህተት ለማረም" በሚል ምክንያት ሊለውጥ ወይም ሊያሻሽል ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208	37303	ኤ.ሲ.ዲ አይ/ቪካ-ኢትዮጵያ እና እነ ሃይደር አሊ (ስምንት ሰዎች)	ጥር 26/2001	40
16	ዳኝነት የሚጠየቅበት መብትና ጥቅም በግልጽ ተለይቶ ያልተመለከተበት አቤቱታ የክስ ምክንያት እንደሌለው የሚቆጠር በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33, 231	38419	የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 አስ/ጽ/ቤት እና አቶ ያሲን ጀማል	የካቲት 5/2001	42
17	ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ክርክር መሠረት በማድረግ አግባብነት ያለውን ጭብጥ ሳይመሰርቱ የሚሰጡት ውሣኔ ህጋዊ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ	37391	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ ስዩም ማሞ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 3/2001	45
18	በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች በሚሰጠው ውሣኔ ጥቅማቸው /መብታቸው/ ሊነካ የሚችል የሆነ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.40	39540	ናስ ፉድስ የድ/ዳ/ጨ/ጨ/ፋብሪካ ተከራይ እና እነ ስንዱ ደጀኔ (ዘጠና ሦስት ሰዎች)	የካቲት 26/2001	47
19	አንድ ጉዳይ ከዚህ ቀደም በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5	36780	ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ እና አቶ ገ/ኪዳን እንግዳ	መጋቢት 3/2001	50
20	ነዋሪነታቸው በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሣ ክርክርን የክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት የሚገኘው ወይም ውል የተደረገው በአንደኛው ክልል እንኳን ቢሆን የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(2)	36460	መሐመድ ሰዓዳይ ረሻ እና እነ አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ ፊረጀ (ሰባት ሰዎች)	መጋቢት 24/2001	57
21	በተከራካሪ ወገኖች የተጠየቀን ዳኝነት አስመልክቶ ግልጽ ፍርድ አለመስጠት ስህተት ስለመሆኑ	39144	አቶ ልዑልሰገድ ቦኔ እና ኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር	መጋቢት 24/2001	60
22	የቀረበበትን ክስ ያመነ ተከሣሽ ባመነው መሠረት ውሣኔ ለመስጠት የሚከለክል በቂ የህግ ምክንያት እስከሌለ ድረስ ውሳኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ	38597	እነ ጋሻው መንግስቱ ካሣ (ሁለት ሰዎች) እና ናይል ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሚያዝያ 6/2001	63
23	በአንድ ዘንግ የሚመደቡ ተከራካሪዎች እና አንድ ጭብጥ ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች ተጣምረው እንዲታዩ ያለማድረግ መሠረታዊ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 11(5)	40024	ሸራተን አዲስ እና እነ አቶ እያሱ መገርሣ	ሚያዝያ 29/2001	65
24	የሥር ፍ/ቤቶች የፈፀሙትን ሥህተት ለማረም በሚል በሥር ፍ/ቤት ተከራካሪ ከነበሩ ወገኖች መካከል አንዱ ወገን ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሌላኛው ወገን ሳይጠራና ሳያከራክር ውሣኔ መስጠት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1)	34504	አቶ አበባው የሺድንበር እና አቶ ካሣ በቀለ	ሚያዝያ 6/2001	68

https://t.me/ethiopianlegalbrief

25	በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣን ክርክር መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 329(1), 182(2)	37761	ገብረመስቀል ንጉሴ እና አዲስ ልብስ ስፌት አ.ማ	ሚያዝያ 20/2001	70
26	ክስ በሚሰማበት የቀጠሮ ዕለት የይግባኝ ባይ አለመቅረብ ጋር በተያያዘ መዝገብ ሊዘጋ የሚችለው መልስ ሰጪው ይግባኙን ሙሉ በሙሉ ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ	38181	የኢትዮጵያ መንግዶች ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ወንድይፍራው (ሁለት ሰዎች)	ግንቦት 4/2001	73
27	ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገን ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የሚጠቅም ያልሆነ እንደሆነና የሰው ምስክር በተጨማሪነት የቆጠረ እንደሆነ ፍትሐዊ የሆነ ውሣኔን ለመስጠት የምስክሮችን ቃል መስማት ያለበት ስለመሆኑ	42706	ላየን ሴኩሪቲ ኩባንያ እና አቶ ጥላሁን ገ/እግዚአብሔር	ግንቦት 25/2001	75
28	በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መለወጥ ወይም መሻሻል ተከትሎ ማናቸውም ተከራካሪ ወገኖች ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚሰጥ ትዕዛዝ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ እንጂ የግድ የሚሰጥ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349(1)	37741	አቶ መኮንን ዘውዴ እና እነ አቶ ተሾመ ሽፈራው (ሦስት ሰዎች)	ሰኔ 4/2001	77
29	ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ጉዳይ ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9(2)	38452	የአ.አ ከተማ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ አለም ገብሩ	ሰኔ 11/2001	79
30	አንድን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማንሣት ስልጣን የለኝም ያለ ፍ/ቤት ጉዳዩ በበላይ ፍ/ቤት ታይቶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ እንዲያከራክር ጉዳዩ የተመለሰለት እንደሆነ ሌላ ተጨማሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለማየት አልችልም ማለት የማይገባው ስለመሆኑ	39014	አለሙ መግራ እና እምነቱ እንዳሻው ህንፃ ተቋራጭ	ሰኔ 23/2001	81
31	የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈበት ተከራካሪ ወገን የሚያቀርበው የማስፈቀጃ ማመልከቻ በበቂ ምክንያት የተደገፈ መሆን/አለመሆኑን ፍ/ቤቶች በጥሞና መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 326(1)	38145	ወ/ሮ አያልነሽ ዘገየ እና አቶ ተስፋዬ ደምሴ	ሰኔ 30/2001	83
32	አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃነት የሚጠቅሳቸው ምስክሮች፣ ሰነዶች ወይም ሌላ አስረጂዎች (የሙያ) ማስረጃው በፍ/ቤቱ በኩል በጭብጥነት ተይዞ ከሚፈታው ፍሬ ነገር ጋር አግባብነት ያለው እና በህግ ተቀባይነት ያለው እስከሆነ ድረስ ቀርቦ መሰማት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111, 249 እና 257	38683	የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት እና አቶ ሣህሉ ወ/ማርያም	ሰኔ 25/2001	85
33	ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአግባቡ ሳይመረምሩ እና ለውሣኔያቸው በቂ ምክንያት ሣይሰጡ መሻር የማይችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1)	38844	የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን እና ጋድ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህ	ሰኔ 25/2001	87
34	ተከራካሪ ወገኖች በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲቀርብላችው የሚጠይቁት ማስረጃ የተያዘውን ጉዳይ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ዕልባት ለመስጠት የሚያስችል እስከ ሆነ ድረስ ጥያቄውን ፍ/ቤቶች ሊቀበሉት የሚገባ ስለመሆኑ	36979	ቤዛ አማካሪ መሀንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ሚስተር ሸሪሃሪ ብራማቫሪ ጐፓል	ሐምሌ 23/2001	91
35	ሦስተኛ ወገኖች በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር እንዲገቡ የሚያስፈልግበት ሁኔታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43	41544	ሰላም የህዝብ ማመላለሻ (አ.ማ) እና ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ	ሐምሌ 8/2001	93
አስሪና ሰራተኛ					95
36	የኘሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀፅ 2/ሰ/	35197	አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና ኤፍሬም ንዋየማሪያም	ጥቅምት 13/2001	96

https://t.me/ethiopianlegalbrief

37	ለኘሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች የተቀጠሩበት የኘሮጀክት ሥራ ሲጠናቀቅ የሥራ ውላቸው የሚቋረጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10/1//ሠ//ሀ/	35621	ሰንሻይን ኮንስትራክሽን እና እነ አቶ ፍቃዱ ገቢሣ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	99
38	በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 ባልተሸፈነ ጉዳይ ላይ በአሠሪና በሠራተኛ መካከል የተደረገ የህብረት ስምምነት መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ	36692	አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት እና ተስፋዬ መኮንን	ጥቅምት 25/2001	101
39	ሠራተኞች ለሚፈፅሙት ጥፋት በህብረት ስምምነት የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች የተቀመጡ በሆነ ጊዜ አሰሪው በሠራተኛው የተፈፀመውን ጥፋት ክብደት በመመዘን ይመጥናል የሚለውን ቅጣት መወሰን የሚችል ስለመሆኑ	37027	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት አሰለፈች ደስታ	ጥቅምት 11/2001	103
40	አንድ ድርጅት እንደስራው ፀባይ በህግ ከተደነገገው ማዕቀፍ ሳይወጣ/ሳይጥስ/ የሥራ ሰዓቱን ማሻሻል ስለመቻሉ አዋጅ 377/96 አንቀፅ 61/1/	36518	ሜታ አቦ ቢራ አ.ማ እና እነ ሳሙኤል ተፈራ (አራት ሰዎች)	ጥቅምት 4/2001	105
41	የአሰሪ ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደል ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1/ተ/	35484	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና አቶ ደረጀ ማሞ	ህዳር 25/2001	107
42	አሰሪ ሠራተኛውን በሣምንት ዕረፍቱ ሥራ እንዲሰራ ለማድረግ የሚችል ስለመሆኑ	37815	አለማየሁ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ እና አቶ አብዮት በፈቃዱ	ህዳር 2/2001	109
43	በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ "የሥራ ቀናት" የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(3)	36377	የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና ተሾመ ኩማ	ህዳር 2/2001	111
44	የኘሮቪደንት ፈንድ ወይም/ እና የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ	37048	የሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ሣህሉ ምትኩ	ህዳር 2/2001	113
45	በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ መውጣት በራሱ አንድን ሠራተኛ ወደ ቀድሞ ሥራ ለመመለስ መብት የሚሰጥ ስላለመሆኑ	37256	አዲስ አበባ የምግብ አዳራሽ አስተዳደር እና ወ/ሮ የውብዳር ጥላሁን	ህዳር 4/2001	116
46	ለአምስት ተከታታይ ቀናት በሥራ ገበታ ላይ ያለበቂ ምክንያት አለመገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ስለመሆኑ	37402	የንኮማድ ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ ቡሽራ በቀለ	ህዳር 11/2001	119
47	ከሥራ ጋር በተገናኘ በሚፈፀም ድርጊት መነሻነት በሠራተኛው ላይ በፖሊስ የሚደረግ ምርመራ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ	37573	የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና አቶ መሐመድ አደን	ህዳር 16/2001	122
48	የሥራ ውል በስምምነት ተቋረጠ ለማለት የሚቻለው ስምምነቱ በፅሁፍ የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ	37575	ቃሊቲ ባሌስትራ ማምረቻ እና ብርሃኑ ልደት ወልዴ	ህዳር 2/2001	124
49	በአሰሪ በተደረገ የሥራ ዝውውር ቅሬታ አድሮብኛል በሚል ምክንያት ከሥራ መቅረት የህግ ድጋፍ የሌለው ስለመሆኑ	37778	አዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪ አከፋፋይ አ.ማ እና አቶ ካሣሁን ከበደ	ህዳር 4/2001	126
50	በአሰሪና በሠራተኛ መካከል የሥራ ውል ግንኙነት አለ ለማለት የሚቻልበት አግባብ	03171	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና ወ/ት ትርሲት ደገፋ	ህዳር 16/2001	129
51	አዲስ መዋቅርን ተግባራዊ ያደረገ ተቋም/ድርጅት/ ሠራተኞቹን "ራሱ ባወጣው መስፈርት" መሰረት ሊመድብ ስለመቻሉ	36210	አቃቂ መለዋወጫ ዕቃዎችና መሣሪያዎች አ.ማ እና አቶ ኃይለ ሳልቫቶር	ህዳር 2/2001	132
52	• አንድ ሠራተኛ በአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበት የሚችልበት አግባብ • በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ "የአሰሪ ንብረት" በሚል የተገለፀው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1//ሸ/	34669	አድማስ ኮሌጅ እና ሠለሞን ሙሉአለም	ታህሣሥ 2/2001	134

https://t.me/ethiopianlegalbrief

53	የተረከበው የአሠሪ ንብረት የጠፋበት ሰራተኛ ንብረቱን ለግል ጥቅሙ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ያዋለው ያለመሆኑን ካላስረዳ በቀር የንብረቱ መጥፋት ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)(ቀ) 14(2)(ለ)(2)	39118	ደሣለኝና ቤተሰቡ ኃላ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ በፈቃዱ በላይ	ታህሣሥ 23/2001	136
54	በህብረት ስምምነት ወይም በሌላ አካኋን የተወሰነ የሥራ ውል የሚቋረጥበት ምክንያት ካለ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ያልተመለከተ ቢሆንም ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 3787/96 አንቀፅ 27/1/	36591	ማታዶር አዲስ ጎማ አ.ማ እና ደረጀ ኡመታ	ታህሳስ 14/2001	139
55	የሥራ መሪ በሆነ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት መስራት ግለሰቡን የሥራ መሪ ከመሆን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 3/2/ /ሐ/	36894	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ መላት ታረቀኝ	ታህሳስ 30/2001	141
56	ለተወሰነ ጊዜ በተደረገ የሥራ ውል ግንኙነት ለሠራተኛው የሚከፈል የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸው ባስቀመጡት መልክ የሚፈፀም ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 35/2/	37201	ማታዶር አደስ ጎማ አክሲዮን ማህበር እና እነ አቶ ኤልያስ በቀለ (አስራ አራት ሰዎች)	ታህሣሥ 30/2001	143
57	የጥበቃ ሥራን የሚሠራ ሠራተኛን በተመለከተ የሥራ ውሉ ያለአግባብ ተቋርጧል በሚል ሊወሰን በአሠሪውና ሠራተኛው መካከል ሊኖር የሚገባው ከፍተኛ መተማመን የሚሻክር በመሆኑ ሰራተኛው ወደ ሥራ እንዲመለስ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43	37454	ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል እና ከበደ ሰይፉ	ታህሣሥ 16/2001	146
58	ወደ ሥራ እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ የሥራ ክርክሮችን የሚወስነው አካል ሠራተኛው አግባብነት ያላቸውን ክፍያዎች ተከፍሎት ከሥራ እንዲሰናበት ሊወሰን የሚችለው በመጀመሪያው ፍርድ መሠረት ያልተፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/	38255	አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አለምሰገድ ኃይሉ	ታህሣሥ 23/2001	149
59	የሥራ ውሉን በፍቃዱ የቋረጠ ሠራተኛ የህብረት ስምምነት የሚፈቅድለት ከሆነ ኘሮቪደንት ፈንድና የሥራ ስንብት የማግኘት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ	37551	አቶ ድካምየለህ ጥበቡ እና አርሾ የህክምና ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር	ታህሣስ 9/2001	152
60	የስራ ውል የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው ተብሎ በተወሰነ ጊዜ የስራ ውሉ የተቋረጠበት ወገን/ሠራተኛ/ ሊወሰኑለት የሚገቡ ክፍያዎች	34476	ኩመላ በጅማ እና ብሔራዊ አስጐብኚና ጉዞ ወኪል	ታህሳስ 2/2001	155
61	አንድ የሥራ ዘርፍ የአሠሪው ቋሚ ሥራ ቢሆንም በዚሁ ዘርፍ ሠራተኞችን ለተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ቀጥሮ ሊያሰራ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሐ)	40305	የኢትዮጵያ ፐልኘና ወረቀት አ.ማ እና እነ አቶ ታመነ ጫላ	ታህሣሥ 21/2001	158
62	አንድ ሠራተኛ ይሰራው የነበረ የሥራ መደብ መሰረዝ ወይም አለመኖር ለሥራ ውሉ መቋረጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1) (መ)	40804	ዳንዲቦሩ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና እነ ተክሉ ኡርጌ ኢደኤ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 26/2001	160
63	አንድ ሠራተኛ ወደ ሥራ ሲሄድና ከሥራ ወጥቶ ወደቤቱ ሲመለስ አሰሪው በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ሲጠቀም አደጋ የደረሰበት መሆኑ ከተረጋገጠ ሦስተኛ ወገኖች ለአደጋው ያደረጉት አስተዋፅኦ መኖር አሰሪው የጉዳት ካሣ ላለመክፈል እንደመከላከያ ሊሆነው ስላለመቻሉ እና የጉዳት ካሣው በጉዳት የተነሣ ህይወቱን ላጣው ሠራተኛ ጥገኞች የሚከፈልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 95/2/, 96/1/, 98/2/, 97/1/, 107/1//ሐ/, 110/ 112	36194	ዶ/ር ማንደፍሮ እሸቴ እና ፍሬድሪክ ኤቨርት ሲቲፍቱንግ	ጥር 28/2001	162
64	በድርጅት ውስጥ በተደረገ የመዋቅር ማሻሻያ የሥራ መደብ የተሰረዘ እንደሆነ የሥራ መደብ የተሰረዘበትን ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚቻልበት አግባብ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1)(መ)	38811	ርሆቦት ሆሊ ሴቪያር ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ አማረ አድማሱ	የካቲት 17/2001	167
65	በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለ የሥራ መደብ በሌላ 3ኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የስራ ውል ለማቋረጥ ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 28	38435	ኤስ.ኦ.ኤስ የህፃናት መንደር እና እነ አቶ ከበደ ኩምሣ (ስድስት ሰዎች)	የካቲት 17/2001	169

https://t.me/ethiopianlegalbrief

66	ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል የሚቋረጠው ማስጠንቀቂያ በመሰጠት ስለመሆኑ	38023	የመንግስት ቤቶች ኤጅንሲ እና ብርሃኑ ደስዩ	የካቲት 17/2001	171
67	በአሰሪያቸው ላይ ክስ አቅርበው ያስፈረዱ ሠራተኞች የአሰሪውን ንብረት በዋስትና ከያዙ ባለገንዘቦች ይልቅ የቅድሚያ ክፍያ መብት ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 167 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀጽ 2857(1) አዋጅ ቁ. 186/94 አንቀጽ 80 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ- መንግስት አንቀፅ 13(2)	40921	አቢሲንያ ባንክ (አ.ማ) እና አብዱ አህመድ (ሁለት መቶ ስልሳ ስድስት ሰዎች)	የካቲት 26/2001	173
68	የአንድ ሠራተኛን ድርጊት ከባድ ቸልተኝነት ነው ለማለት የሥራውን ባህሪ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ	41115	ሜድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ ሞገስ ሽፈራው	የካቲት 26/2001	175
69	አሠሪ የአንድን ሠራተኛ ደሞዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅም ሣይነካ በተመሳሳይ የሥራ መደብ ላይ አዛውሮ ሊያሠራ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 13(2) እና (7)	40938	መገር ሲሚንቶ ኢንተርኘራይዝ እና አቶ ኃይሉ መንግስቱ	መጋቢት 24/2001	178
70	አንድ ሠራተኛ የአሠሪው ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደሉ የተረጋገጠ እንደሆነ አሠሪው ሠራተኛውን በፍ/ብሔር ክሶ ገንዘቡን የማስመለሱ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)	42292	የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ከበደ አቡነቱ	መጋቢት 24/2001	180
71	በአሠሪው ወደሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሠራ የተደረገ ሠራተኛ ዝውውሩን በወቅቱ ሣይቃወም የተዛወረበት የሥራ ገበታ ላይ ለ5 ተከታታይ ቀናት የቀረ እንደሆነ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27 (1)(ለ)	41623	አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ሣሙኤል ኪዳኔ	መጋቢት 8/2001	182
72	• ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛን ከሥራ የማገድ ተግባር ሠራተኛን እንደማሰናበት የማይቆጠር ስለመሆኑ • አሠሪው ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛው ለታገደበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፍል የሚደረግበት አግባብ • ከሥራ ያለአግባብ ታገድኩኝ በሚል የቀረበን ክስ በማስተናገድ ላይ ያለ ፍ/ቤት በክርክሩ ሂደት ሠራተኛው ከሥራ የተሰናበተ መሆኑን ካወቀ የተያዘው ጭብጥ እንዲሻሻል እና ጭብጡ እንዲስተካከል በማድረግ ጉዳዩን ማየት ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(4)	41411	ሙስሙል ዳቦ መጋገሪያ ድርጅት እና አቶ በለጠ ተገኝ	ግንቦት 11/2001	184
73	• አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ከጉዳቱ በኋላ የቀድሞ ስራውን መስራት መቀጠሉ ብቻ አሰሪውን የጉዳት ካሣ ከመክፈል ነፃ የማያወጣው ስለመሆኑ • በሥራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተገናኘ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ውስጥ የተመለከተውና "የመስራት ችሎታ" የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ እና የጉዳት ካሣ መጠንና ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 109, (1) እና (3) , 107, 99(1), 102(3) አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 33	43370	የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና አቶ ጌታቸው ገድሌ	ግንቦት 12/2001	187
74	• የድርጅት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የአሰራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሠራተኛ ቅነሣ የሚደረግበት አግባብ • ቅነሣ የሚደረግበትና ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(2)(ሐ), 29(3)	42752	እነ ወ/ት ማሜ አሠፋ (ሰላሳ ስድስት ሰዎች) እና ብሔራዊ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል(NTO)	ግንቦት 12/2001	190

https://t.me/ethiopianlegalbrief

75	በሠራተኛ እጅ የሚገኙ የአሠሪ ንብረቶች መመለስ ወይም አለመመለስ ጉዳይ ሠራተኛው የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚያነሣቸውን ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ለማስተናገድ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 36, 38	39464	ሐረር ቢራ አክሲዮን ማህበር እና አቶ አብዱልቃድር አብዱረዛቅ	ግንቦት 25/2001	193
76	ቀድሞ ይሰራበት የነበረን የሥራ መደብ በመሰረዙ ምክንያት ሠራተኞችን በማሰናበት ፋንታ በክፍያ አነስተኛ ወደሆነ ሌላ የሥራ መደብ እንዲሰሩ ያደረገ አሠሪ ለሠራተኞቹ በቀድሞው ደመወዝ መሠረት እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	41786	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ አቶ አሰፋ አቤቦ (ሦስት ሰዎች)	ግንቦት 26/2001	195
77	በጥበቃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ እንዲጠብቅ የተሰጠው የአሰሪ ንብረት የጠፋ እንደሆነ ሰራተኛው ለንብረቱ መጥፋት አስተዋጽኦ ያለማድረጉን ማረጋገጥ ካልተቻለ በስተቀር በሃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ	39650	የየረር በር ምስራቅ ፀሐይ ቅዱስ ዑራኤል ቤ/ክ እና እነ ቄስ ሰፊነው ደሣለኝ	ግንቦት 27/2001	198
78	በተጭበረበረ ማስረጃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የማጭበርበር ድርጊቱ የታወቀ/የተደረሰበት/ ከሆነ ማጭበርበሩ የተከሰተው ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ተቆጥሮ ሊያስናብተው የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1) (ሐ)	39543	የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ በረከት ተ/ማርያም	ግንቦት 4/2001	200
79	ለኘሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቅነሣ በሚካሄድበት ወቅት አሰሪው በአዋጅ ቁ.377/96 ላይ የተመለከተውን የሠራተኞች ቅነሣ ሥነ-ሥርዓት መከተል የማይጠበቅበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30(1)	39042	ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ጀማል መሐመድ	ግንቦት 26/2001	202
80	የሥራ መደብ ዝውውርን በመቃወም ቅሬታን በማሰማት ላይ መሆን በስራ ቦታ ላይ ላለመገኘት እንደ በቂ ህጋዊ ምክንያት የሚወሰድ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ)	38189	ሮፖክ ኢንተርናሽናል ኃላ/የተ/የግል ማህበር እና ይደርሳል አእምሮ	ግንቦት 27/2001	204
81	አሠሪ የሥራ መሪ የሆነን ሠራተኛውን ያሰናበተው ያለበቂ ምክንያት ቢሆንም እንኳን ተገቢ የሆነ ካሣ ለመክፈል ከሚገደድ በስተቀር ሠራተኛውን ወደ ሥራ እንዲመልስ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ	37982	የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና አቶ ታደሰ ዘነበ	ሰኔ 16/2001	207
82	ለሥራ ማስኬጃነት የተቀበሉትን የአሰሪ ገንዘብ አጉድሎ መገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)	41720	የእንጨት መሠንጠቂያና መገጣጠሚያ ድርጅት እና ረዲ እንዳለ	ሰኔ 9/2001	210
83	የሥራ ውል የተቋረጠው በህጉ አግባብ ነው ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ የማይከፈል ስለመሆኑ	39861	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ሣምሶን በለጥካቸው	ሰኔ 18/2001	212
84	በቃል ከሥራ ተሰናብትኩ በሚል ክስ የሚያቀርብ ሠራተኛ አሰሪው ከሥራ ያሰናበተው ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ	43610	ናይኮ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ሰለሞን ተሰማ	ሐምሌ 21/2001	214
85	አሠሪ የሆነ ወገን የሥራ ቅልጥፍናን፣ ውጤታማነትን፣ የኢንዱስትሪ ሰላምን ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድን ሠራተኛ የተቀጠረበትን ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በጠበቀ ሁኔታ አሣውሮ ለማሰራት የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 2 (1), 4	44033	መንበረ ፓትሪያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና አቶ ይበልጣል አጥናፉ	ሐምሌ 22/2001	216
86	በህግ ወይም በሕብረት ሥምምነት የተመለከተው የጡረታ እድሜ ሣይደርስ በመንግሥት መመሪያ በጡረታ እንዲገለሉ የተደረጉ ሠራተኞችን በተመለከተ አሰሪ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ለመክፈል የማይገደድ ስለመሆኑ	42906	የኢትዮ-ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ እና እነ ትዕግስት ማሞ (ሰማንያ አንድ ሰዎች)	ሐምሌ 21/2001	218
87	የኮንስትራክሽን ሥራ የሚሰራ ድርጅት የሥራው መጠን በቀነሰ ጊዜ ሠራተኞችን ለማሰናበት የማስጠንቀቂያና ሌሎች የቅነሳ ሥነ-ሥርዓቶችን ሳይከተል ቅነሳ ለማካሄድ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30	42075	አፍሪካዊት የህንፃ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና እነ አቶ እንድሪስ ዓሊ	ሐምሌ 16/2001	221

https://t.me/ethiopianlegalbrief

88	የሥራ ውል አንደተቋረጠ የጡረታ አበል ለማግኘት መብት ያለው ሠራተኛ የሥራ ስንብት የማይከፈለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39 አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2) (ሰ)	39808	ናዝሬት ማሙና ፋብሪካ እና ዘውዴ ኃ/ማርያም	ሐምሌ 21/2001	223
89	የሥራ መሪ ከሠራተኛ ሊለይ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3, አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2	42901	የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና ወ/ሮ ንግስት ለጥይበሉ	ሐምሌ 21/2001	225
90	በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በሚካሄድ የሥራ ክርክር የሚያዘው ጭብጥ አሰሪው ገንዘብ ይከፈለኝ በሚል በሠራተኛው ላይ ክስ ባቀረበ ጊዜ ከሚያዘው ጭብጥ ጋር አንድ አይነት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ	39471	ኤርሚያስ ሙሉጌታ እና በክልቻ ትራንስፓርት አ/ማ	ሐምሌ 29/2001	227
91	በሃይማኖት ተቋም ውስጥ መንፈሳዊ(ሃይማኖታዊ) አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ የሚሸፈን ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	18419	ሐመረወርቅ ቅ/ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና እነ ዲያቆን ምህረት ብርሃን(ስድስት ሰዎች)	ግንቦት 4/1998	229
ቤተሰብ					232
92	የውርስ ሀብት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክስ የማዬታ ውርስ ከተጣራ በኋላ መቅረብ የሌለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1)	34703	እንዳሻው ፍቃዱ እና እነ ወንድማገኝ ፍቃዱ(ሰባት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	233
93	ኑዛዜ ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም በሚል የሚያቀርቡት የመቃወም አቤቱታ ኑዛዜው በተነበበ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973	36604	ወ/ሮ ፅጌ መንግስቱ እና እነ አቶ ወንድይራድ መንግስቱ(ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 25/2001	235
94	ከጋብቻ በፊት የግል የነበረን ንብረት መነሻ በማድረግ በጋብቻ ጊዜ በግብይት የተገኘ ንብረት የግል ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው በፍ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 58(2), 57, 62(2)	37275	ሻ/ባሻ ገዛኸኝ ድልነሣው እና ወ/ሮ ተዋበች ደመቀ	ጥቅምት 18/2001	237
95	ግልፅ ኑዛዜ ህጋዊ እንዲሆን መሟላት ያለበት ፎርማሊቲ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882	36777	አቶ ወንድም አገኝ ዘውዱ እና እነ አቶ ታፈሰ ወንድአፈራሽ (ሶስት ሰዎች)	ጥቅምት 25/2001	241
96	ህፃናትን ማዕከል ያደረጉ ክርክሮች የልጆችን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ መስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ	35710	ወ/ሮ እፀገነት እሸቱ እና ወ/ሮ ሰላሚዊት ንጉሴ	ታህሣስ 16/2001	243
97	የስጦታ ውል የተፈፀመው ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ከሆነ ይኼው ግለሰብ እንደ ምስክር ተደርጎ ባይፃፍም ምስክር ተደርጎ ሊቆጠር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443,881,882	37562	አቶ ማሙኤል ፈረንጅ እና አቶ ግርማ ታፈሰ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 28/2001	248
98	ጋብቻ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው በህግ አግባብ ተፈፅሟል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 28(3)	41896	ወ/ሮ ታደለች ዋለልኝ እና እነ ወ/ሮ አዲስዓለም ፀጋ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 26/2001	251
99	የሟች እዳን ለመክፈያ በአፈፃፀም ሊያዝ የሚገባው በውርስ የተገኘውን ሀብት እንጂ የወራሾች የግል ሃብት ስላለመሆኑ	38691	አቶ ለገሰ ቢራቱ እና አቶ ደረጀ ጅማ ገርግሶ	የካቲት 24/2001	253
100	የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሣይኖር የጋራ የሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት በሌለኛው ተጋቢ የተሸጠ እንደሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ 6 ወር ውስጥ እንዲሁም በማናቸውም ሁኔታ ደግሞ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየት ስለመቻሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 69(2)	38126	ዲያቆን ኃይለጊዮርጊስ ወንድምሲያምረኝ እና እነ ወ/ሮ የሺ ተፈሪ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 22/2001	256
101	በኑዛዜ የተገኘ ንብረት በ10 (አሥር) ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተጠየቀ በስተቀር በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ	38152	የወ/ሮ ገነት ዳምጤ ወራሾች እና እነ አቶ ይልማ አስፋው	ሚያዝያ 29/2001	258

https://t.me/ethiopianlegalbrief

102	የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ ከመረመረ በኋላ የጉዳዩን ጭብጥ በመያዝ ወደ ሥር ፍ/ቤት የመለሰው እንደሆነ አስቀድሞ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ፍርድ እንደሌለ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ	37313	እነ አቶ መሐሪ ተ/ማሪያም (ሁለት ሰዎች) እነ የወ/ሮ ገነት መኮንን ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	ግንቦት 18/2001	261
103	ወራሽ የሆኑ ወገኖች የሚያቀርቧቸውን ተገቢነት ያላቸው ማስረጃ በሙሉ አሰባስቦ በመስማት ያልተከናወነ የውርስ ማጣራት ሪፓርት በህግ አግባብ የተከናወነ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241, 270 እና 345	42525	እነ አቶ አብዱልዋሲቅ አርጋው እና ወ/ሮ አልዋያ አባበሊስ	ግንቦት 27/2001	264
104	የተናዛዡ ህጋዊ ንብረት ባልሆነ ነገር ላይ የተደረገ ኑዛዜ በፍ/ቤት ቢፀድቅም እንኳን የኑዛዜ ሰነዱ ዋጋ የማይኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 865	32817	ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ እና እነ ወ/ሮ ቱቱ ዘውዴ(ሦስት ሰዎች)	ሰኔ 11/2001	266
105	የገበያ ዋጋን መሠረት ያላደረገና የግንባታ ዋጋ ግምት ላይ ብቻ ተመርኩዞ የሚደረግ የውርስ ሀብት ክፍፍል ፍትሐዊ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ	40510	ቴዎድሮስ መንበሩ እና ገ/ህይወት ታደሰ	ሰኔ 23/2001	269
106	ጋብቻ በሁለት የተለያዩ ሥርዓቶች የተፈፀመ ቢሆንም አንድ ጊዜ በህግ አግባብ የተደረገ ፍቺ በቂና ሙሉ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 75(ሐ)	40781	ፍቅረስላሴ ካህሣይ እና ወ/ሮ ሮማን ታደሠ	ሐምሌ 30/2001	271
107	በውርስ ሃብት ክፍፍል ላይ ተወላጅ የሆነ ሰው ከሩብ በላይ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ክፍፍሉ እንዲቀር ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 11/22,913,1060,1037-1051,942	18394	ወ/ሮ ዝናሽ በቀለ ማንደፍሮ እና ወ/ሮ ሐረገወይን በቀለ	መጋቢት 21/1999	274
ውል					278
108	የደረሰው ወይም ይደርሣል ተብሎ የሚጠበቀው ኪሣራ በጉዳት ኪሣራ ሊካስ የሚችል በሆነ ጊዜ ውሉን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776	35472	አቶ መሐመድ ካሣሁን እና አቶ ሰለሐዲን ኑር	ጥቅምት 6/2001	279
109	የፍ/ብ/ህ/ቁ.1723"ን" መስፈርት አላሟላም በሚል ውል እንዲፈርስ የተደረገ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1815	34803	መ/ር መኳንንት ወረደ እና እነ መስከረም ዳኛው (አራት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	282
110	ከአንቺነት ውል ጋር በተያያዘ ለሚኖር የጉዳት ሃላፊነት ካሣ ሊወሰን የሚችልበት አግባብ የንግድ ህግ ቁጥር 595, 596, 597 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790, 2090, 2091, 2092, 2141, 2102	32854	ወ/ሪት ማርታ አድማሱ እና እነ አቶ በረከት ሰብስቤ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 20/2001	293
111	የተከራዩትን ቤት ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት ለውል ማፍረስ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ	36520	የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ይብራህ ግርማይ	ጥቅምት 27/2001	296
112	መሐይምነትን ወይም ዓይነስውርነትን መሠረት በማድረግ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ አቤቱታ በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719,1845	29363	ወ/ሮ ወርቅነሽ አምዴ እና አቶ ጥላሁን አርምዴ	ህዳር 18/2001	299
113	የማይንቀሣቀስ ንብረት የሽያጭ ውል ተደረገ የሚባለው በውል ውስጥ ያሉ ወገኖች በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የሽያጭ ውሉን ከተፈራረሙበት ቀን ጀምሮ እንጂ የአስተዳደር ጉዳዩች ተጣርቶ የመስሪያ ቤቱ ማህተም ካረፈበት ቀን አንስቶ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723(1), 2015(ሀ)	36740	አቶ አብዱልዋሐብ ኢብራሂም እና እነ ወ/ት መሰለች ከፍያለች (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 23/2001	302
114	በማኅበር በመደራጀት የተሠራ ቤትን ለሶስተኛ ወገን ከማስተላለፍ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚነሣ ክርክርን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1723	36294	ወ/ሮ ሠናይት ገነሜ ገንታ እና እነ በቀለ ገመዳ ዳኖ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 9/2001	305

https://t.me/ethiopianlegalbrief

115	በአስሪ ወይም በ3ኛ ወገን ወጪ ትምህርትን ተከታትሎ ለማገልገል በሚል የተገባን ውል (ስምምነት) የጣሰ ሰው ግዴታውን በአማራጭ ሊወጣ የሚችል ስለመሆኑ	33473	ወ/ሮ ሃርሴማ ሰለሞን እና የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ	ህዳር 16/2001	307
116	የዕቃ አስተላላፊነት ሃላፊነትና ተግባር ዕቃን የማንቀሳቀስ የማስረከብ ሥራን የሚያካትት ስለመሆኑ	32571	አቶ ሚፍታህ ከድር እና የባህር ትራንዚት አገልግሎት	ታህሣሥ 9/2001	311
117	ክርክር የሚካሄድበት ጉዳይን አስመልክቶ በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ የሌለ እንደሆነ ስለ ውሎች በጠቅላላ በሚለው ክፍል የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677፣1845	34940	ወ/ሮ ሐጅራ አብሮ እና አቶ ሐሺም ሐጂ አሊዬ	ታህሣስ 28/2001	314
118	• ፍ/ቤት የቀረበለትን የውል ይሰረዝልኝ፣ ጥያቄ ወደጉን በመተው የውል የፎርማሊቲን የተመለከተ ጭብጥ በማንሣትና ምክንያቱን በመለወጥ ውሣኔ መስጠት የማይገባው ስለመሆኑ • በፍ/ብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሰረት ጭብጥ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ	32299	እነ አቶ ሰለሞን ከተማ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ሴንትራል ቬኑ /የተ/የግል ማህበር (አራት ሰዎች)	ጥር 7/2001	316
119	በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161 የንግድ ሕግ ቁ. 124	34586	አቶ አያሌው ድልነሳው እና እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ (አራት ሰዎች)	ጥር 28/2001	321
120	በውል ግንኙነት ውስጥ የራስን ግዴታ ሳይወጡ ሌላው ወገን ግዴታውን አልተወጣም በሚል የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1757	39568	አቶ ሽንቁጤ ተ/ማርያም እና አቶ ገብሬ ጐንጤ	መጋቢት 24/2001	324
121	የማይንቀሳቀስ ንብረት ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጐት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ያላሳወቀ እንደሆነ ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት የመጠየቅ መብቱ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731(1), 1732, 1789 እና 1845	38935	እነ አቶ ወልደፃዲቅ ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ስንታየሁ አያሌው	መጋቢት 3/2001	327
122	በፍ/ብሔር ጉዳዮች የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1846	36756	አቶ ፀጋዬ ምትኩ እና እነ ወ/ሮ አበበች ምትኩ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 17/2001	331
123	ለብድር በዋስትና መልክ የተሰጠን ንብረት ለተበዳሪው መመለስ ብድሩ እንደተከፈለ የሚያስቆጥር ስለመሆኑ	41571	ማህደር አእምሮ እና ላእከ ገ/መድህን	ሰኔ 2/2001	334
124	በህግ ፊት በማይፀና ውል አማካኝነት የተሣሠሩ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ይመለሱ በሚል ውሣኔ መስጠት የሚቻለው መመላለሱ አንደኛውን ወገን በእጅጉ የሚጐዳ ወይም ሌላኛውን ያልተገባ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችል አለመሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ	39336	ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ እና እነ አዱኛ እጅጉ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 7/2001	337
125	በፍ/ቤት በንብረት ላይ የሚሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ተቋቁሟል ለማለት የሚያበቃ ስለመሆኑ	39170	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ክንዴ አፍራሶ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2001	340
126	የባለዕዳውን ዕዳ ለባለገንዘብ የከፈለ ወገን በባለገንዘቡ መብቶች ላይ በመዳረግ (subrogation) ባለገንዘቡ የነበረውን መያዣን መሰረት ያደረገ የቀዳሚነት መብት ሊሰራበት የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1968 - 1974	39778	ሕብረት ባንክ አ/ማ እና አቢሲኒያ ባንክ አ/ማ	ሐምሌ 30/2001	344
127	ፈራሽ የሆነን የስጦታ ውል ተከትለው የተሰሩ ስራዎችን ቀሪ ማድረግና ተዋዋዩችን ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የሚቻለው በቅን ልቦና የተዋዋለ 3ኛ ወገን መብትን የማይጐዳ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1815,1816,1817	41116	ፍሌንስቶን ኢንጀነሪግ እና እነ ወ/ት ሐና ተስፋዬ (ስድስት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2001	350
128	የአክስዮን ድርሻ በመያዣነት እንደተሰጠ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2863 - 2874	39256	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ሞሣ ነጋሽ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2001	353

https://t.me/ethiopianlegalbrief

129	በብድር የተሰጠን ገንዘብ እጥፍ ለመቀበል በሚል የሚደረግ የብድር ስምምነት የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ	43372	አቶ ደረሱ አለሙ እና አቶ ሙሊሣ ወርቁ	ሐምሌ 22/2001	361
130	ስልጣን ያለው የአስተዳደር አካል የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነቱን አውቆለት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ከሰጠው ሰው ጋር የተደረገ የንብረቱ የመያዣ ውል የተሰጠው የምስክር ወረቀት የተሰረዘ ቢሆን እንኳን መያዣ ተቀባዩ በቅንልቦና አለመሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የፀና ሆኖ የሚቀጥል ስለመሆኑ	41388	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ከፍያለው ሞልቶት (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2001	363
131	የማይንቀሣቀስ ንብረት ገዥ ውል እንዲፈፀምለት ሻጭን የመጠየቅ መብቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 384(ሀ), የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2892(3)	39725	እነ ወ/ሮ አለምሸት ካሣሁን (ሦስት ሰዎች) እና አቶ ሽመልስ እንዳለ	ሐምሌ 23/2001	366
132	የማይንቀሣቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚደረግ የስጦታ ውል የማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም በህግ የፀና ውል ተደርጉ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443, 881, 1723(1)	39803	አቶ አለኸኝ ገ/ሀይወት እና እነ እማሆይ አጢነሽ በቀለ (ሦስት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2001	369
አፈፃፀም					372
133	በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ተካሄዶ ሽያጭ የተፈፀመ እንደሆነ ሽያጩ ሊፈርስ የሚችለው በአሻሻጥ ሥርዓቱ የተነሣ መብት ወይም ጥቅም ያለው ሰው ላይ ቀጥተኛ ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 445	31963	አቶ አብዱልሐኪም ሁሴን እና እነ አቶ ቀነኒ ሁንዴ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 20/2001	373
134	የፍርድ ባለመብት ባለመቅረቡ የተዘጋ የአፈፃፀም መዝገብ ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ10(አሥር) ዓመት ይርጋ ካልታገድ በቀር ሊንቀሳቀስ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384	35018	በዛብህ አበበ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ጥቅምት 18/2001	376
135	• የፍርድ አፈፃፀም ክርክር የሚጀመረው የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን በፍርዱ መሰረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378/1/ • የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ወይም የአፈፃፀም የውክልና ስልጣን ለተሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371,372	21359	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ተገኝ ማንደፍሮ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 28/2001	378
136	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥሮች 358 እና 418 ተፈፃሚ የሚሆኑበት አግባብ	32143	መሐመድ አስማኤል ተርቢ እና መሐመድ አህመድ ኑር	ጥቅምት 18/2001	382
137	የአንድ ንብረት ወቅታዊ ዋጋ ማለት ንብረቱ ለጨረታ ሽያጭ ቀርቦ የሚያወጣው ዋጋ ስለመሆኑ	37503	አቶ ወልደዮሐንስ ኃብተየስ እና ወ/ሮ ያምሮት ሸዋረጋ	መጋቢት 24/2001	384
138	የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ሊሸጥ የሚችልበት ሥነ- ሥርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 426,428(2)	39175	ወ/ሮ በለጡ ጋሼ እና እነ አንዱአለም ቴድሮስ (ሦስት ሰዎች)	መጋቢት 24/2001	386
139	በቀጥታ ክስ ወቅት የተገመተ የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቅት በአይነት ካልተገኘ እና የንብረቱ ዋጋ በልጦ ከተገኘ አፈፃፀሙ ሊሆን የሚገባው ንብረቱን በአይነት ለመተካት በሚያስችል የወቅቱ ዋጋ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378, 392	39485	የህፃን ሠላማዊት ቴድሮስ ሞግዚት እና መምህር ሚካኤል ግደይ	መጋቢት 17/2001	389
140	በህግ አግባብ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ የሞራል ወይም የህሊና አስተሳሰብን መሠረት በማድረግ ብቻ ዋጋ አልባ ሊደረግ የማይችል ስለመሆኑ	38041	ታደሠ ገ/መስቀል እና እነ ሙሉጌታ ዘካርያስ (ሰባት ሰዎች)	መጋቢት 22/2001	392

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 33945

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ሣልህ ሁሴን - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ደግፌ ደርቤ - ከጠበቃ ጣሰው ማሞ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡

አመልካች ግንቦት 05 ቀን 1997 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ተጠሪ በስማቸው ተመዝግቦ የሚታወቀውንና በቀድሞው አጠራር ከፍተኛ 09 ቀበሌ 07፣ በአሁኑ አጠራር በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘውን ቁጥሩ 207 እና 206 የሆነ ቤት በመያዣነት አስይዘው ብር 120ዐዐ.00 /አስራ ሁለት ሺህ/ ተበድረው ቤቱን እንዳስረከቧቸው፤ በስምምነቱ ወቅት የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥና መለወጥ ችግር ስለነበር ገንዘቡ የ10 ዓመት መክፈያ ጊዜ ተወስኖለት ጎዳር 20 ቀን 1990 ዓ.ም. ማብቃቱን፤ ጎዳር 20 ቀን 1980 ዓ.ም. በተፃፈ የብድርና የዋስትና ውል ቤትን መሸጥና መለወጥ በመንግሥት ሲፈቀድ አመልካች ብር 50ዐዐ.00 /አምስት ሺህ/ ለተጠሪ በመጨመር ከወሰዱት ብር 120ዐዐ.00 ጋር ተደምሮ በብር 170ዐዐ.00 /አስራ ሰባት ሺህ ብር/ ቤቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ ተጠሪ ውል መፈረማቸውን፤ የቤቱን የእድሣት ወጪዎችም አመልካች እንዲሸፍኑ ተጠሪ ፈቃዳቸውን በውሉ የገለጹላቸው ሆኖ ተጠሪ ከወሰዱት የቤቱ መያዣ ብድር ጋር የእድሣት ወጪ ሲደመር ድምሩ ብር 18787.90 /አስራ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሠማኒያ ሰባት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ መሆኑን፤ የቤት ሽያጭም ከ1982 ዓ.ም. ጀምሮ በመንግሥት መፈቀዱን ዘርዝረው ተጠሪ በስምምነቱ መሠረት የብድሩን ገንዘብ በወቅቱ ካለመመለሣቸውም በላይ የቤቱን ስመ ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ በአማራጭ የገቡትን ግዴታ ስላልፈፀሙላቸው አመልካች ብር 50ዐዐ.00 /አምስት ሺህ/ ለተጠሪ ጨምረውላቸው የቤቱ ስም በአመልካች እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ለማስረጃነትም የጽሑፍና የሰው ምስክሮችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች የክስ ማመልከቻና ማስረጃ ለተጠሪ እንዲደርስ ተደርጎም ተጠሪ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ፍ/ቤቱም የአመልካችን ክስና ማስረጃ መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ ውል የመያዣ ውል ሣይሆን የወለድ አገድ ውል ነው፤ ውሉ በተደረገበት ወቅት የወለድ አገድ ግንኙነት የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 47/67 ስለነበር ይኸው አዋጅ የወለድ አገድ ውልን የሚከለክል በመሆኑ ውሉ ሕገወጥ ስለሆነ ፈራሽ ነው፤ ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ይመለሱ፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ያስረክቡ፤ ተጠሪ ከአመልካች የወሰዱትን ገንዘብና የቤት ማደሻ ብር በገቡት ውል መሠረት ለከሣሽ ያክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶች ጎዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም በአጭሩ የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ቀርበው ባልተከራከሩበት እና የተጠየቀ ዳኝነት በሌለበት ሁኔታ ቤት እንዲረክቡ መወሰናቸው ያላግባብ በመሆኑ ውሣኔው ተሽሮ ጎዳር 20 ቀን 1980 ዓ.ም. በውል ያገኙት መብት ተጠብቆ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በጉዳዩ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ የተሠጠውን ውሣኔ የሕግ አግባብነት ለማጣራት ተጠሪ እንዲቀርብ ተደርጎ ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል። ይዘቱም በአጭሩ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 ድንጋጌን ያገናዘበ፣ የአመልካች ጥያቄ ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2851 ድንጋጌ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው። አመልካች የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የመልስ መልስ ማመልከቻ ተጠሪ ወደ ዋናው ጉዳይ ገብተው ለመከራከር ሥነ-ሥርዓቱ የማይፈቅድላቸው መሆኑን ገልፀውና የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ይህንኑ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም የችሎቱ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጭብጦች፡-

1ኛ/ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ከጠየቁት ዳኝነት በተለየ ሁኔታ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? እና

2ኛ/ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም? የሚሉት ሆነው ተገኝተዋል።

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች ከተጠሪ ጋር ተደርጓል በሚሉት ስምምነት አከራካሪውን ቤት ተረክበው በይዞታቸው ሥር አድርገው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ ሲሆን የጠየቁት ዳኝነትም ቀሪውን ብር ለተጠሪ ጨምረው የቤቱ ስመንብረት እንዲዛወርላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ነው። ይህንኑ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የአሁኑ ተጠሪ ፍ/ቤት ቀርበው ከስር ያልተከራከሩበት ሆኖ የስር ፍ/ቤት ግን የውሉን ሕጋዊነት በራሱ ጊዜ በማንሣት ሕገ-ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ወስኗል። ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የስር ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው የአሁኑ አመልካች በግልጽ ባላመለከቱት እና ባልጠየቁት ዳኝነት ላይ መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182/2/ ድንጋጌ ሥር የተመለከተውን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዳኝነት አሠጣጥ የስልጣን አድማስ በግልጽ የሚፃረር ነው። የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በይግባኝ ሠሚነቱ ስልጣን የስር ፍ/ቤትን የውሣኔ አሠጣጥ ማረም ሲገባው በተመሣሣይ ምክንያት ተቀብሎ ማጽናቱ የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓቱን ያላገናዘበ ነው። የስር ፍ/ቤት ስለውሉ ሕጋዊነት ክርክር ባልተነሣበት ሁኔታ በራሱ ጊዜ ማንሣቱም የክርክር አመራር ስርዓቱ በሚፈቅድለት ሁኔታ አይደለም። ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሣይቀርቡ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ከተወሰነ በኋላ አሁን በሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም። ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሣይቀርቡ ታይቶ በተሰጠው ውሣኔ ለበላይ ፍ/ቤት ሊያቀርቡ የሚችሉት ክርክር ከስር ክስ ተያይዘው የቀረቡትን የከሣሽን ማስረጃዎች አግባብነት፣ ተቀባይነት እና ጥንካሬ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን መሠረት በማድረግ ብቻ የተወሰነ ነው። ስለሆነም ተጠሪ በዚሁ የክርክር ደረጃ ያነሱት ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል። በዚህም መሠረት የስር ፍ/ቤት የውሣኔ አሠጣጥ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ መሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል።

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- በመጀመሪያው ጭብጥ እንደተገለው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ስመ ንብረቱ እንዲዞርላቸው ይወሰን ዘንድ ነበር። የስር ፍ/ቤትም የዚህኑ ጥያቄ አግባብነት በመመርመር ውሣኔ መስጠት እየተገባው ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ ውሣኔ ሰጥቷል። የአመልካች ጥያቄ ተገቢነት ያለው መሆን ያለመሆኑን የስር ፍ/ቤት በጭብጥነት ይዞ በሕጉ አግባብ የሰጠው ውሣኔ ባይኖርም ከተጠየቀው ዳኝነት ይዘት በሰበር ችሎቱ ከዚህ በፊት በተመሣሣይ ጉዳይ ከተሰጠው የሕግ ትርጓሜና ከፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ዓላማ አኳያ ሲታይ በዚህ ችሎት ለጉዳዩ እልባት መስጠቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም መሠረት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የሚያስከስስ ሊሆን ይችላል አይችልም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከአመልካች ክስና ክርክር ማረጋገጥ የተቻለው ከተጠሪ ጋር በተደረገው ስምምነት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ተረክበው ለረጅም ጊዜያት በይዞታቸው ስር አድርገው የሚገኙ መሆኑን፣ ቤቱን የሚመለከቱ አስፈላጊ ሰነዶችም በተጠሪ እጅ ይገኛሉ ተብሎ በክሱ አለመገለጹንና የዳኝነት ጥያቄ ያልቀረበበት መሆኑን በተጠሪ በኩል መፈፀም አለበት የተባለው የቤቱ ስመ ንብረት ማዞር ብቻ መሆኑን ነው፡፡ የስም ዝውውር ተግባር የሚፈፀመው በመንግሥት አስተዳደር ክፍል ፊት እንጂ ሻጭ ነው የተባለው ወገን ሊፈጽም ይገባል ተብሎ ከሕግ ወይም ከውል ይመነጫል ሊባል የማይችል ግዴታ ነው፡፡ የስም ዝውውር ጥያቄ የሚስተናገደው የባለ ሀብትነት የምስክር ወረቀት በሚሠጥ የመንግሥት አስተዳደር አካል ገገርው ውልና አስፈላጊ ሠነዶችን ይዞ ሲቀርብ እንጂ በፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ዳኝነት የሚሰጥበት አይደለም፡፡ አንድ ክስ ሊቀርብ የሚገባው የክስ ምክንያት ሲኖረው ሲሆነ የክስ ምክንያትም ተከሣሽ ለከሣሽ ሊፈጽመው የሚገባው ግዴታ መኖሩ ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ሲረጋገጥ የሚታወቅ ነው፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ተጠሪ የስም ዝውውሩን እንዲፈጽሙ ይወስንልኝ ብለው ዳኝነት መጠየቃቸው በተጠሪ በኩል ሊፈፀም የሚገባ የሕግ ወይም የውል ግዴታ የሌለ መሆኑን ስለሚያሣይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231/1/ሀ/ መሠረት ፍሬ ነገሩ የማያስከስስ ነው ተብሎ መወሰን ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13295 ጥቅምት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 51107 ጎዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም. የፀና ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የስም ዝውውር ጥያቄ ታይቶ ይወስንላቸው ዳኝነት ጠይቀው እያለ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ ውሉ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ ቤቱን እንዲያስረክቡ መባሉ የዳኝነት አሰጣጥ ሥርዓትን የተከተለ አይደለም ብለናል፡፡
3. የአመልካች የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የሚያስከስስ ምክንያት የለውም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36848

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤ/ኃይል ኮርፖሬሽን

ተጠሪዎች፡- 1. መኰንን ግርማይ - ቀረቡ፡፡

2. በዶ ዘለቀ - ቀረበ

3. ፈጠነ አያዩ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሾች የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የኤሌክትሪክ ምሰሶ ጉድጓድ ለመቆፈር ጊዜያዊ ሠራተኞች በመሆን ሠርተናል፤ በኋላም ወደ ረዳት የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋት አሽጋግሮን ስንሰራ ከቆየን በኋላ ካለማስጠንቀቂያ ከስራ ስላሰናበተን ወደ ስራችን ተመልሰን ቋሚ ሠራተኞች እንድንሆን ይወሰንልን በማለት ነው፡፡ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎችም በስራ ላይ ደረሰብን ለሚሉት ጉዳት ያወጡት ወጪ ይተካላቸው ዘንድ በተጨማሪ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በእሱ እና በተጠሪዎች መካከል የተደረገ የስራ ውል እንደሌለ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ ከግራ ቀኝ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪዎች የአመልካች ሠራተኞች ናቸው፤ የስራ ውላቸው የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው፤ በመሆኑም አመልካች በሕጉ መሠረት የሚከፈሉትን ክፍያዎች እንዲሁም በስራ ላይ ሣሉ ለደረሰባቸው የአካል ጉዳት ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መጋቢት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪዎች የአመልካች ሠራተኞች ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪው ነጥብ በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የስራ ውልን መሠረት ያደረገ ግንኙነት ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለው ነው፡፡ ከስር ጀምሮ ከቀረበው የአመልካች ክርክር እንደሚታየው ተጠሪዎች በተባለው የምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ ወይም የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋት ስራ አልተሣተፉም አይልም፡፡ ክርክሩ ይህን ስራ የሰሩት ከኔ ጋር የስራ ውል አድርገው ሣይሆን፣ ስራውን እንዲሠራ ኮንትራት ከተሰጠው ግለሰብ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ነው የሚል ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ይህን ጭብጥ በመያዝ ማስረጃ እንደሰማና በዚህም አመልካች ስራውን በኮንትራት የሰጠው ግዛው ወንዳፍራሽ ለተባለ ሰው እንደሆነ፣ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የቅጥር ግንኙነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሌላቸው፣ ግዛው ወንዳፍራሽ ክፍያውን ሲፈጽም እንደቆየ ማረጋገጡን በአንድ በኩል ሲገልጽ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተከሣሽ /አመልካች/ ከሱ ጋር የቀን ስራ ሲሰሩ አለመቆየታቸውን ሙሉ በሙሉ አልካደም፤ ክፍያው ሲፈፀም የነበረው ከአመልካቹ በተገኘ ገንዘብ ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ እንደሰጠ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የተደረገ የሥራ ውል እንደሌለው በግለጽ በማመልከት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪዎች የተባለውን ስራ ሊሠሩ የቻሉበትን ምክንያትም ከመግለፁም በላይ፣ በቆጠረው ማስረጃም እንደክርክሩ ጭብጥ አስረድቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ ሁኔታ በውሣኔዎቻቸው ላይ በሚገባ አስፍረው ግንዛቤ አግኝተው ሣለ ተቃራኒ የሆነውን ውሣኔ መስጠታቸው ትክክል አይደለም፡፡ ማንኛውም ክርክር ሊወሰን የሚገባው በቀረበው ክርክር ማስረጃ እና በሕጉ መሠረት ብቻ ነው፡፡ እነዚህን መሠረታዊ ቁምነገሮች በማለፍ የሚሰጥ ውሣኔ በማንኛውም መለኪያ ሕጋዊ ሊሆን አይችልም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም ከቀረበው ክርክር፣ከተሰማው ማስረጃ እና ከሕጉ ውጭ የተሰጠ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 06165 መጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05200 መጋቢት 1 ቀን 2000 ያፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የስራ ውል ግንኙነት ስለሌለ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ የመሠረቱት የስራ ክርክርን የሚመለከተው ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ወስነናል፡፡ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35946

ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ማሙሽ ወልደስላሴ
2. ወ/ሮ አፀደ ወልደስላሴ
} ጠበቃ ውብሸት ሥነ ጊዮርጊስ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሰብለ ወንድይራድ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ የሺ ሙላት - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት አቤቱታ ወ/ሮ ውዴ ወልደስላሴ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ነሐሴ 21 ቀን 1989 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ ሟች በሕይወት እያሉ ነሐሴ 9 ቀን 1989 ዓ.ም እማኞች ባሉበት ባደረጉት ኑዛዜ በድሬዳዋ ከተማ ከፍተኛ 1 ቀበሌ 06 በአሁኑ አጠራር በቀበሌ 04 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 839 ለእኛ ለአመልካቾች አውርሰውናል፤ ሁለተኛ አመልካችም አካለመጠን ላልደረሰችው ተማሪ ኮከብ እሱባለው ሞግዚት አድርገው ሾመውኛል፤ ስለዚህ በምናቀርበው ማስረጃ ተረጋግጦ የወራሽነት ማረጋገጫና አካለመጠን ላልደረሰችው ተማሪ ኮከብ እሱባለው የሞግዚትነት ማስረጃ ይሰጠን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የአመልካቾችን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ ትእዛዝ በሰጠው መሰረት የአሁን አመልካቾች በተቃዋሚነት ቀርበው ቀደም ሲል አመልካቾች ተመሳሳይ አቤቱታ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገ ሲሆን በይግባኝም ጸንቷል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ በድጋሜ ያቀረቡ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ውድቅ ሊያደርገው ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን በአማራጭም ሟች ውዴ ወ/ስላሴ አድረገውታል የተባለው ኑዛዜ በእድሜም ሆነ በጤንነት ረገድ እራሳቸውን በማያውቁበት ጊዜ የአሁን አመልካቾች እራሳቸው ፈጥረው ያዘጋጁትና በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ አመልካቾች የወ/ሮ ውዴ ልጅነትም ሆነ የሩቅ ዝምድና ስለሌላቸው የኑዛዜ ወራሽነት ጥያቄው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የድሬዳዋ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አቤቱታው አስቀድሞ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ አግኝቷል የተባለውን በተመለከተ ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ሳይቀበለው የቀረው አንድ ኑዛዜ ከተደረገ በኋላ በዚሁ ኑዛዜ መሰረት ወራሾች የንብረት ክፍፍል ከሚያደርጉ በስተቀር ኑዛዜ በፍ/ቤት እንዲጸድቅ ሕግ ስለማያስገድድ ኑዛዜ ይጽደቅልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመስጠቱ በስተቀር የኑዛዜ ወራሾች ናችሁ ወይንም አይደላችሁም የሚል የመጨረሻ ውሳኔ ስላልሰጠ ጉዳዩ አስቀድሞ እልባት አግኝቷል ተብሎ የቀረበው ክርክር አግባብነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የኑዛዜውን ሕጋዊነት አስመልክቶ የተነሳውን ክርክር በተመለከተም ሟች በጤነኛ አእምሮና በነጻ ፈቃዳቸው ኑዛዜውን ስለማድረጋቸው በአመልካቾች ምስክሮች የተረጋገጠ ስለሆነና ሟችም ንብረታቸውን ለፈለጉት ሰው በኑዛዜ የማስተላለፍ መብት ስላላቸው ተጠሪዎች የአመልካቾችን የኑዛዜ ወራሽነት በመቃወም ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ በሌላ በኩልም ሟች ኑዛዜ ያደረጉበት ቤት ባለሐብትነቱ በከፊል የእራሳቸው በከፊል ደግሞ የሟች ባቤታቸው የነበረ ስለሆነ ከእራሳቸው ድርሻ አልፎ የሟች ባቤታቸውንም ድርሻ ጨምሮ ያደረጉት ኑዛዜ ሕገ ወጥ ስለሆነ በድርሻቸው ልክ የተደረገው ኑዛዜ ብቻ ትክክል ነው ብሎ በዚሁ ልክ አመልካቾች ወራሾች ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለድሬዳዋ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻው ነጥብ የተጠሪዎች የኑዛዜ ወራሽነት በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠው አግባብነት ባለው ሁኔታ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከዚህም አኳያ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪዎች የኑዛዜ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው አቤቱታቸውን ለድሬዳዋ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለትም ይሄው ፍ/ቤት በቅድሚያ የአመልካቾችን/የአሁን ተጠሪዎችን/ ምስክር ከሰማ በኋላ ተቃዋሚ ካለ ይቅረብ በማለት የጋዜጣ ጥሪ አድርጓል፡፡ እዚህ ላይ ተቃዋሚ ቢኖር ይቅረብ ተብሎ የተሰጠው ትእዛዝ አግባብነት ነበረውን የሚለው ነጥብ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ተቃዋሚ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠት የነበረበት አመልካቾች አቤቱታቸውን እንዳቀረቡ ማስረጃ ከመስማቱ በፊት መሆን ይገባው ነበር፡፡ ተቃዋሚ የሚጠራበት አላማ የቀረበውን አቤቱታ ከማስረጃውና በአጠቃላይም ከሚቀርበው ክርክር አኳያ የበኩሉን ማስረጃና ክርክር እንዲያቀርብ እድል ለመስጠት ነው፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ተቃዋሚ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠቱ ተቃዋሚው በምስክሮች አመሰካከር ላይ የሚያነሳውን ክርክር/The right to confront witnesses/ የሚያጠብና ጉልህ የሆነ የሥነ- ሥርአት ጉድለት መፈጸሙን የሚያመለክት ነው፡፡

ስለሆነም የድሬዳዋ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካቾችን /የአሁን ተጠሪዎችን/ ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተቃዋሚዎችን መጥራቱ እንደዚሁም ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይህንኑ ጉድለት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የድሬዳዋ ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00409/99 በሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0134/99 ኅዳር 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሽረነዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የድሬዳዋ ከተማ ነክ ፍ/ቤት የተጠሪ ምስክሮችን በድጋሜ በመጥራት ግራ ቀኙ ባሉበት በመስማት ክርክሩን በድጋሜ ተመልክቶ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36479

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ/- ጠ/አለም ወ/አረጋይ

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሉ ወልዱ - አልቀረቡም

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የተጠሪ የስራ ውል የተቋረጠው በሕገ ወጥ መንገድ ነው ተብሎ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ሲሆን ለሠበር ችሎት የቀረበው የሕግ ጥያቄም ለምስክሮች ስለሚሰጥ መጥሪያ አደራረስ የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ገልፀው ሕጉ የሚፈቅድላቸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ክስ መስርተዋል፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ ያሽከረክሩት የነበረው መኪና ለአቶ አገኘሁ የኔነህ በመሸጡና ከሣሽ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከገዢው ጋር አዲስ የስራ ውል በማድረግ በስራ ቦታ ላይ ያልተገኙ በመሆኑ እንደሆነ ተከራክሮ ስንብቱ ሕጋዊ ነው እንዲባልለት ጠይቋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት መዝገቡንና ማስረጃዎቹን መርምሮ የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ መኪናው ከተሸጠ በኋላም የድርጅቱን መኪና በመያዝ ያገለግሉ እንደነበር አስረድተዋል፤ ተጠሪ መኪናው መሸጡ እንዳልተገለፀላቸው ያስረዱ ሲሆን አመልካች ግን ተጠሪ መኪናው መሸጡን ማወቅ ነበረባቸው ወይም አሣውቁአለሁ የሚል ክርክር ስለሌለው ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት ተጠሪ የኪሣራ እና የስንብት ክፍያዎች እንዲሁም የሐምሌ ወር 1998 ዓ.ም ደመወዛቸው እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ይግባኝ ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በአቤቱታው ተጠሪ ሲያሽከረክሩት የነበረው መኪና በመሸጡ ተጠሪ መኪናዋን ከገዙት ግለሰብ ጋር ለመስራት ተስማምተው በስራ ቦታቸው ባለመገኘታቸው የሥራ ውሉ መቋረጡን መኪናዋን የገዙትን ግለሰብ በምስክርነት ቆጥረናቸው ምስክሩ ሆነ ብለው በመሠወራቸው መጥሪያውን ልንሰጥ ስላልቻልን በሚኖሩበት አካባቢ ባለው ፖሊስ ጣቢያ አማካኝነት እንዲደርሣቸው በድጋሚ መጥሪያ እንዲታዘዝልን ያመለክትን ቢሆንም

ፍ/ቤቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 116 እና 118/2/"ን" በተሣሣተ መንገድ በመተርጎም መጥሪያው በመሐላ ቃል በተደገፈ አቤቱታ ለፍ/ቤቱ ስላልተመለሠ በድጋሚ መጥሪያ አይታዘዝም ማለቱ ስህተት ነው ብለዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ የታዘዘ ሲሆን ተጠሪም ቀርበው ሕጉ በሚፈቅደው ቃለ መሐላ አቅርበው ምክንያታቸውን መግለጽ ሲችሉ ስላላቀረቡ የፍ/ቤቶቹ ውሣኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያላግባብ ተሰናብቻለሁ በማለት ክስ ሲያቀርቡ አመልካች ደግሞ ተጠሪ ሲያሽከረክሩ የነበሩት መኪና በመሸጡ ተጠሪ ንብረቱን ከገዙት ሰው ጋር ለመስራት በመዋዋል በስራ ቦታቸው ባለመገኘታቸው የስራ ውሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቋርጧል ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች ይህንን አባባሉን እንዲያስረዱለት መኪናውን ገዙ የተባሉትን ግለሰብ በመስክርነት ቆጥሯቸው የነበረ መሆኑንና ምስክሩን አግኝቶ መጥሪያ መስጠት ባለመቻሉ ግን መጥሪያው ምስክሩ በሚኖሩበት አካባቢ በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ አማካኝነት እንዲደርሣቸው ጠይቆ ፍ/ቤቱ ይህንን ሁኔታ በቃለ መሐላ አስደግፎ ባለማቅረቡ ድጋሚ መጥሪያ እንዲሰጥ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ስህተት መሆኑን ገልጿል፡፡ በእርግጥ ተያይዞ በቀረበው የሥር ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ ላይ ይህ ስለመሆኑ የተገለፀ ነገር ባይኖርም ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስ ይህንኑ አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለምስክሩ የተላከውን መጥሪያ ምስክሩን አግኝቶ መስጠት አለመቻሉን በቃለ መሐላ በማስደገፍ አለማረጋገጡ በድጋሜ መጥሪያ እንዳይታዘዝ ያስከለክለዋል ወይ? የሚለውን ይህ ችሎት ተመልክቷል፡፡

አመልካች ስንብቱ ሕገ-ወጥ አይደለም በማለት አጠቃቀ የሚከራከረው ተጠሪ የሚነዱት መኪና በመሸጡና ተጠሪም መኪናውን ከገዙት ሰው ጋር ለመስራት ተስማምተው ከስራ ቦታቸው ላይ ባለመገኘታቸው በበቂ ምክንያት ተሰናብተዋል በማለት ነው፡፡ ይህ ለመሆኑም መኪናውን የገዙት ግለሰብ ቀርበው እንዲመሠክሩ ጠይቋል፡፡ አንድ ተከሣሽ ለቀረበበት ክስ የሚያቀርበውን ማስተባበያ በማስረጃ እንዲያስረዳ መብት አለው፡፡ እኛም እንደተገነዘብነው አመልካች የቆጠራቸው መስክር መሰማት ለውሣኔ አሰጣጥ ጠቃሚ እና አስፈላጊ መሆናቸውን ነው፡፡ በእርግጥ የተከሣሽ መከላከያ ማስረጃዎች ልቅ በሆነ መንገድ የሚቀርቡ ሣይሆኑ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት መሆን ይገባዋል፡፡ ስነ - ስርዓቱን ተከትሎ የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ግን ያለ ሕጋዊ ምክንያት ውድቅ ማድረግ የተከሣሹን የመከላከል መሠረታዊ መብት የሚያጣብብ ነው፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 116 ስለምስክሮች መጥሪያ አሠጣጥ ሲገለጽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 118 ሥር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምስክር የሚሰጥ መጥሪያ ሁሉ ለተከሣሾች መጥሪያ ስለመስጠት በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት የሚፈፀም ቢሆንም ከቁጥር 103 እስከ 105 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ግን ተፈፃሚ እንደማይሆኑ ያመለክታል፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ለቆጠራቸው ምስክር የተላከው መጥሪያ ምስክሩ ባለመገኘታቸው ሲመለስ በቃለ መሐላ መረጋገጥ ነበረበት በማለት ለምስክሩ ድጋሚ መጥሪያ እንዳይላክ መከልከሉን ተገንዝበናል፡፡

በእርግጥ ለተከሣሹ መጥሪያ በሚላክበት ወቅት መጥሪያ ሰጪው ተገቢውን ፍለጋ አድርጎ ተከሣሹን ማግኘት ያልቻለ ከሆነ መጥሪያ መስጠት ያልቻለበትን ምክንያት በቃለ መሐላ አረጋግጦ መመለስ እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.103 ያመለክታል፡፡ በመሆኑም መጥሪያ በድጋሚ ለተከሣሽ የሚላከው መጥሪያ ሰጪው የተከሣሹን አለመገኘት በቃለ መሐላ አረጋግጦ መጥሪያውን ሲመልስ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ለምስክር የሚሰጥ መጥሪያ አደራረስ ለተከሣሽ በሚላክበት ዓይነት ቢሆንም ይህ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 103 ግን በምስክር ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው በሥነ ሥርዓት ሕጉ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነ ምስክሩን ማግኘት ባልተቻለ ጊዜ መጥሪያው በግድ በቃለ መሐላ በተደገፈ አቤቱታ ካልተመለሠ በቀር በድጋሚ መጥሪያ ሊላክ አይገባም የሚባልበት የሕግ መሠረት የለም፡፡

በሌላ በኩል ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 118/2/ሀ/ ሥር እንደተመለከተው እንዲቀርብ የተፈለገው ምስክር ለጉዳዩ አወሣሰን ጠቃሚ ከሆነ ፍ/ቤቱ የተላከው መጥሪያ ለባለአድራሻው በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን አረጋግጦ ባለጉዳዩ ተገቢውን ኪሣራ ከፍሎ መጥሪያ እንዲወስድ ማድረግ አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች የሥራ ውሉ ተቋረጠ የሚለው ተጠሪው መኪናውን ገዙ ከተባሉት ግለሰብ ጋር ስራ በመጀመሩ በሥራ መደቡ ላይ ባለመገኘቱ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ መረጋገጡ ለውሣኔው አስፈላጊ ነጥብ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ስለሆነም ይህንን እውነታ ያስረዳሉ የተባሉት ምስክር መጥሪያ ያልደረሣቸው መሆኑ ከተረጋገጠ በድጋሚ እንዲደርሣቸው አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በቀጠሮ መለወጥ ምክንያት በተጠሪ ላይ የሚደርስ መጉላላት ካለም ፍ/ቤቱ አመልካች ተገቢውን ኪሣራ እንዲከፍል ለማዘዝ ይችላል እንጂ ለምስክር ስለሚደረስ መጥሪያ ተፈፃሚነት በሌላው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 103 መሠረት መጥሪያው ያልደረሰበት ምክንያት በቃለ - መሐላ መደገፍ ነበረበት በሚል የአመልካች ጥያቄ ውድቅ መደረጉ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24475 በ23/5/2000 ውሣኔ እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 63168 በ21/06/2000 የተሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

2/ አመልካች የቆጠሯቸው መኪናዋን ገዝተዋል የተባሉት ምስክር መጥሪያ ደርሷቸው ምስክርነታቸውን ከሰጡ በኋላ ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሠረት ጉዳዩ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36412

ጥቅምት 13 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ተስፋሁን ዋኘው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- በጅያክ አግሮ ኮሜርሻያል ኢንተርፕራይዝ - ተወካይ ሙላት ታግሎ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካችና በሌላ ግለሰብ ላይ መጋቢት 27 ቀን 1999 ዓ.ም በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሠረተው የንብረት ጉዳት ካሣ ክስ ነው፡፡ የክሱ ሂደት ቀጥሎም አመልካች የፍ/ቤቱ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ይዘው አለመቅረባቸውና ክሱ በሚሠማበት ቀነ ቀጠሮም አለመቅረባቸው ተረጋግጧል ተብሎ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ብይን ከተሰጠ በኋላ አመልካች በሌሉበት ክርክሩ እንዲታይ የተሰጠው ብይን ተነስቶ ወደ ክርክሩ ገብተው ለመከራከር እንዲፈቀድላቸው አለኝ ያሉትን ምክንያት ገልፀው ጥያቄ ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤት ሣይቀበላቸው ቀርቶ በመጨረሻም በአሁኑ ተጠሪ የቀረበለትን ክስ እና ማስረጃ መርምሮና ተገቢ ነው ያለውን ማስረጃ ሁሉ በማስቀረብና በመመልከት የአሁኑን አመልካችና አንድ ላይ ተከሣ የነበረውን ግለሰብ ለንብረት ጉዳቱ አሳፊ በማድረግ የብር 70,500.00 /ሠባ ሺህ አምስት መቶ/ ካሣ በአንድነትና በነጠላ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሠበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ያሉበትን ምክንያት ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የፍ/ቤቱ መጥሪያ ደርሶ ያልቀረቡት በውሃ ሙላት ምክንያት መሆኑን፣ በብይኑም ሆነ በዋናው ውሣኔ ላይ በአንድነት ይግባኝ የመጠየቅ መብት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተጠበቀላቸው ሆኖ እያለ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በዋናው ውሣኔ ላይ ብቻ ይግባኝ እንደቀረበ በመቁጠር መወሰኑ ከጭብጡ ውጭ መሆኑን በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካችን በብይኑ ላይ በይግባኝ ሣትመጣ በፍሬ ነገሩ ላይ ይግባኝ ማለት አትችልም ሲል ይግባኙን አለመቀበሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ተጠሪን ያስቀርባል ብሎ ተጠሪ ሐምሌ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘትም በአጭሩ የሚሞላ ውሃ የተባለው ሐሰት መሆኑንና ይልቁንም የመኪና መንገድ ያለ መሆኑን ይግባኙ የቀረበውም በዋናው ጉዳይ ላይ መሆኑንና መጥሪያውም በጊዜው የደረሰ መሆኑን በመግለጽ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ይህንኑ የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ትእዛዝ፣ ከግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የቀረበውን የአመልካችን ይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለመመርመሩ አግባብነት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንደሚታወቀው የፍትሐብሔር ክርክሮች የሚመሩት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ነው፡፡ ይኸው የሥነ-ሥርዓት ሕግ አካቶ ከያዛቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የተከራካሪ ወገኖች በክርክሩ ወቅት ያለመቅረብና ውጤቱ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መጥሪያ ተልኮለት በተገቢው መንገድ የደረሰው መሆኑ በተረጋገጠበት ተከሣሽ ላይ ፍ/ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓት ጉዳዩ ተከሣሹ በሌለበት የሚሰማበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70/ሀ/ ስር ተመልክቷል፡፡ የዚህ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ መንፈስ የሚያሣየውም በፍ/ቤቱ መጥሪያ መሠረት ያልቀረበ ተከሣሽ በክርክሩ ሂደት ለማንሣት የሚችላቸውን የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክሮች እንዲሁም በማስረጃ አሰማም ሂደት የመስቀለኛ ጥያቄ የማንሣት መብቱን ሣይጠቀም የሚቀር መሆኑን ነው፡፡ ለተከሣሽ እነዚህ መብቶች የሚቀሩ ሆነው በከሣሽ በኩል የቀረበው ክስ ተያይዘው ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር ተመርምሮ እና በጉዳዩ ላይ መፈፀም ያለበት ሌላ አስፈላጊ ሥርዓት ሁሉ ከተፈፀመ በኋላ ተገቢ ውሣኔ መስጠቱ ፍ/ቤቱ ሊያከናውነው የሚገባው ተከታዩ ሂደት ነው፡፡ ሌላው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከተው ሥርዓት ተከሣሹ ሊከተለው የሚገባው መፍትሔ ነው፡፡ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል የተደረገበት ተከሣሽ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያለመቅረቡን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.72 ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78/1/ አንድ ተከሣሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሣይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሣያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሣኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠ ከሆነ ውሣኔው ወይም ትእዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትእዛዙ ወይም ውሣኔው እንዲነሣለት የማመልከት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ በእነዚህ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች መሠረት አቤቱታ አቅርቦ ተቀባይነት ያጣ ተከሣሽ በተከታዩ ያለው የሥነ-ሥርዓት መፍትሔ ምንድነው ነው? ወደክርክሩ ልግባ ወይም በሌለሁበት የተሰጠው ውሣኔ ይነሣልኝ የሚለው ጥያቄ ውድቅ ሲሆንበት በዚሁ ይግባኝ ማቅረብ ወይስ በዋናው ጉዳይ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ በመጠበቅ በሁሉም ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ? የሚሉት ጥያቄዎች የሥነ-ሥርዓት ሕጉን በመመልከት ግልጽ ድንጋጌ ማግኘትና ምላሽ ለመስጠት የሚቻልባቸው ባይሆኑም የውሣኔ አሰጣጥና የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በመፈተሽ ግን ምላሹን ለማግኘት አስቸጋሪ የሚሆን አይደለም፡፡

በዚህም መሠረት ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትእዛዝ ወይም ውሣኔ የተሰጠበት ተከሣሽ ከላይ በተገለፁት የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች አቤቱታውን አቅርቦ በፍ/ቤቱ ተቀባይነት ካላገኘ በዚሁ ብይን ላይ ቅሬታውን ለበላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ከማሣየት የሚከለክለው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ አለመኖሩን የይግባኝ አቀራረብን በተመለከተ የሚደነግጉት ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ ተከሣሹ ጠብቆ በዋናው ጉዳይ ላይ ከተሰጠው ውሣኔ ጋር አጠቃልሎ ይግባኝ ሊያቀርብ ይገባል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከይግባኝ አቀራረብ የጊዜ ገደብ ሥርዓት ጋር ሊጣጣም የማይችልበት ሁኔታ ከመኖሩም በላይ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ እስኪሰጥ ተጠብቀው በዋናው ጉዳይ ላይ ከተሰጠው ውሣኔ ጋር ተጠቃልለው ይግባኝ ሊቀርብባቸው ይችላል ተብለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320 ንዑስ ቁጥሮች ስር የተመለከቱት ምክንያቶች በባህርያቸው ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸው ሆነው መሠረታዊውን መብት ሊያጣብቡ የማይችሉ ከመሆናቸው ጋር ተዳምሮ ሲታይ የይግባኝ መብት የሚከለክል ሥርዓት የለም፡፡ አንድ ተከራካሪ ወደ ክርክሩ ገብቶ እንዲሣተፍ እድል መስጠት የሕግ ሥርዓት የግድ የሚለው ሲሆን ይህንን ዕድል መንፈግ መሠረታዊውን መብት ማጣበብ በመሆኑ ቅሬታ ያለው ወገን በይግባኝ ሥርዓት ጥያቄውን አቅርቦ ጉዳዩ እንዲታይለት ማድረግ መብቱ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትእዛዝ ተሰጥቶ ይኸው ትእዛዝ እንዲነሣላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ሲያጣ በዚሁ ነጥብ ብቻ ቀደም ብለው ይግባኛቸውን ለበላይ ፍ/ቤት ሣያቀርቡ በዋናው ጉዳይ ውሣኔ ሲሰጥ ግን ይግባኛቸውን አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም አመልካች ጉዳዩ ባለሁበት ይታይልኝ በሚል ጥያቄ ሲያቀርቡ ወደ ክርክሩ ሊገቡ አይገባም ተብሎ ብይን ሲሰጥ በዚሁ ብይን ላይ ይግባኝ ብለው መምጣት ሲገባቸው ውሣኔ ሲሰጥ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ይግባኝ ብለው መምጣታቸው ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም በሚል ምክንያት ፍሬ ጉዳዩን ሣይመረምር መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ የሠበር ችሎት የሚከራከሩት ወደ ክርክሩ ሊገቡ አይገባም የተባለው ያላግባብ መሆኑንና በይግባኝም በዚሁ ነጥብና በዋናው ጉዳይ ወደ በላይ ፍ/ቤት ከመሄድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚከለክል ሥርዓት የለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ወደ ክርክሩ አይገቡም የተባለው ባግባቡ መሆኑንና ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡትም በዋናው ጉዳይ ላይ ብቻ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

የአመልካች ወደ ክርክሩ ልግባ ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በቂ ምክንያት እያለኝ ነው በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መመዘኛው ምን እንደሆነ በግልጽ ያልተመለከተ ሲሆን ባለው አሠራርም ፍ/ቤት የሚቀርብለትን ማስረጃ በመመርመርና የራሱን የህሊና ሚዛን መሠረት በማድረግ ሊያስተናግደው የሚችለው በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚደርሰው ድምዳሜ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ተብሎ በሠበር ችሎት ሊታረም የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር የምንቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ችሎት ሊታይና ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ አመልካች በፍሬ ጉዳዩ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችሉ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

አመልካች ወደ ክርክሩ ለመግባት ጥያቄ አቅርበው ተቀባይነት ካጡ በኋላ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ሊኖረው የሚችለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78/1/ ነው፡፡ የዚህ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ የአማርኛና የእንግሊዝኛው ትርጓሜ ሙሉ ይዘቱ ቀጥሎ የሠፈረው ነው፡፡ ይኸውም

«ቁ.78 ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሣኔ ስለማንሣት

1/ አንድ ተከሣሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሣይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሣያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሣኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ውሣኔው ወይም ትእዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትእዛዙ ወይም ውሣኔው እንዲነሣለት ሊያመለክት ይችላል፡፡»

«Art. 78- Setting aside decree ex-parte against defendant

1. Any defendant against whom a decree is passed or order made ex-parte or in default of pleading may, within one month of the day when he became aware of such decree or order, apply to the court by which the decree was passed or order made for an order to set it aside.»

ከእነዚህ ትርጓሜዎች መረዳት የሚቻለው በድንጋጌው መሠረት ጥያቄ የማቅረብ ምርጫ የተከሣሹ ሆኖ አስገዳጅነት የሌለው ሥርዓት መሆኑን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 72 መሠረት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያጣ ተከሣሽም በዚሁ ነጥብ ብቻ ይግባኝ ማቅረብ ያለማቅረቡ ምርጫው ነው፡፡

በሌላ አገላለጽ ተከሣሹ ወደ ክርክሩ ልግባ በማለት ወይም በሌለሁበት የተሰጠው ትእዛዝ ወይም ውሣኔ ይነሣልኝ ብሎ ጥያቄ ማቅረብ ወይም ይህንኑ በመተው ለበላይ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ ምርጫው በሥነ-ሥርዓቱ የተተወለት መብት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ለበላይ ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ በተሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ሲያቀርብ የይግባኝ አቀራረብ አድማሱ በተወሰኑት ነጥቦች ላይ ብቻ መሆን አንዳለበት የይግባኝ አቀራረብን በተመለከተ የተደነገጉት ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ እንደሚታወቀው የፍትሐብሔር ሙግት አካሄድ ሥርዓታችን በተከራካሪ ወገኖች መነሣት ያለባቸው የክርክር ነጥቦች እንዳሉ ያሣያል፡፡ በክርክሩ ሂደት ተነስተው በፍ/ቤቱ ተገቢ ያልሆነ ውሣኔ ተሰጠብኝ የሚለው ወገንም ነጥቡን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ የይግባኝ ቅሬታ ነጥብ መሆን ያለበት ግን በበታች ፍ/ቤት የተነሣ ነጥብ እንጂ አዲስ ሊሆን እንደማይገባ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329/1/ ያሣያል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተወሰነበት ተከሣሽ ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ ሊኖር የሚችለው በስር ፍ/ቤት በተከራካሪነት ቀርቦ ያላነሣውን ነጥብ እንዳያነሣ ነው ከሚባል በስተቀር ሙሉ በሙሉ ይግባኝ ሊያቀርብ አይችልም የሚባልበት ሥርዓት የለም፡፡ እንደዚህ ዓይነት ተከራካሪ በፍ/ቤቱ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ክሱን፣ የማስረጃዎችን አግባብነት፣ ተቀባይነት እና ጥንካሬ ባግባቡ ያላገናዘበ ሁኔታ አለ የሚል ከሆነ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱ የከሣሽ ክስ ተከሣሽ በሌለበት ስለታየ ብቻ የተጠየቀው ዳኝነት ይሰጣል ተብሎ የማይጠበቅ ስለመሆኑ የዳኝነት አሰጣጥ ሥርዓት ያስገነዝባል፡፡ ፍ/ቤት ከሣሹ ያቀረበውን ክስ አሳሪ ሆነው ከቀረቡት ማስረጃዎች አግባብነት፣ ተቀባይነትና ጥንካሬ አኳያ በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት መስጠት የእለት ተዕለት የሥራ ድርሻው ነው፡፡ በዚህ አኳኋን ታይቶ የተሰጠ ውሣኔ አይደለም የሚል ተከሣሽ በክርክሩ ሂደት ተሣታፊ ያልነበረ ቢሆን አዲስ ክርክር ከማንሣት በመለስ የይግባኝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለልም አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ ያቀረቡት ይግባኝ ሣይመረመር የተዘጋው ጥያቄያቸውን የሚከለክል ግልጽ ሥርዓት በሌለበት ሁኔታ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16249 መጋቢት 03 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ አመልካች ወደ ክርክሩ ሊገቡ ጥያቄ አቅርበው ተቀባይነት ካጡ በኋላ በሌሉበት ጉዳዩ ታይቶ በተሰጠው ውሣኔ ፍ/ቤቱ በሕጉ መሠረት ውሣኔ አልሰጠም በሚሉ ነጥቦች ተወስነው በፍሬ ጉዳዩ ላይ ይግባኝ ለበላይ ፍ/ቤት ከማቅረብ የሚከለክላቸው የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ የለም ብለናል፡፡

3/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ይግባኝ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን ተገንዝቦ ፍሬ ጉዳዩን በመመርመር በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

4/ በዚህ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5/ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36380

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነገረፈጅ አቶ አደም ንጉሴ ቀረቡ

መልስ ሰጭ፡- አቶ ታረቀኝ ገ/ዓዲቅ - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለውሳኔ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በይግባኝ እያከራከረ እያለ ይግባኝ ባይ የነበረው የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ይግባኙን ለመስማት በተቀጠረበት እለት አልቀረበም፡፡ መልስ ሰጭ የነበረው አቶ ታረቀኝ ገ/ዓዲቅም ክዶ ተከራክሯል፡፡ ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሰረት መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ በማለት የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በከ/መ/ቁ. 60818 ላይ የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡

የአሁን አመልካች የተዘጋው መዝገብ ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ እንዲታይለት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዚያው መዝገብ የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት መዝገቡ ይንቀሳቀስ ዘንድ ይግባኝ ባይ ያቀረበው ምክንያት በቂ ባለመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት አሰናብቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መዝገቡን ለመዝጋትም ሆነ የተዘጋው መዝገብ እንደገና ሊንቀሳቀስ አይገባውም ሲል የሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልን በሚል ክርክሩን ዘርዝሮ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም በበኩሉ መዝገቡ ለቃል ክርክር ተቀጥሮ በነበረበት እለት ይግባኝ ባይ ያለመቅረቡን በመገንዘብ የተሰጠው ትእዛዝ ተገቢ ነው፤መዝገቡን መልስ ለመቀበልና የቃል ክርክር ለመስማት በሚል መቀጠር የሚገረረው የሥነ-ሥርአት ሕግ ባለመኖሩ የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ይጽናልን ሲል ተከራክሯል፡፡

እኛም ሁለቱም ወገኖች በሰበር ደረጃ ያቀረቡትን ክርክር ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ መዝገብ ግልባጭ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

የአሁን አመልካች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ባይ በመሆን የአሁን መልስ ሰጭ ደግሞ በመልስ ሰጭነት ተሰይመው በሚከራከሩበት ጉዳይ መዝገቡ ለየካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተቀጥሮ የነበረው የግራ ቀኙን ክርክር ለመስማት እና የመልስ ሰጭን የጽሑፍ መልስ ለመቀበል በሚል እንደነበረ በዚሁ እለት ፍ/ቤቱ በመዝገቡ ላይ ካሰፈረው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በዚሁ እለትም ግራ ቀኙ መቅረባቸውን ለማረጋገጥ ጥሪ በተደረገላቸው ጊዜ ይግባኝ ባይ ሊቀርብ እንዳልቻለም የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይሁን እንጂ በተያዘ ቀጠሮ የቃል ክርክር ማድረግና የመልስ ሰጭን የጽሑፍ መልስ መቀበል በክርክር አካሄድ ሁለቱም እራሳቸውን የቻሉ ሥርአቶች እንጂ አንዱ ሌላውን ሊተካ የሚችል ወይም ደግሞ ተመሳሳይ የክርክር ደረጃዎች አይደሉም፡፡ የሁለቱም ሥርአት አለመፈፀም የሚያስከትለው ውጤት የተለያየ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ አኳኋን ከማዘዙ በፊት ግልጽ በሆነ አኳኋን መዝገቡ ለምን እንደተቀጠረ ለይቶ አለማዘዙ በጉዳዩ አመራር የተፈፀመ ስህተት ነው፡፡

በተለይም የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም ከነበረው ቀጠሮ በፊት መዝገቡ ለቃል ክርክር በሚል ተቀጥሮ እያለ መልስ ሰጭ ጊዜ አጥሮኛል በማለት ባመለከቱት መሰረት ተለዋጭ ቀጠሮው ለየካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሆን ተደርጓል በማለት አመልካች ላቀረበው ክርክር መልስ ሰጭ ይህንኑ አላስተባበለም፡፡ ይህም ከሆነ ከየካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በፊት በነበረው ቀጠሮ መልስ ሰጭ ቀርቦ የቃል ክርክር ማድረግ እየቻለ ቀጠሮ አጥሮብኛል ማለቱ በተከታዩ ቀጠሮ ክርክሩን በጽሑፍ ለማቅረብ እንደፈለገ ስለሚያመለክት መዝገቡ ለየካቲት 14 ቀን ተቀጥሮ የነበረው የቃል ክርክር ለማድረግ ነበር ወደሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከላይ እንደተገለፀው በአንድ ቀጠሮ የቃል ክርክር እና የጽሑፍ መልስ ፣መልስ ሰጭ እንዲያቀርብ ብሎ ማዘዙ ሥነ-ሥርአታዊ ካለመሆኑም በላይ መዝገቡ ተቀጥሮ የነበረው የቃል ክርክር ለማድረግ እንደሆነ በግልጽ ያልተመለከተ ስለሆነ ይግባኝ ባይ በቀጠሮው እለት አልቀረቡም እንኳ ቢባል ስለጉዳዩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ተፈፃሚነት ያለው አይደለም፡፡

የይግባኝ ባይ በቀጠሮው የመቅረብና ያለመቅረብ ጉዳይ ፍ/ቤቱ እንደጀመረው የክርክሩ አቅጣጫ መልስ ሰጭ ላቀረበው የጽሑፍ ክርክር የበኩሉን የመልስ መልስ ለማቅረብ መቻሉ ወይንም ለማቅረብ ያለመቻሉ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች መዝገቡ መታየት በጀመረበት እለት በመዝገብ መደራረብ ምክንያት በሌላ ችሎት በመጠራቱ እንጂ በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ይህንኑ ጉዳይ እየተከታተልኩ ነበር የሚለው ክርክሩ በማስረጃ ከተረጋገጠ የመልስ መልሱን የማቅረብ መብቱን ለማስጠበቅ እንጂ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 ጋር ሊገናኝ የሚችል አይደለም፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 339 እንደተደነገገው የይግባኝ ክርክሩን ለመስማት ሊከተል ከሚችለው ሥርአት አንዱን ለይቶ መከተል ሲገባው በአንድ ጊዜ ሊፈፀሙ የማይችሉትን ሥርአቶች አቀላቅሎ እንዲፈፀም በማዘዙ ምክንያት እና ከሁለቱ ሥርአቶችም መዝገቡ የተቀጠረው መልስ ሰጭ የጽሑፍ መልሱን ለማቅረብ በሚል ነው የሚለውን ነጥብ የመዝገቡ ግልባጭ ስለሚያስረዳ መዝገቡ የተቀጠረው የቃል ክርክር ለማድረግ በሚል ነው፤ በዚሁ እለትም ይግባኝ ባይ አልቀረቡም፤መልስ ሰጭም ክዶ ተከራክሯል የሚለውን መነሻ በማድረግ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሰረት ተዘግቷል ሲል የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሥነ- ስርአት ህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 60818 የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም እና የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጣቸው ትእዛዞች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በነበረው ቀጠሮ በእራሴ ጉድለት ምክንያት ሳይሆን በቀጠሮ መደራረብ ነው የሚለው ክርክሩ ከቀረበው ማስረጃ አኳያ ታይቶ ተከታዩ ሥርአት (የመልስ መልስ የማቅረብ መብቱ) ይጠበቅለት እንደሆነ አስፈላጊው እንዲፈጸም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሰረት መዝገቡን መልሰናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37725

ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. በቀለ ዲሪብሣ ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ደስታ ከፈኔ - ተወካይ ተስፋዬ በቀለ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የምክር በሪሁን - ጠበቃ አቶ ጌትነት የሻነህ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በኮ/መ/ቁ. 10906 የሰጠው ትእዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66589 ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በአመልካቾች እና በሌሎች ሁለት ሰዎች እንደዚሁም በአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ላይ ክስ መስርቶ ሕጋዊ ውሣኔ አሰጥቻለሁ በማለት ያቀረበው የአፈፃፀም ክስና ክርክር ነው፡፡ የክርክሩም ፍሬ ጉዳይ ተጠሪ ያቀረበው የቤት ሽያጭ ውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ ሲሆን የክርክሩ ይዘትም የአሁን አመልካቾች ለወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ መጋቢት 18 ቀን 1984 ዓ.ም በተፃፈ ውል በአዲስ አበባ ወረዳ 17 ቀበሌ 12/13 ቁጥሩ 552 የሚገኘውን ቤት ሸጠው ይህንኑ ቤት ተጠሪ ከእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ግንቦት 21 ቀን 1989 ዓ.ም የገዛሁት ስለሆነ ቤቱን እንዲያስረክቡኝ በስሜ እንዲያዞሩ የሚል ክስ ሲያቀርብ እነ በላይነሽ ካሣዬም በአመልካቾች ላይ ክስ ያቀርባሉ፡፡

የአሁን አመልካቾች በሕግ በሚፀና አኳኋን ለወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ቤት አልተሸጠም፤ ተጠሪም ከእኛ ጋር የገባው ውል ስለሌለ ክስ ሊያቀርብብን አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ጉዳዩ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ከዚያም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ቀርቦ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ አመልካቾችን የሚጠይቅበት ምክንያት እንደሌለ በመግለጽ እንደውሉ ሊፈጽሙ አይገደዱም በማለት በመዝገብ ቁጥር 76720 ኅዳር 13 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ክስ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ የሻረው በመዝገብ ቁጥር 25551 መጋቢት 29 ቀን 1998 የሰጠውን ውሣኔ ነው፤ ይፈፀም የተባለው መስከረም 2 ቀን 1999 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 15170 የተሰጠ ውሣኔ ነው፤ ስለዚህ አፈጻጸሙ ይቀጥል የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በይግባኝ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች የከፍተኛው ፍርድ ቤት እንደ ውሉ ሊፈጸም ይገባል በማለት የሰጠው ፍርድ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሽሯል፤ ተጠሪ ቤት ሸጣልኛለች የሚላት ወ/ሮ በላይነሽ በቤቱ ላይ መብትና ይዞታ የሌላት መሆኑና ውሉም አስገዳጅነት እንደሌለው ተረጋግጧል፤ ከዚህ በኋላ በአፈፃፀም ቤቱን ለተጠሪ እንድናስረክብ የተሰጠው ትእዛዝ በፍርድ የተሻረና የማይፀና ውሣኔን ለማስፈፀም የተሰጠና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ሊሻር ይገባዋል በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በበኩሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሻረው አመልካቾች ከወ/ሮ በላይነሽ ጋር ተከሳሽ መሆን የለባቸውም በማለት ነው፤ ፍርድ ቤቱ እነ ወ/ሮ በላይነሽን አስመልክቶ የተሰጠውን ውሣኔ አልሻረም፤ እኔ የአፈፃፀም ፋይል የከፈትኩት በወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ እና በአቶ ጉልላት ሞላ ብቻ ላይ እንጅ በአመልካቾች ላይ አይደለም፤ ስለዚህ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፤ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች የአፈፃፀም ትእዛዝ የተሰጠበት ጉዳይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በግልጽ የተሻረ ነው፤ ስለዚህ የተሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ መሰረታዊ ስህተት አለበት የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

በሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ የአፈፃፀም ክስ ያቀረበበት ቤት የአመልካቾች ንብረት የሆነና፤አመልካቾች ለበላይነሽ ካሳዬና ለአቶ ጉልላት ሞላ ሸጠውት እነ ወ/ሮ በላይነሽ ለእኔ ሸጠውልኛል የሚለው ቤት ነው፡፡ አመልካቾች ከእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ጋር በሕግ የፀና የቤት ሽያጭ ውል የለንም የሚል ክርክር ያነሱ ሲሆን በአፈፃፀሙ ቤቱን እንዲለቁና ለተጠሪ እንዲያስረክቡ እየተገደዱ ያሉት እነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ሣይሆኑ አመልካቾች ናቸው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው ተጠሪ በእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ላይ አስወስኛለሁ በሚል ፍርድ መነሻ አመልካቾችን በአፈፃፀም ለማስገደድ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ነጥብ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ተጠሪ እነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ለእሱ ቤት የሸጡለት መሆኑን በፍርድ ቢያረጋግጥ እንኳን የቤቱ ስመ ንብረት እና ይዞታ በአመልካቾች ስም በመሆኑ በፍርድ ሊያስፈጽመው የሚችል ውሣኔ የለም፡፡ ምክንያቱም በእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ እና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ መባሉ ብቻውን ተጠሪ ገዝቸዋለሁ የሚለውን ቤት ለመረከብ እና ስመ ንብረቱን ለማዛወር የሚያስችል መብት አያሰጠውም፡፡ ተጠሪ የቤቱ ስመ ንብረት እና ይዞታ እንዲዛወር ለማድረግ የሚችለው እነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ የሸጡለት የራሳቸው ንብረት የሆነ ቤት ከሆነ ብቻ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬና አቶ ጉልላት ሞላ ለእኔ ሸጠውልኛል የሚለው ቤት ስመ ንብረቱም ሆነ ይዞታው በአመልካቾች ስም ያለ ነው፡፡ ተጠሪ እነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ቤቱን የሸጡልኝ ከአመልካቾች ገዝተውት ነው የሚል ክርክር እና ክስ ቢያቀርብም በአመልካቾች እና በእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ መካከል በሕግ የፀና የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት አመልካቾች ክደው ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ጭብጥ ላይ ቤቱን ገዝተዋል የተባሉት በላይነሽ ካሣዬና አቶ ጉልላት ሞላ በአመልካቾች ላይ የውል ይፈፀምልን ክስ አቅርበው በፍርድ የተረጋገጠ መብት አላገኙም፡፡

በመሆኑም በመጀመሪያ በአመልካቾችና በእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ መካከል በሕግ የሚፀናና አመልካቾች የባለቤትነትና የይዞታ መብታቸውን እንዲለቁ የሚያስገድድ ውል ያለ ስለመሆኑ ውሣኔ ባላገኘበት ሁኔታ ተጠሪ እነ በላይነሽ ካሣዬ ከአመልካቾች የገዙትን ቤት ለእኔ ስለሸጡልኝ በውሉ መሰረት ይፈፀምልኝ የሚል ክርክር በማቅረቡ ብቻ አመልካቾች ንብረታቸውን ለተጠሪ ለቅቀው እንዲወጡ ትእዛዝ የሚሰጥበት ምክንያት የለም፡፡

ይህንንም ነጥብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍትሀብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 25551 ሚያዝያ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውሣኔው አመልካቾች ከእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ጋር አድርገውታል ስለተባለው የቤት ሽያጭ ውል በተመለከተ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለው መሆኑን በግልጽ ካሰፈረ በኋላ አመልካቾች ተጠሪ ካቀረበባቸው ክስ ጋር ተያይዞ እንደውሉ እንዲፈጽሙ አይገደዱም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በይግባኝ እልባትና ውሣኔ ያገኘውን ጉዳይ የተሰጠው ውሣኔ ስህተት አለበት የሚል ከሆነ ለሰበር ሰሚ ችሎት ከሚያቀርብ በስተቀር እነ በላይነሽ ካሣዬን ነጥሎ በመክሰስ በተዘዋዋሪ መንገድ የአመልካቾችን ቤት ለመረከብ የተከተለው የክርክር ስልት ተገቢ አይደለም፡፡ አፈፃፀሙን የያዘውም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ለተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክቡ ሊገደዱ የማይገባ መሆኑን በግልጽ በማስፈር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ ወደ ጐን በመተው በአፈፃፀም ተከሳሽ እነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ናቸው የሚል ምክንያት በመስጠት አመልካቾች ቤታቸውን ለተጠሪ አስረክበውና ለቅቀው እንዲወጡ የሰጠው ትእዛዝ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ግልጽ ውሣኔ ዋጋ የሚያሣጣና የሚሽር በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ሥርአትን የሚጥስና የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ገዥነትና የበላይነትን የሚፃረር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ትእዛዝ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብለናል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ይህንን ትእዛዝ የሕግና የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካቾችን ይግባኝ መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ተጠሪ በወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬና አቶ ጉልላት ሞላ ላይ ያስወሰነው ውሣኔ አልተሻረም በሚል ሰበብ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ ለቅቀውና አስረክበው እንዲወጡ በመዝገብ ቁጥር 109064 መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66539 ሚያዝያ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 25551 ሚያዝያ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በሰበር ሰሚ ችሎት ያልተሻረ ወይም ያልተሻሻለ ውሣኔ በመሆኑ ህጋዊ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው ውሣኔ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ቤታቸውን እንዲለቁና ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በአፈጻጸም መገደድ የለባቸውም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ተከራካሪዎች በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37105

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር

መላኩ መለሰ /ነገረ ፡ ፈጅ/ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ሰለሞን አበበ ኮከብ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተውም የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ ተቋርጦብኛል፤ ስለዚህ ውዝፍ ደመወዜ ተከፍሎኝ እና ያልተሰጠኝ የዓመት ፈቃድ ተሰጥቶኝ ወደስራዬ እመለስ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ በተደነገገው መሠረት የስራ ውል ሊያቋርጥ የሚችል ጥፋት በመፈፀሙ ነው፤ ለአምስት የስራ ቀናትም በስራው ላይ ሣይገኝ ቀርቶአል በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሦስት ወር ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራው ይመለስ፤ ለመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት የሚገባውን የዓመት እረፍትም በማካካሻ እረፍት መልክ ይሰጠው በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ቢከራከርም፤ አመልካች ግን የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ በፈፀመው የስራ ውልን የሚያቋርጥ ድርጊት ምክንያት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በአመልካቹ ክርክር እንደተገለፀው ተጠሪ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል ተጠርጥሮ በፖሊስ ምርመራ ተደርጎበታል፡፡ የተጠሪ ስራ የሎደር ኦፕሬተርነት ሲሆን፤ 120 ሊትር ናፍጣ ወስዶ ለግል ጥቅሙ አውሏል በሚል ነው በፖሊስ ተይዞ ምርመራ ሊጣራበት የቻለው፡፡ በዚህ ምክንያት ታስሮ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር የቆየ ሲሆን፣ ከተለቀቀ በኋላም ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ሥራው ላይ ሣይገኝ እንደቀረ በአመልካች ክርክር ተገልጿል፡፡ የእምነት ማጉደልን በተመለከተ አመልካች የቆጠረው ማስረጃ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይህን የምርመራ መዝገብ አስቀርቦ አልተመለከተም፡፡ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ በራሱ በቂ አስረጂ ሊሆን አይገባም በሚል ሣያስቀርበው እንደቀረ ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራው ላይ አልተገኘም የሚለውን ክርክር በተመለከተም ፍ/ቤቱ በቂ የሆነ ማጣራት ሣያደርግ እንዳለፈው ነው ውሣኔው የሚያሣየው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የተካደ ወይም ያልተማመኑበት የፍሬ ነገር ነጥብ የሚነጥረው በማስረጃ ነው፡፡ በግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የተቆጠረው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ በአግባቡ መሰማት አንዱና ዋነኛው የፍርድ አመራር ስርዓት መሠረታዊ መርህ ነው፡፡ በእርግጥ በተከራካሪ ወገን የቀረበ ማስረጃ ሁሉ ያለምንም ምክንያት መሰማት አለበት ማለት አይደለም፡፡ የተቆረጠው ማስረጃ ለተያዘው ክርክር አግባብነት የሌለው ሆኖ ከተገኘ ውድቅ የሚደረገው እንዲሁ በደፈናው ሣይሆን፣ ምክንያቱን በግልጽ በጽሑፍ በማስፈር ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ.138/፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደምናየው የስር ፍ/ቤቶች ወደ ውሣኔ ያመሩት በአመልካች የተቆጠረውን ማስረጃ አስቀርበው ሣያዩ እና ሣይመረምሩ ነው፡፡ ማስረጃው በፖሊስ ምርመራ የተደረገበት የምርመራ መዝገብ ሲሆን፣ ይህም ቢያንስ ተጠርጣሪው /ተጠሪ/ የሰጠው ቃል፣ ተፈፀመ ስለተባለው ወንጀል በተመለከተ የተሰሙ ምስክሮች፣ የመርማሪውን አስተያየት ወይም ግኝት እንደሚይዝ ይገመታል፡፡ አመልካች የምርመራ መዝገቡን በአስረጂነት የቆጠረውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ መገመት የሚያስቸግር አይደለም፡፡ በመሆኑም ፈራጅ የሆነው አካል (ፍ/ቤቱ) ይህን መዝገብ አስቀርቦ ሣይመለከትና ከተያዘው ጭብጥ ጋር አገናዝቦ ሣይመረምር ብቃት ያለው ማስረጃ አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ ሊደርስ አይችልም፤ አይገባምም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ያየነው ከስራ መቅረትን በተመለከተ የተነሣውን ክርክር ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ይህን ነጥብ ያለፈው ተጠሪ የቀረው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ስለነበር ነው በሚል ነው፡፡ እዚህ ድምዳሜ ላይ ሊደርስ የቻለበትን ምክንያት ግን በዝርዝር አልገለፀም፡፡ ተጠሪም በዚህ ድምዳሜ እንደማይስማማ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክር ገልጿል፡፡ ከስራ ቀረሁ የሚለው በመታሰሩ ምክንያት ሣይሆን፣ ታሞ ሐኪም ቤት ሲመላለስ /ሲታከም/ ስለነበረ ነው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ደምረን ስንመለከት ፍ/ቤቱ ወደ ውሣኔ ያመራው ምንም ዓይነት ማስረጃ ሣይሰማ እንደሆነ ነው፡፡ በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረው ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ሣያጣሩ /ሣያነጥሩ/ መወሰን ደግሞ ዋነኛው መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀም ነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21629 ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 60830 መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተከፈተው መዝገብ ቁ. 21629 ክርክሩ እንዲቀጥል በማድረግ እና በአመልካች የተቆጠሩትን ማስረጃዎች በመስማት ክርክሩን መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ ውሣኔው ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37678

ኅዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ድራጋዶስ ጄ ኤንድ ፒ. ጆየንት ቬንቸር - ጠበቃ አቶ ዱቸ ፈለቀ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሳባ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማኅበር ጠበቆች

1. ሲራጅ አብደላ
2. ድልነሣው ታደሰ አቶ ኒቆድሞስ ጌታሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ጉባዔ ከተሰጠ ውሣኔ ጋር በተያያዘ የይግባኝ አቀራረብን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥን እንደተመለከትነው አመልካች ከኢትጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር ከአዲስ አበባ እስከ ጅማ ድረስ ያለውን አውራ መንገድ የማሻሻያና መልሶ ጥገና ሥራ ለመሥራት ውል ተዋውሎ ከመንገድ ሥራ የተወሰነውን በንዑስ ሥራ ተቋራጭ /sub- contract/ ውል ለማሰራት በነበረው ፍላጎት ከተጠሪ ጋር የካቲት 25 ቀን 1996 ዓ.ም የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውል እንደተዋዋሉ በዚህም የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውል አንቀጽ 17 ላይ በውሉ አፈፃፀም ረገድ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር በአዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሥር በተቋቋመው የግልግል ተቋም ታይቶ እንደሚወሰን በተስማሙት መሠረት በክፍያ አፈፃፀም ረገድ በመካከላቸው አለመግባባት በፈጠሩ ተጠሪ አቤቱታውን ግራ ቀኙ ለመረጡት የግልግል ተቋም አቅርቦ ተቋሙም በሚሰራበት የግልግል ደንብ /rules of procedure/ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሮ የካቲት 3 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡

ከዚህ በኋላም የሥር ተከሣሽ የአሁን አመልካች የግልግል ጉባዔው በሰጠው ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባይ ይግባኝ ያቀረበው ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ምክንያት ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መሥርቶ ጉዳዩን በመመርመር አለመግባባቱ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ አስቀድሞ ግራ ቀኙ እንደተስማሙ፣ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት የተመለከተውም ተቋም በአዋጅ ቁጥር 341/95 መሠረት ሥልጣን በተሰጠው አካል እንደተቋቋመ፣ ይግባኝ ባይ ጉባዔው ጉዳዩን እንዲመለከት ከፈቀደ በኋላም በክርክሩ ሂደት ሙሉ በሙሉ እንደተካፈለ፣ የግልግል ጉባዔው የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ እንደሌለውም የግልግል ጉባዔው በሚመራበት ደንብ ላይ እንደተመለከተና ይግባኝ ባይ ይህ የደንቡ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ቢከራከርም ግራ ቀኙ ወገኖች ወደ ግልግል ተቋሙ ሲሄዱ ተቋሙ ክርክሩን የሚመራበት የአሰራሱ ሥርዓት እንዳለው ስለሚታወቅ ይግባኝ ባይ በተቋሙ በመዳኘት እስከመረጠ ድረስ በተቋሙ አሠራር የማይገዛበት ምክንያት ስለሌለ በዚሁ መሠረት በግልግል ውሣኔው ላይ ይግባኝ አይባልበትም ተብሎ በግልግል ደንቡ ላይ የተቀመጠውን እንደተቀበለው ስለሚቆጠር በዚህ ረገድ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የይግባኝ መብቱን ቀሪ ባደረገበት ሁኔታ ስለሆነ አግባብነት የለውም በማለት ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ሰበር ችሎቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የግልግል ተቋሙ የሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይበልበት ነው መባሉ ተጠሪ ባለበት ለሰበር ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍና በቃል አከራክሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የግልግል ተቋሙ የሚመራበትን የሥነ-ሥርዓት ደንብ /rules of procedure/ እና እንደዚሁም በግራ ቀኙ ወገኖች የተደረጉ የተለያዩ መፃፃፎችን ለጉዳዩ አወሳሰን እንደሚረዳ በማመኑ ችሎቱ አስቀርቦ ተመልክቷቸዋል፡፡

የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥም አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ይግባኝ የሚባልበት ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪ የካቲት 25 ቀን 1996 ዓ.ም የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውል ሲዋዋሉ በውሉ አፈፃፀም ረገድ አለመግባባት ሲፈጠር ይሄው አለመግባባት በአዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሥር በተቋቋመው የግልግል ተቋም ታይቶ እልባት እንደሚያገኝ መስማማታቸውን የተገነዘብን ሲሆን ይህን ተቋም /forum/ በመምረጥ ረገድ ስምምነት ስለመደረሱ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የግልግል ተቋሙን በመምረጥ ረገድ በመካከላችን ስምምነት ቢኖርም የግልግል ተቋሙ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ ግራ ቀኛችን አልተስማማንም፡፡ የግልግል ተቋሙ የሚመራበት የግልግል ደንብ ላይ የጉባዔው ውሣኔ ይግባኝ እንደማይባልበት ቢጠቀስም ይህ የደንቡ ቃል በሕገ መንግሥት የተረጋገጠን የይግባኝ መብትን የሚፃረር ከመሆኑም በላይ የግልግል ዳኞች በሚሰጡት ውሣኔ ላይ ከፍ/ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይቻላል ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 350/1/ ላይ የተመለከተውንም የሚጋፋ ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ነው፡፡

ተጠሪም በበኩሉ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውሉ መሠረት የተፈጠረውን አለመግባባት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ም/ቤት ሥር ለተቋቋመው የግልግል ዳኝነት ተቋም አቤቱታው ሲቀርብ ጉባዔው የተጠሪን ክስ እንደዚሁም የግልግል ተቋሙ የሚመራበትን ደንብ ለአመልካች በሸኚ ደብዳቤ እንዲላክና አመልካችም ስለ ደንቡ አንዳንድ ማከራከሪያ ከጠየቀ በኋላ ተቀብሎ የግልግል ጉባዔውን የተለያዩ ድንጋጌዎች በመጥቀስ የተከራከረ ሲሆን ይህም አመልካች ደንቡን ተቀብሎ ሙግቱን መቀጠሉን የሚያሣይ ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በደንቡ ለመግባት ሙሉ ፈቃድን ስለሰጠ የጉባዔው ውሣኔ ይግባኝ አይባልበትም ተብሎም በዚሁ ደንብ ላይ የተጠቀሰውንም እንደተቀበለው ይቆጠራል በማለት ይግባኙን ሣየቀበል መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችና ተጠሪ አለመግባባትን በግልግል ለመፈታት በውል የመረጡት የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም የሚመራበት የግልግል ደንብ የውል ክርክርን ለግልግል ስለማቅረብ በሚደነግገው አንቀጽ 1/1/ ሥር ተዋዋይ ወገኖች ውላቸውን በሚመለከት ለሚነሱ ማናቸውም አለመግባባቶችና ክርክሮች በአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት የግልግል ተቋም የግልግል ደንብ ውሣኔ እንዲያገኝ በጽሁፋቸው ሲስማሙ በዚሁ መሠረት እነዚህ አለመግባባቶች በተቋሙ የግልግል ደንብ ውሣኔ እንደሚሰጣቸው መደንገጉን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ የግልግል ደንብ አንቀጽ 1/1/ ላይ እንደተመለከተው ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ወደዚህ የግልግል ተቋም ሲሄዱ የግልግል ተቋሙ ግራ ቀኙን ማከራከር ከመጀመሩ በፊት ተከራካሪ ወገኖች በዚህ የሥነ-ሥርዓት ደንብ የሚይዙ ስለመሆኑ የጽሁፍ ስምምነት መቀበል እንደሚገባው አከራካሪ አይሆንም፡፡

በእርግጥ የግልግል ጉባዔው ተጠሪ ያቀረበውን ክስና የግልግል ተቋሙም የሚመራበትን ይህንኑ የግልግል ደንብ አያይዞ ለአመልካች እንደላከና አመልካችም ይህንኑ ደንብ መሠረት አድርጎ ክርክሩን መምራቱን መገንዘብ ቢቻልም ሁኔታው ደንቡን ካወጣው ተቋም ሃሣብ /intention/ አንፃር ሲታይ ደንቡን ጠቅላላ ድንጋጌ ተከራካሪ ወገኖች ተገንዝበው በዚሁ መሠረት ለመገዛት ወስነዋል ለማለት የሚቻለው በደንቡ አንቀጽ 1/1/ ላይ እንደተመለከተው ግልጽ የሆነ የጽሁፍ ስምምነት ሲኖር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩልም አመልካች ደንቡ ደርሶት የደንቡንም የተለያዩ ድንጋጌዎች በመጥቀስ ሙግቱን የቀጠለ ስለሆነ ደንቡን እንደተቀበለውና በዚሁ ደንብ አንቀጽ 20/2/ መሠረትም የይግባኝ መብቱን እንደተወ ይቆጠራል ቢባል እኳን ይግባኝ መሠረታዊ መብት እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ መሠረታዊ መብት ተፋላሚ ወገኖች አስቀርተዋል ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚገባ በተገነዘቡ ጊዜ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 350/2/ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን አስቀርተዋል ወይንም ትተዋል ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሙሉ በተረዱበት ደረጃ እርስ በርሣቸው በሚያደርጉት ስምምነት ሲሆን ነገር ግን አለመግባባቱ በግልግል ተቋሙ ዓማካይነት እንዲታይ ጥያቄው በቀረበ ጊዜ /At the stage of submission/ የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚገባ ተገንዝበዋል ለማለት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ናቸው ስለማይባል በዚህ ሁኔታ ይግባኙን ለማስቀረት የሚሰጡት ፈቃድ በሕጉ ላይ እንደተቀመጠው የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚገባ በመገንዘብ እንዳደረጉት የሚቆጠር አይሆንም፡፡

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተመሥርተው ማብራሪያ የፃፉትም ፕሮፌሰር አለን ሴድለር ይህንኑ በማብራሪያቸው ላይ አንፀባርቀውታል፡፡

አመልካች የይግባኝ መብቱን ለመተው አድርጎታል የተባለው ስምምነት የነገሮችን አካባቢ ሁኔታዎች በሚገባ ካለመገንዘብ ነው ከተባለ ደግሞ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 350/2/ ድንጋጌ መሠረት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው ማለት ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የይግባኝ መብቱን ያስቀረ ስለሆነ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ሣይቀበለው መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 29612 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የይግባኝ መብቱን ቀሪ ያላደረገ ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን መርምሮ የበኩሉን እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37762

ታህሣሥ 09 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- ገዋኔ ኢንተርፕራይዝ ኃላ.የተ.የግል ማህበር - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ጎላ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዮሱፍ ይማም - ቀረበ -

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ውል ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰውን የጉዳት ኪሣራ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ ውል ተጠሪ ለአመልካች የመጥረጊያ አለላ በማቅረብ ወደ ውጭ ለመላክ የገባውን ግዴታ ለመወጣት ያመቸው ዘንድ በተጠሪ እግር ተተክቶ በተጠሪ ሠራተኞች የልማቱን ስራ ለማካሄድ ብር 170,609.14 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠኝ ብር ከአስራ አራት ሣንቲም/ ማውጣቱን፣ የተጠሪ የውሃ ፓንፕና ትራክተሮች በዕዳ በመሬት ባለይዞታዎች በመያዛቸው ምክንያት ለዚህ ዕዳ አመልካች ብር 103,445.80 /አንድ መቶ ሦስት ሺህ አራት መቶ አርባ አምስት ብር ከሠማኒያ ሣንቲም/ ወጪ ማድረጉን፣ አመልካች ያጣው የገቢ ትርፍ ዝርዝር ድምሩ ብር 285,980.00 /ሁለት መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ብር/ መሆኑን፣ ተጠሪ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ውሉን በማፍረሱም የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም በተደረገው ውል መሠረት ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ/ የገደብ መቀጫ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በመዘርዘር በአጠቃላይ ብር 471,589.14 /አራት መቶ ሰባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከአስራ አራት ሣንቲም/ ከወጪና ኪሣራ ጋር ተጠሪ እንዲከፈል ይወሰንለት ዘንድ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በዞን ሦስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርበው ታኅሣሥ 17 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በግራ ቀኙ ውል መኖሩን ሣይክዱ በውሉ አለመፈፀም ምክንያት አመልካች ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች፣ ለመሬቱ ባለይዞታዎች ተከፈለ ለተባለው ወጪም አላፊነት የሌለባቸው መሆኑንና የአመልካች ማስረጃዎች አግባብነት እና ተቀባይነት የላቸውም የሚሉባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር መልስ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተውን ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ተገቢ ናቸው ያላቸውን ሁለት ጭብጦችን መስርቶ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች በኩል ወጡ ለተባሉት የተለያዩ ወጪዎች አላፊነት የለባቸውም፣ የገደብ መቀጫውን ግን ተጠሪ ለውሉ መፍረስ ምክንያት ነው ባይባሉም ከአንዳንድ ሁኔታዎች አንፃር ሊከፍሉ የሚገባ ሆኖ ተገኝተዋል በማለት ተጠሪ ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ ለአመልካች እንዲከፍሉና የአመልካች የወጪና ኪሣራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ይኸው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የአሁኑ አመልካች ሕጉ ያስቀመጠውን መስፈርት ተጠቅሞ ውሉን ማፍረስ ሲገባው በሕጉ መሠረት አልፈፀመም የሚል ምክንያት በመዘርዘር የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ ተጠሪ በውሉ አንቀጽ 5.2 ስር የተመለከተውን የገደብ መቀጫ ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ሚያዝያ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሠበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስ ባላቀረቡበት ጉዳይ ባለእዳ እንድንሆን የተወሰነው ያላግባብ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ተከራክረው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲፀና ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ በሠበር ችሎቱ እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ህዳር 10 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሣቸውም ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም የተደረገውን ውል መሠረት በማድረግ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ መሻሩም ሆነ የገደብ መቀጫውን ለአመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ስህተት ባለመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነ/ፈጅ በበኩላቸው የተጠሪን መልስ በመንቀፍ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሣቸውን ህዳር 10 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ለተጠሪ ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ/ እንዲከፍል መወሰኑ ሥነ-ሥርዓታዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በክርክሩ ሂደት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ውል መኖሩ መታመኑ፣ በተጠሪ በኩል በስር ፍ/ቤት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አለመቅረቡ የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ለአመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሠረተው የአሁኑ ተጠሪ የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም እና ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም ከአመልካች ጋር በተዋዋሉት መሠረት የመጥረጊያ አለላ ምርት ለማቅረብ ግዴታ ገብተው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ተቀብለው ምርቱን ሣይሠበስቡና ለአመልካች ሣያስረክቡ የመስኖ እርሻውን ጥለው በመጥፋታቸው በአመልካች ላይ የተለያዩ ወጪዎች መከሰታቸውን በመግለጽ የእነዚህ ወጪዎች ድምር እና የገደብ መቀጫ ለውሉ አለመፈፀም በጉዳት ካሣነት እንዲከፈል ይወሰን ዘንድ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ደረሱ ለተባሉት ወጪዎች ተጠሪ አላፊነት የለበትም በማለት ከወሰነ በኋላ ለገደብ መቀጫው ግን ተጠሪን ተጠያቂ አድርጓቸዋል፡፡

እንግዲህ የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ያልተስማሙበትና ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡበት ነጥብ የገደብ መቀጫውን በተመለከተ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል ከዚህ ውጪ ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት አመልካች በመሆኑ ልጠየቅ አይገባም ከማለት ውጪ የደረሰብኝ ጉዳት ስላለ አመልካች ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት በሥርዓቱ መሠረት የጠየቁት ዳኝነት አለመኖሩን የክርክሩ ሂደት ያሣያል፡፡

በመሠረቱ በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኙን የሚያቀርበው የበታች ፍ/ቤትን ውሣኔ ለማስለወጥ፣ ለማሻሻል ወይም ሙሉ በሙሉ ውድቅ ለማድረግ ነው፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው ያቀረበው ክስ ኖሮት ያላግባብ ውድቅ ከሆነበት ወይም የተጠቀው ዳኝነት በአግባቡ ሣይታይ የታለፈ ከሆነ ነው ዳኝነት ደግሞ በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ የሚያስተናግደው በበታች ፍ/ቤት የተደረገውን የክርክር እና የተጠየቀውን ዳኝነት ይዘት እንዲሁም አግባብነቱን በመመልከት ነው፡፡ በበታች ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረ ወገን የተከሣሽ ከሣሽነት ሥርዓቱን አሟልቶ ሣይጠይቅ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፍርዱ ተለውጦ የፍርድ ባለመብት እንዲሆን ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት የሚጠይቅበት እና ተቀባይነት የሚያገኝበት ሥርዓት አለመኖሩን ስለይግባኝ ፍርድን ለመቃወምና ለፍርድ እንዲሻሻል ወይም እንዲጣራ ስለማመልከት የተደነገጉት ከቁጥር 320 እስከ 370 የተመለከቱት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ ስለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሥልጣን የሚደነግገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ በተለይ ሲታይም ፍ/ቤቱ ማናቸውም ይግባኝ የቀረበለትን ፍርድ ወይም ውሣኔ ለማፅናት፣ ለማሻሻል ወይም ለመሻር የሚችል መሆኑን ከመደንገጉ ውጪ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያልተጠየቀ ዳኝነት የመስጠት ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ አያሣይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182/2/ ስር የተመለከተው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ስልጣንም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አስተያየት መስጠት ወይም መወሰን ይገባው ነበር ብሎ በሚገምተው ጉዳይ ላይ ትእዛዝ ወይም ውሣኔ ለመስጠት የሚችል ስለመሆኑ፣ በተጨማሪም ተገቢ መስሎ የታየውንና ነገሩን ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የሚገመተውን ማናቸውንም ሌላ ውሣኔ ወይም ብይን ወይም ትእዛዝ ወይም ፍርድ መስጠት ስለመሆኑ የተገለፀ ቢሆንም በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተሰጡት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሥልጣንና ተግባራት የሚከናወኑት በበታች ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ሥርዓቱን የጠበቀ ክርክር ሲቀርብና የተጠየቀ ዳኝነት ሲኖር ነው፡፡ አንድ ተከራካሪ በሥነ-ሥርዓቱ መሠረት ክስ ባልቀረበበት ጉዳይ ባለዕዳ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት አመልካች በመሆኑ የገደብ መቀጫውን በውሉ መሠረት ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ክስ ባላቀረበበት ሁኔታ ተጠሪ ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት አይደሉም ወደሚለው ድምዳሜ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከደረሠ በኋላ ተጠሪ የገደብ መቀጫው ለአመልካች ሊከፍል አይገባም በሚል ውሣኔ መቆም እየተገባው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያልተጠየቀ ዳኝነት መስጠቱ ሥነ-ሥርዓታዊ ካለመሆኑም በላይ ለውሣኔው መሠረት ያደረጋቸው የፍትሐብሔር ድንጋጌዎችም አግባብነት የሌላቸው ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ/ ለተጠሪ እንዲከፈል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት የጠየቀውን ዳኝነት ስንመለከተው የአሁኑ ተጠሪ ለውሉ አለመፈፀም ተጠያቂ ስለመሆናቸው እርግጠኛ ያልሆነ ስለመሆኑ ከውሣኔው ላይ "... ውል አፍራሽ ተከሣሽ ነው ባንልም ..." በሚል ከገለፀው ሁኔታ መረዳት የሚቻል ከመሆኑም በላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ለውሉ መፍረስ ምክንያት የሆነው የአሁኑ አመልካች ነው በማለት የወሰነው በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን መዝኖ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ በዚህ ችሎት የሚታይበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በይዘቱ የማስረጃ ምዘና ነውና፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1771/2/ በተመለከተው መሠረት ተጎጂው ወገን የጉዳት ኪሣራ የመጠየቅ መብት የሚኖረው የውሉ አለመፈፀም በገንዘብ የሚተመን ኪሣራ የደረሰበት መሆኑ ሲታወቅ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የበታች ፍ/ቤት በማስረጃ ምዘና የተለያዩ ከመሆናቸው ውጪ በውሉ ወይም በሕጉ አተረጓጎም ረገድ የተለያዩበት ሁኔታ ስለመኖሩ የክርክሩ ሂደት አያሣይም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለገደብ መቀጫው ተጠያቂነት የለባቸውም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው የውሣኔ ክፍል የሚለወጥበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን በዚህ ረገድ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 968 የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ//ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2/ ተጠሪ ለውሉ መፍረስ ምክንያት አይደሉም የተባለው የውሣኔ ክፍል እንዳለ ሆኖ የገደብ መቀጫውን በተመለከተ ግን አመልካች ለተጠሪ ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ/ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡

3/ አመልካች የዞኑ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ያጽናልኝ ሲል ያቀረበውን ጥያቄ አልተቀበልነውም፡፡

4/ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5/ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 38601

ታህሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡-የኢትዩጵያ እህል ንግድ ድርጅት - ብርሃኑ አሻግሬ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ከድጃ ሳቢር ቀረበች ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው የአመልካች ሠራተኛ ለነበረው በሞት ለተለየው ባለቤትዋ ሊከፈል ይገባ ነበር ያለችውን ክፍያ እንዲከፈላት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የተጠሪ ባለቤት በሕይወት እያለ ክስ መስርቶ ከተከራከርን በኋላ በሕጉ መሠረት ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች ሁሉ ተከፍለዋል፡፡ ተጠሪ በአሁኑ ደረጃ ያቀረበችው ክስ የሚስተናገድበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ፣ ብዙዎች በክሱ የተመለከቱት ክፍያዎች ውድቅ ያደረገ ሲሆን፣ ከዓመት ዕረፍት ፈቃድ ጋር ተያይዞ ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ ግን በመቀጠል አመልካች እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በዓፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ ያቀረበው፤ተጠሪ ለባለቤቱ ሊከፈል ይገባው የነበር ነው በማለት ያቀረበችው የክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ነው ወይ? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ እንደተመለከተው የተጠሪ ባለቤት የነበረው መሐመድ ሁሴን ከአመልካች ጋር አድርጎት የነበረው የስራ ውል መቋረጥን መነሻ በማድረግ በአመልካች ላይ ክስ መስርቶ ሲከራከር ከቆየ በኋላ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ሞቶአል፡፡ ከዚህ የተነሣም ተጠሪ ክርክሩን ስትከታተል ቆይታለች፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር በመመርመር አመልካች የማስጠንቀቂያ እና የስራ ስንብት ክፍያዎች እንዲሁም ወጪና ኪሣራ ይከፈል ሲል ወስኖአል፡፡ ተጠሪ በስምዋ አዲስ ክስ የመሠረተችው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ አመልካች የክሱን መቅረብ የተቃወመውም እነዚህን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ነው ፡፡

ከፍ ሲል እንደገለጽነው ተጠሪ በክስዋ ላይ ያመለከተችው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲሰጡአት ሲሆን፣ ከዚህም አንዱ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሚመለከት ነው፡፡ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የተቀበለውም በዚህ ረገድ የተጠየቀውን ክፍያ ብቻ ሲሆን፣ ለመቀበሉ የሰጠው ምክንያትም አመልካች በማመንም ይሁን በመካድ መልስ አልሰጠበትም የሚል እንደሆነ ከውሳኔው ተመልክተናል፡፡ በበኩላችን እንደምናየው አመልካች የክሱን መቅረብ በአጠቃላይ ተቃውሞ ተከራክሮአል፡፡ ለዚህ የሰጠው ምክንያትም የተጠሪ ባለቤት መስርቶት በነበረው ክስ ተጠቃሎ የተጠየቀ ወይም አንድ ላይ ሊጠየቅ ይገባው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የነበረ ነው የሚል ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ መልክ የቀረበውን የአመልካች ክርክር በመገንዘቡ በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ ይህ መሰል መቃወሚያ ሲቀርብም አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ማንኛውም የፍትሐብሔር ክስ ሲቀርብ ስለ ክሱ አቀራረብ በተመለከተ የተቀመጡትን የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ድንጋጌዎች ሊከተል እንደሚገባ የሚያከራክር አይደለም፡፡ የተጠሪ ባለቤት አቅርቦት የነበረው ክስ ከአመልካች ላይ የሚፈለገውን መብት የሚዘረዝር እና ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ አጠቃሎ የያዘ እንደነበር ይገመታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክሱ የተወሰኑትን ክፍያዎች ሳያካትት ቀርቶ ነበር አልተባለም እንጂ ቢባልም ኖሮ ከፍ/ቤት የተገኘ ፈቃድ ሳይኖር በሌላ አዲስ ክስ ሊጠየቅ እንደማይችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.216 (4) ተመልክቷልና፡፡ይህ ጉዳይ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 5 አንፃር ሲታይም በአዲሱ ክስ (ተጠሪ ባቀረበችው) እና ቀደም ሲል ክርክር ተደርጎበት የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘው ክስ መካከል ልዩነት የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረባቸው ክስ በድጋሚ የሚታይበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔም ከዚህ አኳያ ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07717 ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 64777 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348 (1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ የጠየቀችው የዓመት እረፍት ፈቃድ ክፍያ እንደ ሌሎች ክፍያዎች ተቀባይነት የለውም፡፡ ሊከፈላት አይገባም ብለናል፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37742

ታህሣሥ 7 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ጐንፋ ኦሪቲ ቀርቧል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀሐይ ሊበን የሺጥላ አለሙ ጠበቃ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተመረመው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የስር ጣልቃገብ አመልካች ሲሆኑ ተጠሪ የስር ከሳሽ ነበሩ፡፡ ጣልቃ ገብ አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት መቃወሚያ ተጠሪ ከሚች ጋር አብሬ ያፈራሁትን ቁጥሩ 373 የሆነውን ቤት ተከሣሾች ያካፍሉኝ ሲሉ ክስ ያቀረቡት እኔ በጣልቃ ገብ አመልካች (የአሁን አመልካች) ከሚች ባለቤቱ ከነበሩት አቶ ታምሩ አሸናፊ ጋር በባልና ሚስት የጋራ ንብረት በመሆኑና በመሐከላችን በተነሳው ያለመግባባት በፍ/ቤት ውሣኔ ስንለያይ ንብረቱ የጋራችን በመባሉ እኔ ለልጆቼ ስል ሳልካፈል ትቻለው(አልወሰድኩም) ነበር፡፡ ስለዚህ በመብቴ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ጣልቃ እንድገባ በማለት እንዲፈቀድላቸው ጠይቋል፡፡

የመጀመሪያ ደ/ፍ/ቤትም መዝገቡን በመመርመር በሰጠው ብይን የአሁን አመልካች የጣልቃ ልግባ አቤቱታቸው ላይ መሰረት ያደረጉት የሚች አቶ ታምሩ አሸናፊ ሚስት መሆናቸውን እና ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ክስ ያነሱበት ቤት ከሚች ጋር አብረን ሰርተናል በማለት ነው፡፡ ይህ የጣልቃ ልግባ ምክንያት ደግሞ አመልካችን ጨምሮ(የስር ጣልቃ ልግባ ባይን) የአሁን ተጠሪና የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ክርክር ባነሱበት የመ/ቁ. 0057 ላይ የውርስ ንብረት አጣሪ ተሹሞ ሪፖርቱ የፀደቀበት ክርክር ነው ጣልቃ ልግባ ባይ በዚህ የጣልቃ ልግባ አቤቱታቸው በውርስ ንብረት አጣሪ ሪፖርት መሰረት ክርክር በተነሳበት የቤት ቁ. 373 ላይ ድርሻ አለኝ የሚል የጣልቃ ልግባ ምክንያት አላቀረቡም ይህ ከሆነ ደግሞ ከሣሽ ተጠሪ በውርስ አጣሪው ሪፖርት መሰረት በቤት ቁጥር 373 ላይ ክፍፍል ተደርጐ ድርሻዬ ይሰጠኝ ሲሉ ክስ ባቀረቡበት መዝገብ ላይ ጣልቃ ልግባ ባይ (አሁን አመልካች) በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41/2/ መሰረት የጣልቃ ገብነታቸውን ማመልከቻ በክሱ ውስጥ ይገባኛል የሚሉበትን ምክንያት ሳይዘረዝሩና ሳይገልጹ ጣልቃ ልግባ ያሉት ጥያቄ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ሲል ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ(የአሁን አመልካች) በፍ/ቤቱ በተሰጠው ብይን ባለመስማማት ለፌደራል ከ/ፍ/ቤት ይግባኛቸውን አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የተሰጠውን ብይን ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2000 ዓ.ም በዓፋት ማመልከቻ በፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል ጉዳዩ በሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 መሰረት ያቀረበችው የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ውድቅ የተደረገበትን እግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ከሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እኛም የዚህን ክርክር አመጣጥ በአጭሩ ስናየው ለአመልካች የጣልቃ ልግባ ምክንያት ከሟች ባለቤታቸው (አቶ ታምሩ አሸናፊ) ጋር በሚስትነት አብረው ያፈሩአቸው የጋራ ንብረት እንደነበረና ከሟች ጋር ያለመግባባት በመፈጠሩ ምክንያት በፍ/ቤት ተፋተው ንብረቱን በተመለከተ ለልጆቻቸው ጥቅም ሲሉ ሳይካፈሉት እንደቆየ እና የአሁን ተጠሪ በንብረቱ ላይ ውሳኔ እንዳያሰጡብኝ በማለት ነው፡፡

እንግዲህ ከዚህ መገንዘብ እንደቻልነው የአመልካች ጥያቄ ክርክር በተነሳበት ባለው ቤት ላይ መብት አለኝ የጋራ ንብረቴን እንደሚስትነቴ አልተካፈሉም እያሉ ነው አመልካች ከሟች ጋር ባልና ሚስት እንደነበሩ በፍ/ቤት እንደተፋቱ የተካደ ነገር የለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር ከጉዳዩ (ከክርክሩ) ጋር ተያያዝነት ባለው ጉዳይ መብትና ጥቅም እንዳለ ከተገለፀ ጣልቃ ለመግባት በቂ ምክንያት ነው በያዝነው ጉዳይም አመልካች የሟች ሚስት የነበሩ መሆናቸው ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ሌላው የሥር ፍ/ቤት አመልካች በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ይህን ጥያቄ አላቀረቡም ብሏል ይህ ደግሞ የአመልካች በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ጥያቄ የለማቅረብ የጋራዬ ነው ባሉት ንብረት ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚከለክላቸው አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ባለመብትነት የሚወሰነው ወደ ክርክር ከተገባና ግራ ቀኙ ከተከራከሩበት በኋላ ስለሆነ ነው፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት አመልካች በክሱ ውስጥ ያገባኛል የሚሉትን ምክንያት አልዘረዘሩም መብታቸውን አልገለፀም በማለት ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉንና የከፍ/ቤቱም ይህን ማረም ሲገባው ማጽናቱ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፊ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16228 ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.የሰጠው ውሣኔ እና የፊ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61828 በመጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ጣልቃ ገብተው ይከራከሩ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. በፊ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ የግራ ቀኙን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ በሕጉ መሰረት እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341 መሰረት መዝገቡን መልሰናል፡፡

4.ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37502

ታህሣሥ 2 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ሕግ ጉዳዮች ቢሮ - ነ/ፈጅ ታረቀኝ ሞላ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ የኂላሸት ገመዳ ቤኛ - ቀርበዋል፡፡

2. ወ/ሮ ጌጤ ገመዳ ቤኛ - ወኪል ቀርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻው አመልካች ግንቦት 01/2000 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 44930 መጋቢት 15/2000 እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 66633 ሚያዝያ 30/2000 ዓ.ም. የሰጡት ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው በማለት እንዲሻሩለት በመጠየቁ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት በክርክር ጣልቃ ለመግባት ተቃዋሚ የነበር፣ በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ደግሞ ይግባኝ ባይ ሆኖ የተከራከረ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎችም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ደግሞ መልስ ሰጭዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍ/ቤት ለቀረበው ክርክር መነሻው የአሁኑ አመልካች ጎዳር 09/2000 ዓ.ም. በተፃፈ ያቀረበው መቃወሚያ ሲሆን ይዘቱም የስር ፍ/ቤቱ ጥቅምት 29/1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12፣ የቤት ቁጥር 486 የሆነውን ቤት ስር ከሣሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ከሥር ተከሣሾች ከነበሩት /የቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 12 አስ/ጽ/ቤት እና አቶ ለአዚም በደዊ/ እንዲረከቡት መወሰኑ ባለ ንብረት የሆንኩት በክርክሩ ባልተሳፍኩበት በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 358፣ 360 መሠረት ጣልቃ አስገብቶ በማከራከር ቀደም ብሎ የተሰጠውን ፍርድ ውድቅ ያደርግልኝ የሚል ነው፡፡

ከላይ ለቀረበው ጥያቄ ስር ከሣሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ታህሣሥ 24/2000 ዓ.ም. በሰጡት መልስ የመቃወም አመልካቹና ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት አንድ አካልና ተመሣሣይ ክርክር ያላቸው ስለሆኑ አመልካቹ በመጀመሪያው ክርክር እንደተሳተፈ ስለሚቆጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358/360 መሠረት ያቀረበው ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በኮ/መ/ቁ. 44930 መጋቢት 15/2000 ዓ.ም. በሰጠው ብይን የመቃወም አመልካቹና ቀደም ብሎ ማለትም ጥቅምት 29/1999 ዓ.ም. በተሰጠው ፍርድ ውስጥ አንደኛ ተከሣሽ የነበረው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት አንድ አካልና ተመሣሣይ ክርክር ያላቸው በመሆናቸው የመቃወም አመልካቹ በመጀመሪያው ክርክር እንዳልተሳተፈ ስለማይቆጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358/360 መሠረት ያቀረበው ጣልቃ የመግባት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት በመ/ቁ. 66633 ሚያዝያ 30/2000 ዓ.ም. በሰጠው ትእዛዝ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ የሰፈሩትን የስር ፍ/ቤቶቹ ብይኖች በመቃወም የአሁኑ አመልካች ግንቦት 01/2000 ዓ.ም. የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም አከራካሪው ቤት መንግሥት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ወርሶ የሚያስተዳድረው ሃብት ሲሆን ለተጠሪዎቹ የተወሰነላቸው አላግባብና አመልካች በክርክሩ ሳይሳተፍ ነው፤ አመልካችና ስር አንደኛ ተከሣሽ የነበረው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት የየራሳቸውን ህጋዊ ሰውነት ያላቸው የተለያዩ አካላት እንጂ አንድ አይነት ባለመሆናቸው የስር ፍ/ቤቶቹ በክርክሩ ጣልቃ ገብቼ እንዳልከራከር ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብሏል፡፡

ተጠሪዎችም ሐምሌ 17/2000 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ የሰጡ ሲሆን ይዘቱም አመልካችና ቀደም ብሎ የሥር ፍ/ቤቱ አንደኛ ተከሣሽ የነበረው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 /የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር/ አንቀጽ 2 መሠረት የከተማው አስተዳደር የተለያዩ እርከኖች ስለሆኑ ክርክራቸው ተመሣሣይ እንጂ የሚለያይ ባለመሆኑና የአመልካችና የቀበሌው ስልጣን የሚመነጨው ከከተማው አስተዳደር ነው፤ አመልካች የከተማው አስተዳደር አንድ የሥራ ክፍል እንጂ ራሱን የቻለ አካል ባለመሆኑ ቀበሌው ቀደም ብሎ ተከራክሮበት የተወሰነው ጉዳይም የከተማው አስተዳደር ክርክር ተደርጎ መወሰድ ስላለበት የአመልካች ጥያቄ ተገቢነት የለውም፡፡ የስር ፍ/ቤቶቹ የፈፀሙት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም የሚል ነው፡፡

አመልካችም መስከረም 29/2001 ዓ.ም. በተፃፈ የመልስ መልስ የሰጠ ሲሆን አጭር ይዘቱም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 2/1995 አንቀጽ 29 እና እንደገና በተሻሻለው የከተማው አዋጅ ቁጥር 4/2000 /የአዲስ አበባ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ/ መሠረት የተቋቋመ ሲሆን የቀበሌ አስተዳደር አካላት የተቋቋሙት ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተሞችና ቀበሌዎች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1/1995 እንዲሁም የዚሁ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 18/1997 መሠረት የተቋቋሙና የየራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት፣ ስልጣንና ተግባር ያላቸው አካላት ናቸው የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እንደሰፈረው ሆኖ ይህ ፍ/ቤትም አመልካችና የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት አንድ አካል ናቸው ወይስ አይደሉም? የሁለቱ አካላት ክርክር ተመሣሣይ ሊሆን ይችላል ወይስ አይችልም? የሚሉ ጭብጦችን በመመስረት ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት እንደተቻለው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዳይከራከር በስር ፍርድ ቤቱ የተከላከለው ቀደም ብሎ በክርክሩ ተሳትፎ የተወሰነበት የተጠቀሰው ቀበሌ ካቀረበው ክርክር ተመሳሳይ ክርክር የሚያቀርብና በመሠረቱ አንድ አካል ናቸው በሚል ነው፡፡ በርግጥ እነዚህ ሁለት አካላት በአንድ መንግስታዊ መዋቅር /በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር/ ስር የሚገኙ አካላት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ የክልል ወይም የከተማ መንግሥታዊ መዋቅር ስር መገኘታቸው ብቻ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ተመሣሣይ ጥቅምን የሚወክሉ አካላት ናቸው ወደሚል መደምደሚያ የሚደርስ አይደለም፤ እነዚህ ሁለት አካላት የከተማ መስተዳድሩ የተለያዩ እርከኖች ወይም አካላት ሆነው የየራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት፣ ስልጣንና ተግባር እንዳላቸው በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ከወጡት አዋጅ ቁጥሮች 2/1995፣ 4/2000፣ 1/1995 እና 18/1997 መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ቀበሌውና አመልካች አንድ አካል ናቸው በመባል በሥር ፍ/ቤቶቹ የተሰጠው ብይን ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡

ቀበሌው በክርክሩ ቀደም ብሎ ከቀረበው ክርክር አመልካቹ የተለየ ሌላ ክርክር ሊያቀርብ አይችልም የተባለውም ቢሆን ክርክራቸው ተመሣሣይና አንድ አይነት ጥቅም የሚወክል መሆኑና አለመሆኑ የሚታወቀው አመልካቹ በክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ የሚያቀርበውን የክርክር አይነትና የሚወክለውን ጥቅም ቀበሌው አቅርቦት ከነበረው በማነፃፀር የሚታወቅ እንጂ አስቀድሞ ተመሣሣይ ክርክር አለው የሚል ግምት በመያዝ አይደለም፤ ከዚህ ትንታኔ አኳያም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአ/መ/ቁ. 44930 መጋቢት 15/2000 ዓ.ም. እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 66633 ሚያዝያ 30/2000 ዓ.ም. የሰጡት ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካችና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ጥቅምት 29/1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ አንደኛ ተከሣሽ የነበረው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ የየራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት፣ ስልጣንና ተግባር ያላቸው የተለያዩ አካላት በመሆናቸው አመልካቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ይከራከር፤ ይፃፍ።
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፤ ክርክሩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

ት እ ዛ ዝ

ግንቦት 04/2000 ዓ.ም. በዚህ ችሎት የተሰጠው እግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 29861

ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱል ቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ህጽአት ፍስሐጽዮን - ከጠበቃ ይርጉ ሠንበቱ ጋር ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-1ኛ ወ/ሮ አልማዝ ተረፈ - አልቀረቡም

2ኛ በአ.አ ከተማ መስተዳደር ዞን 04 ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ሣሙኤል ድጉማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 36844 ሐምሌ 12 ቀን 1998 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 26905 የካቲት 02 ቀን 1999 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል አመልካች የሠበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኗ አመልካች ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪዎች ደግሞ እንደቅደምተከተላቸው አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሽ ነበሩ የስር ከሣሽ ግንቦት 22 ቀን 1994 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት ክስ በአ.አ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 03 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 314 የሆነውን ቤት ለአንደኛ ተጠሪ ከታህሳስ 23 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ ማከራየታቸውን ገልፀው ተጠሪ ያለባቸውን የቤት ኪራይ ከፍለው ቤቱን እንደነበረ አድርገው ለአመልካች እንዲያስረክቡ ሁለተኛ ተከሣሽም ቤቱን ያላግባብ አንደኛ ተከሣሽ በብር 355,000.00 /ሦስት መቶ አምሣ አምስት ሺህ ብር/ ሽጦ በመገኘቱ ከነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን የሚሠጠውን የአገልግሎት ኪራይ ከአንደኛ ተከሣሽ ጋር ባልተነጣጠለ ሁኔታ እንዲከፍልና ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል የአሁኑ አንደኛ ተጠሪም በክሡ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ የዳኝነት ገንዘብ አለመከፈሉን የቤት ኪራይ ገንዘብ በክፍያ ግምት የሚታገድ መሆኑንና አመልካች ኢትዮጵያዊ ስላልሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን የማይችሉና ክስ ለማቅረብም መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አቅርበው በፍሬ ነገር ረገድም የቤት ኪራይ ውሉ በውሉ መሠረት እንዲራዘም አለመደረጉን ቤቱን ለመረከብ የቀረበ ሠው ካለመኖሩም በላይ የቤቱ ባለቤት የሆኑት ግለሠብ በሞት የተለዩ እና ባለቤት ነኝ የሚሉት አመልካችም አሜሪካን ሀገር የሚኖሩ በመሆኑ የሚረከብ ሠው ያላገኙ መሆኑን ቀበሌ መጥቶ የቤቱን ባለቤት እንዲናገሩ ጠይቋቸውም ከአገር እንደወጡ የተደረገ መሆኑን ገልፀውላቸው ቤቱ ለሽያጭ በጨረታ በመቅረቡ ተጫርተው ነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ ውል ከአስተዳደር ጽ/ቤቱ መግዛታቸውን ጠቅሰው በግዥ ያገኙትን ቤት የሚመልሱበት ምክንያት የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ስም የሚታወቅና አመልካች መብት የሌላቸው መሆኑን በመጥቀስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ቤቱን በመንግስት በወጣው መመሪያ መሠረት መሸጡን እና የሽያጭ ገንዘቡን በዝግ አካውንት ማስቀመጡን በማለፅ ያላግባብ የተጠቀመው ነገር በሌለበት ሁኔታ ተጠያቂነት የለም ሲል ተከራክሯል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የሽያጭ ውሉ ህገ ወጥ ነው በማለት ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡ ከ28/12/93 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የቤቱን ኪራይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ እና ወጭና ኪሣራን በተመለከተ የአመልካችን ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን በተናጠል ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅረበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የይግባኝ መዝገቦችን አንድ ላይ አጣምሮ በመመርመር አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን አላስረዱም፣ የኪራይ ገንዘቡም በጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው የሚሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ከሻረ በኋላ ህጋዊ መብት አለኝ የሚል ሠው ካለ በህጉ አግባብ ክስ ከማቅረብ ውሣኔው የማያግደው መሆኑን በመግለፅ ወስኗል የአሁኑ የሠበር አቤቱታ አቅራቢውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል፡፡ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሚያዚያ 02 ቀን 1999 ዓ.ም በዓፋት 7 /ሠባት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በፍ/ቤቶቹ ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ አመልካች የሚች ሚስት መሆኗን በመ/ቁ 79/83 አሣውቂና ማስረጃ ለፍ/ቤት ቀርቦ እያለ አለመታየቱ ያላግባብ መሆኑ ቤቱ በባል ስም ብቻ መመዝገቡም አመልካችን መብት የላቸውም ለማለት የተሻሻለው የቤተሠብ ህግ የማያስችል መሆኑን የቤት ኪራዩን በተመለከተም ውሣኔው የፍ/ብ/ህ/ቁ 2968 ድንጋጌን መንፈስ አለማገናዘቡንና የኪራይ ገንዘቡ እንደተከፈለ ይቆጠራል መባሉ ያላግባብ መሆኑን ዘርዝረው ውሣኔው እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠያቃቸውን የሚያሣይ ነው የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በተሠጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠሪዎች ቀርበው መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ሠኔ 13 ቀን 1999 ዓ.ም በዓፋት ማመልከቻ የአመልካች በመ/ቁ 79/83 ተሠጠ የሚሉትን ማስረጃ በስር ፍርድ ቤት ያላቀረቡት መሆኑን ፣ ስለኤርትራዊ መሆንና አለመሆን ሲከራከሩም ኤርትራዊ አይደለሁም ሣይሉ በትውልድ ኤርትራዊ ብሆንም የወጣሁት በፖለቲካ አይደለም ብለው መከራከራቸውን፣ የኪራይ ውሉ ስላልተራዘመ ውል አለ ሊባል እንደማይችልና የክፍያ ግዴታ አለመኖሩን፣ ቤቱን በግዥ ምክንያት በመያዛቸውም የኪራይ መክፈል ግዴታ እንዴሌለባቸውና የሽያጭ ውሉ ይፍረስልኝ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል ሁለተኛ ተጠሪ በበኩሉ ሠኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ ማመልከቻ አመልካች በስር ፍ/ቤት የሚች ብርጋዴ ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ሚስት ስለመሆናቸውም ሆነ ልጆቻቸውም ወራሽ ለመሆናቸው አረጋግጠው ማስረጃቸውን ከክስ አቤቱታቸው ጋር አያይዘው አለማቅረባቸውን፣ በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ያላስረዱ መሆኑን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ኢትዩጵያዊ ለመሆናቸው ያቀረቡት አንዳችም ክርክር አለመኖሩ የኪራይ ውሉ የውሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ የኪራይ ገንዘብን ተጠሪ የሚከፍልበት ምክንያት አለመኖሩን ዘርዝሮ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ ባግባቡ በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በሠጡት መልስ የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር ግራ ቀኙ ለማጣሪያ ጥያቄ የሠጡትን መልስ የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት አመልካች ክስ ለማቅረብ ህጉን መሠረት ያደረገ ጥቅም ወይም መብት የላቸውም ተብሎ መወሠኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካች በተወካያቸው አማካኝነት ክስ ሲመሠርቱ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ንብረታቸው መሆኑን መጥቀሣቸውን የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት መከላከያ መልስ አመልካች በቤቱ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት መከራከራቸውን አመልካችም በተጠሪዎች በኩል ለቀረበው ለዚሁ ክርክር በሠጡት የመልስ መልስ አመልካች ከእነልጆቻቸው የብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ሚስትነትና የልጆቹን ወራሽነት በፍርድ ቤት በሥ/ፍ/መ/ቁ 79/83 ጥቅምት 10 ቀን 1984 ማስወሠናቸውንና ውሣኔው በእጃቸው የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው መከራከራቸውን የስር ፍ/ቤትም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የአመልካች መሆኑን አንደኛ ተጠሪ አምኖ በመቀበል መከራየታቸውን የኪራይ ውሉና በሥ/ፍ/መ/ቁ 79/83 መወሠኑ በቀረበው ክስና ክርክር አመልካች ማስረዳታቸውን በመግለፅ አመልካች ባቀረቡት ክስ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን አስረድተዋል እንዲሁም ተጠሪዎች በቤቱ የተሻለ ማስረጃ አቅርበው አላስረዱም በሚል ምክንያት አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም የሚለውን የተጠሪዎችን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉን የአሁኑ ተጠሪዎች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ የቅሬታ ነጥቦች ከሆኑት ውስጥ በተጠሪዎች በኩል የቀረበው መቃወሚያ መታለፍ ያላግባብ መሆኑ አንዱ እንደነበርና ይህንኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነጥብ በተመለከተም ከፍተኛው ፍ/ቤት በጭብጥነት ይዞ ከመረመረው በኋላ በስር ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ ያላግባብ መሆኑን ጠቅሶ አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት መወሠኑን ነው ፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካች በ/ሥ/ፍ/መ/ቁ 79/83 በፍ/ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ አለ የሚሉት በክርክሩ ሂደት ተያይዞ ያልቀረበ እና የማያውቁት መሆኑን ለዚህ ችሎት በሠጡት መልስ ገልፀው ይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት የሚከራከሩ መሆኑንም ተረድተናል፡፡ በአጠቃላይ የክርክሩ ሂደት የሚያሣየው አመልካች የሚች ብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ሚስትነትን እና የልጆቻቸው ወራሽነት በፍ/ቤት ውሣኔ አረጋግጫለሁ የሚሉት ሠነድ በስር ፍርድ ቤት ስለመኖሩ ከመጠቆሙ ውጪ የአመልካች ክስ አባሪ ሆኖ ቀርቦ ተጠሪዎች ይዘቱን በመመልከት ያልተከራከሩበት የስር ፍ/ቤትም ቢሆን አመልካች ባቀረቡት ክስና ክርክር አስረድተዋል ከማለት ውጪ ራሡ የሰነዱን ይዘት በመመልከት ማረጋገጡን በውሣኔው ላይ ያልጠቀሠ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

በመሠረቱ ከሣሽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222 መሠረት አዘጋጅቶ ከሚያቀረበው የክስ ማመልከቻ ጋር በክሱ መሰማት ወቅት ለጉዳዩ ማስረጃ ይሆኑኛል የሚሏቸውን የሠውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 ድንጋጌ ያሣያል በተለይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137/3/ የሠነድ ማስረጃዎችን በተመለከተ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ወይም ከቀነ ቀጠሮ በፊት ወይም በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ ካልቀረበ በቀር ማስረጃው ሊቀርብ ወይም ይቅረብልኝ ተብሎ ሊጠየቅ እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ ይሄው ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኘው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 256 ስር በተመለከተው አኳኋን ማስረጃዎቹ ሣያቀርቡት የቀሩት ከባድና በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍ/ቤቱ ሲረዳ ብቻ ነው፡፡

የማስረጃ አቀራረብን በተመለከተ በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተው ሌላው ደንብ የይግባኝ ሠሚውን ፍ/ቤት ሥልጣን የሚመለከት ነው በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345 ድንጋጌ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በራሡ አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውም ዓይነት ሠነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ ዓይነት ማስረጃ በተጨማሪነት እንዲቀርብለት የማዘዝ ህጋዊ ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 /1/ ድንጋጌም በሌላ ፍ/ቤት የሚገኝ ሠነድ የፁሁፍ ማስረጃ ወይም ፍርድ የተሠጠበት መዝገብ ለውሣኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍ/ቤቱ በራሡ አነሣሽነትም ሆነ በተከራካሪዎቹ ጠያቂነት እንዲቀርብለት ማዘዝ የሚችል ስለመሆኑ ያስረዳል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ውሣኔ የሠጠው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ሚስትነታቸውን በ/ሥ/ፍ/መ/ቁ 79/83 አረጋግጠዋል በማለት በውሣኔው ላይ የገለፀው ሁኔታ በውሣኔው ግልባጭ መኖሩን እየተመለከተ ነው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሠሚው ችሎትም በዚህ ረገድ ቅሬታው ቀርቦለታል፡፡ እንዲህ ከሆነ በአመልካች የተጠቀሠው የፍ/ቤት መዝገብ ከሚገኝበት ፍ/ቤት በየደረጃው ጉዳዩን ባዩት ፍ/ቤቶች አነሣሽነት ጭምር ሊቀርብና ተጠሪዎች በሠነዱ ይዘት የሚያቀርቡት ክርክር ከታየ በኋላ ውሣኔ መስጠት በተገባ ነበር ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤት ሠነዱ ሣይቀርብለት እና ለተጠሪዎች ሣይደርስ ሠነዱ መኖሩን ማመኑ ይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤቶችም የአመልካችን መብትና ጥቅም ያረጋግጣል የተባለው የፍ/ቤት መዝገብ በስር ፍርድ ቤት የውሣኔው ግልባጭ ተገልጾ እያለ መዝገቡ ከሚገኝበት ፍ/ቤት በህጉ በተሠጣቸው ሥልጣን መሰረት እንዲቀረብ ሣያደርጉ የአመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት መወሠናቸው የክርክሩን አመራር ከላይ በተመለከቱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች መሠረት አለመምራታቸውንና በውጤቱም በቤተሠብ ህጉ የተመለከቱትን የአመልካችን መብቶች የጎዳ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሠጡት የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ድንጋጌዎች በማይደግፉትና የፍርድ አካሄዱ ባልተሟላ ሁኔታ በመሆኑ በየርከኑ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሠጠው ውሣኔ እና ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ሊሻሩ የሚገባና የስር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ሁሉንም መከራከሪያ ነጥቦችን እና ስለመኖሩ የተጠቆመውን የፍ/ቤት መዝገብ ሠነድ በማስቀረብ ተመልክቶ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥ ማድረጉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 26905 የካቲት 02 ቀን 1999 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 36844 ሐምሌ 12 ቀን 1998 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 07632 ታህሣስ 28 ቀን 1997 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች በሥ/ፍ/መ/ቁ 79/83 አለ ያሉትን የሚስትነትና የልጆቻቸውን ወራሽነት ማስረጃ በማስቀረብና ተገቢውን በመፈፀም እንዲሁም ተገቢነት አላቸው የሚሏቸውን ማስረጃዎችን ሁሉ በማስቀረብ በግራ ቀኙ ሁሉም የመከራከሪያ ነጥቦች እንደገና ተገቢውን ውሣኔ ይሠጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት ተመልሶለታል ይላፍ፡፡

3/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ.ት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37303

ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው መንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ኤ.ሲ.ዲ.አይ/ቮካ- ኢትዮጵያ - ስራጅ ዓብደላ/ጠበቃ/ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. ሃይደር ዓሊ

2. ሑሴን ሰዒድ ዓብደላ

3. ግርማ ሐጐስ ገ/ጊዮርጊስ

4. ሽምሰዲን መሐመድ ዓሊ

5. አርባ ሑመድ ጠበቃ አወል ሰይድ ቀረበ

6. ወ/ሪት ዛህራ እንድሪስ

7. መሐመድ ኢብራሂም ዑመር

8. ወንድሙ አባቡ አስማረ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኞች መካከል የተነሣውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአፋር ብ/ክ/መንግስት በዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱትም ሳይከፈል ቀርቶአል ያሉትን የበረሃ አበል እንዲከፈላቸው ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የሁሉቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ተጠሪዎች በጠየቁት መሰረት የበረሃ አበል እንዲከፈላቸው ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለክልሉ የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው የከፍተኛው ፍ/ቤት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ የሚሽር ውሳኔ የሰጠው ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም በነበረው ችሎት ሲሆን፣በሌላ በኩል ደግሞ መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም መዝገቡን በማስቀረብ ሌላ ትእዛዝ ሰጥቶአል፡፡ ትእዛዙም እንዳየነው "....ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ ቁ. 208 አስተካክለናል፡፡ ተጠሪዎች ጉዳያቸውን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 142/1/ መሰረት ለአስማሚ እንዲያቀርቡ ብለናል፡፡ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሚያዝያ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የከፍተኛው ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት የተደረገ እርማት ነው፤ በሚል የሰጠውን ትእዛዝ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት በሕጉ መሰረት ሊከፈለን ሲገባ ሳይከፈለን ቀርቶአል ያሉትን የበረሐ አበል እንዲከፈላቸው ሲሆን፣የወረዳው ፍ/ቤትም ሊከፈል አይገባም በማለት ከአመልካች የቀረበውን የመከላከያ ክርክር ባለመቀበል የተጠየቀው የበረሐ አበል መጠኑን ጭምር በመግለጽ እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ አመልካች ለከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ያቀረበውም አበሉ እንዲከፈል መወሰኑ ትክክል አይደለም በማለት ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም የከፍተኛው ፍ/ቤት አበሉ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የተጠየቀው አበል አይከፈልም በማለት ግልጽ የሆነ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔም ሙሉ በሙሉ ሽሮአል፡፡

የክርክሩ መነሻ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት የሚታይ የስራ ክርክር ሲሆን፣የሚመራውም በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕጉ እና አግባብ ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 138 እንደተመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎት የተጀመረ የስራ ክርክር ውሳኔ ካገኘ በኋላ በይግባኝ የሚታየው በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎት ነው(የአዋጁ አንቀጽ 139) በመደበኛው የስራ ክርክር ሂደትም ይግባኝ ሰሚው የስራ ክርክር ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው የሚሆነው፡፡ ይህ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ተከራካሪ ወገን ከዚህ በኋላ አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው ለሰበር ችሎት ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በሆነ ሁኔታም ውሳኔው ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል አይችልም፡፡ ይህ እንግዲህ አጠቃላይ ሂደቱ(ስርአቱ) ሲሆን፣ውሳኔውን በመቃወም ወደ በላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት ወይም አቤቱታ ለማቅረብ የሚፈልግ ተከራካራ ወገን ውሳኔውን በሰጠው ፍ/ቤት ሊታረም የሚገባ ወይም የሚችል ስህተት አለ ብሎ ካመነ ወደ በላይ ፍ/ቤት አቤት ከማለቱ በፊት ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት አቤቱታ የሚያቀርብበት ስርአት እንዳለም ይታወቃል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ጥያቄ የሚነሳውም እዚህ ላይ ነው፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 208 ርእሱ እንደሚያመለክተው “ስህተትን ስለማረም” በሚል የተደነገገ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤት (ውሳኔውን የሰጠው) ሊያርም ወይም ሊያስተካክል የሚችለው በሰጠው ውሳኔና ትእዛዝ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት መኖሩን ካረጋገጠ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ግልጽ ነው፡፡ በክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሳኔ ስህተትን ማረም በሚል ሊያሻሽል ወይም ሊለውጥ አይችልም፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠበት ክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ ተጠሪዎች የጠየቁት የአበል ክፍያ ተገቢነት ያለው ነው ወይስ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህም ፍ/ቤቱ ከመረመረው በኋላ ጥያቄው ተገቢነት የለውም የሚል ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 የተመለተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ በኋላ የሰጠው ትእዛዝ ግን ከጉዳዩ ጋር በፍጹም የሚገናኝ አይደለም፡፡ ከተጠቀሰው ቁ. 208 ድንጋጌም ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ ፍ/ቤቱ ከመጀመሪያውኑ ሊያስተናግደው የሚገባ አልነበረም፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ እግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በአፋር ብ/ክ/መ/የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0974 መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38419

የካቲት 5 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አቶ ወንደሰን በቀለ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ያሲን ጀማል - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የይግባኝ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ስለጠየቀ ነው፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 08 ቀበሌ 06 የቤት ቁጥር 636 በሆነ የይዞታ ማረጋገጫ የካርታ ቁጥሩ 00487 የሆነ የግል ይዞታ አለኝ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በዚህ ይዞታ ላይ ለሠራሁት የግል ቤቱ ኪራይ መክፈል አለብህ በማለት ቁጥሩ አ/አ/ከ/ቁ. 19/002/92 የሆነ ደብዳቤ ሰኔ 10 ቀን 1995 የፃፈልኝ ስለሆነ፣ ደብዳቤው እንዲሰረዝልኝና ኪራይ መክፈል እንደማይገባኝ ይወስንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁን አመልካች ከሥር በተከሳሽነት ቀርቦ ከሣሽ /ተጠሪ/ ከይዞታቸው ውጭ በመንግሥት ባዶ ቦታ ላይ ያለ ፈቃድ በሕገ ወጥ መንገድ ቤት ሠርተው ተገኝተዋል፡፡ ይህንን በመግሥት ቦዶ ቦታ ላይ የተሠራ ቤት ቁጥሩ 636/ሀ/ የሚል ቁጥር ከሰጠነው በኋላ ከሣሽ /ተጠሪ/ የንግድ ሥራ እንዲያከናውኑበት በመስማማት ተከሣሽ /ተጠሪ/ በመኖሩ በቀበሌ ለመክፈል ተስማምተው የኪራይ ውል ፈርመው በገቡት የኪራይ ውል መሠረት ኪራይ እንዲከፍሉ ከመጠየቃችን በስተቀር በሕጋዊ ይዞታቸው ላይ ለሠሩት ቤት ኪራይ እንዲከፍሉ አልጠየቅንም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካች /ተከሣሽ/ ተጠሪ /ከሣሽ/ በባዶ የመንግሥት መሬት ላይ ቤት ሠርተው ካገኘ ቤቱን እንዲፈርስ ከማድረግ በስተቀር ኪራይ የመጠየቅና የመሰብሰብ ስልጣን የለውም፡፡ ስለዚህ አመልካች /ተከሣሽ/ ከተጠሪ /ከሣሽ/ በሕገ ወጥ መንገድ ተሰርቷል ከሚለው ቤት ኪራይ መቀበሉን እንዲያቋረጥ በማለት ወሰኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኙ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ አመልካች ውሣኔው በሰበር እንዲታይ ለከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎበታል፡፡

አመልካች በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ እየከፈልኩ ልጠቀምበት በማለት ጥያቄ በማቅረባቸው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የኪራይ ውል ተፈጽሟል፡፡ ተጠሪ ከጳጉሜ 2 ቀን 1988 ዓ.ም. እስከ 1995 ዓ.ም. የቤት ኪራይ ሲከፍሉ ቆይተው 1995-1998 ያለውን ውዝፍ ኪራይ እንዲከፍሉ ደብዳቤ ተጽፎላቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ተገቢነት የሌለውና የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የተሠራው በሕጋዊ ይዞታዬ ላይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የሰጡት ያለኝን ማስረጃ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማድረግ ነው፡፡ የኪራይ ውል አለን በማለት ያቀረቡት ክርክር በማስረጃ የተደገፈ አይደለም፣ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በማጽናት እንዲያሰናብተኝ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሥር የተደረገው ክርክርና በሰበር አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው፣ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ጥያቄ የክስ ምክንያት አለው ብለው መቀበላቸውና አመልካችንና ተጠሪን አከራክረው አመልካች ከተጠሪ የቤት ኪራይ መቀበሉን፣ እንዲያቋርጥ በማለት መወሰናቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ጥያቄ ይዘት አመልካች ተጠሪ በወረዳ 8 ቀበሌ 6 ቁጥሩ 636/ሀ/ ለሆነው የድርጅት ቤት ያለበትን ውዝፍ ኪራይ እንድከፍል የፃፈው ደብዳቤ እንዲሰረዝልኝና ኪራይ እንዳልከፍል ይወስንልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ፣ ከተጠሪ ጋር ጳጉሜ 2 ቀን 1988 ዓ.ም. በተደረገ የቤት ኪራይ ውል ተጠሪ የተከራየው መሆኑንና እስከ 1995 ድረስ ኪራይ ሲከፍል ቆይቶ፣ 1995 በኋላ ኪራይ መክፈሉን ስላቆመ ማስጠንቀቂያ የተፃፈለት መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም የምንረዳው የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት ጳጉሜ 2 ቀን 1988 በተደረገው የቤት ኪራይ ውል ላይ የተመሠረተ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ፣ ከአመልካች ጋር የተደረገው የኪራይ ውል ሕጋዊ ውጤት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም በፍርድ ታይቶ ፈራሽ መሆን አለበት የሚሉበት፣ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1696 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1710 ከተዘረዘሩት አንዱ ወይም ሌላ ውሉ እንዳይረጋ የሚያደርግ ምክንያት አለኝ ብለው የሚያስቡ ከሆኑ ምክንያታቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ከአመልካች ጋር ያደረጉት የኪራይ ውል እንዲፈርስ መጠየቅ ነበረባቸው ተጠሪ ይህንን አላደረጉም፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጳጉሜ 2 ቀን 1988 የፈፀሙት ውልን ፈራሽ ሣያደርጉ፣ አመልካች በዚህ ኪራይ ውል መሠረት ውዝፍ የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ የፃፈው ደብዳቤ እንዲሰረዝላቸው የኪራይ ገንዘብ እንዳይከፍሉ እንዲወስንላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተጠሪ ከአመልካች የሚጠይቁትን መብትና ጥቅም በግልጽ የማያሣይና የክስ ምክንያት የሌለው ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውንና ይህንን የክስ ምክንያት የሌለውን ጥያቄ ለአመልካች መጥሪያ ከመላኩ በፊት መርምሮ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 231 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ መሠረት ውድቅ ማድረግ ነበረበት፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ከላይ የተገለጹትን ድንጋጌዎች በሚጥስ አኳኋን፣ ተጠሪ ከአመልካች የሚጠየቀውን አመልካች የፃፈው ደብዳቤ ይሠረዝልኝ እና የቤት ኪራይ እንዳልከፍል አቤቱታ በመቀበል ማከራከሩንና ቤቱን በሕገ ወጥ መንገድ ተጠሪ በመግንስት ባዶ ቦታ ላይ የሠራው ቢሆንም ቤቱ እንዲፈርስ ከማድረግ በስተቀር ተጠሪ ኪራይ እንዲከፍል ማድረግ አመልካች ስልጣን የለውም ከሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለውን የቤት ኪራይ ውል ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነክ፣ የይግባኝና ሰበር ችሎትም የሥር ፍርድ ቤት የክስ ምክንያት የሌለውን የተጠሪን ጥያቄ አላግባብ በመቀበል የሰጠውን ውሣኔ ማጽናታቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የቤት ኪራይ ለአመልካች እንዳልከፍል ይወስንልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የክስ ምክንያት የሌለው ሆኖ እያለ በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች አመልካች ከተጠሪ የቤት ኪራይ ለአመልካች እንዳልከፍል ይወስንልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የክስ ምክንያት የሌለው ሆኖ እያለ በየደረጃው፣ ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች አመልካች ከተጠሪ የቤት ኪራይ መቀበሉን እንዲያቆም የሰጡት ውሣኔ፣ ከላይ የዘረዘርናቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02157 መጋቢት 20 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና በመዝገብ ቁጥር 03331 ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዘገብ ቁጥር 06001 መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. ተጠሪ አመልካች በቁጥር 19/00ጋ/95 ሰኔ 10 ቀን 1995 ዓ.ም. የፃፈው ደብዳቤ ይሰረዝልኝ የቤት ኪራይ ገንዘብ እንዳልከፍል ይወስንልኝ በማለት፣ ያቀረበው ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡ ይህ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የካቲት 5 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ፣ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37391

የካቲት 3 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ - ጠበቃ ንጉሴ ገዛኸኝ ቀረበ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. ስዩም ማሞ - ቀረበ፡፡

2. በየነ አበራ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት በአሰሪና ሰራተኞች መካከል የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሾች የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት ጥፋት ሳንፈጽም የገንዘብ ቅጣት/ከደመወዛችን ላይ እየተቀነሰ/ እንድንከፍል ተወስኖብናል፡፡ ማስጠንቀቂያም ተሰጥቶናል፡፡ ስለዚህ ቅጣቱና ማስጠንቀቂያው ይሰረዝልን ዘንድ ይወሰንልን በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሾች ግንቦት 6 ቀን 1999 ዓ.ም በማታው ፈረቃ የነበረውን የስራ ጫና ለማደላደል አለቃ በሚወስነው የአሰራር አፈጻጸም ስርአት መሰረት ከነበሩበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመዜድ እንዲሰሩ አመራር ቢሰጣቸው አመራሩን ሳይቀበሉ በመቅረታቸው ነው ቅጣቱ የተወሰነባቸው፡፡ ቅጣቱ የተወሰነው በሕብረት ስምምነቱ መሰረት በመሆኑ ሕጋዊ ነው፡፡ የሚሰረዝበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ስለመከራከሩ ጎዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ የስራ ክርክር ችሎት ከፃፈው የመልስ ማመልከቻ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ መልክ ክርክር የቀረበለት የስራ ክርክር ችሎትም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ፣ በከሣሾች ላይ ቅጣቱ የተወሰነው በማታ ሽፍት አንሰራም ብለዋል በሚል እንጂ ከነበሩበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተዛውረን አንሰራም ብለዋል በሚል አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት በአመልካች የተሰጠው ቅጣት እንዲሰረዝ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውን በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች ተሰጥቶ የነበረውን የቅጣት ውሳኔ በፍ/ቤቶቹ በተሰጠው ውሳኔ የተሰረዘበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪዎች ቅጣት የተወሰነባቸው በአለቃቸው የተሰጣቸውን የስራ መመሪያ ለመቀበል ፍቃደኛ ሆነው አልተገኙም በሚል ነው፡፡ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የክስ ማመልከቻ እንደሚታየው በአለቃቸው የተሰጣቸውን ትእዛዝ በመቀበል በስራ ቦታው እንደተገኙ ገልጸዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ለቅጣቱ መነሻ ሆኖአል የተባለው ጥፋት /የአለቃ መመሪያ አለመቀበል/ አለመፈጸማቸው በመግለጽ መከራከራቸውን ነው፡፡ አመልካችም ጎዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው መልስ የበኩሉን የመከላከያ ክርክር ያቀረበ ሲሆን፣ይዘቱም ከላይ የተመለከተው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንግዲህ ከግራ ቀኝ ወገኖች የቀረበው የጽሑፍ ክርክር በግልጽ እንደሚያመለክተው አከራካሪው ጭብጥ ቁልጭ ብሎ መውጣቱን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 247/1/ እንደተደነገገው የነገር ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ተከራካሪ ወገን ያመነውን የሕግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ሌላው ተከራካሪ ወገን በማስተባበል የካደ እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ለቅጣቱ መወሰን መሰረት ሆኖአል ያለው የፍሬ ነገር አግባብ በተጠሪዎቹ ተክዶአል፡፡ በመሆኑም ይህ የፍሬ ነገር ጭብጥ እንደየሁኔታው ግራ ቀኝ ወገኖች ከሚያቀርቡት ማስረጃ አንፃር ታይቶ የሚነጥር ነው፡፡ በመቀጠልም በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ እውነታ ካለ አግባብ ካለው ሕግ አንፃር በመመርመር አግባብ ወዳለው ውሳኔ መድረስ ይችላል፡፡

አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ እንደሚታየው ክርክሩ ከፍ ሲል በተመለከተው አኳኋን አልተመራም፡፡ የክርክሩ አመራር የክርክር አመራር ስርአት ወይም አግባብ ተከትሎ ካልተከናወነ ፍትሐዊ ውሳኔ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡ አንድን ክርክር በመምራት ላይ ያለ ፍ/ቤት ሊያከናውናቸው ከሚገባቸው መሰረታዊ ነገሮች አንዱና ዋነኛው የክርክሩን ጭብጥ ለይቶ ማውጣት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ በስር ፍ/ቤቶች ሳይከናወን የቀረውም ይኸው ተግባር ነው፡፡ ትክክለኛው ጭብጥ ባለመያዙም የደረሰበት ድምዳሜ ትክክል ነው ሊባል አይችልም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37409 ጥር 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37391 መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ለተወሰነው ቅጣት መሰረት ሆኖአል የተባለውን ጥፋት ፈጽመዋል ወይስ አልፈጸሙም? የሚለውን የፍሬ ነገር ጭብጥ በግራ ቀኝ ወገኖች በሚቀርብለት ማስረጃ መሰረት እንዲያነጥር /እንዲያረጋግጥ/፤ በመቀጠልም በፍሬ ነገር ረገድ አጣርቶ የደረሰበትን ድምዳሜ አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ የመሰለውን ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ምክንያት ያወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

ት እ ዛ ዝ

ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ የመጣው ቁ. 37409 የሆነው መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ፡፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39540

የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ናስ ፋድስ የድ/ዳ/ጨ/ጨ/ፋብሪካ ተከራይ - ጠበቃ ወንድዬ ግርማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ስንዱ ደጀኔ (93 ሰዎች)

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የክስ ማመልከቻ በአመልካች ድርጅት ለረዥም ዘመናት በተለያዩ የስራ ዘርፎች ተቀጥረው ሲሰሩ ቆይተው መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም የስራ ውላቸው መቋረጡን፣እንዲህ ሲደረግም ሊከፍላቸው የሚገባ የስራ ስንብት ክፍያ፣የ60 ቀን ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ያልተወሰደ የአመት እረፍት ክፍያ ሣይከፈላቸው መቅረቱን ዘርዝረው በህብረት ስምምነቱ መሰረት ለእያንዳንዳቸው የአንድ ወር ደመወዝ በ42% ተባዝቶ የ2 ዓመት ከስድስት ወር ተቆርጦ የተያዘባቸው የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሊዝ ውሉ መሰረት የፕራይቬታይዜሽንና የመ/ል/ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ወደ ክርክሩ እንዲገባ እንዲታዘዝለት የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄም ጊዜውን በተመለከተ ግልጽነት የሌለው በመሆኑ የሥነ-ሥርዓት ጉድለት እንዳለበት በመዘርዘር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ለክሱ ኃፊነት የሌለበት መሆኑን ያሣያሉ ያላቸውን መከራከሪያ ነጥቦችን አንስቶ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጐ ለክሱ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው የአንድ ወር ደመወዝ 42% ለሁለት ዓመታት፣21% ደግሞ ለስድስት ወራት የአገልግሎት ካሣ ክፍያ በአመልካች ሊከፈላቸው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከተው የፋብሪካው ባለቤትና አከራይ በክርክሩ ጣልቃ እንዳይገባ መደረጉ፣አመልካች ፋብሪካውን ከመከራየቱ በፊት ላለ እዳና ሐላፊነት ከፋይና አስከፋይ መደረጉ ከህጉና ከኪራይ ውሉ ውጪ መሆኑንና ጉዳዩም ቀደም ሲል በተመሣሣይ ሁኔታ ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ነው በማለት ዘርዝረው የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች በወኪሎቻቸው አማካኝነት ታህሣስ 09 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገጽ ማመልከቻ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመንቀፍና የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ተገቢነት በመግለጽ ውሣኔው ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጭብጥ በጉዳዩ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በክርክሩ እንዲገባ አመልካች ጠይቆ በበታች ፍ/ቤቶች ጥያቄው ውድቅ ተደርጐ ለክፍያው ኃላፊ መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች ለረኽርም ዘመናት በተለያዩ የስራ ዘርፎች በፋብሪካው ተቀጥረው የሚሰሩ መሆኑን፣ ፋብሪካውን የሚያስተዳደረው የነበረው የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ መሆኑን፣ ፋብሪካውን የአሁኑ አመልካች ከአስተዳዳሪው አካል በኪራይ ከየካቲት ወር 1999 ዓ.ም ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ያህል መከራየቱን ነው፡፡ እንግዲህ አመልካች የፋብሪካው ተከራይ መሆኑ ከተረጋገጠ ከፋብሪካው ጋር ተያይዘው የሚነሱት መብትና ግዴታዎች የኪራይ ውሉንና አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በመመልከት ምላሽ የሚያገኙ ናቸው፡፡ አመልካች ለተጠሪዎች ጥያቄ በተከራይነቱ ኃፊነት የሌለበት መሆኑን፣የተከራዩ እና አከራዩ መብትና ግዴታም በውሉ ላይ መዘርዘሩን ጠቅሶ አከራይ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ይታዘዝለት ዘንድ አመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤትም አመልካች በዋቢነት የጠቀሰውን የኪራይ ውሉን አንቀጽ ሰራተኞች የክፍያ ጥያቄውን በቀጥታ ለአከራይ እንዲያቀርቡ የማያስገድድ፣አመልካችም በመዋቅሩ ምክንያት ከስራ ለሚያሰናብታቸው ሰራተኞች ተገቢውን ክፍያ ከፈፀመ በኋላ ወጪውን ከአከራይ እንዲጠይቅ የሚያስችል ነው በማለት የራሱን እምነት በመግለጽ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተጠየቀውን አካል ሳይጠራ አመልካችን ኃላፊ አድርጐ ወስኗል፡፡

በመሰረቱ በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ሊቀርብና የክሱም ምክንያት የብዙ ሰዎች መብትና ጥቅም የሚነካ ሆኖ ከእነሱ ውስጥ አንዱ ወይም ከፊሉ ክስ ባቀረቡ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑትን ወገኖችም መብትና ጥቅም የሚነካ ሲሆን በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ መስጠት የአለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ እነዚህ ወገኖች ተካፋይ ሣይሆን የሚሰጠው ውሣኔ ወይም ፍርድ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑም ተጠቃሽ ድንጋጌዎች መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም በክሱ ውስጥ መግባት ያለበት ተከሣሽ የሆነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆንና ለቀረበው ክስ መልስና መከላከያውን እንዲያቀርበው ሊያዘው የሚችል ስለመሆኑ ሥነ-ሥርአት ህጉ አስቀምጧል፡፡ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ማለት ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ጥቅማቸው፣መብታቸው ወይም ግዴታቸው የሚነካ በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች ስለመሆናቸውም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የፋብሪካው ተከራይ ሆኖ የኪራይ ውሉ የሚቆይበት ዘመንም ሁለት ዓመት ስለመሆኑ የአከራይና ተከራይ ጥቅም፣መብት ወይም ግዴታዎች በኪራይ ውሉ መዘርዘሩን አመልካች ያስረዳ ሲሆን ከኪራይ ውሉ ይዘት አኳያ ሲታይም በጉዳዩ ላይ የሚሰጥ ውሣኔ የአከራይን ጥቅም፣መብት ወይም ግዴታ ሊነካ አይችልም ሊባል የማይገባው ነው፡፡ በመሆኑም አከራይ በክርክሩ የግድ ተከፋይ መሆን የሚገባው ወገን /Indispensable party/ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት በኪራይ ውሉ ላይ የተመለከተውን አንድ አንቀጽ ብቻ ነጥሎ በመውሰድ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ስነ-ስርአታዊ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22768 ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03845 ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የፋብሪካው አከራይ የተባለው የፕራይዜታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወገን በመሆኑ ለቀረበ ክስና መልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩን እንደገና በመመልከት ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመልስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 36780

መጋቢት 03 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ ወኪል - ክብሮም አስመላሽ - ጠበቃ ካላዩ መሃሪ -ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የአቶ ገ/ኪዳን እንግዳ - ወኪል ኃ/ሥላሴ ገ/ኪዳን - ጠበቃ ገ/አምላክ - ገ/ጊዮርጊስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥነ-ሥርዓት ሕግን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች መጋቢት 01 ቀን 1995 ዓ.ም በፃፉት የክስ ማመልከቻ ግምቱ ብር 1500.00 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ የሆነ በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ጣቢያ አድነት ውስጥ የሚገኝ በምስራቅ 533፣በምዕራብ አደባባይ፣ በሰሜን 530፣ በደቡብ 534 የሚያዋስነው ፣ ስፋቱ በካሬ 600/ስድስት መቶ/ የሆነ የሚች አባታቸው ባሻይ አብርሃ ኪዳኑ ይዞታ በመሆን ከ1960 ዓ.ም ግብር የገበረበት ቦታ መኖሩን በዚህ ቦታ የአሁኑ ተጠሪ በነባር ይዞታነት ይገባኛል ብለው በቻልህ ትግራይ ጋዜጣ በ15/04/1995 ዓ.ም ተራ ቁጥር 755 በስማቸው ተጠንቶ መውጣቱን አመልካች ቦታውን በተመለከተ የይገባኛል ጥያቄ ለሚመለከተው የአስተደደር አካል ቢያቀርበም በመቐለ ዞን ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በቁጥር 10709 /354/94 በቀን 22/5/1995 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ጉዳዩን በፍርድ ጨርሰው አንዲቀርቡ ማዘዙንና የሚች አባታቸው ወራሽ መሆናቸውን ማረጋገጣቸውን ዘርዝረው የቦታው ግማሽ 300 ካ.ሜ እንዲሠጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመቀሌ ደቡብ ወረዳ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነታቸው ቀርበው በሠጡት መልስ በከሣሽ ክስ የተቀመጠው በመቻልሕ ትግራይ ጋዜጣ ከወጣው ጋር የማይገናኝ እና በጉዳዮ ላይ ተከራክረውበት ውሣኔ ተሰጥቶ ተከፋፍለው በየግል ይዘው እንደሚገኙ ገልፀው በክሱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው ተከራክረዋል ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በቃል በሠማበት ወቅት ከሣሽ እየጠየቁ ያሉት ስለተከፋፈሉት ሣይሆን ስለነባር ይዞታ መሆኑን መግለፃቸውን ተቀብሎ ተገቢውን ማጣራት ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በመቻልሕ ትግራይ ጋዜጣ ተራ ቁጥር 755 በቀን 15/04/1995 ዓ.ም በአሁኑ ተጠሪ ስም ተጠንቶ የወጣ ቦታ ለአመልካችም በአባተቸው ድርሻ ግማሽ 300 ካ.ሜ ሊደርሳቸው ይገባል በማለት ወስኗል በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ይኸው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ ሲያፀና ተጠሪ ጉዳዩን በድጋሚ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይኸው ፍ/ቤትም የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ይግባኙን ሠርዞታል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ የበታች ፍ/ቤቶች በተጠሪ በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያለፉት ከሥነ-ሥርዓት ውጪ መሆኑን በምክንያትነት በመያዝ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው ሲል የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ሽሯል የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የሠበር ችሎት ውሣኔ ባለመስማማት በመቃወም ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 5/አምስት / ገጽ የሠበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት ውሣኔ መሠታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቦታ በፍ/መ/ቁ 2/90 አዋሣኙ ከተጠቀሰው የተለየ ስለመሆኑ የዞኑ እና የወረዳ ፍ/ቤቶች አጣርተው በወሰኑት ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ከሚደነግገው ውጭ ጉዳዮ በፍርድ ያለቀ ነው ተብሎ መወሰኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው በማለት ዘርዝረው የክልሉ ሠበር ችሎት ውሣኔ ተሽሮ ሌሎች ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሣኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የአመልካች የሠበር አቤቱታ የቅሬታ ነጥቦች ተቀባይነት የሌላቸው የክልሉ የሠበር ችሎት ውሣኔ አግባብነት ያለው ስለመሆኑ ዘርዝረው ውሣኔው ሊፀና ይገባል ሲሉ በ22/01/2001 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ ማመልከቻ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የፃፉት የመልስ መልስ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የፁሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ዓብይ ጭብጥ ለክሱ መሠረት የሆነው ጉዳይ በመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች መጋቢት 01 ቀን 1995 ዓ.ም በፃፉት ክስ አዋሣኙንና ስፋቱን የገለፁበት ቦታ ቀደም ሲል በወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ ከተጠቀሰውና እኩል እንዲካፈሉ በ07/05/1991 ዓ.ም ፍ/ቤቱ ከወሰነው ቦታ ጋር ተመሣሣይ ስለመሆኑ ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑም የወረዳው እና የዞኑ ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ሲሆን ፍ/ቤቶች የተጠሪን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ያደረጉበት ምክንያት አመልካች በክስ ማመልከቻ ላይ የጠቀሱት አዋሣኝና ስፋት በመ/ቁ 2/90 የተወሰነውን የሚመለከት ቢሆንም ክሱ ሲሰማ በጋዜጣው ላይ የወጣውን ቦታ ስለመሆኑ በመግለፃቸውና በፍሬ ነገር ክርክር ወቅትም በማስረጃ ተጣርቷል በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ የክርክርን ሂደት ለማቀላጠፍና አንድ ደረጃ ላይ ሊደርስ መቋጫ ለማበጀት መሆኑ ይታመናል፡፡ የፍትሐብሔርን ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ እልባት እንዲደረግበት በማቀድ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ጽንሰ ሐሣቦች አንድ የመጨሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውጤት ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን፣በውሣኔ፣ በትእዛዝ፣ ወይም በጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ ለመንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አካኂን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡

ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በ01/07/1995 ዓ.ም ለወረዳው ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አዋሣኙና ስፋቱ የተጠቀሰው ቦታ በመ/ቁ 2/90 በፍርድ ያለቀ በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረትም ግራ ቀኙ ተከፋፍለው በየግላቸው የያዙት መሆኑን በሁለቱም የበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ከወረዳ ፍ/ቤት እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎት የተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት ያጣው አመልካች በክሱ ላይ አዋሣኙን የጠቀሱት ቦታ በፍርድ ያለቀ መሆኑ ቢረጋገጥም በቃል ክርክር ወቅት በጋዜጣው የወጣውን ይዞታ የሚመለከት መሆኑን ስለገለፁና ይህም ቀደም ሲል በፍርድ ካለቀ ጉዳይ የተለየ መሆኑን በተደረገው ማጣራት ተረጋግጧል በማለት መሆኑን ከላይ ገልፀናል እንግዲህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በአቤቱታ ፅሑፋቸው አዋሣኙን የጠቀሱት ቦታ ውሣኔ ያገኘ መሆኑ አከራካሪ አይደለም አከራካሪው ነጥብ በክሱ መሠማት ወቅት በአቤቱታ ጽሑፍቸው የጠቀሱት ሣይሆን በጋዜጣው የወጣው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል በሚል ተቀባይነት ማግኘቱ ሥነ-ሥርዓቱን የጠበቀ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የአቤቱታ ፅሑፎች የሚመሩት በሥነ-ሥርዓቱ በተመለከተው ሥርአት መሠረት ነው፡፡ ህጉ ይህን ያደረገበት መሠረታዊ ዓላማም የፍርድ ሂደቱን ለማቀላጠፍ በተቻለ ፍጥነት እልባት ለመስጠት ነው ። የአቤቱታ ጸሐፊዎች የሚመሩበት ሥርአት መኖር ተከራካሪ ወገኖች ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ በሚያዘው ጭብጥ ወይም ፍሬ ነገር ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የሚረዳቸው ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የአቤቱታ ጽሑፉች ሥርአት ባለው መልክ እንዲቀርቡ ማድረግ ፍ/ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ለመመሥረትም ያግዘዋል፤ በመሆኑም በአቤቱታ ጽሁፍ ላይ ያልተገለፀ ፍሬ ነገር ፍርድ ቤቱ ጭብጥ የሚመሰርትበት አይሆንም፡፡ ጭብጥ ባልተመሠረተባቸው የክርክር ነጥቦች ላይ ደግሞ ክርክሩ በሚሠማበት ወቅት ማስረጃ ሊቀርብባቸው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ማስረጃ የሚሠማው በተጠየቀው ጥያቄ ወይም በቀረበው የመከላከያ መልስ ላይ በግልጽና በዝርዝር በቀረቡት ነጥቦት ላይ ብቻ ነው፤ ሆኖም ፍ/ቤቱ የነገሩን ሁኔታ መርምሮ ሌላኛው ወገን ክሱን ወይም መልሱን እንዲያሻሽል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 91 እና 251 ድንጋጌዎች በተመለከተው መሠረት ሊያዝ ይችል ይሆናል፡፡ ከዚህ የሥነ-ሥርዓት አካሄድ ውጪ በአቤቱታ ፅሑፍ የተገለፁትን ፍሬ ነገሮች በመተው በቃል ክርክር ወቅት የተገለፀውን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ በሌላ ተከራካሪ ወገን የቀረበውን ተቃውሞ ውድቅ ማድረግ ሥነ-ሥርዓቱን የጠበቀ ነው የሚባልበት የክርክር አመራር ሥርዓት ምክንያት የለውም በተያዘው ጉዳይም አመልካች በአቤቱታ ጽሑፋቸው ላይ የጠቀሱትን ነገር በቃል ክርክር ወቅት አለመሆኑን ገልፀዋል ተብሎ የክስ አቤቱታውን ባላሻሻሉበት ሁኔታ ተቀባይነት ማግኘቱ፤ የአቤቱታ ጸሐፊዎች የሚመሩበትን ሥርዓት ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ ተገኝቷል፤ በመሆኑም አመልካች በአቤቱታ ጽሑፋቸው የገለፁትና የዘረዘሩት ፍሬ ነገር ከመ/ቁ 2/90 ከቀረበውና የመጨረሻ ፍርድ ካረፈበት ጉዳይ የተለየ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት ግራ ቀኙ የሚከራከርበት ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ነው ሲል የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ ስለሆነ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት በመ/ቁ 21439 ታህሣስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት በአብላጫ ድምጽ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች መጋቢት 01 ቀን 1995 ዓ.ም በፃፉት የአቤቱታ ጽሑፍ አዋሣኙንና ስፋቱን የጠቀሱት ቦታ በመ/ቁ 2/90 የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ጉዳይ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ ል ዩ ነ ት ሐ ሳ ብ

እኛ ስማችን በሶስተኛው እና በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምነው ዳኞች አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔ ባለመስማማታችን የልዩነት ሀሳባችንና ምክንያታችንን ከዚህ በታች በዝርዝር ገልፀናል፡፡

1. አብላጫው ድምጽ በውሣኔው በመጀመሪያው ገጽ በግልጽ እንዳሰፈረው አመልካች ተጠሪ የአባቱን የጋራ የይዛታ ቦታ ሊያካፍለኝ ይገባል የሚሉትን ቦታ ለማመላከት ሁለት አይነት አገላለጾችን ተጠቅመዋል የመጀመሪያው የወሰን መለያ ምልክቶችን በመጠቀም ተጠሪ በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ጣቢያ ሐድነት ውስጥ የሚገኘውና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሥራቅ 533 በምዕራብ አደባባይ በሰሜን 530፣ እና በደቡብ 534 የሚያዋስነው ስፋቱ 600 ካ.ሜትር ቦታ በማለት በክሳቸው የገለፁ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ተጠሪ እንዲያካፍላቸው የሚፈልጉት ነባር የይዞታ ቦታ የመቀሌ ከተማ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ታህሣሥ 15 ቀን 1995 ዓ.ም በመቃልሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 በተጠሪ ስም የወጣው ነባር የይዛታ ቦታ የአባታቸው የጋራ ይዞታ ስለሆነ ተጠሪ እንዲያካፍላቸው ውሣኔ እንዲሰጥላቸው በክስ ማመልከቻቸው የጠየቁ መሆኑን የወረዳውና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ይህንን የአመልካች የክስ አቀራረብ ከሥነሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ስንመለከተው ከሳሽ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተለየ ነገር በሚሆንበት ጊዜ ነገሩን በመለየት በሚያስችል ሁኔታ ክሱን አብራርቶ የማቅረብ ግዴታ አንዳለበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 225 ንዑጽ አንቀጽ 1 ይደነግጋል በተለይም የከሳሽ ክስ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የተመለከተ በሆነ ጊዜ ከሳሽ በክስ ማመልከቻው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ ምልክቶችን በክስ ማመልከቻው መግለጽ ያለበት መሆኑንና ይህንንም ግዴታውን የሚወጣው

- የማይንቀሣቀሠውን ንብረት የሚለየው የአካባቢ ወሰን በሆነ ጊዜ የአካባቢ የወሰን ምልክቶችን በክሱ ውስጥ በመግለጽ የክስ ማመልከቻው ማቅረብ እንዳለበት ወይም ከዚህ በአማራጭም፣
- የማይንቀሣቀሰው ንብረት በዕርስት መዝገብ የተመዘገበ በሆነ ጊዜ ንብረቱ በዕርስት መመዝገቢያ መዝገብ ላይ የተሰጠውን ቁጥር በመጥቀስ ክሱን ማቅረብ እንዳለበት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ለወረዳው ፍርድ ቤት የክስ ማመልከቻ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገጉት የማይንቀሣቀሥ ንብረት መለያ መንገዶች አንደኛውን አማራጭም ብቻ ሣይሆን ሁለቱንም አማራጮች በመጠቀም የክስ ማመልከታቸውን ገልፀዋል፡፡ አመልካች በክሳቸው ቦታውን ለመለየት የሚያስችሉ የወሰን ምልክቶችን የገለፁ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የመቀሌ ከተማ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ታህሳስ 15 ቀን 1995 ዓ.ም በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 ተጠሪ እንዲያካፍላቸው ተጠይቀዋል፡፡

አመልካች በክስ ማመልከቻቸው ውስጥ የቦታ መለያ የወሰን መልክቶችን በመጥቀስ የገለፁት ቦታውና የመቀሌ ከተማ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በተራ ቁጥር 755 የገለፀው ቦታ በአንድ መልዕካ ምድር ላይ የሚገኝ አንድ ቦታ አይደለም፡፡ አመልካች የወሰን ምልክቶችን በመጥቀስ የጠየቁት ቦታና የመቀሌ ከተማ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በመቀልሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 የወጣው ቦታ በተለያየ መልዕካ ምድር የሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ናቸው፡፡ የሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በቁጥር 755 በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ ያወጣው ቦታ በወሰን ምልክቶች ሲገለጽ በምሥራቅ አቶ ኪዳኑ ፈቃዱ በምዕራብ አቶ አብርሀ ኪዳኑ በሰሜን መንገድ በደቡብ አቶ ግደይ ገብሩ የሚያዋስኑት 600 ካሬ ሜትር ቦታ እንደሆነ፣ በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ በዝርዝር የተገለፀ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በእኛ እምነት አመልካች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁርር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገጉትን ሁሉንም አማራጭዎች በመጠቀም በክስ ማመልከቻቸው የጠየቁት ቦታ ሁለት የተለያዩ ቦታችን ነው፡፡ የአመልካች ክስ ግልጽነት የጐደለው መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም አመልካች ክስ ያቀረበችው በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ሐድነት ጣቢያ ሚገኘው በምስራቅ 533፣ በምዕራብ አደባባይ፣ በሰሜን 530 በደቡብ 534 የሚገኘውንና ከዚህ በፊት አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 1/90 በወረዳው ፍርድ ቤት ተከራክረው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘውን ቦታ ነው የሚለው መደምደሚያ አመልካች የመቀሌ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 አመልካች ተጠሪ እንዲያካፍላት በክስ ማመልከቻዋ ያቀረበችውን ጥያቄ ተጠሪ አመልካች ክስ እንዳላቀረበችበት ተደርጐ የተሰጠ በመሆኑ ተገቢ ነው የሚል እምነት የለንም፡፡ በእኛ እምነት አመልካች የወሰን ምልክቶችን በመግለጽ የጠየቀችው ቦታና ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ ተራ ቁጥር 755 የገለፀውን ቦታ ተጠሪ እንዲያካፍላት ያቀረበችው ጥያቄ ሁለት የተለያዩ ራሳቸውን የቻሉ ቦታዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ አመልካች በክስ ማመልከቻዋ ሁለት የተለያዩ ቦታዎች ተጠሪ እንዲያካፍላት ጠይቃለች ከሚባል በስተቀር አመልካች በመቐለሕ ትግራይ በተራ ቁጥር 755 ዝርዝሩ የተገለፀን ቦታ ተጠሪ እንዲያካፍላት ክስ አላቀረበችም በማለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና አብላጫው ድምጽ የደረሱበት መደምደሚያ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የመቀሌ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ አመልካችና ተጠሪ ለሚከራከሩበት ቦታ ያሰጠውን የቦታ መዝገብ ቁጥር በመጥቀስ የቀረበችውን ጥያቄ እንደ ትክክለኛ የክስ አቀራረብ አማረጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለመውሰድ የተሰጠና የማይንቀሣቀሥ ንብረት ላይ ክስ ለማቅረብ ትክክለኛው እና ብቸኛው የክስ አቀራረብ ሥርዓት የወሰን መለያ ምልክቶችን በመጥቀስ ክስን ማቅረብ እንደሆነ በመቁጠር የተሰጠ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. ከላይ በዝርዝር እንደገለጽነው አመልካች በክስ ማመልከቻዋ የቦታ ወሰን ምልክቶች በመጥቀስ የጠየቀችው ቦታና በመቐለሕ ትግራይ ጋዜጣ ተራ ቁጥር 755 በመዝገብ የሥራና ከተማ ልማለት መምሪያ ያወጣውን ቦታ ተጠሪ እንዲያካፍላት ያቀረበችው ጥያቄ ሁለት በተለያየ መልዕክምድር የሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ናቸው፡፡ አመልካች በክስ ማመልከቻዋ ሁለት የተለየዩ ቦታዎችን ገልጾ የጠየቀች መሆኗንና ተጠሪ ጉዳዩ ከዚህ በፊት በውሣኔ አልቋል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ መሆኑን የተረዳው የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረበው የመጀመሪያ መቃወሚያ ብይን ከመስጠቱ በፊት ፣

   - አመልካች ዳኝነት እንዲታይላቸውና በፍርድ ተጣርቶ የሚፈልጉት በክሳቸው የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ከገለጿቸው ቦታዎች የትኛውን ቦታ እንደሆነ እንዲያብራሩና መልስ እንዲሰጡ፣
   - ተጠሪ ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁጥር 2/90 ተከራክረን የመጨረሻ ውሣኔ አግኝቷል በማለት የሚቃወመው በአመልካች ክስ ከተገለፁት ሁለት ቦታዎች የትኛው እንደሆነ እንዲያብራራና መልስ እንዲሰጥ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 በሚደነግገው መሠረት ተገቢውን የቃል ምርመራ ያደረገ መሆኑንና ፍርድ ቤቱም ባደረገው የቃል ምርመራ አመልካች የወሰን መለያ ምልክቶችን በመጠቀም በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ሐድነት ጣቢያ የሚገኘው በምስራቅ 533 በምዕራብ አደባባይ በሰሜን 530፣ በደቡብ 534 የሚዋሰነው ቦታ ከዚህ በፊት አመልካችና ተጠሪ በዝገብ ቁጥር 2/90 ተከራክረውበት የመጨረሻ ፍርድ የገኘና ቦታውንም አመልካችና ተጠሪ እኩል ተካፍለው በይዞታቸው ሥር አድርገው የሚገኙ መሆኑን አጣርቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች ተጠሪ እንዲያካፍላት የምትፈልገውና ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆናት ቦታ በመቀሌ ከተማ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ታህሣሥ 15 /1995 በመቐለሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 ዝርዝሩ የተገለፀውና ነባር የይዛታ ቦታ ፍርድ ቤቱ ባደረገው የቃል ምርመራ በማያሻማ ሁኔታ ግልጽ ሆኗል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት ባደረገው የቃል ምርመራ አመልካች ተጠሪ እንዲያካፍላት የጠየቀችውና በመቐለሕ ትግራይ ጋዜጣ 755 ዝርዝሩና አዋሳኝ የድንበር ምልክቶቹ የተገለፀው ስድስት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ አመልካችና ተጠሪ ከዚህ በፊት ያልተከራከሩበትና ውሣኔ ያላገኘ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ፍረድ ቤቱ አመልካች በመቀሌሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 ዝርዝሩና አዋሳኝ ድንበሮቹ የተገለፁት ስድስት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የይዞታ መብት አላት ወይስ የላትም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመዘን ከዚህ ቦታ አመልካች ግማሹ ማለትም ሶስት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ በይዞታነት ይገባታል በማለት ወስኗል፡፡ በእኛ እምነት የወረዳው ፍርድ ቤት በአመልካች ክስ ውስጥ ሁለት የተለያዩ ቦታዎች ተገልፀው መቅረባቸውን በመረዳትና አመልካች በዳኝነት ታይቶ እንዲወሰንላቸው የሚፈልጉት በክሳቸው ከገለፁት ውስጥ በየትኛው ቦታ ላይ እንደሆነ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት ተገቢውን የቃል ምርመራ በማድረግ የክርክሩን መሠረተዊ የፍሬ ጉዳይ ጭብጥ መሥርቷል ይኸም የወረዳው ፍርድ ቤት የተከተለው የጭብጥ አመሰራረት ሥርዓት ፍርድ ቤት ጭብጥ ሊመሠርት ስለሚችልባቸው መንገዶች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና የሥነ-ሥርዓት ጉድለት የሌለበት ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የጉዳዮን መሠታዊ ጭብጥ የያዘው በፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428 (ሀ)መሠረት አመልካች በክስ ማመልበቻዋ ያቀረበችውን ጥያቄ የተጠሪ መልስ ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428 (ሐ) በተደነገገው መሠረት የቃል ምርመራ ሲያደርግ አመልካችና ተጠሪ የሰጡትን መልስና ማብራሪያ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትና አብላጫው ድምጽ የወረዳው ፍርድ ቤት በጭብጥ ሲመሠረት የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን እንዳልከተልና መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ጥሰት እንደተፈፀመ አድርገው የሰወጡት ትርጓሜና የደረሱበት መደምደሚያ አሳማኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

3. ከላይ ከክርክር እንደገለፀጽነው አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 1/90 በወረዳው ፍርድ ቤት ተከራክረው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘው በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ሐድነት ጣቢያ ሚገኘው በምሥራቅ 533 በምዕራብ አደባባይ በሰሜን 530 እና በደቡብ 534 የሚያዋስኑት ቦታ ነው፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት የፍትሐብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428(ሀ) እና የፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428(ሐ) ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ከጭብጥነት የያዘውና የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመዘን ውሣኔ የሰጠው የመቀሌ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ታህሣሥ 15 ቀን 1995 በመቐለሕ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 የገለፀው ቦታ ነው፡፡ ቦታው በአዋሳኝ ምልክቶች በሚያሳየው በምስራቅ አቶ ኪዳኑ ፈቃዱ፣ በምዕራብ አቶ አብርሀ ኪዳኑ በሰሜን አደባባይ በደቡብ አቶ ግደይ ገብሩ የሚያዋስኑት ስድስት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠውምና የዚህ ቦታ ግማሽ የአመልካች ግማሹ ደግሞ የተጠሪ ይዞታ ቦታ ነው በማለት ነው፡ የሥር ፍርድ ቤት የክርክሩ ጭብጥ አድርጐ በያዘው በዚህ ቦታ ላይ አመልካችና ተጠሪ ከዚህ በፊት ተከራክረው አያውቁም፡፡ ይኸ ቦታ አመልካችና ተጠሪ በመገንብ ቁጥር 1/90 ተከራክረው ውሣኔ ካገኘው ቦታ የተለየና ራሱን የቻለ ቦታ ነው፡፡ ይህንን መሠረታዊ ፍሬ ጉዳይ የወረዳው ፍርድ ቤት ብቻ ሣይሆን የወረዳው ፍርድ ቤት ውምኔ በይግባኝ ያቀረበላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 272 በሚደነግገው መሠረት በአካል ከቦታው በመገኘትና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሣኔ የሰጡ መሆኑን ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም አመልካች የሰበር አቤቱታ አቅርበውበት በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር አመልካችና ተጠሪ ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁጥር 1/90 ተከራክረው የመጨረሻ ውሣኔ ካገኘው ቦታ የተለያየና ራሱን የቻለ ቦታ ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ አድርጐ የመሠረተውና የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ የሰጠበትና ጉዳዩ መጀመሪያ በይግባኝ ያየው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጨማሪ ማጣራት በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶበት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፀና ውሳኔ ከዚህ በፊት አመልካችና ተጠሪ ያልተከራከሩበትና ውሳኔ ያላገኘ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ከዚህ በፊት ተከራክረው በመዝገብ ቁጥር 2/90 ውሳኔ ያገኘ ቦታ የወረዳው ፍርድ ቤት የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ አድርጐ፣ ከያዘው የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ ከሰጠበትና ጉዳዩንም በይግባኝ አይተው ያፀደቁት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ከሰጡበት ጉዳይ የተለየ ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪ ከዚህ በፊት ተከራክረው ውሳኔ ያገኘው ቦታና በዚህ ጉዳይ የመቀሌ ወረዳ ፍርድ ቤት የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ይዘው ውሳኔ የሰጡበት ቦታ የተለያዩ መሆናቸውን የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በግልጽ እያሳየ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አላግባብ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀጽ በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና በዚህ ችሎት ሊሻርና ሊታረም የሚገባው ነው የሚል እምነት አለን፡፡ በያዝነው ጉዳይ በጭብጥነት የተያዘውና በየደረጃው ያሉ የትግራይ ፍርድ ቤቶች አጣርተው ውሳኔ የሰጡበት ቦታ ከዚህ በፊት አመልካችና ተጠሪ ተከራክረው በውሣኔ ካለቀው ቦታ የተለየ በሆነበት ሁኔታ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ተፈፃሚነት እና አግባብነት የሌለው በመሆኑ በድንጋጌው መንፈስና ዓላማ እንዲሁም ይዘት ጋር የማይጣጣም ትርጉም የመስጠት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ አብላጫ ድምጽ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ማጽናቱ አግባብነት ያለው ነው ብለን ባለማመናችን በሐሳብ ተለይተናል፡፡

4. በእኛ በኩል በበታች ፍርድ ቤቶች በተለይም ክርክሩን በመጀመሪያ አይቶ ውሣኔ በሰጠው በወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ሙግት በሚመለከት በሚመራበት ወቅት የፈፀመው የሥነ ሥርዓት ጉድለት ቀላል የሥነ ሥርዓት ጉድለት ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች በክስ ማመልከቻዋ ከገለፀቻቸው ሁለት ቦታዎች ውስጥ የወሰን መለያ ምልክቶችን ጠቅሶ የጠየቀችው ቦታ ከዚህ በፊት በውሣኔ የተቋጨ እንደሆነ አመልካች ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆነውና በፍርድ ተጣርቶ እንዲወሰንላት የምትጠይቀው በመቐለሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 መዝግቦ የመቀሌ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ የወጣው ቦታ እንደሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት ባደረገው የቃል ምርመራ ግልጽ ሆኗል፡፡

ስለሆነም በአመልካች በክስ ውስጥ የወሰን መለያ ምልክቶችን በመጥቀስ ያቀረበችውን የክስ ክፍል ሙሉ በሙሉ በማውጣት በመቐለሕ ትግራይ ጋዜጣ ተራ ቁጥር 755 የተጠቀሰውን ቦታ አዋሻኝ የድንበር መለያ ምልክቶች በመግለጽ ክሷን አሻሽላ እንድትቀርብ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በራሱ አነሳሽነት ትእዛዝ በመሰጠት ጉዳዮን ለክርክር ክፍተት በማይፈጥርበት ሁኔታ አይቶ መወሰን እየቻለ ፍርድ ቤቱ ይህንን ሥርዓት አልተጠቀመበትም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ፍርድ ቤቱ አመልካች ክሷን እንድታሻሽል ሣያደርግ ክርክሩን ማስቀጠሉ የመከላከል መብቴን የሚያጣብብና የሥነ ሥረዓት ጉድለት ያለበት ነው የሚል እምነት ካለው በወቅቱ የወረዳው ፍርድ ቤት ይህንን የሥነ ሥርዓት ጉድለት እንዲያርመው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

207 መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት የነበራቸው ቢሆንም ተጠሪ ይህንን መብታቸውን ያልተጠቀሙበት መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት በአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ የሰጠው በመቐሌሕ ትግራይ ጋዜጣ ተራ ቁጥር 755 በሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በተጠሪ ስም የወጣው ነባር የይዛታ ቦታ ላይ አመልካች መብት አላት ወይስ የላትም የሚለው ጭብጥ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ድንጋጌዎች መሠረት በመመሥረት በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ክሷን ሳታሻሽል የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ መስጠቱ የተጠሪን የመከላከል መብትና የፍትህ መንደልን ያስከተለ መሠረታዊ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችለን ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም ይኸ የወረዳው ፍርድ ቤት የሥነ ሥርዓት ጉሉት የፈፀመበት የወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ቀርቦበት የከፍተኛው ፍርድ ቤትም የበኩሉን ተጨማሪ ማጣራት ካደረገ በኋላ አጽድቶታል፡፡ ውሣኔ ድጋሚ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦበት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፀድቋል፡፡

አንድ ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ ቀላል ሥነ-ሥርዓት ጉድለት የተፈፀመ ሲሆንና የሥን ሥርዓት ጉድለት የፈፀመው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ቀርቦበት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፀደቀ ከሆነ ውሣኔው በተፈፀመው ቀላል ሥነ ሥርዓት ጉድለት ምክንያት ብቻ ውድቅ እንደማይሆን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት 212 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ክሷን እንድታሻሽል ሣያደርግ አመልካቹንና ተጠሪን አከራክሮ መወሰኑ እንደ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሚቆጠርና ውሳኔውን ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔና በይግባኝ ቀርቦላቸው ያዩት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች ጭብጥ አድርገው ያልያዙትንና ውሣኔ ያልሰጡበትን ጉዳይ አግባብ በመጥቀስ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀጽ 1 አላግባብ በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ የሥር ፍርድ ቤቶች ጭብጥ አድርገው በመያዝ ውሣኔ የሰጡበትን ፍሬ ጉዳይ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ይኸ የሰበር ችሎት ሊሽረውና የተፈፀመውን መሠረታዊ የህግ ስህተት ሊያርመው ይገባል በማለት የልዩነት የውሣኔ ሀሳባችንና ምክንየታችንን ገልፀናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36460

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡-መሐመድ ሰዓዳይ ረጃ - ጠበቃ አበራ ጣሰው ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1/ አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ ፈረጅ - ቀርበዋል

2/ የህፃን ፊልሚያጀላኒ ሞግዚት ሻ/ሸዋነሽ አሰጋኸኝ - አልቀረቡም

3/ አቶ ሙክታር መሐመድ ፈረጅ - አልቀረቡም

4/ የአቶ ማሕሙድ መሐመድ ፈረጅ ወራሾች - አልቀረቡም

5/ ወ/ሮ ጀሚላ ጁሃር መሐመድ - አልቀረቡም

6/ ወ/ሮ ዘምዘም መሐመድ ፈረጅ - አልቀረቡም

7/ ወ/ሮ አለማ መሐመድ ፈረጅ - አልቀረቡም

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 22079፣ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይሻርልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በመቀሌ ከተማ፣ የደቡብ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት በተካሄደው ክርክር የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሾች የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ የነበሩ ሲሆን ስር ከሣሾቹ ጥቅምት 28 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ ክስ ያቀረቡ ሲሆን አጭር ይዘቱም ሰኔ 15 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው ውል ሕጋዊ ስላልሆነ እንዲፈርስና በተከሣሾቹ እጅ በዚሁ ምክንያት የገቡትን ቤቶች ይመለሱልን የሚል ነው፡፡

ተከሣሹም ባቀረቡት ተቃውሞ እርሣቸውም ሆነ ከሣሾቹ በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች እንዲሁም በውጭ አገር የምንኖር ስለሆነ በአዋጅ 25/88 ዓንቀፅ 5/2/ መሠረት ክርክሩን የመዳኘት ስልጣን ያለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንጂ የከተማው ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም ብለዋል፡፡

ከሣሾችም በጠበቃቸው በኩል ከላይ ለሰፈረው ተቃውሞ ታህሣሥ 23 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ መልስ የሰጡበት ሲሆን ይዘቱም ምንም እንኳ ከሣሾች በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ቢሆንም ውሉ የተፈፀመው እና አከራካሪው የማይንቀሣቀስ ንብረት የሚገኘው በመቀሌ ከተማ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፤ አዋጅ ቁ. 25/1988 ዓንቀፅ 5/2/ በውል ላይ በተመሠረተ ክርክር አይደለም፤ ተቃውሞው ውድቅ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ወረዳ ፍርድ ቤቱም የቀረበው ተቃውሞና መልስ ከላይ ከተመለከተው የአዋጁ ይዘት በማገናዘብ ጉዳዩ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስለሆነ ክርክሩን የማካሄድ ስልጣን የለኝም በማለት ጥር 14 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ብይን ሰጥቷል፡፡

ስር ከሣሾቹ ከላይ በሰፈረው ብይን ቅሬታ በማሣደር ወደ መቀሌ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ክርክር ከተካሄደ በኋላ ፍ/ቤቱ ሚያዚያ 05 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ብይን ክርክር የተነሣበት ቤት በመቀሌ ከተማ የሚገኝ በመሆኑ እንዲሁም ውሉ የተፈፀመው በዚሁ ከተማ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 24/1/ እና 25/1/ሀ/ መሠረት ስልጣን አለው በማለት የስር ፍ/ቤት ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

ጉዳዩ በስር ተከሣሹ ይግባኝ አቅራቢነት በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የታየ ሲሆን ይህ ፍ/ቤትም በፍ/ይ/መ/ቁ. 20127፣ ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የወረዳ ፍ/ቤቱ ስልጣን የለኝም የሚል ብይን ከሰጠ በኋላ ስር ከሣሾቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245/3/ መሠረት ክሣቸውን አሻሽለው ወደ ወሰነው ፍ/ቤት ወይም ወደሌላ ፍ/ቤት ማቅረብ የሚፈቅድ ሆኖ እያለ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ የወረዳውን ብይን መሻሩ ተገቢነት የለውም በማለት የወረዳ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

በዚህ የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ቅሬታ በማሣደርም ስር ከሣሾቹ ጉዳዩን ወደ ትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡት ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በመ.ቁ. 22079፣ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ብይን ለመሻር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245/3/ አጣቅሶ ከሣሾቹ ክሣቸውን አስተካክለው ለሚመለከተው ፍ/ቤት ያቀርባሉ እንጂ ይግባኝ ማለት አልነበረባቸውም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነና ስር ከሣሾቹ ይግባኝ ከማቅረብ በሕግ አይከለከሉም በማለት የጠቅላይ ፍ/ቤቱን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ብይን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ አመልካችም ከላይ የሰፈረውን የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልን በማለት መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርበዋል፤ መሠረታዊ ይዘቱም የቀረበው ክስና ተቃውሞ በአዋጅ ቁ. 25/1988፣ ዓንቀጽ 5/2/ መሠረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የሚታይ እንጂ በክልል ፍ/ቤት አይደለም፤ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245 አተረጓጎም ረገድ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ችሎት ስህተት ፈጽሟል ብሎ ማረም ቢችልም ለመሠረታዊ የክርክራችን ነጥብ የሰጠው መልስ የለም፤ ስለሆነም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፤ ይዘቱ ሲታይም እየተከራከሩበት ከመጡት ክርክር ያልተለየ በመሆኑ ደግሞ መዘርዘር ሣያስፈልግ ታልፏል፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም የግራና ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ በመጣው መልኩ በመገንዘብ ፣

በክሱ የተመለከተውን ጭብጥ የመዳኘት ስልጣን ያለው የትኛው ፍርድ ቤት ነው? የክልሉ ፍርድ ቤት ወይስ የፌዴራል ፍ/ቤት?የሚለውን መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው ተከራካሪ ወገኖች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በተለያዩ ክልሎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ እንደሚኖሩ ነው፤ ግራ ቀኙ ወገኖችም በዚህ ነጥብ የሚካካዱ አይደሉም፡፡ አመልካቹ እያቀረቡት ያለው ክርክር ነዋሪነታቸው በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 ዓንቀጽ 5/2/ መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው የሚል ሲሆን ተጠሪዎቹ ደግሞ አከራካሪው ጉዳይ በመቀሌ ከተማ ውስጥ በሚገኝ ቤት የሚካሄድ ስለሆነና ውሉም የተፈፀመው በዚሁ ከተማ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 24/1/ እና 25/1/ሀ/ መሠረት ክርክሩን የመዳኘት ስልጣን ያለው አራካሪው ቤት ባለበት የተቋቋመው የመቀሌ ደቡብ ወረዳ ፍርድ ቤት እንጂ የፌዴራል ፍርድ ቤት አይደለም ባይ ናቸው፡፡ አዋጅ ቁጥር 25/1988 የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም ብቻ ሚናው የታጠረ አይመስልም፤ከዚህም አልፎ በፌዴራል ፍርድ ቤቶችና በክልሉ ፍርድ ቤቶች መካከል ስልጣን የሚደለድል መሠረታዊ ሕግ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ ዓንቀጽ 5/2/ መሠረት ነዋሪነታቸው በተለያዩ የክልል መስተዳድሮች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚካሄድ ክርክር የሚስተናገድው በፌዴራል ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች ነው በማለት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይህ መሠረታዊ ይዘት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ውስጥ በዓንቀጽ 24/1/ እና 25/1/ሀ/ እንደተመለከተው አከራካሪው የማይንቀሣቀስ ንብረት በአንድ ክልል ስለተገኘ ብቻ ወይም ውሉ የተፈፀመው በአንድ ክልል በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ የክልል ፍርድ ቤቶች ተፈጥሯዊ ስልጣን እንዲኖራቸው የሚያደርጋቸው አይደለም፤ ስለሆነም በመጀመሪያ ከስረ -ነገር ስልጣን አኳያ አከራካሪው ጉዳይ ሲታይ የፌዴራል ፍርድ ቤት ስልጣን መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፤ ፌዴራል ፍርድ ቤቶችም ስልጣናቸው በሆኑ ጉዳዮች በእያንዳንዱ ክልል በቀጥታ መዋቅራቸውን ዘርግተው ወይም ደግሞ ለሚመለከተው የክልል ፍ/ቤት ውክልና በመስጠት ዳኝነት እንደሚሰጡ ነው፡፡ ስለሆነም የመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አከራካሪው ቤት በመቀሌ ከተማ በደቡብ ወረዳ በመገኘቱ ብቻ ወይም ውሉ በዚሁ አካባቢ በመደረጉ ወይም የሚፈፀም መሆኑን ብቻ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአዋጅ ቁጥር 25/88 ዓንቀጽ 5/2/ የተመለከተውን ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዳይሆን ስለሚያደርግ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆነው ተገኝተዋል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 04156፣ ሚያዝያ 05 ቀን 1999 የሰጠው ብይን እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 22079 ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡
2. በመቀሌ ከተማ፣ የደቡብ ወረዳ ፍ/ቤት ጥር 14 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች እየተከራከሩበት ያለው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/2/ መሠረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው፤ ስለሆነም ተጠሪዎቹ ክሣቸውን ከፌዴራል ፍርድ ቤት ውክልና በተሰጠው የሚመለከተው የክልሉ ፍ/ቤት አቅርበው ይከራከሩ ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍርድ ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፤ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39144

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ልዑልሰገድ ቦኔ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ኢትዮ - ሌዘር ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግል ማህበር - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ሕግን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች ታኅሣሥ 23 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት የክስ ማመልከቻ ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ያቋቋሙት የስራ ቅጥር ውል ያላግባብ መቋረጡን ዘርዝረው የስድስት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነቱ ቀርቦ አመልካች ከስራ የተሰናበቱት የማታለልና የማጭበርበር ተግባር መፈፀማቸው በማጣራት ተረጋግጦ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም አመልካች ከስራ የተሰናበቱበት መንገድ በሕጉ አግባብ አለመሆኑን ዘርዝሮ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ካለ በኋላ ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄን በተመለተ ግን የስራ ግንኙነቱ መልካም አይሆንም በሚል ምክንያት ባለመቀበል በምትኩ አመልካች የስድስት ወር ደመወዝ በካሣነት ተከፍሏቸው ከስራ እንዲሰናበቱ ሲል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ በስር ፍ/ቤት አመልካች ካሣ ተከፍሏቸው ከስራ እንዲሰናበቱ የተሰጠው ውሣኔ የስራ ዋስትናን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑ በምክንያትነት ይዞ በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የአመልካችን ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄ አስመልክቶ ግን በግልጽ ዳኝነት አላሳረፈበትም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለማሻሻል ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 08 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 2 /ሁለት/ ገጽ የሠበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ የዳኝነት አሰጣጥ ተፈፀመ የሚሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔን ሲለውጥ ለአመልካች የሚገባውን ዳኝነት በግልጽ ያልጠቀሰ በመሆኑ ይሽው ታርሞ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም ለሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡ ተጠሪ የአመልካች ጥያቄ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የማይገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሠረት ውሣኔው በሰጠው ፍ/ቤት ሊስተናገድ ይገባ የነበረ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአመልካች ጥያቄ ለሰበር ችሎቱ መቅረቡ ሥነ ሥርዓቱን በጠበቀ መንገድ ነው?፣ሥነ ሥርዓቱን በጠበቀ መንገድ ነው ከተባለስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ከሻረው በኋላ በአመልካች ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ የዳኝነት ጥያቄ ላይ ግልጽ ውሣኔ ሣያሣርፍ ማለፉ ተገቢነት አለውን? የሚሉት ነጥቦች በጭብጥነት ሊታዩ የሚገባ ሁነው አግኝተናል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ</u>፡- ጉዳዩ መሠረት ያደረገው አዋጅ ቁጥር 377/96 ዓ.ም ሲሆን ይህንኑ አዋጅ መሠረት አድርገው የሚቀርቡ ክርክሮች የሚመሩት በ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና በአዋጁ በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የስራ ክርክርን የማየት የዳኝነት የሥረ ነገር ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት አንዱ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በቁጥር 138 መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማየት የጀመረው የስራ ክርክር ውሣኔ ካገኘ በኋላ በይግባኝ የሚታየው በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 139 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ይህ የሥራ ክርክር ይግባኝ ሰሚው ችሎት በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ አንቀጽ 139 በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር አስቀምጧል፡፡ የስራ ክርክር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለበት ወገን አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው በሰበር ሥርዓት ነው፡፡በመሆኑም በስራ ክርክር ችሎት የተሰጠ ውሣኔ ሊፀና፣ ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል የሚችልበት ሥርዓት ይኸው ስለመሆኑ በቀላሉ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ የይግባኝ ቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት ወጪ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና የሚያስተናግድበት ሥርዓት በሥነ-ሥርዓት ሕጋችን ተመልክቷል፡፡

ከእነዚህ ሠርዓቶች መካከል አንዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ሥር የተመለከተው ስህተት የሚታረምበት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አቤቱታ የቀረበለት ውሣኔው የሰጠው ፍ/ቤት ሊያርም ወይም ሊያስተካክል የሚችለው በሰጠው ውሣኔ እና ትእዛዝ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት መኖሩን ካረጋገጠ ብቻ ነው ስለሆነም በክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሣኔ ስህተትን ማረም ወይም ማስተካከል በሚል መነሻ ውሣኔውን ሊያሻሽል ወይም ሊለወጥ አይችልም፡፡ የክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ ላይ ክርክር ተካሂዶ ውሣኔ ከተሰጠ እና በዚሁ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታ ሊያቀርብ የሚገባው ለበላይ ፍ/ቤት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይም አመልካች ቅሬታ አድሮባቸው ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡት የስር ፍ/ቤት ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄአቸውን ሣይቀበለው ቀርቶ በሕጉ በአማራጭ የተቀመጠውን መፍትሔ /relief/ በመወሠኑ ሁኖ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ሆኖም በአመልካች የተጠየቀውን ዳኝነት በግልጽ አልጠቀሰም፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሠረት ሊታረም ወይም ሊስተካከል ይገባ የነበረ ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ይልቁንም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት በፌ/ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10/1/ መሠረት ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊስተናገድ የሚገባ መሠረታዊ የክርክር ነጥብ ነው ስለሆነም የተጠሪ ጠበቃ በዚህ ረገድ ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ባለማግኘታችን አልፈነዋል፡፡

<u>ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ</u> ፡- ፍርዱ የክርክሩን ሂደት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮችን ባጭሩ መያዝ እንደአለበት፣ ለአፈፃፀም የማያስቸግር መሆን የአለበት ስለመሆኑ ስለፍርድ አሰጣጥ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ፍርዱ የሚፈፀመውን ክፍል በግልጽ ካላመለከተ በፍርድ መፍትሔ /relief/ የመሰጠቱን ዓላማ የሚያጓድለው ይሆናል፡፡ ስለሆነም አንድ ፍርድ ሲሰጥ የውሣኔ አፃፃፍ ይዘትና ቅደም ተከተልን መሠረት ያደረገ ከክርክሩ ሂደት እስከመደምደሚያው የያዘው ነገር ግልጽ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው የፍርድ አፈፃፀም አካሄድ የተሟላ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ በያዝነው ጉዳይም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ተገቢ አለመሆኑን በምክንያት አስደግፎ ከሻረው በኋላ በይግባኝ ደረጃ እንዲወሰን በአመልካች የተጠየቀውን ዳኝነት በግልጽ ሣያሰፍር ማለፉ በፍርድ መፍትሔ የመስጠቱን ዓላማ ያጓደለና የውሣኔውን አፈፃፀም አስቸጋሪ የሚያደርገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍርዱ ሊሰጥ የሚገባውን መፍትሔ በተመለከተ በግልጽ አለመጥቀሱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ስለተገኘ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 60794 ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43/5/ መሠረት ተጠሪ ለአመልካች የአንድ ዓመት ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራው ይመልስ ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38597

ሚያዝያ 6 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካቾች፡- 1. ጋሻው መንግስቱ ካሣ
2. አለሙ አብሬ ደነቦ
} ጠበቃ ሻምበል ተሾመ ደምሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ናይል ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ ምናለ አለሙ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር አመልካቾች ከሣሾች የነበሩ ሲሆን፣በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት የስራ ውላቸው ከሕግ ውጪ መቋረጡን በመግለጽ ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፍላቸው በመጠየቅ ነው፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ ከክፍያዎቹ አንዱ የሆነው የፕሮቪደንት ፈንድ የተጠየቀው በሕጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ነው የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ሌሎች የስረ-ነገር ክርክሮች በማንሳት ክሱ ይሰረዝ ዘንድ ጠይቆአል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ፣የስራ ውሉ የተቋረጠው በአግባቡ ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ በመቀጠልም ለከሣሾች ሊከፈል የሚገባው የስንብት ክፍያ ብቻ ነው፤ የካሣ እና የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያዎች ተቀባይነት የላቸውም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የበኩሉን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ውሳኔውን አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካቾች ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ቀደም ሲል ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ የፕሮቪደንት ፈንድ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆኑ ወይም ማመኑ ተገልፆ እያለ የስር ፍ/ቤቶች የፕሮቪደንት ፈንድ አይከፈልም በማለት የሰጡትን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም መጀመሪያ የአሁኖቹ አመልካቾችን ጨምሮ 53 ሰራተኞች በተጠሪ ላይ ክስ እንደመሰረቱ እና ተጠሪ የበኩሉን የመከላከያ መልስ ከሰጠ በኋላ የአሁኖቹ አመልካቾች ክስ ለብቻው ተነጥሎ እንዲታይ ስለታዘዘ በዚሁ መሰረት አመልካቾች ሌላ ክስ ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ለመጀመሪያው ክስ በሰጠው መልስ(ሚያዝያ 7 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈው) የፕሮቪደንት ፈንድ እና ሌሎች ክፍያዎች ለከሣሾች ሊከፈል እንደሚገባ እንደሚያምን በግልጽ ያመለከተ ሲሆን፣አመልካቾች ተነጥለው ለመሰረቱት ክስ በሰጠው መልስ ግን የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚል መቃወሚያ ማቅረቡን ተመልክተናል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የአመልካቾች ክስ ተነጥሎ እንዲቀርብ የታዘዘው በፍ/ቤቱ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን ትእዛዝ ሊሰጥ የቻለው የሁለቱ ሰራተኞች የስራ ውል የተቋረጠው ከሌሎች ሰራተኞች በተለየ ሁኔታ ነው በመባሉ እንደሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ለመረዳት ችለናል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ግን የፕሮቪደንት ፈንድ እና የሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ የቀረበው በሁሉም ሰራተኞች ነው፡፡ ተጠሪ በመልሱ ላይ ያመነውም ይህንኑ በአጠቃላይ ነው፡፡ በመሆኑም በስነ-ስርአት ሕጉ መሰረት ክርክሩን ለመለወጥ ይችል ዘንድ ጥያቄ አቅርቦ ሳይፈቀድለት እግረ መንገድ ባነሳው የይርጋ መቃወሚያ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክርም የይርጋ መቃወሚያ በአግባቡ አቅርቤአለሁ አላለም፡፡ አጥብቆ የተከራከረው አመልካቾች የፕሮቪደንት ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል ብዬ መልስ አልሰጠሁም በማለት ነው፡፡ ይህ አባባሉ ደግሞ ሚያዝያ 7 ቀን 97 ዓ.ም የሰጠውን ግልጽ የመከላከያ መልስ የሚቃረን ነው፡፡ ስለዚህም አመልካቾች የጠየቁት የፕሮቪደንት ፈንድ የማይከፈልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23556 በጎንደር 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61971 ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካቾች የጠየቁትን የፕሮቪደንት ፈንድም ተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚያዝያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሽራተን አዲስ- አቶ ኃይሉ ንጋቱ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ እያሱ- መገርሣ ቀረቡ

በዚህ መዝገብና በሰበር መዝገብ ቁጥር 40390 የተያዘው ክርክር ተጣምረው መታየታቸው የበታች ፍርድ ቤት በሁለት የተለያዩ መዝገቦች የሰጠውን ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው መሆኑን ለመመርመርና ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘነው በዚህ መዝገብ የቀረበውን ክርክር በሰበር መዝገብ ቁጥር 40024 ከቀረበው ክርክር ጋር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍ/ቤት ሌላ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 62996 ሰኔ 4 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆኑ በሰበር ታይተው ይታረሙልኝ በማለት ነሐሴ 13 ቀን 2000 ዓ.ም እና ነሐሴ 3 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፉ የሰበር አቤቱታዎች በማቅረብ ሁለቱን መዝገቦች በማስከፈቱ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በከሳሽነት ቀርበው ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) 1996 ዓ.ም ጀምሮ በዳቦና ኬክ አዘጋጅነት ቀጥሮ ሲያሰራን ቆይቶ ነሐሴ 19 ቀን 1999 ዓ.ም የስራ ውላችንን ያላንዳች ምክንያት ያቋረጠብን በመሆኑ የስራ ውሉን አላግባብ በማቋረጡ የካሣና የስራ ስንብት ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት፣የሰርቪስ ቻርጅ ብር 2000(ሁለት ሺህ ብር)፣ በሌሊት የሰራንበት፣ ቅዳሜና እሁድ የሰራንበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ እና የዓመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ከስድስት ወር ደመወዛችን ጋር ይከፈለን የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡

አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከስድስት ወር በፊት ያቀረቧቸው የተለያዩ የክፍያ ጥያቄዎች በይርጋ ይታገዳሉ፤ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል የተረጋገጠ መብት የላቸውም ተብሎ ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳይ ረገድም ከሳሾች (ተጠሪዎች) የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ ነው፤ ስብሰባና ሰርግ ሲኖር እየተጠሩ ለተወሰነ ጊዜ የሰሩ ቢሆንም በተከታታይ ለሶስት ዓመት አልሰሩም፤ የሰርቪስ ቻርጅ እና የአዳሪ ክፍያ የሚከፈለው ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች ስለሆነ ሊጠይቁ አይገባም፤ ቅዳሜና እሁድ ለመስራታቸው ማስረጃ አላቀረቡም በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ የሰማ ሲሆን አመልካች አንድ ምስክር አቅርቦ ምስክሩ ተጠሪዎች ስራ ሲበዛ ለማቃለል የተቀጠሩና ደካማ የስራ ውጤት በማሣየታቸው የተሰናበቱ መሆኑን የመሰከረ ሲሆን ተጠሪዎች ራሳቸው በምስክርነት ቀርበው ላልተወሰነ ጊዜ መቀጠራቸውንና በተከታታይ መስራታቸውን መስክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ መዝኖ የስራ ውሉ የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ነው፤ ከሳሾች (ተጠሪዎች) ያቀረቡት የስራ ስንብት ክፍያ፣ የካሣ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ተፈፃሚነት የለውም፤ ትርፍ ሰዓት መስራታቸውን ባለማስረዳታቸው ጥያቄቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቀባይነት የለውም፤ የሰርቪስ ቻርጅ ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠረ ሰራተኛ ብቻ የሚከፈል መሆኑን ተከሳሽ (አመልካች) አላስረዳም፣ ይክፈል፤ የሁለት ዓመት ፈቃድ በገንዘብ ቀይሮ ይክፈል፤ የተለያዩ ክፍያዎች ከስድስት ወር በፊት ያሉት በይርጋ ቀሪ ይሆናሉ፤ የቅዳሜና እሁድ ክፍያ በይርጋ የማይታገደውን ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች የራሱን የይግባኝ ቅሬታ ተጠሪዎች ደግሞ የራሳቸውን የይግባኝ ቅሬታ በማቅረብ ሁለት የይግባኝ መዝገቦች በማስከፈት ክርክር አድርገዋል፡፡ በመጀመሪያ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታና የአመልካችን ክርክር በከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 የሰማው ችሎት ተጠሪዎች የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ነው፤ ስለሆነም የስራ ስንብት ክፍያ የካሣ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ለእያንዳንዳቸው የሁለት ወር ክፍያ በሕጉ መሰረት ተሰርቶ እንዲከፈላቸው በማለት ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ወስኗል፡፡ አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታና ተጠሪዎች ለይግባኙ የሰጡትን መልስ በመዝገብ ቁጥር 62996 ሰምቶ የወሰነው ሌላው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ችሎት ቅዳሜና እሁድ የሰሩ መሆኑን ተጠሪዎች ያላስረዱ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ቅዳሜና እሁድ ለሰሩበት ይከፈላቸው ማለቱ ተገቢ አይደለም በማለት የቅዳሜና እሁድ ክፍያ ብቻ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ሰኔ 4 ቀን 2000 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች በሁለቱም መዝገብ የሰጧቸው ውሳኔዎች መሰረታዊ ስህተት እንዳለባቸው በመግለጽ እነዚህን ሁለት የሰበር መዝገቦች አስከፍቷል፡፡ አመልካች በዚህ መዝገብ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፤ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ካሣና ሌሎች ክፍያዎች መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያመለከተ ሲሆን፤ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 40390 ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የሰርቪስ ቻርጅ የሚከፈለው ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች ብቻ ሆኖ እያለ ብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) ይክፈል መባሉ ተገቢ አይደለም፤ ስለዚህ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች አመልካች በሁለቱም መዝገቦች ያቀረባቸውን የሰበር አቤቱታዎች በመቃወም መልስ ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩና በተከታታይ ያለማቋረጥ ሲሰሩ እንደነበር የአመልካች ምስክር ገልጿል፤ ምስክሩ በስራ ድክመት ተባረሩ የሚል ቃል የሰጠ ቢሆንም ይህንን የሚደግፍ ማስረጃ አልቀረበም፤ የሰርቪስ ቻርጅ እንዲከፈለን መወሰኑ በአግባቡ ነው፤ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጽሑፍ ባቀረቧቸው መልሶች ተከራክረዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥ፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለት የተለያዩ ችሎቶች የተጠሪዎችንና የአመልካችን ይግባኝ መርምረው የሰጡት ውሣኔና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ የተወሰነበት ስርዓት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውና ይግባኝ ባዮች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ስለሆኑ የካሣ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎች እንዲከፈሉ የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች እልባት ማግኘት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅሬታ የተሰማቸው አመልካችም ተጠሪዎችም ናቸው፡፡ ሁለቱም በውሣኔው ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ሆኖም የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአመልካች ቅሬታ አቅራቢነት ከተከፈተው የይግባኝ መዝገብ ቁጥር 62996 በተጠሪዎች ቅሬታ አቅራቢነት ከተከፈተው የይግባኝ መ/ቁጥር 62985 ጋር በፍትሀብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 11 ንኡስ አንቀጽ 5 መሰረት በማጣመር እንዲታይ ማድረግ ሲገባው ከአንድ ውሣኔ የተነሱ ሁለት ይግባኞች በሁለት የተለያዩ ችሎቶች እንዲታዩ በመደረጋቸው እርስ በርሳቸው የሚቃረኑና አንድ ላይ ሊፈፀሙ የማይችሉ ሁለት ውሣኔዎች ተሰጥተዋል፡፡ የስነ- ስርአት ሕጉ በአንድ ዘንግ ከሚመደቡ ተከራካሪዎችና በአንድ ጭብጥ ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች ተጣምረው እንዲታዩ የሚደነግገው በተመሣሣይ ጉዳይ እና ጭብጥ የተለያዩ ችሎቶች የተለያየ ውሣኔ እንዳይሰጡ ለመከላከልና የስራ ቅልጥፍና እና የውሣኔ ወጥነትን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሁለቱ የይግባኝ መዝገቦች ተጣምረው እንዲታዩ ባለማድረጉ ተጠሪዎች ይግባኝ ባሉበት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሎ የፍርድ ባለመብት የሆኑበት፣ አመልካች ይግባኝ ባለበት መዝገብ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሎ ፍርድ ያገኘበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የሁለቱን ችሎቶች ውሣኔዎች በጋራ አይቶ ማስተካከያ ካልተደረገ በስተቀር እርስ በርሳቸው የሚቃረኑና በአንድ ላይ ሊፈጸሙ የማይችሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርአት ግድፈት ያለበት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪዎች በአንድ ወቅት በነበረ የስራ ብዛት ምክንያት ተቀጥረው ለተከታታይ ሲሰሩ ቆይተው ባሳዩት የስራ ድክመት የተሰናበቱ መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ምስክር የመሰከረ መሆኑን በመመዘንና የተጠሪዎችን የምስክርነት ቃል በመመዘን ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው፤ የስራ ውላቸውም የተቋረጠው ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ ነው በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 የሰጠው ውሣኔ በመዝገቡ አመልካችና ተጠሪዎች ያቀረቡትን ማስረጃ በመመዘን የሰጠውና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል።

አመልካች ለተጠሪዎች መክፈል የሚገባቸውን ክፍያዎች በተመለከተም የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 የስራ ስንብት ክፍያ የካሣ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ለእያንዳንዳቸው የሁለት ወር ደመወዝ በሕጉ መሰረት እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም። ከዚህ በተጨማሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62996 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለተጠሪዎች እንዲከፍል የወሰነውን የቅዳሜና እሁድ ክፍያ ብቻ በመሻር አመልካች ለተጠሪዎች ከመጋቢት 29 ቀን 1999 እስከ መስከረም 29 ቀን 2000 በወር ብር 2000(ሁለት ሺህ ብር) የሚታሰብ የሰርቪስ ቻርጅ ክፍያ፣ የሁለት ዓመት የዓመት ፈቃድ በገንዘብ ቀይሮ እንዲከፍል የሰጠውን ውሣኔ በራሱ ብቻውን ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

በአጠቃላይ ጉዳዩ በፍትሀብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 11 ንኡስ አንቀጽ 5 መሰረት ተጠቃልሎ ባለመታየቱ በሁለቱ መዝገቦች የተሰጡ ውሣኔዎች የተለያዩና እርስ በርስ የሚቃረኑ ከመሆናቸው ውጭ በይዘታቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለባቸው ናቸው በማለት ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62996 የሰጠው ውሣኔ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 ከሰጠው ውሣኔ ጋር ተጣጥሞ ተፈፃሚ ሊሆን በሚችልበት ሁኔታ በማጣመር አጽንተናል። ይፃፍ።
2. ተጠሪዎች የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ነው ብለናል። አመልካች የተጠሪዎችን የስራ ውል ያቋረጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎችን ሣይከተል ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ ነው ብለናል።
3. አመልካች የተጠሪዎችን ውል ከሕግ ውጭ በማቋረጡ፣
   - የስራ ስንብት ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት፣
   - የካሣ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር አንቀጽ 377/1996 አንቀጽ 43(4)ሀ መሰረት፣
   - የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የሁለት ወር ደመወዛቸውን፣
   - የስድስት ወር የሰርቪስቻርጅ ክፍያ በሁለት ሺ ብር (2000) ሒሳብ
   - የሁለት ዓመት የዓመት እረፍት ፈቃድ ክፍያ በገንዘብ ተሰልቶ፣ ሊከፍላቸው ይገባል ብለናል።
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል።

የዚህ ፍርድ ግልባጭ ተገልብጦ ከመዝገብ ቁጥር 40390 ጋር ይያያዝ። ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሚያዝያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34504

ሚያዝያ 6 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ አበባው የሺድንበር አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ካሣ በቀለ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የጉዳዩ መነሻ የመንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ፍ/ቤት መስከረም 22 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 14/95 በሆነው በ10/7/99 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው እግድ ትዕዛዝ ስላልተነሳ በመዝገቡ ላይ ክርክር መቀጠል አልተቻለም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 16552 በሆነው ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ብይኑን አጽንቶታል፡፡ እንደገና በይግባኝ የመረመረው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 44/2000 በሆነው መዝገብ ኅዳር 13 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መልስ ሰጭ የሆነውን የአሁኑን አመልካችን ሳይጠራውና ሳያከራክር "ምንም እንኳን ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ባይፈቅድም" በማለት ተጠሪ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር የተሠጠ ውሣኔ የሌለ በመሆኑ የመጀመሪያው ክስ ቢዘጋለትም እንደ ገና እንዲንቀሳቀስለት በተወሰነው መሠረት ክርክሩ እንዲቀጥል የተፈጠረው ስህተት ተስተካክሏል በማለት ውሣኔውን በመለወጡ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፎ ያቀረበው ቅሬታ ለተጠሪ ደርሶት ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር በሕግ ረገድ በአጭሩ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሠረቱ በፍ/ቤቶች የተከራካሪ ወገኖች ማንኛቸውም አቤቱታና ቅሬታ በዳኝነት ሊታይ የሚችለው በሕግ በተመለከቱ ሥርዓቶች ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምንም እንኳን የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ባይፈቅድም በማለት በበታች ፍ/ቤቶች የተፈጠረውን ስህተት ለማረም የአሁኑን አመልካች ሳይጠራውና ሳያከራክረው የአንደኛውን ወገን ቅሬታና ክርክር ብቻ በመስማት ውሣኔ ላይ መድረሱ የአንደኛውን ወገን የመሰማት መበት የተጋፋና ከሥነ - ሥርዓት ሕግ ውጪ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 338/1/ ሥር በግልጽ እንደተመለከተው ይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ያልሠረዘ እንደሆነ ይግባኙ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ወስኖ መልስ ሰጭው ቀርቦ እንዲከራከር መደረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይህን በሕግ የተመለከተውን የመሰማት ሕገ-መንግሥታዊ መብት /the right to be heard/ ባልጠበቀ መልኩ የተሰጠው ውሣኔ በየትኛውም መመዘኛ ፍትሐዊና የሕግ መሠረት አለው ለማለት የሚቻልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ አንደኛውን ወገን ሳይጠራና ሳያከራክር የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 44/2000 በ13/3/2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 338/1/ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲመለስ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የዚህ ፍ/ቤትን ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
4. የውሣኔው ግልባጭ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይተላለፍ ብለን መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37761

ሚያዝያ 20 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ገብረመስቀል ንጉሴ- ጠበቃው ቀርቧል

ተጠሪ፡- አዲስ ልብስ ስፌት አ/ማ- ጠበቃው ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የውል ግንኙነትን መሠረት የደረገ የገንዘብ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በመሐከላችን በተደረገው የመኪና ጥገና ውል መሠረት መኪናዬን ለጥገና ተረክቦ የነበረ ቢሆንም በአግባቡ ያልጠገነ በመሆኑ የከፈልኩትን የጥገና ስራ ዋጋ ይመልስልኝ፤ መኪናው ቶሎ ተጠግኖ ባለመመለሱ ለሠራተኞች ትራንስፖርት ወጪ ያደረግኩትንም ይተካልኝ በማለት ነው፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በተገባው ውል መሠረት መኪናውን ጠግኜ በአግባቡ አስረክቤአለሁ፤ ከሣሽ መኪናውን ፈትሾ ከተረከበና ዋጋውንም ከከፈለ በኋላ ሲገለገልበት ቆይቶ ዋጋውን መልስ ሊለኝ አይችልም፤ ለሠራተኞች ትራንስፖርት ወጣ የተባለው ገንዘብም እኔን አይመለከትም በማለት በአንድ በኩል የተከራከረ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በውሉ መሠረት መኪናውን በድጋሚ ተረክቤ የመለዋወጫ ዕቃዎችን ከውጪ ሐገር በመግዛት የሠራሁ ስለሆነና ከሣሽም በዚሁ ስለተስማማ ለመለዋወጫ ዕቃዎች ያወጣሁትን ገንዘብ ይተካልኝ በማለት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ መሥርቷል፡፡

ክሱን የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሁለቱን ወገኖች ካከራከረ በኋላ የተጠሪን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ አመልካች ያቀረበውን የክፍያ ጥያቄ ተቀብሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ባለመስማማቱ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፤ ፍ/ቤቱም የተጠሪን ክስ በተመለከተ የተሰጠውን ውሣኔ ሲያፀና አመልካች ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ መሠረት የተሰጠውን ውሣኔ ሽሯል፡፡ በዚህም አመልካች ለመለዋወጫ ዕቃዎች አወጣሁት ያለው ገንዘብ ሊከፈለው አይገባም ብሏል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፤ ፍ/ቤቱ ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች የተጠሪን መኪና /አውቶቡስ/ ሲጠግን ለመለዋወጫ ዕቃዎች ያወጣው ገንዘብ ሊከፈለው አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ እንደተገለፀው የተከራካሪዎቹ ግንኙነት የተመሠረተው በውል ላይ ነው፡፡ አመልካች በውሉ የገባው ግዴታ የተጠሪን አውቶቡስ /መኪና/ በጋራዡ ጠግኖ ለማስረከብ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ጠግኖ ለተጠሪ ከማስረከቡም በላይ፤ በውሉ የተመለከተውን የጥገና ዋጋውንም ወስዷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአውቶቡሱ ርክክብ ከተፈፀመ በኋላም ተመልሶ ወደ ጋራዥ ገብቷል፡፡ አመልካችም በውሉ በገባው የዋስትና ግዴታ መሠረት ነፃ የቴክኒክ አገልግሎት በመስጠት መኪናውን ጠግኖ ለተጠሪ አስረክቧል፡፡ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ የመሠረተውም በዚህ ጊዜ ለገጠማቸው የመለዋወጫ ዕቃዎች መግዣ ያወጣው ወጪ እንዲተካለት ነው፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገው ውል የአመልካች ግዴታ የመለዋወጫ ዕቃዎችን በራሱ ወጪ ገዝቶ መግጠምን አያጠቃልልም፡፡ የመለዋወጫ ዕቃ ወጪ የሚሸፈነው በተጠሪ ነው፡፡ በእርግጥ ከብር 1000 /አንደ ሺህ ብር/ በላይ የሚያወጣ የመለዋወጫ ዕቃ ሲገዛ ተጠሪ መፍቀድ እንዳለበት በውሉ ተመልክቷል፡፡ ይሁንና ተጠሪ አመልካች ላቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በሰጠው መልስ የመለዋወጫ ዕቃዎቹ እንዲገዙ አልፈቀድኩም የሚል ክርክር እንዳላቀረበ በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የተባሉት የመለዋወጫ ዕቃዎች በመኪናው ላይ አልተገጠሙም የሚል ክርክርም የለውም፡፡ ይልቁንም መኪናው ለሁለተኛ ጊዜ ጥገና ወደ ጋራዡ እንደገባ የክፍያ ጥያቄ እንደሚነሣ ያወቀና ይህንም ለአመልካች በፃፈው ደብዳቤ ገልጾ እንደነበር በፍ/ቤቱ ውሣኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ገንዘቡ ለአመልካች እንዲከፈል የወሰነው እነዚህን ምክንያቶች እግምት ውስጥ በማግባት እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ እንዳየነው ፍ/ቤቱ አመልካች የመለዋወጫ ዕቃዎቹን አልገዛም ወይም ለመኪናው ጥገና አላዋላቸውም እሚል ድምዳሜ ላይ አልደረሰም፡፡ ገንዘቡ አይከፈልም ያለው ዕቃዎቹ የተገዙት ከተጠሪ ዕውቅና ውጪ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ነው፡፡ ከላይ እንዳመለከትነው ተጠሪ ከኔ እውቅና ውጪ የተገዙ ናቸው የሚል ክርክር አላቀረበም፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክርም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ብቻ ሣይሆን፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክርም የመለዋወጫ ዕቃዎቹ ከኔ እውቅና ውጪ የተገዙ ናቸው የሚል የመከራከሪያ ነጥብ አለማቅረቡን ነው ያረጋገጠው፡፡ በሰበር ችሎት የተከራከረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩ ባይቀርብለትም በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ ትክክል የመሰለውን የመከራከሪያ ነጥብ በመያዝ አከራክሮ መወሰኑ ትክክል ነው በማለት ነው፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ የሚከራከረው ከአመልካች ጋር ያለውን የውል ግንኙነት መሠረት በማድረግ እንደመሆኑ ውሉን መሠረት በማድረግ የሚቀርቡትን የመከራከሪያ ነጥቦች አንስቶ ሊከራከር ይገባል፡፡ በራሱ በተጠሪም እንደታመነው የመከራከሪያ ነጥቡን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አላቀረበውም እንጂ ቢያቀርበውም ኖሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 329/1/ እንደተመለከተው ተቀባይነት የሚኖረው አልነበረም፡፡ በእርግጥ ፍ/ቤቱ የተባለውን ነጥብ በራሱ ማለትም በፍ/ቤቱ የተነሣ ሣይሆን፣ ተጠሪ በይግባኝ ማመልከቻው ገልጾት የነበረ እንደሆነ ነው በውሣኔው ላይ ያመለከተው፡፡ ይህም የሚያሣየው ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 182/2/ በተደነገገው መሠረት የሰጠው ውሣኔ አለመሆኑን ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 329/1/ የተመለከተውን ክልክላ በማለፍ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያልተነሣን ክርክር መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ወሣኔ የሚሰጥበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሊወስን ሲገባው ያልወሰነው ጉዳይ የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.182/2/ አኳያ የሚያይበት የሕግ ምክንያት ነበር የሚባልም አይደለም፡፡ ስናጠቃልለው አመልካች ለመለዋወጫ ዕቃዎች መግዣ ያወጣው ገንዘብ ሊከፈለው አይገባም በሚል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 32885 የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43808 ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለመኪናው ጥገና ለዋሉ የመለዋወጫ ዕቃዎች መግዣ አወጣሁት ያለውና ክስ የመሠረተበት ገንዘብ እንዲከፈለው በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. በሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38181

ግንቦት 4 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢት/መንገዶች ባለሥልጣን - ነ/ፈጅ ጌታቸው አካሣ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ትዕግሥት ወንድይፍራው - ጠ/ላቀ ቀረቡ፡፡

2. አቶ ባህሩ አህመድ - በሌሉበት

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ክስ በሚሠማበት ቀጠሮ የከሣሽ /የይግባኝ ባይ/ አለመቅረብ የሚያስከትለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች ከሣሽ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ በክሱም የአንደኛ ተጠሪ ንብረት የሆነውን መኪና ሁለተኛ ተጠሪ ሲያሽከረክሩ በግልገል ግቤ ወንዝ ላይ የተሠራው ድልድይ ላይ ጉዳት በማድረሣቸው ተጠሪዎች ለደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የከሣሽን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታውን ያቀረበ ሲሆን የይግባኝ ቅሬታው መልስ ሰጪዎች ባሉበት የሚጣራ ነጥብ በማግኘቱ ይግባኙን ለመስማት ቀጠሮ ሠጥቷል፡፡

ይግባኙ በሚሠማበት ዕለትም አመልካች ባለመቅረቡና የአንደኛ ተጠሪ ጠበቃም መዝገቡ እንዲዘጋላቸው ስለጠየቁ ፍ/ቤት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ዘግቷል፡፡ አመልካች የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስ እንዲፈቀድ አመልክቶ ፍ/ቤቱ በቂ ምክንያት አልቀረበም በሚል ጥያቄውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ በቅሬታውም አንደኛ ተጠሪ የተከሠሠበትን ነገር ሣይክድ መዝገቡ እንዲዘጋ በመጠየቁ ብቻ መዘጋቱ ስህተት ነው፤ ለሁለተኛ ተጠሪ መጥሪያ መስጠት እንዳልተቻለ ለፍ/ቤቱ ተገልፆ የርሣቸው ጥሪ ጉዳይ በእንጥልጥል ላይ እያለ ጉዳዩን ለመስማት የሚያስችል ሁኔታ ሣይኖርና ሁለተኛ ተጠሪ በምትክ መጥሪያ ሣይጠሩ መዝገቡ መዘጋቱ ስህተት ነው፤ በቀጠሮው እለት ያልቀረብንበት በቂ ምክንያት እያለ መታለፉ ስህተት ነው፤ በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሮ መዝገቡ ተከፍቶ እንዲታይ አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት የመዘጋቱን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ታዘው ሁለተኛ ተጠሪ አልቀረቡም፡፡ አንደኛ ተጠሪ ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሠምቷል፡፡ ከፍ ሲል የተገለፀው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ሊመለስ የሚገባው የይግባኝ ቅሬታው በሚሰማበት ቀን ይግባኝ ባይ /የአሁን አመልካች/ ያልቀረበ ቢሆንም አንደኛ ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታውን ክደው ሣይከራከሩ መዝገቡ መዘጋቱ በአግባቡ ነው አይደለም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

ስለ ባለጉዳዮች ፍ/ቤት መቅረብና ሣይቀርቡ መቅረት በሚናገረው ምዕራፍ ውስጥ የሚገኘው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 73 ባንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሣይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተከሣሹ ቀርቦ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከሠሠበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሣሹ በሌለበትም ቢሆን ፍ/ቤቱ ተከሣሽ ላመነው ጉዳይ ውሣኔ መስጠት እንደሚችል ተከሳሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን እንደሚዘጋውና ተከሣሹን እንደሚያሠናብት ይደነግጋል፡፡ በእርግጥ ይህ ድንጋጌ ከሣሽና ተከሣሽ እያለ የሚናገር ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ በይግባኝ የሚቀርቡትንም ክርክሮች አጠቃሎ ስለሚይዝ እንደነገሩ አግባብ ከሣሽ የሚለው ቃል ይግባኝ ባይን ተከሣሽ የሚለው ደግሞ መ/ሰጪን የሚተካ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ ቁጥር 32/2/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ቅሬታው በሚሠማበት ቀነ ቀጠሮ ይግባኝ ባይ ካልቀረበ ተፈፃሚነት ያለው ይኸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ነው፡፡ በዚህ የሥነ ሥርዓቱ ድንጋጌ ደግሞ ይግባኙ በሚሠማበት ቀነ ቀጠሮ ይግባኝ ባይ ያልቀረበ ከሆነ መ/ሰጪው ይግባኝ የቀረበበትን ነጥብ በከፊል ወይም በሙሉ ካመነ በእምነቱ መሠረት ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሚሠጥ መሆኑን ነገር ግን ይግባኙን ክዶ የተከራከረ ከሆነ መዝገቡን መዝጋት እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የይግባኙ መዝገብ መዘጋት የሚወሰነው መ/ሰጪው ለቀረበበት የይግባኝ ቅሬታ ከሚሠጠው መልስ አኳያ ታይቶ ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም መ/ሰጪ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ መካድ ማመኑ ሣይረጋገጥ መዝገቡ እንዲዘጋ በመጠየቁ ብቻ መዝገቡ ሊዘጋ የሚችልበትን ሁኔታ ድንጋጌው አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የአንደኛ መልስ ሰጪን መልስ ሣይመለከት መዝገቡን መዝጋቱ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ከአመልካች አቤቱታ እንደተመለከትነው ሁለተኛ ተጠሪ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንዲቀርቡ የተላከላቸውን መጥሪያ መ/ሰጪውን አግኝቶ መስጠት አለመቻሉ ለፍ/ቤቱ ተገልፆለት ሁለተኛ ተጠሪ እንዲቀርቡ ምትክ መጥሪያ ሳይላክ በእንጥልጥል ላይ የነበረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤትም ተጠርተው ያልቀረቡ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ የቀረበ ማስተባበያ የለም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪ በምትክ መጥሪያ እንዲጠሩ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሣይሠጥ አመልካች ይግባኝ በሚሠማበት ቀን አልቀረበም በማለት በሁለተኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ይግባኝም አብሮ መዘጋቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መዝገብ የሚዘጋው ይግባኝ ባዩ የይግባኝ ቅሬታውን ክዶ ከተከራከረ በመሆኑ የአንደኛ ይግባኝ ባይ መልስ ተጠይቆ ሳይረጋገጥ መዝገቡ መዘጋቱም ሆነ ለሁለተኛ ተጠሪ መድረስ አለመቻሉ ተገልፆ ሳለ በምትክ መጥሪያ እንዲቀርብ ሣይታዘዝ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መዘጋቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33199 ግንቦት 5/2000 ዓ.ም. እንዲሁም በዚህ መዝገብ ግንቦት 14/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የተዘጋው መዝገብ ተከፍቶ ነገሩ እንዲቀጥል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 42706

ግንቦት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ላየን ሴኩሪቲ ኩባንያ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ ጥላሁን ገ/እግዚአብሔር -ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ተከሳሽ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በጥበቃ ሰራተኛነት በአመልካች ድርጅት ሳገለግል ቆይቼ ምንም ሳላጠፋ ከሥራ አሰናብቶኛል ስለዚህ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ይህ ካለሆነ የአንድ ወር ደሞዝና ሌሎች የስንብት ክፍያ ይከፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካችም በሰጠው መልስ ተጠሪ መጠጥ ጠጥተው ወደ ሥራ በመግባት አምቧጋሮ ይፈጥራሉ፣ ከባልደረባቸው አይግባቡም በዚህም መሠረት የማስጠንቀቅያ ጽሑፍ ቢሰጣቸውም ሊታረሙ ባለመቻላቸው የ10 ቀን ደሞዝ ተቀጥተዋል ስለዚህ ስንብታቸው በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔውም አመልካች ተጠሪን ለማሰናበት ምክንያት ናቸው ሲል የገለፀው ወይም ያቀረበው ማስረጃ እርስ በርሱ የሚቃረን ነው በተለይም በ8/7/2000 እና በ11/8/2000 ለተጠሪ የተፃፉት ማስጠንቀቂያ የሚጣረስ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በመሆኑም የተጠሪ የ1 (አንድ) ወር ደሞዝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ክፍያን አስመልክቶ በተጠሪ ጥያቄ መሠረት እንዲከፈለው ሲል ወደ ሥራ የመመለስ ጥያቄን አልተቀበልኩም ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርቧል፡፡ መዝገቡ የቀረበለት ፍ/ቤት የሥር ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ጥር 13/2001 ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

በዚህም መሠረት የሰበር ችሎትም ተጠሪን በማስቀረብ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ እንዲታይ የተወሰነውም አመልካች ክሱን ለማስተባበል ያቀረባቸው ምስክሮች ሣይሰሙ ውሳኔ የመሠጠቱን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ የግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ሲታይ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በጥበቃ ሥራ ተቀጥሮ በመስራት ላይ እያለ አመልካች ያለ ጥፋት አሰናበተኝ ስለዚህ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ካልሆነም በሕግ የተቀመጠውን ይክፈለኝ ሲሉ በጠየቁት መሠረት አመልካችም ተጠሪ ጥፋት በመፈፀማቸው ነው ያሰናበትኳቸው ሲል ተከራክሮ፤ ጉዳዩን ያየው የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪ የፈፀሙትን ጥፋት አላስረዳም በማለት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲል ወደሥራ የመመለስ ጥያቄን ውድቅ በማድረግ የተለያዩ ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፈለው ውሣኔ ሰጥቷል፤ የከፍተኛው ፍ/ቤትም ውሣኔውን ጉድለት የለበትም በማለት አፅንቷል።

እኛም ከላይ የተጠቀሰውን የውሣኔ አሰጣጥ መሠረት በማድረግ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምተናል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው አመልካች ያቀረበው ማስረጃ በተለያዩ ጊዜ ለተጠሪ የተፃፈ ማስጠንቀቂያ የስንብቱን ምክንያት በአግባቡ የማያረጋግጥና የተጣረሰ (የሚጋጭ) ነው በማለት ነው። ስለ አመልካች የሰው ማስረጃም ቢሆን በውሣኔው ላይ የጠቀሰው ነገር የሌለ እና መስማት የማያስፈልገው እንኳ ቢሆን የገለፀው ነጥብ የለም አመልካች በመከላከያው መልስ የሰው ምስክር እስከቆጠረ ድረስና የቀረበው የሠነድ ዕሁፍ በአግባቡ የተጠሪን ጥፋተኝነት የሚያረጋግጥለት ከሆነ አግባብነት ያለው ውሣኔ ለመስጠት ሲባል የአመልካችን ምስክር መስማትና ወደ ውሣኔ ሊመጣ ይገባ ነበር። ምክንያቱም የአመልካች የቀረበበትን ክስ የመከላከል መብቱ ሊታለፍ የማይገባው ህጋዊ ነጥብ ነው። በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የቀረቡትን የሰው ምስክር ሣይሰማ ወደ ውሣኔ መድረሱ እና የከፍተኛው ፍ/ቤት ሣያርመው ማለፉ አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13385 በቀን 15/9/2001 እና የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ 75596 በቀን 12/5/2001 የተሠጠው ውሣኔ ተሽሯል። ይፃፍ።
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የሰው ምስክር በመስማት ይወሰን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት መዝገቡን መልሰናል።
3. በዚህ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 14227 ላይ ተላልፎ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ለሚመለከተው ይጻፍ።
4. የግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37741

ሰኔ 4 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ መኮንን ዘውዴ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ተሾመ ሽፈራው- አልቀረቡም

2. ወ/ሮ ዘርፌ ጎባቸው- አልቀረቡም

3. አቶ ጌታቸው መንገሻ- ወራሽ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በደራ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ ሦስተኛ ተጠሪ በገንዘብ እዳ ምክንያት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎችን በደራ ወረዳ ፍ/ቤት ከሰው ካስፈረዱ በኋላ ንብረትነቱ የፍርድ ባለእዳዎቹ /የአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች/ የሆነ ቤት በፍርድ አፈፃፀም ተሸጦ እዳው እንዲከፈል ተብሎ የአፈፃፀም ትእዛዝ ተሰጥቶ ይሄው ቤት ለአመልካች ተሸጦ እዳው እንደተከፈለ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ከዚህ በኋላም የፍርድ ባለእዳዎች የይግባኝ ቅሬታ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ይግባኝ ባዮች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለመ/ሰጭ /ለስር ከሳሹ/ ይክፈሉ ተብሎ የተሰጠውን ዋናውን ውሳኔ በመሻር በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በኋላም ፍርዱን ያስፈጸመው የወረዳ ፍ/ቤት ዋናው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን መሰረት በማድረግ የተሸጠውን ቤት ተከሳሾች እንዲረከቡት በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ቤት በፍርድ አፈፃፀም በኩል በተደረገ ሽያጭ ገዝቼዋለሁ የሚሉት የአሁን አመልካች ይህንኑ የወረዳውን ፍ/ቤት ትእዛዝ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

ከዚህም በመቀጠል የይግባኝ ቅሬታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ዋናው ውሳኔ ከተሻረ ተከራካሪ ወገኖች ቀድሞ ወደ ነበሩበት ሁኔታ ለመመለስ ጥያቄ ካቀረቡ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 349/1/ መሰረት ወደነበሩበት እንዲመለሱ መደረግ አለበት፤ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ተሸጧል የተባለው ቤት ለስር ተከሳሾች እንዲመለስ ሲታዘዝ የሸያጩን ገንዘብ የስር ከሳሽ እንዲመልሱ መደረግ ሲገባው ይህ ያልተከናወነ ስለሆነ በዚሁ መሰረት የሸያጩን ገንዘብ የስር ከሳሹ ለአመልካች እንዲመልሱ በማለት የስር ፍ/ቤትን ትእዛዝ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ወሳኔውን አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት እንደዚሁም የስር ክሳሹ በተጠሪነት ተጣምረው ባለመገኘታቸው እሳቸውን ሦስተኛ ተጠሪ በማድረግ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤታታውም እንደሚከተው ተመርምሯል፡፡

በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠ ፍርድ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተለወጠ ወይም የተሻሻለ እንደሆነ ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ነገሩን በመጀመሪያ ለተመለከተው ፍ/ቤት ሲያመለክት የተወሰደው ገንዘብ ወይም ንብረት እንዲመለስ ተስማሚ መስሎ የታየውን ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 349/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ንብረትነቱ የአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች የሆነው ቤት በፍርድ አፈፃፀም ለአሁን አመልካች ተሸጦ የሸያጩም ገንዘብ የፍርድ ባለመብት ለነበሩት ለአሁን ሦስተኛ ተጠሪ ተከፍሏል፡፡ የአሁን አመልካችም ይህንኑ በፍርድ አፈፃፀም በሽያጭ ያገኙትን ቤት አሳልፈው ለሌላ ወገን መሸጣቸውን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የሰነ-ስርአት ሕጉ ድንጋጌ መሰረት ፍርዱ በይግባኝ በተለወጠ ጊዜ በዚሁ መሰረት ተከራካሪ ወገኖች ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ ትእዛዝ መስጠት የሚቻል ሲሆን ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ቤቱ በፍርድ አፈጻጸም ለአመልካች ከተሸጠ በቤቱ ላይም ለውጥ ከተደረገበት በኋላ እንደገና ለሌላ ወገን የተሸጠ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ ቤቱ ለስር ተከሳሾች /ለአሁን አንደኛ ተጠሪዎች/ ይመለስ መባሉ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የድንጋጌውም ይዘት ሲታይ ፍ/ቤቱ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ተገቢ መስሎ የታየውን ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል የሚያሳይ ፈቃጅ ድንጋጌ እንጂ አስገዳጅ ድንጋጌ አይደለም፡፡

ስለሆነም ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አኳኋን ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሊመለሱ ይገባል ተብሎ እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 48176 በ4/9/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 42032 በ17/5/99 የሰጠው ውሳኔ፣የሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11335 በ28/9/98 የሰጠው ትእዛዝ እንደዚሁም የደራ ወረዳ ፍ/ቤት በ24/8/98 የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በፍርድ አፈፃፀም የገዙትን ቤት ለአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ሊመልሱ አይገባም ብለናል፡፡
3. የቤቱን የሐራጅ ሽያጭ ገንዘብ የስር የፍርድ ባለመብት የነበሩት የአሁን ሦስተኛ ተጠሪ አቶ ጌታቸው መንገሻ ለአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ሊመልሱ ይገባል ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም ግልባጩ ለደራ ወረዳ ፍ/ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38452

ሰኔ 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአ.አ ከተማ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ አቶ ተስፋዬ ዘመድኩን - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ዓለም ገብሩ - ጠበቃ አቶ አታክልት ኃ/ስላሴ ቀርበዋል

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው አመልካች ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 59626 ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/ቁ. 72799 ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጧቸው ፍርዶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ስለሆኑ ይሻሩልኝ በማለቱ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ በስር ፍ/ቤቱ ተከሣሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን፣ ስር ከሣሹ ሚያዚያ 09/1999 ዓ.ም ያቀረቡት የተሻሻለ ክስ መሠረታዊ ይዘቱ ተከሣሹ የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች ለመሸጥ ጨረታ ባወጣው መሠረት በ6ኛ ዙር የጨረታ ሂደት በመሣተፍ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ በቀበሌ 15/16 በአስኮ ሣይት የሚገኙትን ቁጥራቸው AS-B7-00193 እና AS-B8 -00243 የሆኑትን ሁለት ቤቶች እያንዳንዳቸውን በብር 81,330 /ሰማንያ አንድ ሺህ ሦስት መቶ ሰላሣ ብር/ ዋጋ በማሸነፍ የካቲት 21 ቀን 1998 እና መጋቢት 04 ቀን 1998 ዓ.ም የተፃፈ የሽያጭ ውል በማሰር የቤቶቹን ዋጋ ለተከሣሹ የከፈልኩ ብሆንም የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር ቤቶቹን ሊያስረክበኝ ስላልቻለ ቤቶቹን እንዲያስረክበኝ፣ የባለቤትነት ማስረጃም እንዲሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቱም ስር ተከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ትእዛዝ ደርሶት ስላልቀረበና ክርክሩን ለማካሄድ በተቀጠረበት ቀንም በመቅረቱ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ አሏል፡፡ ዋናውን ጉዳይ በተመለከተም ተከሣሹ በክስ የተጠቀሱትን ቤቶች በጨረታ ለከሣሹ እንደሸጣቸውና ዋጋቸውንም ተቀብሎ ውል እንዳሰረ በመግለጽ ቤቶቹን ለከሣሹ ማስረከብ እንዳለበት ወስኗል፡፡ በአሁኑ አመልካች ይግባኝ ባይነት ጉዳዩ ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢቀርብም ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 59626፣ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

ከላይ የሰፈረውን ፍርድ በመቃወምም አመልካቹ ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም አከራካሪው ጉዳይ ማለትም ቤቶቹ በአመልካቹ የሚተዳደሩ በመሆናቸው እንዲሁም የአዲስ አበባ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ከሚዋዋሏቸው ውሎች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 41 መሠረት የዳኝነት ስልጣኑ የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች እንጂ የፌዴራል ፍ/ቤት ስልጣን አይደለም፤ የስር ፍ/ቤቶቹ ስልጣን ሣይኖራቸው የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ እንዲሁም ተጠሪው ቤቶቹን የገዛቸው ለጨረታ በተቀመጠው መነሻ ዋጋ ነው፤ ሆኖም የከተማው አስተዳደር ያወጣው የጨረታ መመሪያ የጨረታ አሸናፊ ለመሆን ከጨረታው መነሻ ዋጋ በላይ መሸጥ እንዳለበት ስለሚያመለክት ሽያጩ ሕጋዊ ባልሆነበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶቹ የሽያጭ ውል አለ በማለት የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ ስለሆነም ውሣኔው ይሻርልን የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ሚያዚያ 2001 ዓ.ም በተፃፈ መልሣቸው አመልካቹ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ጠቅሰው የተከራከሩበት አዋጅ ቁ. 362/95 አንቀጽ 41 የሚል እንጂ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41 የሚል አይደለም ስለሆነም በስር ፍ/ቤት ያልተጠቀሰውን በዚህ ሰበር ችሎት መከራከሪያ ሊያደርጉት አይችሉም፤ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶቹ የፈፀሙት የሕግ ስህተት ስለሌለ ውሣኔያቸው ይጽደቅልኝ ብለዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ በሰፈረው መልክ በመገንዘብ፣ ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው? በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል በሕግ የሚፀና የቤት ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካቹ ባቀረበው ክርክር ይህንን ጉዳይ የማየት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንጂ የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆን የለባቸውም፤ ይህንንም የስልጣን ጉዳይ የስር ፍ/ቤቶቹ በራሣቸው አነሣሽነት ስልጣን እንደሌላቸው መበየን ሲገባቸው ወደ ዋናው ክርክር ገብተው ውሣኔ መስጠታቸው ተገቢነት የለውም ሲሉ ተጠሪው ግን ከላይ የቀረበውን ክርክር ባለመቀበል አከራካሪውን ጉዳይ በተመለከተ የስር ፍ/ቤቶቹ ስልጣን የላቸውም ሊባሉ አይገባም ብለዋል፡፡

እንደሚታወቀው አመልካቹ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካል ሲሆን የክርክሩ መነሻም እሱ የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች አስመልክቶ የተደረገ የሽያጭ ውልን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 እንዳሰፈረው ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ወይም በስሩ ያሉ ሌሎች አካላት የሚገቧቸውን ውሎች በተመለከተ እንዲሁም የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱትን ክርክሮች የመዳኘት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች መሆናቸውን በግልጽ አስፍሯል፡፡ ተጠሪው ባቀረቡት ክርክር አመልካቹ በስር ፍ/ቤት የጠቀሰው አዋጅ ሌላ ነው ከማለት ውጭ ከላይ የሰፈረውን የዳኝነት ስልጣን በቀጥታ አላስተባበሉትም፡፡ የስር ፍ/ቤቶቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9/2/ መሠረት ስልጣን የሌላቸው መሆናቸውን በራሣቸው አነሣሽነትም ቢሆን ጉዳዩን አንስተው ተገቢውን ብይን መስጠት ማለትም የክሱ ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም ብለው መዝጋት ሲገባቸው አከራካሪውን ጉዳይ የማየት ስልጣን እንዳላቸው አድርገው በክርክሩ ዋና ነጥብ ውሣኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 59626፣ጥር 21/2000 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በከ/ቁ. 72799፣ ሰኔ 11/1999 ዓ.ም የሰጧቸው ፍርዶች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡

2/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አከራካሪውን ጉዳይ የማየት ስልጣን የላቸውም፤ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ናቸው ብለናል፡፡

3/ ሰኔ 12/2000 ዓ.ም እና ሐምሌ 28/2000 ዓ.ም የተላለፉት እግዶች ተነስተዋል፤ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39014

ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብልዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ዓለሙ መግራ - ቀረበ

ተጠሪ፡- እምነቱ እንደሻው ህንፃ ተቋራጭ - ነ/ፈጅ ግርማ ወርቁ ቀረቡ

መዝገቡን መርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር ጉዳዩ የስራ ክርክር ሆኖ መጀመሪያ አመልካች ባቀረበው ክስ መነሻ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 19802 በ5/10/99 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች የስራ መሪ እንጂ ሰራተኛ አይደለም በማለት ክሱ በብይን ውድቅ ሲደረግ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 57097 በሆነው ጎዳር 11 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ብይንን መሻር አመልካች የስራ መሪ ሳይሆን ሰራተኛ ነው በማለት በፍሬ ነገር ላይ ውሳኔ እንዲሰጥት በማዘዝ ለመጀመሪያ ፍ/ቤት ጉዳዩ ተመለሰ፡፡ ከዚህ በኋላ ክርክሩ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲካሄድ ሐምሌ 13/99 ዓ.ም በተፃፈ መቃወሚያ የግዛት ክልል ስልጣን የለም የሚለውን መቃወሚያ ቀርቦ ፍ/ቤቱ በማለፍ በፍሬ ነገር ላይ የስራ ውል የተቋረጠው አለአግባብ ነው የ6 ወር ካሳና የ2 ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና የየካቲት ወር ደመወዝ እዲከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት የግዛት ክልል ስልጣን የለውም ተጠሪ ዋና መ/ቤቱ አዋሳ ነው በማለት ውሳኔው በመሻሩ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 2 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ቅሬታ፡-

የተጠሪ ቅርንጫፍ ቢሮ አዲስ አበባ ከተማ ያለ ስለመሆኑ በማረጋገጥ ግንቦት 3 ቀን 2000 ዓ.ም በወጣው ሪፖርተር ጋዜጣ ገጽ 8 የቅጥር ማስታወቂያ ላይ አድራሻ አ.አ መሆኑን የገለጸ ከመሆኑም በላይ በተመሳሳይ የስራ ክርክር በመ/ቁ. 29465 ፣37317 እና 38403 በየካ ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 21206 በቂራ ምድብ ችሎት ጉዳዮች የታዩ መሆኑን በመግለጽ የግዛት ክልል ስልጣን የለም የተባለው ስህተት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡

ይህ ችሎት የግዛት ክልል ስልጣን የለም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ የቃል ክርክር አካሄደዋል፡፡ የተጠሪ የቃል ክርክር አዲስ አበባ ያለው የእቃ ገዥ እና የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንጅ ዋና መ/ቤቱ አዋሳ ነው በማለት ውሳኔው እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመዘገበው ሲሆን እኛም እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አስቀድሞ አመልካች የስራ መሪ ነው በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ጉዳዩ አይታይም ተብሎ ክሱ በብይን ውድቅ ተደርጐ በይግኝ ታይቶ እንደገና እንዲታይ ተወስኖ ሲመለስ የአሁኑ ተጠሪ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን እንደገና ሊያይ የሚችልበት የግዛት ክልል ስልጣን የለውም ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ነው ጉዳዩ እንዲታይ እንዲመለስ የተደረገው በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በይግባኝ እንዲታረምለት አልጠየቀም፡፡ በውሳኔው ተስማምቶ በፍሬ ጉዳይ ላይ ለመሟገት ከመለሰ በኋላ እንደገና የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር የሚያነሳበት የሕግ አግባብ የሌለ ከመሆኑም በላይ ይልቁንም የድርጅቱ ቅ/ጽ/ቤት አ/አበባ ከተማ ለም ሆቴል አካባቢ ኃይሌ ገ/ስላሴ መንገድ እንደሆነ አመልካች በቅሬታው የጠቀሰውን የተጠሪ ጠበቃ በክርክራቸው የእቃ ግዥ እና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የተከራከረ በመሆኑ የግዛት ክልል ስልጣን የለውም በማለት የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 63124 ግንቦት 6 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤቱ የግዛት ክልል ስልጣን አለው ብለናል፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ በሕጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ከሕግና ከማስረጃ አንፃር በማገናዘብ ተገቢውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሰረት ለከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ
4. መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡
5. መ/ቁጥር 19802 በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38145

ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ አያልነሽ ዘገየ- ጠ/ሙሉጌታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ደምሴ- ጠ/ጌታቸው ሞላ ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአመልካችና የተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ ባለሙያ አጣርቶ ለፍ/ቤቱ ውጤቱን የገለጸ ሲሆን ፍ/ቤቱም የቀረበውን ውጤት በአብዛኛው ተቀብሎ በተወሰኑ ጉዳዮች ራሱ መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ፍ/ቤቱ ራሱ መርምሮ ውሣኔ ከሰጠባቸው ነጥቦች ውስጥ አንደኛው የእቁብ ገንዘብን የሚመለከት ነው፡፡ ንብረት አጣሪው በአቶ ታደሰ ተክሌ የሚሰበሰብ እቁብ መኖሩን አረጋግጠው ሁለቱም የእቁብ ገንዘቡን እኩል መካፈል ስላለባቸው ተጠሪ ለአመልካች ብር 247,500(ሁለት መቶ አርባ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብር) እንዲከፍሉ ሲወስኑ በተጠሪ የሚሰበሰበውን እቁብ ግን ፍ/ቤቱ እንዲያጣራው አሣስበዋል፡፡ በዚህ መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አጣርቶ የዚህን ገንዘብ ግማሽ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ ሲወስን በአቶ ታደሰ ተክሌ የሚሰበሰበውን እቁብ በተመለከተ ስለማጽደቁ በውሣኔው ሣይጠቅስ አልፏል፡፡

አመልካችም ለችሎቱ በአቶ ታደሰ ተክሌ ዳኝነት ይሰበሰብ የነበረውን እቁብ በተመለከተ በንብረት አጣሪው የቀረበውን ውሣኔ ፍ/ቤት ሣያጸድቅ ስላለፈው ይታረምልኝ በማለት አመልከተው ፍ/ቤቱም ይህንኑ ማጽደቁን በውሳኔው ሳያሰፍር ያለፈው በዝንጋታ በመሆኑ ይህንንም እቁብ ግራ ቀኙ እንዲካፈሉት የሚለው ዓረፍተ ነገር ቀደም ሲል በሰጠው ውሣኔ ውስጥ እንዲካተት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ በአመልካች የቀረበው ጥያቄ በይግባኝ የሚስተካከል እንጅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት የሚስተካከል አይደለም በማለት የፍ/ቤቱን ትእዛዝ ሽሯል፡፡ በዚህ ላይ አመልካች ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ጠይቀው ይግባኛቸው ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡

ከዚህ በኋላ አመልካች የስር ፍ/ቤት በአቶ ታደሰ ተክሌ ሲሰበሰብ የነበረውን እቁብ አስመልክቶ አጣሪው የሰጠውን ውሣኔ ሣያጸድቅ ማለፉ ስህተት ነው በማለት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይግባኝ የቀረበበት ጉዳይ የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ያለፈ በመሆኑና የይግባኙ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈውም በበቂ ምክንያት ስላልሆነ ይግባኙ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጐታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለዚህ የሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም አመልካች ያቀረቡት ይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ነው ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጐ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በቃል አሰምተዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የንብረት አጣሪው በአቶ ታደሰ ተክሌ ከሚሰበሰበው እቁብ ተጠሪ የወሰዱት 495,000 (አራት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ብር) ግማሽ ለአመልካች እንዲከፈላቸው ወስነዋል፡፡ ፍ/ቤቱ የንብረት አጣሪውን ውሣኔ ሲያጸድቅ ግን ይህን የእቁብ ገንዘብ በተመለከተ የተሰጠውን ውሣኔ ሣያጸድቅ አልፎታል፡፡ አመልካች ይህ የታለፈው ነጥብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲታረምላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ለፍ/ቤቱ ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍ/ቤቱ ይህን ነጥብ ሣያጸድቅ ያለፈው በዝንጋታ መሆኑን በማጤን አጣሪው የሰጡትን ውሣኔ አጽድቋል፡፡ ተጠሪ ግን ይህን ትእዛዝ ተቃውመው ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የአመልካችዋ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚገባው በይግባኝ እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔም በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ፀድቋል፡፡ እንግዲህ ከክርክሩ ሂደት አመልካችዋ ይህን ክርክር ያስነሣውን የእቁብ ገንዘብ በተመለከተ በዳተኝነት ትተውት የተቀመጡ ሣይሆን ለፍ/ቤት ጥያቄ አቅርበው በክርክር ሂደት ላይ ነበሩ፡፡ ሣይፀድቅ የታለፈው የእቁብ ገንዘብ እንዲታረም ተገቢ ነው ባሉበት የሥነ-ሥርአት መንገድ ጥያቄ አቅረበው የነበረ ቢሆንም ጥያቄው የቀረበበት ሰርአት የሥነ-ሥርአት ሕጉን የተከተለ ነው አይደለም በሚል በተነሣ ክርክር የተወሰነ ጊዜ ማለፉን ተገንዝበናል፡፡ የመጨረሻ ፍ/ቤቱም ጥያቄው ሊስተናገድ የሚገባው በይግባኝ ነው በማለት ከወሰነ በኋላ አመልካችዋ ሣይዘገዩ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ በእርግጥ አመልካችዋ ይግባኙን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡበት ወቅት ይግባኝ የተጠየቀበት ውሣኔ ከተሰጠ የ60 ቀናት ጊዜ አልፏል፡፡ አመልካችዋ ያቀረቡት ይግባኝ ጊዜው ያለፈ መሆኑን ፍ/ቤቱ የተረዳው ዋናው ይግባኝ በሚታይበት ጊዜ በመሆኑ አመልካችዋ ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ማቅረቢያ ማስፈቀጃ አላቀረቡም፡፡ ፍ/ቤቱም ጊዜው ማለፉን እንደተረዳ የማስፈቀጃ ማመልከቻ እንዲቀርብ ማድረግ ሲገባው ይህንን ባያደርግም አመልካችዋ ይግባኝ ሣያቀርቡ ጊዜው ያለፈበትን ምክንያት ግን ተመልክቶ በቂ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

አንድ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈበት ምክንያት በቂ መሆኑን ሲረዳ ይግባኙ እንዲቀርብ ሊፈቅድ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 326/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ የቀረበለት ምክንያት በቂ መሆን አለመሆኑን በአግባቡ ሊመረምረው ይገባል፡፡ በእርግጥ በቂ ምክንያት የሚባሉትን ነገሮች ሕጉ ዘርዝሮ ያላስቀመጣቸው በመሆኑ ለመወሰን አስቸጋሪ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የምክንያቱ በቂ መሆን አለመሆን በእያንዳንዱ ጉዳይ ከሚቀርቡ ፍሬ ነገሮች ጋር ተገናዝበው ሊመዘኑ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካችዋ ተጠሪው ከወሰዱት የእቁብ ገንዘብ ግማሹ የሚገባቸው ለመሆኑ በአጣሪው ተወስኖላቸው ይህንን ነጥብ ፍ/ቤቱ ሣያጸድቅ አልፎታል፡፡ ይህ ጉዳይ ሊታረም የሚገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ነው ወይስ በይግባኝ ነው የሚለው ጉዳይ ክርክር እየተደረገበት ስለነበር እንጂ ጊዜው ያለፈው አመልካች መብታቸውን ሣይጠይቁ ዳተኝነት አሣይተው አለመሆኑን በመዝገቡ ከቀረቡት ፍሬ ነገሮች መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈው በበቂ ምክንያት አይደለም በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተጠቀሰውን የሥነ-ሥርአት ሕግ በአግባቡ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 59015 መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አልካች ይግባኝ ሣያቀርቡ ጊዜው ያለፈባቸው በበቂ ምክንያት ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ ተቀብሎ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ የስር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38683

ሰኔ 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ ስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት- ነ/ፈጅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሳህሉ ወ/ማሪያም- ከጠበቃ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ከግንቦት 5 ቀን 1991 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 7 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ ተከሳሽ በከሳሽ ድርጅት በገንዘብ ያዥነት ሲሰሩ በኃላፊነት ከተረከቡት ገንዘብ ላይ ብር 72,710.48 (ሰባሁለት ሺህ ሰባት መቶ አስር ብር ከአርባ ስምንት ሣንቲም) በጉድለት እንደሚፈለግ በኦዲት ምርመራ የተረጋገጠ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ከወለድ ከወጭና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽም ቀርበው በከሳሽ ድርጅት በገንዘብ ያዥነት መስራታቸውን አምነው ነገር ግን በኃላፊነት ሲያንቀሳቅሱት የነበረው ሂሳብ በየወቅቱ ኦዲት እየተደረገ በጉድለት የሚፈለግ ገንዘብ እንዳልነበር ከግንቦት 5 ቀን 1991 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 7 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ በከሳሽ መ/ቤት በገንዘብ ያዥነት በሰሩበት ጊዜ ገንዘብ ስለማጉደላቸው በኦዲት እንዳልተረጋገጠ ገልጸው ክሱ ከኪሳራ ጋር ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ተከሳሽ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ስለማጉደላቸው ከሳሽ በማስረጃነት ባቀረበው የኦዲት ሪፖርት ላይ ያልተረጋገጠ ስለሆነ ክሱ የማስረጃ ድጋፍ የሌለው ነው በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ክሱን ያስረዱልኛል በማለት የቆጠራቸውን የባለሙያ ምስክሮች የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሳይሰማ ውሳኔ መስጠቱ ለሰበር ቀርቦ መመርመር እንዳለበት በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን አቤቱታው ለሰበር ሊቀርብ ይገባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ተጠሪ በኃላፊነት ሲያነቀሳቅሱት የነበረውን ሂሳብ መርምረው ጉድለት መኖሩን ያረጋገጡት ኦዲተሮች ቀርበው የሙያ ምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ አመልካች በማስረጃነት የቆጠራቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃነት የሚጠቅሳቸው ምስክሮች፣ሰነዶች ወይም ሌላ አስረጂዎች እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት ማስረጃው በጭብጥ ተይዞ ከሚፈታው ፍሬ ነገር ጋር አግባብነት(Relevance) ያለው ስለመሆኑና በሕግ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ (Admissible Evidence) ስለመሆኑ ማጣራት እንደሚገባው ከማስረጃ አቀራረብና አቀባበል መርህ አኳያ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የጠቀሳቸው ምስክሮች ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ በኃላፊነት ሲያንቀሳቅሱት የነበረውን ሂሳብ መርምረው ጉድለት መኖሩን በአዲት ያረጋገጡ መሆኑን አመልካች በማስረጃ ዝርዝሩ ላይ ጠቅሷል፡፡ እነዚህ የሙያ ምስክሮች ጉድለት ስለመኖሩ የሚያረጋግጡ ናቸው ከተባለ ተጠሪ የገንዘብ ጉድለት ፈጽመዋል ወይንስ አልፈጸሙም? ተብሎ በጭብጥነት ከሚያዘው ፍሬ ነገር ጋር የተያያዘና አግባብነት ያለው የምስክርነት ቃል እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ በምስክሮቹ የሚሰጥ የሙያ ምስክርነት ቃል በሕግ ተቀባይነት የሌለው (Inadmissible) አይደለም፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ የቆጠራቸው ምስክሮች ቀርበው መሰማታቸው ክርክሩ ከሚመራበት የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111፣249 እና 257 አኳያ እንደዚሁም ከማስረጃ አቀራረብና አቀባበል አኳያ ተገቢነት ያለው ሆኖ ሳለ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እነዚህን ምስክሮች ሳይሰማ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ውሳኔ መስጠቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ጉድለት በይግባኝ ሳያርም መቅረቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22762 በ7/4/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 62605 በ21/8/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች የቆጠራቸውን የሙያ ምስክሮች በመስማት ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38844

ሰኔ 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን- ነገረ ፈጅ ፋሲል በለጠ

ተጠሪ፡- ጋድ ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር- አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 57204 ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሀብሔር ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 33400 ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቹ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለአመልካች አንድ ሺ ቶን አስፋልት በዘጠና ቀን ውስጥ ለማቅረብ የተስማማ መሆኑንና አመልካች በበኩሉ ብር 3,565,000

(ሦስት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሣ አምስት ሺህ) ለመክፈል ተስማምቷል፤ ሆኖም

- አስፋልቱ ከሚመጣበት ግብጽ ሐገር እቃውን በመጫን በስዊዝ ካናል በኩል በወቅቱ በነበረው የአሜሪካና ኢራቅ ጦርነት ምክንያት ከመጋቢት 11 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 25 ቀን 1995 ሊተላለፉ ባለመቻላቸው፣
- የስዊዝ ቦይ ተከፍቶ እቃውን የጫነው መርከብ ሰኔ 19 ቀን 1995 ዓ.ም ጅቡቲ ሲደርስ የምግብ እርዳታ የጫኑ መርከቦች ወደቡን በማጨናነቃቸው አስፓልቱ ሣይራገፍ ሊዘገይ ችሏል፤

ከሳሽ (ተጠሪ) አስፓልቱን በወቅቱ ያላደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ለተከሳሽ (አመልካች) ያሣወቀና ማስረጃ ያቀረበ ቢሆንም ተከሳሽ (አመልካች) አላግባብ አስፓልቱ ለዘገየበት በሚል ምክንያት ብር 356,000(ሦስት መቶ ሃምሣ ስድስት ሺ ብር) ከዋጋው ቀንሶ ያስቀረ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ ብር 420,670 (አራት መቶ ሐያ ሺ ስድስት መቶ ሰባ ብር) እንዲከፍል ይወስንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በበኩሉ በውላቸው መሰረት ከሳሽ(ተጠሪ) ባለማቅረቡ በውሉ መሰረት በቅጣት መልክ መቀነስ ያለበትን ገንዘብ የቀነሰ መሆኑን፤ በአሜሪካና ኢራቅ ጦርነት አስፓልቱን የጫነችው መርከብ መተላለፊያ አጥታ መቆሟን የሚያሣይ ማስረጃ ተጠሪ ያላቀረበ መሆኑን፤ በጅቡቲ ወደብም አስፓልቱን በማራገፍ ሒደት የገጠመ ችግር የነበረ ስለመሆኑ ከወደቡ አስተዳደር ያቀረበው ማስረጃ የሌለ በመሆኑና ተጠሪ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር የገጠመው መሆኑን በውላችን አንቀጽ 10 መሰረት ለተከሳሽ (አመልካች) ያላሳወቀ በመሆኑ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሳያጋጥመው ከሳሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(ተጠሪ) እቃውን በማዘግየቱ በውሉ መሰረት በቅጣት መልክ ያስቀረነውን ክፍያ ለከሳሽ (ተጠሪ) የምንመልስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የከሳሽንና(ተጠሪን) ተከሳሽን (አመልካችን) ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ተጠሪ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር አስፓልቱን ያላቀረበ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሚያዚያ 25 ቀን 1995 ዓ.ም ስለስዊዝ ቦይ እና የአሜሪካና የኢራቅ ጦርነት ይዞት የወጣውን ዜና እና ዩንቨርሳል የተባለ የእቃ አስተላለፊ ድርጅት አስፋልቱን የጫነው መርከብ በጅቡቲ ወደብ አስራ ስምንት ቀን ቆሟል በማለት የፃፈውን ደብዳቤ ነው፤ እነዚህ ማስረጃዎች አስፓልቱን የጫነው መርከብ በስዊዝ ቦይ መተላለፊያ በማጣቱም ሆነ የጅቡቲ ወደብ በመጨናነቁ የዘገየ መሆኑን የሚያስረዱ አይደሉም፤ ስለዚህ ከሳሽ (ተጠሪ) አስፓልቱን በውሉ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ያላደረሱት ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት መሆኑን ያላስረዱ ስለሆነ ተከሳሽ (አመልካች) በቅጣት መልክ ቀንሶ ያስቀረውን ገንዘብ ለከሳሽ (ተጠሪ) የሚከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን ይግባኝና የአመልካችን መልስ ከተቀበለ በኋላ ቅሬታውንና መልሱን እንደመረመርነው ምላሽ ማግኘት ያለበት ጭብጥ ይግባኝ ባይ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት አለ ያለው ነገር መኖሩ በማስረጃ ተረጋግጧል ወይስ አልተረጋገጠም? ከአቅም በላይ የተባሉት ምክንያቶች በሕጉ ይካተታሉ ወይስ አይካተቱም? በመሆኑም እነዚህን ምክንያቶችን በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ሀ/ እና (መ) የሚሸፈኑ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ገንዘቡ ለይግባኝ ባይ ሊከፈል አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብ አይደለም" በማለት አመልካች ብር 356,500 (ሦስት መቶ ሐምሣ ስድስት ሺ አምስት መቶ ብር) ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ ተጠሪ አስፓልቱን ማቅረብ ከነበረበት በሰሚኒያ ሶስት ቀን ዘግይቶ አቅርቧል፤ ተጠሪ መዘግየቱ የተፈጠረው ከአቅም በላይ መሆኑን የሚያስረዳ የሕጉን መስፈርት የሚያሟላ ምክንያትና ማስረጃ አላቀረበም፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማስረጃውን መርምሮ የሕግ ድንጋጌዎችን አገናዝቦ የሰጠውን ውሣኔ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ማስረጃውን ሣይመረምርና ሣይመዝን ከተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ ጋር ያላቸውን ግኑኝነት ሣያገናዝብ በጭብጥነት የያዛቸውን ጭብጦች ሣያይ የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793(ሀ) እና (መ)"ን" በመጥቀስ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፤ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ማጽናቱ ተገቢ ባለመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በአሜሪካና በኢራቅ ጦርነት ምክንያት በስዊዝ ቦይ መርከቦች እንዳይተላለፉ በመከልከሉና በጅቡቲ ወደብ በነበረው መጨናነቅ እቃውን በወቅቱ ለአመልካች ያላስረከብኩ መሆኑንና ይህም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መሆኑን በማገናዘብ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ የአመልካች የሰበር አቤቱታ እንዲሰረዝልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አስፓልቱን ሣያቀርብ የቀረው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት የሰጠው ውሣኔና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንን ውሣኔ በማጽናት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መፈታት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በውሉ መሰረት ለመፈጸም የገደበው ከአቅም በላይ የሆነ ነገር አላጋጠመውም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በአሜሪካን እና ኢራቅ ጦርነት ምክንያት የስዊዝ መተላለፊያ ቦይ የተዘጋ መሆኑንና ለዚህ ጊዜም አስፓልቱን የጫነችው መርከብ ታግዳ የነበረች ስለመሆኗ በቂ ማስረጃ አልቀረበም፤ በማስረጃነት የቀረበው በጋዜጣ ላይ ታትሞ የወጣ ዜና ይህንን አያስረዳም፤ አስፓልቱን የጫነችው መርከብ የጅቡቲ ወደብ በመጨናነቁ ምክንያት ለማራገፍ ባለመቻሏ ነው ለሚለው ፍሬ ጉዳይ ከጅቡቲ ወደብ አስተዳደር የቀረበ ማስረጃ የለም፤ ከግል እቃ አስተላላፊ ድርጅት የተፃፈው ደብዳቤ ታአማኒነትና ክብደት የለውም በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በይግባኝ መወሰን ያለባቸውን ሁለት ጭብጦች ከያዘ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረቡትን ማስረጃዎች ተአማኒነትና ክብደት ከፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793 ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የሰጠውን ምክንያትና ማብራሪያ የማይቀበልበትን ምክንያት ሳይገልጽ ማስረጃዎቹን ሳይመዝንና ከሕጉ ጋር ያላቸውን ተዛማጅነት ሣያብራራ በአንድ መስመር ተጠሪ እቃውን ያላቀረበው በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793(ሀ) እና(መ) መሰረት ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ስለ ውሣኔ አሰጣጥ በፍትሀብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 182 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን የሚጥስ፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በግልጽ በተቀመጠ ምክንያት ሣይሆን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን የመሻር ስልጣን ስላለው ብቻ የሻረው መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ያጋጠመው መሆኑን ለማስረዳት በወቅቱ በአሜሪካና በኢራቅ መካከል ጦርነት መኖሩንና በዚህ ምክንያት በስዊዝ ቦይ መተላለፊያ ችግር የነበረ መሆኑን በጋዜጣ የተዘገበ ዜና ማቅረቡ ብቻውን በቂ አይደለም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉም ከፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 ንኡስ አንቀጽ 1 ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ ተጠሪ በዚያን ወቅት አስፓልቱ በመርከብ ተጭኖ የነበረ መሆኑን፣ አስፓልቱን የጫነችው መርከብ ጉዞዋን ጀምራ ስዊዝ መተላለፊያ ቦይ ስትደርስ በጦርነቱ ምክንያት መተላለፊያ በመዘጋቱ ስንት ቀን እንደቆመች እና በዚህ ምክንያት በውሉ የተገለፀው የጊዜ ገደብ ያለፈ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተጠሪ እነዚህን ዝርዝር ሁኔታዎች የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ የተፈጠረው ጠቅላላ ሁኔታ እሳቸው ውሉን ለመፈጸም ባደረጉት ጥረት ላይ የፈጠረውን እርግጠኛ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ባላስረዱበት ሁኔታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ስለ ጦርነቱ ሁኔታ የተዘገበ ዜና ለስር ፍርድ ቤት በማቅረብ ውሉን ያልፈጸምኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን አስረድቻለሁ በማለት ያቀረቡት ክርክርና የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ክርክር በመቀበል የሰጡት ውሣኔ የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 ንኡስ አንቀጽ (1)"ን" መሰረታዊ መርህ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ በሁለተኛ ምክንያትነት ያነሱት የጅቡቲ ወደብ መጨናነቅ ስለ ወደቡ አስተዳደርና ወደቡ መርከቦችን በማስተናገድ በኩል ስለገጠመው ችግር ማስረጃ የመስጠት ስልጣንና ሐላፊነት ካለው የጅቡቲ ወደብ አስተዳደር የተሰጠ አይደለም፡፡ ተጠሪ ወደቡ በመጨናነቁ አስፓልቱን የጫነችው መርከብ ቆማ የነበረ መሆኑን ዩኒቨርሳል የተባለ እቃ አስተላላፊ ድርጅት የፃፈውን ደብዳቤ በማስረጃነት ያቀረበ ቢሆንም ይህ ማስረጃ ተጠሪ በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ አስፓልቱን ለአመልካች ሣያቀርብ የቀረ መሆኑን የማስረዳት ብቃትና ተአማኒነት የሌለው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ከበቂ ምክንያት ጋር አስቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶች ይህ ማስረጃ በምን ምክንያት ተአማኒነት ሊሰጠው እንደማይገባና ተጠሪ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ያጋጠመው ስለመሆኑ በቂ አስረጂ አድርገው እንደወሰዱት አልገለፁም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ተጠሪ ውሉን በወቅቱ ያልፈጸመው በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 እና በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793 የተደነገጉት ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ያጋጠመው መሆኑን ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክሙን በአግባቡ ያልተወጣ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎቹን ከሕጉ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ የወሰነ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶች የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽረናል ከሚሉ በስተቀር ተጠሪ እርግጠኛ በሆነ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ምክንያት ውሉን ሣይፈጽም የቀረ ስለመሆኑ የሰጡት ምክንያትም ሆነ ማብራሪያ የለም፡፡

በእኛም በኩል ተጠሪ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ስላጋጠመው ውሉን በጊዜው ሣይፈጽም የቀረ መሆኑን ለመደምደም የሚያስችሉ በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 እና 1793 ድንጋጌዎች የሚሸፈኑ ሁኔታዎች በመዝገቡ በተደረገው ክርክር የሌሉ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶች የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአግባቡ ሣይመረምሩ እና ለውሣኔአቸው በቂ ምክንያት ሣይሰጡ ተጠሪ እቃውን በወቅቱ ያላቀረበው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሣኔ መሻራቸው የፍትሀብሔር ስነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 182 ንኡስ አንቀጽ 1 የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 እና የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ እቃውን በውሉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ያላቀረበው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም ብለናል፡፡
3. አመልካች ተጠሪ በውሉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አስፓልቱን ባለማቅረቡ ለተጠሪ ከሚከፍለው ክፍያ በመቀጫ መልክ ቀንሶ ያስቀረውን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ የለበትም፡፡ ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 36979

ሐምሌ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡-ቤዛ አማካሪ መሀንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ ግርማ ኃ/መስቀል ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሚስተር ሸሬሃሪ ብራማቫሪ ጐፓል - ጠበቃ አቶ ሀይልዬ ሣህለ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57672 የካቲት 3 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ ተከሳሽ(የአሁን አመልካች) አላግባብ ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ (ተጠሪ) የድርጅቱ ክፍለሀገራዊ ሥራ አስኪያጅ በመሆናቸው የሥራ መሪ ናቸው፤ ጉዳያቸው በአሠሪና ሠራተኛ ችሎት መታየት የለበትም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን ዘግቶታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ የያዘውን የሥራ መደብ ስያሜ በመመልከት ብቻ የሥራ መሪ ነው ማለት ስለማይቻ ስልጣን የለኝም ያልከው አላግባብ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት አከራክረህ ወሰን በማለት ጉዳዩን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በመሠረቱ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማከራከር ስልጣን የለኝም በማለት ያዘጋው በአግባቡ ነው፡፡ ከተጠሪ ጋር የተደረገው የሥራ ውል እና ከኢትዮጵያ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር በአመልካች ተጠያቂነት ለተጠሪ የተሰጣቸው የሥራ ፈቃድ ማስረጃ ተጠሪ ሪጅናል ማኔጀር እንደሆኑ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ ይህንን ማስረጃ ፍርድ ቤቱ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 145 መሠረት አስቀርቦ እንዲመለከትልን ጠይቀናል፡፡ ፍርድ ቤቱ የጠየቅነውን ማስረጃ አስቀርቦ ሣይመለከት ተጠሪ ሠራተኛ ናቸው ጉዳያቸው በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ይታያል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የሚገባ ስለመሆኑ በውሉ አንቀፅ 7 እና አንቀጽ 12 የተመለከቱትን ሀይለ ቃሎች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች የተጠሪን የሥራ ዝርዝርና የድርጅቱን መዋቅር በማቅረብ ተጠሪ ሥራ መሪ መሆናቸውን አላስረዳም፡፡ ይህ ከሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

"ክፍለሀገራዊ ሥራ አስኪያጅ" የሚለውን ስያሜ በማየት ብቻ ሥራ መሪ ናቸው ሊባል ስለማይገባ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ስለዚህ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ በማለት በፅሑፍ መልስ ሰጠተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቀርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካችና ተጠሪ በፅሑፍ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪው የሥራ መሪ መሆኑን በመግለፅ ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በሌላ በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡ አመልካች ተጠሪን እንድቀጥር የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ያቀረብኩት አቤቱታ መነሻ ለተጠሪ የውጭ አገር ዜጋ በመሆናቸው ከሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የተሰጣቸው የሥራ ፈቃድ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 145 መሠረት ፍርድ ቤቱ አስቀርቦ እንዳይላቸው ጠይቀው ፍርድ ቤቱ ይህንን ማስረጃ ሣያስቀርብ ተጠሪ የሥራ መሪ አይደሉም በማለት ውሣኔ እንደሰጠባቸው በመግለፅ በሰበር ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ መሆናቸውን የሥራ ፈቃድም ያገኙት በዚሁ የሥራ ሀላፊነት ለመሠማራት መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት እንዲቀርብ የጠየቁት ማስረጃ የሥር ፍርድ ቤት ያላስቀረበው በመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 345 ንዑስ አንቀፅ 1(ሀ) መሠረት ማስረጃውን በማስቀረብ ውሣኔ መስጠት ነበረበት፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች እንዲቀርብላቸው የጠየቁት ማስረጃ ሣያስቀርብ መወሰኑ ከላይ የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌ የሚተላለፍ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲቀርብላቸው የጠየቁትን ማስረጃ በማስቀረብና ጉዳዩን በማጣራት ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41544

ሐምሌ 08 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሠላም የሕዝብ ማመላለሻ አ/ማ - ጠ/ረዳይ ባራኪ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ - አልቀረቡም፡፡

ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው ተጠሪ በመልካችና በሌላ ግለሠብ ላይ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የመሠረተው ክስ ነው፡፡ በክሱም ተጠሪ የመድን ሽፋን የሰጠውን መኪና ንብረትነቱ የአመልካች የሆነ መኪና በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ሲሽከረከር ገጭቶ ጉዳት በማድረሱ ጉዳቱን ለማስጠገን ያወጣውን ወጪ ተከሣሾች እንዲተኩለት ጠይቋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ጉዳት አደረሰ የተባለውን መኪና በጨረታ አቶ ተክሉ አስፋው ለተባሉ ግለሰብ ስለተሰጠ ተጠያቂነት የለብኝም መኪናውን የገዙት ግለሰብ በክሱ ውስጥ እንዲገቡ ተደርጎ እኔ ልሰናበት በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍ/ቤት ግን አመልካች መኪናው ለሌላ ግለሰብ ሽጥኩ ይበሉ እንጂ የባለቤትነት ስሙ በገገርው ያልተዛወረና መኪናው አሁንም በአመልካች ስም ስለሚታወቅ ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት በማለት በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፈል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም መኪናውን ገዝተዋል የተባሉት ግለሰብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ሣይቀበል ማለፉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ቀርበው የቃል ክርክሩ ተሠምቷል፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት መኪናውን ገዙ የተባሉት ግለሰብ ወደ ክርክሩ ሊገቡ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ከሚመለከተው ሕግ አኳያ መርምሯል፡፡

በተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት አደረሠ የተባለው መኪና የአመልካች የነበረ ሲሆን አመልካች መኪናዋን ለሌላ 3ኛ ወገን ቢሸጡም የባለቤትነት ስሙ በገገርው ስም አልተዛወረም፡፡ የመኪና ባለቤትነት የሚተላለፈው እንደሌለ ማንኛውም ተንቀሣቃሽ ንብረት ንብረቱን ገዝቶ ወይም በሌላ መንገድ አግኝቶ በእጅ በማድረግ አይደለም፡፡ መኪና ላይ ተንቀሣቃሽ ንብረት በመሆኑ ባለቤትነት የሚተላለፍበት መንገድ በልዩ በሕግ ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት የንብረቱ ባለሃብትነት የሚታለፈው የባለቤትንት ስሙ በገገርው ስም ሲዛወር ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የሰበር ችሎት በመ/ቁ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች መኪናውን ለሌላ ሰው ቢሸጡም የመኪናው የባለቤትነት ስም በአመልካቹ በመሆኑ በባሌቤትነት የሚታወቀው አመልካች ነው፡፡ የመኪና ባለቤት ደግሞ መኪናው በደረሰው ጉዳት ያለጥፋት ኃላፊ መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2081/1/ ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል ግን አመልካች መኪናውን ለ3ኛ ወገን ሸጦ ገገርው መኪናውን መረከቡንና ጉዳቱ በደረሰ ጊዜም መኪናዋ በገገርው ይዞታ ሥር ነበር በማለት ተከራክሯል፡፡ የመኪናው ባለቤት ባይሆንም እንኳን መኪናውን ለግል ጥቅሙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲገለገልበትና ሲጠቀምበት የነበው ሰው መኪናው በይዞታው ሥር በነበረበት ጊዜ ለደረሰው ጉዳት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2082/1/ መሠረት ኃላፊ ነው፡፡ በአጠቃላይ የመኪናው ባለቤትም ሆነ ጉዳቱ በደረሰ ጊዜ መኪናውን ሲጠቀምበት የነበረ ሰው ሁለቱም ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የመኪናው ባለቤትም ያለው መብት ተጎጂውን ክሳሠ በኋላ በአደጋው ጊዜ መኪናውን ይዞ ሲገለገልበት የነበረውን ሰው የካሰውን የገንዘብ መጠን እንዲተካለት መጠየቅ ነው /የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2983/1/ ስለሆነም አመልካች መኪናውን ሸጦ ለሌላ ሰው ያስረከበ ቢሆንም የባለቤትነት ስሙ በገገርው ስም ባለመዛወሩ በሕግ የመኪናው ባለቤት ሆኖ የሚወሰደው እሱ ነው፡፡ ባለቤት በመሆኑም ለጉዳቱ ኃላፊ ነው፡፡

የአመልካች ኃላፊነት እንዳለ ቢሆንም ግን የመጨረሻው የመካስ ኃላፊነት የሚወድቀው መኪናውን ይዞ ሲገለገልበት የነበረው ሰው ላይ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደገለጽነው የመኪናው ባለቤት ተጎጂውን ክሳሠ በኋላ ይህንን ካሣ የሚተካው መኪናውን ሲጠቀምበት የነበረው ሰው ነው፡፡ ተከሣሽ የሆነ ሰውም በክሱ ውስጥ የሌለ ሦስተኛ ወገን ከክሱ ጋር ድርሻ ካሣውን መክፈል አለበት በሚል ይኸው ሰው ወደ ክሱ እንዲገባለት መጠየቅ የሚችል መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ በክሱ እንዲገባ የሚጠየቀው ሰው ካሣውን የሚከፍልበት ምክንያትና የድርሻውም ልክ መገለጽ እንዳለበት ይኸው የሥነ-ሥርዓት ሕግ ያስገድዳል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ከተሟሉ ግን ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ የሚያደርግበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ሦስተኛ ወገኖች ወደ ክሱ እንዲገቡ የሚዳረጉት በአንድ ጉዳይ ሊነሱ የሚችሉትን የመብት ጥያቄዎች በሙሉ በአንድ ክስ መወሰን እንዲችልና በተመሣሣይ ጉዳይ ሊቀርቡ የሚችሉ የተነጣጠሉ ክሶችን ለማስቀረት ነው፡፡ በመሆኑም ተከሣሹ ጣልቃ እንዲገባ በሚጠይቀው ሰው ላይ የሚያነሣውን ጥያቄ ሌላ የተነጠለ ክስ ማቅረብ ሣያስፈልገው በተጀመረው ክስ ሊወሰን ይችላል፡፡ ስለሆነም ተከሣሹ ለክሱ ኃላፊነት ካለበት ጣልቃ ገቡ በቀጥታ ለከሣሽ ሊከፈል ሊወሰን ይችላል ከዚህም በተጨማሪ ጣልቃ ገቡ በክሱ ውስጥ ከገባ በኋላ በክሱ ውስጥ እንዳለ የሚቆጠር በመሆኑ /የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 43/2// ለቀረበው ክስ ያለውን መከላከያ የማቅረብ እድል ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 43 አላማ ከአንድ ግንኙነት የሚመነጩ ጥያቄዎች በሙሉ ተጠቃለው በአንድ ክስ እንዲያልቁ እና የተነጣጠለ ክስ ማስቀረት በመሆኑ ፍ/ቤቶች በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱት መስፈርቶች እስከተሟሉ ድረስ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ የሚችሉበት የሕግ መሠረት የለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ጉዳት ያደረሰው መኪና ጉዳቱን ባደረሰበት ጊዜ ጣልቃ እንዲገቡ በተጠየቁት ግለሰብ ይዞታ ሥር በመሆኑ ግለሰቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2082/1/ መሠረት ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉ ስለሆነና የደረሰውን ጉዳት በሙሉም የመካስ ግዴታ ሊወድቅባቸው የሚችል በመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2083/1/ ሥር መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት ወደ ክርክሩ ጣልቃ ሊገቡ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ጣልቃ እንዲገቡ የተጠየቁት ግለሰብ ያለባቸውን ኃላፊነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት ጣልቃ ሣያስገባ መወሰኑ የሥነ ሥርዓቱን ድንጋጌ ያልተከተለና የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 56353 መጋቢት 5/2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 36956 ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. አደጋው በደረሰ ጊዜ አደጋውን ያደረሰው መኪና ሲጠቀሙበት የነበሩት ግለሰብ በክሱ ውስጥ ጣልቃ ገብተው ተከራክረው ተገቢው ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት ጉዳዩን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሥሪና ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35197

ጥቅምት 13 ቀን 2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ኤፍሬም ንዋየማሪያም - ጠበቃ ቴዎድሮስ ተስፋዬ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ ከየካቲት 29 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በአመልካች ድርጅት ተቀጣሪ ሆነው ሲሠሩ ቆይተው ስራውን በገዛ ፈቃዳቸው ሲለቁ ፕሮቪደንት ፈንድን ጨምሮ የሚገባቸውን ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን አመልካች የከፈላቸው ቢሆንም የስራ ስንብት ክፍያ ያልከፈላቸው መሆኑን ገልፀው የስራ ስንብት ክፍያ ብር 14,994.18/አስራ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ብር ከአስራ ስምንት ሣንቲም/ እና ይኸው ክፍያ ለዘገየበት ደግሞ የሦስት ወር ደመወዝ ብር 9,879.00 /ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ሠባ ዘጠኝ ብር/ በድምሩ ብር 24,873.18 / ሃያ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሦስት ብር ከአስራ ስምንት ሣንቲም/ አመልካቹ እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ለተጠሪ የሚገባውን ጥቅማ ጥቅም መክፈሉን፣ የስራ ስንብት ክፍያ ደግሞ ፕሮቪደንት ፈንድ ወይም ጡረታ ላለው ሠራተኛ እንደማይከፈለው በአዋጅ ቁጥር 494/98 መደንገጉንና በዚህም ምክንያት ክፍያ ሊጠየቅ እንደማይገባ፣ የታመነ ክፍያም በወቅቱ የከፈለ በመሆኑ ክፍያ ለዘገየበት ተብሎ የሚቀጣበት የሕግ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ የተከፈላቸው መሆኑን ማመናቸውን በመግለጽና አዋጅ ቁጥር 494/98 ደግሞ አንድ ሰው ሁለት ጊዜ እንዲከፈለው የሚፈቀድ አለመሆኑን በምክንያትነት በመውሰድ ተጠሪ የስንብት ክፍያ ጥያቄ አይገባቸውም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ባለመስማማትም ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍ/ቤቱ ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥር 19 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ያለባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሯል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የፕሮቪደንት ፈንድ የተከፈለው ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈለው የማይገባ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 494/1998 ተደንግጎ እያለ ከአዋጁ መንፈስ ውጪ መተርጎሙ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመመርመር ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ የተከፈላቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪን ያስቀርባል ብሎ ተጠሪ ሚያዝያ 02 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ የመልሣቸው ይዘትም በአጭሩ፡- የአመልካች የሠበር አቤቱታ የክርክር ነጥቦች ከሕጉ ዓላማና መንፈስ ውጪ መሆናቸውን በጉዳዩ ላይ የተሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍ/ቤቱ ትርጓሜ ግን ተገቢነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 06 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሠበር አቤቱታው የቀረበበትን ውሣኔ፣ የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ በገዛ ፈቃዳቸው ስራውን መልቀቃቸውንና የፕሮቪደንት ፈንድም በወቅቱ ተከፍሏቸው የተሰናበቱ መሆኑን በማመን የሚከራከሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ቢረጋገጥም የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት በሕግ የተጠበቀ መሆኑን ተጠሪ አጥብቀው የሚከራከሩ ሲሆን አመልካች የተጠሪ ጥያቄ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

እንግዲህ የግራ ቀኙን ክርክር እልባት ለመስጠት አግባብነት ያለውን የሕግ ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ መመልከትን የግድ ይላል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 494/1998 ዓ.ም ሲሆን ይህ አዋጅ ከአሻሻላቸው የአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች አንዱ ስለስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት አንዱ ነው፡፡ የማሻሻያ አዋጁ በዚህ ረገድ ያስቀመጠው ድንጋጌ ሙሉ ይዘቱ በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው፡፡ ይኸውም

"የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሠራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት <u>የሌለው</u> ሲሆንና በጡረታ ሕግ የተቀመጠው መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ላይ ደርሶ ከስራ ሲገለል ከአሠሪው የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት አለው፡፡" /አንቀጽ 2/ሰ/ ይመለከታል/ የሚል ሲሆን የድንጋጌው የእንግሊዝኛ ትርጉሙም፡-

> **"A worker who had completed his probation shall have the right to get severance pay from the employer where <u>he has</u> no entitlement to a provident fund <u>or</u> pension right and his contact of employment is terminated up on attainment of retirement age stipulated in the pension law"** በሚል ይደነግጋል፡፡

ከድንጋጌው የአማርኛና የእንግሊዝኛ ትርጉም በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ያለው ሠራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ የስራ ስንብት ክፍያ ከአሠሪው የማግኘት መብት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የፕሮቪደንት ፈንድ እና የስራ ስንብት ክፍያዎች በተመሣሣይ ጊዜ ከአንድ ምንጭ የማግኘት መብት ላይ በሕጉ ክልከላ ተደርጓል፡፡

እንደሚታወቀው የስራ ስንብት ክፍያ ዓይነተኛ ዓላማው በስራ ላይ የቆየ ሠራተኛ አዲስ ስራ ፍለጋ ላይ እያለ ሊደርስበት የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመቀነስ ነው፡፡ የፕሮቪደንት ፈንድ ዓላማም ከዚሁ የተለየ አይደለም፡፡ አላማቸው አንድ ዓይነት ከሆነ ሁለቱም የክፍያ ዓይነቶች በተመሣሣይ ጊዜ ከአንድ ምንጭ እንዲከፈሉ ማድረግ አሠሪን ሁለት ጊዜ እንደመቅጣት ከሚቆጠር በስተቀር ፍትሐዊነት አይኖረውም፡፡ በመሆኑም ሕግ አውጪው የፕሮቪንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ከአሠሪው የስራ ስንብት ክፍያ የመጠየቅ መብቱን የነፈገው ከላይ የተገለፀውን አሠሪን ሁለት ጊዜ እንዳይከፍል ለመጠበቅ ነው ተብሎ ከሚታሰብ ውጪ ሌላ ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡

ሊጠቃለልም ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሆነው ክፍያም የተፈፀመላቸው መሆኑን እያመኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ /ማሻሻያ/ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/ሰ/ ሥር በተመለከተው አኳኋን በሕጉ የከለከሉትን የመብት ጥያቄ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡

በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57691 ታኅሣሥ 21 ቀን 2000 ዓ.ም ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል ሲል የሰጠው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 494/1998 ዓ.ም አንቀጽ 2/ሰ/ ስር በተደነገገው መሠረት የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ያለው ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የለውም ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቁራ ምድብ 2ኛ የስራ ክርክር ችሎት በመ/ቁ. 26971 ሠኔ 20 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35621

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሰንሻይን ኮንስትራክሽን - አልቀረበም

መልስ ሰጭ፡- 1. አቶ ፍቃዱ ገቢሣ - አልቀረቡም

2. አቶ ታዬ ዋሚ - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የታች ተከሣሽ ሲሆን የአሁን መ/ሰጭ የታች ከሣሾች ነበሩ፡፡ መ/ሰጭ በታች ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት በመቀጠር በአናዊነት ሙያ ሲያገለግሉ ቆይተው ሌላ ሣይት (ቦታ) ሥራ እያለው ሥራው አልቋል በማለት ያለ ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሥራ ውላችንን አቋርጦብናል ስለዚህ የአገልግሎት ክፍያ የማስጠንቀቂያ የሁለት ወር የዘገየበት የስንብት የስድስት (6) ወር ክፍያ እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሣሽ (የአሁን አመልካች) ጥቅምት 27 ቀን 1999 ዓ.ም በጽሁፍ ባቀረበው መልስ ከሣሽ (መልስ ሰጭ) ደመወዝ የሚከፈላቸው በቀን ታስቦ እንደሆነና ከአመልካች ድርጅት ጋር የፈፀሙት ጊዜያዊነት ያለው የሥራ ውል የተመደቡበት የአናዊነት ሥራ በሚኖርበት ጊዜ ብቻ የሚከፈላቸው መሆኑን ገልጾ የስራ ውሉ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24(1) መሰረት በሕጋዊ መንገድ እንደተቋረጠ በመግለጽ ተከራክሮ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የመልስ ሰጭ የሥራ ውል መቋረጡ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ጭብጥ ይዞ መዝገቡን መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1) (ሠ) መሰረት ሥራው ምንም እንኳ የአሠሪው ቋሚ ሥራ ቢሆንም አልፎ አልፎ የአናዊነት ሥራው ሲኖር የሚሰራ መሆኑን ተረድቻለሁ በማለት አመልካች መልስ ሰጭን ማሰናበቱ በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 10(1)(ሀ) መሰረት በአግባቡ ነው ሲል ወስኗል፡፡

መልስ ሰጭም በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የታች ፍ/ቤት ማስረጃ ሣያጣራ ወሰነብን በማለት ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታቸውን አቅርቧል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤትም በቀረበለት አቤቱታ መሰረት የአሁን አመልካች መልስ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ ይግባኝ ባይ (የአሁን መልስ ሰጭ) የተቀጠሩት ለየትኛው ፕሮጀክት ነው? ፕሮጀክት በመጠናቀቁ ነው ወይስ አይደለም የተሰናበቱት? የሚለውን ጭብጥ መሥርቶ ከመረመረ በኋላ በቅጥር ውል ላይ "ለምን ስራ፣ እስከመቼ" የሚለውን የሚያስረዳ ባለመሆኑ የአሁን መልስ ሰጭ (የታች ከሳሽ) የተቀጠሩት በአዋጁ አንቀጽ (10) ስር በተደነገጉት መሰረት ነው ተብሎ የሚወሰድበት ምክንያት የለም በማለት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በመሻር ስንብቱ ያለ አግባብ ነው በማለት ለአሁን መልስ ሰጭ የ8 ወር ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈላቸውና ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን የሰበር አቤቱታም የቀረበው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻሩ ቅር ተሰኝቶ ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የጉዳዩን አመጣጥ ካጠና በኋላ የሥር ፍ/ቤት ማስረጃ መስማት እየቻለ መልስ ሰጭ የተቀጠረበት ሥራ መጠናቀቁ እየተገለፀ ወደ ሥራ ይመለሱ መባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩን አስቀርቦታል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ጭብጦች በመያዝ ግራ ቀኙ በጉዳዩ መልስ እና የመልስ መልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ አከራክሯል፡፡

በታች የተሰጡትን ውሳኔዎች ከህጉ በማገናዘብ እንዳየነው መልስ ሰጭ "በፊንጫ ለምለም" ፕሮጀክት ውስጥ በአናፂነት ሥራ ሲሰሩ እንደቆዩ በመግለጽ ሥራ በሌላ ሣይት (ቦታ) እያለ ሥራ አልቋል በመባል መሰናበታቸው ከሕግ ውጭ ነው ሲሉ ባቀረቡት ክስ መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አከራክሮ ስንብቱ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1) (ሀ) መሰረት ሕጋዊ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የመልስ ሰጭ የቅጥር ሁኔታ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሠ) ከተዘረዘሩት ውጭ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ አይደለም በማለት የተጠየቀውን ክፍያ እንዲከፍላቸውና ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ በመወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት የታች ውሳኔን ሽሮታል፡፡

በመሰረቱ ከላይ ከተነሱት ክርክሮች መገንዘብ እንደተቻለው መልስ ሰጭ በአመልካች ድርጅት ለምን ስራ እንደተቀጠሩ በሚለው ነጥብ ቀድሞውንም አልተከራከሩም (አልተካካዱም) የአናፂነት ሥራ ደግሞ በግንባታ ሥራ ውስጥ ወቅቱን ጠብቆ የሚሰራ እና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የተጀመረው ግንባታ እንደሚጠናቀቅ ግልጽ ሆኖ ሳለ ለምን ስራ እና እስከመቼ ይሰራሉ? የሚለውን ነጥብ ማየቱ በተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡ መልስ ሰጭ ቢሆኑም በክሳቸው ውስጥ ድርጅቱ ሌላ ቦታ(ሣይት) እንዳለው በመግለጽ ሥራው አላለቀም በማለት ይከራከራሉ፡፡

በመሰረቱ በሌላ ቦታ ተጨማሪ (ተመሣሣይ) ሥራ መኖሩ የተባለውን የፕሮጀክት ሥራ አላለቀም የሚያስብል አይሆንም፡፡ ድርጅቱም የግድ ከአንድ ፕሮጀክት ወደ ሌላው ፕሮጀክት ሰራተኞችን ይዞ እንዲዞር የሚያስገድደው የሕግ ነጥብ አይኖርም፤ ምክንያቱም ድርጅቱ የራሱ የሆነ የአሰራር ስርአት ይኖረዋል ተብሎ ስለሚገመት፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የሥራውን መጠናቀቅና መኖር በድጋሚ በማስረጃ ማጣራት እየተቻለ ይህ ሣይደረግ በከፍተኛው ፍ/ቤት ስንብቱ ያለ አግባብ ነው መባሉና መልስ ሰጭ የጠየቁት ክፍያ ተከፍሎአቸው ወደ ስራቸው ይመለሱ ተብሎ መወሰኑ የአዋጁን አንቀጽ 10(1) (ሠ)"ን" ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23063 በሰኔ 6 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ ፀንቷል ይፃፍ፡፡
2. በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57553 በታህሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ስንብቱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 36692

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብድልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት

ነገረፈጅ ፋሲካ በለጠ - ቀረበ

ተጠሪ፡- ተስፋዬ መኮንን - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የሚታይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን፣ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ከሐምሌ 1 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ለድርጅቱ ሠራተኞች በሙሉ የአንድ እርከን የደመወዝ ጭማሪ ተደርጎአል፡፡ እኔም የድርጅቱ ሠራተኛ በመሆኔ ጭማሪው ሊሰጠኝ ሲገባ አለአግባብ ተከልክያለሁ፡፡ ስለዚህም ጭማሪ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ ሦስት አራተኛውን ጊዜ በስራ ላይ ስላልነበረ ጭማሪውን ሊያገኝ አይችልም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር የመረመረ ሲሆን፣ በመጨረሻም የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል ተጠሪ በጠየቀው መሠረት የደመወዝ ጭማሪው ይሰጠው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በተመሣሣይ ሁኔታ ወስኖአል /የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል/፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በድርጅቱ ፀንቶ ያለው በሕብረት ስምምነት ጭማሪው የማይደረግበትን ምክንያት አስቀምጦአል እየተባለ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ሕጋዊ የሚሆንበት አግባብ ምንድነው? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ነጥቡን ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሁለቱ ወገኖች ክርክር እና በሥር ፍ/ቤቶች ከተሰጡት ውሣኔዎች ይዘት መገንዘብ እንዲቻል ነው ተጠሪ በተባለው የበጀት ዓመት ውስጥ የዓመቱን 3/4 /ሦስት አራተኛ/ ጊዜ በስራ ላይ አልነበረም፡፡ በወቅቱ ፀንቶ በነበረው /ባለው/ የህብረት ስምምነት አንቀጽ 29/5/ እንደተመለከተው ይህን ያህል ጊዜ በስራው ላይ ያልተገኘ ሠራተኛ ጭማሪው እንደማይሰጠው ደግሞ አላከራከረም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ይህንኑ በሚገባ ስለመገንዘባቸው በውሣኔዎቻቸው ላይ የገለፁ ሲሆን፣ ጭማሪው መሰጠት አለበት በማለት የወሰኑት ግን በሕብረት ስምምነቱ የሌለን ምክንያት መሠረት በማድረግ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ይህ ተጠሪ አመልካች በወሰደው የስራ ውል ማቋረጥ እርምጃ ምክንያት በክርክር ስለመቆየቱ የሚገልጽ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በእርግጥም አመልካች የስራ ውሉን አቋርጦ ስለነበር ተጠሪ ለፍ/ቤት ባቀረበው ክስ መሠረት ክርክር ከተደረገ በኋላ ወደስራው እንዲመለስ ተወስኖለታል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ ሁኔታ ለእርከን ጭማሪው እንደበቂ ምክንያት አድርገው የወሰዱት ተጠሪ በስራው ላይ ሊገኝ ያልቻለው አመልካች በወሰደው ሕገ ወጥ የስራ ውል ማቋረጥ ምክንያት ነው፡፡ ይህንኑም በፍ/ቤት ተረጋግጦ ተወስኖአል በማለት ነው፡፡ በበኩላችን እንደምናየው የእርከን ጭማሪ አሰጣጥን በተመለከተ የተደነገገው የሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 29/5/ በግልጽ የሚያመለክተው በበጀት ዓመቱ ውስጥ 3/4ኛው ጊዜ በስራ ላይ ያልተገኘ ሠራተኛ የእርከን ጭማሪ የማይሰጠው እንደሆነ ነው፡፡ ድንጋጌው ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ ትርጉም የሚያስፈልገው አይሆንም፡፡ አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ሕገወጥ በሆነ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? በሚል ጭብጥ ላይ ተመስርቶ ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔም ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የጠየቀውን የእርከን ጭማሪ ሊያገኝ ይገባል ብሎ ለመወሰን የሚያስችል የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 34178 በታህሣሥ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 63056 የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ በክሱ የጠየቀውን የአንድ እርከን የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኝ የሚደረግበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37027

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ግርማ ማርቆስ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አሰለፈች ደስታ ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት የሥራ ክርክር ክስ ነው፡፡

ተጠሪ ለፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ያለአግባብ የወሰደባቸው የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲሻር፣ ተጠሪ ወደ ቀድሞ የስራ መደብ እንዲመልሳቸው እና የተቋረጠውን የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደባቸው ጥፋተኝነታቸው ተረጋግጦ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች የወሰደውን እርምጃ አሻሽሎ ተጠሪ በ4 ቀን ደመወዝ እንዲቀጡና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ወደ ቀድሞ ስራቸው እንዲመለሱ፤ በደመወዝ ላይ የተደረገው ጭማሪም ተስተካክሎ እንዲሰጣቸው ወስኗል፡፡ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የአመልካችን ይግባኝ ሣይቀበል ቀርቷል፡፡

የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ በህብረት ስምምነቱ የጥፋት አይነቶችና የቅጣት ደረጃዎች ተዘርዝረዋል፡፡ አንድ ሰራተኛ ጥፋት ሲፈጽም እርምጃ የሚወሰድበት ስለጥፋት አይነቶች እና ስለ ቅጣት በሚያስረዳው ሰንጠረዥ መሰረት ሲሆን የጥፋቱን ክብደት ከሚያሳዩት ደረጃዎች ለጥፋቱ ተመጣጣኝ የሆነውን ቅጣት መቅጣት ይቻላል፡፡ የጥፋት አይነቶች እና የቅጣት ደረጃዎች የተቀመጡት የተፈፀመውን ጥፋት ክብደት ለመመዘን እንዲያመች እንጂ የጥፋት ቅደም ተከተልን ለመወሰን አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ ስህተቱ የተፈጠረው በእርሣቸው ስህተት ባለመሆኑና ከድርጅቱ የውስጥ አሰራርና አመራር ጉድለት በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት እንደሌለው ተከራክረዋል፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በህ/ስምምነት ውስጥ ከተዘረዘሩት የቅጣት አይነቶች ቅደም ተከተል ሣይጠበቅ በአንድ ጥፋት በ4ኛ ደረጃ የተቀመጠውን ቅጣት እንዲቀጡ መወሰኑ ሕጋዊ አይደለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ የቅጣት ደረጃው ቅደም ተከተልን የሚያሣይ ሣይሆን በተፈፀመው ጥፋት ክብደት ተገቢውን ቅጣት ለመወሰን የተቀመጡ ናቸው በማለት ተከራክሯል፡፡

ከመዝገቡ ለመረዳት እንደተቻለው የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ጥፋተኝነት ተቀብሎ ወደ ቅጣት ውሣኔው ትክክለኛነት አምርቷል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ ሊቀጡ የሚገባው የህ/ስምምነቱ ከዘረዘረው ቅጣቶች በቅደም ተከተል ነው ወይስ ህ/ስምምነቱ እንደጥፋቱ ክብደት ቅደም ተከተል ሣይጠበቅ ቅጣቱ ይጣል የሚለው ነ1ው፤ አከራካሪ የሆነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤትም በሰጡት መልስ ምንም የፈፀሙት ጥፋት የሌለ ከመሆኑ ውጪ ቅጣቱ በምን ሁኔታ መፈፀም እንዳለበት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የተጠሪን ጥፋተኝነት አረጋግጠው በሰጡት ውሣኔ ላይም የቀረበ አቤቱታ ባለመኖሩ ተጠሪ ጥፋተኛ ናቸው አይደለም ወደሚለው ነጥብ መግባት አስፈላጊ አይሆንም፡፡ አንድ ሰራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ቅጣቱ እንዴት ነው ሊወሰን የሚገባው የሚለውን ስንመለከት የአመልካች መ/ቤት ህብረት ስምምነት እንደሚያሣየው ለተለያዩ የጥፋት አይነቶች የተለያዩ ቅጣቶች ተመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የተመደቡበትን ስራ በቸልተኝነት አለመስራት ጥፋት ለምሣሌ በ5 የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች ሊያስቀጣ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም በመ/ቤቱ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 22(12)(ሀ) ሥር በአንድ ሰራተኛ ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ ሊወሰድ የሚወሰነው ቅጣት ስለጥፋትና ስለቅጣት አይነት በሚያስረዳው ሰንጠረዥ መሰረት ሆኖ የጥፋቱን ክብደት ከሚያሣዩት ደረጃዎች ለጥፋቱ ተመጣጣኝ በሆነ የቅጣት ደረጃ ሊቀጣ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ስለጥፋትና ስለቅጣት አይነት በሚያሣየው ሰንጠረዥ ግርጌም የቅጣት ደረጃው የሚያመለክተው እንደጥፋቱ ክብደትና ቀላልነት የጥፋቱን ደረጃና ለደረጃውም የሚወሰነውን ቅጣት እንጂ የጥፋት ቅደም ተከተልን እንዳልሆነ በማሳሰቢያነት ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም ከህ/ስምምነቱ አንድ ሰራተኛ ጥፋተኛ ሆኖ ስለተገኘ ቅጣቱ የሚጣልበት በሰንጠረዡ ላይ በሰፈረው ደረጃ ቅደም ተከተል ሣይሆን የጥፋቱ ክብደት ታይቶ ተመጣጣኝ ነው ተብሎ በሚገመተው የቅጣት ደረጃ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

በተያዘው ጉዳይም አመልካች ተጠሪ በቸልተኝነት ሥራ ባለመስራት በመ/ቤቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረሣቸው የጥፋታቸው ክብደት በደረጃ አራት ላይ የተመለከተውን የቅጣት አይነት ያስቀጣቸዋል በማለት በዚሁ መሰረት እርምጃ ወስዷል፡፡ የጥፋቱን ክብደት በመመዘን ይመጥናል የሚለውን ቅጣት የመወሰን ተግባር ደግሞ ለአሰሪው ሊተው የሚገባ አስተዳደራዊ ስራ መሆኑን እናምናለን፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ ጥፋተኛ ለሆነበት ድርጊት የተመለከተውን ቅጣት መወሰኑ ህገ ወጥ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የህብረት ስምምነቱን በአግባቡ ሣያጤኑ ቅጣቱ ሊወሰን የሚገባው በቅደም ተከተል ነው በማለት የሰጡት ውሣኔም ከላይ በሰፈሩት ምክንያቶች ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21035 በሐምሌ 2 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58454 በየካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ የወሰደው እርምጃ የህ/ስምምነቱን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም ::
3. ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36518

ጥቅምት 4 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሜታ አቦ ቢራ አክሲዮን ማህበር - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- እነ ሳሙኤል ተፈራ (4 ሰዎች) - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ መሰረት የሚታይ ክርክር ሆኖ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ተከሣሽ ተጠሪዎች ከሣሾች ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች አመልካችን የከሰሱት በድርጅቱ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ የሕክምና ሰራተኞች መሆናቸውን ገልፀው ከጽሁፍ ሥራ ጋር በተያያዘ የተቋረጠባቸውን ክፍያ፣ በሽፍት ለሰሩት ሥራ ሊከፍል የሚገባውን ክፍያ እና የአልጋ ክፍያ እንዲከፍላቸው እንዲሁም የጽዳት ሰራተኛ እንዲመድብላቸው በመጠየቅ ነው፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ አመልካች ቢራ አምርቶ ለመሸጥ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤ ተጠሪዎችም ስራቸው የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ መስጠት ነው፤ ድርጅቱ ባወጣው የፈረቃ ድልደላ መሰረት እሁድ ስራ ላይ ለዋለ ሰራተኛ በቀጣዩ ቀን 24 ሰዓት እረፍት ይሰጠዋል፤ በሣምንት 48 ሰዓት ይሰራሉ፤ ላልሰሩበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሊጠይቁ አይገባም፤ በሽፍት ሥራ ለሚሰራ ሰራተኛ የአልጋም ሆነ የእራት ክፍያ የሚፈጸምበት ህጋዊ ምክንያት የለም፤ የሕክምና መሣሪያቸውን የማጽዳት ሐላፊነት የተጠሪዎች ስለሆነ የጽዳት ሰራተኛ ልመድብላቸው አይገባም፤ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ክርክሩን መርምሮ ተጠሪዎች በሣምንት 48 ሰዓት እንደሚሰሩ እና እሁድ ቀን በሥራ ላይ ከተገኙ በሚቀጥለው ቀን 24 ሰዓት የሚያርፉ መሆናቸውን በመረዳት ተጠሪዎች በሣምንት 48 ሰዓት ብቻ መስራታቸው እየታወቀ በሽፍት ሥራ እንሰራለን በማለት ብቻ ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄ እና የጽዳት ሰራተኛ ይመደብልን ጥያቄ የሕግ ድጋፍ የለውም ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ባለመስማማታቸው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ተከራክረዋል፡፡

የከፍተኛ ፍ/ቤቱም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 61/1/ መሰረት የማንኛውም ሰራተኛ የስራ ሰዓት በቀን ከስምንት ወይም በሣምንት ከ48 ሰዓት አይበልጥም ስለሚል እና የተጠሪዎች ቅሬታ በሣምንት ከ48 ሰዓት በላይ ሰራን ሣይሆን በቀን 16 ሰዓት ሰራን ነው ስለዚህ እንደሰራተኛ በቀን ከ8 ሰዓት በላይ መሥራት ግዴታ ባለመሆኑ አመልካች ተጠሪዎች በቀን 8 ሰዓት ብቻ እንዲሰሩ የሥራ ጊዜውን ያመቻች በማለት በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በጥር 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡

ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በከፍተኛው ፍ/ቤት ለተጠሪዎች የሥራ ሰዓት ይመቻችላቸው በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጁ እና ከሕብረት ስምምነቱ አኳያ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እኛም የጉዳዩን አመጣጥ ስናየው ተጠሪዎች በአመልካች ድርጅት ሲሰሩ ድርጅቱ ባወጣው የሥራ ሽፍት መሰረት ተስማምተው ሲሰሩ የቆዩ እና በድልድሉ መሰረት እሁድ ቀን ከሰሩ በሚቀጥለው 24፡00 ሰዓት እንደሚያርፉ ተገንዝበናል፡፡ አንድ ድርጅት እንደስራው ፀባይ በሕግ ከተደነገገው ማእቀፍ ሳይወጣ (ሳይጥስ) የሥራ ሰዓቱን ለማሻሻል የሚከለክለው ሕግ የለም፡፡ ተጠሪዎችም በዚሁ ተስማምተው በሣምንት ከ48 ሰዓት በማይበልጥ መልኩ በሽፍት ሲያገለግሉ ቆይተው የሌላቸውን (ያልሰሩበትን) የትርፍ ሰዓት ክፍያ የሚጠይቁበት የሕግ ድጋፍ የላቸውም፡፡ ሌላው የጽዳት ሰራተኛ እንዲመደብላቸው የጠየቁትንም በሚመለከት ቀድሞውኑም ተጠሪዎች የህክምና ባለሙያ በመሆናቸው የራሳቸውን የሕክምና መሣሪያ ሌላ ሰው ያጽዳልን ማለታቸው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ስለዚህ የሰራተኛ ምደባው ውድቅ ነው፡፡

ባጠቃላይ ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ በአመልካች ድርጅት እንደሚሰሩ ግልጽ ሆኖ ሳለ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የድርጅቱን የስራ ፀባይ ግምት ውስጥ ሳያስገባ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 61(1) ለመባል ከፈለገው አላማ ጋር በቅጡ ሳያገናዝብ የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚገድብ መልኩ በሣምንት ተጠሪዎች 48 ሰዓት መሥራታቸውን እየገለፀ ከአዋጁ መንፈስ ውጭ 8 ሰዓት ብቻ ለተጠሪ ይመቻችላቸው ብሎ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻል መወሰኑ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11276 በቀን ሰኔ 4 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57620 በጥር 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡ ተጠሪዎች ምንም አይነት ክፍያ ሊጠይቁ አይገባም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ኪሳራ ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35484

ኀዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ደረጀ ማሞ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ መስከረም 15 ቀን 1999 ዓ.ም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በአጭሩ፡- በአመልካች ድርጅት ከጥር 06 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ በፀሐፊነት የስራ መደብ ተቀጥረው እየሰሩ መቆየታቸውን፣ ከዚሁ የስራ መደብ ላይ የቲኬት ሽያጭ ስራ መደብ ደርበው እንዲሰሩ ተደርጉ የብር 5,918.00/አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ስምንት ብር/ የገንዘብ ጉድለት የተከሰተባቸው መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት የድርጅቱን ገንዘብ ለግል ጥቅም አውለዋል ተብለው ያላግባብ ከስራ መሰናበታቸውን ዘርዝረው ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ የተሰናበቱበት ክፍያ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ እና ወጪና ኪሣራ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ሲሆን የአሁኑ አመልካች በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተጠሪ ለግል ጥቅማቸው ያዋሉት መሆኑን አለመካዳቸውን በመጥቀስ በሕብረት ስምምነቱ አባሪ/1/ሀ(3) መሰረት የተወሰደባቸውን እርምጃ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙ የቃል ክርክርና የተከሣሽን ምስክር ቃል ከሰማ በኋላ ተጠሪ የገንዘብ ጉድለት የተገኘባቸው መሆኑ ቢረጋገጥም ጉደለ የተባለውን የገንዘብ መጠን ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ አሣማኝ ማስረጃ ባለመኖሩ አመልካች የሕብረት ስምምነቱን ጠቅሶ ተጠሪን ማሰናበቱ አግባብ አይደለም በማለት ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚህ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- ተጠሪ በስራቸው አጋጣሚ በእጃቸው ሊገባ የቻለውን ብር 5,918.00 ሊጉድልባቸው የቻለው በስልጠና ማነስና ከስራ ጫና የመጣ ነው ከማለት ውጪ ገንዘቡን ለግል ጥቅሜ አላዋልኩም በማለት ባልተከራከሩበት ሁኔታ ገንዘቡን ካልመለሱ ደግሞ ለግል ጥቅማቸው እንዳዋሉ ህጋዊ ግምት የሚወሰድበት ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ተቀባይነት በሌለው መመዘኛ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ ጥፋተኛ ስለመሆናቸው የቀረበ ማስረጃ በሌለበት እና መከላከያ ባልቀረበበት ጉዳይ የክርክር ጭብጥ ተነስቶ የሰበር አቤቱታ መቅረቡ ያላግባብ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው የተጠሪን የመልስ ይዘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመንቀፍ የሰበር አቤቱታውን ደግሞ በማጠናከር የመልስ መልሣቸውን ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በዓፉት ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ በስራቸው አጋጣሚ ወደ እጃቸው የገባውን የአመልካች ገንዘብ ማጉደላቸው ተረጋግጦ እያለ ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል አሣማኝ ማስረጃ አልቀረበም ተብሎ የአመልካች እርምጃ ህገ ወጥ ነው መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ የቲኬት ሽያጭ ሰራተኛ ሆነው ሲሰሩ የገንዘብ ጉድለት የተከሰተባቸው ስለመሆኑ ያመኑ መሆኑ ከመረጋገጡም በላይ በአመልካች በኩል የቀረቡት የሒሣብ ባለሙያም በኦዲት ሪፖርቱ የተገኘውን ውጤት በተመለከተ በሰጡት አስተያየት ገንዘቡ መጉደሉን ያስረዱ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤትም የተገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ተረጋግጦ እያለ አሣማኝ ማስረጃ አልቀረበም የተባለው ተጠሪ ገንዘቡን ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ ስለመሆኑ በማስረዳት ረገድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የስር ፍ/ቤት ድምዳሜ በሕጉ ላይ ያልተመለከተውን መስፈርት መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር ሕጋዊ መሰረቱ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1(ተ) ስር በተመለከተው አኳኋን የአመልካች ድርጅት አለ በማለት የሚከራከረውንና በተጠሪም ያልተካደውን የህብረት ስምምነት አባሪ 1(ሀ)(3)"ገ" ያላገናዘበ ነው በዚህ ድንጋጌ መሰረት የድርጅቱን ወይም በድርጅቱ ኃላፊነት የሚገኝ ንብረት ጥሬ ገንዘብ ወይም በድርጅቱ የስራ ግንኙነት ምክንያት ሰራተኛ እጅ ሊገቡ የሚችሉ የደንበኞችን የሰራተኞችን ንብረት/ገንዘብ መስረቅ፣ መደበቅ፣ ለግል ጥቅም ማዋል ወይ እንዲወሰድ መተግበር ወይም እምነት ማጉደል ወይም የድርጅቱን ንብረት ወይም ቅጥር ግቢ ህገ ወጥ ለሆነ ተግባር መጠቀም ወይም ሌላ ወገን እንዲጠቀምበት ማድረግ ሰራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ማባረር የሚቻል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ የገንዘብ ጉድለት የተከሰተበት የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ ስለማዋሉ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ በመስፈርትነት አያስቀምጥም፡፡ ይልቁንም የገንዘብ ጉድለት/እምነት ማጉደል/ ስለመከሰቱ መረጋገጥ ብቻ ሰራተኛውን ከስራው ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል መሆኑን በግልጽ ያስረዳል፡፡ የገንዘብ ጉድለት የተከሰተበት ሰራተኛ ገንዘቡን ለግል ጥቅም ያላዋለ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ይኖርበታል እንጂ ይህንኑ የገንዘብ ጉድለት መኖሩን ያስረዳ አሰሪ እንዲያስረዳ አይጠበቅም፡፡ የገንዘብ ጉድለት የተከሰተበት መሆኑ የተረጋገጠበት ተከሣሽ ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ ያዋለው ነው ተብሎ ህጋዊ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ የማስረጃ ሕግ መርሆዎች የሚያስገነዝቡት ነጥብ ነውና፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የገንዘቡ ጉድለት መከሰቱን አምነው ገንዘቡን ለድርጅቱ መመለሣቸውን ባላስረዱበት ሁኔታ የአመልካች ድርጅት ማስረጃ አሣማኝነት የለውም መባሉ በጉዳዩ ላይ የቀረበው ማስረጃ የሚመዘንበትን መርህና በግራ ቀኙ መካከል ገዥነት ያለውን የህብረት ስምምነት ይዘት ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች የተጠሪ ክስራ መሰናበት ህገ ወጥ ነው በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ህጋዊነት የሌለውን መነሻ ሐሣብ በመያዝ ሆኖ ስለተገኘ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከመጀ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.39196 ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 60895 ጥር 15 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37815

ህዳር 02 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ዓለማየሁ ጠ/ሥራ ተቋራጭ - ጠ/ሃይለማርያም ኢቲቻ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዮት በፈቃዱ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ ያለአግባብ ከስራ ስለተሠናበቱ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ በሠጠው መልስ አስቸኳይ ስራ ስላለ በሣምንት እረፍት ቀን ስራ እንዲገቡ ተጠይቀው እምቢተኛ ሆነው በአመልካች ላይ ጉዳት በማድረሣቸው ነው ሲል ተከራክሯል ፍ/ቤቱም ተጠሪ በአሁድ ቀን ለምን አልሠሩም ተብለው መባረራቸው ተገቢነት ስለሌለው በግራ ቀኙ የተቆጠሩትን ምስክሮች ማስቀረብ ሣያስፈልግ ስንብቱ ህገወጥ በመሆኑ የተለያየ ክፍያ እንዲከፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤትም የአመልካችን ይግባኝ ቅሬታ ሣይቀበል ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም ለስራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በእረፍት ጊዜ መስራት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ የሚጥለው ግዴታ በመሆኑ ውሣኔው ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ሠበር ችሎትም ይህንኑ ነጥብ ለማጣራት ተጠሪ እንዲቀርቡ በማድረጉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የአመልካችን ቅሬታ የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና ከህጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች ተጠሪን ከስራ ማሠናበቱን ሣይክድ ያሠናበታቸው ግን በሣምንት እረፍት ቀን አስቸኳይ ስራ ገጥሞ እንዲሠሩ ተጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በድርጅቱ ላይ ጉዳት በማድረሣቸው መሆኑን ተከራክሯል፡፡ በመሆኑም በሣምንት እረፍት ቀን ሠራተኛው እንዲሠራ በአሠሪው ታዞ ፈቃደኛ አለመሆኑ ከስራ ለማሠናበት በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑን መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 69(1) መሠረት ማንኛውም ሠራተኛ በሠባት ቀናት ጊዜ ውስጥ ያልተቆራረጠ ከ24 ሠዓት የማያንስ የሣምንት እረፍት ሊያገኝ እንደሚገባ በአስገዳጅነት ተቀምጧል በመሆኑም በመርህ ደረጃ ማንኛውም ሠራተኛ አንድ ሣምንት ጊዜ ውስጥ ከአንድ ቀን ያላነሠ የሣምንት እረፍት የማግኘት መብት አለው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ መርህ በተለየ ሁኔታ ግን ሠራተኛው በሣምንት እረፍቱ ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የሚቻል መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 71(1) ሥር ተመልክቷል፡፡ ይኸውም በዚሁ ድንጋጌ ከፊደል ሀ-ሐ የመለከቱት ምክንያቶች ሲያጋጥሙና የድርጅቱን መደበኛ ተግባር የሚያደናቅፍ ሁኔታዎችን ለማስወገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሠራተኛው በማንኛውም የሣምንት የዕረፍት ጊዜው እንዲሠራ ማድረግ ይችላል፡፡ እነዚህም ምክንያቶች

ሀ/ አደጋ ሲደርስ ወይም የሚደርስ መሆኑ ሲያሠጋ

ለ/ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐ/ በአስቸኳይ የሚሠራ ሥራ ሲያጋጥም ናቸው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሚከራከረው አስቸኳይ ስራ አጋጥሞ ተጠሪ በአረፍት ቀናቸው እንዲሠሩ ቢጠየቁ ፈቃደኛ ሣይሆኑ በመቅረት በአሠሪው ላይ ጉዳት በመድረሱ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ምንም እንኳን በመርህ ደረጃ አንድ ሠራተኛ በሣምንት ውስጥ ከ24 ሠዓታት ያላነሠ የሣምንት እረፍት የማግኘት መብት ቢኖረውም በአስቸኳይ የሚሠራ ስራ ባጋጠመ ጊዜ ግን በማንኛውም የሣምንት እረፍት ሠራተኛው ሥራ የመሥራት ግዴታ ህጉ ጥሎበታል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 13(7) ሥር ሠራተኛው የአዋጁን ድንጋጌዎች ጨምሮ የህብረት ስምምነቱን፣ የስራ ደንቡንና በህግ መሠረት የሚተላለፍ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን የማክበር ግዴታ አለበት ሠራተኛው እነዚህን ህጎችና ደንቦች የሚጥስ መሆኑ ከተረጋገጠ የስራ ግዴታውንና ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ አሠሪው ሊያሠናብተው የማይችልበት ምክንያት የለም፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የአዋጁን ድንጋጌ ባለማክበራቸው የተሠናበቱ መሆኑን አመልካች ተከራክሯል፡፡ አመልካች አስቸኳይ ስራ በማጋጠሙ ተጠሪ በሣምንት እረፍታቸው እንዲሠሩ መጠየቁን እና ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጿል፡፡ የስር ፍ/ቤትም በአዋጁ አንቀፅ 71(1)(ሐ) ሥር የተመለከተው ሁኔታ መከሠት አለመከሠቱን በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ሲገባው በሣምንት እረፍት እንዲሠሩ መጠየቁ ብቻ ህገ-ወጥ ነው በማለት በግራ ቀኙ የተቆጠሩትን ማስረጃዎች ሣይሠማ የሠጠው ውሣኔ ከፍ ሲል የተመለከቱትን የአዋጁን ድንጋጌዎች ያላገናዘበና ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ በ37659 በ28/6/2000 የሠጠው ውሣኔና

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 6704 በ8/9/2000 የሠጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡

2/ ተጠሪ በሣምንት እረፍታቸው እንዲሠሩ የታዘዙት በአዋጁ አንቀፅ 71(1)(ሐ)

መሠረት አስቸኳይ የሚሠራ ስራ አጋጥሞ መሆን አለመሆኑን የግራ ቀኙን

ማስረጃ ሠምቶ በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥ ጉዳዩ ለፌ/መ/ደረጃ

ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሠረት ተመልሷል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36377

ጎዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት - ወይንሸት እንድሪስ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ተሾመ ኩማ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተውም የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ ተቋርጦብኛል፡፡ ስለዚህም ውዝፍ ደመወዜ ተከፍሎኝ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ በፈጸመው ሕገ ወጥ ድርጊት ምክንያት ነው፡፡ ድርጊቱ ከሥራ የሚያሰናብት ነው በማለት የተከራከረ ሲሆን ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣ አመልካች የሥራ ውል የማቋረጥ እርምጃ የወሰደው ድርጊቱ ከተፈጸመ ከአንድ ወር በኋላ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪ የስድስት ወር ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራው እንዲመለስ ወስኖአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መጋቢት 5 ቀን 2000 ዓ.ም. በባፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች የወሰደው የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃ በይርጋ የታገደ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከአመልካች የቀረበውን የስረ-ነገር ክርክር አልሰማም፡፡ ባጭሩ ብይኑን የሰጠው የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው ለውሉ መቋረጥ ምክንያት ነው የተባለው ድርጊት /ጥፋት/ ከተፈጸመ አንድ ወር ካለፈ በኋላ በመሆኑ በይርጋ ታግዶአል በማለት ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ደረጃ ሊመረመርና ውሣኔ ለሰጠው የሚገባው ነጥብ በእርግጥ ለክርክሩ አወሳሰን በዋቢነት የተጠቀሰው የአዋጅ ቁ. 337/96 አንቀጽ 27/3/ የሚለይው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንደሚለው ነው ወይ የሚለው ነው፡፡ ከዚህም ጋር በማያያዝ ድርጊቱ በተፈጸመበት እና አመልካች የሥራ ውል የማቋረጥ እርምጃ በወሰደበት መሃከል ያለው ጊዜ ምን ያሕል ነው የሚለው የፍሬ ነገር ሁኔታም መታየት ያለበት ነው፡፡

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር በተለይ ደግሞ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ ጥፋቱን /ድርጊቱን/ ፈጸመ የተባለው መስከረም 24 እና 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ሲሆን፣ አመልካች የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃ የወሰደው ጥቅምት 25 ቀን ነው፡፡ ይህ እንግዲህ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ሕጉ ምን ይላል የሚለውን ደግሞ ቀጥለን እንመልከት፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 27 አሠሪው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ማቋረጥ የሚችልባቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያቶች /ሁኔታዎች/ በዝርዝር የያዘ ነው፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/"ም" አሠሪው የስራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት በይርጋ የሚቀርበትን ምክንያት ይሏል፡፡ ይህም የሚሆነው /የስራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት በይርጋ ቀሪ የሚሆነው/ ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት ከ30 /ሠላሣ/ የሥራ ቀናት በኋላ እንደሆነ በሕጉ በግልጽ ተቀምጦአል፡፡ እዚህ ላይ በሚገባ ሊተኮርበት የሚገባውም "የስራ ቀናት" የሚለው ሐረግ ነው፡፡ በሕጉ አባባል አሠሪው መብቱን በይርጋ የሚያጣው /የሚቀርበት/ ሠላሣ ቀናት ወይም አንድ መሆን አለባቸው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ከመስከረም 24 ቀን ጀምሮ እስከ ጥቅምት 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜ የሚታሰበው ቢያንስ እሁድን ጨምሮ ነው፡፡ እሁድ የስራ ቀን አይደለም ብለን ብንወስድ አራት እሁዶች እንዳሉ እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ስሌት መሠረትም አመልካች የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃውን የወሰደው ተጠሪ ፈጸመ የተባለው ድርጊት /ጥፋት/ መከሰቱን ባወቀ በ26ኛው የስራ ቀን ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዳለው የአመልካች መብት በይርጋ የታገደ ወይም ቀሪ የሆነ አይደለም፡፡ ተጠቃሎ ቢታይ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 25115 ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57680 ጥር 21 ቀን 2000 በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች የስራ ውል የማቋረጥ መብቱ በይርጋ አልታገደበትም ብለናል፡፡ ስለዚህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር በዚያው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ወይስ ከሕግ ውጪ ነው በሚለው ጭብጥ ላይ ከግራ ቀኝ ወገኖች የሚቀርብለትን ክርክር ከሰማ በኋላ የመሰለውን ውሣኔ ይስጥ በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341 መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37048

ህዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብድልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማ -ነ/ፈጅ መ/ኩ መለሰ

ተጠሪ፡- አቶ ሳህሉ ምትኩ - አልቀረቡም ከተባለ በኋላ እንዳልካቸው ይላቅ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ስንብት ክፍያ የሚከፈልበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡

በአሁኑ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ሥራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ ቢሆንም ከአምስት አመት በላይ የሰሩ በመሆኑ የስራ ስንብት እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪ ከአምስት አመት በላይ የሰሩ ቢሆንም የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ በመሆናቸው የስንብት ክፍያ አይገባቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ አያገኝም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ላይ ተጠሪ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ በጡረታ ህግ የተመለከተውን መደበኛ የጡረታ እድሜ ላይ ደርሶ ከስራ እስካልተገለለ ድረስ ክፍያ አይከለክልም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮ ለተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲሰጣቸው ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

ይህ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያለው መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታውን ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጹሁፍ አቅርበዋል ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ ስህተት ተፈጽሞበታል ከተባለው ውሳኔና አግባብነት ካለው ህግ አኳያ መርምሯል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ስንብት ክፍያ መብትን የሚመለከት ነው፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39 ስር የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈል የሚገባውን ሁኔታዎች ዘርዝሮ አስቀምጧል በዚሁ አንቀጽ ከፊደል "ሀ" እስከ "ረ" ድረስ ተዘርዝረው በተቀመጡት ሁኔታዎች መሰረት የሰራተኛው ጥፋት ባልሆነ ምክንያት አሰሪው የስራ ውሉን ሲያቋርጥ ወይም በአሰሪው ጥፋት ወይም በሰራተኛው የጤና ሁኔታ ሰራተኛው በፈቃዱ ስራውን ሲለቅ የስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 494/98 በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 39(1) ስር አዲስ ድንጋጌዎችን ጨምሯል፡፡ በዚህም መሰረት

ሰ. የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም ጡረታ መብት የሌለው ሲሆንና በጡረታ ህግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ደርሶ ከስራ ሲገለል፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሸ. ቢያንስ አምስት ዓመት በአሰሪው ዘንድ የስራ አገልግሎት ኖሮት በህመም ወይም በሞት የስራ ውሉ ሲቋረጥ ወይም የስራው ላይ የሚያስቆይ ከስልጠና ጋር የተያያዘ ለአሰሪው የውል ግዴታ ሳይኖርበት ስራውን በገዛ ፈቃዱ ሲለቅ

ቀ. በኤች አይ ቪ ኤድስ ህመም ምክንያት በራሱ ጥያቄ የስራ ውሉ ሲቋረጥ

የስራ ስንብት ክፍያ ማግኘት የሚችል መሆኑን ተቀምጧል፡፡

ይህ የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 2 ቀደም ሲል በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 39 (1) ስር ያልተካተቱ አዲስ ሁኔታዎች ተጨምረዋል ይኸውም አንድ ሰራተኛ በገዛ ፈቃዱ ስራውን ቢለቅ እንኳን የተወሰኑ ሁኔታዎች እስከተሟሉ ድረስ የስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ተሰጥቶታል፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች ከፊደል "ሰ" እስከ "ቀ" የተመለከቱት ናቸው ፡፡ በተለይ ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸው በፊደል "ሰ" እና "ሸ" የተመለከቱት ናቸው፡፡ በፊደል "ሸ" እንደተመለከተው ቢያንስ አምስት ዓመት ከሰራና በህመም ወይም በሞት ስራ ውሉ ከተቋረጠ ወይም ከስልጠና ጋር በተያያዘ ስራው ላይ የሚያስቆይ ለአሰሪው የውል ግዴታ ከሌለበት የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ድንጋጌ በተናጠል ሳይሆን በፊደል "ሸ" ስር ከተመለከተው ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰራተኛ ከ5 ዓመት በላይ የሰራ ቢሆንም እንኳን የስንብት ክፍያ ማግኘት የሚችለው የፕሮቪደንት ወይም የጡረታ መብት ከሌለውና የጡረታ ዕድሜው ደርሶ ከስራ ከተገለለ ነው፡፡

የስር ፍ/ቤትም እነዚህ ሁለት ንዑሳን ቁጥሮች በአንድነት ተገንዝበው መተርጎም ያለባቸው መሆኑን ቢቀበልም የስንብት ክፍያ የሚከለከለው የፕሮቪደንት ፈንድ መብት ኖሮት የጡረታ ዕድሜው ደርሶ ከስራ ከተሰናበተ ወይም የጡረታ መብት ኖሮት የጡረታ እድሜው ደርሶ ከስራ ከተሰናበተ መሆኑን አትቷል፡፡ በሌላ አነጋገር የስንብት ክፍያ በመከልከል የፕሮቪደንት ፈንድ መብት መኖርና የጡረታ እድሜ ደርሶ ከስራ መገለል በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የጡረታው ዕድሜ ሳይደርስ በገዛ ፈቃዱ ከስራ የለቀቀ ሰራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ መብት ያለው ቢሆንም ዕድሜው ደርሶ በጡረታ የተገለለ ባለመሆኑ ምክንያት የፕሮቪደንት ፈንድ የማግኘት መብት ያለው ነው በማለት ለድንጋጌው ትርጉም ሰጥቶታል፡፡

ይህ ችሎትም እነዚህ ሁለት ንዑሳን ቁጥሮች ግልፅ ባለመሆናቸው ትርጉም የሚያስፈልጋቸው መሆኑን አምኗል፡፡ ድንጋጌዎች ግልፅ ባልሆኑ ግዜም በመጀመሪያ ሊተረጎሙ የሚገባው የህግ አውጭውን ሐሳብ በመፈለግ መሆኑ የሕግ አተረጓጎም መርህ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የእነዚህ ድንጋጌዎች አላማ ማወቁ ተገቢ ይሆናል፡፡

የስራ ስንብት ክፍያ ዋነኛው አላማ አንድ ሠራተኛ ከስራ ሲሠናበት ችግር ላይ እንዳይወድቅ ራሱን እንዲያቋቁም ለመርዳት ነው፡፡ እንዲሁም የኘሮቪደንትና የጡረታ አላማም ቢሆን አንድ ሠራተኛ ዕድሜው ደርሶ በጡረታ ቢገለል የሚጦርበት የማህበራዊ ዋስትና ስርዓት ነው፡፡ በእርግጥ ኘሮቪደንት ፈንድና ጡረታ ተመሣሣይ አላማ ያላቸው ቢሆንም የጡረታ ክፍያ የሚጀምረው አንድ ሠው የጡረታ ዕድሜው ደርሶ ሲሠናበት ሲሆን አከፋፈሉም በአንዴ ሣይሆን በየወሩ የሚከፈል ነው ፕሮቪደንት ፈንድ ግን ሰራተኛው ከስራ ሲወጣ (የጡረታ ዕድሜው ደርሶ ሊሆን ይችላል ወይም ሳይደርስ) በአንድ ግዜ የሚከፈል ነው፡፡ በመሆኑም በአከፋፈል በኩል በሁለቱ መሣከል ልዩነት መኖሩ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ በአከፋፈል ያለው ልዩነት እንዳለ ሆኖ ግን ሁለቱም ክፍያዎች ሰራተኛው ከስራ ሲሰናበት ችግር እንዳይገጥመው የሚከፈሉ በመሆናቸው የስንብት ክፍያ አላማን የሚጋሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም አንዱ ሰራተኛ ከስራ በሚወጣበት ጊዜ የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም ጡረታ የሚከፈለው ከሆነ በድጋሚ የስራ ስንብት ክፍያ እንዳይከፈለውና በሁለት መንገድ ተጠቃሚ እንዳይሆን ታስበው የወጡ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል አንድ ሰራተኛ ለ5 እና 6 ዓመታት ሰርቶ የጡረታ ዕድሜው ሳይደርስ በራሱ ፈቃድ ከስራ በመልቀቁ ብቻ ከፕሮቪደንት ፈንድ በተጨማሪ ስንብት ክፍያ እንዲያገኝና ሌላው ደግሞ እስከ ጡረታ ዕድሜው ድረስ በመስራቱ ፕሮቪደንት ፈንድ ካለው ስንብት ክፍያ እንዲከለከል ማድረጉ በሰራተኞች መሣከል ልዩነት የሚፈጥርና ፍትሐዊ ባለመሆኑ ህጉ ይህን ልዩነት የመፍጠር አላማ ይዞ የወጣ ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም አንድ ሰራተኛ አምስት አመትና ከዚያ በላይ የሰራ ከሆነና በራሱ ፈቃድ ስራ ከለቀቀ የስራ ስንብት ክፍያ ለማግኘት የሚችለው ስራ በለቀቀበት ሰዓት የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ወይም የጡረታ መብት ተጠቃሚ ካልሆነ ብቻ ነው፡፡

ስራውን በለቀቀበት ሰዓት ፕሮቪደንት ፈንድ የሚከፈለው ወይም በጡረታ መብቱን መገልገል የሚጀምር ከሆነ ግን 5 አመትና ከዛ በላይ መስራቱ ብቻውን የስንብት ክፍያ መብት አያስገኝለትም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የጡረታ እድሜው ደርሶ በጡረታ ከስራ እስካልተገለለ ድረስ ፕሮቪደንት ፈንድ ማግኘት ይችላል በማለት የደረሰበትን መደምደሚያ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ይህንኑ የህጉን ድንጋጌ በተመለከተ በመ/ቁ 35197 የተሰጠውን የህጉን ትንታኔም መመልከት ይቻላል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 59262 በየካቲት 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል ፣
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 26613 በሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል ፣
3. ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ተጠቃሚ በመሆናቸው የስራ ስንብት ክፍያ ሊያገኙ አይገባም ብለናል ፣
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37256

ጎንደር 04 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አዲስ አበባ የምግብ አዳራሽ አስተዳደር - ነ/ፈጅ ኢሣያስ ኃይሉ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የውብዳር ጥላሁን - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ድርጅት ውስጥ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በወር ብር 536.90 (ሦስት መቶ ሰላሣ ስድስት ብር ከዘጠና ሣንቲም) እየተከፈላቸው በገንዘብ ያዥነት እየሠሩ ባሉበት ሁኔታ በዓቃቤ ሕግ በኩል ክስ በመመስረቱ የስራ ውላቸው ተቋርጦ መቆየቱንና በኋላም ይኸው ክስ በመዘጋቱ ምክንያት አመልካች ከታህሣሥ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ስራ የመለሣቸው ቢሆንም የተቋረጠውን ደመወዝ ያልከፈላቸው መሆኑንና ወደ ቀድሞው ስራ ያልመለሣቸው መሆኑን በመዘርዘር ከሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ደመወዝ ወደ ሥራ አስከተመለሱበት ቀን ያለውን አስቦ እንዲከፍላቸውና ወደ ቀድሞው የገንዘብ ያዥነት ሥራቸው ከደመወዝ ጭማሪና ከኪሣራ ጋር እንዲመልሣቸው ይወስንላቸው ዘንድ በአመልካች ላይ ታህሣሥ 22 ቀን 2000 ዓ.ም. በፊዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርቦ ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት ሊታይ የማይችልበትን ምክንያት በመጥቀስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ከመከራከሩም በተጨማሪ በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪ ከስራ የታገዱበት ገንዘብ አጉድሰው በመገኘታቸውና የተወሰነ ገንዘብ መልሰው ቀሪውን ገንዘብ ለመመለስ ፈቃደኛ ሆነው አለመገኘታቸውን፣ ወደ ሥራ የተመለሱትም ካላቸው የቤተሰብ ኃላፊነት ታይቶ መሆኑን ወደ ቀድሞው የሥራ መደብ ለመመለስ ያልቻለው ከተጠሪ ጥፋት አንፃር መሆኑንና ባልነበሩበት ጊዜ የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጥያቄ ማቅረብ የማይችሉ መሆናቸውን በነጥብነት በማንሣት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሠማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ውድቅ ከአደረገው በኋላ የስራ ውል የሚሻሻልበትን የሕግ ምክንያት በመዘርዘርና አመልካች የስራ መደቡን ሲቀይር የስራ ውል የማሻሻል ውጤት የሚኖረው መሆኑን በማለጽ የአመልካችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው በማለት ተጠሪን የአራት ወር ደመወዝ ከፍሎ ወደ ቀድሞ የስራ መደብ እንዲመልሳቸው ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፊዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሠርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የስር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚልባቸውን ምክንያቶች ሚያዝያ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ጉዳዩ መታየት የነበረበት በአስማሚ መሆኑን፣ ተጠሪ የአመልካችን ገንዘብ ማጉደላቸው ተረጋጋጦ እያለ ወደ ቀድሞ ስራቸው ይመለስ መባሉ ስህተት መሆኑን፣ ላልሠሩበትና ታግደው ለቆዩበት ጊዜ የአራት ወር ደመወዝ እንዲከፈል መወሰኑ አግባብነት የሌለው መሆኑና የአመልካች ምስክሮች አለመስማታቸውን ተገቢነት ያለው አለመሆኑን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይገባል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ሐምሌ 03 ቀን 2000 በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጭብጥ ተጠሪ የአራት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ቀድሞው ስራ እንዲመለሱ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በአመልካች ድርጅት በገንዘብ ያዥነት የስራ መደብ ተቀጥረው ሲሠሩ መቆየታቸው በስራው አጋጣሚ ወደ እጃቸው ከገባው የአመልካች ገንዘብ ውሰጥም ብር 4219.00 /አራት ሺህ ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር/ አጉድለው ብር 1950.00 /አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሣ ብር/ መልሰው ቀሪውን ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ከስራቸው ታግደው መቆታቸውና በዚህም ወቅት በዓቃቤ ሕግ በኩል ክስ ተመስርቶባቸው የነበረ ቢሆንም ክሱ ተዘግቶ በነፃ የተሠናበቱ መሆኑ የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው ተጠሪ ገንዘብ ማጉደላቸውን ሣይክዱ በዓቃቤ ሕግ በኩል መዝገቡ ተዘግቶ በነፃ ተሠናብቼአለሁ በማለት ብቻ የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ምላሽ የሚያስፈልገው ጥያቄ ተጠሪ በዓቃቤ ሕግ በኩል በተመሠረተው የወንጀል ክስ ነፃ ወጥቻለሁና ወደቀድሞ ሥራ ልመለስ ይገባል ሲሉ ያቀረቡት ጉዳይ በሕግ በኩል ድጋፍ አለውን? የሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ክስና የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት አድርጎ የሚቀርብ ክስ የተለያየ ይዘትና ዓላማ ያላቸው ከመሆኑም በላይ በማስረጃ አመዛዘን ረገድም የተለያዩ መርሆዎችን መሠረት የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ የወንጀል ክስ ለጠቅላላው ማኅበረሰብ ጥቅም ሲባል የሚወሰድ መንግሥታዊና ማኅበረሰባዊ እርምጃ ሲሆን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት የሚያደርግ ክስ ግን እንደ ወንጀሉ ስፋት ያለው ይዘት የውስጥ ድርጅት እርምጃ ነው፡፡ የወንጀል ክስ እርምጃ ሊያሣካ የሚያልመው ዓላማ በማኅበረሰቡ ሠላምና ደህንነት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሣድሩ ባሕርያትን ማረምና ማደስ ሲሆን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት የሚያደርጉ ክሶች እርምጃቸው ኢንዱስትሪያላዊ ሠላምን ማስፈንና የሥራ ዋስትናን ማስከበር መሆኑ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ሁለቱም ክሶች የተለያየ ይዘትና ዓላማ ያላቸው መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የወንጀል ክስ የማስረጃ ምዘና መርህ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ የፀዳ /Beyond reasonable doubt/ የሚል ሲሆን በዚህ የማስረጃ አመዛዘን መርህ መሠረት በወንጀል ጥፋተኛ ለማሰኘት ጠንካራና የማያሻማ ማስረጃ የሚፈለግ ሲሆን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት የሚያደርግ ክስ በባሕሪይው ከዲሲፕሊን እርምጃ ጋር እጅጉን የተቆራኘ በመሆኑ እንደማንኛውም የዲሲፕሊን ክስ ተፈፃሚነት የሚኖረው የማስረጃ ምዘና መርህ ከወንጀል ክስ የማስረጃ ምዘና ላላ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም በወንጀል ተከሶ ነፃ የሚወጣ ሠራተኛ በዲፕሊን ቢከሠስ አጥፊ ሆኖ የመገኘት ዕድሉ ሠፊ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት የወንጀል ክስ ነፃ በማውጣት ብቻ አንድ ሠራተኛ ወደ ቀድሞ ሥራ ልመለስ ይገባል በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ የሕግ ድጋፍ አይኖረውም፡፡ ስለሆነም የሠራተኛው ጥያቄ ሊስተናገድ የሚገባው ላላ ያለ የማስረጃ ምዘና መሠረት ተደርጎ ለአድራጎቱ ተጠያቂ ሆኖ መገኘት አለመገኘቱን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

እኛችን ወደአለው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ የአመልካችን ገንዘብ ማጉደላቸውን አምነው ተመላሽ ማድረጋቸውን በመግለጽ መከራከራቸውን የሥር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪን ወደቀድሞው ሥራ ባይመልሣቸውም በሌላ የሥራ መደብ በመመደብ እንዲሠሩ ፈቅዷል፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች ይህንኑ የአመልካችን እርምጃ ሕገወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 15 ሥር የተመለከቱትን የሥራ ውል ማሻሻያ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ እና በእነዚህ ምክንያቶች የተፈፀመ ስለመሆኑ አላስረዳም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የተጠሪ የስራ መደብ ለውጥ ያደረገው ተጠሪ የገንዘብ ጉድለት ስለአስከተሉ መሆኑ ሲታይ እርምጃው ይህንን አጠቃላይ መንፈስ የሚጋጭ ነው ሊባል የሚገባው አይደለም ለሠራተኛ አግባብነት ያለውን የሥራ መደብ በመስጠት የማሠራት ኃላፊነትም ከአሠሪው የአስተዳደር ስራ ነፃነት /managerial prerogative power/ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ አሠሪው በንብረቱ ላይ ጉዳት ያደረሰ ሠራተኛን ከስራው ያለማስጠንቀቂያ ለማባረር የሚችል ስለመሆኑም የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1ሸ) ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ ተጠሪ ከወንጀሉ ክስ ነፃ ወጥቻለሁ ከማለት ውጪ የገንዘብ ጉድለት አልተከሠተም በማለት አልተከራከሩምም፡፡ በመሆኑም የገንዘብ ጉድለቱ መከሰቱ አከራካሪ አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ ወደቀድሞ የስራ ገበታቸው የሚመለሱበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ አዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/(ሐ),(መ) እና (ሸ)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎች መሠረት አሰሪው የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ የሚያቋርጥበትን ሁኔታ ያስቀመጠበት ዓላማ ሲታይም ሠራተኛው ስራውን በታማኝነት እንዲያከናውን ለማድረግ መሆኑ ይታመናል፡፡ አንድ ሠራተኛ ታማኝነት የሌለው መሆኑ ከታወቀ በኋላ ደግሞ አሠሪው ወደ ቀድሞ ሥራ እንዲመልሰው ማድረግ ሕጉን ለማሣካት ያለውን ግብ የሚፃረርም ጭምር ነው፡፡

በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት የአመልካች እምርጃ ሕገወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደሰረሰው በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር ባላገናዘበና የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 15"ን" ያለቦታው በመጥቀስ ከመሆኑም በተጨማሪ የሕጉንም አጠቃላይ መንፈስ መሠረት ያላደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23401 የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 64770 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ ወደ ገንዘብ ያዥነት ሥራ ሊመለሱ አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 37402

ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የንኮማድ ኃ.የተ.የግል ማህበር - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ ቡሽራ በቀለ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዮ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ በተከሣሽ ድርጅት ውስጥ በሎደር ኦፕሬተርነት ሙያ ከሚያዝያ 05 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ሲያገለግሉ መቆየታቸውንና በወቅቱም ይከፈላቸው የነበረው ወርሃዊ ደመወዝ ብር 1800.00(አንድ ሺህ ስምንት መቶ) መሆኑን ዘርዝረው ከጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠው የስራ ውል ያላግባብ መቋረጡን ጠቅሰው ውዝፈ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም የተለያዩ ክፍያዎችን በመክፈል ከስራ እንዲያሰናብት ይወሰንላቸው ዘንድ በአሁኑ አመልካች ላይ ሠኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው ፍ/ቤቱም የአሁኑ አመልካች እንዲቀርብ ጥሪ አድርጐ አመልካች መልስ በሚሠጥበት ቀነ ቀጠሮ መልሱን ይዞ ባለመቅረቡ በቂ ምክንያት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ይህንኑ መብቱን ከለሰፈ በኋላ ግራ ቀኙን በቃል አከራክሮ አመልካች ተጠሪ ከአምስት ቀን በላይ ከስራ የቀረ ስለመሆኑ አላስረዳም ተጠሪም ማስረጃ ላቀርብ ስል ተከለከልኩ በማለት ክደው ተከራክረዋል የሚል ምክንያት በመያዝ ተጠሪ ከስራ የተሠናበቱት ያላግባብ ነው ሆኖም ወደ ሥራ ቢመለሱ መልካም የሆነ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ስለማይፈጥር የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለው ተጠሪ ከስራ ይሠናበቱ በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሠበር አቤቱታ ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ በስር ፍ/ቤት መልሱን በጽሑፍ የማቅረብ መብት ያለፈበትን ምክንያት ያላግባብ መሆኑ ተጠቅሶ በቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ውሣኔ ሣይሠጥበት ማለፉ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ተጠሪ ከስራ ላይ ከአምስት ቀን በላይ መቅረትቸውን በቃል ክርክር ወቅት አምነው እያሉ እና የህክምና ማስረጃ ለማቅረብ ስሄድ የድርጅቱ ዘበኛ ከለከለኝ በማለት ተጠሪ የገለፁት ፍሬ ነገር በተጨባጭ ማስረጃ ተደግፎ ባልቀረበበት ሁኔታ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም ወደ አመልካች የማዞር ውሳኔ መሠጠቱ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም ለሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሠኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የአመልካችን የሠበር አቤቱታ ቅሬታ ነጥቦችን ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር መልስ ሠጥተዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ሐምሌ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሠጥቷል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ ከአምስት ቀናት በላይ በተከታታይ ከሥራ መቅረታቸውን ሣይክዱ በሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ የሐኪም ማስረጃውን ለአመልካች ላቀርብ ስል ዘበኛው ከልክሎኛል በማለት ያቀረቡትን ክርክር መሠረት በማድረግ ተጠሪ የተሰናበቱት ያለአግባብ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው ከሥራ እንዲሰናበቱ የወሰኑት ውሳኔ በአግባቡ መሆኑን ያለመሆኑን ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ በስራ ገበታቸው አለመገኘታቸውን በመግለጽ ያልተገኙበት ምክንያት በህመም ሆኖ ይህንኑ ማስረጃ ለአመልካች በወቅቱ ያላቀረቡ መሆኑንና ማስረጃውን ለማቅረብ ያልቻሉበት ምክንያትም የአመልካች ድርጅት ዘበኛ ወደ ግቢው ሊያስገባቸው ፈቃደኛ ባለመሆኑ ስለመሆኑ በመግለጽ ተጠሪ የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ የበታች ፍ/ቶችም ይህንኑ የተጠሪ ክርክር በቃል ክርክር ወቅት ያረጋገጡት መሆኑን ውሣኔው ያሣያል፡፡ ተጠሪ የህኪም ማስረጃውን ለአመልካች ያላቀረቡበት ምክንያት በዘብ ጥበቃ ግቢ እንዳይገቡ በተደረገው ድርጊት ነው ይበሉ እንጂ ይህንኑ ፍሬ ጉዳይ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያላቸው ስለመሆኑ ገልፀው ያልተከራከሩ መሆኑን የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ግልባጭ ይዘት የሚይሣይ ከመሆኑም በላይ ለዚህ ችሎት በሠጡት መልስም በዚህ ረገድ ማስረጃ የነበራቸው መሆኑን በመግለጽ አልተከራከሩም፡፡

እንግዲህ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ከላይ የተገለፁት ከሆኑ የአመልካችን ተግባር ህገ ወጥ ሊያሠኑ የሚችሉት ህጋዊ ምክንያቶች ከአዋጁ ጋር አገናዝቦ መመልከትን የግድ ይሏል፡፡

በመሠረቱ ያለበቂ ምክንያት ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ከስራ ገበታው ያልተገኘን ሠራተኛ አሠሪው ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ማሠናበት መብት ያለው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1)(ለ) ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ይህንኑ የአሠሪን ህጋዊ መብት ሠራተኛው ሊቃወመው የሚችለው በቂ ምክንያት ኖሮት ተቀባይነት ሲያጣ ብቻ ነው ከስራ ገበታው መቅረት አከራካሪ ባልሆነበት ሁኔታ በቂ ምክንያት ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ከስራ ገበታው መቅረቱን ያልካደው ሠራተኛ እንጂ አሠሪ ሊሆን አይችልም እንደሚታወቀው ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የክሱን ፍሬ ነገር እንዲረጋገጥለት ዳኝነት የሚጠይቅ ወገን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ከሣሽ ክሱን የሚያስረዳ ማስረጃ (Prima facie evidence) የማቅረብ ግዴታ አለበት ይኸው ግዴታ ወደ ሌላው ተከራካሪ ወገን ሊተላለፍ የሚችለው ክሱን ለማስረዳት የቀረበው ማስረጃ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ብቃት ነው፡፡

በእኛችን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ከስራ ገበታቸው ቀረሁ የሚሉበትን ምክንያት ለማስረዳት የህክምና ማስረጃ አለኝ ቢሉም ይህኑ ማስረጃ ለአመልካች አላቀረቡም፡፡ ለአመልካች የህክምና ማስረጃውን አለማቅረባቸውን ገልፀው ማስረጃውን ለማቅረብ የተቸገሩበትን ምክንያት በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ይኸው ፍሬ ነገር በማስረጃ የተደገፈ ስለመሆኑ ግን አይገልፅም፡፡ የህክምና ማስረጃውን በወቅቱ ይዘው ለአመልካች ያላቀረቡት ምክንያት በአመልካች ዘብ ጥበቃ በተደረገባቸው ክልከላ መሆኑ የማስረዳት ገዴታ ደግሞ የተጠሪ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ተጠሪ ክደው ተከራክረዋል በሚል ምክንያት ብቻ የማስረዳት ሸክሙን ወደ አመልካች በማዞር ውሣኔ መስጠቱ የማስረጃ አቀራረብ ግዴታ መርህንና የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መንፈስ ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተጠሪ ተገቢውን ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ ደግሞ የአመልካች እርምጃ ህገ ወጥ ነው ሊባል ሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ ከስራ ገበታቸው ከአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ መቅረታቸውን በግልጽ አምነው ተከራክረው እያለና ለዚህ ከስራ ለቀሩበት ጊዜም በቂ ምክንያት ያላቸው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ባልተወጡበት ሁኔታ የማስረዳት ሸክሙ ወደ አመልካች በማዞር እርምጃው ህገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 27785 ህዳር 04 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 60853 መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የፀና ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሠናበተው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል
4. መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 37573

ህዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሠ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት - ነ/ፈጅ አለምፀሐይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መሐመድ አደን - በሌሉበት

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት ሠራተኛው መብቱን የሚጠይቅበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ነው፡፡

በዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ባቀረቡት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ስላሰናበታቸው ወደ ስራ ለመመለስ ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ተጠሪ በፈፀሙት ጥፋት ከስራ መሠናበታቸው በሕጉ መሠረት መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ የዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤትም ስንብቱ ሕገ- ወጥ ነው በማለት ተጠሪ ወደስራቸው እንዲመለሱ አልያም ካሣ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ የይግባኝ ቅሬታ ለዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ክሱ በይርጋ አይታገድም፣ ስንብቱም ሕገወጥ ነው፣ ተጠሪም ወደ ስራ ቢመለሱ መልካም ግንኙነት አይኖርም ተብሎ የሚገመትበት ምክንያት ስለሌለ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራ ይመለሱ በማለት የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አሻሽሏል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ቅሬታውም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ሐምሌ 1/1999 ዓ.ም ሲሆን ክስ የመሠረቱት ጥቅምት 14/2000 ዓ.ም በመሆኑ ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ ይቋረጣል የሚል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የይርጋውን ጥያቄ ያልተቀበሉት በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል የሠበር አቤቱታ ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

እኛም የሠበር አቤቱታውን የሠበር አቤቱታ ከቀረበባቸው ውሣኔዎች እና ከሕጉ አኳያ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ ላይ እንደተመለከትነው ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ሐምሌ 1/1999 ዓ.ም ነው በማለት አመልካች ባቀረበው መከራከሪያ ላይ ተጠሪ ያቀረቡት ተቃውሞ የለም እንደዚሁም ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ ክስ ያቀረቡት ጥቅምት 14/2000 ዓ.ም መሆኑንም ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከስራ ከተሰናበቱበት ቀን ጀምሮ ወደ ስራ ለመመለስ ክስ እስከመሠረቱበት ጊዜ ድረስ ሲታሰብ ከ3 ወር በላይ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/2/ መሠረት ደግሞ ሠራተኛው የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ ተቋርጦብኛል በማለት ወደ ስራው ለመመለስ የሚያቀርበው ክስ ውሉ በተቋረጠ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚቋረጥ ተመልክቷል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካችን የይርጋ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ተጠሪ ፈጽመዋል በተባሉት ጥፋት ክስ ተመስርቶባቸው ሲጣራ ቆይቶ ፖሊስ ከወንጀሉ ነፃ መሆናቸውን ያረጋገጠው መስከረም 18/2000 በመሆኑ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ከዚሁ ቀን ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይርጋ የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች በአዋጁ አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

164 ሥር የተዘረዘሩ ሲሆኑ ፍ/ቤቱ የገለፀው ሁኔታ ይርጋን ያቋርጣሉ ተብለው ከተመለከቱት ሁኔታዎች ስር የሚካተት አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ተጠሪ በወንጀል ድርጊት ተጠርጥረው ጉዳዩ በፖሊስ ተጣርቶ ነፃ መሆናቸው እስኪረጋገጥ ድረስ የነበረውን ጊዜ በይርጋ አቆጣጠር ጊዜ ውስጥ አይካተትም በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህም አልፎ አመልካች ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ላይ ተጠሪ ያቀረቡት መስቀለኛ ይግባኝ እንኳን ሣይኖር ተጠሪውን በሚጠቅም መልኩ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ማሻሻሉ የዳኝነት አሠራር ስርዓት አለመከተሉን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ የተጠሪ ወደ ስራ የመመለስ ጥያቄ ከ3 ወር በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ውድቅ ሊደረግ ሲገባ ይህ ታልፎ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መሠጠቱ መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0/21/2ዐዐ በ28/2/2ዐዐዐ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. በአፋር ክልል የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0993 በ18/4/2ዐዐዐ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረቡት ክስ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 162/2/ በይርጋ ውድቅ ሆኗል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37575

ኅዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ቃሊቲ ባሌስትራ ማምረቻ - ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ ጠበቃ

ተጠሪ፡- ብርሃኑ ልደት ወልዴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪ ከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት በጥበቃ ሙያ እያገለገሉ ቆይተው የሰራተኛ አበል እና ገንዘብ ሰብሳቢ በመሆናቸው በሕገ ወጥ መንገድ እንደተሰናበቱ ገልፀው ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎኝ ወደ ሥራዬ ልመለስ ወይም ተገቢው ክፍያ እንዲፈፀምልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ መልሱን ሲሰጥ ተጠሪ እንደሚለው በጥላቻ ውላቸው አልተቋረጠም የተሰናበቱት የድርጅቱ ስራ ስለቀዘቀዘ ነው፡፡ የሚገባቸውን ክፍያ ወስደው ነው የስራ ውላቸው የተቋረጠው የአገልግሎትና የ"2" ወር የማስጠንቀቅያ ወስዷል፡፡ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበለትን የግራ ቀኙን ክርክር ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል በመሆኑም አመልካች ተጠሪ የተሰናበቱት የድርጅቱ ስራ ስለቀዘቀዘ ነው ይበል እንጂ ይህ ለመሆኑ አላስረዱም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በስምምነት የአገልግሎትና የ"2" ወር የማስጠንቀቂያ ተከፍሎት ይገልፃል ይሁን እንጂ የተደረገው ስምምነት በአዋጁ ቁጥር 24 መሰረት በጽሁፍ ለመደረጉ አላስረዱም ሕጉ በሥምምነት የስራ ውሉን ማቋረጥ በጽሁፍ መሆን አለበት ይላል በእርግጥ ተጠሪ የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ ወስዷል፡፡ የተቀረውን መብታቸውን መተዋቸው በሕግ ፊት ዋጋ የለውም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ውዝፍ ተከፍሎኝ ወደ ስራ ልመለስ ያለውን ፍ/ቤቱ ተቀብሎታል ምክንያቱም ተጠሪ ውላቸውን በጽሁፍ አላቋረጠም በማለት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው የ6 ወር ውዝፍ ከፍሎ ወደ ስራ ይመልሣቸው ሲል ወሰነ፡፡

አመልካችም በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የስር ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት አሻሽሎ ተጠሪ በአዋጁ ቁጥር 43/5/ መሰረት የአንድ አመት ደመወዝ ይከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2000 ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሰረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የተደረገው የሥራ ውል በጽሁፍ አልተቋረጠም ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም የጉዳዩን አመጣጥ እንዳየነው ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ሲሰራ ቆይቶ የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ ክፍያ በመቀበል ከሄደ በኋላ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ ካልሆነም ክፍያ እንዲፈፀምለት የጠየቀ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ምንም እንኳ አመልካችም በስምምነት የሚጠበቅብኝን ክፍያ ፈጽሜ አሰናብቸዋለሁ ቢልም የሥራ ውልን በስምምነት ማቋረጥ የሚቻለው በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 25/2/ መሰረት በጽሁፍ የተደረገ ሥምምነት ሲኖር ነው በተያያዘነው ጉዳይ ግን ይህ አልተፈፀመም ስለሆነም ስንብቱ ሕጋዊ ነው ለማለት አይቻልም፡፡

ይሁን እንጂ ከመዝገቡና ከቀረበው አቤቱታ ለመረዳት እንደቻልነው ተጠሪ የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ ስለመቀበሉ የሥር መዝገብ ይገልፃል፡፡ ይህ ሆኖ እያለ

በሥር ፍ/ቤት ስንብቱን ተከትሎ ተጠሪ ወደ ሥራው ይመለስ ውዝፍ ደሞዝ ይከፈለው ተብሎ ተወስኗል፡፡

ተጠሪ ወደ ሥራው ይመለስ የሚለውን ነጥብ ስናየው ፍ/ቤት በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 43/3/ መሰረት ሰራተኛው ወደ ቀድሞ ስራቸው ቢመለሱ በስራቸው ግንኙነት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ችግር በማጤን ሰራተኛው ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ እንደሚችሉ ሕግ ይደነግጋል ይህ ሆኖ ሳለ ወደ ስራው ተጠሪ ይመለስ መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የውዝፍ ደሞዝን አስመልክቶ ተጠሪ ክፍያዎች (የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ) ተከፍሎት እያለ ተጨማሪ ውዝፍ ደሞዝ ይከፈለው መባሉ አግባብ ያለው ሆኖ አላገኘንም ይሁን እንጂ ተጠሪ ካሣ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ስለዚህ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎት ወደ ሥራው ይመለስ መባሉ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23061 በሐምሌ 20 ቀን 1999 እና በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58532 በመጋቢት 22 ቀን 2000 የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተጠሪ ወደ ስራው ሊመለስም ሆነ ውዝፍ ደሞዝ ሊከፍለው አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ የስንብትና የማስጠንቀቂያ ቀደም ሲል የተከፈለው ስለሆነ ያልተከፈለው ካሣ በሕጉ መሰረት ተከፍሎት ይሰናበት ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭ እና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37778

ጎንደር 04 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አዲስ መለዋወጫ እቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አ.ማ - ጠ/ብስራት መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ካሣሁን ከበደ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በተከሣሽ ድርጅት ከታህሳስ 1 ቀን 1979 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 15 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ማገልገላቸውን፣በመጨረሻ የነበረው የስራ መደብ ደረጃም ግምጃ ቤት ትራንዚት አምስት መሆኑን ከሕብረት ስምምነቱ ውጪ ዝውውር መፈፀሙንና የስራ ውሉም ያላግባብ መቋረጡን በመዘርዘር ዝውውሩ እንዲሻር ወደ ስራ እንዲመለሱም ይወሰንላቸው ዘንድ በአሁኑ አመልካች ላይ መጋቢት 17 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ ክስ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለመሰረቱ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሰረት ቀርቦ በሰጠው የመከላከያ መልስ ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ያለበቂ ምክንያት ከስራ ስለቀሩ በአዋጁና በህብረት ስምምነቱ መሰረት መሆኑን፣ ተጠሪ በደረሰባቸው አደጋ በጊዜአዊነት ደመወዝና የውሎ አበል እየተከፈላቸው በሕብረት ስምምነቱ መሰረት ተመድበው ሣሉ በእምቢተኛነት ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ከስራ መደባቸው ላይ ባለመገኘታቸው በገዛ ፈቃዳቸው ስራውን የለቀቁና የሄዱ መሆናቸውን በመዘርዘር ስንብቱ ባግባቡ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ከሣሽ ዝውውሩ አላግባብ ነው የሚል ተቃወሞ ሲኖራቸው ክስ መመስረት ያለባቸው ወደ የተዛወሩበት ቦታ ሂደው ስራቸውን እየሰሩ መሆን አለበት እንጂ ስራቸውን አቋርጠው መሆን አልነበረበትም በሚል ምክንያት ከሣሽ ከስራ የተሰናበቱት ባግባቡ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ሰራተኛው የተፈፀመበትን ዝውውር ሕገ ወጥ ነው የሚል ቅሬታ ካለው የግድ ወደ ተዛወረበት የስራ ቦታ በመሄድ ጥያቄውን ማቅረብ የለበትም፡፡ ዝውውሩም በህብረት ስምምነቱ መሰረት የተፈፀመ አይደለም፡፡ የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ያሰባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የህብረት ስምምነቱንና የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔን መሻሩንና ዝውውሩ ትክክል አይደለም የሚባል ቢሆን እንኳ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ሣይኖረው ተመልክቶ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ውሣኔው ሊሻር ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው ሐምሌ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን የሰጡ ሲሆን የአመልካች ነ/ፍጅም በበኩላቸው መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው ተጠሪ ወደተዛወሩበት ቦታ ሳይሔዱ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት መቅረታቸውን መሰረት በማድረግ መሆኑንና ተጠሪ በበኩላቸው የሚከራከሩት ወደተዛወሩበት ቦታ ያልሄዱት ዝውውሩ በስራ ላይ ያለውን የህብረት ስምምነት እና አዋጁን ያላገናዘበ በመሆኑ የዝውውር ደብዳቤው ከደረሣቸው ጊዜ ጀምሮ ከስራ ቦታቸው ሣይቀሩ ቅሬታ እያሰሙ ባለበት ሁኔታ በስራህ ላይ አልተገኘህም በሚል ሕጋዊ ሽፋን የስራ ውል ማቋረጥ ሕገ ወጥ ድርጊት ነው በሚል መሆኑን ነው፡፡ እንግዲህ አመልካች ተጠሪን ከአዲስ አበባ ወደ ጐንደር አዛውሮ ተጠሪ የዝውውሩ ደብዳቤ ከተሰጣቸው በኋላ ወደ ተዛወሩበት ቦታ በመሄድ ስራ ሣይጀምሩ አምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ያለፉባቸው፣ ለዚህም በቂ ምክንያት ብለው የሚከራከሩት የዝውውሩን ሕገ ወጥነት በመቃወም ቅሬታ በማሰማት ምላሹን እየተጠባበቁ የነበሩበትን ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ወደ ተዛወሩበት ቦታ አለመሄዳቸውንና ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ላይ አለመገኘታቸውን በማመን የተከራከሩ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡

በመሰረቱ በቂ ምክንያት ሣይኖረው በተከታታይ ለአምስት የስራ ቀናት በስራ ገበታው ያልተገኘ ሰራተኛን ማስጠንቀቂያ መስጠት ሣያስፈልግ ከስራ እንዲያባርረው ለአሰሪው ሕጉ ፈቃድ የሰጠው መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ለ/ ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ ሰራተኛው የአሰሪውን አድራጐት ሊቃወመው የሚችለው ለመቅረቱ በቂ ምክንያት መኖሩን በማስረዳት ነው፡፡ ከስራ ለመቅረት በቂ ምክንያት ሊሰጥ የሚችሉት ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ግን ሕጉ አመልካች ወይም ዝርዝር ሁኔታዎች አላስቀመጠም፡፡ ሆኖም በቂ ምክንያት የሚለው ሐረግ መመዘኛቸው ሰራተኛው ከስራ ቦታው ሊገኝ በማይችልበት ደረጃ ላይ አድረሰውት ነበር ተብሎ ሊታመንበት የሚገባ ስለመሆኑ ከአዋጁ አጠቃላይ አላማና ከተጠቃሹ ድንጋጌ መንፈስ ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ በመሆኑም ከስራ የቀረ ሰራተኛ በቂ ምክንያት ኑሮት ቀርቷል ለመባል የሚቀርበው ማስረጃ ሰራተኛውን በስራ ቦታ ለመገኘት የሚያስችል መሰናክል የነበረ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ሰራተኛው በማይረባ ምክንያት ሁሉ ከስራ ገበታው ባለመገኘት በአሰሪው ምርትና ምርታማነት ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ አይቀሬ ነው፡፡

እኛችን ወደ አለው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ከስራ ገበታቸው ያልተገኙበት ምክንያት የአመልካችን ዝውውር በመቃወም ቅሬታ አቅርበው ምላሽ እየተጠባበቁ ስለመሆኑ ከላይ ተገልጿል፡፡ አንድ ሰራተኛ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መዛወር ደግሞ ሰራተኛው ወደ ተዛወረበት ቦታ በመሄድ በስራው ላይ ለመገኘት የሚያስችል መሰናክል ነው ተብሎ በበቂ ምክንያት መመዘኛ ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡ ሰራተኛው በዝውውሩ ቅሬታ ካለውም ወደ ተዛወረበት ቦታ በመሄድና ስራውን በተገቢው መንገድ እያከናወነ ስልጣን ላለው አካል አቅርቦ ተገቢውን መፍትሔ ከመጠየቅ በስተቀር ከስራ ቦታው ሣይገኝ ቅሬታውን በማቅረቡ ብቻ ከስራ ገበታው በበቂ ምክንያት ቀርቷል ሊባል አይገባም፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ ተቀባይነት ከሌለው የመነሻ ሐሣብ የመነጨ ከመሆኑም በላይ በስረ-ነገር ስልጣኑም የሚወድቅ አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ገበታቸው አለመገኘታቸው እና ያቀረቡት ምክንያትም በቂ ነው ተብሎ የሚወሰድ አለመሆኑ በአግባቡ ተረጋግጦ እያለ የከፍተኛው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ መሻሩ ተቀባይነት ባለው ምክንያት ሆኖ ስላላገኘነው ውሣኔው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ለ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው በሚል ምክንያት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊባል የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58518 ሚያዝያ 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሸሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26458 ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ ዝውውሩን በመቃወም ቅሬታ በማቅረብ ምላሽ እየተጠባበቁ የነበሩ መሆኑ ከስራ ለመቅረት በቂ ምክንያት ነው ተብሎ ሊወሰድ የማይገባ በመሆኑ ተጠሪ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ከስራ ገበታቸው ቀርተዋል በማለት አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ማቋረጡ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 03171

ኅዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢት/ኤሌክትሪክ ኃ/ኩርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ዝግአለ አሰፋ

ተጠሪ፡- ወ/ት ትርሲት ደገፉ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የስራ ውል አመሰራረትን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ድርጅት የምስ/ሪጅን ጽ/ቤት ለክለርክ ታይፒስት ፀሐፊ ደመወዝ ብር 453.00(አራት መቶ ሃምሳ ሶስት) በድርጅቱ ስኬል መሰረት ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ አውጥቶ ተጠሪ ተወዳድረው ማለፋቸው በጥቅምት 27 ቀን 1999 ዓ.ም ተገልያላቸዋል፡፡ ከሕዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምረው የድርጅቱ ሰራተኛ መሆናቸው ከአሻራ ምርመራ በተፃፈ ደብዳቤና በጡረታ ቅጽ ላይ ተገልጿል፡፡ ምድብ ቦታቸው ደደር መሆኑ ተገልያላቸዋል የመጀመሪያ ስራቸውን ለቀው ለመሄድ ሲዘጋጁ ያለበቂ ምክንያት የስራ ውላቸው መሰረዙ በታሕሣስ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ተገልያላቸዋል፡፡ ስለዚህ የስራ ውሉ የተቋረጠው ያለአግባብ በመሆኑ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ፣ ከሕዳር 1 ቀን 1999 - ታህስስ 25 ቀን 1999 ያለው ደመወዛቸው እንዲከፈላቸው፣ የስራ ውላቸው ያለአግባብ ስለተቋረጠ የ6 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ፤በአመልካችና በተጠሪ መሐከል የፀና የስራ ውል የለም፣በድርጅቱ አሰራር መሰረት የተፈፀመ የቅጥር ውል የለም፣ አሻራ ምርመራ እንዲያደርጉ መላክ የስራ ውል መፈፀም ማለት አይደለም፣በቅጥር ውል ለሙከራ ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኛን እንኳን ያለምንም ማስጠንቀቂያ ማሰናበት ይቻላል፡፡ ከስራ ተሰናበትኩ ይበሉ እንጂ የስንብት ደብዳቤ አላያያዙም፣የቅጥር ውል አለ ቢባል እንኳን ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄ በ3 ወር ጊዜ በይርጋ ይታገዳል፣የውል ድርድር አለ ቢባል እንኳን በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1693/1/ እና /2/ መሰረት ድርድሩ እንዳልተደረገ ይቆጠራል፣ከክሣቸው ጋር ያቀረቧቸው ማስረጃዎች የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት መኖሩን አያስረዱም፣ ስለሆነም ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም፣ላልተሰራ ስራ ደመወዝ ሊከፈል አይገባም፣ የመብት ጥያቄ ማንሣት የሚችለው 45 ቀናት ያገለገለ ሰራተኛ ነው፣የአሻራ ምርመራ ደብዳቤው የአሻራ ውጤት ለመውሰድ በመጠባበቅ ላይ ያለ መሆኑን ስለሆነ ውጤቱ ሣይደረስ ቅጥር ሊፈጸም አይችልም በማለት የቀረበበትን ክስ አስተባብሎ ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የቅጥር ውል አለ፣ተጠሪ የ6 ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ምድብ ስራቸው ይመለሱ፣ እንዲሁም ከሕዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ታህሣስ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ያለው ደመወዝ ይከፈላቸው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ በአመልካችና በተጠሪ መሐከል የስራ ውል የለም፣ላልተሰራ ስራ ደመወዝ ሊከፈል አይገባም፣የሚሉ ናቸው፡፡ ይህ ችሎትም የተጠሪ የስራ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቋረጠው ያለአግባብ ነው ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ ተጠሪም ቀርበው ተከራክረዋል፡፡

ከላይ የተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክርና የፍ/ቤቶቹ ውሣኔ ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በዚህም መዝገብ ውሣኔ ማግኘት የሚያሻቸው ነጥቦች 1. በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የስራ ውል አለ? የለም? 2. አለ ከተባለ ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ ሊመለሱ ይገባል? አይገባም የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፣ተጠሪ በክሣቸው በአመልካችና በተጠሪ መሐከል የስራ ውል አለ በማለት ተከራክረዋል፡፡ ለዚህም መሰረት ያደረጉት የአመልካች ድርጅት ምስ/ሪጅን ጽ/ቤት ለክለርክ ታይፒስት ፀሐፊ ደመወዝ ብር 453.00 ማስታወቂያ ወጥቶ ተወዳድረው ማለፋቸውን፣ከዚህ በኋላ አመልካች መስሪያ ቤት ከነዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ የመ/ቤቱ ሰራተኛ መሆናቸውን ገልፆ የአሻራ ምርመራ ደብዳቤ መፃፉንና በጡረታ ቅጽ ላይ ማረጋገጡን፣ምድብ ቦታቸውም ደደር መሆኑን ማሣወቁን ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ከፍ ሲል በተጠሪ የተገለፁትን ፍሬ ነገሮች ክዶ አልተከራከረም፡፡ ነገር ግን ፈተናውን ማለፋቸውም ሆነ ለአሻራ ምርመራ የተፃፈው ደብዳቤ የስራ ውል አይመሰርትም፡፡ በመ/ቤቱ አሰራር መሰረት የተፈፀመ የስራ ውል ስለሌለ ከተጠሪ ጋር ውል አለ ሊባል አይችልም በማለት ተከራክሯል፡፡ በመሆኑም የስራ ውል አመሰራረትን በተመለከተ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 የሚደነግገውን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ አዋጅ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነትን በሚመለከተው ክፍል ስር የሚገኘው ምእራፍ አንድ ዘርፍ አንድ የስራ ውል በምን መልኩ መመስረት እንደሚገባው ይናገራል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 4/1/

> “ ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው፣በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአሰሪው ለመስራት ቢስማማ በሁለቱ ማሐከል የስራ ውል ይመሰረታል፡፡”

በማለት ያስቀምጠዋል፡፡ በመሆኑም የስራ ውል ማለት አንድ ሰራተኛ በአሰሪው መሪነት የአሰሪውን ስራ፤ በውሉ ላይ ለተመለከተው የስራ ጊዜ፤ለመስራት የሚያደርገው ስምምነት መሆኑ በዚህ አንቀጽ ትርጓሜ ተሰጥቶበታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የስራ ውሉ እንዴት መደረግ እንዳለበትና ሊይዛቸው ስለሚገባው ነገሮች በንኡስ ቁጥር 2 እና 3 ሥር ተመልክተዋል፡፡ በዚህም መሰረት የስራ ውል ተዋዋይ ወገኖች በውሉ መሰረት የሚኖራቸው መብትና ግዴታ በማያጠራጥር አኳኋን በሚያውቁበት ሁኔታ በግልጽ መደረግ ያለበት ሲሆን ውሉም የስራውን አይነትና ቦታ፣ ለስራው የሚከፈለውን ደመወዝ መጠን፣ የሰሌቱን ዘዴ፣ የአከፋፈሉን ሁኔታና ጊዜ እና ውሉ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ መያዝ እንደሚኖርበት ተገልፆል፡፡ የስራ ውሉ በዚህ መልክ መደረግ የሚኖርበት ቢሆንም ግን በሕግ በተለየ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር የተለየ ፎርም የሌለው መሆኑ፣ በአንቀጽ አምስት ስር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የስራ ውል፤ሕግ ካላስገደደ በቀር፤በማንኛውም አይነት ሊቋቋም እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከነዚህ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎች አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመረምር አመልካች ለክለርክ ታይፒስት ጸሐፊ ቦታ በወር ብር 453.00 ደመወዝ ለመቅጠር ማስታወቂያ በማውጣቱ ተጠሪ በማስታወቂያው መሰረት ለመቀጠር ቀርበው ፈተናውን ተፈትነው አልፈዋል፡፡ ፈተናውን ማለፍ ብቻ ሣይሆን ከነዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ የድርጅቱ ሰራተኛ መሆናቸው ተገልፆ የአሻራ ምርመራ እንዲደርግላቸው ደብዳቤ ተጽፎ እና የጡረታ ቅጽ ተሞልቶ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተላልፏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምድብ የሥራ ቦታቸው ደደር መሆኑም ተገልፆላቸዋል፡፡ የስራ ውል የተለየ ፎርም የሌለው በመሆኑ አመልካች የክለርክ ታይፒስት ፀሐፊ ለመቅጠር የውል ድርድር ማቅረቡ ተጠሪ ደግሞ ድርድሩን ተቀብለው ፈተና ተፈትነው ማለፋቸው በቀጣይነትም አመልካች ተጠሪ የድርጅቱ ሰራተኛ ሆነው መቀጠራቸን በመግለጽ ለተለያዩ መ/ቤቶች በላከው ደብዳቤና የጡረታ ቅጽ ማረጋገጡ በሁለቱ በሐከል የውል አቀራረብና አቀባበል መኖሩን ያመለክታል፡፡ የተጠሪዋ የምድብ ስራቸው ደደር መሆኑ፣የስራው አይነት የክለርክ ታይፒስት ጸሐፊ መሆኑ የተጠሪዋ ደመወዝ በወር ብር 453.00 እና በድርጅቱ ስኬል መቀጠራቸው ሁሉ ግራ ቀኙ አውቀውት የተስማሙበት በመሆኑ በአዋጁ የስራ ውል አመሰራረት የሚጠይቀውን የሚያሟላ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ጋር የስራ ውል የለንም በማለት ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካቹ ተጠሪ በመ/ቤቱ የአሰራር ደንብ መሰረት አልተቀጠርኩም በማለት የሚከራከር ሲሆን ይህ ደንብ መኖሩንና በዛ ደንብ መሰረት አለመቀጠራቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማስረዳት አለመቻሉን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መሐከል የቅጥር ውል አለ በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሱበት መደምደሚያ የህግ ስህተት አለው ለማለት አልተቻለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የሥራ ውል አለ ከተባለ ውሉ የተቋረጠ ነው? አይደለም? አይደለም የሚባል ከሆነ ውጤቱ ምንድነው የሚለው ነው፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ከተጠሪ ጋር የስራ ውል አልመሰረትንም ከማለት በቀር የስራ ውሉ የተቋረጠበትን ምክንያት አልገለፀም፡፡ በእርግጥ በሰበር ችሎት በቀረበው አቤቱታ ላይ ለውስጥ ሰራተኞች የእድገት ማስታወቂያ ሣይወጣ ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ መውጣቱ ተገቢ ባለመሆኑ ውሉ መሰረዙን ገልጿል፡፡ ይህ ክርክሩ በስር ፍ/ቤት ያልተነሣ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክንያቱም የስራ ውልን ለማቋረጥ በቂ አልነበረም፡፡ የስራ ውል ያለአግባብ ከተቋረጠም ሰራተኛው ወደ ስራው ሊመለስ የሚገባው መሆኑና ወደ ስራ መመለስ ካልፈለገ ግን ካሣ ተከፍሎት ሊሰናበት እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 43/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ የስራ ግንኙነቱ ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ ሰራተኛውን ወደ ስራ ከመመለስ ይልቅ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት መወሰን እንደሚቻል የዚሁ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 3 ያመለክታል፡፡ በተያዘው ጉዳዩ ተጠሪ ወደ ስራ መመለስ የፈለጉ በመሆኑና ወደ ስራ መመለሣቸው በስራ ግንኙነቱ ላይ የሚፈጥረው ችግር ስለመኖር በአመልካች በኩል የተነሣ ክርክር ስለሌለ ተጠሪ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ማለት አልተቻለም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ያላግባብ የስራ ውሉ የተቋረጠበት ሰራተኛ ወደ ስራ እንዲመለስ ሲወሰን በተጨማሪ ከስድስት ወር የማይበልጥ ውዝፍ ደመወዝ እንደሚወሰንለት ከአዋጁ አንቀጽ 43/5/ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚሁ መሰረት ተጠሪ ወደ ስራ ሲመለሱ የ6 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ በአግባቡ ነው፡፡

በሌላ በኩል ክክርክሩ ሂደት ተጠሪ ገና ስራ ሣይጀምሩ ውሉ መቋረጡን መረዳት ችለናል፡፡ ነገር ግን በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 54/1/ መሰረት በሕግ በሌላ አካኋን ካልተወሰነ ደመወዝ የሚከፈለው ለተሰራ ስራ ብቻ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ስራ ሣይሰሩ ከሕዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣስ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ያለው የአንድ ወር ከ25 ቀናት ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19067 በሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03174 በጥር 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ከኅዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣስ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ያለው የአንድ ወር ከ25 ቀናት ደመወዝ ሊከፈላቸው አይገባም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ
4. ይህ ችሎት በመጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36210

ጎዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቃቂ መለዋወጫ እቃዎችና መሣሪያዎች አ/ማ - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ኃይለ ሳልቫልቶር - ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት የሥራ ድልድል አብረውኝ እንደሚሠሩት ሠራተኞች ከደረጃ 6 ወደ 8 ላይ እንድመደብ ይወሰንልኝ ሲል ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ደረጃ 8 ላይ የተመደቡት 19 ዓመት እና በላይ ልምድ ያላቸውና በራሳቸው መስራት የሚችሉትን ነው፡፡ ተጠሪ ልምድም የላቸውም፣ መዋቅሩ መሠረት ያደረገው የሥራ ፍላጎትና ፍቅር፣ ውጤታማነት ታይቶ ነው፤ ስለዚህ ተጠሪ ለቦታው አይገቡም ብሎ ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበለትን የግራ ቀኙን ክርክር ካለው ሕግ ጋር በመመርመር አመልካች የሥራ ምድቡን ለመስጠት መሠረት ያደረገው ልምድና የትምህርት ደረጃ ብቻ አይደለም የታየው፣ ነገር ግን ታማኝነት የስራ አፈፃፀም እና ውጤታማነትም ታይቶ ስለሆነ በአግባቡ ነው ብሎአል፤ ነገር ግን ቦታው ለምን እንደማይገባቸው ከመናገር ውጪ ቦታው እንደማይገባቸው ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡

ተጠሪ አብረውኝ ለነበሩት ደረጃ 8 ሰጥቷል የሚለውን ቅሬታ አመልካች አላስተባበለም በማለት ተጠሪ በደረጃ 8 ላይ እንዲመደብ እና በደረጃ 8 የሚከፈለው ክፍያ እንዲከፈለው ወስኗል፡፡

አመልካችም በዚህ ፍ/ቤት በተሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት ቅሬታውን ቢያቀርብም ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ውሣኔው ጉድለት የሌለበት መሆኑን ገልፆ ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 1 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታውን አቅርቧል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነውም ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት መዋቅር መሠረት ወደ ደረጃ 8 ከፍ ብሎ እንዲመደብ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረት ይህንን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ጉዳይ ለክርክሩ ዋናው ነጥብ የሆነው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በደረጃ 6 ላይ ሲሰራ ቆይቶ ወደ ደረጃ 8 መመደብ ሲገባው የተከለከለ መሆኑን ገልፆ በማመልከቱ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤትም በማከራከር ተጠሪ ወደ ደረጃ 8 እንዲመደብ እና ክፍያውም እንድፈጽምለት ወስኗል፡፡

የአመልካች ድርጅት አዲስ መዋቅር መዘርጋቱን ሳይክድ በዚሁ አዲስ አሰራር ከደረጃ 6 ወደ 8 ሊያድጉ የሚችሉትን /የሚገባቸውን/ ሠራተኞች ራሱ ባወጣው መስፈርት መሠረት እንደለየ እና ተጠሪ ለዚህ ቦታ እንደማይመጥኑ ከምክንያቱ ጋር ገልጿል፡፡ ተጠሪም በዚሁ መሠረት በደረጃ 7 ላይ እንዳሉም መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ተጠሪ ሊመጥን በሚችልበት የተመደበ መሆኑን መገመት ይቻላል፡፡ አሠሪ የራሱን ሥራ ለማቀላጠፍ እና ምርታማ ለመሆን ሰራተኞችን እንደየችሎታቸውና እውቀታቸው ይጠቅሙኛል ባለው ቦታ በሕጋዊ መንገድ መደልደልም ሆነ መመደብ የሚከለክለው ሕግ የለም፡፡ ከሱ /ከድርጅቱ/ በላይ ስለሠራተኞቹ የሚያውቅ ሊኖር አይችልምና፡፡

ስለዚህ የአመልካች ድርጅት ተጠሪን ወደ ደረጃ 8 /ስምንት/ የማታሳድግበትን ምክንያት አላስረዳህም እና ወደ ደረጃ 8 አሳድገህ የመደቡን ክፍያም ፈጽም ተብሎ መወሰኑ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 28621 በቀን 11/4/2000 ዓ.ም. የፌ/ከ/ፍ/በመ/ቁ. 62/09 በቀን 16/5/2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤቶች በድርጅቱ /በአመልካች/ ሥራ ገብተው ሠራተኛን አሳድግ በማለት መወሰን አይችሉም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 34669

ታህሳስ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- አድማስ ኮሌጅ - ጠበቃ አበበ ኃይሌ ቀረበ

ተጠሪ፡- ሠለሞን ሙሉዓለም - በሌለበት የሚታይ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዮ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ መጋቢት 08 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ከታህሳስ 01 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ የካቲት 29 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 1800.00 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ ብር/ እየተከፈላቸው በመምህርነት ስራ ከአመልካች ድርጅት ጋር መስራታቸውን ሆኖም ያላንዳች ጥፋትና ማስጠንቀቂያ አሠሪው ድርጅት ከሥራ ያሠናበታቸው መሆኑን ዘርዝረው የሥራ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሠናበቱ የስራ ማስረጃ እንዲሠጣቸው ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በፈጸሩት መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም የተጠሪን የስራ ስንብት አግባብነት በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ የተጠሪ የስራ ስንብት አግባብ ነው በማለት በምክንያትነት ያቀረባቸው ነጥቦችም ተጠሪን በመደጋገም የስራ ሰዓት አለማክበር የተማሪዎችን ውጤት ከአንድ ወር በላይ በእጁ ማቆየቱና ውጤቱን ሣይመልስ መቅረቱ እንዲሁም ተማሪዎች ያላገኙትን ውጤት መስጠታቸው በኮሚቴ ተጣርቶ መረጋገጡን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የስር ፍ/ቤትም የአመልካችን ምስክሮች ከሠማ በኋላ የተጠሪን ከስራ መሠናበት አግባብነት በጭብጥነት ይዞ ጉዳዮን ከመረመረ በኋላ በስንብት ደብዳቤው ላይ የተገለፀው ጥፋት ተጠሪን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሠናብት አይደለም በማለት የስራ ስንብቱ ያላግባብ ነው ካለ በኋላ የተጠሪ ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄ ተቀባይነት ስለሌለው በአማራጭ የጠየቋቸው የስንብትና የካሣ ክፍያዎች እንዲከፈሉ የምስክር ወረቀትም እንዲሠጣቸው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፈጸሩት ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይሄው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ታህሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ የተማሪዎችን የፈተና ወረቀት ሣይመልስ መቅረቱ ለተማሪዎች ድጋሚ ፈተና መሰጠቱን ይህን ለማድረግም ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜ ማወጣታቸውን ይህም በኮሌጁ ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን የሚያረጋጋጥና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ስር የሚወድቅ ሆኖ እያለ የታለፈው ያላግባብ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባል ተብሎ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ ቢደረግላቸውም ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ታዝዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በህገ-ወጥ መንገድ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ ይሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው በአመልካች ድርጅት በሚሠሩት የመምህርነት ሙያ የተማሪዎችን ውጤት በወቅቱ ሣያስገቡ በመቅረታቸው ስለመሆኑ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ፈተናውን በድጋሚ እንዲወስዱ መደረጉንና እንዲህ ሲደረግም ለተማሪዎቹ ለአንድ ሣምንት ‹‹ቲቶሪያል›› ተሰጥቶ ስለመሆኑ የአመልካች የሠው ምስክሮች መመስከራቸውን ከስር ፍ/ቤት ዋና መዝገብ ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ የተማሪዎችን ውጤት እንዲያስገቡም በስልክና በተለያዩ መንገዶች ተጠይቀው ሊመልሱ ያልቻሉ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

እንዲህ ለስራ ስንብቱ በምክንያትነት የተጠቀሰው የተጠሪ የተማሪዎችን ውጤት በወቅቱ አለመመለስና ይህንኑ አላፊነታቸውን ባግባቡ አለመወጣት ስለመሆኑ የአመልካችን ማስረጃዎች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም ይኸው ፍሬ ጉዳይ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ተገንዝቦ ምክንያቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ስር የሚወድቅ አይደለም ሲል ነው የሥራ ሥንብቱን ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው፡፡ በእርግጥ የስር ፍ/ቤት በስራ ስንብቱ ላይ የተመለከተውን የተጠሪን ጥፋት ይዘቱን በተባለው መልክ ከተመለከተው ጥፋቱ በአዋጁ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሠናበት ከሚያስችሉ ምክንያቶች ውስጥ ሊካተት የማይችል መሆኑን መገንዘብ ይችል ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ በተጠቃሹ አዋጅ ስር የተመለከቱት ምክንያቶች በክርክሩ ወቅት የሚረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮችንና የአዋጁን አጠቃላይ ዓላማ በመመርመር ሊተረጐሙ የሚችሉ ስለመሆናቸው መገንዘብ አያዳግትም፡፡ አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በማለት ነው፡፡ ጉዳት ደረሰ የተባለውም ተማሪዎች እንደገና ሊፈተኑ ሲደረግ የጊዜ፣ የጉልበት፣ የወረቀት ወጪ ከመደረጉም በላይ የኮሌጁ መልካም ስም ጠፍቷል በሚልም ጭምር ነው አመልካች ለዋቢነት የሚጠቅሰው ድንጋጌም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ስር የተመለከተውን ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ በአሠሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሠናበት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ነው፡፡ ንብረት ለሚለው ቃል በአዋጁ ሥር የተመለከተ ትርጓሜ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ከአዋጁ ዓላማና ከአሠሪው ድርጅት ባህርይ እንዲሁም ከንብረት ህግ ጽንሰ ሀሣቦች ጋር በማዛመድ ለቃሉ ትርጉም መሰጠት ፍትሐዊነት ይኖረዋል ምክንያቱም ንብረት ለሚለው ጽንሰ ሀሳብ ሁሉንም የሚያስማማ ትርጉም መስጠት የሚችል አይደለምና፡፡ በመሆኑም የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን አጠቃላይ ዓላማም ሆነ የንብረት ህግ ጽንሰ ሀሣቦች ባህርያት ግንዛቤ ውስጥ ስናስገባ ንብረት ማለት ዋጋና ኢኮኖማያዊ ጠቀሜታ ያለው እንዲሁም በአብዛኛው ሀብትነት ሊያዝ የሚችል ነገር መሆኑን ለመገንዘብ አስቸጋሪ አይሆንም ዋጋና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ሆኖ በባለሀብትነት ሊያዝ የሚችል ነገር ላይ ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ያደረሰ ሰራተኛ ከሆነ በአሠሪው ንብረት ላይ በህጉ አነጋገር ጉዳት አድርሷል ለማለት የማይቻልበት ምክንያት የለም፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም የተጠሪ አድራጐት ለአመልካች ዋጋና ኢኮኖማያዊ ጠቀሜታ ባለው ነገር ጉዳት አላደረሰም የሚል አይደለም በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በተጠሪ የስንብት ደብዳቤ ላይ የተገፀውን ምክንያት እንዳለ በመውሰድ የደረሰበት ድምዳሜ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ ባለመምረጥና አጠቃላይ ይዘቱንና መንፈሱን ባለማገናዘብ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22051 ሰኔ 06 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 57644 ታህሳስ 09 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ወጪና ኪሣራ የራሱን ይቻል ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.39118

ታህሳስ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡-ዓብዱልቃድር መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ደሣለኝና ቤተሰቡ ኃላ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ ወ/ሥላሴ ብርቱ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ፈቃዱ በላይ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት የክስ ማመልከቻ በአመልካች መ/ቤት ከመጋቢት 16 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ በሹፌርነት ተቀጥረው እየሠሩ ባሉበት ሁኔታ አመልካች ያለጥፋትና ማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን በመግለጽና ሊከፈሉ የሚገባቸውን ክፍያዎችን በመዘርዘር በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ሲሆን የአሁኑ አመልካች በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርቦ ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ለስራ ሊገለገሉበት የተሰጣቸውን ብሪጅ ስቶን ጐማ ተረኛ በነበሩበት ጊዜ መውሰዳቸውን ወይም እንዲወሰድ በማድረጋቸው በመሆኑና ይህም አድራጐት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/,/ቀ/ እና 14/2/ለ/ መሠረት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት በመሆኑ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ከመከራከሩም በተጨማሪ ክፍያዎችን በተመለከተም ተገቢነት የላቸውም የሚላቸውን ምክንያቶችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም በአመልካች በኩል የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ሐምሌ 04 ቀን 1998 ዓ.ም ብሪጅ ስቶን ጐማ የጠፋ መሆኑን እና ጠፋ በተባለ ጊዜ ተጠሪ ተረኛ የነበሩ መሆኑን ከሚያስረዱ በቀር ተጠሪ ለእራሱ ወይም ለሌላ ሰው ብልጽግና በመሻት የአመልካችን ንብረት የሆነውን ጐማ ላይ አላግባብ የተጠቀመ መሆኑን፣ አመልካች በግልጽ ሳይፈቅድ ከስራ ቦታ ጐማውን የመውሰድ ህገ ወጥ ተግባር ተጠሪ የፈፀመ መሆኑን አያስረዱም፣ አመልካች የማስረዳት ሸክሙን አልተወጣም የሚሉትን ምክንያቶችን በመዘርዘር የስራ ውል ማቋረጥ እርምጃ አግባብ አይደለም ሲል ከወሰነ በኋላ ክፍያዎችን በተመለከተም ተገቢ ነው ያለውን ወስኗል፡፡ በዚህ የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃ አግባባ አይደለም ተብሎ በተሰጠው የውሣኔ ክፍል የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ይኸው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/ መሠረት የአሠሪው ንብረት ወይም ገንዘብ መጥፋት ብቻውን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ብልጽግና በመሻት የተፈፀመ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቆረጥ በቂ አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ የተረከቡት የስኮርት ጐማ እንደጠፋ ራሳቸው በፃፏቸው የተለያዩ ፅሑፎች ተረጋግጦ እያለ እና ለጠፋው ጐማ ኃላፊ የማይሆኑበትን ምክንያት ማስረዳት ሲገባቸው ሳያስረዱ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/,/ቀ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርቡ ተደርጐ መስከረም 22 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠፋ የተባለውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጐማ በተመለከተ አመልካች ለዓ/ህግ አመልክቶ ክስ ካቀረበ በኋላ ተጠሪ ለስራ ክርክር ችሎት ክስ መስርተው በክርክር ላይ ያሉ መሆኑን አመልካች እያወቀ በዓ/ህግ በኩል የቀረበውን ክስ ማንሳቱ የአመልካችን ንብረት ተጠሪ ያልወሰዱና ለግል ጥቅም አለማዋላቸውን በራሱ የሚያስረዳ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው የወንጀል ክሱ የተነሳበት ምክንያት ለተጠሪ ትብብር ለማድረግ የተደረገ መሆኑንና ይህም አመልካች ጠፋብኝ የሚለውን ተለዋጭ ጐማ አልጠፋም የሚል ማረጋገጫ ያልሰጣቸው መሆኑን እንደሚያሳይ ገልፀው ህዳር 05 ቀን 2001 ዓ.ም መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የፁሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃ አግባብ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ የተረከቡትን የአመልካች መ/ቤት ንብረት የሆነው ብሪጅ ስቶን ጐማ በእጃቸው አለመገኘቱ እና በኋላም ለአመልካች መ/ቤት ያልመለሱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም እስከዚህ ችሎት ባደረጉት ክርክር የአከራካሪው ጐማ መጥፋትን ክደው የማይከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ የሚከራከሩበት የአመልካችን ጐማ ያልወሰዱና ለግል ጥቅማቸው ያላዋሉ መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶችም ተጠሪ የተረከቡት የአመልካች ጐማ መጥፋቱን አመልካች ማስረዳቱን እያመኑ የአመልካች እርምጃ ህገ ወጥ ነው ወደ ሚለው ድምዳሜ የደረሱት አመልካች ጐማው መጥፋቱን ከማስረዳት በተጨማሪ ተጠሪ ድርጊቱን የፈፀሙት ለራሳቸው ወይም ለሌላ ሰው ብልጽግና በመሻት መሆኑን የማስረዳት ሸክም አለበት፣ ይህንኑ ግዴታም አልተወጣም በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሠረቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/መ/ እና /ቀ/ ስር የተመለከቱት ምክንያቶች የስራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች ናቸው፡፡ አመልካች የሚከራከረውም እነዚህን ምክንያቶችን በመጥቀስ ነው፡፡ የሰጠው ምክንያትም ተጠሪ ለስራ ሊገለገሉበት የተሰጣቸውን የብሪጅ ስቶን ጐማ አጥፍተዋል በሚል ነው፡፡ ይኸው ጐማ የጠፋው ተጠሪ ተረኛ በነበሩበት ወቅት ስለመሆኑ እና መጥፋቱም በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ በሹፌርነት ሙያ የተቀጠሩ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ከመሆናቸውም በላይ ጐማው ተረኛ ከነበረው ሌላ ሹፌር አልተረከብኩም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሣያል፡፡ በመሆኑም ከተረኛ ሹፌር መኪናውን ተጠሪ ከተረከቡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/3/ ስር እንደተመለከተው ለስራው የሚሰጡትን መሣሪያዎች በጥንቃቄ የመጠበቅ አላፊነት አለባቸው፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግን ተጠሪ ይህንኑ ግዴታ አለመወጣታቸውን ነው፡፡ ይልቁንም ተጠሪ መኪናውን ተረክበው በራሣቸው ቁጥጥር ስር ባደረጉበት ወቅት ጐማው አለመጥፋቱና ይኸው ጐማው በምን ሁኔታና ምክንያት ሊጠፋ እንደቻለ ተጠሪ ማስረዳት ያልቻሉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14/2/ለ/ ስር እንደተመለከተው የጐማው በህገ ወጥ መንገድ የመጥፋቱ ሁኔታ ከተጠሪው ጋር በቀጥታ ግንኙነት የለውም ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ የተረከቡት ብሪጅ ስቶን ጐማ በእጃቸው አለመገኘቱ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈፀመው የራስን ወይም የሌላ ሰው ብልጽግና በመሻት ጭምር ስለመሆኑ ሊረጋገጥ የሚገባው ነው ተብሎ በህጉ በመስፈርትነት ያልተቀመጠ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ይኸው ነጥብ ንብረቱ መጥፋቱ ከተረጋገጠ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ ከአሠሪና ሠራተኛ እና ማስረጃ ህግ አጠቃላይ መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነውና፡፡ በመሆኑም ከፍ ሲል እንደተገለፀው የጐማው መጥፋት ከተጠሪ ጋር ግንኙነት የለውም የሚባልበት የህግ ምክንያት ካለመኖሩም በላይ ድርጊቱ የተፈፀመው የራስን ወይም የሌላ ሰው ብልጽግና በመሻት ስለመሆኑ አመልካች እንዲያስረዳ የሚገደድበት የማስረጃ ሸክም የሌለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ተጠሪ የአመልካችን ንብረት ያልወሰድኩና ለግል ጥቅም አለማዋሌን የሚያረጋግጠው ጉዳይ አመልካች በዓ/ህግ በኩል መስርቶት የነበረውን የወንጀል ክስ ማንሣቱ ነው በሚል ያቀረቡትን ክርክር ስንመለከተውም የወንጀል ክሱን መተው በፍትሐብሔር ረገድ ያለውን ክርክር ሊያቋርጥ የሚችልበት የህግ ምክንያት እና ሥነ ሥርዓት የሌለ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካች በኩል የቀረቡትን መከራከሪያ ነጥቦች ውድቅ ያደረጉት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/ እና /ቀ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መንፈስ ባግባቡ ባለማገናዘብ በመሆኑ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32262 ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 63030 ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው በህጉ መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36591

ታህሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ማታዶር አዲስ ጎማ አ/ማ - ጠበቃ ደረጀ ታፈሰወርቅ ቀረበ

ተጠሪ፡- ደረጀ ኡመታ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ አቋርጦብኛል በማለት ነው፡፡ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደስራው እንዲመለስ እንዲወሰንለትም ጠይቆአል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ በፈፀመው ጥፋት ምክንያት ነው፡፡ የተፈፀመውም በሕጉ እና በሕብረት ስምምነታችን መሠረት ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ፣ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው፡፡ ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደስራው ይመለስ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተጠሪ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደስራው ይመለስ በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ጥፋት ስለመፈፀሙ በሥር ፍ/ቤቶች ታምኖበት እያለ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በሚል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻለነው አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ እነዚህም ተጠሪ ቀደም ሲል በፈፀመው ጥፋት በገንዘብ /በደመወዙ/ ቅጣትና በማስጠንቀቂያ ታልፎ ነበር የተባለው የማጭበርበር ተግባር እና በምርት ማምረት ሂደት በፈፀመው ጥፋት የጎማ ምርት ከጥቅም ውጪ እንዲሆን አድርጎአል የተባለው ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች በእርግጥም በተጠሪ የተፈፀሙ ለመሆናቸው የስር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ለማለት የበቃው ተጠሪ የፈፀመው ጥፋት ከስራ ለማሰናበት "የሚችል በቂ ኃይል" የለውም፡፡ አመልካች ተመጣጣኝ እርምጃ መውሰድ ሲችል ተጠሪን ከስራ ያናበተው አላግባብ ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የራሱ የተገለፀ ምክንያት የሰጠ ሲሆን፣ ይህም ለሥራ ውሉ መቋረጥ መሠረት የተደረገው ጥፋት በህብረት ስምምነቱ እንጂ በአዋጁ አንቀጽ 27 የተመለከተ አይደለም የሚል እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ቀደም ሲል ፈጽሞት ነበር የተባለው ጥፋት እንዳየነው በአንድ ወቅት ሞተዋል በማለት የሐዘን ፈቃድ የወሰደባቸውን አክስቱን ለሁለተኛ ጊዜ ሞተዋል በማለት የሐዘን ፈቃድ መጠየቁ ስለተረጋገጠበት ነው፡፡ ይህን መሰል ጥፋት የፈፀመ ሠራተኛ ለመጀመሪያ ጊዜ የአስር /10/ ቀን ደመወዝ ከመጨረሻ ደረጃ ማስጠንቀቂያ ጋር እንደሚቀጣና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በማንኛውም ጥፋት ላይ ቢገኝ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከስራ እንደሚሰናበት በህብረት ስምምነቱ ተደንግጎአል፡፡ በእርግጥ ይህ ጥፋት ከሥራ ያሰናብታል ተብሎ በአዋጁ አንቀጽ 27 አልተመለከተም፡፡ አንቀጽ 27 ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ስለሚቋረጥባቸው ምክንያቶች በተመለከተ የተደነገገ ሲሆን፣ በንዑስ አንቀጽ /1/ እንደተመለከተው በህብረት ስምምነት በሌላ አኳኋን የተወሰነ የሥራ ውል የሚቋረጥበት ምክንያት ካለ በአዋጁ ባይመለከትም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ ሕጉ ግልጽ ነው፡፡ በህብረት ስምምነቱ ከሥራ ውል መቋረጥ በቂ ምክንያት ነው ተብሎ የሚቀመጠው ድንጋጌ ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚገባ ሕጉ አላመለከተም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ በተያዘው ጉዳይ እንደምናየው በሕብረት ስምምነቱ ላይ የተቀመጠው ሁኔታ ብቻውን አይደለም ለስራ ውል መቋረጥ በቂ ምክንያት የሚሆነው በህብረት ስምምነቱ የተመለከተውን ጥፋት መፈፀም ተከትሎ የሚፈፀም ጉዳት ሲኖር ነው የስራ ውሉ የሚቋረጠው፤ ይህ ደግሞ በትክክል ተሟልቶአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከአዋጁ አንቀጽ 134/2/ ጋር አነፃጽሮ መመለከቱ ተገቢ የማይሆነውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ሲጠቃለል አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ሕጉንና ሕብረት ስምምነቱን መሠረት በማድረግ በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23162 ሰኔ 10 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 57742 መጋቢት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ተመስርቶ የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 36894

ታህሳስ 30 ቀን 2001 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነገረ ፈጅ ወ/ሮ ኮከብ ስለሺ

ተጠሪ ፡- አቶ ሙላት ታረቀኝ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58378 በመጋቢት 8 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በከሳሽነት በመቅረብ ከታህሳስ ወር 1972 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥሮ በአመልካች ድርጅት ውስጥ የተለያየ ስራ ሲሰራ የቆየ መሆኑን ከገለፀ በኋላ ህዳር 23 ቀን 1998 ሃላፊነትህን አልተወጣህም የሚል ምክንያት በመስጠት አላግባብ ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ የሥራ ስንብቱን ውድቅ እንዲያደርግለት ጠይቋል፡፡ አመልካች በበኩሉ በተከሳሽነት ቀርቦ የይርጋ የጊዜ ገደብ አልፏል፣ የሚልና ተጠሪ ሰራተኛ ሳይሆን የሥራ መሪ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን መቃወሚያ በመቀበል ተጠሪ የሥራ መሪ መሆኑን በመግለጽ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ዘግቶታል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ምክትል የግምጃ ቤት ሐላፊ በመሆን ያገለገለው በጊዜአዊነት ስለሆነ በቋሚነት ተመድበው ያልሰሩበት የሥራ መደብ የሥራ መሪ ሊያሰኛቸው አይችልም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በአሠሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት አከራክሮ እንዲወሰን በማለት መልሶለታል፡፡ አመልካች ይኸ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው፡፡ በሥራቸውም የሚመሯቸውና የሚያስተደድሯቸው ሠራተኞች አሉ፡፡ በምክትል ግምጃ ቤት ሃላፊነት የተመደቡት በጊዜያዊነት ቢሆንም ሙሉ ሃላፊነቱን እና የሚያስገኘውን መብት ተረክበው እስከሰሩ ድረስ በጊዜያዊነት በመመደባቸው ብቻ ሠራተኛ አያደርጋቸውም፡፡ ስለዚህ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/1993 አንቀጽ 3/2/ሐ ድንጋጌና የህብረት ስምምነቱን አንቀጽ 14 የሚተላለፍ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እኔ በቦታው ላይ ተመድቤ እየራ የነበረው በተጠባባቂነት ነው፡፡ የሰራተኛ ወገን እንጅ የአሰሪ ወገን አይደለሁም፡፡ አመልካች ለክርክር ያቀረበው የሥራ መዘርዝር ለእኔ ያልተሰጠኝና እኔ የማላውቀው ነው፡፡ አመልካች በመከራከሪያነት የሚጠቅሰው አስረኛውን የህብረት ስምምነት ሲሆን እኔ ሥራ ላይ በነበርኩ ጊዜ የነበረው ዘጠነኛው የህብረት ስምምነት ነው፡፡ በወቅቱ የሠራተኛ ማህበሩ ከፍተኛ ኃላፊ የነበርኩ ስለሆነ አመልካች ሥራ መሪ ነው ለማለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ነው፣ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ያሰናብተኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በጽሑፍ የመልስ መልስ ያቀረበ ሲሆን፣ ይህ ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቃል ክርክር አዳምጧል፡፡ እንደዚሁም አመልካችና ሠራተኛ ማህበሩ የተስማሙበትን ዘጠነኛውን የህብረት ስምምነትና አስረኛውን የህብረት ስምምነት በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

በሥርና በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች የሥራ መሪ ነው ወይስ ሠራተኛ? የሚለው ነጥብ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድበው ይሰሩበት የነበረው የሂሳብ ክፍል ረዳት ኃላፊ የሥራ ቦታ ላይ የነበረ መሆኑና ተጠሪም የክፍሉን እንቅስቃሴዎች የመቆጣጠር የዕለት ከዕለት የሒሳብ ቁልፎችን መያዝና የሒሳብ ክፋዮችን የዕለት ተዕለት የሥራ ምደባ ፕሮግራም እንደሚያዘጋጅ ተጠሪ ተመድቦ ይሰራበት የነበረው የሥራ መደብ የሥራ መዘርዝር በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም ተጠሪ የሰራተኛነት ሳይሆን የሥራ መሪነት የሥራ ድርሻ የነበረው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድቦ ይሰራበት የነበረው የሥራ መደብ ተጠሪ በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ተፈፃሚነት በነበረው ዘጠነኛ የሕብረት ሥራ ስምምነት መሠረት የሠራተኛ የሥራ መደብ ሣይሆን የሥራ መሪ የሥራ መደብ መሆኑ በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 10 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህም ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድቦ ሲሰራበት የነበረው ምክትል የግምጃ ቤት /የሂሳብ ክፍል/ ኃላፊ የሥራ መደብ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ንዑስ አንቀጽ 3/2/ሐ/ መሠረት የሥራ መሪ የሥራ መደብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ በተጠባባቂነት የሚሰራበት የነበረው የሥራ መደብ የሥራ መሪ የሥራ መደብ ነው ከተባለ ተጠሪ በሥራ መደቡ ይሰራ የነበረው በቋሚነት ሳይሆን በተጠባባቂነት መሆኑ ተጠሪን ሰራተኛ ያሰኘዋል ወይስ አያሰኘውም? የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድበው ሲሰሩ ለቦታው የሚገባውን ጥቅማጥቅም የሚያገኙ እንደነበርና ለሥራው ሙሉ ሀላፊነት ወስደው ይሰሩ እንደነበር በስርና በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያሳያል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 494/1998 ከተደረገው፣ ማሻሻያ መሠረት የሥራ መሪ ማለት በቋሚነት ብቻ ሣይሆን በአሠሪው በተሰጠው ውክልና መሠረት በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ በቦታው ላይ ተመድበው ይሰሩ የነበሩት በተጠባባቂነት መሆኑ ተጠሪ ሠራተኛ ናቸው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ምክንያት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ከላይ የተገለፁትን የህግ ድንጋጌዎች ሳያገናዝብ ተጠሪ ሠራተኛ ነው የሥራ መሪ አይደለም በማለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58378 መጋቢት 8 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 21891 ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፀንቷል ይፃፍ፡፡
3. ተጠሪ የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ ባለመሆኑ ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/1996 በአዋጅ ቁጥር 494/1998 እንደተሻሻለ የሚታይ አይደለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታህሳስ 30 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37201

ታህሳስ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- ማታዶር አዲስ ጎማ አክሲዮን ማህበር ጠበቃ ደረጀ ታፈሰወርቅ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ኤልያስ በቀለ ቀርበዋል

2. አቶ ዲባባ ሞርዶፋ ቀርበዋል

3. አቶ ፍቅረስላም ቦጋለ ቀርበዋል

4. አቶ ፍቃዱ ይመኑ አልቀረቡም

5. አቶ ዓለሙ ወነታ ወኪል አቶ ኤልያስ በቀለ ቀርበዋል

6. አቶ ዮሃንስ ንጋዬ ቀርበዋል

7. አቶ አዲሱ በቀለ ቀርበዋል

8. አቶ ካሳሁን እሸቱ አልቀረቡም

9. አቶ ደረጀ ወ/ሚካኤል ቀርበዋል

10. አቶ ሙሉነህ ካሣ ቀርበዋል

11. አቶ ዋቅቶላ በዳሳ ቀርበዋል

12. አቶ ተክለማርያም ባዩ ቀርበዋል

13. አቶ መለሰ ፋንታሁን ቀርበዋል

14. አቶ ጌትነት ቶፋ ቀርበዋል

ጉዳዩ ለምርመራ በተቀጠረው መሰረት ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተንበታል፣

ፍ ር ድ

ክርክሩ በዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካቹ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 60960 መጋቢት 15/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት በመጠየቁ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአሁኑ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሾች እንዲሁም የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን የተከራከረ ሲሆን ስር ከሳሾቹ ጥቅምት 30/1999 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ያቀረቡት መሰረታዊ ይዘቱ በተከሳሽ ድርጅት በተለያዩ ጊዜያት ቅጥር በመፈፀም በወር ብር 288.66 (ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከስድሳ ስድስት ሣንቲም) እየተከፈለን ስንሰራ ከቆየን በኋላ ምንም አይነት ጥፋት ሳንፈፅም ጥቅምት 21/1999 ዓ.ም አላግባብ ከሥራ ስላሰናበተን ውዝፍ ደሞዛችን ከፍሎ ወደ ስራችን ይመልሰን ይህ ካልሆነ ግን የስንብት ክፍያ የማስጠንቀቂያ ክፍያ፣ ካሳ፣ ክፍያ ለዘገየበት እንዲሁም ከበቂ ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍለን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ስር ተከሳሹ በበኩሉ ታህሳስ 20/1999 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሰጠ ሲሆን፣ ይዘቱም የተጫኑ ጎማዎች እንዲያራግፉ ጥቅምት 19 ቀን 1999 ዓ.ም በቅርብ ኃላፊያቸው ሲታዘዙ በአድማ መልክ ተደራጅተው አናራግፍም እንዳሉና በማግስቱም ይህ እምቢተኝነታቸው በመቀጠሉ በህብረት ስምምነቱ አንቀፅ 4.4 ተራ ቁጥር 5 መሰረት ከስራ ሊሰናበቱ ችለዋል፤ የከሳሾቹ የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ስላልሆነ የሚከፈላቸው ክፍያ የለም ተብሎ ክሳቸው ውድቅ ይሁንልኝ የሚል ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም በግራ ቀኙ ወገኞች መካከል የቃል ክርክር አካሂዷል፤ የግራ ቀኙ ወገኖች ምስክሮችም ሰምቷል፤ የተገኘው ውጤትም ከሳሾቹ ጎማውን አናራግፍም ያሉት እሁድ እለት እንደነበርና በዚሁ ጊዜም በተቋሙ ውስጥ በተፈጠረው የስራ ጫና ምክንያት የትርፍ ሰዓት ክፍያ እየተከፈላቸው ስራቸውን በማከናወን ላይ በነበሩበት ሁኔታ ስለነበርና ስራ በዝቶብናል በሚል ምክንያት ነው የሚል ነበር፤ ፍ/ቤቱም ይህንን ሃቅ ከተገነዘበ እና ተከሳሹም የጎማውን ማራገፍ እስከ ሰኞ ድረስ አቆይቶ አሁንም እንዲያራግፉት ከሳሾችን መጠየቁ በአዋጅ ቁ 337/1996 በአንቀፅ 67 የተመለከቱትን ምክንያቶች እንዳልነበሩ ያሳያል በማለት በአጠቃላይ ከሳሾቹ ስራ ለመሥራት አልፈለጉም ተብሎ በተከሳሽ የተወሰደው ከስራ የማሰናበት ተግባር አግባብነት ያልነበረው በመሆኑ እና ከሳሾቹ በአዋጁ አንቀፅ 10 መሠረት የተቀጠሩ መሆናቸው ማህደራቸው ስለማይገልፅ ተከሳሹ የአዋጁ አንቀፅ 43(4) (ሀ)"ን" መሰረት ያደረገ ካሳ ለከሳሾቹ ሊከፍላቸው ይገባል፤ እንዲሁም የስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜም ክፍያ ጨምሮ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

ከላይ በሰፈረው የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘትም ስር ተከሳሹ ወደ ፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ ወገኖችን ካከራከረ በኋላ መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በኮ.መ/ቁ.60960 በሰጠው ፍርድ ስር ከሳሾቹ በስር ፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ በተከሳሹ ድርጅት ውስጥ በጉልበት ሰራተኝነት ተቀጥረው በመሥራት ላይ እያሉ የኮንትራት ጊዜያቸው ሳያልቅ የስራ ውላቸው እንዳቋረጠባቸው የሚገልፅ በመሆኑና ይህ ደግሞ የስራ ግንኙነቱ ለተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚያሳይ በመሆኑ ሊከፈላቸው የሚገባ ካሳ በአዋጅ ቁ 377/1996 አንቀፅ 43(4)(ሀ) መሰረት ሳይሆን በአንቀፅ 43(4)(ለ) መሰረት ነው፤ የስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያዎች በተመለከተ ግን የስር ፍ/ቤቱ የሰጠው ፍርድ ተገቢ ነው በማለት የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤቱ ውሳኔ አሻሽሏል፡፡

ከላይ በሰፈረው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔም አመልካቹ ቅሬታ በማሳደር ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም በተፃፈ ቅሬታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም የተጠሪዎቹ የስራ ቅጥር ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው እስከተባለ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 35(2) መሰረት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያው በጊዜያዊ የቅጥር ውላቸው በተስማማነው መሰረት የ15 ቀናት ብቻ እንጂ አንዱ የ2 ወር ደሞዝ አይደለም ተብሎ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎቹም መስከረም 27/2001 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው ከፍተኛው ፍርድ ቤቱ ክርክራችን በአግባቡ ሳያገናዝብ የስራ ግንኙነታችን በአዋጁ አንቀፅ 43(4)(ሀ) ሆኖ እያለ ወደ አንቀፅ 43(4)(ለ) መቀየሩ የህግ ስህተት ነው፤ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ የኮንትራት ሰራተኞች እንደሆንን ቢገልፅም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 35(መ) መሰረት የሙከራ ጊዜያችን ያጠናቀቅን በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያው የሁለት ወራት ደሞዝ ክፍያ ሊሆን ይገባል ተብሎ በከፍተኛው እና በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶቹ የተሰጠው ውሳኔ ህግን ያማከለ በመሆኑ ሊፀና ይገባዋል ብለዋል፡፡

አመልካቹም ህዳር 08/2001 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልሱ ተጠሪዎች ቅጥራችን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 43(4)(ሀ) እንጂ በአንቀፅ 43(4)(ለ) አይደለም በማለት እኔ በአቀረብኩት የሰበር አቤቱታ ሊከራከሩ አይችሉም የራሳቸው የሆነ አቤቱታ ሊያቀርቡበት የሚገባ ነው፤ የኮንትራት ሰራተኞች መሆናቸው አምነው የተከራከሩ በመሆናቸው እና የኮንትራት ሰራተኛ ሊከፈለው የሚገባ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በአዋጁ አንቀፅ 35(2) መሰረት በኮንትራት ውሉ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተገለፀው ተብሎ በመደንገጉ በእኛ የኮንትራት ውል ላይ ደግሞ የ15 ቀናት ክፍያ ተብሎ በግልፅ የተቀመጠ በመሆኑ የተጠሪዎቹ መከራከሪያ ነጥብ የህግ ድጋፍ የለውም ብሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ በተቀመጠው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ ለተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ስንት ነው የ2 ወር ደሞዝ ወይስ የ15 ቀናት ብቻ የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው የስራ ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ እንደሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ እንዲሁም እያንዳንዱ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ከፈፀመው ስምምነት መረዳት ይቻላል፤ ሊከፈላቸው የሚገባ ካሳም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 43(4)(ለ) መሠረት ሊሰላ እንደሚገባ ነው፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት መልስ የስራ ግንኙነታችን ለተወሰነ ጊዜ ስላልሆነ ሊከፈለን የሚገባ ካሳም በአዋጁ አንቀፅ 43(4)(ሀ) መሰረት መሆን ይገባል ቢሉም የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ፍርድ በመቃወም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በሌለበት ሁኔታ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል አከራካሪው ነጥብ ለተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ መጠን በተመለከተ ነው፤ የግራ ቀኙ ወገኖች የስራ ግንኙነት በተወሰነ ጊዜ የተደረገ በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 35(2) መሰረት የሚሰላ ነው፡፡ ይህ አንቀፅም ተዋዋዮቹ ወገኖች በስምምነታቸው ባስቀመጡት መልክ እንደሚከናወን ስለሚገልፅና እያንዳንዱ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በፈፀመው ስምምነት አንቀፅ 3.3 መሠረት የ15 ቀናት ደሞዝ ብቻ እንደሆነ ነው፤ የስምምነታቸው በዚህ መልክ ተገልጾ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የማስጠንቀቂያ ጊዜው ክፍያ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤቱ የወሰነውን የ2 ወር ደሞዝ ተቀብሎ ማለፉ የግራና ቀኙ ወገኖች የስራ ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 60960 መጋቢት 15/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፤ ይፃፍ፡፡
2. በአመልካችና በእያንዳንዱ ተጠሪ መካከል ያለው የስራ ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ በመሆኑ ለእያንዳንዱ ተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 44 እና በስምምነታቸው አንቀፅ 3.3 መሰረት የ15 ቀናት ደሞዝ ብቻ ነው ብለናል፡፡
3. ሚያዝያ 20/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተላለፈው እግድ ተነስቷል፣ ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ያካሄዱትን ክርክር በሚመለከት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
   ክርክሩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ፍርዱ በዛሬው ዕለት 07/05/2001 ዓ.ም በችሎት ተነገረ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 37454

ታህሣሥ 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዲልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡ ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ነ/ፈጅ በቀለ ነዲ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ከበደ ሰይፉ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62157 ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና በመዝገብ ቁጥር 32105 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርበው ከሚያዚያ ወር 1993 እስከ መስከረም 25 ቀን 1999 ዓ.ም በጥበቃ ሠራተኝነት ተቀጥሮ ከአመልካች ድርጅት ከማገልገል ላይ እያለ አመልካች አላግባብ የሥራ ውሉን በማቋረጡና ከሥራ በማሰናበቱ ፍርድ ቤቱ ወደ ሥራ እንዲመለስ ይወሰንልኝ ወደ ሥራዬ የማልመለስ ከሆነ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁን አመልካች ሥር በከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበተው በየዕለቱ የዘብ ሥራውን ሲያከናውን የቅርብ አለቃውን ትእዛዝ የማይቀበል በመሆኑ የዕሁፍ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ በቀርብ አለቃው ላይ በመዛቱና የተለያዩ የዕሁፍና የቃል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ሊስተካከሉና ሥራቸውን በአግባቡ ሊያከናውኑ ባለመቻላቸው ነው፡፡ ለተጠሪው (ከሳሽ) ሊፈፀም የሚገባው ክፍያ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች በየጊዜው ለተጠሪ ጽፌአቸዋለሁ ከሚላቸው የጽሑፍ ማስረጃዎች ውጭ ተጠሪ በሥራቸው ላይ አንባገሮ የፈጠሩ መሆኑን የሚያሣይ ማስረጃ አላቀረቡም በማለት የተጠሪን ወደ ሥራ የመመለስ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ተከፍለዋቸው ተጠሪ ከሥራ እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ አመልካችና ተጠሪ ቅር በመሰኘት ሁለቱም በየበኩላቸው ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበው ይግባኝ የሚያስቀርብ ህግ ወይም የፍሬ ገዳይ ምክንያት የለም በማለት በመዝገብ ቁጥር 62157 ሚያዚያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን ተጠሪ ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ ላይ አመልካች መልስ እንዲሰጥ ካደረገ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ወደ ሥራ አይመለሱም ብሎ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ የስምንት ወር ደመወዝ ተከሳቸው ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡

አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሥራ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የእኛን ይግባኝ በመሰረዝና የተጠሪን ይግባኝ በመቀጠል ተጠሪ ወደ ሥራ ቢመለስ የሚፈጠር ችግር የለም በማለት ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጠው ውሣኔ መሠታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪ በበኩሉ የሥር ፍርድ ቤት ካሣ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከፍሎት ይሰናበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ህጋዊነት የሌለው ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት እኔ ያቀረብኩትን ይግባኝ በመመርመር ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ይሁንልኝ በማለት ሀምሌ 18 ቀን 2000 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር በመልስ መልሱ ተከራክሯል፡፡ የሥር የክርክሩ አመጣጥ በዚህ ፍርድ ቤት በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እጅም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ የስምንት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆናቸው በቂና አሣማኝ ማስረጃ አላቀረበም በማለት የሥር ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም አመልካች አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ጉዳዩ የፍሬ ጉዳይ ክርክርና የማስረጃ የምዘና እንጂ መሠረታዊ የሆነ የህግ አተረጓጐም ሆኖ ያላገኘነው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት የፈፀመ መሆኑን የሚያሣይ ማስረጃ የለም በማለት አመልካች የፈፀመው የሥራ ስንብት ህጋዊነት የሌለው ነው በማለት ከወሰነ በኋላ የተጠሪ ወደ ሥራው መመለስ በአሠሪውና ሠራተኛው ግንኙነት ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊና አዎንታዊ ጎን በመመዘን ተጠሪ በአሠራና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን በመክፈል ከሥራ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ምክንያት አላምንበትም ከማለት ውጭ የተጠሪ ወደ ሥራ መመለስ ከአመልካች ጋር መልካም ግንኙነት እና ጥሩ የሥራ ሁኔታ የሚፈጥር ስለመሆኑ የሰጠው ምክንያትና ለዚህም መነሻ የሆኑትን ነባራዊ እውነታዎችና መረጃዎች በዝርዝር አልገለፀም፡፡

ተጠሪ በጥበቃ ሥራ የተሠማራና በእጁም ትጥቅ የሚይዝ ከመሆኑና ከቅርብ አለቆቹ ጋር በተለያየ ጊዜ ግጭት የሚፈጥር ስለመሆኑ ከመገለፀ አንፃር እና ከዚህም መነሻ ከሥራ ተሰናብቶ የቆየ መሆኑና አመልካች ይህንን በበቂ ማስረጃ ባለማስረዳቱና የሥራ ስንብቱን ህጉ የሚጠይቀውን ፎርማሊቲ አሟልቶ ባለማከናወኑ ምክንያት አመልካች የፈረመው የሥራ ስንብት ህጋዊነት የጐደለው ነው እንደተባለ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንድ ሠራተኛ የሥራ ቅጥር አላግባብ ከተቋረጠ ፍርድ ቤቱ ወደ ሥራው እንድመለስ ወይም ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ሊወሰን እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ ሠራተኛው ወደ ሥራው እዲመለስ የሚወሰነው ከሥራ ግንኙነት ጠባይ የተነሳ የሥራ ግንኙነቱ ቢቀጥል ከፍተኛ ችግር ሊከተል ይችላል ብሎ በማያምንበት ጊዜ መሆኑንና ከሥራ ባሕሪው የተነሳ የሥራ ግንኙነቱ ቢቀጥል ከፍተኛ ችግር ያስከትላል ብሎ ካመነ ሰራተኛው ወደ ሥራ ለመመለስ ቢፈልግ እንኳን ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማዘዝ እንደሚችል ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ስናየው የተጠሪ የሥራ ባህሪ የአመልካች ድርጅት ጠቅላላ ንብረት ፀጥታና ደህንነት መጠበቅ ከመሆኑ አንፃርና ይኸም በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የሚጠይቀውን ከፍተኛ የሆነ መተማመን የሻከረውና ግንኙነቱ ቢቀጥል በአመልካች ድርጅት ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳትና ችግር ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን ወደ ጐን በመተው የተጠሪ ወደ ሥራ መመለስ ሊፈጥር የሚችለው ከፍተኛ ችግር ስለሌለ ወደ ሥራ እንዲመለስ በለማት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተገፀውን የህግ ድንጋጌ የሚቃረንና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62105 ሚያዝያ 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32488 ህዳር 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት ታህሣሥ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሣሥ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር ነ/ፈጅ ምናለ በሪሁን ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ዓለምሰገድ ኃይሉ አልቀረበም፡፡

ጉዳዩን በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 03 ቀን 2000 ዓ.ም በተሻረ አቤቱታው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 62997 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲሻርለት በመጠየቁ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት የፍርድ ባለእዳ፣በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ መልስ ሰጭ የነበረ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ በፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት የፍርድ ባለመብት፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ደግሞ ይግባኝ ባይ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የፍርድ ባለመብት የሆኑት የአሁኑ ተጠሪ ታህሳስ 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተሻረ ለፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ቀደም ብሎ ማለትም በመ/ቁ. 36237 ከባለ እዳው ጋር ባደረጉት የስራ ክርክር ወደ ስራቸው እንዲመለሱ፣ውዝፍ ደሞዝና ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው ተወስኖላቸው እንደነበር በማስታወስ ወደ ስራ የመመለሱ ሁኔታ እንደማይፈልጉትና በምትኩ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለዋቸው ከስራ እንዲሰናበቱ ጠይቀዋል፡፡ የመጀ/ደ/ፍ/ቤቱም የፍርድ ባለመብቱ በፍርዱ እንደሰፈረው በአመራጭ የጠየቋቸው ሌሎች ክፍያዎች ያልነበሩ በመሆኑና የአራት ወር የደሞዝ ክፍያ የተከፈላቸው በመሆኑ ወደ ሥራ ለመመለስ እንዳልፈለጉ በመቁጠርና የሚከፈላቸው ሌላ ቀሪ ክፍያ የለም በማለት መዝገቡን ዘግቶ አስናብቷቸዋል፡፡

ከላይ የሰፈረውን ትእዛዝ በመቃወምም የአሁኑ ተጠሪ ወደ ፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም ደቀም ብሎ በተፈረደልኝ መሰረት መልስ ሰጭው ምክንያት እየፈጠረ ወደ ስራ ሳይመልሰኝ በመቅረቱና የስራ ግንኙነታችን በመሻከሩ ወደ ስራ መመለሴ ቀርቶ በካሳ ልሰናበት በማለት ላቀረብኩት ጥያቄ ስራውን እንዳልፈለኩት በመቁጠር ያለምንም መፍትሄ መዝገቡ መዘጋቱ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በሰጡት መልስም በውሳኔው መሰረት ተፈጽሟል፤የተወሰነላቸው ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏቸዋል፤ ወደ መደበኛ ስራቸውም እንዲመለሱ የመኪናው አረካካቢ ተመድቦላቸው እያለ የተዘጋውን መዝገብ እንደገና አንቀሳቅሰው ካሳ ተከፍሎኝ ልሰናበት ማለታቸው አላግባብ ነው ብሏል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍ/ቤትም በኮ/ቁ. 62997 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ይ/ባይ በስር ፍ/ቤት በዋና ክርክራቸው በአማራጭ በካሳ ልሰናበት ብለው ባይጠይቁም ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ በአፈፃፀም መጠየቅ እንደሚችሉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43/3/ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነና የአፈፃፀም መዝገቡ ሳይዘጋ ወደ ስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመለሳቸው ቀርቶ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ የጠየቁ ስለሆነ ወደ ስራ ለመመለስ ፍቃደኛ አልሆኑም በማለት የስር ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ በመሻር በፍርዱ መሰረት ውዝፍ ደሞዝ እንደተከፈላቸው በማረጋገጥና ይህንን ውዝፍ ደሞዝ ይዘው ወደ ስራቸው ይመለሱ ብሏል፡፡

የአሁኑ አመልካችም ከላይ የሰፈረውን የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ሰኔ 03 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት አቅርቧል፤መሰረታዊ ይዘቱም በፍርዱ መሰረት የአራት ወራት ውዝፍ ደሞዝና ወጪና ኪሳራ ለተጠሪው በመክፈል ስራቸውም እንዲጀምሩ ደብዳቤ ጽፈንላቸው እያለና በዚህ ደረጃም ፍርዱ የተፈፀመ መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ ከዚህ በኋላ ተጠሪው ወደ ስራ ከመመለስ ይልቅ ካሳና ሌሎች በፍርዱ ያልተፈረዱላቸውን ክፍያዎች ተከፍሏቸው ከስራ እንዲሰናበቱ ያቀረቡት ጥያቄ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በትክክል የወሰነውን ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በይግባኝ አከራክሮ ወደ ስራ ይመለሱ ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤በአዋጁ አንቀጽ 43/3/ መሰረት ተጠሪው ጥያቄውን ማቅረብ የሚገባው ዋናውን ፍርድ ለሰጠው ፍ/ቤት እንጂ የአፈፃፀም ክርክር ለሚያካሂደው አይደለም፤በመሆኑም የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዋ ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን፣ይዘቱም ያቀረብኩት ጥያቄ አዋጅ ቁ. 377/1996 አንቀጽ 43/3/ መሰረት በማድረግ በዋናው ጉዳይ ፍርድ ከተሰጠ በኋላም ቢሆን ወደ ስራ በመመለስ ፈንታ ካሳ ተከፍሎኝ ልሰናበት ማለት እችላለሁ፤ጥያቄዬ ያቀረብኩት በተዘጋ የፍርድ አፈፃፀም መዝገብ ሳይሆን በቀጠሮ ላይ ወይም በሂደት በነበረ የአፈፃፀም መዝገብ ውስጥ ነው፤ወደ ስራ መመለሱ ይቅርብኝ ያልኩት በመካከላችን ያለው የስራ ግንኙነት የተባላሸ መሆኑ ስለተገነዘብኩኝ ነው፤አመልካች በስር ፍ/ቤት ባደረጋቸው ክርክሮችም ካሳ ተከፍሎኝ እንድሰናበት ፍላጐቱ እንደነበር ነው፤አመልካች ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ እንደመጣው ሲመለከት ተጠሪው ወደስራቸው እንዲመለሱ ማድረጉ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያስ ምንድን ነው ? የሚሉትን መሰረታዊ ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው የአሁኑ ተጠሪ ቀደም ብሎ ማለትም በመ/ቁ. 36237 በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዋና ጉዳይ በቀረበው ክስ መሰረት አመልካች ወደ ስራ እንዲመልሰው፣የአራት ወራት ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈለው እና ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለው በተወሰነለት መሰረት የተጠቀሱት ክፍያዎች አመልካች ለተጠሪው እንደከፈለና ወደ ስራው እንዲመለስም በደብዳቤ አሳውቆት በርክክብ ደረጃ አያለ ተመልሶ ወደ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤቱ በመቅረብ ወደ ስራው ከመመለስ ይልቅ ካሳ የስንብት ክፍያና ሌሎች ክፍያዎች ተከፍለውት ከስራ እንዲሰናበት እንደጠየቀ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 43/3/ ከሰፈረው አካያ ሲታይ ልዩነት ያለው ነው፡፡ በተጠቀሰው አንቀጽ የተቀመጠው መብት ተግባራዊ የሚሆነው ተጠሪው በፍርዱ መሰረት የተወሰነለትን ውዝፍ ደሞዝና ሌሎች ክፍያዎች ሳይወስድ ቢሆን ኖሮ ነው፣በዚህ ጉዳይ ግን ተጠሪው በፍርዱ መሰረት ወደ ስራው እዲመለስ ወስኖ በፍርዱ የተወሰኑለትን ክፍያዎች ከተቀበለ በኋላ ነው፤ስለሆነም በፍርዱ መሰረት መብቱ ከተፈጸመለት በኋላ በአዋጅ አንቀጽ 43/3/ መሰረት ወደ ስራ ከመመለስ ይልቅ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፈለውት በአማራጭ እንዲሰናበት የቀረበ ጥያቄ ነው ማለት አይቻልም፤በመሆኑም ተጠሪው ስራ መስራት እንደማይፈልግ ገልጾ እያለ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ስራው ይመለስ ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 37264፣ጥር 08 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፣ይፃፍ፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 62997፣ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ተጠሪው ካሳና የስራ ስንብት ክፍያ ተከፍሎት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43/3/ መሰረት ከሥራው እንዲሰናበት የጠየቀው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 36237 ፣ሕዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም በወሰነለት መሰረት የአራት ወራት ውዝፍ ደሞዙ ከተከፈለውና ወደ ሥራውም እንዲመለስ በአመልካቹ ደብዳቤ ከተግፈለት እንዲሁም ከውሳኔው በኋላ ደሞዝ መብላት ከጀመረና ፍርዱ ከተፈፀመ በኋላ በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፤ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት የመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37551

ታህሣሥ 09 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ድካምየለህ ጥበቡ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አርሾ የሕክምና ላብራቶሪ ኃላ/የተ/የግል ማኅበር - ጠበቃ ጌታቸው ብሩ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ከሌሎች ከሣሾች ጋር ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ከተጠሪ ጋር የነበራቸውን የሥራ ውል የጡረታ ዕድሜ ደርሷል በሚል ምክንያት መቋረጡን ገልፀው በድርጅቱና በሠራተኛ ማኅበሩ መሃከል በተደረገው የሕብረት ስምምነት በፈቃዱ ሥራ የለቀቀ ሠራተኛ ፕሮቪደንት ፈንድና የሥራ ስንብት ክፍያ እንደሚያገኝ ስለሚደነግግ ተጠሪ ይህንኑ እንዲፈጽም በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ፈቃደኛ ሣይሆን መቅረቱንና መከልከሉን ጠቅሰው የሥራ ስንብት ክፍያና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያ ብር 20,189.00 /ሃያ ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር/ ተጠሪ እንዲከፍል ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪም አመልካች ዕድሜያቸው ለጡረታ በመድረሱ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ተፈጽሞላቸው በሕብረት ስምምነቱ መሠረት ከሥራ የተሠናበቱ በመሆኑ የስራ ስንብት ክፍያ ጥያቄው ሊፈፀም እንደማይገባ፣ ለአመልካቹ ተገቢው ክፍያና ጥቅማጥቅም የተፈፀመላቸው በመሆኑ ክፍያ ለዘገየበት ጥያቄ አላፊነት እንደሌለበት በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም አመልካች በጡረታ የተሰናበቱ መሆኑን አምነው የተከራከሩ ከመሆኑ እና በሕብረት ስምምነት መሠረት የስራ ስንብትና የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ የሚፈፀመው በፈቃድ ለለቀቀ ሠራተኛ ብቻ ነው በማለት የሚደነግግ በመሆኑ እንዲሁም በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ መሠረት የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ በጡረታ የተገለለ ሠራተኛ የስራ ስንብት የማይፈፀምለት መሆኑን የሚደነግግ ነው የሚሉትን ምክንያቶች ጠቅሶ የአመልካችን የሥራ ስንብት ክፍያና ክፍያ ለዘገየበት ጥያቄ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሚያዝያ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የበታች ፍ/ቤቶች ከጡረታ በኋላ ጡረተኛው ከሌላ አሠሪ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ሲቋረጥ ያለውን የሕግ ክለላ እና በሕብረት ስምምነት ለሠራተኛው የበለጠ መብት የሚሠጥ ከሆነ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት መፈፀም ያለበት መሆኑን ባላገናዘበ መልኩ መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በመሆኑ ታርሞ አመልካች ስራቸውን በራሣቸው ፈቃድ የለቀቁ መሆኑ ተረጋግጦ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሠበር ችሎቱ ሊተይ ይገባል በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርብ ተደርጎ ሐምሌ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን ጠበቃቸው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ አመልካች በሁለት መ/ቤቶች ቅጥር እንደፈጽሙ አድርገው ያቀረቡት ክርክር አዲስ በመሆኑ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፣ የስራ ስንብት ክፍያም አመልካቹ በጡረታ የተገለሉና የጡረታ መብትም ተጠቃሚ በመሆናቸው ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑን በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ የማቅረብ መብት ከታለፈ በኋላም ግራ ቀኙ ማጣሪያ ጥያቄ ቀርቦላቸው መልሣቸውን እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄ ውድቅ የተረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በክርክሩ ሂደት አመልካች በጥቁር አንበሣ ሆስፒታል ተቀጥረው ሲያገለግሉ ቆይተው እድሜያቸው ሃምሣ ዓመት ሲሞላ በፈቃዳቸው ስራውን ለቀው ለዚህ አገልግሎታቸው የጡረታ መብት ተጠቃሚ መሆናቸው፣ ከዚህ መስሪያ ቤት በጡረታ ከተገለሉ በኋላ በተጠሪ መስሪያ ቤት ከሐምሌ 19 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ ተቀጥረው ለአስር ዓመታት ያሕል አገልግለው እድሜ ለጡረታ ደርሷል በሚል ምክንያት ከነሐሴ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ከሥራ መገለላቸው የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ተጠሪ አመልካች በሁለት መ/ቤቶች ሁለት የተለያዩ የቅጥር ውሎችን የፈፀሙ መሆኑንና በዚህ ረገድ ያለውን የሕግ ክለላ በሰበር አቤቱታቸው መጥቀሣቸው በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣ አዲስ የክርክር ነጥብ ነው በማለት ያነሱትን መቃወሚያ ስንመለከተው አመልካች የጡረታ መብት ተጠቃሚነታቸው የተጠበቀው በተጠሪ መ/ቤት ላበረከቱት አገልግሎት መሆኑ ያልተረጋገጠ በመሆኑ፣ አመልካች በሁለት የተለያዩ መ/ቤቶች ሁለት የተለያዩ የቅጥር ውሎችን መፈፀሜ እየታወቀ በዚህ ረገድ ያለው የሕግ ክለላ ግንዛቤ ውስጥ ሣይገባ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መስጠታቸው ስህተት ነው፡፡ በማለት በሰበር አቤቱታው ላይ መግለፃቸው በይዘቱም ሲታይ በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣ የክርክር ነጥብ ነው፡፡ ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ጠበቃ በዚህ ረገድ ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስም፤ አመልካች ከተጠሪ ድርጅት የተሠናበቱት የጡረታ ዕድሜ ስለደረሰ ሕጉም ስለሚያስገድዳቸው ጠይቀው ጡረታ ወጡ እንጂ ሥራ መልቀቅ ፈልገው አይደለም በማለት የተጠሪ ጠበቃ ያልቀረቡት መከራከሪያ ሲታይ አመልካች ከጥቁር አንበሣ ሆስፒታል በጡረታ የተገለሉ መሆኑ እየታወቀ በተጠሪ መስሪያ ቤት የተቀጠሩ መሆናቸው ጋር ተዳምሮ ሲታይ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በጡረታ ከተገለሉ በኋላ በተጠሪ መ/ቤት ተቀጥረው ሲሠሩ ቆይተው ስራውን የለቀቁትን በገዛ ፈቃዳቸው እንጂ የጡረታ ዕድሜ ደርሶ ሕጉ የሚያስገድዳቸው ሆኖ አይደለም፡፡ አመልካች ከተጠሪ መ/ቤት ስራቸውን የለቀቁት ዕድሜያቸው የጡረታ ዕድሜ ደርሶ ነው ቢባልም የጡረታ ዕድሜ የደረሰ ሠራተኛ የተጠሪን ጅርጅት ለመልቀቅ ከፈለገ ሊከለከል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ድርጅት የተሠናበቱት በገዛ ፈቃዳቸው ውጪ በሌላ ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት አመልካች በጡረታ የተሰናበቱ መሆኑን አምነዋል ወደሚለው ድምዳሜ መድረሱ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች ስራቸውን የለቀቁት በገዛ ፈቃዳቸው ነው ከተባለ በተከታይ ሊታይ የሚገባው ውጤቱ ነው፡፡ አመልካች በገዛ ፈቃዱ ስራውን የሚለቅ የተጠሪ ሠራተኛ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የመጠባበቂያ መዋጮውንና የአገልግሎት ካሣውን ወዲያውኑ የማግኘት መብት ስላለው ያልተፈፀመልኝ የአገልግሎት ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የጡረታ ዕድሜ ደርሷቸው ከሥራ በሕጉ አግባብ የተለሉ ከመሆኑም በላይ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ስለሆኑ የአገልግሎት ካሣ ሊወስዱ አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሠረቱ አመልካች የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆኑት በተጠሪ ድርጅት ላበረከቱት አገልግሎት አለመሆኑን ከላይ ተመልክተናል፡፡ በተጠሪ ድርጅት አዲስ የስራ ውል ፈጽመው ዕድሜያቸው ከስልሣ ዓመት በላይ እስኪሆናቸው ሠርተዋል፡፡ ዕድሚያቸው ስልሣ ዓመት ሲሞላቸውም በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የጡረታ ዕድሜ ደርሷል በሚል ምክንያት ከሥራ እንዲገለሉ ሣይደረግ ከተጠሪ ጋር ያላቸው የስራ ግንኙነት እንዲቀጥል መደረጉ አመልካች ሥራውን የለቀቁት የጡረታ ሕጉ እና የሕብረት ስምምነቱ ስለማያስገድዳቸው ነው የሚለው የተጠሪ ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ተጠሪ አመልካች የጡረታ መብት ተጠቃሚ በመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ መሠረት የአገልግሎት ካሣ ሊያገኙ አይገባም በማለት ያቀረቡትን ክርክር ስንመለከተውም አመልካች የጡረታ መብት ተጠቃሚነታቸው የመነጨው ለተጠሪ ላበረከቱት አገልግሎት ካለመሆኑም በላይ አዋጅ ቁጥር 494/98 ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓ.ም. በተደረገ ስምምነት የተጠሪን ድርጅት ለመልቀቅ የሚፈልግ ሠራተኛ የድርጅትን የመጠባበቂያ መዋጮውንና የአገልግሎት ካሣውን በጣምራ የማግኘት መብት እንደለው በአንቀጽ 38/1/ ስር የተመለከተ በመሆኑ እና የሕብረት ስምምነቱ ከአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የተሻለ ሁኖ ሲገኝ ደግሞ ተፈፃሚ ሊሆን እንደሚገባ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 134/2/ ሥር የተደነገገ ስለሆነ የተጠሪ ክርክር በሕግ ፊት ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸውን የሥራ ግንኙነት በፈቃዳቸው የለቀቁ መሆኑ ተረጋግጦ እያለና የሕብረት ስምምነቱ ደግሞ ለፕሮቪደንት ፈንዱና የአገልግሎት ካሣ በአንድነት ሊያገኙ የሚገባ መሆኑን የሚደነግግ ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉም ሆነ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22619 ጥር 02 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 63019 መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው እና የአመልካችን የአገልግሎት ካሣና ክፍያው ለዘገየበት ክፍያ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች የአገልግሎት ካሣና ክፍያ ለዘገየበት ብር 20,189.00 /ሃያ ሺህ አንድ መቶ ሠማኒያ ዘጠኝ ብር/ እንዲከፍል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 34476

ታህሳስ 02 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድርመሐመድ

ሂሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ኩመላ በጅሣ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- ብሔራዊ አስገብኚና ጉዞ ወኪል ድርጅት - ነ/ፊጅ በርሃኑ ከፍነው ቀረቡ

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ድርጅት ከሚያዚያ 29 ቀን 1975 ዓ.ም ጀምሮ በሹፌርነት ሙያ ለ24 ዓመታት ማገልገላቸውንና ያገኙት የነበረውን የደመወዝ መጠን ጠቅሰው ተጠሪ ያላግባብ የስራ ውሉን በማቋረጥ ያሠናበታቸው መሆኑን በመዘርዘር የስንብት ክፍያ የማስጠንቀቂያ ጊዜ የ6 ወራት ደመወዝ ካሣ ክፍያ እና ስራ ሠርተው ያልተከፈላቸው የ14 ቀን ደመወዝ እንዲከፈላቸው እንዲሁም የምስክር ወረቀት እንዲሠጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ በአሁኑ ተጠሪ ላይ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ ፍርድ ቤት ቀርቦ በሰጠው መልስ የአመልካች የሥራ ውል የተቋረጠው በተከታታይ አምስት ቀን ከሥራ ገበታቸው በመለየታቸው በሕጉ አግባብ መሆኑን የሚገባቸው ክፍያ አለመኖሩንና በድርጅቱ ውስጥ 24 አመታት ያገለገሉ በመሆኑ የአገልግሎት ጡረታ አበል በእድሜ ልክ ስለሚከፈላቸው የአገልግሎት ካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብት የሌላቸው ሆኑን በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የተጠሪ እርምጃ በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመጥቀስ የሥራ ስንብቱ አላግባብ መሆኑን በማለጸ የአሁኑ አመልካች የጡረታ መብት ተጠቃሚ በመሆናቸው የስንብት ክፍያ እንደማይገባቸው የ14 ቀን ደመወዝ እንደሚገባቸው ይህ ክፍያ ለዘገየበት የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸውና የምስክር ወረቀትም እንዲሰጣቸው ዘርዝሮ ከወሰነ በኋላ የስንብት ወይም የጡረታ መብት ለአመልካች አንዱ ካልተፈፀመ አቤቱታ የማቅረብ መብታቸውን ጠብቆላቸዋል የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ታህሳስ 16 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የስር ፍ/ቤት የጡረታ መብት የመከልከል ሥልጣን ሣይኖረው በዚህ ረገድ የሠጠው ውሣኔ እርስ በራሱ የሚጋጭና ህጋዊ መሠረት የሌለው መሆኑን ስንብቱን ህገ-ወጥ ነው ብሎ ከወሰነ በኋላ በህጉ መሠረት ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎችን ማለፉ ያላግባብ መሆኑን በመዘርዘር ውሣኔው ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርቦ ሐምሌ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን ሠጥቷል፡፡ በመልሱ ላይም የአመልካች የስራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ተብሎ አለመወሰኑን የስር ፍ/ቤት የአመልካችን ዘላቂ የጡረታ መብት ተጠቃሚነት ከልክሎ የሰጠው ውሣኔ አለመኖሩን በመዘርዘር አመልካች የስር ፍ/ቤት ያልሰጠውን ውሣኔ እንደሰጠ በማስመሰል እንዲሁም የማይገባቸው ክፍያ ስር ፍ/ቤት ላይ ያልነበረን ጭብጥ በማንሣት እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ያላግባብ በመሆኑ የሠበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የስር ፍ/ቤት አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት ያላግባብ ነው በማለት ከወሰነ በኋላ የካሣ ይከፈለኝ ጥያቄውን ማለፉና በስንብት ክፍያ ላይ የሠጠው ውሣኔ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመርመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው የአመልካች የስራ ስንብት ያላግባብ ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤት መወሰኑን ነው ተጠሪ ለዚህ ችሎት የጽሑፍ መልስ ሲያቀርብ የአመልካች የስራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው በሚል ውሣኔ አለመሰጠቱን የገለፀ ቢሆንም በመ/ቁ 26844 ሠኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የውሣኔ ግልባጭ ግን የስራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ የለም የሚለው ክርክር መሠረት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

የአመልካች የስራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ከተባለ ጉዳዩ እልባት ሊያገኝ የሚገባው ከህግ ውጪ የሆነ የስራ ውል ማቋረጥ የሚያስከትላቸው ውጤቶችን የሚገዛውን የህጉን ዘርፍ ባገናዘበ መልኩ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት ያላግባብ መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች በተጠሪ እንዲከፈል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው የስራ ስንብቱ ህገ-ወጥ መሆኑ ተገልጾ ከተወሰነ በኋላ እንዲከፈላቸው የተደረገው አመልካች የጠየቋቸው ክፍያዎች ሁሉ አይደለም፡፡ በአመልካች ከተጠየቁት ክፍያዎች ውስጥ የካሣ እና ይዜው ካሣ የዘገየበት የ3/ሦስት/ ወር ደመወዝ ክፍያ በስር ፍ/ቤት በዝምታ የታለፉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የስራ ውል ከህግ ውጪ ነው የተቋረጠው እየተባለ ውጤቱ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት በዝምታ ማለፉ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን ዓላማ የሚፃረር ነው፡፡ የስራ ውል ከህግ ውጪ ሲቋረጥ የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ህጉ የደነገገው ኢንዱስትሪያላዊ ሠላምን በመጠበቅ ምርትና ምርታማነት ለማሣደግ እና ያላግባብ የሚባረርን ሠራተኛ ለመካስ ነው፡፡ በመሆኑም የስራ ውል ከህግ ውጪ መቋረጡ ከተረጋገጠ የኢንዱስትሪውን ሠላም የመጠበቅና የሠራተኛውን የመካስ መብቱን ህጉ ዓላማ ማድረጉን ግንዛቤ ውስጥ ለማስገባት ዳኝነት ሊሰጥ ይገባል በዚህ ረገድ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተግባራዊ የሚደረጉትም ግልጽ ዳኝነት መጠየቁን አግባብነትና ብቁነት ያለው ማስረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

እኛችን ወደተያዘው ስንመለስም አመልካች ሊከፈሉኝ ይገባል የሚሏቸውን ክፍያዎች ዘርዝረው አቅርበው ተጠሪ ክፍያዎቹ አይገባም የሚልበት ምክንያት በዋናነት የስራ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ሲሆን የአመልካች የአገልግሎት ጡረታ አበል የማግኘት መብት በህጉ የተጠበቀ በመሆኑ የአገልግሎት ክፍያ ሊያገኙ አይገባም በማለትም ጭምር ነው፡፡

ይሁን እንጂ የአመልካች የስራ ስንብት ባግባቡ አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡ እንዲሁም አመልካች የ24 ዓመታት አገልግሎት ያላቸው ቢሆንም በጡረታ ህግ የተመለከተውን መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ላይ ደርሶ ከስራ የተገለሉ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያ የማያገኙበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2(ሰ) ድንጋጌ ያገናዝባል፡፡ የስር ፍ/ቤት የስንብት ወይም የጡረታ መብት አንዱ ካልተፈፀመ አመልካች አቤቱታ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለት መወሰኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገርና የተጠየቀውን ዳኝነት እንዲሁም የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው በህገ-ወጥ መንገድ ነው እየተባለ በአመልካች የተጠየቁት ክፍያዎች ውስጥ የካሣ ክፍያና ይህው ክፍያ ለዘገየበት ጊዜ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ጥያቄዎች በዝምታ መታለፋቸውና የስራ ስንብት ክፍያ በአማራጭ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 26844 ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 58367 ጥቅምት 05 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች የስራ ስንብት ክፍያ የማስጠንቀቂያ ጊዜ የሦስት ወር ደመወዝ ክፍያው ለዘገየበት የ3(ሦስት) ወር ደመወዝ የስራ ውል ከህግ ውጪ ስለተቋረጠ የ6(ስድስት) ወር ደመወዝ ስራ ተሰርቶ የልተከፈላቸው የ14 ቀን ደመወዝ ይከፈል ብለናል የምስክር ወረቀትም ይሰጣቸው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 40305

ታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት አ/ማ - ነ/ፊጆ አብዱልቃድር

ተጠሪ፡- እነ አቶ ታመነ ጫላ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳዩ የጀመረው በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሾች ሲሆኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት በተከሣሽ /አመልካች/ ላይ ባቀረቡት ክስ፤ አመልካች ተጠሪዎችን በጥበቃ የሥራ መደብ ቀጥሮ ሲያሰራቸው ቆይቶ ያለአግባብ ከሥራ ስላሰናበታቸው የሥራ መደባቸው በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 10 መሠረት መሆኑ ቀርቶ በአንቀጽ 9 መሠረት ቋሚ ሠራተኛ አድርጎ ወደ ስራቸው እንዲመልሳቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቱ ስልጣን የለውም፣ የመክሰስ መብት የላቸውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ሥራ ለማቃለል ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ስራው ሲቃለል ማሠናበቱ አግባብ ነው፤ በመሆኑም ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ላይ ለምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ ተጠሪዎች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ተጠሪዎች የተቀጠሩት ሥራ ለማቃለል የተቀጠሩ መሆኑን ያላረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ናቸው በማለት አመልካች የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ከፍሏቸው ወደ ሥራቸው እንዲመልሣቸው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም ተጠሪዎች በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ መሠረት የተቀጠሩ ሲሆን ስራው ሲቃለል መሠናበቻው አግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የተጠሪዎች ስንብት ሕገ-ወጥ ነው የመባሉን አግባብነት ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ተጠሪዎች ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተደምጧል፡፡

ከመዝገቡ እና ከክርክሩ ሂደት ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት በጥበቃ የሥራ መደብ ሲሰሩ ቆይተው በመሰናበታቸው የተቀጠሩበት ሥራ ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ቋሚ ሠራተኛ ሆነው ወደ ሥራ እንዲመለሱ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም የተጠሪዎች ክስ ተጠሪዎች ቀድሞውኑ የተቀጠሩት ለተወሰነ ሥራ ወይም ጊዜ መሆኑን ነገር ግን ሥራው ቀጣይነት ስላለው በቋሚነት ለመቀጠር የጠየቁ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከአመልካች ክርክርና ማስረጃም ተጠሪዎች በአ/ቁ. 337/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ መሠረት መቀጠራቸውን ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ የአንድ የሥራ ውል በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10 ሥር በተመለከቱት ሁኔታዎች የተደረገ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር የሥራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል፤ የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ መደረጉን የማስረዳት ሸክም ያለበት ደግሞ አሠሪው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን የፈረሙትን ውል በማቅረብ አስረድቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የሰጠው ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ አልተደረገም በሚል ሣይሆን በእርግጥም አመልካች ተጠሪዎችን ሥራ ለማቃለል የቀጠራቸው ለመሆኑና ያሠናበታቸውም ሥራው በመቃለሉ መሆኑን አላስረዳም በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ ሥራ ለማቃለል መቀጠራቸው ውሉ በሚገባ የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ የሥራ ውላቸው በአዋጁ አንቀጽ 10 መሆኑ ቀርቶ በአንቀጽ 9 መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ እንዲሆን መጠየቃቸው የተቀጠሩት አመልካች እንዳለው ሥራ ለማቃለል መሆኑን ያውቁ እንደነበርና በወቅቱ አመልካችና ተጠሪዎች የነበራቸው ሃሣብ ይኸው መሆኑን በሚገባ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪዎች ሥራ ለማቃለል የተቀጠሩ ላለመሆኑ ያስረዱት ነገር የለም፡፡

ተጠሪዎች ሥራው ቀጣይነት አለው በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ምንም እንኳን ስራው የአሠሪው ቋሚ ስራ ቢሆንም እንኳን መብዛት የሚኖርበት ጊዜ ሥራን ለማቃለል ለተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መፈፀም የሚቻል መሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10/1/ሐ/ የሚፈቅድ በመሆኑ የተጠሪዎች ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ ይመለሱ በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 67773 በ14/11/2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13061 በ05/02/2000 የሰጠውና የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16081 በ17/08/99 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ በመሆኑ ጊዜው ሲያልቅ መሠናበታቸው ሕጋዊ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 40804

ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ዳንዲቦሩ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ - ጠበቃ እስክንድር ዘውዴ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡-1/ ተክሉ ኡርጋ ኢደኤ - ቀረቡ፡፡

2/ ቶሎሳ መገርሳ ባልቻ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት የአሁኖች ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የስራ ውላችን ከህግ ውጭ አቋርጦብናል በማለት ነው ፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የሥራ ውሉ የተቋረጠው የትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሠረት ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር ባለመቻሉ ነው በመሆኑም ከሕግ ውጪ የተፈፀመ ነገር የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ እንደ ክርክሩ ያስረዳል ያለውን ማስረጃ አያይዞ ስለማቅረቡ ክሱን ባስተናገደው ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተገልጾአል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክርም ከሰማ በኋላ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በመነሳትም አመልካች የስራ ውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ ሊከፍሉ የሚገባቸውን ክፍያዎች ለተጠሪዎች ይከፈል ብሎአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጐአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መስከረም 15 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ ነው የተቋረጠው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪዎች በአመልካች ኮሌጅ በመምህርነት ተቀጥረው ሲሠሩ የነበረ ሲሆን፣ አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ተቀጥረው ሲሰሩበት የነበረው የስራ ክፍል በበቂ ምክንያት ተሰርዞአል፡፡ ሥራው የለም በማለት ነው ::ተጠሪዎችም ክሱን የመሠረቱት ሥራው ስላለ ወደ ስራችን እንመለስ በማለት ሳይሆን ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነውና ልዩ ልዩ ክፍያዎች ይከፈሉን በማለት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28(1)(መ) እንደተመለከተው ሠራተኛው ጉዳይ የያዘው የስራ መደብ በበቂ ምክንያት ሲቀርብና ሠራተኛውን ወደ ስራ ቦታ ማዛወር የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የሥራ ውሉ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች ይሠሩበት የነበረው የሥራ መደብ /የማስተማር ስራ/ መንግስት ባወጣው መመሪያ መሠረት መሠረዙን በማስመልከት አመልካች ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎችም ይሄንኑ አልካዱም መንግስት ያወጣው መመሪያ ከመስከረም ወር 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከግል ትምህርት ተቋሞች የሚመረቁ ዕጩ መምህራን በመንግስት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሞች እንደማይቀጠሩ መታዘዙን የሚያመለክት ነው፡፡ ተጠሪዎች ተቀጥረው ይሠሩ የነበሩትም እጩ መምራንን ማሰልጠን ነው፡፡ መመሪያው ከወጣ በኋላ ግን ለመሠልጠን ተማሪ ሊመዘገብ አልቻለም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ተጠሪዎች ይሠሩበት የነበረው የሥራ መደብ የለም ማለት ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች እንደመልሱ ያስረዳልኛል ያለውን ማስረጃ ከመልስ ማመልከቻው ጋር አያይዘን እንዳቀረበለት በውሳኔው ላይ ገልጿል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መዝገቡ ለቃል ክርክር በተቀጠረበት ዕለት ነገረ ፈጁ አልቀረበም፤ የሚል ምክንያት በመስጠትና ማስረጃ እንደሌለው በመግለጽ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ቀደል ሲል እንደተመለከተው አመልካች በዋነኛነት የጠቀሰው ማስረጃ የመንግስት መመሪያ ነው፡፡ በመንግስት የሚወጡ ሕጐች እና መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ወዘተ በግልጽ የሚታወቁ እንደመሆናቸው ፍ/ቤቶች (ዳኞች) ግንዛቤ የሚወሰዱባቸው ናቸው፡፡ ተከራካሪ ወገን ለክርክሩ የሚጠቅመውን ሕግ ከአስረጅነት አላቀረበም በሚል ክርክሩን በያዘነው ጉዳይ እንደምናየው ደግሞ አመልካች ለሥራ ውሉ ማስረጃ ስለማቅረቡ ፍ/ቤቱ በሚገባ መዝግቦለታል፡፡ ጉዳዩ ለቃል ክርክር በተቀጠረበት ዕለት ነገረ ፈጁ ባለመቅረቡ ማስረጃው እንደሌለ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ሲጠቃለል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 30239 ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 68312 ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ ቁ 348 (1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው በሕጋዊ መንገድ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 36194

ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

አመልካች፡-ዶ/ር ማንደፍሮ እሸቴ በራሳቸው እና ሞግዚት ለሆኑላት ለህፃን ጀሲካ ማንደፍሮ ጠበቃ አዳሙ ሽፈራው ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- ፍሬድረክ ኤቨርት ሲቲፍቱንግ- ጠበቃ መሐሪ ዓለማየሁ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሆኖ የጉዳት ካሣንና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክፍያዎችን የሚመለከት ነው ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች የካቲት 02 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ የአመልካች ህጋዊ ባለቤት እና የህፃን ጀሲካ ማንደፍሮ ወላጅ እናት የሆኑት ሟች ዶ/ር ሠብለ ደምሰው በተጠሪ መ/ቤት ከሚያዝያ 25 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ በፕሮጀክት ስራ አስተባባሪነት የሥራ መደብ በወር ደመወዝ ብር 4500.00/አራት ሺህ አምስት መቶ ብር/ በሠራተኛነት ተቀጥረውና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም ከደመወዛቸው በተጨማሪ እየተከፈላቸው በማገልግል ላይ እያሉ ተጠሪ ለመስክ ስራ ወደ አዋሣ ልኳቸው ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ላይ እንዳሉ ተጠሪ ለመስክ ስራ በግልፅ የመደበው መኪና ነሐሴ 09 ቀን 1997 ዓ.ም ተገልብጦ ዶ/ር ሠብለ ደምሠው ህይወታቸው በአደጋው ወዲያውኑ ማለፍን በመጥቀስ የጉዳት ካሣ፣ የቀብር ማስፈፀሚያ፣ የስንበት ክፍያ እንዲሁም የዓመት ፈቃድ ክፍያ እና ክፍያው ለዘገየበት ከበቂ ኪሣራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው ፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነት ቀርቦ የሟች የስራ ቅጥር ውል ባለመሆኑ በስራ ክርክር ችሎት ሊታይ እንደማይገባውና ሟች የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቅጥር ሆነው በተከሣሽ ድርጅት የነበራቸው የአገልግሎት ውል መሆኑን በመግለፅ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ሟች ህይወታቸው ባሉ ጊዜ ከተከሣሽ ጋራ ውል ያልነበራቸው መሆኑን ፣ ህይወታቸው ባለፈበት ጊዜም ወደ መስክ የሄዱት ከተከሣሽ ድርጅት ጋራ ለስራ ውል ግንኙነት ሣይኖራቸው አንደኛ አመልካች ባለቤታቸው በመሆናቸው አንድ ላይ ለመሄድ ፈልገው መሆኑን፣ የመኪና መገልበጥ አደጋው የደረሠውም በተከሣሽ ድርጅት የተመደበ ሹፌር እያለ የስር አንደኛ ከሣሽ አላግባብ መኪናውን ከሹፌሩ በመቀበል በማሽከርከራቸው በመሆኑ ተከሣሽ ድርጅት ለአደጋው ኃላፊ ሊባል እንደማይገባና የተጠየቁትን ክፍያዎችም የስራ ውል ግንኙነት ሣይኖር የሚከፍሉበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ሚያዝያ 04 ቀን 1998 ዓ.ም በፃፈው የመከላከያ መልስ ማመልከቻ ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር እና ማስረጃዎችን ከሠማ በኋላ በተጠሪ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረቡትን የክርክር ነጥቦች ውድቅ በማድረግ በሟችና በተጠሪ መካከል የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የነበረ መሆኑን ተረጋግጧል በማለት ድምዳሜ ከደረሠ በኋላ የጉዳት ካሣውን በተመለከተ አደጋው በደረሠ ጊዜ መኪናውን የሟች ባለቤት የሆኑት አንደኛ አመልካች ሲያሽከረክሩ ስለነበር በስራ ላይ የደረሠ አደጋ ነው ሊባል አይችልም በማለት በዚህ ረገድ የቀረውን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጐ ተከሣሽ ድርጅት የስንብት ክፍያ ብቻ ሊከፈል እንደሚገባ በማለፅ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካቾች ጠበቃ መጋቢት 02 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 4/አራት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የጉዳት ካሣውም ሆነ የቀብር ማስፈፀሚያ ክፍያ እንዳይከፈል የተባለው በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96(1) ስርና ተከታዩቹ ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ መሆኑን አንደኛ የሠበር አመልካች ጥፋት የለባቸውም አለባቸው ቢባል እንኳ የሁለተኛ አመልካች የካሣ ጥያቄ ውድቅ የሚሆንበት አግባብ አለመኖሩን፣ የሟች የቀብር ማስፈፀሚያ የተከላከለውም ህጋዊ መሠረት ሣይጠቀስ መሆኑንና ፣ ሟች ያልወሠዱት የዓመት እረፍት ክፍያ ውድቅ የተደረገውም የሠበር ተጠሪ ባልተከራከርንበትና ባላስረዳ ሁኔታ መሆኑን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ የሞት ጉዳት ካሣ ብር 270,000.00(ሁለት መቶ ሰባ ሺህ) ፣ የቀብር ሥርዓት ማስፈፀሚያ የሟችን የሁለት ወር ደመወዝ፣ ያልተወሰደ የዓመት እረፍት የሟች የሁለት ወር ደመወዝ እና ተጠሪው ክፍያ ላዘገየበት የሟች የሶስት ወር ደመወዝ ለሠበር አመልካቾች ተከፍሎ እስከ ሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሠብ ወለድ ጋር እንዲከፈል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው የአመልካቾች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ በሠበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙም፤ የተጠሪ ጠበቃ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን አቅርበዋል፡፡ በመልሣቸውም የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ማየቱ ተገቢ ያልነበረ ስለመሆኑና ሟች የተጠሪ መደበኛ የቅጥር ሠራተኛ ያልነበሩ ስለመሆናቸው፣ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ካየም ሟች ዶ/ር ሠብለ ደምሰው ከተጠሪ ጋር ባደረጉት የአገልግሎት ውልም መሠረት መወሠን የነበረበት ስለመሆኑ፣ የሟች የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መደበኛ ተቀጣሪ ሆነው ከተጠሪ ዘንድ በተወሠነ ጊዜ በተደራቢነት አገልግሎት መስጠታቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ከተጠሪ ጋር የቅጥር ውል ነበራቸው ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ፣ ሟች የአገልግሎት ውልም ቢሆን ሟች በ09/12/1997 ከመሞታቸው አንድ ወር ተኩል ቀደም ብሎ በ23/10/97 ያበቃ ስለመሆኑ፣ ሟች የሞቱት በስራ ላይ ባልነበሩበትና መኪናውን ለማሽከርከር ከተጠሪ ፈቃድ ባልተሠጣቸው በአንደኛ አመልካች አላግባብ ሲሽከረከር ስለመሆኑ ተጠያቂነትም ቢኖር ክስ አልቀረበበትም እንጂ ከውል ውጪ ባለ ኃላፊነት ስለመሆኑ ይህንን ዓይነት አደጋ ሲያደርስ ሟች ሊካሱ እንዲችሉ ተጠሪ በአገልግሎት ውሉ መሠረት በየወሩ ለሟች ብር 200 የመድን ሂሣብ ለራሣቸው ይከፈል የነበረ ስለመሆኑ፣ የቀረቡት የክፍያ ጥያቄዎች የህግ መሠረት የሌላቸው ስለመሆኑ በመዘርዘር የአመልካቾች የሠበር አቤቱታ ውድቅ ሆኖ በቂ ወጪና ኪሣራ እንዲከፈል ይወሰን ዘንድ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካቾች የተጠሪ ጠበቃ መከራከሪያ ነጥቦች ሥነ ሥርዓቱን ጠበቃው ያልቀረቡ መሆኑን በመለየትና ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር የሠበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ግራ ቀኙ የቃል ክርክር እንዲያደርጉ ታዝዘ ክርክራቸው ታህሣሥ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተደምጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ እና የቃል ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ከላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አደጋው የደረሠው አንደኛ የሠበር አመልካች ያላግባብ መኪናውን ከሾፌሩ በመቀበል ሲያከራክሩ ነው ተብሎ ተጠሪ የጉዳት ካሣ የመክፈል አላፊነት የለበትም መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ? በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች ህይወታቸው ያለፈው የተጠሪ መስሪያ ቤት ንብረት የሆነው መኪና ለመስክ ስራ ከሄደበት ቦታ በመመለስና በአንደኛ የሠበር አመልካች በመሽከርከር እያለ በመገልበጡ ምክንያት መሆኑን፣ በሟችና በተጠሪ መካከልም የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙት መኖሩ ተረጋግጧል ተብሎ በስር ፍ/ቤት መወሠኑን፣ አንደኛ አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤት የስራ ግንኙነት ያላቸው መሆኑንና ሁለተኛ ተጠሪ አካለ መጠን ያላደረሠች የሟች ተወላጅ መሆናቸውን ነው የስር ፍ/ቤት የሟችና የተጠሪ ግንኙነት በአሠሪና ሠራተኛ የሚፈረጅ መሆኑን በመደምደም ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል እንደሚገባ በውሣኔው ላይ መግለፁን ከመዘገቡ ተመልክተናል፡፡ ሌላው ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የሟችና የተጠሪ ግንኙነት በሚያዝያ 25 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ ውል መቋቋሙን፣ በዚህ ውል መሠረት ግንኙነታቸው እስከ ጥቅምት 21 ቀን 1997 ዓ.ም ቆይቶ ከጥቅምት 22 ቀን 1997 ዓ.ም በኋላ ግን የስራ ቅጥር ስምምነት ለመዋዋል እንደሚያቅዱ መስማማታቸውን፣ ከዚህ በኋላ ተደረገ በተባለ ማሻሻያም የውል ግንኙነት እስከ ሠኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ መራዘሙን እንዲሁም ከሚያዝያ - ነሐሴ ወር 1997 ዓ.ም ላሉት ጊዜያት በውሉ ላይ የተመለከቱት ክፍያዎች በሟች ስም ተሠርተው ለአንደኛ አመልካች መከፈላቸው በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮችም ሟች ለመስክ ስራ የሚያስፈልጋቸው የውሎ አበል ክፍያ ተከፍሏቸው ለስራው የሄዱ መሆኑ መመስከራቸውን ነው፡፡ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ጉዳዩች እነዚህ ሆነው የሰበር ተጠሪ ሟች ጋር የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የለንም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሠበር ችሎቱ በሠጠው የጽሁፍና የቃል ክርክር ያቀረበውን ክርክር ሥነ-ሥርዓታዊ መሆን ያለመሆኑን መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

የተጠሪ ጠበቃ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚችንና የተጠሪን ግንኙነት አስመልክቶ በቀረበው ክርክር የተጠሪን ክርክር ባለመቀበል በመካከላቸው የነበረው ውል ከአሠሪና ሠራተኛ የሚመነጭ ዓይነት ውል ስለመሆኑ በመጥቀስ ውሣኔ መስጠቱን አምነው በዚህ ነጥብ ላይ ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያላቀረቡት ለሚቹ ይከፈል የተባለው የስራ ስንብት አነስተኛና የተጠሪን መብት የማይጐዳ ስለሆነ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሠረቱ በአንድ የፍ/ቤት ውሣኔ ይግባኝ ለበላይ ፍ/ቤት የሚቀርበው ውሣኔው ወይም ትዕዛዙ የይግባኝ አቅራቢውን መብት ወይም ጥቅም የነካ ፣ አሊያም ግዴታው ከፍ እንዲል ያደረገ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ስለ ይግባኝ አቀራረብ የተደነገጉት የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡት ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የሚችንና የተጠሪ ግንኙነት የስራ ቅጥር ግንኙነት ስለመሆኑ በመቀበል የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፍል መወሠኑ የተጠሪን መብት ወይም ጥቅም የነካ አይደለም ሊባል የማይችልበት ህጋዊ ምክንያት ስለሌለ የተጠሪ ጠበቃ በሥርዓቱ መሠረት በጉዳዩ ላይ ቅሬታ ሣያቀርቡ በተጠሪና በሚች መካከል የስራ ቅጥር ግንኙነት የለም በማለት በሠበር ደረጃ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክር ሥነ-ሥርዓታዊ ካለመሆኑም በላይ ሚች አደጋው በደረሠባቸው ወቅት ለመስክ ስራ የሄዱት ከተጠሪ መስሪያ ቤት አበል ተከፍሏቸው ነው ተብሎ ከተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ አኳያ ተቀባይነት የለውም ሚች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቋሚ ሠራተኛ መሆናቸውም ከተጠሪ ጋር የስራ ቅጥር ግንኙነት ለማድረግ የሚከለክላቸው አለመሆኑን የአዋጅ ቁጥር 351/1995 አንቀጽ 24 ድንጋጌ በግልፅ ያሣያል፡፡ በመሆኑም በሚችና በተጠሪ መካከል ነበረ የተባለውን ግንኙነት በተመለከተ የተጠሪ ጠበቃ ያነሡት መከራከሪያ ሥነ-ሥርዓቱን ያልጠበቀና የግራ ቀኙን የማስረጃዎች ይዘት እንዲሁም ስለከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የወጣውን አዋጅ ያላገናዘበ በመሆኑ አልፈነዋል፡፡

ወደ ዋናው ጭብጥ ስንመለስም ሚች ህይወታቸው ያለፈው ተጠሪ ለመስክ ስራ የመደበውን መኪና ከተጠሪ ሹፌር አንደኛ አመልካች በመቀበል ሲያሽከረክሩ መሆኑ በግራ ቀኙ ያልተካደ ጉዳይ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች በወቅቱ ወደ መስክ የሄዱት ከተጠሪ ፍላጐት ውጪ ነው ከመባሉ በስተቀር የተጠሪ ሠራተኛ መሆናቸው አልተካደም፡፡

እንግዲህ ሚች የሞቱት 1ኛ አመልካች መኪናውን ሲያሽከረክሩ መሆኑ አሠሪ የሆነውን ተጠሪ ከአላፊነት ያድንዋል ወይ? የሚለው ጥያቄ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡

በመሠረቱ በስራ ምክንያት ለሚመጡ ጉዳቶች አሠሪው አላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ በስራ ምክንያት የሚመጣ ጉዳት ከሆነ አሠሪው አላፊነቱን እንዲወስድ የተደረገ ሲሆን በአዋጁም በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ መሆኑን በቁጥር 95(2) ደንግጓል በአዋጅ አንቀጽ 96(1) "አሠሪው ጥፋት ባይኖረውም....." ተብሎ መመልከቱ የአሠሪው የአላፊነት ዓይነት ጥፋት ሣይኖር አላፊነት /Strict Liability or Liability in the absence of Fault/ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ አሠሪው ከዚህ ዓይነት አላፊነት የሚድነው ጉዳት የደረሠበት ሠራተኛ ሆነ ብሎ በራሡ ላይ ያደረሠው ጉዳት መሆኑን ማስረዳት ሲችል ስለመሆኑ አንቀጽ 98(2) ያስገነዝባል፡፡ሆነ ብሎ ያደረሠው ጉዳት የሚባሉት ሁኔታዎችም ሠራተኛው አስቀድሞ በግል የተሠጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎችን መጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን መተላለፍ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ እፅ ሠክሮ በሥራ ላይ መገኘት መሆናቸውን ህጉ በቁጥር 96(2(ሀ እና ለ)) ስር አመላክቷል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 97(1) ድንጋጌ ሲታይም አንድን አደጋ በስራ ላይ የደረሠ ነው ለማለት ሠራተኛው ስራውን በማከናወን ላይ እያለ ወይም ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሡ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ስራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ በማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት የደረሠበት ጉዳት ስለመሆኑ መርሁን ያስቀመጠ ሲሆን ይኸው ድንጋጌ ከፊደል (ሀ) እስከ ፊደል (መ) በተመለከቱት ንዑስ ድንጋጌዎች የተመለከቱት ምክንያቶች በስራ ላይ የደረሠ አደጋ ተብለው የሚጨመሩ ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ ስለሆነም በመርሁ መሠረት ሠራተኛው የጉዳት ካሣ ለማግኘት ማሣየት የሚጠበቅበት አደጋው ስራውን በማከናወን ላይ እያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የደረሠ መሆኑን፣ ወይም ደግሞ በራሡ ባልሆነ ምክንያት ግን ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው መልኩ የደረሠበት አደጋ መሆኑን ነው ።ከላይ እንደተገለፀው ከስራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ህጉ አስቀምጧል። ለዚህ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በአንቀጽ 97(1(ሐ)) ስር የተመለከተው ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት አሠሪው በመደበው የመጓጓዝ አገልግሎት ሠራተኛው ሲጠቀም ጉዳት ከደረሠ አደጋው በስራ ላይ እንደደረሠ ተቆጥሮ አላፊነቱን ከአሠሪው ሲወሰድ የሚገባ መሆኑ ተመልክቷል። ይኸው ድንጋጌ አሠሪው የመደበው የመጓጓዝ አገልግሎት አደጋው ከደረሠበት በአሰሪው ስር ባለው ሌላ ሠራተኛ ወይም 3ኛ ወገን ከሆነ አሰሪው ለተጐጂው ሠራተኛ የጉዳት ካሣ አላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ አያሣይም ይልቁንም ድንጋጌው በአዋጁ አንቀጽ 96(1) ስር ከተመለከተው የአሠሪ አላፊነት ዓይነት ጋር ተዳምሮ ሲታይ አሠሪው አላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያጠናክር ነው በሌላ አገላለፅ በሠራተኛው ላይ ጉዳት ያደረሠው ሠራተኛው ወደ ስራ ሲሄድና ከስራ ወጥቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ አሠሪው በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ሲጠቀም አደጋ የደረሠበት መሆኑ ከተረጋገጠ 3ኛ ወገኖች ለአደጋው ያደረጉት አስተዋጽኦ ለአሰሪው መከላከያ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም አንደኛ አመልካች የተጠሪን መኪና በወቅቱ ሲያሽከረክሩ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡ ተጠሪን ነፃ ሊያደርገው የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች አደጋው የደረሠው በስራ ምክንያት አይደለም ሲሉ የደረሠበት ድምዳሜ ከላይ የተመለከተቱን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል።

ተጠሪ ለጉዳቱ አላፊነት አለበት ከተባለ የጉዳት ካሣ መክፈል ያለበት ለየትኞቹ የተጐጂ ጥገኞች? የሚለው ጥያቄም በህጉ አግባብ መታየት ያለበት ነው። ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚሠጠው ድንጋጌም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 107(1(ሐ) ስር ተመልክቷል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም በስራ ላይ የሚመጣ ጉዳት የደረሠበት ሠራተኛ የሞተ እንደሆነ ለጥገኞች የጡረታ አበል ወይም ዳረጐት ወይም ካሣ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ ተመልክቷል።የአዋጁ አንቀጽ 110 ድንጋጌ ሲታይም ለሟች ሠራተኛ ጥገኞች የሚከፍሉትን የክፍያ ዓይነቶንና ጥገኛ የሚባሉትን ወገኖች በንዑስ ቁጥር አንድና ሁለት በግልፅ ዘርዝሯል። በዚህም መሠረት ማንኛውም ሠራተኛ ወይም ለማጅ ሠራተኛ በስራ ምክንያት በደረሠበት ጉዳት የተነሣ የሞተ እንደሆነ የጉዳት ካሣ ለጥገኞች፣ የቀብር ሥነ ሥርዓት ወጪ እንደሚከፈልና ጥገኞች የሚባሉትም የሟች ህጋዊ ባል ወይም ሚስት፣ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ የሟች ልጆችና በሟች ሠራተኛ ድጋፍ ይረዱ የነበሩ የሟች ወላጆች ስለመሆናቸው ተመልክቷል። ይሁን እንጂ ህጉ ጥገኝነት ማለት ምን እንደሆነ ትርጓሜ ያልሠጠበት ሲሆን ከህጉ አቀራረፅና ይዘት በመነሣት ግን የቃሉን ትርጉም ለመገንዘብ አያዳግትም። በመሆኑም በህጉ የተመለከተው ጥገኞች የሚለው ቃል ከሟች የምግብ፣ የመጠለያ፣የልብስና ለጤናው አጠባበቅ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንዲሟላላቸው የሚጠይቁትን ወገኖችን የሚመለከት ስለመሆኑ ተገንዝበናል ሥራ ሠርቶ እራሡን ለማስተዳደር የሚችልና ችግረኛ መሆኑ በቅድሚያ ያልተረጋገጠበት ወገን የሟች ሠራተኛ ባል ወይም ሚስት በመሆኑ ብቻ የጉዳት ካሣ የሚያገኝበት ምክንያት አይኖርም። ከጉዳት ካሣ ዓላማ ጋርም አንድ ላይ ይሄዳል ተብሎ እይታሠብም። ስለሆነም የሟች ሠራተኛ ባል ወይም ሚስት መተዳደሪያ የሚሆነው በቂ ሀብት ካለው ጥገኛ ሊባል አይችልም። ከዚህም በተጨማሪ በአንቀጽ 110(1) እና (2) የተመለከቱት ድንጋጌዎች አቀራረፅና ይዘት እንዲሁም በዘርፍ መሠረት የሚደረጉ ክፍያዎች ከገቢ ግብር ነፃ መሆናቸው፣ ሊተላለፍ፣ ሊከበር ወይም በዕዳ ማቻቻያነት ሊያዝ አለመቻሉ በአዋጁ አንቀጽ 112 ስር መመልከቱ የጉዳት ካሣ ዓላማው መተዳደሪያ የሚሆነው በቂ ሀብት የሌለውን የሟች ሠራተኛ ለመደገፍ የታሠበ ነው የሚለውን ክርክር የሚያጠናክር ነው ።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አንደኛ አመልካች የሟች ባል ቢሆኑም በቂ የሆነ መተዳደሪያ ሀብት ያላቸው ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሣያል። ስለሆነም አንደኛ አመልካች የሟች ጥገኛ ባለመሆናቸው የጉዳት ካሣ የሚያገኙበት ህጋዊ ምክንያት የለም።

ሁለተኛ አመልካችን በተመለተ ግን የሟች ልጅና በህጉ አግባብም የሟች ጥገኛ መሆኗ ስለተረጋገጠ የጉዳት ካሣ የሚገባት ሆኖ ተገኝቷል።

የቀብር ሥርዓት ማስፈፀሚያ ክፍያ የስር ፍ/ቤት ያለው አደጋው የደረሠው በስራ ምክንያት አይደለም። በሚል ነው። ሆኖም ከላይ እንደተመለከትነው ተጠሪ በአሠሪነቱ አላፊነት አለበት ተብሏል። ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(1(ለ) መሠረት የቀብር ሥነ ሥርዓት ማስፈፀሚያ የመክፈል አላፊነት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል። የዓመት ፈቃድ ክፍያን በተመለከተ በበታች ፍ/ቤቶች የተሠጠ ውሣኔ የሚነቅፍ ሆኖ አልተገኘም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሠጠው አላፊነትን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የጉዳት ካሣ መጠኑን አልወሠነም ከላይ እንደተመከለተው ተጠሪ ለጉዳቱ አላፊነት ያለበት የሚች ልጅ ለሆነችው ሁለተኛ አመልካች የጉዳት ካሣ የመክፈል አላፊነት ያለበት መሆኑን ተገልጿል። ለጥገኞች የሚከፈል የጉዳት ካሣ መጠን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(3) እና (4) ስር ተመልክቷል ። ስለሆነም የካሣ መጠኑን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ እንዲወሰን ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል።

<u>ውሣኔ</u>

1/ አላፊነትን በተመለተ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 21716 ሠኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 58497 ታህሣሥ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው የውሣኔው ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል።

2/ የስር ፍርድ ቤት የዓመት እረፍት እና የስንብት ክፍያን በተመለከተ የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል።

3/ ሟች የሞቱት በስራ ላይ የደረሠ አደጋ ነው ሊባል በሚችል ምክንያት በመሆኑ ተጠሪ የጉዳት ካሣ የመክፈል አላፊነት አለበት ብለናል።

4/ ተጠሪ የሟች የቀብር ሥርዓት ማስፈፀሚያ የመክፈል አላፊነት አለበት ብለናል።

5/ አንደኛ አመልካች፤ ዶ/ር ማንደፍሮ እሸቱ የሟች ጥገኛ ባለመሆናቸው የጉዳት ካሣ አይገባቸውም ብለናል።

6/ ሁለተኛ አመልካች ህፃን ጀሲካ ማንደፍሮ የሟች ጥገኛ በመሆኗ የጉዳት ካሣ ሊከፈላት ይገባል ብለናል።

7/ ለህፃን ጀሲካ ማንደፍሮ ሊከፈላት የሚገባትን የካሣ መጠንና የሟች የቀብር ሥነ ሥርዓት ማስፈፀሚያ መጠንን በተመለከተ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት መልሰንለታል። ይፃፍ።

8/ በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

መ/ት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 38811

የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ርሆቦት ሆሊሴቪየር ኃ/የተ/የግ/ማ ጠ/ተስፋዬ ክትላ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አማረ አድማሱ ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሥራ ክርክር ችሎት የጀመረ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚሁ ፍ/ቤት በቀረቡት ክስ አመልካች በህገ-ወጥ መንገድ የሥራ ውላቸውን ስላቋረጠው ወደ ስራ እንዲመልሣቸው የማይመልሳቸው ከሆነ ግን የተያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸውና የስራ ም/ወረቀት እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ላቀረበበት ክስ የስራ መሪ በመሆናቸው ክሱ በዚህ ፍ/ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት ከተቃወሙ በኋላ በድርጅቱ በደተረገው የመዋቅር በውስጥ የተጠሪ የስራ መደብ በመሠረዙና ተጠሪን ወደ ሌላ የስራ መደብ አዛውሮ ማሠራት ባለመቻሉ ማሠናበቱንና ይህም ስንብት ህጋዊ እርምጃ በመሆን የተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም አመልካች የማስጠንቀቂያና የስራ ስንብት ክፍያ ለተጠሪ ፈጽሚል የም/ወረቅትም ሠጥቷል በማለት ለፍሬ ጉዳዩ መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ የሥራ መሪ የሚያከናውነው ተግባር ላይ የተሠማሩ ስለመሆናቸው ማስረጃ ስላላቀረበ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም የድርጅቱን ወጪ በመቀነስ የአመልካች የመደበኛ ት/ቤቶች ሀላፊነት የስራ መደብ መሠረዙን ያስረዳ ቢሆንም ተጠሪን ወደ ሌላ ቦታ አዛውሮ ማስረዳት አለመቻሉን የሚያስረዳ ማስረጃ ስላላቀረበ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ስለሆነም የ2 ወር ደመወዝ ከፍሎ ተጠሪን ወደ ስራቸው ይመልሣቸው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይርባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ስንብቱ ህገ-ወጥ በመሆኑ የ2 ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ ይመለሱ የሚለውን ውሣኔ ያፀና ሲሆን ነገር ግን አመልካች ለተጠሪ የ2 ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የስንብት ክፍያ የከፈለ ለመሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ተጠሪ ወደ ስራ ከተመለሱ የተቀበሉትን ክፍያ ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የአመልካች አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ተጠሪ የስራ መሪ ናቸው በተደረገው የመዋቅር መሻሻያ የተጠሪ የስራ መደብ የተሠረዘና ወደ ሌላ የስራ መደብ አዛወሮ ማሰራት ባለመቻሉ የስራ ውሉ መቋረጡ በአግባቡ ነው በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

ይህ የአመልካች አቤቱታ ለሠበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ጥቅምት 18/2001 የተፃፈ መልስ አቅርበዋል ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና ከህጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጀመሪያ አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው በማለት ያቀረበውን ቅሬታ ስንመለከት የተጠሪ የስራ ኃላፊነት የስራ መሪ የሚሠኛቸው ነው ወይስ አይደለም የሚለው በማስረጃ የሚረጋገጥ የፍሬ ነገር ጉዳይ እንደመሆኑ አመልካች ይህንኑ የማስረዳት ሸክም አለበት ነገር ግን ከመዝገቡ እንደተረዳነው በስር ፍ/ቤት አመልካች ይህንን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ የለም በመሆኑም በዚህ በኩል ያቀረበው የሠበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

ወደ ፍሬ ጉዳዩ ስንገባ አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን እንመለከታለን ተጠሪ ከስራ የተሠናበትኩት በህገ-ወጥ መንገድ ነው ሲሉ አመልካች ደግሞ በተደረገው የመዋቅር ማሻሻያ የተጠሪ የስራ መደብ በመሠረዙ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች የድርጅቱን ወጪ ለመቀነስ ባደረገው የመዋቅር ማሻሻያ የተጠሪ የስራ መደብ መሠረዙን አመልካች አስረድቷል የሥር ፍ/ቤቶች ይህንን ካረጋገጡ በኋላ የሥራ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ያሉት አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ ሥራ ማዛወር የማይችል መሆኑን አላስረዳም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28/1/መ/ መሠረት አንድ ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ከስራ የሚሠናበተው የያዘው የሥራ መደብ በበቂ ምክንያት ሲሠረዝና ሠራተኛውን ወደ ሌላ ሥራ ማዛወር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ነው በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ የሥራ መደብ በመዋቅር ማሻሻል ምክንያት የተሠረዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የሥራ መደብ የተሠረዘው በበቂ ምክንያት ነው በሌላ በኩል ግን አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ የሥራ መደብ መዛወር አለመቻሉን የገለፀ ሲሆን ተጠሪ በቃራኒው አመልካች ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ ሊያሠራቸው የሚችል መሆኑን ገልፀው አልተከራከሩም በዚህ በሠበር ችሎት በሠጡት መልካም ቢሆን በአንቀፅ 28/1/መ/ መሠረት የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ማስጠንቀቂያ ሊሠጣቸው ሲገባ አመልካች ማስጠንቀቂያ አለመሰጠቱ ስንብቱን ህገ-ወጥ ያደረገዋል በማለት ከሚከራከሩ በቀር በአመልካች ድርጅት ውስጥ ተዛውረው ሊሠሩበት የሚችሉበት የሥራ መደብ እያለ የሥራ ውላቸው ሊቋረጥ እንደማይገባ ገልፀው አልተከራከሩም በመሆኑም ተጠሪው ይህንን ክርክር አንስተው ሣይከራከሩ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር አለመቻሉን አላስረዳም በሚል ምክንያት ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት የደረሠበት መደምደሚያ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22889 በ26/05/2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 63104 በ4/10/2000 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

3/ የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 28/1/ መሠረት በመሆኑ ህጋዊ ነው

4/ ተጠሪ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ከአመልካች የተቀበሉትን የማስጠንቀኪያ ጊዜ ክፍያ እና የሥራ ስንብት ክፍያ መልሠው ከሆነ አመልካቹ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ መልሠው ከሆነ አመልካቹ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈላቸው የሥራ ምስክር ወረቀት ያልሠጣቸው ከሆነም እንዲሠጣቸው ተወስኗል፡፡

5/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 38435

የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ኤስ ኦ-ኤስ የህፃናት መንደር - ጠበቃ አቶ አይሸሽም መድፍ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡-1. አቶ ከበደ ኩምሳ
2. አቶ ሚደቅሳ ተክሌ
3. አቶ ወልደጊዮርጊስ ሙለታ
4. አቶ ፋሲል ገ/ሕይወት
5. አቶ አበራ ታፈሰ
6. አቶ ጌታሁን በላቸው

ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው የአሁኑ ተጠሪዎች ከሳሾች ሲሆኑ አመልካች ተከሣሽ ነበር፡፡ ከሳሾች ያቀረቡት ክስ በድርጅቱ በጥበቃ ሠራተኛነት ለበርካታ አመታት ስናገለግል የቆየን ሲሆን ስራውን በሌላ ድርጅት ላሠራ ወስኛለሁ በሚል ሰበብ ያለአግባብ ከስራ ውጪ የሥራ ውላችንን ያቋረጠ በመሆኑ ወደ ሥራችን እንድንመለስ፣ የማይመልሰን ከሆነ ካሳና ጥቅማጥቅም እንዲከፈል ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

አመልካችም መጋቢት 5 ቀን 1999 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልሱ የድርጅቱን አሰራር ለማሻሻል ከሳሾች ይሠሩበት የነበረውን የጥበቃ ሥራ የጥበቃ አገልግሎት ለሚሠጥ “ትረስት የጥበቃና የሰው ኃይል አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር” ከተሰኘው ድርጅት ጋር ውል በማድረግ ሥራውን ያስተላለፈ መሆኑን በመግለጽ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 11314 በ13/9/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው የ6 ወር ደመወዝ ካሳ እና የእረፍት ጊዜ ክፍያ ተከፍሎአቸው ይሰናበቱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚህ በፍ/ቁጥር 67186 ሰኔ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የ6 ወር ደመወዝ ካሳ ተከፍሎአቸው ይሰናበቱ ተብሎ የተሠጠውን ውሳኔ ለማጣራት ያስቀርባል እንደገና ተመልሶ እና ትዕዛዙ የ6 ወር ካሳ ክፍያን አይመለከትም ሌሎች ውሳኔዎችን አጽንቼአለሁ ሲል ትዕዛዝ በመስጠቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ዋና ቅሬታ ስንብቱ የድርጅቱን ምርታማነት ለማሳደግ የአሠራር ዘዴ ለመለወጥ የተደረገ በመሆኑ ከሕግ ውጪ ነው መባሉና የ6 ወር ደመወዝ ካሳ እንዲከፈል የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲሻርልን የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ፍ/ቤትም የተጠሪዎች ስንብት ያለአግባብ ነው ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ በአግባቡ መሆኑ አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዞ ተጠሪዎች ሐምሌ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ ውሳኔው እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡እኛም የግራ ቀኙን ክርክር በሕግ ረገድ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥራ ውል ሊቋረጥ የቻለው ተጠሪዎች ይሠሩብት የነበረው የጥበቃ ሥራ ለሌላ የጥበቃ አገልግሎት ለሚሠጠው ድርጅት በመተላለፍ ምክንያት እንደሆነ በተጠሪዎችም አልተካደም ። ይህ ከታመነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 መሠረት አሠሪው አዲስ አሰራርን ለመከተል የድርጅቱን ምርታማነት ለማሻሻልና የአሠራር ዘዴዎች በመለወጡ ምክንያት ሠራተኞቹ ይሠሩበት የነበረው የሥራ መደብ ቢሠረዝ አሠሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውል ለማቋረጥ እንደሚችል በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የበታች ፍ/ቤት ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው ለማለት መሠረት ያደረገው አመልካች የጥበቃ ሥራ በሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲከናወን ተደርጓል ከሚል በስተቀር የሥራ መደቡ ተሠርዟል የሚል ባለመሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 28 ትርጉም ሊሠጠው የሚችል አይደለም የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ነው፡፡ በመሠረቱ አመልካች የሥራ መደቡን ለሌላ ድርጅት ሲሠጥ የጥበቃዎቹ ቅጥር፣ዕድገት፣ዝውውር፣ስንብትና ክፍያ የሚፈፀመው በዚያው ድርጅት ነው ። አመልካች የሥራ መደቡን ሠርዞ ያስተላለፈ በመሆኑ በቃል የክፍያ ስምምነት በማድረግ ለድርጅቱ የሚከፍል ስለሆነ ሥራው የሚያከናውነው በሌላ ድርጅት ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ በተያዘው ጉዳይ ለውሳኔው መሠረት መሆን የሚገባው የሥራ መደቡ መሠረዝ ወይም አለመሠረዝ ብቻ ሳይሆን ስንብቱ ሕጋዊ ነው ወይንስ ከሕግ ውጪ ነው የሚለው ጭብጥ ሆኖ አመልካች የመልስ ሰጭዎችን/የተጠሪዎችን/ የሥራ ውል ለማቋረጥ ሕጋዊና በቂ ምክንያት መኖሩን ማስረዳት ነው፡፡ አመልካች አከራካሪ የሆነውን የሥራ መደብ ለሌላ አካል ማስተላለፍን ተጠሪዎች በክስ ማመልከቻቸውም ላይ የጠቀሱትና ያልተካደ በመሆኑ ሥራን ለሌላ ማስተላለፍ /0ut sourcing/ ሕጋዊ ነው፡፡ ይህ ከሕግ ወጪ ነው የሚል ወገን አለመተላለፍን ማስረዳት ብቻ ነው፡፡ ይህ ክርክር የለም ምናልባት አመልካች ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸው ማሰናበቱ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደ ሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ ሳይሆን ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ማቋረጥ ውጤቱ ለሠራተኛው ሊከፈለው የሚገባውን የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈላቸው ሕጉ ከሚያስገድድ በስተቀር የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደ ሚለው የተለጠጠ የሕግ ትርጉም ላይ የሚያደርስ አይሆንም፡፡

ለማጠቃለል የሥራ መደብ በሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲከናውን አሳልፎ መስጠት/0ut sourcing/ በውጫዊ እይታ ሲታይ የሠራተኛውን መብት የሚነካ ቢመስልም በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ረገድ ሕጋዊ አሠራር ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት የ6 ወር ደመወዝ ካሳ ተከፍሎአቸው ይሠናበቱ በማለት የተሠጠው ውሳኔ ከላይ በተመለከቱ ምክንያቶች መሠረታዊ የሕግ ትርጉም ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የሚከተለውን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 11314 በ 13/9/2000 ዓ.ም ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው በማለት የ6 ወር ደመወዝ ካሳ ተከፍሎአቸው ይሠናበቱ ሲል የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ይፃፍ፡፡

2. ስንብቱ በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 35 መሠረት የማስጠንቀቂያ ሊከፈላቸው ይገባ የነበረውን እንደየአገልግሎት ዘመናቸው አንባር ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡
4. ተጠሪዎች ከ9/12/98/ እስከ ጥር 25 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ያለው የእረፍት ቅጣት ክፍያ እንዲከፈል በተሠጠው ውሳኔ ላይ የቀረበ አቤቱታ ስለሌለ ፀንቷል፡፡
5. ወጪና ኪሳራ የዚህ ፍ/ቤትን ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38023

የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - መሠረት የማነ ቀረበ

ተጠሪ፡- ብርሃኑ ደስዬ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ኪራይ ውልን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተው በወር ብር 8.00 /ስምንት ብር/ ኪራይ እየከፈለ ለመኖር የተከራየው ሰርቪስ ቤት ለዋናው ቤት አገልግሎት እንዲውል የተሠራ በመሆኑ እንዲለቅ ቢጠየቅ ፈቃደኛ ስላልሆነ ተገዶ ይወጣ ዘንድ ይወሰንበት በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ከተጠሪ የቀረበውን መልስ ከሰማ በኋላ ክርክሩን መርምሮ የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ያቀረበው ክስ የተሰረዘበት አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከተደረገው ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የግራ ቀኝ ወገኖች ግንኙነት የተመሠረተው በመሐከላቸው ተደርጎ በነበረው የቤት ኪራይ ውል ላይ ነው የቤት ኪራይ ውሉ የተደረገው ለአንድ ዓመት እንዲቆይ ታስቦ ቢሆንም፤ ለብዙ ዓመታት እንደቆየ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ አመልካችም ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደታደሰ በመቁጥር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2966/1/ በተመለከተው መሠረት ቤቱ ይለቀቅለት ዘንድ ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ አስቀድሞ ሰጥቶአል፡፡ ተጠሪ ደግሞ ማስጠንቀቂያ ቢሰጠኝም ሌላ ተለዋጭ ቤት እስካልተሰጠኝ ድረስ ቤቱን እንድለቅ አልገደድም፡፡ በመሐከላችን የተፈረመው ውልም የሚለው ይኸው ነው በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶችም ይህን ክርክር በመቀበል ነው የአመልካችን ክስ የሰረዙት፡፡

ከመዝገቡ እንዳየነው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት እራሱን የቻለ የመኖሪያ ቤት ሣይሆን፤ ለአፓርታማ ተከራዮች አገልግሎት ይውል ዘንድ የተሠራ ሰርቪስ ክፍል ነው፡፡ አመልካች ሰርቪስ ቤቱ እንዲለቀቅለት እንዲሁም ውሉ ቀሪ እንዲሆን የጠየቀውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል የሚያበቃው ውሉ እንዲያበቃ የሚፈልገው ተዋዋይ ወገን /አከራይ ወይም ተከራይ/ አስቀድሞ በሚሰጠው ማስታወቂያ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2966/1/ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አከራዩ አመልካች ሲሆን የቤቱም ባለቤት ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ሲነፃፀር በቤቱ ላይ የሚኖረው መብት በኪራይ የመጠቀም እንደመሆኑ ከባለሐብትነት ያነሰ ነው፡፡ ስለማይንቀሣቀስ ንብረት ኪራይ ትርጉም በያዘው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2896/1/ እንደተመለከተው ተከራይ የሆነው ወገን በጥሬ ገንዘብ ወይም በሌላ ነገር ለአከራዩ እየከፈለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተወሰነ ጊዜ የሚኖርበትን ግንኙነት የሚፈጥር ነው፡፡ ይህ ግንኙነት ደግሞ ዘለዓለማዊ ወይም ማብቂያ የሌለው ነው የሚባል አይደለም፡፡ ተለዋጭ ቤት ካልተሰጠኝ አልለቅም የሚለው የተጠሪ ክርክርም ከዚህ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡ አመልካች ሌላ ቤት መስጠት አልቻለም በሚልም የባለቤትነት መብቱን ማሣጣት በሕግ የሚደገፍ አይደለም፡፡ ተጠሪ ቤቱን የያዘው ከሰኔ 1 ቀን 1974 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን፣ ከዚህ በኋላ ግን የባለቤቱን ፈቃድ እስካላገኘ ድረስ ቤቱን ይዞ የሚቆይበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ትክክል ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 61614 ታህሣሥ 18 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 53067 መጋቢት 2 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ለአመልካች ያስረክብ ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 40921

የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቢሲኒያ ባንክ (አ.ማ) - ነ/ፈጅ ዱላ መራራ

ተጠሪ፡- እነ አብዱ አህመድ (266 ሰዎች) - ጠበቃ ምትኩ

በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱታ በመ/ቁጥር 42132 ከቀረበው አቤቱታ ጋር በስረ ነገርም ሆነ በጭብጥ ረገድ ተመሳሳይ በመሆኑ ሁለቱም መዛግብት ጐን ለጐን ተመርምረው ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበውም ሆነ በመዝገብ ቁጥር 42132 የቀረበው የሰበር አቤቱታ ከፍርድ አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ሲሆን በዚህ መዝገብ የፍርድ ባለመብቶች የሆኑት የአሁን ተሰጠሪዎች በፍርድ ባለእዳ ጣና ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ላይ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው የፍርድ ባለእዳው ንብረት ተሸጦ በአመልካች ባንክ በዝግ ሂሳብ እንዲቀመጥ የተደረገው ገንዘብ ወጭ ሆኖ እንዲከፈለን ይታዘዝልን በማለት ጠይቀው የአሁን አመልካችም ቀርቦ በፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ የተሰጠባቸው የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ለብድር አከፋፈል በዋስትና የያዛቸው ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2857 መሰረት ከማናቸውም ገንዘብ ጠያቂ በፊት በተሽከርካሪዎቹ ላይ የቅድሚያ መብት ስላለኝ በእነዚህ ተሽከርካሪዎች ላይ የፍርድ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት መቃወሚያ ማቅረቡን ተገንዝበናል፡፡ በተመሳሳይም በመ/ቁ. 42832 ተጠሪዎች የሆኑት እነ አቶ አበራ መለሰ በፍርድ ባለእዳው አበባው ደስታ የግል ትራንስፖርት ላይ የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው የባለእዳው ተሽከርካሪዎች ተሸጠው በአመልካች ባንክ በዝግ ሂሳብ እንዲቀመጥ የተደረገው ገንዘብ ወጭ ሆኖ እንዲከፈለን ይታዘዝልን በማለት አመልክተው በዚህ መዝገብም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2857 መሰረት ከማናቸውም ገንዘብ ጥያቄ በፊት የቅድሚያ መብት እንዳለው መቃወሚያውን አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 167 መሰረት በቅጥር ላይ ከተመሰረተ ግንኙነት የሚመነጭ ማንኛውም የሰራተኛ ክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የእዳ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚኖረው ስለተመለከተ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ በአመልካች ባንክ በዝግ ሂሳብ እንዲቀመጥ የተደረገው ገንዘብ ወጭ ሆኖ ለፍርድ ባለመብቶች እንዲከፈል በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚሁ ትእዛዝ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በዋስትና በያዛቸው ንብረቶች ላይ የቅድሚያ መብት ሳያገኝ መቅረቱ ከአዋጅ ቁጥር 97/90 እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2857 እንደዚሁም ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አኳያ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ በሁለቱም መዛግብት ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍና በቃል አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተሰጠው ሲሆን በበኩላችንም የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ መርምረነዋል፡፡ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፍርድ አፈፃፀሙ ሲቀጥል ለፍርድ ባለመብቶች የአሁን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች ፍርድ ማስፈጸሚያነት እንዲሸጡ ትእዛዝ የተሰጠባቸው የተለያዩ ተሸከርካሪዎች አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ለብድር በዋስትና የያዛቸው ተሸከርካሪዎች እንደሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ባንክ መያዣ የያዛቸውን ንብረቶች እዳው ሳይከፈለው በቀረ ጊዜ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ለተበዳሪው በመስጠት ያለማንም ጣልቃ ገብነት በመያዣ የያዘውን ንብረት በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም ሌላ መያዣ የተቀበለ ባለገንዘብ ከመያዣው ሽያጭ ዋጋ ከሌሎች ባለገንዘቦች ቀድሞ የመቀበል መብት እንዳለውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2857/1/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንጻር አመልካች ከብድር አከፋፈል በመያዣነት በያዛቸው ንብረቶች ላይ የቀደምትነት መብት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም የአሰሪና ሰራተኛን ጉዳዩ በሚመለከተው በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት በቅጥር ላይ ከተመሰረተ የስራ ግንኙነት የሚመነጭ ማንኛውም የሰራተኛ የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የእዳ ክፍያ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚኖረው በአንቀጽ 167 ላይ ተመልክቷል፡፡ አመልካች የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት በአሰሪው ላይ ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ክስ አቅርበው ያሰፈረዱ ባለ ገንዘቦች በሚኖሩበት ጊዜ በፍርዱ መሰረት ለነዚህ ባለገንዘቦች ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሰራተኖች በአሰሪያቸው ላይ ክስ መስርተው ካስፈረዱ ለሰራተኞቹ ቅድሚያ ክፍያ እንደሚፈጽም የሚያመለክት እንጂ ከዚህ አልፎ ባንኩ ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘውን ንብረት ሕጉ በሰጠው ስልጣን መሰረት ሸጦ ለብድሩ እዳ እንዲውል ከሚያደርግ በስተቀር ከተቀበለው የመያዣ ንብረት ሽያጭ ላይ ለባለእዳው ሰራተኞች በቅድሚያ እንዲከፈል ተደርጐ ሊተረጐም የሚገባው አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይሁንና በሕጉ ላይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በቅጥር ላይ ከተመሰረተ የስራ ግንኙነት የሚመነጭ ማንኛውንም የሰራተኛ የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የእዳ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚሰጠው የተደነገገ እንደመሆኑ መጠን የሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች አቋም ተራ ገንዘብ ጠያቂዎች/ordinary creditors/ ወይንም እንደ አመልካች በመያዣ ብድር የሰጠ ባለገንዘብ /secured creditors/ ሆኑም አልሆኑ፤ የሰራተኛው የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚሰጠው ስለተደነገገ ይህ ሁኔታ ግምት ውስጥ ሊገባ እንደማይችል መገንዘብ እያዳገትም፡፡ ሕግ አውጭው የባንክ የክፍያ ጥያቄ ከሰራተኛም የክፍያ ጥያቄ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ሐሳብ ቢኖረው በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 80 ላይ እንደተመለከተው ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የግብር ሰብሳቢው መብት ግብር የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሐብት ላይ ከማናቸውም ሌሎች እዳዎች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል በማለት እንደተደነገገው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅም ላይ ይህንኑ ያንጸባርቀው እንደበር ይታመናል፡፡

ሲጠቃለልም ለሰራተኞች የሚከፈል የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይንም የእዳ ጥያቄ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ የተደነገገው በመያዣ በተያዘም ንብረት ላይ ተፈፃሚነት እንዳለው መገንዘብ ስሚቻል አመልካች በመያዣ በተያዙ ንብረቶች ላይ የቅድሚያ መብት ስላለኝ በእነዚህ ንብረቶች ላይ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት ያቀረበውን አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉት መቅረታቸው በአግባቡ ስለሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33588 በ20/10/2000 እንደዚሁም በመ/ቁ. 33941 በ26/3/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 69727 በ3/2/2001 እና በመ/ቁ. 74069 በ16/4/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት አጽንተነዋል፡፡
2. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ በመ/ቁ. 42132 ላይ ተፈፃሚነት ስላለው የፍርዱ ግልባጭ ከመ/ቁጥር 42132 ጋር እንዲያያዝ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 41115

የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሜድሮክ ኮንስትራክሽን ኃላ.የተ.የግል ማህበር - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ሞገስ ሽፈራው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ክስ በአመልካች ድርጅት በሹፌርነት ተቀጥረው እየሠሩ ባለበት ሁኔታ ያላግባብ ከስራ መሰናበታቸውን ገልፀው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም የካሣ፣ የስራ ስንብት፣ የ65 ሣዓት ትርፍ ሣዓት፣ የ16 ቀን የእረፍት ቀን፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያ ተከፍሏቸው ከስራ እንዲሰናበቱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተጠሪ የድርጅቱን መኪና ባግባቡ የመጠበቅ ኃላፊነታቸውን ባለመጠበቅ ቁልፉን መኪና ላይ ትተው በመሄዳቸው ረዳታቸው መኪናውን አንቀሣቅሶ ግጭት በማድረስ ግምቱ ብር 5,867.24 /አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሣ ሰባት ብር ከሃያ አራት ሣንቲም/ የሆነ የንብረት ጉዳት ማስከተሉንና ጥፋቱም ሁለተኛ በመሆኑ ስንብቱ በደንቡና በሕግ አግባብ መከናወኑን ዘርዝሮ የተጠሪ ወደ ስራ ልመለስና የክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እንዲሁም የትርፍ ሰዓት ክፍያ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የስራ ስንብቱ ሕገወጥ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ የ4 /አራት/ ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ጥያቄ ደግሞ በማስረጃ አለመደገፉን ጠቅሶ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ//ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የተጠሪ ድርጊት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/ስር የሚሸፈን ሆኖ እያለ ከባድ ቸልተኝነት አይደለም ተብሎ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው መባሉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ጠበቃቸው ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ አመልካች ለተጠሪ የአራት ወር ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ ይመልሰው መባሉ ባግባቡ መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በሹፌርነት ተቀጥረው እየሠሩ ባለበት ወቅት በተረከቡት መኪና ላይ ቁልፍ ትተው በመውረዳቸው ረዳታቸው ቁልፉን በማንሣት መኪናውን ሲያንቀሣቅሱ ሌላ መኪና በመግጨት በብር 5,867.24 (አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከሃያ አራት ሣንቲም)የተገመተ የንብረት ጉዳት መድረሱንና በሌላ ወቅትም ተመሣሣይ ጥፋት ፈጽመው በድርጅቱ የዲሲፕሊን ቅጣት ደንብ የአምስት ቀን ደመወዝ ተጠሪ የተቀጡ መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም ተጠሪ የመኪናውን ቁልፍ በመኪናው ላይ ትተው መውረዳቸውን አረጋግጦ ይህ ጥፋት ተጠሪን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት ከባድ ቸልተኝነት ነው ለማለት የማያስችል ነው በሚል ደምድሟል፡፡ በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የተጠሪ አድራጎት በከባድ ቸልተኝነት ስር ሊወድቅ ይችላልን? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ሠራተኛ ለስራው የተሰጡትን መሣሪያዎችና እቃዎች ሁሉ በጥንቃቄ የመጠበቅ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 13/3/ ስር የተመለከተ ሲሆን በአሠሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 27/1/ሸ/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ሆኖም ከባድ ቸልተኝነት የሚለውን ቃል መለኪያ በተመለከተ ሕጉ በግልጽ አያሣይም፡፡ ይሁን እንጂ ቸልተኝነት የጥንቃቄ ጉድለት እንደመሆኑ መጠን የጥንቃቄ ዓይነትና ደረጃ እንደየ ድርጊቱና አድራጊው የስራ ድርሻ አኳያ በመመልከት ምላሽ ለማግኘት አያዳግትም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የጥፋት ደረጃ "ከባድ ቸልተኝነትን" ሊያቋቁም የሚችል መሆን አለመሆኑን ከስራቸው ባህርይ አንፃር መመልከቱ የግድ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ስራቸው ሹፌር ሲሆን ከስራቸው በተያያዘ ሁኔታ ጥንቃቄ ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ የመኪናውን ቁልፍ አያያዝ በተመለከተ ነው፡፡ የመኪናውን ቁልፍ በመኪናው ላይ በማናቸውም ጊዜና ቦታ ትተው ሊወርዱ እንደማይገባ የስራቸው ድርሻ የግድ የሚለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተያዘው ጉዳይ መኪናው ቁሞ የነበረበት ቦታ በአመልካች ድርጅት ግቢ ውስጥ ከመሆኑ እና ቁልፉን አንስተው መኪናውን በማንቀሣቀስ በሌላ መኪና ላይ ጉዳት እንዲደርስ በቀጥታ አስተዋጽኦ ያደገው የመኪናው ረዳት መሆኑ መረጋገጡ ከረዳቱ አስፈላጊነት አንፃር ሲታይ የተጠሪ የጥንቃቄ ጉድለት የከባድ ቸልተኝነት መለኪያ ሊያሟላ ይችላል ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ተጠሪ ቁልፉን በመኪናው ውስጥ ረዳቱ ባለበት ሁኔታ ትቶ መውረዱ ትክክለኛ አእምሮ ባለው ሰውና በተጠሪ የግል ሁኔታ መመዘኛ መሠረት ከባድ ቸልተኝነትን ሊያሣይ የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የተጠሪ ጥፋት ከባድ ቸልተኝነት አይደለም ማለቱ ስህተት ሁኖ አልተገኘም፡፡ የተጠሪ ጥፋት ሁለተኛ ጊዜ ነው ቢባልም ጥፋቱ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ተ/ መሠረት የተደረገ ስምምነት ስለመኖሩ አመልካች አላስረዳም፤ ስለሆነም የስራ ውሉ የተቋረጠበትን መንገድ የስር ፍ/ቤት ከሕግ ውጪ ነው ማለቱ የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ በዚህ ረገድ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ የምንቀበልበትን ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ይሁንና የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ከተባለ ውጤቱን በተመለከተ በአዋጁ ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመመልከት ምላሽ መስጠቱ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የግድ የሚለው ነው፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 43/2/ ድንጋጌ ሲታይም በዚህ ቁጥር በንዑስ ቁጥር አንድ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጅ ቁጥር 24፣25፣27፣28 እና 29 ከተደነገገው ውጪ የቅጥር ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ ወደስራው እንዲመለስ ወይም ካሣ ተከፍሎት የስራ ክርክር ሰሚ አካል ሊወስን እንደሚችል አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም ሕገወጥነቱ እነዚህን የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች በመጣስ የተፈፀመ ዓይነት መሆኑ ከተረጋገጠ ሠራተኛው ወደ ስራ የመመለስ ወይም ካሣ ተቀብሎ የመሰናበቱ ምርጫ ለሠራተኛው ሣይሆን ለፍ/ቤቱ የተተወ ስለመሆኑ የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/1/ እና /2/ ድንጋጌዎችን በአንድነት በማንበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በምን ላይ ተመስርቶ ተገቢውን ውሣኔ መወሰን እንደአለበት ደግሞ የአዋጁ አንቀጽ 43/3/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም ሠራተኛውና አሠሪው አብሮ እንዲቀጥሉ ማድረጉ ለምርታማነትና እንዱስትሪያዊ ሠላም አመቺ ከሆነ ብቻ ግንኙነት እንዲቀጥል ማድረግ የሚቻል ሆኖ የዚህ ተቃራኒ ሁኔታ የሚያጋጥም መሆኑ ከታመነ ግን ፍ/ቤቱ ሠራተኛው የስራ ስንብትና ሌላ ካሣ ተከፍሎት የስራ ውሉ እንዲቋረጥ ለመወሰን ሕጉ የሰጠው ሥልጣን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግን በአመልካችና በተጠሪ መካከል የስራ ግንኙነቱ እንዲቀጥል ማድረጉ ለምርታማነትና ኢንዱስትሪያዊ ሠላም መሰናክል ሊሆን የማይችል ነው ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ስለመሆኑ ተጠሪ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመሣሣይ ጥፋት ሁለት ጊዜ ማጥፋታቸው መረጋገጡ አመላካች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የስር ፍ/ቤትም በተጠሪ የተጠየቀውን ዳኝነት በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ጉዳዮችና በሕጉ ለፍ/ቤቱ ከተተወው ስልጣን አኳያ በመመልከት ተጠሪ ተገቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ መወሰን እየተገባው ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/3/ ስር የተመለከተውን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ካሣ ተከፍሏቸው ከስራ እንዲሰናበቱ ማዘዙ ሕጋዊ ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24603 ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61665 ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካች ለተጠሪ በሕጉ አግባብ ካሣ ከፍሏቸው ያሰናብቷቸው ብለናል፡፡

3. በዚህ ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4. ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 40938

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይዝ - ነ/ፊጅ ሰይፉ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሉ መንግስቱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ህዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም የፃፉት ማመልከቻ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከጥቅምት 22 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ በቅጥር ላይ በተመሰረተ ግንኙነት በጥበቃ ኃላፊነት የስራ መደብ ተመድበው እየሰሩ ባሉበት ሁኔታ ከህብረት ስምምነቱ ውጪ ከጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ድርጅት በፃፈው ደብዳቤ የስራ መደቡን ወደ ማይገለጽ በቅርብ ኃላፊ በሚሰጥ ትእዛዝ መሰረት ብቻ እንዲሰሩ ገልፆ ያዛወራቸው መሆኑን በመዘርዘር የስራ መደብ ዝውውሩ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ወደ ጥበቃ ኃላፊነት የስራ መደብ ተመልሰው እንዲሰሩ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአመልካች ድርጅት ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ አመልካች ድርጅትም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስ ተጠሪ የጥበቃ የኃላፊነት ስራ ባግባቡ ስላልተወጡና ጉዳዩ ተጣርቶ ለሕግ እስኪቀርብ ድረስ ከስራ ደረጃቸውና ከደመወዛቸው ሣይቀንስ ወደ አቻ ሌላ የስራ ቦታ ማዛወሩ ህጋዊ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የተጠሪ የስራ መደብ ዝውውር ከህጉ አግባብ ውጪ ነው በማለት ተጠሪ በፊት ይሰሩበት የነበረውን የጥበቃ ኃላፊ ይዘው እንዲሰሩ ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ተወካይ ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ከፃፉት 3/ሦስት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ የግራ ቀኙ የቃል ክርክርም መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበትና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች የተጠሪ የስራ ደረጃና ደመወዛቸውን ማይቀንስ የስራ መደቡን ዝውውር መፈፀሙ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪ በቀድሞ የስራ መደብ ተመድበው እንዲሰሩ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የተጠሪ የስራ ደረጃና ደመወዛቸው ሣይቀንስ አመልካች ተጠሪን ከጥበቃ ኃላፊነት የስራ መደብ በማንሣት እያሰራ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በጥበቃ ኃላፊነት ያገኙ የነበሩትን ደመወዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሁንም እያገኙ ያሉ መሆኑን ሣይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት የሚሰሩበት የስራ መደብ በመዋቅሩ የማይቃወቅ መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡

በመሰረቱ አሰሪ የሰራተኛውን ደረጃ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ሣይነካ ከአንዱ የስራ መደብ ወደ ሌላ ተመሳሳይ የስራ መደብ አዛውሮ ማሰራት ከተቋሙ አደረጃጀትና ከአሰሪነት መብቱ የሚመነጭ መብት ነው፡፡ የአሰሪ መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም የሰራተኛን መብት በማይነካ ሁኔታ ሰራተኛን ከአንድ የስራ መደብ ወደ ሌላ በተመሣሣይ የስራ መደብ አዛውሮ ማሰራት ህገ ወጥ የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስራ መደብ ዝውውር ስራና ሰራተኛን ለማገናኘት ወይም ስራው እንዳይበደል ታስቦና ተረጋግጦ ከተፈጸመ ህገ ወጥ ሊባል አይችልም፡፡ ይልቁንም የኢንዱስትሪ ሰላምን ይፈጥራል፣ ለሐገር ሁለንተናዊ እድገትና ልማት አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ የአሰሪን ድርጅት መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም የሰራተኛውን ጥቅም የጠበቀ ትእዛዝ የመፈጸምና የማክበር ግዴታ ይኖረዋል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13/2/ እና /7/ ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝበውም ይህንኑ ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ተጠሪን ያዛወረው ከድርጅቱ መዋቅርና አደረጃጀት ውጪ እንዲሁም የተጠሪን ጥቅም ባልጠበቀ ሁኔታ ስለመሆኑ ሣይረጋገጥ አመልካች ተጠሪን በፊት ይሰሩበት በነበረው በደረጃ 10 የጥበቃ ኃላፊ የስራ መደብ ይመልሰው በማለት መወሰናቸውን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 29948 ሚያዝያ 29 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 67189 ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የድርጅቱን መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም የሰራተኛውን መብት በጠበቀ ሁኔታ አንድን ሰራተኛ ከአንድ የስራ መደብ ወደ ሌላ ተመሣሣይ የስራ መደብ የማዛወር ሕጋዊ መብት ስላለው በተጠሪ ላይ የፈፀመው ተግባር ሕገ ወጥ አይደለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪን ወደ ደረጃ 10 የጥበቃ ኃላፊ የስራ መደብ አመልካች እንዲመልሰው የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42292

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢ/ያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን - ነ/ፊጅ ሠረቀብርሃን ተክሌ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ከበደ አቡነቴ - ጠበቃ አበበ አሣመረ- ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ያላግባብ ከስራ ስላገደኝ ያልተከፈለኝ ጠቅላላ ደመወዝ ብር 6569.96 ከፍሎኝ ወደ ስራ እንድመልስ ይወሰንልኝ በማለት በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግሥት በሀዲያ ዞን የሆሣዕና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስም የተጠሪ የስራ ውል የተቋረጠው በአዲት ምርመራ ጉድለት ተገኝቶባቸው መሆኑን፣የደመወዝ ይከፈለኝ ጥያቄም ላልተሠራ ስራ ሊቀርብ የማይገባ መሆኑን ተጠሪ በተከሰተባቸው የገንዘብ ጉድለት በፍ/ቤት በፍትሐብሔር ክስ የተመሠረተባቸው መሆኑንና በወንጀልም ምርመራው እየተካሄደ ስለመሆኑ ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ታግደው መቆየታቸው በግል እና በቤተሰባቸው ህይወት ጉዳት ማድረሱን እና የገንዘብ ጉድለት ቢኖር እንኳን በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ማስወሰን እንጂ ያለውሣኔ ማቆየት ያላግባብ መሆኑን በምክንያትነት በመያዝ የተጠሪን ክስ ተቀብሎ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ተጠሪ ያልተከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ካለ ተከፍሏቸው ወደ መደበኛ ስራ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፊጅ ታኅሣሥ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 3 /ሦስት/ ገጽ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ የመንግሥትን ገንዘብ ብር 182,845.43 /አንድ መቶ ሠማኒያ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አርባ አምስት ብር ከአርባ ሦስት ሣንቲም/ ሆነ ብለው ለግል ጥቅማቸው ለማዋልና ለመበልፀግ ሲሉ በስራ አጋጣሚ በእጃቸው ላይ የገባውን ገንዘብ ማጉደላቸው በድርጅቱ አዲተሮች ምርመራ ተረጋግጦ እያለ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራ እንዲመለሱ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(/1/ሐ/መ/) ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሠምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይህንኑ ከሕጉ ጋር አገናዝበን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ተጠሪ ያልተከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማጥቅም ተከፍሏቸው ወደ መደበኛ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከስራ ታግደው የቆዩት በስራቸው አጋጣሚ ከእጃቸው ከገባው የአመልካች ድርጅት ገንዘብ ውስጥ ብር 182,845.43 ማጉደላቸው በአመልካች ድርጅት ኦዲተሮች የኦዲት ምርመራ ውጤት ከተረጋገጠ በኋላ የድርጅቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴም ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ በማሣለፉ መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም የአመልካችን እርምጃ ሕገወጥ ነው ያለው ተጠሪን ከስራ ከአገደው በኋላ ለበርካታ ጊዜያት ውሣኔ ሣያስተላልፍ ቆይቷል፣ ጎደለ የተባለ ገንዘብ ካለም በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ማስወሰን አለበት በሚል ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር እና የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ማስተዋል የሚቻለው ተጠሪ የአመልካች ገንዘብ የጎደለባቸው መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በስራቸው አጋጣሚ እጃቸው የገባው ገንዘብ ስለመጉደሉ በአመልካች ኦዲተሮች መረጋገጡን ሣይክዱ ይኸው የምርመራ ውጤት የማስረጃነት ብቃት የለውም ተብሎ በፍትሐብሔር ክርክር ችሎት መወሰኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የፍትሐብሔር ክርክሩ የመጨረሻ ውሣኔ ያላገኘ በይግባኝ ደረጃ እየተከራከሩበት ያለ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ የአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚቀርቡ ክርክሮች ውጤታቸው ከፍትሐብሔር ክርክሮች የተለዩ በመሆናቸው የተጠሪ ክርክር ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የስር ፍ/ቤትም ተጠሪ ፈፀሙ የተባሉት ጥፋት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/ መሠረት ከስራ እንዲሰናበቱ ሊያስወሰን የሚችል መሆን ያለመሆኑን መመርመር ሲገባው አመልካች ገንዘቡ ጎድሏል የሚል ቢሆን እንኳ በፍ/ቤት ክስ መሥርቶ ማስወሰን ይገባው ነበር ማለቱ የስር ክርክሮችና የፍትሐብሔር ክርክሮች ውጤታቸው የተለያየ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አለማስገባቱን የሚያሣይ ነው በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ለፍርዱ መደምደሚያ የሰጠው ትንታኔ በበቂ የሕግ ምክንያት ያልተደገፈ ነው፡፡

በእኛ በኩል ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱበትን ምክንያት ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/ አኳያ መርመረናል፡፡ ተጠሪ ብር 182,845.43 ማጉደላቸው በድርጅቱ ኦዲተሮች የሂሣብ ምርመራ ውጤት ተረጋግጧል፡፡ ይህ የሂሣብ ምርመራ ውጤት ተቀባይነት የማያገኝበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡ ተጠሪ የአሠሪ ንብረት የሆነውን ብር 182,845.43 ማጉደላቸው ከተረጋገጠ ደግሞ ከስራቸው ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበቱ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሣያል፡፡ በመሆኑም የአመልካች እርምጃ ሕጋዊ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት አልተገኘም፡፡

በአጠቃለይ አመልካች በስር ፍ/ቤት ተጠሪ የተሰናበቱት የድርጅቱን ገንዘብ ስላጎደሉና ይህም በድርጅቱ ኦዲተሮች ኦዲት ምርመራ ተረጋግጦና በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተቀባይነት አግኝቶ ነው ሲል ያቀረበው ክርክር ታልፎ የገንዘብ ጉድለት ቢኖር እንኳን አመልካች በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ያስወስን እንጂ ማሠናበቱ በአግባቡ አይደለም በማለት ተጠሪን ወደመደበኛ ስራቸው ይመልስ፣ ያልተከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማጥቅም ካለም ይከፈላቸው ሲል መወሰኑ በበቂ የሕግ ምክንያት ያልተገደፈና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/መ/ ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ በሆሣዕና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02087 ጥቅምት 19 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.04777 ታኅሣሥ 15 ቀን 2001 በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 41623

መጋቢት 8 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር - ነ/ፈጅ ቀርቧል

ተጠሪ፡- አቶ ሣሙኤል ኪዳኔ - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት በመካኒክነት ተቀጥሬ እየሰራሁ ሳለ ሳላውቅ የዝውውር ኮሚቴ ሳይሰማ ጥገና ክፍል ለማጠናከር በሚል ሰበብ ወደ ሎግያ ቅርንጫፍ አዛውሮኛል እንድታከም ጠይቄ ከሥራ አግዶኛል እርምጃው ያለ አግባብ ስለሆነ ዝውውሩም እገዳውም አግባብ አይደለም ይባልልኝ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎኝ ወደሥራዬ እንዲመልሰኝ ሲል ጠይቋል፡፡

አመልካችም መልስ እንዲሰጥ ታዞ ሲመልስ አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው የሕብረት ሥምምነቱ ከመውጣቱ በፊት ስለሆነ አዛውሮ ማሰራት ይችላል፣ በወቅቱም ዝውውሩን አልተቃወሙም፣ በሥራቸው ቦታ ላይም አልተገኙም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ከቀረቡት ማስረጃ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል በውሣኔውም አመልካች ተጠሪን እንዳዛወረው የታመነ ሲሆን ሰራተኛውን የማዛወር ሥልጣን አለኝ ያዛወርኩት የሕብረት ስምምነቱ ከመውጣቱ በፊት ነው የሕብረት ሥምምነቱን መከተል አያስፈልገኝም ሲል ተከራክሯል አመልካች ሠራተኛን (ተጠሪን) የማዛወር መብቱ ከሕብረት ሥምምነት የመነጨ አለመሆኑ ግልፅ ነው በግራ ቀኙ ያለው የሥራ ውል የማዛወር ስልጣን የሰጠው መሆኑን አመልካች በማስረጃ አላስረዳም ተጠሪ ዝውውሩ ሲገለፅላቸው ጊዜ ይሠጠኝ አሉ ማለት ዝውውሩን ሕጋዊ ያደርገዋል ማለት ባለመሆኑ ዝውውሩ ሕገወጥ ነው ፅግዱም ያለአግባብ ስለሆነ የዝውውር ውሣኔው ተሰርዞ ተጠሪ በቀድሞ የሥራ ቦታቸው ይመለሱ ፅግዱ የተላለፈበት ቀን አንስቶ ፍርድ እስከተሰጠበት ያለው ደሞዝ ተከፍሎት ስራቸውን ያስቀጥል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህንኑ ውሣኔ ባለመስማማት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኙን ቢያቀርብም ከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን በማስቀረብ ከአከራከረ በኋላ ግድፈት የለውም ሲል የሥር ውሣኔን በፍ/ብ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት አፅንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች በ24/3/2001 ፅፈው ባቀረቡት ማመልከቻ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው ሲል አቤቱታውን አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል ጉዳዩ ለሠበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ የማህበር አባል ስለሆነ ዝውውሩ ተገቢ አይደለም በማለት መወሰኑ ሰራተኛን አዛውሮ የማሰራት መብቱ ነው፣ ይህን ማድረግ ያልፈለገን ሰራተኛ ማሰናበት ሕግ ይፈቅዳል የሚለውን ቅሬታ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ የግራ ቀኙ ወገኖች ባሰሙት ክርክር አቤቱታ ካቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በእኛ በኩል ባጠቃላይ የጉዳዩን አመጣጥ ስናይ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በመካኒክነት ሙያ እያገለገሉ ቆይተው የጥገና ክፍልን ለመጠናከር ሲባል ወደ ሎጊያ ቅርንጫፍ እንዲዛወሩ ተደርገው በቦታው ባለመገኘታቸው ከሥራቸው በመታገዳቸው ምክንያት ዝውውሩ አግባብ አይደለም ደሞዝ ተከፍሎኝ ወደ ሥራዬ ልመለስ ብለው ጠይቀዋል፡፡ ከመዝገቡና ካቀረበው ክርክር መረዳት እንደተቻለው የሥር ፍ/ቤት አመልካች ሰራተኛውን (ተጠሪን) ለማዛወር ያበቃውን ምክንያት ከሕብረት ሥምምነት ወይም ከውል መሆኑን አላስረዳህም በማለትና የቀረቡትን የተጠሪን ማስረጃ ለማስተባበል አልቻልክም በማለት ዝውውሩና እግዱ ሕገወጥ ነው ሰራተኛው ወደ ሥራው ይመለስ የተቋረጠበት ደሞዝ ይከፈለው ሲል ወስኗል፡፡

ቀድሞውንም ቢሆን ተጠሪ ከሥራዬ ታግጃለሁ ወደ ሥራዬ ልመለስ ብሎ እስከጠየቀ ድረስ የሥር ፍ/ቤት ጭብጥ የዞ ሊያከራክር የሚገባው ስንብቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚል መሆን ነበረበት፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቱ ዝውውሩ ሕገወጥ ነው ሲል የሰጠውን ሐሳብ ስናይ አመልካች ተጠሪን የሕብረት ሥምምነት ወይም ከውል ባልመነጨ ምክንያት ስላዛወረው ዝውውሩ ሕገ ወጥ ነው ያለው አባባል አግማኝ አይሆንም ምክንያቱም የአሠሪና የሠራተኛ ሕጉ በሁለቱም ወገን መብትና ግዴታን በማስቀመጥ የሚያገለግል ሕግ ነውና፡፡

ባጠቃላይ ሲታይ የግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር እንዳስተዋልነው ተጠሪ ዝውውሩን በወቅቱ ሣይቃወሙ ከሥራቸው ቦታ ከ5 ቀናት በላይ እንዳልተገኙ በቃል ክርክር ጊዜ ፍ/ቤቱ ተረድቷል፡፡ ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ ከሥራው ከ5 ቀናት በላይ የቀረ ሠራተኛ ደግሞ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) መሠረት ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉ ይቋረጣል፡፡ በዚህም ጉዳይ ተጠሪ በቃል ክርክሩ አልቀረሁም ሲል አልተከራከረም፡፡ በመሆኑም ዝውውሩን በወቅቱ ሣይቃወም ከሥራው ገበታ ላይ መቅረቱ ስለተረጋገጠ ተጠሪውን ወደ ሥራው የሚመለስበት ምንም ምክንያት ሣይኖር የሥር ፍ/ቤት የተጠሪ ዝውውር ሕገ ወጥ ነው የተቋረጠው ደሞዝ ይከፈለው በማለት የሰጡት ውሣኔ የፌ.ከ.ፍ/ቤትም ጉዳዩን አይቶ ማረም ሲገባው ማፅናቱ መሠታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ.የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመቁ 32594 ቀን 9/11/2000 እና የፌ.ከፍተኛ ፍ/ቤት በመቁ 69715 በቀን 12-3-2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በሥራው ቦታ ላይ ከ5 ቀናት በላይ ስላልተገኘ መሰናበት አለበት ብለናል የሚከፈለውም የደሞዝ ክፍያ አይገባውም፡፡
3. የግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41411

ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- መ/ልመ/ል ዳቦ መጋገሪያ ድርጅት - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ በለጠ ተገኝ - ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በክሣቸው አመልካች ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ስላገዳቸው በመሆኑ ከታገዱበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ይህ ካልሆነ ግን የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በተለያየ ጊዜ ሠራተኛ በመደብደብ እና ዛቻ በመፈፀማቸው ሁኔታውን ለማጣራት ከሥራ አገዳቸው እንጂ ከሥራ ስላላሠናበታቸው ከሣሽ የጠየቁት ዳኝነት አግባብ አለመሆኑን ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን ያየው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሥራ ታገዱ እንጂ ከሥራ ስላልተሠናበቱ ያለአግባብ ከሥራ የተሠናበተ ሠራተኛ የሚጠይቀውን የመብት ጥያቄ መጠየቃቸው አግባብ አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን አንድ ሠራተኛ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/4/ መሠረት የሚታገደው ለ30 ቀናት ብቻ ስለሆነ ከዚያ በላይ ማገድ ከሥራ ማሠናበት ተደርጎ ይቆጠራል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አቤቱታው በአጭሩ ተጠሪ ያላግባብ ከሥራ ተሠናብቻለሁ የሚል ክስ አላቀረቡም የእገዳው ጊዜ በማብቃቱ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የማስታወቂያ ጥሪ ተደርጎ ስላልቀረቡ አመልካች ለክሱ መልስ ከሰጠ በኋላ ከሥራ አሰናብቷቸዋል፡፡ ከ30 ቀናት በላይ ማገድ እንደ ስንብት ይቆጠራል የሚል ሕግ የለም የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ የቃል ክርክር አሠምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ሊወሰኑ የሚገባቸው ጭብጦች፡-

1. ከ30 ቀናት በላይ ማገድ ከሥራ እንደመሠናበት ይቆጠራል ወይ?
2. በክርክሩ ሂደት ተጠሪ ከሥራ መሠናበታቸው በክርክሩ ሂደት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚሉት ናቸው፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪ በመጀመሪያ ክስ የመሠረቱት ያለአግባብ ከሥራ ታግጃለሁ በማለት ወደ ስራ ለመመለስ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው በመጠየቅ ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ተጠሪን ከሥራ አገድኩ እንጂ ስላላሰናበትኩ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ክስ ሲመሠርቱ ከሥራ ታግደው እንጂ ከሥራ ተሠናብተው አልነበረም፡፡ ነገር ግን በክርክር ላይ እያሉ አመልካች ተጠሪን ከሥራ ማሠናበቱን ከመዝገቡ ሂደት የተረዳን ሲሆን አመልካችም ይህንን አልካደም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ አዲስ ክስተትም ክስ የቀረበበትን ከሥራ የመታገድ ጉዳይ የክስ ምክንያት የሚያሳጣውና የክርክሩን ጭብጥ እንዲለወጥ የሚያደርገው ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 251/1/ ሥር እንደተደነገገው ፍ/ቤቱ ነገሩን በፍርድ ከመወሰኑ በፊት በተከራካሪዎቹ ወገኖች የተያዘው ጭብጥ እንዲሻሻል ወይም ተጨማሪ ጭብጥ እንዲያዝ አስፈላጊና ተገቢ መሆኑን የገመተ እንደሆነና ይህን ማድረግ ለጉዳዩ መልካም አፈፃፀም ቀና መንገድ የሚያስገኝ መሆኑን ሲረዳው ፍ/ቤቱ ጭብጡ እንዲሻሻል ወይም ተጨማሪ ጭብጦች እንዲያዙ ለማድረግ ይችላል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ የተጠሪ ከሥራ መታገድ ጉዳይ በተጠሪ ከሥራ መሠናበት ምክንያት የክሱ ምክንያት ተቋርጧል፡፡ የክስ ምክንያት በሌለው ጉዳይ ላይ ደግሞ ፍ/ቤቱ ሊሠጥ የሚችለው ውሣኔ የለም፡፡ ይልቁንም ከክሱ በኋላ ተጠሪ ከሥራ በመሰናበታቸው ተጠሪ ክሣቸውን እንዲያሻሽሉ በማድረግ ወይም ደግሞ ለጉዳዩ መልካም አፈፃፀም ቀና መንገድ ለማስገኘት ሲል ጭብጡን በመለወጥ የተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በአግባቡ መሆን አመሆኑን አከራክሮ ተገቢውን ውሣኔ ሲሠጥ ተጠሪ ያለአግባብ ተሠናብቻለሁ የሚሉ ከሆነ በሌላ ክስ ይጠይቁ በማለት መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙ ሲቀርብለት መጀመሪያ ክስ የቀረበበት ጉዳይ የክስ ምክንያቱ በተጠሪ ከሥራ መሠናበት የተቋረጠ በመሆኑ ጭብጡን አስተካክሎ መወሰን ሲገባው በአመልካች የተወሰደውን የሥራ ማገድ እርምጃ መሠረት አድርጎ ውሣኔ መስጠቱ የሥር ፍ/ቤት የፈጸመውን ስህተት መድገሙን ያሣያል፡፡

በእርግጥ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ያለአግባብ ከሥራ ተሠናብተዋል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰውም ተጠሪ ከ30 ቀናት ከሥራ መታገዳቸው እንደስንብት ይቆጠራል በማለት ነው፡፡ ነገር ግን አ/ቁ 377/96 አንቀጽ 27/4/ አንድ ሠራተኛ ሊታገድ የሚችልበትን ከፍተኛውን የጊዜ ገደብ ከማስቀመጥ በቀር ከ30 ቀናት በላይ መታገድ ከሥራ እንደማሰናበት ይቆጠራል የሚል እንድምታ የለውም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ተጠሪ ከ30 ቀን በላይ ከሥራ ስለታገዱ ከሥራ እንደተሰናበቱ ይቆጠራል በማለት ለድንጋጌው የሰጠው ትርጉም ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ከ30 ቀን በላይ መታገዳቸው መሠናበታቸውን ያሣያል በማለት ያለአግባብ ከሥራ ለማሠናበት ሠራተኛ የሚገባውን ክፍያዎች እንዲያገኙ መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ ይልቁኑ ተጠሪ በክርክሩ ሂደት ከሥራ መሰናበታቸው ስለታወቀ ይህ የሥራ ስንብት ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን ጭብጥ ይዞ ግራ ቀኙን በማከራከርና አስፈላጊም ከሆነ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ተገቢውን ውሣኔ ሊሰጥ ይገባው ነበር፡፡

በሌላ በኩል ግን ከክሱ በኋላ ተጠሪ ከሥራ መሠናበታቸውን አመልካችም ስላልካደ የክሱ ምክንያት የተቋረጠውን ከሥራ የመታገዱ ጉዳይ የተወሰደው ይህ የሥራ ስንብት እርምጃ ሕጋዊ ነው አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ውሣኔ ሊሠጥ ይገባ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ክስ የመሠረቱበት ሥራ የመታገድ ጉዳይ ተጠሪ በመሰናበታቸው የክስ ምክንያቱ በመቋረጡ ክሱ እንዲሻሻል እና ጭብጡ እንዲስተካከል በማድረግ ውሣኔ ሊሰጡ ሲገባ የክስ ምክንያቱ በተቋረጠ ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠታቸው ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ ውጪ ግን በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/4/ መሠረት አንድ ሠራተኛ ከሥራ ለማሠናበት የሚያበቃ ጥፋት ከፈፀመ ከሥራ ከማሠናበቱ በፊት አሠሪው ሠራተኛውን እስከ 30 ቀናት ሊያግድ ይችላል፡፡ ከ30 ቀናት በላይ የሚደረግ ከሥራ የማገድ እርምጃ አዋጁን የሚቃረንና ሕጋዊ ያልሆነ ተግባር በመሆኑ አመልካች ተጠሪን ከ30 ቀናት በላይ አግዶ ማቆየቱ ሕገወጥ ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከታገዱበት ከ31ኛው ቀን ጀምሮ አመልካች ተጠሪን ከሥራ እስካሠናበቱበት ጊዜ ድረስ ለተጠሪ ደመወዛቸውን ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ አግኝተንዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37427 ግንቦት 25/2000 የሰጠው ውሣኔ እና በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 68297 በጥቅምት 12 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በአግባቡ ነው አይደለም? የሚለውን ጭብጥ የግራ ቀኙን ክርክርና ሌላ የሚያቀረቡት ማስረጃም ካለ ማስጃቸውን ከመረመረ በኋላ ተገቢ ነው የሚለውን ውሣኔ ይስጥ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች ተጠሪን ከ30 ቀናት በላይ ከሥራ ማገዱ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/4/ የተፈቀደ ባለመሆኑ ተጠሪን ከሥራ ካገደበት ከ31ኛው ቀን ጀምሮ ተጠሪን ከሥራ እስካሠናበተበት ያለውን ደመወዛቸውን ይክፈላቸው ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43370

ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት - ነ/ፈጅ ዳንኤል ያሬድ

ተጠሪ፡- አቶ ጌታቸው ገድሌ - ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው በሥራ ላይ ጉዳት ለደረሰበት ሠራተኛ የሚከፈልን የጉዳት ካሣ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

ጉዳዩ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በመሠረቱት ክስ በሥራ ላይ በደረሰባቸው አደጋ የጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሠጠው መልስ ደመወዛቸው ሣይቋረጥ አሣክሞ መዳናቸው ሲረጋገጥ ወደ ሥራ መልሷቸው እየሠሩ በመሆኑ በተጨማሪ ካሣ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ከጉዳቱ አገግሞ ሥራ መጀመሩ በራሱ የጉዳት ካሣን የሚያስከለክለው ባለመሆኑ አመልካች ለተጠሪ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 109/3/ መሠረት የጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ መ/ሰጪን መጥራት ሣያስፈልገው ይግባኙን ሠርዞታል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታው ተጠሪ በደረሰባቸው አደጋ ታክመው ወደ ሥራቸው የተመለሱና የመስራት ችሎታቸው የቀነሰ ወይም ችሎታቸውን ያጡ ወይም ገቢያቸው ያልቀነሰ በመሆኑ፣ የተጠሪ ሁኔታ የተሻሻለ ወይም የተባባሠ ለመሆኑ በድጋሚ እንዲታከሙ ጠይቀን ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል በድጋሚ ለማከም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ የሕክምና ምርመራው እንዲካሄድ ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው ይህንን አለማድረጉ አመልካች የመንግሥት ልማት ድርጅት በመሆኑና ለደረሰው ጉዳት በገባው የመድን ሽፋን ባለመኖሩ ጉዳት ካሣው ሊከፈል የሚገባው በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት ሆኖ ሣለ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 109/3/ መሠረት እንዲከፈል መወሰኑ እንዲሁም ጉዳት ካሣው መጠን ሊሠላ የሚገባው ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜ ተጠሪ በሚያገኙት ገንዘብ እንጂ ከረጅም ዓመት በኋላ በእድገት ባገኙት የደመወዝ መጠን በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊሻር ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎትም ተጠሪ ከደረሰባቸው ጉዳት ታክመው ተሻሏቸው ወደ ሥራ የተመለሱና የቀድሞ ስራቸውን እያከናወኑ በመሆኑ በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 103/3/4/ መሠረት የተጠሪ ሁኔታ መሻሻሉ ወይም መባባሱ በሕክምና ሣይረጋገጥ ጉዳት ካሣ አመልካች ሊከፍል አይገባም የሚለውንና የአመልካች ቅሬታና ሌሎች ነጥቦችን ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ ለማድረግ ተጠሪም ቀርበው ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በቃል አሠምተዋል፡፡ ችሎቱም የሠበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪ በስራቸው ላይ እያሉ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ በግራ ቀኙ አልተካደም፡፡ ተጠሪም ለዚህ አደጋ የጉዳት ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል ሲሉ አመልካች ሊከፈላቸው አይገባም ይከፈል ቢባል እንኳን ሊከፈላቸው የሚገባው በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 109/3/ መሠረት ሣይሆን በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት ሲሆን መጠኑም ሊሠላ የሚገባው ጉዳቱ በደረሰ ጊዜ ያገኙ በነበረው ደመወዝ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም በዚህ ችሎት መልስ ማግኘት የሚያስፈልጋቸው ጭብጦች

1. አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ካሣ ሊከፍል ይገደዳል ወይ?
2. ይገደዳል የሚባል ከሆነ በየትኛው ሕግ መሠረት ነው ጉዳት ካሣው ሊከፈል የሚገባው?
3. መጠኑስ የሚሠላው እንዴት ነው? የሚሉት ሆነው አግኝተነዋል።

1ኛውን ጭብጥ በተመለከተ በተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑ አመልካችም አልተከራከረም ክክርክሩ ሂደትም በተጠሪ ላይ የደረሰው የጉዳት መጠን 20% ቋሚ የአካል ጉዳት መሆኑ በሃኪሞች ቦርድ መረጋገጡን ተረድተናል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 107 መሠረት ማንኛውም በሥራ ላይ የሚመጣ ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ እንደ ጉዳቱ አይነትና መጠን ክፍያ እንደሚደረግለት ይደነግጋል። በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ካሣ ሊከፍል አይገባም በማለት የሚከራከረው የአካል ጉዳት ማለት የመስራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን የሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 99/1/ ሥር የተመለከተ በመሆኑና ተጠሪ ግን አደጋ የደረሰባቸው ቢሆንም ታክመው ስለተሻላቸው የቀድሞ ስራቸውን ያለምንም ችግር እየሠሩ በመሆኑ የመስራት ችሎታቸው ሣይቀንስ ወይም ችሎታቸውን ሳያጡ ወይም ገቢያቸው ሣይቀነስ ካሣ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ነው። በእርግጥ በአዋጁ አንቀጽ 99/1/ ሥር "የአካል ጉዳት" ማለት የሠራተኛውን የመስራት ችሎታ መቀነስ የሚያስከትል ወይም ጭራሹንም ችሎታውን የሚያሣጣ ጉዳት ነው ተብሎ ተተርጉሟል።

እዚህ ላይም መነሣት ያለበት ጉዳይ "የመስራት ችሎታ" በማለት በድንጋጌው የተመለከተው ሠራተኛው ጉዳት በደረሰበት ጊዜ ይሠራ የነበረውን ሥራ ለመሥራት የሚያስችለውን ችሎታ ብቻ ነው ወይስ ሠራተኛው ከአደጋው በኋላም ቢሆን ሊሠራ የሚችለውን ማንኛውንም ሥራ የመስራት ችሎታ ነው? የሚለው ነጥብ ነው። ይህን ነጥብ ግልጽ ለማድረግ የአዋጁ አንቀጽ 99/1/ የእንግሊዝኛውን ትርጉም ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል።

"Disablement" means any employment injury as a consequence of which there is a decrease or loss of capacity to work /ስርዝ የተጨመረ/

ከዚህ የእንግሊዝኛ ትርጉም በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው የአካል ጉዳት ሠራተኛው ይሠራ የነበረውን ሥራ ለመሥራት የሚያስችለውን የተወሰነ ችሎታውን ብቻ የሚመለከት ሣይሆን በአጠቃላይ ወደፊትም ሠራተኛው በሌሎች የሥራ መስኮች ተሠማርቶ ሌሎች ሥራዎችንም ለመስራት የሚያስችለውን ችሎታ /capacity to work/ የሚመለከት ነው አንድ ሠራተኛ እስከመጨረሻው በመጀመሪያ የተቀጠረበትን ሥራ በመስራት ሣይገደብ ወደፊትም የተለያዩ ሥራዎችን ለመስራት የሚችል መሆኑ ይገመታል። ሕጉም የአካል ጉዳትን ለማያያዝ የፈለገው ሠራተኛው አደጋ በደረሰበት ጊዜ ይሠራ የነበረውን ሥራ ለመስራት የሚያስችለው ውሱን ችሎታ ጋር ብቻ ሣይሆን ይልቁንም የሠራተኛው ወደፊት በተለያየ የሥራ መስክ ተሠማርቶ ለመስራት ከሚያስችለው አጠቃላይ የመስራት ችሎት ጋር ነው። በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በአደጋው ምክንያት 20% ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ለመሆኑ በሀኪሞች ቦርድ ተረጋግጧል። ይህንንም አመልካች አልካደም ይህ የደረሰባቸው ጉዳት ደግሞ ምንም እንኳን አሁን የሚሠሩትን ሥራ በአግባቡ መስራት ቢያስችላቸውም ጉዳቱ ወደፊት የተለያዩ ሥራዎችን ለመስራት ከሚያስችላቸው ችሎታ አኳያ ሊመዘን ይገባል። በመሆኑም አመልካች ተጠሪው አደጋ በደረሰባቸው ጊዜ ሲሰሩ የነበረውን ሥራ ያለችግር በመስራታቸው ብቻ ችሎታቸው አልቀነሰምና ካሣ ሊከፍል አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም።

ሌላው አመልካች የሚከራከርበት ነጥብ የሠራተኛው ሁኔታ የተባባሰ ወይም የተሻሻለ ወይም ትክክል ያልሆነ ምርመራ ተደርጎለት ከሆነ ሠራተኛው በድጋሚ እንዲመረመር ሊደረግ ስለሚችል በዚሁ መሠረት በድጋሚ ተመርምረው ውጤቱ ሣይታወቅ ካሣ ልከፍል አይገባም የሚል ነው። በእርግጥ አመልካች እንዳለው የሠራተኛው ሁኔታ ተሻሽሏል ወይም ተባብሷል የሚባል ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 102/3/ መሠረት ሲጠየቅ ድጋሚ ሕክምና ሊደረግ እንደሚችል አዋጁ ይፈቅዳል። በተያዘው ጉዳይ አመልካች የተጠሪ ሁኔታ ተሻሽሏል የሚል ከሆነ ይህንን የማስረዳት ሸክም አለበት። ይህንን የማስረዳት ሸክም ግን በቂ ማስረጃ በማቅረብ አልተወጣም። ድጋሚ ምርመራ እንዲደረግ የዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታልን ጠይቆ ሆስፒታሉ ፈቃደኛ አለመሆኑን ከመግለጽ በቀር ሌላ ያቀረበው ማስረጃ የለም። ወይም ተጠሪን በድጋሚ እንዲመረመሩ ጠይቆ ተጠሪው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምርመራው ያልተደረገ መሆኑን አልገለፀም። በመሆኑም ቀደም ሲል ተጠሪ ተመርምረው 20% ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን በሐኪሞች ቦርድ የተረጋገጠው ሁኔታ ስለመሻሻሉ ያቀረበው ማስረጃ ሣይኖር ተጠሪ የቀድሞ ሥራቸውን መስራት በመቀጠላቸው ብቻ የጉዳት ካሣ ልከፍል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ስለሌለው የሥር ፍ/ቤቶች የጉዳት ካሣ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም፡፡

2ኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች የመንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 109/1/ ሥርም በሕ/ስምምነቱ በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በቀር በአዋጁ ለሚሸፈኑ የመንግሥት ድርጅቶች ሠራተኞች የሚሠጠው የጉዳት ካሣ አሠሪው በገባበት የመድኅን ዋስትና ወይም በመንግሥት የጡረታ ሕግ መሠረት ካሣው እንደሚከፈል ያመለክታል፡፡ ድርጅቱ መድን ያልገባ ከሆነ በመንግሥት የጡረታ ሕግ ለሚሸፈኑ ሠራተኞች የመንግሥት የጡረታ ሕግ ተፈፃሚ እንደሚሆን ንዑስ ቁጥር 2 አስቀምጧል፡፡

የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 ጉዳት ለደረሰበት ሠራተኛ የሚከፈለው ካሣ መጠን የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ይከፈለው በነበረው መደበኛ የወር ደመወዙ 45% በአምስት ዓመት ተባዝቶ የሚኘው ሂሣብ በመንግሥት ሠራተኛው ላይ በደረሰው ጉዳት መቶኛ ተባዝቶ እንደሆነ አንቀጽ 33 ያመለክታል፡፡

ተጠሪ አመልካች የደረሰውን የጉዳት ዓይነት አመልካች የመድን ዋስትና ገብተው በማለት ያቀረቡት ክርክር ስለሌለ ጉዳቱ መድን ያልተገባለት መሆኑን አምነው እንደተቀበሉት ያስቆጥራቸዋል፡፡ አመልካችም የመንግሥት የልማት ድርጅት በመሆኑና ለጉዳቱ መድን ሽፋን ያልገባ በመሆኑ ተፈፃሚነት የሚኖረው የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ላይ የተመለከተው የካሣ መጠን ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 109/3/ መሠረት ካሣው እንዲከፈል የተሠጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጨረሻውን ጭብጥ በተመለከተ ከፍ ሲል በተገለፀው የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 33 የካሣው መጠን የሚሠላው ሠራተኛው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ይከፈለው በነበረው መደበኛ የወር ደሞዙ መሠረት ነው፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ለተጠሪ የሚከፈለው የካሣ መጠን ሊሠላ የሚገባው በተጠሪ ላይ ጉዳቱ ከደረሰበት ከሠኔ 20/1999 ዓ.ም. በፊት በነበረው ወር ይከፈላቸው በነበረው መደበኛ የወር ደመወዝ መሠረት እንጂ ከጉዳቱ በኋላ በእድገት ባገኙት ደመወዝ መሠረት ሊሆን አይገባም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 36135 በ01/05/2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 75693 በ28/05/2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
3. የጉዳት ካሣውም ሊሠላ የሚገባው በአ/ቁ. 345/95 አንቀጽ 33 መሠረት ተጠሪ ከሠኔ 20/1999 ዓ.ም. በፊት በነበረው ወር ይከፈላቸው በነበረው የወር ደመወዝ መሠረት ነው ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 42752

ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሀይ ታደሠ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- እነ ወ/ት ማሜ አሠፋ (36 ሠዎች) - ወኪል ትዕግስት ድንቁና

ተሾመ ሃይሌ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ብሔራዊ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል (NTO) - ጠ/ብርሃኑ ከፍያለው

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው የሠራተኞችን ቅነሣ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ድርጅት ከስሯል በሚል አዲስ መዋቅር አስጠንቶ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 29(3) ሥር ከተመለከተው ውጪ ቅነሣ በማድረግ የሠጠው ማስጠንቀቂያ ህጋዊ ባለመሆኑ ይታገድልን ብለዋል፡፡

ተጠሪ ድርጅት ለቀረበበት ክስ በሠጠው መልስ በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 28(1) መሠረት ምርታማነትን ለማሣደግ እና የአሠራር ዘዬዎችን ለመለወጥ በተዘጋጀው መዋቅር መሠረት መመዘኛውን ባለሟሟላታቸው ቅነሣውን እንዳካሄደ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ምርታማነትን ለማሣደግና የአሠራር ዘዬን ለመለወጥ አዲስ መዋቅር ማዘጋጀት መብት ያለው ቢሆንም ከጠቅላላ ሠራተኛ ውስጥ የሚቀነሠው ሠራተኛ 10% እና ከዚያ በላይ ሲሆን በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 29(2) የተከተለ ቅነሣ ማድረግ አለበት፡፡ ተጠሪ ግን ሥርዓቱን ያልተከተለ በመሆኑ በአንቀፅ 29(3) ከሀ-ረ ድረስ ባለው ቅደም ተከተል መሠረት ቅነሣውን አከናውኖ እስከሚያቀርብ ጊዜ ድረስ ለአመልካቾች የአንድ ወር ደመወዝ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ይግባኙን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ቅነሣው በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 28(2)(ሐ) መሠረት በተጠናው አዲስ መዋቅር አንድ በአንቀፅ 28(3) ስር እንደተመለከተው የሥራ መደቡ በመሠረዙ አይደለም፡፡ በመሆኑም በአንቀጽ 29(3) ሥር የተመለከተውን መከተል አያስፈልግም በማለት የቦርዱን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ቅነሣው በአንቀፅ 28(2)(ሐ) መሠረት ስለተደረገ በአዋጁ አንቀፅ 29(3) ሥር የተመለከተውን ቅደም ተከተል መከተል አያስፈልግም በማለት የተሠጠውን የህግ ትርጉም አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ቀርቦ ክርክሩን በቃል አሠምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍ ሲል እንደተመለከተው በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ነጥብ በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 28(2)(ሐ) መሠረት ቅነሣ ሲደረግ በአንቀፅ 29(3) ሥር የተዘረዘሩትን ቅደም ተከተል መከተል ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም? የሚለው ነው፡፡

በሥር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወኣኝ ቦርድም ሆነ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ቅነሣውን ያደረገው ምርታማነትን ለማሣደግና የአሠራር ዘዴን ለመለወጥ አዲስ መዋቅር በማዘጋጀቱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ቅነሣው በአዋጁ አንቀፅ 28(2)(ሐ) መሠረት መደረጉን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪም አጥብቆ የሚከራከረው አንቀፅ 29(3) ተፈፃሚ የሚሆነው በአንቀፅ 28(1) እና 28(3) መሠረት በሚደረግ ቅነሣ እንጂ በአንቀፅ 28(2)(ሐ) የሚመለከት አይደለም የሚል ነው፡፡ በመሆኑም አንቀጽ 29(3) ተፈፃሚነቱ ለማነው የሚለውን ነጥብ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡

በአዋጁ አንቀፅ 29 ርዕስ እንደምንረዳው ድንጋጌው የሚመለከተው የሠራተኞችን ቅነሣ ጉዳይ ነው፡፡ የዚሁ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር አንድም የሠራተኞች ቅነሣ ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜውን አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት የሠራተኞች ቅነሣ ማለት በአንቀፅ 28(2) በተጠቀሱት ምክንያቶች ቁጥራቸው ከድርጅቱ ሠራተኞች ቢያንስ 10% የሚያህለውን ወይም የሠራተኞች ቁጥር ከ20 እስከ 50 በሆነው ድርጅት 5 ሠራተኞችን የሚመለከት ከ10 ተከታታይ ቀናት ያላነሠ ጊዜ የሚቆይ ቅነሣ ነው፡፡ በመሆኑም በአንቀፅ 28(2) ሥር በተመለከቱት ሠራተኞቹ የተሠማሩበት ስራ በከፊል ወይም በሙሉ ለዘለቄታው በመዘጋቱ ወይም የድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ በመቀዝቀዝ ወይም ደግሞ ምርታማነትን ለማሣደግና አዲስ የአሠራር ለውጥ ለመጠቀም ሲባል በርካታ ሠራተኞች መቀነስ ሲኖርባቸው ቅነሣው በምን ዓይነት ሥርዓት ሊከናወን እንደሚገባ አንቀፅ 29(3) ያመለክታል፡፡ በእርግጥ የዚህ ድንጋጌ መግቢያ በአንቀፅ 28(1) መሠረት የሠራተኞች ቅነሣ ሲደረግ ቅነሣው ከሥር የተቀመጡትን ቅደም ተከተል መከተል አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን የድንጋጌው መግቢያ "አንቀፅ 28(1)" በማለት የተገለፀው በአግባቡ ግድፈት እንጂ ሊጠቀስ የሚገባው "አንቀፅ 28(2)" መሆኑን ችሎቱ ያምናል፡፡ ለዚህም የሚከተሉት ምክንያቶች ማስቀመጥ ይችላል፡፡ በአንቀፅ 29(3) ሥር የተመለከተው ስርዓት ተፈፃሚ የሚሆነው በአንቀፅ 28(1) በተመለከተው መሠረት ለሚሠናበት ሠራተኛ ነው ማለቱ ትርጉም አይሠጥም፡፡ ምክንያቱም በአንቀፅ 28(1) የሚናገረው አንድን ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ከስራ በማሠናበት ስለሚቻልበት ሁኔታ እንጂ ስለ በርካታ ሠራተኞች ቅነሣ አይደለም አንድ ሠራተኛ የተመደበበትን ሥራ ለመስራት ችሎታው የሌለው በሆነ ጊዜ ወይም በደረሠበት የጤና መታወክ ወይም የአካል ጉዳት ሥራውን ለመስራት ያልቻለ ከሆነ ወይም ድርጅቱ ወደሌላ ቦታ ሲዛወር ሠራተኛው ተዛውሮ ለመስራት ፈቃደኛ ሣይሆን ሲቀር ወይም ሠራተኛው የያዘው የሥራ መደብ ሲሠረዝና ወደ ሌላ ሥራ መደብ ማዛወር ሣይቻል ሲቀር ሠራተኛውን ማስጠንቀቂያ ሠጥቶ የስራ ውሉን ማቋረጥ ይቻላል፡፡ እነዚህ በአንቀፅ 28(1) ሥር የተዘረዘሩትን ምክንያቶች የሚመለከቱት ችግር አለበት የተባለውን ሠራተኛ ብቻ እንጂ ሌሎችን ሠራተኞች ባለመሆኑ ሊሠናበት የሚችለውም ይኸው ሠራተኛ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም አንድን ሠራተኛ ለመሠናበት በአንቀጽ 29(3) ሥር የተመለከቱት በርካታ ሠራተኞች የሚቀነሱበትን ሥርዓት መከተል ተገቢ ነው ማለቱ ትርጉም የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም በአንቀፅ 28(1) ሥር የተመለከቱት ምክንያቶች ሲያጋጥሙ ከስራ ለማሠናበት መከተል የሚያስፈልግ ስርዓት ሣይኖር ችግር አለበት የተባለውን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሠራተኞች በማስጠንቀቂያ ማሠናበት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ግን አንቀፅ 28(2) ሥር የተመለከቱት የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያቶች ሠራተኞቹ የሚሠናበቱት የተመደቡበትን ስራ ለመስራት ችሎታ ሣይኖራቸው ቀርቶ ወይም ሥራውን ለመስራት ፈቃደኝነት ጎድሏቸው ሣይሆን ድርጅቱ ባጋጠመው ችግር ምክንያት ብዛት ያላቸውን ሠራተኞች መቀነስ በመገደዱ ነው፡፡ ብዛት ያላቸው ሠራተኞች ከእነሱ አቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሥራ መሠናበት ካለባቸው ሥንብቱ እንዴት መከናወን አለበት የሚለው ቀጥሎ መፍትሄ ማግኘት የሚገባው ነጥብ ነው፡፡ ስለዚህም ህጉ መፍትሔ ማስቀመጥ አስፈልጎታል፡፡ ህጉ ከፍተኛ የምርት ውጤት የሚያሣዩና ችሎታ ያላቸው በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ ቅድሚያ ሲሠጣቸው ተመሣሣይ የሥራ ችሎታና ተመሣሣይ የምርት ውጤት የሚያሣዩ ሠራተኞች በሚመለከት ደግሞ በአንቀፅ 29/3/ (ሀ-ረ) በተዘረዘሩት መሠረት ቅነሣው እንዲካሄድ ያዛል፡፡ በመሆኑም በአንቀፅ 29(3) ሥር የተመለከተው የቅነሣ ስርዓት ተፈፃሚነት የሚኖረው በአንቀፅ 28(2) እና (3) ሥር በተመለከቱት ሁኔታዎች ላይ እንጂ በአንቀፅ 28(1) ሥር ለተመለከቱት ሁኔታዎች አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አንቀፅ 28 እና 29 በአንድነት ተገናዝበው ሲታዩ በአንቀፅ 29(3) ሥር የተቀመጠው የቅነሣ ሥርዓት ተፈፃሚ የሚሆነው በአንቀፅ 28(2) መሠረት ለሚደረግ ቅነሣ እንጂ በአንቀፅ 28(1) ሥር ለሚደረግ የሥራ ውል ማቋረጥ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በእርግጥ በአንቀፅ 28(2)(ሐ) ሥር የድርጅት ምርታማነት ለማሣደግ የአሠራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሠራተኛ ቅነሣ ማድረግ የሚቻለው በአንቀፅ 29(3) ሥር በተቀመጠው ቅደም ተከተል ቢሆንም ይህን ቅደም ተከተል መከተል ግድ የሚለው ግን የተቀነሱት ሠራተኞች ብዛት ቢያንስ 10% የሚያህለው ወይም የሠራተኞች ቁጥር ከ20-50 በሆነበት ድርጅት ቢያንስ 5 ሠራተኞች ሲቀነሱ ነው፡፡ በመሆኑም አሠሪው የቅነሣ ቅደም ተከተል አይገባም የሚል ከሆነ የሚቀነሱት ሠራተኞች ብዛት ከላይ ከተመለከተው ቁጥር በታች መሆኑን ማስረዳት መቻል ይኖርበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይም ስንመለስ ተጠሪ ሠራተኞቹን በአንቀፅ 28(2)(ሐ) መሠረት የቀነሣቸው ለመሆኑ በቦርድም ሆነ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረጉት ክርክሮች ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከፍ ሲል በተብራራው ምክንያት የቅነሣ ስርዓቱ ሊከናወን የሚገባው በአዋጁ አንቀፅ 29(3) መሠረት ነው፡፡ ተጠሪ ይህንን የቅነሣ ሥርዓት ልከተል አይገባም ማለት የሚችለው የተቀነሱት ሠራተኞች ቁጥር በአንቀፅ 29(1) ሥር ቅነሣ ነው ለማለት እንዲችል በመስፈርትነት ከተቀመጠው የሠራተኞች ቁጥር በታች ነው የሚለውን ፍሬ ነገር በማስረዳት ብቻ ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ ከሥር ጀምሮ የተሠናበቱት የሠራተኞች ቁጥር በህጉ ከተመለከተው በታች ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ እንደውም አመልካቾች የተቀነሱት ሠራተኞች 30% የሚያህሉ ናቸው በማለት በሠበር ችሎት ባቀረቡት አቤቱታ የገለፁትን በማስተባበል መልስ አልሠጠም፡፡ ይህም በአመልካቾች የተነገረውን ፍሬ ነገር እንዳመነ የሚያስቆጥረው ነው፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ የሠራተኞችን ቅነሣ ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28(2)(ሐ) በመሆኑ ቅነሣው ሊደረግ የሚገባው በአንቀፅ 29(3) ሥር የተመለከተውን የቅነሣ ሥርዓት በመከተል በመሆኑ የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ተጠሪ በህጉ የተመለከተውን የቅነሣ ቅደም ተከተል መከተል አይገባውም በማለት ለድንጋጌው የሠጠው ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 70811 ታህሣስ 5/2001 የሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ/ቁ 350/ቀወ1/2000 22/12/2000 ዓ.ም

የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

3/ ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39464

ግንቦት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሐረር ቢራ አክሲዮን ማኅበር - ነ/ፊ ሬድዋን አህመድ

ተጠሪ፡- አቶ አብዱልቃድር አብዱረዛቅ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መ/ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪ የሥር ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በመልካች ድርጅት በሠራተኝነት ከ1974 ዓ.ም. ጀምሮ ስሠራ ቆይቼ በራሴ ፍቃድ ውሌን አቋርጫለው በአዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 39/2/ሸ/ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍለኝ ሲገባ ቤት ከለቀቅክ በሚል ምክንያት ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለክሱ ባቀረበው መልስ ተጠሪ በአዋጅ ቁ 494/98 39/2/ሸ መሠረት የጠየቁት የስንብት ክፍያ የሕግ ድጋፍ የለውም ምክንያቱም ተጠሪ ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ ስለነበረ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ሊፃፍ አይገባም በተጨማሪም ተጠሪ የጡረታ መብት ተጠቃሚ ስለሆኑ የስንብት ሊከፈላቸው አይገባም፣ የአመልካችን /የድርጅቱን/ ንብረት ሳያስረክቡ ክፍያ ሊጠይቁ አይችሉም ሲል ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን በማከራከር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔውም አመልካች ላቀረቡት መቃወሚያ በመመርመር ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ሲወስን ተጠሪ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት ሊዳኙ እንደሚገባ በማመልከት በዚሁ አዋጅ መሠረት ተጠሪ በፈቃዳቸው ስራቸውን በመልቀቃቸው በሕጉ አግባብ ሊከፈላቸው የሚገባውን ክፍያ በጥያቄያቸው መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች ለተጠሪ እንድከፍል በመወሰን አመልካች በክስ መልሱ ላይ ንብረቴን ሳያስረክበኝ ክፍያ ሊጠይቅ አይገባውም ያለውን ነጥብ አልፎ ንብረቱን /ቤት/ አስመልክቶ አመልካች ቤቱ በራሱ ስም ተመዝግቦ መኖሩን አላረጋገጠም፤ የተከሣሽ ከሣሽነትን ማቅረብ ሲገባው ክርክር ማቅረቡ ሕጋዊ አይደለም ሲል ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ለክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ቢያቀርብም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የሥር ውሣኔ ጉድለት የለውም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

በዚህ መሠረት የሰበር ችሎቱ ተጠሪ በአመልካች በኩል ላቀረበው አቤቱታ ቀርቦ መልሱን እንዲሠጥ መጥሪያ ብልክለትም ተጠሪ መጥሪያ ቢደርሰውም ክርክሩ ሊሰማ በተወሰነበት ቀን ሊቀርብ ባለመቻሉና አመልካችም ይህንኑ በማረጋገጡ ተጠሪ በሌሉበት ጉዳዩ እንዲታይ በማድረግ መዝገቡን መርምረናል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተባለውም በሥር ፍ/ቤት ለተጠሪ ሊከፈለው ይገባል ያሉት የስንብት እና የቦነስ ክፍያን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎቱም አቤቱታ የቀረበለትን ውሣኔ የአመልካችን አቤቱታ፣ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡-

እኛም የጉዳዩን አመጣጥ ጠቅላል ባለ መልኩ ስናየው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በማገልገል ቆይተው በራሳቸው ፍቃድ የሥራ ውላቸውን በማቋረጣቸው አመልካች ቤት /ንብረት/ ካላስረከብክኝ በማለት በሕጉ የሚፈቀድልኝን ሊከፍለኝ ፈቃደኛ አልሆነም ብለው በመክሰሳቸው አመልካችም ተጠሪ በእጃቸው የሚገኘውን ንብረት ሣያስረክቡኝ ክፍያ ሊጠይቁኝ አይችልም በማለት በመከራከራቸው ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የተጠሪን የክፍያ ጥያቄ በመቀበል እንዲከፈለው በመወሰን ንብረትን አስመልክቶ በተከሣሽ ከሣሽነት ያልቀረበ ነው በማለት ውድቅ ሲያደርገው የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉድለት የለበትም ሲል የሥር ውሣኔን አጽድቆታል፡፡

እንግዲህ ከቀረበው ውሣኔና የአመልካችን አቤቱታ እንደመረመርነው ምንም እንኳ ክፍያን አስመልክቶ ለማጣራት ጭብጥ ቢያዝም በተንዳኝ አመልካች ተጠሪ ሊያስረክበኝ ይገባል የሚለውን ቤት በዋናነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሠረቱ ተጠሪ በሥር ክሣቸው ተጠሪ ንብረቴን ካላስረከብክኝ በማለት ክፍያ ሊከፍለኝ ፍቃደኛ አልሆነም ሲሉ ክስ መስክረዋል፤ ከዚህ በመነሣት ተጠሪ ከጠየቁት ክፍያ ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 36 መሠረት ሊከፈላቸው የሚገባውን ጠይቋል ይህ አንቀጽም አስፈላጊ ክፍያዎች አሰሪው በሰባት /7/ ቀን ውስጥ ለሰራተኛው ሊከፍል እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ ይህን ካልፈፀመ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 38 መሠረት አሠሪ በራሱ ጥፋት ካልከፈለ ለሠራተኛ ክፍያ የዘገየበትን እንዲከፍል ያዛል፡፡ ለእነዚህ አንቀጾች አግባብ ያለውን ትርጉም ለመስጠት /ክፍያ ዘገየ ወይም አልዘገየም/ ለማለት የንብረቱ ባለይዞታነትና ተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል ወይ? ወይስ አይገባም? የሚለው ነጥብ ሊጣራ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ምክንያቱም የተጠሪን የክፍያ ጥያቄ ምላሽ ለመሰጠት ስለሚረዳ ነው፡፡ በተጨማሪም አመልካች ተጠሪ ንብረቱን ሣያስረክበኝ ክፍያ ፈጽምልኝ ሊለኝ አይገባም የሚል ክርክር ስላለው ነው በመሠረቱ በአመልካች አቤቱታ ላይ ለመረዳት እንደቻልነው አመልካች የተባለውን ቤት ለሰራተኞቹ ማረፊያነት በማሰብ ከክልሉ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር በራሱ ስም እንደተረከባቸው እየገለፀ ነው ይህ ባለበት የሥር ፍ/ቤቶች ቤቱንም ቢሆን የማን ንብረት /በማን ስም/ እንዳለ በራሱ ጊዜ ሊያጣራውና ውሣኔ ሊያሳርፍበት ሲገባ የአመልካች ቤት መሆኑ አልተረጋገጠም የተከሣሽ ከሣሽነት ሊቀርብበት ይገባል በማለት ጥያቄውን ማለፉ አግባብነት የለውም ምክንያቱም ተጠሪም ቢሆን የኔ ንብረት ነው ሲል ያቀረበው ማላመኛ ነጥብ የለምና ነው፡፡ ባጠቃላይ የንብረት ጥያቄው ምላሽ ሣያገኝ የተጠየቀውን ክፍያ ነጥሎ ውሣኔ መስጠቱ የተጠየቀውን ዳኝነት በአግባቡ ምላሽ ተሰጥቶታል ለማለት አዳጋች ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ተጣርቶ ሣይጠናቀቁ በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እና በከፍተኛውም ፍ/ቤት ሣይታረም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሐረሪ ሕዝብ ብ/ክ/መ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27167 ግንቦት 21/2000 እና የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የመ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ በያዙት ቤት ላይ በማከራከር ውሣኔ በሕጉ መሠረት ይስጥ ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሠረት መዝገቡን መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41786

ግንቦት 26 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ - ነ/ፊ ሰለሞን ተክሌ ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ አሰፋ አቤቦ - ክፍለ ታደሰ ጠበቃ

2. አቶ ዋዶ ቱማ

3. አቶ አክሊሉ ጌታሁን

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪዎች የሥር ከሣሾች ነበሩ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ባመልካች ድርጅት በማቴሪያልስ ማኔጅመንት ዲቪዢን አጣዳፊ የአውሮፕላን መለዋወጫ ዕቃ አቅራቢነት የሥራ መደብ እና በኋላም የዕቃ ግዢ በመሆን ተመድበን እየሰራን ወደ አዲሱ የሥራ መደብ ስንዛወር ደሞዝና ጥቅም ተቀንሶብናል፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል የምናገኘው ደሞዝ ይከፈለን፣ ወደ ነበርንበት እንድንመለስ ከደሞዝ ጋር የሚከፈል ክፍያ እንዲመለስልን የነዳጅ አበል እና የበረራ የቅድሚያ ትኬት መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካች በበኩሉ ባቀረበው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዋናው ነገር ግን ተጠሪዎች ሲሰሩበት የነበረው የሥራ መደብ ለተቀላጠፈ የሥራ ውጤት ሲባል እንደገና ሲዋቀር የተጠሪዎች አገልግሎት አስፈላጊ በመሆኑ ከሥራ ከሚሰናበቱ በድርጅቱ የደመወዝ ፖሊሲ መሠረት በአዲሱ የሥራ መደብ ለመሥራት የሚስማሙ ከሆነ እንዲሠሩ ተጠይቀው በፍቃደኝነት በመቀበላቸው ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን ያየው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበውን ክርክር አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ውሣኔ ሲሰጥ ተጠሪዎች ይዘውት የነበረው የሥራ መደብ በመዋቅር ለውጥ ምክንያት ተዘግቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎችን ከማሰናበት ይልቅ ደሞዛቸው ተቀንሶ ወደ አዲሱ የሥራ መደብ እንዲሰሩ ተጠይቀው የቀድሞ የሥራ መደባቸው /የማቴሪያልስ ማኔጅመንት ዲቪዥርን አጣዳፊ የአውሮርላን መለዋወጫ ዕቃ አቅርቦት/ መሠረዙን ሳይክዱ በአዲሱ የሥራ መደብ /የዕቃ ግዢ/ ቦታ ላይ ስምምነት ያደረግነው በማስፈራራትና ተገደን ነው የሚለው መከራከሪያ እና ከተደረገው ስምምነት መረዳት እንደተቻለው በፍቃደኝነት የተመደቡበት የሥራ መደብ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ ጥያቄው ውድቅ ነው በማለት ተጠሪዎች ይሠሩበት የነበረው የሥራ መደብ ስለተሰረዘ በፊት ይከፍለን የነበረው ደሞዝ እንዳይቀነስብን፣ የተቀነሰው ይመለስልን ጥቅማ ጥቅማችን ይጠበቅልን ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚሁ ውሣኔ ባለመሥማማት ይግባኛቸውን ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን በማከራከር ሲወስን የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 28/1/መ በአሰራር ለውጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአንድ ሥራ መደብ ሲታጠፍ አሰሪው ሠራተኛውን ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ ማሰራት ካልቻለ በማስጠንቀቂያ ሠራተኛውን ማሰናበት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 59/1/"ም" በሕግ /በሕ. ስምምነት/ በሥራ ደንብ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር አሰሪው የሠራተኛውን ደሞዝ መቀነስ እንደማይችል ተቀምጧል፡፡ በሌላም በኩል ተጠሪዎች ይሠሩበት ከነበረው የሥራ መደብ አሁን ወደ ተመደቡበት መምጣታቸው ደሞዛቸው እንዲቀንስ መስማማታቸውን አይደለም፡፡ የቀረበውም ሰነድ እንዲህ አይልም፡፡ በተጨማሪም የአዋጁ አንቀጽ 25/1/ መሠረት ሠራተኛው መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት ዋጋ የለውም፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ አግባብ አይደለም በማለት የሥር ውሣኔን በመሻር አመልካች ከተጠሪዎች የቆረጠውን ገንዘብ ተመላሽ ያድርግ ደሞዛቸውን ያስተካክል በማለት ሲወስን የጥቅማጥቅም ጥያቄን አስመልክቶ ግን ተጠሪዎች አሁን ለሚሠሩበት ቦታ የሚገባ መሆኑን አላስረዱም ሲል ጥያቄያቸውን ሣይቀበል ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ታህሣሥ 2/2001 ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልን ይገባል ሲል ጠይቋል፡፡

እኛም በዚህ መሠረት ተጠሪዎችን በማስቀረብ ግራ ቀኙ የካሄዱትን የቃል ክርክር ሰምተናቸዋል፡፡ ጉዳዩም ለሰበር ቀርቦ ሊታይ ይገባል የተባለውም መልስ ሰጪዎች ከአመልካች ጋር ባደረጉት ስምምነት ወደ አዲሱ የሥራ መደብ ለሚያስገኘው የደሞዝ መጠን መመደባቸውን የሥር ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ ያስረዳል ይህ መሆኑ ከተረጋገጠ በዚሁ ፍሬ ነገር የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 25 እና 59 ላይ አስመልክቶ የሰጠውን ትርጓሜ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሠረት አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመሆኑም የጉዳዩን አመጣጥ ባጭሩ ስናይ ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት ክሳቸውን ሲመሠርቱ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በማቴሪያል ማኔጅመንት ድቪዥን አጣዳፊ የአውሮፕላን መለዋወጫ ዕቃ አቅራቢነት ሲሰሩ ቆይተው ወደ አዲሱ የሥራ መደብ "ዕቃ ግዢ" የሥራ መደብ ላይ በመመደባቸው ምክንያት በፊት ሲያገኙት የነበረው የደሞዝ መጠንና የሚያገኙት ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም እንደቀነሰባቸው በመግለጽ ወደነበሩበት ቦታ እንመለስ፣ ቀደም ሲል ሲከፈለን የነበረው ደሞዝ ይከፈለን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ይሠጠን በማለት በመጠየቃቸው አመልካችም ተጠሪዎች ሲሰሩበት የነበረው የሥራ መደብ በመዋቅር መሻሻል /ለውጥ/ ምክንያት ስለተሰረዘ ተጠሪን ከማሰናበት ይልቅ በነሱ ፍቃድ ወደ አዲስ የስራ መደብ እንዲመደቡ የተደረገ ነው፡፡ ለአዲሱ ቦታ የተያዘውን ደሞዝ እየከፈልናቸው ነው፤ በተዘጋ የሥራ መደብ ክፍያ ልንጠየቅ አይገባም በማለቱ ጉዳዩ የቀረበለትም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪዎች የድሮው ቦታ /የነበሩበት የሥራ መደብ እንደተሰረዘ ሣይክዱ በፍቃዳቸው በአዲሱ የሥራ መደብ ላይ ሆነው ወደ ነበርንበት እንመለስ የተቀነሰው ደሞዝና ጥቅማ ጥቅም ይከፈለን በማለት የጠየቁት ጥያቄን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ በተቃራኒው የአዋጁን አንቀጽ 25/1/ በመጥቀስ የቀረበው ሰነድና ተጠሪዎች ከነበረው የሥራ መደብ አሁን ወደ ተመደቡበት መምጣታቸውን እንጂ ደሞዛቸውን እንዲቀነስ መስማማታቸውን አያሣይም፡፡ ስለዚህ የተቆረጠባቸው ደሞዝ ይከፈል በዚሁም ልክ ይስተካከል ሲል የስር ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሮታል፡፡

በመሠረቱ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሥር ውሣኔን ለመሻር ሲል የሰጠውን የሕግ ትንተና የአዋጁን አንቀጾች አተረጓጎም አንባር ስናይ የሥር ውሣኔ የሚነቀፍ አልነበረም፡፡ የሰበር ችሎቱም ቢሆን አጽኖት ሰጥቶ በጭብጥነት የያዛቸው ነጥብም ቢሆን ይህንኑ ለመመርመር ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪዎችና አመልካች በሰበር ችሎት ቀርበው ባደረጉት የቃል ክርክርና ከሥር መዝገብ ለመገንዘብ እንደተቻለው ተጠሪ የነበሩበት የሥራ መደብ የሥራ መሪ የሚያሰኛቸውና እነሱም /ተጠሪዎች/ ያልካዱት ጉዳይ ነው፡፡ ታዲያ ይህ አዲሱ ቦታ /የሥራ መደብ/ በድርጅቱ የመዋቅር ለውጥ ምክንያት መዘጋቱን የተካካዱበት በሌለበት አመልካች ለማሰናበት ያለውን መብት በመተው ከተጠሪዎች አገልግሎት አንባር የእነርሱን ፍቃድ በመጠየቅ በጽሑፍ ተስማምተው ተጠሪዎችም ይህ አዲሱ የሥራ መደብ የደሞዝ መጠን ምን ያሕል እንደሆነ እያወቁ ሥራቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጀመሩ መሆኑ በሰበር ችሎት የግራ ቀኙ ስምምነት በግልጽ ተሰምቷል፡፡ ተገደን ነው የፈረምነው የሚሉት ቢሆን በዚህ ደረጃ ላይ ሊታመን የሚችል አይደለም፡፡

ይህ ሆኖ ግለ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአዋጁን አንቀጽ 28/መ/"ን" በመጥቀስ የሥራ መደብ ሲታጠፍ አመልካች ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ ማሰራት ካልቻለ ተጠሪን ሊያሰናብት ይችል ነበር በማለት ተችቷል፡፡

በመሠረቱ የተጠሪ ጥያቄም ቢሆን ዝውውርን አይመለከትም፡፡ ሌላው እንደ ከፍተኛው ፍ/ቤት አባባል /አተረጓጎም/ አመልካች የመጀመሪያው የስራ መደብ ሲሰረዝ /ሲዘጋ/ የተጠሪዎችን መሰናበት የሚያበረታታ ነው፤ ድርጅቱ ግን የተጠሪዎችን አገልግሎት ከግምት በማስገባት ከማሰናበት ይልቅ በሌላ የሥራ መደብ በፍቃዳቸው ላይ ተንተርሶ እያሰራቸው ነው፡፡ ይህ ድርጊት ፈጽሞ ሊነቀፍ የሚገባው አልነበረም፡፡

ሌላው የአዋጁን አንቀጽ 59/1/ አስመልክቶ በይግባኝ ሰሚው የተሰጠውን ትርጉም ስናይ ሰራተኛው በጽሑፍ ካልተስማማ አሰሪው የሰራተኛውን ደሞዝ ሊቀንስ አይችልም ነው የሚለው በያዝነው ጉዳይ ግን የአመልካች ድርጊት በዚህ መልኩ የሚተረጎም አይሆንም፡፡ ምክንያቱም አመልካች የተጠሪዎች የመጀመሪያው የሥራ መደብ በመሠረዙ ምክንያት አዲስ የሥራ መደብ ላይ በአዲስ መልኩ በመደራደር ወይም /በውል ሰነድ/ በመፈቃቀድ የፈፀሙት ስለሆነ የአንቀጹን መንፈስ የሳተ ትርጉም ነው፡፡ በመጨረሻም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአዋጁን አንቀጽ 25/1/ በመጥቀስ ሠራተኛው መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት ዋጋ የለውም ሲል ነው የሥር ውሣኔን የተቸው፡፡ ይህም ነጥብ ቢሆን ተጠሪዎችም ቢሆኑ የመጀመሪያው የሥራ መደብ ከተሰረዘ በኋላ ነው በሌለ መብት መብትን የሚጠይቁት፡፡ ይህም ማለት መብትን ፈጥሮ የነበረው የሥራ መደብ ራሱ የለምና ነው፡፡

ስለዚህ የከፍተኛው ፍ/ቤት ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ከግምት ሣያስገባ በሌለ የሥራ መደብ ልክ የተጠሪዎች ደሞዝ ይስተካከል ያልተከፈላቸው ተመላሽ ይሁን በማለት የሥር ውሣኔን መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1- የፌዴራል የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65973 ነሐሴ 26/2001 የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34902 በ26/6/2000 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3- ተጠሪዎች አሁን በሚሠሩበት የሥራ መደብ በተያዘው የደሞዝ ልክ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡
4- በመ/ቁ. 47676 ላይ ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5- የግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39650

ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የየረር በር ምስራቅ ፀሐይ ቅዱስ ዑራኤል ቤ/ክርስቲያን የደብሩ ዋና አስተዳደር - ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- እነ ቂስ ሰፊነው ደሣለኝ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪዎች በየግላቸው በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሣቸው ይዘትም በአመልካች ቤተክርስቲያን በጥበቃ ሥራ ተቀጥረው በማገልገል ላይ እያሉ ጥፋት ሣይፈጽሙ ከሥራ መሰናበታቸውን ገልፀው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ መደባቸው እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካችም በተከሣሽነቷ ቀርባ በሠጠችው መልስ ተጠሪዎች ከሥራ የተሰናበቱት የጥበቃ ተግባርና ኃላፊነት ባለማክበርና ባለመወጣት ብር 15,000.00 /አሥራ አምስት ሺህ ብር/ የያዘ ሙዳየ ምጽዋት እንዲሠረቅ በማድረጋቸው በመሆኑ የሥራ ስንብቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ከአንቀጽ 13፣ 27/1/ሸ/ ድንጋጌዎች አኳያ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክራለች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ምስክሮችን ከሠማ በኋላ አመልካች የተጠሪዎችን አሳስረዳችም የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ በመድረስ ተጠሪዎች የ6/ስድስት/ ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ምድብ ስራቸው አመልካች እንድትመልስ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ወኪል ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም. 4/አራት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪዎች ጎዳር 15 ቀን 2001 ዓ.ም. በጋራ በፃፉት የመልስ ማመልከቻ የአመልካችን የሰበር ቅሬታ ነጥቦች በመንቀፍ እና የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ተገቢነት በመዘርዘር ውሣኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ዓቢይ ጭብጥ የተጠሪዎች የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ምድብ ሥራቸው እንዲመለሱ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪዎች በአመልካች ድርጅት ለጥበቃ ሥራ የተቀጠሩ፣ ይህንኑ ስራውን በዕለቱ ሲያከናውኑም ብር 15,000.00 የያዘ ሙዳየ ምስዋት መጥፋቱ መረጋገጡን ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ይህንኑ ፍሬ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ ያረጋገጠው ሲሆን የአመልካችን ክርክር ውደቅ ያደረገው ተጠሪዎች ለገንዘብ መጥፋት ቀጥተኛ ወይም በተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ ያደረጉት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም የሚል ምክንያት ይዞ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ገንዘቡ ተጠሪዎች በጥበቃ ሥራቸው ላይ በነበሩበት ሰዓት አለመጥፋቱን የሚያረጋግጥ ክርክር አልቀረበም፤ የተጠሪዎች ሥራም የቤተክርስቲያኗን ንብረት መጠበቅ ነው፡፡ ገንዘቡ የጠፋው ገንዘቡ ተቀምጦበት የነበረው ሙዳየ ምስዋት ቁልፍ ሣይሰበር ስለመሆኑና ተመሣሣይ ቁልፍም በሌሎች ሰዎች እጅ እንደሚገኝም ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን የዚህ ፍሬ ነገር መረጋገጥ የተጠሪዎችን ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ አስተዋጽኦ ለገንዘቡ መጥፋት በምክንያት በመያዝ ኃላፊነት የለባቸውም ወደሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ዋናው ነጥብ ገንዘቡ የጠፋበት ሰዓት ተጠሪዎች በጥበቃ ሥራ ላይ የሚገኙበት ከሆነ የስራቸው ኃላፊነት የለባቸውም ወደሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ዋናው ነጥብ ገንዘቡ በሚጠፋበት ሰዓት ተጠሪዎች በጥበቃ ሥራ ላይ የሚገኙበት ከሆነ ከሥራቸው ኃላፊነት እና ተግባር ጋር ተያይዞ መታየቱ ላይ ነው፡፡ እንግዲህ የአመልካች ገንዘብ የጠፋው ተጠሪዎች በጥበቃ ላይ በነበሩበት ወቅት መሆኑ ከተረጋገጠ የአመልካች እርምጃ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/3/ እና 27/1/ሸ/ አንፃር ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ተጠሪዎች የሥራ ተግባራቸው ጥበቃ እስከሆነ ድረስ ስራው የሚጠይቀውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉና እንዲወጡ የሥራ ደንቡ የግድ ይላል፡፡ ሥራው የሚጠይቀውን ጥንቃቄ ባለማድረግ ለሚደርሰው ጉዳት ደግሞ በሕጉ አግባብ ኃላፊነት ይከትላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች በጥበቃ ላይ ባሉበት ወቅት የአመልካች ንብረት መገኘቱ ስራው የሚጠይቀውን ጥንቃቄ አለማድረጋቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

በዚህ ተግባራቸው ደግሞ በአሠሪው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/ መሠረት የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በትዕዛዝ በማጽናት ተጠሪዎች ውዝፍ ደመወዝ ከፍሏቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ ማድረጉ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር፣ የተጠሪዎች የሥራ ዓይነት የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/3/ እና 27/1/ሸ/ ድንጋጌዎች ጋር ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ተከታዩን ውሣኔ ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37446፣ 37456፣ 37452 የቀረቡት ጉዳዮች ተጣምረው ታይተው ሐምሌ 02 ቀን 2000 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ እና ይህንኑ ውሣኔ በመ/ቁ. 69644 ሐምሌ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ያፀናው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 39543

ግንቦት 4 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት ነ/ፈጅ ካሣሁን ወርቁ - ቀረበ

ተጠሪ፡- አቶ በረከት ተ/ማሪያም - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ የሥር ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ሰራተኛ መሆናቸውን ጠቅሰው አመልካች የሥራ ውሌን ያለአግባብ ስላቋረጠብኝ ወደ ሥራዬ ይመልሰኝ ካልሆነ በሕጉ የተቀመጡትን ክፍያዎች ይክፈለኝ ሲል ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ሊሰናበቱ የቻሉት አድራሻ የሌለውና ለማስረጃነት ብቁ ያልሆነ የሥራ ልምድ ማቅረባቸው በመረጋገጡ ነው፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበለትን ክስ ግራ ቀኙ ባቀረቡት ክርክር አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች በ26/5/2000 በፃፈው ደብዳቤ ተጠሪ ያቀረቡትን የምስክር ወረቀትን አስመልክቶ ድርጅቱ ተጠይቆ የአይስክሬም ሽያጭ በድርጅቱ እንደማይካሄድ ቢገልፅም፤ አመልካች ተገቢውን አካል መጠየቁንና ሰርቷል የተባለበትን ጊዜ አይገልፅም፣ ማስረጃው ትክክል አልነበረም እንኳ ቢባል በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሐ) መሠረት በሥራ ላይ ተፈፀመ የተባለው ማጭበርበር ድርጊት ሊባል የሚችለው ከቅጥር በኋላ ሰራተኛው ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት የሚፈፅማቸውን የማጭበርበር ድርጊቶችን ነው፡፡ በመሆኑም የተፈፀመው ድርጊት በዚህ አንቀፅ ሥር የሚወድቅ ስላልሆነ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው፡፡ በአዋጅ አንቀፅ 43(2)(5) መሠረት የሁለት ወር ደሞዙ ተከፍሎት ተጠሪ ወደ ሥራቸው ይመለሱ ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 22/2000 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክራቸውን ሰምቷል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የተጠሪ ስንብት ሕገ ወጥ ነው የሁለት ወር ደሞዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ ይመለስ መባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሠረት የግራ ቀኙ ካሰሙት ክርክር አቤቱታው የቀረበበትን ውሣኔ አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩን አመጣጥ ባጭሩ ስናይ የአመልካች ድርጅት ተጠሪን ሲያሰናብት መሠረት ያደረገው በሀሠተኛና ብቃት በሌለው ማስረጃ (የምስክር ወረቀት) በማቅረብ የተቀጠረ መሆኑን ባደረገው ማጣራት ደረስኩበት ሲል በማሰናበቱ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን በማከራከር ተጠሪ ፈፅመዋል የሚባል ድርጊት እንኳ ቢኖር በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 27(1/ሐ) ሥር ሊወድቅ አይችልም በሥራ ላይ እያሉ የፈፀሙት ማጭበርበር አይደለም፣ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው፣ ተጠሪ የሁለት ወር ደሞዝና ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቱ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲል መሠረት ያደረገው የአዋጁን አንቀፅ 27(1/ሐ) በመጥቀስ ትርጉም በመስጠት የተጠሪ ድርጊት በሥራ ላይ እያሉ የተፈጠረ አይደለም ሲል ነው፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 27(1/ሐ)"ን" ሙሉቃል ስናነብ "የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ የሚቻለው ሠራተኛው በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር ሲፈፀም ነው" ይላል፡፡ በመሆኑም የዚህን አንቀፅ ትርጉምና ተጠሪ የፈፀሙትን ማጤኑ አስፈላጊ ነው፡፡ ከመጀመሪያው አመልካች የስንብቱን ምክንያት ሲገለፅ ተጠሪ ባቀረቡት የሐሰት ማስረጃ መቀጠራቸውን የተጠራጠረው ተጠሪ በተቀጠሩበት የአይስክሬም ስራ ብቃት ስላጡና ደንበኛም እየቀነሰ በመምጣቱ እና ባደረገው የማጣራት ሥራ ማስረጃው ለተጠሪ ሰጠ ያለውን ድርጅት በግንባር በመሄድ በድርጅቱ አይስክሬም እንደማይሠራ በማረጋገጥ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተጠሪ ያቀረቡት ማስረጃ በጥርጣሬ ውስጥ የወደቀ መሆኑን ነው፡፡

ባጠቃላይ ተጠሪ ከመጀመሪያውኑ ሲቀጠሩ በሐሰት ማስረጃ እስከሆነና በዚህም ማስረጃ ሥራቸውን መስራት ከጀመሩ በኋላ በመሀከሉ የማጭበርበር ድርጊት መፈፀማቸው እስከተደረሠባቸው ድረስ ይህ ድርጊት ተጠሪ በሥራቸው ላይ (ስራቸውን በማከናወን) እያሉ የፈፀሙት ነው ተብሎ ከመተርጎም ውጪ እንደ የሥር ፍ/ቤት አባባል በተቃራኒው ሊተረጉም የሚገባው አይደለም፡፡ በመጨረሻም ከግራ ቀኙ ክርክር ልንገነዘብ እንደቻልነው ማስረጃ ሰጠ የተባለው ድርጅት የአይስክሬም ሥራ (ሽያጭ) የማይከናወንበት መሆኑ ስለተረጋገጠ የተጠሪ ማስረጃ የተጭበረበረ ለመሆኑ በጥያቄ የሚገባ አይደለም፡፡

ስለዚህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ሣያገናዝብ ለአንቀጽ 27(1/ሐ) አግባብ ያልሆነ ትርጉም በመስጠት ስንብቱ ህገወጥ ነው ሲል፤ የከፍተኛው ፍ/ቤትም ይግባኙን መዝጋቱ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 24723 ቀን 4/10/2000 እና የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ 68331 በቀን 17/11/2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ስንብቱ ሕጋዊ ነው፡፡ ተጠሪ የሁለት ወር ደሞዝ መከፈሉም ሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱ አይገባም ብለናል፡፡
3. የግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39042

ግንቦት 26 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ዩቴክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማኅበር - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- ጀማል መሐመድ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሣን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በአናጺነት በቀን ብር 32.00 እየተከፈለኝ እንድሠራ ተቀጥሬ ስሠራ ቆይቻለሁ፡፡ በኋላ ግን ሥራው እያለ ያለአንዳች ጥፋት ምንም ዓይነት የቃልም ሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ ከሥራ ተሰናብቻለሁ፡፡ ሥራውን በፈቃዱ ለቀአል የሚለውን ደብዳቤ የተቀበልኩት ደብዳቤውን ካልተቀበልክ ደመወዝ አትወስድም ስለተባልኩ እንጂ ፈቅጄ አይደለም፡፡ ስለዚህ በሕጉ የተፈቀዱትን ክፍያዎች በሙሉ ተከፍሎኝ እንድሰናበት ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽን የቀጠርኩት በቋሚነት ወይም በጊዜአዊነት ሳይሆን፣ በቁርጥ ሥራ ነበር፡፡ ሥራውን የለቀቀው በራሱ ፈቃድ ነው፡፡ ሥራውን ሲለቅ ሊከፈለው የሚገባ ክፍያ ሁሉ ወስዶአል፡፡ የቀረበት ክፍያ የለም በማለት እንደተከራከረ ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ ይዘት መገንዘብ ችለናል፡፡

ክሱን የሰማው ፍ/ቤት ከሣሽ /የአሁን ተጠሪ/ የቁርጥ ሥራ ሠራተኛ ለመሆኑ ተከሣሽ አላስረዳም፡፡ ሥራው ከሣሹ በራሱ ፈቃድ ነው የለቀቀው በሚለው ነጥብ ላይም ከተከሳሽ ማስረጃ ይልቅ የከሣሽ ማስረጃ የሚያመዝን ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ ከሣሽ ሥራውን ስለመልቀቁ የሚያሳይ ማስረጃም ተከሣሽ አላቀረበም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት የሥራ ሙሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በመቀጠልም አመልካች የስንብት፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ የአንድ ወር ደመወዝ የካሣ ክፍያ የ6 ወር ደመወዝ እና የዓመት ዕረፍት እንደ አገልግሎቱ መጠን ታስቦ ለከሣሽ /ለተጠሪ/ ይክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ አመልካች ሐምሌ 2 ቀን 2000 ዓ.ም. በዛፉው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በሚል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዛፉው የክስ ማመልከቻ እንዳረጋገጠው የስንብት ደብዳቤ ተቀብሎ ሥራውን ከለቀቀ በኋላ ነው ወደ ክስ ያመራው፡፡ አመልካች በመከራከሪያነት ካነሳቸው ነጥቦች አንዱም ይህኛው ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ ሥራውን ስለመልቀቁ ማስረጃ አልቀረበም በማለት በውሣኔው ላይ ያሰፈረው ትችት ከዚህ አንፃር ሲታይ ስህተት ነው፡፡ በፍሬ ነገር በግልጽ የታመነን ሁኔታ እንደሌለ አድርጎ ማለፍ አይቻልምና፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌላው ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት የተመለከትነው ተጠሪ ይሠራበት የነበረው ሥራ የኮንስትራክሽን /ፕሮጀክት/ ሥራ ነው፡፡ የሥራ መደቡም አናጺነት ነው፡፡ በፕሮጀክት የተያዘ የኮንስትራክሽን ሥራ በተወሰነ ጊዜ የሚያልቅ በመሆኑ በዚህ ሥራ የተቀጠሩት ሠራተኞችም እንደቅደም ተከተሉ የሚሠናበቱ ናቸው፡፡ የተጠሪን የሥራ መደብ ስንመለከት የአናጺነት ሥራ ስለሆነ ምናልባትም ከሌሎቹ ሥራዎች ቀድሞ የሚያልቅ ነው፡፡ ተጠሪ በክሱ እንዳረጋገጠው በአናጺነት ሥራ ልምድ ያለው /ያገኘ/ መሆኑ ተገልጾ ማስረጃ እንዲሰጠው ጠይቆ ከተሰጠው በኋላ የተሰናበተውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30/1/ እንደተመለከተው የኮንስትራክሽን ሥራው እያለቀ ሲሄድ የሥራው መጠን በመቀነሱ ምክንያት በሥራ ተቀጥረው በሚሠሩ ሠራተኞች ላይ ቅነሣ ሊደረግ ይችላል፡፡ ቅነሳው ሲደረግም አሠሪው በአዋጁ የተመለከቱትን የሠራተኞች ቅነሳ ሥነ ሥርዓት መከተል አይኖርበትም፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሆነውም ይኸው ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን ይህን ሁኔታ አገናዝበው ውሣኔ አልሰጡም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29019 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 67143 ሰኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 38189

ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ሮፓክ ኢንተርናሽናል ኃላ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ ያለለት ተሾመ ቀረበ

ተጠሪ፡- ይደርሣል አእምሮ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ህዳር 08 ቀን 1999 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ከሚያዝያ 15 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 1200.00 ደመወዝ እየተከፈላቸው በአመልካች መ/ቤት በዕቃ ግምጃ ቤትነት እስከ 03/13/98 ዓ.ም ድረስ መስራታቸውን ሆኖም ከዚሁ ከተቀጠሩበት የስራ መደብ አመልካች መ/ቤት አንስቷቸው በወር ብር 650.00 በሚከፈልበት የሠዓት ተቆጣጣሪነት የስራ መደብ አዛውሯቸው ቅሬታ ቢያሰሙም ተገቢው ምላሽ በወቅቱ አመልካች ሣይሠጣቸው መቅረቱንና ከስራ ያሠናበታቸው ያላግባብ መሆኑን ዘርዝረው የካሣ፣ የአምስት ዓመት አገልግሎት፣ የዓመት ፈቃድ፣ የህዝብ በዓላት የ14 ቀናት ክፍያ፣ ለዘገየበት ክፍያ እንዲከፍልና የስራ ምስክር ወረቀት እንዲሠጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ አመልካች በተከሣሽነቱ ቀርቦም ተጠሪ የተሠናበቱት ከ22/12/1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 04/13/1998 ዓ.ም ድረስ በስራ ቦታቸው ላይ ስላልተገኙ መሆኑን ገልፆ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ከሠማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ከተቀጠሩበት የስራ መደብ ወደ ሌላ ተዛውረው ቅሬታ እያሠሙ ባሉበት ሁኔታ በስራ ቦታቸው አልተገኙም ማለት ተገቢነት የሌለው ነው የሚለውን ነጥብ በምክንያትነት ይዞ የአመልካችን እርምጃ ከህግ ውጪ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎች ለተጠሪ እንዲከፈሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 29 ቀን 2000 ዓ.ም በዓፉት 2/ሁለት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ከስራ ገበታቸው ከ10 ቀናት በላይ ስለመቅረታቸው ተረጋግጦ እያለ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1/ለ) ስር ከተመለከተው ውጪ በተሣሣተ ትርጉም ተጠሪ ከስራ የቀሩት በበቂ ምክንያት ነው ማለታቸው ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው መልሣቸውን መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፉት ማመልከቻ ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ወደተዛወሩበት የስራ መደብ ያልተገኙት የአመልካች ዘበኞች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ መሆኑንና የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔም የትርጉም ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን ዘርዝረው ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ህዳር 04 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፉት የመልስ ማመልከቻ ተጠሪ ወደ አመልካች ግቢ ለመግባት በዘበኛ ተከልክያለሁ የሚሉት ክርክር አዲስ መሆኑን ገልፀው የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የፁሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ የተመደብኩበት የስራ መደብ ካለሙያ ነው በማለት ከስራ ገበታው ላይ ለ10 ተከታታይ ቀናት በላይ በመቅረቱ አመልካች ከስራ ሲያሰናብተው የስራ ውሉ የተቋረጠው ያለበቂ ምክንያት ነው ተብሎ የአመልካች እርምጃ ህገ ወጥ ነው ሲባል መወሠኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው ተጠሪ በተዛወሩበት የስራ መደብ ሣያገኙ ከ10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ መቅረታቸውን መሠረት በማድረግ መሆኑንና ተጠሪ በበኩላቸው የሚከራከሩት በተዛወሩበት የስራ መደብ ያልተገኙት የአመልካች ዘበኞች ግቢ እንዳይገቡ ስለከለከሏቸው እና የስራ መደብ ዝውውሩን በመቃወም ቅሬታ አሰምተው ውጤቱን እየተጠባበቁ ስለነበር መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡

እንግዲህ አመልካች ተጠሪን ከተቀጠሩበት የስራ መደብ ወደ ሌላ የስራ መደብ በማዛወር ተጠሪ ተገቢው ደብዳቤ ከተሠጣቸው በኋላ በተዛወሩበት የስራ መደብ ሣይገኙ ከ10/አስር/ ተከታታይ ቀናት በላይ የቀሩት በአመልካች ጥበቃ ክልከላ ስለመሆኑ በመጥቀስ ይኸው ተግባር በቂ ምክንያት ነው ሲሉ ተጠሪ የሚከራከሩ ሲሆን የአመልካች ጠበቃ ይህንኑ የክርክር ነጥብ በስር ያልተነሣ ስለመሆኑ ጠቅሰው የመልስ መልስ ሠጥተዋል፡፡ ይህ ችሎትም የስር ፍ/ቤትን ዋና መዝገብ በማስቀረብ ጉዳዩን ሲያጣራው በስር ፍ/ቤት ክሱ በተሠማበት ወቅት ተጠሪ ይህንኑ የክርክር ነጥብ አንስተው ምስክሮቻቸውም የሚያስረዱት ጭብጥ መሆኑን ገልፀው ምስክሮቻቸው መስማታቸውን አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የአመልካች ጠበቃ አዲስ ክርክር ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ከላይ የተጠቀሠውን የክርክር ነጥብ በስር ፍ/ቤት ያነሡት ቢሆንም ጉዳዩን ለማስረዳት የተሠሙት ምስክሮች ግን የአመልካች ጠበቃ ተጠሪን ግቢ እንዳይገቡ የከለከሏቸው ስለመሆኑ የሠጡት የምስክርነት ቃል የለም፡፡ የስር ፍ/ቤትም ተጠሪ በስራ ቦታቸው ላይ ያልተገኙት በአመልካች ጥበቃ ክልከላ አለመሆኑን በመገንዘብ ተጠሪ በስራ መደቡ ለውጥ ምክንያት ቅሬታ እያሰሙ ባሉበት ሁኔታ በስራ ገበታቸው ላይ አልተገኙም ሊባል አይገባም በማለት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በተዛወሩበት የስራ መደብ ከአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ ያልተገኙት በአመልካች ጥበቃ ክልከላ ምክንያት አለመሆኑን ስለተገነዘብን በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ አድርገናል፡፡

የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በስራ ላይ ያልተገኙት ዝውውሩን ተቃውመው ቅሬታ ሲያሠሙ በነበረበት ወቅት መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ ያለበቂ ምክንያት ከስራ ቀርተዋል ሊያስብላቸው አይችልም፡፡ ሲል የደረሠበትን ድምዳሜ ህጋዊነቱን ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ በቂ ምክንያት ሣይኖረው በተከታታይ ለአምስት የስራ ቀናት በስራ ገበታው ያልተገኘ ሠራተኛን ማስጠንቀቂያ መስጠት ሣያስፈልግ የስራ ውሉን ለማቋረጥ ለአሠሪው ህጉ የሠጠው ስልጣን መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1/ለ) ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ሠራተኛው የአሠሪውን እርምጃ ሊቃወመው የሚችለው በቂ ምክንያት ያለው ስለመሆኑ በማስረዳት ነው፡፡ በቂ ምክንያት የሚለው ሀረግ መመዘኛው ደግሞ ሠራተኛው ከስራ ቦታው ሊገኝ የማይችልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ሊያመላክቱ የሚችሉ ምክንያቶች ስለመሆኑ ከአዋጁ አጠቃላይ ዓላማና ከተጠቃሹ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ለመገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከስራ የቀረ ሠራተኛ በቂ ምክንያት ኑሮት ከስራው ቀርቷል ለማለት የሚቀርበው ማስረጃ ሠራተኛው በስራ ቦታው ለመገኘት የሚያስችል መሰናክል የነበረ መሆኑን የሚያስረዳ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህም ሠራተኛው ባልተገባ ምክንያት ከስራው በመቅረት በምርትና ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ሊያደርግ የሚችል ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በስራ ገበታቸው ያልተገኙት ምክንያት የስራ መደብ ዝውውሩን በመቃወም ቅሬታ እያሰሙ በነበሩበት ወቅት ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ገልጿል፡፡ ሆኖም የስራ መደብ ዝውውር መደረግና ሠራተኛው ቅሬታውን በማሠማት ላይ መሆኑ በስራ ቦታ ላለመገኘት እንደ በቂ ህጋዊነት ምክንያት የሚወሠድ አይደለም፡፡ የስራ መደብ ዝውውሩ ሠራተኛው በስራው ቦታ እንዳይገኝ መሠናክል የሚሆንበት ሁኔታ የለምና፡፡ ሠራተኛው በዝውውሩ ላይ ቅሬታ ካለውም ስራውን እየሠራ በህጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት መብቱን ማስጠበቅ አለበት እንጂ ከስራው ሊቀር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይገባም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሣኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 32745 ጥር 05 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 62988 መጋቢት 01 ቀን 2000 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው በህጉ መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37982

ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ታደሰ ዘነበ - ጠበቃ ደርበው ተመስገን

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ከመጋቢት 26 ቀን 1995 ዓ.ም. በተከሣሽ ድርጅት የሥራ መሪ በመሆን በመስራት ላይ እንዳለሁ የአሠሪና አመራር ድክመት አሳይተሀል በሚል ከነሐሴ 1997 ዓ.ም. ጀምሮ በተከታታይ የሶስት ዓመት እረፍት እንድወስድ የተደረገ ሲሆን ከጥር 22 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ ከመምሪያ ሥራ አስኪያጅነትና ከማናጅመንት አባልነት ተከሣሽ እንድነሳ ካደረገ በኋላ ከመጋቢት 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ ከሥራና ከደመወዝ ታግጃለሁ፡፡ በድርጅቱ የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 35/2/ መሠረት ዕገዳ ከአንድ ወር ሊበልጥ እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን ይህንን መመሪያ በመጣስ ተከሣሽን በዕግድ ያቆየው አላግባብ መሆኑ ተገልፆ ወደ ሥራ እንዲመለስና ውዝፍ ደመወዝም እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሽም በሰጠው መልስ የከሣሽ የክፍያ ጥያቄ በ6 ወር ይርጋ ይታገዳል፡፡ ከሣሽ ከሥራ የተነሱት ከባድ የሥራ ጉድለት በመፈፀማቸው ሲሆን የሥራ መሪም ስለሆኑ ወደ ቀድሞ ሥራቸውም ሆነ ወደ ሌላ ተመጣጣኝ ሥራ ለመመለስ ግዴታ የለብንም፡፡ ከሣሽ ላልሰሩበት ጊዜ ደመወዝና አበል እንዲከፈላቸው መጠየቅ አይችሉም፡፡ ስለሆነም ክሱ ተሰርዞ ልንሰናበት ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሐምሌ 1997 ዓ.ም. በሥራ ላይ በዋለው የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 35/2/ መሠረት በጥፋት ምክንያት አንድ የሥራ መሪ ከሥራ ሲታገድ ታግዶ የሚቆየው ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት በዚህ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለዕገዳው ምክንያት በሆነው ጉዳይ ላይ ተከሣሽ በዲስፒሊን ውሣኔ መስጠት አለበት ማለት ነው፡፡ ይህን ውሣኔ ካልሰጠ በከሣሽ ላይ የሰጠው ዕገዳ ተፈፃሚነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ ከመጋቢት 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለውሣኔ አግዷቸው የሚገኙትን ተከሣሽን ወደ ሥራቸው ወይም ከቀድሞ ሥራቸው ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ሥራ ላይ የመመደብ ግዴታ አለበት፡፡ የደመወዝ ክፍያን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2541/1/ መሠረት ከሣሽ በሥራ ላይ ያልተገኙት ተከሣሽ ያለአግባብ እንዳይሰሩ ስለከለከላቸው በመሆኑ ክሱ ያቀረቡበትን የደመወዝ መጠን እና ተያይዞ የተደረገውን ጭማሪ እንደዚሁም ከሣሽ ሥራ ላይ በነበሩበት የ1997 ዓ.ም. የሥራ ዘመን የተከፈለውን ቦነስ ጨምሮ እንዲከፈላቸው በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌደራል ከፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው ያቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ አመልካችን ወደ ሥራ ሊመልሳቸው ይገባል ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/2573 እና 2574 አኳያ አግባብነቱ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ፡-

ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የተወሰነው በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? በአግባቡ አይደለም ቢባል ካሣ ሊከፈላቸው ይገባል ወይስ አይገባም? ውዝፍ ደመወዝስ? የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል ያለው ከላይ እንደተመለከተው በሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 35/2/ ላይ እንደተመለከተው ዕገዳው የሚቆየው ለ1 ወር ጊዜ ብቻ ሆኖ ሳለ ከዚህ ጊዜ በላይ አግዶ ማቆየት ዕገዳው ተፈፃሚ እንደማይሆን ያደርገዋል በሚል ነው፡፡ በተጠቀሰው የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 35/2/ መሠረት አንድ የሥራ መሪ በዲስፒሊን ጉድለት ምክንያት ታግዶ የሚቆየው ለአንድ ወር ጊዜ እንደሆነ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

ነገር ግን አንድ የሥራ መሪ በዲስኘሊን ጉድለት ምክንያት ከሥራ ታገዶ እንዳለ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልተሰጠው ዕገዳው ተፈፃሚ የማይሆን ስለመሆኑ በደንቡ ላይ አልተመለከተም፡፡ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ዕገዳው ተፈፃሚ አይሆንም ወደሚል መደምደሚያ የደረሰው የደንቡን ድንጋጌ በመጥቀስ ሳይሆን የእራሱን ግንዛቤ በመውሰድ ነው፡፡

ስለሆነም የሥራ መሪው ከሥራ ታግዶ የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ወር ከበለጠ ዕገዳው ተፈፃሚ አይሆንም ማለት በደንቡ ባልተሸፈነበት ሁኔታ ነው፡፡

ይልቁንም ይህንኑ በሚያጠናክር ሁኔታ ሥራ መሪው በዲስኘሊን ጉድለት ምክንያት ከሥራ ታግዶ በሚቆይበት ጊዜ ጥፋቱ ተጣርቶ ውሣኔ እስከሚያገኝ ደመወዝ አይከፈለውም ተብሎ በዚሁ የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 35/3/ ላይ መደንገጉ ሲታይ ዕገዳው ከዚህ ጊዜ ከረዘመ ለሥራ መሪው ደመወዝ ሊከፈለው እንደሚገባ ከድንጋጌው ተቃራኒ ንባብ /A contraire Reading/ መረዳት ስለሚቻል የዕገዳው ጊዜ መራዘም ዕገዳውን ሕገ ወጥ ሊያደርገው የሚችል አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2573 መሠረት አሠሪ የሥራ ውሉን ቀሪ ለማድረግ በቂ ምክንያት ባይኖረውም እንኳን ለሠራተኛው ተገቢ የሆነ ካሣ ለመክፈል ከሚገደድ በሥተቀር ሠራተኛውን ወደ ሥራ ለመመለስ ግዴታ እንደሌለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በበቂ ምክንያት አይደለም ቢባል እንኳን ከፍ ብለው በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/2573 መሠረት አመልካች ወደ ሥራ የመመለስ ግዴታ የሌለበት ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተም ተጠሪ ከሥራ የታገዱት በፈፀሙት የዲስኘሊን ጉድለት ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ አመልካች አጥብቆ የተከራከረ ቢሆንም የተወሰደባቸው የዲስኘሊን ዕርምጃ ስለመኖሩ ወይንም ደግሞ ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆናቸው አላስረዳም፡፡ ምንም እንኳን የተጠሪ ጥያቄ ወደ ሥራ የመመለስ ቢሆንም ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ከተባለ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/2573 ደንጋጌ መሠረት ካሣ የማግኘት መብት ያላቸው በመሆኑ ካሳ ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈላቸው ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለውን በተመለከተም ተጠሪ በክስ የጠየቁት ከመጋቢት ወር 1998 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ መስከረም 1999 ዓ.ም. ድረስ የተቋረጠ ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈላቸው ይገባል ያለው ከሣሽ በሥራ ላይ ያልተገኙት ተከሣሽ ያለአግባብ ሥራ እንዳይሰሩ ስለከለከላቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2541/1/ መሠረት ለመክፈል ይገደዳል በማለት ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ተጠሪን ከሥራ ካገደ በኋላ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለዕገዳው ምክንያት በሆነው ጉዳይ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ መስጠት ይጠበቅበት ነበር፡፡ በዚህ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልሰጠ ደመወዝ ለመክፈል እንደሚገደድ መተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 35/3/ ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ መገንዘብ እንደሚችል ከላይ ተመልክተናል፡፡ እንደዚሁም አመልካች ይህንኑ የዕገዳ ጊዜ አራዝሞ መገኘቱ ሠራተኛው ለሥራ ዝግጁ ሆኖ ሳለ በዕገዳው ምክንያት ሥራ እንዳይሠራ ማድረጉን የሚያሳይ እንደመሆኑ መጠን በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/2541/1/ መሠረት ዕገዳው ጸንቶ ከሚቆይበት ጊዜ በላይ ላለው ጊዜ አመልካች በተጠሪ ደመወዝ ለመክፈል ስለሚገደድ ይህም የደንቡን ድንጋጌ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች ዕገዳው ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ውዝፍ ደመወዝና ከደመወዝ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክፍያዎች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 70391 በ8/8/99 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 54707 በ10/8/2000 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/348/1/ መሠረት በማሻሻል ተጠሪ ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል የተባለውን ሽረን የ3 /ሶስት/ ወር ደመወዝ ካሳ ተከፍሏቸው ይሰናበቱ ብለናል፡፡ ለተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ የደመወዝ ጭማሪና ቦነስ ይከፈላቸው ተብሎ የተወሰነውን አጽንተናል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ጽ/ሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41720

ሰኔ 9 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አመልካች፡- የእንጨት መሰንጠቂያና መገጣጠሚያ ድርጅት - ከበደ መኮንን ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ረዲ እንዳለ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተነሳውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ያኔ ከሣሽ የነበረው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው የስራ ውሌን ከሕግ ውጪ ስላቋረጠብኝ ውዝፍ ደመወዜን በመክፈል ወደስራዬ እንዲመልሰኝ ይገደድልኝ፤ይህ ካልተቻለም የስራ ውል ከሕግ ውጪ በሚቋረጥበት ጊዜ ሊከፈሉ የሚገባቸውን ክፍያዎች ከፍሎ ያሰናብተኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው ከሣሽ ለስራ የተሰጠውን ገንዘብ አጉድሎ በመገኘቱ ነው፤ ከዚህ በተጨማሪም የድርጅቱን ንብረት ያለአግባብ ወጪ እንዲሆን አድርጓል፤ በመሆኑም ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት ስለመከራከሩ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ከሣሽ የተከሣሽን ገንዘብ ስለማጉደሉ በማስረጃ የተረጋገጠ እና በከሣሽም ያልተካደ ስለሆነ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ መሰረት ነው በማለት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ታሕሣሥ 1 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ገንዘቡን ስለማጉደሉ እና ለቤተሰቦቹ መንቀሳቀሻ እንደተጠቀመበት በችሎት አምኖ እያለ የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ ነው የተቋረጠው በማለት ውሳኔ የመስጠቱን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ ለስራ ማስኬጃ እንዲውል ተብሎ ከተሰጠው የድርጅቱ ገንዘብ ውስጥ የተወሰነውን አጉድሎ ስለመገኘቱ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ይህን መሰረት በማድረግ እንደሆነም አላከራከረም፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል ተመስርቶ የነበረውን የስራ ውል ስለሚቋረጥባቸው ሕጋዊያን ምክንያቶች በሚመለከት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት የአዋጁ አንቀጽ 27 ሲሆን፣ይህም ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል የሚቋረጥባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር አስቀምጦአል፡፡ ተጠሪ በአሰሪው (በአመልካች) ገንዘብ ያለአግባብ ስለመጠቀሙ ተረጋግጦአል፡፡ ይህ ድርጊት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ከሚያቋርጡ ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ በተጠቀሰው አንቀጽ 27(1)(መ) ተመልክቶአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንግዲህ ሕጉ ይህን ያሕል ግልጽ ከሆነ ከዚህ በተቃራኒ መወሰን የሚቻልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ሲጠቃለል የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተቃራኒው መወሰኑ ትክክል አይደለም፡፡ ውሳኔው በሕጉ አተረጓጐም ረገድ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69766 ጎዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡ ስለዚህም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 25280 ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቶአል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39861

ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢት/ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሣምሶን በለጥካቸው - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ ታኅሣሥ 14 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት የክስ ማመልከቻ አመልካች ከሕግ ውጭ የሥራ ውሉን በማቋረጥ ያሠናበታቸው መሆኑን ዘርዝረው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአመልካች ላይ በደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስ የተጠሪ ስንብት ሕጉን የተከተለ ስለመሆኑና ለዚህም ምክንያቱ ተጠሪ ለቢሮ እቃዎች ጥገና ወጪ የተደረገበት ሰነድ ቀደም ሲል የተፃፈው 20 /ሃያ/ ብር ተደልዞ 100.00 /መቶ ብር/ እንዲሆን የተደረገና ተጠሪ የክፍያ ሰነዱን ራሣቸው ያዘጋጁትና የደለዙት መሆናቸውን፣ ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ ለሥራ አዲስ አበባ ሄጃለሁ በማለት አበል በወሰዱባቸው ቀናት ደብረ ብርሃን ሥራ ላይ የነበሩ መሆኑ በአግባቡ በሰነድ ማስረጃ በመረጋገጡና እርምጃውም በሕጉ የተመለከተውን ቀነ ገደብ ውስጥ የተፈፀመ መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍ/ቤትም አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሠናበተበት ምክንያት ተገቢ በሆነ የጊዜ ገደብ ባለመሆኑ ሕግን የተከተለ የሥራ ስንብት ሊባል የሚችል አይደለም በማለት የተጠሪን ደመወዝ አመልካች መክፈል ካቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ለተጠሪ ከፍሎ ወደ ስራው እንዲመልስ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ይኸው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካች የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ያቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው ካለ በኋላ አመልካች ለተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 39 እና 40 መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያና ካሣ ይከፈለው በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ነሐሴ 06 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት 3 /ሦስት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ከሥራ የተሠናበተው በጥፋቱ ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ ካሣና የስንብት ክፍያ አመልካች ይክፈለው ተብሎ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39 እና 40 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ 2 /ሁለት/ ገጽ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ በመልሣቸውም የተፈፀመ ጥፋት ሣይኖር በሕጉ አግባብ ያለበቂ ማስረጃ ከሥራ የተሠናበትኩ ሆኖ እያለ ካሣና የስንብት ክፍያ ሊከፈል አይገባውም ተብሎ የሰበር ቅሬታ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው ከተባለ የካሣና የስንብት ክፍያ እንዲከፈል መወሰን ሕጋዊነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ውል ግንኙነት የነበረ መሆኑን፣ አመልካች የሥራ ውሉን ማቋረጡንና ያቋረጠበት ምክንያትም ተጠሪ ሠነድ በመደለዝ በሰነዱ ላይ ያለውን የገንዘብ መጠን አበላልጠው በመገኘታቸውና የውሎ አበል ያላግባብ ተጠቅመው መገኘታቸው በመረጋገጡ ስለመሆኑ ነው፡፡ ይኸው የተጠሪ አድራጎት በተገቢው ማስረጃ መረጋገጡንና የሥራ ውሉ የተቋረጠበት መንገድም በሕጉ አግባብ ስለመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ ስንብቱ ከመነሻው ያላግባብ ስለመሆኑ በመግለጽ ለዚህ ችሎት መልስ ሠጥተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ክርክራቸው ሥርዓቱን ተከትሎ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ወይም መስቀለኛ የሰበር መቃወሚያ ሊባል የማይችል በመሆኑ ተቀባይነት ስለሌለው በዚህ የክርክር ደረጃ ሊታይ የሚገባው አይደለም በማለት አልፈነዋል፡፡

በዚህ መዝገብ ወደተያዘው አቢይ ጭብጥ ስንመለስም የቅጥር ውል ሕጋዊ ወይም ሕጋዊ ባልሆኑ ምክንያቶች ሊቋረጥ እንደሚችል፣ ውጤቱም የተለያየ መሆኑን ሕጉ ያስገነዝባል፡፡

የሥራ ውል በሕጋዊ መልኩ ተቋረጠ የሚባውም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24፣ 25፣ 27፣ 28፣ 29፣ 31 እና 32 ድንጋጌዎች መሠረት የቅጥር ውሉ ውጤት እንዳይኖረው ሲደረግ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የሚደረግ የሥራ ውል ማቋረጥ እርምጃ ከሕግ ውጪ ነው፡፡ በእያንዳንዱ የሥራ ውል መቋረጥ ጊዜ አሠሪው በአዋጁ አንቀጽ 12/7/ ላይ በተደነገገው መሠረት የሥራ ልምዱን የሚገልጽ ደብዳቤ የመስጠት ግዴታውን መወጣት ይኖርበታል፡፡ ከክፍያዎች ጋር በተያያዘ ግን የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ሆኖ መገኘት አሠሪው ለሠራተኛው ለመክፈል እንደማይገደድ የአዋጁ አንቀጽ 39 እና 42 እንዲሁም ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ቅርጽና ይዘት ያስገነዝባል፡፡ የሥራ ስንብት ክፍያ አሠሪ ለሠራተኛ ለመክፈል የሚገደደው የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ ሲያቋርጥ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 39/1/ለ/ ድንጋጌ በግልጽ ያሣያል፡፡ ሌላው ሕጋዊ ያልሆነ የሥራ ውል ማቋረጥ ሊያስከትለው የሚችለው ውጤት ካሣ ሲሆን ይህም ሊፈፀም የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 42 ሥር የተመለከተው መመዘኛ ተሟልቶ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕጉ አግባብ ውጪ ስለመሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የካሣ ክፍያ ዓላማም ሕገወጥ እርምጃን መከላከልና የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ የተቋረጠበት ሠራተኛ በተቻለ መጠን ወደነበረበት ቦታ እንዲመለስ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ሕጋዊ የሆነ የሥራ ውሉ የማቋረጥ እርምጃ ካሣን የማስከፈል ውጤት የለውም፡፡ ሲጠቃለልም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው እየተባለ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ የሚከፈልበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ የሰሜን ሸዋ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ በደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07034 ጥር 26 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18364 ግንቦት 22 ቀን 2000 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ የተጠሪ የሥራ ስንብት በሕጉ አግባብ የተደረገ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ የሥራ ስንብት እና የካሣ ክፍያ የሚከፈልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43610

ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጉስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ናይኮን ኃ/የተ/የግ/ማ - ጠ/ማስተዋል ሐብታሙ

ተጠሪ፡- አቶ ሠለሞን ተሠማ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ በክሣቸውም ያለአግባብ ከስራ ስለተሠናበቱ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ካልሆነ ህጉ የሚፈቅደው ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ድርጅቱ ሣይሆን ከስራ ያሠናበታቸው በራሣቸው ፈቃድ ከሥራ በመቅረታቸው ነው ውሉ የተቋረጠው በማለት የተከራከረ ሲሆን ፍ/ቤቱ ተጠሪ በራሳቸው ፍቃድ ነው ስራውን የለቀቁት በማለት ክሱን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሠኝተው ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት የ7 ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ችሎቱም አቤቱታው ለሠበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሠምቷል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ የአመልካች ድርጅት ባለቤት ስልክ ደውለው ከስራ ያሠናበቷቸው መሆኑን ነው የገለፁት በመሆኑም በዚህ መልኩ የስራ ውላቸው መቋረጡን በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም ያለባቸው ተጠሪ ናቸው፡፡ ይህንንም ለማስረዳት ተጠሪ ምስክሮች ቆጥረዋል፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች ግን በተጠሪ የክስ አቀራረብ መሰረት እንዳላስረዱ የሥር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ በስልክ የስራ ውላቸው መቋረጡን አላስረዱም ማለት ነው፡፡ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤትም ቢሆን ስልክ ተደውሎ የተጠሪ የሥራ ውል መቋረጡን ተጠሪ አስረድተዋል አላለም፡፡ ይህም ተጠሪ ክስ የመሠረቱበትን ጉዳይ አለማስረዳታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ይልቁንም ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረቧቸው 3ኛ ምስክር የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ ስልክ ላይ ደውለው የስራ ቦታቸው በመቀየሩ ወደ ተቀየሩበት ቦታ እንዲሄዱና ወደ ቀድሞ ስራ ቦታቸው እንዳይገቡ መከልከላቸውን ነው ያስረዱት፤ ይህ ደግሞ የሚያስረዳው ለተጠሪ በስልክ የተነገራቸው የስራ ቦታቸው መቀየሩን እንጂ የሥራ ውላቸው መቋረጡን አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በስልክ የተገለፀላቸው የሥራ ቦታ ሄደው እንዳይገቡ ወይም እንዳይሠሩ መከልከላቸውን ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ አመልካች ከሥራ ያሠናበታቸው መሆኑን ያለባቸውን የማስረዳት ሸክም ሣይወጡ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የተጠሪ የሥራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 70728 ታህሣስ 28/2001 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 31913 ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. የተጠሪ የሥራ ውላቸው በህገ-ወጥ መንገድ የተቋረጠ መሆኑን ገልፀው ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44033

ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ነ/ፈጅ ወንድሙ መልኬ

ተጠሪ፡- አቶ ይበልጣል አጥናፉ ቀረቡ

ፍ ር ድ

በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ከሣሽ ነበሩ፡፡ በክሣቸውም አመልካች ያለአግባብ ያዛወሯቸው በመሆኑ ቀደም ብሎ ወደነበሩበት የስራ መደብ እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ዝውውሩ ህጋዊ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሎ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የተደረገው ዝውውር ህገ ወጥ ነው በማለት ወደ ነበሩበት የስራ መደብና የስራ ቦታ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ችሎቱም አመልካች ያደረገው ዝውውር ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታውን ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጐ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል፡፡ አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔም ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ተጠሪ በክሣቸው በመ/ቤቱ ውስጥ በደረሰብኝ ድብደባ እንድታረቅ ተጠይቄ ፈቃደኛ ባለመሆኔ ያለአግባብ ወደ ሌላ ሥራ ተዛውሬአለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ተጠሪን ማዛወሩን አልካደም አመልካች የተጠሪ አሰሪ ነው፡፡ አሰሪ ማለት አንድን ወይም ብዙ ሰዎችን ደመወዝ እየከፈለ በእርሱ መሪነት ስራውን እንዲሰሩለት ቀጥሮ የሚያሰራ ግለሰብ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 2/1/ እና 4 ስር መመልከት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አሰሪው ስራውን የሚመራ እንደመሆኑ መጠን አንድ ሰራተኛ የት ቦታ ተመድቦ ቢሰራ ለስራው ይጠቅማል የሚለውን የመወሰን አስተዳደራዊ መብት ሊኖረው ይገባል፡፡ የአሰሪው ስራውን ቅልጥፍና፣ ውጤታማነት፣የኢንዱስትሪ ሰላም ወይም ሌሎች በተለያዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድን ሰራተኛ ከአንድ የሰራ መደብ ወደ ሌላ ወይም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የማዛወር መብቱ ስራ መሪነቱ ወይም አሰሪነቱ የሚመነጭ ነው፡፡ በእርግጥ አሰሪው ይህን የዝውውር እርምጃ ሲወስድ የሰራተኛውን መብትና ጥቅም ሊጠብቅ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ ወደ ሌላ ቦታ የተዛወሩት ደመወዛቸውን ይዘው_ለመሆኑ ክክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ በመ/ቤት ውስጥ በደረሰብኝ ድብደባ ለመታረቅ ባለመፍቀዴ ብቻ ልዛወር አይገባም በማለት ነው የሚከራከሩት ከላይ እንደተመለከተው ግን አሰሪው ለኢንዱስትሪ ሰላም ሲል ወይም ለስራው ይጠቅማሉ ብሎ በሚያምነው ቦታ ላይ የተጠሪን መብት ሣያጓድል ለማዘወር አስተዳደራዊ መብት አለው፡፡ ይህም በአዋጁ የተከለከለ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች የተጠሪ ዝውውር ሕገ-ወጥ ነው ሲሉ የሰጡት ውሣኔ በአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ውስጥ አሰሪው ሊኖረው የሚገባውን አስተዳደራዊ መብቶች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27010 በ27/05/2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 76626 በ20/06/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች የተወሰደው ዝውውር ሕገ-ወጥ ነው በማለት እንዲነሣላቸው ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 42906

ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮ-ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ አ/ማ - ጠበቃ ቴዎድሮስ ኃ/ስላሴ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ ትዕግስት ማሞ (81 ሰዎች) - ወኪል አበበ መገርሳ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥራ ውል መቋረጥን ተከትሎ የቀረበ የልዩ ልዩ ክፍያዎች ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው የሥራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው የጨርቃጨርቅ ፋብሪካው ከመንግሥት እጅ ወጥቶ ወደግል በመዛወሩ ነው፡፡ ተጠሪዎች ከሥራ የተሰናበቱት መንግስት ከ20 ዓመት በላይ ያገለገሉና ዕድሜአቸው 45 ዓመት የሆኑ ሠራተኞች በጡረታ እንዲገለሉ በመወሰኑ ነው፡፡ ተጠሪዎች ክስ የመሠረቱት የሥራ ውሉ እንደሚቋረጥ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ስላልተሰጠን የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ይገባናል፤ ሠርተን ያልተከፈለን ደመወዝ ስላለና ይህም በጊዜው ስላልተከፈለን ከነመቀጫው ይከፈለን፣ ሠራተኛ በጡረታ ሲገለል የሚሰጡ ጥቅማጥቅሞች ይሰጡን፣ ላልተጠቀምንበት የዓመት ፈቃድ እረፍት ጊዜ ገንዘብ ይከፈለን በማለት ነው፡፡

አመልካች በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሾች በመንግስት በጡረታ እንዲገለሉ እንደተወሰነ ሁሉንም በአንድነት ሰብስበን ከማስታወቃችንም በላይ፤ እያንዳንዱን ፎርም በማስሞላትም ከደጋፊ ሰነድ እና ፎቶግራፍ ጋር አያይዘን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ልከናል፡፡ የመጨረሻው ውሳኔ(ውጤት) እስኪደርሰን ድረስም ከሣሾች በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ አድርገናል፡፡ በዚሁ መሠረት እየሠሩና እየተጠባበቁ ሳለ ከአንድ ዓመት በኋላ የመጨረሻው ውሳኔ ስለደረሰ ይህንኑ በፋብሪካው የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ አሳውቀናል፡፡ የሠራተኛ ማህበሩም ይህንኑ አረጋግጦ ገልጾአል፡፡ በመሆኑም አላሳወቃችሁም የምንባልበት ምክንያት የለም፡፡ ቀሪ ደመወዝ እና በሕጉ መሠረት ሊከፈሉ የሚገባቸውን ክፍያዎች ፔይሮል አዘጋጅተን እንዲወስዱ ብንጠይቅም ከሣሾች ለመቀበል ፈቃደኛ ስላልሆኑ ሳይከፈሉ ቀርተዋል፡፡ ሌሎች ጥቅማጥቅሞች (በጡረታ በመገለል ምክንያት) ሊከፈሉ የሚችሉት በፋብሪካው የህብረት ስምምነት መሠረት ሠራተኛው 60 ዓመት ሞልቶት ጡረታ ሲወጣ ነው፡፡ ከሣሾች በጡረታ የተገለሉት በመንግስት ውሳኔ በልዩ ሁኔታ በመሆኑና ይህም የህብረት ስምምነቱ ሥራ ላይ ሲውል አሠሪውና ሠራተኛው ያላዩት ያልተደራደሩበትና ያልተስማሙበት በመሆኑ ልንገደድበት አንችልም፡፡ በማለት ተከራክሮአል፡፡

ክሱ የቀረበለት በምስራቅ ሸዋ ዞን የሎሜ ወረዳ ፍ/ቤትም የግራቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ የተጠሪዎችን ጥያቄ በሙሉ በመቀበል ወስኖአል፡፡ ከዚህ በመቀጠል አመልካች ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ ተፈጽሞአል የሚለውን የሕግ ስህተት በመግለጽ እንዲታረምለት ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው።

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ተመልክተናል። ከዚህም እንደተገነዘብነው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የነበረው ውል የተቋረጠው ተጠሪዎች በመንግስት ውሳኔ መሠረት በልዩ ሁኔታ በጡረታ በመገለላቸው መሆኑን፣ ይህም ውሳኔ ከአንድ ዓመት በፊት ተጠሪዎች እንዲያውቁት ተደርጎ የጡረታ ፎርም ሞልተውና ፎቶግራፋቸውን ሰጥተው ውጤቱን ሲጠባበቁ የቆዩ መሆኑን በመጨረሻም ተጠናቆ በመድረሱ አመልካች ይህንኑ በማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፉንና የሠራተኛ ማህበሩም ይህን ያረጋገጠ ስለመሆኑ አላከራከረም። ተጠሪዎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለመጠየቅ በዋቢነት የጠቀሱት የህብረት ስምምነት ድንጋጌም ጥቅማጥቅሞቹ ሊሰጡ የሚችሉት ሠራተኛው 60(ስድሳ) ዓመት ሞልቶት ጡረታ ሲወጣ ነው በሚል የተደነገገ ስለመሆኑም አከራካሪ ሆኖ አልተገኘም። አከራካሪ ሆነው የተገኙት አልተከፈለም የተባለውን የስምንት ቀን ደመወዝ አከፋፈል፣ ስለማስጠንቀቂያ አሰጣጥ እና ጥቅማጥቅሞቹ የሚከፈሉበትን አግባብ የሚመለከቱ ነጥቦች ናቸው።

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የሥራ ውሉ ከመቃረቡ ከአንድ ዓመት በፊት ተጠሪዎች በጡረታ እንደሚገለሉ (የስራ ውሉ በዚህ ምክንያት እንደሚቋረጥ) አውቀው ፍጻሜውን ሲጠባበቁ ቆይተዋል። በሥር ፍ/ቤቶችም እንደተገለጸው ማስጠንቀቂያ አስፈላጊ የሚሆነው ሠራተኛው የሥራ ውሉ እንደሚቋረጥ አውቆ በራሱ በኩል አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ እንዲችል ነው። ከዚህ አንፃር የተጠሪዎችን ሁኔታ ሲታይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ከተቀመጠው ጊዜ በላይ አግኝተዋል። በአዋጁ አንቀጽ 35 እንደተመለከተው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ከሦስት ወር በላይ የሚረዝምበት ሁኔታ የለም። ማስጠንቀቂያው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ በእጁ ሊሰጠው ይገባ ነበር የሚለው የሥር ፍ/ቤቶች አካሄድም እንዲሁ በደፈናው ትክክል ነው የሚባል አይደለም። ዋናው መታየት ያለበት ሠራተኛው የሥራ ውሉ እንደሚቋረጥበት በትክክል እንዲያውቅ መደረግ አለመደረጉን ነው። በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች የሥራ ውላቸው እንደሚቋረጥ በሚገባ እንዲያውቁ ተደርጎአል ብቻ ሳይሆን ፍጻሜውንም ሲጠባበቁ ቆይተዋል። ውጤቱ እንደመጣም ይኸው ተገልጾላቸው እንዲሰናበቱ ተደርጎአል። በመሆኑም የማስጠንቀቂያ ስርዓት አልተፈጸመም በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተደረሰው መደምደሚያ ሕጉን የተከተለ አይደለም።

ቀጥለን ያየነው አከራካሪ ነጥብ ከቀሪ ደመወዝ(የሳምንት ቀን) እና የተወሰኑ ሠራተኞች የዓመት እረፍት ፈቃድ ክፍያ አከፋፈል የሚመለከት ነው። ይህ ገንዘብ በእርግጥም ሊከፈል እንደሚገባ አመልካችም ያምናል። ክፍያዎቹን አዘጋጅቶ እንዲወስዱ ጠይቆ እንደነበር፤ ነገር ግን ተጠሪዎች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ሌሎች ጥቅሞች አብረው ካልተከፈሉን ይህን ብቻ አንወስድም በማለታቸው ሳይከፈል መቅረቱን በመግለጽም ተከራክሯአል። በበኩላችንም ከአጠቃላይ የክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደቻልነው ገንዘቡ ሳይከፈል የቀረው ተጠሪዎች ለመውሰድ ባለመፈለጋቸው ነው። የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ሌሎች ጥቅሞችም አብረው እንዲከፈሉዋቸው ተጠሪዎች ፍላጎት ቢሆንም አመልካች እነዚህን ክፍያዎች የመክፈል ግዴታ የሉብኝም የሚል ክርክር ስላነሳ ተጠሪዎች ስለፈለጉ ብቻ መክፈል ነበረበት ሊባል አይችልም። የሥር ፍ/ቤቶች ግን የተጠሪዎችን ጥያቄ በመቀጠል በአዋጁ አንቀጽ 38 መሠረት ክፍያው ለዘገየበት በሚል ለእያንዳንዱ ተጠሪ የ3(ሦስት) ወር ደመወዝ በተጨማሪ እንዲከፈል ወስነዋል። በእኛ እምነት ይህ አካሄድ የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም። ተጠሪዎች ሌሎቹን ክፍያዎችም የምናገኝበት የሕግ ምክንያት አለ ካሉ አሁን እንደሚያደርጉት መከራከር ሲገባቸው ሌላውን አንወስድም ማለታቸውም አግባብ ነው አንልም። በመሆኑም አመልካች ለገንዘቡ በጊዜው አለመከፈል ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም።

በመጨረሻ የተመለከትነው በጡረታ ስለተገለልን በህብረት ስምምነቱ መሠረት የሚሰጡ ጥቅሞች እና ክፍያዎች ሊሰጡን ይገባል በማለት ተጠሪዎች ያነሱት ክርክር ነው። በዚህ ረገድ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠው ህብረት ስምምነቱ የሚናገረው 60(ስድሳ) ዓመት ሞልቶት በጡረታ ስለሚገለል ሠራተኛ እንደሆነ ነው። 60 ዓመት ከመሙላቱ በፊት በመንግስት ውሳኔ መሠረት (በልዩ ሁኔታ) በጡረታ ስለሚገለል ሠራተኛ በሚመለከት የሚለው ነገር የለም። ይሁንና የተጠሪዎች ክርክር በጡረታ ከመገለል ጋር ተያይዞ የተነሳ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ ብቻ በመመልከት የተጠሪዎችን ጥያቄ ተቀብለዋል። አመልካች ግን በዚህ አይስማሙም። ያነሳው ክርክርም ቀደም ሲል ተገልጾአል። በመሆኑም እዚህ ላይ ሊመለስ የሚገባው ጥያቄ ተጠሪዎች ይጠቅመናል በማለት የጠቀሱት የህብረት ስምምነት ለተያዘው ክርክር አወሳሰን አግባብነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው እንደሆነ እንገነዘባለን።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የህብረት ስምምነት በአሠሪና ሠራተኛ(ኞች) መካከል ድርድር ከተካሄደ በኋላ የተደረሰውን የሁለቱ ወገኖች ስምምነት የሚይዝ ሰነድ ነው፡፡ ይህ ሰነድ የሁለቱም ስምምነት የያዘ እና ያፀደቁትም በመሆኑ የሚገዙበትና የሚተዳደሩበት ውላቸው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ በአመልካች ክርክር እንደተመለከተው የህብረት ስምምነቱ ሠራተኛው 60 ዓመት ሳይሞላው በመንግስት ውሳኔ መሠረት (በልዩ ሁኔታ) በጡረታ ሲገለል የሚያገኘውን ጥቅም በሚመለከት ስምምነት የተደረገበት አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪዎች አመልካችን የሚያስገድዱበት የህብረት ስምምነት ወይም ውል የለም ማለት ነው፡፡ በክርክሩ እንደተገለጸው በልዩ ሁኔታ (የ60 ዓመት መመሳት ሳይጠበቅ) በጡረታ የተገለሉት ሠራተኞች ወደ 145 የሚጠጉ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ በህብረት ስምምነቱ ያልታየ እና አመልካችም ሆነ ሠራተኞቹ ይሆናል ብለው ያልጠበቁት ነው፡፡ በአመልካች ላይ ሚያስከትለው ወጪም ከፍተኛ ነው፡፡ በህብረት ስምምነቱ አስቀድሞ ስምምነት ተደርጎበት ቢሆን ኖሮ አመልካችም ከዚህ አንጻር ተዘጋጅቶ ይጠብቅ ነበር፡፡ ይህ እንግዲህ በአፈጻጸም ረገድ የሚታይ ችግር ሲሆን ዋናው ግን ሁለቱን ወገኖች የሚገዛ በህብረት ስምምነቱ የተቀመጠ ድንጋጌ ስለሌለ አመልካች የተጠየቀውን ክፍያ እና ጥቅማጥቅሞች እንዲሰጥ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች ሊከፍል የሚገባው የሥራ ውሉ ከመቋረጡ በፊት ለተሠራ ሥራ ያልተከፈለ ቀሪ ደመወዝ ካለ እና የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ላላቸው ሠራተኞች (ተጠሪዎች) ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን የሎሜ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11855 ግንቦት 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የምስራቅ ሸዋዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 16691 ታሕሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለዘገየበት ጊዜ እና በጡረታ መገለልን መሠረት በማድረግ የተጠያቂ ክፍያዎች እና ጥቅማጥቅም ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባው ውሉ ከመቋረጡ በፊት ለሠሩት ሥራ ያልተከፈለ ቀሪ ደመወዝ እና ያልተጠቀሙበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ክፍያ ብቻ ነው፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42075

ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አፍሪካዊት የህንፃ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- እነ አቶ እንድሪስ ዓሊ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በአማራ ክልል የደቡብ ወሎ ዞን ኮንቦልቻ ወረዳ ፍርድ ቤት እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡

ክርክሩ የስራና ሰራተኛ ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች የሚሰራው የኮንስትራክሽን ስራ በከፊል የተጠናቀቀ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎች ከስራ አሰናብቷል፡፡ ተጠሪዎች የስራ ውላችን አላግባብ ተቋርጧል በሚል ክስ አቅርበዋል፡፡ የኮንቦልቻ ወረዳ ፍርድ ቤት የተጠሪዎች ውል አላግባብ ተቋርጧል በማለት ተጠሪዎች የጠየቁትን የተለያዩ ክፍያዎች አመልካች እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ታህሣስ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የኮንቦልቻ ወረዳና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪዎች የተሰናበቱት የግንባታ ስራው እየቀነሰ በመሄዱ ነው፡፡ ተጠሪዎችን ከስራ ያሰናበትኳቸው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24 እና 30 መሰረት በመጨረሻ ጊዜ የሰሩበትን ደመወዝ የእረፍት ሰአት ክፍያና ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ በመለወጥ በመክፈል ነው፡፡ ስለዚህ ከአዋጁ ድንጋጌ መንፈስና ዓላማውም በአንቀጽ 38 እና አንቀጽ 40 እና ሌሎች ድንጋጌዎች መሰረት ልዩ ልዩ ክፍያ እንድንከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ አመልካች የሰሩበትን ደመወዝ የትርፍ ሰአት ክፍያና የአመት እረፍት በገንዘብ በመለወጥ የከፈላቸው መሆኑን ማስረጃ አቅርበን እያለ እና ተጠሪዎችም ይህንን አምነው በክሳቸው ገለፀው እያለ ለእያንዳንዳቸው የአንድ ወር ደመወዝ እንድንከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው አመልካች ያሰናበተን ያለምንም ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ስንሰራ የነበረበት ወር ሣይጠናቀቅ የሰራንባቸውን ቀኖች እና የአመት እረፍት ፈቃድ ክፍያ ከፍሎ አሰናብቶናል፡፡ ስራውን በተመለከተ በስምንት ብሎክ ሶስቱ ተጠናቅቀው አምስቱ ገና ከግንባታ ላይ እንደሆኑ አስረድተናል ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት በጽሑፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ያከናውን የነበረው የግንባታ ስራ መጠን እየቀነሰ እና እያለቀ መሄዱን ተጠሪዎች አልካዱም፡፡ አመልካች በኮንቦልቻ ለሚገነባው ወሎ ዮኒቨርሲቲ ስምንት ብሎክ መገንባት ጀምሮ ሶስቱ ብሎክ ስራቸው ሙሉ በሙሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠናቀቀ መሆኑንና አምስቱ ብሎኮች እየተሰሩ መሆኑን ተጠሪዎች ገልጸዋል፡፡ ይኸም አመልካች ተጠሪዎችን ሲቀጥር የነበረው ስራ የቀነሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ተጠሪዎች ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩት በአናጢነት በድንጋይ ጠራቢነት እና በሰአት ተቆጣጣሪነት የነበረ መሆኑን አመልካችና ተጠሪዎች አልተካካዱም፡፡ ስለዚህ ተጠሪዎች ይሰሩበት የነበረው ብሎክ ስራ ሲጠናቀቅ አመልካች ተጠሪዎችን ማሰናበቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 30 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የተፈጸመ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የኮንስትራክሽን ስራ የሚሰራ ድርጅት በመሆኑ ማስጠንቀቂያ የመስጠትና ሌሎች የቅነሣ ስነ ሥርአቶችን ሣይገልጽ የስራው መጠን ሲቀንስ ወይም ስራው ሲያልቅ ሰራተኞችን ማሰናበት የሚችል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 30 የኮንስትራክሽን ዘርፍ የስራ ባህሪ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሕግአውጭው በልዩ ሁኔታ ደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ ሣይሰጠን ነው ያስናበተን በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ተጠሪዎች ከስራ ሲሰናበቱ የሰሩበትን ደመወዝ እና የአመት እረፍት በገንዘብ ተሰልቶ የተከፈላቸው መሆኑን ለሰበር በሰጡት መልስ የገለፁ ሲሆን ቅሬታቸው በአግባቡ አልተሰላም የሚል ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተ የተነሣው ክርክር የፍሬ ጉዳዩ ክርክር በመሆኑ በዚህ ችሎት የሚስተናገድ አይለም፡፡ ተጠሪዎች ከስራ ሲሰናበቱ የሰሩባቸው ቀናቶች ደመወዝና የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ የተከፈላቸው መሆኑን አምነው በሚከራከሩበት ሁኔታ አመልካች ለተጠሪዎች የአንድ ወር ደመወዛቸውን እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 30 መሰረት ያከናወነውን የስራ ስንብት ህገ ወጥ የስራ ስንብት ነው በማለት ለተጠሪዎች ልዩ ልዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአማራ ክልል የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኮንቦልቻ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ያሰናበተው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪዎች ምንም አይነት ክፍያ የመፈጸም ግዴታ የለበትም ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39808

ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ናዝሬት ሳሙና ፋብሪካ

ተጠሪ፡- ዘውዴ ኃ/ማሪያም /አቶ/

መዝገቡን መርምረን የሚተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተደረገውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ስራዬን በገዛ ፈቅዴ ለቅቄ ስራ ያቋረጥኩ ስለሆነ በሕጉ መሰረት የስንብት ክፍያና የአገልግሎት ክፍያ ይከፈለኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ በፋብሪካው ውስጥ ከ20/ሃያ/ ዓመት በላይ ያገለገለና በፈቃዱ ስራውን የለቀቀ በመሆኑ እድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ አገልግሎት አበል ለእድሜልክ ማግኘት ይችላል፡፡ ስለዚህ የአገልግሎት ክፍያ የማግኘት መብት የለውም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያሰሰተናገደው ፍ/ቤትም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣የአመልካች ክርክር በመቀበል ተጠሪ የጠየቀውን ክፍያ ማግኘት አይችልም በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2000 ዓ.ም በዓፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ባለመቅረቡ ክርክሩ የተሰማው እሱ በሌለበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ የጡረታ የተጠበቀ ቢሆንም፣የስንብት ክፍያም ይከፈለው በሚል የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው ተጠሪ በራሱ ፈቃድ ስራውን በመልቀቁ ምክንያት ነው፡፡ ተጠሪ ወደ ክስ ያመራውም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39 መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ ለመክፈል አመልካች ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኙቱ ነው፡፡ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያው መክፈል የለበኝም የሚለው ተጠሪ ከ20/ሃያ/ ዓመት በላይ ያገለገለ በመሆኑ በጡረታው ሕግ መሰረት የጡረታ አገልግሎት አበል የማግኘት መብት አለው የሚል የመከራከሪያ ነጥብ በማንሳት ነው፡፡ በእርግጥም የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለውና በጡረታ ሕግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ እድሜ ደርሶ ከስራ የተገለለ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2)(ሰ) ተመልክቶአል፡፡ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥብት የስራ ስንበት ክፍያ የሚፈጸምለት ሊቋቋመው የማይችል ድንገተኛ የገንዘብ ችግር እንዳይገጥመው ነው፡፡ ይህ ከሕጉ በስተጀርባ ያለው አስተሳሰብ ወይም ምክንያት ሲሆን በሕጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደተመለከተው ሰራተኛው የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን የጡረታ መብት ካለው ግን የስራ ውሉ ቢቋረጥም፤ ገንዘብ ማግኘቱን ስለሚቀጥል (ስለቀጠለ) የስራ ስንብት ክፍያው አይከፈለውም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የስራ ውሉን ያቋረጠው በፋብሪካው ውስጥ ከ20/ሃያ/ ዓመት በላይ ካገለገለ በኋላ ነው ቢባልም፤በጡረታ ሕጉ መሰረት የጡረታ እድሜ ላይ ስለመድረሱና የጡረታ አበል የሚያገኝ ለመሆኑ አመልካች አላስረዳም፡፡ ተጠሪ የስራ ውሉን እንዳቋረጠ የጡረታ አበል ማግኘቱን ይቀጥላል የሚል ክርክርም ሆነ ማስረጃ ከሌለ ደግሞ ለስራ ስንብት መከፈል መሰረት የሆነውን በሕጉ በስተጀርባ ያለውን ምክንያት መሰረት በማድረግ የስራ ስንብቱን ክፍያ ማስከፈል የግድ ይሆናል፡፡ ሕጉ በዚህ መልክ ካልተተረጐመም ሰራተኛው ለድንገተኛ የገንዘብ ችግር ማጋለጥ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ለወደፊት የጡረታ አበል ያገኛል በሚል መነሻነት አመልካች ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል የስራ ስንብት ክፍያው እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ ይህ ውሳኔ በበኩላችንም የምንደግፈው ነው፡፡ ውሳኔውን የደገፍነው ሕጉ ከላይ በተገለጸም አይነት መተርጐም ያለበት መሆኑን ስለምናምን ነው፡፡ ስለዚህም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሕጉን ትርጉም በሚፈለገው መጠን ባያስቀምጥም፤የደረሰበት መደምደሚያ ግን ትክክል ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06414 ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. ተጠሪ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ክፍያው ይፈጸምለት ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

ት እ ዛ ዝ

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 42901

ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አመልካች፡- የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት - ነገረ ፈጅ አቶ ጌታሁን ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ንግሥት ለጥይበሉ - ጠበቃ አቶ አበራ ታደሰ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የክርክሩ ምክንያት የሥራ ክርክር ጉዳይ ሆኖ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበችው ክስ ያለአግባብ የሥራ ውል የተቋረጠ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ሥራ እንድመለስ አሊያም ተገቢ ክፍያዎች ተከፍሎ እንድሰናበት ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች ከሳሽ የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ አይደለችም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ወጪ ነው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎአት ወደ ሥራ ትመለስ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ጥር 20 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበውን ቅሬታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር ሰምተናል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ የቀረበው ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው ወይንስ አይደሉም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር በመሆኑ ይህንኑ ከግራ ቀኙ ክርክርና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር መረዳት የተቻለው ተጠሪ የድርጅቱ የሀገር ውስጥ ዕቃ ግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ በመሆን እንዲሁም በተጨማሪነት የውጪ ሀገር ዕቃ ግዥ ዋና ክፍልና የሽያጭ ዋና ክፍልን የሚያካትተውን የንግድ መምሪያ ኃላፊነትን ደርበው ይሠሩ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በእነዚህ መደቦች በኃላፊነት ስለመሥራታቸው አልተካደም፡፡ የሥራ መደቡ ዋና ተግባራት ምንድናቸው የሚለው ከተጠሪ የሥራ መዘርዝር /job description/ ሲታይ በአጠቃላይ በድርጅቱ መመሪያ መሠረት ማስተባበር፣ መምራት፣ ማደራጀት እና መቆጣጠር እንዲሁም ዕቅድና በጀት ዝግጅት ላይ መሳተፍ እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን በድርጅቱ ጎብረት ስምምነት አንቀጽ 3 ንዑስ ቁጥር 3.3 እንደተመለከተው ስምምነቱ የዋና ክፍሎችንና የማምረቻ ኃላፊዎችን እንደማይጨምር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪም ከሌሎች ሠራተኞች በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ የድርጅቱ ኃላፊነት የተሠጠች መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ ሥራን የማቀድ፣ የመምራት፣ የመቆጣጠር፣ የማደራጀትና የማስተባበር ተግባራትን የሚያከናውኑ መሆኑን ከክርክሩም ሆነ ከቀረቡ ሰነዶች መረዳት ተችሏል፡፡ ስለዚህ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2 እንደተሻሻለው ተጠሪ ከሥራ ተግባራቸው አንፃር የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ አይደሉም፡፡ በአዋጁ ለሥራ መሪ የተሠጠው ትርጉም "የሥራ መሪ የሚባለው በሕግ ወይም እንደ ድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሠሪው በተሠጠው ውክልና ሥልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈፀም ከዚህ በተጨማሪ ወይም እነዚህኑ ሳይጨምር ሠራተኛን መቅጠር ማዛወር የማገድ የማሰናበት የመመደብ ወይም የሥነ ሥርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውንና የሚወስን ግለሰብ ነው ይላል፡፡" ከዚህ አንፃር የተጠሪ የሥራ ተግባር በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የድርጅቱን ዋና ክፍል ሥራ በኃላፊነት መምራት፣ ማደራጀት መቆጣጠርና ማስተባበር ከመሆኑ አንፃር በሕጉ ትርጉም ከተሠጠው የሥራ ዘርፍ የሚመደቡ በመሆናቸው የሥራ መሪ ናቸው እንጅ፤ ሠራተኛ አይደሉም፡፡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የቦርድም፣ የማናጅመንት አባላት ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ እኔን አይጨምርም በማለት ከተጠሪ የቀረበውን ክርክር በተመለከተ መመሪያው ለቦርድና ማናጅመንት አባላት ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ አስመልክቶ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ እንጅ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚ ስለማይሆን ክርክሩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱ ምክንያቶች እና በሰበር መ/ቁጥር 40055 በተመሳሳይ ጉዳይ ትርጉም የተሠጠበት በመሆኑ ተጠሪ የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ ባለመሆናቸው ጉዳያቸው በሥራ ክርክር ችሎት ክስ ለማቅረብም ሆነ ክርክር ለማካሄድና ዳኝነት ለማግኘት የሚችሉበት የሕግ አግባብ ስለሌለ የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሳኔ በሕግ ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 13197 በ18/12/2000 ዓ.ም እንዲሁም ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 73934 በ18/5/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆናቸው ጉዳያቸው በሌላ ሕግ ከሚታይ በቀር በሥራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይችልም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39471

ሐምሌ 29 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች ፡- ኤርሚያስ ሙሉጌታ - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- በከልቻ ትራንስፖርት አ/ማ - ይልማ ገመቹ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር አቤቱታ አመልካች በተጠሪ ተቀጥሮ በሾፌርነት ሲሠራ በነበረበት ጊዜ ከጅቡቲ አስጭኖ ከመጣው የአርማታብረት ውስጥ 20 ጥቅል ወይም 305 ኩንታል አጉድሎ ተገኝቶአል በሚል ተጠሪ የመሠረተውን ክስ መነሻ በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ የብረቱን ዋጋ በማስላት እንዲከፈለው አመልካችንና ዋሱ ነች የተባለችውን ሰው አጣምሮ የከሰሰ ሲሆን፣ ተከሣሾችም የመከላከያ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ አመልካች ብር 11,250(አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ከወለድ እንዲሁም ከዳኝነትና ከብር 300.00(ሦስት መቶ ብር) ኪሣራ ጋር ይከፈል፤ እሱ ባይከፍል ዋሱ ትክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ እንደአግባቡ ይግባኝ እና አቤቱታ የቀረበላቸው የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት እና የሰበር ችሎትም ውሣኔውን አፅንተዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ ተፈፅሞአል የሚለውን የሕግ ስህተት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም ይህን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉድለት ተጠያቂ ነው መባሉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ነጥብ ላይ በመመስረት ነው፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት ከተደረገው ክርክር በተለይ መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ የሚቃወምበት ዋናው ምክንያት ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር በኔ በኩል ጉድለት እንዳልተገኘ ተረጋግጦ ውሣኔ ተሰጥቶአል፡፡ ክርክሩ የተካሄደው ተጠሪ ጉድለቱን መሠረት በማድረግ የሥራ ውሉ በማቋረጡ ወደ ሥራዬ እንድመለስ በሥራ ክርክር ችሎት ክስ በመመሥረቴ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የስራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል ጥፋት እንዳልተፈፀመ አረጋግጦ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ በመሆኑም በተመሣሣይ ጉዳይ በድጋሚ ክርክር ሊደረግ አይችልም፡፡ በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ ቀደም ሲል ቀርቦ ክርክር የተደረገበት ጉዳይ የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ክርክር ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች የሥራ ውል ሊያቋርጥ የሚችል ጥፋት ፈፅሞአል ወይስ አልፈፀመም የሚል ነው፡፡ በአሁኑ ጉዳይ የተያዘው ጭብጥ ግን አመልካች በክሱ የተመለከተውን ገንዘብ ለመክፈል ይገደዳል ወይስ አይገደድም? የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩቹ ተመሣሣይ አይደሉም በማለት ተከራክሮአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደምንመለከተው በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባው ጭብጥ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠርተው የገንዘብ ይከፈለኝ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 ከተቀመጠው ድንጋጌ አንፃር ታይቶ ውድቅ መሆን የሚገባው ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በፍሬ ነገር ረገድ የቀረበው ክርክር እንደሚያመለክተው ለሁለቱም ክርክሮች መነሻ የሆነው አመልካች ያሽከረክረው በነበረው መኪና ላይ ተጭኖ የነበረው የአርማታ ብረት ጎድሎ ተገኝቶአል የሚለው ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን የመጀመሪያው የሥራ ክርክር በመሆኑም የታየው፤ በስራ ክርክር ችሎት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በፍታብሔር ችሎት ነው የታየው ይህ በመሆኑም ነው በአመልካች የተነሣው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 ላይ የተመሠረተው መቃወሚያ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚል አከራካሪ ጭብጥ ሊያዝ የተቻለው፡፡

ይህ የሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ. 36710 ተመሣሣይ ክርክር ቀርቦለት በሕጉ አተገባበር ረገድ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡ በዚህም በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚካሄደው የሥራ ክርክር የሚያዘው ጭብጥ አሠሪው የገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ /ክስ/ በሠራተኛው ላይ ባቀረበ ጊዜ ከሚያዘው ጭብጥ ጋር አንድ አይነት አይደለም እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በመጨረሻም እንደአሁኑ አመልካች በአሠሪው በጉድለት ይፈለጋል የተባለውን ገንዘብ እንዲከፍል ክስ የቀረበበት ሠራተኛ ቀደም ሲል ተካሂዶ የነበረውን የሥራ ክርክር መሠረት በማድረግ ያቀረበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 ላይ የተመሠረተው መቃወሚያ ውድቅ አድርጎአል፡፡

የሰበር ችሎቱ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በተመሣሣይ ሁኔታ በተሰየመው ችሎት እስካልተለወጠ ድረስ በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው የፌዴራል ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/1/ ተደንግጎአል፡፡ በሰበር መ.ቁ. 36710 የተሰጠው የሕግ ትርጉም አልተለወጠም፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ በቀረበው ክርክርም የተለየ የሕግ ትርጉም የሚሰጥበት አግባብ የለም፡፡ አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝበት ምክንያት የለም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 04076 ሚያዝያ 5 ቀን 99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ፣ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 53326 ህዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 61371 ሚያዝያ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቶዋል፡፡
2. አመልካች በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 18419

ይንበት 4 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረ□ሐ□ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ደ□ት□□ ምህረቱ

መስፍን እቁበዮናስ

□/ት ሃ□ት መለሠ

አመልካች፡- ሐመረ□ርቅ ቅ/ማርያም ቤ/ክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ ጽ/ቤት

መልስ ሰጭዎች፡- 1. □□ቆን ምህረት ብርሃን

2. አጋፋሪ አብርሃም ታደሰ

3. ዲያቆን አስራት □/ትንሣ□

4. ዲያቆን ገዛኸኝ ከበደ

5. □□ቆን ስመኘ□□ ደርማ□

6. ዲያቆን ዓለማየሁ ሞገስ

□ ር □

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበ□□ □θ□ራል □መደመሪ□ ደረየ □/በት መ/ሰጭዎች በአመልካች ቤተክርስቲያን □□ስጨ መንፈሣዊ አገልግሎት ተቀጥረን ስናገለግል ከቆየን በኋላ አመልካች ሕገ-□ጨ በሆነ መንገድ ከስራ ያሰናበተን በመሆኑ□□ድ ስራ እንድንመለስ ይ□ሰንልን በሚል ባቀረቡት ክስ የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎችን ተፈፃሚ በማድረግ ስንብቱ ሕገ-□ጨ ነ□□ በማለት መ/ሰጭዎች ወደስራ እንዲመለሰ□ □ሰ□ ውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀናው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነ□□። ይ□□ዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰ□ው ትእዛዝ መሠረት መ/ሰጭዎች የአመልካች አቤቱታ ደርሷቸ□□ መልስ □ሰ□□ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጓል።

በጉዳዩ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት የሕግ ነጥብ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 3(3)(ለ) መሠረት የሚኒስትሮች ምክር በ□ት ለ□□□ው የሚችለው ደንብ የኃይማኖት ተቋማት መንፈሣዊ አገልግሎት ከሚሰ□□ሰራተኞቻቸ□□ጋር □ላቸ□□ን □ስራ ይንኘ□ቶችም ለ□ ምር □ችላል? □ይስ አይችልም? የሚለው በመሆኑ ችሎቱም ነጥቡን መርምሯል። አዋጅ ቁ.42/85 በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተሻረ ቢሆንም ነጥቡን በሚመለከት ሁለቱ አዋጆች አንድ ዓይነት ድንጋጌዎች የያዙ በመሆኑ ችሎቱ የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎች መሠረት አድርጎ በተጠቀሰ□□ ነጨበ ላ□ □ማሸ□ው የሕግ ትርጉም ለአዋጅ ቁ. 377/96 □ንጋጌዎችም አግባብነት ያለ□□ነ□□።

ይህ ችሎት በዚህ ጉዳይ የሕግ ትርጉም ለሚሰጥበት ከላይ ለተመለከተ□□ ነጨበ ቀጨተኛ አግባብነት ያለው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 3 ነው። ይኸው አንቀጽ አዋጁ በንዑስ አንቀጽ 2 ከተመለከቱት በቅጥር ላይ ከተመሠረቱት የስራ ይንኘ□ቶች □□□ በሰራተኛና በአሰሪ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሠረተ የስራ ግንኙነት ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን ይደነግጋል። የኃይማኖት ተቋማት መንፈሣዊ ተግባር ከሚያከና□ነ□ ሰራተኞች ጋር ያላቸ□□ □ስራ ይንኙነት አዋጁ ተፈፃሚ አንደማይሆንባቸ□ በአንቀጽ 3(2) ከተዘረዘሩት የስራ ግንኘ□ቶች □ውጥ ያልተካተተ ሲሆን ይልቁንም የአዋጁ አንቀጽ 3(3)(ለ) □ኃ□ማኖት □ይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚመሠርቱት የስራ ግንኙነቶች ላይ አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ለ□ስን ይችላል በሚል ይደነግጋል። የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በአዋጅ ቁ. 42/85 መሠረት ለማ□□ሦነ□ስ□ ው በአንቀጽ 3(3)(ለ) መሠረት የተጠቀሰ□ት □ር□ቶች በማ□መሠረቱት □ስራ ይንኙነት አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እስካላ□□ □ረስ □ር□ቶቹ በማ□መሠረቱት □ስራ ይንኙነቶች ላይም አዋጁ ተፈፃሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆናል በማል ነ፡፡ ይህም በስር ፍ/ቤት ለአንቀጽ 3(3)(ለ) ተሰ ው ትርጓሜ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኃይማኖት ድርጅቶች መንፈሣዊ አገልግሎት ከሚሰ ሰራተኞቻቸ ጋር ባላቸ ስራ ደንኙነቶች ላይ የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ እንዳይሆን በደንብ ሊ ስን ይችላል የሚል ድምዳሜን መሠረት ያደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ አተረጓጎም የሕጉን መንፈስ ተከትሎ የተሰጠ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር የአሰሪና ሰራተኛ አዋ ማሸ ናቸ ን ስራ ደንኘት ደ ያች መመልከት የግድ ይላል፡፡

የአሰሪና ሰራተ አዋጅ የስራ ል ስለማመሰረትበት ሀ ታ ስራ ውሉ ስለሚቆይበት ጊዜ፤ የሰራተኛውና የአሰሪ መብትና ደ ታ ስራ ደንኘት ስለማ ረጨቸ ውስን ሁኔታዎች፣ የስራ ውሉ ሕጋዊ ወይም ሕገ- ጨ በሆነ መንደ በሚቋረጥበት ጊዜ ስለሚከተሉ ውጤቶች የያዘ ሆኖ ይታያል፡፡ በአጠቃላይ ሕጉ ከአሰሪና ሰራተ ደንኘት ጋር ተ ኛነት ላቸ፡ ጉዳዮችን በአንዳንድ ሁኔታዎች ከሚያጋጥሙ ልዩ ጉዳዮች በቀር አካቶ የያዘ መሆኑን መረ ት ችላል፡፡

ከላይ የተመለከቱት ከአሠሪና ሠራተ ደንኘት ጋር ተ ኛነት ላቸ፡ ነጥቦች መንፈሣዊ አገልግሎትን በሚመለከት ኃ ማኖት ተ ማት በማመሠርተቸ ሥራ ደንኘቶች ስጠም ማከሰ በሆንም በለለች ስራ ደንኙነቶች ከሚያጋጥሙበት አኳኋን ለየት ባለ መንገድ የሚያጋጥሙ ሁኔታዎችም አሉ፡፡ ምክንያቱም በአንድ የኃይማኖት ተቋም ስጨ ለመሠረት ማችል ተለ ሥራ ደንኙት በመኖሩ ነ፡፡ በአንድ በኩል የሚሠጡት አገልግሎት ድርጅቱ ከሚከተለ፡ እምነት ጋር ቀጥተ ደንኙነት ለ፡ና ከእምነቱ ጋር ተነጥሎ ሊታይ የማይችል ሠራተኛን፤ እንደ ቄስ፣ ካህን፣ ዲያቆን ወዘተ ያሉ ሰ ሆን በለለ በኩል ደግሞ የሚሠጡት አገልግሎት ከእምነቱ ጋር ያልተቆራኘ እንደ ሂሣብ ሠራተ፣ የንብረት ክፍል ሠራተ፣ የስታትስቲክስ ሠራተ ወዘተ አሉ፡፡ በመሆኑም የሃይማኖት ሥራውን ከሚሠሩት ሠራተኞች ጋር የሚነሣ፡ የአሠሪና ሠራተ ሁኔታ ከሌሎቹ ሠራተኞች ጋር ከሚነሣው የተለየ ነው፡፡ ቀጥተኛ የሃይማኖቱን ወይም መንፈሣዊ ስራ የሚሠሩትን ሠራተኞች ስንመለከት የስራቸው ፀባይ የኃይማኖት ተቋሙ ከሚከተለው እምነት የሚመነጭና ከእምነቱ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ መንፈሣዊ አገልግሎቱን ለመስጠት ብቁ ሆኖ ለመገኘት መማሪት ማጅጠቸ ነጻኖች፣ ለምን ያህል ጊዜ አገልግሎቱ ላይ መቆየት እንደሚችል፣ የኃይማኖቱ እና የመንፈሣዊ አገልግሎት ሠጪ፡ መብትና ግዴታ አገልጋዩ መንፈሣዊ አገልግሎቱን እየሠጠ እንዲቀጥል የሚያደርጉ ሁኔታዎች አገልጋዩ አግባብ ባልሆነ መንገድ አገልግሎቱን እንዳይሠጥ በተደረገ ጊዜ የሚከተሉት ሁኔታዎች እና ሌሎች በስራ ግንኙነቱ ለነሱ የሚችሉ ጉዳዮች እያንዳንዱ የኃይማኖት ተቋም ከሚከተለ፡ እምነት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የመንፈሣዳዊ ስራ ግንኙነቱ ማስነሣቸ፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ከእምነቱ ተነጥለው የሚታዩ ባለመሆናቸ በስራ ደንኙቱ ስጨ ልቃ መግባቱ በእምነት ውስጥ ጣልቃ መግባትን ያስከትላል፡፡

በሌላ በኩል ግን ከእምነቱ ጋር ተያያኛነት ለ፡ን ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞች ከድርጅቱ ጋር የሚኖራቸ ደንኙነት ለ ስነሣ ማችለ፡ ጉዳዩ ከእምነቱ ጋር የማይያያዝና ይልቁንም በማን ም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ከሚነሱ ሁኔታዎች የተለየ አይደለም፡፡

ከላይ እንደተመለከተ፡ የመንፈሣዊ የስራ ግንኙነቱ ማስነሣቸ ሀ ታዎች ከኃይማኖቱ ተነጣጥለ ለታዩ ማችለ በመሆናቸ ሥር ቤት ለተ ቀሰው አንቀፅ በሰ ው ትርጉም የሚኒስትሮች ምክር ቤት የመንፈሣዊ ስራ ደንኙነትን በሚመለከት ሕግ የሚያ ጣ ከሆነ በኃይማኖት ጉዳዮችም ጣልቃ መግባቱ ይሆናል ይህ ደግሞ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ- መንግሥት አንቀት 11 "መንይሥትና

ኃ ማኖት ተለዩ ናቸ፡፤ መንግሥት በኃይማኖት ጉዳዮች ጣልቃ አይገባም" በማለት ከተደነገ ጋር ማጋ ሆናል፡፡ ነገር ግን የሃይማኖቱን ሥራ ከሚሠሩት ሠራተኞች ውጪ ያሉና በሃይማኖት ተቋም ከሚሰሩ ሰራተኞች ጋር ያለ ሥራ ደንኙት ማስነሳ ደ ለለው የአሠሪና ሠራተ ደንኙነት ከሚያስነሳ፡ ጋር ተመሣሣይ በመሆኑ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢ.ቁ.42/85 አንቀጽ 3(3)(ለ) መሠረት ሊያወጣ የሚችለው ደንብ እነዚህን ሠራተኛን በተመለከተ እንጂ መንፈሣዊ አገልግሎት ለመስጠት ከኃይማኖት ተቋማት ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነቶች የሚጨምር ሊሆን አይችልም፡፡

በመሆኑም ደንቡ እስካል ጣ ድረስ የአዋጅ ቁጥር 42/85 በመንፈሣዊ የሥራ ግንኙነቶች ላ ም ተ ቋማ ሆናል ማለ ትርዴም ሕይ መሠረት ለለ ሆናል፡፡

ከፍ ሲል በተዘረዘሩት ምክንያቶችም ማን ም የሥራ ክርክር ሰሚ አካላት መንፈሣዊ የሥራ ግንኙነቶች ተመስርቶ ማነሱ ክርክሮች በአ/ቁ. 42/85 መሠረት አይቶ ለመ ሰን ሥል ን ለለቸ ሲሆን ክርክሮቹ የኃይማኖት ተቋማቱ በማቋራቸው አለመግባባቶች በሚፈቱበት መንገድ የሚታዩ ናቸው፡፡ ይህ ችሎትም የስር ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ በታየ ሕይ ነጪበ ሰ ው የሕግ ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

□□ ሣ ኔ

1/ □ፀ / መ/ ደረየ □ / በ□ት በመ/ ቁ. 13549 ህ□ር 24 ቀን 1997 □ሰ□ □□ ው ሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ ቁ. 35562 ጥር 17 ቀን 1997 ዓ.ም የሰ□ ው ትእዛዝ ተሸሯል።

2/ ደራ ቀኙ □ ጨና ኪ ሣራ□ቸ□ን □□ራ ሣቸ□ □ን □ቻለ□።

መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ተ.□

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34703

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- እንደሻው ፍቃዱ - ቀረበ፡፡

ተጠሪዎች፡- እነ ወንድማገኝ ፍቃዱ /ሰባት ሰዎች/

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ አመልካቹ በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው ይዘውት ከሚገኘው የውርስ ንብረት ድርሻውን እንዲያካፍሉት ነው፡፡ ከተጠሪዎች መሃል ስድስቱ ለክሱ በሰጡት መልስ ከሣሹ ልክ እንደኖው ወራሽ ነው፤ ድርሻውን ለማካፈል ዝግጁ ነን፤ በእርግጥ የጠየቀው የውርስ ሃብት ግምት የተጋነነ ነው በማለት ሲከራከሩ አንዱ ደግሞ ጉዳዩ በሽምግልና እየታየ ነው የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ ውርስን የሚመለከት በመሆኑ ከሣሽ የውርስ ሃብቱ ይጣራልኝ የሚል ክስ በቅድሚያ ሊያቀርብ ይገባል የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ሰርዟል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ጉድለት የለበትም ብሏል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ታሕሣሥ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በዓፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የውርስ ማጣራት ስርዓት አልተካሄደም በሚል ምክንያት አመልካች ያቀረበው የውርስ ሃብት ልካፈል ክስ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በአመልካች የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ግልጽ ነው፡፡ ክሱን የመሠረተው በወንድሞቹ እና እህቶቹ ላይ ሆኖ በወራሾች መካከል ካልተከፋፈለው የሁሉም አባት ንብረት ላይ የውርስ ድርሻውን እንዲያካፍሉት ነው፡፡ የክፍያ ጥያቄ ያቀረበባቸውን የውርስ ሃብቶችም /ንብረቶች/ በክስ ማመልከቻው ላይ ዘርዝሮ ስለማቅረቡ አቤቱታ በቀረበበት ብይን ላይ ተመልክቶአል፡፡ አመልካች ተጠሪዎችን የከሰሰበት ምክንያትም ግልጽ ነው፡፡ ይኸውም የውርስ ሃብቶቹን በእጃቸው ይዘው ስለሚገኙ ነው፡፡ ተጠሪዎች ለስር ፍ/ቤትም ሆነ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት መልሳቸው ንብረቶቹን አልያዝንም /በእጃችን አይገኙም/ የሚል ክርክር አላነሱም፡፡ አመልካች ወራሽ አይደለም ወይም ከተባሉት ንብረቶች የሚያገኘው መብት የለም የሚል ክርክርም የላቸውም፡፡ ይልቁንም በክሱ የተጠየቀውን በመቀበል ለአመልካች ድርሻውን ለማካፈል ዝግጁ መሆናቸውን ነው የገለጹት፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ጉዳይ ወራሾቹም ሆኑ የውርስ ሃብቶቹ በግልጽ ተለይተው ታውቀዋል፡፡ ሳይከናወን የቀረው ንብረቶቹን በወራሾቹ መካከል የመከፋፈሉ ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ ከውርሱ ሃብት የሚከፈል ዕዳ እንዳለና በአመልካች ክስ የተመለከተው የንብረት ግምት የተጋነነ እንደሆነ በተጠሪዎች ክርክር ተገልጸአል፡፡ እንደተባለው ከውርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሃብቱ ላይ የሚፈለግ ዕዳ ካለ ክሱ በቀረበበት ፍ/ቤት መሪነት በማስረጃ ተጣርቶ ሊታወቅ የሚችል ነው፡፡ ተጠሪዎችም በእርግጥ ያልተከፈለ እና በትክክልም ከውርስ ሃብቱ ላይ የሚከፈል ዕዳ አለ ካሉ ይህንኑ በማስረጃ አስረግጠው ለፍ/ቤቱ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ዕዳ አለ በመባሉ ምክንያት ሕግና ስርዓት ተከትሎ የቀረበው ክስ የሚዘጋበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

አመልካች ክስ በመሠረተበት /ለክሱ መነሻ በሆነው/ ሃብት ላይ ጥቅም ወይም መብት እንዳለው አረጋግጦ ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 33/፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በጉዳዩ ላይ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የለውም አልተባለም፡፡ ፍ/ቤቱ ክሱን የሰረዘው የዳኝነት ስልጣን የለኝም በሚል ቢሆንም፤ ለዚህ የሰጠው ምክንያት ግን የውርስ ማጣራት ስርዓት አልተካሄደም የሚል ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የውርስ ሃብት ክፍፍልን መነሻ የሚያደርግ ክስ በውርስ አጣሪ በኩል ካላለፈ በቀጥታ ወደ ፍ/ቤት አይቀርብም የሚል አስተሳሰብ ወይም አካሄድ የተያዘ መሆኑን ነው፡፡ በእርግጥ በወራሾች በራሳቸው ወይም በተመረጠ በሌላ ሰው አማካይነት ውርስ እንደሚጣራ በሕጉ ተመልክቶአል፡፡ ከውርስ ማጣራት ተግባራት አንዱ የውርስ ሃብቱን መከፋፈል እንደሆነም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ይህ እንግዲህ አንዱ የውርስ ሃብት የሚከፋፈልበት መንገድ ነው ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ድርሻዬን አላገኘሁም የሚል ወራሽ የውርስ ሃብቱን በያዘው ሰው ላይ በቀጥታ ክስ የመመስረት መብት የለውም ወይም ሕጉ ከልክሎአል ለማለት የሚቻል እንዳልሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የውርስ ሃብቶቹ በተጠሪዎች እጅ ተይዘው እንደሚገኙ አላከራከረም፡፡ አመልካችም ከእነዚህ ሃብቶች ላይ ድርሻውን እንዲያገኝ ነው የጠየቀው፡፡ በመሆኑም እንደማንኛውም የፍትሐብሔር ክርክር ታይቶ እና በማስረጃ የሚጣራ ካለም ተጣርቶ ሊወሰን ሲገባ የውርስ ማጣራት ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ ተደርጎ መወሰዱ ትክክል አይደለም፡፡ ፍ/ቤቱ የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 49517 ሐምሌ 10 ቀን 99 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 32508 ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከፈተው መዝገብ በመቀጠል በግራ ቀኝ ወገኖች የሚቀርብለትን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የመሰለውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 36604

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ጽጌ መንግሥቱ - ጠበቃ ሰሎሞን ገ/ሚካኤል ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. ወንድይራድ መንግሥቱ - ቀረበ

2. ሠይፉ ተረፈ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው ይግባኝ መነሻ የሆነው ጉዳይ ኑዛዜን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ተሰጥቶ የነበረው የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ለመቃወሚያቸው መሠረት አድርገው የጠቀሱት አመልካች የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣት በአስረጂነት ያቀረበችው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት አያሟላም፤ ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም፤ የሚል ነው፡፡ ፍ/ቤቱ አመልካችን አስቀርቦ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ኑዛዜው የኑዛዜ አድራጊዋ ወራሾች የሆኑትን ተቃዋሚዎችን ያለምንም ምክንያት ከውርስ የሚነቅል በመሆኑ ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔ ተሰርዟል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱም ኑዛዜው የሕጉን መስፈርት ያሟላ ሕጋዊ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን /ይግባኝ የተባለበትን/ ውሣኔ የሻረ ሲሆን በመቀጠልም ተጠሪዎችም እንደአመልካች ወራሾች ስለሆኑ የኑዛዜ አድራጊዋን ሐብት እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኖአል፡፡ በመጨረሻም ይህን ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ክርክሩን ከሰማ በኋላ ኑዛዜው ተጠሪዎች በዝምታ ከውርስ የሚነቅል በመሆኑ የሚፀናበት የሕግ ምክንያት የለም፤ የውርስ ሃብቱን ግራ ቀኝ ወገኖች እኩል ይካፈሉት መባሉ ግን ትክክል ነው በማለት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አሻሽሏል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ከስር ጀምራ አቅርባ ስትከራከርበት የቆየችው የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ እንደተመለከተው ተጠሪዎች ኑዛዜውን በመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት ኑዛዜ ከተደረገ ከ16 /አስራ ስድስት/ ዓመት በኋላ ነው፡፡ ኑዛዜው ሟች ከሞቱ /ኑዛዜ አድራጊዋ ከሞቱ/ በኋላ በ80ኛው ቀን ሲፈስ ተጠሪዎች ተገኝተው እንደሰሙ በምስክር ስለመረጋገጡ በውሣኔው ላይ ተገልጿል፡፡ እንደምንመለከተው ተጠሪዎች የኑዛዜውን መደረግ /መኖር/ ብቻ ሣይሆን አመልካች በኑዛዜው መሠረት ተጠቃሚ ሆና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቆየትዋን ጭምር አውቀው ለብዙ ዓመታት በዝምታ ማለትም ሣይቃወሙ ቆይተዋል፡፡ አመልካች መቃወሚያው በይርጋ ቀሪ ሆኗል የምትልበት ዋናው ምክንያትም ይኸው ነው፡፡

ኑዛዜን በመቃወም የሚቀርበው ማናቸውም መቃወሚያ መታየት ያለበት አግባብነት ካላቸው የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ነው፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንዱ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 973 የተመለከተው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል መቃወሚያ ያላቸው ኑዛዜው ሲነገር /ሲፈስ/ የነበሩትን ሰዎች የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ወይም የተወከሉ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም ወይም በኑዛዜው የተነገረ ቃል አይፀናም የሚሉትንና የመሳሰሉትን በመቃወም ክስ የሚያቀርቡ ቢሆን ይህን ማድረግ ያለባቸው ኑዛዜው ከተነበበበት አንስቶ እስከ አስራ አምስት ቀን ድረስ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ክስን የማቅረብ ሃሣብ መግለጫው በጽሑፍ ካልሆነና ለአጣሪው ወይም ለዳኞች ወይም በውርስ ላይ የተነሣውን ነገር ለመጨረስ ለተመረጡት የሽምግልና ዳኞች እንዲደርስ ካልተደረገ በቀር እንደማይፀና /መቃሚያ አለ ለማለት እንደማይቻል/ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 973/2/ ተደንግጓል፡፡ በመጨረሻም መግለጫው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እስከ ሦስት ወር ድረስ ክስ ካልቀረበ መብቱ ከነጭራሹ እንደሚቀር በንኡስ ቁጥር /3/ ተመልክቷል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪዎች ኑዛዜው ሲነገር /ሲፈስ/ በቦታው እንደነበሩ /እንደሰሙ/ አላከራከረም፡፡ መቃወሚያ ያቀረቡት በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 973 በግልጽ የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ እንዳልሆነም ተረጋግጧል፡፡ በሌላም በኩል ኑዛዜው ሲነበብ አልነበሩም ተብሎም ቢሆን ኖሮ መቃወሚያውን ሣያቀርቡ የቆዩት ለ16 /አስራ ስድስት/ ዓመታት ያህል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 974 የተቀመጠው የአምስት ዓመት የጊዜ ገደብ ይከለክላቸዋል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 974/2/ በግልጽ እንደተመለከተው ኑዛዜው ከፈሰሰበት /ከተነበበት/ ጊዜ ከአምስት ዓመት በኋላ ስለኑዛዜው መጽናትም ሆነ ስለክፍያው ድልድል መቃወሚያ ማቅረብ አይቻልም፡፡ ሲጠቃለል ተጠሪዎች ኑዛዜው ሲነበብ /ሲፈስ/ አልነበሩም ወይም አልሰሙም አልተባለም እንጂ ተብሎም ቢሆን ኖሮ በመጨረሻ ያቀረቡት መቃወሚያ በይርጋ ቀሪ ከመሆን የሚድን አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 24280 የካቲት 27 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 45325 ሚያዝያ 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 31177 የካቲት 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪዎች በኑዛዜው ላይ ያቀረቡት መቃወሚያ በይርጋ ቀሪ የሆነ በመሆኑ መቃወም አይችሉም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 37275

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሻ/ባሻ ገዛኸኝ ድልነሣው - ቀረበ

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ተዋበች ደመቀ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን በአብላጫ ድምጽ ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የንብረት ክፍፍል በሚመለከት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 27393 መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት የአሁን አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከፍቺ ውሣኔ ቀጥሎ የንብረት ክፍፍል ይደረግለት ዘንድ የንብረት ዝርዝር አቅርቧል፡፡ ከቀረበውም የንብረት ዝርዝር መካከል ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው በወረዳ 28 በቀበሌ 01 በቤት ቁጥር 610 የተመዘገበው ቤት የጋራ በመሆኑ እኩል እንካፈል ዘንድ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ዳኝነት በመጠየቁ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም በተጠሪነታቸው ቀርበው ይኸው ንብረት ከጋብቻ በፊት ከመጀመሪያ ባለቤታቸው ጋራ ያፈሩትና የግል ንብረታቸው የሆነውን በወረዳ 28 ቀበሌ 01 በቤት ቁጥር 419 በካርታ ቁጥር ኮ/01/152/73 የተመዘገበውን ቤት በመሸጥ በምትኩ ይኸው ክርክር ያስነሣው ቤት በግዥ የተገኘ በመሆኑ የግል ሀብቴ እንጅ የጋራ ሀብት ባለመሆኑ የቀረበው የክፍፍል ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም በኮ/መ/ቁ. 12164 ታህሣሥ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት የቤት ቁጥር 610 የተሰራው አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ መሥርተው አብረው ሲኖሩ የነበሩበትና በቤት ቁጥር 419 የተመዘገበውን ቤት በመሸጥ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የተካደ ነጥብ አይደለም፤ በተጠሪ በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች እንዳረጋገጡት የቤት ቁጥር 610 መኖሪያ ቤት የተሰራው በቤት ቁጥር 419 በተመዘገበው ቤት የሽያጭ ገንዘብ ሲሆን ፤ የቤት ቁጥር 419 የአሁኑ ተጠሪ የግል ንብረት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፤ አመልካችም ይኸው በሽያጭ ገንዘብ የተሰራው የቤት ቁጥር 610 ባልና ሚስቱ በጋብቻ አብረው በሚኖሩበት ጊዜ በግል ጥረታቸው ባገኙት ገቢ የተሰራ እና የተገዛ ስለመሆኑ አላስረዳም፤ ስለሆነም አመልካች የጋራ ሀብት እንደሆነ በመቁጠር የንብረት ክፍፍል ያቀረቡበት የቤት ቁጥር 610 የተጠሪ የግል ሀብት በመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 58/1/ መሠረት የግል ሀብት እንጅ የጋራ ባለመሆኑ ይህንኑ ቤት አስመልክቶ ያቀረበው ክሱ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን በይግባኝ ደረጃ ካከራከረ በኋላ በኮ.ቁ. 44232 መስከረም 29 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ምንም እንኳን የአሁን መልስ ሰጭ ክርክር ያስነሣውንና በቤት ቁጥር 610 የሚታወቀውን ቤት የገዙት የቀድሞ ቁጥሩ 419 የሆነውን መኖሪያ ቤታቸውን ሸጠው መሆኑን በተሻለ ሁኔታ ቢያስረዱም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 58/2/ መሠረት በግዥ የተገኘው ቤት የግላቸው እንዲሆን በፍ/ቤት ወይም በወቅቱ እንደሚቻለው በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባዔ አላስወሰኑም፤ ስለሆነም ተጠቃሹ ቤት የመልስ ሰጭ የግል ሀብት ነው ሲል የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ መድረሱ ውሣኔው ሕጉን በአግባቡ ያላገናዘበ ነው፤ ስለሆነም በአሁኑ አጠራር በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 19 ክልል ውስጥ በቤት ቁጥር 610 ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት የጋራ ሀብት ነው፤ ከተቻለ ግራ ቀኙ በዓይነት እኩል ይካፈሉ፣ ይህ የማይቻል ለመሆኑ ከተረጋገጠ ግን ከተስማሙ አንዱ ለአንዱ የግምቱን አጋማሽ ሰጥቶ ያስቀር፤ በዚህ ባይስማሙ ግን ከተስማሙ በጋራ ሸጠው፤ ካልተስማሙ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል ይካፈሉ በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው የአሁን መልስ ሰጭ የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረቡት መሠረት ጠ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 27393 መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎትም በጋብቻ ጊዜ በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ሀብት ይባልልኝ ብሎ ለፍ/ቤት ጥያቄ አቅርቦ እንዲፀድቅ ያስፈለገበት ምክንያት የጋራ ሀብትን እንደግል ሀብት በማስመሰል 3ኛ ወገኖችን የሚጎዳ ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማድረግ ስለመሆኑ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ረቂቅ - በ1992 ከታተመው የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ረቂቅ ማብራሪያ ላይ ለመረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 58/2/ የተደነገገው የ3ኛ ወገኖችን መብት ለመጠበቅ ሲባል እንጅ በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል ለሚነሣ ክርክር አግባብነት የለውም፡፡ በመሆኑም ለክርክሩ መነሻ የሆነው በቁጥር 610 የተመዘገበው ቤት የይግባኝ ባይዋ የአሁን መልስ ሰጭ የግል ሀብት እንጂ ከመልስ ሰጭው ጋር ሊካፈሉት የሚገባ የጋራ ሀብት አይደለም በማለት ወስኖ አሰናብቷል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይም የቀረበው በዚህ አኳኋን የፌ.ጠ.ፍ/ቤት የሰጠው የሕግ ትርጓሜ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉበትን ክርክር በማቅረብ በሰበር ሰሚው ችሎት እንዲታረምላቸው አመልካች ዳኝነት በመጠየቃቸው ነው፡፡

መልስ ሰጭም ጠ/ፍ/ቤቱ በይግባኝ አይቶ የሰጠው ውሣኔ ትክክለኛውን የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግ ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በዚህ ጉዳይ ክርክር ያስነሣው በቤት ቁጥር 610 የተመዘገበው ቤት በፊት የአሁን መልስ ሰጭ የወ/ሮ ተዋበች ደመቀ የግል ሀብት የነበረው የቤት ቁጥር 419 ተሸጦ በግዥ የተገኘ ስለመሆኑ የማያከራክር የፍሬ ጉዳይ ስለመሆኑ በየደረጃቸው የተሰጡት የውሣኔ ግልባጮች አስረጂ ናቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘውና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም የሚያሰጥ ሆኖ የተገኘው ከጋብቻ በፊት የነበረ ሀብት በመሆኑ የተነሣ የነበረን የግል ሀብት በመሸጥ ሌላ ቤት በግብይት በግዥ በተገኘ ጊዜ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 58/2/ በተደነገገው መሠረት አለመፈፀም የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ ባል ወይም ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀጥሉ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 57 ተደንግጓል፡፡ በዚህ አኳኋን የግል የነበረ ንብረት በግብይት የተነሣ ዓይነቱን ለውጦ በተገኘ ጊዜ የግል ሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ በአንቀጽ 58 የተመለከተውን በመረዳት አስቀድሞ ሊፈፀም እንደሚገባ የሕጉ አደራደር ቅደም ተከተል ያስገነዝባል፡፡ በመርህ ደረጃ በአንቀጽ 58/1/ እንደተመለከተው ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል በሚል ከተቀመጠ በኋላ በዚህ ሁኔታ የተነሣ ንብረቱ የግል ይባልልኝ ብሎ 1ኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብና ፍርድ ቤት ሲያፀድቀው ብቻ ነው በማለት በተለየ ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ይኸው በአንቀጽ 58/2/ መሠረት በስርዓቱ አለመፈፀሙ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ አንቀጽ 58 በእራሱ ገላጭ እንጂ ለትርጉም በር የከፈተ ሆኖ አይገኝም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌው ግልፅነት ይጎድለዋል ከተባለም ድንጋጌዎችን እርስ በእርሣቸው አስተሳስረን ልንመለከት ይገባል ። የአንቀጽ 57 እና 58 ርዕሰ ጉዳዮች ቁጥር 1 እና 2 በሚል የተያያዙ በመሆናቸው ከጋብቻ በፊት የነበረ ሀብት የግል ሆኖ የሚቀጥለው በማናቸውም ዓይነት ምክንያት ዓይነቱን ካልለወጠ እና ለውጦ ከተገኘም የግል ሀብት እንደሆነ ሊቀጥል እንደሚገባ፣ በዚህ መሠረት የግል ሀብት ሆኖ ሊቀጥል የሚገባው ግን በልዋጭ የተገኘው ሀብት የነበረውን የግልነት አቋም ይዞ እንዲቀጥል በፍ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ እነዚህ ተያያዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች በግልጽ ያመለክታሉ። ይህን በአንቀጽ 58/2/ የተመለከተውን ማሟያ አለመተግበር የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ወሰን በእነማን ላይ ያተኮረ ነው የሚለውም ቢሆን አሻሚ በመሆኑ ትርጉም ያስፈልገዋል፤ ለመተርጎምም የሕግ አውጭውን ሀሣብ መፈለግ ይበጃል ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም። በመሠረቱ ከትርጉም ዘዴዎች አንዱ የሕግ አነጋገር ግልጽ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሕጉን እንዳለ ሥራ ላይ ማዋል እንጅ በትርጉም ሽፋን ከሕጉ ይዘት መራቅ የሚያስፈልግ አይደለም። ይተርጎም እንኳ ቢባል የሕግ አውጭው ሀሣብ ምን ነበረ ከሚለው መነሻ ይልቅ የሕጉን ድንጋጌዎች እርስ በእርሣቸው አስተሳስሮ ማየቱ ለትክክለኛው ትርጓሜ የሚያደርስ ነው። በዚህም መሠረት በዚሁ ሕግ አንቀጽ 62/2/ "----በዚህ ሕግ አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በቀር ባልና ሚስቱ ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል" በማለት የባልና ሚስትን የጋራ ሀብት በሚደነግገው ክፍል መጠቀሱ በአንቀጽ 58/2/ የተመለከተውን ሥርዓት አለመፈፀም የሚያስከትለው ውጤት የተጋቢዎች የጋራ ሀብት የቱ ነው ለሚለው ጉዳይ ተፈፃሚ መሆኑን በግልጽ የሚያመለክት ነው።

ስለሆነም የአሁን መልስ ሰጭ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን የግል ሀብት በቁጥር 419 የተመዘገበውን ቤት በጋብቻ ላይ እያሉ በመሸጥ በቤት ቁጥር 610 የተመዘገበውን ቤት ሲገዙ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 58/2/ ሆነ በጊዜው ለጉዳዩ ተፈፃሚነት በነበረው ሕግ መሠረት በግብይት የተገኘው ቤት የግል ሆኖ ይቀጥል ዘንድ አቅርበው በሚመለከተው ክፍል አለማፀደቃቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ክርክር ያስነሣው እና በቁጥር 610 የተመለከተው ቤት የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው ብለናል።

ው ሣ ኔ

1/ በድሮው አጠራር በወረዳ 28 ቀበሌ 01 በአሁኑ አጠራር ደግሞ በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 19 ክልል ውስጥ የሚገኘው እና በቤት ቁጥር 610 የተመዘገበው ቤት የአመልካችና የመልስ ሰጭ/ የባልና ሚስት/ የጋራ ሀብት ስለሆነ እንደ ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ እኩል ይካፈሉ።

2/ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 12164 ታህሣሥ 24 ቀን 1998 ከሰጠው ውሣኔ ይህንን ቤት በሚመለከት ብቻ የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 27393 መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ተሽረዋል።

3/ የከፍተኛው ፍ/ቤት በኮ.ቁ. 44232 መስከረም 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል። ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ። ተዘግቷል።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሐሣብ ልዩነት

ተጠሪ ከአመልካች ጋር ከመጋባታቸው በፊት የግል ቤታቸው የነበረውን የቤ.ቁ. 419 የሆነውን ቤት ከአመልካች ጋር ከተጋቡ በኋላ ሸጠው በምትኩ የቤ.ቁ. 610 መግዛታቸው ተረጋግጧል። ከፍ ብሎ በአብላጫው ውሣኔ ላይ እንደተመለከተው ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ሊሆን እንደሚችልና ይህም ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄውን ለፍ/ቤት አቅርቦ ጥያቄውን ፍ/ቤት ሲያፀድቀው እንደሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 58/1/ እና /2/ ላይ ተመልክቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግል ንብረት ተሸጦ በሌላ ንብረት ሲተካ ወይንም በሌላ ንብረት ሲለወጥ የኋላኛው ንብረት የግል እንዲባልለት የሚፈልገው ወገን ጥያቄውን ለፍ/ቤት ማቅረብ የሚጠበቅበት በሽያጭ ወይንም በለውጥ የተገኘው ንብረት በጋብቻ ውስጥ ከተፈራ ንብረት ጋር የመቀላቀል አጋጣሚ ሊፈጠር ስለሚችል ከጋራ ንብረት ያልተቀላቀለ መሆኑን ጭምር በማሣየት የግል ሀብት መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚቻል ከሕጉ ዓላማ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ቤት በጋብቻ ጊዜ ሸጠው በዚያው የሽያጭ ገንዘብ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ገዝተዋል፡፡ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ቤት ሸጠው በዚያው ገንዘብ በጋብቻ ጊዜ ሌላ ቤት መግዛታቸው ሲታይ ከጋራ ንብረት ጋር ግብይቱ ተቀላቅሏል የሚያሰኝ ካለመሆኑም በላይ ስለመቀላቀሉም አመልካች አላስረዱም፡፡ በዚህ ሁኔታ የተገኘን ቤት የግል ነው እንዲባል በፍ/ቤት እንዲፀድቅ በማድረግ ተጨማሪ ማረጋገጫ ማግኘት ከሕጉ ዓላማ አኳያ ተገቢነት ያለው አይሆንም፡፡

በእርግጥ ተጠሪ የግል ቤታቸውን ሸጠው ሌላ ንብረት ገዝተው ቢሆን ኖሮ ይሄው በግብይት የተገኘ ሌላ ንብረት ጠቀሜታው /purpose/ የተለየ ከመሆኑ አንፃር ለትዳር ጥቅም አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበት እንደተገዛና ከጋራ ንብረት ጋር የመቀላቀልም ዕድሉ የሰፋ እንደሚሆን ስለሚገመት በዚህ መልኩ የተገኘ ንብረት የግል እንዲባል በፍ/ቤት ካልፀደቀ በስተቀር የጋራ ንብረት እንደሚሆን ከሕጉ ዓላማ አኳያ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን አስቀድሞ የነበረን ቤት በትዳር ጊዜ ሸጦ በሌላ ቤት መተካት ወይንም አስቀድሞ የነበረን መኪና ሸጦ በሌላ መኪና መተካት ከጋራ ንብረት ጋር የመቀላቀል ዕድሉ ጠባብ እንደሆነ ስለሚገመት በዚህ ሁኔታ የተገኘን ንብረት የግል ነው እንዲባል ተጨማሪ ማረጋገጫ ከፍ/ቤት እንዲገኝ መጠየቅ ሕጉ ይዞት ከተነሣው ዓላማ ጋር የተጣጣመ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡

ሲጠቃለልም ምንም እንኳን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ሊሆን ይገባል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በአብላጫው ውሣኔ ላይ እንደተመለከተው ከተሣሣተ የመነሻ ሃሣብ /premise/ ቢሆንም ቤቱ የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ግን ከውጤት አኳያ ተገቢነት ያለው ስለሆነ ይሄው ውሣኔ ምክንያቱ ተለውጦ ሊፀና ይገባል በማለት ስሜ በተራ ቁጥር 4 ላይ የተመለከተው ዳኛ በአብላጫ ድምጽ ከተሰጠው ውሣኔ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36777

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ወንድምአገኝ ዘውዱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ 1/ አቶ ታፈሠ ወንድአፍራሽ
2/ ወ/ሮ በለጤ አምደመስቀ ል ሁሉም } ቀርበዋል
3/ ወ/ሮ ቆንጅት ምንዳሁን

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የኑዛዜ አፃፃፍ ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ሟች ውብዬ ምንዳሁን የተውት ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ለፍ/ቤቱ አመልክተው ኑዛዜው ተረጋግጦ ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ኑዛዜው ሃሰተኛ ነው፤ ተናዛዥዋ ራሣቸውን በሣቱበት ጊዜ የተደረገ ነው፤ ሟች መፃፍ የሚችሉ ሆነው ሣለ በአሻራቸው መፈረማቸው ኑዛዜውን እንዳላደረጉ ያሣያል፤ በኑዛዜው በግልጽ አልተነቀልንም በማለት ኑዛዜው ውድቅ እንዲደረግ አቤቱታቸውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት አቅርበዋል፡፡ አመልካችም ቀርበው ኑዛዜው ውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ነው፤ ሟች በአሻራ ቢፈርሙም በውል አዋዋይ እና በምስክሮቹ ፊት ስለተደረገ ተገቢ ነው፤ ተጠሪዎች ተወላጆች ስላልሆኑ ከውርስ የተነቀሉበት ምክንያት ሊገለፅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ኑዛዜው በታይፕ ተጽፎ በምስክሮች ፊት ተነቦ ምስክሮችም ወዲያው መፈረማቸውን፣ ምስክሮቹ ችሎታ ያላቸውና አማርኛ ቋንቋም እንደሚችሉ፣ ሟችም ፊርማቸውን እንዳኖሩበት ተረጋግጧል፤ የምስክሮቹም ብዛት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 መሠረት በቂ ነው፤ የሟች የአእምሮ ሁኔታ ደህንነትን በተመለከተ ኑዛዜውን ያስፈፀሙት ኃላፊ በምስክርነት ተጠርተው አረጋግጠዋል፤ ስለዚህ ኑዛዜው የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ የቀድሞው ውሣኔ አይሻርም በማለት የተጠሪዎችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህንን ውሣኔ በመቃወም ተጠሪዎች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 መሠረት ግልጽ ኑዛዜ በ2 ምስክሮች መፈረሙ በቂ የሚሆነው ከምስክሮቹ አንዱ ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው አካል ከሆነ ብቻ ነው፡፡ በኑዛዜው ላይ ከፈረሙት ሁለት ምስክሮች ውስጥ አንዳቸውም የውልና ምዝገባ ጽ/ቤት ሠራተኛ ስላልሆኑ ኑዛዜው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 የተቀመጠውን መስፈርት አያሟላም ስለሆነም አመልካች የሟች ውብዬ ምንዳሁን የኑዛዜ ወራሽነት መብት የላቸውም ሲል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

አመልካችም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታም ኑዛዜው የተደረገው ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ስራውን በሚያካሂድበት በአ/አበባ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመሆኑ በበቂ ምስክር ተረጋግጧል፤ ሟች ኑዛዜውን ያደረጉትም በነፃ ፍላጎታቸው ነው የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው ኑዛዜው በሕግ የተመለከተውን ስርዓት አልተከተለም፤ ሟች ኑዛዜውን የሰጡት ጤነኛ በነበሩበት ሰዓት አልነበረም ሟች የተማሩ ስለነበሩ በጣት መፈረማቸው በጠና መታመማቸውን ያሣያል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትና ይህም ችሎት አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲጣራ ያደረገበት ነጥብ ሟች ውብዬ ያደረጉት ኑዛዜ በሕጉ ላይ የተመለከተውን መስፈርት ያሟላል አያሟላም የሚለው ነው፡፡ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ግልፅ ኑዛዜ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባው ስርዓቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በ4 ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ፣ ይህም ስርዓት መፈፀሙና የተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ፣ ተናዛዥና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ ነው፡፡ በሟች ተሰጠ የተባለው ኑዛዜም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተደረገ፣ ሁለት ምስክሮች የፈረሙበት፣ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ኑዛዜውን አረጋግጦ የፈረመበት፣ ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ የሚገልጽ እና ተናዛዥዋ የጣት አሻራቸውን ምስክሮቹ ደግሞ ፊርማቸውን ያኖሩበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 ሥር የተመለከቱትን ስርዓቶች ያሟላ ነው፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው የህጉን ሥርዓት አልተከተለም ያለው በኑዛዜው ላይ የተመለከቱት ሁለት ምስክሮች ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጣቸው ሠዎች አይደሉም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ምስክሮች ተብለው የተፃፉት ሁለት ሠዎች ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጣቸው ለመሆኑ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ኑዛዜው የተደረገው ከሁለቱ ምስክሮች በተጨማሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ፊት፣ ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ነው፡፡ ምንም እንኳን እኚህ ሰው ምስክር ተብለው ባይገለፁም ሟች ኑዛዜውን በነፃ ፈቃዳቸው ሲሰጡና ኑዛዜውም ሲነበብ አይተው በኑዛዜው ላይ ፈርመዋል፡፡ የምስክሮች ዋና አስፈላጊነትም ኑዛዜ አድራጊው ኑዛዜውን በነፃ ፍላጎቱ እና በትክክለኛ አእምሮው የሰጠ መሆኑንና የኑዛዜ ቃሉም የእርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው አረጋግጠው ፊርማቸውን ያኖሩ በመሆኑ ምስክር ተብለው ስማቸው ባለመገለፁ ብቻ ምስክር አልነበሩም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ከምስክሮቹ አንዱ ደግሞ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ከሆነና ኑዛዜው ይኸው ሰው ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ከሆነ ሁለት ምስክሮች ብቻ በቂ መሆናቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ በመሆኑ አመልካች የሟች ውብዬ ምንዳሁን የኑዛዜ ወራሽ አይደሉም በማለት የተሰጠው ውሣኔ ስህተት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47307 በ01/09/99 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31022 በ28/06/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡

2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08063 በ4/08/98 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፤ ሟች አደረጉት የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ በመሆኑ አመልካች የሟች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 35710

ታህሣሥ 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ እፀገነት እሸቱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሰላማዊት ንጉሴ - ጠበቃ ይልማ ቻኔ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው የአሁኗ አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት የሰበር ሠሚ ችሎት በሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የሠበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአሁኗ ተጠሪ ግንቦት 15 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ሚች ዘነበ ንጉሴ ታህሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ንብረታቸውንና የሕፃን ናትናዔል ዘነበን አሣዳጊነትና ሞግዚትነት በተመለከተ ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዳኝነት ጠይቀው ይኸው ፍ/ቤትም የተጠሪን አቤቱታ በመቀበል ኑዛዜው የፀደቀ መሆኑን በመግለጽ ሐምሌ 07 ቀን 1997 ዓ.ም ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም የአሁኗ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሠረት ባቀረቡት የተቃውሞ አቤቱታ ሚች ኑዛዜውን ያደረጉት በጋብቻ የጋራ ድርሻ ባለበት ንብረት መሆኑን፣ የሞግዚትነት ስልጣን ከእናት ለመውሰድም ሕጋዊ ክልከላ ያለ ስለመሆኑ፣ ኑዛዜው ግልጽነት የጎደላቸውን ቃላት የያዘ መሆኑን በመዘርዘር ሚች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የፀደቀው ያላግባብ በመሆኑ ሊሠረዝ ይገባዋል በማለት ዳኝነት ጠይቀው ተቃውሞ የቀረበለት ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ኑዛዜው ከንብረት ክፍፍሉ በፊት በጋብቻ የጋራ ንብረት መደረጉን፣ የእናት ሞግዚትነትም ከሕግ የሚመነጭ ሆኖ እያለ አባት በኑዛዜ ለሕፃን አክስት እንዲሆን ማድረጋቸው ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ ኑዛዜው ግልጽ ያልሆነ አሻሚ ቃል ይዞ መገኘቱም ፈራሽ የሚያደርገው ስለመሆኑ የሚሉትን ነጥቦችን በምክንያትነት ጠቅሶ የአመልካችን ተቃውሞ በመቀበል ቀደም ሲል ኑዛዜውን በማጽደቅ የሰጠውን ውሣኔ ሠርዞታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ደረጃ የተመለከተው የከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ ጉዳዩ በሠበር የቀረበለት የከተማው አስተዳደር ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ መዝገቡን በመመርመር በርካታ ምክንያቶችን በፍርዱ ላይ በማስፈር የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ከሻረ በኋላ ሚች ታኅሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ባደረጉት ግልጽ ኑዛዜ የአሁኗን ተጠሪንና ሕፃን ናትናኤል ዘነበን ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ በማድረግ የተውት በመሆኑ ኑዛዜው ፈራሽ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ሠኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን ሲያቀርቡ አመልካች በበኩላቸው ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ግራ ቀኙ በችሎት የቃል ጥያቄ ተደርጎላቸው መልስ ከሰጡ በኋላ ሕፃን ናትናኤል ዘነበ በችሎት ቀርቦ ሐሣቡንና ፍላጎቱን እንዲሰጥ ተደርጎ ቃሉ ተመዝግቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር፣ የሕፃን ናትናዔል ዘነበን አስተያየት የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሚች አቶ ዘነበ ንጉሴ ታህሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ባደረጉት ግልጽ ኑዛዜ የተጠሪና የሕፃን ናትናኤል ዘነበን ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ በማድረግ የተውት ኑዛዜ ፈራሽ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሚች አቶ ዘነበ ንጉሴ እና የአሁኗ አመልካች በጋብቻ ተሣስረው ሲኖሩ ቆይተው ጋብቻው በፍቺ ውሣኔ ታኅሣሥ 22 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ መፍረሱን፣ በዚህ ወቅትም ፍቺው በልጆች አስተዳደግና በንብረት ላይ የሚያስከትለውን ውጤት በተመለከተ ስምምነት እንዲያቀርቡ፣ መስማማት ካልተቻለ አንዳቸው አቤቱታ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቶ መብት ከተጠበቀ በኋላ የፍቺ ጥያቄ የተስተናገደበት መዝገብ መዘጋቱን ነው፡፡ ከዚህም በኋላ የንብረት ክርክር ተደርጎ የጋራ መሆናቸው የተረጋገጡን ዕቃዎች ግራ ቀኙ እንዲካፈሉ፣ በመኖሪያ ቤቱ ላይ የአሁኗ አመልካች ያላቸው ድርሻ 10,171.78/ አስር ሺህ አንድ መቶ ሰባ አንድ ብር ከሰባ ስምንት ሣንቲም/ መሆኑ ተረጋግጦ ሚች አቶ ዘነበ ንጉሴ እንዲከፍሉ ተብሎ መጋቢት 21 ቀን 1997 ዓ.ም በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07941 ተወስኗል፡፡ ሌላው ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሚች ኑዛዜ ያደረጉት ታኅሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ሆኖ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑን፣ የአሁኗ አመልካች የሕፃን ናትናኤል ሞግዚትና አስተዳዳሪ እንዲሆኑ በፍ/ቤት የተወሰነው ግንቦት 27 ቀን 1997 መሆኑን የአሁኗ ተጠሪ ሚች ያደረጉትን ኑዛዜ በፍ/ቤት እንዲፀድቅ ግንቦት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርበው ሐምሌ 07 ቀን 1997 ዓ.ም በፍ/ቤት ፀድቆ መወሰኑን፣ ይኸው ውሣኔ እንዲሠረዝ በአሁኗ አመልካች በኩል የተቃውሞ አቤቱታ የቀረበው ጥቅምት 04 ቀን 1998 ዓ.ም እና የአሁኗ አመልካች በመኖሪያ ቤቱ ላይ ያላቸው ድርሻ በውሣኔው መሠረት ያልተከፈላቸው መሆኑን ጭምር ነው፡፡

በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ከተማነክ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚች አቶ ዘነበ ንጉሤ ኑዛዜ በሕፃኑ ሞግዚትነትና አሣዳሪነት ላይ የተደረገ መሆኑ እየተገለፀለት የአሁኗን ተጠሪንና ሕፃን ናትናኤል ዘነበን የሚቹ ጠቅላላ ወራሾች የሚያደርገው ኑዛዜ ፈራሽ አይደለም በማለት የሞግዚትነትን ጉዳይ በተመለከተ ግልጽ ውሣኔ አለማስፈሩን ከውሣኔ አሰጣጡ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

እንግዲህ በሚች አቶ ዘነበ ንጉሤ ኑዛዜ የተገለፀው የሕፃኑ ሞግዚትነትና ኑዛዜው በጠቅላላው የሚች ንብረት ላይ ያለውን ዋጋ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መመልከትን የግድ ይላል፡፡ በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው ነጥብ ለሕፃን ናትናኤል ዘነበ አክስቱ የሆነችው የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት እንዲሆኑ ሚች ዘነበ ንጉሴ በኑዛዜ መወሰናቸው ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡

እንደሚታወቀው ሕፃናት የተለየ ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ አካል ናቸው፡፡ የዚህም መነሻ ሀሣብ ሕፃናቱ ከእድሜያቸው ለጋነት በተያያዘ ለአደጋ የተጋለጡ የሕብረተሰብ አካላት /vulnerable groups/ የመሆናቸው ጉዳይ ነው፡፡ ይህንኑ አደጋ ለመከላከል እና የተለየ ድጋፍና እንክብካቤ የማድረጉ ሥራ የተሣካ ይሆን ዘንድም የእነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ደህንነት በሚመለከት የተለዩ ስምምነቶች በአለምና በአህጉር አቀፍ ደረጃ ተፈርሞ እየተገበሩ ይገኛሉ፡፡ ከስምምነቶቹ ውስጥም የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን እና የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ሐገራችን ኢትዮጵያ የሕፃናት መብቶች ኮንቬሽንን ህዳር 29 ቀን 1984 ዓ.ም፣ የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ደግሞ እ.ኤ.አ ኦክቶበር 02 ቀን 2002 ዓ.ም አጽድቃለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሕፃናትን መብትንና ደህንነት በሚመለከት የፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት፣ የክልል ሕገ-መንግሥታት እና ሌሎች ሕጎች አሉ፡፡ በዓለም አቀፍ በአህጉርና በአገር ደረጃ ሕፃናትን አስመልክቶ በስራ ላይ ያሉ እነዚህ ሕጎች ደግሞ መሠረታዊ መርሆዎችን የያዙ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን መሠረታዊ ከሆኑት መርሆዎች ውስጥ አንዱ ሕፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት /the best interest of the child/ ቅድሚያ መስጠት የሚለው ስለመሆኑ የአንቀጽ 3.1 ድንጋጌ ሲያሣይ የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተርም በአንቀጽ 4.1 ድንጋጌ ስር ይህንኑ አካትቶ ይዟል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥትም ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የአገሪቱ የሕግ አካል መሆናቸውን በአንቀጽ 9/4/ ስር ከመደንገጉና በሕገ-መንግሥቱ በስፋት ሽፋን የተሰጣቸው መሠረታዊ የመብቶችና የነፃነቶች ድንጋጌዎች ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸውና ዓለም አቀፍ የሠብአዊ መብቶች ሕግጋት፣ ስምምነቶች ወይም ስነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም የግድ ስለመሆኑ በአንቀጽ 13/2/ ከማስቀመጡም በተጨማሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕፃናትን ልዩ ችግር ከግምት ያስገቡ የተለያዩ ንዑስ ድንጋጌዎችን የያዘ ድንጋጌ በአንቀጽ 36 አስፍሯል፡፡ በተለይም የአንቀፁ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ ሁሉ የመንግሥታዊ ወይም የበጎ አድራጎት ተቋማት እንዲሁም ፍ/ቤቶችና የአስተዳደር ባለስልጣናት ወይም የሕግ አውጪው አካላት የሕፃናትን ደህንነት በቀድሞ ትጋት ሊያስቡበት የሚገባ ስለመሆኑ አጽንኦት ባለው መንፈስ፤ በአስገዳጅነት ደንግጓል፡፡ ሕገ-መንግሥቱንም ተከትለው የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎች አቀራረጽ ይዘትና መንፈስ ሲታይም የሕፃናትን መብትና ደህንነት የማስከበር ዓላማ ግንባቤ ውስጥ ያስገቡ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

የሕፃናትን ጥቅምንና ደህንነት ቀደምትነት ከሚለው መርህ በተጨማሪ በዓለም አቀፍና በአህጉራዊ ሠነዶችና ስምምነቶች ውስጥ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ሌላው መሠረታዊ መርህ የሕፃናት ተሣትፎ መርህ ነው፡፡ የዚህ መርህ ዓይነተኛ ይዘት በዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን በአንቀጽ 12 የተመለከተ ሲሆን የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተርም በአንቀጽ 4.2 ስር በግልጽ ሠፍሯል፡፡ አጠቃላይ የዚህ መብት አድማስ ሲታይም ሕፃናት ህይወታቸውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ተሣትፎ ማድረግ እንደሚችሉ፣ በተጨማሪም ጥቅማቸውን በሚመለከቱ ውሣኔዎች ላይ የራሣቸውን ተጽእኖ የማሣረፍ መብት ያላቸው መሆኑ፣ይህም ስፋት ባላቸው የፍርድ ጉዳዮች እንዲሁም መደበኛ የውሣኔ አሰጣጥ በሚመለከቱ በጤና፣ በትምህርትና በአከባቢ ጉዳዮች ሁሉ ሊካተት የሚገባ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ድንጋጌዎቹ ሕፃናት በጉዲፍቻ ወቅት፣ በወላጆች መለያየትና ፍቺን ተከትሎ የትኛው ወላጅ ጋር ማደግ እንደአለባቸው ውሣኔ ሲሰጥ እና በመሣሠሉት ጉዳዮች ላይ አስተያየት መስጠትና ሊደመጡ እንደሚገባ እንዲሁም አስተያየታቸው ከመደመጡ ባሻገር ተገቢው አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የሕፃናቱ ሀሣብና አስተያየት ተገቢውን አፅንኦት የሚያገኘውም የሕፃኑን እድሜንና የአስተሣሠቡን የብስለት ደረጃ ግንባቤ ውስጥ በማስገባት መሆኑንም የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡

እንግዲህ ሕፃንን የሚመለከት አንድ ጉዳይ ሲወሰን ሊታሰብባቸው የሚገባቸውን የተወሰኑ መሠረታዊ መርሆዎችን የሕግ ማቀፋቸውንና የድንጋጌዎችን ዝርዝር ይዘትና መንፈስ ምን እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ የሚጠብቁትን ተቋሚትንና ቅደም ተከተሉን ከአንቀጽ 219-238 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች አስቀምጧል፡፡ በድንጋጌዎቹ መሠረት ወላጆች ከሌላው ሰው በቅድሚያ የአስተዳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን ያላቸው መሆኑ፣ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት በልጁ ወላጅ በኑዛዜ ቃል የሚመረጥ መሆኑ፣ ይህም በፍ/ቤት ሊሻር ወይም ሊሻሻል የሚችል መሆኑ፣ ወላጆች ወይም የወላጅ ኑዛዜ ከሌለ ሦስተኛው መንገድ ከዘመዶቹ መካከል በገዘምድና ቅደም ተከተል የአሣዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን ሊሰጥ እንደሚገባ፣ በመጨረሻም በሕግ የሚመረጡ ዘመዶች ከሌሉ ይኸው ሥልጣን በፍ/ቤቱ በሚመረጥ ሰው ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ ተገልጿል፡፡ ሆኖም የእነዚህ ድንጋጌዎች ቅደም ተከተል ተግባራዊ ሲደረግ ሁልጊዜ ግንባቤ ውስጥ መግባት ያለበት ቁልፉ ነጥብ በሕገ-መንግሥቱ የተመለከተው የሕፃኑ ደህንነት መብት ቀደምትነት ስለመሆኑ ሊረሣ የማይገባው ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የተመለከቱት ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎችም ሆነ በአንቀጽ 113/2/ ስር የተመለከተው ድንጋጌ አቀራረፅ፣ ይዘትና መንፈስ ሲታይ ፍ/ቤቶች አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ አሣዳሪነትና ሞግዚትነት በተመለከተ ውሣኔ ሲሰጡ በሕጉ የተሰጣቸውን ሠፊ ሥልጣን መጠቀም ያለባቸው መሆኑንና የሕፃናትን መብትና ጥቅም የማስከበር ኃላፊነታቸውን መወጣት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ያስረዳል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 13/1/ ስር የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ የሕፃናትን ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ የሚችል ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ደግሞ የሕፃናቱ ሀሣብ ሊደመጥና ተገቢው ክብደት ሊሰጠው የሚገባ ነው ይህንኑ የሚቃረኑ ልማዳዊ አሠራሮችን ተቀባይነት የሌላቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 9/1/ ድንጋጌ በግልጽ ያሣያል፡፡

በዚህም መሠረት የዚህ መዝገብ ጉዳይ ሲታይ ሕፃን ናትናኤል ዘነበ አስተዳዳሪነትና ሞግዚትነትን በተመለከተ የሚቹ ኑዛዜ የሕፃኑን ደህንነትና ጥቅም ቀደምትነት መርህ ለማስከበር እና ተግባራዊ ለማድግ በሚያስችል መልክ የተከናወነ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሕፃን ናትናኤል ዘነበ በዚህ ችሎት ሲደመጥም ከአክስቱ ጋር የመኖር ፍላጎት የሌለው መሆኑንና ከወላጅ እናቱ ተገቢው እንክብካቤ እየተደረገለት በማደግ ላይ ያለ ስለመሆኑ አስተያየት ሰጥቷል፡፡ ሕፃኑ ከአባቱ ሞት በኋላ በአክስቱ በኩል ተገቢው ክትትልና እንክብካቤ ያልተደረገለት ስለመሆኑም አረጋግጧል፡፡ የሕፃኑ እድሜ ሲታይም አስር መሆኑንና አስተሣሰቡም የበሰለ ሊባል የሚችል መሆኑ ይህ ችሎት የተገነዘበው ሲሆን ይህም ለአስተያየቱ ተገቢው ክብደት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያቶች መሠረት ሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ስለሕፃን ናትናኤል ሞግዚትነት የተውት ኑዛዜ ፈራሽ የማይሆንበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላው በሟቹ ኑዛዜ የተገለፀው ነገር የሟቹን ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነትን ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡ በዚህ እረገድ የሟቹ ኑዛዜ ሠነድ ይዘት ሲታይ ፡-

> "... በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 19 ቀበሌ 55 የቤት ቁጥር 1654 የሆነውን መኖሪያ ቤቴን ግቢ ውስጥ ያሉትን ቤቶችንና መኖሪያ ቤት ውስጥ ያለውን ንብረቴን በስሜ በባንክ ያለውን ገንዘብ ሁለት እጁን ለእህቴ ለወ/ሮ ሠላማዊት ንጉሤ ኪዳኔ በራሤ ፈቃድ ተናዝዣለሁ፣አንድ እጁን ለልጄ ለአምስት ዓመቱ ለናትናኤል ዘነበ ንጉሤ አውርሻለሁ፣ የኑዛዜ ተቀባይዋ እህቴ ወ/ሮ ሰላማዊት ንጉሤ ኪዳኔ ከላይ ስሙ የተጠቀሰውን ልጄን አቅመ አዳም እስኪደርስና እራሱን እስኪችል ድረስ በኑዛዜ የተናዘዝኩትን ንብረቴን አንድ እጁን ተንከባክባ እየጠበቀች የቤቱንም ኪራይ እየተቀበለች አስቀምጣ እራሱን ሲችል እንድታስረክበው የእሷን ድርሻ ሁለት እጁን ለራሷ እንድትጠቀምበት ላደረገችልኝ ውለታ መክፈያ መናዘዜንና ልጄን ተንከባክባ እንድታሣድግልኝ ይህንን ኑዛዜ አድርጌአለሁ ..."

የሚል እና በአራት ምስክሮች ፊት የተደረገ ግልጽ ኑዛዜ ነው፡፡

ሟች ለተጠሪ ያደረጉት ኑዛዜ ተጠሪን የሟች ንብረቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደረገው በአንድ በኩል ለሕፃኑ ለሚያበረክቱት መልካም አስተዳደግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለሕፃኑ ከሚያደርጉት መልካም አስተዳደግ በተጨማሪ ለሟቹ ላደረጉት ውለታ ስለመሆኑ የሚጠቅስ ይመስላል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የሕፃኑ ሞግዚትነትና አስተዳዳሪነት በኑዛዜው መሠረት አይገባሽም ከተባልኩ ንብረቱን በተመለከተ ሟች 2/3ኛው ይሠጣት በማለት የተናዘዙት የሚፈርስበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሟች ኑዛዜ አጠቃላይ ይዘቱና መንፈሱ በውል ሲታይ ተጠሪ የሟች ንብረት የኑዛዜ ተጠቃሚ የሚሆኑት ሕፃን ናትናኤልን ተንከባክበው ሲያሣድጉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ተጠሪ ሕፃኑን ሲያሣድጉ አስፈላጊውን ወጪ የሚያደርጉበት ለራሣቸው ድርሻ ይሆናል ከተባለው ስለመሆኑም የኑዛዜው ይዘት ያሣያል፡፡ ምክንያቱም ሟች ለሕፃኑ ከተውት1/3ኛ ድርሻ ተጠሪ ተንከባክበው እንዲጠብቁ፣ የቤት ኪራዩን እየተቀበሉ እንዲያስቀምጡና ለአካለመጠን ሲደርስና ራሱን ሲችል እንዲያስረክቡ በኑዛዜው ላይ በግልጽ መቀመጡ ለሕፃኑ እንክብካቤና አስተዳደግ ወጪ የሚደረገው ከተጠሪ ድርሻ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ታህሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ገደብ ያለበት ኑዛዜ /Conditional legacy/ ስለመሆኑ መገንዘብ አያዳግትም፡፡ የኑዛዜ ስጦታ ጠቅላላ ወይም ልዩ ሊሆን እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 912 ስር የተመለከተ ሲሆን እንደዚህ ዓይነት የኑዛዜ ስጦታዎች አንድ ሁኔታ ሲደርስ የሚፀኑ ወይም የሚቀሩ ሆነው ሊደረጉ የሚችሉ ስለመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 916 ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ሕፃን ናትናኤልን ተንከባክበው ያሣደጉት ሁኔታ የለም፡፡ ተጠሪ ሕፃኑን ከራሣቸው የኑዛዜ ድርሻ ወጪ በማድረግ ተንከባክበው የማሣደግ ሁኔታ ካልተረጋገጠ ደግሞ ተጠሪ የንብረቱ በኑዛዜ ተጠቃሚነት የፀና ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የኑዛዜው ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሕጋዊ ምክንያት ሣይኖር የኑዛዜ ጠቅላላ ወራሽ ናቸው ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ማንኛውም የሚንቀሣቀስም ሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሕጋዊ መብት የሚተላለፈው ለሕፃን ናትናኤል ዘነበ ሆኖ የሕፃኑ ሞግዚትና አስተዳዳሪ አመልካች ሆነው ሊያስተዳድሩት የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አመልካች የሕፃኑን የማይንቀሣቀስ ሀብት መልካም አስተዳደር በሚመለከት የሞግዚትነት ሥልጣን እንዲኖራቸውም መወሰን አለበት ብንልም ሕፃኑ ከሟቹ አባቱ የሚተላለፍለትን ሀብት አጠቃላይ ሁኔታ፣ የአመልካችን ችሎታ፣የክርክሩን አጠቃላይ ይዘትንና የልጁን ጥቅም በማመዛዘን ስለሀብቱ አስተዳደር አመልካች የሚኖራቸውን ሥልጣን ከወዲህ መግለጽ ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች የሚከተለውን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1/ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 04273 ጥር 02 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 1120/98 ሚያዝያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም፣ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ደግሞ በመ/ቁ/ 03383 መጋቢት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጡት ውሣኔዎች በውጤት ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

3/ ሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ታንሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ያአደረጉት ኑዛዜ ፈራሽ ነው ብለናል፡፡

4/ ተጠሪ ከሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ንብረት በኑዛዜው ተጠቃሚ የሚሆኑበት አግባብ የለም ብለናል፡፡

5/ የሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ሕጋዊ ወራሽ ሕፃን ናትናኤል ዘነበ ነው ብለናል፡፡

6/ የሕፃን ናትናኤል ዘነበ አስተዳዳሪና ሞግዚት አመልካች ናቸው ብለናል፡፡

7/ አመልካች በሞግዚትነት ሥልጣናቸው ሕፃኑ ከአባቱ በውርስ ሊያገኝ የሚገባውን የማይንቀሣቀስ ንብረት የሕፃኑ እድሜ አካለመጠን /18 ዓመት/ እስከሚደርስ ድረስ በማናቸውም መንገድ ለ3ኛ ወገን የማስተላለፍ መብት የተገደበ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግን በፍ/ቤት ፈቃድ ተገቢውን መፈፀም ይችላሉ ብለናል፡፡

8/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37562

ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሣሙኤል ፈረንጅ - ጠበቃ አበበ ታዬ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1/ አቶ ግርማ ታፈሰ - ጠበቃ አብርሃም አሰፋ ቀርበዋል፡፡

2/ ወ/ሮ አሰገደች በቀለ - ጠበቃ አብርሃም አሰፋ ቀርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻው አመልካች ግንቦት 04 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ.33004/ የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 ይዘት ከምስክሮች አንዱ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሲባል በስጦታው /ኑዛዜው ፎርም ውስጥ የተመዘገበ ምስክር ከሆነ እንጂ ኑዛዜው ወይም ስጦታው በአዋዋዩ ወይም በዳኛው ፊት መከናወኑ ብቻ የምስክሮቹን ብዛት በተለየ ሁኔታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881/2 ከሚፈለጉት 4 ምስክሮች ወደ ሁለት ዝቅ ማድረግ አይቻልም በማለት የያዘው የሕግ ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርዱ እንዲታረምላቸው ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ የጀመው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካቾች፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተጠሪ የነበሩ ሲሆን፤ አመልካቾቹ ጥር 06/1988 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የሚች ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ ወራሾች መሆናቸውን በመግለጽ በወረዳ 09/ቀበሌ 06 ክልል የሚገኘው የቤት ቁጥር 579 የሆነውና በቤቱ ውስጥ የሚገኙ ቁሣቁሶች እንዲሁም ግሮሰሪ የሚች አውራሻቸው ንብረቶች መሆናቸውን በመግለጽ የውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው የጠየቁ ሲሆን በስር ፍ/ቤቱ ተጠሪ የነበሩ የአሁኑ አመልካችም መጋቢት 05/1988 ዓ.ም በተፃፈ መልሣቸው አመልካቾቹ ያቀረቡት ጥያቄ ሐቅነት እንደሌለው በመግለፃቸው ፍ/ቤቱም የውርስ አጣሪ ሾሟል፣ ውርስ አጣሪውም ሚያዚያ 20 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ ሪፖርት ለፍ/ቤቱ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም አከራካሪው ቤት ተጠሪው ከሚች በስጦታ የተላለፈላቸው እንደሆነና ይህንንም የስር አመልካቾቹ እንደማይቀበሉት የሚገልፀው መሠረታዊ ነጥብ ሲሆን የስር ፍ/ቤቱም ቤቱ ለተጠሪው በሥጦታ እንደተላለፈላቸው በማረጋገጥ አመልካቾቹ በዚሁ ተቃውሞ ካላቸው የስጦታ ይፍረስልኝ ጥያቄ ከሚያቀርቡ በስተቀር ጥያቄያቸው ተቀባይነት እንደሌለው ወስኗል፡፡

አመልካቾቹም የስር ፍ/ቤቱ በኮ/ቁ. 22789፣ ጥር 12 ቀን 1998 ዓ.ም ከላይ የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም የግራና ቀኙን ክርክር ካጢያዜደ በኋላ በኮ/መ/ቁ. 45348፣ ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ይግባኝ ባዮቹ በተለየ መዝገብ የስጦታው ይፍረስልን ጥያቄ ማቅረብ ሣያስፈልጋቸው በውርስ አጣሪው በተደረገው የማጣራት ስራ የስጦታው ሕጋዊ ያለመሆን ክርክር ከማቅረብ የሚከለከሉበት ምክንያት እንደሌለ ካሰፈረ በኋላ አከራካሪው ስጦታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443፣ 881 እና 882 እንደተገለፀው በአራት ምስክሮች ፊት ያልተደረገ እንደሆነና መጋቢት 18 ቀን 1987 ዓ.ም ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ ለመልስ ሰጭው አደረጉት በተባለው ስጦታ የሰፈሩት ሁለት ምስክሮች እንጂ በሕጉ መሠረት አራት እንዳልሆኑ፣ ስጦታው በአዋዋይ ፊት መከናወኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 እንደተጠቀሰው የምስክሮቹ ብዛት ወደ ሁለት አያስቀንሰውም፤ በዚሁ ዓንቀጽ መሠረት ምስክሮቹ ሁለት ሰዎች ብቻ በቂ የሚሆኑት ከምስክሮቹ አንዱ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ዳኛ ሆነው መደበኛ ሥራቸውን እየከናወኑ በነበሩበት ሲሆን ነው፤ በዚህ የስጦታ ጽሁፍ ግን ምንም እንኳ ስጦታው የተደረገው በአዋዋይ ፊት ቢሆንም ከሁለቱ ምስክሮች አንዱ ራሱ አዋዋዩ ባለመሆኑና በሕግ የሰፈረውን አባባል ስለማያሟሉ ተደረገ የተባለው ስጦታ ተቀባይነት የለውም፤ ይግባኝ ባዮቹ በቤቱ ላይ ድርሻ አላቸው በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎትም ከላይ የሰፈረውን የከፍተኛ ፍ/ቤቱ አተረጓጎም ተቀባይነት ያለው መሆኑና የአሁኑ አመልካች ያቀረቡለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 ተቀባይነት እንደሌለው በፍ/ይ/መ/ቁ. 33004 የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ አረጋግጧል፡፡

አመልካቹም ግንቦት 04 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው´አከራካሪው ቤት ከወ/ሮ ጥሩነሽ አበበ በስጦታ እንደተላለፈላቸውና የስጦታ ውሉም በውልና ማስረጃ ጽህፈት ቤት ቀርቦ በቁጥር 167/87 በ26/07/1987 ዓ.ም ተመዝግቦ ከ12 ዓመታት በላይ በይዞታዬ ስር ሆኖ እያለና የስር ፍ/ቤቱ ስጦታው በአግባቡ የተከናወነ ነው ብሎ እያለ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሉ በውልና ማስረጃ ፊት ቢፈፀምም በጽሁፉ ውስጥ አራት ምስክሮች አልተጠቀሱም አዋዋዩ ራሱ በውሉ ውስጥ በምስክርነት እስካልተጠቀሰ ድረስ ሁለቱ ምስክሮች በቂ አይደሉም በማለት የስጦታ ውሉን ማፍረሱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነውና ውሣኔው ይሻርልኝ ብለዋል፡፡

ተጠሪዎቹም ጥቅምት 11/2001 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም በስጦታ ውሉ የተጠቀሱት ሁለት ተራ ሰዎች እንጂ አንዳቸውም አዋዋይ ባለመሆናቸው በሕጉ የተቀመጠው የአራት ምስክሮች መሟላት በሌለበት ሁኔታ ስጦታው ሕጋዊ ሊሆን አይችልም፤ ስለሆነም የከፍተኛው ፍ/ቤት እና የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች ተገቢውን አተረጓጎም የተከተሉ በመሆናቸው ሊፀድቁ ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የግራ ቀኙ ወገኖች የክርክር አመጣጥ ከላይ በሰፈረው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ መጋቢት 18 ቀን 1987 ዓ.ም ለአመልካች ያደረጉት ስጦታ ተገቢውን ፎርማሊቲ ያሟላ ነው ወይስ አያሟላም? የሚለውን መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ጥያቄ በቀድሞ ወረዳ 09፣ ቀበሌ 06 የሚገኘው ቁጥሩ 579 የሆነውን ቤት የአውራሻቸው ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ እንደሆኑ በመግለጽ በውርስ አጣሪ ተጣርቶ ድርሻቸውን እንዲከፈላቸው ሲጠይቁ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ከላይ የተጠቀሰው ቤት ሟች ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ በውልና ማስረጃ ጽህፈት ቤት ቀርበው የሰጧቸው እንደሆነና የውርስ መጣራቱ አካል ሊሆን እንደማይገባው የሚጠቁም መልስ ሰጥተዋል፡፡ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ የተሾመው ውርስ አጣሪ አካል ባደረገው ማጣራት አከራካሪው ቤት ለአመልካቹ በስጦታ የተላለፈ እንደሆነና በውርስ ክፍፍሉ መካተት የለበትም የሚል የውሣኔ ሃሣብ ያቀረበ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱም ይህንን የማጣራት ውጤት ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡ በአሁኑ ተጠሪዎች ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ የስጦታው ሕጋዊነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443፣ 881/2/ እና 882 አኳያ ከሚፈለገው ፎርማሊቲ አንፃር ጉዳዩን በማጤን ምንም እንኳ ስጦታው በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተከናወነ ቢሆንም ውል አዋዋዩ በስጦታው ጽሁፍ እንደ አንድ ምስክር ሆኖ እስካልተጠቀሰ ድረስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 የተጠቀሰው የሁለት ምስክሮች ልዩ ሁኔታ ተሟልቷል ሊባል አይችልም፤ በፍ/ብ/ህ/ቁ.881/2/ በተጠቀሰው መሠረት በስጦታ ውሉ አራት ምስክሮች መጠቀስ ሲገባቸው ሁለት ምስክሮች ብቻ መዘርዘራቸው በቂ ባለመሆኑ ስጦታው በሕግ አስገዳጅነት ያለውን ፎርማሊቲ አላሟላም በማለት ተቀባይነት የለውም ብሏል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎትም የከፍተኛውን ፍርድ ቤት አተረጓጎም በመቀበል አመልካቹ ያቀረበለትን ይግባኝ ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 አተረጓጎም በሚመለከት ይህ የሰበር ችሎት ካሁን በፊት በሰ/መ/ቁ. 36777 ጥቅምት 25/2001 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ሲሆን ይኸውም የኑዛዜ ወይም የስጦታ ውል የተፈፀመው ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ከሆነ አዋዋዩ በኑዛዜው ወይም በስጦታ ውሉ ውስጥ እንደ ምስክር ሆኖ ባይፃፍም ምስክር አይደለም ተብሎ ሊተረጎም እንደማይገባ ነው፤ የኑዛዜው ወይም የስጦታው ሂደት ያለምንም ተጽእኖ በነፃነት እንዲከናወን በማድረግ የምዝገባውን ሂደት የመራ እስከሆነ ድረስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 መሠረት ኑዛዜው ወይም ስጦታው ተቀባይነት እንዲኖረው ሁለት ምስክሮች በቂ ናቸው፤ በተያዘው ጉዳይም ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ አከራካሪውን ቤት በውልና ማስረጃ ጽህፈት ቤት ማለትም ስራውን በማከናወን በነበረ አዋዋይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፊት ቀርበው ለአመልካች መስጠታቸውን ሁሉም የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ነው፤ ስለሆነም አዋዋዩ በስጦታው ሰነድ ስሙ በምስክርነት ባይፃፍም የስጦታ ሂደቱ ሲከናወን የነበረ ምስክር ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የስጦታ ውሉ አራት ምስክሮች ያልፈረሙበት ወይም ደግሞ ከምስክሮቹ አንዱ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ዳኛ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 45348፣ ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡

2/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ 33004 የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡

3/ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ. 22789፣ ጥር 12 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፤ ይፃፍ፡፡

4/ አከራካሪው የስጦታ ውል ስራውን ሲያከናውን በነበረ ውል አዋዋይ ፊት በመቅረብ የተከናወነ በመሆኑ ምንም እንኳ አዋዋዩ በስጦታ ውሉ ውስጥ በምስክርነት ባይጠቀስም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 በተጠቀሰው መንገድ እንደ ምስክር ስለሚቆጠር ስጦታው ተገቢውን የምስክሮች ብዛት /ፎርማሊቲ/ ያሟላ ነው ብለናል፡፡

5/ ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፤ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41896

የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ታደለች ዋለልኝ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ አዲስ አለም ፀጋው በሌሉበት

2. ወ/ሮ ማስተዋል አስማረ አልቀረቡም

3. አቶ እሸቱ ዓለምገና አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 41 መሰረት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በአሁን አንደኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መካከል የነበረውን የጋብቻ ክርክር ፍ/ቤቱ ተመልክቶ በአዲስ አበባ ከተማ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/05 ክልል የሚገኝ ቁጥር 242 የሆነው ቤት የሁለቱ የጋራ ሐብት ነው በማለት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ይህ ውሳኔ መብቴን የነካ ስለሆነ ሊሰረዝ ይገባል ሲሉ የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት መቃወሚያ አቅርበው መዝገቡ ከተከፈተ በኋላ የአሁን አመልካችም በበኩላቸው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 41 መሰረት መቃወሚያ አቅርበው ከሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ/ከአሁን ሦስተኛ ተጠሪ/ ጋር በትዳር እያለን በጋራ ያፈራነው መኖሪያ ቤት የመቃወም ተጠሪዎች ነው ተብሎ መወሰኑ መብቴን ስለነካ ይህ ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ጣልቃ ገብ ከሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ ጋር ጋብቻ የፈጸሙት በ26/3/2000 ዓ.ም እንደሆነ በማስረጃነት ያቀረቡት የጋብቻ የምስክር ወረቀት የሚገልጽ ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የመቃወም ተጠሪዎች የጋራ ሐብት ነው ተብሎ የተወሰነው ደግሞ ጣልቃገብና ሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት በ29/10/99 ዓ.ም ስለሆነ ጣልቃገብ ከሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ ጋር ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት የመቃወም ተጠሪዎች የጋራ ሐብት ነው ተብሎ በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ የተሰጠበት ንብረት የጣልቃገብ እና የሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ የጋራ ሐብት የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለውም፡፡ በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች በዚሁ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ከሦስተኛ ተጠሪ ጋር በባህል የተጋባነው በ1992 ዓ.ም ነው እያሉ የስር ፍ/ቤት ክርክር የተነሳበት ንብረት የተፈራው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካችና ሦስተኛ ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት ነው በማለት የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበል መቅረቱ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን ጠርቷል፡፡

ይሁንና አንደኛ ተጠሪ የፍ/ቤቱን መጥሪያ አልቀበልም ስለማለታቸው በአመልካች ቃለ መሐላ በመረጋገጡ ሁለተኛ ተጠሪም በምትክ መጥሪያ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት እንዲታይ ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ሦስተኛ ተጠሪ ቀርበው ከአመልካች ጋር በባህል የተጋቡት በ1992 ዓ.ም እንደሆነ ገልጸው በአቤቱታው መሰረት ቢወሰን ተቃውሞ የለኝም ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ከሦስተኛ ተጠሪ ጋር በ1992 ዓ.ም በባህል መጋባታቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ በአስረጅነት ለስር ፍ/ቤት ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍ/ቤት አቤቱታቸውን ሳይቀበለው የቀረው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ክርክር የተነሳበት ንብረት የተፈራው አመልካችና ሦስተኛ ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት ስለሆነ በንብረቱ ላይ መብት የላቸውም በማለት ነው፡፡ ለዚህም ውሳኔ መሰረት ያደረገው አመልካችና ሦስተኛ ተጠሪ የፈጸሙት ጋብቻ በ26/3/2000 ዓ.ም በክብር መዝገብ ሹም የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጠውን የጋብቻ የምስክር ወረቀት በመመልከት ነው፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 28/1/ ላይ ጋብቻው የተፈጸመው በማንኛውም የጋብቻ አፈጻጸም ስርአት ቢሆንም አግባብ ባለው የክብር ሹም መመዝገብ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን ጋብቻው ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ጋብቻው ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ 28/3/ ላይ ተመልክቷል፡፡

በአመልካችና በሦስተኛ ተጠሪ መካከል የተፈጸመው ጋብቻ ተመዝግቦው በ26/3/2000 ዓ.ም ቢሆንም ከዚህ ቀን በፊት ጋብቻው የተፈጸመ መሆኑ ከተረጋገጠ ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው ስለሚችል በዚሁ መሰረት ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔ መስጠት ሲገባው ጋብቻው የተመዘገበበትን ቀን መሰረት በማድረግ ከዚህ በፊት ጋብቻ ስለሌለ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19258 በ7/1/2001 ዓ.ም የሰጠው ከፊል ውሳኔና የፌደራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 73407 በ23/3/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካችና በሦስተኛ ተጠሪ መካከል የባህል ጋብቻ መፈጸሙን በማጣራት ክርክር በተነሳበት ንብረት ላይ እንዲወሰን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 343/1/ መሰረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38691

የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ለገሰ ቢራቱ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ደረጀ ጅማ ገርግሶ - ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ የጀመረው በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ አባት አቶ ጅማ ጌርጐሶ አመልካች ላይ በነበረባቸው እዳ ምክንያት እሣቸው በመሞታቸው ተጠሪን ጨምሮ በሚች ባለቤትና ወራሾች ላይ ክስ ተመስርቶ ተፈርዶባቸዋል፡፡ ይህንንም ፍርድ ለማስፈፀም አመልካች በባለእዳዎቹ ላይ የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል፡፡ ለውሣኔው ማስፈጸሚያም እንዲሆን አሁን ክርክር የተነሣበት ቤት በ25/04/98 በተደረገ ጨረታ በብር 38,200 (ሰላሣ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ብር) አሸናፊ የተገኘ ቢሆንም አሸናፊው ገንዘቡን ባለመክፈላቸው አመልካች ቤቱ በድጋሚ ጨረታ እንዲሸጥ አመልክተዋል፡፡ በዚህን ጊዜ የአሁኑ ተጠሪ በ28/04/98 በተፃፈ አቤቱታ በሐራጅ እንዲሸጥ የታዘዘው ቤት የግል ቤታቸው በመሆኑ ጨረታው እንዲቆም ሲሉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የተጠሪን ጥያቄ መርምሮ ተጠሪ አቤቱታውን ያቀረቡት ቤቱ በጨረታ በ25/04/98 ተሸጦ በ03/05/98 ስለሆነና የዘገዩበትን ምክንያትም ስላልገለፁ እንዲሁም የባለንብረትነት ማስረጃም ስላላቀረቡ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ጥያቄ ያቀረቡት አመልካች በመሆናቸው ቤቱ የተጠሪ አባት መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለባቸው አመልካች ናቸው፤ነገር ግን ቤቱ የተጠሪ አባት መሆኑን አላረጋገጡም፤ተጠሪም የወራሽነት መብታቸውን ተጠቅመው አባታቸውን የወረሱ ለመሆኑም አልተረጋገጠም፤ተጠሪ የግብር ደረሰኝና የቀበሌ ማ/ፍ/ቤት ውሣኔ በማስረጃነት አቅረበዋል በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

አመልካች በተራቸው በዚህ ውሣኔ ላይ አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅረበዋል፡፡ ችሎቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ፤ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ ያቀረቡት የመጀመሪያው ጨረታ ከመደረጉ በፊት ነው፤በመሆኑም አቤቱታቸው ሊስተናገድ ይገባል፤ክርክር የተነሣበት ቤት የተጠሪ አባት ቤት ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ በአግባቡ ተጣርቷል ወይ? የሚለው ከመታየቱ በፊት ግን ዋናው ውሣኔ የተሰጠው በአቶ ጅማ ጊርጐሶ ወራሾች ላይ በመሆኑ አፈፃፀሙ ሊቀጥል የሚገባው በወራሾች ንብረት ላይ ነው፡፡ የሚች ንብረት ለወራሾች ከተላለፈ የሚች ንብረት ተብሎ ሊቀርብ የሚችል የለም፡፡ አመልካችም በተጠሪ ንብረት ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የቀረበው ክርክር ከሚች ንብረት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በሚች ንብረት ደግሞ አፈፃፀም ሊቀጥል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለማይችል የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም በሌላ በኩል ግን ተጠሪ የሚች ወራሽ ለመሆናቸው አልተረጋገጠም የተባለው ዋናውን ውሣኔ የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሣኔ አሻሽሏል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የተጠሪ አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት በሐራጅ እንዲሸጥ የታዘዘው ቤት የግል ንብረታቸው በመሆኑ ሐራጁ እንዲቆምላቸው ሲሆን መሰረት ያደረጉትም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 ድንጋጌ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በአፈፃፀም ምክንያት ንብረት እንዲያዝ ሲታዘዝ በዚሁ ንብረት ላይ ተቀዳሚ መብት አለኝ የሚል ተቃዋሚ ሲቀርብ የሚያገለግል ነው፡፡ በመጀመሪያ ክርክር ላይ ተካፋይ ባይሆኑም በሚያዘው ንብረት ላይ መብት አለን የሚሉ ወገኖች የሚያቀርቡትን መቃወሚያ ፍ/ቤቱ ሊመረምር የሚገባው ቢሆንም ተቃዋሚዎቹ መቃወሚያውን በቂ ባልሆነ ምክንያት አዘግይተው ከሆነ ግን መቃወሚያው ላይመረመር እንደሚችል ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ የአመልካችም አቤቱታ ቢሆን ተጠሪ ተቃውሞውን አዘግይተው ያቀረቡ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ሊመረምረው አይገባም ነበር፡፡ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የሰ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጨረታው የወጣው በ25/04/98 ሲሆን መቃወሚያው የቀረበው በ03/05/98 በመሆኑ አላግባብ ዘግይቶ የቀረበ ሲሆን ለመዘግየቱም በቂ ምክንያት መኖሩን ተጠሪ አላስረዱም በሚል የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ ቢያደርገውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሰበር ችሎት ጥያቄው የቀረበው ከጨረታው በፊት ነው በማለት አረጋግጧል፡፡ መቃወሚያው መቼ ቀረበ? የሚለው ነጥብ ደግሞ በማስረጃ የሚረጋገጥ ፍሬ ነገር በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊስተናገድ የሚችል አልደለም፡፡

በሌላ በኩል ግን ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 በሚጠይቀው መሰረት ተቀባይነት ያለው መቃወሚያ ለማቅረባቸው የስር ፍ/ቤቶች በአግባቡ መርምረዋል ወይ? የሚለው መታየት የኖርበታል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰ/ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ ለመሻር መሰረት ያደረገው በሐራጅ እንዲሸጥ የታዘዘው ቤት የተጠሪ አባት ቤት ነው ያሉት አመልካች ስለሆኑ ይህንኑ በቅድሚያ የማረዳት ሸክም ያለባቸው አመልካች ናቸው፡፡ ነገር ግን አላስረዱም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418/3/ ተቃዋሚው ወይም መብት አለኝ ባዩ ከመቃወሚያ ማመልከቻ ጋር በንብረቱ ላይ ያለውን ተቀዳሚነት መብት ወይም ባለይዞታነቱን የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ማስረጃ አያይዞ በማቅረብ በቅድሚያ መብቱን የማስረዳት ሸክም ያለበት ለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍ/ቤቱ ግን በቅድሚያ ሊመረምር የሚገባው የአመልካች ማስረጃ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የተጠቀሰውን የሥነ-ሥርአት ህጉን የተከተለ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠሪ ክርክር የተነሣበት ቤት የራሣቸው እንጂ የአባታቸው ያለመሆኑን በቂ ማስረጃ ያቀረቡ መሆን አለመሆኑን በአግባቡ ሣያጣራ አልፎታል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ በዋናው መዝገብ የተከሰሱት የአባታቸው ወራሽ በመሆናቸው ሲሆን በዚህ መዝገብም ተወስኖባቸዋል፡፡ ይህንን ውሣኔ አባታቸውን የወረሱ ባለመሆኑ ውሣኔው ሊሻር ይገባል፡፡ ብለው በይግባኝ ውሣኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ሰበር ችሎት በዋናው መዝገብ ከተሰጠው ውሣኔ ጋር ይቃረናል በማለት ሽሮታል፡፡ ይህን በተመለከተ ተጠሪ ያቀረቡት አቤቱታ የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የሚች አባታቸው ወራሽ መሆናቸውን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ነገር ግን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በአንድ በኩል ተጠሪ የአባታቸው ወራሽ በመሆናቸው በአባታቸው እዳ ተከሰው የተፈረደባቸው ለመሆኑ እያመነ በሌላ በኩል ግን የተወሰነው በወራሾች ላይ በመሆኑ አፈፃፀሙ ሊቀጥል የሚገባው በወራሾች ንብረት ላይ እንጂ በሚች ንብረት ላይ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

በመሰረቱ በሚች መሞት ምክንያት የሚቋረጡ ካለሆነ በቀር የሚቹ መብትና ግዴታዎች ለወራሾቹና ለኑዛዜ ባለስጦታዎች እንደሚተላለፍ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 826/2/ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑ ወራሾች የአውራሻቸውን ግዴታ በወረሱት የሚቹ ንብረት ወይም ሐብት መጠን እንዲወጡ ይገደዳሉ፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪ እና ሌሎቹ የሚች ወራሾች ተከሰው የተፈረደባቸው በአባታቸው እዳ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም እዳውን እንዲከፈሉ የሚጠየቁት ከአባታቸው በወረሱት ሐብት መጠን ነው፡፡ ስለሆነም ለእዳው መክፈያ በአፈፃፀም ሊያዝ የሚገባው ከአባታቸው በውርስ ያገኙት ንብረትና ሐብት እንጂ የወራሾቹ የግል ሐብት ሊሆን አይገባም፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን የተወሰነው በወራሾች ላይ በመሆኑ ብቻ አፈፃፀሙ ሊቀጥል የሚችለው በወራሾች ንብረት ላይ እንጅ በሚች ንብረት ላይ አይደለም የደረሰበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መደምደሚያ የተሣሣተ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እዚህ የተሣሣተ መደምደሚያ ላይ በመድረሱም ክርክር የተነሣበት ቤት ተጠሪ አባት ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ቀርቦ በአግባቡ መጣራቱን በተመለከተ የያዘውን ጭብጥ ውሣኔ ሣይሰጥበት አልፎታል፡፡

በአጠቃላይ የኦሮሚያ የጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ የሰበር ችሎቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 በሚያዘው መሰረት በቂ የጽሁፍ ማስረጃ መቅረብ አለመቀረቡን ሳያጣሩ የተጠሪን መቃወሚያ ተቀብለው የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ ካደረገበት ምክንያት አንዱ ተጠሪ መብታቸው ለማረጋገጥ ማስረጃ አላቀረቡም የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ከግራ ቀኙ በቃል እንዳጣራውም ቢሆን ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418/1/ መሰረት መቃወሚያ ሲያቀርቡ በቤቱ ላይ ባለመብት ለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የግብር ደረሰኝና የቱሉ ሚልኪ ክተማ 01 ቀበሌ ቤቱ የተጠሪ ለመሆኑ የሰጠው ማረጋገጫ ነው፡፡ እነዚህ ደረሰኞች ደግሞ ክርክር የተነሣበት ቤት ባለቤት ተጠሪ ለመሆናቸው ማስረዳት የሚችሉ በቂ ማስረጃዎች እንዳልሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በዚህም ምክንያት ነው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የቀዳሚነት መብት ያላቸው መሆኑን የሚያስርዳ በቂ ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ ቤቱ በሃራጅ እንዳይሸጥ መከልከሉ አግባብ ሆኖ አላገኘውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38529 በ09/02/2000 ዓ.ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 45292 በ04/09/2000 ዓ.ም ክርክር የተነሣበት ቤት በሐራጅ እንዳይሸጥ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07488 በ18/05/98 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡ ቤቱ በሐራጅ ሊሸጥ ይገባል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38126

መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ዲያቆን ኃ/ጊዮርጊስ ወንድም ሲያምረኝ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ የሺ ተፈሪ (2 ሰዎች) - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አንደኛ ተጠሪ ናቸው፡፡ በክሣቸው ከአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት ሆነው በጋራ የሰሩት የእሣቸው ፈቃድ ሣይኖር ሁለተኛ ተጠሪ ለአመልካች መስጠታቸውን በመግለጽ የሽያጩ ውል ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ጋር የሚቃረንና ሕጉ የሚጠይቀውን ፎርማሊቲ ያልተከተለ በመሆኑ ፈራሽ ነው እንዲባልላቸው ጠይቀዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723(1) መሰረት በህግ የሚጠይቀውን የአፃፃፍ ስርአት አልተከተለም በማለት ውሉ እንዲፈረስ ውሣኔ ሰጠ፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ መልስ ሰጪን መጥራት ሣያስፈልግ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች ዋነኛ ቅሬታ የስር ከሣሽ ያቀረቡት ክስ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አ/ቁ. 213/92 አንቀጽ 69/2/ መሰረት በይርጋ የታገደ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለቱ ተጠሪዎች ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብ ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት አንደኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት የጋራ ቤታቸውን ሁለተኛ ተጠሪ ያለ እሳቸው ፈቃድ ለአመልካች ከመሸጣቸውም በላይ ውሉ በሕግ የተመለከተውን የአፃፃፍ ስርአት ስለማያሟላ እንዲፈርስላቸው ነው፡፡ አመልካች የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚልና ሌላም መቃወሚያ እንዲሁም ለዋናው ጉዳይ በአማራጭ ሙሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ በቅድሚያ ሊታይ ይገባል፡፡

ከመዝገቡ ላይ በአመልካችና በሁለተኛ ተጠሪ መሐከል የሽያጭ ውል የተደረገው ጎዳር 1 ቀን 1995 መሆኑና የስር ከሣሽ ወይም የአሁኗ አንደኛ ተጠሪ ክስ የመሰረቱት በ09/08/1999 ዓ.ም መሆኑን ተረድተናል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ክሱን የተቃወሙት ውል የተደረገበት ቤት ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር ያፈሩት የጋራ ንብረት በመሆኑ ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 68 ፊደል "ሀ" ስር የጋራ የሆነውን የማይንቀሣቀስ ንብረት ለመሸጥ የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ስምምነት ሣይኖር የተደረገ ሽያጭ ውጤቱ ምን እንደሆነ በዚህ ህግ አንቀጽ 69 ስር ተቀምጧል አንደኛው ተጋቢ በሌላኛው ተጋቢ ስምምነት ሣይኖር የጋራ የሆነውን የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ እንደሆነ ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ውሉ እንዲፈርስ ሲጠይቅ እንደሚችልና ፍ/ቤቱ ውሉን ማፍረስ እንደሚችል ተገልጾአል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ በጋብቻ ጊዜ ያፈሩት የጋራ ቤት የአንደኛ ተጠሪ ፈቃድ ሣይኖር ተሸጦ ከሆነ ተጠሪዋ ውሉ እንዲፈረስ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው መገባቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከ6 ወር በኋላ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ እንደማይችል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69/2/ ስር ተደንግጓል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው በሁለተኛ ተጠሪና በአመልካች መሐከል የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው 01/03/95 ሲሆን አንደኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ደግሞ በ09/08/99 ከአራት አመት በኋላ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረገው የስር አንደኛ ተከሣሽ ከሣሽ በሆኑበት መዝገብ አንደኛ ተጠሪ ተከሣሽ ሆነው ቀርበው ተከራክረው ከተወሰነ በኋላ ፍ/ቤቱ የአንደኛ ተጠሪን ክስ የማቅረብ መብት የጠበቀላቸው በመሆኑና ይህም ውሣኔ ከተሰጠ ጀምሮ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ክሱ በመቅረቡ ይርጋው ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ አንድ ክስ ለማቅረብ በህጉ የተመለከተው በይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ክስ ማቅረብ የማይቻል ቢሆንም ነገር ግን አሁንም ህጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ምክንያቶች የይርጋው ጊዜ ሊቋረጥ እንደሚችልና አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር እንደሚጀምር የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1852/1/ ያመለክታል፡፡ ወይም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853 ስር የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም ፍ/ቤቱ የይርጋን መቃወሚያ አልቀበልም ለማለት ይችላል፡፡ ይርጋ የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች የሚባሉት የባለእዳው እዳው ማመኑ፣ ወለድ ወይም ከእዳው ላይ ከፊሉን መክፈሉ፣ መያዣ ወይም ዋስ መስጠቱ ወይም ደግሞ ባለገንዘቡ መብቱ እንዲታወቅለት በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ባለእዳውን ማሣወቁ መሆናቸው ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851(1)(2) መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሽያጭ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አንደኛ ተጠሪ ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ 4 አመት ያለፈው በመሆኑ ክሣቸው በተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 69/2/ መሰረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡ በዚህ አራት አመት ውስጥ ይርጋውን የሚያቋርጡ ሁኔታዎች (በህጉ በተመለከቱት አይነት) ስለማጋጠማቸው የቀረበ ነገር የለም፡፡ ፍ/ቤቱ በጠቀሰው መዝገብ ላይ የአንደኛ ተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት ያላቸው መሆኑ መገለጽ የይርጋውን ጊዜ ለማቋረጥ የሚበቃ ምክንያት አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል በተጠቀሰው መዝገብ አንደኛ ተጠሪ ተከሣሽ እንጂ ከሣሽ ለመሆናቸው መብታቸው እንዲታወቅላቸው በፍ/ቤት ክስ አቅርበዋል ሊባል የሚችሉ ባለመሆናቸው በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851/ለ/ መሰረት የይርጋው ጊዜ ተቋርጧል ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ውሉ ከተደረገ ከ4 አመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ሊቋረጥ ሲገባ የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ማደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58635 በ12/09/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 44809 በ27/11/99 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የከሣሽ የዳኝነት ጥያቄ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 69/2/ መሰረት በይርጋ ይቋረጣል ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38152

ሚያዝያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የወ/ሮ ገነት ዳምጤ ወራሾች - ጠበቃ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- እነ አቶ ይስማ አስፋው - ጠበቃ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የውርስ ሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 11 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 847 የሆነውን ቤት ጥቅምት 19 ቀን 1962 ዓ.ም. ሟች ወ/ሮ ተካበች ሀብተወልድ ባደረጉት ኑዛዜ ለከሣሾችና የተከሣሽ ባለቤት ለሆነው ወንድማችን ሠጥተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አውራሻችን ወ/ሮ ተካበች ሀብተወልድ በባንክ ያስቀመጡትን ብር 4,666(አራት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት) ወንድማችንና የተከሳሽ ባለቤት የሆኑት ወስደው አላካፈሉንም፡፡

ስለዚህ ተከሣሽ ከላይ የተጠቀሰውን ቤትና አብረውት ያሉትን ቤቶች እንደዚሁም ከገንዘቡ እንዲያካፍሉን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሽ /የአሁን አመልካቾች አውራሽ/ ቀርበው በሰጡት መልስ ከሳሾች አውራሻችን የሚሏቸው ወ/ሮ ተካበች ሀብተወልድ ከሞቱ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 ላይ እንደተቀመጠው በ3 ዓመት ጊዜ የውርስ ሀብት ይገባናል በማለት ጥያቄ ያላቀረቡ ስለሆነ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ለፍሬ ጉዳዩም ሙሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም የይርጋ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ ክስ የቀረበበት ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ስለሆነ 2/3ኛውን ከሣሾች ቀሪውን 1/3 ደግሞ ተከሣሽ እንዲወስዱ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ባለመቀበል ውሣኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በሥር ፍ/ቤት በአመልካቾች አውራሽ በኩል የተነሳው የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተጠሪዎች ባሉበት ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ እንደተቻለው ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት ተጠሪዎች ሟች ወ/ሮ ተካበች ሀ/ወልድ በኑዛዜ ሠጥተውናል የሚሉት በ1962 ዓ.ም. ሲሆን ወ/ሮ ተካበች ሀ/ወልድ ደግሞ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በ1968 ዓ.ም.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ የውርስ ንብረቱ ድርሻችንን የአመልካቾች አውራሽ ሊያካፍሉን ይገባል በማለት ክስ የመሠረቱት በ1994 ዓ.ም. ነው፡፡

በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የአመልካቾች አውራሽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 ላይ የተመለከተውን በመጥቀስ ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንዳሰፈረው አንድ እውነተኛ የሆነ ወራሽ ትክክለኛው ወራሽ መሆኑ ታውቆለት ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የውርሱን ንብረት በእጁ ያደረገው ሰው የውርሱን ንብረት እንዲለቅ ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ ነው፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ በአመልካቾች አውራሽ ላይ ክስ ቀርቦ የነበረው ምንም ዓይነት መብት ሳይኖራቸው ይዘውት የሚገኘውን የውርስ ሀብት ድርሻችንን ትልቀቅልን በማለት ስለሆነ የተጠቀሰው ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት አይኖረውም፡፡

ተጠሪዎች በዚህ መልኩ ያቀረቡት አቤቱታ በምን ያሕል ጊዜ መቅረብ እንዳለበት በውርስ ሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ የውርስ ሕጉ በዚህ ረገድ ክፍተት ካለበት ወደ ጠቅላላ ሕግ በመሄድ ለጉዳዩ እልባት መስጠት በሕግ አተረጓጎም መርህ /principles of legal interpretation/ የተፈቀደ ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሕጉ ጠቅላላ ስለውሎች ከተደነገገው አንፃር ተመልክተነዋል፡፡ በዚህ ክፍልም ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆንም በውል ሕግ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዳላቸው በቁጥር 1677/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በውል ሕግ ደግሞ ዋናው የይርጋ ድንጋጌ በቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች በውርስ የተላለፈልንን ድርሻ ንብረታችንን ሊለቁልን ይገባል በማለት በአመልካቾች አውራሽ ላይ ክስ የመሠረቱት ከላይ እንደተመለከተው በ1994 ዓ.ም. ሲሆን ኑዛዜውን አድርገዋል የተባሉት ግለሰብ በሞት የተለዩት ደግሞ በ1968 ዓ.ም. ነው፡፡ ኑዛዜው ከሚሞት ሞት በኋላ ውጤት የሚኖረው እንደመሆኑ መጠን ሟች ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጠሪዎች አቤቱታውን ማቅረብ ሲገባቸው ከ26 ዓመት በኋላ ጥያቄውን ማቅረባቸው በይርጋ የማይታገድበት ምክንያት አይኖርም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 ለዚህ ጉዳይ አግባብነት አይኖረውም ማለታቸው ተገቢ ቢሆንም ነገር ግን ከ26 ዓመት በኋላ የቀረበን የውርስ ንብረት ክፍያ ጥያቄ ከጠቅላላ ሕግ አኳያ በይርጋ የታገደ ሆኖ ሳለ ከዚህ አንፃር የይርጋ ክርክሩን ሳይመለከቱት መቅረታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18669 በ24/01/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 61155 በ21/9/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሃሣብ ልዩነት

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ፣ ተጠሪዎች የወ/ሮ ተካበች ሀብተወልድ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ ንብረቱን ከሚች መካሻ ጌታነህ የአመልካች ባል ጋር በጋራ የያዙትና የባለቤትነት ደብተር በጋራ ያወጡ መሆኑን ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ የተገለፀ በመሆኑ ይህም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1053 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የወራሾቹ የጋራ ንብረት እንደሆነ ስለሚቆጠርና ተጠሪዎች ይህንን የጋራ ሀብታቸውን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1272 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በማንኛውም ጊዜ ለመከፋፈል ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉ በመሆኑ ተጠሪዎች ንብረት ለመካፈል ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ እይቋረጥም በማለት የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬያለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37313

ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካቾች፡- 1. አቶ መሐሪ ተክለማርያም
2. ወ/ሮ መድህን ወልዱ
} ጠበቃ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- የወ/ሮ ገነት መኮንን ወራሾች

1. ወ/ት ሜሮን ብርሃኑ - ቀረበች
2. ወ/ት ህሊና ብርሃኑ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሆኖ ተጠሪዎች ከሳሾች ሲሆኑ አመልካቾች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ክሱም የሚች ብርሃኑ ጫላና የእኔ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሞግዚት አድራጊዎቼ የውርስ ንብረት የሆነውን በወረዳ 25 ቀበሌ 01 ቁጥሩ 714 የሆነውን መኖሪያ ቤት ከሕግ ውጪ የያዙበት ውል ፈራሽ ሆኖ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የባልና ሚስት የጋራ ሀብት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ ኖረው አያውቁም፣ ሚስት ወ/ሮ ዘቢደር አናውጤ እንጅ ከሳሽ አይደሉም ተጠቃሹ ቤት ወ/ሮ ገነት መኮንን ጋብቻ መሠረትን ከሚሉት ከ1973 ዓ.ም በፊት አቶ ብርሃኑ ጫላና ባለቤታቸው ወ/ሮ ዘቢደር አናውጤ 1966 ዓ.ም የገዙት ለመሆኑ ማስረጃ አለ፡፡ ስለዚህ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) መሠረት ለመክሰስ ስለማይችሉ ክሱ ይሠረዝ በማለት መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 06185 በ8/2/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ወ/ሮ ገነት መኮንን የሚች አቶ ብርሃኑ ጫላ ሚስት መሆናቸው በፍ/ቤት በመ/ቁጥር 01783 ከተወሰነ በኋላ ወ/ሮ ዘብይደሩ አናውጤ ተቃዋሚ ሆነው ገብተው ተከራክረው ፍ/ቤቱ ወ/ሮ ገነትን ሚስትነት ስላፀናው ይግባኝ ቀርቦ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 17437 ላይ በ30/5/98 ዓ.ም በዋለው ችሎት የወ/ሮ ዘቢደሩ ምሥክሮች ተሰምተው እንደገና በመቃወሚያ አቤቱታው ላይ ውሳኔ እንዲሠጥበት ጉዳዩን ለታች ፍ/ቤት የላከው ሲሆን ወ/ሮ ዘብይደሩ በክርክሩ ሳይቀጥሉ ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ወ/ሮ ገነት መኮንን የሚች ብርሃኑ ጫላ ሚስት ናቸው፣ሚች ወ/ሮ ገነት እና ሚች አቶ ብርሃኑ ሲጋቡ በ6-10-73 ዓ.ም ባደረጉት የጋብቻ ውል ላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የጋራ እንዲሆን ብለዋል፡፡ የእሳቸው ድርሻ ላይ ፈቃድ ሳይጠየቅ የተደረገ ውል ሊሠረዝ ይገባል በማለት የሽያጩ ውል ተሠርዞ ቤቱን ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 59947 በሆነው መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚስትነት ዙሪያ ያለው ክርክር ሁለቱም ተከራካሪዎች በሕይወት የሌሉ በመሆኑ አመልካቾች ወ/ሮ ገነት ሚስት አይደሉም፣ ወ/ሮ ዘቢደር ሚስት ናቸው የሚል ክርክር የሕግ መሠረት የለም። ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 መሠረት በሕግ ፊት የሚፀና አይደለም በማለት ውሳኔውን በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው።

አመልካቾች ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ያቀረቡት ቅሬታ፡-

- ተጠሪዎች የሚች ብርሃኑ ጫላ ልጆችና ወራሾች መሆናቸው እና የወ/ሮ ገነት መኮንን ሚስትነት የተረጋገጠበት ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተሰርዞ ጉዳዩ እንደገና ታይቶ እንዲወሰን ተብሎ የታዘዘ ቢሆንም ለሥር ፍ/ቤት እንዲያቀርቡ የታዘዘውን ማስረጃዎች ሳያቀርቡ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው በሕግ ፊት የሚፀና የሚስትነት ውሳኔ አልተሠጠም።
- ተጠሪዎችም የሚች ብርሃኑ ጫላ ልጆች ብሎም ሕጋዊ ወራሾች መሆን የሚመሠረተው ሚች እናታቸው የሚች አቶ ብርሃኑ ጫላ ሚስት ናቸው ከሚል ከተረጋገጠ ፍሬነገር በመነሳትና በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ ልጆች አባት የእናታቸው ባል ነው በሚለው የሕግ ግምት መሠረት ነው። ሆኖም የእናታቸው ሚስትነት ሳይረጋገጥ የተጠሪዎች ወራሽነት ተረጋግጧል ለማለት ስለማይቻል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል በማለት ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው።

ቅሬታውን መሠረት በማድረግ የተጠሪዎች እናት የሚች አቶ ብርሃኑ ጫላ ሚስት መሆናቸውና የተጠሪዎች ወራሽነት አልተረጋገጠም እየተባለ ለክርክሩ መንስኤ የሆነው ቤት ያለተጠሪዎች እናት ፈቃድ በሚች የተሸጠው በሕግ አግባብ አይደለም፣ ውሉም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 ላይ የተቀመጠውን መስፈርት አያሟሉም ተብሎ አመልካቾች ቤቱን ያስረክቡ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዞ ግራ ቀኙ በዚህ ፍ/ቤት የጽሑፍና የቃል ክርክር አካሂደዋል። በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ክርክር በአጭሩ በምሥክሮች መስማት ረገድ ለወ/ሮ ዘቢደር መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቁ አጋጣሚ ስለሚፈጠር ምስክሮች ቃል ይሰማ ተብሎ የተሠጠውን ውሳኔ አመልካቾች መከራከሪያ ሊያደርጉ አይችሉም። እንደገና እንዲታይ መመለስ የመክሰስ መብትንና ጥቅምን አያሳጣም። በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የጋብቻ ውል ላይ ተለይቶ የተሠጠ ውሳኔ የለም በማለት ውሳኔው እንዲፀና ተከራክረዋል።

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር እንደሚከተለው መርምረናል።

በቀዳሚነት ሊታይ የሚገባው የሕግ ነጥብ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ጉዳዩን መጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት እንደገና መልሶ እንዲያይ ጭብጥ ይዞ መመለስ የቀድሞውን ውሳኔ የመሻር ውጤት ይኖረዋል ወይንስ አይኖረውም? የሚለው ነጥብ መታየት የሚገባ ነው። የተጠሪዎች ክርክር በጥቅሉ ሲታይ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ቢመለስም የሚስትነትን ውሳኔ አልሻረውም የሚል ነው። የአመልካቾች ክርክር ደግሞ የቀድሞ ሚስትነት ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ክርክር ተካሂዶ ውሳኔው ተሠርዞ ጉዳዩ እንደገና ታይቶና ማስረጃ ተሰምቶ እንዲወሰን በተባለው መሠረት እንዲያቀርቡ የታዘዙትን ምስክሮች ሳያቀርቡ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው በሕግ ፊት የሚፀና የሚስትነት ውሳኔ የለም በማለት ነው። እንግዲህ አንድ ፍ/ቤት የሠጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ክርክር ተሰምቶ ጉዳዩ እንደገና መጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት መልሶ እንዲያየው ከተደረገ የቀድሞ ውሳኔ እንዳልተወሰነ ወይም በውሳኔው የተገኘው መብት እንደሌለ ወይም እንደተሻረ የሚቆጠር ነው። በተያዘው ጉዳይ የተጠሪዎች እናት ሚስት ናቸው ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ማስረጃ ተሰምቶ እንዲወሰን ታች ወደ ወሰነው ፍ/ቤት ተመልሷል። በተመለሰው ውሳኔ መሠረት ክርክር ሳይደረግና የተባለው ምሥክሮች ክርክርም ሳይካሄድ የሚስትነታቸው ጉዳይ በእንጥልጥል ላይ ቀርቷል። በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች እናት ሞግዚትነት የተገኘው የሚች ሚስት ነበሩ ልጆችም የተወለዱት ከሚስትነታቸው ነው ተብሎ በፍ/ቤት በተረጋገጠው ውሳኔ መሠረት ነው። ይህ ውሳኔ ደግሞ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንዳልተወሰነ ተደርጐ እንደገና ምሥክሮች ተሰምቶ እንዲወሰን ከተደረገና ክርክር ተካሂዶበት ውሳኔ ካልተሠጠ በስተቀር በእንጥልጥል ላይ ያለ ጉዳይ ከሚሆን በስተቀር በሕግ ፊት የሚፀና ሚስትነትን የሚያረጋግጥ ውሳኔ አለ ለማለት አይቻልም። የጽሑፍ የጋብቻ ውልን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለይቶ አልወሰነውም የሚለውን ክርክር በተመለከተ የውሳኔው ይዘት ሲታይ በጽሑፍ ውል ላይ ብቻ ተንተርሶ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሠጠው ውሳኔ ያለአግባብ በመሆኑ የምሥክሮች ቃል በመስማት እንዲወሰን መባሉ የጽሑፍና የሰው ማስረጃዎች ሁለቱም ተመዝኖ ሊወሰን የሚገባ መሆኑን የሚያመለክት እንጅ ውሉን አልነካውም የሚያስብል የሕግ መሠረት አይኖርም። የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው በከፍተኛ ፍ/ቤት የሚስትነት ውሳኔ አልተሻረም በማለት ነው። ለሽያጩም ውል መፍረስ ምክንያት የሆነው ያለሚስት ፈቃድ የተደረገው የሽያጭ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሠረዝ ይገባል በማለት የውሳኔው መሠረት ሚስትነት ነው፡፡ የሚስትነት ውሳኔ አልተሻረም የተባለው ውሳኔ ከፍ ሲል እንደተመለከተው እንዳልተወሰነ ወይም እንደሌለ የሚቆጠር ውሳኔ ነው፡፡ ውሳኔው እንደሌለ ወይም እንዳልተወሰነ የሚቆጠር ከሆነ ደግሞ ከዚህ የሚመነጭ መብትም ሆነ ጥቅም ሊኖር አይችልም፡፡ የሽያጩ ውል እንዲሠረዝ ለመቃወም መብት የተገኘው ከሚስትነት ነው፡፡ ሚስትነት ከሌለ ደግሞ መቃወሚያ ማቅረብ አይቻልም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) መሠረት ተጠሪዎች የመክሰስ መብት የላቸውም በማለት ያቀረቡትን ክርክር ፍ/ቤቱ ባለመቀበል የሠጠው ውሳኔ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ማረም ሲገባው በማጽናት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 06185 በ8/2/2000 ዓ.ም እንዲሁም የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 59947 መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡ የፃፍ፡፡
2. ተጠሪዎች የመክሰስ መብት የላቸውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 42525

ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ አቶ ዓብዱልዋሲቅ አርጋው - ጠበቃ ተስፋዬ ተገኘወርቅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አለውያ አባበሊስ - ወኪል ኑርአዲስ አርጋው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ህግን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በውርስ ማጣራት ሂደት ነው፡፡ የውርስ ማጣራቱን ሥራ የውርስ አጣሪው እንዲያከናውንና ሪፖርቱን ለፍ/ቤቱ እንዲያቀርብ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሠጥቶ የውርስ አጣሪው የሚች አቶ አራጋው ከድር የውርስ ንብረት አጣርቶ ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ ሪፖርት ለፍ/ቤቱ አቅርቦ ሪፖርቱ በፍ/ቤቱ ፀድቆ ተመዝግቧል፡፡

ለዚህ የሠበር ክርክር መነሻ የሆነው የሪፖርቱ ክፍል ደግሞ የውርስ አጣሪው በአ/ክ/ክ/ከተማ ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 270 የሆነ የንግድ ሱቅ ድርጅት ተጠሪ ከመንግስት በ1986 ዓ.ም የተከራዩት ነው እንጂ ከሚች አቶ አራጋው ከድር ጋር በጋራ የተከራዩት ንብረት አይደለም በማለት ያቀረበው ነጥብ በፍ/ቤት መፅደቁ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ አመልካቾች የበታች ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚሉበትን ምክንያት ጥር 05 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፉት 5/አምስት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ አመልካቾች ክርክራችን ለማስረዳት ያቀረብናቸው ማስረጃዎች ሣይሰሙ ውሣኔ መስጠቱ ያላግባብ ስለሆነ የበታች ፍ/ቤቶች ትዛዞች ተሽረው ማስረጃዎቻችን ተሰምተው ተገቢው ውሣኔ እንዲሠጠን ይደረግልን የሚል ነው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሚያዝያ 03 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፉት 4/አራት/ ገፅ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሠጡት ማጣራት አድርገውና ከህጉ ጋር አገናዝበው በመሆኑ ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ ከውጪና ኪሣራ ጋር ሊፀና ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው የተጠሪ መልስ የሱቅ ድርጅቱ የተገኘበትን ህጋዊ መንገድ የማይገልፅ እና ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ሚያዝያ 28 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፉት የመልስ መልስ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የገለፀው ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን የፁሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሱቅ ድርጅት በአመልካቾች የተቆጠሩት የሠው ምስክሮች ሣይሠሙ የተጠሪ የግል ንብረት ነው ተብሎ መወሠኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች የሱቅ ድርጅቱ የንብረት ድርሻ ጥያቄ ያቀረቡት አውራሽ የሆኑት ሚች አባታቸው አቶ አራጋው ከድር የንግድ ድርጅት ነበር በማለት መሆናቸውን፣ የንግድ ድርጅቱ ወደ ተጠሪ የተላለፈው ተጠሪ የአመልካቾች ሞግዚትና ንብረት አስተዳዳሪ የነበሩ በመሆኑና ይህንንም በሠውና በሠነድ ማስረጃ ለማረጋገጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ ማቅረባቸውን ቀድሞ የነበረው የሱቅ ንግድ ድርጅት በእግት ቃጠሎ በ1980 ዓ.ም ወድሞም በተቃጠለው ሱቅ ምትክ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የንግድ ሱቅ ተጠሪ በፅጣ የወሠዱ መሆኑንና ይህም ሊሆን የቻለው ተጠሪ በወቅቱ በአቀረቡት የሞግዚትነትና የሚስትነት የፍርድ ውሣኔ መነሻ ስለመሆኑ አመልካቾች ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ሱቁ የግል ንብረታቸው መሆኑ በአግባቡ ተጣርቶ መወሠኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲሁም የውርስ አጣሪው ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሱቅ ድርጅት ማህደር ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ቀርበው በመመልከት የቤት ቁጥር 270 የሆነው የሱቅ ድርጅት ከመንግስት የተከራዩት ተጠሪ ወ/ሮ አለውያ አባቢለስ መሆናቸውን፣ ጊዜውም በ1986 ዓ.ም ሟች አቶ አራጋው ከድር ከሞቱ ከሠባት ዓመት በኋላ መሆኑን ጠቅሰው ለስር ፍ/ቤት የውርስ ማጣራት ሪፖርቱን ማቅረባቸውን ተረድተናል፡፡

በመሠረቱ የውርስ ማጣራት ስራ ተገቢው ሥርዓት ተጠብቆ የወራሾች ክርክርና ማስረጃ ተሠብስቦና ታይቶ የሚከናወን ስራ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 942 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የውርስ ማጣራት ስራ እንዲከናወን ትዕዛዝ የሠጠው ፍ/ቤትም የአጣሪውን ሪፖርት የሚያፀድቀው የማጣራቱ ተግባር በህጉ አግባብ መከናወኑን ከአረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የውርስ ማጣራቱ ስራ የተከናወነው በፍ/ብ/ህ/ቁ 950(1) መሠረት በፍ/ቤት በተሾመ አጣሪ ሆኖ አጣሪው ስራውን ያከናወኑት ግራ ቀኙ ወገኖች ባሉበትና ተገቢው የማስረጃ ማሠባሠብ ስራ አከናውኜአለሁ ካሉ በኋላ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ሱቅ በተመለከተ በአመልካቾች በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች ያልተሠሙበትን ምክንያት የውርስ አጣሪውም ሆነ የአጣሪውን ሪፖርት ያፀደቀው ፍ/ቤት በግልፅ አላስቀመጡትም፡፡ በአንድ ተከራካሪ ወገን የተቆጠረ ማስረጃ የማይሠማው ደግሞ ህጋዊ ምክንያት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ የአመልካቾች ማስረጃዎች በውርስ አጣሪው ያልተሠሙት በህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አልተገለፀም፡፡ የአመልካቾች ክርክር በአባታቸው ስም ይታወቅ የነበረ ቁጥሩ 398 የሆነ የሱቅ ድርጅት እንደነበር፣ ይህ ሱቅ በቃጠሎ መውደሙንና በምትክ ደግሞ አሁን ክርክር ያስነሣውን ሱቅ ቁጥሩ 270 የሆነውን ተጠሪ ከመንግስት መረከባቸውን የሚያሣይና ይህንንም ፍሬ ጉዳይ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን ስለመቆጠራቸው የሚያሣይ ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሱቅ የተያዘበት መንገድ ከላይ የተገለፀው ስለመሆኑ አመልካቾች እየጠቀሡ የሱቁን ማህደር ብቻ በመመልከት ፍትሐዊ ወደሆነው ውሣኔ ለመድረስ አይቻልም፡፡ የውርስ አጣሪው የአመልካቾችን ማስረጃዎች አለመሰማቱ የማጣራቱን ሂደት የተሟላ ነበር ለማለት የማያስችል፣ የአመልካቾችን የመከራከር መብት ያጣበበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ያፀደቀው ፍ/ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤት የአመልካቾችን የማስረጃ ማሰማት መብታቸውን ሣያስተካክሉ ማለፋቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 241 እስከ 270 እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 345 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ ተሽሮ የአመልካቾች ማስረጃዎች ተሠምተው ተገቢ ውሣኔ ይሠጥበት ዘንድ ለስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መመለሱ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 114932 ህዳር 19 ቀን 2001 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ፣ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 74285 ታኅሣስ 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካቾች የተቆጠሩትን ማስረጃዎችን ከሠማ በኋላ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32817

ሰኔ 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ ወኪል ጌታቸው ታደሰ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ እቴቱ ዘውዴ
2. ወ/ሮ መሰረት አድማሱ } ቀረቡ
3. አቶ ደረሰ ዘውዴ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች መጋቢት 25 ቀን 1992 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ መስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ መኖሩን ገልፀው ይኸው ኑዛዜ በፍ/ቤት ፀድቆላቸው የኑዛዜ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው በፊዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ሲሆን፣ የአሁኑ ተጠሪዎችም በተቃዋሚነት ቀርበው አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ጥር 22 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ሟች መስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም እና ግንቦት 05 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጓቸው ኑዛዜዎች ሟች የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ የተሻሩና የተተኩ በመሆኑ ኑዛዜው ሊፀድቅ አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን፣ የአሁኑ ሦስተኛ ተጠሪ ግን መጋቢት 08 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አመልካች እንዲፀድቅላቸው የጠየቁት ኑዛዜ ቢፀድቅ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍ/ቤትም ሟች ከመስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም በኋላ ሁለት የተለያዩ ኑዛዜዎች ማድረጋቸውን፤አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ደግሞ ሟች የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ጥያቄ አቅርበው የአሁኗ አመልካች እና የአሁኑ ሦስተኛ ተጠሪ በተቃዋሚነት ቀርበው ይኸው ኑዛዜ በመ/ቁ. 1169 የካቲት 10 ቀን 1997 ዓ.ም በፍ/ቤቱ መጽደቁን፣ መስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም በተደረገው ኑዛዜ ሟች በወረዳ 3 ቀበሌ 44 የቤት ቁጥር 220 የሆነውን ቤታቸውን ለወ/ሮ የውብዳር እና ለወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ መስጠታቸውን፣ በሙከጡሪ ከተማ ያለውንም ቤት ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ በራሷ ገንዘብ የገዛችው መሆኑን ገልፀው ማንም እንዳይጠይቃት የተናዘዙ መሆኑን፣ ሆኖም እነዚህን ንብረቶች ወ/ሮ እቴቱ ዘውዴ እንዲወስዱ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ መናዘዛቸውን ዘርዝሮ መስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም ተደረገ የተባለው ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 859/2/ መሰረት በሟች ተለውጧል፤ የሚል ምክንያት በመያዝ የአመልካችን የኑዛዜ ይጽደቅልኝ ጥያቄ ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፊዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበውም ይኸው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ወኪል ጥር 04 ቀን 2000 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ሚች የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ በግልጽ ቀኑን ጭምር ጠቅሰው የሻሩት ግንቦት 05 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉትን ብቻ እንጂ አስቀድሞ በ26/1/1984 ዓ.ም የተፃፈውን ኑዛዜ አለመሆኑን፤ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ሚች ኑዛዜ ሲያደርጉ የእድሜ ባለጠጋ እንደነበሩና ኑዛዜ ያደረጉበት ንብረትም የግላቸው ባልሆነው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 865/2/ መሰረት ኑዛዜው ሊፈፀም

የማይችል መሆኑን እንደሚያሣይ፤ አመልካች ከሚች ውርስ ያላግባብ መነቀላቸውን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ ሚች በ26/1/84 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ፀድቆ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው መልሣቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ጥቅምት 03 ቀን 2001 ዓ.ም በዛፉት የመልስ ማመልከቻ ሚች አመልካችን ከውርስ በምክንያት የነቀሏቸው መሆኑን፤ ሚች ኑዛዜ ባደረጉበት ወቅት አእምሯቸው ጤነኛ እንደነበርና የአመልካች ቅሬታ በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን፤ ቤቱም በሚች የግል ገንዘብ የተገዛ መሆኑን፤ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም የተደረገውን ኑዛዜ የተቀበሉት መሆኑን በኮ/መ/ቁ. 463 የተደረገው ክርክር እንደሚያሣይና ይኸው ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.895/3/ መሰረት ተቀባይነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ከበቂ ወጪና ኪሣራ ጋር ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሦስተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ሚች አመልካችን ከውርስ የሚነቅሉበት አንዳችም ምክንያት ሣይኖር መንቀላቸውና በአመልካች ስም የሚታወቀውን ቤታቸውን የሚች አስመስለው በኑዛዜ ለሌላ አሣልፈው መስጠታቸው ያላግባብ መሆኑን በመዘርዘር የመስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም ኑዛዜ ቢፀድቅ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገለፀው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ኅዳር 05 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎችን መልስ በመንቀፍ፣የሦስተኛ ተጠሪን መልስ ደግሞ ተቀባይነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም ሚች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ በሙከጡሪ ከተማ 01 ቀበሌ ይገኛል በተባለው ቁጥሩ 139 በሆነው ቤት አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

ሚች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ መስከረም 26 ቀን 1984፣ ግንቦት 05 ቀን 1988 እና የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ኑዛዜ ማድረጋቸውን፤ በኑዛዜዎቹም የንብረቶችን ምንጭ ከዓይነታቸውና ብዛታቸው ጋር መግለፃቸውን፤ የውርስ ንብረቶቹ ሊተላለፉለት የሚገባውን ወራሽ፣ ለአሁኗ አመልካች ከውርስ ድርሻ ሣይሰጡ ያለፉበትን ምክንያት እንዲሁም በኋላኛው ኑዛዜ የትኛውን ኑዛዜ እንደሻሩ መጥቀሣቸውን፤ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ተደረገ የተባለው ኑዛዜ በፍ/ቤት መጽደቁንና ከዚህ በኋላም የአሁኗ አመልካች በ26/01/1984 ዓ.ም ተደረገ የተባለው ኑዛዜ እንዲጸድቅላቸው ለፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡

ሚች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ የመጨረሻው ሲሆን በዚህ ኑዛዜ ለአመልካች የሰጡት የውርስ ድርሻ ካለመኖሩም በላይ ግንቦት 05 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉትን ኑዛዜ በዚሁ በየካቲት 12 ቀን 1989 የሻሩት መሆኑን፤ ለአመልካች በሙከጡሪ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን ቤት የተናዘዙላት ቢሆንም አመልካቿ ልትንከባከባቸውና ልትጦራቸው ባለመቻሏና ከኑዛዜው በኋላ በቤቱ ውስጥ እንዳይኖሩ ያባረረቻቸው ከመሆኑም በላይ በቤት ውስጥ የነበራቸውን ሐብትና ንብረት ሁሉ የእለት ልብስ ሣይቀራቸው ቀምታ በችግር ላይ እንዳሉ በመግለጽ ያለፉ ስለመሆኑ የኑዛዜ መሻሪያ ሰነዱ ያሣያል፡፡ እንግዲህ የየካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ኑዛዜ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ በሆኑበት ሂደት በፍ/ቤት የፀደቀ ከመሆኑም በላይ በሕግ ረገድ ፎርማሊቲውን ያልጠበቀ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ኑዛዜው ሕጋዊ ፎርማሊቲውን የጠበቀ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ሕጋዊ ፎርማሊቲው አጠያየቂ ካልሆነ መታየት ያለበት የኑዛዜው ይዘት ነው፡፡ አመልካች የኑዛዜውን ይዘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተመለከተ ያቀረቡት ክርክር ከውርስ የሚነቅላቸው መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ በእርግጥ ሟቹ ለአመልካች በኑዛዜው የሰጧቸው የውርስ ድርሻ የለም፡፡ ይህንኑ ሊያደርጉ የቻሉበትን ምክንያት በኑዛዜው መሻሪያ በግልጽ አስፍረዋል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 838/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ስር እንደተመለከተው ተናዛዡ ልጆቹን ወይም ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆቹን ሲነቅል ከውርስ የነቀለበትን ምክንያት በግልጽ ማስፈር እንደሚገባውና ዳኞች የምክንያቱን እውነትነት በመያዝ ተናዛዡ ተወላጆቹን ለመንቀል የሰጠው ምክንያት ከውርስ ለመንቀል የሚያበቃ ነው ወይስ አይደለም በማለት ለመመርመር እንደሚችሉ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ አመልካችን ከውርስ ሐብት ድርሻ እንዳያገኙ ያደረገበት ምክንያት በኑዛዜው መሻሪያ ላይ በግልጽ የተቀመጠና ተወላጆን ለመንቀልም የሚያበቃ ምክንያት ሆኖ ስለተገኘ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ ባደረጉት ኑዛዜ በሙከጡሪ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ ይገኛል የተባለውንና ቁጥሩ 139 የሆነው ቤት ከአመልካች ውጪ ላሉት ወራሾች እንደሚገባ ዘርዝረው የማከፋፈላቸውን ሕጋዊነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 865/2/ እና ተዛማጅነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ኑዛዜ በባህርይው ተራ የሐሣብ መግለጫ ቢሆንም በተናዛዡ በግሉ ብቻ ሊፈፀም የሚገባው ተግባር ነው፡፡ ኑዛዜ በይዘቱ ንብረትን ከማስተላለፍ ተግባር ጋር የተያያዘ ሲሆን ህጋዊ ጥበቃ የሚደረገውም ተናዛዡ የራሱ የሆነውን ህጋዊ ንብረት ለማስተላለፍ ህጋዊ ኑዛዜ አድርጐ ሲገኝ ስለመሆኑ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ ተናዛዡ ህጋዊ ንብረቱ ባልሆነው ላይ ኑዛዜ ቢያደርግና ይኸው ኑዛዜ በፍ/ቤት ቢፀጽቅ የኑዛዜ ሰነዱ ዋጋ የሚያገኝበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም ሟች ባደረጓቸው የተለያዩ ኑዛዜዎች ሙከጡሪ ከተማ ውስጥ ይገኛል የተባለውን ቤት በተመለከተ በማን ገንዘብና ለማን

እንደተገዛ የተለያየ ሐሣብ እንደነበራቸው የኑዛዜ ሰነዶቹ ያሣያሉ፡፡ በ26/01/84 ዓ.ም ተደረገ በተባለው ኑዛዜ ቤቱ በአመልካች ገንዘብ መገዛቱን ጠቅሰዋል፡፡ በሌሎች የኑዛዜ ሰነዶች ግን ቤቱ የተገዛው በሟች ገንዘብ ስለመሆኑ ገልጸዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሁኖ በ02/01/84 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል በውጫሌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. G/F/4028/89 በቀን 07/04/90 ዓ.ም ተረጋግጧል፡፡ ቤቱን የገዙትም አመልካች ስለመሆናቸው ይኸው የፍ/ቤቱ ሰነድ ያሣያል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው በሙከጡሪ ከተማ ውስጥ ይገኛል የተባለው አከራካሪው ቤት ህጋዊ ባለቤት አመልካች እንጂ ተናዛዡ አለመሆናቸውን ነው፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ቤቱ የሟች ነው የሚሉበት ምክንያት አመልካች በወቅቱ የነበራቸውን እድሜ መሰረት በማድረግ ገቢ ስላልነበራቸው ቤቱን ሊገዙ አይችሉም በሚል ነው፡፡ ሆኖም ምክንያታቸው ህጋዊ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ ያደረጉት የኑዛዜ ሰነድ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ ስላልተገኘ በዚህ ረገድ ኑዛዜው የፀደቀበት አግባብ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 01183 የካቲት 03 ቀን 1997 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38849 ግንቦት 09 ቀን 1999 ዓ.ም የፀናውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ በሙከጡሪ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ በሚገኘው ቁጥሩ 139 በሆነው ቤት ላይ ያደረጉት ኑዛዜ ፈራሽ ነው፤ቤቱን አመልካች የገዙት በመሆኑ የግል ንብረታቸው ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ከሟች ውርስ ያላግባብ ተነቅያለሁ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 40510

ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ቴዎድሮስ መንበሩ

ተጠሪ፡- ገ/ሕይወት ታደሰ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የውርስ ንብረት ይገባኛል በሚል የቀረበውን ክስ መሠረት በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው፡፡ አመልካቹ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተው ከሟች እናቱ ድርሻ ላይ በውርስ የማገኘውን ንብረት አካፍለኝ በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የንብረቱ ግምት ለመሬት ልማት አስተዳደር የላኩለት መሆኑን በመግለጽ ከዚሁ ላይ አመልካች ድርሻውን 1/4ኛ ይሰጠው በማለት አዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ባለመስማማት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ እንደገና የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ንብረቱን እንደገና በመሬት ልማት አስተዳደር በማስገመት አመልካች ከዚሁ ላይ ድርሻውን ¼ኛ እንዲወስድ ወስኖአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መስከረም 5 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ስምምነቱን ሳይገልጽ በባለሙያ የቀረበው የንብረቱ (ቤት) ዋጋ መነሻ ተደርጎ ከዋጋው ግምት ¼ኛው አመልካች ይውሰድ በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች በእናቱ በኩል የሚገኘውን የውርስ ድርሻ እንዲሰጠው ነው የጠየቀው፡፡ የውርስ ክፍያ የተጠየቀበት ሃብት የከተማ ቤት ሲሆን፣ ቤቱ የአመልካች እናት እና ተጠሪ በጋብቻ አብረው ሲኖሩ ያፈሩት የጋራ ሃብት እንደሆነ በክርክሩ ተገልጾአል፡፡ የአመልካች እናት ከተጠሪ ሦስት ልጆች እንደወለዱና አመልካችን ግን ከሌላ ሰው የወለዱት እንደሆነ አመልካች አረጋግጦአል፡፡ በመሆኑም ለውርስ ክፍፍል የሚቀርበው ቤቱ እንዳለ በሙሉ ሳይሆን፣ ተጠሪ ግማሽ ድርሻውን ካነሳ በኋላ በሚቀረው የቤቱ ግማሽ ላይ ነው፡፡ ይህም ከሟች በተወለዱ አራቱ ልጆች መካከል የሚከፋፈል ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ነው የአመልካች የውርስ ድርሻ ¼ ነው የተባለው፡፡

ከስር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እንዳየነው አመልካች ተቃውሞ ያነሳው በቤቱ ግምት ላይ ብቻ ነው፡፡ በሰበር አቤቱታው ግን ድርሻዬን መውሰድ ያለብኝ ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ነው የሚል የመከራከሪያ ነጥብ አንስቶአል፡፡ ይሁንና ከፍ ሲል እንደተገለጸው ቤቱ የመኖሪያ ከመሆኑም በላይ፣ ግማሹ የተጠሪ የግማሽ ¾ኛው ደግሞ የሌሎቹ ሦስት ልጆች ስለሚሆን፣ የ1/4 ድርሻ ላለው አመልካች ሲባል ቤቱን በሐራጅ እንዲሸጥ በማድረግ ተጠሪና ልጆቹን ቤት አልባ ማድረግ የሚመረጥ አይደለም፡፡ ከፍትሕ አኳያ ሲታይም ተገቢ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ቤቱ በሃራጅ ሊሸጥ ይገባል የሚለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ክርክር ከጅምሩም ቢሆን ያልተነሳ እና ከፍትሕ አንፃር ሲታይም ተቀባይነት ሊኖረው ስለማይገባ ውድቅ አድርገዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን በመሬት ልማት አስተዳደር ቀረበ የተባለው የቤቱ ግምት የገበያ ዋጋን መሠረት ያደረገ ሳይሆን፣ የግንባታ ዋጋን መሠረት በማድረግ የተሰላ በመሆኑ ይህን ግምት መሠረት ተደርጎ የሚፈጸመው የውርስ ሃብት ክፍፍል ፍትሐዊ ሊባል ይችላል ወይ? የሚለውን ነጥብ ማየቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአከራካሪው ቤት ላይ አመልካችም መብት እንዳለው አላከራከረም፡፡ ከዚህ ንብረት ላይ የውርስ ድርሻውን ማግኘት አለበት ከተባለ ደግሞ በክፍፍል ወቅት ሊጠበቅ የሚገባውን ሁኔታ በጥንቃቄ የሚታይ ነው የሚሆነው፡፡ የአመልካች እናት ድርሻ የሆነው የቤቱ ግማሽ በአራቱም ልጆች መካከል ሲከፋፈል አራቱም ልጆች እኩል ነው የሚታዩት በሌላ አነጋገር ክፍፍሉ የአራቱም ልጆች የእኩልነት መብት ያረጋገጠ መሆን ይገባዋል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የእኩልነት መብቱ የሚረጋገጠው ክፍፍሉ በምን አይነት መንገድ ቢፈጸም ነው የሚለውን ጥያቄ መመለስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አከራካሪው ቤት የተገመተው የገበያን ዋጋ (የወቅቱን የገበያ ዋጋ) መሠረት በማድረግ ሳይሆን የወቅቱን የግንባታ ዋጋ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የግንባታ ዋጋ ማለትም ቤቱን ለመስራት ለሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች መግዣ የሚወጣው እና ለሠራተኞች የሚከፈለው ገንዘብ ብቻ የሚያጠቃልል ነው የሚሆነው፡፡ የገበያን ዋጋ ስንመለከት ግን ከዚህም ያለፈ እንደሆነ ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ የገበያ ዋጋ ከስሙ እንደምንረዳው ቤቱ ለገበያ /ለሽያጭ/ ቢቀርብ የሚያስገኘውን ዋጋ ነው የሚያመለክተው፡፡ የገበያ ዋጋ ለመገመትም ቤቱ የሚገኝበትን አካባቢ፣ በወቅቱ ክፍፍሉ በሚደረግበት ወቅት ያለውን የገበያ ሁኔታ ወዘተ በተጨማሪነት እግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ይህ ደግሞ የቤቱን የወቅቱ ዋጋ በማስላት ረገድ የግንባታን ዋጋ ከሚሰላበት ዘዴ የተሻለ /የሰፋ/ መሠረት ያለው አካሄድ ነው፡፡ ሲጠቃለል ንብረቱን የሚከፋፈሉ ወገኖች የእኩልነት መብት በተሻለ ሁኔታ ማረጋገጥ የሚቻለው ንብረቱ(ቤቱ) በገበያ ዋጋ ግምቱ ቢሰላ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በያዝነው ጉዳይ የግንባታን ዋጋ መሠረት በማድረግ ክፍፍሉ እንዲፈጸም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 01411/99 ጥር 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 0172/2000 በ3/13/2000 የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አከራካሪው ቤት ለክፍፍል በሚቀርብበት ወቅት በሚኖረው የገበያ ዋጋ መሠረት ግምቱ ከቀረበ በኋላ አመልካች ድርሻውን ¼ኛ ይሰጠው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለሥር ፍ/ቤቶች ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ/ቁ. 40781

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሠ

ታፈሠ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ፍቅረሥላሴ ካህሳይ - ጠ/ዳኛቸው ተስፋዬ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሮማን ታደሰ - ጠ/መንበረስላሴ በዛብህ ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የፍቺ ጥያቄን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ክስ ከማቅረባቸው በፊት በግራ ቀኙ መሐከል የነበረው ጋብቻ አውስትራሊያ አገር በሚገኝ ፍርድ ቤት በፍቺ በመፍረሱ የፍቺ ውጤት እንዲሰጥላቸው ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱ የፍቺ ውጤት ለመወሰን በቅድሚያ በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገው ጋብቻ ሊፈርስ ይገባል በማለት አመልካችን ሳይጠራ የተጠሪዋን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህን ውሣኔ በመቃወም ተጠሪዋ ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ነው ተጠሪ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ከአመልካች ጋር ጥር 16 ቀን 1984 ዓ.ም. የመሠረቱት ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ያቀረቡት፡፡ አመልካች የተጠሪ አቤቱታ ደርሷቸው የተለያዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ መቃወሚያቸውን ውድቅ አድርጎ በአመልካች እና በተጠሪ መሃከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ይፍረስ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ አመልካች ያቀረቧቸው ቅሬታዎች ቀደም ብለው በውሣኔ ያለቁ ናቸው በማለት ሳይቀበላቸው ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ፣ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን የላቸውም፣ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የስረ-ነገር ስልጣን የለውም፤ ጉዳዩ ሊዳኝ የሚገባው በአውስትራሊያ ሕግ ነው፣ የኢትዮጵያ ፍ/ቤት ስልጣን አለው ቢባል እንኳን ጋብቻው በፍቺ ፈርሷል፤ የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በአውስትራሊያ አገር ሲኖሩ በዚያው አገር መፋታታቸውን ግራ ቀኙ ሳይክዱ በድጋሚ ፍቺ የመወሰኑ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው በቃል ባደረጉት ክርክር የአመልካች ቅሬታ ቀደም ሲል በውሣኔ ያለቀ ጉዳይ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን ከያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካች በግራ ቀኙ መሃከል የነበረው ጋብቻ በአውስትራሊያ አገር በፍቺ ፈርሷል ስለዚህ ድጋሚ ፍቺ የሚወሰንበት ምክንያት የለም ሲሉ ተጠሪ ደግሞ ይህ ክርክር ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ውድቅ ከተደረገ በኋላ በይግባኝ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያፀናው ስለሆነ በውሣኔው ያለቀ ጉዳይ በመሆኑ ድጋሚ ሊታይ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

እኛም ወደ ፍሬ ጉዳዩ ከመግባታችን በፊት በቅድሚያ ተጠሪ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ቀደም ሲል በፍርድ አልቋል በማለት ያቀረቡትን መቃወሚያ መመልከቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር እንደተደረዳነው ተጠሪ ቀደም ሲል የግራ ቀኙ ጋብቻ በአውስትራሊያ አገር በፍቺ በመፍረሱ የፍቺ ውጤት እንዲወሰንላቸው ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡ ፍ/ቤቱ ደግሞ የአውስትራሊያ ፍ/ቤት በፍቺ እንዲፈርስ የወሰነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግራ ቀኙ በዛው አገር ያደረጉት ጋብቻ እንጂ አስቀድሞ በኢትዮጵያ የተደረገው ጋብቻ ስላልሆነ የመጀመሪያው ጋብቻ ሳይፈርስ የፍቺ ውጤት ሊጠየቅ አይገባም በማለት የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኛቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡ ከክርክሩ ሂደት እንደተረዳነው ፍ/ቤቱ ይህንን ውሣኔ የሰጠው አመልካችን ሳይጠራ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ክርክር አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ስላልነበሩ አሁን አመልካች በሚያቀርቡት ክርክር ላይ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ እንደሰጠ የሚያስቆጥረው አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት በድጋሚ ክስ እንዳያቀርብ ወይም ክርክር እንዳያቀርብ የሚከለክለው በክርክሩ ተካፋይ የሆነን ወገን ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን ተጠሪ በኢትዮጵያ አገር የተደረገው ጋብቻ እንዲፈርስ ባቀረቡት ክስ አመልካች እነዚህን መቃወሚያዎች አቅርበው ፍርድ ቤቱ መቃወሚያዎቹን በብይን አልፎባቸዋል፡፡ አመልካች በብይኑ ላይ ይግባኝ ጠይቀው ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ በኢትዮጵያ የተደረገው ጋብቻ ሊፈርስ ይገባል አይገባም የሚለው ጭብጥ ላይ ፍ/ቤቱ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው በዚህ ሁኔታ የቀረበው መቃወሚያ ላይ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ነው፡፡ ምንም እንኳን አመልካች ባቀረቧቸው መቃወሚያዎች ላይ ብይን የተሰጠና ይህም ብይን በይግባኝ የፀና ቢሆን የፍቺ ጥያቄን አስመልክቶ የተሰጠ ውሣኔ ስለሌለ በዚህ ላይ አመልካች ያቀረቡት ክርክር የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘና በድጋሚ ሊታይ አይገባም ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካች ያነሱት ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ያቀረቡት ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም፡፡

ወደ ፍሬ ጉዳዩ ስንመለስ ከክርክሩ ሂደት አመልካችና ተጠሪ ጥር 16 ቀን 1984 ዓ.ም. በባሕል ጋብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ የተጋቡ መሆኑን እንዲሁም የካቲት 5 ቀን 1985 ዓ.ም. በአውስትራሊያ አገር የብሔራዊ ጋብቻ መፈጸማቸውን ተረድተናል፡፡ እንዲሁም የግራ ቀኙ ጋብቻ አውስትራሊያ አገር በሚገኘው የማጅስትራት ፍ/ቤት በፍቺ መፍረሱንም ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ እንደውም ተጠሪ ከአመልካች ጋራ ያላቸው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን ተቀብለው የፍቺ ውጤት እንዲወሰንላቸው አቤቱታቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የነበረ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ የከፍተኛ ፍ/ቤት በአውስትራሊያ አገር የፈረሰው ጋብቻ በዛው አገር የተደረገው እንጂ በአ/አበባ የተደረገው ጋብቻ ባለመሆኑ ይህ ጋብቻ ሳይፈርስ የፍቺ ውጤት ሊወሰን አይችልም በማለት የተጠሪን አቤቱታ ሳይቀበል አልፎታል፡፡

ጋብቻ ማለት አንድ ወንድና ሴት ባልና ሚስት ሆነው አንድ ላይ ለመኖር የሚያደርጉት ሕጋዊ ስምምነት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ጋብቻ በሶስት ዓይነት መንገድ ሊፈፀም እንደሚችል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 1 ያመለክታል፡፡ በእነዚህ ስርዓቶች በአንደኛው ጋብቻ ከተፈፀመ በድጋሚ በሌላኛው ስርአት ሊፈጸም የሚገባበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ ድጋሚ ተደርጎ እንኳን ቢገኝ ጋብቻው ፀንቶ የሚቆየው የመጀመሪያው ጋብቻ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ በአንድ ወንድና ሴት መሃከል የሚደረግ ጋብቻ ፈርሶ እንደገና ካልተፈፀመ በቀር ጋብቻ አንድ እንጂ ሁለትና ከዚያ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ በኢትዮጵያ ውስጥ በባሕል ከተጋቡ በኋላ በድጋሚ በአውስትራሊያ ጋብቻ ማድረጋቸውን ከክርክር ሂደት ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ የሥር ፍ/ቤት እንዳለው አንድ ጊዜ ጋብቻ ከተመሰረተ ሁለተኛ ጋብቻ የሚፈፀምበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ ተፈጽሞ እንኳን ቢገኝ ጋብቻው ውጤት የሚኖረው የመጀመሪያው ጋብቻ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ አንድ ጋብቻ ከሚፈርስባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንደኛው የፍቺ ውሣኔ ሲሰጥ መሆኑ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 75/ሐ/ ያመለክታል፡፡ ጋብቻ አንድ እንደሆነ ሁሉ ጋብቻው በፍቺ ሊፈርስ የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ሁለት የጋብቻ ስርአቶች መከናወናቸውም ሁለት ጊዜ የፍቺ ውሣኔ እንዲሰጥ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ በመሠረቱ ፍቺ ማለት የሁለት ተጋቢዎችን የትዳር ግንኙት በሕግ መሠረት ማቋረጥ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ተጋቢዎቹ ግንኙታቸውን ማቋረጥ ከፈለጉ ጋብቻው በሁለት አይነት ስርአት ስለተፈፀመ ግንኙቱን ለማቋረጥ እያንዳንዱን ጋብቻ አስመልክቶ የፍቺ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባው አይሆንም፡፡ የሕጉም አላማ ይህ አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤቶች ሁለተኛ ፍቺ ለመስጠት ምክንያት ያደረጉት በአውስትራሊያ የሚገኘው ፍ/ቤት ያፈረሰው ሁለተኛው እና በዛው አገር የተደረገውን ጋብቻ እንጂ በኢትዮጵያ የተደረገው ጋብቻን አይደለም፡፡ ሁለተኛው ጋብቻ ደግሞ አላስፈላጊና ውጤት የሌለው ጋብቻ ነው በማለት ነው፡፡ በመሠረቱ ግራ ቀኙ ጋብቻቸውን መቀጠል ባለመፈለጋቸው ፍ/ቤት ቀርበው ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ጠይቀው አስወስነዋል፡፡ በግራ ቀኙ መሐከል የነበረው ጋብቻ አንድ ብቻ በመሆኑ አውስትራሊያ የተሰጠው የፍቺ ውሣኔ ይህን በመካከላቸው የነበረውን አንድ ጋብቻ እንደፈረሰ ተደርጎ ሊቆጠር ይገባል፡፡ ከላይ እንደተደገለፀው ግራ ቀኙ አውስትራሊያ አገር ከሄዱ በኋላ ሌላ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት መፈፀማቸው ሁለት ትይዩ /Parallel/ ትዳር ውስጥ ነበሩ ሊያሰኛቸው አይችልም፡፡ በመሆኑም በመካከላቸው የነበረው የጋብቻ ግንኙነት አንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመሆኑን ያሕል የሚፈርስውም በአንድ የፍቺ ውሣኔ ነው፡፡ ለፍ/ቤቱ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ግራ ቀኙ አውስትራሊያ አገር ሄደው ሁለተኛ ሥነ-ሥርዓት በመፈፀማቸው ብቻ ሁለት የፍቺ ሥነ-ሥርዓት እንዲያከናውኑ ማድረጉ የቤተሰብ ሕግን አላማና መንፈስ የሚከተል አይደለም፡፡ ሁለተኛ ጊዜ የተደረገው ጋብቻ መፍረሱ ምናልባት በፍቺ ውጤት ላይ ክርክር የሚያስነሳ ካልሆነ በቀር የመጀመሪያው የጋብቻ ሥርዓት ባለመፍረሱ የግራ ቀኙ የጋብቻ ግንኙነት አልተቋረጠም ወደሚለው መደምደሚያ አይወስድም፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ጋብቻው በሁለት አይነት ሥርዓት ተፈጽሞ ቢሆን እንኳን ጋብቻው በፍቺ ሊፈርስ የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ እንጂ ሁለት የጋብቻ ሥርዓት በመፈፀሙ ሁለት አይነት ፍቺ ሊኖር አይችልም፡፡ ስለሆነም የመጀመሪያው ጋብቻ ሥርአት ሳይሆን ሁለተኛ የተደረገው ሥርዓት-በፍቺ መፍረሱ ተጋቢዎቹ እንደተፋቱ አያስቆጥርም በሚል ሁለተኛ የፍቺ ውሣኔ መስጠቱ የሕጉን አላማ የሳተና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ አ/አበባ እና አውስትራሊያ ጋብቻ የፈፀሙ ቢሆንም ግራ ቀኙ የትዳር ግንኙነታቸውን በፍቺ ማቋረጥ ስለፈለጉ በአውስትራሊያ ፍርድ ቤት የፍቺ ውሣኔ አሰጥተዋል፡፡ ይህንንም ፍቺ ሁለቱም ተቀብለውት የራሳቸውን ሕይወት መኖር ቀጥለዋል፡፡ ተጠሪም ቢሆኑ የፍቺ ውጤት ውሣኔ እንዲሰጣቸው ለፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረባቸው በግራ ቀኙ መሃከል የነበረው ግንኙነት በፍቺ የተቋረጠ መሆኑን አምነው መቀበላቸውን ያሳያል፡፡ ግንኙነቱ ከተቋጠ ደግሞ አ/አበባ የተደረገው ጋብቻ ለሁለተኛ ጊዜ በፍቺ ሊፈርስ ይገባል የሚባልበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም ከፍተኛ ፍ/ቤት አውስትራሊያ አገር በተደረገ የፍቺ ውሣኔ ሕልውና ያጣውን ጋብቻ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ እስከሰጠበት ዕለት ድረስ እንደቀጠለ በማሰብ በ12/06/2000 ፈርሷል ማለቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ የፈረሰው የአውስትራሊያው ፍ/ቤት በመካከላቸው የመጨረሻ ውሣኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ሊሆን ይገባዋል ብለናል፡፡ ከማንደሩ ጋር ተያይዘው ከቀረቡት ሰነዶች በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ የፈረሰው ሴፕቴምበር 20/2004 /መስከረም 10 ቀን 1997 ዓ.ም/ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በመካከላቸው የሚነሳ የንብረት ክርክር ካለም ይህን ቀን ታሳቢ ማድረግ አለበት ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 53555 የካቲት 12 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካችና በመልስ ሰጪ መካከል የነበረው ጋብቻ ከመስከረም 10 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ ፈርሷል፡፡
3. የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ይቀጥላል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 18394

መጋቢት 21 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሀ ወርቅነህ

አብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዝናሽ በቀለ ማንደፍሮ - አልቀረቡም፡፡

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ ሐረገወይን በቀለ - ቀርበዋል፡፡

በዚህ መዝገብ የተደረገውን የሰበር አቤቱታና ክርክር መሠረት አድርገን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን አተረጓጎም የሚመለከት ነው፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ነገር ሟች አቶ በቀለ ማንደፍሮ ለአሁንዋ አመልካች በአርሲ ነገሌ የሚገኘውና በ1967 ዓ.ም. በወጣው አዋጅ ቁ. 47/67 የተወረሰውን ቤት በኑዛዜ መስጠታቸው ኑዛዜውን ፈራሽ ማድረግ አለማድረጉን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ኑዛዜው ሊፈፀም የማይችልና ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል የመካፈል መብቴን የሚነካ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለት ከሥር ጀምሮ የተከራከረች ሲሆን መልስ ሰጪ ደግሞ በቤቱ ላይ ሟች አበል ይቀበሉበት ስለነበር ኑዛዜው ፈራሽ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክራለች፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ነጥብ ላይ የተለያየ ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዩን መጀመሪያ የተመለከተው የወረዳ ፍ/ቤት ኑዛዜው ይፀናል ሲል ይግባኙ የቀረበላቸው የከፍተኛና የጠቅላይ ፍ/ቤቶች ኑዛዜው ሊፈርስ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ የይግባኝ ፍ/ቤቶቹ ኑዛዜው ሊፈርስ ይገባዋል በማለት ውሣኔ ለመስጠት የቻሉት በኑዛዜው የተጠቀሰውና በአርሲ ነገሌ የሚገኘው ቤት የከተማ ትርፍ ቤት ለመንግሥት እንዲሆን በወጣው አዋጅ የተወረሠ በመሆኑ የኑዛዜው ውጤት የአመልካች ከውርስ መነቀልን የሚያስከትል ነው፤ ይህ ደግሞ አመልካች ከወራሾች እኩል እንዳትካፈል የሚያደርግ ነው በማለት ነው፡፡ ጉዳዩን መጨረሻ ላይ ያየው የደቡብ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በሌላ በኩል ኑዛዜው የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር ችሎት ኑዛዜው ይጸናል የሚል ውሣኔ ለመስጠት ኑዛዜው የሚመለከተው አርሲ ነገሌ የሚገኘው ቤት የተወረሰ ቢሆንም ሟች አበል ይቀበሉበት ስለነበር ኑዛዜው አበሉን አስመልክቶ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፤ ከዚህም ሌላ ቤቱ የተወረሰ ቢሆንም ሊመለስ የሚችልበት እድል የለም ሊባል ስለማይችል ኑዛዜው ሊፈፀም በማይችል ጉዳይ ላይ የተረገ ነው ሊባል አይችልም፤ የአመልካች ሕጋዊ ወራሽ መሆን የኑዛዜውን ፈራሽነት የሚያስከትል አይደለም፤ የሚሉትን ምክንያቶች ሰጥቷል የሰበር ችሎቱ አመልካች ኑዛዜው ይፍረስልኝ የሚል አቤቱታ ሳታቀርብ ከፍተኛውና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ኑዛዜው እንዲፈርስ ውሣኔ መስጠታቸው ባልቀረበላቸው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠታቸውን ስለሚያመለክት ሂደቱ ግድፈት የነበረበት መሆኑንም በፍርዱ አትቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ዝርዝር ሃሣቦችን ያጠቃለለ ሲሆን በዚህን ፍርድ ቤቱ ከያዘው ዋነኛው ነጥብ ጋር ግንኙነት ያለው ቅሬታ በተወረሰ ቤቱ ላይ የተሰጠው ኑዛዜ እንዲፀና መደረጉ የአመልካችን የወራሽነት መብት የሚጎዳ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ የጽሁፍ መልስ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ የመልሱ ዋነኛ ፍሬ ሃሣብ ኑዛዜው የፀና ነው መባሉ የሕግ ስህተት አይደለም በመሆኑም የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ሊፀና ይገባዋል የሚል ነው፡፡ የመልስ መልሱ የሰበር ማመልከቻውን የሚያጠናክር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ችሎት የቀረበለትን ጉዳይ ከውርስ ሕጉ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምሮአል፡፡ የሚከተሉትን ጭብጦች አስመልክቶ ሕጉ የሚለውን መመልከት ለውሣኔ አስፈላጊ ሆኖም አግኝቶታል፡፡

1/ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በመንግሥት የተወረሰን ቤት የሚመለከት መሆኑ በኑዛዜው የሚያስከትለው የሕግ ውጤት ምንድነው?

2/ ኑዛዜው ይፀናል ከተባለ በክፍፍሉ ላይ የሚኖረው ውጤት ምንድነው?

እነዚህን ሁለት ነጥቦችና ሌሎች ተጓዳኝ ጥያቄዎች በቅደም ተከተል ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

ከሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች ለመገንዘብ እንደቻልነው አርሲ ነገሌ የሚገኘውና ለአሁን አመልካች በኑዛዜ የተተወው ቤት በመንግሥት የተወረሰ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በመሆኑም ሟቹ የተናዘዙት የራሳቸው ባልሆነ ንብረት ነው ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው በራሱ ባልሆነና ሊያዝበት በማይችል ንብረቱ የተናዘዘ እንደሆነ ኑዛዜው የሚኖረው ሕጋዊ ሁኔታ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ በውርስ ሕግ በግልጽ ምላሹ ያገኘ ነው፡፡ የውርስ ሕግ ውስጥ ይህንን ጉዳይ የሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 1047 እንዲህ ይነበባል፡፡

1/ “በኑዛዜው የተደረገው ስጦታ በተለየ ነገር እንደሆነና ሟቹ በሞተበት ቀን በዚህ ነገር ላይ አንዳችም መብት የሌለው እንደሆነ የኑዛዜው ስጦታ ፍርስ ነው፡፡

2/ ስለሆነም ሟቹ ይህን ሁኔታ እያወቀ በኑዛዜው ሰጥቶ እንደሆነ ስጦታው ዋጋ ያለው ይሆናል፡፡

3/ እንደዚህ በሆነ ጊዜ አጣሪው በኑዛዜ የተሰጠውን እቃ ዋጋ መስጠት አለበት”

ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው በመርህ ደረጃ ማንም ሰው ምንም መብት በሌለው ንብረት ላይ የተናዘዘ እንደሆነ የተሰጠው ኑዛዜ ዋጋ አይኖረውም፡፡ በሕግ ፊት የሚፀና ኑዛዜ ለመስጠት ሟቹ ኑዛዜ በተደረገበት ንብረት ላይ መብት ሊኖረው ይገባል በሌላ በኩል በንዑስ አንቀጽ /2/ በግልጽ እንደሰፈረው ሟቹ ኑዛዜ በሚያደርጉበት ንብረት ላይ ምንም መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ ስጦታ የሰጠው እንደሆነ በስጦታው ሕጋዊነት የፀና ይሆናል፡፡ በመሆኑም ኑዛዜ አድራጊው መብት ያለው መሆን አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ስለዚህ ጉዳይ የነበረው ግንዛቤ በኑዛዜው ፍርስ መሆን አለመሆን ላይ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ኑዛዜው ፍርስ የሚሆነው ተናዛዡ ስጦታ ባደረገበት ንብረት ላይ መብት እንደሌለውና ይህም ያወቅ እንዳልነበረ ሲታወቅ ብቻ ነው፡፡ ይህ መደምደሚያ የሚገኘው ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ ሁለት ንዑስ ቁጥሮችን አጣምሮ በማንበብ ነው፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይ ተናዛዥ አርሲ ነገሌ በነበረውና ለአሁን አመልካች በስጦታ በሰጡት ቤት ላይ የባቤትነት መብት አልነበራቸውም፡፡ ቤቱ በአዋጅ የተወረሰ በመሆኑና አበልም ይቀበሉበት ስለነበር ሟቹ ቤቱ ላይ መብት እንደሌላቸው እያወቁ ኑዛዜ ማድረጋቸው ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ኑዛዜው የተሰጠበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ 1047 /2/”ን” መስፈርት የሚያሟላ ነው፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ ቤቱ የተወረሰ በመሆኑ ምክንያት ሟቹ በቤቱ ላይ መብት ባይኖራቸው የኑዛዜ ስጦታውን ያደረጉት ይህ መብት እንደሌላቸው እያወቁ በመሆኑ ኑዛዜው ሊፈርስ የሚባው አይደለም፡፡ ኑዛዜው ፍርስ ሊሆን ይችል የነበረው ሟቹ በቤቱ ላይ መብት እንደሌላቸው የማያውቁ መሆኑ ማስረጃ ቢቀርብ ነበር፡፡

በመሆኑም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት የኑዛዜ ስጦታው ይፀናል በማለት ያቀረበው ምክንያት ትክክል ባይሆንም ውጤቱ ግን ይህም ችሎት የሚስማማበት ነው፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች በተወረሰ ቤት ላይ የተደረገ ኑዛዜ በመሆኑ ብቻ ኑዛዜ ፍርስ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ጉዳዩን የተመለከቱት የሥር ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው በተወረሰ ሀብት ላይ የተሰጠ በመሆኑ የአመልካችን ከውርስ መነቀል ያስከትላል በማለት የኑዛዜ ስጦታውን ፍስር ማድረጋቸው የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ መሻሩ አግባብ ነው፡፡ አንድ ወራሽ አለአግባብ ተነቀለ የሚባል ቢሆን በውርሱ አከፋፈል ላይ የሚታይ እንጂ በአግባቡ የተሰጠን ኑዛዜ ፈራሽነት የሚያስከትል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀጥሎ መታየት ያለበት ግን የኑዛዜ ስጦታው የፀና መሆን በወርስ ክፍፍሉ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለው ጥያቄ ነው። ይህን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ተያያዥነት ያላቸውን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መዳሰስ ያስፈልጋል። በቅድሚያ ከላይ የጠቀስነው የአንቀጽ 1047/3/ ይዘት መመርመር ተገቢ ነው። የዚህ ድንጋጌ መልእክት አንድ ሰው በአንድ ንብረት ላይ መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ የተናዘዘ እንደሆነ ኑዛዜው የሚፀና ከመሆኑም ባሻገር የውርስ አጣሪው የዚህ ንብረት ግምት መስጠት እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው። በዚህ ደንብ መሠረት ተናዛዥ በስጦታ የሰጠው ንብረት በውርሱ ሀብት እንኳን ባይኖር ከውርሱ ሀብት በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት ወይም ገንዘብ ለስጦታ ተጠቃሚው መስጠት ሕጉ ያስቀመጠው ሥርዓት ነው። ሆኖም ይህ ደንብ ተፈፃሚ የሚሆነው ለውርስ ስጦታ /legacy/ ብቻ ነው። በመሆኑም አንድ ኑዛዜ ውስጥ ያለው የተናዛዡ ቃል የውርስ ስጦት /legacy/ መሆን አለመሆኑን መለየት ለዚሁ ድንጋጌ አፈፃፀም መሠረታዊ ነው። አንድ የኑዛዜ ቃል የውርስ ስጦታ መሆን አለመሆኑን ለመለየት ሌሎች የውርስ ሕጉን ድንጋጌዎች መመልከት ያስፈልጋል። አሁን ከያዝነው ጉዳይ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 913 ነው።

913 የኑዛዜ ስጦታና የክፍያ ደንብ

የኑዛዜው ቃል የተናዛዥን ተቃራኒ ሐሣብ የሚገልጽ ካልሆነ በቀር ከውርስ ሃብት አንድ ድርሻን ወይም አንድ ንብረትን ሚቹ ለወራሾች መስጠቱ ተራ የሆነ የክፍያ ደንብ እንጂ እንደ ኑዛዜ ስጦታ ነው ተብሎ አይቆጠርም።

የዚሁ አንቀጽ የእንግሊዝኛ ትርጉም እንደሚከተለው ይነበባል።

913 Legacies and rules of partition

An Assignment of a portion of the succession or of property forming part of such succession made by the testator to one of her heirs shall not be deemed to be a legacy but a mere rule for partition, unless the contrary in tension of the testator emerges from the disposition.

ከዚህ ድንጋጌ ለመገንዘብ የሚቻለው በኑዛዜው የሚከናወኑ ተግባሮች የኑዛዜ ስጦታ /legacy/ ወይም የክፍያ ደንብ /Rule of Partition/ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው። በመርህ ደረጃ አንድ ሰው ከውርስ ሀብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ አያሰኘውም። ይልቁንም ይህ አይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ ነው። በመሆኑም አንድ አውራሽ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዘዝለት የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ /legacy/ አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ /Partition/ በመከተል የሚከናውን ይሆናል።

ኑዛዜው ስጦታን /legacy/ የሚመለከት ከሆነ በፍትሀብሔር ሕጉ አንቀጽ 942 ጀምሮ ባሉ አንቀፆች መሠረት በማጣራት /liquidation/ ሥርዓት የሚከናወን ሲሆን ክፍያ ግን ክፍፍልን /partition/ በሚመለከቱና ከአንቀጽ 1060 ጀምሮ ባሉ ድንጋጌዎች መሠረት የሚስተናገድ ነው።

አሁን በቀረበልን ጉዳይ በአርሲ ነገሌ የሚገኘው ቤት በኑዛዜው ይሰጥልኝ የተባለው የሟች ልጅ መሆንዋ ለተረጋገጠው ለአሁንዋ አመልካች ነው። አመልካች ወራሽ በመሆንዋ ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ 913 መሠረት ኑዛዜው የስጦታ ውል ሳይሆን የክፍያ ሥርዓት የያዘ ነው ማለት ነው ኑዛዜው የስጦታ ነው የሚባል ቢሆን ኖሮ በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥሮች 1037-1051 መሠረት እንዲሁም 1047/3/ መሠረት የተጠቀሰው ንብረት ወይም ግምቱ ለስጦታ ተጠቃሚው በቅድሚያ ይሰጣል። ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው የአሁን አመልካች ወራሽ በመሆንዋ የኑዛዜው ቃል ክፍፍልን በሚያመለክቱ ድንጋጌዎች መሠረት የሚስተናገድ ነው። በዚህ ረገድ ከአንቀጽ 1117 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች አግባብነት አላቸው አንቀጽ 1017 አባትና እናት ወይም ሌሎች ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ለልጆቻቸውና ለሌሎች ተወላጆች ሀብታቸውን ለመስጠትና ለማከፋፈል እንደሚችሉ ይደነግጋል። ይህ ክፍፍል ሥርዓት አንድን ተወላጅ ከሚደርሰው ከሩብ የበለጠ ጉዳት ደርሶበት እንደሆነ የስጦታ አከፋፈሉ እንዲቀር ጥያቄ ማቅረብ እንደማይችል በአንቀጽ 1123 ተደንግጎአል። አንቀጽ 1123/1/ እና በስጦታ አከፋፈል ውስጥ ተቃራኒ ቃል ከሌለ በቀር ወደታች ከሚቆጠሩ ተወላጆች አንዱ ከሚደርሰው ከሩብ የበለጠ ጉዳት ደርሶበት እንደሆነ የስጦታ አከፋፈሉ አንዲቀር ለመጠየቅ ይችላል" ይላል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከቀረበልን ጉዳይ ለመገንዘብ እንደቻልነው ሟቹ ኑዛዜአቸው ላይ ያሉዋቸውን ቤቶች ለልጆቻቸው አከፋፍለዋል፡፡ የዚህ ዓይነት ክፍፍል ሕጉ የሚደግፈው ቢሆንም ማንኛውም ልጅ ከአንድ አራተኛ በላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ የክፍፍል ሥርዓቱ እንዲፈርስ መጠየቅም ሆነ በዚህ መሠረት ውሣኔ መስጠት ይቻላል፡፡ ከመዝገቡ ጋር ከተያያዘው የኑዛዜ ኮፒ ለመገንዘብ እንደቻልነው አውራሹ የነበሯቸውን ቤቶች ሲያከፋፍሉ ለአሁንዋ አመልካች የሰጡት አርሲ ነገሌ የሚገኘውና ተወረሰ የተባለውን ቤት ሲሆን ለመልስ ሰጪ የሰጡት ሌላ በሆሳዕና የሚገኘውን ቦታና ሲኖሩበት የነበረውን ቤት ነው፡፡ ለአመልካች የተሰጠው ቤት የተወረሰ መሆኑ በመረጋገጡ ለአመልካቿ በንብረት ክፍፍል የሚደርሳት ሀብት ከአንድ አራተኛ በላይ የሚጎዳት ከሆነ ክፍፍሉ በአንቀጽ በ1123 መሠረት መስተካከል ይኖርበታል፡፡ አመልካች ይህን አንቀጽ ባትጠቅስም ኑዛዜው እንዲፈርስላት የጠየች በመሆኑና ትክክለኛውን አንቀጽ መጥቀስ የማይጠበቅባት በመሆኑ ያቀረበችው ጥያቄ ከዚህ ድንጋጌ አንፃር መስተናገድ ነበረበት፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ይህን አላደረጉም፣ በመሆኑም ውሣኔአቸው ከላይ በተሰጠው ዝርዝር ምክንያት ሊለወጥ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የደረሰባት ጉዳት ምን ያሕል መሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች ያልተጣራ በመሆኑ ለወራሾች የተከፈለው ንብረት ግምት አስልተው ለአሁን አመልካች የንብረቱ አንድ አራተኛ እንዲሰጡ መደረጉ አግባብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ለማጠቃለል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ኑዛዜው ይፀናል በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ በተሰጠው ዝርዝር ምክንያት ሊሻሻል የሚገባው ነው፡፡ ኑዛዜው የአሁንዋን አመልካች ከአንድ አራተኛ በላይ ስለሚጎዳት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይህን የጉዳት መጠን የሚያስተካክል የአከፋፈል ሥርዓት ሊከተል ይገባል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ጠቅላይፍ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 5017 ጥቅምት 25 ቀን 1997 የተጠሰው ውሣኔ የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ለአሁንዋ አመልካችና መልስ ሰጪ የተሰጠውን ንብረት ግምት እንዲሰላ አድርጎ የአሁንዋ አመልካች የንብረቱ አንድ አራተኛ እንድታገኝ ያድርግ፡፡

3/ ኑዛዜው በአጠቃላይ ፍርስ ባይሆንም ከላይ በተራ ቁጥር 2 በተጠቀሰው መሠረት ሟቹ የሰጡት የክፍፍል ሥርዓት አመልካች የንብረቱ አንድ አራተኛ ታግኝ በሚል ተሻሽሏል፡፡

4/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔው መሻሻሉን እንዲያውቀው የውሣኔ ኮፒ ይላክለት፡፡

5/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35472

ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ መሐመድ ካሣሁን - ጠበቃ አረጋኸኝ መርዕድ

ተጠሪ፡- አቶ ሣልሀዲን ኑር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካችና በሥር አንደኛ ተከሣሽ የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ አቶ ኑር ሁሴን ካሴ ከተባሉት ሸሪኬ ጋር በመሆን በደንቢያ ወረዳ ልዩ ስሙ "ዋዋ" በተባለ ቦታ መሬት ለማልማት በነበረን ፍላጎት 17 ሄክታር መሬት በኪራይ ተሰጥቶን የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተን ከሸሪኬ ከአቶ ኑርሁሴን ካሴ ጋርም ሰኔ 5 ቀን 1988 ዓ.ም የህብረት ሽርክና ውል ተፈራርመን ከዚያም በተፈቀደልን መሬት ላይ አስፈላጊ የሆነውን የማለስለስና የማዘጋጀት ሥራ ሠርቼ በተዘጋጀው መሬት ላይ የተለያየ እህል ዘርቼበት እንዳለ ያለምንም ማስጠንቀቂያ የውሉ ጊዜ ሣይደርስ መሬቱን ከተዘራው እህልና ከተለያዩ የግብርና መሣሪያዎች ጋር አንደኛ ተከሣሽ የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት በመውሰድ ለሁለተኛ ተከሣሽ አሣልፎ ሰጥቷል፤ በማለት፣ ይገባናል ያሉትን የእህልና የጉልበት ዋጋ በመዘርዘር በድምሩ ብር 71.990 እንዲከፈላቸውና መሬቱም እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ በአንደኛ ተከሣሽና በአቶ ኑርሁሴን ካሴ መካከል በተደረገው የመሬት ኪራይ ውል መሠረት ውሉ ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋናው በኪራይ ውሉ አንቀጽ 11/ለ/ መሠረት ተከራዩ ለአከራዩ መክፈል የሚገባውን የመሬት ኪራይ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሣይከፈል በሚቀርበት ጊዜ እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን ተከራዩም በውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት የመሬት ኪራዩን መክፈል ሲገባቸው ባለመክፈላቸው አንደኛ ተከሣሽ ውሉን እንዳቋረጠ ፍ/ቤቱ ስለተገነዘበ በተቋረጠ ውል ላይ በመመስረት ከሣሽ ያቀረቡት ክስ አግባብነት የለውም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ፣ በተደረገው የመሬት ኪራይ ውል መሠረት ተከራዩ መክፈል የሚገባውን የመሬት ኪራይ በየጊዜው ሲከፍል እንደነበር በአስረጂነት የቀረቡት ሰነዶች የሚያረጋግጡ ሆኖ ሣለ የሥር ፍ/ቤት ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል ነገር መኖሩን ሣያረጋግጥ በአንደኛ መ/ሰጭ /የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት/ የቀረበውን መከራከሪያ ብቻ በመቀበል በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ተቋርጧል በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ሽሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው መሬት ለይግባኝ ባይ /ለአሁን ተጠሪ/ እንዲመለስለት በማለት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የክፍያ ጥያቄውን በተመለከተ ግን የሥር ፍ/ቤት በማስረጃ አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት መልሷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች /የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ/ ከወረዳው ገጠር ልማት ጽ/ቤት ጋር ባደረገው ውል ያገኘውን መሬት ለተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲያስረክብ መወሰኑ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍ አከራክሯል፡፡ ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ከሥር አንደኛ ተከሣሽ ከደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ጋር ባደረጉት ውል መሠረት የያዙትን መሬት ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት መወሰኑ አግባብነት አለውን? የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ጭብጥ አኳያም የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ተጠሪ በአመልካችና በሥር አንደኛ ተከሣሽ የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ላይ ክስ ያቀረቡት በኪራይ ውል መነሻነት የተያዘውን 17 ሄክታር መሬት አንደኛ ተከሣሽ ለሁለተኛ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ያለአግባብ አሣልፎ የሰጠ ስለሆነ መሬቱን መልሰው ያስረክቡኝ ኪሣራም እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

የመሬት ኪራይ ውሉ ተደርጎ የነበረው በአቶ ኑርሁሴን ካሴና በወረዳው ግብርና ልማት ጽ/ቤት በኩል የነበረ ቢሆንም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ በየዓመቱ ውሉ ሲታደስ የነበረው በተጠሪ በአቶ ሣልሀዲን ኑር ስም ስለነበር ይህ ሁኔታ ተጠሪን ተዋዋይ ወገን እንዳደረጋቸው ስለሚያስገነዝብ ውሉ በተጠሪ ላይ የመብትም ሆነ የግዴታ ምንጭ ሊሆን ስለሚችል ይህንኑ ውል መሠረት በማድረግ ክስ ማቅረባቸው ክስ ባቀረቡበት ነገር መብትና ጥቅምት /vested interest/ እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ተጠሪ ክስ ባቀረቡበት ነገር መብትና ጥቅም አላቸው ከተባለ ውሉን አስገድዶ ለማስፈፀም /forced performance/ ያቀረቡት ክስ ከሕጉ አኳያ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ መርምረናል፡፡

የሥር አንደኛ ተከሣሽ የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት የውሉ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ከተጠሪ ላይ በመውሰድ ለአመልካች ስለማከራየቱ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት የመሬት ኪራይ ውሉን በተናጠል መሠረዙ /unilateral cancellation/ አግባብነት የለውም ቢባል ውሉ የተሰረዘበት ወገን በውሉ መሠረዝ ምክንያት የደረሰበት ኪሣራ ቢኖር ይህን ከመጠየቅ አልፎ የውሉን ቃል በመፃረር የሠራውን ሥራ እንዲያፈርስና እንደ ውሉ ተገዶ እንዲፈጽም መጠየቅ ስለመቻሉ ከሕጉ አንፃር ተመልክተነዋል፡፡

በዚህም መሠረት ውልን አስገድዶ ለማስፈፀም በሚቀርብ አቤቱታ በውሉ አለመከበር የተነሣ በባለገንዘቡ ላይ የደረሰው ወይም ይደርሣል ተብሎ የሚገመተው ኪሣራ ከባለእዳው ቀጥተኛ የውል አፈፃፀም በስተቀር በጉዳት ኪሣራ መልክ ፈጽሞ ሊካስ የማይችል በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ እንደዚሁም እንደ ውሉ ይፈፀምልኝ ብሎ ለሚጠይቀው ተዋዋይ ወገን የተለየ ጥቅም በሚሰጠው ጊዜና አፈፃፀሙም የባለእዳውን የግል ነፃነት የማይነካ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የውሉ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዜው 17 ሄክታር መሬት ከተጠሪ ያለአግባብ ተነጥቆ ለአመልካች ተሰጥቷል ቢባል እንኳን በተጠሪ ላይ የደረሰው ወይንም ወደፊት ይደርሣል ተብሎ የሚጠበቀው ኪሣራ በጉዳት ኪሣራ መልክ ሊካስ የሚችል በመሆኑ ተጠሪ ኪሣራ ከመጠየቅ አልፈው መሬቱን ተከሣሾች ተገደው ሊያስረክቡኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክስ በውል አፈፃፀም የተለየ ጥቅም /special interest/ ሣይኖራቸውና በአጠቃላይም ሕጉ ውልን አስገድዶ ስለማስፈፀም ከደነገገው መርህ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሥር ተከሣሾች መሬቱን ለሥር ከሣሹ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08167 ታህሣሥ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት የሥር ተከሣሾች ለሥር ከሣሽ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለተፈፀመበት ይህንኑ የውሣኔውን ክፍል በመሻር የኪሣራ ክፍያ ጥያቄውን በተመለከተ በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በኩል ታይቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2/ አመልካችም ሆነ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ለተጠሪ ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡ ይፃፍ፡፡

3/ ይህ ፍርድ የሰበር አቤቱታ ባላቀረበው የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ላይ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 331 መሠረት ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34803

ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- መ/ር መካንንት ወረደ- ወኪል ጌታቸው ወረደ - ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1/ መስከረም ዳኛው

2/ ሃይለየሱስ ዳኛው

3/ አዳነች ዳኛው — ሞግዚት አቶ ጥጋቡ መኮንን - ቀርበዋል፡፡

4/ ዙሪያሽወርቅ ዳኛው

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ. 11282 ሰኔ 04/1999 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 13114 ጥቅምት 20/2000 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ በመሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በሚል ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ተከሣሽና መልስ ሰጭ እንዲሁም የአሁን ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤቶች ከሳሾችና ይግባኝ ባዮች በመሆን እየተከራከሩ የመጡ ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ መሠረታዊ ይዘቱ ደግሞ በደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን በእብናት ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኘውን የአውራሽ አባታችን አቶ ዳኛው አስፋው የሆነውን አዋላጆቹ በምስራቅ የወ/ሮ እንዬ ጥጋቡ ቤትና ቦታ፣ በምዕራብ የአቶ አስማረ አየለ ቤትና ቦታ፣ በሰሜን የሊቀ ትጉሃን ፍስሃ እርቁዬ ቤትና ቦታ እንዲሁም በደቡብ የመልካ አውራ መንገድ የሆነ ቤትና ቦታ ተከሣሽ በኪራይ እየተጠቀመበት ከቆየ በኋላ አባታችን ሲሞት ሊያስረክበን ስላልቻለ ቤቱን ያስረክበን ያልተከፈለ የቤቱ ኪራይም ይከፈለን የሚል ነው፡፡

ስር ተከሣሹም በሰጡት መልስ የተጠቀሰውን ቤት ከሚች ዳኛው አስፋው ሃምሌ 04/1996 ዓ.ም. በተፃፈ የሽያጭ ውል በብር 7250 /ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር/ ሸጠውልኝ ስሙን ሳያዞሩልኝ በስራ ምክንያት ወደ ሰሜን ጎንደር ተዛውረው እንደሞቱ በመግለጽ የከሳሾች ክስ ሕጋዊ ያልሆነ ጥቅምን ለማግኘት ታስቦ የቀረበ ስለሆነ በቂ ኪሣራ ተቆርጦልኝ በነፃ ልሰናበት ይገባል ብለዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገኖች ክርክር በሰውና በጽሁፍ ማስረጃዎች አጠናክሮ ከመረመረ በኋላ የደረሰበት ማጠቃለያ ስር ተከሣሽ ከከሳሾቹ አውራሽ አከራካሪውን ቤት ሐምሌ 04/1996 ዓ.ም. በተፃፈ ውል በሕጋዊ መንገድ በብር 7250 /ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ እንደገዛና ገንዘም ብር 4000 /አራት ሺህ/ ወዲያውኑ ለሻጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማለትም ለአቶ ዳኘው አስፋው እንደከፈሉና ቀሪው ብር 3250 /ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ ሻጭ የቤቱን ስም በገዢ ሲያዛውሩ እንደሚሰጥ እንደተዋዋሉ ከገለፀ በኋላ ውሉ በሕጋዊ መንገድ የተፈፀመ በመሆኑ ተከሳሹ ቤቱን ለከሣሾች የሚመልሱበት ምክንያት እንደሌለ ነገር ግን ሳይከፍሉ የቀሩትን ብር 3250 /ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ ለከሣሾቹ እንዲከፍሉና ቤቱ በተከሣሹ ስም መዛወር እንዳለበት ወሰነ፡፡

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከላይ የቀረበውን ክርክርና ውሣኔ በይግባኝ ቀርቦለት ካከራከረ በኋላ በፍ/ይ/መ/ቁ. 13114፣ ጥቅምት 20/2000 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የግራ ቀኙ ወገኖች የቤት ሽያጭ ውል በሚመለከተው ውል አዋዋይ አካል ወይም በፍርድ ቤት ያልተደረገ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሠረት ውል ነበር ማለት እንደማይቻል በአጠቃላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 21448 በሰጠው ውሣኔ ያስቀመጠውን የሕጉን አተረጓጎም የሚፃረር የቤት ሽያጭ ውል በመሆኑ ውድቅ እንደሆነ በመግለጽ የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር ቤቱ ለስር ከሳሾች /ይግባኝ ባዮች/ ሊመለስላቸው ይገባል ብሏል፡፡

ከላይ የሰፈረው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ጥቅምት 23/2000 ዓ.ም. የተፃፈ አቤቱታ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም በአመልካቹና በተጠሪዎቹ አውራሽ /አባት/ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በተዋዋዮቹ ወገኖች መካከል እንደ ሕግ ስለሚቆጠር የምዝገባ አስፈላጊነት በ3ኛ ወገኖች ዘንድ ውጤትን እንዲያስገኝ ሲባል እንጂ የተደረገውን የሽያጭ ውል ሊያፈርስ አይገባም፤ ይህ ሃሣብም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 ተመልክቷል፤ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ አመልካች ቤቱን በኪራይ መልክ እንደያዝኩ በማስመሰል እንድለቅላቸው የሚጠይቅ ሆኖ እያለ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን ከተያዘው ጭብጥ በመውጣት ውሉ ዋጋ እንደሌለው ለፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 ትርጉም ሰጥቶ ማለፉ አግባብነት የለውም፤ ውሉ ይፈርሳል እንኳ ቢባል አመልካች ለተጠሪዎቹ አውራሽ ማለትም ለሻጭ የከፈልኩት ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ በምን ሁኔታ መተርጎም እንዳለበት ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በዝምታ ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም በሞግዚታቸው በኩል የካቲት 14/2000 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አጭር ይዘቱም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍበት አንዳችም ምክንያት ባለመኖሩ እንዲፀናላቸው፤ አመልካች ለሟች አቶ ዳኘው አስፋው ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ በቤቱ ሽያጭ ምክንያት ከፍለው እንደነበር ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ይህ ገንዘብ እንዲመለስላቸው መጠየቃቸው አግባብነት የለውም፤ ይልቁንስ አመልካች በኪራይ መልክ የያዙትን ቤት የ4 ዓመት ኪራዩን ብር 4800 /አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር/ ስላልከፈሉ እንዲከፍሉ ሆኖ ፍርድ ይሰጠን፤ ወጪና ኪሣራችንም ይታሰብልን የሚል ነው፡፡

አመልካችም መጋቢት 12/2000 ዓም በሰጡት የመልስ መልስ ተጠሪዎች እርስ በርሱ የሚምታታ የኪራይ ጥያቄ ሊያቀርቡብኝ አይችሉም ያሉ ሲሆን ቀሪው በአቤቱታቸው ውስጥ የዘረዘሯቸውን ሃሣቦች የሚያጠናክሩ በመሆናቸው ደግሞ መዘርዘር ሳያስፈልግ ታልፏል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገኖች የክርክር አመጣጥ ከላይ እንደተቀመጠው ከተገነዘበ በኋላ፡-

1. በአመልካችና የተጠሪዎች ወላጅ አባት በሆኑት በአቶ ዳኛው አስፋው መካከል ሐምሌ 04/1996 ዓ.ም. የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም?
2. ውሉ በሕግ መሠረት ያልተደረገ ነው የሚባል ከሆነ አመልካች በውሉ መፈፀም ምክንያት ለተጠሪዎች አባት /አውራሽ/ የከፈሉት ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ ሊመለስላቸው ይገባል ወይስ አይገባም?
3. ተጠሪዎች በመልሳቸው አመልካች እንዲፍላቸው የጠየቁት የ4 ዓመታት የአከራካሪው ቤት ኪራይ ብር 4800 /አራት ሺህ ስምንት መቶ/ የሕግ መሠረት አለው ወይስ የለውም? የሚሉትን ጭብጦች በመመስረት ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ የግራ ቀኙን ወገኖች እያከራከረ ያለው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውል በመካከላቸው መኖር ወይም ያለመኖር ሲሆን አመልካች ከተጠሪዎች አባት /አውራሽ/ ሐምሌ 04/1996 ዓ.ም. በተደረገ ውል በብር 7250 /ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ ቤት እንደገዙ የሚያመለክተው ጽሁፍ ወደሚመለከተው ውል የማዋዋል ስልጣን ያለው አካል ወይም ወደ ፍርድ ቤት ቀርቦ የተመዘገበ አይደለም፡፡ ምንም እንኳ ሻጭና ገዢ እንዲሁም ምስክሮች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውሉ የፈረሙ ቢሆንም ይህ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ሕጋዊ ለመሆን ከላይ የተጠቀሱት አካላት ዘንድ ቀርቦ የመመዝገቡን አስገዳጅነት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 አስቀምጦታል፡፡ የምዝገባው ሂደት ባልተሟላበት ሁኔታ ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረቱ ሽያጭ ሕጋዊ ሊባል እንደማይችል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 21448 ሚያዝያ 30/1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ ግልጽ ትርጉም እንደሰጠበት ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጣቸው የመጨረሻ ፍርዶችም በፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶች ወይም የተለያዩ እርከኖቻቸው ተቀባይነት ሊያገኙ እንደሚገባ አዋጅ ቁጥር 454/1997 አስፍሯል፡፡ ከላይ የተጠቀሰው የሰበር ችሎት ውሣኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ እና 2878 ያላቸውን ልዩነት አስፍሯል፡፡ ይኸውም የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት እንዲደረግ የማድረጉ አስፈላጊነት በተዋዋይ ወገኖቹ መካከል የሚፀና ውል መኖሩን ለማረጋገጥ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 የተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ዓላማ ደግሞ ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት ለማምጣት ሲባል ነው፡፡ ከዚህ የሕግ ይዘትና አተረጓጎም አኳያ የአሁኑ አመልካች የሽያጭ ውሉ በአዋዋይ አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት አለመፈፀሙ ከተጠሪዎች አባት /አውራሽ/ የገዛሁትን አከራካሪውን ቤት ውጤት የሌለው አያደርግብኝም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ነጥብ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን ጭብጥ በሚመለከት የሰጠው ትንታኔ ትክክለኛ በመሆኑ በአመልካች ጥያቄ ላይ የፈፀመው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ ከላይ እየተጠቀሰ የመጣውን አከራካሪ ውል መሠረት በማድረግ አመልካች የተጠሪዎች አባት ለሆኑት ለአቶ ዳኛው አስፋው ብር 4000 /አራት ሺህ/ እንደሰጧቸውና ብር 3250 /ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር/ ቀርታቸው እንደነበር የደቡብ ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰነድና በሰው ምስክር እንዳረጋገጠው ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አከራካሪው ውል ሕጋዊ አይደለም የሚል ውሣኔ ሲሰጥ አመልካች ለተጠሪዎች አባት የከፈሉት ከላይ የተጠቀሰው ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ እንዲመለስላቸው አብሮ መወሰን አልነበረበትም ወይ? የሚለውን ነጥብ በተመለተ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 እንዳስቀመጠው ተዋዋይ ወገኖቹን ወደ ነበሩበት የመመለስ ተግባር መከናወን እንዳለበት ነው፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አኳያ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪዎች አባት በአከራካሪው ውል ምክንያት የከፈሉትን ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ ተጠሪዎች እንዲመልሱላቸው አለመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡

በመጨረሻም የተቀመጠውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪዎች በዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስ አመልካች ያልከፈሉትን የ4 ዓመት የቤት ኪራይ በጠቅላላ ብር 4800 /አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር/ ሕጋዊ አግባብነቱ ሲታይ ተጠሪዎቹ ይህንን ነጥብ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ያቀረቡት ይግባኝ የለም፡፡ ይህንን ጥያቄ እያቀረቡ ያሉት አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት እየተካሄደ ባለው ክርክር ነው፡፡ ይግባኝ ወይም አቤቱታ ባላቀረቡበት ሁኔታ የቤቱ ኪራይ እንዲከፈላቸው ተጠሪዎች መጠየቃቸው ሕጋዊ አካሄድን የተከተለ ባለመሆኑ ከዚህ አኳያ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 13114 ጥቅምት 20/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በአብላጫ ድምጽ ተሻሽሏል፤ ይፃፍ፡፡
2. በአመልካችና የተጠሪዎች አባት /አውራሽ/ በሆኑት በአቶ ዳኛው አስፋው መካከል ሐምሌ 04/1996 ዓ.ም. የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 አኳያ ሲታይ ውል ለማዋዋል ስልጣን ከተሰጠው አካል ያልተመዘገበ ወይም በፍርድ ቤት ፊት ያልተፈፀመ በመሆኑ አመልካች ውሉ እንዲጸናላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ ነገር ግን በሽያጭ ውሉ ምክንያት አመልካች ለተጠሪዎች አባት የከፈሉትን ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 መሠረት ተጠሪዎች ሊመልሱላቸው ይገባል፡፡
3. ተጠሪዎች ይግባኝ ወይም አቤቱታ ሳያቀርቡ በመልሳቸው የጠየቁት የቤት ኪራይ ጥያቄ አግባብ ያለው የክርክር ሂደት ያልተከተለ በመሆኑ ውድቅ ሆኗል፡፡ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የልዩነት ሀሣብ

እኔ ስሜ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔና በተከተለው የሕግ ትርጓሜ ባለመስማማት እንደሚከተለው የልዩነት ሀሣቤን አስፍሬያለሁ፡፡

አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔ በዝርዝር እንደተገለፀው በሥር ፍርድ ቤት ከሣሽ በዚህ ፍርድ ቤት ተጠሪ በሆኑት የእነ መስከረም ዳኘው አውራሽና አባት አቶ ዳኘው አስፋውና በአመልካች ሐምሌ 4 ቀን 1996 ዓ.ም. በጽሑፍ በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል፣ አመልካች ቤቱን በብር 7250 /ሰባት ሺ ሁለት መቶ ሀምሳ ብር/ ገዝተዋል፡፡ በዚህ የውል ስምምነት መሠረት አመልካች ለተጠሪዎች አባት ብር 4000 /አራት ሺ ብር/ በመክፈል ቤቱን ተረክበው በይዞታቸው አድርገው እየተጠቀሙበት የሚገኙ ሲሆን በውላቸው መሠረት ቀሪውን ብር 3250 /ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሀምሣ ብር/ የቤቱ ስመ ንብረት ሲዛወር አመልካች ለተጠሪዎች አውራሽ ለመክፈል ተስማምተዋል፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በጽሁፍ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የተደረገ በመሆኑ በሽያጭ ውሉ መሠረት አመልካች የበኩላቸውን ግዴታ በመፈፀም ቤቱን ከተጠሪዎች አውራሽ ተረክበዋል፡፡ በውሉ መሠረት ያልተፈፀመውና ሊፈፀም የሚገባው የቤቱን ስመንብረት በአመልካች ስም ለማዛወር የሚያስፈልጉ ተግባራትን መፈፀምና ቀሪውን ክፍያ ለተጠሪዎች መክፈል ብቻ ነው፡፡

አብላጫው ድምጽ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በሕግ የሚጸና ውል የለም በማለት የወሰነው ከዚህ በፊት አምስት ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21448 የሰጠው የሕግ ትርጉም በዚህም ጉዳይ ለተያዘው ጭብጥ ያገለግላል የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ አብላጫው ድምጽ የተከተለውን የሕግ ትርጓሜ ትክክለኛነት የማላምንበት በመሆኑና በዚህ መዝገብ ያለው ሁኔታ ራሱን የቻለ ልዩ ባሕሪ አለው ብዬ ስለማምን ከሙያ ባልደረቦቼ ተለይቻለሁ፡፡ አብላጫው ድምጽ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጭብጦች በመያዝ አግባብነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አተረጓጎምን ማስተካከልና ውሣኔ መስጠት ነበረበት ብዬ አስባለሁ፡፡

በእኔ እምነት መሠረታዊው ችግር ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1፣ ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2877 እና ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2878 የተሰጠው የሕግ ትርጓሜ በመሆኑ በሕጉ ድንጋጌዎች የተሰጠውን ትርጓሜ

1. ከጠቅላላው የውል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ግብና ዓላማ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረታዊ ባሕሪ ጋር በመመርመር ድንጋጌው በምን መልኩ መተርጎም እና ተግባራዊ መሆን እንዳለበት መወሰን፤
2. ጠቅላላ የውል ሕግ ድንጋጌዎች ከሽያጭ የውል ድንጋጌዎች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነትና በተለይም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2877 እና 2578 ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት እንደዚሁም ልንከተለው ስለሚገባው የአተረጓጎም ስልት መወሰን፤
3. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በውል አዋዋይ ባለሥልጣን ፊት ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ፊት ያልተደረገ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እንደ ረቂቅ ይቆጠራል በሚል መልክ የተሰጠውን የሕግ ትርጓሜ ተገቢነት መመርመር፤
4. በተራ ቁጥር 3 በተገለፀው መንገድ የተሰጠው የሕግ አተረጓጎም የውሎችን ተፈፃሚነት ወይም ፈራሽነት መርምሮ በመወሰን ሂደት የፈጠረው የተዛባ ግንዛቤና ችግር የፍትህ መዛባት ስለመኖሩና ችግሩን ለመቅረፍ ልንከተለው ስለሚገባው የአተረጓጎም ስልት መወሰን፤
5. ውሎች በጽሁፍ በመደረግ ብቻ ሣይወሰኑ በግማሽ ወይም በሙሉ በተፈፀመበት ሁኔታ በተራ በቁጥር 3 የተገለጸው የሕግ አተረጓጎም ተገቢ ስለመሆኑና በአጠቃላይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 አተረጓጎምን አስመልክቶ ልንከተለው የሚገባውን የአተረጓጎም ስልት በስፋትና በዝርዝር አይቶ መወሰን አስፈላጊ ነው የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ እነዚህና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ነጥቦች በጥልቀት ሣይታዩ ሶስትና አራት የሚሆኑ የሕግ ድንጋጌዎች በማገጣጠም የሚሰጥ ውሣኔ ከችግር ፈቺነቱ ይልቅ ችግር ፈጣሪነቱ የሚያመዝን እንደሚሆን ለመገንዘብ ይኸ የህግ አተረጓጎም ከተሰጠ በኋላ እየተፈጠረ ያለውን የተመሠቃቀለ ሁኔታ በማየት በቂ ትምህርት ለመውሰድ ይቻላል ብዬ አስባለሁ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 2877 መካከል ያለውን ልዩነት ለመረዳት ህግ አውጭው በ1952 ዓ.ም የፍታብሔር ህጉን ሲያውጅ በተለይም ጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችንና የልዩ የውል ህግ ድንጌጋዎችን ሲያውጅ ሊያሟላው የፈለገውን መሠረታዊ ግብ በዝርዝር ማየትና መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ህግ አውጭው የፍትሀብሔር ህጉን በተጠቃለለ መንገድ ሲያውጅ፡-
   - ማንኛውም በአገሪቱ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ወይም ለዕለቱ በእንግድነት በአገሪቱ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ሰው ያለውን የሲቪል መብትና ግዴታ አውቆ መብቱን ለማስከበርና ግዴታውን ለመወጣት የዕለት ከዕለት የኑሮ መመሪያው አድርጐ እንዲጠቀምበት፤
   - ህብረተሰቡ የፍትሀብሔር ህጉ ከመታወጁ በፊት ይሠራባቸውና ይተዳደርባቸው በነበሩ ልማዳዊ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ ደንቦች መሠረት የፈጠራቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንኙነቶች የህብረተሰቡን ልማድ ባህልና ሀይማኖታዊ እሴት ከግምት ውስጥ በማስገባት ታውጇል ብሎ በሚያስበው የፍትሀብሔር ህግ ድንጋጌዎች ግልጽ የሆነ ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግና ህጋዊ ጥበቃ መስጠት፤
   - እያደገ ከመጣው የዓለም የንግድ ልውውጥና ዘመናዊ አሠራር ጋር የማይራመደውን በአገሪቱ የሚከናወን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ወደዳበረና ያደገ ዘመናዊ አሠራር የማሸጋገር ግብ የነበረው መሆኑን ከፍትሀብሔር ህጉ የማጽደቂያ አዋጅና ንጉሰ ነገስቱ በፍታብሔር ህጉ በመግቢያነት ከገለጿቸው ፍሬ ሀሳቦች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ህግ አውጭው የውልን ህግ አስመልክቶ ጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችንና ልዩ የውል ህግ ድንጌጋጌዎችን ሲደነግግ እነዚህን መሠረታዊ ግቦች የማሣካት ሀሳብና ፍላጐት ነበረው ብዬ አስባለሁ፡፡ ህግ አውጭው የልዩና የጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችን ሲደነግግ ህብረተሰቡ ሲፈጽማቸው ለነበረው የውል ግንኙነቶች በተለይም ባህላዊና ልማዳዊ እሴቶችን መሠረት አድርጐ ሲፈጽማቸው ለነበሩ የውል ግንኙነቶች ህጋዊ ዕውቅና እና ጥበቃ መሥጠት አንደኛው ዓላማው እንደነበር የፍትሐብሔር ህጉን መግቢያ ብቻ ሣይሆን ስለቀብድ የተደነገጉ የውል ድንጋጌዎችን በመመርመር ለመረዳት የሚቻል ሲሆን በአገሪቱ የሚደረጉ ውሎች እና የውል ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ከውል የሚመነጩ ጉዳዮች አስተደደርና የችግር አፈታት እንደዚሁም የውሎች ተፈፃሚነት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው መርሆች መሠረት እንዲከናወኑ የማድረግና የውል ግንኙነቶችን ወደ ዘመናዊነት የማሸጋገር ዓላማና ግብ እንደነበረው የውሉን ድንጋጌዎች ዝርዝር ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡

ህግ አውጭው እነዚህን መሠረታዊ ግቦች ለማሣካት በዋነኛነት ሶስት አይነት ባህሪ ያላቸው የውል ህግ ድንጋጌዎች አውጇል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

(i) የመጀመሪያው ፈቃጅነት ያላቸው የውል ህግ ድንጋጌዎች “Permissive provisions of law of contract” ሲሆኑ እነዚህ የህግ ድንጋጌዎች ሰፊ ነፃነት ለተዋዋይ ወገኖች የሚሰጡ ናቸው፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ህግ አውጭው በፈቃጅነት የደነጋገቸውን የውል ድንጋጌዎች መከተል ካልፈለጉ ደግሞ የመተው ነፃነት አላቸው፡፡ የፈቃጅ የህግ ድንጋጌዎች አለመሟላት የውሉ ህጋዊነት ላይ የሚያስከትለው ምንም አይነት ተጽዕኖ የለም፡፡ እነዚህ የህግ ድንጋጌዎች በተዋዋይ ወገኖች ፍላጐትና ፈቃድ ተጠቃሽና ተፈፃሚ የሚሆኑ ሲሆኑ ተዋዋይ ወገኖች በዝምታ ያለፉት ነገር ሲኖርና በዚያም ምክንያት ክፍተት ሲፈጠር ክፍተቱን ለመሸፈን ሊጠቀሱና ሊፈፀሙ የሚችሉ የህግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ፈቃጅነት ያላቸው የውል ህግ ድንጋጌዎች የተዋዋዮቹን የመዋዋል ነፃነት (Freedom of contract) በማክበር ህግ አውጭው በአስገዳጅነት ሣይሆን በአማራጭነት የደነገጋቸው ናቸው፡፡

(ii) በሁለተኛ ደረጃ የሚፈረጁት አስገዳጅነት ያላቸው የውል ህግ ድንጋጌዎች (Mandatory provisions of the law of contract) ናቸው፡፡ እነዚህ የህግ ድንጋጌዎች በባህሪያቸው ተዋዋይ ወገኖች ውል የመዋዋል ነፃነታቸውን ተጠቅመው የውል ስምምነት ሲያደርጉ በግዴታ ሊከተሉት የሚገባውንና ሊያሟሉ የሚገባቸውን መሥፈርቶች የሚደነግጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ድንጌጋጆች ህግ አውጭው ተዋዋይ ወገኖች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ትእዛዝ የሚሰጥባቸው ብቻ ሣይሆኑ ህግ አውጭው በድንጋጌዎቹ የሰጠውን ጥብቅ ትእዛዝ አለመፈፀም ወይም አለማሟላት ውሉን ህጋዊ ህልውና እንዳይኖረው የሚያደርግ ውጤት አልባ (Void) ወይም ውሉ እንከን ያለበትና ፊራሽ (voidable) እንዲሆን የማድረግ ሀይልና ጉልበት ያላቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ተዋዋይ ወገኖች ውላቸው በህግ ፊት የፀና እንዲሆን ከፈለጉ አስገዳጅ የሆኑ የውል ህግ ድንጋጌዎች መከተልና ማሟላት አለባቸው፡፡ የአስገዳጅነት ባህሪ ያላቸውን የውል ህግ ድንጌጋጆች አለማሟላት ውሉን ለማፍረስ የሚያስችል እንከን ያለበት ውል የሚያደርግ ወይም ውሉን ውጤት አልባና ህጋዊ ህልውና የሌለው የሚያደርግ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(iii) አብዛኛውን ጊዜ በህግ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ትምህርቶች እና ስለ ህግ የሚፃፉ ጽሁፎች የአገራችንን የውል ህግ ድንጋጌዎች ፈቃጅ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎች እና አስገዳጅነት ያላቸው የህግ ድንጌዎች በማለት የሚፈርጁ ናቸው፡፡ አብላጫው ድምጽም ሆነ በሰበር መዝገብ ቁጥር 21448 ለፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ትርጓሜ የሰጠው ችሎት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 በባህሪው አስገዳጅነት ያለው የህግ ድንጋጌ ነው የሚል አቋም አላቸው፡፡ በእኔ በኩል አንድ መታየት ያለበት የውል ህጋችን ባህሪ ሣይዳሰስና ሣይታይ ታልፏል የሚል እምነት አለኝ፡፡ የውል ህግ ድንጋጌዎችን ስንመረምር ህግ አውጭው በትእዛዝ መልክ የደነገጋቸው ነገር ግን የአስገዳጅነት ባህሪ የሌላቸው ድንጌጋዎችን እናገኛለን፡፡ የዚህ አይነት የህግ ድንጋጌዎች አዛዥ ወይም መሪ የህግ ድንጋጌዎች (Directory provisions of the law of contract) በሚል መንገድ ይገለፃሉ፡፡ የአዛዥነት ወይም የመምራት ባህሪ የተላበሱ የውል ህግ ድንጌዎች በወቅቱ የነበረውን ህግ አውጭ ፍላጐት የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ በተለይም የፍትሐብሔር ህጉን ሲያወጅ ህግ አውጭው በአገሪቱ ግዛት ክልል የሚፈፀሙ የውል ግንኙነቶችን ወደ ዘመናዊ የውል አሠራርና አስተዳደር ለማሸጋገር በማሰብ የተደነገጉ ናቸው፡፡ አዛዥ ወይም መሪ የህግ ድንጌዎች ህግ አውጭው የውል ግንኙነት ሲቋቋም ወይም ሲፈፀም እንዲሆን የሚፈልገውን ነገር በትእዛዝ መልክ በመደንገግ ህብረተሰቡን ወደሚፈልገው ግብ የሚመራባቸው የህግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የውል ድንጋጌዎች ህብረተሰቡን ወደሚፈለገው ግብ ለመምራት ሚና ያላቸው ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች አዛዥ ወይም መሪ የህግ ድንጌዎች ሣይከበሩና ሣይሟሉ ቢቀሩ መሠረታዊ የሆኑና በውል የተቋቋሙ መብትና ግዴታዎችን ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ የማድረግ ባህሪ የሌላቸው ናቸው፡፡

የህግ መዝገብ ቃላት የአዛዥነት ወይም የመሪነት ባህሪ ያላቸውን ድንጋጌዎች “the observance of which is not necessary to the validity of the proceeding to which it relates. Statutory provisions which do not relate to the essence of things to be done, and as to which compliance is of convenience rather than substance are directory” በማለት ይገልፃቸዋል፡፡

ከዚህ በመነሣት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌን ባህሪ ስመረምረው ድንጌጋው አዛዥ ወይም መሪ የህግ ድንጋጌ እንጂ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ለዚህም ከአንድ በላይ የሆኑ ምክንያቶች መስጠት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የድንጋጌው አቀራረጽና የቃላት አሰካክ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ “የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች ባለቤትነት ወይም የማይንቀሣቀሥ ንብረት ላይ አላባ ጥቅም መብት ወይም መያዣነት ወይም ሌላ አገልግሎት ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎች ሁሉ በጽሑፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት መሆን አለባቸው” በሚል መንገድ የተደነገገ ነው፡፡

የዚህ ድንጋጌ አቀራረጽ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ ስለመሆኑ ከማያከራክረው የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 1728 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ጋር በማነፃፀር ብንመለከተው የፍትሐብሐር ህግ ቁጥር 1723 የንዑስ አንቀጽ 1 “በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት መሆን አለባቸው” ከማለት ውጭ ውሉ በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት አለመደረጉ ውሉን ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ የሚያደርገው ስለመሆኑ አይደነግግም፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ህግ አውጭው የፍ/ሕ/ቁ 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 የደነገገበት ሁኔታ ነው፡፡ ህግ አውጭው በአገሪቱ ግዛት ክልል ውስጥ የማይንቀሣቀሥ ንብረትን አስመልክቶ የሚከናወኑ ውሎች በባለሥልጣን ተረጋግጠው ተመዝግበውና በመንግሥት ጥበቃ ሥር እንዲቀመጡ ፍላጐት ያለው መሆኑን ለመግለጽና ህብረተሰቡ በዚህ መንገድ ውሎችን እንዲፈጽም ለመምራት አስቦ የደነገገው ድንጋጌ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ህግ አውጭው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 በአስገዳጅ የህግ ድንጋጌነት የመደንገግ ሀሳብ ነበረው ብሎ ለመከራከር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በ1952 ዓ.ም የፍትሐብሔር ህጉን ያወጀው ህግ አውጭ በአገሪቱ መልካምድራዊ ግዛት ውስጥ የሚደረጉ የማይንቀሣቀሥ ንብረትን የሚመለከቱ የሽያጭ፣ የመያዣ፣ የአላባ ጥቅም ማስተላለፊያና የሌሎች አገልግሎት ውሎችን የሚመዘግብና ህብረተሰቡ በቀላሉ ሊደርስባቸውና ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ተቋሞችን ገና ያላደራጀ መሆኑና ተቋማቱም በነበሩባቸው ውስን ሥፍራዎች የህጉን ይዘት መንፈስና ዓላማ በአግባቡ ተገንዝቦ ሥራ ላይ ሊያውል የሚችል የሰው ሀይል ገና ያላፈራ መሆኑን ጠንቅቆ የሚያውቅና የሚገነዘብ ነበር ብዬ አስባለሁ፡፡ በህግ አተረጓጐም ሥርዓት ውስጥ ምን ጊዜም ህግ አውጭው ምክንያታዊና የአገሪቱን ነባራዊ ዕውነታዎች በአግባቡ በመመርመርና በመመዘን ህጐችን ይደነግጋል ተብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይገመታል፡፡ ስለዚህ ውሉን ለመመዝገብ የሚችሉ ተቋማትና የሰው ሀይል ባልነበረበት ሁኔታ በአገሪቱ ውስጥ ሲከናወኑ የነበሩ የቤትና የመሬት ሽያጭ፣ የመያዣያ ውልና ሌሎች ውሎች ካልተመዘገቡ በስተቀር ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ መሆን አለባቸው የሚል ሀሳብ ይዞ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1ን ደንግጓል ብሎ መተርጎም ምንም አይነት ማነሻና መሠረት የሌለው አተረጓጎም ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

በአንዛሩ ህግ አውጭው ለደህንትና ለጥንቃቄ “to convenience” በማይንቀሳቀሥ ንብረት ላይ የሚደረጉ ውሎች በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ቢደረጉ የሚመረጥ መሆኑን ለማሣወቅና ህብረተሰቡም በዚህ መልክ ውሎችን እንዲዋዋል ለመምራት በማሰብ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 የንዑስ አንቀጽ 1ን በመደንገግ ይህ ባይሟላ ግን ውሉን ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ የማያደርግ መሆኑን በሚያሣይ መልኩ ድንጋጌውን የቀረፀ መሆኑን ሌሎች የህግ ድንጋጌዎችን መመልከት ሣያስፈልግ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 1728 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አቀራረጽ መካከል ያለውን ልዩነት በማነፃፀርና ድንጋጌው ሲታወጅ በአገሪቱ የነበረውን ነባራዊ ዕውነታና ህግ አውጭው ሊያሣካው ከሚፈልገው ግብና አላማ አንፃር በመመዘን ለመረዳት ይቻላል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በእኛ የህግ ሥርዓት ውስጥ የትኞቹ የህግ ድንጋጌዎች ፈቃጅነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች ናቸው? የትኞች አስገዳጅነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ናቸው? የትኞቹ ድንጋጌዎች ደግሞ የአዛዥነት ወይም የመሪነት ባህሪ ያላቸው ናቸው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስና የድንጌዎቹን ባህሪ ለመለየት የምንጠቀምባቸውን ዘዴዎች ተገቢነት በመመርመር የችግሩን መንስኤና ምክንያት ለመረዳት ጥረት ማድረግ ይገባናል ብዬ አስባለሁ፡፡ እንደሚታወቀው በአገራችን የህግ ሥርዓት ውስጥ በአማርኛው ቅጅ “ሊሆን ይችላል፣ ሊፈፀም ይችላል፣ የተፈቀደ ነው፣....” የሚሉ ቃሎችን በመጠቀም ህግ አውጭው የደነገጋቸውን ድንጋጌዎች ፈቃጅነት ያላቸው የህግ ድንጌጋዎች ናቸው በማለት የምንፈርጅ ሲሆን በእንግሊዘኛው ቅጅ “May, possible, permissible .....” የሚሉና የመሳሰሉ ቃላቶችን የተጠቀመባቸውን ድንጋጌዎች ፈቃጅነት ያላቸው (permissive provisions of law) በማለት እንፈርጃለን፡፡

በሌላ በኩል ህግ አውጭው በአማርኛው ቅጅ “መሆን አለበት፣ ሊፈፀም ይገባዋል፣ ማድረግ አለባቸው .....” የመሳሰሉ ትእዛዝ አዘሎች በመጠቀም የደነገጋቸውንና በእንግሊዘኛው ቅጅ “Shall, ought to be, must, may not...” የሚሉ ቃላትን በመጠቀም የደነገጋቸውን ድንጋጌዎች ሁሉ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች /mandatory provisions of law/ ናቸው የሚል የአብዛኛው የሕግ ባለሙያዎች መደምደሚያ አለ፡፡ ሆኖም እነዚህን ትዕዛዝ አዘል ቃሎች ሕግ አውጪው በአንድ ድንጋጌ ውስጥ መጠቀሙን በማየት ብቻ የድንጋጌዎችን ባህሪ ለመለየት የምንጠቀምበት ዘዴ አሣማችና አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን አዛዥ ወይም መሪ ከሆኑ የሕግ ድንጋጌዎች ለመለየት የማያስችል የአፈራረጅ ዘዴ ነው፡፡

ስለሆነም አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን አዛዥና መሪ ከሆኑ የህግ ድንጋጌዎች ለመለየት ህግ አውጭው ትእዛዝ አዘል ቃላት የተጠቀመ መሆኑን ማየት ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ህግ አውጭው በትእዛዝ መልክ ያስቀመጣቸውን ደንቦች መጣስ ወይም ሣያከብሩ መቅረት የሚያስከትለውን ውጤት በመመርመር ድንጋጌዎችን መለየት ያስፈልጋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

የዚህ አይነት ዘዴ መጠቀም አዲስ አይደለም በህግ መዝገበ ቃላት ውስጥ “Mandatory provisions, they prescribe, in addition to requiring the doing of the thing specified, the result will follow if they are not done where as directory provisions, their terms are limited to what is required to be done” በሚል መንገድ ልዮነታቸው ተገልጾ እናገኛለን፡፡

ህግ አውጭው ከተጠቀመባቸው ቃላት ባሻገር ከላይ የተገለፀውን መሠረተ ሀሳብ አስገዳጅ የህግ ድንጌጋዎችን አዛዥ ወይም መሪ ከሆኑ የህግ ድንጌጋዎች ለመለየት ጥቅም ላይ ማዋል ይገባናል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለሆነም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 በአማርኛው ቅጅ ‹‹በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ፊት መሆን አለባቸው›› የሚል ቃል መኖሩንና በእንግሊዘኛው ቅጅ ‹‹Shall be in writing and registered with a court or notary>> የሚል ቃል መኖሩን በመመልከት ብቻ ድንጋጌው አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ ነው በማለት የተደረሰበት መደምደሚያና የህግ ትርጉም ከላይ ከገለጽኩት የህግ ድንጋጌዎችን ባህሪ መለያ አሠራርና ዘዴ አንፃር እንደገና መታየትና መመርመር አለበት የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም ከላይ በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 የአሃዝነት ወይም የመሪነት ባህሪ ያለው (Directory provision of low) የሕግ ድንጋጌ እንጂ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ እንጂ አብገዳጅ የሕግ ድንጋጌ /mandatory provision of low/ አይደለም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ አብላጫው ድምጽ ይህንን ድንጋጌ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ ነው በሚል እምነት አመልካች ከተጠሪዎች አውራሽ ጋር ያደረገው የቤት ሽያጭ ውል በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ ባለመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ ህግ አውጭው ህጉን ሲያወጅ የነበረውን ሀሳብ ሊያሣካው የሚፈልገውን ግብና ዓላማ ግምት ውስጥ የማያስገባ ከመሆኑም በላይ ውሳኔው ከህግ መተርጎም ያለፈና አዲስ ህግ የማውጣት ያህል ውጤት ያለው በመሆኑ ከሙያ አጋሮቼ ተለይቻለሁ፡፡ 2. የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ከማይንቀሣቀሥ ንብረት ሽያጭ ውል ድንጋጌዎች በተለይም ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2877 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2878 ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመር የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን አስፈላጊ ነው፡፡ የፍታብሐር ህግ ቁጥር 1723 ሁለት መሠረታዊ ደንቦችን በአንድ ላይ አጣምሮ የያዘ ድንጋጌ ነው፡፡ የመጀመሪያው የማይንቀሣቀሥ ንብረት ባለቤትነት የአላባ ጥቅም መብት፣ ወይም መያዣና ሌላ አገልግሎት መብት ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎች ሁሉ በጽሑፍ መደረግ እንዳለባቸው የሚደነግገው ሲሆን፡- ሁለተኛው ውሉ በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ነው፡፡ ይኸ ድንጋጌ በጥቅሉ ሲታይ አሐዝ ወይም መሪ ድንጋጌ ነው የምልበትን ምክንያት ከላይ በዝርዝር ገልጫአለሁ፡፡ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ደንቦች ውስጥ የትኛው ክፍል ለቤት ሽያጭ ውል አስገዳጅ የትኛው ክፍል ደግሞ አሐዝ ወይም የመሪነት ባህሪ ያለው መሆኑን ግልጽ የሚያደርግ ልዩ ድንጋጌ ነው፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚደረግ የቤት ሽያጭ ውል በጽሁፍ ካልተደረገ በስተቀር ፈራሽ እንደሚሆን የፍ/ሕግ ቁጥር 2877 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ይኸ ድንጋጌ ውሉ በጽሑፍ መደረግ አለበት በሚል መንገድ ብቻ የተቀመጠ ሣይሆን ውሉ በጽሑፍ አለመደረጉ የሚያስከትለውን ውጤት ግልጽ የሚያደርግ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለሆነም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ በአሃዝነት ወይንም በመሪነት ካስቀመጣቸው ሁለት ደንቦት ውስጥ “የውሉ በጽሑፍ መሆን” የሚደነግገው ደንብ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማስተላለፍ የግድ መፈፀም ያለበትና አስገዳጅ የሕግ ሁኔታ መሆኑን ግልጽ የሚያደርግ ነው ስለሆነም ድንጋጌዎቹ ጐን በጐን ሊፈፀሙ የሚችሉ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ከያዛቸው ደንቦች ውስጥ ሁለተኛው ክፍል ማለትም “የውሉ በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል በተሰጠው አካል ፊት” መደረግ አለመሟላት ውሉን ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ የማያደርግ በሌላ አነጋገር አስገዳጅ ሣይሆን አሐዝ ወይም መሪ የሕግ ድንጋጌ መሆኑን ግልጽ የሚያደርግ ድንግጌ ነው፡፡ ስለሆነም የቤት ሽያጭ ውል በጽሑፍ ከተደረገ በውል አዋዋይ ፊት ባለመደረጉ ብቻ ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ እንደማይሆንና በተዋዋዮቹ መካከል አስገዳጅነት ያለው የፀና ውል መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 ድንጋጌ ግልጽ የሚደረግ ነው፡፡ ስለሆነም በእኔ እምነት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ ሲሆን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ የአሃዝነት ወይም የመሪነት ባህሪ ያለው የሕግ ድንጋጌ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ስለሆነም የቤት ሽያጭ ውል በጽሑፍ የተደረገ ሆኖ እያለ አስገዳጅነት በሌለው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው በውል አዋዋይ ፊት የመደረግ መስፈርት አላሟላም ተብሎ ውጤት የለውም መባሉና የአመልካች ውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ አግባብነት የለውም የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሌላው በዚህ መዝገብ በጭብጥነት ያልተያዘ ነገር ግን ግልጽ መሆን ያለበት ውል ለማማዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገ ወይም የማይንቀሣቀስ ንብረት መመዝገቢያ መዝገብ ያልተመዘገበ የቤት ሽያጭ ውል ውጤት የማይኖረው በተዋዋዮቹ መካከል ሣይሆን በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ላይ መሆኑን ከላይ በሰፊው በዘረዘርኩት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረታዊ ይዘትና ባህሪና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2878 አስገዳጅ የሕግ ድንግጌ ከመሆኑ አንፃር በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 እና 2878 አስገዳጅ የሕግ ድንግጌዎች በመሆናቸው የአሃዝነት ወይም የመሪነት ባህሪ ካለው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 በላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ናቸው የሚል ሐሳብ ያለኝ ሲሆን አብላጫው ድምጽ የእነዚህን ድንጋጌዎች ባህሪ የተፈፃሚነት ወሰን አስመልክቶ የሰጠው ትርጓሜ ተገቢነት የሌለውና በጥልቀት መታየት አለበት በሚል መነሻ ይህንን የልዩነት ሐሳብ ጽፌአለሁ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አብላጫው ድምጽ እና ከዚያ ቀደም ብሎ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ ነው በማለት ትርጉም የሰጡት ዳኞች የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 "በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ፊት መሆን አለባቸው" ከማለት ውጪ ውሉ በዚህ መንገድ ሣይፈፀም ቢቀር ውጤቱ ምን ይሆናል? ለሚለው ጥያቄ ድንጋጌው ምላሽ እንደማይሰጥ በውል ተገንዝበዋል። የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በውል አዋዋይ ፊት ባይፈፀም ውሉን ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ እንደማይሆን ለማሳየት ሕግ አውጭው ሆነ ብሎ ያለፈውና ድንጋጌው አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ ሳይሆን አሣዝ ወይም በመሪ የሕግ ድንጋጌነት የደነገገው መሆኑን ባለመገንዘብ አብላጫው ድምጽ የተከተለው ትርጓሜ ሕግ አውጭው ሕጉን ካሰበው ሐሳብ ያፈነገጠ እና አዳናጋሪና አፍራሽ ውጤት ያለው ነው። አብላጫው ድምጽ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገ የቤት ሽያጭ ውል እንደረቂቅ እንደሚቆጠር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ጋር በማጣመር በመተርጎም ወስኗል።

በመሰረቱ ይኸ አተረጓጎም መሰረታዊ ስህተት ያለበት ነው ብዬ አስባለሁ። በመጀመሪያ ደረጃ የቤት ሽያጭ ውል የሚፈፀምበት ፎርም ምን መሆን እንዳለበት ሕግ አውጭው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 በግልጽና አስገዳጅ ደንጋጌ ደንግጐ እያለ ፍርድ ቤቱ በትርጉም ሌላ ተጨማሪ የውል ፎርም ለመፍጠር የሰጠው ውሣኔ ከሕግ አተረጓጎም መርህ የወጣና ያፈነገጠ ነው። በሁለተኛ ደረጃ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት አንድን ውል እንደረቂቅ የሚያስቆጥረው የውሉ በሚገባ አኳኋን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1726 መሰረት የተስማሙበትን ሞልተው አለመፃፋቸው፣

በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1727/1/ መሰረት ተዋዋዮች ያልፈረሙበት ሲሆንና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1728 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ተዋዋዮቹ ፊርማቸውን ያላስቀመጡ ሲሆን ነው። ከዚህ ውጭ ውሉ የተዋዋዮቹ ስምምነት በሚገልጽ መንገድ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ተዋዋዮቹ ከፈረሙበት በኋላ ምስክሮች ሣይፈርሙበት ቢቀሩ የውሉን ሰነድ እንደረቂቅ የሚያስቆጥር ጉድለት እንዳልሆነ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1727 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል። በተዋዋዮቹ የተፈረመው ውል ላይ ምስክሮች ሣይፈራረሙ ቢቀሩ ውሉ እንደረቂቅ የሚታይ ሣይሆን ውሉን ውጤት አልባ የሚያደርግ ጉድለት ስለመሆኑ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1727/2/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል በልዩ ሁኔታ የቤት ሽያጭ ውል በጽሑፍ ሳይይደረግ ቢቀር እንኳን እንደረቂቅ የሚታይ ሣይሆን ውሉ ፈራሽ እንደሚሆን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ወይም ውል አዋዋይ ፊት ለመደረግ አብላጫው ድምጽ እንደሚለው የውል ፎርም ለመመሟላት አይደለም። አንድ ውል በውል አዋዋይ ፊት ሲደረግ የሚፈፀሙ ተግባራት ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው። የመጀመሪያው የተዋዋዮቹን ፈቃደኝነት እና የውሉን ለሕግ ወይም ለሞራል ተቃራኒ ያለመሆን በማረጋገጥ ውሉን መመዝገብ ሲሆን ሁለተኛው ተዋዋዮቹ አስፈላጊውን የቴንብር ቀረጥና ሌሎች ሕጋዊ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ማድረግ ነው። ሶስተኛው ውሉን አንድ ኮፒ የማስቀመጥና የመጠበቅ ሥራ መሥራት ነው።

ውልን የመመዝገብ እና የቴንብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታን አለመወጣት ውሉን ፈራሽ እንደማያደርገው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል። ይሕም የሚያሣየው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 በውል አዋዋይ ፊት አለመደረጉ ውሉን ፈራሽ የማያደርገው መሆኑን ነው። ሆኖም አብላጫው ድምጽ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 የተቀመጠውን የመመዝገብ የቴንብር ቀረጥ የመክፈልና በመጨረሻም ኮፒ የማስቀመጥ መስፈርት አለመሟላት ውሉን ፈራሽ ወይም ውጤት አልባ በማድረግ የሚወሰን ሣይሆን ከጅምሩ እንዳልተደረገና እንደረቂቅ ሰነድ ያስቆጥረዋል በማለት የሰጠው ትርጓሜ ተገቢ ነው ብየ አላስብም። ስለሆነም አብላጫው ድምጽ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ ድንጋጌ አስገዳጅ ሣይሆን አሣዝ ወይም መሪ የሕግ ድንጋጌ መሆኑን ባለመገንዘብ በሕጉ ድንጋጌ የተቀመጠው መስፈርት ሳይሟላ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለውን ሕግ አውጭው ሆነ ብሎ በክፍትነት የተወውን በትርጉም በማሟላት ውሉ እንደረቂቅ የሚቆጠር ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ሕግ አውጭው ሕጉን ሲያወጅ ከነበረው ሐሳብ እና ሊደርሰበት ካሰበው ግብና ዓላማ ያፈነገጠ የሕግ አተረጓጎም መርሆችን ያልተከተለ ነው የሚል እምነት አለኝ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. አብላጫው ድምጽ የተከተለውና የተቀበለው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አለመከበር ወይም አለመሟላት ውጤት ውሉን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት እንደረቂቅ ያስቆጥረዋል የሚለው አተረጓጎም ተግባራዊ ምላሽ የሚሹ የበርካታ ችግሮች መንስኤና ምክንያት ሆኗል ብየ አስባለሁ፡፡ የመጀመሪያው ቤት ሽያጭና ቤት ገዥ የፈረሙበትና ምስክሮችም በፊርማቸው ያረጋገጡት የጽሑፍ ውል እንደርቂቅ ሰነድ የሚታይ ነው ተብሎ በመወሰኑ ይህንን የውል ሰነድ የመብትና ግዴታ ማረጋገጫ ሰነድነት በመጠቀም ክስ ለማቅረብ ሲሞክሩ ክስ ለማቅረብ የማያስችልህ መብትና ጥቅም የለህም፡፡ ያቀረብከው የውል ሰነድ እንደ ውል ሣይሆን እንደ ረቂቅ የሚታይ ነው በማለት ጥያቄያቸው በፍታብሔር ስነ ስርአት ሕግ ቁጥር 33/2/ መሰረት የሚሰረዝባቸው ቢያንስ በውሉ መሰረት የከፈሉትን ገንዘብ የማስመለስ መብታቸውን እንዳይጠይቁ መዝገባቸው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231 መሰረት እየተዘጋባቸው ያሉ ሰዎች መኖራቸውን በዚህ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 32226 የተደረገውን ክርክርና የተሰጠውን ውሣኔ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ሰነዱ ረቂቅ ነው ውል አይደለም የሚለው አተረጓጎም ውሉ ሕግ የተደነገገውን ፎርም አያሟላም በሚል ምክንያት ፈራሽ እንዲሆን ለመጠየቅ እና ጥያቄውን ለማቅረብ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1810 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1845 የተደነገገው ጊዜ አልፏል የሚለውን የመከራከሪያ ሐሳብ አንስቶ የመከራከር መብትን አጠያያቂ የሚያደርግ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰነድ ከጅምሩ ረቂቅ ነው ከተባለ ተዋዋዮች ያደረጉት ምንም አይነት የውል ግኑኝነት የለም ማለት ነው፡፡ የሌላ የውል ግኑኝነት እንዲፈርስ በሁለት ዓመት ወይም በአስር አመት ውስጥ መጠየቅ ነበር ብሎ ለመከራከርም ሆነ ውሣኔ መስጠት የሚቻል አይሆንም፡፡ ስለሆነም የዚህ አይነት አደናጋሪ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑና ይኸም ጉዳዮችን በእንጥልጥል የሚያስቀር አተረጓጎም መሆኑን በዚህ ችሎት መዝገብ ቁጥር 24515 ከተደረገው ክርክርና ከተሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ይኸ አተረጓጎም ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ከመፈፀማቸው በፊት ወደ ነበረሩበት ሁኔታ ለማስመለስ የሚያስችል ነው፡፡ ተከራካሪዎች ውል ከመዋዋላቸው በፊት እንዲመለሱ ለማድረግ በመጀመሪያ ውል አለ ውሉ ግን ግድፈት ያለበት ስለሆነ ውጤት አልባ (void) ነው ወይም ፈራሽ (avoidable) ነው የሚለውን መነሻ ይዛ መወሰን ይጠይቃል፡፡ ውሉ ረቂቅ ነው ከተባለ ከውል በፊት የተደረገ ምንም አይነት መብትና ግዴታ የማያቋቁም ተዋዋዮቹም ፈቃዳቸውን ያልገለፁበት ሰነድ ነው የሚል እንድምታና ትርጉም አለው፡፡ ስለዚህ በውል በፊት በጅምር ረቂቅነት ያለን ነገር “void” ውጤት እልባት ወይም (avoidable) ፈራሽ ነው ብሎ ለመፈረጅና ለመወሰን አይቻልም፡፡ በዚህ ምክንያት የሥር ፍርድ ቤቶች ውሉ ረቂቅ ነው የሚለውን የሰበር ትርጉም ተከትለው ውሣኔ ከሰጡ በኋላ ተከራካሪዎች ወደ ነበሩበት ሁኔታ ይመለሱ ብለው እንደማይወስኑ አብላጫው ድምጽ በዚህ መዝገብ ያደረገው ማሻሻያ በቂ ማስረጃ ነው፡፡

በአጠቃላይ ተዋዋይ ወገኖች ፈቅደውና ወደው በፊርማቸው ያረጋገጡትንና በምስክሮች ፊርማ የተረጋገጠ የቤት ሽያጭ ውል ጉድለት ያለበት ስለሆነ ውጤት አልባ ነው ወይም ፈራሽ ነው ከማለት አልፎ እንደረቂቅ ይቆጠራል ተብሎ የተሰጠው ትርጓሜ መነሻ እየተፈጠሩ ያሉትን በርካታ ውስብስብ ችግሮችና ለመፍታት የሚያስችል መንገድ ለማስተካከል ጥረት መደረግ ሲገባው ከዚህ በፊት የተሰጠው የአህግ ትርጉም ባለበት ሁኔታ በችግር ፈጣሪነቱ እንዲቀጥልና ተፈሚ እንዲሆን መደረጉ ተገቢነት የለውም የሚል ሐሳብ አለኝ፡፡

5. በዚህ መዝገብ ያለው ልዩ ሁኔታ የቤት ሽያጭ ውል በመፈራረም ብቻ የቆመ አይደለም፡፡ አመልካችና የተጠሪዎች አውራሽ ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል መሰረት የየበኩላቸውን ግዴታ ከግማሽ በላይ ፈጽመዋል፡፡ አመልካች ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ ለተጠሪዎች አውራሽ የከለፈሉ ሲሆን የተጠሪዎች አውራሽ የቤቱን ይዞታ ከአምስት አመት በፊት ለአመልካች አስረክበዋል፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ከመፈራረም አልፈው በውሉ መሰረት የግዴታቸውን በፈፀሙበት ሁኔት በመካከላቸው ያለው ግኑኝነት ውል ሣይሆን የውል ረቂቅ ነው የሚለው አተረጓጎም ተዋዋዮች የውል ግኑኝነት ከመፍጠር አልፈው ለውላቸው ተገዥ ሆነው በሚታይና በሚጨበጥ መልኩ የውሉን ኃይለ ቃል ለመፈፀም የወሰዱትን እርምጃ ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ አተረጓጎም ነው ይኸ አይነት የሕግ አተረጓጎም ደግሞ የውልና የኢኮኖሚያዊ ግኑኝነት እርግጠኝነትን ለውል ሐይለ ቃለ ማክበርና ተገዥ መሆኑን ሣይሆን እብለትን ክህደትን ተሸላሚ የሚያደርግ በመሆኑ ሊስተካከልና ሊታረም ይገባዋል የሚል አምነት አለኝ፡፡

ሕግ አውጭው ጠቅላላና ልዩ የውል ሕግ ድንግጌዎችን ሲያውጅ በአገሪቱ የሚፈፀሙ የውል ግኑኝነቶች ገዥነት እንዲኖራቸው ውሎች በተወዋይ ወገኖች መካከል እንደ ሕግ ሆነው እንዲያገለግሉና የሕግ ያሕግ ከበሬታና ተፈፃሚነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲኖራቸው በማሰብ ነው፡፡ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረታዊ ባህሪ ጠቀሜታና ውጤት ሕጉ ሲታወጅ ከነበረው የሕግ አውጭው ሐሳብ ዓላማና ግብ ጋር በተጣጣመ መንገድ ሊተረጎምና ሥራ ላይ ሊውል ይገባዋል፡፡ ሕግ ተራ የቃላት ስብስብና ሕግ አውጭው በዘፈቀደ የሰራው አረፍተ ነገር አይደለም፡፡ ሕግ ታስቦበት የአንድን ማህበረሰብ ኢኮኖማያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግር መፍታትና ወደ እድገት ጉዳና የመምሪያ መሣሪያ ነው፡፡

የውል ሕግ ድንጋጌዎች ደግሞ በአገራቱ ውስጥ እየተከናወኑ ያሉ የውል ግኑኝነቶች የፈፃሚነት የንግድ ሥራና ልውውጥ እርግጠኝነት እና ማህበራዊ መረጋጋት በሚፈጥር መንገድ መተርጎምና ሥራ ላይ ማዋል አለባቸው፡፡ የውል ሕግ ድንጋጌዎች ሰዎች ወደውና ፈቅደው ለገቡት ግዴታ ተገዥ እንዲሆኑና የውል ግዴታቸውን እንዲያከብሩ በሚያደርግና በተዋዋዮች ነፃ ፈቃድ የተመሰረተ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ ያለሆነ ውል ከውሉ መሰረታዊ ይዘትና ባህሪ ጋር ግኑኝነት በሌላቸው ጥቃቅን ምክንያቶች ለማፍረስ እና ለማሰረዝ በክፉ ልቦና የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ለመግታት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚያስችል መልኩ መተርጎምና ሥራ ላይ መዋል አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በመዝገብ ቁጥር 21448 የተሰየ ትርጉምና ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ለፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ይዘት የድንጋጌው ባህሪና የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክቶ ፍርድ ቤቶች ሲከተሉት የነበሩት የሕግ አተረጓጎም ሕብረተሰቡ በጽሑፍ የተደረገ ተዋዋይ ወገኖችና ምስክሮች የፈረሙበት የቤት ሽያጭ የመያዣርያና ሌሎች አገልግሎቶች ምስክሮች የፈረሙበት የቤት ሽያጭ የመያዣርያና ሌሎች አገልግሎቶች ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ ያደረጉ ውሎች ህጋዊ ውጤት ያላቸውና በፍርድ ሐይል ተፈፃሚነት አላቸው ብሎ እንዲያምን የሚያደርጉ ነበሩ፡፡ ይህንን አተረጋጎም ለመቀየር የተሰጠው ምክንያትም ሆነ ሕጉ የተተረጎመበት አግባብ አንድ ብቻ ሣይሆን በርካታ ስህተቶች ያሉበት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ በመሆኑም አብላጫው ድምጽ፡-

- ሕግ አውጭው ሕጉን ሲያውጅ የነበረውን ሐሳብ ሕጉን በማወጅ ሊያሣካው ከሚፈልገው ግብና ዓለማ ግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባና ትክክለኛ የሕግ ድንጋጌዎች ባህሪያት መለያ ዘዴ ሣይከተል የአዛገርነት ወይም የመሪነት ባህሪ ያለውን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አስገዳጅ የሕግ ድንግጌ ነው የሚል ትርጉም መስጠቱ፡-
- በአመልካችና በተጠሪዎች አውራሽ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል አስገዳጅና ልዩ የሕግ ድንጋጌ በሆነው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 በተቀመጠው ፎርም የሚያሟላ ሆኖ እያለ አላግባብ የፍታብሐር ሕግ ቁጥር 1723/1/ የተቀመጠውን ፎርም ስለማያሟላ የሽያጭ ወሉ ውጤት የሌለው ረቂቅ ብሎ በመወሰን፡-
- የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ መሰረታዊ ጥቅም ዓላማና ውጤት አስመልክቶ ሌላው የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21448 ሚያዝያ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትርጉም ከላይ የዘረዘርኳቸው ችግሮችና የሕግ አተረጓጎም ነው ብሎ ከውሣኔ ውስጥ በመጥቀስና በመከተል የሰጠው ውሣኔ የተሣሣተ መደምደሚያና ውሣኔ ነው ብዬ ስለማስብ በአመልካችና በተጠሪዎች አውራሽ መካከል በሕግ ፊት የሚዐናና አስገዳጅነት ያለው የቤት ሽያጭ ውል አለ፡፡ ተጠሪዎች በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ሊፈጽሙ ይገባል በማለት በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32854

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ት ማርታ አድማሱ - ጠበቃ ወርቅዬ ዓባይነህ

ተጠሪ፡- 1. አቶ በረከት ሰብስቤ - ቀረቡ፡፡

2. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በ1ኛ ተጠሪና በሥር በአንደኛ ተከሣሽ አቶ ዳዊት ጌታሁን ላይ ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የሁለተኛ ተከሣሽ /የአሁን አንደኛ ተጠሪ/ በሆነና በአንደኛ ተከሣሽ ሹፌርነት ሲሽከረከር በነበረው "ካቻማሊ" የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ተሳፍሬ ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ በመጓዝ ላይ ሳለሁ ሹፌሩ በፈጸመው ጥፋት መኪናው በመገልበጡ የአካል ጉዳት የደረሰብኝ ስለሆነ ይህንኑ ጉዳት በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለመታከም፣ የተቋረጠ ደመወዝ፣ ለሕክምና እና ለመድኃኒት መግዣ ወጭ የሆነ፣ ለትራንስፖርት ለአልሚ ምግብና እንደዚሁም በእጄ ላይ በደረሰብኝ ጉዳት ምክንያት ወደፊት መሥራት ስለማልችል ይሄው ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ዘርዝረው በድምሩ ብር 581,402.25(አምስት መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ አራት መቶ ሁለት ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም) ተከሣሾች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ንብረትነቱ የሁለተኛ ተከሣሽ የሆነው አውቶቡስ መኪና በኢትዮጵያ መድን ድርጅት /የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ/ በኩል የመድን ሽፋን የተገባለት መሆኑን በማረጋገጡ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 43 መሠረት የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ወደ ክርክሩ በማስገባት ግራ ቀኙን አከራክሮ በከሣሽና የመኪናው ባለንብረት በሆኑት ሁለተኛ ተከሣሽ መካከል የአንዱነት ውል መኖሩ የተረጋገጠ ስለሆነና በን/ሕ/ቁ. 595 መሠረት በተሳፋሪ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ የሚሆነው አንገቦ እንደሆነ ስለተመለከተ አንደኛ ተከሣሽ የመኪናው አሽከርካሪ እንጂ አንዱ ስላልሆነ በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለበትም በማለት አንደኛ ተከሣሽን ከክሱ አስወጥቷል፡፡

ሁለተኛ ተከሣሽን በተመለከተም የመኪናው ባለንብረት ስለሆነ በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ካለ በኋላ በንግድ ሕግ ቁጥር 597/1/ መሠረት በጉዞ ላይ ጉዳት ለደረሰበት መንገደኛ የሚከፈለው ካሳ ከብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የማይበልጥ ሲሆን እስከ ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የካሣ ክፍያ ለማግኘትም ቢሆን በአደጋው የደረሰው ጉዳትና የጉዳት መጠን በማስረጃ ተደግፎ መቅረብ እንዳለበት በውሣኔው ላይ አስፍሮ ነገር ግን ከሣሽ በግራ እጁ ላይ በደረሰው የነርቭ ጉዳት በውጭ አገር ለመታከም ብር 200,000(ሁለት መቶ ሺህ) ያስፈልጋል፣ እንደዚሁም በሰውነቱ ላይ ለደረሰ ጉዳት ለሕክምና ብር 25,000(ሃያ አምስት ሺህ ብር) ያስፈልጋል በማለት የጠየቁትና የኮምፒዩተር ሙያ ለመማር የተከፈለ ክፍያና ወደፊት በኮምፒዩተር ሙያ አገልግሎት ሊገኝ የሚችል በማለት የጠየቁት የካሣ ክፍያ በማስረጃ ተደግፎ ያልቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሣሽ በአደጋው ምክንያት ለ4 ወር የመምህርነት ሥራዬ የተቋረጠ ስለሆነ የ4 ወር ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት የጠየቁትንም በተመሣሣይ ከሣሽ በመምህርነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሙያ የምታገለግል ስለመሆኗና በአደጋው ምክንያት ደመወዝ የተቋረጠባት ስለመሆኑ በማስረጃ አላረጋገጠችም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ለጥርስ ማስተከያና ለሕክምና፣ ለመድኃኒት ለአልሚ ምግብና ለትራንስፖርት የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ በተመለከተም መጠኑ የተጋነነ መሆኑን በውሣኔው ላይ አመላክቶ ለጥርስ ሕክምናና ማስተከያ ብር 6,000(ስድስት ሺህ) ፤ ለሕክምና፣ ለመድኃኒት፣ ለአልሚ ምግብና ለትራንስፖርት ብር 2,000(ሁለት ሺህ) በድምሩ ብር 8,000(ስምንት ሺህ) ሊከፈላት ስለሚገባ ይህንኑ ገንዘብ ሁለተኛ ተከሣሽና ለሁለተኛ ተከሣሽ መኪና የመድን ሽፋን የሰጠው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት /3ኛ ወገን ተከሣሽ/ በአንድነትና በነጠላ ለከሣሽ ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሣሽ በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ደርሶብኛል ለሚሉት የአካል ጉዳት ያቀረቡት የካሣ ክፍያ ጥያቄ የማስረጃ ድጋፍ የሌለው ነው በሚል በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ከሕጉ አኳያ አግባብነት አለውን? የሚለው ነው በዚሁ ጭብጥ መሠረት የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ በሆነ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ በመንዝ ላይ እያሉ ስለሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንዳሰፈረው በግራ ቀኙ መካከል የአንገቦነት ውል /Contract of carriage/ ስላለ ይህንኑ የግራ ቀኙን ግንኙነት የሚገዛው የንግድ ሕጉ ስለሆነ ጉዳዩን ከዚሁ የንግድ ሕጉ አኳያ መመልከቱ አግባብነት ይኖረዋል፡፡

በዚህም መሠረት መንገደኞች ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ሥፍራ በሚጓዙበት ጊዜ በጉዞ ላይ የሞት ወይንም የአካል ጉዳት አደጋ ቢደርስባቸው አጓጓዡ ኃላፊነት እንዳለበት በንግድ ሕግ ቁጥር 595 ላይ የተደነገገ ሲሆን አጓጓዡ ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችለው ጉዳቱ ሊደርስ የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ /force majeure/ በሚሆንበት ጊዜ ወይንም በ3ኛ ወገን ድርጊት ወይም በእራሱ በተሳፋሪው ጥፋት መሆኑን ካሣየ እንደሆነ በቁጥር 596 ላይ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ጉዳቱ በዚህ መልኩ የደረሰ መሆኑን አጓጓዡ /አንደኛ ተጠሪ/ ያላሳዩ በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የኃላፊነት ውሣኔ መሰጠቱ አግባብነት ነበረው፡፡

በሌላ በኩልም አንድ ተሳፋሪ በጉዞ ላይ እያለ የሞት ወይንም የአካል ጉዳት አደጋ ቢደርስበት ሊከፈለው የሚችለው የካሣ ክፍያ መጠን ከብር 40,000(አርባ ሺህ) እንደማይበልጥ በዚሁ የንግድ ሕግ በቁጥር 597/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይሁንና በአንድ ተሳፋሪ ላይ ለደረሰው የሞት አደጋም ይሁን የአካል ጉዳት የሚከፈለው የካሣ መጠን ከብር 40,000(አርባ ሺህ) ሊበልጥ እንደማይችል በንግድ ሕጉ ላይ ከመመልከቱ በስተቀር የካሣው መጠን የሚሰላው በደረሰው ጉዳት ልክ ብቻ ወይንም ወደፊት በእርግጠኝነት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚታመን ጉዳትን ጨምሮ ስለመሆኑና በአጠቃላይ የካሣ መጠን አወሳሰን /Damage Assessments/ በንግድ ሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ ይህ ሁኔታ በልዩ ሕጉ ካልተሸፈነ ደግሞ የጠቅላላ ሕግ ድንጋጌዎችን መፈተሽና በዚሁ ላይ ተመስርቶ ለጉዳዩ እልባት መስጠት እንደሚገባ ከሕግ አተረጓጎም መርህ መገንዘብ ስለሚቻል በዚሁ መሠረት በፍትሐብሔር ሕጉ ጠቅላላ ስለ ውሎች የሚለውን ክፍል ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም በውል ግዴታ ውስጥ ባለዕዳ የጉዳት ኪሣራ ከፋይ የሚሆነው ውሉን አሟልቶ ባለመፈጸሙ ወይም ውሉን ከስምምነቱ ውጭ አዘግይቶ በመፈጸሙ በባለገንዘቡ ወይም በሌላው ተዋዋይ ወገን ላይ በገንዘብ የሚተመን ኪሣራ የደረሰበት መሆኑ ሲታወቅ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1790 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌላ ሊከፈል የሚችለው የኪሣራው መጠን ልኩ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት በተደነገገው የፍትሐብሔሩ ምዕራፍ ሥር ባሉ ድንጋጌዎች እንደሚመራም በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 1790/2/ ላይ ተመልክቷል፡፡

ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት የጉዳት ኪሣራ አከፋፈልና ልኩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር የተቀመጠ ሲሆን ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ መሆኑ በሕግ የታወቀው ሰው የሚከፍለው የጉዳት ካሣ ኃላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ካደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን እንዳለበት፣ ለወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተው ጉዳት የተረጋገጠ ሲሆን እስኪፈጸም ድረስ ሳይጠበቅ ካሣ ሊከፈለው እንደሚገባም በቁጥር 2091 እና 2092 ላይ ተቀምጧል፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳት የደረሰበት ወገን የደረሰበትን ጉዳት ልክና ጉዳት አድራሹ ካሣ በመክፈል ረገድ ያለበትን ግዴታ ማስረዳት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2141 ላይ የተመለከተ ቢሆንም ተጎጂው ጉዳት የደረሰበት መሆኑን አረጋግጦ ነገር ግን የካሳውን መጠን ለመገመት አስቸጋሪ ሁኔታ በሚያጋጥም ጊዜ በቁጥር 2102 መሠረት ዳኞች የካሣውን መጠን በርትዕ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በመኪናው መገልበጥ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ባቀረቡት ማስረጃ መረጋገጡን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ በሆነ የሕዝብ ማመላለሻ መኪና ተሳፍረው ሲጓዙ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት በግራ እጃቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑና በአጠቃላይም በሰውነታቸው ላይ የተለያየ ጉዳት ስለመድረሱ በማስረጃ የተረጋገጠ እንደመሆኑ መጠን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ጉዳት ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በንግድ ሕጉ ያለውን ክፍተት ወደ ጠቅላላ ሕግ በመሄድ በፍ/ብሔር ሕጉ ጠቅላላ ስለ ውሎች ከሚለውና ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት ድንጋጌዎች ጋር አያይዞ በመመልከት የካሣውን መጠን በርትዕ መወሰን ሲገባው የካሣ ክፍያ ጥያቄው የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት በተወሰነ ደረጃ ሳይቀበለው መቅረቱና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 44932 መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም. በካሣ አከፋፈል ረገድ የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 30615 ሰኔ 28 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠውን ትዕዛዝ በከፊል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ በማሻሻል በሥር ፍ/ቤት ከተወሰነው የብር 8000 /ስምንት ሺህ/ ክፍያ በተጨማሪ ብር 22,000 /ሃያ ሁለት ሺህ/ አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ በጠቅላላ ከተወሰነው ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ ላይ ሁለተኛ ተጠሪ ለአንደኛ ተጠሪ መኪና በሰጠው የመድን ሽፋን መሠረት ብር 10,000 /አሥር ሺህ/ ለአመልካች እንዲከፍል ቀሪውን ብር 20,000 /ሃያ ሺህ/ አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
2. የዚህን ችሎት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 36520

ጥቅምት 27 ቀን 2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነገረ ፈጅ ሂሩት አስራት ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ይብራህ ግርማይ - ጠበቃ አቶ አበበ ኃይሌ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 42765 ግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 32556 ታህሣሥ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በከሳሽነት በመቅረብ በሥር በተከሣሽነት የተከራከረው ተጠሪ ንጉሴ ግርማይ ላይ ባቀረበው ክስ የአሁን ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 11 የቤት ቁ. 834 የሆነውን ቤት ጥር 1 ቀን 1990 ዓ.ም. በተፈረመ የኪራይ ውል በብር 175 /አንድ መቶ ሰባ አምስት ብር/ ተከራይቷል፤ ሆኖም ይህንን ቤት ከአከራዩ ፈቃድና ዕውቅና ውጭና የኪራይ ውሉን በሚጥስ ሁኔታ ለንጉሴ ግርማይ አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ የኪራይ ውሉ ፈርሶ ቤቱን እንዲያስረክብ ትዕዛዝ ይሰጥልን በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በቤቱ ውስጥ የምኖረው እኔ ነኝ፤ ለአቶ ንጉሴ ግርማይ አሳልፌ አልሰጠሁም፤ የሚል ክርክርና ይህንን ያስረዱልኛል የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረባቸውን ሁለት ምስክሮች ከሰማና በተከሳሽ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ከመዘነ በኋላ የኪራይ ውሉ ፈርሶ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የኪራይ ውሉ የሚቋረጠው /ይግባኝ ባይ/ ተጠሪ ቤቱን ለመኖሪያ ቤት ሣይሆን ለንግድ ቢጠቀምበት ነበር፤ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን ሽሯል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች በኪራይ ውሉ አንቀጽ 6/2/ መሠረት ተጠሪ ቤቱን ራሱ ሊገለገልበት እንጂ ለሌላ ሰው አሳልፎ ለማከራየት ወይም ለመስጠት እንደማይችል ተመልክቷል፤ ተጠሪ ቤቱን ለሌላ ሰው አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ በኪራይ ውሉ አንቀጽ 11/3/ መሠረት ውሉ ይቋረጣል፤ ይህ ሆኖ እያለ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለኪራይ ውሉ አንቀፆች ያልሆነ ትርጉም በመስጠት መወሰኑና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኞችንን መሠረዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በበኩሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠው ከቀበሌ የተፃፈለትን ማስረጃና የሁለት ምስክሮች ቃል ሰምቶ ነው፤ ማስረጃው ቀጥተኛ ማስረጃ ሣይሆን የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ነው፤ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ ነው፤ በተቃራኒው እኔ በቤቱ ውስጥ እንደምኖር የቀበሌ መታወቂያ ደብተርና ደብዳቤ በማቅረብ አስረድቻለሁ፤ ከዚህ በተጨማሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ለኪራይ ውሉ አንቀጽ 6/1/ የሰጠው ትርጉም ተገቢነት ያለው ነው፤ ስለዚህ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ተጠሪ የማስረጃ ተዓማኒነትና ተቀባይነትን አስመልክቶ ያቀረበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ነው፤ የውሉን አተረጓጎም በተመለከተ ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት የለውም በማለት የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካችና ተጠሪ በሰበር ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ ላደረጉት የኪራይ ውል የሰጠው ትርጉም ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መጣራት ያለበት ሆኖ አግኝተዋል፡፡ ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት ስለውል ድንጋጌዎች አተረጓጎም በፍትሐብሔር ሕግ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መመልከት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የውል ድንጋጌዎች መተርጎም ያለባቸው በተዋዋዮቹ መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅንነትና የመተማመን ግንኙነት መሠረት በማድረግና በጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ልቦና መተርጎም ያለባቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1732 የተደነገገ ሲሆን የውል ቃል የሚያሻማ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የተዋዋዮች ሃሣብ ምን እንደነበረ በመፈለግና መሠረት በማድረግ ሊተረጎም እንደሚገባ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1734 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ አመልካች የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፡፡ አመልካች የተቋቋመው የነዋሪዎችን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመቅረፍና በተመጣጣኝ ዋጋ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት ለመስጠት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአመልካችን አገልግሎት ያገኘና የኪራይ ውል የተዋዋለ ሰው ቤቱን በኪራይ ውሉ ከተገለፀው አገልግሎት ውጭ እየተገለገለበት ከተገኘ ውሉ ፈራሽ እንደሚሆን ከኪራይ ውሉ አንቀጽ 6 እና አንቀጽ 11/3/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ቤቱን እራሱ በመኖሪያ ቤትነት ለመገልገል ተስማምቶ የተከራየ ተከራይ በተከራይ አከራይነት ቤቱን ሌላ ሰው ለመኖሪያ ቤትነት እንዲገለገልበት አከራይቶ ቢገኝ ወይም ከአከራይ ስምምነትና ፈቃድ ውጭ በሌላ በማናቸውም መንገድ ቤቱን ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ ሰጥቶ ቢገኝ ቤቱን አከራይ በውሉ ከገለፀው አገልግሎት ውጭ እንደተጠቀመበት ተደርጎ መተርጎም ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም አመልካች የመኖሪያ ቤት የተከራይ አከራይነት መብት በመጠበቅ ውል ያልተዋዋለ በመሆኑ፣ ይህም የአመልካች ሀሣብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1732 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1734 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መታየት ያለበት ነው፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከላይ የተገለጹትን መሠረታዊ የውል ሀይለቃል አተረጓጎም ድንጋጌዎች በመተላለፍና ውሉን አመልካች ከነበረው ሀሣብ በላይ በማስፋት አመልካች የኪራይ ውሉን ለማፍረስ የሚችለው ተጠሪ ቤቱን ከተገለፀው ተግባር ውጭ ለንግድ ድርጅትነት ሲጠቀምበት ብቻ ነው በማለት የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንን ስህተት አለማረሙ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለውን የኪራይ ውል በመተርጎም በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአተረጓጎም ስህተት የተጋራ መሆኑን ያመለክታል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም. እና የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታህሣሥ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፣ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ ከአመልካች ጋር የገቡትን የኪራይ ውል ያላከበሩ በመሆኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቤቱን ለአመልካች ያስረክቡ በማለት ጥቅምት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. በመዝገብ ቁጥር 44194 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፤ ይፃፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፊደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 29363

ነዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ አምደ - ጠበቃ አስናቀ ከፋለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጥላሁን አርምዴ ከጠበቃ ሰብስቤ ባልቻ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ተጠሪ የወንድሜ ልጅ በመሆኑ ከባለቤቴ ሞት በኋላ አብሮኝ እንዲኖር በወረዳ 23 ቀበሌ 10 በሚገኘው ቁጥር 190 በሆነው ቤት አስጠግቼው ሲኖር የግል ሀብቴን ለመውሰድና ለመጠቀም አስቦ ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም አሞኝ በነበረበት ወቅት እንደማላነብና መሐይም መሆኔን በማወቅ የስጦታ ውል አዘጋጅቶ አስፈርሞኛል፡፡ ከዚያም በጥር ወር 1991 ዓ.ም ቤተክርስትያን ሄጀ ስመለስ ወደ ቤቴ እንዳልገባ ከልክሎኛል ስለሆነም ነሐሴ 9/1984 ዓ.ም የተደረገው የስጦታ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱት ክርክርም በዚህ ጉዳይ አስቀድመው በከተማ ነክ ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ተቀባይነት ሣያገኝ የቀረ ሲሆን በዚያው ጉዳይ በድጋሚ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም፡፡ የስጦታ ውሉ ይሻርልኝ ተብሎ የቀረበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚሉ ናቸው፡፡ በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድም የስጦታ ውሉ በሕግ አግባብነትና በአመልካች ሙሉ ፈቃደኛነት እንደተደረገ ጠቅሰው ሊሻር ይገባል ተብሎ የቀረበ አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ አስቀድሞ ጉዳዩ ውሣኔ አግኝቷል በማለት ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ አስቀድሞ ለከተማ ነክ ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረው አቤቱታ ሁከት ይወገድልኝ በማለት እንጂ የስጦታ ውሉ ይፍረስልኝ በማለት ስላልሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 መሠረት መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ይርጋን አስመልክቶ ተጠሪ ያቀረቡትን መቃወሚያ በተመለከተም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 መሠረት የይርጋ መቃወሚያ ማቅረብ የሚቻለው ውሉ ሲመሰረት የችሎታና የፈቃድ ጉድለት አለበት በሚባልበት ጊዜ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቁት ችሎታና ፈቃድ መሠረት አድርገው ሣይሆን መሐይም ነኝ በማለት ስለሆነ የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 ሥር ስለማይሸፈን አቤቱታው በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ የማይንቀሣቀስ ንብረት ስጦታ በሚደረግበት ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 መሠረት ግልጽ ኑዛዜ በሚደረግበት ሥርዓት ሊደረግ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443 ላይ የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን በማስረጃነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበው የስጦታ ውል ሲታይ ግን ስጦታ አድራጊውና ምስክሮች ባሉበት ከተነበበ በኋላ የተፈረመ ስለመሆኑ ስለማያስረዳ ፈራሽ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለተውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባይ የስጦታ ውሉ እንዲፈረስ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 ላይ የተመለከተው የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት በይርጋ ቀሪ አልሆነም ማለቱ ተገቢነት በሌለው ሁኔታ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በአመልካች በኩል የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ግራቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙ አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት የስጦታ ውል ይፍረስልኝ አቤቱታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይርጋ ቀሪ ሆኗል መባሉ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከዚሁ ጭብጥ አኳያም አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም ታምሜ በነበረበትና መሐይም መሆኔንም በማወቅ የመኖሪያ ቤት የስጦታ ውል ያስፈረመኝ ስለሆነ ይሄው የስጦታ ውል ፈራሽ ነው ይባልልኝ በማለት ነው፡፡

ስጦታ እንዲቀነስ ወይም እንዲሻር የሚቀርብ አቤቱታ ስጦታው ከተደረገበት ቀን አንስቶ እስከ 2 ዓመት ባለው ጊዜ ለዳኞች ካልቀረበ ዋጋ እንደሌለው / በይርጋ እንደሚቋረጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441/1/ ላይ ተደንግጓል፡፡

አመልካች የስጦታ ውሉ ተፈርሟል የሚሉት ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም ሲሆን ይሄው የስጦታ ውል ፈራሽ ነው ይባልልኝ በማለት ክስ ያቀረቡት ደግሞ ሰኔ 1 ቀን 1993 ዓ.ም ዘጠኝ ዓመት ሊሞላው ጥቂት ወራት ሲቀር ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም የተፈረመው ሰነድ የስጦታ ውል መሆኑን ያወቅሁት የካቲት 8 ቀን 1991 ዓ.ም ለሚመለከታቸው ክፍሎች አቤቱታ ሣቀርብ ነው ያሉትን በመውሰድ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንኳ ክስ እስካልቀረቡበት ሰኔ 1 ቀን 1993 ዓ.ም ያለው ሲታሰብም 2 ዓመት እንዳለፈው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም የፌዴራል ከፍ/ቤት አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል ያለው በፍ/ብ/ቁ. 1810 ላይ እንደተመለከተው በ2 ዓመት ጊዜ አልቀረበም በማለት ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው የስጦታ ውል እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ ግንኙነት በተለይ የሚገዛው በፍ/ብሔር ሕጉ ስጦታን አስመልክቶ በተደነገጉት ድንጋጌች መሠረት ሲሆን ወደ ጠቅላላ የውሎች ሕግ ድንጋጌዎች መሄድ የሚቻለው በልዩ ሕግ ላይ ተመስርቶ ለጉዳዩ ዕልባት ለመስጠት ካልተቻለ ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ከስጦታ ውል ድንጋጌዎች አኳያ መርምሮ ለይርጋ ክርክሩ እልባት መስጠት ሲገባው ስለ ውሎች በጠቅላላው በሚለው ምዕራፍ ሥር የተደነገገውን የይርጋ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠቱ ከሕግ አተረጓጎም መርህ አንፃር ተገቢነት የሌለው ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1810 ላይ የተመለከተውና ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ ጀምሮ ከ2 ዓመት በኋላ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ አይቀርብም ተብሎ የተመለከተውም ውሉ በችሎታና በፈቃድ ረገድ ጉድለት በሚኖረው ጊዜ ነው፡፡ መሐይምነትን ወይንም ዓይነስውርነትን አስመልክቶ የሚቀርብ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ከውሉ የአፃፃፍ ሥርዓት /ፎርም/ ጋር ተያይዞ እንደሚነሣ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1719 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል እንደመሆኑ መጠን የዚህ ዓይነቱ ጥያቄም በይርጋ የሚታገደው በቁጥር 1845 እንጂ በቁጥር 1810 ላይ እንደተደነገገው ስላልሆነ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ለድንጋጌው የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 64 በ17/6/95 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተሽሯል፡፡

2/ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 18957 ጥር 23 ቀን 1998 ዓ.ም አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሰጠው ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ሲሆን ከውጤት አኳያ የሚነቀፍ ስላልሆነ እንደዚሁም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23712 ጥር 29 ቀን 1999 ዓ.ም ይህንኑ ውሣኔ ማጽናቱ ከውጤት አኳያ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡

3/ አመልካች የስጦታ ውል ይፍረስልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441/1/ መሠረት በ2 ዓመት ጊዜ ስላልቀረቡ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ወስነናል፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

5/ መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሀሣብ ልዩነት

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2434 ድንጋጌዎች መሠረት ጥብቅና በግሏ ብቻ አመልካች ሆነ ብላና አስባበት ልትፈጽመው የሚገባው ተግባር /ስጦታ/ አልፈፀምኩም እያለች ተከራክራለች፡፡ አመልካች ተጠሪ አሳስቶ የስጦታ ውል ያስፈረምኩኝ መሆኑን ያወቅሁት በጥር ወር 1991 ዓ.ም ነው በማለት ተከራክራለች፡፡ እንደዚህ ከሆነ የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ከጥር ወር 1991 ጀምሮ መሆን ይገባዋል፡፡ ውሉ በተንኮል ተቀነባብሮ አመልካች ሣታውቅ የተፈረመ ነው የሚል ክርክር ያለበት በመሆኑ የይርጋ የጊዜ ገደቡም በተንኮል የተዘጋጀ ውል ይታወቅ መፈረሙን ካወቀችበት ከጥር ወር 1991 ዓ.ም ጀምሮ ባለው አስር ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ለእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 እንጅ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2441 አይደለም የሚል አምነት አለኝ፡፡ ስለሆነም ወደ ዋናው ጉዳይ ተገብቶ የስጦታው ሕጋዊነት መመርመር አለበት፡፡ የይርጋ ጊዜ አልፎበታል ተብሎ መዘጋቱ ተገቢ አይደለም የሚል እምነት ስላለኝ ከሙያ አጋሮቸ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36740

ህዳር 23 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሠላሴ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ዓብዱል ዋሀብ ኢብራሂም - ጠ/ ገ/ማርያም ገ/እግዚአብሔር

ተጠሪ፡- 1. ወ/ት መሰለች ከፍያለው
2. አቶ ሰለሞን ከፍያለው
} ቀረቡ ጠበቃ መኮንን አምቦ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ከሣሾች ሲሆኑ አመልካች ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ከሣሾች ባቀረቡት ክስም የከሣሾች አባት በከፍተኛ 24 ቀበሌ 13 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 2011 የሆነውን ቤት በ3/13/1980 ዓ.ም በተፃፈ የወለድ አገድ ውል በብር 29,000 (ሃያ ዘጠኝ ሺህ) ለ10 አመት ለአመልካች/ተከሣሽ ያስያዙት ሲሆን የከሣሾች አባት በ21/6/89 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ አመልካች ገንዘባቸውን ወስደው ቤቱን እንዲያስረክቡን ብንጠይቃው ፈቃደኛ ስላልሆኑ ገንዘቡን ተቀብለው ቤቱን ያስረክቡን፣ ማስጠንቀቂያ ከደረሣቸው ጊዜ ጀምሮ የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የሥር ተከሣሽ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ፤ በ3/13/1980 የተደገውን ውል መሠረት በማድረግ የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል፣ 8 ዓመት ያለፈ የቤት ኪራይ ጥያቄም ቢሆን በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ ይህ ቢታለፍ ግን በ3/13/1980 የወለድ አገድ ውል ተደርጎ ቤቱንና ቤቱን የሚመለከቱ ሠነዶች ተረክቤአለሁ፡፡ ከዚህ በኋላም ለግለሰብ ቤት እንዲሸጥ ስለፈቀደ የተጠሪዎች ወላጅ አባትና ባለቤታቸው ነሐሴ 06/1988 በተፃፈ ውል በአ.አ ከተማ መስተዳድር የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ተፈራርመን የቤት ሽያጭ ውል ፈጽመናል፣ ስለሆነም የወለድ አገድ ውሉ በሽያጭ ውል ስለተተካ ሊከሱኝ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የሽያጭ ውሉ በ6/12/88 መደረጉን ቢገልፁም የተመዘገበው ግን 17/03/1991 ነው፡፡ ውሉ በተመዘገበበት ቀን ደግሞ የከሣሾች አውራሽ በህይወት አልነበሩም በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት የሽያጭ ውል ላይ የተጠሪዎች አባት ሊፈርሙ የማይችሉ በመሆኑ የሽያጭ ውል ፈርመናል የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ የግራ ቀኙ ግንኙነት በ3/13/80 ዓ.ም የተደረገው የመያዣ ውል ነው በማለት ተጠሪዎች የሚፈለግባቸውን ብር 29,000(ሃያ ዘጠኝ ሺህ) ለአመልካች ሲከፍሉ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ፤ የሽያጭ ውል የተፃፈው በ6/12/1988 ሲሆን የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ በኃላፊ የተመራበትና የተፈረመበት የተዋዋይ ወገኖች የምስክሮች ፊርማና መታወቂያ የተረጋገጠው በዚሁ ቀን ቢሆንም የዕዳና እገዳ እስከሚሠራ የፎርማሊቲ ስርዓቱና ክፍያ መፈፀሚያው ተቋርጦ እንደገና ማጣራት ተደርጎ በ1991 ዓ.ም ተረጋግጦ ወጭ ሆኗል ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ውል በፊቱ ሲደረግ አረጋጋጭ እንጂ ውል መዘጋቢ አካል ባለመሆኑና ውል በፊቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደረገው በ6/12/1988 ዓ.ም በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ አመልካች ቤቱን በሕጋዊ ውል የያዙት በመሆኑ ሊያስረክቡ አይገባም፤ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ደግሞ በዚህ ውሣኔ ላይ ቅር ተሰኝተው ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የሽያጭ ውል የተደረገው መቼ ነው የሚለውን ጉዳይ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሠበር አቤቱታውን የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪዎች በአመልካችና በተጠሪዎች አውራሽ መሃከል ያለው የወለድ አገድ ውል ነው ሲሉ አመልካች ደግሞ ከወለድ አገድ ውሉ በኋላ የቤት ሽያጭ ውል ተደርጓል በማለት ተከራክረዋል ተጠሪዎች የሽያጩ ውል ተደረገ የተባለው አውራሻችን ከሞቱ በኋላ በመሆኑ የሽያጭ ውል የለም ሲሉ አስተባብለዋል፡፡ ችሎቱም የሽያጭ ውሉ መቼ ነው የተደረገው የሚለውን አግባብ ካለው ሕግ ጋር አናዝቦ መርምሯል፡፡

አንድ ውል ፍፁም ነው የሚባለው ተዋዋዮቹ በተስማማ አካኋን መፍቀዳቸውን ገልፀው ሲገኙ መሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1680/1/ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ውል አቅራቢው በቃልም ሆነ በጽሁፍ በማያጠራጥር ሁኔታ ግዴታ ለመግባት መፍቀዱን ካሣወቀና ውል ተቀባዩም በተመሣሣይ መልኩ የውል ድርድሩን መቀበሉን ካሣወቀ በሁለቱ መሐከል ስምምነት መደረጉን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1681 መረዳት ይቻላል በእርግጥ ጉድለት የሌለበት ፈቃድ ከመስጠት በተጨማሪ ሕጉ ልዩ የሆነ የሚጠበቅ አፃፃፍ ፎርም እንዲኖር ካስገደደ ይኸው የአፃፃፍ ሥርዓት መሟላቱ ለውሉ ሕጋዊነት ሌላው መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ ስለሆነም ተዋዋዮች ነፃ ፈቃዳቸውን ከመስጠታቸው በተጨማሪ ውሉን ሕጉ በሚያዘው የአፃፃፍ ሥርዓት ሊመሠርቱ ይገባል፡፡ ለምሣሌ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ውሉ በጽሁፍ ከመደረጉ በተጨማሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በዳኛ ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው የቤት ሽያጭ ውል መደረግ ያለበት በጽሑፍ ብቻ ሣይሆን ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በዳኛ ፊት ጭምር ነው፡፡ ውሉ በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት እንዲደረግ ያስፈለገበት ዋነኛ አላማም የተዋዋዮቹ ማንነት ያላቸው ችሎታና መብት ነፃ ፈቃዳቸውን መስጠታቸውን ውሉ የተደረገበትን ቀንም ለማረጋገጥ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪዎች አውራሽ እና አመልካች ውላቸውን በ6/12/1988 ዓ.ም በተፃፈ ሰነድ አዘጋጅተው ሁለቱም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርበው መፈረማቸው የምስክሮቹም ማንነትና ፊርማ በዚሁ ውሉ በተፃፈበት ቀን መረጋገጡን ክርክሩ ሂደት ተረድተናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ አውራሽና አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያደረጉት በ6/12/1988 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ ግራ ቀኙ ውሉን በ6/12/1988 የፈፀሙ ቢሆንም ቤቱን የሚመለከቱ ዕዳና እገዳ ለማጣራትና ክፍያ ለመፈፀም የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በውሉ ላይ ማህተም ሣያሣርፍበትና የፕሮቶኮል ቁጥር ሰጥቶ ሣያረጋግጥበት የተወሰነ ጊዜ ማለፉን ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ አስተዳደራዊ ጉዳዮች እስኪከናወኑ ድረስ በውሉ ላይ ማህተም ሣያርፍበት መቆየቱ ወይም የፕሮቶኮል ቁጥር ሣይሰጠው መዘግየቱ ውሉ እንዳልተደረገ የሚያስቆጥረው ነው ለማለት አያስችልም፡፡

በሌላ በኩል ሠነዱን የፃፈው ወይም የተቀበለው የመንግሥት መ/ቤት ከሆነ ሰነዱ የተፃፈበት እርግጠኛ ቀን ነው የሚባለው የፃፈበት ወይም የተቀበለበት ቀን በመሆኑ /የፍ/ብ/ህ/ቁ.2015/ህ/"ን" ይመለከቷል/ የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የሽያጩን ውል ያፈራረመበትና ሰነዱን የተቀበለበት ነሐሴ 6/1988 ዓ.ም የሰነዱ ትክክለኛ ቀን ተብሎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ሻጭና ገዢ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የሽያጭ ውልን የተፈራረሙበት ቀን ተረጋግጦ እያለ ውሉ ተደረገ ሊባል የሚችለው በዚህ ቀን ሣይሆን አንዳንድ የአስተዳደር ጉዳዮች ተጣርተው መ/ቤቱ ማህተም ያደረገበት ቀን ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 62466 በ22/02/99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33198 በ3/07/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 50414 በ18/11/1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

3/ አመልካች ቤቱን በ6/12/88 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል የያዙት በመሆኑ ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቡ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡

4/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 36294

ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሠላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሠናይት ገነሜ ገንታ - ሣሙኤል ደመቀ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. በቀለ ገመዳ ዳኖ
2. ወ/ሮ ወርቅነሽ ጀቤሣ ኤጎ } ጠበቃ ማረን ወንዴ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውልን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው አመልካች ናት፡፡ ተጠሪዎችን የከሰሰችውም ይቻላል በተሰኘ ማህበር በሸንሻኖ ቁጥር 13 የሚታወቅ 175 ካሬ ሜትር ግቢ ያለው ጅምር ቤት ሸጠውልኝ ውሉ በተደረገበት ዕለት ቀብድ ከፍያለሁ ቀሪውን ደግሞ በማህበሩ በአባልነት ሲያስመዘግቡኝ፣ እዳና እገዳ እንደሌለበት ሲያረጋግጡ፣ ካርታውን ከአስፈላጊው ዶክመንቶች ጋር ሲያስረክቡኝ፣ ጉዳዩ ለማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ ሲቀርብ እንደዚሁም የሽያጭ ውሉ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ሲፈፀም ልከፍል ተስማምተናል፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች እንደውላቸው አልፈፀሙም፡፡ ይልቁንም የጀመርኩትን ግንባታ እንዳላካሂድ ችግር ፈጥረውብኛል፡፡ ስለዚህ በውላቸው መሠረት እንዲፈጽሙ ይገደዱልኝ በውሉ የተመለከተው የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፍሉም ይወሰንባቸው በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበውም ውሉን ለመተግበር ያልቻለችው አመልካች ናት በማለት መቀጫ ትከፍላቸው ዘንድ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ክሱን ከሰማ በኋላ በሁለቱ መካከል ተደረገ የተባለው የሽያጭ ውል የሕጉን መስፈርት አያሟላም የሚል ምክንያት በመስጠት በሁለቱም ወገኖች የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል ክርክር ያስነሣው ጉዳይ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል የሚመለከት ነው ወይስ በማህበርተኝነት የመተካት መብትን የሚመለከት? የሚለውን ነጥብ ለማጣራት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም ግራ ቀኝ ወገኖች የቤት ሽያጭ ውል አድርገናል ብለው ያምኑ እንደነበር፤ በውሉ አፈፃፀም ረገድ ችግር ካጋጠማቸው በኋላ ግን ወደ መካሰስ እንዳመሩ፣ በመጨረሻም በተለይ ተጠሪዎች በሕጉ መሠረት የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የለም ወደሚለው በማዘንበል እንደተከራከሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ክሱን ያስተናገደው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው በግራ ቀኝ ወገኖች መካከል ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1723 የተመለከተውን መስፈርት አያሟላም በረቂቅ ደረጃ የቀረ ነው በማለት ነው፡፡

በእርግጥ የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 የማይንቀሣቀሱ ንብረቶችን የባለቤትነት መብት ለማስተላለፍ የሚደረጉት ውሎች ማሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች ደንግጎአል፡፡ ከዚህ የተነሣም እንደውሉ ይፈፀም ዘንድ ውሣኔ እንዲሰጥ የተጠየቀው ፍ/ቤት የውሉን ሕጋዊነት በቅድሚያ ለማረጋገጥ ክርክሩ ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 አንፃር ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ግን ውል ነው በሚል የቀረበለት ሰነድ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 እንደተመለከተው በእርግጥም የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ለማድረግ ታስቦ የተደረገ ነው ወይስ ሌላ የሚለውን ነጥብም መመርመሩ ተገቢ የሚሆንበት አጋጣሚ እንደሚኖር ማሰቡ ተገቢ ይሆናል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደሚታየው ተጠሪዎች በእነሱ ስም ብቻ ካርታና የባለቤትነት መታወቂያ ተለይቶ የተሰጠው ቤት እንዳላቸው ክርክሩ አያመለክትም፡፡ ይልቁንም ጅምር ነው የተባለው ቤት የሚገኘው ይቻላል በተሰኘ የቤት ሥራ ማህበር አጠቃላይ ይዞታ ስር እንደሆነ ነው መዝገቡ የሚያመለክተው ተጠሪዎች የዚህ ማህበር አባላት እንደመሆናቸው መብት እንዳላቸውም የሚያከራክር አይደለም፡፡ አከራካሪ የሚሆነው ወይም ልዩ ትኩረት በመስጠት ሊታይ የሚገባው ተጠሪዎች በማህበሩ ላይ ያላቸውን መብት ለሦስተኛ ወገን ሊያስተላልፉ ይችላሉ ወይ? የሚችሉ ከሆነስ ስርዓቱ ምንድነው? የሚለው ነው፡፡

ሰዎች በመደራጀት የሕብረት ስራ ማህበር ማቋቋም እና በዚህም በጋራ የመጠቀሙ ሁኔታ በሕግ እውቅና የተሰጠው ነው፣ በዚህ መልክ የሚቋቋሙት ማህበራት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው መብትና ግዴታቸውም በሕግ የተወሰነ ነው፡፡ የህብረት ስራ ማህበራትን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ያለው የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 ነው፡፡ ይህ አዋጅ ስለማህበራት ዓላማ፣ ስለማህበራት አመሠራረት፣ ስለሚመሩባቸው መርሆዎች፣ ስለሕግ ሰውነትና ኃላፊነት፣ ስለመተዳደሪያ ደንብ፣ ወዘተ በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካቶአል፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አወሳሰን ቀጥተኛ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንዱ የአዋጁ አንቀጽ 19 ሲሆን ይህም በአንድ በኩል የማህበር አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ለማስተላለፍ እንደሚችል በመርህ ደረጃ ሲደነግግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የማስተላለፉ ሁኔታም የራሱ የሆነ የተለየ ስርዓት እንዳለው ያመለክታል፡፡ የማህበሩ አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ለማስተላለፍ ቢፈልግ ከማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ የሚለው አንዱ ሁኔታ እንደሆነ በንኡስ አንቀጽ 1/ለ/ ተመልክቶአል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በማህበር ተደራጅቶ የተገኘውን መብት የማስተላለፊያ ስርዓቱ በግል ከተገኘ መብት የተለየ መሆኑን ነው፡፡ መብት የሚተላለፍለት ወገንም በአስተላላፊው መብት መጠቀም የሚችለው በመተካት የማህበሩ አባል መሆን ከቻለ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 ከተመለከተው የማይንቀሣቀስ ንብረት መብት ማስተላለፊያ ስርዓት የተለየ ነው፡፡ በመሆኑም በማህበር በመደራጀት የተሠራውን ቤት ሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕግ ቁ/ 1723 ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር አያይዞ ማየቱ ትክክል አይሆንም በተያዘው ጉዳይም ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የተዋዋሉት በማህበሩ ያላቸውን መብት ለማስተላለፍ በመሆኑ ክርክሩ መታየት ያለበት ከአዋጅ ቁ. 147/91 አንፃር ነው፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች ውሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 መሠረት የተደረገ አይደለም ከሚል በመነሣት የሰጡት ውሣኔ ሕጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19000 ሐምሌ 5 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 49515 ታህሣሥ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል ተፈጠረ የተባለው ግንኙነት መታየት ያለበት ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 አንፃር ሣይሆን ከህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁ. 147/91 አንፃር ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ጥያቄዋን ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ታቅርብ፡፡
4. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 33473

ኅዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሃርሴማ ሰሎሞን - ጠበቃ አቶ አምባቸው ዮሐንስ ቀረቡ፡፡

መልስ ሰጪ፡- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ - ነገረ ፈጅ አቶ ግርማ ገ/ፃዲቅ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ የቻለው የግራ ቀኙን ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በከ/መ/ቁ. 56916 ሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ዳኝነት ተገቢውን የሕግ ትርጉም ያልተከተለ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭ ከሣሽ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ በመሆን በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከራክረዋል፡፡ ከሣሽ ተከሣሽን አስተምሯል፡፡ ተከሣሽም ከትምህርት ተመልሰው ከሣሽን ለማገልገል ግዴታ ገብተዋል፡፡ የማያገለግሉ ቢሆን ለማስተማር ተብሎ የወጣውን ወጭ ብር 290,961 /ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ አንድ ብር/ ለመክፈል ተዋውለዋል፡፡ ስለሆነም እንደውሉ ለአራት ዓመት እንዲያገለግሉ ወይም ገንዘቡን እንዲከፍሉ ይወስንልን የሚል ክስ ቀርቧል፡፡

ተከሳሽም ለዚሁ ክስ የሰጡት መልስ ወጭውን የሸፈነው የኔዘርላንድ ፌሎውሺፕ ፕሮግራም ነው፤ ግዴታውም ወደ አገራቸው ተመልሰው እንዲያገለግሉ እንጂ በከሣሽ ተቋም ለማገልገል አይደለም፤ እንደገቡት ግዴታም ወደ አገራቸው ተመልሰው በማገልገል ላይ ናቸው፤ የቀረበውም ውል በመካከላቸው ያለውን ትክክለኛ መብትና ግዴታ አያሳይም፤ ግልጽ ነፃነትን የሚያሰናክል ስለሆነ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ያየው ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 03727 ግንቦት 02 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ቀርቧል፤ የትምህርት ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ የአንድ ዓመት ዕረፍት ተሰጥቷል፤ የትምህርት ዕድሉም የተሰጠው ባገኙት ተጨማሪ ችሎታ መሠረት እንዲያለግሉ ነው፤ ሲመለሱም ለአራት ዓመት ተኩል ለማገልገል ተዋውለዋል፤ ሰኔ 23 ቀን 1995 ዓ.ም. የተፃፈላቸው ደብዳቤ የትምህርት ዕድሉ የተገኘው በዩኒቨርሲቲው እንጂ በግላቸው አለመሆኑን ያሳያል፤ በመሆኑም እንደግዴታቸው ካላገለገሉ ከሣሽ ወይም 3ኛው ወገን የከፈለለትን ገንዘብ ለአሠሪው መክፈል እንደሚገባው በውሉ ላይ ስለተመለከተ እና መብትና ግዴታው በግልጽ ስለተጠቀሰ በገቡት ግዴታ መሠረት ያገልግሉ ወይም ገንዘቡን ብር 290,961.00 ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች ቅሬታ አቅራቢነት የይግባኝ ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ጉድለት አላገኘሁበትም በማለት በመልስ ሰጭነት የተሰየመውን ሳይጠራ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ ባጭሩ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ ሊታረም ይገባል የሚለውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

የቅሬታው ፍሬ ቃልም፡-

የትምህርት ዕድሉ የተገኘው በግል በመፃፃፍ ሆኖ እያለ ይህ አልታየልኝም፤ ወጭውንም የሸፈነው የትምህርት ዕድሉን የሰጠኝ ድርጅት ነው፤ ስለዚህ የአሁን መልስ ሰጭ በጉዳዩ አመልካች ላይ ክስ የማቅረብ መብት የለውም፤ ትምህርቱን የተማርኩት ከሦስትኛው ወገን ጋር ባደረኩት ስምምነት መሠረት ነው፤ ስምምነቱም ወደ አገር ተመላሼ ለማገልግል ነው፤ ውሉን የፈረምኩትም ካልፈረምሽ የዕረፍት ፍቃዱ አይሰጥሽም የድጋፍ ደብዳቤም አንጽፍም ስላሉኝና አዘጋጅተው በማቅረባቸው እንቅፋት እንዳይፈጠር በመስጋት ነው፤ በግል ያገኘሁት ስለመሆኑ ወጭውንም ሦስተኛው ወገን ስለመሸፈኑ ያስባገኝም ግዴታ ምን እንደሆነ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቀርባለሁ፤ እንደውሉ ይፈፀም እንኳ ቢባል የግል ነፃነቴን ይነካል፤ ለትምህርት ምን ያህል ገንዘብ እንደወጣ እንኳን ሳይረጋገጥ የተሰጠ ውሣኔ ስለሆነ ሊሻር ይገባዋል የሚል ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም የበኩሉን ክርክር አቅርቧል፡፡ ይዘቱም በግሌ የተገኘ የትምህርት ዕድል ነው የተባለው ሀሰት ነው፤ በ1995 ዓ.ም. የኔዘርላንድስ መንግሥት በሰጠው ነፃ የትምህርት ዕድል ዩኒቨርሲቲው ተጠቃሚ እንዲሆን ከትምህርት ሚ/ር በተፃፈ ደብዳቤ መነሻ እንዲወዳደሩ ተደርጎ ያገኙት ለመሆኑ፣ የትምህርት ዕድሉ በዩኒቨርሲቲው ኮታ ለመሆኑ፣ ትምህርቱን እንዲማሩ ስፖንሰር የሆነው መልስ ሰጭ ለመሆኑ በማስረጃው ከመልሱ ጋራ አያይዘናል፤ ውሉን የፈፀሙት በገዛ ፈቃዳቸው እንጂ መገደድ ስላልተፈፀመባቸው በግራ ቀኞችን መካከል የተደረገው ውል እንደ ሕግ ያገለግላል፤ ሦስተኛ ወገን ሳይሆን ደመወዝ ከፍሎና ስፖንሰር ሆኖ ያስተማረ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ክስ ለማቅረብ መብት አለው የሚሉ ናቸው፡፡

አመልካችም በመልስ መልሳቸው ላይ ክርክራቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

በሰበር ደረጃም ሆነ በሥር ፍ/ቤቶች ሁለቱም ወገኖች ያቀረቡት ክርክር ከላይ ባጭር ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤትም ሆነ በዚህ የሰበር ችሎት የሚያቀርቡት የትምህርት ዕድሉን ያገኘሁት በግል ባደረግሁት መፃፃፍ ነው፤ በዚህም የተነሣ ወጭውን የሸፈነው ሦስተኛ ወገን ነው፤ የግዴታውም ዓይነት ወደ አገሬ ተመልሼ እንዳገለግል የሚገልጽ ሲሆን ወደ አገሬም ተመልሼ እያገለገልኩ ስለምገኝ የሚጠበቅብኝ ግዴታ የለም የሚለው የፍሬ ነገር ክርክር ይገኝበታል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አኳኋን የቀረበውን የማስተባበያ የፍሬ ነገር ክርክር ተከራካሪው ወገን በማስረጃ አስደግፎ ማስረዳት ይኖርበታል፡፡ የመዝገቡን ግልባጭ እንዳየነው ይህንኑ ክርክር ሊደግፍ የሚችል ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃ ያልተደገፈ የፍሬ ነገር ክርክር ስለገለፀ ብቻ የቀረበበትን ክስ አስተባብሏል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው አመልካችና መልስ ሰጭ ያደረጉትን የጽሁፍ ስምምነት ስለመሆኑ የውሣኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ይህም የውል ስምምነት ግልባጭ ቀርቦ ከዚህ የሰበር መዝገብ ጋር በመያያዙ ተመልክተነዋል፡፡

አመልካች ይኸው የጽሁፍ ስምምነት ሊያስገድደኝ አይችልም የሚል ክርክር ሲያቀርቡ ለዚህ ክርክር በምክንያትነት የገለጹት ውሉ በመካከላቸው ያለውን ትክክለኛ መብትና ግዴታ አያሳይም የሚለውንና ካልፈረምሽ የዕረፍት ፈቃድ አይሰጥሽም የድጋፍ ደብዳቤም አንጽፍም ስላሉኝ እንቅፋት እንዳይፈጠር በመስጋት ነው የሚለውን በማተት ነው፡፡ ሆኖም የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ማየት እንደሚቻለው በይዘቱ የተዋዋይ ወገኖችን መብትና ግዴታ ለይቶ ያስቀመጠ፣ መብትና ግዴታውም በግልጽና በተነፃፃሪ ሁኔታ የሰፈረበት በመሆኑ በመካከላቸው ያለውን ትክክለኛ መብትና ግዴታ አያሳይም የሚለው ክርክር የሰነዱን ይዘት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በውሉ ላይ የተመለከተውን ፊርማ ላስቀምጥ የቻልኩት በነፃ ፍቃድ አይደለም የሚለውም ክርክር ቀርቧል፡፡ እንደተባለውም በሕግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል ለመያዝ መሟላት ከሚገባቸው ቋሚ ሁኔታዎች አንዱ ጉድለት የሌለበት የፈቃድ ሁኔታ መኖር ነው፡፡ ይኸው ፈቃድ በስህተት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኃይል ወይም በተንኮል የተገኘ እንደሆነ ውሉ እንደማይፀና በሕግ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ከእነዚህ በአንዱ የተነሣ የተሰጠ ፈቃድ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የጠቀሱት የፍሬ ነገር ክርክር ምናልባትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1710 የተጠቀሰውን /መጉዳት/ የሚለውን ያሟላል እንዳይባል አመልካች ይህንኑ ክርክር በአባባል ደረጃ ጠቀሱት እንጂ ካልፈረሙ የዕረፍት ፈቃድ እንደማይሰጣቸው፣ የድጋፍ ደብዳቤም እንደማይፃፍላቸውና በአጠቃላይ እንቅፋት እንዳይፈጠርባቸው በመስጋት የችግራቸው ሁኔታ ገፋፍቷቸው ውሉን እንዲፈፀሙ በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ በሕግ ምክንያቶች የሚያዝ አይደለም፡፡

በአኳያው ግራ ቀኙ ነሐሴ 02 ቀን 1995 ዓ.ም. ያደረጉት ውል አመልካች በውጪ ለመማር የተሰጣቸው ዕድል በተባለው ጊዜ እና የተባለውን የትምህርት ዘርፍ ተከታትለው ተመልሰው በመልስ ሰጭ ተቋም ለምን ያሕል ጊዜ ማገልገል እንዳለባቸው፣ ይህን ባያደርጉ በምትኩ መልስ ሰጭ አሠሪው ወይም ሦስተኛ ወገን የከፈለለትን ሙሉ ገንዘብ ብር 290,961 /ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ አንድ ብር/ አመልካች ለመልስ ሰጭ የመክፈል ግዴታ እንዳለባቸው እና በተመለሱም ጊዜ ያላቸው ተነፃፃሪ መብት ምን እንደሆነ በግልጽ እና በማያሻማ አኳኋን ተገልጿል፡፡

ይህ ውል በይዘቱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1678/ለ/ አንፃር ሲታይም የውሉን ጽናት ሊያስቀር የሚችል አንዳችም ምክንያት የለበትም፡፡ በሕግ ፊት የፀና ውል ያደረጉ ወገኖችም እንደ ውሉ እንዲፈጽሙ ውሉ ሕጋዊ ውጤት እንደሚያስከትል የታወቀ ነው፡፡ እንደ ውሉ ያልተፈፀመለት ወገን እንደ ውሉ እንዲፈፀምለት ከውል ያገኘውን መብት ለማስፈፀም መብት ያለው በመሆኑ የመልስ ሰጭ የክስ አቤቱታ አግባብነት ያለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ውሉ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ወገን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776 እንደተመለከተው ይፈፀም የሚባለው ግዴታ የፈፃሚውን የግል ነፃነት የሚነካ ከሆነ ያለፍላጎቱ ተገዶ ሊፈፀም አይገባም፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች እንደገቡት ግዴታ እንደሙያቸው ለመልስ ሰጪ እንዲያገለግሉ የሚገደዱት የፈቀዱ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በፈቃዳቸው ለተባለው ጊዜ ያሕል ለማገልገል ፈቃደኛ ካልሆኑ ግን በአማራጭ ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ ክፍያ ሊፈጽሙ ይገባል፡፡

ይህንን በሚመለከት ምንም እንኳን ለትምህርቱ ሲባል ሦስተኛ ወገን የከፈለለትን ሙሉ ገንዘብ ብር 290,961.00 /ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ አንድ ብር/ በሚል የገንዘቡ መጠን ተለይቶ የተቀመጠ ቢሆንም ይኸው ገንዘብ ለትምህርት የተከፈለውን ማናቸውንም ወጭ ለመሸፈን ሲባል የተደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለትምህርት ተብሎ የተከፈለው ወጭ ትምህርቱን ጀምረው ከማጠናቀቃቸው በፊት የታወቀ ወይም ሊታወቅ የሚችል ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የታወቀ አይደለም፡፡ እንደ ውሉ አመልካች ለማገልገል ካልፈቀዱ እንደ ውሉ ምትክ ግዴታቸውን በገንዘብ ሊከፍሉ፣ እርሳቸውን ለማስተማር ተብሎ በአሠሪውም ሆነ በሦስተኛው ወገን በእርግጥም ያወጣውን ማናቸውም ወጭ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህንን በሚመለከት መልስ ሰጭ በውሉ ላይ የተጠቀሰውን ብር 290,961.00 የሚለውን በመጥቀስ ለክሱ መሠረት አደረገ እንጂ አመልካችን ለማስተማር ሲባል በመልስ ሰጭም ሆነ በሦስተኛው ወገን በትክክል የወጣውን ወጭ በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች ሊከፍሉ የሚገባውን የትምህርት፣ የትራንስፖርት እና ደመወዝ ሳይከፍሉ ለማገልገል ከፈለጉ የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንደገለፀው እንዲያገለግሉ ይህንን ለመፈፀም ካልፈለጉ ግን አሠሪው ወይም ሦስተኛው ወገን በደመወዝም ሆነ በትራንስፖርት ወይም ማናቸውንም ለትምህርቱ ተብሎ የተከፈለውን ወጭ ዘርዝሮ ሲያቀርብና በማስረጃም አስደግፎ ሲያስረዳ የታወቀውን እውነተኛ ወጭ የአሁን መልስ ሰጭ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776 መሠረት የመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት ፈርደናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03727 ግንቦት 02 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 56916 ሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በገቡት ግዴታ መሠረት በመልስ ሰጭ ተቋም ለማገልግል ከፈለጉ የማገልገል ግዴታቸውን ይፈጽሙ፤ ለዚህ ግዴታ ፈቃደኛ ካልሆኑ ግን አሠሪው የአሁን መልስ ሰጭም ሆነ ሦስተኛው ወገን ለደመወዝ፣ ለትራንስፖርት እንዲሁም ለትምህርት ሲባል ያወጡትን ወጭ መጠን በሚመለከት በግራ ቀኙ መካከል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚቀርበው ክርክርና ማስረጃ ታይቶ እንዲወሰንና በውሣኔ የሚታወቀውን ገንዘብ የአሁን አመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 32571

ታህሣሥ 9 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሽሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሚፍታህ ከድር - ጠበቃ አቶ ከበደ እጉማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የባህር ትራንዚት አገልግሎት - አቶ መላኩ መኮንን ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 20608 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ፤ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በከሣሽነት ቀርበው ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት በመርከብ ያስጫንኩትን የንግድ ዕቃ ተጠሪ /ተከሣሽ/ ከመርከብ አራግፎና የወደብ ፎርማሊቲዎችን አጠናቅቆ ለማስረከብ ተስማምቶ ብር 2870 /የሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ብር/ የአገልግሎት ክፍያ ተከፍሎታል፡፡ ሆኖም አስራሰባት ጥቅል ዕቃዎችን ሲያስረክብ ሁለት ጥቅል ዕቃ ያላስረከበ በመሆኑ የዕቃዎቹን ግምት ብር 37650 /ሰላሣ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሀምሣ ብር/ ከነወለዱ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ የእኔ ግዴታ ከመርከብ የተራገፉትን ዕቃዎች አስፈላጊ የወደብ ፎርማሊቲዎችን በማስፈፀም ዕቃውን አስጭኖ ለባለዕቃው ማስተላለፍ፣ዕቃው የተጎዳ ከሆነ በአንሹራንስ አስመርምሮ የጉዳት ማረጋገጫ መቀበልና ለዕቃው ባለቤት ማስተላለፍ፤ ወይም በእጥረት የተደገፈ ከሆነ የእጥረት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት መቀበልና ለባለእዳው ማስተላለፍ ብቻ ነው፡፡ ከመርከብ የተፈለገውን ዕቃ የማስቀመጥ ኃላፊነት የለበትም፡፡ በመሆኑም በግዴታችን መሠረት የተወጣን በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የማስረዳት ሸክሙን አልተወጣም በማለት ክሱን ውድቅ ያደረገበት ሲሆን፤በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪ በክሱ የተገለፀውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ፣ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ኃላፊ የሚሆንበት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለበትም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፣ ምክንያቱም ተጠሪ አስራዘጠኝ ጥቅል ዕቃ ከመርከብ የተራገፈና ከወደብ የደረሰ መሆኑን በማረጋገጥ በራሱ ደረሰኝ የመጋዘን ክፍያ አስከፍሎኛል፡፡ ይኸ ከሆነ ዕቃውን ስላልተረከብኩ እኔ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሲሆን ለጎደለው ሁለት ጥቅል ዕቃ ተጠያቂ እንደሚሆን አግባብነት ያላቸውን የሕግ ማዕቀፎች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከሕግ ወይም ከውል የሚመነጭ ኃላፊነት ተጠሪ የለበትም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የቅድሚያ ክፍያ የተፈፀመው ዕቃዎቹን ለማስተላለፍ እንጅ ዕቃዎቹን ስለተረከብን አይደለም፤ የወደብ ግልጋሎት የሚሰጠው በኤርትራ የወደብ ባለሥልጣን ስለነበረ እነርሱ ለሚፈጽሙት ስህተት ተጠሪ ተጠያቂ የሚሆንበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት የሌለ በመሆኑ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፣ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካችና ተጠሪ በጽሑፍ ያቀረቡት ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ ይኸ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በማስመጣት በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቷል፡፡ የአመልካችንና የተጠሪን የቃል ክርክር አዳምጧል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ፣ የጠፉትን ሁለት ጥቅል ዕቃ ዋጋ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ጭብጥ በአግባቡ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ "የዕቃ አስተላላፊነት" ተግባር ምንድን ነው? የሚለውን መመለስ ይጠይቃል፡፡ የዕቃ አስተላላፊነት ተግባር ማለት በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕቃ ተቀባይነት ወይም ዕቃ ላኪን ለመወከል የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትና የወደብ ሥነ ሥርዓት እና ሌሎች ሥነ ሥርዓቶችን አስፈጽሞ የገቢ ወይም የወጭ ዕቃዎች ከወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ የማድረግ ተግባር እንደሆነና ይኸም ተግባር የዕቃ ማስረከብን እና ማጓጓዝን ሥራ የሚጨምር ስለመሆኑ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ሰነዶች የተመለከተ ሲሆን በእኛም አገር ይህ ትርጓሜ ሕጋዊ ዕውቅና እና ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስለ ዕቃ አስተላላፊነት ከደነገጋቸው ደንቦች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የተጠሪ የዕቃ አስተላላፊነት ግዴታና ኃላፊነት ከዚህ መሠረታዊ የሆነ ትርጓሜ አንፃር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተጠሪ በአመልካች የተሰጠውን የሥር ትእዛዝ በመቀበል፣ አመልካች ለአስራ ዘጠኝ ጥቅል ዕቃዎች የመጋዘን ኪራይ እና የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍሉ በመጠየቅ ክፍያውን በራሱ ደረሰኝ ተቀብሏል፡፡ ተጠሪ አስራ ዘጠኝ ጥቅል ዕቃዎች ከመረከብ መራገፋቸውንና መጋዘን ውስጥ መግባታቸውን በመግለጽ ከኤርትራ ወደብ አስተዳደር ጋር በተፃፃፋቸው ደብዳቤዎች ግልጽ አድርጓል፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች በተጠሪ በራሱ የተዘጋጁ ሰነዶች ናቸው፡፡ ስለዚህ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2018 መሠረት ሰነዶቹ በአዘጋጃቸው በተጠሪ ላይ ዕቃዎቹ ወደብ ለመድረሣቸውና ለመራገፋቸው የአስረጅነት ዋጋና ክብደት ያላቸው ሲሆኑ ተጠሪ በራሱ የተዘጋጁትን ሰነዶች ይዘትና ታዓማኒነት በመቃወም ሁለት ጥቅል ዕቃ አኔ አልተረከብኩም ስለዚህ በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ ድጋፍና መሠረት የሌለው ነው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ተጠሪ የሥራ ትእዛዝ የተቀበለባቸው ዕቃዎች በወደብ ያልተራገፉና አጥረት የተፈጠረ ከሆነ ኃላፊነት ካለበት አካል የእጥረት ሰርቲፊኬት በማውጣት ለአመልካች የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ አጥብቆ የሚከራከርበት ነጥብ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የሥራ ትእዛዙን እንደተቀበለ ሁለት ጥቅል እቃ እጥረት ያጋጠመ መሆኑን ለእጥረቱ በኃላፊነት ከሚጠይቀው አካል የእጥረት ሰርቲፊኬት አውጥቶ ለአመልካች አልሰጠም፡፡ በተቃራኒው ተጠሪ አስራዘጠኝ ጥቅል ዕቃዎች እንዳሉ በመግለጽ አመልካች ለአስራ ዘጠኝ ጥቅል ዕቃዎች የወደብና የመጋዘን ኪራይ እንደዚሁም የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈለው ጠይቆ ክፍያውን ተቀብሏል፡፡ ተጠሪ ሁለት ጥቅል ዕቃዎች ያጎደሉ መሆኑን ለአመልካች ያሣወቀው ዕቃው ከወደብ ወደ አዲስ አበባ በሚጫንበት ጊዜ ነው፡፡ ይኸም ተጠሪ የአስተላላፊነት ግዴታውን በአግባቡ ያልተወጣና በዚህ ምክንያት አመልካች ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸው ምክንያቶች ተጠሪ የአስራ ዘጠኝ ጥቅል እቃዎች የወደብ መጋዘንና የአገልግሎት ክፍያ ከአመልካች የተቀበለና ለአመልካችም የእጥረት ሰርቲፊኬት ያልሰጠ በዚህም ምክንያት አመልካች ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን አመልካች የሥራ ትእዛዝ ተቀብሎ የወደብ፣ መጋዘንና የአገለግሎት ዋጋ ክፍያ የጠየቀበትንና ክፍያ የተቀበለበትን ግዴታውን በአግባቡ ባለመወጣቱ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1790 መሠረት በኃላፊነት የመጠየቅና ለአመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ በዝርዝር የተቀመጡት የሕግ ድንጋጌዎች እና የአመልካችና የተጠሪ ከውል የመነጨ ተነፃፃሪ ግዴታና ኃላፊነት በአግባቡ ሣይገናዘብ ተጠሪ ከሁለት ጥቅል እቃ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታና ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 20608 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2- ተጠሪ የሁለት ጥቅል ዕቃ ዋጋ ብር 37650 /ሰላሣሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሣ ብር/ ከስ ካቀረበበት ነሐሴ 10 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል ብለናል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
3- በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሣቸው ይቻሉ፡፡ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ታህሣሥ 9 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማየነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34940

ታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሐጅራ አብሮ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሐሺም ሐጂ አሊዬ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በምስ/ሐረ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአወዳይ ከተማ የሰሩትን ቤት ለአባታቸው ትተው ከሄዱ በኋላ አባታቸው ሲሞቱ አመልካች ቤቱን ይዘው ያሉ ስለሆነ እንዲለቁላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ደግሞ ቤት የተሰራበትን ቦታ ባለቤታቸው ከአቶ ዮሴፍ ኡመር ከተባለ ሰው ወስደው በ1969 ዓ.ም ቤቱን የሰሩ በመሆኑ ከ38 አመት በኋላ ሊጠይቁቸው እንደማይችሉ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ቤቱን ከረጅም ጊዜ በፊት የአመልካች ባለቤት ከአመልካች ጋር አብረው ሲኖሩ የሰሩት መሆኑን የግራ ቀኙ ምስክሮች አረጋግጠዋል በማለት ፍ/ቤቱ የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጐታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ክርክር የተነሣበት ቤት በከሣሽ(ተጠሪ) ስም የተመዘገ በመሆኑ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ይልቀቁ ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ አቤቱታ አቅርበው አቤቱታቸው ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካችም ይህ ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት በማለት እንዲታረምላቸው አቤቱታ ለሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ የይርጋ ጥያቄ አንስተዋል ወይ? ካነሱ በየፍ/ቤቶቹ ሣይታይ መታለፉ አግባብ ነው ወይ? ተጠሪስ ያቀረቡት ማስረጃ ባለቤትነትን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚችል ነው ወይ? የሚሉትን ነጥቦች ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተባለው ተጠሪ በአወዳይ ከተማ ቤት ሰርተው ለአባታቸው ሰጥተው መሄዳቸውን ገልፀው አባታቸው በ1978 ዓ.ም ሲሞቱ አመልካች ቤቱን ይዘው መቆየታቸውንና ቤቱንም ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላለሆኑ እንዲለቁላቸው ክስ መስርተዋል፡፡ አመልካችም ቤቱን ባለቤታቸው በ1969 ዓ.ም የሰሩት መሆኑን ገልፀው ቤቱን ለ38 አመታት ይዘው እይኖሩበት በመሆኑ ተጠሪ አሁን ሊጠይቁቸው እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በዚህ ክርክራቸው በግልጽ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት አይግለፁ እንጂ ቤቱን ለ38 አመታት ይዘው እየኖሩበት በመሆኑ አሁን ክስ ሊቀርብባቸው የማይችል መሆኑን መግለፃቸው ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መከራከራቸውን ያመለክታል፡፡ አመልካች ቤቱን ለ38 አመታት ይዘው በመቆየታቸው የገለፁትን ፍሬ ነገር ተጠሪ አላስተባበሉም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ወደ ፍሬ ጉዳዩ ከመግባታቸው በፊት በአመልካች በኩል የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ መርምረው ተገቢውን ውሣኔ ሊሰጡ ይገባ ነበር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244/1/ ይመለከታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቤቱን ለአባታቸው ትቼው ሄጃለሁ የሚሉት በ1969 ዓ.ም ነው፡፡ አባታቸው ከዚህ አለም በሞት የተለዩት በ1978 ዓ.ም ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ቤቱን ለአባቱ ሰጥቼ ሄጃለሁ ካሉበት ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እስከተመሰረተበት እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ 27 ዓመት ያለፈው ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱን ለአባታቸው በአደራ ሰጥተው ለመሄዳቸው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ይህ ተረጋግጧል ቢባል እንኳን አባታቸው በ1978 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ አንስቶ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ 17 አመታት አልፋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ቤታቸው ያለአግባብ በሌላ ሰው ተይዟል በማለት ክስ ማቅረብ የሚችሉት እስከመቼ ነው? የሚለው ነጥብ መታየት ይኖርበታል፡፡ በመሰረቱ ጉዳዩን በቀጥታ የሚመለከት በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ድንጋጌ በሌለ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው የጠቅላላ ውል ህግ ድንጋጌ ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን ግንኙነቱ ከውል የመነጨ ባይሆንም ስለውሎች በጠቅላላው የተነገሩት ድንጋጌዎች እንደሚፈጸሙባቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰው መብቱን መጠየቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ በ10 አመት ውስጥ ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ ቀሪ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ይገልፃል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ ቤቱ ያለአግባብ በአመልካች ተይዟል ካሉበት ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ 17 አመታት ያለፉ በመሆኑ የተጠሪ መብት በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡ አመልካች ከስር ጀምሮ ቤቱን ለብዙ ዓመታት ይዘው እየተጠቀሙ የቆዩ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ እንደሚገባ ተከራክረው እያለ ፍ/ቤቶቹ ይህንን የአመልካችን የይርጋ ክርክር ሣያስተናግዱ በማለፍ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያመለክታል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39769 በ29/02/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በ/ቁ 57751 በ20/3/2000 የሰጠው ትእዛዝ በተጨማሪ በምስ/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01899 በ08/07/98 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ቤት ለመረከብ ያቀረቡት ጥያቄ /ክስ/ በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ. 32299

ጥር 07 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1. አቶ ሰለሞን ከተማ
2. አል ሣልቫቶር ኃ.የተ.የግ.ማ
— ጠበቃ ጥላሁን ደስታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ሴንትራል ቬኑ ኃ.የተ.የግ.ማ
2. ወ/ሮ ሸዋወንድም ተስፋዬ
3. አቶ ዳዊት ከበደ
4. ወ/ት ነጠረች ከበደ
— ጠበቃ ፍፁም ብርሃን ገ/ክርስቶስ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በአመልካቾችና በሁለተኛና ሦስተኛ ተጠሪዎች መካከል ግንቦት 04 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የንግድ ድርጅት እና የንግድ ድርጅት ህንፃ ሽያጭ ውል በህግ መሰረት የተፈፀመ ውል አይደለም ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካቾች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በተጀመረበት በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት የአሁኑ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ሲሆኑ ህዳር 26 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞው በቀበሌ 08 የሚገኘውን በሁለተኛ ተጠሪ ባለቤት እና በሦስተኛ ተጠሪ አባትና አውራሽ በሆኑት በሟች አቶ ከበደ ዘለቀ ስም በካርታ ቁጥር 25116 ተመዝግቦ የሚታወቀውንና በ2825 ካ.ሜ. ቦታ ላይ ሰፍሮ የሚገኘውን ሴንትራል ቬንዩ ሆቴል ከእነ መገልገያ ዕቃዎቹ ጭምር በ04/09/1997 በተፃፈ የሽያጭ ውል ከነመልካም ስሙ በንብረቶቹ ላይ ካሉት የኢትዮጵያ ልማት ባንክና ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የብድር ዕዳዎች፣ የሆቴሉ ሠራተኞች ክፍያ እና የሆቴሉ የአገር ውስጥ ገቢ የግብር ዕዳዎችን ገዥዎች ሸፍነው ከእዳዎቹ ውጪ በብር 1,000.000.00 /አንድ ሚሊዮን ብር/ ከሳሾች ለተከሳሽ መሸጣቸውን፣ ውሉ በተደረገ ዕለት ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ቀብድ መቀበላቸውን ቀሪውን ስመሃብቱ ሲዛወር ተከሳሽ ለመክፈል ግዴታ ውስጥ ገብተው ሆቴሉን ከመገልገያዎቹ ዕቃዎች ጭምር መረከባቸውን፣ ተከሳሹ የሆቴሉን ሥመሃብት ለማዛወር የሚረዱትን በውሉ የተጠቀሱትን ግዴታዎችን ለመፈፀም ፈቃደኛ ባለመሆን ቀሪ ክፍያም ሳይከፍሉ መቅረታቸውንና ለዚህም ህዳር 23 ቀን 1998 ዓ.ም ተከሳሽ ግዴታቸውን ለመፈፀም ፈቃደኛ ባለመሆን ምክንያት ውሉ ፈራሽ እንደሚሆንና ከሳሾች መብታቸውን በህግ አግባብ ለማስከበር የሚገደዱ መሆኑን ገልፀው የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን፣ ተከሳሹ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታቸውን ባለመፈፀማቸው ውሉ መፍረሱንና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስ ማቅረባቸውን ዘርዝረው ተከሳሽ በውሉ ምክንያት የተረከቡትን ሆቴል ከእነ መገልገያ ዕቃዎቹ ለከሳሾች እንዲያስረክቡ፣ በውሉ የተመለከተውን የገደብ መቀጫ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ እንዲከፍሉ፣ በሆቴሉ ድርጅት መልካም ስምና ዝና ለደረሰው ጉዳትና ለተገኘው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ወደፊት ክስ የማቅረብ መብታቸው እንዲጠበቅና በክሱ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አንደኛ አመልካች ላይ ክስ መስርተዋል፡፡ ክስና ማስረጃ ለአንደኛ አመልካች ደርሶም በ24/04/1998 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመከላከያ መልሱን አቅርበዋል፡፡ በመከላከያ መልሳቸውም የሽያጭ ውሉ መደረጉ እውነት ሆኖ ተከሳሹ በውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት የልማት ባንኩን ዕዳ ከፍለው ንብረቱን ከልማት ባንክ መረከባቸውን፣ ለሌሎች ዕዳዎችም ከብር 800,000.00 /ስምንት መቶ ሺህ ብር/ በላይ ከፍለው ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ብቻ መቅረቱን፣ ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ያልቻሉትም ጉዳዩን ለማስፈፀም የተሰጣቸውን ውክልና በከሳሾች በመሻሩ ምክንያት ሆኖ ከዚህ በኋላም ከሣሾች እንደውሉ ለመፈፀም ምንም ዓይነት ጥረት አለማድረጋቸውንና ሌሎች ምክንያቶችን በመዘርዘር ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት ከሳሾች መሆናቸውን በመጥቀስ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ በዚህ ክሳቸውም በውሉ መሠረት የባንክ ዕዳዎችንና ቅድሚያ ክፍያ ጨምሮ ብር 7,470,541.10(ሰባት መቶ ሺህ አራት መቶ ሰባ ሺህ አምስት መቶ አርባ አንድ ብር ከአስር ሳንቲም) ክፍያ ፈጽመው ድርጅቱንና ህንፃውን በመረከብ ከብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ በላይ የሆነ ገንዘብ ወጪ በማድረግ ስራ እንዲጀምር ማድረጋቸውን፣ ቀሪውን የሽያጭ ገንዘብ ስመሃብቱ ሲዛወር ለመክፈል በውሉ መስማማታቸውንና የውሉን ግዴታ የከሳሽ ተከሳሾች እንዲፈጽሙ ቢነገራቸውም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመዘርዘር በውሉ ግዴታ የከሳሽ ተከሳሾች እንዲፈጽሙ ቢነገራቸውም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመዘርዘር በውሉ ግዴታ መሠረት ተከሳሾች ለንግድ ድርጅቱና ለህንፃው ስመ ሀብት መዛወር አስፈላጊ የሆኑትን ማንኛውንም ፎርማሊቲዎች እንዲፈጽሙና በእጃቸው የሚገኘውን ማንኛውንም ሰነዶች ለተከሳሽ ከሳሽ እንዲያስረክቡ፣ ውሉ በግድ እንዲፈፀምና ወጪና ኪሣራም ይከፈላቸው ዘንድ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የከሳሽ ተከሳሾችም ጥር 24 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የተከሳሽ ከሳሽ ክስ ተቀባይነት የለውም የሚሉባቸውን የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያቶችን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አራተኛ ተጠሪ የጣልቃ ገብነት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዙቱም በአጭሩ ለሽያጭ መሠረት የሆነው ሆቴል ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት በመሆኑና በንብረቱ ላይ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ፣ ውሉ በተንኰል የተደረገና የሦስትኛ ወገንን መብት የነካ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን የሚገባው ህገ-ወጥ ውል ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ የጣልቃገብ አቤቱታም አንደኛ አመልካችም ሆነ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጐ አለን ያሉትን መልስ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች መጋቢት 13 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ የጣልቃገብነት አቤቱታ ግንቦት 04 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የንግድ ድርጅትና የንግድ ድርጅቱ ህንፃ ሽያጭ ውል የተፈረመው የአበዳሪ ባንኮችንና የፋይናንስ ተቋማትን ፍላጐት ለማሟላትና ለማመቻቸት ሲባል ሆኖ ጣልቃገብ ሁለተኛ ገዥነት መዋዋሉን፣ የአሁኑን አመልካች ዕዳም ጣልቃገብ ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ባገኘው የብር 6,400,000.00 /ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ብር/ መክፈሉን፣የሆቴሉን ህንፃ እና ጠቅላላ ድርጅቱንም ሐምሌ 01 ቀን 1997 ዓ.ም በተፈረመ የመያዣ ውል ለአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በመያዣነት መስጠቱን፣ በጣልቃገብ ስም በወጣ የንግድ ፈቃድ እና የንግድ ስያሜም ሆቴሉ ንግዱ እየተመራና እየተካሄደ የሚገኝ መሆኑን፣ በገዥዎች በኩል የውል ግዴታ ተጥሷል በሚል የቀረበው ምክንያትም የማይገባ መሆኑን በመዘርዘር የሽያጭ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ የፍሬ ነገርም ሆነ የህግ ምክንያት የለም ከማለቱም በተጨማሪ ውሉ ይፈርሳል ቢባል እንኳ ገዥዎች ወደ ነበሩበት ቦታ ለመመለስ የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን በመጥቀስ የውሉ ቃል ተግባራዊ ይሆን ዘንድ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ በዚህ የጣልቃገብ አቤቱታም ከሣሾች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጐ ጣልቃገቡ የዳኝነት ሳይከፍሉ የሚስተናገድበት ምክንያት አለመኖሩን፣ ጉዳዩም የአሁኑ አንደኛ አመልካች የተከሳሽ ከሣሽነት ክስ ሲያቀርቡ ሳይቀርብ ቀርቶ በኋላ መቅረቡ ሥነ-ሥርዓቱን የጠበቀ አለመሆኑን፣ አንድ ድርጅት በአንድ ቀን ለተለያዩ ግለሰቦች ሊሸጥ የማይችል መሆኑንና በጣልቃገብ በኩል የቀረበው የውል ሰነድም በስህተት የተፈረመ በመሆኑ በህግ ፊት ሊፀና እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ቀደም ሲል ይዙት የነበረውን ጭብጥ በማሻሻል ተገቢ ነው ያለውን ጭብጥ ከያዘ በኋላ አግባብነት አላቸው ያላቸውን የውርስ እና የሽያጭ ህግ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ የሽያጭ ውሉ ህጋዊ የሚባልበት ምክንያት የለም በሚል ምክንያት የሽያጭ ውሉን ፈራሽ ነው ብሎ ከደመደመ በኋላ የአሁኑ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ብር 513,012.20 /አምስት መቶ አስራ ሦስት ሺህ አስራ ሁለት ብር ከሃያ ሳንቲም/ ለአሁኑ አንደኛ አመልካች እንዲከፍሉ አንደኛ አመልካችም የተረከቡትን የድርጅት ቤት ለሻጮች መልሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲያስረክቡ እና የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች በሽያጭ ውሉ ምክንያት ለሻጮች ከፈልኩ የሚለውን በተመለከተ ደግሞ ዳኝነት ከፍሎ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀለት መሆኑን በመግለጽ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የህንፃው ሽያጭ ውል በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውሉ ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ በመሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ሊያሟላ የሚችል አለመሆኑንና በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 21448 ስለ ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ድንጋጌ የሰጠውን ትርጓሜ በመጥቀስ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔን በውጤት ደረጃ የተቀበለው መሆኑን ገልጾ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች ጠበቃ መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አራተኛ ተጠሪም በተመሳሳይ ቀን ለብቻቸው በፃፉት ማመልከቻ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ በተጠሪዎች መልስ ላይም የአመልካቾች ጠበቃ የመልስ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ግራ ቀኙ በቃል እንዲከራከሩ ተደርጉ ህዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክራቸው ተደምጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍና የቃል ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጥያቄ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤት ተገቢነት ያለውን ጭብጥ በመያዝ አግባብነት ያለውን ዳኝነት ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የሆቴል ድርጅትና ህንፃው የሚች የአቶ ከበደ ዘለቀ እና የአሁኑ ሦስተኛ ተጠሪ የጋብቻ የጋራ ሀብት መሆኑን፣ ይህንኑ የሆቴል ድርጅት እና ህንፃ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች የጋራ ባለሃብት ነን በማለት ግንቦት 04 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ለአመልካቾች የሸጡላቸው መሆኑን ነው፡፡ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ውሉ መደረጉን አምነው ለፍ/ቤቱ ክስ መመስረት የቻሉት አንደኛ አመልካች በሽያጭ ውሉ የተቀመጠውን ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ተገቢውን ማስጠንቀቂያ ሰጥተን ውሉን በግላችን ስለሠረዝን ድርጅቱን አንደኛ አመልካች መልሰው ያስረክቡን በሚል ምክንያት መሆኑንም ተረድተናል፡፡ እንዲሁም አንደኛ አመልካች በስር ተከሳሽነታቸው የሰጡት መልስ የውሉን መኖር አምነው በውሉ ለተቀመጡት ግዴታዎች አለመፈፀም ምክንያት የሆኑት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መሆናቸውን በመዘርዘር ውሉ የሚሰረዝበት የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት የለም ሲሉ የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የአሁኗ አራተኛ ተጠሪ ክርክር መሠረት ያደረገውም ለሽያጭ መሰረት የሆነው የሆቴል ድርጅት የሚች አባታቸው ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት ሆኖ እያለ ሽያጩ በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መከናወኑ መብቴን ስለሚነካ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በሚል ነው፡፡ የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ክርክር ደግሞ ለክርክሩ መሰረት የሆነው የሆቴል ድርጅት ከሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከአንደኛ አመልካች ጋር በጋራ የገዛው የአበዳሪ ባንኮችንና የፋይናንስ ተቋማትን ፍላጐት ለማሟላትና ለማመቻቸት ሲባል መሆኑን፣ አንደኛ አመልካች በውሉ መሠረት በገባው ግዴታም ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ፅዳ ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ ተበድሮ ብር 6,400,000.00 /ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ብር መክፈሉንና በራሱ የንግድ ስያሜም የንግድ ሥራውን እየሰራ እንደሚገኝ እንዲሁም ለፋይናንስ ተቋማትና ሌሎች የሻጭ ፅዳዎችን እና ሆቴሉን በዘመናዊ ሁኔታ ለማደራጀት በድምሩ ብር 11,285,889.00 /አስራ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር/ ወጪ ማድረጉን ገልጾ ውሉ የሚሰረዝበት አግባብ የለም የሚል ነው፡፡

እንግዲህ የግራ ቀኙ ክርክርና የዳኝነት ጥያቄ የሚያሳየው ግንቦት 04 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የሆቴል ድርጅት እና ህንፃ ሽያጭ ውል መኖሩ ታምኖ በውሉ በተመለከተው አኳኋን ግዴታውን ያልተወጣው የትኛው ወገን ነው በሚል አመልካቾችና ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የሚከራከሩ መሆኑን፣ አራተኛ ተጠሪ ደግሞ ሽያጩ ባልተከፋፈለ የውርስ ንብረት ላይ የተፈፀመ ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል የሚሉ መሆኑን ነው ከዚህ የክርክር ይዘት የምንገነዘበው ደግሞ በፍ/ቤቱ በጭብጥነት ተይዞ ውሣኔ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ ምን እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምላሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያገኘው የፍትሐብሔር ሙግቶች የሚመሩበትን የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ አንቀጽ 248 የሚያሳያው ጭብጥ የሚያዘው ከሣሽና ተከሳሽ በሥርዓቱ መሠረት የሚያቀርቡት የክስ ማመልከቻና የመከላከያ መልስ፣ ከአባሪ ሠነዶችና በቁጥር 241 መሠረት ከተደረገው ምርመራ የተገኘውን የተከራካሪ ወገኖች ቃል መሠረት በማድርግ መሆኑን ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይም የተከራካሪ ወገኖች የክርክር ሂደት ሊያዝ እና በፍ/ቤት ሊወሰን የሚገባው ጭብጥ ምን እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይኸውም የስር ከሣሾች ጥያቄ ግንቦት 04 ቀን 1997 የተደረገው የሽያጭ ውል ይፍረስልን ሳይሆን ውሉ በግላችን ስለተሠረዘ ድርጅቱን ገገር ያስረክበን የሚል ነው፡፡ ገገርዎች ውሉ ሊሰረዝ አይገባም የሚሉትን ምክንያት ዘርዝረዋል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ዳኝነት የሰጠው ውሉ ፈራሽ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሠረቱ ውል ማፍረስና ውል መሠረዝ በውል የተቋቋሙት ግዴታዎች ከሚቀሩባቸው መንገዶች ውስጥ የሚካተቱ ቢሆንም ምክንያታቸውና ውጤታቸው የተለያዩ መሆኑን በዚህ ረገድ የተደነገጉት የውል ማፍረስ ከውል አመሠራረት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ሲሆን ሲሆነ ውሉ ከአመሰራረቱ በህጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ባለማሟላቱ ግድፈት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የውል መሰረዝ ጉዳይ ከውል አመሰራረት ችግር የሚነሳ ሳይሆን ከተዋዋይ ወገኖች የውል ግዴታውን ካለመወጣት የሚመነጭ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ውል የሚሰረዘው ከመሠረቱ ግድፈት ስላለው አይደለም፡፡ ይልቁንም የውል መሠረዝ ምክንያት ከተዋዋይ ወገኖች የውል ግዴታን ከመፈፀምና ካለመፈፀም ጋር ተያይዞ የሚከሠት ነው፡፡ የውል መሠረዝ ሥርዓትም የራሱ የሆነ አካሄድ አለው፡፡ ይኸውም ውሉን የመሠረዝ ፍላጐት ያለውን ወገን የውሉ ግዴታ ባለመፈፀሙ የተነሳ ከህግ ወይም ከውሉ ከራሱ ባገኘው መብት ተጠቅሞ ውሉን ሊሰርዝ ይችላል፡፡ ይህ መብት ተግባራዊ የሚሆንበት አጋጣሚም ግዴታው ባለመፈፀሙ የተነሳ የደረሰውን ጉዳት ከማረጋገጥ ጋር ተያይዞ የሚታይ እንጂ ጥያቄ አቅራቢው ሁል ጊዜ ተቀባይነት የሚያገኝበት አይደለም፡፡ በመሆኑም የውል ይሰረዝልኝና ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች በህጉ አግባብ የሚስተናገዱ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1784 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በተያዘው ጉዳይም የስር ከሳሾች ጥያቄ ውል ይሰረዝልኝና ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች በሚስተናገዱበት የፍትሐብሔር ህግ ክፍል ምላሽ ማግኘት ሲገባ በህጉ አግባብ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ባልቀረበበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 ስር የተመለከተውን የፎርማሊቲ ጥያቄ በማንሳት ጉዳዩን መወሰኑ የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሠረቱ ፍ/ቤቱ በተከራካሪ ወገኖች የተጠየቀውን ዳኝነት በመተውና በተከራካሪ ወገኖች ያልተነሳለትን የፎርማሊቲ ጥያቄ በራሱ ጊዜ በማንሳት ውሣኔ እንዲሰጥ የሚያስችል የህግ አካሄድ የለም ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታ በቀረበበት ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የውል ይሰረዝልን፤ ሠርዘናል የክርክር ጭብጥ መሠረት አድርጐ የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ዳኝነት መስጠት ሲገባው የፎርማሊቲ ጥያቄን በማንሳት እና ምክንያቱን በመለወጥ ውጤቱን ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የክርክሩን ጭብጥ የውል ይሠረዝ፤ ሠርዘናል አካያ አለመመልከቱን ከላይ ገልፀናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ይኸው ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከተገቢው ጭብጥ አኳያ እንዲመለከትና ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በማድረግ ጉዳዩን መመለሱ ሥነ ሥርዓታዊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም፡-

1ኛ/ የስር ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ሁለተኛ እና ሦስትኛ ተጠሪዎች ውሉን ሰርዘናል ማለታቸው ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም?

2ኛ. የውሉ መሠረዝ ጥያቄ በፍ/ቤት ሊወሰን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

3ኛ. የአሁኗ አራተኛ ተጠሪ ውሉን የመሠረዝ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ? ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ንብረት መብት አላቸው? መብት አላቸው ከተባለስ መብታቸው በምን መንገድ መከበር አለበት? በሚሉትና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ባላቸው ከውል መሰረዝ ጥያቄ ጋር ሊያያዙ የሚችሉትን ተጨማሪ ነጥቦችን በመመልከት ተገቢውን ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 27497 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔው የተሻረ መሆኑን አውቆ ከላይ ከተመለከቱት ሯብጦች አኳያ ጉዳዩን እንደገና በመመልከት ተገቢውን ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34586

ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ያለው ድልነሳው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረግ - አልቀረቡም ከተባለበኋላ ቀረቡ

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ ቀረቡ

3. ወረዳ 22 ቀበሌ 04 አስተዳደር - አልቀረበም

4. አቶ ወሰን ፀጋ - ተቋርጧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአንደኛ ተጠሪ ክሳሽነትና ከሁለት እስከ አራተኛ በተጠቀሱት ተጠሪዎች ተከሳሽነት የነበረውን ክርክር መርምሮ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አንደኛ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሁለት እስከ አራተኛ በተጠቀሱት ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ቤት መንግሥት ስለ ንግድ ቤቶች መግለጫ ካወጣም በኋላ በስሜ ውል ተዋውዬ ባለሀብት ሁኔታ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከአራተኛ ተጠሪ ጋር በውል ላይ ውል በማድረግ የንግድ ቤቱን አሳልፈው የሰጡ ስለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሳሽ ንግድ ቤቶችን አስመልክቶ የመንግሥት መመሪያ ከወጣ በኋላ በስማቸው ተከራይተው በይዞታቸውም ሥር አድርገው በንግድ ቤቱ ሲጠቀሙበት የነበረ ስለሆነና ተከሳሾች መመሪያው ከወጣ በኋላ ከከሳሽ ጋር የተደረው ውል በስህተት እንደተደረገ ከማንሳት ውጭ ውሉ የጸና ሊሆን እንደማይችል ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ ስለሌለ በዚህ ሁኔታ በተከሳሾች የተፈጸመው ድርጊት በሕግ የተፈቀደ መብትን ተከትሎ የተፈጸመ ባለመሆኑ አድራጎቱ ከሁከት ስለሚፈረጅ ባለይዞታ ለሆኑት ለከሳሽ ቤቱ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች በወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 የተመዘገበውን የንግድ መደብር የካቲት 16 ቀን 1992 ዓ.ም በንግድ ቤቱ ላይ እዳና እገዳ እንደሌለበት አጣርቼ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ከሦስተኛ ተከሳሽ /ከአሁን ሦስተኛ ተጠሪ/ ላይ ገዝቼ ሽያጩም ሕጋዊ መሆኑ በቀበሌው አስተዳደር በኩል ታምኖበት የኪራይ ውሉ በስሜ ተዛውሮ ኪራይ የምከፍል ከመሆኑም በላይ የንግድ ፈቃድም አውጥቼ በመስራት ላይ እንዳለሁ የንግድ ቤቱን አስቀድሞ በተሰጠ ፍርድ መነሻነት ለከሳሽ ለአሁን አንደኛ ተጠሪ እንዳስረክብ የተገደድኩ ስለሆነ ይሄው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት ይሰረዝልኝ በማለት አመልክተው ፍ/ቤቱም ከሳሽና ተከሳሾች የነበሩት በመጥራት ካከራከረ በኋ በቀድሞው ውሳኔ ክርክር ያስነሳው የንግድ ቤት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስለ ንግድ ቤቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መግለጫ ከማውጣቱ በፊትም ሆነ በኋላ ከአንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሾች ተከራይተው ይጠቀሙበት እንደነበርና ይዞታቸው እንደሆነ የተረጋገጠ ከመሆኑም ሌላ ከሳሽ መመሪያው ከወጣ በኋላ ከአንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሾች ጋር ያደረጉት ውል ፈራሽ ነው ሳይባል ከሦስተኛ ተከሳሽ ጋር ያደረጉት ውል መብትና ግዴታን ሊያቋቁም እንደማይችል ስለተወሰነና ከዚህም ውሳኔ ሦስተኛ ተከሳሽ አንዳችም መብት እንደሌላቸው መገንዘብ ስለሚቻል የመቃወም አመልካችም የንግድ ቤቱን ገዛሁ የሚሉት መብት ከሌላቸው ከሦስተኛ ተከሳሽ ላይ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ የቀድሞው ውሳኔ ይሰረዝልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይሄው ውሳኔም የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጉድለት የለውም ተብሎ እስከ አዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ እንደፀና ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ለዚህ ችሎት የቀረበውም የሰበር አቤቱታ ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በየደረጃው የሚገኙ የሥር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉ የቀሩበት ምክንያት ተጠሪዎች ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍ አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ፡-

አመልካች ባቀረቡት መቃወሚያ መነሻነት አስቀድሞ የተሰጠው ፍርድ ሊሰረዝ ይገባል ወይንስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ጭብጥ አኳያም የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አንድ ፍርድ በአንድ ፍ/ቤት ከተሰጠ በኋላ ይዜው ፍርድ በዚያው ፍ/ቤት በድጋሚ ከሚታይባቸው ሥርዓቶች መካከል አንዱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 መሠረት መቃወሚያ በሚቀርብበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረትም በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንደዚሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማንኛም ሰው ተካፋይ ባልሆነበት የተሰጠው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ማቅረብ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበትንና ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ቤት አመልካች በስማቸው የንግድ ፈቃድ አውጥተው ሲሰሩበት ከነበረው የሥር ሦስተኛ ተከሳሽ የአሁን አራተኛ ተጠሪ ላይ የካቲት 16 ቀን 1992 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ስለመግዛታቸውና በኋላም የኪራይ ውሉን በስማቸው በማዛወርና የንግድ ፈቃድም በስማቸው በማውጣት የንግድ ሥራ ሲሰሩበት እንደነበር ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ የቀድሞው ውሳኔም መብቱን የነካ ስለሆነ ሊሰረዝ /Set aside/ ይገባል በማለት መቃወሚያ ያቀረቡትም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች መቃወሚያ ሳይቀበሉት የቀሩት ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የኪራይ ውል ቀሪ ባልሆነበት ሁኔታ ሌላ ውል ከአራተኛ ተጠሪ ጋር መደረጉ ተገቢነት የሌለውና ውጤትም ሊኖረው ስለማይችል በዚሁ ውጤት በሌላው ውል ላይ ተመስርቶ በአራተኛ ተጠሪና በአመልካች መካከል የተቋቋመው የንግድ መደብር ሽያጭ ውል የመብትም ሆነ የግዴታ ምንጭ ስለማይሆን መቃወሚያው ተገቢነት የለውም በማለት ነው፡፡

ይሁንና አመልካች ይህንኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውና የንግድ መደብር ከአራተኛ ተጠሪ ሲገዙ ከላይ እንደተጠቀሰው አራተኛ ተጠሪ ንግድ መደብሩን በስማቸው ባደረጉት ውል ይዘውት እንደሚገኙ እንደዚሁም በስማቸው የንግድ ፈቃድ በማውጣት እየሰሩ እንደሚገኙ በማረጋገጥ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ የሸያጩን ውል ከአራተኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉ እንደመሆኑ መጠን ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች አስቀድሞ ከአራተኛ ተጠሪ ጋር ያደጉት የኪራይ ውል ተገቢነት የሌለው ነው ቢባል እንኳን አመልካች ውሉን በቅን ልቦና ያደረጉት በመሆኑ ሕጉ ለቅን ልቦና ተዋዋዩች ከሰጠው ጥበቃ አኳያ ጉዳዩ የማይታይበት ምክንያት አይኖርም በዚህም መሠረት የቅን ልቦና ባለይዞታነትን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ባለሀብት ለመሆን በቅን ልቦና ዋጋ ሠጥቶ ውል የተዋዋለ ሰው የተባለውን ተንቀሳቃሽ ነገር በእጁ ሲያደርግ በቅን ልቦናው ምክንያት የዚህ ንብረት ባለሀብት እንደሚሆን ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የንግድ መደብር ግዙፍነት ባይኖርም ነገር ግን ግዙፍነት የሌለው ተንቀሳቃሽ ንብረት /Incorporeal

https://t.me/ethiopianlegalbrief

movable/ እንደሆነ የንግድ ሕግ ቁጥር 124 ላይ ስለተመለከተ ስለቅን ልቦና ባለይዞታነት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡

አመልካች ይህንኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ መደብር ይዘው የሚገኙት በቅንልቦና በተደረገ ውል መነሻነት ነው ከተባለ አስቀድሞ አንደኛ ተጠሪ ከሁለት እስከ አራት በተጠቀሱት ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት የንግድ መደብሩን ለከሳሽ ለአንደኛ ተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ አመልካች በክርክሩ ተካፋይ ባልሆኑበት መብታቸውን የነካ ውሳኔ አንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በመሆኑም አመልካች የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 በሚፈቅደው መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 አኳያ ታይቶ አስቀድሞ የተሰጠውና የአመልካችን መብት የነካው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት መሰረዝ ሲገባው ከአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እስከ አዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ አቤቱታው ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመቁ 2901/91፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ.ቁ 414/93 እንደዚሁም ሰበር ሰሚው ችሎት በመ/ቁ 01424 በ20/3/2000 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348 (1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 2901/91 የሰጠው ውሳኔ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ መብታቸው የነካ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት ተሰርዟል፡፡
3. አመልካች በወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ መደብር ከአራተኛ ተጠሪ ላይ የገዙት በቅንልቦና ስለሆነ ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፣፣
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 39568

መጋቢት 24 ቀን 2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሽንቁጤ ተ/ማርያም - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ገብሬ ጎንጤ - ቀርበዋል

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ አቤቱታ የቀረበው አመልካች ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 6833፣ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 17074፣ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ ተቀብሎ ማፅናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ከሣሽ፣ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ስር ከሣሹ ህዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡትን ክስ መሠረት በማድረግ ሲሆን አጭር ይዘቱ ደግሞ ወኪል አድራጊዬን በመወከል ሐምሌ 10 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ ውል በወኪል አድራጊዬ ተመዝግቦ የሚታወቀውን የሰሌዳ ቁጥር 3- 08106 ኦሮ የሻንሲ ቁጥሩ 15416፣ የሞተር ቁጥሩ OME 03 - 41-3000-056326 የሆነ ጣሊያን ሰራሽ ፊያት መኪና ለተከሣሹ በብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ ብር/ ሸጨላቸው ከዚህ ገንዘብ ብር 19,000 /አስራ ዘጠኝ ሺህብር ከፍለውኝ እኔም መኪናውን ህዳር 09 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ መረካከቢያ አስረክቤአቸዋለሁ፤ ይሁን እንጂ ቀሪውን ብር 31,000 /ሰላሣ አንድ ሺህ ብር/ ከፍለው መኪናው በስማቸው እንዲያዞሩ ተከሣሹን ብጠይቃቸው ፍቃደኛ ባለመሆናቸው የተጠቀሰው ቀሪው ገንዘብ በመክፈል መኪናውን በስማቸው ተገድደው እንዲያዞሩ ይደረግልኝ፤ በተጨማሪም ታህሣሥ 18 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል ብር 1474 /አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ብር/ ተከሣሹ ተበድረው የወሰዱ ሲሆን ይህንን ብድር እንዲመልሱልኝ እንዲሁም ወለድና ወጪና ኪሣራ አክለው እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሣሹም በሰጡት መልስ ሐምሌ 10 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረግነው የመኪና ሽያጭ ውል ውስጥ መኪናው የካምቢዮን ጥርስ ችግር ስላለው ከሣሹ ወደፊት እስከ ህዳር 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ይህንን ጉድለት እንዲስተካከል አድርገው በስሜ እንዲዛወር የማድረግ ግዴታ ገብተው ሲያበቁ ይህንን ግዴታቸው ባልተወጡበት ሁኔታ ያቀረቡት የመኪናው ሽያጭ ቀሪ ገንዘብ ይስጡኝ ጥያቄ ተገቢነት የለውም፤ እንዲሁም ከመኪናው ሽያጭ ውል ጋር ምንም አይነት ዝምድና የሌለው የብር 1474 /አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ብር/ ብድር አጣምረው መክሰሣቸው ተገቢነት የለውም፤ ከፈለጉ ራሱን በቻለ ክስ መጠየቅ ይችላሉ እንጂ ከመኪና ሽያጩ ጋር አያይዘው ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም ብለዋል፡፡

የሥር ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አግባብነት አላቸው ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ በመ/ቁ. 17074 ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም ፍርድ የሰጠ ሲሆን፣ የፍርዱ ይዘትም ግራ ቀኙ ወገኖች ባደረጉት የመኪናው ሽያጭ ውል መኪናው የካምቢዮ ጥርስ ችግር ያለበትና ይህንን ጉድለት ከሣሹ እስከ ህዳር 30 ቀን 1999 ዓ.ም ለማስተካከል ግዴታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የገቡ ስለሆነ ይህንን ግዴታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ የመኪናው ሽያጭ ቀሪ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ ማንሣታቸው ተቀባይነት የለውም፤ ከብር 19,000 /አስራ ዘጠኝ ሺህ ብር/ በተጨማሪ ከሣሹ ብር 10,416 / አስር ስሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ ከተከሣሹ መቀበላቸው በተከሣሹ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ስለሚያሣይና በከሣሹም ያልተካደ በመሆኑ ከሣሹ ከተከሣሹ ላይ የሚቀራቸው ገንዘብ ብር 31,000 /ሠላሣ አንድ ሺህ ብር/ ሣይሆን ብር 20,584 /ሃያ ሺህ አምስት መቶሰማኒያ አራት ብር/ እንደሆነና ተከሣሹ በቀሪው ያልከፈሉት ገንዘብ መኪናው እንዲታደስና ቀሪ ገንዘብ የመኪናውን ጉድለት ለማሣደስ የማይበቃ ከሆነ በደረሰኝ መሰረት ለሚረጋገጥ ተጨማሪ የማሣደሻ ወጪ ከሣሹ እንዲከፍሉና መኪናውን አሟልተው ለከሣሹ እንዲያስረክቡ፤ ከሣሹና ተከሣሹ ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉት የመኪናው ርክክብ ውል በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ የተመዘገበ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ ከሣሹ ከመኪናው ሽያጭ ውል አለመፈፀም ጋር አያይዘው ያቀረቡት የብር 1474 /አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ብር/ ጥያቄ ራሱን የቻለ ክስ አቅርበው መጠየቅ እንጂ ተጣምሮ መቅረቡ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ከላይ የሰፈረውን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በመቃወም ስር ከሣሹ ወደ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ በፍ/ይ/መ/ቁ. 6833/ስኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡

አመልካቹም በሥር ፍርድ ቤቶቹ የተሰጠውን ፍርድ በመቃወም ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም ስር ተከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በውሉ መሠረት መኪናው እንደተረከቡ የሚገልጽ ሰነድ ፈርመውና ይህ ሰነድም ለስር ፍ/ቤት ቀርቦለት እያለ ስሙን እንዳዞርላቸው እና ቀሪውን ገንዘብ እንዲከፍሉኝ ጥያቄ አቅርቤ እያለሁ መኪናው አሟልተህ ለተጠሪው አስረክብ ብሎ ፍርድ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፤ ተጠሪው መኪናው ተረክበው ሲያበቁ በመኪናው ለሚደርስ ጉዳት ሻጭ አሰራ መባሌ ተገቢ አይደለም፤ ፍ/ቤት ተዋዋይ ወገኖች በውላችን ካስቀመጥነው ግዴታ ውስጥ ሌላ አዲስ ግዴታ ሊፈጥር አይችልም፤ ተጠሪው በመረጡት ጋራጅ መኪናውን ስላሣደስኩላቸው የከፈልኩትን ብር 10,416 /አስር ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ የመለሱልኝን ገንዘብ የስር ፍ/ቤቱ ይህ ገንዘብ ለመኪናው ሽያጭ ተብሎ እንደተቀበልኩ በማድረግ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪም የካቲት 25 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም አመልካቹ ለተጠቀሰው መኪና ሽያጭ ተብሎ ብር 29416 /ሃያ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ ከእኔ ወስዷል፤ አመልካቹ የሸጠልኝ መኪና ጉድለት የነበረበትና በእዳ የተያዘ ነው፤መኪናው ቀደም ብሎ በሌላ ምክንያት ለነበረው ዕዳ መክፈያ እንዲሆን የሐራጅ ሽያጭ ወጥቶበት ይገኛል፤ አመልካቹ በውላችን መሠረት የነበረበትን ግዴታ ሣይወጣ መኪናው ተጠሪው ተረክቧልና እዳ የለብኝም በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተገቢነት የለውም፣ መኪናው እንዲያሣድስልኝ አመልካችን አልወከልኩትም፣ ስለሆነም እኔ ለአመልካች የሰጠሁት ብር 10416 /አስር ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ ለመኪናው ዋጋ ተብሎ የተሰጠው ተጨማሪ ክፍያ እንጂ ለመኪና ማሣደሻ አይደለም፤ ስለሆነም አመልካቹ የወሰደውን ጠቅላላ ገንዘቤ ብር 29416 /ሃያ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ ከሕጋዊ ወለዱ ጋር ደምሮ ሊመልስልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ በመጣው መልኩ በመገንዘብ፣

1/ አመልካቹ በመኪና ሽያጭ ውሉ መሠረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም?

2/ አመልካቹ በስር ፍ/ቤት የመሠረቱት ክስ ተጠሪው የመኪና ሽያጭ ቀሪ ገንዘቤ ይክፈለኝና መኪናው በስሙ ይዛወርለት የሚል ሆኖ እያለ በፍርዱ የተመለከቱትን ሌሎች ግዴታዎች በአመልካቹ ላይ ሊፈረዱ ይገባል ወይስ አይገባም? በሌላ አገላለጽ የፍርዱ ገደብ እስከየት ድረስ ሊሆን ይገባል?

የሚሉትን መሠረታዊ ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ መንፈስ መረዳት የሚቻለው አመልካቹ የሚሉት ከተጠሪው ጋር ባደረጉት የመኪና ሽያጭ ውል መሠረት ከእርሣቸው የሚጠበቅ ማንኛውም አይነት ግዴታ እንደተወጡና መኪናውም ለተጠሪው እንዳስረከቡ በመግለጽ ቀሪ ገንዘባቸውን ተጠሪው ከፍለው መኪናዋ በገዢው ስም እንድትተላለፍ ነው፤ የስር ፍርድ ቤቶቹም አመልካቹ ቀሪ ገንዘብ እንዲከፈላቸው ከመጠየቃቸው በፊት ሊወጡት የሚገባ መኪናውን የማስጠገን ግዴታ አለባቸው ማለታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቹ ፍ/ቤቱ የፈጠረባቸው አዲስ ግዴታ አድርገው ያስቀምጡታል፡፡ ተጠሪው ደግሞ አመልካቹ የሸጡላቸው መኪና ችግር ያለበት እንደሆነና በውላቸውም መሠረት መኪናውን የማስጠገን ወይም የጎደለውን የማሟላት ግዴታ አለባቸው የሚል ነው፡፡ ግራ ቀኙ ወገኖች ሐምሌ 10 ቀን 1998 ዓ.ም አደረጉት በተባለው የመኪና ሽያጭ ውል ውስጥ የአመልካቹ ግዴታ ሆኖ መስፈሩን የስር ፍርድ ቤቱ በውሣኔው የገለፀው መኪናው የካምቢዮ ብልሽት እንዳለውና ይህንን የማሰራት ወይም የመተካት ግዴታ እንዳለባቸው ነው፡፡ የመኪናው ካቢዮን አሰርተው መኪናው ለተጠሪው ስለማስረክባቸው የሚገልጽ ማስረጃ አመልካቹ አላቀረቡም፡፡ ተጠሪው መኪናው ተረክበው በእጃቸው አስገብተዋልና የመኪናው ጉድለት አርሜ መኪናው ማስተላለፌ ያሣያል የሚለው የአመልካቹ ክርክር ሲታይም ምንም እንኳ የስር ፍ/ቤቱ ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተደረገው የመኪናው ማረካከቢያ ውል በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ የተመዘገበ አይደለም በማለት ውጤት እንደሌለው አስመስሎ መወሰኑ ተገቢነት ባይኖረውም በዚህ ሰነድም ቢሆን መኪናው የካምቢዮን ችግር እንዳለበት የተቀመጠ በመሆኑ አመልካቹ በውሉ መሠረት ሊወጡት የሚገባ ግዴታ ሙሉ በሙሉ ተዋጥተዋል ማለት አይቻልም፡፡ በውል የተመለከተ ግዴታቸው ሣይወጡ ደግሞ የቀሪ ገንዘብ ክፍያና የመኪናው ስም መዛወር ጥያቄ ማንሣታቸው አግባብነት የለውም፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1757 እንደደነገገውም ውሉ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ወገን በውሉ መሠረት አስቀድሞ ሊወጣው የሚገባ ግዴታ ከተወጣ በኋላ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቱ አመልካቹ የመኪናው ካምቢዮን የማስተካከል ግዴታቸውን ሣይወጡ የቀሪ ገንዘብ ክፍያ ጥያቄ ማንሣት አይችሉም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል የስር ፍ/ቤቱ ከላይ ከተቀመጠው ማጠቃለያ ማለትም አመልካቹ በውሉ መሠረት አስቀድሞ ሊወጣው የሚገባ ግዴታ ሣይፈጽም ክስ ማቅረብ አይችልም ከሚለው ውሣኔ አልፎ ሌሎች በአመልካቹ መብት ላይ ያስተላለፋቸው ውሣኔዎች ማለትም ተጠሪው ያቀረቡት ክስ ሣይኖር ለአመልካቹ የከፈሉት ተጨማሪ ገንዘብ ብር 10,416 /አስር ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት/ አለ ብሎ ማረጋገጡና ሌሎች ተጨማሪ ነጥቦችን መተንተኑ ክርክር ሂደት አኳያ ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፤ አመልካቹ ግዴታውን ሣይወጣ ክስ ማቅረብ አይችልም ተብሎ ተጠቃልሎ እያለ ፍ/ቤቱ ከዚህ አልፎ ወደ ሂሣብ ስራ ገብቶ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢነት የለውም፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.17074፣ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ.ቁ. 6833/ ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፤ ይፃፍ፡፡

2/ አመልካቹ በመኪና ሽያጭ ውሉ የተመለከተውን ግዴታቸው ሣይወጡ ቀሪ ገንዘብ ተጠሪው ይስጠኝ በማለት ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡

3/ ተጠሪው ክስ ሣያቀርቡ አመልካቹ ባቀረቡት ክስ ተጠሪው ለአመልካች ከመኪናው ሽያጭ ብር 10,416 /አስር ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ ከፍለዋል የተባለውና ሌሎች ትችቶች የክርክር አካሄድ ስርዓት የተከተለ ውሣኔ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣

4/ ታህሣሥ 03/2001 ዓ.ም የተላለፈው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

5/ ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፤ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38935

መጋቢት 3 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ወልደፃድቅ ብርሃኑ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፈንታነሽ ኃይሉ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ስንታየሁ አያሌው - ጠበቃ አቶ ሙሉጌታ ገብሩ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፣ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03131 ሐምሌ 27 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48885 ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርበው በሥር ተከሣሽ የሆነው ተጠሪ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 11 ቀበሌ 19 የቤት ቁጥር 671 የሆነውን የመኖሪያ ቤት ሐምሌ 5 ቀን 1992 ዓ.ም ሸጠውልናል፡፡ ቤቱንና ቤቱ የሚመለከቱ ሰነዶችና ማስረጃዎችም አስረክበውናል፡፡

ሆኖም ተከሣሽ /ተጠሪ/ ከቀድሞው የቤቱ ባለንብረቶች መስከረም 21 ቀን 1986 ዓ.ም ባደረገው የግዥ ውል መሠረት ስመንብረቱን ወደራሱ በማዛወር ካርታውን ለማስረከብ የተስማማ ቢሆንም ቤቱን በሸጡለት እነ አቶ መስፍን አሰፋ ስም የወጣ ቁጥሩ 39348 የሆነ ካርታ ከተረከቡ በኋላ ካርታውን ለእኛ ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ካርታውን እንዲያስረክቡና ስመንብረቱን እንዲያዛወሩ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም በተከሣሽነት ቀርበው ቤቱ በሸጡልኝ ግለሰብ ስም ያለ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ የማይረጋ ነው፡፡ ከሣሾች /አመልካቾች/ ሚያዚያ 30 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እድፈጽምላቸው ማስጠንቀቂያ ሰጥተውኛል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንደውሉ ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን ያወቁ ስለሆነ ክሱን ያቀረቡት ማስጠንቀቂያ ከሰጡኝ ከአንድ ዓመት ከስምንት ወር በኋላ ስለሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ክሣቸው በይርጋ ይታገዳል በማለት የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭ ሌሎች መከራከሪያዎችን አቅርበዋል፡፡ የተጠሪ ሚስት ወ/ሮ ስንታየሁ ሽፈራው በበኩላቸው በጣልቃ ገብነት በክርክሩ ለመግባት ያመለከቱ ሲሆን የበኩላቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪና በጉዳዩ ጣልቃ ለመግባት ባለመለከቱት ወ/ሮ ስንታየሁ ሽፈራው ወደ ቀረቡት ዝርዝር ክርክር ከመግባቱ በፊት የከሣሾች /አመልካቾች/ ክስ በይርጋ ይቋረጣል ወይስ አይቋረጥም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በአመልቾችና በተጠሪ መካከል በውልና ማስረጃ ያልተመዘገበ የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው መስከረም 21 ቀን 1992 ዓ.ም መሆኑን ገለፃና አመልካቾች ለተከሣሹ ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር በኋላ ስለሆነ ይኸም ክሱ የቀረበው አመልካቾች ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር በኋላ ስለሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በይርጋ ይቋረጣል በማለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 245/2/ መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡ አመልካቾች ተጠሪ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ ነኝ ካርታና ፕላኑን አስጨርሽ አስረክባለሁ በማለት ጥር 10 ቀን 1993 ዓ.ም በጽሑፍ መተማመኛ የሰጠ ከመሆኑም በላይ ማስጠንቀቂያ ከፃፍንለትም በኋላ በውሉ መሠረት ግዴታውን ለመፈፀም ፈቃደኛ መሆኑንና ፕሮሰሱን እያስጨረሰ መሆኑን እያነጋገረን ነበር፡፡ በመጨረሻ ሚስቱ ቤቴን በሌለሁበት ነው የገዛችሁት ብላ በነገረችን በሶስተኛ ቀን ክስ መሥርተናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሉ የሚፈፀምበት የጊዜ ገደብ ያልተቀመጠለት ጅምር ቤቱን ተረክበን አሰርተን ያጠናቀቅንና ሠርቪስ ቤቶችም ያሠራን መሆኑንና ተጠሪ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ መሆኑን ሲገልፅልን የቆየ መሆኑን ከግምት ውስጥ ሣያስገቡ፣ ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892/3/ የተሣሣተ ትርጉም በመስጠት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች በውሉ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ከሚያዚያ 30 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እንደማልፈጽምላቸው የሚያውቁ መሆኑን ባቀረቡት ክስ ገልፀዋል፡፡ አመልካቾች በሥር ያላነሱትን ውሉ እንደማይፈፀም የነገረችን ሚስቱ ናት በማለት ያቀረቡት ክርክር በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ክሱን ያላቀረቡ በመሆናቸው ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጽሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታ ያቀረቡትን ክርክር በማጠናከር በጽሑፍ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካቾችና የተጠሪ ጠበቃ የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም በቃል ክርክር አድርገዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይና አመልካቾች እና ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች ክስና ጥያቄ በአንድ ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 በመጥቀስ የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት የማይንቀሣቀስ ንብረት የገዛ ሰው ሻጭ በውሉ መሠረት እንዲፈፀምለት ሰለሚጠይቅበት ሁኔታና ጥያቄውን ስለሚያቀርብበት የጊዜ ገደብ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን፣ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ አመልካቾች ተጠሪ ሐምሌ 5 ቀን 1992 ዓ.ም በገባው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ባለመሆኑ በፍርድ ተገድዶ እንዲፈፀምልን በማለት ያቀረቡት ክስ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1776 እና 2892 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1776 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መሠረት ያቀረቡት የቤት ሽያጭ ውል ይፈጽምልኝ ክስ በሕግ የተደነገገው የይርጋ ሕግ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመወሰን በመጀመሪያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ እንደዚሁም ድንጋጌው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875 መሠረታዊ መርህና ስለ ሽያጭ እና ጠቅላላ ውል ከተደነገጉ ድንጋጌዎች ጋር ሊኖረው የሚገባውን ተፈፃሚነት መመርመር ያስፈልጋል፡፡

1.የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2893 ንዑስ አንቀጽ 3 "ስለሆነም ሻጭ ውሉን እንደውሉ ቃል ለመፈፀም መዘግየቱን ከተረዳበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈፀምለት ካልጠየቀ በቀር ገዢው ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም የማድረግ መብቱን ያጣል" በማለት ይደነግጋል፡፡ እዚህ ላይ በአማርኛው "መዘግየቱን ከተረዳበት" በሚለው ቃልና በእንግሊዘኛው "ascertained" በሚለው ቃል መካከል ልዩነት ያለመሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን፡፡ የድንጋጌው መንፈስ ገዥ በአንድ ዓመት ውስጥ ውሉ እንዲፈፀምለት ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ያለበት ሻጭ በሽያጭ ውሉ መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን ካረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ የእንግሊዘኛውን የቃል አጠቃቀም በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ ሻጭ በሽያጭ ውሉ መሠረት ለመፈፀም እንደማይፈልግ ገዥ ያረጋገጠ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ማን ነው? የሚለው ነው። ለዚህ መሠረታዊ ነጥብ እልባት ለመስጠት ስለውል እና ተዋዋይ ወገኖች በፍትሐብሔር ሕጉ የተቀመጠ የሕግ ግምቶችን ማየት አስፈላጊ ነው።

በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀጽ 1 የደነገገ ሲሆን ውሎች በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነት የመተማመን ግንኙነት መሠረት በማድረግ በቅን ልቦና ሊተረጎሙ እንደሚገባ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1732 ይደነግጋል። ከዚህ አንፃር ስናየው ተዋዋይ ወገኖች በተዋዋሉት የውል ቃል መሠረት ውሉን የመፈፀም ፍላጎትና ቅን ልቦና ያላቸው መሆኑ የውል ሕግ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ በመሆኑ ገዥ ሻጭ በሽያጭ ውሉ በገባው የውል ቃል መሠረት እንደሚፈጽም የተለያዩ የተስፋ ቃሎችን ሲሰጠው የቆየ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ የለበትም።

በተቃራኒው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌን ጠቅሶ የሚከራከር ሻጭ ከገዥ ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ገዥ በማያሻማ ሁኔታ እንዲያውቅ እና እንዲረዳው ያደረገ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት። ሻጭ በውሉ መሠረት ለመፈፀም እንደማይፈልግ በእርግጠኝነት ገዥ እንዲያውቅ ካደረገው ከአንድ ዓመት በኋላ የሽያጭ ውሉ በፍርድ ኃይል እንዲፈፀምለት የጠየቀ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት። ስለሆነም የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ሻጭ የሽያጭ ውሉ መሠረት የቤቱን ይዞታና የባለቤትነት ሰነዶች ለገዥ ያላስረከበ ከሆነ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑንና በጽሑፍና በማያሻማ ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው አይነት ለገዢ ካሣወቀው ከአንድ ዓመት በኋላ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ያቀረበ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል።

- ሻጭ በውሉ መሠረት የቤቱን ይዞታ ለገዥ አስተላልፎ ከሆነ ገዥ ሻጭ በውሉ መሠረት ይፈጽማል የሚለውን ዕምነት የሚያጠናክርና ውሉም በከፊል መፈፀም መጀመሩን የሚያሣይ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2274 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል። ስለሆነም ሻጭ የቤቱን ባለሀብትነት ለገዥ ለማስተላለፍ እንደማይፈልግና የቤቱን ይዞታ ሻጭ በመልቀቅ እንዲያስረክበው የከፈለውንም ገንዘብ ገዥ እንዲወስድ በማያሻማ ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው አይነት ለገዥ ያሣወቀ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል።

- ሻጭ የቤቱን ሰነዶች ለገዥ አስተላልፎ የቤቱን ይዞታ ይዞ በሚገኝበት ጊዜ የቤቱን ሰነዶች ሻጭ እንዲመልስለት የከፈለውን ገንዘብ እንዲወስድ በማያሻማ ሁኔታና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው አይነት ለገዥ ያሣወቀ መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት ሲሆን ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች በአማራጭ ሻጭ ውሉ እንዲፈርስለት ወይም እንዲሰርዝለት በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ገዥ እንዲረዳው ከተደረገ ከአንድ ዓመት በኋላ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ገዥ ያቀረበ መሆኑን ወይም በሕግ እውቅና ላለው የሽምግልና ተቋም ሻጭና ገዥ በነበራቸው ድርድር ሻጭ ውሉን ለመፈፀም እንደማይፈልግ ገዢ እንዲረዳው ከተደረገ ከአንድ ዓመት በኋላ ክሱን ያቀረበው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት። በአጠቃላይ ሻጭ በገባው የሽያጭ ውል ቃል መሠረት ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ካሣወቀውና ገዥም ይህንኑ ከተረዳና ካረጋገጠ ከአንድ ዓመት በኋላ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ገዥ ያቀረበ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት።

ሻጭ በውሉ መሠረት ለመፈፀም የማይፈልግ መሆኑን ገዥ ያረጋገጠ መሆኑን ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት ማስጠንቀቂያ መስጠቱንና ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ሻጭ በውሉ መሠረት አለመፈፀሙን በማየት ብቻ ለማረጋገጥ አይችልም። ሻጭ ገዥ ማስጠንቀቂያ ከሰጠው በኋላም ቢሆን የተለያዩ ችግሮችን እያነሣ በመካከላቸው ያለውን የመተማመንና የቅን ልቦና ግንኙነት ተጠቅሞ ከአንድ ዓመት በላይ ውሉን ሣይፈፀም የሚቆይበት አጋጣሚ ያለ ሲሆን በዚህ ጉዳይም ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት ለመፈፀም የተለያየ ፕሮሰስ እየፈፀመ መሆኑን ለአመልካቾች በመግለጽ አመልካቾች ክስ ከማቅረብ እንደዘገዩ ያደረጋቸው መሆኑን በማንሣት አመልካቾች ተከራክረዋል። ስለዚህ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ይርጋ ተፈፃሚነት የሚኖረው ገዥ ለሻጭ ማስጠንቀቂያ የሰጠበትን ቀን መነሻ በማድረግና ጊዜውን በማስላት ሣይሆን ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ገዥ እንዲያውቀው ያደረገበትን ቀን መነሻ በማድረግ መሆን ይገባዋል። ከዚህ አንፃር ስናየው የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች በውሉ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ የሰጡበትን ቀን መነሻ ጊዜውን አስልቶ የአመልካቾች ክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. በሁለተኛ ደረጃ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው በሻጭና በገዥ መካከል የተደረገው ውል የማይፈፀምበት የመጨረሻ ቀን በጥብቅ የተወሰነ ከሆነ በውሉ የተወሰነው ነው የጊዜ ገደብ ካለፈ ከአንድ ዓመት በኋላ ገዥ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ማቅረቡን በማስረዳት እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875 መሠረታዊ መርህና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2331 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ጋር አጣምሮ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም አንፃር ስናየው በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል፤ ውሉ የሚፈፀምበትን ጭብጥ የጊዜ ገደብ የማያስቀምጥ በመሆኑ በጉዳዩ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2331 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

3. በሶስተኛ ደረጃ የሚነሣው ጥያቄ በዚህ ጉዳይ ተጠቃሽና ተፈፃሚ መሆን ያለበት የይርጋ ሕግ ድንጋጌ የትኛው ነው? የሚለው ነው፡፡ ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ለገዥ በማያሻማ ሁኔታ ያሣወቀ መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ ወይም የሸያጭ ውሉ ውሉ የሚፈፀምበትን ጥብቅ የጊዜ ገደብ ባልተገለፀበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው የአንድ ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ በልዩ የሕግ ድንጋጌ የተቀመጠዉ የይርጋ ጊዜ ገደብ ተፈፃሚነት በማይኖረው ጊዜ ወይም በልዩ ሁኔታ የተደነገገ የይርጋ የጊዜ ገደብ ከሌለ ውል ይፈፀምልኝ በሚል መነሻ የሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ሕግ ድንጋጌ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 እንደሆነ የዚህን ድንጋጌ ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካቾች ውሉን ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ካሣወቀችው ከአንድ ዓመት በኋላ ክሱን ያቀረቡ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ ስለሆነም በዚህ ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ 3 ተፈፃሚነት የለውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥናቸውን ምክንያቶችና የሕግ ድንጋጌዎች ሣያገናዝቡ የአመልካቾች ጥያቄ በአንድ ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2. አመልካች ያቀረቡት የውል ይፈፀምልኝ ክስ በይርጋ የማይታገድ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ ሌሎች ተከራካሪዎች የሚያቀርቡትን ክርክር በመመርመርና በመመዘን ጉዳዩን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሰን ልከንለታል፡፡

3. የአመልካቾች ክስ በይርጋ አይታገድም ብለናል፡፡

4. በሥር ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መጋቢት 3 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

□ሸ/መ/ቁዓ ር 36756

መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

□□ሰ □ር□

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

□ሊ. መሐመ□

አመልካች፡- አቶ ፀጋዬ ምትኩ- ጠበቃ መኮንን አምቦ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1/ ወ/ሮ አበበች ምትኩ - ጠበቃ አረጋ ይ□□ሹ ቀርበ□ል፡፡

2/ አቶ ፈለቀ አላጋው - ጠበቃ አረጋ ይታገሱ ቀርበ□ል፡፡

ጉዳዩ ከተመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

□ ር □

ጉዳዩ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 18885 ህዳር 22 ቀን 1998 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 44695 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ከሣሽ፣ የአሁኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች በመሆን የተከራከሩ ሲሆን፣ ስር ከሣሹ ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የተሻሻለ ክስ አጭር ይዘቱ ተከሣሾች በየካ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 16 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 740 የሆነውን ቤታቸውን የካቲት 02 ቀን 1980 ዓ.ም በተጻፈ የሽያጭ ውል በብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) ሸጠውልኝ ቤቱንና ከቤቱ ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶች በወቅቱ አስረክበውኝ በቁጥጥሬ ስር ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ቤቱ ገና ካርታ ያልወጣለት ስለነበር ካርታ በወቅቱ ሊያስረክቡኝ አልቻሉም ነበር፡፡ አሁን ግን ካርታውን አውጥተው እንዲያስረክቡኝ ወይም ደግሞ ፍርድ ቤቱ የገዛሁትን ቤት በስሜ እንዲዛወርልኝ (በከሣሽ ስም እንዲመዘገብ) የሚያደርግ ውሣኔ ይሰጠኝ የሚል ነው፡፡

ተከሣሾችም ጥቅምት 18 ቀን 1997 ዓ.ም በተጻፈ መልሳቸው ከሣሽ ያቀረቡት የውል ይፈጸምልኝ ጥያቄ ውሉ ተፈጸመ ካሉበት ጊዜ ወዲህ ሲታሰብ ከ16 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ በመሆኑ ክሳቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት በ□ር□ □ሚታገድ ነው፡፡ የሽያጭ ውሉም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት የተፈጸመ ባለመሆኑ፡፡ እንዲሁም እኛ መሐይማን በመሆናችን ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1728/3/ መሠረት ውድቅ ነው ሊባልልን ይገባል ብለ□ል፡፡

□ሥር □/ቤቱም □□ራ ቀኙን ወገኖች ክርክር ከላይ በሰፈረው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ ህዳር 22 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ብይን ወደ ሌሎች መከራከሪያ ነጥቦች ሳይገባ የቀረበው ክስ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበው ጊዜ ያለው ሲሰላ ከ10 አመት በላይ በመሆኑ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 245/2/ መሠረት ዘግቶ□ል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በመ/ቁ/ 44695 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት አፅንቶታል፡፡

ከላይ የሰፈረው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ቤቱ ውሉ ከተፈጸመበት ጊዜ □ምሮ በ□□ □□ለ □ሱ በ□ር□ □ታገዳል ሊባል አይገባም፡፡ ተጠሪዎቹ የቤቱን ካርታ ያወጡት በ1996 ዓ.ም መጨረሻ በመሆኑና እስከዚያ ድረስ ግን ከተጠሪዎች አቅም ውጭ በሆነ ሁኔታ መንግሥት ካርታ እንዳይዘጋጅለት አግዶት የነበር ስለሆነ አመልካች ተጠሪዎቹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካርታ ያስረክቡኝ ብዬ ክስ ልመሰርት አልችልም ነበር። ስለዚህ ይርጋው የሚታሰበው ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ መሆን ሲገባው የቤቱ ሽያጭ ውል ከተፈራረምንበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ መሰላቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው። ይርጋው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1846 መሠረት መሰላት ያለበት ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ጊዜ ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ነው በማለት መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታቸው ገልጸዋል።

መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎትም በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል የቃል ክርክር የተካሄደ ሲሆን አመልካች በአቤቱታቸው ከገለጹት ሃሣብ ውጭ የሆነ ክርክር አላቀረቡም። ተከሣሾቹ በሰጡት መልስ ደግሞ ቤቱን አልሸጥንም፣ ተያያዥ ሰነዶችም አላስረከብንም፣ አለኝ በማለት ያቀረቡት ውል በሐሰት የተዘጋጀ ነው። ክሱ የቀረበው ከ16 □መታት በኋላ የካቲት 30 ቀን 1996 ዓ.ም በመሆኑና ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም የተሻሻለ ክስ በመቅረቡ ውሉ ተደረ□ ከተባለበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ ሲታሰብ በይርጋ ይታገዳል። አመልካች የቤቱ ካርታ በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ነው □ተ□□□· ማለታቸው የይርጋ መቆጠሪያውን ጊዜ ወደኋላ ሊመልስ የሚችል ምክንያት አይደለም። አመልካች የአንደኛ ተጠሪ ወንድም በመሆናቸውና የቤት ችግር የነበረባቸው በመሆኑ በጥገኝነት እንዲኖሩበት የሰጠናቸው እንጂ አልሸጥንላቸውም። ውሉ የመንደር ውል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 መሠረት የማይፀናና ረቂቅ ነው ብለዋል።

□ር□ ቤቱም □□ራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ ባሰፈረው መልኩ በመገንዘብ ክርክሩ በ□ር□ ሊ□□□ ይገባዋል ወይስ አይገባውም ? የሚል መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ባቀረቡት ክርክር የቤቱ ሽያጭ ውል የተደረገው የካቲት 2 ቀን 198ወ ዓ.ም ሆኖ ቤቱንና ከቤቱ ካርታ ውጭ ያሉ የቤቱ ሰነዶች ወዲያው ተረክበው እስካሁን ድረስ እየኖሩበት እንደሆነና ተጠሪዎችም ካርታ በወቅቱ ያልሰጧቸው በሚመለከተው አካል ካርታ እንዳይሰራለት ታግዶ ስለነበር እና በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ግን ካርታ ተዘጋጅቶ ለተጠሪዎች እንደተሰጣቸው ወዲያውኑ ይህ ክስ እንደመሰረቱባቸው እኛም በ□ር□□· □□ መታሰብ ያለበት ከ1996 ዓ.ም መ□ ረሻ □ምሮ እንጂ ውሉ ከተደረገበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ አይደለም የሚል ሲሆን ተጠሪዎቹ ባቀረቡት ክርክር ደግሞ የቤቱ ካርታ በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ተሰጣቸው የሚለውን የአመልካች መከራከሪያ ነጥብ ሳይክዱ የይርጋ ጊዜው መሰላት ያለበት ውሉ ተደረገ ከተባለበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 01845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል የሚል የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተገቢ እንደሆነ የሚገልጽ ነው። የሥር ፍ/ቤቶችም በሌሎች መከራከሪያ ነጥቦች ውሣኔ ሳይሰጡ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ ከ10 ዓመታት በላይ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በሚል ለ□□ዩ መቋጫ ያደረጉ መሆኑ መዝገቡ ያሳያል። ይሁን እንጂ ቤቱ ካርታ እንዳይዘጋጅለት በሚመለከተው አካል ታግዶ እስከ 1996 ዓ.ም መቆየቱ እና በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ግን ካርታ ተዘጋጅቶ ለተጠሪዎቹ እንደተሰጣቸው ግራ ቀኙ ወገኖች የሚተማመኑበት ነጥብ ነው። ይህ በሆነበት ሁኔታ ደግሞ አመልካቹ ተጠሪዎቹን የቤቱን ካርታ ስጡኝ ወይም በስሜ አዘጋጅልኝ ብለው ሊከሱ የሚችሉበት የበሰለ መብት ያለመኖሩ □ሳ□ል። □□/ብ/

ሕ/ቁዓ ር 1846 እንደደነገገ□ም □□ር□ □□ መቆ□ር □ሚ□ምረ□· □ጻ ታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነ ጊዜ ጀምሮ ነው ይላል። አመልካቹ ለተጠሪዎቹ የቤቱን ካርታ በሚመለከተው አካል ከመሰጠቱ ከ1996 ዓ.ም በፊት ቢከሱ ኖሮ ሊፈጸም የማይችል መብት ይሆን እንደነበር ከክርክሩ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶቹ በዚህ ጉዳይ ይርጋው መቆጠር ያለበት ውሉ ከተደረገበት ከየካቲት 02/1980 ዓ.ም □ምሮ

መሆን አለበት የሚል ትርጉም በመያዝ ክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል።

□ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በመ/ቁ/ 18885 ህዳር 22

ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው □ር□ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.

44695 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348

/1/ መሠረት ተሽረዋል። ይጻፍ።

2/ በዚህ ክርክር ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው የቤቱ ሽያጭ ውል ከተደረገበት

ከየካቲት 02/1980 ዓ.ም ሳይሆን የሚመለከተው አካል የቤቱን ካርታ በተጠሪዎቹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስም አዘጋጅቶ ከሰጠበት ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ በመሆኑና አመልካችም በተ
ጠሪዎቹ ላይ ክስ የመሰረቱት የካቲት 30 ቀን 1996 ዓ.ም በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር
1845 መሠረት የይርጋው ጊዜ ያለፈበት አይደለም ብለናል፡፡

3/ ከይርጋ ክርክር ውጭ ባሉ ሌሎች መከራከሪያ ነጥቦች ጉዳዩን መርምሮ የመሰለውን
ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341 መሠረት ለፌዴራል የመጀመሪያ
ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት ተመልሶለ□ል፡፡ □□፡፡

4/ □ራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍርድ ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ
ብለናል፡፡

5/ ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41571

ሰኔ 02 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ማህደር አእምሮ - ጠ/ይሁን ፀሐይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ላእከ ገ/መድህን- ጠ/ሙሉጌታ ገብሩ ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ አመልካች ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ) ተበድረው በተዋዋሉት ቀን ያልከፈሉዋቸው በመሆኑ ዋናውን ገንዘብ፣ወለድ እና የገደብ መቀጫ እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ ገንዘቡን መበደራቸውን አምነው ነገር ግን ጥር 14/1997 ዓ.ም መክፈላቸውንና በዋስትና ያስያዙትን መቆፈሪያ ማሽንና ቼክ ተጠሪ ያስረከቧቸው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የገንዘብ ሰነድ ለባለእዳው መመለሱ እዳው እንደተከፈለ ያስቆጥራል፤ መቆፈሪያ ማሽኑም ገንዘቡ በመከፈሉ ተመልሷል በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር የማስረጃና የሕግ ድጋፍ አለው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጐታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የብድር መመለስን ማስረዳት የሚቻለው በፍ/ቤት በሚሰጥ የእምነት ቃለ መሐላ ወይም በጽሁፍ ብቻ ነው፤ አመልካች ደግሞ ብድሩ ስለመመለሱ ከነዚህ በአንዱም አላስረዱም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ አመልካች ዋናውን ገንዘብ ወለዱንና የገደብ መቀጫ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ በዚህ ውሣኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለተፈፀመ ይታረምልኝ በማለት የቀረበ ነው፡፡ የአመልካች ዋነኛ ቅሬታም ለብድሩ በዋስትና የተያዘው ቼክ እና የመቆፈሪያ ማሽን መመለሱ የብድሩ ገንዘብ መመለሱን ያረጋግጣሉ፤ የስር ፍ/ቤቱ ውሣኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2020 እና 2845 “ን” ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ጋር መርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ለብድሩ በዋስትና የተሰጡት ቼክና መቆፈሪያ ማሽን ለተበዳሪው መመለሳቸው ብድሩ ስለመከፈሉ ያረጋግጣሉ ወይ? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ለአመልካች ብር 120,000(መቶ ሃያ ሺህ) ያበደሯቸው እና ገንዘቡን ግን አመልካች ያልከፈሉ መሆኑን በመግለጽ ክስ የመሰረቱ ሲሆን አመልካችም ብድሩን መውሰዳቸውን ሣይክዱ ነገር ግን ገንዘቡን የከፈሉ መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች መበደራቸውን ያልካዱና ከፍያለሁ የሚሉ ስለሆነ ገንዘቡ ስለመከፈሉ በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ አመልካች ብድሩን ለመክፈላቸው ያቀረቡት ቀጥተኛ ማስረጃ የለም፡፡ የሚከራከሩት ለብድሩ በዋስትና ያስያዙት ቼክና መቆፈሪያ ማሽን ለእርሣቸው መመለሱ ብድሩ እንደተከፈለ የሚያስቆጥረው ነው በማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ቼኩና ማሽኑ ለባለእዳው መመለሱ ገንዘቡ እንደተከፈለ የሕሊና ግምት እንዲወሰድላቸው ነው የሚጠይቁት፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው ከ500 ብር በላይ የሆነን የብድር ውል እንዲሁም ይህንኑ የገንዘብ መጠን የመመለስ ነገር ማስረዳት የሚቻለው በጽሁፍ ወይም ፍ/ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም በቃለ መሐላ ብቻ ነው በማለት ነው፡፡

በእርግጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2472 ስር ይኸው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተገለፀው ነገር ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ ሁኔታዎች ሕጉ አንድ ፍሬ ነገር ከተረጋገጠ ማስረጃ ያልቀረበበት ሌላ አዲስ ነገር እንደተረጋገጠ ግምት እንዲወሰድበት የሚያዝበት አጋጣሚ አለ፡፡ በመሆኑም በህሊና ግምት መርህ (principle) የግምቱ ተጠቃሚ የሆነው ተከራካሪ ወገን የመጀመሪያውን ፍሬ ነገር ካረጋገጠ ሌላኛውን ፍሬ ነገር ለማረጋገጥ ማስረጃ ማቅረብ ሣያስፈልግ ፍ/ቤቱ ይኸው አዲስ ነገር እንደተረጋገጠ ግምት ሊወስድ ይገባል ማለት ነው፡፡ ከነዚህ የሕሊና ግምት ሊወሰድባቸው እንደሚገባ ሕጉ ከሚያስቀምጣቸው አንዱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2020 ስር የተመለከተው ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ሰነድ ለባለእዳው መመለሱ እዳው እንደተከፈለ የሚያስቆጥር መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ባለገንዘቡ እዳውን የሚያረጋግጥ ሰነድ እዳው ካልተከፈለው በቀር ለባለእዳው አይመልስም ተብሎ ስለሚገመት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለወሰዱት ብድር ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ) የያዘ ቼክ መስጠታቸው አላከራከረም፡፡ በተጨማሪም ይህንኑ ለዋስትና የተሰጠውን ቼክ ተጠሪ ለአመልካች የመለሱላቸው መሆኑን በስር ፍ/ቤት በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ቼኩ ለተጠሪው የተሰጠው እዳ መኖሩን በማረጋገጥ ለእዳው አከፋፈል ዋስትና እንዲሆን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እዳ ካልተከፈላቸው ቼኩን ባንክ ወስደው በመመንዘር ለእዳው መክፈያ ከማዋል ሩጉታ እዳው ሣይከፈላቸው ለአመልካች የሚመልሱበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ቼኩን ለተጠሪ ከመለሱ ደግሞ እዳው እንደተከፈለ እንደሚቆጠር ሕጉ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ለአመልካች ቼኩ መመለሱ የብድሩ ገንዘብ እንደተከፈለ የሕሊና ግምት ሊወሰድበት የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለብድሩ በመያዣ የሰጡት የመቆፈሪያ ማሽንም ቢሆን ለአመልካች መመለሱ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ በእርግጥ በክርክሩ ሂደት ማሽኑ በባንክ በመያዣ መያዙን ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን በባንክ በመያዣ መያዙ ብቻ ሣይሆን ተጠሪ በፈቃዳቸው ማሽኑን ለአመልካች መመለሣቸው በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጧል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2846 መያዣ የተቀበለ ባለገንዘብ ሊከፈለው የሚገባው በሙሉ እስኪከፈለው ድረስ የመያዣውን እቃ በእጁ የማቆየት መብት ያለው መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ ሊከፈላቸው የሚገባው እዳ በሙሉ ተከፍሎ ካላለቀ መያዣውን ለአመልካች የሚመልሱበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ለእዳው አከፋፈል በመያዣ የተሰጣቸውን ንብረት ዕዳው ሳይከፈላቸው ለባለዕዳው ይመልሣሉ ብሎ መገመትም ያስቸግራል፡፡ በተቃራኒው መያዣውን የተቀበለ ባለገንዘብ ለእቃ አስያዥ ዕቃውን የሚመልሰው ገንዘቡ ሲከፈለው ወይም በሌላ ምክንያት የመያዣው ውል ሲያልቅ መሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2845/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ተጠሪም በዋስትና የያዙትን ማሽን ለባለገንዘቡ መመለሣቸው አመልካች ያለባቸውን ገንዘብ በመክፈላቸው መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተመለከቱትን የሕጉን ድንጋጌዎች ሣያገናዝብ ብድሩ ስለመከፈሉ በጽሁፍ ወይም በፍ/ቤት በተሰጠ እምነት ቃል ወይም በቃለ-መሐላ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የብድሩን ገንዘብ ከወለድና መቀጫ ጋር ይክፈሉ በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58565 በ06/09/2000 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39461 በ04/02/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 30571 በ20/10/99 የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች ክስ የቀረበበትን የብድር ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መቁ. 39336

ሐምሌ 07 ቀን 2001

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መስፍ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ - ጠ/ ተካ አስፋው ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አዱኛ እጅጉ - ጠ/ መኮንን ሽፈራው ቀረቡ

2. ጤናዬ ገለታ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በክሣቸውም ንብረታቸው የሆነ ህንፃ በረቂቅ የሽያጭ ውል መሠረት አመልካች ስለያዘው እንዲያስረክባቸው እና አላግባብ ለተጠቀመበትም ኪራይ እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ውሉ በውልና ምዝገባ ጽ/ቤት ያልተደረገው በተጠሪዎች ክፉ ልቦና መሆኑን፣ ንብረቱን ፈቅደው ለአመልካች ማስረከባቸው ውሉም ረቂቅ ሣይሆን ያለቀ መሆኑን ኪራይም ሊከፈላቸው እንደማይገባ ተከራክሯል፡፡ በበኩሉም ቤቱን ገዝቶ የያዘው በመሆኑ ስም እንዲይዛወርለት ይህ ካልሆነ ለህንፃው መግዣ የከፈለው ብር 6,500,000 (ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) እንዲመለስለት የተከሣሽ ክሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የሺያጭ ውሉ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው አካል ወይም በዳኛ ፊት ባለመደረጉ በህግ ፊት አይፀናም በማለት ውሉ ፈርሶ አመልካች ህንፃውን ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡና ተጠሪዎች የተቀበሉት ብር

6, 500,000 ለአመልካች እንዲመልሱ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሠኘት ለፊ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታም ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች አንፃር ተመልክቶታል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የተጠሪዎች ክስ የመሠረቱት አመልካች በረቂቅ የሺያጭ ውል የያዘውን ህንፃ ያስረክበን በሚል ነው ከተጠሪዎች ክስም ሆነ ከክርክሩ ሂደት በአመልካችና በተጠሪ መሐከል የህንፃ ሽያጭ ውል የተደረገ መሆኑ፣ በዚህ ውል መሠረት ተጠሪዎች ህንፃውን ለአመልካች ማስረከባቸውና የሺያጩ ገንዘብ ብር 6,500,000 መቀበላቸው አከራካሪ ያልሆኑ ነገሮች ናቸው፤ ተጠሪዎች ለመክሰስ ምክንያት የሆናቸው ይህ የሺያጭ ውል ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው አካል ወይም በዳኛ ፊት ያልተደረገ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት ይህ የሺያጭ ውል ፈርሶ አመልካች ህንፃውን ለጠሪዎች ሊያስረክብና ተጠሪዎችም የሺያጩን ገንዘብ ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል ወይ? የሚለውን ጭብጥ መስርቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነው ግራ ቀኙ የህንፃ የሺያጭ ውል ማድረጋቸውን እንዳልተካካዱ ሁሉ ውሉ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው አካል ወይም በፍ/ቤት ያልተደረገ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረትን የባለቤትነት መብት ለማስተላለፍ የሚደረግ ውል ሁሉ በውሁፍና በሚገባ አኳኋን በፍ/ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው ሰው ፊት መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ህ/ቁ 1723(1) ያመለክታል፡፡ ይህን የአፃፃፍ ሥርዓት መከተል ውሉ በህግ ፊት የፀና እንዲሆን ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች አንደኛው ነው፡፡ ስለሆነም በህግ ፊት ውጤት እንዲኖረው የማይንቀሣቀስ ንብረት ሺያጭ በህጉ የተመለከተውን የአፃፃፍ ሥርዓት ሊከተል ይገባል፡፡ ይህን ስርዓት ካልተከተለ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1808(2) ተገልጿል፡፡ ውሉ በህግ የተመለከተውን የአፃፃፍ ሥርዓት ካልጠበቀ ከተዋዋዩቹ አንዱ ወይም ማንኛውም ጥቅም ያለው ሰው ውሉ እንዲሠረዝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት ውሉ እንዲፈርስ ሊወሰን ይችላል፡፡ የውሉም መፍረስ ውጤቱ በተቻለ መጠን ውለታ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማድረግ ነው፡፡ (በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1815(1)) ተዋዋዩቹ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲወሰን ውለታውን ለመፈፀም የተሠራ ሥራ ሁሉ ቀሪ እና ውጤት የሌለው እንደሚሆን የተጠቀሰው አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 2 ይገልፃል፡፡

በመርህ ደረጃ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ጉድለቶች ሲያጋጥሙ ውሉ ፈርሶ ተዋዋዮች ወደነበሩበት ቦታ የሚመለሱ ቢሆንም የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1817 ጉድለት ኖሮም ቢሆን ውሉ የሚረጋበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይኸው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1817(1) “ውለታውን ለመፈፀም የተሰራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆን ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ሊገኝ ወይም ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ ሲሆን እነዚህ የተሰሩት ሥራዎች እንደረጉ እንዲቀሩ ይደረጋል” በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ትርጉም “Acts done in performance of the contract shall not be invalidated where such invalidation is not possible or would involve serious disadvantages or inconvenience” ይላል፡፡ ከሕጉ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ውለታውና (contract) ውሉን ለመፈፀም የተሰሩ ስራዎች (acts) የሚለያዩ መሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም ውሉ በራሱ በአንድ በኩል፣ ውሉን ለመፈፀም የተከናወኑ ተግባራትን በሌላ በኩል ለይቶ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ተዋዋዮች በፈቃድ ጉድለት፣ በችሎታ ማጣት ወይም በህግ የተመለከተውን የአፃፃፍ ሥርዓት ባለመከተል የውል ስምምነት አድርገው ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንንም ጉድለት ያለበትን ውል ለመፈፀም የተለያዩ ተግባራትን ፈፅመውም ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ውሉ የማይፀናበትን ምክንያት በመግለፅ ውል እንዲፈርስ ሲጠየቅ ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሊመለሱ የሚገባ ቢሆንም ይህ ጉድለት ያለበትን ውል ለመፈፀም የተከናወኑትን ተግባራት (acts) ማፍረስ ፈፀሞ የማይቻል ወይም ከፍ ያለ መሰናክል ወይም አስቸጋሪ የሚሆንበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ዳኞች ሊወስኑ የሚገባው ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ማይሆን የተሰሩት ሥራዎች እንደረጉ እንዲቆዩ ነው፡፡ ምናልባት ወደነበሩበት መመለስ ባለመቻሉ የደረሰ ጉዳት ካለ ጉዳቱን በካሣ መልክ ወይም ፍ/ቤቱ ተገቢ ነው የሚለውን መፍትሔ በመስጠት ሊስተካከል ይችላል (የፍ/ብ/ህ/ቁ/1817(2))፡፡ በመሆኑም ውሉ የሚፈርስበት ወይም የሚሠረዝበት ምክንያት ሲከሰት ውሉ ፈርሶ ግራቀኙ ወደነበሩበት የመመለስ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባው ውሉን ለመፈፀም የተሠራው ሥራ ቀሪ ለማድረግ የሚቻል ከሆነ ብቻ ነው፡፡

በዚህ መሠረት የቀረበልንን ጉዳይ ተመልክተናል፡፡ አመልካች በ1994 ዓ.ም 6,500,000(ስድስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን) ሚሊዮን ብር በመክፈል ከመልስ ሰጪ ሕንፃ መረከቡ ተረጋግጦአል፡፡ ህንፃውን ከተረከቡ በኋላ የኢንሹራንስ ሥራ ለማካሄድ እንዲያስችለው ህንፃው ላይ የተለየዩ ማስተካከያዎች የተደረጉበት ስለመሆኑም ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በሰበር ችሎት ባለጉዳዮች የቃል ክርክር ባደረጉበት ወቅት አመልካች ለመኪና ማቆምያ አገልግሎት የሚውል ሌላ ተጨማሪ ቦታ ገዝቶ የጨመረበት መሆኑንም ለማወቅ ችለናል፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ ችሎት በሙሉ አመሰራረት ሂደት የነበረውን ጉድለት መሠረት በማድረግ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ማድረግ ተገቢ መሆን አለመሆኑን አገናዝቧል፡፡ አሁን በቀረበልን ጉዳይ ተዋዋይ ወገኖችን ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ ማለት አመልካች የከፈለውን ብር 6,500,000(ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) እንዲቀበል በማድረግ መልስ ሰጪዎች ደግሞ ቤቱን እንዲረከቡ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ክፍያውን የመፈፀምም ሆነ ቤቱን የመረከብ ሥራ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1815(2) መሠረት ውለታው ለመፈፀም የተሰሩ ሥራዎች (acts) በመሆናቸው በመርህ ደረጃ ውሉ ሲፈርስ አብረው ዋጋ የሚያጡ ናቸው፡፡ ሆኖም አሁን በቀረበልን ጉዳይ እነዚህን ሥራዎች (acts) ዋጋ እንዲያጡ ማድረግ አስቸጋሪና ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ ሆኖ (involving serious disadvantage and inconvenience) አግኝተነዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በዚህ ችሎት ፅምነት የሺያጭ ዋጋውን በመመለስና ቤቱን በመረከብ ተዋዋዮቹን ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የሚቻል አይደለም፡፡ ገንዘቡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተከፈለበት ከ1994 ዓ.ም ወዲህ በመንግስትም ዕውቅና ያገኘ የገንዘብ ግሽበት (inflation) ያለ በመሆኑ የተከፈለው ገንዘብ አሁን ከሚመለሰው ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ ነው ሊባል አይችልም፡፡ በሌላ በኩል የሚመለሰው ቤት ደግሞ በአንባራዊነት የዋጋ ጭማሪ እንደሚያሳይ ይገመታል፡፡ ይህ ግምት እንኳን ቢታለፍ ቤቱን ገዝቻለሁ በሚል ዕምነት አመልካች በህንፃው ላይ ለያዘው ንግድ የሚመች ለማድረግ የተለያዩ ወጪዎችን አውጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አሁን ያለው ህንፃ መጀመሪያ ከተረከበው ህንፃ ጋር አንድ ዓይነት ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዋጋ ግሽበት ምክንያት የሚረከበው ገንዘብ እሴት (value) በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ከሚያስረክበው ህንፃ ዋጋ በተለያዩ ምክንያቶች መጨመር ጋር ተዳምሮ ወደነበሩበት የመመለሱ ሥራ ለመልስ ሰጪ ያልተገባ ጥቅም የሚሰጥና አመልካችን የሚጎዳ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ኩባንያ ህንፃውን ለንግድ የሚጠቀምበት መሆኑ ህንፃው ከሚገኝበት ቦታ ጋር የተያያዘ መልካም ስም (good will) እንዲያጣ ስለሚያደርገው የጉዳቱም መጠን በዚያው መጠን መጨመሩ የሚቀር አይሆንም፡፡ በክርክሩ ሂደት አመልካች ቤቱን ገዝቻለሁ በሚል ዕምነት ተጨማሪ ለመኪኖች የሚሆን ቦታ ገዝቶ እየተጠቀሙበት መሆኑ ሲታከልበት ደግሞ ወደነበሩበት የመመለስ (reinstatement) አማራጭ በፍትሃብሔር ሕጉ አንቀፅ 1817 እንደተገለፀው ከሞላ ጎደል የማይቻል ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ግራ ቀኙ ያላቸው የሽያጭ ውል በረቂቅ ደረጃ ያለ ነው የሚለው የመልስ ሰጪ ክርክርም ሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ድምዳሜ በመሠረቱ ትክክል ቢሆንም በዚህ ረቂቅ ውል መነሻነት የተፈፀሙ ሌሎች ድርጊቶችን ወደኋላ ተመልሶ እንዳልነበሩ መቁጠር ግን ከላይ በዘረዘርነው ምክንያት ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ፍርድ ቤቶች ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ይመለሱ ብለው ከመፍረዳቸው በፊት በሕጉ እንደሰፈረው የውሉ መፍረስ ወይም መሰረዝ ብቻ ሳይሆኑ ከዚህ ጋር ተያይዘው የተፈፀሙ ሌሎች ሥራዎች (acts) እንዳልተሰሩ የመቁጠር ውጤት ሊመዘኑ ይገባል አሁን በያዝነው ጉዳይ ክሱ የቀረበለት ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤት ክርክርሩን ከዚህ አቅጣጫ ተመልከተው አግባብነት ያለውን የሕግ ድንጋጌ ተፈፃሚ አላደረጉም፡፡ ስለዚህ በግራ ቀኙ የተከናወኑትን ድርጊቶች ከግምት ሣያስገቡ የሥር ፍ/ቤቶች የሽያጭ ውሉ የአፃፃፍ ሥርዓትን ባለመከተሉ ብቻ ውሉ ፈራሽ ሆኖ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ይመለስ በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 56347 በ21/6/2000 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 36804 በ3/11/2000 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. የሽያጭ ውሉ የአፃፃፍ ሥርዓትን ያልተከተለ ቢሆንም ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ማድረጉ አስቸጋሪና ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ በመሆኑ ውሉ ባለበት ሁኔታ እንዲቆይ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1817(1) መሠረት ወስነናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39170

ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ባይሳ ሸኔ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ክንዴ አፍራሶ - ጠበቃ ዳኛቸው ተስፋዬ ቀረቡ

2. አቶ ጅብሪል ኢማም - ጠበቃ ዘውገ ተስፋዬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን የክርክሩም አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ አንደኛ ተጠሪ ለንግድ ስራ ማከናወኛ ብር 421,612.80 (አራት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ስድስት መቶ አስራ ሁለት ብር ከሰማንያ ሣንቲም) በ24/4/83 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል ከአመልካች ላይ ተበድረው ገንዘቡን በውሉ መሰረት ያልከፈሉ ስለሆነ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በ19/11/96 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ተከሳሹ ለከሳሽ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም አመልካች የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ አቅርቦ ንብረትነቱ የፍርድ ባለእዳው የሆነውንና በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ አጠራር በወረዳ 7 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘው የቤት 020 የሆነው ቤት በሐራጅ ተሸጦ እዳው እንዲከፈል ጠይቆ አፈጻጸሙን የያዘው የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት በፍርድ አፈጻጸም መምሪያ በኩል አፈጻጸም የተጠየቀበት ይሄው ቤት በሐራጅ እንዲሸጥና ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ ሰጥቶ በዚሁ መሰረት የፍርድ አፈጻጸም መምሪያ ቤቱን ለመሸጥ ሲንቀሳቀስ የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ እንዲሸጥ የተባለው ቤት የፍርድ ባለእዳው ሳይሆን የእኔ ንብረት ስለሆነ አፈጻጸሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል ስለማይችል በዚህ ረገድ የተሰጠው ትእዛዝ ይነሳልን በማለት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም ቤቱ በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተውን አካል ጠይቆ በአመልካቹ ስም በአሁን ሁለተኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ ስለመሆኑ ሲገለጽለት በፍርድ አፈጻጸም እንዲሸጥ ትእዛዝ የተሰጠበት ቤት የፍርድ ባለእዳ ሳይሆን የአመልካች መሆኑ ስለተረጋገጠ አፈጻጸሙ ይቁም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የፍርድ ባለመብቱ የአሁን አመልካች በዚሁ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን የአመልካችም የቅሬታ ነጥብ ተጠቃሎ ሲታይ አመልካች የብድሩ ገንዘብ እንዲከፈለው በአንደኛ ተጠሪ ላይ ክሱን ካቀረበ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ይህንኑ የአፈጻጸም ክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ከ2ኛ ተጠሪ ባገኙት ውክልና መሰረት ለባለቤታቸው ለወይዘሮ ፀሐይ ጉልማ ገዝተው ስም እንዲዞርም ለሚመለከተው አካል አመልክተው ውሉ ከቤቱ ማኅደር ጋር ተያይዞ እንደሚገኝና እንዲታገድ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ፍ/ቤቱ አምኖበት ቤቱ ተከብሮ እንዲቆይ በ26/11/92 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቶ ይሄው ትእዛዝ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተላፍኗል፡፡ ፍ/ቤቱ ቤቱ እንዳይሸጥ እገዳ ከሰጠ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041 መሰረት በፍርድ የተገኘ የመያዣ መብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(judicial mortgage) እንደተቋቋመና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሰረትም እንደተመዘገበ ማረጋገጥ የሚቻል በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ክርክሩን ከእነዚህ ድንጋጌዎች አኳያ በመመልከት ሁለተኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት እንደሌላቸው ማረጋገጥ ሲገባቸው ቤቱ የሁለተኛ ተጠሪ ስለሆነ አፈጻጸሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ይህም ችሎት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ሁለተኛ ተጠሪ ይዜው ቤት እንዲሸጥ ውክልና ለአንደኛ ተጠሪ በሰጡበት ሁኔታ እንደዚሁም አንደኛ ተጠሪ ቤቱን ተረክበው እየኖሩ ባሉበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች ቤቱ ተመዝግቦ የሚገኘው በ2ኛ ተጠሪ ስም እንጂ በፍርድ ባለእዳው በአንደኛ ተጠሪ ስም ስላልሆነ አፈጻጸሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የተጠሪዎችም ክርክር ተጠቃሎ ሲታይ አንደኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተውን አካል ጠይቆ በሁለተኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ተረጋግጦለታል፡፡ ይህም ሁኔታ ቤቱ በ26/11/92 ዓ.ም በፍ/ቤት ተሰጥቷል የተባለውን እግድ የሚያፈርስና እግድ እንደሌለ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በአስተዳደር ክፍል የተሰጠ የባለሐብትነት የምስክር ወረቀት እስካልተሰረዘ ድረስ የባለሐብትነት ማረጋገጫ እንደሆነ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14554 የሕግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በተያዘውም ጉዳይ ካርታና ደብተሩ ተመዝግቦ የሚገኘው በሁለተኛ ተጠሪ ስም ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች አፈጻጸሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል አይገባም በማለት የሰጡት ትእዛዝ የሰበር ችሎቱ አስቀድሞ ከያዘው አቋም ጋር የተጣጣመ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ አመልካች በቤቱ ላይ በፍርድ የተገኘ የመያዣ መብት አግኝቻለሁ የሚለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041"ን" በመጥቀስ ነው፡፡ ሆኖም ቤቱ ቀድሞውንም ቢሆን በአንደኛ ተጠሪ ባለቤት በወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ ስም ተመዝግቦ ይታወቅ የነበረ ባለመሆኑ ቤቱ ታግዷል ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ በፍርድ የሚሰጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ የሚቋቋመው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3044 መሰረት ሲሆን ይህ የመያዣ መብትም የሚቋቋመው ፍ/ቤቶች በዳኝነት በሚሰጡት ፍርድ እንጂ በእግድ ሰበብ ሊቋቋም አይችልም፡፡

ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈጻጸሙ በሁለተኛ ተጠሪ ቤት ላይ ሊቀጥል አይችልም በማለት የሰጡት ትእዛዝ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የሰበር አቤቱታው ከኪሳራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪም በይዘቱ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ የሆነ መልስ አቅርበዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ዝርዝሩን መመዝገቡ ባለማስፈለጉ ታልፏል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች የጀመረው አፈጻጸም በወረዳ 7 ቀበሌ 17 ክልል ቁጥሩ 020 በሆነው ቤት ላይ ሊቀጥል ይገባል ወይንስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች በብድር የተወሰደ ገንዘብ እንዲከፈለው በክናፍ የቆዳ ውጤቶች አምራችና ላኪ ድርጅት እንደዚሁም በአሁን አንደኛ ተጠሪ በአቶ ክንዴ አፍራሶ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክሱን ካቀረበ በኋላ የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት በሆኑት በወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ ስም የተመዘገበው በወረዳ 7 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘው የቤ.ቁ. 020 የሆነው ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 154 መሰረት እንዲከበርለት አቤቱታ አቅርቦ ፍ/ቤቱም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የተጠቀሰው ቤት ጉዳዩ እልባት ከማግኘቱ በፊት ቢሸጥ ወይም ለሌላ ሦስተኛ ወገን ቢተላለፍ ከሳሽ ወደፊት በፍርዱ ተጠቃሚ ቢሆን ፍርዱን የሚያስፈጽምበት ንብረት በማጣት ሊተካ የማይችል ጉዳት ሊደርስበት እንደሚችል ያቀረበው ቃለመሐላ ተቀባይነት አለው በማለት በትእዛዙ ላይ ካሰፈረ በኋላ የተጠቀሰው ቤት በግለሰቧ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ከሆነ ተለዋጭ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በማናቸው ወገን ለሦስተኛ ወገን ሳይተላለፍ ተከብሮ ይቆይ በማለት ሐምሌ 26 ቀን 1992 ዓ.ም የእግድ ትእዛዝ መስጠቱን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ከዚህ በኋላም ቤቱን ከሁለተኛ ተጠሪ ገዝተዋል የተባሉት የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ በዚህ ቤት ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 154"ን" በሚጸረር ሁኔታ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 158 መሰረት እንዲነሳልኝና ስለመነሳቱም አስቀድሞ የእግዱ ትእዛዝ ተላልፎላቸው ለነበሩት አካላት ይተላለፍልኝ ሲሉ ጥር 18 ቀን 1993 ዓ.ም አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ የእግዱ ትእዛዝ የተሰጠው ቤቱ የክርክሩ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው ተብሎ ሳይሆን ለፍርድ ማስፈጸሚያነት በሚል ስለሆነ አስቀድሞ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሊነሳ አይገባም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው መቅረቱንም ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

በሌላ በኩልም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት አፈጻጸሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል አይገባም የሚል መቃወሚያ በሁለተኛ ተጠሪ አማካይነት ሲቀርብለት የቤቱ ባለቤት በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተው አካል እንዲያረጋግጥ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ባለሐብትነቱ በሁለተኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተው አካል የገለጹለት ቢሆንም ባለሃብትነት ከሕግ ወይም ከውል የሚመነጭ እንደመሆኑ መጠን በ6/4/84 ዓ.ም በተደረገ ውል የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ ይህንኑ ቤት ከሁለተኛ ተጠሪ የገዙ እንደመሆኑ መጠን ባለሐብትነታቸው በውል እንደተቋቋመ መገንዘብ ስለሚቻል የባለቤትነት ስሙ ወደ ገዢ ሳይዛወር በሻጭ ስም ተመዝግቦ መገኘቱ ይህ የሂደት ጉዳይ እንጂ የወሉን አመሰራረት ጥያቄ ውስጥ የሚከተው አይሆንም፡፡ ሐምሌ 26 ቀን 1992 ዓ.ም ፍ/ቤቱ የሰጠው የእግድ ትእዛዝም የሚመለከተው አካል ተቀብሎ ተግባራዊ ያደረገው በዚሁ የሽያጭ ውል መሰረት ቤቱ ከሁለተኛ ተጠሪ ወደ ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ መተላለፉን በማረጋገጡ ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ እግዱ እንዲነሳ ማመልከት ባላስፈለጋቸው ነበር፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041 ላይ እንደተደነገገው መያዣ ከውል ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ከሕግ ወይንም ደግሞ በፍርድ ሊቋቋም ይችላል፡፡ በዚህም ጉዳይ ፍ/ቤቱ በዚህ ቤት ላይ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3044 ላይ እንደተመለከተው ለአመልካች ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብትን (judicial mortgage) ያጐናጽፋል፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም በመ/ቁ. 25863 በሰጠው የሕግ ትርጉም በፍ/ቤት በንብረት ላይ የሚሰጥ የእግዳ ትእዛዝ ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ተቋቁሟል ለማለት እደሚያበቃ በመጥቀስ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ስለሆነም ተጠሪዎች የቤቱ ባለሐብት ሁለተኛ ተጠሪ ስለሆኑ በዚህ ንብረት ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተፈፃሚ አልሆነም በማለት ያነሱት ክርክር ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም የሽያጭ ውሉ በሕግ አግባብነት ያልተደረገ ስለሆነ የሽያጭ ውል አለ ለማለት አይቻልም በማለት ተጠሪዎች ያነሱትን ክርክር በተመለከተም ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ የሚያበቃ ውክልና መስጠታቸውን አልካዱም፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሸያጩን ውል ያደረጉት የሟሚውን ጥቅም በሚጐዳና የጥቅም ግጭት (conflict of interest) ባለበት ሁኔታ ነው ወይንም ደግሞ ውሉን ያደረጉት ከእራሳቸው ጋር ነው የሚሉ ከሆነ አግባብነት ያላቸውን የውክልና ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ ይገባቸው ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ መልኩ የውል ይፍረስልኝ ክስ ያላቀረቡ ሲሆን ይልቁንም በቤቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ ሲሰጥ እግዱ እንዲነሳ አቤቱታ ያቀረቡት ሁለተኛ ተጠሪ ሳይሆኑ ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ መሆናቸው ሲታይ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን በሽያጭ ማስተላለፋቸውን ይበልጥ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

የቤት ሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ ላይ እንደተመለከተው ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ውጤት የሌለው ነው በማለት ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክን በተመለከተ ይህ ጉዳይ በጭብጥነት ተይዞ ሊታይ ይችል የነበረው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808/2/ ላይ እንደተመለከተው በተዋዋይ ወገኖች ወይንም ጥቅም ባላቸው ሦስተኛ ወገኖች የውል ይፍረስልኝ ክስ በቀረበ ጊዜ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ መልኩ የቀረበ አቤቱታ ስለሌለ የሚስተናገድ አይሆንም፡፡

ሲጠቃለልም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ባለሐብትነቱ በሽያጭ ውሉ መሰረት የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት ለሆኑት ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ የተላለፈ ስለሆነና በዚህ የሽያጭ ውልም ላይ ተመስርቶ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3041 እና 3044 መሰረት ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ያለው ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች የቤቱ ባለሐብትነት በሁለተኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተው አካል ያረጋገጠ ስለሆነ አፈጻጸሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል አይችልም ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ የሽያጩን ውሉንም ሆነ ሕጉን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 45991 በ27/11/99 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌደራል ከ/ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 59710 በ9/8/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 7 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘውና ቁጥር 020 የሆነው ቤት ለአንደኛ ተጠሪ ባለቤት ለወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ በሽያጭ በመተላለፉ ምክንያት አመልካች በቤቱ ላይ ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ያቋቋመ ስለሆነ አፈጻጸሙ በዚሁ ቤት ላይ እንዲቀጥል ብለናል፡፡
3. አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ብር 1000(አንድ ሺህ ብር) በድምሩ ብር 2000(ሁለት ሺህ) ወጭና ኪሣራ ለአመልካች እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 39778

ሀምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሕብረት ባንክ(አ.ማ) - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቢሲኒያ ባንክ (አ.ማ) - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 55790 ታህሣሥ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35179 ሀምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆነው የጉለሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ተጠሪ አመልካች ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በአመልካችነት ቀርቦ ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የተባለ የንግድ ድርጅት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በሥር አመልካች ከሆነው ከአቢሲኒያ ባንክ ገንዘብ ተበድሯል፡፡ ተበዳሪው የንግድ ድርጅት ለወሰደው ብድር በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 8 ቀበሌ 05 የሚገኘውን ቁጥሩ 343 የሆነውን ቤትና ድርጅት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአንደኛ ደረጃ መያዣነት፣ ለአቢሲኒያ ባንክ በሁለተኛ ደረጃ መያዣነት አስይዟል፡፡ ሆኖም የአቢሲኒያ ባንክ በሁለተኛ ደረጃ በንብረቱ ላይ ያለውን የመያዣ መብትና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3081 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን በመፃረር የጉለሌ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ንብረቱ የህብረት ባንክ አንደኛ ደረጃ እንደሆነ በማድረግ የመዘገበ ስለሆነ ይኸ ምዝገባ ተሠርዞ ንብረቱ የአቢሲኒያ ባንክ አንደኛ ደረጃ መያዣ ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆነው የጉለሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት በተጠሪነት ቀርቦ ስማቸው ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የማይንቀሣቀሥ ንብረት የሕብረት ባንክ አንደኛ መያዣ መሆኑን የመዘገብኩት ሕብረት ባንክ የንግድ ድርጅቱ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወሰደውን ብድር በመክፈል የንብረቱን የባለቤትነት ሰነድ ከኢትዮጵያ ንግድ በመረከብና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን አስፈቅዶ በመቅረቡ ነው፡፡ ስለዚህ የመያዣ ቀዳሚነት አስመልክቶ ለቀረበው ክርክር ሕብረት ባንክ (አ.ማ) ጣልቃገብቶ እንዲከራከር በማለት አመልክቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሰበር አመልካች በጉዳዩ ጣልቃ ገብ ሆኖ በክርክሩ እንዲገባ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው መልስ በንብረቱ ላይ የመያዣ ቀዳሚነት አለኝ፡፡ ምክንያቱም በባለዕዳው ጠያቂነት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተበደሩትን ብድር በመክፈል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተይዘው የነበሩ ሰነዶች ተቀብያለሁ፡፡ ስለሆነም በንብረቱ ላይ የአንደኛ ደረጃ መያዣ መብት ባለው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተዳረኩ (የተተካሁ) በመሆኔ በንብረቱ ላይ አንደኛ ደረጃ መያዣ እንዳለኝ መመዝገቡ ትክክል ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ አመልካች በመሆን ያቀረበውን አቤቱታና ማስረጃ በሥር ተጠሪ የሆነው የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር እና አመልካች በጣልቃ ገብ ተከራካሪነት ያቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች በንብረቱ ላይ የአንደኛ ደረጃ መያዣ መብት ያለውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዕዳ በመክፈልና በማስፈቀድ በዳረጎት መብቱን ያረጋገጠ ስለሆነ በመያዣው ላይ የቀዳሚነት መብት አለው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካችን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለመዳረግ ቀድሞውንም በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት ያለው መሆን ይገባዋል፡፡ አመልካች ከዚህ በፊት በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት የሌለው በመሆኑ ባለዕዳው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለበትን ዕዳ የከፈለ ቢሆንም በመያዣው ላይ የቀዳሚነት መብት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 2 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ አመልካች ስማቸው ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ህዳር 6 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለበትን የብድር ዕዳ ብር 11862768.72 /አስራ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሣ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከሰባ ሁለት ሣንቲም/ በመክፈል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንድንተካ በጠየቀን መሠረት ክፍያውን በሲፒኦ ቁጥር 046293 ፈፅሟል ገንዘቡ ባለዕዳው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለበትን ዕዳ የተከፈለ መሆኑ በመያዣነያውን ንብረት ሰነድ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተረክቧል፡፡ አመልካች በመያዣው ላይ የቀዳሚነት መብት ያለውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዕዳ በመክፈል በመብቱ የተዳረገ ሆኖ እያለ በባለ ዕዳውና በአመልካች መካከል የተደረገው የብድር ውል ገንዘቡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ዕዳ ለመክፈል የሚውል ስለመሆኑ አይገልፅም በሚል ምክንያት ብቻ የመዳረግና በመያዣው ላይ ያለውን የቀዳሚነት መብት የላቸውም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፍትሐብሔር ሕጉ ስለመዳረግና ስለመተካት የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ለባለዕዳው ብድር የሰጠው ለሥራ ማስኬጃ ማከናወኛ እንጅ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዕዳ ለመክፈል አለመሆኑን በአመልካችና በተበዳሪው መካከል የተደረገው ውል ያሣያል፡፡ አመልካች የቆረጠው ሲፒኦ ገንዘቡ ለተበዳሪው እንጅ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባለዕውን ዕዳ የከፈለ መሆኑን የሚያሣይ ደረሰኝ አላቀረበም፡፡ አመልካች በባለዕዳው ፈቃድ ለመዳረግ የሚያስችሉ እነዚህን መስፈርቶች ባላሟላበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እግር ተዳርጌአለሁ በማለት የሚያቀርበው የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በንብረቱ ላይ አንዳችም የመያዣ መብት ሣይኖረው በንብረቱ ላይ ሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት ያለውን ተጠሪ በመቅደም በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት አለኝ እያለ የሚያቀርበው ክርክርም የህግ መሠረት የለውም፡፡ ስለሆነም ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የህግ ትርጉም ምንም አይነት ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካችን አቤቱታ በመሠረዝ እንዲያሰናብተኝ በማለት በፅሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለባለዕዳው የሚፈልገውን ዕዳ በሙሉ አጠቃልዬ የከፈልኩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሰጥቶኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባለዕዳውን ንብረት በቀዳሚነት በመያዣነት ሲይዝ የተረከባቸውን የንብረቱን ባለቤትነት የሚያረጋግጡ ሰነዶች ለእኛ አስረክቦናል፡፡ እኛም በንብረቶች ላይ አንደኛ የመያዣ መብት ባለው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመዳረግ መያዣውን አስመዝግበናል፡፡ ስለሆነም ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር እንዲታረምልን በማለት በፅሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመዳረግ የባለዕዳውን ንብረቶች በመጀመሪያ ደረጃ መያዣነት የመያዝ መብት አለው ወይስ የለውም? የሚለው የጉዳዩ መሠረታዊ ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ በአማርኛ ቋንቋ “መዳረግ” የምንለው እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ “subrogation” በመባል የሚገለፀው ፅንሰ ሀሳብ ትርጉም ይዘትና ውጤት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ መዳረግ ወይም በእንግሊዘኛ “subrogation” የሚለው ፅንሰ ሀሳብ “The substitution of one person in the place of another with reference to lawful claim, demand or right, so that he who is substituted succeeds to the rights of the

https://t.me/ethiopianlegalbrief

other in relation to debt or claim, and its rights, remedies, or securities" የሚል ትርጓሜ ያለው መሆኑን ለመረዳት እንችላለን፡፡ በአጭር አገላለፅ ዳርጎት ወይም subrogation "The right of one who has paid an obligation which another should have paid to be indemnified by another" የሚል ትርጉምና ይዘት ያለው መሆኑን ለፅንሰ ሀሳቡ በህግ መዝገበ ቃላት የተሰጠውን ትርጓሜ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር አበዳሪው ከባለዕዳው የሚጠይቀውን ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለ ሶስተኛ ወገን በከፈለው ዕዳ ልክ በዋናው አበዳሪ በመተካት አበዳሪው በባለዕዳው ላይ ያሉትን ልዩ መብቶች በዋስትናዎችና ሌሎች ተጨማሪ መብቶች ሊሠራባቸው የሚቻልበትን ሁኔታ "መዳረግ" በሚል መንገድ የሚገለፅ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድ ሶስተኛ ወገን አበዳሪው ከተበዳሪው የሚፈልገውን ዕዳ በመክፈል በአበዳሪው እግር የመዳረግ መብት የሚኖረው ዳረጎቱ በአበዳሪው የተፈቀደ ሲሆን ወይም በተበዳሪው የተፈቀደ ሲሆን ወይም በህግ የተፈቀደ ሲሆን እንደሆነ በዚህ ዙሪያ የተደረጉ የሥነ-ህግ ጥናቶች ይገልፃሉ፡፡ የመዳረግ መብት ምንጩና መሠረቱ የአበዳሪው ፈቃድ ወይም የተበዳሪው ፈቃድ ወይም ህግ ሊሆን እንደሚችል ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በአገራችንም የባለዕዳውን ዕዳ ለአበዳሪው የከፈለ ሶስተኛ ወገን በአበዳሪው መብት ለመዳረግ የሚቻልባቸው ሁኔታዎችና መዳረጉ ስለሚያስከትለው ውጤት ገዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1974 በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ የፍትሐብሔር ህጉ የባለዕዳውን ዕዳ ለአበዳሪው የከፈለ ሶስተኛ ወገን በአበዳሪው ፈቃድ ስለሚዳረግበት ሁኔታ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1968፣ በተበዳሪው ፈቃድ ስለሚዳረግበት ሁኔታ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1969 እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1970 በህግ መዳረግ የሚቻልበትን ሁኔታ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1971 በዝርዝር ደንግጓል፡፡ የተበዳሪው ዕዳ ለአበዳሪው የከፈለ ሶስተኛ ወገን በአበዳሪው መብት ለመተካትና ለመዳረግ የሚቻለው ከሶስቱ የዳረጎት አይነቶች አንደኛው የተሟላ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነና ሶስቱ የዳረጎት አይነቶች የሚጠይቁት መስፈርት የተለያየ መሆኑን ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካች ባለዕዳው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የነበረበትን ዕዳ እንድንከፍልለት በዕሑፍ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ባለዕዳም ስማቸው ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚፈለግበትን ብር 11862768.72 /አስራ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሣ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከሰባ ሁለት ሣንቲም/ በሲፒኦ የከፈለ መሆኑን ይህም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሰጠው ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን በማንሣት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባገኘው ፈቃድ መሠረት በመብቱ የተዳረገ መሆኑንና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመብቱ ለመዳረግ የሚያስችለውን በመያዣነት የያዛቸውን የባለዕዳውን ንብረቶች የባለቤትነት ሰነድ አሳልፎ በመስጠት በንብረቶቹ ላይ ያለውን የቀዳሚነት የመያዣ መብት እንዲሠራበት እንዳደረገው በመግለፅ የተከራከረ መሆኑን ለበታች ፍርድ ቤቶች እና በሰበር ከተደረገው ክርክር ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በባለዕዳው ንብረቶች ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት ባለው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምትክ የመዳረግ መብቴን አረጋግጫለሁ የሚለው በባለዕዳው በስማቸው ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ፈቃድና ስምምነት መሠረት ሣይሆን በአበዳሪው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፍቃድና ስምምነት መሠረት መሆኑን በመግለፅ በየደረጃው ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን የአመልካች ክርክር በጭብጥነት በመያዝ ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የመዳረግ መብቴ ምንጭ ነው ብሎ ያልጠቀሰውን በተበዳሪው ፈቃድና ስምምነት ስለመዳረግ ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1969 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1970 የተደነገጉት ሁኔታዎች አልተሟሉም በማለት ውሣኔ መስጠታቸውን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በአበዳሪው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድ የመዳረግ መብቴን አረጋግጫለሁ በማለት ያቀረበውን ክርክር በማለፍ አመልካች የመዳረግ መብቴ ምንጭና መሠረት ነው ብሎ ባልተከራከረበት በባለዕዳው ፈቃድ ስለመዳረግ የሚደነግጉትን የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1969 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1970 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መወሰናቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

2. አመልካች በንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት ላለው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባለዕዳውን ዕዳ በመክፈል በአበዳሪው ፈቃድ ተዳርጌአሁ የሚለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመብቱ እንድዳረግ ፈቅዶልኛል በማለት ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት መሠረት ተዳርጓል ወይስ አልተዳረገም? የሚለው ነጥብ በዝርዝር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቀራረፅና ይዘት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ “ባለገንዘቡ ስለሚሰጠው ዳረጎት” በሚል ርዕስ የተደነገገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 ንዑስ አንቀፅ 1 “ሶስተኛ ወገን የከፈለውን ገንዘብ ባለገንዘቡ የተቀበለ እንደሆነ በራሱ መብቶች ተደራጊ ሊያደርገው ይችላል” በማለት በአበዳሪው ፈቃድና ስምምነት የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለ ሶስተኛ ወገን ለመዳረግ የሚቻል መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ 2 “የዳረጎቱ ጉዳይ ግልፅ መሆንና የገንዘቡ መከፈል እንደተደረገ መፈፀም ይገባዋል” በማለት ይደነግጋል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 ንዑስ አንቀፅ 2 የእንግሊዘኛው ቅጅ ስንመለከት “subrogation shall be express and effected at the time of payment” በማለት ይደነግጋል፡፡

የመዳረጉ ሁኔታ እንዴት መፈፀም እንዳለበት የሚደነግገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 ንዑስ አንቀፅ 2 የአማርኛው ቅጅም ሆነ የእንግሊዘኛው ቅጅ የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለ ሶስተኛ ወገን አበዳሪውን በመዳረግ መብቱን እንዲሠራበት የተስማማ መሆኑን ግልፅ በሚያደርግ መንገድ ዳረጎቱ መፈፀም እንዳለበትና የመዳረግ ሁኔታው ክፍያው በተፈፀመበት ጊዜ መከናወን እንዳለበት የሚገልፁ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ አበዳሪው የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለ ሶስተኛ ወገን በእሱ መብት ተዳርጎ እንዲሠራበት መሥማማቱን በግልፅ ለማሣየት የሚቻለው እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል፡፡ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1968 ንዑስ አንቀፅ 2 በመስፈርትነት ያስቀመጠው የተበዳሪውን ዕዳ የከፈለው ሶስተኛ ወገን በመብቱ ተዳርጎ እንዲሠራበት አበዳሪው የተስማማ መሆኑን ለባለዕዳው እና ለሌሎች ወገኖች በግልፅ በሚያሣይ ሁኔታ ፈቃዱን መስጠቱን እንጅ አበዳሪው የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለው ሶስተኛ ወገን እንዲዳረግ የተስማማ መሆኑን በሚገልፅ ልዩ ፎርማሊቲ ባለው ዕሑፍ ወይም ስለመዳረግ በተደረገ ውል የመግለፅ ግዴታ እንዳለበት የሚደነግግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት ለመዳረግ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመልካች በመብቱ እንዲዳረግ ፈቃድና ስምምነቱን የሰጠ መሆኑን በማያሻማ መንገድ ለማሣየት የሚችሉ የዕሑፍ ማረጋገጫዎችን ወይም የተለያዩ ተግባራትን የፈፀመ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባለዕዳው የነበረበት ዕዳ በአመልካች የተከፈለው መሆኑን በመግለፅ የሰጠው ማስረጃና በመያዣነት ይዟቸው የነበሩ የባለዕዳውን ንብረቶች የባለቤትነት ሰነድ ለአመልካች አሳልፎ መስጠቱ አመልካች መያዣውን በእሱ እግር ተተክቶ (ተዳርጎ) በቀዳሚነት እንዲያስመዘግብ የተስማማ መሆኑን በግልፅ የሚያሣዩ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመልካች የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለ መሆኑን በማረጋገጥ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች የባለቤትነት ሰነድ ለአመልካች አሳልፎ መስጠቱ አበዳሪው ዕዳውን የከፈለው ሶስተኛ ወገን በመዳረግ መብቱ ሊሠራበት እንዲችል በመያዣነት የያዛቸውን ንብረቶች የባለቤትነት ሰነድ እና ሌሎች ማስረጃዎች አሳልፎ የመስጠት ግዴታውን በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1974 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የተወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የባለዕዳውን ዕዳ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመክፈል በአበዳሪው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት መሠረት በባለዕዳው ንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት ባለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተዳርጓል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በተበዳሪው ፈቃድ ስለመዳረግ የሚደነግጉትንና ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1969 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1970 የተደነገገው መሥፈርት አልተሟላም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት መሻሩና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ተጠሪ በባለዕዳው ንብረቶች ላይ ሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት ያለው መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካች ከዚህ በፊት በባለዕዳው ንብረቶች ላይ ምንም አይነት የመያዣ መብት የሌለው በመሆኑ በባለዕዳው ንብረቶች ላይ ከእኔ የሚቀድም የአንደኛ ደረጃ የመያዣ መብት ሊኖረው አይችልም በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 በመጥቀስ ተከራክሯል የተጠሪ ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው መሆኑን ለመመርመር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 አቀራረፅ ይዘትና ተፈፃሚነት በትኩረት ማየት ያስፈልጋል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 “ስለ መተካት” የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ 1 ማንኛውም የማይንቀሣቀሥ ንብረት መያዣ መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከርሱ በፊት ቀደምትነት ያለውን ገንዘብ ጠያቂ አስፈቅዶ የቀደምትነቱ ተራ መውሰድ ይችላል፡፡ በተራ ተከታይ የሆነው ገንዘብ ጠያቂ ባደረገው ጥያቄ መሠረት የመያዣ መብት የተሰጠበትን የማይንቀሣቀስ ንብረት በፍርድ እንዲያዝ አድርጎ እንደሆነ ግን ከርሱ በፊት የነበረውን ገንዘብ ጠያቂ ማስፈቀድ አስፈላጊው አይደለም በማለት ይደነግጋል፡፡

የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ቅጅ “Any mortgage may pay a creditor having the priority with the consent of the creditor, or where the immovable attached on the cotter’s request with out such

https://t.me/ethiopianlegalbrief

consent" የሚል ነው።ድንጋጌ በይዘቱ ሁለት ገዥ የሆኑ የተለያዩ ደንቦችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው ድንጋጌው በመሠረታዊነት ባለዕዳው ንብረት በቀዳሚነት መያዣ ያደረገው አበዳሪ የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለውን ሶስተኛ ወገን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 መሠረት የመዳረግ መብት ሙሉ በሙሉ የሚከላከል ወይም የሚገድብ አይደለም። ተጠሪ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከባለዕዳው የሚፈልገውን ገንዘብ በመክፈል በንብረቶቹ ላይ ቀዳሚ የመያዣ መብት ሊኖረው የሚችለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይህንን ጥያቄውን ሲቀበለውና ሲፈቅድለት ነው። ስለሆነም ከባለዕዳው የሚፈልገውን ገንዘብ ከሌላ ሶስተኛ ወገን በመቀበል ክፍያውን የፈፀመው ሶስተኛ ወገን አመልካች በመብቱ እንዲዳረግ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1968 የመፍቀድ ወይም በንብረቶቹ ላይ ሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት ካለው ተጠሪ ያበደረውን ገንዘብ በመቀበል ተጠሪ በንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት እንዲኖረው የመስማማትና የመምረጫ መብቱ የተሰጠው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መሆኑን ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 የመጀመሪያው ክፍል ገዥ ደንብ ለመረዳት ይቻላል።

ሁለተኛው ከእሱ የቀዳሚነት መብት ያለውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት ሣይጠይቅ ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መክፈል የሚገባውን ገንዘብ በመክፈል ተጠሪ በንብረቶቹ ላይ ቀዳሚ የመያዣ መብት ሊኖረው የሚችለው ተጠሪ ንብረቶቹን በፍርድ ያሣገደ ስለመሆኑ ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ እንደሆነ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 ሁለተኛው ክፍል ገዥ ደንብ ለመረዳት ይቻላል። ተጠሪ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቀዳሚ መያዣነት የያዛቸውን ንብረቶች በፍርድ ያሣገደ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ ያለ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለመተካትና በመብቱ ተዳርጎ ሊሠራበት አይችልም። ስለሆነም ምርጫውን ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚሰጠውንና ፈቃጅ የሆነውን ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ በመቁጠር ተጠሪ የቀዳሚነት መብት እንዲሰጠው የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

ተጠሪ የባለዕዳውን ንብረት በቀዳሚ መያዣነት ለመያዝ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት ማግኘት አለበት። በሁለተኛ ደረጃ ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መክፈል የሚገባውን ዕዳ አጠቃልሎ የከፈለ መሆን እንደሚገባው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል። ተጠሪ አመልካች ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መክፈል የሚገባውን ገንዘብ ከመክፈሉ በፊት የባለዕዳውን ዕዳ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አጠቃልሎ በመክፈል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ለመዳረግ ያቀረበው ጥያቄ የለም። ተጠሪ የባለዕዳውን ዕዳ አጠቃልሎ በመክፈል መብቱ ለመዳረግ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጥያቄ ሣያቀርብና ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሊከፍል የሚገባውን ገንዘብ ሣይከፍል በባለዕዳው ንብረቶች ላይ ሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት ስላለው ብቻ በንብረቶቹ ላይ ቀዳሚ የመያዣ መብት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ሊረጋገጥልኝ ይገባል በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህጉን ድንጋጌ መሠረታዊ አቀራረፅ፣ ይዘት መንፈስና ዓላማ እና የድንጋጌውን ተፈፃሚነት ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና የህግ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል።

4. ከላይ ከሰጠናቸው የህግ ምክንያቶች በተጨማሪ አመልካች ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መክፈል የሚገባውን ገንዘብ አጠቃልሎ በመክፈል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መብት መዳረጉ ተጠሪ በአበዳሪው ንብረቶች ላይ ያለውን የሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት የሚነካ ወይም የሚያጣብብ አይደለም። ተጠሪ የባለዕዳውን ንብረቶች በሁለተኛ ደረጃ መያዣነት ለመያዝ ያደረገው ስምምነት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአመልካች በድርጎ በመተካቱ ምክንያት ብቻ የሚጣበብ ወይም የሚነካ አይደለም። ተጠሪ ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለበትን ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል ከሌሎች የገቢ ምንጮች በመክፈል ሆነ ብሎ አመልካች በንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት እንዲኖረው ለማድረግ አመልካችና ከአበዳሪው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በመመሳጠር ተግባር የፈፀመ መሆኑን አላስረዳም። በመዝገቡ የተደረገው ክርክርና ማስረጃዎች የሚያሣዩት ባለዳው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወሰደውን ብድር በውሉ መሠረት ለመክፈል ባለመቻሉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቀዳሚ መያዣነት የያዛቸውን የአበዳሪውን ንብረቶች በመሸጥ ዕዳውን ለማስከፈል በመንቀሣቀስ ላይ እያለ አመልካች ዕዳውን አጠቃልሎ የከፈለና ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃም በመያዣነት የተያዙ የባለዕዳው ንብረቶች የባለቤትነት ሰነድ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መቀበል በአበዳሪው መብት ተዳርጎ የሠራበትና በንብረቶቹ ላይ ያለውን ቀዳሚ የመያዣ መብት በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ያስመዘገበ መሆኑን ነው። ተጠሪ ባለዕዳው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወሰደውን ብድር ባለመክፈሉ በንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት ያለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መያዣውን ለመሸጥ ሲንቀሣቀሥ ከባለዕዳው የሚፈለገውን ገንዘብ አጠቃልሎ ለመክፈል ሣይጠይቅና ክፍያ ሣይፈፅም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መብት ለመዳረግ ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍና ምክንያት የሌለው ነው፡፡ ተጠሪ በንብረቶቹ ላይ ያለው ሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምትክ በመዳረጉ ምክንያት አልተሸራረፈም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በባለዕዳው ንብረቶች ላይ ቀዳሚ የመያዣ መብት ያለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከባለዕዳው የሚጠይቀውን ገንዘብ አጠቃልሎ በመክፈል በባለገንዘቡ (አበዳሪው) የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት መሠረት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 ድንጋጌዎች መሠረት ተዳርጓል፡፡ አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመተካት ንብረቶቹን በአንደኛ ደረጃ መያዣነት ለማስመዝገብ የሚያስፈልጉ የባለዕዳው ንብረት ሰነዶችና ማስረጃዎች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1974 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመረከብ ንብረቶቹን በቀዳሚ መያዣነት አስመዝግቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት የሌላቸውን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1969 የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1970 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 ድንጋጌዎች በመጥቀስ አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን የመዳረግ መብት የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከመዝገብ ቁጥር 55790 የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35179 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 74358 መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች የባለዕዳው የሰማቸው ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአንደኛ ደረጃ መያዣነት አሲዟቸው በነበሩ ንብረቶች ላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን በመዳረግ ቀዳሚ የመያዣ መብት አለው ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 41116

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ፍሊነሰቶን ኢንጂነሪንግ - ጠበቃ ብሥራት ሐመልማል - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- እነ ወ/ት ሃና ተስፋዬ /6 ሰዎች/ - ጠበቃ ኮ/መላኩ ካሰኝ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ከሳሾች የነበሩ ሲሆን አመልካች ሁለተኛ ተከሣሽ ነበረ፡፡ ተጠሪዎቹ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ አንደኛ ተከሣሽ ወ/ሮ ወርቅይጠሩ ሰርፀመድኅን ከመሞታቸው በፊት ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት በስጦታ ስለሰጡኝ ይጽደቅልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ የተጠሪዎች አባት ተቃውመው የስጦታ ውሉ በፍ/ቤቱ ፈራሽ እንዲሆን ተወስኗል፡፡ ነገር ግን ቤቱን አንደኛ ተከሣሽ ለአመልካች የሸጡ በመሆኑ ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡና ቤቱን በቁጥጥራቸው ሥር ካዋሉበት ጊዜ ጀምሮ ተከራይቶ የተገኘው ገቢ ብር 201,000 /ሁለት መቶ አንድ ሺህ/ ይክፈሉ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ለአንደኛ ተከሣሽ በቤቱ ላይ መብት ሰጥቷቸው የነበረው የስጦታ ውል የፈረሰ በመሆኑ የሥር አንደኛ ተከሣሽ በቤቱ ላይ ከመነሻው ጀምሮ የባለቤትነት መብት የላቸውም ማለት ይቻላል፡፡ አመልካችም ቤቱን የገዛው መብት ከሌለው ሰው ላይ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ለአመልካች ባለቤትነት የማስተላለፍ ውጤት ያለው ሕጋዊ ድርጊት አይደለም፡፡ አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት ከአስተዳደር አካል የተሰጠው የቤት ባለቤትነት ሰነድ የሚያጎናጽፈው የባለንብረትነት የሕግ ግምት ሰነዱ የተገኘው ሕጋዊ ውጤት በሌለው ውል ላይ ተመስርቶ በመሆኑ ፈራሽ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች ያስረክብ፤ ካሣውን የመክፈል ግዴታ ግን የለበትም፡፡ በሌላ በኩል የሥር አንደኛ ተከሣሽ የስጦታ ውሉ ላይ ክርክር መነሳቱን አውቀው መልስ ከሰጡ ቀን ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ያለውን በወር ብር 500 /አምስት መቶ/ እየታሰበ ከወለድ ጋር ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የስር ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች ቤቱን እንዲመልስ የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንፃር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ በዚሁ መሠረት በዚህ ችሎት ሊመለስ የሚገባው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤትን አስመልክቶ የተሰጠው የስጦታ ውል በመፍረሱ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች ሊመልሱ ይገደዳሉ ወይ? የሚለው ጭብጥ ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ወ/ሮ ወርቅይጥሩ ሰርፀመድኅን ለሥር አንደኛ ተከሣሽ በ28/02/1993 በተፃፈ የስጦታ ውል ሰጥተው የነበረ መሆኑን፤ የሥር አንደኛ ተከሣሽ በ16/04/1994 በስማቸው የቤት የባለቤትነት ማስረጃ ተሰጥቷቸው የነበረ መሆኑን፤ በ28/08/1998 በአዋዋይ ፊት በተደረገ የሽያጭ ውል ለአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሸጡና አመልካችም የቤት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑን፤ ቤቱ ለአመልካች ከተሸጠ በኋላ የስጦታ ውሉ ክርክር ቀርቦበት ስለነበር በ25/02/1997 ዓ.ም. ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑን ተገንዝበናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የሥር አንደኛ ተከሣሽን ባለቤት አድርጓቸው የነበረው የስጦታ ውል መፍረስ ነው፡፡ ስጦታ ከውል አይነቶች አንዱ ነው፡፡ የስጦታ ውል ካለው የራሱ የሆነ ባሕሪ አኳያም የስጦታ ውል ግንኙነትን የሚገዙ የተለያዩ የሕግ ድንጋጌዎች በፍ/ብሔር ሕጋችን ተካተው ይገኛሉ፡፡ ምንም እንኳን የስጦታ ውል በእነዚህ የተለያዩ ድንጋጌዎች የሚዳኝ ቢሆንም ስጦታን የሚመለከቱት እነዚህ ድንጋጌዎች የማይሸፍኗቸው ጉዳዮች ሲገጥሙ ስለ ውሎች በጠቅላላ የተመለከቱት ደንቦች ተፈፃሚ ይሆናሉ /የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1676(1) ይመለከቷል/፡፡ ስጦታን የሚመለከቱ የሕጉ ድንጋጌዎችም የስጦታ ውል ፈራሽ የሚሆንባቸው የተለያዩ ምክንያቶችን የሚዘረዝሩ ቢሆንም የስጦታ ውል ሲፈርስ ምን ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል የሚገልጽ ድንጋጌ ግን አላካተቱም፡፡ ስለዚህ የስጦታ ውል መፍረስ የማያስከትለውን ውጤት በተመለተ ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚገባቸው ስለ ውል በጠቅላላው የሚናገሩት ደንቦች ናቸው፡፡ በእነዚህ ደንቦች መሠረት አንድ ውል ሲፈርስ ወይም ሲሰረዝ ተዋዋዮች በተቻለ መጠን ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ማድረግ ነው /ፍ/ብ/ሕ/ቁ 1815/1/ ይመለከቷል፡፡/ የውል መፍረስ ወይም መሰረዝ ውጤቱ ውሉ ከጅምሩ እንዳልተደረገ መቁጠር በመሆኑ ውለታው ለመፈፀም የተሰሩ ሥራዎች ሁሉ ቀሪ ሆነው በማናቸውም አኳኋን ውጤት አይኖራቸውም /ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815/2//፡፡ አሁን አንዳየነው በመርህ ደረጃ የውል መፍረስ ውጤት ተዋዋዮችን ወደ ነበሩበት ቦታ መመለስ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ምንም እንኳን ውሉ ቢፈርስ ወይም ቢሰረዝም የተለያዩ ሁኔታዎች ባጋጠሙ ጊዜ ውሉን ተክትለው የተሰሩ ሥራዎችን ቀሪ በማድረግ ተዋዋዮችን ወደነበሩበት ቦታ ከመመለስ ይልቅ እንደረጉ መቆየቱ የተሻለ አማራጭ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ተዋዋዮቹን ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ሲሆን አለበለዚያም ከፍ ያለ መሰናክል የሚያስከትል ሲሆን የተሰሩ ሥራዎች እንደረጉ እንዲቀሩ ሕጉ ያዛል /ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1817/1//፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ እነዚህ የተሰሩ ሥራዎች በቅን ልቦና ለተዋዋለ ሦስተኛ ወገን ጠቃሚ ሆነው ከተገኙ የተሰሩ ሥራዎች ሳይፈርሱ እንደረጉ እንዲቆዩ ማድረግ እንደሚገባ ሕጉ ያዛል /ፍ/ብ/ሕ/ቁ 1816/፡፡

ከእነዚህ ድንጋጌዎች አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመረምር ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ለሥር አንደኛ ተከሣሽ በስጦታ የተሰጣቸው በ28/3/1993 ነው፡፡ ተከሣሹም ይህንን የስጦታ ውል መሠረት አድርገው በ16/04/1996 በቤቱ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ አግኝተዋል፡፡ የአስተዳደር ክፍል የአንድን ንብረት ባለሃብትነት በማወቅ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት የሰጠው ሰው የንብረት ባለሃብት ሆኖ እንደሚቆጠር ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በአስተዳደር መስሪያ ቤት ተረጋግጦ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ከተሰጣቸው ቀን ጀምሮ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የቤቱ ባለሃብት ሆነው ይቆጠራሉ ማለት ነው፡፡ ይህንንም ሰነድ ይዘው ነው ቤቱን ለአመልካች በ28/08/1996 የሸጡለት፡፡ አመልካች ቤቱን ሲገዛ የቤቱ ባለቤት የነበሩት የሥር አንደኛ ተከሣሽ ናቸው፤ የሽያጩ ውልም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተደርጓል፤ ከዛም አልፎ የቤቱ ባለሃብትነት ከሥር አንደኛ ተከሣሽ ወደ አመልካች ተዛውሮ አመልካች ቤቱ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት አውጥቶ የቤቱ ባለቤት ሆኗል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ አመልካች ቤቱን ሲገዛ የስጦታ ውሉ አልፈረሰም፡፡ እንግዲህ አመልካች ቤቱን ሲገዛ ቤቱ የሥር አንደኛ ተከሣሽ ሳይሆን የሌላ ሰው እንደሆነ ሊያውቅ የሚችልበት ምንም አይነት ሁኔታ አልነበረም ብቻ ሳይሆን የቤቱ ባለቤት ተብለው በሕጉ ፊት ይቆጠሩ የነበረው እኚሁ የሥር አንደኛ ተከሣሽ ናቸው፡፡ ከመዝገቡ ላይ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ሁሉ አመልካች የቅን ልቦና ተዋዋይ የነበረ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ለሥር አንደኛ ተከሣሽ የተደረገው የስጦታ ውል በመጨረሻ ፈራሽ ቢሆንም የስጦታውን ውል ተከትለው የተሰሩ ሥራዎች ቀሪ ማድረጉና ተዋዋዮቹን ወደነበሩበት ቦታ መመለሱ በቅን ልቦና የተዋዋለውን የአመልካችን መብት በእጅጉ የሚጎዳ በመሆኑ እነዚህ ሥራዎች እንዲረጉ ማድረጉ የተሻለና የሕግ መሠረትም ያለው ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ከላይ የተመለከቱትን የሕግ ድንጋጌዎች በአግባቡ ሳያገናዝቡ የስጦታ ውሉ ፈራሽ በመሆኑ ብቻ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲመልስ መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46947 በ25/02/2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34278 በ07/02/2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 39256

ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነገረፈጅ ደረጀ ባዩ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. አቶ ሞሣ ነጋሽ አልቀረቡም

2ኛ. ጣና ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ጠበቃ አቶ አምሣለፀሐይ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በፅሑፍ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62713 ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38688 ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ሁለተኛው ተጠሪ በፍርድ የተወሰነበትን ብር 2,957,935.30 /ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሣ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ ሰላሣ አምስት ብር ከሰላሣ ሣንቲም/ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል የአፈፃፀም ትዕዛት ይሰጥልኝ በማለት ጠይቋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም በአንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር ከመረመረ በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው የአክሲዮን ድርሻ በሃራጅ ተሸጦ በፍርድ ለተሰወሰነበት ዕዳ መክፈያ እንዲሆን ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ በፍርድ ቤት የተጀመረውን የአፈፃፀም ክርክር ከፍርድ ቤት ውጭ በስምምነት ለመጨረስ ተስማምተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን ጠቅላላ ዋጋቸው 1,427,150 /አንድ ሚሊዩን አራት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አንድ መቶ ሃምሣ ብር/ የሆነ የአክሲዮን ድርሻዎች በዕዳ መክፈያነት በአንደኛ ተጠሪ እንዲተላለፍ እንደዚሁም ሁለተኛው ተጠሪ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2006/2007 ከአክሲዮን ድርሻ ያገኘው ዲቪደንድ በዕዳ መክፈያነት ለአንደኛው ተጠሪ እንዲተላለፍ ተስማምተዋል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ይህንን ስምምነታቸውን ለፍርድ ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአፈፃፀሙን ክርክር የያዘው ፍርድ ቤትም የአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር በስምምነታቸው መሠረት እንዲፈፀም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የአፈፃፀም ክርክሩ በዚህ ሂደት ላይ እያለ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ መብቱን ለማስከበር እንዲፈቀድለት አመልክቷል፡፡ አመልካች አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ባደረጉት ስምምነት ፍርድ ቤቱ ለሁለተኛው ተጠሪ ዕዳ መክፈያነት እንዲውል ትዕዛዝ የሰጠበት ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው የአክሲዮን ድርሻና ሁለተኛ ተጠሪ ከአክሲዮን ድርሻው መሠረት እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር 2006/2007 ዓ.ም የሚከፈለው ዲቪደንድ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው መብቶች ላይ የቅድሚያ መብት አለኝ፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው የአክሲዮን ድርሻ ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለወሰዱት ኦቨር ድራፍት ብድር በመያዣነት ይገዋዋለሁ፡፡ የሁለተኛው ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት የተያዘ መሆኑ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የአክሲዮን መዝገብ ውስጥ ተመዝግቧል፡፡ የሁለተኛው ተጠሪ የአክሲዮን ሰርተፊኬትም በእጃችን ይገኛል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው የአክሲዮን ድርሻና ዲቪደንድ ለአንደኛ ተጠሪ ዕዳ መክፈያነት ወደ አንደኛው ተጠሪ እንዲተላለፍ የሰጠውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ይሰርዝልን በማለት አመልክቷል፡፡

አመልካች በአፈፃፀም ክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ካቀረበው ማመልከቻ ጋር በማያያዝ የፅሑፍ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ አመልካች ክርክሩን ለማስረዳት ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አመልካች የኦቨር ድራፍት ብድር እንዲፈቀድለት ላቀረበው ጥያቄ መያዣ ይሆን ዘንድ ሁለተኛ ተጠሪ አቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 475,000 (አራት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር) የሆኑ የአክሲዮን ድርሻዎችንና ሌሎች ስምንት ሰዎች በአቢሲኒያ ባንክ ያላቸውን የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት ያቀረበ መሆኑን ገልፆ የፃፈው ደብዳቤ ከነ አባሪው

- አመልካች ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኦቨር ድራፍት ብድር ለወሰደው 40,000,000 (አርባ ሚሊዮን ብር) መያዣ እንደሆነ ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 475,000 (አራት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር) የሆኑ የአክሲዮን ድርሻዎችንና የሌሎች ስምንት ሰዎች የአክሲዮን ድርሻዎች በመያዣነት የያዘ በመሆኑ የአክሲዮን ድርሻዎቹ አመልካች በመያዣነት የያዛቸው መሆኑ በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ እንዲመዘገብለት ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የፃፈው ደብዳቤ፣
- የአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር አመልካች ለሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሰጠው የኦቨር ድራፍት ብድር በመያዣነት የያዛቸው የሁለተኛው ተጠሪና የሌሎች ስምንት ሰዎች የአክሲዮን ድርሻዎች አመልካች በመያዣነት የያዛቸው መሆኑ በአክሲዮኖች መመዝገቢያ መዝገብ የተመዘገበና ለሶስተኛ ወገን የማይተላለፍ መሆኑን በማረጋገጥ ለአመልካች በአድራሻው የፃፈውንና ለሁለተኛው ተጠሪ ግልባጭ የተደረገ ደብዳቤ፣
- ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከአመልካች ብር 40,000,000 (አርባ ሚሊዮን ብር) የኦቨር ድራፍት ብድር የወሰደበት የብድር ውልና ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኦቨር ድራፍት የወሰደውን ብድር ከነ ወለዱ ያልከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ፣
- አመልካች ስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ብር 10,000,000 /አስር ሚሊዮን ብር/ በኦቨር ድራፍት ብድር ሲወሰድ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 600,000 /ስድስት መቶ ሺ ብር/ የሆኑ አክሲዮኖች በመያዣነት ያስያዘና መያዣው በመሆኑ በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ እንዲመዘገብለት ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የፃፈው ደብዳቤ፣
- አቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር አመልካች ለእስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሰጠው የኦቨር ድራፍት ብድር በመያዣነት የያዛቸው የሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው ዋጋቸው 600,000 /ስድስት መቶ ሺ ብር/ የሆኑ የአክሲዮን ድርሻዎች በመያዣነት የተያዙ መሆኑ በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ የተመዘገበ መሆኑንና ለሌሎች ሶስተኛ ወገኖች እንደማይተላለፉ በማረጋገጥ ለአመልካች በአድራሻው የፃፈውና ለሁለተኛው ተጠሪ ግልባጭ የተደረገ ደብዳቤ፣
- በአመልካች እጅ የሚገኘውን ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰርተፊኬትና አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት መያዙን ገልፆ ሁለተኛው ተጠሪ የሚደርሰው ዲቪደንድ ለአመልካች ተከፋይ የሚሆንበትን ሁኔታ እንዲመቻች ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር በአድራሻው የፃፈውና ለሁለተኛው ተጠሪ ግልባጭ የተደረገ ደብዳቤ፣
- አቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች አስረኛ መደበኛ ጠቅላላ ስብሰባ የሚካሄድ መሆኑንና ሁለተኛው ተጠሪ ያሉት አርባ ሶስት የአክሲዮን ድርሻዎች በአመልካች በመያዣነት የተያዙ በመሆኑ አመልካች ካልፈቀደለት በስብሰባው ላይ ለመገኘትና ድምፅ ለመስጠት የማይችል መሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር 329/1/ የተደነገገ መሆኑን ገልፆ ሁለተኛው ተጠሪ በስብሰባው ለመገኘትና ድምፅ ለመስጠት ከአመልካች ውክልና ይዞ መቅረብ እንዳለበት ለሁለተኛ ተጠሪ በአድራሻው የፃፈው እና ለአመልካች ግልባጭ ያደረገውን ደብዳቤ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውንና ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ የሆነ አርባ ሶስት አክሲዮኖች ስታር ቢዝነስ ግሩኘ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለወሰዱት ብድር በዋስትና ያስያዘ መሆኑን በመግለፅ፣ ከባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤና ሌሎች ስብሰባዎች በመካፈል ድምፅ ለመስጠት እንዲፈቅድልንና ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ደብዳቤ እንዲፃፍልን በማለት ለአመልካች የፃፈውን ደብዳቤ በማስረጃነት አያይዞ አቅርቧል፡፡

የአመልካች ማመልከቻና ማስረጃ ለተጠሪዎች ደርሷቸው ተጠሪዎች በተናጠል የመከላከያ መልስና ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ባቀረበው የፅሑፍ ክርክር ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከአመልካች የኦቨር ድራፍት ብድር ሲወስድ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት አላስያዘም፡፡ አመልካች ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2828 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የመያዣ ውል ያተዋዋለ መሆኑን የሚያስረዳ የፅሑፍ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ አመልካች ከሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ጋር በተለያየ ጊዜ ያደረጋቸው መፃፃፎች በአመልካችና በሁለተኛ ተጠሪ መካከል የመያዣ ውል አያቋቁሙም፡፡ አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ የህጉን ፎርማሊቲ በማሟላት በመያዣነት ያልያዘ መሆኑን በማመን የአመልካች የክሬዲት አገልግሎትና የሕግ አገልግሎት በተፃፏቸው ደብዳቤዎች አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ ላይ የቀዳሚነት መብት አለኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር እና ስታር ቢዝነስ ግሩኝ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለወሰዱት የኦቨር ድራፍት ብድር እኔ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለኝን የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት ለማስያዝ ከአመልካች ጋር ያደረግሁት የመያዣ ውል የለም፡፡ እኔ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለኝን የአክሲዮን ድርሻ አመልካች በመያዣነት እንዲይዝ አልተስማማሁም፡፡ አመልካች ከእኔ ፍላጐትና ፈቃድ ውጭ የኦቨር ድራፍት ብድር ከወሰዱት የንግድ ድርጅቶችና ከአቢሲኒያ ባንክ ጋር በመፃፃፍ የአክሲዮን ድርሻዎቹን በመያዣነት ይዣለሁ በማለት የቀዳሚነት መብት እንዲረጋገጥለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተገቢ አይደለም፡፡ በማለት ተከራክሯል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ በተናጠል ያቀረቡትን ክርክር ያስረዳልናል በማለት፡-

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንዋር ቅርንጫፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ እና ዋና ሥራ አስኪያጅ የሁለተኛው ተጠሪና የሌሎች ስምንት ሰዎች የአክሲዮን ድርሻ በመያዣ የተያዙበትን አግባብ፣ አስተያየት የተሰዋወጡበት የውሰጥ ሜሞ
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሕግ አማካሪ ዋና ክፍል ለባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሰጠው የሕግ አስተያየት /የውስጥ መፃፃፊያ ሜሞ/ እና አቢሲኒያ ባንክ አክስሲዮን ማህበር አመልካች በመያዣያ የያዛቸውን፣ የአክሲዮን ድርሻዎች በሚመለከት ከአክሲዮን ባለድርሻዎቹ እያቀረቡ ያሉ ጥያቄዎችን በመግለፅ አመልካች ተገቢውን እንዲፈፅም ለመጠየቅ የፃፈውን ደብዳቤ በማስረጃነት አቅርበዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ማመልከቻና ማስረጃ እንደዚሁም ተጠሪዎች ያቀረቡትን መከላከያና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት የያዘ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች በአመልካችና በተጠሪ መካከል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2828 ንዑስ አንቀፅ 2፣ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1725 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1727 ድንጋጌዎች መሠረት የመያዣ ውል የተደረገ መሆኑን አያስረዱም፡፡ ስለሆነም አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ባለው የአክሲዮን ድርሻ ላይ የመያዣና የቅድሚያ መብት የለውም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱም የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚነቀፍበት ምክንያት የሌለ መሆኑን በግለፅ የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞታል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ስታር ቢዝነስ ግሩኝ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለወሰዱት የኦቨር ድራፍት ብድር በመያዣነት ያስያዘ መሆኑን በግልፅ በማመን በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለመሣተፍና ድምፅ ለመስጠት የውክልና ደብዳቤ እንዲፃፍለት አመልካችን የጠየቀበት ደብዳቤ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያለው የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት የተያዘ መሆኑንና በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ የመዘገበ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበናል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ የሚያረጋግጠው የአክሱዮን ሰርተፊኬት እስካሁን በእጃችን እንደሚገኝ አስረድተናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአክሱዮን ድርሻ በመያዣነት የሚያዙበትን ልዩ ሁኔታ ግያገናዝብ አግባብነት የሌላቸውን የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች በመጥቀስና በመተርጉም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይህንን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አፅንቷል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በተናጠል በሰጡት መልስ አመልካች የኦቨር ድራፍት ብድር ሲሰጥ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በዋስትና ለማስያዝ ከአመልካች ጋር አልተዋዋለም፡፡ አመልካች ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር በፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የተዋዋለው የመያዣያ ውል በሌለበት ሁኔታ አመልካች የሚያቀርበው የቀዳሚነት ጥያቄ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ አመልካች የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱን በእጁ ያስገባው ከሁለተኛው ተጠሪ ፈቃድና ፍላጐት ውጭ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ያቀረባቸው የፅሑፍ ማስረጃዎች በአመልካችና በሁለተኛው ተጠሪ መካከል የመያዣ ውል ያለ መሆኑን ስለማያስረዱ የሥር ፍርድቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ ሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያድርግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካችና ተጠሪዎች ለሰበር በፅሑፍ ካቀረቡት ክርክር በተጨማሪ ችሎቱ የአመልካች ነገረ ፈጅና የተጠሪዎች ጠበቆች የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ስታር ቢዝነስ ግሩኘ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለወሰዱት ኦቨር ድራፍት ብድር ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ አስመዝግበን ይዘናል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪም ይህንን በማመን የፃፈው ደብዳቤ አለ፡፡ ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት የአክሲዮን ድርሻ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2828(2) መሠረት አልተያዘም በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ይዘት ያለው ሰፊ የቃል ክርክር አቅርቧል፡፡

በተናጠል የቃል ክርክራቸውን ያሰሙት የአንደኛና የሁለተኛ ተጠሪ ጠበቆች በበኩላቸው አመልካች ለሰጠው የኦቨር ድራፍት ብድር ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያለው የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት ለማስያዝ ያደረገው ስምምነት የለም፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በባለአክሲዮኖች ስብሰባ ለመካፈል አመልካችን በፅሑፍ የጠየቁበት ደብዳቤ በስህተት የተፃፈ ደብዳቤ ነው፡፡ አመልካችም በስህተት የፃፍነው መሆኑን፣ አውቆ ዋናውን ደብዳቤ መልሶ ለሁለተኛው ተጠሪ ሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም የሕጉን መስፈርት የሚያሟላ የመያዣ ውል ግይኖር አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ባለው የአክሲዮን ድርሻ ላይ የቀረበውን የቀዳሚነት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው፡፡ ትዕዛዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው ሰፊ የቃል ክርክር አቅርበዋል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪዎች ያደረጉት ክርክር የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝና በሰበር አመልካችና ተጠሪዎች በፅሑፍና በቃል ያደረጉት ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት ለመያዝ የሚደረገው የመያዣ ውል ሌሎች ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሣቃሽ ንብረቶች ለመያዝ በሚያስፈልገው ፎርማሊቲ መሠረት መፈፀም አለበት ወይ? የሚለው ነጥብ የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የፍታብሔር ሕጉ፣ ስለ መያዣያ ውል /ኘሌጅ/ የደነገጋቸውን ድንጋጌዎች ባህሪና የተፈፃሚነት ወሰን፣ በዝርዝር መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የፍታብሔር ሕጉ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሣቃሽ ንብረቶች በመያዣያ ስለሚያዙበት ሁኔታ የመያዣው ውጤትና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2825 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2862 በዝርዝር ደንግጓል፡፡ የፍታብሔር ሕጉ ግዙፍነት ያላቸውን ተንቀሣቃሽ ንብረቶች ብቻ ግይሆን የገንዘብ መጠየቂያ ሰነዶች እና ሌሎች ግዙፍ ያልሆኑ ሃብቶች በመያዣነት ማስያዝ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ የፍታብሔር ሕጉ የገንዘብ መጠየቂያ ሰነዶች /ክሌምስ/ እና ግዙፍ ያልሆኑ ሌሎች ሃብቶች /ኢንታጀብልስ/ በመያዣነት ስለሚያዙበት ሁኔታና መያዣው ስለሚያስከትለው ውጤት ገኘር የሆኑ ልዩ ድንጋጌዎችን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2863 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2874 ይደነግጋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአክሲዮን ድርሻ አንድ የተፈጥሮ ወይም ሕግ ወለድ ሰው ካፒታሉ አስቀድሞ በታወቀ በአክሲዮን በተከፋፈለና ለዕዳውም ንብረቱ ብቻ ዋስትና በመሆኑ የአክሲዮን ማህበር ውስጥ ያሉትን አክሲዮኖች ብዛትና ዋጋ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አንድ ባለ አክሲዮን በአክሲዮን ማህበሩ ውስጥ በባለቤትነት የያዛቸው አክሲዮኖች ግዙፍ ያልሆኑ ሃብቶች ናቸው፡፡ በአገራችን ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸው ሁለት አይነት አክሲዮኖች እንዳሉ የንግድ ሕግ ቁጥር 325 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡

የመጀመሪያው አይነት አክሲዮን ለአምጭው ተብሎ የተፃፈባቸው አክሲዮኖች ሲሆኑ እነዚህን አክሲዮኖች ለሌላ ሰው ለማስተላለፍም ሆነ በመያዣነት ለመያዝ እንደማንኛውም ተላላፊ የንግድ ወረቀት የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰነዱን አሳልፎ በመስጠት ያለአንዳች አይነት አሰራር /ፎርማሊቲ/ ማከናወን እንደሚቻል የንግድ ሕግ ቁጥር 340 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2866(2) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው አይነት አክሲዮን የባለ አክሲዮኑ ስም የተፃፈበት አክሲዮን ነው፡፡ ስም የተፃፈበት አክሲዮን የአክሲዮን ማረጋገጫ ሰነዱን አሳልፎ በመስጠት ብቻ ለማስተላለፍና በመያዣነት ለማስያዝ አይቻልም፡፡ ስም የተፃፈበት አክሲዮን ለማስተላለፍም ሆነ በመያዣነት ለማስያዝ አክሲዮኖቹ ለሌላ ሰው የተላለፉ ወይም በመያዣነት የተያዙ መሆኑን በአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኘው የአክሲዮን መዝገብ ማስመዝገብ እንደሚያስፈልግ ሕግ ቁጥር 341(2) እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2865(1) ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉት አክሲዮኖች የሁለተኛው ተጠሪ ስም የተፃፈባቸው አክሲዮኖች መሆናቸውን አመልካች በማስረጃነት ካቀረበው የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉት የአክሲዮን ድርሻዎች እንደማንኛውም ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሣቃሽ ንብረት በመቁጠር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2828 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ሌሎች የውል ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መወሰናቸው ከጅምሩ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው ክርክር ግዙፍነት የሌላቸው ሃብቶች (አክሲዮኖች) በመያዣነት መያዝን የሚመለከትና ለጉዳዩም ተፈፃሚነት ያላቸው ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2863 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2874 የተደነገጉትና አግባብነት ያላቸው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሆናቸውን ባለማገናዘብ የተሰጠ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉትን አክሲዮን ድርሻዎች የፍታብሔር ሕጉ የገንዘብ መጠየቂያ ሰነዶችና ግዙፍ ያልሆኑ ሌሎች ሃብቶችን ስለማስያዝ በሚለው ክፍል የደነገጋቸው መስፈርቶች በሚሟላት በመያዣነት ይዟቸዋል ወይስ አልያዛቸውም የሚለው በሁለተኛ ደረጃ በመታየት ያለበት ነጥብ ነው፡፡ የባለአክሲዮኑ ስም የተፃፈበት የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ ሲያዝ የመያዣ ውሉ የሚከናወነው ይህንን መብት በማስተላለፍ በተደነገገው ሥርዓት ወይም /ፎርም/ መሠረት መሆን እንዳለበት ከፍታበሔር ሕግ ቁጥር 2865 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የባለአክሲዮኑ ስም የተፃፈበትን አክሲዮን ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ ይህንኑ በአክሲዮን ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት በሚገኘው የአክሲዮን መዝገብ ማስመዝገብ እንደሚገባ የንግድ ሕግ ቁጥር 341 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡

አመልካች የሁለተኛው ተጠሪ ስም የተፃፈባቸውን ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉት የአክሲዮን ድርሻዎች ለመያዝ ይህንን በሕግ የተደነገገ ፎርማሊቲ ማሟላት ይገባዋል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካሉት የአክሲዮን ድርሻዎች ውስጥ አመልካች ለሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሰጠው ብር 40,000,000 /አርባ ሚሊዮን ብር/ አቮር ድራፍት ብድር መያዣ ይሆኑ ዘንድ ብር 475,000 /አራት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር/ ዋጋ ያላቸው አክሲዮኖች በአመልካች በመያዣነት የተያዙ መሆኑና መያዣው በአቢሲኒያ አክሲዩን ማህበር የአክሲዮን መዝገብ የተመዘገበ መሆኑን አቢሲኒያ ባንክ ሚያዚያ 6 ቀን 1992 ዓ.ም ለአመልካች በአድራሻው ለሁለተኛው ተጠሪ በግልባጭ የፃፈው ደብዳቤ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከአመልካች በአቮር ድራፍት ለወሰደው ብር 10,000,000 /አስር ሚሊዮን ብር/ መያዣ ይሆኑ ዘንድ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካሉት አክሲዮኖች ዋጋቸው ብር 600,000 /ስድስት መቶ ሺ ብር/ የሆኑ አክሲዮኖችን አመልካች በመያዣነት የያዛቸውና መያዣውም በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የአክሲዮን መዝገብ የተመዘገበ መሆኑን አቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ሚያዚያ 4 ቀን 1992 ዓ.ም ለአመልካች በአድራሻ ለተጠሪ በግልባጭ የፃፈው ደብዳቤ ያስረዳል፡፡ ይኸም አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ የሆኑ አርባ ሶስት አክሲዮኖች በፍታብሔር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ ቁጥር 2865 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 341 አንቀፅ 2 የተቀመጠውን ፎርማሊቲ በማሟላት በመያዣነት የያዘ መሆኑን ለማስረዳት የሚችል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪዎች የአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የሁለተኛው ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻዎች በአመልካች በመያዣነት የያዛቸው መሆኑን በአክሲዮን መዝገብ ላይ የመዘገበው ያለ ሁለተኛው ተጠሪ ፈቃድና ስምምነት ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ሁተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያለውን የአክሲዮን ድርሻ አመልካች ለሚና ትራዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ለስታር ቢዝነስ ግሩኘ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ላበደረው የኦቨር ድራፍት ብድር በመያዣነት የያዙ መሆኑን የመዘገበው ሁለተኛው ተጠሪ ሁለቱ እህት ኩባንያዎች ከአመልካች ለወሰዱት ብድር ያሉት የአክስዮን ድርሻዎቹ አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልቶ በመያዣነት እንዲያዙ እንዲያደርግ ግንቦት 26 ቀን 1991 ዓ.ም ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር በፅሑፍ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት መሆኑን ተጠሪዎች በማስረጃነት ይጠቅመናል ብለው ባቀረቡት የአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ግንቦት 14 ቀን 1999 ዓ.ም ከፃፈው ደብዳቤ በመግቢያው ላይ ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉት የአክሲዮን ድርሻዎች አመልካች ለሚና ትራዲንግና ስታር ቢዝነስ ግሩኘ ለሰጠው የኦቨር ድራፍት ብድር በፍላጐቱና በፈቃዱ በመያዣነት ያስያዘ መሆኑን “ኩባንያችን በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የብር 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ ዋጋ ያላቸው አርባ ሶስት አክሲዮኖች ስታር ቢዝነስ ግሩኘ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያና ሚና ትራዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ከባንኩ ለተበደሩት ብድር በዋስትና ያስያዘ መሆኑ ይታወቃል” በማለት አመልካች ከአቢሲኒያ ባንክ የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ለመካፈል እንዲፈቀድለት በቁጥር ጣትኩ 701/37/99 ህዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አቢሲኒያ ባንክ /አ.ማ/ አክሲዮኖቹን በማያዣነት በአክሲዮን መዝገብ ውስጥ ሲመዘገብ ሁለተኛው ተጠሪ በግልባጭ እንዲያውቅ እያደረገ መሆኑን የቀረቡት የፅሑፍ ማስረጃዎች ያሣያሉ፡፡ በአመልካች በኩልና ተጠሪዎች ክርክራቸውን ለማጠናከር ያቀረቧቸው የፅሑፍ ማስረጃዎች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉት አርባሶስት አክሲዮኖች በመያዣነት የያዘውና መያዣው በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ የተመዘገበው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2865 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በሁለተኛው ተጠሪ ፈቃድና ስምምነት መሆኑን የሚያረጋግጥ ግልፅ የፅሑፍ ማስረጃ በቀረበበት ሁኔታ በመሆኑ ተጠሪዎች መያዣው በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን መዝገብ የተመዘገበው ከሁለተኛው ተጠሪ ፈቃድና ስምምነት ውጭ ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ ተጠሪዎች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ለመሣተፍ እንዲፈቀድለት ለአመልካች የፃፈው ደብዳቤ በስህተት የተፃፈ ነው፡፡ የአመልካች የሥራ ኃላፊዎች ሁለተኛው ተጠሪ ያለውን የአክሲዮን ድርሻ የሕጉን መስፈርት በሚያሟላ የመያዣ ውል ያልተያዘ መሆኑን በተፃፃፉት ፅሑፍ አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም አክሲዮን ድርሻው በመያዣነት አልተያዘም ተብሎ እንዲወሰንልን የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የሁለተኛ ተጠሪ እህት ኩባንያዎች የሆኑት ስታር ቢዝነስ ግሩኘ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ሚና ትራዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለአመልካች በኦቨር ድራፍት ብድር ሲወስዱ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት እንዲያዙ የተስማማ መሆኑ በአመልካች የቀረቡት የፅሑፍ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡ አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያለውን የአክሲዮን ድርሻ መያዣ በማድረግ ለሁለቱ የንግድ ድርጅቶች የኦቨር ድራፍት ብድር ፈቅዶ ሁለቱ የንግድ ድርጅቶች ብድሩን ወስደዋል፡፡ **ከዚህ** በተጨማሪ ሁለቱ የንግድ ድርጅቶች ከአመልካች የወሰዱትን የኦቨር ድራፍት ብድር ፈቅዶ ሁለቱ የንግድ ድርጅቶች ብድሩን ወስደዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱ የንግድ ድርጅቶች ከአመልካች የወሰዱትን የኦቨር ድራፍት ብድር አልከፈሉም፡፡ ከዚህ ሁሉ ሂደት በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያሉኘ የአክሲዮን ድርሻዎች አመልካች በመያዣነት የያዛቸው መሆኑን በመግለፅ የፃፍኩት ደበዳቤ በስህተት የተፃፈ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍና ተቀባይነት የሌለው ክርክር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ አመልካች በአክስዮን ድርሻዎቹ ላይ የሕጉን መስፈርት የሚያሟላ የመያዣ ውል የሌለው መሆኑን በመግለፅ የባንክ ኃላፊዎች በፁሑፍ አረጋግጠዋል በማለት የሚከራከረው የባንኩ ኃላፊዎች የውስጥ መፃፃፊያ ሚሞ በማስረጃነት በማቅረብ ነው፡፡ እነዚህ የውስጥ መፃፃፊያዎቹ በዚህ ጉዳይ የአስረጅነት ዋጋ የሌላቸው በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአመልካች ኃላፊዎችና የሕግ ክፍል እርስ በርሳቸው በፅሑፍ የተለዋወጡት ሃሣብ በጉዳዩ ተፈፃሚነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና የሕግ አረዳድ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ /አ.ማ/ ካለው የአክሲዮን ድርሻ ውስጥ ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ የሆኑ የአክሲዮን ድርሻዎችን አመልካች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2865 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 341 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገውን መስፈርት በማሟላት በመያዣነት የያዛቸው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የአክሲዮን ድርሻዎቹን በመያዣነት የያዘውና በአቢሲኒያ ባንክ /አ.ማ/ የአክሲዮን መዝገብ ያስመዘገበው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2865 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በሁለተኛው ተጠሪ ፈቃድና ሙሉ ስምምነት መሠረት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ግዙፍ ያልሆኑ ሃብቶች በመያዣነት በሚያዙበት ወቅት ገኖርነት ያላቸውንና ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚገቡ የሕግ ድንጋጌዎች ሣያገናዝቡ አመልካች የሁለተኛ ተጠሪን የአክስዮን ድርሻ በመያዣነት የያዘ ስለመሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2828 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ሌሎች ጠቅላላ የውል ሕግ ድንጋጌዎችን የሚጠይቁትን ፎርማሊቲ ያላሟላ በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካሉት የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ የሆኑ አርባሶስት አክሲዮኖች የሕጉን ፎርማሊቲ በማሟላት በመያዣነት ይሂል፡፡ አመልካች በመያዣነት የያዛቸው አክሲዮኖች ላይ የቀዳሚነት መብት ይኖረዋል፡፡ አመልካች የቀዳሚነት መብት በሁለተኛው ተጠሪ ላይ ብቻ ሣይሆን በሶስተኛ ወገኖችም ላይ የፀና ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በመያዣነት በያዛቸው አክሲዮኖች ላይ ያለው የቀዳሚነት መብት ሁለተኛ ተጠሪን ከስሶ የፍርድ ባለመብት በሆነው አንደኛው ተጠሪ ላይም የሚሰራ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በመያዣነት የያዛቸውን አርባሶስት አክሲዮኖች የሚያስገኙትን ትርፍ /ዲቪደንድ/ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2867 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የመቀበልና የቀዳሚነት መብት አለው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ሁተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ውስጥ ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ በሆኑ አርባሶስት አክሲዮኖችና ከእነዚህ አክሲዮኖች እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር 2006/2007 ዓ.ም የሚገኘው ዲቪደንድ ለአንደኛው ተጠሪ የፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ስለሆነም ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ካለው የአክሲዮን ድርሻ አመልካች ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ በሆነው አርባ ሶስት አክሲዮኖችና እነዚህ አክሲዮኖች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2006/2007 እና ከዚያ በኋላ ባስገኙት የአክስዮን ትርፍ /ዲቪደንድ/ በቀዳሚነት የመጠየቅና የመቀበል እና ለአበደረው ብድር መክፈያ የማድረግ መብት አለው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ሣያገናዝቡ አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ካለው የአክሲዮን ድርሻ በአርባሶስት አክሲዮኖችና በዲቪደንድ ላይ የሕጉን ፎርም ያሟላ የመያዣ መብት የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62713 ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38688 ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለእስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ለሚና ትሬዲንግ ኃላፊቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኦቨር ድራፍት ብድር ሲያበድር ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ የሆነ አርባሶስት አክሲዮኖች በመያዣነት ይሂል፡፡ በእነዚህ አክሲዮኖች ላይ የቀዳሚነት መብት አለው ብለናል፡፡
3. አመልካች በመያዣነት የያዛቸውና ከላይ ዋጋቸው የተገለፀው አርባሶስት አክሲዮኖች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2006/2007 እና ከዚያ ወዲህ ያስገኙትን የአክሲዮን ድርሻ ትርፍ /ዲቪደንድ/ የመቀበል የቀዳሚነት መብት አለው ብለናል፡፡
4. አንደኛ ተጠሪ ለፍርድ ማስፈፀሚያ ማድረግ የሚችለው አመልካች በመያዣነት ያልያዛቸውን የሁለተኛው ተጠሪ አክሲዮኖችና ከእነርሱ የሚገኘው የአክሲዮን ድርሻ ትርፍ /ዲቪደንድ/ ብቻ ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. ለሰበር ያወጡትን ወጭ አመልካችና ተጠሪዎች ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
6. በትውስት የመጣው የከፍተኛው ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43372

ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ደረሱ ዓለሙ - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሙሊሣ ወርቁ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በምስራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱም ምክንያት በ10/8/98 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል በ29/9/98 ዓ.ም ለመመለስ ብር 11,750 (አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ) ተበድረው በተባለው ቀን ካልከፈሉ እጥፍ አድርገው ብር 23,500(ሃያ ሦስት ሺህ አምስት መቶ) ለመክፈል ገንዘቡን ተቀብለው ስላልከፈሉ በውሉ መሰረት ገንዘቡን እጥፍ አድርገው እንዲከፍሉ እንዲወሰን በማለት ውላቸውን ጨምሮ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ የሚል ነው፡፡

ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት ዋስ የብድሩን ገንዘብ በማመን ከዋናው ተበዳሪ ጋር ይከራከር በማለት መልስ የሰጡ ሲሆን አንደኛ ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች ግን የተበደረውን ያህል ብቻ እንጂ እጥፍ ተደርጐ መክፈል እንደሌለባቸው በመግለጽ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው ፍ/ቤት አመልካች የተበደሩትን ገንዘብ ወለድ በማድረግ 23,500 (ሃያ ሦስት ሺህ አምስት መቶ) በውሉ መሰረት እንዲከፍሉ ዋና ተበዳሪው ካልከፈሉ ዋሱ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት የሰረዘው ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎትም በተመሳሳይ ሁኔታ በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ጥር 3 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ቅሬታ መሰረት የብድሩ ገንዘብ እጥፍ ተደርጐ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተጠሪን በማስቀረብ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

እኛም ክርክራቸውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር በፍሬ ነገረ ረገድ የተረጋገጠውና የማይካካዱት 11,750.00 (አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሐምሳ ብር) አመልካች ከተጠሪ በብድር የወሰዱ መሆኑን ነው፡፡ አከራካሪ የሆነው የተጠቀሰው የብድር ገንዘብ በተባለው ቀን ባለመከፈሉ ምክንያት እጥፍ አድርጐ የመመለሱ ጉዳይ ነው፡፡ በመሰረቱ ተዋዋዮች የብድሩን ገንዘብ እጥፍ አድርጐ ማለትም መቶ ፐርሰንት ወለድ ለመክፈል ቢዋዋሉ የሕግ መሰረት ይኖራል ወይ? የሚለው ነጥብ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባ ነው፡፡ ተዋዋዮች በወለድ የሚከፈለውን ገንዘብ በአመት በመቶ ከአስራ ሁለት በላይ እንዲሆን ለመዋዋል እንደማይቻል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2479/1/ የተመለከተ ከመሆኑም በላይ በወለድ የሚከፈለው ገንዘብ በመቶ አስራ ሁለት በላይ በዓመት እንዲሆን በጽሁፍ የተደረገ ውል ቢኖር እንኳ ተበዳሪው በመቶ ዘጠኝ ብቻ በአመት ወለድ መክፈል እንዳለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2479/3/ በአስገዳጅ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ተዋዋዮች የብድርን ገንዘብ እጥፍ አድርጐ ለመክፈል መስማማትን ሕጉ የማይፈቅድ መሆኑን ከፍ ሲል ከተጠቀሱ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በግልጽ የጠየቁት ዳኝነት አመልካች በ10/8/98 ዓ.ም በተፃፈ ውል በ29/9/98 ሊመልስልኝ በዚህ ቀን ሳይመልስ ቀኑን ካሳለፈ የተበደረውን ገንዘብ እጥፍ አድርጐ ሊከፍለኝ ብር 11,750(አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ) ተበድሮ እስካሁን አልመለሰልኝም፡፡ ስለዚህ በገቡት ግዴታ መሰረት እጥፍ አድርገው ብር 23,500(ሃያ ሦስት ሺህ አምስት መቶ) እንዲከፍሉ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ፍ/ቤቱም እጥፍ ተደርጐ የመከፈሉን ጥያቄ ተቀብሎ በስምምነቱ መሰረት እጥፍ የተባለውን ወለድ ለማድረግ 23,500 ብር እንዲከፍል በማለት መወሰኑ ከፍ ሲል ስለወለድ አከፋፈል በሕጉ የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው፡፡ የተጠሪ ጥያቄ በውሉ በተመለከተው ቀን ባለመከፈሉ ምክንያት ገንዘቡ እጥፍ ተደርጐ እንዲከፈላቸው እንጅ ክፍያው ስላዘገየባቸው ወለድ ተሰልቶ እንዲከፈላቸው አልጠየቁም፡፡ በፍ/ቤቶች መብትም ሆነ ግዴታ በፍርድ ሊረጋገጥ የሚችለው በሕግ በተመለከቱ ስርአቶች ብቻ እና በግልጽ በተጠየቀው ዳኝነት አንፃር ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የብድርን ገንዘብ ከመነሻው እጥፍ አድርጐል ለመክፈል ውል ለመዋዋል ሕጉ የሚከለክል ሲሆን ከፍ ሲል ከተመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎች መንፈስ ባፈነገጠ መልኩ የምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠቀሰውን ገንዘብ እንደወለድ እጥፍ አድርጐ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚም ሆነ ሰበር ሰሚ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ማረም ሲገባቸው በማጽናት የሰጡት ውሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ትርጉም ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18071 በ14/9/2000 ዓ.ም፣የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 52223 በ3/3/2001 ዓ.ም እና እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 74254 በ28/5/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/መሰረት ተሻሽሏል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች 11,750(አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ) ስለመበደራቸውና ይህንኑ ብር ብቻ እንደሚከፍሉ ያመኑ በመሆኑ ከውሉ ጊዜ ማለትም ከ10/8/98 ዓ.ም እስከ 29/9/98 ዓ.ም ድረስ ያለውን የአንድ ወር ከ19 ቀን ብቻ 11,750 ብር የሚያስገኝውን ወለድ 9% በዓመት ስሌት ታስቦ ለተጠሪ እንዲከፈሉ በማለት ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41388

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች ፡-ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ ትዕግስት አሰፋ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. ከፍያለው ሞልቶት
2. የትምወርቅ አሰፋ
} ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩ ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በምዕራብ ሐረርጌ ከፍ/ፍ/ቤት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ላይ በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከሸክ ሁሴን ሚጨታ ድረስ ያለውን መንገድ ለማሻሻል በአደረገው እንቅስቃሴ መሠረት አመልካች ለሠጠው ብድር መያዣ የነበሩት በሚጨታ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች ውስጥ በአቶ ሚካኤል ከፍያለው ስም ተመዝግበው ያሉት የመኖሪያና የድርጅት ቤቶች መፍረሣቸውን፣ ንብረቶቹ አቶ ሚካኤል ከፍያለው ለራሣቸውና ለአቶ መራቸው የማነ ከአመልካች ላይ ለወሠዱት ብድር መያዣ መሆናቸውን፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለፈረሡት ቤቶች የሚከፈለውን ካሣ ለመያዣ ሠጪዎች ለመክፈል በዝግጅት ላይ መሆኑን አመልካች ገልፆ ይኸው አካል ከዚህ አድራጐት እንዲቆጠብ፣ ክፍያውን ለመያዣ ሠጪዎች ሣይሆን ለአመልካች እንዲከፍል እንዲደረግ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ ይኸው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የቀረበለት ፍ/ቤትም "ተከሣሹ" ባለሥልጣን መ/ቤት በተገቢው የክርክር ሂደት ባለመቅረቡ በስነ ሥርዓቱ መሠረት በሌለበት እንዲታይ አድርጐ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ ተጠሪዎች የካሣ ክፍያ እንዳይከፈልባቸው ውሣኔ ያረፈባቸውና በመያዣ ተይዘዋል የተባሉት ንብረቶች ህጋዊ ባለቤቶች መሆናቸውን፣ ከአመልካች ጋር ህጋዊ ወይም ከውል የመነጨ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ዘርዝረው ቀደም ሲል የተሠጠው ውሣኔ እንዲነሣላቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 'ን' መሠረት በማድረግ አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም የተጠሪዎች አቤቱታ ለአመልካች እንዲደርሰው እና ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከአደረገ በኋላ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የብድርም ሆነ የመያዣ ግንኙነት እንደሌለው ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ቀድሞ የተሠጠውን ውሣኔ በማንሣት ለንብረቶቹ ይከፈል የተባለው ካሣ ለተጠሪዎች ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ህዳር 08 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋፋት 7/ሠባት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ ክርክር ያስነሡት ንብረቶች በመያዣነት የተሠጠ በመሆኑ የካሣ ክፍያው ለእኔ ይገባል በማለት አመልካች ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ያጣው ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሠበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ ይህ ሠበር ችሎትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሚያዝያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ሠምቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ያጣው በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የተጠሪዎች ልጅ አቶ ሚካኤል ከፍያለው ለራሣቸው ለአቶ መራቸው የማነ ከአመልካች ላይ ለወሠዱት ብድር መያዣ ይሆኑ ዘንድ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን የመኖሪያና የድርጅት ቤቶችን መስማማታቸውን፣ የመያዣ ንብረቶች ስመ ሀብትም በዚህ ግለሠብ ስም የሚታወቅና የመያዣ ውሉም ንብረቱ በሚገኝበት የሚጨታ ልዩ ቀበሌ መመዝገቡ፣ ተጠሪዎች በአቶ ሚካኤል ከፍያለው ይታወቃል የተባለው የከተማ ይዞታ ምስክር ወረቀት በተጭበረበረ መንገድ የተሠጠ ነው በማለት የሚከራከሩና ይኸው ምስክር ወረቀት እስከአሁን ድረስ በተገቢው አካል እንዲሠረዝ ያላደረጉ መሆናቸውን ነው፡፡ እንግዲህ የአሁን ተጠሪዎች ልጅ አቶ ሚካኤል ከፍያለው ራሣቸውና እና አቶ መራቸው የማነ ከአሁኑ አመልካች ላይ ለወሠዱት የብድር ገንዘብ በካርታ ቁጥር 005፣ 034 እና 084 ላይ የተመለከቱትን በሚጨታ ከተማ የሚገኙትን የመኖሪያና የድርጅት ቤቶች መያዣ መስጠታቸው፣ እነዚህ ንብረቶች የመያዣ ሠጪው ይዞታ ለመሆናቸው የከተማ ይዞታ ምስክር ወረቀት ከመቅረቡም በላይ የሚጨታ ልዩ ቀበሌም ለአመልካቹ ተጨማሪ ደብዳቤ ፅፎለት የመያዣ ውሉ ከተደረገ በኋላ የመያዣ ውል ምዝገባ ማካሄዱ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የስር ፍ/ቤት የምስክር ወረቀቱን ዋጋ ሣይሠጠው ያለፈው የካርታ ቁጥር 005 በሐምሌ 1992 ዓ.ም.፣ የካርታ ቁጥር 034 በግንቦት ወር 1990 ዓ.ም. እንዲሁም የካርታ ቁጥር 005 በጥቅምት ወር 1989 ዓ.ም. ውስጥ የተሠጡ፣ በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ፣ የደርግ መንግስትን የሚመለከትና በተለይም የከተማ ቦታ ስም፣ ወረዳ፣ የመሣሠሉትና በሚለው ላይ ስርዝ ያለው እውነትነቱ አጠራጣሪ ነው በማለት ነው፡፡ ከዚህ የስር ፍ/ቤት መደምደሚያ መገንዘብ የሚቻለው በወቅቱ በክልሉ የሚሠራው በኦሮምኛ ሆኖ የምስክር ወረቀቱ እንዴት በአማርኛ ሊሆን ቻለ ከሚል ጥርጣሬ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ የምስክር ወረቀቱ ሐሰተኛ ስለመሆኑ በተጨባጭ የተረጋገጠ ነገር የለውም፡፡ በምስክር ወረቀቱ ላይ ያሉት እንደ ማህተም ያሉት ነገሮች የአስተዳደር ጽ/ቤት አይደሉም የሚል ግልፅና ተጨባጭ ምክንያት ስለመኖሩም የስር ፍ/ቤት አልገለፀም፡፡ ፍርድ ቤቱ ማህተሙ የአስተዳደር ጽ/ቤቱ አይደለም የሚል በቂ ምክንያት ካለውም ተቃራኒ ማስረጃ እንዲቀርብ ባደረገ ነበር፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ኃላፊነት ያለውና ይመለከተዋል የተባለው የቀበሌ ጽ/ቤቱም ለአመልካች የፃፈው ደብዳቤ የይዞታ ምስክር ወረቀቱን አጠራጣሪነት የሚያሣይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተቃራኒ ማስረጃ ሣይቀርብና የማህተሙ ሀሰተኛ መሆን ሣይረጋገጥ በጥርጣሬ ብቻ የሚደርስ ድምዳሜ ህጋዊ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለሆነም አመልካች ለማስረጃነት ላቀረበው የከተማ ይዞታ ምስክር ወረቀት ዋጋ የማይሠጥበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

የምስክር ወረቀቱ ዋጋ አለው ከተባለ ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች ህጋዊ ባለቤት መያዣ የሠጠው ግለሠብ አቶ ሚካኤል ከፍያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195 ድንጋጌ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የንብረቶቹ ህጋዊ ባለቤት ይኸው ግለሠብ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ከንብረቶቹ ጋር ተያይዞ የሚጠየቀውን ማንኛውንም መብትና ጥቅም ህጉ ጥበቃ የሚያደርገው ለዚሁ ባለንብረት ነው፡፡ ተጠሪዎች በንብረቶቹ ላይ አቶ ሚካኤል ከፍያለው ይዟል የተባለውን የምስክር ወረቀት በተቃራኒ ማስረጃ አላስተባበሉም፤ ስልጣን ባለው አካልም እንዲሠረዝ አላደረጉም ወይም በንብረቶቹ ላይ በህጉ አግባብ ያቋቋሙት የባለሀብትነት መብት የለም፡፡ ይህ የሚያሣየውም ተጠሪዎች በንብረቶቹ ላይ ህጉ ጥበቃ የሚያደርግላቸው መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ላይ መብትና ጥቅም የሌለው ወገን ደግሞ የዳኝነት ጥያቄ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ እና 359 ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ከመነሻውም ቢሆን ህጋዊ መሠረት የሌለው ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡

አመልካች የያዘው የመያዣ ንብረት በህጉ አግባብ የአቶ ሚካኤል ከፍያለው ነው እንጂ የይዞታ ምስክር ወረቀት በተጭበረበረ መንገድ የተያዘ ነው ከተባለም የመያዣ ውሉ ህጋዊ አይደለም ሊባል ይችል የነበረው አመልካች ከቅን ልቦና ውጪ በሆነ ሁኔታ መያዣውን መያዙን ሲረጋገጥ ነበር፡፡ ይህም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 3051/2/ ድንጋጌ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የአስተዳደር ክፍል የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብት መሆኑን አውቆለት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ከሠጠው ሠው ጋር የተደረገ የንብረት መያዣ ውል በህግ ፊት የፀና ሲሆን የምስክር ወረቀቱ የተሠጠበት ማስረጃ ፍርስ ሆኖ የተሠረዘ ቢሆንም በመያዣው የሚከራከረው ሠው በቅን ልቦና አለመሆኑ ካልተገለፀ በቀር የርስት መያዣው ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚፀና ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3051/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ በዚህም መሠረት የአመልካች መያዣ በህግ ፊት የማይፀናበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሣኔ ከላይ የተመለከቱትን የህግ ድንጋጌዎችን ያላገዘበ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በምዕራብ ሐረርጌ ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 04527 ሚያዝያ 09 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሠጥቶ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 55442 ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ በሆኑ ንብረቶች ላይ አመልካች የፀና የመያዣ ውል ስላለው ለንብረቶቹ በሚከፈለው ካሣም መብት አለው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ህዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም. ተሠጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ጽ/ሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39725

ሐምሌ 23 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ዓለምሸት ካሣሁን - ቀረቡ፡፡

2. አቶ ብርሃኑ ካሣሁን

3. አቶ ዳንኤል ካሣሁን

ተጠሪ፡- አቶ ሽመልስ እንዳለ - ጠበቃ ግርማቸው ኢላላ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 05596 ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 59564 ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በመቅረቡ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች የአባታቸው የአቶ ካሣሁን አስረስ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ በፍርድ ቤት የተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ በማያያዝ ሟች አባታችን በህይወት በነበረበት ጊዜ ሚያዝያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም. በተፃፈ የቤት ሽያጭ ውል ተከሣሹ ከአያታቸው አቶ ጥላሁን ሀይሌ በኑዛዜ ወራሽነት ያገኙትን በቀድሞ አጠራር በወረዳ 21 ቀበሌ 25 የቤት ቁጥር 424 የሆነውን በብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ገዝተዋል፡፡ ሆኖም የቤቱ ስመ ንብረት በተከሣሽ /ተጠሪ/ አያት ስም ያለ በመሆኑ የቤቱን ስመ ንብረት ወደራሳቸው ካዛውሩ በኋላ ካርታውን እንዲሰጡን ይወስንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርበው ውል አልተዋዋልኩም፡፡ የከሳሾችን /የአመልካቾችን/ አባት ወክሎ በውሉ ላይ የተፈረመው ሰው ሟችን በመወከል ቤት ለመግዛት ስልጣን የሌላቸው ሰው ናቸው፡፡ ከእኔ ጋር 1989 የተደረገው ውል አባቱ ጋር 1987 የተደረገውን ውል የሚያጣቅሰው ነው፡፡ የቤቱን ሰነድ ለማስረከብ ግዴታ የገቡት ውሉ በተደረገ በአንድ ወር ውስጥ ስለሆነና ከሣሾች በአንድ ዓመት ውስጥ ውሉ እንዲፈፀምላቸው ያልተጠየቁ ስለሆነ ውሉን ለመፈፀም አልገደድም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሣሽ /ተጠሪ/ የአሁን አመልካቾች /ከሣሾች/ በሽያጭ ውሉ ምክንያት የያዙትን ቤት እንዲለቁና ኪራይ እንዲከፍሏቸው ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁጥር 3754 ክስ አቅርበው በአመልካቾች /ከሣሾች/ አባትና በተጠሪ /በተከሣሽ/ መካከል ሚያዝያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም. የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ያለመሆኑ በፍርድ ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ ተጠሪ /ተከሣሽ/ ውሉንና ፊርማቸውን በመካድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች ውሉ ከተደረገበት ከሚያዝያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲፈፀምላቸው ያልጠየቁ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተከሣሽ /ተጠሪ/ ውሉን ተገድዶ የመፈፀም መብታቸውን አጥተዋል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካቾች ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አመልካቾች በውል የተረከቡትን ቤት እንዲያስረክቡትና የቤት ኪራይ እንዲከፍሉት ክስ አቅርቦ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውሉን መደረግና የቤት ሽያጭ ውሉን አስመልክቶ ያቀረቡትን ክርክር ማስረጃ በመመዘን በአመልካቾች አባትና በተከሣሽ መካከል ሕጋዊ የቤት ሽያጭ ውል ያለ መሆኑ በመዝገብ ቁጥር 3754 መጋቢት 20 ቀን 1997 ዓ.ም ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ቤቱን በሕጋዊ ሽያጭ ውል ነው የያዛችሁት ቤቱን ለተጠሪ አታስረክቡም ኪራይም አትከፍሉም በማለት በሌላ መዝገብ ከወሰነ በኋላ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 የተዛባ ትርጉም በመስጠት ውሉን በግዳጅ ለማስፈፀም አትችሉም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕጉን ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የማይንቀሳቀስ ንብረት የሽያጭ ውል አፈፃፀም የሚያስተጓጉል የሕግ ትርጉም በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ሚያዝያ 14 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ አመልካቾች ውሉ በፍርድ ሀይል እንዲፈፀምላቸው የጠየቁት ውሉ ከተደረገ ከዘጠኝ ዓመት ከሁለት ወር ካለፈ በኋላ ነው፡፡ በሌላ በኩል የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3754 ውሣኔ ከሰጠ በሦስት ዓመት በኋላ ስለሆነ ውሉ በግዳጅ ይፈጽምልኝ ብለው የመክሰስ መብታቸውን ያጣሉ በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጉም ስህተት የለበትም፡፡ ስለዚህ በሥር ችሎቱ የኖሩበትን ቤት ኪራይ ከፍለው እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይስጥልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ በዚህ ጉዳይ የሚሠራው የአሥር ዓመት የይርጋ ጊዜ የሚደነግገው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ድንጋጌ እንጂ የሥር ፍርድ ቤት የጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 አይደለም፡፡ ተጠሪ በፍርድ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘውን ጉዳይ ከሥነ ሥርዓት ውጭ በማንሣት ሰበር ችሎቱ ቤቱን እንዲረከብና ኪራይ እንዲከፈለው እንዲወሰንለት ያቀረበው ጥያቄ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካቾችና ተጠሪዎች በሰበር ያደረጉት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአመልካቾች አባትና በተጠሪ መካከል ሚያዝያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም. የተደረገው ውል በፍርድ ቤት ውሣኔና አስገዳጅነት እንዲፈፀምላቸው አመልካቾች ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት ይህ ችሎት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 አተረጓጎም አስመልክቶ በሰበር መዝገብ ቁጥር 38935 መጋቢት 3 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠውን የሕግ ውሣኔና በዚህ መዝገብ ያለውን ልዩ ሁኔታ ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ገዢው ውሉን በፍርድ ቤት ውሣኔ እንዲፈጽምለት ለመጠየቅ የሚችልበት የጊዜ ገደብ ያለፈበት ስለሆነ ውሉን ለመፈፀም አልገደድም የሚለውን መከራከሪያ ማቅረብ የሚችለውና ክርክሩ ተቀባይነት የሚያገኘው ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን ለገዢ በማያሻማ ሁኔታ ያሣወቀ መሆኑን በበቂ ሁኔታ ለማስረዳት ሲችል እንደሆነ ከላይ በተገለፀው መዝገብ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ 1989 ዓ.ም. ጀምሮ አመልካቾች ቤቱን እንዲያስረክቡት ኪራይም እንዲከፍሉት ክስ ከማቅረቡ በፊት ውሉን ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ መንገድ ለአመልካቾች ያሣወቀ ስለመሆኑ የቀረበው ማስረጃ ባለመኖሩ 1989 ጀምሮ አመልካቾች ውሉ እንዲፈፀምላቸው ባለመጠየቃቸው መብታቸውን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ታግዷል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ሻጭ የሸያጭ ውሉን ለመፈፀም ፈቃድና ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ መንገድ ለገዢ ከሚያሣውቅበት አንደኛው መንገድ የሸያጭ ውሉ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት የሚያቀርበው ክስ መሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥር 38935 ሻጭ ለገዢ በማያሻማ መንገድ ውሉን ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን አሳውቋል የሚባለው ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው የሚለውን ነጥብ ለመተንተን በሰጠው ምክንያት በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ሆኖም ሻጭ የቤት ሽያጭ ውሉ ይፍረስልኝ የሚል ክርክር ማቅረቡ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አንፃር የሚኖረው ውጤት ምንድነው? የሚለው ነጥብ ውሣኔ ያላገኘ ነጥብ በመሆኑ በዚህ መዝገብ እልባት ማግኘት ያለበት ነጥብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሻጭ የውል ይፍረስልኝ ክስ ለፍርድ ቤት ማቅረቡ ውሉን ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ለገዢ በማያሻማ መንገድ ከማሣወቅ ያለፈ ምክንያትና ውጤት ያለው ተግባር ነው፡፡ ሻጭ ውሉ እንዲፈርስ ሲጠይቅ ውሉ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለማቋቋም የሚያስችሉ ጉድለቶች ያሉበት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች እንደ ሕግ ሆኖ ሊገዙበት የማይገባ መሆኑን የሚያሣዩ የውሉን ሕልውና ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባና የውል ሕጋዊነት በፍርድ ቤት ተመርምሮ ፈራሽ እንዲባል ወይም እንዲሠረዝ የሚቀርብ ነው፡፡ የውሉ ሕጋዊነትና ሕልውና ጥያቄ ተነስቶ በፍርድ ቤት በሚመረመርበት ጊዜ ገዢ ውሉ ሕጋዊ መሆኑን ከማሣየትና ከማስረዳት አልፎ ውሉ በግዳጅ እንዲፈጽምለት የመጠየቅ ግዴታ አይኖርበትም፡፡ ከዚህ አንፃር ውሉ በፍርድ ቤት ፈራሽ እንዲሆን ወይም እንዲሰረዝለት በውሉ የሚገደድበት ሁኔታ ይቋረጣል፡፡ በሌላ በኩል በክርክሩ ከተረታ ገዢ ሕጋዊ ተፈፃሚነትና አስገዳጅነት ባለው ውሉ ንብረቱን የገዛ መሆኑ ከሻጭ ጋር ባደረገው የውል ሰነድ ብቻ ሣይሆን በፍርድ ቤት ውሣኔ የተረጋገጠለት የፍርድ ባለመብት ይሆናል፡፡ ስለሆነም ገዢ ፍርድ ቤቱ ሕጋዊነቱንና አስገዳጅነቱን መርምሮ በፍርድ ያረጋገጠውን ውል እንዲፈጽምለት ሻጭን የመጠየቅ መብቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 384/ሀ/ በተደነገገው አስር ዓመት ጊዜ ውስጥ እንጂ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው የአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ የሚገደብ አይደለም፡፡ ስለዚህ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀፅ 3 የተቀመጠው የጊዜ ገደብ በዚህ ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ፍርድ ቤቶች ለቀረበላቸው ጉዳይ የሚሰጡት ውሣኔ የተያዘውን ጉዳይ ለመቋጨት የሚችል መሆን እንዳለበት ከፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3754 የሰጠው ውሣኔና በዚህ ጉዳይ የሰጠው ውሣኔ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ እና ጉዳዩ በእንጥልጥል የሚያስቀሩ ናቸው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች ቤቱን እንዲመልስላቸውና ኪራይ እንዲከፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ከአመልካች ጋር የገቡትን የቤት ሽያጭ ውል መሠረት በማድረግ ተቀባይነት የለውም በማለት በመዝገብ ቁጥር 3754 ወስኗል፡፡ አመልካች ያቀረቡት የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ ደግሞ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በማድረግ ውድቅ አድርጓል፡፡ እነዚህ ውሣኔዎች ተጠሪም ቤቱን ለማስመለስ የማይችሉበት አመልካችም የቤቱ ባለሀብት በማይሆኑበት ሁኔታ ጉዳዩን በእንጥልጥል የሚያስቀሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም አመልካች እና በተጠሪ መካከል ሕጋዊ አስገዳጅነት ያለው ውል እንዳለ በፍርድ ካረጋገጠ በኋላ አመልካች ያቀረቡትን የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 በመጥቀስ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ውሉ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት ጥያቄ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረጉትን ውል ለመፈፀም ይገደዳሉ ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39803

ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አለኸኝ ገ/ሕይወት - ጠበቃ አበባው መላኩ

ተጠሪ፡- እነ እማሆይ አጢነሽ በቀለ /3 ሰዎች/ - ጠበቃ ብናልፈው ነጋ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 492 የሆነውን ቤት ሟች ወ/ሮ ደለለች በቀለ በ1974 ዓ.ም. በተደረገ የስጦታ ውል በስጦታ ያስተላለፉልኝ ስለሆነ የስጦታ ውሉ ይጽደቅልኝ የሚል አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤትም ስጦታውን በማጽደቅ ውሣኔ መስጠቱን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን ተጠሪዎች የሟች ወ/ሮ ደለለች በቀለ ሕጋዊ ወራሾች መሆናቸውን ገልጸው ፍ/ቤቱ ስጦታውን በማጽደቁ የሰጠው ውሣኔ መብታቸውን የነካ እንደሆነና የስጦታ ውሉም የተደረገው የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ ላይ እንደተመለከተው ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ የስጦታ ውሉ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1720/1/ ላይ እንደተመለከተው እንደ ረቂቅ ከሚቆጠር በስተቀር የፀና ውል ስላልሆነ ቀደም ሲል በ26/7/99 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ስጦታው ሊጸድቅ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ በማይጸና ውል ላይ ተመስርቶ ስለሆነ ውሣኔው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 360/2/ መሠረት ተሰርዟል በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ 337 መሠረት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የስጦታ ውሉ በሕግ አግባብነት ያልተደረገ ስለሆነ እንደ ረቂቅ ከሚቆጠር በስተቀር የጸና አይደለም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443፣ 881 እና 882 አኳያ አግባብነት ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በቃል አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች አጥብቀው የሚከራከሩት የሚች ወ/ሮ ደለለኝ በቀለ ሕጋዊ ወራሾች ነን፣ አመልካች ስጦታ እንዲጸድቅላቸው ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ቤቱ ተቀባይነት ማግኘቱ መብታችንን የነካ ከመሆኑም በላይ ስጦታውም ቢሆን በሕግ አግባብነት ያልተደረገ ስለሆነ ይህንኑ ስጦታ ፍ/ቤቱ በማጽደቅ የሰጠው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ነው፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ስጦታው የፀና ስላልሆነ የቀድሞው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል ወደሚል መደምደሚያ ሊደርስ የቻለው ስጦታው በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገ እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ ላይ እንደተመለከተው ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ የፀና አይደለም የሚል ነው፡፡

በእርግጥ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ውሎች በሕግ ፊት የፀኑ ለመሆን ሁለት ሁኔታዎችን ማሟላት ይገባቸዋል፡፡ በአንድ በኩል ውሉ በጽሁፍ መደረግ የሚገባው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ውሉ በአዋዋይ ፊት ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ፊት መከናወን ያለበት መሆኑ ነው፡፡

በሌላ በኩልም በአመልካችና በሚች ወ/ሮ ደለለች በቀለ መካከል ተደርጓል የተባለው የስጦታ ውል ሲሆን በማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም በማይንሰሳቀስ ንብረት ላይ መብትን የሚሰጥ ስጦታ በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ አሠራር ዓይነት ካልተደረገ ፈራሽ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2443 ላይ ተመልክቷል፡፡ ግልጽ ኑዛዜ የሚደረግበት ሥርዓት ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 881 ላይ የተመለከተ ሲሆን ኑዛዜ በአራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበና ይህም ሥርዓት ስለመፈጸሙና ኑዛዜውም የተደረገበት ቀን በሰነዱ ላይ ካልተመለከተ እንደዚሁም ተናዛዡና ምስክሮቹ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም የአውራ ጣት ምልክታቸውን ካላደረጉበት ፈራሽ እንደሚሆን በሕጉ ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይም በአመልካችና በሚች ወ/ሮ ደለለች በቀለ መካከል የተደረገው የቤት ስጦታ ውል ይህንን ሥርዓት አሟልቶ የተከናወነ ስለመሆኑ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ መረጋገጡን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

እንግዲህ በአንድ በኩል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ ላይ እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን የሚመለከቱ ውሎች ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ፊት ካልተደረጉ የጸኑ ሊሆኑ እንደማይችሉ የተመለከተ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለተ የሚደረጉ የስጦታ ውሎች ይህንን ሥርዓት ተከትለው መከናወን እንዳለባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2443 ላይም ሆነ 881 ላይ አልተመለከተም፡፡ እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች እርስ በርሳቸው ያልተጣጣሙ ከሆነ ገዢው ድንጋጌ መሆን ያለበት የትኛው ነው የሚለው ዕልባት የሚያሻው ነው፡፡

ከሕጉ አቀራረጽ እንደሚታየው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 የሚገኘው ጠቅላላ ስለ ውሎች በሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕጉ ምዕራፍ ስለ ውሎች አመሠራረት መሪ ደንቦች በሚደነግገው ክፍል ሥር ነው፡፡ በዚህ ጠቅላላ የውል ሕግ ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት ማንኛውም ዓይነት ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ካልተደረገ የጸና ስለማይሆን ፈራሽ ሊሆን እንደሚችልና ለመብትም ሆነ ለግዴታ ምንጭ ሊሆን እንደማይችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና የማይንቀሳቀስ ንብረትን ስጦታ በተመለከተ በተለይ በሚገዛው ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2443 እና 881 ድንጋጌ መሠረት ይህ ሥርዓት መከናወን እንዳለበት አልተመለከተም፡፡ በጠቅላላ ሕግና በልዩ ሕግ መካከል አለመጣጣም ወይንም ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ ልዩ ሕግ የበላይ ሆኖ ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደሚችል /The Special prevail over the general/ ከሕግ አተረጓጎም መርህ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም አመልካችና ሚች ወ/ሮ ደለለች በቀለ ያደረጉት የቤት ስጦታ ውል፣ ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ስጦታ በሚደረግበት ጊዜ ይህ ሥርዓት መከናወን እንዳለበት ለጉዳዩ አግባብነት ባለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443 እና 881 ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የፍትሐብሔር ሕ/ቁ. 1723/1/ በመጥቀሱ የስጦታ ውሉ የፀና አይደለም በማለት ይህንኑ መሠረት በማድረግ አስቀድሞ የተሰጠው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል ሲሉ የሰጡት ውሣኔ ከሕግ አተረጓጎም መርህ አንፃር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35057 በ2/10/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ፣ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 68860 በ10/11/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በሟች ወ/ሮ ደለለኝ በቀለ መካከል የተደረገው ውል በሕግ አግባብ ስለሆነ የጸና ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በ26/7/99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31963

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ዓብዱልሐኪም ሁሴን - ከጠበቃ ወ/ሥላሴ ብርቱ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ቀነኒ ሁንዴ - ከጠበቃ ጋሻው ተገኝ ጋር ቀረቡ

2. ላሊበላ ኢንጅነሪንግ - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ክርክሩም የማይንቀሣቀስ ንብረት በፍርድ አፈፃፀም የሚሸጥበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡

በዚህም መሠረት በአንደኛ ተጠሪና በሁለተኛ ተጠሪ መካከል የነበረው የፍርድ አፈፃፀም ክርክር ቀጥሎ ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ የሆነ ቤት በሐራጅ ተሸጦ ለሁለተኛ ተጠሪ መከፈል የሚገባው ዕዳ እንዲከፈል የአፈፃፀም ትእዛዝ ተሰጥቶ ይኸው ቤት ለአሁን አመልካች ከተሸጠ በኋላ አንደኛ ተጠሪ የሐራጅ ሽያጩ በሚካሄድበት ጊዜ ግዙፍ የሆነ ጉድለት የተፈፀመ ስለሆነ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 445 መሠረት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ የሆነው ቤት የተሸጠው ከግምት በላይ ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 445 መሠረት በማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የተደረገ ጨረታ ሊፈርስ የሚችለው በአሻሻጡ ሥርዓት ላይ ግዙፍ የሆነ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ወይንም የማታለልና የማጭበርበር ተግባር ተፈጽሞ የተገኘ ከሆነና ይህም አቤቱታ በሚያቀርበው ወገን ላይ ቀጥተኛ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ከተረጋገጠ ነው፤ በተያዘው ጉዳይ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ተፈጽሟል ቢባል እንኳን አንደኛ ተጠሪ በዚህ ድርጊት ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ ያላስረዱ ስለሆነ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ የቀረበው አቤቱታ አግባብነት የለውም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የአሁን አመልካችም በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ግራ ቀኙን እንደዚሁም የጣልቃ ገቡን ክርክር መርምሮ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 423/መ/ መሠረት ፍ/ቤቱ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ በሚወጣበት ጊዜ ገዢው ንብረቱን ከመግዛቱ በፊት ማወቅ ይገባዋል ተብሎ የሚገመተውን ማንኛውንም ዝርዝር ሁኔታ በትክክል መግለጽ እንዳለበት የተመለከተ ሲሆን ይሁን እንጂ የፍርድ አስፈፃሚው ተወካይ ከተጫራቾች ለሽያጭ የቀረበው ቤት የፍ/ባለእዳ የግል ንብረት ነው ወይስ የመንግሥት በማለት ለቀረበለት ጥያቄ "የቀበሌ ወይም የኪራይ ቤቶች" ሊሆን ይችላል በማለት በሐራጅ ስለሚሸጠው ቤት ትክክለኛውንና አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ለገዥዎች አለመስጠቱ እንደዚሁም የአሁን አመልካች በጨረታው ለመሣተፍ ከመጡት ሰዎች ለተወሰኑትም ቢሆን ቤቱን ከአሁን አንደኛ ተጠሪ ላይ የተከራዩት መሆኑን በመግለጽ እንዳይጫረቱባቸው ለዚህም ውለታ ብር 1000(አንድ ሺህ) እንደሚሰጡ ይናገሩ እንደነበር በምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑና በአጠቃላይ ሲታይም በጨረታው ከፍተኛ ዋጋ ሊቀርብ ባለመቻሉና ይህም በቀጥታ ተጎጂ የሚያደርገው ይግባኝ ባይን /የአሁን አንደኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪን/ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት እነዚህን ግድፈቶች በአግባቡ ሣይመለከት ጨረታው ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በሚል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ በመቀበል ይግባኙን ሠርሏል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህም ችሎት የሐራጅ ሽያጩ ግዙፍ የሆነ ጉድለት ያለበት ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት በፍርድ አፈፃፀም በሐራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በሽያጩ አካሄድ ጉድለት የተፈፀመ ስለሆነ ሐራጁ ሊፈርስ ይገባል የሚለው ወገን አቤቱታውን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 445 መሠረት ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ይዘትም፡-

"በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት የተሸጠ እንደሆነ የፍርድ ባለገንዘቡ ወይም ከሽያጩ ገንዘብ ድርሻ ያለው ወይም የንብረቱ ተካፋይ የሆነ ወይም በንብረቱ መሸጥ ምክንያት መብቱ የሚነካ ማናቸውም ሰው በአሻሻጡ ሥርዓት ላይ ግዙፍ የሆነ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ወይም የማታለልና የማጭበርበር ተግባር ተፈጽሟል በማለት ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ ማመልከቻ ለማቅረብ ይችላል፡፡

ስለሆነም የተጠቀሰው ተግባር በአመልካቹ መብት ላይ ቀጥታ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ ለማዘዝ አይቻልም"፡፡ በሚል ይነበባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አንደኛ ተጠሪ የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በማለት አቤቱታቸውን ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት በሐራጅ እንዲሸጥ የታዘዘው የቤት ቁጥር 236 ሆኖ ሣለ የተሸጠው ግን የቤ.ቁ. 244 ተብሎ ነው፤ የሐራጅ ሽያጩ በሚከናወንበት ጊዜም ተጫራቾች "ቤቱ የቀበሌ ነው ወይንስ የኪራይ ቤቶች" ብለው ሲጠይቁ አጫራቹ " የቀበሌ ወይንም የኪራይ ቤቶች" ይሆናል ብሎ የተናገረ ከመሆኑም በላይ ቤቱን የገዛው ሰው ሌሎች ተጫራቾች ብልጫ ገንዘብ ሰጥተው እንዳይጫረቱ ለእያንዳንዳቸው ብር 1000(አንድ ሺህ) በቼክ እንደሚሰጣቸው ተናግሯል የሚሉትን በምክንያትነት በመጥቀስ ነው፡፡

በፍርድ አፈፃፀም ማንኛውም ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በሚወሰንበት ጊዜ የሐራጅ ሥርዓቱ የሚከናወንበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 423 ላይ የተዘረዘረ ሲሆን በዚህም ድንጋጌ መሠረት ገዢው በሐራጅ ስለሚሸጠው ንብረት ማወቅ ስለሚገባው ዝርዝር በሐራጅ ማስታወቂያው መጠቀስ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡

በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያው የቤ.ቁ. 244 "ን" እንደሚመለከት ለተጫራቾች ይፋ ሆኖ የተሸጠው ግን የቤት ቁጥር 236 ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ግን በሐራጅ ማስታወቂያው ሽያጩ የሚመለከተው የቤት ቁጥር 244"ን" እንደሆነ ቢጠቀስም በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል የተገመተውና ገዢዎችም እንዲመለከቱት ተደርጎ የተጫረቱት በማስታወቂያው ላይ የተመለከተውን የቤ.ቁ. 244"ን" ሣይሆን ቁጥር 236"ን" እንደሆነም ጭምር መረጋገጡን ተገንዝበናል፡፡ ይህ ሁኔታ በአፃፃፍ ስህተት ምክንያት የተፈጠረ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ሲሆን አንደኛ ተጠሪም በዚህ ስህተት ምክንያት ክፍ ብሎ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 445 መሠረት ቀጥተኛ የሆነ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ አላስረዱም፡፡

ሐራጅ አስፈፃሚው ቤቱ የቀበሌ ወይንም የኪራይ ቤቶች ይሆናል ብሎ ስለመናገሩ አንደኛ ተጠሪ ባቀረቧቸው ምስክሮች የተረጋገጠ ቢሆንም ይህ ሁኔታ ተጫራቾችን እንዳይጫረቱ ስለማድረጉና በዚህም ሣቢያ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡ ምክንያቱም ሕጉ በአሻሻጡ ሂደት ግድፈት /irregularity/ እንዳይኖር የሚከላከለውን ያህል ይህ ተፈጽሟል የሚባል ግድፈት በአመልካቹ መብት ላይ ቀጥተኛ ጉዳት ያደረሰ ስለመሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ጨረታው መፍረስ እንደማይገባው እኩል ጥበቃ ስለሚያደርግ ነው፡፡ ንብረቱን የገዙት ተጫራች /የአሁን አመልካች/ ያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቀናቃኝ ብቻቸውን ለመግዛት ባላቸው ፍላጎት ሌሎች ተጫራቾች እንዳይጫረቱ ለእያንዳንዳቸው ብር 1000(አንድ ሺህ) በቼክ እንደሚሰጡ ቃል ገብተዋል የተባለውን በተመለከተ አንደኛ ተጠሪ ካቀረቧቸው ምስክሮች መካከል የተወሰኑት ይህ ፍሬ ነገር ሲነገር መስማታቸውን በመጠቀስ ለፍ/ቤቱ የምስክርነት ቃል መስጠታቸውን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

በሌላ በኩልም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተሸጠው በ2ኛ ጨረታ ሲሆን 2ኛ ጨረታ በሚከናወንበት ጊዜም የሐራጅ ሽያጩ የሚደረገው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 428 መሠረት ነው፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አኳያም ንብረቱ የሚሸጠው በሁለተኛው ጨረታ ጊዜ ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርብ ተጫራች እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ሁለተኛ የሐራጅ ማስታወቂያ ሲወጣ 44 ሰዎች በጨረታው ተመዝግበው እንደነበር 37 ሰዎች ደግሞ በጨረታው ተካፋይ እንደነበሩና በመጨረሻም 10 ከፍተኛ ዋጋ በሰጡ ተጫራቾች መካከል ፉክክሩ ቀጥሎ አመልካች ብር 101.000/ አንድ መቶ አንድ ሺህ/ በመስጠት ጨረታውን እንዳሸነፉና የቤቱ የግምት ዋጋም ብር 88,830 /ሰማንያ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሠላሳ/ እንደነበር ከመዝገቡ ተገንዝበናል፡፡

ከዚህም የተረዳነው ለጨረታው ከተመዘገቡት 44 ሰዎች መካከል 37 ሰዎች በጨረታው ተሣትፈው መገኘታቸውና በመጨረሻም 10 ሰዎች ቀርተው ጨረታውን መቀጠላቸው ሲታይ አመልካች ሌሎች ሰዎች እንዳይጫረቱ የብር 1000(አንድ ሺህ) ቼክ ለመስጠት ቃል ገብተዋል ተብሎ በአንደኛ ተጠሪ ምስክሮች የተነገረው ጥርጣሬ ውስጥ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በዚህ ምክንያት አንደኛ ተጠሪ ቀጥተኛ የሆነ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑም አላስረዱም፡፡

ሲጠቃለልም አንደኛ ተጠሪ ጨረታው ሊፈርስ ይገባል በማለት በምክንያትነት የጠቀሷቸው ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 445 ላይ እንደተመለከተው በመብታቸው ላይ ቀጥተኛ ጉዳት ያደረሱባቸው ስለመሆኑ ያላስረዱ መሆኑን የተገነዘብን ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጨረታው ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያለው ሆኖ ሣለ ነገር ግን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጨረታው ሊፈርስ ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 21375 በ8/2/98 ዓ.ም ጨረታው ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
2. የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 42380 ጎንደር 26 ቀን 1999 ዓ.ም ጨረታው ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሽረነዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35018

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- በዛብህ አበበ - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ሕይወት ጥላሁን ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

አከራካሪው ጉዳይ ቀደም ሲል በተሰጠው ውሳኔ መሰረት የተጀመረውን የአፈጻጸም ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው የአፈጻጸሙን ክርክር የያዘው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀጠሮው ቀን የፍርድ ባለመብት (የአሁኑ አመልካች) ጠበቃ አልቀረበም በሚል ምክንያት በመስጠት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይህን ተከትሎ የቀረበለትን የመዝገብ ይከፈትልን ጥያቄም ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም መዝገቡ አይከፈትም በመባሉ የተፈጸመ ስህተት(ጉድለት) የለም ብሏል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎችም አመልካች ጥር 10 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የአፈጻጸም መዝገቡ የተዘጋበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ (ትእዛዝ) እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ትእዛዝ የተሰጠበት መዝገብ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም ሲባል የተከፈተ ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መዝገቡን የዘጋው የፍርድ ባለመብቱ ጠበቃ በቀጠሮው ቀን አልተገኘም በሚል ብቻ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን ለምን ዝም ብሎ አይጠብቅም ነበር ወይም ተለዋጭ ቀጠሮ አይሰጥም ነበር ሊባል ስለማይቻል በመዝጋቱ ረገድ ስህተት ነበር ማለቱ ተገቢ አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች እንደፍርዱ/ውሳኔው/ አልተፈጸመልኝም የሚል እስከሆነ ድረስ መዝገቡ ከነጭራሹ አይከፈትልህም (አይንቀሳቀስም) የሚባልበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 384 እንደተደነገገው የአፈፃፀም ጥያቄ እንደገና ለማንቀሳቀስ የማይቻለው በሕጉ እንደተመለከተው በይርጋ ቀሪ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያቀረበው የአፈፃጸም ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኗል አልተባለም፡፡ በመሆኑም ያልተፈጸመ ፍርድ አለ እስከተባለ ድረስ መዝገቡ ተከፍቶ አፈጻጸሙ የማይቀጥልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ትእዛዝ ከዚህ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20286 ሰኔ 5 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ እና ይህን ትእዛዝ በማጽናት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57130 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተከፈተው የአፈፃጸም መዝገብ ተከፍቶ(ተንቀሳቅሶ) አፈጻጸሙ ይቀጥል በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 21359

ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢት/ያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ዝግአለ አሰፋ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ አቶ ተገኝ ማንደፍሮ /ሁለት ሰዎች/ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመው በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሽ፣የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች ሠኔ 05 ቀን 1994 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ተከሣሽ መ/ቤት ቀደም ብሎ ከደንበኞች ከሚሠበሰበው የቆጣሪ ገንዘብ በኮሚሽን እየታሰበ ደመወዝ ሲከፍላቸው ከቆየ በኋላ የአከፋፈሉን ሥርዓት በመለወጥ የኮሚሽን ክፍያውን ከማቋረጡም በተጨማሪ መደበኛ ደመወዝ እንዲስተካከልም የህብረት ስምምነቱ መሠረት ተደርጎ ቃለ ጉባዔ ተይዞ መጋቢት 27 ቀን 1993 ዓ.ም እንደቅጥር ዘመን ደረጃና ደመወዝ እንዲስተካከል መወሰኑንና ሌሎች መሠል ሠራተኞችም በክልላቸው አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክስ አቅርበው በአዋጅ ቁጥር 42/1985 መሠረት የደረጃም ሆነ የደመወዝ መስተካከል የተፈፀመላቸው መሆኑን በማግለጽ ጉዳያቸው አንድና ተመሣሣይ በመሆኑ ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ የገንዘብ አሠባሰብ ሥርዓት ከ1991 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ መለወጡን በማግለጽ የከሣሾች ደመወዝና የደመወዝ ማስተካከያ ጥያቄ ስድስት ወር ውስጥ ሣይቀርብ ከሁለት ዓመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ፣ የመጋቢት 27 ቀን 1993 ዓ.ም ቃለ ጉባዔም በአዲስ አበባና አካባቢው ለሚሠሩት ሠራተኞች የሚሠራ ከመሆኑም በላይ የይርጋ ማቋረጫ ምክንያት ሊሆን እንደማይገባ በመግለጽ ክሱ በብይን ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ቦርድም የግራ ቀኙን ክርክር ከተመለከተ በኋላ የተጠሪዎች ክስ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስኖ በዚህ ውሣኔ ያልተስማሙት የአሁኑ ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለድሬዳዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የተጠሪዎች ጥያቄ የውሣኔ ይፈፀምልኝ ሁኖ እያለ በይርጋ መታየቱ አግባብ አይደለም፣ በውሣኔው መፈፀም ዙሪያም ሆነ በውሣኔው ላይ የቀረበ መቃወሚያ ወይም የተያዘ ጭብጥ የለም በማለት ተጠሪዎች በጥያቄአቸው መሠረት በአመልካች ድርጅት ሊፈፀምላቸው ይገባል ሲል የቦርዱን ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን በአፈፃፀም ሊታይ የሚገባው ነው፤ ማለቱ የተጠሪዎችን የስር ክስ ማመልከቻ በአግባቡ ያላገናዘበ መሆኑን፣ ለፍ/ቤቱ በይግባኝ ሰሚነቱ በአዋጅ የተሰጠው ስልጣን የቦርዱን ውሣኔ ለመሻር የሚያስችል አለመሆኑን በመዘርዘር ውሣኔው የሥነ-ሥርዓት ሕጉንና በስራ ላይ የነበረውን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ስለሆነ ሊሻር ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ተደርጎም ሠኔ 05 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የአመልካችን የሠበር አቤቱታ የቅሬታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነጥቦች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የማያሣዩ መሆናቸውን በሥነ-ሥርዓት ጉድለት ብቻ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የሚሻርበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመዘርዘር መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከመዝገቡ ግልባጭ፣ ከግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክርና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቦርዱን ውሣኔ መሻሩ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የቦርዱን ውሣኔ ለመሻር ምክንያት ከአደረጋቸው ነጥቦች አንዱ ተጠሪዎች ለቦርዱ ያቀረቡት ጥያቄ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ይሠሩ የነበሩት/101/አንድ መቶ አንድ/ ሠራተኞች አቅርበው ያስወሠኑት ውሣኔ መብቱ የሚመለከተን ስለሆነ በክርክሩ ተካፋይ ባንሆንም ተፈፃሚ ሊሆንልን ይገባል የሚል በመሆኑና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5/4/ መሠረትም ተቀባይነት ያለው ነው በሚል ነው፡፡ ይህም የሚያሣየው የተጠሪዎች አቤቱታ ቀጥታ ክስ ሣይሆን የአፈፃፀም ክስ የነበረ ስለመሆኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት ማመኑን ነው፡፡

ይሁን እንጂ ተጠሪዎች ለቦርዱ ክሣቸውን ሲመሠርቱ ሌሎች ተመሣሣይ ስራ በአዲስ አበባና አካባቢው የሚሠሩ እነ አቶ አያሌው ልዑልሰገድ /101 ሠዎች/ የተባሉ ሠራተኞች በክልላቸው በሚገኘው የአሠሪና ሠራተኛ ጉደይ ወሣኝ ቦርድ ጥያቄያቸውን አቅርበው ማስወሰናቸውን ከመግለጽ ውጪ በሌሎች ሠራተኞች ውሣኔ እንዲፈፀምላቸው በግልጽ ዳኝነት መጠየቃቸውን የክርክሩ ሂደት አያሣይም፡፡ በሌሎች ተመሣሣይ በሌላ አካባቢ የተሰጠ ውሣኔ እንዲፈፀምላቸው ዳኝነት ጠይቀው የነበሩ ስለመሆኑም ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ይህ ችሎት መገንዘብ የቻለው የተጠሪዎች ጥያቄ በዋናው ክርክር የተሰጠውን ውሣኔ ቦርዱ እንዲያስፈጽምላቸው የቀረበ የፍርድ አፈፃፀም ክርክር አለመሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የአንድ የፍርድ አፈፃፀም ክርክር አጀማመር "ሥርዓት" በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ የዚህ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ የፍርድ ባለመብት በፍርዱ መሠረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፍ/ቤቱ ሲያቀርብ የፍርድ አፈፃፀም ክርክር እንደሚጀምርና የአፈፃፀም ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ በፍርድ የበሰለ ወይም የተፈረደ ፍርድ መኖሩን የሚያሣይ ማመልከቻ መያዝ እንደአለበት ያስገነዝባል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ይህንኑ ሥርዓት አሟልቶ የቀረበ ማመልከቻ ስለመኖሩ የክርክሩ ሂደት አያሣይም፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5/4/ ለውሣኔው መሠረት ማድረግ ይችል የነበረው የተጠሪዎች ጥያቄ ከላይ በተጠቀሰው የአፈፃፀም ሥነ ሥርዓት አጀማመር ቢሟላ እና ውሣኔውን ለማስፈፀም የእነ አቶ አያሌው ሉዑልሰገድ /101 ሠዎች/ ጉዳይ ተመልክቶ ውሣኔ የሰጠው በአዲስ አበባና አካባቢው የሚገኘው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የአፈፃፀም የውክልና ሥልጣን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 371 እና 372 መሠረት ሰጥቶት በሆነ ነበር፡፡ ከዚህ የውክልና የውሣኔ አፈፃፀም ውጪ ፍርድ ያልሰጠ ፍ/ቤት በሌላ ፍ/ቤት ወይም ወሣኝ አካል የተሰጠ ፍርድ በራሱ የሚያስፈጽምበት ሥነ ሥርዓት የለም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378/1/ ድንጋጌ የሚያሣየውም የፍርድ ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪዎች ጥያቄ የአፈፃፀም ማመልከቻ ነው ቢል እንኳ ፍርዱን ለማስፈፀም የሚያስችለው የሥነ-ሥርዓት መሠረት የለውም፡፡

ከዚህም በላይ የከፍተኛው ፍ/ቤት የቦርድን ውሣኔ የሻረው የስር ክርክሩ በተጀመረበት ወቅት ተፈፃሚነት የነበረው አዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 154/2/ ከሰጠው ስልጣን ውጪ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 188/4/ ድንጋጌ የሚያሣየው አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በስር ክርክር ሰሚ አካላት በመታየት ላይ የነበሩ የስራ ክርክሮች በወቅቱ ተፈፃሚነት በነበረው ሕግ መሠረት በተጀመረበት ሥርዓት ፍፃሜ ሊያገኙ እንደሚገባ ነው፡፡ በመሆኑም ከፍተኛ ፍ/ቤት የቦርዱ ውሣኔ የሕግ ስሕተት ያለበት መሆኑን ካመነበት መያዝና ዕልባት ሊያገኝ የሚገባውን ጭብጥ በመመሥረት ለቦርዱ መመለስ ሲገባው የቦርዱን ውሣኔ በመሻር የራሱን ውሣኔ መስጠቱ በሕግ ተለይቶ ስልጣን ባልተሰጠበት ሁኔታ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረት የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆኑ የሕግ ስህተቶች የተፈፀሙበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ከፍተኛው ፍ/ቤት የቦርዱን ውሣኔ የሻረው በክርክሩ ወቅት መታየትና መወሰን የነበረው ጭብጥ የይርጋ ጥያቄ አለመሆኑን በመግለጽና በአዋጁ ላይ የተመለተው የይርጋ ጊዜም ጉዳዩን የማይመለከት ነው ሲል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህም መረዳት የሚቻለው ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ጥያቄ የአፈፃፀም ነው በማለቱ ይርጋውንም ከዚሁ አንፃር መመልከቱን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ችሎት ከላይ እንደገለፀው ጉዳዩ የአፈፃፀም ጥያቄ ሣይሆን የቀጥታ ክስ መሆኑን ተረድቷል፡፡ ጉዳዩ የቀጥታ ክስ ነው ከተባለ ደግሞ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ሕግ አኳያ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩ የቀጥታ ክስ መሆኑን በመገንዘብ የይርጋ ክርክሩንም ከዚህ አኳያ በማየት እንደገና እንዲወስን ጉዳዩን መመለሱ ሥነ-ሥርዓታዊ ነው ቢባልም ጉዳዩ ከወሰደው ጊዜ አኳያ የይርጋ ጥያቄውን ይህ ችሎት እንዲመረምር እና ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥ ማድረጉ የሥነ ሥርዓት ሕጉን ዓላማ ሊያሣካ የሚችል ሆኖ በመገኘቱ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ለተጠሪዎች ደመወዙ በኮሚሽን ይከፈል የነበረው አሠራር ቀሪ የሆነው ከ1991 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ስለመሆኑ አመልካች ጠቅሶ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪዎች ጉዳዩ በእናት መሥሪያ ቤት ተይዞ መቆየቱን ከመግለጽ ውጪ የተለየ የክርክር ነጥብ አላቀረቡም፡፡ በመሆኑም ደመወዙን በኮሚሽን ሲያስከፍል የነበረው አሠራር ቀሪ የሆነው ከ1991 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪዎች የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ከመጋቢት 27 ቀን 1993 ዓ.ም ቃለ ጉባዔ ጀምሮ መሆኑንና ለይርጋ ጊዜው አቆጣጠር መቋረጫ የሆነ ሕጋዊ ምክንያት እንዳላቸውም በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

በመሠረቱ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ162/1/ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው በቅጥር ላይ ከተመሠረተ ግንኙነት የመነጨ ማንኛውም ክስ የጊዜ ገደቡ በአዋጁ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በቀር የመብቱን ጥያቄ ለማቅረብ ከሚቻልበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ይሆናል፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄ ደረጃና ደመወዝ እንዲስተካከል ሆኖ ለቦርዱ ክስ የቀረበው ሰኔ 05 ቀን 1994 ዓ.ም የደመወዝ በኮሚሽን የክፍያ አሠራር ከተለወጠ ከሁለት ዓመት በላይ ቆይቶ ነው፡፡ ተጠሪዎች የይርጋ ጊዜ ገደቡ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የሚከራከሩት አሠሪው መ/ቤት በገንዘብ ሰብሣቢነት ለተመደብን ሠራተኞች እንደማንኛውም የድርጅቱ ሠራተኞች እኩል ክፍያ እንድናገኝ በቃለ ጉባዔ ከእናት ማህበራችን ጋር በመደራደር ላይ ስለነበር ከዋናው መ/ቤት እስከሚላክ ድረስ እንድንጠባበቅ በመደረጉ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ነው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ የአዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 166 ድንጋጌ አንድ የስራ ክርክርን የሚመለከት ክስ የይርጋ ጊዜ አልፎ ቢቀርብ እና ለጊዜው ማለፍ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መሆኑ በተገቢው ውሣኔ ሠጪ አካል ከተረጋገጠ ክሱ ሊቀርብ የሚችል መሆኑንና የተጠቀሰው ምክንያት በተወገደ በአስር ቀን ውስጥ ካልቀረበ ግን ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠቃሽ ድንጋጌ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሰጠው ትርጉም የለም ድንጋጌው ከአቅም በላይ ሊሠኙ የሚችሉ ምክንያቶችን ያላመለከተ መሆኑም በግልጽ ይታያል፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ትርጓሜንና አመላካች ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1792 እና 1793 ድንጋጌዎች አኳያ መመልከት የሚቻል ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት በ/ቁ. 16648 የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በዚህም መሠረት የስራ ክርክር ክስ በጊዜው ያልተመሠረተው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1792 እና 1793 በተመለከተው አኳኋን መሆኑ ከተረጋገጠ ጊዜው ያለፈበት ክስ ተቀባይነት እንደሚኖረው ተሠምሮበታል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 166 ድንጋጌ ከ"አቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ትርጓሜ ያልሰጠና አመላካች ሁኔታዎችን ያላስቀመጠ ቢሆንም እንደ "በቂ ምክንያት" ተደርገው የሚወሰዱትን ምክንያቶችን አመልክቷል፡፡ እነዚህም ምክንያቶች የሠራተኛው መታመም፣ የሠራተኛው በትእዛዝ ከመደበኛ የመኖሪያ ስፍራ ውጭ መዛወር እና የሠራተኛው ከብሔራዊ ጥሪ ላይ መገኘት መሆናቸውን ገልፆል፡፡ ከድንጋጌው መንፈስ መረዳት የሚቻለውም እነዚህ ምክንያቶች መኖራቸው በበቂና አጥጋቢ ማስረጃ ማረጋገጥ ጊዜው ያለፈበትን የስራ ክርክር ክስ ለመቀበል የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡

በእኛችን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች ለቦርዱ አቅርበውት የነበረው ክስ አመልካች መ/ቤት ቀድሞ ይከተል የነበረውን የደመወዝ ክፍያ አሠራር በመለወጥ አዲስ አሠራር መከተሉንና ሌሎች ሠራተኞችም በሌላ አካባቢ በሚገኘው ቦርድ ጉዳያቸውን አቅርበው ማስወሰናቸውን መጋቢት 27 ቀን 1993 ዓ.ም በተደረገው ቃለ ጉባዔም አገልግሎታቸውን ያገናዘበ የደመወዝ ማስተካከያ እንዲደረግ በመ/ቤቱ ፕርሶኔል ዳሬክተር ቢሮ ተሰብስበው መወሰኑን ይህ ውሣኔም ከእናት መ/ቤት ምላሽ እስከሚሠጠው እንዲጠባበቁ መደረጉ ከአቅም በላይ "የሆነ" ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ የተከራከሩ ሲሆን አመልካች ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል በማለት ተቃውሞውን አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ጉዳይ በእናት መ/ቤት ተይዟል ተብሎ ምላሹን እንዲጠባበቁ መደረጉ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይንስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ ከላይ ከተሰጠው ትርጉም አኳያ መታየት እና ምላሽ ማግኘት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1792 እና 1793 እንዲሁም ከአዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 166 ድንጋጌዎች መንፈስ አንፃር ሲታይ ጉዳዩ በእናት መ/ቤት ምላሽ እንዲሰጥበት የመባሉ ምክንያት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ለማለት የሚያስችል አለመሆኑን ይህ ችሎት ያምናል፡፡ ምክንያቱም ክሱ ቀድሞ ሊታሰብ የማይችል እና ተጠሪዎችም ፍፁም የሆነ መሰናክል የገጠማቸው መሆኑን የሚያሣይ፣ይልቁንም በሕጉ መሠረት መብታቸውን በተገቢው የስራ ክርክር ሰሚ አካል ፊት አቅርበው ተገቢውን ዳኝነት ለመጠየቅ ሠፊ እድል የነበራቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በእናት መ/ቤት መያዙ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ተብሎ የሚፈረጅበትን የሕግ መሠረት አላገኘንም፡፡ ከዚህም በላይ ጉዳዩ በእናት መ/ቤት መያዙን የተጠሪዎች አቤቱታ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ እንዲያስፈጽም ስልጣን በተሰጠው አካል ቀርቦ የነበረ በመሆኑ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር የሚያቋርጠው ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን እንዲያስፈጽም ስልጣን የተሰጠው አካል ማን እንደሆነ እና አሠሪ መ/ቤት ወሣኝ አካል አቤቱታ ማቅረብ አዋጅን እንዲያስፈጽም ስልጣን ለተሰጠው አካል አቤቱታ እንደማቅረብ የማይቆጠር ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት ከላይ በተጠቀሰው የመ/ቁ. 16648 የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች አቤቱታቸውን በአመልካች መ/ቤት የፕሮሶኔል ዳሬክተር ቢሮ በመሰብሰብ አስወስነው ምላሹን ከእናት መ/ቤት በመጠባበቅ የፈፀሙት ድርጊት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠርን የሚያቋርጠው ሁኖ ስላላገኘን በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በዚህም መሠረት ቦርዱ የተጠሪዎች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የድሬዳዋ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00762 ሐምሌ 01 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡

2/ የድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ/ቁ. 239/94 ጥቅምት 20 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 32143

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- መሐመድ እስማኤል ተርቢ

ተጠሪ፡- መሐመድ አሕመድ ኑር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በአፈፃፀም ደረጃ ያለውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ገንዘብ ይከፍለው ዘንድ ያስወሰነ የፍርድ ባለመብት ነው፡፡ እንደውሣኔው ለማስፈፀምም የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍቶ ገንዘቡን ገቢ ለማድረግ ሲባል የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶበት ገዢ አልተገኘለትም የተባለውን የተጠሪን ቤት እንዲረከብ አሣዝዞአል፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ በዚህ ላይ ለበላይ ፍ/ቤቶች ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ክርክሩ ተቀባይነት ባለማግኘቱ አፈፃፀሙን የጀመረው በሶማሌ ብ/ክ/መ/የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪን ቤት አመልካች እንዲረከብ በድጋሚ አዟል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ /ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ እና ሌሎች ስድስት ሰዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርበውልኛል በማለት የቀድሞ ውሣኔውን /የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ውሣኔ በማጽናት ሰጥቶት የነበረውን/ በመለወጥ አመልካች ቤቱን ሊረከብ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ባለመቅረቡ ክርክሩ እሱ በሌለበት ነው የተሰማው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት የቀረበለትን መቃወሚያ ያስተናገደበትን እና የቀድሞውን ውሣኔ የሻረበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ለስር ፍ/ቤቶች ከቀረበው ክርክር፣ ከአመልካች አቤቱታ እና አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እንዲሁም ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምናየው ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ገንዘብ አለ ተብሎ የተወሰነበት ሰው ነው፡፡ ይህን ገንዘብ ለማስከፈል ሲባልም ንብረቱ ነው በተባለው ቤት ላይ የአፈፃፀም ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ይህን የአፈፃፀም ትእዛዝ በመቃወም ለሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የተለየ ትእዛዝ /ውሣኔ/ አሰጥቶ የነበረ ቢሆንም አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ክርክር ከተደረገ በኋላ አፈፃፀሙ የከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ትእዛዝ መሠረት እንዲቀጥል ተወስኗል፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ነው ተጠሪ ተቀዋሚ በመሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ለሰበር ችሎቱ አቤቱታ ያቀረበው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት አቤቱታ /መቃወሚያ/ የሚቀርበው ቀደም ሲል የተሰጠን ውሣኔ ለመቃወም ነው፡፡ መቃወሚያውን ማቅረብ የሚችሉትም ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር ተካፋይ ያልነበሩት ወገኖች ናቸው፡፡ ተጠሪ ቀደም ሲል በተደረገው የአፈፃፀም ክርክር ተካፋይ የነበረ እና የተወሰነበት ሰው ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በኋላ ተቃዋሚ ሆኖ የሚቀርብበት አግባብ የለም፡፡ ሌሎቹ ሰዎችም ተቃዋሚ ሆነው የቀረቡት የአፈፃፀም ትእዛዝ የተሰጠበት ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪ ብቻ ሣይሆን የውርስ ሃብት ነው በሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ እነሱ እንደሚሉት ንብረቱ የእነሱም የውርስ ሃብት ከሆነ የአፈፃፀም መዝገቡ ለተከፈተበት የከፍተኛው ፍ/ቤት በጊዜው ሊያቀርቡ ይችሉ /ይገባቸው/ ነበር፡፡ በአፈፃፀም በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ መብት አለን ባዮች አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 418 መሠረት ሆኖ ማቅረብ ያለባቸውም ሣይዘገዩ እንደሆነ በዚሁ ቁ. 418/1/ ተመልክቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ሰዎቹ አቤቱታቸውን ያቀረቡት አፈፃፀሙን ለያዘው ለከፍተኛው ፍ/ቤት ሣይሆን የመጨረሻ ውሣኔ ለሰጠው ለሰበር ችሎቱ ነው፡፡ ከዚህም በላይ በንብረቱ ላይ ከተጠሪ ጋር የጋራ መብት አለን ባዮች ሆነው ሣለ ተጠሪ በከፍተኛው ፍ/ቤት ከአንዱም ሁለቱ በጠ/ፍ/ቤት እና በሰበር ችሎትም እንደዚሁ በክርክር በቆየበት ጊዜ ተቃዋሚ ሆነው አልቀረቡም፡፡ ይህም ሲታይ ለረዥም ጊዜ በንብረቱ ላይ መብት አለን በማለት መቃወሚያ ሣያቀርቡ ዝም ብለው መቆየታቸውን ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀረበን አቤቱታ ፍ/ቤቱ እንደማይመረምረው በተጠቀሰው ድንጋጌ ተመልክቶአል፡፡ በመሆኑም አቤቱታው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 418 መሠረት እንደቀረበ ይቆጠር እንኳን ቢባል ያለበቂ ምክንያት በመዘግየቱ የተነሣ የሚመረመርበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሰበር ችሎቱ የሰጠው ውሣኔም ከዚህ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. ኤም.ጂ. 12/99 ሰኔ 20 ቀን 99 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 418/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው የአፈፃፀም ጉዳይ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15/95 ሰኔ 26 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ይቀጥል ብለናል፡፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37503

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ወልደዮሐንስ ሀብትየስ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ያምሮት ሸዋረጋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን የአሁን አመልካች አቶ ተክሉ በቀለ በተባሉ ግለሰብ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የሚች ወ/ሮ እልፍነሽ በቀለ የሕግ ባል ነች፡፡ ሚች ባለቤቴ በሕይወት እያለች ሁለት ልጆችን የወለድን ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 19 ቀበሌ 58 ክልል ባለቤቴ ከባንክ ገንዘብ ተበድራ ቤት ሠርታለች፡፡ ይህም ቤት የሚችና የእኔ የጋራ ቤት ሲሆን ተከሣሽ ምንም መብት ሣይኖራቸው ቤቱን ይዘው የሚገኙ ስለሆነ ለቀው እንዲያስረክቡኝና ኪራይም እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሣሽም ተከሣሽም የሚች ባል እንደነበሩ ተረጋግጧል ካለ በኋላ የቤቱ ግማሽ የሚስት ድርሻ ሆኖ ቀሪውን ግማሹን ደግሞ ሁለቱ የሚች ባሎች ድርሻቸው ስለሆነ በዚሁ መሠረት ከሣሽ የቤቱን ¼ኛው ይገባቸዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ ውሣኔም በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንደፀና ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በኋላም አመልካች አፈፃፀም ቀጥለው በክርክሩ ሂደት የፍርድ ባለእዳ የነበሩት አቶ ተክሉ በቀለ በመሞታቸው ምክንያት ባለቤታቸው የሆኑት የአሁን ተጠሪ በፍርድ ባለእዳነት ተመዝግበው አፈፃፀሙን የያዘው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፍርዱን በምን መልኩ ማስፈፀም እንዳለበት ፍርዱን ለሰጠው ችሎት ማብራሪያ ጠይቆ የቤቱ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ¼ኛው ለፍርድ ባለመብቱ በመክፈል በዚሁ መልኩ ፍርዱ እንዲፈፀም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የፍርድ አፈፃፀሙን የያዘው ችሎትም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ቤቶችን የቤት የገበያ ግምት የሚሰጠው የሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ሲሆን በዚሁ መሠረትም የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ከዚሁ አካል ግምቱን አስቀርቦ የባለመብትን ድርሻ ¼ ከባለእዳዎች ላይ ከሚያስከፍል ውጭ ውሣኔውን ከሰጠው ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንዲፈፀም ከተሰጠው ትእዛዝ በመውጣት በሐራጅ ተሸጦ ለባለመብት እንዲከፈላቸው የሚያደርግበት ሥርዓት ስለሌለ የፍርድ ባለመብት በዚህ መልኩ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ስለሌለው በፍርድ አፈፃፀም በኩል የተየዘውን ድርሻቸውን ይውሰዱ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የፍርድ ባለመብት በዚሁ ትእዛዝ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የሥር ፍ/ቤት ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ሠርሂል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ የቤቱ ወቅታዊ ዋጋ ¼ኛው ለአመልካች ይከፈላቸው ተብሎ ፍርድ በተሰጠበት ሁኔታ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከሚመለከተው አስተዳደር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክፍል የተላከለትን ግምት መሠረት በማድረግ ፍርዱ እንዲፈፀም በማለት የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ ተጠሪ ባሉበት ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን የሰበር አቤቱታውም ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ተመርምሯል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው የፍርድ ባለመብት /የአሁን አመልካች/ የቤቱን ወቅታዊ ዋጋ ¼ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ነው፡፡ የከተማው አስተዳደር ቤቱን አስመልክቶ የሚሰጠው የዋጋ ግምትና ወቅታዊ ዋጋ ልዩነት እንዳላቸው መገመት አያዳግትም፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ የቤቱ ወቅታዊ ዋጋ ¼ኛው ለፍርድ ባለመብቱ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ እስከሰጠ ድረስ ወቅታዊ ዋጋውን የሚወስነው በሐራጅ በሚደረግ ሽያጭ ስለሆነ በዚሁ መልኩ ፍርዱን ማስፈፀም ከውሣኔው እንደማፈንገጥ የሚቆጠር አይሆንም፡፡

በሌላ በኩልም በዚህ ችሎት ክርክር ሲደረግ ይሄው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሌላ የአፈፃፀም መዝገብ በሐራጅ እንዲሸጥ ታዞ በብር 364,000 ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም እንደተሸጠ ግራ ቀኙ ወገኖች ተማምነውበታል፡፡ ይህም የቤቱ ወቅታዊ ዋጋ መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 373 አኳያ ተገቢነት የሌለውና የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 65156 ኅዳር 27/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ.ቁ. 61890 በ16/7/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከቤቱ ሽያጭ ላይ ለአመልካች ሊደርሳቸው የሚገባው ¼ኛ ድርሻ ብር 91.000 /ዘጠና አንድ ሺህ/ እንዲከፈላቸው ፍርዱንም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39175

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ በለጡ ጋሼ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ አንዱአለም ቴድሮስ /3 ሰዎች/ - ጠበቃ ዘውዱ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 4931 የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ማጽደቃቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡

የአቤቱታቸው ምክንያት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ የአሁን አመልካች በፍርድ የሚፈለግባቸውን ገንዘብ ከፍለው ያልቀረቡ በመሆኑ ቀደም ሲል በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ቤቱን ተጠሪዎች እንዲረከቡ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህ ትእዛዝ መሰረታዊ ስህተት አለበት በማለት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡

አመልካች የአፈፃፀም ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር ችሎቱ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች አፈፃፀሙን የያዘው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ቤቱ ሁለት ጊዜ በጨረታ፣እንዲወጣ ሣያደርግ ባለእዳዎች እንዲረከቡት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ የመጀመሪያው ጨረታ፣በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ህግ ቁጥር 426 መሰረት ለሰላሣ ቀናት በአየር ላይ ባለመዋሉ ፍርድ ቤቱ ሰርዞ ድጋሜ ጨረታ እንዲወጣ አዝዟል፡፡ ከዚያ በኋላ ቤቱ በህጉ መሰረት ለጨረታ ያቀረበው አንድ ጊዜ ሆኖ እያለ፣ሁለት ጊዜ ለጨረታ ወጥቶ ገዥ እንዳልተገኘ በመቁጥር የተሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፣ ስለዚህ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልክታለች፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ቤቱ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም ለጨረታ ቀርቦ የነበረ ሲሆን ታህሣስ 4 ቀን 1999 ዓ.ም እና ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ለሐራጅ ቀርቦ ገዥ ባለመገኘቱ ነው እኛ እንድንረከብ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ የሰጠው፡፡ ስለሆነም በህጉ መሰረት የተሰጠ የአፈፃፀም ትእዛዝ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ቤቱን ይሸጥ ካለ በኋላ ብር 8000(ስምንት ሺህ) በችሎት እንዲከፍል አድርጓል፡፡ ከዚህ በኋላ ቤቱ ይረከቡ ማለት መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርመረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪዎች ቤቱ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም ለሐራጅ ቀርቦ ነበር በማለት ያቀረቡትን ክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስንመረምረው፣ቤቱ ለሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣበት ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ በአፈፃፀም የተሰጠው ትእዛዝ መብታችንን ይነካል የሚሉ ጣልቃ ገቦች በመቅረባቸው ጨረታው ሂደት አፈፃፀሙን በያዘው ፍርድ ቤት የእግድ ትእዛዝ በመሰጠቱ ምክንያት የተቋረጠ መሆኑን፣የከፍተኛው ፍርድ ቤት መጋቢት 5 ቀን 1998 ዓ.ም ከሰጠው ትእዛዝ ለመገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ተጠሪዎች ቤቱ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶበት ለሐራጅ ቀርቧል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘውም።

ከፍተኛው ፍ/ቤት የጣልቃ ገቦቹን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተቋረጠው የሐራጅ ሂደት እንዲቀጥልና ቤቱ ታህሣስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ለሐራጅ እንዲቀርብ፣የጨረታው ማስታወቂያ እንዲወጣ ጥቅምት 20 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መሰረት የሐራጅ ማስታወቂያው ታህሣሥ 3 ቀን 1999 ዓ.ም ወጥቷል። ፍርድ ቤቱም የሐራጅ ማስታወቂያው በአየር ላይ ለሰላሣ ቀናት መቆየት ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርአት ሕግ ቁጥር 426 የተደነገገ መሆኑን በመግለጽ ይህንን ስርአት ባሟላ መልኩ ቤቱ በሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ለሐራጅ ሽያጭ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል። የሐራጅ ማስታወቂያውም ጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም ወጥቶ ገዥ አልቀረበም ስለዚህ ቤቱን እንድንረከብ በማለት የፍርድ ባለመብት በጠየቁት መሰረት የፍርድ ባለመብት ቤቱን እንዲረከቡ በማለት ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል።

ከዚህ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመብት የሆኑት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲረከቡ በተደጋጋሚ ትእዛዝ ሲሰጥ ቆይቶ ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም አመልካች በፖሊስ ተይዘው እንዲቀርቡ አድርጓል። በዚህ ቀን አመልካች ብር 8000(አምስት ሺህ ብር) የከፈለ ሲሆን ቀሪውን እዳ አጠቃልላ ከፍላ እንድትቀርብ በማለት ለሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል። አመልካች ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም እዳውን አጠቃልለው ከፍለው ባለመቅረባቸው፣የከፍተኛው ፍ/ቤት የፍርድ ባለመብት ቤቱን እንዲረከቡ የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል።

አፈፃጸሙን የያዘው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲረከቡ ትእዛዝ የሰጠው በሕጉ የተቀመጠውን፣ሥርዓት በማሟላት አይደለም። ምክንያቱም የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገውን የሐራጅ ሒደት ራሱ ፍርድ ቤቱ አግዶታል። ከዚህ በኋላ የሚከናወኑ የሐራጅ ሂደቶች እንደ አዲስ መደረግ ያለባቸው ናቸው። ጥር 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተከናወነው፣ሐራጅ የሐራጅ ማስታወቂያው ጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም ወጥቶ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 426 የተደነገገውን አስገዳጅ ስርአት ያላሟላና የሐራጅ ማስታወቂያው ሰባት ቀን ብቻ በአየር ላይ ውሎ የተፈፀመ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ይህ ስርአት ያልተሟላ መሆኑን በማየት ሰርዞታል።

ቤቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 426 መስፈርት ባሟላ ሁኔታ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ለሐራጅ ያቀረበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 428 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የፍርድ ባለመብቱ እንዲረከብ የሚያደርገው የሕጉን ስርአት በተከተለና ባሟላ ሁኔታ ሁለት ጊዜ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶና ቤቱ ለሐራጅ ቀርቦ ገዥ ሣይገኝ ሲቀር ብቻ ነው። በያዝነው ጉዳይ ቤቱ በትክክለኛው መንገድ ለሐራጅ የቀረበው ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ብቻ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ቤቱ በድጋሚ ለሐራጅ እንዲቀርብና የሕጉን ስርአት ባሟላ ሁኔታ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ ሣያደርግ ቀደም ብለው ያወጣውንና የህጉን አስገዳጅ ሁኔታ የማያሟላውን የሐራጅ ስርአት፣ እንደትክክለኛ ሐራጅ በመቁጠር ቤቱ ሁለት ጊዜ ለሐራጅ ቀርቦ ገዥ አላገኘም በማለት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲረከቡ የሰጠው ትእዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 428 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የሚጥስ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ሆኖ አግኝተነዋል።

ከዚህ በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ቤቱን ይረከቡ በማለት የሰጠውን ትእዛዝ በመተው አመልካች እዳቸውን በጥሬ ገንዘብ እንዲከፍሉ የፈቀደና በዚህም መሰረት አመልካች ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም ስምንት ሺ ብር/8000/ በችሎት የከፈሉ መሆኑን የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ያሣያል። ከዚህ በኋላ አፈፃጸሙ በማይንቀሣቀስም ንብረት ላይ እንዲቀጥል ለማድረግ ካስፈለገ፣የአፈፃፀም ስርአቱን እንደ አዲስ በቤቱ ላይ እንዲቀጥልና የሐራጅ ማስታወቂያ ማውጣት ሲገባው የተወውና የተቋረጠውን የአፈፃፀም ስርአት በማስታወስ ቤቱን ተጠሪዎች እንዲረከቡ በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ ግድፈት ያለበት ነው። በመሆኑም የከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈፃፀሙን ሲመራ የጣሳቸውን አስገዳጅ የስነ-ሥርአት ድንጋጌዎች እያሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት ትእዛዙን ማጽናታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወሰነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በፍርድ የተወሰነባቸውን የቀረባቸውን እዳ ለመክፈል የሚችሉ ከሆነ እንደ ክሱ እንዲያደርግ አመልካች እዳውን ለመክፈል ካልቻሉ፣ቤቱ የሕጉን ሥርአት በጠበቀ ሁኔታ በሐራጅ ተሸጦ የተጠሪዎች እዳ እንዲከፈል ያደርግ ዘንድ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ህግ ቁጥር 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39485

መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የህፃን ሰላማዊት ቴዎድሮስ ሞግዚት - ወ/ሮ ፍርቱና ገ/መድህን ቀረቡ

ተጠሪ፡- መምህር ሚካኤል ግደይ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በ17/07/1999 ዓ.ም በፃፉት የአፈፃፀም ክስ በ06/07/1999 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ መሰረት እንዲፈጸምላቸው ይታዘዝላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ ተጠሪ ላይ በማእከላይ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመሰረቱት የአፈፃፀም ክስ መነሻ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪም በፍርድ ባለእዳነታቸው ቀርበው ፍርዱን እንዲፈጽሙና የማይፈጽሙበት ምክንያት ካለም እንዲያስረዱ ተደርገው በዋናው ጉዳይ በተሰጠው ውሣኔ መሰረት መኪናዋን ለፍርድ ባለመብት ለሆኑት ለአሁኗ አመልካች እንዲያስረክቡ ታዝዞ አረካካቢ አካልም ተመድቦና መኪናዋ ላይ ጉድለዋል የሚባሉትን እቃዎችን ከዋጋ ግምት ዝርዝር ጋር ለፍ/ቤቱ እንዲገልጽ ተደርጐ ይኸው ከተፈፀመ በኋላ የአፈፃፀም ከሣሽ የነበሩት አመልካች መኪናዋን ከእነጉድለቷ ተረክበዋል፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤትም በመኪናዋ ላይ ጐደሉ የተባሉት እቃዎች በውሣኔ መኪናዋ ላይ እንዳሉ አረጋግጦ መወሰኑንና የጐደሉትም መኪናዋ በአፈፃፀም ተከሣሽ እጅ እንዳለች በርክክቡ ወቅት መሆኑን አረጋግጦ በርክክቡ ወቅት ጐድሎ የተገኙትን ዝርዝር ንብረቶች በአይነታቸውና በብዛታቸው የሚጨርሱትን ዋጋ በዋጋ ማቅረቢያ ፕሮፎርማ ከሦስት የተለያዩ ድርጅቶች እንዲሰባሰብ አድርጐ ጐደሉ የተባሉት የመኪና እቃዎች ብር 66,520.00(ስልሳ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር) መሆኑን አረጋግጦ ይህንኑ ገንዘብ አፈፃፀም ተከሣሽ ለአፈፃፀም ከሣሽ እንዲተኩላቸው በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትእዛዝ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ይኸው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ጐደሉ በተባሉት የመኪና እቃዎች ላይ የሰጠው ትእዛዝ መኪናዋ በቀጥታ ክስ ጊዜ ተገምታ የቀረበችበትንና በውሣኔው ላይም መኪናውን ከሣሽ ትረከብ ተብሎ ከተወሰነው ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ አፈፃፀሙ የተመራው ከስነ ስርአት ውጪ መሆኑን ጠቅሶ ጐደሉ ለተባሉት የመኪናዋ እቃዎች የአሁኗ አመልካች ሊከፍላት የሚገባው የገንዘብ መጠን በዋናው ክስ ጊዜ የተጠቀሰው ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ነው በማለት የስር ፍ/ቤትን ትእዛዝ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁኗ አመልካች በዚህ ቅር በመሰኘት አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ስላላገኙ በዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካች ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅረበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በዋናው ጉዳይ በተወሰነው ውሣኔ መኪናዋን እንዲረከብ የሚል ሆኖ እያለና በርክክቡ ወቅትም የመኪናዋ እቃዎች በተጠሪ መጉደላቸው የተረጋገጠ መሆኑን አፈፃፀሙን የያዘው የስር ፍ/ቤት በገለፀበት ሁኔታ በዋናው ክስ ላይ የመኪናዋን ዋጋ ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ብለሽ ገምተሻል ተብሎ የእቃዎችን የገበያ ዋጋ ባላገናዘበ መልኩ የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ መሻሩ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተደምጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ትእዛዝና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መረምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የመኪናዋ ርክክብ ሲፈጸም መጉደላቸው የተረጋገጡትን እቃዎችን ለመተካት የታሰበው የእቃዎች ዋጋ ውድቅ ሁኖ የእቃዎቹ ዋጋ ሊሆን የሚገባው የዋናው ጉዳይ ክስ ሲመሰረት በአመልካች የተገለፀው ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካች በቀጥታ ክስ ወቅት መኪናውን የገመቱት በብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ሁኖ የጠየቁት ዳኝነት መኪናዋን እንዲረከቡ ይወሰንላቸው ዘንድ መሆኑን፣በቀጥታ ክስ ወቅት የተሰጠው ውሣኔም አመልካች መኪናዋን እንዲረከቡ የሚል መሆኑንና በአፈፃፀም ወቅት አመልካች መኪናዋን ሲረከቡ የጐደሉት የመኪና እቃዎች ተረጋግጠው በወቅቱ የገበያ ዋጋም የጐደሉትን እቃዎች ለመተካት ዝቅተኛው የጨረታ ዋጋም ብር 66,520.00(ስልሳ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር) መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የአፈፃፀም ክስ የሚቀርበው በውሣኔው መሰረት እንዲፈጸም ስለመሆኑ ከ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ስርአት ህግ ሰባተኛ መጽሐፍ ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመመልከት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አከራካሪውና ምላሽ የሚያስፈልገው ጉዳይ በቀጥታ ክስ ወቅት የተገመተ የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቀት ንብረቱ በዓይነት ካልተገኘ እና ንብረቱን በዓይነት ለመተካት የንብረቱ ዋጋ ቀድሞ ከተገመተው ግምት በልጦ ሲገኝ አፈፃፀሙ ሊሆን የሚገባው በቀድሞው ግምት ወይስ ንብረቱን በዓይነት ለመተካት በሚያስችል የወቅቱ ተገቢ ዋጋ? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ሊገኝ የሚችለው በቀጥታ ክስ ወቀት የተሰጠውን ውሣኔ እና የገበያን ተለዋዋጭ ባህርይ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ሲቻል ነው፡፡ እንዲሁም አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ለአፈፃፀሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ የመስጠት ሥልጣን ያለው መሆኑም ሊስተዋል ይገባል፡፡ በመሆኑም በቀጥታ ክስ ወቀት የነበረው የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቅት ንብረቱ በፍርድ ባለእዳ እጅ በነበረበት ሁኔታ ጉድሎ መገኘቱ ከተረጋገጠ በዓይነት ለፍርድ ባለመብቱ እንዲያስረክብ እስከተወሰነ ድረስ የጐለውን የንብረቱን ክፍል እንዲተካ ማድረግ በዋናው ፍርድ ከተሰጠው ውሣኔ ውጪ ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ የመኪና እቃዎች ዋጋ ከፍና ዝቅ የሚል መሆኑ እየታወቀም አንዱ ተገምቶ የቀረበ ዋጋ ሁል ጊዜ ተቀባይነት አለው ለማለት አይቻልም፡፡ የፍርድ ባለመብት ንብረቱን በዓይነት እንዲረከብ ከተወሰነ እና የፍርድ ባለእዳው እንደፈርዱ የማይፈጽምበት ምክንያት ያለመኖሩ ሲረጋገጥ የፍርድ ባእዳው ንብረቱን በዓይነት እንዲያስረክብ፣ በዚህ ወቅትም ለአፈፃፀሙ ተስማሚ የሆነ መንገድ መከተል የፍርድ አፈፃፀም ስርአት የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ አንድ ፍርድ ለፍርድ ባለመብት እንደፍርዱ ተፈጽሞለታል ለማለት እይቻልም፡፡ በመሆኑም በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የማእከላይ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነችው መኪና ጐደሉ የተባሉትን እቃዎች በተመለከተ ለአመልካች እንዲተካላቸው ፕሮፎርማ እንዲሰባሰብ በማድረግ ዝቅተኛው ዋጋ እንዲከፈል ማድረጉ የአፈፃፀም ክስ አቀራረብና የአፈፃፀም ውሣኔ አሰጣጥ ሥርአትን ባልተከተለ አኳኋን ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ይልቁንም የዚህ ፍ/ቤት አካሄድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 392 ስር የተመለቱትን ድንጋጌዎችንና መኪናዋ በፍርድ ባለእዳ እጅ በነበረችበት ወቅት እቃዎቹ የመጉደላቸውን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ግን አመልካች በዋናው ፍርድ መኪናዋን እንዲረከቡ የተወሰነውን ውሣኔ እና የመኪና እቃዎች የገበያ ዋጋን ተለዋዋጭነት እንዲሁም አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ለአፈፃፀሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ ለመስጠት ስልጣን ያለው መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392/1/ ያስቀመጠውን መንገድ ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ትእዛዝ ሣያርም መቅረቱ ባግባቡ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም መጋቢት 06 ቀን 1999 ዓ.ም በተሰጠው ዋና ውሣኔ ላይ የሰሌዳ ቁጥር ትግ 03-00778 መኪና አመልካች እንዲረከቡ ከተወሰነ በኋላ በአፈፃፀም ደግሞ መኪናውን ሣይሆን ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ይከፈላት ተብሎ መወሰኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 392 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 23377 ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠቶ በዚሁ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በፍ/መ/ቁ. 25095 ሰኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የትግራይ ብ/ክ/መንግስት የማእከላይ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08699 የካቲት 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ለጐደሉት የመኪና እቃዎች ለተጠሪ ለአመልካች ብር 66,520.00(ስልሳ ስድስት ሺህ አምስት አቶ ሃያ ብር) ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 38041

መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ታደሰ ገ/መስቀል - ወኪል በላይነሽ ሽፋው ቀረበች

ተጠሪዎች፡- 1/ ሙሉጌታ ዘካርያስ

2/ ወ/ሮ አበቡ ገበያው

3/ መሐመድ ይማም - ወኪልም ነው ቀረበ

4/ ዘውዴ ይማም

5/ ወ/ሮ ሩቅያ ይማም

6/ ወ/ሮ ዘይነባ ይማም

7/ ወ/ሮ አሚናት ይማም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአፈፃፀም ደረጃ ያለ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የጉዳዩ ታሪክ እንደሚያመለክተው በውርስ ንብረት ክፍፍል መነሻነት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች በአንድ በኩል፤ ከሦስተኛ እስከ ሰባት ድረስ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ በሌላ በኩል በመሆን ክርክር ከተደረገ በኋላ፤ በወቅቱ ከሣሾች የነበሩት ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች በአንደኛ እና በሁለተኛ ተጠሪዎች ላይ አስወስነው የፍርድ ባለመብት ሆነዋል፡፡ ይህን ውሣኔ መሠረት በማድረግም የአፈፃፀም መዝገብ ያስከፈቱ ሲሆን፣ በዚህን ጊዜም አመልካችንም የአፈፃፀም ተከሣሽ አድርገውት እንደነበር እና ፍ/ቤቱ ግን አመልካች ተከሶ የተፈረደበት የፍርድ ባለእዳ አይደለም በማለት ከአፈፃፀም ክሱ ውጪ እንዳደረገው ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ለአንደኛ እና ለሁለተኛ ተጠሪዎች ገንዘብ አበድሮ የነበረ በመሆኑ እና የውርስ ሃብት ነው ተብሎ ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ቤትም በመያዣ ይዞ ስለነበር ይህን የብድር እና የመያዣ ውል መነሻ በማድረግ በአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎችን በመክሰስ ቤቱን እንዲረከብ በፍ/ቤት አስወስኖአል፡፡ አመልካች ይህን ውሣኔ ያሰጠው በ1993 ዓ.ም ሲሆን፣ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በአንደኛ እና በሁለተኛ ተጠሪዎች ላይ ያስወሰኑት በ1997 ዓ.ም እንደሆነ መዝገቡ ያመለክታል፡፡

አመልካች በአፈፃፀም መዝገቡ ተጣምሮ መከሰሱን እንዳየ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ቤቱን በተመለከተ ያሰጡት ውሣኔ መኖሩን ስላወቀ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርቦ ክርክር ከተካሄደ በኋላ ቤቱ በመያዣ የያዘው ከመሆኑም በላይ፤ በፍርድም ለሱ ይገባል ስለተባለ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ ለተጠቀሱት ተጠሪዎች ሊሰጥ አይገባም በሚል ተወስኖለታል፡፡ በዚህም በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ መሠረት ተሽሮአል፡፡ ከዚህ በኋላ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ መሠረት የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም በአማራ ብ/ክ/መ/ ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ሲሆን፣ በስር ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በሚል ይግባኛቸው ሣይስተናገድ ቀርቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች እና አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎችን መልስ ሰጭ በማድረግ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች በመሻር አመልካች በቤቱ ላይ መብት የለውም፡፡ ቤቱ በተጠሪዎች መካከል ይከፋፈል በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ጥር 24 ቀን 1993 ዓ.ም በመ.ቁ. 14/93 ክርክር ባስነሣው ቤት ላይ የሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ባልተሻረበት ሁኔታ የጠ/ፍ/ቤቱ በተጠሪዎች መካከል የነበረውን ክርክር ሲመረምር በመ.ቁ. 14/93 ላይ የተሰጠውን ውሣኔ የመሻሩን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች በመ.ቁ. 14/93 ጥር 24 ቀን 1993 ዓ.ም ባስወሰነው መሠረት ለክርክሩ መንስኤ በሆነው ቤት ላይ የፍርድ ባለመብት ሆኖአል፡፡ ውሣኔው የተሰጠው ከሱ ገንዘብ በተበደሩት እና ቤቱንም በመያዣ በሰጡት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ ይህ ፍርድ ለየትኛውም ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ አልተሻረም፡፡ ከሦስት እስከ ሰባት ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ይህን አመልካች በመክሰስ በቤቱ ላይ መብት አላገኙም፡፡ ከዚህ የተነሣም አመልካች ቤቱን ያስረክባቸው ዘንድ የሚያስገድዱበት ምንም የሕግ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በቤቱ ላይ ያገኘው በፍርድ ላይ የተመሠረተ የባለቤትነት መብት በተመሣሣይ ሁኔታ በፍርድ ሃይል እስካልተነሣ ድረስ ምን ጊዜም የቤቱ ባለቤት ሆኖ የሚቀረው አመልካቹ ነው፡፡

የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በስር ወረዳ ፍ/ቤትም ሆነ በከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠው አመልካችን የቤቱ ባለቤት ባደረገው ውሣኔ ላይ ይግባኝ አልቀረበለትም፡፡ ቤቱ የአመልካች አይሆንም በማለት የወሰነው በይግባኝ ያልቀረበለትን ውሣኔ ተፈፃሚነት የሚኖረው ውሣኔ አይደለም የሚል ትችት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በመሠረቱ በሕግ አግባብ በፍ/ቤት የተሰጠን ውሣኔ የሞራልን ወይም የሕሊናን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ ዋጋ አልባ ሆኖ እንዲቀር ማድረግ በየትኛውም መለኪያ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች በክስ እንደሌሎቹ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ የውርስ መብት እንደነበራቸው ተመልክተዋል፡፡ ቤቱን ለብድር በመያዣነት ለአመልካች የሰጡትም በእነሱ እጅ ስለነበረ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ለምን እነሱ ብቻቸውን በመያዣነት ሰጡ ብሎ መጠየቁም አግባብ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በፊት አመልካች ቤቱን በፍርድ የሱ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በመሆኑም ሌሎችም የውርስ መብት አላቸው ስለተባለ ብቻ ያለምንም ሕጋዊ ምክንያት ፍርዱ ተፈፃሚ እንዳይሆን ወይም ማምከን አይቻልም፡፡ ሲጠቃለል የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 311/2000 ግንቦት 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡ የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጡአቸው ትእዛዝና ውሣኔ ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ጥር 24 ቀን 93 ዓ.ም በመ.ቁ. 14/93 በተሰጠው ውሣኔ በቤቱ ላይ ባለመብት ስለሆነ ለተጠሪዎች ሊያስረክብ አይገደድም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፣፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎችን /ከቅጽ 1 - 7 / ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ቅጽ - 1

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
1	18180	የኬ.ኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ ሰራተኞች ማህበር እና የኬ.ኬ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ	የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ስልጣን፣ የሰራተኛ ቅነሳ ጉዳይን በሚመለከት ስለሚነሳ ክርክር አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 138(1),147	ሐምሌ 29/1997
2	15493	አቶ ጳውሎስ ሩምቾ እና ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ	በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,2024	ሐምሌ 29/1997
3	17361	ወ/ሮ ጋዲሴ ኢርጌ እና ወ/ሮ ወርቅአንጥፉ በቀለ	በስነ-ስርዓት ህጉ የጊዜ ገደብን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.49, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856	ሐምሌ 25/1997
4	17352	ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/ የግ/ ማህበር እና የነገው ሰው ትምህርት ቤት	ተገቢው ዳኝነት ክፍያ ሳይፈፀም በፍ/ቤት በቀጠለ ክርክር ስለማፈፀም ስርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.215,320(2),207,211(2)	ሐምሌ 28/1997
5	14605	የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና እነ ኮሜት ትራንስፖርት ድርጅት (ስድስት ሰዎች)	በመንገዝ ላይ የነበሩ ዕቃዎች መጎዳት በሰው ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን የግጭት አደጋ ለማስወገድ በተወሰደ ርምጃ የደረሰ የመኪና መገልበጥ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ስላለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 590,591, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1792	ሐምሌ 29/1997
6	17068	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ሚ/ር ቢሮኒ አቲክፖ	በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856,2024, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 89	ሐምሌ 19/1997
7	14974	ወ/ት ማህሌት ገ/ስላሴ እና እነ አቶ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች)	አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ባቀረበው ክስ ወካዩን ወክሎ መከራከር ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2188, 2189, 2208, 2209, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 57,58	ሐምሌ 28/1997
8	14184	አቶ ውርጌሳ ታደሰ እና እነ አቶ መለሰ ተካ (ዘጠኝ ሰዎች)	ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73	ሐምሌ 29/1997
9	14047	ዶ/ር ዳንኤል አለሙ እና እነ ወ/ሮ ሮማን ወርቅ የማኑፋክቸሪንግ (ሦስት ሰዎች)	በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1856, 2024	ሐምሌ 28/1997
10	15835	ሼል ኢትዮጵያ አ/ማ እና ወ/ሮ አስቱር ብርሃነ ስላሴ	ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የተከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70,233	ሐምሌ 29/1997
11	15992	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ወ/ት ሶስና አስፋው	በህግ የተደነገገው የውል አፃፃፍ /ፎርም/ የተሰጠ ደንብ አለመፈፀም ስለሚያስከትለው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719, 1720 (1), 1723, 1726, 1727, 1845	ሐምሌ 19/1997
12	17191	ወ/ሮ አስቱር አርአያ እና አቶ ግርማ ወይጆ	በአንዳንድ ውሎች የተመለከተን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለመቀነስ ፍ/ቤት ስላለው ስልጣን የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711, 1731, 1676(2), 2635, 2640, 2646	ሐምሌ 29/1997

ቅጽ 2

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
13	13223	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አስፋው አበበ	ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ባይቀርብለትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማንኛውም ዓይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪ እንዲቀርብለት መስጠት ስላለበት ትዕዛዝ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2) 342, 345(1)(ለ)	ጥቅምት 9/1998
14	14414	የጊምቢ ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት እና ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ	በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ከመ/ቤቱ ጋር ባለው ስራ ክርክር የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 2(1),3(2)(ሠ)	ጥቅምት 1/1998
15	15270	የመቶ አለቃ ተሻገር አስታጥቂ እና አቶ አዊል አው አብዲ	በክተማ ቦታ ላይ ስለሚኖር መብት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33(2), 231, (1)(ሀ), አዋጅ ቁ.47/67	ጥቅምት 28/1998
16	15410	አቶ ተሾመ ጅፋር እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን	አጠቃላይ የአሰሪን የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ስርዓትን ላይሆን የግል ጥቅምን መሰረት አድርጐ የሚቀርብን የደመወዝ ጭማሪ ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 147	ጥቅምት 1/1998

https://t.me/ethiopianlegalbrief

17	16273	የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገንታ ገምአ	ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠርኩ እንደሆንኩ ብቻ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄን የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ እና የግል ጥቅምን መሰረት አድርጐ የሚቀርብን የጥቅማጥቅም ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 9,10, 138, 142, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33	ጥቅምት 22/1998
18	16624	ወ/ት አጅጋየሁ ተሾመ እና የኡቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) መሰረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)	ጥቅምት 18/1998
19	16720	ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ እና እነ የመካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት (አራት ሰዎች)	በከፊል የፍርድ ባለመብት የሆነ ሰው ባለመብት የሆነበት የፍርድ ክፍል እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ክስ ካቀረበ በኋላ በመጀመሪያ የፍርድ ባለዕዳ የሆነበትን ፍርድ በይግባኝ አሸሮ የፍርድ ባለመብት ሲሆን አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ቀደም ሲል የተከፈተው የአፈፃፀም መዝገብ ቢዘጋም እንኳን ማንቀሳቀስ ስለመቻሉ እና በአፈፃፀም ደረጃ ወለድ የሚከፈለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ከተወሰነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378(3)(ሰ)	ጥቅምት 22/1998
20	16896	ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና የኢ.ሊ.ባ.ቦር ዞን ትምህርት መምሪያ	የተዋዋዮች በውሉ አለመግባባት ሲፈጠርና ጉዳዩን በገላጋይ ዳኞች እንዲታይ ሲስማሙ ፍ/ቤት ይህንን ስምምነት ማስፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711,1731(1)	ጥቅምት 16/1998
21	17077	ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ	የዕዳ መክፈያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ባለገንዘቡ ለባለዕዳው የሚያደረገው የዕዳ ክፍያ ጊዜ ማራዘም ዋሱን ከዋስትናው ነፃ የሚያደርገው ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1928(1)እና(2)	ጥቅምት 14/1998
22	17189	የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጭ ድርጅት እና አቶ ንጉሴ ዘለቀ	በአሰሪ "ገንዘብ" ላይ ሰራተኛው ያደረሰው ጉዳት በአሰሪው "ንብረት" የደረሰ ጉዳት ስለመሆኑ እና ሰራተኛ የስራ ውሉ ተቋርጦ ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 27(1) (በ), 53(1),54	ጥቅምት 17/1998
23	17429	ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ እና አቶ ተስፋዬ ከበደ	በግልጽ በሚደረግ ጉባዔ ጉባዔው መነበቡን የሚያመለክት ከሆነ በግልጽ "ተነቧል" የሚል ቃል አለመኖሩ ጉባዔውን ፈራሽ የሚያደርግ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881	ጥቅምት 21/1998
24	17533	የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና ሙሉ ብርሃን	የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሰረት የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ በማድረጉ ወይም ዴክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት በዕቃው ባለቤት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 2(18), 43(1) (ሀ)	ጥቅምት 18/1998
25	17712	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት እና የወ/ሮ ሳዳያ እስማኤል ወራሾች	በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1), 1196 (1)	ጥቅምት 16/1998
26	18307	ንብ ትራንስፖርት አ.ማ. እና አቶ ተገኑ መሸሻ	በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ የሆነ ሰራተኛ ከአሰሪው ጋር ያለው የስራ ክርክር የሚገዛው በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎት መስጠትን ስለሚመለከቱ ውሎች ክፍል በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስለመሆኑ እና የስራ ውሉ ተቋርጦ የስራ መሪው ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2534, 2540 ,2541(1)	ጥቅምት 25/1998

ቅጽ 3

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
27	15815	አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ሰለሞን አበበ	የስራ ውሉ በህግ ወጥ መንገድ የተቋረጠ የስራ መሪ ስለሚያገኘው መፍትሔ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2570, 2573, 2574,2571	ታህሳስ 10/1998
28	16648	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ አንለይ ያየህ (ሃያ ሰባት ሰዎች)	ስለ ስራ ክርክር የይርጋ ጊዜ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162,163,164,165,166, አዋጅ ቁ. 377/96	ታህሳስ 20/1998
29	17483	የኦሮሚያ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እና ወ/ሮ ሮማን ደምሴ	የስራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል የሚቀርብ ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162(1)	ታህሳስ 20/1998
30	11924	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት ትዕግሥት ወርቁ	ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ስለማድረግ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 9,10 እና 24	ህዳር 15/1998
31	14057	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ጌታሁን ኃይሉ	አንድ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት እረፍት ቀናት በገንዘብ ተቀይሮ ስለሚከፈልበት የህግ አግባብ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 79(2)እና (5), 77(5),77(3)	ጥቅምት 30/1998

https://t.me/ethiopianlegalbrief

32	16270	አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ መሐሪ ማታ	በመኪና ግጭት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት ካሣ ለማግኘት የመኪናው ባለቤት ጥፋት እንዳለበት ማስረዳት የማይኖርበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066(2),2086(2),2081,2091,2102 እና 2092	ታህሳስ 17/1998
33	18581	በአዲስ አበባ አስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጥበቃ እና ሲ/ረ ቀቡላ ክድር	በህገ ወጥ መንገድ የስራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ ወደ ስራ እንዲመለስ ስለሚወሰንበት የህግ አግባብ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 23(1),43(3),40(1) እና (2),44	ህዳር 20/1998
34	15631	እነ የሻረግ መንግስት (ሁለት ሰዎች) እና እማሆይ የሻረግ ፈረደ	የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነ ጊዜ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1001(2),1168,1845,1853	ታህሳስ 17/1998
35	15551	ዮናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ እና የኢትዮጵያ መተርና መሐንደስነት ኩባንያ	ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ ተዋዋዮች ወደነበሩብት እንዲመለሱ የሚወሰነው በውሉ መሰረት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716(1), 1815,1816 እና 1817	ጥቅምት 29/1998
36	16062	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ አረጋሽ ክበደ	ከውል ውጭ በደረሰ ጉዳት ካሣ በመጠየቅ የሚቀረብ ክስ መቅረብ ስለሚኖርበት ጊዜ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1),2143(2)	ህዳር 19/1998
37	14554	ወ/ሮ ጽጌ አጥናፌ እና ባላምባራስ ውቤ ሽበሽ	ፍርድ ቤት በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርን የመሰረዝ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808(2),1198(2)	ታህሳስ 20/1998
38	15672	አቶ ታደለ ገለቻ እና አቶ ውድመጣስ ኑሮ	ንብረት በሐራጅ ስለሚሸጥበት የህግ አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 442	ታህሳስ 27/1998
39	16301	ተገኝ እንግዳ እና አስናቀች ኪዳኔ	መጥሪያ አደራረስን አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተናገድበት መንገድ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 99, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103,105	ህዳር 2/1998
40	10797	ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እና እነ ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም (ሦስት ሰዎች)	ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳዩ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378	ታህሳስ 27/1998
41	18199	ዶ/ር ምናሴ እሸቱ እና እነ ግርማ አያና (ሰባት ሰዎች)	በጨረታ ለገዛው ንብረት ገገር ዋጋውን ሳይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ስነ-ስርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 429	ህዳር 7/1998
42	16378	የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ እና የቤ/ት/ክ/መ ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን	የመንግስት ሰራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መስራቱ ስለሚኖረው ውጤት ድንጋጌ ቁጥር 46/53, አዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2)	ታህሳስ 17/1998
43	18342	የማህበራዋ ዋስትና ባለሥልጣን እና እነ አቶ ብርሀኑ ሀሩይ (ሁለት ሰዎች)	የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.38/88 አንቀፅ 11(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4	ታህሳስ 17/1998
44	14699	የኢንጂነር ወርቁ መኮንን ወራሾች እና የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች መምሪያ	ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ህጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀፅ 29	ህዳር 7/1998

ቅጽ 4

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
45	20885	የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገቢሳ የማነ	ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ስለሚደረግ የስራ ውል አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10	ጥር 3/1999
46	15531	የኢት/ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አዱኛ ገመዳ	የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን	የካቲት 6/1999
47	21730	ወ/ሮ ፍሬህይወት እርቁ እና የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን	ወደ ሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5)	መጋቢት 11/1999
48	21119	ቃሲቲ ምግባ አክሲዮን ማህበር እና ማስተዋል ጫኔ	የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠር አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ (2)	መጋቢት 18/1999
49	21961	አቶ ግርማ ነጋሽ እና ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር	የስራ ውልን ስለማቋረጥ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) ሐ	መጋቢት 18/1999
50	20457	የኢት/ንግድ ባንክ እና ወ/ሮ አለሚቱ ሞገስ	የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ ስራ ላልተሰራበት ውዝፍ ደሞዝ የሚከፈል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43,53(1), 54	መጋቢት 20/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

51	24153	አቶ መንግስቱ አባተ እና የባህር ትራንዚት ድርጅት	ስለ መሠረታዊ የህግ ክርክር አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)ሐ	መጋቢት 26/1999
52	16653	ግዮን ሆቴሎች ድርጅት እና ወ/ሮ ስለእናት ወርቅነህ	የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን	መጋቢት 27/1999
53	25526	መምህር ጥላሁን አስፋው እና አዲስ ኮሌጅ	ሰራተኛው በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10	ሚያዝያ 16/1999
54	15662	የኢት/ልማት ባንክ እና ሐዲ አብዲራህማን ቱሲሳ	ውሰታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጉም ስላለመቻላቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2298,1733	መጋቢት 13/1999
55	19081	አቶ ዓሊ ቃሌብ አህመድ እና እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ (ሦስት ሰዎች)	ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሳሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ በሌሎች ላይ ስላለው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677,1901	መጋቢት 18/1999
56	23320	አቶ ገብሩ አብሴ እና እነ የአቶ ሁሴን አብዲረህማን ወራሾች (ሦስት ሰዎች)	የኪራይ ውል በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ስለመሆኑ	መጋቢት 20/1999
57	14493	የኢት/ልማት ባንክ እና አቶ ሚደቅሳ ቱሉማ	ውሰታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጉም ስላለመቻላቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ.2298,1733	መጋቢት 13/1999
58	18786	ወ/ሮ አለሚቱ አግዛቸው እና እነ ወ/ሮ ዝናሽ ሐይሌ	የውል አብዛኛው ግዴታ በተፈፀመ ጊዜ የተወሰነ ቀሪ ገንዘብ አለመከፈሉ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሰረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያስኝ ምክንያት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1), 1785(2), 1789	ሚያዝያ 18/1999
59	21448	ወ/ሮ ጮርፌ ወርቅነህ እና እነ ወ/ሮ አበራሽ ዱባርጌ (ሁለት ሰዎች)	የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1727 ,2877, 2878	ሚያዝያ 30/1999
60	15557	ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁ እና አቶ ብርሀኑ ተሊላ	በአፈፃፀም ጉዳይ በስህተት በፍ/ባለመብት እጅ ስለገባ የከተማ መሬት ይዞታ	መጋቢት 11/1999
61	22260	የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ (ሦስት ሰዎች)	የወጪና ኪሣራ አወሳሰን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 463	መጋቢት 18/1999
62	17984	የጌዲዮን ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት እና ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ	ጉድለት ያለበት ሀራጅ ቀሪ ሲደረግ ሻጭና ገዢን ወደነበሩበት ለመመለስ ስላለመቻል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1) እና (2)	መጋቢት 20/1999
63	19205	አቶ ሽኩር ሲራጅ እና አቶ መላት ካሣ	አንድ ፍርድ ተፈፀመ ሊባል የሚገባው ለፍርድ ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ ሲደርሰው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 395	መጋቢት 25/1999
64	19479	ወ/ሮ አመለወርቅ ገለቱ ወራሾች እና እነ አቶ ቢሻው አሻሜ (አራት ሰዎች)	አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ሆነ የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግስት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገመትና አስፈላጊም ከሆነ እንዲሸጥ የሚያደርግ ውሣኔ መሬትን የመንግስት ለማድረግ የወጣውን ሕግ የሚፃረር ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 47/67	መጋቢት 20/1999
65	16109	አቶ ከበደ አርጋው እና የኢት/ንግድ ባንክ	የሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ተዋዋዮች ውላቸውን በመዝገብ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ የማይጥልባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1587, 1620, 1613, 2878	ሚያዝያ 12/1999
66	14094	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና የአቶ ሰለሞን ወረዳ ወራሽ	ለረጅም አመታት በመንግስት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ያለአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሣኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, አዋጅ ቁ 47/67,ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/	ሚያዝያ 18/1999
67	17937	ወ/ሮ ድንቁ ተድላ እና አቶ አባተ ጫኔ	ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677 መሠረት በቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈፃሚ ስለመሆኑ ፍ/ብ/ህ/ቁ. 17,68, 100,1677,1845	መጋቢት 20/1999
68	20938	ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ እና ወ/ሮ ሣራ ልነጋነ	ስለ ጋብቻ መፍረስ	ሚያዝያ 11/1999
69	22243	ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ እና አቶ አብርሃም ካሣ	ልጅነትን ስለማስረዳት የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126(1),143(መ) እና (ሠ)	ሚያዝያ 16/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

70	17058	አቶ አንበሶ ወ/ገብርኤል እና አቶ መሣይ መኮንን	ኑዛዜ ህጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካሳቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881, 884, 892, 996-1000, ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	መጋቢት 25/1999
71	22712	አቶ እንደሻው በቀለ እና እነ ወ/ት አይናለም ያለው (ሁለት ሰዎች)	የኑዛዜ እያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትና ተናዛዥም ሆነ ምስክሮች /አማኞች/ በኑዛዜ ባሰፈሩት ቃላትና ሃረጎች ሊሰጡ የሚችለውን ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881	ሚያዝያ 9/1999
72	22162	አፍሪካ ኢንሹራንስ እና አቶ ብስራት ጉላ	መድን ሰጭ የካሣን ክፍያ በተመለከተ በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ	ሚያዝያ 9/1999
73	23339	የኢት/ጉምሩክ ባለሥልጣን እና እነ አበሮ ኢር.ጋኖ	የጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚተዳደሩ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀፅ 6(2)ለ	መጋቢት 13/1999
74	16195	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ስላሴ (ስድስት ሰዎች)	ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላላ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 4187 አንቀፅ 11(1), አዋጅ ቁ.47/67 አንቀፅ 21(2) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 74(4)	ሚያዝያ 11/1999
75	22317	የምስራቅ ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እና አቶ አብዱ አሉ አዩ	የጉምሩክ ባለስልጣን በኮንትሮባንድ ወደ ሀገር የሚገቡትን ወይም ከሀገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 5-6 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2010(2)	ሚያዝያ 18/1999
76	12025	አቶ ምናሴ አልማው እና ዓቃቤ ህግ	ጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ የጥብቅና ስራ አሰራሰሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል የማታለል ወንጀል ስለመሆኑ የ1949 ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ.656(ሀ) እና (ለ)	መጋቢት 18/1999

ቅጽ 5

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
77	17320	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ዶ/ር ሻውል ገብሬ (ሁለት ሰዎች)	ንብረትን ለመሸጥ ለመለወጥ ብሎም ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ በሚል የተሰጠ ውክልና ንብረቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችል ስልጣን እና ችሎታን የሚያጐናጽፍ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3049(2),2206(1)	መጋቢት 18/2000
78	20809	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ሃይሌ	በባለስልጣን ፊት በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ያሉትን ፊርማዎችና የሰነዶቹን ይዘት ማስተባበል ስላለመቻሉ	ሐምሌ 10/2000
79	23861	ሊቀ ስዩማን አሰፋ ባሻህውረድ እና የሣህሊተ ምህረትና ክርስቶስ ሣምራ ደብር አስተዳደር	ወኪል የሆነ ሰው ውክልናውን በሚገባ አስካሳየ ድረስ በማመልከቻው ላይ የራሱን ወይም የወካዩን ስም አስቀድሞ መፃፉ ወኪልነቱን ለውጦ ባለቤት የሚያደርገው ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 58	ጥቅምት 14/2000
80	26399	አቶ ኃ/ማርያም ባዩ እና እነ አቶ ሣሙኤል ጐሣዬ (አምስት ሰዎች)	የውክልና ስልጣኑ ቀሪ ከተደረገበት እንደራሴ ጋር በቅን ልቦና ውል ፈፅመው በተገኙ ጊዜ ውሉ እንዲፈርስ ላይወሰን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808, 1816, 2191(2), 2193	ህዳር 5/2000
81	32241	ወ/ሮ ካሰች ተካልኝ እና እነ አቶ ኃ/ማርያም አበበ (ሁለት ሰዎች)	• እንደራሴ የሆነ ሰው የውክልና ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞች (Conflict of interest) ማስወገድ ያለበት ስለመሆኑ • ከእንደራሴው ጋር ውል የፈፀመው ሦስተኛ ወገን እንደራሴው የውክልና ስልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞችን የማስወገድ ግዴታውን አለመወጣቱን ማወቁ ወይም ማወቅ የሚገባው መሆኑ ያደረጉትን ውል ፈራሽ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)	መጋቢት 9/2000
82	21355	አንበሳ የክተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት እና አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ	የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የሰጠ ወገን ከዋናው ውል አለመፅናት ጋር በተያያዘ የዋስትና ውሉ እንዲፈርስ ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1923(2)	ሐምሌ 3/2000
83	25115	አቶ ማሞ ጉበና እና አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም	ተራ ዋስ የሆነ ሰው ከባለዕዳው ጋር ተጣምሮ ክስ በቀረበበት ጊዜ ከገባው የዋስትና ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከኃላፊነት ነፃ ሊደረግ የሚችለው ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለባለገንዘቡ ከመወጣቱ ጋር በተያያዘ ስለመሆኑ	ጥቅምት 5/2000
84	26565	ግሎባል ኢንሹራንስ /አ.ማ/ እና ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/	ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገመት ወይም ሊታሰብና ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚቻል ሁኔታ ድንገተኛ ደራሽ ቢሆን እንኳ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ (Force majeure) ተብሎ የማይወሰድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 1792(2)	ጥቅምት 19/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

85	17742	ወ/ሮ አበበች ታደሰ እና እነ አስር አለቃ ሲሳይ ካብትህይመር (አራት ሰዎች)	በህግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት የሚያስችል ማንኛውም ዳኛ ውል የማዋዋል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678(ለ) እና 1715	መጋቢት 2/2000
86	23921	ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግስቱ እና አስር አለቃ ታደሰ ወርቁ	የስጦታ ውሉ በስጦታ ተቀባዩ ላይ ግዴታ ያልጣለ ቢሆንም እንኳን ስጦታ ሰጪው በድህነት ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ተቀባዩ ቀስብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2458(1)	ጥቅምት 12/2000
87	32337	ወ/ሮ ፀሐይነሽ ይህደጐ እና እነ ወ/ሮ ትሕሽ በርሔ	"የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ተራ የክፍያ ደንብ እንጂ ሌሎች ወራሾች ያላቸውን ውርሱን የመካፈል መብት የማይገድብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 913	ግንቦት 21/2000
88	22891	ወ/ሮ ማና ኃ/ሚካኤል እና እነ አቶ ገ/ማርያም ከበደው (ሁለት ሰዎች)	በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ ምክንያት የተፈጠረ ዕዳ ለጋራ ጥቅም መዋሉ በተረጋገጠ ጊዜ የዕዳው ወደ የጋራ ንብረት ወይም ወደ ሌላኛው ተጋቢ የግል ንብረት በመሄድ ሊከፈል የሚችለው በፍርድ አፈፃፀም ላይ ስለመሆኑና ከዚህ ጋር በተያያዘ በሌላኛው ተጋቢ ላይ ዕዳውን መሠረት በማድረግ ክስ ሊመሰረትበትም ሆነ ፍርድ ሊሰጥበት የማይገባ ስለመሆኑ	ህዳር 24/2000
89	31737	አቶ ገብሩ ገ/መስቀል እና ቂስ ገ/መድህን ረዳ	በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472 መሠረት በባንክ የተሰጠ የሃዋላ ወረቀት ብድርን ለማስረዳት ስለመቻሉ	የካቲት 27/2000
90	24173	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና ወ/ሮ አይዳ ሐሰን	በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት የተላከ ፖስታ /ዕቃ/ በመጥፋቱ፣ መሠረቁ፣ በመበላሸቱ፣ ወዘተ ምክንያት ካሣ የሚጠየቀው መጠኑም የሚወሰነው የፖስታ አገልግሎት ሕግን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 24/58 መሠረት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 24/58 አንቀፅ 50,51,53 እና 54	ህዳር 11/2000
91	24574	የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተ/ቤ/መ/ፖ/ጠ/ጽ/ቤት እና አቶ ይትባረክ ማህሉ	በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሳይሰጥበት የታለፈ ጉዳይ እንደተነፈገ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ	ህዳር 11/2000
92	25434	የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን እና ፋሬተርስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማህበር	በውል ውስጥ አጠራጣሪና ግልፅነት የጐደላቸው ጉዳዬች በፍ/ብ/ህ/ቁ.1738 መሠረት እልባት ሊሰጣቸው የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1738	መጋቢት 25/2000
93	29369	በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ የግብርና ምርምር ማዕከል እና አቶ ተመስገን አድነው	• የባለዕዳው ቀጥተኛ የውል ፈፃሚነት ከውሉ ባህሪ አኳያ ማስፈፀም አለመቻል ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቅ ሳያስፈልግ ኪሣራ ካለ መጠየቅ ስለመቻሉ • በውል መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ ወገንን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል በሆነ ጊዜ በውሉ ግዴታውን የተወጣው ወገን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰውን ኪሣራ ለመጠየቅ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1) እና (2)	መጋቢት 9/2000
94	19338	ዘይነባ ሐሰን እና ፍሬው ተካልኝ	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ተጐጂ የሆነ ወገን የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚኖር ስለመሆኑ ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ዳኞች ለተጐጂው የሚከፈለውን ካሣ በርትዕ መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102	መጋቢት 2/2000
95	21296	የኔዘርላንድ ልማት ድርጅት እና ውበት አድባሩ	የፍ/ብህ/ቁ. 2089 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(1) እና (2)	ታህሳስ 1/2000
96	22509	አቶ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ እና ዳርጊ ሰምሮ	የቀረበን ክስ ለማስረዳት አግባብነት የሌለው ማስረጃን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	ጥቅምት 7/2000
97	24818	ይልቃል በእውቀቱ እና ስዩም አባዲ	ጥቅም በሌለው ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ ሲሄድ አደጋ በመድረሱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው ካሣ ሊጠይቅ የሚችለው የመኪናው ባለቤት ወይም ጠባቂው ጥፋት መፈፀሙን በማስረዳት ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(2)	የካቲት 4/2000
98	27565	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ደምሴ ወርቅነት (ሁለት ሰዎች)	ጉዳት ሊካስ የሚገባው ለደረሰ ጉዳት ብቻ ሳይሆን በጉዳቱ ምክንያት ለሚመጣ ኪሣራ ጭምር ስለመሆኑ	ታህሳስ 1/2000
99	27623	ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ውባየሁ አበበ	• የማህበራዊ ዋስትና መብት ጥቅምን በሚመለከት የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የመዳኘት የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ • የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 38/88 አንቀፅ 5,8 እና 11	ህዳር 24/2000
100	28612	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን	ለደረሰ ጉዳት ሃላፊ የተባለ ሰው ላደረሰው ጉዳት ካሣ አይክፍልም ሊባል የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2091	የካቲት 25/2000
101	28750	የኢትዮጵያ ንምሩክ ባለስልጣን እና	ከውልና ከውል ወጪ በሆነ ግንኙነት ከሁለት የተለያዩ የክስ ምክንያቶች የሚመነጭ ኃላፊነትን መሠረት በማድረግ በአንደኛው ግንኙነት ብቻ ተጠያቂ የሆነን ወገን ሁለቱን የኃላፊነት ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ካሣ እንዲከፍል	ህዳር 24/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	በአንድነትና በነጠላ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2035, 1896	
102	28865	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ካሣ ግዛው	ንብረትን ከመስሪያ ቤት በኃላፊነት የተረከበ ሰው ንብረቱ በጠፋ ጊዜ ከንብረቱ መጥፋት ጋር በተያያዘ ጥፋት ያልፈፀመ መሆኑን ወይም ንብረቱ ከሥራ ሰዓት ውጪ የጠፋ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2027	ህዳር 24/2000
103	30032	የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ወ/ሮ ምንትዋብ የኔነህ	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት የክልሉ መንግስት ቋሚ ሠራተኛ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት የሞተ እንደሆነ ለተተኪዎች የጡረታ አበል እንጂ ሌላ ተጨማሪ ካሣ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የአማራ ክልል አዋጅ ቁ.74/1994 አንቀፅ 46(5) (ሀ)	ታህሳስ 1/2000
104	30442	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሰሜን ምዕራብ ሪጅን እና ወ/ሮ ድንቋ አመኔ	• ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት የሞት አደጋ በደረሰ ጊዜ የሟች የቅርብ ዘመዶች ሊኖራቸው የሚችለው መብት እና • የደረሰውን የሞት አደጋ ተከትሎ የሚቀርብ የቀለብ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095 807, 812	ህዳር 3/2000
105	31099	የተንዳሆ እርሻ ልማት አ/ማ እና ወ/ሮ ርሻን አለማየሁ	ሟች ከመሞቱ በፊት ቀለብ የማይሰፈርለት ግለሰብ በሟች ሞት ምክንያት የጉዳት ካሣ በቀለብ መልክ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095, 2069(1)	ግንቦት 14/2000
106	32144	ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እና ወ/ሮ ኢልሻ ሲራጅ	• በሞት ምክንያት ቀረ የሚባል ጥቅም የሚሰላው ከጠቅላላው የሟች ደሞዝ ላይ የሚቀነሱት በህግ የታወቁት ተቀናሾች ተቀንሰው የሚገኘውን የተጣራ ገቢ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ • የህሊና ካሣ ከአንድ ሺህ ብር ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2116	መጋቢት 23/2000
107	32250	ወ/ሮ አስናቀ ወ/ማሪያም እና እነ አቶ ከተማ ተሰማ (ሁለት ሰዎች)	በሞት አደጋ ምክንያት የተቋረጠ የመተዳደሪያ ጥቅም ጋር በተያያዘ በየወሩ የሚከፈል ካሣ አከፋፈል ስርአት በፍርድ ቤት የተወሰነውን ካሣ አጠቃሎ በባንክ ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም በማስቀመጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095(2)	መጋቢት 25/2000
108	33975	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ወ/ሮ አበበች ስዩም	የመሬት ይዞታ ባለቤት የሆነ ሰው ለህዝብ ጥቅም በሚል ይዞታውን በተጨባጨ እንዲለቅ ባልተደረገበት ሁኔታ ሊጠይቅ የሚችለው የካሣ ክፍያ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀፅ 7(1)	መጋቢት 25/2000
109	34138	እነ ሲስተር ገነት ጌታቸው (ሁለት ሰዎች) እና ወንድወሰን ኃይሉ ወልደ ማሪያም	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ከደረሰበት የአካል ጉዳት በተጨማሪ በደሞዝ ረገድ የቀረበት ጥቅም (ገቢ) መኖሩ ከተረጋገጠ ሊካስ የሚገባ ስለመሆኑ	ግንቦት 26/2000
110	34906	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት እና ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቁ	በሥራ ግንኙነት ውስጥ የቅርብ አለቃ የሆነ ሰው በሥሩ ያሉ ሠራተኞችን አስመልክቶ ለበላይ ኃላፊዎች የሚፅፈውና የሚልከው ሪፖርት ሥም ከማጥፋት ጋር በተያያዘ የፍትሐብሔር ሃላፊነት ሊያመጣበት የማይችል ስለመሆኑ	ግንቦት 5/2000
111	21740	ወ/ሮ አስረስ መስፍን እና ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ	የጋብቻ ጽሁፍ በሌለ ጊዜ ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 699(1), (2)	ጥቅምት 28/2000
112	23021	ወ/ሮ አበባ ወርቅ ጌታነህ እና ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ	በፍቺ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ የቀድሞ ተጋቢዎች እንደ ገና አብሮ መኖር የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ከሆነ ጋብቻ መፈፀሙን የህግ ግምት መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 96 እና 97(1)	ሐምሌ 12/1999
113	23493	ወ/ሮ እንግው ዘገየ እና ወ/ሮ ወርቁ መኮንን	በፍርድ ቤት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ የሟች ባለቤቶችን እኩል የጡረታ አበል የመከፈል መብት የሚሰጥ ስለመሆኑ	ሰኔ 26/1999
114	23632	ወ/ሮ ፀዳለ ደምሴ እና አቶ ክፍሌ ደምሴ	ወላጆች ለህፃናት ልጆቻቸው ሞግዚትና አስተዳዳሪ የመሆን መብታቸው ሊከበር የሚችለው ለህፃናቱ ጥቅምና ደህንነት እስከሰሩ ወይም ሊሰሩ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ስለመሆኑ የደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስተ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/96 አንቀፅ 235(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 36(2)	ጥቅምት 26/2000
115	24625	ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ እና ወ/ሮ ሊህማ አሊ	በህግ ፊት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ የጋራ ሀብትን ሁለቱ ባለቤቶች ግማሹን ለሁለት ቀሪውን ግማሽ ልጆች የሚካፈሉ ስለመሆኑ	ጥቅምት 28/2000
116	25005	መኮንን በላቸው እና ወ/ሮ አለሚቱ አደም	በጋብቻ ውል ላይ የግል ተብሎ ያልተመለከተና ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት ግንባታው የተጀመረ ቤት ግንባታው የተጠናቀቀው በጋብቻ ወቅት ከሆነ የጋራ ንብረት ተደርጎ የሚወሰድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) , 63(1)	ህዳር 3/2000
117	25281	ወ/ሮ መሠረት ፍስሐ እና አቶ ቀልቤሣ አለሙ	የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ነው በሚል የተወሰነ መኖሪያ ቤት ጋር በተያያዘ አንደኛው ተጋቢ ቤቱ የተሰራበትን መሬት (ቦታ) ከጋብቻው በፊት የተመራ በመሆኑ ሌላኛው ተጋቢ የቤቱን ግማሽ ዋጋ ተቀብሎ እንዲለቅ በሚል የሚሰጥ ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 92	ጥር 29/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀፅ 1131,1132	
118	25588	መርየንሃሰን ዑመር እና መውሊድ ተሽልእስማን	አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው መሆኑና አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት እንጂ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ስላለመሆኑ	የካቲት 6/2000
119	26839	ወ/ሮ አስካለ ለማ እና ሣህለ ሚካኤል በዛብህ	ጋብቻ ከመመስረቱ በፊት የግል የነበረ ሃብት ከጋብቻ በኋላ የጋራ ከሆነ ንብረት ጋር ተቀላቅሎ በተገኘ ጊዜ የግል የሆነው ንብረት ተለይቶ የግሉ ለሆነው ተጋቢ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 57,86(1)	ህዳር 10/2000
120	26953	አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ እና ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ	በጋብቻ/በትዳር ላይ/ ከተጋቢዎች መካከል በአንደኛው ተጋቢ አማካኝነት በካሣ መልክ የተገኘ ሃብት የጋራ ሃብት/ንብረት/ ተደርጐ የሚቆጠር ስለመሆኑ	ህዳር 13/2000
121	27697	አቶ ርዕሶም ገ/መድህን እና ወ/ሮ አልማዝ ጊላ ሚካኤል	ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የጋራ ንብረት የተሸጠ ቢሆንም የሽያጩ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንደሚገኝ ካልተረጋገጠ ለጋራ ትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85 -93	ጥቅምት 19/2000
122	27869	ፍቅርና ሠላም ኃ/የተ/የግ/ማ እና እነ ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ (ሁለት ሰዎች)	• የማይንቀሳቀስ ንብረት ለንግድ ማህበር በመዋጮ መልክ የተሰጠ ሆኖ ሲገኝ የንብረቱ ስም በኩባንያው ተመዝግቦ ያለመገኘቱ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ለመሆን የማይችል ቢሆንም ንብረቱ በአይነት መዋጮ መሰጠቱን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ • የጋራ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ አንደኛው ተጋቢ ፈቃድ ለንግድ ማህበር በዓይነት መዋጮ የተሰጠ እንደሆነ ንብረቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 517(ሠ),(ረ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878 የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(1), 69(2)	ህዳር 10/2000
123	29343	እነ ወ/ሮ አምሳለ ተፈራ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ት አበባ አድማሱ	ተጋቢዎች በጋብቻ ወቅት **የተፈራ** ቤታቸውን በትርፍነት ለመንግስት ያስረከቡ እንደሆነ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት የሆነን ቤት ያለምንም ተጨማሪ ስምምነት የጋራ የሚያደርገው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67 አንቀፅ 11(1)	ሚያዝያ 7/2000
124	29402	ወ/ሮ ሐዳስ ታረቀ እና የ፱ አለቃ አስመላሽ ኃይለስላሴ	ቤት የጋራ ሃብት ነው ከተባለ ቤቱ የተሰራበት መሬት ላይ የጋራ ባለሃብቶቹ እኩል የመጠቀም መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ	ጥቅምት 19/2000
125	30959	እነ ወ/ሮ ተወዳጅ ገ/ሥላሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ዘለቀ ዘውዴ(ሁለት ሰዎች)	• ሟች በኑዛዜው አንድን ሰው ልጄ አይደለም በማለት መግለፅ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማፍረስ የሚያበቃ ስላለመሆኑ • በቤተሰብ ህጉ ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቻልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,156,157	ታህሳስ 1/2000
126	31430	ወ/ሮ አዲስአለም አከለ እና የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ	ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የሚገኝ ድጕማ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ የአማራ ብ/ክ/መ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 73(1) እና (2)	ሚያዝያ 7/2000
127	31891	እነ አቶ አንለይ እንየው (ሰባት ሰዎች) እና ወ/ሮ መሬም ጠሃ	የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረዥም ጊዜ መኖርና በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መስርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ተቋርጧል የሚያስብል ስለመሆኑ /የሰ/መ/ቁ. 14290/	ሚያዝያ 14/2000
128	31946	ወ/ሮ ዘውዲቱ ጌታቸው እና ተመስገን ደሳለኝ	የጋብቻ ውል በህግ አግባብ አልተደረገም በሚል ተቃውሞ ያቀረበ ተጋቢ በውሉ መሠረት ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 34(2), 35(2) እና 9(1)	ግንቦት 14/2000
129	32130	እነ እማዋይሽ ካሣ (ስድስት ሰዎች) እና ወ/ሮ አስቱር አህመድ	አንድን ሰው አባት ነው ብሎ ለማለት ለልጅ እንክብካቤ ማድረጉና ልጅም በእሱ ስም መጠራቱ ብቻ ሣይሆን ግለሰቡ ድርጊቱን አባት ነኝ ከሚል ስሜትና መንፈስ በመነጨ ያደርግ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የአማራ ክ/መ/ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 79/95 አንቀፅ 154(ሐ)(ሠ)	መጋቢት 18/2000
130	33411	ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ እና አለቃ ኪሮስ ገብሩ	ተጋቢዎች ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት ወቅት የገዙት ንብረት በስማቸው ያልሠረ ቢሆንም እንኳን ንብረቱ የእኔ ነው በሚል የቀረበ የ3ኛ ወገን ተቃውሞ እስካልቀረበ ድረስ ንብረቱ የጋራ ሀብት ተደርጐ የሚወሰድና ሊከፋፈል የሚገባ ስለመሆኑ	መጋቢት 25/2000
131	33440	ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም እና አቶ ግርማ ገብረ ስላሴ	• ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ጥያቄ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ • ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ የልደት ምስክር ወረቀት ተቃውሞ የማይቀርብበት የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ ሊወሰድ የማይችል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154	ሚያዝያ 21/2000
132	33875	ወ/ሮ የሻረግ አባትኩን እና ወ/ሮ መሠረት አድማሱ	ጋብቻ በባህላዊ መንገድ ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብና መመስረቱን ማስረዳት የሚቻልበት ሁኔታ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 4 እና 97(2)	መጋቢት 25/2000
133	34149	እነ ወ/ሮ ዘለቃሽ በቀለ እና አቶ አለሙ በቀለ	የአንድ ሰው አባት ነኝ በሚል የሚቀርብ ሰው አባትነቱን በህግ አግባብ በማስረጃ ማስረዳትና ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 147(1), 97(2)	መጋቢት 25/2000
134	34387	አቶ ከበደ መሐሌ እና ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ	የጡረታ አበል እንደማንኛውም ገቢ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተደርጐ የሚወሰድ ስላለመሆኑ	ግንቦት 14/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

135	35376	እነ አቶ ዳንኤል አሰፋ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ሒሰን ውበቱ	ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት ላይ ያለን ዕዳ ለመወጣት ከጋብቻ በኃላ ከባልና ሚስት የጋራ ገንዘብ መከፈሉ ንብረቱን የጋራ ንብረት የማያደርገው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) እና 70(1)	ግንቦት 28/2000
136	23389	የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማ እና እነ ባህሩ አብርሃም (አስራ ሁለት ሰዎች)	የአክስዮን ማህበር አባላት የአክስዮን አስተዳዳሪዎች መብታቸውን በሚጐዳ መልኩ መስራታቸውን ማረጋገጥ ክቻሉ በቀጥታ መክሰስ የሚችሉ ስለመሆናቸው የንግድ ህግ ቁ. 367	ሐምሌ 10/1999
137	25306	አቶ ተስፋዬ ገለቱ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ገንዘብን በአደራ ለማድረስ የተቀበለ ባንክ አደራ አስቀማጩ ይሰጥልኝ ላለው ሰው እስካልሰጠ ድረስ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 898(1)	ህዳር 12/2000
138	27161	አቶ ኤልያስ ከፈለ እና እነ አቶ ከድር አህመድ (አራት ሰዎች)	የክሱ መሠረት የሆነው ጉዳይ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ የተረዳ ፍ/ቤት ክሱን መሰረዝ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280	ህዳር 12/2000
139	28923	የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር እና .እነ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር (ሁለት ሰዎች)	የመንግስት ልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማህበራት ሲቀየር በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያልታወቀና ውሣኔ ያልተሰጠበት እንኳን ቢሆን የልማት ድርጅቱ ዕዳ ወደ አክሲዮን ማህበር የማይተላለፍ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 208/92 አንቀፅ 5(1), 6(1)ሐ	ግንቦት 7/2000
140	23608	የኢትዮጵያ ፕራይቬተይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ እና የአቶ ኑርበዛ ተረጋ ወራሾች	በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲም ሆነ በኤጀንሲው ስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ እንደገና ለማየት ፍ/ቤቶች ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ.110/87 አንቀፅ 4(1) እና 5(3)	ህዳር 3/2000
141	27548	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ወ/ሮ ቆፀላ መርሻ (ሁለት ሰዎች)	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አጠራጣሪነቱ በታወቀ ጊዜ ከሚመለከተው አካል ተገቢውን ማብራሪያና ማስረጃ ሳይጠየቅ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1196(1)	መጋቢት 18/2000
142	29822	የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ በቀለች አማረብህ	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ስልጣን ላለው የአስተዳደር ክፍል መመለስና መሰረዝ ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቶች የባለቤትነት ደብተሩ እንዳይመለስ በሚል ውሣኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ 1196(1)	ግንቦት 28/2000
143	29860	ወ/ሮ አስናቀች ሲሻው እና እነ ወ/ሮ አሰለፈች ከተማ (አራት ሰዎች)	በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የባለቤትነት መብት ለመንግስት የተላለፈ መሆኑን እንደመከራከሪያ በማንሳት መሟገት የሚችለው የሚመለከተው የመንግስት አካል እንጂ ግለሰብ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ 47/67 አንቀፅ 13(1)	መጋቢት 18/2000
144	31490	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ሴርኮ አስራሌላዊያን	ተከሳሽ የሆነ ወገን ካቀረባቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች መካከል ፍ/ቤቱ አንዱን ብቻ መሠረት በማድረግና ሌሎቹ ላይ ብይን ሣይሰጥ ክሱን ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ብይን ባልተሰጠባቸው መቃወሚያዎች ላይ ይግባኝ ማቅረብ የማይጠበቅበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244,341	ሚያዝያ 2/2000
145	31682	አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ዘላለም ይልማ ባልቻ (ሦስት ሰዎች)	ተወርሰዋል ተብለው በመንግስታዊና ህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ሥር ያሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሠረት በማድረግ ፍ/ቤቶች መወረስና አለመውረስን በተመለከተ ማስረጃዎችን መርምሮ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67 አዋጅ ቁ.110/87	መጋቢት 12/2000
146	32376	አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሽዋንግዛው	የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸው ቤቶች ላይ የባለቤትነት /የባለቤትነትን መፋለም/ ክርክር በተነሣ ጊዜ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የማይኖራቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 41(ረ)	ግንቦት 19/2000
147	34249	እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ እና እነ አቶ አለሙ ወንድሙ	በክርክር ተካፋይ እንዲሆን የሚያስፈልግ ወገንን ተከራካሪ ወገኖች እንዲገባ ያልጠየቁ ቢሆንም ፍ/ቤቶች ይህንኑ ወገን በራሳቸው ተነሣሽነት በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2)	ሚያዝያ 28/2000
148	22857	እነ አቶ ተክሌ ደግፌ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ በፍቃዱ ኃይሌ (ሁለት ሰዎች)	• በፍርድ ሂደት ላይ ያለ ጉዳይን ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በክርክሩ ማናቸውም ደረጃ ላይ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ በእርቅ እንዲያልቅ ለመጠየቅ የሚችሉ ስለመሆናቸው • በፅሁፍ ተዘጋጅቶ የቀረበ የእርቅ ስምምነት ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ስምምነቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን አረጋግጦ በፍ/ቤት የተያዘውን ጉዳይ ማቋረጥ የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 274(1),275,(1),277(1)	ታህሳስ 15/2000
149	25912	አቶ ብሩ ቆርቾ እና አቶ ክፍሌ ሐብደታ	የግልግል ስምምነት እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3312	ሚያዝያ 2/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

150	29386	ወ/ሮ ወለላ ተሰማ እና እማሆይ በላይነሽ መለሰ	ከወራሾች መካከል አንዱ በሌለበት የተካሄደ የንብረት ክፍፍል በሌለበት ክፍያው የተፈፀመበት ወራሽ በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080	የካቲት 25/2000
151	30536	ወ/ት አለምነሽ ዋቅቶላ እና አቶ ይልቃል ጌጤ (ሁለት ሰዎች)	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ላደረሰ ወገን የመድን ሽፋን የሰጠ አካል በሃላፊነቱ መጠን ለተጐጂው መካሱ ተጐጂው በጉዳት አድራሹ ላይ የሚያቀርበውን ተጨማሪ (ቀሪ) የካሣ ጥያቄ የሚከለክል ስላለመሆኑ	መጋቢት 23/2000
152	20036	ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ	ጋብቻ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ለማሳየት /ለማረጋገጥ/ የሚቻል ስለመሆኑና ይህንንም ለማስረዳት ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ሊቀርብ ስለመቻሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 95,96 እና 97	ግንቦት 16/1998
153	25899	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ር ስዩም ካሣ	የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደሞዝ በሚያስገኝ የመንግስት ስራ ላይ ከተቀጠረ የቅጥሩ ሁኔታ በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ከደሞዝ በተጨማሪ የወሰደውን የጡረታ አበል መመለስ ያለበት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2)	ግንቦት 28/2000
154	26480	የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ እና አቶ ቢንያም አለማየሁ	ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠባቸው ጉዳዩችን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ አዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 12/91 አንቀፅ 9(4)	ጥቅምት 14/2000
155	28883	ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ሚስተር ኒኮላ አስፓፓቻት ዚስ	ከተከራካሪ ወገን አንዱ የውጭ ሀገር ዜጋ ስለሆነ ብቻ ክርክሩ ሁልጊዜ የግለሰብ አለማቀፍ ሕግ ጥያቄ ያስነሳል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 11(2)ሀ	ህዳር 26/2000
156	29005	አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ግርማቸው ይላላ (ሁለት ሰዎች)	በክፍለ ከተማ ስልጣን ክልል ውስጥ የሚነሱ ክርክሮች ላይ ክፍለ ከተማው ጣልቃገብቶ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 10(2),30 አዋጅ ቁ. 18/97 አንቀፅ	ሚያዝያ 14/2000
157	30298	አቶ የሲወንድም አቡሐይ እና አቶ አየነው ማለደ	ጠፋ የተባለ ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹ የተሸጡ ከሆነ ለማግኘት መብት የሚኖረው የንብረቶቹን የሽያጭ ዋጋ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171(1)	ጥር/2000

ቅጽ 6

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
158	08751	ወ/ሮ አበበች በጅጋ እና እነ ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ (ሁለት ሰዎች)	• ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አዲስ ማስረጃ ተገኝቷል በሚል የተሰጠው ፍርድ በድጋሚ ሊታይ የሚችልበት አግባብ • ውሣኔ ያልተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6	ግንቦት 26/2000
159	19142	አቶ መላኩ ማሞ እና እነ ወ/ሮ ፊለቀች ማሞ (ሦስት ሰዎች)	የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጋር በተያያዘ በሚሰጥ ብይን ላይ ፍ/ቤቱ በሥረ- ነገር ረገድ የመጨረሻ ውሣኔ ሣይሰጥ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320 (3)	ጥቅምት 26/2000
160	20465	አዋሽ ኢንተርናሽናል ኩባንያ እና ፀሐይ ዮሐንስ የህፃን ተመስገን ቱጂ ሞግዚትና አሳዳሪ	በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሠረት የቤንሻንጉልን ጨምሮ የአምስት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ባላቸው የውክልና ስልጣን ያዩዋቸውን የፌዴራል ጉዳዩች በይግባኝ ተቀብለው የማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 322/95, የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(2)	ሰኔ 26/2000
161	21270	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ ወይንሸት አበራ	አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከመታገዱ በፊት በባንክ በመያዣነት የተያዘ እንደሆነ ባንኩ በህግ ተሰጠው መብት መገልገል ይችል ዘንድ ፍ/ቤት የሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ማስነሳት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 158, አዋጅ ቁ. 97/90	ሐምሌ 30/1999
162	22556	ታደሰ አብዛ እና እነ የአቶ ጐሳዬ ሩገቶ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	በክርክር አመራር ሂደት የተከራካሪ ወገኖች የመሰማት መብት ተግባራዊ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ	ጥቅምት 14/2000
163	22603	የድሬዳዋ ጊዜ/አስ/ቀበሌ 20 ጽ/ቤት	ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ልዩነት ያላቸው በመሆናቸው ጥርጣሬን የፈጠሩ እንደሆነ ፍ/ቤት ተጨማሪ	ሐምሌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		እና ወ/ሮ ሽሪፍ አሊ	ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ጥርጣሬ ያለበትን ጉዳይ አጥርቶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 255,257	26/1999
164	23363	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ፊርሀን አህመድ (ሦስት ሰዎች)	የመድን ሰጪ አካል ኃላፊነት በመድን ሽፋን ፖሊሲው ላይ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በላይ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 665(2)	ግንቦት 26/2000
165	23628	ሶሎ ሲርካርና ኤ.ኤስ እና እነ.ጌትያን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ (ሁለት ሰዎች)	በውጭ ሀገር ተመዝግቦ የህግ ሰውነት ያገኘ ኩባንያ በኢትዮጵያ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ አቅርቦ በሂደት ላይ ያለ መሆኑ በውጭ አገር ያገኘውን የህግ ሰውነት ቀሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 100	ጥቅምት 21/2000
166	23692	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና እነ አሊ መሐመድ	• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጉም የሚችልበት አግባብና አፈፃፀሙ • በሦስተኛ ወገን ተከሳሽነት በክርክር ውስጥ እንዲገባ የተደረገ ወገን ከተከሳሽ ጋር ከመሚገት በቀር ተከሳሹን ተክቶ ከሣሽን መክራከር አይችልም ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 687, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2), 43	ሐምሌ 03/1999
167	23744	አቶ በቀለ በድዬ እና እነ ወጋገን ባንክ አዋሳ ቅርንጫፍ (ሦስት ሰዎች)	ዳኝነት ሚይከፈል በነባ ክስ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ጥያቄው በፍ/ቤት ትዕዛዝ /ውሣኔ/ ውድቅ የተደረገበት ተከራካሪ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320(1), (3)	ሐምሌ 26/1999
168	23769	ኢንጅነር ጋሪፉፋ እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናት ኢንስቲትዮት	ከአገልግሎት ብዛት ከጥቅም ውጭ የሚሆኑና ሊያስረክቧቸው የማይችሉ ዕቃዎች ላይ የዋጋ ግምታቸውን መጠየቅ የክሱ ምክንያት ቀሪ በሆነ ነገር ላይ ክስ እንደመመስረት የሚቆጠር ስለመሆኑ	ሐምሌ 12/1999
169	24111	የቂርቆስ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን እና ወ/ሮ የዕለተወርቅ ገ/አብ	የተከሳሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ተከሳሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተከሳሹ ሊያጣ የሚችለው መልሱን በፁሁፍ የማቅረብ መብቱን ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 195	የካቲት 11/2000
170	24627	ዶ/ር ቤተልሄም ታደሰ እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ	ከቤት ባለቤትነት ክርክር ጋር በተያያዘ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በመመሪያ፣ በቀላጤ ወይም በቃል ትዕዛዝ ከግለሰቦች የተወሰደና በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ መሆኑ ካልተገለፀ በስተቀር ጉዳዩን ለማስተናገድ ፍ/ቤቶች ስልጣን የሚኖራቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.110/ 87 አንቀፅ 3(1)	ሚያዝያ 30/2000
171	24775	ማታዶር አዲስ ጉማ እና ቢተው ረታ	ተከሳሽ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ዕለት ባለመቅረቡ ብቻ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ በሚል የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241(1), 233	ጥቅምት 21/2000
172	25026	ወ/ሮ ሁዳ መሐመድ እና ሃጂ አህመድ አህመዲን	ተከሳሽ በራሱ ቸልተኝነት በታችኛው ፍርድ ቤት መክራከሪያ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነጥቦችን በስር ፍርድ ቤት ባላነሳበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ውሣኔ መስጠት የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 328(2) እና 182(2)	ግንቦት 14/2000
173	25890	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ዝናሽ አሰፋ (ሁለት ሰዎች)	ሌሎች ተከራካሪዎች በፍርድ ቤት በማካሄድ ላይ ባሉት ክርክር ያገባኛል የሚል 3ኛ ወገን ከውሣኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41	መጋቢት 18/2000
174	26670	አዲስ አለም ሲሳይ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ባለገንዘብ በፍርድ አፈፃፀም ከፍርድ ባለዕዳው የተረከበው ንብረት ከዕዳው በላይ ከሆነ ልዩነቱን ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 428(2)	ህዳር 03/2000
175	27739	አቶ ድንቁ ገላው እና ወ/ሮ ዋለ እሸቱ	ከመሬት ሽያጭ ውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለውና በፍ/ቤት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(2)	ጥቅምት 28/2000
176	27808	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ማይገነት ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች)	ከፍርድ በፊት የሚሰጥ የማገጃ ትዕዛዝ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነን ወገን የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ያገኘውን መብት የማይነካ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 153 (2)	የካቲት 7/2000
177	28522	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ የሞያሌ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት (አራት ሰዎች)	ውሣኔ የተሰጠበትና አዲስ ክስ የቀረበበት ክርክር የሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ የተለያየ ከሆነ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	ህዳር 3/2000
178	28802	እነ ወ/ሮ በየነች ይገዙ እና አቶ ሳሙኤል ዝቅአርጋቸው	በክስ በተጠየቀውና በታመነው መሰረት ውሣኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182(2)	ታህሳስ 8/2000
179	29738	የአፓርታማ 79/6 የመኖሪያ ቤት ንብረት ሥራ ማህበር እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እና ወ/ት ዘርአዳም	የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ አይቶ መወሰን የማይችል ስለመሆኑ	ግንቦት 14/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		አሰገኘኝ	አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10(1)	
180	29761	እነ አቶ ዳባ ደበሌ (አምስት ሰዎች) እና እነ የአቶ ደበበ ተፈራ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	ያላግባብ በመንግስት የተወረሰ ንብረትን ለማስመለስ ሲባል የሚቀርበው የፍትሐብሔር ክርክር በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር የማይወድቅ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ሀ)	ጥቅምት 14/2000
181	29780	እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ አለሙ እና ወ/ሮ ከተማሽ ቸርነት	አስቀድሞ ውሣኔ ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሌላ የክርክር ጭብጥ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	ጥር 29/2000
182	30631	ወ/ሮ ዘቢዳ ሙሣ እና እነ ወ/ሮ አሻ የሱፍ (ሁለት ሰዎች)	በህገ ወጥ መንገድ ተወስዷል /ከአዋጅ ውጭ ተወርሷል/ የተባለ ቤትን ባለቤትነት በማጣራት ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 110/87	ህዳር 10/2000
183	30704	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአቶ በቀለ ወ/ማሪያም ወራሾች (ሦስት ሰዎች)	• አዋጅ ቁጥር 47/67"ን" መሠረት አድርጐ የምርጫ ቤቱ ተወስዷል /ተወርሷል/ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርበው መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ • በመንግስታዊና በህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ይመለሱልኝ እንዲሁም ውዝፍ ኪራይ ይከፈለኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ውሣኔ መስጠት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ የፍ/ቤት ስልጣን ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 110/87, አዋጅ ቁ. 47/67	መጋቢት 18/2000
184	31547	አቶ ኪዳኔ ገ/ጊዮርጊስ እና ወ/ሮ አብርሃ ተስፋሁን	ተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ባላመለከቱት ነገር ላይ ተመስርቶ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182	መጋቢት 7/2000
185	31833	ሀጅ አብዱልቃድር አህመድ እና እነ ወ/ሮ ደስታ ገ/ዮሐንስ (ሁለት ሰዎች)	በቤት ላይ የተደረገ እድሳትና ለውጥ ምን ያህል የመጠንና የአይነት ለውጥ እንዳመጣ ክርክር በተነሣ ጊዜ ልዩ አዋቂ መድቦ በማስጠናት መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136	ግንቦት 14/2000
186	32147	አቶ መሐመድ አብዱ እና አቶ አብዱራሂም አብዲ	የክስ ምክንያት የሌለው አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው በመሆኑ ተከሳሽ የሆነውን ወገን መጥራት ሳያስፈልግ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(1) (ሀ)	መጋቢት 9/2000
187	32376	የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሽዋንግዛው	ከቤት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ባለቤትነትን የመፈለም ክስ ለማየት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የስራ-ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ረ)	ግንቦት 19/2000
188	32638	የቂርቆስ ክ/ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና እነ አቶ ይርጋ ንጋቴ (አራት ሰዎች)	ወደ ክርክር መግባት ያለበት አካል በክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆን የተወሰነው ውሣኔ መብቱን የሚነካ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔው ከመፈፀሙ በፊት ውሣኔው እንዲነሳና ክርክሩ እርሱ ባለበት እንዲቀጥል መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358	መጋቢት 12/2000
189	33606	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ደጀኔ አበበ (አምስት ሰዎች)	በጊዜያዊነት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ ከተደረገ በኋላም ቢሆን በድጋሚ በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ሊቀርብ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158	የካቲት 20/2000
190	34249	እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ እና እነ አቶ አለሙ ወንድሙ	ለክርክር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ የሚታመን ወገን በመካሄድ ላይ በሚገኝ ክርክር ተካፋይ እንዲሆን መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2)	ሚያዝያ 28/2000
191	34313	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ከበደ ታደሰ	የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብ ተከሳሽ ኃላፊነት የሚመነጨው ከተከሳሹ ኃላፊነት ስለመሆኑ እና የሦስተኛ ወገን ተከሳሽ ተጠያቂ የሚሆነው ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ ሲኖር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43(1)	መጋቢት 25/2000
192	35403	አቶ አብዱልነጠፍ መሐሌ እና እነ ትዕግስት በርሃ (ሁለት ሰዎች)	• ተከሳሽ ቀርቦ ያልተከራከረው በበቂ ምክንያት ማለትም መጥሪያ ሳይደርሰው መሆኑ ከተረጋገጠ የተወሰነውን ውሣኔ በማንሳት ግራ ቀኙን ማከራከር የሚገባ ስለመሆኑ • ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆነን ወገን መከላከያ ክርክር ሳይሰማ በማለፍ ውሣኔ ለመስጠት የሚችለው ተከራካሪው በችሎት ሳይቀርብ የቀረው በቂ ባልሆነ ምክንያት መሆኑን በቀረቡለት ማስረጃዎች ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.78	ግንቦት 14/2000
193	22008	የኪራይ ቤቶች አ/ድርጅት እና እነ አቶ አሳና ጥርቅ (ሦስት ሰዎች)	መክፈል የማይገባውን የከፈለ ወገን እንዲመለስለት መጠየቅ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2164	ሐምሌ 3/1999
194	22297	የጀሚ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት እና አቶ ሸዋረገድ አድበር	በፍ/ብሔር ክርክር ሂደት ማን ክርክር መጀመርና ማስረዳት እንዳለበትና የተሻለ ማስረጃ ከማቅረብ አንፃር ለማን ፍርድ ሊሰጥ እንደሚገባ በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን የህግ መርሆዎች ወደጐን በመተው የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ	ሐምሌ 24/1999
195	22469	የጀጀጋ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክ እና እነ አዳነች	• የህዝብ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ	ሐምሌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		መንግስቱ (ሰባት ሰዎች)	• የቤተክርስቲያንን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማረጋገጥ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ አስገዳጅ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1578	5/1999
196	22719	የአ/አ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተተኪ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን እና አቶ ነጋሽ ዱባለ	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን አስመልክቶ በሚመለከተው አካል የሚሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰረዘ በኋላ በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195	ጥቅምት 14/2000
197	23608	የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽና የመንግስት ልማት ድርጅት እና አቶ ኑርበዛ ተረጋ	• የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው ለኤጀንሲው የስራ አመራር ቦርድ እንጂ ለፍ/ቤት ስላለመሆኑ • የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና አሣሪ (Binding) ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.110/87	ህዳር 3/2000
198	24269	የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና ተክለማሪያም መኮንን	• ግለሰቦች በከተማ ቦታ የመጠቀም /የመያዝ/ መብት የሚኖራቸው አግባብ ባለው መንግስት አካል /ባለሥልጣን/ ተፈቅዶ ሲሰጣቸው ስለመሆኑ • ከሚመለከተው ባለስልጣን ፈቃድ ሳይኖር የተሰራ የከተማ ቤት ህጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 292/78 አንቀፅ 7(1)	ህዳር 24/2000
199	26130	አቶ ገ/እግዚያብሔር ከበደው እና ወ/ት ሰላማዊት ወ/ንብርኤል	• የከተማ ቦታ በግል ባለቤትነት ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ • ግለሰቦች በመሬት ላይ ሊኖራቸው የሚችለው የይዞታ መብት እንጂ የባለቤትነት መብት ስላለመሆኑ • ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ የግል ይዞታ ሥር የነበረ መሬት ላይ በጋብቻ ወቅት የጋራ ቤት የተሰራ እንደሆነ ተጋቢዎቹ በመሬቱ ይዞታም ሆነ በቤቱ ላይ እኩል መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67 የኢ...ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 40(3) የትግራይ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85	የካቲት 4/2000
200	27506	እነ ሣሙኤል ውብሸት እና ብዙነህ በላይነህ	• ሁከት እንዲወገድ በሚል በቀረበ ክስ ላይ ተከሳሽ የሚያነሳው ባለቤትነትን የተመለከተ ክርክር አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ • ሁከት ይወገድልኝ በሚል ክስ በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ሊይዝ የሚገባው ጭብጥ ሁከት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም የሚል ጥያቄ አዘል መሆን ያለበት ስለመሆኑ	ሐምሌ 19/1999
201	27600	ሕብረት ባንክ አክሲዮን ማህበር እና እነ አቶ ጀማል መሐመድ (ሁለት ሰዎች)	በመያዣ በተያዘ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በማሻሻልም ሆነ ሌሎች አዲስ የሚሰሩ ስራዎች መያዣው የሚያጠቃልላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.3066	ታህሳስ 06/2000
202	29005	አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ግርማቸው ይላላ (ሁለት ሰዎች)	በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኙና በየክፍለ ከተማው የተደራጁ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤቶች ራሳቸውን የቻሉ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆኑና በስልጣን ክልላቸው ሥር በሚነሱ ክርክሮች ተካፋይ የመሆን መብት ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 36/95 አንቀፅ 10(2) አዋጅ ቁ. 1/95 /አዋጅ ቁ. 18/97	ሚያዝያ 14/2000
203	30101	አቶ ገዛኸኝ አድነው እና እነ ወ/ሮ ዳሳሽ ባይነሳኝ (ሦስት ሰዎች)	በሌላ ሰው የመሬት ይዞታ ላይ በባለይዞታው ፈቃድ ህንፃ የሠራ ሰው የህንፃውን ግምት ተቀብሎ ህንፃውን ለማስረከብ የማይገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179(1) እና (2)	ህዳር 24/2000
204	30461	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ኢማ መሐመድ	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መሬትና ድንጋይ ነክ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን በነፃ መጠቀም የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 80/89 አንቀፅ 6(18)	ህዳር 3/2000
205	33499	አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ዶቶር ደሌቦ	ለጊዜው ለመኖሪያነት የተሰጠ ቦታ ላይ ሳያስፈቅዱ ቤት መስራት የተሰራውን ቤት በገንቢው ወጪ እንዲፈርስ የሚያስደርግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1178(2)	መጋቢት 25/2000
206	33711	በቀድሞ ወረዳ 3 ቀበሌ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ክብርነሽ ቀደመ	የቤት ባለቤት ሳይሆን ወይም ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለኪራይ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስ የሚቀርብ አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ	መጋቢት 23/2000
207	33831	ሃሰን ኢብራሂም እና ኢብራሂም ይመር ሃሰን	በህግ በግልጽ የተረጋገጠ መብት እያለ በህሊና ግምት ላይ የተመሰረተ ፍርድ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ	ሚያዝያ 14/2000
208	33924	ወ/ሮ ንብርኤላ ኒኮላቶማስ እና	ከቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ክስ የሚያቀርብ ሰው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ሁልግዜም ቢሆን በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም ሊኖረው አይችልም ብሎ ለመደምደም የማይቻል ስለመሆኑ	ሚያዝያ 16/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		የኪራይቤቶች ኤጀንሲ	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1)	
209	34406	ወ/ሮ መገርቱ ነጋሣ እና እነ ወ/ሮ ፀሃይ ልጋ	ያላግባብ መበልፀግ ጋር በተያያዘ የሚነሳ የካሣ ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ ከውል ውጭ በሚደርስ ሃላፊነት ሥር የተመለከተው የይርጋ ዘመን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1)	ሚያዝያ 7/2000
210	20295	አቶ ደጀኔ ለገሠ እና እነ አቶ መላኩ ጌታቸው	ወራሽነትን ካረጋገጡ በኋላ ንብረት ተይዞብኛል ይመለስልኝ የሚል ጥያቄ ከሦስት አመት በኋላ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1)	ሐምሌ 5/1999
211	25567	ወ/ት አይናለም አበበ እና አቶ ደገፉ ጉርሙ	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000 ወራሽ ነኝ ወይም ወራሽነቱ ይረጋገጥልኝ ከሚል ጥያቄ ጀምሮ የውርስ ንብረት ያለ አግባብ ተይዞብኛል በሚል ለሚቀርብ አቤቱታ ጭምር ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 999, 1000	ህዳር 12/2000
212	25664	አቶ ተገኝ ይማም እና እነ አቶ ካሣሁን ደሳለኝ	በወራሾችና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ የውርስ ንብረትን የተመለከተ ክርክር በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845	ግንቦት 7/2000
213	26422	ወ/ሮ ስንልሽ ማዘንጊያ እና እነ አቶ ተስፋ ማዘንጊያ	ከውርስ ሀብት ጋር በተያያዘ ወራሽ ነኝ የሚል ወገን መብቱንና የውርስ ንብረቶቹ በሌላ ወራሽ መያዛቸውን ካወቀ ከሦስት ዓመት በኋላ የሚያቀርበው የወራሽነት ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1)	ጥቅምት 28/2000
214	28686	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ግዛው መንጀታ	ውል የመጣስ ተግባር ተጀምሮ ያልቆመ ይልቁንም በመቀጠል ላይ ያለ ተግባር መሆኑ በማናቸውም ጊዜ ግዴታን ለመጠየቅ የሚያስችል ስለመሆኑና በይርጋ ታግዷል ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845, 1846	ህዳር 24/2000
215	28997	ስለ አሶሳ ዞን ግብርና እና ትምህርት መምሪያ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ እና በላይ ወርቁ	የመብት ጥያቄን ከፍርድ ቤት ውጪ ላሉ አስተዳደር አካላት ማቅረብ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1851(ለ)	ታህሳስ 1/2000
216	29920	የባህር ዳር ጨ/ጨ/አ/ማኅበር እና አቶ አመሸ ሰይድ	ዳኝነት የተጠየቀበት ነገር ተቀባይነት ሣያገኝ የታሰፈ እንደሆነ እንደተከለከለ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(3)	ጥቅምት 26/2000
217	31185	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ይርጋ በተቋረጠ ጊዜ ቀድሞ የነበረው የይርጋ ጊዜ እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1852(1)	ግንቦት 12/2000
218	31217	የቱሌኮምኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ጫሊ ሐሰን	የደሞዝ ጭማሪና ቦነስን የተመለከተ ክስ በስድስት ወር ውስጥ አለመቅረቡ መብቱን በይርጋ የሚያሳግድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162(3)	ግንቦት 14/2000
219	31857	መሐመድ አብደላ እና የድሬዳዋ ኢትዮ ጂቡቲ ምድር ባቡር	የአሰሪ የስራ ስንብት እርምጃ የመውሰድ መብት ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከተከሰተበት ጀምሮ በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ተግባራዊ ካልሆነ መብቱ በይርጋ የሚቀር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/97 አንቀፅ 27(3)	መጋቢት 17/2000
220	32788	የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና አቶ ግርማ ተገኝ	አሠሪ የሠራተኛን መብት በጽሁፍ ያወቀ መሆኑ ሠራተኛው በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ገደብ የሚያቋርጥ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 164(3)	መጋቢት 18/2000
221	34011	እልፍነሽ አማረ እና አቶ ግርማ አማረ	ቤት በፍ/ብሔር ህጉ ውስጥ እንደ ርስት የማይቆጠርና የይርጋ መርሆ ተፈፃሚ የሚሆንበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(2)	መጋቢት 25/2000
222	31748	ይስማው ድረስ እና ይበልጣፍ ፍቅር	ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ የሚገዛው የህግ ክፍል ይርጋን አስመልክቶ በተለይ የሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ በሌለ ጊዜ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845	የካቲት 18/2000
223	18832	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ከበደ ቱሉ (ስድስት ሰዎች)	ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ የተወሰነው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የስራ ውሉ ያለ በቂ ምክንያት ከተቋረጠ ሠራተኛው የውሉ ጊዜ ወይም ስራው እንኪያልቅ ቢቆይ ያገኘው የነበረውን ደሞዝ የሚያህል ደሞዝ የሚከፈለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43(4)(ለ)	ህዳር 3/2000
224	20416	አቶ ቢንያም ገረመው እና የቻይና መንገድና ድልድል ስራ ድርጅት	ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ከሆነ ክሱ እንዲሻሻልና ክርክሩ እንዲለወጥ ሊፈቀድ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91	ታህሣሥ 8/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

225	21329	የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ በቀለ ኩምላ	የሥራ መሪ የሆነ ሰው የሥራ ውሉ ተቋርጧል በሚል ማይሰራ ለቆየበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለው የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	ጥቅምት 19/2000
226	22275	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ኃይሌ ገ/ሥላሴ	• አሰሪ የሥራ ውሉ ዘመን ከማለቁ በፊትም ቢሆን በቂና ህጋዊ ምክንያት ካለው የሠራተኛን የሥራ ውል ሊያቋርጥ ስለመቻሉ • በበቂ ምክንያት የተደረገ የሥራ ውል ማቋረጥ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠም በሚል ህገ-ወጥ ስንብት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ • በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለን የስራ መደብ በሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የሥር ውል ለማቋረጥ ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 35	ሐምሌ 10/1999
227	25317	ጥቁር አባይ ትራንስፖርት እና ደሳለኝ አብርሃ	በህገ ወጥ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ በሞተ ጊዜ ለጥገኞቹ ክፍያ የሚፈፀምበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/ 96 አንቀፅ 39(2),110(2), 40	ህዳር 10/2000
228	25511	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ አብራራው ከፍያለው	በህጋዊ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 39	ጥቅምት 2/2000
229	26077	አቶ አይናለም ባይሌ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ከተደነገገው ይልቅ በአሰሪና ሠራተኛው መካከል የሚደረገው የህብረት ስምምነት ለሠራተኛው የተሻለ መብትና ጥቅም የሚያስገኝ በሆነ ጊዜ የህብረት ስምምነቱ ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 134(2)	ሐምሌ 12/1999
230	27704	ድራጋዶስ ጂ እና ፒ የመንገድ ስራ ድርጅት እና አብዲ ሁሴን	የሥራ ውሉ በህገ-ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል ወደሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ ካልሆነ በስተቀር ውዝፍ ደመወዝ የማይከፈል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5)	ጥቅምት 5/2000
231	27959	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ አሊ መሐመድ	• አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ተቋርጦ ለነበረበት ጊዜ የዓመት ዕረፍት ሊያገኝ የማይችል ስለመሆኑ • የዓመት ፈቃድ ከሁለት ዓመታት በላይ ሊተላለፍ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 79(5)	ህዳር 3/2000
232	29692	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ከበደ	አሠሪ ቋሚ ስራ ሆኖ እየተቋረጠ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ እንዳለቀ የሠራተኛን ውል ለማቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ	ጥቅምት 12/2000
233	29740	አቶ ስሜነህ ተክሉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ	ፍርድ ቤቶች በቀረበ ክስ ላይ የዕዳ ማቻቻል ጥያቄ በተነሣ ጊዜ ማስረጃዎችን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ	ሚያዝያ 2/2000
234	29866	ቻይና ዋንቦ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን እና ወርቅነህ ምህረቱ	የውክልና ስልጣን ማስረጃ በወካይና በተወካይ መካከል የቅጥር ውል ስለመኖሩ የሚያስረዳ ስላለመሆኑ	ግንቦት 7/2000
235	29949	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ዋሲሁን አዳነ	ፍርድ ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ የሚሰጥ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ	ሐምሌ 19/1999
236	30956	የወረዳ 5 አጠቃላይ ነጋዴዎች ማህበር እና አቶ በድሉ ጫላ	ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ	ሚያዝያ 9/2000
237	31402	የኢትዮጵያ አገር አቋራጭ ከፍተኛ አውቶብስ የግል ባለንብረቶች ማህበር እና አቶ አያሌው ይርጉ	በጡረታ የተገለለን ወይም የጡረታ ዕድሜው ያለፈን ሠራተኛ ወደ ሥራ መልስ ተብሎ አሰሪ የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 24(3) አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀፅ 12(1)(ሐ)	ሚያዝያ 30/2000
238	32545	አቶ ግርማ ሽፈራው እና የክርስቲያን በጐ አድራጐት ልማት ድርጅት	የፕሮቪደንት ፈንድ ባለመብት የሆነ ሰው በአስር አመት ውስጥ መብቱን ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845	ግንቦት 14/2000
239	33314	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ወልዴ (አስር ሰዎች)	በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ የነበረን ፋብሪካ የተረከበ ባንክ ከሠራተኞች መብቶች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጥ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 16 አዋጅ ቁ. 97/90	ግንቦት 28/2000
240	33513	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ዘውዴ ተናኘ	በአንድ የስራ መደብ ላይ በቋሚነት የደረጃ እድገት ይሰጠኝ በማለት የሚቀርብ ክስን ለማየት የክልል ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 138	ጥር 27/2000
241	34588	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና	በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ የተባለ ሰው በፍትሐብሔር ረገድ ከቀረበበት ክስም የግድ ነፃ ይሆናል ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ስላለመሆኑ	ግንቦት 5/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		ደረጀ ወልደ ኪዳን	አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27	
242	35440	የዋልያ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ድርጅት እና ብርሃኑ አለሜ	ከሠራተኞች ማህበር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር በአሰሪ የሚደረግ የሠራተኞች ቅነሳ የህግ አግባብ ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28(1)	ግንቦት 19/2000
243	29415	ዋተር አክሽን እና ይልማ አሰፋ	አዲስ ወደ ተዛወሩበት ቦታ በመሄድ ስራ አለመጀመር እና ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ገበታ ላይ አለመገኘት በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውልን ለማቋረጥ በቂና ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2)(ለ)	ጥር 27/2000
244	32822	ጂ.ሰቨን የንግድና ኢንዱስትሪ የመኽር ቃጫ ውጤቶች ፋብሪካ እና መኮንን አበራ	ያለ በቂ ምክንያት ከስራ መቅረት አሠሪ የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) (ለ)	ጥር 27/2000
245	32229	መሪጌታ ልሣነወርቅ በዛብህ እና ጠቅላይ ቤ/ክህነት ጽ/ቤት	የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሣኔ መሻር ሳያስፈልገው ጉዳዩ ስልጣን ወዳለው አካል ቀርቦ መታየት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	ሚያዝያ 30/2000

ቅጽ 7

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
246	12719	ሉክሰር የቱሪስትና የጉዞ ወኪል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እና ብሩኔይስ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር	በሁለት ወገኖች መካከል የተፈረመ ሰነድን እንደ ህጋዊ ስምምነት ለመውሰድ የፈራሚ ወገኖችን ሃሳብና ፍላጐት መመርመር አስፈላጊ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1734, 1952/1/	ታህሳስ 17/2000
247	20232	አቶ ትዕግስቱ ብዛ እና አቶ ይሃ ይብሬ	የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች የሚፈጠሩባቸውና የሚረጋገጡባቸው በመሆናቸው የውል ህግ መሰረታዊ ድንጋጌዎች መሟላታቸው አስፈላጊ ሁኔታ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 715, የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706, 1679	ሐምሌ 24/1999
248	23609	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አሰበወርቅ ዘገዬ	የስራ መሪ የሥራ ውል ያለአግባብ በተቋረጠ ጊዜ የስራ መሪው ሊያገኝ ስለሚገባው ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና ጥቅማጥቅም የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2573, 2574/2/, 2570/2/, 2577, 2562	ታህሳስ 15/2000
249	30298	አቶ የሺወንድም አቡሃይ እና አቶ አየነው ማለደ	የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው ንብረቱ ወደ 3ኛ ወገን የተላለፈ በሆነ ጊዜ የንብረቱን ዋጋ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171	ጥር 20/2000
250	16218	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ወ/ሮ አስካለ ሁንዴ(ሁለት ሰዎች)	ባንኮች ከሚሰጡት ብድር እና የመያዣ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች አዋጅ ቁ. 97/90"ን" ዓላማ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በባንኮች የሚወጡትን የፎርክሎዥር መመሪያዎችና አግባብነት ያላቸውን ህግጋት ግምት ውስጥ በማስገባት እልባት ማግኘት ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 እና 4, አዋጅ ቁ. 216/92	መጋቢት 16/2000
251	25863	የኢት/ልማት ባንክ እና የኢት/ንግድ ባንክ (ሁለት ሰዎች)	ለባንክ በመያዣነት በተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚኖር የቀዳሚነት መብት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3088, 3052, 3081,3059	ጥቅምት 26/2000
252	29269	የኢት/ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ዋለልኝ አያሌው(ሁለት ሰዎች)	• በፍርድ የተቋቋመ መያዣ ላይ ፍርዱ እንዲሰጥ ያደረገው ባለገንዘብ መያዣ በሆነው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ እና • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 ተፈፃሚነት የአንድ ፍርድ ባለዕዳ ንብረት በእርሱ ላይ የቀረቡትን ገንዘብ ጠያቂዎች ፍላጐት የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ክፍፍሉ ጋር በተገናኘ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3041, 3044, 3059/1/, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403,154	ጥቅምት 15/2000
253	29375	የት/ንግድ ባንክ እና ተስፋዬ ገ/ጊዮርጊስ	የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት ከተሰጠ በኋላ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ የሚደረግ ማናቸውም የማሻሻል ሥራ የመያዣ ውሉ አካል ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3066 አዋጅ ቁ. 97/90	ጥቅምት 19/2000
254	33295	ወ/ሪት ብርሃኔ አበበ እና እነ አቶ ማርቆስ ተርፋ (አራት ሰዎች)	የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማንኛቸውም ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ ርስተ መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ምንም አይነት ውጤት የማያስገኝ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3052, 3053,1605, 1607, 1606	ግንቦት 21/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

255	23024	ወ/ሮ ፋጤ በሽር እና መልዓክ ገነት ዮሐንስ አምባው እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ	በጣልቃ ገብነት ተሳታፊ ሆኖ የፍርድ ተጠቃሚ የሆነ ወገን ዋና ተከራካሪ ከሆኑት ወገኖች መካከል በአንዱ አነሣሽነት ጉዳዩ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ በሥር ፍርድ ተጠቃሚ የሆነው ጣልቃ ገብ ባልተጠራበት ሁኔታ የሚሰጥ ውሣኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40/5/"ን" የሚሻረር ስለመሆኑ	ሐምሌ 24/1999
256	24221	ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና 4ኡነ ወ/ሮ አረጋሽ አምደሚካኤል	ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ጋር የተደረገን የኪራይ ውል መሰረት በማድረግ የተያዘ ቤትን ያለአከራዩ ፍቃድ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ለኪራይ ውሉ መሰረዝ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ	ህዳር 24/2000
257	25938	ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና የአቶ ገ/ሕይወት ከ7ዶም ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	የኪራይ ውል የተለየ ፎርም መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የሌለ ስለመሆኑ እና በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚፀና ውል /ህጋዊ ውጤት ያለው ውል/ ለመመስረት በሁለቱም መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719/1/,1719-1930, 2898/3/	መጋቢት 25/2000
258	28025	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ታደለ አበበ	ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ለተከራዩ በሚሰጥ ማስታወቂያ በማናቸውም ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ እና የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ/ለማፍረስ ለተከራዩ ማስታወቂያ /ማስጠንቀቂያ/ መስጠት አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966/1/	ጥር 20/2000
259	31601	ወ/ሮ መዓዛ ይሕደጐ እና እነ አየለ ወልዴ (ሁለት ሰዎች)	የኪራይ ውል ተቋርጦ ውዝፍ ኪራይ እንዲከፈሉኝና ቤቱንም ልረከብ በሚል የሚጠየቅ ዳኝነት የኪራይ ገንዘብ የተጠየቀበትን ቤት ግምት ጭምር ታሳቢ ተደርጐ የዳኝነት ክፍያ ሊቀርብበት የሚገባ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 227/2/, 226	የካቲት 11/2000
260	31634	ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአቶ ወርቁ ሚስት ወ/ሮ ጽጌ በየነ (ሰባት ሰዎች)	መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ እስከ 2 ዓመት ድረስ ሳይከፈል የቀረ የኪራይ ዕዳ እንደተከፈለ የህግ ግምት ይወስድበታል ማለት ባለገንዘቡ /አከራዩ/ ክስ መስርቶም ቢሆን ዕዳውን ለማሰብሰብ የማይችል መሆኑን ለማመላከት እንጂ ተከራዩ /ባለዕዳው/ ግዴታውን እንደተወጣ የሚያስቆጥረው ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/መ/	መጋቢት 4/2000
261	32521	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ዳባ ኢኛቶ	የታወቀ የኪራይ ውል ግንኙነት ሳይኖር ወይም ባለቤት ሳይሆኑ በማይንቀሳቀስ ንብረት መገልገል የተገለገለውን ወገን በንብረቱ በበለፀገው መጠን ኃላፊ የሚያደርገው ስለመሆኑ	ሚያዝያ 7/2000
262	34456	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና ወ/ት ደብሪቱ ወልደሃና	ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ውሉ የተደረገበት ጊዜ ካለቀና ውሉ ወደ ያልተወሰነ ጊዜ ከተቀየረ የኪራይ ውሉን በማናቸውም ጊዜ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966	ግንቦት 14/2000
263	18380	አቶ ማሞ ደምሴ እና እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር (ሁለት ሰዎች)	ውል ይጽደቅልኝ በሚል ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1//ሀ/	ጥቅምት 5/2000
264	22448	ኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ክፍል አ/ማህበር እና አቶ መሉነህ ካሰ	ፍርድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ ችሎታ ያለው ፍርድ የተፈረደለት ሰው /ወገን/ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378/1/	ጥቅምት 28/2000
265	22860	ሰንላይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ እና አቶ ካሣዬ ዘውዴ	አንድ ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት ህጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ያዘዘ ካልሆነ በቀር ግዴታው መኖሩን በጽሁፍ፣ በምስክር፣ በህሊና ግምት በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሃላ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2002	የካቲት 18/2000
266	23331	ጀማል ሐሚድ እና እነ ወ/ሮ ለተሃይማኖት ተክሌ (አምስት ሰዎች)	በህግ ፀንቶ ያለ የሽያጭ ውልን መሰረት በማድረግ የተገኘ መብት ውሉ ፈራሽ እስካልተደረገ ድረስ የሚቀጥል ስለመሆኑ	ታህሳስ 1/2000
267	24974	እነ አቶ ፈቃዱ ደሬሌ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ንጉሴ ወርቁ (ሁለት ሰዎች)	በውል ከተገባ ግዴታ አመዛኙ ክፍል ተፈፀመ ወይም/እና አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተከስቷል ለማለት ባልተቻለ ጊዜ ውል እንዲሰረዝ ለመወሰን የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771,1784, 1785	ታህሳስ 8/2000
268	26996	አቶ በቀለ ደቦጭ እና እነ ወ/ሮ አዛለች ደግለኝ (ሰባት ሰዎች)	ውል የተደረገበት ጉዳይ ሊፈፀም የማይችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ቦታ የመመለስ ውጤት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1715, 1815	የካቲት 18/2000
269	27349	ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኪባንያ እና ዘላቂ ግብርና ተሐድሶ ኮሚሽን	ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚፈጠርን አለመግባባት በስምምነት ወይም ደግሞ በአስታራቂ አማካኝነት ለመፍታት የተስማሙ ከሆነ ይኸው ስምምነት ተፈፃሚ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1765, 1731/1/	ታህሳስ 8/2000
270	28663	አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ እና ወ/ሮ አልማዝ ወልዴ	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658 ተጋቢ ወገን ከሦስተኛ ወገን ጋር ያደረገውን ውል ለማፍረስ ምክንያት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658, 686	ጥር 27/2000
271	29233	አቶ ሙሂዲን ፋሪስ እና አቶ እያሱ በዕደ ማርያም	በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተደረገ ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሰረት የተሟላ አይደለም በሚል ውሣኔ ሲሰጥ ተዋዋይ የነበሩ ወገኖች በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815 መሰረት ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1720/1/, 1815	ግንቦት 7/2000
272	32222	አቶ መሐመድ ኢብራሂም እና አቶ ታይደር ማች	ያልነበረ ቤትን ሠርቶ ለማስተላለፍ በሚል የሚደረግ ስምምነትን በተመለከተ	የካቲት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2876, 1723, 3019, 3020/2/	4/2000
273	32899	ወ/ሮ አስካለ ማርያም ታደሰ እና አቶ ተሾመ ካሣዬ	የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን በተመለከተ የተደረገ የሽያጭ ውል ተቀብሎ ከማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ ከማያያዝና ከመፃፍ በስተቀር የሽያጭ ውሉን የማዋዋልና የማረጋገጥ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ	ግንቦት 21/2000
274	23322	ወ/ሮ አዳነች ወርዶፋ እና እነ ወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ	የውርስ ሀብት አጣሪ የንብረት ባለቤትነትን የመወሰን ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 956	ሰኔ 19/2000
275	25869	ወ/ሮ አየለች አልታዬ እና ወ/ሮ አስናቀች አየለ	የማይንቀሳቀስ ንብረት የጋራ ባለሀብት የሆኑ ሰዎች ንብረቱን በአይነት ለመከፋፈል ባልቻሉ ጊዜ ንብረቱ በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡን መካፈል ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1272, 1273	ሰኔ 19/2000
276	30158	እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞግዚት ሐይሉ ሲሳይ እና የክ/ል እሸቱ ተስፋዬ ወራሾች	በፍ/ብ/ህጉ ውስጥ "ከዘር የወረደ ርስት" በሚል የተቀረበው አገላለጽ በህገ-መንግስቱ የተሻረ ወይም ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000/2/ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 40	ሰኔ 19/2000
277	32414	ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ እና እነ ወ/ሮ ሃሳብከፋይ ጌራወርቅ (ሁለት ሰዎች)	ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርብ ክስ እና የተሰጠ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ በሚል የሚቀርብ ተቃውሞ የተለያዩ ይዘትና ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996/1/, 998/1/, 973, 996/2/	ሰኔ 24/2000
278	34076	ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ እና እነ እማሆይ ድብቅነሽ ግዛው (ሁለት ሰዎች)	የውርስ ሃብቶች በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ በሆነ ጊዜ የሚነሱ ክርክሮች የውርሱ ክፍያ በተጀመረበት ቦታ ለሚገኝ ፍ/ቤት የሚቀርቡና የሚስተናገዱ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 23	ሰኔ 10/2000
279	24703	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ት/ቢሮ	በህግ ተቀባይነት ያለው የኢንሹራንስ ውል የሚቋቋምበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1725, 1727 የንግድ ህግ ቁጥር 651, 654, 657	ሚያዝያ 9/1999
280	22069	የአማራ ብ/ክ/መንግስት ፍትሕ ቢሮ እና አቶ አስማማው አራጌ	በወንጀል ህግ የሃሳብ ክፍል የሚረጋገጠው ከወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ በመነሳት ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ቁ. 522 /1/ /ሀ/	ጥቅምት 28/2000
281	22452	የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና አሣምነው ገ/መስቀል	በወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ ሥር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሳቸው የሚቆሙ ስለመሆናቸው የወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/	ሐምሌ 30/2000
282	23855	የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ እና አቶ ፀጋሁን መንግስቱ	የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈፀምበት የመንግስት ቀረጥ ያልተከፈለበት መኪና ይዞ የተገኘ ግለሰብ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ ያልተባለ ቢሆንም ግለሰቡ ተገቢውን ቀረጥ ከፍሎ መኪናውን መረከብ አልያም ደግሞ መኪናው መወረስ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 74 አዋጅ ቁ. 388/95 አንቀጽ 80/3/	ጥቅምት 26/2000
283	24278	ሰለሞን ሄርጃቦ እና የደ/ብ/ብ/ ሕ/ክ/መ/ የሥ/ፀ/መ/ኮ/ዓ/ሕግ	በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ መሠት የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው እንዲጠብቃቸው በአደራ የተረከባቸውን ወይም በሥራው አጋጣሚና ምክንያት በእጁ የገቡትን ንብረቶች የወሰደው/የሰወረው/ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ	ህዳር 10/2000
284	28952	የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ እና አቶ ባንቲ ታኤራ	በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/ መሠረት ከሣሽ አቅርቦት የነበረውን ክስ ካነሣ በኋላ እንደገና ክሱን ለመቀጠል የሚችል ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/, /5/	መጋቢት 16/2000
285	29325	ኤርምያስ ካሣ ተፈራ እና ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ክስ የቀረበበት ሰውን አስመልክቶ ጉዳዩ በሌለበት ነው የታየው ሊባል የሚችልበት አግባብ የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ. 161/1/	የካቲት 18/2000
286	31734	አቶ አስናቀ በቀለ እና ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ተከሶ የተያዘ ሰው ዋስትና በጠየቀ ጊዜ ፍ/ቤት ተከሳሹ ተመልሶ ሊቀርብ አይችልም የሚል ግምት ለመውሰድና ዋስትናን ለመከልከል በቂ ምክንያት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 67/ሀ/	ጥቅምት 15/2000
287	34077	አቶ ሰይድ ይመር እና የአማራ ክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	በወንጀል የተከሰሰ ሰው የሚያነሳው የዋስትና ጥያቄ መታየት ያለበት ሊወሰንበት ከሚችለው ቅጣት አንፃር ስለመሆኑ	መጋቢት 9/2000
288	34280	አቶ ግርማይ ደስታ እና ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ህግ ቅጣት ሊገደብ የሚችልበት አግባብ የወንጀል ህ/ቁ. 192,194	ግንቦት 14/2000
289	34521	የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ እና ስንታየሁ ተፈራ	በወንጀል ህግ ቅጣትን በልዩ የህጉ ክፍል ከተወሰነው መነሻ ዝቅ አድርጐ በማቅለል ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የወ/ህ/ቁ. 184, 179	ሰኔ 3/2000
290	35611	ሻለቃ ታደሰ ካሕሳይ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ህግ ጉዳዩን ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት አቤቱታ አቅራቢው ባልቀረበ ጊዜ አቤቱታው እንዲሰረዝ የሚደረገው አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን በትጋት ያልተከታተለ ወይም በቸልተኝነት የተወው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ 193/1/	ሰኔ 19/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

291	18809	አቶ ሚሊዮን ዑመር እና ዮፌደራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን	በደንብ ቁጥር 75/1993 ኮምፒዮተርን ጨምሮ ከተለያዩ መሳሪያዎች ሀንዛዎችና ሌሎች ዕቃዎች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ለመሰብሰው የተደነገገው መኪናን በማከራየት የሚገኝን ገቢ የሚያካትት ስለመሆኑ ደንብ ቁጥር 75/93 አንቀጽ 2/9/ ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 24/2/ /ሸ/	ሰኔ 12/2000
292	19258	አቶ ተክሌ ዋቅጅራ እና አቶ ሾንጣ ገቡ	የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር መዋጮ መከፈል ያለበት ማህበሩ ሲቋቋም እንጂ ተቋቁሞ ሥራው ከተጀረ በኋላ ስላለመሆኑ	ሐምሌ 12/1999
293	23389	የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኅበር እና እነ ባህሩ አብርሃም (ሁለት ሰዎች)	የአክሲዮን ማህበር አባላት መብታቸውን የሚነካ ድርጊት በማህበሩ አስተዳዳሪዎች በተከናወነ ጊዜ በቀጥታ አስተዳዳሪዎቹን ሊከሱ ስለመቻላቸው የንግድ ህ/ቁ. 364,365,367	ሐምሌ 10/1999
294	28923	የባህር ዳር ጨ/ጨ አክስዮን ማሕበር እና የባህር ዳር ልዩ አስተዳደር እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ	የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ ከመቀየራቸው በፊት ያለባቸውን የዕዳ ክርክር በኃላፊነት ይዞ መከራከር ያለበት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 208/1992 አንቀጽ 5/1/, 6/1/ /ሐ/, አዋጅ ቁ. 182/1992	ግንቦት 7/2000
295	10489	የስራና ከተማ ልማት ሚ/ሮ ተተኪ መሠረተ ልማት ሚ/ር እና የቀድሞ ብሐራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግ/ማ	በበጀት የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት የፍርድ ባለዕዳ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔውን ለማስፈፀም ለሌላ ጉዳይ በበጀት የተያዘውን እና የሰራተኛ ደመወዝን የሚያካትተውን ገንዘብ ከብሔራዊ ባንክ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ለማዘዝ ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 404	ሐምሌ 24/1999
296	18576	ወ/ሮ ደስታ መኮንን እና ወ/ት መሰሉ ጌታሁን	የውርስ ማጣራት ሪፖርት ከፀደቀ ወይም በፍ/ቤት ተቀባይነት ካገኘ በኋላም ቢሆን እንደ ፍርድ ተቆጥሮ በቀጥታ የአፈፃፀም አቤቱታ ሊቀርብበት ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 944, 946, 956, 960, 996	ግንባት 26/2000
297	19283	ወ/ሮ መድሐኒት ኃይሉ እና የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ	ባንክ ለሰጠው ብድር በመያዣነት እጁ ያስገባውን የተበዳሪ ንብረት በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛው የሃራጅ ጨረታ ለሽያጭ አቅርቦ ገዢ ያልተገኘ እንደሆነ ንብረቱን ሊያስቀር የሚችለው ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሰረት ስለመሆኑ	መጋቢት 9/2000
298	22481	አቶ ክፍሌ ወልዴ እና ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	በሀራጅ ጨረታ የአሻሻጥ ስርዓት ላይ "ግዙፍ የሆነ ጉድለት" ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር እንደተፈፀመ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 422/3/, 428/5/, 455, 428/1/	መጋቢት 4/2000
299	22930	ወ/ሮ ታድሬ አባተ እና ወ/ሮ ዓለም ገ/የሱስ	ባልና ሚስት በፍቺ ከተለያዩና የንብረት ክፍፍል ከተደረገ በኋላ ከአንደኛው ተጋቢ የግል ተግባር የሚመነጭ ዕዳ አፈፃፀም የተጠየቀው /የቀረበው/ ከፍቺ በኋላ እስከሆነ ድረስ ለዕዳው ምክንያት ከሆነው ተጋቢ ብቻ የሚጠየቅ ስለመሆኑ	ሚያዝያ 30/2000
300	23733	እነ ሃፍቶም ገ/አራሃ (ሁለት ሰዎች) እና እነ መሉ ካሣ (አራት ሰዎች)	ከንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ በዋናው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ንብረት መካፈል ከተቻለ እንዲካፈል ካልሆነ ደግሞ በባለሙያ ተገምቶ እንዲካፈሉ በሚል የተሰጠን ፍርድ መነሻ በማድረግ የአፈፃፀም ችሎት /ፍ/ቤት/ ከተከራካሪ ወገኖች መካከል አንደኛው ግምቱን ከፍለው ንብረቱን እንዲያስቀሩ በሚል ትዕዛዝ ለመስጠት የማይችል ስለመሆኑ	ህዳር 24/2000
301	23989	አቶ ደስታ ሠርዳ እና የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ	የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ንብረት /ባለቤትነት/ ከሻጭ ወደ ገዥ ያለመዛወሩ ብቻ ሦስተኛ ወገኖች በሻጭ ላይ ሽያጭ የተካሄደበት ንብረት ላይ የጀመሩት አፈፃፀም እንዲቀጥል ለማስደረግ በቂ ሁኔታ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878	ታህሳስ 17/2000
302	25031	ወ/ሮ አልታየወርቅ ኃ/ማርያም እና አቶ ዓለማየሁ ገሰቱ	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሰረት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358,418	ታህሳስ 1/2000
303	26553	የባህርዳር ልዩ ዞን ገንዘብ መምሪያ እና የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ እና ሙክታር መሐመድ	• የማይንቀሳቀስ ንብረት በሃራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በሃራጅ እንዲሸጥ የሚወጣው ማስታወቂያ ለ30 ቀናት መቆየት ያለበት ስለመሆኑ • ንብረቱ በመያዣ የተያዘ እንደሆነም የመያዣው ልክ ምን ያህል እንደሆነ በጨረታ ማስታወቂያ ላይ መገለጽ ያለበት ስለመሆኑ • ሽያጩ ባልተገባ መንገድ ተከናውኗል ከተባለም ጨረታው በድጋሚ መካሄድ ያለበት ስለመሆኑ • በመያዣ የተያዘን ንብረት በሌላ ባለገንዘብ ጠያቂነት እንዲሸጥ ሊደረግ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3084, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 426, 423/2/ /ለ/, 445-447, 415	ሐምሌ 3/1999
304	27574	ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ እና የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማኅበር	በሽምግልና ገባኤ አማካኝነት የተሰጠ ውሣኔ በፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 215/1/, 319/2/	ጥቅምት 26/2000
305	28019	አቶ ብርሀኑ ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ	ፍርድን በአግባቡ ውጤት ለመስጠት የአፈፃፀም ችሎት የፍርዱን ትክክለኛ ቃል እና መንፈስ መከተል ያለበት ስለመሆኑ	ታህሳስ 1/2000
306	28154	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ 3ኛ ወገኖች መብት ያቋቋምን ስለሆነ አፈፃፀም ሊቀጥል አይገባም በሚል አቤቱታ ያቀረቡ እንደሆነ ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በአቤቱታው ላይ ያላቸውን ክርክር በቅድሚያ በመስማት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ	ሚያዝያ 14/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418/1/, 419	
307	29344	ወ/ሮ ዝማም ህሉፍ እና አቶ መረሣ ገ/ዮሐንስ	ውሣኔን የሚያስፈጽም ፍ/ቤት በውሣኔው መሰረት ከማስፈፀም ወጪ በአፈፃፀም ጊዜ ዋናውን ፍርድ ሊለውጥ የሚችልበት የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418	ግንቦት 5/2000
308	29653	አቶ ነጋ ደምሴ እና ሃምሳ አለቃ አዲሱ ደምስ	በዋናው ክርክር ገብቶ ተከራክሮ ውሣኔ ያሳገኘ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ጊዜ ውሣኔ እንዲፈፀምለት ጥያቄ የሚያቀርብበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418	መጋቢት 9/2000
309	33760	ሐጂ ታጁ ለገሠ እና የንንደር ከተማ የመሃል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር	የንግድ ድርጅት /መደብር/ ላይ ያለ መብት የድርጅቱ ንግድ የሚካሄድበትን ቤት የኪራይ መብት የሚያካትት ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 127	መጋቢት 18/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሐበር ችሎት ውሳኔዎች



ቅጽ-9

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ - 9

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት መልዕክት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጀ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው፤ በዚህ ረገድ የሚሠጡ የሰበር ውሣኔዎችን ፍርድ ቤቱ አሣትሞ ማሠራጨት እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሠረትም እስካሁን ድረስ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው ፍርዶች ከቅጽ 1 እስከ ቅጽ 7 ድረስ በማሣተም ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲሠራጨ ተደርገዋል፡፡

እነዚህ ፍርዶች የሀገራችን ፍርድ ቤቶች የሚሠጧቸው ፍርዶች ወጥነትና ተገማችነት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ የማይናቅ ሚና እየተጫወቱ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህን ቀጣይ ለማድረግ ቅጽ 8፣ 9 እና 10 እነሆ ለሕትመት በቅተዋል፡፡

አስገዳጅ የሰበር ውሣኔዎች ሥራ ላይ ከዋሉ አጭር ጊዜያቸው ነው፤ በአንፃራዊነት የብቃትም ሆነ የልምድ ውሱንነቶች በመኖራቸው እነዚህ እጥረቶች በሰበር ፍርዶቻችን ላይ አልፎ አልፎ መንፀባረቃቸው አልቀረም፡፡ በዚህ መስክ የረጅም ዘመናት ታሪክ ያሏቸው ሀገሮችም በተመሣሣይ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው እኛም አቅማችንን በማጠናከር የእነዚህን አገሮች ተሞክሮዎች በማገናዘብና የሀገራችን የሕግ ባለሙያዎች በፍርዶቻችን ላይ የሚሠጡትን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ግብዓት በማድረግ ኃላፊነታችንን በአግባቡ ለመወጣት ጥረታችን እንደሚቀጥል በዚህ አጋጣሚ እየገለጽሁ የሕግ ትምህርት ቤቶቻችን፣ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎችና ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ለጥረታችን እውን መሆን የማይተካ ድርሻ አላቸውና ከጎናችን እንዲቆሙ ጥሪየን አስተላልፋለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፕሬዝዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ2001 እና በ2002 ዓ.ም. የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሣኔዎች

ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ወንጀል				1
1	በወንጀል ጉዳይ የክስ ሂደት የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ ሊመዘን የሚገባ ስለመሆኑ የወ/ሕግ አንቀፅ 543 የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 63	35697	የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ከበደ ወርቅነህ	ጥቅምት 20/2001	2
2	• በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ የተሻሻሉና የተለወጡ ሁኔታዎች ከነባሩ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ጋር በቀጥታ ተጣምረው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባ ስለመሆኑ • በወ/ሕ/ አንቀጽ 543(3) የተከሰሰ ሰው የዋስ መብት የሚከለከል ስለመሆኑ የወ/ሕግ አንቀፅ 543 የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 63	35695	የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና አቶ ተመስገን አዲስ	ህዳር 11/2001	5
3	በተወሰነበት ፍርድ ላይ ይግባኝ እንደሚል ፍላጐቱን አሳውቆ እያለ ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት በኩል በተከሰተ መንተት የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ፍርደኛ የሚያቀርበው የማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ	39722	ግርማ ሃይሌ እና ዐቃቤ ህግ	ታህሣሥ 23/2001	7
4	የዳኝነትን ሥራ በማከናወን ወቅት የሚፈፀሙ ስህተቶች እና ጥፋቶች ሁሉ ዳኛን በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ሊያስጠይቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 214/74	33075	አቶ ብርቁ ገላነው እና የአማራ ብ/ክ/መ/የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ጥር 19/2001	9
5	አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉ የሚቋቋምበት ህጋዊ፣ ግዙፍዊና፣ ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2	38161	እነ ጀሚላ መሐመድ ሐጐስ እና የፌዴራል የመ/ደ/ዐ/ህግ	የካቲት 19/2001	11
6	በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ንብረት የሆነ ንግድ መደብር ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የንግድ መደብሩን በውስጡ ከያዘው ሸቀጦች በመለየት (በመነጠል) የሚሰጡት ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ	44594	የፌ/ሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ እና እነ ካፋ መሐመድ (አራት ሰዎች)	ሐምሌ 15/2001	13
7	በወንጀል ጉዳይ በእስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሰው የእስራት ቅጣቱን ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ወይም እንዲለቀቅ ሊደረግ የሚችለበት አግባብ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 82,192,194	46382	እነ ዳንኤል ገ/ዮሐንስ (አራት ሰዎች) እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ	ሐምሌ 28/2001	16
8	አንድ ተከሣሽ በተፈፀመ ወንጀል ላይ ተካፋይ ነበር ለማለት ተከሣሹ በሙሉ ፈቃዱና ዕውቀቱ በወንጀል ድርጊቱ ተሣታፊ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32, 33, 630, 25	44031	ወ/ሮ ፈለቀች ኃ/ገብርኤል እና የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ	ሐምሌ 30/2001	19
9	ከተሸከርካሪ ጋር በተያያዘ በድንገተኛ አደጋ ለሚከሰት የሰው ህይወት መጥፋት አሽከርካሪው በቸልተኝነት ወንጀል በማድረግ ሊጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 59(1), 543(2) እና (3)፣57 (2)	42703	ፋሲል ብርሃኑ እና ዓቃቤ ሕግ/የኦሮሚያ ክልላዊ ብሔራዊ መንግስት/	ሐምሌ 22/2001	22
	ንብረት				26
10	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ካርታ በማቅረብ ብቻ የሚረጋገጥ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195	36320	ወ/ሮ ዘውዴ ገ/ስላሴ እና ወ/ሮ ህይወት ባህታ	ጥቅምት 18/2001	27

https://t.me/ethiopianlegalbrief

11	የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተገናኘ የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው ንብረቱን ለመገንባት የወጣው ወጪ (BooK value) ብቻ ሣይሆን ንብረቱ በወቅቱ ለገበያ ቀርቦ ሊያወጣ የሚችለው ዋጋ (market value) ጭምር ስለመሆኑ	35003	አቶ አሸናፊ አብዱልቃድር እና እነ ወ/ሮ ሽቶ አብዱራሂም (አራት ሰዎች)	ህዳር 9/2001	29
12	አንድ ተከራካሪ ተገቢነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅርቧል ለማለት ለክርክር መንስኤ የሆነው ንብረት በእጅ አድርጎ መገኘትና በዚሁ ንብረት ላይ በእውነት ለማዘዝ እንዲችል የንብረቱ አያያዝ ያልተጭበረበረና በማናቸውም መንገድ ህገ-ወጥ በሆነ ሁኔታ ያልተገኘ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1)	36645	ረዳት ሳጂን አያኖ አንጀሎ እና እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጫሌቦ	ህዳር 11/2001	31
13	የጋራ ንብረትን ለመካፈል በሚደረግ ሽያጭ የጋራ ባለንብት የሆነ ወገን የቅድሚያ ግዥ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1261(2), 1386 — 1409	37297	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ እታለም ተስፋ	ታህሣሥ 2/2001	35
14	የጋራ ሀብት የሆነ ንብረት በመያዣ የተያዘ በመሆኑ የቅድሚያ መብት ያለ ቢሆንም የጋራ ባለሀብት የሆነ ወገን ንብረቱ በግልፅ ጨረታ ቀርቦ የሚያወጣውን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ግማሽ በመክፈል ማስቀረት የሚችል ስለመሆኑ	37298	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ዋቅጂራ	ታህሣስ 2/2001	38
15	የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታን ለማቅረብ አቤቱታ አቅራቢው ክርክር የቀረበበት ንብረት ባለሀብትነቱን ሳይሆን ባለይዞታነቱን ብቻ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ	38228	ሐጂ መሐመድ አወል ረጃ እና እነ አቶ ዲኖ በሺር (ሁለት ሰዎች)	ታህሣስ 7/2001	40
16	ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንፃ የሰራ ሰው የህንፃው ባለሀብት ሊሆን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179	36638	በላይ አበበ እና እነ አበራሽ ዋቅጅራ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 21/2001	42
17	በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያለው ባንክ በንብረቱ ላይ ሊኖረው የሚችለው የመብት አድማስ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3088/1/, 3110/ሐ/	36013	ወ/ሮ ዘምዘም ኑሩ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ታህሣሥ 21/2001	45
18	የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን የሁከት ተግባር ፈጽሟል ከሚባለው ሰው የተሻለ የይዞታ መብት ያለው መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149	39940	ወ/ሮ ነጂባ ነጋሽ እና ወ/ሮ ዚያዳ ያታሞ	ግንቦት 27/2001	49
19	ንብረትነታቸው የመንግስት የሆኑ ቤቶችን በተመለከተ የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ መንግስትን ወክሎ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2)	38169	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የወ/ሮ ንጋቷ ዘለቀ ወራሽ አቶ እሸቱ ቦጋለ	ግንቦት 12/2001	51
20	የይዞታ መብት ፍፁም ስላለመሆኑ እና በህግ አግባብ ይዞታው የተወሰደበት ሰው ተገቢ የሆነ ካሣ የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1), (2) አዋጅ ቁ. 7/1986 አንቀጽ 2(5), 21, 22, 24, 23 በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ- መንግሥት አንቀጽ 40 (8) አዋጅ ቁ. 455/1997	39539	የአዲስ አበባ አስተዳደር ግብርና ቢሮ እና እነ አቶ አበበ ዓባይ(ዘጠኝ ሰዎች)	ሐምሌ 30/2001	53
21	ከህግ የሚመነጭ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብትነትን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ	38666	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ባላንባራስ ተስፋዬ ገ/እየሱስ	ሐምሌ 9/2001	56
ከውል ውጭ ኃላፊነት					58
22	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 2143 ላይ የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የቀረበው የይርጋ ድንጋጌ የሞት ጉዳትን የሚያካትት ስለመሆኑ	34544	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ፋጤ ዓሊ	ጥቅምት 11/2001	59
23	ማንም ሰው ሥራው በሚያደርሰው ጉዳት ምክንያት ጥፋት ባይኖርበትም ከውል ውጭ ሃላፊነት ሊከተልበት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066- 2089(2069(1))	33201	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና ሼል ኢትዮጵያ	ጥቅምት 27/2001	61
24	ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው (ልጅ) ሃላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሰራ እንደሆነ ወላጆች በፍ/ብሔር በሃላፊነት ሊጠየቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2125, 2124	31721	ወ/ሮ ብዙነሽ ኃ/ዮሐንስ እና ወ/ሮ ስንታየሁ እሸቱ	ጥቅምት 25/2001	63

https://t.me/ethiopianlegalbrief

25	የጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባር ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው በህጉ መሠረት ሊሟሉ የሚገቡትን ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ እንጂ በማናቸውም ጥርጣሬ ምክንያት የግለሰብን ንብረት በመያዝ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.60/89 አንቀጽ 6, 58 አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 2(28) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26(1) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1193(1),(2), 2027, 2035, 2054, 2118	31171	አብልሃሚድ የሱፍ እና የምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት	ጥቅምት 27/2001	65
26	ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ ከሆነና ጉዳቱ በተጐጂው የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ካሣ ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ	35034	እነ ወ/ሮ ጥሩቀለም ደሴ እና እነ ወ/ሮ ጽጌ ከፍያለው	ጥቅምት 6/2001	68
27	ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት የሰው ህይወት የጠፋ እንደሆነና ለጉዳቱ መንስኤ (ምክንያት) የሆነው ወገን ሃላፊነት የተረጋገጠ ከሆነ በጠፋው የሰው ህይወት የተነሣ ጉዳት የደረሰበት ሰው የሞተው ሰው ምን ያህል ጥቅም ያስገኝለት እንደነበር ወይም ምን ያህል ተጨማሪ ዕድሜ ሊኖር እንደሚችል ያላስረዳ ቢሆንም እንኳን ፍ/ቤት የጉዳት ካሣውን በርትዕ ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102	34314	ወ/ሮ ግምጃ ጎበና እና እነ አቶ ወንድወሰን ወልዴ (ስድስት ሰዎች)	ህዳር 11/2001	71
28	የጉምሩክ ባለሥልጣን ያለአግባብ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ ለሚያቆየው ንብረት በባለንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ	31704	አቶ አማረ መኛ እና የድሬዳዋ ሊጋር ጉምሩክ	ጥር 29/2001	74
29	በጥቅም ላይ ባልተመሰረተ ግንኙነት በመኪና ተጣፍሮ የሚሄድ ተጣፋሪ ላይ ለሚደርስ አደጋ የመኪናው ባለቤት ካሣ የመክፈል ሃላፊነት የማይኖርበት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089	38457	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ተመኘሁ እንደሻው	ሰኔ 2/2001	77
	የዳኝነት ስልጣን				79
30	የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ውስጥ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1) (ሸ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996(1)	35657	እነ ወ/ሮ አመቤት መክብብ እና አቶ በድሉ መክብብ	ጥቅምት 6/2001	80
31	የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ለክርክር መነሻ የሆነው ክስ በገንዘብ ሊተመን የማይችል የመብት ጥሰትን የተመለከተ በሆነ ጊዜ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 50(1), 39	36338	ገ/መስቀል ደመወዝ እና ወ/ሮ አፀደ መኮንን	ጥቅምት 25/2001	83
32	የቅኔ መምህርነት ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ሥራ በመሆኑ በሥራ ክርክር ችሎቶች ሊስተናገድ የሚችል ስላለመሆኑ	34440	መንበረፓትሪያክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና መጋቢ ሚስጢር መዝገቡ በላይነህ	ጥቅምት 6/2001	85
33	የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የቤት ባለቤትነት ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ረ)	33841	አቶ አስጨናቂ ረጋሣ እና እነ አቶ ገዛኸኝ ነጋሽ (ስድስት ሰዎች)	ጥቅምት 6/2001	87
34	በመካላከያ ሰራዊት ውስጥ በወታደርነት በማገልገል ላይ የሚገኙ የሠራዊት አባላት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የወንጀል አቤቱታዎችን ለማስተናገድ ወታደራዊ ፍ/ቤቶች ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.27/88, አዋጅ ቁ. 343/94 አንቀፅ 2(9),26(1)	33368	ሻምበል አሰፋ በላይ ዘገየ እና ወታደራዊ አቃቤ ህግ	ህዳር 9/2001	89
35	የአ.አ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች በከተማው አስተዳድር ሥር ካሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን ብቻ ለማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ	34788	የሚች አቶ ሰለሞን ሳሙኤል ወራሾች እና ማርታ ሰለሞን (2 ሰዎች)	ህዳር 2/2001	92
36	በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በፍርድ ቤት ቀርቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ስላለመሆኑ	31906	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የአቶ መርስኤ መንበሩ ወራሾች	ህዳር 4/2001	94
37	በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ከተወረሱና በቀላጤ ከተያዙ ቤቶች ውጭ ያሉ ቤቶችን አስመልክቶ የሚነሣ የቤት ክርክር ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች ማየት የሚችሉ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ.47/67 አዋጅ ቁ. 110/87	37281	አቶ አበበ ዓሊ እና እነ የ08 ቀበሌ ገ/ማህበር (ሦስት ሰዎች)	ታህሣሥ 16/2001	98

https://t.me/ethiopianlegalbrief

38	በውጭ አገር የሚገኝ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክርን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማስተናገድ ስለመቻሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 37, አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ(4)	37339	ወ/ሮ ንግስት ኃይሌ እና አቶ ለገሠ ዓለሙ	ጥር 28/2001	101
39	ወደ ቀድሞ የሥራ መደብ እንድመለስና ለመደቡም የተሰጠው ልዩ ጭማሪ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ የወል ሥራ ክርክር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ142(1) (ሀ)	37016	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ተስፋዬ ማሞ	የካቲት 3/2001	104
40	ከጉምሩክ ፖሊስ አባላት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን ለመደበኛ የሥራ ክርክር ችሎቶች ያልተሰጠ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 368/96 , አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 8(2) , መመሪያ ቁ.4/1996	39085	የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ር አስረሳች ወርቅነህ (ሰማንያ ሰባት የጉምሩክ ፓሊሶች)	የካቲት 3/2001	106
41	ቀደም ብሎ የተሰጠን የፍች ውሣኔ ወደጉን በመተው አዲስ የተደረገን ጋብቻ ህገ ወጥ ነው ማለት የማይቻል ስለመሆኑ	38745	እነ ወ/ሮ ሣሊያ ኢብራሂም (ሁለት ሰዎች) እና ሐጂ ሰማን ኢሣ	መጋቢት 10/2001	108
42	የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የይዞታ ክርክርን ማስተናገድ የማይችሉ ስለመሆናቸው	36677	ወ/ሮ ሻምሺ የኑስ እና ወ/ሮ ኑሪያ ማሚ	ሚያዝያ 30/2001	111
43	የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርብ ይግባኝን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ስለመሆኑ	37866	ሙሉጌታ አባይ እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን	ግንቦት19/2001	113
44	የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶችም ሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳዩችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን በህግ ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ	41608	እነ ሙላቱ አንበርብር እና ወ/ት ታመነች ዮሴፍ መና	ሐምሌ 22/2001	115
ባንክና ኢንሹራንስ					117
45	ዕቃዎችን ለሚያንቀሳቅስ የጭነት መኪና የተገባ የመድን ዋስትና ጋር በተያያዘ በመኪናው ላይ ተሣፍሮ ሲሄድ ለነበረና አደጋ ለደረሰበት ሰው መድን ሰጪው የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ	42139	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ብያን ኡመር	ሰኔ 30/2001	118
46	ኢንሹራንስ ሰጪ በውሉ መሠረት ከፈፀመ በኋላ በተሸሸገ ወይም በሀሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ አጋጥሚል በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባለው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የንግድ ህግ 674(1),(2)	42309	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሰኔ 30/2001	120
ውክልና					122
47	አደራ ተቀባይ የሆነ ወገን በአደራ የተቀበለውን ዕቃ መመለስ ያለበት ለአደራ ሰጪው ወይም ይቀበልልኝ ብሎ ላመለከተው ሰው ስለመሆኑ	38289	ወ/ሮ ነጂሃ ድዋሌ ዋይስ እና አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ	ሰኔ 23/2001	123
48	መንግስታዊ የሆነ ተቋም በሚከስስበትም ሆነ በሚከስበት ክርክር የሚቀርብ ሰነድ የኘሮቶኮል ቁጥር እንዲሁም ስለአቤቱታው ጽሁፍ ትክክለኛነት በሚመለከተው ኃላፊና በወኪሉ መፈረም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 80, 92, 93 እና 92(3)	43875	በወላይታ ዞን የቦዲቲ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና አቶ ወንድሙ ኃይሌ	ሐምሌ 16/2001	125
49	የዕቃ አስተላላፊ አካል እንደ አንኘር ሆኖ የሚቆጠረው ከወደብ የተረከበውን ዕቃ በራሱ ማንጓጓር ካንጓዘ ብቻ ስለመሆኑ ደንብ ቁ.37/90 አንቀጽ 2(1), 3(6),(7) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2251 የንግድ ህግ .ቁ. 683(3)	37799	የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሐምሌ 29/2001	127
50	በወኪል በኩል የሚፈፀም የመኪና ጭነት ውል በአስጫኙ እና በመኪናው ባለቤት መካከል እንደተደረገ የሚቆጠር ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 566 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2251	34621	ኒያላ ኢንሽራንስ አ/ማ እና አቶ ሐጎስ ገ/መድህን	ሐምሌ 30/2001	129
የንግድ ሕግ					132
51	የንግድ ድርጅት በህግ አግባብ ለባለመብቶች ሊከፋፈል የሚችልበት ሁኔታ የንግድ ህግ ቁጥር 127	33954	ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ እና አቶ ዘውዱ ቢረዳ	ጥቅምት 20/2001	133

https://t.me/ethiopianlegalbrief

52	የእሽሙር ማህበር መፍረስ በንብረት ክፍፍል ረገድ የሚያስከትለው ውጤት	33470	ወ/ሮ እጅጋየሁ ታደሰ እና መገርሳ ጉደታ	ህዳር 2/2001	136
53	የጋራ ሀብት የሆነ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደሌላ ማናቸውም ንብረት ባለበት ሁኔታ በዓይነት ሊከፋፈል ወይም ደግሞ በሃራጅ ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 542	34945	ወ/ሮ መስታወት በላቸው እና አቶ ለገሠ ሣህሉ	ህዳር 2/2001	138
54	የንግድ መደብርን የተከራየ ወገን ይህንኑ የንግድ መደብር ለሌላ ሶስተኛ ወገን ያለአከራዩ ፈቃድ ማከራየት ስለመቻሉ የንግድ ህግ ቁጥር 145	31264	ወ/ሮ እመቤት መኮንን እና ወረዳ 20 ቀበሌ 29 አስ/ጽ/ቤት	ጥር 5/2001	140
55	በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161 የንግድ ሕግ ቁ. 124	34586	አቶ ያለው ድልነሳው እና እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ (አራት ሰዎች)	ጥር 28/2001	143
56	ቼክን አስመልክቶ ክስ በቀረበ ጊዜ የተከሰሰው ወገን የቀረበበትን ክስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት የሚያቀርበው ምክንያት ፈቃድ ሊያሰጥ የሚችል መሆን ያለመሆኑን አግባብነት ካላቸው ህግጋት አኳያ መታየት ያለበት ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 717 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 284, 285	43315	ብራንድ ኒው የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል እና አቶ መስፍን ታደሰ	ግንቦት 18/2001	146
አእምሯዊ ንብረት					148
57	አንድን የሥነ-ጥበብ(ኪነ-ጥበብ) ሥራ ያለባለቤቱ ፈቃድ አርጅናሉ ወይም ቅጅው ለህዝብ እንዲታይ ማድረግ የኮፒ ራይት ህግ ጥሰት የሚያስከትል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1791, 1771(1), 1790, 2090-2123 አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀፅ 7	42253	መምህር ሙሉ ኃይለሥላሴ እና ዘመናዊ ማተሚያ ቤት	ሐምሌ 8/2001	149
ልዩ ልዩ					152
58	የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዋቅር ባልተዘረጋባቸው ክልሎች የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ወክለው/ተክተው/ ክርክሮችን ማስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 139/1//ለ/,154/1/,153,140	21214	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ለማ ኩማ (ሦስት ሰዎች)	ህዳር 4/2001	153
59	• የጡረታ መዋጮ በመዘግየቱ ምክንያት በአዋጅ ቁ. 345/95 መሠረት ተጨማሪ ክፍያ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ እና አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 7(3), 52(1),56 • የጡረታ መዋጮ በ2 ዓመት ውስጥ እንደተከፈለ የህግ ግምት ሊወሰድበት የሚችል የክፍያ ዓይነት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ሠ)	35391	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና አንበሣ ጫማ አ/ማ	ህዳር 25/2001	155
60	የጥብቅና ፈቃድን ለማግኘት በህጉ የተቀመጡት መስፈርቶች ራሣቸውን ችለው መታየት ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 8(1)	37375	አቶ ሽምሱ ከድር አህመድ እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር	ህዳር 11/2001	158
61	በክባድ የወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ እና በራሣቸው ወጪ ጠበቃ ለማቆም ያልቻሉ ግለሰቦች በተመለከተ ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት የግለሰቦችን በጠበቃ የመወከል ህገ-መንግሥታዊ መብት መከበሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 13 (1)	37050	ሻምበል ሁሴን አሊ እና የሱማሌ ክልል ዐ/ሕግ	ታህሣሥ 30/2001	160
62	ክዘር የወረደ ርስት ነው በሚል የመሬት ባለቤት ለመሆን የሚቀርብ ክስ ህገ-መንግስታዊ ያልሆነና ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	38237	አቶ በርገና ሽፈራው እና እነ አቶ አብራሃም ሽፈራው(አራት ሰዎች)	ታህሣሥ 21/2001	163
63	በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍ/ብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት ለመወሰድ ብቃትና አግባብነት ያለው ስለመሆኑ	37184	የሰሜን ቀጠና ጉምሩክ እና እነ ቄስ ብርሃን ንዋይ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 9/2001	166

https://t.me/ethiopianlegalbrief

64	የመንግሥት መሥሪያ ቤት በጨረታ አማካኝነት የሸያጭ ውል አካሄዷል ተብሎ ሊገደድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1688(2), 3167(1), 1688(2), 3168	37163	የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን እና ህያብ ገ/መድህን ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ	ታህሣሥ 23/2001	170
65	አማራጭ የማጭት መፍቻ ዘዴዎች ምንነት፣ የሚደረጉበት መንገድና ለአፈፃፀም የሚቀርቡበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3318, 3324, 3325, 3346, 1731 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 315, 319, 350, 357	38794	አቶ መኩሚል መሐመድ እና አቶ ሚፍታህ ከድር	መጋቢት 24/2001	173
66	አስተዳደራዊ የሆኑ መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ ካርታ እንዲሰጥ የሚወሰን ውሣኔ ተገቢ ስላለመሆኑ	39529	ቦሌ ክ/ከተማ የመሬትና ልማት አስተዳደር እና እነ ወ/ሮ ግምጃ በዳኔ (ስድስት ሰዎች)	ግንቦት 11/2001	176
67	ግምቱ ከብር 10,000 ብር በላይ ለሆነ የአፈፃፀም ክስ ሊከፈል የሚገባው ዳኝነት 25 ብር ብቻ ስለመሆኑ የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ. 177/1945 አንቀጽ 2(ሠ)	40752	እነ ወ/ሮ ኤክራም መሃመድ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘኪ መሐመድ	ሐምሌ 28/2001	179
68	ከፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ሠራተኞች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር ምንም እንኳን ሥራው የሚካሄደው በክልሎች ቢሆንም ወይም ሠራተኞቹ የክልል ነዋሪዎች ቢሆኑም ገቢ የሚደረገው ለፌዴራሉ መንግስት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 96(3) አዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ5(2)(ሐ) ደንብ ቁ. 109/96	40133	የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን እና በሶማሌ ብ/ክ/መ የፊደልቱ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ገቢዎች ጽ/ቤት	ሐምሌ 2/2001	181
አሰሪና ሰራተኛ					184
69	የግንባታ ዕቃዎች እጥረት አጋጥሟል በሚል የሚደረግ የሥራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 26,28,30	41385	ጊጋ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና እነ ተረፈ ዘርጋው (ስድስት ሰዎች)	ጥቅምት 3/2002	185
70	የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት አድርጐ ከሚቀርብ ክርክር ጋር በተገናኘ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሣይሰጥ ከተጠየቁት ዳኝነት መካከል ወደ ሥራ የመመለስ ጉዳይ ላይ ብቻ ውሣኔ ከተሠጠና ሠራተኛው ወደ ሥራ መመለስ ሳይፈልግ ቢቀር ቀድሞ ዳኝነት በጠየቀባቸው ነገር ግን ውሣኔ ባላረፈባቸው ነጥቦች ላይ ዳኝነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3)	42361	ወ/ት ትዕግስት ንጉሴ እና ኤስ.ኦ.ኤስ ኢንፋንት ኢትዮጵያ	ጥቅምት 5/2002	187
71	በትርፍ ሰዓት በሌላ መሥሪያ ቤት ስርተሃል በሚል ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ 377/96 አንቀፅ 27	42818	አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ እና ወ/ር ሙለታ ገዳ	ጥቅምት 10/2002	189
72	አሰሪ በግልፅ ባልፈቀደበት ሁኔታ በሁለት ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ መስራት ሠራተኛውን የማታለል ተግባር እንደፈፀመ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ)	41767	የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና አቶ አድማስ ደምሳቸው	ህዳር 8/2002	190
73	አሰሪ የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት እና መለኪያ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ በሠራተኞቹ መካከል በክፍያ ረገድ ልዩነት ማድረግ ስለመቻሉ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 14(1)(ረ) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት 42(1)(መ)	42923	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ነጃት አባስ	ህዳር 22/2002	192
74	ሥራውን በገዛ ፈቃዱ የሚለቅ ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት የሚችለው ቢያንስ የ5 ዓመት አገልግሎት ያለው እንደሆነ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(ሸ)	44410	ወ/ሮ ላይላ ረዲ እና ድሬ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግል ማህበር	ኅዳር 01/2002	195
75	በአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ “በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት” ወይም “በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ” በሚል የተቀመጠው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 95/2/,97,96	47807	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ ፈንታው (ሁለት ሰዎች)	ታህሳስ 06/2002	198

https://t.me/ethiopianlegalbrief

76	አሰሪ ሠራተኞቹን በማስተዳደር ረገድ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች በራሱ አነሣሽነት ሊያርም የሚችል ስለመሆኑ	45889	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን እና ሳሙኤል ቂስቦ	ታህሣሥ 20/2002	201
77	በክርስትና ሃይማኖት ተቋም ውስጥ በዲያቆንነት ሥራ ከማገልገል ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የሥራ ክርክር ጉዳዮች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ሊስተናገዱ የማይችሉ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	47806	የሆሀተሰማይ ቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና ዲያቆን አያሌው አዲሱ	ታህሣሥ 20/2002	203
78	በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኟቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት መብት የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10	47469	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ስዩም ገብረዋዲቅ(ሃያ ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 15/2002	205
79	በሥራ ክርክር ጉዳይ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853 ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 164(3) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853,1852	47784	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አለምፀሐይ አያና	ታህሣሥ 20/2002	208
80	በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት የሥራ ግንኙነት በአንቀፅ 30 መሠረት ሲቋረጥ አሰሪ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 30, 28(2)	49057	አስመላሽ እና ልጆቹ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ዮሐንስ አሸበል	ጥር 5/2002	211
81	የጡረታ መብት ያለው እና መደበኛ የጡረታ ዕድሜው ደርሶ የተሰናበት ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/2(ሰ) እና (ሸ)	46276	ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት እናእነ ኃይሌ ይማም (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 11/2002	213
82	• አንድ ድርጅት በመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኞች የስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው የሚገባ ስለመሆኑ • ድርጅት ለዘለቄታው እንዲቆም የሚያደርግ ሁኔታ ሲከሰት ማስጠንቀቂያ ለሠራተኞች መሰጠት ያለበት ስለመሆኑ	42985	ውድ መጣስ ኑሮ አስመጪና ላኪ ድርጅት እና እነ አቶ ሁነኛው ሰጠ (አስራ አንድ ሰዎች)	የካቲት 25/2002	215
83	የጠብ አጫሪነት ኃይለ ቃልና ዛቻ አዘል ንግግር በሥራ ቦታ ላይ ማድረግ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ረ)	49958	ግዬን ትራቭልና ቱርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ዳንኤል አስፋው	የካቲት 12/2002	217
84	በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ለሠራተኛው ጥገኞች ስለሚከፈል ካሣ፣ ካሣው የሚከፈልበትና የሚሰላበት ሁኔታ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 110	40529	የህፃን ዮናታን ነጋ ተሻገር ጠ/ጥጋቡ ጌጤ እና አቶ ለገሠ አበራ	የካቲት 10/2002	219
85	በአሰሪና ሰራተኛ በኩል በአጠቃላይ ለፕሮጀክት ሥራ በሚል የተደረገ የሥራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አንቀጽ 10(1)(ሀ) መሰረት የተደረገ እንደሆነ ተደርጉ የሚወሰድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሀ)	48648	የግልቁ የትምህርትና የተቀናጀ የልማት ማህበር እናእነ አቶ ታጠቅ ደጀኔ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 24/2002	222
86	ሠራተኞችን ለማበረታታት በሚል የሚደረግ የደመወዝ (ጥቅማጥቅም) ጭማሪን መሠረት በማድረግ ጭማሪውን የሚፈቅደው መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ የሚጠይቀው መብት የሌለ ስለመሆኑ	47825	የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ) እና እነ አቶ ዘርዓየሁ ሰሜ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	224
87	አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ ከሚፈፅመው ጥፋት ጋር በተያያዘ ከሥራ ታግዶ ሊቆይ ስለሚችልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	47535	የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት እና አቶ እንግው ላቀው	መጋቢት 20/2002	226
88	• የአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አሰሪና ሰራተኛ ስምምነት ሊያደርጉባቸው የሚችሉበት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ጥፋትንና ጥቅምን በተመለከተ የተለያየ አቋም የያዘ ስለመሆኑ • አሰሪና ሠራተኛ በህብረት ስምምነታቸው ውስጥ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በሚል የተስማሙበት ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 134(2), 27(1)(ሸ)	49750	በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/01 የመዝናኛ ክበብ እና አቶ ማስረሻ ሁሴን	መጋቢት 30/2002	228

https://t.me/ethiopianlegalbrief

89	አሠሪ የሠራተኛውን የሥራ ውል ያቋረጠበትን ምክንያት በፅሁፍ አለመግለፁ ብቻ ስንብቱ ህገ- ወጥ ነው ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2)	49797	አልሀበሽ ሹገር ሚልስ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ተገኔ ገ/ሃዋሪያት	መጋቢት 30/2002	230
90	በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ውስጥ "እንደ ጥፋቱ ክብደት በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር መፈፀም" በሚል የቀረበው አባባል (አነጋገር) ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ)	50009	የአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል እና አቶ ዮናስ ጥላሁን	መጋቢት 6/2002	232
91	አሠሪና ሠራተኛ የሥራ ውል መቋረጥ ጋር በተያያዘ በሥራ ውሉ ላይ የሚያመለክቱት ሁኔታ የአሰሪና ሠራተኛ ህጉን እስካልተፃረረ ድረስ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ	50205	የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና አቶ ምናለ በሪሁን	መጋቢት 20/2002	234
92	የሥራ ውል በተቋረጠ ጊዜ አሰሪው ከሠራተኛው በህግ አግባብ የሚፈልገው/ የሚጠይቀው ዕዳ ያለ እንደሆነ ለሠራተኛው የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት ከመስጠት ባሻገር የሥራ መልቀቂያ (ክሊራንስ) ለመስጠት የማይገደድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀፅ 78 (1),87	48476	የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና አቶ ደረጀ መኮንን	ሚያዝያ 12/2002	236
93	ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የሚደርስበትን ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ወይም ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት በማለት ለመለየት የሚቻልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 101 (2)	49273	አቶ ደረጀ ውለታው እና ዋሊያ ሌዘርና ሌዘር ኘሮዳክትስ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሚያዝያ 27/2002	238
94	• አንድ ሰው በአፈፃፀም ሊገደድ የሚችለው በህግ አግባብ የተፈረደ ፍርድ ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ • በግልፅ ፍርድ ያላረፈበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378	50148	እነ አቶ ወርቁ ደረጀ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ አባርኪሮ ሁመድ	ሚያዝያ 4/2002	240
95	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ከሠራተኛው ጋር ያለው ግንኙነት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቢመለስ ችግር ውስጥ እንደሚወድቅ በአሠሪው ስለተገለፀ ብቻ ሠራተኛው ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት በሚል የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/	49931	የጎሽና እርግብ መለስተኛና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር እና አቶ ተሰማ ኃይሉ	ሚያዝያ 21/2002	242
96	የድርጅት መዋቅራዊ ለውጥ ያደረገ ተቋም በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መሠረት ሠራተኞቹን አዲስ በሚያወጣው የሥራ መደብ ላይ ተመርኩዞ የሥራ ምደባ ሊያከናውን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28	50838	ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ኘሮጀክት እና እነ አቶ አማረ አበራ (ሰባት ሰዎች)	ሚያዝያ 12/2002	244
97	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪ ሠራተኛው የፈፀመውን ድርጊት መሠረት አድርጐ ለማሰናበት የሚችለው የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት የሆነው ነገር መከሰቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ ሰላሳ ቀናት ውስጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3)	45746	ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ በለጠ ጫላ	ሚያዝያ 6/2002	246
98	ሠራተኛ የተረከባቸውን ንብረቶች አላስረከበም ወይም አጉድሏል በሚል የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚጠይቃቸውን ተገቢ ክፍያዎች ሊጠይቅ አይችልም በሚል በአሠሪው የሚቀርብ ክርክር ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 36,37,38	44405	ፊንፊኔ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ደጃ ደምሴ ጎበና	ግንቦት 19/2002	248
99	ወደ ሥራ እንዲመለስ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነና በአሰሪው ችግርም ሆነ በሠራተኛው ፍላጐት በፍርዱ መሠረት ወደ ሥራ ለመመለስ ሠራተኛው ያልፈለገ ከሆነ ሠራተኛው የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ በምትክነት በሰጠው መብት መሠረት በመመለሱ ፈንታ ካሣ እንዲከፈለው አፈፃፀሙን ለያዘው ችሎት ጥያቄውን ባቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3)	53064	አቶ ደሬሳ ኩቱ እና የአምቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን	ግንቦት 17/2002	250
100	በድርጅት ውስጥ የተከሰተ ተጨባጭ ችግርን ለመቅረፍና የድርጅቱን ትርፋማነት ለማስቀጠል በሚል በተመሳሳይ ሙያና ደረጃ ላይ ካሉ ሠራተኞች መካከል ተለይቼ ወደ ሌላ የሥራ መደብ ስለተዛወርኩኝ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ	50182	የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት እና አቶ አበበ ተፈራ ይልማ	ግንቦት 13/2002	252

https://t.me/ethiopianlegalbrief

101	የሥራ ውል የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ ነው በሚል ክርክር በቀረበ ጊዜ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም የሚኖር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 9	44218	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ታጁ አባጋሮ (ሃያ አንድ ሰዎች)	ግንቦት 13/2002	254
102	አንድ አሰሪ በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበትን ሰራተኛ ወደ ውጭ አገር ልኮ ስለሚያሳክምበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 124,105	46363	ሚሊኒ ኮንስትሩቶሪ ኤስ.ፒ.ኤ እና አቶ ትግሉ ፍሬህይወት	ግንቦት19/2002	257
103	• ከአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጋር በተገናኘ ሁለቱ ወገኖች አዋጅ ቁ. 377/96 "ን" ወደ ጉን በማድረግ በሌላ አገር ህግ ለመዳኘት ስምምነት ያደረጉ በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ህግ ጥያቄን ያስነሳል በሚል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑ • አዋጅ ቁ. 377/96 የውጭ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ የበጎ አድራጎት ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/3/ /ለ/	50923	ፋውንዴሽን አፍሪካ እና አቶ አለሙ ታደሰ	ግንቦት 19/2002	260
104	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚነሣው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚሰላው የሥራ ቀናትን ብቻ በማስላት ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 163(2)	51912	የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና ወ/ሮ ሶፋኒት አጥናፉ	ሰኔ 7/2002	263
105	• በአሰሪ የተፈፀመው የሥራ ስንብት ህጉ ውጥ ቢሆንም ከሥራ ግንኙነቱ ፀባይ የተነሣ ከፍተኛ ችግር የሚፈጠር በሆነ ጊዜ ሠራተኛውን ወደ ሥራ ከመመለስ ይልቅ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ • የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀፅ 43(3) በአንድ በኩል የሠራተኛን የሥራ ዋስትና በሌላ በኩል ደግሞ የኢንዱስትሪን ሰላም በማመዛዘን ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ	55189	አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል እና አቶ ዘላለም መንግስቱ	ሰኔ 30/2002	266
106	በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ‹‹... ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት...›› በሚል የተመለከተው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3)	53358	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ ጥላሁን ኩማ	ሰኔ 18/2002	268
107	አንድ የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9,10	43160	እነ እንደገና ተሾመ (ሁለት ሰዎች) እና ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ነቀምቴ ቅርንጫፍ	ሰኔ 22/2002	270
108	በማናቸውም ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኛው ያልወሰደው የዓመት እረፍት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 77(5) ,24(2)	52459	እነ ወ/ሮ ሙሉ ታደሰ እና አለሙ መራ ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ብረታ ብረት ሥራ ድርጅት	ሐምሌ 16/2002	272
109	በክረምት ወቅት የማስተማር ሥራ እንዲሠራ የሚያዝ ግልፅ ደንብ ወይም መመሪያ የሌለ እንደሆነ ወይም አስተማሪው በክረምት ወራት ለማስተማር የገባው የውል ግዴታ (ስምምነት) በሌለ ጊዜ በክረምት ወቅት ሥራን ለመስራት ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ከሥራ ሊሰናበት የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 13(1)	45170	የቅድስት ማሪያም አፀደ ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እና መ/ት ሲሳይ ሙሉጌታ	ሐምሌ 8/2002	274
የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት					276
110	በክርክር የግድ ተካፋይ ሊሆኑ የሚገባቸው ወገኖች እና የፍ/ቤት ሚና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 39,(1),40(2)	43424	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና እነ አቶ መስፍን /ስምንት ሰዎች/	ጥቅምት 10/2002	277
111	የቃል ክርክር እንዲሰማ በተቀጠረበት ዕለት ግራ ቀኝ የሆኑ ወገኖች ያልቀረቡ እንደሆነ መዝገቡ መዘጋት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 69(2)	43410	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል	ህዳር 30/2002	280
112	አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ይህንን ፍሬ ነገር በማንኛውም የማስረጃ ዓይነት ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ	47551	ንግድ ማተሚያ ድርጅት እና አቶ ካሱ ሙላት	ታህሣሥ 6/2002	282

https://t.me/ethiopianlegalbrief

113	ጣልቃ በመግባት በክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጠይቆ የተፈቀደለትና የጣልቃ ገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባው ይህን ባለመፈፀሙ መብቱ ከተሰረዘበት በኋላ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41,358	40229	ወ/ሮ ኸይሮ መሐመድ እና እነ ወ/ሮ መዲና በያን (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 15/2002	284
114	በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ተከራካሪ ወገን ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አቤቱታው ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 78,69,72	43731	ሲ.ጂ.ሲ.አቪርሲስ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ሊሚትድ እና ሰለሞን እንዳለ	ታህሣሥ 8/2002	286
115	• በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 መሠረት መዝገብ ሊዘጋ የሚችልበት አግባብ • ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ዳኝነት የሚጠይቁበትን ፍሬ ነገር በአግባቡ ከገለፁ ትክክለኛውን የህግ ድንጋጌ አለመጥቀሳቸው መብታቸውን የሚያስቀር ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280,69(2), 70(መ), 71(2)	39581	አቶ ውብሸት ካሣዬ እና የኢትዮጵያ ማዕድን ሃብት ኮርፖሬሽን	ጥር 25/2002	288
116	ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሷቸውን የሰው ማስረጃዎች ሊሰውጡ (ሊቀይሩ) የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223/2/,234	45984	ኘሮፌሰር ረዳ ተ/ኃይማኖት እና አቶ ልመንህ ተፈራ	ጥር 26/2002	290
117	የክርክር ጭብጥ የሚመሰረተው ከሳሽ የሚያቀርበውን ክስና ማስረጃ በተከሳሽ የቀረበውን የመከላከያ መልስና ማስረጃ እንዲሁም ፍ/ቤቱ የቃል ምርመራ ሲያደርግ የሚያገኘውን ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241,248	47252	ወ/ሮ ፑሽፓላት ጆሴፍ እና አቶ ሠይፈ ጎሣዬ	የካቲት 26/2002	292
118	ዳኝነት እንደገና እንዲታይ (Review of judgement) በሚል የሚቀርብ አቤቱታ አስቀድሞ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የተባለበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ ውድቅ ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)(ሀ),(ለ)	43821	ወ/ሮ ትርሃስ ፍስሀዬ እና ወ/ሮ ዘነበች በሪሁን	ጥር 5/2002	295
119	ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ላይ በተሰጠ ትእዛዝ/ብይን ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6(3)(4)	42871	የቀድሞ ወረዳ 07 ቀበሌ 32 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ጆሮ ዋቅጅራ	ጥር 12/2002	301
120	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 421 መሠረት ክስ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418,421	37214	አቶ ተስፋዬ አለሙ እና እነ ሐጂ ይማም መብይን(ሦስት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	304
121	በፍ/ብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ	44634	አቶ ታዬ ሆሳዕና እና ወ/ሮ መሠረት ወልደየስ	የካቲት 22/2002	306
122	ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው ክስ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ በቂ በሆነ ማስረጃ በተገነዘቡ ጊዜ ክሱን ሊዘጉት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280	45371	የገነተ-ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማህበር በኩር ሰንበቱ እና እነ አቶ ማሞ ተሠማ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 8/2002	308
123	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216 መሠረት በድጋሚ ክስ እንዳይቀርብ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216(3)	36776	መብራቱ፣ተ/ማሪያም፣ገ/ማሪያም የሽርክና ማህበር እና አቶ መብራቱ ዓንዳይ	መጋቢት 7/2002	310
124	ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር በዋናው ጉዳይ ላይ የራሱን ውሣኔ ካሣለፈና የበላይ የሆነ ፍ/ቤት ደግሞ የይግባኝ ውሳኔውን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በደፈናው በማፅናት የሚሰጠው ውሣኔ የተከራካሪ ወገን የይግባኝ መብት የሚያጣብብና የሥነ-ሥርዓት ህግ ድንብን የሚጥስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341,342,343	44545	ክፍሉ መሓሪ እና በላይ ከመላ	መጋቢት 7/2002	312
125	የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘ ባለገንዘብ ባንክ መብቱ በይርጋ እስካልታገደ ድረስ የያዘውን ንብረት በጨረታ ለመሸጥ የሚገደድበት ተለይቶ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 97/90 አዋጅ ቁ. 216/92 አንቀፅ 2 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394 - 449	44883	አቶ ፈንታ ምህረቱ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	መጋቢት 8/2002	314

https://t.me/ethiopianlegalbrief

126	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ	39799	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ ገነት ስዩም	መጋቢት 21/2002	317
127	• በተከራካሪ ወገኖች የሚቆጠሩ ማስረጃዎች ሳይሰሙ የሚቀሩት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የሌላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ • ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች የቆጠሩትን ማስረጃ ሳይሰሙ ወደ ጉን በመተው አቤቱታቸውን በበቂ ማስረጃ አላስረዱም በሚል የሚደርሱበት መደምደሚያ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ	43845	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ጌታይዳ ኃ/የተ/የግል ማህበር	መጋቢት 20/2002	320
128	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208 መሠረት በሥር ፍ/ቤት የተደረገ አርማትን መነሻ በማድረግ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ለመለወጥ የሚያስችለው የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 208,209,320,(1) ,348(1)	44931	ወ/ሮ ሰዓዳ ኢድሪስ እና አቶ ረሺድ ቡባ	መጋቢት 20/2002	323
129	የፍ/ቤትን ክብርንና የዳኝነት ሥርዓቱን መልካም አመራር ለማስጠበቅ ሲባል የማንኛውም ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ በችሎት ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 480	48237	ወ/ሮ ሰኢዳ ሁሴን ይመር ተጠሪ፡የለም	መጋቢት 6/2002	325
130	ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ ተከሳሽ የሆነን ወገን በሌለበት ባለዕዳ የሚያደርግ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ተከሳሹ በአግባቡ ስለመጠራቱ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 97, 95(3)	50022	5 ብራዘርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ዓብደላ ኢብሮ ዩሴፍ	መጋቢት 29/2002	327
131	የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በውሳኔው ወቅት ንብረቱን በእጁ አድርጐ የሚገኘው ወገን የንብረቱን ስመ ሐብት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን አዛውሮ ሲገኝ ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት ስለሚገባው አካሔድ	45038	እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጓዱ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ አስረስ አህመድ	መጋቢት 23/2002	329
132	• ሐሰተኛ ቃል ተሰጥቷል በሚል ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 መሠረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሊሰጥ የሚችልበት አግባብ • በአንድ የወንጀል ድርጊት ነፃ የተባለ ሰው እንደገና ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጐ የሚቀጣበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 የወንጀል ህግ ቁ. 452(1)	43005	እነ አቶ አውግቸው እርገጤ (ሦስት ሰዎች) ተጠሪ፡የለም	ሚያዝያ 19/2002	331
133	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 መሠረት ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ለሰጠ ፍ/ቤት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6	45839	ወ/ሮ ይርጋለም ከበደ እና እነ ወ/ሮ ፅጌ ሚካኤል (አምስት ሰዎች)	ሚያዝያ 5/2002	333
134	በፍ/ብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 256, 345, 327	39853	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር (ሁለት ሰዎች)	ሚያዝያ 21/2002	335
135	አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ እንደሆነ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(3), አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10	41526	ትራንስ አፍሪካ ትራንስፖርት አ.ማ እና ሙሉ ኤሌክትሮኒክስ ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ግንቦት 2/2002	338
136	ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ የተሰማሙና ይዜንኑም ስምምነት ለፍ/ቤት በማቅረብ ያስፀደቁ በሆነ ጊዜ ስምምነቱ እንደ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተቆጥሮ መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277	52752	እነ ከድር ሐጂ ሁሴን (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ አሚን ዑስማን (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 16/2002	340
137	ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው አቤቱታ የክስ ምክንያት አለው ወይም የለውም ብሎ ለመወሰን በክስ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሽ የሆነው ወገን የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ህግ ይፈቅድለታል ወይስ አይፈቅድለትም የሚለውን ጥያቄ መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ	45247	አቶ ደጀኔ በላቸው እና አቶ ነስሩ አወል	ሰኔ 17/2002	343
138	ሁለት ሰዎች ተጣምረው በተከሰሱ ጊዜ አንደኛው ወገን ጉዳዩ በሌለበት ከታየ በኋላ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተፈቀደለት እንደሆነ ሌላኛው ተከሳሽ አስቀድሞ ያነሳቸውን መቃወሚያዎች በድጋሚ ልታነሣና ልትከራከር አትችልም ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	49857	ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ፋንታ እና ወ/ሮ በላይነሽ ወ/ኪዳን	ሰኔ 30/2002	346
139	በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሽ ቀርቦ ክርክሩን ባሰማ ጊዜ ስለመሆኑና ድንጋጌው የካሣ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 235(2),83	48632	አቶ ሙልሳ በየቻ እና አቶ ደበሌ በየቻ	ሰኔ 14/2002	348

https://t.me/ethiopianlegalbrief

140	ክስ የቀረበበት ወገን ክሱን ለማስተባበል የሚቆጥራቸው ማስረጃዎችን ተቀብሎ አለመስማት የመከላከል ህጋዊ መብትን የሚያጣበብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ5 223, 234, 137, 249, 256	49660	እነ መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ት/ቤት (ሁለት ሰዎች) እና መምህር ሲሳይ ደጀኔ	ሰኔ 22/2002	350
141	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1) መሠረት በድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀደመው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑና የተከራካሪ ወገኖች አንድነት በመኖሩ ብቻ ሣይሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	52525	ወ/ሮ የትምወርቅ ሰብስቤ እና አቶ ሽዋረጋ ደመቀ	ሰኔ 29/2002	352
142	የሥር ፍ/ቤት በመቃወሚያ ላይ የሰጠውን ውሣኔ የሚለውጥ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠ እንደሆነ በግራ ቀኝ ወገኖችን በኩል የሚቀርቡ የፍሬ ነገር ክርክሮችንና ማስረጃ በአግባቡ ለመስማት ብሎም የተከራካሪዎችን ይግባኝ መብት ላለማጣበብ ሲባል ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለስ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341(1)	43331	አቶ ገመቹ ቡቻላ እና አቶ በቀለ ኩማ (ቡቻላ)	ሐምሌ 19/2002	354
143	ስልጣን ለሌለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብና ክርክር ማካሔድ የይርጋ ጊዜን የሚያቋርጥ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም የሰበር ችሎት በተቃራኒው የሰጠው የህግ ትርጉም የተሰወጠ ስለመሆኑ።) አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 138, 147, 164(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9, 23,(1) (ለ) ,231,(1)(ለ), 278(3) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 (ለ),1852(1) አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀፅ 2(4)	36730	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አማረ ገላው	ሐምሌ 30/2002	356
144	• በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከሣሽ ለሆነ ወገን ከፍ/ቤት የሚላከውን መጥሪያ ለተከሳሹ ሊደርስ የሚችልበትን የተሻለ አማራጭ መንገድ በመለየት ሊላክ የሚገባ ስለመሆኑ • የመኖሪያ አድራሻው በግልፅ ለሚታወቅ ተከሳሽ ፍ/ቤቱ የሚልከውን መጥሪያ በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ብቻ እንዲለጠፍ በማድረግ ተከሳሹ አልቀረበም በሚል በሌለበት ጉዳዩ እዲታይ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ • መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው ያልተደረገ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሣኔ እንዲነሣለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 105(1), 78,	50376	ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ገሰሰ እና በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/08 አስተዳደር ጽ/ቤት	ሐምሌ 12/2002	361

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

negligent homicide
https://t.me/ethiopianlegalbrief
power of cassation bench

የሰ/መ/ቁ. 35697

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አለ. መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ - ዓቃቤ ሕግ አውግቸው መኮንን ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ከበደ ወርቅነህ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13840 ጎዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ታህሣሥ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የምዕራብ ጎጃም ዞን ዓቃቤ ሕግ በከሣሽነት ተጠሪ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ የዞኑ ዓቃቤ ሕግ በተጠሪ ላይ፣ መጋቢት 28 ቀን 1998 ዓ.ም. ከምሽቱ በግምት አራት ሰዓት ሲሆን የግል ተበዳይ የመኩሪያው ተጋፋውን ቤት በማቃጠል በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ተኝተው የነበሩት ይታይሽ አለማየሁ፣ አለባቸው መኩሪያውና ፋሲካ መኩሪያው በእሳት ተቃጥለው እንዲሞቱ ያደረገ በመሆኑና ድርጊቱን የፈፀመው በእሳት ቃጠሎ ምክንያት በውስጥ ያሉ ሰዎች ሊሞቱ እንደሚችሉ እያወቀ በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ 539/1/ሀ/ በመተላለፍ የሆነው ይሁን በሚል ተነሳስቶ በመሆኑ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል፤ ይህ የሚታሰፍ ቢሆን በአማራጭ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/2/ የተመለከተውን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል፤ እንደዚሁም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 494 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ግምቱ ከብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ በላይ የሆነ ንብረት ሙሉ በሙሉ እንዲወድም አድርጓል የሚሉ ክሶችን አቅርቦበታል፡፡

ተጠሪ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ የገለፃቸውን የወንጀል ድርጊቶች አልፈፀምኩም በማለት ክዶ በመከራከሩ ዓቃቤ ሕግ ሁለት ምስክሮች አሰምቷል፡፡ ተጠሪ ለወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 መሠረት የሰጠውን የዕምነት ቃል በሰነድ ማስረጃነት አቅርቧል፡፡ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቤቱ ከውጭ እንደተቆለፈ በእሳት የተቀጣጠለ መሆኑንና በክሱ ስማቸው የተገለፀው ሰዎች በእሳት ተቃጥለው መሞታቸውን ልዩነት በሌለው ሁኔታ የመሰከሩ መሆኑንና ሁለተኛው የዓቃቤ ሕግ ምስክር በእሳት ተቃጥላ የሞተችው ሴት ተከሣሽ መኩሪያው ተጋፋውን ከነ ቤተሰቦቹ ቆልፌ በእሳት አቃጥላለሁ እያለ ይዝት እንደነበር ከዚያ ቀን በፊት ነግራኛለች በማለት የመሰከረ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሣያል፡፡

ሌላው በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ማስረጃ ተጠሪ በወንጀለኛ መቀጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 መሠረት የሰጠው የዕምነት ቃል ሲሆን መጋቢት 29 ቀን 1998 ሌሊት 4 ሰዓት ሲሆን የመኩሪያው ተጋፋውን ቤት አቃጥየዋለሁ፤ ያቃጠልኩት መጋቢት መባቻ ላይ በዱላ ስለመታኝ ነው፤ ቤቱ ከውጭ ተቆልፎ የነበረ በመሆኑና የቤቱ ባለቤት ወደ ማነበር ሲሄድ ስላየሁት ቤተሰቦቹም ሄደዋል ብዬ ነው ያቃጠልኩት፤ ቤቱም ከውጪ ተቆልፎ ነበር የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ በወቅቱ በአካባቢው ያልነበረ መሆኑን ሁለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/3/ የተመለከተውን በመተላለፍ በቸልተኝነት ሶስት ሰዎችን የገደለ ጥፋተኛ ነው፤ እንደዚሁም በወንጀል ሕጉ 691 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ቅጣቱን በተመለከተ ለመጀመሪያው ጥፋት በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር መቀጮ፤ በሁለተኛው ጥፋት በሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና በአምስት መቶ ብር መቀጮ በጥቅሉ በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራትና በሁለት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በእሳት ተቃጥለው የሞቱትን ሰዎች በተመለከተ ተጠሪ ሊያደርገው የሚችለው ጥንቃቄ አልነበረም፤ የሀሣብ ሁኔታው አልተሟላም በማለት ሙሉ በሙሉ በነፃ እንዲለቀቅ የወሰነ ሲሆን የሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና አምስት መቶ ብር ቅጣት በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት አለበት፤ ተጠሪ ቤቱን በማቃጠል የግል ተበዳይ ያደረሰበትን ጉዳት ለመበቀል አስቦ ያደረገው መሆኑ በሰው ምስክርም ሆነ በጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፤ ተጠሪ ከምሽቱ አራት ሰዓት በመሄድ ቤት ያቃጠለው ንብረት ለማውደም ብቻ ሣይሆን ሰዎች የሚተኙበት የእንቅልፍ ሰዓት በመሆኑ የግል ተበዳይን ከነቤተሰቡ በእሳት ለማቃጠል በነበረው ሀሣብ እንደሆነ በማስረጃ አስረድተናል፤ ሆኖም የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአማራጭ የቀረበውን በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ተጠሪን ጥፋተኛ ሲል ዓቃቤ ሕግ ይግባኝ ያልጠየቀ በመሆኑ በከባድ ሰው መግደል ተጠሪ መጠየቅ አለበት ብለን ለመከራከር የሥነ ሥርዓት ገደብ ቢኖርብንም ከዚህ አልፎ የጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት የለም በማለት መወሰኑ ለወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 እና 543/3/ የተዛባ ትርጉም የሰጠና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሰራ መሆኑን ሰለሚያሣይ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች አቤቱታ መልስ ይዞ እንዲቀርብ መጥሪያ የደረሰው ሲሆን መልሱን ይዞ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ቤቱን ከምሽቱ አራት ሰዓት ያቃጠለው ከግል ተበዳይ መኩሪያው ተጋፋው ጋር ከዚያ በፊት ተጣልተው የግል ተበዳይ በዱላ ስለደበደበው መሆኑን የዓቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የግል ተበዳይን ቤት ከውጭ ቆልፌ ከነቤተሰቡ ነው የማቃጥለው በማለት ይዝት እንደነበር አንደኛዋ ሚች ነግራኛለች በማለት አስረድቷል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ መመዘን አለበት በማለት የሰጠው ትችት ተቀባይነት ያለው የማስረጃ አመዛዘን መርህ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ሆኖም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱና መልዕክቱ የመዘነ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ዓቃቤ ሕግ የጽሁፍ ማስረጃ አድርጎ ባቀረበው የተጠሪ ዕምነት ቃል የግል ተበዳይ ወደ ማነበር ሲሄድ ስላየሁት ቤተሰቦቹም ሄደዋል ብዬ በማሰብ ቤቱን አቃጠልኩት የሚል ፍሬ ጉዳይ አለ፡፡ ከዚህም የምንረዳው ተጠሪ በእሳት ቃጠሎ ሕይወታቸው ያለፈው የግል ተበዳይ ቤተሰቦች ወደ ማነበር ሲሄዱ ያላያቸው መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ሚቾች ወደ ማነበር ስለመሄዳቸው እርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ ማነበር ሄደዋል ብሎ ስለገመተ ብቻ ቸልተኝነት የለበትም ለማለት አይቻልም፡፡ ወቅቱ ሌሊት ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የግል ተበዳይን ቤትና ንብረት የሚጠብቅ ሰው ከቤት ሊኖር እንደሚችል ማወቅ ሲገባው ወይም እያወቀ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 የተደነገገውን ቸልተኝነት የሚያሟላ ነው፡፡ የሚቾች ከቤታቸው ውስጥ ተኝተው መገኘት ከተጠሪው አቅም በላይ የሆነ ኃይል ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ማስረጃ ተጠሪ ከግል ተበዳዩ ጋር በነበረው ጠብ በቂም በቀል ተነሳስቶ የግል ተበዳይን ቤት በእሳት ያቃጠለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ተጠሪ በለኮሰው እሳት ተቃጥለው ሰዎች ሞተዋል፡፡ ተጠሪ ቤቱን የማቃጠል እንጂ ሚቾቹን የመግደል ሀሣብ አልነበረውም ቢባል አንኳን በቸልተኝነት ሚቾችን በመግደሉ ተጠያቂ የማይሆንበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ሊያደርገው የሚገባው ጥንቃቄ አልነበረም በቸልተኝነት በሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ መባል የለበትም በማለት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13840 ጎዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 543/3/ በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ሊጠየቅ አይገባውም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ"ዝገብ ቁጥር 14498 ሀምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገውን በመተላለፍ ሟች ይታይሽ አለማየሁ፣ አለባቸው መኩሪያውና ፋሲካ መኩሪያውን በቸልተኝነት የገደለ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡ ለዚህ ጥፋቱም ከፍተኛው ፍርድ ቤት በወሰነው መሠረት በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር መቀጮ ይቀጣል ብለናል፡፡ ይህንን ቅጣት ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ ለክልሉ ፖሊስ ኮሚሽንና ለክልሉ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ክርክር የወጣውን ወጪ አመልካች በራሱ ይቻል ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35695

ጎንደር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አሰማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ - አቃቤ ሕግ አውግቸው መኮንን

ተጠሪ፡- አቶ ተመስገን አዲስ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 15071 ታህሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ለወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 የሰጠው ትርጓሜና ተጠሪ በዋስ እንዲለቀቅ የሰጠውን ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ተጠሪ 1996 ያወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንኡስ አንቀጽ 3 በመተላለፍ በቸልተኝነት ያሽከረክር በነበረው አይሱዙ መኪና እማሆይ ሙሉነሽ ደላላ የተባሉትን ገድሏል በሚል ክስ አቅርቦበታል፡፡ ይህ የወንጀል ክስ በሚታይበት ጊዜ ተጠሪ የዋስ መብቱ ተጠብቆ ከውጭ እየቀረበኩ እንድከራከር ይፈቀደልኝ በማለት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያመለከተ ሲሆን አመልካችን ወክሎ የሚከራከረው አቃቤ ሕግ በበኩሉ በተጠሪ ላይ የተጠቀሰው አንቀጽ እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ስለሆነ በወንጀሉም የሰው ሕይወት ለሕልፈተሞት የተዳረገ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 መሰረት የዋስ መብት የሚያስፈቅድ ባለመሆኑ በእስር ሆኖ እንዲከራከር ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ የዋስ መብት የማያስፈቅድ መሆኑን በመግለጽ የተጠሪን የዋስትና መብት ከጥያቄ ውድቅ አድርጐታል፡፡ ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የዋስትና ጥያቄውን አስመልክቶ የሰጠውን ብይን በመቃወም ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 ሕግ አውጭው የደነገገው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሚያስቀጡ ሆነ ተብሎ የሚፈጸሙ በሰው መግደል የተከሰሱ ሰዎችን የዋስ መብት ለመከልከል እንደሆነ የሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌውን በ1949 ዓ.ም ከወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም፣በአዲሱ የወንጀል ሕግ የቅጣቱ መጠን እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ቢሆንም የሥነ ሥርአት ሕጉን ያወጀው ሕግ አውጭ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀሙ ሰዎችን የዋስ መብት የመከልከል ሐሳብ ያልነበረው በመሆኑ ተጠሪ የብር 2000/ሁለት ሺህ ብር/ ዋስ አቅርቦ እንዲለቅቅ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕግ አተረጓጐምና የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የተከሰሰበት ጉዳይ እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ እያለና በወንጀሉም የሰው ሕይወት ለሕልፈት የተዳረገ መሆኑ በክሱ ውስጥ ተገልፆ እያለ እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች በተሟሉበት ሁኔታ ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት እንደማይለቀቅ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 ንኡስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጐ እያለ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል መፈፀም የዋስትና መብት አያስነፍግም የሚል ትርጓሜ በመስጠት ተጠሪ በዋስ እንዲለቀቅ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል የሚል የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በዋናው ጉዳይ ጥፋተኛ ስለተባልኩ አቤቱታው ውድቅ ይደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ደረጃ የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ የተሻሻሉና የተለወጡ ሁኔታዎች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ያላቸውን ተፈፃሚነትና ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት የሚገባ የሕግ አተረጓጐም ምን መሆን አለበት? የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጓሜ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች መመርመር ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ መሰረታዊ የይዘታና የቅጣት ለውጥና መሻሻል የተደረገባቸው የወንጀል አይነቶች ያሉ መሆኑ አያከራክርም፡፡ ከወንጀል ሕጉ ጐንለጐን የወንጀል ሥነ ሥርአት ሕግ ተሻሽሎ አለመውጣቱ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያነሳቸውን የመከራከሪያ ሐሳቦችና ጥያቄዎች እንዲነሱ ክፍተት የሚፈጥር ስለመሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ሕግ አውጭው በአዲስ የወንጀል ሕግ ያወጣቸውና ያሻሻላቸው ጉዳዮች ባሉበት ሁኔታ በቀጥታ ከነበረው የሥነ-ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ተጣምረው ተፈፃሚ እንዲሆኑና እንዲተረጐሙ ፍላጐትና ሐሳብ አለው ተብሎ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም በአዲሱ የወንጀል ሕግ ቅጣታቸው ከፍ ብሎ የተደነገጉ ወንጀሎች የዋስትና ጥያቄና ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ የሚቀርቡ የሥነ-ሥርአት ጥያቄዎች 1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የነበረውን ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባትና ትርጓሜ መስጠት ሣያስፈልግ የሥነ-ስርአት ህጉን ከአዲሱ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በቀጥታ አጣምሮ በማየት መወሰን ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ አንፃር አዲሱ የወንጀል ሕግ ከመውጣቱ በፊት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት ብቻ ያስቀጣ የነበረው በቸልተኝነት ሰው የመግደል ወንጀል በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንኡስ አንቀጽ 3 እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ይሕ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 ንኡስ አንቀጽ 1 የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟላል ወይስ አያሟላም የሚለውን በመመዘን ብቻ መወሰን ሲገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1949 በወጣው የወንጀል ሕግ የነበረውን ሁኔታ መነሻ በማድረግ የሰጠው የሕግ ትርጓሜ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የተከሰሰበት የሕግ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርአት ሕግ ቁጥር 63 ንኡስ አንቀጽ 1 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላና የዋስ መብት የማያስፈቅድ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ በዋስ እንዲለቀቅ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15071 ታህሣስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዘገብ ቁጥር 2077 ጎንደር 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. አመልካች በዚህ ፍርድ ቤት ያወጣውን ወጪ ራሱ ይቻል ብለናል ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጎንደር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.39722

ታህሣሥ 23 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብ□ልቃ□ር መሐመ□

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- □ርማ ሃ□ሌ -አልቀረቡም

ተ□ሪ፡- ዐቃቤ ሕግ - ቀርቧል

□□□፡- ከተመረመረው በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቶበ□ል፤

□ ር □

ይህ ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት በመ/ቁ.37985 ግንቦት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ □ታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

□ዳዩ የይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን፣ ይኸውም አመልካች በወ/መ/ቁ. 21282 በከፍተኛ ፍርድ/ቤት በወንጀል ተከሶ ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም. በሌለበት በ13 ዓመት ፅኑ እስራት ስለተፈረደበት በጉዳዩ ይግባኝ ለማቅረብ □ል□ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ አልፏል በመባሉ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.191(1) መሰረት ይግባኙን ማቅረብ እንዲችል እንዲፈቀድለት ለፌ/ጠቅ/ፍ/ቤት ወንጀል ችሎት ይግባኝ ቢያቀርብም ችሎቱ በወ/ይ/መ/ቁ. 37983 ፣ ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ውሳኔ የይግባኝ ጊዜው ያለፈው በአመልካቹ ጥፋት በመሆኑ ጥያቄው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.191(3) መሰረት ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ከላይ የሰፈረውን ውሳኔ በመቃወም አመልካቹ ሐምሌ 26 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱ□ □ቀረበ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም በሌለሁበት የተሰጠውን ፍርድ እንዲሻርልኝ ያቀረብኩት ጥያቄ በ03/07/2000 ዓ.ም. ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ተቀባይነት እንዳጣ እኔም በጉዳዩ ይግባኝ እንደምል በ04/07/2000 ዓ.ም. በማረሚያ ቤት በኩል ለፍ/ቤቱ ማመልከቻዬን ልኬያለሁ፤ይሁን እንጂ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የላከልኝ ቅጣት የተወሰነበት የፍርዱ ግልባጭ ሳይሆን ፍርዱ ተለውጦ ባለሁበት እንደገና እንዲታይልኝ አመልክቼ ፍርዱ አይለወጥም ተብሎ ብይን የተሰጠበት በመሆኑ እንደገና ተመልሼ በ29/07/2000 ዓ.ም. ሊልክልኝ የሚገባው ፍርድ የተሰጠበት ግልባጭ መሆኑ ባመለክተውም በመጀመሪያ በ 04/07/2000 ዓ.ም. ያቀረብኩት ማመልከቻ ትቶ ስህተቱን እንዲያርም ተመልሼ የፃፍኩትን የ29/07/2000 ዓ.ም. ማመልከቻ ብቻ አያይዞ ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ በመላኩ ያመለከትኩበትን ጊዜ በአግባቡ ሳይመዘንልኝ አላግባብ ማለትም ከ□ኔ ጥፋት ውጭ በሆነ ምክንያት ጊዜው አልፎበታል ተብያለሁ ፣ ስለሆነም መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለተፈፀመብኝ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

□/ህ□ም በቁ.5 - 2042. ይግባኝ ህዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የአመልካቹን ቅሬ□ በአግባቡ ለማስተናገድ ሲባል ዋናውን የስር መዝገብ አስቀርቦ ከተመለከተ በኋላ የይግባኝ ጊዜው ያለፈው በአመልካቹ ጥፋት መሆኑ ካረጋገጠ በኋላ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የተፈፀመ ስህተት የለም ብሏል፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር ከላይ በተቀመጠው መልክ ከተገነዘበና በአመልካችና በተጠሪ መካከል ክርክር የተካሄደበት ዋናው መዝገብ (የወ/መ/ቁ. 21288) ከከፍተኛ □ርድ ቤት አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አመልካቹ ይግባኝ የማቅረቢያ ጊዜ አልፎበታል ወይስ አላለፈበትም? የሚል መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮ□ል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካቹ በከፍተኛ ፍርድ/ቤት (በወ/መ/ቁ. 21282) በወንጀል ተከሶ ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም. በሌለበት በ13 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ እንደተፈረደበት ነው፤ በሌለበት የተፈረደበትን ፍርድ ተሸሮ እንደገና ባለበት እንዲካሄድለት ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ጥያቄ አቅርቦ እንደነበርና ይህም ጥያቄው መጋቢት 03/2000 ዓ.ም. ተቀባይነት እንደሌለው ከተበየነ በኋላ ለሚቀጥለው ቀን ማለትም መጋቢት 04/2000 ዓ.ም በማረሚያ በኩል ለፍርድ ቤቱ በላከው ማመልከቻ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ እንደሚል ግልባጭ እንዲሰጠው ጠይቆ የተላከለት ቅጅ ጥፋተኛ □ተባለበትና ቅጣት የተሰጠበት የመዝገብ ግልባጭ ሳይሆን ቀደም ብሎ በሌለበት የተሰጠውን ፍርድ እንደገና ባለበት እንዲካሄድለት አመልክቶ የተሰጠውን ብይን የሚያመለክተው ክፍል ብቻ ነው፤ ይህም ስህተት መሆኑ ገልፆ ማለትም ጥቅምት 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሳኔ የሰጠበትን መዝገብ ተገልብጦ □ንዲላክለት መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ጠይቋል። ፍርድ ቤቱም ሚያዚያ 03/2000 ዓ.ም. ገልብጦ እንደሰጠና አመልካቹም ሚ□□□ 15/2000 □ም. ቅሬታው በማዘጋጀት ፣ሚያዚያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም. ለፍርድ ቤቱ እንደደረሰ ነው። የይግባኝ ቅሬታው አመልካቹ ያዘጋጀውና የላከው በዝዋይ ማረሚያ ቤት ሆኖ እንደሆነ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል። ከላይ የሰፈሩት ሃቆች ከወ/ስ/ስ/ህ/ቁ 187 (1) (2) ከሰፈረው አሰራር ጋር በማነፃፀር አመልካቹ ፍርዱ በተሰጠ በ 15 ቀናት ውስጥ ይግባኝ እንደሚል አላሳወቀም ተብሎ የይግባኝ ጊዜ አልፎበታል እንደተባለና የይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄውም በራሱ ጥፋት የተፈፀመ ነው ተብሎ በወ/መ/ሰ/ስ/ህ/ቁ 191 (3) መሰረት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ እንዳልተቀበለው ነው፤ ፍርዱን ከሰጠው ከፍተኛ ፍ/ቤት ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ የወንጀል ችሎት የተላከው በወ/መ/ቁ 21282 በ15/09/2000 ዓ.ም. የተፃፈው የይግባኝ መሸኛ □በ□ቤ እንደሚያመለክተው አመልካቹ መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. ይግባኝ ለማለት እንደሚፈልግ እንዳሳወቀ እንጂ በመጀመሪያ መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግና ቅጅው ተገልብጦ እንዲሰጠው የገለፀበት ሁኔታ አልተገለፀም። አመልካቹ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግ በ04/07 /2000 ዓ.ም. ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ሲያመለክተው የፍርዱን ግልባጭ በጠቅላላው እንደማስተላለፍ የፍርዱ ሂደት እርሱ ባለበት እንደገና እንዲታይለት ላመለከተው ጥያቄ የተሰጠውን ብይን የሚመለከት ብቻ ነጥሎ እንዳስተላለፈ ነው፤ የስር ፍርድ ቤቱ ይህንን ስህተት በመፈፀሙ ምክንያት ደግሞ አመልካቹ በእስር ሆኖ ይህንን ችግር እንዲፈታለት ተመልሶ በ29/07/2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ □ንደጠየቀ ነው። በአጠቃላይ አመልካቹ በተላለፈበት ፍርድና የፍርድ ሂደት ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግ በህጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳያልፍ መጋቢት 04/2000 ዓ.ም. ለፍርድ ቤቱ ጠይቋል ፣ ፍርድ ቤቱም መላክ ያለበትን ግልባጭ በትክክል ገልብጦ እንደመላክ ዋናውን የፍርዱ ቅ□ ሳ□ልክ እንደቀረ ነው፣ ስለሆነም መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. የፃፈው ደብዳቤ ለሁለተኛ □□ የቀረበ ጥያቄና ቀደም ብሎ የተፈፀመውን የማሳረፍ ፍላጎቱ ለማንፀባረቅ የተጠቀመበት ነው ተብሎ እንደመተርጎም ለመጀመሪያ ጊዜ የይግባኝ ጥያቄ እንደቀረበ ተደርጎ መወሰዱ ተገቢነት የለውም ፣ ከዚያም በኋላ የነበሩት መፃፎች አመልካቹ በዝዋይ እስር ቤት ሆኖ በማረሚያ ቤት በኩል ወደ ፍ/ቤቱ ይደረጉ የነበሩ መላላክን አመልካቹ በህጉ መሰረት ይግባኝ ለማቅረብ መዘግየቱ የሚያሳዩ ሆነ□ አይተረጎሙም ፣ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት ይህንን ሁኔ□ በሚገባ ሳያገናዝብ አመልካቹ ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም. ለተላለፈበት የቅጣት ውሳኔ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግ የገለፀው በ29/07/2000 ዓ.ም. እንዳመለከተ እና ይህም አመልካቹ የይግባኝ □□□ እንዲያልፍ ያደረገው በራሱ ጥፋት ነው በማለት ጥያቄው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 191 (3) መሰረት ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ሆኖ ተገኝቷል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ. 37985 ግንቦት 28/2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 195/2/ መሰረት ተሽሯል፤ ይፃፍ።
2. የአመልካቹ የይግባኝ ጊዜ ያለፈው በአመልካቹ ጥፋት ምክንያት ሳሆን የስር ፍ/ቤቱ በፈፀመው ስህተት ስለሆነ □□ባኙ እንዲያቀርብ ተፈቅዶለታል፤ በማረሚያ ቤት በኩል ይፃፍለት፤ ማረሚያ ቤቱ ትዕዛዝ ባደረሰለት በሃያ ቀናት ውስጥ ይግባኙን እንዲያቀርብ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ . 191 (4) መሰረት □□ል፣ □□□።
3. ይህ ውሣኔ በዛሬው ዕለት 15/05/2001 ዓ.ም. ተሰጥቷል፤ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ። መዛግብቶቹ ወደ መጡበት ይመለሱ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief
abuse of power
Criminal Liability of judges judges

የሰ/መ/ቁ. 33075

ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ብርቁ ገላነው /አቶ/ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የአማራ ብ/ክ/መ/የስነ- ምግባርና ፀረ- ሙስና ኮሚሽን - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተውን የወንጀል ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ ማየት እንደተቻለው ተጠሪ በሶስት ወንጀል ድርጊቶች አመልካችን ከሶ የነበረ ሲሆን፣አመልካች በሁለቱ ብቻ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ተወስኖበታል፡፡ ጥፋተኛ የተባለባቸው ክሶች በልዩ ወ/መ/ሕግ አዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 23/1//ሀ/ እና አንቀጽ 17/1/ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ አመልካች እነዚህን የወንጀል ድርጊቶች ፈጸመ የተባለው በወረዳ ፍ/ቤት የዳኝነት ስራው ላይ እንዳለ ነው፡፡ ዝርዝሩም በተከፈተው የፍትሐብሔር መዝገብ ተከሣሽ የከሰረችው ግለሰብ ሳትቀርብ ቀርባ መልስ እንደሰጠች አድርጐ በመመዝገብ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ለፍ/ቤት የተላከውን ሰነድ በመሰረዝ /በመደለዝ/ በሕዝብና በመንግስት ሰነድ ላይ ወንጀል ፈጽሞአል በሚል ሊጠቃለል እንደሚችል ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ መልክ ክሱ የቀረበለት በአማራ ብ/ክ/መ/የምእራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች ወንጀሎቹን ለመፈጸሙ በምስክሮች አረጋግጫለሁ በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ በመስጠት አመልካች በሰባት አመት ጽኑ እስራት እና በብር 200(ሁለት መቶ) መቀጫ እንዲቀጣ አዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማለቱ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በቅጣት ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ ብቻ በማሻሻል አመልካች በሁለት አመት እስራት እና በብር 200(ሁለት መቶ) መቅጫ እንዲቀጣ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 99 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች የዳኝነቱን ስራ በሚሰራበት ጊዜ በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁ. 214/74 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጐ በስልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ፈጽሞአል በሚል የመከሰሱንና ጥፋተኛ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች የተከሰሰው የዳኝነት ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ በስልጣኑ ያለአግባብ ተገልግሎአል እንደዚሁም የመንግስትና የሕዝብ ሰነዶችን ወደ ሐሰት ለውጦአል ተብሎ ነው፡፡ ወንጀሎቹና ፈጸመ የተባለው የፍትሐብሔር ክርክር በሰማበት መዝገብ እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡ እንደሚታወቀው የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕጉ ነው፡፡ በአንደኛው ክስ እንደተገለጸው ተከሣሽ የነበረችው ግለሰብ ሳትቀርብ እንደቀረበች ተደርጐ ተወስኖ ወይም ተመዝግቦ ሊሆን ይችላል፡፡ እዚህ ላይ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነገር እንዳለ ግን ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በእርግጥም በተባለችው ግለሰብ ስም የቀረበ የጽሑፍ መልስ የለም አልተባለም፡፡ በመሆኑም መልሱ ውክልና በሌለው በተሳሳተ/በማይመለከተው/ ሰው ተዘጋጅቶ ቀርቦአል እንኳን ቢባል ይህን መሰል ስህተት ሲከሰት ለማስተካከል በሚል በተደነገጉት የስነ-ስርአት ሕጉ ድንጋጌዎች የሚስተካከል ይሆናል እንጂ የተፈጠረው ስህተት በቀጥታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኛው/አመልካች/ሆነ ብሎ ስልጣኑን ያለአግባብ በመገለገል የፈጸመው የወንጀል ድርጊት ነው ወደሚለው የሚያደርስ የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነውም ሳትቀርብ እንደቀረበች ተደርጐ ተመዝግባ ውሳኔ ተሰጥቶአል የተባለችው ግለሰብ ወይም በዚህ ሂደት መብቱ ተጐድቶአል የሚል ወገን በፍትሐብሔሩ መዝገብ አቤቱታ አላቀረቡም ወይም አቅርበዋል አልተባለም፡፡ ይህን በራሱ የሚያሳየው በክሱ አመራርም ሆነ ውሳኔ የተጐዳ ወገን አለመኖሩን ነው፡፡ የተጐዳ የለም ከተባለ ደግሞ በተቃራኒው ከሕግ ውጪ ውሳኔ የተሰጠበት ወይም የተጠቀመ ተከራካሪ ወገን የለም ማለት ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች በተያዘው የፍትሐብሔር ክርክር ከማንኛውም ተከራካሪ ወገን ጥቅም ወይም መደለያ /ጉቦ/ ተቀብሎአል የሚል ክስ አልቀረበም፡፡ በአጠቃላይ በግለሰብዋ አቀራረብ ወይም መልስ አሰጣጥ ረገድ ስህተት ነበር የሚባል እንኳን ቢሆን፣በግለሰብዋ ወይ ጉዳይ ይመለከተኛል በሚል ወገን አግባብ ባለው የስነ-ስርአት ሕጉ መሰረት አቤቱታ ሲቀርብ የሚታይ እንጂ በአቃቤ ሕግ ክስ እንደተነገረው በልዩ ወ/መ/ሕግ አዋጅ ቁ. 214/74 ድንግጌዎች ስር የወንጀል ድርጊት የሚያቋቁም ጥፋት ተፈጽሞአል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

በ2ኛ ደረጃ የተጠቀሰው ክስም እንዳየነው ለክርክሩ ምክንያት የነበረው ቤት በተመለከተ ከማዘጋጃ ቤት የተጻፈውን ደብዳቤ ቁጥሩንና ቀኑን ለውጦ ጽፎአል በሚል የቀረበ ነው፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ይህን በሰው ምስክር አረጋግጫለሁ በማለት ነው አመልካችን ጥፋተኛ ያደረገው፡፡ ሁሉም በግልጽ እንደሚያውቀው በአንድ የክርክር መዝገብ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው የተሰየመው ዳኛ ቢሆንም፣ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በዳኛው ቁጥጥር ስር ሆኖ ይቆያል ማለት ግን አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ግን በተባለው ደብዳቤ ላይ የቁጥር እና በቀን አጻጻፍ ረገድ የተፈጠረ ችግር አለ በመባሉ ብቻ በዳኛ ላይ የወንጀል ክስ መመስረት የሚቻል አይሆንም፡፡ ሲጠቃለል ተፈጠሩ የተባሉት ክስተቶች ካሉም ከዳኝነት ስራ ስነ-ምግባርና ዲሲፕሊን አኳያ የሚታዩ ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን አመልካች በወ/መ/ሕግ አዋጅ ቁ. 214/74 በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስር ወንጀልን የሚያቋቁም ድርጊት ፈጽሚአል በሚል የቀረበው ክስም ሆነ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የሕግ መሰረት ያለው ነው የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ስለዚህም አቤቱታ የቀረበባቸው በአማራ ብ/ክ/መ/ በምእራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 10588 በ14/07/99 ዓ.ም የተሰጠው እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12083 ሰኔ 13 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ/ቁ. 195/2//ለ//1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡ አመልካችም በነጻ ተለቆአል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

unlawful enforcement of right

የሰ/መ/ቁ. 38161

የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች ፡- እነ ጀሚላ መሐመድ ሀጮስ - ጠበቃ እሸቴ ጓንጉል ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የፌዴራል የመ/ደ/ዓ/ቃህ - ፋሲል ገብሬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ መዝገብ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረምልን ይገባል በማለት ግንባት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዘርዝረው ስላቀረቡ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች ላይ የመሠረተው ክስ የግል ተበዳይ ወ/ሮ ዘርፌ ጥላሁን በአቶ መሐመድ ሐጮስ ቤት በቤት ሰራተኝነት ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ ግለሰቡ በ1990 ዓ.ም ወደ ኤርትራ ሲባረሩ ቤታቸውን በኃላፊነት እየጠበቁ እንዳለ ሐምሌ 21 ቀን 1997 ዓ.ም አመልካቾች የግል ተበዳይን እቃ ከቤት አውጥተው ግቢ ውስጥ በማስቀመጥ በግብረአበርነት በፈፀሙት ህገ ወጥ በሆነ መንገድ መብትን የማስከበር ወንጀል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1ሀ/ እና 436/1/ሀ/ መሠረት ጥፋተኛ ተብለው ሊቀጡ ይገባል የሚል ሲሆን አመልካቾችም የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን ጥፋተኛ አይደለንም ሲሉ አስመዝግበዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የዓ/ህግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ አመልካቾች እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ሰጥቶ የአመልካቾችን የሰው እና የጽሑፍ ማስረጃዎችን በመስማት ጉዳዩን በመመርመር የአመልካቾች የመከላከያ ማስረጃዎች የዓ/ህጉን ማስረጃዎችን ለማስተባበል በቂ አይደሉም የሚል ምክንያት ይዞ አመልካቾችን በዓ/ህግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጐ እያንዳንዳቸውን በብር 800.00 /ስምንት መቶ/ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካቾች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ጥፋተኛ መባላቸው ባግባቡ መሆኑን በመግለጽ ድርጊታቸው የሚሸፈንበትን ድንጋጌ ብቻ በማሻሻል ቅጣቱንም በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን የጥፋተኝነት ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በዓፉት የሰበር ማመልከቻ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠበትን አንቀጽ የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦችን የሚያሟላ የወንጀል አላፊነትን የሚያስከትል መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታዩ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ የአመልካቾች ድርጊት ወንጀሉን የሚያቋቁም መሆኑንና ጥፋተኛ መባላቸውም ባግባቡ መሆኑን ጥቅምት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፈው ማመልከቻ ዘርዝሮ የጥፋተኝነት ውሣኔው ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘበ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም አመልካቾች ፈፀሙ የተባለው ድርጊት የወንጀል ድርጊት ያቋቁማል ወይም አያቋቁምም? የሚለው ነጥብ በቅድሚያ ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

አመልካቾች የተከሰሱትና በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠባቸው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1ሀ/ እና 436/1/ ስር የተመለከተውን ተላልፈዋል በሚል ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ አንቀፁን በመለወጥ አጽንቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካቾችን ጥፋተኛ ያደረጋቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 436/ሐ/ ስር ነው፡፡

ህገ ወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር ድርጊት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 436/ሐ/ መሠረት ሊያስጠይቅ የሚችለው ማንም ሰው መብት ሳይኖረው ወይም ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ በጠቅላላው የሌለውን ወይም በህጉ መሠረት ሊሰራበት የማይችለውን መብት የተጠቀመበት እንደሆነ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የግል ተበዳይ ወ/ሮ ዘርፌ ጥላሁን ቤቱን እንዲለቁ ሲያደርጉ የግል ተበዳይዋ ቤቱን የያዙት በጠባቂነት በነበራቸው ኃላፊነት ስለመሆኑ አንደኛ አመልካች ደግሞ የቤቱ ባለቤት የተባሉት ግለሰብ የአቶ መሐመድ ሐጐስ ልጅ ሁለተኛ አመልካች ደግሞ ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው ላይ የተገኙት ከአንደኛ አመልካች በተሰጣቸው ውክልና መሠረት ስለመሆኑ የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም አንደ1ኛ አመልካች በቤቱ ላይ በጠቅላላው መብት የሌላቸው ወይም በህጉ መሠረት ሊሰሩበት በማይችሉት መብት የተጠቀሙ ሳይሆን በቤቱ ላይ መብት ያላቸው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁምበት ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 23/2/ ስር አስቀምጧል እጃችን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካቾች ድርጊት የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠባቸው የህግ ድንጋጌ የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች የተሟሉበት አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23/2/ እና 436/ሐ/ ስር የተመለከቱትን የህጉን መስፈርቶች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት መ/ቁ. 35370 ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት መ/ቁ. 64237 መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠ ውሣኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ሐ/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ፈጽመውታል የተባለው ድርጊት የወንጀል ባህርይ የለውም ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

corruption https://t.me/ethiopianlegalbrief
injunction of property
principle of proportionality

ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የፌ/የሥነ-ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ - ዐ/ሕግ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- እነ ካፍ መሐመድ /4 ሰዎች/ - ጠበቃ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የጉዳዩ አጀማመር የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ሕግ ተጠሪዎች የተጠረጠሩበትን የወንጀል ድርጊት በመጥቀስ በተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 23 መሠረት በማድረግ ተጠርጣሪዎች መዝብረውታል ለተባለው እና ለወደፊቱ ላደረሱት ጉዳት ማካካሻ የሚሆነውን ንብረታቸውን እንዳያሸሹ ወደ ሌላ ወገን እንዳያዛውሩ እና ወደ ጥሬ ገንዘብ ቀይሮ ስለሚያባክኑ መደብሮቹ እንዲታሹ እና ጥበቃ እንዲደረግለት በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከላይ የተቀጠሱት ተጠርጣሪዎች ዐ/ሕግ ክስ መስርቶባቸው በክርክር ላይ መሆናቸውንና ንብረታቸውን ያሳገደ ቢሆንም ተጠርጣሪዎች የታገደው ንብረት ከደረሰው ጉዳት የበለጠ በመሆኑ ተመጣጣኝ የሆነው ታግዶ ሌላው ሊለቀቅልን ይገባል ያሉትን ክርክር ባለመቀበል ዕግዱ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ /ተጠርጣሪዎች/ በዚሁ ትዕዛዝ ባለመስማማት ክርክራቸውን በማጠናከር የታገደው ንብረትና የደረሰው ጉዳት አይመጣጠንም፣ ደረሰ በተባለው የጉዳት ልክ ብቻ ነው ሊታገድ የሚገባው የቀረው ሊለቀቅልን ይገባል በማለት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የጠቅላይ ፍ/ቤቱም የተሰጠውን ዕግድ እና በተጠርጣሪዎች የተነሣውን ተቃውሞ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁ. 434/97 አንቀፅ 9 መሠረት የታገደው የተጠርጣሪ ንብረት ተፈፅሟል ከተባለው ወንጀል ደርሷል ከተባለው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት በመግለፅ በሥር ፍ/ቤት ዐ/ሕግ ደርሷል የሚለው ከፍተኛ ሲሆን የተጠርጣሪዎችም ንብረቶች በጠቅላላው ከመታገዱ ውጪ የታገዱት ንብረቶች በባለሙያ ተገምተው እንዳልቀረበ ተረድቻለሁ፣ የሥር ፍ/ቤቱም ተመጣጣኝ ነው ያለው በግምት እንጂ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ ስለዚህ የተጠርጣሪዎች /ተጠሪዎች/ የንግድ መደብር ከግለሰብና ከመንግስት ተከራይቶ ሲጠቀሙበት የነበረ ስለሆነ ታሽገው መቆየቱ ተገቢ አይደለም ምክንያቱም በተከራዩም ሆነ በአከራይ ላይ ጉዳት የማያደርስ በመሆኑ ተጠርጣሪዎች በንግድ መደብርነት ሲገለገሉበት የቆዩት ቤቶች ውስጥ የነበሩት ዕቃዎች እንዲወጡ ተደርጐ የንግድ ቤቶቹ ተከፍተው የተለመደው የንግድ ስራ ይከናወን በማለት በማሻሻል ወስኖ የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው መሠረት እንዲያስፈፅም አዟል፡፡

በዚህም መሠረት /በጠቅላይ ፍ/ቤት/ የተሰጠውን እንዲያስፈፅም ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ለአፈፃፀም ይረዳ ዘንድ የቀረበውን የግራ ቀኙን የአማራጭ ሃሣብ መሠረት አድርጐ ቢያከራክርም ሊስማሙ ባለመቻላቸው የጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት በመደብሩ ውስጥ የነበሩት ዕቃዎች አሻጊዎች በተገኙበት ተቆጥሮ ወጥቶ

የኮሚሽኑ ዐ/ሕግ በሚያስቀምጥበት ቦታ አሻሚዎች በተገኙት ታሸጉ ይቀመጥ ተጠርጣሪዎች የንግድ ቤቶቹን እንዲረከቡ በማለት አዟል፡፡

የኮሚሽኑም ዐ/ሕግ በዚሁ ትዕዛዝ ባለመስማማት በቀን 22/7/2001 ባቀረበው የሰበር አቤቱታው የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሣኔ እና የሥር ፍ/ቤቱም የይግባኝ ሰሚውን ውሣኔ ተከትሎ የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

እኛም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ተጠርጣሪዎችን /ጠበቃ/ እና ዐ/ሕጉን በማስቀረብ የቃል ክርክራቸውን ሰምተናል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተፈለገው የንግድ መደብሮቹ ከነበሩበት የንግድ ቤት ወጥተው አመልካች /ዐ/ሕግ/ በሚያዘጋጀው ቦታ እንዲቀመጡ የተሰጠው የፅግድ ማሻሻያ ትዕዛዝ በማስረጃ ሕጉ ስለ እግዱ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንጻር ለመመርመር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ የግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት የቃል ክርክር፣ አቤቱታ ካቀረቡበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበናል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ በተጠርጣሪዎች ላይ በመሠረተው ክስ የንግድ መደብራቸውን በማሳገዱ ተጠርጣሪዎች የታገደው ንብረት ከደረሰው ጉዳት የበለጠ በመሆኑ ተመጣጣኙ ታግዶ ሌላው ይለቀቅልን በማለት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱም የተሰጠው ፅግድ ተመጣጣኝ ነው ሲል ፅግድ ይቀጥል ብሎ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠርጣሪዎቹ ተመሣሣይ ክርክራቸውን በማጠናከር ይግባኝ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረባቸው፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ጥያቄ በመመርመር የታገደው የንግድ መደብርና የደረሰው ጉዳት ይመጣጠናል? አይመጣጠንም? ለሚለው ጥያቄ በሁለቱም ተከራካሪዎች ንብረቱ በባለሙያ ተሰልቶ እንዳልቀረበ ተረድቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ተጠርጣሪዎች የሚነግዱበት የንግድ መደብር ከግለሰብና ከመንግሥት ተከራይቶ ስለሆነ በአከራዩም ሆነ በተከራዩ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል የንግድ ቤቱ ታሸጉ የሚቀመጥበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በመደብሩ ውስጥ የሚገኙትን ንብረቶችን የኮሚሽኑ ዐ/ሕግ አውጥቶ ሌላ ቦታ ያስቀምጥ ድርጅቶቹ ተከፍቶ አገልግሎታቸውን ይቀጥሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ውሣኔ /ትዕዛዝ/ መሠረት በማድረግ አፈፃፀም የቀረበለት የሥር ፍ/ቤትም ተከራካሪ ወገኖች በአፈፃፀሙ ላይ ሊስማሙ ባለመቻላቸው በጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሣኔ መሠረት ይፈፀም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የኮሚሽኑ ዐ/ሕግም ተቃውሞ በዚሁ ላይ ነበር፡፡

ለዚህ የሰበር ችሎት ተያይዘው ከቀረቡት መዝገቦች ለመገንዘብ እንደቻልነው ለአሁኑ ክርክር መነሻ የሆነው የአሁኑ መልስ ሰጪዎች በተጠረጠሩበት የወንጀል ጉዳይ ከፍተኛው ፍ/ቤት እንዲታገዱ ያደረጋቸው ንብረቶች በወንጀሉ ምክንያት ደርሷል ከተባለው ጉዳት የበለጠ ዋጋ ያላቸው በመሆኑ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ንብረቶች ብቻ ታግደው ቀሪዎቹ ይለቀቁልን በማለት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን ማመልከቻ ውድቅ አድርጐታል፡፡ በትዕዛዙ ቅር ተሰኝተው መ/ሰጪዎች ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሲሉ ግን ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በአንድ በኩል የታገደው ንብረት ግምት ደረሰ ከተባለው ጉዳት በላይ ነው ሊባል አይችልም ሲል በሌላ በኩል ግን የታገዱት የመልስ ሰጪ ድርጅቶች ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ፈቅዷል፡፡ በመሰረቱ ከፍተኛው ፍ/ቤት የታገደው ንብረት ደረሰ ከተባለው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ነው? አይደለም? የሚለውን ሲመዝን ግምት ውስጥ ያስገባው አሁን ሥራ ይስሩ የተባሉትን ድርጅቶች እንደ ድርጅት በመውሰድ ነው ጠቅላይ ፍ/ቤትም በመርህ ደረጃ የታገደው ንብረት ከጉዳቱ አይበልጥም የሚለውን መደምደሚያ ተቀብሎታል፡፡ በከፍተኛ ፍ/ቤት ከተያያዙት ሰነዶች ለመገንዘብ እንደቻልነው የፅግድ ትዕዛዝ የተጠየቀውም ሆነ የተሰጠው በንግድ መደብሮችም ጭምር ነው፡፡ የመደብሮቹ ዋጋ ሲሰላም ግምት ውስጥ የሚገባው የመደብሩ ውስጥ የሚገኙ ሸቀጥ ብቻ ሳይሆን የመደብሩ መልካም ስም (good will) ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም የፅግዱ ዓላማ ደረሰ የተባለውን ጉዳት የሚመጥን ንብረት ይዞ ማቆየት እንደመሆኑ መደብሩ ከሸቀጡ ተነጥሎ እንዲታይ መደረጉ የፅግዱን ዋና ዓላማው የሚያስቀር ነው፡፡ በመሆኑም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የመደብሩ ዋጋ ደረሰ ከተባለው አደጋ በላይ ነው ሊባል አይቻልም ካለ በኋላ መደብሩ ከፅግድ ትዕዛዙ ውጪ እንዲሆን መደረጉ እርስ በርሱ የሚጋጭ ውሣኔ መስጠቱን የማያመለክት ነው፡፡ መደብሮቹ ታሸገው መቆየታቸው መልስ ሰጪዎች ሊጐዱ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ ነገር ግን በመልስ ሰጪዎች ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ደረሰ ከተባለው የወንጀል ጉዳት ጋር በማመዛዘን መመልከትም ያስፈልጋል፡፡ በመደብሩ ውስጥ ያሉ ሸቀጦች ተለይተው የተቀመጡም ቢሆን በመልስ ሰጪዎች ላይ የኢኮኖሚ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል መገመት ይችላል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ መደብሮቹን አግዶ ማቆየቱ በአከራይም ሆነ በተከራይ ጉዳት የሚያደርስ ነው በማለት ብቻ ሸቀጡን ከመደብሩ መነጠሉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሻር ያለበት ነው ወደሚል መደምደሚያ ደርሰናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.4180 ጥር 8/2001 በሰጠው ትዕዛዝና የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ትዕዛዝ ለማስፈፀም የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ወ/ቁ. 64231 ህዳር 3 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሠ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አመልካች ፡- 1. ዳንኤል ገ/ዮሐንስ
2. ሚካኤል ፀጋዬ
3. ሚ/ር አሚት አብዶ
4. ቅዱስ ዓለምሰገድ

ጠ/ማረን ወንደሠ

ተጠሪ ፡- ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - ተሾመ አንጁሎ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የወንጀል ክርክር ሲሆን ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ የወንጀል ሕግ ቁጥር 32/1/ሀ/ እና 692/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ሚያዝያ 16 ቀን 2001 ዓ.ም. ከምሽቱ 4፡45 ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 ክልል የግል ተበዳይ አቶ ኢሳያስ ካሣ ግሮሰሪ በመሄድ ውስኪ እንፈልጋለን ብለው መኪና ውስጥ ሆነው አንድ ብላክ ሌብል ውስኪ አዘው እሱን ከተመለከቱ በኋላ ሌላ ብላክ ሌብል ጨምረን ብለው ሲጨምርላቸው ሲሄድ መኪና አስነስተው በማምለጣቸው ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ቀርበው ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ በክሱ ላይ መቃወሚያ እንዳላቸው ተጠይቀው ክሱን እንደማይቃወሙ ካረጋገጡ በኋላ የዕምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ድርጊቱን ፈፅመናል ጥፋተኞም ነን ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 134/1/ መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኋላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ በሰጠው የቅጣት አስተያየት ተከሣሾች የወንጀሉን ድርጊት የፈፀሙት ግብረአበር በመሆን ስለሆነ ፍ/ቤቱ ይህንን በቅጣት አወሳሰን ረገድ ከግምት እንዲያስገባልን ካለ በኋላ ተከሣሾች የትምህርት ደረጃቸው ሲታይ የወንጀልን አስከፊነት ከሌላው ሰው በተሻለ መልኩ ሊያውቁና ሊረዱ የሚችሉ መሆኑን መገንዘብ ስለሚቻል ይህንንም ከግምት በመክተት እንደዚሁም ፍ/ቤት ቀርበው ማመናቸውንም ከግምት በማስገባት ፍ/ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ቅጣት እንዲወስንባቸው በማለት አመልክቷል፡፡

ተከሣሾችም በበኩላቸው ድርጊቱ በአጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን፣ ወጣቶች እንደሆኑ፣ በድርጊታቸውም እንደተፀፀቱና ከግል ተበዳይም ጋር እንደታረቁ ገልፀው የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች መሆናቸውን ጠቅሰው ቅጣቱ በገደብ እንዲሆን ይወሰንልን በማለት የቅጣት አስተያየት መስጠታቸውን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ መልኩ የቅጣት አስተያየት የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተከሣሾች የተከሰሱበት ወንጀል እስከ 3 ዓመት በሚደርስ እሥራት የሚያስቀጣ ቢሆንም ተከሣሾች አስቀድሞ ወንጀል የፈፀሙ ስለመሆኑ ሪከርድ ያልቀረበባቸው ስለሆነና ይህንንም ወንጀል ስለመፈፀማቸው ያመኑ በመሆኑ ይህም ሁኔታ በወንጀል ሕግ ቁጥር 82/1/ሠ/ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅጣት ማቅለያ ተደርጎ ሊወሰድ ስለሚችል ተከሣሾች እያንዳንዳቸው በ6 /ስድስት/ ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሾች የጥፋተኛነት ውሣኔውን ተቀብለው ነገር ግን በቅጣት ማቅለያነት ያቀረቡት ምክንያቶች የተወሰነውን ቅጣት በወንጀል ሕግ ቁጥር 192 መሠረት በገደብ ለማቆየት የሚያስችል ሆኖ ሳለ ቅጣቱ ሳይገደብ መቅረቱ ተገቢነት የሌለው ነው በማለት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በአመልካቾች ላይ የተወሰነውን ቅጣት በገደብ ለማቆየት የሚያበቃ ሁኔታ ስለመኖሩ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብሎ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን በበኩላችንም አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በአንድ የወንጀል ተከሣሽ ላይ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ የተወሰነው የእሥራት ቅጣት ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ሊደረግ የሚችልባቸው ምክንያቶች በወንጀል ሕግ በቁጥር 192 ላይ ተመልክቶ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም የቅጣት ውሣኔ በገደብ ሊቆይ የማይችልባቸው ምክንያቶችም በቁጥር 194 ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት ከቁጥር 192 አኳያ የተወሰነውን የእስራት ቅጣት በገደብ ለማቆየት የሚቻለው ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነው ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑን ፍ/ቤቱ ያመነበት ከሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ቀደም ሲል ወንጀል ስለመፈጸማቸው ሪከርድ ያልቀረበባቸው እንደመሆኑ መጠን ያለፈ የሕይወት ታሪካቸው መልካም እንደነበር ይገመታል፡፡ አሁን ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበትንም ወንጀል በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ የፈፀሙት ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ አመልካቾች ወንጀሉን ከፈፀሙ በኋላ ከግል ተበዳዩ ጋር ወዲያውኑ መታረቃቸው ድርጊቱን በድንገተኛ አጋጣሚ በየዋህነት የፈፀሙት መሆኑና በዚህም መጸጸታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩልም የወንጀል ሕግ ግብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይዘቱም የወንጀል ሕግ ግብ ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ ዕርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወንጀል ሕግ ቁጥር 82 መሠረት ቅጣቱን በማቅለል ከወሰነ በኋላ አመልካቾች ከፍ ብሎ እንደተመለከተው የቀድሞ የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበባቸው ከመሆኑ አኳያ ይህንንም ወንጀል የፈፀሙት በድንገተኛ አጋጣሚ በየዋህነትና ባለማስተዋል ከመሆኑ አንፃር በአጠቃላይም ከወንጀል ሕግ ግብ አኳያ ሲታይ አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ ተሰጥቷቸው የተወሰነባቸው ቅጣት ሳይፈፀም ተግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈፀም ሊታቀቡ እንደሚችሉ ከአጠቃላይ የወንጀሉ አፈፃፀምና ከአመልካቾች ሁኔታ መገንዘብ እየተቻለና ቅጣቱንም በወንጀል ሕግ ቁጥር 194 መሠረት በገደብ ላለማቆየት የሚያበቃ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ቅጣቱን ለመገደብ የሚያበቃ በቂ ሕጋዊ ምክንያት እያለ እንዲገደብ ሳያደርግ መቅረቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ/7933 በ21/8/2001 ዓ.ም. የሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ በማጽናት በመ.ቁ. 45568 በ9/9/2001 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በበኩላችንም በማጽናት ነገር ግን በአመልካቾች ላይ የተወሰነው የ6 /ስድስት/ ወር ቀላል እሥራት ከፍ ብሎ በተመለከቱት ምክንያቶች ሳይፈፀም በ2 /ሁለት/ ዓመት ገደብ ይቆይ በማለት በወንጀል ሕግ ቁጥር 192 እና 197/1/ መሠረት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በአመልካቾች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት የተገደበ ስለመሆኑ እንዲታወቅ ለሥር ፍ/ቤቶችና ለአ.አበባ ማረሚያ ቤት ይገለጽለት ብለናል፡፡
3. አመልካቾች በዚህ ችሎት ክርክር ሲደረግ እያንዳንዳቸው ለዋስትና በሞዴል 85 ያስያዙት ብር 2000 /ሁለት ሺህ/ እንዲመለስላቸው ለሚመለከተው ይፃፍ ብለናል፡፡
4. መዝገቡን ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ጽ/ሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44031

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፈለቀች ኃ/ገብርኤል - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ - የዓቃቤ ሕግ አፀዱ ረጋሣ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታው ውድቅ ከተደረገበት ዮሴፍ ከበደ ጋር በጋራ ባቀረበችው የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በላሎ አሳቢ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ዓቃቤ ሕግ የሰበር አቤቱታው ውድቅ የተደረገበት ዮሴፍ ከበደ ጋር በመሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አንቀጽ 630/2/ሀ በመተላለፍ ነሐሴ 24 ቀን 1998 ከምሽቱ ሶስት ሰዓት በግል ተበዳይ ወ/ሪት ብርቱካን ዱባለን አስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቅርቦ የሰውና የጽሁፍ ማስረጃ አሰምቶ የወረዳው ፍርድ ቤት ተከሣሾች መከላከያ ሣያስፈልጋቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 መሠረት በነሳ እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡ ዓቃቤ ሕግ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ራሱ የአመልካችን መከላከያ ከሰማ በኋላ ከላይ የተሰጠቀሰውን የሕግ ድንጋጌ በተመላለፍ ወንጀል የፈፀመች ጥፋተኞች ናቸው በማለት ዮሴፍ ከበደ በሰባት ዓመት ጽኑ እስራት፣ አመልካች በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት እንድትቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት ያቀረበች ሲሆን ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረበችው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዮሴፍ ከበደ የግል ተበዳይን እንዲደፍር በመላው ሀሣቤና በድርጊት ያደረግሁት አስተዋጽኦ ስለመኖሩ የቀረበብኝ ማስረጃ ሣይኖር አላግባብ ጥፋተኛ ተብዬ መቀጣቴ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ጠይቃለች፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ዮሴፍ ከበደ የግል ተበዳይን እንዲደፍራት ሁኔታውን በማመቻቸት ተሣትፋለች፡፡ ይህንንም በማስረጃ ያስረዳንበት ስለሆነ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረትዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ሐምሌ 10 ቀን 2001 ዓ.ም. በጽሁፍ ባቀረበው መልስ ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ዮሴፍ ከበደ የግል ተበዳይን አስገድዶ ሲደፍር አመልካች የወንጀሉ ተካፋይ በመሆኗን ዓቃቤ ሕግ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 33 እና የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 25 ድንጋጌዎች መሠረት በማስረዳት የአመልካችን ጥፋተኝነት አረጋግጧል ወይስ አላረጋገጠም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓቃቤ ሕግ ክስ ሲያቀርብ ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜና ቦታ እንዲሁም ተከሣሾቹ ከአንድ በላይ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው በወንጀሉ ያላቸውን ተካፋይነት በዝርዝር መግለጽ ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 111 ድንጋጌዎች የተደነገገ ሲሆን ዓቃቤ ሕግ ይህንን በክስ የተገለፀውን ፍሬ ጉዳይ አጥጋቢ በሆነ ማስረጃ የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑን ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 እና 149 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የግል ተበዳይን ወ/ሪት ብርቱካን ዱባለን መድፈሩ ተረጋግጦ በፍርድ የተቀጣው ዮሴፍ ከበደ የአመልካች ባል ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ ዮሴፍ ከበደ ወ/ሪት ብርቱካን ዱባለን የደፈራት ነሐሴ 24 ቀን 1998 ከምሽቱ አራት ሰዓት በአመልካች መኖሪያ ቤት ውስጥ እንደሆነ የገለፀ ሲሆን በጉዳዩ የምስክርነት ቃል የሰጠችው የግል ተበዳይ አመልካች ጊንቢ ከተማ እንሂድ ብላት አብረው ሄደው ዕቃ እንደገዙና ከዚያም በምሽት አመልካች በመኪና ትኬት ቆርጣ ከመኪናው ጋቤና ተቀምጠው እንደመጡና አመልካች እቤቷ አጠገብ ስትደርስ ወርዳ ዕቃውን አያይዥኝ ብላ ጠይቃ እቤት እንደገባችና የአመልካች ባል ዮሴፍ ከበደ ከምሽቱ ስምንት ሠዓት ሲሆን የአስገድዶ መድፈር ወንጀል እንደፈፀመባት የመሰከረች መሆኑን ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የአማርኛ ትርጉም ለመረዳት ችለናል፡፡ ሌሎቹ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የጽሁፍ ማስረጃ አመልካች የወንጀል ተካፋይ ስለመሆኗ የሚያስረዱ አይደሉም፡፡

አመልካች ተካፋይ ሆናበታለች ተብላ የተከሰሰችበት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በወንጀል ሕግ ቁጥር 32 ድንጋጌዎች መሠረት አመልካች ተካፋይ ለመሆን የማትችልበትና ወንጀሉ በተቃራኒው ጾታ (ወንድ) ሊፈጸም የሚቻል በመሆኑ ከጅምሩ ዓቃቤ ሕግ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና አንቀጽ 630 በመጥቀስ የቀረበው ክስ የአመልካች የወንጀል ተካፋይነት ባግባቡ የሚገልጽ አይደለም፡፡ አመልካች በወንጀሉ ተካፋይ ነበረች ለማለት ዓቃቤ ሕግ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33 የተነገገውን ሁኔታ በአጥጋቢ ማስረጃ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33 መሠረት አዲት ሴት ሌላኛዋ ሴት ለተፈፀመባት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ተካፋይ ሆናለች ብሎ ለመክሰስና ጥፋተኛ ለማሰኘት ሴትዮዋ በሙሉ ፈቃዷና ዕውቀቷ የወንጀሉ ተካፋይ የነበረች መሆኑን ከሣሽ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ዓቃቤ ሕግ አመልካች ባሏ የግል ተበዳይን አስገድዶ ሲደፍር በሙሉ ፈቃዷና ዕውቀቷ የወንጀሉ ተካፋይ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረበው ብቸኛ ማስረጃ የግል ተበዳይ የሰጠችው የምስክርነት ቃል ሲሆን ምስክሯ አመልካች ጊንቢ ሃኪም ቤት አብራት እንድትሄድ ጠይቃት ቀን ጊንቢ ከተማ አብረው የዋሉ መሆኑን ከምሽቱ ሶስት ሠዓት አካባቢ የተመለሱና አመልካች የገዛችው ዕቃ ስታወርድ ተሣፍራበት የነበረው መኪናው ጥሏት የሄደ መሆኑን ከምሽቱ ሶስት ሰዓት አመልካችና የአመልካች ባል ዮሴፍ ከበደ ከቤታቸው ያስገቧት መሆኑን ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሲሆን ዮሴፍ ከበደ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የፈፀመባት መሆኑን የመሰከረች መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡፡ ይህንንም ስንመለከተው አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር ጊንቢ ከተማ ሄዳ የዋለችው እና አምሽተው የመጡት ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት በመነሳት ባሏ ዮሴፍ ከበደ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል እንደሚፈጽምባት ሙሉ እውቀት የነበራትና በሙሉ ፈቃደኝነት በወንጀሉ ስራ ተካፋይ መሆኗን የሚያስረዳ የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ አይደለም፡፡ ይልቁንም በግል ተበዳይ ላይ ዮሴፍ ከበደ አስገድዶ መድፈር ወንጀል በፈጸመበት ጊዜ ከሌሊቱ 8 ሰአት አመልካች ያደረገችው ተሣትፎ ያለ ስለመሆኑ የግል ተበዳይ ለመመስከሯ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የአስገድዶ መድፈር ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ማለትም ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት አመልካች የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33 በሚደነግገው መሠረት በሙሉ ፈቃዷና ዕውቀቷ በወንጀሉ ሥራ ያልተካፈለች መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ስለሆነም ዓቃቤ ሕግ በቂ ማስረጃ በማቅረብ አመልካች ባለቤቷ በሌሊት ስምንት ሠዓት ጓደኛዋ በሆነችው የግል ተበዳይ ላይ የፈፀመው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በሙሉ ፈቃዷና ዕውቀቷ ተካፋይ የነበረች መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በወንጀሉ ተካፋይ ልትሆን የምትችልበትን ልዩ ሁኔታና የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 33 ድንጋጌ ሣያገናዝብ አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር ጊንቢ ከተማ ውላ የመጣች መሆኑን የአስገድዶ መድፈር ወንጀሉን ለማመቻቸት ነው የሚለውን ግምታዊ መደምደሚያ በመመልከት ብቻ አመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ከላይ የዘረዘርናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና በስር ችሎት ይህንን ግድፈት ሣያርሙ ማለፋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት ስለ አመልካች የሰጡት ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች ባለቤቷ አቶ ዮሴፍ ከበደ ጥፋተኛ ሆኖ በተቀጣበት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በሙሉ ፈቃዷና ዕውቀቷ ተካፋይ ስላልሆነች በነፃ ትሰናበታለች ብለናል፡፡
4. አመልካች ላይ ተሰጥቶ የነበረው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ የተሻረ መሆኑ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡ አመልካች በዋስትና ያስያዘችው ገንዘብ ካለ ይመለስ፡፡
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42703

ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ፋሲል ብርሃኑ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ዓቃቤ ሕግ /የኦሮሚያ ክልላዊ ብሔራዊ መንግስት/ - አልቀረቡም

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር ችሎት አመልካች በተወሰነበት የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሣኔ ላይ ባቀረበው ማመልከቻ መነሻነት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይህን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ዓቃቤ ሕግ በአመልካቹ ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ በ1/8/2000 ዓ.ም በተሻፈ ክስ አመልካቹ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543(3) በመተላለፍ የካቲት 8 ቀን 2000 ዓ.ም በግምቱ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ በጂማ ዞን ስኮሩ ወረዳ በቲሮ ቀምቢ ቀበሌ ውስጥ ኬላ ጐሼ በሚባል ቦታ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-42631 አ.አ የሆነ አይሱዚ የሕዝብ ማመላለሻ መኪና ያለጥንቃቄ ሲያሽከረክር መኪናው ተገልብጦ መኪናው ውስጥ ሲጓዙ የነበሩትን ሁለት ሰዎች በቸልተኝነት ገድሏል በማለት የወንጀል ክስ መስርቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ሶስት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን፣ የትራፊክ ኘላንና የመኪናው የቴክኒክ ምርመራ መግለጫ ከተቀበለ በኋላ ተከሣሹ እንዲከላከል በማዘዙ ሁለት የመከላከያ ምስክሮችንም ሰምቷል፡፡

ፍርድ ቤት የቀረቡት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ከጂማ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ ላይ እያለ ኩርባ ቦታ ላይ ሲደርሱ መገልበጡን አረጋግጠዋል፡፡ ከእነዚህ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች አንደኛው መኪናው በመካከለኛ ፍጥነት ይጓዝ እንደነበር ሲመሰክር ሁለተኛው የመኪናውን ፍጥነት መገመት እንዳልቻለ ገልጿል፡፡ ሦስተኛው ምስክር ግን ተከሣሹ በፍጥነት ሲያሽከረክር እንደነበርና ፍጥነቱን ሳይቀንስ ኩርባው ላይ በመድረሱ መኪናው መገልበጡን ገልጿል፡፡ ሦስቱም ምስክሮች በዚህ ምክንያት ሁለት ተሳፋሪዎች መሞታቸውንም መስክረዋል፡፡ የተከሣሹ ሁለት የመከላከያ ምስክሮችም እንደዚሁ በመኪናው ተሳፍረው ይጓዙ እንደነበረ ገልፀው በክሱ በተገለፀው ቦታ ላይ ሲደርሱ አንድ በሬና እረኛ ወደ መንገዱ ድንገት ስለገቡበት እነሱን ለማዳን ሲል ተከሣሹ መኪናውን ኩርባው ላይ ከቀኝ ወደ ግራ ሲጠመዝዝ መኪናው ተንሸራትቶ መገልበጡንና በዚህ ምክንያት ሁለት ሰዎች መሞታቸውን መስክረዋል፡፡ ፍጥነቱን በሚመለከት አንደኛው ምስክር በጥሩ ሁኔታ በመንገዝ ላይ እንደነበር ሲመሰክር ሌላኛው ግን በግምት ከ50- 60 ኪ.ሜ በሰዓት ይጓዝ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት ይህን በግራ ቀኙ የቀረበውን ማስረጃ ከተመለከተ በኋላ ተከሣሹ ኩርባ ላይ ከ50—60 ኪ.ሜ በሰዓት በመጓዙ ድንገት የገቡበትን በሬና እረኛ ለማትረፍ ብሎ ወደጐን ሲይዝ መኪናው ተንሸራቶ አደጋው ሊደርስ እንደቻለ ተረድቻለሁ በማለትና ተሳፋሪዎቹ ሊሞቱ የቻሉትም ተከሣሹ ቀስ ብሎ መንዳት በነበረበት ቦታ ላይ በፍጥነት በማሽከርከሩ ነው በማለት ተከሣሹ የወንጀል ሕጉን 543(3) በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው ብሏል፡፡ የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላም በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እና 10,000(አስር ሺህ ብር) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

ተከሣሹ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረቡ የጥፋተኝነት ውሣኔን አፅንቶ ቅጣቱን ወደ ሦስት ዓመት ጽኑ እስራትና አምስት ሺ ብር መቀጮ ዝቅ እንዲልለት አድርጓል፡፡ የኦሮሚያ የሰበር ችሎት ጉዳዩ በአቤቱታ ቀርቦለት በድምፅ ብልጫ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተገኘበትም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ በዚህ ሁኔታ ጥፋተኛ ተብሎ የሦስት ዓመት እስር 5,000 ብር (አምስት ሺህ ብር) መቀጮ የተጣለበት ተከሣሽ ታህሣስ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን በማተት ውሣኔው እንዲሻርለት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚህ ሰበር ችሎት አጥብቆ የሚከራከረው መኪናው የተገለበጠው ድንገት ኩርባ ላይ የገቡትን አንድ እረኛና አንድ በሬ ለማዳን በማሰብ መኪናውን ወደ ግራ አቅጣጫ ስለጠመዘዝኩት ነው፣ በመሆኑም በዚህ ሂደት ህይወታቸው የጠፋው ሁለት ተሳፋሪዎች በአደጋ ምክንያት ሞቱ ከሚባል በስተቀር በኔ ቸልተኝነት ሞቱ ተብሎ እኔ ጥፋተኛ ልሆን አይገባኝም በማለት ነው፡፡ ከዚህ በላይ ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543(3) እግረኛን ገጭቶ ለገደለ እንጂ መኪና ተገልብጦ ሰው ለሞተበት አሽከርካሪ ተፈፃሚ ሊሆን አይገባውም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተሳፋሪዎቹ የሞቱት በአሽከርካሪ ቸልተኝነት ነው ሊባል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን የሕግ ነጥብ ለማጣራት ጉዳዩ ዓቃቤ ሕግም ባለበት ሁለቱ ባለጉዳዮች የቃል ክርክር እንዲያደርጉበት ተደርጓል፡፡

የሰበር ችሎት ከላይ የተጠቀሰው አጠቃላይ የክርክሩ ሂደት አግባብ ካላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና አመልካችና መልስ ሰጪ በዚህ ችሎት ቀርበው ካሰሙት የቃል ክርክር ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡ ከቀረበው ፍሬ ነገርና ከተወሰነው ውሣኔ አንፃርም አመልካችን በወንጀል ጥፋተኛ ለማለት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 543(3) የተጠቀሱት መስፈርቶች ተሟልቷል? ወይስ አልተሟሉም? የሚለውን ነጥብ አጣርቷል፡፡ አመልካቹ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተቀጣ በመሆኑ በሕጉ ቸልተኝነት የሚያቋቁሙ መስፈርቶች መሟላት አለመሟላታቸውን አጣርቷል፡፡ ይህ ችሎት በዋናነት የመረመረው የሕግ ነጥቡን ብቻ ቢሆንም የሕጉን አግባብነት በትክክል ለመመዘን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በቅድሚያ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩ በሥር ፍ/ቤቶች ሲታይ አመልካች ከጂማ ወደ አዲስ አበባ ሲጓዝ መኪናው መገልበጡና ከተሳፋሪዎች መካከል ሁለቱ መሞታቸው ተረጋግጧል፡፡ መኪናው ሊገለበጥ የቻለው መኪናው ከ 50 — 60 ኪ.ሜ በሰዓት ሲጓዝ ከፊት ለፊት አንድ እረኛ በሬውን ለመመለስ በቅርብ ርቀት ስለገባበት እንደሆነም በስር ፍ/ቤቶች ግንዛቤ ተወስዶበታል፡፡ እረኛው መኪናው መንገድ ውስጥ የገባበትና መኪናው የተገለበጠበት ቦታ ኩርባ እንደሆነም በሂደቱ ተጣርቷል፡፡ መኪናው የቴክኒክ ብልሽት ያልነበረበት መሆኑም ከቀረበው የቴክኒክ ሪፖርት ተረጋግጦአል፡፡ እነዚህ በፍርዱ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ሲሆኑ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ሕግ ይዘት ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

አመልካቹ በዓቃቤ ሕግ ክስ የተመሰረተበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(3)"ን" በመተላለፍ ሁለቱ ሰዎች በቸልተኝነት ገድሏል በማለት ነው፡፡ በመሆኑም የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የተጠቀሰውን ሕግ የሚያቋቁሙ መሆን አለመሆናቸው ለማረጋገጥ ሕጉ ቸልተኝነት አለ የሚለው ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57 በግልፅ እንደሰፈረው "ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆንም" በአንፃሩ አንድ ሰው "የፈፀመው ድርጊት በሕግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈፀመ ወይም የደረሰ ሆኖ ሲገኝ በወንጀል ሕግ ሊፈረድበት አይገባውም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 57(2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የሕጉ አጠቃላይ አባባል መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ድርጊቱ የተፈፀመው ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት መሆኑን ነው፡፡ ድርጊቱ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑ ማስረጃ ካልቀረበ ወይም ድርጊቱ ከአቅም በላይ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በተከሣሽ በኩል ከቀረበ የተከሰሰውን ሰው በወንጀል ሕግ ጥፋተኛ ብሎ መፍረድ ከሕጉ መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ቸልተኛ ነበር ወይስ አልነበረም የሚለው ጥያቄ በወንጀል ሕጉ በአንቀፅ 59 የሰፈረውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ የዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ አንድ አሁን ለተያዘው ጉዳይ በቀጥታ አግባብነት ያለው በመሆኑም የሕጉን ይዞታ እንዳለ ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው፡፡ "59(1) ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለው፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(ሀ) ድርጊቱ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን፣ ወይም

(ለ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ነው።"

" የእንግሊዘኛው ትርጉም ደግሞ እንደሚከተለው ይደነግጋል Article 59

1) A person is deemed to have committed a criminal act negligently where he acts:
   a) by imprudence or in disregard of the possible consequences of his act while he was aware that his act may cause illegal and punishable consequences; or
   b) by a criminal lack of foresight or without consideration while he should or could have been aware that his act may cause illegal and punishable consequences."

በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው ውጤቱን እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ደግሞ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ውጤቱን ማወቅ ይችል ነበር ማለት ሲቻል ነው። በመሆኑም ቸልተኝነት አለ ለማለት ሕጉ የሚጠቀምበት ዋነኛ መስፈርት የተከሰሰው ሰው በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ነው። ድርጊቱን የፈፀመው ሰው የነበረው ዕውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባው ዕውቀትና ግንዛቤ የሚመዘነው የሰውዬው ዕድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃው ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነም የሕጉ አንቀፅ 59(1) ይደነግጋል።

አሁን በቀረበልን ጉዳይ አመልካች የሚከራከረው ከላይ የተቀጠሱት መስፈርቶች ስላልተሟሉ በቸልተኝነት ሰው በመግደል ጥፋተኛ ልሆን አይገባም በማለት ሲሆን ዓቃቤ ሕግ በሌላ በኩል የሕግ መስፈርቶች ተሟልተዋል የሚል ሙግት አቅርቦአል። ጉዳዩን መጀመሪያ ያየው የጂማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካችን በቸልተኝነት ሰው በመግደል ጥፋተኛ ያለው ቢሆንም የቀረቡለትን ማስረጃዎች በዝርዝር ሕጉ ካስቀመጠው መስፈርት አንፃር ስለመመዘኑ በፍርዱ በግልፅ ያሰፈረው ነገር የለም።

ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ጥፋተኛ ነህ የተባለው ከጂማ ወደ አዲስ አበባ በአመልካች አሽከርካሪነት ሲደረግ በነበረ ጉዞ መኪናው በመገልበጡና ሁለት ተሳፋሪዎች በመሞታቸው ነው። መኪናው ሲገለበጥ ከ50 - 60 ኪ.ሜ በሰዓት ፍጥነት የነበረው መሆኑ ምስክሮች የገለፀ ሲሆን በጉዞ ላይ እያሉ ኩርባ ላይ ሲደርስ አንድ እረኛ ከበሬ ጋር ወደ መንገዱ እንደገቡበትም ተመስክሯል። መኪናው ሊገለበጥ የቻለው ሹፌሩ እረኛውንና በሬውን ላለመግጨት ሲል ወደ ግራ ሲጠመዘዝ መኪናው በመንሸራተቱ ነው። በዚህ ሁኔታ የተከሰተው የሁለት ሰዎች ሞት አመልካችን ሊያስጠይቅ የሚችለው በአሽከርካሪነት ስራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 59(1) የተገለፀውን ያሟላ እንደሆነ ነው።

ከማህደሩ ዝርዝር ለመገንዘብ እንደቻልነው ሹፌሩ /አመልካች/ መኪናውን ከ50-60 ኪ.ሜ በሰዓት ያሽከረክር ነበር የሚል ምስክርነት የተሰጠው በባለሞያ አይደለም። መኪናው በዚህ ፍጥነት ይጓዝ ነበር ያሉት መኪናው ውስጥ የነበሩ አንድ የዓቃቤ ሕግ ምስክር እና አንድ የከሳሽ ምስክር ናቸው። በመሰረቱ እነዚህ ሁለት ተሳፋሪዎች መኪናው ይጓዝበት የነበረውን ፍጥነት በትክክል ይናገራሉ ብሎ መገመት የሚቻል አይደለም። በመሆኑም ፍ/ቤቱ መኪናው በዚህ ፍጥነት ይጓዝ ነበር በማለት ለደረሰበት መደምደሚያ የሚያበቃ በቂ ማስረጃ አልቀረበለትም።

ከዚያም በላይ መኪናው ከ50 — 60 ኪ.ሜ በሰዓት ይጓዝ ነበር እንኳን ቢባል ከከተማ ውጪ በነበረ ጉዞ በዚህ ፍጥነት ማሽከርከር በአሽከርካሪው በኩል ጥንቃቄ ጉድለት ነበር ለማለት የሚያስችል አሳማኝ ማስረጃ አልቀረበም መኪናው የሕዝብ ትራንስፖርት በመሆኑ ከጂማ ወደ አዲስ አበባ ሲጓዝ በዚህ ፍጥነት መንቀሳቀሱ ጥፋት ሊባል የሚችል አይደለም። መኪናው በተገለበጠበት ቦታ አካባቢ የፍጥነት ጣሪያ የነበረ መሆኑ አልተረጋገጠም ወይም ከጅማ እስከ አ/አ ባለው መንገድ ወይም በአጠቃላይ ከከተማ ውጪ በሚደረግ ጉዞ ከ50 ኪ.ሜ በሰዓት በላይ መንዳት ክልክላ ስለመኖሩም አልተገለፀም። መኪናው ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ማስረጃ የቴክኒክ ችግር እንዳልነበረበት በመረጋገጡ በመኪናው ልዩ ባህርይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት ተከሳሹ ከ50 ኪ.ሜ በሰዓት በታች መንዳት ይጠበቅበት ነበር ሊባል አይችልም። ስለሆነም መኪናው ከመገልበጡ በፊት ሹፌሩ መፈፀም የነበረበት የጥንቃቄ እርምጃ አለመወሰዱ የሚያሳይ ነገር የለም።

መኪናው በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ አንድ እረኛ ድንገት ከገባበት አሽከርካሪው ማድረግ የሚጠበቅበትን ፈፅሟልን? የሚለው ጥያቄ መልስ የሚፈልገው ሌላው ነጥብ ነው። ኩርባው ላይ ሲደርስ በቅርብ ርቀት እረኛና በሬ መኪናው መንገድ ላይ ሲገቡ አሽከርካሪው የተለያዩ አማራጮች እንደነበሩት መገመት ይቻላል። አንደኛው ዕረኛውንና በሬውን ገጭቶ ማለፍ ነው፣ ሁለተኛው ወደ ቀኝ ለመጠምዘዝ እረኛውን ከነከብቱ ለማዳን መሞከር ነው። በማስረጃ እንደተረጋገጠው መኪናው ወደቀኝ ቢጠመዘዝ ገደል ውስጥ ይገባ ነበር። በመሆኑም አሽከርካሪው ይህንን አማራጭ አለመውሰዱ የጥንቃቄ ጉድለት ፈጽሟል ሊያሰኘው አይችልም። ወደግራ በመጠምዘዝ መንገድ ውስጥ ድንገት የገባውን ሰው ለማዳን መሞከሩና እርግጥም ይህንን ሰው ከሞት አደጋ መታደጉም የጥንቃቄ ጉድለት ሊባል አይችልም። እንዲያውም ሰውዬውን ለማዳን ምንም ሙከራ ሣያደርግ ፊት ለፊት የሚያየውን ሰው ጨፍልቆ ቢያልፍ ከፍ ያለ ወንጀል ይፈፅም እንደነበረ ግልፅ ነው። አመልካች የቀረውን የመጨረሻ አማራጭ በመጠቀም መኪናውን ወደግራ ሲጠመዝዝ መኪናው እንደሚገለበጥና ከተሳፋሪዎች መካከል ከፊሎቹ እንደሚሞቱ ያውቅ ነበር? ይህንስ እያወቀ ነው ድርጊቱን የፈፀመው? አያውቅም ከተባለስ የወሰደው አማራጭ ለሰዎች ሞት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ነበረበት ማለት ይቻላል? የሚሉት ጥያቄዎች ቸልተኝነት ነበረ ወይም አልነበረም ለማለት መመለስ የሚገባቸው ጥያቄዎች ናቸው። በመሰረቱ ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት አመልካችን የቸልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል ሊያሰኝ የሚችል ማስረጃ ወይም የሞያ አስተያየት በዓቃቤ ሕግ በኩል አልቀረበም። በበኩላችን ከፊት ለፊት ካጋጠመ አደጋ ለመዳን መኪና ወደ ቀኝ ይሁን ወደግራ ሲጠመዘዝ ሁሌም ይገለበጣል ወይም የመገልበጥ ዕድሉ ሰፊ ነው ለማለት አልቻልንም። በመሆኑም አሽከርካሪው የመኪናውን መገልበጥ ቀደም ብሎ ያውቅ ነበር ለማለት የሚቻል አይደለም። መኪናው ሊገለበጥ እንደሚችል ማወቅ ነበረበት ማለትም የሚቻል አይደለም። በመሆኑም አሽከርካሪው የመኪናው መገልበጥ በጉዞ ላይ በተፈጠረና ከአሽከርካሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ የዕረኛው ድንገት መግባት የተፈጠረ አደጋ (accident) እንጂ በአሽከርካሪው ቸልተኝነት የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ነው ማለት አልቻልንም። ከተሳፋሪዎቹ መካከል የሁለቱ መሞትም የዚሁ አደጋ ውጤት እንጂ የቸልተኛ ድርጊት (negligent act) ውጤት ነው ማለት አልቻልንም። የሰው መሞት በሕግ ሊያስጠይቅ እንደሚችል ግልፅ ነው። ሆኖም ይህ ውጤት በሕግ ሊያስጠይቅ የሚችለው ለሞቱ ምክንያት የሆነው ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ነው። ጥፋተኛ የሚሆነው ደግሞ ድርጊቱ ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ እንደሆነ ነው። አሁን በቀረበልን ጉዳይ የሁለት ተሳፋሪዎች ሞት የተከሰተው በአሽከርካሪው ቸልተኝነት ሳይሆን በድንገተኛ አጋጣሚ በሆነ የመኪና መገልበጥ አደጋ ነው።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የአሁኑን አመልካች በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ያለው የቀረበለትን ማስረጃ ከሕጉ ጋር በተገቢው ሁኔታ ሳያገናዝብ ነው። ለውሣኔው መሰረት ያደረገው የመኪናው መገልበጥ ለሁለት ሰዎች ሞት ምክንያት መሆኑን ብቻ ነው። አመልካቹ ሰዎቹ የሞቱት በአደጋ (accident) እንጂ በቸልተኛ የወንጀል ድርጊት (negligent criminal offence) አይደለም እያለ ከመጀመሪያው ጀምሮ የተከራከረ ቢሆንም ፍ/ቤቶቹ ለዚህ ክርክር ትኩረት በመስጠት በአደጋና በቸልተኛ ድርጊት መካከል ያለውን ልዩነት አልመረመሩም በዚህም ምክንያት በሕጉ መንፈስ ወንጀለኛ መባል ያልነበረበት ሰው ጥፋተኛ በማለት በእስርና በገንዘብ እንዲቀጣ ውሣኔ መስጠታቸው የሕጉን ግልፅ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ስላገኘነው በዚህ ጉዳይ የጂማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትና ሰበር ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ መሻር አለበት ብለናል።

ው ሣ ኔ

1. የጂማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 10769 ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 71726 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ሰበር ችሎት በወ/ቁ 70164 ታህሣሥ ቀን 2001 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ተሽረዋል።
2. አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543(3) ተጠቅሶ ከቀረበበት ክስ ነፃ ነው ብለናል።
3. አመልካች በዚሁ ችሎት ትዕዛዝ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ ካለ ይመለስላቸው።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36320

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘውዴ ገ/ስላሴ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሕይወት ባሕታ - ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በሌሎች 4 ተከሣሾች ላይ ባቀረቡት ክስ ተከሣሾች መብት ሣይኖራቸው የሚኙ አባቴን ቤትና ቦታ ስለያዙ ለቀው ያስረክቡኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ተከሣሾችም ተከራይና አከራይ በመሆናቸው የቤቱ ባለቤት ናቸው የተባሉት የአሁኗ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ተተክተው እንዲገቡ ተደርጎ ተጠሪዋ ቤቱና ቦታው የሣቸው መሆኑንና አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያላቸው ለመሆኑ አግባብ ያለው ማስረጃ ስላላቀረቡ ክሱ ውድቅ እንዲደረግባቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮችን ከሠማ በኋላ ቤቱና ቦታው የአመልካች አባትና የሚስታቸው የአሁኗ ተጠሪ የጋራ ንብረት በመሆኑ ተጠሪ የአመልካች አባት ድርሻ የሆነውን ግማሽ ንብረት ለአመልካች ታካፍል በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትም የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በድምጽ ብልጫ አጽድቆታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ላይ በድጋሚ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ እያከራከረ ያለው የማይንቀሳቀስ ንብረት በመሆኑ ክስ ሊመሠርቱ ይገባ የነበረው የቤትና የቦታውን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ በማቅረብ ነው በማለት ክሱን ለማቅረብ በንብረቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን አላስረዱም ሲል የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተጠሪ ቦታና ቤቱን የያዙት የአባቴ ባለቤት ስለሆኑ እንጂ እራሳቸው ተመርተው አይደለም፤ ቦታውና ቤቱ አሁንም ድረስ በአባቴ የሚጠራ ነው፤ በፈረስ ማይ ከተማ እስካሁን ድረስ ለቤትና ለቦታ የተሰጠ ሰነድ የለም፤ ምክንያቱም ከተማው ራሱ እንደከተማ እየተዋቀረ ያለው አሁን ነው፤ የሚል ነው፡፡ ተጠሪም ለሰበር አቤቱታው መልስ እንዲሰጡ ተደርጎ በሰጡት መልስ አመልካች በንብረቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን አላስረዱም፤ በስር ያልተነሣ ክርክር አሁን ሊነሳ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ክስ በመሠረቱበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም ወይ? የሚለው ነጥብ ሊመረመር ይገባል፡፡

አመልካች በክሣቸው የአባታቸውን ቤት ተጠሪ እንዲያስረክቧቸው ጠይቀዋል፡፡ በእርግጥ አንድ ሰው ክስ በሚያቀርብበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን ካላረጋገጠ በስተቀር ክስ ማቅረብ እንደማይፈቀድለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ክርክር ባስነሣው ቤትና ቦታ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ንብረቱ የአባታቸው መሆኑን ያስረዱልኛል ያሏቸውን የሰው ምስክሮች አቅርበዋል፡፡ የሰበር ችሎቱ ግን ክርክር የሚደረግበት ንብረት የማይንቀሣቀስ ንብረት በመሆኑ መብት መኖሩ ሊረጋገጥ የሚገባው የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ወይም ሰነድ በማቅረብ ነው በማለት ወስኗል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 ላይ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ምስክር ወረቀቱ ለተሠጠበት ንብረት ባለሃብት ሆኖ እንደሚቆጠር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ለአንድ ቤትና ቦታ የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዚሁ ንብረት ባለቤት ለመሆኑ ሕጉ ግምት ይወስዳል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ክርክር የተነሣበት ንብረት የሚገኝበት የፈረስ ማይ ከተማ ለማንኛውም ቤትና ቦታ የሰነድ ማስረጃ ያልሰጠ መሆኑን ጠቅሰው ያቀረቡትን ክርክር ተጠሪም አላስተባበሉም፡፡ ተጠሪም ራሣቸው ቢሆኑ ቦታው የራሣቸው ለመሆኑ ግብር የተከፈለበት ደረሰኝ፣ በሌላ መዝገብ የተሰጠ ውሣኔ እና የሰው ምስክር ከማቅረብ በቀር የቤቱና የቦታው ባለሃብት ለመሆናቸው የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አላቀረቡም፡፡ ይህም የሚያሣየው ክርክር የተነሣበት ቤትና ቦታ የሰነድ /የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት/ ያልወጣለት መሆኑን ነው፡፡ ከፍ ሲል የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው የንብረቱ ባለሃብት ለመሆኑ ሕጉ ግምት ይወስዳል ከማለት በቀር ማንኛውም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነት በሌላ መንገድ ሊረጋገጥ እንደማይችል አያመለክትም፡፡ በአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ብዙ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አልተዘጋጀላቸውም፡፡ ስለዚህ አመልካች ክርክር የተነሣበት ንብረት ላይ በተመለከተ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ባለማቅረባቸው በንብረቱ ላይ ጥቅም ወይም መብት የላቸውም ሊባሉ አይገባም፡፡

በሌላ በኩል ግን ክርክር የተነሣበት ቤትና ቦታ ያለበት አካባቢ በከተማነት እየተዋቀረ መሆኑ የተገለጸ ስለሆነ ይህ ቦታ ቀደም ሲል የማን እንደነበር፣ በአሁኑ ጊዜ ለማን እንደተሰጠ፣ በአሁኑ ጊዜ በስሙ የተመዘገበው ሰው ቦታውን እንዴት እንዳገኘ ከሚመለከተው የከተማ አስተዳደር ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳዩ መጀመሪያ የቀረበለት ፍ/ቤት የቦታው ባለሃብት ማን እንደሆነ በሚገባ አጣርቶ ሊወስን ይገባል ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 21523 ታህሣሥ 11 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ክርክር የተነሣበት ቤትና ቦታ ቀደም ሲል የማን እንደነበር፣ በአሁኑ ጊዜ ለማን እንደተሰጠና በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ከሚመለከተው የከተማው አስተዳደር አካል ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሠረት ለትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35003

ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ አሸናፊ ዓብዱልቃድር - ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ሽቶ ኢብራሂም/ 4 ሰዎች/ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ሟች አባታቸው በኑዛዜ ያወረሷቸውን ቤት ተጠሪዎች እንዲያካፈሏቸው ጠይቀዋል አንደኛ ተጠሪ የሚች ሚስት በሕይወት እያሉ የውርስ ንብረት ክፍፍል ሟች በኑዛዜያቸው ስለገለፁ ክፍፍሉ ሊፈፀም አይገባም በማለት ተጠሪዎች መልስ ሰጥተዋል ፍ/ቤቱም የውርስ ንብረት አጣሪ አቋቁሞ የውርሱ ንብረት እንዲጣራ አድርጎ የውርስ ንብረት የሆነው በሻሸመኔ ከተማ ቀበሌ 08 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 544 የሆነ በ500 ካ.ሜ. ላይ የሠፈረ ቤት መሆኑን ተረጋግጦ ቀርቦለታል፡፡ ከዚህም በኋላ ይኸው ቤት በባለሙያ ተገምቶ ግምቱ ብር 41,078.77 (አርባ አንድ ሺህ ሰባ ስምንት ብር ከሳሰባት ሳንቲም)መሆኑ ተገልጿል፡፡ ፍ/ቤቱም አንደኛ ተጠሪ የሚች ሚስት በመሆናቸው የቤቱ ግማሽ የሟቸው ድርሻ ነው የግምቱን ግማሽ ግን አመልካችና ቀሪዎቹ ተጠሪዎች ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት በመጀመሪያ ለምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀጥሎም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኛቸው ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል በመጨረሻም አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ነው የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ አባቴ ቦታ ላይ በራሴ ገንዘብ የሰራሁት ቤት ግምት ውስጥ አልገባልኝም ቤቱ በገበያ ዋጋ አልተገመተም የሚል ነው ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ መኖሩን በማመን ተጠሪዎች ቀርበው እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡ ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ከተባለው ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው አንደኛ ተጠሪ የሚች ሚስት አመልካችና ቀሪዎቹ ተጠሪዎች ደግሞ የሚች ልጆችና ወራሾች ናቸው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የሚችና የአንደኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት በመሆኑ የቤቱ ግማሽ ለአንደኛ ተጠሪ ይገባል በማለት በሰጠው የውሣኔ ክፍል አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ ባለመኖሩ ውሣኔውን እንደተቀበሉት ይቆጠራል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች በአባታቸው ቦታ ላይ በራሣቸው ገንዘብ የሠሩት ቤት ከግምት ውስጥ ሣይገባ የክፍፍል ውሣኔ እንደተሠጠ ገልፀዋል፡፡ ይህ ቤት በሚች ስም የተመዘገበና ቤቱ የአመልካች ለመሆኑ ምንም ማስረጃ ያልቀረበ ምስክርም ያልተቆጠረ መሆኑን የሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት በውሣኔው አስፍሯል፡፡ በመሆኑም አመልካች ቤቱ በገዛ ገንዘባቸው የሠሩት መሆኑን ማስረዳት ሣይችሉ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌላው የአመልካች ቅሬታ የውርስ ንብረት በገበያ ዋጋ ሣይገመት በአነስተኛ ግምት ክፍፍሉ መፈፀሙ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ በሌላ አነጋጋገር የውርስ ንብረቱ በወራሾች መሃከል እኩል አልተከፋፈለም የሚል ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ክስ ያቀረቡት የውርስ ንብረቱን በሚች ኑዛዜ መሠረት ለመካፈል ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹም የቤቱ ግማሽ የአንደኛ ተጠሪ ድርሻ መሆኑንና ቀሪውን የሚች ግማሽ ድርሻ ልጆቹ እኩል እንደካፈሉ በሰጡት ውሣኔ በግራ ቀኙ የቀረበ ቅሬታ ባለመኖሩ ሚች ንብረቱን በዚሁ መሠረት እንዲካፈሉ የተናዘዙ መሆኑን ችሎቱ ግንዛቤ ወስዷል፡፡ ንብረቱን በዚሁ መሠረት ለመካፈልም የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት የንብረቱ ዋጋ በመሐንዲሶች የቀረበው ግምት ነው በማለት በዚሁ መሠረት ክፍፍሉን መወሰኑን ተረድተናል፡፡ የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ነው ማለት የሚቻለው ግን ቤቱን ለመስራት የወጣው ወጪ /book value/ ብቻ ሣይሆን ይልቁንም ቤቱ በወቅቱ ለገበያ በቀረበ ሊያወጣ የሚችለው ዋጋ /market value/ ነው በሥር ፍ/ቤት እንደተደረገው ቤቱ የተሠራበት ዋጋ ብቻ በባለሙያ ተገምቶ በቀረበው ግምት መሠረት ገንዘቡን መክፋፈሉ ንብረቱን የሚያስቀረው ወገን የበለጠ ጥቅም እንዲያገኝና በሌላው ወገን ላይ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ የእኩልነት መርህን የሚንድ ይሆናል፡፡ ስለሆነም የውርስ ንብረት ክፍፍሉ መፈፀም ያለበት በንብረት የገበያ ዋጋ መሠረት ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ንብረቱ ለመስራት የወጣውን ወጪ መሠረት በማድረግ ክፍፍሉን መወሰናቸው የእኩልነት መርህን የሚጥስ ሆኖ አግኝትነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት የመ/ቁ. ባልተጠቀሰ በ24/6/98 የሰጠው ውሣኔ የምዕ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09775 በ28/07/98 እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40405 በ4/9/98 የሰጡት ትእዛዞች እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 41006 በ07/04/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የውርሱ ንብረት በገበያ ዋጋ ተገምቶ በሚቀርበው ግምት መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈፀም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ጉዳዩ ለሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 36645

ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ረዳት ሳጂን አያኖ አንጀሎ - ቀረበ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ዓለሚቱ ጫሌቦ- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ/ በወላይታ ዞን በአረካ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ ንብረትነቱ የእራሷና የሟች ባለቤቷ የሆነውን በ270 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተሰራ ቤት በ26/10/94 በተጻፈ ውል ሸጣልኝ ቤቱን አስፋፍቼ ለመሥራት እንሰት ለመንቀል ስጀምር አላስነቅልም፣ ቤቱንም ቦታውንም አልሸጥኩም በማለት ሁከት የፈጠረችብኝ ስለሆነ ይሄው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አንደኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ቀርበው ሁከት ተፈጥሮበታል የተባለውን ቤት ለከሳሽ እንዳልሸጡና በውሉ ላይም እንዳልፈረሙ ከሳሽ በቤቱ ውስጥ የሚኖረው በተከራይነት መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል ሁለተኛ አመልካችም በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው የሟች አባታቸው ወራሽ መሆናቸውን ገልጸው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሽያጭ ለከሳሽ እንዳልተላለፈና በቤቱ ውስጥ በኪራይ እንደሚኖሩ ጠቅሰው ከአንደኛ ተከሳሽ ጋር ተመሳሳይ የሆነው ክርክር አቅርበው ክሱ ሊሰረዝ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የአረካ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሽ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ከአንደኛ ተከሳሽ የገዙት መሆኑን ቢገልጽም በአስረጂነት ያቀረቡት ሠነድ በአንደኛ ተከሳሽ ያልተፈረመበት መሆኑ ስለተረጋገጠና ከሳሽም እራሱ በሰነድ ላይ ስለመፈረሙ በዚህ ሁኔታ ሁከት ይወገድልኝ ተብሎ የቀረበው ክስ አግባብነት የለውም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ለጉዳዮ እልባት መስጠት የነበረበት ሁከት አለ ወይንስ የለም? ከሚለው ጭብጥ አኳያ መሆን ሲገባው የውሉን ሕጋዊነት በጭብጥነት ይዞ ጉዳዮን በመመርመር ውሉ በአግባቡ ስላልተደረገ ሁከት የለም በማለት ውሳኔ መስጠቱ በተገቢው አይደለም ካለ በኋላ ሁከት ስለመፈጠሩ በይግባኝ ባይ ማስረጃ መረጋገጡን መገንዘብ ስለሚቻል የተፈጠረው ሁከት ሊወገድ ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም ተጠሪዎች የይግባኝ ቅሬታቸውን በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙ አከራክሮ መልስ ሰጭ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ያቀረቡት በሕግ የማይጸና ውልን መሠረት አድርገው ስለሆነ ጉዳዮን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣኑ በተመለከተው የአረካ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሉ በሕግ አግባብነት ያልተቋቋመ ስለሆነ የቀረበው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ማለቱ አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ውሳኔ መሻሩ በአግባቡ አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመበትም በማለት የሰበር አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ያቀረቡት ክስ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ሆኖ ሳለ የቤት ሽያጭ ውሉ የሚጸና አይደለም ተብሎ መወሰኑ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ መጠራት እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሑፍ አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብስ አኳያ የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እነደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስበቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በሥር ፍ/ቤት አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት የመኖሪያ ቤት በውል ሸጠውልኝ ይህንኑ ቤት አስፋፍቼ ለስራት በነበረኝ ፍላጐት ሥራውን ስጀምር እንዳልሰራ የከለከሉኝ ስለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ነው፡፡

ይዞታው የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተነሳበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንዲመለስለት ወይም የተነሳው ሁከት እንዲወገድለት ዳኝነት መጠየቅ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ1149/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይዞታ ማለት ደግሞ አንድ ሰው አንድን ነገር በእጁ አድርጐ በእውነት የሚያዝበት ሆኖ ሲገኝ እንደሆነም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1140 ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ የሕጉ ድንጋጌ አኳያ አንድ ሰው በአንድ ነገር ላይ ባለይዞታ እንዲባል ነገሩ በእጁ መገኘት እንደሚገባውና የነገሩ በእጁ መገኘትም ይዞታ ያለው ስለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ አንደሆነ መገንዘብ ይቻላል እዚህ ላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ አንድ ሰው ንብረቱ በእጁ አድርጐ በእውነት የሚያዝበት የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ በእውነት የሚያዝበት የሚለው አባባል የሚያስገነዝበው ንብረቱን በእጁ አድርጐ መገኘቱ ብቻ ሳይሆን በዚህ ንብረት ላይ በእውነት ማዘዝ እንዲችል የንብረቱ አያያዝ ያልተጨበረበረና በማናቸውም መንገድ ሕገወጥ በሆነ ሁኔታ ያልተገኘ መሆን እንደሚገባው ነው፡፡

አመልካች ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ቤቱ የያዙት አንደኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል መነሻነት እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪም በበኩላቸው ቤቱን ለአመልካች እንዳልሸጡና በአመልካች በኩልም የሽያጭ ውል መኖሩን ያረጋግጣል ተብሎ የቀረበው ሠነድ በሕግ አግባብነት ያልተቋቋመ መሆኑን ገልጸው ይልቁንም ከሳሽ በቤቱ ውስጥ የሚገኙት በኪራይ ውል መነሻነት እንደሆነ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ የተጠሪ ክርክር ሁከት ተፈጥሮበታል የተባለው ቤት በተጭበረበረ አኳኋን አመልካች እጀ ሊገባ እንደቻለ መገንዘብ አይቻልም፡፡ በመካከላቸው ተደርጓል የተባለው ውል ተገቢውን የአጻጻፍ ሥርአት /Form/ ተከትሎ አልተደረገም ቢባል እንኳን ይህ ሁኔታ በእራሱ አመልካች ቤቱን በተጭበረበረ መንገድ እንደያዙትና በእውነት የሚያዙበት እንዳልሆነ የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ የውሉ ተገቢውን የአጻጻፍ ሥርዓት ተከትሎ አለመደረግ ይዞታው በተጨበረበረ መንገድ ስለመያዙ ወይንም በማናቸውም ሕገወጥ ሁኔታ ስለመያዙና አመልካችም በይዞታው በእውነት ሊያዙበት እንደማይችሉ ስለማያረጋግጥ በዚህ ረገድ ውሉ ጉድለት አለበት ከተባለ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1808(2) ላይ እንደተመለከተው ውሉ ፈራሽ ነው እንዲባል የክስ ምክንያት ከሚሆን በስተቀር ሁከት ይወገድልኝ ተብሎ በቀረበ ክስ ላይ ሊስተናገድ የሚችል አይሆንም ከዚሁ ጋር በተያያዘም አንደኛ ተጠሪ አመልካች ቤቱን ይዘው የሚገኙት በመካከላችን በተደረገው የቤት ሽያጭ ውል መነሻነት ነው በማለት የጠቀሱት ቤቱ በአመልካች በተጭበረበረ ሁኔታ እንዳልተያዘና በተገቢው መንገድ እንደተያዘና በእውነትም የሚያዙበት መሆኑን ይበልጥ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዮን በይግባኝ የተመለከተው የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በጭብጥነት ተይዞ መፈታት የሚገባው ጉዳይ ሁከት አለ ወይንስ የለም? የሚለው ነው በማለት በዚህ ጭብጥ ላይ ተመስርቶ ጉዳዮን በመመርመር በአመልካች ይዞታ ላይ ተጠሪ ሁከት ስለመፈጸማቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ይኸው ሁከት ይወገድ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ በእኛ በኩልም ተቀባይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ነገር ግን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የቤት ሽያጭ ውሉ በሕግ አግባብነት ስላልተቋቋመ በዚህ ውል ላይ ተመስርቶ የቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የለውም ሲል የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ ማጽናቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም በመ/ቁ/21070 የሰጠው ትእዛዝ እንደዚሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 20355 በ2/6/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሽረነዋል፡፡
2. የወላይታ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 06718 በ9/4/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
3. የግራ ቀኙ ወጪና ኪሣሳ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የ ሀ ሳ ብ ል ዩ ነ ት

እኔ በአምስኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አመልካች በተጠሪ ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ የማቅረብ መብት የለውም የሚል እምነት ያለኝ በመሆኑ ከሙያ አጋሮቼ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ፍሬ ጉዳይ ከላይ በአጭሩና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተጠቅሷል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ቤት በውል የገዛ መሆኑንና ቤቱንና ቦታውን ተረክቦ በእጁ ያደረገ መሆኑን ገልጾ የገዛሁትን ቤት አስፋፍቼ ለመሥራት ስሞክርና እንሰት በመንቀል ላይ እያለሁ ተጠሪ ስለ ከለከለከችኝ በይዞታዬ ላይ ሁከት እየፈጠረች ነውና ሁከቱ እንዲወገድ ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት አመልካች ከተጠሪው ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መነሻ ቦታውንና ቤቱን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1140 መሠረት በእጁ አድርጐ የያዘ መሆኑና የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በይዞታው ላይ የተፈጠረ ሁከት እንዲወገድለት የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ ግልጽና የማያከራክር ጉዳይ ነው፡፡

አከራካሪው ነጥብ አመልካች የቤቱና የቦታው በይዞታ እንጅ ባለቤት አይደለም፡፡ አመልካች ቤቱን በግዥ ውል መሠረት ከተጠሪ ተረክቦ በእጁ ያደረገ ቢሆንም የቤቱ የባለቤትነት መብት ገና አልተላለፈለትም፡፡ ስለዚህ በቤቱና በቦታው ላይ አመልካች የይዞታ መብት ያለው ሲሆን ተጠሪ በበኩሏ የባለቤትነት መብት አላት፡፡ ባለ ሀብትነት በአንድ ግዙፍ ንብረት ላይ ከሁሉ ያሰፋ መብትን የያዘ እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1204 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል ከዚህ አንፃር ስናየው አመልካች የንብረቱ ግል ይዞታ የሆነው ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1204 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የባለቤትነት መብቷን ለማስተላለፍ ባደረገችው ስምምነት ነው፡፡ ሆኖም ይኸ ስምምነት ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ አልሆነም፡፡ የሽያጭ ውሉ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ ባልሆነበትና ስመ ንብረቱ በአመልካች ባልተዛወረበት ሁኔታ የንብረቱ ባለቤት የሆነችው ተጠሪ የንብረት ባለ ይዞታ ከሆነው አመልካች የሰፋ መብት አላት፡፡ ተጠሪ የንብረቱ ባለቤት በመሆኗም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1206 መሠረት የባቤትነት መብቷን የማስከበርና የመፋለም መብት አላት፡፡ የአንድ ንብረት ባለቤት የሆነ ሰው ሌሎች ሰዎች በንብረቱ ላይ እንዳይደርሱ ወይም የንብረቱን ባለይዞታና ጠባቂ ከንብረቱ እንዲለቁ የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ከዚህ አንፃር የይዞታ መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስ የአንድን ሀብት ባለቤት የባለቤትነት መብት የሚገድብ ሣይሆን የንብረቱ ባለቤት ሣይሆኑ በይዞታ ጣልቃ የሚገቡ ሌሎች ሰዎችን ለማስቆምና ለመከላከል የሚቀርብ የክስ አይነት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

አመልካች ተጠሪ በቤቱ ላይ ያላትን የባለቤትነት መብት በህግ የሚፀና የቤት ሽያጭ ውል ለማስተላለፍ ተስማምታለች የሚል ከሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2879 ድንጋጌዎች መሠረት የቤቱን ስመ ንብረት ወደ እሱ ለማዛወር የሚያስፈልጉ ሰነዶችን እንድታስረክብና የቤቱን ስመ ንብረት ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ግዴታዎችን እንድታሟላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በንብረቱ ግምት ልክ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 215 ንዑስ አንቀጽ 1 የዳኝነት ክፍሉ ከሚጠይቅ በስተቀር የሽያጭ ውልን መነሻ አድርጎ የቤቱና የቦታው ባለይዞታ የሆነው ስው የንብረቱ ባለቤት የሆነችውን ተጠሪን በይዞታዋ ላይ ሁከት ፈጠረችብኝ ብሎ መክሰሱ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37297

ታህሣሥ 02 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

በላቸው አንሺሶ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ በላይነህ ዓለማየሁ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እታለም ተስፋ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኗ ተጠሪ በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 07 ክልል ውስጥ የሚገኘውን በቁጥር 864 የተመዘገበውን የመኖሪያ ቤት ባለቤታቸው አቶ አብሽሩ ብልሃት ከአመልካች ድርጅት ገንዘብ ሲበደሩ ተጠቃሹን ቤት ከተጠሪ እውቅና ውጪ ለብድሩ በዋስትና ያስያዙ ሁኖ አግኝተው በቤቱ ላይ ያላቸው ድርሻ እንዲጠበቅላቸው ዘንድ በፍ/ቤት ክስ መስርተው ክርክር ከተካሄደ በኋላ ፍ/ቤቱ ተጠሪ በቤቱ ላይ ያላቸውን ግማሽ መብት በመጠበቅ ውሣኔ ሰጥቶ ይህ ውሣኔ በበላይ ፍ/ቤት አለመለወጡን፣ በቤቱ ላይ ያላቸው መብት በፍ/ቤት ውሣኔ ተጠብቆላቸው እያለ ግን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ተጠቃሹን ቤት በሐራጅ ለመሸጥ በጋዜጣ ማስታወቂያ አውጥቶ በዝግጅት ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው በቀድሞ ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመሰረቱት የአፈፃፀም ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በፊት በተሰጠው ውሣኔ መሠረት በንብረቱ ላይ የመያዝ መብት እንዳለው መረጋገጡን፣ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ንብረቱን በሐራጅ በመሸጥ ለተጠሪዋ በፍ/ቤቱ ውሣኔ መሠረት ለመፈፀም በዝግጅት ላይ ባለበት ጊዜ የቀረበ ጥያቄ መሆኑን በመግለጽ የተጠሪዋ የአፈፃፀም ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ክርክር የተነሣበት ንብረት ላይ ተጠሪዋ መብት እንዳላቸው ከዚህ በፊት በተሰጠው ውሣኔ የተረጋገጠ ስለሆነ የተጠሪዋን መብት ወደ ጎን በመተው ንብረቱን በሐራጅ ለመሸጥ ማስታወቂያ ማውጣቱ የሕግ አግባብነት የለውም የሚለውን ነጥብ በምክንያትነት በመያዝ ንብረቱ በሐራጅ የቀረበበትን ዋጋ የብር 16349.50 /አስራ ስድስት ሺህ ሦስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከሃምሣ ሣንቲም/ ግማሽ ብር 8174.75/ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰባ አራት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም/ ተጠሪዋ ለአመልካች ከከፈሉ በኋላ የንብረቱ ስም ወደ ተጠሪዋ እንዲዞር በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ይኸው ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ አመልካች በንብረቱ ግማሽ ላይ የፍርድ ባለመብት ሁኖ እያለ የበታች ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ ይህንኑ ሁኔታ ያላገናዘበ መሆኑን፣ እንዲሁም በቤተሰብ ሕጉ ላይ የተመለከተውን የጋብቻ የጋራ ንብረት ክፍፍል አፈፃፀምን መሠረት ያላደረገ መሆኑን፣ የመሐንዲስ ግምት የገበያ ዋጋ የማይወክል መሆኑን፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ አመልካች በግማሽ መብቱ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ማስፈፀም እንደሚችል ተረጋግጦ እያለ በአፈፃፀም ወቅት መሻሩ ያለአግባብ መሆኑን መበዘርዘር የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ ክርክር ያስነሳው ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት በሀራጅ ተሸጦ አመልካችና ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኩል እንዲካፈሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ሐምሌ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ የመልሣቸው ይዘትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ነጥቦችን ያላግባበነት፣ የበታች ፍ/ቤቶችን ትዕዛዝ ደግሞ ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካችም ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ በመያዣ ንብረት ላይ ያላቸው የድርሻ መብት የሚታሰበው ከሐራጅ የሸያጭ ገንዘብ ሣይሆን በሐራጅ መነሻ ዋጋ መሠረት ነው ተብሎ ተጠሪ የሐራጅ መነሻ ዋጋ ግማሹን ለአመልካች እንዲከፍሉ መወሰኑ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት የመያዣ መብት እንዳለውና በግማሽ የፍርድ ባለመብት መሆኑ፣ ንብረቱ በዓይነት ሊከፋፈል የማይችል መሆኑ እና ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ የተደረገውም የመሐንዲሱን ግምት ግማሽ ዋጋ መሆኑ የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

የአመልካችና የተጠሪ በቤቱ ላይ ያላቸው የጋራ ባለሀብትነት በፍርድ የተቋቋመ ነው፡፡ በሕጉ መሠረት የተፈጠረ የጋራ ባለሀብትነት ደግሞ የሚገዛው አግባብነት ባለው ሕግ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1259-1277 ያሉት ድንጋጌዎች የሚያሣዩትም ይህንኑ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1260/1/ ድንጋጌ የሚገልፀው ደግሞ እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት ድርሻውን ለመሸጥ ወይም በሌሎች መንገዶች የማስተላለፊ ወይም ለማስያዝ መብት ያለው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ስልጣኖች ሌሎች የጋራ ባለሃብቶች እየተቃወሙ ቢሆን እንኳን ባለድርሻው የጋራ ባለሃብት የሚተገብራቸው፣ በሕግ የተጠበቁ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1261፣ 1388 እና 1406 ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይ የጋራ ባለሀብቶች ያልተከፈለውን የጋራ ንብረት ከማንኛውም 3ኛ ወገን በፊት፣ ሊሸጥ የታሰበውን ድርሻ አስገድዶ ለመግዛት የቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑን ያስረዳል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት እንዲገዙት መወሰናቸው የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በዚህ ረገድ የቀረበ የሰበር አቤቱታም የለም፡፡

ይሁን እንጂ የተጠሪ የቅድሚያ ግዢ መብት ሲጠበቅ የቤቱ ዋጋ በመሐንዲስ ተገምቶ በቀረበው መሆን አለበት ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት የቤቱ ትክክለኛ ግምት ተደርጎ ሊወሰድ ከሚገባው ዋጋ መነሻ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡ የመሐንዲሱ ግምት ቤቱን ለመስራት የወጣውን ወጪ /Book value/ ከሚያሣይ በስተቀር የቤቱ የወቅቱ የገበያ ዋጋን /Market value/ በሚያሣይ የተሠላና በዚህ ግንዛቤ የቀረበ አይደለም፡፡ በመሆኑም የመሃንዲስ ግምት የወቅቱን የገበያ ዋጋ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ ሣይረጋገጥ የቤቱ ትክክለኛ የወቅቱ ግምት ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ አይደለም፡፡ አመልካችና ተጠሪ የቤቱን የወቅቱ የገበያ ዋጋ የተስማሙበትም አይደለም፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1261/2/ ድንጋጌ ሕጋዊ የሆነ የቀዳማይነት መብት በስራ ላይ የሚውልበት አኳኋን የሚመራው በፍትሐብሔር ሕጉ ሦስተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 6 ምዕራፍ አራት በተነገረው ድንጋጌ ደንብ መሠረት ስለመሆኑ ያጣቅሣል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የተመለከቱት ስለቀዳሚነት ግዢ ይገባኛል የማለት መብት የሚገዙት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1386-1409 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ደግሞ የሸያጩ አኳኋን በሐራጅ ወይም ያለሀራጅ በሻጭና በገዢ ስምምነት ሊደረግ የሚችል መሆኑን ያሣያሉ፡፡ በመሆኑም የጋራ ንብረቱ ዋጋ ስምምነት ሊቆረጥ ካልቻለ የሸያጭ ሂደቱ በሐራጅ ተከናውኖ የንብረቱ የገበያ ዋጋ ይታወቃል፡፡ በዚህ ሂደት የንብረቱ ዋጋ ሲታወቅ የጋራ ባለሃብቱ የቅድሚያ ግዢ መብት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መንፈስ የላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11851 ኅዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 60273 ጥር 30 ቀን 2000 በትዕዛዝ የፀናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥር 864 የሆነ የመኖሪያ ቤት ግልጽ ጨረታ ከወጣበት በኋላ ተጠሪ ቤቱ ያወጣውን ከፍተኛ ዋጋ ግማሹን ለአመልካች ገቢ በማድረግ የጋራ ንብረቷን በቅድሚያ የመግዛት መብቷን ትጠቀም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ቤቱ በግልጽ ጨረታ የሚያወጣውን ዋጋ ግማሹን ለአመልካች ገቢ ለማድረግ ካልቻሉ ቤቱ ለጨረታ አሸናፊው ተሸጦ የቤቱን ግማሽ ዋጋ የማግኘት መብት የተጠበቀ ነው ብለናል፡፡ ግማሹን ለአመልካች ይከፈል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37298

ታህሳስ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

በላቸው አንሺሶ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ነገረፈጅ አቶ በላይነህ አለማየሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አለምነሽ ዋቅጅራ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ወለጋ ዞን ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 21938 ታህሳስ 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 60274 የካቲት 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሚያዚያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 02 ቁጥሩ 964 የሆነውን የመኖሪያ ቤት በመያዥያነት በመያዝ ብድር ያበደረ ሲሆን ተጠሪ ይኸ ቤት የአቶ ይማሙ ባቲና የእሷ የጋራ ንብረት መሆኑንና የመያዥያ ውሉ እሷ ሣታውቅና ሳትፈቅድ የተፈፀመ በመሆኑ በእሷ ድርሻ ላይ ውጤት እንደሌለው እንዲወሰንላት ክስ አቅርባ አመልካች በመያዥነት የያዘው ቤት የተጠሪ የጋራ ሐብት እንደሆነና የመያዥያ ውሉም የተጠሪን ድርሻ ውጤት የሌለው መሆኑን በፍርድ አስወስናለች አመልካች ቤቱን ለመሸጥ፣የቤቱን ግምት 28,092/ሃያ ስምንት ሺ ዘጠና ሁለት ብር/ መሆኑን በመግለጽ የጨረታ ማስታወቂያ አውጥቷል፡፡ ተጠሪ አመልካች የጋራ ንብረቷን ለመሸጥ ያወጣው ማስታወቂያ በመቃወም የቤቱ ግማሽ ባሐብት መሆኔና መያዥያው የእኔን ድርሻ የማይመለከት መሆኑ በፍርድ የተረጋገጠ ስለሆነ በዚህ መሰረት ይፈፀምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ የቤቱ ግምት ግማሽ ዋጋ ለአመልካች ከፍላ ቤቱን የግሏ ታድርግ በማለት የአፈፃፀም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች ይኸ ትእዛዝ በግማሽ የመያዥያ መብት ያለን መሆኑ የተረጋገጠውን ቤት፣በገበያ ዋጋ በመሸጥ በተሻለ ሁኔታ መብታችንን የማስከበርና እዳችንን የመሰብሰብ መብታችን የሚያሳጣና የቤቱን የመሐዲስ ግምት ግማሽ ዋጋ በመክፈል ተጠሪ ቤቱን እንድትረከብ የሚያደርግ፣ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልን በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪ በበኩሏ አመልካች የእኔን ድርሻ ጨምሮ ለመሸጥ የሚፈቀድለት ሕግ የለም፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤቶች የቅድሚያ የመግዛት መብቴን በመጠበቅ የሰጡት ትእዛዝ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ሐምሌ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረበችው መልስ ተከራክራለች፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ የክርክሩ መሰረታዊ ጉዳይ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንዳየነው አመልካች ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ ከፊል የመያዥያ መብት ያለው መሆኑና ተጠሪዋ በበኩሏ የንብረቱ የጋራ ባለሐብት መሆኗ አያከራክርም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የጋራ ሐብቷ የሆነውንና በከፊል የአመልካች ባለመብት የሆነበትን ቤት ቅድሚያ የመግዛት መብት ያላት መሆኑ በፍታብሔር ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 1261/1/ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ቤቱን የመግዛት መብት አላት በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትእዛዝ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡

ሆኖም ተጠሪ ቤቱን በቅድሚያ የመግዛት መብቷን ተጠቅማ የምትገዛውና ለአመልካች ገቢ የምታደርገው የቤቱን የመሐድስ ግምት ዋጋ መሰረት ነው ወይስ ቤቱ በገበያ የሚያወጣውን እርግጠኛ ዋጋ የሚለው ነጥብ የስር ፍርድ ቤቶች በትኩረት አላዩትም፡፡ ተጠሪ ቤቱን የመግዛት የቅድሚያ መብት ያላት ቢሆንም ቤቱን የምትገዛው በመሐድስ ግምትና መነሻ ዋጋ ግማሹን በመክፈል ሣይሆን ቤቱ ለግልጽ ጨረታ ቀርቦ ያወጣውን እርግጠኛ ዋጋ ግማሹን በመክፈል ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ በቶች ተጠሪ የቤቱን የመሐዲስ ግምት ግማሽ ዋጋ በመክፈል ቤቱን የግሏ ታድርግ በማለት የሰጡት ትእዛዝ የአመልካችን ንብረቱን በዋጋው የመሸጥ መብት የሚጋፋት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ትእዛዝ ተሻሽሏል ይፃፍ፡፡
2. በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 02 የሚገኘውና ቁጥሩ 964 የሆነው መኖሪያ ቤት ለግልጽ ጨረታ ከወጣ በኋላ ተጠሪ ቤቱ ያወጣውን ከፍተኛ ዋጋ ግማሹን ለአመልካች ገቢ በማድረግ የጋራ ንብረቷን በቅድሚያ የመግዛት መብቷን ትጠቀም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ቤቱ በግልጽ ጨረታ የሚያወጣውን ዋጋ ግማሹን ለአመልካች ገቢ ማድረግ ካልቻሉ ቤቱ ለጨረታ አሸናፊው ተሸጦ የቤቱ ግማሽ ዋጋ ለተጠሪ ይከፈላት ብለናል፡፡ ግማሹ ለአመልካች ይከፈለው ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት ታህሣስ 2 ቀን 2001 ዓ.ም በመሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38228

ታህሣሥ 7 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሐጂ መሐመድ አወል ረጃ - ጠ/ደሣለኝ አለሙ ክብረት

ተጠሪ፡- 1. አቶ ዲኖ በሺር
2. ወ/ሮ ዘይቱ አረጋ

} ጠ/ አምሃ ነጋሽ ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሁከትን ጉዳይ የሚመለከትን ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በሰበታ ወረዳ ካራብህርቡ ቀበሌ ገ/ማኅበር ውስጥ ሁለገብ የአረብኛ እና የሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል አቋቁው እየሠሩ ባለበት ወቅት ተጠሪዎች ድንበሩን ለመከላከል የተቆፈረው አፈር በመሙላት፣ የጥበቃውን ቤት በማፍረስና የተማሪዎቹን መኖሪያ በቁፋሮ በማናጋት ሁከት እየፈጠሩ በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ በሁከቱ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ሁከት ተፈጠረበት የተባለው ቦታ በአመልካች ይዞታ ስር መሆኑና በዚሁ ቦታ ላይ ተጠሪዎች ሁከት መፍጠራቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠ ሁከቱ እንዲወገድ፣ በሁከቱ ምክንያት ለደረሰው ተጠሪዎች ብር 4500.00 /አራት ሺህ አምስት መቶ/ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይዞታ የሚረጋገጠው በፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት ከሚመለከተው አስተዳደር መ/ቤት በተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም ካርታ ነው፣ አመልካች ይዞታው የራሣቸው መሆኑን ለማስረዳት ይህን መሰል የሰነድ ማስረጃ አላቀረቡም፣ ስለሆነም ባለይዞታ መሆናቸውን ሳያስረዱ ተጠሪዎች ሁከት ፈጥረዋል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጠረበት ነው በማለት ውሣኔውን ሽሯል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የሁከትን ጉዳይ ለመወሰን አመልካች በፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት ከአስተዳደር መ/ቤት የተሰጠ የባለይዞታነት ማረጋገጫ መቅረብ አለበት በማለት የሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ተጠሪዎችም ለቀረበው የሰበር አቤቱታ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በይዞታቸው ላይ ተጠሪዎች ሁከት እየፈጠሩ በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ በሁከቱ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ኪሣራውን ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ነው፡፡ በይዞታው የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተነሣበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንዲመለስለት ወይም የተነሣው ሁከት እንዲወገድለት እንዲሁም ስለደረሰበት ጉዳት ኪሣራ እንዲሰጠው መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1149/1/ ሥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመልክቷል፡፡ ይዞታ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 1140 ሥር ትርጓሜ ተሰጥቶታል፡፡ ይዞታ ማለት አንድ ሰው አንድን ነገር በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው ባለይዞታ ነው ለማለት በግድ በይዞታው ላይ ባለሃብት መሆን እንደሌለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት አንድን ነገር በእጁ አድርጎ በእውነት ያዝበት የነበረ መሆኑን ካስረዳ ባለይዞታ መሆኑ ይረጋገጣል ወደ ፍ/ሕ/ቁ. 1195 ስንመለስ ግን ይህ ድንጋጌ የሚገናረው ስለባለሃብትነት /ownership/ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው የማይንቀሣቀስ ንብርት ባለሀብት መሆኑ ከሚመለከተው አስተዳደር ክፍል የሚሰጠውን የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ማስረዳት ይችላል፡፡ በእርግጥ መሬት የማይንቀሳቀስ ንብረት ቢሆንም የመሬት ባለሀብት መሆን ባይችልም የመሬቱ የይዞታ ባለሀብት መሆኑን በማረጋገጥ ግን ተመሣሣይ ማስረጃ ማቅረብ ይገባል፡፡ በመሆኑም በፍ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1195 መሃከል የሰፋ ልዩነት አለ፡፡ የመጀመሪያው አንድን ነገር ይዞ መገልገል ባለይዞታ የሚያደርግ መሆኑን የሚልጽ ሲሆን ሁለተኛው ግን አንድን ነገር ይዞ መገልገልን ብቻ ሣይሆን ከዛ ባለፈ የዚሁ ነገር ባለቤት መሆንን ለማረጋገጥ የሚያገለግል ድንጋጌው ነው፡፡ ስለሆነም የሁከትን ክስ ለማቅረብ ከሣሽ ማስረዳት ያለበት ሁከት ተፈጠረ የተባለበትን ነገር በእጁ አድርጎ በውነት ያዝበት የነበረ መሆኑን ብቻ እንጂ የዚሁ ነገር ባለሃብት መሆኑን አይደለም፡፡ ስለሆነም የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት አመልካች ባቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ክስ የፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት አድርጎ መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ሁከት ተፈጠረ የተባለበትን በእጃቸው አድርገው ያዙበት የነበረ ለመሆኑ እና ተጠሪዎችም ሁከት የፈጠሩ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት አይቻልም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58254 በ16/04/2000 የሰጠው ውሣኔ እና በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35850 በ12/07/2000 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19195 በ04/11/99 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች በአመልካች ቦታ ላይ የፈጠሩት ሁከት ሊወገድ ይገባል፡፡ በሁከቱ ምክንያት በደረሰው ጉዳትም ብር 4500.00 /አራት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36638

ታህሳስ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- በላይ አበበ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አበራሽ ዋቅጅራ - ቀረቡ

2. አበበ ኃ/ወልድ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በስር ከሣሽ ተጠሪዎች ደግሞ የስር ተከሣሽ ነበሩ አመልካች ባቀረቡት ክስ አንደኛ ተጠሪ የእንጀራ እናቱ ሁለተኛ ተጠሪ አባቱ ናቸው፡፡ በወረዳ 11 ቀበሌ 15 ክልል በቤት ቁ. 433 ግቢ በራሴ ወጪ ቤት ሰርቼ እንድጠቀም ፈቅደውልኝ 40,000(አርባ ሺህ ብር) አውጥቼ ሰርቼ ይህንንም በህዳር 6 ቀን 1976 በጽሁፍ አረጋግጦልኝ ለ19 ዓመት እየኖርኩበት በሚያዝያ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ መብራትና ውሐ በመቁረጥ ሁከት በመፍጠር ለቅቄ እንድወጣ አድርገውኛል፡፡

ስለዚህ የስራሁትን ቤት እንዲያስረክቡኝ ፍቃደኛ ካለሆኑ ያወጣውትን 40,000 ብር (አርባ ሺህ ብር) እና የደረሰብኝን ኪሣራ ይከፈለኝ ሲል ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ በማዘዝ በመልሳቸውም ተፈረመ የተባለው የስጦታ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443 መሰረት ያልተፈፀመ ነው ስለዚህ ፈራሽ ነው፡፡ ስጦታ ተቀባዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2436 መሰረት መቀበሉን አላረጋገጠም፣ውል ይፈጸምልኝ ለማለት በ1845 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ የቤቱ መለያ ያልታወቀ ነው፡፡ የመክሰስ መብት የለውም 40,000 ብር (አርባ ሺህ) አውጥቶ አልሰራም በኛ ገንዘብ ነው ቤቱ የተሰራው የውሃና የመብራት አልከፍልም በማለት ነው ሁከት ተፈጠረ የሚለው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አግባብነት ካለው ሕግ በማገናዘብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1179/1/ መሰረት ባለመሬቱ ሣይቃወም በሌላ ሰው መሬት ሕንፃ የሰራ ሰው የዚሁ ሕንፃ ባለሐብት ነው ይላል፡፡ በዚህም ጉዳይ አመልካች በተጠሪዎች መሬት ቤት ሲሰሩ አልተቃወሙም ይልቁንስ መፍቀዳቸውን በጽሑፍ አረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት በስጦታ ውል መስፈርት ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1179/1/ መሰረት ነው ስለሆነም አመልካች በቤቱ ውስጥ ሲኖሩ እንደነበር የተረጋገጠ ስለሆነ አመልካች የቤቱ ባለሐበት ናቸው የተፈጠረው ሁከት ይወገድ አመልካች ወደ ቤቱ ይመለሱ፡፡ ተጠሪዎች ይህን የማይፈልጉ ከሆነ ግምቱን ያልተቃወሙ ስለሆነ 40,000 ብር (አርባ ሺህ ብር) ከፍለው ቤቱን የማስቀረት መብት አላቸው ሲል ውሳኔ፡፡

ይግባኝ ባይም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታቸውን አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን በማከራከር ካዩ በኋላ የግራ ቀኙ ክርክር የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄ ነው አንድ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ወገን ሁከት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈጠረበትን ነገር በእጁ አድርጐ በእውነት የሚያዝበት ሆኖ መገኘት እንዳለበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 በግልጽ ተደንግጓል አመልካች ሁከት ተፈጥሮብኛል ሊል የቻለበት በጎንዳር 6 ቀን 1976 ዓ.ም የተፃፈ ውል ቤት ሰርቶ እንዲኖር የተሰማሙበትን ነው፡፡ እንደዚህ አይነት የስጦታ ውል ደግሞ በግልጽ በመደረጉ የጉዛዜ ስርአት መደረግ እንዳለበት ሕጉ ያዛል ከዚህ ስርአት ውጪ የሆኑት ስጦታ ፈራሽ ናቸው ሊል የፍ/ሕጉ /ቁ. 2443 ያዛል በመሆኑም የስጦታው ውሉ ፎርማሊቲን ያላሟላ ስለሆነ ፈራሽ ነው የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ሽሮታል፡፡

አመልካችም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ቢያቀርብም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም በቀረበው ማመልካቻ በፌደራል ከፍ/ቤት እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል አመልክቷል፡፡

እኛም በዚሁም መሰረት አቤቱታ የቀረበበትን የስር ውሣኔ እና የአመልካች አቤቱታን አግባብ ካለው ሕግ ለማገናዘብ ተጠሪዎችን በማስጠራት ሰምተናል በመሆኑም ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ የተባለው አመልካች በስጦታ ውል አገኘሁት የሚሉት ቤት ለመስራት ያወጡት ወጪ ሣይከፈላቸው የስር ፍ/ቤቶች የስጦታ ውሉ ፈርሶ አመልካች ቤቱን ያስረክቡ መባሉ በአግባቡ መሆኑን ለመመርመር ነው፡፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የአመልካች ጥያቄ የነበረው በተጠሪዎች ይዞታ ላይ ባገኘው ፍቃድ ቤት ሰርቶ ለ"19" አመት የኖረበት እና ለግንባታውም 40,000 ብር (አርባ ሺህ ብር)እንዳወጣበት እና ተጠሪዎች በ1975 በተፃፈ ጽሁፍ ተስማምተው እንደሰጡት በመጥቀስና ከግዜ በኋላ መብራትና ውሐ አልከፈልክም በማለት ተጠሪዎች ከቤት እንዳስለቀቁት በመጥቀስ ሁከት ተወግዶ ወደ ቤቱ እንዲመለስ ተጠሪ ካለፈቀደ አመልካች ለቤቱ ግንባታ ያወጣውን 40,000 ብር(አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍሉት ጠይቋል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም አመልካች በተጠሪዎች ፈቃድ ቤት ገንብተው ለ19 ዓመታት የኖሩበት መሆኑን በመረዳት ጉዳዩ መታየት ያለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1979/1/2/ መሰረት የሚታይ እንጂ በስጦታ ውሉ መሰረት መታየት የለበትም ብሎ ሁከት ይወገድ አመልካች ወደ ቤቱ ይመለስ ተጠሪዎች ካልፈቀዱ ለአመልካች 40,000 ብር(አርባ ሺህ ብር) ይክፈሉ ሲል ሲወስን የከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩ የሚታየው በስጦታው ውል መሰረት ነው በማለት የስር ውሣኔን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ሲሽር የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ዘግቶታል፡፡

በመሰረቱ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ፍ/ቤቱ ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የሕጉን አንቀጽ 1179/1/2/ ነው ይህ አንቀጽ ባለመሬቱ ሣይቃወም በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንፃ የሰራ የዚሁ ሕንፃ ባለሐብት ይሆናል በዚህም ጉዳይ አመልካች በቤቱ ውስጥ ለ19 አመት መኖሩ በተጠሪ አልተካደም መብራትና ውሐ ስላልከፈለ ነው የወጣው(የለቀቀው) ሲሉ ተከራክረዋል ይህ ደግሞ ከመጀመሪያውኑ ፍቃድ(ስምምነት) እንደነበረ የሚያመለክት ነው አመልካችም ይህንኑ በግምት በማስገባት ቤቱን ይገነባል ተብሎ ይታመናል በሌላ በኩል ፍ/ቤቱም አመልካች በራሱ ወጪ ቤት ለመስራቱም አረጋግጧል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤትም የስጦታ ውሉን ቢያልፈው (ፈራሽ) ነው ቢል እንኳ አመልካች ያለ ምንም ተቃውሞ ለ19 አመት የኔ ነው በሚል እምነት የኖረበትን እግምት ማስገባት ሲገባው የአመልካች አባት (ወላጅ) ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች ቤቱን ሰርቶ መኖር ከጀመረ በኋላ ቤቱን ለልጄ ሰጥቻለሁ ብለው ጽፈው ለሽማግሌዎች ያስፈረሙትን ጽሑፍ መሰረት በማድረግ ሁከት የለም በማለት የስር ውሣኔን መሻሩና የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንን ማረም ሲገባው መዝገቡን ጉድለት የለበትም ብሎ መዝጋቱ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገቡ ቁ.44725 በጥር 7 ቀን 2000 ዓ.ም እና በጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35834 በ8/7/2000 የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02183 ጥር 4 ቀን 1998 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ተጠሪ አመልካች ወደ ቤቱ እንዲመለሱ ካልፈቀዱ አመልካች ያወጣውን 40,000 (አርባ ሺህ ብር) ይክፈሉ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይካበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36013

ታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘምዘም ኑሩ - ጠ/በረከት በርሔ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢት/ልማት ባንክ - አልቀረቡም፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያለውን ባለገንዘብ የቀዳሚነት መብት የሚመለከት ነው፡፡

በምዕ/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ባቀረቡት ክስ፤ በባሕር ዳር ከተማ 04 የቤት ቁጥር 151 የሆነውን ቤት በአፈፃፀም ከሣሽ ባሕር ዳር ልዩ ዞን አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤትና በአፈፃፀም ተከሣሽ ሐጂ ኑር ሁሴን ምትኩ መካከል በነበረው የአፈፃፀም ክርክር በወጣው ጨረታ ተሣትፈው በማሸነፍ ቤቱን የገዙ መሆኑን፣ የቤቱን የባለቤትነት ስም በስማቸው ለማዛወር ሲሞክሩ የማዘጋጃ ቤቱ በመያዣነት ተይዟል በማለት የከለከላቸው መሆኑን፣ በዚህ ሂደት ላይ ተጠሪ ቤቱ ያለአግባብ የተሸጠ ስለሆነ ጨረታው ይፍረስ በማለት አመልክቶ ጥያቄው ውድቅ መደረጉን፣ ከዚህ በኋላ የቤቱ ባለቤትነት ስም በስማቸው መዛወሩን በስማቸው ካርታና ፕላን ተሰርቶ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ቤቱን በይዞታቸው ሥር አድርገው እየተገለገሉበት እያለ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣቱን ገልፀው በንብረታቸው ላይ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለቀረበት ክስ በሰጠው መልስም ጉዳዩ በሌላ መዝገብ ክርክር ቀርቦበት ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ በድጋሚ ሊታይ አይገባም፣ ተጠሪ ቀደም ሲል በነበረው ክርክር ጣልቃ በመግባት ንብረቱ ላይ ያለው መብት እንዲከበርለት ጠይቆ ፍ/ቤቱ በንብረቱ ላይ ያለውን መያዣ መብት ንብረቱን በመከተል መጠቀም የሚችል መሆኑን በመግለጽ ብይን የሰጠ በመሆኑና ቤቱን ለአቶ ኑር ሁሴን ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘው በመሆኑ የመያዣ መብቱን ንብረቱን ከገዛው ሰው ላይም መጠቀም ይችላል፤ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም አከራካሪ በሆነው ቤት ላይ ተጠሪ የመያዣ መብት ያለው መሆኑን አመልካች አልካዱም በመያዣ የያዘውን ቤት ደግሞ በአ/ቁ. 97/90 መሠረት የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት መሸጥ ይችላል፣ ስለሆነም በጨረታ የያዘውን ንብረት ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣቱ ሁከት ፈጥሯል የሚያሰኝ አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኛቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ፤ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው ተገቢውን ጭብጥ ሣይዝ ነው፣ ተጠሪ ንብረቱን የመከተል መብት የሚኖረው ንብረቱን በዋስትና ካስያዘው ሰው ላይ ገዝቼው ቢሆን ነበር ንብረቱ በሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ከተያዘ በኋላ የተጠሪ መብት ከንብረቱ ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ በቅድሚያ ዕዳው እንዲከፈለው መጠየቅ ነው በመያዣ የተያዘው ንብረት በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡ በባለገንዘቦች ከተከፋፈለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኋላ የመያዣ መብቱ ቀሪ ይሆናል፣ ተጠሪ ከመንግሥት ግብር በፊት ቅድሚያ መብት የለውም እንጂ አለው ቢባል እንኳን መብት ያለው መሆኑ በማሣወቅ ያቀረበው ጥያቄ የለም፣ በመሆኑም የገዛሁትን ንብረት በሃራጅ በድጋሚ የመሸጥ መብት የለውም የሚል ነው።

ይህ ችሎትም አከራካሪው ንብረት በአገር ውስጥ ገቢ ግብር ክፍያ በሃራጅ ከተሸጠ በኋላ በድጋሚ ተጠሪ በሃራጅ ሊሸጠው የሚችል መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ስለተባለ ተጠሪ መልሱን አቅርቧል።

ተጠሪ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ፣ በአ/ቁ. 97/90 እና 98/90 በተሰጠኝ መብት በመያዣ የያዝኩትን ንብረት ለመሸጥ ማስታወቂያ ማውጣቴ ሁከት አይደለም፣ መያዣው በሕጋዊ መንገድ የተቋቋመና የተመዘገበ በመሆኑ ንብረቱን የመከተል መብት አለኝ፣ ንብረቱ በግብር እዳ ተሸጦ ባለቤትነቱ ለሌላ ሰው የተላለፈ ቢሆን እንኳን ንብረቱን የመከተል መብቴን አያስቀርም፣ ቀደም ሲል በነበረው ክርክር ፍ/ቤቱ ንብረቱን የመከተል መብት ያለኝ መሆኑን አረጋግጧል፣ በመያዣ ውሉ ምክንያት የሆነው እዳ የተሰጠው ለአመልካች አባት ነው ቤቱን ሲገዙ እዳ ያለበት መሆኑን ያውቃሉ፤ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና ጠይቋል።

ከዚህ በተጨማሪ ችሎቱ ጎዳር 2/2001 በነበረው ችሎት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል። ከላይ የተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክርና የፍ/ቤቶች ውሣኔ ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ መርምሯል።

ከላይ እንደተመለከተው በዚህ መዝገብ መሠረታዊ የሆነው ጭብጥ ተጠሪ በመያዣነት የያዘው ንብረት በሌላ ገንዘብ ጠያቂ ዕዳ ምክንያት በሃራጅ ከተሸጠ በኋላ የተጠሪ መብት ምንድነው? የሚለው ነው። በመሆኑም ይህንን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው የፍ/ብ/ሕጉ ስለማይንቀሳቀስ ንብረት መያዝ ከተደነገጉት ሕጎች አንፃር መመርመሩ ተገቢ ይሆናል።

ከክርክሩ ሂደት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሐጅ ኑር ሁሴን ምትኩ እና በባሕር ዳር ከተማ ልዩ ዞን አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት በሃከል በነበረው የአፈፃፀም ክርክር ንብረቱ ከመሸጡ በፊት ተጠሪ ለሐጂ ኑር ሁሴን ምትኩ ለሰጠው ብድር በመያዣ የተሰጠው መሆኑን ተረድተናል። አንድ ባለገንዘብ በአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በሕጉ መሠረት የተቋቋመ የመያዣ ውል ካለው ውሉ ሁለት ዓይነት መሠረታዊ መብቶችን ያጎናጽፈዋል። እነዚህም መብቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/ እና /2/ ሥር የተመለከቱት ናቸው። ለውሣኔ ያመች ዘንድ ሕጎቹን በዝርዝር ማስቀመጡ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል። የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059

1. “የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ መብት የተሰጠው ገንዘብ ጠያቂ መያዣው የሚመለከተውን የማይንቀሳቀስ መብት፣ ገንዘብ ጠያቂዎች ያስያዙት እንደሆነ ከንብረቱ ዋጋ ላይ የሚጠይቀው ገንዘብ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በፊት በርሱ በቀዳሚነት እንዲከፈለው መብት አለው”
2. “እንዲሁም የመጀመሪያው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መብት ከተመዘገበ በኋላ፣ መብቱን ባስመዘገበ በሌላ 3ኛ ወገን ባለዕዳው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ቢሸጥ ቢያስተላልፍም እንኳን የመያዣ መብቱን ያስመዘገበው ገንዘብ ጠያቂ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለማስያዝ ይችላል።”

ከእነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች እንደምንረዳው የመያዣ መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣው የሚመለከተው ንብረት በሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ተይዞ ሲሸጥ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ በቅድሚያ ገንዘቡን የማግኘት መብት /right of Preference/ እና ንብረት አስይዞ ንብረቱን ለሌሎች 3ኛ ወገኖች ካስተላለፈ መያዣ የተሰጠበትን ንብረት ከማናቸውም 3ኛ ወገኖች ተከትሎ የማስያዝ /right of persuit/ ይኖረዋል። የመያዣ መብት ያለው ሰው እነዚህ ሁለት መብቶች አሉት ከተባለ መብቶቹን እንዴት ነው የሚገለገልባቸው የሚለውን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል። በመጀመሪያ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/2/ ላይ ያለውን መብት እንመልከት። መያዣ የተሰጠው ባለገንዘብ ባለዕዳው ግዴታውን መፈፀም ሲያቅተው የግዴታውን አፈፃፀም ለማረጋገጥ የሚወስደው እርምጃ ነው። አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ በመሠጠቱ ብቻ ንብረት አስያዥ በንብረቱ ላይ ያለው መብት ቀሪ ይሆንበታል ማለት አይደለም። በንብረቱ ላይ መያዣ የሰጠ ሰው ይህንኑ ንብረት ለመሸጥ፣ ለመለወጥ መብት ያለው ሲሆን ይህንን በሚቃረን መልኩ ማንኛውንም ስምምነት ማድረግ እንደማይቻል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3084/1/ እና /2/ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ምንም እንኳን አንድ ንብረት በመያዣ የተሰጠ ቢሆንም አስያዥ ንብረቱን ለሌላ ሰው ለመሸጥ ለመለወጥ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ ይችላል። ዋናው ባለዕዳም ግዴታውን መፈፀም እስከቻለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድረስ ባለገንዘቡ መያዣ በተሰጠው ንብረት ላይ መብት አይኖረውም፡፡ ነገር ግን ባለዕዳው ግዴታውን መፈፀም ሲያቅተው ንብረቱ ለሎች 3ኛ ወገኖች ተላልፎ እንኳን ቢሆን በማስያዝ የመሸጥ መብት አለው፡፡ ይህ ንብረቱን የመከተል መብት ተፈፃሚም የሚሆነው ንብረቱ ለሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ጥያቄ መሠረት ከመያዙ በፊት ነው፡፡

ንብረቱ በሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ከተያዘ በኋላስ መያዣ የተሰጠው ባለገንዘብ መብት ምንድነው ይህ ጥያቄ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/ ሥር ወደተመለከተው የቀዳሚነት መብት ይወስደናል፡፡ የቀዳሚነት መብት /right of preference/ የሚነሣው በመያዣ የተያዘው ንብረት በሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች እዳ ተይዞ ንብረቱ በሃራጅ ከተሸጠ በኋላ የሚገኘው ገንዘብ በሁሳችንም ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳ ለመሸፈን የማይበቃ ሲሆን ነው፡፡ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ የተሰጠ ቢሆንም መያዣ በሌላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳም ተይዞ ሊሸጥ እንደሚችል ድንጋጌው ራሱ የሚናገር ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1988/1/ ሥር በባለዕዳው ግዴታ አፈፃፀም በሕግ ሊያዙ አይገባውም ተብሎ ክልከላ ካልተደረገባቸው ንብረቶች በቀር ሌሎች የባለዕዳው ንብረቶች ሁሉ ሊያዙ መሆኑ መደንገጉ በፍ/ሕ/ጠ 3059/1/ ሥር የተቀመጠውን ሃሣብ የሚያጠናክር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከአንድ ለበለጠ ዕዳ በመያዣ ሊሠጥ የሚችል መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3088/1/ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በባለዕዳው ላይ መያዣ ያላቸውም ሆነ የሌላቸው ባለገንዘቦች በመያዣ የተያዘውን ንብረት በማስያዝ ለማሸጥ መብት አላቸው፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ መያዣ ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች የመያዣ መብታቸውን ባስመዘገቡበት ቅደም ተከተል ከሸያጩ ገንዘብ ላይ በቅድሚያ ገንዘባቸውን የማግኘት መብት ያላቸው በመሆኑ ንብረቱ በማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ተይዞ ከተሸጠ በኋላ የመያዣ መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ የሚኖረው ብቸኛ መብት ከሸያጩ ገንዘብ ላይ በቅድሚያ ዕዳቸውን መሰብሰብ ነው፡፡ ከዚህ በቀር ንብረቱ ተይዞ ከተሸጠና ከሸያጩ ገንዘብ በቅድሚያ እንዲከፈለው ሣይጠይቅ ቀርቶ ገንዘቡ በሌሎች ባለገንዘቦች መሃከል ከተከፋፈለ በኋላ ንብረቱን የመከተል መብት አለኝ በማለት የሚያነሣው መብት የለም፡፡ ምክንያቱም በመያዣ የተያዘው ንብረት በሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳ ምክንያት ተይዞና በሐራጅ ተሸጦ ዋጋው ለባለመብቶቹ ከተከፋፈለ በኋላ መያዣው ቀሪ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3110/ሐ/ መገንዘብ ይቻላል፡፡ መያዣው ቀሪ ከሆነ ደግሞ መያዣውን መሠረት በማድረግ የሚያነሣው የመብት ጥያቄ አይኖርም ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት ያለው ባለገንዘብ ንብረቱን የመከተል መብት የሚኖረው ንብረቱ በማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ዕዳ ከመያዙና ከመሸጡ በፊት ነው፡፡

የተያዘውን ጉዳይ ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት የሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ስንመረምርም ተጠሪ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት በመያዣ የያዘው መሆኑ አላከራከም፡፡ ነገር ግን የዚሁ ቤት ባለቤት በባሕር ዳር ልዩ ዞን አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ላይ ባለባቸው የግብር ዕዳ ምክንያት ቤቱ ተይዞ በፍ/ቤት በኩል በሐራጅ በአሁኑ አመልካች ተሸጧል፡፡ ቤቱ ከተሸጠ በኋላ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ ሽያጩን ተቃውሟል፡፡ ፍ/ቤቱም ተጠሪ በቤቱ ላይ ባለው የመያዣ መብት መሠረት ንብረቱን ከሚከተል በቀር ሽያጩን ሊቃወም እንደማይችል ገልፆ ጥያቄውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ በእርግጥ በመያዣ የተያዘ ንብረት በሌላ በማንኛውም ባለገንዘብ ዕዳ ተይዞ ሊሸጥ የሚችል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ተጠሪ ሽያጩን በመቃወም ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ አግባብ ነበር፡፡ ሆኖም ንብረቱ በሌላ ሰው ዕዳ ተይዞ በሐራጅ ሲሸጥ ተጠሪ የሚኖረው መብት ከሸያጩ ገንዘብ በቅድሚያ እንዲከፈለው መጠየቅ እንጂ ንብረቱን የመከተል መብት እንዳልሆነ ከላይ ከተመለከትናቸው የመያዣ ሕግ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ንብረቱ በአገር ውስጥ ገቢ እዳ በሐራጅ ሲሸጥ ሽያጩን መቃወም ሣይሆን ከሸያጩ ገንዘብ ቅድሚያ እንዲከፈለው ሊጠይቅ ይገባ ነበር፡፡ ፍ/ቤቱም ንብረቱን የመከተል መብቱን ጠብቆ ሲያሰናብተው በዚሁ ላይ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርቦ የቀዳሚነት መብቱ እንዲጠበቅለት ማድረግ ሲገባው ይህንን አላደረገም፡፡ በመሆኑም በክርክር ላይ ያለው ንብረት በባህር ዳር ልዩ ዞን አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ዕዳ ተይዞ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡ ለባለገንዘብ ከተከፈለ በኋላ ተጠሪ ንብረቱን የመከተል መብት ስላለኝ በሃራጅ ሽያጩ ላይ ተወደድረው ከገዙት የአሁኗ አመልካች ላይ ይገፍ መሸጥ እችላለሁ በማለት ያቀረበው ክርክርና ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ክርክር ተቀብለው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የምዕ/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 17072 በ30/01/2000 የሰጠው ውሣኔ እና የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14659 በ19/05/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 04 የቤት ቁጥር ዲ 151 የሆነውን ቤት በባሕር ዳር ልዩ ዞን አገር ውስጥ ገቢ እዳ ምክንያት ተይዞ በሐራጅ የተሸጠ ስለሆነ ንብረቱን የመከተል መብት ስለሌለው ንብረቱን በጨረታ ለመሸጥ አይችልም ሁከቱ ይወገድ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39940

ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ወ/ሮ ነጂባ ነጋሽ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዚያዳ ዬታሞ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሁከት ይወገድልኝን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኗ ተጠሪ ነሐሴ 15 ቀን 1998 ዓ.ም. በዓፉት ማመልከቻ ሚች አቶ አብዶ ናስር ሼህ ጀቤር ከተባሉት ባለቤታቸው ጋር በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/12 የቤት ቁጥር 1638 የሆነውን ከመንግሥት ተከራይተው ሲኖሩ እንደነበር፣ ተጠሪ ያላግባብ የቤቱን ኪራይ ቀበሌው በስማቸው አድርጎላቸው ቤቱን መያዛቸውን በመዘርዘር ተጠሪ የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ አመልካችም የቤቱ ኪራይ በስማቸው የዞረላቸው የሚቹ ሚስት በመሆናቸው መሆኑን፣ ተጠሪ በወቅቱ በቤቱ ያልነበሩ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የቀበሌው አስተዳደር ተጠሪ በቤቱ ላይ ከአመልካች ጋር አኩል መብት ያላቸው መሆኑን እያወቀ ተጠሪን በማስታወቂያ ሣይጠራና የቤት ኪራይ ስም ዝውውሩን መፈፀሙና ከአመልካች ኪራይ መቀበሉ በተጠሪ ላይ ሁከት መፍጠር ነው በማለት አመልካችና ተጠሪ በቤቱ ላይ በጋራ እንዲገለገሉበትና በጋራ ኪራይ እንዲከፍሉ እንዲደረግ ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ የከተማው የሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተገኘም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 09 ቀን 2000 ዓ.ም. በዓፉት 2 /ሁለት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የተጠሪ የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄ በጊዜ ያልቀረበና የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149 ድንጋጌን ያላገናዘበ ሆኖ እያለ በተከራይነት ባገኘሁት የይዞታ መብትን እንዳካፍል መወሰኑ ሕጋዊነት የሌለው በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ጎዳር 03 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የአመልካችን ቅሬታ ለመንቀፍ፣ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ተገቢነት በመዘርዘር ውሣኔው ሊፀና ይገባል ሲሉ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ሁከት ፈጥረዋል መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የቀበሌው አስተዳደር የሚያስተዳድረው የመንግሥት ንብረት መሆኑን፣ ቤቱን ሟቹ ተከራይተውት ይኖሩበት እንደነበር፣ ከሟች ሕይወት ማለፍ በኋላ በወቅቱ ይዘውት በነበረው የሚስትነት ማስረጃ መሠረት አመልካች የቤቱን የተከራይነት መብት ቀበሌው ያስተላለፈላቸው መሆኑን፣ በዚህ ጊዜ ተጠሪ ከቤት ያልነበሩና ሕጋዊ ጠባቂም ያልነበራቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ይዞታው ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈፀምን ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ወይም ተገቢው መብት እንዲመለስለት ሕጉ ከዘረጋላቸው መንገዶች አንዱ የይዞታ ክስ /Possessory action/ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149/1/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረውና ይህንኑ ሁኔታ በኃይል ሲነጠቅ ነው፡፡ እንዲሁም የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም ዓይነት መብት የሌለው ሰው ሲይዝ ስለመሆኑም ተጠቃሹ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅራቢ ማረጋገጥ ያለበት ንብረቱ በሕግ አግባብ በይዞታው የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የኃይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጢር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ነው፡፡ ይህ የድንጋጌው መንፈስ የሚያስረዳው የሁከት ተግባር የሚኖረው ባለይዞታ የሆነው ሰው በይዞታው ሥር በሚገኘው ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ሲፈጥርበት ወይም ረብሻ ሲፈጥርበት መሆኑን ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች ይዘት የሚያሣዩትም ይህንኑ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ከላይ ከተገለፀው ነጥብ በተጨማሪ የሚያስገንዝቡት ነጥብ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅራቢ የተሻለ የይዞታ መብት ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በቤቱ ላይ ከአመልካች የተሻለ መብት የሌላቸው መሆኑ፣ አመልካች ቤቱን የያዙት በቀበሌው ስምምነት የተከራይነት መብት አግኝተው እንጂ በኃይል አለመሆኑ የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች የተመለከቱት ሕጋዊ መሥፈርቶች አለመሟላታቸውን በቀላሉ ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ተግባር ሁከት ሊባል የሚችልበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. አራ-03095 ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ፣ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05585 መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የዚሁ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት በመ/ቁ. 06753 ሐምሌ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2/ አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጠሩት ሁከት የለም ብለናል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በጋራ የሚገለገሉበት ወይም እኩል ተካፍለው የሚከራዩበት ሕጋዊ ምክንያትም የለም ብለናል፡፡

3/ ለክርክሩ የተደረገውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 38169

ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ.ፈ. ሂሩት አስራት

ተጠሪ፡- የወ/ሮ ንጋቷ ዘለቀ ወራሽ አቶ እሸቱ ቦጋለ - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ከሣሽ ተጠሪ የሥር ተከሣሽ ነበሩ አመልካች ባቀረቡት ክስ በወረዳ 17 ቀበሌ 24 ቁጥር 360 የሆነውን ቤት ወ/ሮ ንጋቷ ዘለቀ ከ1973 ጀምሮ በመያዝ ክራይ ሣይከፍሉና የኪራይ ውል ሣይሞሉ እስከ የካቲት 1990 ድረስ ሲገለገልበት ከቆየ በኋላ ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው የተጠሪ ወራሽ የሚች ወራሽነኝ በማለት ቤቱን በመያዝ ክራይ ሣይከፍሉ ይገለገሉበታል የሥር ሁለተኛ ተከሣሽም የሚች ዘመድነኝ በማለት ቤቱን እየተገለገሉበት ስለሆነ ሁለቱም ተከሣሽ ኪራይ ሣይከፍሉ ከውል ውጭ በሕገ ወጥ መንገድ ቤቱን በመያዛቸው አመልካች አከራይቶ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም አጥቷል፡፡ ስለዚህ ያለ አግባብ የበለፀጉበትን እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 1994 የቤቱን ኪራይ በወር 54 እያከራየ ሊያገኝ የሚገባውን ብር 14,193.76(አስራ አራት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ሦስት ብር ከሰባ ስድስት ሣንቲም) ከወለድ ጋር 150,628.55 በአጠቃላይ(አንድ መቶ ሃምሣ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሃምሣ አምስት ሣንቲም) ብር 164,817.41 (አንድ መቶ ስልሳ አራት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሰባት ብር ከአርባ አንድ ምንቲም) በአንድነትና በነጠላ ከፍለው ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ሲል ጠይቋል፡፡

(ተጠሪ) ተከሣሽ ለቀረበበት ክስ መልሱን ሲሰጥ አመልካች የጠቀሰው የኪራይ ግምት የተጋነነ ነው፡፡ አመልካች በቤቱ ላይ ያለውን መብትና ጥቅም ባለማረጋገጡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2)(3) መሠረት ክስ ማቅረብ አይችልም ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም፡፡ በይርጋ ይታገዳል ካሉ በኋላ በአማራጭም መልሳቸውን ሲሰጡ አውራሻችን ወ/ሮ ንጋቷ እና እኔ በአንድነት ስንኖርበት ቆይተናል ቤቱ የተሰጠን በቀድሞ የደርግ መንግሥት የከተማ ልማት ቤት ምንስተር ትዕዛዝ መሠረት የቤተ መንግሥት አካባቢ በራሳችን ወጪ ሠርተን ስንጠቀምበት ለነበረው ቤታችን በልዋጭነት ነው፡፡ አመልካች በራሱ ተምኖ ያቀረበው ገንዘብ መጠን ሕጋዊ አይደለም ስለዚህ አመልካች ያቀረበው ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባዋል ሲል መልሱን ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበውን ክስ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ውሣኔ ሰጥቷል በውሣኔውም የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ውስጥ በፍ/ሥ/ሥ/ቁ 33(2)(3) መሠረት አመልካች መብትና ጥቅም ስለሌለው ሊከሰን አይገባም ያሉትን ነጥብ ብቻ መርምረዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ ቤቱን ያስረክቡኝ የሚል ነው ይሁን እንጂ አመልካች ለተጠሪም ሆነ ለሌላ ሰው እያከራየ የሚያስተዳድር መሆኑን ወይም ቤቱ መወረሱን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም በቤቱ ላይ አለኝ የሚለውን መብት ወይም ጥቅም ምን እንደሆነ አላረጋገጠም ስለዚህ መቃወሚያውን በመቀበል ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33(2)(3) መሠረት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር አመልካች ይህን ቤት በሥሩ ይዞ የሚያስተዳድረው የገነባው ወይንም በመንግሥት የተወረሰ ለመሆኑ አላስረዳም በተጨማሪም የቀረበው ማስረጃም ቤቱን እንዲያስተዳድር መብት ሊሰጡ የሚችሉ አይደሉም ከቤተ መንግሥት ተዕፏል የተባለው ደብዳቤም ቢሆን ቤቱ የቤተ መንግሥት መሆኑን አያረጋግጥም፡፡ ስለዚህ አመልካች ክስ በቀረበበት ቤት ላይ መብት የለውም ሲል የሥር ውሣኔን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) አፅንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አመልካች በ29/9/2000 ዕፎ ባቀረበው ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ ሲል እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪውን አስቀርቦ ክርክራቸውን ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች መብት ወይም ጥቅም የለውም በማለት የተሰጠውን ውሣኔ ለመመርመር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ይህንን ነጥብ ግራቀኙ ካቀረቡት ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እና የክርክሩን አመጣጥ ባጭሩ ስናይ አመልካች ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን ቤት ተጠሪ ወራሽ ነኝ በማለት ብቻ መብት ሣይኖራቸው ክራይ ሣይከፍሉ በሕገ ወጥ መንገድ እየተገለገሉበት ነው በማለት ውዝፍ ኪራይ ከፍለው ቤቱን እንዲለቁ በመጠየቁና ተጠሪም በበኩሉ ቤቱ የአመልካች እንዳልሆነና ቤቱን በደርግ ትዕዛዝ የከተማ ልማት በራሱ ወጪ ለሰራሁበት ቤት በልዋጭ ያገኘሁት ነው፡፡ ሊከሰኝ አይችልም ሲል በመከራከሩ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም እንዳለው አላስረዳም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

እኛም አመልካች በተጠቀሰው ቤት ላይ ክስ የማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የለህም የተባለው አስመልክቶ በመዝገቡ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ፅሑፍ (ደብዳቤ) ሆነ የግራ ቀኙ በሰበር ችሎት ያካሄዱትን የቃል ክርክር በጥልቀት እንደመረመርነው የተጠሪ አውራሽ (ሟች) የቤተ መንግሥት አገልጋይ የነበሩና የቤተ መንግሥት አስተዳደር በሰጣቸው ቤት ውስጥ ሲኖሩ የነበረ በመሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ይህ ክርክር የተነሳበት ቤት በጦርፍ ምክንያት በመፍረሱ ለቤተ መንግሥት አስተዳደር ቤቱን በጊዜያዊነት የተጠሪ አውራሽ በሕይወት እስካሉ እንዲገለገሉበት የተፈቀደላቸው እንጂ በልዋጭ የተሰጣቸው እንዳልሆነ ፍ/ቤቱ ተረድቷል ቤቱም በወቅቱ በነበረው የከተማ ልማትና የቤት ሚንስተር ትዕዛዝ ነው እንዲኖሩበት የተደረገው ይህ ማለት ደግሞ ቤቱ የመንግሥት መሆኑን ያስረዳል፡፡ ቤቱ የመንግሥት ከሆነ ስለ ቤቱ የመከራከር መብቱ መንግሥትን የወከለው ተቋም ነው እሱም አመልካች (የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ) ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያደርሰናል፡፡

ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ሳያገናዝቡ አመልካች ለመክሰስ መብት ወይም ጥቅም የለውም ሲሉ የሰጡት ውሣኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33(2) መንፈስ ውጪ በመሆኑ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 21285 በቀን 20/1/98 እና የፌ.ከ/ፍ/ቤት በመቁ 43105 መጋቢት 2/2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የመክሰስ መብት አለው ብለናል፡፡
3. የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍሬ ነገሩ ላይ በማከራከር ሕጋዊ ውሣኔ ይስጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት መዝገቡን መልሰናል፡፡
4. የወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39539

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ ስአማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ አስተዳደር ግብርና ቢሮ - ነ/ፈጁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ አቶ አበበ ዓባይ ዘጠኝ ሰዎች - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሁከት ይወገድልንን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪዎች በቂሌንጦ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ክልል ከ26 ዓመታት በላይ ግብር እየገበሩ በቦታው ከ6000(ስድስት ሺህ) ዛፎች በላይ ተክለው ከብቶቻቸውንም የሚያቆሙበትን ቦታ የአሁኑ አመልካችና ሦስት ሰራተኞቹ በኃይል ያስለቀቋቸውና ሁከት የፈጠሩባቸው መሆኑን ገልጸው ሁከቱ ተወግዶ ይዞታቸው እንዲመለስላቸው ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካችና ሰራተኞቹ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ መሬቱ የመንግስት እንጅ የተጠሪዎች አለመሆኑን፣ቦታው ለምለም ቦታ የተከለለ መሆኑን ገልፆ የተጠሪዎች ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረና ተጨማሪ ማስረጃም ተገቢ ነው ካለው አካል ከጠየቀ በኋላ ቦታው ለደን ቦታ ተብሎ የተተከለ ቢሆንም ባለይዞታነቱ ግን የተጠሪዎች መሆኑ መረጋገጡ፣ የደን ክልልም በመንግስት ብቻ የሚከለል ሣይሆን በቀበሌ ማህበረሰብና በግለሰብ ሊከናወን እንደሚችል ከደን አዋጅ መረዳት የሚቻል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ አመልካች ከሰራተኞቹ ጋር ሁኖ የፈጠረው ሁከት አለ በማለት ሁከቱ እንዲወገድ፣በቁጥር ብር 1000.00(አንድ ሺህ) ለተጠሪዎች እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርቦ ይኸው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች ለዚሁ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታው አቅርቦ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 4/አራት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪዎች ለክርክሩ መነሻ በሆነው ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ያላቀረቡ መሆኑን፣ቦታው የመንግስት ስለመሆኑ ሕገ-መንግስቱና አግባብነት ያላቸው አዋጆች እየደነገጉ ከእነዚህ ህግ ጋር አኳያ ጉዳዩ አለመታየቱን፣ደን በቦታው ላይ ለማልማት ስልጣንና ኃላፊነቱ የተሰጠው ለአመልካች ሆኖ በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ላይ በጸደቀው መሰረት የደን ልማት ስራ ማከናወን የሚችል መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱን ዘርዝሮ ሁከት ይወገድ ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ተደርጐ መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ 4/አራት/ ገጽ ማመልከቻ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ቅሬታ ነጥቦች እውነት የሌላቸው፣የፈራጅን ህሊና ሊያሣምን በሚችል መልኩ ተቀነባብረው መቅረባቸውን፣ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቦታ ከ35 ዓመታት በላይ ይዘው የሚጠቀሙት ስለመሆኑና የአመልካች እርምጃ ከሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40/4/ ስር ጥበቃ ከተደረገው መብት ጋር ተቃራኒ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ ሊፀና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነ/ፈጅም ሚያዝያ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ሁከት ፈጥሯል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቦታ ተጠሪዎች ለበርካታ ዓመታት በይዞታችን ስር አድርገን እየተጠቀምንበት የሚገኝ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን፣ፍ/ቤቱ ባደረገው ማጣራትም መሬቱ ለተጠሪዎች በ1991 ዓ.ም ለግጦሽ መሬት ተብሎ የተሰጠ መሆኑን ቀበሌው ያረጋገጠው መሆኑን፣በ1991 ዓ.ም ቦታው የደን ቦታ ተብሎ የተከለለ መሆኑን የስር ፍ/ቤት አረጋግጦ የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው ደን በመንግስት ብቻ የሚከለል አይደለም በማለት ስለመሆኑ ነው፡፡

በመሰረቱ የአመልካች ክርክር ዋቢ ያደረገው የአዲስ አበባ ከተማ መሪ ፕላን ማጽደቂና የአፈፃፀም አዋጅ ቁጥር 7/1986 “ን” ነው፡፡ ይህ አዋጅ በአንቀጽ 2/5/ ስር የመሪ ፕላን ትርጉምንና የሚያዛቸውን ካርታዎች ዓይነት አስቀምጧል፡፡ ለዚህ ክርክር አግባብነት ያለው የካርታ ዓይነትም የለምለም ክልል ካርታ ሲሆን አዋጁ በአንቀጽ 2/5/ሸ/ ስር የተደነገገው ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 21 ስለለምለም ክልል ካርታ ይዘት፣አንቀጽ 22 የለምለም ክልል ማለት ጥበቃና እንክብካቤ፣አንቀጽ 23 ደግሞ የዛፎችና እጽዋቶች ልማትና እንክብካቤ ከደነገጉ በኋላ በአንቀጽ 24 የክልል መስተዳደሩ በለምለም ክልል ካርታው ላይ የተመለከቱትን ክልሎች የመጠበቅ፣ የመንከባከብ፣ ወይም እንዲጠበቁ የማድረግ፣ እንዲለሙ የታቀዱትን የለምለም ክልሎች ስለሚለሙበት፣ ስለሚጠበቁት ሁኔታ አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቦታ ለደን የተከለለ ስለመሆኑ ማረጋገጡን፣ሰራተኞች ጉድጓድ አስቆፍረው በቦታው ላይ ችግኝ ያስተከሉትም ከቢሮው በተሰጠው መመሪያ ስለመሆኑ አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አዋጁ አመልካች ተግባርና ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑ ያሣያል፡፡

ተጠሪዎች ላቀረቡት ክርክር የማስረዳት ብቃት ያለው ማስረጃ ያላቀረቡ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ያሣያል፡፡ ፍ/ቤቱ ተጠሪዎች ያቀረቡት ማስረጃ የማስረዳት ብቃት የሌለው መሆኑን አምኖም ተገቢ ነው ካለው አካል ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪዎች ቦታው ላይ የተደረገውን የአመልካች እንቅስቃሴ ሁከት ነው ለማለት የቻሉት በ1991 ዓ.ም በተደረገው የግጦሽ መሬት ክፍፍል ተሰጥቷቸዋል የሚል ማረጋገጫ ከቀበሌ ገብሬ ማህበር ስለተላከላቸው እንጂ በህጉ አግባብ የይዞታ ማረጋገጫ በማቅረብ አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ የተጠሪዎች ህጋዊ የሆነ የይዞታ መብት ያላቸው መሆኑ ከተረጋገጠም ከፍ/ቤት የሚጠይቁት ዳኝነት የሁከት ይወገድልኝ ሣይሆን የካሣ ጥያቄ ስለመሆኑ የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40/8/ እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የወጣው አዋጅ ቁጥር 455/1997 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ እንደሚታወቀው የአንድ ንብረት ባለ ይዞታ የሆነ ሰው ይዞታውን ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈጸምን ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ወይም ንብረቱ እንዲመለስለት ሕጉ ከአስቀመጣቸው መንገዶች አንዱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149/1/2/ ስር የተመለከተው ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ መቅረብ የሚችለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ነገር በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረው ነው፡፡ እንዲሁም የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም ዓይነት መብት በሌለው ሰው ስለመሆኑም የተጠቃሹ ድንጋጌ መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ በሌላ አገላለጽ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅራቢ ከተከሣሹ የተሻለ የይዞታ መብት ያለው ስለመሆኑ ማሣየት ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም ይህንኑ ያስረዳ ከሣሽ ጥያቄው ተቀባይነት የሚያገኘው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች የተመለከቱትን መብቶች የሚገድብ ሌላ ሕግ በሌለበት ሁኔታ ነው፡፡ የይዞታ መብት ፍጹም አይደለም፡፡ በሕጉ አግባብ ሌላ መፍትሔ ሊሰጥበት የሚችል ነው፡፡ ከእነዚህ መፍትሔዎች መካከልም ይዞታው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲወሰድ ካሣ የሚከፈልበት ስለመሆኑ አንዱ ነው፡፡

የአመልካች ጥያቄም ተጠሪዎች በቦታው ላይ ህጋዊ የባለይዞታነት የላቸውም ከሚል በተጨማሪ በአዲስ አበባ ከተማ መሪ ፕላን ማጽደቂያና አፈፃፀም አዋጅ ቁጥር 7/1986 መሰረት ድርጊቱ ሁከት ሊባል የሚገባ አይደለም የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች በቦታው በዚህ አዋጅ መሰረት የደን ተብሎ አለመከለሉን አላረጋገጡም፡፡ ይልቁንም ቦታው ለደን ተብሎ የተከለለ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤትም አረጋግጧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንግዲህ የአዋጅ ቁጥር 7/1986 አንዱ ዓላማ በአዲስ አበባ መስተዳድር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መሰረት የከተማው እድገት ስርአት እንዲይዝና እንዲፋጠን ማድረግ ስለመሆኑ በመግቢያው ላይ ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የክልል መስተዳደሩ በለምለም ክልል ካርታው ላይ የተመለከቱትን ክልሎች እንደሚጠብቅ እንደሚንከባከብ፣ወይም እንዲጠበቁ የማድረግና እንዲለሙ የታቀደበትን የለምለም ክልሎች ስለሚለሙበት፣ስለሚጠበቁበት ሁኔታ አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑ ተጠቃሹ አዋጅ በአንቀጽ 24 ስር በግልጽ አስፍሯል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ቦታው በደን የተከለለ መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካችና ሰራተኞቹ ጉድጓድ በማስቆፈር ችግኝ ማስተከላቸው በሕጉ የተፈቀደ ተግባር ነው ከሚባል በስተቀር ሁከት ሊባል የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪዎች ቦታውን በሕጉ አግባብ የያዙትና ያለሙት ዛፍ ካለም በሕጉ አግባብ ካሣ የመጠየቅ መብት ይኖራቸዋል እንጂ ይዞታውን ልንለቅ አይገባም፣ሁከቱ ሊወገድ ይገባል በማለት ሊከራከሩ የሚችሉ አይደሉም፡፡ አመልካች ሁከት ፈጥሯል በማለት በማስተር ፕላኑ መሰረት ቦታውን ለአረንጓዴ ክልል በማዋል እንዳይንከባከብና እንዳይጠበቅ ማድረግ ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ሕጋዊ ምክንያት የሚሰጠው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች አድራጉት ሁከት ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንጋጌዎችን ከአዲስ አበባ ከተማ መሪ ፕላን ማጽደቂና የአፈፃፀም አዋጅ ቁጥር 7/1986 አንቀጽ 2/5/፣21፣22፣23 እና 24 ድንጋጌዎች ጋር ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 319/92 ሰኔ 08 ቀን 1996 ዓ.ም ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው በመ/ቁ. 01595 ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም፣እንዲሁም በሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 05481 ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪዎች ላይ የፈጠረው ሁከት የለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ የሚያቀርቡትን ሌላ ህጋዊ ጥያቄ ይህ ውሣኔ አያስቀርም ብለናል፡፡
4. ለክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38666

ሐምሌ 9 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ ታምራት አባተ

ተጠሪ ፡- ባላንባራስ ተስፋዬ ገ/እየሱስ - ጠበቃ ገ/እግዚአብሄር ተስፋዬ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ በትግራይ ብ/ክ/መ/በመቀሌ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ ለአቶ ተስፋዬ ፍትዊ ለሰጠው ብድር መያዣ የሆነ በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ኩሃ ቀበሌ የሚገኝ በ35259 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሠፈረ መጋዘንን ዕዳው ሳይከፈል በመቅረቱ ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 መሠረት አመልካች ከተበዳሪው ላይ ተረክቦ በማስተዳደር ላይ እያለ ተከሣሽ ከዚሁ ባለዕዳ ላይ ለሚፈልጉት ገንዘብ ይሄው ንብረት እንዲሸጥ ጠይቀው በሐራጅ ባለመሸጡ ምክንያት ንብረቱን እንዲረከቡ በፍ/ቤት ትዕዛዝ በመስጠቱ ንብረቱን መረከባቸው ተገቢ እንዳልሆነ በመጥቀስ ይመለስልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽም ቀርበው በሰጡት መልስ ንብረቱን የተረከቡት ዕዳው ሳይከፈል በመቅረቱ ምክንያት የተጠቀሰው መሬትና መጋዘን ባለዕዳው በባለይዞታነት የሚጠቀምበት መሆኑን በመግለጽ ይሄው ንብረት እንዲሸጥ ተጠይቆ ሁለት ጊዜ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዢ ባለመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/428/2/ መሠረት የፍርድ ባለመብቱ እንዲረከበው ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሠጥቶ በዚሁ መሠረት የተረከብኩት ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ የብድር ዕዳው ሳይከፈለው በመቅረቱ ምክንያት ንብረቱን ተረክቤያለሁ ቢልም ንብረቱን ስለመረከቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1723/1/ መሠረት ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ ተከሣሽ ንብረቱን በሐራጅ የሚገዛ በመጥፋቱ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/428/1/ በሚፈቅደው መሠረት የተረከበ ስለሆነ ንብረቱን ሊመልስ አይገባም በማለት የከሣሽን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው ሲል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/337 መሠረት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሠበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በመያዣ ይዞት የነበረውን ንብረት አግባብ ባለው አካል ከማስመዝገብ አልፎ በስሙ በርስት መዝገብ አላስመዘገበም ተብሎ በመያዣ የያዘውን የተረከበውን ንብረት ለተጠሪ እንዲያስረክብ መባሉ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥና ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች አቶ ተስፋዬ ፍትዊ የተባሉ ግለሰብ የተበደሩትን ገንዘብ ባለመክፈላቸው ምክንያት በመያዣ የያዘውንና ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነውን መሬትና መጋዘን አዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 በሚፈቅደው መሠረት ገዢ በመጥፋቱ ምክንያት ተረክቦት እንደነበር መረጋገጡን ተገንዝበናል በሌላ በኩልም የአሁን ተጠሪ በዚሁ ባለዕዳ በአቶ ተስፋዬ ፍትዊ ላይ አስፈርደው አመልካች በመያዣ ይዞት የነበረውና በኋላም የተረከበው መጋዘን በሐራጅ እንደሸጥ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሲሰጥ አመልካች ንብረቱን በመያዣ ይዞት እንደነበረና ዕዳው ባለመከፈሉ ምክንያትም ንብረቱ በሐራጅ ለመሸጥ ተሞክሮ ገዢ በመጥፋቱ ምክንያት ከፍ ብሎ በተጠቀሱት አዋጆች መሠረት ንብረቱን እንደተረከበ በመግለጽና በንብረቱም ላይ መብት እንዳለው በመጥቀስ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/444 መሠረት ሽያጩን በመቃወም አመልካች አቤቱታ አቅርቦ እንደነበረና ፍ/ቤቱም አቤቱታው የቀረበው ዘግይቶ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ማድረጉንም ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

በዚህ መልኩ አቤቱታው ተቀባይነት ሳያገኝ ከቀረ አመልካች በዚህ ጉዳይ ላይ ክስ ከማቅረብ እንደማይታገድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/421 እና 455 ላይ ተመልክቷል፡፡

አመልካች በዚሁ መሠረት አቤቱታውን ሲያቀርብ የከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታውን ሳይቀበለው የቀረው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ንብረቱን ስለመረከቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1723/1/ መሠረት ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ስላልተደረገ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

ይሁንና የንብረት ባለሀብትነት ከሕግ ወይም ከውል የሚያመነጭ ሲሆን አመልካች በዚህ ንብረት ላይ ባለሀብትነትን አቋቁሜያለሁ የሚለው ከውል ሳይሆን ከሕግ ነው፡፡ ይሄውም አመልካች በመያዣ የያዘው ንብረት ዕዳው ባለመከፈሉ ምክንያት በሐራጅ መሸጥ ካልቻለ ንብረቱን መረከብ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 98/90 ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚሁ መሠረትም ይህንኑ ንብረት የተረከበው ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደመሆኑ መጠን አመልካች የንብረቱ ባለሀብት መሆን የቻለው ከሕግ በመነጨ መብት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ/1723 ተፈፃሚነቱ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብትነት በውል ማስተላለፍ በተፈለገ ጊዜ ስለሆነ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ለጉዳዩ ዕልባት መስጠቱ አግባብነት በሌለው ሁኔታ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬትና መጋዘን በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መረከቡ ከተረጋገጠ ይህንኑ ንብረት በሌላ ዕዳ ምክንያት ተጠሪ እንዲረከቡት ትዕዛዝ ሲሰጥ የተረከበውን ንብረት በአመቺው መንገድ በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ የማድረግ መብቱን የሚጋፋ ነው፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የፍርድ ባለመብት የሆኑበት ጉዳይ አመልካች በሕግ አግባብነት የንብረቱ ባለቤት በሆነበትና ለዚህ ክርክር ምክንያት በሆነው መሬትና መጋዘን ላይ አፈፃፀም ሊቀጥል የማይገባው ሆኖ ሳለ የመቀሌ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን ድንጋጌ በመጥቀስ የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የመቀሌ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05134 በ24/6/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 24088 በ8/9/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ኩሃ ቀበሌ የሚገኘው 35259 ካ.ሜትር ቦታ ላይ የሠፈረውን መጋዘን አመልካች በሕግ አግባብነት የተረከበው ስለሆነ ተጠሪ መልሰው ለአመልካች እንዲያስረክቡ ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ መሠረትም እንዲፈጽም የፍርዱ ግልባጭ ለመቀሌ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡
4. የግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሸ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጭ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34544

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን- ነገረ ፈጅ አቶ መስፍን ሃብቱ ይመር - ቀረበ

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ፋጤ ዓሊ - በሌሉበት የሚታይ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ጉዳይ በይግባኝ ተመልክቶ በኮ.መ.ቁ. 48755 ታህሳስ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ የሰበር አቤቱታውን በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡ የአሁን መልስ ሰጭ በጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ በመሆን በባለቤቷ ሞት ምክንያት በእራሷ እና የሞግዚትነት ሥልጣን ባገኘችባቸው ልጆቿ ስም ደረሰ ያለችውን ጉዳት አስልታ የጉዳት ካሣ ገንዘብ በአሁን አመልካች ላይ ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት የተነሳ የክስ አቤቱታ አቅርባለች፡፡

የአሁን አመልካችም በዚህ አካኺን ለቀረበበት ክስ ጉዳቱ ደርሷል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ ሁለት ዓመት ያለፈው በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል የሚለውን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ካቀረበ በኋላ ስለ ፍሬ ጉዳዩም ያለውን የመከራከሪያ ነጥቦች በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡

ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ ክሱ ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው ድርጊት ከተፈፀመ ሁለት ዓመት ካለፈው በኋላ የቀረበ መሆኑ ቢታወቅም ጉዳቱ ሞት ነው፤ የደረሰው ጉዳት ሞት በሆነ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም የሚለውን ምክንያት አስፍሮ ክሱ በይርጋ ሊቋረጥ አይችልም የሚል ዳኝነት ሰጥቶ በአሁን አመልካች ላይ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ጠቅሶ የካሣ ገንዘቡን በሚመለከት ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ ብር) በርትእ እንዲከፈል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ ይኸው ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ ሙሉ ክርክር ካደረገ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውንም ሆነ የኃላፊነቱን ነጥብ በሚመለከት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭ በዚሁ የሰበር አቤቱታው መነሻነት ቀርባ መልስ እንድትሰጥበት ቢታዘዝም ጥሪ ደርሷት ያልቀረበች በመሆኑ ጉዳዩ በሌለችበት ታይቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ በዚህ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው ይርጋን አስመልክቶ ለቀረበው ክርክር የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትርጉም የሕግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡

ምንም እንኳ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ነጥብ በሚመለከት ዳኝነት ያልሰጠበት ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ቢያስረዳም የአሁን አመልካች ለዚሁ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረበውን የይግባኝ ማመልከቻ ቅጅ እንዳየነው የይርጋ ጉዳይ በመቃወሚያነት በመጀመሪያ ደረጃው ፍ/ቤት እንስቶ የተከራከረበት መሆኑን ገልፆ ክሱ በመቃወሚያው ክርክር መቋረጥ የሚገባው ሆኖ እያለ ያለአግባብ መታለፉ ቅሬታ የፈጠረበት መሆኑን ጠቅሶ በይግባኝ የተከራከረበት ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ከክርክር አቀራረብ ሥርዓት አንፃር ይህ የሰበር አቤቱታ ደረጃውን ሳይጠብቅ የቀረበ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ወደ ተያዘው አከራካሪ ነጥብ ስንመለስ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ ጉዳቱ ደረሰ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ የቀረበ ለመሆኑ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የክሱም ምክንያት ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ይህም ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 እንደተደነገገው ማናቸውም የጉዳት ካሣ ክስ ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ካልቀረበ በቀር ክሱ በይርጋ የሚቋረጥ ነው፡፡ ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ሲባል ደግሞ ሞትንም እንደሚያካትት ይኸው ሕግ በማያሻማ አኳኋን ደንግጐ እያለ፤ ክሱ የቀረበለት የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዚህ በግልጽ ከተደነገገው ሕግ በመራቅ የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ጉዳት ሞት ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል አይደለም በማለት የይርጋውን ክርክር ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ቀድሞውንም ቢሆን ስለኃላፊነቱ ከማከራከሩ በፊት ክሱ በይርጋ ይቋረጣል በማለት መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በተሳሳተ የሕግ አተረጓጐም የተነሣ የተሟላ የክስ መስማት ሂደት ማከናወኑ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛው ፍ/ቤት በፍት/መ/ቁ. 6/95 ግንቦት 06 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 48755 ታህሳስ 07 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የአሁን መልስ ሰጭ በአመልካች ላይ ያቀረበችው የጉዳት ካሣ ክስ ከውል ውጭ በሚደርሰው ኃላፊነት ሕግ እንደተመለከተው በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ የተቋረጠ ነው ብለናል፡፡

ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 33201

ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ የሺጥላ ተሾመ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሼል ኢትዮጵያ - ጠበቃ አጥናፉ ቦጋለ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች ንብረትነቱ የተጠሪ በሆነው የነዳጅ ማደያ ላይ በደረሰው የቃጠሎ አደጋ መንስኤነት አመልካች የሚያስተዳድረው አድራሻው ወረዳ 18 ቀበሌ 27 የቤት ቁጥር 303 የሆነው ቤት ተቃጥሎ ጉዳት የደረሰበትን ቤት ተጠሪ በማደስ ለአመልካች ቢያስረክብም በእድሣቱ ምክንያት ቤቱ በመዘጋቱ አመልካች የኪራይ ገቢ ማጣቱን በመግለጽ አመልካች ከኪራይ ገቢ ያጣውን ብር 6375.00 /ስድስት ሺህ ሦስት መቶ ሰባ አምስት ብር/ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር እንዲከፍለው ይወሰንለት ዘንድ በአሁኑ ተጠሪ ላይ ነሐሴ 26 ቀን 1997 ዓ.ም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረተው ክስ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርቦ የአመልካችን ቤት ያጣደሰው የነዳጅ ማደያው ስራ እንዳይቆም እንጂ አላፊነትን በመቀበል አለመሆኑን፣ ለጉዳት አላፊነት ያለበት አካልም በወቅቱ የነዳጁ አጓጓዥ የነበረው ኢነርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የወከለው ቴዲ ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ሹፌር መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት አላፊ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ሲል የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚልበትን ምክንያቶች በ15/01/2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዘርዝሯል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የተቃጠለው የነዳጅ ማደያም ሆነ ለቃጠሎው መንስኤ የሆነው በወቅቱ በመራገፍ ላይ የነበረው ነዳጅ ባለቤት ሼል ኢትዮጵያ ሊሚትድ እንጂ ሌላ ባለመሆኑ ከአላፊነት ነፃ መባሉ ያላግባብ ስለሆነ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊሻር ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን ሠጥቷል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ አመልካች በሰበር ባላነሣው የሕግ ነጥብ የበታች ፍ/ቤቶች ስህተት ፈጽመዋል ሊባል ስለማይገባ የሠበር አቤቱታው ውድቅ ሆኖ ይወሰንልኝ በማለት መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ በበታች ፍ/ቤት የሕግ ድንጋጌ ተጠቅሶ ክርክር አለመቅረቡ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በመለየት ውሣኔ መስጠት የፍ/ቤት የስራ ድርሻ ከመሆኑ አኳያ በስር ያልተነሣ የክርክር ነጥብ ሊባል አይችልም በማለትና የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር መጋቢት 01 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምሮታል እንደመረመረውም ለአመልካች የተቋረጠ የኪራይ ገቢ ይከፈለኝ ጥያቄ ተጠሪ አላፊነት የለበትም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን? በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ የቃጠሎ አደጋ የደረሰበት ነዳጅ ማደያ ባለቤት መሆኑ ቃጠሎውን ያስነሣው መኪና ባለቤት ከተጠሪ ጋር የአጓጓዥነት ስራ የተዋዋለ ሰው መሆኑ፣ በቃጠሎው የአመልካች ቤት መጎዳቱና ተጠሪ ይህንኑ በቃጠሎው የተጎዳውን ቤት በማሣደስ ለአመልካች ማስረከቡ የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የተቋረጠውን የኪራይ ገቢ እንዲከፍል በአመልካች በኩል የቀረበበት ክስ ውድቅ የሆነው ቃጠሎውን ያስነሣው መኪና ሹፌር በፈፀመው ስለሆነ እና ሹፌሩ የተጠሪ ተቀጣሪ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ነዳጁ ሲራገፍ የነበረው ተጠሪ ስራውን በሚያከናውንበት የነዳጅ ማደያ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ የተጠሪ አላፊነት የሚመነጨው ከሚያከናውነው ስራ አደገኝነት አኳያ ታይቶ ነው፡፡ ማንም ሰው ስራው በሚያደርሰው ጉዳት ምክንያት ጥፋት ባይኖርበትም ከውል ውጪ አላፊነት ሊከተልበት እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2066 - 2089 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡

በእጃችን ላለው ጉዳይ አግባብነት የሚኖረው ድንጋጌም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2069/1/ ሲሆን ተጠሪ በሚያከናውነው የነዳጅ ማደያ ስራ ለሚከሰተው አደጋ አላፊነቱን ሊወስድ እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡ ምክንያቱም የነዳጅ ማደያ ስራ ጥንቃቄ የሚያስፈልገውና በቀላሉም የመቀጣጠል ወይም የመፈንዳት ባህርይ ስላለው የአደገኛ ስራ ባህርይነት ኑሮት አጥፊ ሣይሆን አላፊ መሆንን የሚያስከትል ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አላፊነት የለብኝም የሚል ክርክር ሣያቀርብ በስር ፍ/ቤት ተነስቶ ክርክር ያልተደረገበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ በዚህ ችሎት በሰጠው መልስ ተከራክሯል፡፡ ይሁን እንጂ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ መጥቀስ የፍ/ቤት የስራ ድርሻ ከመሆኑ አኳያ የተጠሪ ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329/1/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ባገናዘበ መልኩ ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የአመልካች ቤት በቃጠሎው ከወደመ በኋላ አድሶ ማስረከቡን ሣይክድ ይኸው ተግባሩ አላፊነቱን መቀበሉን አያሣይም የሚል ክርክር ማቅረቡ አሣማኝነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የአሁኑ ተጠሪ ከአላፊነት ነፃ የተደረገው የግራ ቀኙን ክርክር እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2069/1/ ድንጋጌን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57875 ጥቅምት 06 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 51136 ሠኔ 27 ቀን 1999 የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ ተጠሪ በሚያከናውነው ስራ አደገኛነት የተነሣ በአመልካች ንብረት ላይ ባደረሰው ቃጠሎ ምክንያት የተቋረጠውን የኪራይ ገቢ የመተካት አላፊነት አለበት ብለናል፡፡

3/ ተጠሪ ለአመልካች ብር 7968.75 /ሠባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከሰባ አምስት ሣንቲም/ ይክፈል ብለናል፡፡

4/ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5/ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31721

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐሳስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ብዙነሽ ኃ/ዮሐንስ - ጠበቃ መድሕን መሐሪ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ስንታየሁ እሸቱ - በሌለችበት

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ከውል ውጪ የደረሰ ኃላፊነትን መሠረት አድርጎ የቀረበ የካሣ ክፍያ ጥያቄን /ክርክር/ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሶማሌ ብ/ክ/መ/ በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ስትሆን በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችውም የምትወልደው ልጅዋ ሦስት ሕፃናት ልጆቹን አርዶ ስለገደለብኝ በእናትነትዋ ካሣ ልትከፍለኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠችው መልስ ጉዳዩ በፈጸመው ድርጊት ኃላፊ የምሆንበት የሕግ ምክንያት የለም፤ መከሰሴም ያለአግባብ ነው፤ በማለት ስለመከራከርዋ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሣሽ ላደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናት በመሆኑም በጠቅላላው ብር 350000(ሰላሳ አምስት ሺህ) ካሣ ለከሣሽ ትክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማለትዋ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች ብር 78000(ሰባት ሺህ ስምንት መቶ) ካሣ እንድትከፍል ወስኖአል፡፡ በጨረሻም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ከአመልካች በቀረበለት አቤቱታ መነሻነት ክርክሩን ከሰማ በኋላ በጠ/ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ በተደረገላት ጥሪ መሠረት ባለመቅረብዋ ክርክሩ የተሰማው እሷዋ በሌለችበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ የምትሆንበትና ካሣ የምትከፍልበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ ባጭሩ እንደተመለከተው አመልካች የተከሰሰችው እና በመጨረሻም ኃላፊ ነሽ የተባለችው እርስዋ በፈጸመችው ድርጊት ጉዳቱን አድርሳለች በሚል አይደለም፡፡ ጉዳቱን አድርሷል የተባለው የእሷ ልጅ የሆነው ሰው ነው፡፡ እርሱም ልጆቹን ከገደለ በኋላ ራሱንም እንዳጠፋ በተጠሪ ክስ ተገልጾአል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰውየው አካለ መጠን የደረሰና ዕድሜውም ከ40 ዓመት በላይ እንደነበረ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪ ክሱን የመሠረተችው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2125 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ ሲሆን ይህ ድንጋጌ የሚያመለክተው በአባት አላፊነት ምትክ ሆነው ስለሚጠየቁት ሰዎች ነው፡፡ ድንጋጌው የሚገኘው "ለሌላ ሰው ተግባር አላፊ ስለመሆን" በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13 በምዕራፍ 1 /ከውል ውጪ ስለሚደርስ አላፊነት/ በሚለው በክፍል 4 ስር ነው፡፡ ከቁጥር 2125 በፊት ያለው ቁ. 2124 አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ አላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሠራ እንደሆነ በፍትሐብሔር በኩል ለተሠራው ሥራ አላፊ የሚሆነው አባት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ቁጥር 2125 ደግሞ አባት በሌለ ጊዜ በሱ ምትክ ኃላፊ የሚሆኑትን በተመለከተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚደነግግ ነው፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዷ የልጁ እናት እንደሆነችም በዚሁ ቁጥር 2125/ሀ/ ተመልክቶአል፡፡ እንግዲህ እንደተጠሪ ክስ አመልካች ኃላፊ ልትሆን ትችል የነበረው ጉዳቱን አድርሷል /የተጠሪን ልጆች ገድሎአል/ የተባለው ሰው አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ቢሆን ነበር፡፡ ይህ ግን በተጠሪ በኩል አልተረጋገጠም፡፡ ጉዳት አድራሹ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ነው የሚል በተጠሪ ክስም ሆነ ክርክር አልተነሳም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ ጉዳት አድራሹ ሰው ዕድሜው ከ40 ዓመት በላይ የነበረ እና በኔም ስር የሚተዳደር ያልነበረ ነው የሚለውን የአመልካችን ክርክር ከመመዝገብ አልፈው በእርግጥ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ነበር አላሉም፡፡ ይህም የሚያመለክተው ፍ/ቤቶቹ አመልካችን ኃላፊ ያደረጉዋት ኃላፊ የምትሆንበት የሕግ ምክንያት ሳይኖር እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በሶማሌ ብ/ክ/መ/ በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እና በዚህ ውሣኔ ላይ በቀረበው ይግባኝ እና አቤቱታ ማስረጃነት በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እና ሰበር ችሎት በመ/ቁ. GM181/98 ሰኔ 28 ቀን 98 ዓ.ም. እና በመ/ቁ. 09/99 ሚያዝያ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. የተሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1 መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ የምትሆንበትም ሆነ ካሣ የምትከፍልበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31171

ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አብልሃሚድ የሱፍ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የምሥራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አጥሉ ሀብታሙ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንብረት ግምት ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች ጥር 05 ቀን 1997 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ በአወዳይ ከተማ ውስጥ የንግድ ስራ በሕጋዊ መንገድ እያካሄዱ ባሉበት ሁኔታ ተጠሪ የጉምሩክ ፖሊስ እና ሌላ የፖሊስ ኃይል በማስተባበር የሱቁን ቁልፍ በመስበር በሱቁ ውስጥ የነበረውን የንግድ ዕቃ በሙሉ አውጥተው በጭነት መኪና ጭነው በመውሰድ በተጠሪ መጋዘን ማስገባቱን፤ የተወሰዱ ንብረቶችን ተጠሪ ይመልስላቸው ዘንድ ጥያቄ ቢያቀርቡም ተጠሪ ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘቱን፤ የተወሰዱባቸው በሱቁ ውስጥ የነበሩት ንብረቶች ዓይነታቸውና ብዛታቸው እንዲሁም ግምታቸው ምን ያሕል እንደሆነ በመዘርዝር ግምቱ ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ የሆነ ንብረት እንዲመለስላቸው፣ ንብረቶቹ ተሸጠው ይገኝ የነበረውን ትርፍ እንዲከፍሉ፣ ንብረቶቹን ካልመለሱ ግምቱን እንዲከፍሉ እና የተለያዩ ወጪዎችንም ጭምር እንዲከፍሉ ይወስንላቸው ዘንድ የአሁኑን ተጠሪ አንደኛ ተከሣሽ ሌሎች ሁለት የፖሊስ አባላትን ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሽ በማድረግ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በአመልካች በኩል ተዘርዝረው የቀረቡትን የንብረት ዓይነቶች በፍ/ቤት የብርበራ ትዕዛዝና በሕብረተሰቡ ትብብር የኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር እና ለመያዝ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የወሠደ መሆኑን በመግለጽ ተጠያቂነት እንደሌለበት፤ በአመልካች በኩል የቀረቡት ማስረጃዎችም ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑንና ሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦችን በማንሣት ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት በ27/07/97 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ የተጠሪን መከራከሪያ ነጥቦች ውድቅ በማድረግ ተጠሪንና በስር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩትን የጉምሩክ ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ኃላፊን ለድርጊቱ አላፊ አድርጎ የአመልካችን ንብረት በክሱ በቀረበው ዝርዝር መሠረት በእራሣቸው ወጪ ከወሰዱበት ቦታ ከአመልካች ሱቅ እንዲመልሱ ይህን ካልፈፀሙ ግምቱን ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ፣ ወጪና ኪሣራ ዝርዝር የማቅረብ መብት ለአመልካች በመጠበቅ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የተለያዩ ምክንያቶችን ከዘረዘረ በኋላ በአሁኑ አመልካች በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች ንብረቶቹ የአመልካቹ ለመሆናቸው ለማስረዳትና ለማረጋገጥ የማይችሉ አጥጋቢና አሣማኝ አይደሉም ወደሚል ድምዳሜ በመድረስ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር ተጠሪን በነፃ በማሠናበት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ያሉባቸውን ምክንያቶች ሰኔ 03 ቀን 1999 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዘርዝረዋል፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪ ጥር 01 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን አቅርቧል። አመልካችም በተጠሪው መልስ ላይ የካቲት 06 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል። እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ተጠሪ የወሰዳቸው ከአመልካች ሱቅ ነው እየተባለ ንብረቶቹ የአመልካች መሆናቸው አልተረጋገጠም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሆኖ ተገኝቷል።

በክርክሩ ሂደት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ተጠሪ የወሰዳቸው ከአመልካች ሱቅ መሆኑ፣ የአመልካች ሱቅ ቁጥር የለውም ቢባልም በብር 10,000.00 /አስር ሺህ/ ካፒታል ልዩ ልዩ ዕቃዎችንና ሸቀጦችን ለመነገድ ከተገቢው አካል ፈቃድ አውጥተው የሚሠሩበት መሆኑ ተረጋግጧል። ተጠሪ ከአመልካች ሱቅ ንብረቶቹን መወሰዱን ሣይክድ ተግባሩን የፈፀመው በሕጉ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሆኑንና ንብረቶቹ የአመልካች ስለመሆናቸው ተቀባይነት ያለው ማስረጃ አለመቅረቡን በመጥቀስ የሚከራከር መሆኑን ተገንዝበናል። የተጠሪ መ/ቤት ስልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 60/1989 በአንቀጽ 6 እና 58 ስር ተዘርዝሯል። እነዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች የሚያሣዩት የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የጉምሩክ ባለስልጣንና ሹም የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት በዝርዝር መቀመጣቸውን ነው። የጉምሩክ ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 368/1995 ደግሞ ኮንትሮባንድ ማለት ሕጎችንና በሕግ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ወደ ጉምሩክ ክልል ዕቃዎችን በማስገባት ወይም ከጉምሩክ ክልል በማስወጣት፣ በሕጋዊ መንገድ የመጡትን በሕገ ወጥ መንገድ መልሶ ማስባት፣ መያዝ፣ ማከማቸት፣ ማዘዋወር ማስተላለፍ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ለማድረግ መሞከር እና ከእንደዚህ ያሉ ድርጊቶች መተባበርን እንደሚጨምር በአንቀጽ 2/28/ ትርጓሜ ሠጥቶበታል።

ከላይ እንደተጠቀሰው ተጠሪ ተግባሩን ሕጋዊ ነው ብሎ ሲከራከር በተለይ መሠረት ያደረጋቸው የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6/5/ እና 58/1/ለ/ ድንጋጌዎችን ነው። አንቀጽ 6/5/ ሙሉ ይዘቱ ሲታይ ባለስልጣኑ "በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቀሴ ይቆጣጠራል፣ ይከላከላል፣ በዚሁ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችንና ማንጓጓዦችን ይይዛል፣ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል" በማለት ሲደነግግ አንቀጽ 58/1/ለ/ ደግሞ ወደ አገር እንዳይገቡ ወይም ከአገር እንይወጡ የተከለከሉ ገደብ የተደረገባቸው ወይም ቀረጥ እንዳይከፈልባቸው በማሠብ የተደበቁ ዕቃዎች በፍተሻ ሲገኙ ዕቃዎችን የመያዝ እንዲሁም እንደሁኔታው ማንጓጓዣውን የማንጓጓዣውን ኃላፊ ወይም የዕቃውን ባለቤት ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ሥር የማቆየት ስልጣንና ኃላፊነት የጉምሩክ ሹም ያለው መሆኑን ይደነግጋል። ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የጉምሩክ ባለስልጣን በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችንና ማንጓጓዦችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ፣ በሕገ ወጥ መንገድ መገልገያ የሆኑ መንጓጓዦችን ጭምር ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ስር የማቆየት ስልጣን በሕጉ የተሰጠው መሆኑን ነው። እነዚህን ተግባራት የሚያከናውነው ግን ኮንትሮባንድ ተብሎ በሕግ የተሰጠው ትርጓሜ ተሟልቶ ሲገኝ ነው። ማንኛውም የዕቃ እንቅስቃሴ ኮንትሮባንድ ስለመሆኑ አሣማኝ እና በቂ ምክንያት ሣይኖረው ባለስልጣኑ መ/ቤት እንዲይዝና እንዲቆጣጠር ሕጉ ስልጣን ሠጥቶታል ተብሎ አይታሰብም። የአንድን ሰው መኖሪያ ቤት ወይም የንግድ ቤት የኮንትሮባንድ ዕቃ የተደበቀበት ስለመሆኑም ባስልጣኑ ጥርጣሬ ሲኖረው ሰብሮ በመግባት ዕቃዎችን እንዲይዝ ሕጉ ይፈቅድለታል ወደሚለው ድምዳሜ መድረስ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26/1/ ስር ጥበቃ የተደረገለትን የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት ዋስትና የሚያሣጣ ነው። በመሆኑም የጉምሩክ ባለስልጣን ተግባር ሕጋዊ ነው ሊባል የሚችለው በሕጉ መሠረት ሊሟሉ የሚችሉትን ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ ብቻ እንጂ በማንኛውም ጥርጣሬና ምክንያት ሁሉ የግለሰብን ንብረት በመያዝ ሊሆን አይችልም።

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ በተጠሪ ተወሰዱ የተባሉ ንብረቶች በአመልካች ይዞታ ስር የነበሩ መሆኑ ተረጋግጧል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1193/1/ ሥር በተደነገገው አኳኋን አመልካች የንብረቶቹ ባለሀብት መሆናቸውን ሕጉ ግምት ይወስዳል። ይህ ሕጋዊ ግምት ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1193/2/ ድንጋጌ ያስረዳል። በመሆኑም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለይዞታነት የሰው ወይም የጽሁፍ ማስረጃ በማቅረብ ካልፈረሰ በቀር ባለይዞታው የንብረቱ ሕጋዊ ባለሀብት ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድበት እና ባለሀብትነትን የማስረዳት /proof of ownership/ አንዱ ዘዴ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ንብረቶቹ የአመልካች አለመሆናቸውንና በኮንትሮባንድ ስራ ወደ አመልካች እጅ የገቡ ናቸው በማለት የሚከራከረው በአመልካች በኩል የቀረቡትን ደረሰኞች፣ የንግድ ፈቃድ ካፒታል መጠንና የንግድ ዓይነትን መሠረት በማድረግ እንጂ ያላግባብ ወደ አገር ውስጥ ገብቶ የተገኘ መሆኑን በማስረዳት አይደለም፡፡ በተለይም ተጠሪ የአመልካችን ንብረቶች ያገኩ የሚለው በፍ/ቤት የብርበራ ትዕዛዝ ቢሆንም ይኸንኑ ትዕዛዝ ብርበራው ከተፈፀመ በኋላ ፍ/ቤቱ ማንሣቱ መረጋገጡ የተጠሪን ተግባር ሕጋዊነት ቀሪ ማድረጉን ከሚጠቁም በስተቀር አመልካች የንብረቶቹ ሕጋዊ ባለቤት አለመሆናቸውን የማያሣይ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የአመልካች ንብረቶች ኮንትሮባንድ ስለመሆናቸው አላስረዳም፡፡ በአንፃሩ ንብረቶቹን በይዞታቸው በማድረግ ይጠቀሙባቸው የነበረ ስለመሆኑ አመልካች ያረጋገጡ በመሆኑ በማስረጃ ምዘና መርህ ረገድ ሲታይ የተሻለ ማስረጃ ያቀረቡትም አመልካች ናቸው፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ያቀረቡትን ማስረጃዎች የመዘነበት መንገድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1193 /1/እና /2/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ባላገናዘበ ሁኔታ ነው፡፡

ስለሆነም የአመልካች ዕቃዎች ከአመልካች ሱቅ መወሰዳቸው ተረጋግጦ እያለና ንብረቶቹ በኮንትሮባንድ ተግባር ወደ አመልካች ዕጅ የገቡ መሆናቸውን ተጠሪ ባላስረዳበት ሁኔታ ተጠሪ ተጠያቂነት የለበትም መባሉ ባግባቡ ሆኖ ስላልተገኘ ውሣኔው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1193፣ የአዋጅ ቁ. 60/1989 አንቀጽ 6/5/ እና 58/1/ለ/ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 368/1995 አንቀጽ 2/28/ ድንጋጌዎችን መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ የአመልካችን ንብረቶች መወሰዱ በበቂ ሁኔታ ስለተረጋገጠ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2027፣ 2035 እና 2054 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት አላፊ ሊባል የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የካሣውን መጠን በተመለከተም አመልካች ከጠየቁት ዳኝነትና ካቀረቡት ማስረጃ እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2118 አኳያ ሲታይ ተጠሪ ተዘርዝረው የቀረቡትን ንብረቶች በዓይነት እንዲመልስ ወይም ግምታቸውን እንዲከፍል መወሰኑ ፍትሐዊነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32974 ሰኔ 08 ቀን 1998 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26383 መጋቢት 19 ቀን 1999 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02282 ሐምሌ 07 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ከአመልካች ይዞታ ያላግባብ የወሰዳቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ ንብረቶቹን በዓይነት እንዲመልስ ወይም ግምታቸውን ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ የሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35034

ጥቅም 06 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

አሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- እነ ወ/ሮ ጥሩቀለም ደሴ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ ወ/ሮ ጽጌ ከፍያለው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፊዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ክርክሩ ከውል ውጪ አላፊነትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የስር ከሣሾች የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች ሲሆኑ መጋቢት 28 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ የሆነ ታክሲ በሁለተኛ ተጠሪ ሲሽከረከር ተማሪ እየሩሣሌም ስሙር የተባለች የአስራ አንድ ዓመት እድሜ ያላት ሕፃን ልጃቸውን በመግጨት በቀኝ ታፋዋ ላይ ጉዳት በማድረስ አጥንቷ ተሰብሮ እያነከሰች እንደምትገኝ እና በጉዳቱ ምክንያትም ወደፊት ተምራ ልትጦራቸው በማትችልበት ሁኔታ እንደምትገኝ በመጥቀስ ለአካል ጉዳትና ለሞራል ካሣ በድምሩ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የአሁኑ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ የመከላከያ መልስ ማመልከቻ ለአደጋው ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑንና የተቋረጠ ጥቅምም አለመኖሩን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ተገቢ ናቸው ያላቸውን ጭብጦችን በመመስረት ተከሣሾች አደጋው የደረሰው በክሱ ላይ በተጠቀሰው ተሽከርካሪ መሆኑን አምነው መከራከራቸውንና የከሣሾች ማስረጃም ጥፋቱ የአሽከርካሪው መሆኑን ማረጋገጡን ገልፆ ለጉዳቱ ተከሣሾች አላፊ ናቸው ካለ በኋላ የጉዳት መጠኑን በተመለከተ ግን ተጎጂዋ ትምህርቷን በመከታተል ላይ እንደምትገኝ መረጋገጡን፣ የህክምና ማስረጃውም መካከለኛ የሆነ ማነከስ ቢኖርባትም መራመድ እንደምትችል መግለፁን ጠቅሶ ተጎጂዋ ከሣሾችን ወደፊት ልትረዳ የማትችል እና ራሷም ሊቀርባት የሚችል ጥቅም ስለመኖሩ አጠራጣሪ ነው በማለት የአካል ጉዳት ካሣ ጥያቄን ውድቅ አድርጎ የህሊና ጉዳትን በተመለከተ ግን ብር 800.00 /ስምንት መቶ/ ሁለተኛ ተጠሪ ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፊዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም አመልካቾች በእርግጠኝነት በአደጋው ምክንያት በልጅቷ ላይ የደረሰውን የአሁንና የወደፊት ቁሣዊ ጉዳት አላስረዱም ሲል ይግባኙን ሣይቀበል ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ሲሆን አመልካቾች ጥር 08 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሠበር አቤቱታ የቅሬታ ነጥቦችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የስር ፍ/ቤት ጉዳት የደረሰባት ልጅ መካከለኛ ማነከስ ያለባት እንደሆነ በህክምና ተረጋግጧል እያለ በሌላ በኩል ወደፊት ተጎጂዋ ሊቀርባት የሚችል ጥቅም ስለመኖሩ አጠራጣሪ ነው በማለት የጉዳት ካሣ ክፍያ አይገባትም በሚል መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪዎች መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን ሲያቀርቡ አመልካቾች በበኩላቸው ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል። እንደመረመርነውም ተጠሪዎች የአካል ጉዳት ካሣ ለመክፈል ይገደዳሉ ወይስ አይገደዱም? የሚለው ነጥብ የችሎቱ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል።

በክርክሩ ሂደት አንደኛ ተጠሪ የታክሲው ባለቤት ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ በተጎጂዋ ጉዳት አደረሰ የተባለውን ታክሲ በወቅቱ ሲያሽከረክሩ የነበሩ መሆኑ እና ለጉዳቱ መድረስ አንደኛ ተጠሪ የታክሲው ባለቤት በመሆናቸው ብቻ ያለጥፋት ሁለተኛው ተጠሪ ደግሞ በጥፋቱ አላፊነት ያለባቸው መሆኑ ተረጋግጧል። የስር ፍ/ቤት የአመልካቾችን የአካል ጉዳት ካሣ ጥያቄ ያለፈው ተጎጂዋ ወደፊት ሊቀርባት የሚችል ጥቅም ስለመኖሩ እና አመልካቾችንም ልትረዳ የማትችልበት ሁኔታ መኖሩ አጠራጣሪ ሆኖ ተገኝቷል በሚል ምክንያት ነው። ይሁን እንጂ ተጎጂዋ መካከለኛ የሆነ ማነከስ ያለባት መሆኑ በሐኪም ከመረጋገጡ አኳያ እና የካሣ አከፋፈልና ልክ ከሚደነግጉት የፍትሐብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ የስር ፍ/ቤት ድምዳሜ ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም።

በመሠረቱ በፍትሐብሔር ሕጋችን ከውል ውጪ አላፊነትን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎች ጉዳት የደረሰበት ሰው የሚካስበትን ሥርዓት የዘረጉ ናቸው። የእነዚህ ድንጋጌዎች ዓይነተኛ ግባቸውም ጉዳትን የመካስና የጥፋት ባህርይን የመግታት ስለመሆኑ በድንጋጌዎቹ ላይ ማብራሪያ ጽሑፍ ያበረከቱት በቀድሞ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርስቲ የሕግ ትምህርት ክፍል አስተማሪ የነበሩት ቺቺኖቪች ገልፀውታል።

ከውል ውጪ አላፊነትን በተመለከተ የሚገዙት የፍትሐብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች መንፈስ የጉዳትን ጠቅላላ ባህርይና የካሣ ልክ አተማመን ሁኔታዎችን ያስገነዝቡናል። በዚህም መሠረት ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ ችግር ማድረስ መሆኑን፣ ይህም ጥቅም ማቴሪያላዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራላዊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። የተጎዳ ሰው ደግሞ መካስ እንዳለበት ያስረዳሉ። የካሣውን አተማመን በተመለከተም መጠኑ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 ድንጋጌ ያሣያል። የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል /future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል። ለእነዚህ ጉዳዮች ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን ሕጉ በግልጽ ከማስቀመጡም በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብና ሊለያይ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሁኖ በሕጉ ተመልክቷል። በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን የካሣ አከፋፈልን ልክ በሚደነግገው የሕጉ ክፍል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ። በሌላ በኩል የካሣ አተማመን ሥርዓት ጠቅላላ የመሥራት አቅም /General utility/ ሣይሆን ልዩ ጠቀሜታ/specific utility/ መርህን ቢከተል ፍትሐዊነት ያለው አሠራር መሆኑ ይታመናል። ይህም አሠራር በተጨባጭ የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የካሣውን ልክ ያላግባብ ከማጋነንና ከመቀነስ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል። በመሆኑም ጉዳት መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠና ጉዳቱም በተጎጂው የወደፊት ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ መሆኑ ከተረጋገጠ ካሣ መወሰን ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ አኳያ አግባብነት ያለው ነው። መጠኑን በተመለከተ በሕጉ ለዳኞች በተሰጠው ሥልጣን ወይም በጉዳዩ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት በመተመን ለተጎጂው መፍረድ የሚቻልበት ሁኔታ መኖሩን ከላይ ተመልክተናል። ከዚህ ውጪ ጉዳቱ መድረሱ እየታወቀ የአሁንና የወደፊት ቁሣዊ ጉዳት /material damage/ ስለመኖሩ ተጎጂው አላስረዳም ተብሎ የመካስ መብት ማጣት ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማ ያፈነገጠ ነው።

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካቾች ልጅ በደረሰባት የመኪና አደጋ በቀኝ እግሯ ላይ መካከለኛ ማነከስ የደረሰባት መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ጉዳቱ ወደፊት ሊጠፋ የሚችል ስለመሆኑም የተገለፀ ነገር የለም። ተጠሪዎች ጉዳት የደረሰባት ሕፃን ትምህርት እየተማረች ትገኛለች በማለት ከመከራከራቸው ውጪ ከጉዳቱ ሙሉ በሙሉ ስለመዳኗ ያስረዱት ነገር የለም። ስለሆነም በተጎጂዋ ላይ የደረሰው ጉዳት በወደፊት ሕይወቷ አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ የማይቀር ስለመሆኑ የነባራዊው ዓለም ሁኔታዎች ያስገነዝቡናል። በእርግጥ በተጎጂዋ ላይ የወደፊት ሕይወት ጉዳቱ የሚያደርሰውን የካሣ መጠን በትክክል መገመት አስቸጋሪ ይሆናል። ይሁን እንጂ የጉዳት ካሣ መጠኑን በተመለከተ በሕጉ ለዳኞች በተሰጠው ስልጣን መሠረት መተመን የሚቻልበት ሁኔታ ስለመኖሩ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2102 ድንጋጌ ያሣያል። በመሆኑም አመልካቾች በልጃቸው ላይ ጉዳት መድረሱን በሚገባ አስረድተው እያለና ይህ ጉዳትም በተጎጂዋ የወደፊት ሕይወት አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ የማይቀር መሆኑን በምክንያታዊ እርግጠኝነት ከነባራዊው ዓለም መገንዘብ እየተቻለ፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደዚሁም የካሣ አተማመኑም ርትዕን መሠረት ሊያደርግ የሚገባ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች የአመልቾችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው ከውል ውጪ አላፊነቱን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች አጠቃላይ ዓላማም ሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090፣2091፣2092 እና 2102 ስር የተመለከቱትን መርሆዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33351 ግንቦት 03 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57181 ታህሣሥ 16 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ አመልካቾች በልጃቸው ላይ ጉዳት የደረሰባት ስለመሆኑ በማስረጃ ያረጋገጡ ከመሆኑም በላይ ጉዳቱም በወደፊት ህይወቷ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ (Negative impact) ማሣደሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኛነት ያለው ስለመሆኑ ስለተረጋገጠ የካሣ አተማመኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2102 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ በርትዕ ሊወሰን የሚገባው ነው ብለናል፡፡

3/ የካሣ መጠኑን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ከርትዕ አኳያ በመመልከት እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰናል፡፡

4/ በዚህ ችሎት ትእዛዝ መሠረት ተጠሪዎች ለጉዳት ካሣው በአንድነትና በነጠላ አላፊነት ያለባቸው መሆኑን ተገንዝቦ መጠኑን በመተለከተ ይወስን ዘንድ የውሣኔው ግልባጭ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡

5/ በዚህ ችሎት ለተደገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአመስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34314

ጎዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ግምጃ ጎበና - ጠበቃ እንዳልካቸው ይላቅ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. አቶ ወንድወሰን ወልዴ - በሌለበት

2. ወ/ሮ ላይላ አህመድ- ወኪል አብዱልቃድር ቀረቡ፡፡

3. አቶ ተስፋዬ ተሾመ - በሌሉበት

4. አቶ ደረሠ ለገሠ - በሌሉበት

5. አቶ ጋሪሣ ዶረራ - በሌሉበት

6. ናይስ ኢንሹራንስ ኩባንያ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውል ውጪ አላፊነትን መሠረት አድርጎ የቀረበ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ሟች ልጃቸው አዱኛ ደበሌ ዕድሜው 30 /ሠላሣ/ ዓመት የሆነው መጋቢት 14 ቀን 1995 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 1፡00 በሚሆንበት ጊዜ የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ ንብረት የሆነውና በአሁኑ ሦስተኛ ተጠሪ ይሽከረከር የነበረው መኪና እና የአሁኗ ሁለተኛ ተጠሪ ንብረት የሆነውና በአሁኑ አራተኛ ተጠሪ ይሽከረከር የነበረው፣ በአሁኑ 6ኛ ተጠሪ የመድን ሽፋን የተሰጠው መኪና ባደረሱት ግጭት ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን፤ በሕይወት እያለም በግብርና ስራ ተሠማርቶ በዓመት የተለያዩ ሠብሎችን በማምረት ገቢ ያገኝ እንደነበር፤ በዚህ ገቢውም አመልካችን ይረዳቸውና ያስተዳድራቸው የነበረ መሆኑን ዘርዝረው የመኪናዎቹ ባለንብረቶችና አሽከርካሪዎች ለሟች መሞት አላፊ ተብለው ሟች ወደፊት ለ10 /አስር/ ዓመታት ቢኖር ያገኝ ነበር ብለው ያሠሉትን ብር 104000.00 /አንድ መቶ አራት ሺህ ብር/ የተቋረጠ ጥቅም፣ ከዳኝነትና ጠበቃ አበል ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ጥቅምት 02 ቀን 1996 ዓ.ም. በተሻሻለ የክስ ማመልከቻ በፊደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ተከሣሾች ቀርበውም አለን ያሉትን የመከራከሪያ ነጥብ አቅርበዋል፡፡ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ የተጠየቁ ተከራካሪዎችም ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር በአላፊነትና በጉዳት ካሣ መጠን ክርክር ላይ በተለያዩ የክርክር ደረጃዎች ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አላፊነትን በተመለከተ ውሣኔ የተሰጠው መጋቢት 20 ቀን 1998 ዓ.ም. ሲሆን በዚህ ጊዜም የአሁኑ አንደኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ለጉዳቱ አላፊነት የሌለባቸው መሆኑ ተገልፆ በነዛ ሲሰናበቱ የአሁኑ አንደኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች ግን ለጉዳቱ አላፊነት አለባቸው ተብለው የጉዳት ካሣ መጠኑን በተመለከተ የአመልካች ምስክሮች ተሠምተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአመልካች ምስክሮች ቃል በጉዳዩ ላይ ከቀረበው ክርክር አንጻር መመርመሩ ተገልፆ አመልካች ሟች ልጃቸው ምን ያሕል ይረዳቸው እንደነበረ ያላስረዱና ወደፊት ሊኖሩ የሚችሉት ዕድሜም ምን ያሕል እንደሆነ አልገለፁም የሚል ምክንያት መሠረት ተደርጎ የካሣ ጥያቄውን የስር ፍ/ቤት ውድቅ አድርጎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኗ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ይኸው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ አመልካች ከሚች ልጃቸው ጋር እየኖሩ ይጦሩ እንደነበር ተረጋግጦ እያለ አመልካች ምን ያሕል ዓመት ወደፊት እንደሚኖሩ ዕድሜአቸውን ገልፀው አልቀረቡም ተብሎ የካሣ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ተቀባይነት የሌለው ምክንያት መሆኑንና ሚች ከናዝሬት ወደ አዲስ አበባ ተሣፍሮ ይጓዝበት የነበረው የአንደኛ ተጠሪ መኪና በሆነው በሦስተኛ ተጠሪ ይሽከረከር በነበረው ሆኖ እያለ ተገቢው ውሣኔ ሣይሰጥ መታለፉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሮ በስር ፍ/ቤት የተጠየቀውን የመተዳደሪያና የመጦሪያ ካሣ ገንዘብ ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ አላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት አንደኛ፣ ሦስተኛ እና አምስተኛ ተጠሪዎች በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን 4ኛ ተጠሪም የፍ/ቤቱን መጥሪያ ተቀብለው ያልቀረቡ መሆኑ ሰለተረጋገጠ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ 2ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ግን ቀርበው ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የሚች ሕይወት ያለፈው በሁለተኛ ተጠሪ መኪና ተሣፍሮ ሲሄድ ባለመሆኑ አላፊነቱ የአጓጓዥ እንጂ የሁለተኛ ተጠሪ ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን እንደሚገባ፣ ይህ የሚታለፍ ከሆነም አመልካች በስር ፍ/ቤት በልጃቸው ሞት ምክንያት የተቋረጠባቸው ገቢ መኖሩን ገልፀው ያላቀረቡና በሰውም ማስረጃ አስደግፈው ያላቀረቡ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ ውሣኔው ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው መጋቢት 03 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ ይዘትና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በልጃቸው ሞት ምክንያት ተቋርጧል ያሉትን ጥቅም ሊያገኙ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት ለሚች ሕይወት ማለፍ አላፊነት አለባቸው ተብሎ ውሣኔ ያረፈባቸው ወገኖች የአሁኑ ሁለተኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ የአሁኑ አንደኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ለጉዳቱ አላፊነት የለባቸውም ተብሎ መጋቢት 20 ቀን 1998 ዓ.ም. ውሣኔ መስጠቱን የስር ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በአመልካች የሰበር አቤቱታ በአንደኛ እና በሦስተኛ ተጠሪዎች ላይ የስር ፍ/ቤት ተገቢውን ውሣኔ ሣይሰጥ አልፏል ተብሎ የቀረበው ቅሬታ እውነትነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ሥነ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የአሁኑ ስድስተኛ ተጠሪ ለሚች ሕይወት ማለፍ አላፊነት ያለበት አጓጓዡ እንጂ ሁለተኛ ተጠሪ ናቸው ሊባል አይገባም በማለት ያቀረበው የሰበር መከራከሪያ ነጥብ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ከውል ውጪ አላፊነትን በሚመለከት ሕግ ተመልክቶ ለአደጋው አላፊነት የሚወስዱት የአሁኑ ሁለተኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች ናቸው በማለት ውሣኔ የሰጠበት እና በበላይ ፍ/ቤትም የተለወጠ ካለመሆኑም በላይ በይዘቱ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑ የስድስተኛ ተጠሪ ክርክር በሰበር ችሎቱ የሚስተናገድበት ሥርዓት አልተገኘም፡፡

በመቀጠል የስር ፍ/ቤት ሁለተኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች ለሚች ሕይወት ማለፍ አላፊ ናቸው ካለ በኋላ፤ የአመልካችን የጉዳት ካሣ ጥያቄ ውድቅ የማድረጉን አግባብነት መመልከቱ የግድ ይሏል፡፡ ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው በአመልካች በኩል የቀረቡት ሁለት ምስክሮች ሚች የአመልካች ልጅ መሆኑን፣ በግብርና ሥራ ይተዳደር እንደነበር፣ በዓመት ከአርባ እስከ ሃምሣ ኩንታል እህል ያመርት እንደነበር፣ አትክልት በማልማት ደግሞ በዓመት እስከ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ ያገኝ እንደነበር፣ ልጅና ሚስት ያልነበረውና 6/ስድስት/ ቤተሰብ ያስተዳድር የነበረ ስለመሆኑ መመስከራቸውን ነው፡፡ ከዚህም በላይ የአመልካች ልጅ የሆነው ሚች አመልካችን በቤቱ ውስጥ ይዞአቸው ይጦራቸው እንደነበር በአመልካች በኩል የቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ይጠቁማል፡፡ ይህንኑ የአመልካችን ማስረጃ ተጠሪዎች ለማስተባበል ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በሚች ልጃቸው እርዳታ ይጦሩ የነበሩ ስለመሆኑ ከተጠሪዎች በተሻለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታ አስረድተዋል፡፡ ጉዳዩ የፍትሐብሔር እንደመሆኑ መጠንም የማስረጃ ምዘናው የትኛው ተከራካሪ ወገን የተሻለ ማስረጃ አቅርቧል? የሚለው መመዘኛ መሠረት ተደርጎ የሚስተናገድ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የስር ፍ/ቤት የማስረጃ ምዘናም መርሁን ያላገናዘበ ነው፡፡

አመልካች በሟች ልጃቸው ስር ይተዳደሩ የነበሩና ሟች ልጃቸውም ገቢ የነበረው ስለመሆኑ ካስረዱ ደግሞ የራሣቸውን የወደፊት ዕድሜ በማመልከቻቸው አለመጥቀሣቸውና ሟች በትክክል ይሰጣቸው የነበረው የመጦሪያ ገንዘብ መጠን አለመታወቁ የጉዳት ካሣ ጥያቄአቸውን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል የሕግ መሠረት የሌለው ምክንያት ነው፡፡ ይልቁንም አመልካች ልጃቸው ገቢ የነበረውና በስሩ አድርጎ ያስተዳድራቸው የነበረ መሆኑን ማስረዳታቸው የጉዳት ካሣ መጠኑን በርትዕ ለመወሰን መነሻ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ የጉዳት ካሣ መጠኑን በተመለከተ በርትዕ መተመን የሚቻልበት ሁኔታ ስለመኖሩም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2102 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የጉዳት ካሣ መጠኑን በሕጉ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መተመን እየቻለ አመልካች በማስረጃ አላስረዱም በማለት ጥያቄአቸውን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ማድረጉ ከውል ውጪ አላፊነቱን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች አጠቃላይ ዓላማም ሆነ የካሣ አተማመኑን በተመለከተ በሕጉ የተቀረጹትን ሥርዓቶች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33149 መስከረም 29 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 49878 ጥቅምት 08 ቀን 2000 ዓ.ም. በፀናው ውሣኔ የአመልካችን የጉዳት ካሣ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ሁለተኛ ተጠሪ በተሸከርካሪ ባለቤትነታቸው፣ አራተኛ ተጠሪ በአሽከርካሪነታቸው፣ ስድስተኛ ተጠሪ ደግሞ ለተሸከርካሪው በሰጠው የመድን ሽፋን ዋስትና መሠረት በአመልካች ላይ በልጃቸው መሞት ምክንያት ለተቋረጠው የመተዳደሪያ ገቢ ባልተነጣጠለ ሁኔታ አላፊነት አለባቸው ብለናል፡፡
3. የስድስተኛ ተጠሪ የአላፊነት መጠን በመድን ዋስትና ውሉ የተመለከተውን ያሕል ነው ብለናል፡፡
4. አንደኛ፣ ሦስተኛ እና አምስተኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
5. በአመልካች ላይ የደረሰው የጉዳት ካሣ መጠን በርትዕ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ ስለተገኘ ብር 25,000.00 /ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ሁለተኛ፣ አራተኛ እና ስድስተኛ ተጠሪዎች ለአመልካች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
6. በዚህ ጉዳይ ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
7. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ. 31704

ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አማረ መጃ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- የድሬዳዋ ለጋር ጉምሩክ - ነ/ፈጅ አቶ ታደሰ ጎለንዴ ቀርበዋል

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 02 ቀን 1999 ዓ.ም በተሻረ አቤቱታቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግንቦት 10 ቀን 1999 ዓ.ም በፍ/ይ/መ/ቁ. 24665 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይሻርልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የድሬዳዋ ምድብ ችሎት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ስር ከሣሹ ሐምሌ 21 ቀን 1997 ዓ.ም የተሻረ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም የሰሌዳ ቁጥሯ 3-05884 የሆነች ኢሮቶዮታ መኪናዬ ኮንትሮባንድ ጭናለች በሚል ምክንያት ታህሣሥ 09 ቀን 1996 ዓ.ም ተከሣሹ በድሬዳዋ ከተማ በቁጥጥር ስር አውሏት ስትፈተሽ አንድ ቦንዳና 10 ሜትር ብትን የመጋረጃ ጨርቅ ጭና ስለተገኘች መኪናዋ ልትለቀቅልኝ ባለመቻሏ ባቀረብኩት አቤቱታ መነሻነት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በየደረጃው ያሉት ኃላፊዎች ለተያዘው ዕቃ ሊከፈል የሚገባው 36.83 ብር የጉምሩክ ቀረጥ ተመን ተከፍሎ መኪናዋ እንዲለቅ በተደጋጋሚ ደብዳቤ ለተከሣሹ ቢጽፍለትም ሊለቅልኝ አልቻለም፤በመሆኑም ከመኪናዋ አገኝ የነበረው በቀን ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ ሂሣብ ሆኖ ከታህሣሥ 09 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ሰኔ 16 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ ያለውን የተቋረጠ ገቢ ብር 608,000 /ስድስት መቶ ስምንት ሺህ ብር/ ከነወለዱ ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡

ስር ተከሣሹ በ23/02/1998 ዓ.ም በተሻረ መልሱ መኪናው መስከረም 04 ቀን 1998 ዓ.ም ተለቋል፤ መኪናዋን የያዝኩት በአዋጅ ቁጥር 60/1989 ዓንቀጽ 6 በተሰጠኝ ስልጣን መሠረት ነው፡፡ በመኪናዋ ከተጫነው 190 ጣቃ ጨርቅ 10 ሜትር የመጋረጃ ጨርቅ አደባልቆ በራሱ እየነዳ ነው በቁጥጥር ስር የዋለችው፤ የመጨረሻ ውሣኔ እስኪያገኝ ድረስ መኪናዋን በቁጥጥር ስር አውሎ ማቆየት ሕግ ይፈቅድልኛል፤ በተለይም የጉምሩክ ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ ሊያሸከረክር የተገኘው የመኪናው ባለቤት ከሆነ የመጨረሻ የፍ/ቤት ውሣኔ ይጠብቃል ይላል፤ ስለሆነም መኪናው በሕግ አግባብ የተያዘ ነው ብሏል፡፡

የስር ፍ/ቤቱም በመ/ቁ. 01735 መጋቢት 20 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ተከሣሹ መኪናዋን እንዲለቅ በተደጋጋሚ ከበላይ የመዋቅሩ አካላት ደብዳቤ በተደጋጋሚ እየተፃፈለት እምቢተኛ ሆኖ ከሣሽን ለኪሣራ የዳረገ በመሆኑ ከ11/06/96 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 21 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ ያለውን የመኪናዋን የተቋረጠ ገቢ ከሣሹ ለመንግሥት ሪፖርት ባደረጉት ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ሂሣብ ብር 36,111.11 /ሰላሣ ስድስት ሺህ አንድ መቶ አስራ አንድ ብር ከአስራ አንድ ሣንቲም/ ሊከፍላቸው ይገባል ብሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሩ በይግባኝ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱ በፍ/ይ/መ/ቁ. 24665 ግንቦት 10/1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ አዋጅ ቁጥር 60/89 ዓንቀጽ 6 እና 58 መሠረት ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ ኮንትሮባንድ ጭኖ የተያዘን መኪና ይ/ባይ በቁጥጥሩ ስር አድርጎ የማቆየት ስልጣን ስላለው ካሣ ክፈል ሊባል አይገባም በማለት ከላይ የተጠቀሰውን የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/መሠረት ሽሮታል።

ከላይ የተጠቀሰውን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት፣ ይግባኝ ችሎት ውሣኔ በመቃወም አመልካች ሐምሌ 02 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም መኪናዋ በክሱ የተመለከተውን ሕጋዊ ያልሆነ እቃ ጭና የተያዘችው የመኪናው ባለቤት የሆንኩት እያሽከረከርኩ እያለሁ አይደለም፤ ሌላ ሹፌር ነበር ሲያሽከረክራት የነበረው፤ ሕጋዊ ያልሆነ ወይም ኮንትሮባንድ ነው የሚባል እቃ የተጫነበት መኪና ተይዞ እንዲቆም የሚደረገው አሽከርካሪው የመኪናው ባለንብረት ሲሆን ነው፤ ለዚህም የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በቁጥር 10/መ352/201/18/123 በ18/08/1996 ዓ.ም ግልጽ መመሪያ ያስተላለፈበት ነው፤ መኪናው እንዲለቅ ተደጋጋሚ ትእዛዝ ተጽፎለት እያለ ተጠሪ መኪናዋ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገቢዬ አላግባብ እንዲቋረጥ አድርጓል፤ይሁን እና ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከዚህ ነጥብ አኳያ እንደማጤን ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 60/89 ዓንቀጽ 6 እና 58 መሠረት የመኪናዋን በቁጥጥር ስር የማዋልና ችግሩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ በቁጥጥር ስር አድርጎ ማቆየት ይችላል ብሎ ፍርድ መሰጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊሻርልኝ ይገባል የሚል ነው።

ተጠሪም ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም አመልካች መኪናው በሌላ ሹፌር ይሽከረከር ነበር ከማለት ውጭ የዛ ሹፌር ማንነት በስር ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አልጠቀሱም መኪናው ሲያሽከረክሩ የነበሩት ራሣቸው አመልካች ናቸው፤ ኮንትሮባንድ ጭኖ የተገኘን መኪና ችግሩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ በቁጥጥር ስር አድርጌ ማቆየት እንደምችል አዋጅ ቁጥር 60/89 ዓንቀጽ 6/5/፣ 58/1/ለ/፣61 እና 78 ይፈቅድልኛል፤ መኪናዋ ኮንትሮባንድ ጭና መገኘቷ አያከራክርም፤ ስለሆነም የጠቅላይ ፍ/ቤት የፈፀመው የሕግ ስህተት ስለሌለ ፍርዱ ይጽናልኝ የሚል ነው።

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተገለፀ እንደመጣው ሆኖ ይህ ፍርድ ቤትም ተጠሪው የአመልካችን መኪና ይዞ በማቆየቱ የተቋረጠ ገቢ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚል መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከክርክር አመጣጥ መረዳት የሚቻለው የአመልካቹ መኪና በሕጋዊ መንገድ ጭናው ከነበር 190 ጣቃ ጨርቅ ውስጥ አንድ ቦንዳና 10 ሜትር ብትን የመጋረጃ ጨርቅ ሕግን ባልተከተለ መንገድ ተደብቆ እንደተገኘና በዚህ ምክንያም መኪናዋ በተጠሪ በቁጥጥር ስር እንደዋለች ነው በወቅቱ መኪናዋ በአመልካች ሣይሆን በሌላ ሾፌር ትሽከረከር እንደነበር ነው። በግራና ቀኙ ክርክር ጉዳይ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጉት ጭብጥ ልዩነት ያለው ይመስላል የኸውም የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አስተሳሰብ በኮንትሮባንድ ጭና የተገኘት መኪና በአዋጅ ቁጥር 60/89 መሠረት በቁጥጥር ማዋልና ችግሩ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ ይዞ ማቆየት አይቻልም የሚል አይደለም። ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በውሣኔው ያሰመረበት መሠረታዊ ነገር መኪናዋ በሌላ ሾፌር ስትሽከረከር ከላይ የተጠቀሱት ንብረቶች ይዛ መገኘቷ ታውቆ መኪናዋ መለቀቅ እንዳለባት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን የበላይ አመራሮች ወደ ተጠሪው በተደጋጋሚ ደብዳቤዎች ጽፈው እያለ /በቁ.ዘ40/ቀ64/640/05/15 መጋቢት 09/1996፣ በቁ.ዘ30/ቀ64-16/06 መስከረም 28/1997 ዓ.ም፣ በቁጥር ዘ40/ቀ 64-6/03 ነሐሴ 27/1997 ዓ.ም/ ተጠሪው ይህንን ትእዛዝ ወደጎን በመተው የአመልካችን መኪና ጉዳዩን ለማጣራት ከሚገባው ጊዜ በላይ በቁጥጥር ስር አውሎ አመልካችን ለተጨማሪ ወጪ ዳርጓል የሚል ሲሆን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ ደግሞ ከላይ የተመለከተውን የደብዳቤዎች ልውውጥ ግምት ውስጥ ባለማስገባት በአጠቃላይ በኮንትሮባንድ የተጠረጠረች መኪና በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ የማቆየት ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 60/1989 መሠረት ያለው መሆኑን ነው። ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የጠቀሰው አሰራር በሕጉ የተመለከተ ሃቅ ቢሆንም ሁኔታውን በሚባ ተገንዝቦና የጉምሩክ መመሪያን መሠረት በማድረግ የባለስልጣኑ የበላይ አመራሮች መኪናዋ በወቅቱ ትሽከረከር የነበረው በሌላ ሹፌር እንጂ የመኪናዋ ባለቤት በሆኑት በአመልካች ባለመሆኗ በአስቸኳይ እንድትለቀቅ በተደጋጋሚ እያዘዙት ተጠሪው መኪናዋን በወቅቱ ወይም ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ሣይለቅ በቀረበት ሁኔታ ከላይ የተጠቀሰው አዋጅ የያዘው ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ነው ማለቱ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም። በተጠሪው ጥፋት ምክንያት በአመልካቹ ላይ የገቢ መቋረጥ ሲደርስ አዋጅ ቁጥር 60/1989 ሽፋን በማድረግ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተጠሪው ያቀረበው ክርክር መሠረት ያለው አይደለም፤ አዋጁ የጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች ወይም ቅርንጫፎቻቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጥፋታቸው ምክንያት በባለንብረቶች ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት ተጠያቂ እንዳይሆኑ ሽፋን የመስጠት ዓላማ የለውም፤ ስለሆነም በአሁኑ ጉዳይ መኪናዋ ስትሽከረከር የነበረው በሹፌር እንጂ በአመልካቹ አለመሆኗ ተገልያለትና እንዲህ በሆነ ጊዜም መኪናዋ በቁጥጥር ስር አድርጎ ለረጅም ጊዜ ማቆየት በጉምሩክ መመሪያ መሠረት እንደማይፈቀድ ተጠሪው በግልጽ እያወቀ ሆን ብሎ መኪናዋን አለቅም በማለት በአመልካቹ ላይ ጉዳት ማድረሱ የተረጋገጠ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2028፣2031/1/ መሠረት ለደረሰው የገቢ መቋረጥ ጉዳት ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ተጠሪው በተጠቀሰው አዋጅ መሠረት መኪናዋን በቁጥጥር ሥር አውሎ የማቆየት ስልጣን ስላለው ሊጠየቅ አይገባም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፤ ሥለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 24665፣ ግንቦት 10/1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡

2/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ.ቁ. 01735፣ መጋቢት 20 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፤ ይፃፍ፡፡

3/ ተጠሪው ጥፋት መፈፀሙ ስለተረጋገጠ በአመልካቹ ላይ ለደረሰው የገቢ መቋረጥ ኃላፊነት አለበት፤ ሥለሆነም ብር 36,111.11 /ሰላሣ ስድስት ሺህ አንድ መቶ አስራ አንድ ብር ከአስራ አንድ ሣንቲም/ ለአመልካቹ ይክፈል ብለናል፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ችሎት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ በውሣኔ የተቋጨ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 38457

ሰኔ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ተመኘሁ እንደሻው - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በመኪና አደጋ ደረሰ የተባለውን ጉዳት መሠረት በማድረግ የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ ጥያቄ /ክርክር/ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በአመልካች ሹፌር ሲሽከረከር በነበረው መኪናው ተሳፍሬ ስንዝ በነበረበት ጊዜ መኪናው በመገልበጡ በእግሬ ላይ ጉዳት ደርሶአል፡፡ ስለዚህ ካሣ ይክፍለኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ መኪናው ለመንግስት ሥራ የተሰማራ እንጂ ሰዎችን ለማጓጓዝ የተዘጋጀ የንግድ መኪና አይደለም፡፡ ከሣሽ በመኪናው ላይ የተሳፈረው ያለአግባብ እና ለከሣሽ ጥቅም በማይሰጥ ሁኔታ ስለሆነ በሕግ ረገድ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም አመልካች ለደረሰው ጉዳት ሃላፊነት አለበት በማለት ካሣ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በተጠሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች ኃላፊ ነው የተባለበትን አግባብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2089(1) አንፃር ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ሊመረመር እና ትርጉም ሊሰጠው የተፈለገው ሕግ የፍ/ብ/ሕግ ቁ 2089(1) የሚገኘው ከውል ውጪ ስለሚደርስ አላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ በሚለው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13 ሥር ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን የከሰሰውም ከውል ውጪ ደረሰ የሚለውን ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በስር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው ተጠሪ የተባለውን ጉዳት የደረሰበት በአመልካች መኪና በመገጨቱ ሳይሆን፣ በመኪናው ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ መኪናው የአመልካች ንብረት ነው፡፡ ሆኖም ለመንግስት ሥራ የተሰማራ እንጂ ገንዘብ በማስከፈል ሰዎችን የሚያጓጉዝ የንግድ መኪና አይደለም፡፡ ተጠሪ በመኪናው ስለመሳፈሩ እንኳን አመልካች አያውቅም፡፡ ተጠሪን በማሳፈር ያገኘው ጥቅምም የለም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ እነዚህን ሁኔታዎች ከተረጋገጡ ቀጥሎ መታየት ያለበት አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆንበት የሕግ አግባብ አለ ወይስ የለም የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁ 2081(1) እንደተደነገገው የመኪናው ባለቤት መኪናው በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆንበት አግባብ አለ፡፡ ይህ እንግዲህ በአጠቃላይ የተቀመጠ የኃላፊነት መርህ ሲሆን፣ በቁጥር 2089 ደግሞ ልዩ ሁኔታ ማለትም የመኪናው ባለቤት ኃላፊ የማይሆንበትን ሁኔታ ተደንግጎአል፡፡ ከድንጋጌው ርእስ መገንዘብ እንደሚቻለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳቱ የደረሰው ጥቅም በሌለው ግንኙነት ጊዜ ሲሆን፣ የመኪናው ወይም ጉዳቱን ያደረሰው ንብረት ባለቤት ኃላፊነት አይኖርበትም፡፡ ከላይ እንዳመለከትነው ተጠሪ በአመልካች መኪና የተገለገለው ለአመልካች ጥቅም በማያስገኝ ሁኔታ ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች በዚህ ረገድ ጥፋት ፈጽሞአል አልተባለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ኃላፊ የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም በዚህ አግባብ ሕጉን ባለመተርጐማቸው የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 03066 ህዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63179 ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡ ስለዚህም በሥር ፍ/ቤቶች የተወሰነውን ካሣ አይከፍልም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ሥልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35657

ጥቅምት 06 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- እነ ወ/ሮ እመቤት መክብብ - ጠበቃ አስቴር አርአያ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ በድሉ መክብብ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ አመልካች፣የአሁኑ አመልካቾችና ወ/ሮ አልታየወርቅ መክብብ ደግሞ ተጠሪዎች ነበሩ፡፡

የስር አመልካች አቤቱታ ይዘት ሲታይም የሟች ወንድማቸው የአቶ መሉጌታ መክብብ ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን፣ ከስር ተጠሪዎች ጋር በመሆን የውርስ ሐብቱን ለማጣራት ቢፈልጉም ተጠሪዎች ፈቃደኛ ሆነው ውርሱን ለማጣራት ያልቻሉ መሆናቸውን በመግለጽ ውርሱ ይጣራ ዘንድ ፍ/ቤቱ የውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ የስር ተጠሪዎችም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሰረት ቀርበው ፍ/ቤቱ የውርስ አጣሪ ለመሾም በሕግ የተሰጠ ስልጣን የሌለው መሆኑን፤ የውርስ አጣሪን መሾም የማያስፈልግ መሆኑን የሚያሣዩ ምክንያቶች መኖራቸውን በመዘርዘር የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊሆን እንደሚገባ ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የስር ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር በማድመጥ እና አግባብነት አላቸው ያላቸውን ጭብጦች በመመስረት ፍ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41(1)(ሸ) መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንዳለው በመዘርዘር የተጠሪዎችን ተቃውሞ ካለፈ በኋላ የውርስ አጣሪ በመሾም የውርስ ሐብቱ ተጣርቶ ሪፖርቱ ሊቀርብ ይገባል በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች በዚህ የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን እና የሰበር አቤቱታቸውን እንደየቅደም ተከተሉ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሣያገኙ ቀርተዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ነው፡፡

አመልካቾች የካቲት 12 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የቅሬታ ነጥቦችንና በበታች ፍ/ቤቶች ተፈፀሙ ያሏቸውን የህግ ስህተቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአዋጁ የተሰጠው ስልጣን የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለመስጠት እንጂ ውርስ አጣሪ ለመሾም አይደለም፤ የሚልና የውርስ አጣሪ መሾም ለጉዳዩ አስፈላጊ አለመሆኑን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ በሰበር ችሎቱ ተሽሮ በቂ ወጪና ኪሣራ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የውርስ ክርክርን አስመልክቶ በቀረበ ጉዳይ ላይ የውርስ አጣሪ የመሾም ስልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ ተጠሪ እንዲቀርቡና መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት በሕግ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን በመዘርዘር የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የበታች ፍ/ቤቶች ትእዛዝ ሊፀና ይገባል በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካቾች የተጠሪ መልስ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስና የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 39 ስር የከተማው አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችና የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች የሚኖሩት ስለመሆኑ፤ በአዋጁ አንቀጽ 41 መሰረትም የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን መዘርዘሩን ተገንዝበናል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 41(1)(ሸ) ድንጋጌም የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን የማየት የዳኝነት ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን መሆኑን በማያሻማና ግልጽ በሆነ ቋንቋ ይገልፃል፡፡ የስር ፍ/ቤት የውርስ አጣሪን የመሾም ስልጣን አለኝ ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ከላይ የተጠቀሰውን አዋጅና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.996/1/ ድንጋጌን መሰረት በማድረግ የውርስ ሐብቱ ሣይጣራ የወራሽነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ የወራሽ ድርሻ ሊገለጽ አይችልም በሚል ምክንያት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ትርጓሜ አዋጁ ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ ከመሆኑ እና የወራሽነት የምስክር ወረቀት ከውርስ ማጣራት ሂደት ጋር ተያያዥነት ያለው ቢሆንም ሊያስነሣ ከሚችላቸው ሕጋዊ ክርክሮች አኳያ ሲታይ ከውርስ ማጣራት ሂደት ያነሰ የውስብስብነት ባሕርይ ያለው መሆኑን ያላገናዘበ ነው፡፡

በመሰረቱ የተፃፈ ሕግ የሚተረጐመው ግልጽነት ሲጐድለው ነው፡፡ ህጉ ግልጽ በሆነበት ሁኔታ ግን ትርጉም አላስፈላጊ ስለመሆኑ የሕግ አተረጓጐም መርሆዎች ያስገነዝቡናል፡፡ ግልጽ ህግን መተርጐም ፍ/ቤት በትርጉም ሰበብ የሕግ አውጪውን ስልጣን ተክቶ እንደሰራ የሚያስቆጥር ነው፡፡ ስለሆነም የወራሽነት የምስክር ወረቀት የማግኘትና የውርስ ማጣራት ሂደት ሁለት የተለያዩ ሂደቶች መሆናቸው እየታወቀ፣ ህግ አውጪውም የምስክር ወረቀት የማግኘት አቤቱታን በሚመለከት ብቻ ለአስተዳደሩ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን በግልጽ ለይቶ ሰጥቶ እያለ፣ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ማግኘትና የውርስ ማጣራት ተያያዥነት አላቸው በሚል ምክንያት ብቻ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ማየቱ የሕግ አተረጓጐም መርህን በተከተለ መንገድ ሣይሆን ይህንኑ ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 678/99 የካቲት 08 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ በአስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 04083 ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣እንዲሁም በአስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 04951 ጥር 16 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41(1(ሸ)) መሰረት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን በተመለከተ እንጂ የውርስ አጣሪ የመሾም የዳኝነት ስልጣን አይደለም ብለናል፡፡
3. በአዲስ አበባ መስተዳድር ውስጥ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄ የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ልዩነት ውሣኔ

እኔ ስሜ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ባለመስማማት በሚከተለውን በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

1. በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 ንኡስ አንቀጽ 1(ሸ) የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ የመወሰን ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በፍርድ ቤት የሚሰጥ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ወይም ማረጋገጫ ወራሽ የሆነው ሰው ለሟች ወራሽ መሆኑንና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመለክት እንደሚሆን በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 996/1/ ድንጋጌ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የወራሽነት የምስክር ወረቀት ወይም ማረጋገጫ ለመስጠት ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን ማጣራት አለባቸው፡፡ የመጀመሪያው አቤቱታ አቅራቢው የሟች የኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ ወራሽ መሆኑን ማጣራት ሲሆን 2ኛው የሟች የውርስ ንብረት ምን እንደሆነና ወራሽ ድርሻ ያለው መሆኑን የድርሻውንም መጠን ማጣራት አለባቸው፡፡ ይህንን ለማድረግ የውርስ አጣሪ መሾም የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የውርስ አጣሪ የመሾም ስልጣን ያላቸው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41/1/ሸ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 996 ንኡስ አንቀጽ 1 ጋር አጣምሮ በመተርጎም ለመረዳት ስለሚቻል የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ውርስ አጣሪ የመሾም ስልጣን የላቸውም መባሉ ተገቢ አይደለም የሚል እምነት አለኝ፡፡

2. ውርስ አጣሪ የመሾም ጉዳይ በራሱ እንደ ትልቅ ነገር የሚታይና የሥረ ነገር ስልጣኑ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ነው ወይም የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚለውን ክርክር የሚያስነሣ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የፍትሀብሔር ህጉ የሟች ውርስ የማጣራት ስልጣን ያላቸውን ግለሰቦች በቅደም ተከተል የሚዘረዝር ሲሆን እነርሱም፡-
   - ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ ሆኖ ውርሱን እንዲያጣራ የሾመው ሰው ካለ በመጀመሪያ የውርስ አጣሪ እንደሆነ የፍትሀብሔር ህጉ 948/1/ የሚደነግግ ሲሆን፣
   - ሟች በውርስ አጣሪነት በኑዛዜ የሾመው ሰው ከሌለ ጠቅላላ የኑዛዜ ተቀባይ የሆነው ሰው የሟችን ውርስ የማጣራት ስልጣን እንዳለው የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር አንቀጽ 948 ንኡስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡
   - ሟች በኑዛዜ የመረጠው የውርስ አጣሪ ወይም ጠቅላላ የኑዛዜ ተቀባይ የሌለ በሆነ ጊዜ ሁሉ የሟች ያለ ኑዛዜ ወራሾች ያላንዳች ፎርማሊቲ የውርስ አጣሪነት ስልጣን እንዳላቸው በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 947 ተደንግጓል፡፡

በፍርድ ቤት የውርስ አጣሪ የሚሾመው የሟች ወራሾች የማይታወቁ ሲሆን ወይም የሟች ወራሾች ውርሱን ለማጣራት ፈቃደኛ በማይሆኑበት ጊዜ እንደሆነ ከፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 850 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይህንን ሕጉ በቅደም ተከተል ያስቀመጣቸውን ነገሮች የሚፈጽም የውርስ አጣሪ የመሰየም ስልጣን የወራሽነት አቤቱታን ተቀብሎ የማስተናገድ ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የሚፈጽሙት እንጂ የተለየ አቤቱታና ክስ ቀርቦበት ውሣኔ የሚሰጥበት ራሱን የቻለ የዳኝነትና የሥረ ነገር ስልጣን የሚጠይቅ ጉዳይ ተደርጐ መታየት የለበትም፡፡ ውርስ ማጣራትና የውርስ ንብረት መካፈል የተለያዩ ሒደቶች እንደሆኑ በጥልቀት ሊታይ ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

3. ሕግ አውጭው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ የመወሰን ስልጣን ለከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ሲሰጥ ሰዎች የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከተማ ነክ ፍርድ ቤት፣ የውርሱ ንብረት እንዲጣራላቸው ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አንድ ላይ ሊታይና ሊፈፀም የሚችለውን ጉዳይ ከተለያዩ ሁለት ፍርድ ቤቶች እንዲጠይቁና አገልግሎት እንዲያገኙ በማሰብ ነው ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም አዋጅ ቁጥር 361/1995 በሚወጣበት ጊዜ መንግስት በፖሊሲ ደረጃና የተለያዩ የማሻሻያ ፕሮንራሞችን በመንደፍ ሰዎች አንድን ጉዳይ የሚመለከት ማናቸውም አገለግሎት ከአንድ መስሪያ ቤት በተቀላጠፈ መንገድ የሚያገኙበትን ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ በሚንቀሣቀስበት ወቅት ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ የመንግስት ፖሊሲና የማሻሻያ ፕሮግራም አንጻር የአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41/1/ሸ/ ድንጋጌ መታየትና መተርጐም ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ አብላጫው ድምጽ የሰጠው ትርጓሜ ተገልጋዩ ሕብረተሰብ አንድ እና ተያያዥነት ያለውን ጉዳይ ለማስወሰን ሁለት ቦታ ማለትም የውርስ ሰርተፍኬት ለማግኘት አዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት፣ ውርሱ እንዲጣራ ለማመልከት ለፌደራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ጊዜውን፣ ገንዘቡንና ጉልበቱን እንዲያባክን የሚያደርግ ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔ ባለመስማማቴ የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ውርስ አጣሪ የመሾም ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሸ እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 996/1/ መሰረት አላቸው በማለት በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36338

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ገ/መስቀል ደመወዝ - ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አፀደ መኰንን - ቀረበች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በሁከት ይወገድልኝ የክስ መነሻነት የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረውም የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው ከቀበሌ ተከራይቼ የምኖርበትን ቤት ማእድ ቤት ለማደስ ያደረግሁት እንቅስቃሴ እንዳይሳካ ሁከት ስለፈጠረችብኝ ሁከቱ ይወገድ ዘንድ ይታዘዝልኝ በማለት ነው፡፡ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ተጠሪን በማስቀረብ ክርክሩን ከሰማ በኋላ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቹ ውሳኔውን በመቃወም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ እንደገና ተሰምቷል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በማህበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች አሁንም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ክርክሩ እንዲሰማ አድርጓል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ውሳኔ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች የካቲት 5 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆን አለመሆኑ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አመልካች ለቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ክስ ያቀረበው ተጠሪ የማእድ ቤቱ እድሳት እንዳይካሄድ በመከልከል የፈጸመችው ድርጊት ሕገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲወገድ እና እድሳቱን እንዲያካሂድ እንዲወሰንለት በመጠየቅ ነው፡፡ የክሱ ምክንያት ሕገ ወጥ ነው የተባለው ድርጊት እንዲወገድ የሚጠይቅ ከመሆን አልፎ የገንዘብ ጥቅም ወይም በገንዘብ ሊተመን የሚችል መብት የሚጠይቅ አይደለም፡፡ ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በግልጽ እንደሚታወቀው ማንኛውም ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ ተቀብሎ ሊያስተናግድ የሚችለው በክልልም ሆነ በስረ-ነገር ረገድ የዳኝነት ስልጣን ሲኖረው ነው፡፡ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣንን በሚመለከትም ሕጉ ጥብቅ የሆነ ድንጋጌ አስቀምጦአል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.9/1/ እንደተመለከተው በስረ-ነገሩ ለመዳኘት ስልጣን የሌለው ፍ/ቤት የክስ ማመልከቻውን በፍ/ብ/ሕግ ቁ.231 በተደገገው መሰረት ተቀባይነት የለውም ብሎ መመለስ አለበት፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን እርምጃ መውሰድ ያለበት ተከራካሪ ወገን መቃወሚያ እንዲያቀርብለት ሳይጠብቅ በራሱ አነሳሽነት እንደሆነም በዚሁ ቁ.9/2/ በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ የተቀመጠውን አስገዳጅ መርህ ለማስከበር ሲባል የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ነበረው ወይ? የሚለው ጭብጥ መያዙ ተገቢ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየቀበሌው የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች እንዳሉና የመዳኘት ስልጣንም እንደተሰጣቸው በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 39 ተመልክቷል፡፡ የፍ/ቤቶቹን የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን በተመለከተ በሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 50/1/ እንደተመለከተውም ግምታቸው ከብር 5000(አምስት ሺህ) ባልበለጡ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮች ብቻ የተወሰነ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ነው ያላቸው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ክስ በገንዘብ የሚተመን አይደለም፡፡ በገንዘብ የማይተመኑ ወይም የገንዘብ ግምት የሌላቸው፣ ነገር ግን መሰረታዊ የሆነ የመብት ጥያቄ የሚያስነሱ ክሶች የሚታዩበትን ሁኔታ ሕጉ በተለየ ሁኔታ ደንግጓአል፡፡ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች የስረ- ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር እንዲወድቁ ግን አልደነገገም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አነስተኛ ድምጽ የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት ከአብላጫው ድምጽ የተለየውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በበኩላችንም ትክክለኛ ሆኖ ያገኘነው በአነስተኛው ድምጽ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም በአብላጫው ድምጽ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02188 *ታሕሣሥ* 3 ቀን 1998 ዓ.ም ተሰጥቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 02897 *ታሕሣሥ* 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የማይወድቅ በመሆኑ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ክሱን ያስተናገደው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34440

ጥቅምት 06 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- መንበረ ፖትሪያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ቀሲስ መሠረት አፈወርቅ

ተጠሪ፡- መጋቢ ሚስጢር መዝገቡ በላይነህ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ተከሣሽ ደግሞ የአሁኑ አመልካች ነበር፡፡

የሥር ከሣሽ ጥር 26 ቀን 1999 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የክስ ይዘት ሲታይም ከ1957 ዓ.ም ጀምሮ በቅኔ እና አቋቋም መምህርነት ሲያገለግሉ ቆይተው የተከሣሽ መ/ቤት አስተዳደር ጉባዔ ሰኔ 29 ቀን 1986 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ይሠሩበት ከነበረው ከደቡብ ወሎ ሀገረስብከት ወደ አዲስ አበባ ተዛውረው እየሰሩ መሆናቸውን፤ ሆኖም ከሐምሌ 01 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠ ደመወዝ መኖሩን በመግለጽ የተቋረጠው ደመወዝ ከሊሣራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የስር ተከሣሽም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርቦ መጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመከላከያ መልሱን አቅርቧል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ሲታይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑንና የከሣሽ የክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ የሚሆን መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥብነት አንስቶ በፍሬ ነገር ረገድም ከሣሽ አዲስ አበባ መጥተው በሌላ ቤተክርስቲያን አገልግሎት እየሠጡና ደመወዝ እየተከፈላቸው ከመሆኑም በላይ ቀድሞ ይሠሩበት ከነበረው ቦታም ሌላ ሰው ተተክቶ ደመወዝ እየተከፈለ መሆኑን በመጥቀስ የከሣሽ ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያስረዳ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን በቃል ከአከራከረና ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በተከሣሽ በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦች በከፊል ውድቅ በማድረግ የከሣሽን ጥያቄ በከፊል በመቀበል የተቋረጠ ደመወዝ ሊከፈለው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ ታህሣሥ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች ፈፀሙ ያሏቸውን የሕግ ስህተቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ ይኸው ቢታለፍ እንኳ የደመወዝ ጥያቄው ከአስራ ሁለት ዓመታት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚገባው መሆኑን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ መጋቢት 01 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው መሆኑንና የደመወዝ ጥያቄውም ውዝፍ ደመወዝ ይከፈለኝ ባለመሆኑ በይርጋ የሚታገድበት የሕግ አግባብ አለመኖሩን በመዘርዘር እና የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ተገቢነት በመግለጽ ሊፀና ይገባል ሲሉ መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረፈጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በበኩላቸው የተጠሪን መልስ በመንቀፍና የሠበር አቤቱታ ይዘቱን ተገቢነት በማጠናከር መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት መታየቱን በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የተቋረጠው የደመወዝ ክፍያ ጥያቄን ሊያቀርቡ የቻሉት በአመልካች መ/ቤት ከ1957 ዓ.ም ጀምሮ በቅኔ መምህርነት ተቀጥረው ሲያገኙት የነበረው ደመወዝ ከ1/11/86 ዓ.ም ጀምሮ ተቋርጧል በሚል ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ የቅኔ መምህር በመሆናቸውና አገልግሎቱም መንፈሣዊ በመሆኑ በስራ ክርክር ሰሚ ሊታይ እንደማይገባው በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤት ይህንኑ የአመልካች መከራከሪያ ነጥብ ያለፈውም የተጠሪ አገልግሎት ከኃይማኖት ተቋመ ጋር የተያያዘ ቀጥተኛ መንፈሣዊ ስራ አይባልም በሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ የተጠሪ ስራ ለተማሪዎች አገልግሎት የሚሰጥ የቅኔ መምህርነት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ለዚህ ለሰበር ችሎቱ በሰጡት መልስም የቅኔ መምህርነት ከኃይማኖት ተቋመ ጋር የተያያዘ ቀጥተኛ መንፈሣዊ ስራ አይደለም በማለት ያነሱት ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የቅኔ መምህርነት ስራ ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ስራ መሆኑ የሚያከራክር ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ የግራ ቀኙን ክርክር ያላገናዘበ ነው፡፡

ይህ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 18419 ግንቦት 04 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የኃይማኖት ድርጅት ሠራተኞችን በሁለት ከፍሎ በማየት የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ተፈፃሚነትን ወስኗል፡፡ በዚህም መሠረት ከኃይማኖት ድርጅቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና ከእምነት ተነጥሎ ሊታይ የማይችል ስራ የሚሠሩ ሠራተኞች እንደ ቄስ፣ ካህን፣ ዲያቆን --- ወዘተ ከኃይማኖት ድርጅታቸው ጋር የሚያነሡት ክርክር በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ሊዳኝ የማይገባው መሆኑ ተወስኗል፡፡ ሠበር ችሎቱ ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰውም መንፈሣዊ ስራ የሚሠሩት ግለሰቦች ቀጥተኛ ከእምነቱ ወይም የኃይማኖት ድርጅቱ ከሚከተለው እምነት የሚመነጭና ከእምነቱ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ፣ መንፈሣዊ አገልግሎቱን ለመስጠት ብቁ ሆኖ ለመገኘትም በእምነቱ መሠረት መሟላት የሚገባቸው ልዩ ነጥቦች መኖራቸው ይታወቃል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው ተጠሪ የቅኔ መምህር ሆነው ሊቀጠሩ የቻሉት የአመልካች እምነት የሚጠይቀውን ልዩ መመዘኛ አሟልተው በመገኘታቸውና ይህንኑ መንፈሣዊ አገልግሎት ለተማሪዎች ለመስጠት ነው፡፡ ተጠሪ የሚሠጡት አገልግሎት በባህርይው ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ትስስር ያለው መሆኑ እየታወቀ በኃይማኖት ተቋመ እንደሚሠሩ ሌሎች እንደ ሂሣብ ሠራተኛ፣ ንብረት ክፍል ሠራተኛ የስታትስቲክስ ሠራተኛ --- ወዘተ ተቆጥሮ የቅኔ መምህርነት ቀጥተኛ መንፈሣዊ አገልግሎት ሊባል አይገባም መባሉ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የተጠሪ ስራ ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ አገልግሎት ነው ከተባለ ደግሞ ከአመልካች ጋር የሚኖሩት አለመግባባት በስራ ክርክር ሠሚ ቀርቦ ሊታይ የማይገባ፣ ይልቁንም በኃይማኖት ተቋመ አለመግባባቶች በሚፈቱበት መንገድ ሊታይ የሚገባው መሆኑን ከላይ የተጠቀሰው የሰበር ችሎት ውሣኔ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20228 ግንቦት 08 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 55548 ህዳር 25 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ የተጠሪ ጥያቄ በኃይማኖት ተቋመ አለመግባባቶች በሚፈቱበት መንገድ ከሚታይ በስተቀር በስራ ክርክር ሠሚ አካል ቀርቦ የሚዳኝበት የሕግ መሠረት የለም ብለናል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4/ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 33841

ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አስጨናቂ ረጋሣ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ገዛኸኝ ነጋሽ ወኪል ሙሉመቤት - ቀረቡ

2. ወ/ሪት ሙሉእመቤት ነጋሽ - ቀረቡ

3. ወ/ሪት አሰገደች ነጋሽ - አልቀረበችም

4. አቶ ዘላለም ነጋሽ

5. አቶ ዳኛቸው ነጋሽ ወኪል - ቀረቡ

6. አቶ ኤፍሬም ነጋሽ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01973 ግንቦት 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03392 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይሻርልኝ በማለት ጎዳር 9 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ያልተወረሰና አባታችን ከአዋጁ በፊት በወለድ አግድ አስይዞት የነበረ፣እንዲሁም በቅጽ 004 የተመዘገበ የአባታችን አቶ ነጋሽ መንገሻ ንብረት የሆነ ቁጥሩ 668/669 ቤት አመልካችና የወረዳ 4 ቀበሌ 28 አስተዳደር ጽ/ቤት በፍርድ ተገድደው እንዲያስረክቧቸው ለአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችና ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው የወረዳ 4 ቀበሌ 28 አስተዳደር ጽ/ቤት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሰ ነው፤ በማስረጃነት የቀረበው ቅጽ 004 በሚመለከተው የበላይ አካል ያልፀደቀና በቀበሌ ደረጃ ብቻ የተሞላና አስተያየት የተሰጠበት ሰነድ በመሆኑ ቤቱ ያልተወረሰ መሆኑን ለማስረዳት አይቻልም የሚል ክርክር አቅርበዋል፤ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት የተወረሰ ነው በማለት የተጠሪዎችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ቤቱ በቅጽ 004 የተሞላ ተጠሪዎች አውራሽ የምርጫ ቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያለ በመሆኑ ለተጠሪዎች መመለስ አለበት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለከተማ ነክ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ይህ ውሣኔ መሰረታዊ ስህተት አለበት፤ በመጀመሪያም የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይህንን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የሥረ-ነገር ስልጣን የለውም፤ ቤቱ የተወረሰ ነው፤ ቅጽ 004 የተባለው በሚመለከተው አካል የፀደቀ ባለመሆኑ ቤቱ ለተጠሪዎች አውራሽ በምርጫ ቤትነት እንዲይዙት የተወሰነ መሆኑን ለማስረዳት ብቃት የለውም፤ የሚል ክርክር ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፤ ቤቱ በቅጽ 004 በወቅቱ ሕጋዊ ስልጣን ባለው አካል ለአውራሻችን በምርጫ ቤትነት የተሰጠ ነው ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ስህተት የለበትም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት የተወረሰ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለማየትና ቤቱን በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ያልተወሰረ በመሆኑ ለተጠሪዎች ይመልስ በማለት የመወሰን የዳኝነት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውመሰረታዊ የህግ ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ስልጣንና ሐላፊነት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በአንቀጽ 41 የተዘረዘረ ሲሆን የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ንብረትነቱ የከተማው አስተዳደር የሆነ ቤት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን እንዳለው በአዋጅ አንቀጽ 41(1)(ረ) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህም የምንረዳው የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማ አስተዳዳር ለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

ሆኖም ክርክር የተነሳበት ቤት የከተማው አስተዳደር ነው ወይስ የሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚል መሰረታዊ ክርክር ያለበት ከሆነ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ይህንን የቤት ባለቤትነት ጥያቄ አስመልክቶ በከተማው አስተዳደርና በሌሎች ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በዳኝነት አይተው ለመወሰን የሚያስችል የሥረ-ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 (1) (ረ) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የቤቱን ባለቤትነት አስመልክቶ በተጠሪዎች በኩል ክርክር እያቀረቡበትና የጉዳዩም መሰረታዊ ጭብጥ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት ተወርሷል ወይስ አልተወሰረም የሚል በመሆኑ ይህንን ጉዳይ ሰምተውና አከራክረው ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችላቸው የሥረ-ነገር ስልጣን ሣይኖራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ሣይኖራቸው ጉዳዩን ሰምተውና አከራክረው የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 0455 ጥር 5 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01973 ግንቦት 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03392 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የሥረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸው የተሰጡ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪዎች ሥልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይም አካል አቅርበው የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሣኔ አይገድብባቸውም ብለናል፡፡
3. በትውስት የመጣው መዝገብ ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር ይመለስ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ጉዳዩ በውሣኔ የተቋጨ ስለሆነ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 33368

ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሻምበል አሰፋ በላይ ዘገየ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ወታደራዊ ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የወንጀል ክርክርን ይሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በ1949 ዓ.ም በወጣው የወ/መ/ሕ በቁ. 386 እና 642 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ስለፈጸመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት ይገባል በማለት ነው፡፡ ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤቱም አመልካችን አስቀርቦ ከአከራከረ በኋላ አመልካች በተጠቀሱበት የሕግ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶች ስለመፈጸሙ በማስረጃ አረጋግጫለሁ የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በመቀጠልም በአመልካች ላይ የስድስት (6) ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው ቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 30 ቀን 99 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች ተፈጽሞአል የተባለው ወንጀል በወታደራዊ ፍ/ቤት የስረ - ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ለጉዳዮ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ሰበር ችሎት አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ጭብጥ በአመልካች ላይ የተመሠረተው ክስ በወታደደራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ ጉዳዮ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት ስልጣን ምንጭ (በአጠቃላይ) ምንድነው? አንድ ፍ/ቤት ከስልጣኑ ውጪ ጉዳይ ተቀብሎ ዳኝቷል ማለት ምን ማለት ነው? የዳኘው ከስልጣኑ ውጪ ሆኖ ከተገኘስ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚያስነሳ በመሆኑ በጥንቃቄ ለመመርመር የሚባው ነው፡፡

እንደሚታወቀው ፍ/ቤቶች በሕግ የሚቋቋሙ እንደመሆናቸው የዳኝነት ስልጣናቸው የሚመነጨውም ከሕግ ነው፡፡ ከዚህ እንግደህ መገንዘብ የሚቻለው የማንኛውም ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን በሕግ ተወስኖ የተሰጠ (የሚሰጥ) መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ (ክስ) ተቀብሎ ከማስተናገዱ በፊት በጉዳዮ (ክሱ) ላይ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የሚሰጥ ውሳኔ የሕግ መሠረት ያለው ነው ወይም ሕጋዊ ውሳኔ ነው ለማለት እንደማይቻልም በአግባቡ መገንዘቡ ተገቢ ነው የሚሆነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የወታደራዊ ፍ/ቤቶች እንደ ሌሎቹ ፍ/ቤቶች በሕግ የተቋቋሙ እና የዳኝነት ስልጣናቸውም በሕግ ተወስኖ የተሰጠ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ በመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ.27/1988 በአንቀጽ 25 እንደተመለከተው ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ተቋመመዋል ለፍ/ቤቶቹ የተሰጠ የዳኝነት ሥልጣን በተመለከተም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 26፣27 እና 28 በዝርዝር ተገልጿአል፡፡ በ1949 ዓ.ም በወጣው የወ/መሕግ ከቁ.296 እስከ ቁ.331 በተዘረዘሩት ወንጀሎች ተጠያቂ የሚሆኑ ሰዎች ላይ በግዳጅ ላይ ያለ ወታደር በሚፈጽማቸው በማናቸውም ወንጀሎች ላይ በውጪ አገር በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ ካለ ወታደር ጋር አብረው በሚዘምቱ ሲቪሎች ላይ እና በጦር ምርኮኞች ላይ ከተፈፀመ ወንጀል ላይ የወታደራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው አንቀጽ 26 በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተከሣሹ ከቀረቡበት ክሶች መካከል አንዱ በወታደራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል በሆነ ጊዜ ሁሉም ክሶች የሚቀርቡት ለወታደራዊ ፍ/ቤቶች እንደሆነ በአንቀጽ 28 ተመልክቶአል፡፡

በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ስንመለከት ፍ/ቤቶቹ በዚህ ጉዳይ አመልካች በተከሰሰበት የዳኝነት ስልጣን የላቸውም ለሚለው ክርክሩ በዋቢነት የጠቀሰው ከላይ በተመለከተው አንቀጽ 26/1/ የተቀመጠው ድንጋጌ ነው፡፡ በእርግጥም ይህ ንዑስ አንቀጽ ለብቻው ተወስዶ ሲታይ በወ/መ/ሕጉ ከቁ.296 እስከ ቁ.331 ድረስ ያሉትን ድንጋጌዎች ብቻ ስለሚጠቅስ በአመልካች ላይ በቀረበው ክስ የተጠቀሱትን ቁ.386 እና ቁ. 642 አያካትትም፡፡ ከዚህ የተነሣም የአመልካቹ ክርክር ተገቢነት ያለው ነው ሊባል ይችላል፡፡ በአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣(3) እና (4) የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ስንመለከት ግን ለወታደራዊ ፍ/ቤቶች የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በንዑስ አንቀጽ /1/ ከተመለከተው የሰፋ እንደሆነ ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ በንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተውን ድንጋጌ እንኳን ወስደን ስናየው በንዑስ አንቀጽ /1/ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በግዳጅ ላይ ያለ ወታደር በሚፈጽማቸው በማናቸውም ወንጀሎች ላይ ጭምር ፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ነው የምንገነዘበው፡፡ የአመልካቹ ክርክር በጽሑፍ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል ብሎ መደምደምያ የማይቻለውም (ትክክል የማይሆነውም) በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ‹‹ ግዳጅ›› የሚለው ቃል በአዋጁ ባለመተርጐሙ እና አመልካችም የተከሰሰው ከፋይናንስ አስተዳደር ጋር በተያያዘ ወንጀል በመሆኑ አመልካቹ በአዋጁ አንቀጽ 26 (2) አባባል በግዳጅ ላይ እንዳለ በፈጸመው ወንጀል ነው የተከሰሰው ወይም የተከሰሱበት ወንጀል የተፈጸመው በግዳጅ ላይ ሳለ ለማለትም ይቻላል ወይ የሚለው ነጥብ አከራካሪ ይሆናል፡፡

የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ.27/88 በመከላከያ ሠራዊት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁ.343/95 ተሻሽሎአል፡፡ ይህ አዋጅ በግልጽ ካሻሻላቸው አንቀጾች መካከል የቃላትን ትርጓሜ በተመለተ የተደነገገ ነው አንቀጽ 2 እና የወታራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የሚመለከተው አንቀጽ 26 ይገኛሉ፡፡ በዚህም በቀድሞው በትርጓሜ ውስጥ ተካቶ ያልነበረው ‹‹ግዳጅ›› የሚለው ቃል ‹‹ማንኛውም የሠራዊት አባል ከተቀጠረበት ጊዜ አንስቶ ከሠራዊቱ እስኪሰናበት ጊዜ ድረስ በመከላከያ ውስጥ የሚያከናውነው የውትድርና ተግባር ነው›› በሚል በማሻሻያው አዋጁ ቁ.343/95 አንቀጽ 2(9) ተተርጐሞአል፡፡ አንቀጽ 26(2)ም በትርጓሜ ክፍሉ በተተረጐመው ‹‹ግዳጅ›› ከሚለው ቃል በሚስማማ መልኩ ተሻሽሎአል፡፡ በዚህም የወታራዊ ፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ስልጣን ከቀድሞው የበለጠ ሰፍቶአል፡፡ አዋጅ ቁ.27/88‹ን› ማሻሻል ካስፈለገበት ምክንያቶች አንዱም በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ በወታደርነት በማገልገል ላይ ያለ የሠራዊቱ አባል የሚፈጽማቸው ወንጀሎች በወታደራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር እንዲወድቁ በመታሰቡ እንደሆነ ከአዋጁ ማሻሻያ አዋጅ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች የተከሰሰበትን ወንጀል ፈጸመ በተባለበት ጊዜ ሠራዊቱ አባል (ወታደር) ሆኖ ይሠራ እንደነበረ ተረጋግጦአል፡፡ ይህም ማለት በማሻሻያው አዋጅ ቁ.343/95 አንቀጽ 2(9) እንደተደነገገው በግዳጅ ላይ ነበር ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ፈጸመው የተባለው የወንጀል ድርጊት በአዋጁ አንቀጽ 26/1/ በተመለከቱት የወ/መ/ሕጉ ድንጋጌዎች ስር የማይወድቅ ቢሆንም በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ተቀጥሮ (በውትድርና) የሚያከናውነውን የውትድርና ተግባር ሲሰራ በነበረበት ጊዜ የፈጸመው በመሆኑ ክሱ ለወታደራዊ ፍ/ቤት መቅረቡ ትክክል ነው፡፡ ሲጠቃለል የወታደራዊ ፍ/ቤቶች ይህን ክስ ለማስተናገድ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን አላቸው፡፡ ስለዚህም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት ይግባኝ ሰሚ ወታራዊ ፍ/ቤት የመቁ.014/99 መጋቢት 18 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ክሱ ለወታደራዊ ፍ/ቤት መቅረቡ በሕጉ መሠረት ሆኖ ስላገኘነው የአመልካችን ክርክር አልተቀበልንም፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34788

ኅዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የሚች አቶ ሰለሞን ሳሙኤል ወራሾች -ቀርቧል

እነ ወ/ሮ ማረታ ሰለሞን(ሁለት ሰዎች) - ጠበቃ ታደሰ ጉርሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡-ኑረዲን መሐመድ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ጣልቃ ገቦች ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ፡፡

የአሁን ተጠሪ በሥር ተከሣሾች በነበሩት አንደኛ ንግድ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ፣ ሁለተኛ የወረዳ 5 አስተዳደር፣ ሦስተኛ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ላይ ባቀረበው ክስ በድርጅት ቤት፤ የሆቴል ንግድ ሕጋዊ ፈቃድ አውጥቼ በየዘመኑ ፈቃዴን እያሳደስኩ ከኪራይ ቤቶች ተከራይቼ በምሰራው ሆቴል ቤት እየሰራሁ እያለሁ፤የሥር ተከሣሾች ቤቱን ያለአግባብ እንዳልሰራ አሸገውብኛል፡፡ ስለዚህ አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡኝ ሦስተኛ የሥር ተከሣሽ ከእኔ (ተጠሪ) ጋር የነበረውን ውል ሣያቋርጥ(ሳያፈርስ) ሌላ ውል በመፈፀም ያስገባቸውን ግለሰቦች እንዲያስወጣ ውላቸውንም እንዲሰርዝ፣ የቀረብኝን ጥቅምና የደረሰብኝ ጉዳት የመጠየቅ መብቴ ተጠብቆ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

አንደኛ እና ሁለተኛ የሥር ተከሣሾች ለቀረበባቸው ክስ መልስ ሲሰጡ፡- የአሁን ተጠሪ ፍቃዳቸውን ያላደሱ በመሆኑ የጸና የንግድ ፍቃድ የላቸውም ፍቃዳቸው ተሰርዟል፡፡

ከተጠሪ ጋራ ያለን ግንኙነት ስለተቋረጠ የሚጠይቁት ጥቅም ሆነ መብት የላቸውም ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ሲመልስ፤ሁለተኛ የሥር ተከሣሽ በበኩሉ የተባለውን ቤት በጋራም ሆነ በተናጥል አላሸግኩም ሲል መልሷል ሦስተኛ የስር ተከሳሽም በተመሣሣይ መልኩ ድርጊቱን እንዳልፈፀመ ክዶ ተከራክሯል፡፡

በዚሁ ጉዳይ የሥር ጣልቃ ገብ የአሁን ተጠሪ ይህን ቤት በሕጋዊ መንገድ ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ተረክበው በውላቸው መሰረት ይዘውት እንዳሉ ገልጸው የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን በመቃወም ተከራክረዋል፡፡

የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከሕግ ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ የንግድ ፈቃድ ባለማደሳቸው እና በወቅቱ የቤት ኪራይ ክፍያ ባለመፈፀማቸው ምክንያት በኪራይ ይዘውት የነበረውን ቤት ሕግና ደንብ በሚያዘው መሰረት መብታቸውን አጥተዋል፡፡ ስለዚህ ይህን ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 33(2) መሰረት የመክሰስ መብት የላቸውም ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪም በተሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታውን አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አስቀርቦ በማከራከር ካየ በኋላ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የአሁን ተጠሪን የንግድ ድርጅት ያሸገው ያለ አግባብ ነው፣ ሦስተኛ የሥር ተከሣሽ ከአሁን ተጠሪ ጋር ያደረገው የቤት ክራይ ውል ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ከአሁን አመልካቾች ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውል ላይ ውል በመፈፀም ቤቱን ያስረከባቸው በአግባቡ አይደለም፣ የአሁን ተጠሪ እና የሥር ሦስተኛ ተከሣሽ የኪራይ ውላቸውን መቀጠል ይገባል በማለት የሥር ውሳኔን በመሻር ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁን አመልካቾች በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለከተማው ሰበር ሰሚ ለሆነው ፍ/ቤት ቅሬታቸውን በማቅረባቸው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በፍ/ቤቱ ውስጥ ጉዳዩን የማየት ስልጣንን አስመልክቶ የሐሳብ ልዩነት በመፈጠሩ በልዩነት ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አብላጫው ድምጽ ምክንያቱን ሳያስቀምጥ "ምንም እንኳን የፌዴራል መንግስት አካል የሆነው የኪ.ቤ.አ.ድ በዚህ መዝገብ ተከራካሪ ቢሆንም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ነገር የመስተዳድሩ አካላት በነበራቸው የአስፈፃሚነት ስልጣን በመሆኑና እነርሱ የወሰዱትን እርምጃን ተከትሎ የኪ.ቤ.አ.ድ በወሰደው እርምጃ የተከሰሰና ይህም አንድ ድርጊት በመሆኑ ጉዳዩ የዚህ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው" በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ስህተት የለም በማለት የሰበር አቤቱታውን ሰርዞታል፡፡

አነስተኛ ድምፁም በጉዳዩ የተለየበትን ሐሳብ ሲያስቀምጥ፡- "በክርክሩ ጭብጥ ውስጥ ይህንን ቤት በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የኪራይ ቤቶች ድርጅት ቤቱን አላግባብ ለሦስተኛ ወገን አከራየብኝ የሚል በመሆኑ በአዋጅ 25/88 መሰረት መዳኘት የሚኖርበት በፌዴራል ፍርድ ቤት ከመሆኑም በላይ የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤትም በአዋጅ 36/95 አንቀጽ 41/1/ረ ላይ መስተዳድሩ በባለቤትነት ከሚያስተዳድራቸው ሥር የማይሸፈን በመሆኑ በከተማው ፍ/ቤት መታየቱ ከሥልጣን አካያ አግባብ አይደለም" ሲል ልዩነቱን አስፍረዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች ጥር 1 ቀን 2000 ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ በከተማው ይግባኝ ሰሚና በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሣኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታቸውን አቅርቧል፡፡

ይህ የፌዴራል ሰበር ችሎትም አቤቱታውን ምክንያት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምተዋል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የወሰነው የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ይህን ነጥብ ከተነሳው ክርክር፣ በአቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ክሱን ሲመሰርት የሆቴል ቤቱ ያለአግባብ በመስተዳድሩ አካላት እና በቱሪዝም ቢሮ የታሸገበት መሆኑን ብቻ ሳይሆን የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት የሆነውን የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ኪራይ እየከፈልኩ የምሰራበትን የሆቴል ቤት ነጥቆኝ ለሦስተኛ ወገን አከራይቶታል በሚል ምክንያት ነው፡፡

እኛም ተሻሽሎ የወጣውን የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁ. 24/1/ረ ስናይ የከተማው ፍ/ቤት ማየት የሚችለው የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን ነው፡፡ ሕጉ ይህን እያለና ዋና **የቤት** አስተዳደር (ባለቤት) ከተጠሪ ጋራ የውል ግንኙነት እያላቸው በፌዴራሉ ሥልጣን ክስ የሚወድቀውን ክርክር በከተማው ፍ/ቤት መታየቱ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለዚህ በሥር ፍ/ቤት በአበላጫ ድምጽ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ በአናሳው ደምጽ ጉዳዩ የከተማው ፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም ያለው ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአ.አ.ከተማ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት መ/ቁ. 2633/91 ሐምሌ 22 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02703 ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የከተማው ሰበር በመዝገብ ቁ. 05360 በ4/4/2000 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ተሽሮአል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የአ/አ/ከተማ መስተዳድር ፍ/ቤቶች ይህን ክርክር የማየት ስልጣን የላቸውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪ እና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 31906

ኅዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ሒሩት አሥራት

ተጠሪ፡- የአቶ መርስኤ መንበሩ ወራሾች - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ለዚሁ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሟች አባታችን በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 3 ቀበሌ 53 ክልል ቁጥር 849 የሆነውን ቤት በ1957 ዓ.ም. ከቀድሞ ባለ ርስት በጭሰኝነት ተመርተው ተገቢው ኪራይ እየከፈሉ ሲገለገሉ የቆየ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲታወጅ የባለርስትና የጭሰኛ ግንኙነት በመቋረጡ የአፈር ግብር ለመንግሥት እየከፈሉ የቆዩ ቢሆንም የቤት ባለቤትነት ደብተር ለማውጣት በቦታው ላይ ይዞታ እንደነበራቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከፍ/ቤት አስመስክረንና አረጋግጠን እንድንቀርብ የተጠየቅን በመሆኑ የቤት ባለቤትነት ደብተሩን ማግኘት እንድንችል በቦታው ላይ ይዞታ ያለን ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጠን በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች በተጠሪነት ያጣመሩት ባለመኖሩ ፍ/ቤቱ የአመልካካቾችን ምስክሮች ሰምቶ የአመልካቾች አባት ቦታውን በ1959 ዓ.ም. ከልዕልት ተናኘ ወርቅ ላይ በጭሰኝነት ተመርተው ውሃና መብራት በማስገባት ቤት ሠርተው የጋራዥ ድርጅት አቋቁመው ሲሰሩበት እንደበር አዋጅ ቁጥር 47/67 ከታወጀ በኋላ የቦታና የቤት ግብር ለመንግሥት ሲከፍል እንደነበር በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ይዜው ተገልጾ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍላቸው በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ በወቅቱ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት አመልካቾች በይዞታቸው ሥር እንደሆነ ተገልጾ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ትዕዛዝ የተሰጠበት ድርጅት በአዋጅ 47/67 መሠረት የተወረሰና የሚያስተዳድረው መሆኑን ገልጾ በሌለበት የተሰጠው ትዕዛዝ መብቱን እንደነካ በመግለጽ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት በተቃዋሚነት ወደ ክርክሩ ለመግባት ጠይቆ በተፈቀደለት መሠረት ወደ ክርክሩ በመግባት ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ክርክር የተነሳበት ድርጅት በአዋጅ 47/67 መሠረት ተወርሷል አልተወረሰም የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር መወሰኑ ስለተረጋጠ አመልካቾች ከአዋጅ 47/67 መንፈስ ውጭ ተወስዶብናል የሚሉ ከሆነ ይህንኑ ጥያቄያቸውን በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ከሚያቀርቡ በስተቀር በተያዘው መዝገብ እንደማይስተናገድ ጠቅሶ አስቀድሞ ለአመልካቾች ይዞታ ያላቸው መሆኑ ተጠቅሶ እንዲፃፍላቸው የተሰጠው ትዕዛዝ ሊነሳ ይገባል በማለት አንስቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙ አከራክሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ድርጅት በይግባኝ ባዮች ይዞታ ሥር እንደነበርና በአዋጅም እንዳልተወረሰ የቀረቡት ማስረጃዎች የሚያረጋግጡ እንደመሆኑ መጠን መልስ ሰጭው ድርጅቱ መወረሱን ባላረጋገጠበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት ድርጅቱ መወረሱ ተረጋግጧል በማለት አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ ማንሣቱ በአግባቡ አይደለም ሲል በመሻር የቀድሞው ትዕዛዝ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ሰበር ችሎትም ይሄው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመበትም በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ሳይቀረበለው ቀርቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ በሚያከራክረው ንብረት ላይ ተጠሪዎች የይዞታ ማስረጃ እንዲሰጣቸው በፍ/ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ነው ተብሎ የአመልካች መቃወሚያ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን ጠርቷል፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች በአድራሻቸው ሊገኙ ባለመቻላቸው በጋዜጣ ተጠርተው ስላልቀረቡ በጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ በቃል ክርክርም ጊዜ ስላልቀረቡ ችሎቱ የአመልካችን የቃል ክርክር ብቻ አዳምጧል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በቅድሚያ ችሎቱ የተመለከተው አመልካቾች አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ለፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችልና ዳኝነት የሚያፈልገው /Justicable/ መሆኑን በተመለከተ ነው፡፡

ተጠሪዎች በከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ለክርክሩ ምክንያት በሆነው የንግድ ድርጅት ላይ የይዞታ መብት ያለን መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጠን በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች የዚህ ዓይነቱ ማስረጃ ከፍ/ቤቱ እንዲሰጣቸው የጠየቁትም የቤት ባለቤትነት ደብተር ከሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ለማግኘት እንደሆነም በአቤቱታቸው ላይ ጠቅሰዋል፡፡

የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 ላይ የተመለከተ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት የሚሰጠው በመንግሥት የአስተዳደር መ/ቤት በኩል እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንደዚሁም የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት ሥርዓት የአስተዳደር መስሪያ ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት እንደሚወሰንም በዚሁ ድንጋጌ ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም ሰው በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ማግኘት የሚችለው ከሚመለከተው የመንግሥት አስተዳደር መስሪያ ቤት በኩል ሲሆን የሚመለከተው የመንግሥት አስተዳደር መ/ቤት የምስክር ወረቀት አሰጣጡን አስመልክቶ በሚያወጣው የምስክር ወረቀትም እንደሚሰጥ መረዳት ይቻላል፡፡

ሕጉ በዚህ መልኩ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት እንደሚሰጥ ከደነገገ የምስክር ወረቀቱን ለማግኘት እንዲቻል የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲሰጥ ፍ/ቤትን መጠየቅ ከነመነሻውም ቢሆን ጉዳዩ በፍ/ቤት ቀርቦ ዳኝነት የሚያስፈልገው /Jusciable matter/ እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም የዚህ ዓይነቱ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት በፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት ሊስተናገድ እንደማይችል ግልጽ በመሆኑ ከመነሻውም ቢሆን ፍ/ቤቱ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት መመለስ ሲገባው ጉዳዩን ማስተናገዱ አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ የቀድመውን ትዕዛዝ መሰረዙ ከውጤት አኳያ ተቀባይነት ነበረው፡፡ ሆኖም ግን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይህንኑ ትዕዛዝ ምክንያቱን ለውጦ ሊያጸናው ሲገባ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ድርጅት መወረሱ አልተረጋገጠም በማለት መሻሩ ጉድለት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከተማው ይግባኝ ሰማ ሰበር ችሎትም መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ይህንኑ ጉድለት ሳያርም መቅረቱ በአግባቡ ሆኖ አላገኘነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 01998 ሚያዝያ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እንደዚሁም ይግባኙ ችሎቱ በመ/ቁ. 00682 በ30/3/97 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት በአብላጫ ድምጽ ሽረነዋል፡፡
2. ተጠሪዎች የቤት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት እንድችል የይዞታ መብት ያለን መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከፍ/ቤቱ ይሰጠን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ለፍ/ቤት ቀርቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የማይችል ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/Justicable matter/ ስላልሆነ አቤቱታው ከመነሻውም ቢሆን ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ነበር በማለት ወስነናል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የሀሣብ ልዩነት</u>

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ በመጀመሪያ ተጠሪዎች ክርክር የተነሳበትን ቤትና ቦታ በክፍተኛ 3 ቀበሌ 53 ፍርድ ሸንጎ ውሣኔ መሠረት መያዛቸውን አንስተው የተከራከሩ በመሆኑና አመልካችም በበኩሉ ተጠሪዎች ኪራይ እንዲከፍሉ ሚያዝያ 5 ቀን 1981 ዓ.ም. በቀበሌ ሸንጎ አስወስኛለሁ የሚል ክርክር ያለው በመሆኑ የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ጥር 26 ቀን 1973 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና ሚያዝያ 5 ቀን 1981 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት ይህ ሰበር ችሎት በተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በትዕዛዙ መሠረት መዝገቡ አልተገኘም የሚል ምላሽ የቀረበ ሲሆን እነዚህን አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች የፍርድ ባለ መብት ሁነንባቸዋል የሚላቸውን ውሣኔዎች በማግኘት የሚያስችል ሌላ ተለዋጭ ትዕዛዝ መስጠቱን በአዋጅ ቁጥር 47/1967 በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የቀበሌ ሸንጎዎች የሰጡት አስገዳጅ ውሣኔ መኖር አለመኖሩን በማጣራት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ይገባ ነበር፡፡ ይህ ሣይደረግ መዝገቡ አሁን ባለበት ሁኔታ መርምሮ ውሣኔ መስጠቱ፣ ተገቢ አይደለም የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የአንድ ቦታና ንብረት ሕጋዊ ባለይዞታ መሆኔ በፍርድ ይረጋገጥልኝ የሚል ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ወይም በፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብበት ውሣኔ ሊሰጥበት የሚችል /Justicable/ አይደለም የሚለውና የአብላጫው ድምጽ መደምደሚያ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ምክንያቱም ይዞታን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት የመስጠት ስልጣን የአስተዳደር አካላት መሆኑ የማይካድና የይዞታ የምስክር ወረቀትም በአስተዳደር ደንብ መሠረት መከናወን ያለበት መሆኑ ያማያከራክር ቢሆንም የሕጉን ሥርዓትና ደንቡን ያሟላ ባይዞታዎች በአስተዳደር በኩል የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ጠይቀው አላግባብ ቢከለከሉ ይህንንም እስከ መጨረሻው አስተዳደራዊ እርከን ድረስ ለማሣረም ሞክረው የይዞታ የምስክር ወረቀት አታገኙም ተብሎ ቢወስንባቸው ይህንን አስተዳደራዊ ውሣኔ በመቃወም ሕጉንና ደንቡን አሟልተው በቦታው ላይ የሚገኙ ሕጋዊ ባለይዞታዎች መሆናቸውን በፍርድ እንዲረጋገጥላቸው ከመጠየቅ የሚገድባቸው ሕግ የሌለ በመሆኑ ጉዳዩ የክስ ምክንያት የለውም በሚለው መደምደሚያ ባለመስማማት ከሙያ አጋሮቼ በሀሣብ ተለይቻለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረትና ቦታ ሕጋዊ ባለይዞታ መሆኔ በፍርድ ይረጋገጥልኝ የሚለው ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም የሚባል ከሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አንድ የማይነቀሳቀስ ንብረት በይዞታቸው ሥር በማድረግ ለአስራ አምስት ዓመት ግብር እየገበሩ የኖሩ ሰዎች አስተዳደሩ ለአስራ አምስት ዓመት የቦታውና የንብረቱ ባለይዞታ መሆናቸውን እና በስማቸው ግብር መክፈላቸውን የሚያረጋግጥ የይዞታ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ባይቀርብላቸው ይህንን በማስረጃ በማጣራት ፍርድ ቤቱ የንብረቱ ባለይዞታ ብቻ ሣይሆኑ የንብረቱ ባለቤት መሆናቸውን በፍርድ እንዲያረጋግጥላቸው የሚያቀርቡትን ጥያቄ በፍርድ ቤት ሊወሰን አይችልም በሚል መንገድ፣ የሚዘጋበት የሕግ አተረጓጎም እና መደምደሚያ የሚያስከትል ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ሰዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 ንዑስ አንቀጽ 1 የተረጋገጠላቸውን መብት በአስተዳደር አካላት ቢጣስ በፍርድ ቤት ክስ አቅርበው መብታቸውን እንዲያረጋግጡ የሚያደርግ በመሆኑ በጥንቃቄ መታየት አለበት የሚል ሀሣብ አለኝ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ከዚህ በፊት ስልጣን ባላቸው አካላት ታይቶ የተወሰነ መሆኑን ተከራካሪዎቹ ካደረጉት ክርክር ለመረዳት የሚቻል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም እነዚያን ውሣኔዎች ይዘትና ምንነት በመመርመር ለመወሰን የሚያስችለውን ሥርዓት መከተል ነበረበት፡፡ በሌላ በኩል የይዞታ መብት ጥያቄና ይዞታን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የማግኘት ጥያቄ በባሕሪው በፍርድ ቤት የማይታይና ክስ የማይቀርብበት ጉዳይ አይደለም፡፡ አስተዳደሪዊ መፍትሔዎችን አሟጥጦ የጨረሰ ሰው እስከመጨረሻው እርካን ድረስ ባለው አስተዳደራዊ መዋቅር የተሰጠው ውሣኔ ሕጋዊ የይዞታ መብቱ እውቅና የማይሰጥና መብቱን የሚሸራርፍ ነው ብሎ ሲያስብ በበቂ ማስረጃ ለፍርድ ቤቶች ክስ ማቅረብና የቦታውና የነብረቱ ሕጋዊ ባለ ይዞታ መሆኑን፣ በፍርድ እንዲረጋገጥለት መጠየቅና ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶችም ጉዳዩን አይተው ለመወሰን የዳኝነት ስልጣን አላቸው በማለት አብላጫው ድምጽ ከሰጠው የሕግ ትርጉምና ከደረሰበት መደምደሚያ በሀሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37281

ታህሳስ 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አበበ ዓሊ - ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. የ08 ቀበሌ ገ/ማህበር - አልቀረቡም

2. አቶ ዓሊ ሰይድ - አልቀረቡም

3. ወ/ሮ ገዛሽ ስዩም - አልቀረቡም

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ አቤቱታ የቀረበው አመልካች ሚያዝያ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጠ/ፍ/የፍ/ይ/መ/ቁ. 336/2000፣ ጥር 21/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲሻርላቸው በመጠየቃቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን፣ በቃሉ መረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ፣የአሁኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ የመሰረታዊ ይዘቱ ክርክር የተነሳበትን ቤቴን አንደኛ ተከሳሽ (አከራይ) ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ደግሞ (ተከራዮች) በመሆን አላግባብ ይዘው ስለሚገኙና ቤቴን ሊያስረክቡኝ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ከመስከረም 1998 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 100(አንድ መቶ) ሂሳብ ክስ እስከ ቀረበበት ጊዜ ድረስ ታስቦ በጠቅላላ ብር 500(አምስት መቶ ብር) ከፍለው ተገደው እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ክስ የቀረበለት ወረዳ ፍርድ ቤትም በፍ/መ/ቁ.02127/98 ጥር 18 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አከራካሪው ቤት በመንግስት እጅ የሚገኝ በመሆኑና በመንግስት እጅ የሚገኝ የተወረሰ ቤት ደግሞ በአዋጅ ቁ. 110/1987 መሰረት የመወሰን ስልጣን ያለው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ ፍርድ ቤቶች አይደሉም በማለት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ሥራና ከተማ ልማት ቅ/ጽ/ቤት ጥር 08/1999 ዓ.ም ደብዳቤ እንደፃፈ በመግለጽ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም ብሏል፡፡ የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት በፍ/ይ/መ/ቁ. 14649 ካከራከረ በኋላ ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ ያጸናው ሲሆን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ ቢቀርብለትም በጠ/ፍ/የፍት/ሐብሔር ይግባኝ መ/ቁ 336/2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ወደዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም ተጠሪዎቹ በውርስ ያገኘሁትን ቤት አላግባብ ይዘዋል፤ቤቱ በመንግስት የተወረሰ አይደለም፤ ይህ አከራካሪ ቤት እንዲመለስልኝ ለቃሉ ወረዳ ምክር ቤት አመልክቼ ምክር ቤቱም መፍትሄ እንዲሰጠኝ ወደ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ደብዳቤ ጽፎልኝ ኤጀንሲውም በበኩሉ ጳጉሜ 03 ቀን 1996 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ በአዋጁ ከተሰጠው ስልጣን አኳያ ተገናዝቦ ሲታይ በስልጣኑ ስር እንደማይወድቅና የማየት ስልጣን እንደሌለው በግልጽ ወስኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶቹ ያቀረብኩትን ክርክር በአግባቡ ሳይመረምሩ በደፈናው ስልጣን የለንም ማለታቸው ተገቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም፤የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አከራካሪውን ቤት የመመለስ ጉዳይ በተሰጠው ስልጣን ውስጥ እንደማይካተት በግልጽ አስቀምጦ እያለ ፍ/ቤቶቹ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ማለታቸው የፍትህ ጥያቄን ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡

አንደኛ ተጠሪም በቁጥር ፍ/ደ/ማ 19/421/2000 ሐምሌ 03 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፤ይዘቱም አከራካሪው ቤት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን፣ኮምቦልቻ ከተማ 08 ቀበሌ ገበሬ ማህበር ክልል ልዩ ስሙ ሚጢቆሎ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኝ በምስራቅ የአቶ አብዱ ረዲ ቤት፣በምእራብ የ08 ቀ/ገ/ማህበር ጽ/ቤት፣ በደቡብና በሰሜን የመኪና መንገድ የሚያዋስነው ከእንጨትና ከጭቃ የተሰራ ሁለት ክፍል ቤት ሲሆን የአቶ ዓሊ ሙሄ እንደነበር ይታወቃል፣ ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተወረሰ ነው፣የቤቱ ባለቤት የነበሩት አቶ ዓሊ ሙሄ ቤቱ እንዲመለስላቸው ጥረት እያደረጉ የነበረ ቢሆንም ቤቱ እንደማይመለስላቸው በወቅቱ ተነግሯቸዋል፤የአሁኑ አመልካችም ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ፤አቶ ዓሊ ሙሄ በሞት የተለዩት በ1971 ዓ.ም ስለሆነ አመልካች ከ33 ዓመታት በኋላ አሁን ያቀረቡት ክስ በይርጋ እንደሚታገድ ተቃውሞ አቅርቤበት እያለሁ የስር ፍ/ቤቱ ምንም አይነት ብይን ሳይሰጥበት አልፏል፣ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶቹ በአከራካሪው ቤት የሰጡት ፍርድ ተገቢ ስለሆነ ይጽናልኝ የሚል ሲሆን፡፡ ሁለተኛ ተጠሪም ሐምሌ 16 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው አከራካሪው ቤት በመንግስት የተወረሰ ሆኖ እኔ በኪራይ ይገፍዋለሁ፤ተጨማሪ ወጪ አድርጌበታለሁ፤ አመልካች ይህንን ክስ ጊዜውን ጠብቆ ያቀረበው ባለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000 በይርጋ ይታገዳል ብለዋል፤ሦስተኛ ተጠሪ ስላልቀረቡ የሰጡት መልስ የለም፡፡

አመልካችም በመሰረቱ ከአቤቱታቸው ያልተለየ የመልስ መልስ ያቀረቡ በመሆኑ ደግሞ መዘርዘር ሳያስፈልግ ታልፏል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የክርክሩ አመጣጥ ከላይ በሰፈረው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አከራካሪውን ቤት የማየት ስልጣን የለኝም እያለ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም ማለት ነበረበት ወይስ አልነበረበትም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤቱ ባቀረቡት የቤት ይመለስልኝ ክስ የቃሎ ወረዳ ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው ቤቱ በመንግስት የተወረሰ ነው የሚል ክርክር በመቅረቡና የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከተማ ልማት በመንግስት የተወረሱ ቤቶች አይቶ መወሰን የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሰረት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤቶች አይደሉም ያለውን ነው፡፡ በእርግጥ በአዋጅ ቁ. 47/1967 የተወረሱ ቤቶች እንዲሁም ከዚህ አዋጅ ውጭ በደርግ ጊዜ በቀላጤ የተወረሱ ቤቶችን መደበኛ ፍርድ ቤቶች አከራክረው የመወሰን ስልጣን የላቸውም፣ በሚመለከተው የአስተዳደር አካል እንዲሁም በቀላጤ የተወረሱ ከሆነ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 110/1987 መሰረት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ይታያሉ እንጂ በመደበኛ ፍ/ቤቶች አይደለም፡፡ አሁን ክርክር የተነሳበት ቤት በሚመለከት ግን ቤቱ የተወረሰ ነው ከሚል ግምት ውጭ የግራ ቀኙ ወገኖች ማስረጃዎች በዝርዝር አልተመዘኑም፣ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አከራካሪውን ቤት የማየት ስልጣን የለኝም ብሎ ደብዳቤ ጽፏል የተባለው በተገቢው ሁኔታ ተገናዝቦና ተተንትኖ ፍርድ ያረፈበት አይደለም፤የዞኑ የስራና ከተማ ልማት ቅ/ጽ/ቤት ደብዳቤ ስለፃፈ የሚለው ምክንያት በማስቀመጥ ክርክሩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የተሰጠው ፍርድ የተሟላ አይደለም፤ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁ. 47/1967 የተወረሰ ቤት ወይም ከዚሁ አዋጅ ውጭ በደርግ ስርአት ጊዜ በቀላጤ የተወረሰ ቤትን በሚመለከት አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የለኝም ለማለት ይህ መሆኑ በተከራካሪ ወገኖች ወይም በሌላ አካል ስለተጠቀሰ ብቻ ሳይሆን የቀረቡለት ማስረጃዎችና አጠቃላይ የክርክር አቅጣጫዎች በመመዘን ይህ መሆኑ የሚያመላክቱ ሆነው ሲያገኛቸው ነው፤በአሁኑ ክርክር ግን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ጉዳዩ ስልጣኑ እንዳልሆነ ገልጿል እየተባለ ነው፤በአጠቃላይ የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞዎች ሳይመዝኑና ሳይበይኑ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የተሰጠው ፍርድ በመሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የቃሎ ወረዳ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 02127/98 ጥር 18 ቀን 1999 ዓ.ም የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 14649፣ጥቅምት 15 ቀን 2000 እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጠ/ፍ/ይ/መ/ቁ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

336/2000 ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጧቸው ፍርዶች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፤ይፃፍ፡፡

2. የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክርና የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ከማስረጃዎቻቸው አኳያ በተገቢው ሁኔታ ሳያገናዝብ አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁ. 110/87 መሰረት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስልጣን ነው በማለት የቃሉ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን መዝጋቱ የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ተቀብለው ማጽደቃቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፤ስለሆነም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክርና የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ካቀረቡት ማስረጃና የህግ ይዘት አኳያ አገናዝቦ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሰረት ለቃሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ተመልሶለታል፤ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍርድ ቤት ላደረጉት ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፤ጉዳዩ ያለቀ ስለሆነ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37339

ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ንግሥት ኃይሌ - ተወካይ አቶ ኃይሌ በልሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ለገሠ ዓለሙ ጠበቃ - አቶ ብስራት መኮንን ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለመርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57224 ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35533 መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች በከፍተኛው ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርባና ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሣሥረው ሲኖሩ በአገር ውስጥና በአሜሪካን ሀገር የጋራ ሀብት ያፈሩ መሆኑን በመግለጽ፣ ጋብቻችን በፍች ፈርሶ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአገር ውስጥ ያለንን የጋራ ሀብት አስመልክቶ ክርክራችንንና ማስረጃችን በመመርመር ውሣኔ የሰጠ ሲሆን በአሜሪካን አገር የሚገኘው ንብረት በተመለከተ ስልጣኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት ጥያቄን ያልተቀበለኝ ለመሆኑ በውጭ ያለንን የጋራ ንብረት አስመልክቶ አከራክሮ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ የሁለታችንም በዜግነት ኢትዮጵያዊያን ነን፡፡ ንብረቱ በአሜሪካን አገር መኖሩ የዓለም አቀፍ የግል ሕግ ጥያቄ የማያስነሣና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ-ነገር ስልጣን የማያሣጣ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ጉዳዩ የዓለም አቀፍ የግል ሕግ ጥያቄ አያስነሣም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው ከገለፀ በኋላ በአሜሪካን አገር የተገኘ ንብረት ብቻ ተነጥሎ በዚህ ፍርድ ቤት የሚያስተናግድበት ሥርዓት የለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ይግባኝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባታል፡፡ አመልካች ያቀረብነው የጋራ ንብረት ጥያቄ በተመለከተ በአገር ውስጥ የሚገኘውን ሀብት በተመለከተ አከራክሮ ከወሰነ በኋላ በአሜሪካን አገር የተጠራቀመውን 9713.12 ዶላር /ዘጠኝ ሺ ሰባት መቶ አስራ ሶስት ዶላር ከአስራ ሁለት ሣንቲም/ የክፍፍል ጥያቄ በተመለከተ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ ጥያቄ የሚያስነሣ በመሆኑ ስልጣን ባለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይታይ በማለት መዝገቡን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልኳል፡፡ ሆኖም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን የተላከለትን የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመዝጋት ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ አድርጓል፡፡ እኔም አዲስና ራሱን የቻለ ክስ ውጭ ያለውን ገንዘብ አስመልክቶ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ሣቀርብ አላግባብ ውድቅ ሆኖብኛል፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ ያቀረብኩትን የመብት ጥያቄ ውሣኔ ሣይገኝ እየተጉላላሁ ያለሁ በመሆኑና ይኸም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ጠይቃለች፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡትን መዝገብ ዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ሲመልስ ይግባኝ ማቅረብ ሲገባት እንደ አዲስ ክስ ማቅረቧ ተገቢ አይደለም ሕጋዊ ሥርዓትን የተከተለ አይደለም፡፡ ስለዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጨረሻ ውሣኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ እንደገና ክስ ማቅረቢ ተገቢ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካች ፍርድ ቤቶቹ ሥልጣኑ የአንተ ነው እየተባባሉ ጉዳዩን አንጠልጥለው ከማስቀረታቸው ውጭ በጉዳዩ ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ የለም። እንደ አዲስ ክስ ማቅረቤ ተገቢ ነው በማለት በመልስ መልሱ ተከራክሯል።

ከሥር የክርክሩ መነሻና አመጣጥ በሰበር አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል። መዝገቡን እንደመረመርነው ፡

1.ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ነው ወይስ አይደለም?

2. የአመልካች ክስና ጥያቄ በሥር ፍርድ ቤት ሊታይና ሊስተናገድ የሚገባው ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የአመልካችና የተጠሪ ጋብቻ በፍች እንዲፈርስ የወሰነው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ በአገር ውስጥ ያላቸውን የጋራ ሀብት አስመልክቶ ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሣኔ የሰጠ ሲሆን በአሜሪካን አገር አለ ስለተባለው ሀብት ሥልጣኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ውሣኔ ይሰጥበት በማለት መዝገቡን ወደ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ልኮታል። የከፍተኛው ፍርድ ቤት በበኩሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የላከለትን መዝገብ አመልካችን ሣይጠራ በከፊል በሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ ተቀብዬ የማስተናግድበት ሥርዓት የለም በማለት መዝገቡን ዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት የመለሰው መሆኑ ፍርድ ቤቱ ጥር 16 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ለመረዳት ይቻላል። አመልካች በውጭ አገር አለ ያሉትን የጋራ ሀብት አስመልክቶ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 በተሰጠው ስልጣን መሠረት እንዲወሰንላቸው አዲስ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ይህንንም ፍርድ ቤቱ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በግማሽ ጉዳይ ላይ አይቶ ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ እኔ ከፊሉን ጉዳይ አይቼ የምወስንበት ሥርዓት የለም በማለት ዘግቶታል።

ከዚህም የምንረዳው አመልካች በአሜሪካን አገር ያለው የጋራ ሀብት እንዲካፈል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስና ጥያቄ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ ጥያቄ ሊያስነሣ ስለሚችል ይህንን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን የላከው መሆኑንና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ በአገር ውስጥ ስላለው ሀብት ውሣኔ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የተሰጠ በመሆኑ በውጭ አገር የሚገኘውን ሀብት ብቻ አይቼ በከፊል የምወስንበት ሥርዓት የለም በማለት በመወሰኑ ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ ያለና የመጨረሻ ውሣኔ ያላገኘ ሆኖ አግኝተነዋል።

በመሆኑም ተጠሪ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ነው በማለት የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በውጭ አገር ያለው የጋራ ሀብት እንድትካፈል ያቀረበችው ጥያቄ አይቶ የመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን እንደሌለው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ብይን ከሰጠ በኋላ የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር የተሰማበትን የመዝገብ ቁጥር ዐ0289 ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ልኮለታል። የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥሩ 54637 በሆነ ፋይል ከሸፈነ በኋላ በአመልካች ጥያቄ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ትእዛዝ የተላለፈለትን ጉዳይ አመልካችን ሣይጠራ ጉዳዩ የሚያስተናግድበት ሥርዓት የሌለ መሆኑን በመግለጽ የሥር ፍርድ ቤትን መዝገብ የራሱ መዝገብ አካል በማድረግ ወደ መዝገብ ቤት እንዲመለስ ትእዛዝ ሰጥቷል። በዚህ ሒደት ያልተጠራችው ተጠሪ ያቀረበችውን ክስም ውድቅ አድርጓል።

ከዚህም የምንረዳው ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን እኔ አላየውም የሚሉበትን የተለያዩ ምክንያቶች በመጥቀስ በሰጡት ትእዛዝ የአመልካች ጥያቄ በእንጥልጥል የቀረ መሆኑን ነው። ማንኛውም ሰው በዳኝነት ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ በዳኝነት እንዲታይለትና ፍትህ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ተደንግጓል። አመልካች በውጭ አገር አለ የምትለው የጋራ ሀብት ጥያቄ በዳኝነት እንዲታይለትና ፍትህ እንዲሰጣት የመጠየቅ ሕገ-መንግሥታዊ መብቷ ነው። ሆኖም የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን አንደኛው ለሌላው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመግፋት ይህንን ሕገ-መንግሥታዊ መብቷን የሚጥስ ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች ያቀረበችው የዳኝነት ጥያቄ ምላሽ ማግኘትና መስተናገድ ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአመልካች ጥያቄ በየትኛው ፍርድ ቤት ይስተናገድ የሚለውን ነጥብ በተመለከተ ጉዳዩ የዓለምአቀፍ የግል ሕግ ጥያቄ የሚያስነሣ መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57234 ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ብይን አረጋግጧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበችው ክስ የዓለም አቀፍ የግል ሕግ ጥያቄ የሚያስነሣ ነው የሚለው መደምደሚያ ላይ ከደረሰ፣ አመልካች ተጠሪ በአገር ውስጥ ያፈሩት የጋራ ሀብት ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አከራክሮ መወሰኑን እንደከፍተኛ ስህተት በመቁጠር ጉዳዩ በከፊል ለመጀመሪያ ፍርድ ቤት የታየ ስለሆነ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ በሕገ-መንግሥቱ የተረጋገጠውን የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብትና ለፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 4 የተሰጠውን ሥልጣን የሚጥስ ስህተት ያለበት ሆኖ እያለ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማጽናቱ ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57224 ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 35533 መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በውጭ አገር አለ የሚሉትን የጋራ ሀብት ጥያቄና ማስረጃ የተጠሪን መልስና ማስረጃ ሰምቶ እንዲወስን ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ራሣቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. በትውስት የመጣው የከፍተኛው ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 54637 ይመለስ፣ ይፃፍ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጥር 28 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37016

የካቲት 3 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ማሞ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በተከሣሽ ድርጅት በበላይ ገንዘብ ያዥነት /senior teller/ በማገልገል ላይ ሳለሁ በ10ኛው ጉብረት ስምምነት መሠረት የሥራ መደቡ መጠሪያ ስያሜ ተለውጦ ኦፊሻል 3 የሚል መጠሪያ በመሰጠቱ ምክንያት ለሥራ መደቡ ማግኘት የሚገባኝን ልዩ ጭማሪ ብር 219 /ሁለት መቶ አሥራ ዘጠኝ ብር/ ተከሣሽ ከልክሎኛል፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ ከ24/5/99 ዓ.ም. ጀምሮ ማግኘት የሚገባኝን ልዩ ጭማሪ በመክፈል ወደ ቀድሞው የበላይ ገንዘብ ያዥነት የሥራ መደብ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሽም /የአሁን አመልካች/ ቀርቦ በሰጠው መልስ ከሣሽ የሚሠሩበት የሥራ ደረጃ 14 ሲሆን በዚህ ደረጃ የሚከፈለው ደመወዝ አሁን እየተከፈላቸው ካለው ደመወዝ የሚያንስ ሲሆን የተሻለ ደመወዝ እየተከፈላቸው ባለበት ሁኔታ ልዩነት ብር 219(ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር) ሊከፈለኝ ይገባል ያሉት በተገቢው አይደለም፡፡ በከሣሽ ላይ የሥራ ለውጥ ያልተደረገ ሲሆን ተደርጓል ቢባል እንኳን የከሣሽ የትምህርት ዝግጅት ማነስ የሥራ አፈፃፀም ዝቅተኝነት፣ የደንበኞች ቅሬታና የቅርብ ኃላፊዎች ግምገማ ተጨምሮበት በባንኩ የአደረጃጀት የአሠራር ለውጥ /BPR/ መሠረት ከሣሽ እንዲሠሩ የታመነበት አሁን እየሠሩ ያሉበት የሥራ መደብ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማስረጃ ሠምቶ በተከሣሽ መ/ቤት ሥራ የተቋቋመው የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ /BPR/ ኮሚቴ አባላት ቀርበው በሰጡት የምስክርነት ቃል ከሣሽ ለነበሩበት የሥራ መደብ ብቃት እንደሌላቸው የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ቢሆንም የግል ማኅደራቸውን ፍ/ቤቱ አስቀርቦ እንደተመለከተው መልካም የሥራ አፈፃፀም እንደነበራቸው ስለሚያሳይ የኮሚቴው ውሣኔ በበቂ ማስረጃ የተደገፈ ባመሆኑ ከሣሽ ወደ ቀድሞ ከፍተኛ ገንዘብ ያዥነት የሥራ መደብ ሊመለሱ እና የመደቡ የደመወዝ ልዩነትም ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በሚሉት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ ወደ ቀድሞው የሥራ መደብ ሊመለሱ ይገባል ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ አግባብነቱ ተጠሪ ባሉበት ሊጣራ እንደሚገባ በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቅድሚያም ችሎቱ የተመለከተው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው መሆኑን በተመለተ ነው፡፡

ተጠሪ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በክስ አቤቱታቸው ዳኝነት የጠየቁት ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ቀድሞ ስሰራበት ወደነበረው የሥራ መደብ እንድመለስና ለመደቡም የተሰጠው ልዩ ጭማሪ እንዲከፈለኝ በማለት ነው፡፡

የአሠሪና ሠራተኛን ግንኙነት በሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 377/96 ለወልም ሆነ ለግል የሥራ ክርክር የተሰጠ ትርጉም ባይኖርም ነገር ግን አንድ የሥራ ክርክር የወል የሥራ ክርክር ወይንም የግል የሥራ ክርክር ነው ለማለት የሠራተኛው ቁጥር እንደ መለያ መስፈርት ሊያገለግል እንደማይችል ከአዋጁ አንቀጽ 138 እና 142/1/ ዝርዝር ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ክርክሩ የወል ነው ለማለት የጋራ የሆነን የሠራተኞችን መብትና ጥቅም ጋር ግንኙነት ያለው ማለትም የደመወዝም ሆነ የሌላ ጥቅም፣ የቅጥርም ሆነ የዕድገት አሰጣጥ፣ የዝውውርም ሆነ የሥልጠና ከመሣሰሉት ጋር ግንኙነት ኖሮት በጋራ በሆነ ሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት በሚያስከትል ጊዜ እንደሆነ ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው አንቀጽ 142/1/ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ ጥያቄ ወደ ቀድሞ የሥራ መደቤ እንድመለስና ለመደቡም የተሰጠው ልዩ ጭማሪ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል እንደመሆኑ መጠን የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ በአንቀጽ 142/1/ሀ/ እና /ሰ/ ሥር የሚሸፈንና የወል የሥራ ክርክር ተብሎ የሚመደብ ነው፡፡ ክርክሩ የወል ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ የሚታየው በአስማሚ ወይም በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አማካኝነት እንጂ በፍ/ቤት በኩል ስላልሆነ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በዚህ ሁኔታ ጉዳዩን ተቀብሎ ውሣኔ መስጠቱ በአንቀጽ 138/1/ ሥር ከተሰጠው የሥረ-ነገር ሥልጣን ውጭ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በዚህ መልኩ የሰጠው ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21652 በ5/5/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 63054 በ26/7/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39085

የካቲት 3 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን - ነ/ፈጅ አቶ ዳንኤል ጥበቡ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ ወ/ር አስረሳች ወርቅነህ (87 የጉምሩክ ፖሊሶች)

ጠበቃ ሙሉጌታ ወንድማገኘሁ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው የጉምሩክ ፖሊሶች ወደ ስራ እንመለስ የሚል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆኑ አመልካች ተከሳሽ ነበር፡፡ እሱም በድርጅቱ ከተራ ወታደርነት እስከ መኮንንነት ተመድበን ከምንሰራበት በማይታወቅ ሁኔታ ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ ያሰናበተን ከጉምሩክ ፖሊሶች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 4/96 ውጪ በመሆኑ ሕገ-ወጥ ነው እንዲባልና ወደ ስራ እንድንመለስ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለውም በጉምሩክ አዋጅ የመዋቀር ማስተካከያ በማድረግ የሰው ኃይል ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ ስልጣን ተሰጥቷል፡፡ መመሪያው የዲስፒሊን እርምጃን የሚመለከት እንጅ የመዋቅር ማስተካከልን የሚከለክል አይደለም በማለት ስንብቱ ሕጋዊ መሆኑን በማስመልከት የመቃወሚያና በአማራጭ የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ፍ/ቤት ወደ ቀድሞ ስራቸውና ደመወዛቸው እንዲመለስ ሲል ወስኗል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 64577 ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የመጀመሪያ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 7 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ መሰረት በማድረግ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን አለው ወይንስ የለውም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዝዞ ተጠሪዎች ቀርበው እንዲከራከሩ ተደረጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክር አካሄደዋል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የአመልካች ዋና ክርክር በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 8/2/መ እና በአዋጅ ቁጥር 368/1995 በተሻሻለው መሰረት የጉምሩክ ፖሊሶች የሚተዳደሩት የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በሚተዳደርበት አኳኋን ነው፡፡ በዚህ ዓይነት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ፍ/ቤት ማየቱ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ ለሚደርሰው የመብትና የፍትህ መጓደል አቤቱታ የሚቀርብበት በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል ባለመኖሩ መብትና ጥቅማችን የሚያስከብርና ሕጐችን በመተርጐም የሚወሰንልን መደበኛ ፍ/ቤት ብቻ ስለሆነ ክሱን ተቀብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአዋጁ ቁጥር 368/95 እንደተመለከተው የጉምሩክ ፖሊስ ኃይል የሚተዳደረው የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን አዋጅና ደንብ ተከትሎ በሚወጣው መመሪያ መሰረት እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች በግልጽ ባልተመለከቱ ጉዳዮች ስንብት ቢፈፀም በፍ/ቤት እንደሚታይም አልተመለከቱም፡፡ የበታች ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው በመመሪያ ቁጥር 4/1996 ከተመለከተው የጉምሩክ ፖሊስ አገልገሎት ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ውጪ በሆነ ሁኔታ ከመዋቅር ማሻሻያ ጋር ተያይዞ ከመጣው የጉምሩክ ፖሊስ ኃይል አደረጃጀትን የሚመለከት ጉዳይ እንጂ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመመሪያው ላይ ስለስንብት የተመለከተውን ምክንያት የሚሸር ባለመሆኑ ስንብቱ ከመመሪያው ውጪ ነው በማለት ነው፡፡ በመመሪያው ከተመለከቱ ምክንያቶችም ሆነ በመመሪያው ከተመለከቱ ምክንያቶች ውጪ የጉምሩክ ፖሊስ የስራ ስንብት ጉዳይ ሊታይ የሚችለው የፌዴራል ፖሊስ በሚተዳደረው ስርአት እንደሆነ በአዋጁ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ የጉምሩክ ፖሊሶች የስንብት፣በስራ ላይ ማሰማራትም ሆነ የዲስፒሊን ውሳኔ ጉዳዮች በቀጥታም ሆነ በይግባኝ በፍ/ቤት በዳኝነት ሊታይ የሚችልበት ስርአት በአዋጅ ወይም በመመሪያው ባልተመለከተበት ስንብቱ ሕጋዊ ነው ወይንስ ከሕግ ውጪ ነው በማለት በፍ/ቤት ጭብጥ ተይዞ ክርክር ሊካሄድበትና ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

በመሆኑም የበታች ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ብቸኛ ስልጣን ያለው ፍ/ቤት ነው በማለት ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስና ክርክር ተቀብሎ ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው ወደ ስራ መልሷቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ በአዋጅ በግልጽ የፌዴራል ፖሊስ በሚተዳደረው ስርአት (executive provocative) የሚታየውን ጉዳይ ያለስልጣኑ ለጥጦ በመተርጎም በፍ/ቤት የሚታይ ጉዳይ በማድረግ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ማረም ሲገባው በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ከላይ በተመለከቱ ምክንያቶች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 98010 በ14/5/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64527 በ1/11/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጡ ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪዎች ወደ ስራ ሊመለሱም ሆነ ደመወዝ ሊከፈላቸው አይገባም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38745

መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዓልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ሳሊያ ኢብራሂም - ወኪል 2ኛ አመልካች

2. አቶ ሙሐዲን ጀማል - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ሐጂ ሰማን ኢሳ- በሌሉበት

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26/98 ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም እና ሚያዝያ 08 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጣቸው ውሳኔዎች መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆናቸው ይሻሩልን በማለታቸው ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካቾች ተከሳሾች፣የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን፣የስር ከሳሹ ነሐሴ 09 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘቱ አንደኛዋ ተጠሪ ሚስቴ ሆና እያለች ሁለተኛው ተጠሪ የሸሪዓን ህግ በመጣስ ስላገባት በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈፀም ጥፋት ስለፈፀመ በህግ ፊት ቀርቦ የጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጠው የሚል ነው፡፡ ስር ተከሳሾች በቀነ ቀጠሮው ባይቀርቡም የስር ፍ/ቤቱ ሐምሌ 6 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ብይን ጉዳዩ ወንጀል ነክ በመሆኑ አከራክሬ የመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ስር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪም በስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ በማሳደር ጉዳዩን በይግባኝ እንዲታይላቸው ለኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበውት ፍ/ቤቱም ተከሳሾቹ በሌሉበት በመ/ቁ 26/98፣ሚያዝያ 08/1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ አቶ ሙሐዲን ጀማል ወ/ሮ ሳሊያ ኢብራሂም የሐጂ ሰማን ኢሳ ህጋዊ ባለቤት መሆኗን እያወቀ ስላገባት በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈፀም ጥፋት ፈጽሟል በማለት ስር ተከሳሾቹ ለከሳሹ ብር 1700 (አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር) እንዲከፍሉትና በሚመለከተው አካል በወንጀል የመክሰስ መብቱ በመጠበቅ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላም የአሁኑ አመልካቾች ታህሳስ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78/1/2/ መሰረት ባሉበት ክርክሩ እንደገና እንዲካሄድ ፍርዱን ለሰጠው የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት አመልክተው ከተፈቀደላቸው በኋላ ያቀረቡት ክርክር በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንዳልፈፀሙ፣አቶ ሙሐዲን ወ/ሮ ሳሊያን ያገባት ቀደም ብሎ ከሐጂ ሰማን ኢሳ ጋር የነበራትን ጋብቻ /ኒካ/ ከፈረሰ በኋላ እንደሆነና ማስረጃም እንዳላቸው የሚገልጽ ሲሆን ይግባኝ ባዩ ሐጂ ሰማን ደግሞ ከወ/ሮ ሳሊያ ጋር የነበረኝ ጋብቻ በሸሪዓ ፍ/ቤት አልፈረሰም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቱም በኦ/ጠ/ሸሪዓ ፍ/ቤት መ/ቁ. 26/98፣ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ተከሳሾቹ በጋብቻ ላይ ጋብቻ አልፈጸምንም በማለት ያቀረባቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች ማለትም የዘመድ ዳኞች በ27/08/1990 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና የኢልባቦር ዞን የእስልምና ጉዳዮች ጉባኤ በ01/02/1993 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ሲታዩ እነዚህ አካላት ጋብቻውን የማፍረስ ስልጣን የላቸውም በማለት ተከሳሾቹ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽመዋል በማለት ቀደም ብሎ ማለትም በመ/ቁ. 26/98፣ሚያዚያ 08/1999 ዓ.ም ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ ተመልሶ አጽድቆታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ የሰፈረውን ውሳኔ በመቃወምም የአሁኑ አመልካቾች ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም በጋብቻ ላይ ጋብቻ አልፈፀምንም፤ጋብቻችንን የፈጸምነው በአንደኛ አመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው ጋብቻ በህጋዊ አካል ከፈረሰ በኋላና ይህንን መሰረት በማድረግ የኢልባቦር ዞን የእስልምና ጉዳዮች ጉባኤ በቁጥር DHIIL 62/3/3-1/93 ጥቅምት 01/1993 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ወ/ሮ ሳሊያ ኢብራሂም ጋብቻዋ የፈረሰ በመሆኑ የፈለገችውን ማግባት እንደምትችል ማረጋገጫ ከሰጠ በኋላ እንደሆነ፤በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽማችኋል በማለት በብር 1700 (አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር) በወንጀል እንድንቀጣ መወሰኑ መዝገቡን በጥልቀት ሳይመረምር ከስልጣኑ ውጭ እንደሆነ በመግለጽ በኦ/ጠ/ሸሪዓ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይሻርልን የሚል ነው፡፡

ተጠሪው ለቃል ክርክር ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ መጥሪያው ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ፍ/ቤቱ ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ አዞ የተካሄደ ያለ በመሆኑ ተጠሪው መልስ አልሰጡም፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ በመጣው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ አመልካቾቹ ጋብቻ የፈፀሙት አንደኛዋ አመልካችና ተጠሪው መስርተውት የነበረው ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ሳይፈርስ በነበረበት ሁኔታ ነው ወይስ አይደለም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ አንደኛዋ ተጠሪ ከእርሳቸው ጋር ያላት ጋብቻ በሸሪዓ ህግ ሳይፈርስ ሁለተኛው ተጠሪ እንዳገባትና ይህ አድራጎትም በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈጸም ስለሆነ አመልካቾች እንዲቀጡለት የሚጠይቅ ሲሆን አመልካቾቹ ደግሞ ቀደም ብሎ በተጠሪው እና በአንደኛ አመልካች መካከል የነበረው ጋብቻ በአግባቡ ከፈረሰ በኋላ እንጂ ጋብቻው ሳይፈርስ እንዳልተጋቡ መልሰዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያከራከረው የኢልባቦር ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የወንጀል ክርክር ስለሆነ ስልጣን የለኝም ቢልም ጉዳዩን በይግባኝ ያስተናገደው የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ግን በአንደኛዋ አመልካችና በተጠሪው መካከል ቀደም ብሎ የተመሰረተው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁለተኛው ተጠሪ አንደኛዋን ተጠሪ በማግባት በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈፀሙን በማስመር በብር 1700(አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር) እንደቀጣቸው ነው፡፡ ሽማግሌዎች አፋትተውናል ፍርድ ቤትም ተቀብሎታል፤ቀጥሎም የኢልባቦር ዞን የእስልምና ጉዳዮች ጉባኤ አንደኛዋ አመልካች የፈለገችውን ማግባት እንደምትችል በደብዳቤ ገልፆላታል የሚል ክርክር ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ስልጣን የላቸውም በማለት አልፎታል፡፡ ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ በተጠሪውና በአንደኛዋ አመልካች መካከል የነበረው ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበለት የዲዱ ላሎ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩ ወደ ሽማግሌዎች መርቶት ሽማግሌዎቹ ተጋቢዎቹን ለማስታረቅ ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ በመቅረቡ ጋብቻው እንዲፈርስ አስተያየታቸውን ተመልሰው ለወረዳ ፍ/ቤቱ ካቀረቡለት በኋላ የተጠቀሰው ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 48/94፤ሚያዚያ 28 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሽማግሌዎቹን አስተያየት ተቀብሎ ፍቺውን እንዳፀደቀ መዝገቡ ያስረዳል፤የመጀመሪያው ጋብቻ የፍቺ ሂደት በዚህ መልክ ከተጠናቀቀ በኋላ እና የኢልባቦር ዞን እስልምና ጉዳዮች ጉባኤ በቁ. DHIILU 62/3/3-1/93 ጥቅምት 01/1993 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አንደኛዋ አመልካች ከዚህ በኋላ የፈለገችውን ሰው ማግባት እንደምትችል ገልጿል፡፡ የአሁኑ ሁለተኛው አመልካች እነዚህ ሂደቶች ማለትም የመጀመሪያው ጋብቻ ስልጣን ባለው የወረዳ ፍ/ቤት አማካኝነት መፍረሱን አረጋግጠው አንደኛዋ አመልካች እንዳገቡ ነው፡፡ የእስልምና ተከታይ የሆኑ ተጋቢዎች ጋብቻቸው እንዲፈርስ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ወይም ሁለቱም ከፈቀዱ ደግሞ ወደ ሸሪዓ ፍ/ቤት አስቀርበው እንደምርጫቸው ሊያፈርሱት እንደሚችሉ እየታወቀ የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት የዲዱ ላሎ ወረዳ መደበኛ ፍ/ቤት ቀደም ብሎ የሰጠውን የፍቺ ውሳኔ ወደ ጐን በመተው በአንደኛዋ አመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው ጋብቻ አልፈረሰም፤አመልካቾች በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጽመዋል ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 26/98፣ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካቾቹ ጋብቻ የፈጸሙት ቀደም ብሎ በአንደኛዋ አመልካችና በተጠሪው መካከል የነበረው ጋብቻ በዲዱ ላሎ ወረዳ ፍ/ቤት በአግባቡ ከፈረሰ በኋላ በመሆኑ አመልካቾቹ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ባለመፈጸማቸው የተላለፈባቸው የገንዘብ ቅጣት ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡
3. ግራና ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም የተላለፈው እግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ያለቀ በመሆኑ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36677

ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሻምሺ ዩኑስ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ኑሪያ ማሚ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 16/99 የካቲት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. በተሣፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በድሬዳዋ ናኢባ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በድሬደዋ ናኢባ ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርባ ሟች አባቱ በድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 08 በአምስት መቶ ካሬ ሜትር ባለው ቦታ ላይ አመልካች ቦታውን እንድትለቅ ስትጠየቅ ለመልቀቅ ተስማምታ ትንሽ ቤት ሠርታ ትኖር ነበር፤ ቦታውን የያዘችው የዛሬ ሰባት ዓመት ሲሆን ወላጅ አባቱ ከሞተ በኋላ በቦታው ላይ ግንባታ ለማካሄድ ቦታውን እንድትለቅልኝ ስጠይቃት እንቢ ስላለችኝ ቦታውን እንድትለቅ እንዲወሰንልኝ በማለት ክስ ያቀረበች ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በተጠሪነት ቀርባ፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሠረት የመደበኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ የይግባኝ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በፍሬ ጉዳይ እረገድ ቦታው በአዋጅ ቁጥር 47/1967 የተወረሰ ነው የሚሉና ሌሎች ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡

የናኢባ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበችውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማለፍ የፍሬ ጉዳይ ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች ይዞታውን ለተጠሪ እንድትለቅ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለድሬዳዋ ፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ከተከራከሩ በኋላ የከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤቱ የሥረ ነገር ሥልጣንን በተመለከተ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ በማለፍ በፍሬ ጉዳይ በኩል አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 መሠረት መልሶ ልኮለታል፡፡ ሆኖም በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርባ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ የናኢባ ፍርድ ቤት ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የማያንስ ስልጣን አለው ካለ በኋላ በፍሬ ጉዳይ ረገድ፣ የድሬደዋ ፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የናኢባ ወረዳ ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማጽደቅ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፤ ተጠሪ ያቀረባቸው ክስ የወላጅ አባቴን ይዞታ ታስረክበኝ የሚል ሲሆን እኔ ደግሞ 1982 ዓ.ም. ጀምሮ በቦታው ላይ ቤት ሰርቼ እየኖርኩ ያለሁ መሆኔን ገልጬ የናኢባ ፍርድ ቤት ይዞታን አስመልክቶ የሚነሳ ክርክርን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ያቀረብኩትን መቃወሚያ አላግባብ አልፎና በይዞታ ጉዳይ አከራክሮ ወስኗል፤ ስለዚህ ያለበቂ ማስረጃ አከራክሮ ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ፣ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤትም የተፈፀመውን የሕግ ስህተት ያላረመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በበኩሏ ክርክሩ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተደረገው በአመልካች ፈቃደኝነት ነው፤ ስለዚህ የሸሪዓ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች በጽሁፍ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታዋን የሚያጠናክር ክርክር አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥ ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን፣ እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የሸሪዓ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተፈጠረውን የይዞታ መብት ጥያቄ አይቶ የመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከድሬደዋ ናኢባ ፍርድ ቤት፣ ከከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና ከጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የውሣኔ ግልባጭ ለመረዳት እንደቻልነው ጉዳዩ ይዞታ ክርክር ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱ የሟች ወላጅ አባቷ መሆኑንና አመልካች ቤት የሰራችው በአባቷ ፈቃድ ልቀቂ ስትባል ለመልቀቅ ተስማምታ መሆኑን በመግለጽ የምትከራከር ሲሆን፣ አመልካች በበኩሏ ከ1982 ዓ.ም. ጀምሮ ይዞታው የእሷ መሆኑን በመግልጽ የይዞታ ክርክርን የናኢባ ፍርድ ቤት ማየት የለበትም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርባለች፡፡

የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት የወል የዳኝነት ስልጣን በምን ጉዳዮች ላይ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/1992 በአንቀጽ 4 ተደንግጓል፡፡ በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረት በፌዴራል በማናቸውም ደረጃ የሚገኙ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን አይተው የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የሚኖራቸው፡-

> -በማንናቸውም የጋብቻና የፍች፣ የቀለብ አወሳሰን፣ አካለ መጠን ያልደረሱ ሕፃናት ሞግዚትነት እና የቤተሰብ ተዛምዶ ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን አስመልክቶ ጥያቄ ያስከተለው ጋብቻ በእስልምና ሀይማኖት ሥርዓት መሠረት የተፈፀመ የሆነ እንደሆነ ወይም ባለጉዳዮቹ በእስልምና ሀይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት አቅደው እንደሆነ፤

- የእውቅና ስጦታ /ሂባ/፣ ውርስ ወይም ኑዛዜ ጉዳዮችን በተመለከተ አውራሹ ወይም ስጦታ አድራጊ ወይም ተናዛዥ ሙስሊም የሆነ እንደሆነ ወይም ሟች በሞተበት ሰዓት ሙስሊም ሆኖ የሞተ እንደሆነ፤
- ከላይ በተገለጹት ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ክሶችን ኪሣራ የሚመለከት ሲሆን እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለመረዳት እንችላለን፡፡

ከዚህ ውጪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የናኢባ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛው ሸሪዓ ፍርድ ቤትም ሆነ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ክርክር የመስማትና ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የላቸውም፡፡ የያዝነው ጉዳይ የይዞታ ክርክር ጉዳይ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የአንድ ሰው ወራሾች በመሆናቸው ምክንያት የቀረበ የውርስ ንብረት ክፍያ ጥያቄ አይደለም፡፡ ስለሆነም ቦታው የማን ይዞታ ነው የሚለውን ጉዳይ አከራክረው የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሠረት መደበኛ ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የድሬደዋ ናኢባ ፍርድ ቤት ቦታውን አስመልክቶ ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያላነሰ ሥልጣን አለው በማለት መወሰኑ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣው አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ድንጋጌዎች ባለማገናዘብ የተሰጠ ሆኖ ስላገኘነው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና የድሬዳዋ ናኢባ ፍርድ ቤት የይዞታ ጉዳይ አከራክረው የመወሰን የዳኝነት ስልጣን የሌላቸው በመሆኑ ውሣኔያቸው ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. ይህ ውሣኔ ተጠሪ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርባ ከመጠየቅ የሚገድባት አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 37866

ግንቦት 19 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሙሉጌታ አባይ - ቀረበ

ተጠሪ፡- የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን - ኑሪዬ አብተው /ነገረ ፈጅ/ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በፌዴራል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጀመረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አከፋፈል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ለጉባኤው በይግባኝ የቀረበው አመልካች ሲሆን፣ ቅሬታውም በተጠሪ የተጣለብኝ መቀጫ ያለአግባብ ስለሆነ ይነሳልኝ የሚል ነው፡፡ ጉባኤው ከተጠሪ የቀረበውን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ የመቀጮውን መጠን ዝቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የጉባኤውን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በዚህ ደረጃም የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መቀጮን በተመለከተ በሚቀርበው ክርክር /ይግባኝ/ ላይ ስልጣን የለውም የሚል ምክንያት በመስጠት የጉባኤውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት አመልካች ያቀረበለትን ይግባኝ ውድቅ አድርጎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ አመልካች ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረቡለትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ ላይ በሚነሳው ክርክር ላይ ስልጣን የለውም በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

አንደምንመለከተው አከራካሪው ነጥብ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በዋናው ግብር ላይ የሚጣለውን መቀጫ በመቃወም በሚቀርበው ይግባኝ ላይ ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡ በሰበር መ.ቁ 34691 በቀረበው ክርክር በአሁኑ በተያዘው መዝገብ የተነሣው ጭብጥ አከራካሪ ስለነበር የሰበር ችሎቱ ለሕጉ ትርጉም በመስጠት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ አይነት የሰበር ችሎቱ የሚሰጠው ውሳኔ (የሕግ ትርጉም) በችሎቱ እስካልተለወጠ ድረስ አስገዳጅ እንደሚሆን የፌዴራል ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ 454/97 በአንቀጽ 2(4) ተደንግጎአል፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 46438 ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 34888 የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ የማየት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41608

ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካቾች፡- እነ ሙላቱ አንበርብር - ቀርቧል

ተጠሪ፡- ወ/ት ታመነች ዮሴፍ መና ወኪል - ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ የቀበሌ 06 አስተዳደር ማሕበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች የስር ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ ነበሩ አመልካቾች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በተጠሪ የመኖሪያ ቤት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የሆኑ ግለሰቦች ከፍተኛ የድምጽ ማጉያ በመጠቀም በሚያካሂዱት ጩኸት አካባቢውን በማወካቸው በመኖሪያችን ልናርፍ አልቻልንም በሚፈጠረው የድምጽ ብክለት በጤናችን ላይ ጉዳት እያደረሰበን ስለሆነ የድምጽ ብክለቱ ይወገድልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ ይህ የሐይማኖት ጥላቻ በመሆኑ በአድማ የቀረበ ክስ ነው፡፡ የማንንም መብት ሣንጋፋ መንግስት ለሐይማኖትና ለእምነት ነፃነት የሰጠው ሕገመንገስታዊ መብት እንዲከበርልን ተደርጐ የማምለክ መብታችን ተጠብቆ እያለ ድንጋይ እየተወረወረብን በደል እየደረስብን ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የማህበራዊ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ በመመርመር አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ አስመልክቶ ሁከት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ሲል የመሰረት ልማት ቴክኒሻን(ባለሙያ) ወደ ስፍራው በመላክ ሁከት እንዳለ በማረጋገጥ ተጠሪዎች በሌላው ሰው ላይ ሁከት እየፈጠሩ ህገ-መንግስታዊ መብታችን እየተጠቀምን ነው ማለቱ ሕጉን በተሣሣተ መተርጐም ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህ በአዋጅ ቁ. 12/96 አንቀጽ 5/3/ መሰረት፣በወንጀል ሕግ 815/1/ የሌሎችን ስራና ሰላም ማወክ ሆኖ ስላገኘው ተጠሪዎች 100 ብር (መቶ ብር) ይቀጡ መኖሪያ ቤቱ ለተፈቀደለት አላማ ብቻ ይዋል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ጉዳዩ የቀረበለትም ፍ/ቤት የግራ ቀኙን በማከራከር በጭብጥነት የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ መወሰን ስልጣን አለው ወይ? የሚለውን በማየት ሲወስን የክልል 14 መስተዳደር ደንብ ቁጥር 1/1986 አንቀጽ 10/2/ በመጥቀስ ይህን ደንብ የጣሰ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የመንግስት አካል ተገቢውን አስተደደራዊ ውሣኔ እንደሚወሰድበት ከተጠቃሹ ደንብ አንቀጽ 17/1/ሀ/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ ተጠቃሹን ደንብ የጣሰ በቅድሚያ አስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲሰጥበት ማድረግ እንጂ በቀጥታ ክስ በፍ/ቤት ክስ የማይመሰረትበት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይም አመልካቾች ይህን ለማድረጋቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም በአስተዳደር አካል ውሣኔ ካልተሰጠ ደግሞ የስር ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን የለውም በመሆኑም የስር ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ በማለት ሲወስን የአሁን አመልካቾችም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ለአ/አበባ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ጉዳዩ የቀረበለትም ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሣይሰማ አመልካቾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የፍ/ብሔር ክርክር በመሆኑ በስር ፍ/ቤት በተወሰነው መሰረት በቅድሚያ የሚመለከተው አስተዳደራዊ አካል ውሳኔ መስጠት ይገባል መባሉ በአግባቡ ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች ህዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በአ/አ/ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና በከተማው የከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጽመበት በመሆኑ ሊታረምልን ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡

በዚህም መሰረት የተጠሪን እና የአመልካችን የቃል ክርክር በችሎት ሰምተናቸዋል፡፡ ጉዳዩ በሰበር እንዲታይ የቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ መስተናገድ ያለበት በአ/አ/አስተዳደር አዋጅ ቁ. 12/96 አንቀጽ 5/3/ አንፃር ሣይሆን በአስተዳደር ደንብ ቁጥር 1/86 አንቀጽ 10/2/ እና 17/1/ሀ ነው በማለት የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የማህበራዊ ፍ/ቤትን የመሻራቸውን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ የግራ ቀኙ ካሰሙት ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር ማገናዘብ መርምረናል፡፡

በመሆኑም የጉዳዩን አመጣጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ስናይ የአሁን አመልካቾች በስር ክሣቸው የፕሮቴስታንት ተከታዮች በተጠሪ መኖሪያ ቤት ከፍተኛ የድምጽ ማጉያ በመጠቀም በሚያካሄዱት ጩኸት አካባቢውን በማወክ በድምጽ ብክለት በጤናችን ላይ ጉዳት እያደረሱብን ነው፡፡ ይህ ድምጽ ይወገድልን በማለታቸው ምክንያት፡፡ የማህበራዊ ፍ/ቤቱም እንደተባለው የድምጽ ብክለት አለ በማለት ተጠሪ (100) ብር (መቶ ብር) እንዲቀጡ ሲወስን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን በማከራከር ጉዳዩ በፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት በመስተዳደር አካል መታየት ነበረበት ስለዚህ የዳኝነት ስልጣን የለህም በማለት የማህበራዊ ፍ/ቤትን ውሳኔ ሲሽር የከተማው የከፍተኛው ፍ/ቤትም በተመሣሣይ ምክንያት የከተማውን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት አጽንቷል፡፡

እንግዲህ በዚህ ጉዳይ በዋናነት ሊታይ የሚገባው የስር ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል በመጀመሪያ ደረጃ የቀበሌ የማህበራዊ ፍ/ቤቱ አዋጅ ቁ. 12/96 በአዋጅ ቁ. 31/99 መሻሻሉን ከግንዛቤ ሣያስገባ እና ይህ አዋጅ ቁጥር 31/99 ስልጣን ባልሰጠው ሁኔታ ውሣኔ ሰጥቷል የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ይህን በጥልቀት ሣያጤነው ምንም እንኳ የስር ፍ/ቤት ስልጣን የለውም ቢልም ምክንያት ያደረገው የግራ ቀኙ ክርክር መጀመሪያ በአስተዳደራዊ አካል መታየት ነበረበት በሚል ነው፡፡ የከፍተኛውም ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቷል፡፡ በመሰረቱ ለክርክሩ መንስኤ አመልካቾች በተጠሪ ድርጊት የጽምጽ ብክለት ጉዳት አድርሶብናል የሚል ሲሆን ጉዳዩም የፍትሐብሔር ክርክር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ሊስተናገድ የሚገባውም በፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 1225 መሰረት ነው፡፡ ይህንንም ጉዳይ ለማየት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደራዊ አካል እና የአ/አ ከተማ ፍ/ቤቶች ስልጣን አይደለም፡፡

በመሆኑም ይህ ታልፎ በስር ፍ/ቤቶች መታየቱ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአስተዳደሩ ማህበራዊ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0207 በቀን 2/5/2000 የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 877/00 በቀን 01/9/2000 እና የከተማው ይግባኝ ሰሚ በመ/ቁ. 08015 ቀን 12/2/2001 የተሰጡት ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡
2. የማህበራዊ ፍ/ቤትም ሆነ ከአ/አ/ከተማ ፍ/ቤቶች ስልጣን የላቸውም፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባንክና ኢንሹራንስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42139

ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት- ክንፈ ታደለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ብያን ኡመር- ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ክፍያን መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ በምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ ክስ የመሰረተው ጉዳት አደረሰ በተባለው መኪና ባለንብረት እና በሹፌሩ ላይ ነው፡፡ አመልካች ለመኪናው የመድን ዋስትና ግዴታ ገብቷል ስለተባለ ጣልቃ እንዲገባ ተጠይቆ ነው የክርክሩ ተካፋይ የሆነው፡፡ በዚህ አግባብ መሰረት ቀርቦ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የስረ-ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ ሊሆን እንደማይገባው በመግለጽም ተከራክሯል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ተከሣሾቹ እና አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናቸው፤ የጉዳት ካሳውን ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህን ውሳኔ በመቃወም በአሁኑ አመልካች ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ብሏል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ታሕሣስ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጸመ የሚለውን መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ በበኩላችንም ጉዳቱ የደረሰው በተጠሪው ጥፋት ነው እየተባለና አመልካችም የመድን ሽፋን ባልሰጠሁበት ተግባር ላይ ተሰማርቶ በነበረው መኪና ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት መከራከሩ እየታወቀ የጉዳት ካሣ እንዲከፍል መወሰኑ አግባብ ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ግራ ቀኝ ወገኖቹን አከራክረናል፡፡

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች የሰ/ቁ. 3-29779 አ.አ ለሆነው የጭነት (የእቃ) ተሽከርካሪ የመድን ዋስትና ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ጉዳት ደረሰብኝ የሚለው በዚህ መኪና ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ የአመልካች ክርክርም ከዚህ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የቀረበ ነው፡፡ የመድን ዋስትና የሰጠሁት በሕዝብ ማመላለሻነት ለተሰማራ መኪና ሳይሆን፣ እቃዎችን ለሚያጓጉዝ የጭነት መኪና በመሆኑ ከገባሁት ውል ውጪ ኃላፊ የምሆንበት ምክንያት የለም በማለት ነው የተከራከረው፡፡ በተጠሪ በኩል አመልካች ባቀረበው የፍሬ ነገረ ክርክር ላይ ምንም አይነት ማስተባበያ አልቀረበም፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ክርክሩ ውስጥ የገባው የመኪናው ባለንብረት ጣልቃ እንዲገባለት በመጠየቁ ነው፡፡ ባለመኪናው የጣልቃ ይግባልኝ ጥያቄ ያቀረበው ደግሞ የመድን ዋስትና ውል አለኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች እንግዲህ በውልህ ትገደዳለህ ከተባለ የውሉን ይዘት ማየቱ የግድ ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ውሉ ዋስትና በተገባለት የጭነት መኪና ላይ ተሳፍረው በሚጓዙ ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት የሚሸፍን አይደለም፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸው ተጠሪ እንደማንኛውም መንገደኛ በመኪናው ተገጭቶ አይደለም ጉዳት የደረሰበት፡፡ በመሆኑም በማንኛውም ሁኔታ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የደረሰበት ጉዳት አመልካች በነበረው ውል የሚሸፈን አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካችን ኃላፊ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08797 መስከረም 26 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 71528 ጎዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ አመልካችን በሚመለከት ያለው የውሳኔው ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 384/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የስር አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሾች በነበሩት ላይ የተሰጠው ውሳኔ አልተሻረም፡፡ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆንበት የሕግም ሆነ የውል ምክንያት የለም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 42309

ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን - ሳሙኤል ተገኑ ቀረበ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የመድን ዋስትና ውልን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ለአመልካች መኪና የመድን ዋስትና ሰጥቶአል፡፡ መኪናው ሲሽከረከር በነበረ ጊዜ በመገልበጡ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ተጠሪም የገባውን የመድን ዋስትና ግዴታ መሠረት በማድረግ ገንዘቡን ወጪ አድርጎ መኪናው የተገለበጠው በሹፌሩ ሳይሆን በብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠት አቁሞ በነበረበት ጊዜ የተበላሸውን ፍሬን እያስተካከለ የነበረው መካኒክ ሥራውን ሲሞክር መሆኑን ስለደረስኩበት ኃላፊነት ሳይኖርብኝ ለጥገና ያወጣሁት ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት በአመልካች ላይ ክስ መስርቷል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ክሱ በንግድ ሕግ ቁ 674(1) ወይም (2) መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦአል፡፡ የስረ-ነገር ክርክር በማንሳትም ተከላክሎአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከመረመረ በኋላ የተጠሪን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ በመቀበል ክስ የቀረበበትና ገንዘብ ከነወለዱ እና የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፈለው ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ታሕሣሥ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጸመ ያለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም የአመልካችን የይርጋ ክርክር የታለፈው በአግባቡ ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው የክርክር ጭብጭ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ወይስ አልሆነም? የሚለው ነው፡፡ ይህ ጭብጥ ግራቀኝ ወገኖችን ያከራከረ ወይም ግራቀኝ ወገኖች የተለያዩት የሕግ አግባብ /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.246(1)/ በመሆኑ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር ተገናዝቦ የሚታይ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ግን ወደሕጉ ከመኬዱ በፊት ከዚህ የተያያዘው የፍሬ ነገር አግባብ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

በግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንደተመለከተው ተጠሪ ክሱን ያቀረበው ሚያዝያ 3 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሆን ለክሱ መነሻ የሆነው ጉዳት ደረሰ የተባለው ደግሞ ግንቦት 12 ቀን 1994 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ጊዜ ማለትም ጉዳቱ በደረሰበት እና ክሱ በቀረበበት መሃል ያለው ሲታሰብ አራት ዓመት ከአስር ወር በላይ ነው፡፡ ይህ እንግዲህ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ ሲሆን፣ እውነታው ከየትኛው ሕግ ጋር ሲገናዘብ ነው ለይርጋው ክርክር አወሳሰን አግባብነት የሚኖረው የሚለውን ደግሞ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪ ገንዘቡ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት ወደክስ ሊያመራ የቻለው የመድን ሽፋን ባልሰጠሁበት ሁኔታ የወጣ ነው የሚል ምክንያት መሠረት በማድረግ ነው። አመልካች ሁለት የፍሬ ነገር አግባቦችን በመጠቀስ ክሱ በንግድ ሕግ ቁ 674 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ተከራክሮአል። የፍሬ ነገር አግባቦቹም የመጀመሪያው አደጋው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ተጠሪ የአደጋውን መንስኤ ካወቀበት ግንቦት 26 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ ክሱ እስከ ቀረበበት ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ነው። በዚህ መሠረትም ክሱ በንግድ ሕግ ቁ 674(1) ወይም (2) መሠረት በይርጋ ቀሪ ነው ሊባል ይገባል ብሎአል። ተጠሪ በአመልካች ክርክር የተጠቀሱት የፍሬ ነገር አግባቦች ትክክል አይደሉም የሚል ክርክር የለውም። የሚከራከረው ያቀረብኩት ክስ ያለአግባብ የተከፈለን ገንዘብ እንዲመለስ የሚጠይቅ በመሆኑ ተጠሪ በጠቀሰው ሕግ መሠረት በይርጋ ቀሪ አይሆንም። ሕጉ ለተያዘው ክርክር አግባብነት የለውም በማለት ነው።

ተደጋግሞ እንደተገለጸው የግራቀኝ ወገኖች ግንኙት መነሻው የመድን ዋስትና /የኢንሹራንስ/ ውል ነው። ተጠሪ መኪናውን ያስጠገነው የውል ግዴታ እንዳለበት በማመን ነው። በኋላ ግን የጉዳቱን አደራረስ ወይም ሁኔታ ባውቅ ኖሮ መኪናውን አላስጠግንም ነበር። ጉዳቱ የደረሰው በመድን ዋስትና ውሉ ባልተሸፈነ ሁኔታ ነው የሚል ምክንያት አንስቶአል። ይህ አይነቱ የተጠሪ ክርክር ከተገባው ውል ውጪ በተሸሸገ ምክንያት ወይም በሐሰት በቀረበ ጥያቄ መሠረት እኔም ልሳሳት ችያለሁ ከሚል ተለይቶ የሚታይ አይደለም። በተሸሸገ ወይም በሐሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ ያጋጠመ ሲሆን፣ የይርጋው ዘመን የሚታሰበው ኢንሹራንስ ሰጪው የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁ. 674(2) ተደንግጎአል። የይርጋው ዘመን ሁለት ዓመት እንደሆነም በዚሁ ቁጥር ንኡስ ቁ (1) ተመልክቶአል።ተጠሪ ክሱን ያቀረበው የተደበቀ ነገር መኖሩን ካወቀ ከሁለት ዓመት በላይ ቆይቶ እንደሆነም በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል። በመሆኑም አመልካች የንግድ ሕጉን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መከራከሩ ተገቢ ሲሆን የተጠሪ ክርክር ግን የሕግ መሠረት ያለው አይደለም። ሲጠቃለል ተጠሪ ክሱን ያቀረበው በሕጉ በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ በመሆኑ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.86581 ታሕሣሥ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63225 ህዳር 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮአል።
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ በይርጋ ቀሪ በመሆኑ አመልካች ገንዘቡን እንዲመልስ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል።
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውክልና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38289

ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ነጂሃ ድዋሌ ዋይስ - አልቀረበችም፡፡

ተጠሪ፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ - ነ/ፈጅ ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03497 መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው፡፡ በመዝገቡ እንደተመለከተው ጉዳዩ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበችውን የገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ልትመሠርት የቻለችው ድሬዳዋ በሚገኘው ቅርንጫፉ በኩል ተገቢውን የአገልግሎት ኮሚሽን በመክፈል አዲስ አበባ በሚገኘው ሲዳሞ ተራ በሚባለው ቅርንጫፉ አቶ ሽሪፍ ከዲር ለተባለ ሰው እንዲሰጥ የላከችውን ብር 45,000 (አርባ አምስት ሺህ) ለማይመለከተው ሰው ከፍያለሁ በማለት አደራውን አልተወጣም በማለት ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ገንዘቡ አመልካች በገለጸችው ሁኔታ መላኩንና የደረሰው መሆኑን ሳይክድ ነገር ግን ገንዘቡ የተላከልኝ ሰው እኔ ነኝ በማለት መታወቂያ ይዞ ለመጣ ሰው መክፈሉን በመግለጽ ክሱ በነፃ ይሰናበት ዘንድ እንዲወሰንለት ጠይቆአል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም በዚህ መልክ የቀረበውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ ክሱን ውድቅ በማድረግ ተጠሪን በነፃ አሰናብቶአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበል ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጭበርብሮ ገንዘቡን ለማይገባው ሰው የከፈለው ተጠሪ መሆኑ እየታወቀ ገንዘቡን ለአመልካች ለመተካት አይገደድም በሚል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ተገቢውን ኮሚሽን በመክፈል ገንዘቡን ለባንኩ አስረክባለች፡፡ ገንዘቡን ለባንኩ የሰጠችውም ለተላከለት ሰው እንዲያደርስላት ነው፡፡ በእርግጥም ባንኩ የተሰጠው አደራ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ማድረስ እንደመሆኑ የማድረስ ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ባንኩ /ተጠሪ/ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው አላደረሰም፡፡ ይልቁንም ለማይመለከተው /ላልተላከለት/ ሰው መክፈሉ ተረጋግጦአል፡፡ በተጠሪ ክርክር እንደተገለጸው ገንዘቡን የከፈለው የተላከልኝ ሰው እኔ ነኝ የሚል መታወቂያ ደብተር የያዘ ሰው ስለቀረበ ነው፡፡ ይህ ሰው ግን በእርግጥም አመልካች ገንዘብ የላከችለት ሰው አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሁኔታ የተጭበረበረው ተጠሪ /ባንኩ/ እንጂ አመልካች አይደለችም፡፡ አጭበርባሪውን ሰው ከሶ ገንዘቡን ማስመለስ የሚችለውም ተጠሪ እንጂ አመልካች ልትሆን አትችልም፡፡ ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው በአመልካች እና አጭበርብሮ ገንዘቡን ከተጠሪው ባንክ በወሰደው ሰው መካከል ምንም አይነት ግንኙነት የለም፡፡ ተጠሪ ስለተጭበረበረ አመልካችም እንደተጭበረበረች ይቆጠራል ወደሚለው መደምደሚያ የሚደርስ ሁኔታ የለም፡፡ በዚህ መዝገብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተያዘው አከራካሪ ሆኖ የተነሣው ነጥብ ባንክ ሂሣብ /ገንዘብ/ ባላቸው ሰዎች ስም ሌሎች ሰዎች አጭበርብረው ገንዘብ ከሚያወጡበት ሁኔታ ተለይቶ የሚታይ ነው፡፡ ባንክ ገንዘብ ያስቀመጡትን ሰዎች ሰነዶች እና ፊርማ አጭበርብሮ በማግኘት ገንዘብ የሚወስዱ ሰዎች በባለሂሣቦቹም ሆነ በባንኩ ሊጠየቁ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች ባንኩን አጭበርብሮ ገንዘብ የወሰደውን ሰው በመጠየቅ ገንዘቡን የምታስመልስበት አግባብ የለም፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ተጠሪ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ለመስጠት ከአመልካች ሲቀበል የአደራውን ሃላፊነት ወስዶአል፡፡ አደራ ተቀባይ የሆነው ወገን በአደራ ያስቀመጠውን /የተቀበለውን/ ዕቃ መመለስ ያለበት ለአደራ ሰጪው ወይም አደራ ሰጪው ይቀበልልኝ ብሎ ላመለከተው ሰው እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2792/1/ በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪ ከእነዚህ ግዴታዎቹ አንዱንም አልተወጣም፡፡ ስለዚህም ገንዘቡን ለአመልካች አልከፍልም የሚልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም ከዚህ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21113 ጎንደር 20 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03497 መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለአመልካች ይመልስ ብለናል፡፡ በሥር ፍ/ቤቶች እና በዚህ ሰበር ችሎት አመልካች የከፈለችው የዳኝነት ገንዘብም ተጠሪ ይተካላት ብለናል፡፡
3. ሌሎች ወጪና ኪሣራ በተመለከተ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   የውሣኔው ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43875

ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- በወላይታ ዞን የቦዲቲ ከተማ ማዘጋጃ ቤት - ነ/ፈጅ አረታ ቶሩ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ወንድሙ ኃይሌ - ጠበቃ ዳንኤል ገ/ጊዮርጊስ ቀርበዋል፡፡

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቹ የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታው የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ር ሰበር መ/ቁ. 22624፣ ታህሣሥ 17 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በወላይታ ዞን በቦዲቲ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በአፈፃፀም ከሳሽነት እንዲሁም የአሁኑ አመልካች በአፈፃፀም ተከሣሽነት ተከራክረዋል፤ የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤቱ ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘቱ በቦዲቲ ከተማ ምዕራብ ክፍል በ600 ሜ.ካ ያረፈውን ቤትና ቦታ ከወላጅ አባታቸው አቶ ኃይሌ መርሻ እና ከአክስቶቹ ወ/ሮ የሺ መርሻና ወ/ሮ ተዋበች መርሻ በስጦታ አግኝቹ ስጦታው በቦዲቲ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፀደቀልኝ ሲሆን በዚሁ ውሣኔ መሠረት የቦዲቲ ማዘጋጃ ቤት ወደ ስሜ እንዲያዞርልኝ ብጠይቀውም ፍቃደኛ ባለመሆኑ በፍርድ ቤቱ ተገድዶ ይፈጽምልኝ የሚል ሲሆን፣ ሥር ተከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ወደ ሥር ፍ/ቤቱ ቀርቦ በአከራካሪው ቦታ የመንግሥት ቤት ስላለና ጉዳዩ በቤቶች ኤጀንሲ መታየት ያለበት ነው ብሎ መልስ ሰጥቷል፤ ክርክሩ በመጀመሪያ የቀረበለት የቦዲቲ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 00446 ጥቅምት 14/2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ጉዳዩ በቤቶች አጀንሲ መታየት ያለበት እንጂ በቀጥታ ማስፈፀም አይቻልም ያለውን የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 8618፣ ሰኔ 18 ቀን 2000 ዓ.ም. ጉዳዩን በይግባኝ አከራክሮ የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

ከላይ የሰፈረውን የሥር ፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ በመቃወም የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩን ወደ ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳቀረቡትና ፍ/ቤቱም የመንግሥትና የግለሰቡ ይዞታዎች ለይቶ መፈፀም ሲገባ የግለሰቡ /የአሁን ተጠሪ/ መብት በደፈናው መዝጋት አግባብነቱ ለመመርመር ብሎ ጉዳዩን ካቀረበው በኋላ ተከሣሹ ተቋም መልስ እንዲሰጥ ባዘዘው መሠረት ውክልናቸው በተከሣሹ መስሪያ ቤት በሚገባ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የተቋሙ የፕሮቶኮል ቁጥርና ፊርማ በሌለበት ጎዳር 12/2001 ዓ.ም. በተፃፈ ነገረ ፈጁ የተባሉት በሰጡት መልስ የግለሰቡ ቤት ከመንግሥት የውርስ ቤቶችና ቦታ ነጥለን ለማስረከብ ዝግጁ ነን ብለዋል በማለትና መልሱ የተቋሙ የፕሮቶኮል ቁጥርና ፊርማ ባይኖረውም የሚታመን ነው በማለት በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም በመወሰን የሥር ፍ/ቤቶቹ የሰጡትን ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

ከላይ የሰፈረውን የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ር ሰ/መ/ቁ. 22624 ታህሣሥ 17/2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የአሁኑ አመልካች የካቲት 24/2001 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታቸው ውሣኔው እንዲሻርለት ጠይቋል፤ ያቀረበው ምክንያትም ተገቢው ውክልና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባልተሰጠው ነገረ ፈጅ የቀረበው የፕሮቶኮል ቁጥርና ፊርማ የሌለበትን መልስ መሠረት አድርጎ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢነት የለውም የቀረበው መልስ የአመልካች አይደለም፤ ከአዋጅ ውጭ የተወረሱትን ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት አጣርቶ የመወሰን ስልጣን የቤቶች ኤጀንሲ እንጂ የፍ/ቤቱ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካች ስምና ፊርማ እንዲሁም የፕሮቶኮል ቁጥር የሌለውን ደብዳቤ መሠረት በማድረግ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ መሻሩ አግባብነቱን ለመመርመር ብሎ ጉዳዩን በማቅረብ ተጠሪው መልሱን እንዲሰጥ አዟል፤ ተጠሪውም መጋቢት 30 ቀን 2001 የተፃፈ መልስ ሰጥተዋል፤ አጭር ይዘቱም የአመልካች ነገረ ፈጅ ለመሆናቸው ማረጋገጫ የላቸውም የተባሉት አቶ መሠለ ማሞ በትክክል የተቋመ ነገረ ፈጅ ናቸው፤ እኚህ ነ/ፈጅ ባቀረቡት መልስ ለምን የፕሮቶኮል ቁጥርና ፊርማ የለውም ተብለው ሲጠየቁ ከቦታው ርቀት አኳያ ትራንስፖርት እንዳያመልጠኝ ብዬ በመቸኮሌ እንጂ የጽሁፉ /የመልሱ/ ይዘት በትክክል የአመልካቹ መሆኑ ስላስረዱና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም በዚህ አባባላቸው እምነት በማሳደሩና ይህን ማድረጉም ተገቢነት ያለው ነው፤ አመልካቹ ቤቶቹ የተወረሱ ናቸው ይበል እንጂ የተወረሱ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥለት ማስረጃ አላቀረበም፤ ስለሆነም የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ፍርድ ይጽናልኝ የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች የክርክር አመጣጥ ከላይ እየተገለፀ እንደመጣው በመገንዘብ ይህ ፍርድ ቤት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር የመጨረሻ እልባት የሰጠው <u>ከአመልካች ተገቢውን ፎርማሊቲ የጠበቀ መልስ ከቀረበለት በኋላ ነው ወይስ አይደለም?</u> የሚል መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በዚህ ክርክር ለመገንዘብ እንደተቻለው የአመልካቹ ቁልፍ ቅሬታ የሚያተኩረው በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተላለፈብኝ ፍርድ በተገቢው ነገረ ፈጅ ሳልወክልና ነገረ ፈጅ የተባሉት ግለሰብ የሰጡት መልስም የአመልካች የፕሮቶኮል ቁጥርና ፊርማ በተገቢው መንገድ ያላሟላና በዚህ መልስ መሠረት ተደርጎ የተሰጠ ውሳኔም የአመልካች ክርክር በአግባቡ ያካተተ ስላልሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ሲል ተጠሪው ደግሞ ይህንን አይቀበልም፡፡ አመልካች መንግስታዊ ተቋም ሲሆን የመንግስት ተቋም በሚከሰስበትም ሆነ በሚከሰስበት ክርክር ወክሎ የሚከራከር ነገረ ፈጅ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 59 መሠረት በሚመለከተው የመንግስት ተወካይ መወከል አለበት፡፡ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ ዓንቀፅ 80፣92 እና 93 እንደሚገልፁትም ማንኛውም አቤቱታ በዋናው ባለጉዳይ ወይም በጠበቃው መፈረም እንዳለበት ነው፤ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 92(3) በተለይ እንዳሰፈረው ደግሞ መንግስት በሚከሰስበትም ሆነ በሚከሰስበት ጊዜ አቤቱታውን የሚፈርመው ስለዚህ ጉዳይ በተለይ የተወከለ ወይም ስልጣን ያለው ሰው ነው፤ የፅሁፉ ትክክለኛነት የሚያረጋግጠው ደግሞ ጉዳዩን በተለይ የሚያውቀውና ለዚህም የተለየ ስልጣን የተሰጠው ክፍል ሃላፊ እንደሆነ ነው፡፡ በእኛችን ወዳለው ክርክር ስንመጣ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንደ የአመልካች መልስ በመቁጠር ለውሳኔው ግብአት ያደረገው የፅሁፍ መልስ የፕሮቶኮል ቁጥር የሌለውና በሚመለከተው የአመልካች ወኪል ያልተፈረመ ሆኖ እያለ ነገረ ፈጅ ነኝ ብለው የቀረቡት ሰው ትራንስፖርት እንዳያመልጠኝ በመቸኮሌ በሚመለከተው ኃላፊ አላስፈረምኩም ያሉትን ሃሣብ በማመን ብቻ ተመስርቶ የቀረበው መልስ የአመልካቹ ነው ብሎ መውሰዱ ከላይ ከተጠቀሱት ህጎች አኳያ ተገናዝቦ ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈፅሟል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ር ሰበር መ.ቁ 22624 ታህሳስ 17 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡
2. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎቱ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔን የሻረው የአሁኑ አመልካች መልስ መሆኑ በተገቢው መንገድ ባላረጋገጠው ፅሁፍ ተመስርቶ ስለሆነ ተገቢውን ፎርማሊቲ ያሟላ የአመልካች መልስ ተቀብሎ ለጉዳዩ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት ተመልሶለታል፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
4. የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተላለፈው እግድ ተነስቷል፤ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
   ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37799

ሐምሌ 29 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የባህርና ትራንዚት አግልግሎት ድርጅት - ነ/ፈጅ በዛብህ አመዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ሰናይት በዳሣ

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ተጠሪ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የመሰረተው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ክስ ደንበኛው የሆነው አዋሽ ወይን ጠጅ አ/ማ ለፋብሪካው አገልግሎት የሚውል የጠርሙስ ማጠቢያ ማሽን በጉዞ ላይ ለሚደርስበት ጉዳትና ውድመት የመድን ሽፋን ሰጥቷል፡፡ የተጠሪ ደንበኛ የጉምሩክ አስተላላፊነት ውክልና ቀጥሎም የማጓጓዝ ትእዛዝ ለአመልካች የሰጠ ሲሆን ማሽኑን በስር ሁለተኛ ተከሣሽ በነበሩት ግለሰብ መኪና አስጭኖ ሲያመጣ ተሽከርካሪው ተገልብጦ በማሽኑ ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ ማሺኑም ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ በመሆኑ ብር 2,200,856.43(ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ስድስት ከአርባ ሦስት ሳንቲም) ለደንበኛው ስለከፈለ አመልካች በገባው የውክልናና የማጓጓዝ ውል መሰረት፣በንግድ ሕግ ቁጥር 590 ባለበት ሃላፊነት፣ሁለተኛ ተከሣሽም የተሽከርካሪው ባለንብረት በመሆናቸው ሁለቱም ገንዘቡን ሊተኩ ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ተመልክቶ አመልካች እቃውን ያጓጓዘው በውክልና ስልጣን በመሆኑ ሊጠየቅ አይገባም በማለት ሁለተኛው ተከሣሽ ብቻ ገንዘቡን እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ አመልካች እቃውን ያጓጓዘው ራሱን ችሎ እንጂ በውክልና ስላልሆነ ለጉዳቱ ኃላፊ ሊሆን ይገባል በማለት ከስር ሁለተኛ ተከሣሽ ጋር ክስ የቀረበበትን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ማሽኑን ያጓጓዘው በውክልና ነው ወይስ እራሱን ችሎ ነው? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙ ቀርበው ክርክራቸውን በቃል አሰምተዋል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ተመክቷል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የተጠሪ ደንበኛ ያስመጣውን የጠርሙስ ማጠቢያ ማሽን አመልካች ያጓጓዘው መሆኑ አከራካሪ አልሆነም፡፡ አከራካሪ የሆነው ነጥብ አመልካች ማሽኑን ያጓጓዘው እራሱ አጓጓዥ ሆኖ ነው? ወይስ በውክልና ነው? የሚለው ነው፡፡

አመልካች እቃ አስተላላፊ ለመሆኑ ተጠሪም በክሱ ገልፆታል፡፡ እቃ አስተላላፊ ምን ማለት እንደሆነ እና ምን ምን ስራዎችን እንሚሰራ ስለእቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ስራ ፈቃድ አስመልክቶ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 37/90 ያመለክታል፡፡ በዚሁ በተጠቀሰው ደንብ አንቀጽ 2/1/ ስር እቃ አስተላላፊ በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ እቃ ተቀባይነት ወይም እቃ ላኪን በመወከል የጉምሩክ፣የወደብ ወይም ሌሎች ስርአቶች አስፈጽሞ ገቢ ወይም የወጪ እቃዎችን ወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ የሚያደርግ ሲሆን እቃን የማጓጓዝና የማስረከብን ስራም ይጨምራል፡፡ ይህ ድንጋጌ በጥቅሉ ሲታይ እቃ አስተላለፊው ስራውን የሚያከናውነው እቃ ላኪዎችን ወይም ተቀባዮችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመወከል በውክልና ስልጣን መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ በእርግጥ የእቃ ማንጓዝ ተግባሩን እንዴት ሊያከናውን እንደሚችል በደንቡ አንቀጽ 3/6/ እና /7/ ስር ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ በአንቀጽ 3/6/ ስር እቃ አስተላላፊው የራሱ የትራንስፖርት አገልግሎት ካለው የእቃ ማንጓዙን ተግባር የሚያከናውነው እንደ አንጓዥ ሆኖ እንጂ በውክልና ስልጣን አለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም በአንቀጽ 2/1/ ስር የተመለከተው የውክልና ስልጣን ልዩ ሁኔታ(exception) ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን የራሱ ትራንስፖርት ከሌው ወይም ባለእቃው የራሱን ማንጓጉር ካላቀረበ እቃ አስተላላፊው ማንጓጉር ተከራይቶ እቃውን እንደሚያንገዝ በንኡስ አንቀጽ 7 ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ በንኡስ አንቀጽ 6 ስር በግልጽ እንደተመለከተው የማንገዝ ስራውን እንደ አንጓዥ ሆኖ እንደሚሰራ አያስቀምጥም፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው ደግሞ እቃ አስተላላፊ ስራውን ሁሉ የሚያከናውነው በውክልና በመሆኑ በእራሱ ስም ስለራሱ ሆኖ ይሰራል ተብሎ በንኡስ ቁጥር 7 ስር ልዩ ሁኔታ (exception) ስላልተመለከተ የማንገዝ ተግባሩን የሚያከናውነው በውክልና መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች የማንገዝ ውሉን በራሱ ስም መፈጸሙ የማንገዝ ተግባሩን የፈፀመው እንደ አንጓዥ ሆኖ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ግን እቃ አስተላላፊው እቃውን በወደብ ማስተላለፍ፣የወደብና የጉምሩክ ስርአቶችንና የእቃ ማንገዝ ተግባርን በሙሉ የሚፈጽመው በውክልና ነው፡፡ እንደ አንገዥ ሆኖ የሚቆጠረው የማንገዙን ስራ በራሱ ማንጓጉር ካንገዘ ብቻ ነው፡፡ የማንጓጉር ውሉን በስሙ መፈረሙ ብቻ ስራው በውክልና ያልተሰራ መሆኑን አያመለክትም በእርግጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2251 የተገለጸው የእቃ አስተላላፊ በደንብ ቁጥር 37/90 ስር ከተመለከተው ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሣሣይ ተግባር የሚፈጽም ባይሆንም እቃ አስተላላፊው ስራውን የሚያከናውነው በራሱ ስም ሆኖ ለወካዩ ጥቅም መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የእቃ አስተላላፊ በራሱ ስም የሚያደርጋቸው ተግባሮች ለወካዩ ጥቅም በውክልና ስልጣን የሚፈጸሙ ናቸው ማለት ነው፡፡

አመልካች ወኪል ነው ከተባለ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው የውክልና ስራው በክፋት ያደረገ መሆኑ ከተረጋገጠ ብቻ እንጂ ጉዳት ስለደረሰ ብቻ በኃላፊነት ተጠያቂ እንደማይሆን በንግድ ሕግ ቁጥር 683/3/ ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ደግሞ አመልካች ስራውን በክፋት በማከናወኑ ጉዳት ያደረሰ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት የሚጠየቅበት የሕግ መሰረት የለም፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶችም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች ኃላፊ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 28225 በ7/08/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40949 በ5/3/99 የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
3. አመልካች የማንገዝ ስራውን የሰራው በውክልና ስልጣን በመሆኑ ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34621

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ - ጠበቃ አቶ በረከት በርሄ ቀረበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ሐጐስ ገ/ድህን - ጠበቃ አቶ ገ/ሄር ተስፋይ ቀርበዋል

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመር በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 41455 መስከረም 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ግድፈት የተፈጸመበት ነው በማለት እንዲሻርለት ስለጠየቀ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በስር ከሳሽነት፣የአሁኑ ተጠሪ እና ሌሎች በዚህ ሰበር ችሎት ተከራካሪ ያልሆኑ ሁለት ሰዎች ተከሳሾች በመሆን የተከራከሩ ሲሆን የስር ከሳሹ (የአሁኑ አመልካች) መስከረም 14 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ያቀረበው ክስ አጭር ይዘቱ ደንበኛዬ ከጣሊያን ሃገር ገዝቶ ለሚያስገባቸው የጫማ ሶል መስሪያ ኬሚካሎች በጉዞ ላይ እንዳሉ ለሚደርስባቸው ጉዳት የመድን ሽፋን የሰጠሁ ሲሆን እነዚህ የመድን ሽፋን የሰጠኋቸውን ንብረቶች ከጅቡቲ ወደብ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ለማጓጓዝ የተባበሩት የጭነት ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር(አንደኛ ተከሳሽ) ግዴታ በመግባት ተረክቦ በአቶ ሐጐስ ገ/መድህን(ሁለተኛ ተከሳሽ) ንብረት በሆነችው እና በአቶ ፋሲል ሐጐስ(ሦስተኛ ተከሳሽ) ንብረት በሆነችው እና ቁጥሯ 3-37484/3-04254 በሆነች መኪና ተጭኖ በመጓጓዝ ላይ እንዳለ የመኪናው ተሳቢ በመገለበጡ ግምቱ ብር 129,333.93(አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት ብር ከዘጠና ሦስት ሳንቲም) በሆነ 42 በርሜል እና 4 ጀሪካን ኬሚካል ላይ ጉዳት በመድረሱ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ለደንበኛዬ መድህን ከፍያለሁ እና ተከሳሾቹ ይህንን የገንዘብ መጠን ከነወለዱ ይክፈሉኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሾቹም ለቀረበባቸው ክስ መልስ እንዲሰጡ በታዘዘው መሰረት፣

አንደኛ ተከሳሽ በሰጠው መልስ ከሳሹና ደንበኛዬ የሚለው ባለንብረት የፈጸሙት የኢንሹራንስ ውል ተገቢውን የአፃፃፍ ፎርም ያላሟላ በመሆኑ ለከሳሹ የመዳረግ መብት አይፈጥርለትም፤ለከሳሹም የመዳረግ መብት በባለንብረቱ አልተሰጠውም፤እንዲሁም ክሱ በይርጋ ይታገዳል፤በኢንሹራንስ ውሉ የተዋዋይ ወገኖችና የምስክሮች ፊርማ የሌለ በመሆኑ ውጤት የለውም ብሏል፤

ሁለተኛ ተከሳሽ ደግሞ እኔ የማጓጓዙ ውል ተዋዋይ አይደለሁም፤እቃው የተጫነበት ንብረት የእኔ ስለመሆኑም የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፤አደጋው በደረሰ በ7 ቀናት ውስጥም ያልቀረበ ጥያቄ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብሏል፤

ሦስተኛ ተከሳሽም የተባለው እቃ አልጫነኩም፤ክሱም በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት መልሷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍርድ ቤቱም በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል የቃል ክርክር ካካሄደ በኋላ ከላይ ላቀረቡት ክርክሮች እንደሚከተለው ወስኗል፣ይኸውም የስር ከሳሽ የመዳረግ መብት አለኝ በማለት ክሱን ያቀረበው ወይም መብቱ መነጨ የሚለው ኢንሹራንሱን ከከፈለው ደንበኛው ጋር ካደረገው የኢንሹራንስ ውልና ይህ ደንበኛው በሱ መብት ተዳርጐ ክሱን በተከሳሾቹ ላይ ማቅረብ እንደሚችል ከፃፈለት ደብዳቤ በመሆኑና ተደረገ የተባለው የኢንሹራንስ ውል በሚመለከት በንግድ ሕግ አስገዳጅ የሆነ የተለየ ፎርማሊቲ ያልተቀመጠለት በመሆኑ የኢንሹራንሱ ውል የፎርማሊቲ ጉዳይ የሚታየው በፍትሐብሄር ሕጉ በተቀመጠው በጠቅላላ ውል ዓንቀፆች 1725፣1727 እና 1720(1) መሰረት ተደርጐ በመሆኑና ከሳሹ ከደንበኛው ጋር ያደረገው የኢንሹራንስ ውል በግራ ቀኙ ወገኖችና በምስክሮች ያልተፈረመ በመሆኑ ህጋዊ እውቅና የለውም፣አይጸናም፤ ስለሆነም የከሳሹ ደንበኛ በሌለ የኢንሹራንስ ውል ተመስርቶ ለከሳሽ የፃፈለት የመዳረግ መብት ህጋዊ ውጤት የለውም፣ ሁለተኛው ተከሳሽም የንብረቶቹ አጓዥ ተብለው በማጓጓዝ ሰነድ እስካልተጠቀሱ ድረስ የመኪናው ባለቤት በመሆናቸው ብቻ አጓዥ ሊባሉ ስለማይገባ በውልም ሆነ ከውል ውጭ መሰረት ያደረገ ክስ ሊቀርብባቸው አይገባም የሚል ነው፡፡

ከላይ የሰፈረውን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም የአሁኑ አመልካች ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በኮ/መ/ቁ. 41455፣መስከረም 23 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት አጽንቶታል፡፡

በስር ፍ/ቤቶቹ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አመልካቹ ታህሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበ ሲሆን፤አጭር ይዘቱም፡- ከደንበኛዬ ጋር ህጋዊ የሆነ የኢንሹራንስ ውል በማድረግ እቃዎቹ በተጠሪው መኪና ከወደብ ተጭኖ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ላይ እያለ አደጋ በመድረሱ ለደንበኛዬ በክስ የቀረበውን ገንዘብ መክፈሌ ተረጋግጦ እያለ፣የመኪናዋ ባለቤት ተጠሪው መሆናቸው እና የጭነት ውሉ የተደረገው ከወኪላቸው (የስር አንደኛ ተከሳሽ) ጋር በመሆኑ በንግድ ህጉ መሰረት የእቃው አጓዥ መባል ሲገባቸው አጓዥ መሆናቸው በሰነዱ አልተጠቀሱም ስለሆነም አጓዥ አይባልም፤የመኪናዋ ባለቤት ቢሆንም ጉዳዩ የተያያዘው ከውል ጋር በመሆኑ ከውል ውጭ መሰረት በማድረግ ሊጠየቁ አይገባም በማለት የተሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻረልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

ተጠሪውም ነሐሴ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ማህበር የእኔ ወኪል አይደለም፤ እኔ የፈጸምኩት የእቃ አጓዥነት ውል የለም፤አመልካች ገንዘቡ ከስር ሦስተኛ ተከሳሽ እንዲያገኝ ተፈርዶለት እያለ አላግባብ በእኔ ላይ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር ከላይ እየተገለፀ በመጣው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ፣

1. አመልካች ከደንበኛው ጋር የፈጸመው ህጋዊ የኢንሹራንስ ውል አለ ወይስ የለም?
2. አመልካች ለደንበኛው ተክቶ ወይም ተዳርጐ በስር ተከሳሾች (በእነ ተጠሪ) ክስ ሊመሰረት ይችላል ወይስ አይችልም?
3. ተጠሪው የእቃው ማጓጓዝ ውል ወስደዋል ወይስ አልወሰዱም? በሌላ አባባል ተጠሪው በዚህ ጉዳይ አጓዥ ናቸው ወይስ አይደሉም?

የሚሉ መሰረታዊ ጭብጦችን በማውጣት ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡-

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ትርጉም በተጠሪውና በደንበኛው መካከል በሕግ የሚጸና የኢንሹራንስ ውል የለም የሚል ለዚህም የሰጡት ምክንያት በውሉ ላይ ተዋዋይ ወገኖቹና ምስክሮች ስላልፈርሙበት በሕግ የሚፈለግበትን ተገቢ ፎርማሊቲ አላሟላም፤የንግድ ሕጉ የኢንሹራንስ ውል ይዘት ከሚዘረዝር በስተቀር ስለውሉ ፎርማሊቲ የሚለው ነገር ስለሌለ የኢንሹራንስ ውል ፎርማሊቲ በሚመለከት በፍትሃብሄር ሕግ ውስጥ በጠቅላላ ውሉ ዓንቀጽ 1725 እና 1727 በተመለከተው መሰረት መከናወን እንዳለበት ማለትም ውሉ የግድ በጽሁፍ መዘጋጀት ያለበትና ተዋዋይ ወገኖችና ምስክሮች የግድ ሊፈርሙት እንደሚገባ፣ይህ ሳይሟላ ከቀረ ግን በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር ዓንቀጽ 1720(1) መሰረት ውሉ እንደረቂቅ የሚቆጠርና ምንም አይነት ውጤት የማያስከትል ነው፤በመሆኑም አመልካች ከደንበኛው ጋር ያደረገው የኢንሹራንስ ውል በተከሳሾቹ ላይ ግዴታ ሊያስከትል አይችልም የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የንግድ ሕጉ ስለ የኢንሹራንስ ውል ፎርማሊቲ ምንም ነገር አላለም የተባለው ተገቢነት የለውም፡፡ ምክንያቱም የንግድ ሕግ አንቀጽ 657 ስለ ውሉ ፎርማሊቲ የሚደነግግ ሣሳብ አስፍሯል፤ ይኸውም የኢንሹራንስ ውል በኢንሹራንስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል ፖሊሲ በሚባል ጽሁፍ እንደሚደገፍና የመድህን ገቢው ጥያቄ መሰረት በማድረግ በፖሊሲው ላይ መድህን ሰጭው ከፈረመ ህጋዊ የሆነ የኢንሹራንስ ውል ግንኙነት በመድህን ሰጭው እና በመድህን ገቢው መካከል እንደሚመሰረት ነው፤ይህ ሁኔታ ደግሞ የንግድ ሕጉ ልዩ የሆነ የኢንሹራንስ ውል አፈፃፀም የሰፈረ እንጂ ጉዳዩ በጠቅላላ የውል ሕግ የሚመራ ግንኙነት አይደለም፤ይህ ሰበር ችሎትም የኢንሹራንስ ውል አለ ለማለት ተመሳሳይ ትርጉም በሰ/መ/ቁ. 24703 ሚያዝያ 09 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶቹ በአመልካችና በደንበኛው መካከል የተደረገው ውል ሁለቱ ወገኖች እና ምስክሮች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1725 እና 1727 በሚያዙት መሰረት ባለመፈረማቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1720/1/ መሰረት የኢንሹራንስ ውል ግንኙነት የለም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ ሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በደንበኛው መካከል ህጋዊ የሆነ የኢንሹራንስ ውል ግንኙነት አለ ብለናል፡፡

ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ የአመልካች ደንበኛ ሐምሌ 17 ቀን 1995 ዓ.ም የተፃፈ ሰነድ አዘጋጅቶ አመልካቹ በእርሱ እግር ተተክቶ መብቱን የማስከበር ወይም የመዳረግ መብት እንዳለው ቢያረጋግጥም፣የስር ፍ/ቤቶቹ በሰጡት ፍርድ ይህ የመዳረግ መብት ሕጋዊ ከሆነ የኢንሹራንስ ውል የመነጨ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአመልካችና በደንበኛው መካከል ሕጋዊ የሆነ የኢንሹራንስ ውል ግንኙነት እንዳለ በላይኛው ጭብጥ የተረጋገጠ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቹ ን/ሕ/ቁ. 683 መሰረት በደንበኛው እግር ተዳርጎ በተከሳሾቹ ላይ ክስ ማቅረብ የሚያስችለውን መብት ከደንበኛው አግኝቶ እያለ የስር ፍ/ቤቶቹ ሳይቀበሉት መቅረታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡

ሦስተኛውን ጭብጥ በሚመለከት አመልካቹ ተጠሪው የመኪናዋ ባለንብረት በመሆናቸው አጓዥ ናቸው፤በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የተባበሩት የጭነት ማመላለሻ ንብረቶች ማህበር ለተጠሪው ጥቅም ሲባል የሚጫን ነገር ከማፈላለግ ውጭ ጥቅሙ ለተጠሪው የሚውል በመሆኑ በን/ሕ/ቁ. 566/የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2251 መሰረት የትራንስፖርት ስራው በውክልና የሚያስተዳድር አካል ነው፤ስለሆነም ተጠሪው አጓዥ መባል አለበት ሲል ተጠሪው ደግሞ አጓዥ እንዳልሆኑ በመግለጽ የአመልካቹ አባባሉን የሚደግፍለት ማስረጃ አላቀረበም በማለት ይከራከራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳት ያደረሰችውን የአሁኑ ተጠሪ መኪናን በሚመለከት ከአመልካቹ ደንበኛ ጋር የአሁኑ ተጠሪ የመጓጓዣ ውል በቀጥታ የፈጸመው በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው (የተባበሩት የጭነት ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር) ቢሆንም ይህ አካል ያደረገው ውል ተጠሪውን በመወከል ነው፤ምክንያቱም የዚህ አካል የስራ ድርሻ በማህበሩ የታቀፉት መኪኖች የጭነት ስራ እንዲያገኙ ከማድረግ አልፎ የእያንዳንዱ መኪና የጭነት ኪራይ ገቢ የባለቤቱ ነው፣በአሁኑ ክርክርም ተጠሪው መኪናቸው በተባበሩት የጭነት ማመላለሻ ማህበር ከመታቀፏ ውጭ የመኪናው ገቢ በቀጥታ ተጠቃሚ ናቸው፤ስለሆነም በንግድ ሕ/ቁ. 566 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2251 መሰረት ተጠሪው ከአመልካቹ ደንበኛ ጋር የጭነት ማጓዝ ውል የነበራቸው ሆነው እያለ የስር ፍ/ቤቶቹ ተጠሪው አጓዥ አይደሉም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43650፣ሰኔ 16 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 41455፣መስከረም 23/2000 ዓ.ም የሰጧቸው ፍርዶች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪው ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 129,333.93(አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት ብር ከዘጠና ሦስት ሣንቲም) እንዲሁም ክሱ ከቀረበበት ከመስከረም 14/1997 ዓ.ም ጀምሮ 9% ወለድ ተከፍሎ እስኪያልቅ ለአመልካች እንዲከፍለው ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 33954

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

አለ. መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዘውዱ ቢረዳ - ከጠበቃቸው አቶ ፍቅሩ ታደሰ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 30404 ሐምሌ 19 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 59124 ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ህዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ባልና ሚስት የነበሩት አመልካችና ተጠሪ በፍቺ ጋብቻቸው መፍረሱን ተከትሎ የቀረበው የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ አመልካች በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 በተሰጣቸው ብር 100,000 /መቶ ሺ ብር/ የሚገመት የተዘጋጁ የሴት ልብሶችና ጫማ የያዙ የሱቅ የንግድ ድርጅቶች የጋራ ንብረት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ እንዲያካፍላት የጠየቀች ሲሆን ከላይ ከተገለፁት የሱቅ የንግድ ድርጅቶች በተጨማሪ ሌሎች ንብረቶችም እንዲያካፍላት ጠይቃለች፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሱቅ የንግድ ድርጅቶቹ ውስጥ ያለው ሽቀጥ ለብቻው ተቆጥሮ አመልካችና ተጠሪ እንዲካፈሉ የወሰነ ሲሆን በቁጥር 209 እና 210 ያለው የንግድ ድርጅትን በተመለከተ ቤቶቹ የኪቤአድ ንብረት በመሆናቸው በጋራ ንብረትነት የሚካፈሉበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ምክንያት የለም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች የሥር ፍርድ ቤቶች በቁጥር 209 እና 210 ያለውን የንግድ ድርጅት በጋራ ንብረትነት ለመካፈል ያቀረቡትን ጥያቄ ባግባቡ አልመዘነም፤ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውም ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፤ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ አስደግፌ ያቀረብኩትን ሌሎች የጋራ ንብረት ክፍያዎች አላግባብ ያለፈብኝ ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ለሰበር ባቀረቡት አቤቱታ ጠይቀዋል፡፡

ይኸ የሰበር ችሎትም የሥር ፍርድ ቤት በቁጥር 209 እና 210 የሚንቀሣቀሰው የንግድ ድርጅት የሚከናወንባቸው ክፍሎች የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ንብረት በመሆናቸው በጋራ ንብረትነት ለማካፈል አይቻልም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ተገቢነት ለማጣራት ብቻ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ለተጠሪ እንዲደርሰው አድርጓል፡፡ ተጠሪ በቁጥር 209 እና 210 ያለው የንግድ ድርጅትና የመከራየት መብት ከጋብቻ በፊትም ሆነ በኋላ የእኔ የግል ንብረት በመሆኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በቁጥር 209 እና 210 ይከናወን የነበረው የንግድ ድርጅት በእግት ቃጠሎ ምክንያት ከወደመ በኋላ እንደገና በጋራ ሀብታችን የተቋቋመና የተደራጀ ስለመሆኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ክዶ ያልተከራከረ በመሆኑ በሰበር ደረጃ ይህንን ነጥብ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም የሚል የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና የሰበር ችሎት በጭብጥነት የያዘው ነጥብ፣ አመልካችና መልስ ሰጭ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በመጀመሪያ ደረጃ አመልካች የጋራ ንብረት ስለሆነ ድርሻዬ ተከፍሎ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት የጠየቁት ንብረትነታቸው የመንግሥት የሆኑ የንግድ ማከናወኛ ክፍሎችን አይደለም፡፡ አመልካች ለመካፈል የጠየቁት በመርካቶ የገበያ አዳራሽ ውስጥ በቁጥር 209 እና 210 የሆነውን የጫማና የተዘጋጁ የሴት ልብሶች መሸጫ የንግድ ድርጅት ግምታቸው 100,000 /አንድ መቶ ሺ ብር/ የሆነ ሸቀጦችን እንደያዘ እንደሆነ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልጽ አስፍሮታል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች በጋራ ንብረትነት ለመካፈል ጥያቄ ያቀረቡት በሱቅ የንግድ ድርጅት ውስጥ የሚገኙ ሸቀጦችን ለብቻ ንግድ የሚከናወንባቸውን ክፍሎች ደግሞ ለብቻ በመነጣጠል ፍርድ ቤቱ እንዲያካፍላቸው አይደለም፡፡

አመልካች በጋራ ንብረትነት ፍርድ ቤቱ እንዲያካፍላቸው የጠየቁት በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 ያለውን የንግድ ድርጅትና በቁጥር 210 ያለውን የንግድ ድርጅት የንግድ ሕግ ቁጥር 124 በሚደነግገው መሠረት በንግድ ድርጅትነቱ ከውስጡ ካሉ ሸቀጦች ጋር በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ይህንን በማለፍ አመልካች ሸቀጦቹ ለብቻ ቆጠራ ተደርጎ እንዲካፈሉ የንግድ ሥራ የሚከናወንባቸው ክፍሎች ግን የጋራ ንብረት ሣይሆኑ ንብረትነታቸው የመንግሥት ስለሆነ ጥያቄሽ ተገቢነት የለውም በማለት መወሰኑ አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት በቁጥር 209 እና 210 ያለው የንግድ ድርጅቶች በንግድ ድርጅትነታቸው ሣይሆን ነጣጥሎ በማየት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከንግድ ሕግ ቁጥር 127 ድንጋጌዎች ለመረዳት እንደሚቻለው የአንድ የንግድ ድርጅት መሠረታዊ አካል የንግድ ድርጅቱ መልካም ዝና ስምና በደንበኞቹ የተለመደ መሆኑ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ነገሮችን አካትቶ የሚይዝ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ንግዱ የሚከናወንበትን ክፍል የመከራየት መብት የንግድ ድርጅት አንደኛው ክፍል እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 127 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረት በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 በጋራ ንብረትነት አመልካችና ተጠሪ ያላቸውን የንግድ ድርጅት የንግድ ሥራው የሚከናወንበትን ክፍል የመከራየት መብት ጭምር ፍርድ ቤቱ እንዲያካፍላትና እንዲወስንላት ያቀረበችውን ሕጋዊ ጥያቄ የንግድ ሥራ የሚከናወንባቸው ክፍሎች የመንግሥት ንብረቶች ናቸው በሚል ምክንያት ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 ያሉት የሱቅ የንግድ ሥራ ድርጅቶች የተጠሪ የግል ንብረት ናቸው በማለት ሣይሆን የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ቤት የመንግሥት የልማት ድርጅት ንብረት በመሆኑ በጋራ ንብረትነት ለማካፈል አይችልም በማለት በመሆኑ ተጠሪ የሱቅ የንግድ ድርጅቱ የግል ንብረቱ ነው በማለት በሰበር ደረጃ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም አመልካች በጋራ ንብረትነት ለመካፈል የጠየቀችው በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 ያሉትን የሱቅ የንግድ ድርጅቶች በንግድ ድርጅትነታቸው ባሉበት በንግድ ሕግ ቁጥር 124 እና 127 ድንጋጌ መሠረት ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ እነዚህን የሕግ ድንጋጌዎች እና የንግድ ሕግ ቁጥር 145 ንዑስ አንቀጽ 1ን ሣያገናዝብ፣ አመልካች የሌላ ሰው ንብረት የሆነ የንግድ ማከናወኛ ቤት ለመካፈል መጠየቅ አትችልም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ በመርካቶ ገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 ያሉት የሱቅ ንግድ ድርጅቶች አመልካች ለመካፈል ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ይህንን ነጥብ በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ስህተት የለበትም በማለት የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ አመልካች በመርካቶ የገበያ አዳራሽ በቁጥር 209 እና 210 ያሉት የሱቅ የንግድ ድርጅቶች የንግድ ሥራ የሚከናወንበትን ክፍል ከመከራየት መብት ጭምር በጋራ ንብረትነት የመካፈል፣ መብት አላት ብለናል፡፡ በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም የውሣኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3/ በሰበር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 33470

ጎንደር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ እጅጋየሁ ታደሰ - ቀረበች

ተጠሪ፡- መገርሳ ጉደታ - ከጠበቃ ሻለቃ ሃይሉ ቦረና ጋር ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሽርክና ውልን መሰረት ያደረገ የንብረት እና የገንዘብ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ናት፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተችውም በሞት የተለየው ባልዋ እና ተጠሪ በጋራ አቋቁመው ሲሰሩበት ከነበረው ጋራዥ ከተገኘው ገቢ ድርሻዋን እንዲከፍላት ወይም የጋራዡን ግማሽ እንዲሰጣት በመጠየቅ ነው ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ጋራዡ የግሉ እንደሆነ፣ከአመልካች ባል ጋር አድርገውት የነበረው ውል የሽርክና ሳይሆን የደባልነት እንደሆነ በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ ክሱን የሰማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ እና በአመልካች ባል መካከል የተደረገ የሽርክና ውል የለም በማለት ወስኖ የነበረ ቢሆንም፣ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሽርክና ውል መኖሩን በማረጋገጥና በመወሰኑ በጉዳዩ ስረ- ነገር ላይ ክርክሩ ቀጥሎአል፡፡ በመጨረሻም የእሽሙር ሽርክና ውል ተደርጐ ነበር ቢባልም፣በአመልካች ባል ሞት ምክንያት ፈርሶአል፡፡ የሽርክና ውሉ ተዋዋዮቹ ይዘውት የመጡትን ንብረት እንጂ ጋራዡን አይመለከትም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ፍ/ቤቱ አመልካች ያቀረበችውን የገቢና የጋራዥ ድርሻ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበበት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ብለዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የሽርክና ውል አለ እየተባለ የአመልካች የገንዘብ ክፍያ እና የንብረት ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በተጠሪ እና በአመልካች ባል መካከል የእሽሙር የሽርክና ውል እንደነበር በፍ/ቤት ተረጋግጦ የተወሰነ በመሆኑ ይህን በተመለከተ በአሁኑ ደረጃ የሚባል ነገር የለም፡፡ በዚህ ደረጃ ሊወሰን የሚገባው ነጥብ የዚህ ውጤት ምንድነው የሚለው ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሳኔው እንደገለፀው ተዋዋዮቹ ውሉን ሲያደርጉ በየግላቸው የነበሩዋቸውን መሣሪያዎች ይዘው መግባታቸውን በውሉ ላይ በግልጽ በማስፈር ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም የጋራዡን ንግድ ሥራ በጋራ ለማቋቋም ውል አላደረጉም፡፡ በየግላቸው የነበሩዋቸውን መሣሪዎች በመያዝ ሥራ የሚሰሩበት ጋራዥ በተጠሪ ይዞታ ስር እንደሆነና የሚታወሰውም በሱ ስም ብቻ እንደሆነም አላከራከረም፡፡ በንግድ ሕግ ቁ.271 እንደተመለከተው የእሽሙር ማህበር ማህበርተኞቹ እንደፈቃዳቸው የውላቸውን ሁኔታዎች ወስነው የሚያቋቁሙት እንደመሆኑ በተያዘው ጉዳይም ተዋዋዮቹ በሚያመቻቸው መንገድ ወስነው እንዳቋቋሙት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በንግድ ሕግ ቁጥር 273 እንደተደነገገው ደግሞ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር እያንዳንዱ ማህበርተኛ ገቢ ላደረገው መዋጮ ባለሃብትነቱን እንደያዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው የሚቆየው፡፡ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እንደሚታየው ውሉ ከተደረገ በኋላ በጋራ የተገዛ ንብረት ወይም የተደረገ መዋጮ የለም፡፡ ይልቁንም የጋራኘ ንግዱ በተጠሪ ስም ብቻ እንደተመዘገበ ነው የቀጠለው፡፡ የንግድ ፈቃዱም በተጠሪ ስም ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች ባለቤት የጋራገፍም የጋራ ባለሃብት ነው የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች በጋራገፍ ላይ የጋራ ባለሐብትነት መብት እንዳለ በመቁጠር ያቀረበችው ክርክር በስር ፍ/ቤቶች ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡

ቀጥለን የተመለከትነው ሌላው ነጥብ ሚች እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ያለውን የትርፍ ክፍያ እና የሽርክና ውሉ በተደረገበት ጊዜ ይዘዋቸው መጣ የተባሉትን መሣሪያዎች በሚመለከት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የውሳኔውን ክፍል ነው፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበችው አቤቱታ ጭምር እነዚህን ነጥቦች በማንሳት ተከራክራለች፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ እንደተመለከተው አመልካች በትርፉም ሆነ በመሣሪያዎቹ ላይ መብት እንዳላት ግንዛቤ ተወስዶአል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን በጠየቀችው ዳኝነት መሰረት ይህ ይገባሻል ወይም አይገባሽም የሚል ውሳኔ አልተሰጠም፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ ሊታረም የሚገባው ስህተት እንዳለ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ስህተቱ ይስተካከልም ዘንድ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05140 ሰኔ 26 ቀን 1998 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48762 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካች ከባለቤትዋ ሞት በኋላ ያለውን ትርፍ እንድትካፈል ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ ጋራገፍን ግማሽ ልካፈል በማለት ያቀረበችውም እንደዚሁ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. የሽርክና ውሉ በሚች ምክንያት እስከፈረሰበት ቀን ድረስ ለነበረው ጊዜ የተገኘ ትርፍ ካለ አመልካች የመካፈል መብት አላት፡፡ ሚች ለሽርክና ማህበሩ በመዋጮነት ገቢ ያደረጋቸው መሣሪያዎች ካሉም ሊመለሱላት ይገባል፡፡ ተጠሪ በእነዚህ መሣሪያዎች በመጠቀም ያገኘው ገቢ ካለም እንደዚሁ ተጣርቶ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል፡፡ ስለዚህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩ በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በእነዚህ ሦስት ነጥቦች ግራ ቀኝ ወገኖችን ካከራከረ በኋላ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መቁ 34945

ህዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ፡- ወ/ሮ መስታወት በላቸው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ፡- አቶ ለገሠ ሣህሉ - ጠ/መከተ ዳኜ ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍሉ ጉዳይ በቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ሲታይ ቆይቶ ጉባኤው በ06/21/1998 ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ ይህንኑ ውሣኔ እንዲያጸድቅላቸው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ሲያመለክቱ አመልካች ግን ጉባኤው ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት መሠረታዊ የህግ ግንዛቤ የሌለው በመሆኑ የተሠጠውም ከፊል ውሣኔ ከጉባኤው ስልጣን ውጪ በመሆኑና የህግ ስህተቶችም ስላሉበት ጉዳዩን ፍ/ቤቱ ተረክቦ ውሣኔ ይስጥበት በማለት አስተያየታቸውን ሠጥተዋል፡፡ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ግን የአመልካችን መቃወሚያና ክርክር ወድቅ አድርጎ ውሣኔውን በማጽናት የጋራ ናቸው ተብለው ውሣኔ የተሠጠባቸው ንብረቶችን ከተስማሙ በአይነት እንዲካፈሉ ካልተቻለ አንደኛው ለሌለኛው ልዩነቱን እንዲከፍል በማድረግ እንዲካፈሉ በዚህ ካልተስማሙ ንብረቶቹ በሐራጅ ተሸጠው ገንዘቡን እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው አመልካች ለተጠሪ ብድር ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺህ)ስለከፈልኩ ግማሹን ተጠሪ ይክፈሉ በማለት አቅርበውት የነበረውን የዳኝነት ጥያቄ ጉባኤው ሣይቀበል እንዲሁም አመልካች ለተጠሪ የዚህን ገንዘብ ግማሽ እንዲከፍሉ በማለት የሠጠውን ውሣኔ ብቻ በመሻር የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ የረር ሃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር የራሱ የህግ ሠውነት ያለው በስሙ መክሠስና መክሠስ የሚችል ድርጅት መሆኑ እየታወቀ እንዲካፈሉት መወሠኑ ለተጠሪ የግል ዕዳ ከጋራ ገንዘብ የተከፈለ ገንዘብ ለመሆኑ ምስክር ሣይሠማ ጥያቄው ውድቅ መደረጉ እንዲሁም ሌሎች የቤት ቁሣቁሶች በተመለከተ ማስረጃ ሣይሰማ መወሠኑ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎታም የአመልካች አቤቱታ በሠበር ችሎት ሊጣራ የሚገባው መሆኑን በማመን ተጠሪ ቀርበው እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ስህተት ተፈጽሞበታል ከተባለው ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

በዚህ መሠረት ራሱን ችሎ የህግ ሠውነት ያለው ድርጅት በቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ እንዲከፋፈል መወሠኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም ማስረጃ ሣይሠማ ውሣኔ ተሠጥቶበታል የተባለው የንብረት ክፍፍል አግባብ መሆን አለመሆኑን ችሎቱ መርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የረር ኃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር በንግድ ህጉ መሠረት የተቋቋመ እና የህግ ሠውነት ያለው መሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም፡፡ የንግድ ማህበሮች የሚቋቋሙበት እና የሚፈርሱበት ሁኔታ ደግሞ በንግድ ህጉ ውስጥ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የተወሠነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር ሊፈርስ የሚችልበት ምክንያቶች በንግድ ህግ ቁጥር 542 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህ የንግድ ህጉ ድንጋጌ ሥር የተመለከቱት ምክንያቶች ሲኖሩ ማህበሩ በፍ/ቤት አማካኝነት ይፈርሣል፡፡ ከዚህ ውጪ የንግድ ማህበሩ አባላት የህጉን ሥርዓት ሣይከተሉ በራሣቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም በሌላ አካል አማካኝነት ሊፈርስ የሚችልበት የህግ መሠረት የለም፡፡ በፍ/ቤት አማካኝነት ከፈረሠና ሂሣቡ ተጣርቶ የመጨረሻው ውጤት በሂሣብ አጣሪዎች ከታወቀ በኋላ ማህበሩ ከንግድ መዝገብ ተሠርዞ በህግ የተሠጠው መብቱ ቀሪ የሚሆንበትን ሥርዓት የንግድ ህጉ አስቀምጧል ሃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር የህግ ሠውነት ያለውና በራሱ ስም ህጋዊ ተግባራትን ሊፈፅም የሚችል ሊከስና ሊከሠስ የሚችል በመሆኑ የሠራቸው ህጋዊ ተግባራትም የተለያዩ ውጤቶች የሚያስከትሉ በመሆኑም ህጉ በተለየ ሁኔታ እንዲስተናገዱ አድርጓል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን የማህበሩ ብቸኛ የአክስዩን ባለድርሻ ባልና ሚስቱ ቢሆኑ እንኳን እንደሌላ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ማህበሩን በዓይነት የሚካፈሉት ወይም በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡን ሊከፋፈሉ የሚችሉበት የህግ መሠረት የለም፡፡ ስለሆነም የሽምግልና ጉባኤው እንደሌላ ንብረት ማህበሩን እንዲከፋፈሉ የሠጠው ውሣኔ የንግድ ህጉን ያላገናዘበ ነው፡፡

የቀረውን ነጥብ በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የመኖሪያና የጅምናዝየም ዕቃዎች ከቤቶቹ ጋር አብረው የተሸጡ መሆኑ በአግባቡ ሣይጣራ ተወስኖብኛል ያሉ ሲሆንም ከሽምግልና ጉባኤው ውሣኔ ቤቶቹ መሸጣቸውን የሚያረጋግጠው የፁሁፍ ማስረጃ ከቤቶቹ ጋር የቤትና የጅምናዝየም ዕቃዎች አብረው መሸጣቸውን የማያመለክት በመሆኑ በቂ ማስረጃም ያልቀረበበት መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ መስጠቱን ተመልክተናል፡፡

በሌላ በኩል ግን አመልካች እነዚህ የቤት እቃዎችና የጅምናዝየም ዕቃዎች ቤቱን የገዙት ግለሠብ ከቤቱ ጋር አብረው የገዟቸው ስለመሆናቸው ቀርበው እንዲመሠክሩላቸው በማስረጃነት የቆጠሯቸው መሆኑን ከሽምግልና ጉባኤ ውሣኔ ላይ ተገንዝበናል፡፡ እነዚህ ንብረቶች የሚንቀሣቀሱ ንብረቶች በመሆናቸው የንብረቶቹ ሽያጭ የግድ በፁሁፍ መደረግ ያለበት መሆኑ ወይም ንብረቶቹ ለመሸጣቸው ሊረጋገጥ የሚገባው በፁሁፍ /በሠነድ ማስረጃ/ ብቻ ለመሆኑ በህግ ተለይቶ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ በህግ በተለይ ሁኔታ እንዲረጋገጥ ካልተመለከተ በቀር አንድን ጉዳይ በማንኛውም አይነት ማስረጃ ማረጋገጥ እንደሚቻል ከፍ/ብ/ህ/ቁ.2002 እና 1677(1) መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የቤትና የጅምናዝየም እቃዎቹ ስለመሸጣቸው በሰው ምስክር ለማስረዳት እየጠየቁ ጉባኤው በቤት ሽያጭ ውሉ ላይ እነዚህ ንብረቶች ስለመሸጣቸው አልተገለፀም በማለት ክርክርራቸውን ውድቅ ማድረጉ የአመልካችን የመከላከል መሠረታዊ መብት የማያጣብብ ሆኖ አግኝተዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የረር ሃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር እና የቤትና የጅምናዝየም ዕቃዎችን በተመለከተ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሚያዝያ 22/1999 ዓ.ም. በመ/ቁ 55299 የሠጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ህዳር 12/2000 ዓ.ም. በመ/ቁ 55333 የሠጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. የረር ኃ/የተ/የግ/ማ በንግድ ህጉ በተመለከተው መሠረት የሚፈርስና ሂሣቡ የሚጣራ ካልሆነ በቀር እንደሌሎቹ የባልና ሚስት የጋራ ንብረቶች ተገቢዎቹ በዓይነት የሚካፈሉት ወይም ተሸጦ ገንዘቡን የሚካፈሉት ንብረት አይደለም ብለናል፡፡
3. የቤትና የጅምናዝየም ዕቃዎችን በተመለከተ አመልካች በማስረጃነት የቆጠሯቸው ምስክር ቀርበው ከተሠሙ በኋላ ተገቢው ውሣኔ እንዲሠጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 (1) መሠረት ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡
4. ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 31264

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 5 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ እመቤት መኮንን- ጠበቃ ነቃጥበብ በየነ፡፡

ተጠሪ፡- ወረዳ 20 ቀ. 29 አ/ጽ/ቤት ነ/ፈጅ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪና በሥር ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሾች ላይ ባቀረቡት ክስ በወረዳ 20 ቀበሌ 29 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 449 የሆነውን ቤት ከቀበሌው አስተዳደር አንደኛ ተከሣሽ ላይ ተከራይቼ በቤቱ የሆቴል የንግድ ድርጅት በማቋቋም ስጠቀምበት የነበረ ሲሆን ይህንኑ የንግድ ድርጅት ለማስፋፋት ከቤቱ ፊት ለፊት በነበረው 67 ካሬ ሜትር ባዶ ቦታ ላይ ግንባታ ፈጽሜ የድርጅቱ አካል አድርጋ ለመጠቀም ለቀበሌው ጥያቄ አቅርቤ ተፈቅዶልኝ ብር 300,000(ሦስት መቶ ሺህ) ወጭ አድርጌ ገንብቻለሁ፡፡ ከዚህ በኋላም ለሁለተኛ ተከሣሽ /ለአሁን ተጠሪ/ እና ለሦስተኛ ተከሣሽ አውራሽ ወ/ሮ የሻሐረግ ገዳሙ የሆቴል ንግድ ድርጅቱን ከሙሉ የሆቴል ቤት መገልገያዎች ጋር በ3/10/87 ዓ/ም በተደረገ ውል ያከራየሁ ሲሆን ነገር ግን የውሉ ማለቂያ ቀን በሆነው በ2/10/89 ዓ/ም ተከራይ ወ/ሮ የሻረግ ገዳሙ ለከሣሽ መመለስ ሲገባት ከአንደኛ ተከሣሽ ጋር በመተባበር ከሐምሌ ወር 1998 ዓ/ም ጀምሮ ድርጅቱን ቀበሌው ወርሶታል ከዚህ በኋላ የድርጅቱ ሕጋዊ ተከራይ ወ/ሮ የሻረግ ገዳሙ ነች በማለት ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆኑ ስለሆነ ይህንኑ ድርጅት ሶስቱም ተከሣሾች በአንድነትና በነጠላ ለከሣሽ እንዲያስረክቡ ከሣሽ ማግኘት የሚገባኝን የተቋረጠ ኪራይ በድምሩ ብር 342,000 (ሦስት መቶ አርባ ሁለት ሺህ) በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ፡፡

የድርጅቱን ግንባታ ለማከናወን ወጭ ያደረግሁትንም ብር 300,000(ሦስት መቶ ሺህ) በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ እንደዚሁም የወ/ሮ የሻረግ ገዳሙ ወራሾች የሆኑት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሾች በኪራይ ውሉ ላይ የተመለከተውን ብር 4000(አራት ሺህ) የገደብ መቀጫ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሾችም በየበኩላቸው የመከላከያ መልስ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ የክርክር ነጥባቸውም በከሣሽና በቀበሌው አስተዳደር መካከል ተደርጎ የነበረው የኪራይ ውል መንግስት ባወጣው የተከራይ አከራይ መመሪያ መሠረት ተቋርጦ በአንደኛ ተከሣሽና በወ/ሮ የሻረግ ገዳሙ መካከል የኪራይ ውል የተደረገ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ለክሱ መነሻ የሆነውን የንግድ ቤት አንደኛ ተከሣሽ የቀበሌው አስተዳደር ለከሣሽ ማከራየቱን ያልካደ ሲሆን ውሉን ለማቋረጥ ያቀረበው ምክንያት ከሣሽ የቤቱን ኪራይ በወቅቱ ስትከፍል ያልነበረች ከመሆኑም በላይ ለሌላ ሰውም አሳልፋ አከራይታለች በማለት ሲሆን ነገር ግን ይህ ሁኔታ ውሉን በአንድ ወገን በእራሱ ሥልጣን ለማቋረጥ እንደሚያስችለው ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ ስለሌለ በመካከላቸው የነበረው ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው ካለ በኋላ በከሣሽና በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሾች አውራሽ በወ/ሮ የሻረግ ገዳሙ መካከል የተደረገው ውል ጊዜው ያላለቀ ስለሆነ ይህንኑ የንግድ ድርጅት ሦስቱም ተከሣሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለከሣሽ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኪራይ ክፍያ ጥያቄውን በተመለከተም ከሳሽ ከድርጅቱ ኪራይ ያጣቸው ብር 54,000(ሃምሳ አራት ሺህ) ስለሆነ ይህንኑ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ተከሣሾች ለከሣሽ እንዲከፍሉ የንግድ ቤቱን ለማስፋፋት ለግንባታ ወጭ ሆኗል የተባለውና ከሣሽ እንዲተካላቸው የጠየቁት የብር 300,000(ሦስት መቶ ሺህ) ክፍያ በተመለከተ በንግድ ቤቱ ላይ ከተከራይነት ያለፈ መብት እንዳላት ከሣሽ ያላስረዳች ስለሆነ የክፍያ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ የሥር አንደኛ ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ይግባኙን መርምሮ መ/ሰጪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሮ መልስ ሰጭ ልከራየው የምትለው ቤት ንብረትነቱ የቀበሌው አስተዳደር /የይግባኝ ባይ/ ሲሆን ንብረቱ በመሆኑም ከመልስ ሰጭዋ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል በመተው ለሌላ ሰው አከራይቶታል፡፡ በእርግጥ ቤቱ የንግድ ሥራ የሚሰራበት በመሆኑ መልስ ሰጭ የይግባኝ ባይን ፈቃድ ሣትጠይቅ በኪራይ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ እንደምትችል በንግድ ሕግ ቁጠር 145/1/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን ይህ ድንጋጌ የቤቱ ባለሀብት የሆነውን ይግባኝ ባይን ከመልስ ሰጭ ጋር አድርጉት የነበረውን የኪራይ ውል እንዳያቋርጥ የሚያግደው ነው በሚል የሚተረጉም እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡ ይግባኝ ባይ ከፈቃዱ ውጭ ከማይፈልገው ሰው ጋር የኪራይ ውል አድርግ የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ባይ ቤቱን ለመልስ ሰጭ አስረክብ ኪራይም ክፈል መባሉ ትክክል አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔውን ሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ ከማይፈልገው ሰው ጋር የኪራይ ውል አድርግ የሚባልበት ምክንያት የለም ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ አግባብነቱ ከንግድ ሕግ ቁጥር 145 አንፃር ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን በቃል አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ በወረዳ 20 ቀበሌ 29 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 449 የሆነውን ቤት ለአመልካች እንዳከራየና አመልካችም በቤቱ የሆቴል ንግድ ድርጅት በማቋቋም ሲሰሩ እንደነበር ከተጠሪ ባገኙት ፈቃድ መሠረትም የሆቴል ድርጅቱን አስፋፍተው እንዲሰሩና በኋላም ይህንኑ የሆቴል ድርጅት ለሥር ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሾች አውራሽ ለወ/ሮ የሻሐረግ ገዳሙ በ3/10/87 ዓ/ም በተደረገ የንግድ መደብር ኪራይ ውል እንዳከራዩ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪ ከአመልካች ጋር አድርጉት የነበረውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ በምክንያትነት የጠቀሰው አመልካች የቤቱን ኪራይ በወቅቱ አትከፍልም ነበር፡፡ ቤቱንም ለሌላ ሰው አሳልፋ አከራይታለች በማለት ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ መልኩ የቀረበውን የተጠሪን ክርክር ሳይቀበለው የቀረው ይህ ድርጊት በከሣሽ /በአሁን አመልካች/ ተፈጽሟል ቢባል በዚህ ድርጊት መነሻነት ውሉን በአንድ ወገን በእራሱ ሥልጣን ለማቋረጥ ከውሉ ወይም ከሕግ የመነጨ መብት ያለው ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ከሣሽ ውሉን የጣሰ ድርጊት ፈጽማለች ቢባል እንኳን ተከሣሽ በሕጉ አግባብ መብቱን ማስከበር ከሚችል በስተቀር በእራሱ ሥልጣን ውሉን ለማቋረጥ በሕግ የተሰጠው መብት የለም በማለት ሲሆን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረውን ውል በማቋረጥ ከሌላ ሰው ጋር የተዋዋለ ስለሆነና ሁለተኛውን ውል አቋርጦ ከአመልካች ጋር እንዲዋዋል ሊገደድ የማይችል ከመሆኑም በላይ ቤቱ የንግድ ሥራ የሚሰራበት በመሆኑ አመልካች የተጠሪን ፈቃድ ሣታገኝ በኪራይ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ እንደምትችል በንግድ ሕግ ቁጥር 145/1/ ላይ የተደነገገ ቢሆንም ይህ ድንጋጌ የቤቱ ባለቤት የሆነውን ተጠሪን ከአመልካች ጋር አድርጉት የነበረውን የኪራይ ውል እንዳያቋርጥ የሚያግደው ባለመሆኑ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክብና ኪራይም ክፈል መባሉ ተገቢነት የለውም በሚል ነው፡፡

በበኩላችንም ጉዳዩን አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነውም ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ከተጠሪ የተከራዩትን የንግድ ቤት አሳልፈው ለሦስተኛ ወገን በማከራየታቸው ተጠሪ ውሉን በማቋረጥ ከውል ወይንም ከሕግ የመነጨ መብት አለው ወይንስ የለውም? የሚለው በመሆኑ ከዚህ ጭብጥ አኳያ የሰበር አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የንግድ ሕግ ቁጥር 145/1/ ላይ የንግድ መደብርን የተከራየ ወገን ይህንኑ የንግድ መደብር 3ኛ ወገንን የተከራይ ተከራይ አድርጉ ማስተላለፍ እንደሚችል ይህንንም ሲያደርግ የንግድ መደብሩን ባለቤት ፈቃድ እንደማያስፈልገውና የንግድ መደብሩን ለ3ኛ ወገን አሳልፎ ለማከራየት የባለቤቱ ፈቃድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያስፈልጋል የሚል የውል ቃል ቢኖርም እንኳን የዚህ አይነት የውል ቃል/term/ፈራሽና? ዋጋ እንደሌለው እንደዚሁም የማይንቀሣቀስ ንብረትን ለ3ኛ ወገን አሳልፎ ለማከራየት የባለቤቱ ፈቃድ አስፈላጊ እንደሆነ በውል ሊወሰን ይችላል ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2959 ላይ የተደነገገው ለንግድ መደብር ኪራይ ተፈጻሚነት እንደሌለው ተደንግጐ እናገኛለን፡፡

ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለውም የንግድ መደብር የተከራየ ሰው የንግድ መደብሩን ለሌላ 3ኛ ወገን አሳልፎ ላለማከራየት ከንግድ መደብሩ ባለቤት ጋር የውል ግዴታ ቢገባም እንኳን የዚህ ዓይነቱ ስምምነት ውጤት እንደሌለው ስለሚቆጠር አሳልፎ ማከራየት እንደሚችልና የንግድ መደብሩ ባለቤት ይህ ተግባር በመፈጸሙ ምክንያት ውሉን ማቋረጥ እንደማይችል ሲሆን ነገር ግን የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይህ ድንጋጌ የቤቱ ባለቤት የሆነውን ወገን ውሉን ከማቋረጥ አያግደውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ለድንጋጌው የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ለክርክሩ ምክንያት በሆነው የንግድ ቤት ላይ አድርጐት የነበረውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ ከውልም ሆነ ከሕግ የመነጨ መብት እንደሌለው መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪና የሥር ተከሣሾች የንግድ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ አመልካችም ከንግድ ድርጅቱ ያጡትን ኪራይም እንዲከፍሉ በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት ያለው ሆኖ ሳለ ነገር ግን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ከላይ በተመለከተው አኳኋን ይህንኑ ውሣኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27048 ሚያዝያ 19 ቀን 1999 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 15978 ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ ፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ ፊርማ የአምስት ዳኞች አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34586

ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ያለው ድልነሳው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ - አልቀረቡም ከተባለበኋላ ቀረቡ

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ ቀረቡ

3. ወረዳ 22 ቀበሌ 04 አስተዳደር - አልቀረበም

4. አቶ ወሰን ፀጋ - ተቋርጧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአንደኛ ተጠሪ ክሳሽነትና ከሁለተ እስከ አራት በተጠቀሱት ተጠሪዎች ተከሳሽነት የነበረውን ክርክር መርምሮ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አንደኛ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሁለት እስከ አራት በተጠቀሱት ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ቤት መንግሥት ስለ ንግድ ቤቶች መግለጫ ካወጣም በኋላ በስሜ ውል ተዋውዬ ባለሁበት ሁኔታ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከአራተኛ ተጠሪ ጋር በውል ላይ ውል በማድረግ የንግድ ቤቱን አሳልፈው የሰጡ ስለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሳሽ ንግድ ቤቶችን አስመልክቶ መንግሥት መመሪያ ካወጣ በኋላ በስማቸው ተከራይተው በይዞታቸውም ሥር አድርገው በንግድ ቤቱ ሲጠቀሙበት የነበረ ስለሆነና ተከሳሾች መመሪያው ከወጣ በኋላ ከከሳሽ ጋር የተደረው ውል በስህተት እንደተደረገ ከማንሳት ውጭ ውሉ የጸና ሊሆን እንደማይችል ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ ስለሌለ በዚህ ሁኔታ በተከሳሾች የተፈጸመው ድርጊት በሕግ የተፈቀደ መብትን ተከትሎ የተፈጸመ ባለመሆኑ አድራጎቱ ከሁከት ስለሚፈረጅ ባለይዞታ ለሆኑት ለከሳሽ ቤቱ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች በወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 የተመዘገበውን የንግድ መደብር የካቲት 16 ቀን 1992 ዓ.ም በንግድ ቤቱ ላይ እዳና እገዳ እንደሌለበት አጣርቼ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ከሦስተኛ ተከሳሽ /ከአሁን ሦስተኛ ተጠሪ/ ላይ ገዝቼ ሽያጩም ሕጋዊ መሆኑ በቀበሌው አተዳደር በኩል ታምኖበት የኪራይ ውሉ በስሜ ተዛውሮ ኪራይ የምከፍል ከመሆኑም በላይ የንግድ ፈቃድም አውጥቼ በመስራት ላይ እንዳለሁ የንግድ ቤቱን አስቀድሞ በተሰጠ ፍርድ መነሻነት ለከሳሽ ለአሁን አንደኛ ተጠሪ እንዳስረክብ የተገደድኩ ስለሆነ ይሄው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት ይሰረዝልኝ በማለት አመልክተው ፍ/ቤቱም ውሳኔ ከሳሽና ተከሳሾች የነበሩት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጥራት ካከራከረ በኋላ በቀድሞው ውሳኔ ክርክር ያስነሳው የንግድ ቤት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስለ ንግድ ቤቶች መግለጫ ከማውጣቱ በፊትም ሆነ በኋላ ከአንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሾች ተከራይተው ይጠቀሙበት እንደነበርና ይዞታቸው እንደሆነ የተረጋገጠ ከመሆኑም ሌላ ከሳሽ መመሪያው ከወጣ በኋላ ከአንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሾች ጋር ያደረጉት ውል ፈራሽ ነው ሳይባል ከሦስተኛ ተከሳሽ ጋር ያደረጉት ውል መብትና ግዴታን ሊያቋቁም እንደማይችል ስለተወሰነና ከዚህም ውሳኔ ሦስተኛ ተከሳሽ አንዳችም መብት እንደሌላቸው መገንዘብ ስለሚቻል የመቃወም አመልካችም የንግድ ቤቱን ገዛሁ የሚሉት መብት ከሌላቸው ከሦስተኛ ተከሳሽ ላይ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ የቀድሞው ውሳኔ ይሰረዝልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይሄው ውሳኔም የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጉድለት የለውም ተብሎ እስከ አዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ እንደፀና ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ለዚህ ችሎት የቀረበውም የሰበር አቤቱታ ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በየደረጃው የሚገኙ የሥር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉ የቀሩበት ምክንያት ተጠሪዎች ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍ አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ፡፡

አመልካች ባቀረቡት መቃወሚያ መነሻነት አስቀድሞ የተሰጠው ፍርድ ሊሰረዝ ይገባል ወይንስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ጭብጥ አኳያም የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አንድ ፍርድ በአንድ ፍ/ቤት ከተሰጠ በኋላ ይሄው ፍርድ በዚያው ፍ/ቤት በድጋሚ ከሚታይባቸው ሥርዓቶች መካከል አንዱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 መሠረት መቃወሚያ በሚቀርብበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረትም በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንደዚሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማንኛም ሰው ተካፋይ ባልሆነበት የተሰጠው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ማቅረብ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበትንና ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ቤት አመልካች በስማቸው የንግድ ፈቃድ አውጥተው ሲሰሩበት ከነበረው የሥር ሦስተኛ ተከሳሽ የአሁን አራተኛ ተጠሪ ላይ የካቲት 16 ቀን 1992 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ስለመግዛታቸውና በኋላም የኪራይ ውሉን በስማቸው በማዛወርና የንግድ ፈቃድም በስማቸው በማውጣት የንግድ ሥራ ሲሰሩበት እንደነበር ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ የቀድሞው ውሳኔም መብቱን የነካ ስለሆነ ሊሰረዝ /Set aside/ ይገባል በማለት መቃወሚያ ያቀረቡትም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች መቃወሚያ ሳይቀበሉት የቀሩት ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የኪራይ ውል ቀሪ ባልሆነበት ሁኔታ ሌላ ውል ከአራተኛ ተጠሪ ጋር መደረጉ ተገቢነት የሌለውና ውጤትም ሊኖረው ስለማይችል በዚሁ ውጤት በሌላው ውል ላይ ተመስርቶ በአራተኛ ተጠሪና በመልካች መካከል የተቋቋመው የንግድ መደብር ሽያጭ ውል የመብትም ሆነ የግዴታ ምንጭ ስለማይሆን መቃወሚያው ተገቢነት የለውም በማለት ነው፡፡

ይሁንና አመልካች ይህንኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ መደብር ከአራተኛ ተጠሪ ሲገዙ ከላይ እንደተጠቀሰው አራተኛ ተጠሪ ንግድ መደብሩን በስማቸው ባደረጉት ውል ይዘውት እንደሚገኙ እንደዚሁም በስማቸው የንግድ ፈቃድ በማውጣት እየሰሩ እንደሚገኙ በማረጋገጥ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ የሸያጩን ውል ከአራትኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉ እንደመሆኑ መጠን ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች አስቀድሞ ከአራተኛ ተጠሪ ጋር ያደጉት የኪራይ ውል ተገቢነት የሌለው ነው ቢባል እንኳን አመልካች ውሉን በቅን ልቦና ያደረጉት በመሆኑ ሕጉ ለቅን ልቦና ተዋዋዩች ከሰጠው ጥበቃ አኳያ ጉዳዩ የማይታይበት ምክንያት አይኖርም በዚህም መሠረት የቅን ልቦና ባለይዞታነትን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ባለሀብት ለመሆን በቅን ልቦና ዋጋ ሠጥቶ ውል የተዋዋለ ሰው የተባለውን ተንቀሳቃሽ ነገር በእጁ ሲያደርግ በቅን ልቦናው ምክንያት የዚህ ንብረት ባለሀብት እንደሚሆን ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የንግድ መደብር ግዙፍነት ባይኖርም ነገር ግን ግዙፍነት የሌለው ተንቀሳቃሽ ንብረት /Incorporeal

https://t.me/ethiopianlegalbrief

movable/ እንደሆነ የንግድ ሕግ ቁጥር 124 ላይ ስለተመለከተ ስለቅን ልቦና ባለይዞታነት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡

አመልካች ይህንኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ መደብር ይዘው የሚገኙት በቅንልቦና በተደረገ ውል መነሻነት ነው ከተባለ አስቀድሞ አንደኛ ተጠሪ ከሁለት እስከ አራት በተጠቀሱት ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት የንግድ መደብሩን ለከሳሽ ለአንደኛ ተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ አመልካች በክርክሩ ተካፋይ ባልሆኑበት መብታቸውን የነካ ውሳኔ አንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በመሆኑም አመልካች የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 በሚፈቅደው መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 አኳያ ታይቶ አስቀድሞ የተሰጠውና የአመልካችን መብት የነካው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት መሰረዝ ሲገባው ከአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እስከ አዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ አቤቱታው ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመቁ 2901/91 ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ.ቁ 414/93 እንደዚሁም ሰበር ሰሚው ችሎት በመ/ቁ 01424 በ20/3/2000 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348 (1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 2901/91 የሰጠው ውሳኔ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ መብታቸው የነካ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት ተሰርዟል፡፡
3. አመልካች በወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ መደብር ከአራተኛ ተጠሪ ላይ የገዙት በቅንልቦና ስለሆነ ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43315

ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ብራንድ ኒው የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል ኃ/የተ/የግ/ማኅበር ጠበቃ አቶ ቸርነት ወርዶፋ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ መስፍን ታደሰ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሆኖ ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ የክሱ ምክንያት መጋቢት 7 ቀን 2000 ዓ.ም. የሚመነዘር ቼክ ቁጥር ኤኤ 187877 የሆነ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ የያዘ ቼክ ሰጥተውኝ ለክፍያ ባንክ ስቀርብ ሂሣቡ ታግዷል በሚል ምክንያት ቼኩ ሳይከፈል ተመልሷል፡፡ ስለዚህ በቼኩ የተመለከተውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፈል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 286 መሠረት በአጭር ሥነ-ሥርዓት ታይቶ እንዲወሰን በማለት ክስ ቀረበ፡፡

አመልካችም ቼኩ የተሠጠው የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም. ለተደረገው እስክቫተር ሽያጭ ውል ስምምነት መነሻ ሆኖ ከሽያጩ ገንዘብ ውስጥ 200,000 ብር በዕለቱ ተከፍሎ ቀሪው 100,000 ብር መጋቢት 12 ቀን 2000 የሚመነዘር ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቼክ መስጠታቸውን በማስመልከት ለመከላከል እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 123416 በሆነው በ12/2/2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ለመከላከል እንዲፈቀድ የቀረበለትን ጥያቄ ባለመቀበል ክስ የቀረበበትን በቼኩ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 74146 በ26/5/2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎች ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ፍ/ቤትም አመልካች የግል ግንኙነት ያላቸው መሆኑን በመጥቀስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ጥያቄ አቅርቦ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ለሰበር እንዲቀርብ ታዞ መጋቢት 9 ቀን 2001 ዓ.ም. የግራ ቀኙን ክርክር አድምጧል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመዘገበው ሲሆን እኛም ክርክራቸውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 284 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት በአጭር ሁኔታ በሚወሰኑ ክርክሮች ላይ ስለሚፈፀም ሥነ-ሥርዓት በሕጉ የተመለከቱ ሥርዓቶችን መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሠረቱ በአጭር ሥነ-ሥርዓት ዳኝነት ታይቶ እንዲወሰን ክስ የሚቀርብበት ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 285/1/ እንደተመለከተው ከሕጉ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ቁጥር 2 መሠረት ተከሣሽ የሆነው ሰው መጥሪያ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በአሥር ቀናት ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ክሱን ለመከላከል እንዲፈቀድለት ፍ/ቤቱን ፈቃድ እንዲጠይቅ መደረግ እንዳለበት በሕጉ መሠረት ቼኩ የተሠጠበት ምክንያት የኤክስካቬተር ሽያጭ ውል ምክንያት እንደሆነ በመጥቀስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት በቃለ መሐላ የጠየቀ መሆኑን ከክርክሩ መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡ የተጠሪ ዋና ክርክር በቼኩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ ሐተታ ወይም ገደብ የለበትም በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ በሽያጩ ውል ላይ የቼክ ቁጥር ተጠቅሶ ውል የተገባ መሆኑን በመግለጽ የሚከራከር ሲሆን በዚህ ፍ/ቤት የቃል ክርክር ጊዜ ተጠሪም ይህ የውል ግንኙነት በመካከላቸው እንዳላቸው አልካዱም፡፡ በመከላከያ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ላይም ይህ ግንኙነት መኖሩ እስከተገለፀ ድረስ ምንም እንኳን ቼክ እንደ ገንዘብ ለተለያዩ ሰዎች በቀላሉ ሊተላለፍ የሚችል ባሕርይ ያለው የገንዘብ ሰነድ በመሆኑ ቼክ አከፋፈል ላይ ማንኛውም መቃወሚያ ሊቀርብበት እንደማይችል በንግድ ሕጉ የተደነገገ ሲሆን ሕጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር የቼክ ክፍያ በማናቸውም ምክንያት ሊቆምና ሊታገድ የማይችል መሆኑ አካከራካሪ አይደለም፡፡ ነገር ግን በባለ ጉዳዮቹ መካከል ግልጽ የሆኑ ሁኔታዎች ወይም ግንኙነቶች በተፈጠሩ ጊዜ ብቻ ይህን መቃወሚያ ለማድረግ እንደሚቻል በን/ሕ/ቁ. 717/1/ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ይህን መሠረት በማድረግ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ያልተቀበለው የቼክ ክርክር በመሆኑ ብቻ የቼክን ባህርይ መሠረት ለማድረግ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ የፈቃድ ጥያቄ ደረጃ ላይ የቼክ ባሕርይ ሳይሆን መታየት ያለበት አመልካች ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ምክንያት ፈቃድ የሚያሰጥ መሆን አለመሆኑን ነው፡፡ ሌላ የፍሬ ነገር ክርክር ከፈቃድ በኋላ የሚታይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሽያጭ ውል ግንኙነት መሠረት በማድረግ ለመከላከል እንዲፈቀድ ፍ/ቤቱን ለመጠየቅ ሕጋዊ ምክንያት አለው፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ በአጭር ሥነ-ሥርዓት እንዲታይ የሚቀርቡ ክሶች አመራር ሥርዓትን ሳይሆን የተከተለው የቼክ ባሕርይን መሠረት በማድረግ ውሣኔ መደምደሚያ ላይ መድረሱ አግባብ ሆኖ አላገኘንም፡፡ ምክንያቱም ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት በፍ/ቤቱ አግኝቶ የተጠየቀውን ገንዘብ ላለመክፈል በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑ የሚታወቀው ፍ/ቤቱ ከአጭር ሥነ-ሥርዓት ወደ መደበኛ የክርክር ሥነ-ሥርዓት ውስጥ በመግባት ግራ ቀኙን በአግባቡ በማስረጃ ካከራከረ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 123416 ጥቅምት 12 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 74146 ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያለውን መከላከያና ማስረጃ አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በመደበኛ የክርክር ሥርዓት አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341 መሠረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአእምሯዊ ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42253

ሐምሌ 8 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- መምህር ሙሉ ኃይለሥላሴ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዘመናዊ ማተሚያ ቤት ጠበቃ አቶ ዓለሙ ወ/አረጋይ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው መቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱም ተጠሪ መጽሐፍት እንዲያትምልኝ ውል ፈጽሜ በድርጅቱ ሰራተኛ ተሠርቆ በተሸጡት 9 መጽሐፍት ምክንያት ኪሣራ ደርሶብኛልና በአዋጅ ቁጥር 410/96 የተመለከተውን የሞራል ካሣና ሳይሸጡ የቀሩ መጽሐፍት ዋጋ በድምሩ 260,000 /ሁለት መቶ ስድሳ ሺ ብር/ እንዲከፍለኝ የሚል ሲሆን ተጠሪም በሰጠው መልስ ተሰርቋል የተባለው 7 መጽሐፍት እንጂ ሌላውን ለመክፈል አንገደድም ሰረቀ የተባለው ሰው ጣልቃ እንዲገባ ይታዘዝልን ስርቆት ግላዊ ባህርይ በመሆኑ ካሣውን ሊከፍል የሚገባው የሰረቀው ሰው ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱንና ማስረጃውን በማገናዘብ ተሰርቆ ተሸጠ የተባለውን የ9 መጽሐፍት እያንዳንዱን በ20 ብር ግምትና በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34(4) የተመለከተውን የሞራል ካሣ ጭምር 100,180,00 /አንድ መቶ ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ብር/ ለአመልካች ተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ውሣኔውን በአብላጫ ድምፅ በማጽናቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ችሎቱም ተጠሪ ድርጊቱን ሊያውቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት በሌለበት የሞራል ካሣ 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ እንዲከፍል መወሰኑ ስህተት ነው፤ ተሰርቋል የተባለውን የ7 መጽሐፍት ብቻ መሆኑን በማረጋገጥ የ7 መፅሐፍት ዋጋ 140,00 /አንድ መቶ አርባ ብር/ እንዲከፍል በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አመልካች ታህሣሥ 4 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ቅሬታ፡-

ተጠሪው ስርቆቱን ቢያውቅም ባያውቅም በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34/(4) የተመለከተውን አነስተኛ የሞራል ካሣ 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የሚያስቀር አይደለም በማለት ውሣኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡

ይህ ችሎትም የውሳኔውን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዞ መጋቢት 2 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ግራ ቀኙ ቀርበው ክርክርራቸው ተሰምቷል፡፡

ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር በሕግ ረገድ እንደሚከተለው ተመልክቶታል፡፡

የተከራካሪዎቹ ግንኙነት ተጠሪ 5,000(አምስት ሺህ) መጽሐፍት አትሞ ማስረከብ ሲሆን አመልካች ደግሞ ቀሪውን በውል የተመለከተውን ገንዘብ መክፈል ነው፡፡ ከዚህ ግንኙነት አንፃር የግራ ቀኙ ክርክር ሊታይ የሚገባው በውል ነው ወይንስ ከውል ውጪ ነው? የሚለውን ስንመለከተው፡- አንድ ጉዳይ ከውል ውጪ ነው ሊባል የሚችለው አንድ ሰው በራሱ በኩል ምንም የገባው ግዴታ ሳይኖር በራሱ ጥፋት ላደረሰው ጉዳት አላፊ እንደሚሆን ከውል ውጪ የሆኑ የኃላፊነት ምንጮችን ከሚደነግገው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2027 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ ወገኖች ግልጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስምምነት አድርገው የውል ግዴታ ገብተዋል፡፡ ይኸው የውል ግዴታ ከመፈፀሙ በፊት በስምምነቱ ውስጥ የተካተተው መጽሐፍ በተጠሪ ድርጅት ሠራተኛ ተሰርቆ ገበያ ላይ በመዋሉ ምክንያት ግዴታው በተባለው ሁኔታና ጊዜ አለመፈፀም ምክንያት ሆነ ከሚባል በቀር ጉዳዩን የውል ውጪ (extra contractual) አያደርገውም፤ ይልቁንም ውሉ ከሚመለከተው የሕትመት ሥራ አንፃር ውሉ ሳይፈፀም የተወሰኑ መፃሕፍት በሕትመት ሰራተኛ መሠረቅ የውል መጣስ (breach of contract) የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የውል መጣስ ወይም ውሉ በታሰበው አኳኋን አለመፈፀም ጉዳይ የሚታየው በውል ሕግ እንጂ ከውል ውጪ የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ይህን ጉዳይ በየደረጃው ያዩ ፍ/ቤቶች ግዴታውን ከውል የመነጨ ሆኖ እያለ ውሉም ባልተካደበት በድርጅቱ ሰራተኛ በመሰረቁ ብቻ ከውል ውጪ ኃላፊነት ተደርጐ መታየቱ ስህተት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩ ከውል ውጪ መሆኑን ተቀብሎ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34(5) መሠረት ተጠሪው ድርጊቱን ያላወቀ ከሆነ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት የሌለው ከሆነ የሚለውን ትርጉም መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 34(5) የተጠቀሰው “ - - ያላወቀ ከሆነ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት የሌለው ከሆነ - - -” የሚለው የሕጉ ትርጉም መጽሐፍን እንዳለ መሰረቅን የሚመለከት ሳይሆን የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/96 መሠረት ጥበቃ የተደረጉ የአዕምሮ መብቶች ሲጣሱ ማለትም ከመባሐፉ ውስጥ እንደ ቅጅ፣ ማባዛትና ሌሎች ተመሣሣይ ድርጊቶችን ሳያውቅ የጥሰት ተግባር በተፈፀመ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆን እንጂ አሁን በተያዘው ጉዳይ ዓይነት ማተሚያ ቤቱ ሚስጥራዊነቱን ጠብቆ እንዲታተም በተገባው ውል ስምምነት መሠረት አትሞ በመስጠት ሂደት ላይ በማተሚያ ቤቱ ሰራተኛ መጽሐፍት ተራ በሆነ ስርቆት ወጥቶ ቢሸጥ ማተሚያ ቤቱ ሊያውቅ ወይም ማወቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት አለመኖሩን የሚመለከት አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለሕጉ የሰጠው ትርጉም የተሳሳተ ነው፡፡ ተጠሪ ስርቆት ግላዊ ባርይ በመሆኑ መጽሐፍትን የሰረቀው ሰው ካሣውን ሊከፍል ይገባል የሚለውን ክርክር በተመለከተ ሰረቀ የተባለው ሰው ግንኙነቱ በአሰሪነት ከተጠሪ ጋር ነው እንጂ ከአመልካች ጋር አይደለም፡፡ የውል ግንኙነቱ ከተጠሪ ጋር በመሆኑ ይህ ተዋዋይ ወገን እንደውሉ ግዴታውን ያልፈፀመበትን በቂ ምክንያት ካላስረዳና ይህም ምክንያት ከአቅም በላይ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የውሉ አለመፈፀም ከሚያመጣው ኃላፊነት ሊድን እንደማይችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1791(2) ተመልክቷል፡፡ መጽሐፉን የሰረቀው ከውጪ የመጣ ዘራፊ አይደለም፡፡ የድርጅቱ ሰራተኛ በሆኑ የመቆጣጠር ኃላፊነት የተጠሪ ሲሆን ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1792(1) መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይችሉ ኃይል ነው የሚያሰኝ አይደለም፡፡ እንዲያውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1792(2) መሠረት በአዕምሮ ግምት መጽሐፉ ሊሰረቅና ወይም ተደብቆ ሊወጣ ይችላል በሚል ተጠሪው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል ከመሆኑ አንፃር ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ይልቁንም በውሉ አለመፈፀም ምክንያት አመልካች የደረሰበትን የጉዳት ኪሣራ እንዲጠይቀው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1771(1) መብት የሚሰጠው ሲሆን ተጠሪ ምንም ጥፋት ባያደርግ እንኳ በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ ምክንያት ብቻ የጉዳት ኪሣራውን መክፈል እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.791(1) ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ የጉዳት ኪሣራ ከውልም ሆነ ከውል ውጪ ሊከሰት የሚችል ሲሆን ቁሣዊ ጉዳት ብቻ ሣይሆን የህሊና ወይም የሞራል ጉዳትንም የሚጨምር ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1790(2)እና 2090 — 2123 ከተመለከቱ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የመብቱ ባለቤት ከሆነው ከአመልካች ፈቃድ ውጪ የአዕምሮ ሃብቱ የሆነው መጽሐፍት አመልካች ከመረከባቸው በፊት መሠረታዊ የውል ዓላማ ተጥሶ በውል ተቀባይ ድርጅት ሰራተኛ መጽሐፍት ገበያ ላይ መዋላቸው በፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ በሕጉ የመብቱ ባለቤት መብቶች ናቸው የተባሉት ኢኮኖሚያዊና የሞራል መብቶች ሲሆኑ በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 7 የተመለከቱ ኢኮኖሚያዊ መብቶች አንዱ ተጥሶ በተገኘ ጊዜ የሞራል ጉዳት ጥሰት ይኖራል ማለት ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 7 የተመለከቱ ኢኮኖሚያዊ መብቶች እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9 እስከ 19 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥራ አመንጪ ወይም የአንድ ሥራ ባለቤት የሚከተሉትን ለመፈፀም ወይም ሌላ ሰው እንዲፈፅማቸው ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፡፡

   ሀ/ ሥራን የማባዛት፣

   ለ/ ሥራን የመተርጐም፣

   ሐ/ ሥራን የማመሳሰል፣ የማቀናበር ወይም ወደ ሌላ አይነት የመቀየር፣

   መ/ በሽያጭ ወይም በኪራይ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን የማከፋፈል፣

   ሠ/ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ከውጭ ሃገር የማስገባት፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ረ/ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ለሕዝብ የማሣየት፣

ሰ/ ሥራን በይፋ የመከወን፣

ሸ/ ሥራን ብሮድካስት የማድረግ፣

ቀ/ ሥራን በሌላ መንገድ የማሰራጨት፣

እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በፊደል "ረ" የተመለከተው ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጅውን ለህዝብ ማሳየት የሚለው ድንጋጌ በተጠሪ ተጥሷል፡፡ ይኸውም መጸሐፉ ከአመልካቹ ፈቃድ ውጪ ገበያ ላይ ውሎ በሕዝብ መነበቡ ነው፡፡ አንድ ፊልም ከባለቤቱ ፈቃድ ውጪ ኦርጅናሉ ወይም ቅጅው ለሕዝብ ቢታይ የአመንጪው ኢኮኖሚያዊ መብቱ እንደሚጣስ ሁሉ አንድ መጽሐፍም እንዲሁ ከአመልካቹ ፈቃድ ውጪ ገበያ ላይ ውሎ ቢነበብ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጅውን ለሕዝብ ማሳየት (public display of original or copies of the work) የሚለው በሕጉ የተመለከተው የአመልካች መብት ተጥሷል ማለት ነው፡፡ ይህ መብት ተጥሶ የሞራል ጉዳት በደረሰ ጊዜ የካሣው መጠን በአዋጁ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34(4) መሠረት ከ100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የማያንስ የገንዘብ ካሣ ሊከፍል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት በአመልካች ላይ የደረሰውን የህሊና ጉዳት ሞራል ካሣ ተጠሪው በተጠቀሰው አዋጅ መሠረት 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

የከፍተኛ ፍ/ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ እንደተጠቀሰው የግራ ቀኙ ግንኙነት ውል ሆኖ ሳለ ሠራተኛ መጽሐፍ በመሥረቁ ብቻ ከውል ውጪ አድርገው ትርጉም በመስጠት የተመለከቱት በአግባቡ ባይሆንም በውጤት ረገድ ግን በአግባቡ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ድርጊቱን ያላወቀ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት የሌለው ከሆነ የሚለውን ከሕጉ መንፈስ ውጪ የሆነውን ትርጉም መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሣኔ ከፍ ሲል ከተመለከቱት ምክንያቶች አንፃር መሠረታዊ የሕግ ትርጉም ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ከትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 25/99 በ11/3/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ በውጤት ረገድ በአግባቡ ነው ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት በማፅናት አመልካች የሞራል ካሳ 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ እና የሰባት መፃሕፍት ዋጋ ብር 140 /አንድ መቶ አርባ ብር/ በድምሩ 100,140 /አንድ መቶ ሺ አንድ መቶ አርባ ብር/ ይከፈለው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 21214

ህዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1/ አቶ ለማ ኩማ - አልቀረቡም

2/ አቶ አዲሱ ታመነ - አልቀረቡም

3/ አቶ ሺግዛው አስራት - አልቀረቡም

ጉዳዩን ከመረመርን በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የሃረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 00627 ሐምሌ 14/1997 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበትና ይታረምልኝ በሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በሐረሪ ክልል የአሰሪና ሰራተኛ ውሣኔ ቦርድ ሲሆን በዚሁ አካል በተደረገ ክርክር የአሁኑ ተጠሪዎች በከሣሽነት የአሁኑ አመልካች ደግሞ በተከሣሽነት እንዲሁም በሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁኑ አመልካች ይግባኝ ባይ የአሁኑ ተጠሪዎች ደግሞ መልስ ሰጭዎች ነበሩ፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ስር ከሣሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች የካቲት 11/1997 ዓ.ም በተፃፈ ወደ ቦርድ ያቀረቡት ክስ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም በተከሣሽ ድርጅት /የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሃረር ዲስትሪክት/ ውስጥ በቴክኒክ ሠራተኛነት እየሰሩ ያሉ መሆናቸውን ገልፀው ካላቸው አገልግሎትና የትምህርት ደረጃ ጋር በማይመጣጠን ደረጃ 03 ተመድበው እየሰሩ እንደሆነና ተከሣሽ በሚመጥናቸው / በሚገባቸው /ደረጃ/ ግሬድ 06 እንዲመድባቸው ቢጠይቁትም ለመመደብ ፍቃደኛ ባለመሆኑ በቦርድ ውሣኔ እንዲስተካከልላቸው የሚጠይቅ ነው፡፡

ስር ተከሣሹም ክላይ ለቀረበበት ክስ የካቲት 29/1997 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ሰጥቷል፤ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጭብጥ አግባብነት ስለሌለው ዝርዝሩን ማስቀመጥ ሣያስፈልግ ታልፏል፤ ይሁን እንጂ መሠረታዊ ይዘቱ ክርክሩ በአስማሚ አካል ሣይታይ ቦርዱ የማየት ስልጣን እንደሌለው የሚገልጽ ነው፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያከራከረው ቦርድ ሰኔ 03/1997 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ስር ተከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች በዚሁ የቦርድ ውሣኔ ቅሬታ በማሣደር ወደ ሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ.ቁ. 00627 ሐምሌ 14/1997 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በአዋጅ ቁ. 377/1996 ዓንቀጽ 139/1/ለ/ መሠረት የተጠቀሰው ቦርድ የሰጡውን ውሣኔ ተከትሎ ይግባኙን የማየት ስልጣን ለክልል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ማለትም ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንጂ ስልጣኑ የሱ እንዳልሆነ በመግለጽ የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9/2/ መሠረት ውድቅ አድርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አመልካችም ነሐሴ 17/1997 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይዙቱም በሃረሪ ክልል የአሰሪና ሰራተኛ ውሣኔ ቦርድ በቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በአስማሚ አካል ሣይታይ ቦርዱ ጉዳዩን ተቀብሎ በቀጥታ ማከራከር እንደሌለበትና ጉዳዩም በይርጋ ቀሪ እንደሆነ ገልፆ ተከራክሮ እያለ ቦርዱ ሕጉን ሣያገናዝብ በመወሰኑ ተከትሎ የቀረበለትን ይግባኝ የሃረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣኔ አይደለም በማለት ይግባኙን መሠረዝ የለበትም፤ አዋጅ ቁ. 377/1996 ዓንቀጽ 154 እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት ዓንቀጽ 80 መሠረት በማድረግ ሲታይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን ይግባኝ ማስተናገድ የነበረበት ሆኖ እያለ ስልጣኔ አይደለም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው፤ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ቢታዘዙም ሊቀርቡ ባለመቻላቸው ጉዳዩ በሌሉበት እየተካሄደ ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ እየተገለፀ እንደመጣው ሆኖ ይህ ፍርድ ቤትም የሃረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበለትን ይግባኝ የማየት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚል ጭብጥ በመመሥረት ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ ይህ የሥራ ክርክር የተጀመረው በሃረሪ ክልል የአሰሪና ሰራተኛ ወሣኝ ቦርድ ሲሆን ይህ አካል ለቀረበለት ክርክር የመጨረሻ እልባት/ ውሣኔ/ ከሰጠ በኋላ የይግባኝ አቀራረቡ ሥነ-ሥርዓት ምን እንደሚመስል በአዋጅ ቁ. 377/1996 ዓንቀጽ 154/1/ በግልጽ እንደተመለከተው በሕግ በኩል ውሣኔው ተዛብቷል የሚል ወገን ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳለው ነው፤ ቦርድ ያረጋገጣቸው የፍሬ ነገር ክርክሮች በተመለተ ግን የመጨረሻና ክርክር የማይነሣባቸው ነጥቦች በመሆናቸው በአዋጁ ዓንቀጽ 153 ተመልክቷል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ ወቅት መዋቅሩ በእያንዳንዱ ክልል ያልተዘረጋና በዚሁ የፍርድ ቤት የስልጣን እርከን የሚጠቃለሉ ጉዳዮች በክልሎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በስልጣን ደረጃ ተመሣሣይ የሆነው የእያንዳንዱ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ወክሎ /ተክቶ/ ክርክሮችን እያስተናገዱ የሚገኙበት ነው፤ ከዚህ አኳያም የሃረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡለትን ይግባኝ በአዋጅ ቁ.377/1996 ዓንቀጽ 140 እና 154 መሠረት ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው የዓንቀጽ 139/1/ለ/ ይዘት በመውሰድ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የሃረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 00627 ሐምሌ 14/1997 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ተሽሯል፡፡

2/ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የተደረገው ክርክር ከሃረሪ ክልል አሰሪና ሠራተኛ ወሣኝ ቦርድ የጀመረ በመሆኑ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁ. 377/1996 ዓንቀጽ 140 እና 154/1/ መሠረት ተቀብሎ ይግባኙን የማየት ስልጣን አለው፤ ስለሆነም ይግባኙን ተቀብሎ አከራክሮ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት ተመልሶለታል፤ ይፃፍ፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊረማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35391

ኅዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ፈርተውሐል ወ/ጊዮርጊስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አንበሣ ጫማ አ/ማ - ጠበቃ መኮንን ኪዳኔ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጡረታ አዋጅን የተመለከተውን የጡረታ መዋጮ ክፍያን በወቅቱ ገቢ ያለማድረግን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ጥቅምት 24 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ የአሁኑ ተጠሪ የጥር ወር 1992 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ብር 39,974.35(ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት ብር ከሰላሣ አምስት ሣንቲም) ለአመልካች ድርጅት ገቢ ያደረገው ከሦስት ዓመታት በኋላ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም መሆኑን በመግለጽ ለዘገዩበት 2%(ሁለት በመቶ) ተጨማሪ ክፍያ የመክፈል ህጋዊ ግዴታ ያለበት በመሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 ስራ ላይ ከዋለበት ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ ብር 41,573.32(አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሦስት ብር ከሠላሣ ሁለት ሣንቲም)፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ብር 8,474.56(ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ብር ከሃምሣ ስድስት ሣንቲም) በድምሩ ብር 50,047.88 (አምሣ ሺህ አርባ ሰባት ብር ከሰማኒያ ስምንት ሣንቲም) ከነ ህጋዊ ወለድ እና በቂ ወጪና ኪሣራ ጋር ተጠሪ እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነቱ ቀርቦ አዋጁ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ነው፣የክፍያ ጥያቄውም ሁለት ዓመት ያለፈበት በመሆኑ እንደተከፈለ የሚቆጠር ስለመሆኑ የሚሉትን ነጥቦችን በመቃወሚያነት፣ለአመልካች በአዋጅ የተሰጠው ስልጣን ገቢ ባልሆነው የመዋጮ ገንዘብ ላይ ብቻ በመሆኑ እና ተከሳሽም የተጠየቀውን እዳ ስለከፈለ ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ጥያቄ መቅረቡ ከአዋጁ ዓላማ ውጪ መሆኑን የተጠየቀው የጡረታ መዋጮ ተጨማሪ ክፍያ ይመለከተዋል ቢባልም ስሌቱ ተገቢነት የሌለውና በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በፍሬ ነገር መከራከሪያ ነጥብነት በማንሣት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የተጠሪን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን በመመርመር አመልካች የሚጠይቀው መብት በጥር ወር 1992 ዓ.ም እንደመሆኑ መጠን ይህ በ1998 ዓ.ም የተከፈለው እንኳን ቢሆን ከአዋጁ በፊት የተገኘው መብት በአዋጁ መሰረት ሊገዛ ስለማይችል አዋጁ ወደ ኋላ ተመልሶ ተፈፃሚ ሊሆንበት የማይችል ነው በሚል ምክንያት የአመልካችን ክስ ወድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የ1992 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ገቢ የተደረገው ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም መሆኑና ክፍያ የተጠየቀውም አዋጁ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጀምሮ እንጅ ወደ ኋላ አለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ ሕጉ ወደ ኋላ ሂዶ አይሰራም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪ ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ በመልሱ ላይም የአመልካች ጥያቄ የህግ ድጋፍ የሌለው ስለመሆኑ ያሣያሉ ያላቸውን መከራከሪያ ነጥቦች በማንሣት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ ሰኔ 16 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 7/3/ መሰረት የጡረታ መዋጮ ለዘገየበት 2%(ሁለት በመቶ) ተጨማሪ ክፍያ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ድርጅት የጥር ወር 1992 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ብር 39,974.35(ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት ብር ከሰላሣ አምስት ሣንቲም) ለአመልካች ድርጅት ገቢ ያደረገው ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው የአዋጅ ቁጥር 345/95 ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም፣ይሰራል ከተባለም የሁለት ዓመት ጊዜ ያለፈ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/ሠ/ መሰረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው፣ስሌቱም የተሣሣተ ነው የሚሉትን ነጥቦችን በማንሣት ነው፡፡ እኛም እነኚህን የመከራከሪያ ነጥቦች ከህጉ ጋር አገናዝበናል፡፡

በዚህ መሰረት የአመልካች ድርጅት ዳኝነት የጠየቀበት መብት የበሰለው በጥር ወር 1992 ዓ.ም ውዝፍ የጡረታ መዋጮ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ በዚህ ወቅት በተጠሪ ዓይነት አካላት ተፈፃሚነት የነበረው ሕግ የመንግስት የሆኑ ድርጅቶች ሰራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 49/1967 ሲሆን በዚህ አዋጅ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ተጨማሪ ክፍያ የሚከፈልበት ስለመሆኑ የሚያመላክት ድንጋጌ አልነበረም፡፡ ይህንኑ አዋጅ የሻረው አዋጅ ቁጥር 345/1995 ዓ.ም በአንፃሩ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ የ2% /ሁለት በመቶ/ ተጨማሪ ክፍያ እንደሚከፈልበት በአንቀጽ 7/3/ ስር ደንግጓል፡፡ ይህ አዋጅ ስራ ላይ የዋለው ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን የመሸጋገሪያ ድንጋጌም ይዟል፡፡ የአዋጁ መሸጋገሪያ ድንጋጌ አንቀጽ 52/1/ የሚያሣየውም አዋጁ ከመጽናቱ በፊት ለተፈጠሩ ህጋዊ ሁኔታዎች /legal situations/ ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ህጐችና መመሪያዎች ተፈፃሚነት ያላቸው ስለመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ የድንጋጌ መንፈስ በግልጽ መገንዘብ ከሚቻለው የአዋጅ ቁጥር 345/1995 ዓ.ም ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑን ነው፡፡ አዋጁ ተፈፃሚነቱ ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑ በአንቀጽ 56 ስርም በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ የአዋጁ አቀራረጽ መረዳት የሚቻለው መብቶቹ በነባር ህጐችና መመሪያዎች የተፈጠሩ ከሆነ የሚፈፀሙትም በነባሮቹ ህጐችና መመሪያዎች መሆኑን ሲሆን አሁን በተያዘው ጉዳይ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ የመጠየቅ መብት በነባሮቹ ህጐች የተፈጠረ በአዲሱ አዋጅም ቀሪ ስለመሆኑ ያልተመለከተ ሁኖ በዚህ ውዝፍ መዋጮ ተጨማሪ ክፍያ የማስከፈል መብት የተፈጠረው በአዲሱ አዋጅ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪን መጠየቅ የማይችለው ከጥር ወር 1992 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ ያለውን ተጨማሪ ክፍያ እንጂ በአዲሱ አዋጅ መጽናት በኋላ ላሉት ጊዜያት ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ተጨማሪ ክፍያን ሊባል አይገባም፡፡ የአመልካች ጥያቄም ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም በኋላ ያሉትን ጊዜያትን መሰረት ያደረገ መሆኑን አቤቱታው በግል ያሣያል፡፡ ተጠሪ የመክፈል ግዴታ የሚኖረው ውዝፍ የጡረታ መዋጮውን ብቻ ነው፡፡ ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ጥያቄ ከአዋጅ ቁጥር 345/1995 በፊት የተገኘ መብት በመሆኑ በአዋጁ አይገዛም ተብሎ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ አዋጁ ተፈፃሚነት አለው ከተባለ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/ሠ/ መሰረት ተጨማሪ ክፍያው እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው በማለት የሚያቀርበውን ክርክር ስንመለከተው ተጠሪ ዋናውን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ወዲያውኑ አለመክፈሉን እያመነ ተጨማሪ ክፍያው እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት መከራከሩ ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ አመልካች ድርጅት ተጧሪ ባለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/ሠ/ አግባብነት ሊኖረው አይችልም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ገቢ ላላደረገበት ጊዜ ተጨማሪ ክፍያ(2%) ሁለት በመቶ የማይከፈልበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ አመልካች ህጋዊ ወለድ ሊታሰብ ይገባል የሚለው የዳኝነት ጥያቄ ግን ህጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ(2%) ሁለት በመቶ ተጨማሪ ክፍያ ይከፈላል ከሚል ውጪ በድጋሚ እንዲታሰብ የሚፈቅድበት ሁኔታ ምክንያት ባለመኖሩ የምንቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 345/1995 ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለውን ምክንያት ብቻ በመያዝ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት አዋጁ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ መሆን የሚኖረበት ስለመሆኑ ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ ስለተገኘ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 77477 ግንቦት 10 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 56348 ጥር 15 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ከሰኔ 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ የጡረታ መዋጮውን ገቢ ያላደረገ በመሆኑ ገቢ ባላደረገው የጥር ወር 1992 ዓ.ም ገንዘብ ብር 39,974.35/ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት ብር ከሰላሳ አምስት ሣንቲም/ ላይ በየወሩ ሁለት በመቶ (2%) ታስቦ በተጨማሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. አመልካች ክስ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ወደፊት ከሚያስከትለው ተጨማሪ ክፍያና ይህ ገንዘብ ገቢ ሊሆን ከሚችልበት ጊዜ ጀምሮ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ እንዲከፈል ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ አልተቀበልነውም፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷ፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37375

ኅዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሸምሱ ከድር አህመድ - ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር - አልቀረቡም

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ አቤቱታ የቀረበው አመልካች ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻቸው እንደገለፁት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር በቁ. 12 ጥ/2029/2037 ታሕሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ለአመልካች ባሳወቀው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ. 62758 የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 ይግባኙን በመሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟልና ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች መስከረም 9 ቀን 2000 ዓ.ም ለተጠሪ በፃፉት ማመልከቻ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ መግቢያ ፈተና ለመውሰድ እንዲፈቀድላቸው ቢያመለክቱም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአመልካች ጥያቄና ማስረጃ በማገናዘብ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓ.ም በሕግ ዲፕሎማ ከተመረቁ በኋላ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 8/1/ መሰረት በሙያው 5 ዓመት ያላገለገሉ ናቸው በማለት የአመልካች ጥያቄን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ በማሳደር ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 62758 የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 ሰርዞታል፡፡

አመልካችም ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም አግባብነት ባለው የሕግ ሞያ ከ12 ዓመት በላይ ማለትም ከሰኔ 01 ቀን 1981 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1985 ዓ.ም በአውራጃ አቃቤ ሕግነት፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1985 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1988 ዓ.ም ድረስ በወረዳ አቃቤ ሕግ ሐላፊነት እንዲሁም ከጥቅምት 01 ቀን 1989 ዓ.ም እስከ ግንቦት 14 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በነገረ ፈጅነት ያገለገልኩና በ1981 ዓ.ም ለአውራጃ አቃቤ ሕግነት የተሰጠውን ስልጠና በመከተታል የሕግ ስርተፍኬት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማ ያሉኝ ማለትም የኢትዮጵያ መሰረታዊ ሕጐች የማወቅ ነኝ፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 8/1/ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድ ለማግኘት ወደ ፈተና ለመቀመጥ የሚያበቃኝ ሆኖ እያለ ተጠሪው እና የስር ፍርድ ቤቱ ሕጉን አላግባብ በመተርጐም ዲፕሎማው ካገኘህበት ጊዜ ወዲህ ቢያነስ 5 አመት ማገልገል ይጠበቅብሐል ማለታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል፤ በተጠቀሰው አንቀጽ የተመለከተው መስፈርት በተለይም ደግሞ በሞያው 5 ዓመትን የማገልገል ሁኔታ በህግ ዲፕሎማ ከተመረቅኩ ወዲህ ብቻ ሳይሆን ከመመረቁ በፊት የሰጠኋቸውን አግባብነት ያላቸውን አገልግሎቶቼም የሚጨምር ነው፤ስለሆነም የፈፀሙት የሕጉን የአተረጓጐም ስህተት ታርሞልኝ የጠየቀኩትን የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት የሚያስችሉኝን ፈተና እንድወስድ ሆኖ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪም ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሰጠ ሲሆን ይዘቱም አመልካች የሕግ ዲፕሎማውን ካገኙ በኋላ የ5 ዓመት ግልጋሎት ስለሌላቸውና ከዚያ በፊት የነበሯቸው አገልግሎቶች ለተፈለገው የጥብቅና ፍቃድ ብቃት ስለሌላቸው ቦርዱ በአዋጁ አንቀጽ 8/1/ መሰረት የተመለከቱትን መስፈርቶች ያልተሟሉ ሆኖ ስላገኘው የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ በመሆኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጡ ከላይ እንደተገለፀው ሆኖ ፍርድ ቤቱም አመልካች ላቀረቡት የጥብቅና ፈቃድ ጥያቄ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ያሟላሉ ወይስ አያሟሉም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡-

ከላይ እንደተጠቀሰው የአመልካች ጥያቄ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድ ማግኘት ሲሆን ይህ የጥብቅና ደረጃ የሚመለከቱ መስፈርቶች በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 8/1/ በግልጽ የተዘረዘሩ ሲሆኑ እነዚህም በሕግ ዲፕሎማ ያለው፣ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ሕጐችን ማወቅ እንዲሁም አግባብነት ባለው ሞያ ቢያንስ 5 ዓመታትን ማገልገል የሚሉ ናቸው፣ የአመልካች ጥያቄ ከእነዚህ መስፈርቶች አኳያ ሲታይ ደግሞ ቀደም ብሎ የሕግ ሰርተፍኬት (በ1981 ዓ.ም የተሰጠ) የነበራቸውና ነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማ ማግኘታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የትምህርቱን መስፈርት ያሟሉና የኢትዮጵያ መሰረታዊ ህጐች እንደሚያውቁ ነው፡፡ የሰጡት ግልጋሎትም ሲታይ በአውራጃ አቃቤ ህግነት ለ4 ዓመታት፣ በወረዳ አቃቤ ሕግ ሐላፊነት ለ2 ዓመት ከዘጠኝ ወራት እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ ነገረ ፈጅነት ለ6 ዓመት ከ8 ወራት አካባቢ በጠቅላላ ወደ 13 ዓመታት መስራታቸውን ስለሚያሳይ ከዚሁ ውስጥም ለጠየቁት የጥብቅና ደረጃ ከ5 ዓመታት በላይ ማገልገላቸው ያሳያል፤ ቀጥሎ መታየት ያለበት ነጥብ በተጠቀሰው አንቀጽ የሰፈረው የ5 አመታት አገልግሎት የግድ መቆጠር ያለበት ዲፕሎማ ካገኙበት ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ ሕጉ በግልጽ እንደሚያሳየው የ5 አመታት አገልግሎት የግድ በዲፕሎማ ከተመረቁ በኋላ የሰጡት መሆኑ አያሳይም፣ እነዚህ መስፈርቶች ራሳቸውን ችለው የተቀመጡ እንጂ የአገልግሎት ዘመኑ መቆጠር ያለበት የሕግ ዲፕሎማ ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ለጠየቁት የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ በሕጉ የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟሉ ሆነው እያለ ተጠሪው ሚኒስቴርም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መስፈርቱን እንዳላሟሉ በማድረግ ያስቀመጡት የሕጉ አተረጓጐም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ተጠሪ በቁ. 12 ጥ/2029/2037 ታህሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ለአመልካች ያሳወቀው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 62758፣የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ለጠየቁት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጥብቅና ፈቃድ በአዋጅ ቁ. 199/1992 አንቀጽ 8/1/ የተዘረዘሩትን የትምህርት ደረጃ፣ የአገልግሎት ዘመንና የሕግ እውቀት የሚያሟሉ ስለሆነ ተጠሪው ፈተና ሊፈትናቸው ይገባል፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ ጉዳዩ ያለቀ ስለሆነ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37050

ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሊ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሻምበል ሁሴን አሊ - ጠበቃ መድህን መሐሪ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሱማሌ ክልል ዐ/ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከባድ የሆነ የሰው ግድያ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የጅጅጋ ዞን ዐ/ሕግ መስከረም 02 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈው የክስ ማመልከቻ የአሁኑ አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1ሀ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ነሐሴ 26 ቀን 1998 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሲሆን በጅጅጋ ዞን ፖሊስ ጽ/ቤት ፊት ለፊት የሱፍ መሐመድ ሰሊም ይባል የነበረውን ግለሰብ ታጥቆት በነበረው ሽጉጥ አንድ ጥይት በመተኮስ ራሱ ላይ በመምታት ለህልፈት የዳረገው በመሆኑ ሊቀጣ ይገባል በማለት በመሠረተው ክስ መነሻ ሲሆን የአሁኑ አመልካች በተከሣሽነታቸው ቀርበው ክሱ ከተነበበላቸው በኋላ ፍ/ቤቱ ለክሱ የሚከራከርለትን ጠበቃ እንዲፈቅድላቸው ጠይቀው ፍ/ቤቱም ተከሣሹን የክሱ ማመልከቻ የሚለውንና የተነበበው የገባቸውና የተረዱት መሆኑን ጠይቋቸው ተጠሪም የተረዱት መሆኑን ለፍ/ቤቱ ከገለፀ በኋላ የድርጊት አፈፃፀሙን በተመለከተ ግን በዐ/ሕግ የክስ ማመልከቻ በተከሠሡበት ዓይነት አልፈፀምኩም ሲል የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ለጥቅምት 08 ቀን 1999 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ የዐ/ሕግ ምስክሮች እንዲቀርቡ አመልካች ጠበቃቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ተደርጎ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ሊቀርቡ አለመቻላቸው የአመልካች ጠበቃም ያልቀረቡ መሆኑ ተረጋግጦ ተለዋጭ ቀጠሮ ተይዞ የዐ/ሕግ ምስክሮች ሲቀርቡ የአመልካች ጠበቃ በሌላ ቦታ ላይ በነበራቸው ቀጠሮ ምክንያት ያልቀረቡ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ቀጠሮው በአዳሪ /ለተከታዩ ቀን/ እንዲለወጥላቸው ቢጠይቁም በዐ/ሕግ በኩል ነገሩን ያጓትተዋል የሚል ተቃውሞ ቀርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ አዳምጦ ጠበቃው የበለጠ ጊዜ ሊጠበቅ አይቻልም፣ ግራ ቀኙም ተስማምተውበታል በማለት የአመልካች ጠበቃ ሣይቀርቡ ወይም ሌላ ጠበቃ ሣይተካ የዐ/ሕግ ምስክሮች እንዲሰሙ ተደርጓል፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸውን ዐ/ሕግ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በፀዳ ሁኔታ አረጋግጦባቸዋል ተብሎ እንዲከላከሉ ከተደረገ በኋላ መከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብታቸውን መተዋቸውን ገልፀዋል ተብሎ ከታለፈ በኋላ የዐ/ሕግ ተጨማሪ ምስክሮች እንዲሰሙ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በኋላ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን በዐ/ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ በሞት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡ ከዚያም የአሁኑ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ይኸው ፍ/ቤትም በአመልካች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሚያዚያ 04 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 7/ሰባት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ጠበቃ የመወከል መብታቸው ያልተጠበቀላቸው መሆኑን፣ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው በማስረጃ ያልተጋጠባቸው መሆኑን መከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብታቸው የታለፈውም በቂ ጊዜ ሣይሠጣቸው መሆኑን፣ የተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓቱን ያልጠበቀ መሆኑን የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠበት ድንጋም አግባብነት እንደሌለው እና የሞት ቅጣት ፍርዱም ተገቢነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ይሻርላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የክልሉ ዓ/ሕግ ሐምሌ 09 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመለከቻ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ህዳር 10 ቀን 2001 ዓ.ምበተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሱን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች የተከሱበት ጉዳይ ከባድ መሆኑ እየታወቀ በጠበቃ ሣይወከሉ ክርክሩ መካሄዱና ውሣኔ መሰጠቱ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ የክርክር ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በስርፍ/ቤት የቀረቡትና የእምነት ክህደት ቃል የሰጡት መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ሁኖ በዚህ ዕለት ጠበቃ ያልተወከለላቸው መሆኑን፣ ጥቅምት 08 ቀን 1999 ዓ.ም የዐ/ሕግ ምስክሮች እና የአመልካች ጠበቃ እንዲቀርቡ ተገልጾ ቀጠሮ በተያዘበት ቀንም የአመልካች ጠበቃ አለመቅረባቸው፣ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮም የዐ/ሕግ ምስክሮች ቀርበው የአመልከች ጠበቃ ሣይቀርቡ የቀሩበትን ምክንያት አመልካች ለፍ/ቤት ገልፀው የዐ/ሕግ ምስክሮች ጠበቃቸው በበነጋው ሲቀርቡ እንዲሰሙላቸው ቢያመለክቱም ተቀባይነት በማጣት የዐ/ሕግ ምስክሮች አመልካች በጠበቃ ባልተወከሉበት ጊዜ የተሰሙ መሆኑ መረጋገጡን ነው፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር የተያዙና የተከሰሱ ሰዎችን በተመለከተ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት የተካተቱትን መብቶችን የሚገልፁት ድንጋጌዎች አቀራረፅና ይዘታቸው ሲታይ በተቻለ መጠን ወዲያውኑ ሊተገበሩ የሚገባ መሆኑን ያስገነዝቡናል፡፡ ከዚህም በላይ በወንጀል ፍትህ አስተደደር የተያዙና የተከሠሡ ሠዎች ሕገ- መንግሥታዊ መብታቸውን የዳኝነት አካሉ የማክበርና የማስከበር ሕገ መንግሥታዊ ግዴታ ያለበት መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 13/1/ ስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም የተያዙና የተከሠሡ ሰዎች ሕገ መንግሥታዊ መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታ በዳኛው ትከሻ የወደቀ ስለመሆኑ ሊስተዋል ይገባል፡፡ በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ዳኞች ይህንኑ ግዴታ ሲወጡ ደግሞ ማህበረሰቡ የሂደቱን ፍትሃዊነት ከማክበሩም በተጨማሪ የሂደቱን ውጤትም በአክብሮት እንዲቀበል ያደርጋል፡፡ የሕግ ሥርዓቱ በሕገ-መንግሥቱ ጥበቃ የተደረገላቸውን የዜጎች መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ ካልተወጣ ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነትና አክብሮት እንደሚቀንስ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በሕገ-መንግሥቱ የተመለከቱት ሠብአዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር የግድ ይሏል፡፡

አንድ በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ የተያዘና የተከሰሰ ሰው ከሂደቱ መጀመሪያ እስከ ፍፃሜ ድረስ በሕገ-መንግሥቱ ከተረጋገጠለት ሠብአዊ መብቶች መካከል አንዱ በጠበቃ የመወከል መብት ነው፡፡ ይህ መብት ተከሣሹ በራሱ የሚፈልገውን ጠበቃ በማቆም ሊጠቀመው የሚችለው ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣቱ ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም በመንግሥት ወጪ ጠበቃ በማቆም ሊከበርለት የሚገባው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 20/5/ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከድንጋጌው መንፈስ የምንገነዘበውም ተከሣሹ ራሱ በመረጠው ጠበቃ የመወከል ሕገ-መንግሥታዊ መብቱን አንዲጠቀም በቂና አሣማኝ ጊዜ ከመስጠት በተጨማሪ ይኸው መብት እንዳለውም በችሎቱ ሊገለጽለት የሚባው መሆኑን ነው፡፡

ይህ ብቻ ሣይሆን ተከሣሹ ብቃት ባለው ጠበቃ መወከሉም ሊያረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህ ሁሉ የፍ/ቤቱ የስራ ድርሻ ነው፡፡ ስለሆነም በጠበቃ የመወከል መብት ትልቅ ሕገ- መንግሥታዊ መብት መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

እኛችን ወደአለው ጉዳይ ስንመለስም የአሁኑ አመልካች ከሂደቱ መጀመሪያ ጀምሮ እስከመጨረሻው በፈለጉት ጠበቃ የመወከል ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው በቂና አሣማኝ ጊዜ ተሰጥቷቸው በስር ፍ/ቤት የተከበረላቸው አለመሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የአመልካች ሕገ-መንግሥታዊ መብት ሣይከበር የተሰጠ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. ዐ01/99 በቀን ዐ1/ዐ2/1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ በሶማሌ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥር 23 ቀን 2ዐዐዐ ዓ.ም. የፀናው የጥፋተኛነትና የሞት ቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ1/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሸሯል ይፃፍ፡፡
2. አመልካች በመረጡት ጠበቃ የመወከል ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው ሊከበር ይገባል ብለናል፡፡
3. አመልካች በመረጡት ጠበቃ የመወከል ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው ተከብሮ ጉዳዩ ከዚህ በፊት ባላዩት ዳኞች እንደገና ታይቶ ተገቢው ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን ለጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38237

ታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ በርገና ሽፈራው - ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ አብርሃም ሽፈራው
2. አቶ መስፍን ሽፈራው } ወ/ነ/ፈጅ አቶ አብረሃም ሽፈራው ቀረቡ፡፡
3. ወ/ሮ ታሪኳ ሽፈራው
4. ወ/ሮ ሽታዬ ሽፈራው - በሌለችበት የሚታይ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 20032 በሆነው መዝገብ ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪዎች በወረዳ ፍ/ቤት ከሣሾች ሲሆኑ አመልካች ተከሣሽ ነበር፡፡ የክሱም ምክንያት የሚች አባታችን ንብረት የሆነውን የውርስ መሬት ይዞ ስለሚገኝ ድርሻችንን ያካፍለን የሚል ሲሆን አመልካችም በዚሁ መሬት ከዚህ በፊት ታላቅ ወንድማቸው ክስ አቅርቦ ተከራክረን በመ/ቁ. 32/94 በሆነው መዝገብ በ12/9/94 ዓ.ም. የዋለው ችሎት ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ ሌሎች ወንድሞቹ ተመሣሣይ ክስ ቢያቀርቡም በተመሣሣይ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ደግሞ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም፡፡ አባታችን የሞቱት በ1973 ዓ.ም. በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ መሠረት ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ የተከራከረ ስለመሆኑ መዝገቡ የስረዳል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ያከራከረው የምዕራብ አባያ ወረዳ ፍ/ቤት ከዚህ በፊት ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5/1/ መሠረት እንደገና ክስ ሊቀረብበት አይገባም አመልካች ከ15 ዓመት በላይ ግብር እየገበረበት የሚጠቀምበት ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክርን መሠረት በማድረግ የከሳሾችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የጋሞ ጎፋ ዞን የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አጽንቷል፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ወንድማቸው አቶ በለጠ ሽፈራው ስለራሱ ተከራክረ እንጂ ከሣሾችን ወክሎ አልተከራከረም፡፡ ስለዚህ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5/1/ መሠረት በማድረግ የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 3 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፎ ያቀረበው ቅሬታ፡-

- እኔ ከጦር ሜዳ እንደተመለስኩ እንደ እኔ ከጦር ሜዳ ግዳጃቸውን ፈጽመው ለተመለሱ ሲሰጣቸው የተሰጠኝን ይዞታ መሬት አርሼ ለ19 ዓመታት ከተጠቀምኩ በኋላ የተጠሪዎች ታላቅ ወንድም በ1993 ዓ.ም. ክስ መስርቶ ተከራክረን በተወሰነው ጉዳይ እንደማያውቁ ሆነው ክስ ማቅረባቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5/1/ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ መሠረት በይርጋ እንደሚታገድ በማስመልከት ያቀረብኩትን ክርክር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሳያጣራ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ በመሆኑ ተሽሮ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡
- ቅሬታውን መሠረት በማድረግ ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዞ መስከረም 22 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ከ1-3 ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልሱም ፍሬ ሀሣብ አቶ በለጠ ሽፈራው ያቀረበው የይዞታ ክርክር እንጂ የውርስ ንብረት ክርክር አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5/1/ ለክርክሩ አግባብነት የለውም፡፡
- የይርጋ ክርክም በሥር ፍ/ቤት ስላልተነሳ በሰበር ሰሚ ችሎት ማንሳት አይቻልም በማለት በወኪላቸው አማካይነት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አራተኛ ተጠሪ በቀበሌው የማይታወቁና በወረዳውም የሌሉ መሆኑን ከቀበሌው አስተዳደር በመግለጹ መጥሪያው በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ ተለጥፎ ያልቀረቡ በመሆኑ በሌለችበት እንዲታይ ታዟል፡፡

አመልካችም በ5/3/2001 በተፃፈው የመልስ መልስ ወንድማቸው ያቀረበው ክስ የውርስ ጥያቄ ነው፡፡ የይርጋ ክርክርም ቢሆን ከበታች ፍ/ቤቶች ጀምሮ የተከራከርኩበት መዝገብ ያስረዳል በማለት ተከራክሯል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብነት እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ግራ ቀኙ የሚከራከሩት የሚች አባታቸው ይዞታ የነበረ ሙዝና ቋሚ ሰብል ያለበት በውርስ ሊደርሰን የሚገባንን አመልካች ለብቻው ይዞ ይጠቀማልና ድርሻችንን ያካፍለን በማለት ነው፡፡ የአመልካች ክርክር ደግሞ ለ19 ዓመታት በእጄ አድርጌ የምጠቀምበት ነው፡፡ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ይከራከራል፡፡ አባታቸው የሞቱት በ1973 ዓ.ም. መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ ለተጠሪዎች በአመልካች ላይ መሬቱን እንዲያካፍላቸው ክስ ያቀረቡት ሰኔ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. ነው፡፡

በመሠረቱ ከሣሽ መብቱንና የውርስ ንብረቶች በተከሣሹ መያዛቸውን ካወቀ ሦስት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለወራሽነት የሚያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት እንደማይኖረው አመልካች ጠቅሶ በሚከራከረው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ ሥር ተደንግጓል፡፡ አባታቸው ከሞቱበት ከ1973 ዓ.ም. ጀምሮ ይህ ክስ እስከቀረበበት ሰኔ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ 26 ዓመታት ያሕል አስቆጥሯል፡፡ በሕጉ አነጋገር ተጠሪዎች የአባታችን መሬት በዚህ ጊዜ ነው በአመልካች መያዙን ያወቀነው በማለት የይርጋው ጊዜ ሊያሳጥርላቸው የሚችልበትን ለይተው የተከራከሩበት ወይም መያዙን አላወቅንም ሲሉ የተከራከሩበት ወይም በሌላ ምክንያት ይርጋው ሊቋረጥ የሚችልበትን ምክንያት መሠረት በማድረግ ያደረጉት የሕግ ክርክር የለም፡፡ የመሬት ባለቤትነት የኢትዮጵያ ሕዝብና የመንግሥት ከመሆኑ አንፃር ከዘር የወረደ ርስት ነው ተብሎ የሚጠየቅ አይደለም፡፡ ይህ ባልሆነበት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሌሎች የክርክር ነጥቦች በቀዳማይነት ሊታይ የሚገባውንና አመልካችም ከወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ በጥብቅ የሚከራከርበትን የመቃወሚያ ክርክር ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት በሌለበት በዝምታ በማለፍ የወረዳውንና የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ሲል የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ መሠረት በወራሾች መካከል የሚደረግ የውርስ ጥያቄ ክርክር ከ3 ዓመት በኋላ ሊቀርብ እንደማይገባ የተደነገገውን ሕግ ትርጉም የልጠበቀና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 20032 በቀን 01/09/2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የተጠሪዎች ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል ብለናል፡፡
3. የምዕራብ አባያ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች በመሬቱ መሠረት አድርጎ የሰጠው ውሣኔና የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የፀናው በአግባቡ ነው ብለን ውሣኔዎቹን አጽንተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. ወጪና ኪሣራ የዚህ ፍ/ቤትን ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡
ውሣኔው ዛሬ በ22/04/2001 በንባብ ተሰማ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 37184

ታህሣሥ 09 ቀን 2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የሰሜን ቀጠና ጉምሩክ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- 1. ቁስ ብርሃነ ንዋይ - አልተጠራም

2. ሐጂ ዓብዱልቃድር መሐመድ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በኮንትሮባንድነት የተያዘ 71/ሠባ አንድ/ ኩንታል በአደራ ተጠምጦ ከቆየ በኋላ ባለመመለሱ ዋጋው ይከፈለኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ በመረብለኸ ወረዳ በራማ ከተማ በኮንትሮባንድ ወንጀል የተያዘ ሠባ አንድ ኩንታል ቡና በአደራ በመጋዘን ለማስቀመጥና እንዲሁም አቅርብ በተባለበት ጊዜ ለማስረከብ ካልቻሉ ግን እጥፍ አድርገው 142 /አንድ መቶ አርባ ሁለት/ ኩንታል ቡና አድርገው ለመመለስ የውል ግዴታ መግባታቸውን፣ ሁለተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ደግሞ ለአንደኛ ተጠሪ ዋስ ሆነው ተጠሪው ቡናው ካልመለሱ ሰባ አንድ ኩንታል ቡና ለመመለስ ውል መፈረማቸውን በመዘርዘር አንደኛ ተጠሪ በውሉ መሠረት 142 ኩንታል ቡና ዋጋ ብር 340,800.00 /ሦስት መቶ አርባ ሺህ ስምንት መቶ ብር/፣ ይህንኑ መክፈል የማይችሉበት ምክንያት ካለ ደግሞ ሁለተኛ ተጠሪ በገቡት የዋስትና ውል መሠረት የሰባ አንድ ኩንታል ቡና ዋጋ ብር 170,400.00 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አራት መቶ ብር/ እንዲከፍሉ ይወስንለት ዘንድ ዳኝነት በመጠየቅ በተጠሪዎች ላይ በመሠረተው ክስ ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው አለን ያሉትን መከላከያ መልስ አቅርበዋል፡፡ አንደኛው ተጠሪ ባቀረቡት የመከላከያ መልስ በጉዳዩ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡት የፊርማ ሠነድ ባለመመርመሩ እንጂ ተመስክሮባቸው አለመሆኑን፣ ውልም አለመኖሩን፣ ቡናው የሌላ ሰው መጋዘን በጉምሩክ ፖሊሶች ተከራይቶ የተቀመጠ እንጂ ተጠሪ የተረከቡት አለመሆኑን በመዘርዘር የተከራከሩ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ዋስ የሆኑት አንደኛውን ተጠሪ ለማቅረብ እንጂ ሰባ አንድ ኩንታል ቡና ለመክፈል አለመፈረማቸውን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ማዕከላዊ ዞን ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር፣ የምስክሮችን ቃል ከሠማና በውሉ ላይ አለ የተባለው ፊርማ የተጠሪዎች ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት እንዲቀርብ ከአደረገ በኋላ ተገቢ ነው ያለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር በመልካች በኩል የቀረበ ማስረጃ ዝቅተኛ ነው በማለት ተጠሪዎችን በነፃ አሠናብቶ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ሚያዝያ 09 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነው በኮንትሮባንድ ተያዘ የተባለው ቡና አንደኛ ተጠሪ በአደራ ስለመረከባቸው በዚሁ መሠረት መልሰው ባለማስረከባቸው በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው ተቀጥተው ያሉ፣ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ዋስ ሁነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መፈረማቸውን የሚያሣዩ ሰነዶች ቀርበው እያለ ተጠሪዎች ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ሊታረም ይገባል በማለት የቡናውን ዋጋ እንዲከፍሉ ይወስን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው ሰኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቱንና ጥንካሬውን በተመለከተ ምክንያቶችን በመዘርዘር ክርክሩ በበታች ፍ/ቤቶች በሚሠማበት ወቅት የቀረቡት ጭብጦችና የማስረጃዎች ሁኔታ ተጠሪዎችን ኃላፊ ለማድረግ ብቃት ያላቸው ስላልሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነ/ፈጅ በበኩላቸው የተጠሪዎችን የመልስ ማመልከቻ ነጥቦችን አንድ በአንድ በማንሣት ተገቢነት የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር እና የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ሐምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሰነድ ማስረጃዎችን ይዘት ተመልክቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር፣ የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ተጠሪዎች ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሲሆን የአላፊነት መጠኑም ተያይዞ ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ሀ/ አላፊነትን በተመለከተ</u>

አመልካች ክሱን ሊመሰርት የቻለው በኮንትሮባንድ ወንጀል የተያዘ ቡና አንደኛ ተጠሪ በአደራ አስቀምጠው እንዲያቆዩ፣ ሲጠየቁም በተጠየቁበት ጊዜ ለማስረከብ፣ ይህ ካልሆነ እጥፍ አድርገው ለመክፈል ጎዳር 17 ቀን 1989 ዓ.ም. በተፃፈ ሰነድ ስምምነት አድርገው በስምምነቱ መሠረት ሊፈፀምለት ባለመቻሉ ነው፡፡ ይህንኑ ፍሬ ነገር ለማስረዳትም የውሉን ሰነድ፣ አንደኛ ተጠሪ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ስለመሆኑ የሚያሣይ የፍ/ቤት ውሣኔ፣ ለአንደኛ ተጠሪ የተሰጠ ማስጠንቀቂያና የሰው ምስክሮችን አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች በውሉ ላይ ያለውን ፊርማ በመካዳቸው ምክንያትም ፊርማቸው እንዲመረመር ተደርጎ የተጠሪዎች መሆን አለመሆኑ ሊለይ አለመቻሉን በግለጽ መርማሪው አካል በደብዳቤ ገልጿል፡፡ በውሉ ነበሩ የተባሉ ምስክሮች እንደሰሙ ተደርጎም ሁለቱ ምስክሮች ውሉን እንማያውቁና ያልፈረሙበት መሆኑን፣ ቀሪው ምስክር ግን ውሉ መኖሩን በመግለጽ መስክረዋል፡፡

የበታች ፍ/ቤቶች ለእነዚህ የአመልካች ማስረጃዎች ክብደት ያልሰጡት ፊርማው ተመርምሮ ሊለይ አለመቻሉና ሁለት ምስክሮች ውሉን የማያውቁ መሆናቸው ተረጋግጧል በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1726፣ 1727፣ 2709፣ 2787፣ 2802 እና 1922/3/ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ የአመልካች ማስረጃ ዝቅተኛ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በአመልካችና በአንደኛ ተጠሪ መካከል የተቋቋመው ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2779 ሥር የተመለከተውን ትርጓሜ ሊያሟላ የሚችል የአደራ ውል ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት በግልጽ ያሣያል፡፡ በግራ ቀኙ መካከል ያለው ውል የአደራ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ መታየት የሚገባው በዚህ ረገድ የተመለከቱት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ሊተው የሚችሉት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የማያስችሉ ሆነው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ የሕግ አተጓጎም መርህ ያስገነዝባል፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ከአደራ ውል አኳያ የተመለከቱት ስለመሆኑ የውሣኔ ይዘት ቢያሳይም በዚህ ረገድ በዋቢነት የተጠቀሱት ድንጋጌዎችም ሆነ ከጠቅላላ የውል ክፍል የተጠቀሱት ድንጋጌዎች የማስረጃውን ዝቅተኛነት ለማሣየት አግባብነት የሌላቸው መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ለአንድ ውሣኔ በዋቢነት ሊጠቀስ የሚገባው ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው እንጂ ተዛማጅነት የሌለው ሊሆን አይገባም፡፡

አመልካች በክሱ ላይ የተገለፀውን ፍሬ ነገር እርግጠኛነት ለፈራጅ ለማሣመን ያቀረባቸው የሰነድ እና የሰው ምስክሮች ናቸው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከቀረቡት የአመልካች ማስረጃዎች መካከል አንደኛ ተጠሪ በጉዳዩ በወንጀል ተከሠው ጥፋተኛ የተባሉበትና የተቀጡበትን የፍ/ቤት ውሣኔ ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ወይም ብቁነት ሳይገልጽ ስለማለፉ የውሣኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ የተቆጠረው ወይም የቀረበው ማስረጃ ለክርክሩ መነሻ ከሆኑት ፍሬ ነገሮች ጋር ግንኙነት እያለው እና ፍሬ ነገሮችን ለማረጋገጥ በሕጉ ክልክላ ያልተደረገበት የማስረጃ ዓይነት እስከሆነ ድረስ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ሁሉም ማስረጃዎች መመዘን አለባቸው በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ሁሉን ማስረጃዎች በአንድነት ሣይመዘኑ የተወሰኑትን ብቻ ነጥሎ በመወሰድ የሚሠራ ምዘናም ሆነ ውጤት ፍትሐዊነት አይኖረውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ አንደኛ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ በወንጀል ተከሰው በፍ/ቤቱ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑንና በበላይ ፍ/ቤትም አለመለወጡ ተረጋግጦ እያለ ይህ የአመልካች ማስረጃ በሰበር ፍ/ቤት በገዘምታ ታልፏል፡፡ ይህም የማስረጃ አቀባበል ሥርዓትን ያልተከተለ ነው፡፡ የዚህን ማስረጃ አግባብነት እና ብቁነት ስንመለከተውም ለጉዳዩ በማስረጃነት ሊቀርብ ወይም ክብደት ሊሰጠው አይገባም የሚባልበትን የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር በማስረጃነት አግባብነት እና ብቃት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ ሕ/ቁ. 2149 ተቃራኒው ንባብ ያስገነዝባልና፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በወንጀል የተሰጠ ውሣኔ በፍትሐብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት አግባብነት የሚኖረው በወንጀል ክሱ በወንጀል ፍ/ቤት ተከሣሹ ጥፋተኛ ተብሎ ከተወሰነ ስለመሆኑ እና ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት የወንጀል ክስ ማስረጃ አመዛዘን መርህ ከፍትሐብሔሩ የበለጠ ጠንካራና የማያሻማ ማስረጃ የሚጠይቅ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ማስረጃ ክብደት የመዘነው ከፎረንሲክ ምርመራ ውጤት መግለጫና ከተሰሙት ምስክሮች ቃል አንፃር እንጂ በወንጀል ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ አይደለም፡፡

በመሠረቱ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት በውሉ ሰነድ ላይ የተመለከተው ፊርማ የተጠሪዎች አይደለም በሚል የማይገልጽ፣ ይልቁንም ለመለየት ያልተቻለ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መልኩ የተገለፀውን የባለሙያ አስተያየት በውሉ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪዎች አይደለም ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ማስረጃ /conclusive evidence/ አይደለም፡፡ በመሆኑም የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ከተሰሙት የአመልካች ምስክሮች ውስጥም አቶ ጎይቶኦሞ ገ/ሕይወት የተባሉት በ17/03/1989 በተፈረመው የውል ሰነድ ላይ የፈረሙ መሆናቸውን የውሉ ሰነድ የሚያሣይ ከመሆኑም በላይ በወንጀል ችሎት በዓቃቤ ሕግ ምስክርነት ቀርበው የአደራ ውሉን መኖር መመስከራቸው ከመረጋገጡ አኳያ በፍትሐብሔር ክስ ጊዜ ውሉን አላውቀውም፣ አልፈረምኩም ማለታቸው የምስክሩን ቃል ተዓማኒነት በመቀበል የውል ሰነዱንና የወንጀል ችሎት ውሣኔ ሰነድ የማስረጃነት ተገቢነት /admissibility/ ሊያስቀር የሚችል አይደለም ሁለተኛ ተጠሪም በወንጀል ችሎት የመሠከሩ ከመሆናቸውም በላይ በውሉ ሰነድ ላይ መፈረማቸውን ሣይክዱ የፈረሙበት ምክንያት አንደኛ ተጠሪን ለማቅረብ ብቻ ነው ማለታቸውን፣ የውሉ ይዘት ይኸው የነበረ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2006/1/ በሚያዝዘው መሠረት መቃወሚያ ማስረጃ ሣያቀርቡ የሚከራከሩ በመሆኑ ክርክራቸው የሕግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ ሌላው ሁለተኛ ተጠሪ የዋስትና ውሉን በተመለከተ ያቀረቡት የሕግ መከራከሪያ ሲታይም በውሉ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው አንደኛ ተጠሪ የተረከቡትን ቡና ካልመለሱ 71 /ሰባ አንድ/ ኩንታሉን ቡና ለአመልካች ለማስረከብ የተጠቀሰ በመሆኑ ዋሱ እዳውን አውቀው እንደፈረሙ የሚያሣይ ነው ከሚባል በስተቀር የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1922/3/ ድንጋጌን መሰፈርት እያሟላም ሊባል የማይገባ ሆኖ በመገኘቱ በዚህ ረገድ የቀረበው መከራከሪያ ነጥብ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ተጠሪዎች የአመልካች ማስረጃ አቀራረብም ሥርዓቱን ያልጠበቀ፣ በስር ፍ/ቤት ሣይቀርብ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የማይገባ ነው በማለት የተከራከሩ መሆኑንም ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ሆኖም በአመልካች በኩል የተጠቀሱት ማስረጃዎች በስር ፍ/ቤት ተዘርዝረው የቀረቡ መሆናቸውን የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የሚያሣይ በመሆኑ የማስረጃው አቀራረብ ሥርዓቱን ያልጠበቀ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

በመሆኑም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች የበታች ፍ/ቤቶች በተጠሪዎች አላፊነት ላይ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ የተገኘ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ ተሽሮ ተጠሪዎች በአደራ ተቀምጦ ለአመልካች ላልተመለሰው ቡና አላፊ ሊባሉ የሚገባ ነው ብለናል፡፡

<u>ለ/ የአላፊነትን መጠን በተመለከተ፡-</u> ጉዳዩ በአደራ ውል ድንጋጌዎች መገዛት ያለበት መሆኑ ከላይ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች የሃላፊነት መጠን መታየት ያለበትም አደራ ይዘት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት አንደኛ ተጠሪ በአደራ የተረከቡትን ቡና ሲጠየቁ ካልመለሱ እጥፍ አድርገው ለመመለስ በሕዳር 17 ቀን 1989 ዓ.ም. ተደረገ በተባለው ውል የተስማሙ ቢሆንም ይኸው ግዴታቸው በጠቅላላ የውል ድንጋጌዎች መገዛት የሌለበት በመሆኑ፣ የአደራ ተቀባዩ በአደራ የተቀመጠውን ዕቃ እንዲመልስ ሲጠየቅ ያለበት ሕጋዊ ግዴታ በአደራ የተቀመጠውን ዕቃ መመለስ እንጂ ሊመለስ የሚገባው ዕቃ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅምና ሌላ ተያያዥነት ያለው ትርፍ ጋራ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2779 — 2799 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች መንፈስ ስለማያሣይ፣ አመልካች የአንደኛ ተጠሪ የአላፊነት መጠን እጥፍ ሊሆን ይገባል በማለት የጠየቀው ዳኝነት ከአደራ ውል ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ የማይሄድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም፣ የአንደኛ ተጠሪ የአላፊነት መጠን በአደራ ውሉ የተገለፀውን 71 /ሰባ አንድ/ ኩንታል ቡና በዓይነት ለአመልካች መመለስ፣ ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይኸው ብዛት ያለው ኩንታል ቡና በወቅቱ ገበያ በነበረው ዋጋ ብር 170,400.00 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አራት መቶ/ ተብሎ በአመልካች ተገልፆ በተጠሪ በኩል የቀረበ የተቃውሞ ነጥብ የሌለ በመሆኑ አንደኛ ተጠሪ ይህንኑ የገንዘብ መጠን ለአመልካች በአማራጭ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ በአላፊነት መጠኑ ላይ ያቀረቡት ክርክር የዋስትናው ግዴታ መጠን በገንዘብ ያልተጠቀሰ ነው ከሚል ይዘት ውጪ አንድ ኩንታል ቡና በወቅቱ የነበረውን የገበያ ዋጋ መሠረት አድርጎ የቀረበ ባለመሆኑ የአላፊነታቸው መጠን በአንደኛ ተጠሪ አላፊነት መጠን ውጪ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪ የገቡት ግዴታ ተራ ዋስትና ዓይነት በመሆኑ እና በዚህ የዋስትና ዓይነት ደግሞ ዋስ ለባለገንዘቡ የሚገደድበት ባለዕዳው ግዴታውን መወጣት ያልቻለ የሆነ እንደሆነ በመሆኑ ሁለተኛ ተጠሪ አንደኛ ተጠሪ መክፈል ካልቻሉ ብቻ 71 /ሰባ አንድ/ ኩንታል ቡና በዓይነት ለአመልካች የመመለስ ወይም በአማራጭ የ71 /ሰባ አንድ/ ኩንታል ዋጋ ብር 170,400.00 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አራት መቶ ብር/ የመክፈል ግዴታ አለባቸው ተብሎ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም ለክርክሩ መነሻ የሆነው በኮንትሮባንድ ወንጀል ተያዘ የተባለው ቡና አንደኛ ተጠሪ በአደራ ስለመረከባቸው እና በዚህ መሠረት መልሰው ባለማስረከባቸው በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሠው ጥፋተኛ የተባሉበት የፍ/ቤት ውሣኔ በሰነድ ማስረጃነት አመልካች አቅርቦ እያለ የሰው ምስክሮችን ቃል እና ሙሉ በሙሉ መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ የማይችል የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት መግለጫ ብቻ ነጥሎ በመመዘን በ17/03/1989 ዓ.ም. ተደረገ የተባለውን የአደራ ውል ሰነድ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ የማስረጃ አቀባበልና አመዛዘን ሥርዓትን ያልተከተለ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በዞኑ ማዕከላዊ ፍ/ቤት ጥቅምት 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22296 ጥር 28 ቀን 2000 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች 71 /ሰባ አንድ/ ኩንታል ቡና እንዲያስረክቡ ወይም በአማራጭ ብር 170,400.0000 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አራት መቶ ብር/ እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
3. ሁለተኛ ተጠሪ ለባለገንዘቡ አመልካች የሚገደዱት ባለዕዳ አንደኛ ተጠሪ ግዴታቸውን መወጣት ያልቻሉ እንደሆነ ብቻ ነው ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 37163

ታህሳስ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

አመልካች፡- የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ዘመድ ገ/አምላክ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ህያብ ገ/መድህን ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ - ጠበቃ ሰሞን ባርናባስ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ጨረታን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ኀዳር 04 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ የአሁኑ አመልካች የተገለገለባቸውን ብረት ነክ የሆኑ የተለያዩ ንብረቶችን ለፈላጊዎች በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ በአወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት ዝርዝር መመሪያውን በማንበብ በጨረታ የሚሸጡትን ንብረቶች በጠቅላላ የሚገዛበትን ዋጋ በማቅረብ እና ድርጅቱ በተለየ መልኩ በድርድር ንብረቶችን የመሸጥ ሐሣብ ካለው በመደራደር ለመግዛት ፍላጐት ያለው መሆኑን በመግለጽ በተጠሪ ስም በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ ለጨረታው በተከፈተው ሣጥን ማስገባቱን ጨረታው በይፋ በተከፈተበት ቀንም በመደራደር ተጠሪ የተሻለ ዋጋና የድርድር ሃሣብ በማቅረብ ተመርጦ ከጨረታው ኮሚቴ ጋርም በመደራደር ለጨረታው የቀረቡትን ንብረቶች በብር 200.000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ለመግዛት ስምምነት ተደርሶ ኮሚቴው ቃለ ጉባኤ ይዞ ግዥው ፀድቆ ለስራ አስኪያጅ ለፊርማ ከቀረበ በኋላ ጨረታው ውድቅ ነው ተብሎ እንደገና እንዲካሄድ በማለት ስራ አስኪያጁ የጨረታ ውጤቱን መሰረዛቸውን ዘርዝሮ የጨረታው ኮሚቴ በወሰነው መሰረት የተጫረተውን፡፡ ንብረት አመልካች እንዲሸጥና ኪሣራና ወጪ እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ የዳኝነት ጥያቄ በዞን ሦስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በፍ/ቤቱ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ቀርቦ ህዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በዋና ዳይሬክተሩ አማካኝነት መከላከያ መልሱን አቅርቧል፡፡ በመከላከያ መልሱም በጨረታው ላይ የተከሰቱት ጉድለቶች ምን እንደሆኑ በመዘርዘር በእነዚህ ምክንያቶች ጨረታው የተሰረዘ መሆኑንና በስራ አስኪያጁ ባልፀደቀ የጨረታ ውጤት ክስ ሊቀርብ የማይችልበት ስለመሆኑ ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ተጠቃሹ ፍ/ቤትም የጨረታ ኮሚቴ አባላትንና የአመልካችን መ/ቤት የሕግ ክፍል ባልደረባን በምስክርነት ከሰማ በኋላ ለጨረታ የቀረበው ንብረት ለተጠሪ በድርድር መሸጡን ኮሚቴው ገልጾ ያቀረበው የውሣኔ ሐሣብ በአመልካች መ/ቤት ስራ አስኪያጅ ባይፀድቅም ሽያጩ ተግቢነት ያለው ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት በኮሚቴው በተሰጠው የውሣኔ ሐሣብ የአሁኑ አመልካች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተጠሪ ብሩን ከፍሎ ንብረቶችን እንዲያነሣ ወጪና ኪሣራ በድምሩ ብር 5850.50(አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ብር ከሃምሳ ሣንቲም) እንዲከፈለው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ቅሬታውን ለአፋር ቤሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 13 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሯል፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርብ ተደርጐ ግንቦት 22 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልስ ተሰጥቷል፡፡ አመልካችም ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልስ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቅቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የጨረታ ኮሚቴ ተጠሪን የጨረታ አሸናፊ በማድረግ የወሰኑት የውሳኔው ሐሣብ በአመልካች መ/ቤት ስራ አስኪያጅ ሣይፀድቅ እንደ በመጨረሻ ውሣኔ ተደርጐ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ የሚለው ጭብጥ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ የጨረታ ዋጋ ሣይገልጽ የጨረታው ተሣታፊ ሆነው ጨረታው በኋላ ግን ከባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የጨረታ ኮሚቴ ጋር በመደረራደር ጨረታውን በብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ እንደአሸነፉ ተገልጾ የጨረታው ኮሜቴ የውሣኔ ሐሣብ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቦ አለመጽቁን ነው፡፡

በመሰረቱ ማንም ሰው ሐብቱን በሐራጅ የሚሸጥ መሆኑን ባስታወቀ ጊዜ ውል ተፈፀመ ለማለት የሚቻለው በመጨረሻው ሐራጅ ለጨረታ የቀረበው ሐብት ለዋጋ አቅራቢው የተሰጠ ጊዜ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1688/2/ የተደነገገ ሲሆን የጨረታ ሥነ ሥርአትን በሚደነግጉት የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ አስራ ዘጠኝ ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መካከልም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3167/1/ አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ለጊዜው ጽ/ቤቱ ቢመረጥ ውሉ እንደተፈጸመ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1688/2/ ድንጋጌ ከፍ/ህ/ቁ. 3168 ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲታይም የጨረታውን ሥርአት ያስፈፀመው ያስተዳደር መ/ቤት የጨረታውን ውጤት በመቀበል ውሉን ፈጽሟል ሊባል የሚችለው የማጽደቅ ሥራ ከተደረገ በኋላ ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የመንግስት መ/ቤት እንደመሆኑ መጠን የግዥ፣ የሽያጭና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮችን የመንግስት የፋይናንስ አዋጅ ፣ደንብና መመሪያን መሰረት በማድረግ የሚፈጽም መሆኑ የግድ ነው፡፡ የመንግስትን የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት አድርጐ ተፈፀመ የሚባል የግዥም ሆነ የሽያጭ ስራ ስራውን እንዲያከናውን የተቋቋመው ኮሜቴ የራሱን የውሳኔ ሐሳብ ገልጾ ለመ/ቤቱ የበላይ አላፊ አቅርቦ ተገቢ ከማስወሰን ባለፈ የጨረታን ውጤቱን በተመለከተ የመጨረሻ ውሣኔ መስጠት አይችልም፡፡ የጨረታውን ውጤት በተመለከተ የመጨረሻ ውሣኔ የመስጠት ሕጋዊ ስልጣን የመ/ቤቱ የበላይ ሐላፊ ነው፡፡ የጨረታ ኮሚቴ የሚያቀርበው የውሣኔ ሐሣብ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሊሰረዝ፣ ሊሻሻል ወይም ሊፀድቅ ይችላል፡፡ በመሆኑም የኮሚቴው የውሣኔ ሐሣብ ውል እንደተፈፀመበት የሚቆጠረው በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተቀባይነትን አግኝቶ አሸናፊው ተጫራች ተለይቶ ሲጸድቅ ብቻ ነው፡፡ ህግም ጥበቃ የሚያደርገው በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የፀደቀውን የጨረታ ውጤት እንጂ የኮሚቴውን የውሳኔ ሐሣብ አይደለም፡፡ የኮሚቴው የውሣኔ ሐሣብ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከመጽደቁ በፊት ለጊዜው ለተለየው አሸናፊ መብትና ጥቅም ሊያሰጥ አይችልም፡፡

በያዝነው ጉዳይ የጨረታው ኮሚቴ ባቀረበው የውሣኔ ሐሣብ ተጠሪን የጨረታው አሸናፊ አድርጐ ተጠሪ የተመረጠበትን ምክንያት ጭምር በመግለጽ ለመ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ቢያቀርብም ሥራ አስኪያጁ በጨረታው ላይ የተከሰቱ ጉድለቶ አሉ በሚል ምክንያት የኮሚቴውን የውሣኔ ሐሣብ አለማጸደቃቸው ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ የስራ አስኪያጅ ስራ ተገቢ አይደለም ከተባለ ለሚመለከተው የበላይ የአስተደደር አካል ጥያቄ በማቅረብ ተገቢውን ምላሽ ከማግኘት በስተቀር መብትና ጥቅም ሊሰጥ የሚችል ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግንኙነት ሣይኖር መደበኛ ክስ በፍ/ቤት የሚቀርብበት አግባብ የለም፡፡ ሥራ አስኪያጁ በህጉ አግባብ አልሰሩም ከተባለ የመንግስት የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት ተገቢውን አስተዳደራዊ መፍትሔ ከመጠየቅ በስተቀር ከወዲሁ የፍትሐብሔር ክስ የሚቀርብበት ሥርአት አለ ለማለት ስለማይቻል ተጠሪ የስራ አስኪያጁ አድራጐት ሥርአት የለሽ አሰራርን ያሰፍናል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ የጨረታው ኮሚቴ የውሣኔ ሐሣብ እንደመጨረሻ ውሣኔ ታይቶ አመልካችን ለመክሰስ የሚያስችል ከህግ ወይም ከውል የመነጨ መብት የማይሰጥ በመሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠ ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በዞን ሦስት ከፍተኛ ፍ/ቤት ታህሳስ 03 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በአፋር ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 1017 ሚያዝያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር በህጉ አግባብ የፈፀመው የጨረታ ውል ስለሌለ ለጨረታ የቀረቡትን ንብረቶች ለተጠሪ እንዲያስረክብ የሚገደድበት ህጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38794

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አለ. መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሙከሚል መሐመድ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሚፍታህ ከድር - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች ታህሣሥ 03 ቀን 1994 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የንግድ ግንኙነት እንደነበራቸው፣ በመካከላቸው የተፈጠረውን ያለመግባባትም በስምምነት ለመፍታት ተስማምተው ሽማግሌዎችን መምረጣቸውንና የተመረጡት ሽማግሌዎችም ህዳር 08 ቀን 1990 ዓ.ም ውሣኔ መስጠታቸውን፣ በውሣኔው መሠረትም የጋራ ንብረት ክፍፍል ተፈጽሞ ቀሪ ብር 170,122.75 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር ከሰባ አምስት ሣንቲም/ ከአሁኑ ተጠሪ የሚፈለግና ለአመልካች የሚከፈል መሆኑ ተገልፆ በሽማግሌዎች ቢወሠንም ተጠሪ ሊከፍሉ አለመቻላቸውን በመዘርዘር ተጠሪ እንደውሣኔው እንዲፈጽሙላቸውና ወጪና ኪሣራ የመጠየቅ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ዳኝነት ጠይቀው በተጠሪ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት የአፈፃፀም ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በፍርድ ተከሣሽነት ቀርበው ከአመልካች ጋር በግልግል ወይም በሽምግልና ዳኝነት ለመዳኘት የተደረገ የግልግል ስምምነትም ሆነ የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ያለመኖሩን፣ የተደረገውም ስምምነት የእርቅ ውል ስምምነት መሆኑን፣ የእርቅ ስምምነቱ ውሣኔ ከተባለም የግልግል ቃሎችን በጽሑፍ ስላላረጋገጡ የማይገደዱ መሆኑን፣ አስታራቂ ሽማግሌዎችንም የማያውቋቸው፣ የእርቅ ስምምነቱም ጉድለት ያለበት መሆኑን እንዲሁም በ23/02/90 ዓ.ም በተደረገው ስምምነት ባለጉዳዮችን ለማስታረቅና ለማግባባት ተገልፆ እያለ ወደ ግልግል ወይም የሽምግልና ዳኝነት መሄዱ ሕጋዊነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው ሊፈፀም የሚችል ውሣኔ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመርና ምስክሮችን በመስማት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ስምምነት እርቅ /conciliation/ መሆኑንና የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3322/2/ በሚያዘው መሠረት የግልግል ቃሎችን የሚያረጋግጥ የጽሑፍ ግዴታ አለመኖሩን ጠቅሶ የአፈፃፀሙን ክስ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔን አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 3 /ሦስት/ ገጽ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የቤተዘመድ የሽምግልና ጉባዔው ያከናወነው ስራ በግራ ቀኙ በ23/02/90 ዓ.ም በተደረገው ስምምነት መሠረት የግልግል ሁኖ እያለ የእርቅ ስራ ነው መባሉ ስለእርቅና ግልግል የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ መሆኑን የሽምግልና ዳኝነቱ የተሰጠውም የግራ ቀኖችን ማስረጃ መሠረት አድርጎ ሁኖ እያለና ይኸው አካል በጥብቅ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓት እንዲከተል የሚያዝ ሕግ ሣይኖር የሽምግልና ዳኝነቱ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት አካሄድ ያልተከተለ ነው የተባለው ያላግባብ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባዔ ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀም ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተደምጧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበትና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ውድቅ የተደረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ጥቅምት 23 ቀን 1990 ዓ.ም የተደረገ ስምምነት መኖሩን፣ ከዚህ ስምምነት በኋላም ህዳር 08 ቀን 1990 ዓ.ም የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባዔ ውሣኔ መስጠቱን ነው፡፡ ስምምነቱ መኖሩን በተመለከተ የስር ፍ/ቤትም ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን ከውሣኔው ግልባጭ ተመልክተናል፡፡ የስር ፍ/ቤት የጥቅምት 23 ቀን 1990 ዓ.ም ስምምነት እና የህዳር 08 ቀን 1990 ዓ.ም በሽምግልና ጉባዔ አባላት ተሰጠ የተባለ ውሣኔ መኖሩን አምኖ ለጉዳዩ እልባት የሰጠው በሽማግሌዎች ተሰጠ የተባለው ውሣኔ የግልግል ስምምነት /arbitration/ ሣይሆን የግልግል እርቅ /conciliation/ ሆኖ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2322/2/ የተመለከተውን ድንጋጌ ያላሟላ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሠረቱ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ተብለው በአብዛኛው ከሚታወቁት መንገዶች መካከል ድርድር /conciliation/፣እርቅ /mediation/ ግልግል /arbitration/እና ስምምነት /Negotiation/ የሚጠቀሱ ሲሆን በሀገራችን ከሚሠሩት የሽምግልና ዓይነቶች ውስጥ ድርድር፣ ግልግልና እርቅ ይገኙበታል፡፡ የስር ፍ/ቤት ለጉዳዩ እልባት ሲሰጥ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባቸው የሽምግልና ዓይነቶች ድርድር /conciliation/ እና ግልግል /arbitration/ ስለሆነ እነዚህ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች በፍትሐብሔር ሕጉና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ያላቸውን ትርጉምና አፈፃፀም መመልከቱ ተገቢነት አለው፡፡

ድርድር /conciliation/ የሚባለው የሽምግልና ዘዴ 3ኛ ወገን ባለበት ግራ ቀኙ ወገኖች የሚደራደሩበት መንገድ ሲሆን 3ኛ ወገን ከመታዘብ በስተቀር በድርድሩ ጣልቃ አይገባም በፍ/ብ/ሀ/ቁ. 3318 - 3324 የተመለከቱት ድንጋጌዎችም የሚገዙት ይህንኑ ነው ግልግል /arbitration/ የሚባለው የሽምግልና ዘዴ ደግሞ ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን ለ3ኛ ወገን አቅርበው የግልግል ዳኛው የሚሰጠውን ውሣኔ የሚቀበሉበት መንገድ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3325 - 3346 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎችና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315 - 319 እና 350 - 357 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ስለግልግል አደራረግና አፈፃፀም የሚገዙ ናቸው ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ በሕጉ አግባብ የተደረጉ የግልግል ስምምነቶች ሊፈፀሙ የሚችሉ ስለመሆኑ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሀ/ቁ. 3325- 3346 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በተለይ ሲታዩም የግልግል ስምምነቶች እንደ ልዩ ውሎች ሊታዩ የሚገባ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

ስለግልግል ትርጉም የሚያስቀምጠው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3325 ግልግል ውል ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ ውል ግዴታዎች የሚቋቋሙበት፣ የሚለወጡበት ወይም ቀሪ የሚሆኑበት ስምምነት እንደመሆኑ መጠን ውል ስለመኖሩ መሟላት የሚገባቸው ነገሮች /elements/ በግልግል ስምምነትም /arbitral submission/ ተሟልተው ሊገኙ ይገባል በመሆኑም የግራ ቀኙ ወገኖች ችሎታ፣ የግልግሉ ጉዳይ ሕጋዊነት እና በሕጉ የሚፈለግ ከሆነ ፎርም ተሟልተው መገኘት የግልግሉን ስምምነት መኖሩን የምናረጋግጥባቸው ጉዳዮች ናቸው ስለሆነም በግልግል የሽምግልና ዘዴ ቀዳሚው እርምጃ ግራ ቀኙ በሕጉ ፊት የሚፀና /valid/ የግልግል ስምምነት ገብተው መገኘት ነው፡፡

በሕጉ አግባብ በተደረገ የግልግል ስምምነት መሠረት የግራ ቀኙን ጉዳይ ክርክር የግልግል ዳኛ መመልከት ከጀመረ በኋላ ሊከተል የሚገባውን ሥነ ሥርዓት በተመለከተ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3345 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 317/1/ ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ የግልግል ዳኛ ክርክሩን መምራት ያለበት በተቻለ መጠን የመደበኛ ዳኝነት አካሄድን ተከትሎ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተከራካሪ ወገኖች የመስማት፣ ማስረጃዎቻቸውን የማቅረብና የመጠየቅ መብታቸው ሊጠበቅ እንደሚገባ እና የዳኝነት አሠጣጥም በዚህ ረገድ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ሊከተል የሚገባው መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ይሁን እንጂ የግልግል ዳኛ የዳኝነት አካሄድ የመደበኛ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድን መከተል ያለበት ቢሆንም እንደ መደበኛ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድ እጅጉን የጠበቀ እንዲሆን የማይጠበቅ መሆኑን የተጠቃሹ ድንጋጌ መንፈስ ያስረዳል፡፡ በግልግል ዳኛ የሚሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 350 እና ተከታዮቹ መሠረት በበላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ እስካልተለወጠ ድረስ በመደበኛ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በሚፈፀምበት ሥርዓት ቀርቦ ሊፈፀም የሚችል መሆኑንም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3345/2/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም በግልግል ዳኛ የሚሰጥ ውሣኔ የመጨረሻ ነው የግልግል ውሉም ውል እንደመሆኑ መጠን በአግባቡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እስከተቋቋመ ድረስ ተዋዋይ ወገኖችን የሕግን ያህል የሚያስገድድ፣ በቃላቸው እንዲታሠሩ የሚያደርግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3325' ን' ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731 ጋር አጣምረን ስንመለከት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የግልግል ውል አላደረግኩም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሌለና በግልጽ ያልተካደ ስለመሆኑና ይኸው ውል ስለመኖሩ የበታች ፍ/ቤትም ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ የግልግል ውሉ ጥቅምት 23 ቀን 1990 ዓ.ም ስለመደረጉና በአመልካች፣ በተጠሪና በአቶ ሱልጣን ሸኑሪ መካከል ንብረትንና ገንዘብን አስመልክቶ የተነሣውን አለመግባባት ለማስታረቅ ጉባዔዉ መቋቋሙን፣ ጉባዔው ያየውንና የወሰነውን ለመቀበል ተዋዋይ ወገኖች የተስማሙበት እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖችና ሽማግሌዎቹ ፊርማቸውን ያኖሩበት ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ ህዳር 08 ቀን 1990 ዓ.ም የተሰጠው የግልግል ዳኞች ውሣኔም መሠረት ያደረገው ይህንኑ ውል ሁኖ ገንዘብና ንብረትን በተመለከተ ግራ ቀኙን ተዋዋይ ወገኖች በማስተማመንና በማጣራት የተዋዋይ ወገኖች ድርሻ ተለይቶ የተወሰነ መሆኑን ይገልፃል፡፡የስር ፍ/ቤት በ23/2/1990 ዓ.ም የተደረገው ሰነድ የእርቅ ስለመሆኑ አሸማጋይ የተባሉት ግለሰቦች መስክረዋል በማለትና የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3322/2/ ስር የተመለከተውን በመጥቀስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3318-3324 ስር በተመለከቱት የሚገዛ ሣይሆን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3325-3346 ባሉት ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ በ23/2/1990 ዓ.ም የተደረገው የግልግል ውል ይዘቱ ያሣያል፡፡ የህዳር 08 ቀን 1990 ዓ.ም ውሣኔ የተሰጠውም ተዋዋይ ወገኖችን በማስተማመንና ተገቢው ማጣራት ተደርጎ መሆኑ የግልግል ዳኝነት በጥብቅ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት ሥርዓት እንዲከተል ሕጉ የማይጠብቅ መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 317 ከተመለከተው ድንጋጌ አኳያ ተዳምሮ ሲታይ ጉዳዩ በግልግል / arbitration / አልታየም ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ23/02/1990 ዓ.ም በተደረገው የግልግል ውል ሠነድ ላይ ግራ ቀኙ ያስሚሟቸው ሽማግሌዎች የሚወስኑትን እንደሚቀበሉ መስማማታቸውና ውሣኔ የማሣለፍ ሥልጣኑም ለሽማግሌዎች የሰጡ መሆናቸው ተገልፆ እያለ የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው እርቅ /conciliation/ እንጂ ግልግል /arbitration/ አይደለም በማለት ተጠሪ በሽማግሌዎቹ የተወሰነውን ገንዘብ ለአመልካች ሊከፍሉ አይገደዱም ሲል የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 3325- 3346 እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315-319 እንዲሁም ከቁጥር 350-357 ድረስ የተመለከቱትን ለማስረጃነት ከቀረበው ሰነድ ይዘት ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00136 መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 60538 ሚያዝያ 09 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ ተጠሪ በሽማግሌዎቹ የተወሰነውን ገንዘብ ብር 170,122.75 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር ከሰባ አምስት ሣንቲም/ ለአመልካች እንዲከፍሉ ሊገደዱ ይገባል ብለናል፡፡

3/ የፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔውን እንዲያስፈጽም ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

4/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 39529

ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሀጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ቦሌ ክ/ከተማ የመሬትና ልማት አስተዳደር ኀ/ፈ ደረጀ ቀረበ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ግምጃ በዳኔ - በራሳቸውና ሞግዚት በሆኑላት በህፃን ብሩክ ባጫ ስም

ወኪል ብርቱካን ባጫ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሮማን ባጫ

3. ወ/ሮ ብርቱካን ባጫ

4. አቶ አሸናፊ ባጫ

5. ወ/ሪት መቅደስ ባጫ

6. ወ/ሮ ፋንቱ ባጫ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፊደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር አንደኛ ተከሣሽ ተጠሪ ከሣሽ ነበሩ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አንደኛ አመልካች በተጠሪዎች እና በስር ሁለተኛ ተከሣሽ ሥም ካርታ ሰርቷል ተጠሪዎች ካርታውን ለመውሰድ ሲፈርሙ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ለመፈረም ፍቃደኛ አልሆኑም፡፡ በመሆኑም አመልካች ተሰርቶ የተቀመጠውን ካርታ ይስጠን፣ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ቀርበው እንዲፈርሙ ይወሰንልን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

አንደኛ አመልካች በቀጠሮ ቀን መልሳቸውን ባለማያያዛቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ መልስ ሲሰጡ (በፍሬ ጉዳዩ) በግሌ የሰራሁት የቤት ቁጥር 2026ን በቤት ቁጥር 443 ጋር ካርታው ስለተሰራ ለመፈረም አልገደድም፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግና ከቀረበለት ማስረጃ አንፃር መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔውም የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ቀርበው የመፈረም ግዴታ እንዳለባቸው ተጠሪዎች በማስረጃ አላቀረቡም ስለዚህ ጥያቄውን ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፡፡

አመልካች በሕግ ካርታ የመስጠት ሥልጣንና ግዴታ አለበት በዚህም የተነሣ ካርታ የሚጠይቀውን ወገን መብት አረጋግጦ ሲቀርብ አጣርቶ ካርታ የመስጠትም ሆነ የመከልከል ግዴታ የአመልካች ነው ተጠሪዎች የሚች ሚስትና ወራሽ መሆናቸውን በሚች ንብረት ላይ መብት እንዳላቸው አረጋግጠው ካርታ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ጥያቄ በመቀበል ተጠሪዎች መብት ያላቸው መሆኑን አጣርቶ ካርታ ሊሰጣቸው ወይም የማይፈቀድበትን ምክንያት በመግለፅ ውሣኔ ሊሰጥ ይገባል ስለዚህ አመልካች የተጠሪዎችን ጥያቄ ተቀብሎ ክስ በቀረበበት ቤት ላይ መብት ካላቸው ካርታ እንዲሰጣቸው ሲል ወሰነ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካችም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 18/2000 ባቀረበው አቤቱታ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ እና በፌዴራሉ ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል ሲል ጠይቋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ላይ መብት ካላቸው አመልካች ካርታ ይሠጣቸው ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት በመመርመር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ የግራ ቀኙ ወገን ካሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ባጭሩ ስናይ ተጠሪዎች በተሠጣቸውና በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ስም በአመልካች ካርታ ተሰርቶላቸው እያለ ተጠሪዎች ካርታውን ፈርመው ለመውሰድ ፍቃደኛ ሲሆኑ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ካርታው የእኔ የግሌ የሆነውን ቤት አካቶ የተሰራ ስለሆነ ልፈርም አልገደድም ሲሉ ፍቃደኛ ያለመሆናቸውን በመግለፃቸው ምክንያት በቀረበው ክስ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ካየ በኋላ ተጠሪዎች መብት ካላቸው አመልካች ካርታ ይስጣቸው በማለት ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤትም ጉድለት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በእኛም በኩል ከሥር ፍ/ቤት የውሣኔ ሐተታ ልንገነዘብ እንደቻልነው አመልካች መብታቸውን አረጋግጦ የቀረቡለትን ወገኖች በእኩል የማስተናገድና አግባብ ያለው ምላሽ ሊሰጥ እንደሚገባው ገልጿል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ አመልካች በሕግ የተቋቋመ አስተዳደራዊ ተቋም በመሆኑ በሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ሐላፊነት መሠረት አገልግሎት የሚሠጥ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

እንግዲስ ከዚህ የአመልካች ሥልጣንና ተግባር ስንነሳ ሁለት መብት አለን ብለው የሚቀርቡለትን ወገኖች ሊያስተናግድ የሚችለው ባለው ሕጋዊ አሠራር ብቻ መሆኑን እንረዳለን በዚህ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪዎች መብት አለን በማለት ካርታው እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡ በተነጻጻሪ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽም በጉዳዩ መብት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ የተሰራው ካርታ መጠን የግሌን ቤት አካቷል በማለት ቀርበው ሊቀበሉ (ሊፈርሙ) ፍቃደኛ አልሆኑም በመሆኑም በአመልካች በኩል እነዚህን ወገኖች አለን በሚሉት መብት ለማስተናገድ ይህ የጋራቸው የሆነውን ንብረት መቀበል የሚችሉት ፈቅደው በአመልካች መ/ቤት ቀርበው ፈርመው ሲቀበሉ ብቻ ነው፡፡ አመልካች እነዚህን ወገኖች አስተዳደራዊ ተግባሩን ከመወጣት ባሻገር ሊያስገድዳቸው የሚያስችለው አሰራር የሌለው መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ አመልካችም በክርክሩ እንደገለፀው በውሣኔ ተለይቶ ያልቀረበለትንና ሁለት ወገኖች መብት አለን ብለው ያቀረቡለትን ጉዳይ ሌላኛው ባለመብት ባልቀረበበትና ባልተስማማበት ለተጠሪዎች ብቻ አስፈርሞ መስጠቱ ሌላ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ተግባር ሊሆን ይችላል፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የሥር ሁለተኛ ተከሣሽን መብት ሣያገናዝቡ ተጠሪዎች መብት ካላቸው ካርታ ይሠጣቸው በማለት አመልካችን ማስገደዱ እና የፌ.ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ሣያርመው ማለፉ የአመልካችን አስተዳደራዊ ሥራ ላይ ጫና መፍጠር ነው፡፡

ባጠቃላይ ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ስልጣን የለኝም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231 መሠረት መዝገቡን መዝጋት ነበረበት፡፡

በመሆኑም የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 99300 በቀን 27/5/2000 እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 65637 ቀን 24/08/2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤቶች አመልካችን ካርታ እንዲሠጥ ሊያስገድዱ የሚችሉበት ሥልጣን የላቸውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ይቻቻሉ

መዘገቡ ወደ መዘገብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 40752

ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሠ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች ፡- እነ ወ/ሮ ኤክራም መሃመድ /2 ሠዎች/ - ጠ/አብደላ አሊ ቀረበ

ተጠሪ ፡- አቶ ዘኪ መሐመድ - አልተጠሩም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው በአፈፃፀም ጉዳይ ሊከፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ የሚመለከት ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪ በነበራቸው የውርስ ንብረት ክፍፍል ክርክር ጉዳያቸው በቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ከተወሰነ በኋላ አፈፃፀሙን በተመለከተ በፌ/ከፍተኛ ሽሪአ ፍ/ቤት አንስቶ እስከ ፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት ድረስ ደርሶ ውሣኔ አግኝቷል፡፡ ነገር ግን በፍ/ቤት በተሠጠው የአፈፃፀም ውሣኔ መሠረት ሊፈፀም ባለመቻሉ ግራ ቀኙ አፈፃፀሙን በተመለከተ ስምምነት አድርገው ስምምነቱን እንዲመዘግብላቸው የፌ/ከፍተኛ ሽሪአ ፍ/ቤት ጠይቀው ፍ/ቤቱ ጥያቄያቸውን ውድቅ በማድረግ የፌ/ጠቅላይ ሽሪአ ፍ/ቤት በሠጠው ውሣኔ ኋላም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት ባፀናው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀምና የዳኝነት ብር 23,886(ሃያ ሦስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ስድስት) እንዲከፈል ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ለፌ/ጠቅላይ ሽሪአ ፍ/ቤት ይግባኝ ጠይቀው ፍ/ቤቱም የፌ/ከፍተኛ ሽሪአ ፍ/ቤት ዕርቁን የማይመዘግብበት ምክንያት የለም በማለት ዕርቁን እንዲመዘግብ ሲወስን የዳኝነት እንዲከፈል የተሠጠውን ውሣኔ ግን አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካቾች ጥያቄም በህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177/1945 አንቀፅ 2/ሠ/ መሠረት ግምቱ ከብር 10,000(አስር ሺህ) በላይ ለሆነ አፈፃፀም ጉዳይ ዳኝነት መከፈል ያለበት ብር 25.00(ሃያ አምስት) ብቻ ሆኖ ሣለ 23,886(ሃያ ሦስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስድስት) ብር እንዲከፈል መወሠኑ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም ለቀረበው የአፈፃፀም ክስ እንዲከፈል የተወሠነው ገንዘብ ህግን መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ የቀረበው ጥያቄም የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈልን በሚመለከት በመሆኑ ተጠሪው በተከራካሪነት መቅረብ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ባለመገኘቱ መዝገቡ ባለበት ሁኔታ ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት እንደተረዳነው ለሠበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው የውርስ ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ የግልግል ዳኞች የሠጡት ውሣኔ እንዲፈፀም በቀረበ የአፈፃፀም ክስ ነው፡፡ ስለፍ/ቤቶች ዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል የወጣው የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177/1945 አንቀፅ 2/ሠ/ እንደሚያመለክተው ከብር 10,000 /አስር ሺህ/ በላይ ለሆነ የአፈፃፀም ክስ ሊከፈል የሚገባው በዳኝነት ገንዘብ ብር 25.00 /ሃያ አምስት/ ብቻ መሆኑን በግልፅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው የአፈፃፀም ክስ የፍ/ቤት ዳኝነት ገንዘብ አከፋፈል አስመልክቶ ከወጣው ህግ ውጪ ከፍተኛ ገንዘብ እንዲከፈል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1210/93 በ15/07/2000 ዓ.ም. እንዲሁም የፌ/ጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26/2000 በ7/11/2000 ዓ.ም. የዳኝነት ገንዘብ አከፋፈልን አስመልክቶ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የአፈፃፀም ክስ ሲቀርብ የፍርድ ባለመብቱ ተገቢውን የአፈፃፀም ዳኝነት የከፈሉ በመሆኑ አመልካቾች ብር 23,886 /ሃያ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ ስድስት/ በድጋሚ ሊከፍሉ አይገባም ብለዋል፡፡
3. አመልካቾች የከፈሉት በተ.ቁ. 2 ሥር የተጠቀሰው ገንዘብ ለአመልካቾች ሊመለስላቸው ይገባል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይካበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሸ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 40133

ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት - አቶ ግሩም ሙላት - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- በሶማሌ ብ/ክ/መንግሥት የፊልቱ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ገቢዎች ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አሊኑር አቤከር - ቀርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 20/2000 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታው የሶማሌ ብሔራዊ ክልልዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 145/99 ግንቦት 26/2000 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የሊበን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. M105/02/07/99፣ ሰኔ 18/1999 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተቀብሎ በማጽደቁ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለፈፀመ ፍርድ ይሻርልኝ በማለቱ ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤቱ በተካደው ክርክር የአሁኑ ተጠሪ ከሣሽ፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ የነበሩ ሲሆን፣ ሥር ከሣሹ ያቀረበው ክስ አጭር ይዘቱ ተከሣሹ በፊደልቱ መጠጥ ውሀ ፕሮጀክት ስለሚያካሂደው ሥራ መክፈል የነበረበት ብር 183,744 /አንድ መቶ ሰማኒያ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ አርባ አራት ብር/ የሥራ ግብርና ሌሎች ተቀናናሽ ክፍያዎች ባለ መክፈሉ የልማት መስተጓጎል በማድረሱ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን በማስረጃነትም ተከሣሹ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው የግብር አይነት ለወረዳው እየከፈለ እንደነበር የሚያሳዩ ደረሰኞች አቅርቧል፡፡ ሥር ተከሣሹም በበኩሉ በሰጠው መልስ የተጠቀሰው የግብር ዓይነት ለወረዳው /ለከሳሹ/ እየከፈለ ቢቆይም የፊደራል አገር ውስጥ ገቢ ለክልሉ ባስተላለፈው ትእዛዝ መሠረት ግብሩን መክፈል ያለብኝ ለአገር ውስጥ ገቢ እንጂ ለከሣሽ እንዳልሆነ በማወቁ መከፈሉን አቋርጫለሁ፤ ስለሆነም ከሣሽ ያቀረበብኝ ክስ በማይመለከተው ጉዳይ ሰለሆነ ውድቅ ይደረግልኝ ብሏል፡፡ ከመልሱ ጋር በማያያዝም ጉዳዩን በሚመለከት የተፃፉ የተለያዩ ደብዳቤዎችና የፊደራል መንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ አቅርቧል፡፡

የሥር ፍ/ቤቱም ከላይ በተቀመጠው መልኩ ለቀረበለት ክርክር እልባት ለመስጠት አከራካሪው የሥራ ግብር ለማን መከፈል አለበት የሚል ጭብጥ በመያዝ በሰጠው ፍርድ ምንም እንኳ ተከሣሹ የፊደራል መንግሥት የልማት ድርጅት እንደሆነና በአዋጅ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ መሠረትም የፊደራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች አከራካሪውን ግብር ለአገር ውስጥ ገቢ መክፈል እንዳለባቸው ቢገልጽም ድንጋጌው በፊደራል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 96/3/ም በአዋጅ ቁጥር 33/85 አንቀጽ 4 የተቀመጡትን መርሆዎች መሠረት ባደረገ ሁኔታ የተቀረፀ አይደለም፤ ማለትም ግብሩ ገቢ መሆን ያለበት የገቢው ምንጭ ለሆነው ወረዳ ስለሚገልጹ በአዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ 5/2/ሐ/ የተመለከተው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከሣሹ የተከሰሰበትን ጠቅላላ ብር 183,744 /አንድ መቶ ሰማኒያ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ አርባ አራት ብር/ የሠራተኞች የሥራ ግብር እንዲሁም ብር 7000 /ሰባት ሺህ/ የዳኝነት ገንዘብ በአጠቃላይ ብር 190,744 /አንድ መቶ ዘጠና ሺህ ሰባት መቶ አርባ አራት ብር/ ለከሣሹ መክፈል እንዳለበት ወስኗል፡፡

ሥር ተከሣሹም የፊደራል መንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑ በመግለጽ የሰበሰበውን የሥራ ግብር በአዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ 5 መሠረት ገቢ ማድረግ የሚገባው ለፊደራል አገር ውስጥ ገቢ መሆኑ በግልጽ እየታወቀና የሶማሌ ክልል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የገቢዎች ቢሮ በቁ. ኤክስኦ/ ኦኦጄ/3442/3ዐዐ2 በቀን ዐ9/5/99 ዓ.ም. የፃፈውን ደብዳቤ ወደ ጎን በመተው ተገቢ ያልሆነ ትርጉም በመስጠት ግብሩ ለከሳሹ እንድከፍል መወሰኑ ተገቢነት የለውም በማለት ለሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢልም ፍ/ቤቱ በፍ/ይ/መ/ቁ. 145/99፣ ግንቦት 26/2ዐዐዐ ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ ግብሩን እንዲከፍሉ የተደረጉት የይግባኝ ባይ ሠራተኞች የሶማሌ ክልል ተወላጆች በመሆናቸው፣ በጀቱም የክልሉ በመሆኑ እና የሥራ ቦታውም በሶማሌ ክልል ውስጥ በመሆኑ የሚሉትን ምክንያቶች በማስቀመጥ አከራካሪው የሥራ ግብር ገቢ መሆን ያለበት ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ሳይሆን ለክልሉ /ለከሣሹ ወረዳ/ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

ከላይ የሰፈረውን ፍርድ በመቃወምም አመልካች ሰኔ 2ዐ/2ዐዐዐ ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፤ መሠረታዊ ይዘቱም አመልካች በፌዴራል የልማት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁ. 1ዐ9/96 የተቋቋመ የልማት ድርጅት መሆኑ እና የሠራተኞችን ደሞዝና ሌሎች ተቀናናሾች ግብር ለፌዴራል ሃገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን የሚከፈለውን ክፈያ በሶማሌ ክልላዊ መንግሥት ለፊደልቱ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ገቢዎች ቢሮ ክፍያውን እንዲፈፀም የሥር ፍ/ቤቶቹ ውሣኔ መስጠታቸው የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 96/3/ እና አዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ 5/2/ሐ/ ያሰፈሩትን መርህ በመፃረር ስለሆነና ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የሕግ ስህተቱን ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ፍ/ቤትም አከራካሪው የሠራተኞች ግብር መከፈል ያለበት ለማን መሆኑ አከራክሮ ለመወሰን ሲል ጉዩን ወደ ሰበር ችሎት ያስቀረበው ሲሆን ግንቦት 13/2ዐዐ1 ዓ.ም. ግራ ቀኙ ወገኖች የቃል ክርክር አድርገዋል፣ በተጨማሪም ተጠሪው ግንቦት 14 ቀን 2ዐዐ1 ዓ.ም. የተፃፈ የጽሁፍ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጓል፤ አመልካቹ በቃል ክርክሩ ያሰፈረው ሃሣብ በሰበር አቤቱታው ከዘረዘረው የተለየ ባለመሆኑ ደግሞ መዘርዘር ሳያስፈልግ ታልፏል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪው በቃልም ሆነ በጽሁፍ በሰጠው መልስ አመልካቹ የፌዴራል ተቋም ሰለመሆኑ ያስረዳበት ሁኔታ የለም፤ የሥር ፍ/ቤቶቹ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 96/3/ ይዘት አላዛቡም፤ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 97/1/ መሠረት ግብርና ቀረጡ የመሰብሰቡ ስልጣን የእኔ ነው፤ ሕገ-መንግሥቱም ሆነ አዋጅ ቁ. 33/1985 እንዲሁም መመሪያዎች ከወረዳው ሠራተኞች የተሰበሰበው የሥራ ግብር መከፈል ያለበት ለወረዳው እንደሆነ የሚደግፉ እንጂ የሚፃረሩ አይደሉም፤ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 1ዐዐ/1/ እና አዋጅ ቁ. 33/85 እራስን በራስ ከማስተዳደር ትርጉምና ዓላማ ጋር ተያይዘው ሲታዩ የክልሎች ሕልውና መሠረቱ የክልሉን ገቢ መሰብሰብና ማስገባት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶቹ የሰጡት ትርጉም ተገቢ ነው፤ የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ለሶማሌ ክልል፣ ለፊደልቱ ወረዳ ፋይናንስ ቢሮ አስተላለፈ የተባለው መመሪያ ሕገ-መንግሥታዊ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ሊቀበለው አይገባም፤ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶቹ ውሣኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

እንግዲህ የግራ ቀኙ ወገኖች የክርክር አመጣጥ ከላይ ተዘርዝሮ የተቀመጠውን ሲመለከት፣ ይህ ፍ/ቤትም፣

1. አመልካቹ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት ነው? ወይስ አይደለም?
2. አመልካቹ ከሠራተኞቹ የሰበሰበው የሥራ ግብር ገቢ መሆን ያለበት ለፌዴራል መንግሥት አገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ነው? ወይስ ለተጠሪው?

የሚሉትን መሠረታዊ ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪው በዚህ ሰበር ችሎት ባደረገው ክርክር አመልካቹ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑን የሚያስረዳለት ማስረጃ አላቀረበም ብሏል፡፡ ይህ ክርክር የተነሳው አሁን እንጂ በሥር ፍ/ቤቶቹ ባካሄዱት ክርክር ያልተነሣ ነው፤ ይሁን እንጂ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 1ዐ9/1996 አመልካቹ የፌዴራሉ መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ እንደ ተቋቋመ በግልጽ የሚታወቅ ነው፤ ስለሆነም አመልካቹ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም በማለት ተጠሪው በዚህ ችሎት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ሁለተኛው ጭብጥ በሚመለከት ደግሞ ተጠሪው በአመልካቹ ላይ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ቀደም ብሎ ሲያደርገው እንደነበር አመልካቹ ከሠራተኞቹ የሚሰበስበውን የሥራ ግብር ለእኔ ገቢ ሊያደርግልኝ ይገባል ሲል አመልካቹ በሰጠው መልስ ደግሞ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑን በማስመር በአዋጅ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ መሠረት የሰራተኞቹ የሥራ ግብር ገቢ የማድረግ ግዴታው ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ እንጂ ለተጠሪው እንዳልሆነ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪውም አዋጅ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ ከሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 97 እና 1ዐዐ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሰፈሩት የክልሎች ሥልጣንና መርሆዎች የማይጣጣም ነው በማለት በወረዳ ውስጥ ለሚከናወን የክልል ፕሮጀት እንዲሁም የወረዳው ነዋሪ ከሆኑ የአመልካቹ ሠራተኞች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር ገቢ ማድረጉ ሕገ-መንግሥታዊ መብቱና የፌዴራል ሥርዓቱ መሠረት መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ አዋጅ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች ከሠራተኞቹ የሚሰበስበው የሥራ ግብር ለፌዴራል መንግሥቱ ገቢ መሆን እንዳለበት በግልጽ አስፍሯል፤ ተጠሪው በዚህ ሰበር ችሎት ያደረገው ክርክር ሲታይም የዚህ አዋጅ /አንቀጽ/ ይዘት ካለመገንዘብ የሚመነጭ አይመስልም፤ የተጠቀሰው የአዋጁ አንቀጽ ከሕገ መንግሥቱ ጋር ተስማሚ አይደለም የሚል እንድምታ ያለው ክርክር እንደቀረበ ነው፤ የሥር ፍ/ቤቶቹም የተጠሪውን ክርክር እንዳለ በመውሰድ አዋጁ ተጠሪው ከመልካቹ አከራካሪውን ግብር እንዳይሰበስብ የመከልከል ብቃት የለውም በማለት ወስነዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 97 የክልሎች የታክስና ግብር ስልጣን የሚመለከት ሲሆን በዚህ አንቀጽ ከሰፈሩት የክልሎች ስልጣናት ውስጥ የፌዴራል መንግሥቱ የልማት ድርጅቶች ከሰራተኞቻቸው የሚሰበስቡት የሥራ ግብር ገቢ የማድረግ መብት እንዳለባቸው አላሰፈረም፤ በአንፃሩ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 96/3/ እንደደነገገው ይህ አይነቱ ገቢ የፌዴራል መንግሥት ገቢ እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች የሥራ ቦታ አድማስም የግድ የፌዴራል መንግሥቱ ከተሞች በሆኑት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን እንዳግባብነቱ የሥራ አድማሱ በክልሎችም ውስጥ ሊከናወን የሚችል ነው፡፡ የሚቀጥሯቸው ሰራተኞችም የግድ በተጠቀሱት ከተሞች ብቻ የሚወሰን ሳይሆን እንደ ሁኔታው በተለያዩ ክልሎች ነዋሪና ተወላጅ የሆኑ ሠራተኞች ሊኖሯቸው እንደሚችል ነው፡፡ በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 96/3/ እና በአዋጁ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ የተመለከተው ቁልፉ ነገር ሠራተኛው በፌዴራል የልማት ድርጅቱ ውስጥ የተቀጠረ ነው? ወይስ አይደለም? ከሚል ነጥብ አኳያ መታየት ያለበት ነው፡፡ የሠራተኛው የትውልድ ወይም የነዋሪነት ቦታ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በየትኛውም ክልል ወይም ከተማ ቢሆን ሠራተኛው የፌዴራል መንግሥቱ የልማት ተቋም በሆነ አካል ተቀጣሪ ከሆነ ከዚህ ሠራተኛ የሚሰበሰበው የሥራ ግብር በአዋጅ ቁ. 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ መሠረት ገቢ የሚደረገው ለፌዴራል መንግሥቱ እንጂ ለክልሎች አይደለም፡፡ ይህ የገቢ ክፍፍል ስርዓትም በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 97 እና 100 ከተዘረዘሩት ስልጣናት መርሆዎች የሚጋጭ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶቹ አመልካቹ የሚያከናውነው ፕሮጀክት በተጠሪ ውስጥ በመሆኑ እና ሠራተኞቹም የወረዳው ነዋሪዎች ናቸው በማለት በአዋጅ ቁጥር 33/1985 አንቀጽ 5/2/ሐ/ የሰፈረውን ድንጋጌ በሚመለከት የሰጡት ትርጉምና የደረሱበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 145/99፣ ግንቦት 26/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የሊበን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. M105/02/07/99 ሰኔ 18 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡
2. አመልካቹ የፌዴራሉ መንግሥት የልማት ተቋም በመሆኑ ከሠራተኞቹ የሚሰበስበውን የሥራ ግብር ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ለፌዴራሉ መንግሥት እንጂ ለተጠሪው አይደለም ብለናል፡፡
3. ጎዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተላለፈው እግድ ተነስቷል፣ ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
5. ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፤ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አ ሰ ሪ ና ሠ ራ ተ ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41385

ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ጊጋ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር - ሰላማዊት አስደግድግ

ተጠሪዎች፡- 1. ተረፈ ዘርጋው - ቀረበ

2. ፀጋዬ ደበበ - ቀረበ

3. ገመቹ ኡርጋ - ቀረበ

4. በቀለ መኮንን - አልቀረቡም

5. ዑመር መሐመድ - ቀረበ

6. ተስፋዬ ገረመው - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኞች መካከል የተነሳውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት አመልካች በሚያካሂደው የሕንፃ (ኮንስትራክሽን) ስራ በአናሚነት፣ በብረት ስራ እና በፊራዮ ስራ ሲሰሩ መቆየታቸውን ገልጸው አመልካች ከሕግ አግባብ ውጪ የስራ ውላቸው ስላቋረጠባቸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው በመጠየቅ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው በአገሪቱ ባጋጠመው የግንባታ እቃዎች (ብረትና ሲሚንቶ) እጥረት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ ተጠሪዎችን ሲያሰናብት የጥሬ እቃው ሲገኝ ተመልሰው እንዲሰሩ በማስታወቂያ በመግለጽ እንደሆነም በመልሱ ላይ አመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ስንብቱ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 30 መሰረት የሚደገፍ እንደሆነ ገልጾ መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡

ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፣የግንባታ እቃዎች እጥረት አጋጥሞአል በሚል የተደረገ ስንብት በመሆኑ እርምጃው ሕገ-ወጥ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪዎች የጠየቁትን ክፍያ በሙሉ እንዲያገኙ ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት የቀረቡት አንደኛ፣ሁለተኛ፣ ሦስተኛ እና ስድስተኛ ተጠሪዎች በተገኙበት ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አራተኛ እና አምስተኛ ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ እነሱ በሌሉበት ተሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እንደተገለጸው አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ስራ ተጠናቆአል በሚል ሳይሆን፣ለህንፃው ስራ አስፈላጊ የሆኑት የግንባታ እቃዎች እጥረት አጋጥሞአል በማለት ነው፡፡ ምክንያቱ ይህ በመሆኑም የግንባታ እቃዎቹ ተሟልተው ሲገኙ ተጠሪዎች ተመልሰው ሊሰሩ እንደሚችሉ በማስታወቂያ የገለጸላቸው ስለመሆኑ ተመልክቶአል፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የግራ ቀኝ ወገኖች ምስክሮች የተሰሙ ሲሆን፣ምስክሮቹ በሰጡት ቃልም በእርግጥ የተባሉት የግንባታ እቃዎች እጥረት ስለማጋጠሙ ተረጋግጦአል፡፡ በመሆኑም እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ይህን መሰል ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ አሰሪ ሰራተኞችን ቢያሰናብት እርምጃው ሕገ-ወጥ ነው የሚባልበት አግባብ ምንድነው? የሚለው ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው አምልካች የስንብት እርምጃ የወሰደው ከህንፃው ስራ ጠባይ በመነሳት የተወሰኑ ስራዎች ተጠናቅቀዋል በሚል አይደለም፡፡ ይህም ሆኖ ግን የህንፃውን ስራ ለማስቀጠል የማይችልበት ደረጃ ላይ ስለመገኘቱ አልተካደም (አላከራከረም)፡፡ በመሆኑም ስንብቱ በአዋጁ አንቀጽ 30 በተመለተው ድንጋጌ የሚሸፈን ነው የሚለው የአመልካቹ ክርክር መቀበል የሚቻል ባይሆንም፣ስራው በእርግጥ የለም(ቆሞአል) እየተባለ አመልካች የስንብቱን እርምጃ መውሰድ አልነበረበትም? የሚለው በስር ፍ/ቤቶች የተደረሰው ድምዳሜ ግን ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

በአሰሪ አነሳሽነት ስለሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ በሚመለከት በአዋጁ ከአንቀጽ 26 እስከ 30 ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ አሰሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የስራ ውሉን የሚያቋርጥባቸው ሁኔታዎች በአንቀጽ 28 የተቀመጡ ሲሆን፣ከእነዚህም ውስጥ ከድርጅቱ ድርጅትዊ አቋም ወይም የስራ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የተቀመጠ ንኡስ አንቀጽ /2/ ይጠቅሳል፡፡ ሰራተኞች የተሰማሩባቸውን ስራዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቀጥታና ለዘላቂታው የሚያስቆም የሰራተኞች ቅነሳ የሚያስከትል ሁኔታ ሲከሰት አሰሪው በማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል (ሁኔታው የስራ ውሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ተደርጐ እንደሚወሰድ) በተጠቀሰው ንኡስ አንቀጽ/2/ /ሀ/ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች ባጋጠመው የግንባታ እቃዎች እጥረት የተነሣ የጀመረው የህንፃ ስራ ማስቀጠል አልቻለም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በአናዒነት፣በብረት እና በፈራዮ ስራ ቀጥሮ ሲያሰራቸው የነበሩትን ተጠሪዎችን ይዞ የሚጓዝበት ሁኔታ የለም ማለት ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም ያለውን ብቸኛ አማራጭ ማለትም የስራ ውሉን የማቋረጥ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ እርምጃውን መውሰድ ያለበት ግን በሕጉ የተቀመጠውን ግልጽ ስርዓት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ሥርአቱ አስቀድሞ ማስጠንቀቅያ መስጠት ሲሆን፣አመልካች ግን ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ አልሰጠም፡፡ ስለዚህም አመልካች የስራ ውሉን ማቋረጡ ተገቢ ቢሆንም፣ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ የተነሣ ሊኖርበት ከሚገባ ሐላፊነት ግን የሚድን አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ መስጠት ከነበረበት የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ የግንባታ እቃዎች እጥረት አጋጥሞአል በሚል የተደረገ የስራ ስንብት ሕገ ወጥ ነው የሚለው የስር ፍ/ቤቶች ድምዳሜ ግን ሕጉን ያላገናዘበ በመሆኑ በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39571 ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 70771 ጎንደር 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረው የሥራ ውል ያቋረጠው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ማስጠንቀቂያ ባለመስጠቱ እንዲከፍል የተወሰነበት ገንዘብ ይክፈል፡፡ ሌሎቹን ክፍያዎች ግን አይከፍልም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 42361

ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ወ/ሪት ትዕግስት ንጉሴ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ኤስ.ኦ.ኤስ.ኢንፋንት ኢትዮጵያ - ነ/ፈጆ አያንቱ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ የአሁኗ አመልካች ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ የስራ ውሉን አቋርጧል በማለት የመሰረቱት ክስ ከታየ በኋላ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ እርምጃው ሕገ-ወጥ በመሆኑ አመልካችን ወደ ስራ እንዲመልሳቸው በመ/ቁ 38316 ከወሰነላቸው በኋላ አመልካች ወደ ስራ ቢመለሱ ከተጠሪ ጋር መልካም የሥራ ግንኙነት እንደማይኖራቸው ገልፀው ለሕገ-ወጥ ስንብት የሚከፈሉ ክፍያዎችንና የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት የአፈፃጸም ማመልከቻ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የካሳ፣ ስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ትዕዛዝ ሠጥቶ የፕሮቪደንትና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያን ግን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘትም አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ታህሣስ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 4(አራት) ገፅ የሠበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪም በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሱን ሠጥቷል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው አመልካች በስር ፍርድ ቤት በመሰረቱት ዋና ክስ ላይ የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄ ማንሳታቸውን ተጠሪ ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ ፕሮቪደንት ፈንድ ያለመኖሩንና ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ ለፕሮቪደንት ፈንድ የተቆረጠ ምንም ገንዘብ ያለመኖሩን በመግለፅ መከራከሩን ነው፡፡ በዚህ በግራ ቀኙ ክርክር ማስረጃ ተመርምሮ ተገቢው ዳኝነት አልተሠጠበትም፤ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ የአሳረፈው የስራ ውል መቋረጡ ሕገ-ወጥ በመሆኑ ላይ ሲሆን፤ የሠጠውም መፍትሔም (Relief) አመልካች ወደ ስራቸው እንዲመለሱ የሚል የነበረ መሆኑንም ተረድተናል፡፡ አመልካች በፍርድ ቤቱ ውሣኔ መሠረት ወደ ስራ መመለሱን በመተው በምትኩ የተለየዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

በመሠረቱ ወደ ስራ እንዲመለስ የሚል ውሣኔ ያገኘ ሠራተኛ ከዚህ ውሣኔ በኋላም ቢሆን ወደ ስራ ለመመለስ ፍላጎት ከሌለው ካሣ ተከፍሎት ከስራ እንዲሰናበት በማድረግ የሥራ ክርክሩን የሚወስነው አካል ሊወሰን እንደሚችል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 43(3) ስር አስቀምጧል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለውም ቀድሞ የተወሰነ ውሣኔ ከመፈጸሙ በፊት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ወደ ስራ ሊመለሱ ይገባል ተብሎ የተወሰነው ውሣኔ ከመፈፀሙ በፊት በምትኩ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለውኝ ልሰናበት የሚል የአፈፃፀም ማመልከቻ ማቅረባቸው ግራ ቀኙን ያከራከረ ነጥብ አይደለም፡፡ አከራካሪው ነጥብ የፕሮቪደንት ክፍያ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ጥያቄውን ያልተቀበሉት ወደ ስራ የመመለስ አማራጭ ቀርቶ በአዋጁ አንቀፅ 43/3/ መሰረት በካሳ ሠራተኛው እንዲሰናበት ሲደረግ በአፈፃፀም ሊጠየቅ የሚችለው በዋናው የፍሬ ነገር ክርክር ውሳኔ ያላገኘ ክፍያ አይደለም በሚል ነው፡፡ በእርግጥ በአፈፃፀም ሊጠየቅ የሚገባው ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓቱ ከቁጥር 371 ጀምሮ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(3) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ ሳይሰጥ ከተጠየቁት ዳኝነቶች መካከል ወደ ስራ የመመለስ ጥያቄ ላይ ብቻ ውሳኔ ከተሠጠ እና ሰራተኛው ወደ ስራ መመለስ ሳይፈልግ ሲቀር ቀድሞ ዳኝነት በጠየቀባቸው ነገር ግን ውሳኔ ባላረፈባቸው ነጥቦች ላይ ዳኝነት ሊጠይቅ እንደሚችል ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ጥያቄው ሲቀርብ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የቀረበ ማስረጃ በተገቢው መንገድ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ነው፡፡ የአመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ ጥያቄ በተጠሪ በኩል ክርክር የቀረበበት ነው፡፡ ወደ ስራ እንዲመለስ ለተወሰነለት ሰራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፈል የሚወሰንበት የሕግ አግባብም የለም፡፡ እንዲሁም የፕሮቪደንት ፈንድ እንደሌሎች ከአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የሚመነጩ የመብት ጠያቂዎች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ስር በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ ገደቦች የሚታገድ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 ድንጋጌ ስር በተመለከተው የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ የሚታገድ ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሠ/መ/ቁ 32545 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች የፕሮቪደንት ክፍያ ጥያቄ በአፈፃፀም መዝገብ ሳይሆን ሌላ የዋና ክርክር መዝገብ ከፍተው ተገቢ ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42459 ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ እና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 68296 መስከረም 10 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42818

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ - ነገረ ፈጅ ወልደማርቆስ በጋሻው

ተጠሪ፡- ወ/ር ሙለታ ገዳ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ተጠሪ በሌላ መስሪያ ቤት በትርፍ ሰአት ተቀጥሮ መስራቱ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 እንደተሻሻለ እና በአመልካች የሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል በቂ ምክንያት ባለመሆኑ አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው አላግባብ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ሐምሌ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ያለ አሰሪው ፈቃድና እና እውቅና በሌላ መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መገኘቱ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 27 ንኡስ አንቀጽ 1/ሐ/ እና በሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ያለ ማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚችል ምክንያት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ጥፋቱ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል አይደለም ብለው መወሰናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪ በበኩላቸው በትርፍ ሰአት ሌላ ስራ ለመስራት የአሰሪው ፈቃድ መጠየቅ አያስፈልግም፡፡ በአመልካች ሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት ስለመሆኑ አልተደነገገም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጽሑፍ ተከራክሯል፡፡ ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪን ከስራ ለማሰናበት የሰጠው ምክንያት በትርፍ ሰአት ሌላ መስሪያ ቤት መስራቱ ሰራተኛውን ያለ ማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት ስለመሆኑ በአመልካች የሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ያልተደነገገ መሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ በማስቀረብ አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች ተጠሪን ለማሰናበት የሰጠው ምክንያት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 በግልጽ የተደነገገ ምክንያት አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅና የአመልካችን የሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ሲተረጉሙ የፈጸሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያላገኘን በመሆኑ በፍታብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 348 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት አጽንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41767

ኅዳር 8 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ተካ ገ/መድህን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አድማስ ደምሳቸው የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ታህሣሥ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ከጥር 25 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ለአመልካች በጉዳይ አስፈፃሚነት ሲያገለግሉ መቆየታቸውን ገልፀው ለስንብት የሚያበቃ ምክንያት ሳይኖር ወይም ቢኖርም እንኳ ከታወቀ ከአንድ ወር በኋላ ያሰናበታቸው በመሆኑ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እና የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸው እንዲሰናበቱ በጠየቁት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ስንብቱ የተፈፀመው ተጠሪ ሌላ ቦታ በመስራታቸው መሆኑንና ይህንንም እንደአወቀ የስንብቱ እርምጃ መፈፀሙን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች ተጠሪን ባሰናበተበት ጊዜ በቂ እና ሕጋዊ ምክንያት ያልነበረው መሆኑን በመግለጽ ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው በሚል ምክንያት ተጠሪ የስድስት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራቸው ሊመለሱ ይገባል፣መመለስ ካልፈለጉ ተገቢ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይደረግ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ስንብቱ የተፈፀመው ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ድርጊት ከተፈፀመ ሰላሳ የስራ ቀናት ከአለፉ በኋላ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ በይርጋ ይታገዳል፣የአመት እረፍት የሁለት ዓመቱ ለተጠሪ ሊከፈላቸው አይገባም ሲል ምክንያቱን ለውጦ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ኅዳር 30 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ የሰበር ማመልከቻ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም፡- ስንብቱ ጊዜውን ጠብቆ የተደረገ አይደለም ተብሎ ሕገ-ወጥ ነው መባሉ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ማስረጃ ባግባቡ ባለመመልከቱና ጊዜ አቆጣጠሩም ግልጽነት በሌለው ሁኔታ ተሰልቶ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም ይገባል በማለት መከራከሪያቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አመልካች ተጠሪን በመጀመሪያ ከሥራ ያሰናበተበት ምክንያቱን ተመርኩዞ ለስንብት የሚያበቃ ምክንያት የለም ተብሎ እና በተጨማሪም የስንብት ምክንያቱ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ሐምሌ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመርነው አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው በአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ መሰረት በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ አይደለም ተብሎ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የአመልካች መስሪያ ቤት ሰራተኛ ሆነው በሚሰሩበት ወቅት በሌላ ቦታ መስራቱ ሲታወቅ አመልካች የስራ ውሉን በማቋረጥ ያሰናበታቸው መሆኑንና ተጠሪም ይህንኑ ፍሬ ነገር ሳይክዱ የሚከራከሩት ስንብቱ የተፈፀመው ሰላሳ የስራ ቀናት ከአለፉ በኋላ ነው በሚል መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪም ሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የድርጊቱን መፈፀም ያወቀበት ጊዜ በማለት የሚቀበሉት ነሐሴ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሆን የስንብት ደብዳቤ ተሰጠ የሚባለው ደግሞ መስከረም 21 ቀን 2000 ዓ.ም ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ አጥብቀው የሚከራከሩት ይህ ጊዜ ቢያገዝ እንኳ የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ አላለፈም በማለት ነው፡፡ እኛም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ጊዜውን ስናሰላው ከነሐሴ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጳጉሜ 06 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ አስራ አምስት፣ከመስከረም 01 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የስንብት ደብዳቤ አስከተፃፈበት እስከ መስከረም 21 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ደግሞ 13 ተከታታይ የስራ ቀናት መኖራቸውን አረጋግጠናል እነዚህ ቀናት በጠቅላላው 28 ናቸው በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27/3 መሰረት አንድ አሰሪ ህጉ በተፈቀደው ምክንያት መሰረት የሥራ ውሉን የሚያቋርጥበት ጊዜ የስራ ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱ ካወቀበት ከሰላሣ የስራ ቀናት በኋላ ከሆነ በይርጋ እንደሚታገድበት ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ከላይ እንደተመለከተው ሰላሳ ተከታታይ የሥራ ቀናት ከማለፋቸው በፊት አመልካች እርምጃውን ወስዷል፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ድምዳሜ ጊዜውን በተመለከተ ካላንደሩን ባግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የአመልካች እርምጃ በሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ የሚታገድበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስንብቱ መሰረት ያደረገበትን ምክንያት በቂ መሆን ያለመሆኑን ስንመለከተው ተጠሪ አመልካች የማታለል ተግባር ፈጽሟል በማለት የሚያቀረበውን ክርክር ጉዳዩን አመልካች ያውቅ ነበር ከማለት ውጪ ድርጊቱ መፈፀሙን የካዱት ነጥብ አይደለም፡፡ አንድ ሰራተኛ በአሰሪው ላይ የማታለል ተግባር መፈጸሙ ከተረጋገጠ አሰሪው የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ ሕጋዊ መብት ያለው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሐ/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ አሰሪ ግልጽ የሆነ ፈቃድ እስካልሰጠ ድረስ ሰራተኛው በሁለት ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ መስራቱ ከታወቀ አድራጐቱ በስራ ላይ የተፈፀመ የማታለል ተግባር ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይሆንም፡፡ በምርትና ምርታማነት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል በመሆኑ የስራ ውሉን ለማቋረጥ ሕጋዊ እና በቂ ምክንያት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 39185 ሰኔ 13 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 68366 ጎንደር 22 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበትው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 42923

ህዳር 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ታፈሰ ይርጋ

5. አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ነጃት አባስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት ያደረገ የደመወዝ ማስተካከያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘት፤ የሁለት ዓመት የሥራ ልምድ የሚጠይቅ በሙሉ ስታትስቲሺያን የሥራ መደብ ተቀጥረው በወር ብር 1971.00 (አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አንድ ብር) ደመወዝ እየተከፈላቸው በመስራት ላይ የሚገኙ መሆኑን፣ አነስተኛ የሥራ ልምድ ያላቸው እና ተመሳሳይ ስራ የሚሰሩ ሌሎች ሠራተኞች ከፍ ያለ ደመወዝ እንደሚከፈላቸው ገልፀው ድርጊቱ ለአንድ ሥራ እኩል ክፍያ የሚለውን መርህ የሚጥስ በመሆኑ አመልካች የወር ደመወዙን ብር 2366.00(ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስልሳ ስድስት ብር) እንዲያደርግላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሠጠው መልስ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑንና ጥያቄአቸውም በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት፣ በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ የደመወዝ ልዩነት የተደረገው መመሪያውን መሰረት በማድረግ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 14(1/ረ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በዋቢነት በመጥቀስ የአመልካች አሰራር ህገ-ወጥ ነው በማለት ለተጠሪ የደመወዝ ማስተካከያ በማድረግ በፔሮል ላይ ሊተክል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ሠርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 337/96 አንቀፅ 14(1/ረ) አሰሪው መመሪያውን መሰረት በማድረግ ለፈፀመው ተግባር አግባብነት የሌለው በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የስር ፍርድ ቤት አመልካች መስሪያ ቤት ከዘረጋው የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት አልፎ ለተጠሪ የወሰነው የደመወዝ መጠን መነሻን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ ጉዳዩ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በተመሳሳይ ደረጃ በሚገኙ ሠራተኞች መካከል የሚፈጠር የደመወዝ ልዩነት (Equal Pay Discrimination) የተከለከለ ነው የሚለውንና ኢትዮጵያ ያፀደቀችውን ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽንን መሰረት ያደረገ ስለሆነ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለውም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊመረመር ይገባዋል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በስታትስቲሽያንነት ተቀጥረው የሚሰሩ መሆኑን፣ ቅጥሩም በሙሉ ስታትስቲሽያን የስራ የማዕረግ መፈፀሙን በተጠሪና በሌሎች ሠራተኞች መካከል የደመወዝ ልዩነት የተፈጠረው እነዚህ ሠራተኞች ምንም የስራ ልምድ በማይጠይቅ በመለስተኛ ስታትሺያን የስራ መደብ ተቀጥረው ከቆዩ በኋላ በዚህ የስራ መደብ የተቀጠሩ የዲግሪ ምሩቃን ሰራተኞች ወደሚቀጥለው የስራ መደብ የሚያድጉበትን ሁኔታ አመልካች በመመሪያ መወሰኑንና በዚህ መመሪያ መሰረትም ከተጠሪ ጋር ተመሳሳይ ስራ የሚሰሩ የዲግሪ ምሩቃን ከተጠሪ የተለየ ደመወዝ የሚከፈላቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 42(1/መ) ድንጋጌ የሚያሳይ ሲሆን ኢትዮጵያ የተቀበለችው አለም አቀፍ ኮንቬንሽንም ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ሲያደርግ መሰረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14(1/ረ) ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት እና በሌሎችም ሁኔታ በሠራተኞች መካከል ልዩነት ማድረግ ለማንኛውም አሠሪ ሕገወጥ ድርጊት ነው የሚል ነው፡፡ የድንጋጌው እንግሊዘኛ ትርጉሙም “discriminate between workers on the basis of nationality, sex, religion, political outlook, or any other conditions shall be unlawful for an employer.” በሚል ተቀምጧል፡፡

ከድንጋጌው ውስጥ “...በሌሎችም ሁኔታ...” ወይም “.... Any other conditions....” የሚለው ሐረግ ጠቅላላ ቃል መሆኑ ግልጽ ሲሆን እንዲህ በሆነ ጊዜ ቃሉን ህግ አውጪው የተጠቀመው ምንን ለማመላከት ነው የሚለው ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ሲሆን የህግ አተረጓጎም መርሆዎችን መሰረት በማድረግም ምላሹን ማግኘት ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት ከጠቅላላው ቃል በፊት የተዘረዘሩት የቃላት ዝርያ የሚያሳዩትን ሁኔታ በመመልከት ጠቅላላ ቃል ሌሎች ያልተዘረዘሩትን ተመሳሳይ ዝርያ ያላቸውን ቃላት ለመጠቀም ታስቦ የተቀመጠ ነው በሚል እንደሚተረጎም ተቀባይነት ያላቸው የህግ አተረጓጎም መርሆዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14(1/ረ) ድንጋጌ ስር “በሌሎች ሁኔታም” የሚለው ቃል ከቃሉ በፊት የተቀመጡትን የልዩነት ማድረጊያ ድርጊቶችን ዓይነት የሚመለከት እንጂ አሰሪው የእድገት አሠጣጥ ሥርዓቱን በመመሪያ ዘርግቶ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ሠራተኞች መስፈርቱን ካላሟሉ ሰራተኞች የተለየ ክፍያ እንዲከፈል የሚያደርግበትን አሰራር የሚመለከት አይደለም፡፡ መመሪያው በሕገ-መንግስቱ፣ በዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14(1/ረ) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ በተጠሪና በሌሎች ሰራተኞች መካከል የደመወዝ ልዩነት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ መመሪያው መድሎን ለመከላከል የማያስችል ነው ሊባል የሚችልበትን ሕጋዊ ምክንያትም አላገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 23005 ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 70763 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች በተጠሪና በሌሎች ሠራተኞች መካከል ለተመሳሳይ ሥራ የደመወዝ ልዩነት ያደረገው በሕግ የተከለከሉ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ባለመሆኑ ለተጠሪ ብር 2366.00 /ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስልሳ ስድስት ብር/ በፔሮል እንዲተክል የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44410

ኅዳር 01 ቀን 2002

ዳኞች፡- አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አቶ አልማው ወሌ

አቶ ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ላይላ ረዲ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ድሬ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግል ማኅበር - በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው የሥራ ውል ከሕግ ውጪ መቋረጡን ገልፀው የካሣ ክፍያ፣ የስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ክፍያ የዘገየበት ክፍያ፣ የታህሣሥ ወር 2000 ዓ.ም. ደመወዝ፣ ያልተጠቀሙት የ29 ቀናት የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው እንዲሁም የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሠጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሳሽነቱ ቀርቦ አመልካች በታህሣሥ ወር 2000 ዓ.ም. ለ28 ቀናት በመደዳው ቀርተው ማስረጃ ባለማቅረባቸው ደመወዝ ያልተከፈላቸው መሆኑን፣ ወደ ሥራም በሀዘኔታ የመለሳቸው መሆኑን፣ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም. አመልካች ለተጠሪ የስንብት ደብዳቤ ጽፈው ሥራቸውን በራሳቸው ፈቃድ ለቀው መሄዳቸውንና በዚህም ምክንያት ሊከፈላቸው የሚገባ ካሣ አለመኖሩን፣ የሥራ ስንብት ክፍያም አገልግሎታቸው ከአምስት ዓመት በታች በመሆኑ ሊያገኙ እንደማይችሉ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያም በገዛ ፈቃዳቸው ሥራውን ስለለቀቁ እንደማይገባቸው፣ የዓመት እረፍትም በወቅቱ መውሰዳቸውንና ያልወሰዱት ካለም ቀርበው መተሳሰብ እንደሚችሉ ክፍያው ለዘገየበት ለተባለው ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ ኖሮ ያልተከፈላቸው ባለመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት እንደሌለው፣ እንዲሁም የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን የቃል እና የጽሁፍ ክርክር መርምሮ አመልካች ስራቸውን በፈቃዳቸው መልቀቃቸው ተረጋግጧል፣ የታህሣሥ ወር 2000 ዓ.ም. ደመወዝም አመልካች ሥራውን ያልሠሩ መሆኑ ተረጋግጦ ከሥራ ላይ የቀረበትን ሕጋዊ ምክንያት ተገቢውን የሕክምና ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም በማለት በአመልካች የተጠየቁትን ክፍያዎችን ውድቅ አድርጎ አመልካች ያልወሰደችው የዓመት ፈቃድ ከጥቅምት 1999 ዓ.ም. እስከ ጥር 29 ቀን 1999 ላለው ጊዜ ታስቦ በገንዘብ ተለውጦ ተጠሪ እንዲከፍላቸው፣ የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀትም እንዲሠጣቸው ብቻ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት መጋቢት 14 ቀን 2001 ዓ.ም. በዛፉት አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የሥር ፍርድ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም. ተፃፈ የተባለውን ደብዳቤ ይዘቱም ባግባቡ ሳያገናዝብ አመልካች የሥራ ውላቸውን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸው ተረግጧል ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው በስህተት በመሆኑ ታርሞ ሕጋዊ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት የቃል ክርክር ሊሰማ ቀነ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአመልካችን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጦችንም አመልካች ሥራቸውን የለቀቁት በገዛ ፈቃዳቸው ነው /ባግባቡ ነው/? ወይስ አይደለም? አይደለም ከተባለስ አመልካች ሊከፈላቸው የሚገባቸው ክፍያዎች የትኞቹ ናቸው? የሚሉት ናቸው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ስራውን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸው ተረጋጋጧል ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የአመልካችን የምስክሮች ቃል እና በተጠሪ በኩል የቀረበውን አመልካች ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም. ፃፉ የተባለውን ደብዳቤ በመመርኮዝ ስለመሆኑ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩትም የምስክሮች ቃልም ሆነ የደብዳቤው ይዘት ሥራውን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ መሆኑን የማያሳይ ሳይሆን በተጠሪ ድርጅት የአመልካች የቅርብ ኃላፊያቸው በተደጋጋሚ በሚደርስባቸው በደል እና ከሥራቸውም እንዲወጡ በቃል በታዘዙት ምክንያት ከሥራቸው የወጡ መሆኑን ገልፀው ተገቢ ክፍያ እንዲፈፀምላቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን የሚያሳይ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም. በአመልካች ተፃፈ የተባለውን ደብዳቤ ይዘት ተመልክቶታል፡፡ እንደተመለከተውም አመልካች በሥራቸው ቦታ ላይ በቅርብ ኃላፊያቸው የሚደርስባቸውን በደል በመዘርዘር የቅርብ ኃላፊያቸው በራሳቸው ፍላጎት ከሥራቸው ያስወጣቸው መሆኑ ግንዛቤ አግኝቶ ጥቅማ ጥቅማቸው ተጠብቆ የስራ ልምድ እንዲሰጣቸው ለተጠሪ ድርጅት ፐርሶኔል አስተዳደር መፃፋቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታ የቀረበለት የተጠሪ ድርጅት የክፍሉ ኃላፊም በሠራተኛው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንዲስተናገዱ በሚል ለድርጅቱ አስተዳደር አገልግሎት ክፍል ደብዳቤውን መምራቱን የደብዳቤው ይዘት ያሳያል፡፡ እንግዲህ የደብዳቤው ይዘት አመልካች ስራቸውን የለቀቁት የቅርብ ኃላፊያቸው ከስራቸው ስለአስወጧቸው መሆኑን በመግልፅ ተገቢ ክፍያዎችን የጠየቁ መሆኑን ከሚያሳይ በስተቀር የስር ፍርድ ቤት በመዘገበው አይነት አለመሆኑን ይህ ችሎት ከውሣኔው ግልባጭ አረጋግጧል፡፡ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ማስረጃ ይዘት ባግባቡ ባለመመዝገብ የሚደረሰው ድምዳሜ ደግሞ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን በስነ-ስርዓቱ ሕጉ የተመለከተውን የዳኝነት አካሄድ የሚፃረር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ስራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸው ተረጋግጧል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ተግኝቷል፡፡ ስለሆነም ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ብለናል፡፡

ቀጥለን የሕገ-ወጥ ስራ ስንብት ውጤት ከሆኑት ክፍያዎች መካከል ለአመልካች የሚገባቸው የትኞቹ እንደሆኑ ተመልክተናል፡፡

አመልካች ከጠየቁት ክፍያ መካከል ካሣ አንዱ ሲሆን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/4/ መሠረት ካሣ ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሌላው አመልካች ዳኝነት የጠየቁት የሥራ ስንብት ክፍያ ሲሆን ተጠሪ ይህንኑ ክፍያ አመልካች አይገባቸውም በማለት በሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክርክር የአመልካች አገልግሎት ጊዜ አምስት ዓመት አልሞላቸውም የሚል ነው፡፡ ሆኖም የአምስት ዓመት አግልግሎት እንደመመዘኛ የሚወስደው ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለሚለቅ ሠራተኛ የስንብት ክፍያ ሲጠየቅ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/ሸ/ ድንጋጌ መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39/1/ለ/ ድንጋጌ ሲታይም የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሠራተኛ ሕግ ከደነገገው ውጪ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ሠራተኛው ከአሠሪው የስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም የአመልካች የሥራ ውል ከሕግ ውጪ መቋረጡ እና የሙከራ ጊዜያቸውን አመልካች የጨረሱ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የሥራ ስንብት ክፍያ የማያገኙበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 መሠረት ታስቦ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 41 መሠረትም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡ አመልካች በተገቢው ጊዜ ክፍያ ጥያቄ አቅርበው ያልተከፈላቸው በመሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 38 መሠረት ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለልም የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በሚከተለው መልኩ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12978 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 73958 የካቲት 06 ቀን 2001 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/4/፣ 40፣41 እና 38 መሠረት ካሣ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ክፍያው ለዘገየበት ክፍያ እንዲከፍል ወስነናል፡፡
3. የሥር ፍርድ የታህሣሥ ወር 2000 ዓ.ም. ደመወዝን፣ የዓመት እረፍት ክፍያንና የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀትን በተመለከተ የሰጠው ውሣኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ፡- 47807

6/4/2002

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ እሌኒ እሸቱ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ፀሐይነሽ ፈንታው - ቀረቡ

2. ሜታ አቦ ቢራ ፋብራካ አ/ማ - ነ/ፈጅ ሰለሞን ዘገየ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ከሥራ ውል ጋር በተያያዘ የካሳ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን አንደኛ ተጠሪ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ሟች ባለቤቱ አቶ አሸንጋ ዩታ በተከሳሽ ድርጅት ከሰኔ 24 ቀን 1974 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥረው ሲሰሩ ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም በመ/ቤቱ የሥራ ሰዓት ለድርጅቱ ስፖርት ክለብ ውጤት መሳካት ሲባል የስፖርት ልምምድ እንዲያደርጉ ታዘው በልምምድ የተነሳ ወድቀው እራሳቸውን የሳቱ በመሆኑ ሕይወታቸው ሊያልፍ ችሏል። የባለቤቱ ሕይወት በስፖርት ልምምድ እንዳሉ በመውደቃቸው ምክንያት ሊያልፍ እንደቻለ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በጽሁፍና በቃል በነገሩኝ መሰረት የሕይወት ካሳ እንዲከፈለኝ የጠየቅሁ ቢሆንም ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆኑም።

ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የሕይወት ካሳ፣ የቀብር ሥነ -ሥርዓት ማስፈጸሚያ እና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ክፍያዎች እንዲከፈሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል።

ተከሳሽ ቀርቦም በሰጠው መልስ ተከሳሽ ድርጅት በሰራተኞች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት የመድን ዋስትና ሽፋን የገባ ስለሆነ መድን ሰጭው ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ይታዘዝልን በማለት አመልክቷል።

የኢትዮጵያ መድን ድርጅትም የአሁን አመልካች በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ተደርጎ በሰጠው መልስ የሟች ሕይወት ያለፈው በነበረባቸው አጣዳፊ የልብ ሕመም ምክንያት ስለመሆኑ በአስከሬን ምርመራ ተረጋግጧል። ይህም ሟች የሞቱት በበሽታ እንጂ በሥራ ላይ በመጣ አደጋ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው። የሟች ሥራም ስፖርተኛ ሳይሆን ጽዳት የነበረ ሲሆን በትርፍ ሰዓታቸው በስፖርት ሜዳ ተገኝተው ከሆነም የነበረባቸው ሕመም ለሞት አበቃቸው እንጂ በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ሕይወታቸው አላለፈም። ይህ ከሆነ ደግሞ በኃላፊነት ልንጠየቅ ስለማይገባ ክሱ ከበቂ ኪሳራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል የቀረበው የሟች አስከሬን ምርመራ ውጤት ሟችን ለሞት ያበቃቸው አጣዳፊ የሆነ የልብ ጡንቻ ቁስለት እንደሆነ ያሰረዳል። ከሳሽ ሟች የሞቱት በመ/ቤቱ የሥራ ሰዓት ለድርጅቱ ስፖርት ክለብ ውጤት መሳካት ሲባል የስፖርት ልምምድ እንዲያደርጉ ታዘው በልምምድ ላይ እንዳሉ ወድቀው እራሳቸውን ስተው ሞተዋል ቢሉም በዚህ አካኋን ሟች ስለመሞታቸው ያላሰረዱ ከመሆኑም በላይ ሟች በተከሳሽ ድርጅት የፅዳት ሰራተኛ እንጂ ስፖርተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደሉም፡፡ ስለሆነም ሟች የሞቱት በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ሳይሆን በተፈጥሮ ምክንያት እንደሆነ ከቀረበው የሐኪም ማስረጃ መረዳት የተቻለ ስለሆነ ከሳሽ ሟች ባለቤቱ በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ሕይወታቸው አልፏል በማለት ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 97 ሥር የሚሸፈን ባለመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ተከሳሽ አንደኛ መ/ሰጭ ለሁለተኛ መ/ሰጭ በጻፈው ደብዳቤ ሟች በሥራ ላይ ከድርጅቱ ስፖርተኞች ጋር ልምምድ ሲያደርጉ ሕይወታቸው ማለፉን ጠቅሶ በመድን ውሉ መሰረት የካሳ ክፍያ እንዲፈጽምላቸው የጠየቀ ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 95/2/ መሰረት በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ማለት እንደሆነ የተመለከተ ስለሆነ ሟችም ከድርጅቱ ስፖርተኞች ጋር ሥልጠና ሲወስዱ ስለሞቱ ይህም በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት እንደሞቱ ስለሚያረጋግጥ የሥር ፍ/ቤት ተከሳሽ ለደረሰው አደጋ ኃላፊ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት ውሳኔውን በመሻር አንደኛ እና ሁለተኛ መ/ሰጭዎች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ስለሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110/1/ /ሀ/ እና /ለ/ እንደዚሁም በንዑስ አንቀጽ /2/ መሰረት ካሳ ሊከፈሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በአመልካች በኩል የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት የሞቱት በሥራ ላይ እንዳሉ በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ነው ተብሎ ካሳ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ አግባብነቱን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ብሎ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥና ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት የሞቱት በሥራ ላይ በደረሰባቸው አደጋ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 95/2/ መሰረት በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ /occupational injury/ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ /occupational disease/ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ማለት ደግሞ በአንቀጽ 97 ላይ ትርጉም የተሰጠው ሲሆን ማንኛውም ሰራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ሥራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

በዚህ የአዋጁ ድንጋጌ መሰረት የካሳ ክፍያ ጥያቄ የሚያቀርበው ወገን ጉዳቱ የደረሰው በአንቀጽ 97 በተመለከተው አኳኋን በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት መሆኑንና እንደዚሁም በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ቅርብና ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት መኖሩን /proximate cause and effect relation ship/ ማስረዳት እንደሚጠበቅበት ይታመናል፡፡

በሌላ በኩልም የአሰሪው ኃላፊነት በጥፋት ያልተመሰረተ ጥብቅ /strict/ ስለሆነ ካሳ ጠያቂው ወገን ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማሳየት ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ የጉዳት አድራሹን ወይንም የአሰሪውን የአእምሮ ሁኔታ /state of mind/ ማስረዳት እንደማይጠበቅበት ከአንቀጽ 96 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በተገለፀው አኳኋን አንደኛ ተጠሪም ሟች ባለቤታቸው ሕይወታቸው ያለፈው በአንቀጽ 97 በተመለከተው መሰረት ሥራቸውን በማከናወን ላይ ሳሉ ወይንም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሳቸው ውጭ በሆነ ምክንያት በድንገት በደረሰባቸው ጉዳት ሳቢያ ሕይወታቸው ማለፉን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ሟች ባለቤቱ ሕይወታቸው ሊያልፍ የቻለው ለድርጅቱ ስፖርት ክለብ ውጤት መሳካት የስፖርት ልምምድ እንዲያደርጉ በአሰሪው ታዘው ልምምድ ሲያደርጉ ወድቀው ሕይወታቸው ያለፈ ስለሆነ ይህም በሥራ ላይ የደረሰ አደጋ ስለሆነ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ሆኖም ግን ሟች የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት የተቀጠሩበት የሥራ መደብ በስፖርተኛነት ሳይሆን በፅዳት ሰራተኛነት የሥራ መደብ እንደሆነ ከመረጋገጡም በላይ አንደኛ ተጠሪ እንደሚሉትም በአሰሪው በኩል ለድርጅቱ ስፖርት ክለብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውጤት መሳካት ሲባል የስፖርት ልምምድ እንዲያደርጉ በአሰሪው ታዘው የስፖርት ልምምዱን ሲያደርጉ ሕይወታቸው ስለማለፉም አላሰረዱም፡፡

ከዚህም ሌላ ሟች የስፖርት ልምምድ እንዲያደርጉ በአሰሪው ትዕዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር ቢባል እንኳን በስፖርት ልምምድ ላይ እንዳሉ ሕይወታቸው ማለፉ በአንቀጽ 97 ላይ እንደተመለከተው በስራ ላይ በደረሰባቸው አደጋ /accident/ ሳቢያ ሕይወታቸው እንዳለፈ የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የአዋጁ አንቀጽ 95/2/ እና 97 ድንጋጌዎች በጣምራ ሲተረጎም በሥራ ላይ ጉዳት ደርሷል ለማለት በአደጋ ምክንያት በሰራተኛው አካል ላይ ጉዳት መድረሱ መረጋገጥ እንደሚገባው መገንዘብ ስለሚቻል ነው፡፡ በዚህ መልኩም በሟች ላይ በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ ሲሆን ይልቁንም የቀረበው የሟች አስከሬን ምርመራ ውጤት ሟች ለሕልፈት የበቁት አጣዳፊ በሆነ የልብ ጡንቻ ቁስለት ምክንያት መሆኑን ስለሚያረጋግጥ ሟች በሥራ ላይ እንዳሉ በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ለሞት እንዳልበቁና በተፈጥሮ ምክንያት /Natural cause/ እንደሞቱ የሚያሳይ ነው፡፡

ሲጠቃለልም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 95 እና 97 በተደነገገው አግባብ አንደኛ ተጠሪ ሟች ባለቤታቸው በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት ስለመሞታቸው በማስረዳት የካሳ ክፍያ ጥያቄውን ማቅረብ ሲጠበቅባቸው ይህንን የማስረዳት ግዴታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሟች ለሞት የበቁት በሥራ ምክንያት በተፈጠረ አደጋ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የሥር ተከሳሹ /ሁለተኛ ተጠሪ/ ለጉዳቱ ኃላፊ ነው ብሎ በክስ የተጠየቀውን ካሳ ተከሳሹና ጣልቃ ገቡ የአሁን አመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 75634 ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፌዴራል መጀመሪያ ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13539 በ6/4/2001 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ አጽንተናል፡፡

2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

3.መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ወ/ነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 45889

ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ደቡብ ሪጅን

- ነገረ ፈጅ ቢንያም እስጢፋኖስ - ቀረበ

ተጠሪ፡- ሳሙኤል ቄልቦ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አስቀድሞ በተሰጠኝ የደረጃ እድገት መሠረት ይከፈለኝ የነበረው ተጨማሪ ደመወዝ ያለአግባብ ስለተቋረጠብኝ ይኸው ሕገ ወጥ ድርጊት ተወግዶ ጭማሪው ደመወዝ እንዲከፈለኝ ይደረግልኝ በማለት ተጠሪ በመሠረተው ክስ መነሻነት የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ከአመልካች የቀረበውን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ጭማሪው በእድገት ሳይሆን በስህተት ተሰጥቶ የነበረ ለመሆኑ በማስረጃ ማረጋገጡን በመግለጽ የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ አመልካች አንዱ የሰጠውን ውሳኔ በራሱ የሚሸርበት አግባብ የለም የሚል ምክንያት በመስጠት በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 13 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ አቤቱታ ባቀረበበት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቀርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

የተጠሪ የክስ ምክንያት በተሰጠኝ የደረጃ እድገት መሠረት ሲከፈለኝ የነበረው የደመወዝ ጭማሪ ያለአግባብ ተቋርጦብኛል የሚል ሲሆን፣ አመልካች ደግሞ ተጠሪ ቀደም ሲል ሲሠራበት ከነበረው የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅነት ተመሣሣይ ደረጃ ወደሆነው የሪጅን ምክትል ሥራ አስኪያጅነት ነው የተዛወረው፡፡ ሁለቱም ሥራዎች እኩል ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ ዝውውሩ ሲደረግ የደመወዝ ለውጥ ማዘዣው በስህተት በመሠራቱ ነው ችግሩ የተፈጠረው፡፡ የተሠራው ስህተት እንደታወቀም የእርምት እርምጃ ተወስዶአል በማለት እንደተከራከረ ከመዝገቡ ለማየት ችለናል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎትም አመልካች ያቀረበው የፍሬ ነገር ክርክር ትክክል ሆኖ በማግኘቱ ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው የደመወዝና የደረጃ እድገት የተነሳው (የተሰጠው) በአግባቡ ነው እሚል መደምደሚያ ደረሶአል፡፡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ የሻረው በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጠው የተለየ ነገር አግኝቶ ሳይሆን፣ አመልካች እራሱ የሰጠውን ውሳኔ ያለምክንያት መልሶ መለወጥ የሚችልበት አግባብ የለም፣ "እንደ ፍ/ቤት እራሱ የወሰነውን ውሳኔ መከለስ /Review of judgment/ ማድረግ የማይችል ከመሆኑም በተጨማሪ ውሳኔው የሚመረመረው ለመመርመር ስልጣን ባለው በሌላ አካል በjudicial review ነው፡፡" የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት እንደሆነ ከውሳኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደምንመለከተው የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ቀድሞ ከነበረው የተለየ ደመወዝና ጥቅም ወደሚያስገኝ ከፍያለ ደረጃ ወዳለው ቦታ አልተዛወረም እሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ክሱን ውድቅ ያደረገ ሲሆን፣ ተጠሪ ግን አንዱ የተሰጠኝ ደመወዝ ልነጠቅ አይገባም ከማለት አልፎ በእርግጥም በኋላ የተመደበበት ቦታ ከቀድሞው የተለየ እና ከፍ ያለ ደመወዝ የሚያስገኝ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ ይግባኙን የሰማው ጠ/ፍ/ቤትም አመልካች ቀደም ሲል በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት ሲከፈል የነበረውን ደመወዝ በተገቢው የእድገት አሰጣጥ መሠረት የተገኘ አይደለም በማለት የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይችላል ወይስ አይችልም? በሚለው ነጥብ ላይ በመወሰን ውሳኔ ከመስጠት አልፎ በከፍተኛው ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር እውነት አይደለም እሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ የሚችል ማስረጃ አግኝቻለሁ አላለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሰበር ችሎት ሊወሰን የሚገባው ጭብጥ አመልካች የቀድሞ ውሳኔህን መለወጥ ወይም ማረም አትችልም የሚባልበት የሕግ አግባብ አለ ወይ? የሚለው ነው፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ነው፡፡ አመልካች በአሠሪነቱ ተጠሪንም ሆነ ሌሎች ሠራተኞቹ የሚያስተዳድረው፣ የደረጃ እድገት አሰጣጥም ሆነ የደመወዝ አከፋፈል ወይም አመዳደብ የሚወሰነው ባለው አሠራር እና ድርጅታዊ መዋቅሩ መሠረት እንደሆነ ይገመታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በኋላ የተመደበበት የሥራ ቦታ ቀድሞ ከነበረበት የሥራ ቦታ ተመሣሣይ በመሆኑ ተጨማሪ ደመወዝ የሚያገኝበት አግባብ እንደሌለ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ የፍሬ ነገር መሠረት ስለሌለው ስህተት ነው ማለት ነው፡፡ ተጠሪ ተጨማሪ ደመወዝ እንዲከፈለው የሚያዘው ደብዳቤም የተጻጻፈው በተሳሳተ ውሳኔ ላይ በመመስረት በመሆኑ አመልካች ስህተቱን በማረም ተለዋጭ ውሳኔ ከመስጠት የሚያግደው የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በሥራው መሪነቱ (በአሠሪነቱ) ትክክል ነው ብሎ በሚያምነው መሠረት የመወሰን ሥልጣን ያለው እንደመሆኑ ስህተት መስሎ የታየው የራሱንም ውሳኔ ማረም ያለበት እራሱ እንጂ የተሳሳተ ውሳኔ ሰጥቻለሁና አርምልኝ ብሎ ለሌላ አካል አቤቱታ የሚያቀርብበት የህግ አግባብ የለም፡፡ አግባብ የሚሆነው በውሳኔው ተጎድቻለሁ የሚለው ወገን (ሠራተኛ) የውሳኔ ሕጋዊነት ይታይልኝ (ይመርመርልኝ) በማለት ሥልጣን ላለው አካል አቤቱታ ሲያቀርብ ነው፡፡ ተጠሪም ያደረገው ይኸው ሲሆን፣ አመልካች ውሳኔውን ያረመው በአግባቡ ሆኖ በመገኘቱ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን በሰማው ፍ/ቤት ተወስኖአል፡፡ በመሆኑም የጠ/ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው የJudicial Review መርህ በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ውሳኔው በሕግ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 24637 የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በመ.ቁ 5223 ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቶአል፡፡ በዚህ መሠረትም አመልካች የቀድሞውን ውሳኔ ያረመው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸው ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47806

ታህሣሥ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የሆህተሰማይ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት - ሻምበል አሰፋ ወልደ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዲያቆን አያሌው አዲሱ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥራ ውሌ ከሕግ አግባብ ውጪ ተቋርጦብኛል በማለት ተጠሪ የመሰረተውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ከሥራዬ ያላአግባብ አግዶኛል በማለት ሲሆን፣ ሲያገለግል የነበረውም በዲቁና እንደሆነ በክሱ ላይ ገልጾአል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከሥራው ሊሰናበት የቻለው የቤተክርስቲያንዋ ስሞነኛ ቁልፍ ያዥ ሆኖ በሰራበት እለት ከቤተመቅደስ ሙዳየ ምጽዋቶች ተሰብረው ተዘርፈዋል፡፡ ከዚህ የተነሣም ተጠሪ በወንጀል ተከሶአል፡፡ የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ክሱ ውድቅ እንዲደረግለት ጠይቆአል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣አመልካች ተጠሪን ወደ ሥራው እንዲመልስ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ሰርዘናል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 27 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት ሃይማኖታዊ ግንኙነት ነው፡፡ አመልካች በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት መሰረት የተቋቋመ ሃይማኖታዊ ተቋም ሲሆን፣ተጠሪ ደግሞ በዚህ ተቋም ውስጥ የሃይማኖት አገልግሎት እንዲሰጥ አባል ወይም ሰራተኛ የሆነ ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ሙዳየ ምጽዋቶች ተዘረፉ በተባለበት እለት ተጠሪ ቤተመቅደሱን መክፈቱንና በመቀጠልም ቅዳሴ እንደገባ በክርክሩ ገልጾአል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለውም በሐይማኖቱ ሥርአት መሰረት የሐይማኖቱ አገልጋይ በመሆኑ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ ክርክር ቀርቦለት በሰበር መ/ቁ. 18419 ግንቦት 4 ቀን 98 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የሐይማኖት ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የሥራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሚሸፈን አለመሆኑን በማለጽ የሕግ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡ ከዚህ በኋላም በተመሣሣይ ጉዳዮች ቀርበው ቀደም ሲል በተሰጠው የሕግ ትርጉም እንደተሸፈኑ እየተገለጸ ሲወሰን ቆይቶአል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ሥልጣን ሳይኖራቸው ክርክሩን ተቀብለው ማስተናገዳቸው አግባብ አልነበረም፡፡ የሰጡት ውሳኔም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27517 ሰኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04821 ሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተው ክስ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረት የሚታይ ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን የሰሙት ስልጣን ሳይኖራቸው ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 47469

ታህሳስ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. አልማው ወሌ

5. ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- እነ አቶ ሥዩም ገብረዋዲቅ (22 ሰዎች)

- ወኪል ወንድምአገኝ ጌታሁን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ ሕዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ላልተወሰነ ጊዜ ተቀጥረን ስንሰራ ሌሎች ሠራተኞች የሚያገኙትን የበረሃ አበል፣ ቦነስ፣ የሳምንት ዕረፍት ቀን ክፍያ፣ የኤሌክትሪክ ፍጆታ በነፃ መጠቀም፣ የዝናብ ልብስ፣ ጥቅማ ጥቅም የማግኘት መብት እንዲከበርላቸው እና የደመወዝ እርከንና ማሻሻያ ከሌሎች ጋር እኩል እንዲደረግላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ የተጠሪዎች ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ በሚል የተፈረመ ሆኖ አመልካች ግዴታውን እየተወጣ የቆየ መሆኑን፣ ተጠሪዎች በሳምንት የሚሰሩት የስራ ሰዓት ብዛትም በቀን ከስምንት ሰዓት በታች የሚሰሩ መሆኑን፣ የሚያሳይ በመሆኑ የሳምንት የእረፍት ጊዜ ክፍያ ተቀባይነት እንደሌለው ለቋሚ ሰራተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎችም ለተጠሪዎች ሊከፈሉ እንደማይገባ ገልጾ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በአመልካች በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ ካደረገና የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የስራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ አንደተደረገ የሚቆጠር ነው በማለት አመልካች ለተጠሪዎች የሣምንት እረፍት ቀን ክፍያ፣ የበረሃ አበል ክፍያ፣ ነጻ የኤሌክትሪክ፣ ቦነስ ይከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሐምሌ 08 ቀን 2001 ዓ.ም በአምስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሁነው እያለና ቋሚ እንሁን የሚለው ጥያቄም የክስ ምክንያት የሌለው መሆኑ እየታወቀ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል ተብሎ ለቋሚ ሠራተኞች የሚገባቸው ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲከፈላቸው መወሰኑ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የቅጥር ውል፣ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 10(1/ሀ)"ን"፣ የድርጅቱን የህብረት ስምምነት እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 18832 የሠጠውን አስገዳጅ ውሳኔ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑ እየታወቀ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል በማለት አመልካች ድርጅት ለተጠሪዎች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኛቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይክፈላቸው በማለት የሠጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሠምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር ይገባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ድርጅት አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ናቸው በማለት ነው፡፡ ለዚህም መሰረት የሚያደርገው ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉና የስራ ውሉ በጊዜ ተገድቦ በግራ ቀኙ መካከል ውል የተፈፀመበትን ሰነድ ነው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በጡረታ ተገልለው የቆዩ መሆኑን ሳይክዱ በአመልካች ድርጅት ሥራ የጀመሩት የጡረታ ደብተሩን በመመለስና በማስያዝ ስለመሆኑና ይህም በስር ፍርድ ቤት በሚመለከታቸው አካላት የተረጋገጠ መሆኑን፣ እንዲሁም የስራ ውሉ በየጊዜው እየታደሰ ለበርካታ አመታት በአመልካች ድርጅት ሲሰሩ መቆየታቸው የስራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ያስቆጥራል በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ የቅጥር ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ለአንድ አመት እየተባለ ጊዜው ሲያልቅ እንደገና እየታደሰ እንደ አዲስ የሚታይ መሆኑ ይታመናል፡፡ በዚህም መሰረት ጊዜው ሲያልቅ ውሉን ማቋረጥ የሚቻል መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 11924 አግባብነት ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ ድንጋጌዎችን በመመርመር አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የሠጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰራተኛ ከአሰሪ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቆጠረ ሊቆጠር እንደሚገባ ሕጉ ግምት እንደሚወስድ፣ በዚህ የሕግ ግምት የስራ ውሉ ያልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ነው በማለት የሚከራከረው ሠራተኛ ተጠቃሚ በሆኑ ይህን ክርክሩን የሚደግፍለት ማስረጃ በቅድሚያ ያቀርብ ዘንድ እንደማይጠበቅበት፣ ይልቁንም በሕግ በተወሰደለት ግምት ክርክሩን ከማስረዳቱ ግዴታው ነፃ እንዲሆን እንደሚያደርገው፣ በውጤቱም በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረጉ ውሎች በአንቀፅ 10 ስር የሚሸፈኑ ናቸው ሲል በሚከራከር በአሰሪው ላይ የሚወድቅ መሆኑን በመዘርዘር ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ከእዚህ የሰበር ችሎት ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው ሰራተኛው በየዓመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻውን ሰራተኛን ለተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ ሊወሰድ የማይገባ መሆኑን ነው፡፡ ዋናው ሰራተኛው የተቀጠረበት ሥራ ቀጣይነት ያለው መሆኑ ነው፡፡ አሰሪው ይህንኑ ለማስተባበል የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 10 ስር የተመለከቱት ምክንያቶች የስራ ውሉ መፈፀሙን በማስረዳት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለማሳያነት ያቀረበው ማስረጃ በሦስተኛ ተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገ የስራ ውል ሆኖ ውሉ ከሀምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ሀምሌ 01 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 10 ስር በተመለከተው ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ለጥበቃ ሥራ የተቀጠሩ መሆኑን በማለፅ የተፈፀመ ነው፡፡ ተጠሪዎች ሁሉም ለአንድ አይነት ሥራ የተቀጠሩ አለመሆናቸውንም የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ቢያሳይም የቅጥሩ ዓይነት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን ግን ተጠሪዎችም ያልካዱት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታውን የተወጣ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አመልካች ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉ ሆነው በቋሚነት ሊቀጠሩ አይችሉም በማለት ያቀረበው ክርክርም ተጠሪዎች በዕድሜ ጣሪያ በጡረታ የወጡ መሆኑን በዚህ ችሎት በተደረገው የክርክር ሂደት አረጋግጠዋል፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት የጡረታ ደብተራቸውን በመያዝ የመብቱ ተጠቃሚ ሆነው እያለ በአመልካች ድርጅት በመስራት ላይ የሚገኙ ባለመሆኑ ቅጥሩ እንደቋሚ የሚቆጠር፤ ሕጋዊ ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ አሰሪ በጡረታ የተገለለን ሠራተኛ በድጋሚ ላልተወሰነ ጊዜ ቀጥሮ ያሰራል ለማለት የማይቻል መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 18832 አስገዳጅ የሆነ የህግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ከመሆናቸውም በላይ እድሜያቸው በጡረታ ደርሶ ከስራ ከተሰናበቱ በኋላ በአመልካች ድርጅት ውስጥ የተቀጠሩ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት እንዲወሰኑላቸው ያቀረቧቸው የክፍያ ጥያቄዎች ለቋሚ ሠራተኞች የሚሠጡ መሆኑን ተጠሪዎችም በክርክራቸው ገልፀው የሚከራከሩት ነጥብ በመሆኑ ተጠሪዎች ቋሚ ሠራተኞች ካልሆኑ ክፍያዎቹ የሚገባቸው አይሆንም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑ እየታወቀ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል በማለት አመልካች የተጠሪዎች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኟቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን ይክፈላቸው በማለት መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

10“ን” የአመልካች ድርጅት የሕብረት ስምምነትንና ከላይ የተጠቀሱትን የሰበር ችሎት ውሳኔዎችን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19930 የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03718 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች በእድሜ ጡረታ ተገልለው ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች በመሆኑ አመልካች ለቋሚ ሰራተኞች የሚከፍላቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያገኙበት ወይም ሊከፍላቸው የሚገባ ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47784

ታህሣሥ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወል

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነገረፈጅ እሸቱ በቀለ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዓለምፀሐይ አያና - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በኦሮሚያ ክልል የጊንቢ ወረዳ ፍርድ ቤትና የምእራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርባ ሐምሌ 23 ቀን 1984 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ወደ ተላላኪነት የሥራ መደብ አሳድጉኝ ደመወዝና የማነቃቂያ አበል ከፍሎኝ ከጉሊሶ ወደ ጊንቢ ሲያዛውረኝ የቤት ኪራይ አበልና የዝውውር አበል በህብረት ስምምነቱ መሰረት ሊከፍለኝ ሲገባ ያልከፈለኝ በመሆኑ ከተዛወርኩበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልካች ላይ ያቀረበችው ክስ ነው አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የተጠሪ ክስ በይርጋ ይቋረጣል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ተጠሪ በራሷ ፍላጐትና ጥያቄ ከጉሊሶ ወደ ጊንቢ የተዛወረች በመሆኑ የቤት አበልና የዝውውር አበል የማግኘት መብት የላትም፡፡ አመልካች ለተጠሪ ከምትሰራበት ቦታ በመዛወሯ ምክንያት (disturbance allowance) ብር 300/ሦስት መቶ/ተከፍሏል፡፡ ከዚህ ውጭ ያቀረበችው ጥያቄ በሕግም ሆነ በህብረት ስምምነቱ መሰረት የቀረበ አይደለም በማለት የበኩሉን ክርክርና ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የካቲት 12 ቀን 1995 የተፃፈ ማስጠንቀቂያ የሰጣት በመሆኑ ይርጋው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 መሰረት በተጠሪ ላይ አይቆጠርባትም በማለት የወሰነ ሲሆን ተጠሪ ያቀረበችውን የጥቅማ ጥቅም በተመለከተ ከየካቲት 12 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች እንዲከፈላት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ የተጠሪ ጥያቄ ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ የቀረበ ሆኖ አያለ ጥቁው በይርጋ አይታገድም ብለው አግባብነት የሌላቸውን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር በመጥቀስ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰራተኛ በራሱ ጠያቂነት ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ከተዛወረ ከእቃ ማጓጓዣ ወጭ በስተቀር ሌላ ነገር እንደማይከፈለው በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 20(16) እና(17) ተደንግጐ እያለ ለተጠሪ የዝውውር አበልና የቤት አበል እንዲከፈላት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሏ የበታች ፍርድ ቤቶች ይርጋው የተቋረጠ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1852 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 ድንጋጌዎች በመጥቀስ መወሰናቸው ተገቢ ነው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጠበቃዋ በኩል የቃል ክርክር አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ከሆነ እስከ መቼ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድረስ ያለው ጥያቄዋ ነው በይርጋ የሚታገደው? የሚለውና አመልካች ለተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚሉት ጭብጦች ውሳኔ ማግኘት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ ያቀረበችው የዝውውር አበልና የቤት አበል ጥያቄ መጠየቅ ከሚገባው ጊዜ ውስጥ እስከ ስድስት ወር ባለው የጊዜ ገደብ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ንኡስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡ የቤትና የዝውውር አበል በአዋጅ አንቀጽ 162 ንኡስ አንቀጽ 3 “ሰራተኛው የሚያቀርበው የደመወዝ የትርፍ ሰአትና ሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ መጠየቅ ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል” በማለት በደነገገው “ሌሎች ክፍያዎች” በሚለው ውስጥ የሚሸፈኑ ክፍያዎች ናቸው፡፡ የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት የወሰኑት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1852 መሰረት ይረጋው የተቋረጠ መሆኑንና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 መሰረት ተጠሪ ክስ ያላቀረበችው አመልካች ካላት ፍርሐትና ታዛዥነት ምክንያት ነው በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ የወረዳውና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የይርጋው መቋረጥ በምክንያትነት ያቀረቡት አመልካች ተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል የማይገባት መሆኑን በመግለጽ የካቲት 12 ቀን 1995 ዓ.ም የፃፈውን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ነው፡፡ ይህ ደብዳቤ አመልካች ተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል ያላት መሆኑን በሙሉም ሆነ በከፊል በማመን የፃፈው ደብዳቤ ባለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 164 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት ይርጋውን ለማቋረጥ የሚችል አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ይርጋውን ሊያቋርጥ የሚችልና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 164 ድንጋጌዎች የሚሸፈን ምክንያት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሣይቀርብላቸው በጥቅሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1852 በመጥቀስ ይርጋው ተቋርጧል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪ የፃፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያላቀረበችው አመልካችን ስለፈራችና በታዛዥነት ስሜት ነው በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 በመጥቀስ የሰጡት ውሣኔ የህጉን ድንጋጌ አቀራረጽ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበ ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ላለው ግንኙነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 ድንጋጌ አግባብነትና ተፈፃሚነት የሌለው ድንጋጌ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን ድንጋጌ አላግባብ በመጥቀስ አመልካች ከየካቲት 12 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የቤትና የዝውውር አበል እንዲከፍል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ የጠየቁት ቀጣይነት ያለውና ተከታታይነት ባለው ጊዜ ውስጥ ሊከፈላቸው የሚገባ የቤትና የዝውውር አበል ነው፡፡ ተጠሪ ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት የካቲት 6 ቀን 1999 ዓ.ም መሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ በመሆኑ ተጠሪ ከነሐሴ 6 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት አመልካች የቤት አበልና የዝውውር አበል እንዲከፈላት ያቀረበችው ጥያቄ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 163 ንኡስ አንቀጽ 3 በይርጋ ቀሪ የሚሆን በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ከየካቲት 12 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሐሴ 5 ቀን 1998 ዓ.ም ለተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል እንዲከፍል የወሰኑት የይርጋ የጊዜ ገደቡ ያለፈበትን ጥያቄ አላግባብ ተቀብለው በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ከነሐሴ 6 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት ያለው የቤት አበልና የዝውውር አበል ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ተጠሪ ካቀረቡት ጥያቄ ውስጥ ከነሐሴ 6 ቀን 1998 ዓ.ም ወዲህ ላለው ጊዜ የቤትና የዝውውር አበል እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ይህንን ቀሪ ለማይሆነው ጊዜ ለተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ጭብጥ ውሣኔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ከጉሊሶ ወደ ጊንቢ ከተማ የተዛወሩት በራሳቸው ፍላጐትና ጥያቄ አቅራቢነት መሆኑ ክርክር ያስነሳ ፍሬ ጉዳይ ካለመሆኑም በላይ አመልካች ተጠሪ በዝውውሩ እንዲፈቀድላት ጠይቃ መዛወሯን የሚያስረዳ ማስረጃ ያቀረበ መሆኑ ከወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ እንደዚሁም በአስረኛው የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 16 (መ) እና አንቀጽ 17 ማንኛውም ሰራተኛ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ በተመሣሣይ የሥራ መደብ ለመዛወር ጠይቆ ከተፈቀደለት ከዝውውር ጋር ተያይዞ የሚሰጠው ጥቅም የማያገኝ መሆኑን እንደሚደነግግ የወረዳው ፍርድ ቤት በውሣኔው ገልፆታል፡፡ ተጠሪ ከጉሊሶ ወደ ጊንቢ የተዛወረችው በራሷ ፍላጐትና ጥያቄ እንጅ መሣሪያ ቤቱ በዝውውር ስለመደባት አይደለም፡፡፡ አመልካች ለተጠሪ የቤትና የዝውውር አበል እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ከላይ የተገለፀውን የሕብረት ስምምነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌ የሚጥስ ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ከላይ የተጠቀሰውን ግልጽ የህብረት ስምምነት ድንጋጌ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ሲወስን የተጠሪን ወደ ተላላኪ የሥራ መደብ ማደግ መጥቀሱ ተገቢነት የሌለው እና የድንጋጌውን መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም በይርጋ ቀሪ ለማይሆነውም ጊዜ ቢሆን አመልካች ለተጠሪ የቤትና የገዘውውር አበል የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ሆኖ እያለ የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ላይ የሰጡት ውሣኔ የሕግ ወይም የሕብረት ስምምነቱ መሰረት የሌለው ነው፡፡

በአጠቃላይ የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የይርጋ ክርክር ውድቅ በማድረግና የሕብረት ስምምነቱ የተዛባ ትርጉም በመስጠት አመልካች ለተጠሪ ከየካቲት 6 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የቤትና የገዘውውር አበል እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ ከላይ የተዘረዘሩትን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የጊንቢ ወረዳ ፍርድ ቤትና የምእራብ ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ ለሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የቤትና የገዘውውር አበል የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49057

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አስመላሽ እና ልጆቹ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- ዮሐንስ እሺበል - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት የቀረበ የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣አመልካችን የከሰሰው የሥራ ውሌ ከሕግ አግባብ ውጪ አቋርጦብኛል በማለት ነው፡፡ ክሱን መሰረት በማድረግም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉት ጠይቆአል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ተቀጥሮ ሲሰራበት የነበረው የህንፃ ግንባታ ተጠናቅቆአል፡፡ ይሰራ የነበረው በአናጺት ሙያ ሲሆን፣ሥራው የለም፡፡ በመሆኑም የሰራተኛ ቅነሳ ሥርአት መከተል ሳያስፈልገኝ ያለማሰጠንቀቂያ አሰናብቻዋለሁ በማለት ስለመከራከሩ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር ከሰማ በኋላ፣የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በዚህ መሰረትም ለተጠሪ ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉት ወስኖለታል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መስከረም 7 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30 መሰረት የሥራ ግንኙነት በተቋረጠ ጊዜ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታን ያስከትላል ወይስ አያስከትልም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጭብጥ ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ እንደገለጸው ተቀጥሮ ይሰራ የነበረው በአናጺነት የሥራ መደብ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ክርክርም የተመሰረተው በዚህ ላይ ሆኖ የአናጺነት ሥራ በመጠናቀቁ የሥራ ውሉ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30 መሰረት ተቋርጦአል የሚል ምክንያት ሰጥቶአል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ ስለነበረው ሁኔታ አመልካች እና ተጠሪ ልዩነት የላቸውም፡፡ በመሆኑም አከራካሪው ነጥብ ውሉ የተቋረጠው ሕጉ ከደነገገው ውጪ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ ጭብጡ የሕግ በመሆኑ ሊመለስ የሚችለው ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የአዋጁ ድንጋጌ አንፃር በማየት ነው፡፡

አመልካች የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ ኮንስትራክሽን ሲሆን፣ ተጠሪ ተቀጥሮ ይሰራ የነበረውም አመልካች ሲያካሂደው በነበረው የህንፃ ግንባታ ነው፡፡ በህንፃው ግንባታ ሂደት የሚከናወኑ ብዙ የተለያዩ ሥራዎች (የሥራ አይነቶች) እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ተጠሪ ተመድቦበት የነበረው የሥራ አይነትም ከብዙዎች ሥራዎች አንዱ በሆነው የአናጺነት ሥራ ነው፡፡ ሥራዎች ሁሉ በአንድ ጊዜ የሚያልቁ እንዳልሆኑም ከሥራው ባህርይ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም የአናጺነት ሥራው በመጠናቀቁ ተጠሪ ተቀንሶአል፡፡ የዚህ አይነት የሰራተኞች ቅነሳ በሚያጋጥመውበት ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ 30 የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ ድንጋጌው ልዩ ሁኔታን በማስቀመጥ አሰሪው በአዋጁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከቱትን የሰራተኞች ቅነሳ ሥነ-ሥርአት መከተል የለበትም ብሎአል። ይህ ማለት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 28/2/ መሰረት ማስጠንቀቂያ እንዲሰጥ አይገደድም ማለት ነው። የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከአንቀጽ 30 ውጪ በማየቱ አመልካች በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት ነበረበት እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል። በመሆኑም በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ውሳኔ ሰጥቶአል ለማለት ችለናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 42790 ሰኔ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 82438 ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል።
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ብለናል። አመልካች ማስጠንቀቂያ መስጠት አያስፈልገውም ነበር።
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ።

መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት - አንዳርጋቸው በየነ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. ኃይሌ ይማም - ቀረበ፡፡

2. ዓሊ ሐሰን - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኞች መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በዱብቲ ዱአር ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት ሥራችንን በገዛ ፈቃዳችን ለመተው የፈለግን ስለሆነ የአገልግሎት ካሣ ከፍሎና ምስክር ወረቀት በመስጠት እንዲያሰናብተን ይወሰንልን በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች በጡረታ የሚገለሉ ከመሆናቸው በተጨማሪ የአገልግሎት ካሣ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ግን ክርክሩን ውድቅ በማድረግ የተጠየቀውን የአገልግሎት ካሣ እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት በአፋር ብ/ክ/መ/የአውሲ ረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤትም እንደዚሁ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጠሪዎች የአገልግሎት ካሣ /የስንብት ክፍያ/ ይከፈላቸው የመባሉን አግባብነት ከመመርመር አንፃር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር ያልተካደው ወይም የተረጋገጠው ተጠሪዎች የክፍያ ጥያቄን እና ስንብትን መሠረት በማድረግ ክስ የመሠረቱት በጡረታ የሚገለሉበት ጊዜ እንደደረሰ ነው፡፡ አመልካች የክፍያ ጥያቄውን ከሥር ጀምሮ ሲቃወም የመጣውም ተጠሪዎች መደበኛ የጡረታ ዕድሜ የደረሱና የጡረታ አበልም የሚከፈላቸው ናቸው በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎችም በዚህ መልክ ከአመልካች የቀረበውን ክርክር የሚያስተባብል ክርክርም ሆነ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ ተጠሪዎች በአመልካች ዘንድ ማገልገላቸውን ብቻ በማየት ወሰኑ እንጂ በሕጉ የተቀመጠውን ድንጋጌ ከቀረበላቸው የፍሬ ነገር ክርክር ጋር አላገናዘቡም፡፡

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96"ን" ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ እና /ሸ/ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39 እንደተደነገገው የሥራ ስንበት ክፍያ የሚከፈለው ሠራተኛው የፐሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለው ከሆነ እንደዚሁም ሥራውን ሲለቅ መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ያልደረሰ ሲሆን ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች ሥራችንን በገዛ ፈቃዳችን ለቀናልና የስንብት ክፍያ እንዲከፈለን ይወሰንልን በማለት ክስ የመሠረቱት የጡረታ መውጫ እድሜያቸው ሳይደርስና ተገቢውን ዝግጅት እንዲያደርጉ አመልካች ካስታወቃቸው በኋላ እንደሆነ በአመልካች ክርክር ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪዎች ይህ እውነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላለመሆኑ ያሳዩት ነገር የለም፡፡ ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪዎች የጡረታ መብት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ መደበኛ የጡረታ ዕድሜም የደረሱ መሆናቸው ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም የስንብት ክፍያ የሚያገኙበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጠው ውሣኔም ከዚህ አንፃር ሲታይ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአፋር ብ/ክ/መ/ የዱብቲ ደአር ወረዳ ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 0956/2000 ሐምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የአውሲ ረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 1279 ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት የሥራ ስንብት ክፍያ ሊያገኙ አይችሉም በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42985

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ውድመጣስ ኑሮ አስመጪና ላኪ ድርጅት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- እነ አቶ ሁኘኛው ሰጠ (11 ሰዎች) - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪዎች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው በመሆኑ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ መልስ ሲሰጥ የተጠሪዎች የስራ ውል የተቋረጠው ድርጅቱ ለዘለቄታው ስራ በማቆሙ ስለሆነ የተጠየቀው ክፍያ ሊከፈል እንደማይገባና ተጠሪዎችም የቀን ሰራተኞች በመሆናቸው የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን አመልክቷል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች ከስራ የተሰናበቱት ድርጅቱ ለዘለቄታው በመዘጋቱ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት አመልካች የስራ ስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ በቅሬታውም አመልካች ድርጅት የተዘጋው በባንክ እዳ ምክንያት ባንኩ ተረክቦት በመሆኑ ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ አይደለም እንዲሁም ተጠሪዎች በአዋጁ አንቀጽ 10/ሰ/ መሰረት የተቀጠሩ የቀን ሰራተኛ በመሆናቸው ስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ ይህ ችሎት የተጠሪዎች የስራ ስንብት ህጋዊ ከሆነ የስራ ስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈላቸው መወሰኑ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪዎችም ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡም ተመርምሯል፡፡

አመልካች ድርጅት ለዘለቄታው በመዘጋቱ ተጠሪዎች ከስራ መሰናበታቸውን የስር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች በክርክር ድርጅቱ የተዘጋው በባንክ እዳ ምክንያት ባንኩ ድርጅቱን በመረከቡ ስለሆነ የማስጠንቀቂቃ ጊዜ ሊከፈል አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ነገር ግን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/2/ሀ/ ሰራተኞች የተሰማሩባቸውን ስራዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቀጥታና ለዘለቄታው የሚያስቆም የሰራተኛ ቅነሳ የሚያስከትል ሁኔታ ሲከሰት የስራ ውሉ በማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ እንደሚችል ይገልፃል፡፡ ድንጋጌው የድርጅቱ ስራ በከፊል ብቻ ሳይሆን በሙሉ ለዘለቄታው ሲቆም ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ እንደሚገባው የሚያሳይ ነው፡፡ ድርጅቱ በሙሉ ስራ ካቆመ የቅነሳ ጥያቄ ሊነሳ አይችልም፡፡ ይልቁንም ሰራተኞች በሙሉ የሚሰናበቱበትን ሁኔታ ነው የሚያስከትለው፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ድርጅቱ ስራውን በሙሉ ለዘለቄታው የሚያስቆም ሁኔታ በመከሰቱ አመልካች የስራ ውሉን ሲያቋርጥ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይገባዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ የሚገባው ቅነሳ ሲደረግ ብቻ እንጂ ድርጅቱ እንዳለ ሲዘጋ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪዎች የአመልካች ድርጅት ሰራተኞች መሆናቸው በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የቀን ሰራተኞች ናቸው በማለት ይከራከር እንጂ የስር ፍ/ቤቶች ክርክሩን አልተቀበሉትም፡፡ የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሰራተኛ ድርጅቱ በመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የስራ ውሉ ሲቋረጥ የስራ ስንብት ሊከፈል እንደሚገባ የአዋጁ አንቀጽ 39/1/ሀ/ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ድርጅቱ ለዘለቄታው በመዘጋቱ ለተጠሪዎች የስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34121 መስከረም 28 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 70887 ኅዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49958

የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ግዮን ትራቭልና ቱርስ ኃ/የተ/የግ/ማ - ነ/ፈጅ ዳንኤል ወርቅዬ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዳንኤል አስፋው - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ያለአግባብ ከሥራ መሰናበቱን ጠቅሶ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ በአመልካች በኩል ሥር ፍ/ቤት የቀረበው ክርክር ተጠሪው የሥራ ሃላፊው ላይ አላስፈላጊ አምባጓሮ፣ ፀብ፣ ዛቻ፣ ስድብ በመፍጠሩ ተሰናብቷል የሚል ነው ጉዳዩን በመ/ደረጃ የተመለከተው የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ሥራ አስኪያጅ ላይ እንደዛተ እንጂ አምባጓሮ ወይም ፀብ ስለፍጠሩ አልተረጋገጠም በሚል ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ሲል ፈርዷል፡፡ አመልካች የአምስት ወር ደመወዝ ለተጠሪ ከፍሎ ወደ ሥራ እንዲመለስ ሲልም ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው የአመልካች ነ/ፈጅ ጥቅምት 21/2002 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ተጠሪው የነዳጅ ያቀረበው ደረሰኝ የተጋነነ እና ታማኒነት የጐደለው በመሆኑ በሥራ አስኪያጁ ሲጠየቅ በአግባቡ ማስረዳት ሲገባው ጠብ አጫሪነት በመፍጠር ወይ አንተ ወይ እኔ እንኖራለን በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ ረ መሰረት ጥፋት ስለመፈፀሙ መረጋገጡን

ስንብቱ ሕጋዊ ስለመሆኑ በአማራጭ ተጠሪው በአዋጁ አንቀጽ 43/1/ መሰረት ካሣ ተከፍሎት ሊሰናበት እንደሚገባ ራሱ የጠየቀው ዳኝነት የሥር ፍ/ቤቶች ማለፋቸው የሕግ ስሕተት መሆኑን ጠቅሶ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ትሎትም በተጠሪ ተፈጽሟል የተባለው ድርጊት ከአዋጁ አንቀጽ 27/1/ረ አንፃር ለመመርመር የሚገባው ሆኖ ስላገኘው ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት አድርጓል ተጠሪ የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ የሕግ ስሕተት የለውም ሲል እንዲጸና ጠይቋል፡፡

እኛም የቀረበውን አቤቱታ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ተጠሪው የአመልካች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ላይ የዛቻ ኃይለ ቃል እንደተናገረው ተመስክሯል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የተጠሪ ድርጊት የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ረ የተደነገገውን ጥፋት ያሟላል የሚል ክርክር በአመልካች በኩል ቀርቧል፡፡ ይህንኑ ለመመረመር የተጠቃሹን ድንጋጌ ይዘት በዝርዝር መመልከት ይገባል፡፡ አንቀጽ 27/1/ረ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

"እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ቦታ አምባንሮ ወይም ጠብ እጫሪነት ተጠያቂ መሆን" ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ለማቋረጥ ከሚያስችሉ ምክንያቶች ሥር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የሥራ አስኪያጅን "ወይ አንተ ወይ እኔ እንኖራታለን" በማለት የዛተበት ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡ ይህ የተጠሪው ድርጊት ከተጠቀሰው ድንጋጌ አንፃር ሲታይ የጠብ አጫሪነት ኃይለቃል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የተጠሪው የድርጊት ዛቻ ነው ካለ በኋላ ይህ ድርጊት ፀብ ድርጊት ሊባል እንደማይችል ጠቅሶ ይህ ክብደት ሊሰጠው አይገባም ብሏል፡፡ በኛ በኩል ስንመረመረው አንድ ሰራተኛ የአሰሪው ወይም የሥራ ኃላፊው ትእዛዝ ከሕግ ውጪ እስካልሆነ ድረስ ማክበር እና መፈጸም እንዳለበት ልብ ሊባል ይገባል፡፡ አንድ ሰራተኛ አሰሪው ወይም የሥራ ኃላፊው የሚሰጠውን ሕጋዊ ትእዛዛት መፈጸም እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/2/ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ ስለሥራው አካሄድ በሥራ አስኪያጅ ሲጠየቅ አግባብ ባለው ሥርአት ማስረዳት ሲገባው ለምን ተጠየቅኩ በሚል ስሜት ኃይለ ቃል እና ዛቻ ማድረጉ የጠብ አጫሪነት ድርጊት መባል የሚገባው ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡

ድርጊቱም የተፈፀመው በአመልካች ድርጅት የሥራ አስኪያጅ ላይ መሆኑ የተጠሪን ድርጊት ጥፋት ክባድነት አመልካች ነው፡፡ ስለሆነም የተጠሪው ድርጊት የአዋጁን አንቀጽ 27/1/ረ የተመለከተውን ጥፋት አያሟላም ሲል የሥር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሕግ ያስቀመጠውን የሰራተኛውን ግዴታ የሚመለከተውን ድንጋጌ እና የጥፋቱን አደገኛነት ከተጠቃሹ ድንጋጌ አንፃር በአግባቡ ሳያገናዝብ መሆኑን ስለተረዳን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40658 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83563 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ረ መሰረት በመሆኑ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ሊባል አይገባም ብለናል፡፡

ግራ ቀኝ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 40529

የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የሕፃን ዮናታን ነጋ ተሻገር ሞግዚት - ጠ/ጥጋቡ ጌጤ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ለገሰ አበራ - ጠ/ወርቁ መንገሻ ቀረቡ

መዝገቡን መርመረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ለሰራተኛው ጥገኞች ስለሚከፈል ካሣ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110 አተረጓጐምን የሚመለከት ነው፡፡

የአመልካች አባት አቶ ነጋ ተሻገር በተጠሪ ተቀጥረው ለሥራ ሲንቀሳቀሱ ሕይወታቸው በማለፉ ያልተከፈለ ደመወዝ ብር 6,500 /ስድስት ሺህ አስምት መቶ/፣ ያልተከፈለ አበል ብር 9,750 /ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ/፣የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ ብር 2000 /ሁለት ሺህ/ እና ሚች ሌላ ጥገኛ ስላልነበራቸው የሞት ካሣ ክፍያ ብር 60,000 /ስልሳ ሺህ/ እንዲከፈል አመልካች በሞግዚቱ አማካይነት ክስ መሰረተ፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ያቀረቡትን የመጠን ክርክር በማስረጃ አጣርቶ ከካሣ ገንዘብ በተቀረ ሌሎቹን እንደ ክሱ አቀራረብ ወስኗል የሞት ካሣ አከፋፈል አስመልክቶ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110/3/ /ለ/ እድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው ልጆች የእያንዳንዳቸው ድርሻ 10% ብቻ ነው በሚል ከተጠየቀው ብር 60,000 /ስልሳ ሺህ/ ውስጥ 10,000 (አስር ሺህ) ብቻ እንዲከፈል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም ተጠቃሹ ድንጋጌ የአንዱን ጥገኛ ድርሻ ለሌላኛው እንዲከፈል ሕጉ በግልጽ አልደነገገም የሚል ምክንያት ሰጥቶ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 110/3/ በአግባቡ አልተረጐመም፣የሚች ብቸኛ ወራሽ እና ጥገኛ አመልካች ነው፤እንዲሁም ሚች ሚስት አልነበረውም፤የሚስትም ድርሻ ጭምር ታስቦ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል አመልካችም የተወለደው ከጋብቻ ውጪ ነው የአመልካች ሞግዚት አክስቱ ናቸው በሚሉ ፍሬ ነገሮች መነሻ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤት የአዋጁን አንቀጽ 110 አተረጓጐም አግባብነት ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ወላጅ አባት በተጠሪ ተቀጥረው ሥራ ላይ እያሉ ሕይወታቸው ማለፉ አላከራከረም፡፡ የአመልካች አባት በሥራ ላይ በሞት የተለዩ ስለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የሞት ካሣ ለጥገኞች ስለሚከፍልበት ሁኔታ በዝርዝር የተደነገገው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 110 እንመለከታለን፡፡

በተጠቀሰው አንቀጽ 110/1/ የተመለከተው ሊከፈል የሚገባው የክፍያ ዓይነት ነው፡፡ ይህም አንዱ ለጥገኞች የሚከፈል ካሣ ነው፡፡ ለጥገኞች የሚከፈል ካሣ መጠን እና ጥገኞች የሚባሉት እነማን እንደሆኑ ድንጋጌው በቀጣይ ንኡስ አንቀጾች አመልክቷል፡፡ የሚች ጥገኞች ብሎ ሕጉ የዘረዘራቸው የሚች ልጆች ሆነው 18 ዓመት በታች የሆኑ፣የሚች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጋዊ ባል ወይም ሚስት እና በሚች ሰራተኛ ድጋፍ ይረዱ የነበሩ የሚች ወላጆች መሆናቸውን አንቀጽ 110/2/ ዝርዝር ያመለክታል። በተያዘው ጉዳይ ከአመልካች ሌላ የቀረበ የሚች ጥገኛ ነኝ ባይ የሌለ መሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል።

ቀጥሎ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ የካሳ ስሌት እና የአከፋፈሉ ሁኔታ ነው። ሊከፈል የሚገባው ካሳ መጠን አስመልክቶ የአዋጅ አንቀጽ 110/3/ የመጀመሪያው አረፍተ ነገር ይገልፃል። ይኸውም "የሰራተኛው የዐመት ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ የሚገኘው" የገንዘብ መጠን ነው። ስለሆነም የክፍያው መጠን ጣሪያ በሕጉ በግልጽ ተወስኗል። ከዚህ ተከትሎ የሚታየው ይህንን ገንዘብ በጥገኞች መካከል የሚከፋፈልበት ሥርአት የሚያመለክት ድንጋጌ ነው። ለዚህም የሚች ጥገኞች ናቸው ተብለው ከላይ የተዘረዘሩት የእያንዳንዳቸው ድርሻ መጠን በመቶኛ በአንቀጽ 110/3/ ሀ-ሐ ተዘርዝሯል። ከፍ ሲል የተመለከትነው የጥገኞች ማንነት፣ ሊከፈል የሚገባው ካሣ መጠን ጣሪያው እና የስሌቱ አወሳሰን እንዲሁም የጥገኞች ድርሻ መጠን አስመልክቶ በሕጉ የተዘረዘሩትን መሰረተ ሐሳቦች ነው።

ከተያዘው ጉዳይ አንፃር አከራካሪው ሚች አንድ ጥገኛ ብቻ ያለው መሆኑ በታወቀ ጊዜ ሊከፈል የሚገባው የካሳ መጠን ጣሪያው የተወሰነው (100%) ወይንስ ከላይ በዝርዝር በተመለከተው መሰረት የጥገኛው ማንነት ተከትሎ የተቀመጠው መቶኛ የሚለው ጉዳይ ነው። ይህንን አከራካሪ ጭብጥ መልስ ለማግኘት የአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌ አንቀጽ 110/4/ በዝርዝር መመርመር ተገቢ ነው። የዚህ ድንጋጌ ይዘት እንዲህ ይነበባል።

> "በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 የክፍፍል መጠን መሰረት ተሰልቶ የክፍፍሉ መጠን በድምር (100%) (መቶ በመቶ) የሚበልጥ እንደሆነ የክፍፍሉ ድምር መጠን 100%(መቶ በመቶ) እስኪሆን ከእያንዳንዱ ጥገኛ ላይ ጥገኛ በየመጠኑ ይቀነሳል። እንዲሁም የክፍፍሉ መጠን መከፈል ከሚገባው አጠቃላይ መጠን የሚያንስ የሆነ እንደሆነ የክፍፍሉ መጠን መቶ በመቶ እስከሚሆን ለእያንዳንዱ ጥገኛ ድርሻ እንደመጠኑ የጨመራል" ይላል።
>
> አንቀጽ 110/4/ ይመለከታል።

ከዚህ ድንጋጌ የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር መገንዘብ የሚቻለው የእየንዳንዱ ጥገኛ ድርሻ ተዳምሮ ሊከፈል ከሚገባው ጣሪያ (ወሰን) በላይ የሚሆን ከሆነ የእያንዳንዱ ጥገኛ ድርሻ በመቶኛ በሕጉ ከተሰጠው ሊቀነስ እንደሚገባ ነው።

የዚህ ድንጋጌ መንፈስ ሚች ሰራተኛ በርካታ ጥገኞች ቢኖሩት በአዋጁ አንቀጽ 110/3/ ሀ-ሐ በተቀመጠው መጠን ለእያንዳንዱ እየተሰላ የአሰሪውን ሃላፊነት መጠን ከጣሪያው(ወሰን) እንዳያልፍ ወይም የአሰሪው ሃላፊነት በአንቀጽ 110/3/ የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ከተቀመጠው የሥሌት መጠን እንዳያልፍ ለመከላከል ነው። ይህ የሕጉ ሐሳብ ተፈፃሚነት የሚኖረው ሚች ሰራተኛ በርካታ ጥገኞች ኖሮት የእያንዳንዳቸው ድርሻ በመቶኛ ድምር ከጠቅላላው መቶኛ ድምር በላይ ሆኖ ሲገኝ ነው ማለት ነው። አንቀጽ 110/4/ ሁለተኛው ዐረፍተነገር ይዘት ደግሞ ሲታይ ሚች ሰራተኛ ያለው ጥገኛ ቁጥር አነስተኛ ሆኖ የእያንዳንዳቸው ድርሻ ስሌት ተደምሮ አሰሪው ሊከፈል ከሚገባው በታች ሆኖ ሲገኝ ቀሪውን መቶኛ ገንዘብ ሌሎቹ ጥገኞች እንዲያገኙት ለማድረግ እንደሚቻል የታሰበ መሆኑን ነው። ይህም ማለት ሚች ሁለት ልጆች ብቻ ቢኖሩት እና ሚስት ባይኖረው በአንቀጽ 110/3/ /ለ/ መሰረት የልጆቹ ድርሻ 20% ሲሆን ቀሪው 80% ተጠቃሚ (ባለመብት ጥገኛ) የለውም ተብሎ የሚቀር ሳይሆን ለእነዚሁ ልጆች እንደየድርሻው በመቶኛ ሊጨመርላቸው እንደሚገባ የሚያመላክት ነው። የዚህ ድንጋጌ መንፈስ የጥገኞች ቁጥር አነስተኛ ከሆነ የአሰሪ ሃላፊነት ጣሪያ ወሰን ድረስ ያሉት ጥገኞች ተጠቃሚ እንዲሁኑ ለማድረግ ያሰበ መሆኑን ያመለክታል።

በተያዘው ጉዳይ ሚች አቶ ነጋ ተሻገር ከአመልካች ሌላ ጥገኛ ስለመኖሩ የቀረበ የለም። በሥር ፍ/ቤት የተወሰደው አቋም አመልካች ድርሻ 10% ብቻ ነው የሚል ነው። ነገር ግን የአንቀጽ 110/4/ ድንጋጌ ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር እንደሚያስገነዝበው አመልካች ብቸኛ የሚች ጥገኛ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የተጠሪ የሃላፊነት መጠን ጣሪያ ድረስ ካሳው ሊከፈለው ይገባል። ይህም ማለት የአመልካች ድርሻ 10%(አስር በመቶ) ሳይሆን መቶ በመቶ(100%) ነው።

ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንን በአግባቡ ሳይገናዝቡ የአመልካች ድርሻ 10% ብቻ ነው በማለት የአዋጁን አንቀጽ 110/3/ለ በመጥቀስ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለው ሆኖ አግኝተናል።

የአመልካች ድርሻ መቶ በመቶ ነው ከተባለ ስሌቱ ምን ያህል ነው ለሚለው የሥር ፍ/ቤት የአመልካች አባት ደመወዝ በወር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ መሆኑን መሰረት አድርጎ የሰጠው ፍርድ ተጠሪ ስላልተቃወሙ በአንቀጽ 110/3/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት በሞት ምክንያት ሊከፈል የሚገባው የካሣ መጠን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ብር 60,000 (ስልሳ ሺህ ብር) መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22962 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 66031 የሰጠው ውሳኔ የአመልካች የካሣ ድርሻ አስመልክቶ የሰጡት የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎ ተከታዩ ተወስኗል፡፡
2. አመልካች የሟች አቶ ነጋ ተሻገር ብቸኛ ጥገኛ መሆኑ ስለተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110/4/ መሰረት ካሣ ሙሉ ለሙሉ ሊከፈለው ይገባል ብለናል፡፡ ስለሆነም በሟች ደመወዝ ተሰልቶ የቀረበው ብር 60,000 (ሥልሳ ሺህ ብር) ይከፈለው ብለናል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በዚሁ መሰረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡

የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 48648

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓለ መሐመድ

አመልካች፡- የፃልቁ የትምህርትና የተቀናጀ የልማት ማህበር - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. አቶ ታጠቅ ደጀኔ
2. አቶ ተፈሪ በርቤ } ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የቀረበውን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ ሚያዚያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ታህሳስ 13 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በፕሮግራም ማናጀርነት፣ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ከጥቅምት 03 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በኮሚኒቲ ወርከር የስራ መደብ ተቀጥረው እንደሰሩና የስራ ውሉ ያላግባብ ሚያዚያ 08 ቀን 2001 ዓ.ም መቋረጡን ገልፀው ካሳ፣ የስራ ስንብት፣ ክፍያ ለዘገየበት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሚያዚያ ወር ደመወዝ እና የዓመት እረፍት ክፍያ ከወጪና ኪሳራ ጋር ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚይሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ድርጅትም ለክሱ በሠጠው መልስ፣ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ሆነው የስራ ቅጥር ውላቸውም ለማህበሩ በለጋሽ ድርጅቶች የሚሠጠው እርዳታ በመቆሙ ፕሮጀክቱ የተዘጋ ስለሆነ መቋረጡን ገልፆ የስራ ውል የተቋረጠው በሕጉ አግባብ በመሆኑ የተጠየቁት ክፍያዎች ሊከፈሉ አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ክርክሩንና ማስረጃዎችን መርምሮ የስራ ውሉ ለአንድ ፕሮጀክት ተጠሪዎች የተቀጠሩ ስለመሆኑ የማያሳይ፣ ተጠሪዎች ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው ስለማይባሉ፣ በአንድ ፕሮጀክት መዘጋት ምክንያት ተጠሪዎችን ማሰናበቱ ህጋዊ አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የአመልካችን ክርክር ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ ተጠሪዎች ካሳ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሚያዚያ ወር ደመወዝ እና የዓመት ፈቃድ ክፍያ አመልካች ሊከፍላቸው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ስንብቱ ሕገ-ወጥ ተብሎ ውጤቶቹን በተመለከተም የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዞባታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ነሐሴ 01 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪዎች ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩና የተቀጠሩበት ፕሮጀክት የተዘጋ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪዎች የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የተጠሪዎች የስራ ውል ለተለየ ፕሮጀክት የተቀጠሩ መሆኑን የሚያስረዳ ባለመሆኑ ተጠሪዎች ይሰሩበት የነበረው ፕሮጀክት ተቋርጧል በሚል የስራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው መባሉ እና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪዎች ቀርበው ታህሳስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

13 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለጠቅላላ ፕሮጀክት በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ቅሬታ ነጥቦች ተገቢነት የሌላቸው መሆኑን፣ በአንፃሩ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትን ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈፀመም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም ታህሳስ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ የመልስ መልስ ሠጥተዋል፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሮ ግራ ቀኙን ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ያነጋገረ ሲሆን ግራ ቀኙ የስራ ውል ለጠቅላላ ፕሮጀክት የተደረገ መሆኑንና አመልካች ድርጅትም በአሁኑ ወቅት ስራውን እየሰራ እንደሚገኝ ተማምነዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች እርምጃ ሕገ-ወጥ ተብሎ ተጠሪዎች የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ የተወሰነው ባግባቡ ነው ወይም አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ተጠሪዎችን አሰናበትኩ የሚለው ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ፕሮጀክት በመዘጋቱ ነው የሚል ምክንያት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ቅጥሩ ለተዘጋው ፕሮጀክት ሳይሆን ለጠቅላላ ፕሮጀክት ሆኖ ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ ይገኛል በማለት የሚከራከሩ ሆኖ ቅጥሩ ለጠቅላላ ፕሮጀክት ስለመሆኑ በዚህ ችሎት በተደረገው ማጣራት መረጋገጡን ነው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ከተረጋገጠ ደግሞ በተጠሪዎች እና በአመልካች መካከል ያለው ግንኙነት መገዛት ያለበት በመካከላቸው በተቋቋመው ውል በመሆኑ ተጠሪዎች በአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 10(1ሀ) መሰረት ለአንድ ለተለየ ፕሮጀክት የተቀጠሩ ሰራተኞች አለመሆናቸውን መገንዘብ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 30005 ሰኔ 03 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 52383 ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም በከፊል የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ነሐሴ 29 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 47825

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ አስቱር በቀለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ዘርዓየሁ ስሜ
2. አቶ ሽፈራው አራጋው
} ጠበቃ ክፍሌ ታደሠ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ከአመልካች ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት እንደነበራቸው፣ ይህ ግንኙነታቸው የተቋረጠው በተጠሪዎች ፈቃድ መሆኑን፣ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ሊከፈላቸው የሚገባው ደመወዝ ሳይከፈላቸው የቀረ መሆኑን፣ ልዩነቱ መከሰቱን ያወቁት መንግስት የደመወዝ ጭማሪ ወይም ማስተካከያ ማድረጉን የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም ከጻፈው ደብዳቤ መሆኑን፣ የደመወዝ ማስተካከያው ከሕዳር 01 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን መወሰኑን፣ በዚህም መሰረት አንደኛ ተጠሪ ሊከፈላቸው ከሚገባው ደመወዝ ብር 6338.84(ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰማንያ አራት ሳንቲም)፣ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ብር 14430.93(አስራ አራት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ከዘጠና ሶስት ሳንቲም) መሆኑን ገልፀው ይኸው በልዩነት የመጣውን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር መከራከሪያ ነጥቦችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረባቸውን የመከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ ከማድረጉም በላይ ለተጠሪዎች ክስ ኃላፊነት አለበት በማለት የክሱን ገንዘብ ለተጠሪዎች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሐምሌ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር ማመልከቻ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረቡትን የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ ያደረገው ያላግባብ መሆኑን፣ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የነበራቸው የስራ ግንኙነት በገዛ ፈቃዳቸው ከተቋረጠ በኋላ መንግስት ያደረገው የደመወዝ ማስተካከያ እንዲከፈላቸው የተወሰነው ከመመሪያው ዓላማና መንፈስ ውጪ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው ሊሻር ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተጠሪዎች ከአመልካች ድርጅት ስራ ከለቀቁ በኋላ ተፈቀደ የተባለው የደመወዝ ስኬል ጭማሪ ተጠሪዎችን ይመለከታል ወይስ አይመለከታቸውም? የሚለውን እና ሌሎችን ነጥቦች ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የተጠሪዎች ጠበቃ ሕዳር 23 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተገቢነት አለው የሚሉባቸውን ምክንያቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ሕዳር 25 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት በተጠሪዎች ፈቃድ ከጥር 03 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ መቋረጡን፣ በዚህ ወቅት ተጠሪዎች ከአመልካች ድርጅት ሲሰናበቱ በወቅቱ ሊከፈላቸው ይገባል የተባለው የተለያየ ክፍያ መከፈሉን፣ ተጠሪዎች ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ በአመልካች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪ መመሪያው ተፅፎ ከህዳር 01 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ጭማሪው ተግባራዊ እንዲሆን ከተወሰነ በኋላ መሆኑን ነው፡፡ እንግዲህ ተጠሪዎች የመብት ጥያቄው ምንጭ ነው የሚሉት የስራ ውሉ ከመቋረጡ በፊት ለሰሩበት ስራ በደመወዝ ጭማሪ መመሪያው መሰረት ሊከፈለን የሚገባው የደመወዝ ልዩነት አለ በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰራተኛ ከአሰሪው ጋር በሚፈጥረው የስራ ግንኙነት መሰረት ሕጉ የሚፈቀደው ማንኛውም መብት የሚጠበቅለት መሆኑ አከራካሪ አይሆንም፡፡ የአንድ መብት ወይም ግዴታ መሠረት ደግሞ ሕግ ወይም ውል መሆኑ ይታወቃል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ተጠሪዎች የጠየቁትን ክፍያ የሚያገኙበት የሕግ መሰረት አለ ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ተጠሪዎች በገዛ ፈቃዳቸው ስራቸውን ስለለቀቁ መመሪያው በስራ ላይ ያሉትን ሰራተኞች ለማበረታታት የወጣ እንደመሆኑ መጠን ሊከፈላቸው የሚገባ ቀሪ ደመወዝ የለም በማለት ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት አለው የተባለው መመሪያም የወጣበት መሰረታዊ ዓላማ ሲታይ የፋይናንስ ድርጅቶች ሰራተኞች የሆኑት በጭማሪው ተነቃቅተው ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ ስለመሆኑ በመግቢያው ላይ የተገለፀ መሆኑን የሰር ፍርድ ቤትም ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ የመመሪያው መሰረታዊ ዓላማ ይህ ከሆነ መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ስራውን በገዛ ፈቃዱ የለቀቀ ሰራተኛ ወደኋላ ተመልሶ ማስተካከያውን መሰረት አድርጎ ቀሪ ደመወዝ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግም ሆነ የስነ አመክንዮ(ሎጂክ) አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የሰር ፍርድ ቤቶች የተጠሪዎችን የዳኝነት ጥያቄ ከመመሪያው ዓይነተኛ ዓላማ ጋር በማዛመድ መመልከት ሲገባቸው ይህንኑ ሳያደርጉ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ለተጠሪዎች በቀሪነት የሚፈለጉት ደመወዝ ይከፈል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35175 መጋቢት 30 ቀን 2001 ዓ/ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80204 ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የነበራቸውን የስራ ግንኙነት በገዛ ፈቃዳቸው ከለቀቁ በኋላ በወጣው የደመወዝ ጭማሪ ማስተካከያ መመሪያ መሰረት የሚከፈላቸው ቀሪ ደመወዝ የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47535

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ጌሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት - ነ/ፈጅ ታደለ ገ/ወልድ

ተጠሪ፡- አቶ አንማው ላቀው - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በደብረ-ማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ድርጅት ያለአግባብ ከስራና ከደሞዝ ስላገዳቸው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ካልቻለ የስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ድርጅት ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ የፈፀሙት ድርጊት በዲሲፒሊን ታይቶ ተጠሪ ለአንድ ወር በታገዱበት ላለው ጊዜ ደሞዝ ሳይከፈላቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ስለተወሰነ ደሞዝ ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን መርምሮ አመልካች ተጠሪን ያገደው ያለአግባብ መሆኑን አምኖበት ወደ ስራ ስለመለሳቸው የመስከረምና የጥቅምት ወር ደሞዛቸው ይከፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለምስ/ጉጃም አስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ተጠሪን ሳይጠራ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ በድምጽ ብልጫ አቤቱታው ውድቅ ተደርጉበታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው ተጠሪ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው የመጨረሻ የፁሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑ ተገልፆ እያለ ከስራ የታገዱት ያለአግባብ መሆኑ ታምኖበት ወደ ስራ ስለተመለሱ ደሞዛቸው ይከፈላቸው መባሉ ስህተት ነው፣አሰሪ ሰራተኛው ጥፋተኛ ሆኖ ካገኘው ለ30 ቀናት ከደሞዝና ከስራ አግዶ ለማቆየት እንደሚችል አዋጁ ስልጣን ስለሚሰጠው ለታገዱበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፈላቸው የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት ብሏል፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ በቀረበበት የዲሲፒሊን ክስ ምክንያት ለታገደበት ጊዜ ደሞዝ ይከፈላቸው የመባሉን አግባብነት ለመመረመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ለቀረበባቸው አቤቱታ መልሳቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ በመልሳቸውም አመልካች ጥፋት ሳይፈጽሙ ለአንድ ወር ከስራና ከደሞዝ ታግደው የመጨረሻ ደረጃ የፁሁፍ ማስጠንቀቂያ የሰጣቸው ያለአግባብ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እንደሚከተው መርምሯል፡፡

ተጠሪ ከስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት አመልካች ያለአግባብ ከስራና ከደሞዝ ስላገዳቸው ለታገዱበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፈላቸውና ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ለፈፀሙት ጥፋት ጉዳዩ በዲሲፒሊን እስከሚታይ ድረስ ከደሞዝና ከስራ ማገድ ስለሚችል ጥያቄው ውድቅ እንዲሆንለት አመልክቷል፡፡ አመልካች ለክርክሩ መሰረት ያደረገው አ/ቁ. 377/1996 እና የድርጅቱን ህብረት ስምምነት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ተጠሪ ከስራና ከደሞዝ ለታገዱበት ጊዜ ደሞዝ ሊከፈላቸው የሚገባ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ይህንንም ጭብጥ ለመመለስ ችሎቱ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁንና በወቅቱ በስራ ላይ የነበረውን የድርጅቱን ህብረት ስምምነት ተመልክቷል፡፡ በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 27/4/ ስር ያለማስጠንቀቂያ የሰራተኛውን የስራ ውል እንዲቋረጥ ከመደረጉ በፊት ሰራተኛውን ከስራ አግዶ ማቆየት ስለሚቻልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን እንደሚችልና የአገዳው ጊዜ ግን ከ30 ቀናት እንደማይበልጥ ተደንግጓል፡፡ አመልካች የሚከራከረው የድርጅቱ ህብረት ስምምነት ጥፋት የፈፀመ ሰራተኛ ጉዳዩ በዲሲፒሊን እስከሚታይ ለ30 ቀን ከስራና ከደሞዝ አግዶ ማቆየት እንደሚቻል ተደንግጓል በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ጥፋቱን ፈጽመዋል ተብለው ከስራ የታገዱት ከመስከረም 2001 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ ችሎቱ በወቅቱ በስራ ላይ የነበረውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የድርጅቱን የህብረት ስምምነት ተመልክቷል፡፡ በዚህ ህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 51 ስር ማንኛውም ሰራተኛ ከባድ ጥፋት በመፈፀሙ ምክንያት ጥፋቱ ተጣርቶ ውሳኔ አስከሚሰጥበት ድረስ ከ30 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ከመደበኛ ሥራው ያለደሞዝ እንዲታገድ ማድረግ እንደሚቻልና ለውሳኔው መዘግየት ሰራተኛው ራሱ ምክንያት መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ከ30 ቀናት በላይ ላለው ጊዜ ደመወዝ እንደሚከፈለው ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሰራተኛው ጥፋት ሲገኝበት ጉዳዩ እስከሚጣራ ለአንድ ወር ከስራና ደሞዝ ሊያግደው እንደሚችል የአመልካች ድርጅት ህብረት ስምምነት ይፈቅዳል፡፡ ይህ ደግሞ አዋጁን መሰረት አድርጐ የወጣ የስምምነት ቃል በመሆኑ ተጠሪ ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ፈጸሙ ያለውን ጥፋት እስከሚያጣራ ከስራና ላገደበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፍል አይገደድም፡፡ የስር ፍ/ቤት አዋጅንና የህብረት ስምምነቱን ድንጋጌዎች ሳይመረመር ተጠሪ ከስራ ለታገዱበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፈል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ከስራ የታገዱት ለሁለት ወራት መሆኑና የሁለት ወር ደሞዝ ያልተከፈላቸው ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ነገር ግን ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ሰራተኛው ከስራና ደሞዝ ሊታገድ የሚችለው ለ30 ቀናት ብቻ ነው፡፡ የህብረት ስምምነቱ ከ30 ቀን ደሞዝ የማይከፈለው ውሳኔው የዘገየው በሰራተኛው ምክንያት ከሆነ ብቻ እንደሆነ ቢደነግግም አመልካች ውሳኔው በተጠሪ ምክንያት ስለመዘግየቱ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለሁለት ወራት ከስራና ከደሞዝ መታገዳቸው አዋጁንም ሆነ የሕብረት ስምምነቱን የሚቃርን በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ የመስከረም ወር እንዲከፈላቸው መወሰኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደብረ-ማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5852 ታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣ምስ/ጉጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 96588 ጥር 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 00973 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ከስራ ለታገዱበት አንድ ወር ጊዜ ደሞዝ ሊከፈላቸው አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ያልተከፈላቸው የመስከረም ወር 2001 ዓ.ም ደሞዛቸው እንዲከፈል የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 49750

መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/01 የመዝናኛ ክበብ -

ጠበቃ አሰፋ ዝቅአርጋቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ማስረሻ ሁሴን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ ክሳቸውም ሰኔ 01 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ ሁኖ ይዘቱም ባጭሩ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከነሐሴ 01 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥረው በወር ደመወዝ ብር 314(ሦስት መቶ አስራ አራት) እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እንዳሉ ያላግባብ ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም ከስራ የተሰናበቱ መሆኑን በመግለፅ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሠጠው መልስ፤ ስንብቱ የተከናወነው ተጠሪ የድርጅቱን ትዕዛዝ ባለማክበራቸው ስለመሆኑ በመግለፅ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት አመልካች ድርጅት ለተጠሪ የስራ ስንብት፣ የካሣ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ እንዲከፍላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 06 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ የተሰናበቱት የአመልካችን ትዕዛዝ ሊያከብሩ ባለመቻላቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት ለሕብረት ስምምነቱ አፈፃፀም የተዛባ ትርጉም በመስጠት ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም የካቲት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ ሆነው በሚሰሩበት የስራ ሠዓት ወቅት አመልካች የድራፍት በርሜል እንዲረከቡ ትዕዛዝ ሊያስተላልፍላቸው ሊቀበሉ ያልቻሉ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት አረጋግጦ ይህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪ ድርጊት ከስራ ለመሰናበት ሕጋዊ ምክንያት አይደለም ለማለት የቻለው በሕብረት ስምምነቱ እንደጥፋት ቢጠቀስም ሰራተኛው ትዕዛዙ ሕገ-ወጥ እስከሆነ ድረስ ለመቃወም የሚችል ስለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13(2) ድንጋጌ መረዳት ይቻላል በሚል ነው፡፡ በእርግጥ አንድ ሰራተኛ በስራ ውሉ ላይ የተጣለውን ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑ ይኸው የተጠቀሰው ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በአዋጁ በአንቀጽ 27(1/ሸ) ድንጋጌ ሕጉ ካስቀመጣቸው በተጨማሪ በሕብረት ስምምነቱ ላይ ከስራ ሊያስባርሩ የሚችሉ ጥፋቶችን መወሰን እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ተጠሪን ከስራ ሊያሰናብታቸው የቻለው በሕብረት ስምምነቱ መሆኑን በመጥቀስ የሚከራከር ሲሆን የህብረት ስምምነቱ አለመታዘዝ ከማስጠንቀቂያ በኋላ ከስራ ሊያስባርር እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህ የሕብረት ስምምነቱ ክፍል በዚህ መልኩ መቀመጡ የተረጋገጠ ቢሆንም ተቀባይነት የለውም ያለው ለሰራተኛው ከሕጉ ከተቀመጠው ጥቅም ያነሰ ያስገኛል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሕጉ ከሕጉ ከተቀመጡት ጥፋቶች ውጪ በሕብረት ስምምነቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያስባርሩ ይችላሉ ተብሎ መደንገግ የሚቻል መሆኑን ከማስቀመጡም በላይ በአዋጁ አንቀፅ 134(2) መሰረት የሕብረት ስምምነቱ ለሰራተኛው ሕጉ ካስቀመጠው ጥቅም ያነሰ የሚያስገኝ ሆኖ ከተገኘ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ጥፋትና ጥቅምን በተመለከተ ሕጉ የተለያየ አቋም የያዘ መሆኑን እንጂ አሰሪና ሰራተኛ በሕብረት ስምምነቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በማለት የተስማሙበት ድርጊት ተቀባይነት የለውም የሚለውን ነጥብ አይደለም፡፡ አንድ ሰራተኛ የአሰሪውን ትዕዛዝ ማክበርም ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 13(7) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ህጋዊ መሰረት የሌለው ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፤ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 56547 ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 83500 ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የስራ ውል ያቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከፕሮቪደንት ፈንድ ውጪ የሚከፈላቸው ክፍያ የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 49797

መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አልሀበሽ ሹገር ሚልስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር -

ተወካይ አቶ ተካልኝ መለሰ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተገኔ ገ/ሃዋርያት - ከጠበቃ አብዱራህማን መሐመድ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54585 ሀምሌ 17 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጥቅምት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡

ክርክሩ የታየው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ በወር ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) እየተከፈለው በአመልካች ድርጅት ሚሠራ እንደነበር ገልፆ አመልካች መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም ከሥራ አላግባብ ያሰናበተኝ ስለሆነ ወደ ሥራ እንድመለስ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሉኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪን ያሰናበተው መኪናና ሹፌር ተመድቦለት እየተገለገለ እያለ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የድርጅቱን መኪና ቁልፍ ከሹፌሩ በመረከብ በማሽከርከር ላይ እያሉ የድርጅቱን መኪና በማጋጨት ጉዳት አድርሷል፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህጉን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የከሳሽ (ተጠሪ) ጥያቄ ተገቢነት የለውም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ለመደገፍ ያቀረቡትን ማስረጃ ሣይሰማና ሣይመረምር አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው የሥራ ስንብት ደብዳቤ ፅፎ ሣይሆን በቃል በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪ የአምስት ወር ደመወዝ በመክፈል ወደሥራው እንዲመልሰው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ከሥራ የተባረረው በጥፋቱ ነው፡፡ ተጠሪን የጥፋቱ ተጠቃሚ የሚያደርግ ውሣኔ መሠጠቱ የህግ ስህተት ያለበት ውሣኔ ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራ የተባረረው የሥራ ውሉ ሊጠናቀቅ አንድ ወር ሲቀረው በመሆኑ የአምስት ወር ደመወዝ ከፍላችሁ ወደሥራ መልሱ በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ችሎት ማስረጃችንን በመቀበል ውሣኔ ይሰጥልን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እኔ የተቀጠርኩት ላልተወሰነ የሥራ ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች የሥራ ውሉ ሊጠናቀቅ አንድ ወር ሲቀረው ነው ያሰናበትኩት በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በህጉ የተመለከተውን ሥርዓት ሣያሟላ ከሥራ ማሰናበቱ ህገ-ወጥ ስለሚያደርገው የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር ያቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው በፅሑፍ ሣይሆን በቃል መሆኑ ብቻ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስንብቱ ህገ-ወጥ መሆኑን ያሣያል በማለት አመልካች ተጠሪን የአምስት ወር ደመወዝ ከፍሎ እንዲመልስ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ለዚህ ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን መሠረታዊ ጭብጥ በመለየትና በመመሥረት ለክርክሩ እልባት የሰጠ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ አንድ ጭብጥ የሚመሰርተው ከሳሽ በክሱ የገለፀውን ተከሳሹ ክዶ የሚከራከር ሲሆን እንደሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 247 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ አመልካች አላግባብ ከሥራ ያሰናበተው መሆኑን ገልፆ ክስ ያቀረበ ሲሆን አመልካችም ተጠሪን ከሥራ አላሰናበትኩትም የሚል ክርክር አላቀረበም፡፡ አመልካች ተጠሪን ከሥራ አሰናብቸዋለሁ በማለት በግልፅ መልስ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ማቋረጡ ግራቀኙ የሚተማመኑበት ነጥብ በመሆኑ ስንብቱ በፅሑፍ ነው ወይስ በቃል የሚል ማጣሪያ ማድረግ የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት አሠሪው ለሠራተኛው የሥራ ውሉ ያቋረጠበትን ምክንያት በፅሑፍ አለመግለፁ ብቻውን ስንብቱን ህገ ወጥ የሚያደርግ አይደለም፡፡ አሠሪው ይህንን ሣይፈፅም ቢቀርና በፅሑፍ ሣይሆን በቃል ወይም በድርጊት የሥራ ውሉን ቢያቋርጥ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ያለው መሆኑን ከመከራከርና ማስረጃ ከማቅረብ የሚገድብ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሣይሰማና ግራቀኙ የሚከራከሩበትን ጭብጥ ሣይመሰርት ስንብቱ በፅሑፍ ያልተደረገ በመሆኑ ብቻ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል አላግባብ አሰናብቷል በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአንድ ጉዳይ ጭብጥ የሚመሠረተው ከሳሽ ያቀረበውን ክስና ማስረጃ ተከሳሽ የሚሰጠውን የመከላከያ መልስና ማስረጃና ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት በሚያደርገው የቃል ምርመራ የተሰጠ መልስ መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ይደነግጋል፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ማቋረጡ አከራካሪ ጭብጥ አይደለም፡፡ አከራካሪው ጭብጥ አመልካች በድርጅቱ መኪና ላይ ጉዳት በማድረሡና ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ለማሰናበት የሚችል ጥፋት በመፈፀሙ ስንብቱ ህጋዊ ነው የሚል ክርክር ያቀረበና ይህንን ለማስረዳት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ያቀረበ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚካሳዱበትን ይህንን ጭብጥ በመመሥረትና በማስረጃ በማጣራት ውሳኔ መስጠት ሲገባው የሥራ ስንብቱ በቃል የተደረገ መሆኑ ብቻውን ስንብቱ ህገ-ወጥ መሆኑን ያሣያል በማለት የሰጠውን ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሣያርም እንዳለ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ሠራተኛው(ተጠሪ) ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በመፈፀሙ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥና ሌሎች ነጥቦች ለማስረዳት በግራ ቀኙ በኩል ያቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 50009

መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአ/አ ሂልተን ሆቴል - ጠ/ሃሳብከፋይ ጌራወርቅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዮናስ ጥላሁን - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ከሥራው ጋር በተያያዘ ከባድ የማጭበርበር ድርጊት ፈጽሟል በማለት አመልካች ከሥራ ያሰናበተው ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የፈፀመው ድርጊት ከስራ ለማሰናበት የሚያበቃ አይደለም ሲል በመወሰኑ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የተጠሪ ድርጊት የሥራ ውልን ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የቀረበውን ክርክር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው ተጠሪ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪው የሥራ ውል የተቋረጠው ለድርጅቱ ሰራተኞች በተዘጋጅ ካፍቴሪያ የውጪ ሰው አስገብቶ እንዲመገብ አድርጓል በሚል ነው፡፡ ተጠሪው ይህንን ድርጊት አልፈጸምኩም ሲል የካደ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ምስክር ሰምቶ ተጠሪውን ድርጊቱን ፈጽሟል በማለት በውሳኔው አረጋግጧል፡፡ ነገር ግን የተጠሪ ድርጊት ከባድ የማጭበርበር ድርጊት ነው ሊባል አይችልም በማለት ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ብሏል፡፡

ይህ ችሎትም የተጠሪ ድርጊት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሐ/ የሚሸፈን ስለመሆኑ መርምሯል፡፡ የተጠቀሰው አንቀጽ ድንጋጌ ይዘት “እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር መፈጸም” የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ እንደሚያስችል ያመለክታል፡፡ ተጠሪ ሥራው ሹፌር እንደነበር ተጠቅሷል፡፡ ተጠሪ ፈጽሟል የተባለው ድርጊት ደግሞ በሰራተኞች ካፍቴሪያ የውጪ ሰው አስገብቶ ጋብዟል የሚል ነው፡፡ ይህ ተግባር በራሱ በቀጥታ ከተጠሪው ሥራ ጋር የሚያያዝ አለመሆኑን መረዳት አዳጋች አይደለም፡፡ ካፍቴሪያው ደግሞ በራሱ የቁጥጥር ሥርአት መስተንግዶ እና አገልግሎት እንደሚሰጥ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ለዚህ የተመደቡት ሰራተኞች ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ግልጽ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ተጠሪው ከሥራ ጋር በተያያዘ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር ፈጽሟል ለማለት አይቻልም ሲል የሥር ፍ/ቤት የደረሰበትን ድምዳሜ ለማስተባበል የሚያስችል አሳማኝ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት በአመልካች በኩል አልቀረበም፡፡ ከዚህም ባሻገር ተጠሪው ፈጽሟል የተባለው ድርጊት በራሱ እንደሕጉ አገላለጽ እና እሳቤ “ከባድ የማጭበርበር ወይም የማታለል ተግባር” የሚያሰኝ ሁኔታ ስለመኖሩም አመልካች አላስረዳም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የተጠሪ ድርጊት ያልተገባ መሆኑን ተቀብለው እንደ ሕጉ አነጋገር ግን ከባድ የማጭበርበር ድርጊት ሊባል አይችልም በዚህም የተነሳ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለሆነም ባለበት ሁኔታ በማጽናት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 30209 ሐምሌ 22/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83534 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል።
   በዚህ መዝገብ ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል። ይፃፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 50205

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት

ተጠሪ፡- አቶ ምናለ በሪሁን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች የሥራ ውል አላግባብና ማስጠንቀቂያ ሣይሰጠኝ ያቋረጠ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዜን ከፍሎ ወደ ሥራ ይመልሰኝ የሚል ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪ የተቀጠረው ድርጅቱ በፍርድ ቤት የሚከራከርባቸው ጉዳዮች እስኪቃለሉ ድረስ ለጊዜያዊነት ነገረ ፈጅ ሆኖ እንዲሠራ በመሆኑና ሥራው ያለቀ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የነገረፈጅ አገልግሎት የሚጠይቀው ሥራ ያላለቀ በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት አመልካች የስድስት ወር ደመወዝ በመክፈል ወደ ሥራ ይመልሰው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች የአሥራ አምስት ቀን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውሉን የማቋረጥ መብት ያለው መሆኑ በሥራ ውሉ ተገልጿል አመልካች የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚችል ቢሆንም የሥራ ውሉን ያቋረጠው በሥራ ውሉ መሠረት የአስራ አምስት ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ባለመሆኑና ሥርዓቱን ባለመጠበቁ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 የተለያዩ ድንጋጌዎች መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን ይክፈሉ፣ ተጠሪ ወደ ሥራ መልስ ሊባል አይገባውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን አሻሽሎ ወስኗል፡፡

አመልካች የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪን ለማሰናበት እንደምንችልና ማሰናበታችንም ተገቢ ነው ብሎ ከወሰነ በኋላ የተለያዩ ክፍያዎችን ተገቢነት የሌላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ እንድንከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት እኔን በሚጎዳ ሁኔታ ውሉንና ህጉን ከመተርጎሙ ውጭ አመልካችን የሚጎዳ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሥራ ውል በማናቸውም ጊዜ የአስራ አምስት ቀናት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለማቋረጥ የሚችል መሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥራ ውሉን በማስቀረብ እንዳረጋገጠ በውሣኔው ገልጿል፡፡ ተጠሪ ሥራው ከማለቁ በፊት አመልካች የሥራ ውሉን ማቋረጡ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር ከአመልካችና ከተጠሪ የሥራ ውል በግልፅ የተመለከተውን ፍሬ ጉዳይ የሚቃረንና የህግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው በውሉ የተቀመጠውን ሥርዓት ማለትም የአስራ አምስት ቀናት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሣያሟላ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል በውሉ ከተመለከተው ሥርዓት ውጭ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ሁኔታ ሣያጋጥመው ካቋረጠ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 39(1/ለ) መሠረት በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 2፣ በአንቀፅ 44 እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4(ለ) የተደነገጉትን ክፍያዎች ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለው በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል
2. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 4 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48476

ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ በለጠ ቂጤሳ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ደረጃ መኮንን - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 515/1999 "ን" መሰረት ያደረገ የስራ መልቀቂያ ይሰጠኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው፤በዚህ ፍርድ ቤት ያሁኑ ተጠሪ ያቀረቡት ይግባኝ ከስራ ከለቀቁ ከሁለት ወራት በላይ ቢሆናቸውም ለአመልካች መስሪያ ቤት የስራ መልቀቂያ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቅርበው መስሪያ ቤቱ ፈቃደኛ አለመሆኑን፤ከመስሪያ ቤቱ ጋር በገቡት የትምህርት ስልጠና ውል መሰረት የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት የተወጡ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ ከስራ መልቀቂያ ጋር መያያዙ አግባብ አለመሆኑን በተመለተ ከሚመለከታቸው ከሰው ሐብት ስራ አመራር ክፍሎች የተነጋገሩበት መሆኑን፤ይህንኑ መሰረት በማድረግ የውሁፍ ማብራሪያ እንዲያቀርቡ ተስማምተው የውሁፍ ማብራሪያ ማቅረባቸውን የገለፁ ቢሆንም አመልካች መስሪያ ቤት መልቀቂያውን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑን በመጥቀስ አመልካች የስራ መልቀቂያ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ የካቲት 29 ቀን 1996 ዓ.ም ከቀድሞው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ካሁኑ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ጋር የስልጠናና የትምህርት ውል ገብተዋል፤በትምህርት ላይ የቆዩት ለሦስት አመታት ሲሆን ትምህርቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ለስድስት አመት አገልግሎት ለመስጠት ተስማምተዋል፤ትምህርታቸውን አጠናቅቀው በውሉ መሰረት የሰጡት አገልግሎት ሃያ ሁለት ወራት ከአስራ አምስት ቀናት ነው፤ተጠሪ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ሳይወጡ የአገልግሎት ምስክር ወረቀት የሚያገኝበት ምክንያት የለም በማለት ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የአስተዳደር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ተጠሪ በውሉ የገቡትን ግዴታ ካልተወጡ አመልካች መስሪያ ቤት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረብ በስተቀር የስራ መልቀቂያ ማስረጃውን ለውሉ መያዣ እንዲሆን ማድረግ አይችልም የሚል ምክንያት በመያዝ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 87 መሰረት የአገልግሎት ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች መስሪያ ቤት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር ማመልከቻ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ንብረት ሳያስረክብ ወይም የበኩሉን ግዴታ ሳይወጣ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመረመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ሕዳር 10 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በአመልካች ወጪ ለሦስት አመታት የጋዜጠኝነት ትምሕርት የተከታተሉ ሆኖ ከአመልካች ጋራ ባደረጉት ውል ለአመልካች ከምረቃ በኋላ ለስድስት አመታት አገልግሎት ለመስጠት ግዴታ መግባታቸውን፣ከምረቃ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች ሓያ ሁለት ወራትና አስራ አምስት ቀናት የማይበልጥ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ የስራ መልቀቂያ እንዲሰጣቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ አመልካች የትምህርት ስልጠና ውሉ ላይ የተመለከተውን የተጠሪን ግዴታ ምክንያት በማድረግ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 78/1/ ድንጋጌ ሲታይ በሕግ ወይም በውል የተቀመጡ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በማንኛውም ጊዜ የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስራውን በገዛ ፈቃዱ ሊለቅ የሚችል ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን የተጠቀሰው አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ ሁለት ደግሞ በአንቀፁ ንኡስ አንድ ድንጋጌ ስር በተቀመጠው መሰረት የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ አገልግሎቱን ያቋረጠ የመንግስት ሰራተኛ ግዴታውን ባለመወጣቱ ለሚደርሰው ጉዳት እንደተገቢነቱ በፍትሐብሔር እና በወንጀል ሕግ መሰረት ተጠያቂነት ያለበት ስለመሆኑ ተቀምጧል፡፡ የአዋጅ አንቀጽ 87 ድንጋጌ ሲታይም የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ ወይም በማናቸውም ምክንያት አገልግሎት ሲያቋረጥ የስራ ልምድ ማስረጃ ከጠየቀ ሲያከናውን የነበረውን የስራ ዓይነት፣የአገልግሎት ዘመኑና ሲከፈል የነበረውን ደመወዝ የሚገልጽ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የሚሰጠው መሆኑን አስቀምጧል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው የአገልግሎት ምስክር ወረቀት ለማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከስራ ላይ እያለም ቢሆን የማይከለከል መሆኑን ሲሆን ሰራተኛው በመስሪያ ቤቱ የሚፈለግበት እዳ ካለ በሕጉ አግባብ ሰራተኛውን የመጠየቅ መብት ለመስሪያ ቤቱ በሕግ የተጠበቀ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ መስሪያ ቤቱ ከሰራተኛው የሚፈልገው እዳ አለ የሚል ከሆነ ለሰራተኛው የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት ከመስጠት ባለፈ የስራ መልቀቂያ ወይም ክሊራንስ እንዲሰጠው የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ማስረጃዎች መስሪያ ቤቱ ከሰራተኛው ላይ የሚፈልገው እዳ ካለ በሕጉ አግባብ መብቱን ለማስጠበቅ የራሳቸውን የሆነ ጠቀሜታ ያላቸው ናቸውና፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት የመስጠት በሕግ የተጣለበት ግዴታ ሲሆን የስራ መልቀቂያ እና ክሊራንስ ግን ከተጠሪ የሚፈልገው እዳ አለ የሚል እስከሆነ ድረስ በዚህ ረገድ ማስረጃ እንዲሰጥ የሚገደድ አይሆንም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ እንዲሰጠው የወሰኑት በአዋጁ አንቀጽ 87 መሰረት የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንጂ የስራ መልቀቂያ እና ክሊራንስ ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ፍርድ ቤቶቹ ስህተት ፈጽመዋል በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 00721/2001 መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 45242 ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 49273

ሚያዝያ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ደረጀ ውለታው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዋሊያ ሌዘርና ሌዘር ፕሮዳክትስ ኃ/የተ/የግ/ማ

ፍ ር ድ

አመልካች በስራ ላይ በደረሰባቸው አደጋ በሁለቱም እጆቻቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ስለደረሰባቸው የጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸው ክስ መስርተው የስር ፍ/ቤት ጉዳቱ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ነው በማለት ካሳው በዚህ መሰረት እንዲከፈል የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻሉ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በማሽን መጭመቂያ ስራ ተሰማርተው ሲሰሩ በስራ ላይ እያሉ በግራና በቀኝ እጃቸው ላይ ዘላቂ የአካል ጉዳት ስለደረሰባቸው የጉዳት ካሳ፣ ክፍያ ለዘገየበት፣ የስንብት ክፍያና ለማስጠንቀቂያ ጊዜ ሊከፈል የሚገባው እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ጉዳቱ በስራ ላይ መድረሱን ሳይክድ የጉዳቱና የሚከፈለው የጉዳት ካሳ መጠን ላይ ክርክር አቅርቧል፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ላይ የደረሰው ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት በመሆኑ ለአመልካች ብር 24,900 /ሃያ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ/ እና ክፍያ ለዘገየበትና የአገልግሎት ካሳ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱ አመልካች ላይ የደረሰው 65% የአካል ጉዳት ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ስለሆነ የጉዳቱ ካሳ ሊከፈል የሚገባው በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 109(3)(ለ) ነው በማለት የአመልካች የአምስት አመት ደሞዝ በ65% ተባዝቶ የሚመጣው ብር 16,185.00 /አስራ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ አምስት/ እንዲከፈላቸውና ክፍያ ለዘገየበት ግን ሊከፈላቸው አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው የደረሰባቸው ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት በመሆኑ የጉዳት ካሳው ሊከፈል የሚገባው በአ/ቁ. 377/96 109(3) (ሀ) መሰረት ነው የሚል ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ነው ወይስ ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ነው የሚለውን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ተጠሪ ቀርቦ ክርክሩን በፅሁፍ አቅርቧል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካች በስራ ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ በግራ ቀኙ አልተካደም፡፡ አከራካሪው የጉዳቱ መጠን ነው፡፡ ከክርክሩ የአመልካች የቀኝ እጃቸው አራት ጣቶችና የግራ እጃቸው ሶስት ጣቶች መቆረጣቸውን ተገንዝበናል፡፡ የህክምና ቦርድም አመልካች ላይ 65% የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ አረጋግጧል፡፡ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ማለት ጉዳት የደረሰበትን ሰራተኛ ማናቸውም ደሞዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት እንደሆነ አዋ/ቁ 377/96 አንቀፅ 101(2) ያመለክታል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች የሁለት እጆቻቸውን አብዛኛዎቹን ጣቶች አጥተዋል፡፡ ከሞላ ጎደል ሁሉን ስራ ለመስራት የእጆቻችን ጣቶች አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ አመልካች የሁለቱንም እጆቻቸውን አብዛኞች ጣቶቻቸውን ማጣታቸው ደግሞ ማንኛውንም አይነት ደሞዝ የሚያስገኝ ስራ ለመስራት የሚከለክላቸውና የማይድን መሆኑን ተረድተናል፡፡ በእርግጥ የሃኪሞች ቦርድ ጉዳቱ 65% መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ይህ ጉዳት የተሰላው ግን ከአጠቃላይ የሰውነቱ ሁኔታ ጋር በማነፃፀር እንጂ የደረሰው ጉዳት ከመስራት ችሎታ ጋር ተነፃፅሮ የቀረበ አይደለም፡፡ ከፍ ሲል በተገለፀው የህጉ ድንጋጌ ደግሞ የአካል ጉዳቱ ከፊልና ሙሉ ተብሎ የሚከፈለው ከመስራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎታ ጋር በማነፃፀር እንጂ ከአጠቃላይ በሰውነት አካል ጉድለት ጋር ተነፃፅሮ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የደረሰባቸው ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ነው፡፡ በሰራተኛው ላይ የደረሰው ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ከሆነ የሚከፈለው የጉዳት ካሳ መጠን የሰራተኛው የዓመት ደሞዝ በአምስት ተባዝቶ እንደሆነ አንቀፅ 109(3)(ሀ) ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካች የጉዳት መጠን ዘላቂ ከፊል ጉዳት ነው በማለት ካሳው በአንቀፅ 109(3)(ለ) እንዲሰላ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ፀንቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 77981 ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ብር 24,900 (ሃያ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ) ይከፈላቸው፡፡
3. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ክፍያ የዘገየበትን አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 50148

ሚያዝያ 04 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1. አቶ ወርቁ ደረጀ
2. አቶ ወልዱ ገብሩ ወ/ጊዮርጊስ } ጠበቃ መንበረስላሴ በዛብህ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አባርኪሮ ሁመድ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍርድ እና አፈፃፀሙን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ለአፈፃፀሙ መሰረት የሆነው ውሳኔ የተሠጠውም በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1481 ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ነው፡፡ በዚሁ በመ/ቁጥር 1481 ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ሲሆን የክሱ ይዘትም ባጭሩ፤ ተከሳሾች በውላቸው መሰረት ስራውን እራሳቸው ወይም በሚወክሉት ሰው ማሰራት ሲገባቸው ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ውል ሰጪው እራሱ የጨው ምርቱን እያመረቱ ከጨው ማህበር ድርሻቸውን እየወሰዱ መሆናቸውን፣ የጨው ማምረቱን ስራ እራሳቸው ወይም የሚወክሉት ሰው እንዲጀምር በተደጋጋሚ ቢነገራቸውም ተከሳሾች ፍቃደኛ አለመሆናቸውን በመግለፅ የጠየቁት ዳኝነት ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰንላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ውሉ እንዲፈርስ ሲል በግልፅ ወስኗል፡፡ ለአፈፃፀም የቀረበው ውሳኔም ይህ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻቸው ላይ ውሉ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፈርስ መወሰኑን ገልፀው በውሉ መፍረስ ምክንያት የደረሰባቸውን ጉዳት አይነት እና መጠን ዘርዝረው ፍርድ ቤቱ አመልካቾች እንዲከፍሏቸው የአፈፃፀም ትዕዛዝ እንዲሰጥ ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም ለአፈፃፀሙ ክስ በሠጡት መልስ በሕጉ አግባብ የተሠጠና ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ስለሌለ ልንገደድ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን የአፈፃፀም ክርክር በመመርመር አመልካቾች ለተጠሪ ብር 71,000.00፣ 5789 ኩንታል ጨው እንዲሁም የ20343 ኩንታል ጨው 30% እንዲከፍሉ እና እንዲሰጡ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በሕጉ አግባብ የተፈረደ ውሳኔ ሳይኖር አመልካቾች ለተጠሪ ገንዘብ እንዲከፍሉ፣ ጨው በኩንታል እንዲሰጡ መወሰኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን የፍርድ አፈፃፀም ስርዓት ያላገናዘበ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው በፅሑፍ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመረውም የአሁኑ አመልካቾች ለተጠሪ ገንዘብ እንዲከፍሉ እና ጨው በኩንታል እንዲሰጡ በአፈፃፀም መዝገብ የተወሰነው ባለአዳ በሚያደርግ ፍርድ መሰረት ነው? አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ በዋናው ጉዳይ ክስ ሲመሰርቱ ለውሉ መፍረስ ምክንያቶች ናቸው ያሏቸውን ነጥቦች ዘርዝረው ውሉ እንዲፈርስ በጠየቁት ዳኝነት መሰረት ውሉ እንዲፈርስ የሚገልፅ ውሳኔ መሰጠቱን፣ ለአፈፃፀሙም መሰረት የሆነው ውሳኔ ይሕ ሲሆን የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርቡ ግን በውሉ መፍረስ ምክንያት የደረሰባቸውን ጉዳት ዘርዝረው ጉዳቱን አመልካቾች እንዲተኩ እንዲወሰንላቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው በአፈፃፀም ሊገደድ የሚችለው በሕጉ አግባብ የተፈረደ ፍርድ ሲኖር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ በሌላ አገላለፅ አንድ ሰው የፍርድ ባለአዳ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ፍርድ ሳይኖር በአፈፃፀም ሊገደድ አይገባም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ለአፈፃፀሙ መሰረት የሆነው ውሳኔ በመ/ቁጥር 1481 ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ሲሆን ይህ ውሳኔ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል የነበረውን የጨው መሬት ኪራይ ውል እንዲፈርስ በማለት ከመግለፁ ውጪ አመልካቾች ለተጠሪ በዓይነትም ሆነ በመጠን እንዲከፍሉ የተወሰነ የጉዳት መጠን ሁኔታ የለም፡፡ ተጠሪ በውሉ መፍረስ ምክንያት የደረሰባቸው ጉዳት እንዲከፈላቸው የጠየቁት ዳኝነት በዝምታ ታልፏል በማለት በበላይ ፍርድ ቤት ያሳረሙት ሁኔታ የለም፡፡ በእርግጥ ውሉ እንዲፈርስ ሲደረግ ሕጉ ያስቀመጠው አንዱ መፍትሔ የጉዳት ኪሳራ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1771(2) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በዚህ ረገድ ዳኝነት ተጠይቆ በግልፅ የተሠጠ ፍርድ ሲኖር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡ ከዚህ ውጪ በግልጽ ፍርድ ያላረፈበት ፍርድ የሚፈፅምበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ለተጠሪ ብር 71,000.00፣ 5789 ኩንታል ጨው እንዲሁም የ20343 ኩንታል ጨው 30% እንዲከፍሉ እና እንዲሰጡ በማለት የሠጡት ውሳኔ ያልተፈረደ ፍርድን ማስፈፀም ከመሆኑም በላይ የአመልካቾችን የመዳኘት ሕገ-መንግስታዊ መብት ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1631 ሐምሌ 07 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2067 ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካቾችን ባለዕዳነት፣ የተጠሪን ባለገንዘብነት የሚያረጋግጥ ፍርድ ሳይኖር አመልካቾች በፍርድ አፈፃፀም የሚገደዱበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ በለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- በዚህ ችሎት ሕዳር 03 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 49931

ሚያዝያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የጎሽና እርግብ መለስተኛና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር - ጠበቃ ምክሩ ወልደአረጋይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተሰማ ኃይሉ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ያሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ የክስ ይዘት ባጭሩ ከአመልካች ጋር ሕዳር 12 ቀን 2002 ዓ.ም በመሰረቱት የስራ ውል በድርጅቱ የፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ መቆየታቸውን ገልፀው የስራ ውሉ ጥቅምት 19 ቀን 2001 ዓ.ም ከሕግ ውጪ መቋረጡን ጠቅሰው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ የሞባይል ስልክ አበል ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፈል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ያሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳው ክርክር ተጠሪ የስራ መሪ ስለሆነ የስራ ክርክር ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም የሚል ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ በስራ አፈፃፀም ላይ ባሳዩት ጥፋትና የብቃት ማነስ ችግር የተሰናበቱ በመሆኑ እርምጃው ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ለማየት ስልጣን እንዳለው በመግለፅ ዋናውን ክርክርም ተመልክቶ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ በመድረስ አመልካች የስድስት ወራት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ በስራቸው ላይ የብቃት ማነስ ያሳዩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተጠሪ በብቃት ማነስ ምክንያት ለስራው ብቁ አይደሉም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ ተጠሪም በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ቀርበው የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገፅ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመለስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የሰራ ስንብቱን እርምጃ ሕጋዊ ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች ገልፆ ማስረጃ ጠቅሶ የተከራከረ መሆኑና የበታች ፍርድ ቤቶች የቀረቡት ማስረጃዎች የአመልካች ምክንያት በአሳማኝ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመግለፅ ውሳኔ የሰጡ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የተቻለው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ መሆኑን ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይሕ ሰበር ችሎት ስልጣኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በሕግ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈፅሙ ማቃናት ነው፡፡ ይህም በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ ነበር የተባለው የስራውን አሰራር የሚገልፅ ነው በሚል ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት የደመደሙት ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቱም አመልካች የተሳሳተ ነው ብሎ ቢከራከርም ተጠሪ ሪፖርቱ በሰነድ ችግር ያልተሟላ ስለመሆኑ በመግለፅ ለአመልካች የገለጸ መሆኑን አረጋግጠው ሂሳቡ የተሳሳተ ነበር ለማለት ያልቻሉ መሆኑን ያመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ ሲደረግ በጭብጥነት ያልተያዘውን ተጠሪ በስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥሩ ስለሚችሉ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት በአማራጭ አመልካች በመልስ መልሱ ላይ ጠይቋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ተጠሪ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ምክንያት ይሆናል ያለው ነጥብ ተጠሪ ለአለቃ የማይታዘዙ ናቸው የሚለው ሆኖ በስር ፍርድ ቤቶች የክርክር ነጥብ ያልሆነ እና በተገቢው ማስረጃም ያልተረጋገጠ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ ወደ ስራ ከሚመለስ በአማራጭ ካሳ ተከፍሎት እንዲሰናበት የሚደረገው በስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር የሚከሰት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያምን ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43(3) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከድንጋጌው ይዘት በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው ፍርድ ቤቱ የስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገባል ብሎ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊኖር ይገባል፡፡ ያለበቂ ማስረጃና ምክንያት አሰሪ የስራ ግንኙነቱ ችግር ውስጥ ሊወድቅ ይችላል ብሎ ስለተከራከረ ብቻ ድንጋጌውን ተግባራዊ ማድረግ የስራ ዋስትናን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ በአጠቃላይ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14112 ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80323 ጥቅምት 10 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት እ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ሕዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 50838

ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት - ነገረ ፈጅ አንድአርጋቸው በየነ - ቀረበ

ተጠሪ፡- 1. አቶ አማረ አበራ

2. አቶ ሽፈራው ጉደታ

3. አቶ ጌታቸው ይማም

4. አቶ አስማረ ቢሆነኝ

5. አቶ መሐመድ ሰይድ

6. አቶ እሸቱ ማሞ

7. አቶ አያሌው አሠፋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ታህሳስ 1 ቀን 2002 ዓ.ም ስላመለከተ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪዎች በከሳሽነት በመቅረብ ተንዳሆ እርሻ ልማት አክሲዮን ማህበር በነበረበት ወቅት ለሀያሁለት ዓመት በፎርማንነት የሥራ መደብ አገልግለናል፡፡ የተንዳሆ እርሻ ልማት ፈርሶ ወደ ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት በመንግስት ውሣኔ ሲዛወር የሠራተኞች መብት ጥቅም መጠበቅ እንዳለበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 131/99 ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ (አመልካች) መዋቅር ሲያፀድቅ የእኛን የሥራ መደብ መያዝና ማፅደቅ ሲገባው አፍርሶታል፡፡ ስለዚህ ከሙያችንና ከልምዳችን ውጭ በሆነ ሁኔታ ደረጃችንን ዝቅ አድርጎ የመደበን በመሆኑ ተንዳሆ እርሻ ልማት ስንሠራ በነበርንበት የፎርማንነት የሥራ መደብ ይመድበን በማለት አመልክተዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ እየተደራጀ ያለው ከተንዳሆ እርሻ ልማት የተለየ አዲስ ድርጅት ነው፡፡ ስለዚህ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችለው አዲስ መዋቅር ዘርግቷል፡፡ ጥቅማቸውን በማይቀንስ ሁኔታ ባለው መዋቅር መድበናቸዋል፡፡ ድርጅቱ በሌለው የፎርማንነት የሥራ መደብ ለመመደብ ያቀረቡትን ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ አመልካች ተጠሪዎችን በፎርማንነት የሥራ መደብ ይመድባቸው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርቦ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የቦርዱን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ክርክሩ ግላዊ ባህሪ ያለው ነው፡፡ ከድርጅቱ የሥራ ባህሪ በመነሳት አደረጃጀቱና መዋቅሩ ተቀይሯል፡፡ ስለዚህ በሌለ የሥራ መደብ ተጠሪዎችን እንድንመደብ የሰጠው ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28 ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መሠረታዊ ቅሬታችን የሀያ ሁለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓመት አገልግሎታችንን ወደ ጎን በመተው የሠራተኛ ማህበር ተወካይ ባልተገኘበት በአዲስ የሥራ መደብ ላይ በመመደባቸው ነው፡፡ ሥለዚህ ቦርዱና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በስር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪዎች ያቀረቡት ጥያቄ አመልካች አዲስ በዘረጋው መዋቅር የሥራ መደባችን ፈርሷል፡፡ ስለዚህ በፊት የነበረንን የሥራ መደብ በአዲሱ መዋቅር በማካተት በፊት በሠራንበት የሥራ መደብ በፎርማንነት ይመድበን በማለት ነው፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄና የሚሰጠው ውሳኔ በእነርሱ ብቻ የሚወሰን ውጤት ያለው ሣይሆን የሌሎችንም ሠራተኞች ለተመሣሣይ ጥያቄ የሚጋብዝ የወል የሥራ ክርክር ባህሪ ያለው ነው፡፡ ጉዳዩ የወል የሥራ ክርክር ባህሪ ያለው በመሆኑ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ የአመልካችንና የተጠሪዎችን ክርክር ሰምቶ የመወሰን ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 147 መሠረት አለው፡፡ ስለዚህ አመልካች ቦርዱ ጉዳዩን መርምሮ የመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

ቦርዱ ጉዳዩን የማየትና የመወሰን ሥልጣን አለው ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረስን በኋላ የቦርዱ ውሣኔ ህጋዊ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? ሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት በፊት ከነበረው የተንዳሆ እርሻ ልማት አክሲዮን ማህበር የተለየ የሥራ ባህሪ ያለው ድርጅት ነው፡፡ አመልካች ለሥራ ባህሪው የሚስማማ የሥራ መዋቅርና የሥራ መደብ በጥናት ላይ በመመርኮዝ እንዲፀድቅ በማድረግ የሠራተኛ ምደባ አከናውኗል፡፡ ተጠሪዎች በፊት ያላቸው የሥራ ልምድና የትምህርት ዝግጅት አዲስ ለፀደቀው የሥራ መዋቅር የትኛው ቦታ ላይ ሊያስመድባቸው እንደሚችል በኮሚቴ ተጠንቶና ታይቶ በፊት ያገኙት የነበረው ደመወዝ ሣይቀነስ በአዲሱ የሥራ መዋቅር አዲስ ሥራ መደብ ላይ ተመድበዋል፡፡ ድርጅቱ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ሥራውን ለማከናወንና አትራፊና ተወዳዳሪ ለመሆን በሚያስችለው አደረጃጀትና የመደራጀትና የሥራ መደብ የማዋቀር ሥልጣን እንዳለው ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች የተጠሪዎችን ደመወዝ ሣይቀንስ በአዲሱ መዋቅር ሊመጥናቸው በሚችለው የሥራ መደብ መድቦ የማሠራት ሙሉ ኃላፊነት ያለው ሲሆን የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ በአዲሱ መዋቅር ባልተካተተና በሌላ የሥራ መደብ አመልካች ተጠሪዎችን መድቦ እንዲያሠራ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ሠራተኞችን ባለው መዋቅርና አደረጃጀት መድቦ የማሠራት መብት የሚጋፋውን የቦርዱን ውሣኔ በይግባኝ ሣያርም ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   ይህ ፍርድ በፊዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 45746

ሚያዝያ 6 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ነ/ፈጅ አየለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ በለጠ ጫላ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ በተፈጠረ የመኪና ግጭት አደጋ አደጋው ከደረሰ ከ4 ወራት በኋላ መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም ያለአግባብ የስራ ውላቸው ስለተቋረጠ ወደስራቸው እንዲመለሱ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በመልሱ መኪናውን በቸልተኝነት አጋጭተዋል፣ የትራፊክ ፖ/ሊስ ስለአደጋው ውጤቱን የገለፀው የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በመሆኑ እርምጃው በይርጋ አይታገድም፣ በመሆኑም ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የቀረበው የትራፊክ ሪፖርት ተጠሪ ጥፋተኛ መሆናቸውን ስለማይናገር አደጋው በተጠሪ ጥፋት ነው ማለት ስለማይቻልና አደጋው በተጠሪ ቸልተኝነት የደረሰ መሆኑን አመልካች ማስረዳት ስላልቻለ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን በመሰረዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው ተበላሽቶ መንገድ ዳር የቆመ ከባድ መኪና ለማመልከት ተደርድረው የነበሩትን ድንጋዮችና ሌሎች ምልክቶች ደርምሰው በማለፍ አደጋው መድረሱን የትራፊክ ፖ/ሊስ ሪፖርት ስላረጋገጠ ስንብቱ በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 27(1/ሸ) መሰረት ህጋዊ ነው፣ የተረከቡትን የድርጅቱን ንብረትና ገንዘብ ያስረከቡና ያወራረዱ ለመሆኑ ክሊራንስ ባለማቅረባቸው በገዛ ጥፋታቸው የዘገየ በመሆኑ ልንቀጣ አይገባም ብሏል፡፡ ችሎቱም ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ክርክራቸው በፀሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ተጠሪ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው የሚሉት አንደኛው ለስንብቱ ምክንያት የሆነው መኪና ላይ የደረሰው የግጭት አደጋ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ በመከሰቱ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት አደጋው ከደረሰ ከአራት ወራት በኋላ የተወሰደ እርምጃ በመሆኑ ነው፡፡ ችሎቱም አንደኛውን ምክንያት ከማየቱ በፊት በቅድሚያ ስንብቱ በሁለተኛው ምክንያት ህገ-ወጥ ሊባል የሚችል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከክርክሩ ሂደት አደጋው ጥቅምት 23 ቀን 2000 ዓ.ም ከደረሰ በኋላ የተጠሪ የስራ ውል የተቋረጠው መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡ ይህም ተጠሪ የስንብቱ ምክንያት የሆነውን ድርጊት ከፈፀሙ ከ4 ወራት በኋላ ከስራ የተሰናበቱ መሆኑን ያሳያል፡፡ በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 27(3) መሰረት አሰሪው የስራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀ ከሰላሳ ቀናት በኋላ በይርጋ ይታገዳል፡፡ አመልካች በበኩሉ የስራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት በይርጋ አለመታገዱን ተከራክሯል፡፡ በክርክሩም የትራፊክ ሪፖርቱ የደረሰው የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በመሆኑ የይርጋው ጊዜ ሊቆጥር የሚገባው ከዚሁ ቀን ጀምሮ ነው ብሏል፡፡ አመልካች ተጠሪ መኪናውን ያጋጨ ስለመሆኑ ያወቀው የትራፊክ ሪፖርት ሲቀርብለት ሳይሆን ወዲያው አደጋው እንደደረሰ ስለመሆኑ ክክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም እርምጃውን ለመውሰድ የትራፊክ ፖ/ሊስ ሪፖርቱን የሚጠብቅበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ምናልባት የተጠሪን ጥፋተኝነት ለማረጋገጥ ሪፖርቱ ያስፈልግ ነበር የሚባል ቢሆን እንኳን ሪፖርቱ በወቅቱ እንዲቀርብለት መጠየቅ ይገባው ነበር፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የፈፀሙት ድርጊት አመልካች ባወቀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአንድ ወር ውስጥ የስራ ውሉን ያላቋረጠ በመሆኑ መብቱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የስር ፍ/ቤት የይርጋውን መቃወሚያ በዝምታ በማለፉ ተጠሪ ይግባኝ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ ባለማቅረባቸው በሰበር ደረጃ ሊከራከሩበት እንደማይችሉ ተከራክሯል፡፡ ነገር ግን የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በሌላ ምክንያት ቢሆንም ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ብሎ መወሰኑ፤ ተጠሪ ይግባኝ የሚያቀርብበት ምክንያት አይኖርም፡፡ አመልካች ያቀረበውም የይግባኝ ቅሬታ ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ መዝገቡ የተዘጋ በመሆኑ ተጠሪ መስቀለኛ ይግባኝ የሚያቀርቡበት ስርዓት ስለሌለ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች መብቱ በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ የስራ ውሉን ማቋረጡ ህጋዊ ስላልሆነ የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት አልተቻለም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33592 የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 78022 ግንቦት 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. ይህ ችሎት ሰኔ 1 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ፊንፊኔ የቤትና የቢሮ እቃዎች ፋብሪካ ኃ.የተ.የግል ማህበር -

ነ/ፈጅ ወ/ዮሐንስ ይርጉ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ደጃ ደምሴ ጎበና - ወኪል ጥሩነሽ ዘውዴ ቀረቡ

መዘገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ከአመልካች ጋር የመሰረቱትን የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ውል በራሳቸው ፈቃድ ያቋረጡ መሆኑን ገልፀው ስራ ሰርተው ያልተከፈላቸውን የሐምሌ ወር 2000 ዓ.ም ደመወዝ አመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ እና ክፍያው ለዘገየበት ክፍያ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ከተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት የነበረው መሆኑንና ተጠሪ ግንኙነቱን በገዛ ፈቃዳቸው ያቋረጡ መሆኑን እንዲሁም የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ሳይከፈላቸው የቀረና የዘገየ መሆኑን ሳይክድ ክፍያው ያልተፈፀመው ተጠሪ የተረከቡትን ንብረት በአግባቡ ያልመለሱና ጉድለት የታየባቸው መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች በተጠሪ ላይ ጉድለት ታይቷል የሚል ከሆነ ዳኝነት ከፍሎ በሌላ ክስ ከሚጠይቅ በስተቀር የስራ ስንብት ክፍያውን አልከፍልም ለማለት አይችልም የሚል ምክንያት ይዞ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ አመልካች ለተጠሪ የሐምሌ ወር 2000 ዓ.ም ደመወዝ፣ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ እንዲከፍላቸውና ስራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 14 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ አንድ ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ በስራ ምክንያት የተረከቧቸውን ንብረቶች ያጎደሉ በመሆኑ ክፍያውን አመልካች በወቅቱ ያለመፈፀሙ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 መሰረት ሕጋዊ ሆኖ እያለ የአመልካች ክርክር ታልፎ ክፍያውን እንዲፈፅም መደረጉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከሪያቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የተጠሪ ወኪል ቀርበው መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም ባጭሩ አመልካች ተጠሪ አጎደሉ ለተባለው ንብረት ሌላ የፍትሐብሔር ክስ መስርቶ በክርክር ላይ ያሉ መሆኑን ገልጸው በዚህ ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ ግን ሊጸና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል ሲሉ መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ሚያዚያ 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አንድ ገፅ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ በስራ ምክንያት የተረከቧቸውን ንብረቶች ያጎደሉ በመሆኑ ጉድለቱን ሳያወራርዱ የሚፈፀም ክፍያ የለም በማለት ገልጾ ያቀረበው ክርክር ታልፎ አመልካች ክፍያዎችን እንዲከፍል መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱትን የስራ ግንኙነት በገዛ ፈቃዳቸው ያቋረጡ መሆኑን፣ ተጠሪ አመልካች ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ዳኝነት የጠየቁት የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ እና ስራ ሰርተው ያልተከፈላቸው የሐምሌ ወር 2000 ዓ.ም ደመወዝ መሆኑን፣ አመልካች ለተጠሪ ክፍያዎችን አልከፍልም በማለት የሚከራከረው ተጠሪ በስራ ምክንያት የተረከቧቸውን ንብረቶችን ያጎደሉ በመሆኑ የማወራረድ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡

በመሰረቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 ስር የስራ ውል ሲቋረጥ የሰራተኛው ደመወዝና ከደመወዝ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ መከፈል ያለበት ሲሆን የክፍያው ጊዜ ሊራዘም የሚችለው ሠራተኛው ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት የማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማናቸውንም ሂሳብ በማወራረድ የራሱ ጥፋት በሆነ ምክንያት ካዘገየ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሠራተኛው ስለጠየቀው ክፍያ አለመግባባት የተፈጠረ እንደሆነ አሠሪው በአንቀፅ 36 በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሰራተኛው ያመነውን ያህል ሊከፍል እንደሚገባ ደግሞ የአዋጁ አንቀፅ 37 ደንግጓል፡፡ እነዚህን ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ የክፍያ ማዘግየት ውጤቱ በአንቀፅ 38 ስር የተመለከተው የሰራተኛውን እስከ ሶስት ወር ሊደርስ የሚችል ደመወዝ መክፈል ነው፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ሠራተኛው ለአሰሪው ማስረከብ ያለበት ንብረትና ማወራረድ ያለበት ማናቸውም ሂሳብ አለመግባባት የሌለበት መሆን እንዳለበት እና አለመግባባት ካለ ግን ሰራተኛው ክፍያውን ከአሰሪው ለመጠየቅ ክስ ከማቅረብ ሙሉ በሙሉ ሊከለከል የማይችል መሆኑን ነው፡፡ ሠራተኛው ጉድለት ስለአለበት ሂሳቡን ሳያወራርድ ተገቢ ክፍያዎችን ሊጠይቅ አይችልም ከተባለ በሕጉ የጊዜ ገደብ መብቶችን የማስከበር መብቱንም ዋጋ የሚያሳጣ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰራተኛ የማያምንበት ጉድለት ካለ አሰሪው በተገቢው መንገድ ክስ መስርቶ መብቱን ከሚያስከብርና ምናልባት በራሱ ክስ ረቺ የሚሆን ከሆነ በአፈፃጸም ጊዜ ስርአቱን ጠብቆ የዕዳ ይቻቻልልኝ ጥያቄ ከሚያቀርብ በስተቀር ለሠራተኛው መክፈል ያለበትን ክፍያ ከመጠየቅ ክስ ሊቀርብ አይገባም ወይም ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ሲከራከር ተቀባይነት ያገኘል ማለት አለመሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 እስከ 38 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች መንፈስ እና ባሁኑ ጊዜ አመልካችና ተጠሪ በንብረት ጉድለቱ ላይ በፍትሐብሔር ጉዳይ ክርክር ላይ ያሉ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35485 ታህሳስ 27 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75673 ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 53064

ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ደሬሳ ኮቱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአምቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን - ነ.ፈጅ አልቀረቡም

መዝገቡ በአዳሪ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡

ለአፈፃፀሙ መነሻ በሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ጉዳይ ግራ ቀኙ ተከራክረው በተጠሪ በኩል የተደረገው የሥራ ስንብት ህግ ከደነገገው ውጭ ስለሆነ አመልካች ከልዩ ልዩ ክፍያዎች ጋር ወደ ሥራው ይመለስ ተብሎ ተወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የተወሰነለትን ውሳኔ ለማስፈፀም የአፈፃፀም ክስ አቅርቧል፡፡ የጠየቀውም ዳኝነት ወደ ሥራ ለመመለስ እንደማይችል ገልፆ በምትኩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(4) መሠረት ካሣ እና የተወሰነለት ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉት ጠይቋል፡፡

አፈፃፀሙን የያዘው የሥር ፍ/ቤትም በአንቀጽ 43(4) መሠረት ለአመልካች እንዲከፈለው የተወሰነ ነገር የለም፡፡ በውሳኔው ከተገለፀው ውጭ ማስፈፀም አይቻልም በማለት ወደ ሥራ መመለሴ ቀርቶ በምትኩ ካሣ ይከፈለኝ የሚለውን ውድቅ አድርጎ ሌሎች ክፍያዎች እንዲፈፀሙለት አዟል፡፡

የአሁን አመልካች የጠየቀው የካሣ ክፍያ ውድቅ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን በመግለፅ በየደረጃው በይግባኝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኝነት ቢጠይቅም በተመሳሳይ ምክንያት ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በአሠሪው ችግር ምክንያት ወደ ሥራ ለመመለስ አለመቻሉ ከታወቀ በፋንታው በአዋጅ አንቀጽ 43 መሠረት የካሣ ክፍያ ሊከፈለኝ ሲገባ ይህ መታለፉ የህግ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ሲሆን፤ በዚህ ቅሬታ መነሻ ሁለቱም ወገኖች በሰበር የቃል ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ እኛም ጉዳዩን ተመልክተን እንደሚከተለው ተርጉመናል፡፡

በሥር ፍ/ቤትም ሆነ በየደረጃው ባሉት ይግባኝ ሰሚውና ሰበር ሰሚው ችሎት የፍርድ ሐተታ ላይ እንደተገለፀው አፈፃፀም የፍርድን ይዘት መሠረት ሊያደርግ ይገባል፡፡ በአፈፃፀም ጉዳይ ከፍርድ ይዘት ውጭ መጨመርም ሆነ መቀነስ እንደማይቻል ግልፅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሁን በተያዘው ጉዳይ የግራ ቀኙ ክርክር የመነጨው ከሥራ ግንኙነት ሲሆን የሥራ ግንኙነቱም በአዋጅ ቁጥር 377/96 በሆነው የአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚገዛ ነው፡፡ በዚህም ህግ አንቀጽ 43/3/ ላይ አከራካሪ የሆነው ስንብት ህግ ከደነገገው ውጭ ሆኖ በመገኘቱ ወደ ሥራው እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ወደ ሥራ ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ የሥራ ክርክሩን የሚያየው ችሎት መመለሱ ቀርቶ በምትኩ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት በማድረግ ሊወሰን እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ ከዚሁ ድንጋጌ ይዘት አንፃር ይኸው መብት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው ወደ ሥራ እንዲመለስ ከተፈረደለት በኋላ እንደመሆኑ መጠን ይህ የሠራተኛ አማራጭ የሆነው መብት ተፈፃሚ የሚያደርገው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት ፍርዱን በማስፈጸም ላይ የሚገኘው ችሎት ስለመሆኑ እንጂ ቀድሞ ፍርዱን የፈረደው ችሎት ሊሆን አይችልም ወደ ሚለው ትርጓሜ ያደርሰናል፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ሠራተኛው በእራሱ ምርጫም ሆነ በአሠሪው ችግር ምክንያት እንደፍርዱ ወደ ሥራ ለመመለስ ካልፈለገ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ወደ ሥራው እንዲመለስ ፍርድ ማግኘቱ ከተረጋገጠ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(3) መሠረት በምትክነት በሰጠው መብት መሰረት በመመለሱ ፋንታ ካሣ ሊከፈለው ይገባል፤ ይህንንም የሚያስከፍለው አፈፃፀሙን የያዘው ችሎት ሆኖ እያለ ይህንኑ ድንጋጌ በማለፍ ከተፈረደው ፍርድ ውጭ በመውጣት ማስፈፀም አይቻልም በማለት የአመልካችን የካሣ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአፈፃፀም ክሱን በማመልከት ወደ ሥራ በመመለስ ፋንታ ካሣ እንዲከፈል ውሳኔ አላረፈበትም በሚል ምክንያት የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 17733 በ12/5/2001፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 24165 በ17/11/2001 የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፋይል ቁጥር 88091 በ28/3/2002 ዓ.ም የሰጠውን ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ሽረናል፡፡
2. በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/3/ መሠረት እንደተደነገገው ወደ ሥራ እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ወደ ሥራ አለመመለሱ ከታወቀ በምትኩ ካሣ የማግኘት መብት ያለው ስለሆነ ሊከፈለው ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ሊከፈል የሚገባውን የካሣ መጠን በአንቀጽ 43/4/ መሠረት አስልቶ ክፍያውን ያስፈፅም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 50182

ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ አበበ ተፈራ ይልማ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ኅዳር 2 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በሥጋ አከፋፋይ ቡድን መሪነት ሲያገለግል መቆየቱን ገልፆ አመልካች ከግንቦት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ለሥራው ብቁ አይደለህም በማለት ወደ **በፌብልት** ሰራተኛ 11 አዛውረውኛል፡፡ ስለዚህ ወደ ነበርኩበት የሥራ መደብ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የድርጅቱ ደንበኞች ቁጥር በመቀነሱ ምክንያት በተደረገው ጥናት በእርድና ሥርጭት ክፍል ችግር ያለበት መሆኑ ተረጋግጧል ስለዚህ ሥራና ሰራተኛን ለማገናኘት ሰራተኞችን በህብረት ስምምነቱ መሰረት በመመደብ እየሰራን የምንገኝ ስለሆነ የጣስነው ሕግ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ የተማመኑ በመሆኑ ስለጥናቱ ለማስረዳት የተዘረዘሩ ምስክሮች መስማትም ሆነ የጥናት ሰነዱን አስቀርቦ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም በማለት በጥናቱ የከሳሽ (ተጠሪ) ችሎታ ምንም ሳይሆን ጠቅላላ የድርጅቱ ችግር የተገለፀ በመሆኑ አመልካች ተጠሪን የሥራ መደብ በማዛወር ማሰራቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች ተጠሪን ወደ ቀድሞው የእርድና የሥጋ ስርጭት አገልግሎት የቡድን መሪነት የሥራ መደብ እንዲሰራ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ህግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሰራተኞችን የበለጠ ውጤታማ በሚሆኑበት የሥራ መደብ ጥቅምና ደረጃቸውን ሣይቀንስ አዛውሮ ማሰራት የአሰሪው መብትና ሥልጣን ነው፡፡ ተጠሪ አሁን የተመደበበትና የተዛወረበት የሥራ መደብ ደረጃ ስድስት የሆነና ተመሣሣይ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤት አሰሪው ሰራተኞቹን አዛውሮ የማሰራት ህጋዊ ሥልጣንና በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን በመተላለፍ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በነበርኩበት የሥራ መደብ የሥራ ችሎታ ማነስ ያለበኝ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የአዋጅ ቁጥር 377/96 እና የሕብረት ስምምነቱን ድንጋጌዎች በማገናዘብ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጽሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በአመልካች ድርጅት አግልግሎት የሚፈልጉ ደንበኞች መቀነስ ዋናው ምክንያት የእርድና የሥጋ ስርጭት አገልግሎት የሚሰጠው ክፍል ችግር ያለበት መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል፡፡ ምንም እንኳን አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሃያ በላይ የሚሆኑ የእርድና የሥጋ ስርጭት አገልግሎት የቡድን መሪዎች ያሉትና ለድክመቱ ተጠሪ በግል ኃላፊ ናቸው ባይባልም አመልካች የጥናትቱን ውጤት መነሻ በማድረግ ችግሩን ለማስወገድ አስፈላጊ ነው የሚለውን አስተዳደራዊ ማስተካከያ በመውሰድ ድርጅቱን ትርፋማነት ማስቀጠል ይገባዋል፡፡

አመልካች ተጠሪን ከነበሩበት የሥራ መደብ ተመሣሣይ ደረጃ ደመወዝና ጥቅም ወደአለው የሥራ መደብ አዛውሮ ለማሰራት የወሰደው አስተዳደራዊ ማስተካከያ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ያከናወነው ተግባር ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች በሕጉ በግልጽ የተፈቀደለትን አስተዳደራዊ ተግባር እንዳይፈጽም ክስ የሚያቅርብበት ምክንያት የሌለ ሲሆን በተመሣሣይ የሥራ መደብ ተዛውሮ በመሥራቱ የተነካበት መብትና ጥቅም የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ሌሎቹ የእርድና የሥጋ ሥርጭት የቡድን መሪዎች ሣይዛወሩ እኔ ተዛወርኩ በሚል ምክንያት በመነሣሣት ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የሌለው በመሆኑ ከጅምሩ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 33 ንኡስ አንቀጽ እና በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 231 መሰረት መዝጋት ነበረባቸው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች የድርጅት አስተዳደር ሥልጣን በመጋፋት ተጠሪ ወደ ሌላ ተመሣሣይ ደረጃ ወደ አለው የሥራ መደብ በመዛወራቸው የቀረባቸው የደመወዝ ወይም ሌላ ህጋዊ ጥቅም ያለመሆኑን ባላሥረዳበት ሁኔታ ሌሎቹ የቡድን መሪዎች ወደ ሌላ የሥራ መደብ አልተዛወሩም፣ ተጠሪ የችሎታ ማነስ ያለበት ስለመሆኑ አላስረዳህም በሚል ምክንያት አመልካች ተጠሪን ወደ ቀድሞው የሥራ መደብ አዛውሮና መድቦ እንዲያሰራ የሰጠው ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13 ንኡስ አንቀጽ 2 የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የተጠሪ የሥራ ደረጃ ደመወዝና ጥቅም በማይነካ ሁኔታ ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ የማሰራት ሥልጣን አለው ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸ ይቻሉ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44218

ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- እነ አቶ ታጁ አባጋሮ(21 ሰዎች) - የቀረበ የለም

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የስራ ክርክርን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከተቀጠሩበት ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ መታወቂያ፣የበረሃ አበል፣ነፃ የመብራት አግልግሎት፣የደሞዝ ጭማሪ፣የቦነስ መብት፣ጥንድ የስራ ልብስ፣የካሳ መብት፣የአመት እረፍት መብት፣የቅዳሜ ክፍያ መብት፣የጡረታ መብት እንዲሁም በጥር ወር 2000 ዓ.ም የተደረገው 20% የደሞዝ ጭማሪ የማግኘት መብት እንዲጠበቅላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የቋሚነትና የጡረታ መብት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም፣ክሱ የወል የስራ ክርክር ነው፣ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ነው የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ካነሳ በኋላ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች በመሆናቸው በህብረት ስምምነቱ መሰረት ጥቅሞችን ማግኘት አይችሉም 20% የደሞዝ ጭማሪ ተከለከልን ያሉት ሃሰት ነው በማለት መልስ አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ክርክሩ የግል የስራ ክርክር ነው፣ጥያቄውም የክስ ምክንያት አለው፣6 ወር ያለፈው የደሞዝ ጭማሪና አንድ አመት ያለፋቸው ሌሎች የመብት ጥያቄዎች በይርጋ ቀሪ ይሆናሉ ካለ በኋላ ዋናው ጉዳይ በተመለከተ ደግሞ በግራ ቀኙ በተደረገው የቅጥር ውል የጊዜ ገደቡ መቀመጡ ብቻ ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ አያስቆጥራቸውም በማለት ተጠሪዎች ላልተወሰነ ግዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ስለመሆናቸው ግምት በመውሰድና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14 መሰረት በሰራተኞች መሃከል ልዩነት መፍጠር ስለማይቻል ለተጠሪዎች መታወቂያ የማግኘት፣የበረሃ አበል፣ነፃ የመብራት አግልግሎት፣የደሞዝ ጭማሪ፣የቦነስ መብት፣የደንብ ልብስና የዓመት እረፍት የማግኘት መብታቸው እንዲጠበቅላቸውና 20% ደሞዝ ጭማሪ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ ሲጠቃለል፣ጥያቄው የወል የስራ ክርክር ነው፣ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፣የአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 14 ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም፣ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ በመሆኑ የጠየቁት መብቶችና ጥቅሞች ሊያገኙ አይችሉም በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባዋል፣የሚል ነው፡፡ ችሎቱም አመልካች በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን ቅሬታዎች ከስር ፍ/ቤት ውሳኔና ከህጉ ጋር አገናዝቦ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚህ መሰረት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር የተሰማ ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን እንደሚመለከተው መርምሯል፡፡

በቅድሚያ የተጠሪዎች ጥያቄ የወል የስራ ክርክር በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን የለውም የሚለውን የአመልካች ቅሬታ ተመልክተናል፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄ ሌሎች ሰራተኞች የሚያገኙት ጥቅማ-ጥቅሞችና መብቶች ይጠበቁልን የሚል ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው በሕብረት ስምምነቱ መሰረት በተጠሪዎች የተጠየቁት ጥቅማ ጥቅሞች የሚከፈለው ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች በመሆኑና ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ በመሆናቸው ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ ቋሚ ሰራተኞች መሆናቸው ከተረጋገጠ የጠየቁትን መብቶችና ጥቅሞች ሊገኙ የማይገባበትን ሌላ ምክንያት አመልካች አልገለጸም፡፡ በመሆኑም የክፍያ ጥያቄው በተጠሪዎች የቅጥር ውሉ ይዘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚወሰን ስለሆነና ውጤቱም በተጠሪዎቹ ላይ ተወስኖ የሚቀር እንጂ ለሌሎች ሰራተኞች ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽኖ የሚያሳድር ስላልሆነ ጥያቄው የወል የስራ ክርክር ነው ለማለት የሚቻል ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለኝ በማለት መወሰኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የይርጋውን መቃወሚያ በተመለከተ ተጠሪዎች የጠየቁት የመብት ጥያቄዎች ቀጣይነት ያላቸው በመሆኑ 6 ወር ያለፈው ደሞዝ ጭማሪና አንድ አመት ያለፋቸው ሌሎች የጥቅም ጥያቄዎች ብቻ በይርጋ ቀሪ መደረጋቸው ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመቀጠል ችሎቱ የተመለከተው ተጠሪዎች ለተወሰነ ግዜ የተቀጠሩ መሆን አለመሆኑን ነው፡፡ ስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የተደረገው የስራ ውል የጊዜ ገደብ ከማስቀመጡ በቀር በአዋጁ አንቀጽ 10 ስር በተዘረዘሩት ምክንያቶች መቀጠራቸውን ስለማይናገር ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑን ግምት ወስዷል፡፡ ችሎቱም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲያመቸው ተጠሪዎች የተቀጠሩበትን የቅጥር ውል የስር ፍ/ቤትን መዝገብ በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡ የቅጥር ውሉ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 10 መሰረት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ ለሚቀጠሩ ሰራተኞች ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ በርእሱ አመልክቶ በዝርዝር ውስጥ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት የጊዜ ገደብ፣ የተቀጠሩበት ፕሮጀክት እንዲሁም የተቀጠሩት በአዋጅ አንቀጽ 10 መሰረት በጊዜያዊነት በመሆኑ መብቶቻቸውና ጥቅማቸው በቅጥር ውሉ የተመለከቱት ብቻ መሆናቸውን ሌሎችንም ዝርዝር ሁኔታዎች አካቶ የያዘ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ የተቀጠረው ላልተወሰነ ጊዜ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 9 ግምት የሚወስድ ሲሆን አሰሪው የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ነው የሚል ከሆነ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ አመልካች ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ስለመሆናቸው ለማስረዳት ያቀረበው የስራ ውሉን ነው፡፡ በእርግጥ የስር ፍ/ቤት እንዳለው በውሉ ላይ የግዜ ገደብ መጠቀሱ ብቻውን ሰራተኛው ለተወሰነ ግዜ የተቀጠረ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችል አይደለም፡፡ ከጊዜ ገደቡ ባሻገር ግራ ቀኙ ውሉን ሲዋዋሉ ሃሳባቸው ምንድን ነበር የሚለውን መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት ውሉን ስንመረምር የተጠሪዎች ቅጥር በጊዜ ገደብ ከመወሰኑ በተጨማሪ የተቀጠሩት ለግልገል ግቤ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ለደነባ ሳይት መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በውሉ አንቀጽ 4.1.3 ስር ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ በመሆናቸው መብቶቻቸውና ጥቅሞቻቸው የሚወሰኑት በቅጥር ውሉ በተዘረዘሩት መሰረት ብቻ መሆኑ ሰፈሮ ይገኛል፡፡ ይህም የሚያሳየው ምንም እንኳን በውሉ በግልጽ ባይመለከትም ተጠሪዎች ሲቀጠሩ የነበረው የግራ ቀኙ ሃሳብ ተጠሪዎች በውሉ ላይ በግልጽ ለተመለከተው የፕሮጀክት ስራ ብቻ የተቀጠሩ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም በአዋጅ አንቀጽ 10/1/ሀ/ ሥር የሚወድቅ የቅጥር ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በተጠሪዎች መሃከል የተደረገው የቅጥር ውል ይዘት ሲታይ ተጠሪዎች ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች አጠቃላይ የውሉን ይዘት ሳይመረምሩ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው ከተባለ የጠየቋቸውን ጥቅማ ጥቅሞች እና መብቶች ሊያገኙ ይገባል ወይ? የሚለውን ቀጥለን ተመልክተናል፡፡ አመልካች ከስር ጀምሮ የሚከራከረው በህብረት ስምምነቱ መሰረት ተጠሪዎች የጠየቋቸው የመብት ጥያቄዎች ለቋሚ ሰራተኞች የሚሰጡ ናቸው በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቢሆኑ ለሌሎች ሰራተኞች ስለሚከፈል ለእነሱም እንዲከፈላቸው ከመጠየቅ ባለፈ እነዚህ የጥቅማ ጥቅም እና መብቶች ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ለተቀጠሩ ሰራተኞችም ሊከፈል የሚገባበት የውልም ሆነ የሕግ መሰረት ያላቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪዎች ሊያገኙ የሚችሉት ጥቅምም ሆነ መብቶች በውሉ ላይ የተዘረዘሩትን ብቻ መሆናቸው በቅጥር ውሉ ላይ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 14/ረ/ ስር የተመለከተው ልዩነት ያለመፍጠር ግዴታ በድንጋጌው እንደተመለከተው በብሔረሰብ፣በፆታ፣ በሐይማኖት፣በፖለቲካ አመለካከት እና እነዚህን የመሳሰሉትን ሌሎች ሁኔታዎችን የሚመለከት እንጂ የቅጥር ውልን መሰረት በማድረግ ልዩነት እንዳይፈጠር የማይከለክል ስለመሆኑ ይህ የሰበር ችሎት በመ/ቁ 43197 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች በተጠሪዎች የጠየቋቸውን የጥቅማ ቅጥምና ሌሎች የመብት ጥያቄዎች የቅጥር ሁኔታን መሰረት በማድረግ ልዩነት እንዳይፈጥር ሕጉ ክልከላ አላደረገበትም፡፡ በተጠሪዎች የክስ ማመልከቻ ላይ የተጠየቁት ነገሮች በህብረት ስምምነቱ መሰረት ለቋሚ ሰራተኞች ብቻ የሚከፈሉ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር ተጠሪዎች አላስተባበሉም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በክሳቸው የጠየቋቸውን ጥቅማ ቅጥምና ሌሎች መብቶች ለመጠየቅ የሚያስችል ከሕግም ሆነ ከውል ያገኙት መብት መኖሩን ስላረጋገጡ ጥያቄአቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰራተኞች ናቸው በማለት በጥያቄአቸው መሰረት እንዲፈፀምላቸው የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24365 ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69792 ታህሣሥ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች በመሆናቸው ክሳቸው ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የስር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 46363

ግንቦት 19 ቀን 2002

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሣሊኒ ኮንስትሩቶሪ ኤስ ፒ - ኤ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ትግሉ ፍሬህይወት - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤትና የየም ልዩ ወረዳ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ሰኔ 1 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ የአመልካች ሠራተኛ መሆኑን ገልፆ በዋሻ ውስጥ ሥራ በመሥራት ላይ እያለሁ ህዳር 4 ቀን 1999 ዓ.ም በባቡር ግጭት ምክንያት ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደርሶብኛል፡፡ በአገር ውስጥ ህክምና ስከታተል የቆየሁ ቢሆንም የደረሰብኝ ጉዳት በአገር ውስጥ ከሚሰጠው ሕክምና በላይ መሆኑን በማረጋገጥ አምስት ዶክተሮች ውጭ ሄጀ ሕክምና መከታተል ያለብኝ መሆኑን በማረጋገጥ ማስረጃ ሰጥተውኛል፡፡ ተከሳሽ /አመልካች/ ውጭ ሊያሣክመኝ ፈቃደኛ ባመሆኑ በውጭ አገር ህክምና እንድከታተል እንዲያደርግ ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ተጠሪ በአገር ውስጥ አስራ ስምንት ጊዜ አፕሮሽን ያደረገና ህክምና የተከታተለ መሆኑን ገልፆ የውጭ አገር ሀኪሞች /ዶክተሮች/ በሚመጡበት ሆስፒታል በአገር ውስጥ አለ፡፡ ተጠሪን ዶክተሮቹ ጋር ቀርቦ እንዲታከም ብንጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም የውጭ አገር ህክምና ለመሸፈን በውል ያልተስማማን በመሆኑ የተጠሪ ክስ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የአሥራና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 አሠሪው ሠራተኛ በሥራ ላይ ጉዳት ሲደርስበት የማሣከም ግዴታ እንዳለበት ከሚደነግግ በስተቀር ህክምናው በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር መሆኑን ስለማይገልጽ አመልካች የሀኪሞች ቦርድ በሰጠው የሙያ አስተያየት መሠረት ውጭ አገር ልኮ የማሣከም ኃላፊነት አለበት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የየም ልዩ ወረዳ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የፍሬ ጉዳይ ወይም የህግ ስህተት የለም በማለት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 ሠርዞታል፡፡

አመልካች ተጠሪ ታክሞ እንዲድን ያደረግነውን ጥረት ከግምት ውስጥ ሣያስገባ የህክምና ቦርዱ ውሣኔ ግልጽነት ያጐደለው መሆኑን ሣያገናዝብና በአገር ውስጥ የተሻለ ህክምና ሊሰጥ የሚችል የውጭ ዶክተሮች የሚሠሩበት MCM የተባለ ሆስፒታል ልናሣክመው ፈልገን ተጠሪ እንቢተኛ መሆኑን ሣያገናዝብ አላግባብ ውጭ አገር ወስዳችሁ አሳክሙ በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ችሎቱ ተጨማሪ ማስረጃዎን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377(3) መሠረት በመቀበል ውሣኔ እንዲሰጥልን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በአገር ውስጥ ባሉ የህክምና ተቋሞች ታክሜ ከህመሜ ለመዳን ያልቻልኩ በመሆኑ በውጭ ሄጀ መታከም እንዳለብኝ የሀኪሞች ቦርድ አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አመልካች ውጭ አገር ወስዶ ያሣክመው በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪን በውጭ አገር የማሣከም ግዴታና ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይህንን ጭብጥ እልባት ለመስጠት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 ድንጋጌ አሠሪው በሠራተኛው ላይ ያደረሰበት ጉዳይ በውጭ አገር የሚደረግ የህክምና ወጭ እንዲሸፍን ያስገድደዋል ወይስ አያስገድድም? የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 ድንጋጌ ቃልበቃል ሲነበብ “በሥራ ላይ ሚመጣ ጉዳት ለደረሰበት ሠራተኛ ለሚከተሉት ህክምና አገልግሎት የሚያስፈልግ ውጭ አሠሪው ይከፍላል

1. የጠቅላላና የልዩ ህክምና የቀዶ ጥገና ህክምና ውጭዎች
2. የሆስፒታል መድሀኒት ወጭዎች
3. ማንኛውም አስፈላጊ ሰው ሠራሽ ምትክ ወይም የተጨማሪ አካሎችና ጥገና ወጭዎች የሚል ነው፡፡

ድንጋጌው አሠሪው የመሸፈንና የመክፈል ግዴታ ያለበት በአገር ውስጥ ህክምና ተቋማት የሚደረገውን የህክምና ውጭ ብቻ ነው ወይስ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚደረግ የህክምና ወጭ የሚለውን በግልጽ ምላሽ የሚሰጥ አይደለም፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 ድንጋጌ አገላለጽ ጠቅላላ መብቱ የተቀመጠ በመሆኑ አሠሪው ሠራተኛው ላይ በሥራው ላይ የሚደርስበትን ጉዳት የሚያወጣውን የውጭ አገር የህክምና ወጭ መሸፈን አለበት ወይስ የለበትም በሚለው ጥያቄ ግልጽ ምላሽ የማይሠጥ በመሆኑ ድንጋጌውን መተርጉም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 ድንጋጌ ለመተርጉም አዋጁን ሳያወጣ ህግ አውጭው የነበረውን ሀሳብና ሊያሣካው የሚፈልገውን ግብ ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ህግ አውጭው አዋጁን ያወጀው በአገሪቱ ውስጥ አሠሪና ሠራተኛ ግንኙነትና መሠረታዊ የሆኑ መብትና ግዴታዎች ለመቆጣጠር እንደሆነ በአዋጁ መግቢያ ገልፅታል፡፡ አዋጁ በአገሪቱ ውስጥ በየትኛውም ሥፍራና በማናቸውም ሁኔታ የተመሠረቱ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ላይ እኩል ተፈፃሚነት እንዲኖረው ታስቦ የታወጀ በመሆኑ ሁሉም አሠሪዎች ሠራተኛው በሥራ ላይ ለሚደርስበት ጉዳት የውጭ አገር ህክምና ወጭ እንዲሸፍኑ በማሰብ የአዋጁን አንቀጽ 105 ደንግጓል ብሎ ለመደምደም የሚቻል አይደለም፡፡ ስለዚህ ህግ አውጭው ማናቸውም አሠሪና ሠራተኛው በሥራ ላይ ለሚደርስበት ጉዳት በአገር ውስጥ የሚደረገውን የህክምና ወጭ የመሸፈን ግዴታና ኃላፊነት እንዳለበት በማሰብ ህግ አውጭው ድንጋጌውን አውጇል ተብሎ መተርጉም ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት አሠሪው ለሠራተኛው ሊያከብር የሚገባውን ዝቅተኛ ደረጃ ጥበቃ የሚደነግግ ነው፡፡ ሠራተኞች ከአዋጅ ከተደነገገው ጥበቃ በላይ የተሻለ መብትና ጥቅም ለማስከበር ሠራተኞች በአዋጅ ቁጥር 377/96 የሥራ ውል ሲዋዋሉ ወይም አንቀጽ 124 በሚደነግግው መሠረት ከአሠሪው ጋር በመደራደር የህብረት ሥምምነት መዋዋል አለባቸው፡፡ የውጭ አገር የህክምና ወጭ በአሠሪው የሚሸፈን መሆኑ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ ለሠራተኛው የሰጠው ዝቅተኛው ጥበቃ ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 105 አሠሪው ሠራተኛው በሥራ ላይ በሚደርስበት ጉዳት የአገር ወስጥ የህክምና ወጭ መሸፈን እንዳለበት በመደንገግ ዝቅተኛውን ጥበቃ ሰጥቷል፡፡ በውጭ አገር የሚደረግ የህክምና ወጭ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በአሠሪው መሸፈን ያለበት መሆኑ ከፍተኛ ጥበቃ ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ ሠራተኞች ከአሠሪው ጋር በመደራደር በውል ወይም በህብረት ስምምነት ሊያስከብሩት የሚቻሉት መብት እንጂ በህግ በሁሉም አሠሪዎች ላይ ግዴታና ኃላፊነት ሆኖ ተደነገገ አይደለም፡፡ አመልካች ሠራተኞችን በውጭ አገር ለማሣከም ውል ያልተዋዋለ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተገልጿል፡፡ አመልካች ሠራተኞች ለሚደርስባቸው ጉዳት ከአገር ውጭ የህክምና ወጭ በሙሉ ወይም በከፊል የሚሸፈን ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ የህብረት ሥምምነት በአመልካችና በአመልካች ሠራተኞች መካከል የተደረገ መሆኑን የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በተጠሪ ላይ የደረሰውን ጉዳት በውጭ አገር ለማሣከም ግዴታ ከህግ፣ ከውል ወይም ከህብረት ሥምምነት የመነጨ ሀላፊነት የሌለበት በመሆኑ የየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ውጭ አገር ወስዶ እንዲያሣክም የሰጡት ውሣኔና የህግ ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታውና ለሥር ፍርድ ቤት በቀረበው ክርክር መሠረት MCM ሆስፒታል ሌሎች የአገር ውስጥ የህክምና ተቋማት የማሣከምና ሌሎች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 በሚደነግገው መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪን መብትና ጥቅም የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ከዚህ ውጭ አገር ወስዶ የማሣከም ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት እና የየም ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪ ውጭ አገር የማሣከም ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. አመልካች ተጠሪን በ MCM ሆስፒታልና ሌሎች የአገር ውስጥ የህክምና ተቋማት የማሣከምና የተጠሪን መብትና ጥቅም በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የመጠበቅ ግዴታ አለት ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 50923

ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

አመልካች፡- ፋውንዴሽን አፍሪካ -ጠበቃ መላኩ ካሰኝ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዓለሙ ታደሰ- ጠበቃ አብደላ ዓሊ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ሲሆኑ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ የስር ከሣሽ ክስ ይዘት ሲታይም በአመልካች ድርጅት ከጥር 1 ቀን 1977 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 22 ቀን 2001 ዓ.ም. ድረስ ለሃያ አራት አመታት ሲሰሩ እንደቆዩ፣ ከሣሽና ተከሣሽ ታህሳስ 22 ቀን 1996 ዓ.ም. በተፈራረሙት ውል አለመግባባት ከተፈጠረ በኔዘርላንድስ ሕግና ፍርድ ቤቶች ለመዳኘት የተፈራረሙ ቢሆንም ውሉን የተፈራረሙት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚሠራ ስራና ስራው የተሰራውም በኢትዮጵያ ውስጥ በመሆኑ፣ ተከሣሽም በኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግቦ የሚሰራ መሆኑን ገልፀው ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት መሆኑን ገልፀው የስራ ውሉ ያለምንም ጥፋት ስለተቋረጠ ካሣ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የዓመት እረፍት፣ ክፍያ ለዘገዩበት ክፍያ ከተለያዩ ክፍያዎች ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሠጠው መልስም፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ስምምነት ሕጋዊ አለመሆኑን ገልጾ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት መታየት ያለበት ነው ብሎ በዚሁ አንፃር ተመልክቶ ስንብቱን ሕገ ወጥ ነው ሲል ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ችሎቱ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ከሚችል በስተቀር በይግባኝ ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት ዋናውን ጉዳይ ሳይመረምር አልፎታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ታህሳስ 05 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት የሰበር ማመልከቻ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ጉዳዩ የግለሠብ ዓለም አቀፍ ሕግ የሚያስነሳ ስለሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመልክቶ ብይን ይስጥበት ተብሎ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ይኸው ትዕዛዝ በይግባኝ ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በቀረበለት ጉዳይ ብይን ሳይሰጥ ጉዳዮ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚታይ ነው ብሎ ራሱ በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታቸውም ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ ሶስት ገፅ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም. የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዮን በሚከተለው መልኩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የሚገዛው ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሠረት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ነው ካለ በኃላ ጉዳዩን ራሱ በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ማየቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግራ ቀኙ ታህሳስ 22 ቀን 1996 ዓ.ም. ባደረጉት ስምምነት መሠረት በመካከላቸው የሚነሣው አለመግባባት በኔዘርንላድስ ሕግና ፍርድ ቤቶች የሚታይ መሆኑን መስማማታቸውን፣ በመካከላቸው ያለው ግንኙነትም የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት መሆኑን፣ ተጠሪ ኢትዮጵያዊ ሆነው የሚኖሩትና ስራውን ለመስራት ግዴታ የገቡት በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን፣ አመልካች የውጪ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበውና ስራውን የሚሰራው በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2(ሀ) ስር የግለሠብ ዓለም አቀፍ ሕግ (Private international law) የሚመለከቱ ጉዳዮች በሚኖሩ ጊዜ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሔር የዳኝነት ሥልጣን እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ አዋጁ ይህን ድንጋጌ ሲያስቀምጥ የራሱ የሆነ ምክንያት አለው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህም መሠረት ሕግ አውጪው ይህንን ድንጋጌ ያስቀመጠው አንድም ወደፊት በስራ ላይ የሚውለውን የአገሪቱን የግለሠብ ዓለም አቀፍ ሕግ በሕግ አውጪው አካል ፀድቆ በስራ ላይ ሲውል በዚህ ረገድ የሚነሱ የሕግ ክርክሮችን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን አይቶ እንዲወስን ወይም አሁን ባለው ሁኔታ ለኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ለዳኝነት በቀረበ አንድ ጉዳይ ላይ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ የኢትዮጵያ ሕግ ከአመልካቹ አገር ሕግ ወይም ከሌላ አገር ሕግ ጋር ይጋጫል ወይም ይቃረናል በማለት በኢትዮጵያ ሕግ እንዳይዳኝ ወይም በራሱ ወይም በሌላ አገር ሕግ ጉዳይ እንዲታይና እንዲወሰንለት ሲያመለክት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ለዳኝነት የቀረበው ጉዳይ በባሕርይው ከአንድ በላይ የሆኑ የሕግ ሥርዓቶችን ለጉዳዩ አወሳሰን የሚጋብዝና የየትኛው ሥርዓት ሕግ ተመራጭ ሊሆን ይገባል የሚለው ክርክር ሲነሳ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሄር የዳኝነት ሥልጣን አይቶ እንዲወስን ከመደረጉ ውጪ በማናቸውም ሁኔታ ተከራካሪዎች የአገሪቱን ሕግ በሚፃረር መልኩ ስምምነት አድርገው ሲገኙ ሁሉ ተከራካሪ ወገን ክርክር ስላነሳ ብቻ የግለሠብ አለም አቀፍ ሕግ ጥያቄ የሚያስነሣ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ከዚህ አንፃር ግራ ቀኙ አደረጉ የተባሉትን ስምምነት ስንመለከት የኢትዮጵያ አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የሚያደርግ፣ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩን እንዳይመለከቱ የሚገልጽ መሆኑ ሲታይ ስምምነቱ ተቀባይነት አለው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ከአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ዓላማ እና መንግሥት አዋጁ ላይ ካለው ጠቅላላ ፍላጎት አንፃር የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የመንግሥትም ፍላጎት የሚንፀባረቅበት ሕግ ሲሆን ይህን አዋጅ የሚመለከቱ ስምምነቶች ሕጋዊ እና የሕዝብን ጥቅም የማይፃረሩ መሆን ይገባቸዋል፡፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ካልወሰነ በስተቀር አዋጅ ቁጥር 377/96 የውጪ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሠራ የበጎ አድራጎት ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ከአዋጁ ድንጋጌ 3/3/ለ/ ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የወጣ ደንብ የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ አዋጅ ቁጥር 377/96 ለጉዳዮ ተፈጻሚነት ያለው በመሆኑ ጉዳዩ የግለሠብ አለም አቀፍ ሕግ ጥያቄን ስምምነቱን መሠረት አድርጎ ያስነሣል ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈፃሚነት እንዳለው መወሰኑ አግባብነት ያለው ቢሆንም ጉዳዩ የአለም አቀፍ የግለሠብ ሕግ ጥያቄ እንደማያስነሳ በመግለጽ ጉዳዩን ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መመለስ ሲገባው ራሱ በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ መመልከቱ ተገቢነት የሌለውና የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበ ሆኖ ስለተገኘ በዚህ ረገድ የተሠጠው የውሣኔው ክፍል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 78810 ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም. የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ተመልክቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 51912

ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት - ነ/ፈጅ ስዩም ጌራወርቅ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሶፋኒት አጥናፉ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው ጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት ላይ ነው፡፡ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ አመልካች ያለአግባብ ከሥራ እንዳሰናበታቸው ገልፀው የሥራ ስንብት እና ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡ በአመልካች በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበው ፍ/ቤቱ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ እና ክሱ የቀረበው ስድስት ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ እንደሚገባ በሚል ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም በአማራጭ ክርክር አቅርቧል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ የተመለከተው የጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 138 መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን እንዳለው አረጋግጦ የይርጋ ክርክርን በተመለከተ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ሆኖ ጉዳዩ በሶማሌ ብ/ክ/መንግሥት ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት እንዲታይ ተጠሪ አመልክተው ጽ/ቤቱ በ24/11/2000 ዓ.ም ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ክሱ የቀረበው በ10/05/2001 ዓ.ም ጊዜ ድረስ ያለው ሲታይ የስድስት ወር /6/ ጊዜ አላለፈበትም ሲል በብይን መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር ተሰኝቶ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም መቃወሚያውን ባለመቀበል በፍሬ ነገር ረገድ ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ መጠን ብቻ በማሻሻል የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የካሳውን መጠን ብቻ በማሻሻል ወስኗል፡፡

ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ድርጅት ነ/ፈጅ ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም ጽፎ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ክሱ በይርጋ ይታገድ ይገባው እንደነበር እና የሥር ፍ/ቤቶች የይርጋ ክርክሩን ውድቅ ለማድረግ የሰጡት ምክንያት መሠረታዊ የሕግ ትርጉም ስሕተት የተፈፀመበት ስለመሆኑ እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 16648 የተሰጠውን ውሳኔ የሚፃረር መሆኑን፣ በፍሬ ነገር ረገድም የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ውል በአግባቡ ያላገናዘበ ስለመሆኑ በማብራራት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

የሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ የአመልካች ድርጅት የይርጋ መቃወሚያ የታለፈበትን አግባብ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪ ወኪል ሰኔ 4 ቀን 2002 ዓ.ም በጽሑፍ ባቀረቡት መልስ የሥራ ውል ከተቋረጠው ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ክስ እስከቀረበበት ጥር 10 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ 6 ወር ከ10 ቀን መሆኑን አምነው ይህ ጊዜ ያለፈው ተጠሪ ክስ ከማቅረባቸው በፊት ጉዳዩ በክልሉ ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት እንዲታይ አመልክተው እንደነበር እና ጽ/ቤቱም ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት አለመቻሉን ገልፆ በ24/11/2000 ዓ.ም ውሳኔውን ያሳወቃቸው በመሆኑ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከ24/11/2000 ዓ.ም ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና አመልክተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከፍሲል በዝርዝር እንደተመለከተው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም መሆኑ እና ክስ የቀረበው ጥር 10 ቀን 2001 ዓ.ም መሆኑ አላከራከረም፡፡ ይህ ጊዜ ሲሰላም ስድስት ወር ያለፈው መሆኑን ተጠሪም አምነዋል፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረበው ክስ የሥራ ውል የተቋረጠው አለአግባብ ነው በሚል ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲወሰኑ በሚል ነው፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ልዩ ልዩ የመብት ጥያቄዎችን አስመልክቶ ክሱ መቅረብ ያለበትን የጊዜ ገደብ ወስኗል፡፡

ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የአዋጁ አንቀጽ 162(4) የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሠራተኛውም ሆነ በአሠሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ በግልፅ ደንግጓል፡፡ በዚህ መዝገብ የቀረበው የክፍያ ጥያቄም የሥራ ውል ከተቋረጠበት ከሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ክስ እስከቀረበበት ጥር 10 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ ስድስት ወር ያለፈው ስለመሆኑ ተረጋግጧል የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ለማድረግ የሰጡት ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱን አንድ በአንድ እንመረምራለን፡፡ አንደኛው ምክንያት ተጠሪ የሥራ ውል እንደተቋረጠባቸው አቤቱታቸውን ለክልሉ ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት አመልክተው ጽ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው ሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም ስለሆነ የይርጋ ጊዜ መቆጠር ያለበት ከሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ነው የሚል ነው፡፡ በግራ ቀኙ መካከል ያለው ክርክር የሥራ ውል በማቋረጡ ሊከፈል የሚገባ ልዩ ልዩ ክፍያን የሚመለከት ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ላይ የሥራ ውል አመሠራረት እና በግጉኝነት ሂደት የሚፈጠሩት ክርክሮች ለመፍታት የተለያዩ አካላት ሥልጣን የተሰጣቸው ስለመሆኑ የአዋጁን ክፍል ዘጠኝ አንቀጽ 136 እና ተከታዮችን ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ አሁን ለተያዘው ጉዳይ የሥራ ውል በመቋረጡ ሊከፈል የሚገባ ክፍያን አስመልክቶ ሥልጣን የተሰጠው አካል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 138 ድንጋጌ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ ይህንኑ ጥያቄ ለክልሉ ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት አቅርበውም ቢሆን በተያዘው ጉዳይ ላይ ለመወሰን በህግ ስልጣን ያልተሰጠው አካል እንደመሆኑ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በመ/ቁ 16648 የሰጠው የሕግ ትርጉም ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለክልሉ ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ነበር በሚል የይርጋው ጊዜ ከሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ሊቆጠር ይገባል ያሉት የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ችሎት ፍ/ቤት በመ/ቁ 16648 የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት የይርጋ ጊዜው አቆጣጠር የሥራ ቀናትን ብቻ መሠረት ያደረገ ነው የሚል ሲሆን ለዚህም የጠቀሱት የአዋጁን አንቀጽ 163 ነው፡፡ ተጠቃሽ ድንጋጌ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር የሚመለከት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀናት አቆጣጠር የመጀመሪያው እና የመጨረሻውን ቀን የሚያመለክት ነው፡፡ የመጨረሻው ቀን የሥራ ቀን ካልሆነ በተከታዩ የሥራ ቀን እንደሚወሰድ የሚያመለክት ቢሆንም ሙሉ ጊዜው የሚሰላው የሥራ ቀናትን ብቻ በመለየት ነው የሚል ይዘት ያለው ስለመሆኑ የድንጋጌው አንቀጽ 163(2) አያመለክትም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ትርጉም የሕጉን መንፈስ የያዘ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ባጠቃላይ የሥር ፍ/ቤቶች ይርጋ ጊዜው ክሱን አያስቀረውም ለማለት የሰጡት ምክንያቶች በሕግ ረገድ የተሳሳተ ትርጉም የሰጡበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ስለዚህ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 23/2002 የሰጡት ውሳኔ እና የሱማሌ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ የክፍያ ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162(4) መሠረት በይርጋ ታግዷል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይካበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 55189

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፦ ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፦ አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል - ጠ/ ሃሣብ ከፋይ - ቀረቡ

ተጠሪ ፦ አቶ ዘላለም መንግስቱ - ጠ/ ሻምበል የሥጋት - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው በመሆኑ ደሞዝና ጥቅማ ጥቅም ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመልሳቸው አመልክተዋል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት የተለያዩ ጥፋቶች በመፈፀማቸው ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ አመልካች ተጠሪን ከስራ ለማሰናበት ምክንያት ናቸው በማለት በስንብት ደብዳቤው ላይ የዘረዘራቸውን ጥፋቶች ለመፈፀማቸው ያቀረባቸው ምስክሮች ስላላስረዱ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት ተጠሪ የ3 ወር ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታው ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በፈፀሙት ጥፋቶች መሆኑን በበቂ ሁኔታ አስረድቶ እያለ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው መባሉ ስህተት መሆኑን ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ቢባል እንኳን ተጠሪ ወደ ስራ ቢመለሱ መልካም የስራ ግንኙነት ስለማይኖር በአ/ቁ 377/96 በአንቀጽ 43/3/ መሠረት ካሳ ተከፍሏቸው ከስራ ሊሰናበቱ ሲገባ ወደ ስራ መመለሳቸው ተገቢ አይደለም በማለት የሰር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲሻር ጠይቋል፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ ወደ ስራ ቢመለሱ መልካም የስራ ግንኙነት አይኖርም በማለት የቀረበውን አቤቱታ ከአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 43/3/ አንፃር ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ፍሬ ነገርን የሚመለከት እንጂ የህግ ስህተትን የሚመለከት ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካች ተጠሪን ከስራ ማሰናበቱን ሳይክድ የሚከራከረው ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በፈፀሙት ጥፋት በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ነው፡፡ አመልካች ለሰር ፍ/ቤት በሰጠው መልስ ተጠሪ ፈፀሙ ያላቸውን ጥፋቶች ዘርዝሮ ገልጿል፡፡ ጥፋቶቹንም ስለመፈፀማቸው ያስረዳሉ ያላቸውን ምስክሮች ቆጥሮ ተሰምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የምስክሮች ቃል መዝኖ አመልካች በተለይ ተጠሪን ከስራ ሲያሰናብት በስንብት ደብዳቤው ላይ የገለፃቸውን ጥፋቶች ስለመፈፀማቸው እንዳላስረዱ በፍሬ ነገር ረገድ አረጋግጧል፡፡ ይህ ችሎትም በሰር ፍ/ቤት የተረጋገጠን ፍሬ ነገር እንዳለ የሚቀበለው ከሚሆን በቀር ማስረጃውን በድጋሚ ሊመዝን የሚችልበት ስልጣን የለውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከስራ የሚያሰናብታቸው ጥፋት መፈፀማቸው ባለመረጋገጡ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በመባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፃሟል ማለት አይቻልም፡፡

ሌላው ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱ በህገ-ወጥ መንገድ ነው ቢባል እንኳን ወደ ስራ ቢመለሱ መልካም የስራ ግንኙነት ስለማይኖር ካሣ ተከፍሏቸው ሊሰናበቱ ይገባ ነበር በማለት አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ነው፡፡ በእርግጥ በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 43/3/ ስር የስራ ስንብቱ ህገ-ወጥ ቢሆን እንኳን ከስራ ግንኙነቱ ፀባይ የተነሳ ከፍተኛ ችግር የሚፈጥር ከሆነ ሰራተኛውን ወደ ስራ ከመመለስ ይልቅ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ የህጉ ድንጋጌም ሊተረጎም የሚገባው በአንድ በኩል የሰራተኛውን የስራ ዋስትና በሌላ በኩል ደግሞ ኢንዱስትሪን ሰላም በማመዛዘን ሊሆን ይገባል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም ሰራተኛው ወደ ስራ መመለሱ የአሰሪውን ስራ በከፍተኛ ደረጃ ሊጎዳ የሚችል መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ሰራተኛው በሆነው ባልሆነው ከስራ እንዲሰናበቱ ማድረግ ተገቢ አይሆንም፡፡ የህጉም አላማ ይህ አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ ጥፋቶች ናቸው ከሚባሉት ውስጥ አንዱና አመልካች ተጠሪ ስራ ቢቀጥሉ መልካም የስራ ግንኙነት ሊኖር አይችልም በማለት የሚከራከረው የተጠሪ የስራ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ለማስረዳት በአመልካች በኩል የቀረቡ ምስክሮች ደግሞ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው እንደአመልካች ክስ አቀራረብ አላስረዱም፡፡ ከዚህ ውጪ ግንኙነቱ ቢቀጥል የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ላይ ሊጥል የሚችል ሁኔታ ስለመኖሩ አመልካች ያስረዳው ነገር የለም፡፡ የአመልካች የስራ አፈፃፀም ዝቅትኛ መሆኑ ካልተረጋገጠ ደግሞ ተጠሪ ወደ ስራ ቢመለስ የስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ ችግር ላይ ሊወድቅ ይችላል ለማለት ስለማይቻል ተጠሪ ወደስራ ከሚመለሱ ይልቅ ካሣ ተከፍሏቸው ሊሰናበቱ ይገባል በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር ችሎቱ የሚቀበለው አይደለም፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመለሱ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለው ለማለት አልተቻለም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33071 መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 91456 ሚያዚያ 6 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. ይህ ሰበር ችሎት ሚያዚያ 19 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 53358

ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ፖስታ አግልግሎት ድርጅት - ማስረሻ በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጥላሁን ኩማ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣አመልካችን የከሰሰው የሥራ ውሌ ከሕግ አግባብ ውጪ አቋርጦብኛል በማለት ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ የሥራ ውሉን ሊያቋርጥ የቻለው ተጠሪ በፈጸመው ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት ምክንያት እንደሆነ በመግለጽ የተከራከረ ቢሆንም፣ፍ/ቤቱ ግን የሥራ ውል ማቋረጥ እርምጃውን የወሰድከው እርጃውን ለመውሰድ በሕጉ የተፈቀደልህ የይርጋ ጊዜ ካበቃ(ካለፈ) በኋላ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ክርክሩን ውድቅ አድርጉአል፡፡ በዚህ መሰረትም ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራው እንዲመለስ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጸመ የሚለውን ስህተት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ተጠሪ ፈጽሞታል የተባለውን ጥፋት በዲሲፕሊን ኮሚቴ ለማጣራት የወሰደው ጊዜ እግምት ውስጥ ሳይገባ ድርጊቱ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ሰበር ችሎት ሊወሰን የሚገባው የሕግ ጭብጥ የይርጋው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ጉዳዩ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ ጥፋቱ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ነው ወይንስ ጥፋቱ ተፈጽሞአል ከተባለበት ቀን ጀምሮ ነው? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጭብጥ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ድንጋጌ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ የተመለከተው ነው፡፡ አንቀጽ 27 ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችሉ ምክንያቶችን በዝርዝር የያዘ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ አሰሪው ወገን ምክንያቶቹን መሰረት በማድረግ የሚወስደው የሥራ ውል የማቋረጥ እርምጃ በጊዜ ውስጥ የተገደበ መሆኑን የሚያመላክት ድንጋጌ ይዞአል፡፡ ድንጋጌው ከፍ ሲል የተጠቀሰው በንኡስ አንቀጽ /3/ የተቀመጠው ሲሆን፣ይዘቱም አሰሪ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት ከ30/ሰላሣ/ የሥራ ቀናት በኋላ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ በቁልፍነት መታየት የሚገባው "... ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት ..." የሚለው የሕጉ አግባብ ነው፡፡ ከዚህ አባባል መገንዘብ የሚቻለው የመጀመሪያው ሁኔታ አሰሪው ውሉን ለማቋረጥ የማቋረጫ ምክንያቱን ማወቅ ይኖርበታል የሚለው ነው፡፡ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት መኖሩን ማወቅ የግድ ነው ከተባለ ደግሞ መቼ ነው ያወቀው የሚለው በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ይሆናል፡፡ ጥፋቱ ወይም የሥራ ውል ማቋረጫ ምክንያቱ መከሰቱን ለማረጋገጥ የተወሰነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማጣራት ሥራ የሚያስፈልግ ከሆነ ይህ የማጣራት ሥራ ከተከናወነ በኋላ ነው አሰሪው ምክንያት ወይም ጥፋት መኖሩን አውቆአል ሊባል የሚችለው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ምክንያቱ በእርግጠኝነት ያወቀው ጉዳዩን በዲሲፕሊን ኮሚቴ አማካይነት ካጣራ በኋላ እንደሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ ከተረጋገጠ በኋላም የሥራ ውሉን አቋርጧል፡፡ በዚህ መሃልም በተመለከተው ድንጋጌ የተቀመጠው የ30/ሰላሳ/ የሥራ ቀናት ጊዜ አልፎአል አልተባለም፡፡ ሁኔታው ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የሥራ ውሉን የማቋረጥ እርምጃ የወሰደው የይርጋው ጊዜ ካበቃ በኋላ ነው ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከዚህ አንፃር ሲታይ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32585 ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 89003 የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች የሥራ ውል የማቋረጥ እርምጃውን የወሰደው የይርጋ ጊዜው ከማለፉ በፊት ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወደ ጉዳዩ ሥረ ነገር በመግባት የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ላይ ግራ ቀኝ ወገኖችን እንዲያከራክር እና ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሰረት ይመለስለት ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43160

ሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. እንደገና ተሾመ - ቀረቡ፡፡

2. ዳንኤል ባለ - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ነቀምቴ ቅርንጫፍ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኞች መካከል የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር አመልካቾች ከሣሾች የነበሩ ሲሆን፣ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረቱት የሥራ ውላችን ከሕግ ውጪ ስለተቋረጠብን ልዩ ልዩ በአዋጁ የተመለከቱት ክፍያዎች ይክፈሉን በማለት ነው፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ውሉ የተቋረጠው ዘመኑ በማብቃቱ ነው በማለት ሲከራከር፣ ፍ/ቤት ደግሞ ውሉ የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ነው የሚለውን የተጠሪ ክርክር በመቀጠል የአመልካቾች የውሉ ዘመን ከማብቃቱ በፊት ለሚሠሩበት ጊዜ የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈላቸው በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች በውሣኔው ባለመስማማት ይግባኝ ለሚሰማው የበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ ፍ/ቤቱም ውሉ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የተገባ ስለመሆኑ አሠሪው /ተጠሪ/ አላስረዳም የሚል ምክንያት በመስጠት ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው በማለት ደምድሟል፡፡ በዚህ መሠረትም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል የሥራ ውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ ሊከፈሉ የሚገባቸውን ክፍያዎች በሙሉ አመልካቾች ይከፈላቸው በማለት ወስኖአል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ በመቀጠልም የሰበር ችሎቱ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች ሽሮአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካቾች ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም. በዛፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ አቤቱታው ላይ ያለውን መልስ እንዲያቀርብ በተደጋጋሚ እድል የተሰጠው ቢሆንም፣ የሰጠው መልስ የለም፡፡ በመሆኑም ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እንደተመለከተው ተጠሪ በከፍተኛ ትምህርት መስጠት የተሰማራ ሲሆን፣ አመልካቾችን ቀጥሮ ሲያሠራ የነበረው በመምህርነት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የመማር ማስተማር ሥራ ቀጣይነት ያለው ማለትም የማያቋርጥ ባሕርይ ያለው ሥራ ነው፡፡ አመልካቾች የሥራ ውላችን ያለአግባብ ተቋርጦብናል በማለት ክስ በመሠረቱበት ጊዜ ተጠሪ ሥራውን ሲቀጥል እንደነበረም አላከራከረም፡፡ አመልካቾችን የቀጠርኩት ለተወሰነ ጊዜ ነው በማለት ሲከራከር የቆየው ሥራው የለም የሚል ምክንያት በመስጠት ሳይሆን፣ ውሉ የተፈረመው ለተወሰነ ጊዜ ተብሎ ነው በማለት ነው፡፡ በዚህ መልክ ያቀረበው ክርክር ግን በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በፍሬ ነገር ረገድ ሊያስረዳ አልቻለም፡፡ አንድ የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ ነው ሊባል የሚችለው በአንቀጽ 10 ከተመለከቱት ሁኔታዎች በአንዱ ምክንያት የተደረገ ከሆነ ስለመሆኑ በአንቀጽ 9 ተደንግጎአል፡፡ በመሆኑም ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ተብሎ ተፈርሞአል የሚለው የተጠሪ ክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም ከዚህ አንፃር ስናየው በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65098 ኀዳር 1 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13964 ሚያዝያ 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 52459

ሐምሌ 16 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ሙሉ ታደሰ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አለሙ መራ ኮንስትራክሽንና ጠቅላላ ብረታ ብረት ስራ ድርጅት

- ባለቤት ወ/ሮ አልማዝ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የቀሪዎቹ አመልካቾች አባት በተጠሪ ድርጅት ሲሰሩ ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩ የስንብት ክፍያና የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ ስለተደረገባቸው የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካቾች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የቀሪዎቹ አመልካቾች አባት በተጠሪ ድርጅት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በዘበኛነት ተቀጥረው ሲሰሩ የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው የሚገባቸው የአገልግሎት ክፍያና የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ የተጠሪ ድርጅት ባለቤት ቀርበው በሰጡት መልስ የጋራዥ ስራውን መስራት ባለመቻላቸው ለሌላ ሰው በኮንትራት የሰጡ መሆኑንና ሟች ከሳቸው ጋር ያለውን ስራ ውል ከሰኔ 1 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ ተቋርጦ ስራውን በኮንትራት ከያዘው ሰው ጋር ተዋውለው ይሰሩ ስለነበር ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የቀሪዎቹ አመልካቾች አባት የስራ ውል የተቋረጠው በሞት ምክንያት በመሆኑና በዚህ ሁኔታ የስራ ውል ሲቋረጥ የስንብት ክፍያ እንዲከፈል የሚያስገድድ ህግ ስለሌለና የአመት እረፍትም ቢሆን በሞት ምክንያት የስራ ውሉ ለተቋረጠ ሰራተኛ ስለማይሰጥ ጥያቄውን ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው የስር ፍ/ቤት የሟች አገልግሎት ክፍያም ሆነ የአመት እረፍት ለሚስታቸውና ለልጆቻቸው አይከፈልም መባሉ ስህተት በመሆኑ እንዲታረምላቸው አመልክተዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሟች የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ለአመልካቾች ሊከፍል አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ የሟች ስራ ውል የተቋረጠው ከሞታቸው በፊት በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካቾች የጠየቁት የሟቹ አገልግሎት ክፍያና አመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው ነው፡፡ የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄን በተመለከተ ለሰበር ችሎት ያስቀርበዋል ያልተባለ ከመሆኑም በላይ ይህን ነጥብ አስመልክቶ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 45264 ከሰጠው ትርጉም ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ይህንኑ ቅሬታ የምንመለከተው አይሆንም፡፡ ሁለተኛው የክፍያ ጥያቄ የአመት እረፍትን የሚመለከት ነው፡፡ በአ/ቁ 377/1996 አንቀፅ 77(5) በአዋጁ መሰረት የስራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ ያልወሰደው የአመት ፈቃድ ታስቦ በገንዘብ ተለውጦ እንደሚሰጠው ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ የሚሰጠው በአዋጁ ከተደነገጉት የስራ ማቋረጫ ምክንያቶች በተወሰኑት ምክንያቶች ብቻ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ነው የሚል ገደብ አላስቀመጠም፡፡ በመሆኑም በማንኛውም በአዋጁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተመለከቱ ድንጋጌዎች የስራ ውሉ ከተቋረጠ የሰራተኛው የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአዋጁ መሰረት የስራ ውል ከሚቋረጥባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ የሰራተኛው መሞት እንደሆነ ከአንቀፅ 24(2) የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም የሰራተኛው የስራ ውል በሰራተኛው ሞት ምክንያት ከተቋረጠ የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ለወራሾቹ ሊከፈል የማይገባበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት የስራ ውሉ በሞት ምክንያት ሲቋረጥ የአመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል አይገባም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን ተጠሪ ከስር ጀምሮ በተጠሪና በአንደኛ አመልካች ባለቤት እና በቀሪዎቹ አመልካቾች አባት መሃከል የነበረው የስራ ውል ሰኔ 1994 ዓ.ም የተቋረጠና ሟች ጋራገፍን በኮንትራት ከያዙት ሰው ጋር ባደረጉት የስራ ውል የሚሰሩ ስለመሆኑ የሚከራከሩ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ይህን የአመልካች ክርክር ሳይመለከት ማለፉን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳን የሟቹ አመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል የሚገባ ቢሆንም ተጠሪ ክፍያውን የመፈፀም ሃላፊነት ያለባቸው መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39535 ህዳር 7 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 86994 ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾች የሟች የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡ ነገር ግን የስራ ውሉ በሞት ምክንያት በመቋረጡ የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል አይገባም የሚለው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የስር ፍ/ቤት በሟችና በተጠሪ መሃከል የስራ ውል መኖር አለመኖሩን ግራ ቀኙ ካቀረቡት ማስረጃ አኳያ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45170

ሐምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የቅድስተ ማሪያም አፀደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- መ/ት ሲሳይ ሙሉጌታ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪ የክስ ምክንያት አመልካች ያለአግባብ የሥራ ውል አቋርጠብኛል ተገቢው ካሣና ጥቅማጥቅም ይክፈለኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ የክረምት ሥራ እንድትሰራ መመሪያ ተሰጥቷት እያለ ያለፈቃድ ወይም በቂ ምክንያት ከሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሐሴ 5 ቀን 2000 ዓ.ም ሥራ ላይ ባለመገኘቷ የሥራ ውል የተቋረጠው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1//ለ/ መሰረት ነው ሲል ስንብቱ ሕጋዊ ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ጊዜው የመምህራን የዓመት እረፍት ጊዜ ነው በማለት ከሥራ መቅረቷን የተቀበለች ቢሆንም መምህራን በክረምት ወራት ሙሉ ለሙሉ እረፍት ስለመሆናቸው በአዋጅ፣በደንብ ወይም በመመሪያ የተደነገገ የለም፣አሰሪ ስራ እንዲሰራ መመሪያ ከሰጠ መሥራት ይጠበቅበታል በሚሉ ምክንያቶች የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በአግባቡ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባለች፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ መምህራን በክረምት ወራት እረፍት እንደሚያደርጉ ሲሰራበት የቆየ ልምድ ነው በዚህ መዝገብም የቀረቡት ማስረጃዎች ይህንኑ ያረጋግጣሉ ተጠሪም በእረፍት ወቅት ሥራ ላይ አለመገኘታቸው የሥራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ሊሆን አይገባም የሚሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር የሥራ ውል ያለአግባብ ተቋርጧል በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ለተጠሪ የካሣ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ እና ክፍያ የዘገየበት ጊዜ እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የሰራተኛ የዓመት እረፍት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በተደነገገው አግባብ በአሰሪና ሰራተኛ ስምምነት የሚወሰን እንጅ ሰራተኛው በዘፈቀደ የሚወስነው አይደለም፣በት/ቤቱ ደንብ መሰረት የዓመት እረፍቷን በነሐሴ ወር ወስዳለች እንዲሁም የ2000 ዓ.ም የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ተከፍሏል በሚሉ ምክንያቶችን በመጥቀስ የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲታረም አመልክቷል፡፡

ሰበር ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ ከአዋጅ አንቀጽ 13/1/ አንፃር ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪም ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርባለች በይዘቱም የሥር ፍ/ቤት ክርክር በማጠናከር የክረምት ወራት ለመምህራን በተለየ ሁኔታ የእረፍት ጊዜ እንደመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለመሥራት ግዴታ የለብኝም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቃለች፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ ለማየት የተቻለው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ አመልካች አጥብቆ የተከራከረው ተጠሪ በክረምት ወቅት እንድታስተምር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመሪያ ተሰጥቷት ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታለች በሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው የክረምት ትምህርት ለመስጠት አመልካች ከተወሰኑ መምህራን ጋር ውይይት በማድረግ በስምምነት የማስተማር ሥራ ሲያከናውኑ እንደነበር ተመልክቷል፡፡ ይህውም ሐምሌ 4 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገ ስብሰባ የተወሰነ ስለመሆኑ ተገልጧል፡፡ ስለሆነም በዚህ መልክ ተጠሪ ፈቅዳ ግዴታ የገባች ስለመሆኑ በዚሁ ክርክር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር አላገኘንም፡፡ ከዚህም ሌላ ተጠሪን የሚያስገድድ ግልጽ መመሪያ ወይም ደንብ ስለመኖሩ አመልካች አላስረዳም፡፡

ስለሆነም ግልጽ ደንብ ወይም መመሪያ መኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ በክረምት ወቅት ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ አልሆነችም ተብሎ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/1/ የተመለከተውን ግዴታ ጥሳለች ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘንም፡፡

ስለሆነም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ በፍሬ ነገርም ሆነ በሕግ ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

በዚሁ ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04326 በ01/07/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ሚያዝያ 14 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43424

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን

ተጠሪ፡- እነ አቶ መስፍን ጀምበሩ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንብረት ግምት ይከፈለን ጥያቄ ሲሆን፤ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካች ከቡታጅራ ሆሣእና በሚያሰራው መንገድ ምክንያት በሆሣእና ከተማ የሚገኙ ንብረቶቻቸው እንዲነሱ የግምት ስራ ተሰርቶላቸው በዚሁ መጀመሪያ ግምት የከተማው አስተዳደር ንብረቶቻቸውን ያስነሳቸው መሆኑን፣የንብረቶቻቸው ዓይነትና ግምት ምን ያህል እንደሆነ ዘርዝረው አመልካች ካሣ እንዲከፈለን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በሐድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት የተናጠል ክስ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ ለመንገድ ሥራው የዲዛይን ለውጥ ማድረጉንና በተለወጠው ዲዛይን መሰረትም ንብረቶቹ መነሳት የማያስፈልጋቸው በመሆኑ ኃላፊነት እንደሌለበት፣ተነሱ ወይም እንዲፈርሱ የተደረጉ ንብረቶች በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 3/1/ እና 4/1/ ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን ሥርአት ባልተከተለ መልኩ የተከናወነ በመሆኑ ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑን፣እንዲሁም አዋጁን ባልተከተለ መንገድ የራሱን ሥራ ለመስራት ንብረቶችን አስነሳ የተባለው የሆሳእና ከተማ አስተዳደር በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ይታዘዝለት ዘንድ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪዎችን ክርክርና የተለያዩ መዛግብት መርምሮ የሆሳእና ከተማ አስተዳድር ወደ ክርክሩ ይግባልኝ የሚለውን የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጐ አመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎች በጠየቁት ዳኝነት መሰረት ወስኖላቸዋል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይኸው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካራከረ በኋላ መዛግብትን በአንድ ላይ በማጣመር መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይሁንኑ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ-ፈጅ የካቲት 06 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 3(ሦስት) ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- በመጀመሪያ መንገዱ ሊሰራበት በታሰበው ስፋት መሰረት የተሰራው ግምት እጅግ የተጋነነ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው ለከተማ አስተዳደሩ አመልካች ከገለጸለት በኋላ አስተዳደሩም ይህንን አውቆ የዲዛይን ክለሳ እና በዚህም መሰረት የግምት ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀድሞው ዲዛይን መሰረት ተነስቷል ለሚባል ንብረት ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ባልዋለበትና በሕጉ አግባብ ላልተነሳ ንብረት ካሣ ለመክፈል ሕጋዊ ግዴታ የሌለበት መሆኑን በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ሙሉ በሙሉ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው መጋቢት 09 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመረውም አመልካች የሆሳእና ከተማ አስተዳደር ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ያቀረበው ጥያቄ መታለፉ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በመጀመሪያ መንገዱ ሊሰራበት በታሰበው ስፋት መሰረት የተሰራው የንብረቶች ግምት ባልተለመደ ሁኔታ እጅግ የተጋነነ በመሆኑ እንደማይቀበለው ለከተማ አስተዳደሩ ገልጾና አሳውቆ የዲዛይን ክለሳና የግምት ስራ ተጠናቅቆ ከአለቀ በኋላ ንብረቶቹ እንዲነሱ ወይም እንዲፈርሱ ለተደረገው ሁኔታ አመልካች ኃላፊነት እንደሌለበትና ይህንን ድርጊት የከተማው አስተዳደር ለራሱ ሥራ ሲል ስለአከናወነው ኃላፊነት ሊወሰድ ስለሚገባ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ሊታዘዝ ይገባል በማለት የሥነ-ሥርአት ጥያቄ ማንሳቱን ነው፡፡ ይህ የአመልካች ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረበው የተጠሪዎች አመልካች የመንገዱን ስፋት በመቀነስ ዲዛይኑን ስለማስተካከሉ ለማወቃቸው ወይም የከተማው አስተዳደር ንብረታቸውን ያፈረሰው አዲስ በተስተካከለው ዲዛይን ለመሆኑ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የለም፣አስተዳደሩ እውነታውን እያወቀ አፍርሶ ከሆነ አመልካች ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚያደርገው ክርክር ተጠሪዎች መጐዳት የለባቸውም፣አመልካች በውል ወይም በሕግ ከአስተዳደሩ ጋር ግንኙነት ወይም ስምምነት ካለው ከሶ ማስከበር ከሚችል በስተቀር ተጠሪዎችን ሊጐዳ አይገባም በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሰረቱ በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ሲቀርብና የክሱም ምክንያት የብዙ ሰዎችን መብትና ጥቅም የሚነካ ሆኖ ከእነሱ አንዱ ወይም ከፊሉ ክስ በቀረበ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ መብትና ጥቅም የሚነካ ሲሆን በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡ እነዚህ ወገኖች ተካፋይ ሳይሆኑ የሚሰጠው ውሣኔ ወይም ፍርድ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑም የተጠቃሽ ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በክሱ መግባት ያለበት ተከሣሽ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የክርክር ተካፋይ እንዲሆንና በቀረበው ክስ የመልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ ሊያዘው የግድ የሚል ስለመሆኑ ሥነ ሥርአቱ ያሳያል፡፡ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ማለት ደግሞ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው፣መብታቸው ወይም ግዴታቸው የሚነካ፣በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች ስለመሆናቸውም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይም የሆሳእና ከተማ አስተዳደር ከተማውን የማስተዳደር ኃላፊነትና ተግባር ያለበት ሲሆን በከተማው ውስጥ በሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ ቀጥተኛ የሆነ ተሳታፊነት፣ቁጥጥር የማድርግ እና ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን እንደሚያከናውን የሚታመን ነው፡፡ በተለይም በሚያስተዳድረው ከተማ በአመልካች የሚሰራው ዓይነት ሥራ ሲሰራ በመንገዱ ስራ ለሚነሱም ሆነ ለሚፈርሱ ንብረቶች ተገቢው ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ በግምት ወቅትም ሆነ በአከፋፈሉ ጊዜ ተሣታፊነት ያለበት ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የተደነገጉት ሕጐች ያሳያሉ፡፡ በሕጐቹ የተጣሉበትን ግዴታዎችን መወጣት ደግሞ የግድ ይላል፡፡ አመልካች ለሆሳእና ከተማ አስተዳደር የተጠሪዎች ንብረቶች ሊነሱ ወይም ሊፈርሱ የማይገባ መሆኑን ከዲዛይን ክለሳ በኋላ ማሳወቁን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ እንዲህ ከሆነም ደግሞ ንብረቶቹ የተነሱት ወይም የፈረሱት በመንገድ ስራ ምክንያት መሆን አለመሆኑን፣ኃላፊነቱ የየትኛው ወገን እንደሆነ አከራካሪ የሚያደርገውና የከተማ አስተዳደሩን ወደ ክርክሩ እንዲገባ የግድ የሚል ጉዳይ ነው፡፡ ለክርክር ማስረጃ የማቅረብ ጉዳይ ደግሞ ይኸው ሥነ-ሥርአት ከተከናወነ በኋላ የሚከተል ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ተገቢ ባልሆነ የክርክር ደረጃ አመልካች ማስረጃ አላቀረበም በሚል ምክንያት የከተማው አስተዳደር ወደ ክርክሩ ይግባልኝ የሚለውን የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም የሆሳእና ከተማ አስተዳደር ወደ ክርክሩ ሳይገባ የተሰጠው ውሣኔ ሥነ-ሥርአታዊ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. በሐድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 03332፣ 02799፣ 02803፣03388፣ 03302፣02797፣ 03028 እና 02798 ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 57916፣ 57284፣ 59917፣ 64576፣ 64577፣ 66578፣ 66599 ተከፍቶና በመዝገብ ቁጥር 59916 ተጣምሮ ታይቶ ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የሆሳእና ከተማ አስተዳደር በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን ያለበት ወገን በመሆኑ ለቀረበው ክስና መልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ የሐድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩን እንደገና በመመልከት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. ለክርክር የወጣን ወጪና ኪሳራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 43410

ህዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ አሠገደች ጎርፌ

ተጠሪ፡- ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል - አልቀረበም

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስነ-ስርዓት ህግን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ አመልካች ባለመቅረቡና ተጠሪ ቀርበው መዝገቡ እንዲዘጋ በመጠየቃቸው ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) መሰረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ለፍ/ቤቱ በታህሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መዝገቡ እንደገና እንዲከፈትለት የቃል ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ያልቀረበበት ምክንያት በቂ ባለመሆኑ መዝገቡ ሊከፈት አይገባም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ትዕዛዞች ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው የቃል ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ አመልካች ሳይቀርብ ተጠሪ ከቀረበ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት እንጂ በቁጥር 62(2) አይደለም፣ በቀነ-ቀጠሮው የቀረንበት ምክንያትም የብሔር ብሔረሰቦች በዓል የሚከበርበት ቀን ስለነበር መንገድ በመዘጋጋቱ አርፍደን ስለደረስን ስለሆነ መዝገቡ እንዲከፈት ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡ አቤቱታውም ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቀርበዋል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ቃል ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሳይቀርብ ተጠሪ መቅረቡ አልተካደም፡፡ የባለጉዳዮች ወደ ፍ/ቤት መቅረብና አለመቅረብ የሚያስከትለውን ውጤት ምን እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከቁጥር 65 እና ተከታዮች ባሉት ድንጋጌዎች ተዘርዝረው ተቀምጠዋል፡፡ በዚህ መሰረት ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሳይቀርብ ተከሳሹ ቀርቦ ክሱን በከፊል ወይም በሙሉ ያመነ ከሆነ ላመነው ጉዳይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚችልና ክሳደ ደግሞ መዝገቡ እንደሚዘጋ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 ያመለክታል፡፡ በዚህ አንቀፅ ከሳሽና ተከሳሽ የሚለው አነጋገር ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪ እንደሚጨምር ከሥነ-ሥርዓቱ ድንጋጌ አንቀጽ 32(2) ሥር መመልከት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) አግባብነት የሚኖረው ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ሁለቱም ተከራካሪዎች ያልቀረቡ ከሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ክርክር በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ይግባኝ ባይ የነበረው አመልካች ሳይቀርብ ተጠሪ ቀርቧል፡፡ በዚህም ምክንያት አግባብነቱ የሚኖረው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 እንጂ ቁጥር 69(2) አይደለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2)"ን" መሰረት አድርጎ መዝገቡን መዘጋቱ ተገቢ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ ከአመልካች ጋር ሲከራከር የነበረ በመሆኑና ክርክር በሚሰማበት እለት አመልካች ባለመቅረቡ ተጠሪ መዝገቡ እንዲዘጋለት መጠየቁ ተጠቃሎ ሲታይ አቤቱታውን ያላመነ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በቀነ-ቀጠሮው ያልቀረበው በበቂ ምክንያት ነው ቢልም ፍ/ቤቱ ምክንያቱን መዝኖ በቂ አይደለም የሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ የምክንያቱ በቂ መሆን አለመሆን ደግሞ የማስረጃ ምዘና እንጂ የህግ ክርክር ባለመሆኑ ለሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት ነጥብ ነው ሊባል አይችልም፡፡ በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት መዘጋት ሲገባው በቁጥር 69(2) መሰረት መዘጋቱ ትክክል ባይሆንም መዝገቡ በመዘጋቱ ግን መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈፅሟል ማለት አልተቻለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39200 ህዳር 30 ቀን 2001 ዓ.ም እና ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጣቸው ትዕዛዞች ፀንተዋል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ንግድ ማተሚያ ድርጅት - ነ/ፈጅ ጌታቸው ብርሃኑ

ተጠሪ፡- አቶ ካሱ ሙላት - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ያለ አግባብ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን በመግለጽ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለቀረበው ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪ ለ6 ተከታታይ ቀናት ከስራ በመቅረታቸው ከስራ እንደተሰናበቱ በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲሆንለት አመልክቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ከስራ ታመው የቀሩ መሆኑን ቢገልፁም ታመው ስለመቅረታቸው ማስረጃ እንዲያቀርቡ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጠይቀው ማቅረብ አልቻሉም፣ ያቀረቡት የሕክምና ማስረጃ በወቅቱ ያልቀረበና ከስራ ከተሰናበቱ በኋላ የተፃፈ ስለሆነ ከስራ የተሰናበቱት በአግባቡ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው ለማስረዳት የቀረበው አንደኛው ማስረጃ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የሌለው የትርፍ ሰአት ክፍያ የሚመለከት ነው፡፡ ሁለተኛው ማስረጃ የዲሲ□ሊን ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ሲሆን አንድ ሰራተኛ ቀሪ መሆኑን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባው የሰነድ ማስረጃ እንጂ የዲሲ□ሊን ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ስላልሆነ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ የ6 ወር ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በህገ-ወጥ መንገድ ነው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ በስር ክሳቸው በህመም ምክንያት ከስራ በመቅረታቸው አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከስራ የተሰናበቱት ለ6 ተከታታይ ቀናት ከስራ ስለቀሩ መሆኑን ተከራክሯል፡፡ ከክርክሩ ሂደት እደተረዳነው ተጠሪ ከስራ መቅረታቸውን አልካዱም፡፡ ክርክራቸው የቀሩት በህመም ምክንያት ነው የሚል ነው፡፡ ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ግልባጭ በህመም ምክንያት ከስራ ለመቅረታቸው ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ማቅረብ አለመቻላቸውን ተረድተናል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ቢሆን ተጠሪ ማስረጃቸውን ለዲሲፕሊን ኮሚቴ አቅርበዋል አላለም፡፡ ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የአንድን ሰራተኛ ከስራ መቅረት ማስረዳት የሚቻለው በሰነድ ማስረጃ እንጂ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ አይደለም የሚል ነው፡፡ በመሰረቱ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው ክደው አልተከራከሩም፡፡ የሚከራከሩት ከስራ የቀሩት በህመም መክንያት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በህመም ምክንያት ስለመቅረታቸው የማስረዳት ሸክም ያለባቸው ተጠሪው ናቸው፡፡ ተጠሪ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ማቅረብ አለመቻላቸው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከዛ በኋላ ደግሞ ያቀረቡት ማስረጃ ከስራ ከተሰናበቱ በኋላ የተፃፈና እጅግ ዘግይቶ የቀረበ ማስረጃ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ይህን ፍሬ ነገር በማንኛውም የማስረጃ አይነት ከማስረዳት የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ በማስረጃነት ሊቀርብ የማይገባበትን የሕግ መሰረት አልገለፀም፡፡ ቢያንስ ማስረጃነውን መዝኖ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው በበቂ ሁኔታ ማስረዳት የሚችል መሆን አለመሆኑን ሊመዝን ይገባ ነበር፡፡ በመሆኑም በማስረጃነት ሊቀርብ የማይችልበትን ምክንያት ሳይገልጽ በድፍኑ ቃለ-ጉባኤው ሊቀርብ የማይችል ማስረጃ ነው በሚል ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከስራ የቀሩት በህመም ምክንያት መሆኑን ቢገልፁም ይህን ሳያስረዱ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 79174 ሰኔ 12 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27244 መጋቢት 14 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 40229

ታህሳስ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኸይሮ መሐመድ - ጠበቃ አታክልት ሃ/ስላሴ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ መዲና በያን - ቀረቡ

2. አቶ ደኑር አብደላ - አልቀረቡም

መዘገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ሲሆን የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ በአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከተወሰነ በኋላ የንብረት ክፍፍሉንም ፍ/ቤቱ ተመልክቶ በ8-2-2000 ዓ.ም ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት የካቲት 17 ቀን 2000 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ የእኔን ሚስትነት ሰርዘው እኔ በማላውቀው ሁኔታ የባልና ሚስት ፍቺ አስወስነው የንብረት ክፍፍልም እንዲደረግ የተወሰነ ስለሆነ ይህ ውሳኔ የእኔን መብት የሚጎዳ ስለሆነ ይሰረዝልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ የመቃወም አመልካች በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር በቀጠሮ ላይ እንዳለ ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የጣልቃገብነት አቤቱታ አቅርባ አመልካችና ተጠሪ (የአሁን ተጠሪዎች) መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነገር ግን የመቃወም አመልካች ትዕዛዙን ባለማድረሳቸው ድጋሚ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በድጋሚውም ትዕዛዝ መሠረት ባለመፈጸማቸው አቤቱታቸውን ባለመቀበል ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው ደግሞ ክርክር እየተደረገ መሆኑን ያልተገነዘበ ወገን በሌለበት ክርክር ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ መብቱን የነካበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ነገር ግን ክርክር መኖሩን የተገነዘበ ሰው ከበስተጀርባ ሆኖ የክርክሩን ሚዛን በመገምገም እርሱን በሚመለከት አጥጋቢ ፍርድ ባልተሰጠ ጊዜ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ አቤቱታ ማቅረብ ከሥነ-ሥርዓት ሕጉ ዓላማ አኳያ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በዚህም ጉዳይ የመቃወም አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ለመሆን አቤቱታ አቅርባ መጥሪያ እንድታደርስ ለሁለት ጊዜ ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም በትዕዛዙ መሠረት ሳትፈጽም ቀርታ ከውሳኔ በኋላ ወደ ክርክሩ ለመግባት አቤቱታ ማቅረቧ ክርክር መኖሩን እያወቀች ስለሆነ አቤቱታው በተገቢው አኳኋን አልቀረበም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ መ/ሰጭዎችን ሳይጠራ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተገቢነቱን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንደዚሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማንኛውም ሰው ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ለማቅረብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 ላይ ተመልክቷል፡፡

መቃወሚያ ማቅረብ የሚፈቀድበት ደንብ መሠረታዊ ዓላማም ምንአልባት ፍርድ መስጠቱን ያላወቀና በተሰጠው ፍርድም ጥቅሙ የሚነካ ሰው ፍርዱ ቢፈጸም በጥቅሙ ላይ ሊከተል የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል ነው፡፡ አንድ ሰው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ለማቅረብ የሚችለውም በጉዳዩ የሚያገባውና በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 41 መሠረት የክርክሩ ተሳታፊ ሊሆን የሚችል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ነው፡፡ አመልካችም በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር ስለሚመለከተኝ የክርክሩ ተሳታፊ መሆን ይገባኛል ብለው በፍ/ብ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 41 መሠረት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ነበር፡፡ አቤቱታቸውም ተቀባይነት አግኝቶ ፍ/ቤቱ ክርክሩን አግዶ የጣልቃገብነት ማመልከቻው ለተከራካሪ ወገኖች እንዲደርስና መልስ እንዲሰጡበት ከአንድም ሁለት ጊዜ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የጣልቃገብነት አቤቱታ ለተከራካሪ ወገኖች ሳይደርስ የቀረው በአመልካቹ ጉድለት በሆነ ጊዜ ደግሞ ጣልቃገቡ ነገሩን ሆነ ብሎ እንደተወው ተቆጥሮ መብቱ እንደሚሰረዝበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 41(4) ላይ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች በተጠሪዎች መካከል ክርክር እየተደረገ መሆኑን ተገንዝበው በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው የጣልቃገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባቸው ይህን ሳይፈጽሙ ቀርተው መብታቸው ከተሰረዘ በኋላ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ማቅረባቸው ክርክር መኖሩን በሚገባ በተገነዘቡበት ሁኔታ ስለሆነ በዚህ መልኩ የሚቀርብ አቤቱታ ከሕጉ ዓላማ ጋር ስለማይጣጣም የሥር ፍ/ቤቶች አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ እንጂ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 56832 በ20/8/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 67878 በ21/11/2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ሲ.ጂ.ሲ.ኦቨርሲስ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ሊሚትድ - እሌኒ አስራት ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሰለሞን እንዳለ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በሌለሁበት ክርክሩ እንዲሰማ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቶ ወደክርክሩ እንድገባ ይፈቀድልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረ ሲሆን፣ መልስ እንዲሰጥ በተጠራበት ቀነቀጠሮ ባለመቅረቡ ክርክሩ እሱ በሌለበት እንዲሰማ ታዟል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ትዕዛዙ እንዲነሳለት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.72 መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ እንዲፈቀድለት ጠይቆአል፡፡ ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከተመለከተ በኋላ፣ አቤቱታው ትዕዛዙ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑና የአንድ ወር ጊዜው ያለፈው በበቂ ምክንያት ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ትዕዛዙ ሊነሳ አይችልም በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ትዕዛዙን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክርም አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13262 ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ብይን እንደተመለከተው አመልካች ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶለት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ባመለከተበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ አልተሰጠም ነበር፡፡ ከመዝገቡ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች ተከሣሽ የነበረ ሲሆን፣ በቀረበበት ክስ በጽሑፍ መልስ ሰጥቶ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለቃል ክርክር በተቀጠረበት ዕለትም የአመልካቹ ሠራተኛ የሆነ ቀርቦ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ግን ክርክር ለማቅረብ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን የለህም በማለት ክርክሩ አመልካቹ በሌለበት እንዲታይ አዞአል፡፡ ከዚህ በኋላም ነው አመልካች ክርክሩ በሌለበት ይሰማል የሚለው ትዕዛዝ ተነስቶለት ወደክርክሩ እንዲገባ የጠየቀው፡፡ ፍ/ቤቱ በዚህ መልክ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ያደረገው ጥያቄው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78(1) መሠረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አልቀረበም፡፡ በህጉ ከተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለማቅረብ ያልቻለበት በቂ ምክንያት ያለው ለመሆኑም አላስረዳም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት የሚመራው የፍትሐብሔር ክስ በቀረበ ጊዜ ክርክሩን ለመስማት ፍ/ቤቱ በያዘው ቀነቀጠሮ ተከራካሪ ወገኖች ይቀርባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 69(1) ከተቀመጠው ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወይም አንዳቸው ሳይቀርቡ ቢቀሩ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎች በሚመለከት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.69 እስከ 78 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር ተቀምጦአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ክርክሩ እንዲሰማ ቀነ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ሳይቀርብ የቀረው አመልካች (ተከሣሽ የነበረው) ነው፡፡ በዚህ ቀነ ቀጠሮ የአመልካች ወኪል ነኝ በማለት የቀረበው ሠራተኛ የተሟላ የውክልና ሥልጣን የለውም በሚል አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳልቀረበ ተቆጥሮ ክርክሩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ የመታዘዙን አግባብነት ወደኋላ የምንመለከተው ይሆናል፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን እምነት በመያዙና ክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 70(ሀ) መሠረት አመልካች በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ በመስጠቱ የተነሣ አመልካች ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ያቀረበው አቤቱታ የሚስተናገደው በምን አግባብ ነው? የሚለውን ነጥብ በቅድሚያ እንመለከታለን፡፡

በመጀመሪያው ቀነቀጠሮ ባለመቅረቡ ምክንያት ክርክሩ በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ የተሰጠበት ተከሣሽ በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ቀርቦ በቀዳሚው ቀነቀጠሮ ለመቅረብ ያልቻለው በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነና ፍ/ቤቱም ምክንያቱን በቂ አድርጎ የተቀበለው እንደሆነ በቀረበበት ቀን መከላከያውን አቅርቦ እንዲከራከር እንደሚፈቅድለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 ተደንግጎአል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተቀመጡት ዋነኞቹ ነጥቦች አቤቱታው የሚቀርበው በሚቀጥለው ቀጠሮ ማለትም ጉዳዩ በውሳኔ ከመቋጨቱ በፊት መሆኑን እና በቀዳሚው ቀነ ቀጠሮ ላለመቅረብ በቂ ሆኖ የሚገመት ምክንያት (እክል) መኖር ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ድንጋጌው አቤቱታው የሚቀርብበትን ግልጽ የሆነ የጊዜ ገደብ አላስቀመጠም፡፡ በዚህ ይዘቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 78(1) ከተደነገገው የሚለይ ነው፡፡ የኋለኛው “ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ስለማንሳት” የሚል ርእስ ያለው ሲሆን፣ የመጀመሪያው ግን “በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ስለመቅረብ” በሚል የተደነገገ ነው፡፡ ከዚህም በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል ያለውን ልዩነት ጉዳዩን በያዘው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት እና ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በሚል ሊለይ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 እና 78 መካከል ያለው ልዩነት ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ የቀረ ነገር ግን በሚቀጥለው ቀነ ቀጠሮ የቀረበው ተከሣሽ ጥያቄው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 78(1) አኳያ የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቁ. 78(1)“ን” መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ያየው በአግባቡ አይደለም፡፡

በመቀጠል ያየነው አመልካች በአንድ ወር ውስጥ ቀርቦ ያላመለከተበትን ምክንያት አላስረዳም የሚለውን የፍ/ቤቱ ትችት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለጽነው አመልካች አቤቱታውን ለማቅረብ የቀናትም ይሁን የወራት ገደብ አልተቀመጠለትም፡፡ በመሆኑም እንዲያስረዳ የሚጠበቀው ክርክሩ ሊሰማ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበበትን ምክንያት ነው፡፡ ለክሱ መልስ በተሰጠበት ጊዜ በኋላ በቃል የመከራከር የተሟላ ውክልና የለህም የተባለው ሠራተኛው ከመቅረቡም በላይ፤ መልሱን እራሱ ፈርሞ እንዳቀረበው በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ጉዳዩን ለመስማት (በቃል) ቀጠሮ በተያዘበት ዕለትም ይኸው ለመከራከር ይችላል ተብሎ ከአመልካች ውክልና የተሰጠው ሠራተኛ የቀረበ በመሆኑ ቢያንስ በኋላ ትዕዛዙ እንዲነሳለት ላቀረበው አቤቱታ አወሳሰን እንደበቂ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድለት ይገባ ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች ያቀረበው በጽሑፍ የተዘጋጀው መልስ ከመዝገቡ የተያያዘ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ከዚህ በመነሳት ወደፊት ያለውን ክርክሩ መሰማት ሲገባው ወደ ውሳኔ ማምራቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስናጠቃልለው ፍ/ቤቱ ክርክሩን የመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 የተቀመጠውን ድንጋጌ በአግባቡ ሳይጠቀም በመሆኑ አፈጻጸሙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13262 ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 72956 የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ ከገባበት ቀን ጀምሮ ወደፊት ያለውን ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ውብሸት ካሳዬ - ጠበቃ ኃይሉ ገ/ሥላሴ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ማዕድን ሃብት ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ግርማ አለሙ ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው ከፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ከሳሽ ነበሩ፡፡ የክርክሩም አመጣጥ የሚከተለው ነው፡፡ ተጠሪ ያለአግባብ ከስራ አሰናብቶኛል በሚል ክፍያ እንዲከፈላቸውና ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ተጠሪ አመልካች የአሰሪ ወገን ሳይሆኑ የሰራተኛ ወገን ናቸው በሚል መቃወሚያ በማቀረቡ ፍ/ቤት ተጠሪ የአሰሪ ወይም የሰራተኛ ወገን ስለመሆናቸው በስራ ክርክር ችሎት አስወስነው ሲቀርቡ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብታቸውን ጠብቆ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካችም በዚሁ መሰረት በስራ ክርክር ችሎት የአሰሪ ወገን መሆናቸውን አስወስነው መዝገቡን እንዲንቀሳቀስላቸው ሲያመለክቱ መዝገቡ በመጥፋቱ የቀድሞ ክስና የተጠሪ መልስ ተያይዞ ክሱ በአዲስ መዝገብ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ፍ/ቤቱም የአመልካች አቤቱታ ከነአባሪው ለተጠሪ ደርሶ ተጠሪ አስተያየት እንዲያቀርብ አዟል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች በተከታታይ ቀጠሮዎች ባለመቅረባቸው ፍ/ቤቱ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መሰረት ዘግቷል፡፡ አመልካችም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 71(2)"ን" መሰረት አድርገው መዝገቡ እንዲከፈትላቸው ሲያመለክቱ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 የተዘጋ መዝገብ አመልካች በጠቀሱት የሥነ-ሥርዓት ህግ መሰረት ሊከፈት አይችልም በማለት ጥያቄውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት አጥቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካችም በቅሬታቸው በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ለተጠሪ ደርሶ መልስ እና የመልስ መልስ የተቀባበልን ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መወሰን ሲገባው መዝገቡን መዝጋቱ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ትዕዛዝ ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡

ከፍ ሲል የተገለፀው የግራ ቀኙ ክርክርና የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሲሆን በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት የሚያስፈልገው ጭብጥ የስር ፍ/ቤት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መሠረት መዝጋቱ እንዲሁም አመልካች መዝገቡ እንዲከፈት ሲጠይቁ ጥይቄአቸው ውድቅ መደረጉ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች ክስ አቅርበው ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ ተቀባብለው ጨርሰዋል፡፡ ተጠሪ ቀድሞ የቀረበው ክስ፣ መልስ፣ የመልስ መልስ እንደሁም ሌሎች ማስረጃዎች ደርሶት አስተያየት እንዲሰጥ የታዘዘው የቀድመውን ተከሳሽ ተክቶ በክሱ ውስጥ በመግባቱ ብቻ ነው፡፡ ፍ/ቤቱም መዝገቡን በዚጋበት እለት ለመዝገቡ ቀጠሮ ተሰጥቶ የነበረው አመልካች አቤቱታቸውን ከነአባሪዎቹ ለተጠሪ አድርሰው ተጠሪ የሚያቀርበውን አስተያየት ለመቀበል እንጂ ክስ ለመስማት አልነበረም፡፡ አመልካች በቀጠሮው እለት ባለመቅረባቸውም ፍ/ቤቱ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መሰረት መዝገቡን ዘግቷል ይህ የሥነ-ሥርዓቱ ድንጋጌ የሚገኘው ክርክርን ስለማቋረጥ በሚናገረው ሥነ-ሥርዓት ህጉ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ የተጠቀሰው ድንጋጌም ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር ተቋርጦ በሚቀርብበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ስለሚወስደው እርምጃ የሚናገር ሲሆን የድንጋጌው ይዘትም፤ ***"ክሱ በሚቀጥልበት በማንኛውም ጊዜ ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን ፍ/ቤቱ በቂ በሆነ ማስረጃ የተገነዘበ እንደሆነ ስለ ኪሳራና ስለ ካሳ ተገቢ የሆነውን ትእዛዝ በመስጠት ክሱን ይዘጋዋል፡፡ ምክንያቱንም ዘርዝሮ በመዝገቡ ላይ ይሰፍራል፡፡"*** በሚል ይነበባል፡፡ ድንጋጌው ከሚገኝበት ክፍልና ከድንጋጌው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዝርዝር ይዘት በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው ፍ/ቤቱ ክሱን የሚዘጋው የክሱ ምክንያት ሲቋረጥ ወይም ጨርሶ ሲቀር ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ፍ/ቤቱ መዝገቡን የዘጋው የክሱ ምክንያት በመቋረጡ ሳይሆን አመልካች በተከታታይ ቀጠሮ በመቅረታቸው በመሆኑ ፍ/ቤቱ የተጠቀሰውን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ መሰረት አድርጎ መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች መዝገቡ እንዲከፈትላቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 71(2)"ን" መሰረት በማድረግ ለፍ/ቤቱ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ በዚህ ሥነ-ሥርዓት መሰረት መዝገብ እንደከፈት ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69(2) ክስ በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ ከሳሽና ተከሳሽ በመቅረታቸው ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70(መ) መሰረት ከሳሽ ለተከሳሽ መጥሪያ ሳያደርስ በመቅረቱ መዝገቡ ተዘግቶ ከነበረና ከሳሹ የቀረው ወይም ለተከሳሽ መጥሪያ ያልደረሰው በቂ ሆኖ በሚገመት ምክንያት መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች የክስ መዝገብ የተዘጋው ክስ በሚሰማበት ቀነ-ቀጠሮ በመቅረታቸው ስላልሆነ መዝገቡ እንዲከፈት ይህን ሥነ-ሥርዓት መጥቀሳቸው ተገቢ አልነበረም፡፡ ነገር ግን አንድ ተከራካሪ ወገን ፍሬ ነገሩን ከገለፀ ትክክለኛውን የህግ ድንጋጌ አለመጥቀሱ መብቱን ሊያስቀርበት አይችልም፡፡ ይልቁንም ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው ጥያቄ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ተገቢ ነው ያሉትን ውሳኔ የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ፍ/ቤቱ አመልካች ባለመቅረባቸው መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መሰረት መዝጋቱ ሥነ-ሥርዓታዊ ባለመሆኑ ምንም እንኳን አመልካች የጠቀሱት አንቀፅ ለጉዳዩ አግባብነት ባይኖረውም ተገቢውን ድንጋጌ በመጠቀም ስህተቱን ሊያርም ይገባው ነበር፡፡ በክርክሩ ውስጥ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የሆነው ጉዳይ ሲያጋጥም ማንኛውም ተከራካሪ ወገን በሚያቀርበው ጥያቄ ፍ/ቤቱ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የሆነው ነገር በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሰረዝ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 209 ስልጣን ይሰጠዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አመልካች ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ማመልከቻ ከተጠሪ ጋር መልስና የመልስ መልስ ተሰጥቶበት ለውሳኔ ያደረ ጉዳይ መሆኑን በማለፅ መዝገቡ እንዲከፈትላቸው በ21/4/2000 ዓ.ም ስለመጠየቃቸው የስር ፍ/ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ የአመልካች ክስ የክስ ምክንያቱ ሳይቋረጥ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መዝጋቱ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ በመሆኑ አመልካች ባቀረቡት ጥያቄ መነሻነት ይህንን ስህተቱን በማረም መዝገቡን መክፈት ሲገባው አመልካች የጠቀሱትን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ አግባብ አለመሆኑን ብቻ መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 መሰረት የተዘጋ መዝገብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 71(2) መሰረት አይከፈትም በሚል ምክንያት ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎቹን በአግባቡ ያላገናዘበና መሰረታዊ የሥነ-ሥርዓት ህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 92294 ጥር 13 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 64486 ሚያዚያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ክስ ያቀረቡበት መዝገብ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 45984

ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ፕሮፌሰር ረዳ ተ/ኃይማኖት - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ ልመንህ ተፈራ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ስላሰናበቷቸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ተጠሪን በትምህርት ቤታቸው እንዲያስተምሩላቸው ቀጥረዋቸው ተጠሪ የተቀጠሩበትን ስራ በመተው ከሌላ ት/ቤት ተማሪዎች ግቢ ውስጥ በማምጣት የሚያስተምሩ በመሆኑ ማስጠንቀቂያም ቢሰጣቸው ከድርጊታቸው ያልተቆጠቡ በመሆኑና ተጠሪው በአዳማ ልዩ ዞን ትምህርት ቢሮ ፅ/ቤት ተቀጥረው ደሞዝ የሚከፈላቸው በመሆኑ ከስራ የተሰናበቱት በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ይግባኝ ቀርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ወረዳ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ እንዲወስን በመመሪያ ተመልሶለታል፡፡ በዚህ መሰረት ወረዳ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ማዘዙንና ሁለቱም ወገኖች ግን ማስረጃ አለማቅረባቸውን መዝግቦ አመልካች ተጠሪ ፈፀሙ የተባሉትን ጥፋት በማስረጃ ያላስረዱ በመሆኑና በስራ ስንብት ደብዳቤው ላይ ለስንብቱ በምክንያትነት የተጠቀሰው የተማሪዎች ቁጥር መቀነስ እንጂ ተጠሪ ፈፅመዋል የተባለው ጥፋት ባለመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት ተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት ውሳኔውን አፅንተዋል፡፡ የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ ተጠሪ በስራቸው ላይ ጥፋት የፈፀሙ ለመሆኑ የቀረቡትን ማስረጃዎች ፍ/ቤቱ ሳይሰማ ውሳኔ መስጠቱን የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች ማስረጃዎች ሳይሰሙ ውሳኔ የመስጠቱን ህጋዊነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በመልሳቸው በአመልካች የተነገረውን ጥፋቶች ያልፈፀሙ መሆኑን እና አመልካች በማስረጃ ዝርዝራቸው ላይ የቆጠሩዋቸውን ምስክሮች ማቅረብ ሲገባቸው ምስክሮቻቸውን በመለወጣቸው ፍ/ቤቱ ማስረጃቸውን ሳይሰማ ማለፉ አግባብ ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ መልስ ማግኘት ያለበት ጭብጥ አመልካች ያቀረቧቸው ምስክሮች ሳይሰሙ ውሳኔ መሰጠቱ በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት እንደተረዳነው ጉዳዩ ቀደም ሲል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ወደስር ፍ/ቤት የመለሰው ተጠሪ ሙሉ ቀን ሥራ መስራት አለመስራታቸው፣ ሥራ ትተው ሌላ ቦታ ሲሰሩ የቆዩ መሆን አለመሆኑን፣ ከሌላ ት/ቤት ተማሪዎች እያመጡ ያስጠኑ የነበረ መሆን አለመሆኑን፣ በአመልካች ላይ ጉዳት የሚያደርስ ድርጊት መፈፀም አለመፈፀማቸውና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው የነበረ መሆን አለመሆኑን በማስረጃ እንዲረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ማስረጃ እንዲቀርቡ ታዘው አመልካች ምስክሮቻቸውን በሚያሰሙበት ቀነ ቀጠሮ በ29/05/2001 ዓ.ም በተፃፈ በቃለ መሃላ በተደገፈ አቤቱታ ሁለት ምስክሮቻቸው መኖሪያ አድራሻቸውን በመቀየራቸውና አንደኛዋ በመውለዳቸው ምክንያት ሊያቀርቧቸው ባለመቻላቸው ተለዋጭ ምስክሮች እንዲሰሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የአመልካችን ጥያቄ በሁለት ምክንያቶች ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ አንደኛው የምስክሮቹ ስም በመዝገቡ ውስጥ የሌለና ተጠሪ መልስ ያልሰጡባቸው መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አመልካች ምስክሮቻቸውን ሊለውጡ የሚችሉት መልሳቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማሻሻል እንጂ እንዲሁ አይደለም የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገባቸው ምክንያቶች በህጉ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑ መመርመር ይገባል፡፡

የስር ፍ/ቤት ከሰጣቸው ከምክንያቶች ውስጥ አንደኛው ተለውጠው የቀረቡት ምስክሮችን አስመልክቶ ተጠሪ መልስ አልሰጠባቸውም የሚል ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች እንደክሳቸው አቀራረብ የሚያስረዱላቸው ምስክሮች ዘርዝረው ማቅረባቸው አልተካደም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ምስክሮች ሊሰሙ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ በተለያየ ምክንያት መቅረብ ባለመቻላቸው ተለዋጭ ምስክሮች እንዲሰሙ አመልካች በቃለ-መሃላ በተደገፈ አቤቱታ ጠይቀዋል፡፡ በማስረጃ ዝርዝር ላይ የተቆጠሩ ምስክሮችን ማግኘት ባልተቻለ ጊዜ ምስክሮች የሚቀየሩበት የተለየ ሥነ-ሥርዓት በፍትሐ-ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ውስጥ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ጊዜ በማስረጃ ዝርዝር ላይ የተጠቀሱ ምስክሮች በምንም ሁኔታ መለወጥ የማይቻል ስለመሆኑ የሥነ-ሥርዓት ህጉ ያስቀመጠው ገደብ የለም፡፡ በመሆኑም እንደየነገሩ ሁኔታ ፍ/ቤቶች ተለዋጭ ምስክሮች እንዲሰሙ ለመፍቀድ የሚከለክላቸው ህግ የለም፡፡ በተያዘው ጉዳይም ፍ/ቤቱ ተለዋጭ ምስክሮቹ በመከላከያ ማስረጃ ላይ ስላልተጠቀሱ አልሰማም ከማለት በቀር ምስክሮቹን እንዳይሰሙ የሚከለክል ህግ መኖሩን አልጠቀሰም፡፡ በእርግጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223(2) እና 234 መሰረት የክሱ ማመልከቻና ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው የቀረቡት የፅሁፍና ሌሎች ማስረጃዎች እንዲሁም የምስክሮች ዝርዝርና ማንኛውም ለፍ/ቤቱ የደረሱትን መግለጫዎች ትክክለኛ ግልባጮች ለተከሳሹ ሊደርሰው እንደሚገባ ሁሉ ተከሳሹም የሚያቀርበው መልስና የመከላከያ ማስረጃ፣ የምስክሮች ዝርዝር ለከሳሽ ሊደርሰው እና ሊከራከርበት ይገባል፡፡ ፍ/ቤቱም እንዲሰሙ በተጠየቁት አዲስ ምስክሮች ላይ ተጠሪው አስተያየት የመስጠት እድል ሊሰጠው ይገባል የሚል ከሆነ ይህንኑ እድል ከመስጠት ባለፈ አመልካች ማስረጃቸውን እንዳያሰሙ የሚከለክልበት ህጋዊ ምክንያት አልነበረም፡፡ ተጠሪም ቢሆን ምስክሮቹ ሲመሰክሩ መስቀለኛ ጥያቄ በመጠየቅ ፅውነቱ እንዲወጣ የማድረግ መብት ስላላቸው ምስክሮቹ እንዳይሰሙ የሚከለከሉበት የህግ ምክንያት ይህ ችሎት አላገኘም፡፡

ሌላው ፍ/ቤቱ የሰጠው ምክንያት አመልካች ምስክሮቹን የሚለውጡ ከሆነ መልሳቸውን ማሻሻል ነበረባቸው የሚል ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91 መሰረት አቤቱታ ሊሻሻል የሚችለው የአቤቱታው መሻሻል ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራውና ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ የድንጋጌው ይዘት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ክስ ወይም መከላከያ የሚሻሻለው ጉዳዩን በይበልጥ የሚያብራራው ወይም የቀረበውን ክርክር በተሻለ ዓይነት ገልፆ የሚያስረዳው ወይም ሁኔታውን በዝርዝር አገላለፅ የሚያመለክት መሆኑ ሲታመን ብቻ እንጂ ምስክሮች ለመለወጥ ሲባል ብቻ የመልስ አቤቱታ እንዲሻሻል የተጠቀሰው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ አይፈቅድም፡፡ በመሆኑም ስር ፍ/ቤት አመልካች ምስክሮቻቸውን ለመለወጥ የመከላከያ መልሳቸውን ሊያሻሽሉ ይገባ ነበር በማለት አመልካች ምስክሮቻቸውን እንዳያሰሙ መከልከሉ የሥነ-ሥርዓት ህጉን ያልተከተለ እና በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 20(4) ስር የተመለከተውን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብና ምስክሮቻቸውን የማሰማት መብታቸውን ያጣበበ ውሳኔ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 20744 የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 07592 ሚያዚያ 19 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 79715 ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች በተለዋጭ ያቀረቡዋቸውን ምስክሮች ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47252

የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፑሽፓላት ጆሴፍ

ተጠሪ፡- አቶ ሠይፈ ጎሣዬ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66502 ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረን ጋብቻ በፍች ከፈረሰ በኋላ በተስማማነው ሰኔ 27 ቀን 1998 ፍርድ ቤት ባፀደቀው ስምምነት መሠረት አመልካች ከጥቅምት 5 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ትምህርት ቤቱን ለብቻቸው በማስተዳደር ያገኙት ገቢ ተጣርቶ እንድካፈል ይወሰንልኝ በማለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው ከጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም በተጣራው ሪፖርት ላይ ባለሙያዎች ቀርበው መጣራት ያለበት ነጥብ እንዳለ በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጌታቸው ዋቅጅራና ጓደኞቹ የሂሳብ ባለሙያዎች ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ሰኔ 1 ቀን 1998 ዓ.ም ያለውን ሂሳብ አዲት በማድረግ ስቴፕስ ትምህርት ቤት በዚህ ጊዜ ውስጥ ብር 663,863 (ስድስት መቶ ስልሣ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሥልሳ ሶስት ብር) የተጣራ ትርፍ ያገኘ በመሆኑ ግማሹን ማለትም ብር 331,931.50(ሶስት መቶ ሰላሣ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሣ አንድ ብር ከሀምሳ ሣንቲም) ግራ ቀኙ ሰኔ 21 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረጉትና ፍርድ ቤት ባፀደቀው መሠረት አመልካች ለተጠሪ እንድታካፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ጋብቻችን በፍች ከፈረሰ በኋላ የጋራ ንብረታችንን ለመካፈል ባደረግነው ስምምነት ለዋይዜድ ህንፃ እና ለወ/ሮ ራሔል ህንፃ የኪራይ ቤቶችና ሻንበል ግቢ የተከፈለ የኪራይ ገንዘብ የጋራ እዳ እንደሆነ ተስማምተናል፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፍርድ ቤት የኦዲት ሪፖርቱን ከውሉ ጋር ሣያገናዝብና ሌሎች ማየት የሚገባውን ማስረጃ ሣያገናዝብ እኔን እዳ ተሸካሚ እንድሆን በማድረግ ተጠሪ ትርፍ እንዲካፈል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በኦዲት ተረጋግጦ በቀረበው መሠረት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ሚዛናዊ ነው፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው ሁለት ገፅ መልስ አቅርቧል፡፡

በሥርና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች ጋር የነበረን ጋብቻ በፍች ከፈረሰ በኋላ ስለ ጋራ ንብረት ክፍፍል ባደረግነውና በፍርድ ቤት ቀርቦ ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረግነው ስምምነት አንቀፅ 5 መሠረት አመልካች ስቴፕስ ትምህርት ቤት በግሏ ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ሰኔ 1 ቀን 1998 ዓ.ም ያስተዳደረች በመሆኑ በዚህ ጊዜ የተገኘውን የተጣራ ትርፍ በሂሳብ ባለሙያ ተጣርቶ እንድታካፍለኝ በማለት ክስ ያቀረበ መሆኑን አመልካች በበኩሏ በዚህ ጊዜ የተገኘውን ትርፍ ተጠሪ ለመጠየቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችለው በመጀመሪያ በስምምነታችን አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 በጋራ እዳነት የተዘረዘሩት ዕዳዎች ተከፍለው የሚቀር ሲኖር ነው የሚል ክርክር ያቀረቡ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪና አመልካች ያደረጉት ክርክርና የሚለያዩበት ነጥብ ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ከሆነ የሥር ፍርድ ቤት ተገቢውን ጭብጥ በመመሥረት ጉዳዩን ወስኗል ወይስ አልወሰነም? የሚለው ነጥብ በመጀመሪያ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የአንድ ክርክር ጭብጥ የሚመሠረተው ከሳሽ ያቀረቡትን ክስና ማስረጃ በተከሳሽ ያቀረበውን የመከላከያ መልስና ማስረጃ እንዲሁም ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ሥነ- ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት የቃል ምርመራ ሲያደርግ ያገኘውን ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ይደነግጋል፡፡ ተጠሪ አመልካች ስቴፕስ ትምህርት ቤት ለብቻቸው ማስተዳደር ከጀመሩበት ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ትርፍ ተጣርቶ እንዲሰጠው ሲጠይቅ ተጠሪ በበኩሏ ከዚህ በፊትም ሆነ በኋላ (ለዋይ ዜድ ህንፃ የወ/ሮ ራሔል የኪራይ ቤቶችና የሻንበል ግቢ) የኪራይ ዕዳዎች የጋራ እዳ በመሆኑ በስምምነታችን መሠረት ያለብን ዕዳ ተከፍሎ ቀሪ ካለ ብቻ ነው ለመጠየቅ የሚችለው የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርባለች፡፡ ፍርድ ቤት በኡዲት ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሰጠው ስቴፕስ ትምህርት ቤት ከጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ያገኘውን የተጣራ ትርፍ(ገቢ) ነው፡፡ ለውሣኔውም መሠረት ያደረገው በእነዚህ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ያለው ወጭና ገቢ ተሰልቶ የተገኘውን የኡዲት ውጤት ነው፡፡ አመልካች ያቀረበችው ክርክር በኡዲት ዘመኑ የማይሸፈኑ ለህንፃ ኪራይ የተከፈለ ዕዳዎች የተጠሪ የጋራ እዳ መሆናቸው በስምምነታችን አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሠረት የጋራ እዳችን መጀመሪያ ተሰልቶ ነው መወሰን ያለበት በማለት ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በማስረጃነት ያቀረበውንና አመልካችና ተጠሪ ስለ ጋራ ንብረት ክፍያ ያደረጉትን ስምምነት አመልካች ያቀረበችውንና በኡዲት ዘመኑ የማይሸፈን ክፍያ እና የኡዲት ዘመኑ ያወጣውን ወጭና የተገኘውን ገቢ መነሻ በማድረግ ከኡዲት ከተሸፈነው ጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ካለው ጊዜ ውጭ ያለው የአመልካችና የጋራ ዕዳ ተከፍሎ የሚቀር ተጠሪ ሊካፈለው የሚጠይቀው ገንዘብ ያለ መሆን አለመሆኑን በስፋት አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ጭብጥ አልመሠረተም፡፡ ይኸም የሥር ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ድንጋጌዎች መሠረት መመሥረት የሚገባውን ጭብጥ ሣይመሰርት ከጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ስቴፕስ ትምህርት ቤት ያገኘውን የተጣራ ገቢ ብቻ መነሻ በማድረግ ውሣኔ የሰጠና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተጠሪ አመልካች የስቴፕስ ት/ቤት የተጣራ ገቢ እንድታካፍለው የጠየቀው አመልካችና ተጠሪ ስለ ጋራ ንብረት ክፍፍል ተስማምተው ሰኔ 27 ቀን 1998 ፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀውን ውል አንቀፅ 5 መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች በበኩሏ ተጠሪ የተጣራ ትርፍ ልካፈል የሚል ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው በመጀመሪያ በውሉ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 የተገለፁት ዕዳዎች ከተከፈሉ በኋላ ነው የሚልና ውልን መሠረት ያደረገ ክርክር አቅርባለች፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ለውሣኔው ብቸኛ ማስረጃ አድርጎ የወሰደው የኡዲት ሪፖርት አመልካችና ተጠሪ ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ.ም በፍርድ ቤት ያፀደቁትን ውል የተሸፈኑ ጉዳዮች በሙሉ በማጣራት ያቀረበ አይደለም፡፡ የኡዲት ሪፖርቱ ከጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ያለውን የስቴፕስ ት/ቤት ወጭና ገቢ የሚመለከት ነው፡፡ የኡዲት ሪፖርቱ የአመልካችና የተጠሪን ክርክር ለመፍታት እንደ አንድ ጠቃሚ ግብዓት ማስረጃ ከሚያገለግል በስተቀር አመልካች ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት የከፈሉትን የህንፃ ኪራይም ሆነ ከሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም በኋላ የከፈሉትን የህንፃ ኪራይ በተሟላ ሁኔታ የማይሸፍን ማስረጃ ነው፡፡ የኡዲት ሪፖርቱ ከኡዲት ዘመን ውጭ 416,680 (አራት መቶ አስራ ስድስት ሺ ስድስት መቶ ሰማንያ ብር) አመልካች ወጭ ያወጡ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ይህም የሚያሳየን አመልካችና ተጠሪ በውል የገቡትን ግዴታ በሚሸፍንና የተሟላ የሂሳብ ማጣራት ያልተደረገ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችና ተጠሪ ተስማምተውበት በፍርድ ቤት የፀደቀውን ውል በአንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገውን በማለፍ የውሉን አንቀፅ 5 ብቻ ውጤታማ ለማድረግ የሚችል ሂሳብ ተጣርቶ እንዲቀርብ የሰጡት ትዕዛዝና ከጥቅምት 1 ቀን 1998 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ስቴፕስ ትምህርት ቤት ያገኘውን የተጣራ ገቢ ብቻ መነሻ በማድረግ አመልካች ለተጠሪ ብር 331,931.50 (ሶስት መቶ ሰላሣ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሣ አንድ ብር ከሀምሳ ሣንቲም) እንድትከፍል የተሰጠው ውሣኔ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር አንቀፅ 1734 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ.ም በፍርድ ቤት የፀደቀውን ውል አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም በፊትና ከሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም በኋላ ለዋይዜድ ህንፃ፣ የወ/ሮ ራሔል ኪራይ ቤቶችና የሻንበል ግቢ የከፈሉትን የኪራይ ገንዘብ በማስረጃ በማጣራትና በውሉ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የጋራ ዕዳ መሆኑን በመገንዘብ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መልሰንለታል ግልባጩ ይላክለት፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ትርሐስ ፍስሐዬ - ወኪል ዚርኡ ፍስሃዬ - ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘነበች በሪሁን - ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 መሰረት ዳኝነት እንዲታይ የቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ዋናው ክርክር ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው ተጠሪ ስትሆን፣ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጥያቄ ያቀረበችው የአመልካች ባል ከነበረው ሟች ወልጃቸዋለሁ የምትላቸውን ሁለት ልጆች ልጅነት እንዲረጋገጥላት ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ክስ መነሻነት ክርክር ከተካሄደ በኋላም ተጠሪ እንደ ጥያቄዋ ተወስኖላታል፡፡ ውሳኔው እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ደርሶ እንደፀና በመዝገቡ ተመልክቷል፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ነው አመልካች ዳኝነት ይታይልኝ በማለት አቤቱታ ያቀረበችው፡፡ ተጠሪ ያስወሰነችው ሐሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ፍ/ቤቱን በማሳሳት በመሆኑ ጉዳዩ በኋላ በተገኘው እውነተኛው ማስረጃ ተረጋግጦ ሊወሰን ይገባል የሚል ምክንያት በመስጠት ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ለሰማው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታዋን አቅርባለች፡፡ ፍ/ቤቱም የተጠሪንም መልስ ካየ በኋላ፣ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ደርሶ የተወሰነ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ሊስተናገድ አይችልም የሚል ምክንያት በመስጠት አቤቱታውን ውድቅ አድርጐአል፡፡ ጉዳዩን በመጨረሻ ያየው የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም በዚህ ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብሎአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ዳኝነት እንዲታይላት ያቀረበችው ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ እንደሆነ፣የሥር ፍ/ቤቶች ሕጉ ሳይከለከል ጥያቄውን ውድቅ በማድረጋቸው በሕጉ አተረጓጐም ረገድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ የሆነ ስህተት መፈጸማቸውን፣ባቀረበችው ጥያቄ መሰረት ጉዳዩ እንደገና ቢታይ ተጠሪ ቀደም ሲል ያሰጠችው ውሳኔ እንደሚሻር በመግለጽ አቤቱታዋን አቅርባለች፡፡ ተጠሪም ለአቤቱታው በሰጠችው መልስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 “ን” መሰረት በማድረግ ዳኝነት እንዲታይ መጠየቅ የሚቻለው ቀደም ሲል በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ከመባሉ በፊት ነው፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 16624 በሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ከተባለ በኋላ ድንጋጌው ተፈፃሚ እንደማይሆን በመግለጽ የሕግ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡ አመልካች በኋላ አገኘሁ ያለችው ማስረጃም እኔን በወንጀል ሊያሰቀጣ የማይችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የሚሉት ነጥቦች በመከራከሪያነት አቅርባ አቤቱታው ውድቅ እንዲሆን ጠይቃለች፡፡

እኛም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡ አመልካች ያቀረበቸው አቤቱታ በሰበር ችሎት እንዲታይ ተወስኖ ክርክሩ እንዲሰማ የተደረገው ቀደም ሲል ለተሰጠው ውሣኔ መሰረት የሆነው ማስረጃ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው እየተባለ ውሣኔው ይግባኝ ተብሎበታል በሚል ብቻ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ሊስተናገድ አይችልም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ ይግባኝ ከተባለ በኋላ ዳኝነት በድጋሚ ሊታይና አቤቱታው ሊስተናገድ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጥያቄ በአግባቡ መመልስ የሚቻለው የድንጋጌው መንፈስ ምን እንደሆነ ትርጉም በመስጠት አንድ መደምደሚያ ላይ መድረስ ሲቻል ነው፡፡ ከዚህ ችሎት የሚጠበቀውም በዚህ ረገድ ተገቢ ነው የሚለውን የሕግ ትርጉም በመስጠት በተደጋጋሚ እየተነሱ ላሉት ተመሣሣይ ጥያቄዎች እልባት መስጠት በመሆኑ ጉዳዩን እንደሚከተለው በዝርዝር ተመልክተናል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 የተቀመጠው ድንጋጌ አዲስ ክስ የሚስተናገድበት ሥርአት አይደለም፡፡ በቀረበው ክስ መሰረት ክርክር ተካሂዶ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ ጥያቄ የሚቀርብበት ሥርአት የተዘረጋበት ነው፡፡ ጥያቄውን የሚያቀርበው ወገን ለጉዳዩ አዲስ ሳይሆን፣ ከመጀመሪያውም ተከራካሪ የነበረ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት መቃወሚያ ከሚያቀርበው ወገን በተለየ ሁኔታ የሚስተናገድ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኙን ለሚሰማው ፍ/ቤት ሳይሆን፣ውሣኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት በመሆኑ ይህም የድንጋጌውን የተለየ ባህርይ ሊያሳይ እንደሚችል አድርጐ ለማየት የሚያስችል ነው፡፡ እንግዲህ ከእነዚህ ሁኔታዎች መገንዘብ የሚቻለው ሕጉ በቁጥር 6 የተቀመጠውን ሥርአት በመዘርጋት ሊያሳካው የፈለገው አንድ ግብ እንዳለ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም የድንጋጌው ዓላማ ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ ማየቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው አግባብነት የሚኖረው መቼ ነው? ይግባኝ ከመባሉ በፊት ወይንስ ይግባኝ ከተባለ በኋላም ጭምር የሚለውን ለጊዜው አቆይተን ዓላማው ምንድን ነው? የሚለውን እንመለከታለን፡፡፡ በዚህ ረገድ ጠቃሚ ሆነው የምናገኛቸው በንኡስ ቁ. (1)(ሀ) እና (ለ) የተቀመጡት ድንጋጌዎች ስለሆኑ ለአጠቃላይ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ሙሉ ይዘታቸውን እንመልከት፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሀ. የመጨረሻው ፍርድ ወይም ውሳኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠው በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበውን ሰነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሰረት በማድረግ ሲሆንና አቤት ባዩም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጐ ለማወቅ ያለመቻሉን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ በሚል የተደነገገ ሲሆን(ለ) ደግሞ

ለ. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ተግባሮች መፈጸማቸው ቢገለጽ ኖሮ ለፍርዱ መለወጥ ወይም መሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችሉ እንደነበር ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፤

ነው ይላል፡፡ ሁለቱን ድንጋጌዎች አጣምረን ስንመለከት ሕጉ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ያኔ(ውሣኔው ሲሰጥ) ሊደረስባቸው ባልተቻለ ሐሰተኛ እና ወንጀል ጠቀስ የሆኑ ተግባሮችን ወይም ድርጊቶችን መሰረት አድርጐ የተሰጠ ሆኖ ከተገኘ ሕገ ወጥ ነው፡፡ በመሆኑም በሕገ ወጥነቱ ሊቀጥል ወይም ተፈፃሚነት ሊያገኝ አይገባም እሚል መነሻ ይዞ ነው የተደነገገው ወደሚለው ድምዳሜ ነው የምንደርሰው፡፡ ይህ ደግሞ በክርክር ሂደት እውነትን አንጥሮ ማውጣት ዋነኛው የፍርድ አመራር ስርአቱ ግዴታ ነው የሚል መሰረት ያለው እንደሆነ መገመቱ አይከብድም፡፡

ለተያዘው ክርክር መነሻ የሆነው ቁ. 6 በተካተተበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከሚከናወኑት አበይት ተግባራት አንዱ (ዋነኛው) ክርክሩን በተገቢው መንገድ መምራት እና በመጨረሻም እውነትን አንጥሮ በማውጣት ትክክለኛ ፍርድ መስጠት ነው፡፡ በዚህ አግባብ የሚሰጠው ፍርድ ፍትሐዊ እንደሚሆን የሚታመን ሲሆን፣እውነትን ለማውጣት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው ደግሞ ማስረጃ ነው፡፡ የክርክር ጭብጦች የሚነጥሩት በማስረጃ በመሆኑ ሕጉ በዚህ ረገድ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ማስረጃ የሚቀርብበትን ብቻ ሳይሆን፣የሚገኝበት ሁኔታም(መንገድም) የሕግ መሰረት ያለው ወይም ሕጋዊ ሊሆን ይገባል፡፡ የክርክሩ አመራርም እንደዚሁ ሕጋዊ እና ወደ እውነት የሚያደርስ መንገድ ሊከተል ይገባል ብሎ ሕጉ ያምናል፡፡

የሥነ ሥርአት ሕጉ ማስረጃ የሚቀርብበትን አግባብ እና የጊዜ ወሰን በመርህ ደረጃ በአንድ በኩል ሲያስቀምጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከመርሁ ወጣ ባለ ልዩ ሁኔታ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችልበትን አግባብ ደንግጐ እናገኛለን፡፡ በመርህ ደረጃ ማስረጃ ማቅረብ ያለበት በማስረጃው እጠቀማለሁ የሚለው ተከራካሪ ወገን እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223 እና 234 የተደነገገ ሲሆን፣ፍ/ቤቱ እውነት ላይ ለመድረስ የሚቻለው በዚህ ብቻ አይደለም የሚል እምነት ከያዘ ግን በራሱ ተነሳሽነት ማስረጃ አስቀርቦ እንደሚሰማ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 እና በሌሎችም ድንጋጌዎች ተመልክቶአል፡፡ ማስረጃ የሚቀርብበት የጊዜ ወሰንም እንደዚሁ በቁ. 137 የተቀመጠ ድንጋጌ ቢኖርም፣ይህ ጊዜ ካለፈም በኋላ ማስረጃ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ በቁ. 256 ተደንግጓል፡፡ ክሱን በሰማው ፍ/ቤት ያልቀረበን ማስረጃ በይግባኝ ደረጃ የሚሰማበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብ እንዳለም በቁ. 345 ከተቀመጠው ድንጋጌ እንመለከታለን፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች እንግዲህ መገንዘብ የምንችለው አንዱና ዋነኛው ቁም ነገር ማስረጃ እውነትን አንጥሮ በማውጣት ረገድ ካለው ወሳኝ ሚና በመነሳት ከዋናው የማስረጃ አቀራረብ መርህ ወጣ ባለ ሁኔታም የሚቀርብበትና የሚሰማበት አግባብ በሥነ ሥርአት ሕጉ ተቀባይነት ማግኘቱን ነው፡፡ ዓላማውም የሚሰጠው ውሣኔ እውነት ላይ ብቻ የተመሰረተ እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ለዳኝነት እንደገና ይታይልኝ ጥያቄው መሰረት የሆነው ምክንያት የቀድሞው ውሣኔ የተሰጠው በሐሰት ተዘጋጅቶ በቀረበው ማስረጃ ላይ በመመስረት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ውሣኔው እውነትን አንጥሮ ያወጣ አይደለም ወይም እውነት የሆነውን ነገር ሐሰተኛ (ሕገወጥ) በሆነ ማስረጃ ተድበስብሶ ቀርቶአል የሚል መነሻ ያለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች የያዘችው እምነት ዳኝነቱ እንደገና ከታየ የቀድሞው ውሣኔ በእርግጥ ይሻራል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄ የሚቀርብበት አግባብ አክትሞአል ወይም በሩ ዝግ ነው የሚል መከራከሪያ ነው ያላት፡፡ ይህ በተጠሪ የተነሳው የመከራከሪያ ነጥብ ዳኝነቱ እንደገና ታይቶ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ሊገኝ የሚችለውን ውጤት ግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም፡፡ የአመልካች ክርክር ግን እውነት የሚገኝበትን አግባብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም የሕጉ ትርጉም ይህ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ከመድረሳችን በፊት በድንጋጌው ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉት ሁለት አማራጮችን አንድ በአንድ ማየት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጀመሪያው አማራጭ ለቀድሞው ውሣኔ መሰረት የሆነው ማስረጃ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ መሆኑን በክርክሩ ሂደት አረጋግጦ ውሳኔውን መለወጥ ወይም ማሻሻል የሚቻልበት ሁኔታ እንደሚኖር ቢገመትም፣ ድንጋጌው ስለማይፈቅድ(ይግባኝ ስለተባለ) አቤቱታውን ከወዲሁ ውድቅ ማድረግ የሚለው ነው፡፡ የመጀመሪያውን አማራጭ ስንመለከት ክርክሩ በሕግ አግባብ ብቻ ተመርቶ እና በሕግ መሰረት ብቻ የተገኘውን ማስረጃ መሰረት አድርጐ የተሰጠው ውሣኔ እውነትን አንጥሮ ያወጣል የሚለው የሕጉን ዓላማ ስለሚያሳካ ውጤቱ መልካም ነው የሚል ግንዛቤ እንይዛለን፡፡ ሁለተኛው አማራጭ በሁለት መልክ ሊታይ ይችላል፡፡ አንዱ በእርግጥም ሕጉ የሚከለክል ከሆነ ሕግን መጣስ በራሱ ክልክል በመሆኑ ሕጉን አክብሮ መቀበሉ ተገቢ ነው ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ነጥብ እንመለከታለን፡፡

ቀደም ሲል እንዳየነው አከራካሪ የሆነው በንኡስ ቁ. /1/ የተመለከተው ድንጋጌ በተለይም “.....ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ፍርድ ወይም ውሣኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ቅሬታውን አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት” የሚለው ሐረግ ነው፡፡ “ቅሬታውን አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት” የሚለውን ሐረግ ለብቻው ወስደን ቃል በቃል ብንተረጉመው በእርግጥም ዳኝነት እንዲታይ የሚቀርበው ጥያቄ አቤቱታ አቅራቢው በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያደርሳል ልንል እንችላለን፡፡ ይሁንና ድንጋጌው በአጠቃላይ ሊተረጐም የሚገባው በውስጡ ከያዛቸው ሌሎች ሐረጐች እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በንኡስ ቁ. /1/ሀ/ እና /ለ/ ከተቀመጡት ሁኔታዎች እንዲሁም ከጠቅላላው የሥነ-ሥርአት ሕጉ ዓላማ ጋር ተገናዝቦ በመሆኑ በትርጉም የምንደርስበት መደምደሚያ አንድዋን ሐረግ ብቻ ወስደን ቃል በቃል በመተርጎም ከምንደርስበት የሰፋ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

ሌላው ድንጋጌው ሲተረጐም ግምት ውስጥ መግባት ያለበት በድጋሚ ዳኝነት ይታይ ጥያቄ ከይግባኝ በፊት ይቅረብ የተባለበትን ምክንያት ነው፡፡ ውሣኔው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይታረማል (በድጋሚ ይታያል) በሚል እሳቤ ይግባኝ ተብሎበት በክርክር ሂደት ባለበት ጊዜ ውሣኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት የዳኝነት እንደገና ይታይ ጥያቄ ማቅረብ አንድን ጉዳዩ በተመሳሳይ ጊዜ በበታች እና በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንዲሰማ በማድረግ ወጪን፣ጊዜን እና ጉልበትን ያለአግባብ ከማባከን እንደዚሁም ክርክሩ እንዲወሳሰብ ከማድረግ አልፎ የሚያስገኘው ጠቀሜታ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 345 እንዲሁም ቁ. 182 አንፃር በማየትም ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል የሚለውንም እንደ አንድ ታሳቢ ሁኔታ አድርጐ መውሰድ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሕጉ በዚህ ደረጃ የተሻለውንና ምክንያታዊ የሆነውን አካሄድ ቢመርጥም፤ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ከተወሰነ በኋላ ለውሣኔው መሰረት የሆነው በቁ. 6/1/ሀ/ ከተመለከቱት ተግባሮች (ወይም ሁሉም) ነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ብሎ አላሰበም ማለት ግን የሚቻል አይደለም፡፡ ቀደም ሲል በዝርዝር ለማሳየት እንደሞከርነው ከሁሉም በላይ መታየት ያለበት ሕጉ ዓላማ አድርጐ የተነሳው እውነት ላይ መድረስ ነው የሚለው ነው፡፡ እውነት ላይ መድረስ መቻል በፍትሕ አሰጣጥ ረገድ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ውጤታማ ሥራ ነው፡፡ ሕግ ሲተረጐም ተጨባጭ ውጤት ሊሰጥ በሚችል አኳኋን መሆን እንዳለበት ከአጠቃላይ የሕግ አተረጓጐም መርህ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ተጨባጭ ውጤት ሊሰጥ በሚችል አኳኋን ሊተገበር የሚችለው ውሣኔው ሐሰተኛ እና ወንጀል ጠቀስ የሆኑ ተገባሮችን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ነው የሚል አቤቱታ እስከቀረበበት እና በቂና አሣማኝ መሆኑን ፍ/ቤቱ እስካመነበት ድረስ ይግባኝ ይባልበትም አይባልበትም ያለልዩነት ሥራ ላይ እንዲውል በሚያስችል ሁኔታ ሲተረጐም ነው የሚል እምነት መያዙ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በመቀጠል የተመለከትነው በሰበር መ/ቁ. 16624 በተሰጠው ውሣኔ ለድንጋጌው የተሰጠው ትርጉም አሁን በያዝነው መዝገብ ከተሰጠው ትርጉም ጋር እንዴት ይጣጣማል? የሚለውን ነው፡፡ ድንጋጌውን እንደገና በስፋት ማየት ያስፈለገው የዳኝነት በድጋሚ ይታይ ጥያቄ በተደጋጋሚ እየቀረበ በመሆኑና የሚነሳው ክርክርም እውነት ሳይወጣ እየቀረ ነው የሚል ስለሆነ፤ከዚህ በላይ ደግሞ ጥያቄው የሚነሳው ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ውሣኔ ካገኘ በኋላ እንደሆነ ግንዛቤ ስለተወሰደ ነው፡፡ በእርግጥም ጉዳዩ አሳሳቢ ሆኖ በመገኘቱ ከዚህ በፊት የተሰጠው ትርጉም እንደገና አይቶ በተደጋጋሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እየተነሱ ላሉት ጥያቄዎች ምላሽ ሊሰጥ የሚችል እልባት ማድረግ አማራጭ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/1/ በተደነገገው መሰረት ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረውን ትርጉም ለውጠን በዚህ በያዝነው መዝገብ የተሰጠው ትርጉም ገዥ ይሆናል ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠሪ በሰበር መ/ቁ. 16624 የተሰጠውን ውሣኔ መሰረት በማድረግ ያቀረበችውን ክርክር አልተቀበልንም፡፡ በመጨረሻም አመልካች ያቀረበችውን የዳኝነት ጥያቄ በመቀበል ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01789 ጎዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 70413 ታህሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. በሰበር መዝገብ ቁጥር 16624 ተሰጥቶ የነበረው ትርጉም ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ተለውጧል፡፡
3. አመልካች ያቀረበችው የዳኝነት ይታይልኝ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 መሰረት ሊስተናገድ የሚገባው ነው ብለናል፡፡
4. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበችውን አቤቱታ በመቀበል እና ተጠሪ የምትሰጠውን መልስ አይቶ ጉዳዩን በመመርመር ተገቢ ነው የሚለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ይመለስለት ብለናል፡፡
5. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42871

ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የቀድሞ ወረዳ 07 ቀበሌ 32 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ደረጀ ይታገሱ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ጆሮ ዋቅጅራ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ የሚቀርብ አቤቱታ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በተጠሪ በተመሰረተበት የቤት ይለቀቅልኝ ክርክር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መጋቢት 18 ቀን 1994 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ቁጥራቸው 508 እና 509 የሆኑት ቤቶች ለአሁኑ ተጠሪ እንዲመለሱላቸው ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ጥር 13 ቀን 1995 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 መሠረት ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይለት ምክንያቱን ገልፆ ፍርዱን በድጋሚ እንዲያየውና እንዲለውጠው የመጀመሪያውን ፍርድ ለሰጠው ለዚሁ ፍርድ ቤት አቤቱታውን አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በመጀመሪያው ፍርድ ቤት ይግባኝ ከተባለ በኋላ ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብ እንደማይችል፣ እንዲሁም አቤቱታው በቀረበበት ጉዳይ የመጀመሪያው ፍርድ የተሰጠበት አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ሥር የተመለከቱትን ነገሮች ባሉበት ስለመሆኑ በድጋሚ የቀረበው አቤቱታ እንደሚያሳይ ገልፆ ዳኝነቱ በድጋሚ ሊታይ አይገባም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይህ ፍርድ ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 መሠረት አቤቱታ ቀርቦ ከታየ በኋላ ብይኑ ይግባኝ የሌለው በመሆኑ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የማታይበት አግባብ የለም በማለት ዋናውን ጉዳይ ሳይመለከተው መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች አቤቱታውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ በይግባኝ ሰሚው ችሎት የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሰበትም በሚል ውድቅ ሆኖበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤቶች በፍርድ ባለመብት የሆኑበት የባለቤትነት ደብተር ሐሰተኛ መሆኑ ተረጋግጦ በሚመለከተው የአስተዳደር አካል የተሠረዘ ስለመሆኑ በመግለጽ ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ለሥር ፍርድ ቤት አቤቱታ ቀርቦለት ሳይቀበለው መቅረቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስለሆነ ታርሞ ለረጅም ጊዜያት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የነበሩት ቤቶች ላይ ተጠሪ መብት የላቸውም ተብሎ ሊወሰን ይገባል ሲሉ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮም አመልካች ዳኝነት እንደገና እንዲታይለት ያቀረበው ጥያቄ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ስለተጠየቀበትና የቀረበው አዲስ ማስረጃ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ስለመገኘቱ አልተረጋገጠም በሚሉት ምክንያቶች ውድቅ የመደረጉ ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ድንጋጌን በትክክል በመተርጎም መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሦስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሦስት ገጽ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን አድርገዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚፈልገው አቢይ ነጥብ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የመጨረሻ ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላልን የሚለው ነጥብ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይለት አቤቱታ አቅርቦ የሥር ፍርድ ቤት ዳግመኛ ዳኝነት እንዲታይ የቀረበውን አቤቱታ ከመቀበሉ በፊት የአቤቱታው ግልባጭ ለተጠሪ በመላክ አቤቱታው ሊሰማ የማይችልበትን መከራከሪያ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቶ ክርክሩን መስማቱን፣ ክርክሩን ከሰማ በኋላ የአመልካችን አቤቱታ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የተባለበት በመሆኑ ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ የተጠየቀበት ሰነድም በሐሰተኛ መንገድ የተገኘ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ዳኝነቱን በድጋሚ ሊታይ አይገባውም ሲል ብይን መስጠቱን፣ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርቦም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በሚል ምክንያት የአመልካችን ዋናውን ክርክር ሳይመለከተው መዝገቡን ከዘጋው ብኋላ አመልካች በዚህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ተቀባይነት ማጣቱን ነው፡፡ ከዚህ በግልጽ መረዳት የሚቻለው ለዚህ ችሎት ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መሠረት የሆነው ውሣኔ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ሊባል የሚችልበት አይደለም የተባለበትን ውሣኔ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ ችሎት ማየትና ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለበት በዚህ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በፀናው፣ በጉዳዩ ላይ የሰጠው ብይን ይግባኝ የለበትም ተብሎ በተሰጠው ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟልን የሚለውን መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም የሚለውን የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሣኔም ሆነ በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪን ክርክር ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከሩት የሥር ፍርድ ቤት ወደ ዋናው ጉዳይ ገብቶ ሲያከራክር ቆይቷል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሥር ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ የሚያሳየው ፍርድ ቤቱ በአመልካች በኩል ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ አቤቱታ ሲቀርብ ተጠሪን በመጥራት ማከራከሩ አቤቱታው ሊሰማ የማይችልበትን መከራከሪያ እንዲያቀርቡ እድል ለመስጠት ስለመሆኑ ሲሆን ተጠሪ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት ዳኝነቱ በድጋሚ ሊታይ የማይችልበትን ምክንያት አቅርበው ተከራክረዋል፡፡ ይህም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6/3/ ሥር የተመለከተው የሥነ-ሥርዓት አካሄድ ሲሆን ተገቢነት ያለውም ነው፡፡ የሥር ፍርድ በዚህ መሠረት አቤቱታውን ካስተናገደ በኋላ ግን አመልካች ዳኝነቱ እንደገና እንዲታይ ያቀረበውን አቤቱታና ተጠሪ ዳኝነቱ በድጋሚ ሊታይ አይገባውም በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ መሠረት በማድረግ ዳኝነቱ በድጋሚ ሊታይ አይገባውም በማለት ብይን ሰጥቶታል፡፡ ይህ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ በግልጽ የሚያሳየው ፍርድ ቤት ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባዋል በማለት ብይን ከሰጠ በኋላ በዋናው ጉዳይ ግራ ቀኙን አከራክሮ የቀድሞውን ውሣኔ ያፀናው ስለመሆኑ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ነገረ ፈጅ የሥር ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ገብቶ ከአከራከረ በኋላ ውሣኔ ሠጥቶ እያለ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በሚል የከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሆነ የሰበር ችሎት ውሣኔ መስጠታቸው ያላግባብ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የክርክሩን ሂደት ባገናዘበ ባለመሆኑ የምንቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ቀጠሎ መታየት ያለበት ጉዳዩ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም የመባሉን አግባብነት ነው፡፡ አንድ ጉዳይ በድጋሚ ዳኝነት ሲቀርብ ዳኝነቱ በድጋሚ ሊታይ አይገባውም ወይም ይገባል ሲል ፍርድ ቤቱ ውሣኔ ሲሰጥ ይግባኝ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6/3/ እና /4/ ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ በግልጽ ያሳያሉ፡፡ በዚህም መሠረት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ሆነ የሰበር ችሎቱ ውሣኔ ሲታይ ሕጋዊ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይገባ የነበረው ሥርዓቱን ጠብቀው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንጂ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አይደለም፡፡ የዚህ ችሎት ኃላፊነትና ተግባር ደግሞ በበታች ፍርድ ቤት በተሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈፀም ማረም ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ- መንግሥት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና 22 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም የአዲስ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎቱ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት የተሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6/3/ እና /4/ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት የአመልካች ነገረ ፈጅ በዋናው ጉዳይ ላይ ያቀረቡትን ክርክር ለመመርመር የሚያስችል ሥነ-ሥርዓት ባለመኖሩ አልፈነዋል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04111 ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 07548 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም. *መሠረታዊ* የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ *መሠረት* ፀንቷል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤት ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ አይገባውም በማለት በሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ የለውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

መስፍን እቁበዮናስ

ኂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ አለሙ - ጠ/ሃይሉ ንጋቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ሐጂ ይማም ሙዘይን - ጠ/ገብረእግዚአብሔር ተስፋዬ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሳኒያ ሱልጣን
3. አቶ አብዱልናስር አማን

} በሌሉበት

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪ ባልና ሚስት ሆነው የሳሙና ፋብሪካ ድርጅት በብር 450,000 እንደሸጡላቸው፣ አመልካች ብር 250,000 ከፍለው ድርጅቱን ተረክተው ብር 150,000 አውጥተው ግንባታ መስራታቸውን፣ ሁለተኛ ተጠሪ ሆነ ብለው ስንቅ የሌለው ቼክ ለአንደኛ ተጠሪ ሰጥተው ሲፈረድባቸው ለአመልካች የሸጡት ቤት ለውሳኔው ማስፈጸሚያ መያዙን፣ በዚህም ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ አቅርበው መቃወሚያው ውድቅ በመደረጉ ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሰረት ማቅረባቸውን ገልፀው ንብረቱ የተከበረው ያለአግባብ ነው እንዲባልና በድርጅቱ ላይ አመልካች መብት ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ በመ/ቁ. 137/93 በተሰጠው ውሳኔ እና በመ/ቁ. 11684 በተሰጠው ትእዛዝ የመልካች ጥያቄ ውድቅ የተደረገ በመሆኑ ድጋሚ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎችም አመልካች ውል እንዲፈፀምላቸው ክስ አቅርበው እያለ በድጋሚ ይህን ክስ ማቅረባቸው ተገቢ እንዳልሆነና አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪ ጋር ተጣምረው መከሰሳቸው ከሥነ-ሥረአት ውጪ ነው በሚል ክሱን ተቃውመዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አንደኛ ተጠሪ የሚከሰሱበት ምክንያት የለም በማለት ከክሱ ሲያሰናብታቸው ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ደግሞ አመልካች ውል ይፈፀም በሚል ክስ ስላቀረቡ በተመሳሳይ ጉዳይ ዳግመኛ ክስ ሊቀርብ አይገባም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጐታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ አንደኛ ተጠሪ ልከሰስ አይገባም ብለው ሳይቃወሙ ክሱ ውጪ መደረጋቸው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421ን ያላገናዘበ ነው፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 የቀረበ መቃወሚያ ውድቅ ከተደረገ በሁለቱ ወገኖች መሃከል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 “ን” መሰረት መብት ለማረጋገጥ ክስ ሊቀርብ እንማይችል ተደርጐ የተሰጠው ብይን የተሳሳተ ነው፣ እንዲሁም ውል እንዲፈፀም የቀረበው ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤት የተያዘው ክርክር ውጤት እዲጠብቅ ተብሎ የቆመ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ተሰጥቶበት እደገና ክስ እንደቀረበ ተደርጐ የተሰጠው ብይን አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የአመልካች ክስ ካሁን በፊት የታየ ነው በሚል ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህ መሰረት አንደኛ ተጠሪ ቀርበው መልስ የሰጡ ሲሆን ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ግን መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሰረት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች ከሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ላይ ገዛሁት የሚሉት የሳሙና ፋብሪካ በሁለተኛ ተጠሪና በአንደኛ ተጠሪ መሐከል በነበረው ክርክር በአፈፃፀም በመያዙ አመልካች ለፍርዱ አፈፃፀም በተያዘው ንብረት ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀዳሚነት መብት ያላቸው መሆኑን በመግለጽ መቃወሚያ አቅርበው ውድቅ ተደርጐባቸዋል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 421 ስር የቀዳሚነት መብት አለኝ በሚል መቃወሚያ አቅርቦ መቃወሚያው ውድቅ የተደረገበት ሰው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ ክስ ለማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ስለተደረገባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሰረት ክስ ማቅረባቸው የሕግ ድጋፍ አለው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ እንዳሉት ሳይሆን ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን እንደተገነዘበው መዝገቡ ያሳያል፡፡ ፍ/ቤቱ የአመልካች ክስ ውድቅ ያደረገው አመልካች ቀደም ሲል ውል ይፈፀምልኝ የሚል ክስ ያቀረቡ በመሆኑ በተመሳሳይ ጉዳይ ድጋሚ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳው ዘንድ አመልካች ውል እንዲፈፀምላቸው ክስ ያቀረቡበትን መዝገብ ቁጥር 01520 አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ላይ ሳሙና ፋብሪካ ድርጅት መግዛታቸውንና ድርጅቱን መረከባቸውን ገልፀው በውሉ መሰረት የሸጡትን ንብረት በከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 137/93 የተሰጠውን እግድ ትእዛዝ ጨምሮ ከማናቸውም እዳና እገዳ ነፃ በማድረግ የውል ግዴታቸውን እንዲፈጽሙ፣ግዴታቸውን መፈፀም የማይችሉ ከሆነ ውሉ ፈርሶ ወደነበሩበት እንዲመለሱና መቀጫ እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው ክስ መስርተዋል፡፡ ለቀረበው ክስ ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ ከተቀባበሉ በኋላ ፍ/ቤቱ ግንቦት 26 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በአፈፃፀም ምክንያት በመያዙ አመልካች መቃወሚያ ያቀረቡ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በመቃወሚያው ላይ የሚሰጠው ውሳኔ እስኪታወቅ መዝገቡ ለጊዜው እንዲዘጋ አድርጓል፡፡ ነገር ግን የከፍተኛው ፍ/ቤቱ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት ያቀረቡትን መቃወሚያ አይቶ ውሳኔ ከሰጠ በኋላም ቢሆን አምልካች የመ/ቁ. 01520 የሆነውን መዝገብ አላንቀሳቀሱም፡፡ አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሰረት አድርገው በመሰረቱት ክስ የጠየቁት የመብት ጥያቄ በመ/ቁ. 01520 የሚጠይቁት ጋር ልዩነት የለውም፡፡ በዚህ መዝገብ በጠየቁት መሰረት ቢወሰንላቸው በድጋሚ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሰረት ክስ ማቅረብ አያስፈልጋቸውም፡፡ በመሆኑም አመልካች በአንድ በኩል ውል እንዲፈፀምላቸው ክስ መስርተው ይህ ጉዳይ እልባት ሳያገኝ በድጋሚ በሌላ መዝገብ ተመሳሳይ ጥያቄ ማቅረባቸው አግባብ አይደለም፡፡ የቀዳሚነት መብት አለኝ በሚል መቃወሚያ አቅርቦ ጥያቄው ውድቅ የተደረገበት ሰው በድጋሚ ክስ ማቅረብ የተፈቀደለት በአፈፃፀም ችሎቱ የንብረቱ ባለመብትነት በጭብጥነት ተይዞ በመደበኛው የሙግት ስርአት አይነት የአመልካቹ ጥያቄ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንፃር ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ባለመሆኑ ይህንን እድል ለመስጠት ነው፡፡ አመልካቹ ይህንን መብት የሚያስከብርለት ሌላ ክስ የመሰረተ ከሆነ ግን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 421 ክስ ለማቅረብ ስለሚፈቅድ ብቻ በተመሳሳይ ጉዳይ ዳግመኛ ክስ ማቅረብ ስነ-ስርአት ህጉ አላማ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ውል ይፈጽምልኝ በሚል ክስ ያቀረቡበትን መዝገብ በማንቀሳቀስና ክርክሩን መቀጠል እየቻሉ በድጋሚ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ በመደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24926 ሚያዝያ 3 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ብይንና ፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 25423 ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44634

የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ታዬ ሆሳዕና - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መሰረት ወልደየስ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ የጋራና የግል ንብረት ነው የሚሏቸውን ንብረቶች ዘርዝረው ለመካፈል ጠይቀዋል፡፡ በአቤቱታቸውም ከሌሎች ንብረቶች በተጨማሪ የመለዋወጫና የሕንፃ መሳሪያ ሱቅ ከእንቁላል ፋብሪካ ጉለሌ ከነበረበት ወጥቶ ተጠሪ በ22 ማዞሪያ በከፈቱት ሱቅ ውስጥ ስለተቀመጠ ንብረቶቹን በአይነት ለመካፈል ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የመለዋወጫና የሕንፃ መሣሪያው ሱቅ ከፍቺ በፊት ንግዱ ተዘግቶ የንግድ ፈቃዱ መመለሱን በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ነጥብ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ አልፎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ የመለዋወጫና የሕንፃ መሣሪያ ድርጅቱን ከነሙሉ እቃው ክፍፍሉ ውስጥ እንዲገባ ጠይቀው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሳይሰጥ በማለፉ ይኸው እንዲወሰንላቸው አመልክተዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች በስር ፍ/ቤት ድርጅት ለመካፈል አልጠየቁም፣የመለዋወጫ እቃዎችን በተመለከተ የእቃዎቹን ዝርዝር ካለማቅረባቸውም በላይ ተጠሪ እነዚህ ንብረቶች መሸጣቸውን ገልፀው የሚከራከሩ ቢሆንም አመልካች ግን እቃዎቹ ስለመኖራቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን የስር ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ ማለፉ አግባብ ባይሆንም ከውጤቱ አንፃር የሚያመጣው ለውጥ የለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታቸው ላይ ንግድ ፍቃዱም ቢመለስ ንብረቶቹ በተጠሪ እጅ ስለሚገኙ መካፈል ሲገባን መታለፉ ስህተት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የአመልካችን ቅሬታ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት የመለዋወጫና የህንፃ መሳሪያ ለመካፈል ጠይቀዋል፡፡ ነገር ግን በስር ፍ/ቤት እንዲሁም በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር አመልካች የሚጠይቁትን ንብረቶች ዝርዝር አለማቅረባቸውን ተረድተናል፡፡ አንድ ከሳሽ የሚጠይቀውን ነገር ለይቶ ማስቀመጥ እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 225/1/ ያመለክታል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች የሚጠይቁትን ንብረቶች ዝርዝር ለይተው ማስቀመጥ ሲገባቸው ይህ አላደረጉም፡፡ ከዚህ ሌላ ተጠሪ በክርክራቸው የመለዋወጫና የህንፃ መሳሪያ ሱቅ ሲዘጋ እቃዎቹ መሸጣቸውን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ንብረቱ አለ በማለት የሚከራከሩ በመሆኑ ስለንብረቱ መኖር የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ በፍትሐብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም አለበት(one who alleges in the affirmative shall prove it)፡፡ ይህ መብት ወይም ግዴታ መኖሩን ካላስረዳ ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ይገባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ንብረቶቹ አሉ በማለት ይከራከሩ እንጂ ስለመኖራቸው ማስረጃ እንዳላቀረቡ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ እንዲያካፍሏቸው የሚጠይቁት የንብረት አይነቶች ዘርዝረው ያላቀረቡ ከመሆኑም በላይ ንብረቶቹ ስለመኖራቸው እንኳን ማስረጃ ሰላላቀረቡ የስር ፍ/ቤቶች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረጋቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት አይቻልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 51214 ጥቅምት 6 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 60553 ጥር 25 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45371

የካቲት 8 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሃይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የገነተ-ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማህበር በኩር ሰንበቴ - ም/ሰብሣቢ ደሣለኝ ዲባባ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ማሞ ተሰማ - ቀረቡ

2. አቶ ጌታቸው ይልማ - ቀረቡ

3. ወ/ሮ ወይንሸት ሙላት - ቀረቡ

ብ ይ ን

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪች ለፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአመልካች ማሕበር ውስጥ አባል መሆናቸውን ገልፀው ማሕበሩ ያለአግባብ ለ6 ወራት ከማህበሩ ስላገዳቸው ይኸው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ለቀረበው ክስ የተለያዩ መቃወሚያዎችና በአማራጭ መልስ የሰጠ ሲሆን በመልሱም አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎቹ ከማሕበሩ የታገዱት የማሕበሩን ገንዘብ ገቢ አላደርግም በማለታቸው እና ሦስተኛ ተጠሪ ደግሞ በስብሰባ ላይ ፀያፍ ንግግር በማናገራቸው በመሆኑ እገዳው ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች ያቀረባቸውን መቃወሚያዎች ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎቹ ጥፋት ለመፈፀማቸው በቂ ማስረጃ አልቀረበም በሚል እግዱ ተነስቶ ከሙሉ መብታቸው ጋር ወደ ማሕበሩ አባልነት እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታው በዋናነት ተጠሪዎች የታገዱት በማሕበሩ የመጨረሻ የስልጣን አካል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፣ተጠሪዎችም የታገዱት በጥፋታቸው በመሆኑ ውሳኔው ሊሻር ይገባል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ከማህበሩ ያለአግባብ ያገዳቸው መሆኑን ጠቀሰው ይኸው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ነው የጠየቁት፡፡ አመልካች ደግሞ በተጠሪዎችን ከማህበሩ ማገዱን ሳይክድ እርምጃው ተገቢ ነው በማለት ነው የሚከራከረው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ በጭብጥነት ሊመለስ የሚገባው ተጠሪዎቹ ለ6 ወር ሊታገዱ ይገባል አይገባም የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነውም ተጠሪዎች ጥፋት አጥፍተዋል በሚል ከማህበሩ የታገዱት ከጥር 25 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ የታገዱትም ለ6 ወራት ስለመሆኑ ተጠሪዎች በክሳቸውም የጠቀሱት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በክርክር ላይ እያለ ግን ተጠሪዎቹ ከማህበሩ የታገዱበት የጊዜ ገደብ አብቅቷል፡፡ ጊዜው ካበቃ ደግሞ እገዳው አግባብ ነው አይደለም የሚለው ነጥብ መወሰኑ ውጤት የሚኖረው አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ አብቅቷልና ነው፡፡ ክሱ በሚቀጥልበት በማንኛውም ጊዜ ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን ፍ/ቤቱ በቂ በሆነ ማስረጃ የተገነዘበው ከሆነ ክሱን ሊዘጋው እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 280 ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የእገዳውን ግዜ በመጠናቀቁና የክሱም ምክንያት በዚሁ ስለተቋረጠ ክርክሩ ሊቀጥል የሚገባበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ሊታገዱ ይገባል አይገባም የሚለውን ፍሬ ጉዳይ መወሰን ሳያስፈልግ መዝገቡን መዘጋቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ት እ ዛ ዝ

ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር ስለተቋረጠ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 280 መሰረት ተዘግቷል፡፡

መዝገቡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36776

መጋቢት 7 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሃይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- መብራቱ፣ ተ/ማርያም፣ ገ/ማርያም የሽርክና ማሕበር - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ መብራቱ ዓንዳይ - የቀረበ የለም

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች ማህበር በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4) መሰረት ውድቅ በመደረጉ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ የማህበሩ ሊ/መንበር ሆነው በሚሰሩበት ወቅት በእጃቸው የገባውን የማህበሩን ቼክ ለግል መኪና መግዣ የከፈሉት በመሆኑ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ገንዘቡ ከባንክ ከተወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪም ክስ የቀረበበትን ገንዘብ አመልካች ቀደም ሲል አቅርቦ በነበረው ክስ አጠቃሎ ሊያቀርበው ሲገባ ሌላ ክስ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216 መሠረት ተገቢ አይደለም የሚል መቃወሚያና በፍሬ ጉዳይ ላይ ሌሎች ክርክሮች አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም የተጠሪን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ ገንዘቡን ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ቀደም ሲል አቅርቦት የነበረው ክስና አሁን ያቀረበው ክስ ተጠሪ የማህበሩን ገንዘብ ለግል ጥቅም አውለዋል የሚል በመሆኑ ተጠቃለው ሊቀርቡ ሲገባ ለያይቶ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 መሰረት ህጋዊ አይደለም በማለት የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ክስ የቀረበበት ጉዳይ አመልካች ቀደም ሲል ካቀረበው ክስ ጋር ተጣምሮ መቅረብ የሚገባው በመሆኑ ተነጣጥሎ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት ተጠሪ ገንዘቡን ከወለድና ከሌሎች ወጪና ኪሳራ ጋራ እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሳኔ መሻሩ ተገቢ ነው በማለት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ሲያፀናው ዳኝነትን አስመልክቶ የተሰጠውን ውሳኔ ብቻ በማሻሻል አመልካች ብር 1,675.00(አንድ መቶ ሺህ ስድስት መቶ ሰባ አምስት ብር) ብቻ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በአቤቱታው ተጠሪ ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) የያዘ ቼክ ለመኪናቸው መግዣ ያዋሉት መሆኑ የተረጋገጠው የመጀመሪያው ክስ ከቀረበ በኋላ በመሆኑ አመልካች ሆነ ብሎ ቀንሶ ያስቀረው ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216(3) መሰረት ክሱ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ መልስና የመ/መልስ በሬጅስትራር ጽ/ቤት በኩል እንዲለዋወጡ የታዘዘ ቢሆን ተጠሪ መልስ ባለማቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸውን አልፈን መዝገቡን መርምረናል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ የነበረው ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ የማህበሩ ሊ/መንበር ሆነው ሲሰሩ በእጃቸው የገባውን ቼክ ለራሳቸው ለገዙት መኪና መክፈያ አውለውታልና ገንዘቡን ከነወለዱ ይመልሱ በሚል ነው፡፡ ተጠሪም በመልሳቸው አመልካች ቀደም ሲል በተመሳሳይ ጉዳይ ክስ ሲመሰርት ይህንኑ ክስ አጠቃሎ ሊከስ ሲገባ ቀንሶ ባስቀረው ገንዘብ ላይ ድጋሚ ክስ እንዳይመሰርት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 የከለክለዋል የሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በመሆኑም የአመልካች ክስ በተጠቀሰው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ወይ የሚለው ጭብጥ ፍ/ቤቱ መርምሯል፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድ ድንጋጌውን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 በአጠቃላይ ስለ ክስ አቀራረብና አገላለፅ የሚመለከት ድንጋጌ ነው፡፡ በተለየ ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 2 እና 3 ነው፡፡ የንዑስ ቁጥር 2 የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር አንድ ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሙሉ አጠቃሎ መቅረብ እንደሚገባ የሚናገር ሲሆን ንዑስ ቁጥር 3 ደግሞ አንድ ከሳሽ ሊከስበት ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረው ሃብት ምክንያት እንደገና ሌላ ክስ ለማቅረብ እንደማይፈቀድለት ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑት ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን ማቅረብ ሲችል ሆነ ብሎ ቀንሶ ባስቀረው ሃብት ላይ ግን ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ እንደማይችል ከድንጋጌዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የማሕበሩ ሊ/መንበር ሆነው በሰሩበት ጊዜ ያለአግባብ ያባከኑትን የማሕበሩን ገንዘብ ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች እኚሁ ተጠሪ የማሕበሩ ሊ/መንበር ሆነው ሲሰሩ በስራቸው ምክንያት በእጃቸው ከገባው የማሕበሩ ገንዘብ ውስጥ ብር 689,306.49(ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ሦስት መቶ ስድስት ብር ከአርባ ዘጠኝ ሣንቲም) ስላጎደሉ ይህንን ገንዘብ እንዲከፍሉ ሚያዚያ 24 ቀን 1997 ዓ.ም ክስ የመሰረተባቸው ስለመሆኑ ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም በሁለቱም ክስ ጥያቄ የቀረበው ተጠሪ የማሕበሩ ሊ/መንበር ሆነው ሲሰሩ ያጎደሉትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በሁለተኛ ክስ የቀረበውን ጥያቄ በመጀመሪያው ክስ አጠቃሎ ሊያቀርበው የሚገባው ነበር፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው ተጠሪው ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) ቼክ ለመኪናቸው መግዣ የከፈሉ መሆኑ የታወቀው የኦዲት ሪፖርት ከተሰራና የመጀመሪያው ክስ ከቀረበ በኋላ በመሆኑ ሆነ ብሎ ገንዘቡን ቀንሶ ክስ መስርቷል ሊባል አይችልም የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ በእርግጥ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(3) ድጋሚ ክስ እንዳይቀርብ የሚከለክለው ከሳሹ ሊከስ ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረው ሃብት ላይ ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ እንዲያስችለው አመልካች ቀደም ሲል ባቀረበው ክስ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያስከፈቱት መዝገብ ቁጥር 33585ን ተመልክቷል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች የመጀመሪያውን ክስ ያቀረበው ሚያዚያ 24 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑን ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ክስ የተመሠረተው የመጀመሪያው ክስ ከቀረበ 10 ቀን ሳይሞላው በ03/09/1997 ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ ተጨማሪ ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) ማጉደላቸው የተረጋገጠው የመጀመሪያው ክስ እንደቀረበና እንዳውም ተጠሪ ለመጀመሪያው ክስ መልስ ሳይሰጡ በመሆኑ አመልካች ክሱን በማሻሻል በዚህ መዝገብ ክስ ያቀረበበትን ጉዳይም አጠቃሎ ሊያቀርብ ይችል ነበር፡፡ ተጠሪ ላይ የሚፈለግ ተጨማሪ ጉድለት መኖሩን የመጀመሪያው ክስ እንደቀረበ ወዲያው ያወቀው በመሆኑ በመጀመሪያው ክስ አጠቃሎ ሊያቀርበው ሲገባ ሁለተኛ ክስ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216(3) መሰረት የማይቻል በመሆኑ በዚህ ምክንያት ክሱ ውድቅ በመደረጉ ተፈፀመ ሊባል የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 22131 የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት የመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44545

መጋቢት 07 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ኒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ክፍሉ መሓሪ - ወኪል ተ/ገብራይ መሓሪ ቀረቡ

ተጠሪ፡- በላይ ከመላ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አቶ ቄሬንሳ ፌይሳ የግል ቤትና ይዞታቸው የሆነውን ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ደስታ ኩምሳ ጋር በመሆን ሐምሌ 21 ቀን 1984 ዓ.ም በተፃፈ ውል ለአመልካች አባት ለአቶ መሓሪ ገ/እየሱስ ሸጠውላቸው ቤቱን ያስረከቧቸው ሲሆን፤ በእጃቸው ያለውን ቤት በስማቸው እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ አድርጐ ባለመቅረቡ የአቤቱታ አቅራቢውን ማስረጃ አጣርቶ ቤቱ በስማቸው እንዲዛወር ሰኔ 08 ቀን 1985 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ውሳኔውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት በመቃወም አቤቱታቸው ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤትም አቤቱታውን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360(2) መሰረት በመሰረዝ ገዥ ሻጭን የመጠየቅ መብት አለው በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የሚገኘው ከወልመራ ወረዳ ግዛት ክልል ወጪ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄን ከመጀመሪያውኑም ቢሆን ተቀብሎ ማስተናገዱ ያለስልጣኑ በመሆኑ ስህተት ነው የሚለውን ምክንያት በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ከዚያም የአሁኑ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤት በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጠቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የፀናውን ውሳኔ በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ነበረው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 15 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት የወረዳው ፍርድ ቤት ስልጣን አለው ብሎ የዞኑ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ከሻረ በኋላ ጉዳዩ ወደ ዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመልሶ እንዲታይ ሳያደርግ መቅረቱ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመረመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐአል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ ታሕሣሥ 06 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ የተፋጠነ ፍትሕ ከማግኘት መብት አኳያ ተገቢ ነው በማለት ውሳኔ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መሰረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ይግባኝ የቀረበለት የምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው ከሥልጣኑ ውጪ ነው በማለት ፍሬ ጉዳዩን ሳይመረምር ውሳኔውን መሻሩን፣የክልሉ ሰበር በበኩሉ የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው በሚል ምክንያት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሲሽር በፍሬ ጉዳዩ ላይ የዞኑ ፍርድ ቤት እንደገና አከራክሮ እንዲወስን ሳያደርግ መቅረቱን፣ይኸው ፍርድ ቤት ዋናውን ጉዳይ ራሱ የመረመረ ስለመሆኑ በግልጽ ሳያስቀምጥ የወረዳው ፍርድ ቤት የወረዳው የፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ የማጽናት ውጤት ያለው ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት የወረዳው ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ የተቀበለበትን ምክንያት አለመግለፁ ወይም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት አለማድረጉ የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የራሱን ውሳኔ ካላሳለፈና የበላይ ችሎቱ የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ካልተቀበለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341፣342፣343 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ተገቢውን መወሰን አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣንን መሰረት አድርጐ የሰጠውን ውሣኔ ከሻረ በኋላ የወረዳው ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ያለምክንያት ማጽናቱ የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበ እና ስነ-ስርአታዊ ያልሆነ ሆኖ አገኝተነዋል፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 49541 ታህሣሥ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በዋናው ጉዳይ ላይ የምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደገና በማየት ተገቢውን ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰንልታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 44883

መጋቢት 8 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሃይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ፈንታ ምህረቱ - ወኪል አልማዝ ፈንታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - አልቀረበም

ፍ ር ድ

አመልካች በም/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ሁለት ቤቶች በመያዣ አስይዘው ገንዘቡን ባለመክፈላቸው ተጠሪ ቤቶቹን ለመሸጥ ማስታወቂያ አውጥቶ ገዢ ባለመቅረቡ ቢበዛ በ3 ወር ውስጥ ሁለተኛ ጨረታ ማውጣት ሲገባው ከሶስት አመት በኋላ በማውጣቱና አንደኛው ቤት ላይ ከህግ ውጪ ለሶስተኛ ጊዜ ጨረታ አዘግይቶ በማውጣቱ ወለዱ ጨምሮ አመልካች ላይ ጉዳት ስለደረሰ ተጠሪ ብር 152,222.40(አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሃያሁለት ብር ከአርባ ሳንቲም) እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ቤቶቹን ለመሸጥ የመጀመሪያው ጨረታ ሲወጣ ገዢ በመጥፋቱ ሁለተኛ ጨረታ የወጣ ሲሆን ቁጥር 276 ለሆነው ቤት ገዢ ባለመቅረቡ ባንኩ ቤቱን የተረከበው ሲሆን ቁጥር 247 ለሆነው ቤት የቀረቡት ተጫራቾች ግን ከቤቱ ግምት በጣም የወረደ ዋጋ በመጥራታቸው ጨረታው ሰዓት ከመድረሱ በፊት ስለተሰረዘ ሁለተኛ ጨረታ እንደወጣ ሊቆጠር አይችልም፣ ድጋሚ ጨረታ ለማውጣት የዘገየው ቤቱን ለመሸጥ ገበያ ሲፈላለግ ነው፣ በሶስት ወር ውስጥ ጨረታ እንድናወጣ የሚያስገድድ ህግ የለም፣ ይርጋ እስካላገደን ጨረታ ማድረግ እንችላለን፣ ወለድ ልከፍል አይገባም የሚለው ተገቢነት የሌለው ክርክር ነው፣ አመልካች ቤቱን እንዲለቁ ቢነገራቸውም እስከ መስከረም 25 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ ይጠቀሙበት ነበር በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን አመልክቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ጨረታውን ሲያካሂድ አላግባብ አዘግይቷል፣ በሁለተኛ ጨረታ ቤቱ ካልተሸጠ መረከብ ነበረበት፣ ተጠሪ በጨረታው መነሻ ግምት ተረክቦ ዕዳውን የሚቃለልበት መንገድ መፈለግ ነበረበት፣ ሶስተኛ ጨረታ መደረጉ ህጉን የተከተለ አይደለም፣ ሁለተኛ ጨረታ እጅግ ቢዘገይ በሶስት ወር ውስጥ መደረግ ነበረበት፣ ጨረታው ከሶስት አመት በላይ ዘግይቶ በመደረጉ በወለድ ምክንያት ከፍ ላለው ዕዳ ኃላፊ ነው በማለት ተጠሪ ብር 112,738.80(አንድ መቶ አስራ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰማንያ ሳንቲም) እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱ ሁለቱን ወገኖች አቅርቦ ካከራከረ በኋላ ከብድሩም ሆነ ከመያዣ ውሉና እነዚህን ከሚመለከቱ ህጎች አኳያ አመልካች ብድሩን ሳይመልሱ ቢቀሩ ንብረቶቹ በአፋጣኝ እንዲሸጡ ለማስገደድ ወይም ቢዘገይ ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ የሚያስችል መብት የላቸውም፣ አዋጁ ጨረታ የሚወጣበትን ጊዜና ቢዘገይ ወለድ መታሰብ እንዲቆም ብሎ አልደነገገም፣ ቤቱም እስከ መስከረም 25 ቀን 1997 ዓ.ም አመልካች እጅ ስለነበር መያዣው ባለመሸጡ ወይም ባንኩ ባለመረከቡ አመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት የለም፣ ለወለዱ መጨመር ብቸኛ ምክንያት አመልካች ብድሩን አለመክፈላቸው ነው፣ ስለሆነም ባንኩ ሃላፊ የሚሆንበት የህግ አግባብ የለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆን ችሎቱ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም በማለት አቤቱታው ውድቅ አድርጎታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው። የአመልካች አቤቱታ በአጭሩ፤ በአዋጅ ቁጥር 97/90 ተጠሪ አመልካችን ወክሎ መያዣውን ሲሸጥ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2211 የተቀመጠውን የወኪልነት ስነ-ምግባር በመከተል ባለእዳው እዳ እንዳይበዛበት ተግቶ መስራት ይገባዋል፣ በአዋጁ አንቀፅ 6 እንደተመለከተው ሊከተል የሚገባውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 394(2) እና 428(2) ወደጎን በመተው ለዕዳው ተመጣጣኝ በሆነ ቤት ላይ ብቻ ጨረታ ማውጣት ሲገባው በሁለቱም ቤቶች ላይ ጨረታ ማውጣቱ፣ በሁለተኛ ጨረታ ካልተሸጡ ከእዳው ጋር ተመጣጣኝ የሆነውን ቤት በመረከብ እዳውን ዘግቶ አንዱን ቤት ነፃ ሊሆን ሲገባ እንዲዘገይ በማድረግ ወለዱ እንዲቆለል ማድረጉ ተረጋግጦ እያለ የጠቅላይ ፍ/ቤትና ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ነው።

ይህ ችሎትም የመያዣ ንብረቶቹን ከረጅም ጊዜ ቆይታ በኋላ ተጠሪ እንዲረከብ ሲደረግ የተከማቸው ወለድ መታሰቡና አመልካች ያቀረቡት የጉዳት ካሳ ጥያቄ ውድቅ መደረጉን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል። ተጠሪም ህዳር 24 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ክርክሩን አቅርቧል። ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል።

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው አበዳሪ ባንኮች ለዕዳው በመያዣ የያዙትን ንብረቶች ሊሸጡ የሚገባበት የጊዜ ገደብ አለ? ወይስ የለም? አለ ከተባለ በጊዜ ገደቡ ውስጥ ንብረቶቹ ባለመሸጣቸው ኃላፊ ሊሆኑ ይገባል? አይገባም? የሚለው ነው።

ለባንክ በመያዣ የተሰጡ ንብረቶችን በተመለከተ በወጣው አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀፅ 3 መሰረት የማንቀሳቀስ ንብረት በዋስትና የያዘ ባለገንዘብ ባንክ ዕዳው ካልተከፈለው ከሰላሳ ቀናት ያላነሰ ማስታወቂያ ለባለዕዳው በመስጠት ንብረቱን በሃራጅ መሸጥ ይችላል። በተጨማሪ የመጀመሪያ ጨረታ አውጥቶ ገዢ ካልተገኘ ሁለተኛ ጨረታ እንደሚወጣና በሁለተኛው ጨረታ ገዢ ከጠፋ ንብረቱን እንደሚረከብ ያመለክታል። ይህን አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 216/92 አንቀፅ 2 ባንኩ ንብረቱን የሚረከበው በመጀመሪያው ጨረታ መነሻ ዋጋ ስለመሆኑ ይናገራል። ከዚህ በቀር ንብረቱ መሸጥ ያለበት መቼ እንደሆነ ወይም ሁለተኛ ጨረታ በስንት ጊዜ ውስጥ መውጣት እንደሚገባ የጊዜ ገደብ ወስኖ አላስቀመጠም።

በሌላ በኩል ባንኩ የሃራጅ ሽያጩን ሲያከናውን አግባብነት ያላቸውን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 394-449 ያሉትን ድንጋጌዎች በመከተል መሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 6 ስር ተመልክቷል። በመሆኑም የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚሸጥበት ሁኔታና ጊዜ የሚመለከቱትን የሥነ-ሥርዓትቱን ድንጋጌዎች መመርመር ተገቢ ይሆናል። ፍርድን ለማስፈፀም የማይንቀሳቀስ ንብረት በሃራጅ ሲሸጥ በቅድሚያ ማስታወቂያ መውጣት እንዳለበት ንብረቱም ሊሸጥ የሚችለው ማስታወቂያ ከወጣ ጀምሮ ለሰላሳ ቀን ቆይቶ መሆኑን የሥነ-ሥርዓት ህጉ አንቀፅ 423(1) እና 426 ተጣምረው ሲነበቡ የሚያስገነዝቡት ጉዳይ ነው። በመጀመሪያ ጨረታ ገዢ ካልቀረበ ባለገንዘቡ ንብረቱን እንደሚረከብ ይናገራል። ከዚህ ውጪ ጨረታዎቹ የሚወጡበት የጊዜ ገደብ የሥነ-ሥርዓት ህጉ ወስኖ አላስቀመጠም። በመሆኑም ባንኩ መብቱን ለመጠየቅ የሚችልበት የጊዜ ገደብ በይርጋ ቀሪ እስከሚሆንበት ድረስ በመብቱ መጠቀም ይችላል። አበዳሪውን ባንክ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ካሳ መጠየቅ የሚቻለው ደግሞ ባንክ ሽያጩን ሲያከናውን አግባብነት ያለውን ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ባለመከተሉ ጉዳት አድርሶ ከሆነ ነው (የአዋጁን አንቀፅ 7 ይመለከቷል)። በተያዘው ጉዳይ ግን ባንኩ ፈፀመ ሊባል የሚችለው የሥነ-ሥርዓት ህግ ጥሰት አለ ማለት አልተቻለም።

ከዚህ በተጨማሪ በተያዘው ጉዳይ ባንኩ ጨረታውን በሚከናውንበት ጊዜ ሁሉ አመልካች ቤቱን ይዘው ይገለገሉበት እንደነበር ያልካዱት ጉዳይ ነው። በመሆኑም በአንድ በኩል አመልካች ቤቱን ይዘው እየተጠቀሙበት በሌላ በኩል ቤቱ ዘግይቶ ስለተሸጠ ጉዳት ደርሷል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም። ምናልባት ባንኩ ጨረታ ሲያወጣ ቤቱን ከአመልካች ተረክቦ በራሱ ይዞታ ስር አድርጎ ቢሆን ሁኔታው የተለየ ሊሆን ይችል ነበር። አመልካች ቤቱን ይዘው በማከራየት ሆነ በሌላ መንገድ በመጠቀም እዳውን ሊያቀሉ የሚችሉበት ሁኔታ ስለሚኖር ባንኩ ቤቱን በቁጥጥሩ ስር አድርጎ እንደገና ጨረታውን ሳያወጣ ቢያዘገይ በአመልካቹ ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል። በተያዘው ጉዳይ ግን ባንኩ ቤቱን እስከተረከበበት ጊዜ ድረስ በአመልካች ይዞታ ስር ስለነበር ጨረታ ዘግይቶ በመውጣቱ አመልካች ላይ ጉዳት አድርሷል ሊባል አይችልም። በአጠቃላይ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካችን ካሳ ሊጠይቁ አይችሉም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ የህግ ስህተት የለውም። በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 12810 ጥቅምት 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 00557 ጥር 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39799

መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢት/መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ማህሌት አለሙ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ገነት ስዩም - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የመድን ሰጪ የክርክር አድማስ አስመልክቶ የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 ጠቅሶ የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት አለው በሚል ነው፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ጣልቃገብ ተከራካሪ ነበር፡፡ የተጠሪ የክስ ምክንያት ንብረትነቱ በሥር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ቴስትድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሆነ መኪና ሰሌዳ ቁጥር 3-13690 ኢት. በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ እየተሽከረከረ በከሳሽ መኪና ሰሌዳ ቁጥር 3-06622 አ/አ ገጭቶ ጉዳት አድርሷል በሚል ለጥገና የወጣ ወጪ እና የተቋረጠ ገቢ እንዲከፍል እንዲወሰን የሚል ሲሆን አንደኛ ተከሳሽ ቀርቦ መድን ሰጪው (አመልካች) በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43 መሠረት ጣልቃ ገብነት እንዲከራከር እንዲታዘዝ አመልክቷል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤትም አመልካች በክርክሩ እንዲገባ ካደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ተከሳሽ እና ጣ/ገብ አላፊ ናቸው ካለ በኋላ የካሣ መጠን አስመልክቶ ለመኪናው ማስጠገኛ የወጣውን ወጪ ብር 44,451(አርባ አራት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ አንድ ብር) እና የተቋረጠ ገቢ በቀን አንድ መቶ(100) ብር ሂሳብ መኪናው ተጠግኖ እስኪጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ተሰልቶ እንዲከፈል በማለት ይህንንም ጣልቃገብ (አመልካች) እስከ ብር አንድ መቶ ሺህ (100,000) በመድን ውል በሰጠው ዋስትና መሠረት እንዲሸፍን ቀሪውን አንደኛ ተከሳሽ (ባለንብረት) እንዲከፈል ፈርዷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) መሠረት በተከሳሽ ጠያቂነት ወደ ክርክሩ የገባ መሆኑን በመጥቀስ ጣልቃገብ ከተከሳሹ ጋር ያለውን ኃላፊነት ከመከራከር ውጪ ተከሳሽን ተክቶ ከከሳሽ ጋር መከራከር አይችልም በማለት በአመልካች በኩል ቀርቦ የነበረውን የሕግ እና የፍሬ ነገር ክርክር ሳይመረምር የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን አፅንቷል፡፡

አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በፌዴራል መንግሥት የተመዘገበ ድርጅት በመሆኑ በአዋጅ 25/88 አንቀጽ 5(6) መሠረት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም ሲል አቤቱታውን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ለዚህ የቀረበው የሰበር አቤቱታ በዚሁ ላይ ሲሆን አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች የሕግ እና የፍሬ ነገር ስሕተት ያላቸውን ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ተጠሪን አስቀርቦ ሰምቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩን ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት እልባት ሊያገኝ የሚገባው ጭብጥ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) አተረጓጎም አግባብነት እና የአመልካች የክርክር አድማስ(ወሰን) እስከምን ድረስ ነው የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረቱ አመልካች ወደ ክርክሩ የገባው በሥር ፍ/ቤት ተከሳሽ ከነበረው ባለንብረት ጋር ባለው የመድን ውል መሠረት እንደሆነ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡ አንድ ተከሳሽ ከእሱ ጋር ኃላፊነት ሊወስድ ወይም ሊከፈል የሚችል ሦስተኛ ወገን ወደ ክርክሩ እንዲገባለት እንዲታዘዝ ማመልከት እንደሚችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ በዚህ ጥያቄ መነሻ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገ ተከራካሪ ወገን በክርክሩ ውስጥ ሊያነሳ የሚችለው የኃላፊነት እና የኃላፊነት መጠን አስመልክቶ የክርክሩ ዘንግ ከተከሳሽ፣ ከከሳሽ ወይንስ ከሁለቱም ወገን ጋር ሊሆን ይገባል የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ በሁለት አቅጣጫ ምላሽ ሊያገኝ እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም የጣልቃገብ ኃላፊነት ምንጭ ውል ወይንስ ሕግ የሚለው በመሠረታዊ ሕግ ድንጋጌዎች የሚወሰን መሆኑ እና በሌላ በኩልም የክርክሩ አቀራረብ እና ይዘት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በተደነገገው አግባብ መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመድን ሰጪ ኃላፊነት መሠረቱ ውል መሆኑ እሙን ነው፡፡ መድን ሰጪ የሚኖረው መብት እና ግዴታ በውል የተመለከተ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በመሠረታዊ ሕጉ የተደነገጉትን አስፈላጊ እና አስገዳጅ ሁኔታዎችንም መጠበቅ ያለበት ስለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገው ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ሂደት ሊያነሳ የሚችለው ክርክር ምን ድረስ ነው የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ አስመልክቶ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 23692 የሰጠውን የህግ ትርጉም መመልከት አግባብ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በተጠቃሹ መዝገብ ላይ የክርክሩ ተካፋይ ሦስተኛ ወገን የሚያቀርበው ክርክር ሁለት ፈርጅ ሊይዝ የሚችል መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይኸውም “አንደኛው ከተከሳሽ ጋር ሆኖ ድርሻ ክፍያ ወይም ስለተከሳሽ ሆኖ የካሣ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተቀብሎ በተከሳሽ እግር በመተካት ተከሳሽ ለከሳሽ ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን፤ ኃላፊነት አለበት እንኳ ቢባል ሊከፈል በሚገባው የካሣ መጠን ላይ ከከሳሽ ጋር ንጥጥር ማድረግ፤ መሟገት የሚችልበት ክርክር ሲሆን ሌላው እና ሁለተኛው ደግሞ ድርሻ ወይም ካሣ ለመክፈል ለተከሳሽ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መከራከር የሚችልበት መንገድ ነው፡፡” ስለሆነም የድንጋጌው ይዘት ጣልቃገብ ሦስተኛ ወገን ተከሳሽ በክርክሩ ከገባ በኋላ መሟገት የሚችለው ከተከሳሽ ጋር እንጂ ከከሳሽ ጋር ለመከራከር የሚያስችለው መብት የለውም የሚለው ድምዳሜ የሕግ መሠረት የለውም የሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ 23692 ላይ ይህንን ትርጉም ለመስጠት መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ እና የሙግት አመራር ውጤታማነት እንዲሁም የድንጋጌ ቁጥር 43(1) እና 76 እንዲሁም የመሠረታዊ ሕጉ ድንጋጌዎች ውስጥ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1896፣ 1897፣ 1908 እና 1909 አፈጻጸም እንዲሁም በንግድ ሕግ ቁጥር 687,688 እና 683 ድንጋጌዎች በክርክር አመራር ረገድ የሚፈፀሙበትን ሁኔታ እና ግብ መነሻ በማድረግ መሆኑ በፍርዱ ሀተታ ተገልጿል፡፡ ለማጠቃለል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 43 አስፈላጊነትም ተከታታይ ክስ ሳይኖር በአንድነት እንዲታይ በማድረግ የኃላፊነት እና መጠኑን እንዲሁም ከፋዩን ወገን በመለየት የመጨረሻ እልባት መስጠት ማስቻል እንደመሆኑ በተለይ ካሣ (indemnity) የመክፈል ግዴታ ያለበት አመልካችን መሰል የመድን ድርጅት ከከሳሹ ጋር ያለውን አጠቃላይ ክርክር ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ በውሳኔው ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉም እስካልተለወጠ ድረስ በማናቸውም ድርሻ በሚገኙ ፍ/ቤቶች አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(4) ሥር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ከተከሳሽ ጋር እንጂ ከከሳሽ ጋር መከራከር አይችልም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) በመጥቀስ የሰጠው ፍርድ በፈዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ፍርዱ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህም አመልካች በክርክሩ ሊያነሳ የሚችለው የኃላፊነት እና የኃላፊነት መጠን ከተከሳሽ ጋር ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ከከሳሽ ጋር ሊሆን እንደሚችል የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁ 43(1) ይዘት እና የሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም ያስገነዝባል፡፡ በዚሁ መሠረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 47210 መጋቢት 25/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከከሳሽ ጋር በሕግም ሆነ በፍሬ ነገር ረገድ መከራከር የሚችል በመሆኑ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ መዝገቡን አንቀሳቅሶ ይግባኝ ክርክሩን ተመልክቶ የመሰለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 343(1) መሠረት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው ብለናል፡፡ የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43845

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ጌታይዳ ኃ/የተ/የግል ማህበር - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያላግባብ የተከፈለ ቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባሁኑ አመልካች ላይ መጋቢት 07 ቀን 1998 ዓ.ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ ድርጅት ሄርታለን ከሚባል የኔዘርላንድ ድርጅት የፈሳሽ መከላከያና ተዛማጅ እቃዎችን በአምራቹ የመሸጫ ዋጋ መሰረት የጉምሩክ ቀረጥን እየከፈለ ሲያስገባ መቆየቱንና በሦስት የተለያዩ ጊዜያት ከከፈላቸው ክፍያዎች ውስጥ ድምሩ ብር 60,858.82(ስልሳ ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ስምንት ብር ከሰማንያ ሁለት ሳንቲም) የሆነውን ገንዘብ ያላግባብ አመልካች ማስከፈሉንና ይኸው ያላግባብ የተከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ተጠሪ ጥያቄ ቢያቀርብም አመልካች ፈቃደኛ አለመሆኑን በመዘርዘር ክሱ የተመሰረተበትን ገንዘብ ያለአግባብ ከተከፈለበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድና ከክሱ ወጪና ኪሣራ ጋር አመልካች እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር ነጥቦችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የአመልካችን ምስክሮች መስማት አስፈላጊ አለመሆኑን ገልፆ ጉዳዩን በመመርመር የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጐ ለክሱም ኃላፊ በማድረግ ክሱ የተመሰረተበትን ገንዘብ ክሱ ከተመሰረበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ 9%(ዘጠኝ በመቶ) ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የስር ፍርድ ቤት ይርጋን በተመለከተ የቀረበውን መቃወሚያ ማለፉም ሆነ የአመልካችን ምስክሮችንም ሳይሰማ መቅረቱ ያለአግባብ ሆኖ የደረሰበት ድምዳሜም የአዋጅ ቁጥር 68/89 አንቀጽ 48/7/,/11/ እና መመሪያ ቁጥር 10/1996 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን የሚፃርር በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አግባብነት ገልጸው ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የአመልካች ምስክሮች ሳይሰሙ ውሳኔ መሰጠቱ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ክሱን ሊመሰርቱ የቻሉት ያላግባብ የከፈልኩት የቀረጥ ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በሚል ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ክፍያውን ያስፈጸመው በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የዋጋ መረጃን በማየት መሆኑን ገልፆ ያላግባብ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋጋ መረጃ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ጉዳዩን ለማስረዳት የተቆጠሩት ምስክሮችንም መስማቱ አስፈላጊ አለመሆኑን ገልፆ አመልካች በተጨማሪነት የወሰደውን የቀረጥ ገንዘብ ባግባቡ የወሰደ መሆኑን፣አላስረዳም በሚል ምክንያት ክርክሩን ውድቅ ማድረጉን ነው፡፡

የጉምሩክ ባሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም እና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 47 ላይ እንደተመለከተው ወደ ሐገር ውስጥ ለሚገባ ማናቸውም እቃ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሚሆነው በትክክል ለእቃው የተደረገ ጠቅላላ ወጪ ነው፡፡ እቃው የተገዛበት ዋጋ ደግሞ ከወጪዎች አንዱ ነው ስለሆነው ለቀረጥ ማስከፈያ መሰረት የሚሆነው ትክክለኛ የእቃው ዋጋ ስለመሆኑ ሕጉ በዋናነት ያስቀመጠው አስራር ነው፡፡ ከዚሁ የሕጉ መንፈስ መረዳት የሚቻለው ሌላው ቁም ነገር ደግሞ በአስመጪው የሚቀርበው የእቃው ግምት ትክክለኛውን የእቃውን ዋጋ የማይናገር መሆኑ ከተረጋገጠ የቀረጥ ሂሳብን ለማስላት መነሻ(መሰረት) ሊሆን የማይችል መሆኑን ነው፡፡ በመሰረቱ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ እቃ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነና እንዴት እንደሚሰራ በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 48 ስር ተዘርዝሯል፡፡ የተጠቀሰው የአዋጅ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 7 እና 8 ድንጋጌዎች ሲታዩም የጉምሩክ ባለሥልጣን ባስመጪው የቀረበለትን የዋጋ ግምት አልቀበልም በማለት የቀረጥ ሂሳቡን ለማስላት ሌሎች አማራጭ መንገዶችን መከተል የሚችል ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ የተጠቀሰው የአዋጅ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 6 ድንጋጌ ደግሞ፤የጉምሩክ ባለስልጣን በአስመጪዎች የቀረበለትን የዋጋ ግምት አልቀበልም ስለሚልበት ሁኔታ የገቢዎች ቦርድ መመሪያ ማውጣት የሚችል መሆኑን ደንግጓል፡፡ በዚሁ ሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረትም የተጠቀሰው አካል መመሪያውን ማውጣቱ የተረጋገጠ ሲሆን በዚህ መመሪያ መሰረትም በትራንዛክሽን ዋጋ ላይ የተመሰረተ የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ተግባራዊ የማይሆንባቸው ምክንያቶች ተቀምጠዋል፡፡ ከነዚህም ምክንያቶች መካከል ወደ ሐገር ውስጥ የገባው እቃ ዋጋ ከአንድ ዓይነት እና ከተመሳሳይ እቃዎች ዋጋ በጉምሩክ ከተፈቀደው ልዩነት በላይ እንሶ መገኘት ስለመሆኑ መመሪያው በአንቀጽ 1/5/ ስር አስቀምጧል፡፡ ወደ ሃገር በገባ ወይም ከሐገር በወጣ እቃ ላይ የተከፈለው ቀረጥ በማናቸውም ምክንያት ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥ ያነሰ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ደግሞ ባለሥልጣኑ የእቃውን ባለቤት ወይም ወኪሉን በልዩነት ያልተከፈለውን ቀረጥ ማስከፈል እንደሚችል በአንቀጽ 57/1/ ስር በግልጽ አስፍሯል፡፡ በሌላ በኩል በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለክፋዩ ሊመለስ እንደሚገባ አዋጁ በአንቀጽ 55 ስር በግልጽ ደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀረጡን አስከፈልኩ የሚለው በመመሪያ ቁጥር 10/1996 መሰረት ስለመሆኑ፣በዚህ መመሪያ መሰረት የተፈፀመ ስለመሆኑ ደግሞ የሚያስረዱት ምስክሮች ያሉት ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ዘርዝሮ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ አመልካች የቆጠራቸውን ምስክሮች መስማት አስፈላጊ አይደለም ብሎ ከለለፈ በኋላ አመልካች ክርክሩን በማስረጃ አላስረዳም በማለት ለክሱ ኃላፊ አድርጐታል፡፡ በአርግጥ በተከራካሪ ወገን የተቆጠረውን ምስክር ሁሉ ፍርድ ቤቱ እንዲሰማ የማይገደድ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ-ስርአት ሕጉ ስለማስረጃ አቅራረብ እና አቀባበል የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝበን ነጥብ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ስልጣኑን መተግበር ያለበት በዘፈቀደ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሆኑም በተከራካሪ ወገን የተቆጠሩት ምስክሮች ሳይሰሙ የሚቀሩት ለጉዳዩ የሚሰጡት ምስክርነት አግባብነት የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ምስክሮች ሊያስረዱ ይገባል የተባለው አመልካች በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን ባግባቡ በመጠቀም የተጠሪን ጥያቄ ያልተቀበለው ስለመሆኑ እና በመመሪያ ቁጥር 10/1996 መሰረት ብልጫ ቀረጥ የተባለው አለመከፈሉን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በምስክሮች የሚሰጠው ቃል ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው ለማለት የሚያስችል አለመሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ ሳይሰማ ደግሞ ማስረጃውን የቆጠረው ተከራካሪ ክርክሩን በማስጃ አላስደገፈም ሊባል አይችልም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመራው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48 እና መመሪያ ቁጥር 10/1996 እንዲሁም በፍትሐብሔር ስነ ስርአት ሕጉ ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ባገናዘበ መልኩ ባለመሆኑ የፍርድ አካሄዱ የተሟላ ነበር ለማለት አልተቻለም፡፡ የፍርድ አካሄድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይሟላ የተሰጠ ፍርድ ደግሞ የሕግ ሥርአቱን ያልጠበቀ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 66236 ሐምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 59649 ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ቀረጡን ያስከፈለበትን ሁኔታ ለማስረዳት የቆጠራቸው ምስክሮች ተሰምተው እና ሌላም ተገቢ ነው የተባለ ሁሉ ተፈጽሞ በጉዳዩ ላይ እንደገና ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው በመሆኑ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ምስክሮችን በመስማት ጉዳዩን እንደገና አይቶ ይወስን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. እስከአሁን ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44931

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሰዓዳ ኢድሪስ - ወኪል አደም እንድሪስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ረሺድ ቡባ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥነ-ሥርአት ህጉን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በድሬዳዋ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከአውራሻቸው ከወ/ሮ ሉላ መሐመድ በኑዛዜ ያገኘሁትን ቤትና ቦታ የመሬት ልማት ባለስልጣን (የስር አንደኛ ተከሳሽ) መብት ሳይኖረው አሳልፎ ለአመልካች ስለሰጠ ተከሳሾቹ ቤቱና ቦታውን እንዲያስረክቧቸው እንዲወሰንላቸው አመልክተው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የከሳሽ አውራሽ ራሳቸው በቤቱ ላይ መብት የነበራቸው ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጐታል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ የስር ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ የቤቱን ካርታ ቁጥር 6001 ከማለት ፋንታ 001 ብሎ ስለመዘገበው ይኸው የቁጥር ስህተት እንዲታረም ለስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት አመልክተው ፍ/ቤቱ የቁጥሩን ስህተት አርሟል፡፡ ተጠሪም ይህን ትእዛዝ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል በድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ውድቅ የተደረገባቸውን መዝገብ ያንቀሳቅሳሉ፡፡ ፍ/ቤቱም የተዘጋውን ይግባኝ ከቀረበው ማስተካከያ አንፃር ለመመረመር ይግባኙ አመልካችን ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ቤቱ ላይ መብት አላቸው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካችም የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት የዘጋውን የይግባኝ መዝገብ የስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት የሰጠውን እርምት መሰረት በማድረግ እንቀሳቀሶ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ ሥነ-ሥርአት ሕግ ስህተት ነው የሚልና ሌሎች ቅሬታዎች አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ ነጥብ ለመመርመር ሲል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል የስር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የመሬት አስተዳደር የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በሰበር መ/ቁ. 45172 የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም መዝገቡ ከመ/ቁ. 44931 ጋር እንዲታይ ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ በሁለቱ መዝገቦች የቀረበው ጉዳይ ተመሳሳይ በመሆኑም ችሎቱ ሁለቱንም መዝገቦች አጣምሮ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

ተጠሪ የድሬዳዋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኞቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 መሰረት ተዘግቶ መዝገቡ የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ ከማቅረብ ይልቅ የወሰዱት አማራጭ ውሳኔ እንደገና እንዲታይላቸው ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማመልከትን ነው፡፡ ተጠሪ ውሳኔ ያገኘው ጉዳይ እንደገና እንዲታይላቸው ያመለከቱትም የስር ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ የቤቱን ካርታ ቁጥር አሳስቶ የፃፈው መሆኑን በመግለጽ ቁጥሩ እንዲታረምላቸው ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የተሰጠው የማስተካከያ ትእዛዝ መሰረት አድርገው ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ማስተካከያ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ለመሻር ወይም ለማረም ሥልጣን ይሰጠዋል ወይ? የሚለው መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንድ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ ውሳኔው የሚታረመው የይግባኝ ቅሬታ በማቅረብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/1/ እና 348/1/ አገናዝቦ በማንበብ መረዳት ይቻላል፡፡ በእርግጥ በተሰጠ ፍርድ ላይ ይግባኝ ማለት የሚቻል ቢሆንም ውሳኔውን የሰጠው ፍ/ቤት በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ፍርዱን ለማረም ወይም ለማሻሻል ወይም እንደገና ለማጣራት የሚችል ከሆነ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው የኸው ስርዓት ከተፈፀመ በኋላ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320/2/ ያመለክታል፡፡ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤትም የሰጠውን ፍርድ በድጋሚ አይቶ ፍርዱን የሚያርምበት የተለያዩ ሥርአቶች በስነ-ሥርዓት ሕጉ ውስጥ ተካተዋል፡፡ ለምሳሌ በክርክሩ ውስጥ ከሥነ-ሥርአት ውጪ የሆነው ጉዳይ ሲኖር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 209 መሰረት አቤቱታ ሲቀርብ ወይም ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 መሰረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ አቤቱታ ሲቀርብ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት ጉዳዩን በድጋሚ ማየት ይችላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በድጋሚ አይቶ የለወጠው ከፍ ሲል እንዳየነው ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ማስተካከያ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በተሰጠው ፍርድ፣ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ የቁጥር አሳሳፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ ቃል ስህተት መኖሩን ሲረጋገጥ ስህተቱ የሚታረምበትን ስርአት የዘረጋ ድንጋጌ ነው፡፡ በድንጋጌውም እንዲታረም የተፈቀደው የውሳኔውን ይዘት ሊቀይሩ የማይችሉ መሰረታዊ ያልሆኑ የጽህፈት ወይም የቁጥር ስህተቶች ወይም ግድፈቶች ብቻ ናቸው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የካርታ ቁጥሩ መስተካከል ውሳኔውን ሊያስቀይር የሚችል ነው በማለት መዝገቡን ለማንቀሳቀስ የሚችልበት የስነ-ሥርዓት ሕግ የለም፡፡ በመሰረቱ በስር ፍ/ቤት የተጠሪ ክስ ውድቅ የተደረገው ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት እዳንለኝ ያስረዳልኛል ያሉት የቤት ካርታ በስር ፍ/ቤት ቀርቦ ታይቶ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በመጀመሪያ ይግባኙን ውድቅ ሲያደርግም ይህንኑ ሰነድ ተመልክቶ ነው፡፡ የካርታው ቁጥር በመሳሳቱ በውሳኔው ላይ ያስከተለው አሉታዊ ውጤት ስለመኖሩም በተጠሪም በኩል ሆነ በድጋሚ ጉዳዩን ባየው የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰጠውን መጨረሻ ውሳኔ በድጋሚ አይቶ እንዲያርመው ስልጣን የሚሰጠው የሥነ-ሥርአት ሕግ የለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት የሰጠው የቁጥር ማስተካከያ ትእዛዝን ብቻ መሰረት በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ በድጋሚ አይቶ መሻሩ መሰረታዊ የሥነ-ሥርአት ስህተት ነው፡፡

ው ሳ ኔ

1. የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00248/2001 መጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቀደም ሲል ውድቅ ያደረገውን የይግባኝ ቅሬታ ያለህጋዊ ምክንያት በድጋሚ አይቶ ውሳኔውን መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመ/ቁ. 45172 ጋር ይያዝ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48237

መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሰኢዳ ሁሴን ይመር

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 480 ስር የተመለከተውን መሰረት በማድረግ ያስተላለፈውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ነሐሴ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ስላመለከቱ የቀረበ ነው፡፡ አመልካች በጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉት አመልካች ፈፀሙ የተባሉት ድርጊት ስለመፈፀሙ በአሳማኝ ማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን፣ ድርጊቱ ስለመፈፀሙ ከችሎቱ ውጪ ሌላ ምርመራ ተከናውኖ ባግባቡ ሊጣራ ይችል የነበረ እንጂ ለውሳኔው መሰረት የሆነውን ድንጋጌ የማያሟላ መሆኑን፣ ችሎቱ የአመልካችን መከላከያ ማስረጃዎችን የመዘነበት አግባብ የማስረጃ አሰማም እና ምዘና ሥርዓትን ያልተከተለ መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር ነው፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ ለአቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሶሪቲ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ጋር በነበረባቸው የፍትሐብሔር ይግባኝ ክርክር ጉዳዩ ገና በምርመራ ላይ ባለበት ሁኔታ ጉዳዩ አልቋል፣ አስጨርሼአለሁ፣ የተፈረደላችሁን ገንዘብ አታገኙም፣ ጉዳዩን ለማስጨረስ ከዳኞች ጋር ተነጋግሬ ገንዘብም ከፍያለሁ እያሉ ስለመናገራቸው ለጉዳዩ መልስ ሰጪ የነበረው ሶሪቲ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ባቀረባቸው ማስረጃዎች ተረጋግጧል ተብሎ እና ይህ አድራጎት ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 480 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያሟላል በሚል ነው፡፡ አመልካች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ድርጊቱ ስለመፈፀሙ የሰማቸው ምስክሮች ቃል ክብደት ተሠጥቶ በአንፃሩ የአመልካች ምስክሮች ቃል ክብደት ውድቅ ያደረገው ያላግባብ ነው፣ ድርጊቱ ስለመፈፀሙ በቂና አሳማኝ ማስረጃ አልቀረበብኝም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት በቂ ማስረጃ አስቀርቦ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ቃል በመመዘን የወሰነ መሆኑን ስለተገነዘብን እና ይህ ችሎት የማስረጃ ምዘናን በተመለከተ ስልጣን የሌለው በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር የምንቀበለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ሌላው ነጥብ፤ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 480 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የማያቋቁም፣ ራሱን የቻለ ምርመራ ሊደረግበት የሚችል እንጂ ችሎቱ በራሱ ወዲያውኑ በቀጥታ ቅጣት እንዲያስተላልፍ ስልጣን የሚሰጠው አይደለም በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 480 ይዘት ሲታይ የማንኛውም ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ የፍርድ ቤቱን የዳኝነት ስራ አካሔድ ስነ ስርዓት ለማስከበር ማናቸውንም አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል፣ ይህንንም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማስፈፀም ለፍርድ ቤቱ ችሎት ክብር ወይም ለዳኝነቱ ሥነ-ሥርዓት መልካም አመራር ተቃራኒ የሆነ ጠባይ የሚያሳየውን ማናቸውንም ተከራካሪ ወገን ወይም ጠበቃ ወይም በችሎቱ ውስጥ የሚገኘውን ማናቸውንም ሰው ተቃራኒ ተግባር በሰራበት ጊዜ በያዘው መዝገብ ላይ የገንዘብ መቀጮ ሊወስንበት የሚችል ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ ድንጋጌው በፍርድ ቤቱ እይታ ውስጥ ወይም ፊት ለፊት የተፈፀሙ፤ የፍርድ ቤቱን ስራ የሚያውኩ ተግባሮችን ማስቆም፣ አስፈላጊ እርምጃዎች እንዲወሰድ ለፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ በቀጥታ የመወሰን ስልጣን የሚሰጥ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ የድንጋጌው አስፈላጊነትም ተከራካሪ ወገኖችም ሆኑ ማናቸውም ግለሰብ የሚፈፅሟቸው ተግባሮች የፍርድ ቤትን ሥርዓትና ክብር የሚያናጉ፣ ህብረተሰቡ በፍርድ ቤት ላይ ያለውን አመኔታ የሚቀንሱ ከሆነ ማስወገድ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሶሪቲ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ጋር በነበረባቸው የፍትሐብሔር ይግባኝ ክርክር ጉዳዩ ገና በምርመራ ላይ ባለበት ሁኔታ ጉዳዩ አልቋል፣ አስጨርሼአለሁ፣ የተፈረደላችሁን ገንዘብ አታገኙም፣ ጉዳዩን ለማስጨረስ ከዳኞች ጋር ተነጋግሬ ገንዘብም ከፍያለሁ እያሉ ማስወራታቸው በሚገባ በማስረጃ ተረጋግጦባቸው ነው፡፡ ይህ አድራጎት የዳኝነትን ክብርን፣ የዳኝነት አስተዳደርን የሚነካ፣ ሕብረተሰቡ በፍርድ ቤቱ ላይ እምነት እንዳይኖረው የሚያደርግ ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያስወሩት ተግባር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 480 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚያሟላ ነው በማለት አመልካችን ወዲያውኑ በቀጥታ በያዘው መዝገብ ጥፋተኛ በማድረግ በብር 10,000.00(አስር ሺህ) መቅጣቱ ሕጋዊ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሆኖ ስላላገኘነው ውሳኔው ሊፀና የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42643 ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የሠጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 50022

መጋቢት 29 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 5 ብራዘርስ ኃ.የተ.የግል ማህበር - ክበበው ደስታ ቀረበ

ተጠሪ፡- ዓብደላ ኢብሮ ዮሴፍ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ቀደም ሲል በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ እንድገባ በማለት ያቀረብኩት ጥያቄ ከሕግ ውጪ ተቀባይነት አጥቶአል በማለት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ተጠሪ በአመልካች እና ሰሎሞን ጀንበሩ በተባለው ግለሰብ ላይ ክስ መስርቶ የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው አስወስኖአል፡፡ ተጠሪ ክሱን የመሠረተው በሰሎሞን ጀምበሩ ሹፌርነት ሲሸከረከር የነበረው የአመልካች ንብረት የሆነው መኪና ገጭቶ ጉዳት አድርሶብኛል በማለት ሲሆን፣ በፍ/ቤቱ የታዘዘለትን መጥሪያ ለማድረስ ሞክሮ ተከሳሾችን ማግኘት እንዳልቻለ ለፍ/ቤቱ በመግለጹም ፍ/ቤቱ መጥሪያው በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ እንዲለጠፍ በማለት ምትክ የመጥሪያ አደራረስ ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ ከዚህ በኋላም ተከሳሾች ተጠርተው አልቀረቡም በማለት ክርክሩን ተከሳሾች በሌሉበት ሰምቶ ውሳኔውን ሰጥቶአል፡፡ አመልካች ከዚህ በኋላ ነው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ አቤቱታ ያቀረበው፡፡ አቤቱታው የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግን አቤቱታውን ባለመቀበል ብይን የሰጠ ሲሆን፣ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ብይኑን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በአግባቡ ተጠርቶ ሳይቀርብ ቀርቶአል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78 መሠረት የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከቀረበልን ክርክር፣ የሥር ፍ/ቤቶች ከሰጡት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተካሄደው ክርክር እና ፍ/ቤቶቹ ከሰጡት ውሳኔ መገንዘብ እንደቻልነው መጥሪያው በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ እንዲለጠፍ ምትክ የመጥሪያ አደራረስ ትዕዛዝ የተሰጠው ተጠሪ የአመልካችን አድራሻ አላውቅም በማለቱ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን አመልካች የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.97 በተመለከተው አይነት መጥሪያው እንዲደርሰው ስለመታዘዙ ወይም በዚህ መሠረት ትዕዛዙ ተላልፎ ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆን ስለመቅረቱ በተመለከተ ምንም የተባለ ነገር የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ ተጠሪ አመልካችን ፈልጎ ለማግኘት ያልቻለው መጥሪያውን በየትኛው አድራሻው ወስዶ ፍለጋ አድርጎ እንደሆነ አልተረጋገጠም፡፡ አመልካች የንግድ ድርጅት (ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር) ስለሆነ ተመዝግቦ ንግዱን የሚያካሂድበት መስሪያ ቤት ወይም ጽ/ቤት እንዳለው ይገመታል፡፡ ተጠሪ ጉዳቱን ያደረሰበት መኪና የአመልካች ንብረት መሆኑ እስካወቀ ድረስ አድራሻውን ማወቅ አይችልም ማለትም የሚያስችግር ነው፡፡

ተከሳሽን በአግባቡ መጥራት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከተቀመጡት የመስማት መብት ከሚረጋገጥባቸው መርሆዎች አንዱ ነው፡፡ ይህን መርህ ባለመጠበቅ የሚሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ በሕጉ አግባብ እንደተሰጠ አይቆጠርም፡፡ በመሆኑም ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ወደጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ ተከሣሹን ባለዕዳ የሚያደርግ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሹን በአግባቡ ስለመጠራቱ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ክሱን የሰማው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.95(3) እና 97 በተደነገገው መሠረት መጥሪያው ለአመልካች ስለመላኩ አላረጋገጠም፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.105 መሠረት ምትክ የመጥሪያ አሰጣጥ ትዕዛዝ የሰጠው በአግባቡ አልነበረም፡፡ ሲጠቃለል ፍ/ቤቱ አመልካችን በሕጉ አግባብ መሠረት እንዲጠራ አድርጎአል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ሁኔታው ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78(1) መሠረት ያቀረበለትን ጥያቄ አልቀበልም የሚልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ጥያቄውን ውድቅ በማድረጉም የአመልካችን የመከራከር መብት የሚጎዳ ውሳኔ ሰጥቶአል ለማለት የሚቻል በመሆኑ ውሳኔው በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 12201 ሰኔ 3 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 04822 ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78(1) መሠረት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ክሱ አመልካች ባለበት ይሰማ ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችን ወደ ጉዳዩ በማስገባት ክሱን እንደገና ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ብለናል፡፡ ይጻፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45038

መጋቢት 23 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ኒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ዓለሚቱ ጓዱ - ቀረቡ

2. አቶ ዋስ ጓዱ - አልተጠሩም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስረስ አህመድ ወ/አበባ ጓዱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች የውርስ ንብረት ከተጠሪ ለመካፈል ያቀረቡትን የአፈፃፀም ክስ የተመለከተው የምሥራቅ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በብቸና ከተማ የሚገኘው ድርጅት እና መኖሪያ ቤት በአፈፃፀም ተከሳሽ ሳይሆን በሌላ ሦስተኛ ወገን ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ ማዘጋጃ ቤቱ ማረጋገጫ ሰጥቷል በሚል የአመልካቾችን የአፈፃፀም ጥያቄ ሌላ ንብረት አፈላልገው ያቅርቡ በሚል ተዘግቷል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

ለዚህ ሰበር ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ አከራካሪው ንብረት ውሳኔ ያፈረበት መሆኑን ጠቅሰው የአፈፃፀም ሂደት ለማሰናከል ተጠሪ በተንኮል በልጃቸው ስም ያዛወሩ ስለመሆኑ ገልፀው ቀደም ሲል በተወሰነው መሰረት እንዲፈጸም እንዲታዘዝ አመልክቷል፡፡

ሰበር ሰሚ ችሎትም መዝገቡን መርምሮ ውሳኔ ያረፈበትን ቤት በተጠሪ ሳይሆን በሌላ ሰው ስም ነው በሚል አመልካቾች ሌላ ንብረት እንዲጠቁሙ መታዘዙ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪ ህዳር 8/2002 ዓ.ም በጽሑፍ ባቀረቡት መልስ ወ/ሮ አበባ ደርሰሐ በስሟ አዘዋውራ የያዘቸው ቤት በተመለከተ ተጠሪ የፈጸሙት ተንኮል የሌለ ስለመሆኑ የቤቱም መገምት ባለመብት እንደማያደርግ እንዲሁም በብቸና ከተማ ቀበሌ 02 አዲስ ገበያ ተብሎ በሚጠራ የድርጅት ቤት የወ/ሮ ዘምዘም ጓዱ ደርሰህ የግል ሐብት ስለመሆኑ እና የቤት ቁጥር 772 የወ/ሮ አበባ ጓዱ ደርሰህ በሰሟ አዛውራ ይዛ የምትገኝ መሆኑን ዘርዝረው ተጠሪ ኃላፊነት የሌለባቸው ስለመሆኑ አጥብቀው ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም በመልስ መልሳቸው በልጆቻቸው ስም ያዛወሩዋቸው ንብረቶች ውሳኔ ያረፈባቸው መሆን ጠቅሰው ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡ እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ከሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አንፃር መርምረናል፡፡ ስለዚህ የአፈፃፀም ክርክር መነሻ የሆነው ውሳኔ በም/ጐጃም ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 2284 በ2/13/98 ዓ.ም የተሰጠው መሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ከዚህ ውሳኔ ይዘት መረዳት የተቻለው አንደኛ በአዲሱ ገበያ አካባቢ የሚገኝ የድርጅት ቤት ቁጥር አዲስ በአቶ ጓድ ደርሰህ ስም መሆኑ፤ ሁለተኛ በብቸና ከተማ 02 ቀበሌ ከድሮ ገበያ አካባቢ የሚገኘው መኖሪያ ቤት በወ/ሮ አበባ ጓድ ስም መሆኑ እና በሦስተኛ ደረጃ ከብት ገበያ መሔጃ መንገድ ያለው ቤት በወ/ሮ አስረስ አህመድ ስም ያለ መሆኑ ተጠቅሶ ከማዘጋጃው በተሰጠ ማረጋገጫ መሰረት ወደ ከብት ገበያ መሔጃ የሚገኘው ቤት የውርስ ንብረት ሆኖ ግራ ቀኙ እንዲከፋፈሉ መወሰኑን ነው፡፡ እንዲሁም በሚች ስም የሚታወቅ ድርጅት ቤት ከገበያ አካባቢ የሚገኝ እንዲካፈሉ መወሰኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ውሳኔ መነሻ አፈፃፀም ላይ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ውሳኔ ያረፈበትን ቤት እና ድርጅት ተጠሪ ከውሳኔው በኋላ በልጆቻቸው ስም አዛውረዋል የሚል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት በተጠሪ ስም ያለ አንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መኖሪያ ቤት እና በሚች ስም ያለ አንድ ድርጅት ቤት አመልካቾች እንዲካፈሉ ከወሰነ በኋላ በአፈፃፀም ክርክር ሂደት እነዚህ ቤቶች እንዴት ሊተላለፉ እንደቻሉ ሳያጣራ ቤቶቹ በሦስትኛ ወገን ስም የተመዘገቡ ናቸው በማለት ውሳኔውን ሳያስፈጽም መቅረቱን ተረድተናል፡፡

በመሰረቱ አፈፃፀም የያዘው ፍ/ቤት በዋናው ፍርድ የተሰጠውን ውሳኔ ማስፈጸም ይጠበቅበታል፡፡ ፍርድ አስፈፃሚው ፍርድ ቤት እንደ ፍርድ ማስፈጸም አሊያም ያልተፈፀመበትን ምክንያት በመዝርዝር በግልጽ ማመልከት እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 374 ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ዋና ፍርድ ያፈረበትን ቤትና የድርጅት ቤት በአፈፃፀም ተከሳሽ ሳይሆን በሌላ ሦስትኛ ወገን የተመዘገበ ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ላለማስፈጸም መሰናክል መሆኑን የጠቀሰ ስለመሆኑ ከውሳኔው ተረድተናል፡፡ በአመልካቾች በኩል የቀረበው አቤቱታ ደግሞ የሚያመለክተው ተጠሪ ንብረቶቹን በተንኮል ድርጊት ከፍርድ በኋላ በልጆቻቸው ስም አዙረዋል የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤት ያደረገው ማጣራት ሥራ የለም፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ንብረቶቹ የውርስ ንብረት ናቸው ተብሎ ውሳኔ ካረፈበት በኋላ በምን አግባብ ወደ ሦስተኛ ወገን እንደተላለፉ ማጣራት አስፈላጊ እና በመሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም ይህንን ፍሬ ነገር ማጣራት እና ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መወሰን ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህም የሥር ፍ/ቤት ይህንኑ ሳያጣራ አመልካቾች ሌላ ንብረት ይጠቀሙ ሲል የአፈፃፀም መዝገቡን ለጊዜው መዝጋቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የምስራቅ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአፈፃፀም መ/ቁ. 17589 ጥቅምት 2/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ፣የአማራ ብ/ክ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20042 የሰጠው ትእዛዝ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 00580 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በተጠሪ እና በሚች ስም የነበረው ቤት እና ድርጅት የውርስ ንብረት ነው ተብሎ በዋናው ፍርድ እንዲከፋፈሉ ከተፈረደ በኋላ በአፈፃፀም ክርክር ሂደት ንብረቶቹ በሦስተኛ ወገን የተመዘገቡበት አግባብ እና ውጤቱን አስመልክቶ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መዝገቡን ለምሥራቅ ጐጃም ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43005

ሚያዚያ 19 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አብዱራሂም አህመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1. አቶ አውግቸው እርገጤ
2. ወ/ሮ ማህደር ቢተው
3. አቶ አደራጀው ዘውአለ

ሁሉም ከጠበቃ ሳሕሉ ሀብቴ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 ስር የተመለከተውን መሰረት በማድረግ ያስተላለፈውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካቾች ጥር 22 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ስላመለከቱ የቀረበ ነው፡፡

የአመልካቾች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ችሎት የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት በሰበር አቤቱታቸው ላይ ዘርዝረዋል፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካቾችን አቤቱታ ለአቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተያዘው የጉዲፈቻ ውል ይፅደቅልኝ ጥያቄ ሂደት ውስጥ ሐሰተኛ አቤቱታና አስተያየት በማቅረብና ፍርድ ቤቱን ለማሳሳት ሞክረዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሕጻን ሂክማን ኢብራሂምን ተቀብሎ የሚያሳድጋት ብርሃን ሕይወት የሕጻናትና ቤተሰብ መርጃ ድርጅት አቶ አውግቸው እርገጤ ወኪል ለሆኑላቸው ጀርመናዊያን ባልና ሚስት በጉዲፈቻ ለመስጠት ያደረገውን ውል ፍርድ ቤት ለማስፀደቅ ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ ቀርቦለት የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር አስተያየት እንዲሰጥበት ችሎቱ ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱን፣ ለሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የተላከው የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት ቡድን መሪ ለሆኑት ላሁኑ ሁለተኛ አመልካች ቀርቦላቸው የጉዲፈቻ ማንነት ሲመረመር ሕጻናት ማሳደጊያው ተግባሩን እንዳይቀጥል በፍትሕ ሚኒስቴር እንደታገደ በመታወቁ ሕፃኗ በቅድሚያ ሕጋዊ ለሆነው የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ባሁኑ ሦስተኛ አመልካች በሚተዳደረው የእናት ዓለም ሕፃናት ማሳደጊያ እንደተላለፈች፣ ከዚህም በኋላ ያሁኑ አንደኛ አመልካች ከአዲሱ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ጋር የጉዲፈቻ ውል ፈፅመው ሁለተኛ አመልካች አንደኛ አመልካች ሕፃኗን አዲስ ከተረከበው ድርጅት ጋር ያደረጉት የጉዲፈቻ ውል እንዲፀድቅ ታህሳስ 07 ቀን 2001 ዓ/ም አስተያየት መስጠታቸውን ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካቾችን ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት ሊያስተላልፍ የቻለው በተዘጋና እንደገና አስተያየት እንዲሰጥ ባልተጠየቀበት መዝገብ አስተያየት የተሰጠው ፍርድ ቤቱን ለማሳሳት ነው የሚለውን ምክንያት በመያዝ መሆኑን፣ አንደኛ አመልካች ብርሃነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕይወት የሕጻናት እና ቤተሰብ መርጃ ድርጅት መፍረሱን አያውቁም ነበር ተብሎ ታህሳስ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በኋላ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በተሰጠበት መዝገብ ውሳኔ የተሠጠ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 ይዘት ሲታይ በዳኝነት ስራ ላይ ወንጀል ሲፈፀም ፍርድ ቤቱ ጥፋቱ በተደረገበት ጊዜ በያዘው የፍትሐብሔር መዝገብ ወዲያውኑ ቀጥታ ቅጣት ሊያስተላልፍ የሚችል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መንገድ ቅጣት ሊያስከትል የሚችለው ድርጊት በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 452(1) ስር የተመለከተው በተከራካሪ ወገን የሚሰጠው ሐሰተኛ ቃል ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተጠያቂነት የሚመጣው ማንኛውም ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል ዘንድ ቀርቦ እውነት እናዲናገር ታዞ በፍርድ ቤቱ ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለው አካል በሚወሰን ጭብጥ ላይ አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮችን በሚመለከት እያወቀ ሐሰተኛ ቃል የሠጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

የድንጋጌው አይነተኛ ዓላማ የዳኝነትን ክብርን፣ የዳኝነት አስተዳደርን የሚነካ፣ ሕብረተሰቡ በፍርድ ቤቱ ላይ እምነት እንዳይኖረው የሚያደርግ ድርጊት መከላከልና እውነትን መሰረት ያደረገ ፍርድ እንዲሰጥ ማስቻል ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህንን ለማሳካት ደግሞ ፍርድ ቤት ድንጋጌውን ሲያስፈጽም በድንጋጌው ስር የተመለከቱ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች መሟላታቸውንና በተገቢው ማስረጃ መደገፋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ የወንጀል ባሕርይ ያለው እንደመሆኑ መጠን በወንጀል ስነ-ሕግ ተቀባይነት ያላቸው መርሆዎችንና በሕገ መንግስቱ ውስጥ የተካተቱትን መሰረታዊ መብቶችን ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አንደኛ ተጠሪ በጉዳዩ ባንድ መዝገብ ሁለት ጊዜ ውሳኔ የተሠጠባቸው ሲሆን በመጀመሪያው ብይን ይኸው አመልካች በጉዳዩ ላይ የፈፀሙት ድርጊት እንደሌለ ተገልፆ በነጻ ከተሰናበቱ በኋላ እንደገና እንዲቀጡ መደረጉ ተገቢውን ስርዓት በተከተለ ሁኔታ አይደለም፡፡ አንድ ሰው ባንድ የወንጀል ድርጊት ነጻ ተብሎ ከተወሰነ በኋላ በዚያው ጉዳይ እንደገና ሌላ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጎ የሚቀጣበት አግባብ የለምና፡፡ ሁለተኛ አመልካችን በተመለከተም አመልካች ሰጡ የተባሉት አስተያየት በሕጉ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ለሕፃን ጥቅም ማስጠበቅ መሆኑ የሚገለፅ እስከ ሆነ እና ፍርድ ቤቱ አስተያየቱ ተቀባይነት ያለው መሆኑ ያለመሆኑን በመመርመር በጉዲፈቻ ውል መፅደቅ አለመጽደቅ ላይ ተገቢውን ውሳኔ የሚሠጥበት ከሚሆን በስተቀር ሐሰተኛ ነው ተብሎ የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል አይሆንም፡፡ ከሁሉም በላይ ሁለተኛ ተጠሪ አስተያየት ሰጡ የተባሉበት ድርጅት የፈረሰ መሆኑን እያወቁ አስተያየት መሰጠታቸው በእርግጠኝነት የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ሁለተኛ አመልካች ሐሰተኛ ምስክርነት ቃል ሰጥተዋል ሊባሉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ሦስተኛ አመልካችን በተመለከተም የተላለፈውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ስንመለከተው ይኸው አመልካች ተፈፀመ ለተባለው ድርጊት የነበራቸው የድርጊት ተሳትፎ ምን እንደሆነና ሐሰተኛ የምስክርነት ቃል የሚያሳይ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ የገለፀው ነገር የለም፡፡ አንድ ሰው ደግሞ በወንጀሉ ድርጊት የነበረው ተሳትፎ ባግባቡ ሳይረጋገጥ የሚቀጣበት ሕግ የለም፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ያስተላለፉት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሕጋዊ ስርዓቱን መሰረት ያላደረገ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 እና በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 452(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የማያሟላ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128857 ታህሳስ 20 እና 22 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75302 ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናውን የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር አመልካቾችን በነፃ አሰናብተናል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45839

ሚያዝያ 5 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ይርጋአለም ከበደ - ጠ/ደሣለኝ ቀነኒ ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ፅጌ ሚካኤል - ጠ/ወጋየሁ ታደሠ (የ1ኛ,2ኛ,3ኛ,5ኛ ተጠሪዎች ጠበቃ) 4ኛ ተጠሪ አልቀረቡም

ፍ ር ድ

ተጠሪዎች የውርስ ንብረት እንዲጣራላቸው አመልክተው ውርስ ከተጣራ በኋላ ክፍፍሉን አስመልክቶ በስምምነት ስለጨረሱ ይኸው እንዲፀድቅላቸው ለፍ/ቤት አመልክተው ፍ/ቤቱ ስምምነቱን ከመዘገበ በኋላ አመልካች ስምምነቱ ወንጀል መሰል ተግባር የተፈፀመበት በመሆኑ ዳኝነት እንደገና እንዲታይላቸው አመልክተው ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ በማድረጉ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6ን መሰረት በማድረግ ባቀረቡት አቤቱታ አራተኛ ተጠሪ የህፃን ማራናታ ወኪል ሳይሆኑ ወኪል ነኝ በማለት ስምምነቱን መፈረማቸው፣ አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች የአቶ ባቻ ቱሉ ወራሾች ሳይሆኑ ወራሾች ናቸው ተብሎ ስምምነቱ መደረጉ፣ የሚጣራው ንብረት የአቶ ባልቻ ቱሉ ብቸኛ ሃብት ሆኖ እያለና ንብረቱ የወ/ሮ አስካለ የጋራ ንብረት ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር እንዲካፈሉ የተደረገው ስምምነት በወንጀል መሰል ተግባር የተገኘ በመሆኑ ስምምነቱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤትም የአመልካች ልጅ ማራናታ ተስፋዬ የመዝገቡ አካል ሆና በጠበቃም ተወክላ ጉዳዩን ስትከታተል የቆየች በመሆኑ አመልካች ወንጀል ነክ ተግባር መፈፀሙን ሰኔ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ነው ያወኩት በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ እንዲሁም አራተኛ ተጠሪ የልጃቸውን መብት በሚነካ መልኩ ስምምነት ስለማድረጋቸው በማስረጃ አላረጋገጡም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታቸው ለአራተኛ ተጠሪ ውክልና የሰጡት ጠበቃ ወክለው እንዲከራከሩ እንጂ የእርቅ ስምምነት እንዲያደርጉ አለመሆኑ፣ ውክልናውንም የሰጡት እሳቸው እንጂ ልጃቸው ባለመሆናቸው ተጠሪው ልጅቷን ወክለው ስምምነት ማድረጋቸው፣ እንዲሁም አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች አቶ ባልቻ ቱሉ ወራሽ ሳይሆኑ ወራሽ ነን ብለው ስምምነት ማድረጋቸው ሲታይ በሃሰት የተደረገ ስምምነት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ብይንና ውሳኔ እንዲሻርላቸው አመልክተዋል፡፡ ችሎቱም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አከራካሪው ጉዳይ የአመልካች ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ስር የሚወድቅ ነው አይደለም የሚለው ስለሆነ ይህን ድንጋጌ ማየቱ ለጉዳዩ አወሳሰን ይጠቅማል፡፡ ይህ ድንጋጌ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ የተሰጠው በሃሰት ተዘጋጅቶ በቀረበ ሰነድን ሃሰተኛ የምስክርነት ቃልን፣ ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቅሶ የሆነ ተግባርን መሰረት አድርጎ መሆኑን አቤት ባዩ ሲረዳው ጉዳዩ በይግባኝ ከመታየቱ በፊት ውሳኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ራሱ ዳኝነቱን በድጋሚ እንዲያይ ጥያቄ ለማቅረብ መብት የሚሰጠው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሚከራከሩት ፍ/ቤት የመዘገበው ስምምነት ወንጀል መሳይ ተግባር የተፈፀመበት ነው በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እዚህ መደምደሚያ ላይ ያደረሳቸውም አንደኛው ምክንያት አራተኛ ተጠሪ ስምምነቱን የፈረሙት ከውክልና ስልጣናቸው በላይ ነው በማለት ነው፡፡ አራተኛ ተጠሪ ጠበቃ ወክለው እንዲከራከሩ ብቻ ከተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን አልፈው ስምምነት አድርገው ከሆነ አመልካች ስምምነቱን ከመቃወም ወይም በይግባኝ ፍ/ቤቱ ስምምነቱን በመመዝገብ የሰጠው ትዕዛዝ ከሚያስለውጡ በቀር ድርጊቱ ወንጀል ተብሎ ዳግመኛ ዳኝነት ሊጠየቅበት የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ከክርክሩ ሂደትም የአመልካች ልጅ የክርክሩ አካል የነበረችና አመልካች ክርክሩን የሚያውቁ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም በወቅቱ ስምምነቱ እንዳይፀድቅ ወይም በይግባኝ እንዲሻር ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችሉ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ለአራተኛ ተጠሪ ውክልና የሰጡት እሳቸው እንጂ ልጃቸው ባለመሆኗ ተጠሪው የልጃቸው ወኪል በመምሰል ያደረጉ ስምምነት በተንኮል የተደረገ ነው የሚል ክርክር የቀረበ ቢሆንም አመልካች ለአራተኛ ተጠሪ ውክልና መስጠታቸው ያልተካደና አመልካችዋ የልጃቸው ሞግዚት እንደመሆናቸው ልጃቸውን ወክለው ህጋዊ ተግባራትን የሚፈፅሙ እሳቸው በመሆናቸው ከሳቸው በተሰጣቸው ውክልና መሰረት አራተኛ ተጠሪ ስምምነቱን ማድረጋቸው ወንጀል ነክ ተግባር ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመጨረሻም አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪ የሚች አቶ ባልቻ ቱሉ ወራሽ ነን በማለት ያልተከራከሩ መሆኑን አመልካች በሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ወቅት ያመኑ በመሆኑ በውል ስምምነቱ ላይ ወራሽ ነን ብለው በመመዝገብ ፍ/ቤቱን አሳስተዋል በሚል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነው፡፡ በአጠቃላይ የስምምነት ሰነዱ ወንጀል ጠቀስ ተግባር የተፈፀመበት ስለመሆኑ አመልካች ያላስረዱ ስለሆነ ጥያቄአቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ስር አይወድቅም ሲል የስር ፍ/ቤት የደረሰበት መደምደሚያ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት አያስችልም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 12405 መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 39853

ሚያዝያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ

ተጠሪ፡- 1. የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር

2. አቶ ዮሐንስ ወ/አማኑኤል

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች በክሱ በወረዳ 23 ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥር 1801/01 የሆነ ቤት ሰኔ 09 ቀን 1989 ዓ.ም በተፈረመ ውል በወር ብር 900(ዘጠኝ መቶ) ለአንደኛ ተጠሪ አከራይቶ የነበረ ቢሆንም አንደኛ ተጠሪ የውል ግዴታውን በመጣስ ሁለተኛ ተጠሪ እንዲኖሩበት በማድረጉ የኪራይ ውሉ ተቋርጦ ቤቱን እንዲያስረክበውና ከመስከረም 23 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ ያለውን ውዝፍ ኪራይ እንዲከፍል እንዲሁም ሁለተኛ ተጠሪ የውል ግንኙነት ሳይኖራቸው በቤቱ እየተገለገሉ በመሆኑ ያለአግባብ የበለፀጉበትን ኪራዩ ከቅጣቱ ጋር እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስረክቡ ጠይቋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ከታዘዘ በኋላ አቤቱታ አቅርቦ መልስ እንዲያቀርብ የተፈቀደለት ቢሆንም በተደጋጋሚ ቀጠሮ መልስ ባለማቅረቡ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ግን ቀርበው ከአመልካች ጋር ውል ስሌላቸው ክሱ እንደማይመለከታቸው፣ ሁለት አመት ያለፈው ኪራይ ገንዘብ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(መ) መሰረት እንደተከፈለ እንደሚቆጠር፣ ውሉ የተደረገው ለአንድ አመት ስለሆነና ስላልታደሰ ክስ ማቅረብ እንደማይችል፣ ቤቱን የያዙት በአደራ ጠባቂነት መሆኑን እንዲሁም ስምንት አመት ሙሉ ያልታደሰ ውል መሰረት አድርጎ የቀረበው ክስ ተቀባይነት እንደሌለው ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ሁለት አመት ያለፈው ክፍያ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(መ) መሰረት እንደተከፈለ ይቆጠራል፣ ሁለት አመት ያላለፈውን ኪራይ ገንዘብ ከነቅጣቱ አንደኛ ተጠሪ ይክፈል፣ በዚሁ ጊዜ ሁለተኛ ተጠሪ በቤቱ መገልገላቸውን ስላልካዱ ገንዘቡን ይክፈሉ፣ ቤቱን ለአመልካች ያስረክቡ፣ ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን እስኪያስረክቡ በወር ብር 900.00(ዘጠኝ መቶ) ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ በቅሬታውም አንደኛ ተጠሪ ውዝፍ እዳ እንዳለበት ያመነ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2025(ሀ) መሰረት ውዝፍ እዳውን ሊከፍል ይገባል እንዲሁም ከ2ኛ ተጠሪ ጋራ የኪራይ ውል የሌለውና ክሱ የቀረበው አለአግባብ በመበልፀጋቸው በመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(መ) በመጥቀስ የክፍያው ጥያቄ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ችሎቱም ይህን የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ መጥሪያ ቢላክም ሁለተኛ ተጠሪ ብቻ በመቅረባቸው አንደኛ ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡ ችሎቱም የቃል ክርክሩን ሰምቷል፡፡ መዝገቡንም እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአመልካች የቅሬታ ነጥቦች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው አንደኛ ተጠሪ ውዝፍ የኪራይ እዳ ያለበት ለመሆኑ ስላመነ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(መ) ስር የተመለከተው የህሊና ግምት ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም የሚል ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(መ) ስር ለቤቶች ኪራይና ለእርሻ ሃብት ለሆነ የሚከፈል እዳ እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ እንደሚቆጠር ተመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤትም አመልካች ዳኝነት ከጠየቀባቸው ውዝፍ የቤት ኪራይ ገንዘብ ውስጥ ሳይጠየቁ ሁለት አመት ያለፈባቸው እንደተከፈሉ የህግ ግምት የሚወሰድባቸው ናቸው በማለት ውድቅ አድርጓቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች አንደኛ ተጠሪ ያልከፈለው ውዝፍ የቤት ኪራይ እዳ እንዳለበት አምኖ ለአመልካች የፃፈው ደብዳቤ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2025(ሀ) መሰረት ግምቱን ቀሪ ያደርገዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2025(ሀ) ባለእዳው በጽሑፍ እዳውን ያመነ እንደሆነ እዳው እንደተከፈለ መቆጠሩ ቀሪ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አንደኛ ተጠሪ እዳውን ማመን አለማመኑ መረጋገጡ ሁለት አመት ያለፈው እዳ ሊከፈል ይገባል አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ለመፍታት አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ ባቀረበበት ወቅት አንደኛ ተጠሪ መልስ ስላላቀረበ እዳውን በማመንም ሆነ በመካድ የሰጠው መልስ የለም፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ባቀረበበት ወቅት በስር ፍ/ቤት ክስ ከቀረበ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ያልከፈለው ውዝፍ የቤት ኪራይ ገንዘብ እንዳለበት አምኖ ገንዘቡን እንደሚከፍል ደብዳቤ ስለፃፈ ይኸው ማስረጃ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርብለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 327(3) እና 345(ለ) መሰረት ጥያቄውን ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙን መልስ ሰጪን መጥራት ሳያስፈልግ ስለዘጋው ማስረጃዎቹንም አልተመለከተም፡፡

በመሰረቱ ከሳሽ ክሱን ሲያቀርብ አስፈላጊ ማስረጃዎችን በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ፣ ሊያቀርባቸው የማይችላቸውን ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሰረት በፍ/ቤቱ በኩል እንዲቀርቡለት መጠየቅ ይገባዋል፡፡ በመሆኑም ከሳሹ ሊያቀርባቸው ሲችል ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ያላቀረባቸውን ማስረጃዎች በክርክር ሂደት ሁሉ እያንጠባጠበ ሊያቀርብ አይችልም፡፡ የስነ-ስርዓት ህጉ አላማም ይህ አይደለም፡፡ ተጨማሪ ማስረጃዎች ሊቀርቡ የሚችሉት ክሱ በተጀመረበት ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 256 እና በይግባኝ ደረጃ ደግሞ በቁጥር 345 ስር በተመለከቱት የተወሰኑ ሁኔታዎች ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ በይግባኝ ደረጃ ማስረጃ የሚቀርብባቸው ምክንያቶችን ስንመለከት የስር ፍ/ቤት ማስረጃውን ሊቀበል ሲገባ ያለበቂ ምክንያት ያልተቀበለው ከሆነ፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ወይም ተገቢ መስሎ ሲታየው ማናቸውም ምክንያት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ሲያዝ ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 327 መሰረት ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ምስክር እንዲቀርብ ማመልከቻ ከቀረበ ወይም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ከሆነ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በይግባኝ ፍ/ቤት እንዲቀርብለት የጠየቃቸው ማስረጃዎች በስር ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ተጠይቀው ፍ/ቤቱ አልቀበልም ያላቸው አይደሉም፡፡ ነገር ግን አመልካች አንደኛ ተጠሪ ከክስ በኋላ እዳውን በማመን የፃፈው፣ ሁለተኛ ተጠሪም እንዲሁ እዳውን ለመክፈል የፃፉት ደብዳቤዎች ሲሆኑ እነዚህ ማስረጃዎች ክስ ሲቀርብ ያልነበሩ ናቸው፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው አንደኛ ተጠሪ እዳውን ያመነ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2025(ሀ) መሰረት የህግ ግምቱ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም በማለት በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አንደኛ ተጠሪ የህግ ግምቱ ተጠቃሚ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ በትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ተጠሪው እዳውን በማመን ፅፏል የተባለውን ደብዳቤ ሊያስቀርበው ይገባ ነበር፡፡ በተለይ ደብዳቤው ክስ ከቀረበ በኋላ ዘግይቶ የተፃፈ በመሆኑና አመልካች ክስ ሲያቀርብ በማስረጃነት ሊያቀርበው የሚችል ባለመሆኑና ትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚረዳ ማስረጃ እንደመሆኑ ፍ/ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ የቀረበውን ጥያቄ ሳይመረምር ይግባኙን መሰረዙ የተጠቀሰውን የስነ-ስርዓት ህግ በአግባቡ ያላገናዘበ መሆኑን ተረድተናል፡፡

በሌላ በኩልም ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን የያዙት ከአመልካች ጋር የውል ግንኙነት ሳይኖራቸው ከውል ውጪ ነው፡፡ እሳቸውን በተመለከተም ተጠሪው በቤቱ ከመቼ ጀምሮ ይኖሩ እንደነበር እንዲሁም ውዝፍ ኪራዩን ለመክፈል ለአመልካች የፃፉት ደብዳቤ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርብ ተጠይቋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ከውል ውጪ የያዙ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(መ) ስር የተመለከተው የህግ ግምት ተጠቃሚ የሚሆኑበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪው ክስ የቀረበባቸው ቤቱን ያለ ውል ይዘው ያለአግባብ በልፅገዋል በሚል ነው፡፡ ነገር ግን የስር ፍ/ቤት ሁለት አመት ያለፈው የኪራይ ገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት ውድቅ ስላደረገው ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ከመቼ ጀምሮ እንደያዙት ያረጋገጠው ነገር የለም፡፡ ተጠሪው ቤቱን ከመቼ ጀምሮ የያዙት እንደነበር የሚያስረዳው ማስረጃ በስር ፍ/ቤት ክርክር ወቅት ሊገኝ ያልቻለ መሆኑና ኪራዩን ለመክፈል የፃፉት ደብዳቤም ቢሆን ክስ ከቀረበ በኋላ ዘግይቶ የተፃፈ በመሆኑ በስር ፍ/ቤት ሊቀርብ አለመቻሉን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪው ያለአግባብ በልፅገዋል ሊባል የሚችለው ከመቼ ጀምሮ ነው የሚለውንም ለመወሰን ተጨማሪ ማስረጃ መቅረቡ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት በስር ፍ/ቤት ሊቀርቡ ያልቻሉትንና በተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርቡ የተጠየቁትን ማስረጃዎች መርምሮ ሊወስን ሲገባ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት መዝጋቱ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን የሥነ-ሥርዓት ህጉን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 65544 ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርቡ የጠየቃቸው ማስረጃዎች በመቀበል ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ2 41526

ግንቦት 2 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ትራንስ አፍሪካ ትራንስፖርት አ.ማ - ጠበቃ አቶ መከተ ዳኘው-ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሙሉ ኤሌክትሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ኃ.የተ.የግል ማሕበር - ጠበቃ እሸቱ ደምሴ - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የትራንስፖርት አገልግሎት ክፍያ ገንዘብን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘት ባጭሩ ተጠሪና አመልካች ለስምንት ዓመታት ያህል የስራ ግንኙነት የነበራቸው መሆኑን አመልካች ለተጠሪ ጅቡቲ ወደብ ላይ በቃል በተደረገው ውል መነሻነት ለሰጠው የክሊራንግና የትራንዚት አገልግሎት ተገቢውን አገልግሎት ከሰጠ በኋላ በተለያዩ ጊዜያት በተጻፈለት የአገልግሎት ሒሳብ ክፍያ መጠየቂያ ደብዳቤዎችና ኢንቮይሶች ብር 332,834.27(ሦስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከሃያ ሰባት ሳንቲም) የጠየቀ ቢሆንም ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆኑን አመልካች ለተጠሪ ከጅቡቲ አዲስ አበባ ድረስ የጭነት የማጓጓዝ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጥቶ አመልካች ንብረቶችን ከተረከበ በኋላ ብር 39,600.00(ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ) እንዲከፍለው አመልካች ሲጠይቀው ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆኑን ገልፆ ለክሱ መሰረት የሆነው ገንዘብ ብር 332,834.27(ሦስት መቶ ሠላሣ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከሃያ ሰባት ሣንቲም) ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድና ከተለያዩ ወጪና ኪሳራዎች ጋረ እንዲከፈለው ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሠጠው መልስም አመልካች የክሊራንግና የትራንዚት አገልግሎት ሰጥቻለሁ በማለት እንዲከፈለው ያቀረበው ገንዘብ ሕጋዊና ታዓማኒ ሰነድ ወይም ደረሰኝ ያልቀረበበት መሆኑን አመልካች ለማስረጃነት የዘረዘራቸው ኢንቮይስ (የክፍያ ሰነድ) ሁሉ ራሱ ባዘጋጀው ወረቀቶችና ጽሑፎች የተዘጋጀ መሆኑን የጭነት ማጓጓዣ ብር 39,600.00(ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ብር) በቼክ ቁጥር BB430772 በደረሠኝ ቁጥር 03325 ለአመልካች የከፈለው መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ውል መኖሩን ካረጋገጠ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች ብር 38,808.00 (ሰላሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) የከፈለው በመሆኑ ይኸው የገንዘብ መጠን ተቀንሶ ቀሪውን ብር 293,234.27(ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከሃያ ሰባት ሳንቲም) ግን ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ዘጠኝ ከመቶ ወለድና ከተለያዩ ወጪና ኪሳራዎች ጋር እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች የስር ፍ/ቤት ብር 38,808.00(ሰላሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) ለተጠሪ እንዲከፈል ሲል በሰጠው የውሳኔ ክፍል ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤት አመልካች አከራካሪው ብር ተከፍሎበታል የተባለውን ሰነድ ሐሰተኛ መሆኑን የሚያስተባብል ማስረጃ አላቀረበም የሚል ምክንያት ይዞ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የውሳኔ ክፍል ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሕዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ብር 38,808.00 (ሰላሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) ተጠሪ ለአመልካች ስለመክፈሉ ተረጋግጧል የተባለበት ሰነድ ለጉዳዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብነት የሌለው እና ሊታመን የማይችል በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባል ሲሉ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አከራካሪው የሆነው ገንዘብ ብር 38,808.00(ሰላሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) አመልካች አስቀድሞ ተከፍሎታል የሚለው የስር ፍርድ ቤት መደምደሚያ አግባብነት ባለው ማስረጃ የተደገፈ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የተጠሪ ጠበቃ ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ የአመልካች ክርክር በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ገልፀው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ መስከረም 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ አራት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርት አከራካሪውን ገንዘብ ለመጠየቅ መሰረት ያደረገው የተጠሪን ደረቅ ጭነት አጓጉዞ ያልተከፈለው የትራንስፖርት ገንዘብ ክፍያ መኖሩን ሲሆን ተጠሪን ገንዘቡን ለአመልካች መክፈሉን ገልጾ ይህንኑ ክስ ለማስተባበል ደግሞ የገንዘብ መክፈያ ሰነድና ቼክ ለማስረጃነት ማቅረቡን ሲሆን አመልካች የተጠሪ ማስረጃዎች ሐሰተኛ ናቸው በማለት ተከራክሮም ይህንኑ ክርክር የሚደግፍለት ማስረጃ ያለማቅረቡን የበታች ፍርድ ቤቶች በውሳኔአቸው ላይ በግልፅ ያሰፈሩት ነጥብ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች በሰበር ደረጃ የሚከራከረውም ክፍያው መፈፀሙን ያሳያል የተባለው ሰነድ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነበር በማለት ሲሆን ይህንኑ ለማስረዳት በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማስረጃ ያቀረበው ግልጽ ማስረጃ ስለመኖሩ ግን ያረጋገጠው ሁኔታ አለመኖሩን ተመልክተናል፡፡ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የአመልካች የሰበር ክርክር በማስረጃው ምዘና ላይ የሚያተኩር መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ተጠሪ ክፍያውን ፈፅሟል? ወይስ አልፈጸመም? እና ክፍያው የተፈፀመው አመልካች ለተጠሪ ለሠጠው አገልግሎትና ዳኝነት ለጠየቀበት ጉዳይ ወይስ ለሌላ? የሚለው ጉዳይ የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ የሕግ ክርክር የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ በዚህ ረገድ ደግሞ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመርመር ተገቢ ነው ያሉትን የየራሳቸውን ምዘና አድርገዋል ተገቢ ነው ያሉትንም ክብደት ሰጥተዋል፡፡ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ደግሞ በዚህ ችሎት የሚታረምበት የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሳኔ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት እንጂ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ጥያቄ መመዘኛን የሚያሟላ ሆኖ ስላላገኘነው የአመልካችን ክርክርን አልተቀበልነውም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 59208 ጥቅምት 04 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 61553 ጥቅምት 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 52752
ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ
ሂሩት መለሰ
ብርሃኑ አመነው
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1ኛ ከድር ሐጂ ሁሴን
2ኛ ሉሲ ኮሌጅ አ.ማ
} አልቀረቡም

ተጠሪ፡- 1ኛ አቶ አሚን ዑስማን
2ኛ ወ/ሮ ኑሪያ ጀማል
} ጠበቃ ደረጀ ኢታቻ ቀረቡ

መዝገቡን በአዳሪ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የነበረውን የፍርድ ቤት መሰረት በመተው እርቅ ተደርጎ ለፍርድ ቀርቦ ከተመዘገበ በኋላ ያለውን ሕጋዊ ውጤት የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥም በሚከተለው መልኩ የተመዘገበው ነው፡፡

የአሁኖቹ ተጠሪዎች እና አመልካቾች ተጠሪዎች በሉሲ ኮሌጅ አ.ማ ውስጥ ያላቸውን የባለአክሲዮንነት መብት በተመለከተ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ላይ የይግባኝ ክርክር የነበራቸው ሲሆን ክርክሩ በዚህ ደረጃ ላይ እያለ ግራ ቀኙ በመካከላቸው ያለውን አለመግባባት ከፍርድ ቤት ውጪ ለመጨረስ ተስማምተዋል፡፡ በዚህም መሰረት የካቲት 30 ቀን 2000 ዓ.ም በተፈረመ የእርቅ ስምምነት አድርገው በስምምነቱ መሰረትም በፍርድ ቤት እንዲፀድቅ በመገለጹ ስምምነቱ ጉዳዩን በይግባኝ ይመለከተው ለነበረው ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፍርድ ቤቱም የእርቅ ስምምነቱን ግራ ቀኙ ባሉበት ተመልክቶና መርምሮ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 277(1)(2) መሰረት መዝግቦት በእርቁ መሰረት እንዲፈፀም ዘንድ ለስር የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልኮለታል፡፡ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፀደቀውን ስምምነት እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤትም ከተመለከተ በኋላ ተጠሪዎች በአመልካቾች ላይ የተከፈተውን የወንጀል መዝገብ ያላዘጉ ስለሆነ በእርቁ መሰረት ሊፈጸም የሚችል አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የእርቅ ይፈፀምልኝ ጥያቄን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጓል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ተጠሪዎች የወንጀል መዝገብ ለማዘጋት እርቅ አድርገዋል ለማለት እንደማይቻል ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን ዘርዝሮና እርቅ በተቻለ መጠን እንዲፈፀም መደረግ እንዳለበት በመተንተን የስር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በእርቁ መሰረት እንዲያስፈፅም ጉዳዩን መልሶ ልኮለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ በክልሉ የሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ እርቅ ውል እንደመሆኑ መጠን ስለውል አመሰራረትና አተረጓጎም የተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ መታየት እያለበት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ተጠሪዎች የወንጀል መዝገብ ካለማዘጋታቸው ጋር ሳያገናዝብ የሚፈፀም ሕጋዊ እርቅ አለ በማለት መወሰኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነ እርቅ ስምምነት ከአንደኛው ተጠሪ ግዴታ አንጻር ሊፈጸም የማይችል ለህግ ተቃራኒ የሆነ ስምምነት ነው ከተባለ አመልካቾች እንደስምምነቱ ለመፈፀም ተነጻጻሪ ግዴታ ይኖርባቸዋል ወይስ አይኖርባቸውም? የሚለውን ነጥብ ለማየት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተብሎ በመታዘዙ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ተደርጎአል፡፡ የተጠሪ ጠበቃ ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው ውሳኔው ሊፀና ይገባል ሲሉ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡ አመልካቾችም ሰኔ 09 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ጉዳይ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግራ ቀኙ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ይታይ የነበረውን ክርክር በመተው ጉዳዩን በእርቅ ጨርሰው የእርቅ ስምምነቱ ሰነድ ለፍርድ ቤቱ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ሰነዱን ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም በሚል ምክንያት መመዝገቡንና በእርቁ መሠረት እንዲፈጸምም ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን የላከለት መሆኑን በእርቁ ሰነድ በአንቀፅ 4 ስር ደግሞ የተጠሪዎች ግዴታ በፍርድ ቤቶች ያስከፈቷቸውንና የከፈቷቸውን የፍትሐብሔር እና የሌሎች ክርክሮችን ማዘጋት ተብሎ መቀመጡን አመልካቾች ተጠሪዎች በዚህ የእርቅ ሰነዱ አንቀፅ መሰረት ያለባቸው ግዴታ የፍትሐብሔርና የወንጀል መዛግብትን ማዘጋት መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን፣ የወንጀል መዝገብ በተጠሪዎች አቤቱታ ባይሆንም ጉዳዩን ሲመለከቱ በነበሩት ፍርድ ቤቶች የሚያስከስስ አይደለም ተብሎ መዘጋቱ በአሁኑ የክርክር ደረጃ መረጋገጡን ነው፡፡

በመሰረቱ በፍርድ ቤት ጉዳዩ እየታየ ባለበት ሁኔታ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ ጨርሰው ሲመጡና ፍርድ ቤቱ ይህንኑ እንዲመዘገብላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍርድ ቤት የእርቅ ስምምነቱን ሕጋዊነትና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆን መርምሮ ተገቢውን ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችልበት ጉዳይ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 277 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ከመዘገበው እርቁ እንደፍርድ ቤት ውሳኔ ሊታይ የሚችል ስለመሆኑንም ከተጠቀሰው ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት ያስገነዝባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካቾች የእርቅ ስምምነቱን ማድረጋቸውንና በፍርድ ቤት መዕደቁን እንዲሁም ይኸው በፍርድ ቤት የፀደቀው የእርቅ ስምምነት ቅሬታ ያሳደረበት ወገን ኖሮ ቅሬታውን ለበላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ እርቁን አለማስለወጡን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት የእርቅ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ያሉትን የፍትሐብሔር ክርክሮችን ማዘጋት ብቻ ሳይሆን የወንጀል መዛግብትን ጭምር ለማዘጋት በመሆኑ እና የወንጀል መዛግብትን ደግሞ ተጠሪዎች ያላዘጉ በመሆኑ እርቁ የአመልካቾች ፍላጎትና ሐሳብ መሰረት ባደረገ መልኩ ተፈጽሟል ለማለት አይቻልም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የእርቁ ሰነድ ስለወንጀል መዛግብት መዘጋት እንደቅድመ ሁኔታ የማያስቀምጥ መሆኑን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያረጋገጠው ከመሆኑም በላይ ተደርጓል የሚል ድምዳሜ ቢኖር እንኳ ወንጀሎቹ በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚዘጉ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የወንጀል መዛግብት የተባሉት ባሁኑ ጊዜ ጉዳዩ አያስከስስም በሚል ምክንያት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት የተዘጉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የወንጀል መዛግብት አለመዘጋት ለእርቁ ሕጋዊ አለመሆን ምክንያት ሊሆን ይገባል በሚል የቀረበው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የእርቅ ስምምነቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 277 አግባብ የፀደቀ በመሆኑ የማይፈፀምበት ሕጋዊ ምክንያት የለውም፡፡ በዚህም ምክንያት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፤ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81625 ጥር 24 ቀን 2002 ዓ.ም የተሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 08 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45247

ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ደጀኔ በላቸው - ከጠበቃ ዳኜ አዲሴ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ነስሩ አወል- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶታል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውል ይፈፀምልኝ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፤ተጠሪ በብር 149,000.00(አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ ብር) የደረቅ ጭነት ማመላለሻ መኪና ሽጠውላቸው በእለቱ ብር 145,000.00(አንድ መቶ አርባ አምስት ሺህ ብር) ተቀብለው ሊብሬውንና መኪናውን ያስረከቡ መሆኑን፤ቀሪውን ገንዘብ ስም ሃብቱን ሲያዛውሩላቸው አመልካች ለተጠሪ ለመክፈል እንደተስማሙ፤ተጠሪም መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ በማድረግ ስመ ሃብቱን ለማዛወር በውሉ ላይ በግልጽ ግዴታ መግባታቸውን፤ሆኖም ተጠሪ በገቡት ግዴታ መሰረት መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ ለማድረግ እና ስመ ሃብቱንም ለማዛወር ፈቃደኛ ሊሆኑ አለመቻላቸውን ገልጸው በውሉ መሰረት መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ አድርገው ስመ ሃብቱን እንዲያዛውሩላቸው እንዲሁም የገደብ ገንዘብ ብር 10,000.00(አስር ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ በመካከላቸው የመኪና ሽያጭ ውል መደረጉንና በክሱ ላይ የተገለጸውን ገንዘብ በመቀበል መኪናውንና ሊብሬውን ለአመልካች ማስረከባቸውን እንዲሁም በውሉ ላይ መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ ለማድረግ እና ስመ ሐብቱንም ለማዛወር ግዴታ መግባታቸውን ሳይክዱ መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ ሊያደርጉት ያልቻሉት በወንጀል ጉዳይ ዋስ የሆኑላቸው ግለሰብ በመሰወራቸው መሆኑን፤ስመ ሃብቱንም የማዛወር ስልጣን የሌላ አካል እንጂ የተጠሪ አለመሆኑን፤እንዲሁም ውሉ ፈራሽ ነው ያልተባለ በመሆኑም የገደብ መቀጫ የሚጠየቁበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ውሉ መኖሩን ከአረጋገጠ በኋላ ተጠሪን አመልካች ሊጠየቁ የሚገባው ውሉ እንዲፈርስ እንጂ እዳና እገዳውን ነፃ እንዲያደርጉ አይደለም፤ስመ ሃብቱን የማዛወር ስልጣንም የተጠሪ ሳይሆን በሕጉ አግባብ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም ሲል ውድቅ አድርጐታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሚያዝያ 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበው የጽሑፍ መልስ እንዲሰጡ በችሎት ተነግሯቸው የፁሑፍ መልሳቸውን ባለማቅረባቸው የጽሑፍ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመረውም ለስመ ንብረት ዝውውር ሲባል በተሸጠው መኪና ላይ አስቀድሞ የተሰጠውን የእግድ ትእዛዝ ሻጩ እገዳ እንደሚያስነሳ በውሉ ግዴታ መግባቱ ከተረጋገጠ፣ይኸው ግዴታ እንዲፈጸም ክስ ማቅረብ በጉዳዩ ላይ የክስ ምክንያት የለውም ለማለት ይቻላል? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሲሆን ሌሎች ነጥቦች በዚሁ ነጥብ ስር የሚሸፈኑ ሆነው አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት የመነጨው ከመኪና ሽያጭ ውል መሆኑን፣ውሉ ስለመኖሩና በይዘቱ ላይ ግራ ቀኙ ያልተካካዱ መሆኑን፣ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኪና በገዢው ስም ሊዛወር ያልቻለው ተጠሪው ለሌላ ግለሰብ በወንጀል ጉዳይ በብር 10,000.00(አስር ሺህ) በፍርድ ቤት ዋስ ስለሆኑ እግድ በመሰጠቱ መሆኑን፣ እግዱም ለመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ተላልፎ ከመኪናው ማህደር ጋር ስለመያያዙ ተጠሪ ያልካዱት ፍሬ ነገር መሆኑ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ በፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ የክስ ምክንያት አለው ብሎ ለመወሰን የሚቻለው በክሱ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሹ የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ሕግ ይፈቅድለታል ወይ? የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ፍርድ ቤቱ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚችል የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የተፃፉት የማብራሪያ ፅሑፎች ያሳያሉ፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በግራ ቀኙ መካከል የመኪና ሽያጭ ውል መኖሩና ተጠሪ መኪናውን ከእዳና እገዳ ነፃ በማድረግ ስመ ሐብቱን ለአመልካች ለማዛወር ግዴታ የገቡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በክሳቸው የገለፁትም ይህንኑ ፍሬ ነገርና ተጠሪ በገቡት ግዴታ መሰረት ውሉን ያልፈፀሙ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ደግሞ በተጠሪ በኩል ማስተባበያ ያልቀረበበት የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ መኪናው ላይ የተላለፈውን የእግድ ትእዛዝ እንዲያስነሱ ጥያቄ ማቅረባቸው ደግሞ በሕግ የተፈቀደ ነው፡፡ ማንም ሰው በገባው ዋስትና መሰረት በንብረቱ ላይ እግድ ተሰጥቶ ከሆነ ንብረቱን ለሌላ ሰው በሽያጭ ሲያስተላልፍ ገዢው በንብረቱ ላይ የሚያገኘውን የባለቤትነት መብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲችል እግድን የማስነሳት ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ስለክስ ምክንያት አጠቃላይ መንፈስ እና ይዘት በሕጉ ላይ የተመለተውን መመዘኛን ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ክሱ የክስ ምክንያት አለው ከተባለ አመልካች ያላቸውን መፍትሔ ይህ ችሎት በዚሁ የክርክር ደረጃ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ተጠሪ በመኪናው ላይ ያሰጡትን እግድ የማያስነሱበት ሕጋዊ ምክንያት ያላቸው ስለመሆኑ አላስረዱም፡፡ ተጠሪ መኪናቸውን ከሸጡ ደግሞ የመኪናውን ባለሃብትነት ለገዢው ለማዛወር ሕጋዊ ግዴታ የአለባቸው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2273/2/ ድንጋጌ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የመኪናው ስመ ሃብት ሊዛወር የሚችለው ተጠሪ በመኪናው ላይ ያሰጡትን እግድ ሲያስነሱ ነው፡፡ ተጠሪ ስመ ሃብቱን ለማዛወር ስልጣን የላቸውም ቢባል እንኳ በአዋጅ ቁጥር 465/97 አንቀጽ 3/2/ ድንጋጌ መሰረት ሥልጣን ያለው አካል ተግባርን ሊወጣ የሚችለው በፍርድ ቤት የተሰጠው እግድ መነሳቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ስለሆነም በሕጉ አግባብ ስልጣን የተሰጠው አካል ስመ ሃብቱን ለማዛወር እንዲችል ተጠሪ የፍርድ ቤቱ የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ የበኩላቸውን ግዴታ ሊወጡ የማይገደዱበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ስለውል አፈፃፀም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1740 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ደንቦችንም ሆነ የግራ ቀኙን የውል ይዘት ባግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13195 ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 73431 ጥር 19 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ የክስ ምክንያት አለው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በገቡት ውል መሰረት በአሳራካሪው መኪና ላይ የተላለፈውን እግድ በማስነሳት የሚመለከተው አካል ስመ ሃብቱን ለአመልካች እንዲያዛውር እንዲያደርጉ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. በዚህ ችሎት ውሳኔ እንዲያስፈጽምም የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍለት ብለናል፡፡
5. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49857

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ፋንታ - ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ኪዳነ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ በላይነሽ ወ/ኪዳን - ወኪል ተሾመ አባይ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት እና የቦታ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ናት፡፡ ተጠሪ ክስ የመሰረተችው እማሆይ ፀሃይነሽ በተባለች ሰው እና በአሁንዋ አመልካች ላይ ሆኖ አመልካች ባለመቅረብዋ ክርክሩ በሌለችበት ተሰምቶ ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡ አከራካሪ ከነበሩት ጭብጦች አንዱ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በሚል በእማሆይ ፀሃይነሽ የተነሳው መቃወሚያ ስለሆነ የወረዳው ፍ/ቤት መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ በጉዳዩ ሥረ-ነገር ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ እማሆይ ፀሃይነሽ ውሳኔውን በመቃወም ይግባኝ አቅርባ ተቀባይነት እንዳላገኘ እና እስከ ሰበር ድረስም አቤቱታ አቅርባ ውድቅ እንደሆነባት በመዝገቡ ተመልክቶአል፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ መዝገቡ(የወረዳው ፍ/ቤት) የተንቀሳቀሰው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78 መሰረት አቤቱታ በማቅረብዋ ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም የአመልካችን ተቀብሎ ግራ ቀኝ ወገኖችን አከራክሮአል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችና የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል የቀድሞው ውሳኔውን ለውጦአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በየደረጃው ለበላይ ፍ/ቤቶች ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ በማቅረብዋ ጉዳዩ እንደገና ታይቶአል፡፡ ጉዳዩን በመጨረሻ የሰማው የትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ ቀደም ሲል ታይቶ በውሳኔ እልባት ያገኘ በመሆኑ አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ በድጋሚ የሚታይበት አግባብ የለም በማለት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በዓፈችው ማመልከቻ በሥር የሰበር ችሎት በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታዋን አቅርባለች፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ ቀደም ሲል አንደኛ ተከሣሽ የነበረችው የአመልካች እናት አንስታው ውድቅ ሆኖአል በማለት ተቀባይነት ማጣቱ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች እና ተጠሪ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው አመልካች በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ የሆነችው ተጠሪ ክስ ስላቀረበችበት ነው፡፡ በእርግጥ ክሱ በተሰማበት ጊዜ ልትቀርብ ባለመቻልዋ ጉዳዩ በሌለችበት ተሰምቶ ውሳኔ ተሰጥቶ እንደነበረ ግልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጠቀም ወደክርክሩ እንድትገባ ተፈቅዶላታል፡፡ በዚህ የሥነ-ሥርአት ሕግ ድንጋጌ እንደተመለከተው አቤቱታ አቅራቢው ወገን ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ የቀድሞው ውሳኔ ይነሳለታል፡፡ በዚህም ክርክሩ እንደና ይሰማል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ክርክሩ እንደገና ከተሰማ በኋላ የቀድሞው ውሳኔ ሊለወጥ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል ማለትም ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች ለቀረበባት ክስ በሰጠችው መልስ ያዋጣኛል ያለችውን ክርክር አቅርባለች የተከሰሰችው በስምዋ እንደመሆኑ መጠን መከራከር የምትችለው(መከራከር ያለባት) እሷን (በግልዋ) የሚመለከት የመከራከሪያ ነጥብ በማንሳት ነው፡፡ የክርክር አቀራረብ ስልትዋም ሆነ የማስረጃ አቀራረብዋም እንደዚሁ በግልዋ ባቀረበችው ክርክር የሚወሰን ነው፡፡ ይህም ማለት ከስዋ ጋር ተከሳ የነበረችው ሰው ያነሳችው ክርክር የስዋም የመከራከሪያ ነጥብ እንደሆነ ተደርጐ የሚወሰድበት አግባብ የለም፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበችውን የይርጋ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መታየት ያለበት ከዚህ አንፃር ነው፡፡ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የነበረችው እማሆይ ፀሃይነሽ ያቀረበችውን የይርጋ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር የሚያያዝበት አግባብ የለም፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸው አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የሆነችው በግልዋ በቀረበባት ክስ ምክንያት በመሆኑ ክሱን መከላከል የምትችለው የግልዋ የመከራከሪያ ነጥብ እና የመከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ከተመለከተው ድንጋጌ አንፃር የሚታይ አይደለም፡፡ የሥር ሰበር ችሎት የአመልካች የይርጋ መቃወሚያ እማሆይ ፀሃይነሽ ባቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ በተሰጠው ውሳኔ እልባት አግኝቶአል በማለት ያስቀመጠው ትችም ሆነ የደረሰበት መደምደሚያ ከሕጉ አተረጓጐም አንፃር ሲታይ መሰረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ የይርጋው መቃወሚያ በዚህ አግባብ ታይቶ ከመወሰኑ በፊት ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ መወሰኑም ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 30402 መስከረም 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡

2. የሰበር ችሎቱ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖችን እንደገና ካከራከረ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ መ·ልሳ በየቻ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ደበሌ በየቻ - በሌሉበት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት የተሰማ ክስ ላይ ማስረጃ ሳይሰማ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ ነበር፡፡ የተጠሪ ክስ የነበረው አመልካች በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ግምት ብር ሦስት ሺህ አንድ መቶ አሥራ አምስት ብር እንዲከፍል እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡

አመልካች (ሥር ተከሳሽ) ቀርቦ ባለመከራከሩ የሥር ፍ/ቤት በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ በከፍተኛው ፍ/ቤት እና በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፀንቷል፡፡

አመልካች በውሳኔው የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል በማለት ነሐሴ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ የቀረበው ክስ በከሳሽ ማስረጃ ሳይረጋገጥ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም ይህንኑ ለመመርመር ተጠሪ እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም መጥሪያ ተቀብሎ ባለመቅረቡ በሌለበት ጉዳዩ ተሰምቷል፡፡ እኛም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው አመልካች በተጠሪ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል መነሻ ተጠሪ ይገባኛል ያለውን የካሣ መጠን ገምቶ ክስ ያቀረበ ስለመሆኑ ነው፡፡ አመልካች (ሥር ተከሳሽ) ቀርቦ ባለመከራከሩ ጉዳዩ በሌለበት የተወሰነ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት የካሣውን መጠን እንደከሳሽ ጥያቄ የወሰነው ተከሳሽ ቀርቦ አልካደም በሚል ነው፡፡ ይህ አካሄድ ከሥነ-ሥርዓት አንፃር በአግባቡ ስለመሆኑ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 235(2) የሚደነግገው በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል የሚል ሲሆን ይህ ተፈጻሚነቱ ተከሳሽ ቀርቦ ክርክሩን ባሰማ ጊዜ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 83 እንደተመለከተው በመርህ ደረጃ በተከሳሽ በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ የሚቆጠር ቢሆንም የካሣ ጥያቄ ላይ ግን ይህ ግምት ተፈጻሚ ሊሆን እንደማይችል ነው፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀርቦ ያልተከራከረ ቢሆንም የዳኝነት ጥያቄው የካሣ ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን ቀርቦ እንኳ ቢከራከር ፍ/ቤቱ በማስረጃ ጉዳዩን ማጣራት እንዳለበት አመላካች ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ እንደ ክሱ ያስረዳልኛል ያለውን ማስረጃ ሰምቶ መወሰን ሲገባው ተከሳሽ ቀርቦ አልተከራከረም ወይም አልካደም በሚል ብቻ ውሳኔ መስጠቱ ከተጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ እና ከሥነ ሥርዓት ሕጉ የሙግት አመራር መርህ አኳያ ጉድለት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ይህ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05257 የሰበር ውሳኔ እና የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 27266 የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 88090 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት የሥር ከሳሽ (ተጠሪን) ማስረጃ ሰምቶ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መዝገቡን መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49660

ሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ጎሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡-1. መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ት/ቤት
2. መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ጽ/ቤት } ወኪል ይሁን አየነው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- መምህር ሲሳይ ደጀኔ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት አድርጐ የተደረገ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከየካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ከሕግ ውጪ ከመጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ መቋረጡን ገልጸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪን መቅጠሩን ሳይክድ ራሱ ያላሰናበታቸው መሆኑን ገልጾ ልጠየቅ አይገባም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን የተከራከረ ሲሆን አንደኛ አመልካች ደግሞ ተጠሪ የስራ ውልና ቅጥር የፈፀሙት ከሁለተኛ አመልካች ጋር በመሆኑ ክሱ እንደማይመለከተው በመጀመሪያ መቃወሚያነት ጠቅሶ የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ስንብቱ የተከናወነው ተጠሪ ከስራ ገበታቸው በመቅረታቸው፣የስራ ሰዓት ባለማክበራቸው እንዲሁም ያለፈቃድ በሌላ ቦታ እያስተማሩ እንደሚገኙ ገልጾ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተክራክሯል፡፡ የስር

ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኋላ በአመልካቾች በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ውድቅ አድርጐ በፍሬ ነገርም ማስረጃ ያለማቅረባቸውን ጠቅሶ አመልካቾችን ለክሱ ኃላፊ አድርጐ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች ነገረ ፈጅ ጥቅምት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ከስራ ከአምስት ተከትታይ የስራ ቀናት በላይ በመቅረታቸው ነው በሚል ገልፀንና ማስረጃም ቆጥረን እያለ ማስረጃዎቻችን ሳይታዩና ሳይሰሙ ማስረጃዎችን አላቀረቡም በሚል ምክንያት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካቾች የመከላከያ ማስረጃዎች ሳይሰሙ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ ቀርበው ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የአመልካቾችን የሰበር ቅሬታ ነጥቦች ተገቢ አለመሆን ያሳያሉ ያሏቸውን ነጥቦችን በመዘርዘር የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካቾች ነገረፈጅም የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ተጠሪ የስራ ውላቸው ያላግባብ የተቋረጠ መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ላቀረቡት ክስ አመልካቾች ስንብቱ ሕጋዊ ነው የሚሉበትን ምክንያት ጠቅሰው ለዚህም የሰነድና የሰው ምስክሮች ያሏቸው መሆኑን በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ማቅረባቸውን የስር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ በማስቀረብ ተመልክተናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አንደኛ አመልካች ተጠሪ ከስራ የቀሩ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ክስ የመከላከል ሕጋዊ መብት ያለው ሲሆን ፍርድ ቤት ይህንኑ መብቱን ሊያልፍ የሚገባው ተከራካሪ ወገን የቆጠረው ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን እርግጠኛ ሲሆን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 223፣234፣137፣249 እና 256 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ሊሰጥ የሚገባው የማስረጃ አቀራረብ ሥርአት ምዘና ሥነ-ሥርአቱ በሚያስቀምጠው መንገድ ተከናውኖ መሆኑን እነዚህ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ተከራካሪ ወገን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ ቆጥሮ እያለ ማስረጃ ሳይሰማ ፍርድ መስጠት የመከራከር መብቱን የሚያጣብብ ነው፣ ውሳኔውም ሕጋዊ ሥርአቱን ተከትሎ ተሰጥቷል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካቾች ከተጠሪ ጋር የተመሰረተው የስራ ውል የተቋረጠበትን ምክንያት በመከላከያ መልስ ማመልከቻው ላይ ከመግለፃቸውም በተጨማሪ ይህንኑ ፍሬ ነገር ለማስረዳት የሰነድና የሰው ማስረጃዎቻቸውን በመከላከያ ማስረጃው መግለጫ ዝርዝር ላይ ጠቅሰው እያለ እና የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘው ከማቅረባቸውም በላይ የቆጠሯቸውን የሰው ምስክሮችን ለማቅረብ ያልቻሉ መሆኑ ሳይረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ማስረጃ በደፈናው ማስረጃ አላቀረቡም በሚል ምክንያት ማለፉ ስለማስረጃ አቀራረብ ሥርአት የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ድንጋጌዎችን መሰረት ያላደረገ ነው፡፡ አንድ አሰሪ የስራ ውልን ለማቋረጥ ምክንያት ነው ብሎ በስንብቱ ደብዳቤ ላይ የገለፀውን ምክንያት ለማስረዳት የቆጠረውና አግባብነት ያለው ማስረጃ ሊሰማለትና ሊመዘንለት ይገባል፡፡ የኾው ሥርአት ሳይከናወን የሚሰጥ ፍርድ የተሟላ አካሄድ ተከትሎ የተሰጠ ነው ሊባል የማይችልና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በሥነ-ሥርአቱ መሰረት ማስረጃዎቻቸውን ዘርዝረው አቅርበው እያለ የቆጠሯቸው የሰነድና የሰው ምስክሮች ሳይታዩና ሳይሰሙ ማስረጃ አላቀረቡም በሚል የተሰጠው ውሳኔ የአመልካቾችን የመከላከል ሕጋዊ መብት ያጣበበ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 29808 ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 82545 ነሐሴ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ሰምቶ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት እ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 52525

ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ የትምወርቅ ሰብስቤ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሽዋረጋ ደመቀ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የአመልካች የክስ ምክንያት ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠበት ነው በማለት የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ለመሆኑ ለመመርመር ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር የእርሻ መሬት ይዞታን የሚመለከት ነው፡፡ ከሳሽ አመልካች ሆና ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ ተጠሪ ያለአግባብ የያዘውን የእርሻ መሬት እንዲለቀልኝ ስትል አመልካች በሸርካ ወረዳ ፍ/ቤት ክስ ያቀረበች ሲሆን ተጠሪ በተመሳሳይ ጉዳይ በመ/ቁ. 345/97 በ14/6/2001 ዓ.ም ውሳኔ ተሰጥቷል ሲል መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን የወረዳው ፍ/ቤት ቀደም ሲል በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ ያልተሰጠ እና ይልቁንም ከሳሽ ማስረጃ አሟልታ ክስ እንድታቀርብ መብት ተጠብቆላት መዝገቡ የተዘጋ መሆኑን ጠቅሶ መቃወሚያውን ውድቅ ማድረጉን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪውን መሬት ለአመልካች እንዲለቅ ወስኗል፡፡ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በጉዳዩ ላይ ቀደም ሲል ውሳኔ ተሰጥቶበታል ይህ ከሆነ ደግሞ በድጋሚ ሊታይ አይገባም (res judicata) በሚል የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ ቀድሞ ለአመልካች የተጠበቀ መብት የለም መዝገቡ በውሳኔ ተዘግቷል በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡

እኛም ከፍ ሲል ከተመለከተው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ የሻረው ጉዳዩ ቀድሞ ውሳኔ ያገኘ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን ከውሳኔው ተረድተናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ይዘት መረዳት የቻልነው አመልካች ቀደም ሲል ያቀረበችው ክስ በፍርድ ቤቱ ከተሰማ በኋላ የአመልካች ክስ ግልጽነት የሚጐድለውና ማስረጃም ያልተሟላ በመሆኑ ማስረጃዋን አሟልታ ክስ እንድታቀርብ መብት ተጠብቆላት መዝገቡ የተዘጋ ስለመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በፍሬ ጉዳዩ ላይ የተሰጠ ውሳኔ አለ ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ ሙሉ በሙሉ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ፍርድ አልሰጠም፡፡ ይልቁንም ማስረጃ አሟልተሽ ማቅረብ ትችያለሽ የሚል ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ይህ አካሄድ በመርህ ደረጃ አግባብነት ያለው ነው ባይሰኝም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 91/4/ በተደነገገው አግባብ ለጉዳዩ ፍትሐዊ ውሳኔ አሰጣጥ ይበጃል ብሎ ካመነ ፍ/ቤቱ ማሻሻያ እንዲደረግ ማዘዝ ይችላል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከዚህ ይልቅ አመልካች ማስረጃ አሟልታ ክስ እንድታቀርብ በማድረጉ ይህ ውሳኔው ሥነ-ሥርአታዊ አይደለም የሚለው ወገን በይግባኝ አስካላሻረ ጊዜ ድረስ ውሳኔውን መሰረት በማድረግ አዲስ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም ሊባል አይገባም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ ሌላ የቀድሞ መዝገብ ላይ በፍሬ ጉዳይ ረገድ የተሰጠ ውሳኔ ስለመኖሩ አልተጠቀሰም፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አጠቃላይ ይዘት ይህንን የመሰለ መሆኑን ከተገነዘብን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ መሰረት የሚሸፈን ነውን? የሚለውን እንመለከታለን፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ መሰረት በማድረግ ድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀድሚው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑ የተከራካሪ ወገኖች አንድነት ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑም መረጋገጥ አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀደም ሲል በተጠሪ ላይ ያቀረበችው ክስ በተመሳሳይ ፍሬ ነገር ላይ ቢሆንም በቀድሞ መዝገብ በፍሬ ነገር ረገድ የመጨረሻ ውሳኔ እንዳልተሰጠበት ይልቁንም አመልካች ክሷን በማስረጃ አሟልታ እንድታቀርብ መብት የተጠበቀላት መሆኑን ከፍ ሲል ተመልክተናል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ላይ በቀዳሚው መዝገብ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ይህ መለያ እስካልተሟላ ድረስ ደግሞ አመልካች ያቀረበችው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ሥር የሚሸፈን አይሆንም፡፡ ስለዚህም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በድጋሚ የቀረበ ነው (res judicata) በሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 5/1/ ይሸፈናል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በሌላ በኩል አከራካሪው መሬት የማን ነው የሚለውን በተመለከተም ማስረጃ በማጣራት የወረዳው እና ከፍተኛው ፍ/ቤት የተሻለ ማስረጃ የአመልካች መሆኑን ስለማረጋገጣቸው ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ስለሆነም በፍሬ ነገር ረገድ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ማስረጃ መሰረት ያደረገ መሆኑን ስለተገነዘብን ባለበት ሊፀና የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 88224 በ17/05/2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሸርካ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06008 በ4/7/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19080 በ24/11/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43331

ሐምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ገመቹ ቡቻላ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ በቀለ ኩማ(ቡቻላ) - በሌሉበት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ 22866 የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በማጽናቱ በውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ሲል አመልካች አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር የተያዘው ጭብጥ በተጠሪ በኩል ክስ የቀረበለት የወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም ያለውን የከፍተኛው ፍ/ቤት አጽንቶታል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩ የውርስ ክርክር ነውና የወረዳው ፍ/ቤት ሥልጣን አለው ካለ በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙ ወደ ወረዳው ፍ/ቤት ሳይመልስ መወሰኑ እና ቀደም ሲል በክልሉ ሰበር ችሎት የተወሰነ ነው ሲል የጠቀሰው መዝገብ ውሳኔ ይዘት አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪ እንዲቀርብ ታዟል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ተቀብሎ መልስ አልሰጠም በዚሁ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

እኛም የቀረበውን አቤቱታ ከሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ከአመልካች አቤቱታ መረዳት የተቻለው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ክርክር የውርስ ንብረት የሚመለከት ነው፡፡ ቀደም ሲል አመልካች የአባቴን የውርስ ንብረት ድርሻ ያካፍለኝ ሲል ተጠሪ ያቀረበው ክስ በቀበሌው በማህበራዊ ፍ/ቤት ታይቶ ከተወሰነለት በኋላ አመልካች እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 4665 በሰጠው ትእዛዝ የአሁን አመልካች (ሥር ተከሳሽ) የመከላከያ ምስክር ሳይሰማ ውሳኔ መስጠቱን በመንቀፍ ይህው እንዲፈፀም ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱን፣ከዚያም ክርክር ተደርጐ ከተወሰነ በኋላ በይግባኝ በድጋሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲደርስ ተጠሪው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የውርስ ንብረት መጠየቁ ተገቢ አይደለም ተብሎ መሻሩን ተጠቅሷል፡፡ እንግዲህ ለአሁኑ የሰበር ማመልከቻ መነሻ የሆነው ክርክር ከዚህ በኋላ በእደሳ መልክ የተጀመረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ካገኘ በኋላ የውርስ ንብረት ክፍያ ጥያቄ ለወረዳው ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ወረዳው ፍ/ቤት የክልሉን የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 110/99 በመጥቀስ የይዞታ ክርክር በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት መታየት አለበት ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤቱም ይህንኑ አጽንቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ውሳኔ ለመስጠት የጠቀሰው ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል ያለው ክርክር የውርስ ንብረት የሚመለከት በመሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት ሥልጣን አለው የሚል ነው፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ይህንን የመሰለ መሆኑን ከተረዳን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፍሬ ነገሩ ላይ ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ በግልጽ እንደተመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር በመጀመሪያ መቃወሚያ ብቻ የወሰነውን ውሳኔ የለወጠ እንደሆነ የሥር ፍ/ቤት ወደ ክርክሩ ገብቶ እንደገና እንዲመለከተው መዝገቡን ሊመልስለት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በርግጥ የዚህ ድንጋጌ የተቀመጠው መሪ ቃል አስገዳጅ ሆኖ አይታይም፡፡ ነገር ግን በግራ ቀኙ በኩል የሚቀርቡት የፍሬ ነገር ክርክሮች እና ማስረጃዎች በአግባቡ ለማጣራት ይቻል ዘንድ ለሥር ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመለሱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በተለይም በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ክርክር ከመመርመር እና ማጣራት አንፃር የመጨረሻው የሥልጣን እርከን በመሆኑ የግራ ቀኙን የይግባኝ እድል የሚያጣብብ መሆኑንም መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ የመ/ደረጃው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ስልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን መዝጋቱ እንጂ አመልካች ያነሳው የይርጋ ክርክርም እልባት ያልተሰጠው ነጥብ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት በተገቢው ሥነ-ሥርአት ክርክር ያልተደረገበትን ፍሬ ነገር ጉዳይ በዚያው አጠቃሎ ውሳኔ መስጠቱ የሙግት አመራር እና የሥነ-ሥርአቱን የሥልጣን ክፍፍል መነሻ ሐሳቦች በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ከሥነ-ሥርአት መርህ አንፃር ስሕተት ያለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከዚህም ሌላ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ በይዘቱም ሲታይ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ማቅረቡ ተገቢ አልነበረም ሲል ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ጉዳዩ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶ በአዲስ መልክ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ይዞ ክስ አቅርቦ በሥልጣን ጉዳይ ውሳኔ ተሰጥቶበት ከፍተኛው ፍ/ቤት ያፀናውን ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሁለት የከፍተኛ ፍ/ቤት መዛግብት በማጣመር የሰጠው ውሳኔም ሥነ-ሥርአቱን ተከትሎ የቀረበ አይደለም፡፡ በመጨረሻም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የጠቀሰው የሰበር መ/ቁ. 4665 ንብረት ይከፋፈሉ የሚል ሳይሆን የአመልካች የመከላከያ ምስክር እንዲሰማ ወደ ሥር ፍ/ቤት የተመለሰ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የግራ ቀኙ የፍሬ ነገር ክርክር በጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአግባቡ ያልተጣራ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 22866 የሰጠው ውሳኔ ከሙግት አመራር መርህ እና ሥነ-ሥርአት አንፃር መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎትም ይህንኑ ማረም ሲገባው ማለፉ ተገቢ አይደለም፡፡

ስለሆነም ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22866 በ26/03/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 24680 በ27/4/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሎ ተከታዩ ተወስኗል፡፡
2. የግራ ቀኙ ክርክር የውርስ ጉዳይ ነውና የወረዳው ፍ/ቤት የመዳኘት ሥልጣን አለው ሲል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን የፍሬ ነገር ክርክር የወረዳው ፍ/ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሰረት መልሰናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36730

ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ አማረ ገላው - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 27947 መጋቢት 8 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20224 መጋቢት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላመለከተ ነው፡፡

በዚህ መዝገብ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 164 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ እውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸውን መብቶች ለማስከበር የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ጥያቄ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት ኅዳር 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ/ አመልካች/ የደረጃ እድገት እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪ ያቀረበው ክስ ከዚህ በፊት በፍርድ ያለቀ ነው፡፡ የከሳሽ /ተጠሪ/ ክስ በይርጋ ይቋረጣል የደረጃ እድገት በወድድር የሚሰጥ በመሆኑ ከሳሽ ይገባኛል በማለታቸው የሚሰጥ አይደም የሚል ክርክር ለወረዳው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ቀደም ብሎ በአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የደረጃ እድገት እንዲሰጣቸው ክስ አቅርበው የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ውሣኔ ከሰጠላቸው በኋላ የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለጽ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የቦርዱን ውሣኔ የሻረ በመሆኑ ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አልተሰጠበትም፡፡ ክስ በይርጋ ይቋረጣል የሚለው የተከሳሽ/የአሁን አመልካች/ መቃወሚያ በተመለከተ የአሁን ተጠሪ ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተደነገገው የጊዜ ገደብ ሣያልፍ ክስ አቅርቦ የነበረና ክርክር ሒደት እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ደርሶ ቦርዱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን እንደሌለው የተወሰነ በመሆኑ ተጠሪ ለቦርዱ የቀረበው ክስና ክርክር የይርጋው ጊዜ የማያቋርጥ ነው በማለት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ በመቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪና አመልካች በዋናው ጭብጥ ላይ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ለተጠሪ የደረጃ እድገቱን ሊሰጣቸው ይገባል የሚል ውሳኔ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ነገረ ፈጅ መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የአቤቱታቸውን ፍሬ ነገርም የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪ ክስ በይርጋ ይቋረጣል በማለት ያቀረብነው የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ያለፈብን አላግባብ ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የመስጠት የሥራ- ነገር ሥልጣን ለሌለው አካል ማለትም ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ያቀረቡ በመሆኑ የይርጋው ጊዜ መቆጠሩን ያቋርጠዋል በማለት የሰጠው ብይን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 አንቀጽ 164 እና አንቀጽ 147 ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው የወረዳው ፍርድ ቤት ብይን ስለ ይርጋ መቋረጥ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1851/ለ/ የተደነገገውን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ይኸም ቢታለፍ ያለ ውድድር ለተጠሪ የደረጃ እድገት እንድንሰጥ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኛችንን በመሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር የሚጣራ ነጥብ ያለው በመሆኑ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ተጠሪ ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የሚያከራክራቸው ጉዳይ አመልካች ላወጣው የሥራ መደብ የትምህርት ማስረጃዬን ማለትም ለመወዳደር የሚያስችለኝን ዲፕሎማ በማያያዝ ለውድድር ስቀርብ ዲፕሎማውን ሥራ ስትቀጠር ያላስመዘገብከው ስለሆነ እንደማስረጃ አይያዝልህም ብሎ ስለከለከለኝ እየሰራሁ ተምሬ በዲፕሎማ የተመረቅሁበት በፐርቸዚንግ የሥራ ሙያ ያወጣው የሥራ መደብ ብቸኛ ተወዳዳሪ ሆኜ ቀርቤ በእድገት ሊሰጠኝ ሲገባ አላግባብ ሲከለክለኝ በወቅቱ አቤቱታዬን ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ አቅርቤ ቦርዱ የሥራ መደቡ ሊሰጠኝ እንደሚገባ ወስኗል፡፡ አመልካች በውሣኔው ቅር ተሰኝተው ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶት ነበር፡፡ አመልካች ውሣኔው የሕግ ስህተት አለበት በማለት ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው ችሎቱ የግራ ቀኞችንን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩ የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም በሚል ምክንያት የቦርዱንና የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮታል፡፡ ከዚህ በኋላ የሰራተኛ ማህበሩና አመልካች ባደረጉት ውድርድር አመልካች የእኔንና የሌሎች ሰራተኞችን ዲፕሎማ ተቀብሎ መድቦኛል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወሰነው መሰረት ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረብኩትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ለቦታው የቀረብኩ ብቸኛ ተወዳዳሪ በመሆኔ አመልካች ያቀረበው የይርጋ እና የፍሬ ጉዳይ ክርክር የሕግ መሰረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በጽሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካችና ተጠሪ በጽሑፍ ያቀረቡት ክርክር ይዘት በእጭሩ ካላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪ ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎችና ይህ የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 16648 ከሰጠው የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ውሣኔ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካችና ተጠሪ ካቀረቡት ክርክር ለመገንዘብ እንደቻልነው በመጀመሪያ ተጠሪ አመልካች ሥራ ከተቀጠርኩ በኋላ ያገኘሁትን የትምህርት ማስረጃ /ዲፕሎማ/ በመቀበል ብቸኛ ተወዳዳሪ በሆንኩበት የሥራ መደብ የደረጃ እድገት ሰጥቶ ሊመድበኝ ይገባል የሚል ክስ ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ አቅርበው ቦርዱ የአመልካችንና የተጠሪ ክርክር ከሰማ በኋላ ውሣኔ ሰጥቶ ነበር፡፡ አመልካች የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቦርዱን ውሣኔ በማጽናቱ አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው የሰበር ችሎቱ ጉዳዩ የውል የሥራ ክርክር ሣይሆን የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን የማየት የሥራ-ነገር ሥልጣን የለውም በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 28690 ኅዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ከዚህ በኋላ ለደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት ኅዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ አመልካች የደረጃ እድገት እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የተጠሪ ክስ በይርጋ ይቋረጣል በማለት ያቀረበው መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች በሥርና በሰበር የሚከራከረው ተጠሪ የመጀመሪያውን ክስ ያቀረበው ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ ለመስጠት ሥልጣን ለሌለው አካል መሆኑ ይህ የሰበር ችሎት በሰጠው ውሣኔ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ለሌለው አካል ያቀረበው ክስ የይርጋ ጊዜ መቆጠርን አያቋርጠውም በማለት ሲሆን ይህ የአመልካች ክርክርና ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ለሌለው ፍርድ ሰጭ አካል ክስ ማቅረብ ይርጋ አያቋርጥም በማለት በስር መዝገብ ቁጥር 16648 የሰጠውን የሕግ ትርጉም በአጠቃላይ በሕግ የይርጋ የጊዜ ገደብ መደንገግ ካስፈለገበት መሰረታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያትና ፍርድ ቤቶችና ሌሎች የዳኝነት ነክ ሥልጣን ያላቸው አካላት አንድ ጉዳይ ሲቀርብላቸው ሌላኛውን ተከራካሪ ከመጥራታቸው በፊት ስላለባቸው ግዴታና ኃላፊነትና የይርጋ የሕግ ድንጋጌዎችና ይርጋ የሚቋረጥባቸውን ሁኔታዎች መሰረታዊ አተረጓጎም መርሆች በመመርመር ውሣኔ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ጉዳዩ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ላለው አካል ክስ መቅረቡና ክርክር መካሄዱ ይርጋን አያቋርጥም በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ሕግ አውጭው በተለያዩ የሕግ ማእቀፎች መብት አሉኝ ወይም መብቱ ተጥሶብኛል የሚል ማናቸውም የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት መብት ያለው አካል በማቅረብ መብቱን የሚጠይቅበትን የጊዜ ገደብ በሕግ ከሚደነግግበት መሰረታዊ ዓላማ አንፃር መታየት ያለበት ነው፡፡ ሕግ አውጭው ማናቸውም ሰው በሕግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክሱን ለፍርድ ሰጭ አካላት ካላቀረበ ጥያቄው በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን በሕግ የሚደነግግበት አንደኛው ምክንያት መብት አለኝ ወይም መብቴ ተጥሶብኛል የሚል ሰው ተገቢውን ትጋት በማድረግ በሕግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ መብቱን እንዲጠይቅ ለማድረግና መብቱን በሕግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልጠየቅ ዳተኛ የሆነ ሰው ጊዜው ካለፈ በኋላ ክስ የማቅረብ መብቱን ለመገደብና መብቱን ቀሪ በማድረግ ሕግ ማእቀብ መጣልና መቅጣት ነው፡፡ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በተመለከተ የአሰሪና ሰራተኛ የሥራ ክርክር ችሎትና የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተሰጣቸው ስልጣንና ኃላፊነት ያለ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 138 እና ከአዋጅ አንቀጽ 147 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ መብቱን ለማስከበር ተገቢውን ጥረት ማድረግ የደረጃ እድገት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ወሳኝ ቦርድ ነው በሚል እምነት ክሱን ለቦርድ ያቀረበ ሲሆን ቦርዱም ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለኝ በሚል እምነት ተከሳሹ አለኝ የሚለውን ክርክር እንዲያቀርብ መጥሪያ ልኮ የከሳሽና የተከሳሽ ክርክር በመስማት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የቦርዱን ውሣኔ በይግባኝ የተፈፀመ የሕግ ስህተት ካለ መርምሮ የማረም ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቦርዱ ውሣኔ የሰጠው በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሰረትና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት መሆኑን በማረጋገጥ አጽንቶታል፡፡ የትኛው ጉዳይ የግል የሥራ ክርክር ነው?፣ የትኛው የደግሞ የወል የሥራ ክርክር ባህሪ ይኖረዋል? የሚለውን በመተርጎም ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 28690 ቦርዱ ሥልጣን የለውም በማለት መወሰኑ ተጠሪ ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ክስ አቅርቦ እስከ ሰበር ድረስ በተከራከረበት ጊዜ ውስጥ ይርጋ ሊቋረጥለትና ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 182 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ይርጋው እንደ አዲስ ሊቆጠር አይገባውም በማለት ተጠሪ የሚያቀርበው ክርክር በሕግ የይርጋ የጊዜ ገደብ መደንገግ ያስፈለገበትን አጠቃላይ መሰረታዊ ዓላማ ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. በሁለተኛ ደረጃ አመልካች ተጠሪ የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የሌለው በመሆኑ ለቦርዱ ያቀረበው ክስ ይርጋው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 164 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት አይቋርጥም በማለት ያቀረቡት ክርክር ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ሥልጣን በሕግ የሰጠው ሌላ አካል የከሳሽ ክስ ከተቀበለ በኋላ ለተከሳሹ መጥሪያ ከመላኩ በፊት በሕግ እንዲያደርግ ከተጣለበት ግዴታና ኃላፊነት አንፃር መታየት አለበት፡፡ አንድ ጉዳይ ዳኝነት አይቶ ውሣኔ እንዲሰጥ የክስ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት ወይም በሕግ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የተሰጠው አካል ለተከሳሹ ክስ አቤቱታውን ከመጥሪያ ጋር በመላክ ከማከራከሩ በፊት የክስ ማመልከቻውን መመርመርና ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የስረ-ነገር ወይም የግዛት ክልል ስልጣን የሌለው መሆኑን ከተረዳ የቀረበለት የክስ አቤቱታ አይቶ የመወሰን ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለጽ ውሣኔ ሊሰጥ እንደሚገባው ከፍትሐብሔር ሥነ- ሥርአት ሕግ ቁጥር 9 እና 23 ንኡስ አንቀጽ 1/ለ/ ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ወይም ከሕግ የዳኝነት ነክ ሥልጣን የተሰጠው አካል የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የሚችል መሆኑን በማመን ከሳሽ ከተከሳሹ መጥሪያ እንዲያደርስ ትእዛዝ ከሰጠና ተከሳሽም የፍርድ ቤቱን መጥሪያ ወጭ በማድረግ ለተከሳሹ በማድረስ አሳውቆ ከሆነ ይርጋው የሚቋረጥ መሆኑ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1851/ለ/ የተደነገገው ድንጋጌ ከሳሽ ክሱን ሰምቶ ለመወሰን ለሚችል አካል የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ዋንኛው ኃላፊነት የክስ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤት ለተከሳሹ መጥሪያ ከመላኩና ክርክር መስማት ከመጀመሩ በፊት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን መመርመርና መወሰን እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ክርክሩ ይህንን ያሕል ጊዜ የፈጀው ተጠሪ ክሱን ለአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ በማቅረቡ ምክንያት ብቻ አይደለም፡፡ የተጠሪን ክስ የተቀበለው ቦርድ ጉዳዩን ከማየቱ በፊት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው መሆኑን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 231 ንኡስ አንቀጽ 1/ለ/ መሰረት በመመርመር ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የለኝም በማለት ተወስኖ ጉዳዩን ባለመዝጋቱ ምክንያት ነው፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የዳኝነት ነክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጣን የተሰጣቸው አካላት በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት በአግባቡ ባለመወጣታቸው ወይም ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያላቸው ወይም የሌላቸው ስለመሆኑ የሕጉ ድንጋጌ አሻሚ፣በጠቅላላ አነጋገር የተገለፀና ክፍተት ያለበት በመሆኑ ምክንያት አከራካሪና የሕግ ትርጉም መስጠት የሚያሰፈልገው በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩን መወሰን ሥልጣን እንዳላቸው በመተርጎም ክርክሩን ሲሰሙ ለቆዩበት ጊዜ ይርጋው አይቋረጥም በሚሉት ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብቱ ይርጋ እንዲታገድ የሚደረግበት ምክንያት የለም፡፡ በእነዚህ አይነት ሁኔታ የይርጋ ጊዜ መቆጠሩ መቋረጥና ከሳሽ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1852 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት ሥልጣን ላለው አካል ክሱን ሲያቀርብ እንደአዲስ ይጋው ሊቆጠርለት የሚገባ በመሆኑ አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

3.አመልካች ያቀረበው ክርክር ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮችን ለፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 ከደነገጋቸው ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ የይርጋ የሕግ ድንጋጌዎች መብታቸውን ለመጠየቅ ተገቢውን ትጋት ያደረጉና ዳተኛ ያልሆነ ሰዎች ፍትህ የማግኘት መብት በማያሣጣ ሁኔታ በጠባቡ ሊተረጐሙና ፍትህ የማግኘት መብትን በሚያረጋግጥ መንገድ ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ መብታቸውን ለፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል የሕጉ የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ለማቅረብ ተገቢውን ትጋት ያደረጉ ሰዎች ላይ የይርጋ ጊዜ መቆጠሩ እንዲያቋረጥ የሚያደርግ የሕግ አተረጓጐም በመጠቀም የይርጋ ጊዜ አላግባብ እንዲቆጠር በማድረግ የዜጐች ፍትህ የማግኘት መብት እንዳይሸራረፍና በዚህ ምክንያት የፍትህ መዛባት እንዳይደርስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ውስጥ የውል የሥራ ክርክር አይቶ የመወሰን ሥልጣን ባለው የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ክሱን አቅርቦ ክሱ በቦርዱና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በአግባቡ ያቀረበ መሆኑን አረጋግጠው ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡ ጉዳዩ የወል የሥራ ክርክር ነው? ወይስ የግል የሥራ ክርክር? የሚለው እስከ ሰበር ድረስ ያከራከረ ጭብጥ ሲሆን ጭብጡ ይህ በሰበር ችሎት የወሰነው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመስጠት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተጠሪ በመጀመሪያ ክሱን ያቀረበው ሥልጣን ለሌለው አካል ስለሆነ ይርጋው ሊቋረጥ አይገባም በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር መብቱን ለማስከበር ተገቢውን ትጋት በማድረግ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ክስ ያቀረበውን የተጠሪን ሕገ-መንግስታዊ ፍትሕ የማግኘት መብት በሚያጣብብ ሁኔታ ችሎቱ የሕግ ትርጉም እንዲሰጥ የሚጠይቅ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

4. እያንዳንዱ የይርጋ ሕግ ድንጋጌ በራሱና በጠበበ ሁኔታ መተርጐም አለበት የሚለው የሕግ አተረጓጐም መርህ ከላይ የገለጽነውን የዜጐች ፍትህ የማግኘት መብት በማያጣብብ እና አላግባብ የይርጋ ጊዜ እንዲቆጠር በማድረግ የሚደርስ የፍትህ እጦት ለማስቀረት በሚችል መንገድ ተግባራዊ መሆን ይግባዋል፡፡ ይህ አተረጓጐም እኛ ብቻ ሣንሆን የዳበረ የሕግ ሥርአት ያላቸው አገሮች “Limitation periods are to be construed strictly so as not to take away the right of the plaintiffs” በሚል መንገድ የሚከተሉት አተረጓጐም ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በሰበር መዝገብ ቁጥር 16648 የተሰጠውን ትርጉም ለማጠናከር የተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሥነ- ሥርአት ሕግ ቁጥር 278 ንኡስ አንቀጽ 3 በጠባቡና በድንጋጌው ግልጽ በተመለከተው ጉዳይ ብቻ እንዲያገለግልና ተፈፃሚነት በሚኖረው ሁኔታ መጠቀስና መተርጐም ይኖርበታል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መልእክትና ይዘት በስፋት በመተርጐምና የማመሣሰል የትርጉም ዘዴ (Analogy) በመጠቀም ሥልጣን ለሌለው ፍርድ ሰጭ አካል የቀረበ ክስ ይርጋን አያቋርጥም በሚል መንገድ የተሰጠው ትርጉም ከላይ የዘረዘርናቸውን መሰረታዊ የይርጋ ሕግ አተረጓጐም መርሆች የሚጥስ መሻሻል ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜ ገደብ የሚቆጠርበት፣ የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚራዘምበት፣ የይርጋ የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚታገድበት (የሚቋረጥበትን) ሁኔታ ሲተረጉሙ ፍትህና ርትእን መሰረት በማድረግና የይርጋው ድንጋጌ አላግባብ ተፈፃሚ እንዲሆን በማድረግ ምክንያት የሚደርሰውን የፍትህ ማዛባት የሚቀነስ የአተረጓጐም ሥልት መከተልና በሕጉ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ መብታቸውን ለመጠየቅ ተገቢውን ትጋት ያላደረጉና ዳተኛ የሆኑ ሰዎች ክስ የማቅረብ መብት ላይ ማእቀብ በሚጥል መንገድ ብቻ ሕጉን በሥራ ላይ በማዋል የይርጋ የሕግ ድንጋጌዎች በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 የተደነገገውን ፍትህ የማግኘት መብት በማያጣብብና የማይሸራርፍ መንገድ መተርጐምና ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው በመሆኑ አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 በዘረዘርናቸው መሰረታዊ ምክንያቶች ከዚህ በፊት አምስት ዳኞች ተሰይመው በመገብ ቁጥር 16648 የይርጋ ጊዜ አቆጣጠርና ስለ ይርጋ መቋረጥ የሰጡትን የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 4 በሚደነግገው መሰረት በመለወጥና የሕግ ትርጉም በመስጠት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ተጠሪ ያለ ውድድር እድገት ሊሰጠው አይገባም በማለት ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ አመልካች ያቀረበውን ክርክር ለማስረዳት አለመቻሉንና በአንፃሩ ተጠሪ ክርክሩን ያስረዳ መሆኑን በማረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡ አመልካች ለቦታው ብቁ የሆኑ ሰራተኞች እንዲወዳደሩ ማስታወቂያ ያወጣና ተጠሪ መስፈርቱን አሟልቶ ያቀረበ ብቸኛ ተወዳዳሪ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጡበት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ለሰበር ችሎት ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ክርክር በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የወረዳውና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት አጽንተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል የደሴ ወረዳ ፍርድ ቤትና የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ሥልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ክስ ቀርቦ ክርክር ሲደረግ መቆየቱ የይርጋ ጊዜ መቆጠሩን ያቋርጠዋል ብለናል፡፡
3. የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 50376

ሀምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ገሠሠ - ጠበቃ አቶ መከተ ዳኘው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07/08 አስተዳደር ጽ/ቤት

ነገረ ፈጅ አቶ ወንድሙ አድማሱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ችሎት ጥቅምት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ችሎት አመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን የቤት ኪራይና የቤት ባለቤትነት ክርክር ተጠሪ አመልካችን መጥሪያ ለማድረስ በአድራሻቸው አፈላልጎ ማግኘት ባለመቻሉ መጥሪያው ፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ እንዲለጠፍለት ባቀረበው ቃለመሀላ መሠረት መጥሪያው በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ ተለጥፎ አመልካች ባለመቅረባቸው ጉዳዩን አመልካች በሌሉበት አይቶ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ታህሳስ 4 ቀን 2000 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የምትከራከረው በቤት ጉዳይ መሆኑና የመኖሪያ ቤቱ እየታወቀ በሀሰት ተፈልጋ አልተገኘችም ተብሎ ቃለመሃላ ቀርቦ ጉዳዩ በሌሉበት የተሰጠው ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 78 መሠረት ተነስቶ ክርክሩ እኔ ባለሁበት እንዲሰማ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ላይ ካከራከረ በኋላ አመልካች ያቀረቡት ምክንያት የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ ታህሣሥ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ የሚነሣበትና ክርክሩ እንደገና የሚታይበት ምክንያት ያለም በማለት የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች መጥሪያ ለማድረስ ከመኖሪያ ቤቱ የመጣ ሰው የለም፡፡ ተጠሪ የመኖሪያ ቤቴንና አድራሻዬን በሚገባ ያውቀዋል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ በአካል ለእኔ ማድረስ እየቻለ ያላደረሠ ሲሆን ይኸም ቢታለፍ መጥሪያው እኔ ላየው በምችለው ቦታ በመኖሪያ ቤቱ ላይ መለጠፍ ሲገባው እኔ ልደርስበት በማልችል ቦታ መጥሪያው እንዲለጠፍ በማድረግ የፍርድ ባለመብት የሆንኩበት ውሣኔ በሌለሁበት የተሻረ መሆኑን በመረዳት ፍርዱ ተሰርዞ ወደ ክርክሩ እንደገባ ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ለአመልካች መጥሪያ ለማድረስ የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚደነግገው መሠረት ተገቢውን ጥረት አድርገናል ስለዚህ አመልካች በአግባቡ መጥሪያ ሳይደርሰኝ አላግባብ በሌለሁበት ታይቶ ውሣኔ ተሰጥቶብኛል በማለት የሚያቀርቡት ክርክርክ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በህጉ የተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት መጥሪያ አልደረሰኝም በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ የሚሠረዝበት ምክንያት የለም በማለት የተሰጠው ብይን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በህጉ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ መጥሪያ ደርሷቸዋል ወይስ አልደረሣቸውም የሚለው ነጥብ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ጠቀሜታ አለው፡፡ አመልካች ተጠሪ እኔን ፈልጎ አላጣኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ፈልጌ አላገኘኋቸውም በማለት በቃለ መሀላ አረጋግጧል፡፡ ተጠሪና አመልካች የሚከራከሩት በቤት ኪራይና በአመልካች ወጭ የተሠራ ቤት ባለሀብቱ ማን ነው በሚለው ጭብጥ ዙሪያ ነው፡፡ ተጠሪ የአመልካች የቤት አከራይ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን የመኖሪያ ቤት ቁጥር በሚገባ ያውቃል፡፡ ተጠሪ አመልካች የምትኖርበት ቤት ባለቤት ነው፡፡ መጥሪያ ለማድረስ በአማራጭ መጥሪያ ማድረሻ መንገዶች መጠቀም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ መከሰሱንና ፍርድ ቤት ክርክር ያለበት መሆኑን ለማወቅ የሚያስችለውን የተሻለውን አማራጭ የመጠቀም ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤትም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በአካል ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የአመልካች የመኖሪያ አድራሻ በተጠሪ በኩል የሚታወቅና የአመልካችና ተጠሪ የክርክር መንስኤ መሆኑ በመዝገቡ ተመልክቷል የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪ አመልካችን በአድራሻቸው ፈልጌ አላገኘናቸውም በማለት ቃለመሀላ ሲያቀርብለት መጥሪያው በፍርድ ቤቱ ግቢ ውስጥ እንዲለጠፍ ማድረጉ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም አመልካች የመኖሪያ አድራሻ በግልፅ የሚታወቅ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 105 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መጥሪያው በአመልካች የመኖሪያ ቤት ላይ እንዲለጠፍ ትዕዛዝ መሰጠት ነበረበት፡፡ ስለሆነም አመልካች በህጉ የተደነገገው ቅደም ተከተል መሠረት መጥሪያ በወቅቱ በአግባቡ እንዲደርሣቸው ሣይደረግ ክርክሩ ታይቶ መወሰኑ ስለተረጋገጠ የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካች በሌሉበት በማየት ታህሣሥ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 78 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በመሠረዝ አመልካች በክርክሩ ገብተው የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሣኔ መሰጠት ሲገባው ታህሣሥ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠሁትን ውሣኔ የማነሳበት ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጥቅምት 6 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አመልካች በሌሉበት አይቶ ታህሣሥ 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የሰበር ችሎት ጉዳዩን እንደገና አመልካች ባሉበት አይቶ ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎችን /ክቅጽ 1 - 7 / ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ቅጽ - 1

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
1	18180	የኬ.ኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ ሰራተኞች ማህበር እና የኬ.ኬ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ	የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ስልጣን፣ የሰራተኛ ቅነሳ ጉዳይን በሚመለከት ስለሚነሳ ክርክር አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 138(1),147	ሐምሌ 29/1997
2	15493	አቶ ጳውሎስ ሩምቾ እና ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ	በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,2024	ሐምሌ 29/1997
3	17361	ወ/ሮ ጋዲሴ ኢርጌ እና ወ/ሮ ወርቅአንጥፉ በቀለ	በስነ-ስርዓት ህጉ የጊዜ ገደብን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.49, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856	ሐምሌ 25/1997
4	17352	ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/ የግ/ ማህበር እና የነገው ሰው ትምህርት ቤት	ተገቢው ዳኝነት ክፍያ ሳይፈፀም በፍ/ቤት በቀጠለ ክርክር ስለማፈፀም ስርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.215,320(2),207,211(2)	ሐምሌ 28/1997
5	14605	የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና እነ ኮሜት ትራንስፖርት ድርጅት (ስድስት ሰዎች)	በመንገዝ ላይ የነበሩ ዕቃዎች መጎዳት በሰው ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን የግጭት አደጋ ለማስወገድ በተወሰደ ርምጃ የደረሰ የመኪና መገልበጥ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ስላለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 590,591, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1792	ሐምሌ 29/1997
6	17068	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ሚ/ር ቢሮኒ አቲክፖ	በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856,2024, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 89	ሐምሌ 19/1997
7	14974	ወ/ት ማህሌት ገ/ስላሴ እና እነ አቶ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች)	አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ባቀረበው ክስ ወካዩን ወክሎ መከራከር ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2188, 2189, 2208, 2209, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 57,58	ሐምሌ 28/1997
8	14184	አቶ ውርጌሳ ታደሰ እና እነ አቶ መለሰ ተካ (ዘጠኝ ሰዎች)	ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73	ሐምሌ 29/1997
9	14047	ዶ/ር ዳንኤል አለሙ እና እነ ወ/ሮ ሮማን ወርቅ የማነብርሃን (ሦስት ሰዎች)	በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1856, 2024	ሐምሌ 28/1997
10	15835	ሼል ኢትዮጵያ አ/ማ እና ወ/ሮ አስቱር ብርሃነ ስላሴ	ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የተከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70,233	ሐምሌ 29/1997
11	15992	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ወ/ት ሶስና አስፋው	በህግ የተደነገገው የውል አፃፃፍ /ፎርም/ የተቀመጠ ደንብ አለመፈፀም ስለሚያስከትለው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719, 1720 (1), 1723, 1726, 1727, 1845	ሐምሌ 19/1997
12	17191	ወ/ሮ አስቱር አርአያ እና አቶ ግርማ ወይጆ	በአንዳንድ ውሎች የተመለከተን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለመቀነስ ፍ/ቤት ስላለው ስልጣን የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711, 1731, 1676(2), 2635, 2640, 2646	ሐምሌ 29/1997

ቅጽ 2

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
13	13223	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አስፋው አበበ	ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ባይቀርብለትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማንኛውም ዓይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪ እንዲቀርብለት መስጠት ስላለበት ትዕዛዝ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2) 342, 345(1)(ለ)	ጥቅምት 9/1998
14	14414	የጊምቢ ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት እና ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ	በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ከመ/ቤቱ ጋር ባለው ስራ ክርክር የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 2(1),3(2)(ሠ)	ጥቅምት 1/1998
15	15270	የመቶ አለቃ ተሻገር አስታጥቂ እና አቶ አዊል አው አብዲ	በክተማ ቦታ ላይ ስለሚኖር መብት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33(2), 231, (1)(ሀ), አዋጅ ቁ.47/67	ጥቅምት 28/1998
16	15410	አቶ ተሾመ ጅፋር እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን	አጠቃላይ የአሰሪን የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ስርዓትን ላይሆን የግል ጥቅምን መሰረት አድርጐ የሚቀርብን የደመወዝ ጭማሪ ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 147	ጥቅምት 1/1998

https://t.me/ethiopianlegalbrief

17	16273	የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገንታ ገምአ	ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠርኩ እንደሆንኩ ብቻ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄን የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ እና የግል ጥቅምን መሰረት አድርጐ የሚቀርብን የጥቅማጥቅም ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 9,10, 138, 142, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33	ጥቅምት 22/1998
18	16624	ወ/ት አጅጋየሁ ተሾመ እና የኢቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) መሰረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)	ጥቅምት 18/1998
19	16720	ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ እና እነ የመካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት (አራት ሰዎች)	በከፊል የፍርድ ባለመብት የሆነ ሰው ባለመብት የሆነበት የፍርድ ክፍል እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ክስ ካቀረበ በኋላ በመጀመሪያ የፍርድ ባለዕዳ የሆነበትን ፍርድ በይግባኝ አሸሮ የፍርድ ባለመብት ሲሆን አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ቀደም ሲል የተከፈተው የአፈፃፀም መዝገብ ቢዘጋም እንኳን ማንቀሳቀስ ስለመቻሉ እና በአፈፃፀም ደረጃ ወለድ የሚከፈለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ከተወሰነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378(3)(ሰ)	ጥቅምት 22/1998
20	16896	ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና የኢ.ሊ.ባ.ቦር ዞን ትምህርት መምሪያ	የተዋዋዮች በውሉ አለመግባባት ሲፈጠርና ጉዳዩን በገላጋይ ዳኞች እንዲታይ ሲስማሙ ፍ/ቤት ይህንን ስምምነት ማስፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711,1731(1)	ጥቅምት 16/1998
21	17077	ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ	የዕዳ መክፈያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ባለገንዘቡ ለባለዕዳው የሚያደረገው የዕዳ ክፍያ ጊዜ ማራዘም ዋሱን ከዋስትናው ነፃ የሚያደርገው ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1928(1)እና(2)	ጥቅምት 14/1998
22	17189	የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጭ ድርጅት እና አቶ ንጉሴ ዘለቀ	በአሰሪ "ገንዘብ" ላይ ሰራተኛው ያደረሰው ጉዳት በአሰሪው "ንብረት" የደረሰ ጉዳት ስለመሆኑ እና ሰራተኛ የስራ ውሉ ተቋርጦ ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 27(1) (በ), 53(1),54	ጥቅምት 17/1998
23	17429	ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ እና አቶ ተስፋዬ ከበደ	በግልጽ በሚደረግ ጉባዔ ጉባዔው መነበቡን የሚያመለክት ከሆነ በግልጽ "ተነቧል" የሚል ቃል አለመኖሩ ጉባዔውን ፈራሽ የሚያደርግ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881	ጥቅምት 21/1998
24	17533	የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና ሙሉ ብርሃን	የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሰረት የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ በማድረጉ ወይም ዴክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት በዕቃው ባለቤት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 2(18), 43(1) (ሀ)	ጥቅምት 18/1998
25	17712	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት እና የወ/ሮ ሳዲያ እስማኤል ወራሾች	በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1), 1196 (1)	ጥቅምት 16/1998
26	18307	ንብ ትራንስፖርት አ.ማ. እና አቶ ተገኑ መሸሻ	በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ የሆነ ሰራተኛ ከአሰሪው ጋር ያለው የስራ ክርክር የሚገዛው በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎት መስጠትን ስለሚመለከቱ ውሎች ክፍል በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስለመሆኑ እና የስራ ውሉ ተቋርጦ የስራ መሪው ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2534, 2540 ,2541(1)	ጥቅምት 25/1998

ቅጽ 3

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
27	15815	አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ሰለሞን አበበ	የስራ ውሉ በህግ ወጥ መንገድ የተቋረጠ የስራ መሪ ስለሚያገኘው መፍትሔ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2570, 2573, 2574,2571	ታህሳስ 10/1998
28	16648	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ አንለይ ያየህ (ሃያ ሰባት ሰዎች)	ስለ ስራ ክርክር የይርጋ ጊዜ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162,163,164,165,166, አዋጅ ቁ. 377/96	ታህሳስ 20/1998
29	17483	የኦሮሚያ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እና ወ/ሮ ሮማን ደምሴ	የስራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል የሚቀርብ ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162(1)	ታህሳስ 20/1998
30	11924	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት ትዕግሥት ወርቁ	ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ስለማድረግ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 9,10 እና 24	ህዳር 15/1998
31	14057	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ጌታሁን ኃይሉ	አንድ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት እረፍት ቀናት በገንዘብ ተቀይሮ ስለሚከፈልበት የህግ አግባብ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 79(2)እና (5), 77(5),77(3)	ጥቅምት 30/1998
32	16270	አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ መሐሪ ማታ	በመኪና ግጭት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት ካሣ ለማግኘት የመኪናው ባለቤት ጥፋት እንዳለበት ማስረዳት የማይኖርበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066(2),2086(2),2081,2091,2102 እና 2092	ታህሳስ 17/1998

https://t.me/ethiopianlegalbrief

33	18581	በአዲስ አበባ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጥበቃ እና ሲ/ረ ቀቡላ ከድር	በህገ ወጥ መንገድ የስራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ ወደ ስራ እንዲመለስ ስለሚወሰንበት የህግ አግባብ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 23(1),43(3),40(1) እና (2),44	ህዳር 20/1998
34	15631	እነ የሻረግ መንግስት (ሁለት ሰዎች) እና እማሆይ የሻረግ ፊረደ	የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነ ጊዜ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1001(2),1168,1845,1853	ታህሳስ 17/1998
35	15551	ዮናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ እና የኢትዮጵያ መተርና መሐንደስነት ኩባንያ	ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ ተዋዋዮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚወሰነው በውሉ መሰረት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716(1), 1815,1816 እና 1817	ጥቅምት 29/1998
36	16062	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ	ከውል ውጭ በደረሰ ጉዳት ካሣ በመጠየቅ የሚቀረብ ክስ መቅረብ ስለሚኖርበት ጊዜ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1),2143(2)	ህዳር 19/1998
37	14554	ወ/ሮ ጽጌ አጥናፌ እና ባላምባራስ ውቤ ሽበሽ	ፍርድ ቤት በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርን የመሰረዝ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808(2),1198(2)	ታህሳስ 20/1998
38	15672	አቶ ታደለ ገለቻ እና አቶ ውድመጣስ ኑሮ	ንብረት በሐራጅ ስለሚሸጥበት የህግ አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 442	ታህሳስ 27/1998
39	16301	ተገኝ እንግዳ እና አስናቀች ኪዳኔ	መጥሪያ አደራረስን አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተናገድበት መንገድ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 99, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103,105	ህዳር 2/1998
40	10797	ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እና እነ ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም (ሦስት ሰዎች)	ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳዩ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378	ታህሳስ 27/1998
41	18199	ዶ/ር ምናሴ እሸቱ እና እነ ግርማ አያና (ስባት ሰዎች)	በጨረታ ለገዛው ንብረት ገንዘ ዋጋውን ሳይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ስነ-ስርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 429	ህዳር 7/1998
42	16378	የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ እና የቤ/ት/ክ/መ ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን	የመንግስት ሰራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መስራቱ ስለሚኖረው ውጤት ድንጋጌ ቁጥር 46/53, አዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2)	ታህሳስ 17/1998
43	18342	የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እና እነ አቶ ብርሀኑ ሀሩይ (ሁለት ሰዎች)	የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.38/88 አንቀፅ 11(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4	ታህሳስ 17/1998
44	14699	የኢንጂነር ወርቁ መኮንን ወራሾች እና የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች መምሪያ	ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ህጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀፅ 29	ህዳር 7/1998

ቅጽ 4

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
45	20885	የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገቢሳ የማነ	ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ስለሚደረግ የስራ ውል አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10	ጥር 3/1999
46	15531	የኢት/ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አዱኛ ገመዳ	የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን	የካቲት 6/1999
47	21730	ወ/ሮ ፍሬህይወት እርቁ እና የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን	ወደ ሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5)	መጋቢት 11/1999
48	21119	ቃሊቲ ምግባ አክሲዮን ማህበር እና ማስተዋል ጫኔ	የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠር አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ (2)	መጋቢት 18/1999
49	21961	አቶ ግርማ ነጋሽ እና ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር	የስራ ውልን ስለማቋረጥ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) ሐ	መጋቢት 18/1999
50	20457	የኢት/ንግድ ባንክ እና ወ/ሮ አለሚቱ ሞገስ	የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ ስራ ላልተሰራበት ውዝፍ ደሞዝ የሚከፈል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43,53(1), 54	መጋቢት 20/1999
51	24153	አቶ መንግስቱ አባተ እና የባህር ትራንዚት ድርጅት	ስለ መሠረታዊ የህግ ክርክር አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)ሐ	መጋቢት 26/1999
52	16653	ግዮን ሆቴሎች ድርጅት እና ወ/ሮ ስለእናት ወርቅነህ	የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን	መጋቢት 27/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

53	25526	መምህር ጥላሁን አስፋው እና አዲስ ኮሌጅ	ሰራተኛው በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10	ሚያዝያ 16/1999
54	15662	የኢት/ልማት ባንክ እና ሐዲ አብዲራህማን ቱሊላ	ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጐም ስላለመቻላቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2298,1733	መጋቢት 13/1999
55	19081	አቶ ዓሊ ቃሌብ አህመድ እና እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ (ሦስት ሰዎች)	ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሳሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ በሌሎች ላይ ስላለው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677,1901	መጋቢት 18/1999
56	23320	አቶ ገብሩ አብሌ እና እነ የአቶ ሁሴን አብዲረህማን ወራሾች (ሦስት ሰዎች)	የኪራይ ውል በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ስለመሆኑ	መጋቢት 20/1999
57	14493	የኢት/ልማት ባንክ እና አቶ ሚደቅላ ቱሉማ	ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጐም ስላለመቻላቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ.2298,1733	መጋቢት 13/1999
58	18786	ወ/ሮ አለሚቱ አግዛቸው እና እነ ወ/ሮ ዝናሽ ሐይሌ	የውል አብዛኛው ግዴታ በተፈፀመ ጊዜ የተወሰነ ቀሪ ገንዘብ አለመከፈሉ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሰረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሰኝ ምክንያት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1), 1785(2), 1789	ሚያዝያ 18/1999
59	21448	ወ/ሮ ጮርፌ ወርቅነህ እና እነ ወ/ሮ አበራሽ ዱባርጌ (ሁለት ሰዎች)	የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1727 ,2877, 2878	ሚያዝያ 30/1999
60	15557	ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁ እና አቶ ብርሀኑ ተሊላ	በአፈፃፀም ጉዳይ በስህተት በፍ/ባለመብት እጅ ስለገባ የከተማ መሬት ይዞታ	መጋቢት 11/1999
61	22260	የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ (ሦስት ሰዎች)	የወጪና ኪሣራ አወሳሰን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 463	መጋቢት 18/1999
62	17984	የጌዲዮን ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት እና ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ	ጉድለት ያለበት ሀራጅ ቀሪ ሲደረግ ሻጭና ገዢን ወደነበሩበት ለመመለስ ስላለመቻል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1) እና (2)	መጋቢት 20/1999
63	19205	አቶ ሽኩር ሲራጅ እና አቶ መላት ካሣ	አንድ ፍርድ ተፈፀመ ሊባል የሚገባው ለፍርድ ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ ሲደርሰው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 395	መጋቢት 25/1999
64	19479	ወ/ሮ አመለወርቅ ገለቱ ወራሾች እና እነ አቶ ቢሻው አሻሜ (አራት ሰዎች)	አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ሆነ የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግስት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገመትና አስፈላጊም ከሆነ እንዲሸጥ የሚያደርግ ውሣኔ መሬትን የመንግስት ለማድረግ የወጣውን ሕግ የሚፃረር ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 47/67	መጋቢት 20/1999
65	16109	አቶ ከበደ አርጋው እና የኢት/ንግድ ባንክ	የሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ተዋዋዮች ውላቸውን በመዝገብ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ የማይጥልባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1587, 1620, 1613, 2878	ሚያዝያ 12/1999
66	14094	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና የአቶ ሰለሞን ወረዳ ወራሽ	ለረጅም አመታት በመንግስት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ያለአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሣኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, አዋጅ ቁ 47/67,ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/	ሚያዝያ 18/1999
67	17937	ወ/ሮ ድንቁ ተድላ እና አቶ አባተ ጫኔ	ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677 መሠረት በቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈፃሚ ስለመሆኑ ፍ/ብ/ህ/ቁ. 17,68, 1002,1677,1845	መጋቢት 20/1999
68	20938	ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ እና ወ/ሮ ሣራ ልኑጋነ	ስለ ጋብቻ መፍረስ	ሚያዝያ 11/1999
69	22243	ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ እና አቶ አብርሃም ካሣ	ልጅነትን ስለማስረዳት የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126(1),143(መ) እና (ሠ)	ሚያዝያ 16/1999
70	17058	አቶ አንበሶ ወ/ገብርኤል እና አቶ መሣይ መኮንን	ኑዛዜ ህጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በስነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881, 884, 892, 996-1000, ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	መጋቢት 25/1999
71	22712	አቶ እንደሻው በቀለ እና እነ ወ/ት አይናለም ያለው	የኑዛዜ እያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትና ተናዛዥም ሆነ ምስክሮች /አማኞች/ በኑዛዜ ባሰፈሩት ቃላትና ሃረጐች ሊሰጡ የሚችለውን ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ	ሚያዝያ 9/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		(ሁለት ሰዎች)	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881	
72	22162	አፍሪካ ኢንሹራንስ እና አቶ ብስራት ጉላ	መድን ሰጭ የካሣን ክፍያ በተመለከተ በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ	ሚያዝያ 9/1999
73	23339	የኢት/ጉምሩክ ባለሥልጣን እና እነ አበሮ ኢር/ጋኖ	የጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚተዳደሩ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀፅ 6(2)ለ	መጋቢት 13/1999
74	16195	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ስላሴ (ስድስት ሰዎች)	ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 4187 አንቀፅ 11(1), አዋጅ ቁ.47/67 አንቀፅ 21(2), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 74(4)	ሚያዝያ 11/1999
75	22317	የምስራቅ ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እና አቶ አብዱ አሉ አዩ	የጉምሩክ ባለስልጣን በኮንትሮባንድ ወደ ሀገር የሚገቡትን ወይም ከሀገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 5-6 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2010(2)	ሚያዝያ 18/1999
76	12025	አቶ ምናሴ አልማው እና ዓቃቤ ህግ	ጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ የጥብቅና ስራ እሰራለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል የማታለል ወንጀል ስለመሆኑ የ1949 ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ.656(ሀ) እና (ለ)	መጋቢት 18/1999

ቅጽ 5

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
77	17320	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ዶ/ር ሻውል ገብሬ (ሁለት ሰዎች)	ንብረትን ለመሸጥ ለመለወጥ ብሎም ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ በሚል የተሰጠ ውክልና ንብረቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችል ስልጣን እና ችሎታን የሚያጐናጽፍ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3049(2),2206(1)	መጋቢት 18/2000
78	20809	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ሃይሌ	በባለስልጣን ፊት በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ያሉትን ፊርማዎችና የሰነዶቹን ይዘት ማስተባበል ስላለመቻሉ	ሐምሌ 10/2000
79	23861	ሊቀ ስዩማን አሰፋ ባሻህውረድ እና የሣህሊተ ምህረትና ክርስቶስ ሣምራ ደብር አስተዳደር	ወኪል የሆነ ሰው ውክልናውን በሚገባ እስካሳየ ድረስ በማመልከቻው ላይ የራሱን ወይም የወካዩን ስም አስቀድሞ መፃፉ ወኪልነቱን ለውጦ ባለቤት የሚያደርገው ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 58	ጥቅምት 14/2000
80	26399	አቶ ኃ/ማርያም ባዩ እና እነ አቶ ሣሙኤል ጐሣዬ (አምስት ሰዎች)	የውክልና ስልጣኑ ቀሪ ከተደረገበት እንደራሴ ጋር በቅን ልቦና ውል ፈፅመው በተገኙ ጊዜ ውሉ እንዲፈርስ ላይወሰን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808, 1816, 2191(2), 2193	ህዳር 5/2000
81	32241	ወ/ሮ ካሰች ተካልኝ እና እነ አቶ ኃ/ማርያም አበበ (ሁለት ሰዎች)	• እንደራሴ የሆነ ሰው የውክልና ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞች (Conflict of interest) ማስወገድ ያለበት ስለመሆኑ • ከእንደራሴው ጋር ውል የፈፀመው ሦስተኛ ወገን እንደራሴው የውክልና ስልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞችን የማስወገድ ግዴታውን አለመወጣቱን ማወቁ ወይም ማወቅ የሚገባው መሆኑ ያደረጉትን ውል ፈራሽ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)	መጋቢት 9/2000
82	21355	አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት እና አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ	የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የሰጠ ወገን ከዋናው ውል አለመፅናት ጋር በተያያዘ የዋስትና ውሉ እንዲፈርስ ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1923(2)	ሐምሌ 3/2000
83	25115	አቶ ማሞ ጉበና እና አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም	ተራ ዋስ የሆነ ሰው ከባለዕዳው ጋር ተጣምሮ ክስ በቀረበበት ጊዜ ከገባው የዋስትና ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከኃላፊነት ነፃ ሊደረግ የሚችለው ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለባለገንዘቡ ከመወጣቱ ጋር በተያያዘ ስለመሆኑ	ጥቅምት 5/2000
84	26565	ግሎባል ኢንሹራንስ /አ.ማ/ እና ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/	ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገመት ወይም ሊታሰብና ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚቻል ሁኔታ ድንገተኛ ደራሽ ቢሆን እንኳ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ (Force majeure) ተብሎ የማይወሰድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 1792(2)	ጥቅምት 19/2000
85	17742	ወ/ሮ አበበች ታደሰ እና እነ አስር አለቃ ሲሳይ ካብትህይመር (አራት ሰዎች)	በህግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት የሚያስችል ማንኛውም ዳኛ ውል የማዋዋል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678(ለ) እና 1715	መጋቢት 2/2000
86	23921	ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግስቱ እና አስር አለቃ ታደሰ ወርቁ	የስጦታ ውሉ በስጦታ ተቀባዩ ላይ ግዴታ ያልጣለ ቢሆንም እንኳን ስጦታ ሰጪው በድህነት ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ተቀባዩ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2458(1)	ጥቅምት 12/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

87	32337	ወ/ሮ ፀሐይነሽ ይህደጐ እና እነ ወ/ሮ ትሕሽ በርሔ	"የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ተራ የክፍያ ደንብ እንጂ ሌሎች ወራሾች ያላቸውን ውርሱን የመካፈል መብት የማይገድብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 913	ግንቦት 21/2000
88	22891	ወ/ሮ ማና ኃ/ሚካኤል እና እነ አቶ ገ/ማርያም ከበደው (ሁለት ሰዎች)	በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ ምክንያት የተፈጠረ ዕዳ ለጋራ ጥቅም መዋሉ በተረጋገጠ ጊዜ የዕዳው ወደ የጋራ ንብረት ወይም ወደ ሌላኛው ተጋቢ የግል ንብረት በመሄድ ሊከፈል የሚችለው በፍርድ አፈፃፀም ላይ ስለመሆኑና ከዚህ ጋር በተያያዘ በሌላኛው ተጋቢ ላይ ዕዳውን መሠረት በማድረግ ክስ ሊመሰረትበትም ሆነ ፍርድ ሊሰጥበት የማይገባ ስለመሆኑ	ህዳር 24/2000
89	31737	አቶ ገብሩ ገ/መስቀል እና ቂስ ገ/መድህን ረዳ	በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472 መሠረት በባንክ የተሰጠ የሃዋላ ወረቀት ብድርን ለማስረዳት ስለመቻሉ	የካቲት 27/2000
90	24173	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና ወ/ሮ አይዳ ሐሰን	በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት የተላከ ፖስታ /ዕቃ/ በመጥፋቱ፣ መሠረቁ፣ በመበላሸቱ፣ ወዘተ ምክንያት ካሣ የሚጠየቀው መጠኑም የሚወሰነው የፖስታ አገልግሎት ሕግን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 24/58 መሠረት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 24/58 አንቀፅ 50,51,53 እና 54	ህዳር 11/2000
91	24574	የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤ/መ/ፖ'/ጠ/ጽ/ቤት እና አቶ ይትባረክ ማህሉ	በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሳይሰጥበት የታለፈ ጉዳይ እንደተነፈገ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ	ህዳር 11/2000
92	25434	የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን እና ፋሬተርስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማህበር	በውል ውስጥ አጠራጣሪና ግልፅነት የጐደላቸው ጉዳዬች በፍ/ብ/ህ/ቁ.1738 መሠረት አልባት ሊሰጣቸው የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1738	መጋቢት 25/2000
93	29369	በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ የግብርና ምርምር ማዕከል እና አቶ ተመስገን አድነው	• የባለዕዳው ቀጥተኛ የውል ፈፃሚነት ከውሉ ባህሪ አኳያ ማስፈፀም አለመቻል ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቅ ሳያስፈልግ ኪሣራ ካለ መጠየቅ ስለመቻሉ • በውል መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ ወገንን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል በሆነ ጊዜ በውሉ ግዴታውን የተወጣው ወገን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰውን ኪሣራ ለመጠየቅ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1) እና (2)	መጋቢት 9/2000
94	19338	ዘይነባ ሐሰን እና ፍሬው ተካልኝ	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ተጐጂ የሆነ ወገን የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚኖር ስለመሆኑ ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ዳኞች ለተጐጂው የሚከፈለውን ካሣ በርትዕ መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102	መጋቢት 2/2000
95	21296	የኔዘርላንድ ልማት ድርጅት እና ውበት አድባሩ	የፍ/ብህ/ቁ. 2089 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(1) እና (2)	ታህሳስ 1/2000
96	22509	አቶ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ እና ዳርጊ ሰምሮ	የቀረበን ክስ ለማስረዳት አግባብነት የሌለው ማስረጃን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	ጥቅምት 7/2000
97	24818	ይልቃል በእውቀቱ እና ስዩም አባዲ	ጥቅም በሌለው ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ ሲሄድ አደጋ በመድረሱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው ካሣ ሊጠይቅ የሚችለው የመኪናው ባለቤት ወይም ጠባቂው ጥፋት መፈፀሙን በማስረዳት ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(2)	የካቲት 4/2000
98	27565	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ደምሴ ወርቅነት (ሁለት ሰዎች)	ጉዳት ሊካስ የሚገባው ለደረሰ ጉዳት ብቻ ሳይሆን በጉዳቱ ምክንያት ለሚመጣ ኪሣራ ጭምር ስለመሆኑ	ታህሳስ 1/2000
99	27623	ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ውባየሁ አበበ	• የማህበራዊ ዋስትና መብት ጥቅምን በሚመለከት የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የመዳኘት የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ • የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 38/88 አንቀፅ 5,8 እና 11	ህዳር 24/2000
100	28612	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን	ለደረሰ ጉዳት ሃላፊ የተባለ ሰው ላደረሰው ጉዳት ካሣ አይከፍልም ሊባል የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2091	የካቲት 25/2000
101	28750	የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ከውልና ከውል ወጪ በሆነ ግንኙነት ከሁለት የተለያዩ የክስ ምክንያቶች የሚመነጭ ኃላፊነትን መሠረት በማድረግ በአንደኛው ግንኙነት ብቻ ተጠያቂ የሆነን ወገን ሁለቱን የኃላፊነት ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ካሣ እንዲከፍል በአንድነትና በነጠላ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2035, 1896	ህዳር 24/2000
102	28865	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ካሣ ግዛው	ንብረትን ከመስሪያ ቤት በኃላፊነት የተረከበ ሰው ንብረቱ በጠፋ ጊዜ ከንብረቱ መጥፋት ጋር በተያያዘ ጥፋት ያልፈፀመ መሆኑን ወይም ንብረቱ ከሥራ ሰዓት ውጪ የጠፋ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2027	ህዳር 24/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

103	30032	የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ወ/ሮ ምንትዋብ የኔነህ	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት የክልሉ መንግስት ቋሚ ሠራተኛ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት የሞተ እንደሆነ ለተተኪዎች የጡረታ አበል እንጂ ሌላ ተጨማሪ ካሣ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የአማራ ክልል አዋጅ ቁ.74/1994 አንቀፅ 46(5) (ሀ)	ታህሳስ 1/2000
104	30442	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሰሜን ምዕራብ ሪጅን እና ወ/ሮ ድንቋ አመኔ	• ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት የሞት አደጋ በደረሰ ጊዜ የሚች የቅርብ ዘመዶች ሊኖራቸው የሚችለው መብት እና • የደረሰውን የሞት አደጋ ተከትሎ የሚቀርብ የቀለብ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095 807, 812	ህዳር 3/2000
105	31099	የተንዳሆ እርሻ ልማት አ/ማ እና ወ/ሮ ርሻን አለማየሁ	ሟች ከመሞቱ በፊት ቀለብ የማይሰፈርለት ግለሰብ በሟች ሞት ምክንያት የጉዳት ካሣ በቀለብ መልክ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095, 2069(1)	ግንቦት 14/2000
106	32144	ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እና ወ/ሮ ኢልሻ ሲራጅ	• በሞት ምክንያት ቀረ የሚባል ጥቅም የሚሰላው ከጠቅላላው የሟች ደሞዝ ላይ የሚቀነሱት በህግ የታወቁት ተቀናሾች ተቀንሰው የሚገኘውን የተጣራ ገቢ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ • የህሊና ካሣ ከአንድ ሺህ ብር ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2116	መጋቢት 23/2000
107	32250	ወ/ሮ አስናቀ ወ/ማሪያም እና እነ አቶ ከተማ ተሰማ (ሁለት ሰዎች)	በሞት አደጋ ምክንያት የተቋረጠ የመተዳደሪያ ጥቅም ጋር በተያያዘ በየወሩ የሚከፈል ካሣ አከፋፈል ስርአት በፍርድ ቤት የተወሰነውን ካሣ አጠቃሎ በባንክ ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም በማስቀመጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095(2)	መጋቢት 25/2000
108	33975	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ወ/ሮ አበበች ስዩም	የመሬት ይዞታ ባለቤት የሆነ ሰው ለህዝብ ጥቅም በሚል ይዞታውን በተጨባጩ እንዲለቅ ባልተደረገበት ሁኔታ ሊጠይቅ የሚችለው የካሣ ክፍያ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀፅ 7(1)	መጋቢት 25/2000
109	34138	እነ ሲስተር ገነት ጌታቸው (ሁለት ሰዎች) እና ወንድወሰን ኃይሉ ወልደ ማሪያም	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ከደረሰበት የአካል ጉዳት በተጨማሪ በደሞዝ ረገድ የቀረበት ጥቅም (ገቢ) መኖሩ ከተረጋገጠ ሊካስ የሚገባ ስለመሆኑ	ግንቦት 26/2000
110	34906	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት እና ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቁ	በሥራ ግንኙነት ውስጥ የቅርብ አለቃ የሆነ ሰው በሥሩ ያሉ ሠራተኞችን አስመልክቶ ለበላይ ኃላፊዎች የሚፅፈውና የሚልከው ሪፖርት ሥም ከማጥፋት ጋር በተያያዘ የፍትሐብሔር ሃላፊነት ሊያመጣበት የማይችል ስለመሆኑ	ግንቦት 5/2000
111	21740	ወ/ሮ አስረስ መስፍን እና ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ	የጋብቻ ጽሁፍ በሌለ ጊዜ ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 699(1), (2)	ጥቅምት 28/2000
112	23021	ወ/ሮ አበባ ወርቅ ጌታህ እና ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ	በፍቺ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ የቀድሞ ተጋቢዎች እንደ ገና አብሮ መኖር የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ከሆነ ጋብቻ መፈፀሙን የህግ ግምት መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 96 እና 97(1)	ሐምሌ 12/1999
113	23493	ወ/ሮ እንግው ዘገየ እና ወ/ሮ ወርቁ መኮንን	በፍርድ ቤት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ የሟች ባለቤቶችን እኩል የጡረታ አበል የመክፈል መብት የሚሰጥ ስለመሆኑ	ሰኔ 26/1999
114	23632	ወ/ሮ ፀዳለ ደምሴ እና አቶ ክፍሌ ደምሴ	ወላጆች ለህፃናት ልጆቻቸው ሞግዚትና አስተዳዳሪ የመሆን መብታቸው ሊከበር የሚችለው ለህፃናቱ ጥቅምና ደህንነት እስከሰሩ ወይም ሊሰሩ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ስለመሆኑ የደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስተ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/96 አንቀፅ 235(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 36(2)	ጥቅምት 26/2000
115	24625	ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ እና ወ/ሮ ሊህማ አሊ	በህግ ፊት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ የጋራ ሀብትን ሁለቱ ባለቤቶች ግማሹን ለሁለት ቀሪውን ግማሽ ልጆች የሚካፈሉ ስለመሆኑ	ጥቅምት 28/2000
116	25005	መኮንን በላቸው እና ወ/ሮ አለሚቱ አደም	በጋብቻ ውል ላይ የግል ተብሎ ያልተመለከተና ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት ግንባታው የተጀመረ ቤት ግንባታው የተጠናቀቀው በጋብቻ ወቅት ከሆነ የጋራ ንብረት ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) , 63(1)	ህዳር 3/2000
117	25281	ወ/ሮ መሠረት ፍስሐ እና አቶ ቀልቤሣ አለሙ	የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ነው በሚል የተወሰነ መኖሪያ ቤት ጋር በተያያዘ አንደኛው ተጋቢ ቤቱ የተሰራበትን መሬት (ቦታ) ከጋብቻው በፊት የተመራ በመሆኑ ሌላኛው ተጋቢ የቤቱን ግማሽ ዋጋ ተቀብሎ እንዲለቅ በሚል የሚሰጥ ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 92 የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀፅ 1131,1132	ጥር 29/2000
118	25588	መርየንሃሰን ዑመር እና መውሊድ ተኽልእስማን	አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው መሆኑና አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት እንጂ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ስላለመሆኑ	የካቲት 6/2000
119	26839	ወ/ሮ አስካለ ለማ እና ሣህለ ሚካኤል በዛብህ	ጋብቻ ከመመስረቱ በፊት የግል የነበረ ሃብት ከጋብቻ በኋላ የጋራ ከሆነ ንብረት ጋር ተቀላቅሎ በተገኘ ጊዜ የግል የሆነው ንብረት ተለይቶ የግሉ ለሆነው ተጋቢ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 57,86(1)	ህዳር 10/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

120	26953	አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ እና ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ	በጋብቻ/በትዳር ላይ/ ከተጋቢዎች መካከል በአንደኛው ተጋቢ አማካኝነት በካሣ መልክ የተገኘ ሃብት የጋራ ሃብት/ንብረት/ ተደርጐ የሚቆጠር ስለመሆኑ	ህዳር 13/2000
121	27697	አቶ ርዕሶም ገ/መድህን እና ወ/ሮ አልማዝ ጊላ ሚካኤል	ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የጋራ ንብረት የተሸጠ ቢሆንም የሽያጩ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንደሚገኝ ካልተረጋገጠ ለጋራ ትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85 -93	ጥቅምት 19/2000
122	27869	ፍቅርና ሠላም ኃ/የተ/የግ/ማ እና እነ ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ (ሁለት ሰዎች)	• የማይንቀሳቀስ ንብረት ለንግድ ማህበር በመዋጮ መልክ የተሰጠ ሆኖ ሲገኝ የንብረቱ ስም በኩባንያው ተመዝግቦ ያለመገኘቱ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ለመሆን የማይችል ቢሆንም ንብረቱ በአይነት መዋጮ መሰጠቱን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ • የጋራ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ አንደኛው ተጋቢ ፈቃድ ለንግድ ማህበር በዓይነት መዋጮ የተሰጠ እንደሆነ ንብረቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 517(ሠ),(ረ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878 የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(1), 69(2)	ህዳር 10/2000
123	29343	እነ ወ/ሮ አምሳለ ተፈራ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ት አበባ አድማሱ	ተጋቢዎች በጋብቻ ወቅት **የተፈራ** ቤታቸውን በትርፍነት ለመንግስት ያስረክቡ እንደሆነ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት የሆነን ቤት ያለምንም ተጨማሪ ስምምነት የጋራ የሚያደርገው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67 አንቀፅ 11(1)	ሚያዝያ 7/2000
124	29402	ወ/ሮ ሐዳስ ታረቀ እና የ፱ አለቃ አስመላሽ ኃይለስላሴ	ቤት የጋራ ሃብት ነው ከተባለ ቤቱ የተሰራበት መሬት ላይ የጋራ ባለሃብቶቹ እኩል የመጠቀም መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ	ጥቅምት 19/2000
125	30959	እነ ወ/ሮ ተወዳጅ ገ/ሥሌሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ዘለቀ ዘውዴ(ሁለት ሰዎች)	• ሚች በኑዛዜው አንድን ሰው ልጄ አይደለም በማለት መግለፅ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማፍረስ የሚያበቃ ስላለመሆኑ • በቤተሰብ ህጉ ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቻልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,156,157	ታህሳስ 1/2000
126	31430	ወ/ሮ አዲስአለም አክለ እና የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ	ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የሚገኝ ድጐማ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ የአማራ ብ/ክ/መ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 73(1) እና (2)	ሚያዝያ 7/2000
127	31891	እነ አቶ አንለይ እንየው (ሰባት ሰዎች) እና ወ/ሮ መሬም ጠሃ	የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረዥም ጊዜ መኖርና በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መስርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ተቋርጧል የሚያስብል ስለመሆኑ /የሰ/መ/ቁ. 14290/	ሚያዝያ 14/2000
128	31946	ወ/ሮ ዘውዲቱ ጌታቸው እና ተመስገን ደሳለኝ	የጋብቻ ውል በህግ አግባብ አልተደረገም በሚል ተቃውሞ ያቀረበ ተጋቢ በውሉ መሠረት ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 34(2), 35(2) እና 9(1)	ግንቦት 14/2000
129	32130	እነ እማዋይሽ ካሣ (ስድስት ሰዎች) እና ወ/ሮ አስቱር አህመድ	አንድን ሰው አባት ነው ብሎ ለማለት ለልጅ እንክብካቤ ማድረጉና ልጁም በእሱ ስም መጠራቱ ብቻ ሣይሆን ግለሰቡ ድርጊቱን አባት ነኝ ከሚል ስሜትና መንፈስ በመነጨ ያደርግ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የአማራ ክ/መ/ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 79/95 አንቀፅ 154(ሐ)(ሠ)	መጋቢት 18/2000
130	33411	ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ እና አለቃ ኪሮስ ገብሩ	ተጋቢዎች ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት ወቅት የገዙት ንብረት በስማቸው ያልዞረ ቢሆንም እንኳን ንብረቱ የእኔ ነው በሚል የቀረበ የ3ኛ ወገን ተቃውሞ እስካልቀረበ ድረስ ንብረቱ የጋራ ሀብት ተደርጐ የሚወሰድና ሊከፋፈል የሚገባ ስለመሆኑ	መጋቢት 25/2000
131	33440	ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም እና አቶ ግርማ ገብረ ስላሴ	• ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ጥያቄ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ • ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ የልደት ምስክር ወረቀት ተቃውሞ የማይቀርብበት የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ ሊወሰድ የማይችል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154	ሚያዝያ 21/2000
132	33875	ወ/ሮ የሻረግ አባትኩን እና ወ/ሮ መሠረት አድማሱ	ጋብቻ በባህላዊ መንገድ ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብና መመስረቱን ማስረዳት የሚቻልበት ሁኔታ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 4 እና 97(2)	መጋቢት 25/2000
133	34149	እነ ወ/ሮ ዘለቃሽ በቀለ እና አቶ አለሙ በቀለ	የአንድ ሰው አባት ነኝ በሚል የሚቀርብ ሰው አባትነቱን በህግ አግባብ በማስረጃ ማስረዳትና ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 147(1), 97(2)	መጋቢት 25/2000
134	34387	አቶ ክበደ መሐሌ እና ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ	የጡረታ አበል እንደማንኛውም ገቢ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተደርጐ የሚወሰድ ስላለመሆኑ	ግንቦት 14/2000
135	35376	እነ አቶ ዳንኤል አሰፋ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ሔለን ውበቱ	ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት ላይ ያለን ዕዳ ለመወጣት ከጋብቻ በኃላ ከባልና ሚስት የጋራ ገንዘብ መከፈሉ ንብረቱን የጋራ ንብረት የማያደርገው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) እና 70(1)	ግንቦት 28/2000
136	23389	የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማ እና እነ ባህሩ አብርሃም (አስራ ሁለት ሰዎች)	የአክስዮን ማህበር አባላት የአክስዮን አስተዳዳሪዎች መብታቸውን በሚገባ መልኩ መስራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ በቀጥታ መክሰስ የሚችሉ ስለመሆናቸው የንግድ ህግ ቁ. 367	ሐምሌ 10/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

137	25306	አቶ ተስፋዬ ገሰቴ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ገንዘብን በአደራ ለማድረስ የተቀበለ ባንክ አደራ አስቀማጩ ይሰጥልኝ ላለው ሰው እስካልሰጠ ድረስ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 898(1)	ህዳር 12/2000
138	27161	አቶ ኤልያስ ከፈለ እና እነ አቶ ከድር አህመድ (አራት ሰዎች)	የክሱ መሠረት የሆነው ጉዳይ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ የተረዳ ፍ/ቤት ክሱን መሰረዝ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280	ህዳር 12/2000
139	28923	የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር እና .እነ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር (ሁለት ሰዎች)	የመንግስት ልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማህበራት ሲቀየር በፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያልታወቀና ውሣኔ ያልተሰጠበት እንኳን ቢሆን የልማት ድርጅቱ ዕዳ ወደ አክሲዮን ማህበር የማይተላለፍ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 208/92 አንቀፅ 5(1), 6(1)ሐ	ግንቦት 7/2000
140	23608	የኢትዮጵያ ፕራይቬትይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ እና የአቶ ኑርበዛ ተረጋ ወራሾች	በፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲም ሆነ በኤጀንሲው ስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ እንደገና ለማየት ፍ/ቤቶች ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ.110/87 አንቀፅ 4(1) እና 5(3)	ህዳር 3/2000
141	27548	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ወ/ሮ ቆፀላ መርሻ (ሁለት ሰዎች)	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አጠራጣሪነቱ በታወቀ ጊዜ ከሚመለከተው አካል ተገቢውን ማብራሪያና ማስረጃ ሳይጠየቅ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1196(1)	መጋቢት 18/2000
142	29822	የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ በቀለች አማረብህ	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ስልጣን ላለው የአስተዳደር ክፍል መመለስና መሰረዝ ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቶች የባለቤትነት ደብተሩ እንዳይመለስ በሚል ውሣኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ 1196(1)	ግንቦት 28/2000
143	29860	ወ/ሮ አስናቀች ሲሻው እና እነ ወ/ሮ አሰለፈች ከተማ (አራት ሰዎች)	በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የባለቤትነት መብት ለመንግስት የተላለፈ መሆኑን እንደመከራከሪያ በማንሳት መሟገት የሚችለው የሚመለከተው የመንግስት አካል እንጂ ግለሰብ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ 47/67 አንቀፅ 13(1)	መጋቢት 18/2000
144	31490	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ሴርኮ አስራኤላዊያን	ተከሳሽ የሆነ ወገን ካቀረባቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች መካከል ፍ/ቤቱ አንዱን ብቻ መሠረት በማድረግና ሌሎቹ ላይ ብይን ሣይሰጥ ክሱን ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ብይን ባልተሰጠባቸው መቃወሚያዎች ላይ ይግባኝ ማቅረብ የማይጠበቅበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244,341	ሚያዝያ 2/2000
145	31682	አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ዘላለም ይልማ ባልቻ (ሦስት ሰዎች)	ተወርሰዋል ተብለው በመንግስታዊና ህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ሥር ያሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሠረት በማድረግ ፍ/ቤቶች መወረስና አለመውረስን በተመለከተ ማስረጃዎችን መርምሮ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67 አዋጅ ቁ.110/87	መጋቢት 12/2000
146	32376	አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሸዋንግዛው	የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸው ቤቶች ላይ የባለቤትነት /የባለቤትነትን መፋለም/ ክርክር በተነሣ ጊዜ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የማይኖራቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 41(ረ)	ግንቦት 19/2000
147	34249	እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ እና እነ አቶ አለሙ ወንድሙ	በክርክር ተካፋይ እንዲሆን የሚያስፈልግ ወገንን ተከራካሪ ወገኖች እንዲገባ ያልጠየቁ ቢሆንም ፍ/ቤቶች ይህንኑ ወገን በራሳቸው ተነሣሽነት በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2)	ሚያዝያ 28/2000
148	22857	እነ አቶ ተክሌ ደግፌ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ በፍቃዱ ኃይሌ (ሁለት ሰዎች)	• በፍርድ ሂደት ላይ ያለ ጉዳይን ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በክርክሩ ማናቸውም ደረጃ ላይ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ በእርቅ እንዲያልቅ ለመጠየቅ የሚችሉ ስለመሆናቸው • በፅሁፍ ተዘጋጅቶ የቀረበ የእርቅ ስምምነት ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ስምምነቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን አረጋግጦ በፍ/ቤት የተያዘውን ጉዳይ ማቋረጥ የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 274(1),275,(1),277(1)	ታህሳስ 15/2000
149	25912	አቶ ብሩ ቆርቾ እና አቶ ክፍሌ ሐብደታ	የግልግል ስምምነት እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3312	ሚያዝያ 2/2000
150	29386	ወ/ሮ ወለላ ተሰማ እና እማሆይ በላይነሽ መለሰ	ከወራሾች መካከል አንዱ በሌለበት የተካሄደ የንብረት ክፍፍል በሌለበት ክፍያው የተፈፀመበት ወራሽ በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080	የካቲት 25/2000
151	30536	ወ/ት አለምነሽ ዋቅቶላ እና አቶ ይልቃል ጌጤ (ሁለት ሰዎች)	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ላደረሰ ወገን የመድን ሽፋን የሰጠ አካል በሃላፊነቱ መጠን ለተጎጂው መካሱ ተጎጂው በጉዳት አድራሹ ላይ የሚያቀርበውን ተጨማሪ (ቀሪ) የካሣ ጥያቄ የሚከለክል ስላለመሆኑ	መጋቢት 23/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

152	20036	ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ	ጋብቻ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ለማሳየት /ለማረጋገጥ/ የሚቻል ስለመሆኑና ይህንንም ለማስረዳት ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ሊቀርብ ስለመቻሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 95,96 እና 97	ግንቦት 16/1998
153	25899	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ር ስዩም ካሣ	የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደሞዝ በሚያስገኝ የመንግስት ስራ ላይ ከተቀጠረ የቅጥሩ ሁኔታ በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ከደሞዝ በተጨማሪ የወሰደውን የጡረታ አበል መመለስ ያለበት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2)	ግንቦት 28/2000
154	26480	የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ እና አቶ ቢንያም አለማየሁ	ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠባቸው ጉዳዩችን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ አዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 12/91 አንቀፅ 9(4)	ጥቅምት 14/2000
155	28883	ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ሚስተር ኒኮላ አስፓፓቻት ዚስ	ከተከራካሪ ወገን አንዱ የውጭ ሀገር ዜጋ ስለሆነ ብቻ ክርክሩ ሁልጊዜ የግለሰብ አለማቀፍ ሕግ ጥያቄ ያስነሳል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 11(2)ሀ	ህዳር 26/2000
156	29005	አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ግርማቸው ይላላ (ሁለት ሰዎች)	በክፍለ ከተማ ስልጣን ክልል ውስጥ የሚነሱ ክርክሮች ላይ ክፍለ ከተማው ጣልቃገብቶ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 10(2),30 አዋጅ ቁ. 18/97 አንቀፅ	ሚያዝያ 14/2000
157	30298	አቶ የሲወንድም አቡሕይ እና አቶ አየነው ማለደ	ጠፋ የተባለ ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹ የተሸጡ ከሆነ ለማግኘት መብት የሚኖረው የንብረቶቹን የሽያጭ ዋጋ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171(1)	ጥር/2000

ቅጽ 6

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
158	08751	ወ/ሮ አበበች በጅጋ እና እነ ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ (ሁለት ሰዎች)	• ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አዲስ ማስረጃ ተገኝቷል በሚል የተሰጠው ፍርድ በድጋሚ ሊታይ የሚችልበት አግባብ • ውሣኔ ያልተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6	ግንቦት 26/2000
159	19142	አቶ መላኩ ማሞ እና እነ ወ/ሮ ፊለቀች ማሞ (ሦስት ሰዎች)	የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጋር በተያያዘ በሚሰጥ ብይን ላይ ፍ/ቤቱ በሥረ- ነገር ረገድ የመጨረሻ ውሣኔ ሣይሰጥ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320 (3)	ጥቅምት 26/2000
160	20465	አዋሽ ኢንተርናሽናል ኩባንያ እና ፀሐይ ዮሐንስ የህፃን ተመስገን ቱጂ ሞግዚትና አሳዳሪ	በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሠረት የቤንሻንጉልን ጨምሮ የአምስት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ባላቸው የውክልና ስልጣን ያዩዋቸውን የፌዴራል ጉዳዩች በይግባኝ ተቀብለው የማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 322/95, የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(2)	ሰኔ 26/2000
161	21270	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ ወይንሸት አበራ	አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከመታገዱ በፊት በባንክ በመያዣነት የተያዘ እንደሆነ ባንኩ በህግ ተሰጠው መብት መገልገል ይችል ዘንድ ፍ/ቤት የሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ማስነሳት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 158, አዋጅ ቁ. 97/90	ሐምሌ 30/1999
162	22556	ታደለ አብዛ እና እነ የአቶ ጉሳዬ ሩጉቶ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	በክርክር አመራር ሂደት የተከራካሪ ወገኖች የመሰማት መብት ተግባራዊ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ	ጥቅምት 14/2000
163	22603	የድሬዳዋ ጊዜ/አስ/ቀበሌ 20 ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ሸሪፍ አሊ	ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ልዩነት ያላቸው በመሆናቸው ጥርጣሬን የፈጠሩ እንደሆነ ፍ/ቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ጥርጣሬ ያለበትን ጉዳይ አጥርቶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 255,257	ሐምሌ 26/1999
164	23363	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ፊርሀን አህመድ (ሦስት ሰዎች)	የመድን ሰጪ አካል ኃላፊነት በመድን ሽፋን ፖሊሲው ላይ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በላይ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 665(2)	ግንቦት 26/2000
165	23628	ሶሎ ሲርካርና ኤ.ኤስ እና እነ.ጌትያን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ (ሁለት ሰዎች)	በውጭ ሀገር ተመዝግቦ የህግ ሰውነት ያገኘ ኩባንያ በኢትዮጵያ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ አቅርቦ በሂደት ላይ ያለ መሆኑ በውጭ አገር ያገኘውን የህግ ሰውነት ቀሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 100	ጥቅምት 21/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

166	23692	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና እነ አሊ መሐመድ	• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጉም የሚችልበት አግባብና አፈፃፀሙ • በሦስተኛ ወገን ተከሳሽነት በክርክር ውስጥ እንዲገባ የተደረገ ወገን ከተከሳሽ ጋር ከመሟገት በቀር ተከሳሹን ተክቶ ከሣሽን መከራከር አይችልም ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 687, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2), 43	ሐምሌ 03/1999
167	23744	አቶ በቀለ በድዬ እና እነ ወጋገን ባንክ አዋሳ ቅርንጫፍ (ሦስት ሰዎች)	ዳኝነት ሣይከፈል በነፃ ክስ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ጥያቄው በፍ/ቤት ትዕዛዝ /ውሣኔ/ ውድቅ የተደረገበት ተከራካሪ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320(1), (3)	ሐምሌ 26/1999
168	23769	ኢንጅነር ጋሪፉፋ እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናት ኢንስቲትዮት	ከአገልግሎት ብዛት ከጥቅም ውጭ የሚሆኑና ሊያስረክቧቸው የማይችሉ ዕቃዎች ላይ የዋጋ ግምታቸውን መጠየቅ የክሱ ምክንያት ቀሪ በሆነ ነገር ላይ ክስ እንደመመስረት የሚቆጠር ስለመሆኑ	ሐምሌ 12/1999
169	24111	የቂርቆስ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን እና ወ/ሮ የዕለተወርቅ ገ/አብ	የተከሳሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ተከሳሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተከሳሹ ሊያጣ የሚችለው መልሱን በውሁፍ የማቅረብ መብቱን ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 195	የካቲት 11/2000
170	24627	ዶ/ር ቤተልሄም ታደሰ እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ	ከቤት ባለቤትነት ክርክር ጋር በተያያዘ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በመመሪያ፣ በቀላጤ ወይም በቃል ትዕዛዝ ከግለሰቦች የተወሰደና በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ መሆኑ ካልተገለፀ በስተቀር ጉዳዩን ለማስተናገድ ፍ/ቤቶች ስልጣን የሚኖራቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.110/ 87 አንቀፅ 3(1)	ሚያዝያ 30/2000
171	24775	ማታዶር አዲስ ጉማ እና ቢተው ረታ	ተከሳሽ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ዕለት ባለመቅረቡ ብቻ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ በሚል የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241(1), 233	ጥቅምት 21/2000
172	25026	ወ/ሮ ሁዳ መሐመድ እና ሃጂ አህመድ አህመዲን	ተከሳሽ በራሱ ቸልተኝነት በታችኛው ፍርድ ቤት መከራከሪያ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነጥቦችን በስር ፍርድ ቤት ባላነሳበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ውሣኔ መስጠት የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 328(2) እና 182(2)	ግንቦት 14/2000
173	25890	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ዝናሽ አሰፋ (ሁለት ሰዎች)	ሌሎች ተከራካሪዎች በፍርድ ቤት በማካሄድ ላይ ባሉት ክርክር ያገባኛል የሚል 3ኛ ወገን ከውሣኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41	መጋቢት 18/2000
174	26670	አዲስ አለም ሲሳይ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ባለገንዘብ በፍርድ አፈፃፀም ከፍርድ ባለዕዳው የተረከበው ንብረት ከዕዳው በላይ ከሆነ ልዩነቱን ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 428(2)	ህዳር 03/2000
175	27739	አቶ ድንቁ ገላው እና ወ/ሮ ዋለ እሸቱ	ከመሬት ሽያጭ ውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለውና በፍ/ቤት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(2)	ጥቅምት 28/2000
176	27808	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ማይገነት ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች)	ከፍርድ በፊት የሚሰጥ የማገጃ ትዕዛዝ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነን ወገን የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ያገኘውን መብት የማይነካ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 153 (2)	የካቲት 7/2000
177	28522	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ የሞያሌ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት (አራት ሰዎች)	ውሣኔ የተሰጠበትና አዲስ ክስ የቀረበበት ክርክር የሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ የተለያየ ከሆነ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	ህዳር 3/2000
178	28802	እነ ወ/ሮ በየነች ይገዙ እና አቶ ሳሙኤል ዝቅአርጋቸው	በክስ በተጠየቀውና በታመነው መሰረት ውሣኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182(2)	ታህሳስ 8/2000
179	29738	የአፓርታማ 79/6 የመኖሪያ ቤት ንብረት ሥራ ማህበር እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እና ወ/ት ዘርአዳም አሰገኸኝ	የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ አይቶ መወሰን የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10(1)	ግንቦት 14/2000
180	29761	እነ አቶ ዳባ ደበሌ (አምስት ሰዎች) እና እነ የአቶ ደበበ ተፈራ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	ያላግባብ በመንግስት የተወረሰ ንብረትን ለማስመለስ ሲባል የሚቀርበው የፍትሐብሔር ክርክር በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር የማይወድቅ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ሀ)	ጥቅምት 14/2000
181	29780	እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ አለሙ እና ወ/ሮ ከተማሽ ቸርነት	አስቀድሞ ውሣኔ ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሌላ የክርክር ጭብጥ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	ጥር 29/2000
182	30631	ወ/ሮ ዘቢዳ ሙሣ እና እነ ወ/ሮ አሻ የሱፍ (ሁለት ሰዎች)	በህገ ወጥ መንገድ ተወስዷል /ከአዋጅ ውጭ ተወርሷል/ የተባለ ቤትን ባለቤትነት በማጣራት ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 110/87	ህዳር 10/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

183	30704	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአቶ በቀለ ወ/ማሪያም ወራሾች (ሦስት ሰዎች)	• አዋጅ ቁጥር 47/67"ን" መሠረት አድርጐ የምርጫ ቤቱ ተወስዷል /ተወርሷል/ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርበው መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ • በመንግስታዊና በህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ይመለሱልኝ እንዲሁም ውዝፍ ኪራይ ይከፈለኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ውሣኔ መስጠት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ የፍ/ቤት ስልጣን ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 110/87, አዋጅ ቁ. 47/67	መጋቢት 18/2000
184	31547	አቶ ኪዳኔ ገ/ጊዮርጊስ እና ወ/ሮ አብርሃ ተስፋሁን	ተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ባላመለከቱት ነገር ላይ ተመስርቶ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182	መጋቢት 7/2000
185	31833	ሀጅ አብዱልቃድር አህመድ እና እነ ወ/ሮ ደስታ ገ/ዮሐንስ (ሁለት ሰዎች)	በቤት ላይ የተደረገ እድሳትና ለውጥ ምን ያህል የመጠንና የአይነት ለውጥ እንዳመጣ ክርክር በተነሣ ጊዜ ልዩ አዋቂ መድቦ በማስጠናት መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136	ግንቦት 14/2000
186	32147	አቶ መሐመድ አብዱ እና አቶ አብዱራሂም አብዲ	የክስ ምክንያት የሌለው አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው በመሆኑ ተከሳሽ የሆነውን ወገን መጥራት ሳያስፈልግ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(1) (ሀ)	መጋቢት 9/2000
187	32376	የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሽዋንግዛው	ከቤት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ባለቤትነትን የመፈለም ክስ ለማየት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ረ)	ግንቦት 19/2000
188	32638	የቂርቆስ ክ/ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና እነ አቶ ይርጋ ንጋኔ (አራት ሰዎች)	ወደ ክርክር መግባት ያለበት አካል በክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆን የተወሰነው ውሣኔ መብቱን የሚነካ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔው ከመፈፀሙ በፊት ውሣኔው እንዲነሳና ክርክሩ እርሱ ባለበት እንዲቀጥል መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358	መጋቢት 12/2000
189	33606	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ደጀኔ አበበ (አምስት ሰዎች)	በጊዜያዊነት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ ከተደረገ በኋላም ቢሆን በድጋሚ በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ሊቀርብ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158	የካቲት 20/2000
190	34249	እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ እና እነ አቶ አለሙ ወንድሙ	ለክርክር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ የሚታመን ወገን በመካሄድ ላይ በሚገኝ ክርክር ተካፋይ እንዲሆን መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2)	ሚያዝያ 28/2000
191	34313	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ከበደ ታደሰ	የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብ ተከሳሽ ኃላፊነት የሚመነጨው ከተከሳሹ ኃላፊነት ስለመሆኑ እና የሦስተኛ ወገን ተከሳሽ ተጠያቂ የሚሆነው ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ ሲኖር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43(1)	መጋቢት 25/2000
192	35403	አቶ አብዱልአዝጠፍ ሙሐ እና እነ ትዕግስት በርሃ (ሁለት ሰዎች)	• ተከሳሽ ቀርቦ ያልተከራከረው በበቂ ምክንያት ማለትም መጥሪያ ሳይደርሰው መሆኑ ከተረጋገጠ የተወሰነውን ውሣኔ በማንሳት ግራ ቀኙን ማከራከር የሚገባ ስለመሆኑ • ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆነን ወገን መከላከያ ክርክር ሳይሰማ በማለፍ ውሣኔ ለመስጠት የሚችለው ተከራካሪው በችሎት ሳይቀርብ የቀረው በቂ ባልሆነ ምክንያት መሆኑን በቀረቡለት ማስረጃዎች ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.78	ግንቦት 14/2000
193	22008	የኪራይ ቤቶች አ/ድርጅት እና እነ አቶ አሳና ጥርቅ (ሦስት ሰዎች)	መክፈል የማይገባውን የከፈለ ወገን እንዲመለስለት መጠየቅ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2164	ሐምሌ 3/1999
194	22297	የጀሚ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት እና አቶ ሸዋረገድ አድበር	በፍ/ብሔር ክርክር ሂደት ማን ክርክር መጀመርና ማስረዳት እንዳለበትና የተሻለ ማስረጃ ከማቅረብ አንፃር ለማን ፍርድ ሊሰጥ እንደሚገባ በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን የህግ መርሆዎች ወደጐን በመተው የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ	ሐምሌ 24/1999
195	22469	የጀጀጋ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክ እና እነ አዳነች መንግስቱ (ሰባት ሰዎች)	• የህዝብ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ • የቤተክርስቲያንን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማረጋገጥ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ አስገዳጅ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1578	ሐምሌ 5/1999
196	22719	የአ/አ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተተኪ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን እና አቶ ነጋሽ ዱባለ	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን አስመልክቶ በሚመለከተው አካል የሚሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰረዘ በኋላ በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195	ጥቅምት 14/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

197	23608	የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽና የመንግስት ልማት ድርጅት እና አቶ ኑርበዛ ተረጋ	• የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው ለኤጀንሲው የስራ አመራር ቦርድ እንጂ ለፍ/ቤት ስላለመሆኑ • የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና አሣሪ (Binding) ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.110/87	ህዳር 3/2000
198	24269	የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና ተክለማሪያም መኮንን	• ግለሰቦች በከተማ ቦታ የመጠቀም /የመያዝ/ መብት የሚኖራቸው አግባብ ባለው መንግስት አካል /ባለሥልጣን/ ተፈቅዶ ሲሰጣቸው ስለመሆኑ • ከሚመለከተው ባለስልጣን ፈቃድ ሳይኖር የተሰራ የከተማ ቤት ህጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 292/78 አንቀፅ 7(1)	ህዳር 24/2000
199	26130	አቶ ገ/እግዚያብሔር ከበደው እና ወ/ት ሰላማዊት ወ/ገብርኤል	• የከተማ ቦታ በግል ባለቤትነት ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ • ግለሰቦች በመሬት ላይ ሊኖራቸው የሚችለው የይዞታ መብት እንጂ የባለቤትነት መብት ስላለመሆኑ • ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ የግል ይዞታ ሥር የነበረ መሬት ላይ በጋብቻ ወቅት የጋራ ቤት የተሰራ እንደሆነ ተጋቢዎቹ በመሬቱ ይዞታም ሆነ በቤቱ ላይ እኩል መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 40(3) የትግራይ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85	የካቲት 4/2000
200	27506	እነ ሣሙኤል ውብሸት እና ብዙነህ በላይነህ	• ሁከት እንዲወገድ በሚል በቀረበ ክስ ላይ ተከሳሽ የሚያነሳው ባለቤትነትን የተመለከተ ክርክር አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ • ሁከት ይወገድልኝ በሚል ክስ በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ሊይዝ የሚገባው ጭብጥ ሁከት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም የሚል ጥያቄ አዘል መሆን ያለበት ስለመሆኑ	ሐምሌ 19/1999
201	27600	ሕብረት ባንክ አክሲዮን ማህበር እና እነ አቶ ጀማል መሐመድ (ሁለት ሰዎች)	በመያዣ በተያዘ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በማሻሻልም ሆነ ሌሎች አዲስ የሚሰሩ ስራዎች መያዣው የሚያጠቃልላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.3066	ታህሳስ 06/2000
202	29005	አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ግርማቸው ይላላ (ሁለት ሰዎች)	በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኙና በየክፍለ ከተማው የተደራጁ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤቶች ራሳቸውን የቻሉ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆኑና በስልጣን ክልላቸው ሥር በሚነሱ ክርክሮች ተካፋይ የመሆን መብት ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 36/95 አንቀፅ 10(2) አዋጅ ቁ. 1/95 /አዋጅ ቁ. 18/97	ሚያዝያ 14/2000
203	30101	አቶ ገዛሽኝ አድነው እና እነ ወ/ሮ ዳሳሽ ባይነሳኝ (ሦስት ሰዎች)	በሌላ ሰው የመሬት ይዞታ ላይ በባለይዞታው ፈቃድ ህንፃ የሠራ ሰው የህንፃውን ግምት ተቀብሎ ህንፃውን ለማስረከብ የማይገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179(1) እና (2)	ህዳር 24/2000
204	30461	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ኢማ መሐመድ	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መሬትና ድንጋይ ነክ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን በነፃ መጠቀም የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 80/89 አንቀፅ 6(18)	ህዳር 3/2000
205	33499	አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ዶቶር ደሌቦ	ለጊዜው ለመኖሪያነት የተሰጠ ቦታ ላይ ሳያስፈቅዱ ቤት መስራት የተሰራውን ቤት በገንዘቡ ወጪ እንዲፈርስ የሚያስደርግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1178(2)	መጋቢት 25/2000
206	33711	በቀድሞ ወረዳ 3 ቀበሌ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ክብርነሽ ቀደመ	የቤት ባለቤት ሳይሆን ወይም ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለኪራይ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስ የሚቀርብ አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ	መጋቢት 23/2000
207	33831	ሃሰን ኢብራሂም እና ኢብራሂም ይመር ሃሰን	በህግ በግልጽ የተረጋገጠ መብት እያለ በህሊና ግምት ላይ የተመሰረተ ፍርድ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ	ሚያዝያ 14/2000
208	33924	ወ/ሮ ገብርኤላ ኒኮላቶማስ እና የኪራይቤቶች ኤጀንሲ	ከቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ክስ የሚያቀርብ ሰው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ሁልግዜም ቢሆን በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም ሊኖረው አይችልም ብሎ ለመደምደም የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1)	ሚያዝያ 16/2000
209	34406	ወ/ሮ መገርቱ ነጋሣ እና እነ ወ/ሮ ፀሃይ ልጋ	ያላግባብ መበልፀግ ጋር በተያያዘ የሚነሳ የካሣ ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ ከውል ውጭ በሚደርስ ሃላፊነት ሥር የተመለከተው የይርጋ ዘመን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1)	ሚያዝያ 7/2000
210	20295	አቶ ደጀኔ ለገሠ እና እነ አቶ መላኩ ጌታቸው	ወራሽነትን ካረጋገጡ በኋላ ንብረት ተይዞብኛል ይመለስልኝ የሚል ጥያቄ ከሦስት አመት በኋላ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1)	ሐምሌ 5/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

211	25567	ወ/ት አይናለም አበበ እና አቶ ደገፉ ጉርሙ	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000 ወራሽ ነኝ ወይም ወራሽነቱ ይረጋገጥልኝ ከሚል ጥያቄ ጀምሮ የውርስ ንብረት ያለ አግባብ ተይዞብኛል በሚል ለሚቀርብ አቤቱታ ጭምር ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 999, 1000	ህዳር 12/2000
212	25664	አቶ ተገኝ ይማም እና እነ አቶ ካሣሁን ደሳለኝ	በወራሾችና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ የውርስ ንብረትን የተመለከተ ክርክር በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845	ግንቦት 7/2000
213	26422	ወ/ሮ ስንልሽ ማዘንጊያ እና እነ አቶ ተስፋ ማዘንጊያ	ከውርስ ሀብት ጋር በተያያዘ ወራሽ ነኝ የሚል ወገን መብቱንና የውርስ ንብረቶቹ በሌላ ወራሽ መያዛቸውን ካወቀ ከሦስት ዓመት በኋላ የሚያቀርበው የወራሽነት ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1)	ጥቅምት 28/2000
214	28686	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ግዛው መንጀታ	ውል የመጣስ ተግባር ተጀምሮ ያልቆመ ይልቁንም በመቀጠል ላይ ያለ ተግባር መሆኑ በማናቸውም ጊዜ ግዴታን ለመጠየቅ የሚያስችል ስለመሆኑና በይርጋ ታግዷል ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845, 1846	ህዳር 24/2000
215	28997	ስለ አሶሳ ዞን ግብርና እና ትምህርት መምሪያ የቢንሻንጉል ጉምዝ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ እና በላይ ወርቁ	የመብት ጥያቄን ከፍርድ ቤት ውጪ ላሉ አስተዳደር አካላት ማቅረብ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1851(ለ)	ታህሳስ 1/2000
216	29920	የባህር ዳር ጨ/ጨ/አ/ማኅበር እና አቶ አመሻ ሰይድ	ዳኝነት የተጠየቀበት ነገር ተቀባይነት ሣያገኝ የታለፈ እንደሆነ እንደተከለከለ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(3)	ጥቅምት 26/2000
217	31185	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ይርጋ በተቋረጠ ጊዜ ቀድሞ የነበረው የይርጋ ጊዜ እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1852(1)	ግንቦት 12/2000
218	31217	የቴሌኮምኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ጫሊ ሐሰን	የደሞዝ ጭማሪና ቦነስን የተመለከተ ክስ በስድስት ወር ውስጥ አለመቅረቡ መብቱን በይርጋ የሚያሳግድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162(3)	ግንቦት 14/2000
219	31857	መሐመድ አብደላ እና የድሬዳዋ ኢትዮ ጂቡቲ ምድር ባቡር	የአሰሪ የስራ ስንብት እርምጃ የመውሰድ መብት ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከተከሰተበት ጀምሮ በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ተግባራዊ ካልሆነ መብቱ በይርጋ የሚቀር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/97 አንቀፅ 27(3)	መጋቢት 17/2000
220	32788	የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና አቶ ግርማ ተገኝ	አሠሪ የሠራተኛን መብት በጽሁፍ ያወቀ መሆኑ ሠራተኛው በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ገደብ የሚያቋርጥ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 164(3)	መጋቢት 18/2000
221	34011	እልፍነሽ አማረ እና አቶ ግርማ አማረ	ቤት በፍ/ብሔር ህጉ ውስጥ እንደ ርስት የማይቆጠርና የይርጋ መርሆ ተፈፃሚ የሚሆንበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(2)	መጋቢት 25/2000
222	31748	ይስማው ድረስ እና ይበልጣፍ ፍቅር	ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ የሚገዛው የህግ ክፍል ይርጋን አስመልክቶ በተለይ የሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ በሌለ ጊዜ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845	የካቲት 18/2000
223	18832	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ክበደ ቱሉ (ስድስት ሰዎች)	ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ የተወሰነው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የስራ ውሉ ያለ በቂ ምክንያት ከተቋረጠ ሠራተኛው የውሉ ጊዜ ወይም ስራው እንኪያልቅ ቢቆይ ያገኘው የነበረውን ደሞዝ የሚያህል ደሞዝ የሚከፈለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43(4)(ለ)	ህዳር 3/2000
224	20416	አቶ ቢንያም ገረመው እና የቻይና መንገድና ድልድል ስራ ድርጅት	ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ከሆነ ክሱ እንዲሻሻልና ክርክሩ እንዲለወጥ ሊፈቀድ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91	ታህሣሥ 8/2000
225	21329	የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ በቀለ ኩምሳ	የሥራ መሪ የሆነ ሰው የሥራ ውሉ ተቋርጧል በሚል ሣይሰራ ለቆየበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለው የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	ጥቅምት 19/2000
226	22275	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ኃይሌ ገ/ሥላሴ	• አሰሪ የሥራ ውሉ ዘመን ከማለቁ በፊትም ቢሆን በቂና ህጋዊ ምክንያት ካለው የሠራተኛን የሥራ ውል ሊያቋርጥ ስለመቻሉ • በበቂ ምክንያት የተደረገ የሥራ ውል ማቋረጥ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠም በሚል ህገ-ወጥ ስንብት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ • በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለን የስራ መደብ በሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የሥር ውል ለማቋረጥ ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 35	ሐምሌ 10/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

227	25317	ጥቁር አባይ ትራንስፖርት እና ደሳለኝ አብርሃ	በህገ ወጥ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ በሞተ ጊዜ ለጥገኞቹ ክፍያ የሚፈፀምበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/ 96 አንቀፅ 39(2),110(2), 40	ህዳር 10/2000
228	25511	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ አብራራው ከፍያለው	በህጋዊ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 39	ጥቅምት 2/2000
229	26077	አቶ አይናለም ባይሌ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ከተደነገገው ይልቅ በአሰሪና ሠራተኛው መካከል የሚደረገው የህብረት ስምምነት ለሠራተኛው የተሻለ መብትና ጥቅም የሚያስገኝ በሆነ ጊዜ የህብረት ስምምነቱ ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 134(2)	ሐምሌ 12/1999
230	27704	ድራጋዶስ ጂ እና ፒ የመንገድ ስራ ድርጅት እና አብዲ ሁሴን	የሥራ ውሉ በህገ-ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል ወደሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ ካልሆነ በስተቀር ውዝፍ ደመወዝ የማይከፈል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5)	ጥቅምት 5/2000
231	27959	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ አሊ መሐመድ	• አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ተቋርጦ ለነበረበት ጊዜ የዓመት ዕረፍት ሊያገኝ የማይችል ስለመሆኑ • የዓመት ፈቃድ ከሁለት ዓመታት በላይ ሊተላለፍ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 79(5)	ህዳር 3/2000
232	29692	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ከበደ	አሠሪ ቋሚ ስራ ሆኖ እየተቋረጠ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ እንዳለቀ የሠራተኛን ውል ለማቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ	ጥቅምት 12/2000
233	29740	አቶ ስሜነህ ተክሉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ	ፍርድ ቤቶች በቀረበ ክስ ላይ የዕዳ ማቻቻል ጥያቄ በተነሣ ጊዜ ማስረጃዎችን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ	ሚያዝያ 2/2000
234	29866	ቻይና ዋንቦ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን እና ወርቅነህ ምህረቱ	የውክልና ስልጣን ማስረጃ በወካይና በተወካይ መካከል የቅጥር ውል ስለመኖሩ የሚያስረዳ ስላለመሆኑ	ግንቦት 7/2000
235	29949	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ዋሲሁን አዳነ	ፍርድ ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ የሚሰጥ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ	ሐምሌ 19/1999
236	30956	የወረዳ 5 አጠቃላይ ነጋዴዎች ማህበር እና አቶ በድሉ ጫላ	ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ	ሚያዝያ 9/2000
237	31402	የኢትዮጵያ አገር አቋራጭ ከፍተኛ አውቶብስ የግል ባለንብረቶች ማህበር እና አቶ አያሌው ይርጉ	በጡረታ የተገለለን ወይም የጡረታ ዕድሜው ያለፈን ሠራተኛ ወደ ሥራ መልስ ተብሎ አሰሪ የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 24(3) አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀፅ 12(1)(ሐ)	ሚያዝያ 30/2000
238	32545	አቶ ግርማ ሽፈራው እና የክርስቲያን በጐ አድራጐት ልማት ድርጅት	የፕሮቪደንት ፈንድ ባለመብት የሆነ ሰው በአስር አመት ውስጥ መብቱን ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845	ግንቦት 14/2000
239	33314	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ወልዴ (አስር ሰዎች)	በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ የነበረን ፋብሪካ የተረከበ ባንክ ከሠራተኞች መብቶች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጥ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 16 አዋጅ ቁ. 97/90	ግንቦት 28/2000
240	33513	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ዘውዴ ተናኘ	በአንድ የስራ መደብ ላይ በቋሚነት የደረጃ እድገት ይሰጠኝ በማለት የሚቀርብ ክስን ለማየት የክልል ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 138	ጥር 27/2000
241	34588	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ደረጀ ወልደ ኪዳን	በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ የተባለ ሰው በፍትሐብሔር ረገድ ከቀረበበት ክስም የግድ ነፃ ይሆናል ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27	ግንቦት 5/2000
242	35440	የዋልያ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ድርጅት እና ብርሃኑ አለሜ	ከሠራተኞች ማህበር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር በአሰሪ የሚደረግ የሠራተኞች ቅነሳ የህግ አግባብ ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28(1)	ግንቦት 19/2000
243	29415	ዋተር አክሽን እና ይልማ አሰፋ	አዲስ ወደ ተዛወሩበት ቦታ በመሄድ ስራ አለመጀመር እና ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ገበታ ላይ አለመገኘት በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውልን ለማቋረጥ በቂና ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2)(ለ)	ጥር 27/2000
244	32822	ጂ.ሰሸን የንግድና ኢንዱስትሪ የመኸር ቃጫ ውጤቶች ፋብሪካ እና መኮንን አበራ	ያለ በቂ ምክንያት ከስራ መቅረት አሠሪ የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) (ለ)	ጥር 27/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

245	32229	መሪጌታ ልሣነወርቅ በዛብህ እና ጠቅላይ ቤ/ክህነት ጽ/ቤት	የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሣኔ መሻር ሳያስፈልገው ጉዳዩ ስልጣን ወዳለው አካል ቀርቦ መታየት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	ሚያዝያ 30/2000

ቅጽ 7

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
246	12719	ሉክሰር የቱሪስትና የገዛ ወኪል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እና ብሩኔይስ ኃ/የተ/የግ/ማኀበር	በሁለት ወገኖች መካከል የተፈረመ ስነድን እንደ ህጋዊ ስምምነት ለመውሰድ የፈራሚ ወገኖችን ሃሳብና ፍላጐት መመርመር አስፈላጊ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1734, 1952/1/	ታህሳስ 17/2000
247	20232	አቶ ትዕግስቱ ብዛ እና አቶ ይሃ ይብራ	የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች የሚፈጠሩባቸውና የሚረጋገጡባቸው በመሆናቸው የውል ህግ መሰረታዊ ድንጋጌዎች መሟላታቸው አስፈላጊ ሁኔታ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 715, የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706, 1679	ሐምሌ 24/1999
248	23609	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አሰበወርቅ ዘገዬ	የስራ መሪ የሥራ ውል ያለአግባብ በተቋረጠ ጊዜ የስራ መሪው ሊያገኝ ስለሚገባው ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና ጥቅማጥቅም የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2573, 2574/2/, 2570/2/, 2577, 2562	ታህሳስ 15/2000
249	30298	አቶ የሺወንድም አቡሃይ እና አቶ አየነው ማለደ	የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው ንብረቱ ወደ 3ኛ ወገን የተላለፈ በሆነ ጊዜ የንብረቱን ዋጋ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171	ጥር 20/2000
250	16218	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ወ/ሮ አስካለ ሁንዴ(ሁለት ሰዎች)	ባንኮች ከሚሰጡት ብድር እና የመያዣ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች አዋጅ ቁ. 97/90"ን" ዓላማ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በባንኮች የሚወጡትን የፎርክሎዠር መመሪያዎችና አግባብነት ያላቸውን ህግጋት ግምት ውስጥ በማስገባት አልባት ማግኘት ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 እና 4, አዋጅ ቁ. 216/92	መጋቢት 16/2000
251	25863	የኢት/ልማት ባንክ እና የኢት/ንግድ ባንክ (ሁለት ሰዎች)	ለባንክ በመያዣነት በተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚኖር የቀዳሚነት መብት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3088, 3052, 3081,3059	ጥቅምት 26/2000
252	29269	የኢት/ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ዋለልኝ አያሌው(ሁለት ሰዎች)	• በፍርድ የተቋቋመ መያዣ ላይ ፍርዱ እንዲሰጥ ያደረገው ባለገንዘብ መያዣ በሆነው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ እና • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 ተፈፃሚነት የአንድ ፍርድ ባለዕዳ ንብረት በእርሱ ላይ የቀረቡትን ገንዘብ ጠያቂዎች ፍላጐት የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ክፍፍሉ ጋር በተገናኘ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3041, 3044, 3059/1/, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403,154	ጥቅምት 15/2000
253	29375	የት/ንግድ ባንክ እና ተስፋዬ ገ/ጊዮርጊስ	የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት ከተሰጠ በኋላ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ የሚደረግ ማናቸውም የማሻሻል ሥራ የመያዣ ውሉ አካል ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3066 አዋጅ ቁ. 97/90	ጥቅምት 19/2000
254	33295	ወ/ሪት ብርሃኔ አበበ እና እነ አቶ ማርቆስ ተርፋ (አራት ሰዎች)	የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማንኛቸውም ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ ርስተ መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ምንም አይነት ውጤት የማያስገኝ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3052, 3053,1605, 1607, 1606	ግንቦት 21/2000
255	23024	ወ/ሮ ፋጤ በሽር እና መልዓከ ገነት ዮሐንስ አምባው እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ	በጣልቃ ገብነት ተሳታፊ ሆኖ የፍርድ ተጠቃሚ የሆነ ወገን ዋና ተከራካሪ ከሆኑት ወገኖች መካከል በአንዱ አነሣሽነት ጉዳዩ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ በሥር ፍርድ ተጠቃሚ የሆነው ጣልቃ ገብ ባልተጠራበት ሁኔታ የሚሰጥ ውሣኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40/5/"ን" የሚፃረር ስለመሆኑ	ሐምሌ 24/1999
256	24221	ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና 4ኛ ወ/ሮ አረጋሽ አምደሚካኤል	ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ጋር የተደረገን የኪራይ ውል መሰረት በማድረግ የተያዘ ቤትን ያለአከራዩ ፍቃድ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ለኪራይ ውሉ መሰረዝ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ	ህዳር 24/2000
257	25938	ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና የአቶ ገ/ሕይወት ከ7ዶም ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	የኪራይ ውል የተለየ ፎርም መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የሌለ ስለመሆኑ እና በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚፀና ውል /ህጋዊ ውጤት ያለው ውል/ ለመመስረት በሁለቱም መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719/1/,1719-1930, 2898/3/	መጋቢት 25/2000
258	28025	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና	ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ለተከራዩ በሚሰጥ ማስታወቂያ በማናቸውም ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ እና የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ/ለማፍረስ ለተከራዩ ማስታወቂያ /ማስጠንቀቂያ/ መስጠት አስገዳጅ ቅድመ	ጥር 20/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		አቶ ታደለ አበበ	ሁኔታ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966/1/	
259	31601	ወ/ሮ መዓዛ ይሕደጐ እና እነ አየለ ወልዴ (ሁለት ሰዎች)	የኪራይ ውል ተቋርጦ ውዝፍ ኪራይ እንዲከፈለኝና ቤቱንም ልረከብ በሚል የሚጠየቅ ዳኝነት የኪራይ ገንዘብ የተጠየቀበትን ቤት ግምት ጭምር ታሳቢ ተደርጐ የዳኝነት ክፍያ ሊቀርብበት የሚገባ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 227/2/, 226	የካቲት 11/2000
260	31634	ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአቶ ወርቁ ሚስት ወ/ሮ ጽጌ በየነ (ሰባት ሰዎች)	መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ እስከ 2 ዓመት ድረስ ሳይከፈል የቀረ የኪራይ ዕዳ እንደተከፈለ የህግ ግምት ይወስድበታል ማለት ባለገንዘቡ /አከራዩ/ ክስ መስርቶም ቢሆን ዕዳውን ለማሰብሰብ የማይችል መሆኑን ለማመላከት እንጂ ተከራዩ /ባለዕዳው/ ግዴታውን እንደተወጣ የሚያስቆጥረው ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/መ/	መጋቢት 4/2000
261	32521	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ዳባ ኢጃቶ	የታወቀ የኪራይ ውል ግንኙነት ሳይኖር ወይም ባለቤት ሳይሆኑ በማይንቀሳቀስ ንብረት መገልገል የተገለገለውን ወገን በንብረቱ በበለፀገው መጠን ኃላፊ የሚያደርገው ስለመሆኑ	ሚያዝያ 7/2000
262	34456	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና ወ/ት ደብሪቱ ወልደሃና	ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ውሉ የተደረገበት ጊዜ ካለቀና ውሉ ወደ ያልተወሰነ ጊዜ ከተቀየረ የኪራይ ውሉን በማናቸውም ጊዜ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966	ግንቦት 14/2000
263	18380	አቶ ማሞ ደምሴ እና እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር (ሁለት ሰዎች)	ውል ይጽደቅልኝ በሚል ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1//ሀ/	ጥቅምት 5/2000
264	22448	ኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ክፍል አ/ማህበር እና አቶ ሙሉነህ ካሰ	ፍርድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ ችሎታ ያለው ፍርድ የተፈረደለት ሰው /ወገን/ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378/1/	ጥቅምት 28/2000
265	22860	ሰንላይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ እና አቶ ካሣዬ ዘውደ	አንድ ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት ህጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ያዘዘ ካልሆነ በቀር ግዴታው መኖሩን በጽሁፍ፣ በምስክር፣ በህሊና ግምት በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሃላ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2002	የካቲት 18/2000
266	23331	ጀማል ሐሚድ እና እነ ወ/ሮ ለተሃይማኖት ተክሌ (አምስት ሰዎች)	በህግ ፀንቶ ያለ የሽያጭ ውልን መሰረት በማድረግ የተገኘ መብት ውሉ ፈራሽ እስካልተደረገ ድረስ የሚቀጥል ስለመሆኑ	ታህሳስ 1/2000
267	24974	እነ አቶ ፈቃዱ ደሬሌ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ንጉሴ ወርቁ (ሁለት ሰዎች)	በውል ከተገባ ግዴታ አመዛኙ ክፍል ተፈፀመ ወይም/እና አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተከስቷል ለማለት ባልተቻለ ጊዜ ውል እንዲሰረዝ ለመወሰን የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771,1784, 1785	ታህሳስ 8/2000
268	26996	አቶ በቀለ ደቦጭ እና እነ ወ/ሮ አዛለች ደግለኝ (ሰባት ሰዎች)	ውል የተደረገበት ጉዳይ ሊፈፀም የማይችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ቦታ የመመለስ ውጤት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1715, 1815	የካቲት 18/2000
269	27349	ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኪባንያ እና ዘላቂ ግብርና ተሐድሶ ኮሚሽን	ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚፈጠርን አለመግባባት በስምምነት ወይም ደግሞ በአስታራቂ አማካኝነት ለመፍታት የተስማሙ ከሆነ ይኼው ስምምነት ተፈፃሚ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1765, 1731/1/	ታህሳስ 8/2000
270	28663	አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ እና ወ/ሮ አልማዝ ወልዴ	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658 ተጋቢ ወገን ከሦስተኛ ወገን ጋር ያደረገውን ውል ለማፍረስ ምክንያት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658, 686	ጥር 27/2000
271	29233	አቶ ሙሃዲን ፋሪስ እና አቶ እያሱ በዕደ ማርያም	በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተደረገ ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሰረት የተሟላ አይደለም በሚል ውሣኔ ሲሰጥ ተዋዋይ የነበሩ ወገኖች በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815 መሰረት ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1720/1/, 1815	ግንቦት 7/2000
272	32222	አቶ መሐመድ ኢብራሂም እና አቶ ታይደር ማች	ያልነበረ ቤትን ሠርቶ ለማስተላለፍ በሚል የሚደረግ ስምምነትን በተመለከተ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2876, 1723, 3019, 3020/2/	የካቲት 4/2000
273	32899	ወ/ሮ አስካለ ማርያም ታደሰ እና አቶ ተሾመ ካሣዬ	የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን በተመለከተ የተደረገ የሽያጭ ውል ተቀብሎ ከማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ ከማያያዝና ከመፃፍ በስተቀር የሽያጭ ውሉን የማዋዋልና የማረጋገጥ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ	ግንቦት 21/2000
274	23322	ወ/ሮ አዳነች ወርዶፋ እና እነ ወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ	የውርስ ሀብት አጣሪ የንብረት ባለቤትነትን የመወሰን ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 956	ሰኔ 19/2000
275	25869	ወ/ሮ አየለች አልታዬ እና ወ/ሮ አስናቀች አየለ	የማይንቀሳቀስ ንብረት የጋራ ባለሀብት የሆኑ ሰዎች ንብረቱን በአይነት ለመከፋፈል ባልቻሉ ጊዜ ንብረቱ በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡን መካፈል ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1272, 1273	ሰኔ 19/2000
276	30158	እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞግዚት ሐይሉ ሲሳይ እና የክ/ል እሸቱ ተስፋዬ ወራሾች	በፍ/ብ/ህጉ ውስጥ "ከዘር የወረደ ርስት" በሚል የተቀረበው አገላለጽ በህገ-መንግስቱ የተሻረ ወይም ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000/2/ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 40	ሰኔ 19/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

277	32414	ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ እና እነ ወ/ሮ ሃሳብከፋይ ጌራወርቅ (ሁለት ሰዎች)	ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርብ ክስ እና የተሰጠ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ በሚል የሚቀርብ ተቃውሞ የተለያዩ ይዘትና ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996/1/, 998/1/, 973, 996/2/	ሰኔ 24/2000
278	34076	ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ እና እነ እማሆይ ድብቅነሽ ግዛው (ሁለት ሰዎች)	የውርስ ሃብቶች በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ በሆነ ጊዜ የሚነሱ ክርክሮች የውርሱ ክፍያ በተጀመረበት ቦታ ለሚገኝ ፍ/ቤት የሚቀርቡና የሚስተናገዱ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 23	ሰኔ 10/2000
279	24703	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ት/ቢሮ	በህግ ተቀባይነት ያለው የኢንሹራንስ ውል የሚቋቋምበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1725, 1727 የንግድ ህግ ቁጥር 651, 654, 657	ሚያዝያ 9/1999
280	22069	የአማራ ብ/ክ/መንግስት ፍትሕ ቢሮ እና አቶ አስማማው አራጌ	በወንጀል ህግ የሃሳብ ክፍል የሚረጋገጠው ከወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ በመነሳት ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ቁ. 522 /1/ /ሀ/	ጥቅምት 28/2000
281	22452	የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና አግምነው ገ/መስቀል	በወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ ሥር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሳቸው የሚቆሙ ስለመሆናቸው የወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/	ሐምሌ 30/2000
282	23855	የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ እና አቶ ፀጋሁን መንግስቱ	የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈፀምበት የመንግስት ቀረጥ ያልተከፈለበት መኪና ይዞ የተገኘ ግለሰብ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ ያልተባለ ቢሆንም ግለሰቡ ተገቢውን ቀረጥ ከፍሎ መኪናውን መረከብ አልያም ደግሞ መኪናው መወረስ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 74 አዋጅ ቁ. 388/95 አንቀጽ 80/3/	ጥቅምት 26/2000
283	24278	ሰለሞን ሄርጃቦ እና የደ/ብ/ብ/ ሕ/ክ/መ/ የሥ/ፀ/መ/ኮ/ዓ/ሕግ	በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ መሠት የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው እንዲጠብቃቸው በአደራ የተረከባቸውን ወይም በሥራው አጋጣሚና ምክንያት በእጁ የገቡትን ንብረቶች የወሰደው/የሰወረው/ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ	ህዳር 10/2000
284	28952	የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ እና አቶ ባንቲ ታኤራ	በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/ መሠረት ከሣሽ አቅርቦት የነበረውን ክስ ካነሣ በኋላ እንደገና ክሱን ለመቀጠል የሚችል ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/, /5/	መጋቢት 16/2000
285	29325	ኤርምያስ ካሣ ተፈራ እና ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ክስ የቀረበበት ሰውን አስመልክቶ ጉዳዩ በሌለበት ነው የታየው ሊባል የሚችልበት አግባብ የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ. 161/1/	የካቲት 18/2000
286	31734	አቶ አስናቀ በቀለ እና ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ተከሶ የተያዘ ሰው ዋስትና በጠየቀ ጊዜ ፍ/ቤት ተከሳሹ ተመልሶ ሊቀርብ አይችልም የሚል ግምት ለመውሰድና ዋስትናን ለመከልከል በቂ ምክንያት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 67/ሀ/	ጥቅምት 15/2000
287	34077	አቶ ሰይድ ይመር እና የአማራ ክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	በወንጀል የተከሰሰ ሰው የሚያነሳው የዋስትና ጥያቄ መታየት ያለበት ሊወሰንበት ከሚችለው ቅጣት አንፃር ስለመሆኑ	መጋቢት 9/2000
288	34280	አቶ ግርማይ ደስታ እና ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ህግ ቅጣት ሊገደብ የሚችልበት አግባብ የወንጀል ህ/ቁ. 192,194	ግንቦት 14/2000
289	34521	የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ እና ስንታየሁ ተፈራ	በወንጀል ህግ ቅጣትን በልዩ የህጉ ክፍል ከተወሰነው መነሻ ዝቅ አድርጐ በማቅለል ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የወ/ህ/ቁ. 184, 179	ሰኔ 3/2000
290	35611	ሻለቃ ታደሰ ካሕሳይ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ህግ ጉዳዩን ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት አቤቱታ አቅራቢው ባልቀረበ ጊዜ አቤቱታው እንዲሰረዝ የሚደረገው አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን በትጋት ያልተከታተለ ወይም በቸልተኝነት የተወው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ 193/1/	ሰኔ 19/2000
291	18809	አቶ ሚሊዮን ዑመር እና ዮፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን	በደንብ ቁጥር 75/1993 ከምፒዮተርን ጨምሮ ከተለያዩ መሳሪያዎች ህንፃዎችና ሌሎች ዕቃዎች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ለመሰብሰው የተደነገገው መኪናን በማከራየት የሚገኝን ገቢ የሚያካትት ስለመሆኑ ደንብ ቁጥር 75/93 አንቀጽ 2/9/ ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 24/2/ /ሸ/	ሰኔ 12/2000
292	19258	አቶ ተክሌ ዋቅጅራ እና አቶ ሾንጣ ገቡ	የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር መዋጮ መክፈል ያለበት ማህበሩ ሲቋቋም እንጂ ተቋቁሞ ሥራው ከተጀረ በኋላ ስላለመሆኑ	ሐምሌ 12/1999
293	23389	የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኅበር እና እነ ባህሩ አብርሃም (ሁለት ሰዎች)	የአክሲዮን ማህበር አባላት መብታቸውን የሚነካ ድርጊት በማህበሩ አስተዳዳሪዎች በተከናወነ ጊዜ በቀጥታ አስተዳዳሪዎቹን ሊከሱ ስለመቻላቸው የንግድ ህ/ቁ. 364,365,367	ሐምሌ 10/1999
294	28923	የባህር ዳር ጨ/ጨ አክስዮን ማሕበር እና የባህር ዳር ልዩ አስተዳደር እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ	የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ ከመቀየራቸው በፊት ያለባቸውን የዕዳ ክርክር በኃላፊነት ይዞ መከራከር ያለበት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 208/1992 አንቀጽ 5/1/, 6/1/ /ሐ/, አዋጅ ቁ. 182/1992	ግንቦት 7/2000
295	10489	የስራና ከተማ ልማት ሚ/ሮ ተተኪ መሠረተ ልማት ሚ/ር እና	በበጀት የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት የፍርድ ባለዕዳ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔውን ለማስፈፀም ለሌላ ጉዳይ በበጀት የተያዘውን እና የሰራተኛ ደመወዝን የሚያካትተውን ገንዘብ ከብሔራዊ ባንክ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ለማዘዝ	ሐምሌ 24/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		የቀድሞ ብሐራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግ/ማ	ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 404	
296	18576	ወ/ሮ ደስታ መኮንን እና ወ/ት መሰሉ ጌታሁን	የውርስ ማጣራት ሪፖርት ከፀደቀ ወይም በፍ/ቤት ተቀባይነት ካገኘ በኋላም ቢሆን እንደ ፍርድ ተቆጥሮ በቀጥታ የአፈፃፀም አቤቱታ ሊቀርብበት ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 944, 946, 956, 960, 996	ግንባት 26/2000
297	19283	ወ/ሮ መድሐኒት ኃይሉ እና የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ	ባንክ ለሰጠው ብድር በመያዣነት እጁ ያስገባውን የተበዳሪ ንብረት በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛው የሃራጅ ጨረታ ለሽያጭ አቅርቦ ገዢ ያልተገኘ እንደሆነ ንብረቱን ሊያስቀር የሚችለው ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሰረት ስለመሆኑ	መጋቢት 9/2000
298	22481	አቶ ክፍሌ ወልዴ እና ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	በሀራጅ ጨረታ የአሻሻጥ ስርዓት ላይ "ግዙፍ የሆነ ጉድለት" ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር እንደተፈፀመ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 422/3/, 428/5/, 455, 428/1/	መጋቢት 4/2000
299	22930	ወ/ሮ ታድሬ አባተ እና ወ/ሮ ዓለም ገ/የሱስ	ባልና ሚስት በፍቺ ከተለያዩና የንብረት ክፍፍል ከተደረገ በኋላ ከአንደኛው ተጋቢ የግል ተግባር የሚመነጭ ዕዳ አፈፃፀም የተጠየቀው /የቀረበው/ ከፍቺ በኋላ እስከሆነ ድረስ ለዕዳው ምክንያት ከሆነው ተጋቢ ብቻ የሚጠየቅ ስለመሆኑ	ሚያዝያ 30/2000
300	23733	እነ ሃፍቶም ገ/አራሃ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ሙሉ ካሣ (አራት ሰዎች)	ከንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ በዋናው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ንብረት መካፈል ከተቻለ እንዲካፈል ካልሆነ ደግሞ በባለሙያ ተገምቶ እንዲካፈሉ በሚል የተሰጠን ፍርድ መነሻ በማድረግ የአፈፃፀም ችሎት /ፍ/ቤት/ ከተከራካሪ ወገኖች መካከል አንደኛው ግምቱን ከፍለው ንብረቱን እንዲያስቀሩ በሚል ትዕዛዝ ለመስጠት የማይችል ስለመሆኑ	ህዳር 24/2000
301	23989	አቶ ደስታ ሠርዳ እና የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ	የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ንብረት /ባለቤትነት/ ከሻጭ ወደ ገዥ ያለመዛወሩ ብቻ ሦስተኛ ወገኖች በሻጭ ላይ ሽያጭ የተካሄደበት ንብረት ላይ የጀመሩት አፈፃፀም እንዲቀጥል ለማስደረግ በቂ ሁኔታ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878	ታህሳስ 17/2000
302	25031	ወ/ሮ አልታየወርቅ ኃ/ማርያም እና አቶ ዓለማየሁ ገሰቱ	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሰረት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358,418	ታህሳስ 1/2000
303	26553	የባህርዳር ልዩ ዞን ገንዘብ መምሪያ እና የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ እና ሙክታር መሐመድ	• የማይንቀሳቀስ ንብረት በሃራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በሃራጅ እንዲሸጥ የሚወጣው ማስታወቂያ ለ30 ቀናት መቆየት ያለበት ስለመሆኑ • ንብረቱ በመያዣ የተያዘ እንደሆነም የመያዣው ልክ ምን ያህል እንደሆነ በጨረታ ማስታወቂያ ላይ መገለጽ ያለበት ስለመሆኑ • ሽያጩ ባልተገባ መንገድ ተከናውኗል ከተባለም ጨረታው በድጋሚ መካሄድ ያለበት ስለመሆኑ • በመያዣ የተያዘን ንብረት በሌላ ባለገንዘብ ጠያቂነት እንዲሸጥ ሊደረግ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3084, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 426, 423/2/ /ለ/, 445-447, 415	ሐምሌ 3/1999
304	27574	ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ እና የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማኅበር	በሽምግልና ጉባኤ አማካኝነት የተሰጠ ውሣኔ በፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 215/1/, 319/2/	ጥቅምት 26/2000
305	28019	አቶ ብርሀኑ ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ	ፍርድን በአግባቡ ውጤት ለመስጠት የአፈፃፀም ችሎት የፍርዱን ትክክለኛ ቃል እና መንፈስ መከተል ያለበት ስለመሆኑ	ታህሳስ 1/2000
306	28154	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ 3ኛ ወገኖች መብት ያቋቋምን ስለሆነ አፈፃፀም ሊቀጥል አይገባም በሚል አቤቱታ ያቀረቡ እንደሆነ ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በአቤቱታው ላይ ያላቸውን ክርክር በቅድሚያ በመስማት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418/1/, 419	ሚያዝያ 14/2000
307	29344	ወ/ሮ ዝማም ህሉፍ እና አቶ መረሣ ገ/ዮሐንስ	ውሣኔን የሚያስፈጽም ፍ/ቤት በውሣኔው መሰረት ከማስፈፀም ወጪ በአፈፃፀም ጊዜ ዋናውን ፍርድ ሊለውጥ የሚችልበት የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418	ግንቦት 5/2000
308	29653	አቶ ነጋ ደምሴ እና ሃምሳ አለቃ አዲሱ ደምስ	በዋናው ክርክር ጉዳቱ ተከራክሮ ውሣኔ ያላገኘ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ጊዜ ውሣኔ እንዲፈፀምለት ጥያቄ የሚያቀርብበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418	መጋቢት 9/2000
309	33760	ሐጂ ታጁ ለገሠ እና የጎንደር ከተማ የመሃል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር	የንግድ ድርጅት /መደብር/ ላይ ያለ መብት የድርጅቱ ንግድ የሚካሄድበትን ቤት የኪራይ መብት የሚያካትት ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 127	መጋቢት 18/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



ቅጽ-10

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ - 10

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት መልዕክት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጀ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው፣ በዚህ ረገድ የሚሠጡ የሰበር ውሣኔዎችን ፍርድ ቤቱ አሣትሞ ማሠራጨት እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሠረትም እስካሁን ድረስ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው ፍርዶች ከቅጽ 1 እስከ ቅጽ 7 ድረስ በማሣተም ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲሠራጩ ተደርገዋል፡፡

እነዚህ ፍርዶች የሀገራችን ፍርድ ቤቶች የሚሠጧቸው ፍርዶች ወጥነትና ተገማችነት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ የማይናቅ ሚና እየተጫወቱ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህን ቀጣይ ለማድረግ ቅጽ 8፣ 9 እና 10 እነሆ ለሕትመት በቅተዋል፡፡

አስገዳጅ የሰበር ውሣኔዎች ሥራ ላይ ከዋሉ አጭር ጊዜያቸው ነው፣ በአንፃራዊነት የብቃትም ሆነ የልምድ ውሱንነቶች በመኖራቸው እነዚህ እጥረቶች በሰበር ፍርዶቻችን ላይ አልፎ አልፎ መንፀባረቃቸው አልቀረም፡፡ በዚህ መስክ የረጅም ዘመናት ታሪክ ያሏቸው ሀገሮችም በተመሣሣይ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው እኛም አቅማችንን በማጠናከር የእነዚህን አገሮች ተሞክሮዎች በማገናዘብና የሀገራችን የሕግ ባለሙያዎች በፍርዶቻችን ላይ የሚሠጡትን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ግብዓት በማድረግ ኃላፊነታችንን በአግባቡ ለመወጣት ጥረታችን እንደሚቀጥል በዚህ አጋጣሚ እየገለጽሁ የሕግ ትምህርት ቤቶቻችን፣ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎችና ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ለጥረታችን እውን መሆን የማይተካ ድርሻ አላቸውና ከጎናችን እንዲቆሙ ጥሪየን አስተላልፋለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፕሬዝዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ2002 ዓ.ም የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች

ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ቤተሰብ				1
1	በጋብቻ ውል ላይ ባልና ሚስት "መተዳደሪያችን" ነው በሚል ያመለከታቸው ንብረቶች የጋራ ንብረት ተደርገው የሚቆጠሩ ስለመሆናቸው	38544	አቶ ብሩክ ኃ/እየሱስ እና ወ/ሮ ፋናዬ አበበ	ጥቅምት 5/2002	2
2	• በጋብቻ ላይ የተደረገ ጋብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው (void ab initio) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ • የጋብቻ ውል ተጋቢዎች ንብረታቸውን በተመለከተ ጋብቻው የሚያስከትለውን ውጤት ስምምነት የሚያደርጉበት ሰነድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 42,44,33,11	39408	አርጋው አባቹ እና የወ/ሮ አስቱር አበጋዝ ወራሾች (ስድስት ሰዎች)	ጥቅምት 24/2002	4
3	የውርስ ሀብትድርሻ ክፍፍል ጥያቄ በይርጋ የሚታገድበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080(3)	40418	ተስፋዬ ሞላ እና እነ እሸቱ ምነ (ሦስት ሰዎች)	ጥቅምት 10/2002	6
4	አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43	42682	እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ በላይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ	ጥቅምት 10/2002	8
5	ፀንቶ ባለ ጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት በጋብቻ ውስጥ ባል የሆነው ወገን ስለመሆኑና የዚህን ሰው አባትነት ለመቃወም የሚቻልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 144,126,167,168,173	40624	እነ ወ/ሮ መብራት ታደሰ (አራት ሰዎች) እና አቶ ኤፍሬም ዘውዴ	ጥቅምት 12/2002	10
6	የጋራ የሆነን የውርስ ሀብት ከፍቃዱ ውጪ እንዲሸጥ የተደረገበት ወራሽ ከሽያጩ ዋጋ ድርሻውን ለማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1266,1060(1)	41857	አሕመድ ሑሴን እና እነ ወ/ሮ የኔዓለም ተመስገን (ሦስትሰዎች)	ጥቅምት 24/2002	13
7	አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43	42682	እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ	ጥቅምት 10/2002	15
8	ከጋብቻ በፊት የግል የነበረ ንብረት በተጋቢዎች የጋብቻ ውል መነሻነት የጋራ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ	42766	እነ ወ/ት ሠናይት ኃ/ማሪያም እና ወ/ሮ አበበች ወርቁ	ጥቅምት 10/2002	17
9	ልጅነትን በማረጋገጥ በፍ/ቤት የሚሰጥ ውሣኔ የህግ ግምት የሚፈጥር እንጂ አስገዳጅነት ያለው እና የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጎ መወሰድ የሌለበት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,155,156,157	42648	ወ/ሮ ዘነቦች በያን እና ወ/ት ብርቅነሽ ከበደ	ታህሣሥ 6/2002	19
10	አባትነት በህግ አግባብ ሊታወቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126,1(1),(2),128(1),130(2),125,106(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 35(2)	44612	ወ/ሮ ዘውዴ ወ/ጊዮርጊስ እና ወ/ት ኤልሣቤጥ ኪዳኔ	ጥቅምት 10/2002	21

https://t.me/ethiopianlegalbrief

11	• በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት አግባብ • የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1),1000(2),1060,1062	38533	እነ ወ/ሮ ጽጌ ወልደመስቀል (ስድስት ሰዎች) እና አቶ ስዩም ክፍሌ	ህዳር 8/2002	24
12	ልጅነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 156,168,158,169	42569	እነ የዳግማዊ ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ (ሁለት ሰዎች) እና የሃና ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ	ታህሣሥ 21/2002	27
13	ኑዛዜ ሊተረጐም የሚገባው ቃላቶቹና መልዕክቱ ግልፅ ሣይሆን ሲቀር ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 810(2)	47487	አቶ ሐይለራጉኤል ደበላ እና እነ ወ/ሪት አለምፀሐይ ፈለገ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 27/2002	30
14	የስጦታ ውል ሊተረጐም የሚገባው በውሉ ውስጥ የሚገኝን አንድ ሃረግ ነጥሎ በማውጣት ሳይሆን የውሉን አጠቃላይ ይዘት በመመልከት ስለመሆኑ	41893	ወ/ሮ ዮዲት ኃይሉ እና እነ ወ/ሪት ገነት አረጋይ (ሦስት ሰዎች)	ታህሣሥ 21/2002	33
15	የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3)	47957	እነ አቶ ተፈሪ ሐጐስ (ሦስት ሰዎች) እና አቶ ተስፋይ ገ/እግዚአብሔር	ጥር 5/2002	36
16	• የስጦታ ውል ገደብ ያለበት ወይም ግዴታ የተጣለበት እንደሆነ በውሉ ውስጥ የተመለከተው ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ፈራሽ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ • በፍ/ብ/ህ/ቁ. 244(1) ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ በስጦታ ውል ውስጥ የተመለከተ ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ውሉ እንዲፈርስ ሲጠየቅ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2452(1),2464(1),2441(1)	42346	እነ አቶ ፍስሐ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች) ወ/ሮ አለምነሽ ፍስሐ	የካቲት 9/2002	38
17	የጉዲፈቻ ስምምነት የሕፃናትን ጥቅምት ለማስጠበቅ ሲባል ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 195(2)	44101	ሚስስ ፍራንስዊስ ፖስተር እና እነ ሚ/ር ዱክማን ቬኖ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 24/2002	41
18	የውርስ ንብረት በሆነ ቤት ላይ ድርሻ አለን የሚሉ ወገኖች ንብረቱን ህጋዊ የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ይዞ ከነበረ ሰው በመግዛት ስመ ሀብቱን ወደራሱ ስም አዛውሮ የሚገኝን ሰው ለመጠየቅ የማይችሉ ስለመሆኑ	46527	ወ/ሮ ገነት በቀለ እና ወ/ሮ ትዕግስት አሰፋ	የካቲት 24/2002	44
19	ከውርስ ጋር በተያያዘ በቤት ላይ ህጋዊ መብት የሌለው ሰው ሽያጭ አከናውኖ ሲገኝ ትክክለኛው ባለሃብት መብቱን ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገዥ ሣይሆን ሻጩን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 997,2882, 2884,1060(1),1266	47378	አቶ አለማየሁ ከተማ እና እነ ወ/ሮ ላቀች አይተንፍሱ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 24/2002	46
20	ኑዛዜ በፍ/ቤት መፅደቁ በንብረት ላይ ያለ የባለቤትነት መብትን የሚያረጋግጥ ስላለመሆኑ	42482	እነ አቶ ፍሬዘውድ ተካ ጉጂ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሰለሞን ኃ/ማሪያም	የካቲት 3/2002	49
21	የልጆች ቀለብ አከፋፈል ሁኔታ ጋር በተያያዘ ክፍያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ	45819	አቶ ካሣ ፋንታ እና ወ/ሮ እስካዳር ግጨው	የካቲት 12/2002	51
22	በትዳር ወቅት የተወሰደ ብድር የአንደኛው ተጋቢ ፈቃድ የሌለበት ቢሆንም ፈቃዱን ያልሰጠው ተጋቢ የብድር ስምምነቱ እንዲፈርስ ያላደረገ እንደሆነ ወይም ደግሞ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን ማስረዳት ያልቻለ ከሆነ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(መ)	45202	አቶ ድንቁ ወርዶፋ እና ወ/ሪት ኤደን ድንቁ ወርዶፋ	መጋቢት 8/2002	53
23	በተጭበረበረ መንገድ ወራሽነትን አሳውጆ የውርስ ንብረት አካል የሆነን ቤት ስመ ሃብት ወደ ራሱ አዙሮ የሚገኝ ሰው ጋር የሽያጭ ውል በተደረገ ጊዜ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሚል ትክክለኛ ወራሾች የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍብ/ህ/ቁ. 2882, 2884, 997	45370	እነ አቶ ዳንኤል አበበ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 21/2002	56

https://t.me/ethiopianlegalbrief

24	የስጦታ ውል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ 10 (አስር) ዓመታት ውስጥ ለአፈፃፀም ያልቀረበ እንደሆነ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676(1),1845	42691	አቶ አደፍርስ በቀለ እና አቶ ይቁም በቀለ	መጋቢት 22/2002	59
25	• በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጉሙ የሚችሉበት አግባብ • የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1)1002,1060,1062	44237	እነ ወ/ሮ ሙሉሸዋ ቦጋለ (አራት ሰዎች) እና አቶ መስፍን ቦጋለ	መጋቢት 20/2002	61
26	ሞግዚት የሆነ ሰው በሞግዚትነት የሚያስተዳድራቸውን ልጆች ሀብት የሆነን ንብረት ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ ሲል ሊሸጠው የሚችል ስለመሆኑ የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ቤተሰብ ህግ አንቀፅ 292	46490	እነ ወ/ሮ ቦጋለች ደባልቄ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ መሠረት በለጠ	መጋቢት 21/2002	64
27	በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የተደረገ የሽያጭ ውል በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አለመፍረሱ ስለሚያስከትለው ውጤት	51295	አቶ ዮሐንስ ጡእማይ እና ወ/ሮ ምህረት ገብሩ	መጋቢት 6/2002	66
28	ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ባለስልጣን ፊት የሚደረግ ኑዛዜ በህግ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አሟልቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 882	49851	ወ/ሮ ታሪኳ አበበ የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞግዚት ተጠሪ፡የለም	ሚያዝያ 4/2002	68
29	ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ የሆነ ሰው እና ከህግ ውጪ ከውርስ የተነቀለ ያለኑዛዜ ወራሽ የውርስ ሃብትን ሊከፋፈሉ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ 939(3) ,850,,911(1) 912(1)	43069	አቶ አማረ ረታ እና አቶ ሰለሞን ካሣዬ	ሚያዝያ 6/2002	70
30	የጉዲፈቻ ውል እንዲፈርስ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 195(1),(2)	52691	እነ ቤተ ዛታ ችልድረንስ ሆም አሶሴሽን (ሦስት ሰዎች) ተጠሪ፡የለም	ሚያዝያ 22/2002	72
31	ኑዛዜ መኖሩን የማስረዳት ሸክም (ግዴታ) የተጠቃሚዎች ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896,897	53279	ወ/ሮ ትእግስት ግርማ የእነ አቤል ወርቁ ሞግዚት እና አቶ ኤፍሬም መንግስቱ	ሰኔ 8/2002	74
32	በኑዛዜ የውርስ ሀብት ክፍፍል መደረግ ጋር በተያያዘ ወራሽ የሆነ ወገን ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ሀብት መጠን ከአንድ አራተኛ በታች እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ኑዛዜውን እንዲፀና በማድረግ የተናዛዡን ፍላጐት ማክበርና መጠበቅ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 910, 913 1123(1)	50901	ወ/ሮ እልፊ ኃይሌ እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ደበሌ (ሦስት ሰዎች)	ሰኔ 10/2002	76
33	በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ለማስረዳት የሚችሉት በግንኙነቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 98,99,106	46613	ወ/ሮ ኑኑ ሽህሞሎ እና ወ/ሮ አሰገደች ጫኔ	ሰኔ 24/2002	79
34	በተከራካሪ ወገኖች ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ ፍ/ቤቶች በግልፅ በመቀበል ወይም ባለመቀበል ውሣኔ ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ	51866	ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለማየሁ እና ወ/ሮ አዛለች ደበበ	ሐምሌ 2/200	81
35	ከክንዶሚኒየም ቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ከጋብቻ በፊት በአንደኛ ተጋቢ በተደረገ ምዝገባ የተነሣ የቤት ዕጣው የወጣው ብሎም የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው በጋብቻ ወቅት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ለቤቱ መገኘት ምክንያት የሆነው ተጋቢ ቤቱ የግል መሆን አለበት በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(2)	51893	እንዳልካቸው ዘለቀ እና ወ/ሮ ብዙዓለም መንግስቱ	ሐምሌ 8/2002	83
36	በፍ/ቤት የተሰጠ የኑዛዜ ወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የውርስ ሃብት ማጣራት ሳይደረግ የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ሊሰረዝ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	50836	ወ/ሮ ቅድስት ተካ እና ወ/ሮ የኔነሽ ተካ	ሐምሌ 13/2002	85

https://t.me/ethiopianlegalbrief

37	ከውርስ ሃብት ክፍፍል ጋር በተያያዘ ተጠቃሚው በኢንሹራንስ ውል ላይ ባልተገለፀበት ጊዜ የሚች ባል ወይም ሚስት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ከወራሾች ጋር ሊካፈሉ የሚችሉበት አግባብ የንግድ ህግ ቁጥር 705,701(1)(ሀ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 827	44561	ወ/ሮ ገነት በላይ እና አቶ ያፌት ተክሉ	ሐምሌ 28/2002	87
38	ከውርስ ሃብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የውርስ ሃብቱን በእጅ አድርጐ በመገልገል ላይ ያለ ተከራካሪ የሆነ ወራሽ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት በጋራ ይዞ የቆየ ሰው ላይ የሚያነሳው የውርስ ጥያቄ በይርጋ ታግዷል ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	44025	እነ ወ/ሪት ፀሐይ ሐይሌ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ ፈልቃ ቤኛ	ሐምሌ 22/2002	95
39	ወራሽ የሆነ ወገን በውርስ ሃብት ክፍፍል ድርሻው ላይ ከሩብ የበለጠ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለፅ አውራሽ ባደረገው ኑዛዜ መሠረት ክፍፍል እንዳይፈፀም መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1123(1)	47622	ወ/ሮ ትዕግስት ነጋሽ እና እነ ወ/ሮ መንበረ ስላሴ ተሾሌ (አምስት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2002	97
40	የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3)	45587	እነ ወ/ሮ አተረፈች ዘውዴ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘውዱ ወሰኔ	ሐምሌ 29/2002	100
41	በተዘዋዋሪ መንገድ ተወላጅን ከውርስ ያለ በቂ ምክንያት መንቀል የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 938,842,915	42546	አቶ ተስፋልደት ኪዳኔ እና እነ ወ/ሮ ዘሀቡ ይመር (ሦስት ሰዎች)	ሐምሌ 28/2002	103
ውል					107
42	በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ እስከ አሥር ዓመት ድረስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058	44800	አቶ አብዱራዛቅ ሐሚድ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ጥቅምት 05/2002	108
43	ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትና የመተማመን ግንኙነት መሠረት በማድረግና ጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ልቦና ሊተረጐም የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1732(1)	42897	አቶ አየለ ሐብተየስ እና እነ ሚ/ር ኖቼራ ጃካርሎ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 10/2002	110
44	ለጨረታ ማስከበሪያ በሚል የሚያዝ ገንዘብ ጨረታውን ባዘጋጀው አካል ሊወሰድ የሚችለው ተወዳዳሪው ጨረታውን ባሸነፈው መጠን ሆኖ በጨረታው መሠረት ውል ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ	40947	አቶ መዝገቡ መድህኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር	ህዳር 15/2002	113
45	ተከራካሪ ወገኖች ባላነሱበት ሁኔታ ፍ/ቤት የውል አፃፃፍ ሥርዓትን (ፎርማሊቲን) መሠረት በማድረግ በግራ ቀኝ ወገኖች መካከል የተካሄደን ውል ፈራሽ ነው በሚል የሚሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1808(2)	43825	የህፃን ኮከቤ ተረፈ ሞግዚትና አስተዳዳሪ እና እነ አቶ አያሌው ካሳዬ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 6/2002	115
46	• የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) ለባንኮችና ለደንበኞቻቸው መብት ልዩ ጥበቃ የሚያደርገው የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 2473(2) ድንጋጌ ዋጋ በሚያሳጣ መንገድ ተፈፃሚ ሊሆን የማይገባ ስለመሆኑ • የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) በባንኮችና በሌሎች አበዳሪ ተቋማት እና ደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተፈፃሚነት የሌለው የህግ ድንጋጌ ስለመሆኑ • ባንኮች ለደንበኞቻቸው ያበደሩትን የብድር ወለድ ያልተከፈለ መሆኑን በሰው ምስክር፣ የሰነድና ሌላ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(1) ስር የተደነገገውን የህሊና ግምት ለማስተባበል የሚችሉ ስለመሆኑ	29181	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ልየው ቸኮል (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 20/2002	117
47	በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ሪ/ መሰረት እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችለው በብድር የተሰጠ ገንዘብ ሳይሆን የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ ክፍያ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024	35758	እነ አቶ ንብረመድኅን አየናቸው (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሰብስቤ ኃይሌ	ታህሣሥ 20/2002	123
48	የወለድ አግድ ውል ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መቋቋምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በመከተል የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑና በዚህ መሰረት ያልተደረገ መሆኑ ውሉን ፈራሽ ሊያደርገው የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3118,3045,3052	45422	እነ አቶ ፈታኒ ባየህ (ሰባት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ አስራት ባየህ (ሦስት ሰዎች)	ጥር 13/2002	127

https://t.me/ethiopianlegalbrief

49	የስልክ አገልግሎት ከማግኘት ጋር በተያያዘ በአገልግሎት የክፍያ መጠን ላይ በአገልግሎት ሰጪውና በአገልግሎት ተቀባዩ መካከል አለመግባባት በተፈጠረ ጊዜ የተጠየቀው የአገልግሎት ሒሳብ በእርግጥም ስልኩን በይዞታው ስር አድርጐ የሚጠቀምበት ወገን በተገለገለው መጠን የተመዘገበ ስለመሆኑ በባለሙያ እንዲጣራ በማድረግ አልባት መስጠት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732	48967	አቶ ሳዲቅ ሐሰን እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን	ሰኔ30/2002	130
50	መዋዕለ ነዋይን በማፍሰስ ግንባታን ለማካሄድ የከተማ ቦታን ከመንግስት ተረክቦ ግንባታን በተገቢው ጊዜ ለማጠናቀቅ አለመቻል ሊያስከትል የሚችለው ውጤት የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ደንብ ቁ. 41/97 አንቀፅ 8(3) የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ አዋጅ ቁ. 51/94	46052	ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዩርጊስ እና የቦንጋ ማዘጋጃ ቤት ከፋ ዞን	ጥር 19/2002	133
51	ከቤት ኪራይ ውል ጋር በተያያዘ የኪራይ ውልን ለማቋረጥ በቂ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ተከራይ የሚፈፅማቸው የግንባታ አይነቶች የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2953,2954,1732	46394	ወ/ሮ ስንቂ መስፍን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	የካቲት 11/2002	136
52	ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች ወለድን አስመልክቶ በውላቸው ካመለከቱት ሃሳብ ውጪ የራሱን ስሌት መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1731,2478	45559	የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ) እና እነ የአቶ ኃይሉ ፊይሳ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	138
53	ከሽያጭ ጋር በተያያዘ ውል ሊመሰረት ጉድለት የነበረበት መሆኑ ቢረጋገጥም ከውሉ መመስረት በኋላ በተሸጠው ንብረት ላይ ተዋዋይ ወገኖች ተጨማሪ ግንባታ ያካሄዱና ወደ ነበሩበት ለመመለስ አዳጋች ሁኔታ ያለ መሆኑ ከታመነ ውሉ ሊፀና የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1)	47800	ወ/ሮ እመቤት ደርበው እና አቶ ታደሰ ሰዳማ	የካቲት 25/2002	140
54	ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር የኪራይ ውል አከራይ የሆነ ወገን ለተከራይ ማስታወቂያ በመስጠት ምክንያቱን መግለፅ ሳያስፈልገው የኪራይ ውሉን ሊያቋርጥ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966(1)	40336	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የወ/ሮ አስገደች ካሣሁን ወራሽ ሄኖክ ሣሙኤል	መጋቢት 22/2002	142
55	በሌላ ሰው ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠንና ባደረሰው ጉዳት መጠን ኪሣራ ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162	43881	ወ/ሮ ፎዚያ ሁሴን እና አቶ ውብሸት ተ/ወልድ	መጋቢት 10/2002	144
56	ከሳሽ የሆነ ወገን ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ በአንድ ላይና በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ለመክሰስ የሚችል (የሚገባው) የነበረ ቢሆንም ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ቀንሶ ያቀረበው በፍ/ቤት ፈቃድ የሆነ እንደሆነ የቀረው መብት ላይ በድጋሚ ክስ ለመመስረት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4)	43992	እነ አቶ ይልማ አንበሴ (አራት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ እመቤት መንገሻ (አምስት ሰዎች)	መጋቢት 6/2002	146
57	ከሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ የሚያቀርበው የውል ይፍረስልኝ ክስ ገዥ ውል እንዲፈፀምልኝ በሚል ሊያቀርብ የሚችለው አቤቱታ ላይ የሚቆጠረውን የይርጋ ጊዜ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,1851	43636	ወ/ሮ አልማዝ ተሰማ እና እነ አቶ በየነ ወ/ሚካኤል (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 22/2002	150
58	የኪራይ ውልን መሠረት በማድረግ ቤትን የያዘ ወገን የኪራይ ውሉን በቅድሚያ ሣያስፈርስ የባለቤትነት ጥያቄን መሠረት በማድረግ በኪራይ ውሉ አልገደድም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	46947	አቶ ዘነበ ኃ/ማሪያም እና እነ ወ/ሮ አባይነሽ ዘለቀ (ሦስት ሰዎች)	መጋቢት 7/2002	152
59	ከእጅ በእጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ገዢ የሸያጩን ዋጋ የከፈለበትን ደረሰኝ ይዞ መገኘቱ የገዛውን ንብረት እንደተረከበ የሚያሳይ የመጨረሻ (conclusive) ማስረጃ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2266,2278(1) እና (2)	45545	ወ/ሮ ሸዋዬ ኑርዬ እና ምን አዩ ኃ/የተ/የግል ማህበር	መጋቢት 22/2002	154
60	በፍ/ብሔር ጉዳይ ህጋዊ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ዋስትና የሚደረግበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1922	47971	ወ/ሮ ጅቦኒ ቱና እና ወ/ሮ ብርቂ ኢርክታ	ሚያዝያ 5/2002	157
61	ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ ተከራይ የሆነ ወገን የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ በህግ የተጣለበት እንደሆነ አከራይ የሆነው ወገን ይህንኑ ክፍያ ለመፈፀም ይቻል ዘንድ ተከራዩን ለመጠየቅ ስለመቻሉ አዋጅ ቁ. 308/95 አንቀፅ 2(3,5,7,8,9,12),6	48358	አቶ ብርሃነ ንብረሐይሉ እና አንሲዩን ኮንትር ላፋም	ሚያዝያ 7/2002	159

https://t.me/ethiopianlegalbrief

62	• አንድ ሰው ብድሩን አለመክፈሉን አምኖ በሚከራከርበት ሁኔታ የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 2024(ረ) ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ • 2024(ረ) ዋና ብድርን ሣይሆን ለብድር የሚከፈል ወለድን የሚመለከት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ረ)	44691	አቶ ሽባባው ወሌ እና አቶ ሙሉጌታ ዓባይ	ሚያዝያ 8/2002	161
63	አንድ ውል ህግን የሚፃረር /የሚቃረን/ ነው በሚል እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845	48094	እነ ሙና አንድሪስ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ግንቦት 10/2002	163
64	በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት አሰሪው ሠራተኛው በውጭ አገር ትምህርቱን እንዲከታተል ለማስቻል የሚያስፈልጉ ወጭዎችን ደመወዝን ጨምሮ ለመክፈል ሠራተኛው ደግሞ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ አሠሪውን ለማገልገል ውል ገብቶ ሠራተኛው ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለ በሆነ ጊዜ አሠሪው የጉዳት ኪሣራ የመጠየቅ / የመክፈል/ መብት ያለው ስለመሆኑ	49453	የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት እና አቶ ተፈሪ ማሞ	ግንቦት 19/2002	166
65	የሽያጭ ውል በህግ የተቀመጠውን የአፃፃፍ ሥርዓት ባለመከተሉ ፈራሽ ሲሆን ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ወገን ንብረቱን ለውጦ ወይም በንብረቱ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ባወጣው ወጪ መጠን ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1818	49326	ወ/ሮ እታፈራሁ ኃ/ማሪያም እና እነ መምህር በቀለ ታችበሌ (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 28/2002	168
66	በፍ/ብሔር ጉዳይ (ክርክር) የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1846	42700	የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ	ሐምሌ 12/2002	170
67	የእቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024 ሥር በተመለከተው የህሊና ግምት የሚሸፈን ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024	46019	የአቶ ደሣለው ፋንታ ወራሾች እነ ሙሉጌታ ደሣለው እና አየለ ደበላ	ሐምሌ 20/2002	173
68	አንድ የስጦታ ውል በኃይል ወይም በተንኮል ተግባር ተደርጓል በሚል ስለሚፈርስበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2442(3),1698,1699,1704,1706	49900	እነ ወ/ሮ ሐመልማል ዓለሙ(ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ሀረገወይን ዘለቀ	ሐምሌ 19/2002	176
አፈፃፀም					180
69	የውርስ ንብረት በጨረታ እንዲሸጥ ለማድረግ መነሻ ዋጋን ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1083,1084	43888	አቶ ፀሐይ ወንድም እና እነ አቶ አያለው መለስ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 23/2002	181
70	አንድ ተጋቢ በግሉ ያመጣው ዕዳ ከሌለኛው ተጋቢ የጋራ ንብረት እንዲከፈል የሚደረገው ዕዳውን ያመጣው ተጋቢ ዕዳውን ለመክፈል አለመቻሉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የደቡ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ እና የፌዴራል መንግስት የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ	39837	አቶ ስመንተስ አሰፋ እና መ/ት ምህረት ክበበው	ግንቦት 3/2002	183
71	አንድ ንብረት በፍርድ አፈፃፀም የተነሣ ሊያዝ የሚችለው በተሰጠው ፍርድ ባለዕዳ የሆነው ወገን ሃብት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ	46143	ወ/ሮ ድልበጌ ራሕመቶ እና እነ የባህር ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት(ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2002	185
ወንጀል					187
72	የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የንግድ ድርጅት ሠራተኛ፣ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ድርጅቱ በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦባቸው ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 56(1)(3) አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀፅ 50(ለ)(1),22(1) የወንጀል ህግ አንቀፅ 23(3),34(1)	48850	እነ አቶ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ (ሦስት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ታህሣሥ 8/2002	188
73	በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የፈፀመው የግድያ ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1) (ሀ) ሥር የሚያስጠይቅ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)(ሀ),84,86	45927	የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ እና መሰረት መኮንን	ጥር 19/2002	191

https://t.me/ethiopianlegalbrief

74	በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ክስ በዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተሟልቶ አለመቅረብ የክሳሽ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ መዘጋት በቀረበው ወንጀል ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ ከመሆን የሚያግደው ስላለመሆኑ	45572	ወ/ሮ ዘነበች ሽብሩ እና ፌ/ዐ/ህግ	የካቲት 26/2002	194
75	ህጋዊ መካላከልን ከመጠን በማላለፍ የተፈፀመ የሰው መግደል ተግባር በወንጀል ህግ ቁጥር 541(ሀ) የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 540, 541	43501	እነ ረዳት ሳጅን ሽጋ ተካ ሞላ (ሦስት ሰዎች) እና የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ	መጋቢት 15/2002	195
76	በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 እና 567 መሰረት አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543,567	44235	ቁስ ጌታቸው ተሾመ እና ዓቃቤ ሕግ	መጋቢት 28/2002	199
77	አንድ ሰው የማታለል ተግባር ፈፅሟል በሚል በወንጀል ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ የወንጀል ህግ ቁጥር 692(1)	46189	ሐረገወይን ተፈራ እና ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	ሚያዝያ 20/2002	201
78	ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ የዘወትር ፀባይ መልካም የነበረ መሆኑ በተናጠል (በራሱ) ቅጣትን ለማቅለል የሚያስችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 82(1) (ሀ)	53612	እነ አቶ ፍስሐ ዓባይ(ሁለት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ዓ/ህግ	ሚያዝያ 25/2002	203
79	በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ወንጀለኛው በይቅርታ የተለቀቀ መሆኑ አስቀድሞ የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ እንዳልነበረ የሚያስቆጥር (በሪከርድነት እንዳይያዝ የሚያደረግ) ስላለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 230	41248	ቡርቂሶ ዋቆ እና ዐቃቤ ሕግ	ሰኔ 23/2002	206
80	በሥር ፍ/ቤት የተሰጠ የቅጣት ውሣኔ ላይ አነሰ ወይም በዛ በሚል በግልፅ ይግባኝ ባልተጠየቀበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅጣትን ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ውሣኔ ሊሰጥ የማይገባ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(መ)	48617	ተስፋዬ አደላ እና ዐቃቤ ሕግ	ሰኔ 18/2002	208
81	• ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተከራካሪ ወገኖች የማስረዳት ሸክማቸውን ተወጥተዋል ለማለት የሚቻልበት አግባብ • በፍ/ቤት ፊት ቃለ- መሃላ በመፈፀም የተሰጠ የምስክር ቃል እውነት ነው በሚል የሚወሰደው ግምት ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111	51706	አቶ ግርማ ትኩ እና የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ሐምሌ 21/2002	210
ንብረት					218
82	የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041,3052	38681	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እማሆይ ፀሐይቱ አምበሉ	ጥቅምት 3/2001	219
83	ለረጅም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ሥር የነበረ ቤትን ይለቀቅልኝ በሚል አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ አግኝቶ ባለመብትነቱን ሳያረጋግጥ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 47/67	45161	እነ እናኑ ጀንበሬ (ሁለት ሰዎች) እና የደሴ ከተማ ቀበሌ 03 ጽ/ቤት	ታህሣሥ 24/2002	222
84	የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው (ቀሪ ሆኗል) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677,1845,1206,1188-1192	43600	ዳዊት መስፍን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ጥር 05/2002	224
85	የአዋጅ ቁጥር 47/67 በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠን ካርታ መሰረት በማድረግ ክሥ ለመመስረት የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67	48699	አቶ አምሣለ ጀመሪ እና አቶ ፍርዱ ገበያሁ	ሚያዝያ 21/2002	228
86	በአንድ ቤት ውስጥ ሲኖር ያልነበረ ወይም ቤቱን በእጁ አድርጐ ሲያዝበት ያልነበረ ሰው የሚያነሣው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149	43081	አቶ ሣሙኤል ጦኖሮ እና እነ ወ/ሮ አይሻ አርጌሳ (አራት ሰዎች)	ግንቦት 6/2002	231
87	በሃይል ቤቱ ተይዞብኛል እንዲለቀቅልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206,1149	42861	ወ/ሮ አጤነሽ አበበ እና አቶ ማንተጋፋቶት አጥላው	ሰኔ 28/2002	233

https://t.me/ethiopianlegalbrief

88	• አንድን ንብረት በአደራ ለማስተደደር (ለመጠበቅ) የተረከበ ወገን አደራ ሰጪው ንብረቱ እንዲመለስ በጠየቀው ጊዜ ወዲያውኑ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ • ንብረትን በአደራ የሰጠ ወገን ንብረቱ እንዲመለስለት ከመጠየቅ ጋር በተያያዘ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ (ይርጋ)የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2781 (1)(2),2779, 2989(1)	48048	ወ/ሮ ንብርኤላ ኒካላ ቶማስ ናክሶ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ሐምሌ 22/2002	235
89	ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የጉዳት ኪሣራን ጉዳት ለሚደርስበት ወገን በመክፈል የመንገድ መተላለፊያ (servitude right) መብት ሊከበር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1221	48783	ወ/ሮ ሶፊያ ሁሴን እና እነ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 27/2002	237
	ከውል ውጭ ኃላፊነት				239
90	የጉዳት ኪሣራ የሚከፈለው ጉዳት ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090,2091	39601	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ገዛኸኝ መንግስቱ	ጥቅምት 5/2002	240
91	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ገቢ ያልነበረው መሆኑ በርትዕ ሊከፈለው የሚገባውን ካሣ የሚያስቀር ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102	42962	አቶ አየለ አድማሱ እና አቶ አጀቡ ሹሜ	ታህሣሥ 28/2002	242
92	በወንጀል ጉዳይ ተከሰሶ ጥፋት የሌለበት መሆን በራሱ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍትሐብሔር ከቀረበ ክስ ነፃ ለመውጣት እንደ በቂና የመጨረሻ መስፈርት የሚወሰድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149	43843	ዶ/ር ተስፋነሽ በላይ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ	መጋቢት 21/2002	244
93	ለተወሰነ ጊዜም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት በሥራ ወቅት በሌሎች ሰዎች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አሠሪ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2130, 2131, 2132	45735	አቶ ደረጀ ቸርነት እና ወ/ሮ ሕይወት የኃላሸት	መጋቢት 21/2002	247
94	በአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ችሎት ሠራተኛው የፈፀመው ድርጊት ከሥራ ለማሰናበት በቂ አይደለም ተብሎ መወሰኑ አሰሪው በሠራተኛው ላይ በፍ/ብሔር ጉዳይ ሊያቀርብ የሚችለውን ክስ የሚያስቀር የመጨረሻ ፍርድ /ውሣኔ/ ስላለመሆኑ	44588	የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና እነ ኃይለየሱስ ቱኪ (አራት ሰዎች)	ሚያዝያ 4/2002	251
95	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ህይወቱ ካለፈ ሰው ጋር በተገናኘ የሚከፈለው የጉዳት ካሣ መብቱን የሚጠይቀው ሰው ዕድሜ ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ በመሆኑ የተነሣ ብቻ ካሳው ሊከፈለው አይገባም ለማለት የሚያስችል የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2095/1/	50225	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ት ዝናሽ አሰፋ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 5/2002	253
	የዳኝነት ስልጣን				255
96	የአ.አ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ደብተርን ለመሰረዝ የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ	34665	እነ አቶ ናትናኤል ዘውገ (ሁለት ሰዎች)እና እነ ወ/ሮ እግዜሩ ገ/ህይወት(ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 12/2002	256
97	የከተማ ቦታ ያለአግባብ ተወስዶብኝ በሊዝ ለሌላ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የቦታውን መውሰድ ውሣኔ ለሰጠው አካል በቅድሚያ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑና በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ያለበትና ይኼው አካል የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 272/1994	46220	የደቡብ ክልል የሐዋሣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና የሐዋሳ ደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ገዳም	ጥር 18/2002	258
98	በውጪ አገር ሕግ መሰረት የተቋቋመና በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገበ የንግድ ድርጅት ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊዳኝ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 27(1), አዋጅ 25/88 አንቀጽ 11(2)(ሀ)	42928	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ድራጋዶስ ኮንስትራክሽን	ጥር 12/2002	260

https://t.me/ethiopianlegalbrief

99	በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለባለገንዘቡ ሊመለስ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 53(1),55	42866	ብርሃነ ጥዑም እና የጉምሩክ ባለስልጣን	መጋቢት 20/2002	262
100	የሥራ መደብ ወይም እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የወል የሥራ ክርክርን የሚመለከት ስለመሆኑ	48111	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ቂጤሳ ገብሬ	ሚያዝያ 13/2002	265
101	በውድድር አሸንፌ ያገኘሁትን የሥራ መደብ እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ የሥራ ክርክር የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የሚታይ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	52600	የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር እና አቶ ተስፋዬ ኃይሌ	ሚያዝያ 12/2002	267
102	የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በከተማው የሚገኝ ቤት ባለቤትነቱ የማን ነው ከሚል ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚነሣ ክርክርን ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 416/19 አንቀፅ 33	47134	የድሬዳዋ አስተዳደር ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ፋንታዬ ምትኩ	ግንቦት 6/2002	269
103	• የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከ5000 ብር በታች የሆነ ጉዳይን በሙሉ ተቀብሎ ለማስተናገድ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች በሕግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ • የሥረ-ነገር ሥልጣን በሕግ ባልተሰጠው የዳኝነት አካል (ፍ/ቤት) የተሰጠ ፍርድ የማይፀና ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(6),5(9) አዋጅ ቁ. 361/95	52041	የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክ/አ/ማህበር እና የኢት/መድን ድርጅት	ሰኔ 29/2002	272
104	በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ጋር በተያያዘ የሚነሣ ክርክርን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 5(6)	43912	አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና እነ የአቶ ኢብራሂም ሙሣ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 15/2002	274
105	በሰዎች ወይም በሚንቀሳቀስ ሀብት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስን ለማስተናገድ የግዛት ክልል ሥልጣን ስለሚኖረው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 27	48018	አቶ ተክተል ዘካሪያስ እና እነ ወ/ሮ አስቴር ታደሰ(ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 7/2002	276
106	በሽሪአ ፍ/ቤት በሚካሄድ ክርክር ላይ ጣልቃ ገብቶ መከራከር በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ስምምነትን እንደመስጠት የሚያስቆጥር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 188(92) አንቀፅ 5(1)	45806	አቶ ፍፁም በረታ እና እነ ወ/ሮ ሶፊያ ዱላ(አራት ሰዎች)	ሐምሌ 8/2002	278
107	• በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ እጅግ አስፈላጊ የህዝብ አገልግሎት ድርጅቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ተቋማት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ጥያቄን የያዘ የውል የሥራ ክርክር ካልሆነ በስተቀር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ለማስተናገድ የሥረ- ነገር ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ • መሰል ጉዳዬችን ለማየት በህግ ስልጣን የተሰጠው በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰየም ቦርድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 466/97 አንቀፅ 2(2) አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 142(1)(ሀ),(2),(3),136(2)	49152	የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር እና የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት	ሐምሌ 7/2002	282
ባንክና ኢንሹራንስ					286
108	በብድር ለተሰጠ ገንዘብ በመያዣነት የተያዘ ንብረት መድን የተገባለት ሆኖ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ አበዳሪው ንብረቱን በመያዣ የያዘበት ብድር ዋጋ ዋስትና ከተገባለት የገንዘብ መጠን ያነሰ እንኳን ቢሆን መድን ሰጪው እንዲከፍለው ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2858	38572	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ጥቅምት 17/2002	287
109	ባንክ በመያዣ መልክ የያዘውን የተበዳሪ ንብረት በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት በመሸጥ ላይ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ በተበዳሪው ላይ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ ዕዳው እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ	44164	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ሐሰን ኢብራሂም	ታህሣሥ 8/2002	290
110	የኢንሹራንስ ውልን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 674(1),754(1)	46778	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ	የካቲት 24/2002	293
111	የመድን ሰጭ ኃላፊነት በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 665(2)	46808	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና ወ/ሮ ጫልቱ ሚደግሳ	ሚያዝያ 6/2002	295

https://t.me/ethiopianlegalbrief

112	ለአንድ ንብረት መድን የገባ ሰው በንብረቱ ላይ የደረሰው ጉዳት ሙሉ ውድመት ሊባል የሚችል ቢሆንም ካሣ ሊከፈለው የሚችለው ጉዳት በደረሰ ጊዜ ዕቃው ከሚያወጣው ዋጋ ሳይበልጥ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 678	48698	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አቶ ሣሙኤል አለሙ	ግንቦት 19/2002	297
113	መድን ሰጪ የሆነ ወገን በመድን ገቢው እግር በመተካት ባለዕዳ የሆነ ወገን ላይ ጥያቄ ባነሣ ጊዜ ባለዕዳው ከመድን ገቢው ጋር የሚፈጠር አለመግባባትን ከፍርድ ቤት ውጪ በሽምግልና ለመጨረስ የተስማማን በመሆኑ መድን ሰጪው በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ ሊጠይቅ አይችልም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 683(1)	39902	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ	ሰኔ 18/2002	300
114	አስቀድሞ የተደረገ ነገር ግን ባለመታደሱ ምክንያት የተቋረጠ (ያበቃ)ን የመድን ውል መሠረት በማድረግ ሊጠየቅ የሚችል የጉዳት ካሣ ስላለመኖሩ የንግድ ህግ ቁ. 666(2) እና (3)	52910	አቶ አንዳርጌ ታደሰ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሐምሌ 28/2002	302
ጉምሩክ(ግብር)ታክስ					304
115	• የንግድ ቤቶችን የማከራየት እንቅስቃሴ ከታክስ ነፃ ከሆኑ ግብይቶች የማይመደብ ስለመሆኑ • የንግድ ቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 8	39574	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ወ/ሮ ምልአተ ፀጋ ቢዘን (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 3/2002	305
116	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያልተከፈለን ቀሪ ቀረጥ ሊያስከፍል የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ.60/89 አንቀፅ 57(1),48,53(1)	45882	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ እጅጋየሁ አራምዴ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 6/2002	307
117	የጉምሩክ አዋጅን በመተላለፍ ከሚፈፀም የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ የኮንትሮባንድ ተግባር ሃይልን በመጠቀም ወይም ከሌሎች ጋር በማበር የተፈፀመ እንደሆነ አዋጅ ቁ. 60/89 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ	44862	አሸናፊ አበበ እና የጉምሩክ ባለስልጣን	ጥር 5/2002	310
118	የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ክስ ሊቀርብበት የሚገባውና ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲሱ የወንጀል ህግ ሣይሆን በጉምሩክ አዋጆች መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89	48693	ነኢማ አወል እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ጥር 5/2002	312
119	የንግድ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው የድርጅቱን አስተዳደራዊ ሥራ ለሌላ ሰው የወከለ መሆኑ ድርጅቱ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት በመፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ በተባለ ጊዜ ከሚቀርብበት የወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የማያደርገው ስለመሆኑ	54061	አቶ መስፍን ሽፈራው እና የኢትዮጵያ ገቢዎች ባለስልጣን	ሚያዝያ 26/2002	314
120	• የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባሩን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ባለማከናወኑ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ • የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ግዴታውን ለመወጣት ሲንቀሳቀስ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐት ከሚቆየው ንብረት ጋር በተያያዘ የተቋረጠ ጥቅም ወይም የጉዳት ካሣ ሊከፍል የሚችልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ 60/98 አንቀጽ 6(5), 58,74 አዋጅ ቁ 368/95 አንቀጽ 78	49889	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና አቶ ዛኪ ሰይድ	ሰኔ 28/2002	316
121	የግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜና ስሌቱ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 43(1)	48621	አቶ አብደላ ሁሴን ከሰር ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን	ሰኔ 30/2002	319

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውክልና					322
122	ባንክ በሐዋላ ለማድረስ የተቀበለውን ገንዘብ ለተገቢው ሰው አልደረሰም በሚል ኃላፊነት አለበት ሊባል የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር ሳይከተል የቀረ እንደሆነ ወይም መጭበርበሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ	48269	አቶ ሸረፈዲን አብደ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	የካቲት 24/2002	323
123	ወኪል የሆነ ሰው የውክልና ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ የራሱን ወይም ከራሱ ጋር ቤተሰባዊ ወይም ሌላ ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር ያለው ሰውና የወካዩ ጥቅም ሊጋጭ የሚችልበት አጋጣሚ እንዳይፈጠር መከላከል ያለበት ወይም በተፈጠረ ጊዜ አስቀድሞ ለወካዩ ማሳወቅ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)2198,2208,2209	50440	አቶ ሃብቱ ወልዱ እና እነ ወ/ሮ መሰሉ ደስታ (ሁለት ሰዎች)	ግንቦት 16/2002	325
የንግድ ሕግ					328
124	• የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ • በግለሰቦች መካከል በውል የሚፈጠር የሽርክና ማህበር የንግድ ሕግ በሚያዘው መሰረት አይነቱ ተለይቶ ተመዝግቦ የማይገኝ በሆነ ጊዜ እንደ የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ የንግድ ሕግ ቁጥር 211,212,219	46358	ወ/ሮ ብርሃን ፀጋዬ እና እነ አቶ ሚካኤል ፋስሐ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	329
125	ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ሰዎች ማህበሩን ሲያስተዳድሩ በሰሩት ያልተገባ ስራ ምክንያት በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት አግባብ የንግድ ሕግ ቁጥር 580	39608	ወ/ሮ አስቴር አርአያ እና እነ ወ/ሮ አምሳለ በላይ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 11/2002	331
አእምሯዊ ንብረት					334
126	አንድን መዕሐፍ ከተፃፈበት ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የተረጐመ ሰው እንደ ድርሰት አመንጪ ተቆጥሮ የሞራልና የቁሣዊ ጉዳት ሊወሰንለት ስለመቻሉ አዋጅ ቁ.410/96 አንቀፅ 2(2),6(1)	44520	አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት እና ዶ/ር ጌታሁን ሽብሩ	ጥቅምት 10/2002	335
ልዩ ልዩ					338
127	ለዋስትና የተያዘ ገንዘብን የአስያዡን ማንነትን ማረጋገጥ አስከተቻለ ድረስ ገንዘቡን ያስያዘበት ደረሰኝ ኮፒን ያቀረበ እንኳን ቢሆን የተያዘው ገንዘብ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ	53459	አቶ ማሞ ገ/ማሪያም ተጠሪ፡የለም	ሚያዝያ 12/2002	339
128	• በአስፈፃሚ አካላት የሚወጡ የተለያዩ መመሪያዎች በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው የወጡ ወይም በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ አለመሆናቸው ህጋዊ ውጤት እንዳይኖራቸው የሚከለክል ስላለመሆኑ • አዋጅን መሠረት በማድረግ የወጡ መመሪያዎችን የሚሻረር ድርጊት መፈፀም በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 83/86 አንቀፅ 39(2),1, 2, 59(1)(ሸ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁ. ሲቲጂ 001/97	43781	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና አቶ ዳንኤል መኮንን	ሐምሌ 14/2002	341
129	• የሕግ ክርክሮችን በሰበር ማየት /ማስተናገድ/ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠ ስልጣን (power) ስለመሆኑ • በግልግል ዳኝነት (arbitration) የታየ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተዋዋይ ወገኖች የይግባኝ መብትን ለማስቀረት የሚያደርጉት ስምምነት ጉዳዩን በሰበር ችሎት ከመታየት የማያግድ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ።) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3 (ሀ), አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 (4), አዋጅ ቁጥር 25/88, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 350(2) 351 እና 356	42239	ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የተ/የግ/ ኩባንያ እና ዳን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ	ጥቅምት 20/2003	346

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38544

ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ብሩክ ኃ/እየሱስ - ጠበቃ ዘውዱ ወራሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፋናዬ አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በወናጐ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በዚሁ ፍርድ ቤት አመልካች የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ከአሁኑ አመልካች ጋር የመሰረቱት ጋብቻ እንዲፈርስላቸው፣የጋብቻ ውጤት የሆነው ንብረትም ክፍፍሉ እንዲፈጸም የንብረቱን ዓይነትና ግምቱን ዘርዝረው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ ጋብቻው እንዲፈርስ አድርጐ ንብረቱን በተመለከተም ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ውሣኔውም እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሰር ፍርድ ቤቶች በዲላ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚታወቅ ዋና መኖሪያ ቤት የባልና ሚስት የጋራ መሆናቸው ስለተረጋገጠ ከስድስት ሰርቪስ ቤቶች ጋር ፍቺ ከተሰጠበት ጀምሮ የተገኘ ጥቅም እና ቤቶቹ ተሸጠው እንዲከፋፈሉ በማለት በሰጡት ውሣኔ ክፍል ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት መተዳደሪያችን ሆኖ ስለመዋዋላችን በ25/11/1987 ዓ.ም በተፃፈ የጋብቻ ውል ተገልጾ እያለና ተጠሪም ክስ ሲመሰርቱ የግል ሐብቱ ነው ኣሏን አይመለከታትም ብሎ የተዋዋለው ሐይለ ቃል ባለመኖሩ ቤቱ የጋራ ነው የሚል ዳኝነት ጠይቀው እያለ ከጋብቻ በፊት የተፈራውን ንብረት የባልና ሚስት የጋራ ነው በማለት መወሰኑ የደቡብ ብሔር ቤሔረሰቦችን ብሔራዊ ክልልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግን አንቀጽ 66 ድንጋጌና የተዋዋይ ወገኖችን ሐሳብና ፍላጐት ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመ ነው ተብሎ ሊሻር ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ተጠሪ ቀርበው ሐምሌ 17 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሳቸውን አቅርበዋል አመልካች በበኩላቸው መስከረም 11 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚገባ መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም በዲላ ከተማ ቀበሌ 02 የሚታወቅ ዋና መኖሪያ ቤት ከ6/ስድስት/ ሰርቪስ ቤቶች ጋር ፍቺ ከተሰጠበት እለት ጀምሮ ጥቅምና ቤቶቹ የባልና ሚስት የጋራ ሐብት ናቸው፤ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ ከመመስረታቸው በፊት የተሰራ መሆኑን በ25/11/1987 በተደረገው የጋብቻ ውል ቤቱን መተዳደሪያቸው በማድረግ መስማማታቸውን ነው፡፡

በመሰረቱ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው የሚያገኟቸው ንብረቶች በጋብቻ ዘመንም የግል ሆነው ይቀራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት ንብረቶቹ በጋብቻ ውል የጋራ እንዲሆኑ ስምምነት ከሌለ ብቻ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነውን የጋብቻ ውሉ በሕግ ፊት ያለው ተፈፃሚነት ማይሆን በጋብቻ ውሉ የተገለፀው "መተዳደሪያችን" የሚለው ቃል ቤቱ የጋራ ስለመሆኑ ባልና ሚስት መስማማታቸውን ያሳያል ወይስ አያሳይም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ አደረግን የሚሉት የጋብቻ ውል መተዳደሪያችን ብሎ ከሚገልፃቸው ንብረቶች ውስጥ ከአከራካሪው ቤት በተጨማሪ የአመልካች ደመወዝና ብር 10,000.00(አስር ሺህ) ጥሬ ገንዘብ ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ንብረቶች ለማንኛውም የቤተሰቡ ወጪ የሚውሉ መሆኑ ይታመናል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ይህንኑ ጥሬ ገንዘብና ቤቱን እየተጠቀሙ ለአስራ አንድ ዓመታትም አንድ ላይ ኖረዋል፡፡ እንግዲህ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች እነዚህ ከሆኑና የጋብቻ ውሉ ይዘት ትርጉም አከራካሪ ከሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎችን የግራ ቀኙ ፍላጐት ምን እንደነበር መመርመር የግድ ይሏል፡፡

በመሰረቱ በውል ውስጥ የተጠቀሱት ቃላትና ድንጋጌዎች ግልጽ ባልሆኑ ጊዜ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732፣1735-1738 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር በሰፈሩት ደንቦች መሰረት መተርጐም የተፈቀደ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ደንቦች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1734 እና 1736 ሲሆኑ ተዋዋዮች ውላቸውን ከመዋዋላቸው አስቀድሞ ወይም ከተዋዋሉ በኋላ የነበሩበትን ሁኔታዎች፣የፈጸሙትን ተግባር በማመዛዘንና ሐሣባቸውን ምን እንደነበር ለማወቅ መሞከር እና የውሎችን ቃሎች አንዱን ከአንዱ ጋር እያዛመዱ በመመልከት ለውሉ ጉዳይ አግባብ ያለውን ትርጉም መስጠት ተገቢ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ በ25/11/1987 ዓ.ም አደረግን የሚሉት የጋብቻ ውል መተዳደሪያችን ብሎ ከሚገልፃቸው ንብረቶች ውስጥ ከአከራካሪው ቤት በተጨማሪ የአመልካች ደመወዝና ብር 10,000(አስር ሺህ) ጥሬ ገንዘብ ይገኙበታል፡፡ እንደሁም ይህንኑ ጥሬ ገንዘብና ቤቱን እየተጠቀሙ ለአስራ አንድ ዓመታትም አንድ ላይ ኖረዋል፡፡ በመሆኑም አመልካችና ተጠሪ የጋብቻ ውሉን በተዋዋሉበትና ከተዋዋሉ በኋላ የነበሩበት ሁኔታ እና ጥሬ ገንዘቡንም ለመተዳደሪያቸው አድርገው የተዋዋሉ መሆናቸው መተዳደሪያ የሚለውን ቃል በጋብቻ ውሉ የተጠቀሙበት አከራካሪውን ቤት የጋራ ከማድረግ ፍላጐት ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከፍቺ በኋላ በቤቱ የተገኘ ጥቅምም ከጋራ ንብረት የተገኘ መሆኑ አስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ የማያገኙበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳይ ላይ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በወናጐ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 00372 ኅዳር 27 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በጌዶኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0279 የካቲት 07 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም በደ/ብ/ብ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 21204 ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አርጋው አባቹ - ጠበቃ ደገፉ ምሶኔ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስቱር አበጋዝ ወራሾች - እነ ወ/ሪት ንግስት አርጋው (ስድስት ሰዎች)

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሣውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የባልና ሚስት የጋራ ሐብት ነው ወይስ የባልየው የግል ንብረት? በሚል ክርክር ከተነሣባቸው ንብረቶች አንዱ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 20 ቀበሌ 45 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥር 629 የሆነው የመኖሪያ ቤት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ከሁለቱ ወገኖች የቀረበውን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ቤቱ ጋብቻው ከመመስረቱ በፊት አመልካች የሰራው የግል ሐብቱ ነው በማለት የወሰነ ሲሆን፣ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን ቤቱ የተሰራው ከጋብቻ በኋላ (በጋብቻው ወቅት) መሆኑን በማስረጃ አረጋግጫለሁ በማለት ቤቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት ነው ብሎአል፡፡ በመጨረሻ በይግባኝ ጉዳዩን ያየው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አከራካሪው ቤት ከጋብቻ በፊት የነበረ ንብረት ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት የተደረገው ክርክር እያሳየ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት አይደለም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራካሪው ቤት የአመልካች የግል ሃብት ነው በማለት ቢወስንም፣ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን አልተስማማም፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ቤቱ የተጋቢዎቹ የጋራ ሃብት ነው ለማለት የበቃው ቤቱ የተሰራው አመልካች እንደሚለው ከጋብቻ በፊት ሳይሆን፣ ጋብቻው ከተመሰረተ በኋላ በ1966 እንደሆነ በከተማው አስተዳደር የሚገኘውን የቤቱን ማህደር አስቀርቤ አረጋግጫለሁ በማለት ነው፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ በማረጋገጥ ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ እንግዲህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶቹ ውሳኔ የተመሰረተው ተሰማ በተባለው ማስረጃ ላይ ነው፡፡ በማስረጃ አመዛዘን ረገድ የተሻለ መደምደሚያ የደረሰው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው ለማለት የሚያስችል የሕግ ምክንያትም የለም፡፡ ይልቁንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት እንዲያይ ተጠይቆ ያላየውን (አላይም በማለት ያለፈውን) በአስተዳደር ክፍሉ የሚገኘውን የቤቱን ማህደር አስቀርቦ የመረመረ በመሆኑ የተሻለ ስራ ሰርቶአል የሚባለው ይሄው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ የተፈጸመ መሰረትዊ የሕግ ስህተት አለ ለማለት የሚያስችል ምክንያት አላገኘንም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43510 ሚያዝያ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31893 ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. አከራካሪው ቤት የግል ሐብትህ ነው ይባልልኝ በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት አለማግኘቱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቶአል፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ተስፋዬ ሞላ - ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. እሸቱ ሞላ

2. ወ/ሮ እመቤት ሞላ - ቀረበች

3. የጌታቸው ሞላ ወራሾች ሞግዚት ተዘራ ስጠኝ - ቀረበች

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

የሰጠውን ብይን በማጽናት ሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በመ/ቁ. 35810 በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ሃብት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበረው አመልካች ነው ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተው በውር አጣሪ ተጣሪቶ ከቀረበው የውርስ ሃብት ላይ ድርሻዬን ያካፍሉኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎችም ለቀረበው ክስ መልስ የሰጡ ሲሆን፣1ኛ ተጠሪ ክሱን አልተቃወመም፡፡ ከሣሽ ድርሻውን ይውሰድ ብሎአል፡፡ ተጠሪዎች ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ስለሆነ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚለውን መቃወሚያ በመቀበል ክሱን በመሰረዝ ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ብይን ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ብይኑ ጉድለት የለበትም በማለት የይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ነሐሴ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪዎች ያነሱት የይርጋ መቃወሚያ ቀደም ሲል ውርሱ ሲጣራ በነበረበት ወቅት እልባት አግኝቶ እያለ እንደገና ተነስቶ ተቀባይነት የማግኘቱን አግባብነት ለመመረመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ እንደሚያሳየው ጉዳዩን በሚመለከት ሁለት መዝገቦች ተከፍተዋል፡፡ የመጀመሪያው መዝገብ ውርስ እንዲጣራ የቀረበውን ጥያቄ የተስተናገደበት ሲሆን፣ሁለተኛው ደግሞ ውርሱ ተጣርቶ በውርስ አጣሪው የቀረበውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የቀረበበት ነው፡፡ ሌላው ከክርክሩ ሂደት የተገነዘብነው የውርስ ይጣራ ጥያቄ የቀረበው በአመልካቹ ሲሆን፣በዚህን ጊዜም የይርጋ መቃወሚያ ቀርቦ እንደነበር እና ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤት ግን መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ ውርሱ እንዲጣራ ትእዛዝ ሰጥቶ በዚሁ መሰረት መፈጸሙን ነው፡፡ አመልካች የይርጋው መቃወሚያ ሁለት ጊዜ ነው የታየው የሚል የመከራከሪያ ነጥብ ያነሳውም ይህን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደምንመለከተው ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ቀደም ሲል ተነስቶ ውድቅ የተደረገ ስለመሆኑ አከራካሪ አልሆነም፡፡ የውርስ ማጣራት ሂደቱ ተጠናቆ አጣሪው ሪፖርቱን ከፍ/ቤት ያቀረበው ጥር 29 ቀን 1999 ዓ.ም ሆኖ አመልካች የንብረት ክፍፍል ጥያቄ(ክስ) ያቀረበው ደግሞ መጋቢት 3 ቀን 1999 ዓ.ም እንደሆነ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ብይን ላይ ተመልክቶአል፡፡ ይህም ማለት አመልካች ክሱን የመሰረተው ክፍያውን ካወቀ አንድ ዓመት ከማለፉ በፊት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1080 በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት ጥያቄው በይርጋ ቀሪ አልሆነበትም፡፡ ሲጠቃለል አውራሹ ከሞቱበት ቀን አንስቶ የታሰበው የይርጋ ጊዜ የውርስ ይጣራልኝ ክስ በቀረበ ጊዜ ተነስቶ ውድቅ በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 አንፃር ሲታይ በድጋሚ የሚቀርብበት የሕግ ምክንያት የሌለ ስለሆነና የውርስ አጣሪው ባቀረበው ሪፖርት መሰረት የቀረበው የንብረት ልካፈል ጥያቄም በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1080/3/ የተደነገገው የአንድ ዓመት የጊዜ ወሰን ከማለፉ በፊት የቀረበ በመሆኑ ጥያቄው/ክሱ/ በይርጋ ቀሪ ነው በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 53613 ጥር 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35810 ሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው የንብረት ልካፈል ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ክሱ በቀረበበት መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ ግራ ቀኝ ወገኖች በጉዳዩ ሥረ-ነገር ላይ የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ የመሰለውን ውሳኔ ይስጥ በማለት ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሰረት ይመለስለት ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ ሙላቱ - ቀረቡ

2. አለሙ ደምሴ

3. ወ/ሪት ትእግስት ደምሴ

ተጠሪ፡- ሞላ ደምሴ ቀረበ - ጠበቃ ፋንታ አየለ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ልጅነትን ለማረጋገጥ በቀረበው ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ቀደም ሲል ለፍ/ቤት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የሚች ደምሴ ፀጋዬ ልጅ መሆኑ ተረጋግጦ ተወስኖ ነበር፡፡ አመልካቾች ክርክሩ ውስጥ የገቡት ውሳኔውን በመቃወም እንዲሻርላቸው በመጠየቃቸው ነው፡፡ ተቃውሞአቸውም ተጠሪ የሚች ልጅ አይደለም የሚል ስለነበር፤ መቃወሚያው የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪን በማስቀረብ የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም በተጠሪ በኩል የቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በእርግጥም የሚች ልጅ እንደሆነ አረጋግጦአል፡፡ ተቃዋሚዎች ይህን ማስረጃ ማስተባበል አልቻሉም በማለት የቀድሞው ውሳኔውን አፅንቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሚች ልጅ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጽሞአል የሚሉትን ስህተት በመግለጽ ውሳኔው ይሻርላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጠሪ የሚች ልጅ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143 አንፃር ሲታይ አግባብነት ያለው ነው ወይስ የለውም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰማው የግራቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራቀኝ ወገኖችን ያከራከረው የልጅነት ጥያቄ በተመለከተ ማስረጃዎችን ሰምቶአል፡፡ በሰማው ማስረጃም ሚች (አባት ነው የተባለው ሰው) ተጠሪን እንደልጁ በማድረግ ሲንከባከብ እንደነበር፣ ትምህርት ቤት ወስዶ እንዳስመዘገበው፣ ከቤተሰቦቹ ጋር በመቀላቀል ያኖረው እንደነበር ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች በተጠሪ በኩል የተሰማውን ማስረጃ ሊያስተባብሉ እንዳልቻሉ በትችቱ ገልጸአል፡፡ በመጨረሻም በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ (አዋጅ ቁ 213/92) አንቀጽ 143(ሠ) መሠረት አባትነትን ለማረጋገጥ በቂ ምክንያት እንደሆነ በመገንዘቡ ተጠሪ የሚች ልጅ ነው በማለት እንደወሰነ ተገንዝበናል፡፡ አመልካቾችም ቢሆኑ እየተከራከሩ ያሉት የሥር ፍ/ቤት አረጋግጫለሁ ያለውን ፍሬ ነገር አላረጋገጠም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይሆን፣ ተጠሪ ተወልጃለሁ የሚለው ከጋብቻ ውጪ በተፈጸመ የግብረስጋ ግንኙነት በመሆኑ ይህንኑ ግንኙነት በማያጠራጥር ሁኔታ ማስረዳት ሲገባው አላስረዳም በማለት እንደሆነ ከአጠቃላይ የክርክራቸው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143 "በፍርድ ስለሚነገር አባትነት" በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዞአል፡፡ እነዚህም ከንኡስ አንቀጽ(ሀ) እስከ (ሠ) ድረስ ያሉት ሲሆኑ፣ አመልካቾች በመከራከሪያነት ያነሱት ነጥብ በንኡስ አንቀጽ (መ) በተመለከተው ድንጋጌ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በሕግ የታወቀ ግንኙነት ባይኖራቸውም፤ በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ መሆናቸው ከተረጋገጠ አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ሊታወቅ እንደሚችል ስለሚያመለክት እንደሌሎቹ ድንጋጌዎች አንደኛው አባትነትን በፍርድ ውሳኔ የማወቂያ ዘዴ (ሁኔታ) ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው ሁኔታ ባለመረጋገጡ ብቻ አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ማወቅ አይቻልም ማለት አይደለም፡፡ በተጠቀሰው አንቀጽ 143 መሠረት አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ማወቅ የሚቻለው ከንኡስ አንቀጽ (ሀ) እስከ (ሠ) ካሉት ድንጋጌዎች ውስጥ በአንዱ የተመለተው ሁኔታ ሲሟላ ነው፡፡ በመሆኑም ቀጣይነት የግብረሥጋ ግንኙነት ስለመኖሩ ተጠሪ በማስረጃ አላረጋገጠም የሚለው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ስናጠቃልለው የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪን የሚች ልጅ ነው በማለት በሰጡት ውሳኔ የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 27622 ጥቅምት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63272 ህዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት አፅንተናል፡፡
2. ተጠሪ የሚች ልጅ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ መብራት ታደሰ - ጠበቃ አቶ አድማሡ መዓዛ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ትዕግስት ዘውዴ

3. አቶ አንተነህ ዘውዴ

4. አቶ ቢኒያም ዘውዴ

ተጠሪ፡- አቶ ኤፍሬም ዘውዴ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መሠረታዊ መነሻ የአሁን ተጠሪ ሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ወላጅ እናቱን ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁንን አግብተው ሲኖሩ የተወለደ በመሆኑ የሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅና ወራሽ መሆኑ በፍርድ እንዲረጋገጥለት ያቀረበውን አቤቱታና ማስረጃ በመመርመር ተጠሪ የሚች ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅና ወራሽ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ውሣኔ ከሰጠ በኋላ የአሁን አመልካቾች በተቃዋሚነት ቀርበው ሚች አቶ ዘውዴ በእሱፈቃድ 1940 ዓ.ም ለትምህርት ወደ አሜሪካ ሄደው ለሰባት ዓመታት እዚያው የቆዩ ስለሆነ 1945 ተጠሪን ሊወስዱ አይችሉም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሚች ዘውዴ በእሱፈቃድ ከሁለተኛ፣ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪ ውጭ ሌላ ልጅ የሌላቸው መሆኑን ጥር 18 ቀን 1990 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አቶ ኤፍሬም ዘውዴ (ተጠሪ) የሚች ልጅ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ እንዲያነሣልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የአመልካቾች ፍርዱን ለመቃወም ያቀረቡት ማመልከቻ ደርሷቸው አቶ ዘውዴ በእሱፈቃድ 1944 ዓ.ም ተመልሰው በመምጣት ወ/ሮ አድማስወርቅ ሚስታቸውን ጠይቀው ተመልሰዋል፡፡ እኔም ተረግዤ ተወልጃለሁ፡፡ የመቃወም አመልካቾች የእኔ ወላጅ እናት ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁንና አቶ ዘውዴ በእሱፈቃድ በባልና ሚስትነት ተጋብተው አልኖሩም ብለው ባልተቃወሙበት ሁኔታ የሚች ልጅ ልጅ መሆኔ ህግ ግምት የሚያገበትን ጉዳይ በምስክር ለማፍረስ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአመልካቾችንና የተጠሪን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪ ማስረጃ ሚዛን የሚደፋና ተዓማኒነት ያለው የአመልካቾች ማስረጃ ተዓማኒነት አጠራጣሪ መሆኑን በመግለፅ ቀደም ሲል የሰጠሁትን ውሣኔ የሚነሳበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካቾችን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች ተጠሪ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ አሜሪካን አገር ለትምህርት ሄደው ባሉበት ተወለድኩ ያሉ በመሆናቸውና በመጀመሪያ እኔ ከተወለድኩ በኋላ ለትምህርት ሄዱ ያሉ ሲሆን በኋላ በእረፍት መጥተው ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተረገዝኩት በማለት ያቀረቡት ክርክር የሥር ፍርድ ቤት ተቀብሎ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ተጠሪን ለማሣደግ ያደረጉት ተሣትፎ የሌለ በመሆኑና ተጠሪም ይህንን ያላስረዳ በመሆኑ ከሁሉም በላይ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ባደረጉት ኑዛዜ ከሁለተኛ ሶስተኛ እና አራተኛ አመልካቾች ውጭ ልጅ የሌላቸው መሆኑን ያደረጉት ኑዛዜ በቂና አሳማኝ ማስረጃ ሆኖ እያለ ተጠሪ የሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ ነው ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው እኔ የተወለድኩት በወላጅ እናቴና በሚች ዘውዴ በሱፈቃድ መካከል ህጋዊ ጋብቻ ባለበት ጊዜ ውስጥ በመሆኑ የሚች ልጅ መሆኔ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ የተረጋገጠ ነው፡፡ አመልካቾች ይህንን የህግ ግምት ለማስተባበል በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 144 የተደነገጉትን ሁኔታዎች ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኑዛዜ የእኔን ልጅነት ለማሰረዝ የሚችል አይደለም የዚህ አይነት ይዘት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካቾች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያም ሆነ በሰበር አቤቱታቸው የተጠሪ ወላጅ እናት ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁን ከሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ጋር የጋብቻ ግንኙነት አልነበራቸውም፡፡ ተጠሪ የተወለደው የሁለቱ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ነው የሚል መቃወሚያ አላቀረቡም፡፡ አመልካቾች ተጠሪ የተወለደው አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ለትምህርት አሜሪካ ሄደው ባለበት ጊዜ ነው በማለት አጥብቀው የሚያቀርቡትን ክርክር አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ በአንድ ወንድና አንዲት ሴት መካከል ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልዬው እንደሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ የተወለደው በእናቱ ወ/ሮ አድማስወርቅ ጥላሁንና በአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ መካከል የነበረው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ መሆኑ ያልተካደ በመሆኑ የተጠሪ አባት አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ መሆናቸውን ህጉ ግምት የያዘበት ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪ በህግ ግምት የአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ መሆኑን ከማስረዳቱም በላይ አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ባለቤታቸውን ሊጠይቁ ለእረፍት በመጡበት ጊዜ የተረገዘ መሆኑን የአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ የቅርብ ዘመዶች በምስክርነት በማቅረብ አስረድተዋል፡፡ ይኸ በመሆኑ ተጠሪ የአቶ ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ አለመሆኑን ማስረዳት የሚቻለው በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 144 መሠረት ሳይሆን በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 167 መሠረት የመካድ ክስ በማቅረብና በቤተሠብ ህጉ አንቀፅ 168 እስከ አንቀፅ 173 ከተዘረዘሩት አንደኛውን ለማስረዳት የሚችል በቂ ማስረጃ በማቅረብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችለው አባት ነህ ተብሎ በህግ ግምት የተሰጠው እሱ የሞተ እንደሆነ ተወላጆቹ እና ሌሎች ዘመዶቹ በቅደም ተከተል እንደሆነ የቤተሰብ ህጉ ደንግጓል፡፡ አንደኛ አመልካች ዘውዴ እሱባለው ሚስትና የሁለተኛ፣ ሶስተኛና አራተኛ አመልካቾች እናት ብትሆንም በዚህ ጉዳይ ተጠሪ ላይ የመካድ ክስ የማቅረብ መብትና ችሎታ የላትም፡፡ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት መቃወሚያና መቃወሚያቸውን ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃ ታዓማኒነት የሌለው መሆኑና የተጠሪ ማስረጃ ሚዛን የሚደፋ መሆኑ ፍሬጉዳይ የመመዘን ስልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተስማምተውበታል፡፡ ሚች አቶ ዘውዴ በሱፈቃድ አደረጉት የተባለው ኑዛዜም ተጠሪ የሚች ልጅ ላለመሆኑ ብቃት ያለው ማስረጃ ተደርጎ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ህግ የሌለ በመሆኑ በዚህ በኩል የበታች ፍርድ ቤቶች የህግ ስህተት ፈፅመዋል የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካቾች ተጠሪ የሚች ዘውዴ በሱፈቃድ ልጅ አይደለም የሚለውን ክርክራቸውን የቤተሰብ ህጉ በሚደነግገው መሠረት በበቂ ሁኔታ አላስረዱም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ህጉን መሠረት ያደረገና ስህተት የሌለበት ሆኖ ስላገኘነው በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት አፅንተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾችና ተጠሪ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አሕመድ ሑሴን - ጠበቃ ማርቆስ ወ/ሰንበት ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ የኔዓለም ተመስገን - ጠበቃ ደምሰው ዘገየ ቀረበ

2. ወ/ሮ የኔነሽ ሙሉጌታ - ቀረበች

3. ወ/ሮ አስቴር ሙሉጌታ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የውርስ ሃብት ክፍፍልን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አንደኛ ተጠሪ ናት፡፡ ክስ የመሠረተችው በአሁኑ አመልካች፣ በሁለተኛ እና በሦስተኛ ተጠሪዎች ላይ ነው፡፡ በክስዋም ሞግዚት የሆነችለት የኋላእሸት ሙሉጌታ የተባለውን ልጅ የውርስ መብት ለማስከበር ክሱን እንደመሠረተች ገልጻ ያለሞግዚት አድራጊዋ ስምምነት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ እና የቤቱ 1/3ኛ ለሞግዚት አድራጊዋ እንዲሰጥ ይወሰንላት ዘንድ ጠይቃለች፡፡

ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስ የቤቱ ግማሽ የሌላ ሰው መሆኑን በአንድ በኩል ሲገለጹ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቀሪውን (የቤቱን ግማሽ) ለሦስቱ ተከፋፍሎ ከሣሽ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ ድርሻውን 1/3ኛ ሊወስድ ይችላል ብለዋል፡፡ አመልካች ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል መቃወሚያ ከማቅረቡም በላይ፤ ቤቱን የገዛው ስመሃብቱ ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከዞረ በኋላ እንደሆነና ከውሉ በኋላም ስመሃብቱ ለሱ መዛወሩን በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የሁሉን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ በአመልካች፣ በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶአል፡፡ የቤቱ ግማሽ ከተቻለ በአይነት፣ ካልተቻለ ተሸጦ 1/3ኛ ለከሣሽ ሞግዚት አድራጊ ይሰጥ በማለት ወስኖአል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ውሉ ይፈርሳል የሚለውን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ሲያፀና ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች በቤት ሽያጭ ውል ስም የወሰዱት ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) ግን ከነወለዱ ለአመልካች ይመልሱ በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ህዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የቤት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መደረጉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡

ከሥር ጀምሮ በተደረገው ክርክር እንደተመለከተው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት አንደኛ ተጠሪ ሞግዚት ለሆነችለት ልጅ እና ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች በውርስ የተሰጠ ሃብት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውርሱ ከመከፋፈሉ በፊት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ለአመልካች ሸጠውታል፡፡ የአንደኛ ተጠሪ ክርክር የተመሠረተውም የ3ቱም የጋራ የሆነው ንብረት ለመሸጥ የሁሉም የጋራ ባለሃብቶች ስምምነት ሊኖር ይገባል በሚለው ላይ ነው፡፡ በእርግጥም የጋራ የሆነውን ንብረት ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለንብረቶቹ ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1266 የተደነገገ ሲሆን፣ የውርስ ሃብትም አካፋፈሉ እስኪፈጸም ድረስ በወራሾቹ መካከል ውርሱ ሳይነጣጠል እንደሚቆይ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1060(1) ተመልክቶአል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ቤቱን ለአመልካች የሸጡት ስመሃብቱን በራሳቸው ካዛወሩ በኋላ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሺያጭ ውሉ ከመደረጉ ወይም ቤቱን ለአመልካች ከማስተላለፋቸው በፊት ከሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በስማቸው አግኝተው ነበር ማለት ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1195(1) እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት በተሰጠ ጊዜ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሃብት ሆኖ ይቆጠራል፡፡ እንግዲህ በያዝነው ጉዳይ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠውን ሁኔታ ከሕጉ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ቤቱ ያልተከፋፈለ የውርስ ሃብት መሆኑ ቀርቶ የሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች የግል ሃብት እንደሆነ እንደሚቆጠር ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች ቤቱን የገዛው የሺያጮቹን የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት በማየት ሲሆን፣ ይህን በመከተልም ቤቱ በራሱ ስም አዙሮ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ያገኘበት በመሆኑ በአመልካቹ እና በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የሚፈርስበት በሕግ የሚደገፍ ምክንያት የለም፡፡

ሌላው ቀጥለን የተመለከትነው አንደኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ ድርሻ እንዴት ይታያል? የሚለው ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሉ መፍረስ በመስማማቱ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች በቤት ሽያጭ ስም የተቀበሉት ገንዘብ ለአመልካች እንዲመልሱ ወስኖአል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አንደኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅም ከሌሎቹ ወራሾች ጋር በመሆን ከቤቱ ድርሻውን ሊያገኝ ስለሚችል ችግር አይኖርም፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት እምነት ግን ውሉ ሊፈርስ ስለማይገባ ቤቱ በወራሾቹ መካከል ይከፋፈል የሚል አካሄድ አይኖርም፡፡ ወራሾቹ ሊከፋፈሉ የሚችሉት ከቤቱ ሽያጭ የተገኘውን ገንዘብ ነው፡፡ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ቤቱን የእነሱ ሃብት ብቻ እንደሆነ አድርገው ቢሸጡትም፤ በመጨረሻ የታመነው ግን የ3ቱም ወራሾች ሃብት መሆኑ ስለሆነ ከዚህ ሃብት የተገኘው የሺያጭ ገንዘብም የ3ቱ ወራሾች ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም አንደኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ የተለየ ሥነ-ሥርዓት መከተል ሳያስፈልገው ከቤቱ ሽያጭ ከተገኘው ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ድርሻውን 1/3ኛ (አንድ ሦስተኛ) የማግኘት መብት አለው፡፡ በዚህ መሠረትም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07153 ግንቦት 28 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 57214 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. በአመልካች እና በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል አይፈርስም ብለናል፡፡
3. አንደኛ ተጠሪ ሞግዚት የሆነችለት ልጅ ከቤቱ ሽያጭ ከተገኘው ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ድርሻውን 1/3 (አንድ ሦስተኛ) ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ይስጡት ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡
5. በዚህ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለሥር ፍ/ቤቶች ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42682

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ ሙላቱ ቀረቡ

2. አለሙ ደምሴ

3. ወ/ሪት ትእግስት ደምሴ

ተጠሪ፡- ሞላ ደምሴ ቀረበ ጠበቃ ፋንታ አየለ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ልጅነትን ለማረጋገጥ በቀረበው ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ቀደም ሲል ለፍ/ቤት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የሚች ደምሴ ፀጋዬ ልጅ መሆኑ ተረጋግጦ ተወስኖ ነበር፡፡ አመልካቾች ክርክሩ ውስጥ የገቡት ውሳኔውን በመቃወም እንዲሻርላቸው በመጠየቃቸው ነው፡፡ ተቃውሞአቸውም ተጠሪ የሚች ልጅ አይደለም የሚል ስለነበር፤ መቃወሚያው የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪን በማስቀረብ የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም በተጠሪ በኩል የቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በእርግጥም የሚች ልጅ እንደሆነ አረጋግጦአል፡፡ ተቃዋሚዎች ይህን ማስረጃ ማስተባበል አልቻሉም በማለት የቀድሞው ውሳኔውን አፅንቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሚች ልጅ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተፈጽሞአል የሚሉትን ስህተት በመግለጽ ውሳኔው ይሻርላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጠሪ የሚች ልጅ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143 አንፃር ሲታይ አግባብነት ያለው ነው ወይስ የለውም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰማው የግራቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራቀኝ ወገኖችን ያከራከረው የልጅነት ጥያቄ በተመለከተ ማስረጃዎችን ሰምቶአል፡፡ በሰማው ማስረጃም ሚች (አባት ነው የተባለው ሰው) ተጠሪን እንደልጁ በማድረግ ሲንከባከብ እንደነበር፣ ትምህርት ቤት ወስዶ እንዳስመዘገበው፣ ከቤተሰቦቹ ጋር በመቀላቀል ያኖረው እንደነበር ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች በተጠሪ በኩል የተሰማውን ማስረጃ ሊያስተባብሉ እንዳልቻሉ በትችቱ ገልጾአል፡፡ በመጨረሻም በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ (አዋጅ ቁ 213/92) አንቀጽ 143(ሠ) መሠረት አባትነትን ለማረጋገጥ በቂ ምክንያት እንደሆነ በመገንዘቡ ተጠሪ የሚች ልጅ ነው በማለት እንደወሰነ ተገንዝበናል፡፡ አመልካቾችም ቢሆኑ እየተከራከሩ ያሉት የሥር ፍ/ቤት አረጋግጫለሁ ያለውን ፍሬ ነገር አላረጋገጠም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይሆን፣ ተጠሪ ተወልጃለሁ የሚለው ከጋብቻ ውጪ በተፈጸመ የግብረስጋ ግንኙነት በመሆኑ ይህንኑ ግንኙነት በማያጠራጥር ሁኔታ ማስረዳት ሲገባው አላስረዳም በማለት እንደሆነ ከአጠቃላይ የክርክራቸው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143 "በፍርድ ስለሚነገር አባትነት" በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዞአል፡፡ እነዚህም ከንኡስ አንቀጽ(ሀ) እስከ (ሠ) ድረስ ያሉት ሲሆኑ፣ አመልካቾች በመከራከሪያነት ያነሱት ነጥብ በንኡስ አንቀጽ (መ) በተመለከተው ድንጋጌ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በሕግ የታወቀ ግንኙነት ባይኖራቸውም፤ በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ መሆናቸው ከተረጋገጠ አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ሊታወቅ እንደሚችል ስለሚያመለክት እንደሌሎቹ ድንጋጌዎች አንደኛው አባትነትን በፍርድ ውሳኔ የማወቂያ ዘዴ (ሁኔታ) ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው ሁኔታ ባለመረጋገጡ ብቻ አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ማወቅ አይቻልም ማለት አይደለም፡፡ በተጠቀሰው አንቀጽ 143 መሠረት አባትነትን በፍርድ ውሳኔ ማወቅ የሚቻለው ከንኡስ አንቀጽ (ሀ) እስከ (ሠ) ካሉት ድንጋጌዎች ውስጥ በአንዱ የተመለተው ሁኔታ ሲሟላ ነው፡፡ በመሆኑም ቀጣይነት የግብረሥጋ ግንኙነት ስለመኖሩ ተጠሪ በማስረጃ አላረጋገጠም የሚለው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ስናጠቃልለው የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪን የሚች ልጅ በማለት በሰጡት ውሳኔ የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

4. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 27622 ጥቅምት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 63272 ህዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሠረት አፅንተናል፡፡
5. ተጠሪ የሚች ልጅ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
6. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42766

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሀይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካቾች፡- እነ ወ/ት ሠናይት ኃ/ማርያም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አበበች ወርቁ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በአመልካቾች አባት እና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፈረስን ተከትሎ የንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የውርስ አጣሪ ሰይሞ አጣሪውም ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን የቤ.ቁ 084 ጨምሮ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው በማለት ሪፖርቱን ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ይህንኑ ሪፖርት ተቀብሎ ማጽደቁን ተገንዝቦአል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካቾች የቤ.ቁ 084 የሆነው ቤት የሚች አባታችን የግል ንብረት ሆኖ ሳለ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ በውርስ አጣሪ የተደረሰበትን ሪፖርት የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተቀብሎ ሪፖርቱን ማጽናቱ በአግባቡ አይደለም በማለት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የውርስ አጣሪው ቤቱ የጋራ ነው ወደሚል ድምዳሜ የደረሰው የጋብቻ ውሉን መሠረት በማድረግ ሲሆን ነገር ግን ውሉ የጋራ ያደረገው የቤቱን ገቢ እንጂ ቤቱን እንዳልሆነ ከውሉ በግልጽ መረዳት ይቻላል ካለ በኋላ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ይሄው ቤት የአመልካቾች አባት የግል ሀብት ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

የአሁን ተጠሪም በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይግባኝ ባይና የመ/ሰጭዎች አባት ሲጋቡ የቤ.ቁ 084 አስቀድሞ በሚች ተሰርቶ የነበረና ሁለት ክፍል ቤት ብቻ የነበረ ሲሆን ነገር ግን በጋብቻ ላይ እያሉ ቤቱን በተደጋጋሚ ማደሳቸው ይህ ቤት እንዳይሸጥ በማሰብም ሌላ ቤት ሸጠው ለዕዳ መክፈያነት በማዋል ቤቱ ከመሸጥ ስለማዳናቸው ቤቱም በፊት ከነበረው ሁለት ክፍል ላይ ተጨማሪ 9 ክፍል ሰርቪስ ቤቶችን በጋራ ስለመስራታቸውና አስቀድሞ ቤቱ የሚገኝበት ይዞታ 300 ሜ.ካሬ ብቻ የነበረ ሲሆን ነገር ግን በተጨማሪ ግንባታ ሲደረግ ይዞታውም ወደ 578 ካ.ሜትር ከፍ ስለማለቱ በክርክሩ የተረጋገጠ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ ቤቱ የመ/ሰጪዎች አባት የግል ንብረት ነው መባሉ በአግባቡ አይደለም በማለት በመሻር የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው ሲል ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ሊቀርብ ይገባል ብሎ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ ክርክር ያስነሳው ቤት የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው? ወይንስ የባል የግል ንብረት? የሚለው ነው፡፡

ከዚሁ ጭብጥ አኳያም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበራቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ በተሻሻለ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 57 ላይ ተመልክቷል፡፡ የአመልካቾች አባትና ተጠሪ ጋብቻቸውን በፈጸሙ ጊዜ የቤ.ቁ 084 በሚች የአመልካቾች አባት ስም ተመዝግቦ ሁለት ክፍል ቤት ብቻ እንደነበር የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ፍሬ ነገርም ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ሆኖም ግን ግራ ቀኙ ሚያዝያ 13 ቀን 1966 ዓ.ም ያደረጉት የጋብቻ ውል ክርክር የተነሳበትን ቤትም ሆነ ሌሎች በባል ስም ተመዝግበው የሚገኙ ንብረቶችን የጋራ ለማድረግ እንደተስማሙ ከውሉ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ እንደተመለከተው ባልና ሚስቱ ጋብቻቸው ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ቤቱን በተደጋጋሚ ማደሳቸው፣ በንግድ ምክንያት የመጣና በጋራ የሚፈለግባቸውን የግብር ክፍያ በተመለከተም ይሄው ቤት እንዳይሸጥ በማሰብ ሌላ ንብረት ሸጠው የግብር ዕዳውን በመክፈል ቤቱን ማቆየታቸውና ቀድሞ የነበረውንም ይዞታ በማስፋፋት ሌላ ተጨማሪ 9/ዘጠኝ/ ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ስለመስራታቸው የተረጋገጠ እንደመሆኑ መጠን ይህም ቀድሞውንም ቢሆን በጋብቻ ውሉ ቤቱን የጋራ ለማድረግ የነበራቸውን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

ስለሆነም ግራ ቀኙ ባደረጉት የጋብቻ ውል አከራካሪው ቤት የጋራ እንዲሆን የተስማሙ ከመሆኑም ሌላ ጋብቻው ጸንቶ በቆየ ጊዜም የቤቱ አገልግሎት በመሠረታዊነት የተለወጠ ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ቤቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 31335 ታህሳስ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42648

ታህሣሥ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘነበች በያን - ተወካይ አለምነሽ ከበደ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ት ብርቅነሽ ከበደ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ልጅነት ማረጋገጥን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑዋ ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ አባታቸው የ፱ አለቃ ከበደ በያን እና እናታቸው ወ/ሮ ብርሃኔ ኃ/ማሪያም ተጋብተው ሲኖሩ በ1964 ዓ.ም የተወለዱ በመሆኑና አባታቸው ፱ አለቃ ከበደ በያን ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩ የሚቹ ልጅ መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ቀርበው ሟች የ፱ አለቃ ከበደ በያን እና ወ/ሮ ብርሃኔ ኃ/ማርያም ልጅ ያልወለዱና ተጠሪ የወ/ሮ ብርሃኔ የክርስትና ልጅ መሆናቸውን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በግራ ቀኙ የቀረቡትን ምስክሮች ከሰማ በኋላ በተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 156 መሰረት የሟች የ፱ አለቃ ከበደ በያን ልጅ ናቸው ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው የ፱ አለቃ ከበደ በያን እና ወ/ሮ ብርሃኔ ኃ/ማርያም በጋብቻቸው ዘመን ልጅ ያልወለዱና ወ/ሮ ብርሃኔም መሐን የነበሩ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በሚገባ ሳያጣራ ተጠሪ የሟች ልጅ ናቸው ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡ ችሎቱም ተጠሪ የሟች ልጅ ናቸው ተብሎ የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የፁሁፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

በስር ፍ/ቤት አቤቱታ የቀረበው ተጠሪ የሟች የ፱ አለቃ ከበደ በያን ልጅ ስለመሆናቸው እንዲረጋገጥ ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ልጅነትን ማስረዳት የሚቻለው የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ ወይም የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት እንደሆነ ከፍ ሲል የተጠቀሰው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 154 እና 155 ያመለክታሉ፡፡ ከመዝገቡ ሂደት ለመረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ልጅነታቸውን ለማስረዳት የሞከሩት የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ነው፡፡ አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው በማህበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ልጅ ነው ተብሎ ሲገመት መሆኑን ከአንቀጽ 156 መረዳት ይቻላል፡፡ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ማስረዳት ከተቻለ ፍ/ቤት ልጅ ሲል የሕግ ግምት ሊወሰድ የሚችል መሆኑ አንቀጽ 157/1/ ያመለክታል፡፡ ከአንቀፀ መረዳት እንደሚቻለው የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ የመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) ሳይሆን የሕግ ግምት ብቻ ነው፡፡ ግምቱም ቢሆን አስገዳጅነት ያለው የሕግ ግምት አይደለም፡፡ ግምቱን የሚቃወም ወገን ማስረጃ በማቅረብ ግምቱን ማፍረስ እንደሚችል ንኡስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ እንደተረዳነው ሟች የተጠሪ ልጅ ለመሆናቸው የሰው ምስክሮች ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም ቢሆኑ ተጠሪ ልጅ አለመሆናቸውን ለማስረዳት ተቃራኒ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ ሟች እና ወ/ሮ ብርሃኔ ባልና ሚስት በነበሩበት ጊዜ የተወለዱና የአካባቢውም ህብረተሰብ ተጠሪን የሟች ልጅ አድርጐ የሚገምት መሆኑን ሲያስረዱ የአመልካች ምስክሮች ይህንን የሕግ ግምት ማፍረስ አልተቻላቸውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ተጠሪ የልጅነት ሁኔታ መኖርን ስላረጋገጡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 156 መሰረት የ፱ አለቃ ከበደ በያን ልጅ ናቸው ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለው ለማለት አልተቻለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12503 ግንቦት 04 ቀን 2000 ዓ.ም ሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 68578 ጥቅምት 13 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡
2. ተጠሪ የፀ አለቃ ከበደ በያን ልጅ ናቸው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44612

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘውዴ ወ/ጊዮርጊስ - ጠበቃ ፈጠነ ከበደ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ት ኤልሳቤጥ ኪዳኔ - ቀረበች

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ናቸው፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም፤ወላጅ እናቴ ወ/ሮ ቻይና ከበደ ከሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ጋር ከጋብቻ ውጪ ባደረጉት ነዋሪ የሆነ ግንኙነት በ1971 ዓ.ም የተወለድኩ፤እኔ በተፀነስኩበት ጊዜ ሚችና እናቴ በአንድ ግቢ፤ በአንድ ቤት ውስጥ ይኖሩ የነበረ ሲሆን ሚች በሕይወት እያሉ በወር ብር 200.00(ሁለት መቶ) በወላጅ እናቴ አማካኝነት ቀለብ ይከፍሉ ነበር፤ስለዚህ ከሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ መወልደ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 125/1/ መሰረት ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካችም በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ ገብተው ተጠሪ አባትነት እንዲታወቅ ያቀረቡት ክስ የተሟላ ስላልሆነና የተጠሪ እናት ወ/ሮ ቻይና ከበደ ከሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ጋር በሕግ የታወቀ ግንኙነት እንደነበራቸው ያስወሰኑበትን ማስረጃ ስላላቀረቡ አቤቱታቸው የክስ ምክንያት የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪ መቼ ቀንና ወር እንደተወለዱ ስላልጠቀሱ፤ሚች ከተጠሪ እናት ጋር ለአንድም ጊዜ አብረው ኖረው ስለማያውቁ፤ሚች ከተጠሪ እናት በየትኛው ግቢ መቼ እንደኖሩ ስላልተገለፀና ለተጠሪ እናት በወር ሁለት መቶ ብር ቀለብ መክፈል አባት ለልጁ በሕግ ማድረግ የሚገባውን እንክብካቤ መመዘኛዎችን ስለማያሟላና ቀለብም ቆርጠውላቸው ስለማያውቁ፤የተጠሪ ምስክሮች በምን ጭብጥ ላይ ቃላቸውን እንደሚሰጡ በአቤቱታቸው ስላልጠቀሰ፤እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ በሚችና በተጠሪ መካከል የአባትነት እና የልጅት ግንኙነት ሁኔታ ስላልነበረ አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተጠሪ እንደክሳቸው አቀራረብ ሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌና እናታቸው ቻይና ከበደ ተጠሪ የተወለዱበትንና የተፀነሱበትን ጊዜ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 125/1/ እና 106/2/ ድንጋጌዎች መሰረት አላስረዱም፤የምስክሮች ቃልም እርስ በራሱ የሚጋጭ ነው በማለት የተጠየቀውን ዳኝነት ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በምስክሮች ቃል ተከሰተ የተባለው ልዩነት ጊዜን ብቻ የሚመለከት መሆኑን ይህ ልዩነት ከአጠቃላይ የምስክሮች ቃል ይዘት ጋር ተዛምዶ ሊታይ እንደሚገባ በመጥቀስ በተጠሪ ምስክሮች ቃል ፍሬነገር ላይ ቅራኔ ሳይኖርና ምስክርነቱ የተሰጠበት ጊዜ እርዝማኔ ግምት ውስጥ መግባት እንደአለበት በመግለጽ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻር የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 106/1/ እና 125/1/"ን" ጠቅሶ ተጠሪ የሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ልጅ ናት ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኗ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 21 ቀን 2001 ዓ.ም በዓራት 4(አራት) ገጽ የሰበር አቤቱታ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ትእዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪ ቀርበው ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ 4/አራት/ ገጽ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ የሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ልጅ ናት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የተጠሪ ክስ መሰረት ያደረገው ሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ እና ወ/ሮ ቾይና ከበደ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አንድ ላይ ሲኖሩ ተፀንሰው የተወለዱ መሆኑንና ሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ለተጠሪ በወር ብር 200.00(ሁለት መቶ ብር) ቀለብ ይሰጡ የነበረ መሆኑን ሆኖ ይህንኑ ለማስረዳትም የሰው ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩን በተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የተመዘገበው የተጠሪ ምስክሮችን ቃል ይዘት፡-1ኛ ምስክር የአመልካች እናት ሲሆኑ ከሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ጋር ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ዓመት በቤታቻው ውስጥ አብረው ሲኖሩ ተጠሪን ሦስት ወር እርጉዝ ሆነው ሚች ቤት ተከራይተው ከቤታቸው እንደአስወጡ፣በወር ብር 200.00 ይረዷቸው እንደነበርና የቤት ኪራይም ይከፍሉላቸው የነበረ መሆኑን፣ገንዘቡን ሕይወታቸው እስከአለፈ ጊዜ ድረስ መስጠታቸውን፣በሚች ቤት በኪራይ በሱማሌ ጦርነት ጊዜ ከውጪ ዜጋ ጋር ይኖሩ የነበረ መሆኑንና ሚች ልጅ ውለጂልኝ፣ቤት ተከራይቼ አስቀምጥሻለሁ ያሏቸው መሆኑን፣ተጠሪን ዓመተምህረቱን በማያስታውሱት በየካቲት ወር የውጪ ዜጋው ከሄደ ከሁለት ዓመታት በኋላ ከሚች መውለዳቸውንና የባልና ሚስት ፊርማ ግን ያልነበራቸው መሆኑን መመስከራቸውን፣2ኛ ምስክር በበኩላቸው ወ/ሮ ቾይና ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1980 ዓ.ም ድረስ በሰገነት ሆቴል ውስጥ ከፊታውራሪ ኪዳኔ ጋር ሲወጡ ሲገቡ አያለሁ፣ልጅ ግን አልወለዱም በማለት መመስከራቸውን፣3ኛ ምስክር ደግሞ ፊታውራሪ ኪዳኔ እና ወ/ሮ ቾይና በ1970 ዓ.ም ሰገነት ሆቴል ውስጥ አብረው ይኖሩ እንደነበረ፣ወ/ሮ ቾይና ከበደ ወሩን በማያስታውሱት በ1970 ዓ.ም የሦስት ወር ቅሪት ነኝ ብለው የነገሯቸው መሆኑን፣ሚችና ወ/ሮ ቾይና ከበደ እንደ ባልና ሚስት መኖራቸውን እንደሚያውቁ፣በ1970 ዓ.ም መጨረሻ ወደ አዲስ አበባ በመሄዳቸው ልጅ መውለዱን ግን አላውቅም በማለት መመስከራቸውንና 4ኛ ምስክርም በ1973 ዓ.ም ወ/ሮ ቾይና ቤት ተከራይተው ይኖሩ ነበር፣ሚች በሕይወት እስካሉ ድረስ ለረጅም ጊዜ ለተጠሪ ቀለብ እያሉ በየወሩ ሲሰጡ የነበረ መሆኑን እንደሚያውቁ በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሣይ መሆኑን ነው፡፡

በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አባትነት የሚታወቅባቸው መንገዶች፣ በእናትየዋና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩን በማረጋገጥ፣አባትየው ልጁን ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ምክንያት ወይም በፍርድ በሚሰጥ ውሣኔ እንዲታወቅ ሲደረግ የሚሉት ሦስት መንገዶች ናቸው፡፡

አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅበት መንገድ በተዘዋዋሪ የጋብቻ መኖሩን ወይም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን በማስረዳት የሚረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀራረፃቸው ወንድየውና ሴትየዋ በሕግ በታወቀው ግንኙነት መኖራቸውና መኖር የጀመሩበት ጊዜ ከግምት ሊገባና በተገቢው መንገድ ሊረጋገጥ እንደሚገባው ያስገነዝባሉ፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 126 መሰረት ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በልጅ እናትና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩ ከተረጋገጠ ወንድየው የልጁ አባት ነው የሚል የሕግ ግምት እንደሚወሰድ ተመልክቷል፡፡ በዚህ የሕጉ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በልጁ እናትና በወንድየው መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት እንዳለ ወይም የተወለደው በሕግ የታወቀው ግንኙነት ፀንቶ ባለበት መሆኑን ማሣየት የግድ የሚል መሆኑን ነው፡፡ በቤተሰብ ሕጉ “በሕግ የታወቀ ግንኙነት” የሚባሉ ግንኙነቶች ጋብቻ አንዱ ስለመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 1/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች የሚያሣዩ ሲሆን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 35/2/ ድንጋጌ ይዘትም ይህንኑ ያስረዳል፡፡ ሌላው በሕግ የታወቀ ግንኙነት የሚባለው ጋብቻ ሣይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ስለመሆኑም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 98 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡት ነው፡፡ በመሆኑም የሕግ ግምት ተጠቃሚ የሚሆነው ልጅ በጋብቻ ወይም ጋብቻ ሣይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የተጸነሰ ወይም የተወለደ ልጅ ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 128/1/ አንድ ልጅ ጋብቻው ከተፈጸመ ከ180 ቀናት በኋላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ንኡስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ለዚሁ ተቃራኒ የሆነ ማስረጃ ተቀባይነት እንደማይኖረው አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል፡፡ እንዲሁም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 130/2/ ድንጋጌ አንቀጽ 128 ድንጋጌ ሥር የተመለከተው ሕጋዊ ግምት በጋብቻ ተሳስረው በሚገኙ ተጋቢዎች ብቻ ሳይሆን ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ወንድና ሴት ላይም ተፈፃሚ መሆናቸውን ያስገነዝባል፡፡

እንግዲህ ሕጉ እነዚህን ሁኔታዎች ካስቀመጠ በጉዳዩ ላይ የሚቀርበው ማስረጃም በተገቢው መንገድ በጥንዶች መካከል የነበረውን ግንኙነት ዓይቱንና የጽንሱ ጊዜ እንዲሁም የልደት ጊዜው ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ ምስክሮች ቃል የተጠሪ እናትና ሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ የነበራቸውን የግንኙነት ዓይነት በተመለከተ የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩ እንደነበርና ቤተሰቦቻቸውም ሆነ ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው ይገምቷቸው እንደነበር የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ የተጠሪ እናትና ሚች አብረው ይኖሩ ነበር የተባለውን ጊዜ እና ተጠሪ ተወለዱ የተባለውን ጊዜ በተመለከተ ልዩነት ባለበት ሁኔታ መመስከራቸውን ከመዝገቡ ግልባጭ ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይኸው ፍሬ ነገር ስለመኖሩ ግንዛቤ ለተጠሪ ምስክሮች ቃል ክብደት ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው የፍርድ ቤቱ አካሄድ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 128፣130፣106 እና 125 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች አፈፃፀም ተግባራዊነቱን ሊያሣይ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ እናትና በሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሉ መካከል በህጉ አግባብ የተፈጸመ ጋብቻ ሣይኖር እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ለመኖሩ ተጠሪ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 125/1/፣128፣130 እና 106/2/ አንፃር ያላስረዱና ያቀረቧቸው ምስክሮች ቃልም እርስ በእራሱ የሚጋጭ መሆኑን ገልጾ የደረሰበትን ድምዳሜ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሻረው ሕጋዊ በሆነ ምክንያት ሆኖ አልተገኘም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተፈጸመውን ስህተት ማረም ሲገባው ውሣኔውን ማጽናቱ ባግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03729 ጎዳር 09 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 44026 መጋቢት 08 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 15572 የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ የሚች ፊታውራሪ ኪዳኔ ኃይሌ ልጅ አይደሉም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38533

ህዳር 08 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ጽጌ ወልደመስቀል (6 ሰዎች) ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ስዩም ክፍሌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር መዝገብ የቀረበው ክርክር በውርስ ህጉ ውስጥ የተመለከቱትን ይርጋ ድንጋጌዎችን አተረጓጎም እና አፈፃፀማቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ጥቅምት 22 ቀን 1997 ዓ.ም አሻሽለው በአሁኑ አመልካቾች ላይ ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ተጠሪና አመልካቾች የኮሎኔል ክፍሌ ደስታ ወራሾች ለመሆናቸው በአውራጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1009/80 ህዳር 11 ቀን 1980 ዓ.ም ማረጋገጣቸውን፣ የአውራሻቸው ንብረት የሆነ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 ቁጥሩ 228 የሆነ ቤት ከአመልካቾች ጋር በእኩልነት በመካፈል የደረሳቸው እንዳላቸው፣ ቤቱን አመልካቾች ተጠሪን አስወጥተው በመኖሪያነት እና እያከራዩ በመጠቀም ላይ እንደሚገኙ፣ የቤቱ ግምት ድርሻቸውም ብር 33,547.90 (ሰላሳ ሶስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ሰባት ብር ከዘጠና ሳንቲም)፣ የኪራይ ደግሞ ብር 8118.75(ስምንት ሺህ አንድ መቶ አስራ ስምንት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም) እንደሚሆን ገልፀው አመልካቾች ገንዘቡን እንዲከፍሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾችም በተከሳሽነታቸው ቀርበው ክሱ የቀረበው አውራሻቸውን ከሞቱበት ከመስከረም 28 ቀን 1980 ዓ.ም በኋላ ታህሳስ 24 ቀን 1992 ዓ.ም በመሆኑ እና ይህንንም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000(1) ስር የተመለከተው የሶስት ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ የሚያግደው ነው፣ የኪራይ ገንዘብ ጥያቄም ከዘጠኝ ዓመትና ከሰባት ወር በኋላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(መ) መሰረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን አንስተው የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ተገቢነት አሏቸው ያሏቸውን ነጥቦችን በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ብር 7422.50 (ሰባት ሺህ አራት መቶ ሀያ ሁለት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) እንዲከፍሉ፣ ቤቱን በተመለከተም 1/2ኛው ለአንደኛ አመልካች ከተሰጣቸው በኋላ ሌላው ቀሪውን 1/2ኛው ከተቻለ በአይነት፣ ካልተቻለ በስምምነት ወይም በሐራጅ ከተሸጠ በኋላ 1/6ኛው ለተጠሪ እንዲሰጥ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይገባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይርጋን በተመለከተ የቀረበው ቅሬታ፤ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ እንጂ የወራሽነት ጥያቄ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000/1/ መሠረት እንደማይታገድ፣ የኪራይ ገንዘብ ጥያቄም የተከራይና አከራይ ግንኙነት የሌለ በመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2024/መ/ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ የአመልካቾችን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ ካደረገ በኋላ ቤቱን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ያስቀመጠውን ክፍፍል በማሻሻል ተገቢ ነው ያለውን የክፍፍል መንገድ በመጥቀስ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይርጋንና የቤቱን ክፍፍል አስመልክቶ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው

ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000/1/ ሆኖ እያለ የይርጋ ክርክሩ መታለፉና ቤቱን በተመለከተ የተሰጠው የክፍፍል ጥያቄም የአንደኛዋን አመልካች ግማሽ ባለድርሻነት አለማገናዘቡ ተገቢነት የሌለው ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው ጥቅምት 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም የይርጋ ክርክሩ የታለፈው ጥያቄው የውርስ ንብረት ክፍፍል በመሆኑ መሆኑንና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ ድንጋጌ ተፈፃሚነቱ የወራሽነት ጥያቄን በሚመለከት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች ህዳር 1 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነ ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ሲባል ከተያዘው የይርጋ ክርክር የመታለፉ አግባብነት አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የሟች ወራሽነታቸውን ከአመልካቾች ጋር በአንድነት ህዳር 11 ቀን 1980 ዓ.ም በፍርድ ቤት ማስወሰናቸውን፣ አሁን እየተከራከሩ ያሉት የውርስ ንብረት ድርሻቸውን አመልካቾች እንዲያካፍሏቸው መሆኑን ነው፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000 የወራሽነት ጥያቄ የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 996 እስከ 1002 ድረስ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 999 ስር በተመለከተው መሠረት የሚቀርበው የወራሽነት ጥያቄ (Petition hereditists) በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 996 እና ተከታዬቹ ቁጥሮች ከተገለፀው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ጥያቄ አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሐብት በያዘ ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ተፈፃሚነት ባላቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ስር በተመለከቱት ደንቦች መሰረት የሚገደብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የሟች ኮሎኔል ክፍሌ ደስታ ወራሽነታቸውን ህዳር 11 ቀን 1980 ዓ.ም ከሌሎች ወራሾች ጋር በመሆን በፍርድ ቤት ውሳኔ አረጋግጠው የክፍፍሉ ጥያቄ በቀረበበት ቤት ውስጥ ከአመልካቾች ጋር ይኖሩ የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው የሟቹ ወራሾች ተለይተው መታወቃቸውን ነው፡፡ የተጠሪ ጥያቄ ደግሞ የውርስ ክፍያ ነው፡፡ የውርስ ክፍያ ደግሞ ራሱን የቻለ የውርስ ህግ ሆኖ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1060 እስከ 1113 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር የተሸፈነ ጉዳይ ነው፡፡ የውርስ ክፍያ ጊዜን በተመለከተ የፍ/ብ/ሕጉ በአንቀጽ 1062 ስር የደነገገ ሲሆን የድንጋጌው ይዘትም ውርሱ በተጣራ ጊዜ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን እያንዳንዱ የጋራ ወራሾች ውርሱን እንከፋፈል ብለው ለመጠየቅ እንደሚችሉ መደንገጉን የሚያሳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1060 ድንጋጌ ስር ደግሞ የውርስ አከፋፈል እስካልተፈፀመ ድረስ ውርሱ በወራሾች መካከል ሳይነጣጠል እንደሚቆይ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የሟች ወራሽነታቸውን በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ አረጋግጠው ከቆዩ በኋላ የውርስ ንብረቱን የክፍፍል ጥያቄ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ እና /2/ ስር በተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ የሚታገድ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1062 ድንጋጌ መሠረት በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ በመሆኑ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የፈፀመው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡

ሌላው አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት በቤቱ ላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የክፍፍል ሥነ-ሥርዓቱን በተመለከተ ነው፡፡ የውርስ አከፋፈል አሰራርን በተመለከተ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1082 እስከ 1096 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት መፈፀም ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1083 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ በዚህም መሠረት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲታይ በህጉ የተመለከተውን የውርስ አከፋፈል አሰራርንና በቤተሰብ ህጉም የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር የአንደኛ አመልካችን መብትም ሆነ የሌሎችን አመልካቾችን መብት ያጣበበ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካቾች ለተጠሪ የቤቱን ግምት ከፍለው ቤቱን በአይነት ለማስቀረት ከፈለጉም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1060/2/ የጋራ ወራሾች የሆኑ ሰዎች ባልተከፋፈሉት የውርስ ንብረቶች ላይ ያላቸው መብት ስለ የጋራ ባለሐብትነት፣ ስለ ሪምና ስለ ሌሎች ግዙፍ መብቶች በሚለው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ በተነገሩት ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናል በማለት ስለሚደነግግ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት የቤቱን የገቢያ ዋጋ ለተጠሪ በመስጠት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቅድሚያ ግዥ መብት (Right of Recovery) ጥያቄ ከሚያነሱ በስተቀር ከወዲሁ ተጠሪ ቤቱን በሐራጅ እንዲሸጥ መጠየቅ አይችሉም በማለት ሊቃወሙ የሚችሉበት ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቾች ቅሬታም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም፤ ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ ውሳኔ ያሳረፈው ፍርድ ቤት የውርስ ህግ ድንጋጌዎችና አፈፃፀም ላይ የፈፀመው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስላልተገኘ ውሳኔው ሊፀና የሚገባ ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00668 ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 61968 ሚያዚያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም ተሻሽሎ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ሥ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 42569

ታህሳስ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐሳስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- 1. ዳግማዊ ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ወ/ሮ ፍሬህይወት ታመነ

2. ናትናኤል ታዲዮስ

ጠበቃ ፋንታሁን አባተ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የሃና ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ወ/ሮ ቤተልሄም ግርማ - ጠበቃ አልታዬ ወ/አማኑኤል - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ልጅነት ይታወቅልኝ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪ ሞግዚትና አስተዳዳሪ መጋቢት 13 ቀን 1997 ዓ.ም በተባለ አቤቱታ ሕፃን ሐናን ከአቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ የወለድኳት ስለሆነ ሕፃን ሐና የአቶ ታዲዮስ ልጅ መሆኗ በፍርድ ውሳኔ ይታወቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው ፍርድ ቤቱም የአሁኑ አመልካቾች በሌሉበት የተጠሪን ምስክሮችን በመስማት የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 143(መ)"ን" መሰረት በማድረግ ሕጻን ሐና የአቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ናት በማለት ግንቦት 22 ቀን 1997 ዓ.ም ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ውሳኔው መብታችንን የሚነካ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ለመቃወሚያው መሰረት ያደረጓቸው ነጥቦችም ለውሳኔ መሰረት የሆነው የልደት ምስክር ወረቀት የወጣው አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ህዳር 06 ቀን 1997 ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ጥር 18 ቀን 1997 ዓ.ም ነው፣ የጥምቀት ምስክር ወረቀቱም አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ያልፈረሙበት ነው፣ የተሰሙት ምስክሮችም ለውሳኔው መሰረት የሆነው ድንጋጌ የሚጠይቀውን መመዘኛ በሚገባ አላስረዱም የሚሉ ናቸው፡፡ የአሁኗ ተጠሪም በአመልካቾች መቃወሚያ ላይ መልስ ሲሠጡ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት የጽሑፍ ማስረጃዎች የወጡበት ሁኔታ በአሰራር ደረጃ የተለመደ በመሆኑ ማስረጃዎች በሕግ ፊት ተቀባይነት ያላቸው መሆኑንና ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅም ሕፃን ሐናን እንደአባት ሆነው ሲንከባከቧት የነበረ መሆኑ በምስክሮች ባግባቡ መመስከሩን ገልፀው መቃወሚያው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ሕፃን ሐና የሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ስለመሆኗ ልጅነት በፍርድ ከሚታወቅባቸው መንገዶች መካከል በአንዱ አልተረጋገጠም በማለት ቀደም ሲል የሠጠውን ውሳኔ ሠርዞታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኞቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ እና የተጠሪ ምስክሮችን በድጋሚ ከተሰሙ በኋላ ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ከሕፃን ሐና ወላጅ እናት ጋር ቀጣይነት ባለው ግንኙነት ውስጥ እንደነበሩ፣ ሕፃኗን እንደ አባት በመሆን ያሳድጓት እንደነበር መረጋገጡን እና የልደት ምስክር ወረቀትም ማስረጃውን በሠጠው አካል እስካልተሠረዘ ድረስ ተቀባይነት እንዳለው በመግለፅ ሟቹ የአቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ የህፃኗ አባት መሆናቸው በልደት ምስክር ወረቀትና በምስክሮች ቃል ተረጋግጧል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 51348 ሰኔ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተሠጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ጥር 06 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቀርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የልደት ምስክር ወረቀቱ አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ከሞቱ በኋላ የወጣ መሆኑ እየታወቀ እና የተጠሪ ምስክሮች ቃልም የሕፃኗ እናት እና አባት የተባለው ሰው በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ስጋ ግንኙነት አብረው የነበሩ ስለመሆኑ ሕጉ በሚጠይቀው መመዘኛ የመሰከሩ ስለመሆኑ የማያረጋግጥ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተቀመጠውን ጥብቅ መመዘኛ በማለፍ ሟች የሕፃን ሐና አባት ናቸው ብሎ የወሰነው ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ሕፃን ሐና የሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ናት በሚል የተሠጠው የልጅነት ምስክር ወረቀት ሟች ከሞቱ በኋላ የተሠጠ ነው እየተባለ የስር ፍርድ ቤት ይህንን የልጅነት ምስክር ወረቀት ብቻ መሰረት አድርጎ ሟች የሕፃኗ አባት ናቸው በማለት የሠጠው ውሳኔ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ሐምሌ 08 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካቾች ጠበቃም ነሐሴ 20 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ አንድ ገፅ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባዋል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው የልደት ምስክር ወረቀት ለተጠሪ የተሠጠው አቶ ታዲዮስ ሐረገወርቅ ሕዳር 06 ቀን 1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ጥር 18 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑን፣ ይህንኑ የልደት ምስክር ወረቀት የሠጠው አካልም ሥልጣን ያለው ሆኖ ማስረጃውን ያልሰረዘው መሆኑን፣ ተጠሪ ከዚህ የሰነድ ማስረጃ በተጨማሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ማስረጃ የሰው ምስክሮችን የሚጨምር መሆኑን የስር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሠጠው የሰነድ እና የሰው ምስክሮች ቃል በመመዘን መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜም ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ የህፃን ሐና አባት መሆናቸው በልደት ምስክር ወረቀትና በምስክሮች ቃል ተረጋግጧል የሚል ስለመሆኑም የውሳኔው ግልባጭ በግልፅ የሚያሳይ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ ልጅነት ደግሞ በቀዳሚነት በልጅነት የምስክር ወረቀት የሚረጋገጥ ሲሆን የልጅነት ምስክር ወረቀት ከሌለ ደግሞ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማሳየት እንደሚረጋገጥ፣ የልጅነት ሁኔታ የሌለ ከሆነ ሲሆንም ተወላጅነትን በምስክሮች ወይም ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት እንደሚቻል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ እንደቅደም ተከተሉ በአንቀፅ 156፣ 168፣ 158፣ እና 169 ስር ደንግጓል፡፡ አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ደግሞ የልደት ምስክር ወረቀት ለተጠሪ የተሠጠበት ጊዜ ሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ከሞቱ በኋላ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የልደት ምስክር ወረቀት አባት ነው የተባለው ሰው ከሞተ በኋላ የተሠጠ ሆኖ ሲገኝ ዋጋ የለውም የሚል የሕግ ድንጋጌ የሌለ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ማስረጃው በተገቢው አካል እስካልተሰረዘ ድረስ ዋጋ አለው በማለት ከተጠሪ የሰው ምስክሮች ቃል ጋር አዛምዶ በመመዘን ክብደት መስጠቱ በማስረጃ አቀባበል ላይ የተፈፀመ ስህተት ስለመኖሩ የሚያሳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲታይ መሰረት ያደረገው ማስረጃ ምዘናን ነው፡፡ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ደግሞ የሰበር ችሎት ስልጣንና ኃላፊነት አለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 80(3/ሀ) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 እና 22 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ሊፀና የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 57322 ጥቅምት 10 ቀን 2001 ዓ.ም በተሠጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር ታህሳስ 01 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ሕፃን ሐና የሟች ታዲዮስ ሐረገወርቅ ልጅ ናት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 47487

ታህሳስ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሀይለራጉኤል ደበላ - ጠበቃ ገመቹ ሮሮ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሪት አለምፀሀይ ፈለገ
2. አቶ አቦነህ ፈለገ
} ጠበቃ ባርናባስ ደስታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ጥር 13 ቀን 1999 ዓ.ም በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ የአመልካች አባት የነበሩት ሟች አቶ ደበላ ልቡ ከወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ጋር ጋብቻ ከማድረጋቸው በፊት የነበራቸውንና ቁጥራቸው 1056/1057 የሆኑት የግል ቤቶች መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ወ/ሮ ክብነሽ በሕይወት እስከአሉ ድረስ እንዲኖሩ እና እንዲጠቀሙበት ከሞቱ በኋላ ወደ ወራሾች እንዲተላለፍ በማለት መናዘዛቸውን፣ ኑዛዜውም በፍ/ቤት መፅደቁም፣ ኑዛዜው ወ/ሮ ክብነሽ ቤቱን ከፈለጉ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ የሚል ቢሆንም በውርስ እንዲያስተላልፉ የሚያዝ ሆኖ እያለ ለዘመዶቻቸው ማውረሳቸውን ገልፀው ተጠሪዎች ያላግባብ የያዙትን ቤት ለቀው እንዲያስረክቧቸው፣ ተጠሪዎች ለተጠቀሙበት የቤት ኪራይ አመልካች የመጠየቅ መብታቸው ተጠብቆ እንዲወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎችም በተከሳሽነት ቀርበው በሠጡት መልስ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ በሟች አቶ ደበላ ልቡ ኑዛዜ መሰረት ንብረቱን ወደራሳቸው በማዞር የግል ንብረት በማድረግ ሲጠቀሙበት የቆዩ በመሆኑና ክሱም ኑዛዜው ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ በመሆኑ እንዲሁም ኑዛዜውን ለመቃወም የሚቀርብ ክስን ስርዓት ተከትሎ ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚሉ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ሟች አቶ ደበላ ባደረጉት ኑዛዜ ወ/ሮ ክብነሽ ቤቱን ለመሸጥ፣ ለመለወጥ እንዲችሉ ስልጣን የሚሠጥ በመሆኑ ወ/ሮ ክብነሽ ንብረቱን ለሌላ የማስተላለፍ መብት አላቸው ንብረቱንም በስማቸው አዙረው ሲጠቀሙበት ቆይተው ግንቦት 27 ቀን 1996 ዓ.ም በውልና ማስረጃ በተደረገ ኑዛዜ ለተጠሪዎች የሰጧቸው በመሆኑ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጀ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የተጠሪዎችን ክርክር ውድቅ አድርጎ ሟች አቶ ደበላ ልቡ መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል በኑዛዜ ንብረቱን ለማስተላለፍ ሥልጣን የሚሠጥ አይደለም፣ የሟች ደበላ ልቡ ኑዛዜ ከወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ሞት በኋላ ተፈፃሚነት አለው በሚል ምክንያት ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ የቤት ኪራይ በተመለከተ ከቤቱ ጋር ክስ መቅረብ የነበረበት ስለሆነ የአመልካች ወደፊት የመክሰስ መብት ሊጠበቅ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ከአከራካሪው ኑዛዜ ይዘት ጋር በማገናዘብ መርምሮ በኑዛዜው ላይ ሟች አቶ ደበላ ልቡ ወ/ሮ ክብነሽ ሕይወቷ እስካለ ድረስ በከፊል ወይም በሙሉ ለመሸጥ በፈለገች ጊዜ ልትሸጥና ልትለውጥ ትችላለች፣ ለመሸጥ

በፈለገች ጊዜ ወራሾቿ ወይም ወራሾቹ እርሷ ፈቅዳ ካልሰጠቻቸው ሊቃወሟት አይችሉም በሚል ያስቀመጡ ስለሆነና ይህ የተናዛዡ ሀሳብ የሚያስገነዝበው ደግሞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ካልፈቀዱ በቀር ቤቱን ለፈለጉት ሰው ቢሰጡ ከኑዛዜው መልዕክት ውጪ እንዳደረጉ የሚያስቆጥር አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ሟች አቶ ደበላ ልቡ ባደረጉት ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ንብረቱን ለመሸጥ፣ ለመለወጥ ትችላለች ተብሎ የተቀመጠው ሐረግ በኑዛዜ ለሌላ ሰው መሥጠትን ያጠቃልላል ተብሎ የተተረጎመው ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ንብረቱን ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ለመሸጥ፣ ለመለወጥ ይችላሉ የሚል ግልፅ የሆነ ቃል እንጂ ለሌላ ሰው ጥቅም ንብረቱን እንዲለውጡ ወይም እንዲሸጡ የሚል መልዕክት የሌለው ግልፅ ቃል ሆኖ እያለ ይህንኑ ግልፅ ቃል በሚጻረር መልኩ መተርጎሙ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ሟች አቶ ደበላ ልቡ ያደረጉት ኑዛዜ ወ/ሮ ክብነሽ ንብረቱን ሊሸጡ፣ ሊለውጡ እንጂ እርሳቸው በኑዛዜ እንዲያስተላልፉ የሚያስችላቸው እንደሆነ ተደርጎ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መስከረም 26 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው ንብረት የሟች አቶ ደበላ ልቡ የግል ንብረት መሆኑን ተጠሪዎች አለመካዳቸውን፣ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል የሟች አቶ ደበላ ልቡ ሚስት የነበሩ መሆኑን፣ አቶ ደበላ ልቡ ለወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም የተደረገ ኑዛዜ የተውላቸው መሆኑን፣ ይህንኑ ኑዛዜም በከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1553/59፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ በመ/ቁጥር 70/62 ማስፀደቃቸውን፣ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ግንቦት 27 ቀን 1996 ዓ.ም ውል እና ማስረጃ ክፍል ባደረጉት ኑዛዜ ደግሞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት ለሁለተኛ ተጠሪ፣ ለወ/ት ትዕግስት ፈለገ፣ ለወ/ት ኩላገር ፈለገ፣ ለወ/ት ወለላ ፈለገ፣ ለወ/ት ሙላቷ ፈለገ እና ለሕፃን ዮሴፍ እንዳሳ ፈለገ የተናዘዙላቸው መሆኑን ነው፡፡ አከራካሪው ነጥብ ሟች አቶ ደበላ ልቡ በተውት ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል ንብረቱን ከፍጻሜ ሕይወታቸው በኋላ በኑዛዜ ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት/ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል ወይስ አልተሰጣቸውም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ለጉዳዩ እልባት መስጠት ይቻል ዘንድም ሟች አቶ ደበላ ልቡ መስከረም 19 ቀን 1956 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ቃል አግባብነት ያለውን ክፍል ተመልክተናል፡፡ ይኸው የኑዛዜ ክፍል *“የሰጠኋትን ቤት ከነቦታው ሕይወቷ እስካለ ድረስ በስፊል ወይም በሙሉ ለመሸጥ በፈለገች ጊዜ ልትሸጥ ልትለውጥ ትችላለች፣ ለመሸጥ በፈለገች ጊዜ ወራሾቿ ወይም ወራሾቹ እርሷ ፈቅዳ ካልሰጠቻቸው ሊቃወሟት አይችሉም፣ ..... ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ቃል የሰጠኋትን ሀብትና ንብረት ለውጣ እራሷ የምትጦርበት ሲሆን ከርሷ የተረፈ ቢኖር ግን ውርሱ ለልጇ አርያና ለልጅ ልጇ ለኃይለራጉኤል መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከቀሪው ሀብቱ ጋር አንድ ላይ ተደባልቆ ከኔ በተወለዱት ማለት ከሙሉነሽ ላይ ለወለድኳቸው ልጆች ብቻ ከክብነሽ የማደጎ ልጆቿ ጋር እንደየድርሻቸው ሊከፋፈሉ ይችላሉ .....”* በሚል የተቀመጠ ነው፡፡

በመሰረቱ ኑዛዜ ሊተረጎም የሚገባው ቃላቶቹ እና መልእክቱ ግልፅ ሳይሆን ሲቀር ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ኑዛዜው ግልፅ ቃላቶችንና መልዕክትን የያዘ ከሆነ ትርጓሜ መስጠት አያስፈልግም፡፡ ይህንን መሰረታዊ መርህን መከተል ያለብን መሆኑን ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 910(2) ድንጋጌ በግልፅ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የኑዛዜው ቃል መተርጎም ያለበት ስለኑዛዜው መልእክት ጥርጣሬ በሚፈጥርበት ጊዜ አሻሚ ወይም ግልፅ ያልሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህን ደንብ ተፈጻሚ የሚሆንበትን መንገድም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 910(1)፣ 911፣ 925 እና ሌሎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎች ያሳዩናል፡፡ ስለሆነም የኑዛዜው ቃላት ግልፅ የሆኑ እንደሆነ የተናዛዡ እውነተኛ፣ ትክክለኛ ፈቃድ የትኛው ነው ብሎ ትርጓሜ መስጠትና ከኑዛዜው ቃል መራቅ የማይፈቀድ ስለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሟች አቶ ደበላ ልቡ ኑዛዜ ሟች ወ/ሮ ክብነሽ ጎንዱል በሕይወት እስካሉ ድረስ ለመሸጥ፣ ለመለወጥ የሚያስችላቸው እንጂ ከራሳቸው ጥቅም ውጪ ለሌላ ሰው በኑዛዜ እንዲያስተላልፉ የሚያስችላቸው አለመሆኑን ከላይ የተገለፀው የኑዛዜ ክፍል ያሳያል፡፡ በመሆኑም ይኸው የኑዛዜ ክፍል የሟች ፍላጎትና መልዕክት ግልፅ የሚያደርገው ሆኖ እያለ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የኑዛዜውን አንድን ክፍል ብቻ ነጥሎ ትርጉም የሠጠው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 910(1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን የኑዛዜ አተረጓጎም መርህን ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 60988 ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 44232 ሚያዚያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15647 ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41893

ታህሣሥ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዮዲት ኃይሉ የህፃን ሄኖክ ዳንኤል ሞግዚትና አሳዳጊ ቀረበች፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሪት ገነት አረጋይ
2. ወ/ሮ አዜብ አረጋይ } ወበቃ ታምራት ኪዳነ ማሪያም - ቀረበ
3. ወ/ሮ ሰብለ አረጋይ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው አመልካች ስትሆን፣ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል በሰጠው ትእዛዝ መሰረት በውርስ አጣሪ ተጣርቶ የቀረበውን የውርስ ክፍፍል የውሳኔ ሐሳብ በመቃወም ተከራክራለች የውርስ አጣሪው ባቀረበው የውሣኔ ሐሳብ ላይ ባቀረበችው የጽሑፍ አስተያየት በወረዳ 23 ቀበሌ 10 ውስጥ የሚገኘው ቁጥር 1220 የሆነው ቤት ከሟች እማሆይ ምጽላል ተድላ ለወ/ሮ የሺንርኤ በስጦታ የተላለፈ ነው፡፡ ወ/ሮ የሺንርኤ የህፃን ሄኖክ አባትን (ዳንኤል አረጋይን) ጨምሮ አራት ወራሾች አሉዋቸው፡፡ በመሆኑም የቤቱ ¼ኛ ድርሻ የህፃን ሄኖክ አባት ነው፡፡ አጣሪው የወ/ሮ የሺንርኤ ወራሾች ስምንት(8) እንደሆኑ አድርጐ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ የእማሆይ ምጽላል ተድላ 8(ስምንት) ልጆች በማከል ውርሱ እንዲከፋፈል በማለት የውሳኔ ሐሳብ ማቅረቡም ትክክል አይደለም የሚሉትንና ሌሎች ነጥቦችንም በማከል እንደተከራከረች በመዝገቡ ተመልክቶአል፡፡

በወቅቱ ተከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎችም በበኩላቸው ባቀረቡት አስተያየት እማሆይ ምጽላል ተድላ ቤቱን ለወ/ሮ የሺንርኤ የሰጡት በሕይወት እስካሉ ድረስ እንዲጠቀሙበት ብቻ ነው፡፡ ወ/ሮ የሺንርኤ ከሞቱ በኋላ ሐብቱ የሚች እማሆይ ምጽላል ተድላ ስለሚሆን የእማሆይ ምጽላል ተድላ ወራሾች ለሆንነው ለስምንታችን ይከፋፈላል፡፡ ከስምንቱ የእማሆይ ምጽላል ተድላ ልጆች ውስጥ ሚች ወ/ሮ የሺንርኤ አንድዋ ስለመሆኑ የሚደርሳቸው ከቤቱ 1/8ኛ ነው፡፡ ይህ 1/8ኛ ደግሞ ለስምንቱ ልጆቻቸው (ለወ/የሺንርኤ ልጆች) ይከፋፈላል፡፡ ከእነዚህ ልጆች ውስጥ የህፃን ሄኖክ አባት አንዱ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ህፃን ሄኖክ የሚወርሰው የአባቱን ድርሻ ስለሆነ ሊያገኝ የሚችለው ከቤቱ 1/56ኛ ነው በማለት የውርስ አጣሪው ያቀረበው አማራጭ ሃሳብ እንደግፋለን በማለት ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የተጠሪዎችን ክርክር እንዳለ በመቀበል የህፃን ሄኖክ ዳንኤል ድርሻ 1/56ኛ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ታህሣሥ 7 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው እማሆይ ምጽላል ተድላ መጋቢት 14 ቀን 1964 ዓ.ም ላደረጉት ስጦታ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ትርጓሜ አግባብነት

ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ረገድ ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምንመለከተው ለቀረበው ክርክር አወሳሰን በዋንኛነት መሰረት የሆነው እማሆይ ምጽላል ተድላ ለልጃቸው ለወ/ሮ የሺንርኤ ያደረጉት የስጦታ ውል ነው፡፡ የስጦታ ውሉ እማሆይ ምጽላል አከራካሪውን ቤት በወ/ሮ የሺ መሰጠታቸውን ያመለክታል፡፡ ይህ አከራካሪ አልሆነም፡፡ አከራካሪ የሆነው በስጦታው ውሉ ወ/ሮ የሺ ያገኙት መብት የባለሃብትነት ነው ወይስ የመጠቀም ብቻ? የሚለው ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች "…. እስከ እድሜ ልኳ ድረስ ማንም ሰው እንዳይጠይቃት ሰጥቻታለሁ፡፡" የሚለውን ሐረግ ነጥለው በመያዝ ወ/ሮ የሺ በስጦታ ውሉ ያገኙት መብት ከባለሃብትነት በመለስ ያለው ነው የሚል ትርጓሜ ሰጥተዋል፡፡ በበኩላችን እንዳየነው ውሉን በትክክል መተርጎም የሚቻለው አንድዋን ሐረግ ለይቶ በውጣት ሳይሆን፣አጠቃላይ ይዘቱን በማየት እንደሆነ ነው መገንዘብ የቻልነው፡፡ እማሆይ ምጽላል በስጦታ ውሉ የገለጹት ቤቱ የተሰራው በወ/ሮ የሺንርኤ ቦታ ላይ መሆኑን፣ስመ ሐብቱ በእማሆይ ምጽላል ቢመዘገብም፣የሰሩት ግን ወ/ሮ የሺንርኤ እንደሆኑ ለወደፊቱ (የስጦታ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ) ወ/ሮ የሺንርኤ የቦታውን ካርታ በስማቸው አስነስተው አስከ እድሜ ልካቸው ድረስ ማንም ሰው ሳይጠይቃቸው የተሰጣቸው መሆኑን፣በአጠቃላይ እማሆይ ምጽላል ቤታቸውን ለልጃቸው (ለወ/ሮ የሺንርኤ) የሰጡዋቸው መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ በስጦታ ውሉ የተመለከቱት ፍሬ ነገሮች ተያይዘው ሲታዩ በትክክል የሚያረጋግጡት እማሆይ ምጽላል ቤታቸውን ለልጃቸው ያለምንም ገደብ ለመስጠት አስበው መነሳታቸው እና ይህን ሐሳባቸውም በውሉ በቂ በሆነ ሁኔታ መግለፃቸውን ነው፡፡ ወ/ሮ የሺንርኤ የቦታውን ካርታ በስማቸው አስነስተው እንዲይዙ ተፈቀደላቸው ማለት ቤቱ በሃብትነት ተሰጥቶአቸዋል ከማለት ውጪ ሊተረጎም የሚችልበት አግባብ የለም በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በስጦታ ውሉ የሰጡት ትርጓሜ በእርግጥም በውሉ የተገለጸውን የስጦታ አድራጊዋ ሐሳብና ፍላጐት መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የስጦታ ውሉ ክፍ ሲል በተመለተው ሁኔታ የሚተረጐም እስከ ሆነ ድረስ ቤቱ የወ/ሮ የሺንርኤ ሐብት ሆኖአል ማለት በመሆኑ የውርስ ማጣራቱ ሂደትም የኸው የወ/ሮ የሺንርኤ ውርስ የሚመለከት ነው የሚሆነው፡፡ ውርሱን እንዲያጣራ የተሾመው ውርስ አጣሪ የወ/ሮ የሺንርኤ ልጆች 8(ስምንት) እንደሆኑ በማረጋገጥ ንብረቱ ለ8ቱ በማካፈል አመልካች ሞግዚት የሆነችለት ህፃን ሄኖክ ዳንኤል ድርሻ 1/8ኛ እንደሆነ በመግለጽ በአንድ በኩል ሲያቀርብ በሌላ በኩል ደግሞ የእማሆይ ምጽላል 8 ልጆችም የውርሱ ተካፋይ እንደሆኑ በመቁጠር የህፃን ሄኖክ ድርሻ 1/56ኛ ነው የሚል ሁለተኛ አማራጭ አቅርቦአል፡፡ በግልጽ እንደሚታየው የሁለተኛው አማራጭ መነሻ ቤቱ የእማሆይ ምጽላል ሐብት ነው የሚለው ነው፡፡ ይህ የሆነው ግን የስጦታ ውሉን በተሳሳተ ሁኔታ በመተርጐም በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሁለተኛውን አማራጭ በመቀበል የውርስ ክፍፍሉ እንዲከናወን መወሰኑ ትክክል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን የወ/ሮ የሺንርኤ ልጆች (ወራሾች) 8 (ስምንት) መሆናቸው በውርስ አጣሪው የተረጋገጠ በመሆኑ ውርሱ የሚከፋፈለው ለስምንቱ ወራሾች እንጂ አመልካች እንደምትለው ለህፃን ሄኖክ አባት እና ለሦስቱ ተጠሪዎች ብቻ አይደለም፡፡ በዚህ ስሌትም የውርስ አጣሪው ባቀረበው ሪፖርት አንደኛው አማራጭ መሰረት የህፃን ሄኖክ ዳንኤል ድርሻ ከቤቱ 1/8ኛ (አንድ ስምንተኛ) ይሆናል፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች ለስጦታ ውሉ የሰጡት ትርጓሚ የተሳሳተ በመሆኑ ታርሞ የውርስ ክፍፍሉ መደረግ ያለበት ቤቱ የሟች ወ/ሮ የሺንርኤ ሐብት እንደሆነ በመቁጠር ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04749 የካቲት 14 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 54613 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ሞግዚትና አስተዳዳሪ የሆነችለት የህፃን ሄኖክ ዳንኤል ድርሻ የቤቱ 1/8ኛ (አንድ ስምንተኛ) ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47957

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሊ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡-1. አቶ ተፈሪ ሐጎስ

2. አቶ ዛፉወርቅ ሐጎስ } ወኪል አንደኛ አመልካች - ቀረቡ

3. ወ/ሮ ፃጌሃና ሐጎስ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋይ ገ/እግዚአብሔር - ጠ/መድህን መሐሪ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካwች ለምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት መቃወሚያ የእህታቸው ልጅ አቶ ሣምሶን ተስፋይ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን የሚቹ ወራሾች ተጠሪ ብቻ ሣይሆኑ አመልካwችም መሆናቸውን ተጠሪ ግን ለብቻቸው ውርስ አጣርተው በፍ/ቤት ማፀደቃቸውን ገልፀው ይኸው ሪፖርትና ሪፖርቱን መሠረት ተደርጎ ለተጠሪ የተሰጣቸው የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ጠይቀዋል፡፡ በተጨማሪም በሚች ስም የተመዘገበው ቤት ከእናት ወገን የመጣ በመሆኑ ሊወርሱ የሚገባቸው አመልካwች ብቻ መሆናቸው የሚች ገንዘብን በተመለከተ ከተጠሪ ጋር እኩል ሊካፈሉ እንደሚገባና በዚሁ መሠረት የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ለቀረበው መቃወሚያ በሰጡት መልስ ክርክር የተነሣበት ቤት የተሰራበትን ቦታ ወ/ሮ አመዘነች ከማዘጋጃ ቤት ተመርተው ለልጃቸው ለወ/ሮ አበበች ሐጎስ በስጦታ ሰጥተዋቸው ወ/ሮ አበበች ቤት እንደሰሩበት አመልካwች ቦታው የእናታችን ነው በሚል ክስ አቅርበው ተጠሪ ልጃቸውን ወክለው ተከራክረው ቦታው የወ/ሮ አበበች ነው ተብሎ መወሰኑን ቦታው በምሪት የተገኘ እንጂ በውርስ የተላለፈ ርስት ባለመሆኑ የቤተሰብ ንብረት ነው ሊባል እንደማይቻል ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ርስት የሚለው ቃል መሬት የግለሰብ እያለ መሸጥ መለወጥ በሚቻልበት ጊዜ የመጣ ሆኖ በአንድ ወገን ዘር ሐረግ የመጣ ቅርስ መሠረት በማድረግ ነው በተያዘው ጉዳይ የሚች እናት ቦታውን በስጦታ ካገኙ በኋላ ንብረት ያሰፈሩበት ስለሆነ የአንድ ወገን ዘር ሐረግ ነው ሊባል አይችልም፣ የሚች የአቶ ሳምሶን ተስፋይ ብቸኛ ወራሽ ተጠሪ ብቻ ናቸው የሚቹ እናት ሚችን ሣይወርሱ ስለሞቱ አመልካwች እህታቸውን ተክተው ሊወርሱ አይችሉም በማለት የአመልካwች ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካwች ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤትና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡ የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካwች በአቤቱታቸው ወ/ሮ አመዘነች ለሚች እናት በስጦታ የሰጡት ቤት የነበረበት ቦታ ነው ስለሆነ ከእናት ወገን የተገኘ ንብረት ለእናት ወገን ሊሰጥ ይገባል፣ ቤቱን የሰሩት የሚች እናት ናቸው ቢባል እንኳን እህታቸውን ተክተው ሊወርሱ ስለሚችሉ ውርሱ ለተጠሪ ብቻ መተላለፉ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የሚች ገንዘብ በሙሉ ተጠሪ እንዲወርሱ እና ከእናት ወገን የመጣ የማይንቀሣቀስ ንብረት /ቤት/ ለሚች አባት ይገባል በሚል የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርቧል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪ የልጃቸውን ውርስ አጣርተው በፍ/ቤት በማፀደቃቸው አመልካwች ተቀዋሚ ሆነው ቀርበዋል፡፡ አመልካwች መቃወሚያ ያቀረቡት የሚች አቶ ሳምሶን ተስፋይ እናት የአመልካwች እህት በመሆናቸው የሚችን ውርስ እህታቸውን በመተካት የመውረስ መብት ያላቸው መሆኑን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ስለ ተተኪ ወራሽነት በፍ/ሕጉ ውስጥ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842/3/ ስር እንደተመለከተው የሚች ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሲሆኑ ልጆች ቀድመው ከሞቱና ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ትተው ከሆነ ተወላጆቹ ወላጆቻቸውን ተክተው ሚችን እንደሚወርሱ ያመለክታል፡፡ ሚች ልጆች የሌሉት ከሆነ እናትና አባት ሁለተኛ ደረጃ ወራሾች እንደሚሆኑና አባት ወይም እናት ቀድመው ከሞቱም የእነሱን ፋንታ ልጆቻቸው ወይም ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች እነሱን ተክተው እንደሚወርሱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 843/ 844/2 ተመልክቷል፡፡ በአባት ወይም በእናት በኩል ወደታች የሚቆጠር ከሌለ ውርሱ በሙሉ ለሌላው መስመር ላለ ወራሽ እንደሚተላለፍ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 844/3 ያመለክታል፡፡ ከፍ ሲሉ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የተተኪ ወራሽነት የተፈፃሚነት ወሰን ወደታች በሚቆጠሩ ተወላጆች እንጂ ወደ ጎን በሚቆጠር ዝምድና እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካwች የሚች እናት ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ሣይሆኑ ወደጎን የሚቆጠሩ ዘመዶች ወይም እህቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ከጅምሩም ቢሆን የሚችን እናት ተክተው ወራሽ ለመሆን የሚያስችላቸው መብት አልነበራቸውም፡፡ የሚች እናት ትተው የሄዱት ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ስለሌላቸው ውርሱ ሊተላለፍ የሚችለው ለሌላኛው መስመር ወራሽ በዚህ ጉዳይ ለሚች ወላጅ አባት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካwች እህታቸውን ተክተው መውረስ ስለማይችሉ ቀድሞውንም ቢሆን ተቃውሞ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት አልነበራቸውም፡፡ በዚህም ምክንያት የሚች እናት የተረከቡት ባዶ ቦታ ሣይሆን ቤት የተሰራበት ቦታ ነው የሚለው ክርክርም ሆነ የሚችን ገንዘብ ለመካፈል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የሚች አቶ ሳምሶን ተስፋይ ውርስ በሙሉ ለተጠሪ ሊተላለፍ ይገባል በማለት በሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የምዕራባዊ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር ባልተጠቀሰ ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 7370 መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 30799 ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸው ይቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42346

የካቲት 9 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- 1. አቶ ፍስሐ መንግስቱ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ አበባ አርአያ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አለምነሽ ፍስሐ - ቀረቡ ከጠ/ሰለሞን ተፈራ ጋር

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የስጦታ ውልን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት አመልካቾች ሲሆኑ በክሳቸውም ልጃቸው ተጠሪ እንዲጦሯቸውና እንዲንከባከቧቸው ግዴታ በማስገባት በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 03/04 ክልል ውስጥ ቁጥር 1561 የሆነ ቤታቸውን በስጦታ የሰጧቸው ሲሆን የተጣለባቸውን ግዴታ ስላልተወጡ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በመልሳቸው የስጦታ ይፍረስልን ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው፣ቤቱ በስሜ ተዛውሯል፣በመሐከላችን ምንም አይነት የስጋ ዝምድና የለም፣የገባሁት ግዴታም የለም በነፃ ፈቃዳቸው ያደረጉት ውል ስለሆነ ሊፈረስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ በውሉ ላይ አመልካቾችን ለመጦርና ለመቀለብ የገቡት ግዴታ ስለሌለ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካቾች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ተጠሪዎችን ሳይጠራ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች በቅሬታቸው ላይ ለተጠሪ ስጦታ የሰጡት ተጠሪዋ አመልካቾችን ለመጦርና ለመንከባከብ እንዲሁ ሌላ ቤት ገዝታ ለመስጠት ግዴታ በመግባቷና ይህንን ግዴታ ባለመወጣቷ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ብለዋል፡፡ ችሎቱም ተጠሪዋ አመልካቾችን ለመንከባከብና ለመጦር ግዴታ ስላልገቡ ውሉ ሊፈረስ አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካቾች ለስር ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡት የስጦታ ውል እንዲፈርስላቸው ነው፡፡ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቁበት ምክንያት ተጠሪ አመልካቾችን ለመንከባከብና ለመጦር የገቡትን ግዴታ ባለመወጣታቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ተጠሪ ስጦታ የተሰጣቸው መሆኑን አምነው ነገር ግን በውሉ ላይ የገቡት ምንም አይነት ግዴታ እንደሌለ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ተጠሪ አመልካቾችን ለመንከባከብና ለመጦር ግዴታ አልገቡም በሚል ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት ተጠሪ በስጦታ ውሉ ላይ አመልካቾችን ለመርዳት ግዴታ የገቡ መሆኑን እና የስጦታ ውሉ ሊፈርስ የሚገባበት የሕግ ምክንያት መኖር አለመኖሩን መመርመር ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ለዚህ ይረዳው ዘንድ አመልካቾች ለተጠሪ ስጦታ ያደረጉበትን ውል ተመልክቷል፡፡ ጥር 12 ቀን 1991 ዓ.ም የተደረገው የስጦታ ውል በከፊል

"ስጦታ ሰጪዎች ባልና ሚስት ሰንሆን በአ/አበባ ክተማ በወረዳ 12 ቀበሌ 11 የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥር 37655 የሆነውን ቤታችን ለወለድናት ልጃችን ወደፊትም ለምትጦረንና ለምትንከባከበን ጧሪ ቀባሪያችን ለሆነችው ልጃችን በፈለገችው አይነት እንድትጠቀምበት ይህንን ከላይ የተጠቀሰውን ቤታችንን በፍ/ሕ/ቁ. 2427 መሰረት በስጦታ የሰጠናት መሆናችንን በፊርማችን እናረጋግጣለን::" የሚል ነው::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህም የስጦታ ውል ይዘት "... ወደፊትም ለምትጦረንና ለምትንከባከበን ሚሪ ቀባሪያችን..." የሚለው ሐረግ አመልካቾች ለተጠሪዋ ስጦታ ያደረጉበት ምክንያት ተጠሪዋ ወደፊት እንድትንከባከባቸው እና እንድትጦራቸው መሆኑን ማየት የሚቻል ነው። በእርግጥ በኑዛዜው ላይ ተጠሪዋ አመልካቾችን የመንከባከብና የመጦር ግዴታ ገብታለች በሚል ግልጽ አማርኛ አልተቀመጠም። ነገር ግን ውል ሲተረጐም የቅንነትና የመተማመን ግንኙነትን መሰረት በማድረግና በቅን ልቦና ሊሆን እንደሚገባው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732 መገንዘብ ይቻላል። በተያዘውም ጉዳይ አመልካቾች ቤታቸውን ለተጠሪ ሲሰጡ ወደፊት ከልጃቸው እርዳታና እንክብካቤ የሚያገኙ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ለመሆኑ የውሉ ይዘት ያሳያል። በእርግጥ ተጠሪ ከአመልካቾች ጋር ምንም አይነት የስጋ ዝምድና የለችም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም በስጦታ ውሉ ላይ አመልካቾች የተጠሪ ወላጆች መሆናቸው ተጠቅሶ የተቀመጠውን ተጠሪዋም አምነው ስጦታውን መቀበላቸውን ከመዝገቡ ተመልክተናል። በመሆኑም አመልካቾች ለተጠሪ ቤታቸውን የሰጡት ተጠሪ ልጃቸው በመሆናቸውና ወደፊትም እንድትንከባከባቸውና እንድትረዳቸው ግዴታ በማስገባት መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል።

እንግዲህ ተጠሪ አመልካቾችን ለመርዳትና ለመንከባከብ ግዴታ ገብተዋል ከተባለ ይህንን ግዴታቸውን ተወጥተዋል ወይ? የሚለው በመቀጠል ሊታይ ይገባል።። አመልካቾች ተጠሪ ይህንን ግዴታ አልተወጡም በማለት ሲከራከሩ ተጠሪ ግዴታ አልገባሁም ከማለት በቀር አመልካቾችን እየረዱና እየተንከባከቡ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም። ለዚህም ለሰበር ችሎት በሰጡት መልስ የሚከራከሩት አመልካቾች የጡረታ አበልና በኮንትራት እየተቀጠሩ ገቢ የሚያገኙና እርዳታ የማያሻቸው መሆኑን እንጂ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ስለመወጣታቸው በማስተባበል ያቀረቡት ክርክር የለም። ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ በግልጽ ክዶ ካልተከራከረ ወይም በመሸሽ መልስ ከሰጠ ክሱን እንዳመነ እንደሚቆጠር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 235/2/ ያመለክታል። በመሆኑም ተጠሪ በውሉ የተመለከተውን ግዴታቸውን ስላለመወጣቸው በአመልካቾች የተነገረውን በግልጽ ክደው ስላልተከራከሩ እዳመኑ ሊቆጠር ይገባል።

ስጦታ ገደብ ያለበት ወይም ግዴታ የተጣለበት ሊሆን እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2452/1/ ስር ተመልክቷል። ስጦታ ሰጪውም ተቀባዩ ግዴታውን ባለመፈፀሙ ምክንያት ስጦታው እንዲፈርስለት ለመጠየቅ እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2464/1/ ያስገነዝባል። በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ አመልካቾች ለመርዳትና ለመንከባከብ ግዴታ የገቡ በመሆኑና ግዴታቸው ባለመወጣታቸው አመልካቾች ውሉ እንዲፈረስ ለመጠየቅ መብት አላቸው። ተጠሪ የአመልካቾች የስጦታ ይፍረስልን ጥያቄ በይርጋ ይታገደል በማለት ተከራክረዋል። በእርግጥ በመንፈስ መጫን የተደረገ ስጦታ ስጦታው ከተደረገ ጊዜ አንስቶ በሁለት አመት ውስጥ ለዳኞች ካልቀረበ ዋጋ እንደሌለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441/1/ ያመለክታል። በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ውሉን ሲያደርጉ የመንፈስ መጫን ነበር በማለት ይግለፁ እንጂ ስጦታው እንዲፈርስ በዋናነት የጠየቁት ተጠሪ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን እልተወጡም በሚል በመሆኑ ይህ የይርጋ ድንጋጌ አግባብነት የለውም። ስለሆነም ተጠሪዋ በስጦታ ውሉ ላይ የተመለከተውን ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ውሉ ሊፈርስ ይገባል። የውል መፍረስ ውጤቱም ተዋዋዮች ወደነበሩበት ቦታ መመለስ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 ስር ስለተመለከተ አመልካቾችና ተጠሪም በዚሁም መሰረት ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ ይገባል። በአጠቃላይ ውሉ እንዲፈርስ ሊወሰን ሲገባ የስር ፍ/ቤቶች ስጦታው ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24359 መስከረም 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 72830 ጎንደር 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በስጦታ ውሉ ላይ የተመለከተውን ግዴታቻውን ስላልተወጡ ስጦታው ፈራሽ ነው ብለናል፡፡
3. የስጦታ ውሉ በመፍረሱ ምክንያት ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሊመለሱ ስለሚገባ ተጠሪ ከአመልካቾች በስጦታ ያገኙትን ቤት ለአመልካቾች መልሰው ያስረክቡ ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሚስስ ፍራንሱዊስ ፖስተር - ጠበቃ ፈቃዱ ሞላ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. ሚ/ር ዱክማን ቬኖ
2. ሚ/ስ ባርቦት ለቲቲያ } በሌሉበት የሚታይ ነው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዲፈቻ ስምምነት የሚፈርስበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክር የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብርሃነ ሕይወት የሕጻናት እና ቤተሰብ መርጃ ድርጅት የተባለው ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በመሰረተው ክሰ መነሻ ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለውም የአሁኑ ተጠሪዎች ሕፃን ቱሉን በጉዲፈቻ ለመውሰድ በመጠየቃቸው የአሁኑ አመልካች በኃላፊነት የሚመሩት ድርጅት ሕፃኑን በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከነበረው ብርሃነ ሕይወት የሕፃናትና ቤተሰብ መርጃ ድርጅት ተቀብሎ የፍርድ ቤት ስርዓቱን በማከናወን ላይ እያለ ተጠሪዎች ሕጻኑን የመውሰድ ሃሳባቸውን በመቀየራቸው የጉዲፈቻ ስምምነት እንዳይጸድቅ ከውሳኔ በፊት ግልጽ ደብዳቤ በመጻፍ ቢያሳውቁም ይህ ደብዳቤ በወቅቱ ለፍርድ ቤቱ ባለመድረሱ የጉዲፈቻ ስምምነቱ መጽደቁን ለተጠሪዎች ፍርድ ቤቱ የወሰነ ስለመሆኑ የነገራቸው ቢሆንም ሕጻኑን ላለመውሰድ በወሰዱት ውሣኔ በመጽናታቸው ሕፃን ቱሉ የአሁኑ አመልካች በሚያስተዳድሩት ድርጅት ጊዜያዊ ማቆያ ውስጥ ለመቆየት በመገደዱ ማቆያው ለወደፊት የጉዲፈቻ ወላጅ የሆኑትን የአሁኑን ተጠሪዎች ድርጊት የሕፃኑን የወደፊት ሕይወት እና እድገት በከፍተኛ ሁኔታ የሚያሰጋ በመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት እንዲሰረዝ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ ማቅረቡን፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪዎች አድራጐት የሕፃኑን ሕይወት በአደጋ ላይ የሚጥል ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት ሳይቀበለው መቅረቱን ነው፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በይግባኝ በነበረው የክርክሩ ሂደት የተጠሪዎች ወኪል ቀርበው የጉዲፈቻ ውሉ ቢፈርስ ተቋውሞ የለኝም እያሉ ፍርድ ቤቱ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ ለተጠሪዎች በጋዜጣ ጥሪ ቢደረግላቸውም የቃል ክርክሩ በሚሰማበት ወቅት ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጎአል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዲፈቻ ስምምነት ከፀደቀ በኋላ በማናቸውም ምክንያት ሊፈርስ የማይችል ስለመሆኑ በፀንሰ ሃሳብ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 195(1) የሚያሳይ ቢሆንም የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የጉዲፈቻ ስምምነት የሚፈርስባቸውን ምክንያቶችን ደንግጓል። የዚህ ድንጋጌ መንፈስ ሲታይም በጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን በዓለም አቀፍ የሕጻናት እና ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በሚፃረርና የልጁን ጥቅምና ደህንነት በሚጎዳ አኳኋን መያዙን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንዲቀጥል ማድረግ የሚያስገኘው ፋይዳ ባለመኖሩ ጉዳዩን በሚመለከተው ማንኛውም አመልካች ጠያቂነት መሰረዝ እንደሚቻል ታመኖበት ድንጋጌው መቀመጡን የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ሐተታ ምክንያት ያስገነዝባል።

ሕጉ ጉዲፈቻ በሚወሰዱት ልጆች ላይ በተጨባጭ እና በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ማገናዘብ የሚጠበቅበት በመሆኑ የድንጋጌው መካተት የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት ከመጠበቅ አኳያ ጠቀሜታው የጎላ ስለመሆኑም የሚታመን ነው። ድንጋጌው በአተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ ካልተደረገ የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲሰረዝ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው በልጁ አኗኗርና አያያዝ እንዲሁም በወደፊት ሕይወቱ ላይ በተጨባጭ የደረሰ ጉዳት ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳት ስለመኖሩ ማረጋገጥ በሚቻልበት ጊዜ ይሆናል ፍርድ ቤቱም የስምምነቱ መሰረዝ የሚያስገኘው ጠቀሜታ በሚገባ ማጤንና መመዘን የሚጠበቅበት ስለመሆኑ የሕግ መንፈስና ይዘት ያሳያል

በመሠረቱ ጉዲፈቻ በሕግ ጥበቃ የሚያስፈልገው በዋናነት የልጁን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል ነው። የሕፃናትና ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል የተለያዩ ስምምነቶች በዓለምና በአህጉር ደረጃ ተፈርመው በስራ ላይ /እየተተገበሩ/ ይገኛሉ። ከስምምነቶች ውስጥም የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽንና የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ተጠቃሾች ናቸው። ሐገራችን ኢትዮጵያም የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽንን ህዳር 29 ቀን 1984 ዓ.ም የአፍሪካ ሕጻናት መብቶችና ደህንነት ቻርተርን ደግሞ እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 02 ቀን 2002 አጽድቃለች። ከእነዚህም በተጨማሪ የሕጻናትን መብትንና ደህንነትን በሚመለከት የፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ እና ሌሎች ሕጐች በስራ ላይ ይገኛሉ። በዓለም አቀፍም በአህጉርም ሆነ በአገር ደረጃ ያሉት እነዚህ ሕጐች መሠታዊ መርሆዎችን ይዘዋል። በእነዚህ ሕጐች ከተካተቱት መሠረታዊ መርሆዎች አንዱ ሕጻናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ለሕጻናት ጥቅምና ደህንነት (The Best interest of the child) ቅድሚያ መስጠት የሚለው መርህ ይገኝበታል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት ኢትዮድያ ያፀደቀቻቸውን የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የአገሪቱ የሕግ አካል መሆናቸውን በአንቀጽ 9(4) ስር ከመደንገጉና በሕገ-መንግሥቱ በስፋት ሸፋን የተሰጣቸው መሠረታዊ የመብቶችና የነጻነቶች ድንጋጌዎች ሀገሪቱን ከተቀበለቻቸውና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት ስምምነቶች ወይም ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጐም ያለበት ስለመሆኑ ከማስቀመጡም በተጨማሪ የሕጻናትን ልዩ ችግር ከግምት ውስጥ ያስገቡ ንዑስ ድንጋጌዎች የያዘ አንቀጽ 36 ደንግጓል። የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ ሁሉ የመንግስታዊ ወይም የበጐ አድራጐት ተቋማት እንዲሁም ፍርድ ቤቶችንና አስተዳደር ባለስልጣናት ወይም የሕግ አውጪው አካላት የሕጻናትን ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ ያለበት ስለመሆኑ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ደንግጓል። ይህንኑ የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌ ለማስፈፀም የወጡ ፖሊሲዎች ወይም ሕጐችም መንፈሳቸው ሲታይ ለሕፃናት መብትና ደህንነት በተገቢው ሁኔታ የማስከበር ዓላማን ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ናቸው ተብሎ ይታሰባል።

ጉዲፈቻ ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች ተብለው በሕገ-መንግሥቱ ከተጠቀሱት ነገሮች አንዱ መሆኑ የሚያከራክር ነጥብ ካለመሆኑም በላይ ሕገ- መንግሥቱ በአንቀጽ 36(5) ስር መንግሥት ለእንለማውታን ልዩ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ስርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰርቱ እንደሚያበረታታ በግልጽ አስቀምጧል። ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው የጉዲፈቻ ጉዳይ ከሕገ-መንግሥቱ ከተቀመጠው መርህ ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን እንዲሁም ከተሻሻለው የፌዴራሉ ቤተሰብ ሕግና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ሰነዶች ይዘትና መንፈስ በጥንቃቄ መታየት ያለበት መሆኑን ነው። ይህ ችሎት አግባብነት ያላቸውን ሕጐች በመመርመርም የሕፃናት መብትና ጥቅም ለማስከበር በቀደምትነት ሊታይ የሚገባው መርህ የሕፃናት ጥቅምና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደህንነት (the best interest of the child) ስለመሆኑ በመ/ቁጥር 23632፣35710 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት አስገዳጅነት ያለውን ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ሕጐች ይዘታቸው ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሕፃን ቱሉ ከተጠሪዎች ጋር የተደረገለት የጉዲፈቻ ውል እንዲፈርስ ጥያቄ ያቀረቡት ተጠሪዎች ሕፃኑን ላለመውሰድ በመግለጻቸውና በውሳኔያቸውም በመጽናታቸው ሕፃን ቱሉ አመልካች በሚያስተዳድሩት ጊዜያዊ ማቆያ ውስጥ ለመቆየት ግድ ያለ መሆኑን ማቆያውም ለሕፃኑ ሕይወቱ የሚያስፈልጉትን ነገሮችን ያሟላ ባለመሆኑና ለሌላ ወላጅ ለመስጠት ባለመቻሉ በሕፃኑ የወደፊት እድገት የተጠሪዎች አድራጐት ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ሕፃን ቱሉን ላለመውሰድ በወሰዱት ውሳኔ መጽናታቸውን አረጋጋጠው የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበሉት የቀሩት ተጠሪዎች ሕፃኑን ካለመውሰድ የወሰኑት ውሳኔ ሕፃኑ አሳስደሰተንም፣ ህጻኑን ለመውሰድ ፍላጐት አሳሰደሩም፣ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 195(2) ስር የተመለከቱት ምክንያቶች አልተሟሉም በሚል ምክንያት ሆኖ በሌላ ምክንያት የተደገፈ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ነው፡፡

ከፍ ብለን እንደተመለከትነው በጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን በዓለም አቀፍ የሕፃናት እና ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በሚፃረርና የልጁን ጥቅምና ደህንነት በሚጐዳ አኳኋን መያዙን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንዲቀጥል ማድረግ የሚያስገኘው ፋይዳ ባለመኖሩ ጉዳዩን በሚመለከተው ማንኛውም አመልካች ጠያቂነት መሰረዝ እንደሚቻል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 195 እና 196 ተደንግጓል፡፡ አንቀጽ 195(2) በተለይ ሲታይም ጉዲፈቻ አድራጊው በጉዲፈቻ የተቀበለውን ልጅ እንደልጅ ከማሳደግ ፋንታ በባርነት ወይም በባርነት በሚመስል ሁኔታ ወይም ከግብረ ገብ ውጪ በሆኑ ተግባሮች እንዲሰማራ በማድረግ መጠቀሚያ ያደረገው እንደሆነ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጎዳ አኳኋን የያዘው መሆኑን (ሰረዝ የተጨመረ) የተረዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለመሰረዝ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ሕጻን ቱሉ ያለበት ሁኔታ ሲታይ እና ተጠሪዎች ሕፃኑን ለመውሰድ ፍቃደኛ ለመሆን ያለመቻላቸው እንዲሁም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር የተጠሪዎች ወኪል ቀርበው “ልጁን አንደማንወስድ የጉዲፈቻ ውሉ ከመጽደቁ በፊት የገለጽን በመሆኑ ልጁን ለመውሰድ አንገደድም የጉዲፈቻ ስምምነቱ ቢፈርስ አንቃወምም” በማለት መከራከራቸው ሲታይ በሕፃኑ የወደፊት ሕይወት ችግር አያስከትልም ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ክርክር ከሕጉ መንፈስ ጋር ባግባቡ ሳያገናዝቡ የጉዲፈቻ ስምምነት ሊፈርስ አይገባም በማለት መወሰናቸው የሕፃኑን እድገት የሚጐዳ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፈርድ ቤት በመ/ቁጥር 111497 ሕዳር 05 ቀን 2001 እና ታህሳስ 04 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75193 የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ሕፃን ቱሉን ለመውሰድ የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ያደጉት እና መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በፍርድ ቤት የፀደቀ የጉዲፈቻ ስምምነት ውል ፈራሽ ነው ብለናል፡፡ ይህንኑ አውቀው ተገቢውን እንዲፈጽሙ ለስር ፍርድ ቤቶች ይፃፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 46527

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሃይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አለማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ገነት በቀለ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ትዕግስት አሰፋ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በአድአ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በሁለት ግለሰቦች ላይ በመሰረቱት ክስ ተከሳሾች ሞግዚት ለሆኑላቸው ልጃቸው በውርስ ከአባታቸው ሊተላለፍላቸው የሚገባውን ቤት ስለያዙ እንዲመልሱላቸው ጠይቀው ፍ/ቤቱ ተከሳሾቹ ቤቱን እንዲመልሱ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሰረት መቃወሚያ በማቅረብ ቤቱን ከስር ተከሳሾች ገዝተው የባለቤትነት ስሙ በስማቸው ያዛወሩ በመሆኑ ውሳኔው እንዲሰረዝላቸው አመልክተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ሁሉንም ወገኖች አስቀርቦ ክርክራቸውን ከሰማ በኋላ ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ የሚሰረዝበት ምክንያት የለም በማለት ተጠሪን መቃወሚያ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ በምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ተጠሪን ቤቱን ያገኙት በህጋዊ መንገድ ገዝተው በመሆኑ ሊያስረክቡ አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቀጥሎም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም ቅሬታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን ቅሬታው በአጭሩ ተጠሪ ቤቱን የገዙት መብት ከሌላቸው ሰዎች በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች ክስ ያቀረቡት ከአባታቸው በውርስ ሊተላለፍላቸው የሚገባውን ንብረት ለመረከብ ሲሆን ክስ የመሰረቱት ወራሽ ነን በሚሉ ግለሰቦች ላይ ነው፡፡ ከመዝገቡ የስር ተከሳሾች ክርክር የተነሳበትን ቤት የባለቤትነት ስም በስማቸው በማዛወር በ1993 ዓ.ም ቤቱን ለተጠሪ መሸጣቸውን ተረድተናል፡፡ የስር ተከሳሾች ቤቱን በሚሸጡበት ወቅት የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በስማቸው አግኝተው የቤቱ ባለቤት ሆነዋል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195 የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት በተሰጠ ጊዜ ምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለንብረት ሆኖ እንደሚቆጠር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሽያጩ በተከናወነበት ጊዜ ቤቱ የሻጮቹ የግል ንብረት ሲሆን ተጠሪም ቤቱን የገዙት የሻጮቹን የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በማየት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቤቱም ሽያጭ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት መደረጉንና ስሙም ወደ ገዢዋ መዛወሩን መገንዘብ ችለናል፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ ቤቱን በገዙበት ወቅት ቤቱ በሻጮች ስም የነበረ በመሆኑ ሽያጩን ህጉ በሚጠይቀው የአፃፃፍ ስርዓት መሰረት ማከናወናቸው ተጠሪዋ ቤቱን የገዙት በቅን ልቦና መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ምናልባት አመልካች በንብረቱ ላይ ድርሻ አለን የሚሉ ከሆነ ስር ተከሳሾችን ከሚጠይቁ በቀር ተጠሪ በህጋዊ መንገድ የገዙትን ቤት እንዲያስረክቡ የሚደረግበት የህግ አግባብ ስለሌለ ውሳኔው መሰረታዊ ህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15094 መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 65463 ጥር 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 74733 መጋቢት 09 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47378

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ዓለማየሁ ከተማ - ጠበቃ ኃይለማሪያም ኢትቻ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ላቀች አይተንፍሱ - ቀረቡ

2. አቶ ደምሴ ወርቅአፈስኩ - ወራሾች ቀረቡ

3. ወ/ሮ እቴነሽ ኃ/ስላሴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጋራ ውርስ ሃብት ሽያጭ ውል ይፍረስ ጥያቄን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች እና በወ/ሮ አበበች ጫካ ላይ ሕዳር 27 ቀን 1999 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው አጠራር ወረዳ 13 ቀበሌ 21 በአሁኑ አጠራር የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 266/2/ የሆነውን ቤትና ይዞታ ከእናታቸው ከወ/ሮ ጥሩነሽ ወልደየስ ከወ/ሮ አበበች ጫካ ጋር በውርስ የተላለፈላቸው መሆኑን፣ቤቱ ለሰባት ወራሾች ለማከፋፈል አመቺ ካለመሆኑ በላይ ከእናታቸው መታሰቢያነት እንዲሆንና ወራሾችንም በቤቱ ላይ ለመገናኘት ይችሉ ዘንድ ከሚሸጥ ይልቅ ቤት ያልነበራት ወ/ሮ አበበች ቤቱ ውስጥ እንድትኖርበትና ማንኛውም ወራሽ በቤቱ መኖር ከፈለገ መኖር እንደሚችል በቤተ ዘመድ ጉባኤ ውሳኔ መሰጠቱን፣ይህ ሆኖ እያለ ወ/ሮ አበበች ጫካ የሚች ወ/ሮ ጥሩነሽ ወልደየስ ብቸኛ ወራሽ በማስመሰል የወራሽነት ማስረጃ አውጥተው ቤቱን በስሟ ካዛወረች በኋላ ቤቱን ለአሁኑ አመልካች በብር 450,000(አራት መቶ አምሳ ሺህ ብር) በመሸጥ ስመ ሐብቱ ሁሉ በገዥው ስም እንዲዛወር ማድረጓን በመግለጽ በውርስ ንብረታችን ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሰጡት መልስ፡- የሽያጭ ውል ይፍረስልን ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ሽያጩን በሕጉ አግባብ ያደረጉት በመሆኑ ሊፈርስ እንደማይገባ ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ቤቱ የውርስ ሃብት መሆኑን በማረጋገጥ እና ቤቱ የተሸጠው ከሁሉ ወራሾች ፈቃድ ውጪ በመሆኑ ሽያጩ በሕግ ፊት ሊፀና የሚችልበት ምክንያት አለመኖሩን በመግለጽ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ፣አመልካች የሽያጭ ገንዘቡን ብር 270,000(ሁለት መቶ ሰባ ሺህ ብር) ከወ/ሮ አበበች ወልደየስ እንዲቀበሉ፣ቤቱን አመልካች ለወራሾች እንዲመልሱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች እጃቸው ውስጥ ያስገቡት ሕጋዊ በሆነ መንገድ መሆኑ በግልጽ ተረጋግጦ እያለ ሽያጩ ፈራሽ ነው መባሉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በስር አንደኛ ተከሳሽ በነበሩት በወ/ሮ አበበች ወልደየስ ስም ተመዝግቦ የሚታወቀውን አከራካሪውን ቤት ውል ማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት በመቅረብ አመልካች መግዛታቸው ተረጋግጦ እያለ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ አንደኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ፣የሁለተኛ ተጠሪ ወራሾች ደግሞ ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አምስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም ባጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የጋራ ውርስ ንብረት ላይ በተጭበረበረ መንገድ በውልና ማስረጃ የተደረገ የሽያጭ ውል ሕጋዊ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ስለሌለ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃም በተጠሪዎች መልስ ላይ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው ቤት ተጠሪዎች ከወ/ሮ አበበች ጫካ ጋር ከሚች ወ/ሮ ጥሩነሽ ወልደየስ በውርስ የተላለፈላቸው መሆኑን፣ይህንን ቤት በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ አበበች ጫካ ሲያስተዳድሩትና ሲጠቀሙት ቆይተው የቤቱን ስመ ሐብት ወደ ራሳቸው በማዞር ለአሁኑ አመልካች በውልና ማስረጃ ፊት በተደረገ የሽያጭ ውል በብር 450,000(አራት መቶ ሃምሳ ሺህ) መሸጣቸውን፣ከዚህም በኋላ አመልካች የስመ ሃብቱን ወደ ራሳቸው አዙረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ የተጠሪዎች ክርክር መሰረቱም የወራሾች የጋራ የሆነው ንብረት የሁሉም የጋራ ባሃብቶች ስምምነት ሊኖር ሲገባ ወ/ሮ አበበች ጫካ በተጭበረበረ መንገድ ወራሽነት አሳውጀው እና የቤቱን ስመ-ሃብት በማዞር መሸጣቸውን ሽያጩን ሕጋዊ አያደርገውም በሚል ምክንያት ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡ እኛም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከሕጉ ጋር በሚከተለው መልኩ በማዛመድ ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ የውርስ ሃብት አከፋፈሉ እስኪፈፀም ድረስ በወራሾቹ መካከል ሳይነጣጠል እንደሚቆይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1060/1/ ስር የተመለከተ ሲሆን የጋራ የሆነውን ንብረት ለመሸጥ፣ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለሃብቶቹ ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1266 ድንጋጌ ያሳያል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የስር አንደኛ ተከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ አበበች ጫካ አከራካሪውን ቤት የሸጡት የተጠሪዎችን ስምምነት አግኝተው ባይሆንም የቤቱን ስመ-ሐብት ከሽያጩ በፊት ከተገቢው የአስተዳደር አካል ከአገኙ በኋላ ሲሆን ሽያጩም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት ሆኖ ሊቆጠር እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይህን ማስረጃ የያዘ ሰው ደግሞ ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሸጠ ተግባሩ ሕገ ወጥ የሚባልበት ምክንያት የለውም፡፡ አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገዶች ለሌላ ለማስተላለፍ መብት አለውና፡፡ በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ አበበች ጫካ አከራካሪውን ቤት በስማቸው የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት መያዛቸው ንብረቱ የግል ሃብት እንደሆነ የሚያስቆጥር ሲሆን ይህን ማስረጃ በመመልከት ንብረቱን ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የሚገዛ ሰው ሽያጩን ያከናወነው ከሕግ ውጪ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በቤቱ ላይ ሕጋዊ መብት የሌለው ሰው ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሃብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገዥ ሳይሆን ሻጩን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 997፣እና 2882 እስከ 2884 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መንፈስ እና ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በአጠቃላይ አመልካች አከራካሪውን ቤት የገዙት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ከያዙት ግለሰብ ሆኖ ሽያጩንም ያከናወኑት ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ የጋራ ወራሽነት መብት ያላቸው መሆኑ የተረጋገጠ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሆን ያላቸው መፍትሄ የሽያጩን ዋጋ ከስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከነበሩት ከወ/ሮ አበበች ጫካ መቀበል ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33368 ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 81698 ሰኔ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በአከራካሪው ቤት ላይ የተደረገው ሽያጭ ውል ሊፈረስ አይገባም፣አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡

3. ተጠሪዎች በቤቱ ላይ ባላቸው ድርሻ መሰረት የሽያጩን ገንዘብ ከወ/ሮ አበበች ጫካ በሌላ ክስ የመቀበል መብታቸውን ይህ ውሣኔ አያስቀርም ብለናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42482

የካቲት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ፍሬዘውድ ተካ ጐጂ - ቀረቡ

ወ/ሮ ትርሲት ተካ ጐጂ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ሰለሞን ኃ/ማሪያም - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ንብረት የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ የክሱ ምክንያትም ከአያታቸው በኑዛዜ የተላለፈላቸውን የቤት ቁ. 1133 በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ቀበሌ 03 ክልል የሚገኝ ቤት ተጠሪ አላአግባብ ይዞ እየተጠቀመ በመሆኑ እንዲለቅ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ አመልካቾች በኑዛዜ ተሰጠን የሚሉት ቤት የተናዛዢ ባለመሆኑ ለመክሰስ መብት የላቸውም እንዲሁም ቤቱን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድም ቤቱን የሰሩት የእሱ አባት እና እናት መሆናቸውን እና ቤቱ በስጦታ ለእህቱ የተሰጠ ስለመሆኑ እሱም እህቱ በሰጠችው ውክልና ይዞ እየተጠቀመ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድ አመልካቾች ክስ ያቀረቡበት የቤት ቁ. 1133 የሚች ወ/ሮ ጌጤ ሸኔ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት አመልካቾች በተጠቀሰው ቤት ላይ ባለመብት ስለመሆናቸው አላረጋገጡም በሚል ክስ ለማቅረብ የላቸውም ሲል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ እና 244/2/መ በመመርኮዝ ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤት ፍርድን አጽንቷል፡፡ የአመልካቾች ጠበቃ ታህሣሥ 20/2001 ዓ.ም ጽፎ ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሚች ወ/ሮ ጌጤ ሸኔ ጥቅምት 24/1989 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በመ/ቁ. 265 ላይ መቃወሚያ ቀርቦ ተቀባይነት ሳያገኝ ኑዛዜው በፍርድ ቤት የፀደቀ ስለሆነ ይህንን ወደ ጐን በመተው የባለቤትነት ማስረጃ አልቀረበም በሚል የሥር ፍ/ቤት ክሱን ወድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንጂሻር እና እንደክሳቸው እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የአመልካቾች የኑዛዜ ወራሽነት በመ/ቁ. 265 ተረጋግጦ እያለ እና ቀደም ሲል የቀረበው መቃመሚያ ውድቅ ተደርጐ አመልካቾች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ ይህንኑ ቤት ለማስለቀቅ ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉ በግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪ መስከረም 15/2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ሲታይ ኑዛዜ ለማጽደቅ የቀረበው አቤቱታ ላይ ተከራካሪ የነበሩት ተጠሪ እና ወ/ሮ ጉዶ ጐጂ የነበሩ መሆኑንና ኑዛዜው መጽደቁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሐብቱ ላይ የሚቀርበውን ክርክር የሚያግድ ሊሆን እንደማይችል በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ ከመረመረ በኋላ ታህሣሥ 22/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቤቱ ያለበትን ይዞታ እና ቤቱ በማን እንደተሰራ ግራ ቀኙን በቃል በማነጋገር ጉዳዩን በማጣራት ግንዛቤ አግኝቷል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር እና የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን በዚሁም መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ምላሽ የሚሻው ነጥብ ኑዛዜ በፍ/ቤት በመጽደቁ አመልካቾች በንብረቱ ላይ ባለመብት መሆናቸውን ማረጋገጫ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ ኑዛዜ ሕጉ ያስቀመጠውን ሥርአት እና መስፈርቶች አሟልቶ ከተገኘ በራሱ በሕግ ረገድ ውጤት የሚሰጠው ሰነድ እንጂ በፍርድ ቤት ቀርቦ ማፀደቅ አስፈላጊ እንዳልሆነ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 17058 በተሰጠ ውሳኔ የተሰጠ የሕግ ትርጉም መረዳት ይቻላል ከዚህም አልፎ ኑዛዜው በፍ/ቤት ቀርቦ መጽደቅ ሌሎች ባለመብቶች ክርክር ወይም መቃመሚያ እንዳያቀርቡ ሊገድባቸው እንደማይችል በዚሁ ተጠቃሽ መዝገብ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ከዚህ አንፃር አመልካቾች በመ/ቁ. 265 ኑዛዜ ለፍ/ቤት ማፀደቃቸው በራሱ በኑዛዜ በተሰጠው ቤት ላይ ባለሐብት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ብቸኛ ማስረጃ አይደለም፡፡ ከዚህም ሌላ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ቤት የተናዛዢ ስለመሆኑም በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1195 በተደነገገው መሰረት ከአስተዳደር ክፍል የተሰጠ ማረጋገጫ አልቀረበም ይልቁንም ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ ለመረዳት እንደተቻለው የቤት ቁ. 1133 የሚች ወ/ሮ ጌጤ ሸኔ ስለመሆኑ ለማጣራት ሥር ፍ/ቤት ከክፍሉ አስተዳደር ማህደር አስቀርቦ እንደተመለከተ እና ቤቱ የሚች ስለመሆኑ አስረጅ ሰነድ እንዳልቀረበ ተገልጿል፡፡

ይህ በሆነበት ሁኔታ ደግሞ ኑዛዜ አጸድቀናል በሚል ምክንያት ብቻ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት ማጣቱ የሕግ ስህተት ነው ሊባል የሚቻልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቾችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሰጡት ምክንያትና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል ለማለት ስላልተቻለ ባለበት ሁኔታ አጽንተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09779 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 64033 የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45819

የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ካሳ ፋንታ - ጠበቃ ታደሰ መርእድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እስካዳር ግጨው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የልጅ ቀለብን በተመለከተ ለአከፋፈሉ ዋስትና ይሆን ዘንድ የአመልካች የግል መኪና ቀለብ ጠያቂዎቹ አስራ ስምንት ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ ተከብሮ እንዲቆይ የሚል ትእዛዝ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በመጽናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበውን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ትእዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው ታህሳስ 28 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ጥር 17 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ይህ ችሎት ግራ ቀኙን በቃል ሰምቷል፡፡ ጉዳዩንም አቤቱታው ከቀረበበት ትእዛዝ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች የቀለብ ጥያቄው የሚመለከታቸው መሆኑን ሳይክዱ የግል ንብረታቸው የሆነው ሕፃናቱ አስራ ስምንት ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ሊከበር አይገባም የሚሉት ለሌላ እዳ አከፋፈል መኪናውን ለመሸጥ ካሰቡ ችግር የሚፈጥር ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ችሎትም መኪናው ላይ የተላለፈው እግድ እንዲነሳላቸው ከፈለጉ ጥሬ ገንዘቡን ሙሉ በሙሉ በአደራ ሊያስቀምጡ የሚችሉበት መንገድ ካለ በችሎት የአመልካችን ጠበቃ ጠይቆ ከሶስት እስከ አራት ወራት ድረስ ያለውን የቀለብ ገንዘብ ካልሆነ ሕፃናቱ እስከ አስራ ስምንት ዓመት ድረስ ሊከፈላቸው የሚችለውን የቀለብ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ በአደራ ሊያስቀምጡ የማይችሉ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህም በላይ ለሁለቱ ህፃናት በአሁኑ ጊዜ የተቆረጠው የቀለብ ገንዘብ ብር 450.00(አራት መቶ___ሃምሳ) ሲሆን ይህ ገንዘብ ሕፃናቱ አካለ መጠን እኪሞላቸው ድረስ ይህ የገንዘብ መጠን ብቻ ለቀለብ ይበቃል ተብሎ ሊታሰብ የማይችል መሆኑን ከነባራዊው ዓለም እውነታ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የአመልካች የግል ንብረት ለህፃናቱ የቀለብ ጥያቄ አከፋፈል ዋስትና ይሆን ዘንድ መከበሩ ስለቀለብ የተደነገጉትን የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎችንና በሕገ መንግስቱ የተመለከተቱትን የህፃናቱን መብት የሚያስከበር ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45202

መጋቢት 08 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ድንቁ ወርዶፋ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ኤደን ድንቁ ወርዶፋ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የብድር እዳን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች እና የአመልካች ባለቤት በሆኑት በወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ ላይ ሐምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ በአረብ አገር ሰርተው ከሚያገኙት ደመወዝ ለአመልካችና ለባለቤታቸው ገንዘብ በሐዋላ ልከው ወላጅ እናታቸው ገንዘቡን ተቀብለው ለሚፈልጉት ጉዳይ ማዋላቸውን ገልፀው ክሱን ያስነሳውን ገንዘብ ብር 70,500.00(ሰባ ሺህ አምስት መቶ ብር) ከነሕጋዊ ወለድ እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ከተጠሪ ላይ የተበደሩት ገንዘብ የሌለ መሆኑን፣ለማስረጃነት በቀረበው ሰነድ ላይም ያልፈረሙ በመሆኑ የሚከሰሱበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ሲሉ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩትና የአመልካች ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ ደግሞ የተጠሪን ክስ በማመን መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጐ አመልካች እና ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለክሱ ምክንያት የሆነው ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ ክሱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ እና ተገቢው ማጣራት ከተደረገ በኋላ በዚህ ፍርድ ቤትም የአመልካች ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ ቀርበው ገንዘቡን ከተጠሪ ወስደው ለጋራ ጥቅማቸው ማዋላቸውን በድጋሚ በማረጋገጣቸው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ሚያዝያ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካች እዳውን ከወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ(ከባለቤታቸው) ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ተገቢነት በመግለጽ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል ሲሉ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት የመልስ መልስ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ በትዳር ፀንተው በነበሩበት ወቅት ተጠሪ ገንዘብ ያደበሯቸው ስለመሆኑ መረጋገጡን፣በዚህም ወቅት አከራካሪውን ብርድ አመልካች በሰነዱ ላይ ባይፈርሙም ባለቤታቸው የሆኑት ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ መፈረማቸውንና ገንዘቡን ለጋራ ጥቅም ያዋሉ መሆኑን ነው።

ብድሩ አመልካች ሳይፈርሙበት በትዳር ወቅት ወ/ሮ ፀጋዬ ተክሌ ወስደው በጋራ ጥቅም የዋለ መሆኑ ተረጋግጧል። በእርግጥ ከብር 500.00(አምስት መቶ) በላይ የሆነ ብድር ለማበደር ወይም ለመበደር የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት ማስፈለጉ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 68/መ/ ስር የተመለከተ ሲሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢም ውሉ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ በማቅረብ ውሉ እንዲፈርስ ማድረግ የሚችል መሆኑን የቤተሰብ ሕጉ ደንግጐ እናገኘዋለን። የሕጉ መንፈስ ውሉ የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሳይኖር በመደረጉ ብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የማይወስድ ነው። ይልቁንም ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ እስካላደረገው ድረስ ውሉ ውጤት ይኖረዋል። በተያዘው ጉዳይም አመልካች ሳያውቁ የተደረገ ነው ቢባል እንኳ ብድሩ ለጋራ ጥቅም የዋለ መሆኑ እና ፣ውሉን እንዲፈርስ ያላደረጉት መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው።

ብድሩ በትዳር ወቅት የተወሰደ ከሆነ ደግሞ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕግ ግምት የሚወስድበት ሲሆን ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን የማስረዳት ሸክም ያለባቸው አመልካች እንጂ ሌላ ወገን ሊሆን አይችልም። ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የብድር እዳው የጋራ ነው ሲሉ የሰጡትን ውሳኔ ከቤተሰብ ሕጉ መንፈስ አንፃር ሲታይ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም።

በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በአብላጫ ድምጽ ፀንቷል።
2. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ። ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት።

የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተ/ቁ. 2 የተመለከተው ዳኛ አበላጫው ድምጽ ከሰጠው ውሳኔ በሚከተለው ምክንያት በሐሳብ ተለይቻለሁ።

ተጠሪ ክስ የመሰረቱት ገንዘብ አባታቸው ለሆኑት አመልካችና ለስር 2ኛ ተከሳሽ ለሆኑት እናታቸው በሃዋላ ልከውላቸው ገንዘቡን እናታቸው ተቀብለው ለሚፈልጉት ስላዋሉት ገንዘቡን ባልና ሚስቱ እንዲከፍሏቸው ነው። ለዚህም ማስረጃ ይሆናቸው ዘንድ ያቀረቡት ሰነድ በርእሱ መተማመኛ የሚል ሲሆን በይዘቱ ሲታይ ግን የስር 2ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ብር 35,000 ለትዳራቸው ጥቅም ሲሉ የተበደሩ መሆኑን በማረጋገጥ የፈረሙበት ነው። ምንም እንኳን ተጠሪ ለአመልካችና ለባለቤታቸው ገንዘቡን የሰጡት በብድር ይሁን በአደራ በግልጽ ባይናገሩም ከሰነዱ በግራ ቀኙ መሃከል ነበረ ሊባል የሚችለው የብድር ስምምነት ነው። በመሆኑም ለውሳኔው አሰጣጥ ሊያዝ የሚችለው ጭብጥ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የብድር ስምምነት አለ? ወይስ የለም? የሚለው ነው።

ብድር ከውል አይነቶች ውስጥ አንዱ ነው። ውል ማለት ንብረታቸውን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ለማቋቋም ወይም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ባላቸው ተወዳዳሪ ግንኙነት በሁለት ወይም በብዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 1675 ሲያመለክት በህግ ፊት የሚፀና ውል ለማቋቋም በተዋዋዮች መሃከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ከፍ/ሕ/ቁ 1678/ሀ/ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው።

በመሆኑም በሁለት ተዋዋዮች መሃከል ውል አለ ለማለት የተዋዋዮቹ ስምምነት መኖሩ መሰረታዊ ነገር ነው። ወደተያዘው ጉዳይ ስናመራ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ውል መኖሩን ለማስረዳት የቀረበው ሰነድ 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ሆነው ብድሩን የወሰዱ ስለመሆኑ ይጥቀስ እንጂ አመልካች በውሉ ላይ አልፈረሙም። በውሁፍ ውል ላይ ተዋዋዮች ስምምነታቸውን የሚገለፁት ሰነድ ላይ ፊርማቸውን ወይም የጣት አሻራቸውን በማስፈር በመሆኑ አመልካች የብድር ውሉ ላይ ግዴታ ለማቋቋም ስምምነታቸውን ሰጥተዋል ማለት አይቻልም። ብድር የተሰጠው ከብር 500.00 በላይ በመሆኑ ስምምነት መፈፀሙን ማስረዳት የሚቻለው በጽሁፍ ወይም በፍ/ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም በመሐላ ብቻ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2472/1/ ያመለክታል። ውል በውሁፍ እንዲደረግ ህጉ በሚያዝበት ግዜ ደግሞ የጽሁፍ የአፃፃፍ ስርአት ሊከተል እንደሚገባ ከፍ/ሕ/ቁ. 1720/1/ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። በውሁፍ ውል ተዋዋዩን ለማስገደድ እንዲችል በውሉ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ሁሉ ሊፈረሙ እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ. 1727/1/ ያመለክታል። በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች በብድሩ ውል ግዴታ ያለባቸው ለመሆኑ ተስማምተው አልፈረሙም። ሁለተኛ ተከሳሽ ደግሞ አመልካችን ወክለው የብድር ውል ለመፈረም የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ስለመኖሩ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም። ስለሆነም 2ኛ ተከሳሽ እኔና አመልካች ሆነን ብድሩን ወስደናል በማለት አረጋገጠው መፈረማቸው ብቻ አመልካችን ለማስገደድ የሚችል የሕግ መሰረት የለውም። በሌላ በኩል አመልካች ብድር አለመውሰዳቸውን ክደው የተከራከሩና በመሐላ ቃልም ቢሆን ያመኑት ነገር ስለሌለ በተጠሪና በአመልካች መሃከል የብርድ ስምምነት አለ ማለት አይቻልም።

የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ለብድሩ ሃላፊ ናቸው ወደሚለው መደምደሚያ የደረሱት ገንዘቡ ለጋራ ጥቅም ውሏል በማለት የቤተሰብ ህጉን አንቀጽ 71ን በመጥቀስ መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል። በመጀመሪያ ክሱ ተጠሪ ለአመልካች ገንዘብ በማበደራቸው ገንዘቡን እንዲመልሱ እስከሆነ ድረስ ሊያዝ የሚገባው ጭብጥ ብድር አለ? ወይስ የለም? የሚለው እንጂ ገንዘቡ ለጋራ ጥቅም ውሏል አልዋለም የሚል ሊሆን አይገባም ይህ ጭብጥ ደግሞ ሊወሰን የሚገባው የብድር ውልና ስለወጪዎች በጠቅላላው ከሚናገሩት የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ ነው። የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 70/2/ እና 71 ስንመለከትም ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ የሚቆጠር እዳ ከተጋቢዎቹ የጋራ ሃብት ወይም ከባል ወይም ከሚስት የግል ሃብት ሊከፈል እንደሚችል ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌም ግን ምናልባት የተጋቢዎቹ አንደኛው በግሉ ብድር ወይም ሌላ እዳ ውስጥ ቢገባም ገንዘቡ ለጋራ ጥቅም እስከዋለ ድረስ እዳው ከተጋቢዎቹ የጋራ ወይም የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረትም ሊከፈል የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው ይህ ድንጋጌም በአፈፃፀም ግዜ ችግር እንዳያመጣ የተቀመጠ ድንጋጌ ስለመሆኑ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ሃተታ ምክንያት መረዳት ይቻላል። በመሆኑም የስር 2ኛ ተጠሪ የተበደሩት እዳ ለጋራ ጥቅም ከዋለ እዳው ከአመልካችም የግል ንብረት ሊከፈል የሚችይል በቀር አመልካች የወሰዱት ብድር ሳይኖር በስር 2ኛ ተከሳሽ ብቻ የተወሰደው ብድር አመልካችም እንደወሰዱት ብድር ተቆጥሮ ሃላፊ ናቸው መባሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ውሳኔው ሊሻር ይገባል በማለት አብላጫው ድምጽ ከሰጠው ውሳኔ በሃሳብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት።

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45370

መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1. አቶ ዳንኤል አበበ

2. አቶ ኤርሚያስ ቦጋለ - ጠበቃ አቶ ሽፈታው ከበደ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ - አልቀረቡም

2. አቶ አብዱልአዚዝ ሠኢድ - ጠበቃ ሀሰን ሁሴን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሐሰተኛ የወራሽነት ማስረጃ መሰረት ተደርጎ የተከናወነ የውርስ ሃብት ሽያጭ ውል ይፍረስልን ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የሐረሪ ክልል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካቾች በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም አሻሽለው በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም የአመልካቾች አውራሽ ወ/ሮ ታደለች ወ/ገብርኤል በጥር 21 ቀን 1987 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን፣ የሟች ሕጋዊ ወራሾች አመልካቾች እና በክስ ውስጥ ያልገቡ ሁለት ወራሾች መኖራቸውን፣ አንደኛ ተጠሪ ከሟች ወ/ሮ ታደለች ወ/ገብርኤል ጋር ምንም አይነት ለወራሽነት የሚያበቃ ዝምድና ሳይኖራቸው፣ በአንድ በኩል በ1968 ዓ.ም ስጦታ አድርገውልኛል የሚል ሰነድ ለፍርድ አቅርበው ተቀባይነት ሲያጡ ከሟች ጋር የአንድ እናት ልጆች፤ እህትማማቾች ናቸው፣ ሌላ ወራሽ የላቸውም በማለት በሐሰት የሚመለክሩ ምስክሮችን አዘጋጅተው በፍርድ ቤት የወራሽነት ማስረጃ ማግኘታቸውን፣ ይህንኑ ማስረጃ ይዘውም የሟች ወ/ሮ ታደለች ንብረት የሆነውን ቤት ለሁለተኛ ተጠሪ መሸጣቸውን፣ የአንደኛ ተጠሪ ወራሽነት ማስረጃም ሐሰተኛ መሆኑን ዘርዝረው አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም ለክሱ በሰጡት መልስ የቤቱ ስመ ሐብት በአንደኛ ተጠሪ ስም የሚታወቅ በመሆኑ አመለካቾች ክስ ለመመስረት መብት (ጥቅም) የሌላቸው መሆኑን፣ የሽያጭ ውል ይፍረስልን ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ ሽያጩን በሕጉ አግባብ ያደረጉት በመሆኑ ሊፈርስ እንደማይገባ ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ቤቱ ስመ ንብረቱ የሚታወቀው በአንደኛ ተጠሪ መሆኑን፣ ንብረቱን አንደኛ ተጠሪ ወደ እጃቸው ያስገቡትም በአደራ ሊጠብቁ ተብሎ ስለመሆኑ አመልካቾች ገልፀው መከራከራቸውን፣ አንደኛ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ ታደለች ወ/ገብርኤል ወራሽ መሆናቸውን የሚያሳይ የወራሽነት ማስረጃ ይዘው ባሉበት ጊዜ የቤት ሽያጩን ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርበው ያደረጉ ቢሆንም የወራሽነት ማስረጃው ሐሰተኛ መሆኑ መረጋገጡን በመግለፅ አመልካቾች አንደኛ ተጠሪን ከሚጠይቁ በስተቀር የቤት ሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች ሚያዚያ 12 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ ሦስት ገጽ አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ተጠሪዎች የሽያጭ ውሉ የፈፀሙት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ መሆኑ በግልፅ ተረጋግጦ እያለ ሽያጩ ሊፈርስ አይገባም መባሉ ያላገባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ የሽያጩ ውል ሊፈርስ አይገባም መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ አንደኛ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ አምስት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው መስከረም 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሶስት ገፅ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪውን ቤት አንደኛ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ በመያዝና ስመ ሃብቱን በማዞር ለሁለተኛ ተጠሪ ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርበው የሸጡ መሆኑን፣ በውሉ ላይም ለገዥ መድህን ስለመሆናቸው በመግለፅ ግዴታ የገቡ መሆኑን፣ አንደኛ ተጠሪ የያዙት የወራሽነት ማስረጃ ከሽያጩ በኋላ ሐሰተኛ መሆኑ መረጋገጡን፣ የተሸጠው ቤትም የአመልካቾች አውራሽ የሆኑት የወ/ሮ ታደለች ወ/ገብርኤል መሆኑ መረጋገጡን፣ ከሽያጩ በኋላ ሁለተኛ ተጠሪ የስመ ሃብቱን ወደ ራሳቸው አዙረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ የአመልካቾች ክርክር መሰረቱም የአውራሻቸው የግል ንብረት የሆነውን ምንም መብት የሌላት አንደኛ ተጠሪ በተጭበረበረ መንገድ ወራሽነት አሳውጀው እና የቤቱን ስመ ሃብት በማዞር መሸጣቸው ሽያጩን ሕጋዊ አያደርገውም በሚል ምክንያት ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡ እኛም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከሕጉ ጋር በሚከተለው መልኩ በማዛመድ ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው አንድ ንብረት ለሌላ ሰው በሕጋዊ መንገድ ሊያስተላልፍ የሚችለው በንብረቱ ላይ መብት ሲኖረው መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በጥበቃ የማይደረግለት ወይም የሌለ መብት ወደ ሰው ሊተላለፍ አይችልም፡፡ ይህ ተቀባይነት ያለው የሕግ መርሕ ነው፡፡ የሌላ ሰው ንብረት ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ ሕጋዊ የሆነ ስልጣን ሊኖር ይገባል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አንደኛ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት የሸጡት የአመልካቾችን ወይም የአውራሻቸውን ሕጋዊ ስምምነት ወይም ወራሽነት አግኝተው ባይሆንም የሚች ወራሽ መሆናቸውን በፍርድ ቤት አረጋግጠው፣ የቤቱን ስመ ሃብት ከሽያጩ በፊት ከተገቢው የአስተዳደር አካል ከአገኙ በኋላ ሲሆን ሽያጩም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተደደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሠጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሃብት ሆኖ ሊቆጠር እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይህን ማስረጃ የያዘ ሰው ደግሞ ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሸጠ ተግባሩ ሕገ ወጥ የሚባልበት ምክንያት የለውም፡፡ አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገዶች በሌላ ለማስተላለፍ መብት አለውና፡፡ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አንደኛ ተጠሪ ወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ አከራካሪውን ቤት በስማቸው የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት መያዛቸው ንብረቱ የግል ሃብት እንደሆነ የሚያሰቆጥር ሲሆን ይህን ማስረጃ በመመልከት ንብረቱን ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የሚገዛ ሰው ሽያጩን ያከናወነው ከሕግ ውጪ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በቤቱ ላይ ሕጋዊ መብት የሌለው ሰው በውሉ ለገዥው መድህን ለመሆን ግዴታ ገብቶ ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሃብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ የገዛውን ገዥ ሳይሆን ሻጩን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2882 እስከ 2884 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 997 ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሁለተኛ ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አከራካሪውን ቤት የገዙት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ከያዙት ግለሰብ ሁኖ ሽያጩንም ያከናወኑት ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ አመልካቾች በቤቱ ላይ የወራሽነት መብት ያላቸው መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ያላቸው መፍትሔ የሽያጩን ዋጋ ከስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከነበሩት ከወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ መቀበል ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአከራካሪው ቤት ላይ የተደረገው ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም፣ ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካቾች የቤቱን ሽያጭን ገንዘብ ብር 60000.00 (ስልሳ ሺህ) ከወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ እንዲቀበሉ ብለናል፡፡ በዚሁ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈፅም ለስር ፍርድ ቤት ግልባጩ ይድረሰው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42691

መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አደፍርስ በቀለ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ይቁም በቀለ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስጦታ የተገኘ ቤት ልረከብ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ ጥር 21 ቀን 1999 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 (በቀድሞው አጠራር ወረዳ 28 ቀበሌ 15) ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥር 321 የሆነውን ቤት ከሟች ወ/ሮ አለሚቱ በላይነህ በስጦታ የተላለፈላቸው መሆኑን፣አመልካች ወንድማቸው በመሆኑ በጊዜው ሲቸግራቸው ቤቱን እንዲጠቀሙበት ተጠሪ ፈቅደውላቸው ይዘው ሲጠቀሙት ከቆዩ በኋላ ቤቱን እንዲለቁላቸው ሲጠየቁ አመልካች ፈቃኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን ገልፀው አመልካች ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሰጡት መልስ፣ተጠሪ ያቀረቡት የስጦታ ማስረጃ አለመኖሩን፣ግብር መክፈል የቤት ባለቤት እንደማያደርግ እና ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው መብት የሌላቸው መሆኑ፣የቤቱ ግምትም የተጋነነ መሆኑን፣በቤቱ ውስጥ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ መኖር የጀመሩ በመሆኑ ጉዳዩ በይርጋ እንደሚታገድ፣ቤቱ የወ/ሮ አለሚቱ በላይነህ ሆኖ አመልካችም የወ/ሮ አለሚቱ በላይነህ ወራሽ በመሆናቸው ቤቱን ሊለቁ እንደማይገባ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመመረመረ በኋላ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ተጠሪ በስጦታ ውል መሰረት ያገኙት በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ጥር 04 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- በስር ፍርድ ቤት የተነሳው የይርጋ ክርክር የታለፈው ያላግባብ ነው፣የቤቱ ባለቤት መሆኔን የሚያሳይ ማስረጃ ስላለኝ ይቅረብልኝ የሚል ጥያቄ የታለፈው ያላግባብ ነው በማለት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካች ያነሱት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ አንድ ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመለስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ችሎት ግራ ቀኙን ታህሣሥ 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቃል አከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው ቤት የሚች ወ/ሮ አለሚቱ በላይነህ መሆኑን፣ተጠሪ ቤቱን አግኝቼአለሁ የሚሉት ሐምሌ 26 ቀን 1972 ዓ.ም በተደረገው ስጦታ ሆኖ ስጦታው አግባብነት ባላቸው አካላት የተቀመጠ እና የተመዘገበ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ማረጋገጡን፣የቤቱ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ አለሚቱ በላይነህ ከዚህ አለም በሞት እስከተለዩበት ጥር 11 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ በአከራካሪው ቤት ውስጥ ይኖሩበት እንደነበር፣አመልካች በቤቱ ውስጥ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ አስካሁን ድረስ መኖራቸውን፣የቤቱ ስመ ሃብት ከሚች ወደ አመልካችም ሆነ ተጠሪ ያልተዛወረ መሆኑን ነው፡፡

ተጠሪ ለክርክሩ መሰረት ያደረጉት የስጦታ ውል ሐምሌ 26 ቀን 1972 ዓ.ም የተደረገ ሆኖ ክሱ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ለአፈፃፀም ያልቀረበ መሆኑን ክርክሩ በግልጽ ያሳያል፡፡ ስጦታ በምን ያህል ጊዜ መፈፀም አለበት የሚለውን ጥያቄ በዚህ ረገድ የተመለከቱት ልዩ ድንጋጌዎች በግልጽ ያስቀመጡት የጊዜ ገደብ የለም፡፡ ይሁን እንጂ የስጦታ ውል ድንጋጌዎች በዚህ ረገድ ያስቀመጡት የጊዜ ገደብ የለም ተብሎ የስጦታ ውል ይፈፀም ጥያቄ በማናቸውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል ሊባል አይችልም፡፡ በሕጉ በግልጽ ካልተቀመጠ በስተቀር ማንኛቸውም ግዴታ ሊፈፀም የሚገባበት የጊዜ ገደብ ሊኖር ይገባል፡፡ የስጦታ ውልን የሚገዙ ድንጋጌዎች ግልጽ የሆነ ጊዜ ገደብ ባያስቀምጡም ስጦታ ውል እንደመሆኑ መጠን ሊፈፀም የሚገባው በአስር አመት የጊዜ ገደብ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1676/1/ እና 1845 ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ተጠሪ የስጦታ ውሉ ሐምሌ 26 ቀን 1972 ዓ.ም ተደርጐልኛል እያሉ ስጦታ አድራጊያቸው በሕይወት እያሉ አከራካሪውን ቤት በስጦታ ውሉ መሰረት እንዲፈጸምላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የለም፡፡ የስጦታ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከተመሰረተበት ጊዜ እስከ ጥር 21 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በሕጉ የተመለከተው የአስር አመት ጊዜ ገደብ አልፏል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረጉት ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 34508 ሐምሌ 02 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 69852 ግንቦት 06 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ስጦታውን መሰረት አድርገው የአቀረቡት የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ በይርጋ የታገደ ነው፣አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44237

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ኒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉሸዋ ቦጋለ - በራሳቸውን እና ወኪል ለሆኑላቸው

1. አቶ ሳሙኤል ቦጋለ
2. ወ/ሪት መሰረት ቦጋለ } ቀረቡ
3. አቶ ኤርሚያስ ቦጋለ

ተጠሪ፡- አቶ መስፍን ቦጋለ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር መዝገብ የቀረበው ክርክር በውርስ ሕጉ ውስጥ የተመለከቱትን ይርጋ ድንጋጌዎችን አተረጓጐም እና አፈፃፀማቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም በአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ፤የአመልካቾች ወላጆች የሆኑት አቶ ቦጋለ ባሩዴ ሰኔ 06 ቀን 1989 ዓ.ም ፣እና ወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ ደግሞ መስከረም 17 ቀን 1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ወራሽነታቸውን ማረጋገጣቸውን፣ሟቾች በሕይወት እያሉ ያፈሩትን ንብረት የአሁኑ ተጠሪ እንዲያካፍሏቸው ቢጥይቋቸውም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው ለብቻቸው ይዘው እየተጠቀሙ እንደሚገኙ ገልፀው የውርስ ሃብቱን የሚያጣራ የውርስ አጣሪ በፍርድ ቤት እንዲሾምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ የአመልካቾች የውርስ ይጣራልን ጥያቄ አውራሾቻቸው በሞት ከተለዩ በኋላ ከሦስት አመታት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ውድቅ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የአመልካቾች የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ አውራሾቻቸው ከሞቱ በአንድ ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፣ሆኖም አመልካቾች የውርስ ንብረቱን በተመለከተ ገምተው ክስ ማቅረብ ይችላሉ የሚል ምክንያት በመስጠት የአመልካቾችን አቤቱታ (ጥያቄ) ውድቅ አድርጐል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ይርጋን አስመልክቶ የያዘውን ምክንያት በመቀየር የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ በሦስት አመት ያልቀረበ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ምክንያቱን ለውጦ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች መጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አመልካቾች ወራሽነታቸውን በጊዜው አረጋግጠው የውርስ ንብረት ይጣራልኝ የሚለውን ጥያቄ ማቅረባቸውንና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪም የሰጠው መልስ አመልካቾች ለቤቱ ጥበቃ የወጣውን ሂሳብ ለተጠሪ ከፍለው ውርሱ ቢጣራ ተቃውሞ የለኝም የሚል ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ስለሆነ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካቾች የውርስ ይጣራልን ጥያቄ በሦስት ዓመት ይርጋ የታገደ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው አከራካሪውን ንብረት ሟች ወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ እስከእለት ሞታቸው ድረስ ይዘው ሲጠቀሙት የነበረ መሆኑ፣ወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ መስከረም 17 ቀን 1997 ዓ.ም መሞታቸውን፣አመልካቾች የወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ መጀመሪያ ደረጃ ወራሽነታቸውን በመ/ቁ. 612/98 የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም፣ተጠሪ በበኩላቸው የወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ መጀመሪያ ደረጃ ወራሽነታቸውን በመ/ቁጥር 56/98 ታህሣሥ 25 ቀን 1998 ዓ.ም ማረጋገጣቸውን፣አሁን እየተከራከሩ ያሉት የውርስ ንብረት ድርሻቸውን አመልካቾች እንዲያካፍሏቸው መሆኑን ነው፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ .1000 የወራሽነት ጥያቄ የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996 እስከ 1002 ድረስ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 999 ስር በተመለከተው መሰረት የሚቀርበው የወራሽነት ጥያቄ(petition hereditists) በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች ከተገለፀው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ጥያቄ አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሐብት በያዘ ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ተፈፃሚነት ባላቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ስር በተመለከቱት ደንቦች መሰረት የሚገደብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ ወራሽነታቸውን ታሕሣሥ 25 ቀን 1998 ዓ.ም ብቻቸውን፣አመልካቾች ደግሞ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም በመሆን በፍርድ ቤት ውሳኔ አረጋግጠዋል፣የክፍፍሉ ጥያቄ በቀረበበት ንብረት ደግሞ በሟች ወ/ሮ ኢትዮጵያ ናዴ ተይዞ የቆየ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው የሟቿ ወራሾች በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተለይተው መታወቃቸውን ነው፡፡ የአመልካቾች ጥያቄ ደግሞ የውርስ ክፍያ ነው፡፡ የውርስ ክፍያ ደግሞ ራሱን የቻለ የውርስ ሕግ ሆኖ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1060 እስከ 1113 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር የተሸፈነ ጉዳይ ነው፡፡ የውርስ ክፍያ ጊዜን በተመለከተ የፍ/ብ/ሕጉ በአንቀጽ 1062 ስር የደነገገ ሲሆን የድንጋጌው ይዘትም ውርሱ በተጣራ ጊዜ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን እያንዳንዱ የጋራ ወራሾች ውርሱን እንከፋፈል ብለው ለመጠየቅ እንደሚችሉ መደንገጉን የሚያሳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1060 ድንጋጌ ስር ደግሞ የውርስ አከፋፈል እስካልተፈፀመ ድረስ ውርሱ በወራሾች መካከል ሳይነጣጠል እንደሚቆይ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የሟች ወራሽነታቸውን በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ አረጋግጠው ከቆዩ በኋላ የውርስ ንብረቱን የክፍፍል ጥያቄ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ .1000/1/ እና /2/ ስር በተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ የሚታገድ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1062 ድንጋጌ መሰረት በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ በመሆኑ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የያዙት ምክንያትም ሆነ የደረሱበት መደምደሚያ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57313 በሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 71948 ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም ምክንያቱ ተለውጦ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ የውርስ ክፍፍል በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ አይገባም ብለናል፡፡
3. የአመልካቾችን የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄያቸውን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተገቢውን እንዲያሚሉ አድርጐ እንዲያስተናግደው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 46490

መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ቦጋለች ደባልቄ(4 ሰዎች) - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መሰረት በለጠ - አልቀረቡም

ፍ ር ድ

አመልካቾች ለአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ ከነበሩት ግለሰብ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ውሉ እንዲፈርስ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ይግባኝ ሰሚው የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔውን ስለሻረውና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

አመልካቾች በአዋሳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪዋ ከአቶ ፍሬው ለማ ጋር በጋብቻ በነበሩበት ጊዜ ቤት መስራታቸውንና ሁለት ልጆችም መውለዳቸውን ገልፀው አቶ ፍሬው ለማ ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ ግን ተጠሪዋ የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት በስማቸው አዛውረው ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ ስለሸጡና ይህም የህፃናቱን መብት ስለሚጐዳ የሽያጩ ውል እንዲፈርስ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም የሽያጩ ውል በሕጉ አግባብ የተከናወነ በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ተጠሪ በቤቱ ላይ ያላቸው ድርሻ ግማሽ ሲሆን ቀሪው ድርሻ ለህፃናቱ ከአባታቸው የተላለፈላቸው በመሆኑ የህፃናቱን ድርሻ አጠቃለው ቤቱን መሸጣቸው የህፃናቱን መብት የሚጐዳ በመሆኑ የሽያጩ ውል ሊፈርስ ይገባል ማለት በተጠሪ ስም ተሰጥቶ የነበረው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰረዝና በሚች ስም ተመዝግቦ ቤቱ የተጠሪና የህፃናቱ የጋራ ሃብት ሆኖ እንዲቆይ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ሁለቱን ወገኖች አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ከህፃናት መብትና ከሞግዚት ሥልጣን ወሰን አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካቾች የሚጠይቁት ተጠሪ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት በመሸጣቸው ውሉ እንዲፈርስላቸው ነው፡፡ ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚሉትንም ቤቱ የተጠሪ የግል ሃብት ሳይሆን የተጠሪና የሕፃናቱ የጋራ ሃብት በመሆኑ የህፃናቱን ድርሻ አጠቃለው መሸጣቸው የህፃናቱን መብት ይጐዳል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ነው፡፡ አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ስልጣን የሚሰጠው ለልጁ እናትና አባት ሲሆን ከወላጆቹ አንደኛው የሞተ ከሆነ ይህንን ስልጣን ይዞ የሚቆየው በህይወት ያለው ወላጅ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ የልጆቹ አሳዳሪና ሞግዚት ሆነዋል፡፡ የልጆቹ አስተዳዳሪና ሞግዚት በመሆናቸውም የልጆቹን መኖሪያ፣ጤና አጠባበቅ፣አስተዳደግ፣ትምህርት ማህበራዊ ግንኙነቱን በተመለከተ እንዲማሩና እንዲሁም ንብረትን በተመለከተ እንዲያስተዳድሩ ህጉ ለተጠሪ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል፡፡ በመሆኑም ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ ይረዳ ዘንድ የልጆቹን ሃብት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው የመወሰን ስልጣን ስላላቸው የልጆቹን ግማሽ ድርሻ በተመለከተ ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ አስፈላጊ ከሆነ ድርሻቸውን መሸጣቸው ብቻውን የልጆቹን መብት ይነካል ለማለት የሚያስችል አይሆንም፡፡ በእርግጥ በተሻሻለው የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 292 ስር ሞግዚቱ እንዲሸጥ በግልጽ የተፈቀደለት የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን፣አክስዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በመለከተ በህጉ መሸጥ የሚቻል መሆን አለመሆኑ በግልጽ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ ከፍ ሲል የተጠቀሰው ድንጋጌ ሞግዚቱ ሊሸጥ የሚችለውን የንብረት አይነቶች በግልጽ ለይቶ ማስቀመጡ ከዚህ ውጭ ያሉትን ንብረቶች እንዳይሸጥ መከልከሉን ያሳያል የሚባል ቢሆን እንኳን ሞግዚቱ የሕግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ለፈፀማቸው ድርጊቶች ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ስልጣን በላይ በሚሰራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ የክልሉ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 321 ያመለክታል፡፡ ውክልናን በሚመለከቱ የፍ/ህጉ ድንጋጌዎች ስንመለከት ደግሞ ወኪሉ የስልጣን ወሰኑን በማለፍ በስራ ጊዜ ሺሚው ተግባሩን ለማጽደቅ ወይም ለማፍረስ የሚችል ቢሆንም እንኳን ተወካዩ በውክልና ከተሰጠው ስልጣን ውጭ በማለፍ ሰርቶ የተገኘ ስራ በቅን ልቦና የሰራው ከሆነ ወካዩ ስራውን ለማጽደቅ የሚገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2207/1/ ያመለክታል፡፡ ተጠሪም ቤቱን የሸጡት ለልጆቻቸ4ው መልካም አስተዳደግ በተለይ ለትምህርታቸው ስለሚጠቅም ያለባቸውን የሞግዚትነት ስልጣን በአግባቡ ለመወጣት እንደሆነ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች ግን ተጠሪዋ ሌላ ባል ስላገቡ ንብረቱን አዲስ ከመሰረቱት ጋብቻ ንብረት ጋር ይቀላቅላሉ ከማለት ባለፈ አመልካች በልጆቹ አስተዳደግና አጠባበቅ ላይ ጉዳት አድርሰዋል ወይም ንብረታቸውን ያለአግባብ አባክነዋል በማለት በማስረጃ የተደገፈ ተጨባጭ ክርክር አላቀረቡም፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ሞግዚት በመሆናቸው ብቻ የልጆቹን ሃብት እንደፈለጉ ማባከን ስልጣን የላቸውም፡፡ አመልካቾችም ማስረዳት ያለባቸው ተጠሪ ቤቱን መሸጣቸውን ብቻ ሳይሆን ቤቱ በመሸጡ ምክንያት በልጆቹ ላይ የደረሰው ጉዳት ጭርም ነው፡፡ ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ አስከሆነ ድረስ ተጠሪ የራሳቸውንና የልጆቻቸውን የጋራ ሃብት የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጣቸው በራሱ የሽያጩ ውል ለማፍረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቱ የተሸጠው የልጆቹ መልካም አስተዳደግ መሆን አለመሆኑን ሳይመረምር ተጠሪ የራሳቸውንና የልጆቻቸው የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት መሸጣቸውን ብቻ በምክንያትነት በመውሰድ የሽያጩ ውል ሊፈረስ ይገባል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔውን መሻሩ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23385 ጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 26392 መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 51295

መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ዮሐንስ ጡእማይ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ምህረት ገብሩ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ባልና ሚስት በትዳር ወቅት እያሉ አንደኛው ተጋቢ ከሌላው ተጋቢ እውቅና ውጪ ብድር ተበድሮ ሲገኝ ብድር የጋራ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክር የተጀመረው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በውቅሮ በደደቢት ጣቢያ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የአመልካች የካቲት 01 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም ባጭሩ፡- ከተጠሪ ጋር የነበረኝ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ የጋራ ንብረት ክፍፍልም በፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፈፀምልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ ጋብቻው በፍቺ በፍርድ ቤት ቢፈርስ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን፣በጋራ ንብረት ክፍፍልም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመመረመረ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ በፊፀሙት የጋብቻ ውል መሰረት እኩል በእኩል እንዲካፈሉ፣በጋብቻ ወቅት የተወለዱት ሦስት ልጆች ከተጠሪ ጋር እንዲያድጉ ሆኖ ቀለብን በተመለከተ ግን ለእያንዳንዳቸው በወር ብር 70.00(ሰባ ብር) አመልካች እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም ተጨማሪ አመልካች ለአሁኑ ክርክር መሰረት የሆነው ማረት ከተባለ ድርጅትና ከዳሽን ባንክ የተወሰነውን የብድር እዳ በተመለከተ ተጠሪና አመልካች በጋራ የከፈሉት ተቀንሶ ቀሪውን በጋራ እንዲከፍሉት፣እዳው ከተቀነሰ በኋላ የንብረት ክፍፍልም እንዲፈፀም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለውቅሮ ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ሰበር ሰሚው ችሎት የንብረት ክፍፍልን በሚመለከት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሲያፀና በስር ፍርድ ቤቶች የጋራ ነው ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ ግን አመልካች የተበደሩትን ብር በሚመለከት ተጠሪን ሳያሳየው የተበደሩት፣የተበደሩትም ብር በጋራ ጥቅም መዋሉን ያላስረዱ እና እንዲሁም የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ቤት የሆነውን አመልካች ከዳሽን ባንክ ለተበደሩት ብድር አከፍፈል ለዋስትና ሲያስይዙ የተጠሪን ፈቃድ አልጠየቀም የሚሉትን ምክንያቶች በመያዝ አመልካች ከዳሽን ባንክ የተበደሩትን ብር 65,000.00(ስልሳ ስምንት ሽህ ብር) የአመልካች የግል እዳ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ታህሣሥ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ የክልሉ ሰበር ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ብድሩ መኖሩን አውቀው ከስምንት ወራት ያህል እዳውን ከአመልካች ጋር ሲመልሱ የነበሩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ እና አመልካች ነጋዴ በመሆናቸው የተጠሪን ፈቃድ ሳይጠይቁ ብድር መበደርና የጋራ ንብረትን በዋስትና ማስያዝ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ የሚፈቅድ ሆኖ እያለ የተጠሪ ፈቃድ ያልተጠየቀበት እና እዳው ለትዳር ጥቅም የዋለ መሆኑ አልተረጋገጠም ተብሎ እዳው ተጠሪን አይመለከታቸውም መባሉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በአንድ በኩል የአመልካች በንግድ ስራ ከመሰማራታቸውና በሌላ በኩል ደግሞ የባንክ ብድሩ የተወሰደው ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ከመሆኑ አንፃር ብድሩ ለጋራ ጥቅም አልዋለም ተብሎ ተጠሪ ከእዳው ነፃ እንዲሆኑ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐአል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በትዳር ፀንተው በነበሩበት ወቅት አመልካች በንግድ ስራ ተሰማርተው የነበሩ መሆኑን፣በዚህም ወቅት አስራሳሪውን ብድር ተጠሪን ሳያሳውቁ የማይንቀሳቀስ የጋራ ንብረት በዋስትና አስይዘው መውሰዳቸውን፣ከትዳር ላይ እያሉም የተወሰነውን የብድሩን ገንዘብ መመለሳቸውን ነው።

አመልካች በንግድ ስራ የተሰማሩ ነጋዴ ከሆኑ ብድሩን በሚበደሩበት ወቅት የተጠሪን ፈቃድ ማግኘት ነበረባቸው ሊባሉ የማይችሉ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 16 ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ በምንመለከትበት ጊዜ የምንረዳው ነጥብ ነው። ተጠሪ እዳው መኖሩን ያውቁ የነበረ ስለመሆኑም በወቅቱ የብድሩን ገንዘብ በጋራ መመለሳቸው የሚያረጋግጠው ነገር ነው። በመሆኑም ብድሩ አመልካች ነጋዴ ሆነው በትዳር ወቅት ወስደው በጋራ ሲከፈል የነበረ በመሆኑ የተጠሪ ፈቃድ የለበትም ሊባል የሚችል አይደለም። በእርግጥ የባልና ሚስት የጋራ ሐብት የሆነ አንድ የማይነቀሳቀስ ንብረት ሐብትነትን ወይም ሌላ መብት ለ3ኛ ሰው ለማስተላለፍ የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት ማስፈለጉ በቤተሰብ ሕጉ የተመለከተ ሲሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢም ውሉ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ውሉ እንዲፈርስ ማድረግ የሚችል መሆኑን የቤተሰብ ሕጉ ደንግጐ እናገኘዋለን። የሕጉ መንፈስ ውሉ የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሳይኖር በመደረጉ ብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የማይወስድ ነው። ይልቁንም ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ እስካላደረገው ድረስ ውሉ ውጤት ይኖርዋል። በተያዘው ጉዳይም አመልካች ነጋዴ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ብድሩን ተጠሪ እያወቁ ለተወሰነ ጊዜ አብሮ ሲከፍሉ የነበረ፣ውሉን እንዲፈርስ ያላደረጉት መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው።

ብድሩ በትዳር ወቅት የተወሰደ ከሆነ ደግሞ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕግ ግምት የሚወስድበት ሲሆን ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን የማስረዳት ሸክም ያለባቸው ተጠሪ እንጂ አመልካች ሊሆኑ አይችሉም። ስለሆነም የትግራይ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቱ የብድር እዳው የጋራ ነው ሲሉ የሰጡትን ውሳኔ መሻሩ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ባግባቡ ከንግድ ሕጉ እና ከቤተሰብ ሕጉ መንፈስ ሳያገናዝብ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 30245 ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል።
2. አመልካች ከዳሽን ባንክ እና ከማረት ማህበር የወሰዱት ብድር የጋራ እዳ ነው በማለት ወስነናል።
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49851

ሚያዝያ 4 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ታሪኳ አበበ የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞግዚት

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡን መርምርን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ጥቅምት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞላ አያት የነበሩት ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባነሽ ደስታ መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም ውልና ማስረጃ ቀርበው ሁለት ምስክሮች ባሉበትና በውልና ማስረጃ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ፊት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01 የቤት ቁጥር 872 የሆነውን መኖሪያ ቤትና ሌሎች ንብረቶች በሙሉ በኑዛዜ መስጠታቸውን በመናዘዝ ህፃን ሮቤል ንጉሤ የኑዛዜ ወራሻቸው መሆኑን በማረጋገጥ ፈርመውበት ምስክሮችም ፈርመውበትና ባለሥልጣኑም ይህንን አረጋግጦ ኑዛዜውን መዝግቦ አንድ ኮፒ አስቀምጧል፡፡ አንድ ኮፒ በኑዛዜ ተጠቃሚ ተሰጥቷል ስለዚህ ህፃን ሮቤል ንጉሤ የሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባዬ ወራሽ መሆኑ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ሁለት ምስክሮች በማስቅረብ ሰምቷል፡፡ ሟች ውልና ማስረጃ ኑዛዜ ማድረጋቸውን መስክሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የኑዛዜ ሰነዱንና የምስክር ቃል ከመረመረ በኋላ ኑዛዜው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን ፎርም አላሟላም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የውልና ማስረጃ ባለሥልጣን በምስክርነት ስሙ ያልተጠቀሰና ያልተፈረመ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን መስፈርት አያሟላም፡፡ አመልካች ሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባዬ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስትር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር 044/7/2001 ኑዛዜ ያደረጉ መሆናቸው በክፍሉ ባለሥልጣን ተረጋግጦና ተፈርሞ የተሰጠን ማስረጃ አለ፡፡ ኑዛዜው ውል ክፍል ውስጥ በሥራ ቀን ሁለት ምስክሮች ባሉበት የተደረገና ሟችና ምስክሮች የፈረሙበትና በውል ክፍል የሚመለከተው ባለሥልጣን ባለበት የተደረገ መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ እያለ ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተሣሳ የሕግ ትርጉም በመስጠት ኑዛዜው ዋጋ የለውም ተብሎ መወሰኑ የሟችን የኑዛዜ ቃል ዋጋ የሚያሣጣና የህፃኑን መብት ሚጐዳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ የሕግ ትርጉም ስህተቱ በሰበር ታርሞ ኑዛዜው ዋጋ አለው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል በሥርም ሆነ በሰበር ደረጃ ተከራካሪ የሆነ ተጠሪ የለም፡፡

አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ውሣኔና አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባነሽ መስከረም 27 ቀን 2001 ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ቀርበው ያደረጉት ኑዛዜ በሁለት ምስክሮች እና በውልና ማስረጃ ሰራተኛ ፊት የተደረገና ወዲያውኑ ሟችና ምስክሮች የፈረሙበትና የውልና ማስረጃ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ትክክለኛነትን በማረጋገጥ በጽ/ቤቱ ማህተም በማተምና በፊርማው በማረጋገጥ ያደረጉት መሆኑን በሥር ከቀረበው ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህንን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 ድንጋጌ አንፃር መመዘን ያስፈልጋል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 “በግልጽ የሚደረገው ኑዛዜ ከምስክሮቹ መካከል አንዱ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሆኖ ኑዛዜውም የተደረገው ይህ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ሥራቸውን በሚያካሄድበት ክፍል ውስጥ የሆነ እንደሆነ ለኑዛዜው ዋጋ ለማግኘት ሁለት ምስክሮች ብቻ በቂ ናቸው”

የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይህ ድንጋጌ ውል አዋዋይ ባለሥልጣኑ ስሙ በምስክርነት መገለጽ ያለበት መሆኑን እንደሚያስገድድ ኑዛዜው የተደረገው በውል አዋዋይ ባለሥልጣን ፊት ቢሆንም ባለሥልጣኑ በምስክሮች ስም ዝርዝር ስሙ ካልተገለፀ የሕጉን ፎርም ኑዛዜው አያሟላም ኑዛዜው ህጋዊ ውጤት አይኖረውም የሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ይህ አተረጓጐም የህጉን መንስፈና አላማ የሚያሣካ ውጤታማ አተረጓጐም አይደለም፡፡ በቀረበው የኑዛዜ ማስረጃ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ያለው ባለሥልጣን ፊት የተደረገ፣ኑዛዜው ከተነበበ በኋላ ሁለቱ ምስክሮችና ሟች እንደፈረሙበት ይህ ሁሉ ተግባር በፊቱ ሲከናወን ጠቅላላ ሂደቱን የተከታተለው ውል ለማዋዋል ሥልጣን ያለው ባለሥልጣን ሂደቱ በአግባቡ የተፈፀመ መሆኑን በፊርማው በማረጋገጥና ማህተም በመምታትና ቁጥር በመስጠት አንድ ኮፒ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በማስቀረት ቀሪውን ለሟች እንደሰጠ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ይህ መስፈርት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን ፎርም የሚያሟላና ህጉ ኑዛዜው የሟች እርግጠኛ የመጨረሻ ቃል መሆኑን ለማረጋገጥ የደነገገውን መስፈርት የሚያሟላ ነው፡፡ ስለዚህ አጠቃላይ ኑዛዜው የተደረገው ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው ባለሥልጣን ፊት መደረጉን በማረጋገጥ በመሥሪያ ቤቱ ማህተምና ፊርማ የተረጋገጠ ከሆነ የባለሥልጣኑ ስም በምስክሮች ፊት ስም ዝርዝር ውስጥ መጠቀሱ የግድ አስፈላጊ አይደለም፡፡ የባለሥልጣኑ ስም መገለጽ የሚያስፈልገው ከእሱ ውጭ ሌላ አንድ ምስክር ብቻ ከኖረ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ውል አዋዋይ ባለሥልጣኑ ውጭ ሌሎች ሁለት ምስክሮች ያሉ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የሰጠው ትርጉም የሕጉን መንፈስና አጠቃላይ ግብ መሰረት ያላደረገና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ሟች ወ/ሮ ተስፋነሽ አምባዬ ደስታ መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም በህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞላ ያደረጉት ኑዛዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟላና ሕጋዊ ውጤት ያለው ኑዛዜ ነው ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 43069

ሚያዝያ 6 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አማረ ረታ - ወ/መላኩ ረታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሰለሞን ካሣዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የኑዛዜ ወራሽ እና ያለኑዛዜ ወራሽ የሚች ንብረት ይካፈሉ ሲል የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ትርጉም ስሕተት የተፈፀመበት ነው ሲል አመልካች አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁን አመልካች ሚች አቶ ካሣዬ ክፈተው ግንቦት 23 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረጉትን የኑዛዜ ስጦታ መሠረት በማድረግ በአቃቂ ክ/ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ መኖሪያ ቤት ይዞ ያለ ሲሆን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት የሚች ወራሽ መሆናቸውን ጠቅሰው አመልካች ቤቱን እንዲለቅላቸው ዳኝነት ጠይቀው ነበር፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ሚች ተወላጅ እያላቸው ከውርስ የነቀሉ ስለመሆኑም በቂ ምክንያት ሳይሰጡ ያላቸውን ንብረት ለአመልካች በኑዛዜ ማስተላለፋቸውን ጠቅሶ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 939/3/ መሠረት በኑዛዜ ወራሽ እና ያለኑዛዜ ወራሾች ንብረቱን እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቀርቦለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል በማለት ታህሳስ 9/2001 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የሰበር አቤቱታው ይዘት ባጭሩ ለአመልካች በኑዛዜ የተሰጠው የሚች ጠቅላላ ንብረት ሳይሆን አንድ መኖሪያ ቤት ብቻ ነው በሚል የሥር ፍ/ቤት የጠቅላላ የውርስ ስጦታ ነው በሚል የፍ/ብ/ህግ ቁ 939/3/ ያለአግባብ ትርጉም ሰጥቷል በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ በሚች የተሰጠውን ኑዛዜ የሥር ፍ/ቤቶች በማለፍ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁ. 939 እና 852 መሠረት መወሰናቸው በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪም ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ ያለኑዛዜ ወራሾች በሕጉ አግባብ ከውርስ ያልተነቀሉ ስለመሆኑና ሚችም ከተጠቀሰው ቤት ሌላ ንብረት የሌላቸው መሆኑን ጠቅሶ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር መሠረት አድርገን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካች በኑዛዜ የተሰጠውን ቤት ለብቻው ለመውሰድ የሚከራከር ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የሟች ያለኑዛዜ ወራሽ መሆኑን ጠቅሶ ከኑዛዜው ተጠቃሚ ጋር በሥር ፍ/ቤት በተወሰነው አግባብ ለመካፈል እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ የሚያሻው ጉዳይ ሟች ለአመልካች ያደረጉት የኑዛዜ ስጦታ የጠቅላላ ውርስ(ስጦታ) ወይንስ ተለይቶ የታወቀ ንብረት ስጦታ ተብሎ ሊወሰድ ይገባል የሚለው መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች አንድ መኖሪያ ቤት ብቻ ነው በኑዛዜ የተሰጠኝ ሲል ተጠሪ ደግሞ ሟች ከዚህ ቤት ሌላ ንብረትም የላቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ለመፍታት የኑዛዜ ሰነዱን አጠቃላይ ይዘት ማየት ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ሟች ካሣዬ ክፈተው ግንቦት 23 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ እንደሚያመለክተው የወለዷቸው ልጆች እንዳልጠየቋቸው ጠቅሰው ያላቸውን ቤት ከነጣሪያው ከነግድግዳው ከነአፈሩ ለክርስትና ልጃቸው ለአማረ ረታ የተናዘዙ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ቤት ውስጥ ያለ እቃ የኔነው ያለችውን ሚስት እንድትወስድ እንዲሁም በመንግሥት ተወርሷል የተባለ አንድ ክፍል ቤት ለሚስት ወ/ሮ እናት መንግሥቱ መስጠታቸውን ነው፡፡ ሚስት በሕይወት እስካለች ተጠቅማ በኋላ ለአቶ አማረ ረታ እንድታስረክብ የሚል ሀሳብ ተጨምሮ ይገኛል፡፡

እንግዲህ ከዚህ የኑዛዜ ሰነድ ይዘት መረዳት የሚቻለው ሟች አለኝ ያሉትን ንብረት ጠቅሰው የተናዘዙ ስለመሆኑ ነው፡፡ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 911(1) እንደተደነገገው የሟች ተወላጆች እንዳያገኙ በማሰብ ያለውን ንብረት አጠቃሎ ለኑዛዜ ተጠቃሚ ስጦታ ያደረገ መሆኑ ሲታይ ሟች ያለውን ንብረት አጠቃላይ ያስተላለፈ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መልክ ያለውን ንብረት ዘርዝሮ ጠቅላላ በኑዛዜ ስጦታ ያስተላለፈ እንደሆነ ደግሞ ኑዛዜው ጠቅላላ ኑዛዜ ሊባል እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 912(1) መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም አመልካች የጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ነው በሚል በሥር ፍ/ቤት የተደረሰው ድምዳሜ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት አለው ሊባል የሚችልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

አመልካች የሟች ተወላጅ (ያለኑዛዜ ወራሽ) አለመሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካች በጠቅላላ ኑዛዜ የሟች ሀብት በስጦታ የተላለፈለት መሆኑ ከተረጋገጠ በሌላ በኩል ሟች ተወላጆቹን (ያለኑዛዜ) ወራሾችን ከውርስ የነቀለበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ መሆኑ ሲገናዘብ በዚህ ንብረት ላይ በኑዛዜ ወራሽ እና ያለ ኑዛዜ ወራሾች መካከል የሚኖረው መብት ምን ሊሆን ይገባል የሚለው ጥያቄ አስመልክቶ የሥር ፍ/ቤቶች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 939/3/ መሠረት መወሰናቸው ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስ የሚቻለው በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 915/1/ የተመለከተው ሁኔታ ተሟልቶ ሲገኝ እንደሆነ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች በኑዛዜ ጠቅላላ ስጦታ የተሰጠው ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ያለኑዛዜ የመጀመሪያ ደረጃ የሟች ወራሽ ነው፡፡ ይህ ከተሟላ ስለክፍፍሉ ሥርዓት የሚወሰነው ደግሞ መርሁ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 939/3/ ይሆናል፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ የህጉን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ተከትሎ የሰጡት ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊያሰኝ የሚያስችል ምክንያት የለውም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ባለበት ሊፀና ይገባል ብለናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09965 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 68488 የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡

ግራቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገው ክርክር የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 52691

ሚያዝያ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ኂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አብዱራሂም አህመድ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1. ቤተሣታ ችልድረንስ ሆም አሶሴሽን
2. ሚስተር ማይክል አለን ዳቮልት } ከ/ስለሺ ዘዮሐንስ ቀረቡ
3. ሚስ ዴቪስ አን ኸርናዴዝ

ተጠሪዎች፡- የለም

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የጉዲፈቻ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካቾች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በጉዲፈቻ የተወሰደው ልጅ ከውሳኔ በኋላ ሲመረመር የአእምሮ እድገት ዝግመት ያለበት መሆኑ ስለተረጋገጠ የጉዲፈቻ አድራጊዎቹ በዚህ ምክንያት ልጁን ሊቀበሉ ስላልቻሉ ውሳኔው ይሰረዝልን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አይቶ የጉዲፈቻ ውል በመርህ ደረጃ ሊፈርስ እንደማይችል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 195/1/ ስር የተቀመጠ ሲሆን በንኡስ አንቀጽ 2 ስር ደግሞ የጉዲፈቻ ውል ሊፈርስ የሚችልበት ልዩ ሁኔታ መስፈሩን፣በዚህ መሰረት ውሉ ሊፈርስ የሚችለው የጉዲፈቻ ውል ተቀባዩ የጉዲፈቻ ልጅን እንደልጁ በማሳደግ ፋንታ የልጁን የወደፊት ህይወት በሚጐዳ አኳኋን ሲይዘው እንደሆነ፣በተያዘው ጉዳይ ግን ውል እንዲፈረስ የቀረበው ምክንያት ውሉን ለማፍረስ የሚያስችል አለመሆኑን ተችቶ ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካቾች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች በቅሬታቸው ጉዲፈቻ የተደረገው ልጅ በሽታ ያለበት መሆኑ የተረጋገጠው ስምምነቱ ከፀደቀ በኋላ ስለሆነና ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ የዚህ አይነት ችግር መኖሩን ቢያውቁ ህፃኑን መረከብ እንደማይችሉ፣ልጁን እንዲረከቡ ቢገደዱ የልጁን ጤንነት የሚጠይቀውን ወጪ ለማውጣት አቅማቸው የማይፈቅድ በመሆኑ የልጁ የወደፊት ህይወት ባያሌው የሚጐዳ መሆኑን ገልፀው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 195/2/ በአግባቡ ያላገናዘቡ ስለሆነ ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 36/1/ ስር ከተደነገገው የህፃናትን ጥቅም ማስጠበቅ (best interest of the child) መርህ አኳያ ተገቢነቱን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ መዝገቡንም እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 195/1/ በመርህ ደረጃ የጉዲፈቻ ውል ሊፈርስ እንደማይችል ያስቀምጥና በንኡስ ቁጥር 2 ስር ደግሞ ውሉ ሊፈርስ የሚችልባቸውን ልዩ ሁኔታዎች ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት ውሉ እንዲፈርስ የሚደረገው ጉዳፊቻ አድራጊው በጉዲፈቻ የተቀበለውን ልጅ እንደ ልጁ በማሳደግ ፋንታ በባርነት ወይም ባርነት በሚመስል ሁኔታ ወይም ከግብረ-ገብ ውጪ በሆኑ ተግባሮች እንዲሰማሩ በማድረግ መጠቀሚያ ያደረገው እንደሆነ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጐዳ አኳኋን የያዘው መሆኑን የተረዳን እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ውሉ በተለይ “በማንኛውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጐዳው አኳኋን የያዘው” የሚለው ትርጉም የሚያስፈልገው ሲሆን ይህ ችሎት ድንጋጌው እንዴት መተርጐም እንዳለበት በመ/ቁ. 44101 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በዚህም መሰረትም ይህ ድንጋጌ የተቀመጠውም ጉዲፈቻ አድራጊው ልጅን በዓለም አቀፍ የሕፃናት እና ሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በሚፃረርና የልጁን ጥቅምና ደህንነት በሚጐዳ አኳኋን መያዙን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጉዲፈቻ ውሉ እንዲቀጥል ማድረጉ የሚያስገኘው ፋይዳ ባለመኖሩ ጉዳዩ በሚመለከተው ማንኛውም አመልካች ጠያቂነት መሰረዝ እንዲችል ታምኖበት መሆኑን የተሻሻው የቤተሰብ ሕግ ሃተታዘዘምክንያት ማመልከቱን፣ጉዲፈቻ እንዲደረግና የሕግ ጥበቃ እንዲደረግለት ያስፈለገው በዋናነት የሕፃኑን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል እንደሆነ፣የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትም ሆነ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም ዓቀፍ ስምምነቶች ህፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ለሕፃናት ጥቅም ደህንነት (best interest of the child) ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ መሆኑ በመርህ ደረጃ ማስቀመጣቸውን፣በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 36/5/ ስር መንግስት ለእንለማውታን ልዩ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው፣በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ስርአት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋማች እንዲመሰረቱ እንደሚያበረታታ መደንገጉን፣ከፍ ሲል የተመለቱት ድንጋጌዎች ሁሉ የጉዲፈቻ ጉዳይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት መሆኑንና በድንጋጌ አተረጓጐም ላይ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ፣በዚህም መሰረት የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲሰረዝ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው በልጁ አኗኗርና አያያዝ እንዲሁም ወደፊት ሕይወቱ ላይ በተጨባጭ የደረሰ ጉዳት በመኖሩ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳት ስለመኖሩም ማርጋገጥ ሲቻል እንደሆነ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንዲሰረዝ ጥያቄ ያቀረቡት ስምምነቱ ከተደረገና በፍ/ቤት ከፀደቀ በኋላ ልጁ ሲመረመር የአእምሮ እድገት ዝግመት ያለበት መሆኑ በሃኪም በመረጋገጡ ነው፡፡ አመልካቾች በአቤቱታቸው በጉዲፈቻ ለመቀበል የሚችሉት ጤነኛ ልጅ መሆኑና በጉዲፈቻ የተቀበሉት ልጅ ካለበት የጤና ችግር አኳያ ለአስተዳደጉና ለጤንነቱ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ወጪዎችን ለመሸፈን የገንዘብ አቅም የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚህም የአመልካቾች አቤቱታ መረዳት የሚቻለው ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ በጉዲፈቻ የተቀበሉት ልጅ ካለበት የአእምሮ ዝግመት ችግር አኳያ ልዩ እንክብካቤ እና አያያዝ እንዲሁም ክትትል የሚያስፈልገው ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ የጉዲፈቻ አድራጊዎቹ አቅም ያላቸው ለመሆኑና ወጪውንም ለማውጣት ፈቅደው ስምምነቱን ያደረጉ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ በተቃራኒው ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ልጁን እንዲወስዱ ቢገደዱ በልጁ የወደፊት ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል እየገለፁ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ደግሞ ጉዲፈቻ እንዲደረግ የሚፈቅደውና የሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ዋነኛ አላማ የህፃናቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ነው፡፡ የጉዲፈቻ ውሉ እንዲቀጥል ማድረጉ የሕፃኑን የወደፊት ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑ ከወዲሁ ከተረጋገጠ ውሉ ሊሰረዝ ይገባል፡፡ ሕጉም ውሉ እንዲፈርስ የሚፈቅደው ወደፊት ልጁ ላይ በተጨባጭ ጉዳት መድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ አይደለም፡፡ ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ልጁን ወስደው ለማሳደግ የማይችሉ መሆኑንና እንዲወስዱ ቢገደዱ እንኳን ወደፊት ህይወቱ ላይ ከፍተኛ ችግር እንደሚከተል መግለፃቸው ሲታይ ውሉ እንዲቀጥል ማድረጉ የልጁን ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ ህይወቱን አደጋ ላይ መጣል መሆኑን መገንዘብ ስለሚቻል ውሉ አይፈርስም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከፍ ሲል የተመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 136357 ግንቦት 3 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 82881 ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ህፃን ፈጠነን በጉዲፈቻ ልጅነት ለመቀበል ታህሣሥ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ያደረጉትና በፍ/ቤት መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም የፀደቀው የጉዲፈቻ ውል ተሰርዟል፡፡ ይህንኑ አውቆ ተገቢውን እንዲፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

የሰ/መ/ቁ. 53279

ሰኔ 08 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ትዕግስት ግርማ የእነ አቤል ወርቁ ሞግዚት - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኤፍሬም መንግስቱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክር የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ የስር አቤቱታ ይዘት ሲታይም መስከረም 14 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ሆኖ ሟች ወ/ሮ ውዴ ሙሉጌታ መስከረም 18 ቀን 1995 ዓ.ም ኑዛዜ ለምዕራፍ ስለሞን ያደረጉት ስለሆነ ልጅቱ የሟች ኑዛዜ ወራሽ መሆኗና የእኔም ሞግዚትነት ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጠኝ የሚል ነው፡፡ ምስክሮቻቸውን አቅርበውም እንደአቤቱታቸው ይዘት አስመስክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች በተቃዋሚነት ቀርበው ሟች ወ/ሮ ውዴ ሙሉጌታ የአሁኗ አመልካች ሞግዚት የሆኑላቸው እናት መሆናቸውን አድርገውታል የተባለው ኑዛዜም ሟች ማንበብና መፃፍ የሚችሉ በብዕር መፈረም የሚችሉ ሆነው እያለ በጣት የተፈረመ መሆኑ ሐሰተኛ መሆኑን እንደሚያሳይ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች አለመሆኑን ሟች በጣም ታመው መናገርና መንቀሳቀስ የማይችሉ በመሆኑ ከመሞታቸው አንድ ቀን በፊት አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ የሟች ሊሆን እንደማይችል ኑዛዜው በሕጉ መሠረት ስለመነበቡም የሚገልፀው ነገር ስለሌለ መሆኑን ገልፀው ኑዛዜ ፈራሽ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለባቸው ተጠሪ ሲሆኑ ሟች በጣታቸው የፈረሟቸውን ሌሎች ተመሳሳይ ፊርማዎችን አቅርበው በባለሙያ ሊረጋገጥ አልተቻለም በተጨማሪም ሟች በብዕር ይፈርሙ እንደነበርና ኑዛዜውንም ያደረጉት ከመመታቸው በፊት አንድ ቀን ሲቀራቸው ነው የሚሉትን ምክንያትቶችን በመያዝ ኑዛዜው ሟች ያደረጉት ነው ለማለት አሰቸጋሪ ነው ብሎ ኑዛዜው ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ኑዛዜው ትክክል አይደለም የሚለው ወገን ይህንኑ ማስረዳት ግዴታ አለበት የአሁኗ አመልካች ግን ይህንኑ አልተወጡም የሚል ምክንያት በመያዝ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮ ኑዛዜው ህጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ፀንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 22 ቀን 2002ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በኑዛዜው ላይ የሰፈረው ፊርማ የሟች ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም የኑዛዜው ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሆኖ እያለ ይህው ታልፎ ኑዛዜው ሕጋዊ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አከራካሪው የጣት አሻራ የሟች /የተናዛዥ/ መሆኑን በተመለከተ የማስረዳት ሸክሙ ላይ ያለውን ክርክር ለማየት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 07 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመንቀፍና በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ተገቢነት በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ቢሆንም በኑዛዜው ላይ የጣት ፊርማ ማስቀመጣቸውን ነው፡፡

በመሰረቱ የኑዛዜውን ቃልና ይዘት አስመልክቶ ማን ማስረዳት እንዳለበትና ምን አይነት ማስረጃዎች ማቅረብ እንደሚገባው በውርስ ሕግ ውስጥ ልዩ ድንጋጌዎች ተቀምጠው እናገኛለን፡፡ በዚህም መሠረት አንድ የኑዛዜ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሟች በሕይወት ዘመኑ ለእሱ ጥቅም ያደረገው ኑዛዜ መኖሩንና የኑዛዜው ቃልና ይዘትምን እንደሆነ የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896 በግልጽ ያሳያል ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳየው በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሰፈረው ቃል እና ኑዛዜ መኖሩን ማስረዳት ያለበት የኑዛዜው ተጠቃሚ ነኝ የሚለው ሰው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የሟች የኑዛዜ ወራሽ እና ተጠቃሚ ነኝ የሚል ሰው ሟች በህግ ፊት ውጤት ያለውን ኑዛዜ የፈፀመ መሆኑን የኑዛዜውን ቃልና ይዘት እንደዚሁም እሱ እራሱ በሟች ኑዛዜ መሠረት ተጠቃሚ መሆኑን የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ ህጉ ለምን አይነት ኑዛዜ ምን አይነት ማስረጃ መቅረብ እንዳለበትም በግልጽ ማስቀመጡ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 897 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሞግዚት የሆኑላቸው ልጆች የሟች ወራሾች ሲሆኑ ተጠሪ ሞግዚት ለሆኑላት ልጅ የተደረገው ኑዛዜ የተቃወሙት ሟች በብዕር የሚፈርሙ እንጂ በጣት አሻራ የሚፈርሙ አይደሉም በማለት ነው፡፡ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ሞግዚት የሆኑላት ልጅ የኑዛዜው ተጠቃሚና የኑዛዜው ወራሽ ነኝ የምትል በመሆኑ ሟች የጣት አሻራ በሌሎች ጉዳዩች ይፈርሙ የነበረ ስለመሆኑ እንዲያስረዱ ትዕዛዝ ሰጥቶ ይህንኑ ሊፈጽሙ ባለመቻላቸው ኑዛዜው አይፀናም ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ችሎት በሰጡት መልስም የጣት አሻራው የተፈረመው በአራት ሽማግሌዎች ፊት ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የጣት አሻራው የሟች ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም የአመልካች ነው ከሚሉ በስተቀር ሟች በሌሎች ጉዳዮች በጣት አሻራ ይፈርሙ የነበረ መሆኑን ወይም ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሆነው እያለ በጣት አሻራ ሊፈርሙ የቻሉበትን አሳማኝ ምክንያት በስር ፍ/ቤት ያረጋገጡ መሆኑን ገልፀው አልተከራከሩም፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቧቸው ማስረጃዎች ሟች በብዕር ሲፈርሙ የነበሩ ማንበብና መፃፍ ይችሉ የነበሩ መሆኑን በሚገባ ያስረዱ ስለመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ በግልጽ ያሳያል፡፡ እንግዲህ አመልካች ሟች በብዕር መፈረም ይችሉ የነበሩ መሆኑን ከማስረዳት እና በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሰፈረው የጣት አሻራ የሟች አይደለም በማለት መከራከር ብቻ በቂ ሲሆን ይህንኑ የማስተባበል ግዴታ ያለባቸው የኑዛዜው ተጠቃሚ የሆኑት ተጠሪ ሞግዚት የሆኑላት ልጅ ነች፡፡ ተጠሪ ደግሞ የኑዛዜ ተጠቃሚ የሆኑትን ልጅ ወክለው ባቀረቡት ክርክር በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለውን የጣት ፊርማ የሟች ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በሚያስገነዝበው ሁኔታ አላስረዱም፡፡ በመሆኑም የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሻረውም ሆነ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምጽ ያፀናው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896 ድንጋጌ መንፈስ ውጭ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 03848 ሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 07225 ጥር 07 ቀን 2002ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 350/97 ጥቅምት 08 ቀን 1999ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

የሰ/መ/ቁ. 50901

ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐ□ስ □ል□

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

□ሊ. መሐመ□

አመልካች፡- □/ሮ □ል□ ኃይሌ ጠ/መስፍን አድሴ - ቀረቡ

ተ□ሪዎች፡- □ነ ወ/ሮ ትዕግሥት ደበሌ /3 ሰዎች/ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከ□□ን ፍርድ ሰጥተናል፡:

□ ር □

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የውርስ ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ነው፡፡ ሥር ፍ/ቤት ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካች ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ የሟች አባ□ቸው ሀብት ነው ያሉትን የቤት ቁጥር 190/02 የሆነውን ቤት ከሶስት ክፍል ሰርቪስ ጋር ግምቱ ብር 70,000 /ሰባ ሺህ/፣ ሁለት የልብት ስፌት መኪና □ምቱ ብር 4,000 /አራት ሺህ/ እና ሌሎች የቤት እቃዎች በድምሩ ብር 83,190.00 /ሰማንያ ሶስት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ብር/ ግምት ያለው ንብረት ግማሽ ድርሻ አመልካች እንድታካፍላቸው እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል አመልካች ሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት መልስ ተጠቃሹ ቤት የልብስ ስፌት መኪና እና ቴሌቪዥን ሟች ታህሣሥ 25 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረገው ኑዛዜ አመልካች በሕይወት □ስካለች እንድትጠቀም ከ□□ም በኃላ ከሁለቱ ለተወለደችው ለአየለች ደበሌ እንዲሰጥ የተናዘዘ ስለመሆኑ ገልፀው ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ሟች ታህሣሥ 25 ቀን 1998 ዓ.ም አድርጓል የተባለው ኑዛዜ የተከሣሾችን /ተጠሪዎችን/ ጥቅም የሚጐዳ እና እነሱ በሌሉበት የተደረገ መሆኑን ጠቅሶ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 872 ምርኩዝ በማድረግ ኑዛዜው ቀሪ ሆኖ ንብረቶቹ □ንዲከፋፈሉ ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው የወራሾችን የመውረስ መብት የተከለከለበት ምክንያት የማይገልፅ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤት ኑዛዜው እንዲፈርስ መወሰኑ በአግባቡ ነው ሲል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አፅንቷል፡፡

□ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎትም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሕግ ስሕተት የለውም ሲል አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል፡፡

ለዚህ ሰበር የቀረበው አቤቱታ በዚህ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

□ህግሥ 1 ቀን 2002 ዓ.ም ተፅፎ የቀረበው አቤቱ□ ባ□ ሩ ተጠሪዎች ንብረት ለመካፈል እንጂ ኑዛዜ ለማስፈረስ ክስ ሳያቀርቡ የሥር ፍ/ቤቶች ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ ስለመወሰናቸው ተጠሪዎች የውርስ ንብረት ይጣራ ጥያቄ ሳያቀርቡ ንብረት መጠየቃቸው አለአግባብ ስለመሆኑ ኑዛዜው በፍርድ ቤቶቹ እንዲፈርስ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 875 መንፈስ የወጣ ስለመሆኑ እና ንብረቶቹ በአግባቡ ሳይጣሩ □ማሽ እንዲካፈል መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት ወሣኔው እንዲሻር አመልክተዋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም ኑዛዜው ዋጋ አልባ ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተጠሪዎችን አስቅርቧል፡፡ ተጠሪዎችም የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቀርበው ክርክራቸውን አሰምተዋል በክርክራቸውም ኑዛዜው የተደረገላቸው መሆኑን ያወቁት በክስ ሂደት ስለመሆኑ ለእነሱ ተሰጠ የተባለው ቤት በመንግሥት የተወረሰ በእጃቸው የሌለ ስለመሆኑ እና ብር 200(ሁለት መቶ) ብቻ ለእያንዳንዳቸው ተከፍሎ ንብረቱ ለአንደኛዋ ልጃቸው ብቻ እንዲሆን መደረጉ አለአግባብ መብታቸውን የሚጉዳ ስለመሆኑ ዘርዝረው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና አመልክተዋል፡፡

□ኛም □□ራ ቀኙን ክርክር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል በዚህ ችሎት እልባት የሚያሻው ጉዳይ ኑዛዜው ዋጋ አልባ ነው ሲሉ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ስለመሆኑ ኑዛዜው በሕግ አግባብ የተደረገ ነው ከተባለ ሕጋዊ ወጤቱ ምን ሊሆን ይገባል የሚል እና ተያያዥ ነጥቦችን እንደሚከተለው አንድ በአንድ ተመልክተናል፡፡

የአመልካች ባለቤት እና የተጠሪዎች ወላጅ አባት የሆኑት ሟች አቶ ደበሌ ሮቤ ታህሣሥ 25 ቀን 1998 ዓ.ም ያደረጉት ግልፅ ኑዛዜ በተናዛዡ እና በምስክሮች ፊት የተደረገ እና የተፈረመ ስለመሆኑ እና በውልና የክብር መዝገብ አገልግሎት ጽ/ቤት የተረጋገጠ ስለመሆኑ ሰነዱ ያመለክታል፡፡ ግልፅ ኑዛዜ ማሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን መስፈርት ያሟላ ስለመሆኑ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ካለው የኑዛዜ ሰነድ መረዳት ችለናል፡፡

ስለሆነም የወረዳው ፍ/ቤት ኑዛዜው ሲደረግ ተጠሪዎች በቦታው አልነበሩም በሚልና ከፍተኛው ፍ/ቤት ኑዛዜው ወራሾች ባሉበት ስለመነበቡ አልተገለፀም በሚል ሰነዱ በሕግ የተመለከተውን ፎርማሊቲ አላሟላም ከሚል መደምደሚያ መድረሳቸው በሕጉ ያልተመለከተን መስፈርት መሠረት ያደረጉ ስለሆነ ድምዳሜው ስህተት ነው እንላለን፡፡

የኑዛዜው ሰነድ በፎርማሊቲ ረገድ ጉድለት የለበትም፡፡

የኑዛዜው ሰነድ በፎርማሊቲ ረገድ ጉድለት የሌለበት ነው ከተባለ በይዘት ረገድ ያለውን ውጤት እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

ከኑዛዜው ይዘት መረዳት የሚቻለው ሟች ከአመልካች ጋር ካፈሯቸው ንብረቶች ውስጥ በሣጉሬ ከተማ ቀበሌ 02 የሚገኝ የቤት ቁጥር 120/02 የሆነውን መኖሪያ ቤት እና የቤት ቁሳቁስ ድርሻቸውን አመልካች እስከ ሕልፈተ ሕይወቷ እንድትጠቀም በኃላም ለልጃቸው ለወ/ሮ አየለች ደበሌ ሮቢ የግል ንብረት እንዲሆን በሚል ወስኗል፡፡ እንዲሁም ወ/ሮ አየለች ደበሌ ለሌሎቹ ወራሾች /ተጠሪዎችን ጨምሮ አምስት የሟች ተወላጆች/ ለሆኑት ለእያንዳንዳቸው ብር 200 /ሁለት መቶ/ እንድትሰጥ በኑዘዜው አዟል፡፡ ከዚህም ሌላ በሳጉሬ ከተማ የሚገኝ በመንግስት በአዋጅ የተወረሰ ቤት የሚከፈለውን አበል አመልካች እንድትጠቀም ሆኖ ቤቱ የሚመለስ ከሆነ ተጠሪዎች እንዲካፋፈሉት 14 ኢንች ቴሌቪዥን እና የልብስ ስፌት መኪና በገንዘቧ የገዛቸው ወ/ሮ አየለች ደበሌ መሆኗን ገልፆ የግል ንብረት እንዲሆን ተናዟል፡፡

ከዚህ ሰነድ ባጠቃላይ መረዳት የሚቻለው በእጃቸው ያለውን ቤት እና በመንግሥት ተወርሶ አበል የሚከፈልበትን ቤት አበሉን አመልካች እስከ ሕልፈተ ሕይወቷ እንድትጠቀም ተናዛዡ መፍቀዱን ከዚያ በ□ላ በ□□ ያለው ቤትና የቤት ቁሳቁስ የልብስ ስፌት መኪና እና ቴሌቪዥን የወ/ሮ አየለች ደበሌ የግል ንብረት እንዲሆን ሌሎቹ ወራሾች ደግሞ ሁለት መቶ ብር እና በመንግስት እጅ ያለ ቤት ሲመለስ እንዲከፋፈሉ የሚል ማድረጋቸው ነው፡፡

□ንግዲህ በዚህ የኑዛዜ ሰነድ ላይ የተጠቀሱት የኑዛዜው ተጠቃሚዎች ከአመልካች በስተቀር ሌሎቹ የሟች ተወላጆች መሆናቸው ግራቀኙን አላከራከረም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች እስከ ሕይወት እንድትጠቀም የሚል በመሆኑ ንብረቱን በማከፋፈል ረገድ ኑዛዜው የተለየ ጥቅም አላሰጣትም ተወላጆቹ መካከል ግን ክፍፍል ያደረገ ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ ለተወላጆቹ የተሰጠ ኑዛዜ በሕጉ ምን ውጤት አለው የሚለው ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ሟቹ በኑዛዜው ለተወላጆቹ የንብረት ክፍፍል አድርጓል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 913 እንደተደነገገው የተናዛዡ ተቃራኒ ሃሳብ በግልፅ አልተመለከተም አንድን የውርስ ሀብት ለተወላጅ መስጠቱ የክፍያ ደንብ እንጂ የኑዛዜ ስጦታ ተብሎ እንደማይቆጠር ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት ሟቹ በኑዛዜው ንብረቶቹን ለወራሾቹም መደላደል እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ ነገር ግን በድልድል አፈፃፀም ላይ ሌላኛው ተወላጅ ወራሽ መብት ከሩብ የበለጠ ጉዳት የሚደርስበት እንደሆነ □ስፈ□ታ አከፋፈል እንዲቀር ለመጠየቅ እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ ቁጥር 1123/1/ ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ሟች ታህሣሥ 25/1998 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ በሳጉሬ ከተማ ቀበሌ 02 ቁጥር 120/02 የሆነውን ቤት ባለሀብትነት መብት ለወ/ሮ አየለች ደበሌ ብቻ እንዲሆን ተናዟል፡፡ ለተቀሩት ተወላጆች ብር 200.00(ሁለት መቶ) እንዲከፈላቸው እና በመንግሥት እጅ ያለ ቤት የሚመለስ ከሆነ ብቻ እንዲከፋፈሉ አድርገዋል፡፡

ስለሆነም ኑዛዜውን መሠረት አድርጐ ክፍፍሉ በተወላጆች መካከል ሲደረግ ከሩብ ያላነሰ ጉዳት □□ርስባቸዋል የሚያሰኝ ሆኖ ሲገኝ በኑዛዜው መሠረት እንዳይፈጸም ተጠሪዎች መቃወም የሚችሉ ከሚሆን በስተቀር ከወዲሁ ኑዛዜው የተጠሪዎችን መብት የሚጐዳ ነው በሚል የሥር ፍ/ቤት ኑዛዜውን ሙሉ በሙሉ ማፍረሱ ተገቢ አይደለም፡፡

ስለዚህ በወራሾች መካከል በተደረገ የውርስ ንብረት ክፍፍል አፈፃፀም ላይ በገንዘብ ወይም በአይነት ማስተካከል የሚቻል በሆነ ጊዜ ኑዛዜውን በተናዣዥር ሀሳብና ፈቃድ መሠረት ማስፈጸም እንደሚገባም የፍ/ብ/ሕ ድንጋጌ ቁጥር 910 ያመለክ□ል፡፡

በተመሳሳይ ጉዳይላይም ይርጋ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 18394 ውሣኔ ሲሰጥ ስለአፈፃፀሙ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ስለሆነም በተወላጆች መካከል በኑዛዜው መሠረት ክፍፍል ሲደረግ ለተጠሪዎች ከአንድ አራተኛ /ሩብ/ በታች የሚደርሳቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚቻለው የውርስ ንብረት ማጣራት ከተደረገ በኃላ እንደሆን ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ገምተው ከቀረቡት የንብረት ዓይነት እና □□ ላ□ ተ□ኪ□ ማ□ሪ□ ስላልተ□ረ□ የድርሻቸውን መጠን በግልፅ ለመለየት አስቸጋሪ ሆኗል፡፡

በሌላ በኩል ከፍ ሲል እንደተመለከተው የቤት ቁጥር 120/02 እና የቤት ቁሳቁስ አመልካች በሕይወት □ስካለች ጊዜ ድረስ እንድትጠቀም ሟቹ በግልፅ በኑዛዜው ስለተወሰነ ይህም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 920 መሠረት መፈጸም ያለበት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪዎችም ሆኑ ሌሎች ተወላጆች ይህንን ንብረት ለመከፋፈል ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት ከአመልካች እልፈተ ሕይወት በኃላ ነው፡፡ አልያም ከአመልካች ጋር በሚደረግ ስምምነት ብቻ ይሆናል፡፡

ባጠቃላይ የአመልካች በኑዛዜው የተጠበቀላትን የመጠቀም መብት በሚጐዳ ሁኔታ የሥር ፍ/ቤቶች የኑዛዜውን መንፈስ እና የተናዛዡን ፍላጐት ባላገናዘበ ሁኔታ ኑዛዜው ፈራሽ ነው ንብረቶቹን ይከፋፈሉ በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የዲገሎ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 07255 የሰጠው ውሣኔ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 19592 የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 88384 የሰጠው ትዕዛ□ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሎ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

2. አመልካች በሟች በተደረገለት ኑዛዜ መሠረት በሰጉሬ ከተማ ቀበሌ 02 በሚገኝ ቤት ቁጥር 120/02 እና የቤት ቁሳቁስ እንዲሁም በመንግሥት የተወረሰውን ቤት አበል እስከ ሕይወታ ፍፃሜ የመጠቀም መብት አላት ብለናል፡፡

3. ተጠሪዎች እና ሌሎች የሟቹ ተወላጆች የሟችን ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት ከአመልካች ሕልፈተ ሕይወት በኃላ ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. በዚህ ፍ/ቤት የተደረገውን ክርክር ወጪና ኪሣራ □ራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም.አ

የሰ/መ/ቁ. 46613

ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሐሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኑኑ ሸህሞሎ - ቀረበ ጠ/ሰለሞን ታደሰ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አሰገድች ጫኔ - ጠ/መስፍን ጌታቸው ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካችና አቶ አለም ባሕታ በሚከራከሩበት ጉዳይ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ በመሰጠቱ ተጠሪ እግዱ እንዲነሳላቸው አመልክተዋል፡፡ በማመልከቻቸውም ከሥር ተከሣሽ ጋር ባልና ሚስት እንዳልሆኑና ተከሣሹ የተጠሪን ፈቃድ ሳያገኙ የቤቱን ካርታ አስይዘው በመበደራቸው ቤቱ የታገደ በመሆኑ እግዱ እንዲያነሳላቸው ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለቀረበው አቤቱታ በሰጡት መልስ ተጠሪና የስር ተከሣሽ እንደ ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተፈራ ንብረት በመሆኑ የጋራ ንብረት ስለሆነ እግዱ ሊነሳ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በሁለቱ መሃከል እንደ ደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ስላለ እና ንብረቱም በግንኙነቱ ውስጥ የተፈራ ስለሆነ እግድ እንዲነሳ የቀረበውን ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 106/3/ መሠረት በሁለት ሰዎች መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖርን ሁኔታ የሚረጋጠው በግንኙነቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ጠያቂነት ብቻ እንጂ በሌላ ሶስተኛ ወገን ጥያቄ አይደለም፣ ቤቱን በሥር ተከሣሽ ስም ባለመሆኑና የመያዣ ውሉም ስላልተመዘገበ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር በቤቱ ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበውን ይግባኝ ሰርዞታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው ከጋብቻ ውጪ እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ማስረዳት የሚችል በግንኙቱ ውስጥ ያሉት ብቻ ናቸው መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለዋል፡፡ ችሎቱም ይህንኑ ነጥብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ማመልከቻ ከሥር ተከሣሽ ጋር ከጓደኝነት የዘለለ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ገልፀው ተከሣሹ ያለ እሳቸው ፈቃድ ካርታቸውን አስይዞ በመበደሩ ምክንያት ቤታቸው መታገዱ አግባብ አለመሆኑን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው በስር ተከሣሽና በተጠሪ መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ መኖሩን ተከራክረዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ማስረዳት የሚችሉት በግንኙቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ የተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 98፣ 99 እና 106 በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ አለ የሚባለው መቼ እንደሆነና የግንኙነቱ መኖር በምን አይነት መንገድ ማስረዳት እንደሚቻል ከሚያመለክቱ በቀር ግንኙነት ስለመኖሩ ለማስረዳት መጠየቅ የሚችሉት በግንኙቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ እንዲሆኑ ገድቦ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ በአንቀጽ 106/3/ ግንኙነት መኖሩን “እንደኛው ወገን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ” በማለት የተቀመጠው በግንኙቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች መሃከል የሚነሳውን ክርክር ታሳቢ በማድረግ እንጂ ሌላ 3ኛ ወገን ግንኙነቱን ማስረዳት እንዳይችል ለመከልከል አይደለም፡፡ በመሆኑም የግንኙነቱ መኖር አለመኖር በሶስተኛ ወገኖች መብት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ካለ ይኸው ሶስተኛ ወገን ግንኙነቱን ከማስረዳት የሚከለክለው የሕግ መሠረት ስለሌለ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩን ማስረዳት የሚችሉት በግንኙነቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ማመልከቻ ያቀረቡት ንብረቱ ነው በሚሉት ቤት ላይ የተሰጠው እግድ እንዲነሳቸው ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት በተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ቅሬታ የተሰማው ወይም ያለአግባብ ነው የሚለው ወገን ለፍ/ቤት ጥያቄ ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ በቂ ምክንያት መኖሩን ያመነ ከሆነ የሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ማሻሻል፣ ማንሣት ወይም ጨርሶ መሰረዝ ይችላል፡፡ ተጠሪ እግዱ ይነሳልኝ የሚሉት ቤቱ የግል ንብረቱ ነው በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው በተጠሪና በሥር ከሣሽ መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ያለና ንብረቱም የተፈራው በዚህ ግንኙነት ውስጥ በመሆኑ የተጠሪ ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን አመልክተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በዚህ ጉዳይ በዋናነት ሊያስተናግድ የሚገባው የእግድ ትዕዛዝ ሊነሳ ይገባል? አይገባም? የሚለው ቢሆንም ከዚህ አልፎ በተጠሪና በሥር ተከሣሽ መሃከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖር አለመኖሩ እንዲሁም የንብረቱን ባለቤት አስመልክቶ ውሣኔ አሳርፏል፡፡ ከመዝገቡም መረዳት እንደሚቻለው እነዚህ ጉዳዮች በዋና ጭብጥነት ተይዘው በመደበኛ የሙግት ስርዓት ተገቢው ክርክርና ማስረጃ ቀርቦባቸው የተወሰኑ አይደሉም፡፡ የተሰሙት ምስክሮች የሰጡት ምስክርነትም ቢሆን የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 106 የሚያስቀምጠውን ሁኔታ የሚያሟላ መሆን አለመሆኑ ሳይመዝን እንዲሁም ቤቱ የተሰራው መቼ እንደሆነ ሳይረጋገጥ የተሰጠው ውሣኔ የተጠሪን መብት በእጅጉ የሚጎዳ መሆኑን መረዳት ችለናል፡፡ ፍ/ቤቱ እግድ የተሰጠበት ንብረት የተጠሪ የግል ንብረት ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ያልቀረበለት ከሆነ የተጠሪን የእግድ ይነሳልኝ ጥያቄ ውድቅ ማድረግ እንጂ በጭፍጫፊ ጉዳይ መደበኛ ክርክርና ማስረጃ ሳይቀርብና ጉዳዩ በአግባቡ ሳይመረመር ተጠሪ ከሥር ተከሣሽ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና የንብረት ባለቤትነት መብት በማረጋገጥ የሰጠው ውሣኔ የሙግት ስርዓትን ያልተከተለና ስነ ሥርዓታዊ ግድፈት የተፈፀመበት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ምንም እንኳን ተጠሪ በንብረቱ ላይ ያላቸውን መብት በሌላ መንገድ የማረጋገጥ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሥር ፍ/ቤት ዕግድ የተሰጠበት ንብረት የተጠሪ የግል ሃብት መሆን አለመሆኑ በበቂ ሁኔታ ስላልተረጋገጠ በንብረቱ ላይ የተሰጠው እግድ እንዳይነሳ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69894 ታህሣሥ 25 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 43288 መጋቢት 25 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08135 ሐምሌ 7 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ብይን በተጠሪና በሥር ተከሣሽ መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ አለ እንዲሁም የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ቤት በዚህ ግንኙት መሃል የተፈራ ነው በማለት የሰጠው ትችት ውድቅ ተደርጓል፡፡ የእግድ ትዕዛዙ ሊነሳ አይገባም ሲል የሰጠውን ብይን ግን ፀንቷል፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. *51866*

ሐምሌ *02* ቀን *2002* ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለማየሁ - ቀረቡ

ተጠሪ፣ ወ/ሮ አዛለች ደበብ - ጠበቃ ደርበው ተመስገን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የጋብቻ ማስረጃን መስጠት በመቃወም የተጀመረ ነው፡፡ የጉዳዩ አጀማመር ለተጠሪ የተሰጠ የጋብቻ ማስረጃ አለአግባብ ነው፤ ሊሰረዝ ይገባል በማለት አመልካች መቃወሚያ በማቅረባቸው የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቀደም ሲል ለተጠሪ የሰጠው ማስረጃ በመሰረዝ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ በተጠሪ እና በሚች መካከል ጋብቻ መኖሩን አምነው ጋብቻው ፈርሷል የሚል መከራከሪያ ያቀረቡ ስለሆነ ጋብቻው ፈርሷል? አልፈረሰም? የሚለውን ማጣራት ይገባው ነበር ካለ በኃላ በዚህ ምክንያት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሯል፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት በዚሁ ላይ ሲሆን ይዘቱም በተጠሪ እና በሚች ጫኔ በዛብህ መካከል ጋብቻ አልነበረም አለ ከተባለም በሕይወት እያሉ ተፋትተው የተለያዩ በመሆኑ ይህ ሳይጣራ የተሰጠው ውሣኔ አለአግባብ ነው ሲሉ እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን መርምሮ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጋብቻ ፈርሷል ወይስ አልፈረሰም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በራሱ ሳያጣራ ወይም በሥር ፍ/ቤት ተጣርቶ እንዲወሰን ሳያደርግ በደፈናው የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል የተጠሪ ጠበቃ ሚያዚያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበዋል በይዘቱም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ እንዲፀና ያመለከቱበት ነው፡፡

እኛም የክርክሩን አመጣጥ አስመልክቶ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመረ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከሥር መዝገብ መረዳት የተቻለው አመልካች ለተጠሪ የተሰጠው የጋብቻ ማስረጃ እንዲሰረዝ አቤቱታ ሲያቀርቡ በተጠሪ እና በሚች መካከል የነበረው ጋብቻ ቀድሞ ፈርሷል በሚል መነሻ ምክንያት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት በሚች እና በተጠሪ መካከል ጋብቻ ነበር ወይስ አልነበረም? ጋብቻ ነበር ከተባለ ቀድሞ በፍቺ የፈረሰ ወይንስ በሚች ሞት ምክንያት? የሚሉት ነጥቦች በአግባቡ ሳያጣራ የተወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም በውሣኔው በግልፅ እንዳመለከተው በተጠሪ እና በሚች መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሷል? ወይስ አልፈረሰም? የሚለው ነጥብ ያልተጣራ መሆኑ ሲረዳ ይህ ነጥብ እንዲጣራ ማድረግ አለ.ያም ሥር ፍ/ቤት ጉዳዩ እንዲጣራ ማድረግ ይገባው ነበር ይህ ሳይጣራ በደፈናው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር ብቻ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት አግኝቷል ለማለት አያስችልም ምክንያቱም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ በግልፅ በመቀበል ወይም ባለመቀበል የተሰጠ ውሣኔ ባለመኖሩ ነው፡፡ ስለሆነም የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሙግት አመራር እና ጭብጥ አያያዝ ስህተት ያለው መሆኑን ከተረዳ ማረም ሲገባው ማለፉ እና የአመልካችን ጥያቄ ግልፅ ዳኝነት ያልሰጠበት ከመሆኑም አንፃር በክርክሩ አመራር ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የአ/አ ከተማ ፍርድ ቤቶች ሰበር ችሎትም ይህንን ማረም ሲገባው ማለፉ ተገቢ አይደለም፡፡

ስለሆነም ይኸው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ በመ/ቁ 1234/99 በ3/01/02 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10849 በ9/03/02 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የአ.አ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት በመ/ቁ 12433 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. በሚች እና በተጠሪ መካከል ጋብቻ ነበር በአመልካች ስላልተካደ፤ ጋብቻ ነበር ከተባለስ ጋብቻው በፍቺ ፈርሷል? አልፈረሰም? የሚለው የአመልካች መቃወሚያ ነጥቦች ላይ ግራቀኙን አከራክሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መዝገቡን ለአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ እንዲመለስ አዝዘናል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. *51893*

ሐምሌ *8* ቀን *2002* ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ እንዳልካቸው ዘለቀ ጠ/ቱ/ም/ድሮስ ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፣ ወ/ሮ ብዙዓለም መንግሥቱ ጠ/ዩሴፍ ደስታ ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መሃከል የነበረው ጋብቻ ከፈረሰ በኃላ ተጠሪ የጋራ ንብረት ለመካፈል የንብረት ዝርዝር አቅርበዋል፡፡ ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ውስጥም ለክርክር ምክንያት ሆነው ቤት የጋራ በመሆኑ አመልካች እንዲያካፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ የተመዘገቡት ከጋብቻ በፊት መሆኑንና ሐምሌ 4 ቀን 1999 ዓ.ም ከአ/አ ከተማ አስተዳደር የክ/ቀ/ክ/ከ/ የቤት ማስተላለፊያ ጽ/ቤት ጋር የቤት ሽያጭ ውል የፈረሙ አመልካች ብቻ እንጂ ተጠሪ አለመፈረማቸውን ገንዘቡንም አመልካች ከመ/ቤት ካገኙት ብድር እና ወደፊትም ከደሞዛቸው የሚከፈል በመሆኑ ቤቱ አመልካች የግል ንብረት ሊባል እንደማይችል ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ግራቀኙ ጋብቻ የመሠረቱት ሚያዚያ 22 ቀን 1998 ዓ.ም ሲሆን ፍቺ የተፈፀመው መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም ነው አከራካሪ የሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት እጣ የወጣውና ሽያጭ ውሉ ከአ/አ መስተዳድር ጋር የተፈረመው በጋብቻ ወቅት ሐምሌ 4 ቀን 1999 ዓ.ም በመሆኑ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው በሚል ከተቻለ በአይነት ካልተቻለ በሃራጅ ተሸጦ እንዲካፈሉ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የይግባኝ ቅሬታቸው ተሰርዞባቸዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው የኮንዶሚኒየም ቤት ምዝገባ የተከናወነው ከጋብቻ በፊት በመሆኑ የቤቱ ግዥ የተፈፀመው አመልካች ከአ/አበባ መስተዳድር የከ/ቀ/ክ/ከ የቤት ማስተዳደር መምሪያ ጋር በፈረሙት ውል መሆኑ የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ከአመልካች ደሞዝ በተወሰደ ብድር መሆኑ ለቀሪው ክፍያ ከባንክ ጋር የብድር ውል የፈረሙት አመልካች ብቻ በመሆናቸው እንዲሁም የቤቱ ርክክብ በጋብቻ ጊዜም ሆነ በፍቺ ወቅት ያልተፈፀመ በመሆኑ ቤቱ የአመልካች የግል ሃብት ነው በማለት ስር ፍ/ቤት ቤቱን አስመልክቶ የሰጠው ውሣኔ እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም ምንም እንኳን የኮንደሚኒየሙ እጣ በጋብቻ ወቅት የወጣ ቢሆንም አመልካች ምዝገባ ያደረጉት ከጋብቻ በፊት መሆኑና ከባንክ የተወሰደው ብድር ጋብቻው ከፈረሰ በኃላ ከአመልካች የሚከፈል ከመሆኑ አንፃር ተጠሪ ያላቸው መብት ምንድነው? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባለ ብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ግራቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የግራቀኙ የጋራ ንብረት ነው ወይስ የአመልካች የግል ንብረት ነው የሚለው ነው ስለ ባልና ሚስት የጋራ ንብረት የሚደነግገው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 62 በንዑስ ቁጥር ሁለት ስር በጋብቻ ወቅት በግብይት የተገኙ ንብረቶች የጋራ ንብረቶች እንደሆኑ ተመልክቷል በተያዘው ጉዳይ አከራካሪውን ቤት አመልካች የተመዘገቡት ከጋብቻ በፊት ስለመሆኑና ዕጣው የደረሰው ግን የሁለቱ ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ወቅት ስለመሆኑ ክርክር አላስነሳም ይህም ብቻ ሳይሆን አመልካች ከአ/አበባ አስተዳደር የቤት ማስተዳደር መምሪያ ጋር የቤቱን የሽያጭ ውል ያደረጉት ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ነው፡፡ አመልካች ለኮንዶሚንየሙ ቤት የተመዘገቡት ከጋብቻ በፊት ቢሆንም የቤቱ ባለቤት የሚያደርጋቸውን የሽያጭ ውል ያደረጉት ግን በጋብቻ ወቅት በመሆኑ ቤቱ በግብይት ተገኘ ሊባል የሚችለው የሁለቱ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ወቅት ነው አመልካች ውሉን ለብቻቸው መፈረማቸው ብቻውን ቤቱን የግል ንብረታቸው አያደርገውም የሽያጩን ውል ለብቻቸው ማድረጋቸው ቀርቶ በጋብቻ ወቅት የተገኘው ቤት በስማቸው መመዝገቡ እንኳን ንብረቱን የግል ንብረት እንደማያደርገው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 63/1/ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የሽያጩን ውል አመልካች ብቻ መፈረማቸው ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት ነው አያሰኘውም ሌላው አመልካች ቤቱ የግል ሊሆን ይገባል በማለት የሚከራከሩት ለቤቱ የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ከአመልካች ደመወዝ በብደር የተገኘ ገንዘብ መሆኑ እንዲሁም ቀሪውን ዕዳ ለመክፈል አመልካች ለብቻቸው ከባንክ ብድር መውሰዳቸውን ነው ይሁን እንጂ አመልካች ለቤቱ ግዥ ከደሞዛቸውም ሆነ ከባንክ ለወሰዱት ብድር ተጠሪም የጋራ ባለእዳ ከሚሆኑ በቀር ንብረቱን የአመልካች የግል ንብረት አያደርገውም በአጠቃላይ ምንም እንኳን አመልካች ለቤቱ የተመዘገቡት ከጋብቻ በፊት ቢሆንም እጣው የወጣው በጋብቻ ጊዜ ስለመሆኑና የቤቱ ባለቤት የሚያደርጋቸው የሽያጭ ውልም የተፈረመው በጋብቻ ውስጥ በመሆኑ ቤቱ የግል ነው መባሉ ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 62/2/ አኳያ ሲታይ ተገቢ በመሆኑ ቤቱን ከተቻለ በአይነት እንዲካፈሉ ካልተቻለ አንፋ ለሌላኛው የቤቱን ግምት ከፍሎ እንዲያስቀር በዚህም ካልተስማሙ ቤቱ በሃራጅ ተሽጦ የሚገኘውን ገንዘብ ግራቀኙ እንዲካፈሉ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ማለት አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል ግን ግራቀኙ ክርክር የቤቱን ዋጋ ለመክፈል ብድር ስለመወሰዱና ወደፊትም የቤቱ ቀሪ እዳ መከፈል ያለበት መሆኑን መረዳት ችለናል ተጠሪ የቤቱ የጋራ ባለሃብት ናቸው የተባለ በመሆኑ ቤቱ ለተገዛበት የብድር ገንዘብ እንዲሁም ቀሪ ክፍያም ካለ የጋራ ባለእዳ ሊሆኑ ይገባል በመሆኑም ለቤቱ መግዣ አመልካች ከደሞዛቸውም ሆነ ከባንክ ለወሰዱት እዳ እንዲሁም የቤቱ ቀሪ ክፍያ ካለም ግራቀኙ ለእዳው በጋራ ሃላፊ ሊሆኑ ስለሚገባ የስር ፍ/ቤት ይህን በተመለከተ ሳይወሰን ማለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 57488 የካቲት 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 80996 የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አከራካሪው የኮንደሚኒየም ቤት የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ እንዲካፈሉ መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም ቤቱን ለመግዛት አመልካች የወሰዱት ብድር እና እንዲሁም ከቤቱ ለሚፈለገው ቀሪ እዳ አመልካችና ተጠሪ በጋራ ባለእዳ ናቸው ብለናል፡፡ በመሆኑንም የሚፈለገውን እዳ ግማሽ ተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፣፣

3. ወጨና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም.አ

የሰ/መ/ቁ 50836

ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ቅድስት ተካ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የኔነሽ ተካ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወራሽነት ማስረጃን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በሟች ወ/ሮ መሠረት በሪ መጋቢት 7 ቀን 1995 ዓ.ም ኑዛዜ መሠረት የኑዛዜ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ኑዛዜውን በማጽደቅ አመልካች የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት አመልካች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሰረዝ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በመቃወሚያቸውም ኑዛዜው በህጉ የተመለከተውን መስፈርት አያሟላም ሟች ኑዛዜው ያደረጉበት የራሳቸው ባልሆነ ንብረት ላይ ነው የሟች ኑዛዜ ተጠሪን ነቅሏል ንብረቱም በተጠሪ የተሰራ ነው የሚሉ ክርክሮችን አንስተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪን መከራከሪያዎች በሙሉ ውድቅ በማድረግ ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞባቸዋል፡፡ በመቀጠልም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበው ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ማመልከቻ ሲቀርብ ፍ/ቤቱ ወራሽነትንና የውርስ ሃብቱን ድርሻ በማረጋገጥ ማስረጃ መስጠት ስላለበት በቅድሚያ የውርስ ሃብት ሊጣራ ይገባል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የውርስ ሃብት ተጣርቶ ባልቀረበበት ሁኔታ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወራሾች የውርስ ሃብት አጣርተው ሲቀርቡ መሆኑን የማንቀሳቀስ መብታቸው ተጠብቆ ውሳኔውን ሽሮታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ዋነኛ ቅሬታ በግራ ቀኙ መሃከል ያለው ክርክር ሟች ወ/ሮ መሠረት በሪ ያደጉት ኑዛዜ ሊፀና ይገባል አይገባም? የሚል ሆኖ ሳለ ተከራካሪዎቹ ያላነሱትን ክርክር መሠረት አድርጐ ውሳኔ መስጠቱ የህግ ስህተት ስለሆነ መታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ኑዛዜው ይሰረዝልኝ የሚል ሆኖ ሳለ በቅድሚያ የውርስ ሃብት እንዲጣራ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ቀርበው በፁሁፍ በሰጡት መልስ ፍ/ቤት የሚሰጠው ማስረጃ ወራሽነትን የማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን የሚደርሰው የውርስ ሃብት ድርሻም የሚያረጋግጥ መሆን ስላለበት ህጉ በአግባቡ ተተርጉሟል በማለት ውሳኔው እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች የኑዛዜ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው አመልክተው ፍ/ቤቱ በዚሁ መሠረት አመልካች ኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው ተገልጾ ማስረጃ ሰጠቷቸዋል፡፡ ተጠሪ ኑዛዜው በህጉ የተመለከተውን የአፃፃፍ መስፈርት ስላላሟላ ሟች ኑዛዜውን ያደረጉት የራሳቸው ሃብት ባልሆነ ንብረት ስለሆነና እንዲሁም ኑዛዜው ተጠሪን የነቀለ በመሆኑ አመልካች የኑዛዜው ወራሽ ሊባሉ አይችሉም በሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍ/ቤት መቃወሚያውን መርምሮ ተጠሪ ያቀረቡት መከራከሪያዎች ተቀባይነት የላቸውም ሲል የቀድሞውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን የወራሽነት ምስክር ወረቀት የሚሰጠው ወራሽነትን በማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን የወራሹን የውርስ ሃብት ድርሻም በማረጋገጥ ስለሆነ በቅድሚያ የውርስ ሃብት ሊጣራ ይገባል በማለት አመልካች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሸ) መሠረት የወራሽነት ምስክር ወረቀት የመስጠት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት ለአመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ወይም ምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል፡፡ የተሰጠው የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ጥያቄ ሲቀርብም ፍ/ቤቶች በቂ ምክንያት ሲኖር የሰጡትን ምስክር ወረቀት ሊሰርዙ እንደሚችሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 998(1) ስር የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪ ተቃውሞ ያቀረቡት አመልካች የውርስ ተጠቃሚ የሆኑበት ኑዛዜ ህጋዊነት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶቹ ሊመረምሩ የሚገባው የአመልካችን የውርሱ ተጠቃሚ ያደረጋቸው ኑዛዜ በህግ ፊት ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑን ነው፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን ኑዛዜው በህግ ፊት ተቀባይነት አለው የለውም የሚለውን መመርመር ሲገባው በግራ ቀኙ ክርክር ያልተነሳበትን ነጥብ መሠረት አድርጐ በቅድሚያ የውርስ ማጣራት ሳይደረግ የወራሽነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊሰጥ አይገባም ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ በኑዛዜ ለአመልካች የተሰጠውን ንብረት አመልካች ሊወስዱ አይገባም የሚሉ ሲሆን በንብረት ክፍፍል ጊዜ ተቃውሞ ከሚያቀርቡ በቀር የውርስ ሃብቱ ባለመጣራቱ ብቻ የአመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ሊሰረዝ የሚችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ሲገባው በግራ ቀኙ ክርክር ያልተነሳውን የውርስ ሃብት ማጣራት ጉዳይ አንስቶ ውሳኔውን መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 08219 መስከረም 22 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ችሎቱ የስር ፍ/ቤቶች የኑዛዜው ህጋዊነት አስመልክቶ የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር ተገቢ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 44561

ሐምሌ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ገነት በላይ ጠበቃ - ኮሎኔል መላኩ ካሣዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ፈኔት ተክሉ - ሞግዚት ነጋ ቦንገር በሌሉበት ይታያል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት መጋቢት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

10 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአቶ ተክሉ ነጋ ውርስ እንዲጣራ ለውርስ አጣሪ መርቷል፡፡ የውርስ አጣሪው የሟች አቶ ተክሉ ነጋ ወራሾች ህፃን ኬሩዝ ተክሉና ህፃን ፌኔት ተክሉ መሆናቸውንና የውርሱ ንብረት ክፍል የሚሆነውን ጥሬ ገንዘብና ያክሲዮን ድርሻ በመዘርዘር የውሣኔ ሐሳብ አቅርቧል፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ለአሁን አመልካች ለሥር ተጠሪ ከፔፕሲ ኮላ ዓለም አቀፍ መስሪያ ቤት የተከፈላቸው መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠው 166,449.97 የአሜሪካን ዶላር/አንድ መቶ ስልሣ ስድስት ሺ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ ከዘጠና ሰባት ሣንቲም/ የአሜሪካን ዶላር ለአመልካች ጥቅም የተገባ የኢንሹራንስ ፖሊስ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባለመኖሩ የውርስ ሃብት ነው በማለት የውርስ አጣሪው ያቀረበው ሃሳብ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡ የውርስ አጣሪው ከላይ መጠኑ የተገለፀው የአሜሪካን ዶላር አመልካች እንዲካፍሉ ያቀረበውን የውሣኔ ሐሳብ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማጽደቁ ተጠሪ ይህንን በመቃወም ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዋ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ ሟች አቶ ተክሉ ነጋ ከፔፕሲ ኮላ ዓለም አቀፍ ተጠሪ ጽ/ቤት ለአፍሪካ አህጉር ሥራ አስኪያጅ በሆኑበት ጊዜ የሕይወት ኢንሹራንስ የገባው እንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር 07/01/98 (ከታህሣሥ 19 ቀን 1990 ዓ.ም) እስከ አውሮፖውያን አቆጣጠር 05/21/2001 (ከግንቦት 13 ቀን 1993 ዓ.ም) ነው በዚህ ጊዜ 166,449.97(አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከዘጠና ሰባት ሣንቲም) የአሜሪካን ዶላር ለአሁን አመልካች (መልስ ሰጭ መክፈሉ ተረጋግጧል)፡፡ ይህ ገንዘብ የውርስ ንብረት ክፍል ሆኖ በወራሾች መካከል ብቻ ሊከፋፈል ሲገባው የሥር መልስ ሰጭ የአሁን አመልካች የሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ሣይሆኑ የገንዘቡ ተጠቃሚ እንደሆኑ መደረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ይግባኝ አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች በበኩላቸው ለከፍተኛው ፍ/ቤት መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት መስቀለኛ ይግባኝ ሟች አሜሪካዊና የሕይወት ኢንሹራንስ የገባው በአሜሪካን አገር በሚገኝ ኩባንያ ኢንሹራንስ ከፋዩም የአሜሪካን ኩባንያ በሆነበት ሁኔታ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የወሰነው የሥረ ነገር ሥልጣን ሳይኖረው ነው በማለት አመልክተዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተጠሪዋ ላቀረቡት ይግባኝ የሰጡትን መልስና የአሁን ተጠሪዎች ለአመልካች የመስቀለኛ ይግባኝ የሰጡትን መልስ ከተቀበለና ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ ጥያቄ ስላልተነሣ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው፡፡ የአሁን አመልካች የኢንሹራንስ ክፍያው ለሟች አሰሪ መስሪያ ቤት የከፈላቸው መሆኑን እንጂ የሕይወት ኢንሹራንስ ለእሳቸው ጥቅም የተደረገ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን ለማጣራት የኢንሹራንስ ውሉ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ ውሉ ተፈልጐ እንዳልተገኘ መሥሪያ ቤቱ ጥር 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች የሕይወት ኢንሹራንስ ውል የተለየ ተጠቃሚ መሆናቸውን የኢንሹራንስ ውሉ በማቅረብ ያላስረዱ ስለሆነ የሕይወት ኢንሹራንሱ የሟች የውርስ ንብረት ክፍል በመሆን ለሟች ልጆችና ወራሾች ብቻ የሚተላለፍ ነው በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ መሰረት በማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከኢንሹራንስ ገንዘቡ ግማሹን ትውሰድ በማለት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የሌለበት መሆኑን በመግለጽ ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ጉዳዩን ማየትና መወሰን የሚችለው በአሜሪካን ግዛት ውስጥ ያለ የስረ ነገር ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት መሆን ሲገባው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን አለኝ በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 በመተርጐም ረገድ የከፍተኛው ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሰርቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሕይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ የሚሆኑ ባል ወይም ሚስት መብት ሙሉ በሙሉ በሚያሣጣና የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን ወደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚች ወራሾች ሙሉ በሙሉ ለማስተላለፍ በሚችል መንገድ መተርጉም የለበትም፡፡ አመልካች የኢንሹራንስ ገንዘብ ተከፍሏቸዋል፡፡ የህይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ባይሆኑ ኖሮ አይከፈላቸውም ነበር ስለዚህ በህይወት ኢንሹራንስ ልዩ ተጠቃሚ ስለመሆናቸው አላስረዱም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ ድንጋጌዎች ከግምት ውስጥ ሣያስገቡ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ ሞግዚታቸው የተሻረ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዋ ፌኔት ተክሉ በሚል ስም በጋዜጣ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቶ በጋዜጣ ጥሪ የተደገላቸው ቢሆንም ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክር አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አመልካች ሚች ከገባው የሕይወት ኢንሹራንስ የምታገኘው ድርሻ የላትም የሕይወት ኢንሹራንስ ክፍያው የሚች ውርስ ንብረት ክፍል ስለሆነ የሕይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን የሚች ልጆችና ወራሾች ብቻ ይካፈሉ በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ትርጉምና የተፈፃሚነት ወሰን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ነጥቦች በዝርዝር መመርመር የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ የተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ አመልካች የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን በተመለከተ የዳኝነት ሥልጣን የላቸውም? የሚች አሰሪ መሥሪያ ቤት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ለእኔ መክፈሉ የሕይወት ኢንሹራንስ ውሉ ልዩ ተጠቃሚ መሆኔን ያስረዳል በማለት ያቀረቧቸውን ክርክሮች ተገቢነት ማየት ያስፈልጋል፡፡

1. አመልካች ሚች የህይወት ኢንሹራንስ ክፍያ 166,449.97(አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ ከዘጠና ሰባት ሣንቲም) ዶላር የተከፈላቸው መሆኑን በመግለጽ የኢንሹራንስ ውሉ የተገባው ከኢትዮጵያ ውጭ በመሆኑ የኢንሹራንስ ገንዘቡን የሚከፍለው የኢንሹራንስ ኩባንያ በውጭ አገር ያለ በመሆኑ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የላቸውም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ክርክር የተነሣው አመልካችና የሚች ወራሾች ማግኘት የሚገባቸውን የኢንሹራንስ ገንዘብ የኢንሹራንስ ኩባንያው ስላልከፈላቸው በኢንሹራንስ ኩባንያውና በአመልካችና የሚች ልጆች መካከል አይደለም፡፡ የሚች አሰሪ መሥሪያ ቤት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ከፍሏል፡፡ የመድን ሽፋን የሰጠው የኢንሹራንስ ኩባንያም በውሉ መሰረት ግዴታና ኃላፊነቱን ተወጥቷል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ የሕይወት ኢንሹራንስ የመድን ሽፋን የሰጠው ድርጅት በሚች መሥሪያ ቤት በኩል የከፈለው የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ ላይ መብት ያለው ማን ነው? የሚለው ነው፡፡ አመልካችም ሆኑ ተጠሪ በዜግነት ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሚች ውርስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 944 ድንጋጌ መሰረት የተጣራው በኢትዮጵያ ሕግ በኢትዮጵያ ግዛት ክልል ውስጥ ነው፡፡

የውርስ ማጣራት አንደኛው ተግባር የሚች ወራሾች እነማን እንደሆኑ መለየት የሚች ውርስ ሐብት ክፍል የሚሆነውንና የሚችን እዳ አጣርቶ መለየትና መወሰን የሚያጠቃልል ነው፡፡ በውርስ ማጣራት ሒደት አመልካች የተቀበሉት 166,447.97(አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ ከዘጠና ሰባት ሣንቲም) የአሜሪካን ዶላር የውርስ ንብረት ክፍል ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ጭብጥ ሲሆን ጥያቄው በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ለመወሰን የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው በመሆኑ አመልካች ጉዳዩን ለማየትና ለመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የላቸውም በማለት ያቀረቡት ክርክር በመዝገቡ የተያዘው ክርክሩ በአመልካችና የሚች ወራሾች በሆኑ ሁለት ኢትዮጵያውያን መካከል መሆኑን፣የክርክሩም መሰረታዊ ጉዳይ በሚች አሰሪ መስሪያ ቤት በኩል የተከፈለው ወደ አገር ውስጥ የተላከው የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ የሚች ውርስ ንብረት ክፍል ነው ወይስ አይደለም? የሚልና በውጭ አገር የሚገኙ የሕግ ወይም የተፈጥሮ ሰዎች በክርክሩ ተካፋይ የማይሆኑበት መሆኑን ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነው፡፡

2. ሁለተኛው ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ አመልካች የህይወት ኢንሹራንስ ክፍያው ለእኔ ተከፍሎኛል፡፡ ይህም የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ልዩ ተጠቃሚ መሆኔን የሚያስረዳ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ አመልካች የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ የተለዩ ተጠቃሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆናቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ በተለይም አመልካችን የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ በማድረግ ሚች የመድን ዋስትና ከሰጠው የመድን ድርጅት ጋር የገባውን ውል እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ውሉን ሊያቀርቡ አለመቻላቸው በሥር ፍርድ ቤትና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ለአንድ ለተለየ ተጠቃሚ የሚደረግ የህይወት ኢንሹራንስ ውል በዝርዝር የሚይዛቸው ጉዳዮችን የንግድ ሕግ አንቀጽ 195 በዝርዝር ይደነግጋል፡፡ አመልካች የኢንሹራንስ ፖሊሲው ልዩ ተጠቃሚ ነኝ ካሉ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 195 እና 701/1/ የተደነገጉትን ዝርዝር ጉዳዮች የሚያሥረዳ የኢንሹራንስ ውልና ፖሊሲ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታ አለባቸው፡፡ አመልካች ይህንን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በመደበውና ተቀብሎ ሪፖርቱን ባፀደቀው የውርስ አጣሪና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

አመልካች የሚች ልጆች ሞግዚትና የሚች ሚስት በመሆናቸው ምክንያት ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት በሚች መኖሪያ ቤት በኩል የኢንሹራንስ ገንዘቡ ተከፍሏቸዋል፡፡ የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡ አመልካች መክፈሉ ብቻውን አመልካች በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ መሆናቸውን አያስረዳም ከሚል መደምደሚያ ላይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የደረሰው ሚች የህይወት መድን ሽፋን ከሰጠው የኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር ያደረገው የኢንሹራንስ ውል እንዲላከለት ትእዛዝ ሰጥቶ የህይወት ኢንሹራንስ የውል ሰነዱ ተፈልጐ ሊገኝ አለመቻሉ የሚች አሰሪ መሥሪያ ቤት ከገለጹለት በኋላ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ መሆናቸው የተገለፀ መሆኑን አግባብነት ያለው ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ የሰጡት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉን ለማስቀረብና ፍሬ ጉዳዩን ለማጣራት ተገቢውን ጥረት ካደረጉ በኋላ በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ማስረጃ በመመዘን በመሆኑ አመልካች የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ መሆኔን አስረድቻለሁ በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተገቢነት የሌለውና የሰበር ችሎት በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሚች የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 695 በተደነገገው መሰረት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉን ያደረገው ለአመልካች ወይም ለልጆቹ ህፃን ኬራዝ ተክሉና ህፃን ፌኔት ተክሉ ልዩ ጥቅም ያደረገ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ የህይወት መድን ውል በመድን ውል በተጠቃሚነት ለተገለፀው ሰው ወይም ሰዎች ወይም ኢንሹራንስ ከገባው ሰው መብት ላላቸውና ስማቸው በተጠቃሚነት ላልተገለፀ ሰዎች ሊደረግ እንደሚችል ከንግድ ሕግ ቁጥር 692 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሚች በገባው የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ የሚሆነውን ሰው በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 የገለፀ በሆነ ጊዜ የኢንሹራንስ ውሉ መሰረት ገንዘብ ለማን ይከፈላል የሚለው ጥያቄ በዚህ መዝገብ አከራካሪ ጭብጥ ሆኖ አልቀረበም፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሚች ያደረገው የኢንሹራንስ ውል ለአመልካች ወይም ለልጆቹ ልዩ ጥቅም የተደረገ መሆኑን የማይገልጽና ለተለየ ተጠቃሚ ያልተደረገ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ ተገቢነት ያለው ቢሆንም ሚች ባደረገው የህይወት ኢንሹራንስ ውል በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ ወይም ተጠቃሚዎች ያልገለፀ በሆነ ጊዜ በህይወት ኢንሹራንስ ውል መሰረት በሚከፈለው ገንዘብ ላይ መብት የሚኖራቸው እነማን ናቸው? ጉዳዩስ የትኛውን የሕግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ይወስናል የሚለውን ሰፊ የሕግ ክርክር ያስነሳ ጭብጥ አስመልክቶ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔና የደረሱበት መደምደሚያ በዝርዝር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ሚች የተዋዋለው የህይወት ኢንሹራንስ ውል የኢንሹራንስ ውሉን ተጠቃሚ የማይገልጽ በሆነ ጊዜ የኢንሹራንስ ገንዘቡ ይገባናል ብሎ ለመጠየቅ የሚያስችሉ ሶስት የሕግ ድንጋጌዎች ያሉ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕጉንና የንግድ ሕጉን ድንጋጌዎች በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ የሕይወት ኢንሹራንሰ ውሉ ተጠቃሚ ባልተገለጸበት ጊዜ የሚች ወራሾች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የንግድ ሕግ ቁጥር 705 ድንጋጌዎችን በመጥቀስና መሰረት በማድረግ የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ እንዲሰጣቸው ጥያቄ የሚያቀርቡ መሆኑን የተጠሪ ሞግዚት በዚህ መዝገብ ያቀረቡትን ክርክርና የድንጋጌዎቹን ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ሚች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያደረገው የህይወት የኢንሹራንስ ውል የተለየ ተጠቃሚ ባልገለፀ ጊዜ ወይም የህይወት ኢንሹራንስ ውሉን ለወራሾቹ ጥቅም ያደረገው መሆኑን በኢንሹራንስ ውሉ ባልገለፀ ጊዜ የሟች ባል ወይም ሚስትና የኢንሹራንስ ውሉ ሲፈረም የተወለደው ልጅ የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡ እንዲሰጣቸው የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ እና /ለ/ በመጥቀስ የሚጠይቁና የሚከራከሩ መሆኑን አመልካች ከሥር ጀምሮ ያቀረቡትን ክርክርና የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በዚህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ የከተከራከሩበትን ጭብጥና ውሣኔ ለመስጠት ከላይ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎች ይዘት መሰረታዊ ግብና ዓላማ በተናጠል ማየትና የሕግ ድንጋጌዎች በአንድ ላይ ለማስፈፀም በሚሞክርበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮችንና ችግሮቹን ለመፍታት ለሕግ ድንጋጌዎቹ ሊሰጣቸው የሚገባውን ትርጉም በዝርዝር ማየትና ውሣኔ ላይ መድረስ የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጋዎች፣ ይዘት መንፈስና ዓላማና በአንድ ላይ ተፈፃሚ በማይደረጉበት ጊዜ የሚያጋጥመን ተጨባጭ ነባራዊ ችግር በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

ሀ. የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ ባህሪ ለመረዳት በኢትዮጵያ የውርስ ሥርአት ከሟች ወደ ወራሾች የሚተላለፈው መብትና ግዴታ በተመለከተ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን ጠቅላላ መርህ ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ በርካታ አገሮች ለምሣሌ ሩሲያ ከሟች ወደ ወራሾቹ በውርስ ሊተላለፉ የሚችሉ ንብረቶችና መብቶች በዝርዝር ያስቀምጣሉ፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826/2/ የሟች ውርስ ክፍል ሆነው ለወራሾቹ ሊተላለፉ የሚችሉ ንብረቶችና መብቶች ምንምን እንደሆኑ ከመዘርዘር ይልቅ በሟች መሞት የሚያቋርጡ የሟች መብቶችና ግዴታዎች ለሟች ወራሾችና የኑዛዜ ባለስጦታዎች የሚተላለፉ መሆኑን በመርህነት የሚደነግግ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ማለት በሟች መሞት ምክንያት ቀሪ የሚሆኑና ሟች በግሉ ብቻ ሊሰራባቸው የሚችሉ መብቶችና ሟች በግሉ ብቻ እንዲፈጽማቸው የሚገደድባቸው ግዴታዎች ውጭ ያሉ በሟች መሞት ምክንያት የማይቋረጡ መብትና ግዴታዎች ለሟች ወራሾች የሚተላለፉ መሆኑ በአጠቃላይ መርህነት ተደንግጓል፡፡

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 828 በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ጠቅላላ መርህ ለየት ባለ ሁኔታ ሕግ አውጭው የደነገጋቸው ልዩ የሕግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 “በውርስ ውስጥ የሚገኘው ስለሕይወት ኢንሹራንስ ውል” በሚል እርስ ንኡስ አንቀጽ 1 “ሟች ተጠቃሚውን ያልወሰነ እንደሆነ ወይም ኢንሹራንሱ ለሟች ወራሾች ጥቅም የተደረገ እንደሆነ ሟች በፈረመው ስለ ህይወት ኢንሹራንስ ውል አፈፃፀም የሚከፈሉ ገንዘቦች የውርስ ንብረት ክፍል ይሆናሉ” በማለት የሚደነግግ ሲሆን ንኡስ አንቀጽ 2 “ተቃራኒ ሁኔታ ሲኖር የውርስ ክፍል አይሆንም” በማለት ይደነግጋል፡፡

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ድንጋጌ በሞት ጊዜ እንዲከፈል የተደረገ የህይወት ኢንሹራንስ ውል መሰረት የሚከፈል የኢንሹራንስ ገንዘብ በሟች መሞት ምክንያት የማይቋረጥ ይልቁንም ገንዘቡ የሚጠየቀው ኢንሹራንስ ገቢው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ መሆኑን በመገንዘብ ሕግ አውጭው በሞት ጊዜ የሚከፈል የህይወት ኢንሹራንስ ውል በንግድ ሕግ ቁጥር 695 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ ወይም ተጠቃሚዎች የተደረገ በሆነ ጊዜ የኢንሹራንስ ገንዘቡ የውርስ ንብረት ክፍል እንደማይሆንና ወራሾቹ ድርሻ አለን ብለው የመብት ጥያቄ ሊያነሱ የማይችሉ መሆናቸውን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 2 በግልጽ የሚደነግግ ሲሆን፣የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ተከፋይ የሆነ ገንዘብ የሟች የውርስ ሐብት ክፍል የሚሆነው በመጀመሪያው ሟች “ለወራሾቹ” በሚል መንገድ ኢንሹራንስ ውሉ በተጠቃሚነት የገለፀ ከሆነ መሆኑን ሁለተኛው ሟች የኢንሹራንስ ተጠቃሚ ማን እንደሆነ ሣይገልጽ በቀረ ጊዜ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ጠቅላላ መርህ በተለየ ሁኔታ በህይወት ኢንሹራንስ ውል መሰረት የሚከፈል ገንዘብ በምን ሁኔታ የሟች የውርስ ሐብት ክፍል እንደማይሆንና የሟች ወራሾች የመብት ጥያቄ እንደማያነሱ የሚደነግግ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለ/ የንግድ ሕግ ቁጥር 705

የንግድ ሕግ ቁጥር 705 የህይወት ኢንሹራንስ ክፍያ የሚች የውርስ ክፍል ስለሚሆንባቸውን ሁኔታዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገጉትን ሁኔታዎች የሚያሰፋ ነው። ድንጋጌው የሕይወት ኢንሹራንስ ውሉ ለተለየ ተጠቃሚ የተደረገ መሆኑን በማይገልጽበት ጊዜ ብቻ ሣይሆን ሚች የኢንሹራስን ውሉ ተጠቃሚ ነው ብሎ የገለፀውን ሰው በንግድ ሕግ ቁጥር 703 መሰረት በመሻር ሌላ ተጠቃሚ ያልገለፀ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ወይም ተጠቃሚው ፈቃዱን ሣይገልጽ በመሞቱ ምክንያት ውድቅ በሆነ ጊዜ የኢንሹራንስ ገንዘቡ የሚች የውርስ ንብረት ክፍል እንደሚሆንና ለሚች ወራሾች እንደሚተላለፍ የሚገልጽ ነው። የንግድ ሕግ ቁጥር 705 "ተጠቃሚው ሣይለይ የተደረገ ኢንሹራንስ" በሚል ርእስ "ተጠቃሚው ተለይቶ ያልታወቀ እንደሆነ ወይም ተሸሮ እንደሆነ ወይም በሕይወት የሌለ በመሆኑ ውድቅ የሆነ እንደሆነ ስለሞት የተደረገው የኢንሹራንስ ዋናው ገንዘብ የሚከፈለው ኢንሹራንሱን ለተዋዋለው ሰው ውርስ ነው" በማለት በግልጽ ይደነግጋል።

ከዚህ በላይ የተደነገጉት የሕግ ድንጋጌዎች የተጠሪ ሞግዚት ሚች ባደረገው የሕይወት ኢንሹራንስ ውል መሰረት አመልካች የተቀበሉት ገንዘብ የሚች ውርስ ክፍል በመሆኑ ለሚች ወራሾች ብቻ ሊከፋፈል ይገባል በማለት የሚያቀርቡትን ክርክር የሚደግፍና የሚች ወራሾች የኢንሹራንስ ተጠቃሚው በኢንሹራንስ ውሉ ተለይቶ ባልተገለፀበት ጊዜ የሚኖራቸውን ሰፊ መብት የሚደነግጉና የሚችን ባል ወይም ሚስት በኢንሹራንስ ገንዘቡ መብት የሌለው መሆኑን የሚያሣዩ ናቸው።

ሐ. የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2

የንግድ ሕግ ቁጥር 701 "ለሞት በሆነ ኢንሹራንስ ተጠቃሚ የሆነ ሰው" በሚል ርእስ ሥር በንኡስ አንቀጽ 2 "ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም /ሀ/ ጋብቻው የተደረገው የኢንሹራንስ ውሉ ከተፈረመ በኋላ ቢሆን እንኳን የኢንሹራንስ ውል የፈረመው ባል ወይም ሚስት /ለ/ የኢንሹራንስ ውል ሲፈርም የተወለዱት የኢንሹራንስ ውል ፈራሚ ልጆች ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ተብለው ይቆጠራሉ" በማለት ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ ሚች የኢንሹራንስ ውሉን ተጠቃሚ ሣይገልጽ የኢንሹራንስ ውል ባደረገ ጊዜ ከኢንሹራንስ ውሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በኋላ ኢንሹራንስ ውል የተዋዋለው ሰው ጋር በጋብቻ የተሣሰሩ ሚስት ወይም ባልና የኢንሹራንስ ውሉ ሲፈረም ተወልደው የነበሩ ልጆቹ የኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ የሚሆኑ መሆናቸውን የሚደነግግ ነው። በዚህ ድንጋጌ መሰረት የኢንሹራንስ ውል ፈራሚው ባል ወይም ሚስት የሚች ወራሽ ባይሆኑም ተጠቃሚው ተለይቶ ያልተገለፀበት የህይወት ኢንሹራንስ ውል የሕግ ተጠቃሚና ባለመብት እንደሚሆኑና የሚች አንደኛ ደረጃ ወራሾች ከሚሆኑት ከሚች ልጆች መካከል የኢንሹራንስ ውሉ ሲፈረም የተወለዱት የኢንሹራንስ ውሉ የሕግ ተጠቃሚ እንደሚሆኑና የኢንሹራንስ ውሉ ከተፈረመ በኋላ የተወለዱት በዚህ ድንጋጌ መሰረት የተጠቃሚነት መብት የሌላቸው መሆኑን የሚደነግግ ነው።

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የንግድ ሕግ ቁጥር 705 ድንጋጌዎችና የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች እንዲሁ እንዳሉ በአንድ ላይ ተፈፃሚ ለማድረግ በምክር የተለያየ ውጤት የሚያስከትሉ መሆኑን በአመልካችና በተጠሪ መካከል በዚህ መዝገብ የተደረገው ክርክርና ፍርድ ቤቶቹ በየደረጃው የሰጡት ውሣኔ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል። ሚች የሕይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ ሣይገልጽ የገባው የህይወት መድን ገንዘብ የይገባኛል ጥያቄን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የንግድ ሕግ ቁጥር 705 ድንጋጌ ብቻ መሰረት በማድረግ የወሰነው ከፍተኛ ፍ/ቤት የኢንሹራንስ ገንዘቡ ለሚች ወራሾች (ልጆች ብቻ) ይከፋፈል በማለት የወሰነውን ሲሆን በተቃራኒው ጭብጡን የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ብቻ የሚወስን አመልካችና የኢንሹራንስ ውሉ ሲፈረም የተወለደችውን የሚች ልጅ ብቻ የኢንሹራንስ ተጠቃሚ እንደሆኑ የሚወሰንበት ሁኔታ እንደሚኖር ከላይ ይዞታቸውንና ዓላማቸውን በዝርዝር ያየናቸውን ድንጋጌዎች ያላቸውን ልዩነትና የሚያስከተሉት ህጋዊ ውጤት በመመርመር ለመገንዘብ ይቻላል።

4. በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን እነዚህ ተቃራኒ ይዘትና በተግባራዊ አፈፃፀምም የተለያየ ውጤት የሚያስከትሉ የሕግ ድንጋጌዎች ማለትም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 የንግድ ሕግ ቁጥር 705 እና የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች በምን መንገድ ቢተረጐሙ ሕግ አውጭው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያሰበውን ግብና ዓላማ ለማሣካትና ሁሉም ድንጋጌዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ለማድረግ ይቻላል? የሚለውን ጥያቄ በቅድሚያ መመለስ ያስፈልጋል፡፡

በሁለት የሕግ ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና በአንድ ላይ ሲፈፀሙ የሚያስከትሉትን ተቃራኒ ውጤት ለማስቀረት ፍርድ ቤቶች የተለያዩ የሕግ አተረጓጐም መርሆችን በመጠቀም የሕግ ትርጉም በመስጠት ችግሩን የሚያቃልሉ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ከላይ በተገለፁት ድንጋጌዎች በመካከል ያለውን መሰረታዊ ቅራኔ ለመፍታት ሌሎች ድንጋጌዎችን ለማስታረቅ ዘወትር የምንከተላቸው የሕግ አተረጓጐም ዘዴዎች (ጥበቦች) አገልግሎት የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤቶች የዚህ አይነት ችግር ሲያጋጥም የሚከተሉት የሕግ አተረጓጐም ጥበብ አንደኛው ከሁለቱ ሕጐች ማንኛው ቀድሞ እንደታወጀ ማንኛው በኋላ እንደታወጀ በመመርመር በኋላ የወጣው ሕግ ቀድሞ በወጣው ሕግ የተደነገገውን ድንጋጌ እንዳሻሻለው ወይም እንደሻረው ይቆጠራል የሚለውን የሕግ አተረጓጐም ዘዴ በመከተል በኋላ የታወጀውን ሕግ ተፈፃሚ በማድረግ ችግሩን ያቃልላሉ፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕጉም ሆነ የንግድ ሕጉ በአንድ ቀን ማለትም ሚያዝያ 27 ቀን 1952 ዓ.ም የታወጀ መሆኑን በመግቢያቸው የተገለፀ በመሆኑ ይኸ የአተረጓጐም ዘዴ ከላይ በገለጽናቸው የሕግ ድንጌዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለመፍታት የሚያስችለን ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሁለት የሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና በውጤት በአንድ ጉዳይ ልዩነት የሚያስከትል ሲሆን ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ሌላው የሕግ አተረጓጐም ዘዴ ስለ ልዩ ሁኔታ የተደነገገው ድንጋጌ በጠቅላላ የሕግ ድንጋጌዎች ላይ የበላይነትና ተፈፃሚነት ይኖረዋል የሚለው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 2 ለተደነገገው መሰረታዊ ጠቅላላ መርህ በልዩ ሁኔታ የተደነገገ ልዩ ድንጋጌ ሲሆን የሕይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ የሟች የውርስ ክፍል የሚሆንባቸውንና የማይሆንባቸውን ልዩ ሁኔታዎች የሚደነግግ ነው፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የንግድ ሕግ ቁጥር 705 ተጠቃሚው ሣይለይ የተደረገ ኢንሹራንስ የሚመለከት ደንቦችን የያዘ ልዩ ድንጋጌ ሲሆን የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎችም በሞት ጊዜ የሚከፈልና ተጠቃሚው ያልተገለፀበት የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ በልዩ ሁኔታ ባል ወይም ሚስት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የሚደነግግ ልዩ ድንጋጌ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች አንደኛውን ጠቅላላ የሕግ ድንጋጌ ሌላውን ልዩ የሕግ ድንጋጌ ነው ብሎ ለመፈረጅ የማይቻልና ልዩ የሕግ ድንጋጌ በጠቅላላ የሕግ ድንጋጌ ላይ የበላይነትና ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ የሚለውን የሕግ አተረጓጐም መርህ ለመከተል የሚያስቸግር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በእኛ በኩል በድንጋጌዎቹ መካከል ያለውን ልዩነት ለመፍታት ሕግ አውጭ እያንዳንዱን የሕግ ድንጋጌ የደነገገው በነባራዊ ህይወት ውስጥ ተፈፃሚ እንደሆነና አንድ ማህበራዊ ችግር እንዲፈታ አስቦ ነው፡፡ ስለዚህ ለአንደኛው የሕግ ድንጋጌ የሚሰጠው የሕግ ትርጉም ሌላውን ድንጋጌ ሙሉ በሙሉ ውጤት አልባ በማያደርግ መንገድና ሁሉም ድንጋጌዎች ውጤታማ የሚሆኑበትን የሕግ አተረጓጐም መከተል አለበት የሚለውን የሕግ አተረጓጐም መርህ ጠቃሚና አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ አተረጓጐም መሰረት ተጠቃሚው በኢንሹራንስ ውሉ ባልተገለፀበት ጊዜ የሟች ባል ወይም ሚስት የኢንሹራንሱን ገንዘብ ከሟች ወራሾች ጋር የሚካፈሉበትን ልዩ ሁኔታ በመከተል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 የንግድ ሕግ ቁጥር 705 እና የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ ድንጋጌዎች በማጣጣም የሟች ወራሾችም ሆኑ የሟች ባል ወይም ሚስት በሕግ የተሰጣቸውን መብት ሙሉ በሙሉ ሣያጡ የኢንሹራንሱ ገንዘብ እንዲካፈሉ በማድረግ ሁሉም የሕግ ድንጋጌዎች ውጤታማ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ የተሻለው የሕግ አተረጓጐም መንገድ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 705 ተጠቃሚው ተለይቶ ባልተገለፀበት የህይወት ኢንሹራንስ ውል መሰረት በሚከፈል የኢንሹራንስ ገንዘብ የመካፈል መብት ያላቸው የሟች ወራሾችና የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሰረት የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ የመሆን መብት ያላቸው የሟች ሚስት ወይም ባል የኢንሹራንስ ገንዘቡን የመጠየቅ በሕግ እንደ ልዩ ተጠቃሚ የሚቆጠር መብት ያላቸው በመሆኑ አንድ ላይ የኢንሹራንስ ገንዘቡ ተጠቃሚና ተካፋይ ሊሆኑ ይገባል ብለናል፡፡

5. የሟች ወራሾችና የሟች ባልና ሚስት ተጠቃሚው ተለይቶ ያልተገለፀበት የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ የጋራ ተጠቃሚ በሚሆኑበት መንገድ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 የንግድ ሕግ ቁጥር 705 እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ መተርጉም ያለባቸው መሆኑ መደምደሚያ ላይ ከተደረሰ በኋላ የሚነሣው ሌላው ጥያቄ የሚች ወራሾችና የሚች ባል ወይም ሚስት የኢንሹራንስ ገንዘቡን በምን ሁኔታ ሊካፈሉ ይገባል የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በእኛ በኩል አሁን ባለው የሕግ ሥርአት ሚስት ባሏን ባል ሚስቱን ያለኑዛዜ ለመውረስ የማይፈቀድላቸው መሆኑ ግምት ውስጥ በማስገባት የህይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚውን ሣይገልጽ የተዋዋለው ሚች በኢንሹራንስ ውሉ መሰረት ወቅታዊ ክፍያ ከባለንብረት የተከፈለ መሆኑ ካልተረጋገጠ የባልና ሚስት የጋራ ገቢ ከሆነው ገንዘብ (ደሞዝ) እየቀነሰ ሲከፍል የቆየ ነው የሚል ግምት የመያዝ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ግማሽ የሚች ባል ወይም ሚስት እንዲወስዱ ማድረግና የኢንሹራንስ ገንዘቡን ግማሽ የሚች ወራሾች ተካፍለው በመውሰድ የሚች የውርስ ሐብት ክፍል በማድረግ በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚደርሳቸውን ድርሻ የሚካፈሉበትን ሁኔታ መከተል ከሌሎች አማራጮች የተሻለና ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 የንግድ ሕግ ቁጥር 705 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ ሕግ አውጭው ሲደነግግ የነበረውን ሐሳብና ግብ ለማሣካት የሚያስችል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም የአመልካችና የተጠሪ ክርክርም ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥነውን የሕግ አተረጓጎም በመከተል መፍታት ሲገባቸው የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ለአመልካች በንግድ ሕግ ቁጥር 701 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ/ የተረጋገጠላትን መብት ሙሉ በሙሉ ዋጋ በሚያሣጣ ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 ንኡስ አንቀጽ 1 በመተርጉም የኢንሹራንስ ገንዘቡ የሚች የውርስ ክፍል ስለሆነ አመልካች መብት የላትም፡፡ የኢንሹራንስ ገንዘቡን የሚች ልጆችና ወራሾች ብቻ እኩል ይካፈሉ በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ- ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/መሰረት በማሻሻል አመልካች ከሚች ልጆችና ወራሾች ጋር የኢንሹራንስ ገንዘቡ ተጠቃሚ የመሆን መብት አላት በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ በሆነው 166,449.97(አንድ መቶ ስልሣ ስድስት ሺ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ) የአሜሪካን ዶላር ከጠዘና ሰባት ሳንቲም በተመለከተ የሚች ሚስት የሆኑት አመልካችና የሚች ልጆች ወራሽ የሆኑት ሕፃን ኬሩዝ ተክሉና ህፃን ፌኔት ተክሉ በሕግ ጥበቃ የተሰጠው መብትና ጥቅም አላቸው ብለናል፡፡
3. አመልካች የኢንሹራንስ ገንዘቡን ግማሹን ብር 83,224(ሰማኒያ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሃያ አራት) የአሜሪካን ዶላር ይውሰዱ ብለናል፡፡
4. የሚች ልጆች ወራሾች የሆኑት ህፃን ኬሩዝ ተክሉና ህፃን ፌኔት ተክሉ(ተጠሪ) ቀሪውን 83,224(ሰማኒያ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሃያ አራት) የአሜሪካን ዶላር እኩል ይካፈሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44025

ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሪት ፀሃይ ሃይሌ - ቀረበች

2. ወ/ሪት ጤናዬ ሃይሌ - ቀረበች

3. ወ/ሪት ኤልሳቤጥ ሃይሌ - አልቀረበችም

4. መስፍን ሃይሌ - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፈልቃ ቤኛ - ጠበቃ መላት ፈለቀ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65587 ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ክርክሩ በአሁኖቹ አመልካቾች ከሣሽነት የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካቾች ተጠሪን የከሰሱት ከአባታችን ልናገኝ የሚገባውን የውርስ ድርሻ ይዛ እየተጠቀመች ስለሆነ ውርስ አጣሪ ተሾሞ ድርሻችን እንዲለይ ይታዘዝልን በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጠችው ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበች ሲሆን፣ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን በመቀበል ክሱን ውድቅ አድርጐአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚሉበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካቾች የቀረበው የውርስ ይጣራልን ክስ /ጥያቄ/ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ የአመልካቾች አባት ሚስት ናት፡፡ የአመልካቾች አባት እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ አመልካቾች በዚሁ የአባታቸው እና የተጠሪ የጋራ ነው የተባለው ቤት ውስጥ በአባታቸው እና በተጠሪ ሲያድጉ ቆይተዋል፡፡ አባታቸው ከሞቱም በኋላም ተጠሪ እንደእናት በመሆን ስታሳድጋቸው እንደቆየች እና ንብረቱንም በጋራ ይዘው ሲያስተዳድሩት እንደነበር አመልካቾች በክርክራቸው ገልጸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት እንዲለይ እና የአባታቸውን ድርሻ በወራሽነታቸው ማግኘት ይችሉ ዘንድ ክስ የመሰረቱት ተጠሪ እነሱ ባላወቁት ምክንያት ከቤት ወጥታ በመሄድ ዘመዶቼናቸው ከምትላቸው ሰዎች ጋር በመቀመጥዋ እንደሆነ በሰበር አቤቱታቸው ላይ በግልጽ በማመልከት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪም ለሰበር አቤቱታው በጽሑፍ መልስ የሰጠች ሲሆን በአመልካቾች ክርክር በግልጽ በተነሱት ነጥቦች ላይ ምንም ማለት አልቻለችም፡፡ በዚህ ረገድ የመረጠችው በዝምታ ማለፍ ነው፡፡ በእርግጥ ከዚህ በፊት በሰበር ችሎቱ የተሰጡትን ውሳኔዎች በመጥቀስ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ትክክል ነው እንዲባልላት ተከራክራለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ችሎቱ ከጠበቃው ላቀረበው ጥያቄ ከተሰጠው ምላሽ ተጠሪዎች በፍሬ ነገር ረገድ ያነሱት ክርክር ትክክል እንደሆነ ለማረጋጥ ችለናል፡፡ የተጠሪ ጠበቃ ለቀረበለት ጥያቄ በሰጠው መልስ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ንብረቱ/ቤቱ/ በአመልካቾች ይዞታ ሥር እንደሆነ አረጋግጦአል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካቾች የውርስ ድርሻ የጠየቁበት ንብረት ሁለቱም ወገኖች ይዘውት በጋራ ሲያስተዳድሩት የነበረ በመጨረሻም (ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ) በአመልካቾች ይዞታ ሥር ያለ ነው፡፡ አመልካቾች ወደ ክስ ያመሩትም ንብረቱ በዚህ ደረጃ ላይ እንዳለ ተጣርቶ የአባታቸው ድርሻ እንዲታወቅና ወራሽነታቸው ለእነሱ እንዲሆን እንዲወሰንላቸው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ ንብረቱ በተጠሪ እጅ (ተይዞ) እንደቆየ በማድረግ የተጠሪን የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት ይኖረዋል የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪ የሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ. 24675 እና 28317 የሰጣቸውን ውሳኔዎች በመጥቀስ ያቀረበችው ክርክርም እንዳየነው ውሳኔዎቹ የተሰጡት በዚህ መዝገብ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር የተለየ በሆነ ፍሬ ነገር ላይ በመመስረት በመሆኑ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ በማለት የወሰኑት በፍትሐብሔር ሕጉ የተቀመጠውን የይርጋ ድንጋጌ እና የይርጋ መሰረተ ሃሳብ እንዲሁም የክርክሩን ፍሬ ነገር እግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባት በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 108209 የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65587 ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩ በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግና ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር በመግባት ግራ ቀኝ ወገኖችን በማከራከር ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት ይመለስለት ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

የሰ/መ/ቁ. 47622

ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ትእግስት ነጋሽ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ መንበረስላሴ ተኽሌ ለሁሉም - ጠ/ፈቃዱ ሞላ ቀረቡ

2. አቶ ሃብታሙ ነጋሽ

3. አቶ አሰፋ ነጋሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. ወ/ት መሳይ ነጋሽ

5. አቶ ደሳለኝ ነጋሽ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የውርስ ሃብት ለመካፈል የቀረበን ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የሟች አባታቸው አቶ ነጋሽ ደሳለኝ ወራሽ መሆናቸው ገልጸው የሟችና የአንደኛ ተጠሪ የጋራ ሃብት የሆነ ቤት ከነሰርቪሱና ሌሎች ንብረቶችን አንደኛ ተጠሪ ስለያዙ ውርስ እንዲጣራ አመልክተው ተጠሪዋ የአመልካችን ልጅነት ሳይክዱ ሟች በሰጡት ኑዛዜ አመልካች እንዲያገኙ ከተናዘዙት ብር 5,000(አምስት ሺህ) ውጪ ሊጠይቁ አይችሉም ብለው የተቃወሙ ሲሆን ሟች በቤቱና በሰርቪሱ እንዲሁም በቤት ቁሳቁስ ላይ ያላቸውን ድርሻ አንደኛ ተጠሪ በስማቸው አዛውረው እንዲጠቀሙና እሳቸው ስለሞቱ ንብረቱ በሙሉ ለቀሪዎቹ ተጠሪዎች እንዲተላለፍ ተናዘዋል፡፡ ሟች ለአመልካች ብር 5,000(አምስት ሺህ) ከመስጠት በቀር እንደሌሎቹ ልጆች አላካፈሉኝም፡፡ ከኑዛዜው ነቅለውኛል፡፡ በመሆኑም ኑዛዜው ሊፈረስ ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ጥያቄው ከ3 ወር በኋላ የቀረበ በመሆኑ ይርጋ ያግደዋል፣ ኑዛዜው ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ነው፣አመልካች ብር 5,000(አምስት ሺህ) ስለተሰጣቸው ከውርስ አልተነቀሉም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ቀሪዎቹም ተጠሪዎች ወደክርክሩ ጣልቃ ገብተው ባቀረቡት ክርክር ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ነው፣ድርሻ አንሶኛል ለምትለው ድርሻዋን ለማወቅ የውርስ አጣሪ ስለተሾመ የአጣሪውን ሪፖርት መጠበቅ ግድ ይላል፣ውርስ የመጣራቱ ሂደት እስኪጠናቀቅ መዝገቡ ተዘግቶ ይቆይ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ተመልክቶ የይርጋ መቃወሚያው ውድቅ ካደረገ በኋላ ኑዛዜው ለአመልካች በግልጽ 5,000(አምስት ሺህ) ይከፈላት ስለሚል ለመፈፀም የሚቻል ነው፣በኑዛዜው ስጦታ ስለተደረገላቸው ተነቅያለሁ ማለት አይችሉም፣ሟች ለወራሾቻቸው በፈለጉት መጠን ሃብታቸውን በኑዛዜ ማከፋፈል ይችላሉ፣ስለሆነም ኑዛዜው የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጉ አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ ብር 5,000(አምስት ሺህ) የጠበቃ አበል እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ጠበቃ አበል እንዲከፍሉ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ብቻ ለመመርመር ሲያስቀርብ ኑዛዜውን በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ ግን ውድቅ አድርጉታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው፣በኑዛዜው የተመለከተው ድርሻ ማነሱን፣ገንዘቡ ከየትኛው ሃብት ላይ እንደሚከፈልና ማን እንደሚከፍል ስለማያመለክት ለመፈፀም የሚቻል እንዳልሆነ፣ ያለምንም ህጋዊ ምክንያት ከኑዛዜ የተነቀሉ መሆኑን ገልጸው ኑዛዜ እንዲፈረስ ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፣በማለት ውሳኔ እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም ይህን የአመልካች አቤቱታ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪዎችም በሰጡት የፁሁፍ መልስ፤ሟች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 920 በሚፈቅደው መሰረት የጋራ ሃብት ድርሻቸውን አንደኛ ተጠሪ በሕይወት እያሉ ወራሾች እንዳይካፈሉ አግደዋል፣ከ2-5 ያሉት ተጠሪዎች ከአንደኛ ተጠሪ የተወለዱ በመሆኑ ተጠሪዋ በህይወት እያሉ እንደማይጠይቁ በመገመት ለአመልካች ብር 5,000(አምስት ሺህ) ሰጥተዋል፣በማለት የሰር ፍ/ቤት ውሳኔ የሕግ ስህተት ስለሌለው ውሳኔው እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ሟች አባታቸው በተውት ኑዛዜ ለልጆቻቸው ያደረጉት ክፍፍል ከማነሱም በላይ ያለምንም ምክንያት ከውርስ የነቀሏቸው በመሆኑ ኑዛዜው እንዲሻርላቸው ነው፡፡ ከውርስ ተነቅያለሁ የሚለውን በተመለከተ በኑዛዜው አመልካች ብር 5,000(አምስት ሺህ) የተሰጣቸው መሆኑን አመልካችም አልካዱም፡፡ ክርክራቸው አነስተኛ ድርሻ ማግኘታቸው ከውርስ ሃብት እንደተነቀሉ የሚያስቆጥር መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ከውርስ መነቀል ማለት ደግሞ ከውርስ ሃብቱ ምንም አይነት ድርሻ አለማግኘት እንጂ አነስተኛ ድርሻ ማግኘት ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ሟች የውርስ ሃብት ክፍፍል ሲያደርጉ ለአመልካች ከሚገባቸው በላይ አሳንሰው ሰጥተዋቸዋል የሚል ክርክር ያቀርባሉ፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.913 የኑዛዜ ቃል የተናገሩን ተቃራኒ ሃሳብ የሚገልጽ ካልሆነ በቀር በውርስ ሃብት አንድ ድርሻን ወይም አንድ ንብረትን ሟቹ ለወራሾቹ መስጠቱ ተራ የሆነ የክፍያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደንብ እንጂ እንደ ኑዛዜ ስጦታ እንማይቆጠር ያመለክታል፡፡ ይህ ድንጋጌ በኑዛዜ የኑዛዜ ስጦታ (legacy) እንዲሁም የክፍያ ደንብ (rule of partition) ማድረግ እንደሚቻል የሚናገር ነው፡፡ በመርህ ደረጃ አንድ ሰው ከውርስ ሃብት መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ አያስኘውም፡፡ ይልቁንም ይህ አይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ወራሽ ለወራሹ አንድን ሃብት ሲናዘዝ የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ(legacy) አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብን (partition) በመከተል የሚከናወን ነው፡፡ የክፍያ ደንብ የሚከናወነውም ከአንቀጽ 1117 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ይህ የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 18394 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ አመልካች የሚች ልጅ በመሆናቸውም ለእርሳቸው የተሰጠው ብር 5,000(አምስት ሺህ) ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት የክፍያ ደንብ ነው፡፡ ምንም እንኳን ሚች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1017 መሰረት ውርስ ሃብታቸውን በሚፈልጉት መልክ መደልደል ቢችሉም ድልድል ሲያደርጉ ግን አንድ ተወላጅ ከሚደርሰው ከሩብ የበለጠ ጉዳት ደርሶበት ከሆነ ክፍፍሉ እንዲቀር ጥያቄ ማቅረብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1123/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ቢሆን ሚች ሃብታቸውን በሙሉ አንደኛ ተጠሪ በሕይወት እስካሉ እንዲጠቀሙበትና ከእሳቸው ህይወተ-ህልፈት በኋላ ግን ሃብቱ በሙሉ ለሌሎች ልጆች እንዲሰጥ ተናዘዋል፡፡ ለአመልካች እንዲሰጣቸው የተናዘዙት ብር 5,000(አምስት ሺህ) ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የሚቹ ድርሻ ንብረታቸው ተጣርቶ አመልካች ሊደርሳቸው ከሚገባው ከሩብ የበለጠ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ አለመሆኑ ሊረጋገጥ ይገባ ነበር፡፡ ከ2 እስከ 5 ያሉት ተጠሪዎችም ቢሆኑ በስር ፍ/ቤት የአመልካች ድርሻ እንዲታወቅ ውርሱ ሊጣራ እንደሚገባ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ግን አመልካች የደረሰባቸው ጉዳት ምን ያህል መሆኑን ሳያጣራ አመልካች ብር 5,000(አምስት ሺህ) የተሰጣቸው በመሆኑ ከኑዛዜ አልተነቀሉም በሚል ብቻ ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ ምንም እንኳን አመልካች ከውርስ ተነቅያለሁ የሚል ክርክር ቢኖራቸውም በተጨማሪ ግን በክፍፍሉ ድርሻቸው ያለአግባብ ማነሱንና ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን የሚያሳይ ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት አመልካች አልተነቀሉም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ቢሆንም የአመልካችን የክፍያ ደንብ ጥያቄ ሳይመረምር አልፎታል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት አመልካች ክፍያውን በተመለከተ ያቀረቡት ጥያቄ ሳይመረምር ማለፉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ተከታዩ ውስኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 145134 ሰኔ 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 82145 ሐምሌ 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የሚች የአቶ ነጋሽ ደሳለኝ የውርስ ሃብት እንዲጣራ አድርጐ አመልካች የደረሰባቸውን ጉዳት ካረጋገጠ በኋላ የኑዛዜውን ውጤት አስመልክቶ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 45587

ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ አተረፈች ዘውዴ - ወኪል ዶ/ር ደረጀ አሻጋሪ - ቀረቡ

ስለ ሁለተኛ አመልካች ጠበቃ ወኪል እስራኤል ተክሌ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ዘውዱ ወሰኔ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሳይናዘዝ የሞተ ሰው ውርስ ተጠቃሚዎችን በሚመለከት በሕጉ ያለውን ቅደም ተከተልና አፈፃፀሙን የሚመለከቱትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ አያልነሽ ዘውዴ ወራሽ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ መያዛቸውንና የሟቿ ንብረቶች በተጠሪዎች መያዛቸውን ገልጸው ውርስ እንዲያጣራላቸው የውርስ አጣሪ በፍርድ ቤት እንዲሾምላቸው ህዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም በስር ፍርድ ቤት ቀርበው ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃውን ያገኙት የሟች እህትና ወንድም መኖራቸውን በመደበቅ በመሆኑ የወራሽነት ማስረጃው ተቀባይነት የለውም በማለት የተጠሪ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄ ወድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዮን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለተው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙ ከሟች ጋር ያላቸውን የዝምድና ደረጃ በማጣራት ተጠሪ የሟች እናት እህት ልጅ ስለሆኑ ሟችን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 842 እና ተከታዮቹ መሠረት ሊወርሱ ይችላሉ ወደ ሚለው ድምዳሜ በመድረስ የሟች ወ/ሮ አያልነሽ ዘውዴ የውርስ ሐብት እንዲጣራ በማለት አዟል፡፡ በዚህ ፍርድ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ አመልካቾች ተጠሪ ያገኙትን የወራሽነት ማስረጃ ሳያሰርዙ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄን መቃወም እንደማይችሉ ገልፆ ውርስ አጣሪው በፍርድ ቤት እንዲሾም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት የይግባኝ ባዩችን ቅሬታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቀርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 843 እና 844(3) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች የሟች ወንድምና እህት ተጠሪ ደግሞ የሟች እናት እህት ልጅ ስለሆኑ ውርሱ ሊጣራ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ የጽሁፍ መልሳቸው እንዲያቀርቡ በችሎት ተነግሯቸው ከሄዱ በኋላ በተሰጣቸው ቀነ ቀጠሮ ሳያቀርቡ በመቅረታቸው በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ የሟች እናት እህት ልጅ በመሆን የሟች ወንድም እና ልጅ እያሉ ሟችን ሊወርሱ ? ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚለው ጭብጥ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የሟች ወራሽነታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ከተገቢው ፍርድ ቤት ካገኙ በኋላ የሟች ውርስ ንብረት እንዲጣራላቸው ለስር ፍርድ ቤት አቤቱታ ሲያቀርቡ አመልካቾች የሟች እህትና ወንድም እያሉ ተጠሪ ሊወርሱ አይችሉም በማለት የውርስ ማጣራት ሂደት እንዳይጀመር ተቃውሞ ማንሳታቸውን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ተቃውሞ ሳይቀበለው የቀረው ተጠሪ የሟች እናት እህት ልጅ ስለሆነ በተተኪነት ወራሽ ሊሆኑ ይችላሉ በሚል ምክንያት ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ ተመልክቷል፡፡

በመሰረቱ በውርስ ህጋችን ውስጥ ያሉት ደንቦች ሳይናዘዝ የሞተ ሰው ወራሾች በቀጥታ ከሟች ውርስ ተካፋይ ሊሆኑ የሚችሉ የሟች የስጋ ዘመዶች እና እነዚህ ወገኖች ከሌሉ እነዚህን ወገኖች በመተካት የሚወርሱ ወገኖች በሚል በሁለት መንገዶች ከፍለው ያስቀምጣሉ፡፡ በሌላ አገላለጽ የሟች የስጋ ዘመዶች በሟች ውርስ ሊካፈሉ የሚችሉት በቀጥታ ወራሽነት ወይም በተተኪነት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 842 ተከታዩቹ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ሕጉ የሟችን ወራሾች ቅደም ተከተል አስቀምጧል፡፡ የሟቹ የመጀመሪያ ወራሽ የሟች ልጆች እንደሆኑ ሕጉ በአንቀጽ 842 ስር በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከሌለ የሟች ንብረት ለሁለተኛ ደረጃ ዘመዶች እንደሚተላለፍ እነዚህ ሁለተኛ ደረጃ ዘመዶች የሚባሉበትም የሟች እናትና አባት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆናቸውን የሚች አባትና እናት ሚችን ቀድሞ ከሞቱ የእነርሱ ተወላጆች ማለትም የሚች ወንድምና እህት ወይም የወንድሞቹና የእህቶቹ ተወላጆች እናትና አባቱን በመተካት በሚች ውርስ እንደሚካፈሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 843 እና 844 ድንጋጌዎች ይዘት የሚያሳየን ጉዳይ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 844(3) ድንጋጌ ከሚች እናት እና አባት በአንዱ መስመር ወራሽ ቢታጣ የሚች ውርስ ወደ ሌላው መስመር በሙሉ ሊተላለፍ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ተተኪ ወራሽነት የተፈጻሚነት ወሰን ወደታች በሚቆጠሩ ተወላጆች እንጂ ወደ ጎን በሚቆጠር ዝምድና ትስስር አለመሆኑን ነው፡፡ ይህ ችሎትም የድንጋጌዎቹ አፈፃፀም በዚህ መልኩ ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 47957 በቀረበው ተመሣሣይ የህግ ክርክር ከአዋጅ ቁጥር 454/97 በየትኛውም እርከን የሚገኘውን ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካቾች የሚች ወ/ሮ አያልነሽ ዘውዴ እህቶች ናቸው ሚች ሌሎች እህትና ወንድሞች ያላቸው መሆኑንም ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የሚች እናት እህት ልጅ መሆናቸውን በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጅ ሳይሆኑ የሚች እናት እህት የሆኑት (የሚች አክስት) ልጅ ሲሆኑ የተጠሪ እናት ወደ ጐን የሚቆጠሩ የሚች የስጋ ዘመድ ናቸው፡፡ በዚህ አግባብ የሚቀርብ የወራሽነት ጥያቄ ምላሽ የሚያገኘው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 843 እና 844 ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ ሚች ወ/ሮ አያልነሽ ዘውዴ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ (ልጅ) የሌላቸው ሲሆን እነዚህ ወገኖች አለመኖራቸው ከተረጋገጠ የሚችን ውርስ ሊወስዱ የሚገባቸው የሚች እናት እና አባት ሲሆኑ በውርሱ የሚካፈሉት በሁለተኛ ደረጃ ወራሽነት ነው፡፡ የሚች እናት እና አባት በሕይወት አለመኖራቸው የተረጋገጠ ሲሆን እነዚህ ወገኖች ሳይኖሩ ሲቀሩ በሚች ውርስ ሊካፈሉ የሚገባቸው የሚች እህትና ወንድሞች ናቸው፡፡ የሚች እህትና ወንድሞች ሚችን የሚወርሱት ደግሞ ወላጆቻቸውን ተክተው ነው፡፡ የሚች እናት ወደታች የሚቆጠር ሌላ ልጅ አልተዉም፡፡ ለሚች እህትና ወንድም ያሉት በአባት መስመር ብቻ ስለመሆኑ ተጠቅሷል፡፡ እንዲህ ሲሆን የሚች ውርስ ተጠቃሊሎ የሚሄደው በአባታቸው ልጆች በኩል እንጂ ሚችን ወደ ጎን በሚቆጠሩ የአሁኑ ተጠሪ እናት ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 843 እና 844 ድንጋጌዎችን አፈጻጸም በሚገባ ሳይለይ በደፈናው ተጠሪ ተተክተው ሚች ወ/ሮ አያልነሽን መውርስ ይችላሉ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ወራሽ ሊሆን የማይችል ሰው ደግሞ የሚች ውርስ ንብረት ይጣራልኝ የሚልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከመነሻውም የሚች ውርስ እንዲጣራላቸው ይዘው የቀረቡት ማስረጃ ሕጋዊ ባለመሆኑ የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታውን ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም አልነበራቸውም ለማለት የሚያስችል ነው፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተጠሪ የያዙት የወራሽነት ማስረጃ በማስረጃነቱ በማንኛውም የክርክር ደረጃ ተቃውሞ የሚቀርብበት ሆኖ እያለ ማስረጃው ባልተሰረዘበት ሁኔታ አመልካቾች የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ሊከራከሩ አይችሉም ሲል የአመልካቾችን ይግባኝ ሳይቀበል ማለፉና የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆ5ኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 132791 ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77713 መጋቢት 21 ቀን 2001 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የሚች ወ/ሮ አያልነሽ ዘውዴ እናት እህት ልጅ በመሆናቸውና ሚች ደግሞ እህትና ወንድም ያላቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 843 እና 844 መሠረት ተተኪ ወራሽ ሊሆኑ አይችሉም የሚች ውርስ ይጣራልኝ በማለት አቤቱታ ለማቅረብም መብትና ጥቅም የላቸውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.42546

ሀምሌ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ተስፋልደት ኪዳኔ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ዘሀቡ ይመር

2. አቶ ፀጋዬ ኪዳኔ የሶስቱም } ጠበቃ አቶ ዘመነ ፍቅሬ - ቀረቡ

3. አቶ ገብረህይወት ኪዳኔ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የአመልካችና የተጠሪዎች የክርክር መነሻ አቶ ኪዳኔ ንዎቱ በህይወት በነበሩበት ጊዜ አድርገውታል የተባለውን ኑዛዜ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተጠሪዎች ሚች ኪዳኔ ንዎቱ ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ አለ በማለት ለቀድሞው ልደታ አውራጃ ፍርድ ቤት በማቅረብ ሚያዝያ 24 ቀን 1984 ዓ.ም አስወስነዋል፡፡

የአሁን አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሚች አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ ስለ ግልፅ ኑዛዜ አደራረግ የተደነገገውን መሥፈርት የማያሟላ ሚች ካሏቸው ወራሾች ልጅና ወራሹ የሆንኩትን እኔን አመልካችን የረሣና የእኔን መብትና ጥቅም የሚጎዳና በዝምታ የሚነቅል ትክክለኛ የሚች ኑዛዜ ሣይሆን የሀሰት ሰነድ በመሆኑ ከዚህ በፊት የልደታ አውራጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 631/84 ሚያዝያ 24 ቀን 1984 ዓ.ም ኑዛዜው ህጋዊ መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠው ውሣኔ ይሰርዝልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሚች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም አደረጉት የተባለው ኑዛዜ ራሳቸው የፃፉት ወይም እርሳቸው እየተናገሩ ሌላ ሰው የፃፈው መሆኑን አይገልፅም፡፡ ኑዛዜው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 ንዑስ አንቀፅ 2 ፎርማሊቲ የማያሟላ ስለሆነ ፈራሽ ነው በማለት የአውራጃው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሰርዟል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ኑዛዜው "እኛም ከላይ በስም የተገለፅነው አቶ ኪዴኔ ንዎቱ ክፍሌ ሀብትና ንብረታቸውን ለ.... በኑዛዜ ሲሰጡ አይተንና ሰምተን ፈርመናል" የሚል ሀረግ ያለው መሆኑን በመግለፅ ኑዛዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን መሥፈርት ያሟላል በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የሌለበት መሆኑን በመግለፅ ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ- ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ጥር 5 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች የኑዛዜ ተጠቃሚና ወራሽ መሆናቸውን ለማስረዳት ያቀረቡት ኑዛዜ ትክክለኛ ሰነድ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች በኑዛዜው ላይ በምስክርነት የተገለፁትን ሰዎች በፍርድ ቤት በማስረጃነት ያላቀረቡት ኑዛዜው በሀሰት የተዘጋጀ መሆኑን ያሣያል፡፡ ኑዛዜው ህጋዊ ነው ቢባል እንኳን ሚች ያለምንም ምክንያት እኔን ከውርሱ የሚነቅል ኑዛዜ በማድረግና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 938 መሠረት ከውርስ የነቀለበትን ምክንያት ስላልገለፀና ኑዛዜው የሚች ወራሽ የሆንኩት የረሣና ጉዳት ያደረሰብኝ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1123 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረብነው ክርክር አላግባብ የታለፈብኝ በመሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው 1984 ዓ.ም በፍርድ ቤት ታይቶ ህጋዊነቱ የተረጋገጠውን ኑዛዜ አመልካች ኗሪነታቸው በውጭ አገር ነው በማለት ኑዛዜውን በሌለንበት ለማስፈረስ ያደረጉትን ጥረት ዘርዝረን ያቀረብነውን ይግባኝ የከፍተኛው ፍረድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ ኑዛዜው የህጉን ፎርም ያሟላ ነው አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር የህግ መሠረት የለውም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1123 በመጥቀስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የፅሑፍ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ሚች አቶ ኪዳኔ ንዎቱ ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በተጠሪዎች የሚያስገኘውን መብትና በአመልካች የወራሽነት መብት ላይ የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው? የሚለውን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. አመልካች ሚች አቶ ኪዳኔ ንዎቱ ያደረጉት ግልፅ ኑዛዜ በሀሰት የተዘጋጀ ነው፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 881 ፎርማሊቲ አያሟላም በማለት ያቀረቡት ክርክር ማስረጃ የመመዘንና ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የአመልካችንና የተጠሪን ማስረጃዎችና የኑዛዜ ሰነዱን በመመርመር ኑዛዜው ህጋዊ ፎርማሊቲዎችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚሉና የሚች ያደረጉት ትክክለኛ ኑዛዜ መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር የቀረበውም የኑዛዜውን ትክክለኛነትና ህጋዊ መስፈርት ያሟላ መሆኑን በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ሣይሆን ኑዛዜው የሚያስከትለውን ውጤት አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ውሣኔ ለመስጠት ነው፡፡ ስለሆነም በማለት በሰበር የሚያቀርበው ክርክር ህጋዊ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. ሚች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ትክክለኛና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 881 ድንጋጌዎች መስፈርት የሚያሟላ ሰነድ ነው፡፡ ሆኖም ሚች ያደረጉት ኑዛዜ በባህሪው የተለያዩ የህግ ጥያቄዎችን የሚያስነሣ ይዘት ያለውና የሚች ኑዛዜ በህግ ረገድ የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው? የሚች ኑዛዜ ተፈፃሚነትስ በምን መንገድ መሆን አለበት የሚሉትን ጥያቄዎች የሚያስነሣ ነው፡፡

ሚች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ መሠረታዊ ይዘት ሲታይ “እኔ አቶ ኪዳኔ ንዋቱ ክፍል በአዲስ አበባ ከፍተኛ 24 ቀበሌ 13 የቤት ቁጥር 1370 ነዋሪ የሆንኩ በሰው ልጅ ላይ በመኖር መሞትም ስላለ ሐብትና ንብረቴን በሙሉ ለግል ቤቱ ወ/ሮ ዘሀቡ ይመር ችኮልና ልጆች 1/ አቶ ፀጋይ ኪዳኔ ንዎቱ 2/ አቶ ገብረህይወት ኪዳኔ ንዎቱ በእኔ ስም ያለውን ሀብትና ንብረቴን በሙሉ ለልጆችና ለባለቤቱ የሰጠኋቸው በመሆኔ በትክክል አእምሮዬ አስቤ የተናዘዝኩ ስለሆነ ከእነዚህ ሌላ በእኔ ንብረት ተጠቃሚ እንደሆኑ ያልፈቀድኩና ሐብትና ንብረቴም ወራሾች መሆናቸውን አረጋግጬ ተናዝጥለሁ የሚል ነው፡፡

ይኸ የሚች ኑዛዜ መሠረታዊ ዓላማው የሚች ንብረት ወራሾች በኑዛዜው ውስጥ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪዎች ብቻ መሆናቸውን ማረጋገጥ መሆኑን በኑዛዜው ውስጥ “ከእነዚህ ሌላ በእኔ ንብረት ተጠቃሚ እንደሆኑ ያልፈቀድኩና የሐብትና ንብረቴ ወራሾች መሆናቸውን አረጋግጬ ተናዝጥለሁ፡፡ በማለት ካደረጉት የኑዛዜው ማደማደሚያ ሀረግ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሚች በኑዛዜው የንብረታቸው ጠቅላላ ወራሾች ተጠሪዎች ብቻ እንደሆኑ ሀሳብና ፍላጎት የነበራቸው መሆኑንና በኑዛዜው ውስጥ ስማቸው ያልተገለፀ ሌሎች የሚች የህግ ወራሾች በውርሣቸው ተካፋይ እንዳይሆኑ እንደሚፈልጉ ከእነዚህ ሌላ በእኔ ንብረት ተጠቃሚ እንደሆኑ ያልፈቀዱ መሆኑን በመግለፅ ኑዛዜ ትተው አልፈዋል፡፡

አመልካች የሚች አቶ ኪዳኔ ንዎቱ ልጅና ወራሽ መሆናቸውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መጋቢት 26 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች ይኸንን የአመልካች በፍርድ የተረጋገጠ ወራሽነት የሚያስቀርና ፍርዱ የተሰረዘ ወይም የተሻረ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ውሣኔ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸም ሚች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 842 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚች ልጅና አንደኛ ደረጃ ወራሽ መሆናቸው በፍርድ በተረጋገጠው በአመልካች የወራሽነት መብትና ከሚች ውርስ ንብረት ድርሻቸው እንዲሰጣቸው በሚያቀርቡት ጥያቄ ላይ ምን ህጋዊ ውጤት ያስከትላል? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ሚች በኑዛዜው ስማቸው ከተጠቀሱት ውጭ ያሉ ወራሾች በውርሳቸው እንዲካፈሉ ያልፈቀዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይኸም ሚች በስም ሣይጠቅሱ ከተጠሪዎች ውጭ ያሉ ያለ ኑዛዜ ወራሾች በሙሉ በውርሳቸው እንዳይካተት ግልፅ በሆነ ቃል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 937 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መሠረት ለመንቀል ኑዛዜ ያደረጉ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ ሚች ከተጠሪዎቹ ውጭ ያለ ኑዛዜ ወራሽ ነኝ ብሎ በውርሱ ተካፋይ ለመሆን የሚመጣ ማንኛውም ወራሽ ከውርሣቸው እንዲሣተፍ ፈቃድ የሌላቸው መሆኑን በመግለፅ አመልካችን በቀጥታ ስማቸውን በመጥቀስ ሣይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ከውርስ ለመንቀል ኑዛዜ አድርገዋል፡፡ ሆኖም ሚች አመልካችና ሌላ ያለ ኑዛዜ ወራሽ ነኝ ብሎ የሚመጣ ሰው በውርሣቸው ተካፋይ እንዳይሆን በመግለፅ ያደረጉት ኑዛዜ አመልካች በሚች ውርስ በወራሽነት እንዳይሣተፉ የማድረግ ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡ ምክንያቱም አመልካች የሚች ልጅና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው ከውርስ ለመንቀል የደረሰበትን ምክንያት በኑዛዜው ውስጥ ካልገለፀ በቀር ልጁን ወይም ወደታች የሚቆጠር ተወላጁን ከውርስ ለመንቀል ያደረገው ኑዛዜ የማይፀናና ህጋዊ ውጤት እንደማይኖር የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 938 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ የሚደነግግ በመሆኑ ነው፡፡

ሚች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ባደረጉት ግልፅ ኑዛዜ ውስጥ ስሙ ያልተገለፀ ወራሻቸው በውርሳቸው እንዲሳተፉ ፈቃድ የሌላቸው መሆኑን የገለፀ ቢሆንም በኑዛዜው ስማቸው ከተገለፁት ሁለት ልጆቻቸው ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪ ውጭ ያሉ ወራሾቻቸውን ለምን በውርሳቸው ተካፋይ እንደሆኑ እንዳልፈለጉና ከውርስ በኑዛዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲነቀሉ በኑዛዜው ውስጥ የሰጡት ምክንያት የለም፡፡ አመልካች የሚች ልጅና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 842 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ በመሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሚች ምክንያቱን ሣይገልፅ ከውርስ ለመንቀል ያደረጉት ኑዛዜ የማይፀና መሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 938 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ ሚች ያደረጉት ኑዛዜ አመልካች በሚች ውርስ በመሣተፍ ድርሻውን ከመጠየቅ የሚገድበው አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ያደረጉት ኑዛዜ አመልካች በሚች ውርስ በወራሽነት እንዳይሣተፍ የማድረግና ከውርሱ የመነቀል ውጤት የሚያስከትል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ሚች ያደረጉት ኑዛዜ የአመልካችን ከውርስ መነቀል ህጋዊ ውጤት ካላስከተለ ያሚች ሚስትና የኑዛዜ ተጠቃሚ ለሆኑት አንደኛ አመልካች የሚያስገኘው መብት ምንድን ነው? የሚለው ነጥብ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው ነው፡፡ ሚች አንደኛ ተጠሪ ከልጆቻቸው ከሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ጋር በመሆኑ የጠቅላላ ሀብትና ንብረት ወራሽ መሆናቸውን በኑዛዜአቸው ገልፀው ሚች አንደኛ ተጠሪ ካላቸው ሀብት ውስጥ አንድ የተለየ ንብረት እንደወሰዱ ሣይሆን ከሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ጋር በመሆኑ ያላቸው ሀብት በጠቅላላ ወራሽ እንደሆኑ የተናዘዙ በመሆኑ አንደኛ ተጠሪ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 912 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት የሚች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ ናቸው፡፡

የሚች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ የሆነ ሰው በኑዛዜው ውስጥ ሚች ተቃራኒ ውጤት ያለው መሆኑን ካልገለፀ በስተቀር የሚች ያለኑዛዜ ወራሽ እንደሆነ እንደሚቆጠር በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 915 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሚች አንደኛ ተጠሪ በሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪዎች ጋር የጠቅላላ የንብረታቸው ወራሽ መሆናቸውን ከመግለፅ ውጭ ሌላ የገለፁት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ አንደኛ ተጠሪ እንደ ሚች ያለኑዛዜ ወራሽ (አንድ ልጅ) ተቆጥረው በውርሱ የመካፈል መብት ይኖራቸዋል፡፡ ስለሆነም ሚች ጥር 30 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ሚስታቸው የሆኑት አንደኛ ተጠሪ እንደሚች አንድ ወራሽ ተቆጥረው በውርሱ የመሣተፍ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

4. የመጨረሻውና እልባት ሊያገኝ የሚገባው ሚች ለሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪ ያደረጉት ኑዛዜ ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው የሚለው ነው፡፡ ሚች በኑዛዜአቸው ሁለተኛ ተጠሪና ሶስተኛ ተጠሪ ልጆቻቸው መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ሚች ያደረገው ኑዛዜ ከአለው የውርስ ንብረት አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የትኛውን መውሰድ እንዳለባቸው የሚዘረዝር አይደለም፡፡ ኑዛዜው አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር በመሆን የጠቅላላ ሀብትና ንብረቱ ወራሽ መሆናቸውን የሚገልፅ ነው፡፡ ስለሆነም የሚችን ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪ ያደረገው ኑዛዜ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 913 በሚደነግገው መሠረት የተደረገ የክፍያ ደንብ ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል ኑዛዜው ሁለተኛ ተጠሪና ሶስተኛ ተጠሪ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር በመሆን የሚች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን ከሚገልፅ በስተቀር እያንዳንዳቸው ከውርሱ ንብረት ስለሚደርሳቸው ድርሻ የማይዘረዝር በመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2017 መሠረት የተደረገ የሀብት ክፍፍል ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኑዛዜው ሚች ልጃቸውና አንደኛ ደረጃ ወራሻቸው የሆነውን አመልካች በውርሱ እንዳይካፈል ለመንቀል አስበው ያደረጉትና አመልካችን ለመንቀል የተናገሩት ቃል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 938 ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀውን መስፈርት የማያሟላ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የሌለው በመሆኑ ሚች ለሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪዎች ያደረጉት ኑዛዜ ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ልጆቻቸውና ወራሾቻቸው መሆናቸውን ከማረጋገጥ ውጭ የተለየ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ ሚች ጥር 30 ቀን 1984 ያደረጉት ኑዛዜ ህጋዊ ውጤት ስንመረምረው ኑዛዜው አመልካች ከውርስ የሚነቀል የሚያስከትል አይደለም፡፡ አንደኛ ተጠሪ እንደ ሚች አንድ ወራሽ ተቆጥረው በሚች ውርስ እንዲሳተፉ የሚያስችልና ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች የሚች ልጆችና ወራሾች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ሚች ያደረጉት ኑዛዜ ህጋዊና ፎርሙን ያሟላ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ኑዛዜው አመልካችና በተጠሪዎች መብት ላይ የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት ምን እንደሆነ ሣይዘረዝሩ ማለፋቸው ተገቢ ሆኖ ባለማግኘታችን ውሣኔአቸውን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት አሻሽለናል፡፡ በዚህ መሠረት አንደኛ ተጠሪና የሚች ሚስት እንደ አንድ የሚች ልጅና ወራሽ ተቆጥረው የሚችን ውርስ ከልጆቻቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጋር የመካፈል መብት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የሚችን የውርስ ሀብት አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ ሶስተኛ ተጠሪና አንደኛ ተጠሪ እኩል ድርሻ የማግኘት መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የሚች ኑዛዜ በከፊል ህጋዊ ውጤት የሌለው በመሆኑ የሚች የውርስ ንብረት አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ ሶስተኛ ተጠሪና አንደኛ ተጠሪ በወራሽነት ተሣትፈው በእኩል ድርሻ ያገኛሉ በማለት ወስነናል፡፡
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44800

ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አብዱራዛቅ ሐሚድ - ጠ/አስቻለው አሻግሬ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ መንበረ አድማሱ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የመያዣ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ነው፡፡ አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ሐሚድና ቤተሰቡ የግብርና ውጤቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከተጠሪ ላይ ለወሰደው ብድር አመልካች በአ/አበባ ከተማ ወረዳ 23 ቀበሌ 12 ውስጥ የሚገኘውን ቤት በመያዣ ያስመዘገቡ ሲሆን አቶ ሐሚድ ይስሐቅ የተባሉ ግለሰብም 2 ቤቶች በመያዣ ሰጥተዋል፡፡ ተበዳሪው ብድሩን አጠናቆ ባለመክፈሉ ባንኩ በመያዣ የያዛቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች በሃራጅ ለመሸጥ በመንቀሳቀሱ ባንኩ የአቶ ሐሚድ ይስሐቅ ቤቶችን በሐራጅ ሽጦ እዳውን በሙሉ ከፍሎ አጠናቋል፡፡ እዳው ተከፍሎ ስለተጠናቀቀ በመያዣ የሰጠሁት ቤት ካርታ እንዲመልስልኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ የመያዣው ውሉ ከተፈረመ 10 አመት ያለፈው በመሆኑ ቀሪ ሆኗል፡፡ ስለዚህ ባንኩ ቤቱን በሐራጅ ለመሸጥ የጀመረውን እንቅስቃሴ እንዲያቆም የያዘውን ካርታ እንዲመልስ፣ ያልተከፈለ እዳ ካለ የሂሳብ መግለጫ እንዲያቀርብና ቀሪውን ገንዘብ ከፍዬ ቤቴ ከመያዣነት እንዲለቀቅልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተበዳሪው የወሰደው ብድር ተከፍሎ ያልተጠናቀቀ በመሆኑና በፍ/ብ/ህ/ቁ 3058(1) የተመለከተው የ10 አመት ጊዜ ከማለፉ በፊት በመያዣ ንብረቱ ላይ እንቅስቃሴ የጀመረ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ዋነኛ አቤቱታ የመያዣው ውል ከተመዘገበ 10 አመት ስላለፈው በፍ/ብ/ህ/ቁ 3058(1) መሰረት መያዣው ቀሪ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የአመልካችን ቅሬታ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች ሐሚድና ቤተሰቡ የግብርና ውጤቶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለወሰደው ብድር ቤታቸውን በመያዣ ሰጥተዋል፡፡ የመያዣ ውሉም የተመዘገበው በ1987 ዓ.ም መሆኑን እንዲሁም ተበዳሪው ድርጅት ብድሩን መክፈል ባለመቻሉ ተጠሪ ለአመልካች ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ መስጠቱን አመልካች አልካዱም፡፡ አመልካች መያዣው ቀሪ ነው በማለት የሚከራከሩት የፍ/ብ/ሕ/ቁ 3058(1)"ን" በመጥቀስ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ድንጋጌ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ አመልካች የጠቀሱት ይህ ድንጋጌም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አስር ዓመት ድረስ ነው፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ የመያዣ ውል ውጤት የሚኖረው መያዣው ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ እስከ 10 አመት ድረስ ነው፡፡ በመሆኑም በመያዣ ውሉ ምክንያት በሚገኙ ማናቸውም መብቶች መገልገል የሚቻለው ይኸው የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ የጊዜ ዘመን ሊራዘም የሚችለው 10 ዓመቱ ከማለፉ በፊት ውሉ እንዲታደስ አዲስ ምዝገባ ተከናውኖ ከሆነ ብቻ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 3058(2) እንገነዘባለን፡፡ በመሰረቱ ይህ ህግ አመልካች እንደሚሉት የይርጋ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ይርጋ ማለት በህግ ተለይቶ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ በአንድ ጉዳይ ክስ ለማቅረብ የሚከለከልበት የህግ ፅንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ በመሆኑም ይርጋ አንድ ሰው በጉዳዩ ላይ መብት ያለው ቢሆንም እንኳን ይህንን መብቱን ለመጠየቅ የማይችልበትን ገደብ የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ክልከላም ተፈፃሚ የሚሆነው ክስ ከቀረበ በኋላ ተከሳሹ የይርጋ መቃወሚያ አንስቶ የተከራከረ ከሆነ ነው፡፡ ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ ክስ አቅርቦ ተከሳሽ ክሱ በይርጋ ቀሪ መሆኑን በመግለፅ ካልተቃወመ ክሱ ተቀባይነት አግኝቶ መታየት ይቀጥላል፡፡ የጊዜ ገደቡ በማለፉ ብቻ ፍ/ቤት የይርጋውን በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ክሱን ውድቅ ሊያደርግ አይችልም፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 3058(1) የሚያስቀምጠው የይርጋን ጽንሰ-ሐሳብ አይደለም፡፡ የተጠቀሰው አንቀፅ የሚናገረው በህጉ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ማለፍ የመያዣው ውሉን ቀሪ (lapse) የሚያደርገውና ከዚሁ ጊዜ በኋላ መያዣ ውሉ ተጠቃሚ የሆነው ሰው በመያዣው ላይ ያለው መብት የሚያበቃበትን ሁኔታ ነው፡፡ የመያዣ ውሉ ከተመዘገበ በኋላ 10 ዓመት ሆኖት እንደሆነና እንዲታደስ ካልተጠየቀ ጠያቂ ባይኖርም አቃቤ መዝገቡ መያዣውን እራሱ ሊሰርዘው እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1632(2) ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም መያዣ ሰጪው 10 አመት በማለፉ መያዣው እንዲሰረዝ ጥያቄ ባያቀርብም መዝጋቢው አካል ራሱ ምዝገባውን ሰርዞ መያዣውን ቀሪ ሊያደርገው ይገባል፡፡

በሌላ በኩል መያዣው ነሐሴ 17 ቀን 1987 ዓ.ም የተመዘገበ ቢሆን በመያዣ የተያዘው ቤት አመልካች ክስ እስከመሰረቱበት ህዳር 12 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ አለመሸጡን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካችም ይህንኑ ጊዜ መሰረት አድርገው ነው መያዣው ቀሪ ነው ሲሉ የሚከራከሩት፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መያዣው ከተመዘገበ በኋላ ተበዳሪው እዳውን ባለመክፈሉ 10 አመቱ ሳያልፍ ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ለአመልካች በመስጠቱ መያዣው ቀሪ አልሆነም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች የተባለው ማስጠንቀቂያ የደረሳቸው መሆኑን አልካዱም፡፡ ክርክራቸው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የይርጋ ጊዜን ማቋረጥ የሚቻለው ለዋና እዳ እንጂ ለማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ አይደለም የሚል ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው በፍ/ብ/ህ/ቁ 3058 ስር የተቀመጠው የጊዜ ገደብ የይርጋ ጊዜ ገደብ ባለመሆኑ ስለይርጋ ማቋረጫ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል ግን ባለገንዘቡ የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ 10 ዓመት ከማለፉ በፊት በመብቱ መገልገል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጀምሯል ሊባል የሚችለው መቼ ነው? የሚለው ሊታይ ይገባል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ለሰጠው ብድር መያዣ የያዘ ባንክ ብድሩ ካልተከፈለው የ30 ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ንብረቱን ለመሸጥና የባለቤትነት ስሙን ለገዢ ለማስተላለፍ እንደሚችል በቁጥር 3 ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ባንኮች የመያዣ መብታቸውን መገልገል የሚጀምሩት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለመሆኑ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ቢሆን ተጠሪ ለአመልካች ጥቅምት 24 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ በመስጠት በመብቱ መገልገል ጀምሯል፡፡ መያዣው ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው 10 ዓመት ሳያልፍ ነው፡፡ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ቤቱን ሳይሸጥ የ10 ዓመቱ ጊዜ አልፎ ሊሆን ይችላል፡፡ የቤቱ ሽያጭ ሳይጠናቀቅ 10 አመቱ ማለፉ ብቻውን ግን መያዣውን ቀሪ አያደርገውም፡፡ ሊታይ የሚገባው ተጠሪ በመብቱ መገልገል የጀመረበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ደግሞ መያዣው ቀሪ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለው ለማለት አልተቻለም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 78317 ታህሳስ 09 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 64469 ጥር 05 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ውሳኔው ስለፀና ይህ ችሎት ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ትዕዛዙ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 42897

ጎንደር 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አየለ ሐብተየስ - ጠ/ውብሸት ክብሩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ሚ/ር ኖቼራ ጃካርሎ
2. ሚ/ር ኖቼራ ፍሪንኮ

} ጠ/ሻምበል ተሾመ ደምሴ ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው አመልካች ለፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ ከተጠሪዎች ለፎቶ ቤትነት ለ10 አመት የተከራዩትን ቤት መብራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሐ በመቁረጥ የፎቶ ቤት ስራው ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥ ስላደረጉ መብራቱን ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ላሉት 76 ቀናት የተቋረጠ ጥቅም ብር 64,752(ስልሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት) ተጠሪዎች እንዲከፍሉና መስመሩን እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው አመልካች የተከራዩት ቤቱን እንጂ ውሐና መብራቱን አይደለም፣የኤሌትሪክ ቆጣሪው የሚገኘው የሕብረት ባንክ የተከራየው ህንፃ ውስጥ ነው፣ለስራ እንዲያመቸው ባንኩ የኤሌክትሪኩንና የውሐውን መስመር ለግሉ እንድናደርግ ስለጠየቀ ተገቢ ማስጠንቀቂያ ለአመልካች በመስጠት መስመሩ መቋረጡ በሕግም ሆነ በሞራል የሚያስነቅፍ ስላይደለ የተቋረጠ ገቢ ልንከፍል አይገባም፣ክፈሉ እንኳን ከአገር ውስጥ ገቢ በሚቀርብ ማስረጃ ሊወሰን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የመብራት መስመሩ በኪራይ ስምምነት ውስጥ ስላልተካተተ እና ህብረት ባንክ በሚጠቀምበት ህንፃ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ የመብራት መስመሩ ይቀጠልልኝ ሊሉ አይችሉም፡፡ ነገር ግን ተጠሪዎች አመልካች ሌላ የሃይል አቅርቦት አማራጭ ለመፈለግ የሚያስችል ቢያንስ የ1 ወር ጊዜ መስጠት ሲገባቸው ከቅን ልቦናና ከልማዳዊ አሰራር ውጪ የሆነ ተግባር በመፈፀማቸው የ1 ወር ትርፍ የመተካት ሐላፊነት ስላለባቸው በርትእ ብር 4000(አራት ሺህ) እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅረበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪዎች ቤቱን ያከራዩት ለፎቶ ቤት ንግድ ስራ በመሆኑና ከፎቶ ማንሳት፣ማጠብና ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች በአሌትሪክ ሃይል አማካኝነት የሚሰሩ እንደመሆኑ መስመሩን ማቋረጣቸው አይነተኛ የውል መጣስ ተግባር ስለሆነ ለተቋረጠ ገቢ ብር 64,572(ስልሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሁለት) ኪለፈሉ ይገባ፣የተቋረጠውን መስመር መልሰው ይቀጥሉ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን ሽሮ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ችሎቱም አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ ሊታይ የሚገባቸው ጭብጦች ተጠሪዎች የኤሌትሪክ መስመሩን መቁረጣቸው የውል መጣስ ተግባር መሆን አለመሆኑ ነው ከተባለ ተጠሪዎች በውሉ መሰረት ሊፈጽሙና በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ሊከፍሉ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ አለመሆኑ ናቸው፡፡ ተጠሪዎች ለአመልካች ቤት ማከራየታቸውን ሳይክዱ የሚከራከሩት ያከራዩት ቤቱን ብቻ እንጂ የኤሌትሪክ መስመር አለመሆኑ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ቤቱን ከመከራየት ጋር በኤሌትሪክ መስመሩ የመጠቀም መብት አግኝተዋል አላገኙም የሚለውን ከግራ ቀኙ ስምምነት እና አግባብ ካለው ሕግ አኳያ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የተጠሪዎችን ንብረት አመልካች በቅን ልቦና ከሌሎች ሰዎች ላይ ተከራይተው ፍጹም ፎቶ የሚል ድርጅት ከፍተው የሚጠቀሙበት በመሆኑና በቤቱ ላይ ላወጡት ወጪ ማካካሻ ይሆን ዘንድ ለ10 አመት ያለምንም ክፍያ እንዲጠቀሙበት ግራ ቀኙ ተስማምተዋል፡፡ በዚህ ስምምነት ላይ በግልጽ አመልካች የኤሌትሪክ መስመር ስለመከራየታቸው የተመለከተ ነገር የለም የፌ/መ/ደረጃ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የተከራዩት ቤቱን ብቻ እንጂ የመብራት መስመር አይደለም ያሉትም በስምምነቱ ላይ የኤሌትሪክ መስመር ስለመከራየታቸው በግልጽ ባለመመልከቱ ነው፡፡ ነገር ግን ከስምምነቱ አመልካች ቤቱን የሚጠቀሙት ለፎቶግራፍ ማንሳት፣ማጠብና ማተም ስራ መሆኑን ተጠሪዎች ለአመልካች ቤቱን ሲያከራዩ ሚያውቁት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ አንድ ውል ደግሞ ሊተረጉም የሚገባው በተዋዋዮች መሃከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትና የመተማመን ግንኙት መሰረት በማድረግና ጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርአት በመከተል በቅን ልቦና ሊሆን እንሚገባው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732/1/ ያመለክታል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪዎች ቤቱን ለአመልካች ሲያከራዩ አመልካች ቤቱን ለምን አገልግሎት እንደሚጠቀሙበት ያውቁ የነበረ በመሆኑና የአመልካችም ስራ ያለኤሌትሪክ መስራት የማይቻል መሆኑን ሊገነዘቡ የሚችሉ ሆኖ ሳለ ቤቱን ብቻ እንጂ ኤሌትሪኩን እንዲጠቀሙ አልተስማማንም የሚለው የተጠሪዎች ክርክር የቅን ልቦና ተቃራኒ የሆነ ነው፡፡ በተጨማሪ ውል ሲተረጉም ተዋዋዮች ውላቸውን ከማድረጋቸው በፊት ወይም በኋላ የነበሩበት ሁኔታ ሊመዘን እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ. 1734/2/ ያመለክታል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪዎች አመልካች ቤቱን ብቻ እንጂ ኤሌትሪክ መስመሩን አብረው አልተከራዩም ይበሉ እንጂ ስምምነት ካደረጉበት ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ መስመሩን እስካቋረጡበት ጊዜ ድረስ አመልካች በኤሌክትሪኩ መስመር ሲጠቀሙ መቆየታቸው ግራ ቀኙ ስምምነት ባደረጉ ጊዜ ሃሳባቸው ምን እንደነበረ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ለአንድ ቤት የሚዘረጋው አንድ የኤሌትሪክ መስመር ከመሆኑ አኳያ ተጠሪዎች ቤቱን ሲያከራዩ ተከራይ በዚሁ የኤሌትሪክ መስመር የመጠቀም መብት ሊኖረው ይገባል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1355 ስር እንደተመለከተውም በአንድ ቤት ከፊል ላይ ብቻ የመኖር መብት ያለው ሰው ለጋራ አገልግሎት በተቋቋሙት ነገሮች ለመጠቀም መብት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ የኤሌትሪክ መስመርም ለአጠቃላይ ቤቱ እንዲያገለግል የሚዘረጋ በመሆኑ አመልካች ለተከራዩት ቤት በኤሌትሪክ መስመሩ የመጠቀም መብት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከክርክሩ እንደተገነዘብነው ተጠሪዎች መስመሩን ያቋረጡት የመብራት ቆጣሪው ህብረት ባንክ በተከራየው የሕንፃው ክፍል ውስጥ የሚገኝ በመሆኑና ለስራ እንዲያመቸው መስመሩን ብቻውን እንዲጠቀምበት በመጠየቁ ነው፡፡ ነገር ግን አከራዩ ከፊል ህንፃውን ካከራየ በኋላ ሌሎች የህንፃውን ክፍሎች ሲያከራይ የመጀመሪያውን ተከራይ ጥቅም መጠበቅ እንዳለበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2947 ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ለህብረት ባንክ ከፊል ህንፃውን ሲያከራዩ አመልካችን በመብት እና ጥቅም በሚጐዳ መልኩ ሊሆን አይገባም፡፡

የአመልካች ጥያቄ ወድቅ የተደረገበት ሌላኛው ነጥብ አመልካች ቤቱን እንዲገለገሉበት የተሰጣቸው በነፃ በመሆኑ ውሉ ለተጠሪዎች ግዴታን ብቻ የጣለ በመሆኑ ሊተረጐም የሚገባው ተጠሪዎችን በሚጠቅም መልኩ ነው በሚል ነው፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን አመልካች ቤቱን ያለምንም ክፍያ እንዲገለገሉበት የተስማሙ ቢሆንም ለዚህ ስምምነት ምክንያት የሆነው ግን አመልካቾች በቤቱ ላይ ከፍተኛ ወጪ ያወጡበት በመሆኑ ላወጡት ወጪ ማካካሻ እንዲሆን ነው፡፡ ስለሆነው የተደረገው ውል አመልካች ቀደም ሲል ያወጡት ወጪ ከኪራዩ ገንዘብ ጋር እንዲጣጣ ታሳቢ ተደርጐ የተደረገ እንጂ ተጠሪዎች ምንም አይነት ጥቅም ያላስገኘ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ውሉም ፈጽሞ ጥቅም ለማስገኘት እንዳልተደረገ ውል ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1739 መሰረት ግዴታው በቀላል አኳኋን ሊተረጐም ይገባል መባሉ አግባብ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም አመልካች ቤቱን ብቻ እንጂ የኤሌትሪኩን መስመር አልተከራዩም የሚለው የተጠሪዎች ክርክር ከፍ ሲል በተዘረዘሩት ምክንያቶች ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች የአምስት ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት የኤሌትሪክ መስመሩን መቁረጣቸው መሰረታዊ የውል መጣስ ተግባር መሆኑን ተረድተናል፡፡

ተጠሪዎች የውል መጣስ ተግባር ፈጽመዋል ከተባለ ቀጥለን ይህ ድርጊት ስለሚያስከትለው ሃላፊነት እንመለከታለን፡፡ ውል ያልተፈፀመለት ሰው ውሉ እንዲፈፀምለት ወይም ውሉ እንዲፈርስለት ሊጠይቅ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1771/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እንደ ውሉ እንዲፈፀምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎችም የውል መጣስ ተግባር አለመፈፀማቸውን እንጂ እንደውሉ መፈጸም የማይገደዱበትን ሌላ ምክንያት ያልገለፁ ስለሆነ የኤሌትሪክ መስመሩን ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተዋዋይ ወገን ግዴታውን ባልፈጸመ ጊዜ ውሉን በግዴታ እንዲፈጽም ከመደረጉም በተጨማሪ ለደረሰው ጉዳት ካሳ እንዲከፈል እንደሚገደድ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1790/1/ ገልጿል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ኤሌትሪክ መስመር በመቆረጡ ምክንያት ስራ ስላቆመ የብር 64,572(ስልሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሁለት) ኪሳራ የደረሰባቸው መሆኑን ገልፀዋል ሲገልፁ ተጠሪዎች በበኩላቸው የአመልካች የንግድ ፈቃድ ተሰርዞ የነበረ በመሆኑ ኪሳራ ሊከፍሉ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪዎች ሊያረጋግጡ የሚገባቸው አመልካች ያልሰሩና ገቢ ያላገኙ መሆኑን እንጂ የአመልካች ንግድ ፈቃድ መሰረዙን አይደለም፡፡ አመልካች ስራ ሰርተው ገቢ ያገኙ የነበረ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ያለ ንግድ ፈቃድ መስራታቸው በሚመለከተው ክፍል ተገቢው እርምጃ ሊያስወስድባቸው የሚችል ከሚሆን በቀር ተጠሪዎችን ኪሳራ ከመክፈል ነፃ የሚያደርጋቸው አይሆንም፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ከአመልካች ጋር ተመሳሳይ ስራ የሚሰራ ድርጅት የሚያገኘውን ገቢ አስመልክቶ የላከውን መረጃና በአመልካች ድርጅት ውስጥ የሚሰሩትን ሰራተኞች ስለ አመልካች ገቢ በምስክርነት ሰምቶ አመልካችን በክሱ ላይ የተመለከተውን ገቢ ያጡ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የተረጋገጠውን ኪሳራ ተጠሪዎች የመክፈል ሃላፊነት አለባቸው፡፡ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ከተሰረዘ የንግድ ፈቃድ ኪሳራ እንዲከፈል ማድረግ ሕገ ወጥነትን ማበረታታት ነው ከማለት ውጪ አመልካች የተቋረጠባቸው ገቢ ሰላለመኖሩ ያጣራው ነገር እንደሌለ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች የ5 ቀናት ማስጠንቀቂያ ብቻ ሰጥተው መስመሩን በማቋረጣቸው በአመልካች ላይ ለደረሰው ኪሳራ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን የኪሳራ ገንዘብ ተገቢ ነው ማለቱ አመልካች የተቋረጠባቸው ገቢ የነበረ መሆኑን መቀበሉን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪዎች አመልካች የተከራዩትን ቤት የኤሌትሪክ መስመር መቁረጣቸው የውል መጣስ ተግባር አይደለም በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15812 መጋቢት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24407 ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47038 ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች የቆረጡትን የኤሌትሪክ መስመር ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ መስመሩን በመቁረጣቸው በአመልካች ላይ የደረሰውን ኪሳራ ብር 64,572 (ስልሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሁለት) የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ይክፈሉ ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

የሰ/መ/ቁ. 40947

ህዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሃይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ መዝገቡ መድህኔ - ጠ/ሐጎስ ደበሱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአ.አ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ አትርሣው ወልዴ ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ተጠሪ ላወጣው ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ሊመለስ አይገባም ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በፌ/መ/ደረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ባወጣው የጨረታ ብር 2,000,000(ሁለት ሚሊዮን) የሚያወጡ 32 አይነት እቃዎች ለማቅረብ የተወዳደሩ ቢሆንም ያሸነፉት በሁለት አይነት እቃዎች ብቻ በመሆኑ ውል እንዲሞሉ የቀረበላቸውን ጥያቄ ባለመቀበላቸው ተጠሪ ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ አልመልስም በማለቱ ገንዘቡን እንዲመልስላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ አመልካች ባሸነፉባቸው ሁለት አይነት እቃዎች ውል እስካልፈረሙ ድረስ ገንዘቡ ሊመለስላቸው እንደማይገባ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች በዋስትና ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ግዴታ እስካልተወጡ ድረስ ገንዘቡ ሊመለስላቸው አይገባም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የነበረ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉም ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ አመልካች 32 አይነት እቃዎች ለማቅረብ ተወዳድረው ለጨረታ ማስከበሪያም የእነዚህ እቃዎች ዋጋ አንድ በመቶ ማስያዛቸውን ክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አመልካች የተወዳደሩበት የጠቅላላ ንብረቶቹ ዋጋ ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) ስለሆነ የተያዘው ገንዘብ ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ስለመሆኑና አመልካች ከተወዳደሩበት 32 አይነት እቃዎች ውስጥ ያሸነፉት በሁለት እቃዎች ብቻ ለመሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ አከራካሪው ጉዳይ አመልካች ላሸነፉበት ሁለት እቃዎች ውል አለመፈረማቸው ያስያዙት ብር 20,000(ሃያ ሺህ) እንዳይመለስላቸው ይከለክላል ወይስ አይከለክልም? የሚለው ነው፡፡

የጨረታ ማስከበሪያ ማለት አንድ ተጫራች ጨረታውን ቢያሸንፍ ውል የሚፈፅም ለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን የሚያዝ ገንዘብ ነው፡፡ ለውል መፈፀም ዋስትና ሲባል የሚያዝ ገንዘብ እንደመሆኑም መጠን የጨረታው አሸናፊ ባሸነፈው መሰረት ውል ካልፈረመ የጨረታው ማስከበሪያ ይያዝበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) ለሚያወጡ 32 ዓይነት እቃዎች ተጫርተዋል፡፡ ለጨረታ ማስከበሪያም የተጫረቱባቸውን ጠቅላላ እቃዎች ዋጋ አንድ በመቶ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ) አስይዘዋል፡፡ ከክርክሩ ሂደትም አመልካች ከተወዳደሩባቸው እቃዎች ውስጥ ያሸነፉት በሁለቱ እቃዎች ብቻ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ተጠይቀውም ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ያልሆኑት እነዚህን ሁለት እቃዎች በተመለከተ ነው፡፡ አመልካች 20,000(ሃያ ሺህ) ብር የጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ጠቅላላ ለተጫረቱበት እቃዎች በመሆኑ ጠቅላላው የጨረታ ገንዘብ ሊያዝ የሚገባው አመልካች በተወዳደሩባቸው እቃዎች በሙሉ አሸናፊ ቢሆኑና በዚሁ መሰረት ውል አልፈርምም ቢሉ ነበር፡፡ አመልካች ያሸነፉት ግን በሁለት እቃዎች በመሆኑ ለነዚህ እቃዎች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የጨረታው ማስከበሪያ ሊያዝ የሚገባው አሸናፊ በሆኑባቸው እቃዎች ዋጋ መጠን የተያዘው ገንዘብ እንጂ አመልካች ለ32 አይነት እቃዎች ላስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ በጠቅላላ ሊሆን አይገባም ባላሸነፉባቸው ዕቃዎች ቀድሞውንም ውል ለመዋዋል ስለማይችሉ ለነዚህ እቃዎች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ ውል አልፈፀሙም ተብሎ ሊያዝባቸው የሚገባበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ላሸነፉት ሁለት አይነት እቃዎች ውል አልፈረሙም በሚል ለ32 አይነት እቃዎች ያስያዙት ብር 20,000(ሃያ ሺህ) በሙሉ ሊያዝ ይገባል በሚል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01619 ጥቅምት 25 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 43929 ሐምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለ32 ዓይነት እቃዎች ካስያዙት ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ሊያዝባቸው የሚገባው ጨረታ ያሸነፉባቸው ሁለት እቃዎች ዋጋ አንድ በመቶ ብቻ ስለሆነ ይኸው ገንዘብ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ እንዲመለስላቸው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 43825

ታህሣሥ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የህፃን ኮከቤ ተፈረ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ፀሐይ በየነ ቀረበ

ተጠሪ፡- 1. አቶ አያሌው ካሳዬ - አልቀረቡም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አቶ ጣእመ ካሳዬ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች በሞግዚታቻው አማካኝነት ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው የአመልካች እናት ንብረት ለማስተዳደር እንጂ ለመሸጥ ስልጣን ሳይኖራቸው ለአመልካች ከአባታቸው በውርስ የሚተላለፍላቸውን ቤት ለአንደኛ ተጠሪ የሸጡ በመሆኑና ሁለተኛ ተጠሪም ወኪል ነኝ በማለት ቤቱን ይዘው ስለሚገኙ የሽያጩ ውል ፈርሶ ወደነበርበት እንዲመልሱ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ክሱ ለተጠሪዎች ደርሷቸው በሰጡት መልስ ክሳሽ ክሱን ለማቅረብ መብት የላቸውም ክሱም በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት የላቸውም የሚለውን መቃወሚያ ውድቅ ካደረገ በኋላ በአመልካች እናትና በአንደኛ ተጠሪ መሐከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በፀሁፍና ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በፍርድ ቤት ፊት ያልተከናወነ በመሆኑ ረቂቅ እንጂ በህግ ፊት የሚፀና ውል ስላልሆነ ውል በሌለበት ሁኔታ የውል ይፍረስልን ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም፣የይርጋ መቃወሚያም ሊቀርብበት አይችልም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የስር ውሳኔን አጽቶታል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎት የውል አፃፃፍ ፎርም አለመከተል በተዋዋይ ወገን ወይም በማናቸውም ያገባኛል ባይ ውል እንዲፈርስ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ የሚታይ ነው ወይስ ፍ/ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት ሊያየው ይችላል? የሚለውን የሕግ ነጥብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፀሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡ መርምሯል፡፡

አመልካች በሞግዚታቸው አማካኝነት ያቀረቡት ክስ በአመልካች እናትና በአንደኛ ተጠሪ መሐከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስና ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቢሆኑ ይህ ውል ስለመደረጉ አምነው ሌሎች ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤት የቤት ሽያጩ ውል በፀሁፍና ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ወይም ፍ/ቤቱ ያልተደረገ በመሆኑ ክርክር ሊቀርብበት የሚችል ውል የለም በማለት ወስኗል፡፡ በእርግጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ውል በፀሁፍና ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ወይም በፍ/ቤት ካልተደረገ ውጤት የሌለው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ስር ተመልክቷል፡፡ ይህን በሕጉ የተመለከተው የአፃፃፍ ስርአትን አለመከተል የሚያስከተለው ውጤት ምን እንደሆነ ደግሞ በዚሁ ሕግ ቁጥር 1808/2/ ስር ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት የአፃፃፍ ስርአት ያላሟላ ውል የሚፈርሰው ከተዋዋዮቹ በአንዱ ወይም ማናቸውም ጥቅም ያለው ሰው ሲጠየቅ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህም አንድ የአፃፃፍ ስርአትን ያላሟላ ውል በሕጉ በተመለከቱት ሰዎች እንዲፈርስር ጥያቄ አስካልቀረበበት ድረስ ከጅምሩ ፈራሽ ነው ሊባል እንደማይችል ያስገነዘበናል፡፡ ውሉ የአፃፃፍ ስርአትን ባለመከተሉ ምክንያት እንዲፈርስ ጥያቄ እስካልቀረበ ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት የአፃፃፍ ስርዓቱን ምክንያት በማድረግ ውሉን ከጅምሩ ውድቅ ሊያደርግ የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት የስር ፍ/ቤት በውሉ የአፃፃፍ ስርአትን ባለመከተሉ ምንም አይነት ክርክር ሊቀርብበት አይችልም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14336 በሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 59734 ጎንደር 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የመልካችን እና የተጠሪዎችን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 29181

ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ልየው ቸኮል

2. አቶ ሚሊዮን መንግስቱ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በብድር የተሠጠን ገንዘብ የመክፈያ ጊዜ ጋር በተያያዘ ዕዳው እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችልበትን የሕግ አግባብና ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ ለንግድ ስራቸው ማስፋፊያ የሚውል ታህሳስ 11 ቀን 1987 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል ብር 10,000.00(አስር ሺህ ብር) የተበደሩ መሆኑን፣ ዋናውን ብድርና ልዩ ልዩ ወጪዎችን ጨምረው በዓመት 14% /አስራ አራት በመቶ/ ወለድ እየታሰበ ከታህሳስ 11 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ ብር 900.00(ዘጠኝ መቶ) እየከፈሉ ሳያቋርጡ እስከ ታህሳስ 10 ቀን 1988 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከፍለው ለማጠናቀቅ መስማማታቸውን፣ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ አንደኛ ተጠሪ ለተበደረው ለዚሁ የገንዘብ መጠን የአንድነትና የነጠላ ዋስ በመሆን መፈረማቸውን በመግለፅ ዋናውን ብድር ብር 10,000.00(አስር ሺህ) እስከ ሐምሌ 24 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ የታሰበ ወለድ ብር 13,783.64(አስራ ሦስት ሺህ ሠባት መቶ ሰማንያ ሦስት ብር ከስድሳ አራት ሣንቲም) እና ለኢንሹራንስ የተከፈለ ብር 1,813.80(አንድ ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሦስት ብር ከሰማኒያ ሣንቲም) ስለመሆኑ በመዘርዘር በድምሩ ብር 25,097.54(ሃያ አምስት ሺህ ዘጠና ሰባት ብር ከሃምሳ አራት ሣንቲም) ያልተከፈለ ዕዳ የመቀጫ ወለድ 3% ጨምሮ በድምሩ 17% ወለድ እየታሰበ ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አንደኛ ተጠሪ ቀርበው የቀረበባቸውን ክስ በመቃወም ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፣ መክፈል ያልቻልኩት በደረሰብኝ ኪሳራ ስለሆነ ለመክፈል የማልችል ስለሆነ ባንኩ ተገንዝቦ ከአስር ዓመት በላይ ስለቆየ ክሱ ውድቅ ነው የሚሉትን ክርክሮች አንስተው ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ባንኩ በተበዳሪው ላይ ክስ መስርቶ ሀብቱን ሣያጣራ በዋሱ ላይ ክስ መመስረቱ ያላግባብ መሆኑን፣ ባንኩ በአዋጅ በተሠጠው ሥልጣን መጠቀም ሲገባው ክስ መመስረቱም ከአዋጁ ዓላማ ውጪ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሁኖ በነፃ ልሰናበት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ የሠጠው ብድር ክፍያ መጠናቀቅ የነበረበት በውላቸው መሠረት እስከ ታህሳስ 10 ቀን 1988 ዓ.ም ነው፣ አመልካች በዚህ ጊዜ ውስጥ አልጠየቀም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሠረት አበዳሪው የተወሠነ ጊዜ ተበጅቶለት በዓመት ወይም ከዓመት በፊት የሚከፈለውን የገንዘብ ዕዳ ሣይጠይቅ እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ከቆየና ከሁለት ዓመት ጊዜ በኋላ ከጠየቀ ገንዘቡ በተበዳሪው እንደተከፈለ ወይም ዕዳው ምህረት እንደተደረገለት ሕግ ግምት ይወስዳል፣ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በሠ/መ/ቁጥር 17068 በሰጠው ውሣኔ ላይ በሕግ ግምት የሚሽፈን የፍሬ ነገር ክርክር ተከሳሽ ፍሬ ነገሩን ካደ አልካደ ፍርድ ቤቶች የሕግ ግምቱን ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው የሚል አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሠጥቷል የሚል ምክንያት በመያዝ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፣ ገንዘቡ በጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው የተጠሪዎች ግዴታ ቀሪ ሆኗል በማለት ወስኗል። አመልካች በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞበታል። የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ለማስቀየር ነው።

የአመልካች ነገረ ፈጅ የካቲት 22 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት 3(ሦስት) ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ የሥር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ መሠረት ያደረገው ድንጋጌ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ የሰበር ችሎት ለፍ/ህ/ቁጥር 2024 የሰጠው ትርጉምም አምኖ ለሚከራከር ተከራካሪ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ውሣኔው መሠታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ ተሸሮ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ክስ መሠረት በብድር ዕዳ የሚፈለግባቸውን ብር 25097.54(ሃያ አምስት ሺህ ዘጠና ሰባት ብር ከሃምሳ አራት ሣንቲም) ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 17% (አስራ ሰባት በመቶ) ወለድ እየታሰበ ከክርክሩ ወጪና ኪሣራ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው። ይህ የሠበር ሠሚ ችሎትም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሰረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በሚል ውድቅ እንዲሆን የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል።

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ሁለተኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ያልቀረቡ ሲሆን አንደኛ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 28 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል። ይዘቱም ባጭሩ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2024(ረ) ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆኑን፣ የሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 17068 የሠጠው የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆኑን ዕዳው አለመከፈሉን አምነው የተከራከሩት ሁኔታ አለመኖሩን ገልፀው የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት የተከራከሩ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነው። የአመልካች ነገረ ፈጅም ሐምሌ 25 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሠረት ውሳኔ እንዲሠጥ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን ክርክር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባዋል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪዎች ያበደረውን ብድርና ወለድ እንደተከፈለው ይቆጠራል በማለት ፍርድ ለመስጠት መሰረት ያደረጉት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተውን የሕግ ግምት በመሆኑ በዚህ አንቀፅ የተጠቀሰው የሕግ ግምት ለባንኮች የሚሰራ መሆን አለመሆኑ ይሰራል የሚባል ቢሆን አመልካች በምስክር፣ በሰነድና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ግምቱን ለማስተባበል ይችላል ወይስ አይችልም? የሚሉት ነጥቦች መፈታት ያለባቸው ጭብጦች ሆነው አግኝተናቸዋል። ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት በቅድሚያ የሕግ ግምት ምንነት ባሕርያት በጠቅላላውና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌን ይዘትና ባህሪን በትኩረት ማየትና መመርመር ያስፈልጋል።

የሕግ ግምት የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ስንመለከተው ሕግ አውጪውን ለግምት መነሻ ከሚሆኑ የተወሰኑ ፍሬ ጉዳዮች በመነሳት አንድ ድርጊት ተፈፅሟል ወይም አልተፈፀመም ብሎ የሚደርስበትን መደምደሚያ በሕግ

የሚደነግጋቸውን ሁኔታዎች የሚያመላክት ነው፡፡ የሕግ ግምቶች ዳኞች አንድን ፍሬ ጉዳይ የተፈፀመ ወይም ያልተፈፀመ መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ ረገድ የሚገጥማቸውን ክፍተት በመሙላትና የማስረዳት ሸክም ያለበትን ወገን ጫናውን በማቃለል በኩል የላቀ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑ ይታመናል፡፡ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይም የሕግ (የህሊና) ግምት ዓይነተኛ ዓላማ የማስረዳት ሸክም ያለበትን ወገን ጫና የማቃለል፣ ውሳኔ ሠጪ አካልንም ተገቢና ግልፅ ሆኖ የሚታይ የጠራ ማስረጃ ካላገኘ ወደ ውሳኔ በአፋጣኝ እና በቀላሉ እንዲደርስ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሠጥ መሆኑ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ወደሆነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስንመጣ ይህ ድንጋጌ በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብን (Legal Presumptions) የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌዎቹ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት የሕግ የህሊና ግምት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 የተለያዩ የክፍያ አይነቶች የሚዘረዝር ሆኖ ድንጋጌው በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች (እዳዎች) በዚሁ የሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠየቁ የቀሩ እንደሆነ ክፍያውን(እዳውን) የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ (እዳ) እንደተከፈለ የሕግ ግምት እንደሚወሰድበት ያስገነዝባል፡፡

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ፣ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ በተጠቀሰው ቁጥር በፊደል(ረ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው፡፡

<u>ቁ 2024 በሁለት አመት የተወሰነ ጊዜ</u>

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው

(ረ) በብድር ለተሰጠ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሳኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

የዚሁ ድንጋጌ የእግሊዘኛው ቅጂም፡-

<u>Art.2024 presumption of payment after two years</u>

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

(f) interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical intervals. በሚል ተቀምጧል፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት አቀራረፅ እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፓራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት አመት ያለፋቸው እዳዎች(ክፍያዎች) እንደተከፈሉ ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታይ የተዘረዘሩት ንዑስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሕግ ግምት የሚወሰድባቸውን የክፍያ (እዳ) ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ በድንጋጌው ፊደል(ረ) ስር የተመለከተው ሲታይ በብድር የተሠጠ ወይም ለማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከአመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች (እዳዎች) ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ይህ ድንጋጌ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ግምት መሆኑ የመጀመሪያው ባህሪው ሲሆን ማናቸውም የተፈጥሮም ሆነ የሕግ ሰው(ባንክና ሌሎች አበዳሪ ተቋማት) የገንዘብ ብድር ካበደረ በኋላ ብድሩ ተከፍሎ የሚያልቅበትን የጊዜ ገደብ ካበቃ ከሁለት ዓመት በኋላ የብድሩ <u>የወለድ ይከፈለኝ ጥያቄ</u> በሕግ እንደተከፈለ የሚገመት መሆኑን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው የሕግ ግምት ለዳኞች የሕሊና ሚዛን እድል የማይሰጥ ዳኞች የነገሩን ሁኔታ በማየት ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት፣ ከነገሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታ አንፃር አስፈላጊ ሆኖ ካላገኙት የሚተውት ፈቃጅ የሆነ የሕግ ግምት አይደለም፡፡ በአንጻሩ ይኸው ድንጋጌ የሚሸፍነው ጉዳይ ባጋጠማቸው ጊዜ ዳኞች ያለምርጫ ሊከተሉትና ሊፈፅሙት የሚገባ አስገዳጅ የሕግ ግምት ነው፡፡

በዚህ ድንጋጌ ስር የሰፈረው የሕግ ግምት ሁሉንም አይነት ዕዳዎች በአጠቃላይ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ባንኮች በሚሠጧቸው ብድሮችም ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ጭምር የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ይኸው አንቀፅ ባንኮች ለሚያቀርቡት ክስ አግባብነት የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሌላው ነጥብ ይኸው የሕግ ግምት የሚመለከተው ወለዱን ብቻ ነው ወይስ ዋናውን ዕዳ ያጠቃልላል የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድንጋጌውን በመጠቀስ ወለዱ ብቻ ሳይሆን ዋናውን ዕዳ ጭምር ሁለት ዓመት ካለፈው እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ባንክ ይህ ትክክለኛ ትርጉም አይደለም በማለት ይከራከራል፡፡

በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ ለመፍታት የድንጋጌውን አቀራረፅ እና መንፈስ በጥንቃቄ መመርመር ይስፈልጋል፡፡ አከራካሪ የሆነው የሕግ አንቀፅ <u>በብድር ለተሠጠ የገንዘብ ወለድና</u> በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሳኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ...(ሰረዝ የተጨመረ) በማለት የሚደነግግ ነው፡፡ ከዚሁ የሕግ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው የድንጋጌው የመጀመሪያው ክፍል በብድር የተሠጠ የገንዘብ ወለድን በልዩ ሁኔታ ጠቅሶ በሁለት ዓመቱ የሕግ ግምት ውስጥ እንደሚካተት ያስቀምጣል፡፡ ሕግ አውጪው በዚሁ አንቀፅ የሰፈረው የሕግ ግምት ዋናውንም ዕዳ እንደያጠቃልል ቢፈልግ ኖሮ ወለዱን ለይቶ ያስቀምጣል ተብሎ አይገመትም፡፡ ስለዚህ በድንጋጌው የመጨረሻ ክፍል የሚገኘውና **"ሊከፈል የሚገባው ዕዳ"** የሚለው ሐረግ ብድርን ለመመልከት የገባ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው ወለዱንና ዋናውን ዕዳ ለይቶ በሕግ ግምት የሚሸፍነው ወለዱ ብቻ እንደሚሆን አድርጊ እያለ በመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት ዋናው ዕዳ ጭምር ሁለት ዓመት ካለፈው በሕግ ግምት እንደተከፈለ ይቆጠራል ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተደነገገው የሕግ ግምት በማስረጃ ቀሪ ሊሆን የሚችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ድንጋጌ ስር በተመለከቱት መንገዶች ነው፡፡ ሆኖም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስር የተቀመጠውን የሕግ ግምት ለማፍረስ የሚያስፈልጉት ማስረጃዎች በጣም ውስንና በሕግ በግልጽ የተደነገጉ መሆናቸውን ማየትና በጥብቅ ሥርዓት እና በውስን የማስረጃ ዓይነቶች ብቻ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት መሆኑን መገንዘብ የግድ ይላል፡፡ በዚህም መሰረት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተደነገገው የሕግ ግምት ቀሪ ሊሆን የሚችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ስር እንደተመለከተው ባለዕዳው በዐሐፍ ዕዳውን ያመነ እንደሆነ በሕግ የተደነገገው የጊዜ ውሳኔ ሳይደርስ ባለገንዘቡ ገንዘቡን እንዲከፍለው ባለዕዳውን ከፍርድ ቤት አስጠርቶ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ድንጋጌ ሲታይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው በሕግ የተሸፈነ የፍሬ ነገር የህሊና ግምት ከመሓላ ቃል በስተቀር በሌላ ማስረጃ ሊፈርስ እንደማይችል ደንግጓል፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው የሕግ ግምት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 ስር በተመለከቱት ሁለት ዓይነት ማስረጃዎች ቀሪ የሚሆን ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ንዑስ ቁጥር ሁለትና ሦስት ድንጋጌዎች መሰረት ደግሞ በመሓላ ቃል ካልሆነ በቀር በሌላ አይነት ማስረጃ ሊስተባበል የማይችል ማስረጃ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026(1) ድንጋጌ በግልፅ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተውን የሕግ ግምት ለማስተባበል ያለው ዕድል ውስንና ጠባብ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ እንግዲህ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 አስገዳጅ የሆነ እና በውስን መንገዶች ብቻ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት መሆኑ ሁለት ግልፅና የተለዩ ባሕርያት ያሉት ድንጋጌ መሆኑን ከላይ ከገለፅናቸው ህጋዊ ምክንያቶች መገንዘብ የምንችለው ነጥብ ነው፡፡

በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ ስር የተደነገገውን የሕግ ግምት ባንኮች ለማስተባበል የሚችሉት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌ ስር በተመለከቱት ማስረጃዎች ብቻ ነው ወይስ የሰው ምስክር የሰነድና ሌሎች ማስረጃዎችን በማቅረብ የሕግ ግምቱን ማፍረስና ማስተባበል ይችላሉ? በሌላ አገላለፅ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ መሰረት ባንኮች ያበደሩትን ብድርና ወለድ

ያልተከፈላቸው መሆኑን ለማስረዳት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ ተፈፃሚነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለጥያቄው ተገቢውን ምላሽ ለማግኘት ይቻል ዘንድም ባንኮችና ሌሎች ገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ገንዘብ ያበደሩ መሆኑን ያበደሩት ገንዘብ ያልተከፈላቸው መሆኑን ለማስረዳት ሊያቀርቡ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት እንደዚሁም በተመሳሳይ ሁኔታ የባንክና የሌሎች ገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ደንበኞች ገንዘብ ያለመበደራቸውን ወይም ብድር መክፈላቸውን ለማስረዳት ሊያቀርቡ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473 ንዑስ አንቀፅ ሁለት የተደነገገውን ማየትና ማገናዘብን ያስፈልጋል፡፡

በመሰረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472(1) በብድር የተሰጠ ገንዘብ ከአምስት መቶ የኢትዮጵያ ብር በላይ ሲሆን የብድሩን ውል በፁሑፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሓላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት የማይቻል መሆኑን በአስገዳጅ ኃይለ ቃል የደነገገ ሲሆን የተጠቀሰው ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ በንዑስ ቁጥር አንድ ከተመለከተው ልዩ የሰነድ ማስረጃ በስተቀር ለብድር ውል ማናቸውም ሌላ ማስረጃ ለማቅረብ የማይቻል መሆኑን ደንግጓል፡፡

ሆኖም በባንክ፣ በአበዳሪ ተቋማት እና በደንበኞቻቸው መካከል ያለውንና የሚኖረውን የጠበቀ እምነትና ግንኙት፣ ባንኮችና አበዳሪ ተቋማት የዕለት ተዕለት የሥራ ተግባራቸው ብድር በመስጠትና ተከፋይ የብድር ገንዘብ በመሰብሰብ ቀልጣፋ የፋይናንስና የንግድ ግንኙነት እንዲኖር በማድረግ በኩል ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑን በማገናዘብ ሕግ አውጪው ባንኮችና ሌሎች አበዳሪ ተቋማት ደንበኞቻቸው ገንዘብ የተበደሩና የተበደሩትን ገንዘብ ያልከፈሉ መሆኑን ለማስረዳት በተመሳሳይ ሁኔታ የባንክ ተበዳሪ ብድር ያልወሰደ ወይም የወሰደውን ብድር የከፈለ መሆኑን ለማስረዳት በሰው ምስክር እና በሕሊና ግምት ለማስረዳት የሚችሉ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473(2) ስር ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲነበብ በባለባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ስላለ ግንኙነት ሊቀርብ የሚችለውን ማስረጃ አይነት በተመለከተ አመላካች የሕግ ድንጋጌ በመሆኑ ባንኮችም ሆነ ተበዳሪዎች የሰነድ የሰው ማስረጃ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን በማቅረብ ለማስረዳት የሚችሉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473 ንዑስ ቁጥር ሦስት ድንጋጌ በተለየ ሲታይም በባለባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ስላሉ ግንኙነቶች የብድርን ውል ወይም የተበደረውን ገንዘብ መልሶ መክፈልን በምስክሮች ወይም በአእምሮ ግምት ለማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ መደንገጉ ከላይ የተመለከተውን ምክንያት የሚያጠናክር ነው፡፡

የባንክ ደንበኞች የተበደሩትን የብድር ወለድ የከፈሉ መሆኑን በሕሊና ግምት ለማስረዳት ከሚችልባቸው ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ ስር የተመለከተው የሕግ ግምት አንደኛው ሲሆን ይህ ከሆነ አበዳሪው ባንክ ደንበኛው በህሊና ግምት ከፍዬዋለሁ በማለት ያቀረበበትን ክርክር ለማስተባበልና የብድሩ ወለዱ ያልተከፈለው መሆኑን ለማስረዳት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473(2) ስር በተደነገገው መሰረት የሰው ምስክር፣ የህሊና ግምት፣ የሰነድና ሌሎች ማስረጃዎችን በማቅረብ ግምቱን ማስተባበል የሚችል በመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026 ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ለባንኮችና ለደንበኞቻቸው መብት ልዩ ጥበቃ የሚያደርገውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473 ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌን ዋጋ በሚያሳጣ መልኩ ሊተረጎምና ተፈፃሚ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሰረቱ የብድር አገልግሎት መስጠት፤ ከተሰጠውም ብድር በማትረፍ የተሻለ አገልግሎት መስጠት የባንክ እና አበዳሪ የፋይናንስ ተቋማት ዋና ተግባር ብቻ ሳይሆን ለእነዚህ ተቋማት ሕልውና መሰረት ሲሆን ተበዳሪዎች ብድሩን ለማንኛውም የኢኮኖሚ መስክ ለማዋል የሚችሉት ይኸው የአበዳሪ ገንዘብ ተቋማት ህልውና ሲጠበቅ ነው፡፡ ይህ ሊሳካ የሚችለው ደግሞ ህግ አውጭው ለእነዚህ ተቋማት ያደረገውን ልዩ ጥበቃ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሕጉ ሊፈፀም የሚችል ውጤት የሚሠጥ ትርጉም በመሰጠት መሆኑን አምነንበታል፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ሕጋዊ ምክንያቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2026(1) ስር የተመለከተው ድንጋጌ በባንኮች፣ በሌሎች አበዳሪ ተቋማት እና በደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተፈፃሚነት የሌለው የሕግ ድንጋጌ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ባንኮች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር በተመለከተው የሕግ ግምት የሚገዙ ቢሆንም ለደንበኞቻቸው ያበደሩት የብድር ወለድ ያልተከፈለ መሆኑን የሰው ምስክር፣ የሰነድና ሌላ ማስረጃ በማቅረብ ይህን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕግ ግምት ለማስተባበል የሚችሉበት የፍርድ ሂደት መኖር ይገባዋል፡፡ በዚህ መሰረት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የብድሩ ወለዱ ያልተከፈለው መሆኑን ለማስረዳት እድሉን ሳይሠጡ፣ ያቀረባቸውንም ማስረጃዎችን ሳይመረምሩና ሳይመዝኑ ውሳኔ መስጠታቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2473(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መንፈስና ዓላማውን ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ ስለአገኘነው ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

በስር ፍርድ ቤት በዋና ተበዳሪነት የተከሰሱት የአሁኑ አንደኛ ተጠሪ ከስር ጀምሮ ያቀረቡትን ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስር የሰፈረው የሕግ ግምት እና አመልካች ካቀረባቸው ማስረጃዎች አንፃር ነገር ስንመለከተው በአመልካች የተጠየቀው እዳ ያልተከፈለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም አንደኛ ተጠሪ የሕግ ግምት ተጠቃሚ ቢሆኑም አመልካች ይህንን የሕግ ግምት ሊያፈርስ የሚችል በቂ ማስረጃ ያቀረበ በመሆኑ በክርክሩ ሂደት በተረጋገጠው መሰረት አንደኛ ተጠሪ ዕዳውን የማይከፈሉበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ የሁለተኛ ተጠሪ ክርክር ሲታይም አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ክስ መስርቶ ሃብት ሳያጣራና በህጉ በተሠጠው ስልጣን መሰረት መብቱን ሳያስከብር ዋሱ ላይ ክስ መመስረት አይችልም በማለት የሚከራከሩ የነበረ መሆኑንና በዚህ ችሎትም ካለመቅረባቸውም በላይ የአንደኛ ተጠሪ ክርክር የሚጠቅማቸው አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የገቡት የዋስትና ዓይነት የአንድነትና የነጠላ እንደመሆኑ መጠን አመልካች ተጠሪን ከዋናው ተበዳሪ ጋር በአንድ ላይ መክሰሱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1933(1) ድንጋጌ አንፃር ህጋዊ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረትም የተሠጠውን ሥልጣን ባንክ የሚጠቀመው መያዣ በአስያዥ ተበዳሪዎች ላይ ሆኖ በእነዚህ ተበዳሪዎችም ቢሆን ባንክ በአዋጁ የተሠጠውን ሥልጣን በመተው ፍርድ ቤት ክስ ከመመስረት የሚከለክልበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ሕጎቹ ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪም በገቡት ግዴታ አይነትና በክርክሩ ሂደት በተረጋገጠው መሰረት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ገንዘብ ለአመልካች የማይከፍሉበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 09312 ሚያዝያ 26 ቀን 1998 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02227 ሕዳር 27 ቀን 1999 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ክስ መሰረት በብድር ዕዳ የሚፈለግባቸውን ብር 25097.54(ሃያ አምስት ሺህ ዘጠና ሰባት ብር ከሃምሳ አራት ሳንቲም) ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 17%(አስራ ሰባት በመቶ) እየታሰበ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት ወስነናል፡፡

3. አመልካች ለዳኝነት ያወጣውን ወጪ ደረሰኝ በመሰከረው መሰረት ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ ብለናል፡፡

4. በክርክሩ የወጡትን ሌሎች ወጪዎችና ኪሳራዎችን የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

የዚህ መዝገብ ውሳኔ ግልባጭ በመ/ቁጥር 26363፣ 32196፣ 32199፣ 32202፣ 32203፣ 32205፣ 33222፣ 33282፣ 34329 እና 35605 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 35758

ታህሣሥ 20 ቀን 2002

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ገብረመድንን አየናቸው
2. እንግዳ አየናቸው
} ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. አቶ ሰብስቤ ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በብድር የተሰጠን ገንዘብ የመክፈያ ጊዜ ጋር በተያያዘ ዕዳው እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችልበትን የሕግ አግባብና ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ መጋቢት 16 ቀን 1997 ዓ.ም. በዓፋት አቤቱታ የአሁኑ አመልካቾች ጥር 24 ቀን 1990 በተዛፈ የብድር ውል ብር 32,000.00 /ሠላሣ ሁለት ሺህ ብር/ የተበደሩ መሆኑን፣ ብድሩን በየሣምንቱ ብር 250.00 እየከፈሉ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1992 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከፍለው ለማጠናቀቅ መስማማታቸውን፣ ተበዳሪዎች በጋራ በጠቅላላው ብር 9090 /ዘጠኝ ሺህ ዘጠና ብር/ የመለሱላቸው ስለመሆኑ በመዘርዘር ቀሪውን ብር 22,910.00 /ሃያ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስር ብር/ ከነወለዱ አመልካቾች እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎችም ቀርበው የቀረበባቸውን ክስ በመቃወም ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፣ ፈርመን የወሰድነው ገንዘብ የለም፣ አበዳሪው ፊርማችንን የሚያውቁ በመሆናቸው እራሳቸው ውሉን አዘጋጅተውና ገንዘቡን በመሰላቸው ሞልተው ያቀረቡት ሠነድ ነው፣ የቀረበው የብድር ውሉ ሠነድ ትክክል ነው ቢባል እንኳ ውሉ በተፈፀመበት ጊዜ ለዕለት የምንመገበው ያጣን ችግረኞች ስለነበርን ይህንኑ አጋጣሚ ተጠቅመው ጥቂት ገንዘብ አበድረው በ70% /ሰባ በመቶ/ አስበው ካበደሩን ገንዘብ ጋር ደምረው ያስፈረሙን ሕገ-ወጥ የአራጣ ብድር ውል በመሆኑ ፈራሽ ነው የሚሉትን ክርክሮች አንስተው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በብድር ውሉ ላይ አለ የተባለውን ፊርማ በፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ እንዲከናወን ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የተበዳሪዎች መሆኑ ተረጋግጧል፣ ውሉ ሕገ-ወጥ ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም በማለት የተጠሪዎችን መከራከሪያ ውድቅ ከአደረገ በኋላ ለክሱ ኃላፊ በማድረግ በክሱ የተጠቀሰውን ብር 22,910.00 /ሃያ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስር ብር/ ክሱ ከቀረበበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች የካቲት 17 ቀን 2000 ዓ.ም. በዓፋት 3 /ሦስት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የሥር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/"ን" ድንጋጌ መሠረት ተደርጎ የቀረበውን ክርክር ውድቅ ማድረጉ ያላግባብ መሆኑን፣ ውሣኔውም ለዚሁ ድንጋጌ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁጥር 17068፣ 14047 እና 15493 የሰጠውን ትርጉም ያላገናዘበ መሆኑን በመጥቀስ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሮ አመልካቾች በተጠሪ በብድር ዕዳ የሚፈለግባቸው ገንዘብ የለም ተብሎ ከክርክሩ ወጪና ኪሣራ ጋር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት በፍ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ መሠረት ያቀረቡት ክርክር የመታፋን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ሐምሌ 24 ቀን 2000 ዓ.ም. በዓፋት ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ- የፍ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ በሥር ፍርድ ቤትም ያልተነሳ መሆኑን፣ አመልካቾች ዕዳው ያልተከፈለ መሆኑን ስለአመኑ ክርክራቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልፀው የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት የተከራከሩ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች ጥቅምት 04 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ የመልስ መልስ ማመልከቻ የፍ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/"ን" መሠረት ያደረገ ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያነሱ መሆኑን በመጥቀስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሠረት ውሣኔ ይሠጥልን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በተጠሪ እና በአመልካቾች መካከል የብድር ውሉ የተፃፈው ጥር 24 ቀን 1990 ዓ.ም. ሆኖ የብድሩ አመላለስም በየሣምንቱ ብር 250.00 /ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ አየተከፈለ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1992 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ሊጠናቀቅ መስማማታቸውን፣ የአሁኑ ተጠሪ የብድር ገንዘቡን አመልካቾች አልመለሱም፤ ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት በፍርድ ቤት ክስ የመሠረቱት መጋቢት 16 ቀን 1997 ዓ.ም. መሆኑ እና አመልካቾች ስለ ውሉ ህጋዊ አለመሆን በውሉ ላይ ያለው ፊርማ የእነሱ አለመሆኑና ውሉም አራጣ ሊባል የሚችል መሆኑን በመጥቀስ ኃላፊነት የለብንም በማለት መከራከራቸውን ነው፡፡ በዚህ ችሎት አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት የስር ፍርድ ቤት የብድር እዳው ክፍያ ጥያቄ በሁለት ዓመት የጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ ሊቆጠር ይገባል በማለት ያቀረብነውን ክርክር ያለፈው ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ ይህ የአመልካቾች ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ በዚህ ችሎት መከራከሪያ ሊሆን አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በሕግ የሚሸፈን የፍሬ ነገር ክርክርን በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሳው የሚችለው ጉዳይ በመሆኑና ይህም ስለመሆኑ ይህ ችሎት ከዚህ በፊት በሰ/መ/ቁጥር 17068 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ማንሣት አለማንሳታቸው ሊያስከትል የሚችለው የሰነ-ሥርዓት ግድፈት ስለሌለው ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር የምንቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ጉዳይ ዋናውና የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነጥብ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ድንጋጌ አግባብነቱ ለዋናው የብድር ገንዘብ ነው? ወይስ ለብድሩ ገንዘብ ወለድ ብቻ? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ስለ የሕሊና ግምት ምንነትና ዓይነቶች እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ድንጋጌን ይዘት፣ አቀራረጹንና መንፈሱን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በመሠረቱ የሕሊና ግምት /Presumption/ ሲባል ቀደም ብሎ በነገሮች መካከል የነበራቸውን የግንኙነት ልምድ መሠረት በማድረግ /Experience of previous connections/ ከታመኑ ወይም በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ

ነገሮች በመነሳት በአንዣሩ ሌላ አዲስ ፍሬ ነገር መከሰትን ወይም እውነትን በአእምሮ መቀበል /inference/ ማለት ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የተፃፉት የሕግ ምሁራን ጽሁፎች ያሳያሉ፡፡ የዚህ ጽንሰ ሀሳብ ውጤትም አንድን አከራካሪ የሆነ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖር በማስረጃ ማረጋገጥ ሳያስፈልግ እንዳለ መቀበል ስለመሆኑም ያሰምሩበታል፡፡ ይሁን እንጂ የሕሊና ግምት ዓይነቶች የተለያዩ ስለሆኑ ውጤታቸውን ፍርድ ቤት የሚቀበልበት መንገድም የተለያየ ነው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይም የሕግ የሕሊና ግምት ዓይነተኛ ዓላማ የማስረዳት ሸክም ያለበትን ወገን ጫና የሚያቃልል ውሣኔ ሰጪ አካልንም ተገቢና ግልጽ ሆኖ የሚታይ የጠራ ማስረጃ ካላገኙ ወደ ውሣኔ በአፋጣኝ እና በቀላሉ እንዲደርስ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሠጥ መሆኑ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ወደሆነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስንመጣ ይህ ድንጋጌ በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብን /Legal presumptions/ የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት /not freely rebuttable/ የሕግ የሕሊና ግምት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 የተለያዩ የክፍያ ዓይነቶች የሚዘረዝር ሆኖ ድንጋጌው በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች /እዳዎች/ በዚሁ የሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠይቁ የቀሩ እንደሆነ ክፍያውን /እዳውን/ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ /እዳ/ እንዲከፈለ የሕግ ግምት እንዲወሰድበት ያስገነዝባል፡፡

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ በተጠቀሰው ቁጥር በፊደል /ረ/ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው፡፡

<u>ቁ 2024 በሁለት ዓመት የተወሰነ ጊዜ</u>

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው፡፡

/ረ/ በብድር ለተሰጠ፣ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሣኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጂም፡-

Art. 2024 presumption of payment after two years

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

/f/ Interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical intervals. በሚል ተቀምጧል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት አቀራረጽ እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፓራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት ዓመት ያለፋቸው እዳዎች /ክፍያዎች/ እንደተከፈሉ ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታታይ የተዘረዘሩት ንዑስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሕግ ግምት የሚወሰድባቸውን የክፍያ /እዳ/ ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ በድንጋጌው ፊደል /ረ/ ስር የተመለከተው ሲታይ በብድር የተሰጠ ወይም ለማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከዓመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች /እዳዎች/ ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም የሚያስገነዝበው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ስር የተመለከተው ድንጋጌው ተፈፃሚነት የሚኖረው በብድር ለተሰጠ ገንዘብ ወለድ ላይ መሆኑንና ዋናውን የብድር ገንዘብ የማይጨምር መሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም ድንጋጌው ዋናውን የብድር ገንዘብ የሚጨምር ቢሆን ኖሮ ሕግ አውጪው የብድርን ገንዘብንና ወለድ በማለት ያስቀምጠው ነበር እንጂ ለብቻው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነጥሎ የብድር ገንዘብ ወለድን በማለት አይጽፈውም ነበር፡፡ ብድር ዋናው ዓላማ ሰዎች ዘርፈ ብዙ የሆኑ የግልና ማኅበራዊ ችግሮቻቸውን ማቋቋሚያ መንገድ ሆኖ ለኑሮ ድኅነትንና መድኅን መሆን ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ሕጉም የዚህ ዓይነት ዓላማ ያለውን የሰዎች ሕጋዊ ግንኙነት መጠበቅ አለበት፡፡ ሕግ ሲተጎምም ሊፈፀም የሚችል ውጤት እንዲኖረው በማድረግ ስለመሆኑም ጠቅላላ የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የግድ የሚሉት ነው፡፡ በመሆኑም ከብድር አስፈላጊነትም ሆነ ከሕግ አተረጓጎም ደንብ አንፃር ሲታይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ሥር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነቱ በብድር ለተሰጠ የገንዘብ ወለድ እንጂ ለዋናው የብድር ገንዘብ አለመሆኑን ከድንጋጌው ይዘት፣ አቀራረጽና መንፈስ የምንገነዘበው ነጥብ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርቱ ዳኝነት የጠየቁት ዋናውን የብድር ገንዘብ ሲሆን አመልካቾች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት የሚከራከሩት ይህንኑ ዋናውን የብድሩ ገንዘብ ነው፡፡ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የብድር ውል ስምምነት የብድር ገንዘቡ በብድሩ ወቅት ወለድ የሚታሰብበት ስለመሆኑ አይገለጽም፡፡ ተጠሪ ዳኝነት ሲጠይቁ ወለድ እንዲታሰብላቸው የገለጹትም ከክሱ በኋላ ያለውን ሕጋዊ ወለድ ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ መሠረት በሁለት ዓመት ጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ ሊቆጠር እና በፍ/ቤቱ የሕግ ግምት የሚወሰድበት የብድር ወለድ በተያዘው ጉዳይ የለም፡፡ አመልካቾች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ብር 22,910 /ሃያ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስር ብር/ ለተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ዘጠኝ በመቶ /9%/ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03288 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 59093 ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45422

ጥር 13 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ፈታሂ ባየህ

2. ወ/ሮ ጽጌ ባየህ

3. ወ/ሮ ተዘራ ባየህ

4. ፍሬሕይወት ባየህ

5. አቶ ዘውገ ባየህ

6. ሰብለሥላሴ ባየህ

7. ወ/ሮ ማስረጃ ባየህ

በራሣቸውና በሌሎች ወኪሎቻቸው አቶ ፈታሂ ባየህ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አስራት ባየህ - ከክርክሩ ውጪ ሁነዋል፡፡

2. ዲያቆን ገ/ሕይወት ንጋቱ

3. ቀኝ ጌታ ልሳነወርቅ

ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ቤት ይለቀቅልን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካቾች ግንቦት 02 ቀን 1998 ዓ.ም. አሻሽለው በዛፉት እና በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ በመሠረቱት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- አመልካቾች እና አንደኛዋ ተጠሪ ከሟች ወላጆቻቸው ከአባኸር ባየሕ ገ/ኪየሱስና ከእናታቸው ከወ/ሮ ደብሪቱ ኃ/ጊዮርጊት በውርስ የተላለፈላቸው በአዲስ አበባ ከተማ፣ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16/17 ወስጥ የሚገኙ በአባታቸው ስም ተመዝግበው የሚታወቁትን፣ ቁጥራቸው 922፣ 738፣ 739 እና 740 የሆኑ ቤቶች እንዳላቸው፣ የቤቶቹን ስመ ሃብት አንደኛ ተጠሪ በራሳቸው ስም በማድረግ ቁጥራቸው 739 እና 740 የሆኑትን ቤቶች ከሁለተኛ እና ለሦስተኛ ተጠሪዎች በወለድ አግድ በማስያዝ ብድር ተበድረው ለግላቸው እንደሚጠቀሙበትና በስምምነት ክፍፍል እንዲደረግ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው የውርስ አጣሪ ተሹሞ ውርሱ እንዲጣራ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች በማመላከት ፍርድ ቤቱ የውርስ አጣሪ በመሾም ውርሱ ከተጣራ በኋላ ሪፖርቱ ለፍርድ ቤቱ ጥር 14 ቀን 1998 ዓ.ም. ተልኮ የካቲት 09 ቀን 1998 ዓ.ም. ፍርድ ቤቱ የመዘገበው መሆኑን፣ በዚህ የውርስ አጣሪው ሪፖርት አጠቃላይ የውርስ ሃብት ግምት እና የወራሾች ድርሻ እንዲሁም የተጠቀሙበት ሀብት መጠን ተለይቶ መቀመጡን፣ አንደኛ ተጠሪ ያላግባብ ቤቱቹን ሕጋዊ ባልሆነ የወለድ አግድ ውል ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ያሰያዙ መሆኑንና በወለድ አግድ ውል ቤቶቹን የያዙት ተጠሪዎችም አስያዢ መብት ሳይኖራት እያወቁ የያዙት መሆኑን ዘርዝረው ቁጥራቸው 739 እና 740 የሆኑ ቤቶችን ተጠሪዎች እንዲያስረክቡ፣ አጠቃላይ የውርስ ሃብት የሆኑ ንብረቶች ከእነ ይዞታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአውራሽ አባታቸው ስም የነበረው የባለቤትነት ማረጋገጫ ስም በአመልካቾች ስም እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቀቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ፣ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በአዋጅ ተወርሷል ተብሎ የቀበሌው መስተዳደር አከራይቶ ቆይቶ እያለ አንደኛ ተጠሪ ከአዋጅ ውጪ ያላግባብ፣ የተወረሰ /የተወሰደ/ ነው በማለት በፍርድ ቤት ክሰው በፍርድ ኃይል አስለቅቀው በመረከብ በፍ/ቤት ውሣኔ ባለመብት ሆነው፣ የቤት ባለቤትነት ደብተርና ካርታም በስማቸው አረጋግጠው፣ ይዞታቸው በመሆኑ፣ መጋቢት 01 ቀን 1994 ዓ.ም. በተፃፈ የውል ሰነድ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ/ ተቀብለው ቁጥሩ 739 የሆነውን ቤት እስከ መጋቢት 1999 ዓ.ም. ድረስ የሚቆይ ወለድ አግድ ውል፤ ለአምስት ዓመት በማስያዝ የተዋዋሉ መሆኑን፣ ቤቱም ተረክበው ይዘው እንደሚገኙና አንደኛ ተጠሪ የተበደሩትን ገንዘብ ሲመልሱ ቤቱን እንደነበረ ሊያስረክቧቸው መዋዋላቸውን፣ አመልካቾች በስምምነት ድርሻቸውን ይዘው እየተጠቀሙ የሚገኙ በመሆኑና በቤቱ ላይ አንደኛ ተጠሪ በሕጉ አግባብ ባለመብት ከሆኑ በኋላ ያቋቋሙት የወለድ አግድ ውል ሕጋዊ መሆኑን እንዲሁም አንደኛ ተጠሪ ቤቱን በብዙ ድካምና ወጪ አስመልሰው መያዛቸውን እያወቁና እየተረዱ መብት ሳይኖራቸው ቤቱን አስይዘዋል ማለታቸው በሕግ ተቀባይነት የሌለው ነው በሚል ተከራክረዋል፡፡ አንደኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው የጽሁፍ መልስ መስጠት መብት የታፈባቸው ሲሆን ሦስተኛ ተጠሪ በቃል ክርክር ወቅት ቀርበው ቁጥሩ 740 የሆነ ቤት በወለድ አግድ ውል ለሰባት ዓመታት እንደያዙ፣ የውሉ ዘመንም እስከ ጥር 2007 ዓ.ም. መሆኑን ገልፀው ጊዜው ሳያልቅ ቤቱን የሚያስረክቡበት ምክንያት እንደሌለ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ በቤት ቁጥር 739 የተቋቋመው የወለድ አግድ ውሉ የውል ዘመኑ ማብቃቱን በማግለጽ አንደኛ ተጠሪ የተቀበሉትን ብር 10,000.00(አስር ሺህ) ለሁለተኛ ተጠሪ መልሰው ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካቾች እና ለአንደኛ ተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ቤቱንም አመልካቾችና አንደኛ ተጠሪ እኩል ሊካፈሉት ይገባል ሲል የወሰነ ሲሆን የቤት ቁጥር 740 የሆነውን በተመለከተ ደግሞ የወለድ አገድ ውሉ እስከ ጥር 2007 ዓ.ም. ድረስ የሚቆይ በመሆኑ ሦስተኛ ተጠሪ ቤቱን ሊያስረክቡ እንደማይገባ፣ የውሉ ዘመን ሲያልቅ በውሉ የተገለፀውን ገንዘብ አንደኛ ተጠሪ ለሦስተኛ ተጠሪ መልሰው ሦስተኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካቾችና ለአንደኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡና ቤቱንም ሊከፋፈሉት እንደሚገባ፣ እንዲሁም በቤት ቁጥር 739 እና 740 እስኪከፋፈሉ ድረስ በአመልካቾችና በአንደኛ ተጠሪ ስም የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ በጋራ ሊያወጡበት ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወምና ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች ሚያዝያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አንደኛ ተጠሪ በአከራካሪው ቤቱ ላይ ሙሉ መብት የሌላቸው ሆኖ እያለ እና የወለድ አግድ ውሉም በሕጉ አግባብ ያልተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የውርስ ንብረቱ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች እንደያዙት እንዲቆዩ የተደረገው እና ውሉ ሕጋዊ ነው መባሉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የወለድ አግድ ውሉ ሕጋዊ ነው መባሉ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ጎዳር 10 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሦስት ገጽ የመልስ ማመልከቻ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ነጥብ በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ስለመሆኑ እና ውሉ ሕጋዊ ነው የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከክርክሩ ውጪ እንዲሆኑ ተደርጎአል፡፡ አመልካቾች ታህሣሥ 08 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ክስ ይዘት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤቶች በውርስ ያገኟቸው መሆኑን፣ በእነዚህ ቤቶች ላይ አመልካቾችና አንደኛ ተጠሪ ያላቸው ድርሻ በውርስ አጣሪ ተለይቶ መታወቁንና ቤቶቹን ለማካፈል አንደኛ ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን እንዲሁም ሕጋዊ ባልሆነ የወለድ አግድ ውል ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ቤቶቹን አንደኛ ተጠሪ አስተላልፈው እንደሚገኙ ገልፀው ቤቶቹን እንዲያስረክቧቸውና የቤቶቹ ስመ ሃብት ወደ ወራሾች እንዲዞር ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡ የአሁኑ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ደግሞ የወለድ አግድ ውሉ በሕጉ አግባብ የተደረገ ስለሆነ ቤቶቹን ልናስረክብ አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ የሚቻለው አመልካቾች በግልጽ እየተቃወሙ ያሉት የወለድ አግድ ውሉ በሁለት ምክንያቶች ሕጋዊ አይደለም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም አንዱ ውሉ የተደረገው በንብረቱ ላይ ሙሉ መብት በሌላቸው አንደኛ ተጠሪ በመሆኑ ሕጋዊ አይደለም የሚል ሲሆን ሌላው ተደረገ የተባለው የወለድ አግድ ውልም ቢሆን ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገና ያልተመዘገበ ስለሆነ ሊፀና የሚገባው አይደለም የሚል ነው፡፡ እንግዲህ የአመልካቾች ክርክር ቤቱ ያላግባብ ተይዞብናል የሚል ስለመሆኑ በቀላሉ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች የአመልካቾች ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1810 ያላገናዘበ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የአመልካቾችን የስር ክርክር ይዘቱን ባግባቡ መሠረት ያላደረገ ስለሆነ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም የወለድ አግድ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገና ንብረቱ በሚገኝበት መዝገብ ያልተመዘገበ ስለመሆኑ ተጠሪዎች በማመን የሚከራከሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የወለድ አግድ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገና ያልተመዘገበ ከሆነ ውጤቱ ምንድነው? የሚለውን በዚህ ረገድ የተደነገጉትን የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች በማየት ምላሽ ማግኘት የሚችለው ነጥብ ነው፡፡

በመሠረቱ የወለድ አግድ ውል የሚቋቋመው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣን መቋቋም የሚመለከቱት ድንጋጌዎችን በመከተል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3118 ድንጋጌ ያጣቅሳል፡፡ በዚህ አግባብ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3045 እና 3052 ሲሆኑ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ የመያዣ ውል በጽሁፍ መሆን እንዳለበትና የማይንቀሳቀስ ንብረት በሚገኝበት መዝገብ መመዝገብ እንዳለበት የስገነዝባሉ፡፡ ይህን ያላሟላ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል የሕግ ውጤት አይኖረውም፡፡ በመሆኑም የወለድ አግድ ውል በሕጉ ጥበቃ የሚደረግው በሕጉ አግባብ ተቋቁሞ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን በዚሁ መንገድ የተደረገ የወለድ አግድ ውሉ የለም፡፡ ስለሆነም ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች አበድረናል የሚሉትን ገንዘብ ከሚመለከተው ሰው በሕጉ አግባብ ከሚጠይቁ በስተቀር ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤቶች የሚይዙበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም የወለድ አግድ ውል የተባለው በሕጉ አግባብ የተቋቋመ መሆን አለመሆኑን ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡት ቤቶቹን ተጠሪዎች ሊለቁ አይገባም በማለት የሰጡት ውሣኔ አመልካቾችን በውርስ የተላለፈላቸውን የባለቤትነት መብትን ያጣበበ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10218 ጥቅምት 01 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 62724 የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር አድርገናል፡፡ የሚሉት የወለድ አግድ ውል ፈራሽ ነው ብለናል፡፡
3. ሁለተኛ ተጠሪ የቤት ቁጥር 739፣ ሦስተኛ ተጠሪ ደግሞ የቤት ቁጥር 740 ለአመልካቾች ሊያስረክቡ ይገባል፡፡
4. አመልካቾች እና አንደኛ ተጠሪ በቤቶቹ ላይ በጋራ ያላቸውን መብትና ጥቅም በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ እንደተጠበቀ ነው ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 48967

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሳዲቅ ሐሰን - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ነገረ ፈጅ

አቶ ጌታነህ ቸሬ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ለውጭ አገር የተደወለ የስልክ አገልግሎት ክፍያ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ከታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር መስከረም 2004 ዓ.ም ድረስ የተጠቀመበትን ብር 19,793.52(አስራ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ሦስት ብር ከሃምሳ ሁለት ሣንቲም) እና የስልክ ቀፎ ዋጋ ብር 249.55(ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ አምስት ሣንቲም) በድምሩ ብር 20,043.07 (ሀያ ሺ አርባ ሶስት ብር ከሰባት ሣንቲም) የስልክ አገልግሎት ክፍያና የቀፎ ዋጋ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ የተጋነነ ሒሳብና ያልደወሉበት የውጭ አገር የስልክ ሒሳብ የተጠየቁና ይኸም በኮንፒዩተር ስህተት የመጣ መሆኑን በማስፅ ጉዳዩ እንዲመረመር ለአመልካች መሥሪያ ቤት ያመለከቱ መሆኑንና በዚህ መሠረት የታህሣሥ ወር ክፍያ ተመርምሮ ከብር 891.25(ስምንት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም) ወደ ብር 92.26 (ዘጠና ሁለት ብር ከሃያ ስድስት ሣንቲም) ዝቅ ያለ መሆኑን ገልፀው ሒሳቡ ሣይመረመር በዓለም ላይ ወደ ሌላ አገር USSR ደውለህል ተብዬ መከሰሴ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ የታህሣሥ ወር በአማካኝ ክፍያ እንዲፈፅሙ ስለተደረገ እንጅ ተመርምሮ ስህተት በመሆኑ ሒሳቡ አልተቀነሰም የተገለገሉበትን ስልክ ዋጋ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በክሱ የተገለፀውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የጠየቅሁት የስልክ ግልጋሎት ክፍያ በኮንፒዩተር ስህተት ምክንያት ተጋንኖ የተጠየቀ ነው፡፡ ይኸ እንዲመረመርልኝ ያቀረብኩት አቤቱታ በመቀበል እንዲመረመር ሣይደረግ ተጠሪ የጠየቀውን ሂሳብ እንድከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ያቀረብነው ክስ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ከአመልካች ላይ የጠየቀው የስልክ ግልጋሎት ዋጋ የተጋነነ በኮምፒዩተር ስህተት የመጣ ነው የሚለውን የአመልካች አቤቱታ መሠረት በማድረግ ጉዳዩ በባለሙያ ሣይመረመር ተጠሪ የጠየቀውን ሂሳብ በሙሉ አመልካች እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የስልክ መስመሩ ተገልጋይና የስልክ ቀፎው ባለይዞታ መሆኑ በእሱ ስልክ ቁጥር ወደ ውጭ አገርም ሆነ በአገር ውስጥ የተደረገው የስልክ ግንኙነት በእሱ የተፈፀመ ነው የሚል ግምት የሚያሣድር ነው፡፡ ሆኖም አመልካች የተጠየቀው የስልክ ግልጋሎት ዋጋ ከወትሮው የተለየና የተጋነነ መሆኑን አመልካች እስከ አዲስ አበባ ዋናው መሥሪያ ቤት ድረስ ያመለከተ መሆኑንና እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የታህሳስ ወር 2003 ብር 891.25(ስምንት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም) ተጠይቀው የነበረውን 92.26 /ዘጠና ሁለት ብር ከሀያ ስድስት ሣንቲም/ እንዲከፍል መደረጉን አመልካችና ተጠሪ አልተካካዱም፡፡ አመልካችና ተጠሪ የተለያዩበት ዋናው ነጥብ አመልካች ኮንፒዩተሩ ተመርምሮ ስህተት ሆኖ በመገኘቱ በፊት የተጠየቅሁት ገንዘብ ተቀንሶ ከፍያለሁ ሲል ተጠሪ በበኩሉ በአቨሬጅ ወጥቶና በዚያ መሠረት ተሰልቶ ነው እንዲከፍል የተደረገው በማለት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የሚካካዱበት ምክንያት ቢሆንም እንደ አውሮፓዊውያን አቆጣጠር ከታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ ከአመልካች የሚጠይቀው የስልክ ግልጋሎት ክፍያ አመልካች በደንበኝነት በቆዩበት ጊዜ ይከፍሉት ከነበረው አቨሬጅ ክፍያ በየወሩ ስምንት እጥፍ ብልጫ ያለውና የተጋነነ በመሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸንንም ሁኔታ በመቃወም አመልካች እንዲመረምርላቸው ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን ከበታች ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አመልካች የተገለገለበትን የስልክ ግልጋሎት ዋጋ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሲሆን በተነሣሪው ተጠሪ የአመልካች የስልክ መስመር ከአመልካች ውጭ ሌላ ሰው እንዳይገለገልበት ተገቢውን ጥበቃና ጥንቃቄ የማድረግና አመልካች ላገኘው ግልጋሎት የአገልግሎት ዋጋ የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ተጠሪ ደንበኞቹ የተጠየቁት የአገልግሎት ክፍያ ትክክለኛነት በሚጠይቁበት ወቅት የማስመርመሪያ ገንዘብ ከፍለው እንዲመረመር የሚያደርግ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ያላቸው የውል ግኑኝነትና በውል አፈፃፀም የሚነሡ ችግሮች በመጀመሪያ ተጠሪ በልምድ ባዳበረው አሠራር መሠረት መታየትና መጣራት ያለበት ነው፡፡ ይኸም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሊኖር የሚገባው ግኑኝነት ቅንነትንና መተማመንና በጉዳዩ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል ሊፈታ የሚገባው በመሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1732 ድንጋጌ ለመገንዘብ ስለሚቻልና ተጠሪ ደንበኞቹ የተጠየቁት የአገልግሎት ክፍያ የተጋነነ ነው ወይም ጥሪ ያላደረግሁበትን የውጭ አገር ስልክ አገልግሎት ዋጋ እንድከፍል ተጠይቄአለሁ በሚሉበት ወቅት ደንበኞቹ የተወሰኑ ሁኔታዎችን በማሟላት የሚመረመርበት በልምድ የዳበረ አሠራር ያለው በመሆኑ ተጠሪ እ.ኤ.አ በታህሳስ ወር 2003 የተጠየቀው ሂሳብ የተጋነነ መሆኑን አቤቱታ ሲያቀርብ ተገቢው ምርመራ ማድረግ ሲገባው ምርመራ አለማድረጉና እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከጥር ወር 2003 እስከ መስከረም 2004 ድረስ ያለው ሒሳብም ሣይመረመር አመልካች እንዲከፍሉ መጠየቁና የበታች ፍርድ ቤቶችም በጉዳዩ ተገቢው ምርመራ ተደርጎ ዕውነታው ሣይረጋገጥ ተጠሪ የጠየቀውን ገንዘብ አመልካች ሙሉ በሙሉ እንድከፍል መወሰናቸው አመልካችን ግዴታና ኃላፊነትና በልምድ የዳበረውን የተጠሪን አሠራር ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለማስመርመር የሚገባውን ግዴታና ኃላፊነት እንዲወጣ በማድረግና የአመልካች መስመር እንዲመረመር በማድረግ በሚቀርብለት ውጤት መሠረት ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 46052

ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሃይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ - ጠበቃ ውብሸት ሥ/ጊዮርጊስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የቦንጋ ማዘጋጃ ቤት ከፋ ዞን ዐ/ህግ - ነ/ፈጅ ደበበ ወንድሙ ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው ክስ አመልካች ዘመናዊ ሆስፒታል ለመገንባት ቦታ ጠይቀው 1,931 ካ.ሜ ቦታው ተሰጥቷቸው ግንባታውን ስላቋረጡ ውሉ ተሰርዞ ግንባታው በራሳቸው ወጪ አፍርሰው ቦታውን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ እንዲሁም ከ1996 ዓ.ም - 1999 ዓ.ም የቦታና የቤት ግብር ብር 52,782.35(ሃምሳ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺህ ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም) እንዲከፍሉ በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካቀረቡ በኋላ ለዋናው ጉዳይ በሰጡት መልስ ግንባታው የተቋረጠው በፕሮጀክቱ ሳይት ላይ ተጠሪ የኮንቴነር ሱቆች በማቆሙና ይህም የግንባታ እቃዎች በመኪና ተጭነው እንዳይገቡና እንዳይራገፍ እንቅፋት በመሆናቸው በተጨማሪም የግንባታ እቃ ዋጋ በመናሩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን፣ ለሆስፒታል አገልግሎት ለሚውል ጅምር ቤት ፕሮጀክቱ ሳይጠናቀቅ የቦታና የቤት ግብር ሊከፈል የማይገባ መሆኑንና በግራ ቀኙ መሃከል ውል ባለመኖሩ ክሱ ውድቅ እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን መርምሮ አመልካች ሳይት ፕላኑ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ግብር የመክፈል ሃላፊነት አለባቸው፣ የግንባታ ዕቃዎች ወደ ግቢው በመኪና ተጭኖ እንዳይገባ ያገደው ነገር የለም፣ ግራ ቀኙን የሚገዛ ህጋዊ ውጤት ያለው ውል አለ፣ ከዲዛይኑ አኳያ ከግማሽ በላይ የተከናወነ በመሆኑ ውሉ ተሰርዞ ለጅምር ግንባታው ግምቱን ተጠሪ ለአመልካች ከፍሎ ግንባታውን ከነይዞታው ይረከብ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ግራ ቀኙ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የሁለቱን ወገኖች ክርክር ተመልክቶ አመልካች የቦታና የቤት ግብር ሊከፍሉ አይገባም፣ ግንባታው የተቋረጠው በአመልካች ድክመት ወይም ጥፋት ሳይሆን ተጠሪ ባቆማቸው የኮንቴነር ሱቆች ችግር ምክንያት ለመሆኑ የፍ/ቤት ዳኛው ቦታው ድረስ በመሄድ አረጋግጠዋል፣ የግንባታ ዕቃዎች እጥረት ለግንባታው መቋረጥ አስተዋፅኦ አድርጓል፣ ተጠሪ ያቀረበው የይዞታ ማረጋገጫ ም/ወረቀት አመልካች የሆስፒታል ግንባታ በሚመለከት የፀና ውል መኖሩን አያስረዳም፣ ውል አለ ቢባል እንኳን በውሉ መሰረት እንዳይፈፀም አስተዋፅኦ ያደረገው ተጠሪ ስለሆነ ውሉ ሊሰረዝ የሚችልበት ሁኔታ የለም አለ ቢባል እንኳን ግንባታው ከ55% በላይ ስለተገነባ ወደነበሩበት መመለስ አስቸጋሪ ይሆናል በማለት ለግንባታው እንቅፋት የሆኑት ኮንቴነሮች ተጠሪ እንዲያነሳና ግንባታው ይቀጥል፣ አመልካች የቦታና ቤት ግብር አይከፍሉም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች የቤትና ቦታ ግብር ሊከፍሉ ይገባል፣ አመልካች ቀሪ ግንባታውን ሊያጠናቅቁ የሚገባበት ጊዜ ተጠሪ ወስኖ እንዲያሳውቃቸው፣ ተጠሪ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ማጠናቀቅ ካልቻሉ ውሉ ተሰርዞ ተጠሪ ቦታውንና ግንባታውን ባለበት ሁኔታ የመረከብ መብቱ ተጠብቋል፣ ለግንባታ ስራው እንቅፋት የሆኑት ኮንቴነር ሱቆች ተጠሪ በየደረጃው በመለየት እንዲያፈርስ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው ግንባታውን ያላጠናቀቁት በእርሳቸው ጥፋት ሳይሆን በፕሮጀክቱ ሳይት ዙሪያ ህገ-ወጥ የኮንቴነር ሱቆች እንዲለጠፉና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግንባታው ግብዓቶች ለመጫንና ለማራገፍ ባለመቻሉ መሆኑን፣ ተጠሪ እነዚህን ኮንቴነሮች በማንሳት ግንባታው እንዲቀጥል የማድረግ ኃላፊነቱን አለመወጣቱን፣ ግንባታው መጠናቀቅ የሚገባበትን የጊዜ ገደብ ተጠሪ ወስኖ እንዲያስታውቅ መደረጉ የህግ መሰረት እንደሌለው የቦታና የቤት ግብር ሊከፈል የሚገባው ግንባታው ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ስራ ላይ በዋለ ቤት በመሆኑ ግብር ሊከፍሉ እንደማይገባ ለፕሮጀክቱ ግንባታ ከፍተኛ መጠን ያለው መዋለ ንዋይና የሰው ሃይል ስለፈሰሰበት የተፈጠረው መሰናክል ተወግዶ ግንባታውን ተጠሪ እንዲረከብ መወሰኑ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎት ግንባታው የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ ተጠሪ ወስኖ ለአመልካች እንዲያሳውቅ እና አመልካች ለቦታና ቤት ግብር እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ከተገቢው ህግ አኳያ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንዳየነው አመልካች ሆስፒታል ለመገንባት ቦታ የተረከቡ ቢሆንም ግንባታውን አለማጠናቀቃቸው ያልተካደ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ተጠሪም ይህንን መሰረት አድርጎ ነው ውሉ እንዲፈርስ የጠየቀው፡፡ አመልካች በበኩላቸው ግንባታውን ያላጠናቀቁት በግዴለሽነት ሳይሆን በፕሮጀክት ሳይቱ ላይ ተጠሪ የኮንቴነር ሱቆች በማቆሙና ይህም የግንባታ እቃ ለማስገባትና ለማራገፍ እንቅፋት በመሆኑና በሃገሪቱ የግንባታ እቃም ዋጋ በከፍተኛ መጠን በመናሩ በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ ከመዝገቡ ላይ አመልካች ቦታውን ሚያዚያ 1993 ዓ.ም ተረክበው እስከ 1996 አጋማሽ ድረስ ግንባታውን ያከናውኑ እንደነበር ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፕሮጀክት ሳይቱ ላይ የኮንቴነር ሱቆች የቆሙት በ1997 መጨረሻ ወይም በ1998 መጀመሪያ ላይ ለመሆኑ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ማረጋገጡን ከውሳኔ ግልባጩ ተመልክተናል፡፡ ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠው የዳኝነት ስልጣን አንፃር ይህ ችሎት በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ትክክል ነው አይደለም የሚለውን ሳይመረምር እንዳለ የሚቀበለው ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ለግንባታው ስራ እንቅፋት ሆኑብኝ በማለት የሚጠቅሷቸው የኮንቴነር ሱቆች በሳይቱ አካባቢ የቆሙት አመልካች የግንባታ ስራውን ካቋረጡ እጅግ ዘግይቶ ነው፡፡ በመሆኑም ግንባታው በተጠሪ አስተዋፅኦ መቋረጡን በማንሳት ያቀረቡት ክርክር ፍ/ቤቱ ውድቅ በማድረጉ የሰራው የህግ ስህተት አለ ለማለት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል የክልሉ ደንብ ቁጥር 41/97 አንቀፅ 8(3) የግንባታ ቦታ የተረከበ አስገንቢ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ሥራውን መጀመር እንዳለበት እና እስከ ሁለት አመት ማጠናቀቅ እንዳለበት ያስጠነቅቃል፡፡ ትልልቅ ግንባታዎችን በተመለከተ ግን ውል ሰጪውን አካል በማስፈቀድ ጊዜውን ማራዘም እንደሚቻል ይፈቅዳል፡፡ ከፍ ሲል እንዳየነው አመልካች ቦታውን የተረከቡት ሚያዚያ 1993 ዓ.ም ነው፡፡ ነገር ግን ግንባታውን እስካሁን አላጠናቀቁም፡፡ እንደውም ከ1996 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ ግንባታው ተቋርጧል፡፡ ቀደም ብሎ እንደተመለከትነው ግንባታው የተቋረጠው በኮንቴነር ሱቆቹ ምክንያት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ለግንባታው መቋረጥ ሌላው የሰጡት ምክንያት የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ መናርን ነው፡፡ በእርግጥ በአገሪቷ ውስጥ የግንባታ ዕቃ ዋጋ መናር ተከስቶ እንደነበር የስር ፍ/ቤቶች ተቀብለውታል፡፡ ነገር ግን በዚህ ችግር ምክንያት ግንባታው የሚዘገይ ከሆነ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ደንብ መሰረት ውል ሰጪው አካል ጊዜውን እንዲያራዝም መጠየቅና ማራዘም በተገባቸው ነበር፡፡ ይህንን ስለማድረጋቸው ግን ማስረጃ አለመቅረቡን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ በመሆኑም በህጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ሳይጠይቁና በዚሁ ጊዜ ውስጥ ግንባታውን ሳያጠናቅቁ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ከዚህ ሌላ አመልካች ተጠሪ ግንባታው ሊጠናቀቅ የሚገባበት ጊዜ ወስኖ እንዲያሳውቅ መወሰኑ የህግ መሰረት የለውም በማለት ይከራከሩ እንጂ በክልሉ ደንብ መሰረት በደንቡ ግንባታ ለማጠናቀቅ የተቀመጠው ጊዜ እንዲረዝም ፈቃድ የሚሰጠው ውል ሰጪው አካል እንደመሆኑ መጠን የጊዜውንም እርዝመት እራሱ እንደሚወስን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ መሰረት ተጠሪ አመልካች ግንባታውን ማጠናቀቅ የሚገባቸውን ጊዜ ወስኖ እንዲያሳውቃቸው መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ማለት አልተቻለም፡፡

በመጨረሻም አመልካች ለጅምርና ጥቅም ላይ ላልዋለ ቤት የቦታና የቤት ግብር እንድከፍል የተሰጠው ውሳኔ የህግ ድጋፍ የለውም ይበሉ እንጂ በክልሉ አዋጅ ቁጥር 51/1994 እና በደንብ ቁጥር 41/1997 የከተማ ባለይዞታ የሆነ ማንኛውም ሰው ግንባታ ቢጨርስም ባይጨርስም የአገልግሎት ተጠቃሚ በመሆኑ ብቻ የተጠቀሱት ግብሮች እንደሚከፍል ይደነግጋል፡፡ አመልካች በተቃራኒው ለጅምር ቤት የቤትና የቦታ ግብር እንዳይከፈል የሚከለክል ህግ ስለመኖሩ የጠቀሱት ነገር የለም፡፡ በመሆኑም በዚህም በኩል የተሰጠው ውሳኔ የህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39394 የካቲት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. ይህ ችሎት ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 46394

የካቲት 11 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ወ/ሮ ስንቂ መስፍን - ጠበቃ ካሣሁን አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ጅፋር አባገሮ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኪራይ ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፊዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ መጋቢት 11 ቀን 2000 ዓ.ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በቀድሞ ወረዳ 02 ቀበሌ 09 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 026/3 የሆነ የተጠሪን ቤት ከአመልካች ጋር መጋቢት 01 ቀን 1998 ዓ.ም በተጻፈ የኪራይ ውል በወር ብር 629.00(ስድስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር) ተጠሪ ሊከፍሉና ከአከራይ ፈቃድ ውጪ ግንባታ ላያከናውኑ ግዴታ ገብተው (በመግባት) ውል ማድረጋቸውን ሆኖም አመልካች በውሉ ላይ የገቡትን ግዴታ በመጣስ የተጠሪን የጽሑፍ ፈቃድን ሳያገኙ የቀድሞውን ማቴሪያል በመቀየር ሽክላ አልብሰው እንደተገኙና እንዲሁም የጭስ ቤቱን ጣሪያ ከፍታ ጨምረው መሰራታቸውን ዘርዝሮ ውሉ ተቋርጦ ቤቱን እንዲያስረክቡ እስኪያስረክቡ፣ ድረስ የሚኖረውን ኪራይም እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሠጡት መልስ በቤቱ የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ፅዳቱ እንዲጠበቅለት በማሰብ ተጠሪን በተደጋጋሚ እንዲያስጠግንና እንዲያድስ ጠይቀው በተገቢው ጊዜ ተገቢው ምላሽ ስላልተሠጣቸው በሆቴሉ ስራ አስፈላጊ የሆነ ስራ መስራታቸውንና ይህንም ስራ በቀበሌ አስተዳደሩ አግባብነት ያለው መሆኑ መረጋገጡን ገልፀው ግንባታው የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት አይደለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የኪራይ ውሉ ተቋርጦ አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል እስኪያስረክቡ ድረስ ያለውን ኪራይም ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፊዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሰኔ 02 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሦስት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በቤቱ ላይ አድርገዋል የተባለው ተግባር/ሥራ/ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ የሚያበቃ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ተብሎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ሕዳር 09 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ከሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያቋቋመው የኪራይ ውሉ እንዲቋረጥ ዳኝነት የጠየቀው አመልካች በኪራይ ውሉ የገቡትን ግዴታ በመጣስ ያለተጠሪ ፈቃድ ግንባታ አከናውነዋል በሚል መሆኑን አመልካች ግንባታውን ማከናወናቸውን ሳይክዱ የተከናወነው ግንባታ ቤቱ ለሆቴል ስራ አገልግሎት የሚውል በመሆኑ ለስራው አስፈላጊ መሆኑን ይህም በቀበሌው ጽ/ቤትም ታይቶ ተገቢነቱ መረጋገጡን ማስረዳታቸውን ነው፡፡ እንግዲህ በኪራይ ውሉ ላይ አመልካች በቤቱ ላይ የሚያከናውኑትን ግንባታ ለተጠሪ በቅድሚያ የማሳወቅ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ አከራካሪ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አከራካሪው ለኪራይ ውሉ መቋረጥ ምክንያት የሚሆነው ምን አይነት ግንባታ ነው? የሚለው ነው፡፡ በተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገው የኪራይ ውል ማንኛውም ግንባታ የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት ስለመሆኑ እንደሚያሳይ ተጠሪ ገልፆ አለመከራከሩን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ ጉዳዩ በጠቅላላ የውል ሕግ ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ስለውሎች አተረጓጎም ደንቦችንና ኪራይን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ እልባት ሊሰጠው የሚገባው ነው፡፡ በዚህም መሰረት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1732 ድንጋጌ ሲታይ በተዋዋዮች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትንና የመተማመንን ግንኙነት መሰረት በማድረግና በጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ስርዓት በመከተል ውሎች በቅን ልቦና ሊተረጎሙ እንደሚገባ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2953 ተከራዩ ሊያድሳቸው የሚገባውን የተከራያቸውን ቤቶች በራሱ ኪሳራ ለማደስ የሚገደድ ስለመሆኑ ሲደነግግ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2954 የማደስ ትርጉምን አስቀምጧል፡፡ ይኸውም ተከራዩ ቤቶችን ማደስ ይገባዋል የተባሉትን(የሚባለውን) በኪራዩ ውል ተከራዩ ይፈጽማቸዋል ተብሎ የተወሰኑትን ስለመሆኑ ተቃራኒ የሚሆን ስምምነት ከሌለ በቀር ቤቶችን የማደስ ስራዎች ተብለው የሚቆጠሩት ደግሞ መዝጊያዎችን ወይም መስኮቶችን፣ የቤት ወለሎችን ወይም ጓጠፎችን፣ የውሃ መቅጃ መዘውሮችንና የውሃ መስደጃዎችን ለማደስ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን እንደሆነ እንደዚሁም በተከራየው ቤት ለመጠቀም አስፈላጊ የሆኑትን ቤቶችን የማፅዳትና በደንብ የመያዝ ስራዎች ቤቱን እንደማደስ ያሉ ተግባሮች ስለመሆናቸው ይደነግጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያከናወኗቸው የግንባታ ስራዎች በቤቱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ያመጡ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠው ግንባታው ለሆቴሉ ስራ አስፈላጊ ይልቁንም በሆቴሉ ተነስቶ ለነበረው የእሳት አደጋ ተጠቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ የሚያስችል ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አመልካች ያከናወኑት የግንባታ ስራ የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት ሊሆን የማይችል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሉን በኪራይ ውሉ ላይ የተመለከተውን “ግንባታ” የሚለውን ቃል ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1732፣ 2953 እና 2954 ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ ማገናዘብ ሲገባቸው ውሉ ሊቋረጥ ይገባል ሲሉ የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 105945 ሰኔ 20 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 69864 መጋቢት 28 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በቤቱ ላይ አድርገዋል የተባለው ተግባር/ሥራ/ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ የሚያበቃ አይደለም ብለናል፡፡ የኪራይ ውሉ በሌላ ሕጋዊ ምክንያት እስካልተቋረጠ ድረስ አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45559

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ አ/ማ - ነ/ፈጅ አስቱር በቀለ ቀረበች

ተጠሪዎች፡- 1. የአቶ ኃይሉ ፈይሳ - ወራሾች በሌሉበት

2. ወ/ሮ ብርቁ ዘለቀ - በሌሉበት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍ/ቤት የወለድ ስሌት እስከቀረበበት ቀን የተጠየቀውን ዳኝነት አልፎ ውሳኔ ከተሰጠበት በማለት የሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ ያደረጉትን ውል ባለማገናዘብ የተሰጠ በመሆኑ እንዲታረም የሚል ነው፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች ለተጠሪዎች የሰጠው የብድር ገንዘብ በከፊል ሳይከፈል የቀረ ስለመሆኑ ቀሪውን ገንዘብ ከልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት በመጠየቁ ነው፡፡ የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 370,295.81 ውሳኔ ከተሰጠበት ነሐሴ 15/1999 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 10.5% ወለድ፣ለዳኝነት የተከፈለውን ብር 9,150.09 እና ወጪዎች በቁርጥ ብር 200.00 ብር ጋር በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ወለዱ መታሰብ ያለበት ክስ ከቀረበበት ግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም መሆን ይገባዋል ሲል የሥር ፍ/ቤት ሥህተት እንዲታረም ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው የብድር ውል እዳው ተከፍሎ አለቀ ድረስ ያለማቋረጥ ከነወለዱ ለመክፈል መስማማታቸው ጠቅሶ የሥር ፍ/ቤት ወለዱን ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን እንዲታሰብ በማድረጉ አመልካች በልዩነት ብር 8,841.45(ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አርባ አንድ ብር ከአርባ አምስት ሣንቲም) እንዳያገኝ አድርጓል በሚል ይኸው እንዲታረም አመልክቷል፡፡

ሰበር ሰሚው ችሎትም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በሥር ፍ/ቤት የታለፈው በአግባቡ ስለመሆን አለመሆን ለመመረመር ተጠሪዎች እንዲቀርቡ አዟል፡፡ ተጠሪዎች በጋዜጣ ጥሪ ተደርጐላቸው ስላልቀረቡ ክርክሩ በሌሉበት ተሰምቷል፡፡

የአመልካችን አቤቱታ ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች የዋናው ገንዘብ ወለድ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ እንዲታሰብ ዳኝነት ጠይቆ ሳለ የሥር ፍ/ቤት ያለፈው የተለየ ምክንያት ያለው ስለመሆኑ በውሳኔው ያልጠቀሰ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ የገንዘብ ብድር ውል በግራ ቀኙ መካከል ሲደረግ ወለዱን ጨምሮ ለመክፈል ስምምነት የተደረገ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪዎችም በሥር ፍ/ቤት የተጠየቀውን ገንዘብ ወለድ የማይከፍሉበት ምክንያት ስለመኖሩ አላስረዱም፡፡ ይህ ሁኔታ በሌለበት የሥር ፍ/ቤት ወለዱ መታሰብ ያለበት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ነው ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ከግራ ቀኙ ውል እና በተጠሪዎችም ባልቀረበ ክርክር መነሻ በመሆኑ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ግራ ቀኙ ባደረጉት የገንዘብ ብድር ውል ተጠሪዎች ከነወለዱ ሳያቋርጡ ለመክፈል ግዴታ የገቡ በመሆኑ ስለውሎች በተደነገገው ፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1731 እና 2478 መሰረት ወለድንም ጭምር የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡ ወለዱንም ጭምር ከጅምሩም መክፈል ያለባቸው ስለመሆኑ በውለታቸው የተመለከተ መሆኑ ከታወቀ አመልካች ቅጣት 3% ጭምር ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ እንዲታሰብ የጠየቀውን ዳኝነት የሥር ፍ/ቤት ማለፉ ያላግባብ በመሆኑ እና በዚህ ረገድ የግራ ቀኙን ስምምነት ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህም ወለድን አስመልክቶ አመልካች እስካቀረበበት ከግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ 10.5% ወለድ እንዲታሰብ መወሰን ሲገባው ውሳኔ ከተሰጠት ቀን ማለትም ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ እንዲታሰብ በመወሰኑ በልዩነት አመልካችን ብር 8,841.45(ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አርባ አንድ ብር ከአርባ አምስት ሣንቲም) ማሳጣቱ ስህተት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ረገድ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02175 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03481 የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በከፊል ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች ያልከፈሉትን ቀሪ የብድር ገንዘብ ወለድ ማለትም ሥር ፍ/ቤት ክስ ከቀረበበት ከግንቦት 22/1999 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን ብር 8,841.45 (ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አርባ አንድ ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም) በሥር ፍ/ቤት ከተወሰነው ገንዘብ ጋር በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተሻሻለው ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም ለሥር ፍ/ቤት ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47800

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሃይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ወ/ሮ እመቤት ደርበው - የቀረበ የለም ከጠ/ሃይሉ አግዘው ጋር ቀረቡ

መ/ሰጪ፡- አቶ ታደለ ሰዳማ - የቀረበ የለም ከተባለ በኋላ ጠ/ሰመረ አሰፋ ቀረቡ

በዚህ መዝገብ የቀረበልንን ጉዳይ ተመልክተን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ እንደቻልነው አሁን በቀረበልን ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች ጣልቃ ገብ በመሆን በሆሳእና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበውት የነበረው የውል ይፍረስልኝ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካችዋ ውል ይፍረስልኝ በማለት ጥያቄ ያቀረቡት ያለእርሳቸው ፈቃድ ባለቤታቸው የጋራ ንብረት የሆነውን ድርጅት ለአሁኑ መልስ ሰጭ ሸጦአል በማለት ነው፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት በውሉ አፈፃፀም መሟላት የሚገባቸው የፎርም ቅድመ ሁኔታዎች እንደነበሩ ካረጋገጠ በኋላ ከውሉ መፈፀም በኋላ የተፈጠሩ ሌሎች በርካታ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ይመለሱ ሊባል አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጠ፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቢያቀርቡም ይግባኝ የቀረበለት የሐድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን አጽንቷል፡፡ ይግባኝ ፍ/ቤቱ ውሳኔው ሲያፀና ከውሉ መፈፀም በኋላ ድርጅቱን የገዛው የአሁን መልስ ሰጪ በርካታ ንብረት ሲያሰፍሩበት አመልካች በአጠገቡ ስለሚኖሩ ያውቁ እንደነበርም አትቷል፡፡ ከክርክሩ ሂደት አሁን አከራካሪ የሆነው ሽያጭ የተፈፀመው በ1992 ዓ.ም ሲሆን ጣልቃ ገብ ይፍረስልኝ ብለው የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ያቀረቡት የአሁኑ መልስ ሰጪ ስም ይዛወርልኝ በማለት ሐምሌ 11 ቀን 1997 ባቀረቡት ማመልከቻ መሰረት በተመሰረተው ክስ ነው፡፡

ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው የሰበር ማመልከቻ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበበት የወፍጮ የሽያጭ ውል ሕጉ የሚጠይቀውን የሁለቱም ተጋቢዎች ፈቃድና የምዝገባ ፎርማሊቱ አለማሟላቱ ከተረጋገጠ ሌላ ምክንያት በማቅረብ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት ሊመለሱ አይገባም መባሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚያመለክት ነው የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጪ በጽሑፍ ባቀረቡት መልስ የፎርማሊቱ ጥያቄውንም ሆነ የፈቃድ ጉዳዮችን ከውሉ በኋላ ከተደረገው ኢንቨስትመንት ጋር በማነፃፀር ውሉ አይፈርስም ተብሎ መወሰኑ አግባብ ነው ስለዚህ ውሣኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

እኛም ውሉ ከተፈፀመ በኋላ በተገዛው ንብረት ላይ የተደረገውን ለውጥ ግምት ውስጥ በማስገባት ውሉ እንዲፀና መወሰኑ አግባብ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎችና ይህ ፍርድ ቤት ቀደም ብሎ ከሰጣቸው የሕግ ትርጉም ውሣኔዎች ጋር በማያያዝ ተመልክተናል፡፡ በመሰረቱ የፈቃድ ወይም የፎርም ጉድለት ያለበት ውል ሕጉ መብት በሚሰጠው ሰው የይፍረስልኝ ጥያቄ ሲቀርብበት ፈራሽ እንደሚሆን በመርህ ደረጃ በሕጉ በግልጽ የሰፈረ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ውሉ በሚፈፀምበት ወቅት ጉድለት የነበረበት መሆኑ ከተረጋገጠ ውሉ እንዲፈርስና ባለጉዳዮች ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማዘዝ ከፍርድ ቤት የሚጠበቅና ሕጉም የሚያዘው መርህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ /የፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1815 ይመለከታል/ ሆኖም ይህ ተዋዋዮችን ወደነበሩበት የመመለስ መርህ ተፈፃሚ ማድረግ የማይቻል ከሆነ ወይም ለአንደኛው ተዋዋይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ ውሉን ለመፈፀም የተከናወኑ ተግባራት ፀንተው እንደሚቆዩ የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1817 በግልጽ ደንግጐታል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ውሉ ሲመሰረት ጉድለት የነበረበት መሆኑን ቢያረጋግጥም ውሉን ማፍረስ የማይቻል ወይም ለአንደኛው ወይም ለሁሉም ወገን ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን በሂደት ከተረዳ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ሊመለሱ አይገባም በማለት ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ ትርጉም ይህ የሰበር ችሎት በሌሎች በርካታ ጉዳዮችም የተከተለው ነው፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይም ፍ/ቤቱ የተከተለው ይህን መርህ ነው፡፡ ውሉ ሲመሰረት ጉድለት እንደነበረበት አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ውሉ በ1992 ዓ.ም ከተፈፀመ በኋላ በመልስ ሰጪ በኩል ተጨማሪ ንብረት የታከለበት መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቷል፡፡ አመልካችም በሰበር አቤቱታቸው ጭምር በተሸጠው ንብረት ላይ ተጨማሪ ግንባታ የተካሄደበት መሆኑን አይክዱም፡፡ ሁኔታው ይህ ከሆነ ደግሞ ፍ/ቤቶች የውሉ መፍረስ የሚያስከትለው ጉዳት በዝርዝር ገልጸው ውሉን ከማፍረስ ይልቅ ፀንቶ እንዲቆይ ማዘዛቸው የሕጉን አንቀጽ 1817/1/ መንፈስና ግልጽ ቃል የተከተለ እንጂ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተሰራበት ውሳኔ ሰጡ ለማለት የሚያበቃ ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም በዚህ ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊፀና የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በደ/ብ/ብ/ሕ/መ በሃዲያ ዞን የሆሳእና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0024/98 እና የሐድያ ዞን በመ/ቁ. 04688 የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ የራሳቸውን ወጪ ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 40336

መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ወንድወሰን ጥሩነህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የወ/ሮ አስገደች ካሣሁን ወራሽ ሄኖክ ሣሙኤል - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኪራይ ቤትን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጥቅምት 08 ቀን 2000 ዓ.ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በቀድሞው አጠራር በወረዳ 21 ቀበሌ 01 (ባሁኑ አጠራር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15) ቁጥር 288/45 የሆነውን ቤት ከሳሽ የሚያስተዳድረው ቤት አካል የሆነውን ቤት ተጠሪ ክሱ በስር ፍርድ ቤት እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ይዘው እየተጠቀሙ መሆኑን፣ቤቱን እንዲያስረክቡ ሲጠየቁም ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን ገልጾ ቤቱን እንዲያስረክቡ፣ቤቱን እስኪያስረክቡ ያለውን ኪራይ እና በዚህ ክስ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉ እንዲወሰንለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ አውራሼ ቤቱን ተከራይታ ስትኖርበት የነበረ ሲሆን ኪራዩን ባግባቡ እየከፈልኩ የምኖርበት ነው፣አመልካች ቤቱን ልቀቅ ሲል ያቀረበው ምክንያትም የለም፣የሰጠኝ ተለዋጭ ቤትም የለም፣ስለሆነም ተወልጄ ያደግሁበት ቤት እንድለቅ የቀረበው ክስ አግባብ ስላለሆነ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር በአመልካችና በተጠሪ መካከል የአከራይ ተከራይ ግንኙነት መጀመሩን፣ አመልካች ይህ ሆኖ እያለ ተጠሪን ቤቱን ልቀቅ የሚልበትን ምክንያት ሳይገልጽ ቤቱን እንዲለቅለት ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አግባብነት እንደሌለው በምክንያትነት በመያዝ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት የሚያስረክብበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ነሐሴ 28 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ በመጠየቁ ውሉ ሊቋረጥ የተፈለገበት ምክንያት አልተገለፀም በሚል አይቋረጥም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ነገረፈጅም የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር ይገባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪው ቤት ባለቤትነቱ የመንግስት ሆኖ የሚያስተዳድረው የአሁኑ አመልካች መሆኑን፣ቤቱን በተከራይነት የአሁኑ ተጠሪ ወላጅ እናት የሆኑት ሟች ወ/ሮ አሰገደች ካሳሁን ይዘው ሲጠቀሙት የቆዩ መሆኑን፣ተጠሪም በቤቱ በቤተሰብነት የኖሩበት ከመሆኑም በላይ አውራሻቸው ሲሞቱ ኪራዩን እየከፈሉ መጠቀም መቀጠላቸውን፣አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ቤቱን እንዲያስረክቡ ጥያቄ ቢያቀርብም ተጠሪ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ክስ ሊመሰርት የቻለ መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት እነዚህን ፍሬ ነገሮች አረጋግጦ የአመልካችን ክስ ውድቅ ሊያደርግ የቻለው አመልካች ቤቱን ተጠሪ እንዲለቅ ጥያቄ ሲያቀርብ ቤቱን ተጠሪ የሚለቁበትን ምክንያት አልገለፀም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ተጠሪ አውራሽ ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጊዜው ያልተቆረጠለት የኪራይ ውል በመካከላቸው መመስረቱንም ከክርክር ሂደት መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጥያቄ የዚህ አይነት የኪራይ ውል የሚቋረጠበት አግባብ እንዴት ነው? የሚለው ነው፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2966/1/ ሲታይ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውልን አከራዩ ተከራዩን ወይም ተከራዩ አከራዩን በማስታወቅ ሊያልቅ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በአከራዩም ሆነ በተከራዩ ላይ በሕጉ በተጣለው ግዴታ ማስታወቂያ መስጠት ሲሆን የዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ውሉ አለቀ የሚባለው በኪራዩ ውል ወይም በሕጉም መሰረት ተከታዩ የኪራይ ዘመን ዋጋ በሚከፈልበት ቀን ወይም የኪራዩ ውል ስለማለቅ ማስታወቁን ባይሰጥ ኑሮ ኪራዩ ሊከፈልበት ይገባው በነበረበት ቀን ስለመሆኑ ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ የምንገነዘበው ነጥብ ተከራይ እና አከራይ የኪራይ ውልን ማስታወቂያ በመስጠት ለማቋረጥ የሚችሉ መሆኑን እንጂ ውሉ የሚቋረጥበትን ምክንያት ጭምር የመግለጽ ግዴታ ያለባቸው አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ የሚፈልግበትን ምክንያት ጭምር መግለጽ ይኖርበታል በማለት ክሱን ወድቅ ያደረጉት በሕጉ አግባብ ያልተጣለበትን ግዴታ በመጨመር ሁኖ ስለተገኘ ውሳኔው ከላይ የተጠቀሰውን ድንጋጌ መንፈስ ያላገናዘበ፣የአመልካችን የመንግስት ቤቶችን የማስተዳደር ስልጣን ያጣበበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69842 ጥቅምት 02 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 62626 ሰኔ 04 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በቀድሞው አጠራር በወረዳ 21 ቀበሌ 01 (ባሁኑ አጠራር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15) ቁጥር 288/45 የሆነውን ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ፣ቤቱን እስኪያስረክቡ ያለውን ኪራይ እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 43381

መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፎዚያ ሁሴን

ተጠሪ፡- አቶ ውብሸት ተ/ወልድ

ፍ ር ድ

ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካችና በሌላ ግለሰብ ላይ በመሰረቱት ክስ በወረዳ 17 ቀበሌ 24 ክልል ውስጥ ቁጥር 050 የሆነው ቤት በወር 500.00(አምስት መቶ ብር) ለአመልካች አከራይተው የነበረ ቢሆንም አመልካች ያልከፈሉት የቤት ኪራይ መኖሩን፣ የኪራይ ውሉ ዘመን ካበቃ በኋላም አመልካች ቤቱን ያለአግባብ ይዘው ስለተጠቀሙ እንዲሁም ቤቱን ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ በማስተላለፍ ሁለቱም ያለአግባብ ስለበለፀጉ አመልካች ያልከፈሉት የኪራይ ገንዘብ ብር 26,000(ሃያ ስድስት ሺህ) እንዲከፍሉ እንዲሁም ሁለቱም ተከሳሾች በቤቱ ያለአግባብ በመበልፀጋቸው ኪሳራ እንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ቤቱ በመንገድ ስራ ምክንያት በመፍረሱ የቤቱን መመለስ አስመልክቶ በቀረበው ጥያቄ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ የለም በማለትና አመልካችን በተመለከተ የቀረቡትን ሌሎች የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ አመልካች ከተጠሪ ላይ ቤት ተከራይተው የውሉ ዘመን ሲያበቃ ቤቱን መመለስ ሲገባቸው ይዘው ያለአግባብ በመበልፀጋቸው ብር 26,000(ሃያ ስድስት ሺህ) ኪሳራ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ሁለቱን ወገኖች ሰምቶ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሆኖ ቅሬታው በአጭሩ የቤቱ ባለንብረት ነን በማለት ከአመልካች ኪራይ ሲቀበል የነበረው ቀበሌ ጣልቃ እንዲገባ ጠይቁ መከልከሉ አግባብ ስላልሆነ፣ ውሉ ፀንቶ ከሚቆይበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ድረስ 10 አመት ስለሚያልፍ ክሱ በይርጋ ቀሪ በመሆኑ፣ አላግባብ መበልፀግን መሰረት በማድረግ ክስ ለማቅረብ የንብረቱ ባለቤት መሆን ስለሚያስፈልግ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊሻር ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት አመልካች ከቤቱ ባለንብረት ጋር የኪራይ ውል በማድረግ ኪራይ ሲከፍሉ የነበረ በመሆኑ በዛው ጉዳይ አላግባብ መበልፀግ በሚል ገንዘብ እንዲከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አኳያ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ባለንብረት ቀበሌው መሆኑ፣ ቤቱን በቅድሚያ ከቀበሌው የተከራዩት ተጠሪ መሆናቸው፣ አመልካች ቤቱን መጀመሪያ የተከራዩት ከተጠሪ ላይ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ቀበሌው ከተጠሪ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል ሰርዞ ቤቱን ለአመልካች ማከራየቱን ተጠሪ ክደው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በሌላ ሰው ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠንና ባደረሰው ጉዳት መጠን ለባለሃብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው ኪሳራ ሊከፍል እንደሚገደድ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2162 ይናገራል፡፡ በመሆኑም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ድንጋጌ መሰረት ኪሳራ የሚጠይቀው ሰው የንብረቱ ባለሃብት መሆኑን ማረጋገጥና ተከሳሹ በንብረቱ ያለበቂ ምክንያት መገልገሉን ማስረዳት አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የቀበሌው መሆኑ አልተካደም፡፡ ተጠሪም በአንድ ወቅት ቤቱን የተከራየ ግለሰብ እንጂ ባለሃብት አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቤቱ ባለሃብት የሆነው ቀበሌው ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የቤት ኪራይ ውል አቋርጦ ከአመልካች ጋር ከነሐሴ 1988 ዓ.ም ጀምሮ የኪራይ ውል አድርጓል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የቤቱ ላይ የነበራቸው የተከራይነት መብትም ቢሆን አክትሟል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላም ተጠሪ በቤቱ ላይ ያገኙት የተከራይነት መብት ስለመኖሩ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በተጨማሪም አመልካች በቤቱ ሲገለገሉ የቆዩት ከቤቱ ባለቤት ከሆነው ቀበሌ ተከራይተው በመሆኑ በቤቱ ያለበቂ ምክንያት ተገልግለዋል ለማለት አይቻልም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በቤቱ ያለበቂ ምክንያት ያለአግባብ መገልገል በልጽገዋል በማለት ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ከፍ ሲል በተገለጹት ምክንያቶች ተቀባይነት የለውም፡፡ የስር ፍ/ቤትም ተጠሪው በአንድ ወቅት ቤቱን ከቀበሌ ተከራይተው ለአመልካች ማከራየታቸውን ብቻ በመመልከት አመልካች ያለአግባብ በልፅገዋል ሲል ብር 26,000(ሃያ ስድስት ሺህ) እንዲከፍሉ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 48820 ህዳር 6 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 52062 ህዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች አለአግባብ በልፅገዋል ሊባል ስለማይችል ብር 26,000(ሃያ ስድስት ሺህ) ለተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43992

መጋቢት 6 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሃይ ታደሰ

ኒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1. አቶ ይልማ አንበሴ
2. ወ/ሮ አስቴር ሃይሌ
3. አቶ ብሩክ ይልማ
4. አቶ ትእዛዙ አንበሴ

ጠ/ካሣሁን አሠፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ እመቤት መንገሻ
2. ወ/ሮ ቤተልሔም ግርማ
3. አቶ ብሩክ ግርማ
4. አቶ ሱራፌል ግርማ
5. አቶ በቃ ግርማ

አልቀረቡም

ፍ ር ድ

አመልካቾች በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ሆቴላቸውን ተከራይተው የኪራዩ ዘመን ሲያበቃ ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ተከሰው በፍርድ ሆቴሉን ስለመለሱ ከውል ውጪ ሆቴሉን ይዘው ለተገለገሉበት ጊዜ የኪራይ ገንዘብና ያላግባብ ለበለፀጉበት በበለፀጉበት መጠን እንዲከፍሉ ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱ ከ2-4 ያሉትን አመልካቾች ከክሱ ነፃ በማድረግ አንደኛ አመልካች ከውል ውጪ በሆቴሉ ለ86 ወራት በመገልገል ያለአግባብ የበለፀጉበትን ብር 602,000.00(ስድስት መቶ ሁለት ሺህ) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ በመወሰኑና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሳኔ በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

ተጠሪዎች በክሳቸው ዝርዝር አመልካቾች ሆቴሉን የውሉ ዘመን ካበቃ በኋላ ሆቴሉን ያለአግባብ ይዘው በመገልገላቸው ኪሳራ ከፍለው ሆቴሉን እንዲለቁ ስለተወሰነባቸው ከጎዳር 2 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ ሆቴሉን ለተጠሪዎች እስካስረከቡበት ታህሳስ 26 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የድርጅቱን ኪራይና ወለድ፣መብት ሳይኖራቸው ይዘው ባይጠቀሙ ኖሮ ተጠሪዎች ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን ጥቅምና ወለድ እንዲሁም ከ1995-1996 ዓ.ም ያገኙትን ትርፍ በአጠቃላይ ብር 2,102,261.35(ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ብር ከሠላሣ አምስት ሣንቲም) እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች ለስር ፍ/ቤት በሰጡት መልስ ከ2-4 ያሉት አመልካቾች ላይ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሰረት ውድቅ ነው፣ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው፣ድርጅቱን የያዝነው በመንግስት መመሪያ መሰረት ከኪ.ቤ.አ.ድ ተከራይተን ስለሆነ አላግባብ በልጽጋችኋል ልንባል አይገባም፣ከ2-4 ያሉት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች በድርጅቱ ስለመስራታችን የቀረበ ማስረጃ የለም፣ተጠሪዎች አጥተዋል ሊባል የሚችለው ኪራይ ብቻ በመሆኑ የታጣ ገቢ ሊጠይቁ አይችሉም፣ከውል ውጪ ደረሰ በሚሉት ጉዳት ወለድ መጠየቅ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በአመልካቾች የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ ካደረገ በኋላ ከ2-4 ያሉት አመልካቾች ድርጅቱን ይዘው ተገልግለዋል ማለት አይቻልም ተብሎ በመ/ቁ. 11597 ስለተወሰነና ስለመገልገላቸው ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ከክሱ ነፃ ናቸው፣አንደኛ አመልካች ግን በፊ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ በፊ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የሆቴል ድርጅቱን ያለአግባብ ይዘው በመቆየታቸው ተጠሪዎች ላይ ለሚደረሰው ጉዳት ሃላፊ ስለሆኑ ኪሳራ ሊከፍሉ ይገደዳሉ ስለተባለ ሃላፊ ናቸው በማለት ከጎንዳር 1989 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 27 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የ86 ወር ብር 602,000.00(ስድስት መቶ ሁለት ሺህ ብር) ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፊ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካቾች ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2143 በይርጋ ሊታገድ ይገባል፣አንደኛ ተጠሪ ድርጅቱን የተገለገልኩት በመንግስት መመሪያ ከኪ.ቤ.አ.ድ ጋር ባደረኩት የኪራይ ውል በመሆኑ ያለበቂ ምክንያት እንደተገለገልኩ ተደርጐ ያለአግባብ በልጽገሃል ልባል አይገባም፣ተጠሪዎች ቀደም ሲል ሲከሱ ድርጅቱ እስኪለቀቅላቸው ድረስ ኪራይ መጠየቅ ሲችሉ ነጥለው ባቀረቡት ክስ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 መሰረት ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ አይችሉም፣ የሰራሁት ከ2-4 ካሉት አመልካቾች ጋር ኃ/የተ/የግ/ማህበር ማቋቋም በመሆኑ ብቻዬን ሃላፊ ልባል አይገባም፣ለኪ.ቤ.አ.ድ በወር ብር 4,767.00(አራት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት) ስከፍል ስለነበር ይኸው ገንዘብ ሊቀነስ ይገባል፣ወለድ ልከፍል አይገባም፣ሊከፈል ይገባል ከተባለም ያለአግባብ መበልጸጌ በፍ/ቤት ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይገባል፣ከ2-4 የተጠቀሱት አመልካቾች ወጪና ኪሳራ ሊታሰብላቸው ይገባል በማለት ስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡ ይህ ችሎት አመልካቾች ያቀረቧቸው ቅሬታዎች ለሰበር ችሎት ቀርበው እንዲታዩ በማዘዙ ተጠሪዎች ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት ካቀረቡት ቅሬታ አኳያ ይህ ችሎት ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል ብሎ ያመነባቸው፣

1. ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል? አይገባም?
2. ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216/4/ መሰረት በድጋሚ ሊቀርብ አይችልም? ይችላል?
3. አንደኛ አመልካች ብቻቸውን ለክሱ ሃላፊ ናቸው? አይደሉም?
4. ሃላፊ ናቸው ከተባለ መጠኑን አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት? የለበትም?
5. አንደኛ ተጠሪ ወለድ ሊከፍሉ ይገባል? አይገባም?
6. ከ2-4 ያሉት አመልካቾች ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው አለመወሰኑ መሰረታዊ ሕግ ስህተት ነው? አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡ ችሎቱም እያንዳንዱን ጭብጥ በየተራ ተመልክቷል፡፡

1. <u>ይርጋ በተመለከተ</u>

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት አንደኛ ተጠሪ ከውልና ከሕግ ውጪ የተጠሪዎችን የሆቴል ድርጅት ይዘው በመገልገል ያለአግባብ በመበልፀጋቸው ኪሳራ ከፍለው ድርጅቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ስለተወሰነባቸው የፍ/ቤቱ ውሳኔ ካረፈበት ዘመን ጀምሮ ድርጅቱን እስካስረከቡበት ጊዜ ድረስ ያለአግባብ በድርጅቱ በለፀጉበት መጠን እንዲከፍሉ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ክሱ የቀረበው ነሐሴ 16 ቀን 1996 ዓ.ም ስለሆነ ከነሐሴ 16 ቀን 1994 ዓ.ም በፊት ያለው በፍ/ሕ/ቁ. 2143 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 ሳይሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ እና 1845 ነው በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን እንደመረመረው አግባብነት ያለው የትኛው የሕግ ድንጋጌ ነው የሚለው እንዳለ ሆኖ አንደኛ አመልካች እንደሚሉት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 ነው ቢባል እንኳን ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ቀደም ሲል በነበረው ክርክር አንደኛ አመልካች ድርጅቱን የውሉ ዘመን ካበቃ በኋላ ድርጅቱን ያለአግባብ በመያዛቸው ድርጅቱን እንዲለቁና ኪሳራ እንዲከፍሉ ጥቅምት 22 ቀን 1989 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ በፍ/ቤት ክርክር ሲደረግበት ቆይቶ በመጨረሻ በጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ያገኘው ሚያዝያ 21

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀን 1995 ዓ.ም ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ አስመልክቶ ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡት ነሐሴ 16 ቀን 1996 ዓ.ም ነው፡፡ ይርጋ ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች አንደኛው ባለገንዘቡ መብቱ እንዲታወቅለት በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለባለእዳው አስታውቆ የተገኘ እንደሆነ መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1851/ለ/ ስር የተመለከተ በመሆኑ ተጠሪዎች መብታቸውን ለማረጋገጥ ያቀረቡት ክስ ይርጋውን ስለሚያቋርጠውና በዚህ መዝገብ በቀረበው ጉዳይ ላይ ክስ የቀረበው የቀድሞው ክስ የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኋላ ሁለት አመት ሳይሞላው በመሆኑ አንደኛ አመልካች ይርጋውን በተመለከተ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

2. <u>ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216/4/ መሰረት ድጋሚ ሊቀርብ አይገባም የተባለው በተመለከተ</u>

ተጠሪዎች ቀደም ሲል ባቀረቡት ክስ አንደኛ አመልካች የኪራይ ዘመኑ ካበቃ በኋላ የሆቴል ድርጅቱን ይዘው ስለተገለገሉ ክስ እስከቀረበበት ግዜ ድረስ ያለውን ኪራዩን ከፍለው እንዲወጡና ክስ ከተመሰረተ በኋላ ላለው ጊዜ የመክሰስ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም አንደኛ አመልካች ያለአግባብ የሆቴል ድርጅቱን ስለያዙ ክስ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ያለውን ኪሳራ ሲወስን ከክሱ በኋላ ላለው ጊዜ በሕጉ መሰረት የመክሰስ መብታቸውን ጠብቆላቸዋል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216/2/3/ መሰረት ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ አጠቃሎ ማቅረብ እንዳለበትና ክስ ለማቅረብ ሲችል ሆነ ብሎ ቀንሶ ባስቀረው ንብረት ላይ ድጋሚ ክስ ለማቅረብ የማይቻል መሆኑን አጠቃላይ መርህ ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤትን በማስፈቀድ ሊጠየቅ ይገባው ከነበረው ውስጥ ቀንሶ ማስቀረት እንደሚቻልና በከፊል በቀረው መብት ላይም ድጋሚ ክስ ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ ንኡስ ቁጥር 4 ልዩ ሁኔታን አስቀምጧል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪዎች ከክሱ በኋላ ላለው ጊዜ የመክሰስ መብታቸውን ፍ/ቤቱ የጠበቀላቸው በመሆኑ ቀደም ሲል ሊከሱ ሲገባ ቀንሰው ስላስቀሩ በድጋሚ ሊከሱ አይገባም የሚለው የአንደኛው አመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

3. <u>አንደኛ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ሃላፊ ናቸው አይደሉም? የሚለውን በተመለከተ</u>

ቀደም ሲል ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አንደኛ አመልካች የተጠሪዎች ሃብት መሆኑን እያወቁ በውል ወይም በሕግ ሆቴሉ ላይ ያገኙት መብት ሳይኖር ከተጠሪዎች ፈቃድ ውጪ በእምቢተኝነት ይዘው በመቆየታቸው ተጠሪዎች ራሳቸው ሰርተው እንዲጠቀሙበት ወይም ለአንደኛ አመልካች ባከራዩት መንገድ ለሌላ ሰው አከራይተው የኪራይ ገቢ እንዳያገኙበት በማድረግ ጉዳት በማድረሳቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2027/2/ እና 2028 መሰረት በሃላፊነት ሊጠየቁ የሚገባ ከመሆኑም በላይ በፍ/ሕ/ቁ. 2162 መሰረት ኪሳራ ሊከፍሉ ይገደዳሉ በማለት አንደኛ አመልካች ብቻቸውን ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የአንደኛ አመልካች ሃላፊነት ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ ብቻቸውን ኪሳራ የመክፈል ሃላፊነት አለባቸው፡፡

4. <u>የኪሳራውን መጠን በተመለከተ</u>

ይህን ነጥብ አስመልክቶ አንደኛ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ቤቱን መንግስት ባወጣው መመሪያ መሰረት ከኪ.ቤ.አ.ድ ከታህሣሥ 1 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምሮ ተከራይተው ለድርጅቱ በወር ብር 4,767.00(አራት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት) ሲከፍሉ ስለነበር የስር ፍ/ቤት ይህንኑ ገንዘብ ሊቀነስ ይገባ ነበር የሚል ነው፡፡ አንደኛ አመልካች የሆቴል ድርጅቱን ያለበቂ ምክንያት ይዘው በመገልገላቸው አላግባብ በበለፀጉበት መጠን ሃላፊ መሆናቸው ተወስኗል፡፡ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሲሰጥ የኪሳራው መጠን ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበትና ተጠሪዎች ያጡት ጥቅም በኪራይ መጠን ልክ ታስቦ መሆን እንዳለበት የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት አስቀድሞ መወሰኑን ከግምት በማስገባት ተጠሪዎች የሚገባቸው ድርጅታቸው ከውል ወይም ከህግ ውጪ በአንደኛ አመልካች በመያዙ ምክንያት እነሱ ባጡት ልክና አመልካቹ ራሳቸውን ባበለፀጉበት መጠን ሲሆን ይህም የድርጅቱ የኪራይ መጠን ነው በማለት በወር ብር 7,000.00(ሰባት ሺህ) ታስቦ የ86 ወር ብር 602,000(ስድስት መቶ ሁለት ሺህ) ወስኗል፡፡ በሌላ ሰው የስራ ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልግል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠንና ለባለሃብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው አድራጉቱ ባደረሰው ጉዳት መጠን ለባለሃብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው ኪሳራ መክፈል እንደሚገደድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2162 ስር ተመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች ላይ የደረሰው የጉዳት መጠን በድርጅቱ ኪራይ መጠን እንደሆነ ቀደም ሲል የፌ/ጠቅላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤት ሆነ በዚህ ጉዳይ ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ወስነዋል፡፡ ነገር ግን አንደኛ አመልካች ለታህሣሥ 1 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምረው ከኪ.ቤ.አ.ድ ጋር ባደረጉ የኪራይ ውል ለድርጅቱ ብር 4,767.00 ኪራይ ይከፍሉ እንደነበር የገለፁትን ተጠሪዎች ክደው አልተከራከሩም፡፡ በመሆኑም አንደኛ አመልካች አላግባብ በለፀጉ ሊባል የሚችለው ከድርጅቱ የኪራይ መጠን ላይ ለኪ.ቤ.አ.ድ ሲከፍሉ የነበሩ ኪራይ ተቀንሶ በልዩነት በሚገኘው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ 1ኛ አመልካች በአንድ በኩል ለኪ.ቤ.አ.ድ ኪራይ ሲከፍሉ ቆይተው በድጋሚ ለተጠሪዎች ገንዘቡን ይክፈሉ ማለት አለአግባብ ከበለጸጉበት ገንዘብ በላይ እንዲከፍሉ ማድረግ በመሆኑ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተመለከቱት የኪሳራ አከፋፈል ደንብን የሚጥስ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አንደኛ አመልካች ያለአግባብ ከበለጸጉበት በላይ እንዲከፍሉ መወሰናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

5. <u>ወለድን በተመለከተ</u>

አንደኛ አመልካች ያለአግባብ በልጽገዋል ተብሎ ለቀረበ ክስ ወለድ ሊከፈል እንደማይገባና ይገባል የሚባል ቢሆን እንኳን ሊከፈል የሚገባ ያለአግባብ መበልፀጋቸው በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ አንደኛ አመልካች የተጠሪዎች የሆቴል ድርጅት ከሕግና ከውል ውጪ ይዘው በመገልገል ያለአግባብ መበልፀጋቸው በመረጋገጡ ኪሳራ እንዲከፍሉ ተወስኖባቸዋል፡፡ በመሆኑም ገንዘቡን ከፍለው እስኪያጠናቅቁ ድረስ ወለድ የማይከፍሉበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በሌላ በኩል እኚሁ ተጠሪ አላግባብ መበልፀጋቸው የተረጋገጠው በዚህ መዝገብ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ቀደም ሲል የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሚያዝያ 21 ቀን 1995 ዓ.ም ውሳኔ ሲሰጥ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አንደኛ አመልካች በዚህ ጉዳይ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ገንዘቡን እንዲከፍሉ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም፡፡

6. <u>ወጪና ኪሣራን በተመለከተ</u>

በስር ፍ/ቤት ከሁለት እስከ አራት ያሉት አመልካቾች ክሱ በነፃ በመሰናበታቸው በጉዳዩ ረቺ መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.462 ስር እንደተመለከተው ፍ/ቤቱ በክስ ምክንያት የሚከፈለውን ወጪና ኪሳራ በተመለከተ ሊከፈል የሚገባው መሆን አለመሆኑን፣ማን እንደሚከፍልና ምን ያሕል እንደሚከፈል ፣ከምን ሃብት ላይ እንደሚከፈል በአጠቃላይ ትክክል መስሎ በሚገመተው ሁኔታ ትእዛዝ መስጠት የሚያስችለው ሰፊ ስልጣን አለው፡፡ በመሆኑም የክርክሩን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ እንዲቻቻሉ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ለማለት አላስቻለንም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33915 ሰኔ 28 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31943 ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አንደኛ አመልካች የተጠሪዎችን የሆቴል ድርጅት ያለአግባብ ይዘው የበለፀጉበትን መጠን በወር ብር 7000(ሰባት ሺህ) በመሆኑና ከዚህ ገንዘብ ውስጥ አንደኛ አመልካች ለኪ.ቤ.አ.ድ ሲከፍሉ የነበረው ብር 4,767.00 (አራት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት) ሊቀነስ ስለሚገባ አንደኛ ተጠሪ የ86 ወራት በወር ብር 2,233.00(ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሶስት) ታስቦ በጠቅላላው ብር 192,038(አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ሺ ሰላሳ ስምንት) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪዎች ይክፈሉ፡፡
3. ቀሪው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. በተሻሻለው ውሳኔ መሰረት መፈፀም ይቻል ዘንድ ይህ ችሎት ሚያዝያ 13 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43636

መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ተሰማ - ጠ/ደሣለኝ ደምሴ

ተጠሪ፡- 1. አቶ በየነ ወ/ሚካኤል
2. ወ/ሮ ዕጌ ተሾመ
} የቀረበ የለም

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ውል ይፈፀምልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ ተጠሪዎች ቤት ሸጠውላቸው አብዛኛውን ገንዘብ የተቀበሉ መሆኑን ገልፀው ቀሪውን ክፍያ ተቀብለው ቤቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎችም ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ አመልካች እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁት ውል ከተደረገ 10 አመት ያለፈው በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የመ/ደረጃ መቃወሚያና ሌሎች ክርክሮች አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ውሉ የተደረገው የካቲት 18 ቀን 1985 ዓ.ም ሲሆን ክስ የቀረበው ደግሞ ከ14 ዓመት በኋላ ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው ተጠሪዎች ቀሪ ገንዘብ አልተከፈለንም በማለት በአመልካች ላይ ክስ አቅርበው ውሉ አይፈርስም ተብሎ ህዳር 15 ቀን 1993 ዓ.ም ውሳኔ ስለተሰጠ ይርጋው ይቋረጣል፣ ውሉ ሊፈርስ ይገባል? አይገባም? የሚለው ክርክር ውጤት ሳያገኝ ውል ሊፈፀም ይገባል? አይገባም? የሚል ክርክር ሊቀርብ ስለማይገባ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ ለክርክር ምክንያት የሆነው የሽያጭ ውል ይፈርሳል አይፈርስም? በሚለው ነጥብ ላይ በፍ/ቤት ሲከራከሩ የቆዩ መሆኑ ከተረጋገጠ የአመልካች የንብረት ልረከብ ጥያቄ በይርጋ ሊታገድ ይገባል የሚለውን ዳኝነት አግባብነት ለማየት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘ ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት ከተጠሪዎች ጋር ባደረጉት የሽያጭ ውል መሰረት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካች እየጠየቁ ያሉት ውል እንዲፈፀምላቸው ነው፡፡ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈፀም ወይም ካለመፈፀሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በአስር አመት ይርጋ እንደሚቀር ፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 ይናገራል፡፡ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት መቃወሚያ አመልካች የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ ያቀረቡት ውሉ ከተደረገ ከ10 አመታት በኋላ በመሆኑ ጥያቄው በይርጋ ሊታገድ ይገባል በሚል ነው፡፡ ከስር ፍ/ቤት መዝገብ እንደተረዳነውም በግራ ቀኙ መሃከል የሽያጭ ውል የተደረገው የካቲት 18 ቀን 1985 ዓ.ም ሲሆን ክሱ የቀረበው ግን ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም ከ14 አመት በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል የሚለው መከራከሪያ አግባብነት አለው፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ምንም እንኳን ውሉ ከተደረገ 10 አመት ያለፈው ቢሆን ተጠሪዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሉ እንዲፈርስላቸው ክስ መስርተው ክርክር ሲደረግ ቆይቶ ውሉ አይፈርስም በሚል የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠው ህዳር 15 ቀን 1993 ዓ.ም በመሆኑ ይርጋውን ያቋርጠዋል እንዲሁም ውል ይፈርሳል አይፈርስም የሚለው ጭብጥ ክርክር ላይ እያለ ይኸው ውል ሊፈፀም ይገባል የሚል ክርክር እንዳይቀርብ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8 ይከለክላል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ቢኖርም ይህ የይርጋ ጊዜ ግን በተለያዩ ምክንያቶች ሊቋረጥ እንደሚችል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 ያስቀምጣል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ይርጋ ከሚቋረጥበት ምክንያት አንዱ ባለገንዘቡ መብቱ እንዲታወቅለት በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ለባለእዳው አሳውቆ የተገኘ እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የሚከራከሩት ውል እንዲፈርስ ክስ አቅርበው የነበሩት ተጠሪዎች እንጂ አመልካች ባለመሆናቸው ይርጋው ሊቋረጥላቸው አይችልም በማለት ነው፡፡ ከመዝገቡም እንደተረዳነው በእርግጥም ቀደም ሲል ውሉ እንዲፈርስ ክስ አቅርበው የነበሩ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በቀረበውም ክስ ፍ/ቤቱ የያዘው የሽያጩ ውል ሊፈርስ ይገባል አይገባም የሚለውን ጭብጥ ግን ውሉ ሊፈፀም ይገባል አይገባም ከሚለው ጭብጥ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም ውሉ ሊፈርስ ይገባል ከተባለ ውጤቱ ግራ ቀኙ ውሉን ለመፈፀም የሰሯቸው ስራዎች ሁሉ ቀሪ ሆነው ወደነበሩበት መመለስ ሲሆን ውሉ የማይፈርስ ከሆነ ደግሞ ውሉ እንዲፈፀም ለሚጠይቀው ወገን የውሉን መፈፀም እንዲጠይቅ መብት የሚሰጠው በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የውሉን አፈፃፀም በተመለከተ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ክርክር ይርጋውን የሚያቋርጠው ነው፡፡ በአጠቃላይ ግራ ቀኙ በውሉ መፍረስ አለመፍረስ ክርክር ላይ በነበሩበት ወቅት አመልካች ውል እንዲፈፀምላቸው ክስ ስላላቀረቡ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 6841 መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 66753 ህዳር 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም ብለናል፡፡ በመሆኑም በፍሬ ጉዳዩ ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 46947

መጋቢት 07 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ዘበነ ኃ/ማሪያም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ አባይነሽ ለገሰ

2. ወ/ሮ አስካለ ወ/ሐዋሪያት } ቀረቡ

3. ወ/ሮ ጽጌ ተሰማ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኪራይ ገንዘብን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆኑ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች ከተጠሪዎች አንድ ክፍል የፀጉር ቤት ሱቅ በወር ብር 155.00(አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ብር) ለመክፈል ተስማምተው፣ተከራይተው ከሐምሌ 1999 ዓ.ም እስከ ሕዳር 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን ውዝፍ የቤት ኪራይ እዳ ያልከፈሉ መሆኑን በመግለጽ በገቡት የኪራይ ውል ግዴታ መሰረት እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ በማንሳት የተከራከሩት የኪራይ ውል ከተጠሪዎች ጋር ማድረጋቸውን ሳይክዱ ውሉ የተደረገው ተጠሪዎች በፀጉር ቤቱ ላይ መብት ሳይኖራቸው በማጭበርበር በመሆኑ አዲስ የኪራይ ውል ከሕጋዊ ባለቤት (ሬድባር ከተባለ የንብረሰናይ ድርጅት) ጋር አድረገው ኪራዩን ለዚሁ ህጋዊ ባለቤት ለሆነው ማህበር በደረሰኝ እየከፈሉ ሱቁን የሚሰሩበት መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት ክርክሩን ከመረመረ በኋላ አመልካች የኪራይ ውሉን ከሱቁ ህጋዊ ባለቤት ጋር አድርጌአለሁ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው፣ህጋዊ ነው የተባለ ድርጅትም ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጐ አለመከራከሩ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጐ ለኪራይ ገንዘቡ ኃላፊ በማድረግ ብር 2,870.00(ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ብር) ለተጠሪዎች እንዲከፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ ከዚያም አመልካች በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት በሰበር አቤቱታ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ሰኔ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በዛፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱት በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪዎች በሱቁ ላይ ሕጋዊ መብት ሳይኖራቸውና የኪራይ ገንዘቡን አመልካች በአዲስ ኪራይ ውል መሰረት ለሕጋዊ አከራይ የኪራይ ገንዘቡን ከፍለው ባለበት ሁኔታ ተጠሪዎች ቀደም ሲል የኪራይ ውል አድርገዋል ተብሎ የኪራይ ገንዘቡን አመልካች በድጋሚ እንዲከፍሉ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፣አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ተጠሪዎች ያከራዩኝ የእነርሱ ያልሆነ ቤት ነው እኔ ከቤቱ ትክክለኛ ባለንብረት ጋር የቤት ኪራይ ውል ተዋውዬ ለቤቱ ባለቤት ኪራይ ከፍያለሁ በማለት ካቀረቡት ክርክርና ማስረጃ ታልፎ ለተጠሪዎች የቤት ኪራይ ይክፈሉ መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪዎች ቀርበው ታሕሳስ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎችንና አመልካች የኪራይ ውል ማድረጋቸውን፣አመልካች ለተወሰነ ጊዜ የኪራይ ገንዘቡን ለተጠሪዎች ከከፈሉ በኋላ ማቋረጣቸውን፣አመልካች የኪራይ ገንዘቡን ለተጠሪዎች አልከፍልም በማለት የሚከራከሩት የሱቁ ሕጋዊ ባለቤት አይደሉም፣ምንም መብት የላቸውም በማለት ስለመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች ቤቱን ሬድባር ከተባለ የግብረሰናይ ድርጅት ያገኙት መሆኑን ጠቅሰው መከራከራቸውን ተገንዝበናል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው በአመልካች በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች ተቀባይነት የማያገኙበትን ምክንያት በመግለጽ ነው፡፡ እንዲሁም አመልካች የኪራይ ገንዘቡን ከፍዬአለሁ የሚሉት ድርጅት ወደ ክርክሩ እንዲገባ አለመጠየቁም ተገቢነት የለውም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ በስር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት በግልጽ መገንዘብ የተቻለው ውሳኔው የተሰጠው በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የኪራይ ውል መሰረት አድርጐ መሆኑን ሲሆን የኪራይ ውሉ በሕጉ አግባብ ውድቅ ባልተደረገበት ሁኔታ አመልካች የተጠሪዎችን የባለቤትነት መብት መሰረት በማድረግ በኪራይ ውሉ አልገደድም የሚሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ ውል በሕጉ አግባብ እስካልፈረሰ ድረስ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አስገዳጅነት አለውና፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ የኪራይ ውሉን መሰረት ያደረገ መሆኑ ተረጋግጦ አመልካች በገቡት ግዴታ ውዝፍ ኪራዩን እንዲከፍሏቸው መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት እ ዛ ዝ

- ይህ ችሎት ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሰጥቶት የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.45545

መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሸዋዬ ኑርዬ - ጠበቃ አቶ አበራ ማሬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ምንአዩ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ አበራ ታደሰ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ አመልካች ስላቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርበው ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የእጅ በእጅ ሽያጭ ውል ብር 120,540.00(አንድ መቶ ሀያ ሺ አምስት መቶ አርባ ብር) ዋጋ ያለው የቢሮ ዕቃ ከተጠሪ(ተከሳሽ) ለመግዛት በመስማማት ብሩን ወዲያውኑ የከፈሉ መሆኑንና ተጠሪ ግን የገዛሁትን የቢሮ ዕቃ ወዲያውኑ አላስረከበኝም፡፡ ተጠሪ ዕቃውን ስላላስረከበኝ ከሃምሌ 1998 ጀምሮ ውሉን ማፍረሴን ለተከሳሽ አሳውቄአለሁ፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን ሊመልስልኝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ከከሳሽ (አመልካች) ጋር ያደረግሁት ውል የለም፡፡ ከሳሽ ያቀረቡት የእጅ በእጅ ሽያጭ የክፍያ ደረሰኝ ሰነድ ዕቃውን ሰነዱን የያዘው ሰው የተረከበበትን ቀን የሚገልፅ ስለሆነ ሰነዱ ዕቃውን ስለመረከባቸው በቂ አስረጅ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለት ጭብጦችን መስርቷል፡፡ የመጀመሪያው በተጠሪና አመልካች መካከል የእጅ በእጅ ሽያጭ ተፈፅሟል ወይስ አልተፈፀመም? የሚል ሲሆን ሁለተኛው አመልካች ዕቃውን ተረክበዋል ወይስ አልተረከቡም? የሚሉ ናቸው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪና በአመልካች መካከል የእጅ በእጅ ሽያጭ የተፈፀመ መሆኑን በቂ ማስረጃ አልቀረበም፣ የሽያጭ ውል አለ ቢባል እንኳን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278(1) አመልካች ክፍያ ሲፈፅም ዕቃውን የሚረከብ መሆኑ ስለተደነገገና ይህንን በምስክር ማስተባበል ስለማይቻል ከሳሽ(አመልካች) ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት የሽያጭ ውል የለም በማለት የወሰነው እኔ ባቀረብኩት ሰነድ ስም አልተጠቀሰም በማለት ነው፡፡ ሆኖም እኔ ያቀረብኩት ክፍያ የፈፀምኩበት ደረሰኝ ነው፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በፅሑፍ እንዲደረግ ህግ አያስገድድም፡፡ እኔ ደረሰኙን ይገፍ መገኘቴ ከተጠሪ ጋር የዕቃ ግዥ የፈፀምኩ መሆኑን የሚያስረዳ ደጋፊ ማስረጃ ነው፡፡ ተጠሪ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዕቃውን አላስረከበኝም፡፡ ተጠሪ የሸጠውን ዕቃ የሚያስረክብበት የራሱ ሥርዓት ያለው ሲሆን በዚያ ሥርዓት መሠረት ዕቃውን ስለማስረከቡ አላስረዳም፡፡ በእኔ በኩል ተጠሪ የገዛሁትን ዕቃ ለማስረከብ የቆጠርኳቸውን ምስክሮች ለማስረዳት ያቀረብኩትን ጥያቄ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 እና ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2006 የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ውሉ እንዲፈርስና ወደ ነበርንበት እንድንመለስ አለመወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የያዙት ደረሰኝ ተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበት ደረሰኝ እንጅ የሽያጭ ውል መኖሩን የሚያስረዳ አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278(1) የሰጠው ትርጉም ስህተት የለበትም፡፡ ድርጅታችን በመጋዘን የሌለን ዕቃ እና ወዲያውኑ የማናስረክበውን ዕቃ ዋጋ የመቀበል ልምድ የለውም፡፡ አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ከሀያ ስምንት ቀናት በኋላ መሆኑ ውሉን አጠራጣሪ ያደርገዋል የሚል ክርክር አቀርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የዕሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው አመልካች የቢሮ ዕቃ ከተጠሪ የገዙ መሆኑን የዕቃውን ዋጋ ገቢ ያደረጉ መሆኑንና ዕቃውን ከተጠሪ ተረክበው ያልወሰዱ መሆኑን ለማስረዳት የዕሑፍ (የሰነድ) ማስረጃና የሰው ምስክሮች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የእጅ በእጅ ሽያጭ ውል በማለት ውሣኔ የሰጠው ተጠሪ ለአመልካች የቢሮ ዕቃ የሸጠ መሆኑን ለሽያጭ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2266 በተሰጠው ትርጉም መሠረት አመልካች ለማስረዳት ያቀረቧቸውን ሁሉንም ማስረጃዎች በመመርመርና በመመዘን ሣይሆን አመልካች በሰነዱ ማስረጃነት ያቀረቡትን የዕቃ ዋጋ የተከፈለበትና የተጠሪ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሰበሰበ መሆኑን የሚያረጋግጠውን ከአመልካች እጅ የሚገኘውን ደረሰኝ ብቻ በመመርመር ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የቢሮ ዕቃ ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ የወሰነው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን በአመልካች በኩል የቀረቡ ማስረጃዎችን በመስማትና በመመርመር አለመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ሥርዓት ጉድለት የፈፀመ መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡት ደረሰኝ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278(1) የተሸጠውን ዕቃ ማስረከብ ከዋጋው መከፈል ጋር አንድ ላይ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ አመልካች ገንዘብ በተቀበለበት ጊዜ ዕቃዎቹን መረከቡን ደረሰኙ ያስረዳል ሌላ ማስረጃ መሰማት አይቻልም በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉም ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ “በውሉ የተነገረ ተቃራኒ ነገር ከሌለ በቀር የተሸጠውን ማስረከብ ከዋጋው መከፈል ጋር በአንድ ጊዜ መሆን አለበት” የሚል ነው ይህ ድንጋጌ በሻጭ ላይ ግዴታ የሚጥል ድንጋጌ ነው፡፡ የእጅ በእጅ ሽያጭ በሆነ ጊዜ የዕቃው ዋጋ ሲከፈል የተገዛውን ንብረት ወዲያውኑ ለገዥ የማስረከብ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 2 ሻጭ ዕቃውን ለገዥ ሣያስረክብ ሊቆይ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ ይደነግጋል፡፡

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 በተደነገገው መሠረት ገዥ ገንዘቡን ከከፈለ ከግማሽ ሠዓት በኋላ ከሶስት ሠዓት በኋላ ወይም በማግስቱ ለመረከብ ተስማምቶ የነበረ መሆኑን በማናቸውም አይነት ማስረጃ ሊያስረዳ የሚችል ስለመሆኑ “በውሉ የተነገረ ተቃራኒ ቃል ከሌለ በቀር” ከሚለው የድንጋጌው ሐረግ ለመረዳት እንችላለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ገዥ የዕቃውን ዋጋ ሙሉ በሙሉ የከፈለ ቢሆንም ሻጭ ዕቃውን ወዲያውኑ በማስረከብ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት ያልተወጣ መሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳትን መብቱን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ የሚገደብ አይደለም፡፡ ከላይ የተገለፀትን ሁኔታዎች በማስረጃ በማረጋገጥ ገዥ የዕቃውን ዋጋ ለሻጭ ከፍሎ ዕቃውን ያልተረከበ መሆኑን በማስረዳት ሻጭ ዕቃውን እንዲያስረክበው ወይም የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ገንዘቡን እንዲመልስለት መጠየቅ የሚችል መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2278 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ የማይገደብ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የዕቃውን ዋጋ ከፍዬ ዕቃውን አለመረከቤን በማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላረጋግጥ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ለህጉ ድንጋጌ የተሣሣተ ትርጉም በመስጠት ዕቃውን አለመረከብህን በማስረጃ ለማረጋገጥ አትችልም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከላይ የተገለፀው የዳኝነት አካሄድ ግድፈትና የህግ አተረጓጎም ስህተት ያለበትን ውሣኔ ሣያርም ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪ ጋር የቢሮ ዕቃዎች ለማግዛት ውል የተዋዋለ መሆኑን፣ አመልካች ለዕቃዎቹ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን ወይም አለመሆኑንና አመልካች ዕቃዎቹን ተረክቦ የወሰደ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በአመልካችና በተጠሪ በኩል የሚቀርቡለትን አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመስማትና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47971

ሚያዝያ 05 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጅቦኒ ቱና - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ብርቂ ኢርክታ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ዋስትናን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኗ አመልካች እና በሌሎች ሁለት ግለሰቦች በስር ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ አመልካች ሁለት ግለሰቦች (አቶ ፈደሳ ሽኑ እና አቶ ዘውዱ ሽመልስ) የተጠሪን መኖሪያ ቤት ሰብረው ገብተው ስምንት ላደና ገብስ ሰርቀዋል ተብለው በተጠረጠሩበት ጉዳይ በአካባቢ ሽማገሌዎች እና በአከባቢው ቡድን ፊት ቀርበው ፈደሳ ሽኑ ልጃቸው ስለሆነ፣ ዘውዱ ሽመልስ ባለቤታቸው ስለሆነ በተጠረጠሩበት ጉዳይ ሌባ እንዳልሆኑ ቦኩ ላይ ቀርበው ካልማሉ የተጠቁትን የእህል ግምት ገንዘብ እከፍላለሁ በማለት የዋስትና ግዴታ በግዴታዋ መሰረት የተጠረጠሩትን ሰዎች በቦኩ አቅርባ ካለማስማሏ በተጨማሪ ሰዎቹን ሸሽገው የእህሉን ግምት ሳያስከፍሉ የቀሩ መሆኑን ገልፀው የእህሉን ግምት እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካችም የገቡት ግዴታ አለመኖሩን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የአሁኗን አመልካች ለክሱ ኃላፊ በማድረግ የእህሉን ግምት ብር 686.00(ስድስት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር) እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለወረዳው ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 01 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ከጉዳዩ ለማስረጃነት በቀረበው ሰነድ ላይ የተገለፀው የአመልካች ግዴታ ተጠርጣሪዎቹን ለማቅረብ ሆኖ እያለ ለተጠረጠሩበት እህል ግምት ክፍያ ትፈፅሚያለሽ መባሉ ከዋስትና ሕግ ድንጋጌዎች መንፈስ ውጪ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታቸውም ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች የገቡት የዋስትና ግዴታ አለ ወይስ የለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ ዋስትና በሕጉ ጥበቃ የሚያገኘው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1922 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ዋስትና ግልፅ መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ ከተደረገው ውል ወሰን ለማለፍ የማይችል እና ለግዴታው ዋስ የሆነበት የገንዘቡ ልክ በዋስትናው ውል መገለፅ አለበት፡፡ ዋስትና ይህን ፎርማሊቲ ከማሟላቱም በተጨማሪ ለዋስትናው መሰረት የሆነው ዋናው ጉዳይም ሕጋዊ መሆን አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ፈረሙ በተባሉት ሰነድ የዋስትና ገንዘቡ በግልፅ ተገልጾ የተቀመጠ ካለመሆኑም በላይ ለግዴታው መሰረት ነው የተባለው ዋናው ጉዳይም ተጠርጣሪዎች በሕግ አስገዳጅነት በሌለው ሁኔታ ቦኩ ሂደው እንዲምሉ የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሕጉ አግባብ ጥበቃ የሚደረግለት የዋስትና ግዴታ አለ ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በጀርማ ኮርጫሳ ቀ/ገ/ማ/ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 050/2001 መጋቢት 02 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በኤልፋታ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09144 ሰኔ 02 ቀን 2001 ዓ.ም፣ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 86060 ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48358

ሚያዝያ 07 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ብርሃነ ገብረ ሐይሉ - ጠበቃ ሐጐስ ደበሱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አንሲዮን ኮንትር ላፋም - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በቤት ኪራይ የሚከፈለውን የተርን ኦቮር ታክስ ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በመሰረቱት ክስ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 በቁጥር 459 የተመዘገበና የአመልካች ንብረት የሆነውን ቤት ሰኔ 26 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የቤት ኪራይ ውል በኪራይ ይዞ ለሦስት አመታት በቢሮነት እና በማከማቻነት መገልገሉን፣ በዚህም መሰረት የቤት ኪራይ በድምሩ ብር 612,000.00(ስድስት መቶ አስራ ሁለት ሺህ) መክፈሉን፣ ለማከማቻነትና ለመሳሰለ አገልግሎት በኪራይ ለተያዘ ቤት በሚከፈል የቤት ኪራይ ላይ በመቶ አስር(10) የሆነ የተርን ኦቨር ታክስ በአገልግሎት ተጠቃሚ የሆነው ተከራይ እንዲከፍል፣ አከራዩም ታክሱን ከቤቱ ኪራይ ጋር ከተከራዩ ላይ እየሰበሰበ ሥልጣን ላለው ግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ገቢ እንዲያደርግ የውክልና ስልጣን እንደሰጠውና ግዴታ የሚጥልበት መሆኑን፣ በኪራይ ውሉም ተከራይ ከታክሱ ነፃ እንዳልሆኑ ታክሱ ከቤት ኪራይ ገቢ ጋር ስላልተከፈለ አመልካች በህጉ መሰረት ለታክሱ ክፍያ በቅድሚያ ተጠያቂ ሆነው ላንድ አመት በተከፈለ የቤት ኪራይ ገቢ ብር 204,000.00(ሁለት መቶ አራት ሺህ ብር) ላይ የታሰበ ተርን ኦቮር ታክስ ብር 20,400.00(ሃያ ሺህ አራት መቶ ብር) ለግብር ሰብሳቢ አካል መክፈላቸውን፣ ለተጨማሪ የሁለት ዓመት ጊዜ በተከፈለ የቤት ኪራይ ክፍያ ብር 408000.00(አራት መቶ ስምንት ሺህ ብር) ላይ የሚታሰብ የተርን ኦቨር ታክስ ብር 48000.00(አርባ ስምንት ሺህ ብር) እንዲከፈል፣ እንዲሁም የታክስ እዳው ብር 61,000.00(ስልሳ አንድ ሺህ ብር) በሕግ በተወሰነው የመክፈያ ጊዜ ውስጥ ባለመከፈሉ ምክንያት መቀጫ ተጨምሮበት እንዲከፈል የአዋጁ ድንጋጌ እንደሚያስገድድ፣ ለጠበቃ ብር 11,000.00(አስራ አንድ ሺህ ብር) የተርን ኦቨር ታክስ ለመክፈል ግዴታ መግባታቸውን ገልጸው ተጠሪ በድምሩ ብር 61,200.00(ስልሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ የቤት ኪራይ መኖሩን ሳይክድ ሕጉ ተከራይ ታክሱን እንዲከፍል የሚያስገድድ ነው ቢባል እንኳ በውሉ አንቀጽ 6 ስር በመንግስት ባለስልጣናት የሚጣለው ማንኛውም ቀረጥ አከራይ እንዲከፍል በማያሻማ መልኩ የተቀመጠ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለው ውሉ መሆኑን፣ ታክሱ በወቅቱ ባለመከፈሉ ለሚጣለው መቀጮ ግዴታ ያለበት አከራይ መሆኑን በመግለፅ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር አመልካች ብር 20,400.00(ሃያ ሺህ አራት መቶ ብር) ለግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት መክፈላቸው ስለተረጋገጠና ተከራይም የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግለፅ ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪ ለአመልካች ከዳኝነት ገንዘቡ እና ከጠበቃ አበል ከሆነው ብር 2040.00(ሁለት ሺህ አርባ) እንዲሁም ከቴምብር ቀረጥ ጋር እንዲከፍላቸው፣ ብር 61,200.00(ስልሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ) ግን አመልካች ለታክስ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት መክፈላቸውን ሳያረጋግጡ ተከራዩን(ተጠሪን) ሊጠይቁ አይችሉም በማለት ውድቅ አድርጎባቸዋል፡፡ ተጠሪ ብር 61,200.00 ሊከፍሉ አይገባም በተባለው የውሳኔ ክፍል አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የውሳኔ ክፍል ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተርን ኦቨር ታክሱን አመልካች ከፍለው ካጠናቀቁ በኋላ ነው መጠየቅ የሚችሉት በሚል የተሠጠውን ውሳኔ ክፍል አግባብነቱን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልሳቸውን በፁሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪው የአመልካችን ቤት በኪራይ ይዞ በቢሮነትና በማከማቻነት እንደተገለገለበት እንዲሁም ቤቱ ለተጠቀሰው አገልግሎት በመዋሉ ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 308/1995 መሰረት ለአመልካች ለተከፈላቸው የቤት ኪራይ ገቢ ላይ ከመቶ አስር (10%) የሚከፈል ተርን ኦቨር ታክስ የሚከፈልበት ስለመሆኑ በተጠሪ ማስተባበያ ማስረጃ ያልቀረበበት ከመሆኑም በላይ በስር ፍርድ ቤትም የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለታክሱ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አምኖ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ያልተቀበለው አመልካች ብር 40,800.00 (አርባ ሺህ ስምንት መቶ ብር) ለታክስ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት መክፈላቸው አልተረጋገጠም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀፅ 2(3፣ 5፣ 7፣ 8፣ 9 እና 12) እና 6 ድንጋጌዎች መሰረት ታክሱን ለአስከፋይ ባለሥልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህንን በሕጉ የተጣለባቸውን ግዴታ ለመወጣት ደግሞ ታክሱን ለታክስ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ገቢ ከማድረጋቸው በፊት ከአገልግሎት ገቸርው ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ክፍያ መጠየቅ የሚከለክላቸው ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ታክሱን ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ ሲያደርጉ ነው መጠየቅ የሚችሉት በማለት ያስቀመጠው ምክንያት በሕጉ ያልተመለከተ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በሕጉ የተጣለባቸውን ግዴታ ለመወጣት ተጠሪን ክፍያ እንዲፈፅሙ መጠየቃቸው ተቀባይነት የማያገኝበት አጥጋቢና ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 133650 ጥር 08 ቀን 2001 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77649 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች ብር 40,800.00(አርባ ሺህ ስምንት መቶ ብር) እንዲከፍል ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጡትን ሌሎች ወጪዎችን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሽባባው ወሌ - ጠበቃ ጌታቸው ውብሸት ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሙሉጌታ ዓባይ - ጠበቃ አቶ እንዳልካቸው ይላቅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርበው ተጠሪ ብር 7000(ሰባት ሺህ ብር) እስከ ግንቦት 30 ቀን 1991 ዓ.ም ሊመልስ ብድር ወስዶ ያልከፈለኝ ስለሆነ ሊከፍለኝ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ከነ ወለዱ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ የአመልካች ጥያቄ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 መሰረት ሁለት ዓመት ያለፈው በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል፡፡ አክሲዮን ማህበር ለማቋቋም ውል ተዋውለን ብር 8000(ስምንት ሺህ ብር) ስለወሰደ እንዲቻቻልልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የብድር ገንዘቡ ሊከፈል ከሚገባው ከሁለት ዓመት በላይ የቆየ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 መሰረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የሰጠው ትርጉም የተሣሣተ መሆኑን በመተንተን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሯል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024 የሰጠው ትርጉም ስህተት መሆኑን በመግለጽ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ ጊዜ ተወስኖለት በየወቅቱ ለሚከፈል ገንዘብ እንጂ በአንድ ጊዜ ለሚከፈል ወለድ የሚያገለግል አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ እዳውን አልካደም የመቻቻል ጥያቄም ያቀረበ መሆኑ በመልሱ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የታመነ የብድር እዳ እንደከፈለ ይገመታል ተብሎ መወሰኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2025 ድንጋጌ የሚጥስ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው፡፡ በሁለት ዓመት ያልተከፈለ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ ቀሪ ይሆናል በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ብድሩን አለመክፈሉን በማመን የመቻቻል ጥያቄ እንዳቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ አንድ ሰው ብድሩን አለመክፈሉን አምኖ በሚከራከርበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ ተፈፃሚነት የሚኖረው አይደለም፡፡ ይኸም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2025/ሀ/ ድንጋጌ ለመገንዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሳሽ በክሱ የገለፀውን ፍሬ ጉዳይ ተከሳሽ በከፊል ወይም በሙሉ ካመነ በእምነቱም መሰረት ውሣኔ ሊሰጥ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 242/ረ/ በግልጽ የሚደነግግ በመሆኑ ተጠሪ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024/ረ/ ድንጋጌ እንደ ይርጋ ድንጋጌ በመቁጠር ብድሩን አለመክፈሉን ገልፆ መልስ ሰጥቶ ለሁለት ዓመት ስላልጠየቀ ልከፍል አይገባኝም በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ በዋናው ብድር ሣይሆን ለብድር የሚከፈለን ወለድን የሚመለከት ድንጋጌ መሆኑ የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35758 ታህሣሥ 20 ቀን 2002 ዓ.ም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ወለድ የሚከፈልበት የብድር ውል የሌላቸው በመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ በእነርሱ መካከል ያለውን የብድር ግንኙነት የሚመለከት አይደለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ባይ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ከአመልካች የተበደረውን ብር 7000(ሰባት ሺህ) በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ሰኔ 13 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48094

ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ ሙና እንድሪስ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን አመልካቾች በተጠሪና በሥር አንደኛ ተከሳሽ ላይ ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 6 ቀበሌ 13 ክልል ቁጥር 563 የሆነው ቤት ለከሳሾችና ለአንደኛ ተከሳሽ ከወላጆቻችን በውርስ የተላለፈልን ንብረት ሲሆን አቶ ጅላል አብዱልመናን የተባሉ ግለሰብ ከሁለተኛ ተከሳሽ ላይ ገንዘብ ሲበደሩ አንደኛ ተከሳሽ አላለመጠን ባላደረሱት ወራሾች ላይ የተሰጠውን የሞግዚትነት ሥልጣን መሠረት አድርጎ የጋራ የውርስ ንብረት የሆነውን ቤት በመያዣነት ሠጥቷል፡፡ በአንደኛ ተከሳሽ የተፈጸመው ተግባር ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/300 እና 1266 አኳያ ሕገ-ወጥ ስለሆነ ሐምሌ 7 ቀን 1987 ዓ.ም እና ጥቅምት 16 ቀን 1987 ዓ.ም የፈረመው የመያዣ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ እንዲወሰንና የቤቱንም ካርታ ሁለተኛ ተከሳሽ እንዲመልስ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሾች ክስና ማስረጃ ለተከሳሾች ደርሶ መልስ እንዲሰጡ ታዞ አንደኛ ተከሳሽ ተጠርቶ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ሁለተኛ ተከሳሽ/የአሁን ተጠሪ/ ቀርቦ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት በመያዣነት መያዙን አምኖ ይህንን ለማድረግ የቻለው አንደኛ ተከሳሽ በቤተዘመድ ጉባኤ ዓማካይነት በ24/1/87 ዓ.ም የሞግዚትነት ሥልጣን ተሰጥቶት ፍ/ቤትም ቀርቦ በመፅደቁ ምክንያት እንደሆነና የተሰጠውም የሞግዚትነት ሥልጣን ሞግዚት በሆነላቸው ሰዎች ስም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በዋስትና ለመስጠት እንደሚችል በሰነዱ ላይ ስለተመለከተ በመሆኑ ለአንደኛ ተከሳሽ በተሰጠው የሞግዚትነት ሥልጣን ላይ ተመስርቶ የመያዣ ውሉ መፈረሙ በአግባቡ ስለሆነ የመያዣ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ተከላክሏል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም የመያዣ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ መስርቶ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የቤተዘመድ ጉባኤ አንደኛ ተከሳሽን ሞግዚት አድርጎ የሾመው በ18/10/81 ዓ.ም ሲሆን ጥቅምት 11 ቀን 1987 ዓ.ም የሞግዚትነት ሥልጣኑ ፍ/ቤት ቀርቦ ፀድቋል፡፡ በሞግዚትነት ማፅደቅ ውሳኔውም ላይ ከከሳሾች መካከል አንደኛ እና ሁለተኛ ከሳሾች ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ የወጡ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ሞግዚት በሆነላቸው ስም የተመዘገበ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ወይም ዋስትና ለመስጠት የተፈቀደለት ቢሆንም የመያዣ ውሉን በተፈራረሙ ጊዜ አንደኛ እና ሁለተኛ ከሳሾች ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ወጥተው የነበረ ስለሆነ ያለ እነሱ ስምምነት የመያዣ ውሉን መፈራረሙ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1266"ን" የሚጻረር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም በወረዳ 6 ቀበሌ 13 ክልል የቤ.ቁ 563 ተመዝግቦ የሚገኘው የከሳሾችና የአንደኛ ተከሳሽ የጋራ የውርስ ሀብት ሆኖ እያለ አንደኛ እና ሁለተኛ ከሳሾች ስምምነታቸውን ሳይሰጡ በአንደኛ ተከሳሽ በኩል ከሁለተኛ ተከሳሽ ጋር የመያዣ ውል የተፈጸመው የሕጉን ድንጋጌ ባልተከተለ ሁኔታ ስለሆነ ጥቅምት 1987 ዓ.ም እና ሐምሌ 1987 ዓ.ም የተደረገ የመያዣ ውል ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች በውሳኔው ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ አንድ ውል እንዲፈርስ ተዋዋይ ወገን ያልሆኑ ሦስተኛ ወገኖች አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1808(2) እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ ውሉ የማይፈጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ አንስቶ ከ2 ዓመት በኋላ የውል ይሰረዝልኝ ክስ ሊቀርብ እንደማይችል ጉዳቱ የደረሰበት ሰው አካለመጠን የደረሰ ሰው ከሆነ ክሱን ማቅረብ የሚገባው ውሉ በተደረገ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810(1) ላይ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከተራ ቁጥር 1-3 የተጠቀሱት መ/ሰጭዎች ውሉ ሲደረግ ለአቅመ አዳም የደረሱ መሆናቸው ከ4ኛ-7ኛ የተጠቀሱትም መ/ሰጭዎች ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ለአካለመጠን የደረሱ መሆናቸው በመ/ሰጭዎች ያልተካደ በመሆኑ የውል ይሰረዝልኝ ክሱ 2 ዓመት ያለፈው መሆኑን ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል፡፡ ስለሆነም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810(1) መሠረት የውሉ ይሰረዝልኝ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

የሥር ከሳሾች/የአሁን አመልካቾች/ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ የአመልካቾች የውል ይፍረስልኝ ክስ በ2 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ መጣራት የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ይህ ችሎት አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጐ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አንድ ውል በሚመሰረትበት ጊዜ የችሎታ ወይንም የፈቃድ ጉድለት ያለበት ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ችሎታ አልነበረኝም ወይንም ፈቃዴን በአግባቡ አልሰጠሁም በሚለው ተዋዋይ ወገን ብቻ ጠያቂነት ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል እንደዚሁም ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ለሕግ ወይንም ለሞራል ተቃራኒ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜና የውሉ አጻጻፍ ሥርዓትም ባልተጠበቀ ወቅት ከተዋዋይ ወገኖች መካከል ወይንም በውሉ ጥቅም አለኝ በሚል 3ኛ ወገን ዓማካይነት የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ሲቀርብ ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1808(1) እና (2) ላይ ተመልክቷል፡፡

የውል ይፍረስልኝ ክስ ማቅረቢያ ጊዜውን በተመለከተም ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ አንስቶ በ2 ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ሊታገድ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810 ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሉ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ ውሳኔ የተሰጠው የጋራ ባለንብረቶች የሆኑት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ፈቃዳቸውን አልሰጡም በሚል ምክንያት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810 ላይ የተመለከተው የ2 ዓመት ይርጋ ጊዜ ተፈጻሚነቱ ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ቀሪ በሚሆንበት ጊዜ ሲሆን ይህም የሚመለከተው ከአንደኛው ተዋዋይ ወገን ችሎታ ወይንም ፈቃድ ጉድለት ጋር የተያያዘ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡ ውሉ ከችሎታ ወይንም ከፈቃድ ጋር በተያያዘ ጉድለት አለበት በሚባልበት ጊዜ ይህንኑ መሠረት አድርጎ ክስ የሚያቀርበው ወገን በ2 ዓመት ክሱን ካላቀረበ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810 መሠረት በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን መገንዘብ ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ውሉ እንዲፈርስላቸው የጠየቁት አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾች ለውሉ መፍረስ በምክንያትነት የጠቀሱት የጋራ የሆነውን የውርስ ሀብት ለመሸጥም ሆነ በመያዣ ለመስጠት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1266 መሠረት የጋራ ባለሀብቶች ስምምነት አስፈላጊ ሆኖ ሳለ የሥር አንደኛ ተከሳሽ ያለ እኛ ስምምነት የጋራ የውርስ ሀብት የሆነውን ቤት ለሁለተኛ ተከሳሽ/ለአሁን ተጠሪ/ በመያዣነት የሰጠ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ነው፡፡ አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾች ተዋዋይ ወገን ካልሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1808(1) መሠረት ውሉ የችሎታ ወይንም የፈቃድ ጉድለት ያለበት ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል በማለት ሊጠይቁ የማይችሉ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810 ላይ የተመለከተው የ2 ዓመት ይርጋ ጊዜ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት አይኖረውም፡፡

በሌላ በኩልም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 318 ላይ የተቀመጠውን የይርጋ ጊዜ በተመለከተም አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ በሞግዚቱ ላይ የሚያቀርበውን ክስ አስመልክቶ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን በዚህ ጉዳይ ግን ውሉ ፈራሽ ነው የተባለው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ወጥተዋል በተባሉት አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾችን አስመልክቶ ስለሆነ ድንጋጌው ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

እንግዲህ ተጠሪ ያነሳው የይርጋ ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1810 እና በቤተሰብ ሕጉ የሚሸፈን ባይሆንም የጋራ የሆነን ንብረት ለማስተላለፍ ወይንም በዋስትና ለመስጠት የሁሉንም የጋራ ባለንብረቶች ስምምነት ማግኘት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1266 ላይ የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን የጋራ ባለንብረት ከሆኑት መካከል አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች በመያዣ ውሉ ስምምነታቸውን ያልሰጡ ስለሆነ ይህም ውሉ ሕግን የሚጻረር መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ አንድ ውል ሕግን የሚቃረን ነው በሚባልበት ጊዜ እንዲፈርስ ጥያቄ መቅረብ ያለበት በ10 ዓመት ጊዜ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካቾች ክሱን ቀረቡት ደግሞ በሕጉ ላይ የተቀመጠው የ10 ዓመት ጊዜ ከማለፉ በፊት ስለሆነ አቤቱታቸው በይርጋ የታገደ አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካቾች ክስ በ2(ሁለት) ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል ያለው ለጉዳዩ አግባብነት በሌለው ድንጋጌ ላይ ተመስርቶ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 65139 በ1/9/2000 ዓ.ም የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 46909 ሐምሌ 28 2001 ዓ.ም ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ሽረነዋል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ የበኩሉን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49453

ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ተፈሪ ማሞ - በሌሉበት

ፍ ር ድ

ተጠሪ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ የነበሩ ሲሆን የኤም.ኤስ.ሲ ትምህርት እንዲከታተሉ ከአመልካች ጋር ባደረጉት ውል አመልካች በትምህርት በሚቆዩበት ጊዜ ደመወዝ፣ የት/ቤት ክፍያ፣ ለምርምር ማካሄጃ የሚፈልጉትን ሊከፍልና ተጠሪ ደግሞ በትምህርት ለቆዩባቸው እያንዳንዱ ወር የሁለት ወራት አገልግሎት ለመስጠት ግዴታ ገብተው ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ በግዴታቸው መሰረት ግልጋሎት ስላልሰጡ በውሉ መሰረት እንዲፈፅሙ ወይም አመልካች ያወጣውን ወጪ ብር 326,092.57 ከነወለዱ እንዲከፍሉ በማለት አመልካች ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ለክሱ መልስ እንዲሰጡ ተጠርተው ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤትም አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 19 ቀን 1994 ዓ.ም ባደረጉት ውል አመልካች ለ24 ወራት ደሞዝ እየከፈለ ተጠሪን ለማስተማርና ተጠሪ ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ በአመልካች መ/ቤት ለመስራት ግዴታ መግባታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ተጠሪ በውሉ መሰረት እንዲፈፅሙ ማድረጉ የግል ነፃነታቸውን የሚጋፋ በመሆኑ፣ ግራ ቀኙ ባደረጉት ውል ላይ ተጠሪ ግዴታቸውን ባይፈፅሙ አመልካች ያወጣውን ገንዘብ ለመመለስ ግዴታ ስላልገቡና አመልካችም ውል እንዲፈርስ ስላልጠየቁ ገንዘቡን እንዲከፍሉ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው፤ ተጠሪ ወደውና ፈቅደው የፈረሙት ውል የግል ነፃነታቸውን ይነካል የሚል እምነት የለንም፣ በውሉ መሰረት ቢፈፅሙ የግል ነፃነታቸውን ይነካል የሚባል ቢሆን እንኳን ውሉ በአመልካች በኩል ተፈፅሞ ያበቃ በመሆኑና ተጠሪ ግዴታቸውን ስላልተወጡ ውሉ የሚፈርስበት ሁኔታ አይኖርም፣ ውሉን መፈፀም ግዴታቸውን የሚነካ ከሆነ ግዴታቸውን በአይነት ወይም በገንዘብ የመመለስ የውልም ሆነ የህግ ግዴታ አለባቸው በማለት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር ጠይቋል፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች ለተጠሪ ትምህርት ያወጣቸው ወጪዎች ሳይከፈል የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪ እንዲቀርቡ ተጠርተው ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካች ክስ የመሰረተው ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ውል መሰረት አመልካች ግዴታውን ከፈፀመ በኋላ ተጠሪ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው በውሉ መሰረት እንዲፈፅሙ ካልሆነ የከፈላቸውን ደሞዝና የትምህርት ቤት ወጪዎች እንዲተኩለት ነው፡፡ ተጠሪ አልፈፀሙም የተባለው ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ተመልሰው በአመልካች መ/ቤት ግልጋሎት የመስጠት ግዴታቸውን ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካች አንደኛው የዳኝነት ጥያቄ ተጠሪ በውሉ በገቡት ግዴታ መሰረት በመ/ቤቱ ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ነው፡፡ ነገር ግን የስር ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳለው ተጠሪ በግድ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረጉ የግል ነፃነታቸውን የሚነካ በመሆኑና እንዲህ ባለ ጊዜ ደግሞ ውሉ በግድ እንዲፈፀም ማድረግ የተከለከለ በመሆኑ (የፍ/ብ/ህ/ቁ 1776 ይመለከቷል) ውሉ በግድ እንዲፈፀም የቀረበው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

በአማራጭ የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ስንመለከት ተጠሪ በውሉ መሰረት ለመፈፀም ካልፈቀዱ ተጠሪ በትምህርት ላይ በቆዩበት ወቅት አመልካች ለተጠሪ የከፈለው ደሞዝና የትምህርት ቤት ወጪዎች እንዲተካለት የሚጠይቅ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ይህን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በግራ ቀኙ በተደረገው ውል ተጠሪ ግልጋሎት ባይሰጡ አመልካች ያወጣውን ወጪ ለመተካት ግልፅ ግዴታ አልገቡም በማለት ነው፡፡ ግራ ቀኙ ካደረጉት ውል አመልካች ተጠሪ በትምህርት በሚቆዩበት ጊዜ ደሞዛቸውንና ሌሎች ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ወጪዎች ለመሸፈን ተጠሪ ደግሞ ትምህርታቸውን ጨርሰው ሲመለሱ አመልካች ድርጅት ውስጥ ለማገልገል ግዴታ መግባታቸውን የስር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ትምህርታቸውን ተምረው የጨረሱ በመሆኑ አመልካች ግዴታውን ፈፅሟል፡፡ ተጠሪ ግን በእርሳቸው በኩል የሚፈለገውን ግዴታ አልፈፀሙም፡፡ ተዋዋይ ወገን የውሉን ግዴታ ያልፈፀመ ከሆነ ሌላው ወገን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት ካለ የጉዳት ኪሳራ እንዲከፈለው ለመጠየቅ እንደሚችል ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1771(2) እና 1790(1) መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን ነጥብ በተመለከተ ይህ የሰበር ችሎት በመ/ቁ 29169፣ 29170 እና በሌሎችም መዝገቦች ላይ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ በውሉ መሰረት ባለመፈፀማቸው ኪሳራ እንዲከፈለው መጠየቁ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ኪሳራ ሊከፈለው ይገባል የሚባል ከሆነ የኪሳራው መጠን ምን ያህል ሊሆን ይገባል የሚለው በቀጣይነት ሊታይ ይገባዋል፡፡ ተዋዋይ ወገን ግዴታውን ሳይፈፅም ቀርቶ በሌላው ወገን ላይ ጉዳት ደርሶ ከሆነ የኪሳራው ልክ ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነት በሚመለከተው ድንጋጌዎች መሰረት ሊወሰን እንደሚገባ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1790(2) ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ሊካስ የሚገባው ከደረሰበት ጉዳት ጋር ተመዛዛኝ የሆነ ኪሳራ እንደሆነ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2090(1) እና 2091 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ በትምህርት ላይ እያሉ ምን ያህል ደመወዝ እንደከፈላቸው እንዲሁም ከትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ጉዳዮች ምን ያህል ወጪ እንዳወጣ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ነገር ስለመኖሩ መዝገቡ አያሳይም፡፡ የኪሳራውን ልክ ለመወሰን ደግሞ እነዚህ ነገሮች ሊረጋገጡ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ተጠሪ ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ በራሳቸው በኩል ያለውን የውል ግዴታ ባለመፈፀማቸው አመልካች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኪሳራ ሊከፍሉ ሲገባ ወጪውን ለመተካት በውሉ ላይ በግልፅ አልተስማሙም በሚል ጥያቄው ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 34503 ህዳር 08 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 75952 ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በትምህርት ላይ በቆዩበት ጊዜ አመልካች ያወጣውን ወጪ ተጠሪ የመክፈል ግዴታ አለባቸው ብለናል፡፡
3. አመልካች ተጠሪ በትምህርት ላይ በቆዩበት ጊዜ ያወጣውን ወጪ ለማስረዳት ያቀረበውን ማስረጃ መሰረት አድርጎ በማጣራት የኪሳራውን መጠን እንዲወስን ጉዳዩን ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጣውን ወጪ አመልካች ራሱ ይቻል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49326

ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ እታፈራሁ ኃ/ማርያም - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. መምህር በቀለ ታችበሌ
2. መምህር አዜብ ታደሰ } የቀረበ የለም

ፍ ር ድ

ገዳዩ ተጠሪዎች የሸጡላቸው ቤት በሚገኝበት ቦታ ላይ ተጨማሪ ግንባታ ያከናወኑ ቢሆንም ተጠሪዎቹ ስም ስላላዛወሩላቸው ለቤቱ መግዣ የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸውና በተጨማሪ ለሰሩት ቤት ግምቱ እንዲከፈላቸው ጠይቀው ፍ/ቤቱ ተጠሪዎች የሸያጩን ገንዘብ እንዲከፍሉ ሲወስን አመልካች ተጨማሪ ሰራሁ ያሉትን ቤት ግምት ክፍያ ውድቅ በማድረግ በሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪዎች በድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ ካላቸው ይዞታ ላይ ቀንሰው ከሸጡላቸው እና ብር 29,000(ሃያ ዘጠኝ ሺህ) ከከፈሏቸው በኋላም ስመ-ርስቱን ለማዛወር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ በይዞታው ላይ ብር 80,000(ሰማኒያ ሺህ) የሚያወጣ ቪላ ቤት ስለሰሩ ይህንኑ ገንዘብ እንዲመልሱላቸውና በአደራ ያስቀመጡት እቃ ዋጋ እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው የሸያጭ ውል ማድረጋቸውን ሳይክዱ ስመ-ርስቱን ለማዛወር ፈቀደኛ ስለሆኑ የሸያጩን ገንዘብ የሚመለሱበት ምክንያት የሌለ መሆኑንና አመልካች በረቂቅ የሸያጭ ውሉ ካልተስማሙ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ከሚሄዱ በቀር የቤቱን ግምት የሚከፍሉበት ምክንያት የሌለ መሆኑን በተጨማሪም በአደራ የተረከቡት ንብረት አለመኖሩን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የቤት ሽያጭ ውሉ ህጉ በሚጠይቀው መሰረት በውል አዋዋይ ፊት ወይም በዳኛ ፊት ስላልተደረገ ረቂቅ ቢሆንም ይህንን መነሻ በማድረግ አመልካች ብር 29,000(ሃያ ዘጠኝ ሺህ) ለተጠሪዎች ስለከፈሉ ተጠሪዎች ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉ በቦታው ላይ አመልካች ሰራሁ የሚሉትን ቤት ስለከፈሉ ተጠሪዎች ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉ በቦታው ላይ አመልካች ሰራሁ የሚሉትን ቤት በተመለከተ ምንም እንኳን በቦታው ላይ አመልካች ቤት መስራታቸውን ተጠሪዎች ያልካዱ ቢሆንም አመልካች የገለፁትን ያህል ገንዘብ ለማውጣታቸው ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም አመልካች ለተጠሪዎች በአደራ የሰጡት ንብረት ስለመኖሩ በማስረጃ ስላላስረዱ በዚህ ረገድ የቀረበው ክስም ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው አመልካች በይዞታው ላይ ቤት ስለመስራታቸው ተጠሪዎች ስላመኑ ግንባታው በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ ማድረግ ወይም ቢያንስ ተጠሪዎች ያወጣል ያሉትን ግምት እንኳን እንዲከፈል ማድረግ ሲችል መታለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ችሎቱም ተጠሪዎች አመልካች ለቤት መስሪያ ያወጣችውን የተወሰነውን እንከፍላለን እያሉ የስር ፍ/ቤት ጥያቄውን ውድቅ የማድረጉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሰምቷል፡፡ ተጠሪዎች አመልካች ቤት መስራታቸውን ሳይክዱ በመጠኑ ላይ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት ከተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ሊፈፀም ባለመቻሉ በሽያጩ ውል ምክንያት የከፈሉት ገንዘብ እንዲሁም ቤቱን ገዝቸዋለሁ በሚል ሃሳብ በይዞታው ላይ የሰሩት ተጨማሪ ቤት ግምት እንዲከፈላቸው ነው፡፡ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስ በሽያጩ ውል መሰረት ለመፈፀም ፈቃደኛ በመሆናቸው ገንዘቡን ሊመልሱ እንደማይገባ ገልፀዋል፡፡ ምንም እንኳን አመልካች ክስ ሲመሰርቱ ውሉ ይፍረስልን በሚል በግልፅ ያስቀመጡት ነገር ባይኖርም የክሱ ይዘት ሲታይ ውሉ ፈርሶ ወደነበርንበት እንድመለስ የሚል ጥያቄ ያዘለ ነው፡፡ ተጠሪዎችም የሚከራከሩት በውሉ መሰረት ለመፈፀም ፈቃደኛ በመሆናቸው ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ለክርክር ምክንያት የሆነው የሽያጭ ውል ህጉ የሚጠይቀውን የአፃፃፍ ፎርምን የተከተለ አለመሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ በህጉ የተመለከተውን የአፃፃፍ ፎርም አለመከተልም ውሉን ለማፍረስ በቂ ምክንያት እንደሚሆን በፍ/ብ/ህ/ቁ 1808(2) መገንዘብ ይቻላል፡፡ ውሉ መፍረሱ የሚያስከትለው ውጤትም ተዋዋዮቹን በተቻለ መጠን ውለታው ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በውሳኔ ላይ አመልካች የውል ይፍረስልኝ ክስ አላቀረቡም በማለት ቢተችም ከፍ ሲል እንደተመለከተው የአመልካች ክስ ይዘት ይኸው ሲሆን ፍ/ቤቱም ቢሆን ውሉ የህጉን መስፈርት ያላሟላ በመሆኑ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሊመለሱ እንደሚገባ ተቀብሏል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪዎች በሽያጩ ውል ምክንያት የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ ወስኗል፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት የሚመለሱት ተጠሪዎች የሽያጩን ገንዘብ እንዲከፍሉና አመልካች ቤቱን እንዲያስረክቡ በማድረግ ብቻ አይደለም፡፡ አመልካች ተጨማሪ ቤት ሰርቻለሁ በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎችም አመልካች ቤት መስራታቸውን አልካዱም፡፡ ክርክራቸው ሊከፍሉ በሚገባቸው የቤት ግምት መጠን ላይ ነው፡፡ ተጠሪዎች ፍ/ብ/ህ/ቁ 1179 እና 1180 መሰረት አመልካች በይዞታው ላይ ለገነቡት ቤት ሊከፍሉ የሚገባው የቤቱን ግምት ¼ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ እነዚህ የህጉ ድንጋጌዎች ባለይዞታ ሳይቃወም በይዞታው ላይ የተሰራውን ግንባታ ለማስለቀቅ ስለሚችልበት ሁኔታ የሚናገሩ ናቸው፡፡ አመልካች ግን ግንባታውን የሰሩት በዚህ አይነት ሁኔታ ሳይሆን በግራ ቀኙ በተደረገው የሽያጭ ውል መሰረት ቤቱን ገዝቻለሁ፣ የቤቱ ባለቤት ሆኛለሁ በሚል እምነት ነው፡፡ ምንም እንኳን ውሉ በህግ የተደነገገውን የአፃፃፍ ስርዓት ባለመከተሉ ፈራሽ ቢሆንም ውሉ በመፍረሱ ወይም በመሰረዙ ምክንያት ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰው ንብረቱን ለውጦ ወይም በዚሁ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ባወጣው ወጪ መጠን ሊጠይቅ እንደሚገባ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1818 ያመለክታል፡፡ ስለሆነም አመልካች ቤቱን እንዲለቁ ሲደረግ ተጠሪዎች ሊከፍሉ የሚገባው አመልካች በይዞታው ላይ የሰሩት ቤት የሚያወጣውን ዋጋ በሙሉ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1179 እና 1180 መሰረት አይደለም፡፡ ተጠሪዎች በዚህ የሰበር ችሎት አመልካች ቤቱን ያለ ግንባታ ፈቃድ የሰሩት በመሆኑ የቤቱን ግምት ልንከፍል አይገባም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ይህ ክርክር በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍ/ቤት አመልካች ቤት ለመስራታቸው በተጠሪዎችም መታመኑን ተቀብሏል፡፡ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ቤቱን ለመስራት ብር 80,000(ሰማኒያ ሺህ) ለመውጣቱ አመልካች ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ነገር ግን ቤት መስራቱ እስካልተካደ ድረስ የቤቱን ዋጋ ግምት ለማወቅ ምትክ ዳኛ ሊሾም የሚችል መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 132 ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤት ግምቱ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ ማድረግ ሲችል አመልካች አላስረዱም በሚል ብቻ ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 25476 መጋቢት 9 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 04566 ሐምሌ 11 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የሰሩትን ቤት ዋጋ ግምት ተጠሪዎች የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡ የስር ፍ/ቤት ቤቱን በባለሙያ አስገምቶ ግምቱን ካጣራ በኋላ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.42700

ሀምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት

- ነ/ፈጅ አቶ መላኩ መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ወ/ሮ መርከቧ ሽጉጤ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ትርጉም ስህተት ያለበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በአጭር ሥርዓት እንዲታይለት ባቀረበው ማመልከቻ ከተጠሪ ጋር እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1978 ዓ.ም የትራንዚት አገልግሎት የሰጠና የደንበኝነት ውል ያለው መሆኑን ገልፆ አመልካችና ተጠሪ ሂሳብ ተሣሥበው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1978 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1970 ዓ.ም እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም አመልካች ለተጠሪ ለሰጠው አገልግሎት ያልተከፈለ ብር 7,955,271.42(ሰባት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሣ አምስት ሺ ሁለት መቶ ሰባ አንድ ብር ከአርባ ሁለት ሣንቲም) ያለ መሆኑን በማረጋገጥ ተጠሪ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 23-09-99 እና ግንቦት 28 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፉ ሰነዶችን ፈርሟል፡፡ ስለዚህ ገንዘቡን እንዲከፍል በማለት ክስ አቅርቧል ተጠሪ በይርጋ ጊዜ ያለውን ዕዳ አመልካች በአጭር ሥርዓት ታይቶ እንዲወሰንለት የጠየቀ በመሆኑ መከላከያ እንዲያቀርብ ይፈቀድልኝ በማለት ጠይቋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበው ብቁ መከላከያ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎ ተጠሪ አመልካች በክሱ የጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች አስራስድስት ዓመት ካለፈ በኋላ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈለው የጠየቁ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ አመልካች ለሰበር ባቀረበው አቤቱታ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሣኔ የሰጠው የህግ ትርጉም በተከራካሪ ያልቀረበና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1846 ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የረዥም ጊዜ ደንበኞች ቢሆንም በየወቅቱ ሂሳባቸው እያጣሩ የሚዘጉ አልነበረም፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የከፈለው የአገልግሎት ዋጋና ያልከፈለው ሂሳብ ተጣርቶ የታወቀው እንደ ኤ.አ 23-9-99 በጋራ ሒሳቡን በማስታረቅ በተሠራው ሥራ ነው፡፡ አመልካች ክፍያውን ለመጠየቅ የሚችለው ሒሳቡ ተጣርቶ የሁለቱ ወገኖች ሂሳብ ለማስታረቅ ሥራ ከተሠራና ሒሳቡ ከተለየ በኋላ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አገልግሎት የተሰጠበትን ዓመት መነሻ በማድረግ ይርጋው አልፏል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በይግባኝ ችሎት አተረጓጎም የአስር ዓመት ይርጋ ያላለፈበትን እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 23-9-89 እስከ 23-9-99 ያለውን ሒሳብ አላግባብ በይርጋ ይቋረጣል በማለት መወሰኑ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በበኩሉ የይርጋ ጊዜው መታሰብ ያለበት አመልካች አገልግሎቱን ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ መሆን አለበት፡፡ አመልካች የትራንዚት ሥራውን ጨርሶ ንብረቱን ለተጠሪ ካስረከበበት ወይም በውሉ በእሱ በኩል ያለውን ግዴታ ከተወጣበት ቀን ጀምሮ ሒሳቡን ከመጠየቅ የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ የይርጋ መከራከሪያ ክሱን ለመከላከል ጠቃሚ ነጥብ መሆን አንስተን የከፍተኛ ፍርድ ቤትን ጠይቀናል ስለዚህ በተከራካሪዎች ያልተነሣ ነጥብ ይግባኝ ሰሚው በጭብጥነት በመያዝ የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡ ስለዚህ የአመልካች ማስረጃዎች አመልካች ክፍያ የጠየቀው ክስ ካለፈ በኋላ መሆኑን የሚያስረዱ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው የህግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዕሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የአመልካች ክስ የይርጋ የጊዜ ገደብ ያለፈበት በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የይርጋ የጊዜ ገደቡ መቆጠር ያለበት ከመቼ ጀምሮ ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስና በሁለተኛ ደረጃ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ በይርጋ ቀሪ ነው ብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

1. የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ከመቼ ጀምሮ ነው የሚለውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረንን ሂሳብ በጋራ አስልተን ሐሳባችንን ያስታረቅነው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 23-9-1999 ዓ.ም በመሆኑና ሒሳቡ ከመስማማቱ በፊት የአገልግሎት ዋጋ መጠየቅ ስለማንችል ይርጋው ጊዜ መሰላት ያለበት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 23-9-1999 ጀምሮ መሆን አለበት በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1846"ን" በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የትራንዚት ሥራ ሰርቶ ዕቃውን ካስረከበበት ቀን ጀምሮ ሒሳቡን መጠየቅ ስለሚችልና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1846 ይህንንም የሚደነግግ በመሆኑ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው አመልካች አገልግሎቱን ከሰጡት ዕቃውን ካስረከበበት ጊዜ ጀምሮ መሆን አለበት በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1846 ድንጋጌ የየራሳቸውን ትርጉም በመስጠት ነው፡፡ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1846 "የይርጋው መነሻ ጊዜ" በሚል ርዕስ "የይርጋው ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም ውሉ የሚሰጠው መብት ከሚሠራበት ቀን ጀምሮ ነው" በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚህን ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ አመልካችና ተጠሪ ካላቸው ግንኙነት አንፃር ስንመለከተው አመልካች ተጠሪ ከውጭ አገር የሚያስገባቸውን ዕቃዎች አስፈላጊ የሆኑ የወደብና የጉምሩክ ፎርማሊቲዎች በማሟላት ዕቃውን ለተጠሪ እንዲረከብ የማድረግ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑና ተጠሪ አመልካች ለሰጠው የትራንዚት ግልጋሎት ዋጋ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ግራቀኙ አልተካካዱም፡፡ አመልካች አስፈላጊ የሆኑ የወደብ አስተዳደራዊ ፎርማሊቲዎችና የጉምሩክ ፎርማሊቲዎች በማሟላት አንድ ዕቃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ለሰጠው አገልግሎት ወዲያውኑ ተጠሪ ክፍያ እንዲፈፅምለት የመጠየቅና ተጠሪ እንቢተኛ ቢሆን በፍርድ ከስሶ የአገልግሎት ዋጋውን ከመቀበል የሚያግደው ነገር የለም፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የትራንዚት የአገልግሎት ዋጋ የሚከፍለው በየወቅቱ የነበራቸው ሒሳብ በጋራ ተሰርቶ የአመልካችና የተጠሪ ሒሳብ መስማሚያ ሰነድ ሲቀርብ ስለመሆኑ አመልካችና ተጠሪ የተስማሙበት ልዩ የውል ስምምነት ያላቸው ስለመሆኑ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የዚህ አይነት ግልፅ የውል ስምምነት ከሌለ አመልካች የተጠሪን ዕቃ ለማስገባት አስፈላጊ የሆኑ የትራንዚት አገልግሎት ሰጥቶ ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ካስገባና ተጠሪ እንዲረከብ ካደረገበት ቀን ጀምሮ ክፍያ የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ተጠሪ ለሰጠው አገልግሎት ክፍያ የመጠየቅ መብቱን አገልግሎቱን ከሰጠ በኋላ በሚቀጥለው ቀን እንዳይሠራበት የሚከለክለው ግልፅ የሆነ የውል ቃል ወይም የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ለተጠሪ ለሰጠው እያንዳንዱ የትራንዚት አገልግሎት አገልግሎቱን ከሰጠበት ቀን ጀምሮ የአገልግሎት ክፍያ ተጠሪ እንዲከፍል መጠየቅ የሚቻልና በመብቱ ሊሠራበት የሚቻል በመሆኑ አመልካች የአገልግሎት ክፍያ ለመጠየቅ የሚችለው ሂሳቡ በጋራ ተሰርቶ ከታረቀበት ቀን ጀምሮ ነው ተብሎ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1846 ይተርጎምልኝ በማለት ያቀረበው ክርክር የፍትሐብሔር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ ቁጥር 1846 ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም የአስር ዓመቱ የይርጋ የጊዜ ገደብ መቆጠር ያለበት አመልካች ለተጠሪ የትራንዚት አገልግሎቱን ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ መሆን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካች ተጠሪ ለሰጠው የትራንዚት አገልግሎት ክፍያ እንዲፈፅምለት የጠየቀው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1978 ዓ.ም እስከ ጁን 30 ቀን 2004 ያለውን ሒሳብ ነው፡፡ ይህም የሚያሣየው አመልካች በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ1970 ዓ.ም እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ በሰጠው አገልግሎት ክፍያ ተጠሪ እንዲከፍለው የጠየቀ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የትራንዚት አገልግሎት ክፍያ እንዲከፍለው መጠየቅ የሚቻለው አገልግሎቱ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ውስጥ መሆን ያለበት መሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1845 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የይርጋው ጊዜ ሲቆጠር አመልካች በክሱ ከጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ ውስጥ አስር ዓመት ካለፈባቸው በኋላ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ህዳር 12 ቀን 2000 ክስ የቀረበባቸው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር 1970 ዓ.ም እስከ ህዳር 11 ቀን 1990 ዓ.ም ለሰጠው አገልግሎት የጠየቀው ሒሳብ ነው፡፡ አመልካች በአጭር ሥነ- ሥርዓት ክስ ያቀረበው ህዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው ገልጿል፡፡ ስለሆነም ከህዳር 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ተጠሪ ክፍያ እንዲፈፅምለት ያቀረበው ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 የተደነገገው የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ አላለፈበትም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ከህዳር 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ለሰጠው አገልግሎት ተጠሪ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል በመጠየቅ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ በከፊል ትክክል ሲሆን በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላገኘነው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 11 ቀን 1990 ዓ.ም ለሰጠው የትራንዚት አገልግሎት ተጠሪ ክፍያ እንዲፈፅም በፍርድ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ በአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ይታገዳል ብለናል፡፡
3. አመልካች በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከህዳር 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ለሰጠው የትራንዚት አገልግሎት ተጠሪ ክፍያ እንዲፈፅም በፍርድ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡
4. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር አመልካች ከህዳር 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ለሰጠው የትራንዚት አገልግሎት ተጠሪ ሊከፍለኝ ይገባል የሚለውን የአገልግሎት ክፍያ ለይቶ እንዲያቀርብ በማድረግና የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሰንለታል ይላፍ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 46019

ሐምሌ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአቶ ደሳለው ፋንታ ወራሾች - እነ ሙሉጌታ ደሳለው ጠበቃ ግሩም አየለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አየለ ደበላ - ጠበቃ ኤሊያስ ተ/ብርሃን ቀረቡ

መዝገቡን መረምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በእቁብ ገንዘብ የመክፈያ ጊዜ ጋር በተያያዘ እዳው እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችልበትን የሕግ አግባብና ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ የካቲት 08 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ የአሁኑ አመልካቾች አውራሽ በተጠሪ የሚሰበሰበው እቁብ በአባልነት ተመዝግበው ዋስ ቆጥረው ብር 650,000.00(ስድስት መቶ ሃምሳ ሺህ) መውሰዳቸውን፣ተከሳሽ በተመዘገቡበት እጣ እቁብ ከተጀመረበት ከሕዳር 03 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ እስከ ጥቅምት 02 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ 28 ክፍያዎችን ከከፈሉ በኋላ ኅዳር 7 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ እቁቡ ማለቂያ እለት ድረስ መክፈል የሚገባቸውን 29 ክፍያዎችን ሳይከፍሉ መቅረታቸው በመግለጽ ተከሳሽ ከእቁቡ የሚደርሳቸውን ገንዘብ ከወሰዱ በኋላ መክፈል ሲገባቸው ያልከፈሉትንና ባለመክፈላቸው በእቁቡ ስምምነት መሰረት ሊከፈል የሚገደዱበትን በቀን የሚታሰብ ተጭማሪ ክፍያ በድምር የሆነውን ብር 342,600.00 (ሦስት መቶ አርባ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ) ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ቀርበው በሰጡት መከላከያ መልስ የተጠሪ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ስር በተመለከተው የክፍያ ግምት መሰረት ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከተመለከተ በኋላ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ የከሳሽን ክስ ውድቅ አድርጓአል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ለእቁብ ገንዘብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ ጉዳዩን ለስር ፍ/ቤት መልሶለታል፡፡ ጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ያሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/"ን" ተደርጐ የቀረበውን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው ያላግባብ መሆኑን፣ድንጋጌው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677/1/ ድንጋጌ አንፃር ሲታይ ለእቁብ ገንዘብ አግባብነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጉላቸው ቀርበው ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም በዛፉት ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/ረ/ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣የአመልካቾች አውራሽ የእቁብ ገንዘቡን ያልተከፈሉ በመሆኑ ክርክራቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልፀው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት የተከራከሩ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነው። የአመልካቾች ጠበቃ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም በዛፉት ሦስት ገጽ የሰበር ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በተጠሪ እና በአመልካቾች አውራሽ መካከል ያለው ግንኙነት የእቁብ ገንዘብን የሚመለከት መሆኑን፣የአመልካቾች አውራሽ ተጠሪ በሚሰበስቡት እቁብ ውስጥ አባል ሆነው እጣው ደርሷቸው ገንዘቡን በመውሰድ 28 እጣዎችን ከከፈሉ በኋላ 29 እጣዎች ሲቀሩ መክፈላቸውን ማቋረጣቸውን ገልጸው ተጠሪ ክስ መመስረታቸውን፣የእቁቡን ገንዘብ የሚከፈልበት ጊዜም የተቆረጠ መሆኑን ነው። በዚህ ችሎት አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የእቁብ እዳው ክፍያ ጥያቄ በሁለት አመት ጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ ሊቆጠር ይገባል ማለት ያቀረብነውን ክርክር ያለፈው ያላግባብ ነው በሚል ነው።

ዋናውና የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጉዳይ፡- የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ድንጋጌ ለእቁብ ገንዘብ እግባብነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ድንጋጌን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል።

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብን (legal presumptions) የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2025 እና 2026 ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት (not freely rebuttable or rebuttable but in limited way) የሕግ የሕሊና ግምት ነው። የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር የተለያዩ የክፍያ አይነቶች የሚዘረዝር ሆኖ 2024 በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች(እዳዎች) በዚሁ የሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠየቁ የቀሩ እንደሆኑ ክፍያውን (እዳዎች) የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ (እዳ) እንደከፈለ የሕግ ግምት እንደሚወስድበት ያስገነዝባል። ድንጋጌው እቁብን ለይቶ አላስቀመጠም።

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ ተብሎ በአመልካቾች የሚጠቀሰውን በስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት ያገኘው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024 ድንጋጌ በፊደል/ረ/ ስር የተመለከተው ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው።

<u>ቁ. 2024 በሁለት አመት የተወሰነ ጊዜ</u>

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው፡-

/ረ/ በብድር ለተሰጠ፤ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሳኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው እዳ የሆነ እንደሆነ ነው። የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጂም፡-

<u>Art.2024 presumption of payment after two years</u>

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

(f) interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical interval. በሚል ተቀምጧል። ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘትና እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፓራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት አመት ያለፋቸው እዳዎች(ክፍያዎች) እንደተከፈሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታይ የተዘረዘሩት ንኡስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሚወሰንባቸውን የክፍያ (እዳ) ዓይነቶችን የሚዘረዘር ነው። በድንጋጌው ፊደል/ረ/ ስር የተመለከተው ሲታይ በብድር የተሰጠ ወይም ለማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከአመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች (እዳዎች) ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል። በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ስር የተመለከተው ድንጋጌው ተፈፃሚነት የሚኖረው <u>በብድር ለተሰጠ ገንዘብ ወለድ</u> ላይ ሲሆን ዋናውን የብድር ገንዘብ <u>የማይጨምር</u> መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና አቀራረጽ ያስገነዝባል። ምክንያቱም ድንጋጌው ዋናውን የብድር ገንዘብ የሚጨምር ቢሆን ኖሮ የብድር ገንዘብንና ወለድ በማለት ያስቀምጠው ነበር እንጂ ለብቻው ነጥሎ የብድር ገንዘብ ወለድን በማለት አይጽፈውም ነበር። ይህ ስለመሆኑም ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 29181 እና የሰ/መ/ቁ. 35758 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም እቁብ ከመሰረቱ ብድር አይደለም፤የብድር ባህርይም የለውም። እቁብ ሰዎች ባላቸው አቅም መሰረት ገንዘብ ለማጠራቀም የሚጠቀሙበት ማህበራዊ እሴት ነው። እቁብ ዋናው ዓላማ አባላቱ የቁጠባ ባህል እዲኖራቸው የሚያደርግ ነው። በመሆኑም የእቁብ አባል ለሌላው አባል እንደ ተበዳሪ ወይም አንዱ ለሌላው ከወዲሁ ባለገንዘብ ነው ሊባል የሚችልበት የስምምነት አይነት አይደለም። ምናልባት አባሉ እጣው ደርሶት ከተጠቀመ በኋላ ቀሪውን እጣ ካልከፈለ እንደማንኛውም ደንበኛ እቁቡን ካልከፈለው አባል ላይ ግዴታ የሚጥል ነው የሚል ክርክር ተቀባይነት ይኖረዋል። ይህም ጉዳይ ተቀባይነት የሚኖረው በጠቅላላው ሕጉ የተመለከቱትን ይርጋ ደንቦችን መሰረት አድርጎ ሲቀርብ ሊሆን ይገባል። የአመልካቾች ጠበቃ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ለጉዳዩ አግባብነት ይኖረዋል በማለት የሚሬከሩት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677/1/ ድንጋጌን በማጣቀስ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የጠቅላላ ውል ድንጋጌዎች በአንድ ጉዳይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚደረገው ከጉዳዩ ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ ነው። ስለሆነም ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስር የተመለከቱት ጉዳዮች ተለይተው በተቀመጡበት ሁኔታ ለእቁብ ተፈፃሚ የሚሆንበት የሕግ አተረጓጎም ደንብ የለም። ሕጉም እቁብ የሚቋቋምበትን ዓላማ የመጠበቅ ሐሳብ ያለው ነው ተብሎ ይታሰባል። ሕግ ሲተረጐምም ሊፈፀም የሚችል ውጤት እንዲኖረው በማድረግ ስለመሆኑም ጠቅላላ የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የግድ የሚሉት ነው። በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነቱ በብድር ለተሰጠ የገንዘብ ወለድ እንጂ ለዋናው የብድር ገንዘብ አለመሆኑን ከድንጋጌው ይዘትና አቀራረጽ የምንገነዘበው ነጥብ በመሆኑ ለእቁብ ገንዘብ ተፈፃሚ የሚሆንበትን አግባብ አላገኘንም። በዚህም ምክንያት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024/ረ/ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለት መወሰናቸው ሕጋዊ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተናል፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64158 በሕዳር 01 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 42252 የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/መሰረት ፀንቷል።
2. የእቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ስር የተመለከተው የሕሊና ግምት የሚሸፈን አይደለም ብለናል።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 49900

ሀምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ ሐመልማል ዓለሙ - ከጠበቃ ይነሡ በላይ ጋር ቀረቡ

2. አቶ ዓለሙ አበረቱኝ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ሀረገወይን ዘለቀ ከጠበቃ አቶ አብይ ደግፌ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቾች ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩን መነሻ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርበው ያለ ፍላጐቱ በተንኮልና በማስገደድ ለአንደኛ አመልካች/አንደኛ ተከሳሽ/ ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የስጦታ ውል እንድፈፅም ያደረገችኝ በመሆኑ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስና አንደኛ ተከሳሽ/ አመልካች/ ምንም አይነት ግንባታ እንዳታከናውን ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካችና በሥር በተከሳሽነት ቀርበው

አመልካች ወደውና ፈቅደው በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ቀርበው ባደረጉት የሥጦታ ውል መሠረት አንደኛ አመልካች ቤት ገንብተው እየኖሩበት የሚገኙ መሆኑን ገልፀው የተጠሪ ጥያቄ ውድቅ እንዲደረግላቸው ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል ያቀረቡት ምስክሮች ሁለተኛው አመልካች ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች የስጦታ ውል እንዲፈርሙላት ብቻና ማስፈራራት ይፈፅሙ ነበር ስጦታው ከመደረጉ በፊት ሁለተኛ አመልካችና ተጠሪ ስጦታው መደረግ አለበት የለበትም በሚል ምክንያት ይጨቃጨቁ ነበር በማለት የመሰከሩ መሆኑን መዝግቦ በተጠሪ ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የተደረገው የስጦታ ውል በማሣሣትና በተንኮል የተደረገና ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2442/3/ መሠረት የስጦታ ውሉ ፈርሷል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካቾች አንደኛ አመልካች ብር 600.000 /ስድስት መቶ ሺ ብር/ ያላነሠ ወጭ በማውጣት ተጠሪ ከሁለተኛው አመልካች ጋር በመሆን ከነበራቸው ሰፊ ግቢ ከፋፍለው 261 ካ.ሜ ቦታ ላይ የነበረ ጅምር ቤት በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ቀርበው በሰጧቸው ላይ ትልቅ ቤት ገንብተዋል፡፡ ተጠሪ የስጦታ ውሉን በፈረሙበት ጊዜ መገደድም ሆነ ማታለል ያልተደረገባቸው መሆኑን የተጠሪ ምስክሮች ለፍርድ ቤት አስረድተው እያለ፣ ከህጉ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ሁኔታ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በበኩላቸው የስጦታ ውሉን ሲፈርሙ ተጠሪ በሁለተኛ አመልካች ስለመገደዳቸው የንስሀ አባታቸው መሥክረዋል። የሁለተኛው አመልካች አድራጎት ባልና ሚስት የጋራ ሀብታቸውን በማስተዳደር በኩል እኩል መብት ያላቸው መሆኑን የሚደነግገውን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ፣ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ሰፊ ክርክር አቅርቧል። አመልካቾች በቃል ክርክር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች ያደረጉት የጅምር ቤት ስጦታ ውል ይፈርሣል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ በዝርዝር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ተጠሪ የህጉን መስፈርት የሚያሟላ የውል ማፍረሻ ምክንያት ያላቸው መሆኑን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም የሚለውን ነጥብ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች ያደረጉት የስጦታ ውል እንዲፈርስ የወሰነው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2442 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ በመጥቀስ ነው። በእርግጥ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች የቀጥታ ንባብ የስጦታ ሰጭው ወራሾች ሰጭው በህይወት ሣለ ስጦታው እንዲፈርስ ያቀረበውን ክስ ለመቀጠል ስለሚችሉበት ሁኔታ የሚደነግግ ድንጋጌ ነው። ሆኖም የድንጋጌውን መሠረታዊ ግብ እና አላማ መሠረት በማድረግ ስናገናዝበው ስጦታ ሰጭው በስህተት ወይም በተንኰል የተደረገ ስጦታ እንዲፈርስለት ክስ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን ያመለክታል። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2442 ድንጋጌ በተያዘው ጉዳይ

በቀጥታም ባይሆን በትርጉም ግንኙነት ያለው ቢሆንም የስጦታ ውል ለማፍረስ የሚያስችል " ስህተት" ምን አይነት ስህተት ነው; የስጦታ ውል በተንኮል ተደርጓል ተብሎ የሚፈርሰው ምን ሁኔታዎችን ሲሟላ ነው; የሚሉትን መሠረታዊ ሁኔታዎች የሚደነግግ ባለመሆኑ እነዚህን ነጥቦች ለመረዳት ስለ ጠቅላላ ውል የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

1. የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች ያደረጉት የጅምር ቤት ስጦታ እንዲፈርስ የወሰነው የስጦታ ውሉ በስህተት የተደረገ መሆኑን በመግለፅ ነው።

አንድ ውል በመዋዋል የደረሰው ስህተት የውል ማፍረሻ የሚሆነው ተዋዋዩቹ አስፈላጊ አቋም ነው ሲሉ በሚቀበሉበት አኳኋን ላይ የተደረገ ስህተት ሲሆንና ውሉ ሲፈፀም በአኳኋኑ በቅን ልቦና አስፈላጊ አቋም በሚሆነው ላይ መሆኑ ሲገመት እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1698 ተደንግጓል። አንድ ውል በስህተት ምክንያት የሚፈርሰው በተለይ በውሉ ዓይነት ላይ ስህተቱ የደረሰ እንደሆነ ወይም አንደኛው ተዋዋይ ወገን በሰጠው ቃል ስለመሣሣቱ የሚያቀርበው መከራከሪያ ከፍ ያለ አስረጅነት የሚያገኝ ሲሆን እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1699 ይደነግጋል። በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ለአንደኛ አመልካች በሰነዶችና ውል ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው ያደረጉት ውል የስጦታ ውል መሆኑን ሣያውቁ በስህተት ያደረጉት ስለመሆኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በምስክርነት ቀርበው የሰጡት ቃል እንኳን አያረጋግጥም። ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች የጅምር የቤት ስጦታ እንዲያደርጉ በተደጋጋሚ በሽማግሌዎች ሁለተኛ አመልካች እንዳስጠየቋቸው የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል። ስለዚህ ተጠሪ የስጦታ ውል ያደረጉ መሆኑን አውቀውና ተገንዝበው ያደረጉትና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1698 እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1699 ድንጋጌዎች በተደነገገው መሠረት ውሉን

ለማፍረስ የሚያስችል ስህተት የፈፀሙ መሆኑን በማስረጃ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ተጠሪና ሌሎች ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመመርመር ለመገንዘብ ችለናል። ስለሆነም ተጠሪ ውል በማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ቀርበው የሚያደርጉትን የስጦታ ውል መሆኑንና ስጦታ ተቀባይ አንደኛ አመልካች መሆናቸውን ሙሉ ግንዛቤ ይዘውና በስጦታ የሚሰጡት ጅምር የመኖሪያ ቤት መሆኑን ተረድተው ያደረጉት የስጦታ ውል ለማፍረስ የሚያስችል መሠረታዊ የሆነ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1698 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1699 መሠረት ሣያስረዱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የበታች ፍርድ ቤቶች የስጦታ ውሉ የተፈፀመው በስህተት ስለሆነ ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች ያደረጉት የጅምር የመኖሪያ ቤት ስጦታ እንዲፈርስ ሲወስን የጠቀሰው ሌላው ምክንያት የስጦታ ውሉ በተንኮል የተደረገ ነው የሚል ነው፡፡
አንድ ውል በተንኮል የተደረገ ውል ነው በሚል ምክንያት ፈራሽ የሚሆነው ከተዋዋዬቹ አንደኛው ወገን ውሉ እንዲያደርግ ያደረገው በሁለተኛው ተዋዋይ ላይ ተንኮል ባይደርስበት ኖሮ ውል የማያደርግ የነበረ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1704 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የስጦታ ውል ከአንደኛ አመልካች ጋር እንዲያደርጉ በሽማግሌ የተጠየቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪን ለማስፈረም እውነታውን የመደበቅ ወይም ተጠሪ ዕውነታውን እንዳይረዱ የሚያደርጉ የተንኮል ተግባራት በአንደኛ አመልካች በኩል ስለ መፈፀሙ ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት አቅርበው ያሰሟቸው ምስክሮችም ሆኑ ተጠሪ የሰጡት የምስክርነት ቃል አላስረዱም፡፡ ተጠሪ በአንደኛ አመልካች በፈፀሙት የተንኮል ተግባር ምክንያት በሰነዶችና ውል ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የስጦታ ውል የፈረሙ ስለመሆኑ የማስረጃነት በማስረዳት የማስረዳት ሸክማቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2442 ንዑስ አንቀጽ 3"ን" በመጥቀስ ውሉ በተንኮል የተደረገ ስለሆነ ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የስጦታ ውል እንዲፈርስላቸው የጠየቁት ተጠሪ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1704 ድንጋጌ መሠረት በተንኮል ውል የተዋዋሉ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ መሆኑን ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው መደምደሚያ የስጦታ ውሉ መፍረሻ ምክንያት አድርጎ ባይገልፀውም፤ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤትና በሰበር የሚከራከሩት የስጦታ ውሉን የፈረምኩት ባለቤቴ /ሁለተኛው አመልካች/ በፈፀመብኝ ዛቻና ማስፈራራት ምክንያት ነው በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ቀርበው የሰጡት ውሉን በሰነዶችና ውል ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የፈረሙት ሁለተኛ አመልካች የስጦታ ውሉን ካልፈረምሽ ከዚህ ቤት መኖር አትችይም እያለ ስለአስፈራራኝና ስለዛተብኝ ነው በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ ውሉን እንዲፈርም የማስገደድና የማስፈራራትና የዛቻ ተግባራትን ተፈፅሞብኛል የሚሉት በስጦታ ተቀባይዋ አንደኛ አመልካች ሳይሆን ከተጠሪ ጋር በስጦታ ሰጪነት ያፈረሙት በሁለተኛ አመልካች ነው፡፡
ሁለተኛ አመልካች የስጦታ ውሉ ተጠቃሚና ስጦታ ተቀባይ ባይሆኑም ተጠሪ የስጦታ ውሉን እንዲፈፅሙ የማስገደድ ተግባር መፈፀማቸው ከተረጋገጠ

የውሉ ማፍረሻ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1707 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም በውሉ በስጦታ ሰጪነት ከተጠሪ ጋር ፈራሚ የነበሩት ሁለተኛ አመልካች ተጠሪ ውሉን እንዲፈርሙ የማስገደድ ተግባር ፈፅመዋል ወይስ ወይም አልፈፀሙም? የሚለው ነጥብ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1706 ድንጋጌዎች አንፃር መመዘን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አንድ ውል በሀይል ሥራ ወይም በመገደድ የተፈፀመ ነው ተብሎ የሚፈርሰው፤ ተዋዋዩን ራሱን ወይም ወላጆቹን ወይም ተወላጆቹን ወይም ባልን ወይም ሚስትን ከባድና የማይቀር አደጋ በህይወቱ፣ በአካሉ፣ በክብሩ ወይም በንብረቱ እንደሚመጣበት ያሳመነው ሲሆንና ተዋዋዩን ሥጋት ላይ የጣለው ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይችላል፡፡

በህጉ መስፈርት በተዋዋዩ ላይ የሚደርሰው አደጋ ከባድ የማይቀር ነው የሚል እምነት የሚያሣድርና ለስጋት የሚዳርግ መሆኑን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት ውሉ በመገደድ የፈፀምኩት ስለሆነ ሊፈርስልኝ ይገባል በማለት የሚጠይቀው ወገን ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የስጦታ ውሉን የፈረምኩት ሁለተኛ አመልካች ውሉን ካልፈረምሽ እዚህ ቤት እትኖሪም በማለት ስላስፈራራንና ስለዛተብኝ ነው የሚል ምስክርነት ቃል የሰጡ ሲሆን ሌሎችም ምስክሮች ተጠሪ ሁለተኛ አመልካችና ፈፅመውብኛል እያሉ የነገሯቸው መሆኑን የሚመሰክሩ ናቸው፡፡ ሆኖም ዝቅተኛ አደጋ የሚያስከትል መድረሱን እርግጠኛ ያልሆነ ዛቻና ማስፈራራት ተደርጎብኛል በሚል ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ እንደማይቻልና የሀይል ተግባሩ በህይወቱ ወይም በአካሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም በንብረቱ ላይ ከባድና የማይቀር አደጋ እንደሚደርስበት የሚያሣምን መሆን እንዳለበት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1706 የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ በሰነዶችና ውል ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ለአንደኛ አመልካች የስጦታ ውል ያደረግሁት ሁለተኛው አመልካች ውሉን ካልፈረምሽ እዚች ቤት አትኖሪያትም ብሎ ስለዛተብኝና ስላስፈራራኝ ነው በማለት የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ተጠሪ ያቀረቡት ጥያቄ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1707 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1706 ድንጋጌ መሠረት ያላደረገና ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም በሰነዶችና ውል ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው በውል አዋዋይ ባለሥልጣን ፊት ፈርመው ለአንደኛ አመልካች የጅምር የመኖሪያ ቤት ስጦታ ውል ያደረጉት በፍትሐብሔር ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት በመሣሣት፤ በተንኮል ወይም በመገደዳቸው መሆኑን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነታቸውን አልተወጡም፡፡ ተጠሪ በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ውል ጉድለት ያለበትና የሚፈርስበት በቂ ህጋዊ ምክንያት ያለ መሆኑን በማስረዳ ሣያስረዱና ሣያረጋግጡ የበታች ፍርድ ቤቶች አንድ ውል በስህተት የተደረገ ነው፤ በተንኮል የተፈፀመ ወይም በመገደድ የተፈፀመ ነው ተብሎ የሚፈርሰውም ምን ምን ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ አንደሆነ ከላይ በዘረዘርናቸው የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች የተቀመጠውን መሥፈርት ሣያገናዝቡ የስጦታ ውል በስህተትና በተንኮል የተፈፀመ ስለሆነ እንዲፈርስ በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

ተጠሪ እና ሁለተኛ አመልካች ለአንደኛ አመልካች ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉት ጅምር የመኖሪያ ቤት ስጦታ ውል ህጋዊ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው ውል ነው ብለናል፡፡

በዚህ ፍርድ ቤት አመልካቾችና ተጠሪ ያወጡትን ውጭ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፍ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43888

መጋቢት 23 ቀን 2002ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ፀሐይ ወንድም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1/ አቶ አያለው መለስ - አልቀረቡም

2/ ወ/ት ፍሬህይወት - ተመስገን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዮን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውሳኔ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ በአይነት ለመከፋፈል ከስምምነት ለመድረስ አለመቻላቸውን ጠቅሶ በጨረታ ተሸጦ ውጤቱ እንዲቀርብ ሲል የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአፈፃፀም መዝገብ የሰጠውን ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች በማጽናታቸው አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካች የካቲት 26 ቀን 2001ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የውርስ ሐብቱን ስመሐብት ወደ ስማቸው ለማዞር ያቀረቡትን አቤቱታ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳይሰጥበት ማለፉ እና የቤቱ ዋጋ በባለሙያ ወይም በሽማግሌ ሳይገመት ቤቱ በወር በሚያስገኘው የኪራይ ገቢ መነሻ በጨረታ እንዲሸጥ መደረጉ መብታቸውን እንደሚጎዳ ጠቅሰው ንብረቱን በስምምነት ለመሸጥ ወይም ለማከራየት እንዲችሉ እንዲወሰን አመልክተዋል፡፡

ይህ ችሎትም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ የስር ፍ/ቤት አፈፃፀሙን የሰራው በተከራከሪ ወገኖች ፈቃድ እና በውሳኔው መሠረት መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎችን አስቀርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ጥር 25 ቀን 2002ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ በውሳኔው መሠረት ቤቱን ማስረከቡን ገልጿል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ጥር 3 ቀን 2002ዓ.ም በጽሑፍ በሰጡት መልስ ከአመልካች ጋር ወራሽ መሆናቸውን ጠቅሰው ቤቱን በአይነት ለመከፋፈል አመቺ አለመሆኑን አመልካች እያወቁ ቤቱን ይዞ አፈፃፀሙን ማጓተት ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሰው ቤቱ በጨረታ ተሸጦ ገንዘቡን እንዲካፈሉ እንዲወሰን አመልክተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በዚህ ፍ/ቤት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በዚህ ፍ/ቤት ምላሽ የሚያሻው ነጥብ ግራ ቀኙ ንብረቱን በስምምነት ለመከፋፈል ያልቻሉ እንደሆነ የጨረታው ሽያጭ መነሻ ዋጋ ተብሎ የተወሰደውን አግባብነት እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከከፍተኛው ፍ/ቤት ትዕዛዝ መረዳት እንደተቻለው የጨረታ መነሻ ዋጋ ተብሎ የተጠቀሰው ብር 16,527.29(አስራ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሰባት ከሃያ ዘጠኝ ሣንቲም) ቤቱን የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ማከፋፈያ የተከራየበት ግምት መሆኑ ነው፡፡ ይህ ገንዘብ የቤቱ የአመት የኪራይ ዋጋ ስለመሆኑ አመልካች በአቤቱታቸው ገልፀዋል፡፡ ተጠሪዎች ይህ ሐሰት ነው አላሉም፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ሲታይ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ሲወሰን የቤቱ ዋጋ ተብሎ ሊወሰድ የሚገባው የኪራይ ዋጋ ማለት እንዳልሆነ መረዳት የሚያዳግት አይደለም፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ግን የኪራይን ዋጋ ለቤቱ ሽያጭ የጨረታ መነሻ ዋጋ አድርጎ ወስዶታል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1083 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የውርስ ንብረት ግምት አፈፃፀም ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የንብረቱ ግምት በወራሾች ስምምነት ሊወሰን የሚችል ሲሆን ከስምምነት ካልደረሱ እነሱ በመረጧቸው የሽምግልና ዳኞች አሊያም ፍ/ቤቱ በሚመርጣቸው የሽምግልና ዳኞች ሊገመት እንደሚችል ተጠቅሷል፡፡ ይህም ካልተቻለ በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1084 መሠረት በባለሙያ እንዲገመት ማድረግ ይገባል፡፡

ይህ ግምት የሚከናወነው የንብረቱን ይዞታ እና የገቢያ ዋጋ ለማመልከት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ፍ/ቤቱ የንብረቱ ግምት ነው ብሎ የኪራይ ዋጋ ግራ ቀኙ የተስማሙበት ነው በማለት ለሽያጭ መነሻ ዋጋ ግምት አድርጎ መውሰድ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም በዚህ ገረድ ፍ/ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ የግራ ቀኙን መብት የሚያጣብብ ከመሆኑ አንፃር እንዲሁም በሕጉ ከተመለከተው አግባብ ውጪ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የምሥራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 25564 የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ እና የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 01020 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የውርስ ንብረት ዋጋ በግራ ቀኙ ስምምነት አሊያም በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ የሐራጅ ሽያጭ እንዲደረግና በውጤቱም መሠረት እንዲያስፈጽም መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት ለምሥራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ አዝዘናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39837

ግንቦት 03 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ኂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሰመንጉስ አሰፋ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- መ/ርት ምህረት ክበበው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጋብቻ ወቅት በግል ለመጣ እዳ ለአፈፃፀም የሚውለውን ንብረት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በይርጋለም ከተማ የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት የአፈፃፀም ማመልከቻ ነው፡፡ የአፈፃፀም ማመልከቻ ይዘቱም ባጭሩ፡- አመልካች የአሁኑ ተጠሪ ባለቤት በነበሩት በአቶ ፀጋዬ ከበደ ላይ የብድር ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ አቅርበው በዋናው ጉዳይ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ አቶ ፀጋዬ ከበደ የብድር ገንዘቡን ለአሁኑ አመልካች እንዲከፈላቸው የተወሰነ መሆኑን ገልፀው አፈፃፀሙ በተጠሪ ደሞዝ እንዲቀጥልላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አፈፃፀሙ ቀጥሎ ተጠሪ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጐ ከተጠሪ ደመወዝ 1/3ኛ እየተቆጠረ ለአፈፃፀሙ እንዲውል የሚል የፍርድ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ እዳውን የማያውቁት መሆኑን ገልፀው በሌሉበት የተሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ እንዲነሳላቸው አመልክተው የስር ፍርድ ቤት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ እዳው የመጣው በተጠሪ ባለቤት በነበሩት ግለሰብ የግል ጉዳይ በመሆኑ በተጠሪ ደመወዝ አፈፃፀሙ ሊቀጥል የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለውም የሚለውን ምክንያት በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን

ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ይህ ውሳኔ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚውም ሆነ ሰበር ሰሚው ችሎት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመወሰኑ ተጠሪ ቀርበው መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አንድ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ያስፈረዱት ፍርድ በተጠሪ ደመወዝ ላይ እየተቆጠረ ሊፈፀም አይገባም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ዋናውን ፍርድ ያስፈረዱት በተጠሪ ባለቤት በነበሩት አቶ ፀጋዬ ከበደ ሲሆን እዳውም በግል የመጣ መሆኑ በፍርድ መረጋገጡን ነው፡፡ እንዲሁም አቶ ፀጋዬ ከበደ የግል ንብረት የሌላቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡

በመሰረቱ አንድ ተጋቢ በግሉ ያመጣው እዳ ከሌላኛው ተጋቢ የጋራ ንብረት እንዲከፈል የሚደረገው እዳውን ያመጣው ተጋቢ በግሉ መክፈል ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ እና እዳው የመጣው በጋብቻ ወቅት ሆኖ ተጋቢዎቹ እዳው በሚከፈልበት ወቅት የፀና ጋብቻ ውስጥ ያሉ ከሆነ ስለመሆኑ ለውሳኔው መሰረት ከሆነው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግም ሆነ ከተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ (አዋጅ ቁጥር 213/92) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ እዳው በአቶ ፀጋዬ ከበደ በግል የመጣ እና ለቤተሰቡ የጋራ ጥቅም ያልዋለ መሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ በላይ ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ነጥብ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪ ከአቶ ፀጋዬ ጋር እዳው ሲወሰድ ጋብቻ መስርተው ነበር ተብሎ ለጋራ ጥቅም ላልዋለውና በግልጽ አቶ ፀጋዬ ለግል ጉዳይ ብለው ለተበደሩት ገንዘብ የተጠሪ ደመወዝ የሚቆረጥበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በአቶ ፀጋዬ የግል ንብረት ላይ አፈፃፀሙን ከሚቀጥሉ በስተቀር በተጠሪ ደመወዝ ላይ አፈፃፀሙን እንዲቀጥሉ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ በሥነ-ሥርአትም ሆነ በመሰረታዊ ሕግ ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 08543 ታህሣሥ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመ/ቁ. 21205 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም፣በሰበር ችሎቱ በመ/ቁጥር 22419 ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 46143

ሐምሌ 2 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ድልበጌ ራሕመቶ

ተጠሪዎች፡- 1. የባህር ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት - ነ/ፈጅ መላኩ መኰንን

2. የአቶ መሐመድ ዑስማን ወራሾች - ሙሡማ መሐመድ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአፈጻጸም ጊዜ የተነሳን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አንደኛ አመልካች የፍርድ ባለመብት ሲሆን የሁለተኛ ተጠሪዎች አውራሽ አቶ መሐመድ ዑስማን ደግሞ የፍርድ ባለዕዳ ነው፡፡ አመልካች ክርክሩ ውስጥ የገባችው የፍርድ ባለመብቱ የአፈጻጸም ትዕዛዝ (በሐራጅ ይሸጥ) ያሰጠበት ቤት የፍርድ ባለዕዳ ንብረት አይደለም፡፡ ቀደም ሲል ኑርሑሴን በርሄ የተባለው ሰው ንብረት የነበረ፤ በኋላም ከዚህ ሰው ወራሾች (እነ ዘይኑ ኑርሑሴን) ላይ የገዛሁት ነው፡፡ በንብረቱ ላይ የተሰጠው የሐራጅ ትዕዛዝ እና እግድ ይነሳልኝ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418 መሠረት በማለት መቃወሚያ በማቅረብዋ ነው፡፡ መቃወሚያው የቀረበለት ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ የአመልካችን መቃወሚያ በመቀበል የሐራጁ ሽያጭ ቀሪ ሆኖ ቤቱ ለአመልካች ይለቀቅ በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንደኛ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም አመልካች ቤቱን ገዝቻለሁ በማለት ውል ከማቅረብዋ ውጪ ስመሃብቱን በስምዋ አላዛወረችም፡፡ ባለቤት ናት ለማለት የሚያስችል ማስረጃ የላትም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም ብሎአል፡፡ በዚህ መሠረትም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በውል መገዛት እየታወቀ በስምሽ አልተመዘገበም በሚል ምክንያት መቃወሚያዬ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚለውን የአመልካች አቤቱታ ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሩ በአፈጻጸም ደረጃ ያለን ጉዳይ የሚመለከት ስለመሆኑ ከላይ ተገልጾአል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ቤቱን በአፈጻጸም እንዲያገዘለት የጠየቀው የፍርድ ባለዕዳው የአቶ መሐመድ ዑስማን (የሁለተኛ ተጠሪዎች አውራሽ) ንብረት ነው በማለት ነው፡፡ አመልካች ቤቱን ገዛሁት የምትለው ደግሞ ከፍርድ ባለዕዳው ላይ ሳይሆን፣ አቶ ኑርሁሴን በርሄ ከተባለው ሰው ወራሾች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረበችው መቃወሚያ አንደኛ ተጠሪ ከአቀረበው ክርክር አንፃር ከመታየቱ በፊት በእርግጥ ቤቱ የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ለመሆኑስ ተረጋግጦአል ወይ? የሚለውን ነጥብ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በዚህ ረገድ አንድም ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ሲከራከር የቆየው አመልካች የሽያጭ ውል ከማቅረብ አልፋ የቤቱን ስመሃብት በስምዋ አላዛወረችም በሚለው ነጥብ ላይ ብቻ በመመስረት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን የክርክር አቅጣጫ ተከትለው ነው የወሰኑት፡፡ በበኩላችን እንደምናየው ግን ለሽያጭ የቀረበው /አንደኛ ተጠሪ በአፈጻጸም ያስያዘው/ ቤት በእርግጥም የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ለመሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህ ከተረጋገጠ በኋላም ነው በአመልካች እና በአንደኛ ተጠሪ መካከል ያለውን ክርክር ማየት የሚገባው፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው አመልካች ቤቱን የገዛችው ከፍርድ ባለ ዕዳ ላይ እንዳልሆነ አላከራከረም፡፡ አንደኛ ተጠሪም ቤቱ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ለመሆኑ ወይም የአቶ ኑርሁሴን በርሄ ንብረት ላለመሆኑ በማስረጃ ሊያስረዳ ቀርቶ በክርክር ደረጃ እንኳን ምንም ያለው ነገር የለም፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክርም የአንደኛ ተጠሪ ነገረ-ፈጅ ተጠይቆ የሰጠው መልስም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ በሁለተኛ ተጠሪነት የቀረቡት የሥር የፍርድ ባለዕዳ ወራሾችም ቤቱ የእነሱ እንዳልሆነ በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ስናየው ቤቱ አንደኛ ተጠሪ በሁለ ተኛ ተጠሪ ባስፈረደው ገንዘብ ምክንያት በአፈጻጸም የሚያገበት የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 68424 የካቲት 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 44935 ሚያዝያ 19 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነው በአፈጻጸም ሊያገዝ አይችልም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48850

ታህሣሥ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለስ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- 1. አቶ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ

2. ካሌብ ጌጣጌጥ ኃ/የተ/የግ/ማህበር } ጠበቃ ፊሊጶስ አይናለም ቀረቡ

3. አቶ ለአከ ፍስሐ

ተጠሪ፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ነ/ፊጂ ሌንሳ ዳንኤል

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ጋር በተያያዘ የቀረበ የወንጀል ክስ ሲሆን ተጠሪ በአመልካቾችና በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ ላይ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሾች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እና እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ እና 50/ለ//1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ሦስተኛ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/1/ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ እና አንቀጽ 50/ለ/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ አራተኛ ተከሳሽም የተጨማሪ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 55 እና እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ መጋቢት 26 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 5፡45 ሰዓት ላይ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ በካሌብ ጌጣጌጥ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች ቀርበው ክሱን እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ክሱን እንደማይቃወሙ ገልጸው ድርጊቱን አልፈጸምንም ጥፋተኞችም አይደለንም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የዓ/ሕግ ማስረጃን ሰምቶ ተከሳሾች በክሱ ላይ በተጠቀሰው ጊዜና ሥፍራ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ በካሌብ ጌጣጌጥ ኃ/የተ/የ/ማህበር ድርጅት ውስጥ የአንገት ሐብል ሽያጭ ስለማከናወናቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ይከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቶ ተከሶሾች መከላከያ ማስረጃቸውን አሰምተዋል፡፡ ከዚያም ተከሳሾች የወንጀሉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድርጊት ስለመፈጸማቸው በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ተረጋግጦባቸው በመከላከያ ማስረጃቸው ማስተባበል እንዳልቻሉ ፍ/ቤቱ ዘርዝሮ የመከላከያ ምስክሮቻቸውን ቃል ውድቅ ከአደረገ በኋላ ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ናቸው ካለ በኋላ አንደኛ እና አራተኛ ተከሳሾች እያንዳንዳቸው በአንድ ዓመት እሥራትና በብር 10ሺህ የገንዘብ መቀጫ እንዲቀጡ ሦስተኛ ተከሳሽም በብር 60 ሺህ የገንዘብ መቀጫ እንዲቀጣ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ግን በተከሰሰበት ወንጀል ኃላፊነት የለበትም በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 149/2/ መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

ከ1-3 የተጠቀሱት ተከሳሾች የአሁን አመልካቾች በውሳኔው ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካቾች ጥፋተኛ ተብለው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጐ ግራ ቀኙ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከሕጉ አኳያ አግባብነቱ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ እንደተቻለው አመልካቾች ፈጽመዋል ተብለው የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ለማስረዳት አቃቤ ሕግ ሁለት ምስክሮች በፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቦ ያሰማ ሲሆን እነዚህም ምስክሮች የሰጡት ቃል ተጠቃሎ ሲታይ መጋቢት 26 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 5፡45 ሰአት ሲሆን ወደ አንደኛ አመልካች የጌጣጌጥና ወርቅ መሸጫ ድርጅት ሄደን ባለ 18 ካራት የወርቅ የአንገት ሐብል ጠይቀን 5.9 ግራም ወርቅ በብር 2100 ተሰማምተን ሐብሉን ከገዛን በኋላ የድርጅቱ የሽያጭ ሰራተኛ የነበረውን ሦስተኛ አመልካችን የባት ደረሰኝ እንዲሰጠን ስንጠይቀው የቢዝነስ ካርድ ሰጠን ከዚያም ማንነታችንና የመጣንበትን ስንገልጽለት ስልክ በመደወል ደረሰኝ እንዲመጣለት ጠይቆ አንደኛ ተከሳሽ የባት ደረሰኙን ይዘው ወደ ሱቁ መጥተዋል የሚል ነው፡፡

ማንኛውም በተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ድርጅት የሚያካሂደውን ማንኛውንም ሽያጭ ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ካከናወነ ድርጊቱ ሕገወጥ እንደሆነና እንደሚያስቀጣም የተጨማሪ እሴት ታክስን ባሻሻለው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 50/ለ/ /1/ ላይ ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም ማንኛውም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ የተመዘገበ ድርጅት ታክስ የሚከፈልበትን ሽያጭ ያከናወነ ሰው ደረሰኝ ለገዢው ወዲያውኑ መስጠት እንዳለበት በዚሁ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 22/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም የሁለተኛ አመልካች የካሌብ ጌጣጌጥ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሽያጭ ሰራተኛ የሆኑት ሦስተኛ አመልካች ከፍ ብሎ በተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች መሰረት የወርቅ ሽያጩን ካከናወኑ በኋላ ደረሰኝ ለገዢዎች ወዲያውኑ መስጠት ሲገባቸው ደረሰኙን ወደያውኑ ሳይሰጡ መቅረታቸው በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ተረጋግጦባቸው በመከላከያ ማስረጃ ያላስተባበሉ በመሆኑ ጥፋተኛ መባላቸው የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩልም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል (Body corporate) በወንጀል ተጠያቂ ለመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/3/ መሰረት ወንጀል የመፈጸም ሐሳብ(criminal intention) ግዑዝ ከመሆኑ አኳያ እንዲሟላ የሚጠበቅ ሳይሆን ኃላፊነቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1/ ላይ እንደተመለከተው ከድርጅቱ ኃላፊዎች ወይንም ከሰራተኞቹ አንዱ የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ ባለመወጣት የድርጅቱን ጥቅም ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለማራመድ ተንቀሳቅሰው በሚገኙበት ጊዜ ሊመነጭ ይችላል፡፡ በሁለተኛ አመልካች ድርጅትም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመወጣት ረገድ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አኳኋን የድርጅቱ ሰራተኛ በሆኑት ሦስተኛ አመልካች ዓማካኝነት የተፈጸመ እንደመሆኑ መጠን በወንጀል ሕግ ቁጥር 34/1/ እና በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ መሰረት ድርጅቱ ጥፋተኛ መባሉ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚሁ ጋር በተያያዘም የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነ ድርጅት አዋጁን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ በሚገኝ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በድርጅቱ የተፈጸመውን ጥፋት እንደፈጸመ ተቆጥሮ በአዋጁ የተጣለው ቅጣት ተፈፃሚ እንደሚሆንበት በዚሁ አንቀጽ 56/1/ ሥር የተመለከተ ሲሆን ሥራ አስኪያጁ ከኃላፊነት ነፃ የሚሆነው በንኡስ አንቀጽ /3/ ላይ እንደተመለከተው ጥፋቱ የተፈጸመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ሲቀር እንደዚሁም ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያሳይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈጸም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን ተገቢውን ትጋትና የአሰራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስዶ የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

ሆኖም ግን ከጉዳዩ መገንዘብ እንደተቻለው አንደኛ አመልካች እንደ ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅነታቸው አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ሽያጭ በሚከናወንበት ጊዜ ገዢዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ወዲያውኑ እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ሥርአት መዘርጋት ሲገባቸው ይህንን በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ ባለማክበር የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኙ ሽያጩ ከተከናወነበት ሱቅ ወደ ሌላ ሱቅ ሁልጊዜ እየተወሰደ የኦዲት ሥራ እንዲሰራ መደረጉ ኦዲት ተደርጐ እስከሚመጣም ሱቁ ያለደረሰኝ እንዲቆይ ግድ ስለሚያደርገው የኦዲት ሥራው በዚያው ሱቅ ደረሰኙ ሳይወሰድ እንዲከናወን ማድረግ ከአንድ ጠንቃቃ ሥራ አስኪያጅ የሚጠበቅ ተግባር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኙ ወደ ሌላ ሱቅ እንዲሄድ ማድረግ ከውጤት አኳያ ያለደረሰኝ ሽያጭ ለማካሄድ እንደመወሰን የሚቆጠርና የማያመች አሰራርን በመከተል ሕጉ የታለመለትና ዓላማና ግብ እንዳያገኝ የሚያበቃ ነው፡፡

በመሆኑም አንደኛ አመልካች እንደ ሥራ አስኪያጅነታቸው በሕግ የተጣለበባቸውን ግዴታ በመከተል ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረጉና ይልቁንም የዘረጉት የአሰራር ሥርአት ያለደረሰኝ የሚደረገውን ግብይት አውቀውና ፈቅደው እንደሚከናወን ከክርክሩና ከማስረጃው መገንዘብ የተቻለው ስለሆነ በአንደኛ አመልካችም ላይ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻልም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካቾች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው መገኘታቸው በሕጉ አግባብ ከመሆኑም በላይ በቅጣቱም ላይ ከአመልካቾች ቅሬታ አኳያ የሕግ ስህተት የተፈጸመ ሆኖ አላገኘውም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 144166 በ12/9/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 80867 ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45927

ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ - ዮሴፍ ሐጎስ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- መሠረት መኮንን - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ ሕዳር 13 ቀን 2000 ዓ.ም. በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበበት ክስ በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ሚች ሲያኔ ታሬሳን ተከሣሽን ባለማግባትዋ ምክንያት ቂም ይዞ ሲሳይ በተባለው ሆቴል ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም. አብሯት አድሮ በንጋታው ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. በጩቤ ሆዷንና ግራ እግሯን ወግቶ በግፍ ስለገደለ በፈፀመው ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ሊጠየቅ ይገባል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል በክሱ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን በመግለጽ የወንጀል ድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን ስለመፈፀሙ አምኖ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ዓቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ተጠሪ እንዲከላከል አድርጎ የመከላከያ ማስረጃዎችን ሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ የተጠሪ መከላከያ ማስረጃዎችን የዓቃቤ ሕጉን ማስረጃዎችን ማስተባበል ያልቻሉ መሆኑን በመግለጽ የመከላከያ ምስክሮችን ቃል ውድቅ ከአደረገ በኋላ ተጠሪን ለሰው ግድያ ወንጀሉ ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል ካለ በኋላ ድርጊቱ ሊሸፈን የሚችለው በዓቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበው አንቀጽ ሥር ሳይሆን በወ/መ/ሕ/ቁጥር 540 ሥር ነው በማለት በዚሁ አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ አድርጎ የቅጣት አስተያየት ተቀበሎ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ የቅጣቱን መጠን 14 /አስራ አራት ዓመት/ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታውን ደግሞ ለሰበር ችሎቱ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች ግንቦት 07 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ድርጊቱ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎበት በቂም በቀል የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ፤ ተራ ሰው ግድያ ወንጀል በሚያስጠይቅበት ድንጋጌ ሥር ይወድቃል መባሉ ያላግባብ ስለሆነ የጥፋተኝነት ውሣኔው በወ/መ/ሕ/ቁጥር 539/1/ሀ/ ሥር ተሰጥቶ ተመጣጣኝ ቅጣት ሊጣል ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ/ ሥር የተመለተውን ከባድ የግድያ ወንጀል ያቋቁማል አያቋቁምም? የሚለውንና የዚሁ ተከታይ የሆነውን ቅጣት መጠን ለማየት ሲባል በሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ መስከረም 15 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ 2 ገጽ የሰበር አቤቱታ መልሱን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ሚችን በቂም ተነሳስቶ በጩቤ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቿን በመውጋት ለሕልፈት ዳርጓል በሚል አመልካች ክስ መስርቶ የድርጊቱን መፈፀም ተጠሪ ሳይክድ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለቱ ዓቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰነድና የሰው ምስክሮችን አቅርቦ ማሰማቱን ነው፡፡ በዓቃቤ ሕግ የሰው ምስክሮች ቃል የተነገረው ፍሬ ነገር ሲታይም በነቀምቴ ቴሌኮሙኒኬሽን አካባቢ፣ ሲሳይ ማሞ ሆቴል ፊት ለፊት ቁመው መኪና ሲጠበቁ ከቆዩ በኋላ በመኪናው ሥር ቁመው ባሉበት ሁኔታ ተጠሪ ሚችን ይዟት ጩሃ እያዩአቸው ጉድኗን በጩቤ ወግቶ ከጣላት በኋላ ጨምሮ ሁለት ጊዜ ደግሞ ጭኗን /እግሯን/ ወግቶ ወጣሉን ከዚህም በኋላ የተጠሪን እጅ ምስክሮች በመምታት ጩቤውን በማስጣል ተጠሪን ፖሊስ መያዙን እንዲሁም ሚችን ሆስፒታል ወስደዋት በእለቱ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ መሞቷን መመስከራቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ተጠሪ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 35 መሠረት ለወረዳው ፍርድ ቤት በሰጠው ቃል ሲሆን ይዘቱም ሲታይ ሚች ጓደኛዬ /ፍቅረኛዬ/ ሆና ለሦስት ዓመት በየወሩ ብር ሦስት መቶ እየረዳት በነቀምቴ መምራን ኮሌጅ ሲያስተምራት ቆይቶ በሽምግልና ሲያስጠይቃት እምቢ ስላለችው ገንዘቡን እመልስለታለሁ፣ አልፈልገውም ብላ ስለተናገረች ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም. ሲሳይ ማሞ ሆቴል አብረው አድረው ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. ጠዋት ላይ በጩቤ ሚችን ወግቶ የገደላት መሆኑን ቃሉን በነፃ ፈቃዱ መስጠቱን የሚያስረዳ ነው፡፡ ሌላው በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ከነቀምቴ ሆስፒታል የተሰጠ የሕክምና ማስረጃ ሲሆን ይዘቱም በሚች አካል ላይ በሦስት በተለያዩ ክፍሎች የተለያየ መጠን ያላቸው ቁስሎች የነበሩ ስለመሆኑና በዚሁ ምክንያትም መሞቷን የሚያሳይ ነው፡፡ እንግዲህ በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ከላይ የተመለከተው ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶችም ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን በተጠሪ መከላከያ ማስረጃም ይኸው ፍሬ ጉዳይ የተስተባበለ ወይም ሌሎች ሁኔታዎች ባሉበት የተፈፀመ ስለመሆኑ የተነገረ ነገር የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ ሲያደርግ በዓቃቤ ሕግ በኩል የተጠቀሰውን አንቀጽ ዝቅ ወደአለ አንቀጽ መቀየሩ ባግባቡ ነውን? የሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚያስፈልገው ነው፡፡

በመሠረቱ የሰው ግድያ ወንጀል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ/ መሠረት ድርጊት ፈፃሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በመዘጋጀት ሲፈፀም ወይም በአንቀጽ 84 ወይም 86 ሥር የተመለከቱት አክባጅ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ስለመሆኑ ተጠቃሹ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ሥር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች በየራሳቸው መቆም የሚችሉ ነጥቦች ስለመሆናቸው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ሚችን የገደለው ፍቅረኛው ሆና ትምህርት በራሱ ወጪ ሲያስተምራት ቆይቶ አላገባህም፣ ገንዘብህን እመልስልሃለሁ ስላለችው በዚህ መልሷ ቂም ይዞ ቆይቶ እንዲሁም ወንጀሉ ከመፈፀሙ በፊትም አንድ ቀን ቀደም ብለው አብረው በሆቴል ውስጥ አድረው ከወጡ በኋላ በጩቤ ደጋግሞ በመውጋት ለሕልፈት የዳረጋት ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ተጠሪ የግድያ ወንጀሉን አስቦበትና ቀድሞ ተዘጋጅቶበት በጭካኔ ወይም በአደገኛነት የፈፀመው ስለመሆኑ ያሳያሉ ከሚባሉ በስተቀር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በእለታዊ ፀብ እና አለመግባባት ምክንያት የፈፀመው ድርጊት ነው ለማለት የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በዓቃቤ ሕጉ ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር ማገናዘብ ሲገባቸው ያለ ምክንያት በተጠሪ ላይ ተጠቅሶ የቀረበውን ድንጋጌ መቀየራቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ ለፈፀመው የሰው ግድያ ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539/1/ሀ/ ሥር እንጂ በአንቀጽ 540 ሥር ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ላይ የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሠረት ለውጠን ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539/1ሀ/ ሥር ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በዚህ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ ሥር በተመለከተው ቅጣት አንፃር ነው፡፡ ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82፣ ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም፡፡ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን ሰለመፈፀሙ በዝርዝር ማመኑ፣ ሪኮርድ ያልቀረበበት መሆኑም መልካም የነበረ መሆኑን እንደሚያሳይ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ እነዚህ ነጥቦች ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82/1/ሀ/ እና /ሠ/ መሠረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ሲሆኑ መጠኑም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 179/ለ/ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪን ተጠያቂ ያደረጉበት ድንጋጌ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት ያላደረገና በምክንያትም ያልተደገፈ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሲሆን የተጠሪን አድራጎት በከባድ የሰው መግደል ወንጀል የሚሸፈንና የቅጣት መጠኑንም ከፍ ብሎ መወሰን ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአመልካቾች ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539/ሀ/ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በጉዳዩ የታሰረው የሚታሰብለት ሆኖ ሊቀጣ የሚገባው በ20 /ሃያ/ ዓመት ጽኑ እስራት ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/2/ለ2/ መሠረት አሻሽለን ወስነናል፡፡
4. ውሣኔው የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማ/ቤት ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45572

የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘነበች ሽብሩ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌ/ዐ/ህግ - ፈቃዱ አብዲሣ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የዐ/ህግ ምስክሮች ተሟልተው ባለመቅረባቸው መዝገቡ ለጊዜው ሲዘጋ ያለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ተጠሪ ያቀረበውን የወንጀል ክስ በሚያስተናግድበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ የተቆጠሩት ምስክሮች ተሟልተው ባለመቅረባቸው የዐ/ህግ ክስ ምስክሮቹ ተሟልተው ሲቀርቡ ይቀጥል ዘንድ ትዕዛዝ ሠጥቶ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡትን ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ጥር 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሠምቷል፡፡ እኛም ጉዳዩን ከስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ይዘትና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካች ላይ ተጠሪ የመሠረተው ክስ ለጊዜው የተዘጋው የዐ/ህግ ምስክሮች ሲሟሉ ዐ/ህግ ክሱን የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆለት መሆኑን ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ አጥብቀው የሚከራከሩት ይህ የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ገደብ የለሽ ሆኖ አመልካች በስጋት ውስጥ እንደኖሩ የሚያደርግ ነው በሚል ነው፡፡ ሆኖም የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ በጉዳዩ በህጉ የተመለከተውን የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ አይሆንም የሚል አንድምታ የሌለው በመሆኑ የአመልካች ጠበቃ ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ አፅንተነዋል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 43501

መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. ረዳት ሣጅን ሽጋ ተካ ሞላ — ከማ/ቤት ቀርበዋል ዋ/ኢ/ር ደጀኔ

2. ኮን/ል ሐብታሙ ዝናቡ ወንድሙ — ወንድሜነህ ጋር ቀረቡ

3. ኮን/ል ሐብታሙ መኮንን ኩምሣ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት በማጽናታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡

አመልካቾች የተከሰሱት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ለ/ እና 540 የተመለተውን በመተላለፍ በቀን 09/05/99 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ላይ በሻክሶ ወረዳ ቀንጢቻ ቀበሌ በታንታለም ፋብሪካ አጠገብ ሰው በመሞቱ ምክንያት ተሰብስቦ ካለው ሕዝብ ውስጥ አንደኛው ተጠሪ ሚች ጴጥሮስ ቦሩን ጉኑ ላይ መትቶ በመግደሉ፣ሁለተኛው ተጠሪ ሚች በደሳ ሚጣ ከለቻን መትቶ በመግደሉ ሦስተኛው ተጠሪ ሚች በቀለ ጂሎና ዱከሌ ደረስ ላይ ተኩሶ በመግደሉ እንዲሁም ሁለተኛ ክስ በሦስተኛው ተጠሪ ላይ የወንጀል ሕግ ቁጥር 27/1/ እና 540 በመተላለፍ በአንደኛው ክስ በተገለፀው ቦታና እና ቀን በብዛት ቆመው ባሉት ህዝብ ላይ ደግሞ ተኩሶ ተበዳይ ጂሎ ጡኔን እግሩን፣ዲጉ ገናሌን፣እያሱ ደደቻን ግራ እጅ እና ዋጨሎ ሙደን በጥይት መትቷቸው የግድያ መከራ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የጉጂ ዞን ዓ/ሕግ ክስ መስርቶባቸዋል፡፡

አመልካቾች ጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርበው ወንጀል አለመፈፀማቸውን ክደው ተከራክረዋል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ በተከሰሱበት የወንጀል አንቀጽ ጥፋተኛ ናቸው ካለ በኋላ አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾች በ15 (አስራ አምስት ዓመት) ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሦስተኛው አመልካች በአንቀጽ 540 በሁለት ድርጊት ጥፋተኛ ነው በሚል በሃያ ዓመት (20) ጽኑ እስራት እንዲቀጣ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፈርዷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ስሕተት የለውም በሚል አጽንተዋል፡፡

አመልካቾች በፌ/ፖ/ኮ/ሕግ አገልግሎት ነ/ፈጅ በኩል ሚያዝያ 5 ቀን 2001 ዓ.ም የተሻሻለ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ችግሩ በተፈጠረበት ቦታ ቁጥራቸው ከ300 በላይ የሚሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ክላሽ ጠመንጃ፣ጦርና ገጀራ በመያዝ ቃንጥቻ የሚገኘውን የታንታለም ማምረቻ ፋብሪካን ለመዝረፍ ሲንቀሳቀሱ በተፈጠረ ግጭት ከሕዝቡ በተተኮሰ ጥይት የፖሊስ አባላትም የቆሰሉ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ አመልካቾችን ጥፋተኛ ማድረጉ የግራ ቀኙን ማስረጃ በአግባቡ ሳያገናዝብ ነው በሚል የሥር ፍ/ቤት ፍርድ ተሽሮ አመልካቾች በነፃ እንዲሰናበቱ አመልክቷል፡፡

የሰበር ችሎትም አመልካቾች ድርጊቱን ፈጽሟል ቢባል እንኳ ጥፋተኛ የመባላቸውን አግባብነት ከወንጀል ሕጉ መርህ እና ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር ሲል ዓ/ሕግ መልስ እንዲሰጥ አዟል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ በ28/12/2001 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካቾች የተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸማቸው ከጥርጣሬ ውጪ የተመሰከረባቸው ስለሆነ በሥር ፍ/ቤት የተወሰነው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ እንዲፀና በማለት አመልክቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና የሥር መዝገብ ውሳኔ ይዘት ከመረመረ በኋላ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ምላሽ የሚያሻው የሕግ ጥያቄ ሆኖ ያገኘው አመልካቾች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወ/ሕ/ድንጋጌ አንቀጽ 540 ወይንስ 541 የሚለውን ነው፡፡ ይህንኑ ለመፍታት የጉዳዩን አፈፃፀም እና መነሻ ሁኔታዎች በአጭሩ መመለከት ተገቢ ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ፍሬ ነገር ወንጀሉ ተፈፀመ ከተባለበት ቀን አስቀድሞ ሌሊቱን በታንታለም ፋብሪካ አጠገብ አንድ ሰው ተገድሎ የነበረ ስለመሆኑ፣ይህንንም መነሻ በማድረግ የአካባቢው ሕዝብ እዚያው ፋብሪካ አጠገብ የተሰበሰበ ስለመሆኑ፣የተሰበሰበው ሕዝብ ክላሽ፣ገጀራና ጦር ይዞ የነበረ ስለመሆኑ እና የታንታለም ፋብሪካ ሰራተኞችም ወደ ሥራ እንዳይገቡ እንዳይወጡ በዚሁ በተሰበሰበው ሕዝብ ሁከት የተፈጠረ ስለመሆኑ ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች እና ሌሎች ባልደረቦቻቸው ወደ ቦታው የተንቀሳቀሱት ይህንኑ የፋብሪካው ሥራ መስተጓጎልና ሌላ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል እንዲቻል ስለመሆኑም በምስክሮች ተነግሯል፡፡

አመልካቾች እና ባልደረቦቻቸው በቦታው ሲደርሱ እነሱን በያዘው መኪና እና አባሎቻቸው ላይም ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑም ተመስክሯል፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች የተከሰሱበትን ወንጀል ስለመፈጸማቸውም በሥር ፍ/ቤት በቀረቡት ማስረጃዎች የተመሰከረ ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ እንግዲህ አጠቃላይ የወንጀሉ አፈፃፀም ሁኔታ ይህንን የሚመስል ሲሆን አመልካቾች ወንጀሉን አልፈጸምንም በማለት እዚህም ፍ/ቤት ዘንድ አጥብቀው የተከራከሩ ቢሆንም ስለወንጀሉ አፈፃፀም እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን የሚታይ ባለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር እንዳለ በመቀበል በሕግ ረገድ የሚኖረውን ውጤት ብቻ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካቾች የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት የፈፀሙት በታንታለም ፋብሪካ ላይ የተቃጣን አደጋ ለመከላከል እንደሆነ ከፍ ሲል የተመለከተው ፍሬ ነገር እና ከወንጀሉ አፈፃፀም ከባቢያዊ ሁኔታ መረዳት ይቻላል፡፡

ድርጊቱ ወንጀል ነው ቢባልም በሕግ በተመለከተ ልዩ ሁኔታ በሕግ በተፈቀዱ ድርጊቶች የማያስቀጡት እና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተመለከተውን ድንጋጌ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ማየት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለተያዘው ጉዳይ ቀጥታና አግባብነት ያለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 78”ን” እንመለከታለን፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሰረት የራሱን ወይም የሌላውን ሰው መብት ሕገወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ሕገ-ወጥ ጥቃት ለማዳን ጥቃቱ እንዳይደርስ ለማድረግ ሌላ መንገድ ሳይኖር ከሁኔታው መጠን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለማለፍ የተፈፀመ ድርጊት አያስቀጣም ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተከሳሹ ከቅጣት ነፃ የሚሆነው ሕገ-ወጥ ጥቃት በራሱ ወይም በሌላው ሰው መብት ላይ የተሰነዘረ ወይም በእርግጠኛነት ሊደርስ የሚችል ጥቃት ስለመኖሩ፣ይህንንም ለማስወገድ ወይም ለመከላከል ሌላ አማራጭ የሌለው ስለመሆኑ እና የወሰደው የመከላከል ወይም ጥቃቱን የማስወገድ እርምጃ ከተሰነዘረው ጥቃት ጋር ተመጣጣኝ ኃይል የተጠቀመ መሆኑን ማስረዳት ሲችል ብቻ ነው፡፡ ይህንኑ የሕጉን መንፈስ እና ይዘት መሰረት አድረገን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት በአመልካቾች በኩል የቀረበው ፍሬ ነገር በታንታለም ፋብሪካ አካባቢ የተሰበሰበው ሕዝብ የፋብሪካውን ሥራ ስለማወኩ፣ ሕዝቡም የተለያዩ መሣሪያዎችን ያየዘ ስለመሆኑ፣ አመልካቾች ፀጥታ ለማስከበር ያደረጉትን ጥረት በፀጥታው ሃይል አባላት እና ንብረት ላይ ጥቃት የተሰነዘረ ስለመሆኑ እና በፋብሪካውም ላይ አደጋ ሊሰነዘር የተቃጣ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ ፍሬ ነገር የሚያስገነዝበን በፋብሪካውም ሆነ በፀጥታ አስከባሪዎች ላይ የተቃጣ ሕገ-ወጥ ጥቃት ስለመኖሩ ነው ይህንን ጥቃት ለማስወገድ አመልካቾች ተኩሰው ሰው መግደላቸው እና ማቁሰላቸው ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ተከትሎ የሚነሳው ጥያቄ አመልካቾች የተሰነዘረውን ጥቃት ለማስወገድ ሌላ አማራጭ ያልነበራቸው ስለመሆኑ እና የወሰዱት አማራጭም ተመጣጣኝ ስለመሆኑ አስረድተዋል ወይ? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ያስረዱት ፍሬ ነገር የለም፡፡ አመልካቾች ሕገ-ወጥ ጥቃትን ለማስወገድ እርምጃ ስለመውሰዳቸው የተመለከተ ቢሆንም እርምጃው ሌላውን አማራጭ ያሟጠጠ ስለመሆኑ እና ተመጣጣኝ ስለመሆኑ ለማስረዳት ያልቻሉ ስለሆነ በወ/ሕ አንቀጽ 78 የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት አሟልተዋል ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለዚህም ድርጊታቸው ሕገወጥ ጥቃትን ለማስወገድ ነው የሚያስብል መነሻ ቢኖረውም የፈፀሙት የነፍስ ግድያ ወንጀል በሕጉ ከተመለከተው መጠን በማሳለፍ መሆኑን መገንዘብ ችለናል፡፡

ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ደግሞ ከቅጣት ነፃ የማያደርግ ስለመሆኑ የወ/ሕ ድንጋጌ ቁጥር 79/1/ ያመለክታል፡፡ ይልቁንም ይህ አድራጐት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስለመሆኑ ይህ ድንጋጌ ቁጥር 79/1/ ይገልፃል፡፡ ይህንን መሰረታዊ ጉዳይ ከተረዳን የአመልካቾች ድርጊት ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚገባው በየትኛው የወ/ሕጉ ድንጋጌ ነው? የሚለውን መሰረታዊ ጭብጥ ወደ ማየት ስንመለስ የአመልካቾች ድርጊት ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን ማሳለፍ መሆኑ መሰረት በማድረግ የወ/ሕጉ ልዩ ክፍል በዚህ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆን ድንጋጌ እንዳለው እንረዳለን፡፡ ይኸውም በወ/ሕጉ አንቀጽ 541/ሀ/ ሥር ከተመለከቱት የድንጋጌው ማቋቋም ምክንያቶች አንዱ ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የነፍስ ግድያ ወንጀል እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው የወ/ሕጉ አንቀጽ 79/1/ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አድርጐ በገለፀው አኳኋን አንቀጽ 541/ሀ/ ሁለተኛው ሐረግ ደግሞ ወንጀሉን ለማቋቋም እንደሚችል ደንግጓል፡፡

እንዲህ ያለ ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ ደግሞ በወ/ሕጉ አንቀጽ 82/2/ እንደተደነገገው ድርጊቱን ለማቋቋም የተደነገገው ልዩ ክፍል ተፈፃሚነት ይኖርዋል፡፡ ይህንን ለማለት የወ/ሕጉን ድንጋጌ ቁጥር 82/2/ እና 84/2/ ይዘት እና አቀራረጽ አገናዝቦ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ስለሆነም አመልካቾች የፈፀሙት የወንጀል ድርጊት የወ/ሕጉን አንቀጽ 540 የሚያቋቁም ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ የድርጊቱን አፈፃፀም ከባቢያዊ ሁኔታ እና ምክንያት በአግባቡ ባለማገናዘብ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን መረዳት ችለናል፡፡

ስለሆነም አመልካቾች የፈፀመት የወንጀል ድርጊት ሊደርስ ይችል የነበረን ሕገ-ወጥ ጥቃት ለማስወገድ እና ለመከላከል መሆኑን ነገር ግን አፈፃፀማቸው ሲታይ ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ በመሆኑ የወ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 541/ሀ/ ያቋቁማል ብለናል፡፡

ስለዚህም በአንደኛው ክስ አንደኛ፣ሁለተኛ እና ሦስተኛ አመልካቾችን በወ/ሕ ቁጥር 32/1/ (ሀ)ና(ለ) እና 540 ሥር እንዲሁም በሁለተኛው ክስ ሦስተኛ አመልካችን በወ/ሕግ ቁጥር 27/1/ እና 540 ሥር ጥፋተኛ መባላቸው አግባብ ሆኖ ስላላገኘው ሕጉን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2/ መሰረት ለውጠን በአንደኛው ክስ ሦስቱም አመልካቾች በወ/ሕግ ቁጥር 32/1/ (ሀ)ና(ለ) እና 541/ሀ/ ሥር እንዲሁም በሁለተኛው ክስ ሦስተኛ አመልካች በወ/ሕግ ቁጥር 27/1/ እና 541/ሀ/ ሥር ጥፋተኞች ናቸው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅጣትን በተመለከተ አመልካቾች በዚህ ፍ/ቤት ጥፋተኛ የተባሉበት አንቀጽ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እንደሚያስቀጣ ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ በመሰረቱ ቀላል እስራት በመደቡ የሚጣለው ከአሥር ቀን እስከ ሦስት ዓመት የሚደርስ ስለመሆኑ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106/1/ ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ቀላል እስራት ቅጣት ከዚህ መደብ ጣሪያ ከፍ ብሎ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችለው በዚሁ አንቀጽ ሥር የተመለከቱት ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ስለመሆኑም ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ በማገናዘብ አመልካቾች ላይ ሊፈፀም የሚገባውን ቅጣት እንደሚከተለው ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02204 ታህሣሥ 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ፣የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 60135 መጋቢት 19/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 64351 ነሐሴ 20/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት ሻሽለናል፡፡
2. በዚሁ መሰረት በአንደኛው ክስ አንደኛ፣ሁለተኛ፣እና ሦስተኛ አመልካቾች በወ/ሕግ አንቀጽ 32/1/ (ሀ)ና(ለ) እና 541/ሀ/ ድንጋጌ በሁለተኛው ክስ ሦስተኛ አመልካች በወ/ሕግ አንቀጽ 27/1/ እና 541/ሀ/ ድንጋጌ በመተላለፍ ጥፋተኞች ናቸው ብለን ወስነናል፡፡
3. አንደኛ እና ሁለተኛ አመልካቾች በዚህ ጉዳይ እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በሦስት(3)ዓመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ ብለናል፡፡ ሦስተኛው አመልካች በሁለት ቀላል ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በአምስት (5) ዓመት ቀላል እስራት እንዲቀጣ ብለናል፡፡
4. የጥፋተኝነት አንቀጽ እና ቅጣቱ የተሻሻለ መሆኑን እንዲያውቅ የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ግልባጭ ለጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ማረሚያ ቤቱ በዚህ ችሎት በተሻሻለው ቅጣት መሰረት እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
6. የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ ቁጥር 02204 በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44235

መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ቂስ ጌታቸው ተሾመ

ተጠሪ፡- ዓቃቤ ሕግ

ፍ ር ድ

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ሁለት የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ተብለው በሁለት አመትና በ300.00 ብር እንዲቀጡ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት በሚል ይህን የሰበር አቤቱታ ሊያቀርቡ ችለዋል፡፡

በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቃቤ ሕግ ባቀረበባቸው አንደኛ ክስ የወንጀል ሕግ ቁጥር 543/1/"ን" በመተላለፍ የካቲት 29 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ 5 ሰዓት ድርጊቱ ሞትን ሊያስከትል እንደሚችል ማሰብ ሲገባው ባለመጠንቀቅ የቡዳ መድሃኒት ነው ብሎ ቅጠላቅጠል አጪሶ በማጠንና ማረሻ አግሎ ከፊቷ ላይ በመተኮስ ሟችን የገደለ በመሆኑ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሷል፣እንዲሁም በሁለተኛ ክስ ጉጂነቱ ጉዳቱ በተረጋገጠ ልማዳዊ ድርጊት የቡዳ መድሃኒት ነው ብሎ ቅጠላ ቅጠል አጪሶ በማጠን ማረሻ አግሎ ፊትዋን በተመተኮስ ለሞት ያበቃት በመሆኑ በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል በማለት ክስ መስርቶባቸዋል፡፡ አመልካች ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለታቸው አቃቤ ሕግ ሶስት የሰው ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እንደክስ አቀራረቡ አስረድተዋል በማለት አመልካች ክሱን እንዲከላከሉ በማለቱ አመልካች ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት እለት ሟች ቤት ያልነበሩ ስለመሆናቸው ይመሰክሩልናል ያሏቸውን ሁለት ምስክሮች አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካች ምስክሮች ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭና የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ያስረዱትን ለማስተባበል ያልቻለ ነው በማለት በሁለቱም ክሶች አመልካችን ጥፋተኛ በማለት በአንደኛው ክስ ሁለት አመት ቀላል እስራት በሁለተኛው ክስ 300.00(ሶስት መቶ ብር) እዲቀጡ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ይግባኙ ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታም አቅርበው ችሎቱ በአብላጫ ድምጽ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታቸው ጥፋቱን ለመፈፀማቸው ከጥርጣሬ በላይ የተረጋገጠባቸው መሆኑን፣ሟች ቀድሞውኑ ታማ ስለነበር ለሞቷ ምክንያት የሆነው የያዛት ህመም መሆኑን፣ባትታመም ኖሮ ቅጠሉ ወይም ማረሻው ጉዳት ያደርስ እንደሆነ እንጂ ለሞት የማያበቃት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን፣ቅጠሉ ሰው ገዳይ ለመሆኑ በህክምና አለመረጋገጡን እንዲሁ በተደራራቢ ክስ መከሰሳቸው አግባብ አለመሆኑን በመዘርዝር የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔው እንዲሻር ይህ የሚታለፍ ከሆነ ደግሞ በወ/ሕ/ቁ. 567 ብቻ ተጠያቂ እንዲሆኑ ጠይቀዋል፡፡ ይህ ችሎት አመልካች በወ/ሕ/ቁ. 543 እና 567 መሰረት መከሰሳቸው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች የተከሰሱት በቸልተኛነት ሰው ገድለዋል እንዲሁም በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት አድርሰዋል በማለት በሁለት የወንጀል ድርጊቶች ነው፡፡ አመልካችም በሁለት ተደራራቢ ወንጀሎች ልጠየቅ አይገባም በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪም በቃል ክርክር ወቅት አመልካች በተደራራቢ ወንጀሎት መከሰሳቸው አግባብ አልነበረም በማለት ገልጿል፡፡ ችሎቱም ተፈፀመ ከተባለው ድርጊት አኳያ አመልካች በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል ወይ የሚለው ጭብጥ መርምሯል፡፡ አመልካች በሁለቱም ክሶች ፈፀሙ የተባለው ሚችን የቡዳ መድሃኒት ነው ብለው ቅጠላ ቅጠል አጭሰው በማጠንና ማረሻ አግለው ፊትዋን በመተኮስ ለሞት ዳርገዋታል በማለት ነው፡፡ አመልካች በክሱ የተገለፀውን ድርጊት መፈፀማቸው ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ፈጽመዋል የተባለው ይኸው ድርጊትም በግል ተበዳዩዋ ላይ ጉዳት ማድረስ ብቻ ሳይሆን ሞትን በማስከተሉ ሁለት ክስ መቅረቡን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ ሃሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ሲሆኑ አድራጊው በተመሳሳይ ባህሪ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች እንደማይቀጣ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61/1/ ያመለክታል፡፡ አመልካች መፈፀማቸው የተረጋገጠው የቡዳ መድሃኒት ነው በሚል ቅጠላ ቅጠል አጭሶ በማጠንና ማረሻ አግሎ በመተኮስ የግል ተበዳይ ድርጊቱ ከተፈፀመ ከአንድ ሰአት በኋላ እንድትሞት ማድረጋቸው ነው፡፡ አመልካች በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት ያደረሱና ጉዳቱም ሞትን ያስከተለ ቢሆንም ወንጀሉን የፈፀሙት በአንድ ቸልተኛነት ድርጊት በመሆኑ በተደራራቢ ቅጣት ሊቀጡ አይገባም፡፡ በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 567 እንደተመለከተው ማንም ሰው ኢሰብአዊነቱ በታወቀና ጭፍነቱ በህክምና ሙያ በተረጋገጠ በልማዳዊ ድርጊት አማካኝነት በሌላ ሰው ላይ አካል ወይም አእምሮ ጉዳት ወይም ሞት እንዲደርስ ያደረገ ከሆነ በወንጀል ይቀጣል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን አመልካች የፈጸሙት ጭጂ ልማዳዊ ድርጊት ሞትን ያስከተለ ቢሆንም ድርጊቶቹ በሙሉ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር የሚሸፈን በመሆኑ አመልካች በቸልተኛነት ሰው በመግደል የወንጀል ድርጊት ሊቀጡ የሚገባበት የሕግ መሰረት የለውም፡፡ በመሆኑም አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 ጥፋተኛ መባላቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡

በሌላ በኩል ግን የተፈፀመው ልማዳዊ ድርጊት ሞትን ያስከተለ ከሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በአንቀጽ 561 ወይም 562 ከተመለከቱት ቅጣቶች አንዱ ተፈፃሚ እንደሚሆን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 567 ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት ወንጀል ሕጉን 561/2/ ስንመለከት የሞት አደጋ የተከሰተው በቸልተኛነት የሆነ እንደሆነ አንቀጽ 543 ተፈፃሚ ሊሆን እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት አምልካች ከስድስት ወር እስከ ሶስት አመት ቀላል እስራት ወይም ከሁለት ሺህ ብር እስከ አራት ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ሊቀጡ እንደሚችሉ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/1/ ያስገነዝበናል፡፡ አመልካች ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው በሕመም ላይ ያለን ሰው ቅጠል አጭሰው በማጠንና ማረሻ አግለው በመተኮስ ለሞት መዳረጋቸው ሲታይ ድርጊቱ አስከፊ መሆኑንና በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቹ ያልተማሩና የ9 ቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆናቸው ቅጣቱን ሊያቀል የሚችል መሆኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት የስር ፍ/ቤት አመልካችን በሁለት አመት ቀላል አስራት እንዲቀጡ የሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሰሜሽ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 19090 ግንቦት 19 ቀን 2000 ቀን ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 6880 መስከረም 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 00683 ታህሣስ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በድምጽ ብልጫ የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 ጥፋተኛ ናቸው ተብሎ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች የወንጀል ሕግ ቁጥር 567"ን" በመተላለፍ በፈፀሙት በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት ማድረስ ወንጀል የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ አመልካች በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ ስለተባሉ በሁለት አመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ የተሰጠውም የቅጣት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ድርጊት የሚያስቀጣው በቀላል እስራት ወይም በአማራጭ በገንዘብ መቀጮ በመሆኑ አመልካች ብር 300.00 እንዲቀጡ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

የሰ/መ/ቁ. 46189

ሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ኒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ዓብዱራሂም አህመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሐረገወይን ተፈራ - ጠበቃ ጥበቡ ምህረቱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ ወርቁ ገመቹ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ሲሆን አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በጠበቃቸው አማካኝነት ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ጥቅምት 25 በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ፣ ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች እንዲሁም አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች የተከሰሱት፡- በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/መ/ሕ/ቁ. 32(1(ሀ) እና (ለ)) እና 692/1/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የማይገባቸውን ብልጽግና ለማግኘት አስቀድሞ በማሰብ ክሱ በስር ፍርድ ቤት ከተቋረጠው ከአቶ ዘላለም ተስፋዬን የሰሊጥ ነጋዴና አቅራቢ በማስመሰል ለግል ተበዳይ ሽቶ በቀለ ካስተዋወቀች በኋላ የግል ተበዳይን በማሳመን ወደ ተሳሳተ እምነት በመምራት ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 5፡30 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ከኢምፔሪያል ሆቴል በስተጀርባ ከሚገኘው የግል ተበዳይ ድርጅት በሆነው ፐርፍ ኢንተርናሽናል ትራዲንግ ግቢ ውስጥ ክስ የተቋረጠበት ግለሰብ ለድርጅቱ ብዛቱ 6000(ስድስት ሺህ) ኩንታል ሰሊጥ በብር 3,618,000(ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ብር) ለማቅረብ ከተነጋገሩ በኋላ የቅድሚያ ክፍያ ያስፈልገኛል በማለት በእለቱ ብር 500,000(አምስት መቶ ሺህ) የያዘ ቼክ በመቀበል እንዲሁም ግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም ብር 50,000(አምሳ ሺህ ብር) ጎንደር ከሚገኘው የአቢሲኒያ ባንክ እንዲቀበል በአቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው በቀለ ስም ተልኮለት በአጠቃላይ ብር 550,000(አምስት መቶ አምሳ ሺህ ብር) ወጪ አድርጐ ከወሰደ በኋላ ገንዘቡን ይዞ በመሰወሩ ሁለቱም የማታለል ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካች በክሱ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ የድርጊት አፈፃፀሙን በመካዳቸው አቃቤ ሕጉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ለማስረጃነት አቅርቦ አመልካች ክሱን እንዲከላከሉ ተደርጐ የወንጀሉ ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜና ቦታ ተገኝተው በሰሊጥ ውሉ ላይ በእማኝነት መፈረማቸውን በጭብጥነት አሲይዘው የሰነድና የሰው ማስረጃዎችን አቅርበዋል፣ አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካችን በመከላከያ ማስረጃ በሰሊጥ ውሉ ላይ በእማኝነት ስለመፈረማቸው እና የግል ተበዳይም በአቶ ዘላለም ተስፋዬ የፍትሐብሔር ክስ አቅርበው ገንዘቡ እንዲመለስላቸው ማስፈረዳቸው ቢረጋገጥም የግል ተበዳይን ወደ ስህተት እንዲመሩ አላደረጉም ለማለት የሚያስችል አይደለም በማለት በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቀሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጐ በአንድ ዓመት ቀላል አስራት እንዲቀጡ እና የቅጣቱ አፈፃፀም በሦስት አመት ገደብ እንዲሆን ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአመልካች በዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር በአመልካች በኩል የተፈፀመው ድርጊት የማታለል ወንጀልን የሚያቋቁም አይደለም በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በአንፃሩ ድርጊቱ የማታለል ወንጀልን የሚያቋቁም ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ይህ ችሎትም በአመልካች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ የማታለል ወንጀልን ያቋቁማል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692/1/ መሰረት ተጠያቂ የሚሆነው የማይገባ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታልሎ የራሱን ወይም የሦስትኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጐዳ አድራጐት እንዲፈፀም ያደረገ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ እንግዲህ አንድ ሰው የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2/ ስር እንደተመለከተው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ፈፀሙ የተባለው ክሱ የተቋረጠውን አቶ ዘላለም ተስፋዬን የሰሊጥ ነጋዴና አቅራቢ በማስመሰል ለግል ተበዳይ ለአቶ ሽቶ በቀለ አስተዋውቀው የግል ተበዳይ ገንዘብ ላይ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አቶ ዘላለም ተስፋዬ የሰሊጥ ነጋዴ አለመሆናቸው ካለመረጋገጡም በላይ አመልካች ይህንኑ እያወቁ ለግል ተበዳይ የተሳሳተ ነገር እውነት አስመስለው የተናገሩበት ሁኔታ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም አቃቤ ሕጉ የሰሊጥ ነጋዴ ሳይሆኑ ነጋዴ ናቸው የተባሉትን ግለሰብ በተመለከተ ክሱን ያቋረጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የግል ተበዳይም ከአቶ ዘላለም ተስፋዬ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ፍትሐብሔራዊ የነበረ ስለመሆኑ ተረጋግጦ በፍትሐብሔር ችሎት ውሳኔ ተሰጥቶ ገንዘባቸው እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየው አመልካች የማታለል ተግባር አለመፈፀማቸውን ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች ተግባር የማታለል ተግባርን የሚያቋቁም ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 23/2/ እና 692/1/"ን" ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 54121 ጥቅምት 25 እና ኅዳር 04 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 42198 የካቲት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ተግባር የማታለል ወንጀልን የሚያቋቁም አይደለም ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 53612

ሚያዝያ 25 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ኂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1ኛ. አቶ ፍሰሐ ዓባይ

2ኛ. ወ/ሪት ህይወት የሰራው ጠበቃ አቶ ሰለሞን ደምሴ

ተጠሪ፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ዓ/ሕግ አቶ ገ/እግዛብሔር መኖናቸው ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ የቻለው በአመልካቾች ላይ በቀረበው የወንጀል ክስ ጉዳይ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች ጉዳዩ ሲታይ ቆይቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ አመልካቾች ቅር ተሰኝተው የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩም አመጣጥ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡ የገቢዎችና ጉምሩክ አቃቤ ሕግ በአልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ አመልካቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እና እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ እና መ/ለ/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ፈጽመዋል፡፡ የሚል ሲሆን፣ አመልካቾች ይህንኑ የወንጀል ድርጊት አልፈፀምንም በማለት ክደው በመከራከራቸው ክርክር ቀጥሎ ሁለቱም ወገኖች በየፊናቸው ማስረጃ አቅርበው አሰምተዋል፡፡

የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በከ/መ/ቁ. 144285 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ሁለተኛ አመልካች ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ስለመፈጸሟ የተረጋገጠ ሲሆን፤አንደኛ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ድርጅቱ ላለቤት እንደመሆናቸው ግብይት ያለደረሰኝ እንዳይከናወን አስፈላጊውን ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው በሰራተኛ ለተፈፀመው ድርጊት ኃላፊነት አለባቸው በማለት በሁለቱም ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በቅጣት ረገድም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ካገናዘበ በኋላ 1ኛ ተከሳሽ በብር 20,000.00(ሃያ ሺ. ብር) እና በ1(አንድ) ዓመት እስራት ሁለተኛ አመልካች በብር 10,000.00 (መቶ ሺ.) ብር እና በ1(አንድ) ዓመት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

በዚህ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አመልካቾች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ተመልክቶ የአሁን አንደኛ አመልካች በተፈፀመው ድርጊት ቀጥተኛ ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ በነፃ ይሰናበታል በማለት ሲወስን፤ከጠቅላይ ፍ/ቤት የውሳኔ ግልባጭ ላይ መረዳት፣ እንደሚቻለው የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የእስራት ቅጣት አንሷል በማለት አቅርቦት የነበረው የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ በጥፋተኝነትም ሆነ በቅጣት ረገድ በሰጠው ውሳኔ የገቢዎችና ጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ ሁለተኛ የይግባኝ አቤቱታ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረቡ፤የጠቅላይ የፍ/ቤቱ ሁለቱም ወገኖች ክርክር ካዳመጠ በኋላ በወ/ይ/መ/ቁ. 51336 የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በጥፋተኝነት ውሳኔ አሰጣጥ በኩል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአንደኛ አመልካች ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ከፀና በኋላ በቅጣት አጣጣል ረገድ አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉበት ድንጋጌ ሥር ከተመለከተው ዝቅተኛ የቅጣት መነሻ በታች ለመውረድ የሚያበቃ ህጋዊ ምክንያት አልተገኘም በማለት የገንዘብ መቀጮውን ሳይነካ ሁለቱም አመልካቾች እያንዳንዳቸው በሁለት ዓመት እስራት እንዲቀጡ በማሻሻል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ዝርዝር ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ለዚህም የሰበር ቅሬታ ተጠሪ የገቢዎችና ጉምሩክ አቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጐ በሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1ኛ. አመልካች ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ተፈጽሟል በተባለበት ጊዜ በተፈፀመው አድራጐት ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአንደኛ አመልካች የጥፋተኝነት መሰረት ሆኖ የተያዘው በአድራጐቱ የተነሣ ለፈፀመው ጥፋት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እንደተመለከተው ድርጅቱ አዋጁን በመተላለፉ ስለፈፀመው ጥፋት ተተክቶ ተጠያቂ ሊሆን በመቻሉ ነው በዚህ መሰረት ከተጠያቂነት ለመዳን የሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/3/ የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ በጠቅላይ ፍ/ቤት የውሳኔ ሐተታ እንደተመለከተው ይህ ስለመሆኑ አንደኛ አመልካች ሕጉ የጣለበትን ግምት ለማስተባበል የሚያስችል የመከላከያ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 56/1/ “...አንድ ድርጅት....“ የሚለውን አባባል ከአንቀጽ 56/4/ ድንጋጌ ሥራ አስኪያጅ የሚለው አባባል ለየትኞቹ ድርጅት የሚለውን ጥያቄ ሊያስነሳ እንደሚችል የተረዳን ቢሆንም በአዋጁ መግቢያ “ትርጓሜ” ለሚለው አንቀጽ 2/5/ እና 2/11/ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ድርጅት ማለት በሽርክና ማህበር በኩባንያ እና በሰዎች ህብረት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ አይታይም፡፡

ሁለተኛ አመልካችንም ቢሆን ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ቦታ ተገኝታ ከፈፀመችው ካደረገችው እና ከተናገረችው አድራጐት አንፃር በድርጊቱ አፈፃፀም ቀጥተኛ ተሳትፎ ስለመሆኑ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔን አስመልክቶ የተሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል የጠቅላይ ፍ/ቤት በተጠሪ ይግባኝ መነሻ በአመልካቾች ላይ ተጥሎ የነበረውን የአንድ ዓመት እስራት ወደ ሁለት ዓመት እስራት ለውጦ በማሻሻል ሊወሰን የቻለው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 82/1//ሀ/ ከተመለከተው ዝርዝር የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አንዱ የሆነው የጥፋተኛው የዘወትር ጠባይ መልካም መሆን ብቻውን እንደ ቅጣት ማቅለያ ሊወሰድ አይችልም፡፡ የዘወትር ጠባዩ መልካም መሆን ብቻ ሳይሆን ያጠፋውም በእውቀት ማነስ፣ባለማወቅ፣በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ እንደሆነ ጭምር መሆን ይገባዋል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ የዘወትር ጠባይኑና የአፈፃፀሙን ሁኔታም "እና" በሚለው ምፃሃረ ቃል መያያዙ ሁለቱም ሁኔታዎች ድርብ የቅጣት ማቅለያ ማሟያ ምክንያቶች መሆናቸውን አመልካች ነው የሚለውን በመያዝ እንደሆነ ከመዝገቡ ግልባጭ ተረድተናል፡፡

ይሁን እንጂ ቅጣትን የማቅለልና ለቅጣት ነፃ የማድረግ ደንብን አስመልክቶ በተመለተው የሕግ ክፍል በወ/ሕ/ቁ. 179 ላይ "ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሰረት ቅጣትን ለማቅለል እንደሚችል በሕግ በተደነገገ ጊዜ ሁሉ……" ለሚለው አነጋገር "በሕግ በተደነገገ ጊዜ ሁሉ…." የሚለው ሐረግ ስለቅጣት ማቅለል በወ/ሕ/ቁ. 82/1/ሀ/ የተመለከተው ድንጋጌ ብቻ ሳይሆን ከቅጣት አወሳሰን ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስለቅጣት አጣጣል አግባብነትና ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር አጣቅሶ ማየት እንደሚያስፈልግ አመላካች ነው፡፡

ከዚህም አኳያ በወ/ሕግ ቁጥር 88/2/ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ያለፈ የሕይወት ታሪክ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነ መደንገጉ አንድ አጥፊ ወንጀሉን እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የዘወትር ጠባዩ መልካም የነበረ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ለቅጣት ማቅለያነት የማይወሰድበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ይህም ሁሉ ታልፎ በወንጀል ሕግ ቁጥር 82/1/ሀ/ የተመለከተው የቅጣት ማቅለያ ወጥነት ያለው የተጣመረ ምክንያት ነው እንኳ ቢባል በሥር ፍ/ቤቶች የቅጣትን አስተያየት አስመልክቶ በግራ ቀኙ በየደረጃው ከተደረጉት ክርክሮች፣ ከድርጊቱ አፈፃፀም ወንጀሉን ላቋቋመው ድንጋጌ ወይም ሕግ ጋር ሁሉ ተገናዝቦ ሲታይ በዚህ አከራካሪ በሆነው ድንጋጌ "እና" ከሚለው ቀጥሎ ካሉት ወይም በሚል ምሕጻረ ቃል ከተያያዙት አንዱን ምክንያት ቢሆን እንኳ አመልካቾች አላሟሉም ማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም የተነሣ ቅጣቱ በመደበኛ የቅጣት ማቅለያ ደንብ መሰረት ማውረድ አይገባም የሚለውን ታሳቢ በማድረግ አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉት ድንጋጌ ሥር የተመለከተውን መነሻ የሁለት ዓመት እስራት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መጣሉ/መወሰኑ የቅጣት አጣጣል ሥርአትን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሳ ኔ

1. በቅጣት አወሳሰን ረገድ ላይ ብቻ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 51336 የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡ በዚህ ረገድ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 144285 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የጣለው ቅጣት ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾች በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ እንደተገለፀው አንደኛ አመልካች በብር 20,000.00(ሃያ ሺህ ብር) እና በአንድ ዓመት፣ሁለተኛ አመልካች በብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) እና በአንድ ዓመት እስራት ይቀጣሉ በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት አሻሽለን ወስነናል፡፡ ለፌዴራል ማ/ቤቶች ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41248

ሰኔ 23 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ቡርቂሶ ዋቆ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ዓቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በጋሞ አካባቢ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ክሱ አመልካች በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1/ እና 540 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ መጋቢት 09 ቀን 1997 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ሲሆን የግል ተበዳይ ሳራ ሳንቃ የተባለ ሰው ለመግደል ሞክሯል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌለ መሆኑን ገልጾ የወንጀል ድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን የክህደት ቃል ሰጥቷል፡፡ አቃቤ ሕግ በበኩሉ እንደክሱ የሚያስረዱለት የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ያሉት መሆኑን ገልፆ የግል ማስረጃዎቹን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች እንዲከላከል ተደርጉ የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን በማረጋገጡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት አመልካች በመከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ለማስተባበል ያልቻለ መሆኑን ገልፆ አመልካችን በአቃቤ ሕጉ በኩል ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጉ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኝን አስተያየት በመቀበል እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ አመልካች ቀድሞ የወንጀል ሪኮርድ ያለበት መሆኑን አረጋግጦ በአስራ ስምንት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው የጥፋተኛነትና እና የቅጣት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጸሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ አቃቤ ሕግ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ ባላስረዳበት ሁኔታ በሐሰተኛ ማስረጃዎች ጥፋተኛ መባሌ ያላግባብ ነው፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም ከብዶ የተወሰነው ከወ/መ/ሕ/አንቀጽ 230 ድንጋጌ ውጪ ነው በማለት ዘርዝሮ ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ፈጸመ የተባለው የወንጀል ተግባር አንዳችም ውጤት ያላመጣ ከመሆኑ እንፃር እና አመልካች በምህረት የተለቀቀበትን ምክንያት የስር ፍርድ ቤት እንደ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት አድርጐ በመውሰድ የአስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ ሰኔ 03 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች የወንጀል ድርጊቱን አለመፈጸሙን ገልጾ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ ማስረጃ አቅርቦ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን በሚገባ አኳኋን ማረጋገጡን የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታም ከግል ተበዳይ ጋር በእለቱ ከመገፋታተር ወጪ ሌላ ድርጊት የፈጸመ ስለመሆኑ አልተመሰከረም በማለት የሚከራከር ሲሆን ይህንኑ መከራከሪያ ነጥብ የሚያስረዳ መከላከያ ማስረጃ ግን በስር ፍርድ ቤት አላቀረበም፡፡ በመሆኑንም አመልካች ስለድርጊቱ አፈፃፀም በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌ መሰረት ያለው ሥልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም እንጂ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት ጉዳይ የማጣራት ስልጣን ካለመሆኑ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሌላው አመልካች በቅሬታ ነጥብነት ያነሳው ክርክር በሌላ የመግደል ሙከራ ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ በስምንት አመት ጽኑ እስራት የተቀጣበት ጉዳይ የእስራት ቅጣቱን ከመጨረሱ በፊት በይቅርታ የተፈታበትን እንደሪከርድ ተወስዶ ቅጣቱ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎት ለአመልካች የተሰጠው ይቅርታ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ለአመልካች የተሰጠው ይቅርታ ነው ከተባለ ይቅርታ ጽንሰ ሐሳቡና ውጤቱ ምን እንደሆነ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 230 ስር አስቀምጧል፡፡ በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር ሁለት ፓራግራፍ ሁለት መሰረት ይቅርታ ሲሰጥ በተቀጪው ላይ የተወሰነው ፍርድ ከሚያስከትለው ውጤት ጋር በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ እንደሚኖር ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ይቅርታ የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዳልነበረ የሚያስቆጥር አይደለም፡፡ በመሆኑም የወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚኖር በመሆኑ በሪከርድነት የማይያዝበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት በምህረት የወጡበትን ጉዳይ በቅጣት ማክበጃነት ተጠቅመዋል በማለት ያቀረቡት ቅሬታ የስር ፍርድ ቤቱ ሊጽፈው ከፈለገው እና በትክክልም ለአመልካች የተሰጠው ይቅርታ እንጂ መህረት ያለመሆኑ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

አመልካች ተደጋጋሚ ወንጀለኛ መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች መሰረት አድርገው በአስራ ስምንት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰናቸው ስለቅጣት የተመለከቱትን አጠቃላይ መርሆዎችን ያላገናዘበ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካችን የበታች ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ በማለት በአስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት መቅጣታቸው ባግባቡ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአመልካች ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤ/ን

የሰ/መ/ቁ. 48617

ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ተስፋዬ አደላ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቃቤ ሕግ (መርማሪ ከሳሽ) - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ አመልካች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555(ለ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ቀኑ ባልታወቀ ጊዜ መስከረም ወር 2001 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 2፡00 - 3፡00 ባለው ጊዜ ሕጋዊ ባለቤቱን በቦክስ በመምታት አንድ ጥርስ ሲያወልቅ ሌሎች ሁለት ጥርሶች ላይም ጉዳት አድርሶ በሐኪም እንዲወልቅ በመደረጉ በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ክሱ ደርሷቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ በክሱ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ስለድርጊቱ አፈጻጸም ግን የክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ አቃቤ ህግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ ከዚያም አመልካች እንዲከላከሉ ተደርጎ የባለቤታቸው ጥርስ በሌላ ምክንያት የወለቀ መሆኑን የሚያሳይ ጭብጥ በማስያዝ የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አሰምተዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካች ምስክሮች በግል ተበዳይ ጥርስ በሌላ ምክንያት የወለቀ ስለመሆኑ የማያስረዱና የአቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን የማያስተባብሉ መሆኑን በመግለጽ ውድቅ አድርጎ አመልካችን በአቃቤ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ በሁለት አመት ጽኑ እስራት ወይም በብር 500.00(አምስት መቶ ብር) እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለአዋሳ ከተማ መደበኛ ችሎት ይግባኝ አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን በከባድ የአካል ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ካለሰ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኋላ በድንጋጌው ላይ ያልተመለከተውን የገንዘብ መቀጮ በአማራጭነት በመጠቀም ቅጣት መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ምክንያት ይዞ ቅጣቱን በመጨመር አመልካች በአምስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ድርጊቱ የተፈፀመው በቸልተኝነት እንጂ ሆነ ተብሎ አይደለም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅጣቱን ጨምሮ የወሰነው ባልተጠየቀ ዳኝነት ነው በማለት ምክንያታቸውን ዘርዝረው ውሳኔው እንዲሻርላቸው ወይም በገደብ እንዲለቀቁ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካች ጥፋተኛ ተብለው በሁለት አመት እስራት ወይም በብር 500.00(አምስት መቶ) እንዲቀጡ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ አቃቤ ሕግ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጸ 555(ለ) አማራጭ ቅጣት የማይደነግግ ሆኖ ሳለ አማራጭ ቅጣቱን መወሰኑ አግባብነት የለውም በማለት ባቀረበው ይግባኝ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አማራጭ ቅጣቱን የመሻር አግባብነት እንደተጠበቀ ሆኖ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የወሰነውን የሁለት አመት እስራት ቅጣት ወደ አምስት አመት እስራት ከፍ አድርጎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ አቃቤ ሕግ በቁጥር 1230/85/2002 በቀን 26/04/2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ለ) ስር ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው እንደነገሩ ሁኔታና እንደ ጉዳቱ ከባድነት ከአስራ አምስት አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ወይም ከአንድ አመት በማያንስ ቀላል እስራት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች የተቀመጡት በቀላል እስራት ስለመሆኑ በውሳኔው ላይ አልገለፀም ይህንኑ ተጠቅሞ እስራቱን በገንዘብ በአማራጭ ስለመቀየሩም ያስፈለገው ነገር የለም(ቅጣቱ አንቀጽ 179"ን" መሰረት ተደርጎ የተወሰነ መሆኑን አያሳይም)፡፡ የሆኖ ሆኖ ግን ተጠሪ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ ለይግባኙ ምክንያት ያደረገው አመልካች ጥፋተኛ ከተባሉት ድንጋጌ አንጻር በገንዘብ መቀጮ በአማራጭ ሊቀጣ አይገባም በሚል ስለመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ በግልፅ ያሳያል፡፡ ተጠሪም በዚህ ችሎት ባቀረበው መልስ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ተገቢው ቅጣት እንዲወሰን ይግባኝ ብለናል ከማለት ውጪ የእስራት ቅጣቱም ቢሆን ያነሰ ስለሆነ ሊጨምር ይገባል በማለት ይግባኝ አቅርበናል የሚል ክርክር የለውም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበው በአማራጭ የገንዘብ ቅጣት መተላለፉ ያላግባብ ነው በሚል ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ እንግዲህ በወንጀል ጉዳይ ውሳኔ ሲሰጥ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን የሚያቀርብበት ሥርዓት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195 ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ስለቅጣት በተለይ የተደነገገው የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሁለት በፊደል "መ" ስር የተመለከተው ሲሆን ይዘቱም ቅጣት አነሰ በዛ በሚል በግልጽ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለሆነም በግልፅ ጥያቄው ካልቀረበ ፍርድ ቤት ቅጣት ጨምሮ ሊወሰን የሚችልበት ሥርዓት የለም፡፡ እንዲህ ሆኖ ከተገኘ ባልተጠየቀ ጉዳይ ዳኝነት እንደመስጠት የሚቆጠር ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በአመልካች ላይ የተጣለው የእስራት ቅጣት አንሷል በሚል የይግባኝ ቅሬታ ባላቀረበበት ሁኔታ የበላይ ፍርድ ቤቶች የሁለት ዓመቱን የእስራት ቅጣት ወደ አምስት አመት እስራት ቅጣት ከፍ አድርጎ መወሰናቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በመ/ቁጥር 06214 መጋቢት 21 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 28011 ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም በዚሁ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ በመ/ቁጥር 29101 ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17231 መጋቢት 03 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
3. አመልካች ሊቀጡ የሚገባው በሁለት አመት ፅኑ እስራት ነው ብለናል፡፡
4. አመልካች በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ማናቸውም የእስር ጊዜ በቅጣቱ ላይ የሚታሰብላቸው መሆኑን ተገንዝቦ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ተገልፆ ለማረሚያ ቤቱ ይፃፍ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዘገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 51706

ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ትኩ - ከማረሚያ ቤት ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45521 ጥቅምት 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ጥር 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ መጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 በመተላለፉ ሁለት ወንጀሎችን እንደፈፀመ በመግለጽ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ከአቶ መሐመድ ኑር በአቶ ዮናስ ገብርአብ በኩል ብር 2,300(ሁለት ሺህ ሦስት መቶ) ጉቦ ተቀብሏል ተብሎ የተከሰሰበትን ወንጀል ተጠሪ እንደ ክሱ አቀራረብ ባለማሥረዳቱ አመልካች በከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲያሰናበት ብይን በመስጠቱና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን ለይግባኝ ሰሚ ችሎት የፀና በመሆኑ በዚህ መዝገብ የግራ ቀኙ የመከራከሪያ ጭብጥ ሆኖ አልተያዘም፡፡

በዚህ መዝገብ አከራካሪ ሆኖ የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ሐምሌ ወር 1999 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ፕሬዚዳንት ሆኖ ሲሰራ በልደታ ምድብ በመዝገብ ቁጥር 03453 እነ ካልዩ ኡመር በሚል በሚጠራው ፋይል ተከሳሽ የሆኑት አቶ አልዬ ኡመር ጉዳዩ እንዲወሰንለት ከፈለገ ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ይክፈል በማለት አብረሐም ገብረክርስቶስ በተባለ አደራዳሪ አማካኝነት ጉቦ እንዲሰጠው በመጠየቅ የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ተጠሪ የቀረበውን ማስረጃ የአመልካችን መከላከያ ማስረጃና በፍርድ ቤት ተጣርተው እንዲቀርቡ የተደረጉ ማስረጃዎችን በመመርመር የከፍተኛው ፍርድ አመልካች በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ውሣኔ ተጠሪ በይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በሥር የተደረገው ክርክር መሰረታዊ ይዘት ስንመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ የቀረበውን አንደኛ ክስ ለማስረዳት ሶስት ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ አንደኛውን ለማስረዳት የቀረበው የመጀመሪያው የተጠሪ ምስክር ለተጠሪ የወንጀል ክስ በግል ተበዳይነት ስማቸው የተጠቀሰው አቶ ኡመር አልዬ ናቸው፡፡ ምስክሩ 1989 ዓ.ም በሊዝ ቦታ ገዝቶ የነበረ ቢሆንም በፍርድ ቤት ክርክር የነበረበት በመጀመሪያ ጉዳዩን የያዙት ዳኛ ሌላ ዳኛ የነበሩ መሆኑንና አመልካች ጉዳዩን የያዙት ዳኛ በእድገት ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ከተዛወሩ በኋላ ማየት እንደጀመሩ ጉዳዩ ስለተንተባተበኝ ጉዳዩን ብርሃኑ ለተባለ ጠበቃ እንዳማክሩትና ጠበቃውም አብርሐም ገብረክርስቶስ የሚባለውን የተጠሪ ምስክር አመልካችን ስለሚያውቀው ይጨርስልሐል ብሎ ያማከረው መሆኑን አስረድቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ምስክሩ ሌላውን የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ ደውሎ ለሆነ ጉዳይ እፈልግሐለሁ እንዳለውና ጉዳዩን ለመወሰን ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ) አመልካች እንደሚፈልግ አብርሃም ገብረክርስቶስ የነገረው መሆኑን፣ከአመልካች ቢሮ በመሄድ ገንዘቡ ስለሚበዛ እንዲቀንስለት እንደጠየቀው አመልካችም ስልክህን ስጠኝ እደውልልሃለሁ በማለት እንደጠየቀውና ምስክሩ ስልኩን ሰጥቶት እንደወጣ መስክሯል፡፡ ምስክሩ ከዚህ በኋላ ግንቦት 23 ቀን 1999 የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር እንዳመለከተ ገልፆአል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ስልክ ደውሎ ተዘጋጅተሐል ወይ ብሎ እንደጠየቀውና ደሴ ሆቴል አካባቢ እንዲመጣ እንደነገረው ምስክሩም ለአመልካች መልሶ ስልክ እንደደወለለትና ደሴ ሆቴል ሄዶ እየጠበቀው እንዳለ አመልካች ስልክ ደውሎ ቆዳ ጃኬትና ነጭ ሸሚዝ ለለበሰ ሰው እንዲልክ የነገረው መሆኑን ምስክሩም በተነገረው ምልክት መሰረት የተላከውን ሰው ደሴ ሆቴል አግኝቶ ሰላሣ ሺህ ብር እንደሰጠው መሥክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምስክሩ በዚያው እለት ገንዘቡን ሰጥቶ ተመልሶ ቁራ አካባቢ እንደደረሰ አመልካች ስልክ ደውሎ ገንዘቡ ለምን ከብር 50,000(ሃምሳ ሺህ)እንደቀነሰ እንደጠየቀውና አስር ሺህ ብር ካልጨመረ እንደማያስወስንለት የሰጠው ገንዘብ እንደማይመለስ የገለፀለት መሆኑን ምስክሩም በሐሳቡ በመስማማት ቀደም ብሎ 30,000(ሰላሳ ሺህ ብሩን) የተቀበለው ሰው ደውሎለት ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) እንደሰጠ መሥክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ምስክሩ ገንዘቡን የተቀበለውን ሰው አግኝቶት ዓለም ባንክ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ወደሚገኘው የተከሳሹ(አመልካች) መኖሪያ ቤት ውሣኔ ከመስጠቱ ከአንድ ቀን በፊት በግምት ከዘጠኝ እስከ አስር ሰዓት ባለው ጊዜ ሄደው አመልካች ከቤቱ ወጥቶ ተቀብሏቸው መኪና ውስጥ እንደገባ ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) ምክስሩን ከዚህ በፊት ገንዘብ ለተቀበለው ሰው እንደሰጠና ሰውየውም ተቀብሎ ለአመልካች እንደሰጠው ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ እንደሰጠው ከዚህ በኋላ ለሥነ- ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት እንዳደረገ መሥክሯል፡፡አመልካች ለተጠሪ ምስክር ኡመር አልዬ ይደውልላቸው የነበረው ቁጥራቸው 0911-18-54-60 እና 0911-64-14-31 በሆኑ የሞባይል ስልኮች እንደነበርና የምስክሩ የሞባይል ስልክ ቁጥር 0911-20-00-79 መሆኑን አስረድተው የተመለሱ መሆኑን ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ የቀረበውን አንደኛ ክስ ለማስረዳት አቅርቦ በምስክርነት የሰማው አቶ አስማረ ገበየሁን ሲሆን አመልካችን ከተጠሪ ምስክር አብርሃም ጋር ያስተዋወቀው መሆኑን ከዚያ በኋላ ለአራት ወራት ለመስክ ሥራ መሄዱንና ከመስክ ሲመለስ አብርሃም አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ጠይቋል በሚል ምርመራ እየተጣራበት መሆኑን ሲነግረው በመደናገጥ ለአመልካች ደውሎ የሰማውን ሲነግረው አመልካች በመቆጣት መረጃው ሐሰተኛ መሆኑን የማያውቀው ነገር ውስጥ እንዳይገባ እንደነገረው መስክሯል፡፡ ይኸው ምስክር አብርሃምን በመጠራጠር መረጃው የመነጨው ከእሱ አለመሆኑን ተከሳሹን (አመልካችን) ለማሣመን እንድችል አብርሃም መረጃውን በድጋሚ እንድነግረው በማድረግ የአብርሃምን ንግግር በሞባይል ቀድቶ ለአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳሰማው አመልካች አብርሃም ወስላታ ነው አትመነው እዳለውና ከዚህ በኋላ አብርሃምን ያላየኸውን ያልሰማኸውን የምታወራው ለምንድን ነው ሁለተኛ አትደውል ብሎ የነገረው መሆኑንና የአመልካችና የአብርሃም ግንኙነት እንደተቋረጠ መሥክሯል፡፡ አብርሃምን የቀዳው አብርሃም ሣያውቅ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የፀረ ሙስና ኮሚሽን መርማሪዎች ጠይቀው ሞባይል ውስጥ የነበረውን ንግግር ቅጅ ወስደዋል በማለት የመሠከረ ነው፡፡

የተጠሪ የመጨረሻው ምስክር አቶ አብርሃም ገ/ክርስቶስ ሲሆን ይኸው ምስክር አመልካችን ቀደም ብሎ እንደሚያውቀውና አስማረ ገበየሁ የተጠሪ ምስክር አመልካችን እንዳስተዋወቀው ከገለፀ በኋላ መሐመድ የሚባል የተጠሪ የመጀመሪያ ምስክር የሆኑት የአቶ ዑመር አልዬ ልጅ ጋር ቀደም ሲል ጓደኝነት የነበረው መሆኑንና መሐመድ የሚባለው የዑመር አልዬ ልጅ አሁን አሜሪካን አገር የሚኖር መሆኑን ከገለፀ በኋላ መሐመድ የእኔና የአመልካች ጓደኞሞች መሆናችንን ያውቅ ስለነበር በመጀመሪያ የተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ አመልካች የያዘው ጉዳይ እንዳለው ሲነግረው የእኔና የአመልካች ግንኙነት ንፁህ ጓደኝነት ነው ብሎ እንደመለሰለትና በዳኝነት በያዘው ጉዳይ ማነጋገር እንደማይፈልግ እንደገለፁለት ይህንን ጉዳይ ሁለተኛ እንዳያነሳበት በመግለጽ እንደመለሱለት መሥክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ ልጅ መሐመድ ከአሜሪካን አገር ደውሎ የጓደኛህ በችሎት ላይ እየሰደበው አባቴን አሞታል በማለት የነገረው መሆኑንና እሱም ለማጣራት ለአቶ ዑመር አልዬ ሲደውል ጓደኛህ ከባለጋራዎቹ ፊት በችሎት ስለሰደበኝ በዚህ ምክንያት ታምሜአለሁ ብሎ የነገረው መሆኑን ገልጿል፡፡ ይኸው ምስክር ይህንኑ ጉዳይ ደውሎ ለአመልካች እንደነገረውና ለአመልካች ስም ጥሩ እንዳልሆነ እንደገለፁለት አመልካችም አቶ ዑመር አልዬ ጉዳያቸው በተለየ መልኩ የተያዘ አስመስለው ችሎት ላይ ኦቨር አክት በማድረጋቸው እንደተቆጣቸው የገለፁለትና ቢሮ ላካቸው አነጋግራቸዋለሁ እንዳለ መስክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ አመልካች ቢሮ በመሄድ እንዳነጋግራቸው ጉዳዩን አመልካች በብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ሊይዝልኝ ነው በማለት አቶ ዑመር እንደነገሩትና ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው የለኝም ብሎ ምስክሩ አቶ ዑመርን እንደመለሰለትና ስለዚህ ጉዳይ አመልካችን እንዳልጠየቀው አቶ ዑመር አልዬ ቤት ሲመጣ የለም ብለው እንዲመልሱት ለቤተሰቦቹ መናገራቸው ስልኩንም ማንሣቱን በማቆም ግንኙነቱ እንዳቋረጥ ከአቶ ዑመር አልዬ ጋር የሚከራከሩት መክታርና ሴኮ የሚባሉ ወንድማማቾች አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ተቀብሎ ሊወስንብን ስለሆነ አመልካችን አናግርልን ብለው የጠየቁት መሆኑንና አመልካች ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋርጦ የነበረ በመሆኑ ለአመልካች እንዳልነገረው መመሥከሩን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል ተጠሪ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 03453 በዳኝነት ተሰይሞ የነበረውና ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አስማረ ገበየሁ የተባለው የተጠሪ ምስክርና አብርሃም ገብረክርስቶስ የተባለው የተጠሪ ምስክር የተለዋወጡትን ንግግር ቅጅ የያዘ ሲዲ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ አመልካች አምስት የመከላከያ ምስክሮች ቃል ያሰማ ሲሆን ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች የመዝገብ ቁጥር 05016 የሰጠው ውሣኔ እንዲያያዝለት አድርጓል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ የተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ እና በአመልካች መካከል የስልክ ልውውጥ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚያዝያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም በተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬና በአመልካች መካከል የተደረገ የስልክ ጥሪ መኖሩን አጣርቶ እንዲልክ ለቴሌኮሚኒኬሽን ተደጋጋሚ ትእዛዝ ሰጥቶ መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሽኝ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ ስድስት ገጽ ማስረጃ ተልኮለታል፡፡ ከቴሌኮሚኒኬሽን በተላከው ደብዳቤ መሰረት የአመልካች ስልክ ነው በማለት የተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ ቁጥራቸውን የገለፃቸው ሞባይሎች ቁጥር 0911-18-54-60 የሆነው በአቶ ሰይድ አደም ዑመር ስም ቁጥሩ 0911-64-14-31 የሆነው በአመልካች ስም ያሉ መሆኑን ተረጋግጧል ከዚህ በተጨማሪ፡፡

- የተጠሪ ምስክር የሆነው የአቶ ዑመር አልዬ ነው የተባለው ቁጥሩ 0911-20-00-79 እና የአመልካች ስልክ ናቸው በተባሉት ቁጥራቸው 0911-18-54-60 እና 0911 40-90-99 መካከል የተደረገ የስልክ ግንኙነት ፍርድ ቤቱ በጠየቀው ጊዜ ውስጥ አለመኖሩንና ከተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ ስልክ ነው በተባለው ቁጥር 0911-20-00-79 የተከሳሹ ስልክ ነው ወደተባለው ቁጥሩ 0911-64-14-31 ወደሆነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሞባይል በፈረንጆች አቆጣጠር ጁላይ 8 ቀን 2007 ዓ.ም አንድ ጥሪ ጁላይ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ሁለት ጥሪዎች በድምሩ ሶስት ጥሪዎች መደረጋቸው ተረጋግጧል፡፡

- ከዚህ በተጨማሪ የተከሳሽ ነው ከተባለው ቁጥሩ 0911 64-14-31 ከሆነው ሞባይል የተጠሪ ምስክር የአቶ ዑመር አልዬ ስልክ ነው ወደተባለው ቁጥሩ 0911-20-00-79 ወደሆነው ሞባይል የተደረገ የስልክ ጥሪ የሌለ መሆኑን በቀረበው ማስረጃ ተገልጿል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪ ምክስርና የግል ተበዳይ ነኝ የሚሉት አቶ ዑመር አልዬ አመልካች በስልክ ደውሎ ገንዘቡን እሱ በምልክት ለላከው ሰው አቀብያለሁ በማለት የሰጡት ምስክርነት ከአመልካች ወደ ተጠሪ ምስክር ስልክ የስልክ ጥሪ ያልተደረገ መሆኑ ከቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የምስክሩ ቃል ታዓማኒነት የለውም በማለት አመልካች በነፃ እንዲሰናበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 149/2/ መሰረት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ የይግባኝ ችሎቱ መዝገቡ ለአስራ ሁለት ቀጠሮዎች የተቀጠረ መሆኑ በቴሌኮሚኒኬሽን የመጣው መረጃ የአቃቤ ሕግ ማስረጃ የሚያጠናክር ሆኖ እያለ ለጉዳዩ ግንኙነት የለውም መባሉ ተገቢ አይደለም የግል ተበዳዩ ቤቱ ድረስ መሄዳቸውን 10,000(አስር ሺ ብር) መስጠታቸው የመሰከሩ በመሆኑንና ምስክሩ እውነቱን ይመሰክራሉ ተብለው ስለሚገመቱ የአቃቤ ሕግ ማስረጃ አመልካች ወንጀሉን መፈፀሙን አረጋግጦል በማለት አመልካች በክሱ የተጠቀሰበትን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብሎ በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 1000/አንድ ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ጥር 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በሕግ የተጣለበትን የማስረዳት ሸክም አልተወጣም፡፡ የአቃቤ ሕግ ማስረጃ ወንጀሉን አለመፈፀሜን የሚያስረዱ ናቸው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት ውሣኔ የሰጠው በአቃቤ ሕግ ምስክሮች የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ መሰረት በማድረግ ሣይሆን የራሱን የሕሊና ግምት በውሰድ ነው፡፡ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተገለፀው ፍሬ ጉዳይ እና ወንጀሉን የፈፀምኩ ስለመሆኔ ለማቋቋም ብቃት የሌላቸው ናቸው የተጠሪ ምስክር ከግል የነበራቸውን ጥላቻ መነሻ በማድረግ በሰጡት የሐሰት ምስክርነት መነሻ በማድረግ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የቅጣት ውሣኔም የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ያገናዘበ አይደለም የሚል ይዘት ያለው አስራዘጠኝ ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የሰበር ችሎቱን የሚጠይቀው የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ስህተት እንዲታረምለት ነው፡፡ አመልካች የግል ተበዳዩን ከአስራ ሁለት ቀጠሮ በላይ በማጉላላት የግል ተበዳይ ጉቦ እንዲሰጣቸው ያስገደዷቸው መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለህሊና ግምት ሣይሆን በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ መሰረት በማድረግ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው ሰፊ የቃል ክርክር አቅርቧል አመልካች በቃል ክርክሩ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የግራ ቀኙ መካከል በሥር ፍርድ ቤት የቀረበው ክርክርና በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃ ይዘት የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ማስረጃ ተዓማኒነት በመመርመር ረገድ በመለያየት የሰጡት የተለያየ ፍርድ ይዘትና በሰበር አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች በክሱ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት የፈፀሙ ስለመሆኑ በሕግ የተጣለበትን ሸክም ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚለውን ጭብጥ በወንጀል ጉዳይ ተከራካሪዎች ስላለባቸው የማስረዳት ግዴታ ኃላፊነት (Burden of proof) ፍርድ ቤቶች የተከራካሪዎቹን ማስረጃ ታዓማኒነት በሚመረምሩበት ወቅት ሊከተላቸው የሚገባቸውን መሰረታዊ የማስረጃ ሕግ መርሆችንና ሌሎች አግባባነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በዝርዝር ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የከሳሽ(ተጠሪ) የማስረዳት ሸክምና ኃላፊነት የሚወጣው በምን ሁኔታ ነው? የሚለውንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ነጥቦች መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የመጀመሪያውን ነጥብ አንድ ተከራካሪ የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል ወይም አልተወጣም የሚለው ጭብጥ ለመወሰን የመጀመሪያው ማነጣፀሪያ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ ለመመለሥ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣንና ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ሰጭ አካላት በትኩረት ሊመረምሩት የሚገባውን ጉዳይ ለማየት ያስችላል፡፡ በወንጀል ጉዳይ ወንጀል ተፈጽሟል በማለት የወንጀል ክስ የቀረበ ተከሳሽ የወንጀሉ ድርጊት ስለመፈፀሙ ብቻ ሣይሆን ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜ ወንጀሉ እንዴት እንደተፈፀመና ወንጀሉ በእነማን እንደተፈፀመ ዝርዝር ሁኔታዎችን ግልጽ በሚያደርግ መንገድ የማቅረብ ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርአትም አንድ የወንጀል ክስ ውስጥ ሊገለፁ የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 111 ተደንግጓል፡፡

የወንጀል ክስ የቀረበ ከሳሽ ጉዳዩን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን ተወጥቷል ወይም አልተወጣም? የሚለው ጭብጥ ለመወሰን የመጀመሪያው የማነጣፀሪያና የመመዘኛ መስፈርት ራሱ ከሳሽ ያቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አንድ ድርጊት የተፈፀመ መሆኑን በመግለጽ ክስ ያቀረበ ወገን በክሱ የገለፀውን ፍሬ ጉዳይ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለበት የሚለው የማስረጃ ሕግ መርህ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ ጉዳዩን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚለው ነጥብ እልባት የሚሰጠው ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ውስጥ የተገለፁትን ፍሬ ጉዳዮች ትክክለኛነት ተጠሪ የወንጀል ክሱን ለማስረዳት ባቀረባቸው የተለያዩ ማስረጃዎች የሚያረጋግጡና በወንጀል ክሱ ውስጥ የተገለፀው ፍሬ ጉዳይና ክሱን ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃዎች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና ተያያዝነት ያላቸው ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ በአጠቃላይ ካሳሽ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ለጉዳዩ ያላቸው አግባብነት (Relevancy of Evidence) እና የከሳስ ማስረጃ የአስረጅነት ዋጋ ያላቸውና ታዓማኒነት ያላቸው መሆኑ የሚመረመረው ከሳሽ በወንጀል ክስ ማመልከቻው የገለፃቸውን ፍሬ ጉዳዮች መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ተጠሪም ክሱን የማስረዳት ሸክሙን(ክሱን የማስረዳት ግዴታውን) የተወጣ መሆኑ ወይም አለመሆኑ መመርመር ያለበት ተጠሪ በክሱ ማመልከቻው የገለፃቸውን ፍሬ ጉዳዮች እውነት መሆናቸውን በተጠሪ ማስረጃ የተረጋገጡ መሆኑንና ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ተደጋጋፊ እና እርስ በርሳቸው የማይቃረኑ መሆናቸውን መሰረት በማድረግ ማስረጃዎቹን በመመርመር ነው፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት ተመሣሣይ ይዘት ያላቸውን ማስረጃዎች ታዓማኒነት አስመልክቶ የተለያዩበት ዋናው ምክንያት የተጠሪ ማስረጃዎች እውነተኛ መሆናቸው መመርመር ያለበት ከምን አንፃር ነው በሚለው መስፈርት ላይ ከተጠሪ ክስ አንፃር ባለመመርመራቸው ነው፡፡ ተጠሪ በክሱ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 408 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተውን በመተላለፍ በሐምሌ ወር 1999 በመዝገብ ቁጥር 03453 ተከራካሪ የነበሩትን አቶ ዑመር አልዬ(የተጠሪ ምስክር) ብር 50,000(ሃምሣ ሺህ ብር) ይክፈል በማለት በሶስተኛ የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ በተባለ አደራዳሪ በኩል ጉቦ ጠይቋል የሚል ክስ አቅርቧል፡፡

የተጠሪ ክስ አመልካች በአብርሃም ገብረክርስቶስ በኩል ጉቦ ጠይቋል በሚል ሲሆን የግል ተበዳዩና አንደኛ የተጠሪ ምስክር አብርሃም እንዲያነጋግርልኝ አድርጌ ብር 50,000(ሃምሣ ሺህ ብር) አምጣ ተብለሐል ብሎ ነገረኝ በማለት የመሰከረ ሲሆን በወንጀል ክሱ አደራዳሪና ጉቦ ለአመልካች የተጠሪ ምስክርና የግል ተበዳዩ እንዲሰጥ ጠየቀ የተባለው ሶስተኛው የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ አመልካች የግል ተበዳይ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) ይሰጠኝ ብሎ ያልጠየቀው በመሆኑ በተቃራኒው አመልካች ስለያዘው ጉዳይ የአቃቤ ሕግ ምስክር የሆነው የግል ተበዳይ እንዳያነሳበት እንደነገረው የአቶ ዑመር አልዬ አሜሪካን አገር የሚኖር መሐመድ የተባለ ልጅ አባቴን ጓደኛህ በድሎት ታሞ ተኝቷል ብሎ እንደደወለለት እሱም ወደ አቶ ዑመር አልዬ ስልክ ሲደውል ከባለጋራዎቼ___ ፊት ሰደበኝ አዋረደኝ በዚህ ምክንያት ታምሜአለሁ ብለው እንደነገሩት እሱም አመልካችን ለስሙ ጥሩ እንዳልሆነና የተባለውን ስነግረው ምስክሩ በችሎት ከሥርአት ወጥተው ስለነበር እንደተናገራቸውና ቢሮ ላካቸው አነጋግራቸዋለሁ በማለት እንደነገረውና የተጠሪ አንደኛ ምስክር ዑመር አልዬ ከአመልካች ቢሮው ውስጥ እንዳነጋገራቸውና በብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ሊሰራልኝ ተስማምተናል ብለው እንደነገሩት አብርሃም ገብረክርስቶስ ስለዚህ የሚያውቀው የሌለ መሆኑን ገልፆ ከግል ተበዳይ ጋር የነበረውን ግንኙነት እንዳቋረጠ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሥክሯል፡፡ በሌላ ጊዜ ከተጠሪ አንደኛ ምስክር ጋር የሚከራከሩ ሰዎች አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ተቀብሎ ሊፈርድብን ነው ብለው እንደነገሩት መሥክሯል፡፡

ተጠሪ በክሱ የተገለፀውን ፍሬ ጉዳይ "አመልካች በአብርሃም ገብረክርስቶስ በኩል ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ጉቦ እንድሰጠው የግል ተበዳይ ዑመር አልዬን መጠየቁን ያስረዳልኛል" በማለት ያቀረበው የተጠሪ ምስክር አብርሃም ገብረክርስቶስ አመልካች በዚህ አይነት ጥያቄ ያላቀረበለትን የግል ተበዳዩ ሰደበኝ ብሎ ስሞታ ከተናገረ በኋላ ቢሮው ሄዶ እንዲያነጋግረው ከተደረገ በኋላ በብር 50,000(ሃምሳ ሽህ ብር) ሊይዝልኝ ተስማምተናል በማለት የግል ተበዳይ ራሱ ለተጠሪ ምስክር አብርሃም እንደነገረው መስክሯል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ያቀረባቸው ምስክሮች ዕርስ በርሱ የሚቃረን ማስረጃ (contradictory evidence) የሰጡ መሆናቸውን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጠሪ ማስረጃ ዕርስ በርሱ የሚደጋገፍና በክሱ የተገለፀውን ፍሬ ጉዳይ የማያረጋግጥ በሆነ ጊዜና በተቃራኒው የተጠሪ ማስረጃና በክስ የተገለፀው ፍሬ ጉዳይ በሌላ የተጠሪ ማስረጃ እውነትነት የሌለው መሆኑ በተገለፀ ጊዜ ተጠሪ ክሱን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን በአግባቡ ተወጥቷል ከሚል መደመደሚያ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ክስ የተገለፀውንና በግል ተበዳይ የተሰጠውን የምስክርነት ቃል ተጠሪ ክሴን ያስረዳልኛል በማለት ባቀረበው አብርሃም ገብረክርስቶስ በሰጠው የምስክርነት ቃል እውነትነት የሌለው መሆኑ የተገለፀ ሆኖ እያለ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብይን መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ተጠሪ ባቀረበው ክስና በተጠሪ አንደኛ ምስክር ቃልና በተጠሪ ሶስተኛ ምስክር ቃል መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት በማየት ሣይመረምር ማለፉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ ይህ ጉዳይ የፍሬ ጉዳይ ክርክር እንጅ የሕግ ስህተት አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

2. ተጠሪ አመልካች በክሱ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት በአጥጋቢ ማስረጃ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 141 እና 149 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ተጠሪ ክሱን የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል የሚባለው ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ታዓማኒነት ያላቸውና ክሱን ለማስረዳት የሚችል ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ የማስረጃ ታዓማኒነት የሚለካው ማስረጃው በይዘቱ ወጥነት ያለውና ዕርስ በርሱ የሚፋለሱ ፍሬ ጉዳዮችን ያልያዘ መሆኑን በመመርመርና በማስረጃው የተገለፀው ፍሬ ጉዳይ ያንኑ ክስ ለማስረዳት ከቀረቡት ሌሎች ማስረጃዎች ጋር የሚጣጣም ተደጋጋፊና ተመሣሣይ ፍሬ ጉዳይ ለማስረዳት የሚችል መሆኑን በማገናዘብ ነው፡፡

ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) በመዝገብ ተከራካሪ የነበሩት አቶ ዑመር አልዬ ከሶስተኛ የተጠሪ ምስክር(አብርሃም) አደራዳሪነት እንደሰጡት ጠይቋል ከማለት ውጭ አመልካች ከግል ተበዳይ ገንዘብ የተቀበለ መሆኑ መቼ እንደተቀበለና በማን በኩል እንደተቀበለ የገለፀ አለመሆኑን ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ እነዚህ ነገሮች ግልጽ በማድረግ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 119 መሰረት ትእዛዝ መስጠት ነበረበት፡፡ ተጠሪ በወንጀል ክሱ በዝርዝር ያልገለፃቸው ፍሬ ጉዳዮች የግል ተበዳይና የተጠሪ ምስክር በሆኑት አቶ ዑመር አልዬ ተገልፆዋል፡፡ ይኸው ምስክር በአንድ ቀን አመልካች በራሱ ስልክ ሶስት የስልክ ጥሪ ያደረገለት መሆኑን በመጀመሪያ ተዘጋጅተሐል ወይ ብሎ እንደጠየቀውና ደሴ ሆቴል አካባቢ እንደነገረው ከዚያም ምስክሩ ወደ አመልካች ስልክ በመደወል ደሴ ሆቴል እየጠበቀው መሆኑን ነግሮት እንደዘጋ ከዚያ በኋላ አመልካች ስልክ በመደወል ቆዳ ጃኬትና ነጭ ሸሚዝ ለለበሰ ሰው እንዲልክ እንደነገረው ምስክሩ በተነገረው መሰረት ደሴ ሆቴል ሰውየውን አግኝቶ ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) እንደሰጠው ከዚያ በኋላ ተመልሶ ወደ ቁራ አካባቢ ሲደርስ አመልካች ለሶስተኛ ጊዜ ስልክ ደውሎ ገንዘቡ ለምን ከ50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) እንደቀነሰ እንደጠየቀውና አስር ሺህ ብር (10,000) ካልጨመረ እንደማይሰራለት እንደነገረው መሥክሯል፡፡ አመልካች ከግል ተበዳይና የተጠሪ ምስክር ጋር ግንኙነነት ያደርግ የነበረው በስልክ መሆኑን የተጠሪ ምስክር ገልጿል፡፡ የተጠሪ ምስክር ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ ብር) ማንነቱን ለማላውቀው ሰው ሌዘር ጃኬትና ነጭ ሸሚዝ የለበሰ የሚል ምልክት አመልካች በስልክ ደውሎ ነግሮኝ ሰጥቻለሁ ያለበትን ቀን ሰዓት አልገለፀም፡፡ ምስክሩ ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ስሙ ማንነቱ ለማይታወቅ ሰው ሰጠሁ ባሉበት ቀን ብቻ አመልካች በእሱ የስልክ ሞባይል ሶስት ጥሪያዎችን እንዳደረገላቸው መስክረዋል፡፡ ይሕ የተጠሪ ምስክር በእምነታቸው መሰረት ቃለ መሐላ ፈጽመው ለፍርድ ቤቱ የመሰከሩት እና የገለፁት ፍሬ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ይህንን ምስክርነት እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ምስክሩ ቃለ መሐላ መፈፀማቸው ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የምስክሩ ቃል ታዓማኒነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚያዚያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም የምስክሩ ጉዳይ ውሳኔ እስካገኘበት ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከአመልካች ወደ ምስክሩ የስልክ ጥሪ ስለመደረጉ እንዳያረጋግጥ የቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ተጠይቆ እንኳንስ በአንድ ቀን አመልካች ለተጠሪ ምስክር ሶስት ጊዜ ስልክ ሊደውል ይቅርና በሶስት ወራት ውስጥ አመልካች ለተጠሪ ምስክር ያደረገው የስልክ ጥሪ የሌለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡፡

ምስክሩ እንደ አውሮፖ አቆጣጠር ጁላይ 8 ቀን 2007 አንድ ጥሪ ጁላይ 21 ቀን 2007 ሁለት ጥሪዎች ወደ አመልካች ማድረጉ ምስክሩ ተጠሪ በቀን ሶስት ጊዜ ያሕል ደውሎ የት ቦታ እንደምጠብቀው ገንዘቡን ለማን እንደምሰጥና ለምን ገንዘቡ 30,000(ሰላሣ ሺህ) ሆነ አስር ሺህ ብር ጨምር በማለት አናግሮኛል በማለት የሰጠው ምስክርነት እውነት መሆኑን አያረጋግጥም፡፡ ስለዚህ የተጠሪ አንደኛ ምስክርና የግል ተበዳይ ነኝ ባዩ ዑመር አልዬ እውነት ነው በማለት ለፍርድ ቤት ስለወንጀሉ አፈፃፀም ያስረዱት ፍሬ ነገር ጭራሹኑ አመልካች የተደረገላቸው የስልክ ጥሪ የሌለ መሆኑ በተረጋገበት ሁኔታ ምስክሩ የሰጡት ቃል ታዓማኒነት ያለው ነው በማለት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መደምደሙ አንድ ማስረጃ ሊመርመርና ሊመዘን የሚገባው ከነ ሙሉ ይዘቱ እንጂ ተከሳሹን የሚጠቅመውን ክፍል ነጥሎ በማውጣትና ከሳሽ ካቀረበው ክስ ጋር የሚጣጣመውን የማስረጃ ክፍልና ይዘት ለይቶ በመያዝ መሆን እንደማይገባው በበርካታ አገሮች ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ታዓማኒነት ምርመራና ምዘና መርህ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. በያዝነው ጉዳይ አመልካች ጋር ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ተስማማን በማለት ለሶስተኛ የተጠሪ ምስክር የተናገረው የግል ተበዳይ ነኝ ያለው አቶ ዑመር አልዬ እንደሆነ ሶስተኛ ምስክር መስክሯል፡፡ ሁለተኛው የአቃቤ ሕግ ምስክር ስማሁ የሚለው ከሶስተኛው ምስክር ከአብርሃም ነው፡፡ ለአመልካች እንዲሰጥ በመጀመሪያ 30,000(ሰላሳ ሺህ ብር) ቀጥሎ አስር ሺር ብር /10,000/ በመጨረሻ አስር ሺህ ብር /10,000/ ከአመልካች መኖሪያ ቤት ሄጀ ሰጠሁ የሚለው ማንነቱን ያልገለፀው የለበሰውን ልብስ ብቻ በምልክት ከገለፀው ሰው ጋር ነው፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ጉቦ ጠየቀኝም ጉቦ ሰጠሁትም የሚለው ወሬ ብቸኛ ምንጭ የግል ተበዳዩ ዑመር አልዬ ሲሆን ሌሎቹ የግል ተበዳይ አወራን ወይም አብርሃም ሲያወራ ሰማሁ በማለት ሁለተኛ ምስክር የመሰከረ መሆኑንና የስሚ ስሚ ማስረጃ መሆናቸው ለመገንዘብ ይችላል፡፡

አንደኛ የተጠሪ ምስክርና የግል ተበዳይ አመልካች ጉቦ የጠየቀው በአብርሃም አደራዳሪነት እንደሆነ በምስክርነቱ የገለጸ ሲሆን አብርሃም የተጠሪ ምስክር ሆኖ በመቅረብ ይህ የግል ተበዳይ ምስክርነት በሚቃረን መንገድ መሥክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምስክሩ አመልካች በችሎት ሰደበኝ በሚል ምክንያት ታሞም እስከመተኛት ደርሶ የነበረ መሆኑንና ይህንን ሁኔታ የግል ተበዳይ ውጭ የሚኖር ልጅ ጭምር ሰምቶ ከውጭ አገር አብርሃምን ስልክ ደውሎ እንዳናገረው የተጠሪ ምስክር አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግል ተበዳይ ብር 30,000(ሰላሣ ሺህ ብር) ሰጠሁ ባሉበት አንድ ቀን ውስጥ ብቻ አመልካች በእሱ ስልክ ሶስት ጊዜ ደውሎ ነበር በማለት የሰጡት ምስክርነት ከሚያዚያ 1 ቀን 1999 እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ አመልካች ለተጠሪ ምስክርና የግል ተበዳይ ዑመር አልዬ ያደረገው የስልክ ጥሪ አለመኖሩን በማረጋገጫ የቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ከሰጠው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይህንን ያለፈው ከተጠሪ ምስክር ዑመር አልዬ ቃለ መሐላ ፈጽመው የሰጡት የምስክርነት ቃል እውነት ነው ተብሎ ይገመታል በማለት ነው፡፡ ሆኖም ከላይ የተገለፁት ማስረጃዎች ምስክሩ እውነተኛ አለመሆናቸውን የሚያሣዩ ግምቱን የሚያፈርሱ መሆኑን ሣይመረምር ማለፉ በራሱ ተገቢነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል አንድ ዳኛ የዳኝነት ሥራውን ከማናቸውም ሰው ጣልቃገብነት ነፃ ሆኖና ገለልተኛ ሆኖ ያከናውናል ተብሎ የሚገመት መሆኑ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መርህ ነው፡፡ ዳኛው በጉቦ ወስኗል የሚል ወገን ይህንኑ ፍሬ ጉዳይ ተዓማኒነት ያለው በቂ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ አመልካች በዳኝነት በያዘው ጉዳይ በችሎት አዋርዶኛል፣ጉዳዩን አጓትቷል የሚል ቅሬታ ያላቸው መሆኑ ተጠሪ ምስክሬ ነው በማለት ባቀረበው አብርሃም ገብረክርስቶስ በኩል ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) ሰጥቻለሁ የሚለው አመልካች በዳኝነት ባየው ጉዳይ ተከራካሪ የነበረው አቶ ዑመር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልዬ ከሰጠው የምስክርነት ቃል ውጭ አመልካች ይህንን ገንዘብ መቀበሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ተጠሪ አላቀበም፡፡ የተጠሪ ምስክር አቶ ዑመር አልዬ ገንዘቡን ሰጠሁ የሚሉበትና አመልካች ጠየቀኝ የሚሉበት ሁኔታ በተለይ አመልካች ስልክ ደውሎ የት ቦታ እንደሚጠብቁት ከዚያም ሁለተኛ ደውሎ ገንዘቡን ለማን እንደሚሰጡ ሶስተኛ ደውሎ ገንዘቡ ለምን አነሰ ብሎ እንደጠየቃቸው የሰጡት ምስክርነት ከአመልካች ወደ ምስክሩ የተደረገ የሥልክ ጥሪ አለመኖሩ ስለተረጋገጠ እውነትነት የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይኸም የተጠሪ ምስክር የአቶ ዑመር አልዬ የምስክርነት ቃል ታዓማኒነት የሌለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ ከላይ በተገለፀው መንገድ ተጠሪ ክሱን የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን አልተወጣም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በመሻር በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ1/ መሰረት ሽረናል፡፡

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ-2/ መሰረት አጽንተናል፡፡

3. አመልካች በነፃ የተሰናበተ ስለሆነ ከእስር እንዲፈታው ለማረሚያ ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 38681

ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሀይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- እማሆይ ፀሐይቱ አምበሉ - ወኪል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 12269 ሰኔ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቀረቡ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ የተጀመረው በምዕራብ ጉጃም ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በጅጋ ከተማ በ500 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት ከሳሽና ሟች ባለቤቴ ቁስ አለሙ ከበደ ወ/ሮ አስካለ አድማሱ ከተባሉት ግለሰብ ገዝተን ባለሀብትነቱን በባለቤቴ ስም አዙረን ከዚያም ባለቤቴ ሲሞቱ በከሳሽ ስም ዞሮ ከነሐሴ 1975 እስከ ሰኔ 1998 ዓ.ም ድረስ ከሳሽ ግብር እየከፈልኩ ለ23 ዓመት በባለሀብትነት ይገኘው የምገኝ ሲሆን ቤቱን መያዣ ለማድረግ የሚያበቃ ውክልና ሳይኖር ተከሳሽ መያዣ አድርጌዋለሁ በማለት በጨረታ ለመሸጥ የጋዜጣ ማስታወቂያ ያወጣ ስለሆነ ባንኩ ቤቱን ለመሸጥ ከሕግ ወይንም ከውል የመነጨ መብት ሳይኖረው ሊሸጥ ስለማይችል መብት የለውም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ ክስ የቀረበበትን ቤት ተከሳሽ በሐራጅ ለመሸጥ የተነሳው ከአቶ ምንውየለት ዓለሙ ጋር ባደረገው የብድር ውል ተበዳሪው መጋቢት 4 ቀን 1987 ዓ.ም ለንግድ ሥራ ማስፋፊያ የሚያውሉት ብር 30 ሺህ በብድር ሲወስዱ መያዣ ስለሰጡ ነው፡፡ ይህም የሆነው ቤቱ በተበዳሪው ስም የተመዘገበ ስለመሆኑና ዕዳና ዕገዳ የሌለበት ስለመሆኑም የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በሰጠው ማረጋገጫ መሠረትና መያዣውም በማዘጋጃ ቤቱ በመመዝገቡ ነው፡፡ ስለሆነም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የምዕራብ ጉጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር የተነሳበትን ቤት ከሳሽና ባለቤታቸው የገዙት ነው ወይንስ የተበዳሪው የአቶ ምንውየለት ዓለሙ ነው? የሚል ጭብጥ መስርቶ ጉዳዩን በመመርመር ከሳሽ ከባለቤታቸው ቁስ ዓለሙ በላይ ጋር በትዳር አብረው በነበሩ ጊዜ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ከወ/ሮ አስካለ አድማሱ ላይ ገዝተናል ቢሉም ይህንን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካለማቅረባቸውም በላይ ስመ ንብረቱም ከወ/ሮ አስካለ አድማሱ ወደ ቁስ ዓለሙ በላይ ስለመዞሩ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኘው በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ካልተጻፈ በስተቀር በ3ኛ ወገኖች ዘንድ ውጤት እንደሌለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2878 ላይ የተመለከተ ስለሆነ ከሳሽም በስማቸው ከ1975-1998 ዓ.ም ግብር የከፈሉ ስለመሆኑ ቢረጋገጥም የሽያጭ ውሉ ሥልጣን ባለው አካል ካልተመዘገበ ውጤት የሌለው ነው ካለ በኋላ አቶ ምንውየለት ዓለሙ ከተከሳሽ ገንዘብ ሲበደሩ ይህንኑ ቤት አስይዘው መሆኑን እንደዚሁም የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ክርክር የተነሳበት ቤት የአቶ ምንውየለት ዓለሙ መሆኑን ያረጋገጠ ስለሆነ ከሳሽ የቤቱ ባለቤት ስለሆንኩ ተከሳሽ መብት የለውም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነውን ቤት፤የይግባኝ ባይ ባለቤት የነበሩት ቁስ ዓለሙ በላይ ከወ/ሮ አስካለ አድማሱ ገዝተው ስም ንብረቱ መዞሩንና በስማቸው መመዝገቡን በደረሰኝ ቀጥር 29764 በሆነ ለውል ማስመዝገቢያ መክፈል የሚገባውን በማስከፈል የመዘገበ መሆኑን የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሰጠው ማስረጃ ያስረዳል፡፡ ከዚያ በኋላም ይግባኝ ባይና ባለቤታቸው የከተማ ቦታ ኪራይ ለመንግስት እየከፈሉ እስከ 1977 ዓ.ም ይዘውት እደቆዩና ከዚያም ቁስ ዓለሙ በላይ ሲሞቱ ይግባኝ ባይ በስማቸው በማዛወር የከተማ ቦታ ኪራይ ለመንግስት ሲከፍሉ እንደነበር የቀረቡት ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ ካለ በኋላ በሌላ በኩልም መ/ሰጭ ቤቱ የተበዳሪው የአቶ ምንውየለት ዓለሙ መሆኑን ያቀረበው ማስረጃ የጅጋ ከተማ ልዩ ቀበሌ ፍርድ ሸንጎ በማስረጃ አረጋግጦ በመስጠቱና የከተማው ማዘጋጃ ቤትም የተበዳሪው ቤት መሆኑን በማረጋገጥ የጻፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ግን ቤቱ የተበዳሪው ቢሆን ኖሮ ጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እያለ የከተማ ቤትና ቦታን የማስተዳደርና የመመዝገብ ሥራ እንደሚሰራ እየታወቀ ከዚሁ አካል ቤቱ የተበዳሪው መሆኑን ማረጋገጥ እየተገባ በቀበሌ ፍርድ ሸንጎ በኩል ይህንን ማረጋገጥ ሥልጣን አለው ለማለት አይቻልም፡፡ የጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤትም ክርክር የተነሳበት ቤት የተበዳሪው መሆኑን ቢገልጽም የመያዣ ውሉን ተቀብሎ ስለመመዝገቡ ያላረጋገጠ ስለሆነ የመያዣ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3052 አግባብ መሠረት ተመዘግቧል ለማለት ስለማይቻል በዚህ ሁኔታ መ/ሰጪ ቤቱን መያዣ አድርጎታል ተብሎ የይግባኝ ባይ መብት ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ በአግባቡ አይደለም በማለት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ቤትና ይዞታው የይግባኝ ባይ ነው ሲል ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መ/ሰጭም (የአሁን አመልካች) በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የመያዣ መብት የለውም ተብሎ በአማራ ክልል ጠቅላይና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ሰበር ችሎት ምላሽ የሚሻው የጉዳዩ ጭብጥ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ አመልካች የመያዣ መብት አለው? ወይንስ የለውም? የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3041 ላይ እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በቀጥታ ከሕግ፣ ከፍርድ ወይንም ከውል ሊመነጭ ይችላል፡፡ አንድ የመያዣ ንብረት በመያዣ ከተሰጠ በመብቱ ለመገልገል እንዲቻል መያዣው አግባብ ባለው አካል መመዝገብ እንዳለበትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3052 ላይ ተመልክቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ አቶ ምንውየለት ዓለሙ የተባሉት ተበዳሪ ከአመልካች ላይ ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ሲበደሩ በጅጋ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል የሚገኘውንና ቁጥር 835 የሆነውን ቤት በመያዣነት ሲያቀርቡ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ይሄው ቤት በተበዳሪው በአቶ ምንውየለት ዓለሙ ስም እንደተመዘገበና ዕዳና ዕገዳም እንደሌለበት ለአበዳሪው ባንክ (ለአመልካች) በማረጋገጥ መያዣውንም የመዘገበ ስለመሆኑ በምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ባቀረበው ማስረጃ መረጋገጡን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የመያዣ መብት የለውም ወደሚል መደምደሚያ ለመድረስ የቻለው ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ብድሩ በሚሰጥበት ወቅት ቤቱ የተበዳሪው መሆኑን ያረጋገጠው የከተማው ማዘጋጃ ቤት ሳይሆን የቀበሌው ፍርድ ሸንጐ ስለሆነ ይህ አካል ይህንን የማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን የለውም እንደዚሁም መያዣው ስለመመዘገቡ አልተረጋገጠም የሚሉ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ሆኖም ግን የቀበሌው ፍርድ ሸንጐ የቤት ባለቤትነትን በማረጋገጥ ማስረጃ የመስጠት ሥልጣን የለውም ቢባል እንኳን ቤቱ በተበዳሪው ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝና ዕዳና ዕገዳም እንደሌለበት የከተማው ማዘጋጃ ቤት ከማረጋገጡም በላይ፤ ተበዳሪው አቶ ምንውየለት ዓለሙ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከፍኖተሠላም ቅርንጫፍ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውንና ቤት በዋስትና አስይዘው ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ሲበደሩ መያዣውንም ተቀብሎ መመዝገቡንም የከተማው ማዘጋጃ ቤት ያረጋገጠ እንደመሆኑ መጠን ተበዳሪው የቤቱ ባለቤት ስለመሆኑ ሥልጣን ባለው አካል በተሰጠ ማስረጃ አልተረጋገጠም መያዣውም አልተመዘገበም መባሉ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪ የዚሁ ቤት ባለሀብት ስለመሆናቸው አጥብቀው የተከራከሩ ቢሆንም የንብረት ባለሀብትነት ከሕግ ወይንም ከውል የሚመነጭ ሲሆን ይህንኑ መሠረት አድርጎ በዚሁ ክርክር ባስነሳ ቤት ላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195(1) መሠረት ከመንግስት አስተዳደር አካል ባለሀብትነታቸውን በማወቅ የተሰጠ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ወይም ባለሀብትነትን የሚያሳይ ማስረጃ በማቅረብ ባለሀብትነታቸውን ያላረጋገጡ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ የቤቱ ባለሀብት ናቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሳኔ ማጽናቱ የአመልካችን የመያዣ መብት የሚጻረርና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 12269 ሰኔ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 32718 ሰኔ 29 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ሽረናል፡፡
2. የምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 14676 የካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት አጽንተናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 45161

ታህሣሥ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- 1. እናኑ ጀንበሬ - ቀረቡ፡፡

2. ላቀች ጀንበሬ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. የደሴ ከተማ ቀበሌ 03 ጽ/ቤት - ወኪል በአንተአምላክ አንተነህ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡

አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ የከሳሾች እናትና አባት በሕይወት በነበሩ ጊዜ በደሴ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል በገዙት ቦታ ላይ ቁጥር 045 እና 046 የሆኑ ቤቶችን ሠርተዋል፡፡ ከእነዚህ ቤቶች ውስጥ ቁጥር 045 የሆነው ቤት በአዋጅ 47/67 በትርፍነት ያልተወረሰ ሲሆን ከሳሾች በማናውቀው ሁኔታ አንደኛ ተከሣሽ ለሁለተኛ ተከሣሽ አከራይቶት ይገኛል፡፡ ከሣሾች ቤቱ እንዲመለስልን ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አመልክተን ጉዳዩ አይመለከተኝም በማለት ይህንኑ በደብዳቤ አረጋግጠናል፡፡

ስለሆነም አንደኛ ተከሣሽ ቤቱን ይዞ ለሁለተኛ ተከሣሽ በማከራየት ላይ የሚገኘው በአዋጅ ባልተወረሰበት ሁኔታ ስለሆነ ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡን ኪራይም እንዲከፍሉ ይወሰንልን ብለናዋል፡፡

የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ክስ የቀረበበት ቤት በአዋጅ ተወርሷል ወይንስ አልተወረሰም? የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ቀደም ሲል ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ይህንኑ ቤት አስመልክቶ አቤቱታውን ሳይቀበለው መቅረቱ ቤቱ አልተወረሰም ተብሎ ውሣኔ እንደተሰጠ የወረዳው ፍ/ቤት በመቁጠር ለከሣሾች ሊመለስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም ብሎ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ ሽሯል፡፡

የሥር ከሣሾችም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት አቤቱተው ለሰበር አይቀርብም ብሎ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ የደሴ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አመልካቾች ከፕራይቤታይዜሽን ኤጀንሲ ውሣኔ አላሰጡም በሚል ምክንያት የወረዳው ፍ/ቤት ውሣኔ መሻሩ አግባብነቱን ለማጣራት አቤቱተው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙንም በቃል አከራክሯል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቾች ክስ ያቀረቡት በውርስ የተላለፈልንን ቤት ተጠሪዎች ከሕግ ውጭ ይዘው ስለሚኙ ያስረክቡን በማለት ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርና በዚህ ችሎትም በተደረገው ማጣራት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ይዘው የሚገኙት ከ1973 ዓ.ም. ጀምሮ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የኪራይ ውል መነሻነት እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ክርክር የተነሳበት ቤት ለረጅም ዓመታት በመንግሥት እጅ የቆየ ከሆነ አመልካቾች ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ተፈቅዶላቸው ባለንብረት ስለመሆናቸው ወይንም ደግሞ ከአዋጅ ውጭ ያለአግባብ ተወስዶብናል የሚሉ ከሆነም ለሚመለከተው አካል አቤቱታ አቅርበው ውሣኔ አግኝተው ባለመብት ስለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ አመልካቾች በዚህ መልኩ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ካላረጋገጡ ደግሞ ከመነሻውም ቢሆን ክስ ባቀረቡት ነገር መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ለረጅም ጊዜ መንግሥት ተረክቦ ሲያስተዳድራቸው የነበሩ ቤቶች ሊመለስልኝ ይገባል በማለት ክስ የሚያቀርብ ወገንም ከላይ እንደተጠቀሰው በአዋጅ 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል አቤቱታ አቅርቦ ውሣኔ አንኝቶ ባለመብት መሆኑ ካልተረጋገጠ ክስ በቀረበበት ነገር ላይ መብት ወይም ጥቅም እንደሌለው እንደሚቆጠር ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14094 የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ስለሆነም በተያዘውም ጉዳይ አመልካቾች ቤቱ ሊመለስልን ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡት በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ባላረጋገጡበት ሁኔታ ስለሆነ የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ቤቱ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት የሰጠውን ውሣኔ የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተለየ ምክንያት ቢሽረውም ከውጤት አኳያ ግን የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. ዐ0ዐ5 በ19/3/2ዐዐ1 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. ዐ0751 በ14/5/2ዐዐ1 ዓ.ም. የሰጠውን ትዕዛዝ ምክንያቱን ለውጠን አጽንተነዋል፡፡

አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑን ስላላረጋገጡ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 43600

ጥር 05 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ዳዊት መስፍን

ተጠሪ፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የባለሀብትነት መብትን መሰረት በማድረግ የቀረበው የቤት ይለቀቅልኝ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሳሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የነበረው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 118 ቀበሌ 05 ክልል የሚገኘውን፣ ቁጥር B-8/8008/30 በሚል የሚታወቀውን ቤት እንዲያስረክበው ይወሰንለት ዘንድ ጠይቀዋል። ለማስረጃነትም ጥቅምት 23 ቀን 1985 ዓ.ም በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ተሰጠኝ ያሉትን ቁጥር 18/31246 የሆነ የከተማ ቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አቅርበዋል። የአሁኑ ተጠሪም በተከሳሽነት ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ፤ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል። ጉዳዮን በመጀመሪየ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ እና 1845 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት በብይን የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጓል። በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስቀየር ነው።

እኛም አመልካች ጥር 22 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት የሰበር ማመልከቻ ያቀረቡትን ቅሬታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው። በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኙ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል።

አመልካች በሰበር አቤቱታው ያነሷቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ለክሱ መነሻ የሆነው ንብረት /ቤት/ የማይንቀሳቀስ ሀብት በመሆኑ ክርክቱ መታየት ያለበት በንብረት ሕግ መሠረት ነው። ከንብረት ሕጉ አንፃር ሲታይም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 መሰረት የተሰጠኝ የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አልመነከም። በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196 በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት ደብተሩ ይሰረዘልኝ የሚል ጥያቄ ለሚመለከተው አካልም አልቀረበም። የሚመለከተውን የአስተዳደር ክፍልም ደብተሩ ሕገወጥ ነው አላለውም። በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168 መሰረት ንብረቱ የኔ ነው የሚል ጠያቂ ወገን አልቀረቡም የሚሉ ናቸው። ተጠሪ በበኩሉ ይርጋን በሚመለከት የተያዘው ጭብጥ ላይ ተመስርቶ ክርክሩን አቅርቧል። በዚህም መሠረት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ድንጋጌ ስር የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት አለው። ድንጋጌው ውልን መሰረተ አድርጐ ለሚነሳ ክርክር ብቻ ነው አግባብነት ያለው የሚለው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም። ግዴታዎች ከውል ባይመነጩም የውል ደንቦች ተፈፃሚ እንደሚሆንባቸው በሕጉ ተደንግጓል የሚሉትን የመከራከሪየ ነጥቦችን አቅርቧል።

ግራ ቀኙ ወገኖች ከስር ጀምረው ያደረጉት ክርክር ተጠቃሎ ሲታይ የሚያስነሳው ጭብጥ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚቀርበው የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት አግባብ አለ ወይ? የሚለው ነው። ጭብጡ የሕግ ጭብጥ በመሆኑ መልስ ሊያገኝ የሚችለው በዚህ ረገድ አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌዎችን በመፈተሽ ነው።

አመልካች ክሱን የመሰረቱት የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን ገልፀውና በዚህ ረገድ የባለቤትነተ ማረጋገጫ ደብተር እንዳላቸው በማመልከት ነው። ጥያቄው የቤቱ ባለሐብት በመሆኔ ከሕግ ውጪ ይዞብኝ የሚገኘውን ተጠሪ በፍርድ ኃይል እንዲለቅ ይደረግልኝ በሚል በግልጽ የቀረበ ነው። በመሆኑም ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን የመፋለም ክስ (petitory action) የሚመለከት መሆኑ ግልጽ ነው። ክሱ በዚህ መልክ ቢቀርብም ተጠሪ የክሱ መቅረብ አግባብ አለመሆኑን የሚመለከቱና ይጠቅሙኛል የሚላቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማንሳት መከላከያውን ያቀርባል ተብሎ ይገመታል። በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ለመከላከያ ይጠቅሙኛል ያላቸውን የመከራከሪያ ነጥቦችን ያቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ይርጋን መሰረት ያደረገ መቃወሚያ ነው። ለዚህ ክርክሩ በዋቢነት የጠቀሰው በፍትሐብሔር ሕጉ በአራተኛ መፀሐፍ “ስለግዴታዎች” በተደነገገው በአንቀጽ 12 ስር ካሉት ድንጋጌዎች ስር የሚገኘውን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ስር የተመለከተውን የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ነው። እንግዲህ ይህ ድንጋጌ የሚገኘው በፍትሐብሔር ሕጉ ሦስተኛ መፀሐፍ “ስለንብረት” ከሚለው አንቀጽ ስድስት እና “ስለግል ሐብት” ከሚለው ከአንቀጽ ሰባት ውጪ በመሆኑ ከተያዘው የይርጋ መቃወሚያ አግባብነት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ከማየታችን በፊት አግባብነት ያላቸው የንብረት ሕጉ ድንጋጌዎችን ሁኔታ መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል።

በመሰረቱ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ በሕግ የተከበረ መሆኑ፣ ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሌሎችን ዜጐች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን የሚያካትት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 40/1/ ስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡

የንብረት ሕጉ በጥቅሉ ሲታይ ደግሞ ንብረት ምንድን ነው?፣ ንብረት ወይም ሀብት የሚገኘው እንዴት ነው?፣ ሀብት ከአንድ ወደ ሌላ የሚተላለፈው በምን አግባብ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልስልናል፡፡ ባለሀብትነት ስለሚቀርበት ሁኔታ እና ስለባለሀብትነት ማስረጃም ዝርዝር ድንጋጌዎችን ያስቀምጣል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1126 ስር እንደተመለከተው ንብረቶች ግዙፍነት ያላቸው ሆነው ተንቀሳቃሽ የሆኑና የማይንቀሳቀሱ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ ይህን ክፍፍል በመከተልም ሐብቶች የሚገኙበትን፣ የሚተላለፉበት፣ ባለሐብትነት ቀሪ የሚሆንበት አግባብ እንደዓይነታቸው የተለያዩ እንደሆኑ በሕጉ ተመልክቷል፡፡ የያዝነው የማይንቀሳቀስ ንብረትን /ሀብት/ የሚመለከት በመሆኑ በአብዛኛው ትኩረታችን በዚህ ላይ ይሆናል፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት ከሚሆንባቸው ወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት የሚገኝባቸው ሁኔታዎች በበፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168/1/ ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን የሚያሟላ ይዞታ ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡ ሌላው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1184 እና 1186 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ሲሆን በዚህ አግባብ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት መሆን የሚቻለው በሕግ ወይም በውል የወይም በኑዛዜ መሰረት ነው፡፡ በውል ወይም በኑዛዜ መሰረት ባለሐብት ለመሆንም የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ማስመዝገብ የግድ እንደሚል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1553 እስከ 1646 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ባለሐብትነት በእነዚህ መንገዶች ይገኛል ካልን ቀጥለን ደግሞ ባለሐብትንት ቀሪ የሚሆንበት አግባብ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ አግባብት ያላቸው ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1188 እስከ 1192 ድረስ ያሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ሁለቱንም የንብረት አይነቶች የሚመለከቱ ሲሆን ባለሀብትነት ቀሪ ስለሚሆንበት ይርጋም ይጨምራሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በሕግ መሰረት “ ባለሀብትነቱ ለሌላ ሰው የሆነ ወይም የተላለፈ እንደሆነ” በሚል የተደነገጉት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1189 አና 1190 እና ባለሐብትነትን የሚያስቀር የይርጋ ዘመን በሚለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1192 ስር የተመለከተውን መጥቀስ በቂ ይሆናል፡፡

እንደምንመለከተው እስካሁን ድረስ ካየነው ሂደት ንብረቱ የኔ ነው በሚል የመፋለም ክስ የሚመሰረተው ከሳሽ ሊያቀርባቸው የሚችላቸው ሕጉን መሰረት ያደረጉ የመከራከሪያ ነጥቦች ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ ግንዛቤ እናገኛለን፡፡ ክርክር የንብረት ባለሃብትነትን መሰረት ያደረገ የመፋለም ክርክርን የሚመለከት በመሆኑ ወደሌላው መጽሐፍ ከመሻገራችን በፊት የንብረት ሕጉን መሰረት በማድረግ ሊነሳ የሚችሉ /የሚገባቸው/ የመከራከሪያ ነጥቦችን በቅድሚያ ማየትም ነው አግባብ የሆነው፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነቱ ያቀረበው የመጀመሪያው የመከራከሪያ ነጥብ ይርጋን የሚመለከት በመሆኑ በንብረት ሕጉ የተቀመጠውን የይርጋ ድንጋጌ አስቀድሞ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ከላይ እንደገለጽነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1192 ስር የተመቀጠው ድንጋጌ ይርጋን የሚመለከት ነው፡፡ ባለሀብትነትን የሚያስቀር የይርጋ ዘመን” በሚል ርእስ ያለው ሆኖ ይዘቱም በሚንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለውን መብት በአስር ዓመት የጊዜ ወሰን /ይርጋ/ ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ ያመላክታል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ግን አያሳይም፡፡ ድንጋጌው ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ለያዝነው ክርክር እልባት ለመስጠት ሁለት አማራጮችን አነሳጽረን ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተደነገጉትን የንብረት ሕግ ድንጋጌዎች ስንመለከት ባለቤትነት ከሁሉ የሰፋ መብት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በሕግ የተቀመጡትን ገደቦችንና ወሰኖችን (Restriction and Limitations) ሳያልፍ የአንድ ንብረት ባለቤት በንብረት እንደፈለገው የመጠቀምና የመገልገል መብቱን ነፃነቱ በሕግ የተከበረለት ስለመሆኑም ድንጋጌዎቹ ያሳያሉ፡፡ ለባለሀብቱ የባለቤትነት መብት ከሚሰጣቸው መብቶች መካከልም ንብረቱ ያለእርሱ ፈቃድ ከሕግ ውጪ በሌላ ሰው ወይም ኃይል ከተወሰደ ንብረቱን ካለበት ድረስ በመከታተል የማስመለስ ወይም የመፋለም መብት አንዱ ስለመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206 ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና አቀራረጽ መረዳት የሚቻለው ሁለት መሰረታዊ የሆኑ ነጥቦችን ነው፡፡ ይኸውም የመፋለም መብት ባለሐብቱ ንብረቱን ማንም ያልተፈቀደለት ሰው ሕገ ወጥ በመሆነ መንገድ እንዳይነካ፣ በማንኛውም መልኩ ወደ ራሱ ወይም ወደ ሌላ እንዳይዛወር ወይም የንብረቱን ህልውና እና ደህንነት እንዳያውክ በኃይል ተጠቅሞ የማስወገድ (the right to apply force against any act of intervention or usurpation) መብት አንዱ ሲሆን ሌላው ደግመ ያለባለቤቱ ፈቃድ ወይም ከሕግ ውጪ ደንብረቱ ተወስዶ ከሆነ ባለቤቱ ይህን ንብረት የመከተልና እንዲመለስለት በዳኝነት የመጠየቅ መብት (Right to bring petitory action) ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206 ባለሀብት የሆነ ሰው መብት ሳይኖረው እጁ ካደረገው ሰው ወይም ከያዘው ሰው ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐብቱ ይገባኛል ሲል ለመፋለምና ማናቸውንም የኃይል ተግባር ለመቃወም ይችላል ሲል የማደነግገው እንዝህን ነጥቦች የሚያረጋግጥ ሲሆን የባለቤትነት መብት ከሁሉ የሰፋ መብት መገለጫ ከሆኑትም ዋናው ንብረቱን ተከታትሎ በዳኝነት የመጠየቅና የማስመለስ መብትን ለባለሃብቱ ማጐናፀፉ መሆኑ ይታመናል፡፡

ምንም እንኳ አንድ ሰው በሕግ ያገኘው ወይም በመተላለፍ የተጐናፀፈው የንብረት ባለቤትነት ቋሚነት /ዘላለማዊነት/ (prrpetutiy) እንደለው ቢታወንም በራሲ በባለመብቱ ፈቃድ ወይም ያለፈቃዱ ይኸው በአንድ ወይም በተወሰኑ ንብረቶቹ ላይ የባለቤትነት መብት የሚጠፋበት፣ ቀሪ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ የባለቤትነት መብት ቀሪ (extinction of ownership) የሚሆንባቸው ሁኔታዎች በፍትሐብሔር ህጋችን ከቁጥር 1188 እስከ 1192 ድረስ መመለከታቸውን ከላይ ጠቅሰናል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1190 በተለይ ሲታዩ በማይንሰሳቀስ ንብረት ላይ የተቋቋመ የባለቤትነት መብት ቀሪ የሚሆነው የዚህ ሰው የባለቤትነት መብቱ ከማይንቀሳቀሰው ንብረት መዝገብ ሲሰረዝ /ሲፋቅ/ ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡

እንግዲህ ይህን ያክል በሕጉ ጥበቃ የተደረገው መበት ቀሪ የሚሆነው መቻ ነው? የሚለው ጥያቄ ከመብቱ ጠቅላላ ባህርይና ከሕግ አውጪው ሐሳብ አንፃር ቀጥተኛ፣ ተፈፃሚነትና አግባብነት ካለው የሕጉ ክፍል ጋር ተዛምዶ ታይቶ ተገቢ ምላሽ ሊሰጥበት የሚችለው ነው፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት በሚመለከት የሚቀርበው የመፋለም ክስ (petitory action) ለመቃወም የሚቀርበው የይርጋ ክርክር መታየት ያለበት በንብረት ሕጉ መሰረት ነው የሚለውን አማራጭ ከያዝን የምንደርስበት መደምደሚያ ግልጽ ነው፡፡ ሕጉ የይርጋ ወሰን ያስቀመጠው ለሚንቀሳቀስ ንብረት ብቻ በመሆኑ የይርጋው መቃወሚያ ለማይንቀሳቀስ ንብረት የመፋለም ክስ አግባብነት የለውም ወደሚለው ነው የምንደርሰው፡፡ የተጠሪን ክርክር በመቀበል ሁለተኛውን አማራጭ ብንይዝ ደግሞ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት በሚመለከት የሚነባው የይርጋ መቃወሚያ ከንብረት ሕጉ ወጥቶ በሌላው የሕጉ ክፍል /አራተኛው መጽሐፍ/ ነው የሚታየው የሚለውን አካሄድ መከተል ሊኖርብን ነው፡፡ ይህ ግን በእርግጥም ሕጉ ሊደርስበት የፈለገው ምክንያታዊ የሆነ አካሄድ ነው ለማለት የሚያስቸግር ነው የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1192 የሚንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት የሚቀረው በአስር አመት የጊዜ ገደብ ነው ለማለት ካስቀመጠ በኋላ ስለማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሐብትነት ቀሪ መሆን በዝምታ ያለፈው ለጉዳዩ ቀጥተኛ ፈተፃሚነት በሌለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ስር የተመለከተውንና ተመሳሳይ የሆነ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ለማድረግ ነው ብሎ ማሰብ ምክንያታዊ ሊሆን አይችልምና፡፡

ቀደም ሲል ለማመልከት እንደሞከርነው ንብረቶች የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀስ በሚል በሁለት የሚከፈሉ ቢሆንም፣ የሚገኙበት፣ የሚተላለፉበት እንዲሁም ባለሀብትነታቸው ቀሪ የሚሆኑበት አግባብ በንብረት ሕጉ ነው የሚገዛው፡፡ በዚህ ረገድ ሕጉ ያልታሰበበት ክፍተት ትቶአል ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ ይልቁንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሚንቀሳቀን ንብረት በተለየ ሁኔታ የዘላቂነት /ነዋሪነት/ ባህሪይ ያለው እና ከትውልድ ወደ ትውልት በቋሚነት የሚተላለፍ በመሆኑ ቀሪ የሚሆንበት አግባብ ከሚንቀሳቀስ ንብረት የጠበበ እንደሆነ ሕጉ ፍልጓል የሚለው አስተሳሰብ ነው ከሕጉ መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168 በተደነገገው መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት በእጁ አድርጐ እና በተከታታይም ለአስራ አምስት አመታት ያክል በስሙ ግብር የገበረ ሰው የንብረቱ ባለቤት ይሆናል ሲባል የቀድሞው ባለቤት ነኝ የሚል ቢመጣ እንኳን ባለሃብትነቱ ቀሪ ስለሚሆን ንብረቱን ሊያስመልስ አይችልም ማለት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተቀመጠው የጊዜ ወሰን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ከተቀመጠው የረዘመ ነው፡፡ የንብረቱ ባለሀብት ነው በሚል አሳቤ ለረኸርም አመታት በስሙ ግብር እየገበረ ንብረቱን ሲቆጣጠር የቆየው ሰው የሚያቀርበው መከራከሪያ ይህን ያክል ጥብቅ እይታ የሚፈልግ ከሆነ እንዲሁ ማለትም ግብር ሳይገብር የያዘው ሰው የሚያቀርበው መከራከሪያ በቀላል የሚታይ ነው ለማለት የሚያስቸግር ነው የሚሆነው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች በአጠቃላይ ደምረን ስንመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነት ቀሪ የሚሆነው በይርጋ ሳይሆን በሌሎች ሁኔታዎች ይሆን ዘንድ የሕጉ ፍላጐት እንደሆነ ነው መገንዘብ የምንችለው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶች ሊያደርጉ የሚገባው ጉዳይ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ክሱን ማቋረጥ ሳይሆን ክሱ እንዲቀጥል በማድረግ ከሳሹ በእርግጥም የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማጣራት፣ ባለቤትነት ከነበረም ሕጋዊ በሆነ ስርአት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የባለቤትነት መብቱ መቋረጥ አለመቋረጡን በማስረጃ በማጣራት እና ተገቢ የሆነውን ውሣኔም መወሰን ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የባለቤትነት ባሕርይ ቀጣይነት (perpetuity) በመሆኑ ፍርድ ቤቶች በዚህ የህግ ትርጉም መሰረት አንዱ ክሱ በይርጋ አይታገድም ከማለታቸው በፊት የክሱ መሰረታዊ ይዘት የባለቤትነት መፋለም (petitory action) መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከባለቤትነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነገር ግን ከመፋለም መብት ውጪ ያሉ ሌሎተ ክሶች እነደሚጠይቁ መፍትሔ (remendy) እና ለክሱ ምክንያት እንደሆነው ጉዳይ አይነት /ጋብቻ፣ ውርስ፣ ሽያጭ ወ.ዘ.ተ../ በሌሎች ል ሕጎች የይርጋ ደንቦች የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የይርጋ ጉዳይ ክስ ይቀጥል አይቀጥል የሚለውን ነጥብ የሚመለከት ብቻ በመሆኑ ሙግቱ ከጠተናቀቀ በኋላ በፍሬ ነገሩ የሚሰጠው ውሣኔ በሕጉ ይዘትና ተከራካሪ ወገኖች በሚያቀርቡት ማስረጃ ጥንካሬ የሚወሰን መሆኑን የሰር ፍርድ ቤቶች የዚህን ውሣኔ የሕግ ትርጉም በዚህ መንፈስ ሊረዱት ይገባል፡፡ ከላይ ከተሰጠው ትንታኔ አንፃር አቤቱታ የቀረበበት ብይን የንብረት ሕጉን መሰረተ ሐሳብ ያልተከተለ፣ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 93723 ጥር 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 6752 ታህሳስ 09 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የማይንቀሳቀስ ንብረት የመፋለም መብት ክስ (petitory action) በይርጋ ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወደ ክሱ ስረ-ነገር በመግባት ግራ ቀኙን ወገኖች ከአከራከረ በኋላ ተገቢ ነው የሚለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 48699

ሚያዝያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አብዱራሒም አህመድ

አልማው ወሌ

ዓለ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አምሣለ ጀመሪ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ፍርዱ ገበያሁ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43302 ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ነሐሴ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ተግፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ጉዳዩን አይቶ ጥር 23 ቀን 1998 ዓ.ም ተጠሪንና አመልካችን በማከራከር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም በውሣኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ቀርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በዚህ ክርክር ተካፋይ ያልሆነችው የወ/ሮ አስካለ ወ/አማኑኤል ወራሾችን በክርክሩ ተካፋይ በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥ ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን መልሶ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የላከለት መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመረዳት ችለናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በከፍተኛው ፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የወ/ሮ አስካለ ወ/አማኑኤል ወራሾች እንዲቀርቡ በጋዜጣ ጥሪ አድርጎ ባለመቅረባቸው ጉዳዩን በሌሉበት አይቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ከዚህ በፊት ጥር 23 ቀን 1998 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በወ/ሮ አስካለ ወ/አማኑኤል ወራሾች እንደተሰጠ ይቆጠራል ውሣኔውን የሚያስቀይር ጉዳይ የለም በማለት መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በወረዳ 20 ቀበሌ 40 በቁጥር 320 የተመዘገበው ቤት የአመልካች መሆኑን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) ያቀረቡ መሆኑንና ካርታውም ማህተም ያለውና የአመልካች ስም የተፃፈበት መሆኑን በመግለፅ ቤቱ አመልካች ከአገር ከወጣ በኋላ አልተመለሰም በሚል የህዝብ ደህንነትና ጥበቃ አስተዳደር 1970 የተያዘ መሆኑን ገልፆና ጉዳዩ የሁለት ግለሰቦች ክርክር በመሆኑ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለኝም ያለ በመሆኑ ቤቱ የአመልካች ነው፡፡ ተጠሪ ክርክር ያስነሣውን ቤት ከነቦታው ለይግባኝ ባይ ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ “ይግባኝ ባይ (የአሁን ተጠሪ) ቤቱን እንዴት አገኙ የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ መልስ ሰጭ (የአሁን አመልካች) መልስ ሰጭ ቤቱን ያስረክቡኝ በማለት ክስ ሲመሠርቱ በቅድሚያ ከሚመለከተው አካል ቤቱ የተሰጣቸው መሆኑን አረጋግጠው የቤት ባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡” የሚል ትችት ከሰጠ በኋላ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ በንብረቱ ላይ ጥቅም ወይም መብት ያላቸው መሆኑን አላስረዱም በማለት በትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) በመጥቀስ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ በመጀመሪያ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በጭብጥነት ያልቀረበለትንና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁጥር 46056 ግንቦት 15 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ሽሯል፡፡ ተጠሪ ከዚህ በፊት የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 46056 በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ አላቀረበም፡፡ አሁን ባቀረበው ይግባኝ መነሻ በፊት ተሰጥቶ የነበረ ውሣኔ መሻር መሠረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ስህተት ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 46056 በክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚገባቸውን ወ/ሮ አስካለ ወልደአማኑኤል በማስገባት ከተከራካሪዎች መካከል የቤቱ ባለሀብት ለመሆን የሚያስችለው ማስረጃ ያለው ማን ነው የሚለውን መዝኖ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) ጭብጥ መሥርቶ የመለሰለት ሲሆን ይህንን ውሣኔ ይግባኝ ሣይቀርብበት መሻሩ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ለአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 የሰጠው ትርጉም የአዋጁንና የህጉን ድንጋጌ መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አመልካች ካርታው ሣይለወጥ የቀረው በኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ በብድር መያዣነት ተይዞ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱን መንግስት ወርሶት ሲያስተዳድረው የነበረና ለወ/ሮ አስካለ ወ/አማኑኤል በምትክ ትቶ የተሰጠ ነው፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት መታየት የለበትም፡፡ አመልካች ያቀረቡት የባለቤትነት ካርታ በ1953 ዓ.ም የተሰጠና በሚኒስትሩ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ያልፀደቀ በመሆኑ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የለውም ማስረጃውም በማህተም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያልተረጋገጠ ነው፡፡ ቤቱ 1983 ዓ.ም በቅሎ ቤት አካባቢ ተፈጥሮ በነበረው ከፍተኛ ፍንዳታ ምክንያት የወደመ ሲሆን እኔ ከወ/ሮ አስካለ ወ/አማኑኤል ወራሾች ተከራይቼ ለጋራዥ እየተጠቀምኩበት እገኛለሁ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ክርክር ባስነሳው ቤት ተጠሪ እንዲለቅለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል የክስ ምክንያትና መብትና ጥቅም አለው ወይስ የለውም በሚለው ጭብጥ እልባት ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን ጭብጥ እልባት ለመስጠት አመልካች ያቀረበው ክርክር ከአዋጅ ቁጥር 47/67 አጠቃላይ ግብና አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ማገናዘብና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ሌሎች የህግ ማዕቀፎች መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በቀድሞው ወረዳ 20 ቀበሌ 40 ቁጥር 320 የሆነው ቤትና የቦታው ሥፋት 855 ካሬ ሜትር የሆነው ንብረት ባለቤት መሆኑንና ይህንንም ንብረቱን ለኮንስትራክሽንና ልማት ባንክ በመያዣነት የተያዘ መሆኑን በመግለፅ የተከራከረና ይህንንም የሚያሣዩ ማስረጃዎችን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ጉዳዩን በይግባኝ ላየው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በንብረቱ ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለህ መሆኑን አላስረዳህም በማለት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) በመጥቀስ ውሣኔ የሰጠው የቤቱና የቦታው ካርታና ፕላን አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት የተሰጠና በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በሚኒስትሩ አልፀደቀለትም በሚል ምክንያት ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 ተፈፃሚነትና ውጤት አዋጁ አጠቃላይ ግብና ዓላማና አግባብነት ካላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም አለበት፡፡ የአዋጁ ዓላማ አንድ ሰው ወይም ቤተሠብ ለመኖሪያ የሚሆነው አንድ ቤትና ለድርጅት የሚሆነው አንድ ቤት ካለው ይህንን አንድ ቤት መውረስና የመንግስት ማድረግ እንዳልሆነ በመግቢያው በሰፊው ተዘርዝሯል፡፡ የአዋጁ መሠረታዊ አላማ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንቀፅ 3 “ትርፍ ቤት” በሚለው ትርጉም የሚሸፈንና ከአንድ በላይ የመኖሪያ ቤት ወይም የድርጅት ቤት ያለውን ሰው ቤትና ቦታ በመውረስ የመንግስትና የሕዝብ ንብረት ማድረግና በከተሞች የሚታየውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ማቃለል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ቦታ ያለው ቤተሠብ ወይም ግለሰብ ሌላ መኖሪያ ቤት የሌለው ከሆነ በቦታው ላይ የባለይዞታነት መብት እንደሚኖረው በአዋጁ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 ከላይ የተጠቀሰውን መሠረታዊ ዓላማና አዋጁ ከመታወጁ በፊት አንድ የመኖሪያ ቤትና የይዞታ ቦታ ያላቸው ሰዎች በአዋጁ የተሰጣቸውን መብት ሙሉ በሙሉ በሚያሣጣ መንገድ መተርጎም የለበትም፡፡

ሚኒስትሩ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረትና በአዋጁ አንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በአገሪቱ ከተሞች የሚገኙ ሁሉንም ቤቶች በመመዝገብ አዲስ የባለቤትነት ማስረጃ ለሁሉም በአዋጁ የመኖሪያ ቤት ባለቤት ለመሆን ለሚፈቀድላቸው ሰዎች ሰጥቶ አጠናቅቋል ብሎ መደምደም የማይቻል መሆኑ በዚህ መዝገብና በሌሎች መዝገቦች በቀረቡ ክርክሮች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሚኒስትሩ በነበረበት የማስፈፀም ችግር ወይም ቤቱ በባንክ በመያዣነት በመያዙ ወይም በሌሎች በፍርድ ቤት ሊጣሩና በማስረጃ ሊረጋገጡ በሚችሉ አጥጋቢ ምክንያቶች የቤቱን ባለሀብትነት በማፅደቅ አዲስ የባለቤትነት ማስረጃ ያልሰጠው ሰው በንብረቱ ውስጥ ገብቶ ያገኘውን ማናቸውንም ሰውና በአዋጅ መሠረት ሣይወረስ ቤቱን የያዘውን አካል በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 37 መሠረት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ሰጭ አካል ክስ አቅርቦ ከመጠየቅ የሚገድበው አይደለም፡፡ በያዝነው ጉዳይ ቤቱ በግለሰቦች እጅ በመሆኑ ጉዳዩን አከራክሮ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የሌለው መሆኑን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በዕሑፍ ላመልካች ያሣወቀው መሆኑን ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ስለዚህ አመልካች ከእሱ ፈቃድና ስምምነት ውጭ በቤቱ ውስጥ ገብተውና ቤቱን ይዘው የሚገኙ ሰዎች ከቤቱ ለማስለቀቅና የቤቱ ባለሀብት መሆኑን በፍርድ ለማረጋገጥ በቤቱና መብትና ጥቅም ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 ተፈፃሚነትና ውጤት አጠቃላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ሊያሟላው ከሚፈልገው መሠረታዊ ግብ ከአዋጁ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3 እና ከአዋጁ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል። ከዚህ አንፃር አመልካች ጉዳዩ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንደማይታይ ከተገለፀለት በኋላ የቤቱ ባለሀብት የነበረ መሆኑን የሚያሣይ ካርታና ፕላን በማስረጃነት በማቅረብ ቤቱ ያልተወረሰ መሆኑንና ከቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ቤቱን ለመጠቀም የሚያስችላቸው መብትና ጥቅም የሌላቸው በመሆኑ ቤቱን እንዲለቁለት የመጠየቅ መብት አለው። የቤቱ ባለቤትነት ካርታና ፕላን በሚኒስትሩ አለመፅደቁ በቤቱ ላይ መብትና ጥቅም የለውም ከሚለው መደምደሚያ ላይ አያደርስም። ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 የሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
2. አመልካች ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ አመልካች በቤቱ ላይ መብትና ጥቅም ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ብለናል።
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት አመልካች ቤቱ ላይ መብትና ጥቅም ያለው መሆኑንና ክስ ማቅረብ እንደሚችል በመገንዘብ በይግባኝ በቀረቡለት ሌሎች ነጥቦችንና ክርክሮችን በመመርመርና በመመዘን ውሣኔ እንዲሰጥባቸው ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል።
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ።

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 43081

ግንቦት 6 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ኂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሳሙኤል ጦኖሮ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ አይሻ አርጌሳ (4 ሰዎች) - አልቀረቡም

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው። ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከ1957 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታቸው ስር ያለው ቤት በእርጅና ምክንያት በመፍረሱ ለማደስ ስራ ሲጀምሩ አመልካች ስራው እንዳይጀመር ሁከት ስለፈጠሩ ሁከቱ እንዲወገድላቸው ጠይቀዋል። አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ቤቱ የተጠሪዎች ሳይሆን የአመልካች ባለቤት ወላጆች መሆኑን፣ የባለቤታቸው ወላጆች ወደ ውጪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አገር ሲሄዱ ቤቱን የአመልካች ባለቤት እንዲያስተዳድሩ ውክልና መስጠታቸውን፣የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት በቤቱ በመጀመሪያ በኪራይ በኋላም ኪራይ መክፈል ሲያቅታቸው በነፃ እንዲኖሩበት መፍቀዳቸውን፣ አንደኛ ተጠሪ ባለቤት በ1995 ዓ.ም ታመው አዲስ አበባ ለህክምና እንደሄዱ በዛው መሞታቸውን፣ቤቱ በተጠሪዎች እጅ አለመኖሩን እና ቤቱ በእርጅና ምክንያት በመፍረሱ ፍራሹን ለጐረቤት በአደራ እንዲጠብቁ ማድረጋቸውን በማለጽ ሁከት እንዳልፈጠሩ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱን ጉዳዩን መርምሮ ቤቱ አንደኛ ተጠሪ በይዞታቸው ስር አድርገው እየተጠቀሙበት እንደነበር በምስክሮች ተረጋግጧል በማለት አመልካች የፈጠሩት ሁለት እንዲወገድ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለከምባታና ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ በተመሳሳይ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጐታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው አንደኛ ተጠሪ አካባቢውን ለቀው ከሄዱ ከ15 ዓመት በላይ ቆይቶ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፣የቤቱ ባለቤቶች የአመልካች ባለቤት ወላጆች ስለመሆናቸው በቂ የሰነድ ማስረጃ ቀርቧል፣እነሱ ወደ ውጪ ሲሄዱ ቤቶቹን የአመልካች ባለቤት እንዲያስተዳድሩት ውክልና ሰጥተዋል፣በዚህ መሰረት የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት እንዲኖርበት አድርገዋል እንዲሁም በቤት ውስጥ ተጠሪዎች ስላልነበሩ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር በማለት ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም ክርክር ያስነሳው ጉዳይ የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ሊታይ የሚገባው መሆን አለመሆኑን ይህ ቢታለፍ እንኳን አመልካች ሁከት ፈጥረዋል የመባሉን አግባብነት ማየት እንዲቻል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪዎች ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት ከባለቤታቸው ጋር ከ1957 ዓ.ም ጀምሮ ይዘው የሚገለገሉበት ሁለት ክፍል ቤቶች በእርጅና ምክንያት በመፍረሳቸው ለማደስ ስራ ሲጀምሩ አመልካች ሁከት ፈጥረዋል በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው ቤቱ የአመልካች ባለቤት ወላጆች እንጂ የተጠሪዎች አለመሆኑና ተጠሪዎች የሚኖሩት በሌላ ቦታ እንደነበር እንዲሁም ቤቱ በተጠሪዎች ይዞታ ስር አለመሆኑ ተከራክረዋል፡፡ አንድ ሰው በይዞታው ላይ ሁከት ሲፈጠር ወይም ይዞታው በሃይል ሲነጠቅ ሁከቱ እንዲወገድ ወይም በሃይል የተወሰደው ነገር እንዲመለስ ክስ ማቅረብ የሚችል መሆኑን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149 መመልከት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት ሁከት ተፈጥሮብናል በማለት በመሆኑ ሁከት ተፈጠረበት ያሉበት ንብረት በይዞታቸው ስር እንደሚገኝና በዚህ ይዞታቸው ላይ የሁከት ተግባር የተፈፀመበት ስለመሆኑ ማረጋገጥ ይገባቸዋል፡፡ ይዞታ ማለት ደግሞ አንድ ሰው አንድን ነገር በእጁ አድርጐ በእውነት የሚያዝበት ሆኖ ሲገኝ መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1140 የተመለከተ በመሆኑ ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳውን ቤት በእጃቸው አድረገው ሲያዙበት የነበረ ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ ከክርክሩ ሂደት እንደተረዳነው የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት ቤቱን እስከ 1995 ዓ.ም ድረስ ይኖሩበት እንደነበርና ከዛ በኋላ ታመው ለህክምና አዲስ አበባ ሲሄዱ ቤቱን ለሌላ ሰው አደራ ሰጥተው በመሄዳቸው ቤቱ በተጠሪዎች እጅ አልነበረም፡፡ ተጠሪዎች ለቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰጡት መልስ ባለቤታቸው ታመው ወደአዲስ አበባ ሲሄዱ ቤቱን በአደራ ለሌላ ሰው በአደራ ሰጥተው መሄዳቸውን ግልፀዋል፡፡ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርም አንደኛ ተጠሪ በአላባ ከተማ እየኖሩ ቤቱን እየተመላለሱ ይከታተሉ እንደነበር ምስክሮች ማስረዳታቸው ተመዝግቧል፡፡ ይህም የሚያሳየው ተጠሪዎች በቤቱ ውስጥ ይኖሩ ያልነበረ ወይም ቤቱን በእጃቸው አድርገው በእውነት የሚያዙበት አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ቀድሞውንም ቢሆን ተጠሪዎች ቤቱን በእጃቸው አድርገው የሚያዙበት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149 መሰረት ሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርቡበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ይልቁንም የክርክሩ ሂደት ክርክሩ ከሁከት ጥያቄ ይልቅ ክርክር ያስነሱት ሁለት ቤቶች ባለቤት ማነው? በሚል ጭብጥ ላይ የሚያተኩር ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡ ይህ ጥያቄ ደግሞ ንብረቱ ተገምቶ የባለቤትነት መፋለም ክስ የሚቀርብበት እንጂ የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚቀርብበት ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪዎች በክሳቸው ሁከት ይወገድልኝ በማለት መጠየቃቸው ብቻ የተጠሪዎችን ትክክለኛ ጥያቄ በአግባቡ ሳያገናዝቡና ሳይረዱ ሁከት እንዲወገድ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00928 የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣የከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02325 ሐምሌ 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 23840 ጎንደር 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ሁከት እንዲወገድ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

የሰ/መ/ቁ. 42861

ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አጤነሽ አበበ - ጠ/ታረቀኝ ተፈራ

ተጠሪ፡- አቶ ማንተጋፍቶት አጥላው - ጠ/ደመቀ ሠገደ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለተጠሪ ባለቤት ያከራዩዋቸውን ቤት ባለቤታቸው ሲሞቱ ተጠሪ ይዘው ኪራይ ስላልከፈሉና ቤቱንም ለመመልቅ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ቤቱን እንዲለቁና ኪራዩን እንዲከፍሉ ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ ስለተወሰነ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 04 ክልል የቤት ቁጥር 34 በሆነው ቤት ውስጥ ያለው ለከብት ቤትነት ይጠቀሙበት የነበረውን ቤት በወር 100.00(መቶ ብር) ለተጠሪ ባለቤት አከራይተው ቆይተው ባለቤታቸው በ1992 ዓ.ም ሲሞቱ ተጠሪ ኪራይ ለመክፈልም ሆነ ቤቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ቤቱን እንዲለቁ ኪራይ የአንድ አመት ብር 1200.00(አንድ ሺህ ሁለት መቶ) እንዲከፍሉ እንዲሁም ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ቤቱን እስከሚያስረክቡ ድረስ የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ለቀረበባቸው ክስ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተጠሪ ቤቱን ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን የያዙና ቤቱን በአመልካች ፈቃድ የያዙ ለመሆኑ አመልካች ስላሳዩ ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1149 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ውሳኔው ፀንቶባቸዋል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው ለተጠሪ ሚስት ያከራዩትን የግል ቤታቸውን ተጠሪ እንዲያስረክቧቸው እንጂ ሁከት እንዲወገድላቸው ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ማለቱ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ችሎቱም ግራ ቀኙን ከሚያከራክረው ጉዳይ አኳያ ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149 በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርምር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ቀርበው አመልካች በክሳቸው ቤታቸውን በተጠሪ በኃይል የተያዘባቸው መሆኑን ገልፀው ክስ የመሰረቱ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የሌለበት መሆኑን በመግለፅና በፍሬ ጉዳዩ ላይ ያላቸውን ክርክር በመዘርዘር አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት ተጠሪ ቤቱን ባለቤታቸው ከአመልካች ጋር ባደረጉት የኪራይ ውል ሰበብ ይዘው ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ኪራዩን ከፍለው ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ነው፡፡ ከአመልካች ክስ በግልፅ ማየት የሚቻለው ክሱ ባለሃብት የሆኑበትን ቤት ለማስለቀቅ የቀረበ ባለቤትነትን የመፋለም ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በመልሳቸው አመልካች በክሳቸው ተጠሪ ቤቱን በሃይል መያዛቸውን በመግለፃቸው ክሱ ሁከትን የሚመለከት ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ክስ የመሰረቱት ባለሃብት የሆኑበትን ቤት ለተጠሪ ባለቤት አከራይተው የነበረ ቢሆንም ተጠሪ በዚህ ሰበብ ይዘው አለቅም በማለታቸው ቤቱን እንዲለቁ እንጂ ይዞታዬን በሃይል አስለቅቀውኛል በሚል ያቀረቡት ክስ የለም፡፡ በሃይል ይዘዋል ማለታቸው ብቻ ክሱን የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያሰኘው አይደለም፡፡ ባለሃብት የሆነው ሰው መብት ሳይኖረው እጁ ካደረገው ሰው ወይም ከያዘው ሰው ላይ ሃብቱ ይገባኛል ሲል ለመፋለም እና ማናቸውንም የሃይል ተግባር ለመቃወም እንደሚችል ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1206 መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ፍ/ቤት ግን የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው ይዞታን የሚመለከተውን የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149"ን" መሰረት አድርጎ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ይዞታው በሃይል የተወሰደበት ወይም ሁከት የተፈጠረበት ሰው ለሚያቀርበው ክስ ነው፡፡ ይዞታና ባለቤትነት የሚመለከቱ ጉዳዮች የተለያዩ እንደመሆናቸው የሚሸፈኑት በተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች ነው፡፡ በተያዘውም ጉዳይ አመልካች ክስ የመሰረቱት ባለቤትነትን የሚመለከት በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በይዞታ ድንጋጌዎች ጉዳዩን አይቶ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በዋናው ጉዳይ ላይ ዝርዝር ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ዋናው ጉዳይ በስር ፍ/ቤት ክርክር ተደርጎበት የተወሰነ ባለመሆኑ በአሁኑ ደረጃ የሚታይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 70007 ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 65433 ጥቅምት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡ በመሆኑም በፍሬ ጉዳዩ ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት ጉዳዩን ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 48048

ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ ወ/ሮ ገብርኤላ ኪካላ ቶማስ ናክሶ - ጠበቃ አስቴር አርአያ ቀረቡ

ተጠሪ፣ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ሚካኤል ጌታቸው ቀረቡ

ፍ ር ድ

አመልካች ተጠሪ በአደራ ያዘ የሚሉትን ቤታቸውን እንዲመልስላቸው ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በመባሉ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የአባታቸው ንብረት የነበረና በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 10 ክልል ውስጥ የሚገኘው ፎቅና ምድር የሆነ የመኖሪያና የድርጅት ቤት አባታቸው ሲሞቱ ልጆቻቸው በአገር ውስጥ ባለመኖራቸው የቤቶቹን ቁልፍ በግሪክ ኤምባሲ እጅ ቆይቶ በመጨረሻ ተጠሪ ቤቱን ከነንብረቱ ወራሾች እስኪመጡ ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በአደራ ተረክቦ በማከራየት ላይ የሚገኝ በመሆኑና የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴርም ቤቱን ተጠሪ ተረክቦ ወራሾች ሲመጡ ቤቱን ባለበት ሁኔታ ለወራሾች እንዲያስረክብ ትዕዛዝ የሰጠ በመሆኑና አመልካችም ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ቢቀርቡም ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ቤቱን በቤቱ ውስጥ ከነበሩት ንብረቶች ጋር እንዲያስረክባቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም አመልካች ቤቱን የሚመለከት የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስላላቀረቡ የመክሰስ መብት የላቸውም እንዲሁም ክሱ የቀረበው ክርክር የተነሳበትን ቤት ተጠሪ ከያዘው ከአስር አመት በኃላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው የሚሉ የመጀመሪያ መቃወሚያዎች አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ ያደረገ ሲሆን አመልካች እስከ ፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቀርበው ተከራክረው በቤቱ ላይ መብት ወይም በጥቅም ስላላቸው ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወሰን ጉዳዩ ለስር ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡ በዚህ መሠረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በድጋሚ ካየ በኃላ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ መሠረት ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆኑም በውል ህግ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ስለሚሆኑና አመልካች በውርስ የሚገኝ ንብረት ያለአግባብ በተጠሪ ተይዞብኛል ብለው ያቀረቡት የመብት ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 መሠረት በአስር አመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ሲገባው ከ25 አመት በላይ ቆይተው ያቀረቡ በመሆኑ ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ብይን ላይ ነው ፡፡ የአመልካች ዋነኛ ቅሬታ ተጠሪ ቤቱን የተረከበው ወራሾች እስከሚመጡ በአደራ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ችሎቱ የግራቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ ተጠሪ በክርክሩ የአመልካች አባት የሞቱት በ1973 ዓ.ም በመሆኑና አመልካች ክስ የመሠረቱት በ1998 ዓ.ም በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1677/1/ እና 1845 መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብሏል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካች ክስ የመሠረቱት የአባታቸውን ንብረት አባታቸው ሲሞቱ ወራሾቻቸው እስከሚመጡ ተጠሪ በአደራ ተረክቦ እያስተዳደረው የቆየ በመሆኑና አመልካች ወራሽነታቸው አረጋግጠው ስለቀረቡ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክባቸው ነው፡፡ ስለሆነም የአመልካች ጥያቄ በይዘቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 999 “ገ” መሠረት ያደረገ የወራሽነት ጥያቄ ሳይሆን ተጠሪ በአደራ ተረክቦ የሚያስተዳድረውን ቤት እንዲያስረክብ የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የአመልካች ጥያቄ መታየት የሚገባው አደራን በሚመለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ መሆን አለመሆኑን ስለአደራ ከተመለከቱት የፍ/ብ/ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ እንመለከታለን፡፡ አደራ ማለት አደራ ተቀባዩ የአደራ አስቀማጩን እቃ ተቀብሎ በአደራ ጠባቂነት እንዲያስቀምጥለት የሚገባ የውል ግዴታ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2779 ይናገራል፡፡ አደራ ተቀባዩም እቃውን ይዞ የሚጠብቅ እንጂ የእቃው ባለቤት ሆኖ የሚቆየው አደራ ሰጪው ነው /የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2781/1/፡፡ በሌላ በኩል አደራ ተቀባዩ በአደራ የሚጠብቀውን እቃ መመለስ ስለሚገደድበት የጊዜ ገደብ ስንመለከት አደራ ተቀባዩ በአደራ የተቀበለውን እቃ የሚመልስበት የጊዜ ገደብ በውሉ ተመልክቶ ከሆነ ይህ ጊዜ ሲያበቃ እቃውን መመለስ የሚገባው ሲሆን /የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2781/2/ ይመለከታል/ በውሉ ላይ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ ከሌለ ግን አደራ ሰጪው እንደጠየቀ ወዲያውኑ እቃው እንደሚመልስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2989/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ የህጉ ድንጋጌ አደራ ተቀባዩ እቃውን የሚመልስበት የጊዜ ገደብ ከሌለው በቀር አደራ ሰጪው በአደራ እንዲቀመጥ የሰጠው እቃ ያለምንም የጊዜ ገደብ በማንኛውም ጊዜ እንዲመለስለት ለመጠየቅ እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሚከራከሩት ተጠሪ ቤቱን በአደራ የያዘው ወራሾች እስከሚመጡ በማለት ነው፡፡ ከዚህም ክርክር ተጠሪ በአደራ ተረክበ የተባለውን ቤት የሚመለስበት የጊዜ ገደብ ተወስኖ አለመቀመጡን መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ተጠሪም የጊዜ ገደብ ተወስኖ ተቀምጧል በማለት ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ቤቱ እንዲመለስላቸው ይርጋ ሳያግዳቸው በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ በእርግጥ ተጠሪ በዚህ የሰበር ችሎት በተደረገው የቃል ክርክር ቤቱን በአደራ መያዛችንን በስር ፍ/ቤት አላምንም በማለት ተከራክሯል፡፡ ይህ ችሎትም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቢሆን የአመልካች ክስ አደራን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በይርጋ አይታገድም አለ እንጂ ተጠሪ ቤቱን በአደራ ይሏል ወደሚለው መደምደሚያ ላይ አልደረሰም፡፡ ተጠሪ ቤቱን አመልካች በክሳቸው እንደገለፁት በአደራ የያዘው ነው ወይስ አይደለም? ቤቱንስ ሊያስረክብ ይገደዳል? ወይስ አይገደድም? የሚለው ክርክር ወደፊት ፍ/ቤቱ የግራቀኙ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የሚወሰነው ነው፡፡

ሲጠቃለል የአመልካች ክስ ተጠሪ በአደራ የያዘውን ንብረት እንዲመልስላቸው ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ይህንን የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአግባቡ ሳይረዳ ክሱ የወራሽነት ጥያቄን የሚመለከት ነው በማለት ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ እና 1845 "ን" መሠረት በማድረግ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል የሰጠው ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 48823 የካቲት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45911 ሰኔ 17 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ቤቱን በአደራ የያዘው ነው? አይደለም? ቤቱንስ ሊያስረክብ ይገደዳል? አይገደድም? የሚለውን ጉዳይ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ነው ያለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48783

ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ ወ/ሮ ሶፊያ ሁሴን - ጠ/አሉወርቅ ደጀኔ ቀረቡ

ተጠሪዎች፣ 1. የአራዳ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር - ነ/ፈጅ ሰሎሞን ተመቸው --ቀረቡ

2. አቶ ገዛኸኝ ሀብቴ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመተላለፊያ መንገድ የማግኘት ጥያቄ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአመልካች ከሣሽነት ነው የዳኝነት ጥያቄያቸውም የመተላለፊያ መንገድ ስለጠበባቸው ለአስተዳደሩ አመልክተው ከሁለተኛ ተጠሪ 1.10 ሜትር ተቀንሶ መንገድ እንዲያገኙ በአስተዳደሩ ከተወሰነ በኃላ ባልታወቀ ምክንያት አፈፃፀሙ በአንደኛ ተጠሪ ስለታገደ እና ሁለተኛ ተጠሪም የፈረሰውን አጥር መልሶ እያሰራ ስለሆነ ሁከት ተወግዶ በቀድሞ የአስተዳደሩ ውሣኔ መሠረት መንገዱ እንዲከፈት እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

አንደኛ ተጠሪ ሥር ፍ/ቤት የሰጠው መልስ የአስተዳደሩ ውሣኔ አፈፃፀም በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ከሚያደርስው ጉዳት አንፃር ቴክኒካዊ መፍትሔ በአስተዳደሩ ባለሙያዎች ቀርቦ አመልካች ባለመስማማታቸው ሊፈጸም ያልቻለ መሆኑን ሲገልፅ በሁለተኛ ተጠሪ በኩል ሥር ፍ/ቤት የቀረበው መልስ ለሚፈርሰው አጥርና ቤት እንዲሁም ለሚቀንስበት ይዞታ አመልካች ካሣ እንዲከፍሉ በአስተዳደሩ የተሰጠውን ውሣኔ ባለመፈፀማቸው አፈፃፀሙ እንዲታገድ መደረጉ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1221 በተደነገገው መሠረት አመልካች /የሥር ከሣሽ/ በቂ መተላለፊያ ለማግኘት ለባለይዞታው ተገቢውን ማካካሻ መክፈል ሲገባቸው ይህንን ለመፈጸም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መንገድ እንዲከፈትላቸው ማስገደድ አይችሉም በማለት የዳኝነት ጥያቄውን ውድቅ አድርጓል፡፡

የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና የሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ውሣኔ አፅንተዋል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ሲሆን የአመልካች ጠበቃ ጸጉሜ 2 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት አቤቱታ የመተላለፊያ መንገዱን አጠር ለማስገመት ለባለሙያ ሃምሣ ብር /50/ አመልካች መክፈላቸውን ገልፀው ከሁለተኛ ተጠሪ ይዞታ ላይ ለሚቀነሰው 1.10 ሜትር የአጥር ግምት ኪሣራ ለሁለተኛ ተጠሪ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ጠቅሶ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ተሽሮ ሁለተኛ ተጠሪ አጥር እንዲያፈርስ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ አመልካች የጉዳት ኪሣራ እከፍላለሁ እያሉ የመተላለፊያ መንገድ መከልከላቸው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ተጠሪዎችን አስቀርቧል፡፡ ነ/ፈጅ ስለአንደኛ ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ሥር ፍ/ቤት ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማካካሻና የአጥር ግምት ለመክፈል ፈቃደኛ አልነበሩም ፍርድ ቤቶቹም ይህንኑ አረጋግጠዋል፤ በዚህ ሰበር ላይ የቀረበው አዲስ ክርክር ነው በማለት ኪሣራ ተወስኖ መዝገቡ እንዲዘጋ ጠይቋል ሁለተኛ ተጠሪ በበኩሉ የመተላለፊያ መንገድ ለመክፈት በአመልካች በኩል እንዲፈፀም የቀረበውን መፍትሄ ባለመፈፀም ግዴታቸውን ሳይወጡ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡

እኛም የግራቀኙን ክርክር እና ሕጉን በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መረዳት የተቻለው አመልካች መንገድ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ በአስተዳደሩ ተቀባይነት አግኝቶ በተጓዳኝ ደግሞ አመልካች ሊፈጽሙት የሚገባ ግዴታ በአስተዳደሩ በኩል የተወሰነ ስለመሆኑ ነው፡፡ በአስተዳደሩ የተወሰነው የኪሣራ ገንዘብ ለመክፈል አመልካች ፈቃደኛ መሆናቸውን በሰበር አቤቱታ የገለፀ ሲሆን በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ክርክር አመልካች ፈቃደኛ እንዳልነበሩ በሥር ፍ/ቤት ተረጋግጧል የሚል ነው፡፡ በእርግጥም አመልካች በአስተዳደሩ የተወሰነውን ለመፈጸም ፈቃደኛ ያለመሆናቸው የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው አረጋግጧል፡፡ አመልካች እዚህ ሰበር ችሎት ላይ ያቀረቡት ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ ሥር ፍ/ቤት ያልተረጋገጠ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ግዴታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔን መቃወማቸው በሕጉ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡

የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው በግልፅ ያመለከተው አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1221 መሠረት ተጠሪ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተገቢውን ካሣ ሳይከፍሉ ተጠሪ መንገድ እንዲሰጣቸው ሊያስገድዱ እንደማይችሉ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች በአስተዳደሩ የተወሰነው የመካካሻ ግዴታ ሳይወጡ ተጠሪን ማስገደድ አይችሉም የሚለው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የሚፈልግባቸው ተነፃፃሪ ግዴታ በአስተዳደሩ ውሣኔ መሠረት ከፈፀሙ በሕጉ መሠረት የመተላለፊያ መንገድ የማግኘት መብታቸው ወደፊትም ሊጠይቁ አይችሉም ተብሎ ውሣኔው የመጨረሻ ሊሆን አይገባም ምክንያቱም አመልካች እዚህ ሰበር ላይ እያቀረቡ ያለው ክርክር ካሣ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆናቸው እና በማንኛውም አካል ያለመጠየቃቸውን የሚያመለክት ሆኖ ስላገኘነው ነው፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ አሁን ባለበት ሁኔታ እንዲፀና ብለን ይህ ውሣኔ ግን የአመልካችን መብት እስከመጨረሻው የሚያሳጣ ሊሆን የሚገባ አይደለም ብለናል፡፡ በዚሁ መሠረት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03564 በ23/3/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09112 በ12/06/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 9816 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በአስተዳደሩ ውሣኔ መሠረት ግዴታቸውን ከተወጡ በኃላ የመተላለፊያ መንገድ የማግኘት መብታቸውን ይህ ውሣኔ አይከለክልም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጭ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39601

ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - አክሊሉ ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ገዛኸኝ መንግስቱ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በመዝገቡ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ለንግድ የሚውሉ እህሎችን ይዞ የነበረው መጋዘን በመታሸጉ ምክንያት ደርሶአል የተባለውን ጉዳት(ኪሣራ) ለማስከፈል በሚል የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ አቅርቦት የነበረው ክስ የተለያዩ እህሎችን ሲነግድበት የነበረው የንግድ ቤት መጋዘን ከሕግ ውጪ አሸጐ ሁከት የፈጠረበት መሆኑን፣በዚህ ምክንያትም ሁከቱ ይወገድለት ዘንድ በፍ/ቤት ክስ መመስረቱን፣አመልካች ለክሱ መልስ እንዲሰጥ ታዞ መቅረቡና ክርክር መደረጉን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ሁከቱ ይወገድ ሲል በመወሰኑ መጋዘኑ መከፈቱን በአንድ በኩል ሲገልጽ፤በሌላ በኩል ደግሞ የቀረበው ክስ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ መጋዘኑ ለአራት ወር ያህል ተዘግቶ በመቆየቱ ምክንያት በእህል ዋጋ ረገድ ደረሰ የተባለው ኪሣራ ብር 9,959(ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ) እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ተጠሪ የጠየቀውም ይኸው ብር 9,959(ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ) ከወለድና የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፈለው እንዲወሰንለት ሲሆን፣ፍ/ቤቱም በጥያቄው መሰረት ወስኖለታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በዓፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረም ዘንድ አቤቱታ አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ክርክሩን አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ተጠሪ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ክስ የመሰረተው ሁለት ጊዜ ነው፡፡ የመጀመሪያው ከሕግ ውጪ ተደረገ የተባለውን እሸግ እንዲነሳለት የሚጠይቅ ሲሆን፣ሁለተኛው ደግሞ መጋዘኑ በመታሸጉ ምክንያት ደረሰ ያለውን ኪሣራ እንዲከፈል የሚጠይቅ ነው፡፡ የኪሣራው መጠን ያሰላው የእሕሉን የመሸጫ ዋጋ ነው(ነበር) ያለውን መሰረት በማድረግ እንደሆነም በክሱ ተመልክቶአል፡፡ አመልካች በበኩሉ በሁለተኛው ክስ የተጠየቀው ኪሣራ በመጀመሪያው ክስ ሊጠየቅ ይገባው የነበረ በመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ኪሣራው በእርግጥ ለመድረሱ ማስረጃ እልቀረበም የሚል የፍሬ ነገር ነጥብ በማንሳት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱ ሁለቱንም የመከራከሪያ ነጥቦች አልተቀበለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱን ያስተናገደው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዳየነው ተጠሪ በመጋዘኑ መታሸግ ምክንያት በእህሉ ላይ የደረሰውን ብልሽት ወይም ኪሣራ የሚያሳይ ማስረጃ እንዳላቀረበ ፍ/ቤቱ ስለመገንዘቡ በውሳኔው ላይ በግልጽ አመልክቶአል፡፡ "... ከሣሽ ከተለየ የእህል ንግድ ላይ ያጣውን የገንዘብ መጠን አሟልቶ በዚህ ላይ መዘረዘሩ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ረገድ ይህንን ያሕል ገቢ ለማግኘቱም ሆነ ለማጣራቱ የተመሰከረ ነገረ የለም፡፡ ይህንን የራሱን ገቢ ተከሣሽ በክርክሩ ላይ እንደተቃወመው የተመዘገበ የገቢ ግብር የተከፈለበት ለመሆኑ ማስረጃ የለም.." በማለትም በውሳኔ ሐተታው ላይ ተችቶአል፡፡ የደረሰበት መደምደሚያ ይህ እንደሆነ ከገለጸ በኋላም ነው ተጠሪ ካሣ(ኪሣራ) ይገባዋል በማለት ገንዘብ እንዲከፈል የወሰነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ፍ/ቤቱ በተጠሪ ላይ ኪሣራ ለመድረሱ ምንም አይነት ማረጋገጫ አላገኘም፡፡ ይህንንም እንዳመነበት በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ ገንዘቡ መከፈል አለበት ለማለት የቻለው በእርግጥም ኪሣራው ስለመድረሱ በተጨባጭ ማስረጃ አረጋግጦ ሳይሆን፣መጋዘኑ ታሽጐ ከቆየ ተጠሪ ያጣው ማስረጃ አረጋግጦ ሳይሆን፣መጋዘኑ ታሽጐ ከቆየ ተጠሪ ያጣው ነገር የለም ለማለት አይቻልም ከሚል ግምት በመነሳት እንደሆነ በውሳኔው ማጠቃለያ ላይ በግልጽ አመልክቶአል፡፡ ኪሣራ ሊከፈል የሚችለው ጉዳት ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2090 እና 2091 ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ግን የደረሰ ጉዳት ለመኖሩ በምንም አይነት መንገድ አልተረጋገጠም፡፡ በመሆኑም ክሱ ለሁለተኛ ጊዜ እንደቀረበ ይቆጠራል ከሚል መነሻ አመልካች አቀርቦት የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቢታለፍ እንኳ በክርክሩ ፍሬ ነገር ተገብቶ የደረሰ ጉዳት አለ ለማለት የሚያስችል የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት ስለሌለ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07105 ኅዳር 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47571 ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው ኪሣራ የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42962

ታህሣሥ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አየለ አድማሱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አጀቡ ሹሜ ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጉዳት ካሳን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የተጠሪ መኪና ገጭቶ የአካል ጉዳት ስላደረሰባቸው ጉዳት ካሳ ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ) እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ የጉዳት ካሳው መጠን የተጋነነ ነው፣አደጋው በአመልካች ላይ ቀሪ የአካል ጉዳት ለደረሰ በመሆኑና ለህክምና ያወጡት ወጪ ከግንዛቤ ሳይገባ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪ መኪና አመልካችን ገጭቶ በአካላቸው ላይ 18% ጉዳት ማድረሱን ካረጋገጠ በኋላ አመልካች ከጉዳቱ በፊት ገቢ ያገኙ እንደነበር ስላላስረዱ በአደጋው ምክንያት ያጡት የገንዘብ ጥቅም ስለሌለ የሚከፈላቸው የጉዳት ካሳ አይኖርም በማለት የአመልካችን የካሳ ጥያቄ ውድቅ አድርጐታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱ ተረጋግጦ እያለ የጉዳት ካሳ ሊከፈላቸው አይገባም የተባለበትን የሕግ አግባብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው የተጠሪ መኪና አመልካችን ገጭቶ የአካል ጉዳት ያደረሰባቸው ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም ቢሆኑ መኪናቸው አመልካች ላይ ጉዳት ማድረሱን አልካዱም፡፡ አንድ ተሽከርካሪ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ ከተገኘ የተሽከርካሪው ባለቤት ለጉዳቱ አስተዋፆ ባይኖረውም እንኳን የመኪናው ባለቤት በመሆኑ ብቻ ለደረሰው ጉዳት አላፊነት እንደሚኖርበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2981/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ ምክንያት ተጠሪ ጥፋት ባይኖርባቸው እንኳን አመልካች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት የአደጋው አድራሽ መኪና ባለቤት በመሆናቸው ብቻ የጉዳት ካሳ የመክፈል ሃላፊነት አለባቸው፡፡ የስር ፍ/ቤትም ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊ መሆናቸውን ተቀብሏል፡፡ አከራካሪ የሆነው አመልካች የጉዳት ካሳ ሊከፈላቸው ይገባል አይገባም የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ምንም እንኳን አመልካች የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ቢሆን ከጉዳቱ በፊት ገቢ ያገኙ እንደነበር ስላላረጋገጡ ያጡት የገንዘብ ጥቅም ስለሌለ ካሳው ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡ ይህ የፍ/ቤቱ ውሳኔ አንድ ሰው በደረሰበት አደጋ ምክንያት የአካል ጉዳት ቢደርስበት ካሳ ሊከፈለው የሚገባው ከአደጋው በፊት ገቢ የሚያገኝ መሆኑና ይህም ገቢው የተቋረጠ መሆኑን ካስረዳ ብቻ ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚወስድ ነው፡፡ ይህም ድምዳሜ በዋናነት የሚያሳይው የታጣ የገንዘብ ጥቅም ከሌለ በቀር ምንም አይነት የአካል ጉዳት ቢደርስ ካሳ ሊከፈል የማይገባው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ችሎቱ የጉዳት ካሳ የሚከፈለው መቼ ነው? የሚለውን ጭብጥ መርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 14 ሥር “ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት የመኖር፣የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው” (ሰረዝ የተጨመረ) ተብሎ የተቀመጠ ሲሆን አንቀጽ 16 የአካል ደህንነት መብት ምን እንደሆነ ያብራራል፡፡ ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት እንዳለው የሃገሪቱ የበላይ ሕግ ያስገነዝባል፡፡ መንግስትም ሆነ ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው የአካል ደህንነት የመጠበቅ የሕግ ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ህግ በመተላለፍ በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለደረሰው የአካል ጉዳት ተጐጂው ካሳ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ በህገ-መንግስቱ የተቀመጠው ይህን የሰብአዊ መብት ከሚያረጋግጡ ዝርዝር ሕጐች ውስጥ በፍ/ሕጉ ውስጥ የጉዳት ካሳን አስመልክቶ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ይገኙባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰው በጥፋቱ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ላደረሰው ጉዳት አላፊ ሆኖ ካሳ ሊከፍል እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2028 አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም በመርህ ደረጃ የጉዳት ካሳ ሊከፍል የሚገደደው በጥፋቱ ጉዳት ያደረሰ ሰው ሲሆን በአንዳንድ የተለያዩ ጉዳዮች ደግሞ አንድ ሰው ጥፋት ሳይኖርበትም ኃላፊ እንደሚሆን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2066 እና ተከታዮቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ህጉ ለይቶ ካስቀመጣቸው ጉዳዮች አንዱ የተሸከርካሪ ባለቤት ተሸከርካሪው ላደረሰው ጉዳት ጥፋት ሳይኖርበት አላፊ እንደሚሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2081/1/ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በሌላ ሰው አካል ላይ ለደረሰ ጉዳት አላፊ የሆነ ሰው ለደረሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ግዴታ በፍ/ሕጉ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሊታይ የሚገባው የካሳው መጠን ነው፡፡ ለጉዳቱ አላፊ የሆነ ሰው የሚከፍለው የካሳ መጠን ከጉዳቱ ጋር ተመዛዛኝ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090 እና 2091 ስር ተመልክቷል፡፡ ወደፊት ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ጉዳት የተረጋገጠ ከሆነ እስኪፈፀም መጠበቅ ሳያስፈልግ ካሳው ሊከፈል እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2092 ይናገራል፡፡ በሌላ በኩል ካሳ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን አለበት ሲባል መታየት ያለበት በአጠቃላይ በተጐጂው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ የመስራት ኃይል ቅነሳ አንፃር እንጂ ከጉዳቱ በፊት ሲሰራው የነበረውን ስራ ላለመስራት ጉዳቱ ያስከተለው ልዩ ጫናና የቅነሳ መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት አለመሆኑን ለዚህም ምክንያት የሚሆነው እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ስራ ለመስራት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ አንድ ሰው ለመኖር የተለያየ ፋይዳና ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ እንደሆነ ይህ የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 19338 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት 18% ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍ/ቤት አመልካች ላይ ጉዳት መድረሱን ቢያረጋግጥም ከፍ ሲል እንደተገለፀው ከጉዳቱ በፊት ገቢ ያገኙ እንደነበር አላስረዱም በሚል ካሳ ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡ ነገር ግን ጉዳት መድረሱ በተጨባጭ እስከተረጋገጠ ድረስ ለተጐጂው ከደረሰበት ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ሊከፈለው ይገባል፡፡ ምክንያቱም መታየት ያለበት ተጐጂው ከጉዳቱ በፊት ያገኘው ገቢ ሳይሆን በጉዳቱ ምክንያት ወደፊት በመስራት ችሎት ላይ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ ነው፡፡ አመልካች ላይ የደረሰው አካል ጉዳት ሙሉ ለሙሉ የመስራትን ችሎታቸውን ያሳጣ ነው ባይባልም በ18% በመቶ የመስራት ችሎታቸውን የቀነሰ ስለመሆኑ በሕክምና ተረጋግጧል፡፡ በእርግጥ ለዚህ ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ለመወሰን አስቸጋሪ ቢሆንም የካሳውን መጠን በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ የካሳው መጠን በርትእ ሊወሰን እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2102/1/ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አመልካች ላይ ጉዳት መድረሱና ጉዳቱም 18% የመስራት ችሎታቸውን መቀነሱ ስለተረጋገጠ የካሳውን መጠን በትክክል ማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳን በርእት መወሰን ሲቻል አመልካች ገቢ ያልነበራቸው በመሆኑ ብቻ ካሳ አይከፈላቸውን ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የጉዳት ካሳ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት 107806 ሚያዚያ 24 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 68949 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ላይ 18% የአካል ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ በርትእ ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 43843

መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ዶ/ር ተስፋነሽ በላይ - ጠበቃ አቶ ይርሣው ጌትነት ቀረቡ

ተጠሪ፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ነገረፈጅ መኮንን ሽፈራው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ ያታየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ የመድን ሽፋን የሰጠሁት የሰሌዳ ቁጥር 3-15680 የሆነውን መኪና ንብረትነቱ የተከሳሽ (የአመልካች) የሆነው የሰሌዳ ቁጥር 2-4443 አ.አ የሆነው መኪና ጥቅምት 12 ቀን 1999 ዓ.ም በመግጨት ጉዳት አድርሶበታል፡፡ ጉዳቱ ያደረሰውም የተከሳሽን (አመልካችን) መኪና ያሽከረክር በነበረው ሰው ጥፋት ምክንያት መሆኑ በትራፊክ ሪፖርትና መርመራ የተረጋገጠ ነው፡፡ ከሳሽ (ተጠሪ) ባሉበት የውል ግዴታ መሰረት ብር 116,735.49 (አንድ መቶ አስራ ሰድስት ሺ ሰባት መቶ ሰላሣ አምስት ብር ከአርባ ዘጠኝ ሣንቲም) ወጭ በማድረግ የደንበኛውን መኪና አስጠግኖ ያስረከበ ስለሆነ ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው የእኔን መኪና ያሽከረክር የነበረው ሰው በወንጀል ተከስሶ ነፃ በመሆኑ ጉዳቱ የደረሰው የእኔን መኪና በሚያሽከረክረው አሽከርካሪ ጥፋት ሣይሆን የከሳሽን መኪና በሚያሽከረክረው አሽከርካሪ ጥፋት ነው፡፡ ጉዳቱ በሁለት ተሽከርካሪዎች ግጭት የተከሰተ በመሆኑና የእኔም መኪና ጉዳት ደርሶበት በንብ ኢንሹራንስ የተጠገነ በመሆኑ የየራሳችንን መቻል ይገባናል፡፡ ተጠሪ(ከሳሽ) ፐርፎርማ ሣይሰበሰብ በሞኤንኮ ኩባንያ ብቻ ጥገናው እንዲከናወን ያደረገ በመሆኑ በቂ ማስረጃ አላቀረቡም የትራፊክ ፖሊስ የምርመራ መዝገብ ቀርቦ ይታይልኝ በማለት የተከራከሩ ሲሆን ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያም በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ አለኝ የሚለውን ክርክር አቅርቧል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ያቀረበውን የትራፊክ ፖሊስ የምርመራ ሪፖርት ከመረመረ በኋላ አመልካች የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ይቅረብ ብለው ያቀረቡት ጥያቄ የምርመራ መዝገቡ ከቀረበው ሪፖርት የተለየ የሚያስረዳ ስለመሆኑ አልገለፁም ስለዚህ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ የአመልካችን መኪና የሚያሽከረክረው ሹፌር በወንጀል ተከስሶ ነፃ መውጣቱ የፍትሐብሔር ኃላፊነትን የሚያስቀር አለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2149 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ሹፌር ጥፋት ምክንያት መሆኑ ስለተረጋገጠና አመልካች የመኪናው ባለቤት በመሆናቸው ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት ይጠየቃሉ በማለት ከወሰነ በኋላ የካሣውን መጠን በተመለከተ አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር እንደዚሁም ሌሎች ወጭዎችን ይክፈሉ፣ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ውስጥ ጣልቃገቡ ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ ብር 75,000/ሰባ አምስት ሺህ ብር/ ይከፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የእኔ መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር በወንጀል ተከስሶ ነፃ ሆኖ እያለ የወንጀል መዝገብ አስቀርቦ ማይመለከት ኃላፊነት አለባችሁ ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ለመኪና መለዋወጫ አውጥቻለሁ በማለት ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ ታአማኒነት የሌለው ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት ተቀብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት በርካታ የሕግና የፍሬ ጉዳይ ስህተት ፈጽሞ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማያርም ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጉዳቱ የደረሰው የአመልካችን መኪና ያሽከረክር በነበረው ሹፌር ምክንያት መሆኑን የተሻለና ሚዛን የሚደፋ ማስረጃ በማቅረብ አስረድተናል፡፡ የፍርድ ቤት የወንጀል ውሣኔ በእኛ በኩል ያቀረበውን የትራፊክ ምርመራ ሪፖርት የሚያስተባብል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የማስረጃ አቀራረብ ስርአትን ተከትለው በስር ፍ/ቤትም ሆነ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን ማስረጃ የበታች ፍርድ ቤቶች እንዳለፉባቸው በመግለጽ በሰበር አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር ህጋዊ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በማለት መልስ ሰጥቷል አመልካች በጽሑፍ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመንው አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ማስረጃ ማያስቀርብና የእኔን መኪና የሚያሽከረክረው ሰው ከወንጀል ክስ ነፃ ሆኖ እያለ ለጉዳቱ ኃላፊነት አለብሽ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረቡትን የመከራከሪያ ሐሳብ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ምላሽ ማግኘት ያለባቸው ነጥቦች ሆኖ አግኝተናቸዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ አመልካች ተጠሪ ያቀረበባቸውን ክስ ለመከላከል በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 234 እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 223 ድንጋጌዎች መሰረት ያቀረቡትን የማስረጃ ዝርዝር ተመልክተናል፡፡ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት የካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ የትራፊክ ፖሊስ የምርመራ መዝገብና አቃቤ ሕግ በቁራ ምድብ ችሎት የወንጀል ክስ አቅርቦ የተከራከረበት የፍርድ ቤት መዝገብ ፍርድ ቤቱ በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 145 መሰረት የጠየቁ መሆኑን በተራ ቁጥር 1 እና በተራ ቁጥር 2 ካቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር ለመረዳት ችለናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እነዚህን መዝገቦች አስቀርቦ ማየት ያላስፈለገበትን ምክንያት በውሣኔው በግልጽ አስፍሯል፡፡ አመልካች እንዲቀርብላቸው የጠየቁት የትራፊክ ፖሊስ የምርመራ መዝገብ በትራፊክ ፖሊስ የሚመለከተው ክፍል ተዘጋጅተው ከተላከው የትራፊክ ፖሊስ ምርመራ ውጤትና መግለጫ ከተገለፀው ፍሬ ጉዳይ ምን የተለየ ፍሬ ጉዳይ ሊያስረዳ እንደሚችል ባቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ አለመገለፁን እንዲሁም የወንጀል ችሎት የአመልካች መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሰውና በዓቃቤ ሕግ መካከል ክርክር የተደረገበት መዝገብ አሽከርካሪው በወንጀል ተከስሶ ነፃ ከመሆኑ ውጭ ሌላ የሚያስረዳው ፍሬ ነገር ያለ መሆኑን የማስረጃ ዝርዝር መግለጫው የማያሣይና በወንጀል ነፃ መሆን የፍትሐብሔር ተጠያቂነት እንደማያስቀር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2149 የተደነገገ መሆኑን በመግለጽ ውሣኔ እንደሰጠ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አመልካች አንድ ማስረጃ ቢቀርብ ምን አይነት ጭብጥ ሊያስረዳላቸው እንደሚገባ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 223 እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 145/2/ ድንጋጌዎች መሰረት በመግለጽና በመዘርዘር የመጠየቅ ግዴታና ኃላፊነት አለባቸው፡፡ አመልካች መዝገቦቹ ቢቀርቡ ለሥር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ከቀረበው የትራፊክ ፖሊስ የምርመራ ውጤት መግለጫ ሊያስረዱ የሚችሉት የተለየ ፍሬ ጉዳይ ስለመኖሩ ማያረጋግጡና ማይገልጹ እንደዚሁ በደፈናው መዝገቦቹ ቀርበው ይታዩልኝ በማለት በማስረጃ ዝርዝር መግለጫው ስለጠየቁ ብቻ የሥር ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 145 መሰረት መዝገቦቹን የማስቀረብ ግዴታና ኃላፊነት የለበትም፡፡ ፍርድ ቤቱ መዝገቦቹ እንዲቀርቡ ትእዛዝ የሚሰጠው ይቅረቡ የተባለው ማስረጃ ከክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ ጋር ያለውን አግባብነትና ማስረጃው ቢቀርብ ሊያረጋግጥ የሚችለው ፍሬ ጉዳይ በመጀመሪያ ማስረጃው ይቅረብልኝ የሚለው አካል በበቂ ሁኔታ ዘርዝሮና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

145 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት አረጋግጦ ሲጠይቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በፍትሐብሔር በሥነ- ሥርአት ሕግ ቁጥር 145/2/ ድንጋጌዎች መሰረት እንዲቀርቡ የጠየቋቸው ማስረጃዎች ምን አይነት ፍሬ ጉዳይ እና ጭብጥ ለማስረዳት እንደሚጠቅሙ ሣይገልጽና ሣያረጋግጡ የሥር ፍርድ ቤት ማስረጃዉን ሣያስቀርብ ወሰነብኝ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የአመልካችን መኪና ያሽከረክር የነበረው ሹፌር በወንጀል ተከስሶ ነፃ መሆኑ አመልካች በፍትሐብሔር ተጠያቂነት ነፃ የሚያደርግ አይደለም፡፡ አመልካች መኪናቸውን ከሚያሽከረክረው ሹፌር ጥፋት ውጭ በሆነ መንገድ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳን የመኪናው ባለቤት በመሆናቸው ብቻ ለጉዳቱ ተጠያቂ እንደሚሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081 ንኡስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አደጋው ያደረሰው የአመልካችን መኪና በሚያሽከረክረው ሹፌር ጥፋት መሆኑን በፍትሐብሔር ክርክር የቀረበውን ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች የወንጀል ችሎት የሰጠው ውሣኔ መኪናቸውን ያሽከረክር የነበረው ሰው ጥፋት የሌለበት መሆኑ የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ (conclusive Evidence) ተደርጉ መወሰድ አለበት በማለት ያቀረቡት ክርክር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2149 በወንጀል ነፃ መሆን የፍታብሔር ኃላፊነትን የሚያስቀር አይደለም በማለት ሕግ አውጭው በግልጽ የደነገገውን ድንጋጌ ያላገናዘበና የሕግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የክርክሩን ሥርአት በሚመሩበት ጊዜም ሆነ ለጉዳቱ ኃላፊ ያለባቸው አመልካች ናቸው ብለው በሰጡት ውሣኔ የፌፀሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ውሣኔያቻውን አጽንተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45735

መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ደረጀ ቸርነት - ጠበቃ አቶ በሻዳ ገመቹ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሕይወት የኋላሸት - ጠበቃ አቶ ደሣለኝ ዓለሙ ክብረት ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22411 ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 40544 የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ የታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች በከሳሽነት ቀርቦ ንብረትነቱ የእሱ የሆነውና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-00055 አዋሣ የሆነ ኤኔትሬ የነዳጅ መጫኛ መኪና ሐምሌ 22 ቀን 1990 ዓ.ም ከተጠሪ የነዳጅ ማደያና ዲፖ ነዳጅ መራገፍ ላይ እያለ በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆነውና በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ በሆነው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የሚባለው የተጠሪ ሰራተኛ በአስነሣው እሳት ምክንያት መኪናው ሙሉ በሙሉ የወደመ በመሆኑ የመኪናውን ዋጋ ብር 200,000(ሁለት መቶ ሺህ ብር) በመኪናው አገኝ የነበረውን ገቢ አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ክስ እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ በወር 15,00(አስራ አምስት ሺህ ብር) ሒሳብ 120,000(መቶ ሃያ ሺህ ብር) በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ቶታል ሜር ዩኘር ኤስ ኤ፣ተጠሪና አቶ አስጨናቂ ኩምሣ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት አመልካች በእሱ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል በቂ ምክንያት የሌለው መሆኑን በማንሣት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በሁለተኛ ተከሳሽነት ቀርበው ሶስተኛው ተከሳሽ አስጨናቂ ኩምሣ ሰራተኛ ባለመሆኑ በኃላፊነት የምጠየቅበት ምክንያት የለም፡፡ እሳት ሊነሣ የቻለው የከሳሽ(አመልካች) ሰራተኞች በመኪናው ጋቢና በኩል ባስነሱት ምክንያት ነው ስለዚህ ለጉዳቱ አላፊነት የምጠየቅበት ምክንያት የለም በማለትና የመኪናውን ዋጋ ግምትና የመኪናውን ገቢ በመቃወም ተከራክረዋል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበረው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የሁለተኛ ተከሳሽ (የተጠሪ ድርጅት) ሰራተኛና ድርጅቱን በመላላክ የሚያገለግል መሆኑንና ጆሮውም የማይሰማ መሆኑን ገልፆ አደጋው በተከሰበት እለት እኔ በቦታው አልነበርኩም ፍ/ቤቱ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ያቁምልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሥር አንደኛ ተከሳሽ ተደርጉ የተጠቀሰው ድርጅት ሙሉ በሙሉ ከክሱ እንዲወጣ ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እሣቱ የተነሳው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኃላፊነት የጐደለው ተግባር መሆኑን በበቂ ማስረጃ መረጋገጡን ወስኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበረው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ ለፖሊስ በሰጠው የተከሳሽነት ቃልና ለፍርድ ቤት በሰጠው መልስ ማረጋገጡንና ሶስተኛው ተከሳሽ የሁለተኛ ተከሳሽ (የተጠሪ) ሰራተኛ መሆኑ በሌላ ምስክር ቃል የተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ በእሳት አደጋው ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ሶስተኛ ተከሳሽም ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ ተጠሪና ሶስተኛ ተከሳሽ ለጉዳቱ በአንድነትና በነጠላ በኃላፊነት ይጠየቃሉ ብሎ ወስኗል የካሣውን መጠን በተመለከተ የመኪናው የገበያ ዋጋ ብር 170,000 (አንድ መቶ ሰባ ሺ ብር) እንደሚያወጣ አግባብ ካለው አካል ተገለጿል፡፡ የመኪናው ወርሃዊ ገቢ ብር 12,000 (አስራ ሁለት ሺ ብር ነው) ስለዚህ ተጠሪና ሶስተኛ ተከሳሽ የመኪናውን ዋጋ ብር 170,000(አንድ መቶ ሰባ ሺ ብር) እና የአስር ወር ገቢ ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺ ብር) እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረውን አዋጅ ቁጥር 42/1985 ድንጋጌዎች በመጥቀስና በተጠሪና በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ መካከል ያለው የሥራ ውል በጽሑፍ የተደረገ ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን በመግለጽ አመልካች አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ መሆናቸውን ስላላስረዱ ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በከፍተኛው ፍርድ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ መሆኑን በማመን መልስ ሰጥቷል፡፡ ፖሊስ ባጣራው የወንጀል የምርመራ መዝገብ በሰጠው የተከሳሽነት ቃልም አረጋግጧል በሌላ ማስረጃም ይኸን ፍሬ ጉዳይ አስረድተናል፡፡ ለተጠሪ ያቀረበችው ማስረጃ ሣይኖር ተጠሪ በአስጨናቂ ኩምሣ ስም የከፈላቸው የገቢ ግብር አለመኖሩንና ሌሎች ህጋዊ መሰረት የሌላቸውን ምክንያቶች በማቅረብ ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምኝ በማለት ያላመለከቱ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የሥር ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል በአግባቡ አልገለጹም፡፡ መስቀለኛ ጥያቄ ያልቀረበበትን ለፖሊስ የተሰጠ የተከሳሽነትና የምስክርነት ቃል ተጠቅሟል፡፡ ነዳጁ እስከ ታንከሩ ተገልብጦ እስኪያልቅ ድረስ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት ያለበት ጫኙ (አመልካች) ነው፡፡ አስጨናቂ ኩምሣ ተቀጣሪ ሰራተኛ አይደለም ስለዚህ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያደረጉት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው

- ተጠሪ አደጋው ያደረሰው በአመልካች ሰራተኞች ጥፋት ነው በማለት በሰበር ደረጃ ያቀረበው ክርክር ህጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለም?

- ተጠሪ በእሳት አደጋው ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናቸው ወይስ አይደሉም?

የሚሉ ጭብጦችን አግባብነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እልባት ማግኘት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ የእሳት አደጋው የተነሣው በአመልካች ሰራተኛ ጥፋት ነው በማለት በሰበር ሰፊ ክርክር አቅርበዋል፡፡ የእሳት አደጋው የተከሰተው በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ በነበረው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት ምክንያት መሆኑን በማረጋገጥ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ተጠሪን ከኃላፊነት ነፃ ናቸው በማለት የወሰነው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ አይደሉም በማለት ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የእሳት አደጋው በአቶ አሥጨናቂ ኩምሣ ጥፋት ነው የሚለውን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ አልሻረውም፡፡ ስለሆነም መኪናውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለውድመት የዳረገው እሳት አደጋ የተነሳው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም አደጋው ያደረሰው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ አለመሆኑን "ሌሎቹን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ ጸንቷል" በማለት በግልጽ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም የእሳት አደጋው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት መሆኑን ማስረጃ የመመዘንና ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥተውበት እያለ ተጠሪ አደጋውን ያደረሰው በአመልካች ሰራተኛ ጥፋት ነው በማለት ለሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ ያቀረበው ክርክር ለሰበር ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የቀረበ ሆኖ ስላገኘነው አልተቀበልነውም፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የእሳት አደጋው የተነሣው በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት መሆኑ በስር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በአመልካች መኪና ላይ በእሳት አደጋው ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚለው ጭብጥ የሚፈታው ተጠሪ ለአቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት ምክንያት ለደሰረሰው ጉዳት ተጠያቂነት አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚለውን ጭብጥ በመመለስ ነው፡፡ አመልካች የጉዳቱን መንስኤና ምክንያት የደረሰውን የጉዳት መጠንና ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊ መሆናቸውን የማስረዳት ሸክም እንዳለባቸው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2141 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ይህንን የማስረዳት ሸክማቸውን ለመወጣት ስለአደጋው በፖሊስ የተጣራው የምርመራ መዝገብ ቀርቦ እንዲታይላቸው አመልክተዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት መጠየቅ አለባቸው በማለት የሚከራከሩት ለእሳት አደጋው መከሰት ጥፋት የፈፀሙት አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ ናቸው በማለት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ ለሥር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ በተጠሪ ድርጅት በተላላኪነት የሚያገለግል ሰራተኛ መሆኑን በመግለጽ መልስ የሰጠ ሲሆን ለፖሊስ ባደረገው ምርመራም አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ እንደሆነ በአቶ አስጨናቂ ኩምሣና በሌሎች ምስክሮች መረጋገጡን በሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገልጿል፡፡

አመልካች አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ የነበረ መሆኑን ሊያስረዳለት የሚችል ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን በጥፋቱ የእሳት አደጋውን ያስነሳው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ ለሥር ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 92 መሰረት አረጋግጦ በሰጠው መልስ የተጠሪ ሰራተኛ እንደሆነ በማመን መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ አቶ አስጨናቂ ኩምሣ ሰራተኛቸው አለመሆኑንና በእለቱ በቦታው የተገኘው በድንገተኛ አጋጣሚ ወይም በሌላ እሳቸው በማያውቁት ሁኔታ መሆኑን ለማስተባበል ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ጉዳቱን ያደረሰው ሰው የተጠሪ ሰራተኛ መሆኑንና ተጠሪም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2130 መሰረት ለጉዳቱ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ለማስረዳት የሚችል ማስረጃ በማቅረብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2141 የተጣለበትን የማስረዳት ሸክሙን የተወጣ ሲሆን ተጠሪ የአመልካችን ማስረጃ የማስተባበልና የማፍረስ ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በተጠሪና በአቶ አስጨናቂ ኩምሣ መካከል ያለው የሥር ውል በጽሑፍ የተደረገ መሆኑን ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ በአንድ ሰውና በአሰሪው መካከል የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት መኖሩን በጽሑፍ በተደረገ የሥራ ውል በማቅረብ ካልሆነ በስተቀር በሌሎች ማስረጃዎች ለማስረዳት እንደማይቻል በመግለጽ የሰጠው ውሣኔ ህጋዊ መሰረት የለውም፡፡ የሥር ውል ቋሚ ወይም ጊዜዊ ሊሆን እንደሚችልና የሥራ ውሉ በጽሑፍ ወይም በሌላ አይነት ሁኔታ ሊፈጸም የሚችል መሆኑ አሰሪው የሥራ ውሉን በጽሑፍ በማድረግ በአስር ቀናት ውስጥ የመስጠት ግዴታና ኃላፊነት እንዳለበት በወቅቱ ሥራ ላይ በነበረው አዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 6 እና አንቀጽ 7 የተደነገገ መሆኑን የከፍተኛ ፍርድ ቤት ጠቅሷል፡፡

ሆኖም የከፍተኛው ፍርድ ቤት መልስ ሣይሰጠው ያለፈው አንድ ቁልፍ ጥያቄ ያለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይኸውም አሰሪው በሕግ የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት ሣይወጣ አንድ ሰራተኛ በቃል ወይም በሌላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አካኂን በተደረገ የሥራ ውሉ ከአስር ቀናት በላይ ለወራት ወይም ለአመታት ሲያሰራ ቢቆይ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው ነው፡፡ አሰሪው በአዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 6 እና በአንቀጽ 7 የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት ሣይወጣ መቅረቱ በሥራ ውሉ ህጋዊነት ላይም ሆነ በሰራተኛው መብትና ጥቅም ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ጉዳት የሌለ መሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 8 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 48/1985 አንቀጽ 7 የተደነገገውን ግዴታና ኃላፊነታቸውን አለመወጣታቸው የተሰጠሪ ሰራተኛ መሆኑን በመግለጽ የሚከራከረውና የተጠሪ ሰራተኛ መሆኑ በሌሎች ማስረጃዎች የተረጋገጠው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ ጥፋት ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ከአላፊነት ነፃ የሚያደርጋቸው አይደለም፡፡ ስለሆነም በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል የሥራ ውል መኖሩን በጽሑፍ የተደረገ የሥራ ውል ለማቅረብ ብቻ ሣይሆን በጽሑፍ የተደረገ የሥራ ውል በሌለ ወይም ሊገኝ ባልቻለ ጊዜ ማናቸውንም ተዓማኒነት ያለውን ማስረጃ በማቅረብ ለማስረዳት የሚቻል በመሆኑና አመልካች ጉዳቱን ያደረሰው ሰው የተጠሪ ሰራተኛ መሆኑን በበቂ ማስረጃ አረጋግጦ እያለና ተጠሪ የአመልካችን ማስረጃ ሊያስተባብል የሚችል ማስረጃ ባላቀረበበት ሁኔታ በሕግ ያልተደነገገ መስፈርት አላግባብ በማውጣት የሥራ ውሉ መደረጉን የሚያሣይ በጽሑፍ የተዘጋጀ የሥራ ውል አመልካች በማስረጃነት ያላቀረበ በመሆኑ አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሕግ በግልጽ የሥራ ውልን ለማስረዳት ተቀባይነት የላቸውም ያልተባሉ ማስረጃዎች የስራ ውል ለማስረዳት ተቀባይነት እንደሌላቸው በመግለጽ የሰጠው ውሣኔ በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል የአሰሪና የሰራተኛ ግንኙነት መኖሩን ስለማስረዳት የተደነገጉ ከላይ የተጠቀሱትን ደንቦችን የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳቱን ያደረሰው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የተጠሪ ሰራተኛ መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ የሆነው አቶ አስጨናቂ ኩምሣም በግልጽ በማመን መልስ የሰጠ ሲሆን በሌሎች ማስረጃዎችም ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠውን ይህን ፍሬ ጉዳይ የሚያስተባብል ወይም ለማፍረስ የሚችል የተሻለ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ ሰራተኛው ላደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2130 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የተጠሪ ሰራተኛ የሆነው አቶ አስጨናቂ ኩምሣ የሥራ ተግባሩን ሲያከናውን እሳቱ የተነሣ መሆኑን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2131/1/ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2032/1/ መሰረት ያስረዳ ሲሆን ተጠሪ ይህንን ለማስተባበል ወይም ለማፍረስ የሚቻል ማስረጃ እንዳላቀረቡ የሥር ፍርድ ቤት አረጋግጦል፡፡ ስለዚህ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ መባላቸው ሕጋዊ መሰረት ያለው ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥራ ውሉ መኖሩን ለማረጋገጥና ለማስረዳት የሚቻለው በጽሑፍ የተደረገ የሥራ ውል በማቅረብ ነው የሚል የተሳሳተ የሕግ ተርጉም በመስጠት ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለባቸውም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ በአመልካች መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናቸው ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44588

ሚያዝያ 4 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች- የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት

ተጠሪ፡- 1. ኃይለየሱስ ቱኪ

2. አብዲሣ ኦላና

3. ሌሊሣ ለታ

4. ሰብሌ አብዲሣ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ያቀረበው አመልካች የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሾች በመሆን ተክራክረዋል፡፡ አመልካች የተለያዩ አይነት ጤፍ የመሸጫ ዋጋ ከበፊቱ የጨመረ መሆኑ ከተነገራቸውና የፋክስ መልክት ከደረሳቸው በኋላ በፊት በነበረው ዋጋ የሸጡ በማስመሰልና ብር 16,818.10(አስራ ስድት ሺ ስምንት መቶ አሥራ ስምንት ብር ከአስር ሣንቲም) ድርጅቱ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዲያጣ አድርገዋል በማለት አመለከቱ፣ አንደኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች በሥር ቀርበው አልተከራከሩም ሁለተኛ፣ አራተኛ ተጠሪዎች በሥር ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የእጅ በእጅ የጤፍ ሽያጭ እንዲከናውን ትእዛዝ እልሰጠሁም በደረሰኝ ላይም አልፈረምኩም የሥራ ድርሻዬ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አራተኛ ተጠሪ በበኩላቸው በተከሳሽነት ቀርበው ከዚህ በፊት ከሳሼ ማለትም የአሁን አመልካች ብር 4,204.53(አራት ሺ ሁለት መቶ አራት ብር ከሐምሣ ሶስት ሣንቲም) በመክፈል ከሥራ አሰናብቶኝ ነበር፡፡ እኔ ለጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቤ እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተከራክረን ወደ ሥራ የተመለስኩ ስለሆነና ከዚህ በፊት በጉዳዩ ተከራክረን ፍርድ ያገኘ ስለሆነ ሁለተኛ ጊዜ ክስ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አራተኛ ተጠሪ ከዚህ በፊት በአሰሪና ሰራተኛ ችሎት ተከራክሮ ተፈፀመ የተባለው ጥፋት የማያስጠይቃት መሆኑ ተረጋግጦ አራተኛ ተጠሪ ወደ ሥራ እንድትመለስ ተወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔ እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ድረስ ቀርቦ ፀንቷል ስለዚህ ተከሳሾችን የሚያስጠይቃቸው አይደለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ውሣኔው በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ፀንቷል፡፡

አመልካች ተጠሪዎች ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ከእያንዳንዱ ኩንታል ብር 10.00/አስር ብር / ቀንሰው መሸጣቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርበናል በአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት አራተኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ጥፋት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልፈፀመችም ተብላ ወደ ሥራ እንድትመለስ መወሰኑ የፍትሐብሔር ኃላፊነትን የሚያስቀር አይደለም፡፡ ስለዚህ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ሆነ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር አቤቱታውን አቅርቧል አንደኛ፣ ሁለተኛና አራተኛ ተጠሪ በየግላቸው መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሰጡት መልስ ይዘትም ከጤፍ ሽያጭ ቀንሰው ለግል ጥቅማቸው ያዋሉት ገንዘብ የሌለ መሆኑንና ይህንንም የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ ያላቸው በመሆኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ነው፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አራተኛ ተጠሪ አሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት ተከራክረው ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት አልፈፀሙም ተብሎ መወሰኑ ተጠሪዎች በድርጅቱ ላይ አድርሰዋል የተባለውን ኪሣራ እንዲከፍሉ አመልካች ካቀረበው ክስ በኃላፊነት አይጠየቁም ብሎ ለመወሰን የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት ሰራተኛው ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት አልፈፀመም በማለት የሚሰጠው ውሣኔ አሰሪው ሰራተኛውን በፍትሐብሔር ክስ አቅርቦ ከመጠየቅ የሚገድብ እንዳልሆነና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 5 ንኡስ አንቀጽ 1 መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል ከዚህ በፊት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36710 ጥር 21 ቀን 2001 ዓ.ም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት የሚወሰነው መሰረታዊ ጭብጥ ሰራተኛው በፍትሐብሔር ተጠያቂነትና ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ሣይሆን አሰሪው ሰራተኛውን ከሥራ ለማሰናበት የሚያበቃ በቂ ምክንያት አለ ወይስ የለም? የሥራ ስንብቱ የሕጉን ሥርአት ተከትሎ የተፈፀመ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪዎች ተሻሽሎ በተተመነው የጤፍ በመሸጫ ዋጋ በታች በመሸጣቸው ብር 16,818.10(አስራ ስድስት ሺ ስምንት መቶ አሥራ ስምንት ብር ከአስር ሣንቲም) በድርጅቱ ላይ ጉድለት አድርሰዋል በማለት ክስ የቀረበ ሲሆን ክሱን ያስረዱልኛል የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ ሁለተኛና አራተኛ ተጠሪ ለጉድለቱ ተጠያቂ አይደለንም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ይህንን ክርክር የሚደገፍ ማስረጃ ዝርዝር አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ደረሰ የሚለው የብር 16,818.10(አስራ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከአስር ሣንቲም) ኪሣራ በእርግጥ በድርጅት ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ወይስ አይደለም? ጉድለቱ የደረሰ ነው የሚባል ከሆነ ተጠሪዎች በኃላፊነት ይጠየቃሉ ወይም አይጠየቁም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን ውሣኔ መስጠት ሲገባው አሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት የአራተኛ ተጠሪ ከሥራ መሰናበታቸው አላግባብ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ የፍትሐብሔሩን ክስ የሚያስቀር የመጨረሻ ውሣኔ አድርጐ በመውሰድ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስና ማስረጃና ተጠሪዎች የሚያቀርቡትን መልስና ማስረጃ በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ 341/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሳቸው ይቻሉ

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 50225

ሐምሌ 5 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- 1. ወ/ት ዝናሽ አሰፋ
2. አቶ መላት አሰፋ
} የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ባለቤት ላይ በመሠረቱት ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሠረት ባደረገ ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ይዘት ባጭሩ፡- የተጠሪዎች አባት በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ተገጭታ ሕይወታቸው በማለፉ አባታቸው በሕይወት እያሉ በሚሰሩት ሥራ በቀን ብር 22.00 /ሃያ ሁለት ብር/ እያገኙ ከዚሁ ገቢ ስልሳ ከመቶ የሚሆነውን እየሰጧቸው ያስተዳድሯቸው የነበሩ መሆኑንና ሟች አባታቸው በመኪና ግጭት ሲሞቱ እድሜያቸው 40 ዓመት እንደበሩ፣ ወደፊትም እስከ ስልሳ አምስት ዓመት ሊደርሱ ይችሉ እንደነበር በመግለጽ በዚሁ ጉዳት ምክንያት በአጠቃላይ የብር 125,230.00 /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሣ ብር/ ጉዳት እንደደረሰባቸው በመጥቀስ ይህንኑ የጉዳት መጠን እንዲተካላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የመኪናው ባለቤትና አሽከርካሪው በሌሉበት ጉዳዩ የታየ ሲሆን የአሁኑ አመልካች በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ ገብቶ የተጠሪዎች አባት በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ተገጭተው ሕይወተቸው ሲያልፍ እድሜያቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ የሆኑና ራሳቸውን መቻል እና ማስተዳደር የሚችሉበትና ከዚህም አልፎ አባታቸውን ሊጦሩ የሚችሉ መሆኑን በመግለጽና ለክሱ ኃላፊነት እንደሌለው በመጥቀስ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095/1/ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ ዋቢ በማድረግ ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መሠረት በማድረግ የተሽከርካሪውን ባለቤት ለጉዳቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2081 መሠረት ኃላፊ አድርጎ አመልካችን ተጠያቂ አድርጎአል፡፡ የጉዳት መጠኑንም በአጠቃላይ ብር 21,000.00 /ሃያ አንድ ሺህ/ አድርጎ አመልካች እስከ ሰላሳ ሺህ ብር በገባው የዋስትና ግዴታ መሠረት እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሕዳር 01 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪዎች ጉዳቱ ሲደርስ እድሜያቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ ሆነው እያለ ጉዳቱ በቀለብ መልክ እንዲከፈል ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095/1/ እና ስለቀለብ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን መንፈስ ያላገናዘበ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም እድሜያቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ ለሆናቸው ተጠሪዎች አመልካቹ ከሚቹ አባታቸው ሲያገኙ የነበረውን ቀለብ በካሣ መልክ ይክፈል የመባሉን አግባብነት ለማየት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክር ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች አባታቸው በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ተገጭተው ሲሞቱ እድሜአቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ መሆኑን፣ በወቅቱ ተማሪዎች ሆነው በሚች አባታቸው ሲረዱና ሲተዳደሩ የነበሩ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ከማረጋገጡም በላይ አመልካች በዚህ የሰበር ችሎትም ሆነ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች እድሜአቸው አስራ ስምንት ዓመት ሞልቷቸዋል ብሎ ከመከራከር ውጪ በእርግጥም ራሳቸውን ይችሉ የነበረ ሁኔታ ስለመኖሩ ግልጽ አለመከራከሩን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች እድሜአቸው አስራ ስምንት ዓመት በላይ ስለሆነ ብቻ በመኪና ግጭት ሕይወቱን ያጣውን አባታቸውን ካሣ አይገባቸውም ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የጉዳት ካሣ በቀለብ መልክ እንዲከፈል ሕጉ ሲፈልግ እድሜው አስራ ስምንት ዓመት የሞላው ሁሉ ሊጠይቅ አይችልም ማለት እንደሆነ ስለቀለብ የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚያስረዱት ጉዳይ ነው፡፡ ዋናውና ትልቁ ቁም ነገር ቀለብ ጠያቂው ያለበት ሁኔታ ነው፡፡ ቀለብ ጠያቂው ቀለቡን ሊያገኝ የማይችልበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑ ከተረጋገጠ አካለ መጠን የመድረሱ ጉዳይ ግምት ውስጥ የሚገባበት ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪዎች በወቅቱ ተማሪዎች የነበሩ መሆናቸው ሲታይም ትምህርታቸውን እየተማሩ በቀላሉ ራሳቸውን የማስተዳደር አጋጣሚ ይኖራቸዋል ብሎ ለመደምደም ከነባራዊ ሁኔታ አንፃር ሲታይ የማያስኬድ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ሚች አባታቸው በመኪና ሲገጩ አስራ ስምንት ዓመት ስለሞላቸው ብቻ የጉዳት ካሣውን በቀለብ መልክ ሊያገኙ አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095/1/ እና ስለቀለብ ስለተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው ሆኖ አላገኘውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሣኔ በተጠሪዎች በኩል የቀረቡትን ክርክሮችንና ማስረጃዎችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በሕጉ አተረጓጎምና አተገባበር ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01931 ሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35340 ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ጎዳር 04 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 34665

ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- 1. አቶ ናትናኤል ዘውገ
2. አቶ ኃይለየሱስ ዘውገ
} ጠበቃ አበራ ጣሰው ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ እግዜሩ ገ/ሕይወት ጠ/አለም ወ/አረጋይ ቀረቡ

2. የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ደስታ ሊበን ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካቾች በአንደኛ ተጠሪ ላይ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የመሰረቱት ክስ ነው፡፡ አመልካቾች ከሚች አባታቸው በውርስ ያገኙትን በወረዳ 1 ቀበሌ 8 ውስጥ የሚገኘውን የቤ/ቁ 1273 የሆነውን ቤት አንደኛ ተጠሪ ቀድሞ ከሚያስተዳድረው ሁለተኛ ተጠሪ መከራየታቸውን ምክንያት በማድረግ አለቅም ስላሉ የቤቱ ኪራይ ከፍለው ቤቱን እንዲያስረክቡ ክስ መስርተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ለክሱ መልስ እንዲሰጡና ሁለተኛ ተጠሪም በክርክር ውስጥ እንዲገባ ከተደረገ በኋላ ፍ/ቤቱ የአመልካቾች የቤት ባለቤትነት ደብተር በአ/አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የስራና ከተማ ልማት ቢሮ የተሰረዘ በመሆኑ አመልካቾች ቤቱን ለመረከብ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች ውሳኔውን ለማስለወጥ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑም የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካቾች ዋነኛ ቅሬታ የአ/አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የስራና ከተማ ልማት ቢሮ የባለቤትነት ደብተሩን ለመሰረዝ ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የስራና ከተማ ልማት ቢሮ ደብተሩን የሰረዘው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲል አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው በሰበር ችሎት ለመመርመር የቀረበው ነጥብ የአ/አበባ ከተማ የስራና ከተማ ልማት ቢሮ የአመልካቾችን የባለቤትነት ደብተር ለመሰረዝ ስልጣን አለው የለውም የሚለው ነው፡፡ ከክርክሩ የአ/አበባ ከተማ ስራና ከተማ ልማት ቢሮ ደብተሩን የሰረዘው የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር በ22/07/1991 ዓ.ም በተሻሻለ ደብዳቤ በሚ/ር መስሪያ ቤቱ ይገኙ የነበሩ የቤት ጉዳዮች ከስራተኞቹ ጋር ለአ/አበባ መስተዳድር ምክር ቤት እንዲያስረክብ ከጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት በተላለፈው ትእዛዝ መሰረት ከየካቲት 1 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ እነዚህ ጉዳዮች በአ/አበባ መስተዳድር ምክር ቤት ስራና ከተማ ልማት ቢሮ እንዲያስተዳድር በመግለፁ ምክንያት መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገንዝበናል፡፡ የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ስራ የመከታተልና በበላይነት የመቆጣጠር ስልጣን ያለው እንደመሆኑ መጠን የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር ቤቶችን የሚመለከት ጉዳይ ለአ/አበባ ስራና ከተማ ልማት ቢሮ እንዲያስተላልፍ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ስራውንና ሰራተኞቹን ለቢሮው አስተላልፏል፡፡ በዚህ መሰረት ቢሮው ስራውን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በዚህም ወቅት ነው የአመልካቾች የቤት ባለቤትነት ደብተር የተሰረዘው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ደብተሩ ስልጣን በሌለው አካል ነው የተሰረዘው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ የስር ፍ/ቤትም አመልካቾች የቤት ባለቤትነት ደብተር ስልጣን ባለው አካል የተሰረዘ በመሆኑ ክሳቸውን ተቀባይነት የለውም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19448 ሐምሌ 28 ቀን 1996 የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33840 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 46220

ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የደቡብ ክልል የሐዋሣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት - ነ/ፈጅ ከተማ ጌታነህ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የሐዋሳ ደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ገዳም - ጠበቃ ቸርነት ገ/ሕይወት - ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነ ተጠሪ በሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች እና በሌሎች ሁለት ተከሣሾች ላይ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በክሳ ከቤ/ክርስቲያኗ ይዞታ 1632 ካ.ሜ. ለሥር አንደኛ ተከሣሽ ለጊዜያዊ ማረፊያነት ተሰጥቷቸው የነበረ መሆኑን፣ ተከሣሹ አሁን ቤት መስራታቸውን፣ ተከሣሹ ካርታና ፕላን ጠፋብኝ ብለው አዲስ ካርታ እንዲሰጣቸው ለወረዳ ፍ/ቤት አመልክተው እንዲሰጣቸው ማድረጋቸውን፣ አመልካችም ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ አንደኛ ተከሣሽ ከያዙት ቦታ ላይ ለ832 ካ/ሜ ይዞታ ካርታ ሲሰጣቸው ቀሪው 800 ካ/ሜ ለሥር ሁለተኛ ተከሣሽ በሊዝ በመምራት ካርታና ፕላን መስጠቱን በመግለጽ ለሁለቱም ተከሣሾች የተሰጠው ካርታና ፕላን ተሰርዞ ይዞታው ለተጠሪ ይመለስ በማለት ጠይቃለች፡፡ አመልካችም ለቀረበው ክስ ቤ/ክርስቲያኗ ያቀረበችው ማስረጃ ከአ/ቁ 47/67 በፊት የተሰጠ ስለሆነ ከአዋጁ በኋላ መሠረዙን፣ ከአዋጁ በኋላ የተሻሻለውን ምስክር ወረቀት አለመወሰዷን፣ ካርታውና ፕላኑ የተሰጠው በፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት መሆኑን፣ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቦታ ከመንግሥት የተወረሰ መሆኑን፣ ለሥር ተከሣሾቹ ካርታና ፕላን የተሰጠው በሊዝ ኮሚቴ ስለሆነ አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው ለሊዝ ቦርድ ኮሚቴ እንደሆነ፣ ለከፍተኛ ፍ/ቤት የሚቀርበው የካሣ ጉዳይ ብቻ እንደሆነ በመከራከር ክሱ ውድቅ እንዲሆንለት ጠይቋል፡፡ ሌሎቹም ተከሣሾች መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ይዞታው ከአ/ቁ. 47/67 ወዲህ በተጠሪ እጅ አይደለም፣ አንደኛ ተከሣሽ ይዞታው በሠራተኛነት ሳይሆን በባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸዋል፣ ከይዞታቸው ከፊሉ በሊዝ ኮሚቴ ፀድቆ ባለቤት ሆነዋል፡፡ ቀሪውን በሊዝ ኮሚቴ ለሁለተኛ ተከሣሽ ተሰጥቷል፤ አመልካች በሊዝ ኮሚቴ ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት ነው የሚፈጽመው፣ በሊዝ ኮሚቴ ውሣኔ ቅር ከተሰኘች ቅሬታው ማቅረብ ያለበት ለሊዝ ኮሚቴ ነው፣ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በፍርድ ሊሰረዝ አይችልም፣ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል። በዚህ ውሣኔ ላይ ተጠሪ ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል። ይህ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበች ሲሆን ችሎቱ ይዞታው የተጠሪ መሆኑ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ፣ ይዞታው የተሰጠው ለሕዝብ አገልገሎት ሳይሆን ለሌላ ግለሰብና መ/ቤት በመሆኑ ሕጋዊ አይደለም፣ ለሕዝብ ጥቅም ቦታ ስለማስለቀቅ በወጣው አዋጅ መሠረት ተገቢው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ እንዲለቁ የተደረገ ስላለሆነ ፍ/ቤቶቹ ስለቦታ ማስለቀቅ የተመለከቱት አዋጆች ተጠቅመው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ሊሉ አይችልም በማለት ተከሣሾቹ ይዞታውን ለተጠሪ እንዲመልሱ ወስኗል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው። ይህ ችሎትም ካርታው እንዲሰረዝ በፍ/ቤት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል። በዚህም መሠረት ግራ ቀኙ ቀርበው ክርክራቸው ተሰምቷል። ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል።

አመልካች ክስ ያቀረበችው ከይዞታዋ ላይ ተቀንሶ ለሥር አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሽ የተሰጣቸው ስለሆነ የተሰጣቸው ካርታና ፕላን ተሰርዞ ይዞታውን ተከሣሾቹ እንዲመልሱላት ነው። ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል። ለዚህም መሠረት ያደረገው ሁለት ነገሮችን ነው። አንደኛው አከራካሪው ይዞታ ለሥር አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሾች የተሰጠው በሊዝ ቦርድ ኮሚቴ ስለሆነ በኮሚቴው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን ማቅረብ ያለበት ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንጂ ለፍ/ቤት አይደለም የሚል ሲሆን ሁለተኛው የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በፍርድ ለመሠረዝ የማይቻል ለመሆኑ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ውሣኔ ሰጥቷል በሚል ነው። ይህ ችሎትም በቅድሚያ ክስ የቀረበበትን ጉዳይ ለማስተናገድ ፍ/ቤቶች ስልጣን ያላቸው መሆን አለመሆኑን መርምሯል።

ከመዝገቡ ሂደት ተጠሪ ይዞታዬ ነው የምትለውን የቦታ ይዞታ ቀንሶ ለሥር አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሾች ሰጠው የሊዝ ቦርድ ኮሚቴ መሆኑን ተረድተናል። የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው የፌዴራል አ/ቁ. 272/2994 እንዲሁም ክልሉ ይህንን አስመልክቶ ያወጣቸው አዋጅና ደንቦች የሊዝ ቦርድ ኮሚቴ በሰጠው የቦታ ማስለቀቅ ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን ማቅረብ ያለበት በቅድሚያ ውሣኔውን ለሰጠው አካል ሲሆን በዚህ አካል ምላሽ ካልተስማማ ይግባኙን ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ነው። በካሣ ጉዳይ ላይ ካልሆነ በቀር ጉባኤው የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል። በመሆኑም አንድ ሰው ይዞታውን እንዲለቀቅ የተደረገው በሕግ የተመለከቱትን ሥርዓቶች ሳይከተል ከሆነ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችለው ለጉባኤው ነው። ለፍ/ቤት ይግባኝ ሊቀርብ የሚችለው የካሣውን ጉዳይ በተመለከተ ብቻ ነው። በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪ ከይዞታዋ ላይ ተቀንሶ ለሥር ተከሣሾች የተሰጠው በሊዝ መሆኑ ስለተረጋገጠ ይዞታው የተሰጠው በሕጉ አግባብ ካልሆነ ይህንኑ ቅሬታ በቅድሚያ ውሣኔውን ለሰጠው አካል፣ በመቀጠል ደግሞ ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ነበረባት። በመሆኑም ከጅምሩም ቢሆን ክስ የቀረበበትን ጉዳይ ፍ/ቤቶች አይተው ለመወሰን ስልጣን አልነበራቸውም። ከፍ ሲል በተጠቀሱት ምክንያቶችም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሊዝ ኮሚቴ የተወሰነውን ጉዳይ አከራክሮ ውሣኔ መስጠቱ ያለስልጣኑ በመሆኑ መሠረታዊ ሕግ ስህተት ፈጽሟል። ስለዚህም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል።

ው ሣ ኔ

1. የደ/ብ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 27382 ሚያዝያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
2. የሐዋሣ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05446 ታህሣሥ 1 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23971 የካቲት 4 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል።
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 42928

ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ አክሊሉ አበባው - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ድራጋዶስ ኮንስትራክሽን - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም. በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ አካባቢ የመንገድ ሥራ ሲያከናውን በአመልካች ንብረት ላይ ግምቱ ብር 25,569.85 /ሃያ አምስት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ አምስት ሳንቲም/ የሆነ ጉዳት ማድረሱን ገልፆ ይህንኑ ገንዘብ ከነወለዱ ወጪው ጋር እንዲተካ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተከሣሽ ድርጅት በግሪክ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመ አድራሻውም አቴንስ የሆነ የውጭ ሀገር ኩባንያ ነው፣ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥም አልተመዘገበም ስለዚህ በመልካችና በተጠሪ መካከል የሚነሳ አለመግባባት በየትኛው ሀገር ሕግ ይታያል፣ በየትኛው ፍርድ ቤት ይታያል የሚል የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ስለሚያስነሳ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስቶ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ይህንኑ የተጠሪን መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ጉደዩን መርምሮ ጉዳዩ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ የሚያስነሳ በመሆኑና ሥልጣኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም ሲል የአመልካችን ክስ በብይን ዘግቷል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርቦ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በተጠሪና በአመልካች መካከል ያለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ጉዳቱ የደረሰው ተጠሪ ኢትዮጵያ ውስጥ ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት ስለሆነ እና በንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት ደግሞ ክሱ መመስረት ያለበት ጉዳቱ በደረሰበት ሀገር ሕግና ፍርድ ቤት መሆኑ እየታወቀ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2ሀ/ ያላግባብ ተጠቅሶ ክሱ መዘጋቱ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን መዘጋቱ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ጉዳዩ በቃል ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይንና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች ክስ መሠረት ያደረገው ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚመለከት የሚገዙ ድንጋጌዎች መሆኑ፣ ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ጉዳት ያደረሰው ስራውን በኢትዮጵያ ውስጥ ሲያከናውን መሆኑን ክሱ የቀረበውም ጉዳቱ በደረሰበትና ንብረቱ በሚገኝበት ክልል በሚገኘው ፍርድ ቤት መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ክርክር የንብረት ጉዳት ካሣ በመሆኑ ክሱ ሊመሠረት የሚገባው የገንዘቡ መጠን ግንዛቤ ውስጥ ሲገባ የገንዘብ መጠኑን መሠረት አድርጎ የሚወሰነው የሥረ- ነገር ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጉዳቱ በደረሰበትና ንብረቱ በሚገኝበት ክልል በሚገኘው ፍርድ ቤት ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 27/1/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ አንፃር ተገንዝቦ አይቶ የመወሰን ስልጣን የራሱ ሆኖ እያለ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2/ሀ/ ድንጋጌን ያለቦታው ጠቅሶ የአመልካችን ክስ መዘጋቱ እና ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይህንኑ መቀበሉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09737 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 69916 ሕዳር 15 ቀን 2001 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው በመሆኑ የአመልካችን ክስ ተቀብሎ ግራ ቀኙን በቀሪ መከራከሪያ ነጥቦች ላይ በማከራከር ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42866

መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ብርሃነ ጥዑም - ሙሉጌታ ወንድም ቀረቡ

ተጠሪ፡- የጉምሩክ ባለሥልጣን - ዳንኤል ጥበቡ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያላግባብ የተከፈለ ቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባሁኑ ተጠሪ ላይ ሚያዝያ 01 ቀን 1990 ዓ.ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በዲክላራሲዮን ቁጥር 718/90፣ 719/90 እና 1600/90 የተመዘገቡትንና በቻይና፣ ማለዥያ፣ ኮሪያ እና ጃፓን ሃገር የተሰሩትን የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ከባንክ በተገኘ የውጭ ምንዛሬ በመግዛት በምዕዋ ወደብ በኩል ወደሃገር ውስጥ ሲያስገቡ የተጠሪ ድርጅት ዛለአንበሳ ጣቢያ ብር 87,760.65(ሰማንያ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ከስልሳ አምስት ሳንቲም) የቀረጥ ክፍያ አመልካች እንዲከፍሉ ጠይቋቸው ክፍያ ከፈፀሙ በኋላ ተጠሪ ቀሪ የቀረጥ ሂሳብ አለብህ በማለት እቃዎችን በመያዙ ምክንያት ያላግባብ ብር 244,866.10(ሁለት መቶ አርባ አራት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ስድስት ብር ከአስር ሳንቲም) እንዳስከፈላቸው ገልፀው ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪ ከነወለዱ እና ከክሱ ወጪና ኪሳራ ጋር ይወሰንልት ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚይሳይ ነው፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሠጠው መልስ ቀረጡን በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያስከፈለ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃዎችን በመመርመር ተጠሪ ቀረጡን ያስከፈለበት አግባብ ከመመሪያ ቁጥር 10/96 ውጪ ነው በማለት የተጠሪን ክርክር ውድቅ አድርጎ ለክሱም ኃላፊ በማድረግ ክሱ የተመሰረተበትን ገንዘብ ከሚያዝያ 08 ቀን 1990 ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር ተጠሪ የቀረጡን ገንዘብ የሚመልስበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥር 04 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበውን የተጠሪ መከራከሪያ ነጥብ መሰረት አድርጎ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ስነ-ስርዓታዊ የሆነውን ምክንያት መነሻ በማድረግ የሠጠውን ዳኝነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) አንፃር አግባብነቱንና የጉዳዩን ፍሬ ነገር የሕግ ክርክር ተመልክቶ ውሳኔ መስጠት ነበረበት ወይስ አልነበረበትም? የሚሉትን ነጥቦች ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ ተጠሪም በነገረ ፈጁ አማካኝነት ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 68/89 አንቀፅ 48(7/11)፣ 53 እና መመሪያ ቁጥር 10/1996 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ውሳኔው ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ጠበቃም የካቲት 15 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል ወይስ አልተፈፀመበትም? የሚለው ጥቅል ጭብጥ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ክሱን ሊመሰርቱ የቻሉት ያላግባብ የከፈልኩት የቀረጥ ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ ክፍያውን ያስፈፀመው በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የዋጋ መረጃን በማየት መሆኑን ገልፆና ያላግባብ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም እና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀፅ 47 ላይ እንደተመለከተው ወደ ሃገር ውስጥ ለሚገባ ማናቸውም ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሚሆነው በትክክል ለዕቃው የተደረገ ጠቅላላ ወጪ ነው፡፡ ዕቃው የተገዛበት ዋጋ ደግሞ ከወጪዎች አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ለቀረጥ ማስከፈያ መሰረት የሚሆነው ትክክለኛ የዕቃው ዋጋ ስለመሆኑ ሕጉ በዋናነት ያስቀመጠው አሰራር ነው፡፡ ከዚሁ የሕጉ መንፈስ መረዳት የሚቻለው ሌላው ቁም ነገር ደግሞ በአስመጪው የሚቀርበው የእቃው ዋጋ ግምት ትክክለኛውንም የዕቃውን ዋጋ የማይናገር መሆኑ ከተረጋገጠ የቀረጥ ሂሳብን ለማስላት መነሻ (መሰረት) ሊሆን የማይችል መሆኑን ነው፡፡ በመሰረቱ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነና እንዴት እንደሚሰራ በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀፅ 48 ስር ተዘርዝሯል፡፡ የተጠቀሰው የአዋጁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 እና 8 ድንጋጌዎች ሲታዩም የጉምሩክ ባለስልጣን በአስመጪው የቀረበለትን የዋጋ ግምት አልቀበልም በማለት የቀረጥ ሂሳቡን ለማስላት ሌሎች አማራጭ መንገዶችን መከተል የሚችል ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ የተጠቀሰው የአዋጅ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 6 ድንጋጌ ደግሞ የጉምሩክ ባለስልጣን በአስመጪዎች የቀረበለትን የዋጋ ግምት አልቀበልም ስለሚልበት ሁኔታ የገቢዎች ቦርድ መመሪያ ማውጣት የሚችል መሆኑን ደንግጓል፡፡ በዚሁ ሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረትም የተጠቀሰው አካል መመሪያውን ማውጣቱ የተረጋገጠ ሲሆን በዚህ መመሪያ መሰረትም በትራንዛክሽን ዋጋ ላይ የተመሰረተ የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ተግባራዊ የማይሆንባቸው ምክንያቶች ተቀምጠዋል፡፡ ከእነዚህም ምክንያቶች መካከል ወደ አገር ውስጥ የገባው እቃ ዋጋ ከአንድ ዓይነት እና ከተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ በጉምሩክ ከሚፈቀደው ልዩነት በላይ አንሶ መገኘት ስለመሆኑ መመሪያው በአንቀፅ 1(5) ስር አስቀምጧል፡፡ ወደ ሃገር በገባ ወይም ከሀገር በወጣ ዕቃ ላይ የተከፈለው ቀረጥ በማናቸውም ምክንያት ሊከፈል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚገባው ቀረጥ ያነሰ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ደግሞ ባለሥልጣኑ የእቃውን ባለቤት ወይም ወኪሉን በልዩነት ያልተከፈለውን ቀረጥ ማስከፈል እንደሚችል በአንቀጽ 57(1) ስር በግልፅ አስፍሯል። የዋጋ ኢንቮይስ ውድቅ የሆነበት ቀረጥ ከፋይ ቅሬታ ካለው በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 53 መሰረት ለተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አቅርቦ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ የሚችል ሲሆን፤ በዚሁ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ቅሬታ ካለው ብቻ ወደሚመለከተው ፍርድ ቤት መሄድ የሚችል መሆኑን ተመልክቷል። ይህ ስርዓት ሳይፈፀም በቀጥታ በፍ/ቤት ክስ የሚመሰረትበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከተጠቀሰው ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው። ይህ በሕጉ ላይ የተመለከተው የስነ-ስርዓት ጥያቄ ነው። ይኸው የስነ-ስርዓት ጉዳይም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት ባግባቡ መፈፀም አለበት። የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎም ይታሰባል።

በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለከፋዩ ሊመለስ እንደሚገባ አዋጁ በአንቀፅ 55 ስር በግልፅ ደንግጓል። ተጠሪ ቀሪ የቀረጥ ክፍያ መኖሩን አረጋግጦ ተገቢ ነው ያለውን የክፍያ ጥያቄ አመልካች እንዲፈፅሙ ጠይቋል። ይህም የሚያሳየው የአመልካች ኢንቮይስ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ሲሆን አመልካች በአዋጁ አንቀፅ 53(1) መሰረት ያነሱት እና የተጠቀሙበት ተቃውሞ አለመኖሩን ነው። በመሆኑም አመልካች ክስ የመሰረቱበትን የቀሪ ቀረጥ ክፍያ ጥያቄ በተጠሪዎች በኩል በአዋጁ አንቀጽ 53(1) መሰረት ተቃውሞ ቀርቦ ተገቢው ለውጥ ባልተደረገበት ሁኔታ በፍርድ ቤት ክስ መስርተው ተቀባይነት ማግኘታቸው ስነ ስርዓቱን ያልጠበቀ ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ የሚነቀፍበት የስነ-ስርዓትም ሆነ የመሰረታዊ ሕግ ምክንያት የለም። ስለሆነም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 36410 ሕዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35369 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል።

በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48111

ሚያዝያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ታሪኳ ላዕከ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ቂጤሳ ገብሬ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድን የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክሱን ያቀረቡት በአመልካች ድርጅት በጥበቃ ስራ ላይ ተመድቤ በማገልገል ላይ እያለሁ አመልካች በብረታ ብረት ብየዳ ስራ ሰራተኞችን አወዳድሮ ለማሳደግ የካቲት 19 ቀን 1999 ዓ.ም ባወጣው የውስጥ ማስታወቂያ የተጠየቀውን መስፈርት አሟልቼ በመስሪያ ቤቱ የውስጥ አሰራር መመዘኛ መሰረት 30% ሲቀየር 11/40/30 አምጥቻለሁ፣ ይህ ውጤት ከሌላው የስራ ምዘና ውጤት ጋር ሲደመር 54.76% በመሆኑ የሚያሳልፈኝ ሆኖ ሳለ አመልካች የተግባር ፈተና ማለፊያ ነጥብ 60% በላይ መሆን ስላለበትና የስራ መደቡም ከፍተኛ ችሎታና ጥንቃቄ የሚጠይቅ ስለሆነ በተግባሩ ስላላለፍክ እድገቱን ልታገኝ አይገባም በማለት ማስታወቂያ ስላወጣ ማስታወቂያ ተሰርዞ እድገቱ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በሚል ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በዚህም መሰረት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪ ዝቅተኛ ነጥብ ያመጡ በመሆኑ ቦታ ሊሰጣቸው እንደማይገባ እና በውድድር ቅጥሩን ለመፈፀም ማስታወቂያን ማውጣቱ ተገቢ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ በግራ ቀኙ በኩል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመርመር ተጠሪ የተግባርና የውሉፍ ፈተናውን ስለማለፋቸው ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን፣ በተቃራኒው አመልካች ድርጅት ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች የሚያስረዱት ተጠሪ ፈተናውን ወስደው ከተቀመጠው መስፈርት ዝቅተኛ ያመጡ መሆኑን ጠቅሶ ክሱን ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ብቸኛ ተወዳዳሪ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በጠቅላላ ውጤት ከመቶ 54.76 በማግኘት ከ50% በላይ ያገኙ ሆኖ እያለ በተግባርና በውሉፍ ፈተና ከመቶ 60 ስላጡ በሕብረት ስምምነት ወይም በሌላ መመሪያ በግልጽ እስካልተደነገገ ጊዜ ድረስ ይህንን ስላላሟላ ተብሎ ከውጪ ተወዳዳሪ እንዲቀርብ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚለውን ምክንያት በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ የቦታውን መስፈርትና ውጤት ስለሚያሟሉ ሊሰጣቸው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 14 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ያሁኑ አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ሕዳር 09 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ ክሱን የመሰረቱት የእድገት ደረጃ ይሰጠኝ በሚል ሲሆን አመልካች ለተጠሪ ደረጃው ሊሰጥ አይገባም በማለት የሚከራከረው ተጠሪ የተወዳደሩበት የብየዳ የሥራ መደብ በወጣው የውስጥ ማስታወቂያ ሆኖ እንዲወዳደሩ እድል ተሰጥቷአቸው በሕብረት ስምምነት አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 2፣ 3 እና 7 ድንጋጌዎች መሰረት ከመስፈርቶቹ አንዱ የሆነውን የተግባርና የፅሑፍ ፈተና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምርታማነት ማሻሻያ ማዕከል ፈተና እንዲወስዱ ተልከው ፈተናውን ተፈትነው ያገኙት ውጤት 38% በመሆኑና የማለፊያ ነጥብ ደግሞ 60% እንደሆነ፣ ተጠሪ ያገኙት ነጥብም ዝቅተኛ መሆኑን ማዕከሉ በፅሁፍ የገለፀው ውጤትም ለመራጭ ኮሚቴ ቀርቦ የተወዳደሩበት የስራ መደብ የብየዳ ስራ በመሆኑ እና ይህ ደግሞ የተግባር ስራ ሆኖ ከፍተኛ እውቀትና ችሎታ እንደሚያስፈልገው ገልጾ ተጠሪ ይህንን ባለማለፋቸው ለቦታው ብቁ እንዳልሆኑ በመግለፅ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት ለቦታው ብቁ የሆነ ሰው ለመምረጥ የራሱ የሆነ መስፈርትና ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ የሚከራከሩት መስፈርቱና ሥርዓቱን ስለማሟላ ቦታው ይገባኛል በማለት ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 18180 አግባብነት ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ድንጋጌዎችን በመመርመር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን የወል የስራ ክርክሮችን ማየት መሆኑን፣ አንድ የስራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ የሆነ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን፣ ባንፃሩ አንድ የስራ ክርክር የወል ሳይሆን የግል የስራ ክርክር ነው ሊባል የሚችለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወሰኖ የሚቀር ሆኖ ሲገኝ ነው በማለት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከማየቱ በፊት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በራሱ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(1(ሀ)) ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ ያስገነዝባሉ፡፡ ክርክሩ በየትኛውም ደረጃ ቢገኝ ይኸው መረጋገጥ አለበት፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ የስራ መደቡ ይሰጠኝ በማለት ያቀረቡት ክስ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆኖ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሲሆን የወል የስራ ክርክር ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የሰራተኛ እና አሰሪ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እንጂ ፍርድ ቤት አይደለም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ፍርድ ቤቱ አይቶ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31367 ጥቅምት 05 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 73044 ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም የተሻረው ውሳኔ ፍርድ ቤቶቹ ስልጣን ሳይኖራቸው የተሰጠው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ክርክር የወል የስራ ክርክር እንጂ የግል ባለመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 52600

ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር - ጠበቃ ጌታቸው ዓለሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድን ስልጣን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክሱን ያቀረቡት በወጣው ክፍት በሌጦ ክረስት አዘገጃጀት ምርት ፎርማን ስራ መደብ ላይ ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ተወዳድሬ በማሸነፍ እድገቱ እንዲሰጠኝ መደረግ ሲገባው ስለተከለከልኩ እድገቱ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በዚህም መሰረት የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪ ለግሉ ባቀረበው ጥያቄ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ በሕብረት ስምምነቱ ደንብ አንቀፅ 15(4) እና በደረጃ እድገት አፈጻፀም መመሪያ አንቀጽ 11/1 እና 11/2 መሰረት የተጠሪ የደረጃ እድገት ኮሚቴ ውሳኔ የአሰሪው ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ሳያፀድቅ የሻረው በመሆኑ ከሕግና ስርዓት ውጪ ተጠሪ የደረጃ እድገቱ በወሳኝ ቦርዱ እንዲወሰንላቸው ክስ ማቅረባቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለፅ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምስራቅ ሸዋ ዞን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድም የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦች ውድቅ አድርጎ ለተጠሪ የስራ መደቡ እንዲሰጣቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ቦርዱ የሠጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 04 ቀን 2002 ዓ/ም በጻፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ለማየት ስልጣን የነበረው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ መጋቢት 29 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም ሚያዚያ 08 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 18180 አግባብ ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ድንጋጌዎችን በመመርመር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን የወል የስራ ክርክሮችን ማየት መሆኑን፣ አንድ የስራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ የሆነ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን፣ ባንፃሩ አንድ የስራ ክርክር የወል ሳይሆን የግል የስራ ክርክር ነው ሊባል የሚችለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ ሲገኝ ነው በማለት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ የስራ መደቡ ይሰጠኝ በማለት ያቀረቡት ክስ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆኖ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የስራ ክርክር አይደለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት እንጂ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አይደለም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ቦርዱ ለማየት ስልጣን አለው ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ሸዋ ዞን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመ/ቁጥር 650/01/2001 መስከረም 29 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87699 ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ክርክር የግል የስራ ክርክር እንጂ የወል ባለመሆኑ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47134

ግንቦት 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ኂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የድሬዳዋ አስተዳደር ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፋንታዬ ምትኩ - ወኪል ሻ/ል አባይነህ መብራቱ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች በሌሎች የቤቱ ተከራይ በተባሉት አራት ግለሰቦች ላይ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- የሚች አባታቸውን ወራሽነት በፍርድ ቤት ያረጋገጡ መሆኑን፣አባታቸው በሕይወት እያሉ በቀድሞ ቀበሌ 15(በአሁኑ ቀበሌ 05) ክልል ውስጥ ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በፊት በቦታ ካርታ ቁጥር 3911 የሚታወቅ፣በቦታ ስፋት 136 ካሬ ሜትር ውስጥ የተሰራ ቤትና ቦታ እንዳፈሩ፣ይህንኑ ቤትና ቦታ በተጠሪ ስም ካርታ ተሰርቶ እንዲሰጣቸው ለቀድሞ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ለአሁኑ የቦታ አስተዳደርና የመሬት ልማት አቤቱታ አቅርበው ይኸው አካል ካርታው በተጠሪ ስም ተሰርቶ እንዲሰጥላቸው ለድሬዳዋ አጠቃላይ ምክር ቤት ደብዳቤ የፃፈላቸው መሆኑን፣ተጠሪም ሚች አባታቸው በቤቱ የበሉትን አበል በደረሰኝ ለቀበሌው ገቢ ማድረጋቸውን፣ሆኖም ከዚህ በኋላ እንዲመለስላቸው የተባለውን ቤት ቀበሌው ከተከራዮች አስለቅቆ ለተጠሪ ሊያስርክባቸው ያልቻለ መሆኑን ገልፀው ቤቱን እንዲያስረክባቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረው ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ በመሆኑ ተጠሪ ክስ ለመመስረት መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን፣ጉዳዩም በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ጉዳዩን ለማየትም ፍርድ ቤት ስረ-ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያሳዩ ነጥቦችን ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ተጠሪ ቤቱ እንዲመለስላቸው ተወስኗል የሚሉት ስልጣን ያላቸው አካላት የሰጡትን ውሳኔ መሰረት በማድረግ አለመሆኑንና ክርክራቸው በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር በአመልካች በኩል የቀረቡትን የክርክር ነጥቦችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጐ አከራካሪውን ቤት አመልካች ተከራዮችን አስለቅቆ ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ውሳኔው ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ወኪል ሰኔ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶ ለረሻርም አመታት ቀበሌው ሲያስተዳድር የቆየው እና ተጠሪ ቤቱ እንዲመለስ ተወስኖልኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር ሥልጣን የሌላቸው አካላት የሰጡት ውሳኔ ሁኖ እያለ ቤቱ እንዲመለስላቸው ተወስኗል ተብሎ ቀበሌው ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ ተብሎ መወሰኑ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች ለተጠሪ ያስረክብ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ የተጠሪ ወኪል ቀርበው ሕዳር 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አራት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አግባብነት ያሳያሉ ያሏቸውን ነጥቦች በማንሳት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ወኪል በበኩላቸው መጋቢት 08 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመለስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ ጉዳዩን የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ለማየት የሥረ-ነገር ስልጣን አለው ወይስ? የለውም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች ሊያስረከብ ይገባል የሚሉት ቤቱ በወቅቱ ሥልጣን ባላቸው አካላት እንዲመለስ ተወስኖ የቤቱ ካርታም በተጠሪ ስም ተሰርቶ በቤቱ ማህደር ጋር ተያይዞ ይገኛል በሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት መንግስት ወርሶት ቀበሌው የሚያስተዳድረውና ለተጠሪ ቤቱ እንዲመለስ ውሳኔ ተሰጥቷል የሚባለው ስልጣን ባላቸው አካላት አለመሆኑን ገልፆ የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኙ ንብረቶች ወይም መነሻቸው በዚሁ አስተዳደር ክልል በሆኑ እጅግ በርካታ አይነት ጉዳዮች ላይ ሰፊ የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አሉ፡፡ ከዚህ ደግሞ መገንዘብ የሚቻለው በዚህ ረገድ በተለይ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን በሚመለከት ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ያላቸው የዳኝነት ሥልጣን በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/96 አንቀጽ 33 ሥር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በዚህ አንቀጽ ለፍርድ ቤቶቹ የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን በንኡስ አንቀጽ 1/ረ/ የተመለከተው የከተማው አስተዳደር ከሚያስረዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱት ጉዳዮችን ያጠቃልላል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ሲታይም የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የሚኖረው አከራካሪው ቤት ባለቤትነቱ የመንግስት ሆኖ በከተማው አስተዳደር የሚተዳደር መሆን የሚገባው መሆኑን ያስገነዘባል፡፡ ይህም ማለት ቤቱ የማን ንብረት ነው የሚል ወይም ስለቤቱ ባለሐብትነት በተመለከተ የሚነሳ ክርክር ሊኖር አይገባም፡፡ ክርክር ቢነሳ ሊሆን የሚችለው ከባለቤትነት መብት በመለስ ያሉትን ለምሳሌ ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱትን ጉዳዮች በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ በከተማው ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቀውም ይኸው ከባለቤትነት በመለስ ያለ ክርክር ብቻ ነው፡፡ ክሱ ወይም ክርክሩ የባለሃብትነት ጥያቄ የሚያስነሳ ከሆነ ግን ከከተማው ፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር የዳኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥልጣን ውጭ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚነሳ ክርክር የስረ-ነገር የዳኝት ሥልጣን የሚኖራቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ባለቤትነት አከራካሪ የሆነ በመሆኑ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ክርክሩን የሰሙት የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖራቸው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌላቸው በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00423/99 ሚያዝያ 12 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00299/2001 ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ሥር የሚወድቅ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቶቹ ወደ ክሱ ስረ ነገር ገብተው ውሳኔ የሚሰጡበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ለክርርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 52041

ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሐሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክ/አ/ማኅበር - ነ/ፈጅ ጌታቸው ደጉ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢት/መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ጽጌረዳ ተሻገር - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲመረመር የቀረበው የአ/አ/ ከተማ ማኅበራዊ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ክርክር የመዳኘት ሥልጣን በተመለከተ ነው፡፡ የጉዳዩ አጀማመር ሲታይ ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ ነበር፡፡ የተጠሪ የክስ ምክንያት ንብረትነቱ የአመልካች የሆነው መኪና የተጠሪን ደንበኛ መኪና ገጭቶ ጉዳት አድርሷል በሚል ተጠሪ የከፈለውን ብር አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሰባት /4977.00/ አመልካች እንዲተካ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከተው በአ/አ ከተማ በቂርቆስ ክ/ከተማ የቀበሌ 04 ማኅበራዊ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ እንደ ክሱ አቀራረብ ወስኗል፡፡ በይግባኝ ሰሚ የአ/አ ከተማ ፍርድ ቤቶችም ይኸው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ከቀረበው አቤቱታ አንፃር ይህ ችሎት የተመለከተው ማኅበራዊ ፍ/ቤቱ ይህንን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ሲሆን በዚህ ረገድ የተጠሪ ነ/ፈጅ ባቀረቡት የክርክር መልስ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50 መሠረት ማኅበራዊ ፍርድ ቤት እስከ ብር አምስት ሺህ በሆነ የፍትሐብሔር ጉዳይ አከራክሮ የመወሰን ሥልጣን አለው ሲሉ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል ባጭሩ የተመለከትነው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ሕጉን አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው የተጠሪ ክስ ምክንያት ከውል ውጪ ኃላፊነት የሚመለከት ሲሆን ለመክስ መነሻው ግን ተጠሪ ከደንበኛው ጋር አለኝ በሚል የመድን ውል መነሻ በንግድ ሕጉ በተመለከተው የመዳረግ መብት የቀረበ ስለመሆኑ ነው፡፡ በዚህ መዝገብ የቀረቡት ተከራካሪ ወገኖች አንደኛው ብቻ ሳይሆን ሁለቱም በፌዴራል መንግሥት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ ስለመሆናቸውም መረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም በዚህ መነሻ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ ለመወሰን የአ/አ ከተማ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን አለውን? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በተጠሪ የተጠቀሰውን አዋጅ ቁጥር 361/95 ከአዋጅ ቁጥር 25/88 ጋር በማገናዘብ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የአ/አ ከተማ ፍርድ ቤቶችና የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት አደረጃጀት እና ሥልጣንና ኃላፊነት በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 361/95 ከአንቀጽ 39-50 ድረስ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የዳኝነት አካላቱ ሥልጣን መሠረት ያደረገው የከተማው አስተዳደር ተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት በሚመለከቱ አስተዳደራዊ ጉዳዮች እንዲሁም በከተማው ነዋሪዎች መካከል የሚነሱ የፍትሐብሔር እና የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ላይ አከራክሮ የመወሰን ኃላፊነት የተሰጠ ስለመሆኑ ነው፡፡ በተለይም ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው የአዋጁ አንቀጽ 50/1/ የክርክር መጠኑ ከብር አምስት ሺህ ያልበለጠ የንብረት እና የገንዘብ ክርክሮችን ማኅበራዊ ፍ/ቤቶች እንዲዳኙ ሥልጣን ሲሰጥ ከፍ ሲል ከተመለከተው አጠቃላይ ዓላማ እና ወሰን ጋር መታየት ያለበት መሆኑን መገንዘብ አዳጋች አይደለም፡፡

በዚህም እጅግ ቀላል የሆኑ ጉዳዮች እና ውስብስብ የሕግ ጥያቄ የማያስነሱ ክርክሮች በአጭር እና በቅርበት ለማኅበረሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል ስለመሆኑ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ የአዋጁ ግብ ይህ መሆኑ የሚታወቅ ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር አምስት ሺህ በታች በመሆኑ ብቻ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ የመወሰን ሥልጣን ያሰጠዋል የሚለውን የተጠሪ ክርክር ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንፃር መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 25/88 የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ሲዘረዝር በዋነኛነት ታሳቢ ያደረገው የፌዴራል መንግሥት አወቃቀር እና የፌዴራል ሥርዓቱን የሥልጣን ክፍፍል መርህ በመጠበቅ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ወሰን በግልጽ በሌላ ሕግ እስካልተሻረ ድረስ በገዘምታ ወይም ኋላ በወጣ ሕግ ተተክቷል ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክር ማለትም በአዋጅ ቁጥር 25/88 የተደነገገው ቢኖርም አዋጅ ቁጥር 361/95 ኋላ የወጣ በመሆኑ ተፈፃሚነት አለው የሚለው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ እና 5/9/ ሥር በግልጽ እንደተደነገገው በፌዴራል መንግሥት የተቋቋመ ተቋም ተከራካሪ የሆነበት ጉዳይ ከመሆኑ አንፃር እና የክርክሩ መነሻም የመድን ውል መሆኑ ሲታይ በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑ በግልጽ በሕግ የተደነገገ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች በግልጽ በተሰጠ የዳኝነት ሥልጣን የገንዘብ መጠኑን ብቻ መሠረት በማድረግ የአ/አ ከተማ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን ነው በማለት በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡

ስለዚህ በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ላይ ያሉት ተከራካሪ ወገኖች ማንነት እና በክርክሩ የሚነሳው የሕግ ጥያቄን መሠረት በማድረግ ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንፃር ተመልክቶ ባለው አግባብ ሊስተናገድ የሚገባው ሆኖ ሳለ የአ/አ ከተማ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ተቀብሎ የሰጠው ፍርድ የሥራ-ነገር ሥልጣን በሕግ በግልጽ ያልተሰጠው በመሆኑ ሊፀና የሚችል ፍርድ የለም ብለናል፡፡

ስለሆነም የማኅበራዊ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ተገንዝቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 231/1/ለ/ መሠረት መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ የመሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

በቂርቆስ ክ/ከተማ የቀበሌ 04 ማኅበራዊ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 953/97 የሰጠው ውሣኔ፣ የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02451 የሰጠው ፍርድ እና የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08207 በ20/02/2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 43912

ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ጠበቃ ረዳኢ ባራኺ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. የአቶ ኢብራሂም ሙሣየ- ወራሾች በሌሉበት

2. ሰይድ ኢብራሂም - በሌለበት

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በመኪና ላይ ደረሰ የተባለውን ጉዳት መሰረት በማድረግ የቀረበ የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተው የመድን ዋስትና የገባለት የደንበኛው መኪና በሁለተኛ ተጠሪ ሾፌርነት ሲሽከረከር በነበረው በአንደኛ ተጠሪዎች መኪና ተገጭቶ ጉዳት ስለደረሰበትና በዚህ ምክንያትም መኪናውን ለማስጠገን ወጪ በማድረጉ ይህንኑ እንዲተኩለት ነው፡፡ በአንደኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት የተሰማ ሲሆን፣ሁለተኛ ተጠሪ ግን ቀርቦ መልሱን እንደሰጠ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ከሁለቱ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ሁለተኛ ተጠሪን ከክሱ ነፃ በማድረግ በአንደኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ብር 22,387.79(ሃያ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሰባ ዘጠኝ ሣንቲም) ከነወለዱ እንዲከፍሉ ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በውሳኔው ስላልተስማማ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ የነበረ ሲሆን፣ፍ/ቤቱ ክሱ የቀረበው የግዛት ሥልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ካለመቀበሉም በላይ፣በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔም ሽሮታአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በሥር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ የተሰማው በሌሉበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግዛት ሥልጣንን መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን የተመለከተው ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የግዛት የዳኝነት ሥልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም? የሚለው ጭብጥ አንዣር ነው፡፡ ለሰጠው ውሳኔ በዋቢነት የጠቀሰውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥሕ/ቁ. 27/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን ድንጋጌ ለመጥቀስ የበቃው የክሱ መነሻ በሚንቀሳቀስ ንብረት የደረሰ ጉዳት ነው የሚል ምክንያት በመያዝ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁንና በተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በቁጥር 27/1/ የተመለከተው ሳይሆን፣በቁጥር 24/3/ የተመለከተው እንደሆነ ነው በበኩላችን ለመገንዘብ የቻልነው፡፡ አመልካች በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ማህበር እንደመሆኑ ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(6) መሰረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 24/3/ በግልጽ እንደተቀመጠው በኢንሹራንስ ውል አፈፃፀም ምክንያት ክርክር የተነሳ እንደሆነ ክሱ የኢንሹራንሱ ኩባንያ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ባስቻለው ባለሥልጣን ፍ/ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች የኢንሹራንስ ኩባንያ ነው፡፡ ዋና መሥሪያ ቤቱ በዚህ በአዲስ አበባ ስለመሆኑም ይታወቃል፡፡ ክሱም የቀረበው በዚህ በአዲስ አበባ ላስቻለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የግዛት ክልል የዳኝነት ሥልጣን የለውም የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ያየው የተሳሳተ ወይም ለጉዳዩ ተገቢነት የሌለውን ሕግ መሰረት በማድረግ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48183 ኀዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከፈተው የይግባኝ መዝገብ ጉዳዩን እንዲቀጥል በማድረግ እና ወደ ጉዳዩ ሥረ ነገር በመግባት ክርክሩን ሰምቶ ተገቢው ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ይመለስለት ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር አመልካች ወጪና ኪሣራውን ራሱ ይቻል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48018

ሐምሌ 7 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ተከተል ዘካሪያስ - ወኪል አዳነች ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አስቴር ታደሰ - ጠበቃ አቶ ፍቃዱ ያሚ ቀረቡ

2. አቶ ገነነ ደምሴ - በሌሉበት ይታያል

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቹ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው ስለጠየቁ ነው፡፡ በሥር ክርክሩ የታየው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ የሆነ ተሽከርካሪ በሁለተኛ ተጠሪ ሹፌርነት ሲሽከረከር በሰበታ ሐዋሳ ወረዳ ቀበሌ 01 ገጭቶ ጉዳት ያደረሰብኝ ስለሆነ ካሣ ይከፈለኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ አመልካች ክሱን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 መሰረት ጉዳቱ በደረሰበት ቦታ የሥረ-ነገርና የክልል ግዛት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለባቸው በማለት ተቃውመዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ጉዳዩን ለማየት የግዛት ክልል ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ያቅርብ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይኑ በይግባኝ መርምሮ አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በሁለት ክልል ኗሪዎች መካከል የሚነሣው ክርክር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መታየት እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 25/88 ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 10 እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 19 ሊወድቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ ጉዳቱ የደረሰበት ቦታ ብቻ ነው መክሰስ ያለባቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል አንደኛ ተጠሪ በበኩላቸው የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 በጉዳት ካሣ ጊዜ የክልል ሥልጣን ያለው የትኛው የፍርድ ቤት እንደሆነ የሚደነግግ ልዩ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የሕግ ትርጉም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡

በሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አከራካሪው ጭብጥ ጉዳዩን የማየት የግዛት ክልል ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የትኛው ነው? የሚለው ነው፡፡ በመርህ ደረጃ በሰዎች ወይም በሚንቀሣቀስ ሐብት ላይ በደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስ ጉዳቱ በደረሰበት ሥፍራ የሥረ-ነገረ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት መቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 27 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ይህም የሆነው የደረሰው የጉዳት እና ከጉዳቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ጉዳቱ በደረሰበት አካባቢ በቀላሉ ማስረጃ ለማግኘትና ማስረጃም ለማቅረብ የሚቻል በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 ንኡስ አንቀጽ 1 ከላይ የተገለውን የሕጉን ዓላማ በአግባቡ ማሣካት የማይከለክል በሆነ ጊዜ በሰው ወይም በሚንቀሣቀስ ንብረት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስ ተከሳሽ በሚኖርበት ቦታ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ጉዳቱ የደረሰው ሰበታ አካባቢ መሆኑ የተጠሪዎች የመኖሪያ ቦታ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መሆኑና ምስክሮችና ሌሎች ማስረጃዎችን ለማቅረብ የሚያጋጥም የትራንስፖርትና ሌሎች ችግሮች ቀላል በመሆኑ አመልካች ክሱን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማቅረባቸው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 27 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ የሚቃረን ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ክሱን ተቀብሎና አከራክሮ በፍሬ ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት ሲገባው የግዛት ክልል ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ስህተቱን ማረም ሲገባው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይንና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የክልል ግዛት ሥልጣን አለው ብለናል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪዎች በፍሬ ጉዳይ ላይ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 341 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት መልሰንለታል ይፃፍ፡፡

በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45806

ሀምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ፍፁም በርታ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሶፊያ ዱላ

2. ወ/ሪት መሪማ በርታ

3. አቶ ሚፍታ በርታ - ጠበቃ አቶ ታየ ቀረቡ

4. አቶ ማርዬ በርታ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አባቴ አቶ በርታ ሰይድ ሀምሌ 24 ቀን 1995 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ሟች አባቴ በውልና ማስረጃ መጋቢት 5 ቀን 1985 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ ስለሆነ ኑዛዜው ፀድቆ የኑዛዜ ወራሽነቱ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ለአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበው ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪዎች በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት አመልክተው በክርክሩ ጣልቃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው በኋላ ተጠሪዎች በሸሪዓ ፍርድ ቤት የሚች ወራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አቤቱታ አቅርበው አመልካቹ በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እየተከራከረ ስለሆነ ጉዳዩ በአንድ ጊዜ በሁለት ፍርድ ቤቶች መታየት የለበትም የሚል መቃወሚያና በአማራጭ ሌሎች መከራከሪያዎችን አቅርበዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች በዚህ መዝገብ በተያዘው ጉዳይ ላይ በመከራከር እያሉ የአሁን ተጠሪዎች አመልካች የአሁን አመልካች ጣልቃገብ ተከራካሪ የሆኑበት በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተያዘው መዝገብ መስከረም 25 ቀን 1997 ዓ.ም ውሣኔ አግኝቷል፡፡ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተወሰነ መሆኑን በመግለፅና አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ላይ ማከራከር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 8(1)"ን" የሚጥስ መሆኑን በመግለፅ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎበታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙን አልተቀበለውም፡፡ አመልካች ለአዲስ አበባ አስተዳደር የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ግንቦት 6 ቀን 2001 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ እኔ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆኜ የገባሁት ወላጅ አባቴ በፍትሐብሔር ህጉ መሠረት ያደረገው ኑዛዜ ስላለ ውርሱ መታየት የሚገባው በመደበኛው ፍርድ ቤትና በፍትሐብሔር ህጉ መሠረት መሆን አለበት የሚለውን መቃወሚያ ለማቅረብ ነው፡፡ እኔ በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት መጥሪያ ተልኮልኝ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆኔን በመግለፅ ፎርም ሞልቼ ያላቀረብኩ በመሆኑ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ሙሉ ፈቃድን አልሰጠሁትም፡፡ መቃወሚያ ለማቅረብ ጣልቃ መግባቴ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃድ ሰጥቷል ተብሎ የተሰጠው የህግ ትርጉም አባቴን የመውረስ መብቴን የሚያሣጣና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው እኛ የአንደኛ ተጠሪ የሚች ሚስትና ወራሽ ከሁለተኛ ተራ ቁጥር እስከ አራተኛው ተራ ቁጥር ስማችን የተገለፀው ተጠሪዎች የሚች ልጆችና ወራሾች መሆናችንን በሸሪዓ ፍርድ ቤት በሸሪዓ ህግ መሠረት ለማረጋገጥ ባቀረብነው ማመልከቻ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ እያለ አመልካች ነሐሴ 27 ቀን 1995 ዓ.ም በተባለ አቤቱታ በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት አመልክቷል፡፡ አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ከተፈቀደለት በኋላ አንደኛ ተጠሪ የሚች ሚስት አይደለችም ሚች በህይወት በነበሩበት ጊዜ ያደረጉት ኑዛዜ ስላለ ኑዛዜው ይፅደቅልኝ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ስለጉዳዩ በሸማግሌዎች እንዲጣራ በማድረግ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎበታል፡፡ አመልካች በሙሉ ፈቃዱ በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ኑዛዜው እንዲፀድቅለትና አንደኛ ተጠሪ የሚች ሚስት አይደሉም ተብሎ እንዲወሰንለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አመልክቶ ውድቅ ከተደረገበት በኋላ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ስምምነት አልሰጠሁም በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተገቢ አይደለም በማለት በፅሑፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ሚች አባቴ ኑዛዜ ያደረጉ በመሆኑ በሸሪዓ ህግ መሠረት የሚች ውርስ መታየት የለበትም የሚል መቃወሚያ ለማቅረብ በክርክሩ ጣልቃ መግባቴ በሸሪዓ ህግ መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃድ እንደሰጠሁ ሊቆጠር አይገባውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኑዛዜው በሸሪዓ ፍርድ ቤት ታይቶ ውሣኔ አልተሰጠበትም የሚል ይዘት ያለው የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ በፅሑፍ ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በሸሪዓ ህግ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃዱን ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሚች አድርገውታል የተባለውን ኑዛዜ አይቶ ውሣኔ ሰጥቶበታል ወይስ አልሰጠበትም? የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ማመልከቻ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. አመልካች በሸሪዓ ሕግ መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃድ አልሰጠሁም በማለት ሰፊ ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ፈቃዱን ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? የሚለውን ጭብጥ ለመፍታት አመልካች ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ሆኖ የገባበትን ሁኔታና አመልካች በሸሪዓ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ሆኖ ከገባ በኋላ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ያቀረበውን ጥያቄና ክርክር ይዘት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች አንደኛ ተጠሪ የሚች አቶ በርታ ሠይድ ሚስትና ወራሽ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ እና አራተኛ ተጠሪዎች የሚች ልጆችና ወራሾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆናቸው በሸሪዓ ህግ መሠረት ተረጋግጦ እንዲወሰንላቸው ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 7/96 ባስከፈቱት ክርክር ጣልቃ ለመግባት የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ እንዲፈቅድለት አመልክቷል። አመልካች በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሠረት ተጠሪዎችን ወራሽነት ጥያቄና ክርክር ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር ሲጠይቅ በክርክሩ ሒደት በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀፅ 6(1) መሠረት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ለውሣኔአቸው መሠረት ሊያደርጉት በሚገባው በሸሪዓ ህግ መሠረት ለመዳኘት ፍላጎትና ፈቃድ ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ምክንያቱም የክርክሩን የአመራር ሥርዓት ካልሆነ በስተቀር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሥረ-ነገር ሥልጣናቸው ሥር የሆኑ ጉዳዮች የሚቀርብላቸውን አቤቱታና ክርክር የሚወስኑት የሸሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/92 በአንቀፅ 6(1) በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ አንድ ሰው ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ሲያቀርብ ሥነ ሥርዓታዊ ከሆነው ጭብጥና ጥያቄ ውጭ የሆኑት ጉዳዮች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘትና ፈቃድ የሰጠ መሆኑን የሚያሣይ በመሆኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በሸሪዓ ህግ መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃዱን የሰጠ መሆኑን ወይም አለመሆኑን አመልካች በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከፈቀደለት በኋላ ያቀረበውን ክርክር ይዘትና የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኝነት በማየት እንዲወሰንለት ያቀረበውን ጭብጥ በመመርመር ውሣኔ መስጠት ግድ ይላል።

አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ከፈቀደለት በኋላ ሁለት መሠረታዊ ጭብጦች ፍርድ ቤቱ አይቶ ውሣኔ እንዲሰጥለት ጠይቋል። የመጀመሪያው አንደኛ ተጠሪ የሟች አባቴ አቶ በርታ ሠይድ ሚስት አይደሉም። ስለሆነም አንደኛ ተጠሪ የሟች ሚስትና ወራሽ ነኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ሟች አባቴ በህይወት እያለ ያደረገው የኑዛዜ ሰነድ ስላለ የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ያፅድቅልኝ የሚል መሆኑን በመዝገብ ቁጥር 7/96 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ ለመገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም አመልካች የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጣልቃገብ ተከራካሪ እንዲሆን የጠየቅሁት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በሸሪዓ ህግ መሠረት ጉዳዩን እንዳይወስን ተቃውሞ ለማቅረብ ነው በማለት በሰበር አቤቱታው ያቀረበው መከራከሪያ ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል። አመልካች ለፌዴራል የሸሪዓ ፍርድ ቤት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ክርክሩን እንዲያሰማ ያቀረበው ማመልከቻና አመልካች በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ከተፈቀደለት በኋላ የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ የጠየቀው ዳኝነትና ያቀረበው ክርክር በአንድነት ሲታዩ አመልካች በሸሪዓ ህግ መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ሙሉ ፈቃድን የሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው።

አመልካች በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆኔን በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 5(1) እና ከአዋጁ ጋር በተያያዘው አባሪ(ፎርም) በመሙላት አልሰጠሁም በማለት ክርክር አቅርቧል። ሆኖም ከአዋጁ ጋር የተያያዘውን ፎርም በመሙላት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ከቀጠሮ ቀን በፊት ለሬጅስትራር እንዲገልፅ የሚገደዱት በጉዳዩ ተከሳሽ ወይም በተጠሪነት ቀርበው መልስ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች መሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 5(1) በግልፅ ተደንግጓል። አስፈላጊ የሆነ ሥነ ሥርዓቶችና ፎርማሊቲዎች በማሟላት ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ያቀረበ ከሳሽ ወይም አቤቱታ አቅራቢ ክሱን ወይም አቤቱታውን ለሸሪዓ ፍርድ ቤት አንዲታይ ፈቃደኛ መሆኑን ፎርም በመሙላት መግለፅ አያስፈልገውም። ስለሆነም አመልካች የሸሪዓ ፍርድ ቤት አቤቱታውን አይቶና በአቤቱታው ዳኝነት የጠየቀባቸውን ጉዳዮች አጣርቶ እንዲወሰንለት ግልፅ ጥያቄ አቅርቦና ተከራክሮ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘትና ጉዳዩ በሸሪዓ ህግ መሠረት እንዲወሰን ፈቃዱን አልሰጠሁም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የአዋጁን አንቀፅ 5(1) ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል።

2. የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሟች አቶ በርታ ሠይድ መጋቢት 5 ቀን 1985 ዓ.ም አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ በሸሪዓ ህግ መሠረት ህጋዊ ውጤት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝና አግባብነት ያላቸውን የሀዲስ ድንጋጌዎች (በሸሪዓ) ስለ ኑዛዜ ዋጋ መኖር ከተደነገጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ያልፀደቀ በመሆኑ በሸሪዓ መሠረት ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት ያለው አይደለም በማለት እንደወሰነ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት መስከረም 25 ቀን 1997 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ በግልፅ ተመልክቷል። የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ በፊቱ የቀረበለትን የኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ ወራሽነት ጥያቄ የሚወስነው የሸሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 6(2) የተደነገገ በመሆኑ አመልካች የሟች ኑዛዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይፅደቅልኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ አግባብነት ያላቸውን የሸሪዓ ህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሚች አቶ በርታ ሠይድ ያደረጉት ኑዛዜ የሸሪዓ ህግ የሚጠይቀውን መሥፈርት ያሚላና ህጋዊ ውጤት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ሲወስን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አግባብነት ያላቸውን የሸሪዓ ህግ ድንጋጌዎች አልጠቀሰም ወይም የሸሪዓ ህግ ድንጋጌ ሲተረጉም ሥህተት ሠርቷል የሚል ሀሳብ ካላቸው አመልካች ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የማረም ሥልጣን ላለው የፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ነበረባቸው፡፡ አመልካች ይህንን በማድረግ ፋንታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በጭብጥነት በመያዝ ግልፅ ውሣኔ የሰጠበት የሚች ኑዛዜ እንደተጠቃሚ መሆናቸውን እንዲረጋገጥላቸው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄ የህግ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክር በሚሰማበት መዝገብ ጣልቃ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸውና የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ የሚች ያደረገው ኑዛዜ ስላለ በኑዛዜ ተጠቃሚ መሆናቸው እንዲወሰን ጥያቄ አቅርበው ጉዳዩ በሸሪዓ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ እያለ የሚች ኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ ውሣኔ እንዲሰጥላቸው ለአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ ይኸ የአመልካች የክርክር ስልት በአገራቱ ሰዎች በፈቃዳቸው በሀይማኖት ወይም በባህል ህግ መሠረት የመዳኘት መብት እንዳላቸው በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 5 የተረጋገጠውን መብት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሞከሩ መሆናቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ምክንያቱም ህገ-መንግስቱ ሰዎች የግልና የቤተሰብ ጉዳይ በተመለከተ በፈቃደኝነት በሀይማኖት ወይም በባህል ህግ መሠረት የመዳኘት መብት ያላቸው መሆኑን የደነገገው ተከራካሪዎቹ ጉዳያቸውን የሚያቀርቡበትን ፍርድ ቤትና ጉዳያቸው በየትኛው ህግ መሠረት መታየት እንዳለበት በሙሉ ፈቃድና ፍላጎታቸው እንዲመርጡ እድል ለመስጠት እንጅ በአንድ ጊዜ አንድ ጉዳይ በሀይማኖት ህግ መሠረት እንዲታይ ለሀይማኖት የዳኝነት ተቋማትና በሌሎች ህጎች መሠረት እንዲታይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት አቅርበው እንዲከራከሩ ለመፍቀድ አይደለም፡፡ አመልካች የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበውንና የሸሪዓ ፍርድ ቤት መሠረታዊ ጭብጥ አድርጎ ይዞ በማጣራት ላይ የነበረውን ጉዳይ በተመሣሣይ ጊዜ ውስጥ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን ያቀረበው ጥያቄ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 5 እና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 8 ንዑስ አንቀፅ 1 የሚጥስ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የሚች ኑዛዜ በጭብጥነት ይዘው በማጣራት ላይ እያሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ቀድሞ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ቀድሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪዓ ፍርድ ቤት በፍርድ የተቋጨ ጉዳይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየቱ እንዲቀጥል ማድረጉ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ የሚጥስና አስቀድሞ በፍርድ የተቋጨ ጉዳይ በድጋሚ በሌላ ፍርድ ቤት እንዲወሰን የቀረበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎት አመልካች ሚች አባቴ ያደረጉት ኑዛዜ ተጠቃሚ መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማ ነክ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 49152

ሐምሌ 07 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ የኮንስትራክሽን ስራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር - ወኪል አህመድ በዳኔ ቀረቡ

ተጠሪ፣ የኮንሽትራክሽን ስራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት - ጠበቃ መንበረስላሴ በዛብህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት ያደረገ የቦነስና የደመወዝ ጭማሪ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ አካል ክሱን ያቀረበው የአሁኑ አመልካች ሲሆን ተጠሪ ከሣሽ ነበር የአመልካች የክሱ ይዘት ተጠሪ ድርጅት በ1999 ዓ.ም የበጀት ዓመት ተጠሪ ካገኘው ትርፍ በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 24/1/ መሠረት የደመወዝ ጭማሪና የቦነስ ክፍያ ተጠሪ እንዲከፍል ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበው ክርክር የደመወዝና የቦነስ ጭማሪ ጉዳይ ለማየት ፍርድ ቤቱም ሆነ ቋሚ ቦርዱ ሥልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በአዋጁ አንቀጽ 138 መሠረት ስልጣን የሌለው መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመግለጽ ክሱን ዘግቶታል፡፡ ይህ ብይን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ቀርቦም ፀድቋል፡፡ ከዚህ በፊትም ጉዳዩ ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ቀርቦ ቦርድም የአዋጁን አንቀጽ 147፣ 142/1/ሀ/2/3// እና 136/2/ ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት ክሱን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራቀኙ ከተከራከሩ በኃላ የቦርዱ ውሣኔ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ በታየው ጉዳይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ መስከረም 07 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ጥያቄው የጋራ ጥቅምን የሚነካ የወል የስራ ክርክር ነው ተብሎ ተወስኖ ሆኖ እያለ ጥያቄው በፍርድ ቤቱም ሆነ በቦርዱ የሚታይ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩ በቋሚ ቦርድ ቀርቦ ሊታይ በሚችል አኳኋን ሕጉ ሊተረጎም ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጥያቄ ለማየት እንዲቻል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ በጠበቃው አማካኝነት ህዳር 02 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ የመልሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ጉዳዩ ከአዋጅ ቁጥር 136/2/ እና 147/1 ሀ/፣ 147/2/ አንፃር ሲታይ በሁለቱም አካላት የሚታይ ባለመሆኑ አመልካች ያለው መብት በአዋጁ አንቀጽ 157 መሠረት መብቱን ማስከበር ነው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች ማህበር የዳኝነት ጥያቄ መሠረት ያደረገው ከተጠሪ ጋር ያለውን የሕብረት ስምምነት መሆኑን ጥያቄውም በ2000 ዓ.ም የበጀት ዓመት ተጠሪ ድርጅት ከብር 78,000,000 (ሰባ ስምንት ሚሊዮን) በላይ ማትረፉን በግልፅ በማረጋገጡ በህብረት ስምምነቱ መሠረት ለሁሉም ሠራተኛ የደመወዝ ጭማሪና ቦነስ የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑን አመልካች ጠቅሶ የሚከራከር መሆኑና ተጠሪ እንደዚህ አይነት ጥያቄ በቋሚ ቦርድ ሊታይ አይገባም በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 138፣142 እና 147 ድንጋጌዎች መሠረት የስራ ክርክር ጉዳዮች የሚታዩበትን ስርዓት ሲዘረጋ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባው የወልና የግል የስራ ክርክሮች በሚል ነው፡፡

የስራተኞችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም አወሳሰን በሚመለከት የሚነሳውን የወል የስራ ክርክር በቋሚው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሊታይ እንደማይችል በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 147/1/1ሀ/ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የደመወዝ ጭማሪና የቦነስ ጥያቄን ማስተናገድ የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 142/3/ በተጠቀሰው መሠረት በአዋጅ አንቀጽ 136/2/ ስር እጅግ አስፈላጊ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተብለው የተጠቀሱትን ድርጅቶች የሚመለከት ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ሕግ አውጪው ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ ለይቶ ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ ተጠሪ ደግሞ ከእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የሚካተት አይደለም፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 136 ስር ከተዘረዘሩት እጅግ አስፈላጊ የሆነ የሕዝብ ግልጋሎት ሰጭ ድርጅቶች ውጪ ያሉትን ድርጅቶች ጋር ሰራተኛው የሚያነሳውን የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ጉዳይ ቋሚ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት ግልፅ የሆነ የሕግ አውጪ ክልከላ ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ሲሆን የእነዚህ ድርጅቶ ጉዳይ በየትኛው አካል ሊታይ እንደሚገባ ሕጉ ያስቀመጠው ስርዓት መኖሩንና አስፈላጊነቱ ምን እንደነበር መመለከቱ የግድ ይላል፡፡

ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም የወል የስራ ክርክር ሆነውም በቦርዱ በተለየ ሁኔታ የማይታዩት ጉዳዮች በሕጉ ተለይተው ተቀምጠዋል ወይስ አልተቀመጡም? የሚለው ጥያቄ መነሳት ያለበት ነው፡፡ በዚህ ችሎት እምነት ከላይ እንደተጠቀሰው ሕግ አውጪው ክርክሩ የወል የስራ ክርክር ቢሆንም በቋሚ ቦርዱ ሊታይ የማይገባበትን ሥርዓት ዘርግቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 141 እና 142 ሲታዩ ይህንኑ የሚመልሱ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት በአዋጅ አንቀጽ 136/2/ ድንጋጌ ስር ከተዘረዘሩት ድርጅቶች ውጪ ያሉ ድርጅቶች የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጉዳይ የአስማሚ ተግባርና ኃላፊነት ሆኖ ሊታይ የሚገባው በአዋጁ ምዕራፍ ሶስት በፌዴራሉ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚመድበው አስማሚ ነው፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 142/1ሀ/ ከተጠቀሰው የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጉዳዮች ብቻ አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ማቅረብ ይቻላል ይህንኑም ከተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሶስት ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ጉዳዩ የሚታየው በአዋጁ ምዕራፍ ሶስት በሚቋቋም አስማሚ እንጂ በአዋጅ ምዕራፍ አራት ስር በሚቋቋም ቦርድ /ቋሚም ይሁን ጊዜያዊ/ አይደለም ይህ ስለመሆኑም አንዳንድ በዋቢነት የሚጠቀሱት ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አዋጅ ቁጥር 377/96 ማሻሻያ ላይ የቀረበው ውይይት አንዱ ነው፡፡ ከአዋጁ ማሻሻያ ሐሳቦች አንዱ የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጉዳይ በአስማሚ ሊታይ አይገባውም የሚል እንደነበር ይታወቃል ማሻሻያው ተቀባይነት ያለማግኘቱ የሚታወቅ ነው፡፡ የማሻሻያው ጥያቄ ውድቅ የተደረገበት አብይ ምክንያትም የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጉዳይ ከአለው እጅግ አስፈላጊና ወሳኝነት ባህርይው የተነሳ በተደጋጋሚ ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪና ጥቅማጥቅም በፈለጉ ቁጥር በአሰሪዎቻቸው ላይ የሚያነሷቸው የማያባሩ ጥያቄዎች ስለሆኑ ሁለቱም ወገኖች በፈቃዳቸው በመረጧቸው አስማሚዎች የሚስማሙባቸው ወይም የሚኒስትሩ መ/ቤት በሚመድበው አስማሚ እንዲያልቅ በማስፈለጉ መሆኑ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ለወሳኝ ቦርድ ይቅረቡ ቢባል ሰራተኞችና አሰሪዎች ጊዜያቸውን ከመስማማት ይልቅ በመካሰስ ያላግባብ እንዲያጠፉና በድርጅቶች ምርትና ምርታማነት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ግን ስምምነት ላይ ባይደርሱ ሠራተኞች የሚወስዱት እርምጃ በአገልግሎት ላይ ችግር ስለሚያስከትል የደመወዝና ጥቅማጥቅም ጉዳይ ከመንግስት ፖሊሲ /Public polic/ አንጻር የእነዚህ ድርጅቶች ጉዳይ ብቻ በቦርድ እንዲታይ ሕግ አውጪው ያደረገው ሊፈጠር ከሚችለው ችግር አንጻር መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑን ሀተታ ዘምክንየት ያሳያል፡፡ የአዋጅ አንቀጽ 147/1/ ድንጋጌ ሲታይ ሥልጣንን በተመለከተ ቋሚው የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ከሚመለከቱት የስራ ክርክር ጉዳዮች ውጪ በአዋጁ በአንቀጽ 142 ንዑስ አንቀጽ አንድ ስር የተመለከቱትን ጉዳዮች ማየትና ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን እንዳለው ተመልክተዋል፡፡ የደመወዝ ጭማሪ እና የጥቅማ ጥቅም ጥያቄን የሚመለከቱት የስራ ክርክሮችን ቋሚ ቦርዱ የማየትም ሆነ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን እንዳይኖረው ማድረግ ያስፈለገውም የደመወዝ ጭማሪ እና የጥቅማ ጥቅም ጥያቄ ጉዳይ የአሰሪውና የሰራተኛው ወገኖች በሚያደርጉት ድርድር አሊያም አንዱ ወገን በሌላው ላይ በሕጋዊ መንገድ ተጽእኖ በማሳደር ኢኪኖሚያዊ ጥቅሙን ለማግኘት ሊወሰድ በሚችል እርምጃ ሊፈታ የሚገባው እንጂ በቦርድ መወሰን የሚገባው ባለመሆኑ ስለመሆኑ የሕጉ ማሻሻያ ሀተታ ዘምክንያት ያሳያል፡፡ በአሰሪና ሠራተኛ ወገኖች መካከል በደመወዝና በጥቅማ ጥቅም ጉዳዮች ላይ አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠር በዚህ አካል ጉዳዩ እንዲታይ ማድረግ የኢንዱስትሪ እርምጃዎችን /ስራ ማቆም ሆነ ስራ መዝጋት/ መብቶች ይገደባል የሚል እሳቤ አለ፡፡ ስለሆነም የተከራካሪ ወገኖች ስምምነት በሌለበት ሁኔታ ወይም ስራ ማቆምና ስራ መዝጋት መብቶች የሌላቸው አካላት ካልሆነ በስተቀር ተከራካሪ ወገኖች በአስገዳጅ የግልግል ዳኝነት ስር እንዲወድቁ ማድረግ አግባብነት እንደሌለው በመታመኑ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እነዚህ ጉዳዮችን እንዳይመለከት መደረጉን ሐተታ ዘምክንያቱ ያሳያል፡፡ የስራ መቆምና የስራ መዝጋት መብቶች በአዋጅ አንቀጽ 157 እና ተከታዮቹ ጥበቃ ያገኙ ጉዳዮች ናቸው በዚህም መሠረት ሕግ አውጪው በአዋጅ አንቀጽ 147/2/ መሠረት እጅግ አስፈላጊ የሕዝብ አገልግሎት ድርጅቶች የሚባሉት ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የሠራተኞችም ሆኑ የአሰሪው ወገን በተጠቀሱት የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጉዳዮች ላይ የሚነሳን ክርክር በድርድር ለመፈታት ባይችሉ እንደሌሎቹ የስራ ማቆም ወይም የስራ መዝጋት እርምጃ የመወሰድ መብት የሌላቸው በመሆኑ ሰራተኞቹም ሆነ አሰሪዎቹ ለጉዳዩ መፍትሄ እንዲያገኙ ክርክር በተፈጠረ ቁጥር በጊዜያዊነት ሊቋቋም ለሚችለው የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን መስጠቱ ታምኖት ግልጽ ድንጋጌ አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም የአዋጅ አንቀጽ 147/2/ ከአንቀጽ 142/3/ ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ሊኖረው የሚገባው ትርጉም በአንቀጽ 136/2/ ስር እጅግ አስፈላጊ የሕዝብ አገልግሎት ድርጅቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ተቋማት ጋር ተያይዞ የሚቀርበውን የደመወዝ እና የሌሎች ጥቅማጥቅሞች ጥያቄ ጋር ተያይዞ የሚነሳን የወል የስራ ክርክር ካልሆነ በስተቀር ከሌሎች ድርጅቶች የሚቀርበውን የደመወዝና የሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን የወል የስራ ክርክሮችን አይቶ የመወሰን የስረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አይደለም፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ጥያቄ የወል የስራ ክርክር ነው ቢባልም ሕግ አውጪው በተለየ ሁኔታ በቋሚ ቦርዱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊታዩ ይገባል ብሎ ከዘረዘራቸው ድርጅቶች ውጪ ያሉ ድርጅቶችን በተመለከተ ቋሚ ቦርዱ ሊመለከት አይገባም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 18180 እና 38933 የሰጠውን ውሣኔ ለዚህ ጉዳይ ያለውን አግባብነት ስንመለከተውም በእነዚህ መዛግብት የተሰጠው ውሣኔ የወል የስራ ክርክር ብሎ ለመለየት የሚቻልባቸውን መንገዶች ተንትኖ ውሣኔ የሰጠበት ሁኔታ እንጂ ያሁኑ አይነት ክርክር ቀርቦ በቦርዱ ሊታይ የሚገባው ነው በማለት ግልፅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ጉዳዩ በቋሚ ቦርድ ሊታይ የሚገባው አይደለም ከተባለ ሊታይ የሚገባው በየትኛው አካል ነው የሚለው ጥያቄ መነሳቱ የግድ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚገኘውም ከአዋጅ አንቀጽ 142/1ሀ/ ስር ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ስለደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች አወሳሰን በተመለከተ የሚቀርብ የወል የስራ ክርክር መታየት ያለበት ተከራካሪዎችን በማስማማት ለጉዳዩ አልባት በሚሰጠው በአዋጅ አንቀጽ 141/1/ መሠረት በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰየም አስማሚ ቦርድ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 466/1997 አንቀጽ 2/2/ ሲታይም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ ቋሚ ቦርዱም ሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባንክና ኢንሹራንስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38572

ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አቶ ናሆም ሽዋንግዛው

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ወ/ሮ ሀና አባይ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት የትሐታብሔር ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ የአሁን ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ አቶ ሐጎስ ተድላ ከንፋስ ስልክ ቅርንጫፍ ለወሰዱት ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ንብረትነቱ የተበዳሪው የአቶ ሀሰን አብደላ የሆነ የሠሌዳ ቁጥሩ 3-16015 እና የተሳቢው መለያ ቁጥር 3-03383 የሆነ መኪና በመያዣነት ይዘናል፡፡ ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና ተበዳሪው አቶ ሐጎስ ተድላ መያዣው የመድን ዋስትና እንደገባለት በተስማሙት መሠረት በመያዣነት የተያዘው መኪና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ምስራቅ አብይ ቅርንጫፍ ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ተገምቶ ኢንሹራንስ መድን ተገብቶ የአረቦን ክፍያ ስንከፍል ቆይተናል፡፡ የመድን ውሉ እየታደሰ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ህዳር 28 ቀን 1988 ዓ.ም መኪናው በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ ከጥቅም ውጭ ስለሆነና ተከሳሽ (አመልካች) ከመያዣው ግምት ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) እንዲከፍል ብንጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆነ እና ተበዳሪው ብድሩን ያልከፈሉ በመሆኑ በመያዣነት የያዝነውን የመድን ዋስትና የገባለትን መኪና ዋጋ እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከተጠሪ ጋር ቀጥተኛ የሆነ የውል ግንኙነት ስለሌለኝ ክስ የማቅረብ ችሎታ የለውም፡፡ መኪናው የተገለበጠው አሽከርካሪው መሪ እንቢ ብሎኝ ነው በማለት ያቀረቡት መግለጫ በቴክኒክ ማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ሀላፊነት የለብንም፡፡ በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት በባለሙያ አልተረጋገጠም፡፡ መክፈልም ካለብን ሰባ አምስት ሺ ብር ነው የሚሉ መከራከሪያዎችን አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል የቀረቡትን መከራከሪያዎች ውደቅ በማድረግ አመልካች ለተጠሪ መያዣው በአደጋ በመውደሙ ምክንያት የደረሰበትን ጠቅላላ ጉዳት ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀሣሳ ሺ ብር) ከህዳር 8 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የጉዳቱ መጠን አልተረጋገጠም በሚልና በሌሎች ነጥቦች የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና ታይቶ እንዲወሰን ጭብጦችን በመለየት ለሥር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡ ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት አቅርቦ ችሎቱ የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በተበዳሪው ብድሩ ያልተከፈለው መሆኑን ሣያረጋግጥ ክስ እንዲያቀርብና እንዲከራከር መደረጉ መሠረታዊ የሆኑ የኢንሹራንስ መርሆችና ዓላማ የሚቃረን ነው፡፡ ተጠሪ ተበዳሪው ከተበደረው ውስጥ የከፈለውን ያልከፈለውን ለይቶ አላቀረበም ተጠሪ ያበደረው 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ሆኖ እያለ ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ጠይቋል ተጠሪ ብድሩ ባለመከፈሉ የነበረውን ወለድ እና ትርፍ መጠየቁ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ህግ እና የንግድ ህግ በመተላለፍ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት በዕሑፍ ያመለከተ ሲሆን ይህንኑ የሚያጠናክር የቃል ክርክር አቅርቧል ተጠሪ በበኩሉ ተበዳሪው እዳውን በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያት ወለዱና ሌሎች በብድሩ አለመከፈል ምክንያት መከፈል ያለበት ገንዘብ ሲታሰብ ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ጉዳት የደረሰብን መሆኑን አስረድተናል፡፡ ተጠሪ የመድን ሽፋን ለማግኘት ከአመልካች ጋር የመድን ውል እንደገባ ያደረገውና የአረቦን ክፍያ ሲከፍል የኖረው ለተበዳሪው ለሰጠው ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ሣይሆን ይህ ብድር በወቅቱ ባይከፈል ለብድሩ መያዣ ለሆነውና ዋጋው ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ለሆነው በመያዣነት ለያዝነው መኪና ነው፡፡ የጠየቅነው ገንዘብ በመድን ውሉ ከተሰጠው ሽፋን የበለጠ አይደለም ስለዚህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ክርክር ተጠሪ ላበደረው ብድር በመያዣነት የያዘው መኪና ለሚደርሰው ጉዳት እስከ ብር 350,000 አመልካች የመድን ሽፋን ሊሰጥ፣ መኪናውን ያስያዘው ሰው ወይም ተጠሪ በየጊዜው መክፈል የሚገባውን አረቦን ሲከፍሉ ነው፡፡ ተጠሪ የመድን ሽፋን ለተገባለት ንብረት መከፈል የሚገባውን አረቦን ያለ ማቋረጥ የከፈለ መሆኑንና በዚህ ሐደት መኪናው አደጋ የደረሰበት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች መኪናው ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ አልሆነም የሚል መከራከሪያ ያቀረበ ቢሆንም ተጠሪ ካቀረበው ማስረጃ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ ክርክሩን ያላስረዳ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በዚህ በኩል አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ የመኪናው ባለቤት ለሆኑት ተበዳሪ ብር 75,000 (ሰባ አምስት ሺ ብር) ሲያበድሩ ለብድሩ አከፋፈል ዋስትና ይሆነው ዘንድ ግምቱ 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) የሆነ መኪና በመያዣነት ይዟል፡፡ አመልካች ላበደረው ብድር አከፋፈል ዋስትና እንዲሆነው በመያዣነት በያዘው ንብረት ላይ ያለው መብት ብድሩ ባለመከፈሉ ቀሪ የሆነ ዋናው ገንዘብ፣ ይህ ብድር በብድር ውሉ መሠረት ባለመከፈሉ የሚወልደው ወለድ፣ የወለድ ወለድ መቀጫና ሌሎች ወጭዎችን ሁሉ ባለመከፈላቸው መያዣውን ሸጦ ገቢ የማድረግ መብቱን የሚያጠቃልል መሆኑና ጠቅላላ ጣሪያው በመያዣ ውሉ የተገለፀው የገንዘብ መጠን እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2858 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ ተበዳሪው ብድሩን ባለመክፈሉ ምክንያት ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ዋናው ብድር ወለድና ሌሎች ክፍያዎች ከተበዳሪው እንደሚፈልግ በሥር ፍርድ ቤት አስረድቷል፡፡ ተጠሪ ለዚህ ገንዘብ አከፋፈል ይረዳው ዘንድ በመያዣነት የያዘው ንብረት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በመያዣነት የያዘው ንብረት በባህሪው ተንቀሣቃሽና ለአደጋ ተጋላጭ መሆኑን በመረዳት በመያዣነት የያዘውን ንብረት በብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) የመድን ሽፋን እንዲገባለት አድርጓል፡፡ ይህንንም ያደረገው ተጠሪ ያበደረውን ገንዘብ፣ ወለድና ሌሎች ክፍያዎች የማስመለስ እድሉን ለማስፋት እና እርግጠኛ ለመሆን ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካች እንድከፍለው የጠየቀውና የሥር ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ለተጠሪ ብር 350,000 (ሦስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ከህዳር 8 ቀን 1988 ዓ.ም ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል የወሰኑት የንግድ ህግ ቁጥር 678 ድንጋጌ መሠረት በማድረግና የኢንሹራንስ ውሉን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘነው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎትና በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44164

ታህሳስ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነገረ ፈጅ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ሐሰን ኢብራሂም - ጠበቃ ስለሺ ዘዮሐንስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የብድር ውልን የተመለከተ ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪ በ05/08/87 ዓ.ም በተፈረመ ውል ብር 200,000.00(ሁለት መቶ ሺህ) ተበድረው በየወሩ ብር 18,000(አስራ ስምንት ሺህ) እየከፈሉ ከሚያዝያ ወር 1988 ዓ.ም የተስማሙ ቢሆንም ብድሩን በውሉ መሠረት አልከፈሉም፡፡ በመሆኑም በመያዣነት ለአመልካች ከሰጧቸውና አመልካች የመድን ሽፋን ከገዛላቸው ተሽከርካሪዎቻቸው ውስጥ ሁለቱን ያስረከቡ ቢሆንም በሊብሬያቸው ላይ የተጭበረበረና የተምታታ ነገር በመኖሩ ሊሸጡ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ በዓመት 14% ወለድና 3% የወለድ መቀጫ ለመክፈል በተስማሙት መሠረት የሚፈለግባቸውን ብር 396,904.52(ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አራት ብር ከሃምሳ ሁለት ማንቲም) እና ሌሎች ወጪዎችን እንዲከፍሉ ይወሰንልን ሲል ባቀረበው ክስ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ተሽከርካሪዎቹ ለፎርክሎዠር የሐራጅ ሽያጭ የቀረቡ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 244(2/ሐ) መሠረት አንደኛው የህግ እርምጃ እየተካሄደ ሳለ በተደራቢነት ክስ ሊመሠረትብኝ አይገባም በማለት ቅድመ መቃወሚያ አቅርበው በፍሬ ጉዳዩ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አመልካች ለተጠሪ ገንዘብ በብድር ሰጥቶ ለብድሩም መያዣዎችን ይዟል፡፡ ብድሩ ባልተከፈለው ጊዜ በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ወይም በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የያዘውን ንብረት በሐራጅ በመሸጥ ገንዘቡን ማስመለስ ይችላል፡፡ ይህ ማለት ግን ሁለቱንም አማራጮች በአንድ ጊዜ በአንድ ላይ ይጠቀማል ማለት አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች ያበደረውን ገንዘብ ለማስመለስ በፍ/ቤት ክስ ያቀረበው በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የያዘውን ንብረት ተረክቦ በሐራጅ ለመሸጥ በእንቅስቃሴ ላይ እያለ ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በሌላ በፍ/ቤት (በባንኩ በራሱ) ተይዞ እያለ እና ተሽከርካሪዎቹ ተሸጠው የሚያወጡት ገንዘብ ለብድሩ ወይም ለዕዳው በቂ መሆን አለመሆኑ ሳይረጋገጥ በዚህ ፍ/ቤት ክስ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 244(2/ሐ) መሠረት ተቀባይነት ስለሌለው ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 245(2) መሠረት ተዘግቷል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ብድሩን ሲወስዱ ለመያዣነት ከአስያዟቸው መኪናዎች መካከል የሰሌዳ ቁጥር 2-13518 አ.አ. በብር 17,500.00(አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ) የካቲት 29 ቀን 1998 ዓ.ም በወጣው ጨረታ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-26916 የሆነው ደግሞ ነሐሴ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በወጣው ጨረታ በብር 152,000.00(አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ) መሸጣቸው እና ሌላው መኪናም ሊገኝ አለመቻሉ ተገልጾ እያለ፤ አዋጅ ቁጥር 97/90 ባንክን ክስ ከመመስረት የሚከለክለው ባለመሆኑ የብድር እዳ እንዲመልሱ በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ የፎርክሎዠር ሥርዓቱን ሳይጨርስ መቅረብ የለበትም ተብሎ ውድቅ መደረጉ የአዋጁን መንፈስ ያላገናዘበ ስለሆነ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ክሱ ከቀጠለ በኋላ አመልካች በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች ሸጧል መባሉ በክርክሩ ሂደት የሚቀር ዕዳ መኖሩንና አለመኖሩን አረጋግጦ ክስ እንዲቀጥል ወይም እንዲቋረጥ በማድረግ ፋንታ በመያዣ የተያዙ ንብረቶች መሸጫውን ብቻ መነሻ በማድረግ ክርክሩን የሚያቋርጥ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክር ሐምሌ 08 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር ይገባዋል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች የወሰዱትን ገንዘብ በወቅቱ ባለመመለሳቸው አመልካች በመያዣነት ከያዛቸው ተሽከርካሪዎች መካከል በሕጉ በተሠጠው ሥልጣን መሰረት ራሱ ለመሸጥ እንቅስቃሴ እያደረገ ባለበት ጊዜ በፍ/ቤት ተጠሪ ብር 396,904.52(ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አራት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም) ከወለድና ከሌሎች ወጪዎች ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ በተጠሪ ላይ ክስ በመመስረቱ ፍርድ ቤቱ አመልካች የፎርክሎዠር ሥልጣኑን ሳይጨርስ በፍ/ቤት ክስ መመስረትን ስነ-ሥርዓቱ አይፈቅድም በማለት ክሱን ለጊዜው የዘጋው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች የፍርድ ሂደትን ማለፍ ሳያስፈልግ በሐራጅ የመሸጥ ሕጋዊ መብት ያለው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በእነዚህ ህጎች በተሠጠው ሥልጣን ባንኩ ሲጠቀም ሊከተለው የሚገባው ሥነ-ሥርዓትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 394 እስከ 449 ድረስ ያሉትን ድንጋጌዎች ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ድንጋጌ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚገኙት ደግሞ ስለፍርድ አፈፃፀም በሚገዛው የተጠቃሽ ሥነ-ሥርዓት ሰባተኛ መፅሐፍ ስር ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው የባንኩ ስራ ተበዳሪውን በመወከል የመያዣ ንብረቱን ሸጦ ለብድሩ ዕዳ እንዲውል ማድረግ ሲሆን ይሕም በይዘቱ የአፈፃፀም አካል ሊባል የሚችል ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት አዋጆች ባንኮች በራሳቸው ምርጫ በብድር የሰጡትን ገንዘብ የመሰብሰብ ተግባር እንዲከተሉ አስገዳጅ መንገድ ስለመሆኑ የሚያሳይ ድንጋጌ አልያዙም፡፡ በሌላ አገላለፅ ባንኮች ብድራቸውን ለማስመለስ በፍርድ ቤት በኩል ክስ ሲመሰርቱ ጉዳዩ በአዋጅ መሰረት ሊፈፀም ይገባል ሊባል የማይችል ሲሆን መያዣ ንብረቶች ላይ ከአዋጁ ባገኙት መብት መሰረት እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመራቸው በሁለት መንገድ ክስ ቀርቧል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ባንኮች በራሳቸው ምርጫ በብድር የሰጡትን ገንዘብ የመሰብሰብ ተግባር ሳይፈፅሙ በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርቱ ወይም በመረጡት መንገድ የመሄድ ሁኔታ አዋጁ ከወጣበት ዓላማ ጋር ሊጻረር ይችላል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም፡፡ የአዋጁ አይነተኛ ዓላማ ባንኮች በተቻለ ፍጥነት በብድር የሠጡትን ገንዘብ በመሰብሰብ እንደገና መዋዕለ ንዋዩን ለኢንቨስትመንት ስራ እንዲውል በማድረግ በአገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ አዎንታዊ ሚና መጫወት ነው፡፡ ስለሆነም ባንኮች በአዋጁ የተሠጣቸውን ሥልጣን በመተው ወይም እንቅስቃሴውን ጀምረው እያለም ቢሆን በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርቱ ተቀባይነት የለውም ወይም በቅድሚያ የተጀመረው እንቅስቃሴ ሊያልቅ ይገባል የሚባልበት ሕጋዊ መሰረት ያለው ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2/ሐ) ድንጋጌም በአንድ ፍርድ ቤት የቀረበ ክስ በሌላ ፍርድ ቤት እየታየ ከሆነ የሚከለክል እንጂ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ላለው አይነት ክርክር አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካች በአዋጁ በተሠጠው ሥልጣን መሰረት እንቀስቃሴን ቀጥሎ በፍርድ ቤት ክስ ከመሰረተ በኋላ መያዣ ንብረቶችን ለመሸጥ እንቅስቃሴ እያደረገ በፍርድ ቤት ክስ ቢመሰርት ወይም የመያዣ ንብረቶችን ክሱ እየቀጠለ ባለበት ሁኔታ መሸጡ ቢረጋገጥ ሊኖረው የሚችለው ውጤት የሚቀር እዳ መኖሩንና አለመኖሩን አረጋግጦ ክስ እንዲቀጥል ከማድረግ ወጪ ክሱን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም፡፡ ንብረቶቹ የሚሸጡበት ዋጋ በአፈጻጸም ጊዜ የሂሳብ መተሳሰብ ተሰርቶበት ሊቀናነስ የሚችል ከመሆኑ ውጪ የአመልካችን በፍ/ቤት ክስ ከመቀጠል የሚያግደው አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ባንክ ሊከተለው የሚገባው መንገድ አንድ ብቻ ነው ተብሎ ባልተደነገገበት ሁኔታ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2/ሐ) ድንጋጌን ያለቦታው በመጥቀስ በአመልካች ባንክ የተፈፀመ ድርጊት የተጠሪን የሂሳብ እንተሳሰብ ጥያቄ በአፈፃፀም ከማንሳት የማይከለክልባቸው ሆኖ እያለ የአመልካችን ክስ ማቋረጡ ሕጋዊ ባለመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ከአመልካች ባንክ የወሰዱት የገንዘብ ብድር አለመከፈሉን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት በመያዣ የተያዙ ንብረቶች በሓራጅ መሸጣቸውን በመግለፅ በመሆኑና ይህ ደግሞ በኃላፊነታቸው መጠን ካልሆነ በሌላው ላይ የተለየ ውጤት ሊያስከትል የማይችል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሠጥበት ጉዳዩን እንደገና መመለሱ የፍትሃ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረታዊ ዓላማ ክርክሮች በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ እልባት እንዲያገኙ ማስቻል ከመሆኑ አንፃር ሲታይ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊያን ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58998 ታህሳስ 02 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 64410 የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ሚያዝያ 05 ቀን 1987 ዓ.ም በተፈረመ የብድር ውል ከአመልካች ለወሰዱት ገንዘብ የከፈሉት ማንኛውም ገንዘብ እና የመያዣ ንብረቶች ሽያጭ ዋጋን በአፈፃፀም ወቅት ከአመልካች ጋር የመተሳሰብ መብታቸው የተጠበቀ ሆኖ በስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበትን ብር 396,904.52(ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አራት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም) ወለድን በስምምነታቸው መሰረት ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ፣ እንዲሁም የመድን አረቦኑን ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት ወስነናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 46778

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ጎሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአረቦን ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ጎዳር 01 ቀን 2000 ዓ.ም በአሁኑ አመልካች እና በአቶ አህመድ ማሞ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥር 3-33558 ሆኖ ንብረትነቱ የአቶ አህመድ ማሞ ለሆነው ተሽከርካሪ አመልካች ጋር በጠየቁት መሰረት የመድን ውል ማድረጉን፣ከእ.ኤ.አ ከ18/08 እስከ 18/08/2004 ድረስ ከሚፈለግባቸውን የአረቦን መድን ክፍያ ውስጥ ብር 24,472.89(ሃያ አራት ሺህ አራት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሰማንያ ዘጠኝ ሳንቲም) ያልከፈሉ መሆኑን ገልፆ ይህንኑ ገንዘብ ከነ ሕጋዊ ወለድና ከልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር አመልካችና አቶ አህመድ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስ፣የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣የመድን ውሉ ተዋዋይ ባለመሆኑ ክስ ሊቀርብበት እንደማይገባ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም የተጠየቀው የአረቦን ገንዘብ ክፍያ ጥያቄ የውል ዘመኑ አልፎ ውሉ ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው፣ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት ያልተደረገ በመሆኑ በሕግ ፊት የሚፀና አለመሆኑን፣የአረቦን ክፍያ አልከፈለም ከተባለ ተጠሪ ውሉን ከማቋረጥ ውጪ አረቦን ይከፈለኝ በማለት ክስ ማቅረብ እንደማይችል ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአሁኑን አመልካች መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ በማድረግ ለክሱ ገንዘብ ኃላፊ አድርጐ ብር 24,472.89(ሃያ አራት ሺህ አራት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሰማንያ ዘጠኝ ሳንቲም) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ 9%(ዘጠኝ ከመቶ) ወለድና ከልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር ከአቶ አህመድ ማሞ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል ሲል ወስኖበታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ድርጅት ነገረ ፈጅ ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-ጉዳዩ በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ የሚታገድ ሆኖ እያለና ውሉም መሰረትም የተፈፀመ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የን/ሕ/ቁ. 666 እና 674 እንዲሁም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገው የመድን አረቦን ውል ሳይኖር የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731 እና 1952 ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ አመልካችን ለአረቦን ገንዘብ ክፍያ ጥያቄ ኃላፊ ማድረጋቸው ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የተከራከረው ክርክር መታለፉ ከን/ሕ/ቁ. 674 ድንጋጌ አንፃር አግባብ መሆን ያለመሆኑን ለመመረመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ የተጠሪ ነገረ ፈጅ ጎዳር 10 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የጽሑፍ መልስ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አግባብነት ይደግፋሉ ያሏቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር ውሳኔው ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች አቶ አህመድ ማሞ ከተባሉ ግለሰብ ጋር በመሆን የመድን አረቦን ገብቶ የተዋዋለ መሆኑን፣የመድን ውልም እንዲታደስ ጥያቄ አቅርቦ በጥያቄው መሰረት ተጠሪ ማደሱን፣ግራ ቀኙን የሚያከራክረው የአረቦን ገንዘብ ክፍያ መከፈል በነበረት ጊዜ ባለመከፈሉ ተጠሪ የይከፈለኝ ጥያቄ ማቅረቡ በይርጋ የታገደ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው የሕግ ጥያቄ ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች ለክርክሩ መሰረት ያደረገው የን/ሕ/ቁ.674/1/ ሲሆን የድንጋጌው ሙሉ ይዘትም፡- በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ የሚታገደው ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከተደረገበት ወይም በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ ከሁለት አመት በኋላ ነው የሚል ሲሆን የእንግሊዝኛው ትርጉምም፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

Any claim arising out of a contract of insurance shall be barred after two years from the occurrence giving rise to the claim or from the day when the parties knew of the occurrence. በሚል ተቀምጧል፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሰረት በኢንሹራንስ ውል ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ማንኛውም ክስ ጥያቄውን ለማቅረብ የሚያስችለው ምክንያት በተከሰተ ወይም ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳዩን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመድን አረቦን መከፈል የነበረበት ጊዜ ሁለት ዓመት ያለፈው ስለመሆኑ ተጠሪም የማይክደው ፍሬ ጉዳይ ሲሆን ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው ለጉዳዩ

አግባብነት ያለው ድንጋጌ በንግድ ሕጉ የተመለከተው ሳይሆን በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1845 ስር የተመለከተው ነው በማለት ነው፡፡ ሆኖም ጉዳዩ የኢንሹራንስ ውልን መሰረት ያደረገ እንደመሆኑ መጠን በንግድ ሕጉ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የማይኖርበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ ከመሆኑ አንፃር የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 754/1/ ስር የተመለከተው ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677 እና 1845 መሰረት በማድረግ አመልካች ያቀረበውን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረገው ያላግባብ ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 102951 ጥቅምት 05 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 72894 ግንቦት 03 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የጠየቀው የመድን አረቦን ይከፈለኝ ጥያቄ በሁለት አመት ይርጋ ጊዜ የታገደ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 46808

ሚያዝያ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ጫልቱ ሚደግሳ - በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመድን ሰጪ የኃላፊነት መጠን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው የሰሌዳ ቁ 3ኦሮ 03004 የሆነ የሕዝብ ማመላለሻ ንብረትነቱ የአቶ ሐብታሙ አለነህ ሆኖ በአቶ ጌታነህ አለነህ ሲሽከረከር የሰሌዳ ቁጥር 3 ኢት 16818 የሆነ መኪና ገጭቶ በመኪናው ውስጥ የነበሩ አቶ ተመስገን ሚደግሳ እና ወ/ሮ ስኳሬ ዲቲን የገደለ በመሆኑ የካሣ ጥያቄ ክስ በወራሾች ቀርቦ አመልካችም በመድን ውል መነሻ በክርክሩ እንዲገባ መደረጉን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ የአሁን አመልካች ኃላፊነት እና የካሣ መጠንን አስመልክቶ ክርክር ያቀረበ ቢሆንም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከተው የኢሉባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሾች ለጉዳቱ ኃላፊ ናቸው ካለ በኋላ የካሣ መጠኑም ብር 106,400(አንድ መቶ ስድስት ሺህ አራት መቶ) ብር እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የካሳ መጠኑን በማሻሻል ባጠቃላይ ብር 68,200(ስልሳ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ) እንዲከፈል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ሲል ሰኔ 16/2001 ዓ.ም በጠበቃው አማካይነት ባቀረበው አቤቱታ የሚች ወራሾች በቀጥታ ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ፣ የካሳ መጠን አስመልክቶ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ስሕተት እንደሆነ እና ካሣ መከፈል ለለበት ከተባለም የአመልካች የኃላፊነት ወሰን ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ለአንድ ሰው እንደመሆኑ በጠቅላላ ከስልሳ ሺህ(60,000) በላይ የሚከፍልበት አግባብ ባለመኖሩ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በዚህ ረገድ እንዲታረም ሲል አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ የአመልካች የኃላፊነት ወሰን ከብር 60,000(ስልሳ ሺህ) በላይ መወሰኑ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪ እንዲቀርቡ አዝዟል፡፡ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌለበት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲወሰን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

የአመልካች ኃላፊነት የመነጨው ከመድን ውል ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ አመልካች ለሥር ተከሳሽ የሰጠው የመድን ሽፋን የሦስተኛ ወገን ኃላፊነት ስለመሆኑ እና ለአንድ ሰው የሚከፈለው ካሣ መጠን ጣሪያው ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ስለመሆኑም አላከራከረም፡፡ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው የሥር ተከሳሽ መኪና ጉዳት ያደረሰው በሁለት ሰዎች ላይ ስለመሆኑም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡

ስለሆነም በውሉ መሠረት የአመልካች ኃላፊነት ወሰን ብር 60,000(ስልሳ ሺህ) መሆኑ ታውቋል፡፡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 665(2) መሠረት ደግሞ የመድን ሰጪው ኃላፊነት በመድን ውሉ የተመለከተውን የገንዘብ ወሰን መሠረት ካሣ መክፈል ግዴታ አለበት፡፡ አመልካችም እየተከራከረ የነበረው የኃላፊነት መጠን በውል ከተወሰነው በላይ ሊሆን እንደማይገባ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በግልፅ ውሉን እና ሕጉን መሠረት አድርጉ ክርክሩን አቅርቦ እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ባለማገናዘብ አመልካች ከውል ግዴታው በላይ ብር 68,200(ስልሳ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ) እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ስለሆነም በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማረም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. አመልካች በዋስትና ውል በተመለከተው መሠረት ለመክፈል የሚገደደው ብር ስልሳ ሺህ (60,000) ብቻ ነው ብለን የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የመ/ቁ 62171 መጋቢት 22/2002 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስነናል፡፡
2. በኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የተወሰነውን ቀሪ የካሣ ገንዘብ የሥር አንደኛ ተከሳሽ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ተሻሽሎ በተወሰነው መሠረት የኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 48698

ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ - አልቀረቡም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ፡- አቶ ሣሙኤል ዓለሙ - ጠበቃ ፈቃዱ አስፋው ቀረቡ

መዝረቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ኩባንያ የመድን ሽፋን የገባሁለት የሠ.ቁ 3-34603 የሆነ መኪና በደረሰበት አደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል፡፡ በመድን ውሉ መሠረት ተከሳሽ ተገቢውን ካሣ እንዲከፍለኝ ብጠይቅም ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ጉዳት የደረሰበትን መኪናዬን ሙሉ ዋጋ ብር 235,000(ሁለት መቶ ሠላሣ አምስት ሺህ) እንደዚሁም መኪናው በጊዜው ባለመጠገኑ ወይንም ዋጋውን ባለመክፈሉ ምክንያት በከሳሽ ላይ የደረሰውን የጥቅም መቋረጥ ብር 58,000(ሃምሣ ስምንት ሺህ) ጨምሮ ክሱ ካስከተለው ወጭና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው ከመድን ውሉ ውጭ ሁለት ሰዎችን ጭኖ ሲያንገዝ ሲሆን የመድን ሽፋን የተገባው ጭነት ጭኖ ሲጓንዝ ለሚደርስ ጉዳት ነው፡፡ ስለሆነም የከሳሽ መኪና ሰው ጭኖ ሲጓንዝ ለደረሰው ጉዳት ከመድን ውሉ አኳያ ተከሳሽ ካሣ ለመክፈል ግዴታ የለበትም፡፡ የክፍያ መጠኑን በተመለከተም ከሳሽ የደረሰበት መኪና ሊጠገን የማይችል ስለመሆኑ ባላስረዱበት ሁኔታ ሙሉ ዋጋ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ተገቢነት የለውም፡፡ በመድን ውሉ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠንም መኪናው የመድን ሽፋን በተሰጠው ጊዜ የተገመተ እንጂ አሁን ያለውን የመኪና ዋጋ ስለማያስረዳ በዚህ ልክ ካሣ ሊከፈል አይገባም፡፡ በመድን ውሉ መሠረትም ተከሳሽ ለተቋረጠ ጥቅም ኃላፊነት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ኃላፊነትን በተመለከተ ተከሳሽ በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው ሰው ጭኖ ሲጓዝ እንጂ ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ ስላልሆነ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ቢከራከርም ሰው ጭኖ ጉዳት ስለመድረሱና የሰዎችን መጫን ከአደጋው ጋር ያለውን ግንኙነት አላስረዳም፡፡ ይልቁንም በማሰረጃነት የቀረበው የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው መሐል መንገድ ላይ የገባን ሰው ለማዳን ሲሞክር መኪናው መንገዱን ስቶ ከዛፍ ጋር በመጋጨቱ ምክንያት እንደሆነ የሚያረጋግጥ ስለሆነ ሰው ጭኖ መጓዙ የአደጋው መንስኤ ባለመሆኑ ተከሳሽ በመድን ውሉ መሠረት በመኪናው ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

የካሣ መጠኑን በተመለከተ ፍ/ቤቱ ጉዳት የደረሰበትን የከሳሽ መኪና በባለሙያ እንዲገመት አድርጎ ጉዳቱ በመቶኛ ሲሰላ 83.48% በገንዘብ ሲሰላ ደግሞ ብር 196,546.98(አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ዘጠና ስምንት) አረጋግጦ ከ75% በላይ ጉዳት ከደረሰ እንደ ሙሉ ውድመት /Total loss/ ስለሚቆጠር የመኪናውም ግምት ብር 235,000(ሁለት መቶ ሠላሳ አምስት ሺህ) እንደሆነ ግራ ቀኙ ባደረጉት የመድን ውል ላይ ስለተመለከተ ተከሳሽ ይህንኑ ገንዘብ ለከሳሽ እንዲከፍል የተቋረጠ ጥቅምን በተመለከተ ግን በመኪናው ላይ የደረሰው ሙሉ ውድመት ስለሆነ ተከሳሽ ለመክፈል አይገድድም በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በተጠሪ መኪና ላይ በአደጋ ምክንያት ጉዳት በደረሰ ጊዜ 2 ሰው ጭኖ መገኘቱ ከመድን ውሉ አኳያ አመልካች ኃላፊ ነው መባሉ ተገቢነቱን ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጐ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን እንደሚከተው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? በአግባቡ ነው ከተባለስ የካሣ ክፍያው መጠን ተገቢነት አለው ወይንስ የለውም? የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ኃላፊ መባል የለብኝም በማለት አጥብቆ የሚከራከረው በተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት ያደረሰው ሰው ጭኖ ሲጓዝ እንጂ ዕቃ ጭኖ ባለመሆኑ ከመድን ውሉ አኳያ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በመኪናው ላይ 2 ሰዎች ተጭነው እንደነበረ አምኖ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች የተጫኑት የመኪናውን አገልግሎት ከዕቃ መጫን ሰው ወደመጫን አገልግሎት በመቀየር ሳይሆን በወቅቱ ተጭኖ የነበረው የመብራት ኃይል መ/ቤት ምሶሶዎችን ለመደገፍ፣ ለመጫንና ለማውረድ ተብሎ የጭነት ሥራ ለመሥራት ነው በማለት መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በመድን ውሉ መሠረት ካሣ ለመክፈል የምንገደደው መኪናው ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ ለሚደርስበት ጉዳት እንጂ ሰው ጭኖ በሚጓዝበት ጊዜ አይደለም የሚል ክርክር ቢኖረውም የተጠሪ መኪና ሁለቱን ሰዎች የጫነው ከጭነት ሥራ ጋር በተያያዘ ያልተጫኑ ስለመሆኑና ሰዎችን ለማጓጓዝ ታስቦ የተጫኑ ስለመሆናቸው ማስረዳት የሚጠበቅበት ከመሆኑም በላይ ሰው የመጫኑም ሁኔታ ለአደጋው መንስኤ /Risk Possibility/ መሆኑንም ጭምር ማስረዳት ይጠበቅበታል ሆኖም ግን አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ይልቁንም ጉዳት የደረሰው በጉዞ ላይ መሐል መንገድ ላይ የገባን ሰው ለማዳን ሹፌሩ ጥረት ሲያደርግ መንገዱን ስቶ በመውጣት ከዛፍ ጋር በመጋጨቱ ምክንያት እንደሆነ በትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት ላይ የተገለፀ ስለሆነ በተጠሪ መኪና ላይ የተጫኑት ሰዎች ኃላፊነቱን ከሚያስከትለው ሁኔታ ጋርም ሆነ ከካሣ ክፍያው ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ስለሌለ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የካሣ ክፍያ መጠኑን በተመለከተ የተጠሪ መኪና ከአደጋው በኋላ ተገጭቶ ጉዳቱ በድምሩ ብር 196,546.98(መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ስድስት ብር ከዘጠና ስምንት ሣንቲም) መሆኑ ተረጋግጧል የሥር ፍ/ቤቶች ለተጠሪ ካሣ እንዲከፈላቸው ውሣኔ የሰጡት የመኪናው ዋጋ ብር 235,000(ሁለት መቶ ሠላሳ አምስት ሺህ) እንደሆነ በመድን ውሉ ላይ ስለተመለከተ ይህንኑ አመልካች ለተጠሪ መክፈል አለበት በማለት ነው፡፡

ሆኖም ግን ለአንድ ንብረት ወይም ዕቃ መድን የገባ ሰው ካሣ ሊከፈለው የሚችለው ጉዳት በደረሰ ጊዜ ዕቃው ከሚያወጣው ዋጋ ሳይበልጥ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 678 የተመለከተ ሲሆን የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳት የደረሰበት የተጠሪ መኪና በባለሙያ እንዲገመት ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ግምቱ ሲቀርብ በዚሁ ግምት መሠረት ካሣ እንዲከፈል መወሰን ሲገባው ከግምት በኋላ ተመልሶ በመድን ውሉ ላይ የተቀመጠው የመኪናው ግምት እንዲከፈል መወሰኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 108121 በ12/2/2001 ዓ.ም. የሰጠው የኃላፊነት ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 80957 ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም. ይህንኑ የኃላፊነት ውሣኔ በማጽናት የሰጠውን ትዕዛዝ አጽንተናል፡፡ በሌላ በኩልም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ በተጠቀሰው የመ/ቁጥር በ28/7/2001 ዓ.ም. አመልካች ብር 235.00 ካሣ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ ከንግድ ሕግ ቁጥር 678 ጋር ያልተገናዘበ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት አሻሽለን የተጠሪ መኪና በጉዳቱ ጊዜ በተገመተው መሠረት ብር 196,546.98/አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር አምስት መቶ አርባ ስድስት ከዘጠና ስምንት ሣንቲም/ ካሣ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 39902

ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አብዱራሂም አህመድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች፡- የኢት/መድን ድርጅት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ብሪ ሙሲሳ - በሌሉበት

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ለፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ለደንበኛው ለኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ናፍጣና ቤንዚን የጉዞ መድን ሽፋን የሰጠ ሲሆን ከነዳጁ ውስጥ 31,513 ሊትር የስር ተከሳሾች በሆኑት መኪና ሲጓጓዝ መኪናው ተገልብጦ 18,153 ሊትር የፈሰሰ በመሆኑና የነዳጁን ዋጋ ብር 45,927.09(አርባ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሰባት ብር ከዘጠኝ ሣንቲም) ለደንበኛው ስለከፈለ ይህንኑ ገንዘብ ከተከሳሾች መጋከል ኃላፊነት ያለበት ተለይቶ እንዲከፍሉ እንዲወሰንለት አመልክቷል፡፡ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ ከክሱ ወጪ የሆኑ ሲሆን ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ጉዳዩ በእርቅ ማለቅ ያለበት ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ በዋናው ጉዳይ ላይም በሰጡት መልስ ነዳጁን የጫነው መኪና ባለቤት ስላልሆኑ ኃላፊነት እንደሌለባቸው ከነዳጁ ባለቤት ጋር ያደረጉት የማጓጓዝ ውል አለመኖሩን እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖቹ የኢት/ነዳጅ ድርጅትና የጣና ፈሳሽ ማጓጓዣ ባለንብረቶች ማህበር ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ጠይቀዋል፡፡ ሦስተኛ ተከሳሽ የነበረው ወይራ ትራንስፖርት ድርጅት ክስ የተመሰረተበትን ነዳጅ የጫነው ተሳቢ ነዳጁ ፈሰሰ ከተባለበት ቀን በፊት ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ ያስተላለፈ በመሆኑ ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪ ጭነት መኪና ወደኋላ ተንሸራቶ እየተገለገሉበት ያለውን ነዳጅ የጫነውን ተሳቢ እንዲገለበጥ በማድረጉ ተጠሪ ለጉዳቱ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2081(1) እና (2) መሰረት ኃላፊ ናቸው ሦስተኛ ተከሳሽ የነበረው ተሳቢውን አደጋው ከመድረሱ በፊት ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ ያስተላለፈ በመሆኑ ኃላፊነት የለበት በማለት ተጠሪ በክስ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ በኢት/ነዳጅ ድርጅትና በጣና ፈሳሽ መጓጓ ጥ ባለንብረቶች ማህበር መጋከል በተደረገው ውል አንቀጽ 18 መሰረት ከውሉ ትርጉምና አፈፃፀም ጋር ግንኙነት ባላቸው ምክንያቶች የሚነሳ አለመግባባት ሁለቱ በመረጧቸው ገላጋይ ዳኞች አማካኝነት እንደሚታይ ስምምነት ተደርጓል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው በን/ህ/ቁ 683 ባገኘው የመዳረግ መብት በመሆኑና ይህ የመዳረግ መብት ደንበኛው ባለው መብት ልክ ስለሆነ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የሚነሳው ክርክር በስምምነት ማለቅ ስላለበት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የይግባኝ ሰሚውን ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው በአመልካች ደንበኛና በጣና ፈሳሽ ማጓጓዣ ባለንብረቶች ማህበር መሃከል የተደረገው ውል ተፈፃሚነት የሚኖረው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መሃከል ለሚነሳ ክርክር እንጂ ለተያዘው ጉዳይ አይደለም፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የቀረበው የተረከቡት ነዳጅ ላይ ጉዳት በመድረሱ የአጓጓዥ ኃላፊነት ስላለባቸው በመሆኑ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን ውል መሰረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የአመልካች ደንበኛ ከጣና ፈሳሽ መጓጓዣ ባለንብረቶች ማህበር ጋር ጉዳዩን በእርቅ ለመጨረስ ስለተስማማ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በፍ/ቤት ሊታይ አይገባም በሚል የተሰጠው ውሳኔን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪ በህይወት ስለሌሉ ወራሾቻቸው እንዲቀርቡ በጋዜጣ ጥሪ ቢደረግም ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሰረተው በተጠሪ የጭነት መኪና እየተሳበ በነበረው ተሳቢ ላይ ተጭኖ የነበረው ነዳጅ ተሳቢው በመገልበጡ ምክንያት ፈሶ ስለባከነ ለደንበኛው የከፈለው ገንዘብ ተጠሪ እንዲተኩ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ አይገባም በማለት የወሰነው የአመልካች ደንበኛ ከጣና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፈሳሽ ማንጓጉ ባለንብረቶች ማህበር ጋር ባደረገው ውል በሁለቱ መሃከል የሚነሳ ማንኛውም አለማግባባት በእርቅ ለመጨረስ ያደረገው ስምምነትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ውል በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ላለው ክርክር ተፈፃሚነት አለው? የለውም? የሚለውን ጭብጥ ችሎቱ መርምሯል፡፡

ውል ተዋዋዮች የገቡቢቸው ግዴታዎች በመሃከላቸው አስገዳጅ እንዲሆኑ ወደውና ፈቅደው የሚመሰርቱ በመሆኑ ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታቸውን በፈቃዳቸው ወስነው ያቋቋሙት ውል ሌላ ሦስተኛ ወገንን ሊያስገድድ የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ በዚህም ምክንያት ነው ውሎች ተፈፃሚነታቸውና አስገዳጅነታቸው ውሉን ባቋቋሙ ተዋዋይ ወገኖች መሃከል ብቻ መሆኑ ፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731 ስር ተደንግጎ የምናገኘው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ደንበኛና ጣና ፈሳሽ ማንጓጉ ባለንብረቶች ማህበር ባደረጉት ውል በሁለቱ መሃከል የሚነሳ ማንኛውም አለመግባባት በእርቅ ለመጨረስ ተስማምተዋል፡፡ የዚህ ውል ተዋዋዮች ሁለቱ ብቻ ሲሆኑ ተጠሪ ተዋዋይ ወገን አልነበሩም፡፡ ስለሆነም ይህ ውል ተፈፃሚነቱ ወይም አስገዳጅነቱ ውሉን ባቋቋሙት ተዋዋይ ወገኖች ላይ ብቻ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይህ ውል በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ተፈፃሚነት አለው የሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የቻለው በደንበኛው መብት ተደርጎ ስለሆነ የሚኖረው ደንበኛው ያለው መብት ነው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ በን/ህ/ቁ 683(1) መድን ወጪው ለደንበኛው በከፈለው የካሳ መጠን ልክ ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነውን ሰው የሚጠይቀው በደንበኛው መብት ተደርጎ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ግን መድን ሰጪው የከፈለውን የካሳ መጠን በሚመለከት ብቻ እንጂ የደንበኛው ሌሎች መብቶችና ግዴታዎችን ሁሉ የሚመለከት ስላልሆነ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ደንበኛ ከጣና ፈሳሽ ማንጓጉ ጋር ያደረገው ውል አመልካች በተጠሪ ላይ ለመሰረተው ክስ ተፈፃሚነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ተጠሪ በዚህ ውል ተዋዋይ ወገን አልነበሩም፡፡ ምንም እንኳን አመልካች በከፈለው የካሳ መጠን ልክ የደንበኛውን መብት ተደርጎ የቀረበ ቢሆንም የአመልካች ደንበኛ ከተጠሪ ጋር የሚነሳ አለመግባባትን በእርቅ ለመጨረስ የተስማማበት ውል የለም፡፡ በመሆኑም የአመለካች ደንበኛ ከሌላ 3ኛ ወገን ጋር የተደረገው ውል ከተያዘው ጉዳይ ጋር ግንኙነት ስለሌለው አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በእርቅ ሊያልቅ የሚገባው ስለሆነ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የላቸውም መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 44024 ሰኔ 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 32239 ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ስላለው ይግባኝ ሰሚው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ ተቀብሎ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 52910

ሐምሌ 28 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አንዳርጌ ታደሰ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ጉዳዩን የጀመረው በባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር በመኪናቸው ላይ ለሚደርስ አደጋ ለአስራ ሁለት አመታት የቆየ የመድን ውል ግንኙነት የነበራቸው መሆኑን ገልፀው በመኪናቸው ላይ በደረሰው የመገልበጥ አደጋ መኪናው ከጥቅም ውጪ በመሆኑ ተጠሪ ብር 400,000(አራት መቶ ሺህ) እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ የመድን ውሉ የተቋረጠው ኅዳር 7 ቀን 2000 ሆኖ አደጋው የደረሰው ኅዳር 26 ቀን 2000 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ በአማራጭም ሌሎች ክርክሮች አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ታህሳስ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ለተጠሪ ባቀረቡት ማመልከቻ ለአስራ ሁለት አመት በነበራቸው ውል ምንም አደጋ ባለመድረሱ ውሉ ሳይታደስ ጊዜው ቢያልፍም ኅዳር 26 ቀን 2000 ዓ.ም ለደረሰው አደጋ ድርጅቱ አስተያየት አድርጐ ብር 100,000(መቶ ሺህ) እንዲከፍላቸው መጠየቃቸውን፣እንዲሁም የአመልካች ምስክር አመልካች ውሉን ሊያድሱ ተጠሪ ዘንድ ሂደው መኪናው ላይ አደጋ በመድረሱ ክፍያ አንቀበልም ማለቱን መመስከራቸውን ገልፆ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ያለው የውል ግንኙነት በመቋረጡ አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በአቤቱታቸው የውሉ ዘመን ከማለቁ በፊት ባሉት ጥቂት ቀናት ውሉን እንዳድስ ጠይቆኝ ስምምነቱን ስለገለጸኩ አረቦን ባለመክፈሌ ብቻ ውሉ ሊቋረጥ እንደማይችል የን/ህ/ቁ. 666/2//3/ አይችልም፣የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች ጥያቄ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከን/ህ/ቁ. 666 አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ የን/ህ/ቁ. 666 ተፈፃሚነት የሚኖረው ውሉ ፀንቶ ባለበት ጊዜ መሆኑንና የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል የሚልባቸውን ሌሎች ክርክሮች አቅርቧል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው አመልካች በባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የመሰረቱት ተጠሪ ለመኪናቸው የመድን ሽፋን ለመስጠት በገባው ውል መሰረት መኪናቸው ላይ አደጋ በመድረሱ የመድን ዋስትና እንዲከፍላቸው ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አደጋው በደረሰበት እለት በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የነበረው የመድን ውል ተቋርጦ ስለነበር አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ክሱን ተቃውሟል፡፡ በመሰረቱ ማንኛውም ሰው ክስ ለማቅረብ የሚፈቀድለት ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሃብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ሲኖረው እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ ድንጋጌ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ አመልካችም ግራ ቀኙ ካደረጉት የመድን ውል የሚመነጭ መብት ያላቸው መሆኑን በማመን ነው ክስ የመሰረቱት፡፡ ነገር ግን በግራ ቀኙ መሃከል የተደረገው የመድን ውል ኅዳር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ማብቃቱን ከመዝገቡ ተመልከተናል አመልካች ይህንን አላስተባበሉም፡፡ ክርክራቸው ውሉ ሊያበቃ ጥቂት ቀናት እንደቀሩት ተጠሪ ውሉ እንዲታደስ ጠይቆኝ ፈቃደኛነቱን የገለጸኩ ስለሆነ አረቦን ክፍያ ባለመክፈሌ ብቻ ውሉ ሊቋረጥ አይችልም በማለት ነው፡፡፡ ነገር ግን አመልካች በመኪናቸው ላይ አደጋ የደረሰው ውሉ ከመታደሱ በፊት በመሆኑና ቀደም ሲል በነበረው የ12 አመታት የመድን ውል ግንኙነት በመኪናቸው ላይ አደጋ ባለመድረሱ ድርጅቱ አስተያየት አድርጐ ብር 100,000(መቶ ሺህ) እንዲከፈላቸው ማመልከታቸውን የስር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ ይህንም በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የነበረው የመድን ውል ከተቋረጠ በኋላ አደጋው መድረሱን አመልካች ራሳቸው አምነው የተቀበሉት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በሌላ በኩል ውሉ እንደታደሰ የሚቆጠረው ተጠሪ ውሉ እንዲታደስ አመልካችን ስለጠየቀ ብቻ ሳይሆን አመልካች ውሉን ለማደስ ፈቃደኛ ሆነው በሕጉ አግባብ ውሉን ሲያደርጉ ነው፡፡ ይህን ስለማድረጋቸው አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በአጠቃላይ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የተደረገው የመድን ውል ኅዳር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ካበቃ በኋላ ውሉ ስላልታደሰ የውል ግንኙነታቸው ተቋርጧል፡፡ አመልካች የጠቀሱት የንግድ ሕጉ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

666 ስንመለከተውም ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው በመድን ሰጪውና በመድን ገቢው መሃከል የፀና ውል ኖሮ መድን ገቢው በውሉ በተመለከተው መሰረት የአረቦን ክፍያ መክፈል ሲያቋርጥ እንጅ የመድን ውል በሌለበት ሁኔታ አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን በአመልካችና በተጠሪ መሃል የነበረው ውል ጊዜው አብቅቶ ተቋርጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች ይህንን ድንጋጌ መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክርክር የድንጋጌውን መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ በሌላ በኩል የመድን ዋስትና እንዲከፈለው የተጠየቀበት መኪና አደጋ የደረሰበት ጎዳር 26 ቀን 2000 ዓ.ም ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አደጋው የደረሰው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መሃከል የነበረው የውል ግንኙነት ከተቋረጠ በኋላ በመሆኑ አመልካች የመድን ዋስትና እንዲከፈላቸው ለመጠየቅ የሚያስችል መብት የላቸውም፡፡ በዚህም ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06284 ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 77050 ጎዳር 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉምሩክ (ግብር) ታክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 39574

ጥቅምት 03 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ጌታቸው ምንተስኖት - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ምልእተፀጋ ቢዘን - አልቀረቡም

2. አቶ ፍፁም ገዛኸኝ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ለአንደኛ ተጠሪ በወር ብር 350.00(ሦስት መቶ ሃምሳ ብር) ያከራያቸው ሲሆን ተከራይዋ ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ ያስተላለፉ በመሆኑ የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የቤት ኪራይ፣ቅጣት፣የውሃ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረክቡ፣በተጨማሪም ቤቱን እስኪያስረክቡ ላለው ጊዜ ኪራይ እንዲከፍሉ በማለት ጠይቋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ተጠርተው ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት የታየ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ ግን ቀርበው ለቀረበባቸው ክስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ እንዲከፈል ሳይጠየቅ 2 አመት ያለፈው የቤት ኪራይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሰረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው፣ ቀሪውን ውዝፍ የቤት ኪራይ፣የውሃ ክፍያና ተጨማሪ እሴት ታክስ ተጠሪዎች ይክፈሉ፣የኪራይ ውሉ ተቋርጧል፣ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ያስረክቡ፣ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ ያለውን የቤት ኪራይ ሁለተኛ ተጠሪ ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም አንደኛ ተጠሪ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ በየወሩ የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ ቢወሰንም ከኪራዩ ጋር ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍሉ ውሳኔ ስላልተሰጠ ይኸው እንዲታረምለት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም አመልካች ለንግድ አገልግሎት ከሚያከራያቸው ቤቶች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመሰብሰብ ግዴታ በአዋጅ የተጣለበት በመሆኑ ቤቱን እስኪረከብ ድረስ ተጠሪዎች ከውርሃዊ ኪራይ ጋር ተጨማሪ እሴት ታክስ ሊከፍሉ ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ሁለተኛ ተጠሪ ቀርበው መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ግን ተጠርተው መልስ ያልሰጡ በመሆኑ ችሎቱ መዝገቡን መርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ችሎት ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ ወርሃዊ ኪራይ እንዲከፍሉ ሲወሰን ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍሉ ሳይወሰን መታለፉ አግባብ ነው? አይደለም? የሚለውን ነጥብ መርምሯል፡፡

አመልካች ለንግድ ድርጅትነት የሚያከራያቸው ቤት ላይ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 መሰረት ታክስ የመሰብሰብ ግዴታ ያለበት ለመሆኑ ያቀረበውን ክርክር ሁለተኛ መልስ ሰጪ ክደው አልተከራከሩም፡፡ የሁለተኛ መልስ ሰጪ ክርክር ፍርድ ቤቱ የኪራይ ውሉን ያፈረሰው በመሆኑ በሌለ የኪራይ ውል የተጨማሪ እሴት ታክስ መሰብሰብ አይችልም በማለት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 መሰረት የንግድ ቤቶች የማከራየት የንግድ እንቅስቃሴ ከታክስ ነፃ ከሆኑት ግብይቶች ውስጥ እንደማይካተት የአዋጁ አንቀጽ 8 ያመለክታል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ቢሆን ይህንኑ የአመልካች ግዴታ ተገንዝቦ የኪራይ ውሉ እስከተቋረጠበት እለት ድረስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል አንደኛ ተጠሪ የኪራይ ገንዘቡን ባለመክፈላቸው የኪራይ ውሉ የፈረሰ ቢሆንም ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ይዘው እየተገለገሉበት በመሆኑ ላገኙት ግልጋሎት የቤቱን ኪራይ በየወሩ እንዲከፍሉ ተወስኖባቸዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪው ያቀረቡት ቅሬታ የለም፡፡ የንግድ ቤቱ ይዘው ስለሚገለገሉበት የኪራይ ገንዘብ የሚከፍሉ ከሆነ ደግሞ ኪራዩን ተከትሎ የሚመጣውን ተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ሊወጡ ይገባቸዋል፡፡ ይህ ግዴታ ደግሞ ከውል ሳይሆን ከሕግ የመነጨ ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የኪራዩ ገንዘብ እንዲከፈል ሲወስን የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፈለው ሳይወሰን ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

መ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 43032 ጥር 19 ቀን 2000 ዓ.ም ሰጠው ውሳኔና የፌ/ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65580 ግንቦት 08 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽለዋል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ ከሚከፍሉት የኪራይ ገንዘብ ጋር ተጨማሪ እሴት ታክስ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡

ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 45882

ታህሳስ 06 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡ መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ነ/ፈጅ ወንዱ ለማ ቀረቡ

ተጠሪ፡ 1. ወ/ሮ እጅጋየሁ አራምዴ - ጠበቃ ብስራት ወ/መስቀል

2. ጌታቸው ተ/አረጋይ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ - የተመለከተው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ከጉምሩክ ቀረጥ አከፋፈል ጋር የተያያዘ ሲሆን አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በቀረበው ክስ አንደኛ ተጠሪ የተለያዩ ኤሌትሮኒክስ ዕቃዎችን በሕጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ አስገብተው በወኪል ደንበኞቸው ሁለተኛ ተከሣሽ አማካይነት ዲክለራሲዮን በመሙላት ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ከሚያስፈልጉ ሠነዶች ጋር በማቅረብ የዕቃዎቹ ዝርዝር ዋጋቸው በዳታ ቤዝ ሲፈለግ 23 የሚሆኑት ዕቃዎች ዋጋቸው ባለመገኘቱ ትክክለኛ ዋጋቸው ከዋናው መ/ቤት እስከሚላክልን ድረስ ዕቃው እንዳይቆይ ዋጋው በኘሮፖርሽን ተሰልቶ ብር 285,259.85(ሁለት መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ብር ከሰማንያ አምስት ሣንቲም) ከፍለው ንብረቱን ተረክበው ወስደዋል፡፡

ሆኖም የእነዚህ 23 ዕቃዎች ዋጋቸው ከዋናው መ/ቤት ተገልጾልን በዚሁ መሠረት ቀረጥና ታክስ ሲሰራ መክፈል የነበረበት ብር 47,638.34 ሳይከፈል የቀረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ቀረጥና ታክስ በማንኛውም ምክንያት ከዋጋቸው በታች የተከፈለ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት ከሆነ ያልተከፈለውን ቀሪ ቀረጥ ወይም ታክስ የማስከፈል ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 60/89 በአንቀጽ 57/1/ መሠረት ለከሣሽ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ በዚሁ መሠረት ተከሣሾች በቀረጥነት የሚፈለገውን ክስ የቀረበበትን ብር 47,638.34(አርባ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር ከሰላሳ አራት ሣንቲም) ከነወለድ እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው በማለት ጠይቀዋል፡፡

አንደኛ ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ ተከሣሽ አሟልቶ ማቅረብ የሚገባውን ሠነዶች በሙሉ ለከሣሽ አቅርቦ ከሣሽም ሂሳቡን አሰልቶ የሸቀጡን ዋጋ ትክክለኛነት አረጋግጦ ቀረጡን የተቀበለ ስለሆነ በቀረጥ ሰብሳቢው ታምኖበት ቀረጥ ተከፍሎ ዕቃው ከወጣ በኋላ ቀሪ ሂሳብ ለመጠየቅ ከሣሽ መብት የለውም፡፡ ከሣሽ በክሱ ኘሮፖርሽን ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ በምን ሂሳብ ስሌት እንደተሰላ እና የዕቃዎቹን ዋጋ ግኝት ምንጩን በመጥቀስ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48 መሠረት ወደ አገር ስለሚገባ ዕቃ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በዝርዝር አላስረዳም፡፡ ስለሆነም ከሣሽ በክሱ በሕጉ መሠረት እንዴት ተመርምሮ ቀሪ ሂሳብ እንደተገኘ በአዋጅ መሠረት ያላስረዳ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁለተኛ ተከሣሽም የቀረበልኝ ዶክመንት ትክክል መሆኑን አረጋግጪ ለከሣሽ መ/ቤት በማቅረብ በየደረጃው ያሉ የጉምሩክ ሠራተኞች አይተው የዋጋ ማስተካከያ ካደረጉ በኋላ የቀረጡን ትክክለኛነት አምነውበት በፊርማቸው ካረጋገጡ በኃላ ክፍያው የተፈጸመ ስለሆነ ክሱ ያላአግባብ የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዮን ከሣሽ ቀሪ የቀረጥ ክፍያ ጥያቄው እንዴት እንደተገኘ እንዲያስረዳ በታዘዘው መሠረት የከሣሽ መ/ቤት የታሪፍና ትመና መምሪያ ክፍል ሠራተኛ ቀርበው ሲያስረዱ አንደኛ ተከሣሽ ያስገቡት ዕቃ የዋጋ ስጋት ካለባቸው አገር የመጡ በመሆኑ በጉምሩክ መመሪያ ቁጥር 3/1996 አንቀጽ 8 ከተራ ቁጥር 1-3 በተመለከተው መሠረት ቀረጡ በኘሮፖርሽን የተሰራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ የተባለውን መመሪያ አስቀርቦ እንደተመለከተው መመሪያው የወጣው ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለሌላ ወገን በሚተላለፋበት ጊዜ የእርጅና ቅናሽ ስለሚታሰብበት ሁኔታ ሲሆን የመመሪያው አንቀጽ 8 ቀረጥ በኘሮፖርሽን እንደሚሰካ የማይደነግግ በመሆኑ የከሣሽ ክርክርም ሆነ የምስክርነት ቃሉ ተቀባይነት የለውም ካለ በኃላ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48/1/ መሠረት ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ለዕቃው መግዣ፣ዕቃውን እስከ ኢትዮጲያ የመጀመሪያ የጉምሩክ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝ እንደዚሁም ለመድን ዋስትና አረቦን የወጣው ወጭ ድምር እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን እነዚህ በአስመጪው በኩል የሚቀርቡት ሠነዶች ተቀባይነት የላቸውም ተብሎ በጉምሩክ ባለሥልጣን ከተወሰነ ቀረጡ ሊሰላ የሚገባው በአንቀጽ 48/3/ እስከ 10 ድረስ በተመለከተው አኳኃን መሆን እንዳለበት ተመልክቶአል፡፡ ሆኖም አንደኛ ተከሣሽ ከውጭ አገር ያስገባው ዕቃ ዋጋ ተቀባይነት የለውም፡፡ ተብሎ ቀሪ ቀረጥ እንዲከፍል የተጠየቀበት አግባብ በአንቀጽ 48 ላይ በዝርዝር በተደነገገው መሠረት ስለመሆኑ የባለሙያ ማስረጃ በማቅረብ ከሣሽ ያላስረዱ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ከሣሽ በውሣኔው ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪዎች ተጨማሪ ቀረጡን ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ ውሣኔ መሰጠቱ ከሕጉ አኳያ ተገቢነቱ ተመርምሮ ሊወሰን እንደሚገባው በመታመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የአመልካች የቀሪ የቀረጥ ክፍያ ጥያቄ አግባብነት ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ወደ አገር የሚገባ ዕቃ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነና እንዴት እንደሚሰራ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 48 ሥር ተዘርዝሯል፡፡ በሌላ በኩልም ወደ ሃገር በገባ ወይም ከሀገር በወጣ ዕቃ ላይ የተከፈለው ቀረጥ በማናቸውም ምክንያት ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥ ያነሰ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ባለሥልጣኑ የዕቃውን ባለቤት ወይም ወኪሉን በልዩነት ያልተከፈለውን ቀረጥ ማስከፈል እንደሚችል በአንቀጽ 57/1/ ላይ ሥልጣን ተሠጥቶታል፡፡

አመልካች በቀሪነት የሚፈለግ የቀረጥ ክፍያ ስላለ ተጠሪዎች ይህንኑ ቀሪ ክፍያ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ክሱ የተመሠረተው ተጠሪዎች ያስገቡት ዕቃ ኢንቮይሳቸው ዋጋው በመ/ቤቱ ከሚገኘው ዳታ ቤዛችን ጋር ሲወዳደር አንሶ በመገኘቱ ውድቅ ተደርጎ በዳታ ቤዙ መሠረት ዋጋ ሲፈለግ የተወሰኑት ዕቃዎች ዋጋቸው ስላልተገኘ በተገኙትና ባልተገኙት መካከል ያለውን ልዩነት የመ/ቤቱ መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት በኘሮፖርሽን ተሰርቶ ቀረጡን እንዲከፍሉ ከተደረገ በኃላ ዝራዝራቸው በዳታ ቤዝ ያልተገኙ ዕቃዎች ዋጋቸው ከዋናው መ/ቤት ሲላክልን በልዩነት የሚፈለግ ቀሪ የቀረጥ ክፍያ መኖሩን አረጋግጠናል በሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም አመልካች በኘሮፖርሽን ቀረጥ ለማስከፈል የሚያስችል የሕግ ድጋፍ የለውም ተገቢ ሰነዶችንም አቅርበን ቀረጡ የተከፈለ ስለሆነ ቀሪ ክፍያ አለ ተብሎ የቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖም ግን የአመልካች መ/ቤት የዋጋ ዝርዝራቸውን በዳታ ቤዝ በተገኘውና ባልተገኘው መካከል ልዩነቱን በኘሮፖርሽን ስሌት መሠረት እንደሚያስከፍል ለተጠሪዎች ሲገልጽ ተጠሪዎች ተቀብለው ቀረጡን ከፍለዋል፡፡ አመልካች ቀረጡን የማስከፍላችሁ በኘሮፖርሽን ስሌት ነው ካለ በሌላ አገላለጽ የተጠሪዎችን ኢንቮይስ ውድቅ ማደረጉን የሚያመለክት ስለሆነ በአዋጁ አንቀጽ 53/1/ በተቀመጠው አግባብ መሠረት ተቃውሟቸውን አስመዝግበው የጉምሩክ ሹመ በሚወሰነው መሠረት ቀረጥ መክፈል ይገባቸው የነበረ ሲሆን በዚህ መልኩ ተቃውሞ ካላደረጉ በኘሮፖርሽን ስሌት የተጠየቀውን የቀሪ ቀረጥ ክፍያ ጥያቄ እንደተቀበሉት የሚቆጠር ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች ክሰ የመሠረተበትን የቀረጥ ክፍያ ጥያቄ በተጠሪዎች በኩል በሕጉ አንቀጽ 53 አግባብ ተቃውሞ ያልቀረበበት እንደመሆኑ መጠን የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች ተቃውሞ ባላቀረቡበት ሁኔታ አመልካች በኘሮፖርሽን ቀረጥ ለማስከፈል የሚችልበትን አግባብ አላስረዳም በማለት የክፍያ ጥያቄውን ሳይቀበለው መቅረቱ ከአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 57 እና 53/1/ አኳያ ተገቢነት የሌለውና የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 68030 ሕዳር 19 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 76136 መጋቢት 2 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች አመልካች ክሰ ያቀረበበትን ብር 47,638.24/አርባ ሰባት ሺ ስድስት መቶ ሠላሳ ስምንት ብር ከሀያ አራት / ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሠብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44862

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አሸናፊ አበበ - ጠበቃ ኒቆዲሞስ ጌታሁን ቀረበ

ተጠሪ፡- የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ - ታደለ ተስፋዬ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉምሩክን ሕግ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል በማለት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አመልካች እና በወቅቱ ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ታደለ ገብሬ ኪዳኔ የተባለው ግለሰብ የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 228 እና 66/2/ ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የጉምሩክ ሥነ-ሥርአት ያልተፈጸመባቸውን አልባሳት ይዘው የማስተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋልና ቅጣት ይወሰንባቸው በማለት ጠይቆአል፡፡

ተከሣሾቹ ለክሱ በሰጡት መልስ በክሱ የተነገረውን ድርጊት አልፈጸምንም፤ ጥፋተኛም አይደለንም በማለት በመከራከራቸው ፍ/ቤቱ በዓቃቤ ሕጉ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ ተከሣሾች ሊከላከሉ ይገባል በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ መሰረትም የመከላከያ ማስረጃዎች የሰማ ሲሆን፣በመጨረሻም ተከሣሾች እንደክሱ አቀራረብ ተመስክሮባቸዋል፡፡ ለማስተባበልም አልቻሉም በማለት በተጠቀሰባቸው ሕግ መሰረት ጥፋተኞች ናቸው ብሎአቸዋል፡፡ ሲያስተላልፉት የተገኘው አልባሳት እንዲወረስ፣ለአልባሳቱ ሊከፈል ይገባ የነበረው የቀረጥና ታክስ መጠን በሚያህል ገንዘብ ብር 10,520.33(አስር ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር ከሠላሣ ሦሥት ሣንቲም) ለመንግስት እንዲከፍሉ እና በአስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣በመቀጠልም ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መጋቢት 28 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ለተፈጸመው ድርጊት በአቃቤ ሕግ የተጠቀሰው የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 66/2/ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ዓቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ የጠቀሰው ድንጋጌ አግባብነትን ለመመርመር የክስ ቻርጁን ይዘት ማየት አስፈላጊ በመሆኑ ተመልክተነዋል፡፡ በቻርጁ ላይ የተገለጸው አመልካች አልባሳቱ ተጭነው የተገኙበትን መኪና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲያሽከረክር እንደነበር፣አብሮ የተከሰሰው ታደለ ገብሬ ኪዳኔ የተባለው ደግሞ አልባሳቱን ያስጫነ እንደሆነ፣ መኪናው የመጣው ከናዝሬት መስመር ወደ አዲስ አበባ ሲሆን፣አመልካች አቃቂ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ኬላ ላይ እንደደረሰ የጉምሩክ ሰራተኞች ለፍተሻ እንዲቆም ሲጠይቁት ኬላውን ጥሶ መሄዱን፣በኋላም በተደረገው ክትትል በተለምዶ ሃና ማሪያም አካባቢ ተይዞ ፍተሻ ሲደረግ አልባሳቱ መገኘታቸውን ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ ባቀረባቸው ማስረጃዎች ልክ እንደ ክሱ እንዳስረዳ አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ ተመልክቶአል፡፡ በክሱ የተጠቀሰው የጉምሩክ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 66/2/ የኮንትሮባንዱ ድርጊት/ጥፋት/ የተፈጸመው ሃይል በመጠቀም ወይም ከሌሎች ጋር በማበር ሆኖ በተገኘ ጊዜ የሚጠቀስ እንደሆነም ከድንጋጌው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በመሆኑም መጠቀሱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 136351 ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 76902 መጋቢት 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው የሰበር ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48693

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡-ነኢማ አወል

ተጠሪ፡- የገቢዎች እና ጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ ኃ/ስላሴ ገ/መድህን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መሰረት የሆነው ጉዳይ የጉምሩክ አዋጅ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽማለች በማለት ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተውን የወንጀል ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች የተከሰሰችው በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 66/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ከዱባይ ወደ ኢትዮጵያ በቦሌ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ ስትገባ የጉምሩክ ሥነ-ሥርአት ያልተፈጸመባቸው የተለያዩ የሞባይል መለዋወጫዎችን እና የተዘጋጁ አልባሳቶችን ይዛ ተገኝታለች ተብላ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠችው መልስ በአቃቤ ሕግ ክስ የተነገረውን ወንጀል አልፈጸምኩም በማለት በመከራከርዋ ክሱ የቀረበለት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ሰምቶአል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች ልትከላከል ይገባል በማለት ብይን በመስጠት የመከላከያ ማስረጃዋን ሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ጥፋተኛ መሆንዋን በማረጋገጡ ይዛው የተገኘችው እቃ እንዲወረስ፣በእቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በሚያህል የገንዘብ መቀጮ ብር 114,076.46(አንድ መቶ አስራ አራት ሺህ ሰባ ስድስት ብር ከአርባ ስድስት ሳንቲም) እንድትከፍል እና በሁለት ዓመት እስራት እንድትቀጣ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ነሐሴ 26 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች የተከሰሰችበት የወንጀል ድርጊት መታየት ያለበት በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሰረት ነው ወይንስ በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 60/89? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ፣እንደዚሁም የሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ. 42753 እና 43806 ከሰጣቸው ውሳኔዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ እንዳመለከትነው የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን የሰሙትና በመጨረሻም ውሳኔ የሰጡት የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡ የሰበር ችሎቱ ክፍ ሲ.ል በተጠቀሱት መዝገቦች ተመሣሣይ አቤቱታ ቀርቦለት በእርግጥም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የጉምሩክ አዋጅ አንደሆነ በመግለጽ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህም ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው አዲሱ የወንጀል ሕግ ነው በሚል የቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጐአል፡፡ በያዝነው ጉዳይም ይኸው ቀደም ሲ.ል የተሰጠው የሕግ ትርጉም አስገዳጅነት ያለው ስለሆነ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 139937 መጋቢት 21 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 79028 ነሐሴ 2 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 195/2/ለ(2) መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 54061

ሚያዝያ 26 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ መስፍን ሽፈራው

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎች ባለሥልጣን - ገብረእግዚአብሔር ሙናቸው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መጋቢት 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች የዘሽ ትሬዲንግ ሥራ አስኪያጅ መሆናቸውን ገልፆ ድርጅቱ ሚያዝያ 8 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ አራት ሠዓት ከአርባ ደቂቃ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ፈፅሟል፡፡ ስለዚህ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) መሠረት የወንጀል ተጠያቂነት አለበት በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክረዋል ድርጅቱ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱን ዐቃቤ ህግ ገልጿል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ሥራውን በውክልና ለወ/ሮ ድርሻዬ ከበደ ለተባለች ሠራተኛ በውክልና ሰጥቻለሁ የሚል ክርክር ያቀረቡ ሲሆን የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አመልካች ለሥራው ሙሉ ውክልና አልሰጠም፡፡ የቃል ማስጠንቀቂያ ከመስጠት ውጭ የዘረጋው ሥርዓት የለም በማለት በክሱ በተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ጥፋተኛ ብሎ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር እሥራትና በብር 20,000(ሀያ ሺህ ብር) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በውሣኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ትክክለኛ ፍትህ ይረዳሉ የተባሉ የማጣሪያ ምስክሮች በመስማት የሥር ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች የሥር ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የድርጅቱ ሠራተኛ ወ/ሮ ድርሻዬ ከበደ ሥራውን ወክያት እየሠራች የነበረ ሲሆን በዚሁ ጉዳይ ጥፋተኛ ተብላ ተቀጥታለች፣ ወንጀሉ ሲፈፀም እኔ በቦታው አልነበርኩም፣ ግብይቱ የተፈፀመው ያለ እኔ ፈቃድና ስምምነት ነው፣ ከድርጅቱ ሠራተኞች ያለባት ደረሰኝ ግብይት እንዳይፈፅሙ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 34 እና የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) የማይጣጣሙ በመሆኑ ተከሳሹን በሚጠቅም መንገድ መተርጎም አለባቸው፡፡ ቅጣቱ ውሣኔም ተገቢ አይደለም መገደብ ነበረበት በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የሚመራው ድርጅት በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ተቀጥቷል ስለዚህ አመልካችን ተጠያቂ ለማድረግ ሌላ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የለብንም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት ተገቢውን ቁጥጥር ባለማድረግና ሥርዓት ባለመዘርጋታቸው ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ተገቢውን ማጣራት አድርጎ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 3 መካከል የሀሳብ አለመጣጣም አለ በማለት ያቀረበው ክርክር በወንጀል ህጉ አንቀፅ 3 የተደነገገውን ከግንዛቤ የማያስገባና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ አመልካች በሥራ አስኪያጅነት የሚመሩት የንግድ ድርጅት የአመልካች ሠራተኛ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት በመፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ በመርህ ደረጃ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56(1) ጥፋተኛ የሚባሉ መሆኑ በህጉ ተደንግጓል፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56 ንዑስ አንቀፅ 3 የተመለከቱትን ልዩ ሁኔታዎች በማስረዳት ከተጠያቂነት ነፃ ለመሆን የመከላከያ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም አመልካች ለድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ያልቀጠሩና ያልወከሉ መሆኑና የአስተዳደር ሥራዎን ብቻ ለወ/ሮ ድርሻዬ ከበደ የወከሉ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ለሠራተኞቹ የቃል ማስጠንቀቂያ የሰጠ መሆኑን ያስመሠከረ ቢሆንም አመልካች የቃል ማስጠንቀቂያ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 56 ንዑስ አንቀፅ 3(ለ) በተደነገገው መሠረት ማንኛውም በጎ አሳቢ ሰው ሊያደርገው የሚችለውን ጥንቃቄ ያደረገና ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ድርጅቱን በመምራት ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘነው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2(ለ)(2) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍርድ ፀንቷል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49889

ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ዛኪ ሰይድ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሕጉ በተሰጠው ስልጣን ተግባሩን በሚፈጽምበት ጊዜ ለሚደርሰው የገቢ መቋረጥና የንብረት ጉዳት ያለውን ኃላፊነት ስለሚገዛ የሕግ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት ያሁኑ ተጠሪ ሲሆን ተከሣሽ የአሁኑ አመልካች ነበር፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ ቁጥሩ 3-24062 ኢት መኪና አመልካች ከሕግ ውጪ በማቆሙ በፍርድ ቤት ውሣኔ የተሰጠ ቢሆንም መኪናው በቆመበት ጊዜ ተጠሪ በአጠቃላይ ብር 216,250.00 /ሁለት መቶ አስራ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ገልጸው ይህንኑ ገንዘብና መኪናውን እስኪረከቡ ድረስ ያለውን ገቢ ከመጠየቅ መብታቸው ጋር አመልካች እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያነት የቀረበው ክርክር ቀድሞ ተጠሪ ክስ አቅርበው ባለቀ ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይችሉ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ አመልካች መኪናውን ይዞ ሊያቆም የቻለው መኪናው ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ እቃ ጭኖ ወደ ውጪ ሊወጣ ሲል በመሆኑና ይህን ዓይነት ተግባር ደግሞ አመልካች ለመቆጣጠር ተገቢ ነው ያለውን እርምጃ ለመውሰድ በሕጉ ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም፣ መኪናው መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. በቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላም በዚሁ ጊዜ ለፍርድ ቤት ያሳወቀ በመሆኑ ጥፋት የለብኝም ብሎ መከራከሩን የሚገልጽ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበውን ክርክር የተጠሪ የቀድሞ ክስና የበኋለኛው ክስ ፍሬ ነገር ተመሣሣይ ባለመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት አይቻልም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎ የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር አመልካች የተጠሪ መኪናውን ያላግባብ በማቆም ገቢ እንዲያጡ አድርጓል፤ በመኪናው ሽራ እና ባትሪ ላይም ጉዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማድረሱን አላስተባበለም በማለት ብር 52,019.40 /ሃምሳ ሁለት ሺህ አስራ ዘጠኝ ብር ከአርባ ሳንቲም/ አመልካች ለተጠሪ ይክፈለው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥቅምት 18 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 58/ለ/ አንፃር /በሰ/መ/ቁጥር 22317 ከተሰጠው ትርጉም/ ሲታይ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ የካቲት 04 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ ተገቢ ነው የሚሉበትን ምክንያት ገልጸው ውሣኔው ሊጸና ይገባል ሲሉ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባባነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ ማንም ሰው በራሱ ጥፋት ወይም በሌሎች ሰዎች ጥፋት የተነሳ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ካደረሰ ከውል ውጪ ኃላፊነት የሚከተልበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2027/1/ እና /3/ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ጥፋት ደግሞ ታስቦ ወይም በቸልተኝነት ሊፈፀም እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2028/1/ ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ የጥፋት ትርጉም ደግሞ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2028 እስከ 2037 ሥር የተመለከተ ሲሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2038 እስከ 2065 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች የተፈፀመው ተግባር ጥፋት መሆን አለመሆኑን የሚገዙ ናቸው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ክስ ኃላፊነት አለበት የተባለው ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚገዙት የሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ያሳያል፡፡ አመልካች ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተገቢነት የለውም በማለት የሚከራከረው በአዋጅ ቁጥር 60/1989 ከተሰጠው ኃላፊነት እና ተግባር አንፃር ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አመልካች በጉምሩክ ወደቦች በወሰን አከባቢዎች እንዲሁም በሌሎች የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ማቋረጫ መስመሮች በኩል የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመፈተሽ፣ የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ተፈጽሞባቸው መግባታቸውንና መውጣታቸውን የማረጋገጥ ስልጣንና ተግባር ተሰጥቷል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 74 በተለይ ሲታይ አመልካች የሕገ ወጥ እቃዎችን ዝውውር የመቆጣጠር ኃላፊነትና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 6/5/ እና 58 ስርም ይኸው ተግባር የአመልካች ሕጋዊ ግዴታ ስለመሆኑም የሚያስገነዝብ የሕጉ አቀራረጽ ይታያል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ድንጋጌ ያሻሻለው የአዋጅ ቁጥር 368/1995 አንቀጽ 78 ድንጋጌም አመልካች ኮንትሮባንድ ወይንም ሕገ-ወጥ እቃ ጭኗል ብሎ ያመነበትን ተሽከርካሪ በቁጥጥር ሥር ማዋል እንደሚቻል በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ይህንኑ በሕጉ ተለይቶ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በተገቢው መንገድና በተገቢው ጊዜ ያከናውናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ አመልካች ይህንኑ ስልጣንና ተግባሩን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ባለማከናወን በሌላ ሰው ንብረት ላይ በሚያደርሰው ጉዳት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027/1/ እና /3/ ድንጋጌዎችና አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች የማይጠየቅበት ወይም ኃላፊ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በሕጉ ተለይቶ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ያላግባብ ባለመወጣቱ በሰው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱ ከተረጋገጠ ካሳ የማይከፍልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በዚህም መሠረት በአመልካች ተገቢ ያልሆነ ተግባር ጉዳት ደርሶብኛል የሚል ሰው የአመልካች ተግባር በሕጉ ከተሰጠው ኃላፊነትና ተግባር የሚዛር ወይም በምክንያታዊ መንገድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ማስረዳት ከቻለ በአመልካች ሊካስ የሚገባው መሆኑን ይህ ችሎት ያምናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የተጠረጠረውን ማንኛውንም ዕቃ ይዞ የመፈተሽና እቃውን የጫነውን ተሽከርካሪም ይዞ የማቆየት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶችም የተቀበሉት ጉዳይ ሲሆን ፍርድ ቤቶቹ የአመልካችን ተግባር ኃላፊነትን የሚያስከትል ነው ለማለት የቻሉት የተጠረጠረውን መኪና ለአንድ መቶ አስራ ሰባት ቀናት ያሕል መያዙ ተገቢነት የለውም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ይህን የሚያሕል ጊዜ መኪናው ተይዞ እንዲቆይ ያደረገው የወንጀሉ ጉዳይ በፍርድ ቤት ተይዞ እየታየ ባለበት ጊዜ ሲሆን በፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔም መኪናውን እንዲለቅ መወሰኑ የክርክሩ ሂደት ያስገነዝባል፡፡ አመልካች ከዚህ ጊዜ ውጪ መኪናው ያላግባብ የተያዘ ስለመሆኑ ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ የወንጀል ጉዳይ ሲታይ በነበረበት ጊዜ ደግሞ ጉዳዩ የኮንትሮባንድ አይደለም ተብሎ ስለተወሰነ ብቻ በአመልካች ላይ የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሙሉ በሙሉ ያስከትላል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በሕጉ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ባግባቡ ለመወጣት እንዲቻል መኪናውን ይዞ ማቆሙ ተገቢ ሲሆን በዚህ ጊዜ ለታጣ ገቢ ደግሞ የሚጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 22317 በቀረበው ተመሣሣይ ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁጥር 60/1989 ድንጋጌዎችን በመመርመር በአዋጅ ቁጥር 454/1997 መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ አመልካች መኪናውን ይዞ ጉዳዩ በወንጀል ችሎት እየታየ መቆየቱን ከክርክሩ መገንዘብ የምንችለውና በዚህ ሂደት የባከነው ጊዜ ከነባራዊው ዓለም አንፃር ሲታይ ምክንያታዊ ነው ከሚባል በስተቀር ያላግባብ የዘገየ ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 69/1989 አንቀጽ 6/5/፣ 58፣ 74 ድንጋጌዎች እና ከአዋጅ ቁጥር 368/1995 አንቀጽ 78 ድንጋጌ አንፃር ሲታይ መኪናውን ማቆሙ በሕጉ መሠረት የተሰጠውን ስልጣን በሕጉ አግባብ ለመወጣት እንዲያስችለው የወሰደው እርምጃ ያላግባብ ያልተከናወነ እና በተገቢው ጊዜ ውስጥ የተፈጸመ ነው ከሚባል በስተቀር በውሉ ውጪ ኃላፊነትን የሚያስከትል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው በታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ አመልካች በተጠሪ መኪና ባትሪና ሽራ ላይ ጉዳት አድርሷል ተብሎ ግምቱን እንዲከፍል ነው፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ የተሰጠውን የበታች ፍርድ ቤቶችን ሕጋዊ መሠረት የለም በማለት በዚህ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በግልጽ ያልተከራከረበት ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት በቀረበው ክርክርም ቢሆን በመኪናው ባትሪና ሽራ ላይ መኪናው በአመልካች ቁጥጥር ሥር ውጪ በነበረበት የደረሰ ወይም በራሱ ቁጥጥር ሥር ውስጥ እያለ በሌላ ምክንያት የደረሰ ነው የሚል ክርክርም አላቀረበም፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ንብረቶች ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑ ማስረጃን የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ሲሆን አመልካች ጉዳቱ በሌላ ምክንያት የደረሰ ስለመሆኑ የሚያሳይ ክርክርና ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ በመሆኑም አመልካች በኮንትሮባንድ ድርጊት /ሥራ/ ተሰማርቶ የተገኘን ተሽከርካሪ ለጊዜው ማቆም የሚችል መሆኑን ሕጉ ስልጣን ቢሰጠውም ንብረቱን ግን ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ መኪናው በራሱ ቁጥጥር ስር በነበረበት ጊዜ ለሚደርሰው የመኪናው አካል ጉድለት ጉድለቱ በሌላ ሕጋዊ ምክንያት የደረሰ ስለመሆኑ እስካላስረዳ ድረስ ኃላፊነቱ የአመልካች የማይሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ ከፍ ብለው በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ሊሻሻል የሚገባው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04134 ሐምሌ 10 ቀን 2001 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 72896 ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የተጠረጠረውን ዕቃ ይዞ የመቆየት ሥልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 69/1989 አንቀጽ 6/5/፣ 58/1/ለ/ እና 74 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 368/1995 አንቀጽ 78 መሠረት ያለው በመሆኑና ጊዜውም ምክንያታዊነት የሌለው ነው ለማለት የሚቻል ባለመሆኑ መኪናው በቆመበት ጊዜ ለታጣ ገቢ ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. አመልካች መኪናውን ይዞ ባለበት ጊዜ ለደረሰው የመኪና ባትሪ እና ሽራ ጉዳት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ የሁለት ባትሪ ዋጋ ብር 4,500.00 /አራት ሺህ አምስት መቶ/ እና የሽራ ዋጋ ብር 7000.00 /ሰባት ሺህ/ በድምሩ ብር 11,500.00 /አስራ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ለተጠሪ እንዲከፍል ብለናል፡፡ በዚህ መሠረት ያስፈጽም ዘንድ የዚህ ችሎት ውሣኔ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- በዚህ ችሎት ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 48621

ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አብደላ ሁሴን ከሰር ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ አቶ ሣሙኤል ኤፍሬም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን - ዓቃቤ ሕግ ግርማ ወልደማሪያም -ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሰጠው የገቢ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ማስታወቂያ ባለመስማማት ይግባኝ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ለማቅረብ በሕጉ መሰረት ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ በወቅቱ አስይዘዋል ወይስ አላስያዙም የሚለው ነጥብ ነው፡፡

አመልካች የገቢ ግብር ማስታወቂያና የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ማስታወቂያ ከደረሳቸው በኋላ በሰላሣኛው ቀን ማለትም ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም ለሁለቱም ግብሮች CPO በማሰራት ከተጠሪ ቢሮ ድረስ መሄዳቸው ለገቢ ግብር ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ 8/10/99 አስይዘው የጨረሱ መሆኑንና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም ለማስያዝ ከተጠሪ ቢሮ አስራ አንድ ሰዓት በኋላ ያቀረቡ ቢሆንም ሰራተኞችና የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ወጥተው ስለነበር ሣያስይዙ ተመልሰው ተከታዮቹ ቀናት የቅዳሜና እሁድ ስለነበሩ 11/10/99 ገንዘቡን የማስያዝ ሂደቱን አጠናቅቀው ይግባኙ እንዲታይላቸው ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርበዋል፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ይግባኙ የቀረበው በአዋጅ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

285/94 አንቀጽ 43 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በሠላሣ ቀን ውስጥ መያዝ ያለበት ገንዘብ ተይዞ ባለመሆኑና ጊዜው ካለፈ በኋላ ያቀረበ በመሆኑ ይግባኙ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው አልፏል ወይስ አላለፈም የሚለው ክርክር የፍሬ ጉዳይ ክርክር እንጅ የሕግ ነጥብ ባመለሆኑ ይግባኙን አልተቀበልኩትም በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጐታል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች የገቢ ግብር ማስታወቂያ ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ ያለብንን CPO እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ ያለብንን ገንዘብ በCPO አሰርተን ተጠሪ መሥሪያ ቤት የቀረብነው 8/10/99 ነው፡፡ የገቢ ግብሩን ተቀብሎ ደረሰኝ ሲሰጠን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመክፈል ያቀረብነውን CPO በተመለከተ ኮንፒውተር ብለሸት አጋጥሞታል በሚልና በሌሎች ምክንያቶች ደረሰኝ ሣይሰጠን ተመልሰናል፣እለቱ አርብ ስለነበር ቅዳሜና እሁድ ቆይተን ሰኞ 11/10/99 ደረሰኝ ተቀርጦ የተሰጠን ሲሆን ለክፍያ ያቀረብነው 8/10/99 መሆኑን በደብዳቤ ገልፆ ጽፎልናል፡፡ የተጠሪ ምስክሮችም ይህንን አስረድተዋል፡፡ በግብር ተቀባዩ መሥሪያ ቤት (ተጠሪ)ለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ደረሰኝ ሣናገኝ 8/10/99 መመለሳችንና ደረሰኙ 11/10/99 ተቀርጦ የተሰጠን መሆኑ በእኛ ቸልተኝነት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው እንዳለፈ የሚያስቆጥር አይደለም፡፡ ይህ የሕግ ትርጉም የሚጠይቅ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ እያለ የፍሬ ጉዳይ ክርክር ነው ተብሎ መታለፉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ለተጨማሪ እሴት ታክሱ ደረሰኝ የተሰራላቸው 11/10/99 መሆኑን አመልካች አምነዋል፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ጊዜው አልፏል ወይስ አላለፈም የሚለውን አጣርቶ መያዣው በወቅቱ ያልተከፈለ መሆኑን በማረጋገጥ መያዣቸው ጊዜው ካለፈ በኋላ የተከፈለ መሆኑን አረጋግጦ የሰጠው ውሣኔ የፍሬ ጉዳይ ክርክር እንጅ የሕግ ክርክር ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የፈጸሙት የሕግ ስህተት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ ያለባቸውን ገንዘብ ያስያዙት መቼ ነው? ይግባኝ ለማቅረብ መያዝ የሚገባው ገንዘብ ጊዜው ከማለፉ በፊት በማስያዝ አመልካች ይግባኝ አቅርቧል ወይስ አላቀረበም የሚለው ነጥብ የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ በCPO ለማሰራት ከተጠሪ ቢሮ ሰላሣ ቀን ከማለፉ በፊት ቀርበው የገበሩ መሆኑና ተጠሪ የገቢ ግብር ይግባኝ ለማቅረብ በCPO ያቀረቡትን መያዣ ደረሰኝ ቆርጦ 8/10/99 ዓ.ም የሰጠ ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ በመያዣነት ያቀረቡትን CPO 8/10/99 ከተቀበለ በኋላ በተለያየ ምክንያት ደረሰኝ ቀርቦ መስጠት እንዳልቻለና ደረሰኙን 11/10/99 ዓ.ም ቆርጦ የሰጠ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ መያዣው በሚፈፀምበት ሥርአት በCPO አሰርተው ለተጠሪ ጊዜው ከማለፉ በፊት ማቅረባቸው ከተረጋገጠ CPO ለክፍያ ያቀረበውን ገንዘብ አወራርዶ ደረሰኝ ለመስጠት ተጠሪ በአጋጠመው የአሰራር ወይም ሌላ ችግር ምክንያት ቀናት ወይም ወራት ቢወስድበት ይግባኝ ባዩ ይግባኝ ለማለት መክፈል ያለበትን ገንዘብ በጊዜው አልከፈለም ሊባል ይገባዋል ወይ? የሚለው ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ከሕጉ አጠቃላይ መንፈስና ዓላማና ሕግ አውጭ ሊያሣካው ከሚፈልገው ግብ አንፃር መመርመርና ውሣኔ ማግኘት አለበት፡፡ ሕግ አውጭው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ የደረሳቸው ሰዎች የውሣኔ ማስታወቂያ በደረሳቸው በሰላሣ ቀን ውስጥ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ 50% ለግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት በማስያዝ ይግባኝ ማቅረብ እንዳለባቸው በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 43/1/ ሲደነግግ ግብር ከፋዩ ለግብር አስገቢው መሥሪያ ቤት ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ለማስገደድ እንጅ ገንዘቡ ገቢ ሆኖ ግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ደረሰኝ ሣይሰጥ ቢቆይ ለመሥሪያ ቤቱ የአሰራር ድክመትና ችግር ምክንያት ግብር ከፋይ ይግባኝ የማቅረብ መብቱ እንዲጣበብ በማሰብ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች ተጠሪ ክፍያ በሚቀበልበት ሥርአት በማሟላት ማለትም በCPO መክፈል አለብህ ተብሎ የተወሰነበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ 50% የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ በደረሰው በሰላሣኛው ቀን ማለትም 8/10/99 ለተጠሪ ገቢ አድርጓል፡፡ የህም አመልካች ከላይ ከተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት ለተጠሪ ገቢ አድርገዋል፡፡ ተጠሪ ሰላሣ ቀኑ ከማለፉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፊት በCPO ገቢ ለሆነለት ገንዘብ ደረሰኝ ቆርጦ ያሰጠው ከሶስት ቀን በኋላ ማለትም 11/10/99 መሆኑ ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ ያለበትን ገንዘብ አመልካች ከሰላሣ ቀን በኋላ ነው ገቢ ያደረገው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት በኩል ያሉ የአሰራር ችግሮችና ጉድለቶች መሰረታዊ የሆነውን የአመልካችን ይግባኝ የማቅረብ መብት በማያጣብብ ሁኔታ በመተርጐም የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሣኔ የሕጉን ድንጋጌ አተረጓጐምና ተፈፃሚነት የሚመለከት እንጅ የፍሬ ጉዳይ ክርክር አይደለም፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ጉዳዩ የፍሬ ጉዳይ ክርክር ነው በማለት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ለአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 43 ንኡስ አንቀጽ 1 የሰጠውን የተዛባ ውሣኔ ሣያርሙ ማለፋቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት የመያዣነት መከፈል የሚገባውን ገንዘብ ለተጠሪ ያስያዙ በመሆኑ የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመርና የግራ ቀኙን ክርክር በማስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት መልስን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውክልና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48269

የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ጌሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሸረፈዲን አብደላ - ጠበቃ አብዶ መሐመድ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ማርታ አስፋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ በሐዋላ የተላከውን ገንዘብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ናቸው፡፡ ተከሳሽ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ የአመልካች የስር ክስ ይዘት ባጭሩ፡- አቶ አህመድ ኢሳ ኪይሮ የተባሉ ግለሰብ በተጠሪ ባንክ ሚዛን ተፈሪ ቅርንጫፍ ታህሣሥ 16 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. በ25/12/2006) በመቅረብ ብር 145,860.00(አንድ መቶ አርባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ብር) ለአመልካች ገቢ በማድረግ ማስተላለፋቸውን፣አመልካች ይሕንን ገንዘብ ለማውጣት ገንዘቡን እንዲከፍል ለታዘዘው አየር ጤና ቅርንጫፍ ቢሄዱ ገንዘቡን ለሌላ ግለሰብ እንደከፈለ በመግለጽ ክፍያው ለአመልካች ሊፈፀምላቸው የማይችል መሆኑን የገለፀ መሆኑን በመግለጽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ክፍያው ይፈፀም ይችል ከነበረበት ከጥር 01 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድና ከተለያዩ ወጪዎች እና ኪሳራዎች ጋር ተጠሪ እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም አመልካች በገንዘቡ ላይ መብት ወይም ጥቅም ስለሌላቸው ክስ ለመመስረት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አለመኖሩን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ክፍያው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና የተለመደውን አሰራር በመከተል የፈፀሙ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ክፍያውን የፈፀመው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና የተለመደውን አሰራር በመከተል በመሆኑ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 12 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፋት አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ክፍያውን የፈፀመው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግና የተለመደውን አሰራር በመከተል ነው ተብሎ ገንዘብ ላኪው ግለሰብ እንኳ ቀርቦ እንዲመሰክር ሳይደረግ ውሳኔ መሰጠቱ ያላግባብ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ተጠሪ ገንዘቡን እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ተገቢውን ጥንቃቄ ወስዶ በሐዋላ የተላከውን ገንዘብ በመክፈሉ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ባግባቡ መሆኑ ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ የተጠሪ ነገረ ፈጅ ጥር 07 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አመልካችም በ11/06/2002 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለክሱ መሰረት ያደረጉት ምክንያት ገንዘቡ በስህተትና በሐሰት ለሌላ ሰው ተከፍሎብኛል የሚለውን መሆኑን፣ተጠሪም ገንዘቡ በላኪው ግለሰብ በተላለፈው መሰረት ገንዘቡ ለተላከለት ሰው ከፍያለሁ ብሎ የሚከራከር መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመርመር ተጠሪ ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ከፍያለሁ የሚለው ከአመልካች ጋር ተመሳሳይ ስም ላለው ሰው ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር በመከተል ስለመሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት በመያዝ ተጠሪን ከክሱ ኃላፊነት ነፃ ማድረጉን ነው፡፡

በመሰረቱ ባንክ በሐዋላ የተላከውን ገንዘብ ለተላከለት ሰው በትክክል የማድረስ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡ ባንኩ በሐዋላ ለማድረስ የተቀበለውን ገንዘብ ለተገቢው ሰው ካላደረሰ ኃላፊነት የሚኖርበት ሲሆን ኃላፊነቱ የሚከተለው ግን ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር ሳይከተል መቅረቱ ወይም ራሱ ባንኩ መጭበርበሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ባንክ ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር መከተሉን የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን አመልካች ገንዘቡን ከባንኩ የወሰዱት ግለሰብ ባንኩን ያጭበረበሩት ስለመሆናቸውን በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ ገንዘቡን ለአመልካች ላኩ የተባሉት ሰው ለማስረጃነት አመልካች የቆጠሯቸው ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ በመሆኑ አመልካች የስር ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኚህን ግለሰብ ሳይሰማ ማለፉ ያላግባብ ነው በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል የተደነገጉትን የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የማስረጃው አቀባበልና አመዛዘኑ ባግባቡ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና 22 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ይዘትና መንፈስ እንደሚያስገነዝበው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ጉዳይ ሳይሆን የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ሆኖ ስለአገኘን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና የሚገባው ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 100405 ግንቦት 04 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69684 ግንቦት 14 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 50440

ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሃብቱ ወልዱ - ጠ/አማረ ተሻለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ መሰሉ ደስታ
2. ወ/ሮ አማከለች ገ/ሕይወት } አልቀረቡም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በመቐለ መካከለኛ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት አመልካች ሲሆኑ በክሳቸው በመቀሌ ከተማ ቀበሌ 1ይ ወያን የሚገኝ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ የሚገኘውን በቁጥር ሐ/116 በስማቸው የተመዘገበውን ቤት አንደኛ ተጠሪ እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲቆጣጠሩ፣ እንዲሸጡና እንዲለውጡ ውክልና ሰጥተዋቸው የነበረ ቢሆንም ከውክልናቸው ውጪ እናታቸው ለሆኑት ለሁለተኛ ተጠሪ በስጦታ በመስጠት ስሙን ያዛወሩ በመሆኑ የስጦታው ውሉ ፈርሶ የማህበሩ ቤት ከሁለተኛ ተጠሪ ወደ ስማቸው እንዲዞርላቸው ጠይቀዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ ከመሸጥ በቀር በስጦታ እንዳልሰጡ፣ ሽያጩ ሊከናወን የሚገባውም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና በንግድ ህጉ እንጂ በፍ/ህጉ አለመሆኑንና በተሰጣቸው ውክልና መሰረት በህጉ አግባብ ያደረጉ ሽያጭ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪም አመልካች በቤቱ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ስለሌላቸው የመክሰስ መብት የላቸውም፣ አንደኛ ተጠሪ በተሰጣቸው ውክልና መሰረት በሽያጭ እንጂ በስጦታ አልተላለፈም፣ ቤቱም ሊሸጥ የሚችለው በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብና በንግድ ህግ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሰረት አይደለም፣ ቤቱ በስማቸው ስለተመዘገበ ሽያጩ ሊፈርስ አይገባም፣ ይፈርሳል የሚባል ከሆነ መቀጫ ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በስር ሦስተኛ ተከሳሽ የነበረው 1ይ ወያነ ቤት ስራ ህብረት ስራ ማህበር የተደረገ የስጦታም ሆነ የሽያጭ ውል የለም፣ አንደኛ ተጠሪ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የተቀመጠ ውሳኔና በመሸጫ አሰራር ከትዳር ነፃ መሆናቸውን በማምጣት ስም ማዛወሪያ ሞልተው ወደ ሁለተኛ ተጠሪ አዘዋውረዋል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ አንደኛ ተጠሪ ለእናታቸው ለሁለተኛ ተጠሪ ሸጫለሁ ያሉት በተዘዋዋሪ የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ስለሆነ የጥቅም ግጭት አለ፣ የተሸጠውም ቤትና ቦታ በመሆኑ ሽያጩ ለማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጫ የሚመለከተውን የህጉን ድንጋጌ አያሟላም፣ በመሆኑም ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ቤቱ ከሁለተኛ ተጠሪ ወደ አመልካች ስም እንዲዛወር ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ላይ ለትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ ተጠሪዎች በመቀጠል ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ክስ የመሰረቱት አንደኛ ተጠሪ ከተሰጣቸው ውክልና ውጪ ቤታቸውን በስጦታ ለሁለተኛ ተጠሪ ስለሰጡ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቶቹ ክሱ ውጪ በመውጣት የሽያጭ ውሉ ይፍረስ ብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ውጪ ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የሽያጩ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች በተሰጣቸው ውክልና ስልጣን ለወላጅ እናታቸው ያደረጉት የሽያጭ ውል የጥቅም ግጭት ያለበት ነው፣ በምንም አይነት ውል የጥቅም ግጭት ካለ ለውጥ ስለማያመጣ የሰበር ችሎቱ የጥቅም ግጭት መኖር አለመኖሩን መመርመር ሲገባው ወደ ውሉ አይነት ገብቶ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል ብለዋል፡፡ ይህ ችሎትም የጥቅም ግጭት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በማለቱ ተጠሪዎች መልሳቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ በመልሳቸውም ቤቱን አንደኛ ተጠሪ በተሰጣቸው ውክልና መሰረት አትርፈው የሸጡት እንጂ በስጦታ ያስተላለፉ ባለመሆኑ የጥቅም ግጭት አለ ሊባል አይችልም፣ አመልካች በተደረገው ሽያጭ ውል መሰረት የደረሰባቸው ጉዳት ስለመኖሩ በማስረጃ አስደግፈው አላረጋገጡም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች ክስ የመሰረቱት አንደኛ ተጠሪ እንዲያስተዳድሩላቸው፣ እንዲቆጣጠሩላቸው፣ እንዲሸጡላቸውና እንዲለውጡላቸው ውክልና የሰጧቸውን ቤት ከውክልናቸው ውጪ በስጦታ ለሁለተኛ ተጠሪ ስላስተላለፉ ውሉ እንዲፈርስላቸው ነው፡፡ ተጠሪዎቹ በሰጡት መልስ ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ የተላለፈው በሽያጭ እንጂ በስጦታ አለመሆኑ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በስር ፍ/ቤት በተደረገው የቃል ክርክር የሽያጭ ውልም ቢሆን አንደኛ ተጠሪ ውሉን ያደረጉት ከእናታቸው ጋር በመሆኑ የጥቅም ግጭት አለ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ቤቱ የተላለፈው በሽያጭ መሆኑን ተቀብሎ ነገር ግን አንደኛ ተጠሪ ከእናታቸው ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል የጥቅም ግጭት ያለበት በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ የሰበር ችሎቱ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ የሻረው ክሱ የስጦታ ውል ይፍረስልኝ ሆኖ ሳለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሽያጭ ውል እንዲፈርስ መደረጉ በክሱ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ ነው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ አመልካች ቤታቸው ለሁለተኛ ተጠሪ የተላለፈው በስጦታ ነው በሚል ክስ ቢመሰርቱም ዋናው ጥያቄአቸው ቤቱ ወደ ሁለተኛ ተጠሪ የተላለፈበት ውል እንዲፈርስ ነው፡፡ በቃል ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜም አመልካች ቤቱ በሽያጭ መተላለፉን ሲረዱ የሽያጩም ውል ቢሆን የጥቅም ግጭት ያለበት ነው በማለት ይኸው ነጥብ ክርክር ተደርጎበታል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባልተነሳ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሰጥቷል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የተሳሳተ ነው፡፡

በሌላ በኩል ይህ ችሎት አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ ያደረጉት የሽያጭ ውል የጥቅም ግጭት አለበት ወይ? የሚለውን ነጥብ ተመልክቷል፡፡ ተወካዩ በፈፀመው ውል ምክንያት የወካዩና የወኪሉ ጥቅሞች የሚቃወሙ የሆኑ እንደሆነ ይህን ውል የፈረመው 3ኛ ወገን ሁኔታውን ያወቀና ሊያውቀው የሚገባ የሆነ እንደሆነ ወካዩ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1) ያስረዳል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አንደኛ ተጠሪ የአመልካች ወኪል ሲሆኑ በተሰጣቸው ውክልና መሰረት የአመልካችን ቤት ለእናታቸው ሸጠዋል፡፡ ውክልና ተወካዩ ለወካዩ እንደራሴ ሆኖ አንድ ወይም ብዙ ህጋዊ ስራዎችን በወካዩ ስም ለማከናወን የሚደረግ ስምምነት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2198 ያመለክታል፡፡ ይህም ስምምነት ወካዩ የውክልናው ስራ በሚፈፅምበት ጊዜ የወካዩን ህጋዊ ሁኔታዎች የመለወጥ ስልጣን የሚሰጠው በመሆኑ ተወካዩ የውክልናውን ስልጣን ተጠቅሞ ሲሰራ ለወካዩ ፍፁም ታማኝ እና በስራው ሁሉ የወካዩን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ይህንን ለወካዩ ፍፁም የሆነ ታማኝነቱንና ሙሉ ለሙሉ የወካዩን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚከለክለው ፍላጎት ወይም ታማኝነቱን የሚከፋፍል ሁኔታ የሚያስከትል የጥቅም ግጭት ሲፈጠር ተወካዩ በስራው አፈፃፀም ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እነዚህም ግዴታዎች በፍ/ብ//ህ/ቁ. 2208 እና 2209 ስር ተመልክተው የምናገኛቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ተወካዩ የራሱን ጥቅም ብቻ ሳይሆን የቤተሰቡ፣ የጓደኛው ወይም ቅርብ ግንኙነት ያለው ሰው ጥቅምን በሚመለከት ጉዳይ ሲያጋጥመው ሁኔታውን ለወካዩ ሳያሳውቅና ሳይስማማ ስራውን እንዳይሰራ ይከለክላል፡፡ ይህም የሚሆነው የውክልና ስራውን በሚሰራበት ጊዜ የራሱን ወይም ከራሱ ጋር ቤተሰባዊ ወይም ሌላ ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር ያለው ሰውና የወካዩ ጥቅም በሚጋጭበት ጊዜ ከራሱ ወይም ከቤተሰቡ ጥቅም ይልቅ የወካዩን ጥቅም በማስቀደም ለወካዩ ጥቅም ብቻ ይሰራል ተብሎ ስለማይገመት ነው፡፡ በመሆኑም ወኪሉ በፈፀመው ውል ምክንያት የወካዩ እና የተወካዩ ጥቅሞች የሚጋጩ ከሆነ ውሉን የፈረመው 3ኛ ወገን ይህን ሁኔታ ያወቀውና ሊያውቀው የሚገባ የሆነ እንደሆነ በወካዩ ጥያቄ መሰረት ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል በህጉ ተካቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች አንደኛ ተጠሪን ክርክር ያስነሳውን ቤት እንዲያስተዳድሩ እንዲሸጡና እንዲለውጡ የውክልና ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በመሆኑም አንደኛ ተጠሪ በወካያቸው ስም ሲዋዋሉ ፍፁም ታማኝና ሙሉ ለሙሉ የወካያቸውን የአመልካችን ጥቅም በሚያስጠብቅ ሁኔታ ውሉን የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ቤቱን የሸጡ እናታቸው ለሆኑት ለሁለተኛ ተጠሪ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ደግሞ አንደኛ ተጠሪ በውክልናቸው መሰረት ቤቱን የሸጡት የቤተሰባዊ ጥብቅ ትስስር ላላቸው እናታቸው በመሆኑ በወካያቸው ጥቅምና ውሉን ባደረጉት እናታቸው ጥቅም መሃከል ግጭት መኖሩ የሚታመን ነው፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ አንደኛ ተጠሪ ሁኔታውን ለአመልካች ሊያሳውቁና የአመልካችን ይሁንታ ሊያገኙ ይገባል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ውሉን ከመፈፀማቸው በፊት ለአመልካች ያሳወቁና ስምምነታቸውን ያገኙ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ወይም አንደኛ ተጠሪ ቤቱን የአመልካችን ጥቅም ብቻ በሚያስጠብቅ መልኩ ተገቢው ጥንቃቄ በማድረግ ቤቱ በተሸጠበት ጊዜ ሊያወጣ በሚችለው የገበያ ዋጋ ሽያጩን ያከናወኑ መሆኑና የአመልካች ጥቅም በምንም መልኩ ያልተጎዳ መሆኑን በስር ፍ/ቤት ሊያስረዱ ይገባል፡፡ ይህ ለመሆኑ ደግሞ ተጨባጭ ማስረጃ አቅርበው ያስረዱት ነገር ስለመኖሩ መዝገቡ አያሳይም፡፡ በሌላ በኩል አንደኛ ተጠሪ ቤቱን በውክልና ስልጣናቸው የሸጡላቸው በመሆኑ የጥቅም ግጭት እንደሚኖር ሁለተኛ ተጠሪ ያውቃሉ ወይም ሊያውቁ ይገባል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሰረት የአመልካችን ቤት ለእናታቸው ለሁለተኛ ተጠሪ መሸጣቸው የጥቅም ግጭት መኖሩን የሚያሳይ በመሆኑም አመልካች ውሉ እንዲፈርስላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል አንደኛ ተጠሪ ከቤቱ ሽያጭ ያገኙትን ገንዘብ ለአመልካች የከፈሉ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ባለመረጋገጡ የተከፈለ ገንዘብ ካለ አንደኛ ተጠሪ አመልካችን ከሰው የመጠየቅ መብታቸውን ፍ/ቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠብቆላቸዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪም ቤቱ ለመግዛት የከፈሉትንና በቤቱ ላይ ተጨማሪ ወጪ አውጥቻለሁ የሚሉ ከሆነ ያወጡትን ወጪ አንደኛ ተጠሪን ከሰው የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤት የሽያጩ ውል ሊፈርስና በሁለተኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበው የቤትና የቦታ እጣ በአመልካች ስም እንዲመዘገብ የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት የህግ መሰረት የለም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 32155 ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የመቐሌ መሃከለኛ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 00654 ሰኔ 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 07667 ሰኔ 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 46358

የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ብርሃን ፀጋዬ - አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ጠበቃ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ሚካኤል ፍስሐ - ቀረቡ

2ኛ. ናሰው ኮንስትራክሽን - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሽርክና ውል የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ክስ የተመሰረተው በአመልካች አማካይነት ነው፡፡ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ያቋቋሙት የሽርክና ውል ፈርሶ የተገዛው ንብረት ተሸጦ እንዲከፋፈሉ እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሽርክና ውል የለንም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ኤክስካቫተር ማሽን ባለቤት መሆኑን በመጥቀስ በክርክሩ ገብቶ ለመከላከል ጣልቃገብ ሆኖ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የተፈረመው ውል የሽርክና ውል እንጂ የአሸሙር ማህበር አይደለም በማለት የሽርክና ውሉ ደግሞ በንግድ ሕግ አንቀጽ 219 /ሐ/ መሰረት አልተመዘገበም በሚል ምክንያት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤትም ይህንኑ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ በአመልካች እና በአንደኛ ተጠሪ መካከል መጋቢት 4/1994 ዓ.ም የተፈረመው ውል

“የአሸሙር ሽርክና ማህበር” መሆኑን አጥብቀው በመከራከር የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ተሽሮ እንደክሱ የዳኝነት ጥያቄ እንዲወሰን አመልክቷል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በግራ ቀኙ

መካከል የተደረገው ውል በሕግ ረገድ የሚኖረው ውጤት ምንድነው? የሚለውን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ የአንደኛ ተጠሪ ወኪል ታህሣሥ 30/2002 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ የሥር ፍ/ቤት ክርክርን አጠናክረው አቅርበዋል፡፡

እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ አመልካች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር የሽርክና ማህበር ያቋቋሙ ስለመሆኑ ለማስረዳት መጋቢት 3 ቀን 1994 ዓ.ም የተፃፈ ውል አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የሽርክና ውል የለኝም ይበል እንጂ የቀረበውን ሰነድ ለማስተባበል በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክርም ሆነ ማስረጃ ስለመኖር የሥር መዝገብ አያስረዳም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የቀረበውን ሰነድ ውድቅ ያደረገው ሰነዱ የእሽሙር ማህበር ስለመኖሩ አያስረዳም በሚል ነው፡፡

ከቀረበው ሰነድ መረዳት የተቻለው አመልካችና አንደኛ ተጠሪ የሽርክና ማህበር ለማቋቋም ውል ማድረጋቸውን ነው የውል ሰነድ "የሽርክና ውል ስምምነት" ከሚል በስተቀር ምን ዓይነት የሽርክና ማህበር እንደሆነ አያመለክትም፡፡ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 211 መረዳት የሚቻለው የሽርክና ማህበር ጠቅላላ ስያሜ እንጂ የማህበሩን ዓይነት ለይቶ የሚያመለክት አለመሆኑን ነው፡፡ የማህበሮቹ ስያሜ እና ዓይነታቸውን በተመለከተ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ ቁጥር 212 በዝርዝር አመልክቷል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል አለ የተባለው የሽርክና ማህበር ስያሜው ተለይቶ አልተመለከተም፡፡ ከዚህ መነሻ ሲታይ የሽርክና ውሉ አልተመዘገበም የሚለው የሥር ፍ/ቤት አቋም ምን ዓይነት የሽርክና ውል የሚለውን አልለየም፡፡ ምክንያቱም ምዝገባ የሚያስፈልገው እና ምዝገባ የማያስፈልገው የሽርክና ማህበር በንግድ ሕጉ ተለይቷል፡፡

በግራ ቀኙ ክርክር ይዘት ከመዝገቡም መረዳት እንደተቻለው የአመልካች ክርክር የሽርክና ማህበሩ የእሽሙር የሽርክና ማህበር ስለሆነ ምዝገባ አያስፈልገውም ሕጉ አያስገድድም የሚል ነው፡፡ በአንደኛ ተጠሪ በኩል ያቀረበው ዋነኛ ክርክር እስከነጭራሹም የሽርክና ውል የለም የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ በአመልካች በኩል የቀረበው ሰነድ

የሽርክና ውል ስለመኖሩ የሚያስረዳ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤትም ተቀባይነት ያገኘ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የሽርክና ውሉ የእሽሙር ሽርክና ማህበር ወይንስ ሌላ አይነት ማህበር አቋቁሟል? የሚለውን ለመለየት የሥር ፍ/ቤት በውሳኔው በዝርዝር አላመላከተም፡፡

በሕጉ አገላለጽ ሌሎች የሽርክና ማህበራት ምዝገባ የሚያስፈልግ ሲሆን የእሽሙር ሽርክና ማህበር ግን ምዝገባ አያስፈልገውም፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 219 ይመለከታል፡፡

አመልካች ያቀረቡት ሰነድ የሽርክና ማህበር መመሥረቱን የሚያመላክት ሲሆን ባለመመዝገቡ የእሽሙር ሽርክና ማህበር ነው ተብሎ በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር አንደኛ ተጠሪ በማስተባበል ያቀረበው ክርክር የለም፡፡

ስለሆነም በስምምነት የተቋቋመው ማህበር የእሽሙር ሽርክና ማህበር ስለመሆኑ ከቀረበው ሰነድ ለመረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም የሽርክና ውሉ አልተመዘገበም በሚል ምክንያት የሥር ፍ/ቤት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15059 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61426 የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች እና በአንደኛ ተጠሪ መካከል መጋቢት 3 ቀን 1994 ዓ.ም የተደረገው የሽርክና ውል የእሽሙር ክርክር መሆኑ በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ ስለተረጋገጠ የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት የመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሰረት እንዲመለስ ታዟል፡፡

ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስቴር አርአያ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ አምሳለ በላይ - ጠበቃ ተሾመ ገ/እግዚአብሔር ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ጥበበ ተገኔ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የንግድ ማኅበር ሥራ አስኪያጆች ለማያደርሱት ጥፋት ለአባላቱ ያለባቸውን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የጀመረው በፊ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት ከሳሾች የነበሩ ሲሆን ክስ ያቀረቡት በአሁኗ አመልካችና ዶ/ር አለሽኝ መኮንን በተባሉት ግለሰብ ላይ ነው፡፡ በክሳቸውም ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሣ ሺህ/ የሚያወጡ እጣዎችን ለመግዛት ተስማምተው በተለያዩ ጊዜ ለተከሣሾቹ በቀጥታና በሌሎች ሰዎች አማካኝነት የአሜሪካን ዶላር እንደከፈሉ፣ እንዲሁም ለጋዜጣ ማውጫና ለኮምፒውተር መግዣ ለተከሳሾቹ ገንዘብ መክፈላቸውን፣ ዶ/ር አለሽኝ መኮንን የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሲሆኑ በዚህ መዝገብ አመልካች የሆኑት ደግሞ ከታህሣሥ 24 ቀን 1999 ዓ.ም. ከሥራ አስኪያጁ በተቀበሉት ውክልና መሠረት ማኅበሩን በሥራ አስኪያጅነት ሲመሩ እንደነበረ፣ ተከሣሾቹ ማኅበሩን አቋቁመናል ከሚሉ በቀር እንዳችም እንቅስቃሴ እንዳላደረጉ፣ የማኅበሩ ካፒታል ነው የተባለው አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር (1,100,000)የማኅበሩ ደረሰኝ እንዲቆረጥለት ተጠይቀው ፈቃደኛ አለመሆናቸውን፣ በዚህ ምክንያት ማኅበሩ ስለከሰረ እንዲፈርስ መወሰኑን፣ ተከሣሾቹ ማኅበሩን ያቋቋሙት በቅን ልቦና ነግዶ ለማትረፍ ሳይሆን የንግድ ስሙን ሽፋን በማድረግ ከሌሎች ሰዎች ላይ ገንዘብ ለመውሰድ መሆኑን በመግለጽ ተከሣሾቹ የወሰዱትን ገንዘብ በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ ወለድን ጨምሮ ብር 912,733(ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ስላሳ ሶስት) እንዲከፍሉ ጠይቀዋል፡፡ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የነበሩት ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ ተጠሪዎች አዋጣን የሚሉት ገንዘብ ከ10 ዓመት በፊት ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ነው፤ ገንዘቡን አዋጣን የሚሉትም ለማኅበሩ ስለሆነ ማኅበሩን ከሚጠይቁ በስተቀር አንደኛ ተከሣሽን መጠየቅ አይችሉም፣ አንደኛ ተከሣሽ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከተጠሪዎች ገንዘብ አልተቀበሉም፣ ስለሆነም የአንድነት ኃላፊነት የለባቸውም፣ አንደኛ ተከሣሽ ሥራ አስኪያጅ የነበሩ ቢሆን ሥራውን የካሂዱ የነበሩት ሥር ሁለተኛ ተከሣሽ /በዚህ መዝገብ አመልካች/ ስለሆኑ ስለ ሂሣቡ ሊጠየቁ የሚችሉት እሳቸው ናቸው በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ተከፈለ የተባለውን ገንዘብ ተከሣሽ አንድ ላይ የተቀበልነው ስላልሆነ ተጣምረን ልንከሰስ አይገባም፤ ተጣምረን ባንከሰስ ኖሮ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አይኖረውም፤ ገንዘቡ ተሰጠ ከተባለ 10 ዓመት ስለሚያልፈው ይርጋ ያግደዋል፤ ክሱ ሊቀርብ ይገባ የነበረው ማኅበሩ እንዲፈርስ በተጠየቀበት መዝገብ ስለነበር በድጋሚ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፣ ተጠሪዎች ለአመልካች በሁለት ቼክ ከፈልን ካሉት በስተቀር ገንዘብ ስለመክፈላቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፣ የተቀበልኩትንም ገንዘብ ለማኅበሩ ገቢ አደረኩ እንጂ በግሌ አልበለፀኩም፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማኅበርተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካዋጣው መዋጮ በላይ ኃላፊ ሊሆን የማይችልበት ነው፣ ማኅበሩ በመፍረሱ አመልካችም እንደ ሌሎቹ አባላት ጉዳት የደረሰብኝ በመሆኑ ሥራ አስኪያጅ ስለነበርኩ ብቻ በክስ ለተጠየቀው ገንዘብ ኃላፊ ልሆን አይገባም በማለት ክሱ እንዲሰረዝላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ መቃወሚያዎቹን ውድቅ ካደረገ በኋላ ተከሣሽ በሕግና በንግድ ልማድ አግባብ መሠረት የማኅበሩን ሂሣብ የመያዝና የሂሣብ መዛግብት ሪኮርድ የማስቀመጥ ግዴታ እንዳለባቸውና የሥራ አስኪያጅነት ኃላፊነታቸውን በትጋትና በጥንቃቄ መሥራት እንዳለባቸው በመመስረቻ ጽሁፉና በንግድ ሕጉ ላይ የተመለከተውን ግዴታቸውን ባለመወጣት የማኅበሩን ንብረት ለግል ጥቅማቸው አውለውም ሆነ በሌላ መልኩ አለአግባብ እንዲበላክን አድርገዋል ስለዚህ በን/ሕ/ቁ 530 መሠረት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ናቸው በማለት ተከሣሾች ብር 300,000 /ሦስት መቶ ሺህ/ ገንዘብ ገቢ ተደርጓል ከተባለበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የሥር አንደኛ ተከሣሽም በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 32488 ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ በሁለቱም መዝገቦች የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 31907 በሰጠው ውሣኔ በዚህ መዝገብ አንደኛ ተከሣሽ የነበሩት ደግሞ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 32488 በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅር በመሰኘት በመ/ቁ 40866 የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም በሁለቱም መዝገቦች አመልቾች ኃለፊ የመባላቸውንና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦችን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት በሁለቱም መዝገቦች ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ በሁለቱም መዝገቦች የቀረበው ጉዳይና ተከራካሪዎቹም ተመሣሣይ በመሆናቸው ችሎቱ ሁለቱን መዝገቦች አጣምሮ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪዎች ክስ የመሠረቱት ከሥር ተከሣሽ ጋር በመሆን “ፈታሄ ቴክኒካል ኢንኮርፖሬትድ /ኢትዮጵያ/ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር” የተባለ የንግድ ድርጅት ለመመስረት በመስማማት እያንዳንዳቸው ብር 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) የሚወጣ እጣ ለመግዛት ገንዘብ አዋጥተው የነበረ ቢሆንም የማኅበሩ ሥራ አስኪያጆች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ባለመወጣት ገንዘቡን ስላባከኑና ድርጅቱ ስለፈረሰ ገንዘቡን እንዲከፍሉ ነው፡፡ ተጠሪዎች ድርሻቸውን ብር 300,000(ሦስት መቶ ሺህ) ስለማዋጣታቸው በጋዜጣ ማስታወቂያ ከመገለጹም በተጨማሪ የሥር ፍ/ቤት የማኅበሩ ሂሣብ በባለሙያ ተጣርቶ ከቀረበው ሪፖርት ተጠሪዎች ገንዘብ ማዋጣታቸውን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከክርክሩ ሂደት የሥር አንደኛ ተከሣሽ የነበሩት የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ እንደነበሩና እሳቸውም በነበራቸው ስልጣን በዚህ መዝገብ አመልካች ለሆኑት ውክልና ሰጥተዋቸው አመልካችዋ በውክልና ማኅበሩን ሊያስተዳድሩ የነበሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሥራ አስኪያጆች ማኅበሩን ሲያስተዳድሩ በሰሩት ሥራ ኃላፊ የሚሆኑበትን የሕግ አግባብ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተከሾች ሲያስተዳድሩት የነበረው ማኅበር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሲሆን የዚህ ማኅበር ሥራ አስኪያጆች ያለባቸው ኃላፊነትም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 530 ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት በንግድ ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ወይም የማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብ በመጣስም ቢሆን በሥራ አስኪያጅነታቸው በሰሯቸው ጥፋቶችም ስህተቶችም ቢሆን በማኅበሩና በ3ኛ ወገኖች ፊት በየራሳቸው ወይም በአንድነት ሳይከፋፈል እንደ ነገሩ ሁኔታ ኃላፊዎች እንደሆኑ ያመለክታል በተያዘው ጉዳይ የሥር ተከሣሾች ማኅበሩን በሥራ አስኪያጅነት በጋራ ሲመሩ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የማኅበሩን ሂሣብ የሰሩት የሂሣብ ባለሙያዎች የማኅበር ሂሣብ መርምረው ማኅበሩ የገቢና ወጪ ሰነድ እንደሌለው፣ አዲት ተደርጎ እንደማያውቅ፣ ማኅበሩ ገንዘብ የሚያስቀምጥበት የባንክ ሂሣብ እንደሌለው አወጣሁ ለሚላቸው ወጪዎችም በሕግ አግባብ የወጪ ሰነዶች እንደሌሉት፣ ማኅበሩ ምንም ሥራ ያልጀመረ ቢሆንም ለደመወዝ፣ለቤት ኪራይና ለአበል የካፒታሉን 88.38% ወጪ ማድረጉንና በአጠቃላይ የማኅበሩ አሰራር ትክክል እንዳልነበረ አብራርቷል፡፡ ተጠሪዎች በሥራ አስኪያጅነታቸው የማኅበሩን ሥራ አካሄድ፣ የማኅበሩን የሂሣብ አሰራር እና አያያዝ ሌሎችንም የማኅበሩን ሥራዎች ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ በትጋትና በቅን ልቦና መስራት በሕግም በመተዳደሪያ ደንባቸውም የተጣለባቸው ኃላፊነት ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ግን ሥራ አስኪያጆቹ ማኅበሩ ሥራ ሳይጀምር የካፒታሉን 88.38% ለቤት ኪራይ፣ ለደመወዝና ለአበል ወጪ በማድረግ፣ በአጠቃላይ የማኅበሩ አሰራር ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጎደለውና በማንኛውም መለኪያ ትክክል ባልሆነ መንገድ ሲሰሩ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የሥር ተከሳሽ ሥራ አስኪያጆች ሆነው ሲሰሩ በሰሩት ጥፋትም ሆነ ስህተት በግል ሆነ በአንድነት ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ የንግድ ሕጉ ቁጥር 580 ስለሚያስረዳ የሥር ፍ/ቤት በዚህ መዝገብና በመ/ቁ. 40866 አመልካቾች ኃላፊነት አለባቸው በማለት ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች ለአመልካቾች ከድርሻቸው መጠን ካዋጡት ገንዘብ ሌላ ተጨማሪ ገንዘብ ለሁለቱ አመልካቾች መስጠታቸውን በመግለጽ ገንዘቡ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ቢሆንም ለዚህ ያቀረቡ በቂ ማስረጃ ባለመኖሩ አመልካቾቹ ማዋጣታቸው የተረጋገጠው ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ/ ብቻ ገንዘቡ ከተዋጣበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ መወሰኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት በሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 44250 ግንቦት 27 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31907 እና 32488 ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ከመ/ቁጥር 40866 ጋር ይያያዝ
4. በዚህ መዝገብ ጥር 7 ቀን 2001 ዓ.ም. የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ትዕዛዙ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አእምሯአዊ ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44520

ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት - ጠበቃ አርአያ ጌታሁን - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዶ/ር ጌታሁን ሽብሩ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁ. 410/96 በተመተላለፍ የመብት ጥሰት ተፈጽሞአል በሚል የቀረበውን የካሣ ጥያቄ መነሻ በማድረግ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ከሣስሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ክሱም እንዳየነው ርቱዐ ኢምላክ በሚል የብዕር ስም "የተሰበሩ ክንፎች" በሚል ርዕስ ትርጉም መጽሐፍ አዘጋጅቶ መስከረም 24 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገ ውል ተከሣሽ(የአሁኑ አመልካች) 5000(አምስት ሺህ) ኮፒ እንዲያትምለት መስጠቱን፣ተከሣሽም በስምምነቱ መሰረት የህትመቱን ጠቅላላ ዋጋ ግማሽ ብር 14,929.50(አስራ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር ከሃምሣ ሣንቲም) ተቀብሎ ህትመቱን በሦስት የስራ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ለማስረከብ ግዴታ መግባቱን፣ነገር ግን ስራው ተጠናቆ ተጠሪ ከመረከቡ በፊት "የተሰበሩ ክንፎች" በሚል ስያሜ የታተመው መጽሐፍ ቅጂዎች በሌሎች ሰዎች (ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሣሽ ተብለው በክሱ ተመዝግበው በነበሩት) አማካይነት በገበያ ውስጥ ሲሸጥ መገኘቱን ይገልፃል፡፡ በመጨረሻም ቁሳዊ እና የሞራል ጉዳት ደርሶብኛል በማለት በጠቅላላው ብር 160,079.50 (መቶ ስልሳ ሺህ ሰባ ዘጠኝ ብር ከአምሳ ሳንቲም)እንዲከፈል እንዲወሰን ይጠይቃል፡፡

አመልካች እና ተጣምረው የተከሰሱት ሰዎችም የየበኩላቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማንሳት ክሱ በነጻ ይሰናበቱ ዘንድ የተከራከሩ ሲሆን፣ፍ/ቤቱም ክርክሩንና ክርክሩን ለመደገፍ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ፣መጽሐፉን ሲሸጡ ተገኝተዋል የተባሉትን ተከሣሾች በነዓ በመልቀቅ አመልካች ላይ ለደረሰው የመብት ጥሰት ተጠያቂ ነው ብሎአል፡፡ በዚህ መሰረትም ተጠሪ በቁሳዊ እና በሞራል ረገድ ለደረሰበት ጉዳት ካሣ እንዲከፈለው ወስኖአል፡፡ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም አመልካች መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀጽ 8 መሰረት የሞራል ካሣ የማግኘት መብት ተፈፃሚ የሚሆነው ለስራው ተርጓሚ ጭምር ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡

ተጠሪ መጽሐፉን ተርጉሞ እንዲታተምለት ለአመልካች በውል ስለመስጠቱ አከራካሪ አይደለም፡፡ መጽሐፉ ታትሞ ለተጠሪ ከመድረሱ በፊት በገበያ ሲሸጥ ስለመገኘቱም በስር ፍ/ቤቶች በማስረጃ ተረጋግጦአል፡፡ በሰበር ችሎቱ ከቀረበው አቤቱታ ዋነኛ መሰረት ሆኖ በአመልካች የተጠቀሰው የመከራከሪያ ነጥብ ተጠሪ የመጽሐፉ ደራሲ ሳይሆን፣ተርጓሚ በመሆኑ እንደ ድርሰቱ አመንጪ ተቆጥሮ የሞራልና የቁሳዊ ጉዳት ካሣ ሊወሰንለት አይችልም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ የቅጅ መብትም እንደድርሰት መብት እውቅና ያገኘና ጥበቃ የተደረገለት በመሆኑ የሞራልም ሆነ የቁሳዊ ጉዳት ካሣ እንዳገኝ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የመከላከያ ክርክሩን አሰምቶአል፡፡

ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ሕግ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁ.410/96 ነው፡፡ ይህን አዋጅ ማውጣት ያስፈለገው የአንድን ሃገር ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ልማትን በማፋጠን ረገድ ትልቅ ሚና የሚጫወቱት የስነ ጽሁፍ፣የኪነጥበብ እና ተመሣሣይ የፈጠራ ስራዎች የሚበረታቱበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስችል በመታመኑ እንደሆነ ከአዋጁ መግቢያ አጠቃላይ መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አዋጅ የሕግ እውቅና ሊሰጣቸውና ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል ከተባሉት የፈጠራ ስራዎች አንዱ የስነ ጽሑፍ ስራ ሲሆን፣ይህም ከድርሰት ስራዎች ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ነጥብም ድርሰትን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በተጠሪ የተሰራው የትርጉም ስራ በሕጉ እውቅና የተሰጠውና ጥበቃ የሚደረግለት ስለመሆን አለመሆኑ በተመለከተ መልስ ሊገኝ የሚችለው የአዋጁን ዝርዝር ድንጋጌዎች በመመልከት ነው፡፡

አመልካች የተጠሪ ስራ በሕጉ ጥበቃ የተደረገለት አይደለም በማለት የተከራከረው ተጠሪው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተሰራውን የድርሰት ስራ ወደ አማርኛ ቋንቋ መለስ(ተረጉመ) እንጂ ስራውን (ድርሰቱን) አላመነጨም ከሚል መነሻ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው የአንድ ስራ አመንጪ ወይም የፈጠራ ባለቤት ነው ሊባል የሚችለው ምን አይነት ስራ ሰርቶ ሲገኝ ነው? የሚለው ነጥብ አግባብነት ካለው የአዋጁ ድንጋጌ ጋር አገናዝቦ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ “የሥራ አመንጪ” የሚለው ሐረግ በአዋጁ አንቀጽ 2/2/ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ትርጓሜ መሰረት የስራ አመንጪ የሚባለው የአንድን የአእምሮ ውጤት የሆነን ስራ የፈጠረ ማንኛውም ግለሰብ ነው፡፡ እዚህ ላይ ግልጽ ሆኖ የሚታየው ስራው የአእምሮ ውጤት መሆን እንዳለበትና ይህ ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥም በሕግ እውቅና የሚያገኝና ጥበቃም የሚደረግለት እንደሆነ ነው፡፡ ጥበቃ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎችም በአዋጁ አንቀጽ 6 የተቀመጡ ሲሆን፣ለያዝነው ጉዳይ አግባብነት ያለው ንኡስ አንቀጽ/1/ ማንኛውም የስራ አመንጪ የስራው አላማና የጥራት ደረጃ ግምት ውስጥ ሳይገባ ስራውን በማውጣቱ ምክንያት ብቻ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ጥበቃ እንደሚያገኝ ያመለክታል፡፡ በእርግጥ ስራው ጥበቃ ያገኝ ዘንድ ወጥ(ኦርጂናል) ሊሆን ይገባል፡፡ እንደዚሁም የተቀረጸ ወይም ግዙፍነት ያገኘ መሆን ይኖርበታል፡፡ በማለትም ሕጉ ደንግጓል፡፡

ተጠሪ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተሰራውን ድርሰት(መጽሐፍ) ወደ አማርኛ ቋንቋ ለመተርጐም ሲነሳ ዓላማ ያደረገው መጽሐፉ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ በሆነ ህብረተሰብ ዘንድ እንዲታወቅና እንዲነበብለት እንደሆነ መገመቱ አይከብድም፡፡ ቋንቋ የተናጋሪውን ህብረተሰብ ባህልና ወግ መሰረት ያደረገ ወይም ከእነዚህ ጋር ከፍተኛ ትስስር ያለው በመሆኑ በአንድ ቋንቋ የተፃፈን መጽሐፍ(ድርሰት) ወደ ሌላ ቋንቋ ሲተረጉም ባህልና ወጉም ግምት ውስጥ እየገባ እንደሆነ ወይም ሊሆን እንደሚገባም መገመት ይቻላል፡፡ ተጠሪ የሰራው ስራ መታየት ያለበትም ከዚህ አንፃር ነው፡፡ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈውን መጽሐፍ ወደ አማርኛ ቋንቋ ሲመልስ(ሲተረጉም) የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪው (አንባቢው) የድርሰቱን ባህርይ በትክክል እንዲገባውና ከራሱ ባህልና ወጉ ጋር አገናዝቦ እንዲያጣጥመው በሚያስችለው ሁኔታ አመቻችቶ እንደሚያዘጋጀው ይታወቃል፡፡ ይህን ስራ የሚሰራው አእምሮው በፈቀደለት መጠን እውቀቱን በመጠቀም ነው፡፡ በአጭሩ የትርጉም ስራው የአእምሮው ጭማቂ ወይም ውጤት የታከለበት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ መልክ ያለው ስራም በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈ(ከእንግሊዝኛው የተለየ) መጽሐፍ በመሆኑ በአንቀጽ 6/1/ እንደተደነገገው ወጥ(ኦርጅናል) የሆነና ግዙፍነትም ያገኘ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የስራው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመንጪ አይደለምና ጥበቃ አይደረግለትም በማለት አመልካች ያቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ የሕግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ሕጉን መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ስንመለከትም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል ለማለት አልቻልንም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 54181 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39233 መጋቢት 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንተዋል፡፡

2. አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

3. ተጠሪ የሞራልና የቁሳዊ ጉዳት ካሣ ሊያገኝ ይገባል መባሉ ተገቢ ነው ብለናል፡፡

4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 53459

ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ኂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ማሞ ገ/ማሪያም

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድና የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ችሎት የሰጡት ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ክስ በቀነ ቀጠሮ እየቀረበ የሚከራከር ስለመሆኑ ዋስትና ይሆን ዘንድ በሞዴል 85 በደረሰኝ ቁጥር 109993 ያስያዘው ብር 200/ሁለት መቶ/ ብር ነው፡፡ አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58128 ታህሣሥ 9 ቀን 2002 ዓ.ም በነፃ የተሰናበት መሆኑን በመግለጽ ያስያዘው ገንዘብ እንዲመለስለት ሲጠይቅ ገንዘብ ያስያዝክበት ዋናውን ደረሰኝ ካላቀረብክ አይመለስልህም በማለት የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ጥያቄ በድምጽ ብልጫ ውድቅ አድርጐታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለተጠሪ ያቀረበ ቢሆንም የሰበር ችሎቱ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡ አመልካች በተከሰሰከበት ወንጀል በነፃ የተለቀቅሁ መሆኑን በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በማቅረብ አስረድቻለሁ፡፡ ገንዘብ ያስያዝኩበት ደረሰኝ ስለጠፋብኝ ኮፒውን ይዜ በመቅረብ እንዲከፈለኝ ያቀረብኩት ጥያቄ የበታች ፍርድ ቤቶች አለመቀበላቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካች ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ቀርቦበት የነበረውን የወንጀል ክስ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ቀነ ቀጠሮ እያከበረ የሚቀርብና የሚከታተል ለመሆኑ ዋስትና ይሆን ዘንድ ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ በሞዴል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰማኒያ አምስት እስይዞ ጉዳዩን ሲከታተል የነበረ መሆኑንና ከተከሰሰበትም ወንጀል በነፃ የተሰናበት መሆኑን የመንግስት ሰነድ የሆኑት የፍርድ ቤት መዝገቦችና በውሣኔው ግልባጭ በማየትና በማጣራት ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡

አመልካች ያስያዘው ገንዘብ አይመለስልህም የተባለው ገንዘቡን ገቢ ያደረገበት ዋናው ደረሰኝ ሣይሆን የዋናው ኮፒ ይዞ በመቅረቡ ነው፡፡ በአርግጥ በሰነድ የተገለፀን ፍሬ ጉዳይ ለማስረዳት ማቅረብ የሚገባው ዋናው ሰነድ መሆን እንዳለበት (Best evidence rule) መሰረታዊ መርህ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም ዋናው ሰነድ ሊገኝ በማይችልበት ሁኔታ የዋናው ሰነድ ኮፒ/Secondary evidence/ በማቅረብ ጉዳዩን ከማስረዳት የማይከለክል መሆኑን በስፋት ተቀባይነት ያላቸውን የማስረጃ ሕግ መርሆች በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ገንዘቡን ያስያዘው አመልካች ስለመሆኑ አመልካች ይዞት በቀረበው የደረሰኝ ኮፒ ብቻ ሣይሆን በወንጀል ተከስሶ ጉዳዩ ከታየበት የጊዜ ቀጠሮ መዝገቦችና ክርክሩን ተከታትሎ በነፃ ከተለቀቀበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል መዝገብ ጋር በአንድነት አጣምሮ በመመዘን ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች በአደራ በሞዴል 85 ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ ያስያዘ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ እያለ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ያቀረብከው ማስረጃ ዋናውን ደረሰኝ ሣይሆን ፎቶ ኮፒውን ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎት የሰጡት ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በሞደል 85 በደረሰኝ ቁጥር 109993 ያስያዙት የዋስትና ገንዘብ ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ ይመለስላቸው ብለናል፡፡

ይኸ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43781

ሐምሌ 14 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐ/ህግ ወርቅነህ

ዓለማየሁና ታደለ ተስፋዬ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዳንኤል መኮንን አልቀረቡም

በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱታ ተጠሪ የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት በሕግ አያስጠይቀውም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ሲል አመልካች ይኸው እንዲታረም በመጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ ተጠሪው ነሐሴ 22 ቀን 1996 ዓ.ም መጠኑ 46.96(አርባ ስድስት ነጥብ ዘጠና ስድስት) ኪ.ግ የሆነ የሀገር ውስጥ ጥፍጥፍ ወርቅ በሕገወጥ መንገድ ከአገር ለማስወጣት ወደ ጅቡቲ በማጓዝ ላይ እያለ በክትትል በወለንጪቲ እና በመተሐራ መካከል በመያዙ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 368/95 እንደተሻሻለው አንቀጽ 2(28) እና አንቀጽ 66/2/ በመተላለፍ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ክስ የቀረበበት ሲሆን በአማራጭ የገንዘብ እና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59/2/ለ ሥር የተጠቀሰውንና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለወርቅ ግብይት ቁጥጥር ያወጣውን መመሪያ ቁጥር CTG/001/97 አንቀጽ 1 እና 2 በመተላለፍ በሕገ-ወጥ መንገድ ወርቅ ሲያዘዋውር በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከባድ ወንጀል ፈጽሟል በማለት አመልካች ተጠሪ ላይ ክስ መስርቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የመጀመሪያውን ክስ በተመለከተ ተጠሪ በመከላከያ ማስረጃ አስተባብለዋል በማለት ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡ በአማራጭ የቀረበውን ክስ በተመለከተ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት በክሱ መሠረት ጥፋተኛ ነው ሲል ፈርዷል፡፡ ቅጣቱንም በተመለከተ ጥፋተኛ በተባለበት አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59/2 (ለ) መሠረት በአምስት ዓመት (5) ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ብር አንድ ሚሊዮን የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍል የተያዘው ወርቅ በመንግሥት እንዲወረስ እና ለሦስት (3) ዓመት ጊዜ ምስክር ከመሆን መምረጥ እና ከመመረጥ መብት ተገድቧል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ላይ ተጠሪ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ 1ኛው ክስ የኮንትሮባንድ ወንጀል ስለመፈጸሙ የዐ/ሕግ ማስረጃ አላረጋገጠም በማለት ሲወስን በአማራጭ የቀረበውን ክስ በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59/2/(ለ) ላይ ወርቅን አስመልክቶ ያስቀመጠው ክልከላ የለም፤ መመሪያ ቁጥር 001/97 ሕግ ሆኖ አስገዳጅነት እንዲኖረው በአዋጅ ቁጥር 3/87 እና 14/88 መሠረት በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ያልወጣ እንዲሁም በአማርኛ ቋንቋ ያልተፃፈ በመሆኑ ሕግ ሆኖ ቅጣት ሊጥል አይችልም በወንጀል ተጠያቂ ሊያሰኝ አይችልም በሚል ምክንያት ተጠሪው እንዲከለከል ብይን መስጠቱ ተገቢ አልነበረም ሲል በውሳኔው ሐተታ ገልጿል፡፡

በፍሬ ነገር ረገድም ወርቁን ወደ ጅቡቲ ሳይሆን ወደ ጎንደር ያጓጓዘ መሆኑን በመከላከያ ማስረጃ በተሻለ ሁኔታ አረጋግጧል በሚል የሥር ፍ/ቤት ጥፋተኛ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት እንደለሌው ወስኗል፡፡ ባጠቃላይ በሕግም ሆነ በፍሬነገር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ ስሕተት ነው በማለት ተጠሪ(ተከሳሽ) በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ጠቅላይ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ተጠሪ በአማራጭ የተከሰሰበት ድርጊት መመሪያው በሕግ መልክ ስላልወጣ የወንጀል ክልከላ ተደርጓል ሊባል አይችልም በማለት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሕገወጥ የወርቅ ዝውውር አስመልክቶ አዋጅ ቁጥር 52/85 እና 83/86 መሠረት አድርጐ የወጣው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር CTG/001/97 ተፈጻሚነት ያለው ስለመሆኑ መመሪያው በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ያለመውጣቱ ሕጋዊነቱን እንደማያሳጣው፣ መመሪያው በአማርኛ ቋንቋ ያልተፃፈው ከብሔራዊ ባንክ የሥራ ባህርይ የተነሳ ስለመሆኑ እንዲሁም ወንጀል ድርጊቱ የቅጣት አወሳሰን አዋጁ ወይም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 357 እና 358 ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደሚገባ በመጥቀስ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡

የሰበር ችሎቱም የቀረበውን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ በዚህ ጉዳይ በአማራጭ የቀረበውን ክስ አስመልክቶ በአዋጅ መሠረት የወጣው መመሪያ በአማርኛ ተተርጉሞ ያለመገኘቱ ሁኔታ በጉዳዩ ላይ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? መመሪያው ተፈጻሚ ነው ከተባለ ተፈፀመ የተባለውን ድርጊት ሊሸፍን የሚችል ነው ወይስ አይደለም? ይህም ቢታለፍ የገንዘብ እና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 በ1949 ዓ.ም ከወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 357 እና 358 አንፃር ሲታይ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ የተጠሪ ጠበቃ ህዳር 23 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቀርበው የግራ ቀኙ ክርክርም በችሎቱ ተሰምቷል፡፡

በተጠሪ ጠበቃ በኩል የተነሱት የመከራከሪያ ነጥቦች ሥር ፍ/ቤት የባንክ ሥራ ሰርቷል ተብሎ ክስ ያልቀረበ ስለመሆኑ የኮንትሮባንድ ወንጀል ነው ተብሎ የቀረበው ክስ ውድቅ ስለመደረጉ በአማራጭ የቀረበው ክስም አዋጅ እና መመሪያ ከመጥቀስ ውጪ ድርጊቱን በተመለከተ ጥፍጥፍ ወርቅ አዘዋውሯል እንዳልተባለ መመሪያው ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደማይገባ እንዲሁም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 357 እና 358 መመሪያው ሕጋዊነት የሌለው በመሆኑ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚሁ አግባብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና አመልክተዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍሲል በአጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከፍሲል እንደተጠቀሰው በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር የተያዘው የመጀመሪያው ጭብጥ በብሔራዊ ባንክ የወጣው መመሪያ ቁጥር ሲቲጂ/001/97 በአማርኛ ተተርጉሞ ያለመውጣቱ በጉዳዩ ላይ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለውን አስቀድመን እንመረምራለን፡፡ ለዚህ ጭብጥ ምላሽ ለማግኘት የሕጎች ተዋረድ እና አወጣጥ በመጠኑም ቢሆን መዳሰስ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመርህ ደረጃ ሕግ የማውጣት ሥልጣን በሥልጣን ክፍፍል መርህ መሠረት የሕግ አውጪው አካል ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሕግ አውጪው የመንግስት አካል የሚወጡ ሕጎች ቀዳማዊ /primary legislations/ ተብለው የሚታወቁ ሲሆን ሌሎቹ እንደአስፈላጊነታቸው አግባብ ባለው አካል የሚወጡ የበታች ሕጎች (subsidiary legislations) ተብለው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ሕግ አውጪው የመንግሥት አካል በተለያዩ ቴክኒካዊና ማህበራዊ ምክንያቶች ቀዳሚውን ሕግ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ዝርዝር ሕጎች ያስፈልጋሉ ብሎ ባመነ ጊዜ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው አካል የበታች ሕጎችን እንዲያወጣ ሥልጣን ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡ ይህ አሰራር በሕግም በምክንያትም የተደገፈ እና የዳበረ ልምድ ስለመሆኑ ግልፅነው፡፡ አሁን በተግባር ሥራ ላይ ያለው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 14/88 አንቀጽ 2(1) እንደሚያመለክተው ሕግ የሚላቸው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሲሆኑ እነዚህ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሲወጡ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ መውጣት እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ከፍ ሲል እንደተመለከትነው በሌሎች የመንግሥት አካላት የሚወጡት የበታች ሕጎች ማለትም ደንቦች እና መመሪያዎች በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጡ የሚያስገድድ ድንጋጌ በዚህ አዋጅ አልተመለከተም፡፡ ከዚህም ሌላ ከመነሻውም ይህ አዋጅ ቁ.14/88 የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት የሚመለከት እንደመሆኑ በሌሎች አካላት የሚወጣን የበታች ሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት አስመልክቶ ምላሽ የሰጥ አይደለም፡፡ በርግጥ በዚህ ረገድ የሌሎች ሀገሮች ልምድ ሲታይ በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚወጡት የበታች ሕጎች ሥነ ሥርዓታዊ ጉዳዮች የሚወሰነው የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት ሕግ በሚሰኝ የሕግ ዓይነት መሆኑን የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በሀገራችን የወጣ ሕግ የለም፡፡ ይህም በመሆኑ በየአስፈጻሚ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚወጡ የበታች ሕጎች እንዲታተሙ እና በተወሰነ ቋንቋዎች እንዲፃፉ የሚያስገድድ ሕግ የለንም፡፡ ከዚህም የተነሳ በርካታ የበታች ሕጎች በተለያዩ ተቋማት በተለያየ መልክ ወጥተው በተግባር ላይ ውለው እናገኛለን፡፡ በተለይም መመሪያ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ሲወጣ አልተስተዋለም፡፡

በተግባር ያለው እውነት ይህ መሆኑን የምንረዳው ከመሆኑ አንፃር አሁን በእጃችን ያለው ጉዳይ ስንመለከት ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ ቁጥር ሲቲጂ/001/97 በአማርኛ ቋንቋ አልተፃፈም በነጋሪት ጋዜጣም አልታተመም ሲሉ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ይህ እንዲደረግ የሚያስገድድ ግልፅ ሕግ በሌለበት ሁኔታ እና በተግባር ያለውን እውነታ ባለማገናዘብ በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይህ አካሄድም በተግባር ሥራ ላይ ያሉትን በርካታ መመሪያዎች ተፈጻሚነት ዋጋ የሚያሳጣ ነውና፡፡ ይልቁንም ለዚህ መመሪያ መውጣት ዋና ወይም እናት ሕግ የሆነው አዋጅ ቁጥር 83/86 ለባንኩ ሥልጣን ስለመስጠቱ መመሪያው በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ለማስፈጸም በሚያስችል መልኩ የተቀረፀና የሚጣጣም ስለመሆኑ በማገናዘብ ውጤት በሚያስገኝ እና የእናት ሕግ ዓላማና ግብ ለማስፈጸም በሚያስችል አግባብ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ይገባል የሚል እምነት አለን፡፡ ስለሆነም መመሪያው በአማርኛ ቋንቋ አልተፃፈም በሚል ምክንያት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተያዘው ጭብጥ የመመሪያውን ተፈጻሚነት የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶቹ መመሪያው የወንጀል ድንጋጌ የለውምና ተፈጻሚነት የለውም በማለት የመ/ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽረዋል፡፡ በዚህ መሠረት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ምክንያት አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 39/2/ እና ተያያዥ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር ተገቢ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ባንኩ ተጠቃሹን መመሪያ ያወጣው በአዋጁ አንቀጽ 39/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ስለመሆኑ የመመሪያው መግቢያ ዐረፍተነገር ያመለክታል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 39/2/ የተመለከተው ድንጋጌ የሚያስገነዝበን ስለወርቅና ስለውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ባንኩ መመሪያ ማውጣት ስለመቻሉ ነው፡፡ ከዚህ ድንጋጌ እና ከአዋጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጠቃላይ መንፈስ መረዳት የሚቻለው የገንዘብ እና የወርቅ ሥራ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ያለውን አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት በመመልከት በተለየ ሁኔታ ሥርዓት እንዲበጅለት እና ቁጥጥር እንዲደረግበት የታሰበ ስለመሆኑ ነው፡፡ ይህንንም ለማሳለጥ ይቻል ዘንድ በአዋጁ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ባንኩ በገርገር መመሪያ ሊወሰን እንዲችል ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም መመሪያው በአንቀጽ 1 እና 2 ስለወርቅ ንግድና ዝውውር መያዝ ወይም ማኖር የባንኩ ፈቃድ አስፈላጊነት እና የመጠኑም ገደብ አስመልክቶ ድንጋጌ ይዟል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሲጣስ በየትኛው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጠው ደግሞ ራሱ ዋናው አዋጅ ሆኖ እናገኛለን፡፡ ይህም አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሸ) ላይ እንደተመለከተው አዋጁን ወይም አዋጁን ተከትሎ የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የተላለፈ ሰው የሚቀጣበትን አግባብ ደንግጓል፡፡ ስለሆነም የወንጀል ተጠያቂነትን አስመልክቶ የተደነገገው በአዋጁ መሠረት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከዚህ አንፃር በመመሪያው የተመለከተውን ገደብ በመተላለፍ ለተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ተጠያቂነት በአዋጁ በተመለከተው አግባብ የሚፈፀም በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ላይም መመሪያው ተፈጻሚነት አለው ብለናል፡፡

መመሪያው ተፈጻሚነት አለው ካልን በኋላ በተጠሪ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት በዚህ መመሪያ የሚሸፈን ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ በተጠሪ ላይ ሥር ፍ/ቤት በአማራጭ የቀረበው ክስ በባንኩ የወጣውን መመሪያ በመተላለፍ ያለባንኩ ፈቃድ ከአሥር(10) አውንስ በላይ ወርቅ ሲያዘዋውር ተገኝቷል የሚል ሲሆን ተጠሪም በክሱ የተጠቀሰውን 46.96 ኪ.ግ ወርቅ ይዞ መገኘቱን አልካደም፡፡ ይልቁንም ጎንደር ከተማ ለሚገኝ ደንበኛው የሸጠ መሆኑንና ወደዚያው እንዲጓጓዝ ማድረጉን የእምነት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም በፍሬ ነገር ረገድ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠው ባንኩ ካወጣው መመሪያ ውጭ ያለባንኩ ፈቃድ እውቅና ከፍተኛ ዋጋ ያለው የወርቅ መጠን ማዘዋወሩና ስለመያዙ ነው፡፡ ይህ ድርጊቱ በመመሪያው አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተውን ክልከላ የተላለፈ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ ስለዚህም የተጠሪ ድርጊት በመመሪያው የሚሸፈንና የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ሆኖ አግኝተናል፡፡

ተጠሪ የፈፀመው ድርጊት በአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 39/2/ ለባንኩ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የወጣውን መመሪያ ቁጥር ሲቲጂ 001/97 አንቀጽ 1 እና 2 የተላለፈ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 59/1//ሸ/ መሠረት ጥፋተኛ የሚያሰኝና ቅጣት የሚያስከትል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የቅጣት አወሳሰን በተመለከተ በዐ/ህጉ በሥር ፍ/ቤት በቀረበው ክስ እና የመ/ደረጃ ፍ/ቤት ከወንጀሉ አፈጻጸም ባህሪይ እና ከተፈፀመው ድርጊት ዓላማና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ከደረሰ ጉዳት አንፃር በአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(2)(ለ) ሥር በተመለከተው አግባብ የተወሰነው ጥፋተኝነት እና ቅጣት ዓይነትና መጠን መሠረታዊ የሕግ ጉድለት አለው ለማለት የሚያስችል የሕግ ምክንያት ስላላገኘንበት ባለበት እንዲፀና ብለናል፡፡

የተጠሪ ጥፋት እና የቅጣት አወሳሰን በአዋጅ ቁ.83/86 እና በመመሪያው የተሸፈነ መሆኑን ከፍሲል ስለተመለከትን ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ /የ1949 ዓ.ም ወ/መ/ሕግ/ አንቀጽ 357 እና 358 አንፃር ለመመርመር የተያዘው ጭብጥ መመርመር አስፈላጊ ስላልሆነ አልፈነዋል፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ በአማራጭ በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ አይደለም ሲሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከፍሲል በዝርዝር በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በዚሁ መሠረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/ወ/መ/ቁ 56547 ሐምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ቁ 32664 ህዳር 26 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)ሀ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ 46204 ግንቦት 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ቅጣት ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ተጠሪ ላይ የተሰጠው የእስራት ቅጣት በዚህ ወንጀል እስከ አሁን የታሰረው ታሳቢ ተደርጐ ቀሪው እንዲፈፀምበት ብለናል፡፡ የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪን ይዞ ለማረሚያ ቤት እንዲያስረክብ እና ማረሚያ ቤቱም ይህንኑ እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የገንዘብ መቀጮ እና የሚወረሰውን ንብረት በተመለከተ አመልካች ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42239

ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
ሓጎስ ወልዱ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
በላቸው አንሺሶ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሁልጣን አባተማም

አመልካች፡-ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃላ.የተ. የግል ኩባንያ
ተጠሪ፡- ዳኒ ድሪሊንግ ኃላ.የተ. የግል ኩባንያ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወርቅ ማዕድን ፍለጋ የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ውል ስምምነትን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ነው። በአመልካችና በተጠሪ የተቋቋመው የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ/ም በሠጠው ውሣኔ አመልካች ለተጠሪ ብር 579,450.35(አምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር ከሠላሣ አምስት ሣንቲም) እንዲከፍል ወስኗል። ይህንኑ ውሳኔ አመልካች በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 351 መሠረት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዘባታል። የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ለማስቀየር ነው።

የአመልካች ጠበቃ ታኅሣስ 17 ቀን 2001 ዓ/ም በዓፉት አራት ገፅ የሠበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሣኔ በፍሬ ነገር እና በሕግ ረገድ ተፈፀሙ የሚሉባቸውን ስህተቶች ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ በራሱ አነሳሽነት ውሉን ባቋረጠበትና ዉሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ስራ ለፈታበት ሰላሳ አምስት ቀናት ብር 700,000. 00 ቅጣት አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ የውልም ሆነ የሕግ መሠረት የሌለው መሆኑን፣የግልግል ጉባኤ ዳኝነቱን የመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 317(1) ስር በተመለከተው ሣይሆን ከዚህ ውጪ ተገቢውን ጭብጥ ሣይይዝ መሆኑን፣ውሣኔው በፍትሐብሔር ሕጉ የተመለከቱትን የውል አተረጓጎም ድንጋጌዎችን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑን፣ተጠሪ በወቅቱ ማስጠንቀቂያ ባልሰጠበት ሁኔታም ቅጣት መጠየቅ እንደማይችል፣ተጠሪ ውሉ አልተፈፀመልኝም የሚል እንደመሆኑ መጠን ሊደርስ የሚችለውን ኪሣራ ለመቀነስ በሕጉ ግዴታ ያለበት ሲሆን ጉዳት ሳይደርስበት ቅጣት እንዲከፈለው መጠየቁ ያላግባብ መሆኑንና በውሉ ላይ ዓይነተኛ መጣስ የሌለ ስለሆነ ውል እንዲፈርስ ዳኞች ውሣኔ ማሳለፍ እንደማይችሉ፣እንዲሁም በጉዳዩ የተሠጠው ውሣኔ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በሚገባ ያልመዘነ መሆኑን በሰፊው በመዘርዘር የግልግል ዳኞችና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሣኔ በማስረጃ ምዘናም ሆነ በሕጉ አተረጓጎም እንዲሁም አፈጻጸም ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ ሊሻር ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ጠበቃው መጋቢት 01 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፈ አራት ገፅ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል። የመልሱ ይዘትም የጉባኤው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን 23-05-1998 ዓ/ም ግራ ቀኙ በፈፀሙት ውል የተስማሙ መሆኑን ገልፀው ለሠበር ችሎቱ የሠበር አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለሆነ በዚህ ምክንያት ችሎቱ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ እንዲያደርግ፣ይህን የሚያልፍ ከሆነም ለአቤቱታው መሠረት የሆኑት የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ክርክሮች ተቀባይነት የሌላቸው በመሆኑ ውድቅ ሊደረጉ ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው። የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው የሠበር ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት ሕገ-መንግስታዊ ሥልጣን ያለው መሆኑን በመዘርዘር የተጠሪ ጠበቃ መቃወሚያ የሕግ መሠረት የለውም በማለት የተቃወሙ ሲሆን ሌሎችን ነጥቦችን በተመለከተም የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር መጋቢት 18 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፉት የመልስ መልስ ማመልከቻ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልጉት አበይት ጭብጦች፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1ኛ/ ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሠረት አመልካች ቅሬታውን ለሠበር ችሎት ለማቅረብ ይችላል? ወይስ አይችልም?፣

2ኛ/ አመልካች ለሰላሳ አምስት ቀናት የጉዳት ካሳ ለተጠሪ እንዲከፈል ተብሎ የተወሰነው የውሳኔ ክፍል በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ውል መሰረት አመልካች ግዴታውን ስለአለመወጣቱ ተጠሪ አስረድቶ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ሲሆን ሌሎች ነጥቦች በዚሁ ጭብጥ ስር እልባት ሊያገኙ የሚችሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

<u>1.የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ</u>:- ይህን ጭብጥ ለመመለስ በአገራችን ውስጥ የሰበር ስርኣት እና ስለአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎች አላማና በሕጉ ያላቸውን ማእቀፍ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

የሰበር ስርዓት አይነተኛ አላማ ከሆኑት አንዱ በአንድ ሀገር ውስጥ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎም እና አፈጻጸም(Uniform interpretation and application of the law) መኖሩን ማረጋገጥ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሰበር ሥርዓት የሕግ የበላይነት ማረጋገጫ ዘዴ ነው ተብሎም ሊታሰብ የሚችል ነው፡፡ የሕግ የበላይነት በሰበር ሥርዓት ሊከበር ወይም ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ ጥራት፣ወጥነት ያለው ፍርድ/ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን በተሰጣቸው አካለት በሰጡት ውሳኔ ላይ የዳኝነት አካሉ በራሱ ዳኝነታዊ ቁጥጥር(Judicial Control) ሲኖረው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተመሳሳይ ጉዳዮች በተመሳሳይ መንገድና ሁኔታ ማየትን የፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓት የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የፍትሕ መሰረቱ ተመሳሳይ ጉዳዮችን በተመሳሳይ መንገድ ማስተናገድ ነው ተብሎም ይታሰባል፡፡ ይህ የሚተገበረውም አዋጆች፣ደንቦችና መመሪዎች እንዲሁም ፖሊሲዎች በትክክልና በወጥነት ሲተረጎሙና ሲፈጸሙ ነው፡፡ ወጥነትና ትክክለኛነት ያለው የሕጎች አተረጓጎምና አፈፃፀም መኖሩ የሚረጋገጠው ደግሞ በዳኝነት አካሉ በመጨረሻ ደረጃ በሚገኝ በሰበር ተቋም ነው፡፡

ሌላው ጉዳይ የሕጎች ወጥነት ያለው አተረጓጎምና አፈፃፀም መኖር የዜጎችን በሕግ ፊት እኩል የመሆን መብት የሚጠበቅ መሆኑ የሚታመን ሲሆን የዳኝነት አካሉ የዜጎችን በሕግ ፊት እኩል የመሆን መብት የማክበርና የማስከበር ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ደግሞ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 13(1)፣ 25 እና 85(1) ድንጋጌዎች ስር ከአሰፈረው ሁኔታ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የሰበር ሥርዓት ይህንኑ ግዴታ የዳኝነት አካሉ የመወጣቱን ሁኔታ የሚቆጣጠርበት መሆኑም የሚታመን ነው፡፡ ሌላው በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ተቀባይት ያለው ጉዳይ የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ ሊቆይ የማይገባው ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡ የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ እንዲቆይ ማድረግ በዳኝነት አካሉ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ያስከትላል፡፡ ምክንያቱም የሕግ ስህተት ያለበትን ውሳኔ ጸንቶ እንዲቆይ ማድረግ ሕብረተሰቡ በዳኝነት አካሉ እምነት እንዳይኖረው የሚያደረግ ነውና፡፡ በመሆኑም የሰበር ሥርአት የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ እንዳይቆይ በማድረግ የዳኝነት አካሉ በሕብረተሰቡ ዘንድ የሚታመን፣ከበሬታ የተቸረው እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው የሰበር ሥርአት ለሕግ ስርዓቱ፣ለዳኝነት አካሉና ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ ተብሎ የሚቋቋም መሆኑን ነው፡፡ ይህ ስርአት በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ውስጥ ተካቶ ለረዥም ጊዜያት ሲሰራበት የቆየ ሲሆን በ1987 ዓ/ም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀፅ 83 ስር ተመልክቶ ከመገኘቱም በላይ ዝርዝሩ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አዋጅ ቁጥር 454/97 የተደነገገለት ሥርዓት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 80 ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ስር የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለው ሲደነግግ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ደግሞ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል ሲል ደንግጓል፡፡ ሕገ-መንግስቱ በፌዴራልና በክልል ጉዳዮች የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያላቸውን ፍርድ ቤቶች ለይቶ ካስቀመጠ በኋላ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስልጣን ያለው መሆኑን በአንቀጽ 80(3(ሀ)) ስር ደንግጓል፡፡ ሰበር ችሎት ይህ ስልጣን የተሰጠው ከላይ የተመለከቱትን አላማዎች ለማሳካት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ በተለይ አዋጅ ቁጥር 454/1997 ሲታይ ከአምስት ያላነሱት ዳኞች በተሰየሙት ችሎት የሚሰጥ የሕግ ትርጉም ይኸው ችሎት ራሱ በሌላ ጊዜ እስካልለወጠው ድረስ በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት ላይ የአስገዳኝነት ኃይል(Precedence) ያለው ስለመሆኑ በአንቀፅ 2(4) ስር አስቀምጧል፡፡ ይህም የሰበር ስርዓት በዳኝነት ስልጣን ተዋረድ በመጨረሻ እርከን ላይ ሆኖ ሕጎች በትክክልና በወጥነት መተርጎማቸውንና መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ለተከራካሪ ወገኖች ጥቅም ወይም መብት ብቻ ሳይሆን ለዜጎች ጥቅም ተብሎ የተዘረጋ ሥርአት ወይም አሰራር መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ሰበር ሕጋዊ ያልሆኑ ውሳኔዎች የሚሰበሩበት ወይም ጸንተው እንዳይቆዩ የሚደረግበት ሥርአት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ሰበር መደበኛ የይግባኝ ማቅረቢያ አሰራር ሳይሆን ፍርድ ቤቶች በውሳኔዎቻቸው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል በሚባልበት ልዩ ሁኔታ ብቻ የሕጉ አተረጓጎም ወይም አተገባበር የሚቃናበት ወይም የሚታረምበት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህም ሥርአት የሕግ አንድ ወጥ አተረጓጎምና አፈፃፀም በፍርድ ቤቶች ሁሉ ይረጋገጣል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደ አመራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች አላማ ስንመለስ ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የመስማማት መብት ያላቸው መሆኑን ያሳዩናል፡፡ የግልግል ዳኝነት የሚቋቋምበት አይነተኛ አላማ ተካራካሪዎቹ ወገኖች ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት በመሄድ የሚያጠፉትን ጊዜና ገንዘብ ለማስቀረት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ጉባኤው የሚቋቋመውም በተካራካሪ ወገኖች ስምምነት ሲሆን ተካራካሪዎቹ ባላቸው የመዋዋል ነፃነት ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የሚስማሙት ሁኔታ መኖሩ በራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ የተቋቋመው ጉባኤ በተገቢው ጊዜና በአነስተኛ ወጪ ጉዳያቸውን ለመወሰን ይችላል የሚል እምነት ኑራቸው ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሁም በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከቁጥር 315-319 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ይህንኑ የሚያስገነዝቡን ሲሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 350(2) በተለይ ሲታይ ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በሚል ለመስማማት መብት ያላቸው ስለመሆኑ ያስረዳናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ስምምነት ከተደረሰም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 356 ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች በስተቀር የጉባኤው ውሳኔ በፍርድ እንዲሻርላቸው ለመጠየቅ እንደማይችሉ ተደንግጓል፡፡ ይህ ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ ስምምነት ያላቸው ከሆነ የሚፈፀም ስነ ስርዓት ሲሆን ስምምነት ባይኖርም ይግባኝ የሚቻለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 351 ስር በተመለከቱት ውስን ምክንያቶች ብቻ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 351"ም" ሆነ 356 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለው የግልግል ጉባኤ ውሳኔ በሰበር ስርዓት የሚታይበት አግባብ ስለመኖሩ አይጠቁምም፡፡ በሌላ አገላለፅ ድንጋጌዎች የሚያወሱት በግልግል ታይቶ የተወሰነ ጉዳይ በይግባኝ የሚታይበትን ሥርዓት ብቻ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ድረስ በተመለከቱት ድንጋጌዎችና በፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ለመጨረስ መሰረቱ ሕጋዊ ውል መኖሩ ሲሆን ውል ደግሞ የተከራካሪ ወገኖች መብትና ጥቅም ማስገኛ ምንጭ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ውሉ መብትና ጥቅም የሚሰጠው ለተዋዋይ ወገኖች ወይም መብትና ጥቅሙ በሕጉ አግባብ ለተላለፈላቸው ለሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ነው(የፍ/ህ/ቁጥር 1731 እና 1957 ይመለከቷል)፡፡እ ንዲሁም ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ ለመጨረስ መብት ያላቸው መሆኑ በሕጉ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ሕጉ ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ ያላቸውን ሚናም ደንጓጓል፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች በ1952ቱ የፍትሐብሔር ሕግና በ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕጋችን ውስጥ ያሉት ሲሆኑ ከእነዚህ ሕግጋት በኋላ የወጡት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትና አዋጅ ቁጥር 25/1988 እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 454/97 ስለሰበር ሥርዓት ደንግገው እናገኛለን፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ስልጣን ያለውና የሚሰጠው የሕግ ትርጉምም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት እስካልተለወጠ ድረስ የፌዴራልንም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶችን የሚያስገደድ መሆኑ በሕጉ የተቀመጠና አላማው በአገሪቱ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎምና አፈጻጸም እንዲኖር ማረጋገጥ ነው ከተባለ ተከትሎ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ከሆኑት አንዱ በሆነው በግልግል ዳኝነት (arbitration) ጉዳዩ ቢታይና ይኸው አካል በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የሌለው የመጨረሻ ስለመሆኑ(Arbitration Finality Clause) ተከራካሪ ወገኖች ገልፀው ስምምነት ቢያድርጉ ጉዳዩ በሰበር ሊታይ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ ይኸው ጥያቄም ስለሰበር ሥርዓት አላማና ከሕጎቻቹ አወጣጥ ቅደም ተከተል እንዲሁም በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ፍርድ ቤቶች በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ላይ ካላቸው ሚና አንፃር ታይቶ ምላሽ የሚሰጠው ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከላይ እንደተመለከተው የሰበር ሥርዓት ዓላማ ወጥ ለሆነ የሕግ ትርጉም እና አፈፃጸም ከፍተኛ ሚና መጫወት ሲሆን ይህንንም በ1987ቱ ሕገ-መንግስትም ሆነ ይህንኑ ተከትለው ከወጡ አዋጆች(25/1988 እና 454/97) የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ እነዚህ አዋጆች ከ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በሁዋላ የወጡ ሲሆን ተቀባይነት ባለው የሕግ አተረጓጎም ደንብ መሰረትም ከ1958ቱ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ቅድሚያ ተፈጻሚነት ያላቸው ናቸው፡፡ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች በኢትዮጵያ የሕግ ስርዓት ውስጥ ተካተው የሚገኙ ሲሆን እነዚህን የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ፍርድ ቤቶች የሚያበረታቱበት ሁኔታ እንዳለ ሁሉ የሚቆጣጠሩበት አጋጣሚም ያለ መሆኑን ከላይ የተመለከቱት የፍትሓ ብሔር ሕጉም ሆነ የፍትሓ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የአንድ ጉዳይ ለሰበር የመቅረብ ሁኔታ በሕገ መንግስቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ በመሆኑ ሥርዓቱ ሊጫወተው ከተፈለገው አቢይ አላማ አንፃር ሲታይ ጉዳያቸው በግልግል ዳኝነት እንዲታይላቸው የተስማሙበት ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው በማለት ስለተስማሙ ብቻ ጉዳዩ በሰበር ሥርዓቱ እንዳይታይ ፍላጎት አሳይተዋል ተብሎ መሰረታዊውን የሕግ ስህተት ላለማረም ምክንያት ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 21849 በቀረበው ጉዳይ ሁለት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት(Arbitration) ለመጨረስ ከተዋዋሉና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በማለት በውላቸው ላይ ከተስማሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ አይገባም በማለት የሠጠው ውሳኔ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀፅ 2(4) መሰረት መለወጥ ያለበት ሁኖ ተገኝቷል። ስለሆነም ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ በሰበር ችሎት ሊቀርብና ሊታይ የሚገባ አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል።

2.ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

ተጠሪ ውሉን ማቋረጡን ሳይክድ የሰላሳ አምስት ቀናት ቅጣት አመልካች እንዲከፍለው ዳኝነት የጠየቀውንና የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ውሳኔ ያሳረፈው በአመልካችና በተጠሪ መካከል በጥር 23 ቀን 1998 ዓ/ም የወርቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ውል ተፈፅሞ፣ቅድሚያ ክፍያ በየካቲት 09 ቀን 1998 ዓ/ም ተከፍሎ ስራው መጀመር ከሚገባበት ቀን ሰላሳ አምስት ቀናት በመዘግየት በ30–7-1998 ዓ/ም ለመጀመሩ ምክንያቱ አመልካች ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ነው። አመልካች በዚህ ረገድ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ገልፆ የሚከራከረው የማዕድን ፍለጋ ጉድጓድ ቁፋሮ ወደሚካሄድበት ቦታ የሚያድረሰውን ለተሸከርካሪ እንቅስቃሴ አመቺ የሆነ መዳረሻ መንገድ የማዘጋጀት ኃላፊት የራሱ መሆኑ በውሉ መገለጹን ሳይክድ ይህንኑ ግዴታ ለመወጣት ቡልዶዘሩን ከተጠሪ መከራየቱን፣ሆኖም በሁለት ቀናት ውስጥ ቡልዶዘሩን ወደ መቀሌ ለማጓጓዝ የሚያስችል መኪና አዘጋጅቶ ለማስጫን በሚሄድበት ጊዜ የቀረበው ቡልዶዘር ለታቀደው ስራ ብቃት የሌለው መሆኑ በአመልካች ኤክስፐርት በመረጋገጡና ይህ ሁሉ ሲደረግ ተጠሪ የወሰዱት አንዳችም እርምጃ የለም በሚል ነው። ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክር የአመልካች ክርክር በስር የግልግል ዳኝነት ያልተነሳ ነው በማለት ከመከራከር ውጪ ከላይ የተመለከተው ግዴታ በግራ ቀኙ መካከል መገባቱን በግልፅ አይክድም። ይሁን እንጂ አመልካች በስር የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ከላይ የተመለከተውን ክርክር ያነሳ መሆኑን የግልግል ጉባኤ ውሳኔ ግልባጭ በገጽ 3 እና 4 ያሰፈረው በመሆኑ ተጠሪ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1)መሰረት በማድረግ ያነሳው ተቃውሞ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ውድቅ ሆኖ ለሰላሳ አምስት ቀናት የቅጣት ገንዘብ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ስንመለከተው ደግሞ ምላሹ ከግራ ቀኙ ውል፣ክርክርና ስለውሎች አተረጓጎም በጠቅላለው በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት መታየት ያለበት ጉዳይ ነው።

በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጥር 23 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገው ውል አመልካችን ለባከነ ጊዜ ክፍያ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በአንቀጽ 4፣3.11 እና 9.1 ስር ካስቀመጣታቸው ድንጋጌዎች እንገነዘባለን። በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አመልካች ለተጠሪ ኃላፊነት የሚኖረው የመቆፈሪያው መሳሪያ ከአመልካች ጋር በተያያዘ ኃላፊነት ያለስራ ቢቀመጥ ስለመሆኑ ተቀምጧል።ድንጋጌዎቹ በግልፅ እንደሚያሳዩት የባከነ ጊዜ ክፍያ(Idle time Payment) የመቆፈሪያው መሳሪያ በስራ ላይ እያለ ውል ሰጪ በሆነው አመልካች ምክንያት ቢቆም፣መሳሪያው ስራ ለመስራት እየቻለ ቁሞ ያላግባብ ለጠፋው ጊዜ፣አመልካች ኃላፊ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው። በሌላ አገላለፅ የመቆፈሪያ ማሽን(Rig) በስራው ቦታ ላይ ተገኝቶ በአመልካች ምክንያት ስራ ቢፈታ አመልካች ኃላፊነቱን የሚወሰድ መሆኑን ያስገነዝባል። በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ለሰላሳ አምስት ቀናት ስራ ፈታሁ ይበል እንጂ በአመልካች ምክንያት ስራ መፍታቱን በፍሬ ነገር ደረጃ አልተረጋገጠም። ተጠሪ ስራውን የፈታሁ በአመልካች ምክንያት ነው ብሎ እስከተከራከረ እና አመልካችም ለመሳሪያው መቆም ምክንያት የሆነው ድርጊት በራሱ በኩል የተፈጸመ አለመሆኑን ገልፆ እስከተከራከረ ድረስ ክሱን የማስረዳት ሸክም ከሳሽ የሆነው ወገን የተጠሪ ግዴታ ነው። የመቆፈሪያው መሳሪያ ከስራ ቦታ አለመድረሱ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። የግልግል ጉባኤው አመልካችን መሳሪያው ስራውን ለፈታበት ጊዜ ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ላይ የደረሰው ከላይ የተጠቀሱትን የውሉን ድንጋጌዎች በመጥቀስና መቆፈሪያ መሳሪያ ወደ ስራ ቦታ ተንቀሳቅሶ የሚሄድበትን መንገድ አመልካች ሊያዘጋጅ አልቻለም፣የዶዘር ኪራይ ውልን መሰረት በማድረግ ክስ አልመሰረተም በሚል ነው። ሆኖም ተጠሪ ስራውን ከሚያዚያ 01 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ መስራት እንደሚችል በፁሑፍ ተነግሮት ሚያዚያ 12 ቀን 1998 ዓ/ም ስራው መጀመሩ፣የሰላሳ አምስት ቀናት ጊዜ ባክኗል የተባለው ደግሞ ከየካቲት24 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 30 ቀን 1998 ዓ/ም ድረስ ስለመሆኑ በስር ክርክር የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ናቸው። ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የመቆፈሪያ ማሽኑ ወደ ስራ ቦታው በመሄድ በአመልካች ምክንያት ስራውን መስራት ያልቻለ መሆኑን ሳይሆን ከመነሻውም መቆፈሪያ ማሽኑ ወደ ስራ ቦታ ያልተንቀሳቀሰ መሆኑን ነው።በግራ ቀኙ ውል አንቀፅ 3.11 ስር የተቀመጠው ድንጋጌ የመቆፈሪያ መሳሪያ ከአሰሪው ጋር በተያያዘ ኃላፊነት ያለስራ ቢቆም ....በሚል ሐረግ የተቀመጠ ሲሆን ይህም ድንጋጌ በግልጽ መሳሪያው ከስራ ቦታ መድረሱንና ደርሶ ስራ መስራት እየቻለ በአመልካች ምክንያት ስራውን ሳይሰራ ቢቀር አመልካች ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ነው።ግልፅ ውል ሊተርጎም የማይገባ መሆኑን ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1733 ድንጋጌ ያስረዳል። የግልግል ጉባኤ ውሉ ግልፅ ሆኖ እያለ እና ተጠሪ አመልካች ለባከነው ጊዜ ምክንያት መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ የተጠሪን የማስረዳት ሸክም ወደ አመልካች በማዞር አመልካች ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት የደረሰበት መሆኑን አላስረዳም በማለት ለባከነ ጊዜ ቅጣት እንዲከፍል ሲል የሠጠው የውሳኔ ክፍል የግራ ቀኙን ክርክርና የውል ይዘት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ስለማስረዳት ሸክም የተቀመጡትን ሥርዓቶች፣በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 1732 እስከ 1738

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድረስ ስለውሎች አተረጓጎም ከተመለከቱት ደንቦች ጋር ያላገናዘበና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም አመልካች መቆፈሪያ ማሽኑ ስራ ሳይሰራ በመቆሙ ምክንያት ባከነ ለተባለው ለሰላሳ አምስት ቀናት ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር የሚከፍልበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የተሰሠጠው የውሳኔ ክፍል ሊለወጥ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪ በውሉ መሰረት ለተከናወኑ ስራዎች መከፍል አለባቸው ተብለው የታሰቡት፤የሞቪላዜሽን ሂሳብ(ብር 90,000.00)፤ለ661.77 ሜትር ጥልቀት ጉድጓድ ቁፋሮ ሂሳብ(ብር 704,124.00)፤ለኬዚንግ ስራ(ብር138,000430.00)፤ለቁፋሮ ስራ ከጉድጓድ ወደ ጉድጓድ ለተደረገ እንቅስቃሴ የሚታሰብ(ብር 4,150.00)፤ስራ ላይ ለዋለ አምስት ከረጢት ሲሚንቶ የሚታሰብ(ብር 750.00)፤ከውሃ ቦቴ ኪራይ የሚታሰብ(50,000.00)እና የዶዘር ኪራይ(ብር 3,818.40) በጠቅላላ ድምር ብር 991,272.40(ዘጠኝ መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከአርባ ሳንቲም) ተጨማሪ እሴት ታክስ ተጨምሮበት ብር 1,139,962.86 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ ዘጥ ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሁለት ብር ከሰማኒያ ስድስት ሳንቲም)እንዲከፍል የተወሰነውን የውሳኔ ክፍል ስንመለከተው በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ውል፤ክርክርና ማስረጃ መሰረት አድርጎ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች የሰበር ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አመልካች ክፍያ ለዘገዱበት ብር 40,321.60(አርባ ሺህ ሶስት መቶ ሃያ አንድ ብር ከስልሳ ሳንቲም) ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑም ፍሬ ነገርን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው ባለመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ሌላው አመልካች ተጠሪ ውሉን በራሱ ጊዜ አቋርጦ መሄዱ ያላግባብ ነው በማለት በተከሳሽ ከሻስነት በግልግል ጉባኤው ያቀረበው ክርክር የታለፈው ባግባቡ አይደለም በማለት የሚከራከርበትን ነጥብ ስንመለከተውም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1786 እና 1788 ድንጋጌዎች አንጻር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ በግልግል ጉባኤ ታይቶ በሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን አንድ ተከራካሪ ወገን ቢስማማም ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ቅሬታውን ለሰበር ችሎቱ ከማቅረብ የሚከለከል ባለመሆኑና ጉባኤው አመልካች የሰላሳ አምስት ቀናት መቆፈሪያው ያለስራ ለቆመበት አመልካችን ተጠያቂ ያደረገበት አግባብ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ፤እንዲሁም ጉባኤው ወጪና ኪሳራ ያሰላበት አግባብ ይህ ችሎት ለአመልካች የሚቀንሰውን የገንዘብ መጠን መሰረት ባደረገ መንገድ የሚሰራ ሆኖ በሌሎች ነጥቦች ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሣኔ

1.ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 21849 በቀረበው ጉዳይ ሁለት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት(Arbitration) ለመጨረስ ከተዋዋሉና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በማለት በውላቸው ላይ ከተስማሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ አይገባም በማለት የሠጠው ውሳኔ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(4)መሰረት ተለውጧል፡፡

2 ሁለት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት(Arbitration) ለመጨረስ ከተዋዋሉና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል በማለት በውላቸው ላይ ከተስማሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ የሚችል ነው ብለናል፡፡

3.አመልካች ለተጠሪ የሰላሳ አምስት ቀናት ቅጣት የተባለውን ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ ለመክፈል የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት በዚህ ረገድ የግልግል ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ሽረነዋል፡፡

4.ወጪና ኪሳራን በተመለከተ የግልግል ጉባኤው የሰጠው የውሳኔ ክፍል አመልካች ብር 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በዚህ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ ግንዛቤ ባስገባና በጉባኤው ስሌት መሰረት የሚሰራ ሁኖ በወጪና ኪሳራ፤በጠበቃ አበል እንዲሁም በሌሎች ነጥቦች ላይ የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

5.በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎችን /ክቅጽ 1 - 7 / ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ቅጽ - 1

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
1	18180	የኬ.ኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ ሰራተኞች ማህበር እና የኬ.ኬ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ	የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ስልጣን፣ የሰራተኛ ቅነሳ ጉዳይን በሚመለከት ስለሚነሳ ክርክር አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 138(1),147	ሐምሌ 29/1997
2	15493	አቶ ጳውሎስ ሩምቾ እና ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ	በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,2024	ሐምሌ 29/1997
3	17361	ወ/ሮ ጋዲሴ ኢርጌ እና ወ/ሮ ወርቅአንጥፉ በቀለ	በስነ-ስርዓት ህጉ የጊዜ ገደብን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.49, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856	ሐምሌ 25/1997
4	17352	ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/ የግ/ ማህበር እና የነገው ሰው ትምህርት ቤት	ተገቢው ዳኝነት ክፍያ ሳይፈፀም በፍ/ቤት በቀጠለ ክርክር ስለሚፈፀም ስርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.215,320(2),207,211(2)	ሐምሌ 28/1997
5	14605	የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና እነ ኮሜት ትራንስፖርት ድርጅት (ስድስት ሰዎች)	በመንገዝ ላይ የነበሩ ዕቃዎች መጎዳት በሰው ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን የግጭት አደጋ ለማስወገድ በተወሰደ ርምጃ የደረሰ የመኪና መገልበጥ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ስላለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 590,591, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1792	ሐምሌ 29/1997
6	17068	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ሚ/ር ቢሮኒ አቲክፖ	በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856,2024, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 89	ሐምሌ 19/1997
7	14974	ወ/ት ማህሌት ገ/ስላሴ እና እነ አቶ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች)	አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ባቀረበው ክስ ወካዩን ወክሎ መከራከር ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2188, 2189, 2208, 2209, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 57,58	ሐምሌ 28/1997
8	14184	አቶ ውርጌሳ ታደሰ እና እነ አቶ መለሰ ተካ (ዘጠኝ ሰዎች)	ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73	ሐምሌ 29/1997
9	14047	ዶ/ር ዳንኤል አለሙ እና እነ ወ/ሮ ሮማን ወርቅ የማነብርሃን (ሦስት ሰዎች)	በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1856, 2024	ሐምሌ 28/1997
10	15835	ሼል ኢትዮጵያ አ/ማ እና ወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ	ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የተከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70,233	ሐምሌ 29/1997
11	15992	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ወ/ት ሶስና አስፋው	በህግ የተደነገገው የውል አፃፃፍ /ፎርም/ የተቀመጠ ደንብ አለመፈፀም ስለሚያስከትለው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719, 1720 (1), 1723, 1726, 1727, 1845	ሐምሌ 19/1997
12	17191	ወ/ሮ አስቴር አርአያ እና አቶ ግርማ ወይጆ	በአንዳንድ ውሎች የተመለከተን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለመቀነስ ፍ/ቤት ስላለው ስልጣን የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711, 1731, 1676(2), 2635, 2640, 2646	ሐምሌ 29/1997

ቅጽ 2

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
13	13223	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አስፋው አበበ	ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ባይቀርብለትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማንኛውም ዓይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪ እንዲቀርብለት መስጠት ስላለበት ትዕዛዝ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2) 342, 345(1)(ለ)	ጥቅምት 9/1998
14	14414	የጊምቢ ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት	በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ከመ/ቤቱ ጋር ባለው ስራ ክርክር የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ ስለመሆኑ	ጥቅምት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		እና ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ	አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 2(1),3(2)(ሠ)	1/1998
15	15270	የመቶ አለቃ ተሻገር አስታጥቂ እና አቶ አዊል አው አብዲ	በከተማ ቦታ ላይ ስለሚኖር መብት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33(2), 231, (1)(ሀ), አዋጅ ቁ.47/67	ጥቅምት 28/1998
16	15410	አቶ ተሾመ ጅፋር እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን	አጠቃላይ የአሰሪን የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ስርዓትን ሳይሆን የግል ጥቅምን መሰረት አድርጐ የሚቀርብን የደመወዝ ጭማሪ ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 147	ጥቅምት 1/1998
17	16273	የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገንታ ገምአ	ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠርኩ እንደሆንኩ ብቻ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄን የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ እና የግል ጥቅምን መሰረት አድርጐ የሚቀርብን የጥቅማጥቅም ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 9,10, 138, 142, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33	ጥቅምት 22/1998
18	16624	ወ/ት አጅጋየሁ ተሾመ እና የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) መሰረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)	ጥቅምት 18/1998
19	16720	ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ እና እነ የመካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት (አራት ሰዎች)	በከፊል የፍርድ ባለመብት የሆነ ሰው ባለመብት የሆነበት የፍርድ ክፍል እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ክስ ካቀረበ በኋላ በመጀመሪያ የፍርድ ባለዕዳ የሆነበትን ፍርድ በይግባኝ አሸሮ የፍርድ ባለመብት ሲሆን አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ቀደም ሲል የተከፈተው የአፈፃፀም መዝገብ ቢዘጋም እንኳን ማንቀሳቀስ ስለመቻሉ እና በአፈፃፀም ደረጃ ወለድ የሚከፈለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ከተወሰነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378(3)(ሰ)	ጥቅምት 22/1998
20	16896	ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና የኢሊባቦር ዞን ትምህርት መምሪያ	የተዋዋዮች በውሉ አለመግባባት ሲፈጠርና ጉዳዩን በገላጋይ ዳኞች እንዲታይ ሲስማሙ ፍ/ቤት ይህንን ስምምነት ማስፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711,1731(1)	ጥቅምት 16/1998
21	17077	ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ	የዕዳ መክፈያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ባለገንዘቡ ለባለዕዳው የሚያደረገው የዕዳ ክፍያ ጊዜ ማራዘም ዋስትን ከዋስትናው ነፃ የሚያደርገው ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1928(1)እና(2)	ጥቅምት 14/1998
22	17189	የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጭ ድርጅት እና አቶ ንጉሴ ዘለቀ	በአሰሪ “ገንዘብ” ላይ ሰራተኛው ያደረሰው ጉዳት በአሰሪው “ንብረት” የደረሰ ጉዳት ስለመሆኑ እና ሰራተኛ የስራ ውሉ ተቋርጦ ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 27(1) (በ), 53(1),54	ጥቅምት 17/1998
23	17429	ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ እና አቶ ተስፋዬ ከበደ	በግልጽ በሚደረግ ጉባዔ ጉባዔው መነበቡን የሚያመለክት ከሆነ በግልጽ “ተነቧል” የሚል ቃል አለመኖሩ ጉባዔውን ፈራሽ የሚያደርግ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881	ጥቅምት 21/1998
24	17533	የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና ሙሉ ብርሃን	የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሰረት የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ በማድረጉ ወይም ዴክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት በዕቃው ባለቤት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 2(18), 43(1) (ሀ)	ጥቅምት 18/1998
25	17712	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት እና የወ/ሮ ሳዲያ እስማኤል ወራሾች	በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1), 1196 (1)	ጥቅምት 16/1998
26	18307	ንብ ትራንስፖርት አ.ማ. እና አቶ ተገኑ መሸሻ	በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ የሆነ ሰራተኛ ከአሰሪው ጋር ያለው የስራ ክርክር የሚገዛው በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎት መስጠትን ስለሚመለከቱ ውሎች ክፍል በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስለመሆኑ እና የስራ ውሉ ተቋርጦ የስራ መሪው ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2534, 2540 ,2541(1)	ጥቅምት 25/1998

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
27	15815	አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ሰለሞን አበበ	የስራ ውሉ በህግ ወጥ መንገድ የተቋረጠ የስራ መሪ ስለሚያገኘው መፍትሔ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2570, 2573, 2574,2571	ታህሳስ 10/1998
28	16648	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ አንለይ ያየህ (ሃያ ሰባት ሰዎች)	ስለ ስራ ክርክር የይርጋ ጊዜ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162,163,164,165,166, አዋጅ ቁ. 377/96	ታህሳስ 20/1998

https://t.me/ethiopianlegalbrief

29	17483	የኦሮሚያ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እና ወ/ሮ ሮማን ደምሴ	የስራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል የሚቀርብ ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162(1)	ታህሳስ 20/1998
30	11924	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት ትዕግሥት ወርቁ	ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ስለማድረግ አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 9,10 እና 24	ህዳር 15/1998
31	14057	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ጌታሁን ኃይሉ	አንድ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት እረፍት ቀናት በገንዘብ ተቀይሮ ስለሚከፈልበት የህግ አግባብ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 79(2)እና (5), 77(5),77(3)	ጥቅምት 30/1998
32	16270	አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ መሐሪ ማታ	በመኪና ግጭት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት ካሣ ለማግኘት የመኪናው ባለቤት ጥፋት እንዳለበት ማስረዳት የማይኖርበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066(2),2086(2),2081,2091,2102 እና 2092	ታህሳስ 17/1998
33	18581	በአዲስ አበባ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጥበቃ እና ሲ/ረ ቀቡላ ከድር	በህገ ወጥ መንገድ የስራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ ወደ ስራ እንዲመለስ ስለሚወሰንበት የህግ አግባብ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 23(1),43(3),40(1) እና (2),44	ህዳር 20/1998
34	15631	እነ የሻረግ መንግስት (ሁለት ሰዎች) እና እማሆይ የሻረግ ፊረደ	የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነ ጊዜ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1001(2),1168,1845,1853	ታህሳስ 17/1998
35	15551	ዮናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ እና የኢትዮጵያ መተርና መሐንደስነት ኩባንያ	ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ ተዋዋዮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚወሰነው በውሉ መሰረት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716(1), 1815,1816 እና 1817	ጥቅምት 29/1998
36	16062	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ	ከውል ውጭ በደረሰ ጉዳት ካሣ በመጠየቅ የሚቀረብ ክስ መቅረብ ስለሚኖርበት ጊዜ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1),2143(2)	ህዳር 19/1998
37	14554	ወ/ሮ ጽጌ አጥናፌ እና ባላምባራስ ውቤ ሽበሽ	ፍርድ ቤት በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርን የመሰረዝ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808(2),1198(2)	ታህሳስ 20/1998
38	15672	አቶ ታደለ ገለቻ እና አቶ ውድመጣስ ኑሮ	ንብረት በሐራጅ ስለሚሸጥበት የህግ አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 442	ታህሳስ 27/1998
39	16301	ተገኝ እንግዳ እና አስናቀች ኪዳኔ	መጥሪያ አደራረስን አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተናገድበት መንገድ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 99, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103,105	ህዳር 2/1998
40	10797	ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እና እነ ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም (ሦስት ሰዎች)	ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳዩ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378	ታህሳስ 27/1998
41	18199	ዶ/ር ምናሴ እሸቱ እና እነ ግርማ አያና (ስባት ሰዎች)	በጨረታ ለገዛው ንብረት ገገር ዋጋውን ሳይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ስነ-ስርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 429	ህዳር 7/1998
42	16378	የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ እና የቤ/ጉ/ክ/መ ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን	የመንግስት ሰራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መስራቱ ስለሚኖረው ውጤት ድንጋጌ ቁጥር 46/53, አዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2)	ታህሳስ 17/1998
43	18342	የማህበራዋ ዋስትና ባለሥልጣን እና እነ አቶ ብርሀኑ ሀሩይ (ሁለት ሰዎች)	የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.38/88 አንቀፅ 11(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4	ታህሳስ 17/1998
44	14699	የኢንጂነር ወርቁ መኮንን ወራሾች እና የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች መምሪያ	ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ህጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀፅ 29	ህዳር 7/1998

ቅጽ 4

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
45	20885	የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገቢሳ የማነ	ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ስለሚደረግ የስራ ውል አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10	ጥር 3/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

46	15531	የኢት/ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አዱኛ ገመዳ	የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን	የካቲት 6/1999
47	21730	ወ/ሮ ፍሬህይወት እርቁ እና የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን	ወደ ሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5)	መጋቢት 11/1999
48	21119	ቃሊቲ ምግባ አክሲዮን ማህበር እና ማስተዋል ጫኔ	የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠር አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ (2)	መጋቢት 18/1999
49	21961	አቶ ግርማ ነጋሽ እና ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር	የስራ ውልን ስለማቋረጥ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) ሐ	መጋቢት 18/1999
50	20457	የኢት/ንግድ ባንክ እና ወ/ሮ አለሚቱ ሞገስ	የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ ስራ ላልተሰራበት ውዝፍ ደሞዝ የሚከፈል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43,53(1), 54	መጋቢት 20/1999
51	24153	አቶ መንግስቱ አባተ እና የባህር ትራንዚት ድርጅት	ስለ መሠረታዊ የህግ ክርክር አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)ሐ	መጋቢት 26/1999
52	16653	ግዮን ሆቴሎች ድርጅት እና ወ/ሮ ስለእናት ወርቅነህ	የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን	መጋቢት 27/1999
53	25526	መምህር ጥላሁን አስፋው እና አዲስ ኮሌጅ	ሰራተኛው በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10	ሚያዝያ 16/1999
54	15662	የኢት/ልማት ባንክ እና ሐዲ አብዲራህማን ቱሊላ	ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጎም ስላለመቻላቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2298,1733	መጋቢት 13/1999
55	19081	አቶ ዓሊ ቃሌብ አህመድ እና እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ (ሦስት ሰዎች)	ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሳሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ በሌሎች ላይ ስላለው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677,1901	መጋቢት 18/1999
56	23320	አቶ ገብሩ አብሌ እና እነ የአቶ ሁሴን አብዲረህማን ወራሾች (ሦስት ሰዎች)	የኪራይ ውል በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ስለመሆኑ	መጋቢት 20/1999
57	14493	የኢት/ልማት ባንክ እና አቶ ሚደቅሳ ቱለማ	ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጎም ስላለመቻላቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ.2298,1733	መጋቢት 13/1999
58	18786	ወ/ሮ አለሚቱ አግዛቸው እና እነ ወ/ሮ ዝናሽ ሐይሌ	የውል አብዛኛው ግዴታ በተፈፀመ ጊዜ የተወሰነ ቀሪ ገንዘብ አለመከፈሉ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሰረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሰኝ ምክንያት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1), 1785(2), 1789	ሚያዝያ 18/1999
59	21448	ወ/ሮ ጮርፌ ወርቅነህ እና እነ ወ/ሮ አበራሽ ዱባርጌ (ሁለት ሰዎች)	የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1727 ,2877, 2878	ሚያዝያ 30/1999
60	15557	ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁ እና አቶ ብርሀኑ ተሊላ	በአፈፃፀም ጉዳይ በስህተት በፍ/ባለመብት እጅ ስለገባ የከተማ መሬት ይዞታ	መጋቢት 11/1999
61	22260	የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ (ሦስት ሰዎች)	የወጪና ኪሣራ አወሳሰን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 463	መጋቢት 18/1999
62	17984	የጌዲዮን ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት እና ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ	ጉድለት ያለበት ሀራጅ ቀሪ ሲደረግ ሻጭና ገዢን ወደነበሩበት ለመመለስ ስላለመቻል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1) እና (2)	መጋቢት 20/1999
63	19205	አቶ ሽኩር ሲራጅ እና አቶ መላት ካሣ	አንድ ፍርድ ተፈፀመ ሊባል የሚገባው ለፍርድ ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ ሲደርሰው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 395	መጋቢት 25/1999
64	19479	ወ/ሮ አመለወርቅ ገለቱ ወራሾች እና እነ አቶ ቢሻው አሻሜ (አራት ሰዎች)	አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ሆነ የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግስት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገመትና አስፈላጊም ከሆነ እንዲሸጥ የሚያደርግ ውሣኔ መሬትን የመንግስት ለማድረግ የወጣውን ሕግ የሚፃረር ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 47/67	መጋቢት 20/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

65	16109	አቶ ከበደ አርጋው እና የኢት/ንግድ ባንክ	የሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ተዋዋዮች ውላቸውን በመዝገብ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ የማይጥልባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1587, 1620, 1613, 2878	ሚያዝያ 12/1999
66	14094	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና የአቶ ሰለሞን ወረዳ ወራሽ	ለረጅም አመታት በመንግስት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ያለአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሣኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, አዋጅ ቁ 47/67,ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/	ሚያዝያ 18/1999
67	17937	ወ/ሮ ድንቁ ተድላ እና አቶ አባተ ጫኔ	ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677 መሠረት በቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈፃሚ ስለመሆኑ ፍ/ብ/ህ/ቁ. 17,68, 1000,1677,1845	መጋቢት 20/1999
68	20938	ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ እና ወ/ሮ ሣራ ልነጋነ	ስለ ጋብቻ መፍረስ	ሚያዝያ 11/1999
69	22243	ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ እና አቶ አብርሃም ካሣ	ልጅነትን ስለማስረዳት የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126(1),143(መ) እና (ሠ)	ሚያዝያ 16/1999
70	17058	አቶ አንበሶ ወ/ገብርኤል እና አቶ መሣይ መኮንን	ኑዛዜ ህጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881, 884, 892, 996-1000, ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	መጋቢት 25/1999
71	22712	አቶ እንደሻው በቀለ እና እነ ወ/ት አይናለም ያለው (ሁለት ሰዎች)	የኑዛዜ እያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትና ተናዛዥም ሆነ ምስክሮች /አማኞች/ በኑዛዜ ባሰፈሩት ቃላትና ሃረጎች ሊሰጡ የሚችለውን ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881	ሚያዝያ 9/1999
72	22162	አፍሪካ ኢንሹራንስ እና አቶ ብስራት ጉላ	መድን ሰጭ የካሣን ክፍያ በተመለከተ በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ	ሚያዝያ 9/1999
73	23339	የኢት/ጉምሩክ ባለሥልጣን እና እነ አበሮ ኢርጋኖ	የጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚተዳደሩ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀፅ 6(2)ለ	መጋቢት 13/1999
74	16195	የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ስላሴ (ስድስት ሰዎች)	ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 4187 አንቀፅ 11(1), አዋጅ ቁ.47/67 አንቀፅ 21(2), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 74(4)	ሚያዝያ 11/1999
75	22317	የምስራቅ ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እና አቶ አብዱ አሉ አዩ	የጉምሩክ ባለስልጣን በኮንትሮባንድ ወደ ሀ-ገር የሚገቡትን ወይም ከሀገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 5-6 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2010(2)	ሚያዝያ 18/1999
76	12025	አቶ ምናሴ አልማው እና ዓቃቤ ህግ	ጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ የጥብቅና ስራ አሰራለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል የማታለል ወንጀል ስለመሆኑ የ1949 ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ.656(ሀ) እና (ለ)	መጋቢት 18/1999

ቅጽ 5

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
77	17320	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ዶ/ር ሻውል ገብሬ (ሁለት ሰዎች)	ንብረትን ለመሸጥ ለመለወጥ ብሎም ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ በሚል የተሰጠ ውክልና ንብረቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችል ስልጣን እና ችሎታን የሚያጐናጽፍ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3049(2),2206(1)	መጋቢት 18/2000
78	20809	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ሃይሌ	በባለስልጣን ፊት በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ያሉትን ፊርማዎችና የሰነዶቹን ይዘት ማስተባበል ስላለመቻሉ	ሐምሌ 10/2000
79	23861	ሊቀ ስዩማን አሰፋ ባሻህውረድ እና የሣህሊተ ምህረትና ክርስቶስ ሣምራ ደብር አስተዳደር	ወኪል የሆነ ሰው ውክልናውን በሚገባ እስካሳየ ድረስ በማመልከቻው ላይ የራሱን ወይም የወካዩን ስም አስቀድሞ መፃፉ ወኪልነቱን ለውጦ ባለቤት የሚያደርገው ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 58	ጥቅምት 14/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

80	26399	አቶ ኃ/ማርያም ባዩ እና እነ አቶ ሣሙኤል ጐሣዬ (አምስት ሰዎች)	የውክልና ስልጣኑ ቀሪ ከተደረገበት እንደራሴ ጋር በቅን ልቦና ውል ፈፅመው በተገኙ ጊዜ ውሉ እንዲፈርስ ላይወሰን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808, 1816, 2191(2), 2193	ህዳር 5/2000
81	32241	ወ/ሮ ካሰች ተካልኝ እና እነ አቶ ኃ/ማርያም አበበ (ሁለት ሰዎች)	• እንደራሴ የሆነ ሰው የውክልና ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞች (Conflict of interest) ማስወገድ ያለበት ስለመሆኑ • ከእንደራሴው ጋር ውል የፈፀመው ሦስተኛ ወገን እንደራሴው የውክልና ስልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞችን የማስወገድ ግዴታውን አለመወጣቱን ማወቁ ወይም ማወቅ የሚገባው መሆኑ ያደረጉትን ውል ፈራሽ ስለማድረጉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)	መጋቢት 9/2000
82	21355	አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት እና አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ	የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የሰጠ ወገን ከዋናው ውል አለመፅናት ጋር በተያያዘ የዋስትና ውሉ እንዲፈርስ ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1923(2)	ሐምሌ 3/2000
83	25115	አቶ ማሞ ጐበና እና አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም	ተራ ዋስ የሆነ ሰው ከባለዕዳው ጋር ተጣምሮ ክስ በቀረበበት ጊዜ ከገባው የዋስትና ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከኃላፊነት ነፃ ሊደረግ የሚችለው ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለባለገንዘቡ ከመወጣቱ ጋር በተያያዘ ስለመሆኑ	ጥቅምት 5/2000
84	26565	ግሎባል ኢንሹራንስ /አ.ማ/ እና ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/	ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገመት ወይም ሊታሰብና ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚቻል ሁኔታ ድንገተኛ ደራሽ ቢሆን እንኳ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ (Force majeure) ተብሎ የማይወሰድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 1792(2)	ጥቅምት 19/2000
85	17742	ወ/ሮ አበበች ታደሰ እና እነ አስር አለቃ ሲሳይ ካብትህይመር (አራት ሰዎች)	በህግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት የሚያስችል ማንኛውም ዳኛ ውል የማዋዋል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678(ለ) እና 1715	መጋቢት 2/2000
86	23921	ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግስቱ እና አስር አለቃ ታደሰ ወርቁ	የስጦታ ውሉ በስጦታ ተቀባዩ ላይ ግዴታ ያልጣለ ቢሆንም እንኳን ስጦታ ሰጪው በድህነት ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ተቀባዩ ቀሰብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2458(1)	ጥቅምት 12/2000
87	32337	ወ/ሮ ፀሐይነሽ ይህደጐ እና እነ ወ/ሮ ትሕሽ በርሔ	"የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ተራ የክፍያ ደንብ እንጂ ሌሎች ወራሾች ያላቸውን ውርሱን የመካፈል መብት የማይገድብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 913	ግንቦት 21/2000
88	22891	ወ/ሮ ማና ኃ/ሚካኤል እና እነ አቶ ገ/ማርያም ከበደው (ሁለት ሰዎች)	በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ ምክንያት የተፈጠረ ዕዳ ለጋራ ጥቅም መዋሉ በተረጋገጠ ጊዜ የዕዳው ወደ የጋራ ንብረት ወይም ወደ ሌላኛው ተጋቢ የግል ንብረት በመሄድ ሊከፈል የሚችለው በፍርድ አፈፃፀም ላይ ስለመሆኑና ከዚህ ጋር በተያያዘ በሌላኛው ተጋቢ ላይ ዕዳውን መሠረት በማድረግ ክስ ሊመሰረትበትም ሆነ ፍርድ ሊሰጥበት የማይገባ ስለመሆኑ	ህዳር 24/2000
89	31737	አቶ ንብሩ ገ/መስቀል እና ቂስ ገ/መድህን ረዳ	በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472 መሠረት በባንክ የተሰጠ የሃዋላ ወረቀት ብድርን ለማስረዳት ስለመቻሉ	የካቲት 27/2000
90	24173	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና ወ/ሮ አይዳ ሐሰን	በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት የተላከ ፖስታ /ዕቃ/ በመጥፋቱ፣ መሠረቁ፣ በመበላሸቱ፣ ወዘተ ምክንያት ካሣ የሚጠየቀው መጠኑም የሚወሰነው የፖስታ አገልግሎት ሕግን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 24/58 መሠረት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 24/58 አንቀፅ 50,51,53 እና 54	ህዳር 11/2000
91	24574	የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤ/መ/ፖ/ጠ/ጽ/ቤት እና አቶ ይትባረክ ሣህሉ	በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሳይሰጥበት የታለፈ ጉዳይ እንደተነፈገ ይቆጠራል የሚለው የሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ	ህዳር 11/2000
92	25434	የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን እና ፋሬተርስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማህበር	በውል ውስጥ አጠራጣሪና ግልፅነት የጐደላቸው ጉዳዬች በፍ/ብ/ህ/ቁ.1738 መሠረት እልባት ሊሰጣቸው የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1738	መጋቢት 25/2000
93	29369	በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ የግብርና ምርምር ማዕከል እና አቶ ተመስገን አድነው	• የባለዕዳው ቀጥተኛ የውል ፈፃሚነት ከውሉ ባህሪ አኳያ ማስፈፀም አለመቻል ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቅ ሳያስፈልግ ኪሣራ ካለ መጠየቅ ስለመቻሉ • በውል መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ ወገንን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል በሆነ ጊዜ በውሉ ግዴታውን የተወጣው ወገን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰውን ኪሣራ ለመጠየቅ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1) እና (2)	መጋቢት 9/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

94	19338	ዘይነባ ሐሰን እና ፍሬው ተካልኝ	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ተጐጂ የሆነ ወገን የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚኖር ስለመሆኑ ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ዳኞች ለተጐጂው የሚከፈለውን ካሣ በርትዕ መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102	መጋቢት 2/2000
95	21296	የኔዘርላንድ ልማት ድርጅት እና ውበት አድባሩ	የፍ/ብህ/ቁ. 2089 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(1) እና (2)	ታህሳስ 1/2000
96	22509	አቶ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ እና ዳርጊ ሰምሮ	የቀረበን ክስ ለማስረዳት አግባብነት የሌለው ማስረጃን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	ጥቅምት 7/2000
97	24818	ይልቃል በእውቀቱ እና ስዩም አባዲ	ጥቅም በሌለው ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ ሲሄድ አደጋ በመድረሱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው ካሣ ሊጠይቅ የሚችለው የመኪናው ባለቤት ወይም ጠባቂው ጥፋት መፈፀሙን በማስረዳት ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(2)	የካቲት 4/2000
98	27565	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ደምሴ ወርቅነት (ሁለት ሰዎች)	ጉዳት ሊክስ የሚገባው ለደረሰ ጉዳት ብቻ ሳይሆን በጉዳቱ ምክንያት ለሚመጣ ኪሣራ ጭምር ስለመሆኑ	ታህሳስ 1/2000
99	27623	ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ውባየሁ አበበ	• የማህበራዊ ዋስትና መብት ጥቅምን በሚመለከት የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የመዳኘት የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ • የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 38/88 አንቀፅ 5,8 እና 11	ህዳር 24/2000
100	28612	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን	ለደረሰ ጉዳት ሃላፊ የተባለ ሰው ላደረሰው ጉዳት ካሣ አይክፍልም ሊባል የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2091	የካቲት 25/2000
101	28750	የኢትዮጵያ ንምሩክ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ከውልና ከውል ወጪ በሆነ ግንኙነት ከሁለት የተለያዩ የክስ ምክንያቶች የሚመነጭ ኃላፊነትን መሠረት በማድረግ በአንደኛው ግንኙነት ብቻ ተጠያቂ የሆነን ወገን ሁለቱን የኃላፊነት ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ካሣ እንዲከፍል በአንድነትና በነጠላ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2035, 1896	ህዳር 24/2000
102	28865	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ካሣ ግዛው	ንብረትን ከመስሪያ ቤት በኃላፊነት የተረከበ ሰው ንብረቱ በጠፋ ጊዜ ከንብረቱ መጥፋት ጋር በተያያዘ ጥፋት ያልፈፀመ መሆኑን ወይም ንብረቱ ከሥራ ሰዓት ውጪ የጠፋ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2027	ህዳር 24/2000
103	30032	የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ወ/ሮ ምንትዋብ የኔህ	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት የክልሉ መንግስት ቋሚ ሠራተኛ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት የሞተ እንደሆነ ለተተኪዎች የጡረታ አበል እንጂ ሌላ ተጨማሪ ካሣ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የአማራ ክልል አዋጅ ቁ.74/1994 አንቀፅ 46(5) (ሀ)	ታህሳስ 1/2000
104	30442	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ስሜን ምዕራብ ሪጅን እና ወ/ሮ ድንቋ አመኔ	• ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት የሞት አደጋ በደረሰ ጊዜ የሟች የቅርብ ዘመዶች ሊኖራቸው የሚችለው መብት እና • የደረሰውን የሞት አደጋ ተከትሎ የሚቀርብ የቀለብ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095 807, 812	ህዳር 3/2000
105	31099	የተንዳሆ እርሻ ልማት አ/ማ እና ወ/ሮ ርሻን አለማየሁ	ሟች ከመሞቱ በፊት ቀለብ የማይሰፈርለት ግለሰብ በሟች ሞት ምክንያት የጉዳት ካሣ በቀለብ መልክ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095, 2069(1)	ግንቦት 14/2000
106	32144	ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እና ወ/ሮ ኢልሻ ሲራጅ	• በሞት ምክንያት ቀረ የሚባል ጥቅም የሚሰላው ከጠቅላላው የሟች ደሞዝ ላይ የሚቀነሱት በህግ የታወቁት ተቀናሾች ተቀንሰው የሚገኘውን የተጣራ ገቢ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ • የህሊና ካሣ ከአንድ ሺህ ብር ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2116	መጋቢት 23/2000
107	32250	ወ/ሮ አስናቀ ወ/ማሪያም እና እነ አቶ ከተማ ተሰማ (ሁለት ሰዎች)	በሞት አደጋ ምክንያት የተቋረጠ የመተዳደሪያ ጥቅም ጋር በተያያዘ በየወሩ የሚከፈል ካሣ አከፋፈል ስርአት በፍርድ ቤት የተወሰነውን ካሣ አጠቃሎ በባንክ ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም በማስቀመጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095(2)	መጋቢት 25/2000
108	33975	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ወ/ሮ አበበች ስዩም	የመሬት ይዞታ ባለቤት የሆነ ሰው ለህዝብ ጥቅም በሚል ይዞታውን በተጨባጩ እንዲለቅ ባልተደረገበት ሁኔታ ሊጠይቅ የሚችለው የካሣ ክፍያ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.455/97 አንቀፅ 7(1)	መጋቢት 25/2000
109	34138	እነ ሲስተር ገነት ጌታቸው (ሁለት ሰዎች) እና	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ከደረሰበት የአካል ጉዳት በተጨማሪ በደሞዝ ረገድ የቀረበት ጥቅም	ግንቦት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		ወንድወሰን ኃይሉ ወልደ ማሪያም	(ገቢ) መኖሩ ከተረጋገጠ ሊካስ የሚገባ ስለመሆኑ	26/2000
110	34906	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት እና ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቁ	በሥራ ግንኙነት ውስጥ የቅርብ አለቃ የሆነ ሰው በሥሩ ያሉ ሠራተኞችን አስመልክቶ ለበላይ ኃላፊዎች የሚፅፈውና የሚልከው ሪፖርት ሥም ከማጥፋት ጋር በተያያዘ የፍትሐብሔር ሃላፊነት ሊያመጣበት የማይችል ስለመሆኑ	ግንቦት 5/2000
111	21740	ወ/ሮ አስረስ መስፍን እና ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ	የጋብቻ ጽሁፍ በሌለ ጊዜ ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 699(1), (2)	ጥቅምት 28/2000
112	23021	ወ/ሮ አበባ ወርቅ ጌታነህ እና ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ	በፍቺ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ የቀድሞ ተጋቢዎች እንደ ገና አብሮ መኖር የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ከሆነ ጋብቻ መፈፀሙን የህግ ግምት መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 96 እና 97(1)	ሐምሌ 12/1999
113	23493	ወ/ሮ እንግው ዘገየ እና ወ/ሮ ወርቁ መኮንን	በፍርድ ቤት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ የሟች ባለቤቶችን እኩል የጡረታ አበል የመከፈል መብት የሚሰጥ ስለመሆኑ	ሰኔ 26/1999
114	23632	ወ/ሮ ፀዳለ ደምሴ እና አቶ ክፍሌ ደምሴ	ወላጆች ለህፃናት ልጆቻቸው ሞግዚትና አስተዳዳሪ የመሆን መብታቸው ሊከበር የሚችለው ለህፃናቱ ጥቅምና ደህንነት እስከሰሩ ወይም ሊሰሩ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ስለመሆኑ የደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስተ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/96 አንቀፅ 235(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 36(2)	ጥቅምት 26/2000
115	24625	ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ እና ወ/ሮ ሊህማ አሊ	በህግ ፊት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆ የጋራ ሀብትን ሁለቱ ባለቤቶች ግማሹን ለሁለት ቀሪውን ግማሽ ልጆች የሚካፈሉ ስለመሆኑ	ጥቅምት 28/2000
116	25005	መኮንን በላቸው እና ወ/ሮ አለሚቱ አደም	በጋብቻ ውል ላይ የግል ተብሎ ያልተመለከተና ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት ግንባታው የተጀመረ ቤት ግንባታው የተጠናቀቀው በጋብቻ ወቅት ከሆነ የጋራ ንብረት ተደርጎ የሚወሰድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) , 63(1)	ህዳር 3/2000
117	25281	ወ/ሮ መሠረት ፍስሐ እና አቶ ቀልቤሣ አለሙ	የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ነው በሚል የተወሰነ መኖሪያ ቤት ጋር በተያያዘ አንደኛው ተጋቢ ቤቱ የተሰራበትን መሬት (ቦታ) ከጋብቻው በፊት የተመራ በመሆኑ ሌላኛው ተጋቢ የቤቱን ግማሽ ዋጋ ተቀብሎ እንዲለቅ በሚል የሚሰጥ ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 92 የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀፅ 1131,1132	ጥር 29/2000
118	25588	መርየንሃሰን ዑመር እና መውሊድ ተሽልእስማን	አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው መሆኑና አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት እንጂ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ስላለመሆኑ	የካቲት 6/2000
119	26839	ወ/ሮ አስካለ ለማ እና ሣህለ ሚካኤል በዛብህ	ጋብቻ ከመመስረቱ በፊት የግል የነበረ ሃብት ከጋብቻ በኃላ የጋራ ከሆነ ንብረት ጋር ተቀላቅሎ በተገኘ ጊዜ የግል የሆነው ንብረት ተለይቶ የግሉ ለሆነው ተጋቢ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 57,86(1)	ህዳር 10/2000
120	26953	አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ እና ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ	በጋብቻ/በትዳር ላይ/ ከተጋቢዎች መካከል በአንደኛው ተጋቢ አማካኝነት በካሣ መልክ የተገኘ ሃብት የጋራ ሃብት/ንብረት/ ተደርጎ የሚቆጠር ስለመሆኑ	ህዳር 13/2000
121	27697	አቶ ርዕሶም ገ/መድህን እና ወ/ሮ አልማዝ ጊላ ሚካኤል	ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የጋራ ንብረት የተሸጠ ቢሆንም የሽያጩ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንደሚገኝ ካልተረጋገጠ ለጋራ ትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85 -93	ጥቅምት 19/2000
122	27869	ፍቅርና ሠላም ኃ/የተ/የግ/ማ እና እነ ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ (ሁለት ሰዎች)	• የማይንቀሳቀስ ንብረት ለንግድ ማህበር በመዋጮ መልክ የተሰጠ ሆኖ ሲገኝ የንብረቱ ስም በኩባንያው ተመዝግቦ ያለመገኘቱ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ለመሆን የማይችል ቢሆንም ንብረቱ በአይነት መዋጮ መሰጠቱን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ • የጋራ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ አንደኛው ተጋቢ ፈቃድ ለንግድ ማህበር በዓይነት መዋጮ የተሰጠ እንደሆነ ንብረቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 517(ሠ),(ረ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878 የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(1), 69(2)	ህዳር 10/2000
123	29343	እነ ወ/ሮ አምሳለ ተፈራ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ት አበባ አድማሱ	ተጋቢዎች በጋብቻ ወቅት **የተፈራ** ቤታቸውን በትርፍነት ለመንግስት ያስረከቡ እንደሆነ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት የሆነን ቤት ያለምንም ተጨማሪ ስምምነት የጋራ የሚያደርገው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67 አንቀፅ 11(1)	ሚያዝያ 7/2000
124	29402	ወ/ሮ ሐዳስ ታረቀ እና የ፱ አለቃ አስመላሽ ኃይለስላሴ	ቤት የጋራ ሃብት ነው ከተባለ ቤቱ የተሰራበት መሬት ላይ የጋራ ባለሃብቶቹ እኩል የመጠቀም መብት የሚኖራቸው	ጥቅምት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ስለመሆኑ	19/2000
125	30959	እነ ወ/ሮ ተወዳጅ ገ/ሥሌሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ዘለቀ ዘውዴ(ሁለት ሰዎች)	• ሟች በኑዛዜው አንድን ሰው ልጄ አይደለም በማለት መግለፅ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማፍረስ የሚያበቃ ስላለመሆኑ • በቤተሰብ ህጉ ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቻልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,156,157	ታህሳስ 1/2000
126	31430	ወ/ሮ አዲስአለም አከለ እና የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ	ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የሚገኝ ድጕማ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ የአማራ ብ/ክ/መ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 73(1) እና (2)	ሚያዝያ 7/2000
127	31891	እነ አቶ አንለይ እንየው (ሰባት ሰዎች) እና ወ/ሮ መሬም ጠሃ	የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረዥም ጊዜ መኖርና በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መስርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ተቋርጧል የሚያስብል ስለመሆኑ /የሰ/መ/ቁ. 14290/	ሚያዝያ 14/2000
128	31946	ወ/ሮ ዘውዲቱ ጌታቸው እና ተመስገን ደሳለኝ	የጋብቻ ውል በህግ አግባብ አልተደረገም በሚል ተቃውሞ ያቀረበ ተጋቢ በውሉ መሠረት ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 34(2), 35(2) እና 9(1)	ግንቦት 14/2000
129	32130	እነ እማዋይሽ ካሣ (ስድስት ሰዎች) እና ወ/ሮ አስቱር አህመድ	አንድን ሰው አባት ነው ብሎ ለማለት ለልጅ እንክብካቤ ማድረጉና ልጅም በእሱ ስም መጠራቱ ብቻ ሣይሆን ግለሰቡ ድርጊቱን አባት ነኝ ከሚል ስሜትና መንፈስ በመነጨ ያደርግ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የአማራ ክ/መ/ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 79/95 አንቀፅ 154(ሐ)(ሠ)	መጋቢት 18/2000
130	33411	ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ እና አለቃ ኪሮስ ገብሩ	ተጋቢዎች ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት ወቅት የገዙት ንብረት በስማቸው ያልዞረ ቢሆንም እንኳን ንብረቱ የእኔ ነው በሚል የቀረበ የ3ኛ ወገን ተቃውሞ እስካልቀረበ ድረስ ንብረቱ የጋራ ሀብት ተደርጐ የሚወሰድና ሊከፋፈል የሚገባ ስለመሆኑ	መጋቢት 25/2000
131	33440	ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም እና አቶ ግርማ ገብረ ስላሴ	• ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ጥያቄ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ • ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ የልደት ምስክር ወረቀት ተቃውሞ የማይቀርብበት የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ ሊወሰድ የማይችል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154	ሚያዝያ 21/2000
132	33875	ወ/ሮ የሻረግ አባትኩን እና ወ/ሮ መሠረት አድማሱ	ጋብቻ በባህላዊ መንገድ ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብና መመስረቱን ማስረዳት የሚቻልበት ሁኔታ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 4 እና 97(2)	መጋቢት 25/2000
133	34149	እነ ወ/ሮ ዘለቃሽ በቀለ እና አቶ አለሙ በቀለ	የአንድ ሰው አባት ነኝ በሚል የሚቀርብ ሰው አባትነቱን በህግ አግባብ በማስረጃ ማስረዳትና ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 147(1), 97(2)	መጋቢት 25/2000
134	34387	አቶ ክበደ መሐሌ እና ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ	የጡረታ አበል እንደማንኛውም ገቢ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተደርጐ የሚወሰድ ስላለመሆኑ	ግንቦት 14/2000
135	35376	እነ አቶ ዳንኤል አሰፋ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ሐሊን ውበቱ	ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት ላይ ያለን ዕዳ ለመወጣት ከጋብቻ በኃላ ከባልና ሚስት የጋራ ገንዘብ መከፈሉ ንብረቱን የጋራ ንብረት የማያደርገው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) እና 70(1)	ግንቦት 28/2000
136	23389	የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማ እና እነ ባህሩ አብርሃም (አስራ ሁለት ሰዎች)	የአክስዮን ማህበር አባላት የአክስዮን አስተዳዳሪዎች መብታቸውን በሚጐዳ መልኩ መስራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ በቀጥታ መክሰስ የሚችሉ ስለመሆናቸው የንግድ ህግ ቁ. 367	ሐምሌ 10/1999
137	25306	አቶ ተስፋዬ ገሰቴ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ገንዘብን በአደራ ለማድረስ የተቀበለ ባንክ አደራ አስቀማጩ ይሰጥልኝ ላለው ሰው እስካልሰጠ ድረስ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 898(1)	ህዳር 12/2000
138	27161	አቶ ኤልያስ ከፈለ እና እነ አቶ ከድር አህመድ (አራት ሰዎች)	የክሱ መሠረት የሆነው ጉዳይ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ የተረዳ ፍ/ቤት ክሱን መሰረዝ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280	ህዳር 12/2000
139	28923	የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር እና .እነ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር (ሁለት ሰዎች)	የመንግስት ልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማህበራት ሲቀየር በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያልታወቀና ውሣኔ ያልተሰጠበት እንኳን ቢሆን የልማት ድርጅቱ ዕዳ ወደ አክሲዮን ማህበር የማይተላለፍ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 208/92 አንቀፅ 5(1), 6(1)ሐ	ግንቦት 7/2000
140	23608	የኢትዮጵያ ፕራይቬትይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ እና የአቶ ኑርበዛ ተረጋ ወራሾች	በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲም ሆነ በኤጀንሲው ስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ እንደገና ለማየት ፍ/ቤቶች ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ.110/87 አንቀፅ 4(1) እና 5(3)	ህዳር 3/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

141	27548	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ወ/ሮ ቆፀላ መርሻ (ሁለት ሰዎች)	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አጠራጣሪነቱ በታወቀ ጊዜ ከሚመለከተው አካል ተገቢውን ማብራሪያና ማስረጃ ሳይጠየቅ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1196(1)	መጋቢት 18/2000
142	29822	የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ በቀለች አማረብህ	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ስልጣን ላለው የአስተዳደር ክፍል መመለስና መሰረዝ ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቶች የባለቤትነት ደብተሩ እንዳይመለስ በሚል ውሣኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ 1196(1)	ግንቦት 28/2000
143	29860	ወ/ሮ አስናቀች ሲሻው እና እነ ወ/ሮ አሰለፈች ከተማ (አራት ሰዎች)	በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የባለቤትነት መብት ለመንግስት የተላለፈ መሆኑን እንደመከራከሪያ በማንሳት መሟገት የሚችለው የሚመለከተው የመንግስት አካል እንጂ ግለሰብ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ 47/67 አንቀፅ 13(1)	መጋቢት 18/2000
144	31490	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ሴርኮ አስራኤላዊያን	ተከሳሽ የሆነ ወገን ካቀረባቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች መካከል ፍ/ቤቱ አንዱን ብቻ መሠረት በማድረግና ሌሎቹ ላይ ብይን ሣይሰጥ ክሱን ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ብይን ባልተሰጠባቸው መቃወሚያዎች ላይ ይግባኝ ማቅረብ የማይጠበቅበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244,341	ሚያዝያ 2/2000
145	31682	አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ዘላለም ይልማ ባልቻ (ሦስት ሰዎች)	ተወርሰዋል ተብለው በመንግስታዊና ህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ሥር ያሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሠረት በማድረግ ፍ/ቤቶች መወረስና አለመውረስን በተመለከተ ማስረጃዎችን መርምሮ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67 አዋጅ ቁ.110/87	መጋቢት 12/2000
146	32376	አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሽዋንግዛው	የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸው ቤቶች ላይ የባለቤትነት /የባለቤትነትን መፋለም/ ክርክር በተነሣ ጊዜ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የማይኖራቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 41(ረ)	ግንቦት 19/2000
147	34249	እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ እና እነ አቶ አለሙ ወንድሙ	በክርክር ተካፋይ እንዲሆን የሚያስፈልግ ወገንን ተከራካሪ ወገኖች እንዲገባ ያልጠየቁ ቢሆንም ፍ/ቤቶች ይህንኑ ወገን በራሳቸው ተነሣሽነት በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2)	ሚያዝያ 28/2000
148	22857	እነ አቶ ተክሌ ደግፌ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ በፍቃዱ ኃይሌ (ሁለት ሰዎች)	• በፍርድ ሂደት ላይ ያለ ጉዳይን ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በክርክሩ ማናቸውም ደረጃ ላይ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ በእርቅ እንዲያልቅ ለመጠየቅ የሚችሉ ስለመሆናቸው • በፅሁፍ ተዘጋጅቶ የቀረበ የእርቅ ስምምነት ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ስምምነቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን አረጋግጦ በፍ/ቤት የተያዘውን ጉዳይ ማቋረጥ የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 274(1),275,(1),277(1)	ታህሳስ 15/2000
149	25912	አቶ ብሩ ቆርቾ እና አቶ ክፍሌ ሐብደታ	የግልግል ስምምነት እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3312	ሚያዝያ 2/2000
150	29386	ወ/ሮ ወለላ ተሰማ እና እማሆይ በላይነሽ መለሰ	ከወራሾች መካከል አንዱ በሌለበት የተካሄደ የንብረት ክፍፍል በሌለበት ክፍያው የተፈፀመበት ወራሽ በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080	የካቲት 25/2000
151	30536	ወ/ት አለምነሽ ዋቅቶላ እና አቶ ይልቃል ጌጤ (ሁለት ሰዎች)	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ላደረሰ ወገን የመድን ሽፋን የሰጠ አካል በሃላፊነቱ መጠን ለተጎጂው መካሱ ተጎጂው በጉዳት አድራሹ ላይ የሚያቀርበውን ተጨማሪ (ቀሪ) የካሣ ጥያቄ የሚከለክል ስላለመሆኑ	መጋቢት 23/2000
152	20036	ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ	ጋብቻ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ለማሳየት /ለማረጋገጥ/ የሚቻል ስለመሆኑና ይህንንም ለማስረዳት ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ሊቀርብ ስለመቻሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 95,96 እና 97	ግንቦት 16/1998
153	25899	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ር ስዩም ካሣ	የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደሞዝ በሚያስገኝ የመንግስት ስራ ላይ ከተቀጠረ የቅጥሩ ሁኔታ በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ከደሞዝ በተጨማሪ የወሰደውን የጡረታ አበል መመለስ ያለበት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2)	ግንቦት 28/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

154	26480	የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ እና አቶ ቢንያም አለማየሁ	ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠባቸው ጉዳዩችን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ አዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 12/91 አንቀፅ 9(4)	ጥቅምት 14/2000
155	28883	ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ሚስተር ኒኮላ አስፓፓቻት ዚስ	ከተከራካሪ ወገን አንዱ የውጭ ሀገር ዜጋ ስለሆነ ብቻ ክርክሩ ሁልጊዜ የግለሰብ አለማቀፍ ሕግ ጥያቄ ያስነሳል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 11(2)ሀ	ህዳር 26/2000
156	29005	አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ግርማቸው ይላላ (ሁለት ሰዎች)	በክፍለ ከተማ ስልጣን ክልል ውስጥ የሚነሱ ክርክሮች ላይ ክፍለ ከተማው ጣልቃገብቶ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 10(2),30 አዋጅ ቁ. 18/97 አንቀፅ	ሚያዝያ 14/2000
157	30298	አቶ የሲወንድም አቡሐይ እና አቶ አየነው ማለደ	ጠፋ የተባለ ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹ የተሸጡ ከሆነ ለማግኘት መብት የሚኖረው የንብረቶቹን የሽያጭ ዋጋ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171(1)	ጥር/2000

ቅጽ 6

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
158	08751	ወ/ሮ አበበች በጅጋ እና እነ ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ (ሁለት ሰዎች)	• ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አዲስ ማስረጃ ተገኝቷል በሚል የተሰጠው ፍርድ በድጋሚ ሊታይ የሚችልበት አግባብ • ውሣኔ ያልተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6	ግንቦት 26/2000
159	19142	አቶ መላኩ ማሞ እና እነ ወ/ሮ ፈለቀች ማሞ (ሦስት ሰዎች)	የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጋር በተያያዘ በሚሰጥ ብይን ላይ ፍ/ቤቱ በሥረ- ነገር ረገድ የመጨረሻ ውሣኔ ሣይሰጥ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320 (3)	ጥቅምት 26/2000
160	20465	አዋሽ ኢንተርናሽናል ኩባንያ እና ፀሐይ ዮሐንስ የህፃን ተመስገን ቱጂ ሞግዚትና አሳዳሪ	በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሠረት የቤንሻንጉልን ጨምሮ የአምስት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ባላቸው የውክልና ስልጣን ያዩዋቸውን የፌዴራል ጉዳዩች በይግባኝ ተቀብለው የማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 322/95, የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(2)	ሰኔ 26/2000
161	21270	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ ወይንሸት አበራ	አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከመታገዱ በፊት በባንክ በመያዣነት የተያዘ እንደሆነ ባንኩ በህግ ተሰጠው መብት መገልገል ይችል ዘንድ ፍ/ቤት የሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ማስነሳት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 158, አዋጅ ቁ. 97/90	ሐምሌ 30/1999
162	22556	ታደሰ አብዛ እና እነ የአቶ ጐሳዬ ሩገቶ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	በክርክር አመራር ሂደት የተከራካሪ ወገኖች የመሰማት መብት ተግባራዊ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ	ጥቅምት 14/2000
163	22603	የድሬዳዋ ጊዜ/አስ/ቀበሌ 20 ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ሽሪፍ አሊ	ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ልዩነት ያላቸው በመሆናቸው ጥርጣሬን የፈጠሩ እንደሆነ ፍ/ቤት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ጥርጣሬ ያለበትን ጉዳይ አጥርቶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 255,257	ሐምሌ 26/1999
164	23363	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ፊርሀን አህመድ (ሦስት ሰዎች)	የመድን ሰጪ አካል ኃላፊነት በመድን ሽፋን ፖሊሲው ላይ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በላይ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 665(2)	ግንቦት 26/2000
165	23628	ሶሎ ሲርካርና ኤ.ኤስ እና እነ.ጌትያን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ (ሁለት ሰዎች)	በውጭ ሀገር ተመዝግቦ የህግ ሰውነት ያገኘ ኩባንያ በኢትዮጵያ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ አቅርቦ በሂደት ላይ ያለ መሆኑ በውጭ አገር ያገኘውን የህግ ሰውነት ቀሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 100	ጥቅምት 21/2000
166	23692	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ	• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጉም የሚችልበት አግባብና አፈፃፀሙ	ሐምሌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		እና እነ አሊ መሐመድ	• በሦስተኛ ወገን ተከሳሽነት በክርክር ውስጥ እንዲገባ የተደረገ ወገን ከተከሳሽ ጋር ከመሟገት በቀር ተከሳሹን ተክቶ ከሣሽን መከራከር አይችልም ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 687, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2), 43	03/1999
167	23744	አቶ በቀለ በድዬ እና እነ ወጋገን ባንክ አዋሳ ቅርንጫፍ (ሦስት ሰዎች)	ዳኝነት ሣይከፈል በነዋ ክስ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ጥያቄው በፍ/ቤት ትዕዛዝ /ውሣኔ/ ውድቅ የተደረገበት ተከራካሪ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320(1), (3)	ሐምሌ 26/1999
168	23769	ኢንጅነር ጋሪፉፋ እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናት ኢንስቲትዮት	ከአገልግሎት ብዛት ከጥቅም ውጭ የሚሆኑና ሊያስረክቧቸው የማይችሉ ዕቃዎች ላይ የዋጋ ግምታቸውን መጠየቅ የክሱ ምክንያት ቀሪ በሆነ ነገር ላይ ክስ እንደመመስረት የሚቆጠር ስለመሆኑ	ሐምሌ 12/1999
169	24111	የቂርቆስ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን እና ወ/ሮ የዕለተወርቅ ገ/አብ	የተከሳሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ተከሳሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተከሳሹ ሊያጣ የሚችለው መልሱን በውሁፍ የማቅረብ መብቱን ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 195	የካቲት 11/2000
170	24627	ዶ/ር ቤተልሄም ታደሰ እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ	ከቤት ባለቤትነት ክርክር ጋር በተያያዘ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በመመሪያ፣ በቀላጤ ወይም በቃል ትዕዛዝ ከግለሰቦች የተወሰደና በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ መሆኑ ካልተገለፀ በስተቀር ጉዳዩን ለማስተናገድ ፍ/ቤቶች ስልጣን የሚኖራቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.110/ 87 አንቀፅ 3(1)	ሚያዝያ 30/2000
171	24775	ማታዶር አዲስ ጉማ እና ቢተው ረታ	ተከሳሽ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ዕለት ባለመቅረቡ ብቻ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ በሚል የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241(1), 233	ጥቅምት 21/2000
172	25026	ወ/ሮ ሁዳ መሐመድ እና ሃጂ አህመድ አህመዲን	ተከሳሽ በራሱ ቸልተኝነት በታችኛው ፍርድ ቤት መከራከሪያ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነጥቦችን በስር ፍርድ ቤት ባላነሳበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ውሣኔ መስጠት የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 328(2) እና 182(2)	ግንቦት 14/2000
173	25890	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ዝናሽ አሰፋ (ሁለት ሰዎች)	ሌሎች ተከራካሪዎች በፍርድ ቤት በማካሄድ ላይ ባሉት ክርክር ያገባኛል የሚል 3ኛ ወገን ከውሣኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41	መጋቢት 18/2000
174	26670	አዲስ አለም ሲሳይ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ባለገንዘብ በፍርድ አፈፃፀም ከፍርድ ባለዕዳው የተረከበው ንብረት ከዕዳው በላይ ከሆነ ልዩነቱን ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 428(2)	ህዳር 03/2000
175	27739	አቶ ድንቁ ገላው እና ወ/ሮ ዋለ እሸቱ	ከመሬት ሽያጭ ውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለውና በፍ/ቤት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(2)	ጥቅምት 28/2000
176	27808	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ማይገነት ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች)	ከፍርድ በፊት የሚሰጥ የማገጃ ትዕዛዝ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነን ወገን የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ያገኘውን መብት የማይነካ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 153 (2)	የካቲት 7/2000
177	28522	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ የሞያሌ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት (አራት ሰዎች)	ውሣኔ የተሰጠበትና አዲስ ክስ የቀረበበት ክርክር የሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ የተለያየ ከሆነ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	ህዳር 3/2000
178	28802	እነ ወ/ሮ በየነች ይገዙ እና አቶ ሳሙኤል ዝቅአርጋቸው	በክስ በተጠየቀውና በታመነው መሰረት ውሣኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182(2)	ታህሳስ 8/2000
179	29738	የአፓርታማ 79/6 የመኖሪያ ቤት ንብረት ሥራ ማህበር እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እና ወ/ት ዘርአዳም አሰገኸኝ	የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ አይቶ መወሰን የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10(1)	ግንቦት 14/2000
180	29761	እነ አቶ ዳባ ደበሌ (አምስት ሰዎች) እና እነ የአቶ ደበበ ተፈራ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	ያላግባብ በመንግስት የተወረሰ ንብረትን ለማስመለስ ሲባል የሚቀርበው የፍትሐብሔር ክርክር በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር የማይወድቅ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ሀ)	ጥቅምት 14/2000
181	29780	እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ አለሙ እና ወ/ሮ ከተማሽ ቸርነት	አስቀድሞ ውሣኔ ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሌላ የክርክር ጭብጥ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	ጥር 29/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

182	30631	ወ/ሮ ዘቢዳ ሙሣ እና እነ ወ/ሮ አሻ የሱፍ (ሁለት ሰዎች)	በህገ ወጥ መንገድ ተወስዷል /ከአዋጅ ውጭ ተወርሷል/ የተባለ ቤትን ባለቤትነት በማጣራት ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 110/87	ህዳር 10/2000
183	30704	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአቶ በቀለ ወ/ማሪያም ወራሾች (ሦስት ሰዎች)	• አዋጅ ቁጥር 47/67"ን" መሠረት አድርጐ የምርጫ ቤቱ ተወስዷል /ተወርሷል/ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርበው መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ • በመንግስታዊና በህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ይመለሱልኝ እንዲሁም ውዝፍ ኪራይ ይከፈለኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ውሣኔ መስጠት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ የፍ/ቤት ስልጣን ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 110/87, አዋጅ ቁ. 47/67	መጋቢት 18/2000
184	31547	አቶ ኪዳኔ ገ/ጊዮርጊስ እና ወ/ሮ አብርሃ ተስፋሁን	ተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ባላመለከቱት ነገር ላይ ተመስርቶ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182	መጋቢት 7/2000
185	31833	ሀጅ አብዱልቃድር አህመድ እና እነ ወ/ሮ ደስታ ገ/ዮሐንስ (ሁለት ሰዎች)	በቤት ላይ የተደረገ እድሳትና ለውጥ ምን ያህል የመጠንና የአይነት ለውጥ እንዳመጣ ክርክር በተነሣ ጊዜ ልዩ አዋቂ መድቦ በማስጠናት መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136	ግንቦት 14/2000
186	32147	አቶ መሐመድ አብዱ እና አቶ አብዱራሂም አብዲ	የክስ ምክንያት የሌለው አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው በመሆኑ ተከሳሽ የሆነውን ወገን መጥራት ሳያስፈልግ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(1) (ሀ)	መጋቢት 9/2000
187	32376	የኢቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሽዋንግዛው	ከቤት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ባለቤትነትን የመፈለም ክስ ለማየት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ረ)	ግንቦት 19/2000
188	32638	የቂርቆስ ክ/ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና እነ አቶ ይርጋ ንጋኔ (አራት ሰዎች)	ወደ ክርክር መግባት ያለበት አካል በክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆን የተወሰነው ውሣኔ መብቱን የሚነካ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔው ከመፈፀሙ በፊት ውሣኔው እንዲነሳና ክርክሩ እርሱ ባለበት እንዲቀጥል መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358	መጋቢት 12/2000
189	33606	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ደጀኔ አበበ (አምስት ሰዎች)	በጊዜያዊነት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ ከተደረገ በኋላም ቢሆን በድጋሚ በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ሊቀርብ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158	የካቲት 20/2000
190	34249	እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ እና እነ አቶ አለሙ ወንድሙ	ለክርክር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ የሚታመን ወገን በመካሄድ ላይ በሚገኝ ክርክር ተካፋይ እንዲሆን መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2)	ሚያዝያ 28/2000
191	34313	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ከበደ ታደሰ	የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብ ተከሳሽ ኃላፊነት የሚመነጨው ከተከሳሹ ኃላፊነት ስለመሆኑ እና የሦስተኛ ወገን ተከሳሽ ተጠያቂ የሚሆነው ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ ሲኖር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43(1)	መጋቢት 25/2000
192	35403	አቶ አብዱልአጠፍ ሙሐ እና እነ ትዕግስት በርሃ (ሁለት ሰዎች)	• ተከሳሽ ቀርቦ ያልተከራከረው በበቂ ምክንያት ማለትም መጥሪያ ሳይደርሰው መሆኑ ከተረጋገጠ የተወሰነውን ውሣኔ በማንሳት ግራ ቀኙን ማከራከር የሚገባ ስለመሆኑ • ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆነን ወገን መከላከያ ክርክር ሳይሰማ በማለፍ ውሣኔ ለመስጠት የሚችለው ተከራካሪው በችሎት ሳይቀርብ የቀረው በቂ ባልሆነ ምክንያት መሆኑን በቀረቡለት ማስረጃዎች ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.78	ግንቦት 14/2000
193	22008	የኪራይ ቤቶች አ/ድርጅት እና እነ አቶ አሳና ጥርቅ (ሦስት ሰዎች)	መክፈል የማይገባውን የከፈለ ወገን እንዲመለስለት መጠየቅ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2164	ሐምሌ 3/1999
194	22297	የጀሚ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት እና አቶ ሸዋረገድ አድበር	በፍ/ብሔር ክርክር ሂደት ማን ክርክር መጀመርና ማስረዳት እንዳለበትና የተሻለ ማስረጃ ከማቅረብ አንፃር ለማን ፍርድ ሊሰጥ እንደሚገባ በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን የህግ መርሆዎች ወደጐን በመተው የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ	ሐምሌ 24/1999
195	22469	የጀጀጋ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክ እና እነ አዳነች መንግስቱ (ሰባት ሰዎች)	• የህዝብ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ • የቤተክርስቲያንን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማረጋገጥ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ አስገዳጅ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1578	ሐምሌ 5/1999

https://t.me/ethiopianlegalbrief

196	22719	የአ/አ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተተኪ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን እና አቶ ነጋሽ ዱባለ	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን አስመልክቶ በሚመለከተው አካል የሚሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰረዘ በኋላ በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195	ጥቅምት 14/2000
197	23608	የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽና የመንግስት ልማት ድርጅት እና አቶ ኑርበዛ ተረጋ	• የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው ለኤጀንሲው የስራ አመራር ቦርድ እንጂ ለፍ/ቤት ስላለመሆኑ • የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና አሣሪ (Binding) ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.110/87	ህዳር 3/2000
198	24269	የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና ተክለማሪያም መኮንን	• ግለሰቦች በከተማ ቦታ የመጠቀም /የመያዝ/ መብት የሚኖራቸው አግባብ ባለው መንግስት አካል /ባለሥልጣን/ ተፈቅዶ ሲሰጣቸው ስለመሆኑ • ከሚመለከተው ባለስልጣን ፈቃድ ሳይኖር የተሰራ የከተማ ቤት ህጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 292/78 አንቀፅ 7(1)	ህዳር 24/2000
199	26130	አቶ ገ/እግዚያብሔር ከበደው እና ወ/ት ሰላማዊት ወ/ንብርኤል	• የከተማ ቦታ በግል ባለቤትነት ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ • ግለሰቦች በመሬት ላይ ሊኖራቸው የሚችለው የይዞታ መብት እንጂ የባለቤትነት መብት ስላለመሆኑ • ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ የግል ይዞታ ሥር የነበረ መሬት ላይ በጋብቻ ወቅት የጋራ ቤት የተሰራ እንደሆነ ተጋቢዎቹ በመሬቱ ይዞታም ሆነ በቤቱ ላይ እኩል መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67 የኢ...ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 40(3) የትግራይ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85	የካቲት 4/2000
200	27506	እነ ሣሙኤል ውብሸት እና ብዙነህ በላይነህ	• ሁከት እንዲወገድ በሚል በቀረበ ክስ ላይ ተከሳሽ የሚያነሳው ባለቤትነትን የተመለከተ ክርክር አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ • ሁከት ይወገድልኝ በሚል ክስ በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ሊይዝ የሚገባው ጭብጥ ሁከት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም የሚል ጥያቄ አዘል መሆን ያለበት ስለመሆኑ	ሐምሌ 19/1999
201	27600	ሕብረት ባንክ አክሲዮን ማህበር እና እነ አቶ ጀማል መሐመድ (ሁለት ሰዎች)	በመያዣ በተያዘ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በማሻሻልም ሆነ ሌሎች አዲስ የሚሰሩ ስራዎች መያዣው የሚያጠቃልላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.30666	ታህሳስ 06/2000
202	29005	አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ግርማቸው ይላላ (ሁለት ሰዎች)	በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኙና በየክፍለ ከተማው የተደራጁ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤቶች ራሳቸውን የቻሉ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆኑና በስልጣን ክልላቸው ሥር በሚነሱ ክርክሮች ተካሳይ የመሆን መብት ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 36/95 አንቀፅ 10(2) አዋጅ ቁ. 1/95 /አዋጅ ቁ. 18/97	ሚያዝያ 14/2000
203	30101	አቶ ገዛኸኝ አድነው እና እነ ወ/ሮ ዳሳሽ ባይነሳኝ (ሦስት ሰዎች)	በሌላ ሰው የመሬት ይዞታ ላይ በባለይዞታው ፈቃድ ህንፃ የሠራ ሰው የህንፃውን ግምት ተቀብሎ ህንፃውን ለማስረከብ የማይገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179(1) እና (2)	ህዳር 24/2000
204	30461	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ኢማ መሐመድ	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መሬትና ድንጋይ ነክ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን በነፃ መጠቀም የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 80/89 አንቀፅ 6(18)	ህዳር 3/2000
205	33499	አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ዶቶር ደሌቦ	ለጊዜው ለመኖሪያነት የተሰጠ ቦታ ላይ ሳያስፈቅዱ ቤት መስራት የተሰራውን ቤት በገንዘው ወጪ እንዲፈርስ የሚያስደርግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1178(2)	መጋቢት 25/2000
206	33711	በቀድሞ ወረዳ 3 ቀበሌ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ክብርነሽ ቀደመ	የቤት ባለቤት ሳይሆን ወይም ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለኪራይ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስ የሚቀርብ አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ	መጋቢት 23/2000
207	33831	ሃሰን ኢብራሂም እና ኢብራሂም ይመር ሃሰን	በህግ በግልጽ የተረጋገጠ መብት እያለ በህሊና ግምት ላይ የተመሰረተ ፍርድ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ	ሚያዝያ 14/2000
208	33924	ወ/ሮ ገብርኤላ ኒኮላቶማስ እና	ከቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ክስ የሚያቀርብ ሰው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ሁልግዜም ቢሆን በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም ሊኖረው አይችልም ብሎ ለመደምደም የማይቻል ስለመሆኑ	ሚያዝያ 16/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		የኪራይቤቶች ኤጀንሲ	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1)	
209	34406	ወ/ሮ መገርቱ ነጋሣ እና እነ ወ/ሮ ፀሃይ ልጋ	ያላግባብ መበልፀግ ጋር በተያያዘ የሚነሳ የካሣ ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ ከውል ውጭ በሚደርስ ሃላፊነት ሥር የተመለከተው የይርጋ ዘመን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1)	ሚያዝያ 7/2000
210	20295	አቶ ደጀኔ ለገሠ እና እነ አቶ መላኩ ጌታቸው	ወራሽነትን ካረጋገጡ በኋላ ንብረት ተይዞብኛል ይመለስልኝ የሚል ጥያቄ ከሦስት አመት በኋላ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1)	ሐምሌ 5/1999
211	25567	ወ/ት አይናለም አበበ እና አቶ ደገፉ ጉርሙ	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000 ወራሽ ነኝ ወይም ወራሽነቱ ይረጋገጥልኝ ከሚል ጥያቄ ጀምሮ የውርስ ንብረት ያለ አግባብ ተይዞብኛል በሚል ለሚቀርብ አቤቱታ ጭምር ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 999, 1000	ህዳር 12/2000
212	25664	አቶ ተገኝ ይማም እና እነ አቶ ካሣሁን ደሳለኝ	በወራሾችና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ የውርስ ንብረትን የተመለከተ ክርክር በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845	ግንቦት 7/2000
213	26422	ወ/ሮ ስንልሽ ማዘንጊያ እና እነ አቶ ተስፋ ማዘንጊያ	ከውርስ ሀብት ጋር በተያያዘ ወራሽ ነኝ የሚል ወገን መብቱንና የውርስ ንብረቶቹ በሌላ ወራሽ መያዛቸውን ካወቀ ከሦስት ዓመት በኋላ የሚያቀርበው የወራሽነት ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1)	ጥቅምት 28/2000
214	28686	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ግዛው መንጀታ	ውል የመጣስ ተግባር ተጀምሮ ያልቆመ ይልቁንም በመቀጠል ላይ ያለ ተግባር መሆኑ በማናቸውም ጊዜ ግዴታን ለመጠየቅ የሚያስችል ስለመሆኑና በይርጋ ታግዷል ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845, 1846	ህዳር 24/2000
215	28997	ስለ አሶሳ ዞን ግብርና እና ትምህርት መምሪያ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ እና በላይ ወርቁ	የመብት ጥያቄን ከፍርድ ቤት ውጪ ላሉ አስተዳደር አካላት ማቅረብ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1851(ለ)	ታህሳስ 1/2000
216	29920	የባህር ዳር ጨ/ጨ/አ/ማኅበር እና አቶ አመሸ ሰይድ	ዳኝነት የተጠየቀበት ነገር ተቀባይነት ሣያገኝ የታሰፈ እንደሆነ እንደተከለከለ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(3)	ጥቅምት 26/2000
217	31185	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ይርጋ በተቋረጠ ጊዜ ቀድሞ የነበረው የይርጋ ጊዜ እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1852(1)	ግንቦት 12/2000
218	31217	የቴሌኮምኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ጫሊ ሐሰን	የደሞዝ ጭማሪና ቦነስን የተመለከተ ክስ በስድስት ወር ውስጥ አለመቅረቡ መብቱን በይርጋ የሚያሳግድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162(3)	ግንቦት 14/2000
219	31857	መሐመድ አብደላ እና የድሬዳዋ ኢትዮ ጂቡቲ ምድር ባቡር	የአሰሪ የስራ ስንብት እርምጃ የመውሰድ መብት ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከተከሰተበት ጀምሮ በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ተግባራዊ ካልሆነ መብቱ በይርጋ የሚቀር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/97 አንቀፅ 27(3)	መጋቢት 17/2000
220	32788	የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና አቶ ግርማ ተገኝ	አሠሪ የሠራተኛን መብት በጽሁፍ ያወቀ መሆኑ ሠራተኛው በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ገደብ የሚያቋርጥ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 164(3)	መጋቢት 18/2000
221	34011	እልፍነሽ አማረ እና አቶ ግርማ አማረ	ቤት በፍ/ብሔር ህጉ ውስጥ እንደ ርስት የማይቆጠርና የይርጋ መርሆ ተፈፃሚ የሚሆንበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(2)	መጋቢት 25/2000
222	31748	ይስማው ድረስ እና ይበልጣፍ ፍቅር	ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ የሚገዛው የህግ ክፍል ይርጋን አስመልክቶ በተለይ የሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ በሌለ ጊዜ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845	የካቲት 18/2000
223	18832	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ክበደ ቱሉ (ስድስት ሰዎች)	ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ የተወሰነው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የስራ ውሉ ያለ በቂ ምክንያት ከተቋረጠ ሠራተኛው የውሉ ጊዜ ወይም ስራው እንኪያልቅ ቢቆይ ያገኘው የነበረውን ደሞዝ የሚያህል ደሞዝ የሚከፈለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43(4)(ለ)	ህዳር 3/2000
224	20416	አቶ ቢንያም ገረመው	ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ	ታህሣሥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		እና የቻይና መንገድና ድልድል ስራ ድርጅት	ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ከሆነ ክሱ እንዲሻሻልና ክርክሩ እንዲለወጥ ሊፈቀድ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91	8/2000
225	21329	የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ በቀለ ኩምላ	የሥራ መሪ የሆነ ሰው የሥራ ውሉ ተቋርጧል በሚል ማይሰራ ለቆየበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለው የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	ጥቅምት 19/2000
226	22275	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ኃይሌ ገ/ሥላሴ	• አሰሪ የሥራ ውሉ ዘመን ከማለቁ በፊትም ቢሆን በቂና ህጋዊ ምክንያት ካለው የሠራተኛን የሥራ ውል ሊያቋርጥ ስለመቻሉ • በበቂ ምክንያት የተደረገ የሥራ ውል ማቋረጥ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠም በሚል ህገ-ወጥ ስንብት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ • በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለን የስራ መደብ በሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የሥር ውል ለማቋረጥ ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 35	ሐምሌ 10/1999
227	25317	ጥቁር አባይ ትራንስፖርት እና ደሳለኝ አብርሃ	በህገ ወጥ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ በሞተ ጊዜ ለጥገኞቹ ክፍያ የሚፈፀምበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/ 96 አንቀፅ 39(2),110(2), 40	ህዳር 10/2000
228	25511	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ አብራራው ከፍያለው	በህጋዊ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 39	ጥቅምት 2/2000
229	26077	አቶ አይናለም ባይሌ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ከተደነገገው ይልቅ በአሰሪና ሠራተኛው መካከል የሚደረገው የህብረት ስምምነት ለሠራተኛው የተሻለ መብትና ጥቅም የሚያስገኝ በሆነ ጊዜ የህብረት ስምምነቱ ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 134(2)	ሐምሌ 12/1999
230	27704	ድራጋዶስ ጂ እና ፒ የመንገድ ስራ ድርጅት እና አብዲ ሁሴን	የሥራ ውሉ በህገ-ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል ወደሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ ካልሆነ በስተቀር ውዝፍ ደመወዝ የማይከፈል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5)	ጥቅምት 5/2000
231	27959	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ አሊ መሐመድ	• አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ተቋርጦ ለነበረበት ጊዜ የዓመት ዕረፍት ሊያገኝ የማይችል ስለመሆኑ • የዓመት ፈቃድ ከሁለት ዓመታት በላይ ሊተላለፍ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 79(5)	ህዳር 3/2000
232	29692	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ከበደ	አሠሪ ቋሚ ስራ ሆኖ እየተቋረጠ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ እንዳለቀ የሠራተኛን ውል ለማቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ	ጥቅምት 12/2000
233	29740	አቶ ስሜነህ ተክሉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ	ፍርድ ቤቶች በቀረበ ክስ ላይ የዕዳ ማቻቻል ጥያቄ በተነሣ ጊዜ ማስረጃዎችን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ	ሚያዝያ 2/2000
234	29866	ቻይና ዋንቦ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን እና ወርቅነህ ምህረቱ	የውክልና ስልጣን ማስረጃ በወካይና በተወካይ መካከል የቅጥር ውል ስለመኖሩ የሚያስረዳ ስላለመሆኑ	ግንቦት 7/2000
235	29949	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ዋሲሁን አዳነ	ፍርድ ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ የሚሰጥ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ	ሐምሌ 19/1999
236	30956	የወረዳ 5 አጠቃላይ ነጋዴዎች ማህበር እና አቶ በድሉ ጫላ	ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ	ሚያዝያ 9/2000
237	31402	የኢትዮጵያ አገር አቋራጭ ከፍተኛ አውቶብስ የግል ባለንብረቶች ማህበር እና አቶ አያሌው ይርጉ	በጡረታ የተገለለን ወይም የጡረታ ዕድሜው ያለፈን ሠራተኛ ወደ ሥራ መልስ ተብሎ አሰሪ የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 24(3) አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀፅ 12(1)(ሐ)	ሚያዝያ 30/2000
238	32545	አቶ ግርማ ሽፈራው እና የክርስቲያን በጐ አድራጐት ልማት ድርጅት	የፕሮቪደንት ፈንድ ባለመብት የሆነ ሰው በአስር አመት ውስጥ መብቱን ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845	ግንቦት 14/2000
239	33314	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ወልዴ	በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ የነበረን ፋብሪካ የተረከበ ባንክ ከሠራተኞች መብቶች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጥ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 16	ግንቦት 28/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		(አስር ሰዎች)	አዋጅ ቁ. 97/90	
240	33513	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ዘውዴ ተናኘ	በአንድ የስራ መደብ ላይ በቋሚነት የደረጃ እድገት ይሰጠኝ በማለት የሚቀርብ ክስን ለማየት የክልል ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 138	ጥር 27/2000
241	34588	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ደረጀ ወልደ ኪዳን	በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ የተባለ ሰው በፍትሐብሔር ረገድ ከቀረበበት ክስም የማድ ነፃ ይሆናል ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27	ግንቦት 5/2000
242	35440	የዋልያ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ድርጅት እና ብርሃኑ አለሜ	ከሠራተኞች ማህበር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር በአሰሪ የሚደረግ የሠራተኞች ቅነሳ የህግ አግባብ ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28(1)	ግንቦት 19/2000
243	29415	ዋተር አክሽን እና ይልማ አሰፋ	አዲስ ወደ ተዛወሩበት ቦታ በመሄድ ስራ አለመጀመር እና ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ገበታ ላይ አለመገኘት በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውልን ለማቋረጥ በቂና ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2)(ለ)	ጥር 27/2000
244	32822	ጂ.ሰቨን የንግድና ኢንዱስትሪ የመኸር ቃጫ ውጤቶች ፋብሪካ እና መኮንን አበራ	ያለ በቂ ምክንያት ከስራ መቅረት አሠሪ የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) (ለ)	ጥር 27/2000
245	32229	መሪጌታ ልሣነወርቅ በዛብህ እና ጠቅላይ ቤ/ክህነት ጽ/ቤት	የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሣኔ መሻር ሳያስፈልገው ጉዳዩ ስልጣን ወዳለው አካል ቀርቦ መታየት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	ሚያዝያ 30/2000

ቅጽ 7

ተ.ቁ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን
246	12719	ሉክሰር የቱሪስትና የጉዞ ወኪል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እና ብሩኔይስ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር	በሁለት ወገኖች መካከል የተፈረመ ሰነድን እንደ ህጋዊ ስምምነት ለመውሰድ የፈራሚ ወገኖችን ሃሳብና ፍላጐት መመርመር አስፈላጊ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1734, 1952/1/	ታህሳስ 17/2000
247	20232	አቶ ትዕግስቱ ብዛ እና አቶ ይሃ ይብራ	የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች የሚፈጠሩባቸውና የሚረጋገጡባቸው በመሆናቸው የውል ህግ መሰረታዊ ድንጋጌዎች መሟላታቸው አስፈላጊ ሁኔታ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 715, የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706, 1679	ሐምሌ 24/1999
248	23609	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አሰበወርቅ ዘገዬ	የስራ መሪ የሥራ ውል ያለአግባብ በተቋረጠ ጊዜ የስራ መሪው ሊያገኝ ስለሚገባው ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና ጥቅማጥቅም የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2573, 2574/2/, 2570/2/, 2577, 2562	ታህሳስ 15/2000
249	30298	አቶ የሺወንድም አቡሃይ እና አቶ አየነው ማለደ	የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው ንብረቱ ወደ 3ኛ ወገን የተላለፈ በሆነ ጊዜ የንብረቱን ዋጋ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171	ጥር 20/2000
250	16218	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ወ/ሮ አስካለ ሁንዴ(ሁለት ሰዎች)	ባንኮች ከሚሰጡት ብድር እና የመያዣ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች አዋጅ ቁ. 97/90"ን" ዓላማ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በባንኮች የሚወጡትን የፎርክሎዠር መመሪያዎችና አግባብነት ያላቸውን ህግጋት ግምት ውስጥ በማስገባት አልባት ማግኘት ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 እና 4, አዋጅ ቁ. 216/92	መጋቢት 16/2000
251	25863	የኢት/ልማት ባንክ እና የኢት/ንግድ ባንክ (ሁለት ሰዎች)	ለባንክ በመያዣነት በተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚኖር የቀዳሚነት መብት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3088, 3052, 3081,3059	ጥቅምት 26/2000
252	29269	የኢት/ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ዋለልኝ አያሌው(ሁለት ሰዎች)	• በፍርድ የተቋቋመ መያዣ ላይ ፍርዱ እንዲሰጥ ያደረገው ባለገንዘብ መያዣ በሆነው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ እና • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 ተፈፃሚነት የአንድ ፍርድ ባለዕዳ ንብረት በእርሱ ላይ የቀረቡትን ገንዘብ ጠያቂዎች	ጥቅምት 15/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ፍላጐት የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ክፍፍሉ ጋር በተገናኘ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3041, 3044, 3059/1/, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403,154	
253	29375	የት/ንግድ ባንክ እና ተስፋዬ ገ/ጊዮርጊስ	የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት ከተሰጠ በኋላ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ የሚደረግ ማናቸውም የማሻሻል ሥራ የመያዣ ውሉ አካል ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3066 አዋጅ ቁ. 97/90	ጥቅምት 19/2000
254	33295	ወ/ሪት ብርሃኔ አበበ እና እነ አቶ ማርቆስ ተርፋ (አራት ሰዎች)	የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማንኛቸውም ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ ርስተ መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ምንም አይነት ውጤት የማያስገኝ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3052, 3053,1605, 1607, 1606	ግንቦት 21/2000
255	23024	ወ/ሮ ፋጤ በሽር እና መልዓክ ገነት ዮሐንስ አምባው እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ	በጣልቃ ገብነት ተሳታፊ ሆኖ የፍርድ ተጠቃሚ የሆነ ወገን ዋና ተከራካሪ ከሆኑት ወገኖች መካከል በአንዱ አነሣሽነት ጉዳዩ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ በሥር ፍርድ ተጠቃሚ የሆነው ጣልቃ ገብ ባልተጠራበት ሁኔታ የሚሰጥ ውሣኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40/5/"ን" የሚፃረር ስለመሆኑ	ሐምሌ 24/1999
256	24221	ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና 4እነ ወ/ሮ አረጋሽ አምደሚካኤል	ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ጋር የተደረገን የኪራይ ውል መሰረት በማድረግ የተያዘ ቤትን ያለአከራዩ ፍቃድ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ለኪራይ ውሉ መሰረዝ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ	ህዳር 24/2000
257	25938	ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና የአቶ ገ/ሕይወት ከ7ዶም ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	የኪራይ ውል የተለየ ፎርም መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የሌለ ስለመሆኑ እና በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚፀና ውል /ህጋዊ ውጤት ያለው ውል/ ለመመስረት በሁለቱም መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719/1/,1719-1930, 2898/3/	መጋቢት 25/2000
258	28025	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ታደለ አበበ	ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ለተከራዩ በሚሰጥ ማስታወቂያ በማናቸውም ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ እና የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ/ለማፍረስ ለተከራዩ ማስታወቂያ /ማስጠንቀቂያ/ መስጠት አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966/1/	ጥር 20/2000
259	31601	ወ/ሮ መዓዛ ይሕደጐ እና እነ አየለ ወልዴ (ሁለት ሰዎች)	የኪራይ ውል ተቋርጦ ውዝፍ ኪራይ እንዲከፈልኝና ቤቱንም ልረከብ በሚል የሚጠየቅ ዳኝነት የኪራይ ገንዘብ የተጠየቀበትን ቤት ግምት ጭምር ታሳቢ ተደርጐ የዳኝነት ክፍያ ሊቀርብበት የሚገባ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 227/2/, 226	የካቲት 11/2000
260	31634	ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአቶ ወርቁ ሚስት ወ/ሮ ጽጌ በየነ (ሰባት ሰዎች)	መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ እስከ 2 ዓመት ድረስ ሳይከፈል የቀረ የኪራይ ዕዳ እንደተከፈለ የህግ ግምት ይወስድበታል ማለት ባለንገዘቡ /አከራዩ/ ክስ መስርቶም ቢሆን ዕዳውን ለማሰብሰብ የማይችል መሆኑን ለማመላከት እንጂ ተከራዩ /ባለዕዳው/ ግዴታውን እንደተወጣ የሚያስቆጥረው ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/መ/	መጋቢት 4/2000
261	32521	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ዳባ ኢጃቶ	የታወቀ የኪራይ ውል ግንኙነት ሳይኖር ወይም ባለቤት ሳይሆኑ በማይንቀሳቀስ ንብረት መገልገል የተገለገለውን ወገን በንብረቱ በበለፀገው መጠን ኃላፊ የሚያደርገው ስለመሆኑ	ሚያዝያ 7/2000
262	34456	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና ወ/ት ደብሪቱ ወልደሃና	ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ውሉ የተደረገበት ጊዜ ካለቀና ውሉ ወደ ያልተወሰነ ጊዜ ከተቀየረ የኪራይ ውሉን በማናቸውም ጊዜ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966	ግንቦት 14/2000
263	18380	አቶ ማሞ ደምሴ እና እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር (ሁለት ሰዎች)	ውል ይጽደቅልኝ በሚል ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1//ሀ/	ጥቅምት 5/2000
264	22448	ኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ክፍል አ/ማህበር እና አቶ መሉነህ ካሰ	ፍርድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ ችሎታ ያለው ፍርድ የተፈረደለት ሰው /ወገን/ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378/1/	ጥቅምት 28/2000
265	22860	ስንላይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ እና አቶ ካሣዬ ዘውደ	አንድ ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት ህጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ያዘዘ ካልሆነ በቀር ግዴታው መኖሩን በጽሁፍ፣ በምስክር፣ በህሊና ግምት በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሃላ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2002	የካቲት 18/2000
266	23331	ጀማል ሐሚድ እና እነ ወ/ሮ ለተሃይማኖት ተክሌ (አምስት ሰዎች)	በህግ ፀንቶ ያለ የሽያጭ ውልን መሰረት በማድረግ የተገኘ መብት ውሉ ፈራሽ እስካልተደረገ ድረስ የሚቀጥል ስለመሆኑ	ታህሳስ 1/2000
267	24974	እነ አቶ ፈቃዱ ደሬሌ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ንጉሴ ወርቁ (ሁለት ሰዎች)	በውል ከተገባ ግዴታ አመፃኙ ክፍል ተፈፀመ ወይም/እና አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተከስቷል ለማለት ባልተቻለ ጊዜ ውል እንዲሰረዝ ለመወሰን የማይቻል ስለመሆኑ	ታህሳስ 8/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771,1784, 1785	
268	26996	አቶ በቀለ ደቦጭ እና እነ ወ/ሮ አዛለች ደግለኝ (ሰባት ሰዎች)	ውል የተደረገበት ጉዳይ ሊፈፀም የማይችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ቦታ የመመለስ ውጤት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1715, 1815	የካቲት 18/2000
269	27349	ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኪባንያ እና ዘላቂ ግብርና ተሐድሶ ኮሚሽን	ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚፈጠርን አለመግባባት በስምምነት ወይም ደግሞ በአስታራቂ አማካኝነት ለመፍታት የተስማሙ ከሆነ ይኼው ስምምነት ተፈፃሚ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1765, 1731/1/	ታህሳስ 8/2000
270	28663	አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ እና ወ/ሮ አልማዝ ወልደ	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658 ተጋቢ ወገን ከሦስተኛ ወገን ጋር ያደረገውን ውል ለማፍረስ ምክንያት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658, 686	ጥር 27/2000
271	29233	አቶ ሙሂዲን ፋሪስ እና አቶ እያሱ በዕደ ማርያም	በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተደረገ ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሰረት የተሟላ አይደለም በሚል ውሣኔ ሲሰጥ ተዋዋይ የነበሩ ወገኖች በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815 መሰረት ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1720/1/, 1815	ግንቦት 7/2000
272	32222	አቶ መሐመድ ኢብራሂም እና አቶ ታይደር ማች	ያልነበረ ቤትን ሠርቶ ለማስተላለፍ በሚል የሚደረግ ስምምነትን በተመለከተ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2876, 1723, 3019, 3020/2/	የካቲት 4/2000
273	32899	ወ/ሮ አስካለ ማርያም ታደሰ እና አቶ ተሾመ ካሣዬ	የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን በተመለከተ የተደረገ የሽያጭ ውል ተቀብሎ ከማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ ከማያያዝና ከመፃፍ በስተቀር የሽያጭ ውሉን የማዋዋልና የማረጋገጥ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ	ግንቦት 21/2000
274	23322	ወ/ሮ አዳነች ወርዶፋ እና እነ ወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ	የውርስ ሀብት አጣሪ የንብረት ባለቤትነትን የመወሰን ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 956	ሰኔ 19/2000
275	25869	ወ/ሮ አየለች አልታዬ እና ወ/ሮ አስናቀች አየለ	የማይንቀሳቀስ ንብረት የጋራ ባለሀብት የሆኑ ሰዎች ንብረቱን በአይነት ለመከፋፈል ባልቻሉ ጊዜ ንብረቱ በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡን መካፈል ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1272, 1273	ሰኔ 19/2000
276	30158	እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞግዚት ሐይሉ ሲሳይ እና የክ/ል እሸቱ ተስፋዬ ወራሾች	በፍ/ብ/ህጉ ውስጥ "ከዘር የወረደ ርስት" በሚል የተቀረበው አገላለጽ በህገ-መንግስቱ የተሻረ ወይም ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000/2/ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 40	ሰኔ 19/2000
277	32414	ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ እና እነ ወ/ሮ ሃሳብከፋይ ጌራወርቅ (ሁለት ሰዎች)	ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርብ ክስ እና የተሰጠ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ በሚል የሚቀርብ ተቃውሞ የተለያዩ ይዘትና ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996/1/, 998/1/, 973, 996/2/	ሰኔ 24/2000
278	34076	ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ እና እነ እማሆይ ድብቅነሽ ግዛው (ሁለት ሰዎች)	የውርስ ሃብቶች በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ በሆነ ጊዜ የሚነሱ ክርክሮች የውርሱ ክፍያ በተጀመረበት ቦታ ለሚገኝ ፍ/ቤት የሚቀርቡና የሚስተናገዱ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 23	ሰኔ 10/2000
279	24703	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ት/ቢሮ	በህግ ተቀባይነት ያለው የኢንሹራንስ ውል የሚቋቋምበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1725, 1727 የንግድ ህግ ቁጥር 651, 654, 657	ሚያዝያ 9/1999
280	22069	የአማራ ብ/ክ/መንግስት ፍትሕ ቢሮ እና አቶ አስማማው አራጌ	በወንጀል ህግ የሃሳብ ክፍል የሚረጋገጠው ከወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ በመነሳት ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ቁ. 522 /1/ /ሀ/	ጥቅምት 28/2000
281	22452	የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና አሣምነው ገ/መስቀል	በወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ ሥር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሳቸው የሚቆሙ ስለመሆናቸው የወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/	ሐምሌ 30/2000
282	23855	የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ እና አቶ ፀጋሁን መንግስቱ	የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈፀምበት የመንግስት ቀረጥ ያልተከፈለበት መኪና ይዞ የተገኘ ግለሰብ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ ያልተባለ ቢሆንም ግለሰቡ ተገቢውን ቀረጥ ከፍሎ መኪናውን መረከብ አልያም ደግሞ መኪናው መወረስ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 74 አዋጅ ቁ. 388/95 አንቀጽ 80/3/	ጥቅምት 26/2000
283	24278	ሰለሞን ሄርጃቦ እና የደ/ብ/ብ/ ሕ/ክ/መ/ የሥ/ፀ/መ/ኮ/ዓ/ሕግ	በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ መሠት የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው እንዲጠብቃቸው በአደራ የተረከባቸውን ወይም በሥራው አጋጣሚና ምክንያት በእጁ የገቡትን ንብረቶች የወሰደው/የሰወረው/ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ	ህዳር 10/2000
284	28952	የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ እና	በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/ መሠረት ከሣሽ አቅርቦት የነበረውን ክስ ካነሣ በኋላ እንደገና ክሱን ለመቀጠል የሚችል ስለመሆኑ	መጋቢት 16/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		አቶ ባንቲ ታኤራ	የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/, /5/	
285	29325	ኤርምያስ ካሣ ተፈራ እና ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ክስ የቀረበበት ሰውን አስመልክቶ ጉዳዩ በሌለበት ነው የታየው ሊባል የሚችልበት አግባብ የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ. 161/1/	የካቲት 18/2000
286	31734	አቶ አስናቀ በቀለ እና ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ተከሶ የተያዘ ሰው ዋስትና በጠየቀ ጊዜ ፍ/ቤት ተከሳሹ ተመልሶ ሊቀርብ አይችልም የሚል ግምት ለመውሰድና ዋስትናን ለመከልከል በቂ ምክንያት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 67/ህ/	ጥቅምት 15/2000
287	34077	አቶ ሰይድ ይመር እና የአማራ ክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	በወንጀል የተከሰሰ ሰው የሚያነሳው የዋስትና ጥያቄ መታየት ያለበት ሊወሰንበት ከሚችለው ቅጣት አንፃር ስለመሆኑ	መጋቢት 9/2000
288	34280	አቶ ግርማይ ደስታ እና ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ህግ ቅጣት ሊገደብ የሚችልበት አግባብ የወንጀል ህ/ቁ. 192,194	ግንቦት 14/2000
289	34521	የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ እና ስንታየሁ ተፈራ	በወንጀል ህግ ቅጣትን በልዩ የህጉ ክፍል ከተወሰነው መነሻ ዝቅ አድርጐ በማቅለል ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የወ/ህ/ቁ. 184, 179	ሰኔ 3/2000
290	35611	ሻለቃ ታደሰ ካሕሳይ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	በወንጀል ህግ ጉዳዩን ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት አቤቱታ አቅራቢው ባልቀረበ ጊዜ አቤቱታው እንዲሰረዝ የሚደረገው አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን በትጋት ያልተከታተለ ወይም በቸልተኝነት የተወው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ 193/1/	ሰኔ 19/2000
291	18809	አቶ ሚሊዮን ዑመር እና ዮፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን	በደንብ ቁጥር 75/1993 ኮምፒዮተርን ጨምሮ ከተለያዩ መሳሪያዎች ህንፃዎችና ሌሎች ዕቃዎች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ለመሰብሰው የተደነገገው መኪናን በማከራየት የሚገኝን ገቢ የሚያካትት ስለመሆኑ ደንብ ቁጥር 75/93 አንቀጽ 2/9/ ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 24/2/ /ሸ/	ሰኔ 12/2000
292	19258	አቶ ተክሌ ዋቅጅራ እና አቶ ሾንጣ ገቡ	የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር መዋጮ መከፈል ያለበት ማህበሩ ሲቋቋም እንጂ ተቋቁሞ ሥራው ከተጀረ በኋላ ስላለመሆኑ	ሐምሌ 12/1999
293	23389	የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኅበር እና እነ ባህሩ አብርሃም (ሁለት ሰዎች)	የአክሲዮን ማህበር አባላት መብታቸውን የሚነካ ድርጊት በማህበሩ አስተዳዳሪዎች በተከናወነ ጊዜ በቀጥታ አስተዳዳሪዎቹን ሊከሱ ስለመቻላቸው የንግድ ህ/ቁ. 364,365,367	ሐምሌ 10/1999
294	28923	የባህር ዳር ጨ/ጨ አክስዮን ማሕበር እና የባህር ዳር ልዩ አስተዳደር እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ	የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ ከመቀየራቸው በፊት ያለባቸውን የዕዳ ክርክር በኃላፊነት ይዞ መከራከር ያለበት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 208/1992 አንቀጽ 5/1/, 6/1/ /ሐ/, አዋጅ ቁ. 182/1992	ግንቦት 7/2000
295	10489	የስራና ከተማ ልማት ሚ/ሮ ተተኪ መሠረተ ልማት ሚ/ር እና የቀድሞ ብሐራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግ/ማ	በበጀት የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት የፍርድ ባለዕዳ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔውን ለማስፈፀም ለሌላ ጉዳይ በበጀት የተያዘውን እና የሰራተኛ ደመወዝን የሚያካትተውን ገንዘብ ከብሔራዊ ባንክ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ለማዘዝ ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 404	ሐምሌ 24/1999
296	18576	ወ/ሮ ደስታ መኮንን እና ወ/ት መሰሉ ጌታሁን	የውርስ ማጣራት ሪፖርት ከፀደቀ ወይም በፍ/ቤት ተቀባይነት ካገኘ በኋላም ቢሆን እንደ ፍርድ ተቆጥሮ በቀጥታ የአፈፃፀም አቤቱታ ሊቀርብበት ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 944, 946, 956, 960, 996	ግንባት 26/2000
297	19283	ወ/ሮ መድሐኒት ኃይሉ እና የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ	ባንክ ለሰጠው ብድር በመያዣነት እጁ ያስገባውን የተበዳሪ ንብረት በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛው የሃራጅ ጨረታ ለሽያጭ አቅርቦ ገዢ ያልተገኘ እንደሆነ ንብረቱን ሊያስቀር የሚችለው ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሰረት ስለመሆኑ	መጋቢት 9/2000
298	22481	አቶ ክፍሌ ወልዴ እና ጌትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	በሀራጅ ጨረታ የአሻሻጥ ስርዓት ላይ "ግዙፍ የሆነ ጉድለት" ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር እንደተፈፀመ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 422/3/, 428/5/, 455, 428/1/	መጋቢት 4/2000
299	22930	ወ/ሮ ታድሬ አባተ እና ወ/ሮ ዓለም ገ/የሱስ	ባልና ሚስት በፍቺ ከተለያዩና የንብረት ክፍፍል ከተደረገ በኋላ ከአንደኛው ተጋቢ የግል ተግባር የሚመነጭ ዕዳ አፈፃፀም የተጠየቀው /የቀረበው/ ከፍቺ በኋላ እስከሆነ ድረስ ለዕዳው ምክንያት ከሆነው ተጋቢ ብቻ የሚጠየቅ ስለመሆኑ	ሚያዝያ 30/2000
300	23733	እነ ሃፍቶም ገ/አራሃ (ሁለት ሰዎች) እና	ከንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ በዋናው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ንብረት መካፈል ከተቻለ እንዲካፈል ካልሆነ ደግሞ በባለሙያ ተገምቶ እንዲካፈሉ በሚል የተሰጠን ፍርድ መነሻ በማድረግ የአፈፃፀም ችሎት /ፍ/ቤት/ ከተከራካሪ	ህዳር 24/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		እነ ሙሉ ካሣ (አራት ሰዎች)	ወገኖች መካከል አንደኛው ግምቱን ከፍለው ንብረቱን እንዲያስቀሩ በሚል ትዕዛዝ ለመስጠት የማይችል ስለመሆኑ	
301	23989	አቶ ደስታ ሠርዳ እና የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ	የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ንብረት /ባለቤትነት/ ከሻጭ ወደ ገዥ ያለመዛወሩ ብቻ ሦስተኛ ወገኖች በሻጭ ላይ ሽያጭ የተካሄደበት ንብረት ላይ የጀመሩት አፈፃፀም እንዲቀጥል ለማስደረግ በቂ ሁኔታ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878	ታህሳስ 17/2000
302	25031	ወ/ሮ አልታየወርቅ ኃ/ማርያም እና አቶ ዓለማየሁ ገሰቱ	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሰረት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358,418	ታህሳስ 1/2000
303	26553	የባህርዳር ልዩ ዞን ገንዘብ መምሪያ እና የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ እና ሙክታር መሐመድ	• የማይንቀሳቀስ ንብረት በሃራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በሃራጅ እንዲሸጥ የሚወጣው ማስታወቂያ ለ30 ቀናት መቆየት ያለበት ስለመሆኑ • ንብረቱ በመያዣ የተያዘ እንደሆነም የመያዣው ልክ ምን ያህል እንደሆነ በጨረታ ማስታወቂያ ላይ መገለጽ ያለበት ስለመሆኑ • ሽያጩ ባልተገባ መንገድ ተከናውኗል ከተባለም ጨረታው በድጋሚ መካሄድ ያለበት ስለመሆኑ • በመያዣ የተያዘን ንብረት በሌላ ባለገንዘብ ጠያቂነት እንዲሸጥ ሊደረግ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3084, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 426, 423/2/ /ለ/, 445-447, 415	ሐምሌ 3/1999
304	27574	ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ እና የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማኅበር	በሽምግልና ጉባኤ አማካኝነት የተሰጠ ውሣኔ በፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 215/1/, 319/2/	ጥቅምት 26/2000
305	28019	አቶ ብርሀኑ ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ	ፍርድን በአግባቡ ውጤት ለመስጠት የአፈፃፀም ችሎት የፍርዱን ትክክለኛ ቃል እና መንፈስ መከተል ያለበት ስለመሆኑ	ታህሳስ 1/2000
306	28154	የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ 3ኛ ወገኖች መብት ያቋቋምን ስለሆነ አፈፃፀም ሊቀጥል አይገባም በሚል አቤቱታ ያቀረቡ እንደሆነ ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በአቤቱታው ላይ ያላቸውን ክርክር በቅድሚያ በመስማት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418/1/, 419	ሚያዝያ 14/2000
307	29344	ወ/ሮ ዝማም ህሉፍ እና አቶ መረሣ ገ/ዮሐንስ	ውሣኔን የሚያስፈጽም ፍ/ቤት በውሣኔው መሰረት ከማስፈፀም ወጪ በአፈፃፀም ጊዜ ዋናውን ፍርድ ሊለውጥ የሚችልበት የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418	ግንቦት 5/2000
308	29653	አቶ ነጋ ደምሴ እና ሃምሳ አለቃ አዲሱ ደምስ	በዋናው ክርክር ንብቶ ተከራክሮ ውሣኔ ያላገኘ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ጊዜ ውሣኔ እንዲፈፀምለት ጥያቄ የሚያቀርብበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418	መጋቢት 9/2000
309	33760	ሐጂ ታጁ ለገሠ እና የጎንደር ከተማ የመሃል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር	የንግድ ድርጅት /መደብር/ ላይ ያለ መብት የድርጅቱ ንግድ የሚካሄድበትን ቤት የኪራይ መብት የሚያካትት ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 127	መጋቢት 18/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች



ቅጽ- 11

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች
ቅጽ- 11

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ - 11

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



ህዳር 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/ ሥር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ እነዚህን የሰበር ውሣኔዎች አሣትሞ ማሠራጨት ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኃላፊነት እንደሆነም ተመልክቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሠጠባቸውን የሰበር ውሳኔዎች ማሣተም የተጀመረ ሲሆን ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህም ከቅፅ 5 እስከ ቅፅ 10 ያሉትን አሣትመን አሠራጭተናል፡፡ እነሆ አሁን ደግሞ ቅፅ 11 እና ቅፅ 12 የሰበር ውሣኔዎች ሊታተሙ በቅተዋል፡፡ ይህም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሠጠባቸው የሰበር ውስኔዎቻችንን የማሣተሙ ሥራ ወቅቱን የጠበቀና ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲሆን የምናደርገው ጥረት ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን ያሣያል፡፡

ባለፉት እትሞች መልእክቴ እንደገለፅሁት እነዚህ ፍርዶች ምንም እንከን የላቸውም የሚባሉ እንዳልሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በፍርድ ቤቶቻችን በየትኛውም ደረጃ ላይ ባለን ዳኞች በአንፃራዊነት የልምድም ሆነ የብቃት ውስንነቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ እነዚህ እጥረቶች በሰበር ፍርዶችና ውሳኔዎች ላይ አልፎ አልፎ ቢታዩ ሊገርመን አይገባም፡፡ የብዙ ዓመታት ተሞክሮ ያላቸው ሀገሮች ልምድም የሚያሣዩን ይህንኑ ነውና፡፡

የሀገራችን ፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ወጥና ተገማች እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የሰበር ውሣኔዎች ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ይህን አጠናክሮ ለመቀጠልና ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን በሰበር ውሣኔዎቻችን ላይ

በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሠማሩ የሕግ ምሁራንና ተማሪዎች ገንቢ አስተያየቶችን እና ትችቶችን ሊሠጡበት ይገባል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እነዚህ አስተያየትና ትችቶች ከሌሎች በተመሣሣይ ጎዳና ካለፉ ሀገሮች ከምናገኛቸው ልምዶች ተደምረው አቅማችንን በማሣደግ የተጣለብንን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት ጉልበት ስለሚሆኑን የሙያው ባለቤቶችና መላው ህብረተሰባችን ለጥረታችን መሣካት የሚጠበቅባቸውን ሀገራዊ ኃላፊነት እንዲወጡ በአክብሮት እየጠየቅሁ ውሳኔዎቻችንን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረ ገፅ ላይ ማግኘት የሚቻል መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ2003 ዓ.ም. የሰበር ችሎት

የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ቤተሰብ				
1.	• ባል ሁለት ሚስቶችን በአንድ ጊዜ አግብቶ የሚኖር በሆነ ጊዜ በመካከላቸው የሚፈራ ንብረት ለተጋቢዎቹ ሊከፋፈል የሚችልበት አግባብ • ሚስቶች ጋብቻ እንደተፈፀመ ከሚቆጠርበት ጊዜ ጀምሮ ከባል ጋር ያፈሩትን ሀብት ብቻ መካፈል ስለመቻላቸው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ 213/96 አንቀጽ 62/1/	50489	ወ/ሮ ዘይነባ ከልፋ እና ወ/ሮ ከድጃ ሲራጅ	መስከረም 24/2003	
2.	የኮንዶሚንየም ቤት ለማግኘት የተደረገ ምዝገባ ከጋብቻ በፊት ቢሆንም ዕጣ የወጣው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ከሆነ ተጋቢዎቹ የመካፈል መብት የሚያገኙ ስለመሆኑ	46606	አቶ ገ/ሥላሴ ጫኔ እና ወ/ሮ አብረሽት ተጫኔ	ጥቅምት 02/2003	
3.	ወራሽ የሆነ ሰው ወራሽ ባልሆነ ሰው ላይ ንብረቱ ይለቀቅልኝ በሚል የሚያቀርበው ክስ /አቤቱታ/ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ይርጋ የሚቆጠረው ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን አንስቶ ሳይሆን ንብረቱ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ	47201	እነ በላቸው አስፋው እና ወ/ሮ መኪያ አወል	ጥቅምት 05/2003	
4.	የጋብቻ ውል አስገዳጅ የህግ ድንጋጌን እስካልተቃረነ ድረስ በፍቺ ምክንያት የሚከተለውን የተጋቢዎች የንብረት ክፍፍል እልባት በመስጠት ረገድ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 42, 47, 73, 44	47889	እነ ወ/ሮ ሠላማዊት አስራት /አምስት ሰዎች/ እና ወ/ሮ መሠረት ዘውዴ	ጥቅምት 04/2003	
5.	በሁለት የተለያዩ ክተሞች የሚገኙ ቤቶች የጋብቻ ፍቺን ተከትሎ ለባልና ሚስት ሊከፋፈሉ የሚችሉበት አግባብ	49171	ዶ/ር ደስታ አቡኑ በለጡ እና ሲ/ር አስቱር ካሣ ወልደየስ	ጥቅምት 16/2003	
6.	የውርስ ሀብትን አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ገደብ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851/ለ/ መሰረት ሊቋረጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ስለመኖራቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851	49359	ወ/ሮ ቀለሚ ወርቅነህ እና ሻምበል ጌታሁን ንብሬ	ጥቅምት 04/2003	
7.	• ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ሰዎች ግንኙነታቸው በንብረት ረገድ ያለውን ውጤት በተመለከተ በውል ሊወሰኑ ስለመቻላቸው • በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ አላባ የመጠቀም መብት ጥቅም ተቀባዩ ሲሞት የሚቋረጥና ለወራሾቹ	53663	እነ አቶ ጊላጋብር ንብረሀይወት /ሦስት ሰዎች/ እና	ጥቅምት 29/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የማይተላለፍ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731, 1322/1/		እነ ወ/ሮ አረጋሽ አብረሃ /ሁለት ሰዎች/		
8.	የኑዛዜ መኖርን የማስረዳት ሸክም ስላለበት ወገንና ኑዛዜውን ለማስረዳት ሊቀርቡ ስለሚገቡ ማስረጃዎች የፍ/ብ/ህ/ቁ. 896, 897	49831	ወ/ሪት ሮማን ግዛው እና አቶ ግርማ አብርሃም	ጥቅምት 02/2003	
9.	በኑዛዜ ላይ ስለሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ እና ተፈፃሚነት ስላለው የይርጋ ደንብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973, 974	53223	እነ አቶ ሐዲስ ዓለመስላሴ እና ወ/ሮ ብሌን ዓለመስላሴ	ጥቅምት 15/2003	
10.	• የጋብቻ መኖርን አስመልክቶ ቀዳሚና ዋናው ማስረጃ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ • በማንኛውም ሥርዓት የተፈፀመ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ቀርቦ ሊመዘገብ የሚችልና በዚህ መልኩ የሚገኘው ሰነድ የጋብቻ መኖርን ለማረጋገጥ ብቃት ያለው ስለመሆኑ • በዚህ መልኩ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የተመዘገበ ጋብቻ ውጤት አለው ለማለት የሚቻለው ምዝገባው ከተከናወነበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን የጋብቻው ሥርዓት ከተፈፀመበት ዕለት አንስቶ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/1992 አንቀጽ 28/3/	54258	ወ/ሮ ዘነበች በቀለ እና አቶ ዮናስ ፀጋዬ	ህዳር 02/2003	
11.	• በትዳር ወቅት የተወሰደ /በአንደኛው ተጋቢ/ ብድር ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚገመት ስለመሆኑና ከዚህ በተቃራኒ የሚከራከር ተጋቢ ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም ያልዋለ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • ደመወዝ የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ነው በሚል ሊወሰድ የሚችለው ተጋቢዎቹ በጋብቻ ባሉበት ወቅት የትዳርን ወጪ ከመሸፈን አኳያ መሆን ያለበት ስለመሆኑ • ተጋቢዎች ከህጋዊ ፍቺ በፊት ተለያይተው በቆዩባቸው ግዜያት በግል ያገኙት ደመወዝ የጋራ ነው ለማለት የሚቻል ስላለመሆኑ • በጋብቻ ወቅት የተወሰደና በፍቺ ወቅት ተከፍሎ ያላለቀ ዕዳ እንደ የጋራ ዕዳ የሚወሰድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ 213/92 አንቀጽ 62/1/	56184	ወ/ሮ ኑን ስንታየሁ ጉዝ እና አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል	ህዳር 02/2003	
12.	ባል/ሚስት በጡረታ መልክ የሚያገኘውን ክፍያ ሌላ ባል/ሚስት ባገባ ጊዜ የሚቋረጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 209/55 አንቀጽ 21 አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 35/2/	52569	ወ/ሮ ሙሉወርቅ ዋቹ እና ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን	ህዳር 13/2003	
13.	• የውርስ ሃብት እንዲጣራ በሚል በንብረቱ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ ከሚች ጋር ህጋዊ ግንኙነት ባልነበረበት ሁኔታ ነው በሚል ክርክር በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቶች ይህንን እንደ ጭብጥ በመያዝ እልባት ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ • በዚህ ጉዳይ ላይ ፍ/ቤት የሚሰጠው ብይን ጊዜያዊ አገልግሎት እንዳለው ትዕዛዝ የሚወሰድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320/3/, 247/1/	46726	ኑጋሲ አየለ ኢትቻ እና እነ ሳሙኤል ዮሃንስ ገ/እግዚአብሔር /ሁለት ሰዎች/	ታህሳስ 13/2003	
14.	• ጋብቻ ሳይኖር እንደ ባልና ሚስት መኖርን ማስረዳት የሚቻልበት አግባብና ይዜው ግንኙነት በህግ ጥበቃ ያለው ነው ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ • ጋብቻ ሳይኖር እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በንብረት ረገድ ውጤት ሊያስከትል የሚችለው ግንኙነቱ ሦስት ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ የፀና ከሆነና በዚሁ ጊዜም የተፈራ ንብረት ያለ እንደሆነ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 106/2/, 95	50580	ዶ/ር አለልኝ መኮንን እና ወ/ሮ አስቱር አርአያ	ታህሳስ 14/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

15.	• ሚች ካለው ሀብት እጅግ አነስተኛ የሆነ መጠን ያለው ንብረት ለተወላጁ እንዲሰጠው የተናገረ እንደሆነ ተናግሮ በተገዋዋሪ መንገድ ተወላጁን እንደነቀለው የሚቆጠር ስለመሆኑ • የሚች ኑዛዜ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ በሆነ ጊዜም የተነቀለ ተወላጅ ከኑዛዜ ተቀባዩ ጋር እኩል ሊካፈል የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 951, 938, 939, 937, 912	54385	አቶ ፍቃዱ ሽፈራው እና አቶ ግሩም ኤድሚያስ	ጥር 27/2003	
16.	• የጋብቻ ውል በአግባቡ ተደርጓል ሊባል የሚችልበት አግባብ • የጋብቻ ውል በሚል በተጋቢዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ከነሙሉ ይዘቱ ሊታይና ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 40 እና ተከታታዮቹ 73, 46/1/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 826/2/ 2427 2428 857	56157	እነ ወ/ሮ ፀሐይ ተሰማ /ሁለት ሰዎች/ እና የህፃን አማኑኤል ወንደሰን ሞግዚት	ጥር 09/2003	
17.	አባትነት በፍርድ ሊነገር የሚችልባቸው ሁኔታዎች ላይ ሳይንሳዊ የደም ምርመራ (DNA test) በማስተባበያ ማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል ስለመሆኑና ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች በዚህ ረገድ የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች በአግባቡ ሊያስተናግዱ የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 144, 143 /ሠ/, 145	62041	ጥሩወርቅ ወርዶፋ እና ጥሩነሽ ወርዶፋ	የካቲት 11/2003	
18.	ማየት የተሳናቸው ሰዎች የሚያደርጉት ኑዛዜ በውል አዋቂ ፊት ካልሆነ በስተቀር አይፀናም ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881/3/, 1728/3/, 340, 343/2/	50971	አቶ ሃይሌ ስሙጋ እና ሰላማዊት ተኮላ	የካቲት 25/2003	
19.	ከውርስ ሃብት ጋር በተያያዘ ወራሽ የሆነና አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ላይ የይርጋ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው አካለመጠን ከደረሰበት ወይም በመብቱ መጠቀም ከቻለበት ጊዜ አንስቶ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845	57114	ወ/ሮ ሃና ፀጋዬ እና ወ/ት ጣዕመ- ደስታ	ግንቦት 03/2003	
20.	በጋብቻ ውስጥ የተወለድኩ በመሆኔ ልጅነቴ እንዲረጋገጥልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ህጋዊ መሰረት ያለውና ፍ/ቤቶችም ተቀብለው በፍሬ ነገር ረገድ ሊጣሩ የሚገቡትን በማጣራት መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37/1/	57607	ኤርምያስ ኪስታንትናስ ግሊፕትስ እና ሰለሞን ኪስታንቲናስ ግሊፕትስ	ግንቦት 30/2003	
21.	• ኑዛዜ አድራጊ "ስታመም አላስታመመኝም " በሚል ምክንያት ተወላጅን በኑዛዜ ለመንቀል የሚያስችለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ • ኑዛዜ በተደረገበት ንብረት ሚች መብት የሌለው በሆነ ጊዜ ሊከተል ስለሚችለው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1047, 938, 939, 915, 912	57836	ወ/ሮ አስናቀች ደሳለኝ እና የድርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን	ግንቦት 17/2003	
22.	• ኑዛዜ ህጋዊ አይደለም እንዲሻር በሚል ተቃውሞ እስከቀረበ ድረስ በየትኛውም ህጋዊ መስፈርት መሰረት ፍ/ቤት ኑዛዜውን ውድቅ ሊያደርገው ስለመቻሉ • በኑዛዜ ላይ የነበሩ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ስለሚኖረው ዋጋ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881-883	59268	ወ/ሪት ዝባድ ታዬ እና እነ ብዙአን ታዬ /ሦስት ሰዎች/	ግንቦት 03/2003	
23.	ከውርስ ጋር በተገናኘ በህግ ወራሽ የሆኑ ሰዎች ሚችን ለመውረስ ያልተገቡ ናቸው ሊባል የሚችልበት ሁኔታ ሚች በኑዛዜው ከውርስ ሊነቅላቸው ከሚችልበት ሁኔታ የተለየ ስለመሆኑ	49713	እነ የጥሩነሽ አየለ ወራሾች /አራት ሰዎች/	ሚያዝያ 03/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 838, 937/1/, 938/2/, /3/		እና ወ/ሮ ወጋየሁ ሠለሞን		
24.	• ተናዛዥ የሆነ ሰው ተወላጁ የሆነ ሰው በውርስ ሊደርሰው ከሚገባው ድርሻ ከፋብ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ለማድረግ የሰጠው ምክንያት በቂ መሆን ያለመሆኑ በዳኞች ሊመረመር የሚገባው ስለመሆኑ • "ስላልረዱኝ ወይም ስላልጠየቁኝ" የሚል ምክንያት በመስጠት ተወላጅን ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ድርሻ ሩብ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 913, 1123	55648	እነ ወ/ሮ እቱቱ ሽፈራው /ሦስት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ መንበረ ሽፈራው /ሦስት ሰዎች/	ሚያዝያ 20/2003	
25.	የልጅ አባት ነህ የተባለ ሰውን በተመለከተ የመካድ ክስ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 177/3/	61677	አቶ ፈቃደ መክብብ እና አቶ ዳንኤል ብስራት	ሚያዝያ 18/2003	
26.	ከጋብቻ በሞት መፍረስ ጋር በተገናኘ የሚቀርብ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው ጋብቻው ከፈረሰበት ዕለት አንስቶ እንጂ ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1846, 826/1/	59539	እነ አቶ ስዩም ወ/መስቀል /አራት ሰዎች/ እና ወ/ሪት አምሳለ ሙሉነህ	ሰኔ 29/2003	
27.	አስቀድሞ የተደረገን የጋብቻ ውል በማሻሻል የተደረገ የጋብቻ ውል ህጋዊ ተቀባይነት እንዲኖረው ፍ/ቤት ቀርቦ መጽደቅ ያለበት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 47/1-3/	60725	አቶ አብርሃ የኋላሸት እና ወ/ሮ አበባ ዘመን	ሰኔ 27/2003	
28.	ባልና ሚስት በፍቺ ወቅት የጋራ ንብረታቸውን ለመካፈል ስምምነት ላይ ያልደረሱ ከሆነና ንብረቱ በአይነት ሊካፈል የማይችል እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን ዋጋ እኩል እንዲካፈሉ መደረግ ያለበት እንጂ በእጣ እንዲካፈሉ ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 103/1/	61788	ወ/ሮ ጥሩወርቅ ለማ እና ታፈሰ ተሰማ	ሰኔ 14/2003	
29.	በሁለት ሰዎች መካከል የጋብቻ ሁኔታ መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያዝ ጭብጥ በሁለቱ ሰዎች መካከል ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ለማረጋገጥ በሚል ከሚያዘው ጭብጥ የተለየ ወይም አንድ አይነት ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92	60691	ወ/ሮ ገዛችን ገብሩ እና ወ/ሮ ዓለምነሽ በየነ	ሐምሌ 12/2003	
30.	አባትነትን /ልጅነትን/ ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ በሚቀርብ አቤቱታና ክርክር የዲኤን.ኤ (DNA) ምርመራ እንዲደረግለት በመጠየቅ ክርክር የሚያቀርብ ወገን ለዚሁ የህክምና ማስረጃ የሚያስፈልገውን ወጪ የመሸፈን ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 259/1/	63195	ገረመው መሜቻ እና ወ/ሮ አሰፋ ነበበ	ሐምሌ 26/2003	
31.	ጋብቻ ሳይፈርስ የትዳር ግንኙነቱን ትቶ የሄደ ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት የተፈራን ንብረት የጋብቻ ውጤት ነው በማለት የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ በጋብቻ ወቅት የተፈራን ንብረት የጋራ ይሆናል በሚለው የህግ ግምት ተጠቃሚ ሊሆን የማይገባ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/1/	43988	ወ/ሮ ሰኒያ ሼሳ ተማም እና እነ ወ/ሮ በላይነሽ ማቴቦ /ሁለት ሰዎች/	መስከረም 24/2003	
32.	ወደ ሌላ አገር ለሥራ በሄደበት ወቅት ህይወቱ ያለፈ ሰው ጋር በተያያዘ የግለሰቡ መደበኛ መኖሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ውርሱ በኢትዮጵያ ውስጥ መከፈት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/በ/ህ/ቁ. 826/1/	65621	እነ ወ/ሮ ታደለች መንግስቱ /አምስት ሰዎች/ እና ተጠሪ፡ የለም	ሰኔ 27/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

33.	• የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በሦስት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ/ • ከውርስ ሀብት ክርክር ጋር በተገናኘ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ንብረቱ በእጅ ከተደረገበት ጊዜ እንጂ ስመሃብቱ ከተዛወረበት ጊዜ አንስቶ ስላለመሆኑ /	52407	እነ ወ/ሮ ውለታ ደስታ ወ/ማርያም /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ እቱቴ ደስታ	ህዳር 24/2003	
34.	• የውርስ ሃብት አጣሪ ሪፖርት በፍ/ቤት መጽደቅ ውጤት • በፍ/ቤት የፀደቀ የውርስ ሃብት አጣሪ ሪፖርትን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 አግባብ ተቃውሞ ሊቀርብበት ይገባል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358	45905	ሚስስ ሚላን ፒሲጂ ማልጂ እና እነ ሃንድሬ ፒስ ማልጂ /ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 03/2003	
35.	ከጋብቻ በፊት አንደኛው ተጋቢ የግል መኖሪያ ቤት ኖሮት ከጋብቻ በኋላ ሌሎች ተጨማሪ ቤቶችና ግንባታዎች ተካሂደዋል በሚል ከጋብቻ በፊት በስሙ ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት በጨረታ ተሸጦ ለተጋቢዎቹ እንዲካፈል በሚል የሚሰጥ ውሣኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ	53814	እነ አቶ ነስሩ ሰማን /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ መ·ህሊሳ ኒጋኒ	ጥቅምት 05/2003	
36.	በፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 መሰረት የተደረገ ግልጽ ጉባዔ ላይ ያለን የተናባገዩ የጣት አሻራ በተመለከተ ክርክር በቀረበ ጊዜና በፎረንሲክ ምርመራ ለማረጋገጥ ካልተቻለ በጉባዔው የተገኙ ምስክሮች ቀርበው እንዲመሰክሩ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881, 1677/1/, 2007/2/, 897/1/, 896	54013	ወ/ሮ አስመረት ነጋሲ እና ወ/ሮ ጽጌረዳ ስዩም	ጥር 12/2003	
37.	• በጋብቻ ውስጥ የሚወለድ ልጅ አባት ባል እንደሆነ የህግ ግምት ሊወሰድ የሚችልበት አግባብ • የዚህ የህግ ግምት የሚቋቋምበት አግባብ እና እንደ ማስረጃ ተወስዶ በፍ/ቤት እውቅና ሊያገኝ የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 126, 143	54024	አቶ ገ/ሊባኖስ ረዳ እና ወ/ሮ አዜብ አሰፋ	ጥር 10/2003	
38.	አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ሞግዚት የልጁ ሀብት የሆነን የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ ለመሸጥ የማይችል ስለመሆኑ የኦ/ብ/ክ/መ/ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 69/95 አዋጅ ቁ. 83/96 አንቀጽ 294, 316 የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 277/1/, 292	54827	እነ ሮም ወርቁ ተስፋዬ /አምስት ሰዎች/ እና አሰግድ ሽነገለኝ	ሚያዝያ 21/2003	
39.	አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሞግዚት የልጁ ንብረት የሆነን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ በህግ ስልጣን ያልተሰጠው ስለመሆኑ	54129	አቶ ክፍያለው በቀለ እና ወጣት ሶፊያን አብዱልቃድር	ህዳር 01/2003	
40.	• ከውርስ በዝምታ ወይም ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ የኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሆኖ የሚችን የውርስ ሃብት ሊካፈል የሚገባ ስለመሆኑ • "በህይወቱ ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥረውብኛል" የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ተወላጅን ለመንቀል የማይቻል ስለመሆኑ • ሟች ካለው ሃብት እጅግ አነስተኛ የሆነ ንብረት /ሀብት/ ለተወላጁ በኑዛዜ የሰጠ እንደሆነ በውጤት ደረጃ ተወላጁ የተነቀለ መሆኑን መገንዘብ የሚቻልና ተወላጁ ከሌሎች የጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚዎች ጋር እኩል መካፈል ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 912, 938, 939, 915, 1014, 1123	58338	እነ አቶ ዳንኤል ጽጌ /ሁለት ሰዎች/ እና የህፃን አሳለፈ ጽጌ ሞግዚት	ሚያዝያ 06/2003	
41.	• የውርስ ሃብት አጣሪ የሆነ ሰው የሚችን ንብረት በማጣራት ረገድ ሊኖረው የሚችለው የስልጣን አድማስ • በወራሾች መካከል አንድን ንብረት በተመለከተ የውርሱ ሃብት አካል ስለመሆኑ ክርክር በተነሳ ጊዜ አጣሪው ግራ	66727	ወ/ሪት ዝናሽ ዘውዱ እና	ሐምሌ 29/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ በሪፖርቱ ላይ በማስፈር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍ/ቤት ማቅረብ እንጂ ማስረጃዎቹን በራሱ መዝኖ አከራካሪው ንብረት የውርስ ሃብት አካል ነው ወይም አይደለም በማለት ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 956		የወ/ሮ መድሐኒት ካሣ ወራሽ እነ ወ/ሮ ደብሪቱ ስዩም		
42.	ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ የተፈራ ቤት በጋብቻ ወቅት እድሳት የተካሄደለት መሆኑ ብቻ ንብረቱን የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት የማያደርገው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥ. 213/92 አንቀጽ 42/1/, 57	45207	ወ/ሮ አየለች ከበደ እና በላቸው ዋለ	ሰኔ 16/2002	
43.	• ተወላጅ የሆነ ሰው ከውርስ ተነቅሏል ሊባል የሚችለው ተናዛዡ ንብረቱን በጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ለሌሎች ተወላጆች ወይም ሌሎች ሰዎች የሰጠ እንደሆነ ስለመሆኑ • ሟች ያለው አንድ የታወቀ ንብረት ብቻ ሆኖ ይህንኑ ከተወላጆቹ መካከል አንዱን ወይም ሁሉንም ሳያካትት ለሌሎች ሰዎች በኑዛዜ የሰጠ እንደሆነ ተነቀልኩ የሚል ወገን ኑዛዜው ላይ ተቃውሞ ሊያነሳ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 937-939, 842/2/, 915	47917	እነ ወ/ሮ መልካምሥራ አለበል /አራት ሰዎች/ እና ወ/ሮ አንለይ ሊበን	ግንቦት 05/2003	
	አሠሪና ሠራተኛ				
44.	• በህብረት ስምምነት ውስጥ በሌላ አካኋን ካልተገለፀ በስተቀር የህብረት ስምምነት ከተፈረመበት ዕለት አንስቶ የሚፀና ስለመሆኑ • የህብረት ስምምነት በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ እንዲመዘገብ የሚደረገው ድርድር ተደርጉበት ከተፈረመበት በኋላ ስለመሆኑ • በተደራዳሪ ወገኖች በተሟላና በአግባቡ ያልተፈረመ የህብረት ስምምነት በፍርድ ሃይል እንዲመዘገብ የሚደረግበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 124-135	54451	የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ እና የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ መ/ሰ/ማህበር	መስከረም 27/2003	
45.	አንድ ሰራተኛ ለሥራ ከሚጠቀምበት መሳሪያ ብልሽት መከሰት ጋር በተገናኘ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው አሰሪው ግዴታና ኃላፊነቱን በአግባቡ የተወጣ እንደሆነ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 12/1//ሀ/	48945	አቶ አየለ አበበ እና የፊንፊኔ የደን ድርጅት	ህዳር 27/2003	
46.	የህብረት ስምምነት የሌለው አሰሪ ሰራተኛው የዲሲፕሊን ጉድለት ፈጽሟል የሚልበትን ጉዳይ ለማጣራትና ለመመርመር ሰራተኛውን ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ ለማገድ ስለመቻሉ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/4/	53985	ዳሽን ባንክ አ.ማ እና አቶ ዘነበ ድንቁሳ	ህዳር 13/2003	
47.	በህብረት ስምምነት ላይ ከተመለከቱ ሁኔታዎች ውጪ ሰራተኛን ያለአግባብ አዛውሮ የማሰራት ተግባር ህጋዊ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ	54326	አንበሳ ጫማ አ.ማ እና ወ/ሮ እትሁን አያሌው	ህዳር 03/2003	
48.	በስራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተያያዘ የአሰሪው ኃላፊነት በጥፋት ላይ ያልተመሰረተ (strict liability) ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96, 97	57068	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ሰናይት መጫ /ሦስት ሰዎች/	ህዳር 28/2003	
49.	ከስራ ተሰናበትኩ በማለት አቤቱታ የሚያቀርብ ሠራተኛ በእርግጥም ስለመሰናበቱ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማቅረብ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ	57541	የቻይና መንገድና ድልድይ ሥራ ድርጅት እና ግርማ ቡሽራ	ህዳር 14/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

50.	በአዋጅ በተቋቋመ የት/ት ተቋም ውስጥ በሚገኝና በራሱ ገቢና በጀት የሚተዳደርና ሠራተኞችን ቀጥሮ በሚሠራ ክበብ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ እና ተቋሙን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ተፈፃሚ ይሆናል ለማለት የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አዋጅ ቁ. 515/96 አዋጅ ቁ. ደንብ ቁጥር 61/96	46075	አቶ ንጉስ ሃዱሽ እና የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ዲን	ታህሳስ 25/2003	
51.	ከሥራ ክርክር ጋር በተገናኘ አሰሪና ሠራተኛው ያደረጉት የሥራ ቅጥር ውልን አስመልክቶ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩን የሚገዛው ከኢትዮጵያ ሌላ /ውጭ/ የሆነ አገር ህግ መሆኑንና የሥራ ቦታውም ቢሆን ከኢትዮጵያ ውጪ እንዲሆን የተስማሙ እንደሆነ ጉዳዩ በአጠቃላይ የአለም አቀፍ የግለሰብ ህግ (private international law) ጥያቄን የሚያስነሳ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው?፣ በየትኛው አገር ህግ መሰረት?፣ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ስልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 11/2/	60685	አቶ በዛብህ እሸቱ እና ሳሊኒ ኮንስትራክሽን	የካቲት 21/2003	
52.	አንድ ሰራተኛ በአሰሪው ታግዶ /የሥራ ውሉ ተቋርጦ/ በነበረበትና ባልሰራበት ዓመት አሰሪው ለሌሎች ሠራተኞች የከፈለውን የቦነስ ክፍያ ለመክፈል የማይገደድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43, 45/5/, 53	59320	ጊዮን ሆቴሎች ድርጅት እና አቶ ስለሺ አምዴ	ግንቦት 15/2003	
53.	አሰሪ ሠራተኛው ጥፋት እንደፈፀመ አውቆ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማሰናበት እርምጃ አለመውሰዱ ስንብቱን ህገ ወጥ የሚያደርገው ቢሆንም ሠራተኛውን ወደ ሥራው እንዲመልስ ላይገደድ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/	64079	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ጌትነት መኮንን	ግንቦት 17/2003	
54.	በሥራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተያያዘ የጉዳቱን አይነትና መጠን መለየት የሚቻልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 109/3/ /ሀ/ለ/ 101/2/ 100 96/1/ 99/1/	60464	የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ግርማ ወዩሳ	መጋቢት 06/2003	
55.	ከአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪው ሠራተኛው የሚጠይቀውን የገንዘብ ክፍያ በማመን የፃፈው ደብዳቤ ሠራተኛው መብቱን ለማስከበር በሚያቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ የሚቆጠረውን ይርጋ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 164/3/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1852/1/	63635	አቶ ጉልላት ወልዴ እና የሸቀጦች ጅምላ	ሰኔ 27/2003	
56.	• አንድ ሠራተኛ ቦነስ ወይም ድጐማ ሊያገኝ የሚችለው ከአሰሪው ጋር በሚደረግ /በሚኖር/ ስምምነት እንጂ በህጉ አሠሪ ለሠራተኛው በቦነስ ድጐማ እንዲከፍል በአስገዳጅነት የተመለከተ ነገር የሌለ ስለመሆኑ • የቦነስና ድጐማ አሰጣጥና አፈፃፀምን በተመለከተ በህብረት ስምምነት የተመለከተ ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 4, 12, 13, 53	64758	እነ ተመስገን ገ/እየሱስ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ሰኔ 17/2003	
57.	•አንድ ሠራተኛ አሰሪው በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መሰረት ሊከፍለው የሚገባውና ያልከፈለው ክፍያ መኖሩን /እንዳለ/ በተረዳ ጊዜ አሰሪውን የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ •የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት በቀጠለበት ሁኔታ ሠራተኛው በአንድ ወቅት ሊከፈለኝ /ሊጠበቅልኝ/ ይገባል በማለት ያቀረበው የመብት ወይም የክፍያ ጥያቄ በፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ በሌላ ጊዜ መብቱን ከመጠየቅ የሚያግደው	66242	ወ/ሮ ሙሉ ደምሴ እና ሸራተን አዲስ	ሐምሌ 13/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 12 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 216				
58.	በአዋጅ ቁ. 147/91 መሠረት በተቋቋመ ማህበር ውስጥ ላሉ ሰራተኞች አዋጅ ቁ. 377/96 ተፈፃሚ ስለመሆኑ	59579	ወ/ሮ አሞኘሽ ገብሬ እና የአቃቂ መለዋወጫ ዕቃዎች የእጅ መሣሪያዎች አ/ማ ሠራተኞች የገንዘብና ቁጠባ ብድር ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ግንቦት 16/2003	
59.	የጡረታ መብት ያለው የመንግስት ልማት ድርጅት ሠራተኛ ሊያገኝ ስለሚገባው ካሣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9/1/	65427	ሜታ አቦ ቢራ አ.ማ እና ወ/መድህን ቢረዳ	ግንቦት 15/2003	
60.	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ሠራተኞች እየሠሩ የሚገኙትን ሥራ በተመለከተ የሥራ ውል አላደሱም ወይም ለማደስ ፈቃደኛ አይደሉም በሚል ለማሰናበት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ	62370	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ እዮብ መለሰ /አራት ሰዎች/	ታህሳስ 26/2003	
61.	• በአዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት የሠራተኛ ማህበር ለማቋቋም የሚቻልበት አግባብ • የሰራተኛ ማህበር ለማቋቋም መብት የተሰጣቸው በአዋጅ ቁ. 377/96 የሚተዳደሩ ሰራተኞች ብቻ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 114, 115, 118, 2/4/, 113 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 42/1/ /ሀ/, 31	55731	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሰራተኛ ማህበር እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ማህበራዊ ጉዳይ ሚንስቴር	የካቲት 22/2003	
62.	• የሠራተኛ ደመወዝ ሊቀነስ የሚችለው በህግ፣ በህብረት ስምምነት፣ ወይም በሥራ ደንብ በተወሰነው መሰረት ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ብቻ ስለመሆኑ • አሰሪ የሠራተኛን ደመወዝ በራሱ ውሣኔ ሊቀንስ፣ ሊይዝ ወይም የዕዳ ማቻቻያ ሊያደርግ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 59/1/	59666	የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ አቡ ጉበና	ግንቦት 04/2003	
63.	• የደረጃ እድገት በድርጅት ውስጥ በሥራ ላይ ባለ የእድገት አሰጣጥ ስርዓት እና ደንብ መሰረት የሚካሄድ ስለመሆኑ • የደመወዝ ጭማሪ ሊገኝ የሚችለው በእድገት ወይም አሰሪው የደመወዝ ጭማሪ ማድረግ የሚችልበት አግባብ ኖሮት ሲጨመር ስለመሆኑ • በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) መሠረት የተደረገ የሥራ ምደባ የደመወዝ ጭማሪ የማያስገኝ ስለመሆኑ	64821	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃየል ኮርፖሬሽን እና አያሌው ሕብስት	ግንቦት 01/2003	
64.	ከአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በፍ/ቤት የተሰጠ ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርብ አቤቱታ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ	53527	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ በዳሶ መልካቶ	መስከረም 27/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

65.	የመከላከያ ሰራዊት አባል ያልሆነ የመንግስት ሰራተኛ በፍቃዱ ሥራ በለቀቀ ጊዜ የስንብት ክፍያ ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95	61872	የኢትዮጵያ ፖልፕና ወረቀት አ/ማ እና አብዱልቃድር አደም	የካቲት 10/2003	
66.	ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለውና በባለሃብትነት ሊያዝ የሚችልን የአሰሪ የሆነ ነገር ላይ ሠራተኛው ሆን ብሎም ሆነ በቸልተኝነት በማናቸውም ሁኔታ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/	64988	ዳሸን ባንክ አ/ማ እና አቶ ሃይሉ ሽመልስ	ግንቦት 30/2003	
67.	• የመንግስት ሰራተኞች አዋጅን መሰረት በማድረግ የሚነሳ ክርክር የሚስተናገድበት ህግና የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ • ይግባኝ ለማቅረብ ጊዜ ያለፈበትን አቤቱታ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚቻልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀጽ 76/2/ አዋጅ ቁ. 6/2000 አንቀጽ	61843	ሰይፉ ናስር እና የአ.አ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ህግ ጉዳዮች	መጋቢት 23/2003	
68.	ለተወሰነ ጊዜና ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ ጊዜው ደርሶ መሰናበቱ ምንም እንኳን ሌሎች ሠራተኞች በእሱ ምትክ የተቀጠሩ ቢሆንም ህገ ወጥ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ	57337	አድቬንቲስት የልማት ተራድኦ ድርጅት እና አቶ ገበየሁ ወ/ሚካኤል	ሰኔ 15/2003	
69.	በአሰሪና ሰራተኛ ስምምነት የሚዘጋጅ የህብረት ስምምነት ውስጥ የተካተቱ ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችሉ ምክንያቶች ጥፋትን መሰረት ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1//ተ/	64734	ካንትሪ ክለብ ዴቨሎፐር የረር ቪው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት እና አነ አቶ በቀለ ለማ /ሦስት ሰዎች/	ሰኔ 16/2003	
70.	የግንባታ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት ከ3ኛ ወገን ጋር ባደረገው የግንባታ ሥራ ውል መነሻነት የቀጠረውን ሰራተኛ የግንባታ ሥራው ውል በመቋረጡ ምክንያት ማሰናበቱ ህገ ወጥ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24/4/, 4/1/, 10, 9	66306	አምሳሉ ወረዳ ኮንስትራክሽን አ/ማ እና እነ አቶ መሐመድ ሰይድ /ስድስት ሰዎች/	ሰኔ 03/2003	
71.	የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል በመጠርጠሩ የተነሳ ከሥራ ታግዶ የነበረና በኋላም የተሰናበት ሠራተኛ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ የፍ/ቤት ውሣኔ ያልቀረበ በመሆኑ ብቻ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑና ጉዳዩን በማስተናገድ ላይ የሚገኝ ፍ/ቤት የሠራተኛውን ስንብት አግባብነት ለመወሰን ማናቸውንም ማስረጃ አስቀርቦ በመመልከት ለጉዳዩ አልባት መስጠት ያለበት ስለመሆኑ	59906	የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት እና ኃይለማርያም ሻረው	የካቲት 09/2003	
72.	ከሥራ ጋር ባልተገናኘ /ተፈጥሮአዊ/ ሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሥራ ስንብት ክፍያ የማይከፈል ስለመሆኑ	18495	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ወ/ሮ አሚናት ገበየሁ	መጋቢት 18/1999	
73.	• የቦነስ ክፍያ ለሠራተኛ የሚከፈለው በሥራ ላይ ያለ ሰራተኛ ወደፊት በርትቶ እንዲሰራ ለማበረታታት ብቻ	20869	አቶ አዲሱ አቦሴ	ሰኔ 30/1998	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሳይሆን በሥራ ላይ በነበረበት ወቅት የሰራው ሥራ ለአሰሪው ትርፋማ ውጤት በማስገኘቱ የትርፉ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ጭምር ስለመሆኑ • የቦነስ ክፍያ ተጠቃሚ ለመሆን ሠራተኛው ድርጅቱ /ተቋሙ/ ትርፋማ ውጤት ባስገኘበት ዓመት በሥራ ላይ የነበረና አስተዋጽኦ ያደረገ መሆን ያለበት ስለመሆኑ		እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን		
		ንብረት			
74.	ቤትና ቦታዬን ያለአግባብ ተነጠቅሁ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት ታይቶ ፍርድ ሊሰጥበት የማይችል አስተዳደራዊ ጉዳይ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4	48217	ወ/ሮ አባዲት ለምለም እና እነ የዛለአንበሳ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 03/2003	
75.	የመሬት ይዞታ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በተወሰደ ጊዜ ካሣ የሚከፈለው በተወሰደው ይዞታ ላይ ንብረት የነበረ መሆኑ እንዲሁም ንብረቱን ለመተካት ከሚያስፈልገው ወጪ ጋር ተመጣጣኝነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 401/96 አንቀጽ 9/1/, 10 አዋጅ ቁ. 455/97	52496	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና እነ አቶ ከድር ኃሌጅንሶ /አስራ ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 16/2003	
76.	• አንድ ሰው የንብረት ባለቤት የሚሆነው በንልበቱ፣ በፈጠራ ችሎታው ወይም በገንዘቡ ንብረትን ያፈራ እነደሆነ ስለመሆኑ • የፍርድ ባለዕዳ የሆነ ሰው ንብረቱ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዳይውል አስቦ አካለ መጠን ባልደረሰ ህፃን ልጁ ስም ማዞሩ ብቻ ከኃላፊነት ሊያድነው የሚያስችል ስላለመሆኑና ይህ በመሆኑም ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የለም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/2/	55081	ወ/ሪት ራሔል ሥነ ፀሐይ እና አቶ መስፍን ታምራት	ጥቅምት 18/2003	
77.	• መንግስት አንድን የግል ንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚወስድበት ጊዜ ሊከተለው ስለሚገባው ሥነ ሥርዓት • ለህዝብ ጥቅም ሲባል ንብረቱ የተወሰደበት ሰው የተሰጠው ግምት ከንብረቱ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ አይደለም በሚል ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1460-1488	50810	እነ አቶ ፀጋዬ መሠረት /ሰባ ዘጠኝ ሰዎች/ እና የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን	ጥቅምት 30/2003	
78.	የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ስመ ሃብት ይዞ መገኘት የንብረቱ ባለቤት አድርጐ የማያስቆጥር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196	47139	አቶ የሱፍ ሁሴን እና አቶ አደን አብደላ	ህዳር 30/2003	
79.	አዋጅ ቁ. 47/67 ከመውጣቱ በፊት የተደረገ የመሬት ኪራይ ውል ህጋዊ አስገዳጅነት ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67	48086	እነ ወ/ሮ አሰለፈች ወልደሚካኤል /ሁለት ሰዎች/ እና ቶታል ኢትዮጵያ አክሲዮን	ህዳር 03/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ማህበር		
80.	• ፍ/ቤቶች በሚቀርቡላቸው አቤቱታዎች ላይ ህግን ተፈፃሚ ለማድረግ የቀረበውን የክስ አርእስት ብቻ ሳይሆን ይዘት ጭምር መመልከት የሚገባቸው ስለመሆኑ • ከንብረት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149/1/ መሰረት ሁከት የተፈጠረበት ሰው እንዲወገድለት ይዞታው የተወሰደበት ሰው ደግሞ እንዲመለስለት በሚል ዳኝነት የሚጠየቀው አቤቱታ የቀረበበት ንብረት ተገምቶ ተገቢው ዳኝነት ከተከፈለበት ቡኋላ ስለመሆኑና በጥቅሉ የተፈጠረ ሁከት እንዲወገድ (cessation of interference) እንደሆነ ተቆጥሮ ልክ አቤቱታቸው በገንዘብ የማይገመቱ አቤቱታዎች አይነት ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑና የይርጋ ደንብ ተፈፃሚ የማይሆን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149/2/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 16, 226/3/	49985	ሻለቃ አሰፋ አየለ ደምሴ እና ፍቃዱ ሙሉጌታ	ህዳር 28/2003	
81.	መሬት በፍ/ብሔር ግንኙነት የተፈጠረን ዕዳ ለመክፈል ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/3/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678/2/	49200	አቶ ጋሻው በጮሰው እና አቶ አለበል መኮተ	ህዳር 01/2003	
82.	የከተማ መሬት ይዞታን እንዲለቅ የተደረገ ባለይዞታ በተወሰነለት የካሣ መጠን ላይ ካልተስማማ አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት በከተማው አስተዳደር ሥር ለተቋቋመ የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አካል ስለመሆኑ እና በመደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ ሊታይ የሚችለው በይግባኝ ብቻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 11/2/, /4/	57271	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ጃዳ ብሩ	ታህሳስ 27/2003	
83.	• የማይንቀሳቀስ ንብረት /ህንፃ/ ግንባታ ሥራ ጋር በተገናኘ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ድንጋጌዎች • የሥራ ተቋራጭነት ውል ተፈጽሟል /አለ/ ለማለት የሚቻልበት አግባብ • የግንባታ ሥራ ውል በልዩ ፎርም መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3019-3040	47526	ዛፍኮ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ብሔራዊ መሐንዲሶች ስራ ተቋራጭ ድርጅት	ግንቦት 15/2003	
84.	• የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በቅን ልቦና የተደረገ ነው በሚል ምክንያት ብቻ በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የማይችል ስለመሆኑ • በህግ ፊት በማይፀና ሁኔታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው ይህንኑ ንብረት ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የሚያደርገው የሽያጭ ውል ህጋዊ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ • የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ መብት ከሌለው ሰው እያወቀ የሽያጭ ውል የፈፀመ ገዢ በቅን ልቦና የተደረገ ነው በሚል የሕግ ጥበቃ የሚደረግበት ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196, 2882-2884	60720	ወ/ሮ ሄርያ መሐመድ ግርግቦ እና አቶ ሽምሱ የሱፍ	ግንቦት 15/2003	
85.	ተከራይ ለሆነ ወገን በተከራየው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የባለቤትነት ወይም ሌላ መብት አለን በማይሉ 3ኛ ወገኖች አድራጉት ለሚነሳ ሁከት አከራይ ዋስትና እንዲሰጥ የማይገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2914/1/, /2/, 2913/1/, /2/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158	63042	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ሰለሞን ነጋሽ	ግንቦት 01/2003	
86.	ለህዝብ ጥቅም ሊባል ይዞታውን እንዲለቅ የተደረገ ሰው በመሬቱ ላይ የሰፈረውን ንብረት ለመተካት ከሚከፈለው ካሣ በተጨማሪ በይዞታው ላይ የነበረው ንብረት በመፍረሱ የተነሳ የተቋረጠ ገቢ /የታጠ ጥቅም/ ካሣ ሊከፈል የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀጽ 2/1//ለ/, 7/1/2/ ደንብ ቁ. 135/99	63352	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ቱሌ አብዶ	ሐምሌ 13/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

87.	• ተከራይ በይዞታው ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት አከራይ ባለበት ዕዳ ምክንያት ባለገንዘብ የሆነ ወገን ንብረቱን መረከቡ በተከራዩ ላይ የሁከት ተግባር ፈጽሟል የማያስብል ስለመሆኑ • የተከራዩ እና በንብረቱ ላይ መብት ያለው ባለገንዘብ የሚኖራቸው ተነፃፃሪ መብት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140 1149 2933/1/ 2899 2931 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 6	62858	ፕዝፋ ይንደር ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ እና አነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ /ሁለት ሰዎች/	ግንቦት 16/2003	
88.	ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚመለከተው የአስተዳደር አካል እንዲፈርስ መረጃ የደረሰው በመሆኑ ቤቱን ያፈረሰ ሰው የአስተዳደር አካሉ የዲዛይን ለውጥ አድርጐ ቤቱ ከፈረሰ በኋላ የግለሰቡን ይዞታ /ንብረት/ መፍረስ የማያስፈልግ መሆኑን መግለፁ ካሣ የመክፈል ግዴታውን ቀሪ የማያደርግ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 322/97 አዋጅ ቁ. 455/97 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት art. 40/2/	62293	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አነ አቶ መስፍን ጀንበሩ /ሁለት ሰዎች/	ግንቦት 15/2003	
89.	• አንድ ሰው የሌለውን ነገር ሸጦ በተገኘ ጊዜ ገዢው በህግ ሊያገኝ ስለሚገባው መፍትሔ • በሌለ መብት መሥራት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2884/1/ /2/, 2282-2285, 1716	51034	ታሪክ ጌታቸው እና አነ ወ/ሮ አልጋነሽ ተጠምቀ /ሁለት ሰዎች/	የካቲት 22/2003	
90.	• የኮንዶሚንየም ቤትን ዋጋ በአጠቃላይ የከፈለ የኮንዶሚንየም ቤት ባለቤት በፍርድ የተወሰነበት የሌላ ሰው ዕዳ ያለበት በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ቤቱ በአፈፃፀም ተሸጦ ለዕዳው መክፈያነት እንዲውል ለማዘዝ የሚችሉ ስለመሆኑ • የኮንዶሚንየም ቤት ባለሀብት የሆነ ሰው በራሱ ፈቃድ ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ ወይም ለ3ኛ ወገን ለማስፈላለፍ የሚችለው ያለበትን የቤቱን ዋጋ አጠናቅቆ ከከፈለበት ጊዜ ጀምሮ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 19/97 አንቀጽ 21, 14/2	56011	አቶ ሳሙኤል ታደሰ እና ወ/ሮ እጥፍወርቅ ኃይለማርያም	መጋቢት 23/2003	
91.	• በህጋዊ መንገድ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ውል ያገኘ ገዢ የሚመለከተውን የአስተዳደር አካል የስም ዝውውር እንዲፈጽምለት በፍ/ቤት ለመክሰስ የሚችል ስለመሆኑ • የሚመለከተው የአስተዳደር አካል በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት ካልተወጣ ገዥ መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ የሚገባው በዚሁ የአስተዳደር አካል ላይ ስለመሆኑ የአማራ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ. 91/96 እና ደንብ ቁጥር 12/2000	49428	እነ ወ/ሮ ከበቡሽ ልሳነወርቅ /ሁለት ሰዎች/ እና እነ አቶ ፀዳሉ አዳነ /ሁለት ሰዎች/	ህዳር 28/2003	
92.	ሚች ከቀበሌ ተከራይቶት የነበረን መኖሪያ ቤት ወራሽነትን በማረጋገጥ ብቻ በቤቱ ውስጥ የመኖር ህጋዊ መብት ሊገኝ የማይችል ስለመሆኑና ተቀባይነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሊቀርብ ስላለመቻሉ	57045	የልደታ ክ/ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት እና አቶ ተስፋዬ አሰፋ	ጥር 25/2003	
	ጉምሩክ /ቀረጥ/ ግብር				
93.	በስህተት ለጉምሩክ የተከፈለ ቀረጥ ተመላሽ የሚደረገው ስህተቱ መኖሩን ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወቀና ዕቃውም የጉምሩክ ስነ ስርዓትን አጠናቅቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ውጭ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ ባለው 6 ወር ውስጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 15	53749	የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ እና አቶ አዱኛ አበሉ	ጥቅምት 18/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 53, 55				
94.	ከቀረጥ ነፃ በሆነ መልኩ ለግል አገልግሎት እንዲውል የገባ መኪናን ለንግድ ማዋል በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/, 78	54203	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ወ/ሮ መሉእመቤት ኃ/ሚካኤል	ህዳር 27/2003	
95.	ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎችን አስመልክቶ ስለሚካሄድ የቅድመ ጭነት ምርመራ ሥርዓት እና በዕቃው ላይ ስለሚከፈል ግብር /ታክስ/ አዋጅ ቁ. 173/91 አንቀጽ 6/1/, 4/1/	50375	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ ለተብርሀን አድሀኖም /ሁለት ሰዎች/	ህዳር 13/2003	
96.	የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግን ተላልፏል በሚል በወንጀል የተከሰሰና ስራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው አልነበረም ወይም አያውቅም በሚል ምክንያት ከወንጀል ኃላፊነት ነፃ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 56/1/ 55 አዋጅ ቁ. 609/209 አንቀጽ 22/1/ 50/ለ//1/	51090	እነ ዘ ቲዊንስ ባርና ሬስቶራንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/ እና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን	ታህሳስ 12/2003	
97.	• የጉምሩክ ባለስልጣን ኮንትሮባንድ እንደተፈፀመበት በበቂ ሁኔታ የጠረጠረውን ተሽከርካሪ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ ለሚያደርገው ማጣራት ለባለንብረቱ የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፈል የማይጠየቅ ስለመሆኑ • ባለስልጣኑ በቁጥጥሩ ሥር የሚያውላቸው ተሽከርካሪዎች የተያዙበትን ጉዳይ ለማጣራት ከሚያስፈልገው ተገቢና ምክንያታዊ ጊዜ በላይ የሆነ እንደሆነ የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ • በባለስልጣኑ ቁጥጥር ሥር የቆዩ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የተቋረጠ ገቢ ይከፈለን በሚል አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤት የተጠየቀውን ገቢ ህጋዊነት እና ትክክለኛነት በማረጋገጥ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 6/5/ 58/1//1 አዋጅ ቁ. 368/95	43996	የሰሜን ምስራቅ ጉምሩክ ሚሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና በረከት አሰፋ	ጥር 10/2003	
98.	• አንድ ግብር ከፋይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ግብር ከፋይነት ተመዘገበ የሚባለው በባለሥልጣኑ ከተመዘገበበት ዕለት ወይም ምዝገባው እንደሚፀና ከተገለፀበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ • የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ተመዝጋቢ የሆነ ሰው ከተመዘገበበት ዕለት ጀምሮ ለሚያደርገው ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለተጠቃሚው ወዲያውኑ ያልሰጠ መሆኑ በወንጀል የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ • እውቅና ያልተሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ መጠቀም በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 471/98 አንቀጽ 5 አዋጅ ቀ. 285/94 አንቀጽ 64, 3/1/ኘ/2/, 22/1/ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 117 ደንብ ቁጥር 139/99 አንቀጽ 22 መመሪያ ቁጥር 46/99	59851	አቶ አለሙ ጋባ እና የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	የካቲት 11/2003	
99.	• በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 368/95 /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 74 ሥር ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ሊጣልበት ስለሚችለው የቅጣት አይነትና መጠን	48628	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ሕግ	ግንቦት 05/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• በኮንትሮባንድ ዕቃ ሲያንገብግ የተገኘ ተሽከርካሪ ሊወረስ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 60/89 አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 64/4/, 74		እና አቶ በርሄ ሐጐስ		
100.	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አስቀድሞ በዋስትና ለሌላ ሰው ያልተሰጡ የግብር ከፋይ ንብረቶች ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/, 78/1/	57100	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጅማ ቅ/ጽ/ቤት እና እነ አቶ አዳራ ሰይድ /ሁለት ሰዎች/	ግንቦት 30/2003	
101.	የተሸከርካሪ ባለንብረትና ሹፌር በመሆን የኮንትሮባንድ ወንጀል በተሸከርካሪ በመታገዝ የተፈፀመ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የግለሰቡን የወንጀል ጥፋተኝነት ውሣኔ ተከትሎ ተሽከርካሪው እንዲወረስ ትዕዛዝ መሰጠት ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 91/2/, 2/1/	64819	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና አቶ አንተነህ ካሣዬ	ሰኔ 30/2003	
102.	ከቀረጥ ነፃ፣ በቅናሽ ቀረጥ ወይም በጊዜያዊነት ከቀረጥ ነፃ የገባን ዕቃ ህግን በሚቃረን መልኩ የቀረጥ ነፃ መብቱ ከተሰጠበት ምክንያት ውጪ መጠቀም /ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት/ የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/ /ሀ/ /ለ/ /2/	58266	ወ/ሮ አልማዝ ደሴ እና የጉምሩክ ዓ/ህግ	ሰኔ 03/2003	
103.	• አንድ ዕቃ /ንብረት/ ኮንትሮባንድ ነው ወይም የጉምሩክ ስርዓት ያልተፈፀመበት ነው በሚል በቁጥጥር ስር ሊውል የሚችልበት አግባብ • የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ማስገባት ወይም ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት ዕቃው ኮንትሮባንድ እንዲባል የሚያደርግ ስለመሆኑና የኮንትሮባንድ ወንጀልን የሚያቋቁም ስለመሆኑ • "የጉምሩክ ክልል" በሚል የተጠቀሰው ሃረግ አጠቃላይ የኢትዮጵያ የግዛት ክልልን የሚያመላክት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 2/17/, 12/4/, 13/1/, 91/1/, 2/7/	60400	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ኤፍታታ እና ቢኤም ኤም ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ሐምሌ 12/2003	
104.	በህግ አግባብ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተፈፀመበት ዕቃ/ንብረት/ የኮንትሮባንድ ዕቃን ለማሳለፍ በሸፋንነትና በክለላነት ያገለገለ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ የጉምሩክ ባለስልጣን ይህን በሸፋንነትና በክለላነት ያገለገለውን ዕቃ ለመውረስ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 6/5/ 58/1/ /ለ/ 16-18 አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 22	65656	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና ወ/ሪት ትዕግስት ጥላሁን	ሐምሌ 26/2003	
105.	የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃን በማንገዝ የተያዘ ተሽከርካሪ እንዲወረስ ላይታዘዝ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 104/3/ /ሀ/ አንቀጽ 91/1/	57243	የሚሌ ገቢዎች እና ጉምሩክ እና አቶ ደረጀ ከፍያለው ሲማ	መስከረም 27/2003	
106.	• ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • በደረሰ የአካል ጉዳት ወይም በሞት አደጋ ምክንያት ከሚሰጥ የካሣ ክፍያ በስተቀር ሌሎች በማናቸውም ሁኔታ የሚከፈሉ የካሣ ክፍያዎች ከግብር ነፃ ናቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ • ከሥራ መሰናበት ጋር በተገናኘ ለሰራተኞች የሚሰጥ የመልሶ ማቋቋሚያ የድጋፍ ክፍያ የሥራ ግብር	65330	የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር እና እነ አቶ ተክሌ ጋረደው /ስድስት ሰዎች/	ሰኔ 30/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የሚከፈልበት ገቢ ነው ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 10/1/, 2/10/, 1/11/				
107.	በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ግብር ከፋይ ይግባኙን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ለማቅረብ የሚችለው በጉባኤው የተወሰነበትን ግብር ይግባኝ ሙሉ በሙሉ ሲከፍል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 112/4/ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 43/4/	59711	ሸበል ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ህግ	ሰኔ 14/2003	
	ከውል ውጭ ኃላፊነት				
108.	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት በመኪና ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ የመኪናው ባለቤት በደረሰው ጉዳት የተነሳ ሊከተል የሚችለውን ኪሣራ ለመቀነስ ተገቢውን ጥረት የማድረግ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2091, 2097/1/ /2/	54021	አቶ ዱላ ያሲን እና ወ/ሮ አበበች እሸቱ	ህዳር 03/2003	
109.	የህንፃ ተቋራጭ ሠራተኛ በመሆን በሚሠራው ህንፃ ላይ ሥራውን በማከናወን ላይ እያለ ከህንፃው ወድቆ ጉዳት የደረሰበት ሰው የሚሰራውን ህንፃ ባለቤት ከውል ውጭ የሆነ ግንኙነትን መሰረት በማድረግ የጉዳት ካሣ ሊጠይቅ የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2077	52595	ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት እና እነ ወ/ሮ ሻሎም ተስፋዬ /አራት ሰዎች	ታህሳስ 15/2003	
110.	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የዘረጋቸው የኤሌክትሪክ መስመር ገመዶች ለሚያደርሱት ጉዳት ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችለው ጉዳቱ የደረሰው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በተጐጂው ጥፋት መሆኑን በማስረዳት ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2086/2/	57904	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ወልዱ ገ/ስላሴ	ታህሳስ 15/2003	
111.	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ተፈፃሚ ከሚሆነው የይርጋ ጊዜ ጋር በተገናኘ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት የሆነው ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣና ጥፋት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ አጥፊው በወንጀል ጉዳይ ክስ ያልቀረበበትና ያልተቀጣ እንኳን ቢሆን በወንጀል ህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 /1/ እና /2/	58920	አለምነው አበበ አካሌ እና ህብረት ኢንሹራንስ አ.ማ	የካቲት 22/2003	
112.	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ፍ/ቤቶች የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የሚሰጡት ውሣኔ በይግባኝ ሊለወጥ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2152, 2153	53598	አቶ ይልማ ደጀኔ እና ወ/ሮ መዲና ዲታሞ	ግንቦት 19/2003	
113.	የባንክ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ጥፋት ፈጽሟል በሚል በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልበት ብሎም ላደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍል ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2524/2/, 1676/1/, 1790/2/, 2090	44427	አቶ ለገሰ ጥቀኔር እና ንብ ኢንተርናሽናል አ.ማ	መጋቢት 09/2003	
114.	• አንድ ሰው የሌላውን ሰው የሥራ ድካም ወይም በሌላው ሰው ሀብት በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ እንደሆነ አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሀብቱ ወይም በጉልበቱ ለደከመው ሰው የመካስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • አንድ ሰው ባለዕዳ መሆኑን ያመነ እንደሆነ ዕዳው የታመነለት ሰው ባለዕዳው ዕዳውን ያመነበትን ምክንያት የማስረዳት /የማረጋገጥ/ ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162 2164 2019	59698	አቶ ሚኪያስ ክበደ እና እነ ወ/ሮ ምስራቅ ንጉሴ /ሁለት ሰዎች/	መጋቢት 06/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

115.	• በህክምና ጉድለት ሀላፊነት ሊከተል የሚችልበትና ካሣ የሚከፈልበት አግባብ • የጉዳት ካሣን ለመወሰን የጉዳቱን ልክ በማስረጃ ለማረጋገጥ አዳጋች ሲሆን በርትዕ ለመወሰን የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090, 2102	64590	ሜሪስቶፕስ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ እና ወ/ት ሠናይት ዓለማየሁ	ሚያዝያ 18/2003	
116.	የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥ ተሽከርካሪ ተሳፋሪ በመሆን ሲጓዙ ለሚደርስ ጉዳት አጓዡ ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችልባቸው ልዩ ሁኔታዎች፣ ኃላፊ በሆነ ጊዜ የኃላፊነቱ መጠን እንዲሁም አጓዡ በህግ ከተደነገገው የጉዳት ካሣ መጠን በላይ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች የንግድ ህግ ቁ. 595, 596, 599, 588, 597 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2130, 2092, 2091	67973	አቶ በቀለ ወልቻም እና አቶ ጥበቡ ጦራ	ሐምሌ 25/2003	
117.	• መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ልዩ የምዝገባና የባለሀብትነት ስም ዝውውር የሚያስፈልገው ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ንብረት ስለመሆኑ • የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤትነት /ባለሃብትነት/ ወደ ሌላ ሰው ተላልፏል ሊባል የሚችልበት አግባብ • መኪኖች እና ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ለሚያደርሱት ጉዳት በኃላፊነት ስለሚጠየቀው ወገን የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1186/1/ /2/, 2081/1/, 2082/2/, 2083/1/, 2267/2/, 2324/1/ አዋጅ ቁ. 256/60 አንቀጽ 6 አዋጅ ቁ. 468/97 አንቀጽ 21 ደንብ ቁ. 360/61 አንቀጽ 6 7/1/ /3/, 8, 11/1/ /2/, 42-45	24643	ወ/ሮ አስናቀች ወ/ማርያም እና አቶ አለማየሁ አህመድ	ሐምሌ 29/2000	
118.	ባለሞተር ተሽከርካሪ ከሚያደርሰው ጉዳት ጋር በተያያዘ የመጨረሻው ኃላፊነት (ultimate liability) የሚወድቀው መኪናው ሲሸከረክር የነበረው ባለቤቱ በቀጠረው ሹፌር እንኳን ቢሆን በወቅቱ በመኪናው ሲገለገል የነበረው ሰው ላይ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2082/1/, 208/1/, 2083/1/	55228	አቶ አብራር ሳቢር እና እነ ወ/ሮ አለምፀሐይ ወሰኔ /ሁለት ሰዎች/	ጥር 25/2003	
119.	ከውል ውጭ የሌላ ሰው ሃብት የሆነን ነገር በመያዝ ለተገለገለበት ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል በሚል የቀረበ አቤቱታ ጋር በተያያዘ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024 ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024	54518	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ፀሐይ ዘሙይ /ሁለት ሰዎች/	የካቲት 14/2003	
120.	• ለአካለ መጠን ያልደረሱ ህፃናት ላይ ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ሲደርስ የጉዳት ካሣ መክፈል የሚገባው ስለመሆኑና የካሣ አወሳሰኑ ስሌት • በገንዘብ ለመተመን የሚያዳግት የአካል ጉዳት በደረሰ ጊዜ ካሣ በርትዕ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090, 2091, 2092/2/, 2095/2/	38117	አቶ ብርሃኑ ፈይሳ ቢፍቱ እና እነ ናይል ኢንሹራንስ /ሁለት ሰዎች	ሐምሌ 09/2001	
አፈፃፀም					
121.	በዕዳ ምክንያት በፍ/ቤት የተከበረ ንብረት እንዲሸጥ በተደረገ ጊዜ ንብረቱን ያስከበረው ወገን የሚኖረው መብት ከሽያጭ ገንዘቡ ላይ የቀዳሚነት መብት ካላቸው ባለገንዘቦች የሚተርፍ ካለ መውሰድ ነው እንጂ ንብረቱን በሽያጭ ውል የተነሳ ባለቤት የሆነን ወገን መጠየቅ ወይም ንብረቱን የመከተል ስላለመሆኑ	48042	ጉና ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ እና እነ ቡሬ ባጉና የማዕድን ውሃ	ጥቅምት 03/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ፋብሪካ /ሦስት ሰዎች/		
122.	የአፈፃፀም ክስና መጥሪያው ደርሶት የፍርድ ባለዕዳ ሳይቀርብ በሚቀርበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ሥርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/"ን" ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ስላለመሆኑ እና የተሰጠን ትዕዛዝም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 መሠረት ለማስነሳት የሚቻልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/, 78	53943	እነ ወ/ሮ አስካለ ደሣለኝ /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ የትምወርቅ ታደሰ /ሁለት ሰዎች/	ህዳር 16/2003	
123.	በአንድ የፍርድ ባለዕዳ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ ባለገንዘቦች አፈፃፀም ሊቀጥል የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403, 378	40945	ኮለኔል ግርማ ሃይለስላሴ እና አቶ አስማማው መንግስቱ	ጥር 13/2003	
124.	ፍርድን የሚያስፈጽም የአፈፃፀም ችሎት የተሰጠውን ፍርድ በአግባቡ ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የገመተውን ትዕዛዝ ለመስጠት የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 392/1/	62804	እነ አቶ ብርሃን ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ለታይ ገ/ጊዮርጊስ	ሰኔ 15/2003	
125.	በፍ/ብሔር ክርክር የተፈረደበት ሰው የፍርዱ አፈፃፀምን ለማሰናከል የተንቀሳቀሰ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ እስከ ስድስት ወር በሚደርስ እስራት ሊቀጣ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 389/1//ሀ//ለ/	63754	አቶ ዓለም ባህታ እና ወ/ሮ ኑኑሽ ሸህምሎ	ሰኔ 15/2003	
126.	• ፍርድን የሰጠ ፍርድ ቤት ፍርዱ በውክልና እንዲፈፀም ለሌላ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ባስተላለፈ ጊዜ በውክልና ፍርድ ለማስፈፀም ስልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ፍርድ ከሰጠው ፍርድ ቤት ማረጋገጫ እንዲላክለት ለመጠየቅ የሚችለው የፍርዱ ወይም የትዕዛዙ ግልባጭ ትክክለኛነት የሚያጠራጥር ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ካለው ብቻ ስለመሆኑ • ፍርድን በውክልና እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ የደረሰው ፍርድ ቤት ስለፍርዱ ትክክለኛነት ወይም በግልባጮቹ ላይ ስለሰፈረው ነገር ሌላ መግለጫና ማብራሪያ ሳይጠይቅ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ማስፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 373/2/ 371/1/	66988	አቶ ቀደመ ተሾመ እና አቶ ኢብራሂም ሐመዱ	ሐምሌ 25/2003	
127.	ፍርድን የሰጠ ፍ/ቤት ፍርዱ እንዲፈፀምለት ለሌላ ፍ/ቤት የውክልና ስልጣን ስለሚሰጥበት አግባብና የፍርድ አስፈፃሚ ፍ/ቤት የስልጣን አድማስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371-455	64354	አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና ወ/ሮ ኡልባሬ ሰማን	ሰኔ 13/2003	
128.	ፍርድ የማይፈፀመው ፍርዱ በይግባኝ ስርዓት የተሰወጠ እንደሆነ ወይም ፍርዱን ላለመፈፀም ህጋዊ ምክንያቶች ያሉ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378, 386	59301	መምህርት አታቱ ከበደ እና ስቱፕስ አት.ኢዲኬሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር	ግንቦት 04/2003	
129.	በአፈፃፀም ደረጃ የሚገኝ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78/1/ ያለው አግባብነት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 /1/	52110	እነ ወ/ሮ ይህደጋ ሳሙኤል /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ አሰፉ ሳሙኤል /አራት ሰዎች/	ታህሳስ 26/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

130.	• በክርክር ሂደት ተሳታፊ ያልነበረና ፍርድ ያልተሰጠበት ሰው ንብረት በፍርድ አፈፃፀም ሲያዝበት /በሃራጅ ሲሸጥበት/ ሊከተለው ስለሚገባው አካሄድ • በፍርድ ሊያዝ ስለሚችል ንብረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447/1/, 418, 234/1/ /ሠ/, 235/2/, 414/2/, 423, 425, 443, 453/1/ /3/	58009	እነ አቶ ስለሺ ወርቅነህ /ሦስት ሰዎች/ እና እነ አቶ ሁሪሳ ደመሳ /ሁለት ሰዎች/	ጥር 262003	
131.	ከግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተያያዘ በአፈፃፀም ደረጃ የሚቀርብ የቀዳሚነት መብት ይከበርልኝ ጥያቄ የህግ መሰረት ያለውና ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 32/1/ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418	48997	የቦሌ ክ/ከ/ገቢዎች መምሪያ እና እነ አቶ መዓዛ ሽፈራው /ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 16/2003	
	ልዩ ልዩ				
132.	በጤና ጥበቃ ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ከጤና ሥነ ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ በጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ ክስ በቀረበባቸው ጊዜ በተገቢው መንገድ መልስ የመስጠትና የመሰማት መብታቸው ሊጠበቅ የሚገባ ስለመሆኑ የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎችን መማክር ጉባኤ ማቋቋሚያ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 16/1/ /2/	56934	እነ አሰገደች የእናቶች እና የህፃናት ሆስፒታል እና የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	መስከረም 26/2003	
133.	በውጭ አገር የተደረጉ ሰነዶች (foreign documents) በኢትዮጵያ ውስጥ ህጋዊ ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 26/1/	32282	ሚ/ር ካርሎ ካስቴሊ እና የወ/ሮ ዘውዴ ደሚኒኮ ውርስ አጣሪ አቶ ታምራት ኪዳነ ማርያም	መስከረም 25/2003	
134.	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሻሻለ አዲስ የባንክ ስራ ፈቃድና የዳይሬክተሮች እና የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሹመትን አስመልክቶ የሚያወጣው መመሪያ ህጋዊ መሰረት ያላቸውና በተግባር ሊውሉ የሚገባ ስለመሆኑ መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ/39/ 2006 አንቀጽ 5.1.4 አንቀጽ 5.1.5 አዋጅ ቁ. 83/89 አዋጅ ቁ. 84/86	44226	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና እነ ህብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ /ሦስት ሰዎች	ታህሳስ 15/2003	
135.	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በህግ ከተጣለበት የጡረታ አበል የመክፈል ግዴታው ጋር በተያያዘ የአንድን ሰው ባልነት /ሚስትነት/ በማረጋገጥ የተሰጠ ውሣኔን የመቃወም መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ህ/ቁ. 358	53221	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ንጋት ወ/ሰንበት	ታህሳስ 27/2003	
136.	የጥብቅና ፈቃድ ክልከላ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ ለሚመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ ታይቶ የሚወሰን እንጂ በቀጥታ ክልከላ እንዲወገድ በሚል ለፍ/ቤት አቤቱታ የሚቀርብበት ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 29/1/	59261	የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር እና አቶ ታዬ በዛብህ ፊኖ	ጥር 24/2003	
137.	በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40/8/ መሰረት ለተወሰደ ንብረት የሚጠየቅ ካሣ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1143 እና 2143 በሁለት ዓመት ይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ	59979	የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ከበደ ወዳጆ	የካቲት 09/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

138.	የቡና ላኪነት ፈቃድ አውጥቶ በግብይት ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅን ጥሷል በሚል በወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ መሰረት ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 602/2000 አንቀጽ 14/3/, 15/3/ ደንብ ቁ. 159/2001 የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር መመሪያ	58008	እነ ኤርሰዶ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	ግንቦት 16/2003	
139.	በጡረታ የተገለለ ሰው በሌላ ሥራ ላይ በተቀጠረበት ጊዜ መንግስት ለጡረተኞች ያደረገውን የጡረታ ጭማሪ መሰረት በማድረግ አሰሪው የደመወዝ ጭማሪ እንዲያደርግለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	60025	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ወለዴ በየነ /አራት ሰዎች/	ግንቦት 02/2003	
140.	• ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ “እስከመጨረሻ ድረስ በመያዝ ለመከራከር” በሚል የሚያደርገው ስምምነት ጉዳዩ ሊያስኬድ የሚችል እስከሆነ ድረስ በአንድ ፍ/ቤት ሳይወሰን በይግባኝና በሰበር ደረጃ ሁሉ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ • ጠበቃ ከደንበኛ ጋር ባለው ግንኙነት ደንበኛው ማድረግ ያለበትን ነገር ከህግ አንፃር የማስረዳትና ግልጽ የማድረግ ብሎም የማማከር ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም በአንፃሩ አከራካሪ ጉዳይ በሌለበት ሁኔታ ክስና ክርክር ለማቅረብ የማይገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1732 ደንብ ቁ. 57/92 አንቀጽ 28, 8/2/	60353	አቶ ባልቻ ወ/ፃድቅ እና አቶ ግርማ ቀለታ	ግንቦት 04/2003	
141.	የፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በህግ የተሰጠውን ስልጣን መሰረት በማድረግ አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ በድጋሚ በማየት የተለየ ውሣኔ በሰጠ ጊዜ የተለወጠውን /የተሻረውን/ ውሣኔ መሰረት በማድረግ የተከናወኑ ተግባራትን ለማስተካከል ወይም የተከራካሪ ወገኖችን መብት ለማስተካከል ተገቢ የሆነ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349, 6	60508	እነ ወ/ሮ ሮዛ አባተ /አራት ሰዎች/ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ግንቦት 15/2003	
142.	በፌዴራል ፍ/ቤቶች በጥብቅና ለመስራት የሙያ ፈቃድ የሚሰጥበት አግባብ	67280	የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚ/ር እና እነ አቶ ተስፋዬ በርሄ /አምስት ሰዎች/	ግንቦት 15/2003	
143.	የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራን ዜግነት መርጦ የያዘ ሰው “የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ” ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 270/94 አንቀጽ 2/2/ ደንብ ቁ. 101/96 አንቀጽ 2/1/	55238	እነ የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ህዳት ፍስሃ ጽዮን	መጋቢት 09/2003	
144.	• ጠበቃ የሆነ ሰው ደንበኛውን ወክሎ ለፍ/ቤት የሚያቀርበው አቤቱታ እውነት ስለመሆኑ በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • ማንኛውም ጠበቃ የህግ ሙያውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሁሉ ለደንበኛው፣ ለሌሎች የህግ ባለሙያዎች፣ ለተከራካሪ ወገኖች፣ ለፍርድ ቤት፣ ለሙያው ብሎም በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ኃላፊነቱን በቅንነት፣ በታማኝነት እና በእውነተኛነት የመወጣት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 92/1/ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁ. 57/92 አንቀጽ 3 29/2/ 56/4/ /6/	67146	ሻምበል ተሾመ ደምሴ እና የፍትህ ሚኒስቴር ዓ/ህግ	ሐምሌ 01/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

145.	እጣው ከመድረሱ በፊት አባልነቱን ያቋረጠ የእቁብ አባል ለእቁብ የከፈለውን ገንዘብ ይመለስልኝ በሚል የኃላፊነት ጥያቄ ሊያቀርብባቸው ስለሚችሉ አካላት	55794	አቶ ለማ አበበ እና ወ/ሮ ሃና አሰፋ	ጥር 24/2003	
146.	• በፍርድ ቤት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ፀንቶ ባለበት ወቅት እግድ የተሰጠበት ንብረት ተሸጦ በተገኘ ጊዜ የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን ሊኖረው ስለሚችለው መፍትሔ • የፍርድ ቤትን የእግድ ትዕዛዝ አለማክበር /መጣስ/ ኃላፊነትን የሚያስከትል ተግባር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2028, 2035, 2126	54567	የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና እጎ የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ /ሦስት ሰዎች/	የካቲት 10/2003	
147.	• በአንድ በቀረበ ክርክር ላይ የተሰጠው ውሣኔ የቀረቡትን ማስረጃዎች ይዘት ወይም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነጥብ ከሕጉ ጋር በአግባቡ ተዛምዶ አልታየም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የሕግ ነጥብ /ክርክር/ እንጂ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ነው ተብሎ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል አይደለም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ • የሰበር ችሎት በሥር ፍ/ቤቶች የቀረበን ማስረጃ ክብደትና ተዓማኒነት ለመመርመር በህግ ስልጣን ያልተሰጠው ስለመሆኑ	44804	ወ/ሮ ሰናይት ተመስገን እና ወ/ሮ እጥፍወርቅ በቀለ	ጥቅምት 04/2003	
148.	በወንጀል ድርጊት በኤግዚብትነት ተይዞ የነበረ ወርቅ ከተሸጠ በኋላ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ከተሻረ ሻጩ አካል የወርቁን ዋጋ መክፈል ያለበት በተሸጠበት ወቅት በነበረው ዋጋ ስለመሆኑ	58822	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ሕግ እና አይንሸምስ ሁሴን	መጋቢት 05/2003	
149.	• የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ስበር ችሎት በአንድ ወቅት በአንድ ጉዳይ /ጭብጥ/ ላይ የሰጠው የህግ ትርጉም እንደተለወጠ /እንደተሻሻለ/ ሊቆጠር የሚችለው በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ በህግ አግባብ የተለየ ግልጽ ትርጉም በሰጠ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ • የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ ተቀብሎ ማስተናገድ ብሎም የውርስ አጣሪ መሾም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በህግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ/ /የሰ/መ/ቁ. 35657፣ 42015፣51329 ይመለከቷል/ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41 አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/4/	52530	እነ አቶ ሰናይ ልዑልሰገድ /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ኃይሌ	ህዳር 14/2003	
150.	የይርጋ መርህ ክስን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከትና ንብረትን በመያዝ ወይም ባለይዞታ በመሆን የባለሀብትነት መብት ከሚገኝበት መርህ የሚለይ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1168, 1808	53328	ዓብዱል መሐመድ እና ወ/ሮ ዘበናይ ኃይሌ	ጥቅምት 18/2003	
151.	• የድምጽ ብክለት ተከስቷል ለማለት የሚቻለው የሚሰማው ድምጽ ከመጠን በማለፉ በሌሎች ላይ ሁከት የሚፈጥር መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ • የድምፅ ብክለት (Nuisance) ተፈጥሮብኛልና እንዲወገድ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በሁለት ዓመት ይርጋ ታግዷል ሊባል የማይችል ስለመሆኑ • አንድ ሥራን ለመስራት የንግድ ፍቃድ የሰጠ አካል ሥራው የሚፈጥረው የድምጽ ረብሻ አለ በሚል የንግድ ፈቃዱን የሚሰረዝበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 10 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1225, 1226, 1149	42824	አቶ ብርሃነ ተሰማ እና እነ አቶ ታምራት ኪዳኔ /ሁለት ሰዎች/	ህዳር 08/2002	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

152.	• የአስተዳደር አካል የሰጠው ውሣኔ ወይም የወሰደው እርምጃ ህገ ወጥ መሆኑን እስካረጋገጠ ድረስ ውሣኔውን ለማረም /እንዲስተካከል ለማድረግ/ ስለመቻሉ • በተሳሳተ መንገድ በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሣኔ ቅን ልቦና አድሮበት ለኪሣራ የተዳረገ ሰው ኪሣራ ለመጠየቅ ስለመቻሉ • በስህተት በተሰጠ የግንባታ ፈቃድ ግንባታ ያካሄደ ሰው የአስተዳደር አካሉ ስህተቱን በማረም ግንባታው እንዲፈርስ መግለጫ በሰጠ ጊዜ የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ	57044	እነ የልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 04/14 ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ታሪኩ ኡርጌሳ	ጥር 25/2003	
153.	• ለዳኝነት የቀረበው ጉዳይ በባህሪይው ከአንድ በላይ የሆኑ የህግ ስርዓቶችን ለጉዳዩ አወሳሰን የሚጋብዝና የየትኛው ሥርዓት ህግ ተመራጭ ሊሆን ይገባል የሚል ጥያቄን የሚያስነሳ እንደሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የፍ/ብሔር ስልጣኑ ሊታይ የሚችል ስለመሆኑ • ተዋዋይ ወገኖች በማናቸውም ሁኔታ የአገራቱን ህግ ወደ ጉን በማድረግ ወይም በሚፃረር መልኩ ስምምነት ስላደረጉና ክርክር ስለተነሳ ብቻ አንድ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ህግ ጥያቄን/private international law issue/ የሚያስነሳ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ • በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ካልተወሰነ በቀር አዋጅ ቁጥር 377/96 የውጭ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/3//ለ/ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 11/2/ /ሀ/	54121	ሲ.ኤ.ኤስ ኮንስልቲንግ ኢንጂነርስ ሳልዝ ጊተር ጂ.ኤም.ቢ.ኤች እና አቶ ካሣሁን ተወልደብርሃን	ህዳር 01/2003	
154.	• የክስ ይዛወርልኝ (change of Venue) ጥያቄ ከተከራካሪ ወገኖች የሚነሳ ስለመሆኑና ፍ/ቤትም ጥያቄውን ሊያስተናግድ የሚችለው በህግ የተመለከቱት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ • የክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክሶችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸው ለማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 136/3/, 138/2/, /1/, 139/1/ /ሀ/ አዋጅ ቁ. 322/95 አዋጅ ቁ. 25/88	66945	የእንግሊዝ ህፃናት አድን ድርጅት እና አቶ ገለሰ አስማን	ሰኔ 02/2003	
155.	ለብድር በመያዣነት የተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ውሉ መሰረት በህጉ አግባብ በዋስትና ከመያዙ በፊት በሽያጭ ለሦስተኛ ወገን ተላልፎና ስመ ሃብቱ ለገገርው ተላልፎ በተገኘ ጊዜ ሊኖር ስለሚችለው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3051/2/	65688	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ንጉሴ በያን	ሐምሌ 27/2003	
156.	የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 14/1//ረ/, 66/1/ አዋጅ ቁ. 2/95 አንቀጽ 52	53551	የቀበሌ 10 ባለአደራ ቦርድ እና አቶ ዳንኤል አድርሴ	መስከረም 25/2003	
157.	ይዞታን አስመልክቶ ከሚነሳ የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር ያለበት አቤቱታ አቅራቢው የይዞታ መብቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ካገኘበት ቀን ጀምሮ እንጂ አቤቱታ የቀረበበት ድርጊት መፈፀም ከጀመረበት ዕለት አንስቶ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149, 1146/1/, 1144/2/	60392	አቶ ጌትነት የኔ እና አቶ እዮብ ቢንያም	ታህሳስ 26/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስከረም 24 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘይነባ ከልፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ከድጃ ሲራጅ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በአላባ ቆሊቶ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

በተጠሪ እና በተከሳሽ አቶ ሐጂ መሐመድ ሐሊስ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ እንዲፈርስ መደረጉን ተከትሎ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ተጠሪ አቅርባለች፡፡ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ከተከሳሽ ጋር ከ1984ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሳስራ ያለች መሆኗን ገልፃ የሚሰጠው ውሳኔ መብቷን የሚነካ ስለሚሆን ጣልቃ ገብታ ለመከራከር አመልክታለች፡፡ የከተማው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ጣልቃገብ ለመካፈል የጠየቀችው ንብረት በተጠሪ እጅ ያለ ከመሆኑም ሌላ ይህንን ቤት የገነባች ለመሆኑ አልያም ወጪ ያወጣች ስለመሆኑ አላስረዳችም በሚል በቤቱ መብት የላትም ሲል አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጎ ተጠሪና ባለቤቷ ሐጅ መሐመድ ሐሊስ ለሁለት እኩል እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝታ ለአላባ ልዩ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረበች ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 23 ቀን 2002ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የስር ፍ/ቤት አመልካች ነዋሪነቷ ሳውዲ አረቢያ በመሆኑ ገንዘብ ልካ ለጣውንቷ ቤት ትሰራለች ተብሎ አይታመንም የሚለው አገላለጽ የተሳሳተ መሆኑን ቤቱ የተሰራው የአመልካች ባለቤት/የሥር ተከሳሽ/ ከሳውዲ አረቢያ በላከው ገንዘብ ስለመሆኑ የአመልካች እና የስር ተከሳሽ ጋብቻ አሁንም ፀንቶ ያለ ስለመሆኑና በክልሉ የቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ አንቀጽ 71/2/ መሠረት በባለቤቷ ስም የተፈራ ንብረት የጋራ ስለመሆኑ ጠቅሰው በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

የሰበር ችሎቱም የሰበር አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ሚስት መሆኗ ካልተካደ እና ከባለቤቷ ጋር የምትኖር መሆኗ ከተረጋገጠ የንብረት ክፍፍል ድርሻ ጥያቄዋ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ወይም አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ ተጠሪ መጋቢት 27 ቀን 2002ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም አመልካች ከሐጅ መሐመድ ሐሊስ ጋር ጋብቻ ያልመሰረተች ስለመሆኑ ንብረቱንም በሚመለከት ቤቱ የተሰራው በተጠሪ እና ባለቤታቸው ሐጅ መሐመድ ሐሊስ የጋራ ጥረት ብቻ ስለመሆኑ ስር ፍ/ቤት በማስረጃ ስለማረጋገጡ አመልካች ንብረቱን በማፍራት ረገድ ያደረገችው አስተዋጽኦ ስለመኖሩ በስር ፍ/ቤት ጭብጥ አስይዛ ያላስረዳች መሆኑን በመዘርዘር በተጨማሪም ለማዘጋጃ ቤቱ ከ1990-2001ዓ.ም ድረስ ግብር ብር 16,516.50 ውስጥ ግማሽ ድርሻውን ብር 8,258.25 የከፈሉ መሆኑን ጠቅሰው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች ጠበቃም የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልስ በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃርና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው ፍሬ ነገር አመልካች ከሐጅ መሐመድ ሐሊስ ጋር በ1984ዓ.ም ጋብቻ መስርታ አብረው ሳውዲ አረቢያ የሚኖሩ ስለመሆኑ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ በ1987ዓ.ም ከሐጂ መሐመድ ሐሊስ ጋር ጋብቻ የመሠረተች ሲሆን ባለቤቷ ለረዥም ዓመታት ውጪ አገር የሚኖር በመሆኑና እሷንም ወደ ውጪ እወስድሻለሁ ብሎ የገባውን ቃል ባለማክበሩ ፍቺ እንዲወስን ለመጠየቅ ምክንያት እንደሆናት ነው፡፡ እንግዲህ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ጉዳይ ተጠሪም ሆኑ አመልካች ከሐጅ መሐመድ ሐሊስ ጋር ጋብቻ መስርተው የነበሩ ስለመሆኑ ነው፡፡ የተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ እንዲፈርስ መደረጉን ተከትሎ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ከመቅረቡ ወጪ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈፀመ በሚል የቀረበ ክስ ስለመኖሩ አልተጠቀሰም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ሁለቱም ሚስቶች በየፊናቸው ከአንድ ወንድ ጋር ጋብቻ መስርተው ሲኖሩ ቆይተው ጋብቻው በአንደኛዋ ተጋቢ ጥያቄ በፍቺ ሲፈርስ የንብረት ክፍፍል አፈፃፀም በምን መልክ ሊከናወን ይገባል የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡

የፌዴራሉም ሆነ የክልሎች የቤተሰብ ሕግ የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል የሚደነግገው ክፍል አንድ ጋብቻ ብቻ መኖርና መፍረስን ታሳቢ በማድረግ እንጂ ጋብቻ ላይ ጋብቻ ሲኖር የሚከተለውን ውስብስብ ጥያቄ ታሳቢ ያላደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሕጉ በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንዳይፈፀም ግልጽ ክልከላ ያደረገ በመሆኑ ነው፡፡

ሆኖም ግን በማህረሰቡ በተግባር እየተከናወነ ያለተግባር እንደመሆኑ ክርክር በተነሳ ጊዜ የሚሰጠው ውሳኔ ማህበራዊ ቀውስ እንዳያስከትል ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የዳኝነት አካሉ ኃላፊነት ይሆናል፡፡

ስለሆነም የሕጉን መሠረታዊ ዓላማና ግብ ለማሳካት በሚቻልበት አግባብና ፍትሀዊ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችል አግባብ ለሕጉ ትርጉም መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ የሚከራከሩት በአላባ ቆሊቶ ከተማ በ1250 ካ.ሜ ቦታ ላይ የተሰራ ቤትን በሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በዚህ ቤት ላይ ከባለቤቷ ጋር ገንዘብ በማውጣት የሰራች መሆኑን በመጥቀስ የቤቱ ግማሽ (50%) የባለቤቷ የተቀረው ግማሽ (50%) ለእሷ እና ለተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲካፈል እንዲወሰን የጠየቀች መሆኑን የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ይዘት ያመለክታል፡፡ ተጠሪ ደግሞ ይህንን ቤት የሰራችው በራሷ እና በባለቤቷ እንዲሁም ቤተዘመዶቻቸው ጥረት መሆኑን ገልፃ ቤቱ የተጠሪ እና የባለቤቷ ብቻ እንደሆነ ትከራከራለች፡፡ በዚህ ረገድ የግራ ቀኙን ማስረጃ የሰማውና የመረመረው የወረዳ ፍ/ቤት አመልካች በቀጥታ ባለመብት ሊያደርጋት የሚያስችል አስተዋጽኦ ስለማድረጓ አላስረዳችም ሲል ደምድሟል፡፡

ይልቁንም ቤቱ የተሰራው ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ከተፈፀመ በኋላ መሆኑን እና ተጠሪ ቤቱን ተቆጣጥረው ይዞታዋ ስር ያለመሆኑን በመጥቀስ በተሻለ ማስረጃ ባለመብት መሆኗን አረጋግጣለች ብሏል፡፡

ይህንን የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መነሻ አድርገን ከሕጉ ማገናዘብ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመርህ ደረጃ ጋብቻ ሲፈርስ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት እኩል የሚከፋፈል መሆኑ በፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግም ሆነ በክልሉ ተቀባይነት ያለው መሠረት ሐሳብ ነው፡፡የማጣራቱ ተግባርም በስምምነት አለያም በሕጉ ሊወሰን ይችላል፡፡ ንብረቱ ሲጣራ ተጋቢዎች የግል ንብረታቸውን አስቀድሞ እንዲለዩና እንዲወስዱ ከዚያም የጋራ ንብረት ላይ እኩል መብት እንዳላቸው ሕጉ ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠቃሹ ቤት የተጠሪና የባለቤቷ የሐጂ መሐመድ ሐሊስ የጋራ ንብረት ነው ሲል የስር ፍ/ቤት ደምድሟል፡፡ የአመልካች ክርክር ባለቤቷ ሐጂ መሐመድ ሐሊስ ያፈራው ንብረት ነው ቢባል እንኳ በሕጉ ህሳቤ መሠረት ግማሽ ድርሻ ይገባኛል ባይናት፡፡

የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 62/1/ እንደሚያመለክተው በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት ከግል ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች የጋራ ሐብታቸው ይሆናሉ፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተጠቀሰውን ንብረት ለማፍራት አስተዋጽኦ ስለማድረጓ አላስረዳችም ቢባልም በባሏ ጥረት የተፈራ ንብረትም ቢሆን የጋራ መብት እንደሚያስገኝላት ሕጉ ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተፈራ ንብረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሐብት ነው እስካልተባለ ድረስ የጋራ እንደሆነ ሕጉ ግምት የሚወስድ በመሆኑ ነው፡፡

ስለሆነም ተጠቃሹን ቤት በተመለከተ ተጠሪ ቤቱ ላይ ቀጥታ አስተዋጽኦ ስለነበራት 50% /አምሳ በመቶ/ ድርሻ አላት ሲል የስር ፍ/ቤት የደረሰበትን ድምዳሜ ከማስረጃ የመነጨ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ነው ቢባልም በተቀረው 50% /አምሳ በመቶ/ ላይ አመልካች ድርሻ የላትም ሊባል የሚገባ አይደለም ምክንያቱም በሕጉ አገላለጽና እሳቤ አመልካች ባለቤቷ በስሙ ያፈራው ንብረት ላይ ድርሻ እንዳላት ተመልክቷልና፡፡ ስለዚህም የስር ፍ/ቤቶች አመልካች በአከራካሪው ቤት ላይ ምንም ድርሻ የላትም ሲሉ የሰጡት ውሳኔ የሕጉን መንፈስና ዓላማ በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ስለዚህም አመልካች ከባለቤቷ ድርሻ ላይ እኩል የመካፈል መብት ይኖራታል ማለት ነው፡፡

በክርክሩ ሒደት እንደተገለጠው በአመልካች እና በባለቤቷ /ሐጅ መሐመድ ሐሊስ/ መካከል ያለው ጋብቻ ያልፈረሰ በመሆኑ አከራካሪውን ንብረት ይካፈሉታል ባይባልም አመልካች ድርሻ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳላት ሊታወቅ ይገባልና፡፡ በዚሁ መሠረት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማረም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአላባ ቆሊቶ ከተማ የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 02464 በ10/09/2001ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የአላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01969 በ4/10/2001ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መ/ቁ 29217 በ05/02/2002ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሎ ተከታዩ ተወስኗል፡፡
2. በአላባ ቆሊቶ ከተማ በ1250 ካ.ሜ ቦታ ላይ የሰፈረው ቤት በሐጅ መሐመድ ሐሊስ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ተጠሪና ሐጅ መሐመድ ሒሊስ ለሁለት ከተካፈሉ በኋላ በሐጅ መሐመድ ሐሊስ ድርሻ ላይ አመልካች እኩሌታ መብት አላት ብለናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ መጋቢት 7 ቀን 2002ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 2 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ገብረሥላሴ አማረ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አብርሽት ተጫኔ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የሚያከራክረው ጉዳይ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍያ የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍች መፍረሱን ገልፀው በጋብቻ ወቅት በጋራ ያፈሩት የቤት ቁሣቁስ በልደታ ክፍለ ከተማ ተከራይተው ከሚኖሩበት ቤት ግቢ ውስጥ የሰሩት አንድ ክፍል ቤትና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ 2 ሣይት ህንፃ ቁጥር 29 የቤት ቁጥር ቢ29/48 የሆነ ኮንደሚኒየም ቤት የጋራ ስለሆነ ያካፍለኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በቀበሌ ቤት ግቢ ውስጥ የተሰራው ቤት ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ከመፈፀማቸው በፊት የተሰራ መሆኑን የኮንደሚኒየም ቤቱ ደግሞ ከተጠሪ ጋር የነበረንን ጋብቻ ታህሣሥ 18 ቀን 1999 ዓ.ም በስምምነት አፍርሰን ተጠሪ ብር 1300/አንድ ሺ ሶስት መቶ ብር/ ተቀብላ ከሄደች በኋላ የደረሰኝ ስለሆነ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከቀበሌ ከተከራዩት ግቢ የተሰራው አንድ ክፍል ቤት አመልካች ተጠሪን ከማግባቱ በፊት የሰራው የግል ንብረቱ መሆኑን በተሻለ ማስረጃ አስረድቷል፡፡ የኮንደሚኒየም ቤቱ የደረሰው የአመልካችና የተጠሪ ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሣኔ በፍች ከመፍረሱ በፊት ነው፡፡ የተጠሪና የአመልካች ጋብቻ የፈረሰው መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም እንጂ ታህሣሥ 18 ቀን 1999 ዓ.ም አይደለም፡፡ ስለዚህ ኮንደሚኒየም ቤቱ የጋራ ንብረት ስለሆነ በቤቱ ላይ ያለውን መብትና ግዴታ አመልካችና ተጠሪ እኩል ይካፈሉ ፡፡ የቤት ቁሣቁስ ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ኮንደሚኒየም ቤት ለማግኘት የተመዘገብኩት ተጠሪን ከማግባቱ በፊት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እኔና ተጠሪ በስምምነት ጋብቻችንን ጎዳር 23 ቀን 1999 ዓ.ም አፍርሰናል፡፡ ስለዚህ የተመዘገብኩት ተጠሪን ከማግባቱ በፊት እጣ የወጣልኝና ያገኘሁት እኔና ተጠሪ በስምምነት ጋብቻችንን ካፈረስን በኋላ በመሆኑ ኮንደሚኒየም ቤቱ የጋራ ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስህተት አለበት በማለት ሰኔ 8 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ክቤት የወጣሁት በስምምነት ጋብቻችንን በማፍረስ ሣይሆን አመልካች ስለሚደበድቡኝ የቀለብ ገንዘብ ሰጥተውኝ ነው፡፡ ኮንደሚኒየም ቤቱ የደረሰን ጋብቻው ከመፍረሱ በፊት በመሆኑና አስር ፐርሰንት የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ከጋራ ንብረት በመሆኑ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው መባሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መረምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአመልካችና የተጠሪ ጋብቻ መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በፍርድ ቤት ውሳኔ መሆኑንና ኮንደሚኒየም ቤቱ የደረሳቸው ጋብቻው በፍች ከመፍረሱ በፊት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ለኮንደሚኒየም ቤት የተመዘገብኩት ተጠሪን ከማግባቴ በፊት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክርም ቤቱን እዲገዙ እጣ የወጣበት ጊዜ ጋብቻው ፀንቶ እስካለ ድረስ ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት ስለተመዘገቡ ብቻ ቤቱ የግል ንብረት እንደማይሆን ከተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ ለቤቱ ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ የሚከፈለውን ክፍያ ከአመልካች ጋር አብረው የመጋራትና ግማሹን የመክፈል ግዴታ እንዳለባቸው ግልጽ በማድረግ አመልካችና ተጠሪ በኮንደሚኒየም ቤት ላይ ያለውን መብትና ግዴታ እኩል እንዲካፈሉ በማለት መወሰኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ ስላገኘነው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት አጽንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካቾች፡- 1. በላቸው አስፋው ቀረበ

2. መክታር አሕመድ ቀረበ

3. ወ/ሮ ዙሪያሽ ወ/አረጋይ ቀረበች

4. አተረፈ ማሞ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መኪያ አወል ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በሰበር ችሎቱ ሊመረመር በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ የይርጋ መቃወሚያን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ጉዳዩ ያለአግባብ የተያዘው ቤት ይለቀቅልኝ በማለት ተጠሪ ባቀረበችው ክስ መነሻነት የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ይለቀቅልኝ የምትለው ቤት አመልካቾች ይዘውት የሚገኝ ሲሆን፣በተጠሪ ክርክር እንደተገለጸው ባለንብረት የሆኑት ወ/ሮ አፀደ ገ/የሱስ የተባሉት ሴት ናቸው፡፡ ወ/ሮ አፀደ ገ/የሱስ ቤቱን አቶ ማንደፍሮ ቸርነት እና ወ/ሮ እልፍነሽ ቸርነት ለተባሉት ሰዎች በስጦታ ውል እንዳስተላለፉት፣በኋላም ወ/ሮ እልፍነሽ ቸርነት ድርሻቸውን በፈቃዳቸው ለአቶ ማንደፍሮ ቸርነት እንደተው፣አቶ ማንደፍሮ ቸርነት ደግሞ የተጠሪ አውራሽ እንደሆኑ በተጠሪ ክስ ተገልጾአል፡፡ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስ በየበኩላቸው ከአቶ ማንደፍሮ ቸርነት ጋር ባደረጉት የሺያጭ ውል ቤቱን መግዛታቸውን፣ በገዙት መጠን ቤቱን ይዘው ከ11 እና ከ13 ዓመት በላይ ሲጠቀሙ መቆየታቸውን፣ወ/ሮ አፀደ ገ/የሱስ ለአቶ ማንደፍሮ ቸርነት እና ለወ/ሮ እልፍነሽ ቸርነት አደረጉት የተባለው የስጦታ ውል በሕጉ አግባብ ፍፃሜ አላገኘም፣በዚህ አይነትም ከ21 ዓመት በላይ ቆይቶአል፣በመሆኑም ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚሉትን ነጥቦች በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ክርክሩን የመረመረ ሲሆን፣በመጨረሻም አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ በማድረግ ቤቱን ለተጠሪ እንዲለቁ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣በአመልካቾች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጨረሻም ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ በዚህ ደረጃም ክርክር የተሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ ይልቀቁ በማለት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካቾች ሰኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ከግራ ቀኝ ወገኖች የቀረበውን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ሰበር ችሎት የሚመረመረው ጭብጥ አመልካቾች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ተደርጐ ቤቱን ይልቀቁ የተባለው በአግባቡ ነው ወይ? የሚለው ጭብጥ ነው፡፡ አመልካቾች በተለይ ከ1 እስከ 3 ያሉት ቤቱን የያዙት ከአቶ ማንደፍሮ ቸርነት ጋር የሽያጭ ውል አድርገው በመግዛት እና የሺያጭ ዋጋውንም በመክፈል እንደሆነ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ቢሆን የሽያጭ ውል አልተደረገም አላለም፡፡ የሺያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 የተመለከቱትን መስፈርቶች አያሟላም የሚል ምክንያት በመስጠት ነው ውልን በማስመልከት አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ያደረገው 4ኛ አመልካችም ቦታውን በቃል በተደረገው ስጦታ ተላልፎልኝ ቤቱን በራሴ ወጪ ሰርቻለሁ በማለት ቢከራከርም፤ስጦታው በጽሑፍ አልተደረገም በሚል ክርክሩ ተቀባይነት ሳያገኝ እንደቀረ ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቤቱ በአቶ ማንደፍሮ ቸርነት ስም አልተላለፈም (የስጦታ ውሉ ተፈፃሚ አልሆነም) የሚል ክርክር በአመልካቾች መነሳቱንና ተጠሪ ይህን በግልጽ አለማስተባበልዋን ተገንዝበናል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካቾች ቤቱን የያዙት ተጠሪ አውራሽ ነው የምትለው ሰው (አቶ ማንደፍሮ ቸርነት) በሕይወት በነበረበት ጊዜ ሆኖ ተጠሪ ክስ የመሰረተችው አመልካቾች ቤቱን ከያዙ ከ11 እና 13 ዓመታት በኋላ ነው፡፡ የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበትም አመልካቾች ቤቱን ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ አገኘሁ ከምትልበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ተጠሪ የወራሽነት ማረጋገጫ ያወጣችበትን ወይም አቶ ማንደፍሮ ቸርነት የሞቱበትን ቀን መነሻ በማድረግ በይርጋ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ መወሰኑ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካቾችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ በሕጉ አተረጓጐም ረገድ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲለቁ በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.31107 ሐምሌ 11 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይህን ውሳኔ በማጽናት በመ/ቁ. 43519 ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47889

ጥቅምት 04 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ሰላማዊት አስራት (አምስት ሰዎች) ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መሰረት ዘውዴ ከጠበቃ መስፍን እሸቱ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ጋብቻ በሞት መፍረስን ተከትሎ በሚች ወራሾችና በሕይወት በቀረው ተጋቢ መካከል የተነሣውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት አመልካች የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች ሲሆን በአቤቱታቸውም የአሁኗ ተጠሪ ባለቤት የነበሩት ማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን፣ ገለፀው የሚቹ ውርስ እንዲጣራላቸው የውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ተጠሪን በመልስ ሰጪነት በመጥራት የውርስ አጣሪው እንዲሾም በማድረግ ውርስ አጣሪው የውርስ ሐብቱን በማጣራት ሪፖርቱን እንዲያቀርብለት አድርጐ ውርስ አጣሪው ሪፖርቱን ሲያቀርብለት ግራ ቀኙ አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡ ከዚህም በሁዋላ በአዲስ አበባ ከተማ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/03 ክልል ውስጥ ይገኛል የተባለውና ቁጥሩ 1539 የሆነ ቤት ሚች ማስተር ቴክኒሽያን አስራት መኮንን በግላቸው የነበራቸው ቤት በመሆኑ እና በቤተሰብ ሕጉም የጋብቻ ውል ሲደረግ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ መፃረር እንደሌለበት በመግለጽ ቤቱ የሚች የግል ቤት ነው በማለት ተጠሪ ቤቱ በጋብቻ ውል የጋራ ተደርጓል በማለት ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ አድርጐ ወስኗል፡፡ ከዚህ በሁዋላም የአሁኗ ተጠሪ ቤቱ የሚች የግል ነው ተብሎ በተወሰነው የውሳኔ ክፍል ቅር በመሰኘት ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲያቀርቡ አመልካቾች በበኩላቸው በቤቱ ላይ ከተጠሪ በፊት ከሚች ማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን ጋር ጋብቻ መስርተው የነበሩት የአመልካቾች እናት ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ነው ሲሉ ያቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት መታለፉ ያላግባብ መሆኑን ገልጸው የመስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ አከራካሪው ቤት ላይ የአመልካቾች እናት ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ድርሻ እንደሌላቸው በማረጋገጥ ቤቱ የሚች ማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን የጋራ ንብረት እንዲሆን በጋብቻ ውል ስምምነት የተደረገበት በመሆኑ ቤቱ የጋራ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር ወስኗል፡፡ ከዚህ በሁዋላም አመልካቾች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አከራካሪው ቤት ግማሹ የአመልካቾች እናት ከሟች አስራት መኮንን ጋር በነበሩበት ጊዜ የተፈራ ሁኖ እያለና ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረትን በጋብቻ ውል የጋራ ንብረት ለማድረግ የማይቻል ሁኖ እያለ ቤቱን በጋብቻ ውል የጋራ አድርገውታል ተብሎ ግማሹን ተጠሪ እንዲወስዱ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸውም ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ተጠሪ ቀርበው በጠበቃቸው አማካኝነት የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ የጋብቻ ውሉንና ሕጋዊ ውጤቱን መሰረት ያደረገ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካቾች አውራሽ ማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት የአመልካቾችን እናት ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻን አግብተው ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ መሆኑን፣ከፍቺው በሁዋላም የንብረት ክፍፍል ተደርጐ አሁን እያከራከረ ያለው ቤት ለማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን እንዲሆን በወቅቱ በተሰየመው የቤተዘመድ ጉባኤ ተወስኖ ይህ ውሳኔ ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቁን፣ከዚህም በኋላ ሟች አቶ አስራት መኮንን ከተጠሪ ጋር ጋብቻ መስርተው ሐምሌ 27 ቀን 1972 ዓ.ም ባደረጉት የጋብቻ ውል አሁን እያከራከረ ያለውን ቤት የጋራ ማድረጋቸውን ነው፡፡ አመልካቾች የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ነው የሚሉት ሁለት ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አንደኛው ቤቱ ላይ የእናታቸው ግማሽ ድርሻ አለበት የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጋብቻ ውል የግል ንብረትን የጋራ ንብረት ለማድረግ አይቻልም በሚል ነው፡፡ እኛም እነዚህን ቅሬታዎች መሰረት በማድረግ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

የአመልካቾች እናት ወ/ሮ ፈትለወርቅ መነገሻ ከሟች አባታቸው ጋር የነበራቸውን ጋብቻ በፍቺ ካፈረሱ በሁዋላ ውጤቱን በተመለከተ ደግሞ በቤተዘመድ ጉባኤ ታይቶ ይኼው አካል የሰጠው የንብረት ክፍፍል ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ጸድቋል፡፡ በፍርድ ቤት በፀደቀው የቤተዘመድ ጉባኤ ውሳኔ ደግሞ አሁን እያከራከረ ያለው ቤት ለሟች ማስተር ቴክኒሺያን አስራት መኮንን ተሰጥቷል፡፡ ይህ ውሳኔ በየትኛውም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አልተለወጠም፡፡ እንዲህ ከሆነ ቤቱ የሟች አስራት መኮንን የግል ንብረት መሆኑ ከተረጋገጠ በሁዋላ ሟች አስራት መኮንን ከተጠሪ ጋር ጋብቻ የፈፀሙ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ቤቱ የሟች አስራት መኮንን የግል ንብረት ነው ተብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መወሰኑ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን የግራ ቀኙን ክርክሮችንና ማስረጃዎችን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍ ሁኖ ስላላገኘን በዚህ ረገድ አመልካቾች ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ነው።

ሌላው በዚህ ችሎት አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ሚች አስራት መኮንን ከተጠሪ ጋር ሐምሌ 27 ቀን 1972 ዓ.ም የተደረገው የጋብቻ ውል አስገዳጅነት ያለውን በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 57 ስር የተደነገገውን የሚፃረር ነው የሚል ነው።

በመሰረቱ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 57 ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸውን ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው የሚያገኟቸውን ንብረቶች በጋብቻ ዘመንም የግል ሁነው ይቀራሉ በማለት በአስገዳጅነት ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት ንብረቶቹ በጋብቻ ውል የጋራ እንዲሆኑ ስምምነት ከሌለ ብቻ ነው። የጋብቻ ውል ሲደረግ ደግሞ ሊከተለው የሚገባው ፎርማሊቲ ስለመኖሩ የተጠቀሰው ሕግ በአንቀጽ 44 ስር ደንግጓል። ይኸው ሕግ በአንቀጽ 42 ንኡስ ቁጥር አንድና ሁለት ስር ተጋቢዎች ንብረታቸውንና ግላዊ ግንኙነታቸውን በተመለከተ ለመወሰን እንደሚችሉ ይገልፃል። ሕጉ የጋብቻ ውል አስገዳጅ የሆኑ የሕጉ ድንጋጌዎችን መፃረር እንደሌለበትም በአንቀጽ 42/3/ ስር በግልጽ አስቀምጧል። የሕጉ አንቀጽ 47 እና 73 ድንጋጌዎች ሲታዩም የጋብቻ ውል የሚሻሻልበትን ሥርአት ያስገነዝባሉ። ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው የጋብቻ ውጤት በጋብቻ ውል ሊቋቋም፣ሊቀር ወይም ሊሻሻል የሚችል መሆኑን ነው። ሌላው ከድንጋጌዎች መረዳት የምንችለው ተጋቢዎች የጋብቻቸውን ውጤት በጋብቻ ውል ከወሰኑ እና ውሉም አስገዳጅ ድንጋጌዎችን የማይቃረን መሆኑ ከተረጋገጠ የተጋቢዎች የንብረትም ሆነ ግል ግንኙነት ሊገዛ የሚባው በጋብቻ ውሉ መሆን ያለበት መሆኑን ነው። ሕጉ የባልና ሚስት የንብረትና የግል ግንኙነት ክርክር ሲቀርብ ተፈፃሚ የሚሆነው የጋበቻ ውሉ ያልሸፈነው ክፍተት ካለ ብቻ ነው። በመሆኑም "የጋብቻ ውል አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎችን እስካልተቃረነ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል..." የሚለው ሐረግ አስገዳጅነት ያላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ማለት የትኞቹ ናቸው? የሚለውን መመልከትን የግድ የሚል ነው። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የጋብቻ ውል ሲመሰረት ሊከተላቸው የሚገባቸው ፎርማሊቲዎች እና በጋብቻ ውሉ ስምምነት የሚደረግባቸው ግንኙነቶች ምን እንደሆነ በሕጉ ተመልክተዋል። የጋብቻ ውሉ ፎርማሊቲው ሲከተል ሊያሳካ የታሰበው ግብም ስምምነቱ የተጋቢዎችን ነፃ ፈቃድ አግኝቶ የመዋዋል ነፃነታቸው ተከብሮ የተገኘ መሆኑን ማረጋገጥ መሆኑ ይታመናል። እንዲህ ከሆነ ሕጉ ከጋብቻ በፊት የተገኘ ንብረትን የግል ንብረት ነው በማለት ጥበቃ የሚያደርገው በሕጉ አግባብ በተደረገ የጋብቻ ውል መሰረት የጋራ ያልሆነውን ንብረት ብቻ ነው። ስለሆነም አስገዳጅ የሆኑትን የሕግ ድንጋጌዎችን የጋብቻ ውሉ ሊፃረር አይገባም የሚለው የሕጉ አነጋገር ከጋብቻ ውል አደራረግ ጋር የተያዙትን የፎርማሊቲ ጉዳዮችንና ከተጋቢው ግላዊ ነፃነት ጋር የተገናኙት ጉዳዮች እንጂ ከንብረት ጋር የተያያዙትን አይደለም። ከጋብቻ በፊት የተፈራን ንብረት በሕጉ አግባብ በተደረገ የጋብቻ ውል የጋራ ማድረግ አስገዳጅ የሆኑ የቤትሰብ ሕግ ድንጋጌዎችን መፃረር ነው ሊባል የሚችል አይደለም። አንድ ንብረት ከጋብቻ በፊት የተገኘ መሆኑ ንብረቱ የተጋቢው የግል ንብረት ሁኖ እንዲቀር ሕጉ ያስቀመጠው ሁኔታ ጠቅላላ ደንብ ሲሆን ይህ ጠቅላላ ደንብ ተፈፃሚ የሚሆነው ንብረቱን የጋራ የሚያደርግና ልዩ ደንብ የሆነው የጋብቻ ውል በሌለበት ሁኔታ ብቻ ነው። በመሆኑም ሕጋዊ የጋብቻ ውል ልዩ ደንብ (exception) ሲሆን በአንቀጽ 57 ስር የተመለከተው ሁኔታ ደግሞ መርህ ሊባል የሚችል ነው። በሕግ አተረጓጎም ደንብ ደግሞ ተፈፃሚነት ያለው ልዩ ሁኔታ የሆነው ሕግ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለልም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አከራካሪው ቤት በጋብቻ ውል የአመልካቾች አባትና ተጠሪ የጋራ ሀኗል በሚል ምክንያት የቤቱ ግማሽ ድርሻ የተጠሪ ይሆናል በማለት መወሰኑ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 42፣44 እና 57 ድንጋጌዎችን ያገናዘበ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 73357 ግንቦት 05 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 46813 ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ዶ/ር ደስታ አቡኑ በለጡ

ተጠሪ፡- ሲስተር አስቴር ካሣ መልደየስ - ጠበቃ አየለ ማሞ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሣውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ በአዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ነው፡፡ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ፍ/ቤቶቹ ከሰጡአቸው ውሣኔዎች ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ግራ ቀኝ ወገኖች በጋብቻቸው ወቅት ያፈሩዋቸው ናቸው ተብለው ለክፍፍል ከቀረቡት ንብረቶች መካከል ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆኑት በሁለት የተለያዩ ከተሞች የሚገኙት የመኖሪያ ቤቶች ናቸው፡፡ ክርክሩን በመጨረሻ ደረጃ የሰማው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በወላይታ ሶዶ ያለው ቤት ለአመልካች፤ በሃዋሣ ከተማ ያለው ቤት ደግሞ ለተጠሪ እንዲሆን ወስኖአል፡፡ የሃዋሣው ቤት በወላይታ ሶዶ ካለው ቤት ብልጫ ስላለው ተጠሪ ልዩነቱን በገንዘብ ለአመልካች እንድታካክስም በተጨማሪ አዞአል፡፡ አመልካች በዚህ መልክ የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ነው የአሁኑን የሰበር አቤቱታ ያቀረበው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገውም ግራ ቀኝ ወገኖቹ ባልተስማሙበት ሁኔታ የተሰጠው የንብረቶቹ ክፍፍል ውሣኔን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረት ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በጋብቻ ተሳስረው የቆዩ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በፍቺ ሲያፈርሱ በንብረት ረገድ የነበራቸው ግንኙነትም እልባት ማግኘት አለበት፡፡ ይህ የሚሆነው ንብረቱን በመከፋፈል ሲሆን፣ ክፍፍሉ የሚከናወነው አግባብ ባላቸው የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በፌዴራል መንግሥቱ የወጣውም ሆነ የአሁኑ ክርክር በተነሳበት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት የወጣው የቤተሰብ ሕግ በንብረቱ ክፍፍል ረገድ የሚከተሉት መርህ የእኩልነት መርህ ነው፡፡ የእኩልነት መርህ ድንጋጌዎቹ መሠረትም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34/1/ የተቀመጠው ድንጋጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ሌላው በንብረቱ ክፍፍል ሂደት ሊታይ የሚገባው ጉዳይ የባለጉዳዮቹ ስምምነት መኖር እንደሆነም በቤተሰብ ሕጎቹ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ቤቶቹን በሚመለከት በተደረገው የክፍፍል ሂደት ወይም ሁኔታ አመልካች አልተስማማም፡፡ ላለመስማማቱ የሰጠው ምክንያትም የክፍፍል ሂደቱ የእኔን የእኩልነት መብት ያስጠበቀ አይደለም የሚል እንደሆነ ከክርክሩ ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ ደግሞ እኔ የምኖረው በሃዋሣ ከተማ በመሆኑ እና አመልካች የሚኖረው ከሃዋሣ ወጪ ስለሆነ የሃዋሳው ቤት ለኔ ቢሰጥ የበለጠ ተጠቃሚ እሆናለሁ በማለት ነው የምትከራከረው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ቤቱ ለእስዋ እንዲሰጥ የወሰነውም ይህንኑ የበለጠ ተቃሚነት የሚለውን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡

እንደምናየው አመልካችም ሆነ ተጠሪ በሁለቱም ቤቶች ላይ ያላቸው መብት የእኩል ነው፡፡ ክፍፍሉ መደረግ ያለበት ይህን መሠረት በማድረግ በመሆኑ ሁለቱም ከሁለቱ ቤቶች እኩል ድርሻ ሊያገኙ ይገባል፡፡ ቤቶቹ በተለያዩ ከተሞች /አካባቢዎች/ እንደመገኘታቸው መጠን የሚኖራቸው ዋጋም እንደዚሁ እንደሚለያይ መገመቱ አይከብድም፡፡ የቤቶቹ አሠራር እና ያሉበት ልዩ አካባቢም /ቦታም/ በሚያወጡት ዋጋ ላይ የራሱ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታወቃል፡፡ በእርግጥ እነዚህ ልዩነቶች ቢኖሩም ግራ ቀኝ ወገኖች ስምምነት ላይ ከደረሱ ያለምንም ችግር በስምምነቱ መሠረት ሊከፋፈሉ ይችላሉ፡፡ ስምምነት ከሌለ ግን በሕጉ የተቀመጠውን የእኩልነት መርህ እና አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች የተቀመጠውን የክፍፍል ሥርዓት መሠረት በማድረግ ክፍፍሉ እንዲፈጸም መወሰን የግድ ይሆናል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ለክፍፍሉ አፈፃፀም መሠረት ያደረገው የበለጠ በንብረቱ የመጠቀም ሁኔታ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ እንደ ትክክለኛ የክፍፍል ሥርዓት ተቆጥሮ ተቀባይነት የሚያገኝ አይደለም፡፡ በበኩላችን ትክክለኛ የክፍፍል ሥርዓት ሆኖ ያገኘነው በቅድሚያ ሁለቱም ቤቶች በገበያ ዋጋ መሠረት የሚያወጡት ዋጋ እንዲታወቅ ማድረግ፤ በመቀጠልም ግራ ቀኝ ወገኖች የገበያ ዋጋን መሠረት በማድረግ በዓይነት ለመከፋፈል ስምምነት ላይ ከደረሱ የበለጠ ዋጋ ያለውን ቤት የሚወስደው ወገን ገበያ ባስገኘው ዋጋ መሠረት ሌላኛውን ወገን ልዩነቱን በገንዘብ እንዲያካክስ፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ በሕጉ በተቀመጠው የመጨረሻው አማራጭ ቤቶቹ ተሸጠው ገንዘቡን እንዲከፋፈሉ ማድረግ ነው፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ክፍፍሉን በዚህ መሠረት እንዲከናወን ባለመወሰኑ ውሣኔው በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሃዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በፍ/ብ/መ/ቁ. 14336 ሚያዝያ 8 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ፣ የአዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በፍ/ብ/መ/ቁ. 6945 ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ/ቁ 28643 ነሐሴ 7 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. በሃዋሣ ከተማ እና በወላይታ ሶዶ ከተማ ያሉት ቤቶች በቅድሚያ በገበያ ዋጋ መሠረት ተገምተው ዋጋቸው እንዲታወቅ እንዲደረግ፤ በመቀጠልም ግራ ቀኝ ወገኖች የሚስማሙ ቢሆን የቀረበውን የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ቤቶቹን በዓይነት እንዲካፈሉ፤ ከፍተኛ ዋጋ ያለውን የወሰደው ወገንም ሌላኛውን ወገን ልዩነቱን በገንዘብ እንዲያካክስ፤ በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት ተስማምተው መክፋፈል ካልቻሉ ግን ሁለቱም ቤቶች ተሸጠው ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስነናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 4 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ቀለሚ ወርቅነህ ሺበሺ

ተጠሪ፡- ሻምበል ጌታሁን ገብሬ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የሚች እህትዋ ወራሽ መሆንዋን መሠረት በማድረግ ያቀረበችው የውርስ ንብረት የመካፈል ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ውድቅ በመደረጉ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ከተጠሪ የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል እና በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1000/1/ የተቀመጠውን የሦስት ዓመት የጊዜ ወሰን መሠረት በማድረግ ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ብታቀርብም፤ ውሣኔው ጉድለት የለበትም ተብሎ ይግባኙ ተሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 21 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ አቤቱታ ባቀረበችበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱን የሚያርም ውሣኔ ይሰጥላት ዘንድ ጠይቃለች፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የተባለው በአግባቡ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን በማስመልከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ክስ የመሠረተችው የወራሽነት መብትን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ለክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት ባለሃብት ነበረች የተባለችው የአመልካች እህት የሞተችው መጋቢት 11 ቀን 88 ዓ.ም ሆኖ አመልካች የውርስ ንብረቱ እንዲሰጣት ክስ የመሠረተችው ደግሞ ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ ያቀረበው ከዚህ በመነሣት ሲሆን፣ የሥር ፍ/ቤቶችም ተመሣሣይ ምክንያት በመስጠት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ወስነዋል፡፡ አመልካች ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ትክክል አይደለም በሚል ክርክርዋን በመግፋት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች፡፡ በዚህ ረገድ የሰጠችው ምክንያት ሚች እህቴ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተወችልኝን ኑዛዜ በፍ/ቤት ሳላስፀድቅ በውርስ ንብረቱ ላይ ጥያቄ ማንሣት አልቻልኩም ነበር። ስለዚህም ኑዛዜው እንዲፀድቅልኝ ለፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቤ ስከራከር ከቆየሁ በኋላ ሲፀድቅልኝ በንብረቱ ላይ ክስ መሥርቻለሁ የሚል ነው። ተጠሪ ኑዛዜው መጽደቅ የለበትም በማለት ሲከራከራት እንደቆየም በአቤቱታዋ የገለፀች ሲሆን፣ ተጠሪም ይህ እውነት አይደለም የሚል መልስ ወይም ክርክር አላቀረበም።

ከቀረበው ክርክር እንደምንገነዘበው በእርግጥ አመልካች በንብረቱ ላይ ክስ የመሠረተችው ሚች ከሞተች ከአሥራ ሦስት /13/ ዓመት በላይ ቆይታ ነው። ነገሩ ከዚህ ሁኔታ ብቻ በመነሳት ሲታይ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ለማለት ይቻላል። ኑዛዜውን በፍ/ቤት ሣላስፀድቅ በውርስ ንብረቱ ላይ ክስ መመሥረት አልችልም ነበር የሚለው ክርክርም እንዳለ በቀጥታ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም። ኑዛዜው እስካለ ድረስ ወይም አመልካች የሚች እህት ነኝ እስካለች ድረስ በንብረቱ ላይ በቀጥታ መክሰስ እየቻለች ኑዛዜ በፍ/ቤት አስፀድቃለሁ በማለት ጊዜዋን ካሣለፈች ይርጋን በተመለከተ ለቀረበበት መቃወሚያ መከራከሪያ አድርጋ ልታቀርበው አትችልም። ኑዛዜው ዋጋ የሚኖረው በፍ/ቤት ስለፀደቀ ሣይሆን በሕግ የተቀመጡትን የኑዛዜ መሠረቶች ወይም መስፈርቶች ሲያሟላ ነው። ይህ የሰበር ችሎትም ከዚህ በመነሣት ኑዛዜ ለፍ/ቤት ቀርቦ መጽደቅ በኑዛዜው ሕጋዊነት ላይ የሚጨምረው ነገር የለም በማለት ቀደም ሲል በሰጣቸው ውሣኔዎች ለሕጉ ትርጉም ሰጥቶአል። በመሆኑም ኑዛዜውን በፍ/ቤት ሳላስፀድቅ በውርስ ንብረቱ ላይ ክስ መመሥረት አልችልም ነበር የሚለው የአመልካች ክርክር በሕግ ረገድ ተቀባይነት ያለው አይደለም።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተነሣው ክርክር ከሌላም አቅጣጫ መታየት እንደለበት ከክርክሩ አመጣጥ እና ልዩ ባህርይ ለመገንዘብ ችለናል።

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው የኑዛዜውን መጽደቅ በተመለከተ በቀረበው አቤቱታ ተጠሪም ተካፋይ እንደነበረ የራሱ ምክንያት በመስጠት ኑዛዜው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ሲከራከር እንደቆየ ተገንዝበናል። የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 03103 ግንቦት 23 ቀን 98 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ እንደተመለከተው አመልካች ኑዛዜ ይጽደቅልኝ የሚለውን አቤቱታ ለፍ/ቤቱ ያቀረበችው መጋቢት 17 ቀን 88 ዓ.ም ነው። ይህም ማለት ሚች ከሞተች /መጋቢት 11 ቀን 88 ዓ.ም/ በስድስት /6/ ቀን ውስጥ አቤቱታው ቀርቦአል ማለት ነው። ተጠሪ መልስ የሰጠው ሚያዝያ 3 ቀን 89 ዓ.ም ሲሆን፣ የኑዛዜው መደረግ አጠራጣሪ ነው፣ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ ከሟች ፊርማ ጋር አይመሳሰልም፣ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የኔም የጋራ ሐብት ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክሮአል። ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክርክሩን ሲያይ ቆይቶ ውሣኔ የሰጠው ግንቦት 23 ቀን 98 ዓ.ም እንደሆነ ተመልክተናል። እነዚህን ሁኔታዎች ደምረን ስንመለከት አመልካች በጊዜው በንብረቱ ላይ ክስ ሣትመሠርት የቀረችው ተጠሪም ባደረገው አስተዋጽኦ እና ፍ/ቤቱ ባጭር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ባለመስጠቱ ነው ለማለት ችለናል። አመልካች እና ተጠሪ ሲከራከሩ የቆዩትም አመልካች በኑዛዜው መሠረት ንብረት ልትወርስ የምትችልበት አግባብ አለ ወይስ የለም ከሚለው ጋር በተያያዘ ሁኔታ እንደሆነ መመልከቱ የሚከብድ አይደለም። ከዚህ የተነሣም ይርጋው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1851/ለ/ በተመለከተው መሠረት ተቋርጦአል ለማለት የሚቻል ነው። ሲጠቃለል አመልካች ያቀረበችው ክስ በይርጋ ተቋርጦአል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ሕጉን በአግባቡ በማየት የተሰጠ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 26317 ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 0498 ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ//ሥ/ሥ/ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ አለመሆኑን በመገንዘብ ግራ ቀኝ ወገኖች በጉዳዩ ስረ- ነገር ላይ የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት ይመለስለት፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፣ 1. አቶ ጊላጋብር ገብረህይወት
2. ወ/ሮ ለተሀዋርያት ገብረህይወት — ጠበቃ ስሜነህ ተክሉ ቀረቡ
3. ወ/ሮ ምዕላል ዓለም

ተጠሪዎች፣ 1. ወ/ሮ አረጋሽ አብርሃ — አልቀረቡም
2. አቶ በርሀ አርጋው

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ከፍተኛ 20 ቀበሌ 29 የቤት ቁጥር 139 የሆነ መኖሪያ ቤትና የሰሌዳ ቁጥር 3-13285 አ.አ የሆነ ቦቴ መኪና በህይወት እስካሉ ድረስ አባታችን አቶ ገብረህይወት ሊያዙበት እሳቸው ሲሞቱ ወ/ሮ ብሬ አስከህይወታቸው ተጠቅመው ንብረቱ ለእኛ እንዲተላለፍ ስምምነት አድርገዋል፡፡ የሚች አቶ ገብረህይወት ባለቤት ወ/ሮ ንግስቲ ስምምነቱ የተደረገው በእኔ የጋራ ንብረት ነው በማለት ክስ አቅርበው ወ/ሮ ብሬና እኛ ግማሹን የቤትና የመኪና ግምት እንድንከፍል ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ ወ/ሮ ብሬ በቤቱ ሲገለገሉ ቆይተው ጥቅምት 19 ቀን 2001 ዓ.ም በሞት ተለይተዋል፡፡ በቤቱ መብት ያለን እኛ ስለሆን በሥር ተከሣሽ የነበሩት አንደኛ ተጠሪ አላግባብ የያዙ ስለሆነ ቤቱን ለቅቀው እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት አመልክተዋል፡፡

አንደኛ ተጠሪ በሥር በተከሣሽነት ቀርበው በቤቱ ውስጥ የምኖረው ሚች ወ/ሮ ብሬ እየረዱኝ በጥገኝነት ነው ስለዚህ በቤቱ ላይ መብት የሌለኝና በሚች ወራሾች ፈቃድ የምኖር በመሆኑ ክሱ ተዘግቶ በነፃ እድሰናበት በማለት የተከራከሩ ሲሆን ሁለተኛው ተጠሪ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ በመሆን የሚች ወ/ሮ ብሬ ወራሽ መሆኑን ገልፆ ወ/ሮ ብሬና ሚች አቶ ገብረህይወት ያደረጉት ውል በህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፊት የሚፀና ባለመሆኑና አመልካቾች /የሥር ከሣሾች/ የወ/ሮ ብሬ ወራሾች ባለመሆናቸው ውሉም በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ቤቱ የወ/ሮ ብሬ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ውሉ መኖሩ ባልተካደበት ሁኔታ የውሉ ፎርም መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36887 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ ጣልቃ ገቡ በወ/ሮ ብሬና በአቶ ገብረሀይወት መካከል የተደረገው ውል ፎርሙን አላሟላም በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ አልተቀበልኩትም ቤቱ የሚች አቶ ገብረሀይወት መሆኑ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 በሁለቱ በወ/ሮ ብሬና በአቶ ገብረሀይወት መካከል የተደረገው ውል ስለሚያስረዳ ተከሣሹና ጣልቃ ገብ /የአሁን ተጠሪዎች/ ቤቱን ከሣሾች /አመልካቾች/ ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ውሉ የስጦታ ውል ነው የስጦታ ውል መስፈርት የማያሟላ በመሆኑ ከሣሾች ቤቱ ከወ/ሮ ብሬ ጋር አባታችን ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲኖሩ የተገዛ የጋራ ንብረት ነው በማለት ከሚጠይቁ በስተቀር የስጦታ ውል መሠረት በማድረግ ቤቱን እንረከብ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 6 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የይግባኝ ማመልከቻ በመጀመሪያ በሠራተኝነት የገቡትና ኃላም ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩት ወ/ሮ ብሬ መሲሳና አባታችን አቶ ገብረሀይወት ደበሣይ ወ/ሮ ብሬ እኛን ማሣደጋቸውንና ልጅ የሌላቸው መሆኑን ምክንያት በማድረግ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ውል ተዋውለዋል፡፡ በውላቸውም በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 20 ቀበሌ 29 ቁጥሩ 139 የሆነው መኖሪያ ቤትና ቦቴ መኪና ገዝተው ስሙ በሚች ብሬ መሲሳ ሆኖ ንብረቱን በሙሉ ባለሀብትነት የሚያዙበት አባታችን አቶ ገ/ሕይወት ደበሣይ እንደሆኑ አባታችን ሲሞቱ ወ/ሮ ብሬ በንብረቱ ህይወታቸው እስካለ ተጠቅመው በሚች አቶ ገብረሀይወት ልጆች ንብረቱን ሊያስተላልፉ ተስማምተው የውል ግዴታ ገብተዋል ይኸ ውል ከተፈረመ ከሶስት ዓመት በኃላ ሚች አቶ ገብረሀይወት በሞት የተለዩ ሲሆን ወ/ሮ ብሬ ከአስራ አምስት ዓመት በኃላ በሞት ተለይተዋል፡፡ ውሉ ስለንብረት ባለቤትነትና ንብረትን ስለመጠቀም በሚች አቶ ገብረሀይወት ደበሣይና በሚች ወ/ሮ ብሬ መሲሳ የተደረገ ሆኖ እያለ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሉ ስጦታ ውል ነው ስጦታ ውሉ የህጉን ፎርም ባሟላ መልኩ የተደረገ አይደለም በማለት ግልፅ የሆነውን የውል ስምምነት ከተዋዋይ ወገኖቹ ፈቃድና ፍላጎት የራቀ ትርጉም በመስጠት ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ቤቱና መኪናው የተገዙት አቶ ገብረሀይወት ጋር ሲኖር በተፈራ የጋራ ሀብት ነው ብለው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01302 በሚች ብሬ ሞሲሳና በእኛ ላይ ወ/ሮ ንግስቲ ገ/እግዚ ክስ አቅርበውብን መኪናውና ቤቱ የተገዙት በሚች ገብረሀይወትና በወ/ሮ ንግስቲ የጋራ ንብረት ነው በማለት ውሣኔ የተሰጠ በመሆኑ ሚች ብሬ ሞሲሳ ከሚች አቶ ገብረሕይወት ጋር ያደረጉት ውል ህጋዊ ነው ሊፀና ይገባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት በመዝገብ ቁጥር 01302 ከወ/ሮ ንግስቲ ጋር የተከራከሩበት ሆኖ እያለ የሚች ወ/ሮ ብሬ ወራሽ ነን የሚሉት ሁለተኛው ተጠሪ ውሉ ፈራሽ ነው ብሎ ያቀረበው ክርክር አውራሽ አምኖበት ለፍርድ ቤት ያረጋገጠውን ወራሹ መካዱ ተገቢ ባለመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይህንን ክርክር በመቀበል ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ንብረቱ የተገዛው በሚች አቶ ገብረህይወት ገንዘብ ነው ተብሎ በውሉ መጠቀሱ ንብረቱን የሚች አቶ ገብረህይወት ንብረት አያደርገውም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የሚረጋገጠው በአስተዳደሩ ክፍል በሚሰጥ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1195 ተደንግጓል፡፡ አመልካቾች ቤቱ የሚች ወ/ሮ ብሬ አይደለም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ይህን የህግ ግምት የማያፈርስ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 የተመለከተ ምክንያት ባለመሆኑ አቤቱታቸው የህግ መሠረት የለውም፡፡

አመልካቾች በአንድ በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሉ የስጦታ ውል ነው የህጉን ፎርም አላሟላም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት እያሉ በሌላ በኩል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01302 አቶ ገብረህይወት ለሚች ወ/ሮ ብሬ ያደረጉት የስጦታ ውል የወ/ሮ ንግስቲ የጋራ ንብረትና ድርሻ ያለበት ስለሆነ ግማሹን እንዲከፍሉ ብሎ የሰጠውን ውሣኔ በመከራከሪያነት ማንሣታቸው እርስ በርሱ የሚቃረን መከራከሪያ ነው በእርግጥ ሚች ወ/ሮ ብሬ የወ/ሮ ንግስቲ ድርሻ ግማሹን እንዲከፍሉ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ ሰጥቷል ሆኖም ውሣኔው አልተፈፀመም በአጠቃላይ የአመልካቾች ክርክር የህግ መሠረት የሌለውና ዕርስ በርሱ የሚቃረን በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ሚች አቶ ገብረህይወት ደበሣይና ሚች ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ያደረጉት ውል የስጦታ ውል ማሟላት ያለበትን ፎርማሊቲ ያላሟላ ስለሆነ ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ቤት ለአመልካቾች የማስረከብ ግዴታ የለባቸውም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመመስረት ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ ሚች አቶ ገብረህይወት ደበሣይና በሚች ብሬ ሞሲሳ መካከል የነበረውን ግንኙነት መሠረታዊ ባህሪ እንደዚሁም ሚች አቶ ገብረህይወትና ሚች ወ/ሮ ብሬ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ያደረጉት ውል መሠረታዊ ይዘቱ እና በሕግ ረገድ የሚያስከትለውን ውጤት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ሚች አቶ ገብረህይወት ደበሣይና ሚች ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ለረዥም ጊዜ አብረው የኖሩ መሆናቸውንና ወ/ሮ ብሬ ሚች አቶ ገብረህይወት ደበሣይ ከሌሎች ሴቶች የወለዷቸውን ልጆች እንደ ወላጅ እናት ተንከባክበው ያሣደጉ መሆኑ በአመልካቾች የተገለፀና ተጠሪዎችም ያልካዱት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ለረጅም ጊዜ አብረው የኖሩት አቶ ገብረህይወትና ወ/ሮ ብሬ ባልና ሚስት የሚያሣዩአቸውን ሁኔታዎች የሚታዩባቸው የነበሩ መሆኑንና በመካከላቸውም የመተሣሠብ የመተማመን ሁኔታ የነበረ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ባልና ሚስት ከጋብቻቸው በፊት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም ጋብቻ በሚፈፅሙበት ወቅት በንብረት ረገድ ስለሚኖራቸው ግንኙነት የጋብቻ ውል የሚያደርጉበት ሁኔታ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 42 የተደነገገ ሲሆን በተመሳሳይ መንገድ ባልና ሚስት ነን እየተባባሉ ከጋብቻ ውጭ በግብረ*ሥጋ* ግንኙነት አብረው የሚኖሩ ሰዎች በመካከላቸው ያለውን የንብረት ግንኙነት የሚመለከት ውል ቢዋዋሉ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄ የሚያስነሳ ሲሆን የባልና የሚስት ሁኔታ እያሟዩ ከጋብቻ ውጭ በግብረ*ሥጋ* ግንኙነት አብረው የኖሩ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ስለግላዊ ግንኙነታቸውና በንብረት በኩል ስለሚኖራቸው ግንኙነት የመዋዋል ነፃነታቸውን በሚያሳጣና ውል እንዳይዋዋሉ የሚከለክል ግልፅ የህግ ድንጋጌ የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ህግ አውጭው የመዋዋል ነፃነታቸውንና የሚዋዋሉበትን *መሠረታዊ* ጉዳይ በህግ በግልፅ ክልከላ ካላደረገ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678 *መሠረታዊ* ሁኔታዎች በማሟላት እንደባልና ሚስት የሚኖሩት አንድ ወንድና አንዲት ሴት ከጋብቻ ውጭ በግብረ*ሥጋ* ግንኙነት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ስለሚኖራቸው የግል ግንኙነትና የንብረት ግንኙነት ውል የመዋዋል ነፃነት ያላቸው መሆኑንና ይህም በውል ህግ ድንጋጌዎች *መሠረት* የሚመራና ውጤት ያለው መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1676/1/ ውሎች አይነታቸውና ምክንያታቸው ማንኛውም ቢሆን በዚህ አንቀጽ ጠቅላላ ደንቦች ይመራሉ በማለት የደነገገውን ገዥ ድንጋጌ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ሟች አቶ ገብረህይወት ደበሣይና በሟች ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ *ታህሣሥ* 22 ቀን 1983 ዓ.ም ያደረጉት ውል እንደባልና ሚስት ከጋብቻ ውጭ በግብረ*ሥጋ* ግንኙነት ሲኖሩ በንብረት ረገድ የሚኖራቸውን ግንኙነት አንዳቸው በሞት ሲለዩ በተለይ አቶ ገብረህይወት በድንገት በሞት ሲለዩ በቀሪው እድሜ ወ/ሮ ብሬ በንብረቱ ላይ ስለሚኖራቸው መብት ውል አይደለም ሁለቱም ነፃ ሁነው ፈቃዳቸውን የሰጡበት የውል ሰነድ እንጅ፡፡ በዚህ በኩል ተጠሪዎችም በሆኑ ውሉ የፈቃድ ጉድለት ያለበት ነው በማለት ከሥር ጀምሮ ያቀረቡት ክርክር የሌለ መሆኑን በመዝገቡ ከተያያዙት የፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የውሉን ይዘት ስንመለከተው አምስት *መሠረታዊ* ነጥቦችን የያዘ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የመጀመሪያው ውሉ በአቶ ገብረህይወትና በወ/ሮ ብሬ መካከል ያለው ግንኙነት በምን መንገድ እንደተጀመረና ውሉን በሚዋዋሉበት ጊዜ በምን ሁኔታ ወይም ደረጃ እንደሚገኝ በስምምነታቸው የገለፁበት ነው፡፡ በውሉ ወ/ሮ ብሬ በመጀመሪያ በቤት ሠራተኝነት ተቀጥረው የገቡ ቢሆንም ከዚያ በኃላ ግንኙነታቸው ከጋብቻ ውጭ በግብረ*ሥጋ* ግንኙነታቸው እንደ ባልና ሚስት አብረው የኖሩ መሆኑን በግልፅ ያመለክታል፡፡

ሁለተኛው ወ/ሮ ብሬ አቶ ገብረህይወት ከሌሎች ሴቶች የወለዷቸውን ልጆች በእናትነት በመንከባከብና በማሳደጋቸው ከአቶ ገብረህይወት ጋር ለረዥም ጊዜ አብረው በመኖራቸው የሰሌዳ ቁጥር 3-13285 የሆነ ቦቴ መኪናና በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው ከፍተኛ 20 ቀበሌ 29 ቁጥሩ 139 የሆነው ቤት በወ/ሮ ብሬ ስም እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ ሶስተኛው ከላይ የተገለፁትና በወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ ስም የተመዘገቡት ንብረቶች የተገዙት ወ/ሮ ብሬና አቶ ገብረህይወት ሠርተው ባገኙት የጋራ ገቢ /የጋራ ሀብት/ ሣይሆን ሙሉ በሙሉ በአቶ ገብረህይወት የግል ገንዘብ የተገዙ መሆናቸውን በግልፅ የሚያብራራ ሲሆን አራተኛ ንብረቶቹ በወ/ሮ ብሬ ስም ያሉ ቢሆንም አቶ ገብረህይወት በህይወት እስካሉ ድረስ በንብረቶቹ ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ያላቸው መሆኑን በቤቱም ሆነ በመኪናው ገቢ የሚያዙበት አቶ ገብረህይወት መሆናቸውን በግልፅ የሚደነግግ መሆኑ ነው፡፡ አምስተኛው ወ/ሮ ብሬ ከአቶ ገብረህይወት በፊት በሞት ቢለዩ ንብረቱ ሙሉ በሙሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአቶ ገብረህይወት እንደሆነ የሚያረጋግጥና ድንገት አቶ ገብረህይወት ከወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ በፊት በሞት ቢለዩ በንብረቶቹ ላይ ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ በህይወት እስካሉ የመጠቀምና አላባ የመሰብሰብ መብት ያላቸው መሆኑን "..... ሞት በሰው ላይ ያለ የተፈጥሮ ግዴታ ስለሆነ ከእሳቸው በፊት ህይወቱ ቢያልፍ ንብረቱ የራሳቸው ገንዘብ ስለሆነ የመኪናውም ሆነ የቤቱ ባለመብት ናቸው ከእኔ ህይወት በፊት የእሳቸው ህይወት ቢያልፍ ህይወቱ እስካለ ድረስ በመኪናውና በቤቱ ተጠቃሚ እኔ ሆኜ ከህይወት በኃላ እኔ ላሣደግኳቸው የሁለተኛ ተስማሚ ልጆች 1ኛ ህይወት ገ/ሕይወት 2ኛ ጊላ ገብረህይወት 3ኛ ለተሃዋሪያት ገብረህይወት እንዲተላለፍ በፈቀዱት መሠረት ለእነዚሁ ልጆች ቤቱና መኪናው የሚተላለፈው ባለመብት የሚሆኑት ልጆች መሆናቸውን በፊርማየ አረጋግጣለሁ በማለት ወ/ሮ ብሬ የተስማሙና አቶ ገብረህይወትም ስምምነቱን የተቀበሉ መሆኑን የሚያረጋግጥ የውል ሰነድ ነው።

ይህ ውል ከተደረገ በኋላ አቶ ገብረህይወት በሞት ሲለዩ አመልካቾች የውሉን ድንጋጌ በመጣስ ወ/ሮ ብሬ ንብረት ያካፍሉን የሚል ክስ ያላቀረቡ መሆኑን በግራቀኙ በኩል ከተደረገው ክርክር ለመገንዘብ ይቻላል። የአሁኑ ክርክር መነሻ ወ/ሮ ብሬ በህይወት እስካሉ ድረስ በንብረቱ የመጠቀም መብታቸውን ተጠቅመው ካለፉ በኃላ ሁለተኛ ተጠሪ ንብረቱን ልወርስ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር ነው። በህግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋማቸው ሰው ላይ ህግ ናቸው በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1731/1/ የሚደነግግ ሲሆን አንድ ሰው በሞት ሲለይ በሚች መሞት ምክንያት የሚቋረጡ ካልሆኑ በስተቀር በውርሱ ውስጥ የሚገኙት መብቶችና ግዴታዎች ለወራሾቹ ወይም የኑዛዜ ባለስጦታዎች የሚተላለፍ መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 826/2/ ተደንግጓል።

ሁለተኛ ተጠሪ ሊወርስ የሚችለው በወ/ሮ ብሬ መሞት ምክንያት የማይቋረጡ መብቶችና ግዴታዎችን ነው። ሚች ወ/ሮ ብሬ አከራካሪው ቤት በስማቸው የተመዘገበ ቢሆንም ቤቱ በሚች አቶ ገብረህይወት የግል ገንዘብ የተገዛ የአቶ ገብረህይወት የግል ሀብት እንደሆነ ወ/ሮ ብሬ አብረው እስካሉ ድረስ በጋራ የመጠቀም ሚች አቶ ገብረህይወት ከወ/ሮ ብሬ በፊት በሞት ቢለዩ በህይወት እስካሉ ድረስ በንብረቱ የመጠቀምና አላባ የመሰበሰብ መብት ብቻ ያላቸው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ በመግለፅ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ከአቶ ገብረህይወት ጋር ከጋብቻ ውጭ በግብረሥጋ ግንኙነት ሲኖሩ በንብረት ረገድ ስላላቸው መብትና ግዴታ በመዘርዘር ባደረጉት ውል ተስማምተዋል አቶ ገብረህይወት በሞት ከተለዩ በኃላ በዚህ ውል መሠረት ወ/ሮ ብሬ በንብረቶቹ ላይ ያላቸው መብት ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1309 በተደነገገው መሠረት በንብረቶቹ የመጠቀምና አላባ የመሰብሰብ መብት መሆኑ በውሉ በግልፅ ተገልፆል፡ በሚንቀሳቀስም ሆነ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ የአላባ የመጠቀም መብት /Usufruct Right / የአላባ ጥቅም ተቀባዩ ሲሞት ቀሪ የሚሆን መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1322/1/ የተደነገገ በመሆኑ ሚች ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ በአከራካሪው ቤት ላይ ያላቸው የመጠቀምና አላባ የመሰብሰብ መብት በመሞታቸው ምክንያት የሚቋረጥና ለወራሻቸው ለሁለተኛው ተጠሪ የማይተላለፍ መብት መሆኑን ከላይ የተገለፁትን የህግ ድንጋጌዎች በማገናዘብ ለመረዳት ችለናል።

ስለሆነም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሚች አቶ ገብረህይወትና ወ/ሮ ብሬ ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ያደረጉት ውል ከጋብቻ ውጭ እንዳባልና ሚስት ከግብረሥጋ ግንኙነት አብረው ሲኖሩ በንብረት ረገድ ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ያደረጉት ውል ሆኖ እያለ የስጦታ ውል ነው በማለት ከውሉ መሠረታዊ ይዘትና ባህሪ ውጭ የራሱን ትርጉም መስጠቱና ውሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 881 የተደነገገውን ፎርም አላሟላም በማለት የማይረጋ ነው ብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ወ/ሮ ብሬና አቶ ገብረህይወት ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም ያደረጉት ውል በንብረት ረገድ ያላቸውን ግንኙነትና ሁለቱም ያላቸውን መብትና ግዴታ በሙሉ ፈቃዳቸው የተስማሙበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ድንጋጌዎች መሠረት በተዋዋዬቹና በምስክሮች የተፈረመ ህጋዊ ውጤት ያለው ውል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በውሉ ሚች ወ/ሮ ብሬ በአከራካሪው ቤት ባለሀብት አለመሆናቸውና አቶ ገብረህይወት ከሞቱ በኃላ ወ/ሮ ብሬ በአከራካሪው ቤት ላይ የነበራቸው በንብረቱ የመጠቀምና ፍሬ የመሰብሰብ መብት እንደሆነ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ወ/ሮ ብሬ በቤቱ ላይ ያላቸው የአላባ ጥቅም መብት ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ምክንያት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1322/1/ መሠረት ቀሪ ስለሆነ ሁለተኛ ተጠሪ የአመልካቾች አባትና አውራሽ የአቶ ገብረህይወት ደበሣይ የግል ንብረት የሆነውን አከራካሪውን ቤት የሚወርሰበት ምክንያት የሌለው በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በውጤት ደረጃ ፀንቷል
3. አከራካሪውን ቤት ተጠሪዎች ለአመልካቾች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡
4. በሚች ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳና በሚች አቶ ገብረህይወት ደበሣይ መካከል ታህሣሥ 22 ቀን 1983 ዓ.ም የተደረገው ውል ህጋዊ አስገዳጅነትና ውጤት ያለው ውል ነው ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 2 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሮማን ግዛው - ጠበቃ አቶ ግርማ

ተጠሪ፡- አቶ ግርማ አብርሃም - ጠበቃ አቶ አምደ አበበ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ስላመለከቱ ነው፡፡ የጉዳዩ መነሻ ሚች ወ/ሮ አስካለ ወልደየስ መስከረም 10 ቀን 1993 ዓ.ም. አመልካችን ኑዛዜ ወራሽና ተጠቃሚ የሚያደርግ ኑዛዜ አድርገዋል፡፡ የሚች የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ ይታወቅልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ በመመርመር አመልካች የሚች ወ/ሮ አስካል ወልደየስ የኑዛዜ ወራሽ መሆኗን በማረጋገጥ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካቲት 21 ቀን 1997 ዓ.ም. ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ይህንን ፍርድ በመቃወም የሚች የወንድም ልጅ የሆንኩት እኔ እያለሁ አመልካች የኑዛዜ ወራሽ ነኝ በማለት በፍርድ ያስወሰኑችው አላግባብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሚች በአመልካች ያደረጉትን ኑዛዜ ጥቅምት 9 ቀን 1997 ዓ.ም. ባደረጉት ኑዛዜ ተክተውታል በማለት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርቧል፡፡ በተጨማሪም ኑዛዜውን ሚች ያላደረጉት ነው የሚል መከራከሪያም አቅርበዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ተጠሪ ሚች ያደረጉትን ኑዛዜ ያውቃሉ በኑዛዜው መሠረት ለሌሎች ሰዎች ሲፈፀም በምስክርነት ተገኝተዋል፡፡ ፊርማው የሚች ነው፡፡ ዋናው የሚገኘው በሌላ ሰው እጅ በአደራ ተቀምጦ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የኑዛዜ ዋና ቅጂ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ የአመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ማመልከቻ ተቀብሎ በሚያጣራበት ሰዓት ቀርቦ ከኮፒው ጋር የተገናዘበ መሆኑን ኮፒው ላይ ዳኛ አረጋግጦ የፈረመበት መሆኑን በመተቸትና በአሁኑ ወቅት ዋናው አለመቅረቡ የፖሊስ ምርመራ ባይደረግም ማስረጃ ተዓማኒነት ያለውና ሚች ያደረጉት ኑዛዜ ነው፡፡ ሚች ጥቅምት 9 ቀን 1997 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ በፊት ካደረጉት ኑዛዜ የተለየና ሚች ለአመልካች ያደረጉትን ኑዛዜ ጋር የማይቃረንና የማይተካ ነው በማለት የተጠሪን የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ኑዛዜውን በመቃወም የሚች ፊርማ እንዳልሆነ ገልፆ ሲከራከር ፊርማውን ለማስመርመር ዋናው ኮፒ ሲፈለግ አመልካች ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ አመልካች ዋናውን ኑዛዜ በማቅረብ ትክክለኛነቱን ማስረዳት ስላልቻሉ ኑዛዜው ሕጋዊ ተቀባይነት የለውም በማለት የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው የሰበር ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች እኔ የሚች የኑዛዜ ወራሽ መሆኔን ባመለከትኩበት መዝገብ የኑዛዜው ዋና ኮፒ ከቀረበው ፎቶ ኮፒ ጋር ተገናዝቦ ትክክለኛነቱ ምልክት ተደርጎበት ምስክሮችን አስመስክሬ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡት ይህ ሁሉ ሂደት ሲከናወን እያወቁ ቆይተው ነው፡፡ ዋናው ኮፒ አንድ ጊዜ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ከታየ ከተረጋገጠ በኋላ መጥፋቱ ኑዛዜውን ለማስረዳት የሚችል ማስረጃ የለሽም የሚያስብል አይደለም፡፡ ኑዛዜው የሚች ኑዛዜ መሆኑ በሰው ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ለሕጉ የተዛባ ትርጉም በመስጠት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ያቀረቡት ፎቶ ኮፒ በሬጅስትራር ቀርቦ መረጋገጡን አያመለክትም፡፡ ዋናውን ሰነድ ለማስቀረብ የተሰጠውን ተደጋጋሚ ትዕዛዝ አመልካች ሊፈጽሙ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ አመልካች በሕግ በተደነገገው መሠረት የኑዛዜውን ዋና ኮፒ በማቅረብ ለማስረዳት ስላልቻሉ የበታች ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው በሕግ ፊት ውጤት የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልሰ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የአዲስ አበባ ከተማ የሰበር ችሎት አመልካች የኑዛዜ ወራሽና ተጠቃሚ መሆኗን የኑዛዜውን ዋናውን ሰነድ አቅርባ ባለማስረዳቷ ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘናል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ኑዛዜውን የማስረዳት ሸክም ስላለበት ወገንና ኑዛዜውን ለማስረዳት ሊቀርቡ ስለሚገቡ ማስረጃዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 896 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 የተደነገገውን ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ኑዛዜ መኖሩንና በኑዛዜው የሰፈረውን ቃል የማስረዳት ግዴታ ያለበት የኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ የሚለው ሰው መሆን እንዳለበት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 896 ይደነግጋል፡፡ የኑዛዜ ተጠቃሚው መብቱን ያገኘው በግልጽ ወይም በተናዛዥ ጽሁፍ በተደረገ ኑዛዜ በሆነ ጊዜ የኑዛዜውን መኖር ለማረጋገጥ የኑዛዜውን ጽሁፍ ዋናውን ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ዘንድ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ትክክለኛ ሆኖ የተመሳከረ ግልባጭ በማቅረብ እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀጽ 1 የሚደነግግ ሲሆን ኑዛዜዎቹን ለማስፈፀም በማናቸውም ሌላ መንገድ ማስረዳት እንደማይቻል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚች ወ/ሮ አስካለ ወልደየስ መስከረም 10 ቀን 1993 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ ተጠቃሚና ወራሽ መሆኗን አረጋግጦ እንዲወስንላት ስታመለክት የኑዛዜው ዋና ሰነድ በወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ እጅ መሆኑን ገልፀው ፍርድ ቤቱ ዋናውን በማስቀረብ እንዲመለከተው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 223 መሠረት የካቲት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. ባቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ጠይቀዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤትም የኑዛዜው ዋና ሰነድ ለየካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም. እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም. የኑዛዜው ዋና ሰነድ ቀርቦ የታየና የተረጋገጠ መሆኑን በኮፒው ጀርባ የዳኛ ፊርማ የተፈረመበት ሲሆን ዋናው የኑዛዜ ሰነድ የቀረበውም ፍርድ ቤቱ የኑዛዜውን ዋና ሰነድ እንዲቀርብ ትዕዛዝ በሰጠበት የካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም. መሆኑን ይህ የሰበር ችሎት በትዕዛዝ ካስቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ/ቁ. 1185/97 ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የኑዛዜው ዋና ሰነድ በእጃቸው የነበረው ወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ ለፍርድ ቤት በምስክርነት ቀርበው ሟች ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑን የመሰከሩ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ ባቀረበበት ጊዜ ወ/ሮ ትዕግሥት የኑዛዜውን ዋና ሰነድ ለፍርድ ቤት ያቀረቡ መሆኑና ዋናው ሰነድ እንዳልተመለሰላቸው የገለጹ መሆኑን የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውሣኔው ገልፆታል፡፡

ከዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች የኑዛዜ ተጠቃሚና ወራሽ መሆኗን ለማስረዳት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት ዋናውን የኑዛዜ ሰነድ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም የተረጋጠውን በማቅረብ አስረድታለች ወይስ አላስረዳችም የሚለው ነው፡፡ ሟች ወ/ሮ አስካለ ወልደየስ ኑዛዜ ያደረጉት በሁለት ኮፒ እንደሆነና አንደኛው ኮፒ በወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ ሁለተኛው በአባ ማሞ አርጋው እጅ መቀመጥ እንዳለበት በኑዛዜው የገለጹ መሆኑን ሰነዱ ያሣያል፡፡ የኑዛዜው ዋና ሰነድ ወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ እጅ የነበረና በሌላ ሰው እጅ የካርቦን ኮፒው የነበረ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የኑዛዜ ወራሽነቷን የሚያረጋግጥላት ሰነድ በወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ እጅ እንደሚገኝ በማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ላይ በመግለጽ ወ/ሮ ንግሥት መታፈሪያ ዋናውን ሰነድ ለፍርድ ቤት የካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም. እንድታቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የካቲት 17 ቀን 1997 ዓ.ም. ዋናው ሰነድ ቀርቦ ከዋናው ጋር የተረጋገጠ መሆኑ በኮፒው ጀርባ ዳኛ ጽፎ የፈረመበት በመሆኑ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት የኑዛዜውን ዋና ሰነድ በማቅረብ አላስረዳችም በማለት የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎት የሰጡት የሕግ ትርጉም ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች ዋናው የኑዛዜ ሰነድ በአደራ ይዘውት በነበሩት ሴት በኩል ቀርቦ ትክክለኛነቱ በዳኛ ከታየና ከተረጋገጠ በኋላ ተጠሪ ተቃውሞ ሲያቀርብ ይህ ሰነድ አለመቅረቡና መጥፋቱ አመልካች ኑዛዜ መኖሩን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አላስረዳችም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ተጠሪ ፊርማውን የካደ ቢሆንም በግልጽ ኑዛዜው ሲደረግ የነበሩ ምስክሮች ኑዛዜው ላይ የሚች መሆኑን ገልፀው የመሰከሩና የኑዛዜ ሰነዱም በአመልካች እጅ ሣይሆን በሌላ ሰው እጅ በአደራ ተቀምጦ የቆየ መሆኑን በማገናዘብ ኑዛዜው የሚች ኑዛዜ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897 ንዑስ አንቀጽ 1 የተሣሣ ትርጉም በመስጠት መሻራቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የአዲስ አበባ ከተማ የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል
3. አመልካች ሚች መስከረም 10 ቀን 1993 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ ተጠቃሚና ወራሽ ናት ብለናል፡፡
4. በትውስት የመጣው መዝገብ ይመለስ፡፡
5. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ አቶ ሐዲስ ዓለመስላሴ - ጠበቃ ጌታቸው ውብሸት ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- ወ/ሮ ብሌኔ ዓለመስላሴ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው ይግባኝ መነሻ የሆነው ጉዳይ ኑዛዜን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘትም የአሁኑ አመልካቾች እናት ሐምሌ 30 ቀን 1986 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካቲት 27 ቀን 1990 ዓ.ም መጽደቁን ገልፀው ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም በማለት ኑዛዜው እንዲፈርስላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም ለክሱ በሰጡት መልስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም ተጠሪ ክስ ለመመስረት መብት ወይም ጥቅም የላቸውም ኑዛዜውን ለመቃወምም ይርጋ ያግዳቸዋል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሲያቀርቡ በፍሬነገር ደረጃም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ተጠሪ ኑዛዜውን የተቃወሙት ኑዛዜው ከተደረገ ከአስራ ሁለት አመታት በሁዋላ ስለሆነና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 974(2) ድንጋጌ ተቀባይነት የሌለው ነው በሚል ምክንያት አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኗ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኝ‘ቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የተጠሪ ጥያቄ ኑዛዜው የተደረገው መብት በሌላቸው ንብረት ስለሆነ ይፍረስልኝ የሚል በመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 974 ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን በመሻር በሌሎች ነጥቦች ላይ አከራክሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት መልሶለታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

እኛም የአመልካቾች ጠበቃ የካቲት 18 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካቾች ከስር ጀምረው አቅርበው ሲከራከሩበት የቆዩት የይርጋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቃወሚያ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው።በዚህ መሠረትም ይህ ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

የስር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ እንደተመለከተው አከራካሪው ኑዛዜ የተደረገው ሐምሌ 30 ቀን 1986 ሲሆን ተጠሪ ኑዛዜውን በመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት ሕዳር 19 ቀን 1999 ኑዛዜ ከተደረገ ከ12 /አሥራ ሁለት/ አመት በኋላ ነው። ይሁን እንጂ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ የኑዛዜው አድራጊ ወራሽ ስለሆንኩ ኑዛዜው መብቴን /ጥቅሜን/ ነክቷል ይስተካከልልኝ ሳይሆን ኑዛዜው የተደረገው በተናዛዡ ንብረት ላይ ብቻ ሳይሆን በሌላ ሰው ሀብት (በተጠሪ አውራሽ ሀብት) ጭምር ነው ኑዛዜው ተፈጻሚነት የለውም በሚል ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ ተገልጾአል።

ኑዛዜን በመቃወም የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ መታየት ያለበት አግባብነት ካላቸው የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ነው። የአመልካቾች ጠበቃ ለጉዳዩ አግባብነት አለው በማለት ከሚጠቅሱት ድንጋጌዎች አንዱ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.973 የተመለከተው ነው። ይህ ድንጋጌ ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል መቃወሚያ ያላቸው ኑዛዜው ሲነገር /ሲፈስ/ የነበሩትን ሰዎች የሚመለከት ነው። ይህም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ወይም የተወከሉ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም ወይም በኑዛዜው የተነገረ ቃል አይፀናም የሚሉትንና የመሳሰሉትን በመቃወም ክስ የሚያቀርቡ ሲሆን ይህን ማድረግ ያለባቸው ኑዛዜው ከተነበበት አንስቶ እስከ አስራ አምስት ቀን ድረስ እንደሆነ ያመላክታል። ከዚህም በተጨማሪ ክስ የማቅረብ ሃሣብ መግለጫው በጽሑፍ ካልሆነና ለአጣሪው ወይም ለዳኞች ወይም በውርስ ላይ የተነሣውን ነገር ለመጨረስ ለተመረጡት የሽምግልና ዳኞች እንዲደርስ ካልተደረገ በቀር እንደማይፀና /መቃወሚያ አለ ለማለት እንደማይቻል/ በዚሁ ቁጥር 973/2/ ስር ተደንግጓል። በመጨረሻም መግለጫው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እስከ ሦስት ወር ድረስ ክስ ካልቀረበ መብቱ ከነጭራሹ እንደሚቀር በንኡስ ቁጥር /3/ ተመልክቶአል። በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 974/2/ በግልጽ እንደተመለከተው ኑዛዜው ከፈሰሰበት /ከተነበበት/ ጊዜ ከአምስት ዓመት በኋላ ስለኑዛዜው መጽናትም ሆነ ስለክፍያው ድልድል መቃወሚያ ማቅረብ አይቻልም። እነዚህ ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያሳዩት ስለወራሾች መቃወሚያ አቀራረብና የጊዜ ገደቡ ነው እንጂ ወራሽ ያልሆነ ሰው ስለኑዛዜ የሚቃወምበትን የጊዜ ገደብ አይደለም።

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪ የኑዛዜ አድራጊ ወራሽ አይደሉም መቃሚያ ያቀረቡት በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 973 በግልጽ የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ እንዳልሆነም ተረጋግጧል። በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 973 እና 974 ድንጋጌዎች ለጉዳዩ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ተፈጻሚነት የላቸውም። ሲጠቃለል ተጠሪ የወ/ሮ የሸዋዘርፍ ዓለማየሁ ወራሽ ነኝ ኑዛዜ ሲነበብ /ሲፈስ/ አልነበርኩም ወይም አልሰማሁም በማለት ክስ ባላቀረቡበት ሁኔታ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 973 እና 974 ድንጋጌዎች መሠረት ሁነው ተቃውሞአቸው በይርጋ ቀሪ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመ.ቁ 04142 ሕዳር 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የዚሁ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 06022 ሕዳር 19 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. ተጠሪ በኑዛዜው ላይ ያቀረቡት መቃወሚያ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 54258

ህዳር 2 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘነበች በቀለ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዮናስ ፀጋዬ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጋብቻ መመስረት አለመመስረትን በተመለከተ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ከአሁኗ አመልካች ጋር ህዳር 03 ቀን 1998ዓ.ም በአገር ባህል መሰረት ጋብቻ ፈጽመው ሲኖሩ ልጅ አለመውለዳቸውን፣ የጋራ ንብረት ግን ያፈሩ ቢሆንም ተጠሪ የጋራ ንብረት እያሸሸች በመሆኑ አብሮ መኖር እንደማይችሉ ገልፀው ፍቺ ተወስኖ የጋራ ንብረት የመጠየቅ መብታቸው እንዲጠብቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካችም ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስ ጋብቻው የተፈፀመው ተጠሪ በገለፁት ህዳር 3 ቀን 1998ዓ.ም ሳይሆን ታህሳስ 21 ቀን 2001ዓ.ም መሆኑን ገልጸው ያለምንም ማስላሰያ ጊዜ ፍቺ ቢወሰን ግን ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ጋብቻው የተፈፀመው በተጠሪ በተገለፀው ህዳር 3 ቀን 1998ዓ.ም መሆኑን በመደምደም ጋብቻው እንዲፈርስ ወስኖ የግራ ቀኙን የጋራ ንብረት ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ ወስኗል፡፡ አመልካች ጋብቻው ህዳር 3 ቀን 1998ዓ.ም ተፈጸመ ተብሎ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የውሳኔ ክፍል ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ምክንያት ጊዜውን ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት መጋቢት 20 ቀን 2002ዓ.ም በዓፉት የሰበር አቤቱታ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ03/03/1998ዓ.ም የባህል ጋብቻ መፈፀሙን ያረጋግጣል የተባለው አመልካች ያልተሳተፈችበት ሰነድ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 27 መሠረት የባህል ጋብቻ የተፈፀመ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ መሆን ያለመሆኑ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተደርጎላቸው ቀርበው ሐምሌ 08 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሳቸውን የሰጡ ሲሆን አመልካችም መስከረም 10 ቀን2002ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መሠረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የባህል ጋብቻ ህዳር 03 ቀን 1998ዓ.ም ስለመፈፀሙ ያረጋግጣል የተባለው ከድሬደዋ 02 ቀበሌ ስለመቅረቡና በ20/04/2001ዓ.ም ተጠሪ ብቻቸውን ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ስለመሰጠቱ የተረጋገጠው ሰነድ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ጋብቻው መፈፀሙን ያሳያል የሚሉት ሰነድ ደግሞ ግራ ቀኙ በተገኙበት በድሬደዋ አስተዳደር ከተማ ስ/አ/ጽ/ቤት በ21/04/2001ዓ.ም መመዝገቡን የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መሠረት ለጋብቻ መኖር ቀዳሚና ዋናው ማስረጃ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ሲሆን ይህ ሰነድ ጋብቻው በተፈፀመበት እለት ወይም ከዚያ በኋላ በክብር መዝገብ ሹም የሚሰጥ፣ ስለጋብቻው መፈፀም ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው፡፡ ሕጉ ምዝገባው በክብር መዝገብ ሹም ፊት ለተፈፀሙ ጋብቻዎች ብቻ ሳይሆን በሐይማኖት ወይም በባህል ስርዓት ለተፈፀሙ ጋብቻዎች ሁሉ ተፈፃሚነት እንዳለው ያሳያል፡፡ በመሆኑም በየትኛውም ስርዓት ጋብቻ ቢፈፀም የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የጋብቻ መፈፀሙ ምዝገባ ስርዓት በክብር መዝገብ የሚከናወነው በሕጉ በልዩ ሁኔታ ከተገለጹት ሁኔታዎች ውጪ ተጋቢዎች ባሉበት ጊዜና ቦታ ነው ተብሎም ይታሰባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ አመልካች ጋር ጋብቻ በባህላዊ መንገድ ስለመፈፀማቸው የሚያረጋግጠው እና በሕጉ አግባብ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ የሚያሳየው ጋብቻው ታህሳስ 21 ቀን 2001ዓ.ም መፈፀሙን ነው፡፡ ይህ ሰነድ ጋብቻው ከዚህ በፊት የተፈፀመ /ህዳር 3 ቀን 1998ዓ.ም/ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 30/ሐ/ ድንጋጌ አነጋገር መሠረት ይገልፃል፡፡ እንዲህ ከሆነ ጋብቻው ውጤት አለው የሚባለው ምዝገባ ከተወናወነበት ጊዜ ሳይሆን ከህዳር 03 ቀን 1998ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ይህም በአዋጅ አንቀጽ 28/3/ ድንጋጌ ስር በግልጽ የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካችና ተጠሪ በባህላዊ የፈፀሙት ጋብቻ ስለመኖሩ ታህሳስ 21 ቀን 2001ዓ.ም በተሰጠው የጋብቻ ምስክር ወረቀት የተረጋገጠ በመሆኑ እና ይህንኑ የሚያስተባብል ማስረጃም አመልካች ያላቀረቡ መሆኑን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ ስለተገኘ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1/ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕዳር 02 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኑን ስንታየሁ ጎዝ - ጠበቃ ሙሉቀን ልመንህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ክርክርን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ባልና ሚስት የነበሩ ሲሆን የካቲት 07 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍቺ ውሳኔ ጋብቻው ፈርሷል፡፡ ከዚህም በሁዋላ አመልካች አይነቱንና መጠኑን በመለየት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲያቀርቡ ተጠሪም የጋራ ሊሆን የማይችለውን ንብረት አይነቱንና ብዛቱን በመለየት ለአመልካች ክስ መልስ ከመስጠታቸው በተጨማሪ የጋራ ነው የሚሉትን ንብረትም ለይተው እንዲካፈሉ ይወሰን ዘንድ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶና ተገቢ ነው ያለውን ሁሉ አጣርቶ ጉዳዩን በመመርመር በእያንዳንዱ ንብረት ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ በአመልካች በኩል የጋራ እዳ ተብሎ በተጠቀሰው ገንዘብና አመልካች ከተጠሪ ከተለዩ በኋላ ፍቺው በፍርድ ቤት እስከሚወሰን ድረስ የወሰዱትን ደመወዝ ላይ እንዲሁም አንድ አንድ ንብረቶች ላይ አመልካች የግሌ ናቸው በሚል ካቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ላይ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ፍቺ ከመፈፀሙ በፊት ያገኙ የነበሩትን ገቢ እኩል ይካፈሉ አመልካች ከመስሪያ ቤታቸው የተበደሩትን የብድር ገንዘብ ተጠሪን አይመለከታቸውም ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሲያፀናው የአመልካች የግል ንብረቶች መሆናቸውን ያረጋግጣቸውን ንብረቶችን ለይቶ ለአመልካች እንዲመለስላቸው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች ፍቺ ከመፈፀሙ በፊት አመልካች ያገኙት የደመወዝ ገቢ ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ አመልካች ከመስሪያ ቤታቸው የተበደሩት እስከ ፍቺው ጊዜ ድረስ አለመከፈሉ የተረጋገጠው የብድር ገንዘብ ግን ተጠሪን አይመለከትም ተብሎ በተወሰነው የውሳኔ ክፍል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ተጠሪ እንዲቀርቡ ተደርጐ ሐምሌ 08 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም መስከረም 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በትዳር ተሳስረው በነበረበት ዘመን ብር 265,827.10 (ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ሰባት ብር ከአስር ሳንቲም) የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ ከአስራ አንድ አመት በፊት አመልካች ከሚሰሩበት ከተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የብድርና ቁጠባ ሕብረት ሥራ ማህበር ላይ በተለያዩ ጊዜአቶችና በተለየዩ የወለድ መጠኖች ወስደው ለቤት መኪና መግዣ ለተጠሪው የግል መኪና የሞተር እድሳትን ጨምሮ ለሌሎች እድሳቶች፣ ለተለያዩ የቤት እቃዎች ማሟያ ለባለ አንድ ፎቅ መኖሪያ ቤት መስሪያና ለሌሎች የቤተሰብ ወጪዎች ማሟያ አገልግሎት እንደአዋሉ እዳው በትዳር ዘመን ከአመልካች ደመወዝ እየተቆረጠ ሲከፈል ቆይቶ የፍቺ ውሳኔ በተሰጠበት የካቲት 07 ቀን 1995 ዓ.ም ብር 147,852.10 (አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር ከአስር ሳንቲም) መቅረቱ በንብረት አጣሪዎቹ ትእዛዝ ከሕብረት ስራ ማህበሩ በቀረበ ማስረጃ መረጋገጡን አመልካች ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ተጠሪ የብድር ገንዘቡን እንደማያውቁት እና በአመልካች ለተጠቀሱት ነገሮች ያልዋለ ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ ያልተረጋገጠ መሆኑንና ቤቱ የተሰራውም ከባንኩ ያጠራቀሙትን ገንዘብ ወጪ አድርገው መሆኑን ገልፈፀሙ ለእዳው ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ብድሩ በአመልካች ከመስሪያ ቤቻው ስለመወሰዱም ሆነ በትዳር ዘመን ከአመልካች ደመወዝ እየተቆረጠ ሲከፈል ቆይቶ እስከፍቺው ውሳኔ ጊዜ ድረስ ቀሪ ያልተከፈለ እዳ ያለ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነገር ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት እዳው የጋራ ሊባል የሚችል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አመልካች ከመስሪያ ቤታቸው የተበደሩትን ገንዘብ በስማቸው ወይም ከተጠሪ ጋር በጋራ በባንክ ስለማስቀመጣቸው አላስረዱም፣ በአቢሲኒያ ባንክ ገነት ቅርንጫፍ እና ቦሌ ቅርንጫፍ ከሚገኘው ሂሳብ ከመጋቢት 04 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 27 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ 151,651.74 (አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ አንድ ብር ከሰባ አራት) ወጪ መደረጉ መረጋገጡ ቤቱ የተሰራውና ለተለያዩ አገልግሎት የሚውል ብድር ወስደናል በማለት አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እንዲሁም አመልካች በብድር የወሰዱትን ገንዘብ በአቤቱታቸው ለዘረዘሯቸው ነገሮች መግዣ መዋላቸውን አላስረዱም በሚል ምክንያት ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡ በዚህም መሠረት በአዋጁ አንቀጽ 68(መ) ስር እንደተመለከተው በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ከብር አምስት መቶ በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ ሰው ዋስ ለመሆን የተጋቢዎች ስምምነት የግድ ያስፈልጋል፡፡ የስምምነት አለመኖር ስለሚያስከትለው ውጤትም ሕጉ በአንቀጽ 69 ስር ያስቀመጠ ሲሆን የተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ እንደኛው ተጋቢ በአንቀጽ 68 ስር የመለከተውን ባለማክበር የውል ግዴታ ገብቶ የተገኘ እንደሆነ ሌላኛው ተጋቢ ለፍርድ ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ ግዴታው ሊፈርስ እንደሚችል፣ በንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ የይፍረስልኝ ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው መግባቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከስድስት ወር በኋላ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ብድሩን ከተጠሪ ጋር ፈርመው ወስደዋል ባይባልም ብድሩ ትዳሩ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ከመስሪያ ቤታቸው ተወስዶ ከአስራ አንድ አመታት በላይ ከአመልካች ደመወዝ እየተቆረጠ ሲከፈል የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ብድሩ ከአመልካች ደመወዝ እየተቆረጠ ሲከፈል የነበረ መሆኑ ሲታይ ደግሞ ተጠሪ ስለብድሩ እውቅና አልነበራቸውም ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ብድሩ ስለመኖሩ ተጠሪ ያወቁ እንደነበር የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ብድሩ ለትዳር ጥቅም የዋለ መሆን አለመሆኑ ላይ ነው፡፡ ብድሩ በትዳር ወቅት የተወሰደ መሆኑ ከተረጋገጠ የሕግ ግምት ለትዳር ጥቅም የዋለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይኸው የሕግ ግምት ሊስተባበል የሚገባው ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም አልዋለም ብሎ በሚከራከረው ተጋቢ ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑም ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 71 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ቤት ለመስራት ወይም ለቤተሰቡ የተለያዩ ወጪዎች ብድሩ አለመዋሉን የማስረዳት ሸክም ባልተወጡበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች ለቤት መስሪያ በሌላ ባንክ ገንዘብ የነበረ መሆኑ ተረጋጋጧል በሚል ምክንያት ብቻ ተጠሪ ትዳር ከመፍረሱ በፊት አስራ አንድ አመታት በፊት ከመስሪያ ቤታቸው የወሰዱትን የብድር ገንዘብ ከወርሃዊ ደመወዝ እየከፈሉ ቆይተው ተጠሪ ምንም ተቃውሞ ባላነሱት ሁኔታ ብድሩ የጋራ ሊሆን አይገባም ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው አመልካች ፍቺ በፍርድ ቤት ከመወሰኑ በፊትና ከተጠሪ ጋር አብሮ መኖር ትተው በግላቸው ሲኖሩ በነበሩበት ጊዜ ያገኙት ደመወዝ የጋራ ገቢ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተመልክተናል፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 62(1) መሠረት ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሃብቶቻቸው እንደሚሆኑ የተደነገገ ሲሆን ከግል ጥረት ከሚገኙት ገቢዎች አንዱ ደመወዝ መሆኑ ይታመናል፡፡ ሕግ አውጪው ደመወዝ የተጋቢዎች የጋራ ሀብት ነው በማለት የደነገገው የትዳርን ወጪ ለመሸፈን ሲሆን የትዳር ወጪን ደግሞ ተጋቢዎች እያንዳንዳቸው እንደ የአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ የማድረግ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 72 ስር ከመመልከቱም በላይ በገቢው መፈጠር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሌላው ተጋቢም አስተዋጽኦ አለው ተብሎ የሚታሰብ መሆኑ እሙን ነው ለዚህም ምክንያቶች ደመወዝ የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ነው ተብሎ በሕጉ ከተመለከተ ምላሽ የሚያስፈልገው ጥያቄ ፍቺው ከመፈፀሙ በፊት ተጋቢዎች ተለያይተው በኖሩበት ወቅት የተገኘ ደመወዝ የጋራ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይገባል ወይ የሚው ነጥብ ነው፡፡ የሕጉ ዓላማ ከላይ የተመለከተው ከሆነ ተጋቢዎች ተለያይተው በነበሩበት ጊዜ የተጠሪ ደመወዝ ለቀለቡ ጥያቄ በሕጉ አግባብ ከሚስተናገድ በስተቀር እንደሌላው ሀብት የጋራ ነው ተብሎ የሚወሰድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህም ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ ከአስራ አንድ አመታት በፊት ጀምሮ ንብረት ማፍሪያና ለትዳር ጥቅም የተወሰደውን ብድር ተጠሪው የጋራ እዳቸው መሆኑ ያውቁ የነበረ በመሆኑ እስከፍቺው ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድረስ አለመከፈሉ የተረጋገጠውን ብር 147,852.10 (አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር ከአስር ሳንቲም) ግማሽ ብር 73,926.05 (ሰባት ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ስድስት ብር ከዜሮ አምስት ሳንቲም) ለአመልካች እንዲተኩ ብለናል፡፡

3. አመልካች ከተጠሪ ተለይተው ከቤት ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ካገኙት ደመወዝ ለተጠሪ ግማሹን የሚከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕዳር 13 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉወርቅ ዋቺ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ ፡- ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ሞገደገኝ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጡረታ ተጠቃሚነት የሚቋረጥበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች የሚች አቶ ጋቲሶ ሚስት ስለነበሩ የጡረታ አበል ተወስኖላቸው ሲቀበሉ ከቆዩ በሁዋላ ሌላ ባል አግብተውም ከሕግ ውጪ አበሉን መቀበሉን መቀጠላቸውን ገልጾ ባል ሲያገቡ መቋረጥ ሲገባው የተቀበሉትን መጠኑ ብር 5478.56 /አምስት ሺህ አራት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም/ የጡረታ አበል እንዲመልሱ ይወሰንልት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት ክርክርም በሌላ መዝገብ በቀረበ ክርክር ሚች አቶ ጋቲሶ አዲሶ ከሞቱ በሁዋላ ሌላ ባል ያላገቡ መሆኑ መረጋገጡን የሚገልጽ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ያቀረቡት ክርክርም የጡረታ አበሉን እየተቀበሉ ባሉበት ጊዜ ሌላ ባል ያላገቡ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን ከመረመረ በሁዋላ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መልስ ሠጪን ሳይጠራ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥር 17 ቀን 2002 ዓ/ም ዕፈው ባቀረቡት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አመልካች ሌላ ባል ያላገቡ መሆኑ በሌላ መዝገብ ተረጋግጦ ውሳኔ አግኝቶ እያለ ይኸው ታልፎና ተጠሪም አመልካች ሌላ ባል ስለማግባታቸው ሳያስረዳ ሌላ ባል አግብተዋል ተብሎ የጡረታ አበሉን እንዲመልሱ የተሰጠው ውሳኔ ያላግባብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ የጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡ የአመልካች ጠበቃም የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል; ወይስ አይቻልም; የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሌላ ባል ያገቡ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን ይኸውም አመልካች ሌላ ባል ያገቡ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን ይኸው ፍሬ ነገር በሕጉ አግባብ ተቀባይነት ባለው ማስረጃ ተረጋግጧል ተብሎ ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡ ይኸውም አመልካች ሌላ ባል አግብተው የሚኖሩ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ነጥብ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱን ነው፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ የቀረቡትን የተጠሪ ማስረጃዎችን ያላስተባበሉ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልፅ ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን መከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ ያደረገው ቃላቸው አመልካች ባል ማግኘቷን የሚገልፅ ቢሆንም ታአማኒነት የለውም በሚል ነው፡፡ ውሳኔው በግልፅ የሚያሳየው የአመልካች ምስክሮች ቃል ውድቅ የተደረገው የግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል ክብደቱ ተመዝኖ መሆኑን ነው፡፡ አንድ ጡረታ አበል የሚቀበል ተጋቢ ሌላ ተጋቢ ማግባት አለማግባቱን በሰው ምስክር ለማረጋገጥ የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ ይህ ሁኔታ በሰው ማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል ነው ከተባለ ደግሞ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ እንጂ የሕግ አተረጓጎምን የሚመለከት አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ይህ ችሎት ጉዳዩን የሚመለከትበት አግባብ የለም፡፡ አመልካች ባል ማግባታቸው በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው ከተባለ በአዋጅ ቁጥር 209/1955 አንቀጽ 21 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 35/2/ መሰረት ባል አግብተው እያለ የጡረታ አበል መቀበል ሕጋዊ ባለመሆኑ ገንዘቡን የማይመልሱበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፍ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 46726

ታህሣሥ 13 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ነጋሲ አየለ ኢትቻ ጠበቃ ገመቹ ዱራሣ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1/ ሣሙኤል ዮሐንስ ገ/እግዚአብሔር /ጠበቃ ገ/ሚካኤል

2/ የሕፃን ዮሐንስ ሐጎስ ሞግዚት ወ/ሮ ማንአለበሽ በየነ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውርስ ሐብት ክፍፍል ጥያቄ ጋር ተያይዞ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የሟች እናታችን ወ/ሮ ዘነበች በየነ ወራሾች ስለሆንን የውርስ ንብረት ይጣራልን በማለት ነው፡፡ አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከከሣሾች እናት ጋር የጋብቻ ግንኙነት የለኝም፡፡ አብረን በጋራ ያፈራነው ንብረት የለም፡፡ ከሣሾች እኔን በመክሰስ የሚጣራላቸው ንብረት የለም በማለት ስለመከራከሩ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ከሣሾች የሟች እናታቸው ወራሾች እስከሆኑ ድረስ እናታቸው የተጠሪ ሚስት ብትሆንም ባትሆንም የአውራሻቸው ውርስ እንዲጣራ የመጠየቅ መብት አላቸው በማለት የሟች የውርስ ሐብት ይጣራ በማለት ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙ የቀረበው የመጨረሻ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ከተጠሪዎች አውራሽ /ሟች/ ጋር የጋብቻ ግንኙነት የለም የሚለው የአመልካች ክርክር አስቀድሞ ሣይወሰን ውርስ እንዲጣራ የመወሰኑን አግባብነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምንመለከተው የክርክሩ መነሻ የሚች ውርስ ይጣራ የሚል ቢሆንም፤ አመልካች ግን ወደውርስ ማጣራቱ ከመገባቱ በፊት በእሱ እና በሚች /የተጠሪዎች እናት/ መካከል ስላለው ግንኙነት በሚመለከት ክርክር አንስቶአል፡፡ ክርክሩም ከሚች ጋር የጋብቻ ግንኙነት የለኝም፤ በጋራ ያፈራነው ንብረት የለም በሚል በግልጽ የቀረበ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሚች ውርስ ይጣራ በሚል ጥያቄ እኔ ተከሣሽ የምሆንበት ምክንያት የለም የሚል ክርክር ከአመልካች ቀርቦአል ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው በሞተ ጊዜ ትቶት የሄደውን ንብረት መካፈል የሚችሉት በሕጉ አግባብ ወራሾቹ እንደመሆናቸው የውርስ ሐብቱን ይዞ በሚገኝ ሰው ላይ ክስ በማቅረብ ሐብቱን ሊያገኙ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ ውርስ ከመጣራቱ በፊት መከፋፈል ያልተቻለ በሆነ ጊዜም ወራሾቹ ወይም ከወራሾቹ አንዱ ውርሱ ይጣራ ዘንድ እንዲታዘዝላቸው ለፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችሉ በፍትሐብሔር ሕጉ ከፍ/ብሔር ህ/ቁ. 942 እና ቀጥለው ካሉት ድንጋጌዎች እንገነዘባለን፡፡ ውርሱ እንዲጣራ ሲጠየቅም ተከሣሽ መሆን ያለበት የውርሱን ሐብት የያዘ ወይም ወራሽ በሆነው ሰው ላይ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ በተጠሪዎች ክስ ይጣራ የተባለው ንብረት የሚች እናታቸው መሆኑ ቢገለጽም የተከሰሰው ግን አመልካች ነው፡፡ ተጠሪዎች አመልካችን በተከሣሽነት ያጣመሩት በእሱ እና በእናታቸው መካከል የጋብቻ ግንኙነት አለ /ነበረ/ በማለት እንደሆነ ከክርክራቸው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ ፍሬ ነገር በአመልካች ተክዶአል፡፡ የተጠሪዎችን እናት አላገባሁም አብረንም ያፈራነው ንብረት የለም በማለት እንደተከራከረም ተመልክተናል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በዚህ አይነት የቀረበን ክርክር ለመወሰን የሚያስችለውን የነገር ጭብጥ መሥርቶ ግራ ቀኝ ወገኖችን አላከራከረም፡፡

አመልካች አጥብቆ እንደሚከራከረው በተጠሪዎች እናት እና በእሱ መካከል በሕግ የሚታወቅ ግንኙነት ከሌለ በሚች ውርስ ማጣራት ሂደት እሱ ተከሣሽ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በእሱ እና በተጠሪዎች እናት መካከል በእርግጥም በሕግ የሚታወቅ ግንኙነት መኖሩ እና ንብረትም በጋራ ማፍራታቸው ከተረጋገጠ በቀረበው ክስ መሠረት ውርሱ እንዲጣራ ይደረጋል፡፡ አሁን እያየን ያለው ግን በተጠሪዎች እናት እና በአመልካች መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ ከመረጋገጡ ወይም በዚህ ረገድ የተነሣው ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 247/1/ በተደነገገው መሠረት ተገቢው ጭብጥ ተይዞለት ከመወሰኑ በፊት ወደውርስ ማጣራት እንዲገባ ነው የተበየነው በመሆኑም አካሄዱ የክርክር አመራር ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ክርክሩ በሥርዓት አልተመራም የሚል ይግባኝ ቀርቦለት እያለ ውርሱ እንዲጣራ በማለት የተሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 320/3/ እንደተመለከተው ጊዜአዊ አገልግሎት እንዳለው ትእዛዝ አድርጎ መቁጠሩ ትክክል አይደለም፡፡ ጉዳዩ እኔን በተከሣሽነት አስገብቶ ንብረቴን በውርስ ሐብትነት ተይዞ እንዲጣራ የሚያስደርግ አይደለም በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር አለመቀበል ጊዜአዊ አገልግሎት ያለው ትእዛዝ እንደመሰጠት የሚቆጠር አይደለም፡፡ ስናጠቃልለው አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 47254 መጋቢት 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 79397 ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ከተጠሪዎች እናት ጋር ግንኙነት የለኝም፡፡ ንብረትም በጋራ አላፈራንም በማለት ያነሣው ክርክር ተጠሪዎች ከሚያቀርቡት የመከራከሪያ ነጥብ ጋር በማገናዘብ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመመሥረት በቅድሚያ በዚህ ጭብጥ ላይ ውሣኔ ይሰጥ በማለት ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. *50580*

ታህሣሥ 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ ዶ/ር አለኸኝ መኮንን ጠበቃ ኃይሉ ንጋቱ ጋር ቀረበ

ተጠሪ፣ ወ/ሮ አስቴር አርአያ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአሁኑ አመልካች ጋር መስከረም 24 ቀን 1980 ዓ.ም በባህላዊ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ፈፅመው አብረው በመኖር ንብረት ማፍራታቸውን ገልፀው ጋብቻው ፈርሶ የጋራ ሃብት ክፍፍል እንዲወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን በአማራጭም ከአመልካች ጋር ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብረው በመኖር የተለያዩ የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ያፈሩ መሆኑን ዘርዝረው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጡት መከላከያ መልስም ከተጠሪ ጋር የመሠረቱት ጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንዳባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የሌላቸው መሆኑንና በግልም ሆነ በጋራ ያፈሩት ንብረት አለመኖሩን፣ በህዳር ወር 1986 ዓ.ም ፈታሂ ቴክኒካል ኮርፖሬትድ ኢትዮጵያ ኃ.የተ.የግል ማህበር የተባለ የንግድ ድርጅት በባለአክሲዩንነት ከማቋቋም በስተቀር ሌላ ግንኙነት እንደሌላቸው ተጠሪ እስከ መጋቢት 28 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ አቶ አያሌው ተድላ የተባሉትን ግለሰብ አግብተው ይኖሩ እንደነበርና በተጠሪ በኩል የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎችም ይህንኑ የሚያስረዱና አመልካችም የሚያምኑባቸው መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ የነበረው ግንኙነት ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት መኖር ነው በማለት የደመደመ ሲሆን በዚህ ጊዜ መፈራቱ የተረጋገጠውና በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው አጠራር በወረዳ 23 ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 1317 የሆነና በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት የጋራ በመሆኑ እንዲካፈሉት በማለት የአከፋፈሉን ቅደም ተከተልና ሥርዓቱን ለይቶ ወስኗል፡፡ ሌሎች ንብረቶች ላይ የቀረበውን የተጠሪ ጥያቄ በማስረጃ አልተደገፈም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሕዳር 01 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ በሰር ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ከአመልካች ጋር ጋብቻ እያላቸው ገልፀው ክስ ከመሠረቱ በኋላ ክስነ ሥርዓቱ መንፈስ ውጪ በአማራጭ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩን ጠቅሰው ዳኝነት መጠየቃቸው ያላግባብ መሆኑን በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ግንኙነትም ተጠሪ ባላቸው የሕግ ሙያ የደምበኝነት እንጂ የባልና ሚስት አለመሆኑን ተጠሪ በሰር ፍርድ ቤት የቆጠሯቸው ምስክሮች ሕጋዊ ግንኙነት ስለመኖሩ ያላስረዱ መሆኑን ተጠሪ እስከ መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ ከሚች አቶ አያሌው ተድላ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ መስርተው ይኖሩ የነበረና ሚስትነታቸውም በፍርድ ቤት መረጋገጡን ገልፀው ከተጠሪ ጋራ የነበራቸው ግንኙነት ጋብቻ ወይም ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር እንዳልሆነ ምንም አይነት ንብረት ያላፈሩ መሆኑን ገልፆ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በአመልካችና በተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አለ የመባሉን አግባብነትና አለ እንኳ ቢባል ከመቼ ጀምሮ የሚለው ጥያቄን አስመልክቶ የሰር ፍርድ ቤት የሰጠው ዳኝነት ማስረጃን ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የግራቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለው ነጥብ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ክስ የመሠረቱት ከአመልካች ጋር በባህላዊ ሥርዓት ብቻ ፈፅመው ይኖሩ የነበረ መሆኑና በግንኙነቱም ወቅት ንብረት ማፍራታቸውን ገልፀው ጋብቻው ፈርሶ የጋራ ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ እንዲወሰንላቸው ወይም ከአመልካች ጋር ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የነበራቸውንና ንብረት ያፈሩ መሆኑን ጠቅሰው የንብረት ክፍፍል ውሣኔ እንዲሰጥ ዳኝነት ጠይቀው ለማስረጃነትም የተለያዩ የሰነድና የሰው ምስክሮችን የዘረዘሩና የተሰሙላቸው መሆኑን አመልካች በበኩላቸው ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ግንኙነት የባለአክሲዩንነትና የጥብቅና አገልግሎት ውክልና ውል ከመሆኑ ውጪ ጋብቻ ወይም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አለመሆኑን ጠቅሰው ይልቁንም አመልካች ከሚች አቶ አያሌው ተድላ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ የነበራቸው መሆኑ የሚታወቅ መሆኑን ገልጸው መከራከራቸውን ለማስረጃነትም የተለያዩ በተጠሪ የተቆጠሩ ሰነዶችና የሰው ምስክሮችን የቆጠሩና የተሰሙላቸው መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ክስ ሲመሠርቱ ሁለት የተለያዩ የግንኙነት አይነቶች ከአመልካች ጋር የነበራቸው መሆኑን እየገለጹ ይህንንም ክስ ላሻሸል በሚል ምክንያት ከአንዱም ሶስት ጊዜ የጠቀሱ መሆኑንም ከሰር ፍርድ ቤት መዝገብ የተመለከትን ሲሆን ተጠሪ ለማስረጃነት ከቆጠሯቸው እና አመልካችም ለመከላከያነት ይጥቀሙኛል ብለው ከጠቀሷቸው የሰነድ ማስረጃዎች መካከል ተጠሪ ከአቶ አያሌው ተድላ ጋር ሐምሌ 12 ቀን 1960 ዓ.ም ጋብቻ ፈፅመው ሲኖሩ አቶ አያሌው ተድላ ከዚህ አለም መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም በሞት መለየታቸውን በግንኙነቱ ወቅትም ልጆችን የወለዱ መሆኑን ገልፀው የሚች ሚስትነታቸው ልጆቹ ደግሞ የሚች የመጀመሪያ ደረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ለፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አጣርቶ ተጠሪ ከሐምሌ 12 ቀን 1960 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ የሟች አቶ አያሌው ተድላ ሕጋዊ ሚስት የነበሩ መሆናቸውን ገልፆ ሚስትነታቸውን የልጆችን የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነታቸውን አረጋግጦ ማስረጃ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት ባሰሙት የቃል ክርክር ይኸው ማስረጃ በራሳቸው ጥያቄ የተሰጠ መሆኑን ሳይክዱ ማስረጃውን የጠየቁበት ዓላማ የልጆችን ወራሽነት በማረጋገጥ የሟችን ንብረት ለልጆች ጥቅም ለማስከበር አስበው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንግዲህ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ከላይ የተመለከቱት ሲሆን እኛም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር አዛምደን በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ከአመልካች ጋር ተጠሪ የነበራቸው ግንኙነት እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰ ሲሆን ይህ ችሎትም እንዲመለከተው የተያዘው አንዱ ጭብጥ ይኸው ግንኙነት አለ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆኑን አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ሁለት የተለያዩ ግንኙነቶችን በመጥቀስ የቀረበ መሆኑ በራሱ ከክስ አመሠራረት መርህ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ሥነ ስርዓታዊ መሆን ያለመሆኑ ጥያቄ የሚያስነሳ ቢሆንም ይህንኑ ከመመልከት በማለፍ በስር ፍርድ ቤት አለ የተባለው ግንኙነት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ያገናዘበ መሆኑን ያለመሆኑን መመልከቱ የተሻለ ሆኖ እግኝተናል፡፡

በመሠረቱ ጋብቻ ስለመፈፀሙ በቀዳሚነት ሊቀርብ የሚገባው የጋብቻ ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 94 ድንጋጌ ሲያስቀምጥ ጋብቻ ስለመኖሩ ይኸው ማስረጃ ከሌለ የጋብቻ ግንኙነት ስለመኖሩ በትዳር ሁኔታ ማረጋገጥ ስለመቻሉም የተጠቀሰው ሕግ በአንቀጽ 95 ደንግጓል፡፡ ይህ የጋብቻ መኖር አለመኖርን በተመለከተ ሊቀርብ የሚገባው የማስረጃ አይነትና ቅደም ተከተሉ ነው፡፡ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ስለመኖሩ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ግን ጉዳዩን ለማስረዳት የሚቀርበውን ቀዳሚ የማስረጃ አይነት በሕጉ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ለማስረዳት የሚቀርበው ማስረጃ የፍሬ ነገር ጉዳይ በመሆኑ ግንኙነቱን በማሳየት ብቻ ማስረዳት ይቻላል፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 106/2/ ድንጋጌ ሲታይም ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ለሚኖሩ ሰዎች የሚፈለገው ማስረጃ ወንዱና ሴትዩዋ የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው የሚገምቷቸው መሆኑን ማሳየት እንደአለበት ያመለክታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ ራሳቸው ለፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 92 መሠረት እውነትነቱን አረጋግጠው ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ከሟች አቶ አያሌው ተድላ ጋር ከሐምሌ 12 ቀን 1960 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሳስረው ጋብቻው በሞት እስከ ፈረሰበት እስከ መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ይኖሩ የነበሩ መሆኑ የተጠቀሰ ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ የቀረበውን አቤቱታ አረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጥ የተጠየቀው ፍርድ ቤትም ይህንኑ አረጋግጦ ተጠሪ እስከ መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ የሟች አቶ አያሌው ተድላ ሚስት የነበሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መስጠቱን የሚያሳይ ውሣኔ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ ይህ የፍርድ ቤት ውሣኔ የማስረጃ ዋጋ ሳይሰጠው የሚታለፍበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያስሟቸው በርካታ ምስክሮችም ቢሆኑ እንደተጠሪ የክስ አመሰራረት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጋብቻ በባህላዊ ሥርዓት የፈጸሙ መሆኑን እናውቃለን በማለት ጊዜውን ቦታውንና የአፈፃፀሙን ሥርዓት አልመሰከሩም፡፡ በምስክሮቹ ቃል የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ በጥቅሉ ሲታይ ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደባልና ሚስት የሚገምቷቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚች ጋር ጋብቻ ፈጽመው ይኖሩ የነበረ መሆኑን ራሳቸው እያረጋገጡና ምስክሮቻቸውም ከአመልካች ጋር እንደባልና ሚስት ይኖሩ የነበሩ ስለመሆኑ ሳያረጋግጡ በፍርድ ቤት የሚስትነት ማስረጃ ጥያቄ ያቀረብኩት ከሚች ለተወለዱት ልጆች የውርስ ጥያቄ መብት ለማስከበርና ለንብረት አስተዳደር ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ምክንያት ሆኖ አግኝተናል፡፡ አንዲት ሴት ከአንድ ወንድ ጋር በሕግ አግባብ ጥበቃ የሚደረግለትን ጋብቻ በመሰረተችበት ጊዜ ከሌላ ወንድ ጋር እንዳባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አላት ተብሎ ይኸው ግንኙነት በሕግ ጥበቃ የሚደረግበት በቂና ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከ1980 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1987 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ከአመልካች ጋር ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ ሲኖሩ ነበር በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ጋብቻ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት ተቋም መሆኑንና ከጋብቻ ውጪ እንዳባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በሕጉ ጠበቃ የሚደረግለትን ሁኔታ ባግባቡ ያላገናዘበ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ጋር ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 25 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ መስርቼ ነበርኩ የሚሉት ግንኙነት በሕጉ አግባብ ጥበቃ የማይደረግለት መሆኑን ከላይ በተመለከተው ምክንያት ድምዳሜ ከያዝን ከመጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ የነበረው ግንኙነትን አይነቱንና ውጤቱን መመልከቱ የግድ ይሆናል፡፡ አመልካች በዚህ ጊዜ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ሲታይ ተጠሪ ከሚች አቶ አያሌው ተድላ ጋር የመሠረቱት ጋብቻ በሞት የፈረሰበት ወቅት ነው፡፡ አመልካች በተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችም ተጠሪን በሚስትነት የሞሉ መሆኑ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን በአመልካች ስም በተከፈቱ መዝግቦች ላይ ተረጋግጧል፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች በስር ፍርድ ቤቶች ታይተው ሊሰጣቸው የሚገባው ክብደት ተሰጥቷቸው አመልካች ሊያስተባብሉ አለመቻላቸው ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከመጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ያለው የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ነው ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች የተደመደመው የውሣኔ ክፍል የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የነበረው ከመጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም በኃላ እስከ 1996 ዓ.ም ነው ብለናል፡፡

ውጤቱን በተመለከተ ተጠሪ ከአመልካች ጋር አፍርተናል የሚሉት መኖሪያ ቤት የተፈራው ከመጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም በፊት ቦታው በ1975 ዓ.ም በአመልካች ተገኝቶ የቤቱ ግንባታ ፈቃድም በ1979 የተሰጠ መሆኑ እንዲሁም ቤቱ የተሰራው በ1980-1984 ዓ.ም ድረስ ባሉት ጊዜያት መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪ መኖሪያ ቤቱን ከአመልካች ጋር የሚካፈሉበት ምክንያት የለም፡፡ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በንብረት ላይ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው እንደባልና ሚስት አብሮ የሚኖሩት ሰዎች ከሶስት አመታት ላለነሰና ከዚያ በላይ አብሮ ሲኖሩና ንብረቱ በዚህ ጊዜ የተፈራ መሆኑ መረጋገጡ ሲታወቅ መሆኑን የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 102 ያሳያል፡፡ በመሆኑም በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው አጠራር በወረዳ 23 ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 1317 የሆነው በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ በኖሩበት ጊዜ ውስጥ ሳይሆን ቀድሞ የተፈራ በመሆኑ ተጠሪ ሊካፈሉ የሚገባበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 37094 የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁጥር 78790 ጥቅምት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ድረስ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አልነበረም ብለናል፡፡

3. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የነበረው ከመጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም በኃላ ሆኖ እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ነው ብለናል፡፡

4. በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው አጠራር በወረዳ 23 ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 1317 የሆነና በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ሊካፈሉ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡

5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ፍቃዱ ሽፈራው - ቀረቡ

መልስ ሰጪ፡- አቶ ግሩም ኤርሚያስ - ጠበቃ ወርቅነህ በረደድ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ስለውርስ ንብረት ክፍፍል የተደነገጉትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አተረጓጎምን የሚመለከት ነው፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ነገር ሟች ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየሱስ ሚያዚያ 08 ቀን 1998 ዓ.ም የተውት ኑዛዜ ነው፡፡ አመልካች የሟቿ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ፣ተጠሪ ደግሞ የሟቿ የልጅ ልጅና የኑዛዜም ወራሽ መሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አሁን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ሟች የተውት ኑዛዜ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ሟች ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየሱስ የተውት ኑዛዜ የሕጉን ፎርማሊቲ ያልጠበቀና ከውርስ የነቀለኝ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል፣ ተጠሪ የሟቿ የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 እና 360 መሠረት ሊሰረዝ የሚገባው ነው በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ኑዛዜው በሕጉ የሚፈለገውን ፎርማሊቲ ያሟላ ከመሆኑም በላይ ሟች ለአመልካች ብር 100.00 /አንድ መቶ / እንዲሰጣቸው በኑዛዜው ላይ የተገለፀ በመሆኑ አመልካችን ከውርስ ነቅሏል ሊያስብል የሚችል አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ኑዛዜው ፎርማሊቲውን ያሟላ ነው፣ አመልካች ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ እንዲሰጣቸው ሟች የተናዘዙ መሆናቸው ደግሞ ከውርስ ነቅለዋል ለማለት የሚያስችል አይደለም የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ ተጠሪ የሟች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው በማለት የሰጠውን ውሣኔ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ሲሆን የአቤቱታው መሠረታዊ ነጥብም ሟች ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየሱስ የተውት ኑዛዜ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የሆኑት አመልካች ከውርስ የነቀለና የጎዳ በመሆኑ ሊፈርስ የሚገባው ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም የሰበር አቤቱታውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመመርመር አመልካች በኑዛዜው ላይ ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ ብቻ ያገኛል ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 ድንጋጌ አንፃር ተገቢነቱ ሊታይ የሚገባ መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ከአዘዘ በሁዋላ ለተጠሪ ጥሪ አድርጎላቸው ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከውርስ ሕጉ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮአል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች ወ/ሮ በላየነሽ ገ/እየሱስ ሚያዚያ 08 ቀን 1998 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በፎርማሊቲ በኩል ፈራሽ ሊያደርገው የሚገባ ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ እና አመልካችም በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊ አይደለም በማለት ያቀረቡት የሰበር ክርክር የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ ኑዛዜው የሕጉን ፎርማሊቲ ያሟላ ነው ከተባለና በኑዛዜ አንድ ወራሽ አለአግባብ ተነቀለ የሚባል ቢሆን በውርሱ አከፋፈል ላይ የሚታይ እንጂ በአግባቡ የተሰጠን ኑዛዜ ፈራሽነት የሚያስከትል የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ የኑዛዜ ስጦታው የፀና መሆን በውርስ ክፍፍሉ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ይህን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ተያያዥነት ያላቸውን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መመለከት ያስፈልጋል፡፡ አሁን ከያዝነው ጉዳይ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 913 ሲሆን ይህ ድንጋጌ የኑዛዜው ቃል የተናዛዥን ተቃራኒ ሐሣብ የሚገልጽ ካልሆነ በቀር ከውርስ ሃብት አንድ ድርሻን ወይም አንድ ንብረትን ሟቹ ለወራሾች መስጠቱ ተራ የሆነ የክፍያ ደንብ እንጂ እንደ ኑዛዜ ስጦታ ነው ተብሎ አይቆጠርም በማለት ያስቀምጣል፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይ ሟች አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኘውንና ብቸኛ ንብረት የሆነውን ቤታቸውን በኑዛዜው ይሰጥልኝ ያሉት የእህት የልጅ ልጅ ለሆነው ለአሁኑ ተጠሪ ሲሆን ልጅ ለሆነው የአሁኑ አመልካች ደግሞ በተጠሪ ብር 100.00/ አንድ መቶ/ ብቻ እንዲሰጣቸው ነው፡፡ ተጠሪ የሟች እህት ልጅ ልጅ በመሆናቸው ክርክሩ የሚያረጋግጥ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 ስር የተመለከተው ድንጋጌ መሠረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1117 በመሆኑ በዚህ አግባብ የሚታይ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም አሁን የቀረበው ክርክር በተወላጆች መካከል አይደለምና፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ በዚህ ረገድ የተያዘውን ጭብጥ አልፈነዋል፡፡ በጭብጥነት ተይዞ መታየት ያለበት ጉዳይ አመልካችን ሟች ከውርስ ነቅለዋል ሊባል ይቻላል? ወይስ አይቻልም?፣ ነቅለዋል ከተባለስ ተግባሩ በሕግ ፊት ተቀባይነት አለው? ወይንስ የለውም? የሚሉት ነጥቦች ሁነው አግኝተናል፡፡

ከቀረበልን ጉዳይ ለመገንዘብ እንደቻልነው ሟቿ ኑዛዜአቸው ላይ ያሏቸውን ንብረቶች በሙሉ የሰጡት ለተጠሪ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ክፍፍል ሕጉ የሚደግፈው ቢሆንም አንድ ወላጅ ተወላጅን ከውርሱ ያለሕጋዊ ምክንያት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሲነቅል ግን ተቀባይነት ሊኖረው የማይችል መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 937፣938 እናና 939 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ /ነጥብ/ ነው፡፡ ሟች ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየስ ልጃቸው የሆኑትን አመልካችን ካላቸው ንብረታቸው ብር 100.00 /አንድ መቶ/ ብቻ እንዲሰጣቸው በኑዛዜው ላይ ገልፀዋል፡፡ ሟች ተጠሪ እንዲወስዱ የተናዘዙት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የማይንቀሣቀስ ንብረት ነው፡፡ ከዚሁ ንብረት አይነትና ካለው ዋጋ አንፃር ሲታይ ሟች በኑዛዜው ላይ ለአመልካች ብር 100.00

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብቻ እንዲሰጣቸው መጥቀሣቸው ከውርሱ በተዘዋዋሪ ነቅለዋቸዋል ከሚባል በስተቀር ሌላ ምክንያት ሊሰጠው የሚችል ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ሟች አመልካችን በተዘዋዋሪ ነቅለዋል ከተባለ ደግሞ የነቀሉበት ምክንያት በቂና ሕጋዊ መሆን ሊታይ የሚገባው ሲሆን ሟች በዚህ ረገድ በኑዛዜው ላይ ያስቀመጡት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በተዘዋዋሪ መልኩ በገዘምታ ከሟቿ ውርስ የነቀሉ መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ወላጅ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ወይም በገዘምታ ከነቀለም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት ከውርስ በገዘምታ ወይም ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሁነው የውርስ ንብረቱን ሊከፋፈሉ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ ወደዚህ ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት በወላጅ የተደረገ የኑዛዜ ስጦታ አይነቱ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ መሆን ያለመሆኑን በቅድሚያ መለየት አለበት፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912 ስር እንደተመለከተው የኑዛዜ ስጦታ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ሲባልም ተናዛዡ ሀብቱን ጠቅላላ ወይም ከመላ ንብረቱ አንዱን ክፍል በሙሉ ሀበትነት ወይም በሌላ ርስትነት ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች የሚያወርስበት የኑዛዜ ቃል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912/1/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ማንኛውም ሌላ የኑዛዜ ቃል ሁሉ እንደ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡ አንድ ኑዛዜ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014 ድንጋጌ ቅደም ተከተል መሠረት የሚከፈል ይሆናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየስ የነበራቸውን አንድ መኖሪያ ቤት ለአሁኑ ተጠሪ እንዲሆን በኑዛዜ ስጦታ ሰጥተዋቸዋል፡፡ ሌሎች ንብረቶች ያላቸው መሆኑን የክርክሩ ሂደት አያሣይም፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንፃር ተናዛዢ ያደረጉት ኑዛዜ ስጦታ አይነቱ ሲታይ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ እንጂ ልዩ የሆነ የኑዛዜ ስጦታ አይደለም ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014/ሠ/ ስር በተመለከተው መሠረት እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ ለልዩ ኑዛዜ ተቀባዩ የሚከፈል ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ድንጋጌዎች ታይቶ ተወላጅ ከውርስ ተነቅሏል፣ ከኑዛዜ ተቀባዩ ጋር እኩል ሊካፈል ይገባል ሊባል የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ወ/ሮ በላይነሽ ገ/እየስ ያደረጉት ኑዛዜ አመልካችን በተዘዋዋሪ መንገድ ከውርስ የነቀለ መሆኑን በመለየት የኑዛዜ ስጦታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912፣ 915፣937፣938 እና 939 አንፃር በማየት መወሰን ሲገባቸው የአመልካችን ጥያቄ ሙሉ ሙሉ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 51/2001 መጋቢት 09 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09721 መጋቢት 23 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ፡ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 10029 ጥር 28 ቀን 2002 ዓ.ም በውሣኔ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአጠቃላይ ፍርስ ባይሆንም ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተጠቀሰው መሠረት አመልካችና ተጠሪ የሚችን ንብረት እኩል የመውረስ መብት አላቸው ብለናል፡፡
3. የስር ፍርድ ቤት ውሣኔው መሻሻሉን እንዲያውቀው የውሣኔው ኮፒ ይላክለት፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ 1. ወ/ሮ ጸሐይ ተሰማ
2. ወ/ሮ አለምነሽ ተሰማ
ጠበቃ ታደሠ ወ/ጊዮርጊስ ቀረበ

ተጠሪ፣ ህፃን አማኑኤል ወንድወሰን ሞገዚት ወ/ሮ ብርሃኔ ባየህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጋብቻ ውል አንዱ ተጋቢ ለሌላው ተጋቢ የማይንቀሳቀስ ንብረት አጠቃቀምን የሚመለከት መብት በሕይወት ለሚቀረው ተጋቢ እስከ እለተሞት ድረስ እንዲጠቀምበት በማለትና በሕግ አግባብ ተወላጅ ያልሆነውን ሰው የድርሻ ንብረቱ ተጠቃሚ በማድረግ ውል ገብቶ ሲገኝ ስለሚኖረው ውጤት የሚመለከተውን ክርክር መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ሞገዚት በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አቶ ታፈሰ ተፈራ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን የአቶ ታፈሰ ተፈራ ልጅና የህፃን አማኑኤል እናት የሆኑት ወ/ሮ ትዕግስት ታፈሰም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን ህፃኑ የወላጅ እናቱ ወራሽ መሆኑና ሞገዚትም የተሾመለት መሆኑን ህፃኑ ወላጅ እናቱን በመተካት አያቱን መውረስ እንደሚገባው አቶ ታፈሰ ተፈራ በሕይወት እያሉም በአዲስ አበባ ከተማ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ውስጥ ቁጥሩ 1011 የሆነና በስማቸው የተመዘገበ መኖሪያ ቤት ያፈሩ መሆኑን ይህን ቤት የአሁኑ አመልካቾች ይዘው በማከራየት እየተጠቀሙ እንደሚገኙና ለማካፈልም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልፀው የቤቱን ግምት ግማሽ 50,000.00 /ሃምሳ ሺህ ብር/ እንዲያካፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስም አከራካሪው ቤት የ1ኛ አመልካችና የሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ መሆኑን ሳይክዱ ሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ እና 1ኛ አመልካች የጋብቻ ውላቸውን ሲያድሱ ቤቱን 1ኛ አመልካች በሕይወት እስካሉ ድረስ እንዲጠቀሙና ከሣሽ ሞገዚት አድራጊ እናትና 2ኛ አመልካች ከ1ኛ አመልካች ሕይወት ፍጻሜ በኋላ የሟች ድርሻን እንዲተላለፍላቸው መስማማታቸውን ይህንኑ በመገንዘብና የጋብቻ ውሉን በማክበርም የሕጻኑ እናት በሕይወት እያሉ ጥያቄ ሳያቀርቡ የቆዩ መሆኑን 2ኛ አመልካችም በቤቱ ውስጥ ያሉት በቤተሰብነት መሆኑንና ቤቱ የሚከራየውም በብር 550.00 ሳይሆን በብር 350 መሆኑን በመግለፅ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር በመመርመር የጋብቻ ውሉ በሶስተኛ ወገን ላይ ግዴታ ሊጥል የሚችል ሊሆን አይገባም በሚል ምክንያት የ1ኛ አመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገ ሲሆን 2ኛ አመልካችን በተመለከተ ደግሞ ልጅ ስላልሆኑ ሟች አቶ ታፈሰ ተፈራን ሊወርሱ አይገባም፣ ተጠሪ ሟችን እናታቸውን ተክተው መውረስ የሚችሉ ናቸው በማለት አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ግማሹ የተጠሪ በመሆኑ ከተቻለ በአይነት ለሁለት ተከፍሎ ግማሹ ለተጠሪ ግማሹ ደግሞ ለ1ኛ አመልካች ይኸው ካልተቻለ ግን ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ የሽያጭ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራቀኙ ከተከራከሩ በኃላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 46ን የተረጎመው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826/2/ ጋር አዛምዶ ባለመመልከት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ቀርበው የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ ሕጋዊነት በመግለፅ ሊፀና ይገባል ሲሉ ሕዳር 08 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች ታህሣሥ 08 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤተታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ 1ኛ አመልካች ከሟች ታፈሰ ተፈራ ጋር በጋብቻ ተሳስረው ሲኖሩ አከራካሪ የሆነውን ቤት በጋራ ያፈሩ መሆኑን ሟች አቶ ተፈራ ታፈሰ በህይወት በነበሩበት ጊዜ ግንቦት 05 ቀን 1986 ዓ.ም ከ1ኛ አመልካች ጋር ባደረጉት "የጋብቻ ውል እድሳት ስምምነት" በሚል ሰነድ 1ኛ አመልካች ዋናውን ሶስት ክፍል ቤትም ሆነ ሰርቪሶቹን ከአቶ ታፈሰ ተፈራ ሞት በሁዋላ እድሜዋ እስከፈቀደላት ድረስ የግልዋ ሆኖ ለመሸጥም ሆነ ለመለወጥ ከፈለገች ግን የአሁኑ ተጠሪ እናት የሆኑት ሟች ትዕግስት ታፈሰና የአሁኗ 2ኛ አመልካችን በመያዝ መለወጥም ሆነ መሸጥ ትችላለች ልጆቹም እናታቸው እስካሉ ድረስ ንብረቱን በሙሉ የእናታቸው የግልዋ መሆኑን አውቀው መቀመጥ አለባቸው በማለት መግለፃቸውን ነው ይህ ሰነድ ስለመኖሩም የተካደ ነገር አይደለም ተጠሪም ሟች አያቱን በተተኪነት መውረስ የሚችል ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የሰነዱን መኖርና በሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ መደረጉን በመቀበል ሕጋዊ ውጤት የለውም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 46/1/ን በዋቢነት በመጥቀስ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታ ሊጥል አይችልም በሚል ምክንያት ስለመሆኑም ከውሣኔው ግልባጭ ተመልክተናል፡፡ ይህንኑ ግንዛቤ በመውሰድም የሰነዱን ይዘት ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ሊኖረው የሚገባውን ውጤት መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጋብቻ ውል ሕጋዊ ድርጊትና ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል መሆኑን የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 40 እና ተከታዩቹ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባሉ የጋብቻ ውል ከሚያስከትላቸው ሕጋዊ ውጤቶች መካከል አንዱ በተጋቢዎች የንብረት ግንኙነት ላይ ስለመሆኑ የተጠቀሰው አዋጅ በአንቀጽ 42/1/ ድንጋጌ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ በጋብቻ ውል የተቋቋሙ አንዳንድ ውጤቶችም በውል ሊቀሩ ወይም ሊሻሻሉ እንደሚችሉ ተጠቃሹ ሕግ በአንቀጽ 40 ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሆን ይህ ተግባር በሕግ ፊት ውጤት የሚኖረው በአንቀጽ 73 አግባብ ሲደረግ ነው እንዲሁም የአዋጁ አንቀጽ 46/1/ ድንጋጌ ሲታይም ተጋቢዎች በጋብቻቸው ውል ውስጥ በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታን የሚያስከትሉ ስምምነቶችን ማድረግ አይችሉም በሚል ተቀምጧል የስር ፍ/ቤት የጋብቻ ውል አፈፃፀሙንና ውጤቱን በተመለከተ ሊኖረው ስለሚገባ ሥርዓት ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ከተገነዘበው በሁዋላ በአሁኗ 1ኛ አመልካችና በሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ መካከል ግንቦት 05 ቀን 1986 ዓ.ም የተደረገ የጋብቻ ውል እድሳት ስምምነት ውጤት ሊኖረው አይገባም በማለት ውድቅ ያደረገው በሶስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታ በሚያስከትል መልኩ ስምምነቱ ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሶስተኛ ወገን የተባለው በጉዳዩ ላይ ክርክር ያቀረበው የአሁኑ ተጠሪ የሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ ተተኪ ወራሽ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826/2/ መሠረት ተተኪ ወራሽ ሊተላለፍለት የሚችለው አውራሽ የነበረው ግዴታና መብት ሆኖ አውራሽ በመሞቱ ምክንያት ሊቋረጡ የማይችሉ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ወራሽ ሊሰራበት የሚችለው መብትና ግዴታ አውራሽ በሚኖረው መብትና ግዴታ መጠን ነው ይህም የሚያሳየው ወራሽ አውራሹ በሚያደርጋቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ውስጥ አውራሹን ተክቶ የሚሰራ ከአውራሹ ጋር ተመሳሳይ አቋም ያለው መሆኑን እንጂ አውራሹ ለፈጸማቸው ድርጊቶች ሶስተኛ ወገን ሊባል የሚገባ አለመሆኑን ነው በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 46/1/ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826/2/ እና 842 ጋር በማዛመድ ሳይመለከተው ተጠሪን እንደሶስተኛ ወገን መቁጠሩ ያላግባብ ሆኖ ተገኝቷል ይህ ሰነዱ የጋብቻ ውል አይደለም እንጂ ነው እንኳ ቢባል ሊደርስበት የሚችለው ድምዳሜ ነበር፡፡

ከሁሉም በላይ በሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ እና በአሁኗ 1ኛ አመልካች መካከል ግንቦት 05 ቀን 1986 ዓ.ም የተደረገው "የጋብቻ ውል እድሳት ስምምነት" የሚል ርዕስ የተሰጠው ሰነድ ይዘቱ መታየት ያለበት እና የውሉ አይነት ተለይቶ በየትኛው የሕግ ክፍል መገዛት አለበት? የሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የጋብቻ ውል ሕጋዊ ድርጊትና ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል ሲሆን ውጤቱ በተጋቢዎች የግል ወይም የንብረት ግንኙነት ላይ መሆኑን በዚህ ረገድ የተደነገጉት የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ የጋብቻ ውል ውጤት የሚኖረውም ተጋቢዎች በጋብቻ ላይ ፀንተው ባሉበትና ጋብቻም ከፈረሰ በኋላ ሊሆን እንደሚችል በስምምነቱ ሊወሰን የሚችል መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ግን ሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ ከአሁኗ 1ኛ አመልካች ጋር የጋብቻ ውል እድሳት ስምምነት የሚል ሰነድ ያደረጉት የጋራቸውን የሆነውን ቤት ከራሳቸው ሕልፈተ ሕይወት በኃላ 1ኛ አመልካች በግላቸው እንዲጠቀመበት ነው፡፡ በስምምነቱ መሠረት 1ኛ አመልካች ላይ ወይም በሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ ላይ ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ስለቤቱ አጠቃቀም 1ኛ አመልካች ያገኙት ልዩ መብት የለም በሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ ላይም የተጣለ ገደብ የለም፡፡ አቶ ታፈሰ ተፈራ በቤቱ ካላቸው ሰፊው የባለቤትነት መብት ለ1ኛ አመልካች ከራሳቸው ፍፃሜ ሕይወት በኃላ የሰጡት የመጠቀም መብታቸውን ብቻ ነው፡፡ በስምምነት ሰነዱ ላይ 1ኛ አመልካች ቤቱን ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ ከፈለጉ የአሁኗን 2ኛ አመልካችንና የህፃን አማኑኤል ወንድወሰን እናት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሆኑትን ሚች ትዕግስት ታፈሰን በመያዝ ስለመሆኑ መጠቀሱ 1ኛ አመልካች የተሰጣቸው በቤቱ የመጠቀም መብት ብቻ ስለመሆኑ አስረጂ ነው በመሆኑም የስምምቱ ይዘት ሲታይ በሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ ላይ በሕይወት እያሉ የሚጥለው ግዴታ የሌለ መሆኑና 1ኛ አመልካችም በቤቱ ላይ የመጠቀም መብታቸው የሚኖረው አቶ ታፈሰ ተፈራ ከሞቱ በኃላ መሆኑን የሚያስገነዝብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲህ ከሆነ ስምምነቱን የሚገዛው የትኛው የህግ ክፍል ነው? የሚለው ጥያቄ ተያይዞ የሚነሳ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2427 ድንጋጌ ሲታይ ስጦታ ማለት አንድ ወገን ተዋዋይ ማለትም ሰጪው ተቀባይ ተብሎ ለሚጠራው ለሌላ ሰው ችሮታ በማድረግ አሳብ ከንብረቶቹ አንዱን የሚለቅበት ወይም ግዴታ የሚገባበት ውል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ስጦታ ደግሞ ሰጪው ሲሞት ይፈፀማል ተብሎ ሊደረግ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል ይህንኑ መሠረት አድርገን ሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ እና 1ኛ አመልካች ግንቦት 05 ቀን 1986 ዓ.ም ያደረጉትን ስምምነት ይዘት ስንመለከተው በሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ ላይ በሕይወት እያሉ ምንም ግዴታ የማይጥል ከሕልፈተ ሕይወታቸው በኃላም ቢሆን 1ኛ አመልካች ሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ ካላቸው ንብረቱን የማውደም የመጠቀምና የማስተላለፍ ሰፊ የባለቤትነት መብታቸው ውስጥ ቤቱን የመጠቀም መብታቸውን ብቻ ተግባራዊ ሲያደርጉ በ1ኛ አመልካች ላይ ግዴታ የማይጥል ችሮታ ላይ የተመሠረተ እንዲሁም 1ኛ አመልካች የሚች አቶ ታፈሰ ተፈራን ድርሻ የመጠቀም መብት ተግባራዊ የሚያደርጉት ከአቶ ታፈሰ ተፈራ ሕልፈተ ሕይወት በኃላ መሆኑ የተጠቀሰበት በመሆኑ ሰነዱ የስጦታ ሰነድ ሊባል የሚገባ እና ስለስጦታ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የሚገዛ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የሰነዱን ይዘት በአግባቡ ሳያገናዝብ የጋብቻ ውል እድሳት ስምምነት በሚል በአርእስትነት በመቀመጡ ብቻ ሰነዱ የጋብቻ ውል ነው ወደሚለው ድምዳሜ መደረሱም ተገቢ ሆኖ አለገኘነውም፡፡ እንግዲህ ስምምነቱ ሲታይ የስጦታ ውል ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያደረሰን ሲሆን ውሉ የሚኖረው ውጤት በዚህ ረገድ የተደገጉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መልስ የሚያገኝ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ሰጪው ሲሞት ይፈፀማሉ ተብለው በተወሰኑት ስጦታዎች ላይ ስለኑዛዜ የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈጻሚዎች እንደሚሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 ስር በግልፅ ተደንጓል፡፡ በመሠረቱ ኑዛዜ የሚቹ ጥብቅ የሆነ ራሱ የሚፈፅመው ስራ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 857/1/ ስር የተመለከተ ሲሆን ኑዛዜው የሚሻርበትንና በሕግ ፊት ውድቅ የሚሆንበትን ምክንያት ሕግ አውጪው አስቀምጧል፡፡ ኑዛዜ ሰጪ ኑዛዜ ሊያደርግ የሚችልበት ሥርዓትም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881፣ 882 እና 884 ስር ተመልክቷል፡፡ ኑዛዜ አድራጊ በሕጉ በተመለከቱት መንገዶች መሠረት ንብረቱን ለስጋ ዘመዱ ወይም የስጋ ዘመድ ላልሆነው ሊያስተላልፍ የሚችልበት አግባብም በሕጉ ጥበቃ የተደረገለት ተግባር ነው፡፡ ከዚህም በላይ ኑዛዜ ገደብ ያለበት ሆኖ ሊደረግ እንደሚችልም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 916 ስር ተመልክቷል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ እና 1ኛ አመልካች ግንቦት 05 ቀን 1986 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 መሠረት በኑዛዜ ድንጋጌዎች የሚገዛ ሆኖ በአፃፃፍ ሥርዓቱም ሆነ በውጤቱ ሕጋዊ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም 1ኛ አመልካች እስከ እለተሞታቸው ድረስ ቤቱን የመጠቀም መብታቸው የሚያጡበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ 2ኛ አመልካች ደግሞ ከሚች አቶ ታፈሰ ተፈራ የማትወለድ ቢሆንም ሚች ከድርሻቸው እንዲሰጣት ሕጋዊ ስጦታ እስካአደረጉላት ድረስ ከተጠሪ ጋር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 እና 915 ድንጋጌዎች መሠረት እንደአንድ ወራሽ ተቆጥረው እኩል ተጠቃሚ የማይሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረት የ1ኛ አመልካችን የመጠቀም መብት የ2ኛ አመልካችን ደግሞ በስጦታ የተሰጣቸውን የሚች ድርሻ ግማሽ የማግኘት መብታቸውን ማሣጣቱ የስምምነት ሰነዱን ይዘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሕጉ ጋር ባላገናዘበና ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 63108 ሰኔ 03 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 82805 ሚያዚያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ሟች አቶ ታፈሰ ተፈራ ከ1ኛ አመልካች ጋር ግንቦት 06 ቀን 1986 ዓ.ም ባደረጉት የስጦታ ውል መሠረት 1ኛ አመልካች ወ/ሮ ፀሐይ ተሰማ በአከራካሪው ቤት የሟች ድርሻ ላይ እስከእለተሞታቸው ድረስ የመጠቀም መብት አላቸው 1ኛ አመልካች ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በሁዋላ ደግሞ 2ኛ አመልካች /ወ/ሮ አለምነሽ ታፈሰ/ ከተጠሪ /ህፃን አማኑኤል ወንድወሰን/ ጋር የሟች አቶ ታፈሰ ድርሻን የመውሰድ መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲቲ 11 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ጥሩወርቅ ወርዶፋ - ጠበቃ ብርሃኑ ወልደዮሐንስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጥሩነሽ ወርዶፋ - ጠበቃ ደጀኔ አባተ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ልጅነትን የሚመለከት ክርክርን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ የሚች አቶ ወርዶፋ በዳሳ ልጅነት ይረጋገጥልኝ በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ የሰጠው የልጅነት ማስረጃ በሐሰት የተሠጠ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ በአቤቱታቸው ላይም የአሁኑ ተጠሪ ከሚች አቶ ወርዶፋ በዳሳ እና ከወ/ሮ አፀደ ወ/ጊዮርጊስ ተወልጀአለሁ ያሉት ሐሰት ነው፣ ሕጋዊ ግንኙነት አልነበራቸውም፣ የአቶ ወርዶፋ በዳሳ ብቸኛ ልጅ አመልካች ነኝ፣ ተጠሪ የሚች ልጅ ነኝ የሚሉ ከሆነ የደም ምርመራ(DNA) ሊደረግ ይገባል በማለት ገልፀው ለተጠሪ የተሰጣቸው የልጅነት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ ተጠሪም ለአሁኗ አመልካች የመቃወም አቤቱታ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎም ባቀረቡት መከራከሪያ የሚቹ ልጅ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆኑንና የደም ምርመራም የመቃወም አመልካች ሊጠይቁ እንደማይችሉ ገልፀው የመቃወም አመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የ“DNA” ምርመራ ጥያቄን አልፎ የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የአመልካችን መቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ አድርጎ ተጠሪ የሚች አቶ ወርዶፋ በዳሳ ልጅ ናቸው በማለት የሰጠውን ውሳኔ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ የሚች ወርዶፋ ልጅ ናቸው ተብሎ የተሰጠው የልጅነት ማስረጃ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ የተወሰነው በተገቢው ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሲሆን የ“DNA” ምርመራ ጥያቄም የታለፈው ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ የሚች አቶ ወርዶፋ በዳሳ ልጅ ናቸው ተብሎ መወሰኑም ሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ“DNA” ምርመራ ጥያቄ የመታለፉን ተገቢነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ያቀረቡት በሳይንሳዊ መንገድ የደም ምርምራ ጥያቄ ታልፎ ተጠሪ የሚች አቶ ወርዶፋ ልጅ ናቸው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሚች አቶ ወርዶፋ በዳሳ ልጅ እና ወ/ሮ የሺመቤት አየነው በጋብቻ ተሳስረው የተወለዱ ስለመሆናቸው የተረጋገጠ ሁኖ በተጠሪ በኩል የቀረበ ማስተባበያ ክርክር የሌለ መሆኑን፣ ተጠሪ የሚቹ ልጅ ነኝ በማለት የሚከራከሩት ሚች እንደአባት በመሆን ሲንከባከቧቸው የነበረ በመሆኑና ይህም በማስረጃ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች የተጠሪን ማስረጃዎች ለማስተባበል በማስረጃነት እንዲቀርብላቸው ከሚፈልጉት ማስረጃዎች አንዱ ደግሞ ሳይንሳዊ የደም ምርመራ ዘዴ ነው፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን የማስረጃ ይቅረብልን ክርክር ሳያጠናቅቅ ማለፉን መዝገቡ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ የተጠሪ የሚች አቶ ወርዶፋ በዳሳ ልጅነት ተረጋግጧል የተባለው በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 143(ሠ) መሰረት ሲሆን በአንቀጽ 143 ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች አባትነት በፍርድ ሊነገር የሚገባቸው ሁኔታዎች መሆኑ፣ ከእነዚህ ሁኔታዎች ውጪ አባትነት በፍርድ ሊነገር የማይችል ስለመሆኑ የተጠቀሰው አዋጅ በአንቀጽ 145 ስር በግልፅ ደንግጓል፡፡ አዋጁ አባትነት በፍርድ ሊነገር የሚችልባቸው ሁኔታዎች ላይ ማስተባበያ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችለው በአንቀጽ 144 ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች ስለመሆኑ በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ደግሞ “ሣይንሣዊ” ደም ምርመራ አንዱ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ጥያቄ ያልተቀበለበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ በውሳኔው ላይ የገለጸው ነገር የለም፡፡ ይህ ደግሞ የፍርድ አካሄዱን የተሟላ ሳያደርግ ፍርድ የሰጠ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን አመልካች ሚቹ በሕጋዊ ጋብቻ ውስጥ የወለዷቸው ስለመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ከተጠሪ ጋር የደም ምርመራ ይደረግልኝ ብለው ያቀረቡት ክርክር የሚታለፍበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች የደም ምርመራ ጥያቄ የታለፈው ያላግባብ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 27962 ሐምሌ 16 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 97440 ጥቅምት 25 ቀን 2003 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በአመልካች ወጪ የአመልካችና የተጠሪ የ“DNA” ምርመራ እንዲካሄድ በማድረግ የሚቀርበውን ውጤት መሰረት አድርጎ ጉዳዩን እንደገና በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ እንዲሠጥበት ለፊዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሀመድ

አመልካች፡- አቶ ኃይሌ ስሙጋ - ጠበቃ አቶ መኸዲ ሁሴን ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሠላማዊት ተኮላ - ጠበቃ አቶ አንተነህ ተካልኝ ቀረቡ

መዝገቡን የቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ማየት የተሳነው ሰው የሚያደርገውን የኑዛዜ አደራረግ ሥርዓት በሚመለከት ግራ ቀኙ ያደረጉትን ክርክር ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሟች ወ/ሮ መሠረት መንገሻ ሚያዚያ 6 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉት የኑዛዜ ሰነድ ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪ ይኸው የኑዛዜ ሰነድ በፍ/ቤት እንዲፀድቅላቸው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ጉዳዮን ተመልክቶ በን/ላ/መ/ቁ/ 1806/99 ሚያዚያ 05 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተቀብሎ አፅድቆታል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሠረት የሟች ወ/ሮ መሠረት መንገሻ አባት ነኝ ሟች ልጅ የላትም ዓይነስውርና የስኳርና HIV/AIDS በሽተኛ የነበረች ስለሆነ በአዋዋይ ፊት ያልተደረገው የኑዛዜ ሰነድ ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡ ስለሆነም ቀደም ሲል ኑዛዜው ፀድቋል በሚል የተሰጠው ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪም ዓይነ ስውር፣ የስኳር እና የ HIV/AIDS በሽተኞች ኑዛዜ ማድረግ አይችሉም የሚል ህግ የለም ኑዛዜውን ሲያደርጉ አእምሯቸው ጤነኛ እንደነበር ይኸው ፍ/ቤት በምስክሮች አረጋግጦታል፡፡ ውሳኔው ሊሰረዝ አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የመቃወም አመልካችን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ

ድዳ፣ ደንቆሮ፣ ዕውር የሆኑና ነዋሪ በሆነ ደዌ ምክንያት እራሳቸውን ችለው ለመተዳደር ወይም ንብረታቸውን ለማስተዳደር ችሎታ ለሌላቸው ሰዎች ስለ አእምሮ ጎደሎዎች የተነገሩትን እርዳታዎች ለመጠየቅ ይችላሉ ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 ተደንግጓል፡፡ ሟችም አይነ ስውር እንደመሆናቸው መጠን የኑዛዜ ሰነዱን በእገዛ አይተውና ለይተው የፈረሙበት መሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልተረጋገጠም፡፡ ስለሆነም የኑዛዜ ሰነዱ ፀድቋል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 360(2) መሠረት ተሽሯል፡፡ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ ሟች ኑዛዜውን ሲያደርጉ አእምሯቸው ደህና የነበረ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱ ኑዛዜውን ሳያፀድቅ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፣ ዓይነስውር በአዋዋይ ፊት ኑዛዜ ማድረግ አለበት የሚል ህግ የለም የኑዛዜ አደራረግ ሥርዓት በልዩ የህግ ክፍል የተደነገገ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1728 ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የለውም የሚሉትን ነጥቦች መሠረት አድርገው ውሳኔው በይግባኝ እንዲታረም የይግባኝ አቤቱታ በማቅረባቸው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ባለበት ጉዳዩን ተመልክቷል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 ድንጋጌ ዓይነስውራን ድጋፍ ሊጠይቁ እንደሚችሉ እንጂ በአዋዋይ ፊት ያልተደረገ ኑዛዜ ፈራሽ ነው ብሎ በአስገዳጅነት አላስቀመጠም፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1728 ተፈፃሚነቱ ውሎች ላይ እንጂ ይህንን ጉዳይ አይመለከትም፤ በዚህ ጉዳይ የኑዛዜው አደራረግ የፎርማሊቲ ጉድለት አለት፣ አልተባለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ኑዛዜውን ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ቀርበው ያላደረጉት ስለሆነ አጠራጣሪ ነው በሚል ምክንያት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል ሲል ዳኝነት ሰጥቷል፡፡ የከተማው ፍ/ቤቶች ስበር ሰሚ ችሎት ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ የህግ ስህተት አልተገኘበትም የሚል የመጨረሻ ዳኝነት ስለሰጠበት ይህ የሰበር ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከዚህ በፊት በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች ከቀረቡት በይዘቱ የተለዩ አይደለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ግራ ቀኙን የሚያከራክራቸው የኑዛዜ ሰነድ በህግ ፊት የፀና ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

ኑዛዜ አድራጊዋ ሟች ወ/ሮ መሠረት መንገሻ ኑዛዜ ባደረጉበት ጊዜ ማየት የተሳናቸው የነበሩ ስለመሆኑም በግራ ቀኙ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

ማየት የተሳነው ሰው ኑዛዜ የማድረግ ተግባር ሲፈፀም ይህ ተግባር በህግ ፊት የፀና፤ ማናቸውንም ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል እንደሆነ በህግ መሟላት የሚገባቸው ነጥቦች ምን ምን ናቸው? በሚለው ነጥብ ላይ ነው የተለያዩት፡፡

ይህን አከራካሪ ነጥብ ለማስረዳት በግራ ቀኙ የቀረቡት የፍሬ ነገር ክርክሮች እና ጉዳዩን ለመወሰን የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ዳኝነት የጠቀሱት ትንታኔ በህግ ፊት የፀና ተግባር ለመፈፀም አስፈላጊ ሁኔታዎች ናቸው በሚል ህጉ በየቅል ያስቀመጣቸውን ማሟያ ሁኔታዎች አንዱን ከሌላው በማቀላቀል እየተጠቀሱ የቀረቡ እና የተተቹ መሆኑን ከውሳኔዎች ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

ይኸውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 ድውዮች በሚል ርዕስ በተቀመጠው ድንጋጌ ማናቸውንም ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ተግባር ለመፈፀም ችሎታ አስፈላጊ ነው፡፡ ችሎታ አለ ወይስ የለም? ማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚቻለው መቼ እና እንዴት ነው የሚለውን በዝርዝር በሚደነግገው ክፍል የሚገኝ ነው። ችሎታ ከዕድሜ፣ ችሎታ በከባድ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት፣ ችሎታ ከአእምሮ በሽታ ጋር በተያያዘ የእያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ በያዘው የህግ ክፍል የሚገኝ ሆኖ በተለይም በአእምሮ መጎደል ወይም በድውይነት የተነሣ አንድ ሰው የሚሠራው ተግባር ምን ውጤት እንደሚያስከትል የማያውቅ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ይህ ሰው ማናቸውንም ተግባር እንዳያከናውን በማድረግ በፍርድ በመከልከል በህግ ጥበቃ ከሚደረግበት ክፍል ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች በፍርድ ሊከለክሉ የሚገባቸው ስዎች የትኞቹ ናቸው የሚለውን ለመለየት በመሠረትነት ለተቀመጠው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 339 ቀጠሎ የሚገኝ ድንግጌ ነው። ድውዮችም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የአእምሮ ጎደሎነት እንዳለባቸው ሰዎች ተቆጥረው የፍርድ ክልከላ እንደሚደረግባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 351(3) መመልከቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 ድንጋጌ ይዘትና አስፈላጊነት አንድ ሰው ተግባሩን ለመፈፀም ችሎታ ነበረው ወይስ አልነበረውም የሚለውን ለመለየት እንጂ አካላዊ ጎዶለነት ያለባቸው ሰዎች ህጋዊ ተግባር ለመፈፀም በፈለጉ ጊዜ የአደራረጉ ሥርዓት በምን አኳኋን ሊፈፀም ይገባል ከሚለው ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት የለውም የሚሠሩት ሥራ ምን ውጤት እንደሚያስከትል የማያውቁ ሰዎች ስለሆኑ የፈፀሙት ተግባር ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? በማለት ያደረጉትን ተግባር ህጋዊነት (Validity) ለመመርመር መሠረት የሚሆን ድንጋጌ እንጂ እነዚህ ስዎች ተግባራቸውን የት? እና እንዴት ማከናወን አለባቸው ከሚለው የውል አደራረግ ሥርዓት ጋር የተዛመደ አይደለም።

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 368(1) የተከለከለ ሰው ክልከላው በፍርድ ከተነገረ በኋላ ኑዛዜ ለማድረግ አይችልም በሚል የተደነገገውን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 እና 351(3) ጋር በማገናዘብ ስንመለከተው ይህንኑ የትርጉም መስመር፣ ይበልጥ የሚያጠናክር ሆኖ ይገኛል።

እንደዚሁም ኑዛዜ ዋጋ እንዲኖረው የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች በሚለው ክፍል ችሎታ አስፈላጊ ከሆኑ የሥራ ነገር ሁኔታዎች አንዱ ሆኖ ኑዛዜ ለማድረግ ችሎታ ከዕድሜ አንፃር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 860፣ ችሎታ ለአእምሮ መጓደል ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 861 — 864 በዝርዝር መደንገጉና የኑዛዜ አደራረግ ሥርዓትን በማመልከት ግን እራሱን በቻለ የኑዛዜ ፎርምና ማስረጃ በሚል ንዑስ ክፍል መቀመጡ ኑዛዜ የሚያደርጉ እነማን ናቸው? ኑዛዜ የሚደረግበት ሥርዓት እንዴትና በምን አኳኋን ነው? የሚሉት ነጥቦች በየቅል የሚታዩና ጉዳዮቹን የሚገባው የህግ ክፍል በየነጥቦቹ አግባብ የተቀመጠ መሆኑ እየታወቀ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 የተመለከተውን ድንጋጌ ከውል አደራረግ ሥርዓት ጋር በማያያዝ የሰጠው ትንታኔ እና ትችት አግባብ ሆኖ አላገኘነውም።

ከዚህም አንፃር ሟች ወ/ሮ መሠረት መንገሻ ማየት የተሳናቸው መሆኑ ከመረጋገጡ በቀር በዚህ አካላዊ ጉድለት ምክንያት ለእራሳቸውም ሆነ ሌሎች መብታቸው የሚያከብሩላቸው ሰዎች ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል በፍርድ የተከለከሉ አይደሉም። በፍ/ብ/ሕ/ቁ 343(2) መሠረት በፍርድ ባይከላከሉም ድውይነታቸው አስራሪ የሆነውን ተግባር ለመፈፀም የሚያስችላቸው ነበረ ብሎ ከችሎታ ጋር በማያያዝ ለመተርጎምም መነሻ የሆኑ ፍሬ ነገሮች አላገኘንም።

በዚህ ሁሉ ምክንያት የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 340 አንፃር በማየት አስራሪ የሆነው ኑዛዜ ህጋዊ ውጤት አያስከትልም በሚል የሰጠው ውሳኔ ከተሳሳተ መነሻ የመነጨ በመሆኑ አተረጓጉሙ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሁለተኛ ደረጃ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ማየት የተነሳው ሰው ኑዛዜ የሚያደርግበትን የአደራረግ ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡

የአሁን አመልካች ከሥር ጀምሮ አንስቶ የተከራከረበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1728(3) ድንጋጌ ስለውሎች አደራረግ ሥርዓት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678(ሐ) የተመለከተውን መሪ ድንጋጌ በሚያብራራው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1719(2) እስከ 1730 በተመለከተው የውል አደራረግ ሥርዓት ከሚደነግጉት ዝርዝር ድንጋጌዎች አንዱ በመሆኑ ክርክሩ አግባብነት ያለው ነው፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ የሚገኘው ስለውሎች በጠቅላላው ክፍል እንደ መሆኑ መጠን ስለውሎች በጠቅላላው የተመለከቱት ደንቦች ከውሎች ባሻገር ስለሌሎች ጉዳዮች ያላቸው አግባብነትና ተፈፃሚነት በመሸጋገሪያ ድንጋጌው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1676 በተመለከተው መሠረት ነው፡፡ በዚህም ድንጋጌ አነጋገር የኑዛዜ አደራረግ ሊከተል የሚገባውን ሥርዓት በተመለከተ ስለኑዛዜ በሚያወራው ልዩ ህግ የኑዛዜዎች ፎርምና ማስረጃ በሚለው ርዕስ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 880 ጀምሮ የተደነገገ በመሆኑ ገኘው ህግ ይህ የልዩ ሕግ ክፍልእንጂ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1719 — 1730 የተመለከቱት ድንጋጌዎች አንዱ የሆነው ቁጥር 1728(3) ሊሆን አይችልም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 881 በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡና ምስክሮች በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም የአውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረግ እንዳለባቸው እንጂ አካላዊ ጉድለት፣ ያለበትን ተናዛዥ አካሉ ከተስተካከለው ለይቶ ያስቀመጠው መስፈርት የለም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1728(3) መሠረትም የጣት ምልክት ፊርማቸውን በአዋዋይ ፊት ማድረግ እንደሚገባ ሲደነግግ ኑዛዜን አስመልክቶ በተቀመጠው በዚህ ልዩ ድንጋጌ 881(3) ማህይማን የጣት ምልክታቸውን ወዲያውኑ ማስቀመጥ ያለባቸው መሆኑን እንጂ በተለይ በአዋዋይ ፊት እንዲያደርጉ አልደነገገም፡፡ ይህም በአንድ ጉዳይ ላይ በተለያዩ መንገድ በተለያዩ የህግ ክፍል መደንገጉ ጉዳዮች እንደየ አግባብነታቸው ሊታዩ የሚገባ መሆኑን ስለሚያስገነዝብ ለዚህ ለተያዘው ጉዳዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1728(3) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከላይ ከጠቀስናቸው ምክንያቶች አንፃር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሆነ ሰበር ሰሚው የሰጡት ዳኝነት መሠታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 እንደተደነገገው የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት በተፈፀመባቸው የመጨረሻ ውሳኔዎች ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡

ው ሳ ኔ

(1) የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/መ/ቁ 12033 በ17/03/2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡

(2) የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡

በዚህ የሰበር ጉዳይ ግራ ቀኙ ላወጡት ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፣ ወ/ሮ ሃና ፀጋዬ ጠበቃ አሰፋ ዝቅአርጋቸው ቀረበ

ተጠሪ፣ ወ/ት ጣዕሙ ደስታ ጠበቃ ገመቹ ሮሮ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ይጣራ ጥያቄን መነሻ ያደረገን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሾች የነበሩት ዳዊት ፀጋዬ የተባለው የአሁንዋ አመልካች ወንድም እና አመልካች ናቸው፡፡ ክሱ በተጠሪ ላይ ሊቀርብ የቻለው የውርስ ንብረት ልታካፍል ይገባል በመባሉ ነው ተጠሪ ለክሱ በሰጠችው መልስ ክሱ የቀረበው የከሣሾች አባት ከሞቱ ከአሥር ዓመት በላይ ቆይቶ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ተከራክራለች፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የዳዊት ፀጋዬ ሞግዚት በመሆን ያሳደገችው መሆንዋን ከመረጋገጡም በላይ እስዋም ይህን መሠረት በማድረግ በዳዊት ላይ አንስታው የነበረውን የይርጋ መቃወሚያም መተዋን እንደገለጸች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ተመልቶአል፡፡ ክሱ የቀረበለት ይኸው ፍ/ቤት ሁሉም ወገኖች ያሰሙትን ክርክር ከመረመረ በኃላ የአሁንዋ አመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ጥያቄዋን ውድቅ አድርጎአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው ተጠሪ የአመልካች እንጀራ እናት መሆንዋ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦ እያለ ይርጋው በአመልካች ላይ ተፈጻሚነት አለው የመባሉን አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና የተሰጠውን ውሣኔ ይዘት ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በዋናነት ለመገንዘብ የቻልነው ተጠሪ የአመልካችም የእንጀራ እናት መሆንዋን ነው፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ሞግዚት የነበረችው ለዳዊት ፀጋዬ ብቻ እንጂ አመልካች በተጠሪ ሞግዚትነት ሥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልነበረችም፡፡ ይህም ሆኖ ግን አመልካችም እንደወንድምዋ /ዳዊት ፀጋዬ/ በወቅቱ ለአካለመጠን ያላደረሰች የነበረች ስለመሆንዋ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ፍ/ቤቱ በተጠሪ የተነሳው የይርጋ መቃወሚያ በአመልካች ላይ ብቻ ተፈጻሚነት አለው ለማለት ከበቃበት አንደኛው ምክንያትም አመልካች የሞግዚትነት እና የአሳደሪነት ሥልጣን በነበራቸው ስዎች አማካይነት መብትዋን በወቅቱ ማስከበር ነበረባት የሚል ነው፡፡ ይህን ምክንያት መነሻ በማድረግም የአመልካች አባት የሞቱበትን ጊዜ ለይርጋው ጊዜ አቆጣጠር እንደሁለተኛ ምክንያት አድርጎ ወስዶአል፡፡ በሌላ በኩል ግን ፍ/ቤቱ የተጠሪን የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት አለው ለማለት እነዚህን ምክንያቶች መሠረት ቢያደርግም አመልካች ከሞግዚት አስተዳደር መቼ ነፃ እንደወጣች በውሣኔው ላይ አላመለከተም ተጠሪም ብትሆን የአመልካች አባት የሞቱበትን ጊዜ መነሻ በማድረግ የአሥር ዓመትን የይርጋ ጊዜ /የፍትብ/ሕግ ቁ 1845/ በመጥቀስ ከመከራከር አልፋ አመልካች ጊዜውን ያሳለፈችው ለአካለ መጠን ከደረሰች በኃላ /ከሞግዚት አስተዳደር ከወጣች በኃላ/ ነው የሚል መከራከሪያ አላነሳችም፡፡

በበኩላችን እንደምናየው የተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ በዳዊት ፀጋዬ ላይ ተፈጻሚነት የለውም ከተባለ በአመልካችም ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የማይታይበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የአመልካች ሞግዚት ነበሩ የተባሉት ሰዎች በወቅቱ መብትዋን አላስከበሩላትም የሚለው አካሄድም እንደዚሁ የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ዋናው መለየት ያለበት አመልካች የሚች አባትዋ ወራሽ መሆንዋን እና ለማስከበር የተነሳችውም የወራሽነት መብትዋ እንደሆነ ነው፡፡ የይርጋው ጊዜ ሊቆጠርባት የሚገባውም በመብትዋ መጠቀም ከቻለችበት /አካለመጠን ከደረሰችበት/ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በመሆኑም የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 14168 መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 79963 ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካች ያቀረበችው የውርስ ይጣራልኝ ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ብለናል፡፡ ስለዚህም የአመልካች የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄም ከዳዊት ፀጋዬ ጥያቄ ጋር አብሮ ይታይ በማለት ወስነናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 57607

ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ኤርሚያስ ኪስታንትኖስ ግሊፕትስ -ወኪል ጸሐይ መለሰ - ቀረበር

ተጠሪ፡- ሰለሞን ክስታንቲኖስ ግሊፕትስ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወቀረቀት ይሰጠኝ በሚል በቀረበው ጥያቄ መነሻነት የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን መዝገቡ የተከፈተው አሁኑ አመልካች ባቀረበው የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠን ጥያቄ መሠረት ነው፡፡ ፍ/ቤትም ጥያቄውን በመቀበል የምስክር ወረቀቱን ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ የምስክር ወረቀቱ የሚሰጥበት ህጋዊ ምክንያት የለም፤ ኤርሚያስ የሚች ኪስታንቲኖስ ግሊፕትስ ልጅ አይደለም በማለት መቃወሚያ በማቅረቡ መዝገቡ እንደገና ተንቀሣቅሶ ሁለቱ ወገኖች እንዲከራከሩ ተደርጐአል፡፡ በመጨረሻም የአሁኑ አመልካች የሚች ኪስታንቲኖስ ግሊፕትስ ልጅ ስለመሆኑ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት /የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት/ አረጋግጦ ማስረጃ አልመጣም በማለት ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል ሰጥቶት የነበረውን ማስረጃ ሰርዞአል፡፡ በየደረጃው ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ የቀረበላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰር ችሎትም በመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንተዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረው የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰረዘው በአግባቡ ነው ወይ በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡

በዚህ መሠረትም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን በማስመልከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከስር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና የተሰጡትን ውሣኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የሰማው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ መገንዘብ እንደቻልነው ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረው የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተጠሪ ባቀረበው መቃወሚያ ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አመልካች በሚመለከተው /ስልጣን ባለው/ ፍ/ቤት ልጅነቱን አረጋግጦ ይቅረብ የሚል ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ውጤቱን ለመጠበቅ በሚልም ቀጠሮ ተይዞ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የልጅነት ይረጋገጥ ጥያቄ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ልጅነት አረጋግጦ የሰጠው ውሣኔ የለም የሚል ምክንያት በመስጠት ፍ/ቤቱ የተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል ውሣኔ እንደሰጠ ተመልክተናል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ሆነ የይግባኝ ሰሚው ሰበር ችሎትም ይህን መስመር ተከትለው ነው የወሰኑት፡፡

በበኩላችን እንዳየነው የልጅነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ /አቤቱታ/ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ በእርግጥ አመልካች የሟች አቶ ኬስታንቲኖስ ግሊፕስ ልጅ ነው፡፡ ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡ ፍ/ቤቱ ከአመልካች ካቀረበው አቤቱታ /ማመልከቻ/ ይዘት በመነሣት ብቻ መዝገቡን እንደዘጋው እና የሰጠው ምክንያትም በጋብቻ ውስጥ ተወልዳለሁ ካልክ በህጉ ልጅ መሆንህ ስለሚገመት ጥያቄህ በፍ/ቤት የሚረጋገጥ አይደለም የሚል እንደሆነ በመዝገቡ ተያይዞ ከቀረበው ውሣኔ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የአመልካችን የይግባኝ ክርክር ያልተቀበለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ከምትጠይቅ ውጪ በዚህ በኩል የሚደረግ የለም በማለት እንደሆነም ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው አመልካች የሟች ልጅ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ አከራካሪ ሆኖአል፡፡ ተጠሪ ቀደም ሲል የተሰጠው የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሚከራከረው አመልካች ሟች እና እናቴ በጋብቻ ተሳስረው ይኖሩ በነበሩበት ጊዜ የተወለድኩ ልጅነኝ የሚል መከራከሪያ ይዞ ነው የምስክር ወቀረቱን እንዲሰጠው የጠየቀው በእርግጥ አመልካች በጋብቻ ውስጥ ስለመወለዱ ከመግለጽ አልፎ ይህ ሁኔታ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ የለም፡፡ በዚህ ምክንያትም ነው አመልካች አቤቱታውን ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ የተጠየቀው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት አመልካች የሟች ልጅ ነኝ የሚለውን ክርክር አለመቀበሉ ትክክል ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን የልጅነት ማረጋገጫ ውሣኔ መስጠት ያለበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ በአግባቡ ሣያስተናግድ በመቅረቱ ብቻ አመልካች ፍትህ የሚያገኝበትን መድረክ እንዲያጣ ማድረጉ አግባብ አይሆንም፡፡

በፍርድ ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ ያለው ማንኛውም ሰው ጉዳዩን ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሣኔ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገመንግስት አንቀጽ 37 /1/ ተደንግጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች በጋብቻ ውስጥም ይወለድ ከጋብቻ ውጪ ልጅነቱን ይረጋገጥላት ዘንድ ለፍርድ ቤት አቤቱታ /ጥያቄ/ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ጥያቄው በፍርድ ሊወሰኑ ከሚገባቸው ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ስለዚህም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ በመደበኛው የክርክር አመራር ስርዓት መሠረት አለማስተናገዱ ወይም ከወዲሁ መዘጋቱ ትክክል አይደለም፡፡ በጋብቻ ውስጥ ተወልጃለሁ የሚል ሰው ልጅ መሆኑን የህግ ግምት መውሰድ የሚቻለው ሰውየው በእርግጥም በጋብቻ ውስጥ ስለመወለዱ በቅድሚያ በፍሬ ነገር ረገድ ሲረጋገጥ እንደሆነም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በእኛ ግንዛቤ እና እምነት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተያዘው ጉዳይ እልባት ከማግኘቱ /ከመወሰኑ/ በፊት አመልካች ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው የልጅነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ /አቤቱታ/ ውሣኔ ማግኘት አለበት፡፡ አመልካች ፍትህ እንዲያገኝ ማድረግ የሚችለውም በዚህ አግባብ ጉዳዩ ሲሰራ ነው ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመ/ቁ. 1803/96 ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13497 ሰኔ 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13689 ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. በአመልካች አቤቱታ /ጥያቄ/ አቅራቢነት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተከፈተው ቁጥር 43257 የሆነው መዝገብ እንዲንቀሣቀስ እና ፍ/ቤቱም የአመልካችን ጥያቄ መሠረት በማድረግ እንደዚሁም ለጉዳዩ አወሣሰን ተገቢ የሆነውን ጭብጥ በመያዝ ውስጥ ይስጥ ብለናል፡፡

3. ተጠሪም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠቃሚ ነኝ የሚል ከሆነ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረውን መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሊቀጥል ይችላል ብለናል፡፡

4. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስናቀች ደለለኝ ጠበቃ ዘውዴ ተሰማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን ጠበቃ በርናባስ ደስታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ የድርሻ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ታህሣሥ 14 ቀን 1993 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ በወረዳ 08 ቀበሌ 05 ቁጥሩ 145/ለ/ የሆነ ፣ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ቁጥር 8/02601 የተሠጣቸውን መኖሪያ ቤት ለተጠሪ እንዲሆን በኑዛዜ መስጠታቸውን ገልጻ በኑዛዜ መሠረት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣት ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ስታቀርብ የአሁኗ አመልካች ይኸው የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ይሰጠኝ ጥያቄ ተገቢነት የለውም የሚሉባቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር ጣልቃ ገብተው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት በስር ፍርድ ቤት ያቀረቧቸው ምክንያቶች ሟች ትተውታል በተባለው ኑዛዜ የባለቤታቸውን የአቶ ደለለኝ ስሻን ድርሻ ንብረትን የሚያካትት በመሆኑ ኑዛዜው ሕጋዊነት ያለውም፣ በኑዛዜው ላይ የሰፈረው ፊርማም የሟቿ አይደለም፣ ኑዛዜውን ባደረጉበት ወቅትም በእድሜ መግፋት ምክንያት የሚሰሩትን አያውቁም ነበር ከውርስ ንብረቱም ያለ በቂ ምክንያት ነቅለውኛል የሚሉ ናቸው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ፊርማውን በተመለከተ በተገቢው አካል ተመርምሮ ውጤቱ እንዲቀርብለት በማድረግ ፊርማው የሟች ማርታ ዳኛቸው መሆኑን ውጤቱን አረጋግጦ ከቀረበለት በሁዋላ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ በሌሎች ነጥቦች ላይ የቀረቡትን የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ተመልከቷል፡፡ በዚህም መሠረት ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ኑዛዜውን ያደረጉት ከባላቸው ጋር ባፈሩት የጋራ ንብረት ላይ በመሆኑና ይህም ሕጋዊነት የሌለው መሆኑን እንዲሁም አመልካችን ያለሕጋዊና በቂ ምክንያት ከውርስ የነቀሏቸው መሆኑን ዘርዝሮ ኑዛዜው እንዲፀድቅ የቀረበውን አቤቱታ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኟን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርባ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ባደረጉት ኑዛዜ መሠረት ተጠሪ ወራሽ ናት በማለት የስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታውን ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ሚች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ኑዛዜውን ያደረጉት ከነባለቤታቸው ድርሻ ጭምር ሁኖ እያለና አመልካችን ከውርሱ ያለሕጋዊና በቂ ምክንያት የነቀሉ መሆኑ ተረጋገጦ እያለ ተጠሪ የኑዛዜ ወራሽ ናት ተብሎ መወሰኑ ከሕጉ ውጪ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ጠበቃው ቀርበው መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ አመልካችን ሚች ከውርስ የነቀሏት ምክንያት ጠቅሰው በመሆኑ ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ እንዲፀና ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም የካቲት 16 ቀን 2003 ዓ/ም በጻፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ሚች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ታህሣሥ 14 ቀን 1993 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም አመልካችንስ ከሚች ውርስ ነቅሏል ወይስ አልነቀለም? ውጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉት ነጥቦች በጭብጥነት ሊታዩ የሚገባቸው ሁነው አግኝቷቸዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የቻለው ሚች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ታህሣሥ 14 ቀን 1993 ዓ.ም ግልፅ ኑዛዜ የተው መሆኑን አመልካች የሚጀ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ/ልጅ/ ተጠሪ ደግሞ የሚች የኑዛዜ ወራሽ መሆኗን ሚች ይኖራቸዋል ተብሎ የተጠቀሰው ንብረት መኖሪያ ቤትና የቤት ቁሣቁስ ሁኖ ለአመልካች ብር 1000 እና የቤት ቁሳቁስ እንዲሰጣቸው የገለፀ መሆኑን ይህንን ለማድረግ በምክንያትነት የጠቀሱት ደግሞ አመልካች ትዳር ከያዘች ጊዜ ጀምሮ ተገቢውን እንክብካቤ አላደረገችልኝም ስታመምም እናቴ ብላ አላስታመመችኝም የሚል መሆኑን ነው፡፡ አከራከሪው ቤት የተናዛዟ እና የአቶ ደለለኝ ስሻን የጋራ ሃብት ስለመሆኑ አከራካሪ አለመሆኑንም በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ጭምር ተገንዝበናል፡፡

የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ኑዛዜው ሕጋዊ ነው በማለት የወሰኑት ሚች ለአመልካች ድርሻቸውን ሰጥተዋል፣ የድርሻ ማነስ ደግሞ የውርስ መነቀል ነው ሊባል የሚችል አይደለም የሚል እንድምታ ያለውን ምክንያት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ በኑዛዜው የሚከናወኑ ተግባሮች <u>የኑዛዜ ስጦታ</u> /legacy/ ወይም <u>የክፍያ ደንብ</u> /Rule of partition/ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመሀር ደረጃ ደግሞ አንድ ሰው ከውርስ ሀብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ አያሰኘውም፡፡ ይልቁንም ይህ አይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ አውራሽ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዘዝለት የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ /legacy/ አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ /partition/ በመከተል የሚከናውን ይሆናል፡፡ ሆኖም በኑዛዜው ላይ የሚሰጠውን ክፍያ መጠን በመገለፁ ብቻ ሁል ጊዜ የክፍያ ደንብ ነው ሊባል የሚችል አይሆንም፡፡ በመሆኑም የተሰጠው የንብረት መጠን ከሚቹ የውርስ ንብረት ግምት ጋር ታይቶ ውጤቱም በዚህ ረገድ መለየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ አገላለፅ ሟች በኑዛዜው ላይ የሚያስፍረው የንብረት መጠን ከሚቹ የውርስ ንብረት መጠን ጋር እየታየ የመነቀል ጉዳይ ነው ወይስ የክፍያ ማነስ ነው? የሚለው ነጥብ የሚለይ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ከሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች ለመገንዘብ እንደቻልነው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በወረዳ 8 ቀበሌ 05 ክልል ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 145/ለ/ በሚል የተመዘገበውና በ343 ካ.ሜትር ስፋት ቦታ ላይ የሰፈረው መኖሪያ ቤት የባለቤትነት ደብተር ስሙ ተመዝግቦ የሚገኘው በአቶ ደለለኝ ስሻን ስም መሆኑን ንብረትነቱም የአቶ ደለለኝ ስሻን እና የወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው የጋራ ሃብት መሆኑን የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ለስር ፍርድ ቤት በዓፈው ደብዳቤ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑ ያላከራከረ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ሟቿ የተናዘዙት የራሳቸው የግል ንብረት ብቻ ባልሆነ ንብረት ነው ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው በራሱ ባልሆነና ሙሉ በሙሉ ሊያዝበት በማይችል ንብረቱ የተናዘዘ እንደሆነ ኑዛዜው የሚኖረው ሕጋዊ ሁኔታ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ በውርስ ሕግ በግለጽ ምላሹ ያገኘ ነው፡፡ የውርስ ሕግ ውስጥ ይህንን ጉዳይ የሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 1047 እንዲህ ይነበባል፡፡

1. “በኑዛዜው የተደረገው ስጦታ በተለየ ነገር እንደሆነና ሟቹ በሞተበት ቀን በዚህ ነገር ላይ አንዳችም መብት የሌለው እንደሆነ የኑዛዜው ስጦታ ፍርስ ነው፡፡
2. ስለሆነም ሟቹ ይህን ሁኔታ እያወቀ በኑዛዜው ሰጥቶ እንደሆነ ስጦታው ዋጋ ያለው ይሆናል፡፡
3. እንደዚህ በሆነ ጊዜ አጣሪው በኑዛዜ የተሰጠውን እቃ ዋጋ መስጠት አለበት”

ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው በመርህ ደርጃ ማንም ሰው ምንም መብት በሌለው ንብረት ላይ የተናዘዘ እንደሆነ የተሰጠው ኑዛዜ ዋጋ አይኖረውም፡፡ በሕግ ፊት የሚፀና ኑዛዜ ለመስጠት ሟቹ ኑዛዜ በተደረገበት ንብረት ላይ መብት ሊኖረው ይገባል በሌላ በኩል በንዑስ አንቀጽ /2/ በግልጽ እንደሰፈረው ሟቹ ኑዛዜ በሚያደርጉበት ንብረት ላይ ምንም መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ ስጦታ የሰጠው እንደሆነ በስጦታው ሕጋዊነት የፀና ይሆናል፡፡ በመሆኑም ኑዛዜ አድራጊው መብት ያለው መሆን አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ስለዚህ ጉዳይ የነበረው ግንዛቤ በኑዛዜው ፍረስ መሆን አለመሆን ላይ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ኑዛዜው ፍርስ የሚሆነው ተናዛዡ ስጦታ ባደረገበት ንብረት ላይ መብት እንደሌለውና ይህንም ያውቅ እንዳልነበረ ሲታወቅ ብቻ ነው ፡፡ ይህ መደምደሚያ የሚገኘው ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ አንድና ሁለት ንዑስ ቁጥሮችን አጣምሮ በማንበብ ነው፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይ ተናዛዧ በአከራካሪው ቤት ለአሁኗ ተጠሪ በስጦታ በሰጡት ቤት ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት አልነበራቸውም፡፡ ቤቱ በጋብቻ የተፈራ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት በመሆኑና ከአቶ ደለለኝ ስሻን ሞት በሁዋላ ይዘውት ይጠቀሙበት ስለነበር ሟቿ ቤቱ ላይ ሙሉ መብት እንደሌላቸው ሳያውቁ ኑዛዜ ማድረጋቸው ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ኑዛዜው የተሰጠበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ 1047/1/ ን መስፈርት የሚያሟላ ነው፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ ቤቱ የጋብቻ የጋራ ንብረት በመሆኑ ምክንያት ሟቿ በቤቱ ላይ ሙሉ መብት ባይኖራቸው የኑዛዜ ስጦታውን ያደረጉት ይህ መብት እንደሌላቸው ሳያውቁ በመሆኑ በሟች አቶ ደለለኝ ስሻን ድርሻ ላይ የተደረገው ኑዛዜ ሊፈርስ የሚገባው ነው፡፡ ኑዛዜው ፍርስ ሊሆን አይችል የነበረው ሟቿ በቤቱ ላይ ሙሉ መብት እንዳላቸው የሚያውቁና ከሟች ደለለኝ ስሻን የተላለፈላቸው መብት ያለ መሆኑ ማስረጃ ቢቀርብ ነበር ፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበችው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም በአቶ ደለለኝ ስሻን ድርሻ ላይ የተደረገው የኑዛዜ ክፍል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1047/1/ መሠረት ፈራሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሆን የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሆኖም ይህ ምክንያት በሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ድርሻ ላይ የተደረገውን ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ፈራሽ የሚያደርገው አይደለም፡፡

ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው አመልካችን ከድርሻ ንብረታቸው ውርስ ነቅለዋል ወይስ አልነቀሉም? የሚለውን ነጥብም ተመልክተናል፡፡ በመሰረቱ አንድ ተናዛኘ/ወላጅ/ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለህጋዊና በቂ ምክንያት እንዲሁም በዝምታ ከውርስ ለመንቀል እንደማይችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 ድንጋጌዎች ይዘት በግልፅ ያሳያል፡፡ ወላጅ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ወይም በዝምታ ከነቀለም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት ከውርስ በዝምታ ወይም ያለበቂ ሕጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሁነው የውርስ ንብረቱን ሊከፋፈሉ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤት ወደዚህ ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት በወላጅ የተደረገ የኑዛዜ ስጦታ አይነቱ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ መለየት አለበት፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912 ስር እንደተመለከተው የኑዛዜ ስጦታ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ሲባልም ተናዛዡ ሀብቱን ጠቅላላ ወይም ከመላ ንብረቱ አንዱን ክፍል በሙሉ ሀብትነት ወይም በሌጣ ርስትነት ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች የሚያወርስበት የኑዛዜ ቃል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912/1/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ማንኛውም ሌላ የኑዛዜ ቃል ሁሉ እንደ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ እንደሚቆጠር ይነደገጋል፡፡ አንድ ኑዛዜ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014 ድንጋጌ ቅደም ተከተል መሠረት የሚከፈል ይሆናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ሟች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ሀብታቸውን ሙሉ በሙሉ ተጠሪ እንድትወርስ ለአመልካች ደግሞ ብር 1000 እና የቤት ቁሳቁስ የሰጡ መሆኑ ከኑዛዜው ሰነድ ይዘት ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ሟች አላቸው ከተባለው የማይንቀሳቀስ የውርስ ንብረት አንፃር አመልካች እንዲወስዱ በማለት የተናዘዙት የንብረት መጠን ሁኔታ ሲታይ እግምት ውስጥ የሚገባ ወይም የድርሻ ጥያቄ አነሰ የሚል ክርክር የሚያስነሳ ነው ሊባል የሚችል ሳይሆን በውጤቱ የመነቀል ውጤትን ያስከተለ ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡ ሟች ለአመልካች ብር 1000 እና የቤት ቁሣቁስ እንዲሰጥ በማለት የተናዘዙት “ትዳር ከመሰረተች በሁዋላ አልተንከባከበችኝም ፣ ስታመምም እናቴ ነች ብላ አልጠየቀችም ” በሚል ምክንያት ነው፡፡ የዚህ ሐረግ አገላለፅ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938/2/ መሠረት እንደእውነት የሚወሰድ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከውርስ ለመንቀል የሚያስችል ሕጋዊ እና በቂ ምክንያት መሆኑን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938/3/ መሠረት መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም አንጻር በሟች የተሰጠው ምክንያት አመልካችን ከውርስ ለመንቀል ሕጋዊና በቂ ምክንያት ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፎርማሊቲ ረገድ ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የሌለ ሲሆን ሟች የአቶ ደለለኝ ስሻንን ድርሻ አጠቃልለው መናዘዛቸው ግን ሕጋዊ አይደለም፡፡ ሟቿ አላቸው ከተባለው ጠቅላላ የውርስ ንብረት መጠን አንፃር ሲታይ ለአመልካች የተሰጠው የገንዘብ መጠን በውጤት ደረጃ አመልካችን ነቅሏል ከሚባል በስተቀር ድርሻቸውን አግኝተዋል፣ ውጤቱም በፍ/ብ/ሕቁጥር 1123 ሊታይ የሚችል ነው ሊባል የሚችል ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንጻር ተናዛኟ ያደረጉት ኑዛዜ ስጦታ ሲታይ በውጤቱ አመልካችን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ከውርስ የነቀለ ሁኖ ዓይነቱ ልዩ የሆነ የኑዛዜ ስጦታ ሳይሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ አይነት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕቁጥር 1014/ሠ/ ስር በተመለከተው መሠረት እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ ለልዩ ኑዛዜ ተቀባዩ የሚከፈል ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ድንጋጌዎች ታይቶ ተወላጅ ከውርስ ተነቅሏል ፣ ከኑዛዜ ተቀባዩ ጋር እኩል ሊከፈል ይገባል የሚባልበት ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡ የክፍያ ማነስ አለማነስ ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር ጉዳዩ እንዳይስተካከል ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1117 የተቀመጠው መርህ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 ጋር ተዛምዶ ሲታይ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ የሚች ተወላጅ ወይም ወደ ላይ የምትቆጠር ወላጅ አይደለችምና፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በሚች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ድርሻ ላይ በፍ/ሕ/ቁጥር 915 መሠረት እንደጠቅላላ ኑዛዜ ወራሽ ተወስዳ ከአመልካች ጋር እኩል ተካፋይ ናት ተብሎ ሊወሰን ሲገባው የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከውርስ ንብረት ክፍያ ማነስ ጋር በማያያዝ የሰጡት ውሣኔ የኑዛዜውን ውጤት ሚች አላቸው ከተባለው ንብረት ግምት መጠን ጋር ባለማገናዘብ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 05380 መጋቢት 23 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 13512 ግንቦት 18 ቀን 2002 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1178/96 ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ/ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
3. ሚች ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው ታህሣሥ 14 ቀን 1993 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በውጤቱ ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት አመልካችን የነቀለ በመሆኑ በአመልካች ላይ ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፤ ኑዛዜው ተጠሪን በሚጀ /ወ/ሮ ማርታ ዳኛቸው/ ድርሻ ንብረት ላይ አንድ ወራሽ የሚያደርግ በመሆኑ አመልካች የሚችን ድርሻ ንብረት ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ ብለናል፡፡
4. የአቶ ደለለኝ ስሻን ድርሻ ላይ ተጠሪ በኑዛዜው ተጠቃሚ የምትሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 03 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሪት ዝባድ ታዬ ጠበቃ አማረ ጋሻው ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡-1. ብዑአን ታዬ ሞግዚት አሰለፈች ለገሠ ቀረቡ፡፡

2. ዳኛቸው ታዬ
3. አቶ አቤል ታዬ } ጠበቃ ዘለቀ ደሬሣ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኑዛዜ ተጠቃሚነት ይሰረዝልኝ ጥያቄን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘትም ባጭሩ ፡- ተጠሪዎች የሚች አቶ ታዬ ድንቅነህ ኑዛዜ ወራሾች ነን በማለት ያቀረቡት ሰነድ በሚች ያልተደረገና ፊርማውም የሚች ባለመሆኑ ፊርማው ሊመረመር ይገባል በማለት ዘርዝረው ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች የሚች ታዬ ድንቅነህ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው ሲል የሰጠውን ማስረጃ ሊሰርዝ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም በፍርድ ቤቱ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቀርበው ኑዛዜው የሚች ነው፣ ፊርማውም የሚች ነው፣ ኑዛዜው የተደረገውም ምስክሮች ባሉበት ነው በማለት ገልፀው በፍርድ ቤቱ የተሰጣቸው የኑዛዜ ወራሽነት ሊሰረዝ እንደማይገባ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በኑዛዜው ላይ አለ የተባለውን ፊርማ በፎረንሲክ እንዲመረመር አድርጎ በኑዛዜው ላይ ነበሩ ተብሎ ስማቸው የጠቀሰውን ሰዎች በምስክርነት ሰምቶና ፊርማውን በተመለከተ ፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱ የሚች ነው ወይም አይደለም ብሎ ለመለየት መቸገሩን የሚመለከተው አካል ከገለፀለት በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለጉዳዩ በምስክርነት የቀረቡት ሰዎች ኑዛዜው ሲደረግ የነበሩበት ሁኔታ እርስ በራሱ ሊጣረስ በሚችል ሁኔታ የመሰከሩ ስለሆነ ቃላቸው ታዓማኒነት የለውም የሚል ምክንያት በመያዝ የአመልካቾችን የኑዛዜ ወራሽነት በማረጋገጥ የተሰጠውን ማስረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 360/2/ መሠረት ሰርዞታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሚች አይደለም የሚል ሆኖ እያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የምስክሮችን ቃል በመመርመር ስለኑዛዜው መነበብ መሠረት ተደርጎ ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም ተብሎ መወሰኑ በመቃወሚያነት ከተጠቀሱት ነጥቦች ውጪ የተሰጠ ውሳኔ ነው የሚል ምክንያት በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር የተጠሪዎችን የኑዛዜ ወራሽነት ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል። የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም ። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው።

የአመልካች ጠበቃ ነሐሴ 05 ቀን 2002 ዓ/ም በተጻፈ ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ የሻረው በቂና ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖረውና በፍ/ብ/ሕ/ቁ/881 - 883 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ባግባቡ ባላገናዘበ ሁኔታ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ስህተቱ እንዲታረምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 881 እስከ 883 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ በፁሑፍ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች ታዬ ድንቅነህ ሰኔ 10 ቀን 1999 ዓ/ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ አይነቱ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ዓይነት መሆኑን ነው። ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትና ይህም ችሎት አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲጣራ ያደረገበት ነጥብ ሟች አቶ ታዬ ድንቅነህ ያደረጉት ኑዛዜ በሕጉ ላይ የተመለከተውን መስፈርት ያሟላል? አያሟላም ? የሚለው ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ግልጽ ኑዛዜ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው። ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባው ስርዓቶች በፍ/ሕ/ቁ/881 ሥር ተዘርዝረዋል፣ ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ፣ ይህም ስርዓት መፈፀሙና በተግፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ ፣ተናዛዥና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ መሆኑ ነው። በሟች ተሰጠ የተባለው ኑዛዜም ሰነዱ ሲታይ አራት ምስክሮች የፈረሙበት ፣ ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ የሚገልጽ እና ተናዛዡ የጣት አሻራቸውን ፣ምስክሮቹ ደግሞ ፊርማቸውን ያኖሩበት መሆኑን ተገንዝበናል። በመሆኑም ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ሕ/ቁ/ 881 ሥር የተመለከቱትን ስርዓቶች የሟላ ነው። የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ኑዛዜው ፈራሽ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የሕጉን ሥርዓት አልተከተለም በሚል ግልጽ ምክንያት ሳይሆን በኑዛዜው ላይ የተጠቀሱት ምስክሮች ኑዛዜው ሲደረግ የነበሩትን ምስክሮችንና ተጠሪዎችን እንዲሁም ኑዛዜውን ያነበበውን ሰው ማንነት በሚጣረስ መልኩ መስክረዋል በሚል ምክንያት ሲሆን ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው በአመልካች በኩል ከቀረበው መቃወሚያ ይዘት ውጪ ነው በሚል ነው። በመሠረቱ የምስክሮች ዋና አስፈላጊነት ኑዛዜ አድራጊው ኑዛዜውን በነፃ ፍላጎቱ እና በትክክለኛ አእምሮው የሰጠ መሆኑንና የኑዛዜ ቃሉም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የእርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሕግ ጥያቄ ነው፡፡ አመልካች ኑዛዜው ፈራሽ ነው ብለው እስከተከራከሩ ድረስ የሕጉን ሥርዓት ያሟላ መሆን ያለመሆኑን መርምሮ ተገቢውን መወሰን የፍርድ ቤት የስራ ድርሻ ከሚሆን በስተቀር በየትኛው ሕጋዊ ምክንያት ኑዛዜው ፈራሽ እንደሆነ ተከራካሪ ወገን ለይቶ ሊከራከር ይገባል የሚባልበት ሕጋዊ አካሄድ የለም፡፡ በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ አለመሆኑን፣ አመልካች ተጠሪዎች የሟች ታዬ ድንቅነህ የኑዛዜ ወራሽ አይደሉም፣ ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መሻሩ በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 881— 883 የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 11876 መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 13442 ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/938/2001 በ19/02/2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348/1/ መሠረት ፀንቷል፣ሟች አደረጉት የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያላሟላ በመሆኑ ተጠሪዎች የሟች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ሊባሉ አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊረማ አለበት፡፡

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49713

ሚያዚያ 3 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- የወ/ሮ ጥሩነሽ አያለ ወራሾች

1. ወ/ሮ የምሥራች ግርማ
2. አቶ ዘላለም ግርማ
3. አቶ ሚሊዬን ግርማ
4. አቶ አዲስ ግርማ

ጠበቃ አቶ በለው አብዲ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ወጋየሁ ሰለሞን - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካቾች የአዲሰ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡት ማመልከቻ በሰበር የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት የመዝገብ ቁጥር 310198 በማስቀረብ ለመረዳት እንደቻልነው በሥር ፍርድ ቤት የአመልካቾች አውራሽ ወ/ሮ ጥሩነሽ አየለ የፍርድ ተቃዋሚ ተጠሪ ደግሞ የመቃወም ተጠሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት የአመልካቾች አውራሽ በመቃወም አመልካች ሆነው በመቅረብ በመዝገብ ቁጥር 0068/96 ወ/ሮ ወጋየሁ ሰለሞን የሚች የወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3680 ጥር 23 ቀን 1995 የወሰነ በመሆኑ የመቃወም ተጠሪዋ የሚች የወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ የልጅ ልጅና ተተኪ ወራሽ ናት በማለት የሰጠውን ውሣኔ ይሰርዝልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት የመቃወም ተጠሪ ሆነው ቀርበው ወንድ አያቴ ታፈሰ በላቸውን ታህሣሥ 7 ቀን 1968 ዓ.ም ከዚህ ዓለም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሞት ተለይተዋል። ሴት አያቴ ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ የካቲት 24 ቀን 1994 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። የአቶ ታፈሰ በላቸውና የወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ልጅ አባቴ አቶ ሰለሞን ታፈሰ ታህሣሥ 28 ቀን 1977 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። ስለዚህ ፍርድ ቤቱ የሁለቱ ሟቾች ተተኪ ወራሽ ናት በማለት የሰጠውን ውሣኔ የሚሠርዝበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል። አመልካች ተጠሪን ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ከውርስ የነቀሏት መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል።

የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሟች አቶ ታፈሰ እና የወ/ሮ እታለማሁ ያልጅ ልጅ ናት። ተጠሪ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 በሚደነግገው መሠርት ሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል የፈፀመች መሆኑ በፍርድ አልተረጋገጠም። ስለሆነም ሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ተጠሪዋ የመግደል ሙከራ እንደፈፀመችባቸው በኑዛዜያቸው የገለፁ ቢሆንም የመቃወም ተጠሪ ወ/ሮ ወጋየሁ ሰለሞን በመግደል ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ ያልተባሉ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 መሠረት የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ተቀባይነት የለውም ስለሆነም የመቃወም ተጠሪ ወ/ሮ ወጋየሁ ሰለሞን የሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ተተኪ ወራሽ ናቸው በማለት የሰጠሁት ውሣኔ የሚሠርዝበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል።

አመልካቾች የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበዋል። ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአምልካቾችን ይግባኝ ውድቅ በማድረግ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል። አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለከተማው ሰበር ችሎት አቅረበዋል። የከተማው ሰበር ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም። አመልካቾች ጥቅምት 9 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተጠሪ አባት ከሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ በፊት የሞተ በመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 830 በሚደነግገው መሠረት ሟችን የመውረስ ችሎታ የለውም። ስለዚህ ተጠሪ አባቴን በመተካት ሟችን እወርሳለሁ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም። ሟች ወ/ሮ እታፈራሁ ተጠሪ በተኙበት ቦታ ሌሊት ልትገድሳቸው በዱላ ስትደበድባቸው ጎረቤት ደርሶ ህይወታቸውን እንዳተረፋቸው በኑዛዜቸው በመግለጽ ከውርስ የነቀሏት ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሟች ወ/ሮ እታለማሁ ተተኪ ወራሽ ናት በማለት የሰጠውን የተሣሣተ ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የከተማው የሰበር ችሎት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል። ተጠሪ በበኩላቸው ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ መልስ እኔ የሟች ወ/ሮ እታለማሁ ተተኪ ወራሽ መሆኔን በማረጋገጥ የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም። አመልካቾች ተጠሪን ሟች በኑዛዜ ነቅለዋታል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ህጋዊ መሠረት የለውም። መከራከሪያም በሰበር ደረጃ የቀረበ ነው። ሟች የተናዘዘችው በራሷ ንብረት ላይ ብቻ ሣይሆን በወንድ አያቴ ንብረት ላይ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል። አመልካቾች ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት ተጠሪ የሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ተተኪ ወራሽ ናቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም; የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል። ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪን ጥያቄ በመቀበል የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት በመዝገብ ቁጥር 0068/96 መጋቢት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ሊሠረዝ አይገባውም በማለት የሰጠውን ውሣኔ በአግባቡ ነው በማለት የደረሡበትን መደምደሚያ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ መሠረት የተሰጠ መሆኑንና በውሣኔው ይዘት ተገቢ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ፡- የአመልካቾች አውራሽ ወ/ሮ ጥሩነሽ አየለ ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ግልፅ ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑን በመግለፅ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሚች ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ወራሽ መሆኑን አረጋግጦ እንዲወሰንላቸው ባቀረቡት ማመልከቻ መሠረት ኑዛዜው ሲደረግ የነበሩ ምስክርና የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ የህጉን መስፈርት ያሟላ ነው፡፡ ወ/ሮ ጥሩነሽ አየለ የሚች የወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ወራሽ ናቸው በማለት በመዝገብ ቁጥር 3680 ጥር 23 ቀን 1995 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ በህይወት ዘመናቸው ያደረጉት ኑዛዜ የሌለ መሆኑን በመግለፅ ተጠሪ የሚች የልጅ ልጅና ተተኪ ወራሽ እንደሆኑ እንዲወሰንላቸው ለአዲስ አበባ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ጥያቄ አቅረበዋል፡፡ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪን ማስረጃ በመዝገብ ቁጥር 0068/96 በመስማት ተጠሪ የሚች የልጅ ልጅና ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ መጋቢት 15 ቀን 1997 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአመልካቾች አውራሽ ተጠሪ ሚች ወ/ሮ እታለማሁ በህይወት ዘመናቸው ኑዛዜ አላደረጉም በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የተሣሣተ ነው፡፡ የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንን የተሣሣተ አቤቱታ በመቀበል መጋቢት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ስህተት ያለበትና የእኔን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ነው፡፡ ሚች ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑን እና የሚች ኑዛዜ ህጋዊ መስፈርት የሟላ መሆኑ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አስቀድሞ በፍርድ የተወሰነ ነው በማለት ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ መሠረት ሲጣራ ሚች ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑንና ኑዛዜው ህጋዊ መስፈርቶችን ያሟላና ህጋዊ ውጤት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥር 23 ቀን 1995 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሚች ወ/ሮ እታለማሁ በነፃ ፈቃዳቸው በህግ የተደነገገውን መስፈርት በሟሟላት ያደረጉትና ህጋዊ ውጤት ያለው ኑዛዜ መሆኑን በማረጋገጥ ጥር 23 ቀን 1995 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠበት ሚች ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በይዘቱ ተጠሪን ከውርስ የሚነቅልና የአመልካቾችን አውራሽ የሚች ወ/ሮ እታለማሁ የኑዛዜ ወራሽ የሚያደረግ መሆኑን ለማስረዳት የአመልካቾች አውራሽ በማስረጃነት ካቀረቡት የኑዛዜ ሰነድ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ የቀረበለት የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ህጋዊነቱ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ ጥር 23 ቀን 1995 ዓ.ም የተሰጠውን ውሣኔ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 በሚደነግገው መሠረት ውሣኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት የፍርድ መቃወሚያ በማቅረብ ካላሻሩት በስተቀር በመዝገብ ቁጥር 0068/96 መጋቢት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በተሣሣተ ፍሬ ጉዳይ ላይ የተመሠረተና በሌላ ፍርድ ቤት አስቀድሞ ውሣኔ በተሰጠበት ጭብጥ ላይ የተሰጠ መሆኑ የአመልካቾች አውራሽ ካቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ጋር አያይዘው ባቀረቡት የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ውሣኔና ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ባደረጉት የኑዛዜ ሰነድ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0068/96 መጋቢት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ያደረጉት ኑዘዜ የለም በማለት ተጠሪ ያቀረቡትን የተሣሣተ ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ የተሰጠና ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ያደረጉት ኑዛዜ የህጉን መስፈርት ያሟላና ህጋዊ ውጤት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ አስቀድሞ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን ባለማወቅ መሆኑን ገልፆ ውሣኔውን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 360/2/ መሠረት መሠረዝ ነበረበት፡፡ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5/1/ መሠረት አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ መሆኑንና ተጠሪ የኑዛዜውን ህጋዊነትና የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት አስመልክቶ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3680 ጥር 23 ቀን 1995 የሰጠውን ውሣኔ ላይ የፍርድ መቃወሚያ በማቅረብ ሣያሰርዙ ከውርስ የተነቀሉ መሆኑን የሚገልፅ ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ያደረጉት ኑዛዜ መኖሩን በማረጋገጥ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ እያለ ተጠሪ የሚች ወ/ሮ እታለማሁ ተተኪ ወራሽ ናቸው በማለት የሰጠሁትን ውሣኔ የምሰርዝበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ መስጠቱ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5/1/ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ያደረጉት ኑዛዜ ህጋዊ መስፈርቱን የሚያሟላና ህጋዊ ውጤት ያለው ነው በማለት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ይዘት እንደ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመመርመር ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ በኑዛዜቸው የገለፁት ምክንያት ተጠሪን ከውርስ ለመንቀስ የሚያበቃ አይደለም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የሆኑትን የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5/1/ ፣ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 እና የፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 360/2/ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ሚያዚያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የሥነ ሥርዓት ህግ ግድፈት ብቻ ሣይሆን በይዘቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ አተረጓጎም ችግር ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ምክንያቱም ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ከተራ ቁጥር 2 "ያሣደጓት የአቶ ሰለሞን ታፈሰ ልጅ ወ/ሮ ወጋየሁ ሰለሞን ከልጅነት ጀምሮ አሣድጌ ለቁም ነገር ከአደረስኳት በኋላ እኔ ሣላስበው ከተኛሁበት ቦታ ልትገለኝ በዱላ ደብድባኝ ጎረቤት ደርሶ ህይወቴን ያተረፍኩት ስለሆነ ከልጅነት ጀምሮ በማሣደጌ ብር 1,000/አንድ ሺ ብር/ ተሰጥቷት ከምንም ንብረቴ እንዳትደርስ በዚህ ኑዛዜ ቃል አውግዥር አግጃታለሁ" በማለት የተናዘዙ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ከተያያዘው የኑዛዜ ሰነድ ተረድተናል፡፡

የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች አውራሽ ይህንን የኑዛዜ ሰነድ በመጥቀስ ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው ሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ተጠሪ የመግደል ሙከራ የፈፀመችባቸው መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ተጠሪ በመግደል ሙከራ ወንጀል ጥፋተኛ ያልተባሉ በመሆኑ ኑዛዜው የፍታብሔር ህግ 838 ድንጋጌ መስፈርት አያሟላም በማለት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ለውሣኔ መሠረት በማድረግ የጠቀሰው እና የተረጉመው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 ከተዘረዘሩት ወንጀሎች አንደኛውን መፈፀሙ በፍርድ ተረጋግጦበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥፋተኛ የተባለ ወራሽ ሟችን እንዳይወርስ በውርስ ህግ ክልከላና ማዕቀብ ይደረግበታል፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 የሚደነግገው በሟች ወይም በሟች ሚስት ወይም ባል ወይም በሟች ወላጆችና ተወላጆች ላይ በህጉ ከተመለከቱት አንደኛውን ወንጀል የፈፀመ መሆኑ በወንጀል ችሎት ተረጋግጦ የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 830 መሠረት ሟችን የመውረስ ችሎታ እንዳይኖረው በህግ ክልከላና ማዕቀብ የሚደረግበትና ሟችን ለመውረስ ያልተገባ /unworthy/ በመሆኑ በህግ ክልከላ /ማዕቀብ/ ይደረግበታል፡፡ ሟች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 841 በተደነገገው መሠረት ይቅርታ ካላደረገለት በስተቀር በፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 ከተዘረዘሩት ተግባራቶች አንደኛውን መፈፀሙ ተረጋግጦ በፍርድ ጥፋተኛ የተባለ ወራሽ በሟች ወርስ እንዳይካፈል ክልከላ የሚያደርግበትና ማዕቀብ የሚጥልበት ሟች ሣይሆን በውርስ ህግ ድንጋጌ ህግ አውጭው በደነገገው የፍታብሔር ቅጣት /civil sanction/ መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 830 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 ድንጋጌዎች ይዘትና ህጋዊ ውጤት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የአመልካቾች አውራሽ የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡት ተጠሪ ሟች ለመውረስ ያልተገባች ናት በማለት አይደለም፡፡ የአመልካቾች አውራሽ የተከራከሩት ሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰን ታህሣሥ 2 ቀን 1993 ባደረጉት ኑዛዜ ከውርስ ነቅለዋታል በማለት ነው፡፡ ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ስለመሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 በተደነገገውና አንድ ሰው በግልፅ በሚያደርገው ኑዛዜ ተወላጆቹን ከውርስ ለመንቀል ስለሚችልበት ሁኔታ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 937 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 938 በተደነገገው መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ ከውርስ መንቀል "Dishersion" የሚባለው ተናዛዡ የውርስ ህግ በሚደነግገው መሠረት ባደረገው ኑዛዜ ውስጥ ምክንያቱን በመግለጽ ወይም በዝምታ ከወራሾቹ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑት ወራሾቹ በውርሱ እንዳይካፈሉ ያደረገውን ኑዛዜ በውርስ ህግ ዕውቅናና ውጤት የሚሰጠው በሆነ ጊዜ ከውርሱ እንዳይሣተፍ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡ ተናዣዡ ከወራሾቹ አንደኛውን ከወራሽነት ለመንቀል የሚችል መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 937/1/ የሚደነግግ ሲሆነ ተናዣዡ ልጅን ወይም ወደታች የሚቆጠረውን በኑዛዜ ለመንቀል የደረሰበትን ምክንያት በኑዛዜው ውስጥ ካልገለፀ በቀር ልጅን ወይም ተወላጅን ለመንቀል ያደረገው ኑዛዜ እንደማይፀና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 938/1/ ተደንግጓል፡፡

ተጠሪ የሟች እታለማሁ ታፈሰ የልጅ ልጅ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ሟች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ተጠሪን ከውርስ ለመንቀል የደረሱበትን ምክንያት ተጠሪ አደረገቸው ያሉትን ተግባር በኑዛዜያቸው ገልፅዋል፡፡ ሟች በኑዛዜ ፈፀመችው በማለት የገለፁት ተግባር ማለትም ሟች "ሣያስቡት ሌሊት ከተኙበት የደበደበቻቸው መሆኑንና ጎረቤት ደርሶ ህይወታቸውን ያተረፋቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሟች በኑዛዜያቸው የገለፁት ምክንያት ሙሉ በሙሉ ዕውነት ነው የሚል የህግ ግምት ያለ ሲሆን ህጉ ተጠሪ ተቃራኒ ማስረጃ ሊያቀርቡበት የማይችሉና /የማይስተባበል የህግ ግምት/ መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 938/3/ ተደንግጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሟች ወ/ሮ እታለማሁ ተወላጆቻቸውን ተጠሪን ከውርስ ለመንቀል በኑዛዜቸው የገለፁትን ምክንያት ዕውነት ነው ብሎ በመቀበል ሟች የሰጡት ምክንያት ተጠሪን ከውርስ ለመንቀል በቂ ነው ወይስ አይደለም; የሚለውን ነጥብ መርምሮ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 938/2/ መሠረት መወሰን ነበረበት፡፡ ሟች በኑዛዜቸው የገለፁት ምክንያት ከባድና ተጠሪውን ከውርስ ለመንቀል የሚያስችል በቂ ምክንያት መሆኑ ሟች በኑዛዜቸው ከገለፁት ምክንያት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 937/1/ እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 938 ድንጋጌዎች መሠረት መርምሮ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 በመጥቀስ ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 838 መሠረት በሟች ላይ የመግደል መከራ ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፈፀመች መሆኑ በፍርድ ጥፋተኛ የተባለችበት ማስረጃ አልቀረበም በማለት የአመልካቾችን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 310/98 ሚያዚያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት 07155 የካቲት 3 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 10061 ሀምሌ 17 ቀን 2001 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ ለተጠሪ ከተናዘዙት ብር 1,000/አንድ ሺህ ብር/ ውጭ በውርሳቸው እንዳይሳተፉ በኑዛዜ የነቀሏቸው ስለሆነ ተጠሪ የሚች ተተኪ ወራሽ አይደሉም ብለናል፡፡
3. አመልካቾች የሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3690 ጥር 23 ቀን 1995 የሰጠው ውሣኔ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት አለው በማለት ወስነናል፡፡
4. ተጠሪ የሚች አቶ ታፈሰ በላቸው ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት አለው በማለት ወስነናል፡፡
5. ከሚች ወ/ሮ እታለማሁ ታፈሰ የውርስ ንብረት አመልካቾች ለተጠሪ ብር 1,000/አንድ ሺ ብር/ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት አለባቸው ብለናል፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቶች፡- 1- ወ/ሮ እቴቱ ሽፈራው
2- አቶ አሸናፊ ሽፈራው — ጠበቃ አቶ ግርማቸው ይላላ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1- ወ/ሮ መንበረ ሽፈራው
2- አቶ ይድነቃቸው ሽፈራው
3- አቶ ዮናስ ሽፈራው — ጠበቃ አቶ ሀይሉ ነጮ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካቾች የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ጭብጥ ተይዞ ለሰበር ችሎት የቀረበ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች አመልካች አመልካቶች ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎች ለሥር ፍርድ ቤት የአንደኛ ተጠሪ ወላጅ አባት አቶ ሽፈራው ወልደማርያም ህዳር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ምንም አይነት ኑዛዜ ሣይተው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ እንደዚሁም የአንደኛ ተጠሪ ወላጅ እናትና የሁለተኛና የሶስተኛ ተጠሪዎች አያት የሆኑት ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ፈንታ ጥር 17 ቀን 2000 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩና ጥር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ተጠሪዎችን የኑዛዜ ተጠቃሚ የሚያደርግ ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑን በመግለፅ አንደኛ ተጠሪ የሚች ሽፈራው ወልደማርያም ያለኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲሰጣቸውና ተጠሪዎች የሚች የወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው እንዲረጋገጥላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካቶች በሥር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ በመሆን ገብተው የሚች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ልጆችና ህጋዊ ወራሾች ነን፡፡ ጥር 7 ቀን 2000 ዓ.ም እናታችን ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ አደረጉት የተባለው ኑዛዜ ሚች ካላቸው ንብረት እኛ ብር 500/አምስት መቶ ብር / እንዲሰጠን የሚልና እኛን ከውርስ የመንቀል ያህል ውጤት ያለው ነው፡፡ ሚች ኑዛዜውን ያደረጉት በትክክለኛ አእምሮ አለመሆኑን ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች የልጅ ልጆቻቸው ሆነው እያለ ልጆቹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ያደረጉት ኑዛዜ ያስረዳል ስለዚህ ኑዛዜው ውድቅ ሊደረግልን ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ኑዛዜ አድራጊዋ ሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ አንድ ሚሊዮን ከሚያወጣው የውርስ ሀብት ውስጥ አመልካቾች ብር 500 /አምስት መቶ ብር / እንዲወስዱ ኑዛዜ ሲያደርጉ የሰጡት ምክንያት በቂ ምክንያት ባለመሆኑ ኑዛዜው እንዲሻሻል በማድረግ አመልካቶች ጣልቃ ገቦች የሚችን የውርስ ሃብት እኩል ይካፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሟች በኑዛዜ የፈለጋችውን ያህል ሀብት ለወራሾች በኑዛዜ የመስጠት ስልጣን እንዳላቸው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 913 የተደነገገ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ኑዛዜ እንዲሻሻል የሰጠው ውሣኔ የህግ መሠረት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻር በሟች ኑዛዜ መሠረት ተጠሪዎች ይወርሳሉ በማለት ወስኗል፡፡

ይህ ውሣኔ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግለፅ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የከተማው የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ለአመልካቾች ብር 500/አምስት መቶ ብር/ የሰጡበትን ምክንያት በኑዛዜው የገለፁ ስለሆነ የአመልካቾች ተቃውሞ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 913 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1123/1/ ድንጋጌን የሚቃረን ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት አፅንቶታል፡፡

አመልካቾች ሚያዝያ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የአዲስ አበባ ከተማ የሰበር ችሎት ሟች እናታችን ያደጉት ኑዛዜ ከሟች ውርስ ከሚደርሰን አንድ አራተኛ በላይ ጉዳት እንደሚያደርስብን ካረጋገጠ በኋላ ሟች በኑዛዜያቸው ምክንያት የገለፁ መሆኑን ብቻ በማየት የሟች ምክንያት በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ሣይመዝን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1113/1/ በመጥቀስና በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ሟች የአመልካቾችን ድርሻ ዝቅ በማድረግ ብር 500/አምስት መቶ ብር/ እንዲወስዱ ያደረጉት ኑዛዜ ተገቢ ነው አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1123ን በመጥቀስ ያልተከራከሩ በመሆኑ በሰበር ደረጃ ማንሣታቸው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329ን የሚጥስና በሰበር ያቀረቡት አዲስ ክርክር ነው የከተማው የሰበር ችሎት ለፍታብሔር ህግ ቁጥር 1123/1/ የሰጠው ትርጉም ተገቢ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ታህሣሥ 8 ቀን 2003 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ የስር ፍርድ ቤት ሟች ያደረጉትን ኑዛዜ ያሻሻለው በህግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው የተጠሪዎች ክርክር የህግ መሠረት የለውም የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአመልካቾች እናትና አውራሽ የሆኑት ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ አመልካቾች ከውርስ ከሚደርሳቸው አንድ አራተኛ /ሩብ/ በላይ ጉዳት እንደደረሰባቸው በማሰብ ጥር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል በማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1123 ንዑስ አንቀፅ 1 በስጦታው አከፋፈል ውስጥ ተቃራኒ ቃል ከሌላ በቀር ወደ ታች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚቆጠሩ ተወላጆች አንዱ ከሚደርሰው ከሩብ የበለጠ ጉዳት ደርሶበት እንደሆነ የስጦታ አከፋፈሉ እንዲቀር ለመጠየቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ሟች ካላቸው የውርስ ንብረት አመልካቾች እያንዳንዳቸው ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ ብቻ እንዲሠጣቸው ያደረጉት ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል ከሚለው መደምደሚያ ላይ ያደረሱት ሟች በኑዛዜው ውስጥ ይህንን ያደረጉበትን ምክንያት ገልፀዋል በማለት ነው፡፡

ሟች አመልካቾች የአብራካቸው ክፋይ ልጆቻቸው መሆናቸውን ገልፀው እነርሡ ግን ያልጠየቁኝ ያልረዱኝ በመሆኑ ከውርሱ ንብረት ብር 500/አምስት መቶ ብር / እንዲወስዱ በማለት በኑዛዜው ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ሟች በኑዛዜው ውስጥ የገለፁት ምክንያት እውነት ነው ብለን ወስደን ምክንያቱ አመልካቾችን ከሟች ውርስ ከሚደርሳቸው ድርሻ ከሩብ በላይ ለማሣጣት በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ መወሰን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሟች ወ/ሮ ዳርቻ በኑዛዜው ውስጥ የሰጡት ምክንያት አመልካቾች ከውርሱ ንብረት ከሚደርሳቸው ድርሻ ከሩብ /አንድ አራተኛ/ በላይ ለማሳጣት የሚያስችል በቂ ምክንያት ባለመሆኑ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የከተማው የሰበር ችሎት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 913 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1123 ንዑስ አንቀፅ 1ን በመጥቀስ የሟች ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ መሆን ይኖርበታል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም ሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ አመልካቾች ብር 500/አምስት መቶ ብር/ ብቻ እንዲወስዱ ያደረጉበትን ምክንያት የገለፁ ቢሆንም ሟች በኑዛዜቸው የገለፁት ምክንያት ዕውነት እንደሆነ በመውሰድ ምክንያቱ በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ዳኞች መመዘን የሚችሉ ስለመሆኑ የፍትብሔር ህግ ቁጥር 1123 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 938 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ጋር በጣምራ በመተርጎም ለመረዳት የሚቻል በመሆኑ ወ/ሮ ዳርቻ አመልካቶች ስላልረዷቸውና ስላልጠየቋቸው ከውርሱ ከሚደርሳቸው ድርሻ ከአንድ አራተኛ /ሩብ/ በላይ እንዲያጡ ለማድረግ የሚያስችል በቂ ምክንያት ባለመሆኑ ኑዛዜው አመልካቾች የሚያጡት መብት ከድርሻቸው አንድ አራተኛ /ሩብ/ በላይ መሆን አይገባውም፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾች ከውርሱ ንብረት ከሚደርሳቸው ከሩብ /አንድ አራተኛ/ በላይ ሊያሳጣቸው የሚችል አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ሟች ወ/ሮ ዳርቻ መንግስቱ ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾች ከውርሱ ከሚደርሳቸው ድርሻ እስከ አንድ አራተኛ /ሩብ/ ድረስ ብቻ የሚያሳጣቸው በመሆኑ ኑዛዜው በዚሁ መንገድ ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው ተደርጎ ሊተገበር ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሃ/ዲ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚያዚያ 18 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፈቃደ መክብብ ጠበቃቸው አቶ አምደ አበበ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዳንኤል ብሥራት ጠበቃቸው ወ/ሮ አበባ መንግስቱ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት በስር አመልካች ወይም በአሁን ተጠሪ ዳንኤል ብሥራትና በስር ተጠሪ ሞገስ ብሥራት መዝገብ የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡

በሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ያሁን ተጠሪ ባቀረበው አቤቱታ ሟች አባታችን አቶ ብሥራት ኪዳኑ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ምድብ የመ/ደ/ፍ/ቤት ከተጠሪ /ሞገስ ብሥራት/ ጋር ወራሽ ነኝ የሚል ግለሰብ እኔን ያሁን አመልካችን ወራሽ አይደለም በማለት ውሳኔ በማሰጠቱ አመልካች በይግባኝ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ሳይሽር ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ልጅነት አረጋግጩ ስቀርብ ከውርስ ልነቀል አይገባም በሚል መከራከር እንደሚችል ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ የሟች ብሥራት ኪዳኑ ልጅ ስለመሆኔ ይረጋገጥልኝ ብሏል፡፡

የስር ተጠሪ የነበረው አቶ ሞገስ ብሥራትም በሰጠው መልስ አመልካች ከሟች አቶ ብሥራት ኪዳኑ እና ከወ/ሮ ውድነሽ ይደግልኝ ህዳር 25 ቀን 1959ዓ.ም የተወለደ በአባትም በእናትም የምንገናኝ ወንድሜ ነው፣ ልጅነቱም እውነት ስለሆነ በጥያቄው መሠረት ቢረጋገጥለት ተቋውሞ የለኝም ብሏል፡፡

የሥር አመልካችን አቤቱታና የተጠሪን መልስ የመረመረው የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤትም አመልካች ከሟች ብሥራት ኪዳኑ ስለመወለዱ ተጠሪ ወይም የአመልካች ወንድም ያልተቃወመ በመሆኑ አመልካች የሟች ብሥራት ኪዳኑ ልጅ ነው በማለት በቤተሰብ ህግ ቁጥር 143 መሠረት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የስር የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ የአሁኑ የሰበር አመልካች ቅር በመሰኘት ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ እንዲታረምለት ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛው ፍ/ቤቱ በ25/01/2003 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዋለው ችሎት መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡

የሰበር አመልካችም በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ጥቅምት 22ቀን 2003ዓ.ም የተጻፈ ቅሬታ አቅርቧል፡፡ በሰበር አቤቱታ የተጠቀሱት ዋና ዋና የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- ሚች አጐቴ አቶ ብሥራት ኪዳኑ በሕይወት ዘመናቸው ያደረግኩላቸውን ውለታ በማለጽ በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 04/06/07 ክልል የሚገኘውን ቁጥሩ 288 የሆነውን የግል መኖሪያ ቤታቸውን በታህሳስ 15 ቀን 1994ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት 4 ምስክሮችን ይዞ በመቅረብ የተናዘዙልኝ በመሆኑ ይህንኑ መሠረተ በማድረግ የኑዛዜ ወራሽነቴን በቦሌ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 373/2000 እንዲረጋገጥ ያደረግኩ ሲሆን ያሁኑ ተጠሪና አቶ ሞገስ ብሥራት ኑዛዜውን ተቃውመው የሚች ኑዛዜ በፎረንሲክ ላብራቶሪ ተመርምሮ የሚች ፊርማ መሆኑ በመረጋገጡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ወራሽነቴን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በኋላ ተጠሪው እንደገና ሳያገኝ አቶ ሞገስ ብሥራት የተባለውን በተጠሪነት መዝግቦ በቀጥታ አቤቱታ በማቅረቡ የሥር መ/ደ/ፍ/ቤትም አመልካቹን የሚች ልጅ ነው ሲል ውሳኔ በመሰጠቱ ያሁን አመልካችም በዚሁ ውሳኔ መቃወሚያ ባቀረብም የሥር ፍ/ቤት በቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/1-3/ መሠረት የመቃወም መብት የለህም ማለቱ የህግ ስህተት ነው፣
- በሥር ፍ/ቤት በተጠሪነት የተመዘገበው አቶ ሞገስ ብሥራት በቦሌ ምድብ የመ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ፣ ሰሚው ፍ/ቤት የተከራከረኝ ሲሆን እንደ ህጉ ዓላማ ከሆነ በተጠሪነት መመዝገብና መጠራት የሚገባኝ እኔ ያሁኑ አመልካች ነበርኩ፡፡ ይህ ታልፎ ከዚህ በላይ በስም የተጠቀሰውን ግለሰብ ተጠሪ ማድረጉ የህግ ስህተት ነው፣ የሚሉ ሲሆኑ ተጠሪው የሚች ብሥራት ኪዳኑና የወ/ሮ ውድነሽ ይደግልኝ ልጅ ሳይሆን የአቶ መኮንን በላይና የወ/ሮ ሰማያት ይደግልኝ በመሆኑ ተጠሪው ፍ/ቤቱን ሳያስፈቅድና ፍ/ቤቱም ሳይፈቅድለት ከሚች የተወለደ ልጅ ነው በሚል የተሰጠ ውሳኔ ይሻርልኝ ሲል ጠይቋል፡፡

ለቀረበው የሰበር ቅሬታ ተጠሪው በሰጠው መልስ፡- አባትነትን መቃወም ለማንም የተለቀቀ ሳይሆን ለቅርብ የቤተሰብ አባላት የተሰጠ መብት ነው፡፡ አመልካች የሚች ወንድም በመሆኑ በቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/1-3/ ሥር ከተመደቡት የዘር እርከን ውስጥ አይሸፈንም፡፡ ተጠሪን የሚች ብሥራት ኪዳኑ ልጅ አይደለም በማለት የሚከራከረውም ሚች ንብረታቸውን በኑዛዜ ሰጥተውኛል በሚል ሲሆን በቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/3/ ከጥቅም ግጭት የተነሳ አባትነትን ለመቃወም ከተገለጹት ወራሽና ወኪል አንዱ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሚች አቶ ብሥራት ኪዳኑ ለአመልካች በኑዛዜ ንብረታቸውን የሰጡ መሆኑንና ይህንኑ ተጠሪና ወንድሜ ተቃውመን ኑዛዜው የሚች ነው በሚል በመረጋገጡ አሁን ለዚህ ችሎት ከቀረበው የልጅነት ጥያቄ ጋር የሚያናኝ ነገር የለም፡፡ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ይጽናልኝ ሲል ጠይቋል፡፡

ተጠሪው ላቀረበው መልስ አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስ የተጠሪው መልስ በሥር ፍ/ቤቶች የተፈፀመውን የህግ ስህተት የሚያስተባብል ባለመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ ይሻርልኝ በሚል ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የቀረበ ሲሆን እኛም የሰበር አመልካች ተጠሪው የሚች ብሥራት ኪዳኑ ልጅ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ያቀረበውን የመቃወሚያ አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው ክርክሩን መርምረናል፡፡

አመልካች የፍታብሔር ሥ/ሥ/ህግ ቁጥሮችን 35/፣359 እና 360 በመጥቀስ ባቀረበው የፍርድ መቃወሚያ በ29/8/2002ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ የሚች ብሥራት ኪዳኔ ልጅ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ይሻርልኝ በማለት ሲሆን ለዚህም እንደምክንያት የጠቀሰው ተጠሪ ከሚች ብሥራት ኪዳኔና ከወ/ሮ ውድነሽ ይደግልኝ አልተወለደም የሚል ነው፡፡ እንደ አመልካች አባባል የተጠሪ አባት አቶ መኮንን በላይ እናቱ ደግሞ ወ/ሮ ሰማያት ይደግልኝ ናቸው፡፡ ከተጠሪ በኩል ከቀረቡት የመከራከሪያ ሐሳቦች ምላሽ ማግኘት ያለበት አመልካች ተጠሪው የሚች ብሥራት ኪዳኔ ልጅ አይደለም በማለት የመከራከር ህጋዊ መብት የለውም የሚል ነው፡፡ ለዚህም ተጠሪው ጠቅሶ የሚከራከረው የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 177 /1-3/ ያሉ ድንጋጌዎችን ነው፡፡

በመሠረቱ በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ሲሆን ክሱንም የሚያቀርበው የልጅ አባት ነህ የተባለ ሰው ነው፡፡ ሆኖም በህግ ግምት የልጁ አባት ነህ የሚባለው ሰው የሞተ ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አባት ነህ የተባለው ሰው ችሎታያጣ እንደሆነ ከተወላጆች አንዱ በርሱ ፋንታ ሆኖ የመካድ ክስ ማቅረብ እንደሚችል የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/1/ ይደነግጋል፡፡

ነገር ግን ተወላጆች የሌሉ እንደሆነ አባት እና እናት የመካድ ክስ የማቅረብ መብት ያላቸው ሲሆን እነዚህም በሌሉ ጊዜ ደግሞ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች አንዱ መብቱን ሊሠራበት እንደሚችል ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ህግ አንቀጽ 177/2/ ተጠቅሷል፡፡ በመጨረሻም ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች የሌሉ እንደሆነ በመካድ መብት ሊሠራበት የሚችለው ከወንድሞቹ ወይም ከእህቶቹ አንዱ እንደሆነ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/3/ ይናገራል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይም አመልካች የሚች ወንድም በመሆኑ የሚች ተወላጆች ወይም ወላጆች (Descendants or Ascendants) በሕይወት አለመኖራቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 177/3/ መሠረት የመካድ ክስ ወይም ሚች ብሥራት ኪዳኑ የተጠሪ አባት አይደለም በማለት ሚች የተጠሪ አባት ነው ተብሎ የተሰጠውን ፍርድ እንዲነሳ መቃወሚያ ማቅረብ አይችልም፡፡

በመሆኑም ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 169057 በቀን 29/8/2002ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔና የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 96603 በ25/01/2003ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ አጽንተናል፡፡
2. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ አመልካችና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59539

ሰኔ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡-1. አቶ ስዩም ወ/መስቀል - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ዘነቡ ወ/መስቀል

3. ወ/ነት ጠግባቸው ወ/መስቀል

4. ወ/ሮ ጽዬሐና ወ/መስቀል

ተጠሪ፡- ወ/ት አምሣለ ሙሉነህ - ጠበቃ ዳንኤል ገ/ጊዮርጊስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፊ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ አውራሻችን ሟች ወ/ሮ ሙሉሸዋ ወ/መስቀል ከሟች አቶ አበበ ተክሉ ግር ጋር ጋብቻ ፈጽመው በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 14/15 የቤት ቁጥር 1654 እና የተለያዩ የቤት ዕቃዎችን በጋራ አፍርተዋል፡፡ ተከሣሽ የሟች አውራሻችንን ንብረት ይዘው እየተጠቀሙ ሲሆን እንዲለቁ ቢጠየቁ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው በህግ ተገደው ንብረቱን እንዲያካፍሉን ወይም ንብረቱ ተሸጦ የድርሻችን ክፍያ እንዲፈጸምልን የሚል ነበር፡፡

ተከሣሽ /የአሁን ተጠሪ/ በሰጡት መልስ የተጠቀሰው ቤት የባልና ሚስት ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረቡም እና ቤቱም በተከሣሽ ስም የተመዘገበ በመሆኑ የመክሰስ መብት የላቸውም፤ አውራሻቸው ከሞቱ ከመጋቢት 04/1990 ጀምሮ ከ10 ዓመት በኋላ የቀረበ ክስ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ተከራክሯል፡፡

የፊ/ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ የመክሰስ መብት የላቸውም በማለት የተነሣውን ተቃውሞ ውድቅ በማድረግ ቢያልፈውም ይርጋን በተመለከተ ግን ተቀባይነት ያለው ተቃውሞ መሆኑን በመግለጽ የቀረበውን ክስ በዚሁ በይርጋ ውድቅ አድርጐታል፡፡ አመልካቾች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፊ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ነሐሴ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በ4 ገጽ በተጻፈ አቤቱታ ፍሬ ሃሣብ አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃቸውን ከያዙ በጥቂት ወራት ውስጥ ያቀረቡት ክስ በመሆኑ ተጠሪ ተሰጠኝ የምትለው በስጦታ በመሆኑ የተደረገው ደግሞ መጋቢት 04 ቀን 1993 ዓ.ም በመሆኑ የይርጋ ጊዜ ከዚህ ጀምሮ ሲቆጠር 10 ዓመት ያልሞላው በመሆኑ እና ተጠሪም በይዞታቸው ስር አደረጉ እንኳ ቢባል ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በ2 ገጽ የተጻፈ የመልሣቸዉ ፍሬ ሃሣብ የአመልካቾች አውራሽ ከሞቱ ከ10 ዓመት በኋላ የቀረበ ክስ በመሆኑ በይርጋ ውድቅ ይሆናል፡፡ የስጦታው ውል ለውርስ ጥያቄ የይርጋ መቋጠሪያ መነሻ ጊዜ ሊሆን አይችልም እና ወራሽነታቸውን ያረጋገጡበት ቀንም እንደ ይርጋ መቋጠሪያ መነሻ ሊያገለግል ስለማይችል የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተክረክሯል፡፡ የአመልካቾች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡ በግራቀኙ መካከል የነበረው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን ከተነሱት ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ፡-

አመልካቾች ያቀረቡት የውርስ ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም የሚለው ጭብጥ ተይዞ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የአመልካቾች አውራሽ የሞቱት መጋቢት 04 ቀን 1990 ዓ.ም እንደሆነ፣ አመልካቾች ወራሽነታቸውን ያረጋገጡት በ2000 ዓ.ም ውስጥ እንደሆነና ክስ ያቀረቡት ደግሞ መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም እንደሆነ አላከራከረም፡፡

የአመልካቾች አውራሽ በሞቱበት ጊዜ ስራ ላይ የነበረው የቤተሰብ ህግ በፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 683 እስከ 689 ጋብቻ ከተጋቢዎቹ በአንዱ መሞት ሊፈርስ እንደሚችልና መብት አለን ባዮች የድርሻቸውን መጠየቅ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም እስከ መቼ ድረስ መጠየቅ እንደሚገባቸው ስለማያመለክት ክርክሩም ደግሞ በወራሾች መካከል ባለመሆኑ በፍ/ብሔር ህግ ኡንቀጽ 1677/1/ እና 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ መታየት እንዳለበት ከዚህ በፊት በመዝ.ቁ. 17937 እና ሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

ጊዜው መቆጠር ያለበት አውራሻችን ነው የተባለው ሰው ከሞተበትና ጋብቻውም በዚያው ምክንያት ከላይ እንደተመለከተው ከፈረሰበት ጊዜ ጀምሮ መሆን እንዳለበት ከላይ የተመለከተው የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች እና የይርጋ ዘመን አቆጣጠርን የተመለከቱ የህግ ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም የይርጋ ዘመን አቆጣጠርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ከመቼ መቆጠር እንደሚጀምሩ በምንመለከትበት ጊዜ በአንደኛው ተጋቢ መሞት ምክንያት ከፈረሰ ጋብቻ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ጋብቻው በሞት ከፈረሰበት ዕለት ጀምሮ መሆን እንዳለበት ከመውረስ መብት አኳያ ሲታይም በፍ/ብ/ህግ ቁ. 826/1/ መሠረት ውርሱ የሚከፈተው የአመልካቾች አውራሽ በሞቱበት ቦታና ቀን እንደሆነ ስለሚደነግግ እና የይርጋ ዘመን መቀጠር የሚጀምረው በፍ/ብ/ህግ ቁ. 5 እና 1846 መሠረት መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ የይርጋው ዘመን መቆጠር ያለበት የአመልካቾች አውራሽ ከሞቱበት ቀን ጀምሮ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ምክኒያቱም የአመልካቾች መብት ሊበሰል ወይም መጠየቅ ይችላሉ የሚባለው ወይም ንብረቱ በዕጅ ይገኛል የተባለው ሰው የማስረከብ ግዴታ አለበት የሚባለው አውራሻቸው ከሞቱበት ቀን ጀምሮ ስለሚሆን ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የአመልካቾች አውራሽ ከሞቱ ከ10 ዓመታት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ከመሆኑም በላይ አመልካቾች የይርጋው ዘመን መቆጠር ያለበት ወራሽነታችንን ካረጋገጥንበት ቀን ጀምሮ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም ደግሞ ለተጠሪ ስጦታ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የህግ መሠረት የላቸውም ብለናል፡፡
በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 50871 ግንቦት 25 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 65579 በቀን 16-2-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡት የውርስ ክስ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ከፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የመጣው የመ/ቁ. 65579 ወደ መጣበት ይመለስ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 60725

ሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አብርሀ የኋላሸት - ጠበቃ ፍሰሀ ሐጐስ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አበባ ዘመን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ክርክር ሲሆን በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የተጀመረው በግራ ቀኙ የቀረበውን የንብረት ክፍፍል ጥያቄን በሚመለከት ነው፡፡ ለአሁኑ ቅሬታ መሠረት የሆነው በአመልካች ስም ያለው በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 የቤቱ ቁ. 708 የሆነ መኖሪያ ቤት ሲሆን ተጠሪ የጋራ ንብረታችን ነው በማለት የተከራከረች ሲሆን አመልካች በበኩሉ በቀን 05-11-80 ዓ.ም በስሜ የተመዘገበና የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶት አሁን ያለውን ቤት ሰርቶ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የምኖርበት በመሆኑ ከተጠሪ ጋር ደግሞ በ1993 ዓ.ም በባህላዊ ጋብቻ የተገባን መሆኑና በዚህ ጋብቻ ውልም የጋራ ንብረት ያልተደረገና በድጋሚ ተደርገ የተባለው የጋብቻ ውል እኔ ታምሜ በአማኑኤል ሆስፒታል በነበርኩበት ወቅት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩሏ የተባለው ቤት ከጋብቻ በፊት 3 ክፍል ጭቃ ቤት የነበረ መሆኑ ከተጋባን በኋላ የኮርኒስ ስራ በር ቀለም እንዲሁም 10 ቅጠል ቆርቆሮ ጨምረን በጋራ እድሣት ሰርተናል፣ አንድ መኝታ እና አንድ ሣሎን ክፍል እንዲሁም አንድ 4x5 ክፍል ቤት ሰርተናል ፣ በኋላም በ1999 ዓ.ም በተደረገ የጋብቻ ውል የጋራ ንብረት ያደረግንና ይሄው የጋብቻ ውል በክብር መዝገብ ሹም ቀርቦ የተመዘገበ በመሆኑ የጋራ ንብረታችን ነው በማለት ተከራክራለች፡፡

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ ለዚህ ቅሬታ መነሻ የሆነውን ቤት እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ የጠየቀ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጸንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደተመረመረውም ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኖሪያ ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ /ጭብጥ/ ተይዞ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኖሪያ ቤት ግራ ቀኙ ከመጋባታቸውም በፊት በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በተመሣሣይም በግራ ቀኙ መካከል ቀድሞ የተደረገው የጋብቻው ውል ማለትም በቀን 18-12-1992 ዓ.ም የተደረገ ስለመኖሩና በዚህም የጋብቻ ውል የተመለከተው መኖሪያ ቤት የጋራ ንብረት ያልተደረገ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በግራ ቀኙ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ታህሣስ 12 ቀን 1999 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የጋብቻ ውል ሲሆን የተጠሪ ክርክር በዚህ ጋብቻ ውል መሠረት በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 19/20 የቤት ቁጥሩ 708 የሆነ ቤት የጋራ ንብረት እንዲሆን ተስማምተናል የሚል ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ደግሞ ከላይ በድጋሚ ተደረገ የተባለውን የጋብቻ ውል የማያውቁ መሆናቸውን ፣ በወቅቱ የአዕምሮ በሽተኛ ሆኖ አማኑኤል ሆስፒታል ሲታከም የነበረ መሆኑን ፣ ተጠሪ ራሷ አዘጋጅታ ያቀረበችው በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የተነሳውን የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸው ከፌዴራል የቤተሰብ ህግ ጋር ስንመረምር በእርግጥ የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/1992 አንቀጽ 47/1-3/ ስንመለከት ቀድሞ የተደረገውን የጋብቻ ውል ማሻሻል እንደሚቻል የሚደነግግ ሲሆን ለፍ/ቤት ቀርቦ የተደረገው የጋብቻ ውል መሻሻል የቤተሰብን ጥቅም የማይጎዳ ከሆነ ሊጸድቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይሄ የተሻሻለው የጋብቻ ውል ለፍ/ቤት ቀርቦ ማጽደቅ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል በዚህ አንቀጽ ስር መልስ የሚሰጥ ባይሆንም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 73 ጋር አያይዘን ስንተረጉም ፍ/ቤት ካላጸደቀው በስተቀር ተቀባይነት የለውም የሚለውን ትርጉም ይሰጠናል፡፡ በዚሁ መሠረት ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ከላይ የተመለከተው በግራ ቀኙ መካከል በድጋሚ ተደርገ የተባለው የጋብቻ ውል በክብር መዝግብ ሹም ፊት ቀርቦ የተመዘገበ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ቢሆንም ከላይ በተመለከተው አግባብ ለፍ/ቤት ቀርቦ የጸደቀ ስለመሆኑ ተጠሪ ያስረዳች ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ታህሣስ 12 ቀን 1999 ዓ.ም በድጋሚ ተደርገ የተባለው የጋብቻ ውል ከላይ በተመለከተው ምክንያት ሊጸና አይችልም ቢባልም በተጠሪ በኩል ተነስቶ የነበረው ሌላው ክርክር መኖሪያ ቤቱ በተጠሪ ስም የነበረና ሶስት ክፍል ጭቃ ቤት የነበረበት መሆኑን ሆኖም ከተጋቡ በኋላ ለዚሁ ቀድሞ ለነበሩት ክፍሎች አጠቃላይ እድሣት ያደረጉ ከመሆኑም በላይ በተጨማሪ ከሶስት የማያንሱ ክፍሎችን ጨምሮ የሰሩ መሆናቸዉን የተከራከሩ ሲሆን አመልካች ደግሞ ውጪ አገር ሆኖ በላከው ገንዘብ እንደተሰሩ ተከራክሯል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ የሚያነሷቸው ክርክሮች ባላቸው ማስረጃ ተጣርተው ያልተወሰነ በመሆኑ እና የግራ ቀኙ በመኖሪያ ቤቱ ላይ ያላቸው መብት ተገቢው መጣራት ከተደረገ በኋላ መወሰን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም ግራ ቀኙ ሲጋቡ የተጠቀሰው መኖሪያ ቤት የሚገኝበት አጠቃላይ ይዘት እንዴት እንደነበር ፣ አብሮ ባሉበት ጊዜ የተደረገው መሻሻል ምን ያህል እንደሆነ እና ክሱ ሲቀርብ የመኖሪያ ቤቱ አጠቃላይ ይዘት በግራ ቀኙ ማስረጃ ተጣርቶ በቤቱ ላይ የግራ ቀኙ መብት ምን ይሆናል? የሚለውን የበታች ፍ/ቤቶች መወሰን ሲገባቸው ማለፋቸው መሠረታዊ የሆነ የሙግት አካሄድ መርሆቹን የተከተለ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁ መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 92430 ነሐሴ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 155334 በቀን 29-7-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 የቤት ቁ. 708ን በተመለከተ የተሰጠው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ በፍርድ ሐተታው በተመለከተው መሠረት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰናል፤ ይጸፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ የደረሰውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጥሩወርቅ ለማ

ተጠሪ፡- ታፈሰ ተሰማ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን ፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተደረገውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሃዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ሲሆን ፣ ፍ/ቤቱ በሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር ከተመለከተ በኋላ የንብረት ክፍፍሉ በፅጣ እንዲሆን በማዘዝ አከፋፍሎአል በወጣው ፅጣ መሠረት ለአመልካች የደረሰው ቤት ለተጠሪ ከደረሰው ቤት በዋጋ የሚበልጥ ነው በማለትም አመልካች ብር 31,585.65 ለተጠሪ ትክፈል ብሎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በውሣኔው ባለመስማማት ለሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረብዋ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን ፣ ችሎቱ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ጥቅምት 23 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የንብረት ክፍፍሉ የተመራው በሕጉ አግባብ ነው ወይ? የሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን መሠረት በማድረግ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ለክፍፍል የቀረቡት ንብረቶች በፍቺ የተለያዩት ባልና ሚስት /ተከራካሪዎች/ የጋራ ሃብት ናቸው፡፡ ከዚህ ደግሞ በቅድሚያ መገንዘብ የሚቻለው ሁለቱም በሃብቶቹ ላይ እኩል የሆነ መብት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመብት ረገድ አንደኛው ከሌላኛው አያንስም ወይም አይበልጥም ከተባለ ደግሞ የክፍፍሉ ሥርዓትም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መከናወን ያለበት፡፡ የእኩልነት መርሁ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 35/1/ እና/2/ የተቀመጠ ሲሆን ፣ ቀጥለው በወጡት የፌዴራል እና የክልል ቤተሰብ ሕጎችም እንደዚሁ በግልጽ ተቀምጦአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የቤተሰብ ሕግ “የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 ” ሲሆን የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ለሁለቱም እኩል እንደሚከፋፈል በአንቀጽ 101/1/ ደንግጎአል፡፡ በእርግጥ ባልና ሚስቱ ሃብታቸውን በስምምነት ለመከፋፈል ከፈለጉና ከቻሉ ሕጉ ይህን ስምምነታቸውን እንደሚያከብርላቸውም ተመልክቶአል፡፡ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ በስምምነት መከፋፈል ካልቻሉ/ካልፈለጉ / የክፍፍሉ ሥርዓት እንዴት ሊከናወን ይችላል? የሚለው ነው፡፡

ከፍ ሲል የተጠቀሰው የቤተሰብ ሕግ የክፍፍል ሥርዓቶቹን በቅደም ተከተል በዝርዝር አስቀምጦአል /በአንቀጽ 102/2/ እና በአንቀጽ 103/1/ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች በአይነት ሊከፋፈሉ የሚችሉ ናቸው አልተባለም፡፡ ችግሩ የተፈጠረው በአይነትም ለመከፋፈል ሁለቱም ወገኖች ስምምነት ላይ ባለመድረሳቸው ነው፡፡ አመልካች እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ እየተከራከረች ያለችው በእጣ ደርሶሻል የተባልኩት ከስምምነቴ ውጪ ነው፡፡ በዕጣ የደረሰኝ ነው የተባለውን ንብረት ብወስድ እጎዳለሁ፡፡ ተጠሪ አልተጎዳሽም የሚል ከሆነ ለኔ ደርሶአል የተባለውን ንብረት ብር 31,585.65 በመክፈል ጠቅልሎ ይውሰድ ፤ እኔ ደግሞ ለእሱ የደረሰውን ልውሰድ በማለት ሲሆን፣ ተጠሪ ግን በዚህ አይስማማም ፡፡ እየተከራከረ ያለው አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት ነው፡፡ ከዚህም በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው በንብረት ክፍፍሉ ግራ ቀኝ ወገኖች አለመስማማታቸውን ነው፡፡ እጣ እንዲወጣ ያዘዘውም ፍ/ቤቱ /በራሱ አነሳሽነት / እንጂ ተከራካሪ ወገኖቹ ክፍፍሉ በዕጣ ይሁን ብለው ስለተስማሙ እንዳልሆነም ከተሰጡት ውሣኔዎች ይዘት ጭምር ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ፍ/ቤቱ ወደ ዕጣ አማራጭ የሄደው ግራ ቀኝ ወገኖች በስምምነት ለመከፋፈል ባለመቻላቸው እና ንብረቱም በአይነት የማይከፋፈል በመሆኑ እንደሆነ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰጠው ውሣኔ ተመልክቶአል፡፡

በንብረቱ ክፍፍል ረገድ ችግር ሲያጋጥም ማለትም ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነና ባልና ሚስቱን ንብረቱ ከሁለቱ ለአንዳቸው እንዲሰጥ ለማስማማት ሳይቻል የቀረ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን እንዲከፋፈል እንደሚደረግ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 103/1/ ግልጽ ባለሁኔታ ተመልክቶአል፡፡ ይህ ድንጋጌ ንብረቱ በዕጣ የሚከፋፈልበትን የክፍፍል ሥርዓት በአማራጭ አላስቀመጠም፡፡ ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ ከሕጉ በመውጣት ውሣኔ መስጠት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ሕጉ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው /አንቀጽ 103 / ቀደም ሲል የተመለከትነውን የእኩልነት መርህን ግንዛቤ ውስጥ በማግባት እንደሆነም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በመሆኑም የንብረቱ ክፍፍል በዕጣ እንዲሆን በማለት የተሰጠው ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሃዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በመ.ቁ 20692 በ28/10/2002 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፣ የሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 08513 በ8/11/2002 ዓ.ም የሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትዕዛዝ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ 44349 በ27-1-2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. አመልካች እና ተጠሪ ንብረቱን መከፋፈል ያለባቸው በቤተሰብ ሕጉ በተዘረጋው የክፍፍል ሥርዓት መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 12 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- ወ/ሮ ገዛችን ገብሩ - ከጠበቃቸው ከአቶ ተክለ አብ ስዩም ጋር ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዓለምነሽ በየነ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ክስ የተጀመረው በሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኗ የሰበር ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ፍሬ ቃልም ከሟች አቶ ፀጋዬ ተክለሃይማኖት ጋር ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ እንደ ባልና ሚስት አብረን ለአምስት ዓመታት ስንኖር ህፃን ገሊላ ፀጋዬ የተባለችውን ልጅ የወለድን ሲሆን በጋራ ከሟች ጋር የነበረንን ኮድ 3.03110 የሆነውን የጭነት መኪና የሟች ሚስት ነኝ የሚሉት 2ኛ ተከሳሽ ይዘው ስለሚገኙ ድርሻዬን እንዲያካፍሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር 2ኛ ተከሣሽም /ያሁኗ አመልካች/ በክሱ በሰጡት መልስ ከሳሽ ከሟች ጋር እንኳን ለአምስት ዓመታት ቀርቶ ለወራት እንኳን እንደ ባልና ሚስት አልኖሩም፡፡ ከሳሽ ለመካፈል የጠየቁትን መኪና እኔና ባለቤቱ የነበረንን ኮድ 3.50133 የሆነውን አይሱዙ መኪና ሸጠን የገዛነው በመሆኑ ከሳሽን የሚመለከት አይሆንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትም ከሳሽ በማስረጃነት ያቀረቡትን በመ/ቁ 20488 ሰኔ 09 ቀን 2000 ዓ/ም የተሰጠውን ውሳኔ ከመረመረ በኋላ በዚህ በማስረጃነት በቀረበው ውሳኔ ከሳሽ ከ1991 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ከሳሽና ሟች ፀጋዬ ተክለሀይማኖት በተከራዩት ቤት እንደ ባልና ሚስት ሲኖሩ እንደነበር ሆኖም ግን ጋብቻ ይፈጽሙ አይፈጽሙ እንደማያውቁ ምስክሮች ያስረዱ ስለሆነና ከሳሽ የጋራ ሀብት ነው በሚል የጠየቁት ኮድ 3.03110 የሆነው መኪና የተገዛው ጥቅምት 21 ቀን 1993 ዓ/ም መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በማረጋገጡ መኪናው ከሳሽና ሟች እንደ ባልና ሚስት አብረው በነበሩበት ጊዜ የተገዛ ነው በማለት በመኪናው ከሳሽ እና 2ቱም የሥር ተከሳሾች እያንዳንዳቸው 1/3ኛ ድርሻ አላቸው ብሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሥር 2ኛ ተከሳሽ ይግባኝ ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ከፍተኛው ፍ/ቤትም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት መልስ ሰጪዋን መጥራት ሳያስፈልግ የይግባኙን መዝገብ በመዝጋት ይግባኝ ባይዋን አሰናብቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ሲሆን በዋናነት አመልካች ያቀረቡት ቅሬታም ተጠሪዋ ክርክር ባስነሳው መኪና መብት ሳይኖራቸው የአመልካች ድርሻ ከመኪናው 1/3 ብቻ እንዲሆን መወሰኑ ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዋ በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት ጋር እንደ ባልና ሚስት በኖሩበት ወቅት አከራካሪው መኪና የተገዛ መሆኑን በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ባቀረቡት ክርክር ተጠሪዋ ከመኪናው መብት የላቸውም ሲሉ የተከራከሩት የህግ መሠረት የለውም ብለዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም ተጠሪዋና ሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት እንደ ባልና ሚስት ኖረዋል? ወይስ አልኖሩም? የሚለው ጭብጥ በሥር ፍ/ቤት በአግባቡ ተረጋግጧል? ወይስ አልተረጋገጠም የሚለውን ነጥብ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የአሁኗ የሰበር ተጠሪ ከሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት ጋር እንደ ባልና ሚስት ሲኖሩ እንደነበር በማለጽ የጋራ ሀብት ነው የሚሉት የጭነት መኪና ድርሻቸው እንዲሰጥ ሲጠይቁ አመልካች ባቀረቡት መልስ ካነሷቸው ነጥቦች አንዱና ዋናው ከሳሽ /ያሁን ተጠሪ/ ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት አልኖሩም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ በዚህ መልኩ ክርክር እስከቀረበ ድረስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተቀበለው የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤትም ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች የተለያዩበትን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ መስጠት ሲገባው በመቃወም አመልካች /የአሁኗ አመልካች/ እና በመቃወም ተጠሪ /ያሁኗ ተጠሪ/ በመዝገብ ቁጥር 20488 የአሁኗ ተጠሪ የሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት ሚስት ናቸው ተብሎ በ11/10/96 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ እንዲሰረዝ ክርክር ባቀረቡበት ወቅት የቀረቡት ምስክሮች የአሁኗ ተጠሪና ሟች እንደ ባልና ሚስት ሲኖሩ እንደነበር አረጋግጠዋል በማለት በመ/ቁ 20488 ለተያዘው ጉዳይ ውሳኔ ለማሰጠት የቀረቡትን ማስረጃዎች በዚህ መዝገብ /60691/ በተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንዳላቸው በመቁጠር ፍ/ቤቱ የምስክሮቹን ቃል ለውሣኔው መሠት ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘንም፡፡ ይኸውም በመ/ቁ 20488 የክርክሩ ጭብጥ የአሁኗ ተጠሪ የሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት ሚስት ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ከተረጋገጠ በኋላ ሚስት አለመሆናቸው ተረጋግጦ በ11/10/96 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተጠሪዋ ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠ ውሣኔ እንዲሰረዝ የተደረገበት ሲሆን በዚህ መዝገብ በተያዘው ጉዳይ ግን ክሱ የቀረበው ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት በመኖራችን የጋራ ሀብት የሆነው መኪና ተካፍሎ ድርሻ ይሰጠኝ በሚል ነው፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪዋ ላቀረቡት ክስ አግባብነት የሌለውን በመ/ቁ 20488 የተሰጠውን የምስክርነት ቃል መሠረት በማድረግ በተጠሪና በሟች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት መካከል እንደ ባልና ሚስት የመኖር ሁኔታ መኖር አለመኖሩን በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መሠረት ተገቢውን ማጣሪያ ሳያደርጉ ተጠሪዋ ከመኪናው 1/3ኛውን ድርሻ ያግኙ ሲሉ የወሰኑት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 68308 በቀን 22/8/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 95917 በቀን 29/10/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
3. በተጠሪዋና በሚች ፀጋዬ ተክለሃይማኖት መካከል እንደ ባልና ሚስት የመኖር ሁኔታ የነበረ መሆኑንና አለመሆኑን የግራ ቀኙን ማስረጃዎች የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሰማ በኋላ ለቀረበው የጋራ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ በተሻሻለው የፌ/የቤተሰብ ሕግ መሠረት ተገቢውን እንዲወስን ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ አመልካችና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠ/መ/ቁ. 63195

ሐምሌ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ገረመው መሙቻ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አሰፉ ነበበ - ጠበቃ አልማዝ አሰፋ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በአሁንዋ ተጠሪ ክስ አቅራቢነት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካችን የከሰሰችው በቤት ሰራተኛነት ተቀጥራ በነበረበት ጊዜ አስገድዶ ደፍሮኝ በማርገዜ ልጅ ወልጃለሁ፡፡ ልጅቷን አምኖ ሊቀበለኝ አልቻለም፡፡ ስለዚህም የህፃን መታደል ወላጅ አባት መሆኑ ተረጋግጦ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሳሽ ክሱን የመሰረተችው ተደፈርኩ ካለችበት ጊዜ ከአሥር ዓመት በላይ ቆይታ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ በኔ ቤት የቆየችው ለአንድ ወር ተኩል ያህል ከመሆኑም በላይ፣ በ85 ዓመት ዕድሜዬ ለመድፈር የአካልም ሆነ የሞራል ብቃትም የለኝም /አልነበረኝም/፡፡ ከሣሽ በእኔ ስለመደፈርዋ ማስረጃ የላትም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም በዚህ መልክ የቀረበለትን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች ህፃን መታደል አባት ነው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ታህሣሥ 8 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የሥር ፍ/ቤቶች ወደ ውሳኔው ለመድረስ የተከተሉት አካሄድ /የክርክር አመራር/ አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች እና ተጠሪ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና የተሰጡትን ውሣኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ ክስ ስትመሰርት ሰዎችን በምስክርነት የቆጠረች ሲሆን፣ የዲ.ኤን.ኤ /D.N.A/ ምርመራ እንዲደረግለትም ስለመጠየቅዋ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ከተደረገበት መዝገብ ጭምር ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ አመልካችም በበኩሉ ሰዎችን በመከላከያ ምስክርነት ቆጥሮ ማሰማቱን ተመልክተናል፡፡ ክሱን የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖችን ምስክሮች ከመስማት አልፎ የዲ.ኤን.ኤ /D.N.A/ ምርመራ እንዲደረግ አላዘዘም፡፡ በዚህ ረገድ የሰጠው ምክንያትም አመልካች የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ማድረግ እንደማይችል እና እንደማይገደድ ገልጾ መልስ ሰጥቶአል የሚል እንደሆነ ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ /ክርክር/ በዋነኛነት የተመሰረተውም በዚሁ ነጥብ ላይ ነው፡፡ ከሣሽ ተጠሪ ሆኜ ሳለ በአስረጂነት የጠቀሰችው የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ በኔ በተከሣሽ ወጪ ይደረግ መባሉ ትክክል አይደለም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ተጠሪ በበኩልዋ ለአቤቱታው በሰጠችው መልስ አባትነቱን በምስክር ያስረዳሁ ስለሆነ እና አቅምም ስለሌለኝ የምርመራው ወጪ መሸፈን ያለበት አባት አይደለሁም የሚለው አመልካች ነው በማለት ተከራክራለች፡፡

ተጠሪ ከሣሽ እንደመሆንዋ እንደ ክሱ ያስረዱልኛል ያለቻቸውን ምስክሮች እና የሕክምና ማስረጃ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 223 በተደነገገው መሠረት በዝርዝር ስለማቅረቧ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ከተደረገበት መዝገብ ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰማው ምስክሮችን ብቻ እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ ከማስረጃዎችዋ አንዱ የዲ.ኤን.ኤ /D.N.A/ ምርመራ እንደሆነ በማስረጃ ዝርዝር መግለጫዋ ገልፃ ሳለ ፍ/ቤቱ ግን በዚህ ረገድ የተጠየቀውን ማስረጃ አልሰማም፡፡ ማስረጃውን ያልሰማበትን ሕጋዊ ምክንያት ያለው ስለመሆኑም አልገለፀም፡፡ ምክንያት ያደረገው አመልካች /በወቅቱ ተከሣሽ/ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ አይደለሁም ወይም አልገደድም ብሎአል የሚል ነው፡፡ ክርክር የተደረገበት መዝገብ አስቀርበን እንዳያነው ፍ/ቤቱ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ እንዲደረግ ወይም የምርመራው ውጤት ይቀርብለት ዘንድ የሰጠውን ትዕዛዝ አላገኘንም፡፡ አመልካች ለክሱ የሰጠው መልስ እንዳየነው ደግሞ በራሴ ገንዘብ /ወጪ/ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ለማድረግ አልገደድም የሚል ግልጽ የመከራከሪያ ነጥብ ያለው ነው፡፡ አመልካች ይህን የመከራከሪያ ነጥብ ሊያነሳ የቻለው ተጠሪ የዲ.ኤን.ኤ /D.N.A/ ምርመራው በተከሣሽ /በአሁኑ አመልካች/ ወጪ ይደረግልኝ በማለት በማስረጃ ዝርዝር መግለጫዋ ላይ በመግለጽዋ /በመጠየቅዋ/ እንደሆነም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ፍ/ቤቱ አመልካች የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ የደረሰውም ከዚህ በመነሳት ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱ አካሄድ የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው ተጠሪ ከሣሽ እንደመሆንዋ እንደ ክስ አቀራረብዋ የሚያስረዳላትን ማስረጃ አቅርባ የማሰማት ግዴታ /ሸክም/ አለባት፡፡ የዲ.ኤን.ኤ /የህክምና ማስረጃ/ እንደ ሌሎቹ ማስረጃዎች አንዱ የተጠሪ ማስረጃ ሆኖ በመቆጠሩ ማስረጃው ቀርቦ ይሰማ ዘንድ የማድረግ ግዴታ የተጠሪ እንጂ ማስረጃውን በመከላከያነት ያልቆጠረው የአመልካች ግዴታ ሊሆን አይችልም፤ አይገባምም፡፡ ከሣሽ የሆነው ወገን የከሣሽነት ቃሉን በመስጠት መመሥረት የሚገባውን ጭብጥና ያቀረበውን ክስ የሚደግፍለትን ማስረጃ እንደሚያቀርብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 259/1/ መመልከቱን መገንዘቡም ተገቢ ነው፡፡ የሕክምና ማስረጃው የተቆጠረው በኔ ቢሆንም፤ መቅረብ ያለበት በአመልካች ወጪ ነው የሚለው የተጠሪ ክርክር ሲታይ ከመሠረታዊ የማስረጃ ሕግ መርህ የወጣ እና ከሳሽ እንደሚያቀርብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 259/1/ የተቀመጠውን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላም በኩል የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ የሕክምና ዘዴን /ሳይንሳዊ/ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማድረግ የሚከናወን በመሆኑ የአስረጂነት ዋጋው ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ ፍ/ቤቱም በሂደቱ መጨረሻ እውነት ላይ መድረስ ሲገባው ማስረጃውን ሳይሰማ የሚያልፍበት በቂ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወደ ውሳኔ ያመራው የክርክሩ እና የማስረጃ አሰማም ሂደቱን በሕጉ አግባብ ሳያጠናቅቅ ነው ለማለት ችለናል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተመሣሣይ መንገድ በመከተል ውሳኔውን ከማፅናት አልፎ ማስረጃውን አልሰማም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በክርክር አመራር እና ማስረጃ አቀባበል ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 16229 ሚያዝያ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 94681 ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የሆነችው እና ማስረጃውን የቆጠረችውም ተጠሪ በመሆንዋ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራው መደረግ ያለበት በተጠሪ ወጪ ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ የዲ.ኤን.ኤ /D.N.A/ ምርመራውም በተጠሪ ወጪ እንዲደረግ ትዕዛዝ በመስጠት ውጤቱን ካስቀረበ በኋላ ተገቢውን ይወሰን ዘንድ ጉዳይ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 343/1/ መሠረት ወስነናል፡፡
4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

ዓልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሰኒያ ሼን ተማም - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ በላይነሽ ማቴቦ

2. አቶ ሸሪፍ አህመድ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ ወንድ ከሁለት ሴቶች ጋር ጋብቻ ፈጽሞ ሲኖር ከቆየ በሁዋላ ከአንደኛዋ ጋር በፍቺ ሲለያይ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚስተናገድበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ በጉራጌ ዞን መስቃን ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የመሠረቱት ክስ ይዘት ባጭሩ ሲታይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሲኖሩ በእንሲኖ ከተማ ውስጥ አንድ ክፍል ቆርቆሮ ቤት ማፍራታቸውንና የገጠር መሬት አራት ጥማድ የነበራቸው መሆኑን ገልፀው እነዚህን ንብረቶች 2ኛ ተጠሪ እንዲያካፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም 1ኛ ተጠሪ ጋር የተጋቡት በ1988 ዓ.ም ሆኖ እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ ቆይታ መሄዷንና በ1994 ዓ.ም ሌላ ጋብቻ አለኝ በማለታ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ፈጽማ የነበረችው ጋብቻ እንዲፈርስ መወሰኑን በጋራ ያፈሩት ንብረት አለመኖሩን ንብረቶቹ የተፈሩት ከአሁኗ አመልካች ጋር መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች ወደ ክርክሩ በጣልቃ ገብነት ለመግባት ማመልከቻ አቅርበውና የስር ፍርድ ቤት ፈቅዶላቸው ባቀረቡት ክርክር ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ ፈጽመው ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ያፈሩት አመልካች እንጂ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ያለመሆናቸውን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የገጠር መሬትን በተመለከተ የጋራ ባለይዞታዎች የአሁኗ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ መሆናቸውን የቆርቆሮ ቤቱን በተመለከተ ግን የጋራ ባለሀብቶች ተጠሪዎች ስለሆኑ እኩል ሊካፈሉ የሚገባቸው መሆኑን ገልፆ ወስኗል፡፡ በዚሁ የቆርቆሮ ቤቱን በተመለከተ በተሰጠው የውሣኔ ክፍል አመልካች ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉት ፍ/ቤቶች ይግባኝና የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፋት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዙቱም ባጭሩ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ በ1980 ዓ.ም በመመስረት አከራካሪውን ቤት ስለማፍራታቸው ማስረጃ አቅርበውና አረጋግጠው ባለበት ሁኔታ ንብረቱ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የአመልካችና 2ኛ ተጠሪ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ በእንሲኖ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት የተሰራ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ እንዳለ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሣያል ስለሆነም ቤቱ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ጋብቻ ፀንቶ እያለ የተሰራ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ንብረቱ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 30 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካችና የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ሕጋዊ ጋብቻ በ1980 ዓ.ም መሥርተው እስካሁንም አንድ ላይ ያሉ መሆኑን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ከአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ጋር በ1988 ዓ.ም ጋብቻ መሥርተው እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ ከኖሩ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ጥለው በመሄድ በሌላ ቦታ ቆይተው በ1994 ዓ.ም የፍቺ ጥያቄ አቅርበው መለያየታቸውን በእንሴኖ ከተማ ውስጥ ይገኛል በተባለው ቦታ ቀድሞውንም የሳር ቤት የነበረና ይህ ቤት ፈርሶ 2ኛ ተጠሪና አመልካች አንድ ላይ ሁነው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት መስራታቸው በማስረጃ መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት አይገባቸውም በማለት ሊወስን የቻለው ቤቱ የተሰራበትን ቦታ የያዙበትን መንገድና መቼ እንደያዙ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ መብት የሌላቸው መሆኑን አላስረዱም፣ ንብረቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የጋራ ስለማድረጋቸውም የሚያሣይና በፍርድ ቤት የተመዘገበ የፅሑፍ ማስረጃ አላቀረቡም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ከሣሽ ክስ ሊመሠርት የሚገባው ለክሱ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለው ስለመሆኑ በማረጋገጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ለክሱ ምክንያት በሆነው ነገር ላይ ከሣሹ መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ የከሣሽ እንጂ የተከሣሽ ሊሆን አይገባም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት መብት የላቸውም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች የተወሰነው 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት የሌላቸው ስለመሆኑ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ ምስክሮች አልተመሰከረም በሚል ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ቤቱ የተሰራው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በጋብቻ ፀንተው በነበሩበት ጊዜ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን የአመልካችን ክርክር ውድቅ ሊያደርግ የቻለው ቦታው በምን መልኩ እንደተያዘና መቼ እንደተያዘ እንዲሁም ቤቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የጋራ ስለመደረጉ በፍርድ ቤት የተመዘገበ ማስረጃ አላቀረቡም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባዶ ቦታ ባለቤትነቱ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝቦች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገመንግሥትና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተረጋገጠ ሲሆን አንድ ሰው በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት በሕጉ አግባብ የተሰጠው የባለይዞታነት መብቱ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው በተገቢው መንገድ ባለይዞትነቱን ሲያረጋግጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ የነበራቸው ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን አከራካሪው ንብረት ግን በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ የተሰራ እንጂ በ1ኛ ተጠሪና በ2ኛ ተጠሪ የተሰራ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ የነበራቸው ቢሆንም ጋብቻቸውን በ1990 ዓ.ም ትተው መሄዳቸውና አከራካሪው ቤትም በዚሁ ወቅት ስለመሰራቱ መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት የውሣኔ ግልባጭ ያሣያል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ጋብቻቸውን በተገቢው መንገድ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያፈረሱት በ1994 ዓ.ም ቢሆንም ለአከራካሪው ቤት መሰራት ግን ያደረጉት አስተዋጽኦ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም፡፡ በእርግጥ ጋብቻው በሕጉ አግባብ ሣይፈርስ የተፈራ ንብረት የባልና ሚስት የጋራ ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ነጥብ ነው፡፡ ሆኖም ጋብቻው በተገቢው መንገድ ሣይፈርስ ጋብቻውን ትቶ የሄደ ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት ሌላው ተጋቢ ያፈራውን ንብረት የጋብቻ ውጤት ነው በማለት የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ ንብረቱ በዚህ ሁኔታ የተፈራ ስለመሆኑ የተረጋገጠ የሆነ እንደሆነ ጋብቻውን ትቶ የሄደ ተጋቢ ንብረቱ የጋራ ነው የሚለውን የሕግ ግምት ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም፡፡ ለንብረቱ መፈራት ምክንያት የሆነው ተጋቢ የንብረቱ የግል ባለሀብት ይሆናል እንጂ ምንም አስተዋጽኦ ያላደረገ ተጋቢ እንዲካፈል ማድረግ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/1/ስር የተቀመጠውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚጥስና የሕግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ የቤተሰብ ሕጉ በጋብቻ ጊዜ የተፈራ ንብረት የጋራ ነው የሚል ሕጋዊ ግምት የወሰደውም ተጋቢዎች ለንብረቱ መፈራት የየራሣቸውን አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ታሣቢ በማድረግ ነው ተብሎም ይገመታል፡፡ ይህ ግምት ግን በተቃራኒ ማስረጃ የማይስተባበልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ ጋብቻው በሕጉ አግባብ ሣይፈርስ አንደኛው ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት ቀሪው ተጋቢ ሌላ ሰው አግብቶ ንብረቱን ማፍራቱ በሚገባ እስከተረጋገጠ ድረስ ጋብቻውን ትቶ የሄደ ተጋቢ በሌላ ጊዜ በመምጣት በሌለበት የተፈራውን ንብረት ልካፍል በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ በሕገ መንግሥቱ ስለንብረት ማፍራት መብት የተደረገውን ጥበቃ እና በቤተሰብ ሕጉም ስለባልና ሚስት የጋራ ንብረት የተዘረዘረትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መሠረት ያደረገ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች አከራካሪውን ንብረት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት ሁኖ እያለ ድርሻ የላቸውም የተባለው ያላግባብ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በእንሴኖ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ቆርቆሮ ቤት እኩል ሊካፈሉ የሚገባቸው ተጠሪዎች ናቸው በማለት የሰጡት የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር እኩል መብት ያላቸው አመልካች እንጂ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ /ወ/ሮ በላይነሽ ማተቦ/ አይደሉም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ተ.ወ የማየነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 65621

ሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ታደለች መንግስቱ - ቀረበች

2. ኢሣያስ ሐለፎም - ቀረበ

3. ወ/ሪት ረድኤት ሐለፎም

4. ወ/ሮ ገነት ሐለፎም

5. ያዕቆብ ሐለፎም

ተጠሪ፡- - የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሚስትነት እና የወራሽነት ማረጋገጫ ይሰጠን በማለት የቀረበውን አቤቱታ /ጥያቄ/ የሚመለከት ነው፡፡ አቤቱታው የቀረበው በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፣ ፍ/ቤቱ ሟች /የ1ኛ አመልካች ባለቤት እና የሌሎቹ አመልካቶች አባት/ ከዘጠኝ አመት በፊት ወደኤርትራ ተመልሶ የኤርትራ ነዋሪ መሆኑን አረጋግጫለሁ /ተገንዝቤአለሁ/ በማለት አቤቱታውን ሣያስተናግድ ቀርቶአል፡፡ በዚህ ብይን ላይ አቤቱታ የቀረበላቸው የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠ/ፍ/ቤትም ብይኑ ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካቾችን ይግባኝ ሰርዘዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካቾች የካቲት 15 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን አቤቱታው ከቀረበበት ብይን እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ በሰበር ችሎቱ ሊመረመር ይገባል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ ሟች የኤርትራ ነዋሪ ናቸው በማለት የአመልካቾች ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት የሰጠው ብይን እንዳየነው የአመልካቾች ጥያቄ ማስረጃ ይሰጠን የሚል ነው ቢባልም ፣ የጠቀሱት ድንጋጌ /ህግ/ ግን በፍ/ብ/ህግ ቁ. 826/1/ የተመለከተው ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የአመልካቾች ኃላፊነት ከሟች ጋር ያላቸውን ግንኙነት /ዝምድና/ ተረጋግጦ ውርሱ እንዲከፈትላቸው መሆኑን ነው፡፡ በእርግጥም ሟች የሞተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኤርትራ ውስጥ እንደሆነ በአቤቱታቸው ላይ ገልጸዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ይህን መሠረት በማድረግ ብቻ ሚች ዋና መኖሪያው ስፍራ ኤርትራ ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በበኩላችን እንደምናየው ግን ሚች ወደ ኤርትራ ሄዶ ሣይመለስ እዛው በመሞቱ ብቻ ዋና መኖሪያው ስፍራ ኤርትራ ነው ወደሚለው ብቸኛ መደምደሚያ መድረሱ ትክክል አይደለም፡፡

ከአመልካቾች አቤቱታ መገንዘብ እንደቻልነው ሚች በመደበኛነት ሲኖር የነበረው በሐረር ከተማ ውስጥ ከአመልካቾች /ሚስቱ እና ልጆቹ/ ጋር ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ወታደር እንደነበር ፣ ከወታደርነት በጡረታ ከተገለለ በኋላም በመካኒክነት ስራ በግሉ ተሰማርቶ ከቦታ ወደቦታ እየተዘዋወረ ሲሰራ እንደነበር ወደ ኤርትራ የሄደውም በዚሁ የመካኒክነት ስራ ለመስራት ሲሆን ፣ ጊዜውም በየካቲት ወር 1990 ዓ.ም እንደሆነ ፣ በኋላ ወደቤተሰቦቹ /ሐረር/ ሊመለስ ያልቻለው በግንቦት ወር 1990 ዓ.ም በተነሣው የድንበር ግጭት /ጦርነት/ ምክንያት መውጣት ባለመቻሉ እንደሆነ ፣ ዜግነቱም ኢትዮጵያዊ እንደሆነ አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት ገልጸዋል፡፡

የስር ፍ/ቤቶች እነዚህን ሁኔታ እውነት ስለመሆን አለመሆናቸው ለማጣራት ስለመሞከራቸው በብይኑ አልተገለጸም፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው ለሰጡት ብይን ዋና መሠረት ያደረጉት ሚች ወደ ኤርትራ ከሄደ በኋላ ሣይመለስ እዛው ሞቶአል የሚለውን ፍሬ ነገር ብቻ እንደሆነም ነው ለማየት የቻልነው፡፡ ይህ አይነቱ አካሄድ እንዳለ ተቀባይነት ይኑረው ቢባል ለስራ ወይም ለተለያዩ ምክንያቶች ከአገራቸው ወጥተው ሣይመለሱ ሊሞቱ በሚችሉት ኢትዮጵያውያን የውርስ አከፋፈት ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል መገመቱ አይከብድም፡፡ በፍ/ብ/ህግ ቁ. 826/1/ የተመለከተው ድንጋጌ፤ በተለይም "...ዋና መኖሪያው ስፍራ..." የሚለው ሐረግ መተርጐም ያለበትም ከዚህ አንጻር እየታየ ሊሆን እንደሚገባ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ይህን ታስቢ በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ብይን ስናየው ለጉዳዩ አወሣሰን አግባብነት ያላቸው ፍሬ ነገሮች በአግባቡ ሣይጣሩ የተሰጠ ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሐረር ህዝብ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 33899 ህዳር 21 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣ የሐረር ህዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 07698 ጥር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና በሐረር ህዝብ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01792 ጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የሐረር ህዝብ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካቾች ያቀረቡለትን አቤቱታ በተከፈተው መዝገብ ማሰማቱን እንዲቀጥል ፣ ይህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያላቸው ናቸው ያላቸዉን ሁኔታዎች እና ሌሎችም ፍ/ቤቱ አግባብነት አላቸው የሚላቸዉን ፍሬ ነገሮች እንዲያጣራ በመጨረሻም ፍሬ ነገሮችን አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

እ.ከ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኅዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ውልታ ደስታ ወ/ማሪያም - ወ/ኤያስ እጅጉ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ደጅይጥኑ ደስታ ወ/መሪያም አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እቱቴ ደስታ ጠ/መታሰቢያ ፈቃዱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ንብረት አጣሪ እንዲሾም አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በይርጋ ታግዷል ተብሎ መወሰኑን በመቃወም ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ ይዘት መረዳት እንደተቻለው የመልካቾች እና የተጠሪ አውራሽ ሟች ወ/ሮ በቀለች ደስታ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በ1977 ዓ.ም ሆኖ አመልካቾች የውርስ ንብረት አጣሪ ተሹሞ በተጠሪ እጅ ያለ የውርስ ንብረት ተጣርቶ እንዲቀርብ ለፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም በመሆኑ አቤቱታው ከ22 ዓመታት በኋላ የቀረበ ነው ስትል ተጠሪ ያቀረበችው መቃወሚያ የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1677/1/ እና 1845 መሰረት የ10 ዓመት ጊዜ አልፎበታል ሲል አቤቱታውን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ሰርዟል፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት ወደ ስማቸው ያዛወሩት በ1997 ዓ.ም ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ይርጋ አቆጣጠርን በሚመለከት በሥር ፍ/ቤቶች ግምት ውስጥ ያለመግባቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት የሰጡት መልስ የውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጥያቄ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ሟች ከሞቱበት ጊዜ እንጂ ስመ ሐብቱ በተጠሪ ከተዛወረበት ጊዜ ሊሆን እንማይገባ ገልፀው የስር ችሎቱ የሰጠውን ውሳኔ መዝገብ በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካቾችም ሆኑ ተጠሪ የሚች ወ/ሮ በቀለች ደስታ ወራሾች መሆናቸው አላከራከረም፡፡ ሚች ወ/ሮ በቀለች ደስታ የሞቱት በ1977 ዓ.ም ስለመሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ ሆኖ ሳለ የሚች የውርስ ንብረት በተጠሪ ተይዟልና የውርስ ንብረት አጣሪ ይሾምልኝ ሲል አመልካቾች ሥር ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡

እንግዲህ ግራ ቀኙ የሚች ወራሾች መሆናቸው እስከተረጋገጠ ድረስ የውርስ ንብረት በአንደኛው ወራሽ እጅ ነውና ውርስ አጣሪ ተሾሙ ይጣራልን የሚለውን ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው እስከመቼ ጊዜ ድረስ ነው? የሚለው ጉዳይ ምላሽ የሚያሻው ነው፡፡ በዚህ ረገድ ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ የሰበር መዝገቦች የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 17937 የሰጠው የሕግ ትርጉም እንደሚያስገነዝበው በወራሾች መካከል የሚነሳ የውርስ ንብረት ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ በተደነገገው አግባብ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ሲሆን ወራሽ በሆነ እና ወራሽ ባልሆነ ተከራካሪ ወገን መካከል የሚቀርበው የውርስ ንብረት ጥያቄ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1677 እና 1745 መሰረት በአሥር /10/ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ መብቱ በይርጋ እንደሚታገድ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በፌዴራልም ሆነ በክልል ፍ/ቤቶች ተፈፃሚነት እንደሚኖረው አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ በሥር ፍ/ቤት የተጠቀሰው 10 ዓመት ጊዜ ሳይሆን 3 ዓመት ጊዜ ገደብ ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች አጥብቀው የተከራከሩት ተጠሪ ቤቱን እንድትጠቀም የተደረገው በግራ ቀኙ መካከል በተደረገ ስምምነት እና ተጠሪ ታላቅ እህታችን በመሆኗ በአዘኔታና በአክብሮት ስለሆነ ይርጋ ሊቆጠርብን አይገባም የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1853/1/ እንደሚያመለክተው በግራ ቀኙ መካከል ያለው ዝምድና ወይም ታላቸርነት፤ የመፍራት ወይም የማክበር ስሜት መኖር ሲታመን የይርጋ መቃወሚያ ቀጣይነት ሊያጣ እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር በስምምነትና በአክብሮት ስሜት እንድትኖር ፈቅደናል ብሎም ፍ/ቤቱን ሊያሳምን የሚችል ማስረጃ እንዳላቀረቡ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በግልጽ ያመላክታል፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቾች ክርክር ለመቀጠል አልተቻለም፡፡ ከዚህም ሌላ የይርጋ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው ተጠሪዋ የቤቱን ስመ ሐብት ወደ ራሷ ካዛወረችበት ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ሊሆን ይገባል የሚል አማራጭ ክርክር በአመልካቾች በኩል ቀርቧል፡፡ በዚህ ረገድም ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መ/ቁ. 36975 በሰጠው ውሳኔ እንደተመለከተው የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ቤቱን በእጅ ካደረገበት ጊዜ እንጂ ስመ ሃብቱን በስሙ ካዞረበት /ካደረገበት/ ጊዜ ስላለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ እንደቅድመ ሁኔታ እንዳልተቀመጠ ጠቅሷል፡፡ በዚህም አግባብ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ /እንዲሁም የሰበር መ/ቁ. 44932 ይመልከቱ፡፡/

በአጠቅላይ የውርስ ንብረት አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1000/1/ መሰረት ሚች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ ይህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰበር ችሎት በተለያዩ የሰበር ችሎቱ መዝገቦች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰጠቱን ከተያዘው ጉዳይ ጋር በማገናዘብ የሥር ፍ/ቤት በአሥር ዓመት ይርጋ የአመልካቾች ጥያቄ ቀሪ ሆኗል የሚለው ምክንያት ከሰበር ችሎቱ ትርጉም የሚጣጣም ባይሆንም በውጤት ደረጃ ግን የአመልካቾች ጥያቄ በ3 ዓመት ይርጋ ቀሪ መሆኑን ስለተረዳን ውሳኔውን በውጤቱ ተስማምተን አጽንተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29647 ሰኔ 19 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83973 ኅዳር 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በውጤቱ ብቻ በመስማማት አጽንተነዋል፡፡
2. የአመልካቾች ጥያቄ በ3 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 03 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሚስስ ሚላን ፒሲጂ ማልጂ

ሚስስ ሲልቪ ፒሲጂ ጠበቃ የሸጥላ አስፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ሐንድሬ ፒስ ማልጂ

2. ወ/ሪት ሞኒካ ፒስጂ ማልጂ ወኪል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍርድን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት ፍርድ መቃወሚያ የሚቀርብበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ከሣሽ የነበሩ ሲሆን ተከሣሽ ሚስተር ጆርጅ ፔስልዲ ማልጂ ነበሩ፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች የአያታቸውን የማዳም ፔግሩሂ ፔስጂ ማልጂ ወራሾች መሆናቸው እንዲጣራላቸው ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ውርስ አጣሪው ተሹሞ ውርስ ተጣርቶ ቀርቦ ፍርድ ቤቱ ከመዘገበው በሁዋላ ይህንኑ በመያዝ የውርስ ሐብት ክፍፍል ድርሻ ይገባናል በማለት በስር ተከሣሽ ሚስተር ጆርጅ ፔስጂ ማልጂ ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ ክርክሩ ከተካሄደ በኋላም የውርስ ሐብቱን የአሁኑ ተጠሪዎች እና ሚስተር ጆርጅ እንዲካፈሉት ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ የአሁኑ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ያቀረቡትም ከዚሁ የውርስ ሐብት ክፍፍል በኋላ ነው ፡፡ የአሁኑ አመልካች የመቃወሚያ አቤቱታ ይዘትም የሟች እናታችንና የሟች እህታችን ወራሾች በመሆናችን በተወላጅነት ከእናታችን፣ በተተኪነት ደግሞ የእህታችንን ድርሻ ስለሚገባን የተሰጠው የውርስ ሐብት ክፍፍል ውሣኔ መብታችን ስለሚነካ ፍርዱ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአሁኑ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ለስር ከሣሾችና ተከሣሽ እንዲደርስ አድርጎ አቤቱታቸውን ከሰማ በሁዋላ ውርሱ የተጣራው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሾመው የውርስ አጣሪ መሆኑን ይህ የውርስ ሪፖርት ደግሞ የአሁኑን አመልካችን የማያውቃቸው መሆኑን በመግለጽ የፍርድ መቃወሚያው ሪፖርቱን ለአፀደቀው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሚቀርብ በስተቀር የውርስ ሐብት ክፍፍል ውሣኔ ለሰጠው ፌዴራል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የለም በሚል ምክንያት የአመልካችን ጥያቄ ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 05 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የውርስ አጣሪ ሪፖርት አመልካችን ያላካተተ ከመሆኑም በላይ ከማስረጃነት አልፎ እንደፍርድ የማይቆጠር በመሆኑ ተቃውሞው ሪፖርቱን ለአፀደቀው ፍርድ ቤት ይቅረብ መባሉ ያለአግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ የተጠሪዎች ጠበቃ ቀርበው ህዳር 03 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሶስት ገጽ ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ህዳር 29 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ አንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አመልካች መቃወሚያ ማቅረብ መደረጉ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በመሠረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ የክርክሩ ተሣታፊ ያልሆነ ወገን አንድ በሕግ አግባብ የተሰጠ ፍርድ የሚቃወምበትን ሥርዓት የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ የአቤቱታው አቀራረብን በተመለከተም ሥነ ሥርዓት ሕጋችን በቁጥር 359 ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው የክርክሩ ተሣታፊ ያልሆነ ወገን መብቱን ወይም ጥቅሙን የሚነካ ፍርድ ከተሰጠ ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት መቃወም የሚችል መሆኑንና ፍርድ ቤቱም የመቃወሚያ አቤቱታው በተገቢው ሥርዓትና በተገቢው ማስረጃ የተደገፈ ሁኖ ከአገኘው ቀድሞ የሰጠውን ፍርድ ማረም የሚችል መሆኑን ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች አቤቱታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌን መሠረት አድርጎ የቀረበ መሆኑን ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያለመሆኑን ከመመርመራችን በፊት በውርስ ሕጋችን ስለውርስ አጣሪ ስልጣን የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መመልከት ለጉዳዩ አወሳሰን አስፈላጊ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

ውርስ አጣሪ በሟች ንብረት ላይ መብት አለን የሚሉትን ወገኖችን ወይም ወራሾችን የመወሰን፣ የሟች ኑዛዜ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥና በኑዛዜው ተጠቃሚዎችን የመለየት ውርሱን የማስተዳደር የውርሱን ተከፋይ ገንዘብ መሰብሰብና እዳዎችን መክፈል፣ የሟች ንብረት ማጣራትና ማፈላለግ እንዲሁም የኑዛዜ ስጦታዎችን የመክፈል ሥልጣን ያለው መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 944፣ 946 እና 956 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 960 ድንጋጌ ሲታይም የውርስ አጣሪው የማጣራቱን ተግባር ከአከናወነ በኋላ ሪፖርቱ ለወራሾችና ለፍርድ ቤት ማቅረብ እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ በዚሁ መሠረትም ተገቢው ክርክር ከተደረገ በኋላ የውርስ ማጣራቱ ተግባር ሲጠናቀቅ በአጣሪው ሪፖርት መሠረት ወራሾች የወራሽነት ምስክርነት ወረቀት /Certificate of Succession/ ከፍርድ ቤቱ እንደሚሰጥ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 996 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም የውርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጣሪ ስልጣኑና ተግባሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የማጣራቱ ውጤትም እያንዳንዱ ወራሽ ከውርሱ የሚደርሰውን ድርሻ ተለይቶ የወራሽነት የምስክር ወረቀት የሚሰጥ መሆኑ በሕጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌዎቹ የሚያስገነዝቡት ውርሱ ተጣርቶ ለወራሽ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ወራሹ የምስክር ወረቀቱን መሠረት በማድረግ የውርስ ሀበት ክፍፍል መፈፀም፣ በወራሾች መካከል አለመግባባት ከአለ የክፍፍሉን ጥያቄ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት የሚያቀርብ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍርድ ቤት መጽደቅ በራሱ ፍርድ ሁኖ ለአፈፃፀም የሚቀርብ ሣይሆን እንደማስረጃ የሚያገለግል ነው፡፡ በመሆኑም ሪፖርቱ የማስረጃነት ዋጋ አለው ከተባለ ደግሞ የክፍፍሉ ክርክር ሲቀርብ በማስረጃነቱ ላይ ክርክር ቢቀርብ ክርክሩ መቅረብ ያለበት በውርስ አጣሪና ሪፖርቱን በአፀደቀው ፍርድ ቤት ነው ተብሎ ውድቅ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በውርስ ሐብት ድርሻ ያላቸው መሆኑንና የድርሻቸው መሠረትም ከሟች ጋር ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ እና የተተኪነት ወራሽነት መሆኑን ይህ ሁኖ እያለ በውርስ አጣሪ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑን ገልፀው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀረበው የክፍፍል ጥያቄ የተሰጠው ውሣኔ መብታቸውን ሊነካ የሚችል መሆኑን ጠቅሰው መብታቸው እንዲጠበቅ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ አቀራረብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌን መሠረት ያደረገ ሲሆን የአመልካችን መብት ይነካል የተባለው እና ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የተሰጠው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ከማስረጃነት ዋጋ ውጪ ሌላ ዋጋ የሌለውን የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት ሊቃወሙ ይገባል የሚባልበት አግባብ የለም፡፡ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍርድ ቤት መጽደቁ ሪፖርቱን ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የሚያደርገው አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ የተደረገው የውርስ አጣሪ ኃላፊነትና ተግባር እንዲሁም የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍርድ ቤት መጽደቅና ውጤቱ ምን እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ መንፈስና ይዘት ጋር ባልተገናዘበ መልኩ ሁኖ ስለአገኘነው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 44715 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመ/ቁጥር 42272 መጋቢት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችሉት በውርስ ሐብት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ውሣኔ ለሰጠው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንጂ የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን ለአፀደቀው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አይደለም ብለናል፡፡
3. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀብሎና የግራ ቀኙን ቀሪውን ሁሉን ክርክር በመመርመር ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ 1. አቶ ነስሩ ሰማን ቀረቡ

2. አቶ አብዱራህማ ሰማን ቀረቡ

ተጠሪ፣ ወ/ሮ መህሊሣ ኒጋኒ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች በአቶ ሰማን መሐመድ ላይ ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ጋብቻቸው በፍች የፈረሰ መሆኑን ገልፀው በኮልፌ ቀራንዩ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 የቤት ቁጥር 808 የጋራ ንብረት ስለሆነ እንዲያካፍለኝና ሌሎች ንብረቶችንም እንዲያካፍለኝ በማለት ክስ መሥርተዋል አመልካቾች ወላጅ አባታቸው አቶ ሰማን መሐመድ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን ገልፀው በክርክሩ ጣልቃ ገብተው ባቀረቡት ክርክር በኮልፌ ቀራንዩ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 የቤት ቁጥር 808 አመልካቾች ሚች አባታችን ከመጋባታቸው በፊት የነበረ ስለሆነ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው የቃል ክርክር የአመልካቾች ወላጅ አባትና ተጠሪ ከተጋቡ በኃላ ከዋናው ቤት ውጭ ያሉት ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤቶች የተሠሩ መሆኑንና ዋናው ቤት ተጠሪ ከሚች ጋር ከመጋባታቸው በፊት 1949 ዓ.ም የተሰራ መሆኑን ምስክሮች ያረጋገጡ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው ካሰፈረ በኃላ 1949 ዓ.ም የተሰራ ቤት እስካሁን ይኖራል ተብሎ አይገመትም በማለት ደምደሚል በውሣኔው ማጠቃለያ በኮልፌ ቀራንዩ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ቁጥር 808 ተመዝግቦ የሚገኘው ከዋናው ቤት ውጪ ያሉ ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤቶች ተጠሪና የሚች የጋራ ንብረት ነው የቤቶቹን ግማሽ ተጠሪ ወስደው ግማሹን አመልካቾች ይካፈሉት ካልተቻለ ዋናው ቤት በመሀንዲስ ተገምቶ ከተሸጠ በኃላ ይከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፅንቶታል፡፡ አመልካቾች ለሰበር ባቀረቡት አቤቱታ በኮልፌ ቀራንዬ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ቁጥር 808 የሚች አባታችን የግል ንብረት ነው፡፡ ተጠሪ በዋናው ቤት ላይ ድርሻ አላቸው ሣይባል ዋናው ቤት በመሀንዲስ ተገምቶ እንዲሸጥ በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው እኔ ሚች አቶ ሰማን መሐመድና ወ/ሮ መህድያ መሐመድ ያፈሩትን ንብረት በማመን ተከራክሬለሁ የሰርቪስ ቤቶቹ እኔና አቶ ሰማን መሐመድ በጋብቻ ባለንበት ጊዜ የተሰሩ ስለሆነ የጋራ ንብረቱ ናቸው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በኮልፌ ቀራንዬ ቀበሌ 16 ቁጥሩ 808 የሆነው ዋናው ቤት ሚች ሰማን መሐመድ ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት የተሰራ መሆኑን ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የቃል ክርክር ያመኑ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው የተመዘገበ ሲሆን የቤት ቁጥር 808 የሆነው ዋናው ቤት ተጠሪ ከሚች አቶ ሰማን መሐመድ ጋር ከመጋባታቸው በፊት የተሰራ መሆኑ በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በኮልፌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 የሚገኘው የቤት ቁጥር 808 ዋናው ቤት የተጠሪ የጋራ ንብረት አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ሚች ጋር ጋብቻ ከመሠረቱ በኃላ ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤት የተሰራ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በኮልፌ ቀራንዬ ክፍለ ከተማ የቤት ቁጥር 808 ይዞታ ሥር የተሰሩት ሰርቪስ ቤቶች እና ሽንት ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት ናቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪ የጋራ ንብረቶች ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤቱ መሆኑን ካረጋገጡ በኃላ የኮልፌ ቀራንዬ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 የሚገኘው 808 ዋናው ቤት በመሀንዲስ ተገምቶ እንዲሸጥና በሚች ወራሾችና ለተጠሪ እንዲከፋፈል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና የተሻሻለውን የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ የሚጥስ ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. በኮልፌ ቀራንዬ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ቁጥሩ 808 የሆነው ዋናው ቤት የተጠሪ የጋራ ንብረት አይደለም ብለናል፡፡
3. በኮልፌ ቀራንዬ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ቁጥሩ 808 ከሆነው ዋና ቤት ውጭ የተሰሩ ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤት የተጠሪና የሚች አቶ ሰማን መሐመድ የጋራ ንብረት ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. የሚች አቶ ሰማን መሐመድ ወራሾችና ተጠሪ ከዋናው ቤት ውጭ ያሉትን ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤት በአይነት ይከፋፈሉ፡፡ ሰርቪስ ቤቶቹንና ሽንት ቤቶቹን በአይነት ለመከፋፈል የማይቻል ከሆነ ሰርቪስ ቤቶችና ሽንት ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ግማሹ ለተጠሪ ቀሪውን ደግሞ የሚች ወራሾች ይውሰዱ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡ ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 12 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስመረት ነጋሲ በይን አቶ ግርማቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ጽጌረዳ ስዩም ከነጠበቃቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ለቀረበው ጉዳይ መነሻ ሆኖ የተገኘው ሟች አቶ ወልደማርያም ወልደጋብር ሐምሌ 29 ቀን 1996 ዓ.ም በፍታብሄር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት አድርገዋል የተባለው ግልጽ ኑዛዜ እንዲፀድቅ ተደርጐ በዚሁ በፍትሐብሄር ሕጉ ቁጥር 996(1) መሠረት የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ይሰጠኝ በሚል ቀርቦ የነበረ ጥያቄ ነው፡፡

ሟች ኑዛዜውን አድርገዋል የተባለው ለአሁኗ አመልካች ሲሆን የአሁኗ አመልካችም የኑዛዜ ይጽደቅልኝ ጥያቄውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ በኑዛዜው ሰነድ በምስክርነት ፈርመዋል የተባሉት ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ካደረገ በኋላ ምስክሮቹ በአቤቱታው መሠረት አስረድተዋል የኑዛዜው የሰነድ ማስረጃም ቀርቧል፡፡ ስለዚህ ኑዛዜው ፀድቋል አመልካችም የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጧል የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁኗ ተጠሪ ወ/ሮ ጽጌረዳ ስዩም በዝምድና የዘር ሐረግ የሟች ወራሽ እኔ ነኝ፤ አመልካች ሟች ኑዛዜ አድርገውልኛል ያሉት ሀሰት ነው የቀረበው የሟች ኑዛዜ አይደለም በኑዛዜው ላይ የሰፈረው ፊርማ የሟች አይደለም በሚል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ በማቅረባቸው የኑዛዜው ጉዳይ እንደገና እንዲጓቀሳቀስ ተደርጓል፡፡ ፍ/ቤቱ በኑዛዜው ጉዳይ ላይ ሁለቱን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በመቃወሚያ አቅራቢ በኩል በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሰፈረው ፊርማ የሟች አይደለም ተብሎ ስለተካደ በሰነዱ ላይ በጣት አሻራ የተፈረመው የሟች መሆን አለመሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ ተጣርቶ ውጤቱ ይቅረብ ብሎ አዞ የቴክኒክ ባለሙያው ፊርማውን ከሌሎች ፊርማዎች ጋር ለማመሳከር አልተቻለም የሚል መልስ በመስጠቱ ሌላ የሰማው ማስረጃ ሣይኖር ወደ ውሣኔ መስጠት አምርቷል፡፡ በሰጠው ውሣኔም መቃወሚያ አቅራቢዋ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች አይደለም ቢሉም የሟች ፊርማ ስላለመሆኑ ለማስረዳት አልቻሉም በሚል ምክንያት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 360(2) መሠረት አጽድቆታል፡፡ በዚሁ ውሣኔው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቃወሚያ አቅራቢዋ የአሁኗ ተጠሪም የሚች ህጋዊ ወራሽ መሆኔ ይረጋገጥልኝ ብለው ያቀረቡትን ጥያቄም አብሮ በማየት የሚች ወራሽ ናቸው ብሏል፡፡

በአሁኗ ተጠሪ የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ጉዳዩ ቀርቦለት የተመለከተው የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም መርምሮ ይግባኙ አያስቀርብም ብሎታል፡፡

በእነዚህ ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ አቤቱታ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ሰበር ችሎት ደግሞ በጉዳዩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ በመጨረሻም መርምሮ ኑዛዜው ይጽደቅልኝ ብለው ያቀረቡት የአሁኗ አመልካች በኑዛዜው ላይ ያለው የሚች ፊርማ ስለተካደ የሚች ፊርማ ስለመሆኑ በሕጉ የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ ነገር ግን አመልካች የሚች ፊርማ ስለመሆኑ ለማስረዳት ያሰሙት ማስረጃም ሆነ ለማሰማት ያዘጋጁት ምስክር የለም፣ ስለዚህ የሚች ፊርማ ስለመሆኑ ስላላስረዱ የሚች የኑዛዜ ወራሽ መሆን አለብኝ በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ይኼው ሣይረጋገጥ ወ/ሮ አስመረት ነጋሲ የሚች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሠረት ተሽሯል የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም በከተማ ነክ ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል ምክንያት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) መሠረት የቀረበ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ በመባሉ ማመልከቻው ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮላቸው እንዲቀርቡ ተደርጐ የግራ ቀኙ ጠበቆች በተገኙበት ክርክሩ ተሰምቷል፡፡

የአመልካች ጠበቃ አመልካች በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለው የጣት አሻራ ፊርማ የሚች ስለመሆኑ አስቀድመው ምስክሮች አቅርበው በማረጋገጥ ውሣኔ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ መቃወሚያ ካቀረቡ በኋላም ቢሆን በሰነዱ ላይ ያለው የጣት አሻራ የሚች ስለመሆኑ በምርመራ ይጣራ ተብሎ ሲላክ ቀለም የበዛበት ስለሆነ ከሌሎች ፊርማዎች ጋር ማመሳከር አይቻልም ተብሎ ተመለሰ እንጂ የሚች ፊርማ አይደለም አልተባለም፣ ስለዚህ ተጠሪዋ የሚች ፊርማ አይደለም ካሉ የማስረዳት ሸክሙ የተጠሪዋ እንጅ የአመልካች ሊሆን አይችልም የሚል ክርክር ያቀረቡ ሲሆን የተጠሪዋ ጠበቃ ደግሞ በቀረበው መቃወሚያ መነሻ በሰነዱ ላይ ያለው ፊርማ የሚች መሆን አለመሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ ተጣርቶ እንዲቀርብ ታዞ ተልኮ ቀለም የበዛበት በመሆኑ የሚች ፊርማ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አይቻልም ተብሎ ስለተመለሰ በተጠሪዋ በኩል የሚች ፊርማ ስላለመሆኑ አስረድተናል የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለው የጣት ምልክት ፊርማ የሚች ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ያለበት የትኛው ተከራካሪ ወገን ነው በሚል የተነሣውን ክርክር በተመለከተ በኑዛዜው የሰፈረውን ቃልና ኑዛዜው መኖሩን ማስረዳት ያለበት በዚሁ ኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ የሚለው ሰው መሆኑን የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 896 ያስረዳል፡፡

የአስረጂውን አይነት በሚመለከት በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 897(1) ላይ እንደተመለከተው በግልጽ ወይም በተናዛዡ ጽሑፍ የተደረገ ኑዛዜ ስለመኖሩ የሚረጋገጠው የኑዛዜውን ጽሑፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዋናውን በማቅረብ ወይም ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ሰው ዘንድ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ሹም ትክክለኛ ሆኖ በተመሰከረ አንድ ግልባጭ በማቅረብ ነው።

እንዲህ አይነቱን ኑዛዜ አድርጓል የተባለው ሰው ህጋዊ ወራሽ መሆኑ የታወቀ ሰው በኑዛዜው ላይ የሚያቀርበውን የተቃውሞ ክርክር በተመለከተም በፍትሐብሄር ሕግ አንቀጽ 1677(1) ላይ ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም ስለውሎች በጠቅላላው የተመለከቱት ደንቦች በማሚያነት ይፈፀሙባቸዋል ተብሎ በተደነገገው መሠረት ስለውል ጉዳይ ማስረጃዎች በሚመለከተው ምዕራፍ ሥር የሚገኘው የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2007(2) ለኑዛዜም ጉዳይ ስለሚያገለግል ወራሹ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ ወይም ጽሑፍ የአውራሹ ስለመሆኑ አላውቅም ማለቱ ብቻ ይበቃል። ፊርማው ወይም ጽሕፈቱ የሱ ነው የተባለው ሰው ስለመሆን አለመሆኑ ለማረጋገጥ ደግሞ ዳኞች እንዲመረመር ሊያዙ እንደሚችሉ የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 208 ላይ ተገልጿል።

በዚህም ጉዳይ የአሁኗ አመልካች ሟቹ አቶ ወልደማርያም ወልደጋብር ሐምሌ 29 ቀን 1996 ዓ.ም ያደረጉልኝ ግልጽ ኑዛዜ አለ ብለው የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን እንዲረጋገጥ የኑዛዜውን ጽሑፍ በማስረጃነት አቅርበዋል። የአሁኗ አመልካች በመጀመሪያ የኑዛዜውን ጽሁፍ ብቻ ሣይሆን ኑዛዜው ሲደረግ በምስክርነት ተገኝተው በኑዛዜው ላይ ፈርመዋል የተባሉትን አራት ምስክሮች ጭምር ፍ/ቤት በማቅረብ አስመስክረዋል። ፍ/ቤቱም ማስረጃውን መርምሮ ኑዛዜው በሕጉ መሠረት የተደረገ ነው በማለት በጥያቄአቸው መሠረት በማጽደቅ የአሁኗ አመልካች የሟች የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ውሣኔ ሰጥቷል።

ከዚህ ውሳኔ በኋላ የአሁኗ ተጠሪ በዝምድና የዘር ሐረግ የሟች ህጋዊ ወራሽ እኔ ነኝ፣ አመልካች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ የተወሰነው የወራሽነት መብቴን የሚያሳጣ ነው፣ ሟች አድርገዋል የተባለው ኑዛዜ ሀሰት ነው፣ ፊርማው የሟች አይደለም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ በማቅረብ እንደገና በኑዛዜው ጉዳይ ላይ ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ የአሁኗ ተጠሪ የሟችን ኑዛዜ የመቃወም መብት የላቸውም ህጋዊ ወራሽ አይደሉም በሚል የተነሣ ክርክር የሌለና ህጋዊ ወራሽ ነኝ ብለው ባቀረቡት መሠረት እንዲቀጥል የተደረገ ስለሆነ ከፍሲል እንደተገለፀው በመቃወም አመልካችዋ የአሁኗ ተጠሪ በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሰፈረው የጣት ምልክት ፊርማ የአውራሼ የሟች ስለመሆኑ አላውቅም ማለታቸው ብቻ በሕጉ በቂ ይሆናል። ተጠሪዋ ግን ከዚህ አልፈው በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የሟች አይደለም በማለት በግልጽ በመካድ ተከራክረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሰፈረው የጣት ምልክት ፊርማ የሟች መሆን አለመሆኑን አረጋግጦ ለመወሰን እንዲቻል በፎረንሲክ ምርመራ እንዲጣራ ያዘዘ ቢሆንም የተላከለት የቴክኒክ ምርመራ ክፍል በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለው የጣት ምልክት ፊርማ ቀለም የበዛበት ስለሆነ ከሌሎች ማመሳከሪያዎች ጋር በማመሳከር ለመመርመር አይቻልም ብሎ መልሶታል።

በኑዛዜው ጽሑፍ ላይ ያለው ፊርማ ቀለም የበዛበት በመሆኑ ምክንያት የሟች ፊርማ ነው አይደለም የሚለው በፎረንሲክ ምርመራ ሊረጋገጥ ባልቻለበት ሁኔታ የኑዛዜው ተጠቃሚ ነኝ የሚሉት የአሁኗ አመልካች የተጣለባቸውን የማስረዳት ሸክም አልተወጡም የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አይቻልም። አመልካች የአሁኗ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ በማንሣት ከመቅረባቸው በፊት በኑዛዜው ላይ ተገኝተው ፈርመዋል የተባሉትን አራት ምስክሮች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጭምር በማስረጃነት ቆጥረው ቀርበው እንዲሰሙ አድርገው የነበረ ሲሆን ተጠሪዋ መቃወሚያውን ካቀረቡ በኋላ ግን ምስክሮቹ እንደገና ቀርበው እንዲመሰክሩ ሣይደረግ ታልፏል። የከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ላይ ያለው የጣት ምልክት ፊርማ የሚች አይደለም ተብሎ የተረጋገጠበት መንገድ ሣይኖር እና በኑዛዜው ላይ ያሉት አራት ምስክሮች መቃወሚያው ከቀረበ በኋላ እንደገና ቀርበው እንዲመሰክሩ ሣይደረግ የአሁኗ አመልካች የማስረዳት ግዴታቸውን አልተወጡም ያለው ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኑዛዜው ሰነድ ላይ ያለው የሚች ፊርማ ነው የተባለው ቀለም ስለበዛበት በፎረንሲክ ምርመራ ለማጣራት አይቻልም ተብሎ ሲመለስ ፊርማው የሚች ስላለመሆኑ ማስረዳት ያለባቸው የሚች ወራሽ ነኝ ብለው መቃወሚያ ያቀረቡት የአሁኗ ተጠሪ ናቸው ያለውም ትክክል አይደለም።

በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 881 መሠረት ግልጽ ኑዛዜ ተደርጓል ተብሎ በቀረበው የኑዛዜው ጽሑፍ ላይ ተናዛዡ በጣት ምልክት ፊርመዋል የተባለው በቀለም መብዛትም ሆነ ቆይቶ በመደብዘዙ ምክንያት በፎረንሲክ ተመርምሮ ሊረጋገጥ የሚችል አይደለም የሚባል ሆኖ ከተገኘ ምን ሊደረግ ይችላል? ሚች ኑዛዜውን ሲያደርጉ በምስክርነት ተገኝተው በኑዛዜው ሰነድ ላይ ፊርመዋል የተባሉት አራት ምስክሮች በማስረጃነት በቀረበው የኑዛዜ ሰነድ መሠረት ስለኑዛዜው መደረግ እና ሚች በኑዛዜው ሰነድ ላይ በጣት ምልክት ፊርመዋል ተብሎ በቀረበው መሠረት ስለመፈረማቸው ለማስረዳት ይችላሉ አይችሉም? የሚለው ሲመረመር በሕጉ በኩል የሚከለክል ነገር የለም። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ችሎት በውሣኔው ላይ የአሁኗ አመልካች ስለኑዛዜው ጉዳይ ለማስረዳት ያሰሙትና ለማሰማትም ያዘጋጁት ምስክር እንደሌለ አድርጉ ይግለጽ እንጂ አመልካች ከመጀመሪያው የኑዛዜ ይጽደቅልኝ ጥያቄውን ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲያቀርቡ በኑዛዜው ሰነድ ላይ ፊርመዋል የተባሉትን አራት ምስክሮች ቆጥረው ቀርበው እንዲሰሙ ማድረጋቸውን የመጀመሪያው የፍ/ቤቱ ውሣኔ ያስረዳል። የአሁኗ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርበው የኑዛዜው ጉዳይ እንደገና ተንቀሳቅሶ ክርክሩ በሚደረግበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ ነበሩ የተባሉት ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ መደረግ ሲገባው ፍ/ቤቱ አልፎታል። የተቆጠሩት ምስክሮች በመጀመሪያ ያልነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ባሉበት እንደገና ቀርበው እንዲሰሙ ማድረጉ የፍ/ቤቱ የሥራ ድርሻ ስለሆነ የተከራካሪዋ የአሁኗ አመልካች ጉድለት ተደርጉ የሚታይ አይደለም። ሰበር ችሎቱ ይህንን ከመዝገቡ ተመልክቶ በመቃወሚያው የክርክር ሂደት ሣይሰሙ የታለፉትን የአሁኗን አመልካች አራት ምስክሮች የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንደገና ምስክሮቹን ሰምቶ በኑዛዜው ጉዳይ ላይ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት መመለስ ሲገባው አመልካች ያሰሙትና ለማሰማት ያዘጋጁት ምስክር ስለሌለ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም በማለት የወሰነው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም የሚከተለው ተወስኗል።

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ችሎት በመ/ቁ 07902 የካቲት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮ በኑዛዜው ሰነድ ላይ ፊርመዋል የተባሉት አራት ምስክሮች ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት ቀርበው በጽሑፍ ማስረጃነት በቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ላይ በተገለፀው መሠረት ስለኑዛዜው መደረግ እና በኑዛዜው ሰነድ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚች በጣት ምልክት ፈርመዋል ስለተባለው ተጠይቀው የሚሰጡት ምስክርነት ከተሰማ በኋላ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን እንዲወሰን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት ተመልሷል፡፡

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ መሠረት እንዲፈጽም ታዟል፡፡ ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ መዝገብ በተደረገው ክርክር የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ 54024

ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ አቶ ገብረሊባኖስ ረዳ ጠበቃ ከበደ መንገሻ ቀረበ

ተጠሪ፣ ወ/ሮ አዜብ አሰፋ ጠበቃ አዲሱ ሽባባው ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው አባትነትን ስለማስረዳት ዳኝነት በተጠየቀ ጊዜ አባትነትን የማስረዳት ጉዳይ እና የውሣኔ አሰጣጥ አስመልክቶ በግራቀኙ ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ መነሻ በማድረግ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ እንደሚከተለው ነው፡፡ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ባለው በሰበር መ/ቁ 54062 ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተሰጠው የሰበር ውሣኔ ላይ እንደተገለፀው የአሁን ተጠሪ ከሚሸ አቶ መዝሙር አፈወርቅ ጋር በጋብቻ እየኖሩ እያለ ህፃን ሜሮን እንደተወለደች ገልፀው አባቷ አቶ መዝሙር አፈወርቅ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ስለሆነም የህፃን ሜሮን ወራሽነት ይረጋገጥልኝ በማለት ለአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ህፃን ሜሮን የሚሸ አቶ መዝሙር አፈወርቅ ወራሽ ናት በሚል ከተወሰነ በኃላ የአሁን አመልካች ይህቺ ህፃን የተወለችው ከአሁን ተጠሪ ጋር በትዳር እያሉ መሆኑን የጋብቻውን ዘመን እና ህፃኗ የተወለደችበትን ቀን በመጥቀስ ካስረዱ በኃላ አባት እኔ ሆኜ እያለ ሚሸ አቶ መዝሙር አፈወርቅ አባት እንደሆኑ ተደርጎ የተሰጠው ውሣኔ የእኔን መብት ይነካል ይሰረዝልኝ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ጥያቄ አቅርበው ይኸው ጉዳይ እስከ ከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የህፃን ሜሮን አባት ማን ነው? የሚለውን የልጅነት ጉዳይ ያስነሳ ክርክር ሆኖ በመገኘቱ ይህ ዓይነት ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ሥር የሚወድቅ እንጂ የአ/አበባ ፍ/ቤቶች ተመልክተው ለመዳኘት ሥልጣን የላቸውም ስለሆነም የህፃን ሜሮን አባት ማን ነው? የሚለው ሥልጣን ባለው የፌዴራል ፍ/ቤት ተወስኖ እስከሚታወቅ ድረስ ህፃን ሜሮን የአባቷ የአቶ መዝገሙር አፈወርቅ ወራሽ ናት በሚል ቀደም ሲል በአ/አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሰጥቶት የነበረውን የውሣኔ ክፍል ለጊዜው አግዶ ግራቀኙን አሰናብቷቸዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህም የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ፍርድ ምክንያት የሆነው በዚህ መሠረት የሜሮን አባት ማን ነው? የሚለው አከራካሪ ነጥብ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ታይቶ ዳኝነት እንዲሰጥበት የአሁን አመልካች አቶ ገ/ሊባኖስ ረዳ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው።

የአቤቱታቸውም ይዘት ከተጠሪ ጋር ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ በፍቺ እስከተለያየንበት እስከ 1994 ድረስ በጋብቻ ላይ እያለን ከወልድናቸው ሌሎች ልጆች በተጨማሪ ህፃን ሜሮን ገ/ሊባኖስን ግንቦት 13 ቀን 1989 ዓ.ም ተወልዳለች ተጠሪ ከእኔ ጋር በጋብቻ ተሳስራ እየኖረች እያለ ይህቺ ህፃን ተወልዳ እያለ ተጠሪ ይህንን በመካድ ከሚች ከአቶ መዝሙር አፈወርቅ ጋር ከጥር 28 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ እያሉ ሜሮን ከአቶ መዝሙር አፈወርቅ እንደተወለደች አድርገው የወራሽነት ማስረጃ ለማግኘት ጥረት ማድረጋቸውን ስለተረዳሁ የእኔ አባትነት በፍርድ ይረጋገጥልኝ የሚል ነው።

ተጠሪም የህፃን ሜሮን አባት ሚች አቶ መዝሙር እንጂ አመልካች እንዳልሆነ በሚያስረዳ አኳኋን ክደው በመከራከራቸው ክሱ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 42739 ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በክስ አቤቱታቸው የገለፁት ሜሮን የተወለደችው ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው በሚኖሩበት ጊዜ ነው በጋብቻ ጊዜ ለተወለደ ህፃን አባቱ በጋብቻው ያለው ሰው እንደሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 126 ላይ የህግ ግምት ተቀምጧል። በዚህ የህግ ግምት አመልካች የሜሮን አባት ናቸው ይህንን የህግ ግምት ተጠሪ እናቲቱ አባቷ ሌላ ሰው ነው በማለት ውድቅ ማድረግ አይችሉም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 በፍርድ ቤት ውሣኔ አባትነት የሚታወቀው የልጅ አባት ያልታወቀ ወይም አባቱ ልጁን የካደው እንደሆነ ነው አመልካችም ሜሮን ልጄ አይደለችም ብለው የመካድ ክስ አላቀረቡም በሕግ ግምት ደግሞ አመልካች የሜሮን አባት ናቸው ስለሆነም የሜሮን አባት የታወቀ በመሆኑ አባቷ ለታወቀ ሰው ልጅነቷ በፍርድ ቀርቦ የሚረጋግጥበት አግባብ የለም ክሱ ለፍርድ የሚቀርብ አይደለም በማለት የፍርድ ሐተታ አስፍሮ የአመልካች አቤቱታ ለፍርድ የሚቀርብ ባለመሆኑ የክስ አቤቱታው ተሰርዟል በማለት ተወስኗል።

ይህም ፍርድ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ስህተት የሌለበት መሆኑ ተገልፆ የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነትን ሳያገኝ በመቅረቱ ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ ችሏል።

የሰበር አቤቱታው ፍሬ ቃልም የህፃን ሜሮን አባት ማን ነው? የሚለው ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ሊረጋገጥ ካልቻለ እንደኔ ፍትህ ማግኘት ይቻላል? የሚለውን የሚያብራራ ነው።

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል እንደመረመርነውም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራቀኙን ያከራከረው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው አይደለም ከሚል መደምደሚያ ሊደርስ የቻለው በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 በአንቀጽ 126 እና 143 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና ትርጉም አዛብቶ በመተርጎሙ የተነሳ እንደሆነ ተገንዝበናል ይኸውም አባትነት የሚረጋገጥባቸው ሶስት መንገዶች ያሉ ሲሆን እነዚህም መንገዶች በቀደም ተከተል ተደንግገዋል። በቅድሚያ የተቀመጠው ጋብቻ መኖርንና ክርክር የተነሳበት ህፃን በዚህ ጋብቻ ጊዜ የመወለድን ሁለት መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች መነሻ በማድረግ የልጅ አባት ወይም አባቷ ባል የሆነው ሰው ይሆናል የሚል ግምት ህጉ የወሰደበት ነው ይህ የህግ ግምት ነው ይህ የህግ ግምት መረጋገጥ በሚገባቸው ፍሬነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው እነዚህን ፍሬ ነገሮች ማረጋገጥ የቻለ ወገን ሌላ የተለየ ማስረጃ ማቅረብ ሳይጠበቅበት ህግ በእራሱ ግምት የወሰደለት መሆኑን የሚያሳይ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የህግ ግምት ህግ አውጭው ከተለያዩ መነሻ ሀሳቦች በመነሳት ህጉ የሚገመተው ነገር እንደማስረጃ ሆኖ እንዲያገለግል ያስቀመጠው እንጂ በህጉ የተቀመጠው ግምት ያለ ፍርድ ቤት ዕውቅና በእራሱ ተፈፃሚ እንዲሆን አይደለም የህግ ግምት እንደማስረጃ ከሚወሰዱት እንደ ሰነድ፣ የሰው ምስክርነት ቃል፣ የእምነት ቃል ገላጭ ማስረጃ ወዘተ ሆኖ ሊያገለግሉ ከሚችሉት የማስረጃ ዓይነቶች የሚመደብ እንጂ በእራሱ እንደፍርድ ሊቆጠር የሚችል አይደለም፡፡

የህግ ግምት ተጠቃሚ የሆነው ወገን በቅድሚያ በህጉ ግምት መነሻ የሆኑትን መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ ከሌላው ወገን ተከራካሪ መብት አንፃር እነዚህን መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ማረጋገጡና አለመረጋገጡ ክርክሩን በሚያየው ፍ/ቤት ዳኝነት የሚያስፈልገው ነው አረጋግጦ የህግ ግምት በማስረጃነት እንዲያለግለው ወይም እንዲጠቅመው ከማድረግ ደረጃ እንኳ ቢደርስ እንደ ግምቱ ዓይነት ሁኔታ ሊስተባበል የሚችል ከሆነም ሌላው ተከራካሪ ወገን በተራው እነዚያ የህግ ግምት መነሻ የሆኑት ፍሬነገሮች ያልተሟሉ ያልተረጋገጡ መሆኑን በፍ/ቤት በማስረዳት የህጉን ግምት የማፈረስ መብት አለው ይህ ሁሉ ተግባር በክርክር ሂደት በፍርድ ቤት ሊረጋገጥ የሚችል የዳኝነት ሥራን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ እየታወቀ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በክስ አቤቱታው የገለፃቸው ፍሬ ነገሮች እንዳሉ እውነት አድርጎ በመያዝ እና በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 126 እንደተነገረው የህፃን ሜሮን አባትነት በህግ ግምት ተረጋግጧል ሌላ የፍርድ ቤት ተጨማሪ ሥራ የሚያስፈልገው አይደለም ከሚለው መደምደሚያ የደረሰው ከላይ በዝርዝር እንዳሰፈረው የህግ ግምት የሚቋቋምበትንና የህግ ግምት እንደማስረጃ ሊወሰድ የሚችል መሆኑን ካለማገናዘብ በስህተት መተርጉሙን የሚያሳይ በመሆኑ በአተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በፈፀመው ስህተት መነሻነትም ለተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 ተፈፃሚነት ውስጥም በስህተት እንዲተረጎም አድርጎታል /አብቅቶታል/፡፡

አባትነት በፍርድ ሊነገር የሚችልበት ሁኔታ በአንቀጽ 143 ሲቀመጥ በቅድሚያ አባትነት ከህግ ግምት የሚመነጭ በህግ ግምት የሚረጋገጥ ከሆነ በዚህ አኳኋን በጋብቻ ጊዜ የመወለድ ሁኔታ ካለ በአንቀጽ 126 በተመለከተው በህግ ግምት የሚረጋገጥ እንጅ አንቀጽ 143 ሥራ ላይ የማይውል መሆኑን እንዲሁም የጋብቻ ግንኙነት ወይም በህግ የታወቀ ግንኙነት ሳይኖር የተወለደን ልጅ አንድ ሰው አባት ነኝ በሚል በፅሑፍ ያወቀ እንደሆነ በዚሁ ሥርዓት አባትነትን ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑን ከላይ በተቀመጡት ሁኔታዎች በማይሸፈኑት በቁጥር 143 የተዘረዘሩት ምክንያቶች ባጋጠሙ ጊዜ እንደ ሶስተኛ የአባትነት ማረጋገጫ መንገድ አባትነት በፍርድ የሚነገርበትን አግባብ የደነገገ በመሆኑ የአሁን አመልካች አባትነቴ በአንቀጽ 126 መሠረት ታይቶ ይረጋገጥልኝ በማለት ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ልክ በአንቀጽ 143 አባትነት በፍርድ ይረጋገጥልኝ በማለት እንደቀረብ የዳኝነት ጥያቄ አድርጎ መተርጎሙ ከመጀመሪያው ስህተት የመነጨ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የግራቀኙ ክርክር በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው በየፊናቸው ያቀረቡት የህግና የፍሬ ነገር ክርክር በየተራቸው በሚያቀርቡት የማስረጃ አግባብነት ጥንካሬ ታይቶ ፍርድ ሊያርፍበት የሚችል ሆኖ እያለ በተሳሳተ የህግ ትርጓሜ መነሻ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ሆኖ አልተገኘም በማለት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁ 42739 በ14/5/2002 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ እና በመ/ቁ 89823 በ18/6/2002 የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በግራቀኙ መካከል የተነሳውን ክርክር በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ስለሆነ በፍርድ ሀተታው እንደተገለፀው በጉዳዩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮን ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡
3. ግራቀኙ እዚህ ሰበር ድረስ ክርክር ለማድረግ የበቁበት የሥር ፍ/ቤቶች በፈፀሙት የህግ ስህተት ሳቢያ በመሆኑ ግራቀኙ የየራሳቸውን ወጭና ኪሣራ ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚያዝያ 21 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቶች፡- 1- የሮም ወርቅ ተስፋዬ በራስዋ እና ሞግዚት በሆነችላቸው ኤልሲ ተስፋዬ ፣ ፋሲል ተስፋዬ እና ደረጀ ተስፋዬ ፣ ወ/ሮ የሮም ወርቅ ቀረበች

2- አሸናፊ ተስፋዬ ቀረበ

ተጠሪ፡- አሰግድ ሸነገለኝ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውልን መሠረት በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው ክርክሩ በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣ አመልካቾችን የከሰሰው ከእናታቸው ጋር በመሆን በውል የሸጡልኝን ቤት ያስረክቡኝ፣ የባለቤትነት መብቱንም በስሜ ያዛውሩልኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ በመሃከላችን የተደረገ ሕጋዊ ውል ስለሌለ እንድንፈጽም አንገደድም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ክርክሩን ከመረመረ በኋላ የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ ግራ ቀኝ ወገኖች ከውሉ በፊት ወደ የነበሩበት እንዲመለሱም አዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ በመሻር አመልካቾች በውሉ መሠረት ለመፈጸም ይገደዳሉ በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካቾች ሚያዝያ 7 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ በሕግ ረገድ ያለው አግባብነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ እንደተመለከተው የሽያጭ ውሉ ተደረገ የተባለው በ5/9/93 ዓ.ም ሆኖ ተጠሪ ክስ ያቀረበው ደግሞ በ27/9/99 ዓ.ም ነው፡፡ በክሱ እንደገለጸው ኤልሲ/ኤልሳቤት/ ፣ ፋሲል እና ደረጀ በወቅቱ አካለመጠን ያላደረሱ/ ክሱ ሲቀርብም/ በመሆናቸው የተወከሉት በሞግዚታቸው በሮምወርቅ ተስፋዬ ነው፡፡ ተጠሪ የቤት ሽያጭ ውሉን አደረግሁ የሚለው ከእነዚህም ህፃናት ጋር ጭምር ነው፡፡ ቤቱን ገዛሁ የሚለው በብር 200,000 እንደሆነ እና ውሉ በተደረገበት ጊዜም ብር 57,285 ብቻ እንደከፈለ ቤቱን ግን እንዳልተረከበም በክሱ አመልክቶአል፡፡ ከላይ እንዳመለከትነው አመልካቾች በፍሬ ነገር ረገድ የተከራከሩት ከውሉ ሕጋዊነት ጋር በማያያዝ ሲሆን፣ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ውሉ ተከሣሾችን /አመልካቾችን/ የማስገደድ ሃይል የለውም የሚል ምክንያት በመስጠት ነው ክሱን ሳይቀበል የቀረው ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው ፍ/ቤት ደግሞ ውሉ መደረጉ እስከ ታመነ ድረስ የማይፈጸምበት ምክንያት የለም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡

በበኩላችን እንደምንገነዘበው በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ውሣኔ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ሊያዝ የሚገባው ጭብጥ በውሉ መደረግ አለመደረግ ወይም በመታመን አለመታመን ላይ የሚመሠረት ሳይሆን፣ ውሉ ሊያስከትለው በሚችለው ሕጋዊ ውጤት ላይ የሚመሠረት ነው አመልካቾች እንደውሉ እንዲፈጽሙ በፍርድ ሊገደዱ የሚችሉት ውሉ በሕጉ አግባብ ውጤት ሊሰጥ የሚችል ነው ለማለት የሚቻል ከሆነ ነው ፡፡ ደጋግመን እንዳመለከትነው አመልካቾች ውሉ በሕግ ረገድ ውጤት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ውሉ ተደረገ በተባለበት ጊዜ ኤልሲ /ኤልሳቤት/ ፣ ፋሲል እና ደረጀ እንደቅደም ተከተላቸው የ12 ፣ የ14፣ እና የ10 ዓመት ህፃናት እንደነበሩ ተጠሪው ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ ጭምር ተረጋግጦአል፡፡ ይህም ማለት የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው በሞግዚታቸው አማካይነት ነው ማለት ነው ቤቱ የሁሉም አመልካቾች የጋራ ሃብት በመሆኑ ሊሸጥ ወይም ለሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ የሚችለው የሁሉም አመልካቾች የጋራ ስምምነት ሲኖር እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1226 ተደንግጎአል፡፡ ለዚህም ነው ተጠሪ አመልካቾች አንድ ላይ በመሆን ቤቱን ሸጠዉልኛል በማለት ክስ የመሠረተው ይሁንና ከጋራ ባለሃብቶቹ ከፊሎች ለአካለ መጠን ያላደረሱ ህፃናት በመሆናቸው /ውሉ ተደረገ በተባለበት ጊዜ/ እና ውሉ ሕጋዊ ውጤት የለውም የሚል ክርክርም ስለተነሳ ሕጉ ለአካለ መጠን ያላደረሱ ልጆችን /ህፃናት/ ንብረት አጠባበቅ በሚመለከት ያደረገውን ጥበቃ በዝርዝር ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ክርክር የተነሳው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/በመሆኑ የተሰማውም በክልሉ ፍ/ቤቶች ነው፡፡ የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የራሱ የሆነ የቤተሰብ ሕግ በአዋጅ ቁ 69/1995 /በአዋጅ ቁ 83 /1996 የተሻሻለው / አውጥቶአል፡፡ ይህ የቤተሰብ ሕግ አካለ መጠን ስላላደረሱ ሰዎችን በሚመለከት በአዋጅ ምዕራፍ አሥራ ሁለት ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካቶአል፡፡ አካለ መጠን ያላደረሰውን ሰው አሳዳሪ እና ሞግዚት ሥልጣን በሚመለከትም በክፍል ሶስት ሥር የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ሲኖሩ ከእነዚህም መካከል ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት ያለው በአንቀጽ 294 የተመለከተው እንደሆነ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ ድንጋጌ እንደተቀመጠው ሞግዚቱ መሸጥ የሚችለው አካለ መጠን ያላደረሰውን ሰው ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን አክሲዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ነው፡፡ ሞግዚቱ አካለ መጠን ያለደረሰውን ሰው ንብረት የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ እንደሚችል በዚህ ድንጋጌ አልተመለከተም፡፡ ይልቁንም ሕጉ የመረጠው /የተከተለው/ ሞግዚቱ ሊሸጣቸው የሚችላቸውን ንብረቶች በግልጽ አስቀምጦ /ደንግጎ / ማለፍ ነው ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ በተቃራኒው አስተሳሰብ ሲታይ ሞግዚቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕጉ በቀጥታ ያልተፈቀደለት መሆኑን ነው፡፡ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግም እንደዚሁ በአንቀጽ 277/1/ ተመሣሣይ ድንጋጌ አስቀምጦአል፡፡

እንደምንመለከተው ሕጉ አካለመጠን ላላደረሱ ሰዎች ልዩ ጥበቃ ይኖር ዘንድ ግልጽ ድንጋጌዎችን በቤተሰብ ሕጉ አካቶአል፡፡ እንኳንስ አካለመጠን ባላደረሰው ሞግዚት የተደረገው ቀርቶ በራሱ አካለ መጠን ባላደረሰው ሰው ወይም ልጅ የተደረገው ውልም ፈራሽ እንደሆነ በኦሮሚያ ቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 316 እንደዚሁም በተሻሻለው የፌዴራል መንግስት የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 299 ተደንግጎአል፡፡ እነዚህን ድንጋጌዎችን ቀደም ሲል ከተቀጠቀሱት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ስናየው በዚህ መዝገብ ለቀረበው ክስ መነሻ የሆነው የቤት ሽያጭ ውል በሕጉ ረገድ ተፈጻሚነት ያለው ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት እና የጠ/ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት የደረሱበት መደምደሚያ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሕጉን በአግባቡ በመተርጎም የተደረሰ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 31454 ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 100903 መጋቢት 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነው በ5/9/93ዓ.ም ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል የሚፈጸም አይደለም ብለናል፡፡ በዚህ መሠረትም የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 16777 በ5/3/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 54129

ኅዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ከፍያለው በቀለ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወጣት ሶፊያን አብዱልቃድር - ቀረበ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ አካለ መጠን ያላደረሰን ልጅ ንብረት በሞግዚትነት ሲያስተዳድሩ የነበሩት ወላጆች በሽያጭ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ባስተላለፉ ጊዜ አካለ መጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ይኸው ተግባር የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለውን የሕግ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

የነገሩ መነሻ የአሁን አመልካች ከተጠሪ ወላጆች የማይንቀሳቀስ ንብረት ቤት በውል ገዝቻለሁ፤ ውል ሊፀድቅልኝ ይገባል የሚል አቤቱታ አቅርቦ፣ ከሻጮች ጋር ከተከራከረ በኋላ እንደ ጥያቄው ምላሽ የሚሰጥ ውሣኔ አግኝቷል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁን ተጠሪ የተሸጠው ንብረት ስመሃብትነት በእኔ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ነው በተሸጠበት ጊዜ በወላጆቼ የሞግዚትነት ሥልጣን ሥር የምተዳደር አካለ መጠን ያልደረስኩ ልጅ ነበርኩ፡፡ ወላጆቼ የሸያጭ ተግባሩን ለመፈፀም የሚያስችል ከሕግ የመነጨ መብት የላቸውም፡፡ በዚህ በሕግ ረገድ ተቀባይነት በሌለው ተግባር መነሻ እኔ በሌለሁበት ገዢና ሻጭ ናቸው ተብሎ በተነሣው ክርክር የሸያጭ ውል ይጽደቅ በሚል የተሰጠው ውሣኔ መብቴን ስለሚነካ ውሣኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 360 መሠረት ሊሰረዝ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት እራሱን በቻለ መዝገብ አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ከዚህ ቀደም በአሁን አመልካችና በተጠሪ ወላጆች መካከል የተነሣውን ክርክር ተመልክቶ ውሣኔ የሰጠው የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ነጥብ ላይ አመልካችና ተጠሪን ካከራከረ በኋላ በአሁን ተጠሪ ከላይ በተገለፀው አኳኋን የቀረበውን ክርክር መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀደም በሌላ መዝገብና የሸያጭ ውል ይጸድቃል በማለት የሰጠው ውሣኔ ውጤት እንደማይኖረው አድርጎ ሰርዞ ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ መነሻ በተሰጠው ውሣኔ ሁለቱም ወገኖች በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተጠሪ የአቤቱታ አቀራረብ የተፈፀመው ሥነ ሥርዓታዊ ጉድለት መሠረታዊ ሆኖ በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ በመሰረዝ የሰጠውን ዳኝነት ለማስለወጥ የሚያበቃ አይደለም፡፡

አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ የማይንቀሳቀስ ንብረት በሞግዚትነት ሥልጣን ወላጆቹ በማናቸውም መንገድ ቢሆን ለማስተለለፍ ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ በክልሉ ሕግ አልተደነገገም፤ ስለሆነም በዚህ ረገድ የወረዳው ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት ሻጮች ለገዢው የሽያጭ ውል ሊያፀድቅ ይገባል በሚል አስቀድሞ ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔ ተሰርሿል ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም የሚለውን ጠቅሶ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት መጓደልን ምክንያት በማድረግ የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር በየደረጃው ባሉት የሥር ፍ/ቤቶች በየፊናቸው አቅርበውት ከነበረው የተለየ አይደለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፣ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በዚህ ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ በሆነው የሽያጭ ውል ላይ ተሸጧል የተባለው የማይንቀሳቀስ ንብረት /ቤት/ ስመ ሃብትነቱ በአሁን ተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ አከራካሪ የሆነ ጉዳይ አይደለም የአሁን አመልካች አጠንክሮ ከሚከራከርበት ነጥብ አንዱ ምንም እንኳ ስመ ሃብትነቱ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ ይገኝ እንጂ በተሸጠበት ጊዜ ተጠሪ ንብረት ለማፍራት በሚችልበት የዕድሜ ክልል ስላልነበረ ንብረቱንም በውርስ አግኝቻለሁ ስለማይል ሀብትነቱ የሻጮች በመሆኑ በፈፀሙት ሕጋዊ ተግባር ሊገደዱ ይገባል የሚለው ነው፡፡ ሆኖም የተሸጠው ንብረት ባለቤት ማን ነው? የሚል እንደ አሁኑ ያለ ጥያቄ በተነሣ ጊዜ አከራካሪ ከሆነው ንብረት ዓይነት አንፃር የንብረት ምዝገባን መሠረት በማድረግ ሕጉ ምላሽ የሚሰጥበት በመሆኑ በአመልካች በኩል በፍሬ ነገር ላይ ተመርኩዞ የቀረበው ክርክር ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ንብረቱን በግዢ አግኝቼ ለ14 ዓመታት በእጄ አድርጌ ከቆየሁ በኋላ በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በሚል ጊዜን መነሻ በማድርግ የቀረበውን ክርክር በሚመልከት ገዝቻለሁ ካለ በኋላ እንደጠቀሰው ለዓመታት ያሕል በእጁ ይዞ የቆየ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጡት ውሣኔዎች ላይ ያልተረጋገጠ የፍሬ ነገር ክርክር ከመሆኑም በላይ ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው አንድ ተከራካሪ መሆን ይገባው የነበረ ሰው የክርክር ተካፋይ ሳይሆን የተሰጠው ውሣኔ መብቱን ይነካል ብሎ በቀረበ ጊዜ አቤቱታው መቼ መቅረብ አለበት ለሚለው የጊዜ ማሟያ እንደ ውሣኔው የሚፈፀም እና ያለመፈፀም ጉዳይ ብቻ በመሆኑ ክርክሩ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ከዚህም አንፃር እንደ ውል ይጽደቅልኝ ብሎ ካስወሰነ በኋላ እንደ ውሉ ያልፈፀመ ስለመሆኑም ገልፆ አልተከራከረም ስለሆነም ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሌላውና ከሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ ጋር በተያያዘ የተነሣው ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን አቤቱታ ወይም መዝገብ ያልከፈተበት አግባብነት ነው፡፡ ለአቤቱታው መሠረት አድርጎ ያቀረበው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ እንደሚያስረዳውና የነገሩ አመጣጥ እንደሚያስገነዝበው የተጠሪ የአቤቱታ አቀራረብ እኔ የክርክር ተካፋይ ባልሆንኩበት ተሰጠ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተባለውን ውሣኔ በያዘው መዝገብ ላይ በመቅረቡ የተዘጋውን መዝገብ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ ሲገባው እራሱን የቻለ አዲስ መዝገብ ማስከፈቱ እንደ ሥርዓት አነጋገር ግድፈት የተፈፀመበት ሆኖ ቢገኝም መብቱን ለማስከበር አንኳር የሆኑ ማሟያ ምክንያቶች ተሟልተው እስከተገኙ ድረስ በየትኛው መዝገብ ክርክሩ መካሄድ ነበረበት የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ የሕግ ጉዳይ ሆኖ የጉዳዩን ውጤት ለማስለወጥ የሚያበቃ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመ መሆኑን አያሳይም፡፡

የሞግዚትነትን የሥልጣን ውልን በሚመለከት የተነሣው ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች ትርጉም የሰጡበት አንድ የሕግ ክርክር እንደሆነ ከመዝገቡ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው የሕግ ትርጉም ላይ እንደተተቸው የሞግዚቶች ንብረትን ወደ ሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ ሥልጣን አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ የሚንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተያያዘ እንጂ የማይንቀሳቀስን ንብረት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚያስችል ሥልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ ይኸው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የክልሉ ሕግ ግልባጭ ንባብ አስረጂ ነው፡፡ ይህንኑ በሕግ የተገደበ ሥልጣን ተላልፈው ንብረት ባስተላለፉ ጊዜ ንብረቱ የተላለፈለት ወገን ሊኖረው የሚችለው ማስተካከያ ምን እንደሆነ በሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ ጥበቃው አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ከመሆኑ በቀር ከዚህ የተለየ ውጤት ለገዢው የተደረገ ጥበቃ ስለመኖሩ በሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ ስለሆነም ሻጮች በሌላቸው ሥልጣን የፈፀሙት ተግባር መሆኑን መነሻ በማድረግ ሻጮች የሸያጭ ውሉን ሊያፀድቁ ይገባል፣ በውጤት ደረጃ ስመሃብትነት ሊያዛውሩ ይገባል በሚል ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ምክንያቶች ውጤት እንዳይኖረው በማድረግ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በዚህ ጉዳይ የወረዳው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04306፣ የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05885 እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፋይል ቁጥር 81290 የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ የፀና ሲሆን በተቃራኒው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 71141 የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፤ ሆኖም ሻጮችን የሚጠይቅበት አግባብ የተጠበቀ ነው፡፡

ይህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚያዝያ 06 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1- አቶ ዳንኤል ጽጌ

2- ወ/ሮ ጽዮን ጽጌ — ጠበቃቸው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- ህፃን አሳለፈ ጽጌ ሞገዚት ኢ/ር ታምራት ብሩ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ የድርሻ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ሟች አቶ ፅጌ ዘገኑ ሐምሌ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ለሕፃን አሳለፍ ፅጌ ያደረጉትን ኑዛዜ መሠረት በማድረግ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የሕፃኗን የኑዛዜ ወራሽነት በማረጋገጥ ማስረጃ ከሰጠ በሁዋላ የአሁኑ አመልካቾች ይኸው የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ አመልካቾች ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት መቃወሚያ የሟች አቶ ፅጌ ዘገኑ ልጆች ሁነው እያለ ሟች ባደረጉት ኑዛዜ አመልካቾች በህይወቱ ላይ ከፍተኛ ችግር ስለአደረሱብኝ ከመጡ ለእያንዳንዳቸው ብር 5/ አምስት / እንዲሰጥ በማለት መግለፃቸው ከውርስ ንብረቱ ያለምክንያት የነቀሏቸው መሆኑን ዘርዝረው ለተጠሪ የተሰጠው የኑዛዜ ወራሽነት ተሰርዞ አመልካቾች የሟች ወራሾች ናቸው ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የሟች ኑዛዜ አመልካቾችን ያለምክንያት ከውርስ የነቀለ ነው በሚል ምክንያት ለተጠሪ የሠጠውን የኑዛዜ ወራሽነት በማሻሻል አመልካቾችና ተጠሪ የሟችን ውርስ እኩል እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ሟች ባደረጉት ኑዛዜ የአመልካቾችን ድርሻ ከማሳነስ ውጪ ከውርስ አልነቀሏቸውም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ ኑዛዜው የጸና ነው በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በሁዋላ አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ጉዳዩ ተመርምሮ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካቾች ጠበቃ ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ/ም በጻፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ሚች ባደረጉት ኑዛዜ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾቻቸው ለሆኑት አመልካቾች ግምቱ ብር 600 ሺህ በላይ ከሆነው ንብረታቸው ለእያንዳንዳቸው ብር 5/አምስት ብር / ብቻ እንዲሰጣቸው መናዘዛቸው አመልካቾችን በውጤት ከውርስ የነቀሏቸው መሆኑን የሚያሳይ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የውርስ ንብረት ድርሻ አንሷል ከሚባል በስተቀር ከውርስ መነቀል አይደለም በማለት መወሰናቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 ድንጋጌዎችና ይዘትና መንፈስን ያላገናዘበ ነው፣ ይኸው እንኳ ቢታለፍ ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 ድንጋጌ አንፃር መታየት ሲገባው መታለፉ ያላግባብ ነው በማለት ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ እንዲሻሻል ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርመሮም ለሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በይዘቱ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ካቀረቡት ጋር ተመሳሳይ የሆነ መልሰ ሠጥተዋል፡፡ የአመልካቾች ጠበቃም ጥር 16 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት አንድ ገጽ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ሚች አቶ ጽጌ ዘገኑ ሐምሌ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾችን ነቅሏል አልነቀለም?፣ ውጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉት ነጥቦች በጭብጥነት ሊታዩ የሚገባቸው ሁነው አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሚች አቶ ፅጌ ዘገኑ ሐምሌ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ግልፅ ኑዛዜ የተው መሆኑን አመልካቾች የሚቹ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች/ ልጆች/ ፤ ተጠሪ ደግሞ የሚች ወንድም ልጅ መሆኑን ፣ ሚች ይኖራቸዋል ተብሎ የተጠቀሰው የንብረት ግምት ከብር 600 ሺህ በላይ ሁኖ ለአመልካቾች ለእያንዳንዳቸው እንዲሰጣቸው የገለፁት ገንዘብ ብር 5/አምስት ብር / ብቻ መሆኑን ይህንን ለማድረግ በምክንያትነት የጠቀሱት ደግሞ በሕይወቱ ላይ ከፍተኛ ችግር ስለፈጠሩብኝ የሚል መሆኑን ነው፡፡ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ኑዛዜው ሕጋዊ ነው በማለት የወሰኑት ሚች ለአመልካቾች ድርሻቸውን ሰጥተዋል የድርሻ ማነስ ደግሞ የውርስ መነቀል ነው ሊባል የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ በኑዛዜው የሚከናወኑ ተግባሮች የኑዛዜ ስጦታ /legacy/ ወይም የክፍያ ደንብ / Rule of partition/ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመርህ ደረጃ ደግሞ አንድ ሰው ከውርስ ሀብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ አያሰኘውም፡፡ ይልቁንም ይህ አይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ አውራሽ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዘዝለት የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ / legacy/አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ /partition/ በመከተል የሚከናውን ይሆናል፡፡ ሆኖም በኑዛዜው ላይ የሚሰጠው ክፍያ መጠን በመገለፁ ብቻ ሁል ጊዜ የክፍያ ደንብ ነው ሊባል የሚችል አይሆንም፡፡ በመሆኑም የተሰጠው የንብረት መጠን ከሚቹ የውርስ ንብረት ግምት ጋር ታይቶ ውጤቱም በዚሁ ረገድ መለየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ሚች በኑዛዜው ላይ የሚያስፍረው የንብረት መጠን ከሚቹ የውርስ ንብረት መጠን ጋር እየታየ የመነቀል ጉዳይ ነው ወይስ የክፍያ ማነስ ነው? የሚለው ነጥብ የሚለይ ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል አንድ ተናዛኝ/ ወላጅ/ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለህጋዊና በቂ ምክንያት እንዲሁም በዝምታ ከውርስ ለመንቀል እንደማይችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 ድንጋጌዎች ይዘት በግልፅ ያሳያል፡፡ ወላጅ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ወይም በዝምታ ከነቀለም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት ከውርስ በዝምታ ወይም ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሁነው የውርስ ንብረቱን ሊከፋፈሉ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤት ወደዚህ ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት በወላጅ የተደረገ የኑዛዜ ስጦታ አይነቱ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ መሆን ያለመሆኑን በቅድሚያ መለየት አለበት፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912 ስር እንደተመለከተው የኑዛዜ ስጦታ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ሲባልም ተናዛዡ ሀብቱን ጠቅላላ ወይም ከመላ ንብረቱ አንዱን ክፍል በሙሉ ሀብትነት ወይም በሌጣ ርስትነት ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች የሚያወርስበት የኑዛዜ ቃል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912/1/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ማንኛውም ሌላ የኑዛዜ ቃል ሁሉ እንደ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡ እንደ ኑዛዜ ላይ የኑዛዜ ስጦታ መሆኑ የተረጋገጠ ደግሞ እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014 ድንጋጌ ቅደመ ተከተል መሠረት የሚከፈል ይሆናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ሟች አቶ ፅጌ ዘገኑ ሀብታቸውን ሙሉ በሙሉ ተጠሪ እንዲወርስ ለአመልካቾች ደግሞ ለእያንዳንዳቸው ብር 5/ አምስት/ የሰጡት መሆኑ ከኑዛዜው ሰነድ ይዘት ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ሟች አላቸው ተብሎ ከተገመተው የብር 600 ሺህ ብር የውርስ ንብረት አንፃር ለአመልካቾች እያንዳንዳቸው ብር 5/አምስት ብር/ እንዲወስዱ በማለት የተናዘዙት ሁኔታ ሲታይ እግምት ውስጥ የሚገባ ወይም የድርሻ ጥያቄ አነሰ የሚል ክርክር የሚያስነሳ ነው ሊባል የሚችል ሳይሆን በውጤቱ የመነቀል ውጤትን ያስከተለ ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡ ሟች ለአመልካቾች ለእያንዳንዳቸው ብር 5/ አምስት / እንዲሰጥ በማለት የተናዘዙት **“በሕይወቴ ላይ ከፍተኛ ችግር ስለፈጠሩብኝ”** በሚል ምክንያት ነው፡፡ ሆኖም በሕይወቱ ላይ ከፍተኛ ችግር ስለፈጠሩብኝ የሚለው ሐረግ ዝርዝር ይዘቱ ግን በኑዛዜው ላይ አልተገለጸም፡፡ የዚህ ሐረግ አገላለፅ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938/2/ መሠረት እንደእውነት የሚወሰድ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከውርስ ለመንቀል የሚያስችል **ሕጋዊ እና በቂ ምክንያት** መሆኑን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938/3/ መሠረት መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም አንጻር በሕይወት ላይ ችግር መፍጠር የተለያየ ደረጃና መንገድ ያለው በመሆኑ ሟች አመልካቾችን በዚህ ምክንያት ብቻ መንቀሉ ሕጋዊና በቂ ምክንያት ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፎርማሊቲ ረገድ ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የሌለ ሲሆን ሟች አላቸው ከተባለው ጠቅላላ የውርስ ንብረት መጠን አንፃር ሲታይ ለአመልካቾች የተሰጠው የገንዘብ መጠን በውጤት ደረጃ አመልካቾችን ነቅሏል ከሚባል በስተቀር ድርሻቸውን አግኝተዋል ውጤቱም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 ሊታይ የሚችል ነው ሊባል የሚችል ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንፃር ተናዛዡ ያደረጉት የኑዛዜ ስጦታ ሲታይ በውጤቱ አመልካቾችን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ከውርስ የነቀለ ሁኖ ዓይነቱ ልዩ የሆነ የኑዛዜ ስጦታ ሳይሆን ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ አይነት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014/ሠ/ ስር በተመለከተው መሠረት እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ ለልዩ ኑዛዜ ተቀባዩ የሚከፈል ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ድንጋጌዎች ታይቶ ተወላጅ ከውርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተነቅሷል፣ ከኑዛዜ ተቀባዩ ጋር እኩል ሊካፈል ይገባል የሚባልበት ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በፍ/ሕ/ቁጥር 915 መሠረት እንደጠቅላላ ኑዛዜ ወራሽ ተወስደው ከአመልካቾች ጋር እኩል ተካፋይ ናቸው ተብሎ ሊወሰን ሲገባው የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከውርስ ንብረት ክፍያ ማነስ ጋር በማያያዝ የሰጡት ውሣኔ የኑዛዜውን ውጤት ሚች አላቸው ከተባለው ንብረት ግምት መጠን ጋር ባለማገናዘብ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12988 መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 13364 ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 137/02 የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ/ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ሚች አቶ ጽጌ ዘገኑ ሐምሌ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በውጤቱ ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት አመልካቾችን የነቀለ በመሆኑ በአመልካቾች ላይ ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፣ ኑዛዜው ተጠሪን በሚቹ ድርሻ ንብረት ላይ አንድ ወራሽ የሚያደርግ በመሆኑ አመልካቾች የሚችን ድርሻ ንብረት ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 66727

ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሪት ዝናሽ ዘውዱ - ጠበቃ ሙሉጌታ ወንድምአገኘሁ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የወ/ሮ መድኃኒት ካሳ ወራሽ - እነ ወ/ሮ ደብሪቱ ስዩም አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲሆን የአመልካች አባት አቶ ዘውዱ አበበና የተጠሪዎች ልጅ እህት የሆኑት ወ/ሮ ሰናይት ስዩም በጋብቻ አብረው ሲኖሩ ወ/ሮ ሰናይት ስዩም ታህሳስ 25 ቀን 1995 ዓ/ም ከዚህ አለም በመለየታቸው ምክንያት ጋብቻው በሞት መፈረሱን ገልጸው ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብላቸው ተጠሪ ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም አመልካችን አስቀርቦ አመልካች የይርጋ ክርክር ቢያነሱም ይኸው ታልፎ የውርስ ንብረቱ ተጣርቶ እንዲቀርብ የውርስ አጣሪ ሹሞ የውርስ አጣሪውም ሀብቱን አጣርቶ ለፍርድ ቤቱ ሪፖርቱን ሲያቀርብ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ ፍርድ ቤቱ የውርስ አጣሪው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 የቤት ቁጥር 497 ግቢ ውስጥ ከዋናው ቤት ትይዩ የሚገኝ ሁለት ክፍል ቤቶችና አንድ ክፍል እቃ ቤት በአጠቃላይ ሶስት ክፍል ቤት የአመልካች የግል ቤት ነው በማለት የውርስ አጣሪ የደረሰበት መደምደሚያ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 መሰረት የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ባልቀረበበት ሁኔታ ነው በማለት ውድቅ አድርጎ ዋናው ቤትና ሰርቪስ ቤቶች በሙሉ የውርስ ሀብት ናቸው በማለት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት አሻሽሎ አፅድቆታል፡፡ አመልካች የሰሩት ቤት ካለ ግምቱን ጠቅሰው ዳኝነት ከፍለው የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለትም ትእዛዝ ሰጥቶበታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የውርስ አጣሪው በ23/04/2002 ዓ.ም ያቀረቡት ሪፖርት በአግባቡ የቀረበ ሁኖ እያለ ፍርድ ቤቱ አከራካሪው ቤት የግል አይደለም ማለቱ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የውርስ አጣሪው ከሟች ሞት በኋላ የተሰራውን ሶስት ክፍል የአመልካች የግላቸው ነው በማለት ያቀረበው ሪፖርት በፍርድ ቤቶቹ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የውርስ ንብረት አጣሪውን ሪፖርት በሰርቪስ ቤቶችና በእቃ ቤት ላይ ተቀባይነት የለውም በማለት ውደቅ ያደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነውም የውርስ አጣሪው ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ሪፖርት ቁጥሩ 497 በሆነው ዋና ቤት ከወ/ሮ ሰናይት ስዩም ሞት በሁዋላና ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶችና አንድ ክፍል እቃ ቤት መሰራቱን በምስክሮች ቃል መረጋገጡን የገለፁ ሲሆን ይህ ድምዳሜ በበታች ፍርድ ቤቶች ቤቶቹን የአመልካች የግል አያደርጋቸውም ተብሎ ውሳኔ የተሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 1195 መሰረት ከአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አልቀረበም፣ ባለሀብትነቱ በሰው ማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት ነው።

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 956 እንደተደነገገው የአጣሪው ሥራ ሟቹ አንድ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግና በመጨረሻም ውርሱ የሚደርሳቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ፣ የውርሱን ሃብት ማስተዳደር፣ መክፈያቸው የደረሰውን የውርስ እዳዎች መክፈል እና ሟቹ ኑዛዜ ያደረገባቸውን ስጦታዎች መክፈልና የኑዛዜውን ቃል ለመፈፀም ማንኛቸውም ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎች ማድረግ ነው። እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት በሚያከናውንበት ጊዜ ደግሞ በኑዛዜው የውርስ ንብረት መሆናቸውን ጠቅሶ የክፍፍል ስርዓትም የተቀመጠላቸውና ወራሾች በሙሉ የተስማሙባቸው ንብረቶችና መክፈያቸው የደረሰው የውርስ እዳዎች ሲኖሩ በወራሾቹ ስምምነት መሰረት ንብረቶቹን ሊያከፋፍልና እዳዎችንም ሊከፍል ይችላል። በኑዛዜው ላይ በተጠቀሱትና ባልተጠቀሱት ንብረቶች የውርስ ሃብት መሆን ያለመሆን ላይ ወራሾቹ ያልተስማሙና ክርክር ያነሱ ከሆነ የአጣሪው ሥራና ኃላፊነት ወራሾች የተስማሙባቸውን ንብረቶች የውርስ ሃብት መሆናቸውን መመዝገብ፣ ወራሾች ያልተስማሙባቸው ንብረቶችና እዳዎች ካሉ ደግሞ ማስረጃ በመስማት ማስረጃው ምን እንደሚያስረዳ ሪፖርቱ ላይ በማስፈር እንዲያጣራ ላዘዘው ፍ/ቤት ማቅረብ እንጂ ንብረት አጣሪው ይህ ንብረት የውርስ ሐብት አይደለም የሚሉ ወራሾች ቢኖሩም ማስረጃ በመስማት የውርስ ሃብት መሆኑን ስለተገነዘብኩኝ ንብረቱ የውርስ ሃብት ነው በማለት ወስኛለሁ ወይም ደግሞ ማስረጃውን እንደተመለከትኩት ንብረቱ የውርስ ሐብት ያለመሆኑን ስላረጋገጥኩኝ የውርስ ሐብት አይደለም ወይም የእገሌ የግል ንብረት ነው በማለት ወስኛለሁ ለማለት የሚያስችለው ሥልጣን የለውም።

በዚህ ጉዳይ የውርስ አጣሪው ያደረጉትን የማጣራት ሥራ ስንመለከተው ወራሾቹ የውርስ ሐብት ናቸው በሚሉዋቸው ዋና ቤት እና በሰርቪስ ቤቶች ላይ ገና ከጅምሩ አንስቶ ያልተስማሙና ክርክር ያነሱ በመሆኑ አጣሪው ማስረጃ መስማታቸው በአግባቡ ነው። ሆኖም አጣሪው በወራሾች መካከል የተደረገው ክርክር እንደነበረ፣ የኑዛዜ ወራሾችና የሕግ ወራሾች እነማን እንደሆኑ፣ የግራ ቀኙ ማስረጃ ምን እንደሚመስል፣ እንዲሁም ወራሾች የተማመኑባቸውና ያልተማመኑባቸው የውርስ ንብረቶችና እዳዎቹ ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ሪፖርት ማዘጋጀት ሲኖርባቸው ከዚህ አልፈው ወራሾችን አከራክረው ማስረጃ ከሰሙ በኋላ ክርክሩንና ማስረጃውን ከሕግ ጋር በማገናዘብ ይህ ንብረት የአመልካች እንጂ የሟች የወ/ሮ ሰናይት ስዩምና የሟች ዘውዱ አበባ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት መወሰናቸው ከተሰጣቸው የውርስ አጣሪነት ሥልጣን በላይ በመሄድ መደበኛ ፍ/ቤት በሚያከናውነው የዳኝነት ሥራ ውስጥ መግባት መሆኑንና ይህም ተገቢ ያለመሆኑን ተገንዝበናል። ውርስ አጣሪው አዘጋጅተው ያቀረቡት ሪፖርት ውሳኔም ጭምር ያዘለ በመሆኑ ሪፖርቱ በቀረበለት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በውርስ አጣሪ ውሳኔ መሰጠት እንደማይገባ ሊገለፅና ሂደቱ ሕጋዊ አይደለም ተብሎ ውድቅ መደረግ ሲገባው መታለፉ ያላግባብ ሁኖ አግኝተነዋል። የባለቤትነት ክርክር በውርስ ማጣራት ሂደት ከተነሳ ጉዳዩ መታየት ያለበትና እልባት ሊያገኝ የሚገባው በመደበኛው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሰረት ተገቢው ጭብጥ ተይዞ የግራ ቀኙ ማስረጃዎች ተሰምተው ሊሆን ይገባል። ፍርድ ቤት የባለሀብትነት ክርክር ሲቀርብ ሊያረጋግጥ የሚገባው ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን ሁሉ ሰምቶና ተገቢውን የማስረጃ ምዘና መርህ ተከትሎ ነው።

በመሰረቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለቤትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የዚሁ ንብረት ባለሃብት ሁኖ እንደሚቆጠር የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195(1) ድንጋጌ ያሳያል። የዚህ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያሳየው የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የንብረቱ ባለሃብት እንደሆነ ሕጉ ግምት የሚወስድ መሆኑን ነው። ይህ የሕጉ ግምት ሊስተባበል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችል ስለመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ስር የተመለከተው የሕጉ ግምት ባለሃብትነት በሌላ መንገድ የማይረጋገጥ አይደለም በሚል የተቀመጠ አይደለም፡፡ በዚህ መሰረትም አንድ ንብረት በአንድ ሰው ስም ስለመመዝገቡ በአስተዳደር መስሪያ ቤት ታውቆለት የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት ከተሠጠውና ይኸው ምስክር ወረቀት የተገኘበትን መንገድ ሕጋዊ አለመሆኑን ክርክር ከቀረበ ፍርድ ቤቱ ንብረቱ በማን እንደተፈራ፣ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ሰው ስም እንዴት ሊመዘገብ እንደቻለ ከተገቢው አካል የቤቱ ማህደር ቀርቦ ወይም ሌሎች ማስረጃዎች ቀርበው እንዲታዩ የቀረበውን ክርክር በመመልከትና ጉዳዩን በማስረጃ በማንጠር ወደ እውነት የሚደርስበት ይሆናል እንጂ ስመ ሀብቱ የተመዘገበው ሰው የንብረቱ ባለሃብት ነው ወይም ስመ ሀብቱ ካልተመዘገበ አንድ ሰው የንብረት ባለቤት ሊሆን አይችልም፣ ወይም በሰው ማስረጃ ሊያስረዳ አይችልም በሚል ደምድሞ ከወዲሁ ክርክሩን ወይም ክሱን ውድቅ የሚያድርግበት አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ቤቱን ራሳቸው ያፈሩት ስለመሆኑና በግራ ቀኙ ማስረጃዎቻቸው ሳይነጥርና ተገቢውን የማስረጃ ምዘና መርህ በመከተል ሳይመዘኑ ከአስተዳደር አካል የተሰጠ የምስክር ወረቀት የለም ተብሎ የሰው ምስክሮች ቃል ከወዲሁ ውድቅ የተደረገው የአመልካችን የክርክር ይዘት ባለገናዘበና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 እንዲሁም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) እና (2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት አከራካሪውን ቤት የሰራው ማን ነው? የሚለው ጭብጥ ተይዞ በዚህ ረገድ የሚቀርቡት የግራ ቀኙ ማስረጃዎች በፍርድ ቤት ፊት ቀርበው ተሰምተው ምስክሮቹ የሚሠጡት ቃል ከንብረት ባለቤትነት መብት ሕግጋት ጋር ተዛምዶ ውሳኔ መሰጠት ሲገባው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባለሀብትነት ሊረጋገጥ የሚገባው በአስተዳደር አካል በሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው በሚለው ነጥብ ላይ ብቻ በማተኮር የሠጠው ውሳኔ አመልካች ንብረቱን ያፈሩት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ከፍ ብለን ከጠቀስናቸው የፍትሐብሔር ድንጋጌዎችና የህገ መንግስት ድንጋጌዎች ጋር ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካች የቤቶችን ግምት ጠቅሰው ዳኝነት ከፍለው በሌላ መዝገብ ይጠይቁ ተብሎ መወሰኑም የፍትሐ ብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ መሰረታዊ አላማ ጋር አብሮ የማይሄድ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195(1) ድንጋጌ የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የንብረቱ ባለሀብት እንደሆነ ሕጉ ግምት ይወስዳል ከማለት ውጪ ማንኛውም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት በሌላ መንገድ አይረጋገጥም የማይል ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 36322 ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 66774 የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ/ም በጉለሌ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ በሚገኝ የቤት ቁጥር 497 ግቢ ውስጥ ከዋናው ቤት ትይዩ የሚገኝ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች እና አንድ ክፍል እቃ ቤት በአጠቃላይ ሶስት ክፍል ቤቶች የውርስ ሀብት ናቸው ተብሎ ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 91243 መጋቢት 05 ቀን 2003 ዓ/ም የጸናው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 የቤት ቁጥር 497 ግቢ ውስጥ ከዋናው ቤት ትይዩ የሚገኝ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች እና አንድ ክፍል እቃ ቤት በአጠቃላይ ሶስት ክፍል ቤቶች በማን እንደተሰሩና ሕጋዊ ባለሀብት ማን እንደሆነ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 66774 በሆነው ቀጥሎ ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ይጻፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡ ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡ ወ/ሮ አየለች ከበደ - ቀረበች

ተጠሪ፡ በላቸው ዋለ ከጠበቃ ውብሠራ ሹመቴ ጋር - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የጋራ ናቸው ያለቻቸውን ንብረቶች በመዘርዘር ድርሻዋን ትወስድ ዘንድ እንዲወሰንላት ጠይቃለች፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ የሚክደውን በመካድ የሚያምነውን ደግሞ በማመን ክርክሩን አቅርቦአል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የቀረበለትን ክርክር መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በውሳኔው ባለመስማማትዋ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሚያዝያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአዲስ አበባ ከተማ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤት የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት ነው፡፡ የብሎኬት ማምረቻና የገበያ ማዕከል እንዲሁም በሱልልታ ከተማ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ሥራዎች የግምቱን ግማሽ ለአመልካች ሰጥቶ ተጠሪ ያስቀረው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራቀኙ ወገኖች የተያዘውን ጭብጥ በሚመለከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከሥር ጀምሮ በግራቀኝ ወገኖች የተደረገውን ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ እንደምናየው በግራ ቀኝ ወገኖች አከራካሪ ሆነው ከቀረቡት ነጥቦች አንደኛው የመኖሪያ ቤቱን የሚመለከት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ አመልካች ከሥር ጀምራ የተከራከረችው የመኖሪያ ቤቱን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ከሥር ጀምራ የተከራከረችው ቤቱ በሞት ከተለየው ከቀድሞ ባለቤቱ ጋር በትዳር ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ የተሠራ የቀድሞ ባለቤቱ እና የኔ የጋራ ሃብት ነው፡፡ ባለቤቱ ከሞተ በኋላም በእኔ እና በልጆቻችን ስም ተመዝግቦና ካርታ ወጥቶለት ይዘነው ቆይተናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በዚህ ቤት ላይ የጋራ ባለሃብት ነኝ ሊል አይችልም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ በእርግጥ ቤቱ አመልካች እንደምትለው እሱ እና ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት የነበረ፣ በእስዋ እና በልጆችዋ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ አይክድም፡፡ ቤቱ የኔም የጋራ ሃብት ነው በማለት የሚከራከረው ከአመልካች ጋር ከተጋባን በኋላ ፈርሶ እንደ አዲስ ተሠርቶአል የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤትም ይህንኑ የተጠሪ ክርክር በመቀበል ነው ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት ነው ሲል የወሰነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ቤቱ የታደሰው አመልካች እና ከቀድሞ ባለቤትዋ የወለደቻቸው ልጆችዋ በጋራ በመሆን የእድሳት ፈቃድ ለሚሰጥ አስተዳደር /በጉለሌ ክ/ከተማ የቀበሌ 13/14 አስተዳደር ጽ/ቤት/ ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት እንደሆነ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አረጋግጦአል፡፡ በእርግጥ በዚህ ጊዜ የአመልካች እና የተጠሪ ጋብቻ አልፈረሰም ነበር፡፡ ተጠሪም ይህን መሠረት በማድረግ ነው እየተከራከረ ያለው፡፡ በቤቱ ላይ የተደረገው እድሳት አዲስ ቤትን እንደመሥራት የሚቆጠር በመሆኑ እና ይህ የሆነው ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ስለሆነ ቤቱ የጋራ ሀብቱ ነው በማለትም ነው ክርክርሩን ያሰማው፡፡

እንደምናየው ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ ጋብቻ ከመመሥረቱ በፊት የነበረ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የቤቱ ባለሃብቶች አመልካች እና ከሟች የተወለዱ ልጆችዋ እንደሆኑ ተረጋግጦ ከሚመለከተው የመንግሥት አስተዳደር ክፍል ማስረጃ የተሰጠ ስለመሆኑ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤት አረጋግጦአል፡፡ እነዚህ የቤቱ የጋራ ባለሃብቶች ቤቱን እንዲያድሱ እንዲፈቀድላቸው ቀበሌውን በጋራ የጠየቁትም የተረጋገጠላቸውን የባለሃብትነት መብታቸውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ቤቱ የታደሰው የአመልካች እና የተጠሪ ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ስለሆነ ብቻ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት /በጋብቻ ጊዜ የተፈራ/ ነው ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች የግል ንብረቶች ሆነው እንደሚቀሩ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 57 መመልከቱንም እዚህ ላይ ማንሳቱም ተገቢ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጋቢዎች ጋብቻቸው ንብረታቸውን በተመለከተ ስለሚያስከትለው ውጤት በውል መወሰን እንደሚችሉ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 42/1/ የተደነገገ ቢሆንም፣ አመልካች እና ተጠሪ ግን በዚህ ድንጋጌ መሠረት ያደረጉት ውል ስለሌለ አመልካች ቤቱን የተጠሪም የጋራ ንብረት እንዲሆን ፈቅዳለች የሚባልበት አግባብ የለም፡፡ ስለዚህም ቤቱ የኔም የጋራ ሃብት ነው በማለት ተጠሪ ያቀረበው ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን ክርክር በመቀበል የሰጡት ውሳኔ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመቀጠል በሁለተኛ ደረጃ የተመለከትነው የቡሎኬት ማምረቻና ሱፐር ማርኬት/ የገበያ ማዕከል/ እንዲሁም በሱሉልታ ከተማ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን በሚመለከት የተነሳውን ክርክር ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ እንዳየነው መሠረት ያደረገው ንብረቶቹ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት አይደሉም የሚል አይደለም፡፡ ንብረቶቹ የጋራ ሃብት አንደሆኑ ፍ/ቤቱ አረጋግጦአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የንብረቶቹን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግምት ግማሽ ለአመልካች በመስጠት ያስቀራቸው በማለት ወስኖአል፡፡ አመልካች የተቃወመችው ይህን ውሳኔ ነው፡፡ ንብረቶቹ የጋራችን እስከሆኑ ድረስ መካፈል ያለብን እኩልነታችን ተጠብቆ ነው በማለትም ነው የተከራከረችው ተጠሪም ቢሆን ንብረቶቹ የጋራ አይደሉም የሚል መከራከሪያ የለውም፡፡ ክርክሩ አመልካችም በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘውን ቤት ለኔ ድርሻዬን ግምት ከፍላ እንድታስቀር ስለተወሰነላት ይህንኑ ለማቻቻል ተብሎ የተደረገ ነው የሚል ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤት የአመልካች እና የልጆችዋ ብቻ በመሆኑ ተጠሪ የዚህ ቤት እኩል ድርሻ አለኝ የሚልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በሌሎች ንብረቶች የተሰጠው ውሳኔ ከመኖሪያ ቤቱ ጋር የሚያያዝበት ሁኔታ እንዳለ በማድረግ ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ እዚህ ላይ በአግባቡ መታየት ያለበት ጉዳይ ሌሎቹ ንብረቶች የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት መሆናቸው ከተረጋገጠ ክፍፍሉ መፈጸም ያለበት በምን አይነት ሁኔታ ነው የሚለው ነው፡፡ ባልና ሚስት በጋራ ያፈሩአቸው የጋራ ሃብቶች መከፋፈል ያለባቸው በእኩልነት መርህ ላይ በመመሥረት እንደሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 35/2/ እና በተሻሻለው የቤተሰብ አንቀጽ 90 ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የእኩልነት መርህ መጠበቅ አለበት ከተባለ ደግሞ አንዱ ከሌላው ያነሰ ወይም የበለጠ አይወስድም ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብቶች ናቸው የተባሉት የቡሎኬት ማምረቻ እና የገበያ ማዕከል እንዲሁም በሱሉልታ ከተማ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ስራዎች በባለቤትነት /በተግባር/ እንዲረከብ ወይም እንዲወስድ የተባለው ተጠሪ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተቀባይነት ይኑረው ከተባለ አመልካች ልታገኝ የምትችለው የንብረቶቹ ግምት/ገንዘብ/ ግማሽ ብቻ ነው፡፡ አመልካች ግን አልተስማማችም፡፡ ገንዘቡን የምትወስደው በፍርድ ስለተገደደች እንጂ ፈቅዳ አይደለም ማለት ነው ተጠሪ ንብረቱን መውሰድ አለብኝ እንደሚለው ሁሉ አመልካችም የንብረቱን ግምት ግማሽ በገንዘብ ተለውጦ እንድትወስድ አልገደድም የማለት ከእኩልነት መርህ የሚነሳውን ክርክርዋ ከሕግ አግባብ ውጪ እንዳለመቀበልም ነው የሚቆጠረው፡፡ በእኛ እምነት እና ግንዛቤ የንብረት ክፍፍሉ መከናወን ያለበት ሕጉ ባስቀመጠው የእኩልነት መርህ እና በቤተሰብ ሕጉ በተመለከተው የክፍፍል ሥርዓት መሠረት ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው አመልካች እና ተጠሪ ንብረቶቹን በስምምነት ሊከፋፈሉ አልቻሉም፡፡ ከዚህ የተነሣም ሕጉ ወደአስቀመጠው የክፍፍል ሥርዓት መሄዱ የግድ ነው፡፡ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 91 እንደተመለከተው ሃብቱን በአይነት መከፋፈል የሚቻል ከሆነ ከንኡስ አንቀጽ /1/ እስከ ንኡስ አንቀጽ /3/ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት እንዲፈጸም የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡ በዚህ ሁኔታ ለማከፋፈል የማይቻል ከሆነ ደግሞ ቀጥሎ ባለው አንቀጽ 92 መሠረት ንብረቱን በመሸጥ ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ ማድረግ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የንብረት ክፍፍሉ በዚህ ሥርዓት መሠረት እንዲፈጸም አላደረጉም፡፡ በመሆኑም ውሳኔው በሕጉ አተገባበር /አተረጓጎም/ ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

በመጨረሻም ያየነው በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤት ሲታደስ እኔም ገንዘብ አዋጥቻለሁ የሚለው የተጠሪ ክርክር በምን አግባብ ሊታይ ይገባል የሚለው ነው፡፡ የሥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቶች ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት ነው ብለው በመደምደማቸው ሌላውን አማራጭ አላዩም፡፡ በበኩላችን እንደተገነዘብነው ቤቱ የአመልካች እና የልጆችዋ የጋራ ሃብት ነው ቢባልም፤ ሲታደስ በጥቅም ላይ ከዋለው የእድሳት ወጪ/ገንዘብ/ ውስጥ ግማሹ የአመልካች መሆኑ የሚታመን ሲሆን ይኸው ገንዘብ የአመልካች የግል ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ከተጠሪ ጋራ የጋራ ሃብት ነው ተብሎ የሕግ ግምት የሚወስድበት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ያለው መብት አመልካች ለእድሳት ካወጣችው ወጪ ግማሽ ገንዘብ ውስጥ ግማሹን ማለትም የቤቱን መቶ ፐርሰንት ሃያ አምስት ከመቶ /ፐርሰንት/ መውሰድ ነው፡፡ ይህ መጠን ደግሞ በሥር ፍ/ቤት ሊረጋገጥ የሚገባው ነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/54406 ነሐሴ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.72805 ሚያዝያ 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13/14 ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 1005 በሆነው የመኖሪያ ቤት ላይ ተጠሪ የጋራ ባለሃብትነት መብት የለውም ብለናል፡፡
3. የቡሎኬት ማምረቻው እና የገበያ ማእከሉ /ሱፐርማርኬት/ እንዲሁም በሱሉልታ ከተማ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ሥራዎች/የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ በተራ ቁጥር 6 የተመለከቱት/ በአይነት ለማከፋፈል የሚቻል ከሆነ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 91 መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም፤ በዚህ መሠረት ማከፋፈል ካልተቻለ ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 92 በተደነገገው መሠረት ተሸጠው አመልካች እና ተጠሪ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስነናል፡፡
4. ተጠሪ ለቤቱ እድሳት ከወጣው ወጪ ውስጥ ሊያገኝ /ሊመለስለት/ የሚገባው መጠን ምን ያህል እንደሆነ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲወስን በዚህ ነጥብ ብቻ ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
5. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣ ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራቀኝ ወገኖች ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፍ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. *47917*

ግንቦት *05* ቀን *2003* ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፣ 1. ወ/ሮ መልካምስራ አለበል

2. አቶ ጌትነት አለበል

3. አቶ ሁልጊዜ አለበል

4. ወ/ሮ ማንእንዳንቺ አለበል

ከጠበቃ ደመቀ ዘነበ ቀረቡ

ተጠሪ፣ ወ/ሮ አንለይ ሊበን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ የውርስ ይጣራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ሟች ወ/ሮ አረጋሽ ተሰማ ወራሾች መሆናቸውንና የሟች ሀብት የሆነው ቤት በተጠሪ ይዞታ ስር የሚገኝ ቢሆንም ተጠሪ የውርስ ሃብቱን ለመካፈል በመፈለጋቸው ውርስ አጣሪ እንዲቋቋም ይታዘዝላቸው ዘንድ ለደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም በተከሣሽነት ቀርበው ሟች አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ኑዛዜ የተው መሆኑን ኑዛዜው እንዲፀድቅ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ የአሁኑ ተጠሪ የሚያውቁትና ያልተቃወሙት ጉዳይ መሆኑን ገልፀው ቤቱን ለመካፈል ተጠሪ ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ እንዲሆንላቸው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር መርምሮ ኑዛዜው ሕጉ የሚጠይቀውን የአፈፃፀም ስርዓት የተከተለ መሆኑን ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ሲፀድቅ ተጠሪ እያወቁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያልተቃወሙና ከውርስ ተነቅዬአለሁ የሚል ክርክርም ስለሌላቸው የተጠሪ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ምንም እንኳ ኑዛዜው በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተደረገ ቢሆንም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው በምስክርነት ያልተጠቀሰ በመሆኑ ኑዛዜው ዋጋ የለውም ዋጋ አለው ቢባል እንኳን ተጠሪን ከውርስ የነቀለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚሉ ምክንያቶች በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔን ሽሮ ውርስ አጣሪ እንዲቋቋም ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለዚሁ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ መሠረታዊ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ ኑዛዜው በፍርድ ቤት ሲፅድቅ የነበሩና ሁኔታውን እያወቁ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የወራሽነት ማስረጃ በመያዝ ውርስ አጣሪ እንዲቋቋም አቤቱታ ማቅረባቸው ከስነሥርዓት ውጪ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ በሶስት አመት ይርጋ ጊዜ ገደብ የሚታገድ ነው የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረነገር ስልጣን የላቸውም ክርክሩ የቀረበው አንድን ቤት ለመካፈል ስለሆነ ውርስ አጣሪ ሊቋቋም የሚገባው ጉዳይ አይደለም ኑዛዜው ሕጋዊ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኑዛዜ አፃፃፍ ፎርምን አስመልክቶ ለፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 882 ድንጋጌ የሰጠው ትርጉምና ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን የመነቀል ክርክር መሠረት በማድረግ ውሣኔ የመስጠቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮላቸው መጥሪያውን ለመቀበል ፍቃደኛ አልሆኑም በሚል ቃለመሃላ በአመልካቾች በኩል በመቅረቡ ይህ ችሎት ጉዳዩ ተጠሪ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩን በመመርመር በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ሚያዚያ 05 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሣኔ ሰጥቶ ነበር፡፡ ከዚህ በኃላ ተጠሪ ጉዳዩ በሌለሁበት እንዲታይ የተደረገው ከሕግ ውጪ ነው በማለት በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሣኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት ታይቶ እንዲወሰን ጥያቄ አቅርበው ይህ ችሎትም በዚህ ረገድ በቀረበው አቤቱታ ግራቀኙን አከራክሮ ተጠሪ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገው ያላግባብ መሆኑ አረጋግጦ ሚያዚያ 05 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠውን ውሣኔ በማንሳት ጉዳዩ ተጠሪ ባሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ በዋናው ጉዳይ ላይ በሰጡት መልስ አመልካቾች አለ የሚሉትን ኑዛዜ የማያውቁት መሆኑና በሕጉ የተመለከተውን አፃፃፍ ሥርዓት ያላሟላና ጥቅማቸውን የጎዳ እንዲሁም ሟችም ቀድመው ከውርስ ያልነቀሏቸው መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በሌሎች የበላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ እንዲጸናላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾችም በተጠሪ በኩል በዋናው ጉዳይ ላይ የቀረበው የሰበር አቤቱታ መልስ ይዘት በጉዳዩ ላይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሰጥቶት የነበረውን ውሣኔ የሚለውጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረውና የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት የመልስ መልሳቸው ላይ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ሟች ወ/ሮ አረጋሽ ተሰማ ጽጌ ዘገኑ ሐምሌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

07 ቀን 1998 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾችን ነቅሏል አልነቀለም? ውጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉት ነጥቦች በጭብጥነት ሊታዩ የሚገባቸው ሆነው አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች አቶ ፅጌ ዘገኑ ነሀሴ 07 ቀን 1991 ዓ.ም ኑዛዜ የተው መሆኑን አመልካቾችም ሆኑ ተጠሪ የሟቿ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች /ልጆች/ መሆናቸውን ሲሆን ተጠሪ ውርስ አጣሪ እንዲቋቋምላቸው አቤቱታ ሲያቀርቡ አመልካቾች በአከራካሪው ቤት ላይ ኑዛዜ በሟች መደረጉንና የውርስ ማጣራት ለዚህ አንድ ንብረት ሲባል ሊቋቋም እንደማይገባ እና የተጠሪ ድርሻም በቤቱ ላይ በኑዛዜ ቀሪ የሆነ መሆኑን ገልፀው መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡ ሌላው ከመዝገቡ የተረዳነው ዋናው ቁምነገር አከራካሪው ኑዛዜ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተደረገ መሆኑን ኑዛዜው ላይ ሁለት ምስክሮች መፈረማቸውን በኑዛዜው ላይ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው በምስክርነት በሟች ኑዛዜ ላይ አለመፈረማቸውን ነው፡፡ ተጠሪ ኑዛዜው ላይ ያለውን ቀንና ኑዛዜው ፀደቀ የተባለበትን ጊዜ መሠረት አድርገው ኑዛዜው ሐሰተኛ ነው የሚል ክርክር ያቀረቡ ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም ይኸው በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክር የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያላረጋገጡት ነጥብ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ// እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት ከተሰጠው የመሠረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር በዚህ የክርክር ደረጃ ተቀባይነት የሚያገኝበትን የሕግ አግባብ ያላገኘን በመሆኑ እንደተረጋገጠ ፍሬ ነገር አድርገን የምንወሰደው አይደለም፡፡ እንግዲህ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡት ነጥቦች ከላይ የተመለከቱት ከሆኑ ኑዛዜው በሕጉ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን ያለመሆኑን መመርመር የግድ ይሆናል፡፡

ተጠሪ ሟች ወ/ሮ አረጋሽ ተሰማ ነሐሴ 07 ቀን 1991 ዓ.ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ሕጋዊ አይደለም የሚሉበት ምክንያት በአራት ምስክሮች ፊት አልተደረገም በሚል ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜው የሕጉን ፎርማሊቲ ያሟላ አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ግን ኑዛዜው በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ቢሆንም አዋዋዩ በምስክርነት አልተጠቀሱም በማለት ነው፡፡ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ግልፅ ኑዛዜ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባቸው ስርዓቶች በፍ/ሕ/ቁ 881 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ ይህም ስርዓት መፈፀሙና የተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ ተናዛዥና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ ነው፡፡ በሟች ተሰጠ የተባለው ኑዛዜም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተደረገ ሁለት ምስክሮች የፈረሙበት ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ኑዛዜውን አረጋግጦ ማህተም ያሰፈረመበት ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ የሚገልጽ እና ተናዛዥዋ የጣት አሻራቸውን ምስክሮቹ ደግሞ ፊርማቸውን ያኖሩበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ሕ/ቁ 881 ሥር የተመለከቱትን ስርዓቶች ያሟላ ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው የህጉን ሥርዓት አልተከተለም ያለው በኑዛዜው ላይ ከተመለከቱት ምስክሮች ውስጥ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጣቸው ሰው በምስክርነት አልተጠቀሱም ወይም ምስክር አይደሉም በማለት ነው በእርግጥ ምስክሮች ተብለው የተፃፉት ሁለት ሰዎች ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጣቸው ለመሆኑ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ኑዛዜው የተደረገው ከሁለቱ ምስክሮች በተጨማሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ፊት ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ነው፡፡ ምንም እንኳን እኚህ ሰው ምስክር ተብለው ባይገለፁም ሟች ኑዛዜውን በነፃ ፈቃዳቸው ሲሰጡና ኑዛዜውም ሲነበብ አይተው በኑዛዜው ላይ ፈርመዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የምስክሮች ዋና አስፈላጊነትም ኑዛዜ አድራጊው ኑዛዜውን በነፃ ፍላጎቱ እና በትክክለኛ አእምሮው የሰጠ መሆኑንና የኑዛዜ ቃሉም የእርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው አረጋግጠው ፊርማቸውን ያኖሩ በመሆኑ ምስክር ተብለው ስማቸው ባለመገለፀ ብቻ ምስክር አልነበሩም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ከምስክሮቹ አንዱ ደግሞ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ከሆነና ኑዛዜው ይኸው ሰው ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ከሆነ ሁለት ምስክሮች ብቻ በቂ መሆናቸው በፍ/ሕ/ቁ 882 ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ አይደለም የተባለው ምክንያት ሕጋዊ ባለመሆኑ የምንቀበለው አይደለም፡፡ ኑዛዜው በሕጉ የተመለከተውን አጻጻፍ ስርዓት የተከተለ መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያምንበት ሲሆን ተጠሪ በጠቅላላው የሚከራከሩት ኑዛዜው መብቴን የጎዳኝ በመሆኑ ፈራሽ ነው በሚል የሕግ ጥያቄ በማንሳት በመሆኑ የኑዛዜው ውጤት አግባብነት ባለው የውርስ ድንጋጌዎች መሠረት ሊታይ የግድ የሚል ይሆናል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜውን ውድቅ ያደረገበት ተጨማሪ ምክንያትም ኑዛዜው ተጠሪን ከሟች ውርስ ነቅሏቸዋል በሚል ሲሆን አመልካቾች ይህንኑ ክርክር ተጠሪ ሳያነሱት ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ማንሳቱ አግባብነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት አጠቃላይ ክርክር ማንሳታቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ኑዛዜው ፈራሽ የሚሆንበትን የሕግ አግባብ ፍርድ ቤቱ ለይቶ መወሰኑ በተጠሪ ያልተነሳን ክርክር አንስቷል ለማለት የሚያስችል አይደለም ምክንያቱም የሕጉን ጥያቄ ለይቶ የመወሰን ተግባር የፍርድ ቤቱ የስራ ድርሻ እና የዳኝነት አካሄዱ የግድ የሚለው ጉዳይ ነውና፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከሟች ውርስ ተነቅለዋል አልተነቀሉም የሚለውን ጉዳይ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ተናዛዥ /ወላጅ/ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለህጋዊና በቂ ምክንያት እንዲሁም በዝምታ ከውርስ ለመንቀል እንደማይችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 ድንጋጌዎች ይዘት በግልፅ ያሳያል፡፡ ወላጅ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሹን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ወይም በዝምታ ከነቀለም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ አንድ ልጅ ከውርስ ተነቅሏል ሊባል የሚችለው ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ለሌሎች ልጆቹ ወይም ሰዎች ሲደረግ እንደሆነ ስለመነቀል የተደነገጉት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች /ከቁጥር 937-939 ድረስ ያሉት/ ያሳያሉ፡፡ በኑዛዜው የሚከናወኑ ተግባሮች የኑዛዜ ስጦታ /legacy/ ወይም የክፍያ ደንብ /Rule of partition / ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመርህ ደረጃ ደግሞ አንድ ሰው ከውርስ ሀብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ አያሰኘውም፡፡ ይልቁንም ይህ አይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ አውራሽ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዘዝለት የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ /legacy/ አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ /Partition/ በመከተል የሚከናወን ይሆናል፡፡ ሆኖም በኑዛዜው ላይ የሚሰጠው ክፍያ መጠን በመገለፀ ብቻ ሁል ጊዜ የክፍያ ደንብ ነው ሊባል የሚችል አይሆንም፡፡ በመሆኑም የተሰጠው የንብረት መጠን ከሟቹ የውርስ ንብረት ግምት ጋር ታይቶ ውጤቱም በዚሁ ረገድ መለየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ሟች በኑዛዜው ላይ የሚያሰፍረው የንብረት መጠን ከሟቹ የውርስ ንብረት መጠን ጋር እየታየ የመነቀል ጉዳይ ነው ወይስ የክፍያ ማነስ ነው? የሚለው ነጥብ የሚለይ ይሆናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ሟች ወ/ሮ አረጋሽ ተሰማ ባደረጉት ኑዛዜ አንድ መኖሪያ ቤታቸውን ነው፡፡ ተጠሪዎች የውርስ ንብረቱ ይጣራ ጥያቄ በአንድ ቤት ላይ የቀረበ በመሆኑም ግምቱ ተቀምጦ ክሱ ከሚቀርብ በስተቀር የውርስ አጣሪ እንዲቋቋም የሚደረግበት አግባብ የለም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚል ክርክር ከስር ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩበት ጉዳይ ሲሆን ሟች ከዚህ ንብረት ውጭ የውርስ ንብረት ያለስለመሆኑም በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን ከአጠቃላይ የክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ያላቸው ንብረት ይኸው በተጠሪ ይዞታ ስር ይገኛል የተባለ ቤት ብቻ ከሆነ አመልካቾች እንደጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ ሊወሰዱ የሚገባቸው ሲሆን በውጤት ደረጃ ደግሞ ተጠሪ በኑዛዜው በገዘምታ የተነቀሉ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 939/2/ መሠረት ተቀባይነት የሌለው ሲሆን በውጤት ደረጃ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 842/2/ እና 915 ድንጋጌዎች ይዘት አንፃር ሲታይ ተጠሪን ከአመልካቾች ጋር እኩል እንዲካፈሉ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከውርስ በገዘምታ ወይም ያለበቂ ሕጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሆነው የውርስ ንብረቱን ሊከፋፈሉ የሚችሉ መሆኑን ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤት ወደዚህ ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት በወላጅ የተደረገ የኑዛዜ ስጦታ አይነቱ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ መሆን ያለመሆኑን በቅድሚያ መለየት አለበት፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912 ስር እንደተመለከተው የኑዛዜ ስጦታ ጠቅላላ ወይም ልዩ ኑዛዜ ስጦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ሲባልም ተናዛዡ ሀብቱን ጠቅላላ ወይም ከመላ ንብረቱ አንዱን ክፍል በሙሉ ሀብትነት ወይም በሌጣ ርስትነት ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች የሚያወርስበት የኑዛዜ ቃል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 912/1/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ማንኛውም ሌላ የኑዛዜ ቃል ሁሉ እንደ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡ አንድ ኑዛዜ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014 ድንጋጌ ቅደም ተከተል መሠረት የሚከፈል ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ቤቱ ለአመልካቾች የተሰጠበት አግባብ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1014/ሠ/ ስር በተመለከተው መሠረት እንደውርስ እዳ ተቆጥሮ ለልዩ ኑዛዜ ተቀባዩ የሚከፈል ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 938 እና 939 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915 ድንጋጌዎች ታይቶ ተወላጅ ከውርስ ተነቅሏል ከኑዛዜ ተቀባዮች ጋር እኩል ሊካፈል ይገባል የሚባልበት ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በፍ/ሕ/ቁጥር 915 መሠረት እንደጠቅለላ ኑዛዜ ወራሽ ተወስደው ከአመልካቾች ጋር እኩል ተካፋይ ናቸው ተብሎ ውርሱ እንዲጣራ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ በበላይ ፍርድ ቤቶቹም መፅናቱ ህጋዊ እንጂ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19946 ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273/2001 ጥር 13 ቀን 2001 ዓ.ም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01275 ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ሟች ወ/ሮ አረጋሽ ተሰማ ነሐሴ 07 ቀን 1991 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በውጤቱ ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ተጠሪን የነቀለ በመሆኑ በተጠሪ ላይ ተፈፃሚት የለውም ብለናል ኑዛዜው አመልካቾችንና ተጠሪን በሚቹ ድርሻ ንብረት ላይ እኩል ወራሽ የሚያደርግ በመሆኑ ውርሱ በውርስ አጣሪ ተጣርቶ የሚገኘው ውጤት አመልካቾች የሚችን ድርሻ ንብረት ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ ብለናል፡፡
3. ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ መዝገብ ሚያዚያ 05 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተፈፃሚት የሌለው ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ም.አ *የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሥሪና ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልድ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡-የፊንጫአ ስኳር ፋብሪካ - ጠበቃ ፍቅሬ ሞያ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ መ/ሰ/ማህበር - ነ/ፈጅ ኤልያስ አበበ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሠረት አድርጐ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቋሚ ቦርድ ሲሆን አመልካች የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 131 መሠረት መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም ከአሁኑ አመልካች ተወካዮች ጋር በሕብረት ስምምነት ላይ ድርድር ጀምሮ በዓመቱ ማለትም መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም መጨረሱን፣ ሆኖም የአሁኑ አመልካች የሕብረት ስምምነቱን የተደራደሩት ወኪሎቹ ከውክልና ስልጣናቸው ውጪ ተደራድረዋል በሚል ምክንያት ሕብረት ስምምነቱን ልቀበል አልችልም በማለት መግለፁን በመዘርዘር ሕብረት ስምምነቱ ቀርቦ እንዲመዘገብና ሰራተኛውም በድርድሩ መሠረት የተገኙትን መብቶችና ጥቅማ ጥቅሞችን እንዲያገኝ እንዲወስንለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የአመልካች ወኪሎች ከተሰጣቸው ስልጣናቸው ውጪ በተወሰኑት ነጥቦች ላይ መደራደራቸውንና የተወሰኑት ነጥቦችም በሕብረት ስምምነቱ የማይሸፈኑ መሆናቸው በመረጋገጡ አስፈላጊው ማሻሻያ እንዲደረግ ለአሁኑ ተጠሪ ምላሽ መስጠቱን በመግለጽ ክሱ ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ቋሚ ቦርድም በጉዳዩ ላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ የሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር አስማሚ አስተያየቱን እንዲሰጥበት ከአደረገ በሁዋላ የአሁኑ አመልካች ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ ሕብረት ስምምነቱ ድርድሩ ያለቀለት ስለሆነ በሁለቱ ወገኖች ተፈርሞ አስፈላጊው ቅጂ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 131 መሠረት ለመዝጋቢው አካል ተልኮ ይመዝገብ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃው መጋቢት 23 ቀን 2002 ዓ.ም በዓፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የአመልካች ተወካዮች በተወሰኑት ነጥቦች ላይ ከስልጣናቸው ውጪ የፈፀሙት ድርድር መሆኑን የአመልካች ማኔጅመንት አረጋግጦ እነዚህ ነጥቦች እንዲወጡ ያቀረበው ሐሣብ በተጠሪ ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቶ ክሱ ተቀባይነት ማግኘቱ ከውክልና ሕግ ድንጋጌዎችና ከሕብረት ስምምነት ድርድር ሐሣቦች ጋር በማይዛመድ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የአመልካችን መስሪያ ቤትን በመወከል ከተጠሪ ጋር የሕብረት ስምምነት ድርድር ያደረጉት ግለሰቦች በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ስለመሆኑ መጣራት ያለበት ነው በሚል ምክንያት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት ጠበቃው ቀርበው ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከተጠሪ ጋር የሕብረት ስምምነት ለማድረግ ግለሰቦችን በመወከል ድርድር ሲያካሂድ የቆየ ሲሆን ድርድሩ ተጠናቅቆ ጉዳዩን የአመልካች የማኔጅመንት አካል ሲመለከተው አመልካች የወከላቸው ግለሰቦች ድርድሩን ያካሄዱት ከተሰጠቸው ሥልጣን ውጪ እና የህብረት ስምምነት በማይሸፍናቸው ጉዳዮች ሁኖ በማግኘቱ ይህንኑ ለተጠሪ እንዳሣወቁ እና ማሻሻያ እንዲደረግ ጥያቄ ማቅረቡን ነው፡፡ ተጠሪ የሚከራከረው ደግሞ ድርድሩ ላይ የተሣተፉት የአመልካች ወኪል ግለሰቦች ከስልጣናቸው ውጪ የሰሩት ነገር አለመኖሩንና በሕብረት ስምምነት የማይሸፈን የመብት ወይም የጥቅማ ጥቅም ጥያቄ የለም በሚል ስለመሆኑም ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ አዋጅ ቁጥር 377/96 “አንቀጽ” 124 እስከ አንቀፅ 135 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ስለህብረት ስምምነት ትርጉም ስለህብረት ስምምነት ድርድር የህብረት ስምምነት ድርድር፣ የህብረት ስምምነት ድርድር ሥነ ሥርዓት፣ ስለህብረት ስምምነት አመዘጋገብ፣ የሕብረት ስምምነት የሚፀናበት ሁኔታ እና የሕብረት ስምምነት ተፈፃሚነት ወሰን ደንግጎ እናገኛለን፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 124/2/ እና የአዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ሲታዩ ተደራዳሪ ወገኖች በስራ ላይ ያለውን ህብረት ስምምነት የስራ ዘመኑ ከማለቁ ወይም ቀደም ብሎ ሕብረት ስምምነቱን እንዲሻሻል ወይም በሌላ እንዲተካ መወሰን ያለባቸው መሆኑን የሚያስገነዝቡን ሲሆን በዚሁ መልክ በሚደረስበት ውሣኔ መሠረት ተደራዳሪዎች የህብረት ስምምነቱን ድርድር ተቀራርበው መስራት ያለባቸው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 3 በግልጽ ያሣያል፡፡ አዋጁ የሕብረት ስምምነት ድርድር ሊደረግ የሚችልባቸውን ነጥቦችና ድርድሩን ለማድረግ የሚችሉ ወገኖች እነማን እንደሆኑም በአንቀጽ 124/2/ እና 126 ስር ደንግጎ እናገኛለን፡፡ በመሆኑም ድርድሩ ስለስራ ሁኔታዎች ወይም ስለህብረት ስምምነት ወይም የሕብረት ስምምነትን ለማደስና ለማሻሻል በአሰሪዎችና በሰራተኞች ማህበር ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻቸው መካከል የሚደረግ ክርክር (NEGOTITON) ስለመሆኑ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች አስፈላጊነት ሲታይም የአሰሪና ሰራተኛ ወገኖች የመደራደርና ሕብረት ስምምነት የማድረግ መብታቸው በአግባቡና በቀና መንፈስ እንዲጠቀሙ ማስቻል ስለመሆኑ በአዋጁ ማሻሻያ ላይ የተደረገው የውይይት ሰነድ / ሀተታ ዘምክንያት/ ያሣያል፡፡ የሕብረት ስምምነት ከተፈረመ በሁዋላ የስምምነቱ አስፈላጊ ቅጅ በተዋዋይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገኖች አማካኝነት ለሰራተኞና ማህበራዊ ሚኒስቴር ለምዝገባ እንደሚላክ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 131 ስር ሰፍሯል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 133/2/ ድንጋጌ ሲታይም በህብረት ስምምነቱ በሌላ አካኋን ካልተወሰነ በስተቀር አንድ የሕብረት ስምምነት ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና እንደሚሆን ያስገነዝባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የሕብረት ስምምነት ድርድር አመልካች ውክልና በሠጣቸው ወኪሎችና በተጠሪ መካከል ስለመከናወኑ የተረጋገጠ ሲሆን አከራካሪው የሕግ ጥያቄ አመልካች ሰነዱ በሕብረት ስምምነት ሊፀድቅ አይገባም በማለት ተቃውሞ አቅርቦ እያለ ወኪሎቹ ስለፈረሙ ብቻ በሕግ ፊት የፀና ይሆን ዘንድ የድርድሩ ውጤት በሚመለከተው አካል እንዲመዘገብ ዳኝነት ሊያርፍበት የሚገባው ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የሕብረት ስምምነቱ እንዲመዘገብ የሚደረገው ከተፈረመ በሁዋላ ነው፡፡ አመልካች በድርድሩ ወቅት የተሣተፉ ወኪሎቹ ሰነዱ ህብረት ስምምነት እንዲሆን ስምምነት የደረሱና የፈረሙ ስለመሆኑ ሣይክዱ የወኪሎቹን ተግባር የሕብረት ስምምነቱ በሚመለከተው አካል ከመመዝገቡ በፊት ተቃውሞታል፡፡ የሕብረት ስምምነት ድርድሩ በሕጋዊ ወኪሎቹ እንዲከናወን ያደረገ አሰሪ በድርድሩ መሠረት የተደረሰን ስምምነት ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ከመመዝገቡ በፊት ቢቃወመው ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ አዋጅ ቁጥር 377/96"ም" ሆነ የዚሁ አዋጅ ማሻሻያ የሆኑት አዋጅ ቁጥር 466/97 እና 494/98 ድንጋጌዎች ምላሽ አይሰጡም፡፡ ይሁን እንጂ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድርድሩ በሕጋዊ ወኪሎች የሚደረግበትን አግባብ የዘረጋ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕጉ ስለእንደራሴነት የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ማየቱ አግባብነት ያለው ይሆናል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2190 ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ከስልጣኑ ውጭ ወካይ የተወካይነት ተግባር ለማጽደቅ ወይም ለማፍረስ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ወኪሎቹ በሕብረት ስምምነት ድርድር ላይ ክርክር ሲያደርጉ ቆይተው ሰነዱ የሕብረት ስምምነት እንዲሆን በፊርማቸው ያረጋገጡበትን ሁኔታ ያልተቀበለው መሆኑን ምክንያቱን ገልጾ እንዲመዘገብ ፍላጎት የሌለው መሆኑን መግለፁ ከመነሻውም ስምምነቱ ገና ወደሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ ያልፀደቀ ከመሆኑ በድርድር ደረጃ ያለ በመሆኑና በወካይነት ስልጣኑም የወኪሎቹ ተግባር ሕጋዊ ግዴታ እንዳይጥልበት የማድረግ ሕጋዊ መብት ያለው በመሆኑ የሕብረት ስምምነቱን በፍርድ ኃይል እንዲያስመዘግብ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በሕጉ አግባብ የሕብረት ስምምነት የፀና ነው የሚባለው በተገቢው መንገድ በአሰሪው መፈረሙና የወኪሎቹን ተግባር ማጽደቁ ሲረጋገጥ ነውና፡፡

ተጠሪ ድርድሩ የበረሃ አበልን የማይመለከትና በአመልካች ተገቢ ባለሥልጣን ተፈርሞ እንዲመዘገብ የሚል ሃሣብ መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የቀረበ ሁኖ እያለ የአመልካች ጠበቃ የሰበር አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም በሚል ያቀረበው ክርክር ሲታይም በሕጉ አግባብ አመልካች የሰበር አቤቱታውን የተወው መሆኑ እስካልተረጋገጠ እና ጉዳዩን አይተው ዳኝነት ባጣራት አካላት ፊትም ተጠሪ ይህንኑ ክርክር አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ ስለመሆኑ የሚያመለክት ሁኔታ በሌለበት ይህ ችሎት የሚቀበለው የክርክር ነጥብ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች ተገቢ ባለሥልጣን ሰነዱ የሕብረት ስምምነት እንዲሆን የበርሃ አበልን በተመለከተ የተቀመጠው ጉዳይ እንዲወጣ ሀሣብ አቅርቦ እያለ ሰነዱ በወኪሎቹ ተፈርሟል በሚል ምክንያት ብቻ በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ እንዲመዘገብ የተደረገው ያላግባብ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአስሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ/ቁጥር 383/ቀወ1/2001 ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 90031 መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ወኪሎቹ ያደረጉትን ድርድር ያለመቀበል ሥልጣን ያለው በመሆኑ በተገቢው ባለስልጣን ያልተፈረመ ስነድ የሕብረት ስምምነት ሁኖ እንዲመዘገብ እንዲያስደርግ የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸን ይቻሉ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ አቶ አየለ አበበ ቀረቡ

ተጠሪ፣ የፊንፊኔ የደን ድርጅት ነገረፈጅ ጋንገና ገብረሚካኤል ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ አመልካች የድርጅቱ ንብረት ዲ 7 ኤች ተብሎ በሚጠራው ዶዘር ላይ ጉዳት በማድረሱ ብር 227,594.18 ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካች ማሽኑን ለሥራ ከማንቀሳቀሱ በፊት ቅባት ዘይትና ውሃ ማየት የነበረበት ቢሆንም ይህንን ሳይፈትሽ በመንዳት እንዲሰባበር በማድረጉ ለጥገና ብር 227,594.18 /ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አምስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአስራ ስምንት/ ሣንቲም ወጭ አድርገናል፡፡ ስለዚህ አመልካችና የአመልካች ወኪል ይህንን ገንዘብ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ማሽኑ የተሰበረው በእኔ ችሎታና ሙያ ሊፈተሹ የሚችሉ የሞተር ቅባት ዘይትና ውሃ ሣልፈትሽ ስለነዳሁት አይደለም፡፡ ማሽኑ የተሰበረው በቴክኒክ ባለሙያ ስሌትና ክትትል ሊደረግበት የሚገባው የመጨረሻ ክፍሎች /Final Drive/ በደረሰበት ጉድለት ነው፡፡ የፋይናል ድራይቭ ዘይት መፈተሸና መፍታት የእኔ ሥራ ድርሻ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኃላ ሬይስ ኢንጀነሪንግ የሰጠውን ሙያዊ አስተያየት በመመርመር ለማሽኑ ብልሽት አመልካች ፋይናል ደራይቭ ዘይት ሣይፈትሽ በመንዳቱ ነው በማለት አመልካች ብር 227,594.18 /ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አምስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአስራ ስምንት ሣንቲም/ የመክፈል ሃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት ያቀረበ ቢሆንም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታቸውን አልተቀበላቸውም፡፡

አመልካች መስከረም 4 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተበላሸው የዶዘር ክፍል /ፋይናል ድራይቭ/ በኦፕሬተር በቀላሉ የማይፈታና ሰርቪስ የማይደረግ መሆኑ ከሬስ ኢንጅነሪንግ የተላከው ባለሙያ በማረጋገጡ ወደ ሥራዬ ተመልሼ እየሠራሁ እገኛለሁ፡፡ በወንጀልም ተከሣሼ በነፃ ተሰናብቻለሁ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ማስረጃ ሣይመረምርና ስህተቱ የእኔ አለመሆኑን ሳያገናዝብ አለአግባብ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በሥራ ክርክር ችሎት የሰጠው ውሣኔም ሆነ በወንጀል ችሎት የሰጠው ውሣኔ የጉዳት ካሣ ከመጠየቅ የሚገድበን አይደለም፡፡ ማሽኑ የተበላሸው በአመልካች ጥፋት መሆኑን አስረድተናል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በቃል ክርክር መልስ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኃላ ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰበር ችሎቱ ባቀረባቸው ጥያቄዎች አመልካችና ተጠሪ በቃል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በፅሑፍና በቃል የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል መዝገቡን እንደመረመርነው የተጠሪ ንብረት የሆነው ዲ. 7 ኤች ተብሎ የሚታወቀው ዶዘር ላይ ጉዳት ያደረሰው አመልካች በሥራው ሂደት ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ሣያደርግ ዶዘሩን በማንቀሳቀሱ ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረትና ድጋፍ አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የዶዘሩ ኦፕሬተር መሆኑና የአመልካች የሥራ ድርሻና ሃላፊነት ማሽኑን ኦፕሬት በማድረግ መስራት የሚገባውን ሥራ መሥራት መሆኑ በግራቀኙ የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ የአንድ የዶዘር ኦፕሬተር ጠቅላላ የሥራ ሃላፊነት የሞተር የመሪ ዘይትና ሌሎች በቀላሉ ሊፈተሹ የሚችሉ የዶዘሩን አካላት ዶዘሩን ከማንቀሳቀሱ በፊት መፈተሽና የተገደሉ ነገር ቢኖር እንዲሟላ ማድረግ እንደሆነ በአመልካችና በተጠሪ በኩል ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አሁን ዶዘሩን ለብልሽት የዳረገውና ተጠሪውን ለጥገና ከፍተኛ ወጭ ያስወጣው /ፋይናል ድራይቭ/ የሚባለው የማሽኑ ክፍል እንደሆነ ይህንን ክፍል ለመፈተሽ የተለየ መፍቻና የተለየ ሥልጣና የሚያስፈልግ መሆኑን አንድ የዶዘር ኦፕሬተር የፋይናል ድራይቭ ልዩ መፍቻ ከተሰጠው ፋይናል ድራይቭ እንዴት እንደሚፈታና እንደሚፈተሽ ሥልጠና ከተሰጠውና ይኸው በሥራ መዘርዝሩ በግልፅ ከተካተተ ፋይናል ድራይቭ ዘይት መፍታት የሚችል መሆኑና የመፈትሸም ግዴታ እንዳለበት በማብራራት ሬስ ኢንጅነሪንግ በፅሑፍ የሰጠውን መግለጫ እንድያብራራ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 64587 አስቀርቦ የሙያ ምስክርነታቸውን የሰማቸው የሬስ ኢንጅነሪንግ ባለሙያ በሰጡት ምስክርነት ያረጋገጡ መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሀምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ገልያል፡፡

ምንም እንኳን በሥራና አሠሪ ክርክር ችሎት የተሰጠ ውሣኔ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5/1/ መሠረት የአሠሪውን የፍታብሔር ክስ የማቅረብ መብት የማይገደብ ቢሆንም የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ችሎት ውሣኔ ለፍታብሔር ክርክር በማስረጃነት አንዳይቀርብ የሚከለክል ግልፅ የህግ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ውሣኔውን ሠራተኛው በአሠሪው የቀረበበትን ክስ ለመከላከል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማስረጃነት ቢያቀርበው በህግ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ የፍታብሔር ክሱን የሚያየው ፍ/ቤት ይህንን ማስረጃ ተቀብሎ የመመዘን ግዴታና ሃላፊነት አለበት፡፡

በያዝነው ጉዳይ ሬስ ኢንጅነሪንግ በዕሑፍ የሰጠው ሙያዊ አስተያየት ጥቅልና ግልፅነት የጎደለው በመሆኑ የሬስ ኢንጅነሪግ ባለሙያ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አሠራና ሠራተኛ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጣሪያ ምስክርነት ቀርበው አንድ ኦፕሬተር “ፋይናል ደራይቭ” የተባለው የዶዘር ክፍል በመፍታት ዘይት ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ለመፈተሽ የሚችለው ሶስት መሠረታዊ ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ መሆኑን አስረድቷል፡፡ ሶስቱ መሠረታዊ ሁኔታዎችም ፋይናል ድራይቭ ለመፍታትና ለመግጠም የሚያስችል ልዩ ስልጠና ለሠራተኛው በአሠሪው የተሰጠ ሲሆን ፋይናል ደራይቭ ለመፍታት የሚያስችል ልዩ መፍቻ ለሠራተኛው የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥና በሠራተኛው የሥራ መዘርዝር ፋይናል ደራይቭ የመፍታትና የመፈተሽ ሃላፊነት የኦፕሬተሩ መሆኑ በግልፅ ተፅፎ የተሰጠው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የፋናል ደራይቭ መፈተሽ የሞተር ዘይት የራዲያተር ውሃና የሀይድሮሊክ ዘይትና የትራንስሚሽን ዘይት እንደመፈተሽ አመልካች ሊፈፅመው የሚገባው ሥራ ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም ተጠሪ አመልካች የዶዘሩን ፋይናል ደራይቭ ለመፈተሽ የሚያስፈልገውን ልዩ ሥልጣና የሰጠ መሆኑንና ይህንን የዶዘሩን ክፍል ለመፍታት የሚያስችል ልዩ መፍቻ ተጠሪ ለአመልካች የሰጠው ስለመሆኑ በማስረጃ ሣይረጋገጥ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለጉዳቱ ሃላፊ ነው በማለት የወሰነ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ለአመልካች ፋይናል ደራይቭ ለመፍታትና ለመፈተሽ አስፈላጊ የሆነውን ልዩ ሥልጠና ያልሰጠና ይህንን የማሽን ክፍል ለመፍታት የሚያስችለው ልዩ መፍቻ ያልሰጠው መሆኑ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክሩን በይግባኝ ሰምቶ በወሰነው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካችን ለጉዳቱ በኃላፊነት ለመጠየቅ በመጀመሪያ ማሟላት ያለባቸው ሶስት ሁኔታዎች መሞላታቸውን ሣያረጋግጥ አመልካች የዶዘሩን ፋይናል ድራይቭ ዘይት ሣይፈትሹ ማሽኑን አንቀሣቅሰዋል በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎት ማፀናታቸው አሠሪው ግዴታና ሃላፊነቱን በአግባቡ የተወጣ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ /1/ሀ የተደነገገውን የሚጥስ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ዶዘር ላይ ለደረሰው ጉዳት በሃላፊነት አይጠየቅም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡት ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 53985

ህዳር 13 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ዳሸን ባንክ አ.ማ ነ/ፈጅ የሺወርቅ ይመር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዘነበ ድንቁሣ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአመልካች ድርጅት ውስጥ ላይ በማገልገል ላይ እያሉ በጋዜጣ ላይ አስተያየት ሰጥተሃል በሚል ሰበብ አመልካች ድርጅት ከታህሳስ 14 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ያላግባብ ከሥራ ያገዳቸው መሆኑን በመግለጽ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የታህሳስ ወር ደመወዝ ከተለያዩ ወጪና ኪሳራዎችጋር እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ተጠሪ በአመልካች ላይ ከባድ ጉዳት እያደረሱ በመሆኑ ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ ከስራ መታገዳቸውን ገልፆና እግዱም በአግባቡ የተሰጠ መሆኑን ጠቅሶ እግዱ ሊነሳ አይገባውም ላልሰሩበት ጊዜ ደመወዝ ሊከፈላቸው እንደማይገባ ገልጾ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዮን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካች ተጠሪን ከስራ ያገዳቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 18 መሠረት ለማገድ የሚያበቁ ሕጋዊ ምክንያቶች በሌሉበት ሁኔታ መሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የአዋጅ አንቀጽ 27(4) ድንጋጌ ሲታይም እግድ የሚፈቀደው በሕብረት ስምምነት ላይ በተመለከተው መሰረት መሆኑን ገልፆ ሕብረት ስምምነቱ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪን አመልካች ከሥራ ማገዱ ሕገ ወጥ ነው በሚል ድምዳሜ ተጠሪን የታህሳስ ወር 2002 ዓ.ም ደመወዝ በመክፈል አመልካች ወደ ሥራ እንዲመለስ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(4) ድንጋጌ ጥፋት መኖሩን አሰሪው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እስከሚያጣራ ድረስ ሰራተኛን ከስራ በማገድ ጉዳዩን ለማጣራት የሚችል መሆኑን ፈቃጅ በሆነ አገላለጽ ደንግጎ እያለ የሕብረት ስምምነት ከሌለ ተፈጻሚነት የለውም በሚል የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው መስከረም 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም ጥቅምት 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ተጠሪን ከስራ እና ደመወዝ ያገዳቸው ተጠሪ በድርጅቱ ላይ ጉዳት እያደረሱ ነው በሚል ጉዳዩን እስከሚያጣራ ድረስ ሲሆን ለእርምጃው ህጋዊነት በዋቢነት የሚጠቅሰውም አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/(4) ስር የተመለከተውን መሆኑን ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት ሕብረት ስምምነት ሳይኖር በአዋጁ አንቀጽ 27(4) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የለውም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነጥብ የሕብረት ስምምነት የሌለው አሠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(4) መሠረት የማገድ እርምጃ መውሰድ አይችልም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ የቅጥር ውል ባይቋረጥም አሰሪውና ሰራተኛ ከግዴታዎቻቸው ለተወሰነ ጊዜ ነፃ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች ያሉ ስለመሆኑ አዋጁ ቁጥር 377/96 ከአንቀጽ 17 እስከ 22 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ የቅጥር ውል ሲታገድ ምክንያቶቹ የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎችና ከአንቀጽ 27(4) እና 184 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ለአሁኑ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የአገዳ አይነት በአዋጁ አንቀጽ 27(4) ስር የተመለከተው ከዲስፕሊን ጋር ተያይዞ የሚፈፀምና የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችሉ ጥፋቶችን ለማጣራት የሚደረግ እገዳ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በአንቀጽ 27 ስር በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ እንዲቋረጥ ከመደረጉ በፊት ሰራተኛውን ለአንድ ወር ያህል ከስራ አግዶ ማቆየት ስለሚቻልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን ይችላል ተብሎ ተደንግጓል፡፡ የድንጋጌው ዓይነት ዓላማ አሰሪው በአስተዳደራዊ ሥልጣኑ ሰራተኛው ለሚፈጽመው ጉድለት ተገቢውን የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ይችል ዘንድ ሠራተኛው ፈፀመ የተባለውን የሥነ ምግባር ጉድለት በተገቢው መንገድ ለማጣራትና ለመመርመር እንዲችል ማድረግ ነው፡፡ ሕጉ ይህንን አላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ እገዳ ማድረግን የሚፈቅድ ሲሆን እገዳው የሚቆይበትን የጊዜ ገደብም ከአንድ ወር መብለጥ እንደሌለበት ያስቀምጣል፡፡ ሕጉ አሰሪው እገዳውን ሲፈጽም ከድርጅቱ ሰራተኛ ማህበር (በህብረት ስምምነት መሠረት) ጋር በመስማማት ለመወሰን እንደሚችል ያሳያል፡፡ ሆኖም የህብረት ስምምነት የሌለው ድርጅት ሰራተኛውን ቢያግድ እገዳው ሕገ ወጥ ሊባይ ሚችል ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘትና አቀራረጽ አያሳይም፡፡ የእገዳው አላማ በሰራተኛው ተፈፀመ የተባለውን የስነ ምግባር ጉድለት በተገቢው መንገድ ማጣራትና ለመመርመር አሰሪውን ለማስቻል ነው ከተባለ የሠራተኛ ማህበር የሌለው (የሕብረት ስምምነት (የሌለው) ድርጅት ሰራተኛው ፈፀመ ለተባለ ጉድለት እገዳ በማድረግ የዲስፕሊን ግድፈቱን ለማጣራት ወይም ለመመርመር እይችልም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለም፡፡ ድንጋጌው በይዘቱ ሲታይ ፈቃጅ እንጂ ክልከላ ያበጀ አይደለም፡፡ እገዳው የሚደረግበት አላማ ሲታይ እውነቱ በትክክል እንዲወጣ በሕጋዊ ምክንያት የስራ ውል እንዲቋረጥ ለማድረግ፣ ሰራተኛውም ለአሰሪው ታማኝ በመሆን አገልግሎቱን እንዲሰጥ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሰላምን ማስፈን ነው፡፡ ሕግ ሲተረጎምም ይህንን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ መሆን እንዳለበት ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያስገነዝቡን ሐቅ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ሕግ ሲተረጎም የሚገባው የሕጉን አላማ በሚያሳካ መልኩ ስለመሆኑ የሕግ አተረጓጎም መርሆዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም አንድ የሕብረት ስምምነት የሌለው አሰሪው ሰራተኛው የዲስፕሊን ጉድለት ፈጽሟል የሚልበትን ጉዳይ ለማጣራትና ለመመርመር ሰራተኛውን ከአንድ ወር ጊዜ ላልበለጠ ጊዜ ቢያግድ እርምጃው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(4) የሚሸፈን አይደለም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ መሠታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 48933 ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 89046 መጋቢት 01 ቀን 2002 ዓ/ም በትእዝዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የህብረት ስምምነት ባይኖረውም ተጠሪ ፈፀሙ የተባሉትን ድርጊት ለማጣራት ወይም ለመመርመር በአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(4) መሠረት ለአንድ ወር ጊዜ ያህል ማገድ ይችላል ብለናል፣ እገዳው ተነስቶ ተጠሪን ወደ ስራ ይመልስ ተብሎ ሊገደድ አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኅዳር 03 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አንበሳ ጫማ አ/ማህበር -የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እትሁን አያሌው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት አድርጐ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በምእራብ አማራ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር የግል ስራ ክርክር ሲያደርጉ ከቆዩ በሁዋላ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም በሰ/መ/ቁ. 44515 የቅጥር ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው በማለት ውሳኔ ከሰጠ በሁዋላ ታህሣሥ 16 ቀን 2002 ዓ.ም በቁጥር 11/መ/485/2-3 በተፃፈ ደብዳቤ ከባህር ዳር ሽያጭ መደብር ወደ ሃዋሳ ሽያጭ መደብር ያለበቂ ምክንያት ያዛወራቸው መሆኑን በመግለጽ ዝውውሩ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ክሱ የግል የስራ ክርክር በመሆኑ በቋሚ ቦርድ ሊታይ የማይገባው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከሩ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ግን ድርጅቱ ዝውውሩን ለማድረግ የወሰነው ድርጅቱ ያለበት ቦታ ለኢንቨስትመንት የተሰጠ በመሆኑ በህብረት ስምምነቱ መሰረት መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ቋሚ ቦርድም ጉዳዩን መርምሮ ዝውውሩ በህብረት ስምምነቱ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውጪ የተፈፀመ መሆኑን በማረጋገጥ ዝውውሩ ተገቢ አይደለም በማለት ሰርዞታል፡፡ ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶችም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ድርጅት ወኪል መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ቦርዱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን አይችልም፣ዝውውሩም የተከናወነው በሕብረት ስምምነቱ መሰረት ነው የሚሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የተጠሪ ዝውውር ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐአል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ ቀርበው የፁሁፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ላይ የግል የስራ ክርክር አቅርበው በዚህ ሰበር ችሎት ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረች ሰራተኛ ነች ተብሎ ውሳኔ ጥቅምት 25 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ አመልካች ድርጅት ታህሣሥ 16 ቀን 2002 ዓ.ም ዝውውሩን መፈፀሙን፣ ዝውውሩን ለመፈፀም አመልካች በምክንያትነት የጠቀሰው ድርጅቱ ያለበት ቦታ ለኢንቨስትመንት በመፈለጉ ቦታውን እንዲለቅ ከሚመለከተው አካል ትእዛዝ የደረሰው መሆኑን፣ሆኖም ዝውውሩ በሁሉም ሰራተኛ የተከናወነ ሳይሆን በተጠሪ ላይ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ቋሚ ቦርድም ዝውውሩ በህብረት ስምምነቱ ላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሰረት የተደረገ ሳይሆን ከሕጋዊ ምክንያቶች ውጪ መከናወኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጡን ከቦርዱ ውሳኔ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያላቸው ቦርድና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ዝውውሩ በህብረት ስምምነቱ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጪ ስለመፈፀሙ በፍሬ ነገር ደረጃ የተስማሙበት ከሆነ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የፍሬ ነገር ወይም የማስረጃ ምዘና እንጂ የሕግ ትርጉም ጥያቄ አይደለም፡፡ ፍሬ ነገርና ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ደግሞ የዚህ ሰበር ችሎት ሥልጣን አለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ዝውውሩ ሕገ ወጥ ነው የተባለው ተጠሪ ከአመልካች ላይ የነበራቸው ክስና ከዚህ በሁዋላ የተከናወኑትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፤ማስረጃዎቹም ተመዝነው በመሆኑ የመሰረታዊ የሕግ ስህተት መመዘኛን የማያሟላ እና በዚህ ችሎት ሊታይ የሚችል ሁኖ አላገኘውም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 06880 መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም የቦርዱን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 57068

ሕዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ማህሌት ዓለሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ሰናይት መጫ (3 ሰዎች) - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስራ ላይ ስለሚደርስ የሞት ጉዳትና የካሳ አከፋፈሉን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በግልግል ጊዜ ቁጥር II ሣሊኒ ኮንስትራቶሪ ኤስ.ፒ.ኤ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አቶ ሙላቱ ገብረ ማርያም በተከሳሽ ድርጅት ተቀጥሮ ሚያዚያ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በዋሻ ውስጥ ስራ ላይ እያለ የኦክስጅን እጥረት ገጥሞት ከዋሻው ወደ ውጪ በባቡር ፉርጐ ሲወጣ ከፉርጐው ተንሸራቶ በመውደቅ በኩላሊቱና በጎን አጥንት መቀጥቀጥ አደጋ ደርሶበት ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን ገልፀው በስራ ላይ የደረሰ አደጋ ካሳ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ተከሳሽ ለክሱ በሰጠው መልስም ሟች በአደጋ ምክንያት ሕይወቱ ለማለፉ ከሳሾች ማስረጃ አለማቅረባቸውን በተቃራኒው ሟች እንደታመመ የፉፋ ጤና ጣቢያ በካርድ ቁጥር 760 የጻፈው ሪፈራል የሟች በሽታ ታይፎይድ እና የሽንት ቧንቧ ኤንፌክሽን የሚል ስለሆነ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ ተወስዶ ካሳ የሚከፈልበት ምክንያት የለም በማለት መልሱን ከሰጠ በሁዋላ ባለው የመድን ውል መሠረት የአሁኑ አመልካች ድርጅት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከርለት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለስር ተከሳሽ ሠራተኞች የስራ ላይ ጉዳት የመድን ሽፋን የሠጡ መሆኑን በመግለጽ ሟች በስራ ላይ አደጋ አልደረሰበትም፣ የሞተው በወባና በታይፎይድ ስለሆነ በስራ ምክንያት የመጣ አደጋ ነው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ ካሳ የሚያስከፍል አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የስር ተከሳሽን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(2) እና 110(3) ድንጋጌዎች መሠረት የሞት ጉዳት ካሳ ለሟች ጥገኛ ለሆኑት ተጠሪዎች እንዲከፈል የአመልካች የኃላፊነት መጠንም በሰበር ተከሳሽ ጋር ባለው የመድን ውል መሠረት እንዲሆን እንዲሁም ክፍያው ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ እንዲከፈል ገልፆ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለመስማማት ይግባኙን ለየም ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፣ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩ የፌደራል በመሆኑ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚገባ አይደለም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሰኔ 7 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ሟች ሕይወቱ ያለፈው በስራ ላይ በመጣ አደጋ ሳይሆን በታይፎይድ በሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽንና ወባ ስለመሆኑ የሕክምና ማስረጃ እየገለፀ የሰው ምስክሮች የሰጡት ቃል መሠረት ተደርጉ አደጋው በስራ ላይ የደረሰ ነው ተብሎ የሟች ጥገኞች ካሳ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 97፣ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005፣ 2011 እና 2012 ድንጋጌዎች ውጪ ነው በማለት ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የሞት መንስኤው በስራ ላይ በመጣ ጉዳት ሳቢያ ነው? ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጉላቸው ቀርበው መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ስድስት ገጽ የአመልካችን ቅሬታ ነጥቦችም በመንቀፍ፣ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ህጋዊነት በመዘርዘር መልሳቸውን የሰጡ ሲሆን አመልካችም ጥቅምት 07 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት ምላሽ ያስፈልጋል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ ሟች አቶ ሙላቱ ገ/ማሪያም የሞቱት በስራ ላይ በደረሰባቸው አደጋ ነው? ወይንስ በሌላ ምክንያት? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ (Occupational injury) ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ (occupational disease) እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 95(2) ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የአዋጅ አንቀጽ 97 ደግሞ በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ማለት ማንኛውም ሰራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ስራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ እንደሆነ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት የካሳ ክፍያ ጥያቄ የሚያቀርበው ወገን ጉዳቱ የደረሰው በአንቀጽ 97 በተመለከተው አካኋን በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት መሆኑንና እንደዚሁም በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ቅርብና ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት መኖሩን (Proximate cause and effect relationship) ማስረዳት እንደሚጠበቅበት ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል የአሰሪው ኃላፊነት በጥፋት ላይ ያልተመሰረተ (strict) ስለሆነ ካሣ ጠያቂው ወገን ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማሳየት ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ የጉዳት አድራሹን ወይንም የአሰሪውን የአእምሮ ሁኔታ (State of Mind) ማስረዳት እንደማይጠበቅበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ሟች ሙላት ገ/ማሪያም በስር ተከሳሽ ድርጅት ተቀጥሮ ሚያዚያ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በዋሻ ውስጥ ስራ ላይ እያለ የኦክስጅን እጥረት ገጥሞት ከዋሻው ወደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውጭ በባቡር ፉርጎ ሲወጣ ከፍርጎው ተንሸራቶ በመውደቅ አደጋ ደርሶበት ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን ተጠሪዎች ገልፀው በስራ ላይ የደረሰ አደጋ ካሳ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት የለብኝም የሚለው ሟች በስራ ላይ በደረሰ አደጋ መክንያት ሕይወቱ ለማለፉ ተጠሪዎች ማስረጃ አለማቅረባቸውን በተቃራኒው ሟች እንደታመመ የፉፋ ጤና ጣቢያ በካርድ ቁጥር 760 የጻፈው ሪፈራል የሟች በሽታ ታይፎይድ፣ ወባ እና የሽንት ቧንቧ ኤንፌክሽን የሚል ስለሆነ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ የሚቆጠር አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን ምስክሮችን አቅርቦ የሰማ ሲሆን የተጠሪዎች ምስክሮች በክሱ በተገለፀው መሠረት መመስከራቸውን ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍ/ቤቶች የተቀበሉት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ይኸው የተጠሪዎች ምስክሮች ቃል ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚለው የሕክምና ማስረጃው ከሚገልፀው ይዘት ውጪ ነው በማለትና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005፣ 2011 እና 2012 ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሟች ጉዳቱ ደረሰ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ በሕክምና ሲረዳ የቆየ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የሕክምናው ማስረጃ በሟች ላይ ምርመራ በተደረገበት ወቅት ታዩ የተባሉ ሁሉም ምልክቶች ከመነሻ የተከሰቱና ለሞቱ ምክንያት መሆናቸውን የሚገልጽ አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልጽ የሚያሳየው ደግሞ በተጠሪዎች በኩል የቀረቡት የሰው ምስክሮች ከመነሻው የነበረውን ሁኔታና በሟች ላይ የደረሰውን ጉዳት ገልፀው ለሞቱ ምክንያት የሆነው ነገር የተከሰተው ሟች በስራ ላይ እንዳለ ስለመሞቱ ማስረዳታቸውን በመቀበል የህክምና ማስረጃው ደግሞ የተጠሪዎችን ምስክሮች ቃል ሊያስተባብል አለመቻሉን በመግለጽ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎች መመዘናቸውን ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የቀረቡትን ማስረጃዎች በማመዛዘን ውሳኔ የሰጡ ሲሆን የሕክምና ማስረጃው ይዘት ሲታይም ተጠሪዎች በሟች ላይ በደረሰው አደጋ የኩላሊት መቀጥቀጥ የደረሰ መሆኑን የገለጹትን የህክምና ማስረጃ ሟች የሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽን ደርሶበት የነበረ መሆኑ የሚገልጽ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የሕክምናው ማስረጃ በይዘቱ ከሰው ምስክሮች ቃል ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው ለማለትም የሚያስችል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘን አደጋው በስራ ቦታ ላይ የደረሰ ስለመሆኑ የደመደመ በመሆኑ ክብደቱ ለሕክምና ማስረጃ የግድ መሰጠት አለበት ሊባል የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ፍሬ ነገርን የጣራና ማስረጃዎቹን የመዘነ ከሆነ ይኸው ተገቢ መሆን ያለመሆኑ መሠረት ተደርጐ ጉዳዩ በዚህ ሰበር ችሎት የሚታይበት አግባብ የሌለ መሆኑን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሟች በስራ ቦታ ላይ በደረሰው አደጋ መሞታቸውን በሕጉ አግባብ መረጋገጡን መሠረት አድርጐ የተሰጠ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፦ ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ የቻይና መንገድና ድልድይ ሥራ ድርጅት

ተጠሪ፣ ግርማ ቡሽራ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው የሥራ ውሌን ያለአግባብ አቋርጦብኛል በማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍለው እንዲወሰንለት ጠይቆአል አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ እራሱ ሥራውን ትቶ ሄደ እንጂ እኔ አላባረርኩትም ሥራውን ትቶ የሄደው በብድር የወሰደውን ገንዘብ ላለመክፈል ነው በማለት ተከራክሯል ክሱን የሰማው የባህር ዳር ወረዳ ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር አልተቀበለም፡፡ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለትም አመልካች የተጠየቀውን ክፍያ ለተጠሪ ይከፍል ዘንድ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ ያፀና ሲሆን በመጨረሻ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረውን የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራቀኙ ወገኖች ጭብጡን መሠረት በማድረግ ያሰሙት ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ከተሰሙት ውሣኔዎች ይዘት መገንዘብ እንዳቻልነው ተጠሪ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ ነው በማለት ሲከራከር፤ ተጠሪ ደግሞ በኔ በኩል ተጠሪን አላሰናበትኩም ሥራውን ትቶ የሄደው እራሱ ነው ይህን ያደረገውም በብድር የወሰደውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብር 2000 አጠቃሎ ላለመክፈል ለመሸሽ በማሰብ ነው በማለት ተከራክሮአል ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤትም በእርግጥ ተጠሪ በአሠሪው ድርጅት የበላይ ሃላፊ ወይም ሠራተኛን የማሰናበት /የሥራ ውል እንዲቋረጥ የመወሰን/ ሥልጣን ባለው ሃላፊ ስለመሰናበቱ ወይም ሥራውን እንዲለቅ ስለመደረጉ አላረጋገጠም በውሣኔው እንዳመለከተው አመልካች ይሰራው በነበረው የአስፖልት መንገድ አካባቢ ተጠሪ እና አንድ ቻይናዊ ሲጣሉ አይተናል የሚሉ መንገደኞች የሰጡትን ምስክርነት ብቻ በመያዝ ነው ወደውሣኔው ያመራው ይህ ማለት ግን ተጠሪ በድርጅቱ ከሥራው ስለመሰናበቱ ያመለክታል ማለት አይደለም ከፍ ሲል እንዳመለከትነው አመልካች እኔ ተጠሪን አላሰናበትኩም በማለት እስከተከራከረ ድረስ በእርግጥ በአመልካች ስለመሰናበቱ ተጠሪ የማስረዳት ግዴታ ነበረበት፡፡ እንደምንመለከተው ግን ተጠሪ የማስረዳት ሸክሙን /ግዴታውን/ አልተወጣም በሌላ አነጋገር በእርግጥ በአመልካች ኃላፊዎች የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ስለመሆኑ ሊያስረዳለት የሚችል ማስረጃ ከነጭራሹ አላቀረበም፡፡ ከዚህ የተነሳም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት ያለው ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የሕግ መሠረት የሌለው ውሣኔ ደግሞ ትክክለኛ ውሣኔ ሊባል ስለማይችል አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 18489 መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 39337 ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና በአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 09846 ሰኔ 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ ተቋርጦአል በማለት የጠየቃቸው ክፍያዎች ሊከፈሉት አይገባም ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ አቶ ንጉስ ሐዱሽ አልቀረቡም

ተጠሪዎች፣ የመቀሌ ዩንቨርሲቲ የተማሪዎች ዲን አልቀረቡም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የግራቀኙን ከሥራ ቅጥር የመነጨን ክርክር የሚገዛው የትኛው ህግ ነው የሚለውን ለይቶ ዳኝነት ለመስጠት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በተጠሪ ጽ/ቤት በሻሂ ማሽን ሠራተኝነት በደመወዝ ተቀጥሮ ሲሰራ የቆየ ለመሆኑ እና በመጨረሻም ተጠሪ በሰጠው ምክንያት ከሥራ የተሰናበተ ለመሆኑ ተጠሪ የካደው ጉዳይ አይደለም፡፡

በዚህ መነሻ በተጠሪ በኩል የተፈፀመው የሥራ ስንብት የአሠሪና ሠራተኛ ህግ ከደነገገው ውጭ ስለሆነ ልዩ ልዩ ክፍያ ይገባኛል በማለት የአሁን አመልካች ለቀረበው ክስ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት በጥሪው መሠረት የበኩሉን መልስ ለማቅረብ አልቻልም በሚል ምክንያት ክሱ የቀረበለት የወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን የክስ አቤቱታ እና እንደ አቤቱታው ለማስረዳት ያቀረበውን የሰውና የሰነድ ማስረጃ ተመልክቶ በግራቀኙ መካከል የሥራ ቅጥር ግንኙነት እንዳለ እና ከዚህ የቅጥር ግንኙነት የተነሳው ክርክር የሚዳኘው በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት መሆኑን ገልፆ ሠራተኛው ለቀጣሪው ከሰጠው የአገልግሎት ዘመን አንፃር ሊሰጠው የሚገባው የአንድ ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ብቻ ሆኖ አልተገኘም የማስጠንቀቂያ አሰጣጥ ሥርዓቱ የተሟላ ሆኖ አልተገኘም ስለሆነም ከአዋጅ አንቀጽ 35/1/ለ/ አንፃር ሲታይ ስንብቱ ህግ ከደነገገው ውጭ ሆኖ ተገኝቷል በማለት ልዩ ልዩ ክፍያ እንዲከፈለው ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ የአሁን ተጠሪ በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራቀኙን አከራክሯል፡፡

ዋነኛ የይግባኝ አቤቱታውም የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የሚተዳደረው በአዋጅ ቁጥር 515/99 እና በደንብ ቁጥር 61/99 መሠረት በመሆኑ ዩኒቨርቲው ተከራካሪ የሆነበትን ይህን መሰል ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚተዳደርበት አዋጅ መሠረት እንጂ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚገዛ አይደለም የሚለው ይገኝበታል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የአሁን ተጠሪ እንደሚለው ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚዳኝ አለመሆኑን የሥር ፍ/ቤት ተገናዝቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 9 እና 231/1/ለ/ መሠረት መዝገቡን መዝጋት ነበረበት በሚል ምክንያት ተችቶ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አለማግኘቱን ገልፆ ለዚህ የሰበር ጉዳይ ምክንያት የሆነውን የሰበር አቤቱታ የአሁን አመልካች አቅርቧል፡፡

የሰበር ቅሬታው ይዘትም የሥር ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን የወሰነው የአሁን ተጠሪ በሌሉበት ስለሆነ ይህ ተጠሪ በዚያው ጉዳይ ተከራካሪ ለመሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78 መሠረት በክርክሩ እንዲገባ ካልተደረገ በቀር በቀጥታ የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ መብት የለውም ይህን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አላየውም እኔን የቀጠረኝ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት ሲሆን የተቀጠርኩትም ለሻሂ ክብብ በሻሂ ማሽን ሠራተኛነት ነው የምሰራበት ክበብ በእራሱ ገቢና በጀት የሚተዳደር በተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት ቁጥጥር የሚንቀሳቀስ በመሆኑ በቀጥታ በአዋጅ ቁጥር 515/99 ሆነ በደንብ ቁጥር 6199 የሚገዛ የሚሸፈን አይደለም የሚለውን በግራቀኙ መካከል ለተነሳው የህግ ጥያቄ መነሻና አንኳር የሆነውን ክርክር አቅርቧል፡፡

በዚህ የሰበር አቤቱታ ላይ የአሁን ተጠሪ ቀርቦ የበኩሉን ክርክር ማቅረብ ይችል ዘንድ መጥሪያ ተልኮለት መጥሪያው የደረሰው ለመሆኑ በእራሱ ማህተም ካረጋገጠ በኃላ እንደ ጥሪው የመደመጥ መብቱን ሊጠቀም አልቻለም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች በተጠሪ በኩል የተጠቀሱት አዋጆች ለግራቀኛችን የቅጥር ሁኔታ ተፈፃሚነት የላቸውም በማለት ለቀረበው ክርክር በተጠሪ በኩል ሊቀርብ የሚችል ማስተባበያ ካለ በአከራካሪ ነጥብነቱ ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት መስጠት አልተቻለም የተለየ ማስተባበያ እስካልቀረበ ድረስም አመልካች እንዳለው እንዲያገለግል የተቀጠረበት የሻሂ ክበብ በእራሱ ገቢና በጀት የሚተዳደር ከሆነ ከዚህ መሰል ቁጥር የመነጨን ክርክር ተጠሪ የጠቀሳቸው ህጎች የማይገዙ ይልቁንም ክፍተቱ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚሸፈን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ስለተገኘ ወይም ለዩኒቨርሲቲው የህ/ሰብ ክፍል አገልግሎት ስለሰጠ ብቻ በደፈናው በሲቪል ሠራተኛ አስተዳደር ህግ ይገዛል ለማለት የሚያበቃ አለመሆኑ እየታወቀ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኙ ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ የሚገዛ አይደለም በዚህም ሳቢያ የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 7229 በ19/6/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 29531 በ30/7/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከሥራ ቅጥር የመነጨውን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሥልጣን ባለው የወረዳ ፍ/ቤት ታይቶ ዳኝነት የተሰጠበት ስለሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነቱ ስልጣን የመ/ቁጥር 7229

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀሳቅሶ በሌላው ጉዳይ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጠበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት መልሰናል፡፡ ግልባጩ ይድረሰው፡፡

አመልካች ለዚህ ክርክር ያወጣውን ወጭ በእራሱ ይሸፍን ብለናል፡፡ መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 60685

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ በዛብህ እሸቴ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሳሊኒ ኮንስትራክሽን - ጠበቃ አቶ አሥራኤል ተክሉ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ተቀብሎ በማስተናገድ የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው? የሚለውን አስመልክቶ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመለየት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች አሠሪዬ የአሁን ተጠሪ ያለአግባብ ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ይህ ካልሆነ ያለአግባብ በመሰናበቴ ምክንያት ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ይፈፅምልኝ በማለት ባቀረቡት ክስ በማስረጃነት የቀረቡት ግራ ቀኙ ያደረጉትን የሥራ ቅጥር ውል ነው፡፡

የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ከዚህ የቅጥር ውል በመነሳት የሥራ ቅጥር ውሉ የተደረገው በተባበሩት አረብ ኤምሬት የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ነው፡፡ የሥራ ቦታውም በዚሁ ሀገር በሚገኘው የተጠሪ ቅርንጫፍ መ/ቤት መሆኑ ተረጋጋጧል፡፡ ይህም ከሆነ ጉዳዩ በዓለም አቀፍ የግል ሕግ መሠረት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባ አስረጂ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11/2/ መሠረት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንጂ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባለመሆኑ ሥልጣን የለኝም በማለት አመልካችን አሰናብቷል፡፡

የአሁን አመልካች የቅጥር ውል የፈፀምኩት ኢትዮጵያ ከሚገኘው የተከሳሽ መ/ቤት ጋር ነው፤ ይህ አልታየልኝም በማለት ክርክር በማቅረቡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክርክሩን እንደ አዲስ የቀረበ መሆኑን ተገንዝቦ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲረዳ ለዚሁ ክርክሩ ማስረጃ እንዲያቀርብ ቀጠሮ ቢሰጠውም ይህንኑ መፈፀም አለመቻሉን አይቶ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው ክርክርም በሥር ፍ/ቤት አንስቶ ከተከራከረበት በይዘቱ የተለየ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሥራ ቅጥር ውል የተፈፀመው ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚኘው ቅርንጫፍ መ/ቤት ጋር ነው የሚለውን ክርክር በሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለማረጋገጥ የተሳነው መሆኑ የተገለፀ ስለሆነና የዚሁ ክርክር ይዘት በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችልን ፍሬ ነገር ጉዳይ የሚመለከት በመሆኑ በሰበር ደረጃ ሊታይ የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ግራ ቀኙ ያደረጉት የሥራ ቅጥር ውል ጋር በተያያዘ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩን የሚገዛው የተባበሩት አረብ ኢምሬት ሀገር ሕግ ስለመሆኑና የሥራ ቦታውም በዚሁ አገር ውስጥ ለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

ይህም ከሆነ ክርክሩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ቢነሳ በየትኛው ሀገር ሕግ ታይቶ ዳኝነት ማግኘት የሚገባው ስለመሆኑና የሥራ ቦታውስ ኢትዮጵያ ውስጥ ሳይሆን በውጭ ሀገር መሆኑን ሁሉ ጠቅሰው በውል ለይተው አስቀምጠውታል፡፡ ይህም ከሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች የየትኛው ሀገር ነው? ጉዳዩስ የሚታው በየትኛው ሀገር ሕግ ነው የሚሉትን ጥያቄዎች ስለሚያስነሳ ይህን መሰል የሕግ ጥያቄ ያካተተ ጉዳይ ደግሞ በዓለም አቀፍ የግል ሕግ መሠረት ታይቶ የሚዳኝ ነው፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ለማቋቋም በወጣው ሕግ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11/2/ መሠረት በክርክሩ ውስጥ የተካተተው የገንዘብ መጠን ይብዛም ይነስም ክርክሩ የዓለም አቀፍ የግል ሕግን የሚመለከት ሆኖ ከተገኘ ከጉዳዩ ዓይነት አንፃር ብቻ በማየት ጉዳዩ ለመጀመሪያ ጊዜ አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

የሥር ፍ/ቤትም የክርክሩን ባህሪ በማየት በዚሁ ሕግ መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም፡፡ ጉዳዩ መታየት ያለበት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው በማለት የሰጡት ትርጉም በአግባቡ የተሰጠ እንጂ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በየትኛው ደረጃ በሚገኘው ፍ/ቤት ነው? የሚለውን ለይተው ዳኝነት ሰጡበት እንጂ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የሚያስችላቸው ሥልጣን የላቸውም ከሚል ትርጉም ላይ አልደረሱም፡፡ ዳኝነት በዚህ አካኋን የተሰጠ መሆኑ እየታወቀ የአሁን ተጠሪ ጉዳዩ በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ሊታይ የሚችል አይደለም የሚለው የሰበር ክርክሩ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ እንደ ሥርዓቱ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ዳኝነት ለማሳረም ቀርቧል እንኳ ቢባል ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የሥራ ክርክር ለመዳኘት ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/3/ መሠረት እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት በሰበር ሊተረጎም የሚገባው የመጨረሻ ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው በዚህም መሠረት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት በየትኛው ደረጃ የሚገኘው የፌዴራል ፍ/ቤት ነው የሚለውን አስመልክቶ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በከ/መ/ቁ. 45888 ታህሣስ 12 ቀን 2002 ዓ.ም. እና በከ/መ/ቁ. 87855 ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጡት ብይን እና ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለት ያቀረበው የሰበር ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም

ይህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፦ ጊዬን ሆቴሎች ድርጅት ነገረፈጅ እሱባለው ዋለልኝ ቀረቡ

ተጠሪ፦ አቶ ስለሺ አምደ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው ተጠሪ አመልካች ህዳር 5 ቀን 2001 ዓ.ም አላግባብ ከሥራ አግዶትና አሰናብቶት በፍርድ ቤት ውሣኔ ጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ.ም ወደሥራ የተመለሰ መሆኑን ገልፆ በጥቅምት ወር 2001 ዓ.ም የሰራሁበት የሃያ ቀን ደመወዝ የ2001 ዓ.ም የበጀት ዓመት ቦነስና የሰርቪስ ቻርጅ እንደዚሁም ከሀምሌ 2001 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም አስር ፐርሰንት የደመወዝ ጭማሪ እንዲከፍል ውሣኔ ይስጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ የሃያ ቀን የደመወዝ ክፍያ በይርጋ ይታገዳል፡፡ ከሣሽ /ተጠሪ/ የ2001 ዓ.ም የበጀት ዓመት ቦነስ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ በህግም ሆነ በህብረት ስምምነቱ የማይገባቸው ክፍያ በመሆኑ ክሱ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ አመልካች ትርፍ በተገኘበት 2001 ዓ.ም የበጀት ዓመት ስድስት ወር ያልሰሩ በመሆኑ ያቀረቡት የቦነስ ክፍያ ህግንም ሆነ በህብረት ስምምነቱን መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ ተከሣሽ /አመልካች/ ለከሣሽ /ተጠሪ/ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተጠሪን አላግባብ ከሥራ ያባረረው አመልካች በመሆኑ አመልካች ተጠሪ የጠየቀውን የቦነስና ሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ የመክፈል ሃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ነሐሴ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አስራአንድ ወራት እንዳልሰሩ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ባልሰሩበት ወቅት ለተገኘው ትርፍ የሚከፈለው የቦነስ ክፍያ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ እንድንከፍል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የህብረት ስምምነቱን ግልፅ ድንጋጌ የሚጥስና የህግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በትምህርት ዝግጅቱና በሥራ ልምድ ከሌሎች ሠራተኞች በተሻለ ሁኔታ ላይ ነበርኩኝ በ2001 ዓ.ም ያልሰራሁትና የሥራ አፈፃፀም ያልተሞላልኝ አመልካች ከህግ ውጭ ከሥራ ስላሰናበተኝ በመሆኑ ጥፋቱ የተጠሪ ሣይሆን የአመልካች ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች በህብረት ስምምነቱ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዳላሟላ ከህግ ውጭ ከሥራ አሰናብቶኝ የቆየ በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገቢና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች መጋቢት 19 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ለተጠሪ የ2001 ዓ.ም የበጀት ዓመት ቦነስ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ እንዲከፍል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች የቦነስ ክፍያ የሚከፍለው የሥራ አፈፃፀሙ ተመዝኖ በአማካኝ ከሃምሳ ፐርሰንት በላይ መሆኑ ሲረጋገጥና ሠራተኛው በበጀት ዓመቱ ከስድስት ወር በላይ የሠራ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ በአስረኛው የህብረት ስምምነት በአንቀጽ 34/5/ለ እና አንቀጽ 356/ሐ/ ተደንግጓል፡፡ የሰርቪስ ቻርጅ የሚከፈለውም በወቅቱ ሥራ ላይ ለነበሩና አገልግሎት ለሰጡ ሠራተኞች እንደሆነ በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 28/4/ የተመለከተ ሲሆን የደመወዝ ጭማሪ የሚደረገው የሠራተኛው የሥራ አፈፃፀም ከተመዘነ በኃላ እንደሆነ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አንድ ሠራተኛ አሠሪው ጥቅም እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚችለው በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የሥራ ውል የህብረት ስምምነቱን ወይም የአሠሪና ሠራተኛ ህግን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሥራ ውል አመልካች ተጠሪን አላግባብ ከሥራ ያገደ ወይም ያሰናበተ መሆኑ ተረጋግጦ በፍርድ ሲወሰን ተጠሪ ባልሰራበት የበጀት ዓመት የሚከፈል የቦነስ ክፍያ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ የሚከፍል ስለመሆኑ እንደማይገልፅ ግራቀኙ በሰበርና በሥር ፍርድ ቤት ካደረጉት ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ተጠሪን ከሥራ ሲያግደውና ሲያሰናብተው ሥራ ላይ የነበረው አስረኛው የህብረት ስምምነት ተጠሪ ከሥራ ታግዶ ወይም ከሥራ ተሰናበቶ በነበረበት ጊዜ የተገኘ የቦነስ ክፍያ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ አመልካች እንዲከፍል የማያስገድደው መሆኑን ከላይ ከጠቀስናቸው የህብረት ስምምነቱ ድንጋጌዎች ይዘት ተገንዝበናል፡፡

አሰሪው አላግባብ ከሥራ የተሰናበተ መሆኑ ተረጋግጦ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ወደ ሥራው እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ በመጀመሪያ ደረጃ የሥራ ክርክር ችሎት ከስድስት ወር ያልበለጠ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው ፍርድ ቤቱ የሚወሰንለት መሆኑንና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ሥራ የመመለስ ውሣኔው ከፀና ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ውዝፍ ደመወዝ እንደከፈለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት እንደሚወሰንለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 5 ተደንግጓል፡፡ "ደመወዝ" ማለት አንድ ሠራተኛ በሥራ ውሉ መሠረት ለሚያከናውነው ሥራ የሚከፈለው መደበኛ ክፍያ ማለት እንደሆነ በአዋጅ አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአሠሪው የሚሰጥ ጉርሻ /ቦነስ/ እንደ ደመወዝ ክፍያ የማይቆጠር መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች አመልካች ተጠሪን አላግባብ ከሥራ አሰናብቶ በመገኘቱ ተጠሪን ወደ ሥራ እንዲመልስ የአሠሪና ሠራተኛ የመጀመሪያ ደረጃ የሥራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር ችሎትና የይግባኝ ችሎት ሲወስኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት እስከ ስድስት ወር ወይም እስከ አንድ ዓመት የሚደርስ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፍል ከሚወሰን በስተቀር ተጠሪ ባልሠራበት ዓመት ለሌሎች ሠራተኞች የተከፈለው ቦነስ የሰርቪስ ቻርጅና የደመወዝ ጭማሪ እንዲከፍል ለመወሰን የሚያስችል የህግ መሠረት የለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከህግ ውጭ አሰናብቶት በፍርድ ቤት ውሣኔ የተመለሰ በመሆኑ ባልሠራበት ዓመት የተገኘው ትርፍ ለሠራተኞች የተከፈለውን የቦነስ ክፍያ የደመወዝ ጭማሪና የሰርቪስ ቻርጅ ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ የሚጥስና የህብረት ስምምነቱን መሠረት ያላደረገ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠ/መ/ቁ 64079

ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ ጌትነት መኮንን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የጅማ ወረዳ ፍርድ ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ተጣርቶ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች አላግባብ ከሥራ አሰናብቶኛል ወደ ሥራ እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ የመብራት ቢል ሰብሳቢ ሆኖ ሲሰራ ብር 11,177.01 /አስራ አንድ ሺ አንድ መቶ ሰባ ሰባት ብር ከዜሮ አንድ ሣንቲም/ ለግል ጥቅሙ ያዋለ መሆኑ በኦዲተር ተረጋግጧል በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ጥፋቱ መፈፀሙን በአወቀ በሰላሣ ቀን ውስጥ ከሥራ አላሰናበተኝም፡፡ ስለዚህ በአዋጅ ቁጥር 277/96 አንቀፅ 37/3 በመተላለፍ የፈፀመው የሥራ ስንብት ህገወጥ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከላይ የተገለፀው ገንዘብ ዋጋ ያላቸውን ቢሎች ወስዶ ለግል ጥቅሙ ያዋለ መሆኑ ከህዳር 21 ቀን 2002 ዓ.ም እስከ ህዳር 29 ቀን 2002 በተደረገው የኦዲት ምርመራ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከሥራ የተሰናበተው ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ነው፡፡ ስለዚህ ስንብቱ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 3 የሚጥስ በመሆኑ ህገ ወጥ ነው በማለት አመልካች የተጠሪን የስድስት ወር ደመወዝ ከፍሎ ወደ ሥራ እንዲመልሰው ወስኗል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት በማድረግ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች ጥር 9 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ 11,177.01 ብር ቢል ለግል ጥቅም ያዋለ መሆኑን ኦዲተሮች ሪፖርት ያደረጉት ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም ነው አመልካች ተጠሪን በማገድ በህብረት ስምምነቱ መሠረት የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ካደረገ በኋላ ተጠሪ ከሥራ እንዲሰናበት የካቲት 4 ቀን 2002 ዓ.ም ተወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደብዳቤው ውጭ የሆነበትንና ተጠሪ የወሰደበትን ጊዜ ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም በማየት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ጥር 4 ቀን 2003ዓ.ም በተፃፈ መልስ ከሥራ ለማሰናበት የፃፈው ደብዳቤ ወጭ የሆነው ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን በሰበር ማመልከቻው አምኗል፡፡ አመልካች በእኔ በፃፈልኝ የስንብት ደብዳቤ የኦዳተሮች ሪፖርት የደረሰው ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑና ከሥራ ያገደኝ ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑንና ከሥራ ያሰናበተኝ ሚያዚያ 1 ቀን 2002 መሆኑን በግልፅ ካሰፈረ በኋላ ዕውነታውን የሚሸፋፍን የሰበር አቤቱታ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ እንዲያቀርብ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ የመልስ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ወደ ሥራ እንዲመልስ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ተጠሪ በስህተት በተደራቢነት ከተሰጠው የደንበኞች የሒሳብ መሰብሰቢያ ቢል ለግል ጥቅሙ በማዋል ብር 11,177.01 ሣንቲም ያጎደለ መሆኑ በኦዲት ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ ይህንን ጥፋት ያጠፋ መሆኑ በኦዲተሮች ሪፖርት የተደረገለት በህዳር ወር መጨረሻ እንደሆነ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው በወረዳው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ለተጠሪ የፃፈው የስራ ስንብት ደብዳቤ ወጭ የሆነው ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ እንዲሰናበት የተወሰነው የካቲት 4 ቀን 2002 ዓ.ም ነው፡፡ ደብዳቤው ወጭ ሣይሆን የቀረው የተጠሪን መምጣት ስንጠብቅ ነው በማለት በሰበር አቤቱታው የገለፀ ቢሆንም አመልካች ለተጠሪ የሥራ ስንብት ደብዳቤ ወጭ አድርጎ የሰጠው ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም እንደሆነ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች የተጠሪን ጥፋት ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሣ ቀን ውስጥ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሥራ ስንብት ደብዳቤ ያልፃፈ በመሆኑ የአመልካች እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 3 በተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል በማለት የወረዳውን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

2. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ በመሆኑ ህገወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው፡፡ ሆኖም የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪ የሥራ ስንብት ህገወጥ ነው የሚባል ከሆነ ተጠሪ ወደ ሥራ ቢመለስ መልካም የሥራ ግኑኝነት ስለማይኖረን በአማራጭ በአዋጅ ቁጥር 43 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለውት ተጠሪ እንዲሰናበት ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን አማራጭ የዳኝነት ጥያቄ ማለፋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በህግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ የሥራ ውሉን ባለማቋረጡ እንጅ ተጠሪ ከባድ የዕምነት ማጉደል ተግባር የፈፀመ መሆኑ በአመልካች አዲተሮች ተረጋግጧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የደንበኞች ቢልና ክፍያ ሰብሳቢ የነበረ መሆኑ አመልካችና ተጠሪ ካደረጉት ክርክር ተረድተናል፡፡ ተጠሪ ሲሰራበት የነበረው የሥራ መደብ ከፍተኛ የሆነ ዕምነት የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ በኋላ ተጠሪ ወደ ሥራ ቢመለስ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የመተማመን መንፈስ እና የመልካም የሥራ ግኑኝነት ይኖራቸዋል ብሎ ለመደምደም የማይቻል በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በአማራጭ ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 3 በሚደነግገው መሠረት ለተጠሪ ካሣ ከፍሎ እንዲያሰናብተውና ክፍያውም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት ታስቦ እንዲከፍለው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የጅማ ወረዳ ፍርድ ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ወደ ሥራ ቢመለስ ከአመልካች ጋር መልካም የሥራ ግኑኝነት ሊኖረው የማይችል በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ካሣ ከፍሎ እንዲያሰናብተው በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43/4/ መሠረት ወስነናል፡፡ የክፍያው መጠን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43/4/ መሠረት ተደርጎ ሊሰላ ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 8 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን

ተጠሪ፡- አቶ ግርማ ወዮሳ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ የተቀጠረበትን የአሠሪውን ሥራ በመሥራት ላይ እያለ ድንጋይ ወድቆበት ሁለት የእግሮቹ ጣቶች ተቆርጠው ዘላቂ የአካል ጉዳት ደርሶበታል ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(3) መሠረት ካሣ ብር 57,442.66 እንዲከፈለው በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) መሠረት የቀረበ ነው፡፡

የጉዳት ካሣውን ክስና ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ውሣኔውን የሰጠው የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ቀጥሎም የኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት ክርክሩን ከሰማ በኋላ መርምሮ በሰጠው ውሣኔ ወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት አጽንቶታል፡፡ በመጨረሻም የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው ዘላቂ የአካል ጉዳት ደርሶበታል ተብሎ ካሣ እንዲከፈለው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን አቅርቦ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ በሰጠው ውሣኔ በወረዳው ፍ/ቤትም ሆነ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ሊያፀናው ችሏል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ በዚህ ምክንያት የቀረበ ሲሆን የአመልካች ነገረ ፈጅ በ13/1/2003 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የካሣውን ጉዳይ በየደረጃው ያዩት የክልሉ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ተብሎ በመወሰኑ ማመልከቻው ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ በ23/5/2003 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች በእኔ ላይ ጉዳት ስለመድረሱ እያየና በህክምና ማስረጃም ተረጋግጦ እያለ ሊከፈለኝ የሚገባውን ካሣ እንዳይከፈል ለማድረግ ለሰበር ችሎት አቤቱታ ማቅረቡ ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም፣ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፣ ኪሣራ ተቆርጦልኝ መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም በተጠሪው በኩል በቀረበው መልስ ላይ በጽሑፍ የመልስ መልስ ሰጥቶበታል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ አጥብቆ የሚከራከረው የቀረበው የሕክምና ማስረጃ በአሁኑ ተጠሪ አካል ላይ ስለደረሰው ጉዳት መጠን የሚያረጋግጥ ስላልሆነ ቋሚ ሙሉ የአካል ጉዳት ደርሶበታል ተብሎ ካሣ ሊወሰንለት አይገባም፤ የጉዳቱ መጠን ባልተገለፀበት ሁኔታ ካሣ እንዲከፈለው መወሰን ስለማይቻል እንደገና ወደ ሆስፒታል ተልኮ የጉዳቱ መጠን ተገልጾ መቅረብ አለበት በማለት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንደመረመረውም በአሁኑ አመልካችና በተጠሪው መካከል የአሠሪና ሠራተኛ የሥራ ውል ግንኙነት መኖሩና ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ በአሠሪው የተቀጠረበትን ሥራ በማከናወን ላይ እያለ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ የሚያከራክር ሆኖ የተገኘው የአካል ጉዳት መጠን ደረጃው የሚመደበው በጊዜያዊ የአካል ጉዳት ነው ወይንስ ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ወይንም ደግሞ በዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መሆን አለመሆኑ እና የካሣው መጠን እንዴት ይወሰናል የሚለው ነው፡፡

በሠራተኛው /በአሁኑ ተጠሪ/ ላይ ጉዳት የደረሰው በየትኛው አካሉ ላይ ነው? በቀረበው የሕክምና ማስረጃስ የተረጋገጠው ምንድነው? የሚለውን በተመለከተ፡-

ተተርጉሞ ከዚህ መዝገብ ጋር ተያይዞ በቀረበው የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ተጽፎ የሚገኘው እና ቀጥሎ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሣኔ ላይ የገለፀው ፍሬ ነገርም ሆነ የማስረጃ ሁኔታ የተምታታ ከመሆኑም በላይ በዚህ መዝገብ በነበረው የክርክር ሂደት ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ በግንባር በችሎት ተገኝቶ ስለደረሰበት የአካል ጉዳት ተጠይቆ ከገለፀውና ካሣየው ጋር የማይገናኙ ነገሮች ያሉበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ የአሁኑ ተጠሪ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ ላይ የፃፈው ነው ብሎ ያሰፈረው በእግሩ ላይ ድንጋይ ወድቆበት እግሩ የተሰበረና ሲሰራ የነበረውን ግንበኝነት ለመሥራት የማያስችለው ዘላቂ የአካል ጉዳት የደረሰበት ስለመሆኑ የሚገልጽ ሲሆን የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ በውሣኔው ላይ በክሱ የተገለፀ ነው ብሎ የፃፈው ለድልድይ የሚሆን ድንጋይ እየጠረበ እያለ ድንጋይ ወድቆበት ሁለት የእግር ጣቶቹ ተቆርጠው እግሩም ተሰብሯል የሚል ነው፡፡ የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤትም በውሣኔው ላይ የፍቼ ሆስፒታል የሃኪሞች ቦርድ የፃፈው የህክምና ማስረጃ በአሁኑ ተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰበት በእግር ጣቱ ላይ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ነው በሚል መንገድ ገልጾታል፡፡ ሆኖም ከሣሹ የአሁኑ ተጠሪ በአካል ቀርቦ ሲጠየቅ የተቆረጡት የእግር ጣቶቹ ሣይሆኑ የግራ እጁ ሁለት ጣቶች እንደሆኑ አሣይቷል፡፡ ሲታይም የግራ እጅ ሁለት የመሀል ጣቶች ተጐምደዋል፡፡ እግሬም ተሰብሯል ብሏል፡፡ በእርግጥ የአሁኑ ተጠሪ ለወረዳው ፍ/ቤት የቀረበው የፍቼ ሆስፒታል የህኪሞች ቦርድ የሰጠው የሕክምና ማስረጃ ነው በማለት ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ አድርጉት የተገኘው በእንግሊዘኛ የተፃፈው ሲታይ፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

…… Patient Girma Weysswa Boru ……

…. X-ray showing fracture of the femur, and amputation of tip of two fingers from left hand for which reason referred to Tukur Anbassa Hospital.

But he developed mal union and shortening of the high and difficulty in using his leg as previously.

Thus the board decided the above named patient can't work as carpainter.

በሚል የሚነበብ ሲሆን ይህም ተጠሪው ቀርቦ የደረሰብኝ ጉዳት ነው ብሎ ያሣየውን የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የሕክምና ቦርድ ጽፏል ብሎ የጠቀሰው የሕክምና ማስረጃ በሚመለከት ተጠሪው ተጠይቆ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሂዶ አለመታከሙን ስላረጋገጠ ፍ/ቤቱ ከየት አምጥቶ በውሣኔው ላይ ሊጽፈው እንደቻለ ለመረዳት አልተቻለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሄጀ አልታከምኩም እያለ በውሣኔው ላይ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሄዶ የታከመበት ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጐ የህክምና ቦርድ በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂነት ያለው በፊት ሲሰራ የነበረውን የአናጺነት ሥራ ለመሥራት እንደማይችል አረጋግጧል ተብሎ የተፃፈውን ለመቀበል አይቻልም፡፡

ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ የተቀጠረበትን የአሠሪውን ሥራ በመሥራት ላይ ሳለ ጉዳት የደረሰበት ሆኖ ከተገኘ አሠሪው የአሁኑ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ መሠረት ኃላፊነት አለበት፡፡

በሠራተኛው /በአሁኑ ተጠሪ/ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት መጠን በተመለከተም፡-

የአዋጁ አንቀጽ 99(1) "የአካል ጉዳት" ማለት የመሥራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡

በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "2" ሥር በሥራ ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት ውጤቶች፡-

- ጊዜያዊ የአካል ጉዳት
- ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት
- ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት እና
- ሞት

መሆናቸው ተዘርዝሯል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 100 "ጊዜያዊ የአካል ጉዳት" የሚለውን ሠራተኛው ሥራውን ለተወሰነ ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ለማከናወን እንዳይችል የሚያደርገው የአካል ጉዳት እንደሆነ የሚገልጽ ሲሆን አንቀጽ 101 ደግሞ ዘላቂ ከፊል ወይም ሙሉ የአካል ጉዳት የሚባለው እንዴት እንደሆነ የሚያብራራ ነው፡፡ በዚህ የሕጉ ትርጓሜ መሠረት ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ማለት ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛን የመሥራት ችሎታ የሚቀንስ የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ማለት ደግሞ ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛ ማናቸውንም ደመወዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ በሠራተኛው ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት የሚለውን የሚያሟላ መሆን አለመሆኑ ከዚሁ ከአዋጅ አንቀጽ 101(2) አንፃር ሲመረመር የፍቼ ሆስፒታል የሕክምና ቦርድ የሰጠው የሕክምና ማስረጃ በአሁኑ ተጠሪ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ማናቸውንም ደመወዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን የአካል ጉዳት ስለመሆኑ የሚያሳይ ባለመሆኑ በሕጉ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ተጠሪው የፍቼ ሆስፒታል የህክምና ቦርድ በፃፈው የሕክምናው ማሥረጃ ላይ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሂዶ እንዲታይ ባለው መሠረት ሣይሄድ መቅረቱን ራሱ ያረጋገጠ ሲሆን አመልካች ተጠሪው እንደገና በሌላ ሆስፒታል ታይቶ የጉዳቱ መጠን ተረጋግጦ እንዲቀርብ የጠየቀውንም ከሰጠው መልስ እንደሚታየው የሚስማማበት ሣይሆን ባለው ታይቶ እንዲወሰን የሚጠይቅ በመሆኑ የደረሰበት የአካል ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ስለ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ነው ተብሎ ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

አሁን ባለው ሁኔታም ሲታይ በተጠሪው ላይ የደረሰው ጉዳት በሕጉ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት የሚባል ሆኖ ባይገኝም የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሕክምናው ማስረጃም የደረሰበት የአካል ጉዳት ተቀጥሮ ሲሰራ የነበረበትን ሥራ ለመሥራት እንደማያስችለው ተገልጿል፡፡ አመልካችም በክርክሩ ላይ ተጠሪ ተቀጥሮ ሲሰራ የነበረበትን ሥራ ተመልሶ መሥራት ይችላል አላለም፡፡ አመልካች በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ካሣ ሊከፈለው አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 109(3)(ለ) በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ከዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መጠን በታች ሆኖ ከተገኘ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) ክፍያ መሠረት ሆኖ ከአካል ጉድለት ደረጃው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ እንደሚሰጠው የሚደነግግ ነው፡፡

በአሁኑ ተጠሪም ላይ የደረሰው ጉዳት ከዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መጠን በታች ነው ለማለት ስለተቻለ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ተመጣጣኝ የሆነ የጉዳት ካሣ እንዲያገኝ መወሰን ይኖርበታል፡፡ ሕጉ እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የካሣውን መጠን በርትዕ መሠረት አይቶ መወሰን ስለሚፈቅድ በዚሁ መሠረት በማመዛዘን ታይቶ የአሁኑ አመልካች ለሠራተኛው ለአሁኑ ተጠሪ ብር 24000 (ሃያ አራት ሺህ) ካሣ ሊከፍለው ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በአሁኑ ተጠሪ ላይ የደረሰውን ጉዳት በአዋጅ አንቀጽ 109(3)(ለ) መሠረት አይተው የካሣውን መጠን መወሰን ሲገባቸው የደረሰበት ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መሆኑ ሣይረጋገጥ የደረሰበት ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ነው በማለት በአዋጅ አንቀጽ 109(3)(ሀ) መሠረት የአመት ደመወዙ በአምስት ተባዝቶ ካሣ እንዲከፈለው በሚል የሰጡት ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 108579 በ10/01/2003 የሰጠው ውሣኔ፣ የኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 28436 በ30/09/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 08697 በ16/06/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሎ አሠሪው የአሁኑ አመልካች ለሠራተኛው /ለአሁኑ ተጠሪ/ የጉዳት ካሣ ብር 24000 (ሃያ አራት ሺህ) እንዲከፍለው ተወስኗል፡፡
2. በዚህ መዝገብ በተደረገው የሰበር ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
4. በዚህ መዝገብ በ26/01/2003 ዓ.ም በግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት የተከፈተው አፈፃፀም እንዳይቀጥል ተብሎ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይዣፍ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ጉልላት ወልደ ጠበቃ ሰይፈ ረታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ነገረ ፈጅ ገ/ማርያም ዋዩሮ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ሲሆን በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች ከሣሽነት የተጀመረ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ ከሣሽ በተከሣሽ ድርጅት በወር ብር 2847 እየተከፈላቸው ሲሰሩ ቆይተው ያላቸው የሥራ ውል በጡረታ ምክንያት ከሰኔ 01 ቀን 2001 ዓ.ም የተቋረጠ መሆኑን ገልፀው ከሥራ ከመገለሌ ጋር ተያይዞ ሊከፈለኝ ከሚገባው የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ብር 7051.49 ስላስቀሩብኝ ለዚህ ክስ ያወጣሁት ወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፍለኝ የሚል ነው፡፡

ተከሣሽ ለቀረበው ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር መልስ የሠጡ ሲሆን ቀርቦ የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ከሣሽ ከሥራ የተሠናበቱበትና ክስ ያቀረቡበት ጊዜ መካከል ከ6 ወራት በላይ ያለፈ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል ነው፡፡

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ከካራከረ በኋላ ከሣሽ ከሥራ በጡረታ ከተገለሉበት ቀን ሰኔ 01 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ሚያዚያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም መካከል ያለው ጊዜ በአዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 162/4/ የተደነገገውን የይርጋ ዘመን ደንብ የሚፃረር በመሆኑ እና በወቅቱ የቀረበ ክስ ባለመሆኑ በይርጋ ውድቅ ይሆናል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 337 መሠረት አፅንቶታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን አመልካች ታህሣሥ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በ2 ገፅ ጽፈው ያቀረቡት የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ተጠሪ ያለበትን የክፍያ ጥያቄ ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ያመነ ሲሆን በአሁኑ አመልካች መተማመኛ ያልተደረገበትን ዕዳ ተቀናሽ በማድረግ ክፍያ የፈፀመው ደግሞ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በመሆኑ ይርጋው የተቋረጠ መሆኑን እየተከራከርኩ ውድቅ መደረጉ ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሳሉ ተጠሪ የካቲት ቀን 2003 ዓ.ም በ2 ገፅ ፅፎ መልስ የሠጠ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ አመልካች ይርጋ ቀሪ ስለሚሆንበት አግባብ በሥር ፍርድ ቤት ያልተከራከረ በመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አዲስ ክርክር ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረቡትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም የቀረበው የክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ አመልካች ለቀረበበት የይርጋ ተቃውሞ ይርጋው ሊቋረጥ ይገባል የሚለውን መከራከሪያ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቧል ወይስ አላቀረበም? የሚለውን ነጥብ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ አመልካች ይርጋውን ሊያቋርጥ ይችላል ብሎ የሚከራከረውን በተጠሪ የተፃፈ ደብዳቤ ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀረበ በመሆኑ ፣ ከዚያ በመቀጠል የይርጋ ተቃውሞ በተጠሪ ሲቀርብበት ተጠሪ ያለበትን ክፍያ በማረጋገጥ የፃፈው ደብዳቤ ይርጋን ያቋርጣል በማለት የተከራከረ መሆኑን ችሎቱ ተረድቷል፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት ያላቀረበውን ክርክር እያቀረበ ነው የሚባል አይደለም፡፡ ይልቁንም በበታች ፍርድ ቤት ሲያነሣው የነበረ እና ፍርድ ቤቱ ሣይመለከተው ያለፈው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑ በሰበር ሰሚ ደረጃ የተነሣ አዲስ ክርክር ነው በማለት ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል የአመልካችን ክርክር አግባብነት ስንመለከት በእርግጥ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162/4/ መሠረት ከሥራ ውሉ መቋረጥ ጋር ተያይዞ ሊከፈለኝ የሚገባ ክፍያ አለኝ በማለት የሚቀርበው ክስ በ6 ወር ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ተጠሪም እየተከራከረ ያለው አመልካች በጡረታ የተገለለበት ጊዜ እና ክስ ያቀረበበት ጊዜ መካከል ያለው ጊዜ ከ6 ወራት በላይ ሆኖአል የሚል ነው፡፡ ይሄንን የይርጋ ተቃውሞ በተመለከተ አመልካች ከበታች ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ እየተከራከረ ያለው ተጠሪ በፃፈው ደብዳቤ የይርጋ ዘመኑ ይቋረጣል በሚል ነው፡፡ ይሄንን በተመለከተ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጠሪ ተፃፈ በማለት የተነሳው ነጥብ ስለመፃፍ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ በዚህም ደብዳቤ ለአመልካች የሚከፈል ክፍያ እንዳለና ሆኖም የሚቀናነሱ ክፍያዎች በዚሁ ደብዳቤ የተገለፀ መሆኑን ችሎቱ ተረድቷል፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 164/3/ መሠረት ይርጋን ለማቋረጥ ከሚችሉት ምክንያቶች አንዱ በመሆኑ ይርጋው በዚሁ ደብዳቤ ይቋረጣል ብለናል፡፡ ይርጋ ዘመን ከተቋረጠ ደግሞ አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምር ስለመሆኑ ስለዚሁ የሚደነግግ የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1852/1/ ሥር የተደነገገ በመሆኑ ከጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ጊዜውን ስንቆጥር ክስ እስከቀረበበት ሚያዚያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ 6 ወራት ያላለፈው በመሆኑ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም ብለናል፡፡

በዚሁ መሠረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ከላይ እንደተመለከተው መወሰን ሲገባው የቀረበው ክስ በይርጋ ውድቅ ነው በማለት መወሰኑና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይሄንን ሣያስተካክል ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ክ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ 96677 በቀን 02/03/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁ 33762 በቀን 07/10/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ስለማይሆን በፍሬ ጉዳይ ተገቢውን ማጣራት ከተደረገ በኋላ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲሠጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ላይ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ከፌ/የመ/ደ/ፍቤት የመጣው የመዝ.ቁ . 33762 ወደ መጣበት ይመለስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 64758

ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- እነ ተመስገን ገ/እየሱስ ጠበቃ ግርማ ዓለሙ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ኮከብ ስለሺ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቦነስ ክፍያ ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካቾች የተጠሪ ድርጅት ሠራተኞች ሁነው ካገላገሉ በሁዋላ በራሳቸው ፈቃድ ከባንኩ በቅርቡ የለቀቁ መሆኑን ፣ ተጠሪ በ2001 የበጀት አመት አትራፊ በመሆኑ በዚሁ የበጀት አመት ላገለገሉ ሰራተኞች የሁለት ወር ደመወዝ ቦነስ የሠጠ ቢሆንም አመልካቾችን ግን ሕጋዊ ባልሆነ ምክንያት የከለከለ መሆኑን ገልጸው የአንድ ወር ደመወዛቸው በቦነስነት ፣ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት ደግሞ የድጎማ ክፍያ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካቾች የቦነስ ክፍያው ያልተከፈላቸው ሕብረት ስምምነቱን መሠረት አድርጎ በወጣው መመሪያ ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ስለማያሟሉ ነው በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በ06/12/2001 ዓ/ም የወጣው የቦነስ አከፋፈል መመሪያ የተጠሪ ባንክ ሠራተኛ ማህበር ኘሮዝዳንት እና ምክትል ኘሬዝዳንት እንዲሁም የተጠሪ ባንክ ሰራተኛ ማህበር ጸሐፊን ጨምሮ የባንኩ የተለያዩ ክፍል ኃላፊዎች በተገኙበት ስምምነት የተደረሰበት መሆኑን እንደሚያስረዳ በማረጋገጥ በመመሪያው ሕጋዊነት ላይ የተነሣውን የአመልካቾች ክርክር ውድቅ ያደረገ ሲሆን የቦነስ ክፍያ ጥያቄውን ደግሞ በተጠቃሹ መመሪያ ቁጥር 2/ለ/4/ መሠረት አንድ ሠራተኛ ወይም የስራ መሪ ለቦነስ ክፍያው ብቁ የሚሆነው ይህ ቦነስ ክፍያ ተፈቅዶ ክፍያ እስከተፈጸመበት እለት ድረስ ድርጅቱን በማገኛውም ምክንያት ከለቀቀ ወይም ለመልቀቅ ማመልከቻ ያላስገባ ሲሆን ብቻ መሆኑን ፣ በእድሜ ጣሪያ ምክንያት በጡረታ የተገለሉ በመመሪያው ላይ የሰፈሩትን መስፈርቶች ያሟሉ ከሆነ ክፍያ የሚከፈላቸው መሆኑን መደንገጉን በመመልከትና አመልካቾች ከስራ የተሰናበቱት በዕድሜ ጣሪያ ምክንያት በጡረታ ስለተገለሉ ሳይሆን እያንዳንዳቸው አመልካቾች ከመመሪያው ተግባራዊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፊት ስራ ለመልቀቅ ባቀረቡት መልቀቂያ ማመልከቻ መሆኑን እንዲሁም የድጎማ ክፍያ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የሚከፈለውም በእድሜ ጣሪያ ከስራ ለተገለለ ሰራተኛ መሆኑን በማረጋገጥ የአመልካቾችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም ተጠሪ የአመልካቾችን መብት በሚያጣብብ መልኩ ያወጣው የቦነስና የድጎማ ክፍያ መመሪያና የህብረት ስምምነት ተቀባይነት ማግኘቱ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 134/2/ ድንጋጌ ጋር የማይሄድ ከመሆኑም በላይ የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 20869 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለአመልካቾች የቦነስ ክፍያው አይገባቸውም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት በመቅረብ የሰበር ችሎቱ አስገዳጅ ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑና የተጠሪዎች ጥያቄ ውደቅ የተደረገው ባግባቡ መሆኑን ጠቅሶ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

በክርክሩ ሂደት አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት ተቀጥረው ሲያገለግሉ ቆይተው እድሜያቸው የጡረታ ጣሪያ ሳይደርስ በገዛ ፈቃዳቸው ስራውን የለቀቁ ፣ ተጠሪ መስሪያ ቤትም የቦነስና የድጎማ ክፍያ ለአመልካቾች አይገባም በማለት የሚከራከረው ሕብረት ስምምነቱንና ይህንኑ መሠረት አድርጎ የወጣውን መመሪያ በመመርኮዝ መሆኑን ነው፡፡ አመልካቾች የሕብረት ስምምነቱ ህጋዊነት ተፈፃሚነት ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር የታለፈው ሕብረት ስምምነቱ የወጣው ሥርአቱን ተከትሎ እና የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ስምምነት ተደርሶበት መሆኑና በሕብረት ስምምነቱ ላይም የቦነስ አከፋፈል መመሪያና ማውጣት እንደሚቻል ፣ ሰራተኛ ስራ ሲለቅ ድጎማ የሚከፈልበት አግባብ በሕብረት ስምምነቱ መመልከቱ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ ሲሆን በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃም አመልካቾች የሚከራከሩት የህብረት ስምምነቱ የተሻለ መብት የማይጠብቅ በመሆኑ ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ በተመሣሣይ ጉዳይ በሕግ ከተደነገገው ይልቅ የሕብረት ስምምነቱ ለሰራተኞች የበለጠ ጥቅም የሚያስገኝ ሆኖ ሲገኝ ስምምነቱ ተፈፃሚ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 134/2/ ሥር ተደንግጓል፡፡ ለጉዳዮቹ የተደነገገው ሕግ ለሰራተኞቹ የበለጠ ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ግን ሕጉ በስራ ላይ ሊውል የሚገባ መሆኑን ይኸው ድንጋጌ በኃይለ ቃል አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም ህብረት ስምምነቱ ተፈጻሚነት የሚኖረው ከአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የተሻለ ሁኖ ሲገኝ ሲሆን ከሕጉ ተቃራኒ ወይም ያነሰ ጥቅም የሚያስገኝ ሁኖ ከተገኘ ደግሞ ስራ ላይ የማይውል መሆኑን ከድንጋጌው መንፈስ ፣ ይዘትና ቅርፅ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካቾች ጥያቄ የቦነስና የድጎማ ጥያቄ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ ቦነስ ወይም ድጎማ ሊያገኝ የሚገባው ከአሰሪው ጋር በሚኖረው ስምምነት እንጂ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ለሰራተኛው አሰሪው በአሰሪነቱ የግድ እንዲከፍል ተለይቶ የተቀመጠ ጉዳይ አለመሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 4፣ 12፣ 13፣ እና 53 ድንጋጌዎች ቅርጽ ፣ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የሕብረት ስምምነቱ ከአሰሪና ሠራተኛ ሕግ የተሻለ ጥቅም የማይጠብቅ በመሆኑ ተፈፃሚነት ሊኖረው አይችልም በማለት ያቀረቡት ክርክር በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ የተጠበቀ መብት ባለመሆኑ አግባብነት ያለው ክርክር ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ ሕብረት ስምምነቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተፈጻሚ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ሕብረት ስምምነቱ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ከተባለ ደግሞ የቦነስ ክፍያ ጥያቄ የሚፈፀምበት አግባብ በመመሪያ ሊወጣ እንደሚችል በህብረት ስምምነቱ የተመለከተ ሁኖ ይህንኑ መሠረት አድርጎ ተጠሪ ነሐሴ 06 ቀን 2001 ዓ/ም መመሪያ አውጥቶ ስራ ላይ አውሏል፡፡ በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 4 ላይ ከስራ በጡረታ የተገለሉና ሌሎች መስፈርቶችን የሚያሟሉ ቦነስን እንደሚያገኙ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ በመመሪያው ተራ ቁጥር 4 የቦነስ ክፍያ ተፈቅዶ እስከ ተፈጸመበት እለት ድረስ በማንኛውም ምክንያት ከሰራ ሰራተኛው ከለቀቀ ወይም ለመልቀቅ ማመልከቻ ያላስገባ ሲሆን ብቻ ቦነሱ እንደሚከፈል መመልከቱን የስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ አመልካቾች ይህንኑ የመመሪያውን ይዘት ትክክል አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር የሌለ ሲሆን አመልካቾች ስራቸውን ለመልቀቅ ማመልከቻቸውን ያስገቡትና ከስራ የተሰናበቱት መመሪያው ነሐሴ 06 ቀን 2001 ዓ/ም ከመውጣቱ በፊት መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ የድጎማ ክፍያን በተመለከተ ደግሞ የሕብረት ስምምነቱ በአንቀፅ 34/1/ እና /4/ መሠረት ሊከፈል የሚችለው ሰራተኛው በእድሜ ብቁነት በጡረታ ከስራ ሲገለል መሆኑን የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በእድሜ ብቁነት ሳይሆን በገዛ ፈቃዳቸው ስራቸውን የለቀቁ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ሕብረት ስምምነቱም ሆነ የቦነስ ክፍያ መመሪያው የሚከለክሏቸው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ አመልካቶች አጥብቀው የሚከራከሩት የሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 20869 የሰጠው የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈጻሚነት አለው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ አንድ ሰራተኛ በበጀት አመቱ ለሚገኘው ትርፍ አስተዋጽኦ ማድረጉ እስከተረጋገጠ ድረስ ስራውን ቢለቅም ቦነሱ ሊከፈለው እንደሚገባ ሰበር ችሎቱ በተጠቃሹ መዝገብ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ መዝገብ የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ከሰ/መ/ቁጥር 20869 ከተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ጋር ሙሉ ሙሉ ተመሳሳይነት አለው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ቦነስ ከአሰሪው ለሰራተኛው የሚሰጥ ጉርሻ /የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 53/2/ሐ/ ይመለከታል/ እንደመሆኑ መጠን አከፋፈሉን በተመለከተ ተጠሪ ሥርዓቱን ዘርግቷል፡፡ በዚህ ስርዓት መሠረት ደግሞ አመልካቾች የቦነሱና የድጎማ ተጠቃሚ ለመሆን ሁኔታዎችን የሚያሟሉ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቾች ክርክርም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካቾች የቦነስና የድጎማ ክፍያ አይገባቸውም ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 45679 የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 90211 ጥር 17 ቀን 2003 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች የቦነስና የድጎማ ክፍያ አይገባቸውም ተብሎ የተወሰነው ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 13 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉ ደምሴ - ጠበቃ ከበደ ወርቁ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሽራተን አዲስ - ጠበቃ ግርማ ሀይሌ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በምግብ ዝግጅት የስራ መደብ ተቀጥረው የሰሩ መሆናቸውን ገልጸው ተጠሪ የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው በማለት ለሌሎች ሰራተኞች የሚሰጠውን ጥቅማጥቅም የማግኘት መብት ነፍገውኛል፡፡ ስለሆነም ከመስከረም ወር 2002 ዓ.ም ጀምሮ የቲፕ ክፍያ ቦነስ የሁለት ወር ደመወዝ የደመወዝ ጭማሪ አስር ፐርሰንት በየዓመቱ የስድስት ወር ፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተከሣሽ የመድን ሽፋን እንዲሰጠኝ የህክምና ወጭ እንዲሸፍንልኝ የደመወዝ መክፈያ ጊዜ ከሌሎች ሰራተኞች ጋር እንዲያስተካክልልኝና የስራ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ ይወስንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ /አመልካች/ ከዚህ በፊት ክስ አቅርበው የቲፕና ዓመታዊ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገ በመሆኑ በድጋሚ የቀረበችው ክስ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 መሠረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ከሣሽ ሌሎቹን ጥያቄያቸውን ከዚህ በፊት ካቀረቡት ክስ ጋር ዘርዝረው ያላቀረቡ በመሆኑ አሁን ማቅረባቸው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 216 የሚጥስ ነው፡፡ ከሣሽ የጠየቋቸው ጥቅማጥቅሞች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ነው፡፡ ከሣሽ ለተወሰነ የስራ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኛ በመሆናቸው ያቀረቡት የጥቅማጥቅም ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች ቲፕ እንዲከፈላቸው በመዝገብ ቁጥር 18403 ጠይቀው ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገ በመሆኑ በዚህ መዝገብ ክስ መልሰው መጠየቃቸው በፍርድ የመጨረሻ ውሣኔ ባገኘ ጉዳይ ያቀረቡት ስለሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 የሚታገድ ነው፡፡ እንደዚሁም በመዝገብ ቁጥር 22230 አመልካች /ከሣሽ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስር ፐርሰንት የደመወዝ ጭማሪና የህክምና ክፍያ አልጠየቁም፡፡ ከሣሽ የሰርቪስ ቻርጅ በቀጣይነት እንዲከፈላቸው ነው ክስ ያቀረቡት ስለሆነም ከሣሽ ክሣቸውን ነጥለው ያቀረቡ ስለሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 216 ቀሪ ነው በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡

በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት የአመልካች የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው ተጠሪ የሁለት ወር ቦነስ ሊከፍል ይገባል፡፡ የመድን ሽፋንና የደመወዝ መክፈያ ጊዜ ይስተካከልኝ ጥያቄ ግልጽነት የጐደለው ነው፡፡ ተጠሪ የስራ ምስክር ወረቀት ይሰጣት በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች መጋቢት 2 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል መሆኑን ከወሰነ በኋላ አመልካች ያቀረቡትን የመብትና የጥቅማጥቅም ጥያቄዎች ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 216 በመጥቀስ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ስለሆነም ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች የከፈላቸውን መብቶችና ጥቅማጥቅሞች እንዲያከብር ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አመልካች በሶስት መዝገቦች ማለትም በመዝገብ ቁጥር 18403 በመዝገብ ቁጥር 22230 እና ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሣኔ በተሰጠበት የመዝገብ ቁጥር 33375 የተለየዩ ጥያቄዎችን አቅርበው በፍርድ ቤት ውድቅ የተደረገ በመሆኑ አሁን የሚያቀርቡት ክርክር የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 የሚቃረን ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሰኔ 6 ቀን 2003 ዓ.ም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቧቸውን የጥቅማጥቅምና የመብት ጥያቄዎች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 216 በመጥቀስ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተነዋል፡፡

አመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል መሆኑን በስር ፍርድ ቤት ተወስኗል፡፡ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል ላይ የተመሰረተ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት በህግ አግባብ እስከሚቋረጥ ድረስ ቀጣይነት ያለው ግንኙነት እንደሚሆን የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ልዩ ባህሪ የስራን ውል መነሻ በማድረግ ሊቀርቡ ከሚችሉት የመብት ጥያቄዎችና እነዚህ የመብት ጥያቄዎች ላይ ተፈጻሚነትና ገዥነት ካለው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ማንኛውም አሰሪ በስራ ውሉ ከተስማማባቸው ልዩ ግዴታዎች በተጨማሪ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 12 የተዘረዘሩት በህግ የተጣለበት ግዴታዎች እንዳሉበት ከህጉ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ለሰራተኛው ደመወዙንና ሌሎች ክፍያዎችን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ወይም በህብረት ስምምነት መሠረት የመክፈል ግዴታ አሰሪው እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡

ይኸም የሚያሣየው ሰራተኛው አሰሪው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ መሠረት ሊከፍለው የሚገባውና ያልከፈለው ክፍያ መኖሩን ወይም በህብረት ስምምነቱ መሠረት ሊከፍለው የሚገባው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክፍያና ሊያከብርለት የሚገባው መብት እንዳለ በተረዳ ጊዜ አሰሪውን የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን ነው፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ካለው ቀጣይነትና ዘላቂነት አንጻር ስንመለከት ሰራተኛው በአንድ ወቅት ሊጠበቅልኝ ወይም ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበው የመብት ወይም የክፍያ ጥያቄ በፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ በሌላ ጊዜ መብቱን ወይም ክፍያውን ለመጠየቅ የሚያስችለውን የስራ ውል የህግ ድንጋጌ ወይም የህብረት ስምምነት ዋቢ በማድረግ እንዳይጠይቅ የሚገድበው አይደለም፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠሪ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሰራተኛው በአንድ ወቅት ክስ ሲያቀርብ ክፍያዉን ለመጠየቅ የሚያስችለው የስራ ውል፣ የህግ ድንጋጌ ወይም የህብረት ስምምነት ባለመኖሩ ያልጠየቀውን ክፍያ ወይም የመብት ጥያቄ በሌላ ጊዜ እንዲከፈለው ከመጠየቅ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 216 ይገድበዋል የሚል መደምደሚያና ትርጉም ላይ መድረስ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነትን እና የስራ ውል አስመልክቶ የሚነሱ የመብት ጥያቄዎችና ክርክሮች ከሌሎች ጉዳይ ከሚደረጉ ክርክሮች አንፃር ያላቸውን ውስብስብና ልዩ ባህሪ ያላገናዘበና የአሰራና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ዓላማና ግብ የማያሳካ የህግ አተረጓጎም ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ ለተደረጉ የስራ ውል ላላቸው ሰራተኞች የሚያከብራቸውን መብቶችና የሚጠብቃቸዉን ጥቅማጥቅሞች ተጠሪ እንዲያከብርላቸው ያቀረቧቸውን ጥያቄዎች ከፊሎቹን የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 216 በመጥቀስ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህ ላይ ከተገለጸው በተጨማሪ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18403 እና በመዝገብ ቁጥር 22230 ክስ አቅርበው ከተጠሪ ጋር የተከራከሩበት መሠረታዊ ጭብጥ ለዚህ ክርክር መነሻ ከሆነውና ለስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 33375 ካቀረቡት ክርክርና ጥያቄ በባህሪውም ሆነ በይዘቱ የተለየ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በተለይም አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 22230 የተከራከሩት አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የስራ ውል መቋረጥና ከስራ መሰናበቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው መሠረታዊ ጭብጥ ላይ ሆኖ እያለ ይህንን መዝገብ በመጥቀስ አመልካች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠርኩ ሰራተኛ ስለሆንኩ ለቋሚ ሰራተኞች የሚከበረው መብትና የሚከፈላቸው የጥቅማጥቅም ጥያቄ ለእኔም ይከፈለኝ በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪ ለሌሎች ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች የሚያሟላውን መብትና የሚከፍላቸውን የጥቅማጥቅም ክፍያዎች ለእኔም እንዲያከብር ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 5/1/ እና አንቀጽ 216 በመጥቀስ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኛ ስለሆኑ ተጠሪ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፍል በማለት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት የውሣኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. በድርጅቱን የህብረት ስምምነትና ደንብ መሠረት ተጠሪ ላልተወሰኑ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች የሚያከብረውን መብትና የሚከፍለውን የጥቅማጥቅም ክፍያ ለአመልካች ሊያከብርላትና ሊከፍላት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ወልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ አሞኘስ ገብሬ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- በአቃቂ መለዋወጫ ዕቃዎች የእጅ መሥሪያዎች ኢ/ማ የሠራተኞች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ነገረ ፈጅ አዳነ አረጋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን በበታች ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ስትሆን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ በአሰሪ መስሪያ ቤቷ ላይ ባቀረበችው ክስ ተከሳሽ መስሪያ ቤቷ ባቀረበው ተቃውሞ ከሳሽ የስራ መሪ እንጅ ሰራተኛ አይደሉም፡፡ የከሳሽና ተከሳሽ ክርክር መዳኘት ያለበት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ሳይሆን የራሱ የሆነ ሕግ ስለአለ በአዋጅ ቁ. 147/91 እና 402/96 መሠረት መሆን አለበት በማለት ተከራክሯል፡፡

በእነዚህ በቀረቡት መቃወሚያዎች ላይ ፍርድ ቤቱ ካከራከረ በኋላ ከሳሽ የስራ መሪ ናቸው በማለት የቀረበውን ተቃውሞ በተመለከተ ከሳሽ የሂሳብ ሰራተኛ ባለሙያ እንጂ ለአሰሪ መስሪያ ቤት የምታቀርበው የውሣኔ ሃሳብ ባለመኖሩ ተቀባይነት የለውም በማለት ሲወስን ሁለተኛውን የተቃውሞ ነጥብ /ተፈፃሚነት ያለውን ህግ በተመለከተ/ እንደዚህ አይነት የህብረት ሥራ ማህበራት ተቋም ሂደታቸው የሚመራው በአዋጅ ቁ. 147/91 አንቀጽ 49/3/ እና 52 እና አዋጅ ቁ. 402/96 አንቀጽ 8 መሠረት መሆኑን በማብራራት አለመግባባቶች ሲከሰቱ መጀመሪያ በእርቅ፣ በእርቅ ካልተቻለ ደግሞ በሽምግልና ዳኝነት መታየት እንዳለበትና እነዚህ አካላት በሚወስኑት ውሣኔ ላይ ቅሬታ ካለ ወደ ሚመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችሉ ስለሚደነግግ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ጉዳዩን ለሽማግሌዎች አስፈላጊውን መመሪያ በመስጠት እንዲያዩት እንዳዘዘና መዝገቡን እንደዘጋ ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

የአሁኑ ይግባኝ ሊቀርብ የቻለው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሲሆን በ18/12/2002 ዓ.ም የተፃፈ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥሬ ስሰራ የቆየሁ ሲሆን ተጠሪ ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሌን አቋርጦ ከስራ ስላሰናበተኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቋረጠብኝ ጥቅም ተጠብቆ ወደ ስራዬ እንድመለስ ትዕዛዝ እንዲሰጠኝ የበታች ፍርድ ቤት ብጠይቅም ጉዳዩ መታየት ያለበት በእርቅ ወይም በሽምግልና ዳኛ ነው በማለት መዝገቡን ዘግተውብኛል፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የስራ ውል እንደመሆኑ መጠን በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መታየት ሲገባው በመጀመሪያ በእርቅ ይዜም ካልተቻለ በሽምግልና መታየት አለበተ በማለት መዝገቡ መዘጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤት በህጉ አግባብ ዳኝነት እንዲያዩልን ውሣኔ እንዲሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ በመታዘዙ በተወካያቸው አማካኝነት በ27/382003 ዓ.ም በ2 ገጽ ጽፈው ባቀረቡት መልስ የበታች ፍርድ ቤት ይዜ ጉዳይ በህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ 147/91 መታየት አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ ምንም ዓይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም በ20/4/2003 ዓ.ም በ2 ገጽ ባቀረቡት የመልስ መልስ ቅሬታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆኑ እኛም የቀረበውን ቅሬታ የበታች ፍርድ ቤት ከሰጡት ውሣኔ ከተያዘው ጭብጥና ጉዳዩ ከሚመለከተቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአመልካች የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት ክስ መቅረብ ያለበት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 396/96 ነው ወይስ በህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁ. 147/91 ነው የሚለው ጭብጥ ተይዞ መፍትሄ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ጉዳዩን ስንዳስሰው በእርግጥ በአዋጅ 147/91 አንቀጽ 49 ስር አለመግባባቶች ሲኖሩ እንዴት ሊፈቱ እንደሚገባቸው ይደነግጋል፡፡ ይዜውም በመጀመሪያ ደረጃ በእርቅ መታየት እንዳለበት በእርቅ ካልተቻለ ደግሞ በሽምግልና ታይቶ በዚህ አካል በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው አካል በይግባኝ ወደሚመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ መሄድ እንደሚቻል ይዳነግጋል፡፡ ሆኖም ምን አይነት ጉዳዮች ናቸው በእንደዚህ አይነት ሂደት መታየት ያለባቸው የሚለውን በምናይበት ጊዜ በዚሁ አንቀጽ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው ለሽምግልና ዳኝነት የሚቀርቡት ጉዳዮች በዝርዝር ስለአንድ ማህበር አቋም ስለስራው አካሄድ ወይም ስለስራው አፈፃፀም እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ የዚሁ አንቀጽ መግቢያ የእንግሊዝኛ ትርጉም “The arbitrators shall have the power to hear disputes not settled by arbitration regarding the organization, management or operation of a society…” ይላል፡፡ የዚህን አንቀጽ አቀራረጽ ስናይ አጠቃላይ የህብረት ስራ ማህበሩን እንቅስቃሴ ወይም ህልውና የሚመለከቱ በተለይም አደረጃጀቱን አመራሩና የስራ እንቅስቃሴን መሰረት ያደረገ አለመግባባት እንጅ ማህበሩ እንደማንኛውም ህጋዊ ሰውነት እንዳለው ተቋም ሊቀጥራቸውና ሊያሰራቸው ወይም በስሩ የሚተዳደሩትን ሠራተኞች በዚሁ የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ለመምራት ያሰበ ስለመሆኑ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ የአንቀፁን መንደርደሪያ ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው ከአሰራተኞቹ ጋር ሊፈጠር የሚችለውን የስራ ክርክር ሂደት ከላይ በተጠቀሰው የሙግት አመራር ስርዓት ለማስኬድ የህግ አውጪው ሃሳብ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነገር የለም፡፡

የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁ. 147/91 አጠቃላይ ትኩረት ተመሳሳይ ፍላጐት ባላቸው ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የህብረት ስራ ማህበራትን በመፍጠር ገንዘብን፣ እውቀትን፣ ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር ቁጠባንና እርስ በርስ መደጋገፍ የሚጐለብትበትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚመራበትን የህግ ማዕቀፍ መፍጠር እንደሆነ ከዚሁ አዋጅ መግቢያ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአዋጁ አንቀጽ 4/1-9/ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ስንመለከት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለየብቻቸው ሆነው ሊከብዳቸው የሚችለውን ጉዳይ በመተባበር ሊደርሱባቸው የሚችሉበትን የአደረጃጀት ማዕቀፍ ከመዘርጋት አኳያ እንጅ እንደማንኛውም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም አሰሪ የሚሆንላቸውን ሠራተኞች በዚህ አዋጅ መሠረት ሊፈጠሩ የሚችሉትን አለመግባባቶች ለማስኬድ የታሰበ ስለመሆኑ የሚያሳይ አይደለም፡፡

በተጨማሪ መነሳት ያለበት ጉዳይ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የስራ ክርክርን በተመለከተ የተለየ ህግ በመሆኑና በህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ ያሉ ሰራተኞች በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ሊተዳደሩ አይገባም ሊባል የሚችልበት አጋጣሚ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/2/ /ሠ/ መሰረት የሚተዳደሩበት የራሳቸው ዝርዝር ህግ ወጥቶላቸው ቢሆን ኖሮ ነበር፡፡ ከዚህ አኳያም የወጣ ነገር የለም፡፡ እንደማንኛውም ሕጋዊ ሰውነት እንዳለው ተቋም ሰራተኛ ሊቀጥርና ሊያስተዳድር የሚችል ተቋም መሆናቸው ቢታመንም ባላቸው የስራ ግንኙነት ምክንያት ወይም የስራ ውል መሰረት ያደረገ አለመግባባት ሲፈጠር የሚመራበት የተለየ ህግ በሌለበት ሁኔታ፣ የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ቢባል እንኳ የትኛውን ህግ መሰረት ያደርጋል? ሠራተኛው ከሚያነሳው የመብት ጥያቄ አኳያ የሚሰጠው መፍትሔ (remedy) ምንድነው? የሚለው ጥያቄ በአዋጁ መልስ አላገኘም፡፡ በሌላ በኩል በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የሚነሱትን የስራ ውል ተያያዥ ክርክሮችን ለምሳሌ የሥራ ስንብት፣ የካሳ አከፋፈል እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መፍትሔ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ሕግ አውጪው ጉዳዩን በአዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት ተፈፃሚ እንዲሆን ያሰበ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በግልጽ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ተፈፃሚነት የለውም ባልተባለበት ሁኔታ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አይመራም መባሉ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ውስጥ እየተጠቀሰ ያለው የቅሬታ አፈታት ስርዓት ከላይ በተመለከተው ምክንያት ለሌላ ዓላማ የተቀመጠ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁ. 377/96 ይሆናል ብለናል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በአንድ ወጥ በሆነ የህግ ማዕቀፍ ለማስተዳደር መሠረታዊ የሆነ የህግ አውጭው ሐሳብ እንደሆነ ከወጣው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መግቢያ ንባብ ከመረዳታችን በላይ በህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ ላሉት ሰራተኞች የተለየ ህግ ማስፈለጉን በግልጽ ባልተደነገገበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች የወሰዱት አቋም አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ሆነ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይሄንን ሳያገናዝቡ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለንም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ያለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 44428 በ21/5/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይንና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 90023 ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ መታየት ያለበት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት በመሆኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበውን ክስ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን ፍርድ እንዲሰጥ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለደረሰው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- ሜታ አቦ ቢራ አ/ማ ነገረ ፈጅ አቶ ሰለሞን ዘውዴ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ወ/መድህን ቢረዳ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ ተጠሪ ለሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ በተከሳሽ ድርጅት /የአሁን አመልካች/ በዩቲሊቲ ክፍል ሃላፊ ሆኜ ስሰራ ቆይቼ ማያዝያ 26 ቀን 2001 ዓ.ም በሥር ላይ በደረሰብኝ አደገ በህክምና የተረጋገጠ 7% ጉዳት የደረሰብኝ ስሆን ተከሳሽ ክፍያ የፈፀመልኝ ካደረሰብኝ ጉዳት ባነሰ በመሆኑ ቀሪውን ገንዘብ ከነ ወለዱ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሽም በሰጠው መልስ ተከሳሽ በገባው የመድን ዋስትና መሰረት ለከሳሽ የሚገባውን የካሣ ገንዘብ ከፍሏል፡፡ ስለሆነም ቀሪ የሚከፈለው ካሣ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በበኩሉ ወደ ክሱ ጣልቃ በመግባት የተከራከረ ሲሆን የሥር ተከሳሽ በገባው የመድን ሽፋን መሠረት ክፍያ መፈፀሙን ገልጿል፡፡ የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም በሰጠው ፍርድ ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/2/ መሠረት ለከሣሽ ተገቢውን ካሣ የከፈለ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

የሥር ከሣሽም በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበው የቅሬታ ነጥብይ መልስ ሰጪው ቀደም ሲል ከከፈለኝ ገንዘብ ብር 7500 በተጨማሪ ብር 8649 ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ያቀረብኩትን ክስ የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

ከፍተኛ ፍ/ቤትም የመልስ ሰጪዎችን መልስ ከቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ጋር ከመረመረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/1/ ድንጋጌ መሠረት ለሠራተኛ የሚከፈል የጉዳት ካሣ አሠሪው በገባበት የመድን ዋስትና ተፈፃሚ ይሆናል ተብሎ የተገለፀው የመንግስት ሠራተኞችን የሚመለከት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በ1ኛ መልስ ሰጪ /የአሁን አመልካች/ እና 2ኛ መልስ ሰጪ /የኢት/መድን ድርጅት/ መካከል የተደረገው የመድን ሽፋን ውል ህግ ሆኖ የሚገዛው ሁለቱን ተዋዋይ ወገኖችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንጂ ይግባኝ ባይ /ያሁን ተጠሪን/ የውሉ ተገዢ ለማድረግ ሙሉ በሙሉ የሚያስገድድ አይደለም በማለት 1ኛ መልስ ሰጪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ መሠረት ከደረሰው የአካል ጉዳት ጋር ተያይዞ ቀሪ የካሣ ክፍያ ብር 8649 የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት ፈርዷል፡፡

በሥር የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲል አመልካች ለዚህ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም አመልካች የመንግስት የልማት ድርጅት ሲሆን ተጠሪው ደግሞ የመንግስት ሠራተኛ ነው፡፡ በመሆኑም አሰሪው ካሣ መክፈል ያለበት በአዋጅ አንቀጽ 109/1/ መሠረት አሰሪው በገባበት የመድን ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ህግ መሠረት ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም አመልካች በገባው የመድን ዋስትና መሠረት ከሚገባው ካሣ በላይ ለተጠሪው ከፍሏል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ን ለውሣኔው መሠረት ያደረገ ሲሆን ይህ አንቀጽ ከ109/2/ ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው፡፡ ምክንያቱም ድንጋጌው በጡረታ ህግ ላልተሸፈኑ ሠራተኞች አሰሪው በአንድጊዜ ስለሚከፍለው ካሣ ሲሆን ተጠሪ ግን የጡረታ ሽፋን ያለውና እንደማንኛውም ሠራተኛ ዕድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ መብት የሚከበርለት ነው፡፡ ስለሆነም የስር የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳይ በተጠቀሰው ህግ አንቀጽ 109/3/ለ/ ሥር የሚሸፈን ነው በማለት ተጠሪው በተጨማሪነት እንዲከፈለው የጠየቀውን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ያለአግባብ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ አመልካች ለሠራተኛው የገባው የመድን ዋስትና የሚያስገኘው ጥቅም አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ ለሠራተኛው የሚሰጠው ጥቅም ያነሰ ነው፡፡ የህብረት ስምምነቱም የካሣ ክፍያን አስመልክቶ ለሠራተኛው የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ካስቀመጠው ያነሰ ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ተፈፃሚነት የለውም ተጠሪም እንዲከፍለኝ የጠየቅኩት የህብረት ስምምነቱ ያስቀረብኝን ጥቅም በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም ሲል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው ብሏል፡፡

አመልካችም ለተጠሪ መልስ በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር ከዚህ በላይ የቀረበ ሲሆን እኛም አመልካች በቀረነት የሚፈለግበትን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ለተያዘውን ጭብጥ ምላሽ ለመስጠት ስለ ጉዳት ካሣ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109 የተደነገገውን መመልከት ተገቢነት ያለው ነው፡፡ የተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 109/1/ የሚናገረው በመንግስት ድርጅቶች ሠራተኞች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ካሣ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ሲሆን አከፋፈሉም አሠሪው በገባበት የመድን ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ህግ መሠረት መሆኑን ይገልፃል፡፡ አንቀጽ 109/2/ ደግሞ ተፈፃሚ የሚሆነው በጡረታ ህግ ላልተሸፈኑ ሠራተኞች ሲሆን የጉዳት ካሣውም የሚከፈለው በጡረታ ህግ መሠረት ሳይሆን በአንድ ጊዜ ክፍያ ነው፡፡ የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር 3 ደግሞ ከንዑስ ቁጥር 2 ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ ስለ ጉዳት ካሣው መጠን ስሌት የሚናገር ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በደንብ ቁጥር 64/85 የተቋቋመ ሲሆን ተጠሪውም የመንግስት ሠራተኞች ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪው የደረሰበት ጉዳት 7% እንደመሆኑ መጠን መደበኛ ሥራውን እያከናወነ ያለና በጡረታ ህግ የተሸፈነና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዕድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ አበል ጭምር የሚያገኝ መሆኑን አመልካች ያስረዳ ሲሆን ተጠሪው ግን ይህን በሚያስተባብል መልኩ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡

ስለሆነም የአመልካችና የተጠሪው ክርክር መወሰን ያለበት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደጠቀሰው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/3/ለ/ ሳይሆን በአንቀጽ 109/1/ መሠረት ነው፡፡ በዚህ በተጠቀሰው አንቀጽ ማለትም 109/1/ መሠረት አንድ የመንግስት ድርጅት በሰራተኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ የሚከፍለው በገባበት የመድን ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ህግ ሲሆን ይህ ሊቀየር የሚችለው አሠሪውና ሠራተኛው በህብረት ስምምነታቸው በተቃራኒ ተስማምተው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም በህብረት ስምምነት በተቃራኒ የተወሰነ ወይም የተደረገ ስምምነት ስለመኖር በሥር ፍ/ቤት በአስረጂነት የቀረበ ነገር የለም፡፡

አመልካችም የጉዳት ካሣውን ገንዘብ የከፈለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/1/ መሠረት ለተጠሪው በገባለት የመድን ዋስትና ሲሆን የዋስትና ሽፋኑም ብር 7500 በመሆኑና ይህንኑ ገንዘብ ለተጠሪው መክፈሉን ገልጿል፡፡ በአንቀፁ የጉዳት ካሣው አሰሪው በገባበት የመድን ዋስትና ሊሆን እንደሚችል ከተደነገገው በተጨማሪ በአመልካች እና በሜታ አቦ ቢራ አክስዮን ማህበር መሠረታዊ የሠራተኞች ማህበር መካከል በ2000 ዓ.ም በተደረገው የህብረት ስምምነት አንቀጽ 32 ድርጅቱ /አመልካች/ ለማንኛውም ሰራተኛ በሥራውና ከሥራው ውጪ ለሚደርስበት አደጋ የሕይወት መድን ዋስትና ይገባለታል የተባለ ሲሆን ለአካል ጉዳትና የሕይወት መድን ዋስትና ድርጅቱና ሠራተኛው በጋራ በሚያዋጡት አረቦን ዓመታዊ የህይወት ዋስትና እንደሚገባለት አንቀፁ ይናገራል፡፡

በመሆኑም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 እና በ2000 ዓ.ም በተደረገው የህብረት ስምምነት መሠረት ለሠራተኞች /ተጠሪን ጨምሮ/ የመድን ዋስትና ገብቶላቸው ተጠሪውም ዓመታዊ አረቦን ማዋጣቱን እያወቀ ለደረሰበት ጉዳት አመልካች ለተጠሪው በገባለት የመድን ሽፋን መሠረት የከፈለውን የጉዳት ካሣ አንሶኛል በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መርምሮ የጉዳት ካሣ በአግባቡ ተከፍሏል በማለት የወሰነውን የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109/ለ/ በመጥቀስ ቀሪ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል ሲል የወሰነው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 99288 በቀን 02/05/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16634 በቀን 03/02/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡ ውሣኔውም የህግ ስህተት የሌለበት ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/62370

ታህሣስ 26 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ዕዮብ መሰለ
2. አቶ ደምመላሽ አቦዬ
3. አቶ ወንድማገኝ ይርጉ
4. አቶ ፍቃዱ ደጀኔ

} ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥራ ውል ማቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪዎች ሥር ፍ/ቤት ከሣሽ ነበሩ፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረውን የሥራ ውል ከሕግ አግባብ ውጪ አቋርጧል በሚል ወደ ሥራ እንዲመልሳቸው ወስኗል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የ6 ወር ደመወዝ ከፍሎ ተጠሪዎችን ወደ ሥራ ይመለስ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ታህሣስ 1 ቀን 2003 ዓ.ም. የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ በአመልካች በተያዘው የፕሮጀክት ሥራ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያየ ቦታና የሥራ መደብ ሲሠሩ መቆየታቸውን ገልፀው የሥራ ውል ማደስ አስፈላጊ ነው ከተባለም ይሠሩ ከነበሩበት ሙያ ጋር በሚጣጣም መልኩ ባለመቅረቡ እንጂ ውል ለማደስ ፈቃደኛ መሆናቸውን ዘርዝረው በዚህም ምክንያት የሥራ ውል ማቋረጥ ከሕግ ውጭ ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ፍርድ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች አቤቱታውን ከጠናክሮ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ከተያዘው ጭብጥ አንፃርና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረውን የሥራ ውል ለማቋረጥ ምክንያት ያደረገው ተጠሪዎች የውል እድሳት ውል ለመፈረም አልፈቀዱም አዲስ የውል ሁኔታን አቅርበዋል በሚል ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንደተረጋገጠው ተጠሪዎች በአመልካች በተያዘው የፕሮጀክት ሥራ ውስጥ በነዳጅ ቀጅነትና በብየዳ ሥራ ላይ ይሠሩ እንደነበር እና የሥራ ውል ሊታደስ የሚገባ ከሆነም በዚሁ አግባብ እንጂ ጫኝ እና አውራጅ በሚለው የሥራ መደብ መሆን የለበትም የሚል ነው፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዎች ለውል እድሳት ያቀረቡት ሁኔታ ቀድሞ አልነበረም ተጠሪዎች የተቀጠሩት በዩኒቨርሳል ኤሌክትሪፊኬሽን አክሰስ ፕሮጀክት ውስጥ የተወሰነ ሥራ ለመሥራት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10/1/ሀ መሠረት ነው፡፡

በመሠረቱ የሥራ ውል ባህሪ የሚወሰነው በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 9 እና 10 በተደነገገው አግባብ መሆኑ እሙን ነው፡፡ አሠሪው የሥራ ውል በአዋጅ አንቀጽ 10 ሥር በተደነገገው አግባብ የተፈፀመ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ማስረዳት ከቻለ ደግሞ የሥራ ውል ታደሰም አልታደሰ ሥራው ሲያልቅ ወይም ጊዜው ሲያበቃ የሥራ ውል ሊቋረጥ እንደሚችል አዋጁ በግልፅ ደንግጓል፡፡

በተያያዘው ጉዳይ አመልካች ተጠሪዎች የተቀጠሩበት የፕሮጀክት ሥራ ተጠናቋል የሚል ክርክር በአመልካች በኩል አልቀረበም፡፡ ስለሆነም የፕሮጀክት ሥራው አሁንም ቀጥሎ ያለ ስለመሆኑ መረዳት አዳጋች አይደለም፡፡ ስለዚህም ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ሥራ አመልካች እንደሚለው በአንቀጽ 10/1/ሀ ሥር የሚሸፈን ነው እንኳ ቢባል የፕሮጀክቱ ሥራ ተጠናቋል፡፡ እስካልተባለ ጊዜ ድረስ የሥራ ውል አድሰዋል ወይም አላደሱም አሊያም ለማደስ ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል ምክንያት ብቻ የሥራ ውልን ለማቋረጥ የሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ስለሆነም አመልካች ያቀረበውን መከራከሪያ ነጥብ ውድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ በሕግ ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡

ስለዚህም ውሣኔው ባለበት እንዲፀና ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 50103 ሰኔ 25 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 98347 በ30/02/2003 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በዚህ መዝገብ ላይ ህዳር 17 ቀን 2003 ትዕዛዝ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ መልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ማህበር - አቤነዘር በወንጌል ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የሕግ ተወካይ

አቶ ፈቃዱ ደጀኔ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ተቋቁሞና ሕጋዊ ዕውቅና እና ሕልውና አግኝቶ የኖረ ማህበር መሆኑን ገልፆ ከታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የብሔራዊ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 377/96 እንደማይተዳደርና በልዩ ሕግ የሚታዳደር መሆኑ በሕግ የተደነገገ በመሆኑ ማሕበሩ እንዲፈርስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ዓላማዬን ማሣካት አልቻልኩም ብሎ የመፍረስ ጥያቄ ማቅረብ የማሕበሩ እንጂ የከሳሽ (ተጠሪ) መብት አይደለም ማሕበሩ የሚፈርስበት ምክንያት የለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ሠራተኛው ከአዋጅ ቁጥር 377/96 ውጭ በተለየ ደንብ መታዳደሩ ማሕበሩን ለማፍረስ ያማያስችል አይደለም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የብሔራዊ ባንክ ሠራተኞች በደንብ ቁጥር 157/2001 የሚተዳደሩ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 3/1/ሠ/ የሚሸፈኑ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ማሕበሩ ሊፈርስ አይገባም ሲል የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ አመልካች ማሕበር እንዲፈርስ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ግንቦት 2 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ማሕበሩ ለሰላሣ ሦስት ዓመት ያሕል ዕውቅና አግኝቶ የሠራተኛውን መብትና ጥቅም ሲያስጠብቅ የኖረ ነው፡፡ ሠራተኛው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በደንብ ቁጥር 157/2001 የሚተዳደር መሆኑ ማህበሩ ያለውንና ቀደም ሲል የነበረውን ህልውና ለማስጣት የሚቻል አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 120 ድንጋጌና የአገሪቱን ሕገ መንግስት አንቀፅ 31 እንደዚሁም ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ድርጅት በኩል ያፀደቁትን ስምምነቶች በተለይም ቁጥር 87 እና ቁጥር 98 የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ታሕሣሥ 7 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር መልስ የብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁ. 591/2000 የባንኩን ሠራተኞችና የአስተዳደር አካላትን በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እንድያወጣ ሥልጣን ይሰጣል፡፡ በዚህ መሠረት ደንብ ቁጥር 157/2001 ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ የባንኩ ሠራተኞች በዚህ ልዩ ሕግ የሚተዳደሩና በአዋጅ ቁጥር 377/96 የማይተዳደሩ በመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2/ሠ/ መሠረት በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ያቋቋመው አመልካች ሕልውና ኖሮት ተግባሩን ሊያከናውን አይችልም ፡፡ አመልካች የአዋጅ ቁ/ 377/96 አንቀፅ 120ን በመጥቀስ ያቀረበው አቤቱታ ከተያዘው ክርክር ጋር አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 31 እና ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ድርጅት ስምምነቶች ቁጥር 87 እና ቁጥር 98ን በመጥቀስ ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በልዩ ሕግ የሚተዳደሩ እንደ ፖሊስ ዐቃቢያነ ሕግ ዳኞች የመንግስት ሠራተኞች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የተደራጀ ማሕበር እንደማይኖራቸው ሁሉ አመልካች የተለየ የሚሆንበት ምክንያት የሌለ በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያስናብተን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ በሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች እንዲፈርስ ተጠሪ ያቀረበው ጥያቄና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው ጭብጥ መመርመር ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 31 ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ የመደራጀት መብት እንዳለው የተደነገገ መሆኑን ገልፆ በተጠሪ የተመዘገበውን የምስክር ወረቀት የተሠጠው የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ማሕበር የሚፈርስበት ሕጎዊ ምክንያት የለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች በሕገመንግስቱ አንቀፅ 31 እና ሌሎች የሕግ ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ እንደተቋቋሙት ሌሎች የሙያ ማሕበራት የሚቆጠር ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

የሠራተኛ ማህበር የማቋቋም መብት በህገመንግስቱ አንቀፅ 31 ከተደነገገው በተለየ ሁኔታ በህገመንግስቱ አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች ገበሬዎች የእርሻ ሠራተኞች ሌሎች የገጠር ሠራተኞች ከተወሰነ ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግስት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚውን ሁኔታ ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው ይህ መብት የሠራተኛ ማሕበራትን ሌሎች ማሕበራትን በማደራጀት ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብት ያካትታል በማለት ይደነግጋል፡፡ በህገመንግስቱ አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚቋቋም የሠራተኛ ማህበር በህገመንግስቱ አንቀፅ 31 እና በሌሎች የህግ ማዕቀፎች ከሚቋቋሙ ማህበራት በአደረጃጀቱ በዓላማውና በተግባሩ የሚለይበት ሁኔታ እንዳለ በህገመንግስቱ አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ 1/ለ/ እና በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 42 የንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሠራተኛ ማሕበር የሚመዘገበበትና የምስክር ወረቀት የሚያገኝበት መንገድ ሌሎች ማሕበራት ከሚመዘገቡበትና ዕውቅና ከሚያገኙበት የተለየ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 118 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ "የሠራተኛ ማህበር" በህገ መንግስቱ አንቀጽ 42 መሠረት የመመሥረት መብት ያላቸው "ሠራተኞች" ሲሆኑ ማንኛውም ሰው ዓላማውን እደግፋለሁ በሚል ምክንያት የአንድ ሠራተኛ መሕበር አባል መሆን አይችልም ፡፡ የሠራተኛ ማሕበር የመመስረት የሠራተኛ ማሕበር አባል መሆንና የመሣተፍ መብት ያላቸው "ሠራተኞች" ብቻ መሆናቸውን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 113 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የሠራተኛ ማሕበር ማለት ሠራተኞች በአንድነት ሆነው የሚያቋቁሙት ማህበር እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 113 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ ተደንግጓል፡፡

"ሠራተኛ ' ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 በተመለከተው መሠረት ከአሠሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው በማለት አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 2/4/ ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም በአንድ ተቋም ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች የሠራተኛ ማህበር ለማቋቋም የሚችሉት ወይም ቀደም ሲል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አቋቁመውት የነበረው ማህበር ህጋዊ ህልውና ኖሮት በሠራተኛ ማህበርነቱ ሊቀጥል የሚችለው የተቋመ ሠራተኞችና የማህበሩ አባላት በአዋጅ ቁጥር 377/96 እና በህገመንግስቱ አንቀጽ 42 መሠረት የሠራተኛ ማህበር የማደራጀት መብት ያላቸውና "ሠራተኛ ' የሚለውን ትርጓሜ የሚያሟሉ ሁነው ሲገኙ እንደሆነ ከላይ በዝርዝር ከገለፅናቸው ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ተቋቁሞ በተጠሪ ተመዝግቦና የምስክር ወረቀት ተሰጥቶት የተደረጀና ሕጋዊ ህልውናውን ይዞ የሚቆይ የሠራተኛ ማህበር ከሌሎች ማህበሮች የተለየና "ሠራተኞች'ን ብቻ በአባልነት የያዘ መሆን እንደሚገባው ስለ ሠራተኛ ማህበር አመሠራረት በሚደነግገው አንቀፅ 114፣ ስለሠራተኛ ማሕበር ተግባር ከሚደነግገው አንቀፅ 115 ስለ ማሕበራት ምዝገባና ሕጋዊ ሕልውና ከሚደነግገው አንቀፅ 118 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የሠራተኛ ማሕበር የመመስረት መብት በአዋጅ ቁጥር 377/96 "ሠራተኛ ' የሚለውን ትርጉም የሚያሟሉ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚተዳደሩ ሠራተኞች መብት ብቻ መሆኑን ከሕገመንግስቱ አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ 3 እና ከአሥሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ዝርዝር ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካች አባላቱ በአዋጅ ቁ. 377/96 በሚተዳደሩበት ጊዜና ከዚህ የሕግ ማዕቀፍ በፊት በነበረው አዋጅ ቁጥር 42/68 መሠረት ተደራጅቶ የነበረ መሆኑ ክርክሩ ለመገንዘብ ችለናል፡፡በአዋጅ ቁጥር 42/1968 እና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አባላቱ "ሠራተኛ" የሚለውን የሕግ ትርጓሜን በሚያሟሉበት ወቅት የተደራጀ የሠራተኛ ማሕበር ተቋመ የሚተዳደርበት የሕግ ማዕቀፍ ከተቀየረና አባላቱ "ሠራተኛ" የሚለውን የሕግ ትርጉም የማያሟሉበት ሁኔታ ከተፈጠረ "በሠራተኛ ማህበርነቱ' ተሰጥቶት የነበረው ምዝገባና እውቅና እንዲሁም የምስክር ወረቀት ለሚመለከተው ክፍል እንዲመልስ ተጠሪን ከመጠየቅ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 120 ድንጋጌዎች የሚከለክል አይደሉም፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 120 በባህሪው የአመልካች ክርክር (Indicative) የህግ ድንጋጌ እንጂ “Exhaustive” አሳሪ ወይም አሚጣጭ የህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡

ስለሆነም አባላቱ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ጥር 377/96 በሚተዳደሩበትና ሠራተኛ የሚለውን ትርጓሜ በሚያሟሉበት ወቅት በሠራተኛ ማህበርነት ተመዝግቦና ከተጠሪ የምስክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወረቀት ወስዶ በህገመንግስቱ አንቀፅ 42 እና በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አንቀጽ 115 የተመለከቱትን ተግባራት ሲፈፅም የቆየው አመልካች የተቋሙ ሠራተኞች በደንብ ቁጥር 157/2001 መተዳደር ከጀመሩበትና "ሠራተኞች' የሚለውን ትርጓሜ የሚያሟሉ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(ሠ) ከተዘረዘሩት መካከል የሚመደቡ በመሆናቸው ከተጠሪ የተደረገለትን ምዝገባና የምስክር ወረቀት ይዞ በሠራተኛ ማሕበርነት የሚቀጥልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካችን በአዋጅ ቁጥር377/96 በአንቀጽ 118 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በመመዝገብ የሰጠው የምስክር ወረቀት እንዲሠረዝለት ማመልከቱ ተገቢና ሕጋዊ መሠረት ያለው ሲሆን የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የተጠሪን ጥያቄ በመቀበል የሰጠው ውሣኔ የህገመንግስቱን አንቀፅ 42 ድንጋጌዎችና በአዋጅ ቁጥር 377/96 ከላይ የተገለፁትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59666

ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ሠላማዊት ኃይሉ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አቡ ጉበና ከጠበቃቸው ከአቶ ተካልኝ ነጋሣ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በአሁኑ የሰበር ተጠሪ አቅራቢነት ለሥር ወረዳ ፍ/ቤት ነሐሴ 27 ቀን 1999 ዓ/ም የቀረበው ክስ በተከሣሽ /በአሁኑ አመልካች / መ/ቤት ከ1989 እስከ የካቲት 1999 ዓ/ም በተለያዩ የሥራ መደቦች በወር ብር 2110 ደመወዝ እየተከፈለኝ ከቆየሁ በኋላ ተከሣሹ ከሥራ ሲያስናበተኝ የአገልግሎት ካሣ እና የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ ብር 13,187.50 ካሰበልኝ በኋላ ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ ታክስ ብር 2,203.87 ከቀነሠ በኋላ በሥልጣኑ ለት/ቤት የከፈልኩት ነው በማለት ብር 6,792.57 ቆርጦብኝ ብር 4,191.04 ብቻ ከፍሎኛል፡፡ የከፈለኝን ገንዘብም ቢሆን መክፈል ከሚገባው ጊዜ 2 ወር በማዘግየት የሚያዝያ ወር 1999 በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 337/96 በአንቀጽ 36 በተደነገገው መሠረት በ7 ቀን ውስጥ አልከፈለም፡፡ የት/ቤት ክፍያም ቢሆን በህብረት ስምምነታችን አንቀጽ 25 ከ12ኛ ክፍል በላይ ለሆነ ትምህርት የት/ቤት ክፍያ ተከሣሽ መ/ቤት 50% እንደሚከፍል ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ተከሣሽ መ/ቤት ያለ አግባብ የቆረጠብኝ ገንዘብና ክፍያ ባዘገየበት የ3 ወር ደመወዜን እንዲከፍለኝ ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሳሹም በነገረ ፈጁ አማካይነት በሰጠው መልስ ከሳሽ ለ11 ዓመት አገልግያለሁ የሚለው ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ከሣሽ ከመስከረም 1 ቀን 1989 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1992 ድረስ የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ሰራተኛ ነበር፡፡ የመንግስት ሠራተኛ ከሆነ ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 ጥቅማጥቅም ማግኘት አይችልም፡፡ ከሣሽ በተከሳሽ መ/ቤት የተቀጠረው ከሐምሌ 1 ቀን 1992 ጀምሮ ስለሆነ የአገልግሎት ካሣ ማግኘት ያለበት ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከሣሽ በየጊዜው የትምህርት ቤት ክፍያ እየጠየቀ ተከሳሽ መ/ቤት ሲከፍል የቆየ በመሆኑ በመካከላችን ውል የለም ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/ለ/ ሥር የተጠቀሰውን ግዴታ አልተወጣም በማለት የከሣሽ ክስ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ወረዳ ፍ/ቤትም ዕዳን አንድ ሠራተኛ ከሚያገኘው የአገልግሎት ካሣ ማቻቻል አይቻልም። ተከሣሽ አለኝ የሚለው መብት ካለ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት መጠየቅ እንጂ ከደመወዙ ጋር ተያይዞ የሚገኝ ነገር ላይ ማቻቻያ ሊደረግ አይገባም። ይህ ሆኖ ሣለ ተከሣሽ ከከሣሽ ደመወዝ መቁረጡ በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 1833 /11/ የተደነገገውን የሚፃረር ነው በማለት ተከሣሽ ከከሣሽ የቆረጠውን ገንዘብ ብር 6,792.57 ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝና ኪሣራ ብር 500 እንዲሁም የጠበቃ አበል 10% እንዲከፍል ወስኗል።

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ይግባኝ ባይ /የሥር ተከሣሽ/ የ11 ዓመት የአገልግሎት ካሣ ለመልስ ሰጪው ከከፈለ በኋላ የ11 ዓመት አገልግሎት በተከሣሽ መ/ቤት የለውም ሲል የተከራከረው ያለአግባብ ነው፤ ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪውን ያስተማረ ቢሆንም ምን ያህል እንደሚያገለግል የተማረው መቼ እንደሆነና ግዴታውን ተወጥቷል የሚባለው መቼ ነው የሚሉትን ነጥቦች ያላስረዳ በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ የሚነቀፍ ነገር የለም በሚል ውሣኔውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348/1/ መሠረት አጽንቷል።

የአሁኑ የሰበር አመልካች ለሥር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲል በማመልከቱ የሥር ሰበር ሰሚው ችሎትም የግራቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ ከአገልግሎት ካሣ ክፍያ ውስጥ ለትምህርት የተከፈለውን በሚመለከት ተመላሽ የሚደረግ ስለመሆኑ ውል መኖር አለበት። ውል በሌለበት አስተማርኩ በሚል ብቻ ከአገልግሎት ካሣ ቆርጦ ማስቀረት ተቀባይነት የለውም። ክፍያ ለዘገየበት አመልካች ያመነውን ከፍሎ ያላመነውን ያልከፈለ ስለሆነ በክፉ ሀሳብ ተጠሪን ለመጉዳት አዘግይቷል ለማለት አይቻልም በማለት አመልካች ለተጠሪ የ3 ወር ደመወዝ መክፈል የለበትም ሲል የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በማሻሻል ወስኗል።

በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር የተሰኘው የሰበር አመልካችም ለዚህ ችሎት ባቀረበው ቅሬታ ተጠሪው ከመስከረም 01 ቀን 1989 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ወር 1992 ዓ/ም ድረስ በአመልካች መ/ቤት ያገለገለው በአሠሪና ሠራተኛ ህግ መሠረት ሳይሆን በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ በመሆኑ የሶስት ዓመት ከአሥር ወር የአገልግሎት ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ሊከፈለው አይገባም። ተጠሪው ሥራውን በገዛ ፈቃዱ የለቀቀው የ2ኛ ዲግሪውን ትምህርት መንግስት እየከፈለ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ የሚፈለግበትን አገልግሎት ሳይፈጽም በመሆኑ በተሻሻለው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ መሠረትና አንቀጽ 39/ሸ/ የውል ግዴታ ስላለበት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ የለም፣ ገንዘቡም ለመንግስት ተቆርጦ ገቢ መደረጉ ተገቢ ነው። ምንም ዓይነት ስምምነት ከአመልካች ጋር የለኝም በሚል ያቀረበው ክርክርም ቢሆን የህብረት ስምምነት አንቀጽ 26 በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ ባለመፈረሙ ብቻ ግዴታውን የሚያስቀርለት አይሆንም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ እስከአሻሽለው ድረስ የጠበቃ አበል 10% እና ኪሣራ ብር 500 አሻሽሎ መወሰን አሊያም መሠረዝ ይገባው ነበር በማለት ከመስከረም 1 ቀን 1989 - ሰኔ 30 ቀን 1992 ያለው የ3 ዓመት ከ10 ወር የአገልግሎት ካሣ አመልካች ለተጠሪው ይከፍላል የተባለው እንዲሠረዝ አመልካች ከተጠሪው የአገልግሎት ካሣ ውስጥ ለትመህርት የከፈለውን ቆርጦ ማስቀረቱ ያለአግባብ ነው የተባለው ተሽሮ ገንዘቡ ለአመልካች ገቢ እንዲሆን እንዲወሰን፣ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነበት የጠበቃ አበልና ኪሣራ እንዲሠረዝ ጠይቋል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ላቀረበው የሰበር ቅሬታ ተጠሪው በሰጠው መልስ ከመስከረም ወር 1989 ዓ/ም ጀምሮ ያለውን የአገልግሎት ካሣ አስቦ የከፈለኝ ራሱ የአሁኑ አመልካች ስለሆነ ተጠሪ ክስ ከመሠረትኩበት በኋላ የአገልግሎት ካሣው የተከፈለው በስህተት ነው ብልም ከመስከረም 01 ቀን 1989 ዓ/ም ጀምሮ ሠራተኛ ስለመሆኔ በሥር ፍ/ቤት በቀረበው የዕሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የህብረት ስምምነት አንቀጽ 26/2/ ከትምህርትና ሥልጠና ጋር በተያያዘ የውል ግዴታ መግባት እንደሚያስፈልግ ይናገራል፡፡ ተጠሪም የውል ግዴታ ገብቼ የፈረምኩት ሠነድ የለም፡፡ አመልካችም በማስረጃነት ያቀረበው ሠነድ የለም፡፡ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 39/1/ሸ/ ከሥልጠና ጋር በተያያዘ ለአሠሪው የውል ግዴታ ሳይኖርበት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ሠራተኛው ሲለቅ የአገልግሎት ካሣ እንደሚከፈለው ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም የሰበር ተጠሪ ከአሠሪው መ/ቤት ጋር የገባሁት የትምህርት ውል ስለሌለ የአገልግሎት ካሣ ከማግኘት የሚከለክለኝ ነገር የለም፡፡ ስለሆነም በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የቀረበ ሲሆን እኛም በሥር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ለተጠሪ ሊከፈለው ይገባል በሚል በተወሰነው ገንዘብ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚለው በአገልግሎት ካሣ፣ በጠበቃ አበል እና በኪሣራ ገንዘብ አከፋፈል ነው፡፡

የአገልግሎት ካሣን በሚመለከት ግራ ቀኙን የሚያከራክራቸው ጠቅላላ የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠርና የአግልግሎት ካሣ ለተጠሪው ይገባል በማለት አመልካች ከወሰነው ገንዘብ ውስጥ አመልካች ለተጠሪው የትምህርት ቤት ክፍያ ፈጽሜአለሁ በማለት የቀነሰው ገንዘብ ነው፡፡

ተጠሪው ከመስከረም 1989 እስከ የካቲት 1999 ዓ/ም ለአሥራ አንድ ዓመት በአመልካች መ/ቤት ማገልገሉን በመጥቀስ ሲከራከር አመልካች ግን ተጠሪው ከ1989 መስከረም ወር ጀምሮ እስከ 1992 ሰኔ ወር ድረስ ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 377/96 የማይተዳደርና የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ሠራተኛ ነበር በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ የተነሣም የ3 ዓመት ከ 10 ወር የአገልግሎት ካሣ አይገባውም ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች መ/ቤት ቀደም ሲል በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ የሚተዳደር የነበረና ከዚያም በአዋጅ ቁ. 377/96 ማለትም ስለ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በወጣው አዋጅ እንዲተዳደር መደረጉን ነው፡፡ ተጠሪም ቢሆን ቀደም ሲል በአመልካች መ/ቤት የመንግስት ሠራተኛ የነበረ ሲሆን አመልካች መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/96 እንዲተዳደር ሲደረግ ተጠሪውም በተመሳሳይ ሁኔታ በተጠቀሰው አዋጅ የሠራተኛን ትርጉም በማሟላት በአመልካች መ/ቤት ሲሠራ ቆይቷል፡፡ አመልካች መ/ቤትም ተጠሪው ለ11 ዓመት ያህል በአመልካች መ/ቤት ማገልገሉን በማመን የ11 ዓመት የአገልግሉት ካሣ በማስላት አጠቃላይ የሚከፈለው የአገልግሎት ካሣ መጠን ከታወቀ በኋላ ለትምህርት ቤት የከፈለውን በመቀነሥ ለራሱ አስቀርቷል፡፡ ይሁን እንጂ አሠሪው ማለትም ያሁን አመልካች የተጠሪው የአገልግሎት ዘመን 11 ዓመት መሆኑን ተቀብሎ ምን ያህል የካሣ መጠን እንደሚከፈለው ካረጋገጠ በኋላ በፍ/ቤት በተጠሪ ከሳሽነት ክስ ሲቀርብ የተጠሪውን ቀደም ሲል የመንግስት ሠራተኛ ነበር በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የአገልግሎት ካሣ ማግኘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለበት ከሐምሌ 1992 ጀምሮ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ህጋዊ ውጤት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪን የአገልግሎት ዘመን በሁለት በመክፈል ካሣ ሊከፈለው የሚገባ ው በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 መተዳደር ከጀመረበት ጊዜ ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍ/ቤት ያልተቀበለው በአግባቡ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪው 11 ዓመት አገልግሎት አለው ተብሎ በዚሁ መጠን የ11 ዓመት የአገልግሎት ካሣ ሊከፈለው አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍ/ቤት ውድቅ በማድረጉ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ከዚህ ከካሣ አከፋፈል ጋር ተያይዞ የሚነሣው አመልካች ለተጠሪው የሚገባውን የካሣ መጠን በስሌት ካረጋገጠ በኋላ የተጠሪው 2ኛ ዲግሪ ሲማር አመልካች የት/ቤት ክፍያ ከፍሏል በማለት ብር 6,792.57 ከካሣው ገንዘብ መቁረጡ ነው፡፡፡ አመልካች ለት/ቤት የከፈለውን ገንዘብ የቀነሠው ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በአመልካች መ/ቤት ማገልገል ሲገባው ግዴታውን አልተወጣም፡፡ ስለሆነም አመልካች ለት/ቤት ያወጣውን ወጪ ከተጠሪው ለመቀበል በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ሸ/ መሠረት መብት አለው ምክንያቱም በአመልካችና ተጠሪ መካከል የውል ግዴታ አለ የሚል ነው፡፡ የውል ግዴታውም ሊመሠረት የቻለው ተጠሪው የትምህርት ቤት ክፍያ እንዲከፍልለት በየጊዜው እየጠየቀ አመልካችም ይከፍልለት ነበር በማለት ነው፡፡ ሆኖም ከአመልካች አለ የሚለውን የውል ግዴታ ተጠሪው የፈረምኩት ሠነድ የለም በማለት ይከራከራል፡፡

እዚህ ላይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የትምህርት ቤት ክፍያን በሚመለከት ውል አለ ወይስ የለም? የሚለውን ነጥብ ሳይሆን አመልካች ለተጠሪው ከሚገባው የአገልግሎት ካሣ የትምህርት ቤት ክፍያ ቆርጦ ማስቀረት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ነጥብ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ እንደተገለፀው አመልካችና ተጠሪ የሚተዳደሩት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ሲሆን የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች በአዋጁ የተቀመጡትን መብትና ግዴታ ማክበር ይጠበቅባቸዋል ፡፡ በአዋጁ ከተጠቀሱት መብቶች አንዱ የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኛው ደመወዙንና ከደመወዙ ጋር የተያያዙትን ክፍያዎችን በህጉ በተወሠነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መክፈል ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ክፍያው አከራካሪ ሆኖ ከተገኘ የሕጉን አካሄድ መከተል የግድ ይላል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ የመንግስት ግብር ተቀንሶ ተጠሪው የአገልግሎት ካሣ ማግኘት ያለበት ብር 10,983.63 መሆኑን ሲገልጽ ይኸንኑ የገንዘብ መጠን አመልካችም ትክክል መሆኑን ያምናል፡፡ ይሁን እንጂ የት/ቤት ክፍያ ብር 6,792.57 መቀነሱ አግባብ ነው ይላል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 የደመወዝ ቅነሣን በሚመለከት በአንቀጽ 59 የተደነገገ ሲሆን ይኸው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ደመወዝ የሚቀነሰው በህግ በህብረት ስምምነት ወይም በሥራ ደንብ በተወሰነው ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ መሠረት ካልሆነ ወይም ሠራተኛው በጽሁፍ ካልተስማማ አሠሪው ከሠራተኛው መቀነሥ እንደማይችል ወይም በዕዳ ሊይዝ ወይም ሊያቻችል እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ የአገልግሎት ካሣም ቢሆን ለዕዳ የሚያዝ ወይም የሚቀነሥ ከሆነም በተጠቀሰው የህግ አንቀጽ መሠረት መቀነስ ወይም ሊያዝ ከሚችል ውጪ አሠሪ በራሱ ውሣኔ ሊቀንስ ሊይዝ ወይም ለዕዳ እንዲቻቻል ማድረግ አይችልም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የሰበር አመልካች ቆርጦ ያስቀረው የአገልግሎት ካሣ ገንዘብ ለተጠሪ እንዲመልስ በሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌላው አመልካች እንደመሠረታዊ የህግ ስህተት የጠቀሰው የጠበቃ አበል 10% አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ተጠሪው ክርክር ያካሄደው በግሉ ስለመሆኑ አልተከራከረም፡፡ ነገር ግን 10% ለጠበቃው አበል መወሰኑ አለአግባብ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ጠበቃው ሙያዊ አገልግሎት መስጠቱ እስካልተካደ ድረስ ደግሞ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 42 በተደነገገው መሠረት ተገቢና ሚዛናዊ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ተገቢና ሚዛናዊ ክፍያ ነው የሚባለው ደግሞ በተጠቀሰው የህግ ቁጥር ከንዑስ ቁጥር 1-8 የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች መሠረት በማድረግ የተወሰነ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ አመልካች ግን የሥር ፍ/ቤት 10% የጠበቃ አበል ሲወስን በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 42 ሥር የተዘረዘሩ መመዘኛዎች የተጣሱ ስለመሆናቸው ያቀረበው የህግ ክርክር የለም፡፡ ይህ ችሎትም የቀረበውን የጠበቃ አበል ቅሬታ ከተጠቀሰው ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 42 እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 462ና 463 ድንጋጌ ጋር እንዳገናዘበው በደንቡ የዘረዘሩት መመዘኛዎች የተጣሱ ስለመሆናቸው አመላካች የሚሆን ነገር አላገኘም፡፡ በመሆኑም በጠበቃ አበል አወሣሠን ላይ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የለም፡፡

አመልካች ያቀረበው ሌላው ክርክር የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በማሻሻል እስከወሰነ ድረስ የብር 500 /አምስት መቶ / ኪሣራ መቀነስ ወይም መሰረዝ ነበረበት የሚል ሲሆን ይህ ችሎት ተጠሪ በክርክር ወቅት ከብር 500(አምስት መቶ) ያላነሠ ኪሣራ እንደሚደርስበት ያምናል፡፡ የኪሣራው መጠን ከዚህ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ያንሣል ቢባል እንኳ የአመልካችን ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን በጎላ መልኩ የሚጉዳ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ አሻሽሎ በመወሠኑ ብቻ ኪሣራ መቀነሥ አለበት ወይም ሙሉ በሙሉ መሠረዝ አለበት ለማለት ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም ፡፡ በመሆኑም የሥር ሰበር ሰሚው ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔን አሻሽሎ ሲወስን ኪሣራውን ግን በማጽናቱ የተጣሰ ህግ የለም፡፡ ስለሆነም በኪሣራ አወሣሠን ረገድም የሥር ፍ/ቤት የፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 90368 በቀን 14/10/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፣ በውሳኔው የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ተብሏል፡፡
2. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ፡፡
3. ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን ፡፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 1 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - አንበሴ መኮንን /ነገረ ፈጅ/ ቀረበ

ተጠሪ፡- አያሌው ሕብስት ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሣውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ሚያዝያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋለው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ መሠረት በተደረገው ምደባ ከደረጃ 11 ወደ ደረጃ 14 አድጌ እንድሠራ የተደረገ ቢሆንም ለቦታው የተመደበው ደመወዝ ግን አልተከፈለኝም በማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ያለአግባብ ሳይከፈለኝ ቀርቶአል የሚለውን የሁለት እርከን ጭማሪ ምደባው ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ታስቦ እንዲከፍለው ይወሰንለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የሥረ ነገር ክርክር አቅርቦአል፡፡ በሥረ ነገር ረገድ ያቀረበው ክርክር ከሣሽ ደረጃውን ያገኘው በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ አጠቃላይ ምደባ እንጂ በእድገት አይደለም፡፡ እድገት የሚሰጠው ወይም የሚገኘው በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 11 መሠረት ነው፡፡ በዚህ አግባብ የተሰጠ የደረጃ እድገት ስለሌለ ክሱ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም የሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ የአመልካችን ክርክር በመቀበል የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ በመሻር ተጠሪ የጠየቀው የሁለት እርከን የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠው በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጠሪ የጠየቀው የሁለት እርከን የደመወዝ ጭማሪ የሕግ መሠረት ያለው ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጭብጥ ግራቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና የተሰጡትን ውሳኔዎች በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የቻልነው ተጠሪ ተመድቤበታለሁ የሚለው በደረጃ 14 የሚታወቀው (የተሰየመው) የሥራ መደብ በኮርፖሬሽኑ (አመልካች) ባለው የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት እና ሂደት መሠረት የተገኘ አለመሆኑ በፍሬ ነገር መረጋገጡን ነው፡፡ በእርግጥ ኮርፖሬሽኑ አጠቃላይ የሆነ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በማካሄድ ከሥራ ሂደት ለውጡ መካሄድ በፊት የነበረው አደረጃጀትና የሥራ መደቦች ስያሜ ተለውጠዋል፡፡ ይህ ደግሞ የኮርፖሬሽኑ የሥራ አደረጃጀትን በተመለከተ የተደረገ አጠቃላይ ለውጥ እንጂ ሠራተኞችን ለማሳደግ (በእድገት ለማስቀመጥ) በሚል የተደረገ ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ በግልጽ እንደሚታወቀው የደረጃ እድገት ሊገኝ የሚችለው እራሱን በቻለ የአሠራር ሥርዓት እና ደንብ መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ማካሄድ እና የደረጃ እድገት መሰጠት ወይም አሰጣጥ በዓላማም ሆነ በውጤት ረገድ የተለየዩ የየራሳቸውን ግብ ይዘው የሚነሱ እንደሆኑ መገንዘቡ ተገቢ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው በአመልካች ኮርፖሬሽን የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት እና ደንብ መሠረት ተጠሪ የደረጃ እድገት አግኝቶአል አልተባለም፡፡ የደመወዝ ጭማሪ ሊገኝ የሚችለው በእድገት ወይም አሠሪው የደመወዝ ጭማሪ ማድረግ የሚችልበት አግባብ ኖሮት ሲጨምር ነው፡፡ ተጠሪ የጠየቀው የሁለት እርከን የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኝ በፍ/ቤት ሊወሰን የሚችለውም ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሁለት እርከን ደመወዝ ጭማሪ ሊያሰጥ የሚችል የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር መሠረት አልነበረውም፡፡ ሲጠቃለል ተጠሪ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 95369 ጥር 12 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበው የሁለት እርከን የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠኝ ጥያቄ የሕግ መሠረት የለውም ብለናል፡፡ በዚህ መሠረትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 33360 ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቶአል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ፖሊስ አግልግሎት ድርጅት ነ/ፈጅ ማስረሻ በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ በዳሶ መልካቶ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ታይቶ የተወሰነውን ውሳኔ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዳማ ቱሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በዚሁ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የፍርድ ይፈፀምልኝ ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 07667 ላይ ቀርቦ የተወሰነውን ውሳኔ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በዋናው ጉዳይ ላይ የአሁኑ ተጠሪ የስራ ውላቸው ያላግባብ የተቋረጠባቸው መሆኑን በመግለጽ ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም ተገቢ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የአሁኑ አመልካች የአሁኑን ተጠሪን ወደ ስራ እንዲመለስ ወይም ተገቢ ክፍያዎችን እንዲከፍል ሲል ተወስኗል፡፡ እንዲፈፀም የቀረበው ውሳኔውም ይህ ሲሆን ዋናውን ፍርድ ተጠሪ ከአገኙና ከመፈፀሙ በፊት ግን ተጠሪ የመንግስት ገንዘብ አጉድለው ተገኝተዋል በሚል ምክንያት በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሰው ጥፋጽ በመፈጸሙ ጥፋተኝነታቸውም በፍርድ ተረጋግጦ በአንድ አመት ጽኑ እስራት እና በብር 1000.00(አንድ ሺህ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ተወስኖባቸዋል፡፡ ይህንኑ ቅጣት ጨርሰው ከወጡ በኋዋላ በአስሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ እንዲፈጸምላቸው የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርቡም የአሁኑ አመልካች ተጠሪ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው ተረጋጋጦባቸው ቅጣቱን ጨርሰው ከወጡ በሁላ ሊፈጸምላቸው የሚገባ ፍርድ የለም በማለት እንደ ፍርዱ የማይፈጽምበትን ምክንያት ቀርቦ አስረድቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ፍርዱ የማይፈፀምበት ምክንያት የለም በማለት ተጠሪን አመልካች ወደስራው እንዲመልሰው ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትእዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 377 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ መጋቢት 01 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ትእዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ በእምነት ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ተገቢው ቅጣት ተላልፎ ቅጣቱን ጨርሰው ከወጡ በሁዋላ ቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ወደ ስራ የሚመለሱበት ምክንያት የለም በማለት ዘርዝረው ትእዛዙ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የፍርድ አፈፃፀም ሂደቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ስር የተመለከተውን ከፍተኛ የይርጋ ጊዜ መሰረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓአል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮላቸው ተጠሪ ቀርበው በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ፍርድ ባልተለወጠበት ሁኔታ ፍርድ ሊፈጽም አይችልም ሊባል የሚችልበት ምክንያት የሌለ መሆኑንና አመልካች ከፈለገ በአማራጭ የተለያዩ ክፍያዎችን በመክፈል ሊያሰናብታቸው የሚገባ መሆኑን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ሲሉ ግንቦት 23 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ ማመልከቻ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነገር ፈጅም ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት የመልስ መልስ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የመንግስት ገንዘብ አጉድለው በመገኘታቸው በወንጀል ተፈርዶባቸው የእስራት ጊዜውን አጠናቅቀው ከወጡ ከአንድ አመት በሁዋላ በአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ችሎት ቀደም ብሎ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም አቤቱታ አቅርበው የስር ፍርድ ቤት ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚከለክለው ነገር የለም በሚል ምክንያት አመልካች ተጠሪን ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ትእዛዝ መስጠቱን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍርድ ስልጣን ባለው አካል እስካልተሻረ እና በሕጉ የተመለከተውን የይርጋ ጊዜ መሰረት አድርጐ ለአፈፃፀም እስከቀረበ ድረስ እንዲሁም የማይፈፀምበት ሌላ ሕጋዊ ምክንያት እስከሌለ ድረስ የማይፈፀምበት ምክንያት የሌለ መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉም ሆነ በሌሎች ተፈፃሚነት ባላቸው ሕጐች የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡ አፈፃፀሙ የሚመራበት ሁኔታም እንደጉዳዩ አግባብነት መታየት ያለበት ስለመሆኑ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ልዩ ሕግ ካለ ተፈፃሚነት የሚኖረው ይኸው ልዩ ሕግ ነው፡፡ ጠቅላላ ሕግ ተፈፃሚነት የሚኖረው ጉዳዩን የሚገዛው ልዩ ሕግ በሌለበት ሁኔታ ስለመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጐም መርሆዎች የሚሳዩት ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ጉዳዩ መሰረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 377/96 “ን” ሲሆን ይህ ሕግ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የሚነሳን ክርክር የሚገዛ ነው፡፡ በዚህ ሕግ ውስጥ የተለያዩ የመብት ጥያቄዎች የሚቀርቡበት የዳኝነት አካልና የመብት ጥያቄዎች የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ ተመልክቷል፡፡ ሕጉ ግልጽ የሆነ የይርጋ ጊዜ ያልተቀመጠለት እና ምንጩ የአሰሪና ሰራተኛ የሆነ ማናቸውም የመብት ጥያቄ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እስካልቀረበ ድረስ የማይስተናገድ ስለመሆኑ በአንቀጽ 162 ስር አስቀምጧል፡፡ አዋጁ በግልጽ ላልተመለከቱ ጉዳዮች ከፍተኛውን የይርጋ ዘመን በተመለከተ አንድ አመት ስለመሆኑ ከማስቀመጡም በተጨማሪ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጐች ስር የተመለከቱት የይርጋ ጊዜያት ተፈፃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በአንቀጽ 162/5/ ድንጋጌ ስር አስፍሯል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ለሚቀርቡ ክርክሮች አግባብነት ካላቸው ሕጐች መካከል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንዱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ነው፡፡ ይህ ስነ ሥርአት ከያዛቸውና ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንዱ ደግሞ በቁጥር 384 ስር የተመለከተው የአፈፃፀም ይርጋ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ፍርድ ለአፈፃፀም ሊቀርብ የሚገባው በአስር አመት ጊዜ ውስጥ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ አንድ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክር ሰሚ አካል የተሰጠ ውሳኔ ለአፈፃፀም ሊቀርብ የሚገባው ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ በስንት ጊዜ ውስጥ ነው የሚለው? ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 በዚህ ረገድ ያስቀመጠው ግልጽ ድንጋጌ የለም፡፡ ሆኖም ግን አዋጁ በግልጽ ባያስቀምጥም ተገቢውን የሕግ ትርጉም መስጠት የግድ የሚል ነው፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ተገቢውን የሕግ አተረጓጎም መንገዶችን መከተል አግባብነት ይኖረዋል፡፡ ሕግ ሲተረጐምም ሕጉ ሊፈፀም የሚችል ውጤት እንዲኖረው በማድረግ ስለመሆኑም ጠቅላላ የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የግድ የሚሉት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ አይነተኛ ዓላማ ሲታይ የኢንዱስትሪ ሰላምን በማስፈን አጠቃላይ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለአገር ኢኮኖሚ አዎንታዊ ሚና መጫወት ስለመሆኑ በአዋጁ መግቢያ ላይ የተገለፀ ጉዳይ ነው፡፡ የሕጉ አይነተኛ አላማ ይህ ከሆነ ደግሞ በአዋጁ የተካተቱት ድንጋጌዎች ሊተረጐሙና ሊፈፀሙ የሚገባው ይህንኑ የሕጉን አላማ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰራተኛ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕጉ ስር በተመለከተው የአስር አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ የአፈፃፀም መዝገብ ማስከፈት ይችላል ከተባለ አዋጅ ቁጥር 377/96 ሊያሳካ ያሰበውን ግብ ችግር ውስጥ የሚከተለው ይሆናል፡፡ ሰራተኛው በጊዜውና በቦታው ተገኝቶ ስራውን ካልሰራ አሰሪው ምርትና ምርታማነትን ያሳድጋል ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት የሚኖረው በአዋጅ ቁጥር 377/96 ስር የተመለከተው ከፍተኛው የአንድ አመት የይርጋ ጊዜ ለአፈፃፀም ማመልከቻም ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረጉ የአዋጁ አላማ ግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ አፈፃፀም የሚቀርብለት ፍርድ ቤትም የፍርድ ይፈጸምልኝ ጥያቄው በዚህ ጊዜ ውስጥ የቀረበ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ የፍርድ ይፈጽምልኝ ጥያቄውን በአንድ ጊዜ ውስጥ ያለማቅረባቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይርጋውን ለማቋረጥ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የነበራቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ ሁኔታም የለም፡፡ በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 377/96 ከአንድ አመት በላይ የረዘመ ክርክርን የማያስተናግድ ሁኖ እያለ ተጠሪ ይህንኑ ጊዜ ያሳለፈ ፍርድ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱ የአዋጅ ቁጥር 377/96 “ን” አይነተኛ አላማና በዚሁ አዋጅ መሰረት የተወሰኑት ውሳኔዎች የፈጸሙበትን አግባብ ያላገናዘበ በመሆኑ አመልካች ተጠሪን ወደ ስራ እንዲመልሳቸው የተሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዳማ ቱሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0925 ጥር 03 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 23879 የካቲት 18 ቀን 2002 ዓ.ም የጸናው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት የአፈፃፀም ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/1/ መሰረት በአንድ አመት ይርጋ የታገደ ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች ተጠሪን ወደ ስራ እንዲመልስ ወይም በአማራጭ የተለያዩ ክፍያዎች ከፍሎ እንዲያሰናብት አይገደድም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት *10* ቀን *2003* ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

አመልካች፣ የኢትዮጵያ ፕልፕና ወረቀት አ/ማ ታፈሰ አበበ ቀረበ

ተጠሪ፣ ዓብዱልቃድር አደም ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በአመልካች ፋብሪካ ለ38 /ሰላሳ ስምንት/ ዓመት ካገለገልኩ በኃላ ለጡረታ አራት /4/ ዓመት ሲቀረኝ በራሴ ፍላጎት ሥራውን የለቀቅሁ በመሆኑ የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ነው አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ ሊሟላ የሚገባው ሁሉ ተሟልቶለት ጡረታ የወጣ በመሆኑ የስንብት ክፍያ ሊከፈለው አይገባም፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ አይፈቅድለትም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኃላ ፍ/ቤት ክርክሩን የመረመረ ሲሆን በመቀጠልም የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ተጠሪ የሥራ ስንብት ይከፈለው በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ ከተሰማ በኃላ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ በመጨረሻው የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት አይደለም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈለው በማለት የተሰጠው ውሣኔ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ 377/96ን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ 494/98 በአንቀጽ 2 ከተመለከተው ድንጋጌ አንፃር ሊመረመር የሚገባው ነው በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ በራሱ ፍላጎት የሥራ ውሉን ያቋረጠው /ከሥራ የተሰናበተው/ 38 /ሰላሳ ስምንት/ ዓመት ካገለገለ በኃላ እንዲሁም ዕድሜው 60 /ስድሳ/ ዓመት ሊሞላ 4 /አራት/ ዓመት ሲቀረው እንደሆነ አላከራከረም የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፈለኝ ይገባል የሚለው በአርግጥም በአሁኑ ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጡረታ አበል አላገኝም /አይከፈለኝም/ በማለት ሳይሆን ሥራውን በራሴ ፍላጎት በመለቀቁ እና በሕጉ የተመለከተውን የመጨረሻ የጡረታ መውጫ ዕድሜ 60 ዓመት ስላልሞላኝ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት አለኝ በማለት እንደሆነም ከክርክሩ ይዘት ተገንዝበናል አመልካች ደግሞ ተጠሪ ሥራውን የለቀቀው /የተሰናበተው/ ሊሟላለት የሚገባው ሁሉ ተሟልቶለት በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የጡረታ አበል እየተከፈለው ነው፡፡ የጡረታ አበል የሚያገኝ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያም እንዲከፈለው ሕጉ አያዝም ይልቁንም ሁለቱ ክፍያዎች በአንድ ጊዜ እንዳይከፈሉ ሕጉ በግልፅ ይከለክላል በማለት ተከራክሮአል፡፡

እንደምንመለከተው አከራከሪው ጭብጥ የሕግ ነጥብ በመሆኑ ሊፈታ የሚችለው አግባብ ባለው የሕጉ ድንጋጌ ነው፡፡ ክርክሩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሳ በመሆኑም በቅድሚያ መታየት ያለበት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 ነው በዚህ አዋጅ ስለሥራ ስንብት ክፍያ በሚመለከት ተደንግጎ የሚገኘው በአንቀጽ 39 ሲሆን ይህ ድንጋጌ አዋጁን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ. 494/98 ተሻሽሎአል፡፡ በዚህ ማሻሻያ አዋጅ አንቀጽ 2/ሰ/ እና /ሸ/ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተጣምረው ሲታዩ አንድ ከሥራው የተሰናበተ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈለው በጡረታ ሕግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ላይ ደርሶ ከሥራው በሚገለልበት ጊዜ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለው ሲሆን ወይም ደግሞ ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ በሕመም ወይም በፈቃዱ ሲለቅ /ሥራው ላይ የሚያስቆይ ከሥልጠና ጋር የተያያዘ የውል ግዴታ ሳይኖርበት የለቀቀ ሲሆን/ እንደሆነ ነው በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ሥራውን የለቀቀው በገዛ ፈቃዱ ሲሆን እንደለቀቀም በጡረታ መብት ተጠቃሚ ሆኖአል፡፡ በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 13/3/ እንደተመለከተው ቢንያስ ሃያ አምስት ዓመት ያገለገለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ያልሆነ የመንግስት ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ አምስት ዓመት ከሚቀረው ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕድሜ ልኩ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፡፡ ተጠሪ ሥራውን በራሱ ፈቃድ የለቀቀው 60 ዓመት ሊሞላው 4 ዓመት ሲቀረው በመሆኑ በዚህ ሕግ መሠረት አበሉን እያገኘ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡

ከፍ ሲል በዝርዝር እንዳመለከትነው የጡረታ አበል እና የሥራ ስንብት ክፍያ አንድ ላይ እንዲከፍሉ ሕጉ አልፈቀድም፡፡ ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ ከሕጉ መውጣት የሚቻል አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንደምናየው ሕጉን መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ ይልቁንም ሕጉን በግልጽ በሚቃረን መልክ የተሰጠ ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡ ከዚህ የተነሳም አቤቱታው የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39748 ሰኔ 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የምሰራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 25367 ጥቅምት 17 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 116497 ጥቅምት 25 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡
2. ተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚያገኝበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

ም.አ ***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 64988

ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች - ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዳሽን ባንክ አ.ማ - ነገረ ፈጅ ዓለማየሁ ገበየሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሀይሉ ሽመልስ- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ የካቲት 01 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ከሐምሌ 15 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥረዉ በመስራት ላይ ከቆዩ በኋላ አመልካች ድርጅት ከታህሳስ 28 ቀን 2002 ዓ/ም ያለአግባብ ከስራ አግደዋቸው ቆይቶ ከታገዱበት ቀን ጀምሮ የተሰናበቱ መሆኑን ጥር 25 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የገለፀላቸው መሆኑን ገልፀው ከህግ ውጭ የተከናወነ ስንብት በመሆኑ ወደ ስራ እንዲመለሱ እና ያልተከፈላቸው ደሞዝ ከኪሳራ ጋር እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠቀዋል፡፡ የአሁን አመልካች በክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ ባንኩን በተመለከተ ማንኛውንም መግለጫ የመስጠት ስልጣን ሳይኖራቸው በጋዜጣ የሰጡት አሉታዊ መግለጫ በባንኩና በሰራተኞች ላይ መረብሸን፣በደንበኞች ላይ ደግሞ መደናገጥን፣ለወደፊቱ የባንኩ ደንበኞች ሊሆኑ የሚችሉት ላይም ጥርጣሬን እና የህዝብ አመኔታን የሚያሳጣ በመሆኑ መሰናበታቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1//ሸ/ መሰረት ባግባቡ ነዉ በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ማስረጃዎችን በመመርመር አመልካች ለጉዳዩ ማስረጃዎችን ያለማቅረቡንና ጥር 25 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ የስንብት ደብዳቤ የገለፀላቸው ድርጊቶችም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1/ስር ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት ከተጠቀሱት ህጋዊ ምክንያቶች ውስጥ የሚወድቁ አይደሉም የሚሉ ምክንያቶችን በመያዝ ስንብቱ ከህግ ውጭ የተከናወነ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ አመልካች ተጠሪን የስድስት ወር ደመወዝ እና በእገዳ ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ከፍሏቸው ወደ ስራቸው ሊመልስ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ነገረ ፈጅ የካቲት 02 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዙቱም በአጭሩ ተጠሪ በጋዜጣ ላይ የሰጡት መግለጫ ሀሰተኛ ሆኖ በባንኩ ክብርና እና ዝናው ላይ የተፈፀመ ሆኖ ይህም በባንኩ ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን የሚያረጋግጥ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27/1//ሸ ስር የሚወድቅ ሆኖ እያለ በበታች ፍርድ ቤቶች የታለፈው ያለአግባብ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው ግራቀኙ በፁሁፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የስራ ውሉ የተቋረጠው በህገወጥ መንገድ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው ስለአመልካች ባንክ ጋዜጣዊ መግለጫ የመስጠት ሃላፊነት የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ሐሰተኛ የሆነ መግለጫ በመስጠት በባንኩ ሰራተኞች ላይ መደናገጥ፣በደንበኞቹ ላይ ጥርጣሬንና በህዝቡ አመኔታ እንዳይኖረው አድርገዋል በሚል ምክንያት መሆኑ ሲሆን ተጠሪ የሰጡት መግለጫ ሀሰተኛ ስለመሆኑ ሳይክዱ ለስንብቱ ምክንያት ነው በማለት የሚከራከሩት በስንብት ደብዳቤ ጥር 25 ቀን 2002 ዓ/ም የተፃፈው ሳይሆን በሪፖርተር ጋዜጣ የካቲት 03 ቀን 2002 ዓ/ም ወጣ የተባለውን መግለጫ በሚል መሆኑን ተረድተናል፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው ተጠሪ የሰጡት ሀሰተኛ መግለጫ የለም በሚል ሳይሆን ሀሰተኛ መግለጫ መስጠታቸው መረጋገጡን ተቀብሎ ይኸው ድርጊት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1//ሸ/ ስር አይወድቅም፣ በባንኩ ሰራተኞች ላይ መረበሽን፣በባንኩ ደንበኞች ላይ ደግሞ ጥርጣሬን መፈጠሩን አመልካች በማስረጃዎቹ አላስረዳም በሚል ነው፡፡

እንግዲህ ለስራ ስንብቱ ምክንያትነት የተጠቀሰው የተጠሪ ስለባንኩ ሀሰተኛ መግለጫ በጋዜጣ መስጠትና ይኸውም ድርጊታቸው በባንኩ ሰራተኞችና ደንበኞች የፈጠረውንና ሊፈጥር የሚችለው ችግርን ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም የሀሰተኛ መግለጫ ፍሬ ጉዳይ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ተገንዝቦ ምክንያቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ስር የሚወድቅ አይደለም ሲል ነው የስራ ስንብቱ ህገወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው፡፡ በርግጥ የስር ፍ/ቤቱ በስራ ስንብቱ ላይ የተመለከተው የተጠሪን ጥፋት ይዙቱን በተፃፈው መልክ ከተመለከትነው ጥፋቱ በአዋጁ መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት ከሚያስችሉ ምክንያቶች ውስጥ ሊካተት የማይችል መሆኑን መገንዘብ ይቻል ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ በተጠቃሹ አዋጅ ስር የተመለከቱት ምክንያቶች በክርክሩ ወቅት የሚረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮችንና የአዋጁን አጠቃቀም አላማና አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ በመመርመር ሊተረጎም የሚችሉ ስለመሆናቸው መገንዘብ አያዳግትም፡፡ አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ የሰጠው ሀሰተኛ መግለጫ በባንኩ ስምና ክብር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያለው ሆኖ በባንኩ ንብረት ላይ ጉዳት እንደደረሰ ሊቆጠር የሚገባው ነው በማለት ነው፡፡ ጉዳት ደረሰ የተባለውም የባንኩ መልካም ስም ጠፍቷል በሚልም ጭምር ሲሆን አመልካች ለዋቢነት የሚጠቅሰው ድንጋጌም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27/1//ሸ/ ስር የተመለከተውን ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ በአሠሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸዉም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ሰራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ነው፡፡ ንብረት ለሚለው ቃል በአዋጁ ስር የተመለከተ ትርጓሜ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ከአዋጁ አላማና ከአሠሪው ድርጅት ባህርይ እንዲሁም ከንብረት ህግ ፅንሰ ሀሳቦች ጋር በማዛመድ ለቃሉ ትርጉም መስጠት ህጋዊነት ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም ንብረት ለሚለው ፅንሰ ሀሳብ ሁሉንም የሚያስማማ ትርጉም መስጠት የሚቻል አይደለምና፡፡ በመሆኑም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን አጠቃላይ አላማም ሆነ አጠቃላይ የንብረት ህግ ፅንስ ሀሳቦች ባህርያት እንዲሁም በንግድ ህጉ ስለመልካም ስም(Good Will) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ግንዛቤ ውስጥ ስናስገባ ንብረት ማለት ዋጋው ኢኮኖሚያዉ ጠቀሜታ ያለው እንዲሁም በአብዛኛው ሀብትነት ሊያዝ የሚችል ነገር መሆኑን ለመገንዘብ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ ዋጋው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ሆኖ በባለሀብትነት ሊያዝ የሚችል ነገር ላይ ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ያደረሰ ሰራተኛ ከሆነ በአሠሪው ንብረት ላይ በህጉ አነጋገር ጉዳት አድርሷል ለማለት የማይቻልበት ምክንያት የለም፡፡

እኛችን ወዳለዉ ጉዳይ ስንመለስ የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት የተጠሪ አድራጎት ለአመልካች ዋጋው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባለው ነገር ላይ ጉዳት አላደረሰም የሚል ግልፅ ምክንያት በመያዝ ሳይሆን በሀሰተኛ መግለጫ ምክንያት በባንኩ ሰራተኞች ላይ መረበሽ በባንኩ ደንበኞች ላይ ደግሞ ጥርጣሬ ስለመድረሱ አመልካች ማስረጃ አላቀረቡም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአመልካች በኩል የቀረበው የፅሁፍ ማስረጃ የተጠሪን ጥፋቶች በግልፅ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችም ተጠሪ በሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 21.6 መሰረት ሀሰተኛ ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት የማይችሉ መሆኑን የሚያሳዩ ሲሆን ሐሰተኛ መግለጫ በባንኩ መልካም ስም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊኖረው አይችልም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ አንድ ሰው ሀሳቡን የመግለፅ ህገመንግስታዊ መብት ያለው ቢሆንም ሀሰተኛ ቃል በመስጠት ግን በሌላ ሰው መልካም ስምና ክብር ላይ ወዲያውኑ ወይም ወደ ፊት ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ተግባር ሊፈፅም አይገባም፡፡ የባንክ ስራ በተለይ ሲታይም የህዝብ ጥቅም የበለጠ የሚንፀባረቅበት በመሆኑ መልካም ስም ሊጠበቅለት የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከህጉ መንፈስ ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሌላው የስር ፍ/ቤት የአመልካችን እርምጃ ህገ ወጥነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አንድ ሰራተኛ ከስራ የሚታገደው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ/18 መሰረት ነው፣የአመልካች እርምጃ ግን ይህንኑ ድንጋጌ የተከተለ አይደለም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድን ሰራተኛ ጥፋት ፈፅሟል የሚል አሠሪ ሰራተኛውን ከስራው አግዶ ለማቆየት የሚችል መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/4/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያሳይ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜም የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤት በተጠሪ የስንብት ደብዳቤ ላይ የተገለፀውን ምክንያት እንዳለ በመውሰድ የደረሰበት ድምዳሜ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ ባለመምረጥና አጠቃላይ ይዘቱንና መንፈሱን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመ/ቁ 50691 ሕዳር 06 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 99417 ጥር 25 ቀን 2003 በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ወጪና ኪሳራ የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሂ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 61843

መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሰይፉ ናስር ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ እና ህግ ጉዳዮች ኀ/ፈጅ ዓለም ቱፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 515/99 "ን" መሠረት አድርጎ የቀረበን የዲሲፕሊን ክርክርንና ይህንኑ መሠረት አድርጎ የተሠጠውን የቅጣት ውሣኔ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አመልካችን የዲስፕሊን ግድፈት ፈፅሟል በማለት ከስራ እንዲሰናበቱ የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይኸው ፍርድ ቤት ተጠሪ መስሪያ ቤት አመልካችን ከስራ ያሰናበተው በአዋጅ ቁጥር 515/99 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 77/94 መሠረት ጉዳዩ በዲስፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ የውሣኔ ሀሣብ ሳይቀርብ ከባድ የዲስፕሊን ግድፈት ተፈጽሟል በሚል ምክንያት ነው፣ ይህ ደግሞ ሥነ ስርዓቱን ያሟላ አይደለም በማለት ጉዳዩ በዲስፕሊን ኮሜቴ ከታዬና ከተጣራ በሁዋላ ተገቢውን ውሣኔ ሊያገኝ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ መስሪያ ቤት ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይህ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በሁዋላ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የቢሮ ኃላፊ የሰጡትን ውሣኔ አፅንቶ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል በፍሬ ጉዳዩ ላይ የቀረበውን የአሁኑ አመልካች ቅሬታ ተገቢነቱ ሳይመረመር የቢሮው ኃላፊ ውሣኔ መጽናቱ ስነ ሥርዓታዊ አይደለም በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክር ተጣርቶ ተገቢው እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን ለአዲስ አበባ ከተማ የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት መልሶለት ይኸው ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ የቢሮው ኃላፊ በአመልካች ላይ ያስተላለፉት ቅጣት ተገቢነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ አመልካች የሶስት ወር ደመወዝ ተቀጥተው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በሁዋላ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ከስራ እንዲሰናበቱ ተብሎ በተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የተሠጠው ውሣኔ ሕጋዊ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱን አስመልክቶ የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በችሎቱ ላይ የተሰየሙት ዳኞች ጉዳዩን ገለልተኛ ሁነን ለማየት አንችልም በማለት መዝገቡን ዘግተውታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው የይግባኝ ጊዜ ከአለፈ በሁዋላ ከመሆኑም በላይ በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጠው ውሣኔም በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ ውሣኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው ፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታመኑም ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በፅሑፍ መልሱ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ከአላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአንድ ጉዳይ የተሰጠውን ፍርድ ማረም የሚችለው በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ሲሰጥና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ቀርቦለት ዋናውን ጉዳይ ሳይመለከት የቀረው ጉዳዩን ዳኞቹ ገለልተኛ ሁነው ሊመለከቱ አይችሉም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ያልሰጠበት ቢሆንም ችሎቱ ካለው የመሰረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አኳያ እና ጉዳዩ ከዚህ በፊት ከወሰደው ጊዜ እንዲሁም ከጉዳዩ ባህርይ አንጻር ይህ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎትም መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም ሥልጣኑ በመሆኑ ጉዳዩን መመልከቱ ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡

በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት ያለበት የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ጠብቆ ቀርቦለት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ የሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሲሆን ይህ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሰጠው ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ/ም ነው፡፡ ይህ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል ፣ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜም ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ የሚታሰቡ ሰላሳ ቀናት መሆናቸውን የአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 76/2/ እና የአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 አንቀጽ 77/2/ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሰጠው ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ/ም ሲሆን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኙ የቀረበው ደግሞ ሐምሌ 21 ቀን 2002ዓ/ም ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ስለማለፉ የአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 76/2/ ን በመጥቀስ ያረጋገጠው ሲሆን በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ያደረገው አዋጅ ቁጥር 515/99 ተፈጻሚነት የሚኖረው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ነው፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት ይግባኙን የሚያየው በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 43/3/ መሠረት ሁኖ የሚመራውም በ1958ቱ የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ነው፣ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተፈጻሚነት የሚኖረው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ስልሳ ቀናት ነው፣ አዋጅ ቁጥር 515/99 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት አለው ቢባል እንኳ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት ማመልከቻ ወደያውኑ ለአመልካቹ በመዝገብ ቤት ሹመ እንደሚመለስለትና በአስር ቀናት ጊዜ ውስጥ የይግባኝ ማስፈቀጃ እንዲያቀርብ የሚደረግ በመሆኑ በመዝገብ ቤት ሹም ተከፍቶ ወደ ችሎት የቀረበ የይግባኝ መዝገብ በችሎት የሚታረም አይደለም የስነ ስርዓት ግድፈቱ በችሎት ሊስተካከል የሚገባው አይደለም በሚሉ ምክንያቶች ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች አዋጅ ቁጥር 515/99 እና አዋጅ ቁጥር 6/2000 ሲሆኑ ጉዳዩ የሚመራበትን ሥርዓትም በእነዚህ ሕጎች የተመለከተው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 43/3/ መሠረት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ቢኖረውም ከዚህ አዋጅ በሁዋላ የወጡት አዋጅ ቁጥር 515/99 እና 6/2000 ጉዳዩ የሚመራበትን ሥርዓት በግልጽ ዘርግተው ይገኛሉ፡፡ እንዲህ ከሆነ በሕግ ተዋረዳዊ አቀማመጥ/ hierarchy of Laws / በሁዋላ የወጣ ሕግ ቀድሞ የወጣውን ሕግ በመቀደም ስራ ላይ የሚል መሆኑን ተቀባይነት ያለው የሕግ አተረጓጎም መርህ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 43/3/ እና በፍትሓ ብሔር ስነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከተው የይግባኝ ማቅራቢያ ጊዜ ነው በማለት የሠጠው ምክንያት ከሕግ አተረጓጎም መርህ አንፃር ሲታይ ሕጋዊ አይደለም፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 515/99 እና አዋጅ ቁጥር 6/2000 ሲሆኑ እነዚህ አዋጆች በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ውሣኔ በተሰጠ በሰላሳ ቀናት መሆኑን ይደነግጋሉ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አዋጆቹ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት አላቸው ቢባል እንኳ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 324/1/ ስር በተመለከተው ሁኔታ ችሎት የሥነ ሥርዓት ግድፈቱን ሊያስተካክል የሚችለው አይደለም በማለት ደምድሟል፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 324/1/ መሠረት ለአንድ ፍርድ ቤት መዝገብ ሹም የተሰጠው ሥልጣን ይግባኝ ማቅራቢያ ጊዜ ማለፍ አለማለፉን በመመልከት ይግባኝ መዝገቡ እንዲከፈት ማድረግ ሲሆን ይግባኙ ጊዜውን ጠብቆ ያልቀረበ ከሆነ ማመልከቻውን መመለስ፣ ማመልከቻው የተመለሰበት ወገን የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ሕጋዊ ምክንያት ካለው ማስፈቀጃ አቤቱታውን በማቅረብ ይኸው ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ራሱን የቻለ አቤቱታ አቅርቦና ይህ መዝገብ ተከፍቶ ጉዳዩ ለችሎት ቀርቦ ችሎቱ የይግባኝ ማስፈቀጃውን በመመርመር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 325 እና 326 መሠረት ተገቢ ነው ያለውን ትእዛዝ የሚሰጥበት ነው፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 324/1/ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 325 እና 326 ድንጋጌዎች ጋር አንድ ላይ ሲነበቡ የመዝገብ ቤት ሹም ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ለችሎት እንዲቀርብ የመፈቀድ ስልጣን የሌለው መሆኑን የሚያሳዩ ሲሆን ፋይሉ ተከፍቶ ቀርቦ ከሆነም ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ይግባኙ የቀረበው ጊዜው ከአለፈ በሁዋላ ነው በማለት መዝገቡን ከመዝጋት የሚከለክለው አይደለም፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 324/1/ ድንጋጌን ይዘቱንና መንፈሱና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 325 እና 326 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር አዛምዶ ሳይመለከት የመዝገብ ቤት ሹም የይግባኝ ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ መዝገብ ከፍቶ ከአቀረበ ችሎቱ ሊያስተካክለው የሚችለው አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ሕጋዊ መሠረት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያላቸው የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 515/99 ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 በመሆናቸውና በእነዚህ አዋጆች መሠረት በሚታይ ጉዳይ ላይ ውሣኔ ሲሰጥ ይግባኙ የሚቀርበው በሰላሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ መሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደነገገ በመሆኑና የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ሁኔታ በስርዓቱ መሠረት የማስፈቀጃ አቤቱታ ለችሎት ቀርቦ የሚታይ ከሚሆን በስተቀር በመዝገብ ቤት ሹም የሚታይ ባለመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሣኔ የይግባኝ ጊዜው አልፎበት እያለ ተቀብሎ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የስነ ስርዓት ሕግ ግድፈት በመፈፀም ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13951 ነሐሴ 27 ቀን 2002 ዓ/ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የአዲስ አበባ ከተማ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ/ም በሰጠው ውሣኔ ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበው የሰላሳ ቀናት የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜያት ከአለፋ በሁዋላ በመሆኑና በሥርዓቱ መሰረትም ተገቢውን የማስፈቀጃ አቤቱታ ያላቀረበ በመሆኑ ይግባኙ የሚስተናገድበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. የአዲሰ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 158/02 ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ/ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገበ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 57337

ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አለ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አድቬንቲስት የልማት የተረድኦ ድርጅት - ጠበቃ ዶ/ር ዘወድነህ በየነ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ገበየሁ ወ/ሚካኤል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የቀረበው ጉዳይ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ሲሆን የቀረበው በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪ ከሣሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ በተከሣሽ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው በመስራት ላይ እንዳሉ ያለአግባብ ከስራ የተሰናበቱ መሆኑን በመግለጽ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲወሰንላቸው የጠየቁ ሲሆን በማስረጃም የጽሁፍ የሰው ምስክሮች ዝርዝር አቅርቧል የሚል ነው፡፡ ተከሣሽ ድርጅት ቀርቦ በሰጠው መልስ ከሣሽ የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ይሄው ሲያበቃ ያሰናብተዋል፤ ከሣሽ ለረሃብተኞች እንዲከፋፈል ተብሎ የተሰጣቸውን ስንዴ እንዲበላሽ በማድረጋቸው በስራ ቦታ ላይ አለቃቸውን በመሳደባቸው እንደሁም የስራ ሰዓት ባለማክበራቸዉ ተሰናበተዋል በማለት በአማራጭ የተከራከረ ሲሆን ከማስረጃም አኳያ የጽሁፍ ሰነድና የሰው ምስክሮች ዝርዝር ቀርቧል የሚል ነው፡፡

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ በግራቀኙ መካከል የነበረው የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ሆኖ የሚቆየው ከሰኔ 2000 ዓ.ም እስከ ታህሣስ 2001 ዓ.ም ድረስ በመሆኑ ይሄ ጊዜ ሲያልቅ የሚቋረጥ በመሆኑ ስንብቱ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24/1/ መሠረት የተፈጸመ በመሆኑ ህጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ክፍያን በተመለከተ የፕሮቪደንት ፈንድ ብር 5086,96 ተከሣሽ ድርጅት ለከሣሽ በአንድ ዓመት የአገልግሎት ዘመን ውስጥ ለተሰራ የአራት ወር ከ20 ቀን የአመት ፍቃድ ክፍያ እንዲከፍለው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁን ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ካከራከረ በኋላ የቅጥር ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ቢሆንም የተቀጠሩት ለፕሮጀክቱ ስራ እስከ ሆነ ድረስ ፕሮጀክቱ ደግሞ የሚጠናቀቀው የስራ ዘመኑና የበጀት ዘመኑ አንድ ዓመት ነው በመባሉ ፕሮጀክቱ ስለመጠናቀቁ ደግሞ ተጠሪ /የአሁን አመልካች/ ያቀረበው ማስረጃ ባለመኖሩ ከስራ ተጠሪን ያሰናበተው ያለአግባብ ነው በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር አመልካች ለአሁን ተጠሪ ፕሮጀክቱ እስከሚጠናቀቅ ቢቆየ ኖሮ ሊከፈላቸው የሚችል የነበረው ደግሞ ማለትም ከታህሣስ 22 እስከ ሰኔ 30/01 ድረስ ያለውን ደሞዛቸው ታስቦ እንዲከፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም ተጽፎ በቀረበው ቅሬታ ተጠሪ በሙሉ ፍቃድ ተቀብሎ የስራ ውል የገባው ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ይሄ ጊዜ ደግሞ የሚያበቃው ታህሣስ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በመሆኑ ስራውም የፕሮጀክት ስራ ሆኖ እያለ ስንብቱ ህጋዊ ነው መባል ሲገባው ተጠሪ ያልሰራበትን ደሞዝ እንዲከፈለው መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የተጠሪ ጠበቃ ታህሣስ 04 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ፡- የቀረበው ቅሬታ ግልጽነት የለውም የተቀጠርኩበት የውል ስምምነት ለተወሰነ ጊዜ ቢልም ተፈጻሚነት ያለው ግን የተቀጠርኩበት የስራ ጸባይ በመሆኑ የተቀጠርኩት ለፕሮጀክት ስራ ስለመሆኑ በመ/ደ/ፍ/ቤት ያልቀረበ በመሆኑ የስራ ውሉ የተቋረጠው ያለአግባብ ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ በመሆኑ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ጠበቃ ታህሣስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው የመልስ መልስ የቀረበውን ቅሬታ በማጠናከር የሰጠ ሲሆን በተጨማሪ ፕሮጀክቱ በአሜሪካ አለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት የሚታገዝ በመሆኑ ጊዜው የሚጠናቀቀው ማለትም የበጀት ዓመቱ ታህሣስ 2001 ዓ.ም ሆኖ ሣለ ሰኔ 30 /2000/ ያልቃል በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲሻርልን በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራቀኙ የቀረበው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በተጠሪና በአመልካች መካከል የነበረው የስራ ውል ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪ ፈጽሟቸዋል በማለት አመልካች ያቀረበችውን ጥፋቶች በተመለከተ ደግሞ ከስራ ለማሰናበት በቂ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የበታች ፍርድ ቤት ማጣራት ውስጥ ያልገባ በመሆኑ ይሄ ችሎትም ወደዚህ ጭብጥ የሚያስመጣ አግባብ ካለ ከላይ በተያዘው ጭብጥ ውጤት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ለጊዜው እናልፈዋለን፡፡

ወደተያዘው ጭብጥ ስንመለስ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የስራ ውል በውላቸው ውስጥ በግልጽ እንደተቀመጠው ከሰኔ /2000 ዓ.ም እስከ ታህሣስ 22 ቀን 2001 ዓ.ም የሚመለከት መሆኑ አላከራከረም፡፡ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ የውሉ ቃል ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ መሆኑ ሣይሆን መታየት ያለበት ከተቀጠርኩበት የስራ ጸባይ አኳያ መሆን ይገባዋል የሚል ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ደግሞ ውሉ ግልጽ ከመሆኑም በላይ ስራው የፕሮጀክት በመሆኑ የሚጠናቀቀው በታህሣስ ወር 2001 ዓ.ም ሆኖ ተገምግሞ ይቀጠል አይቀጥል የሚለው ውሣኔ ሲያገኝ ብቻ የሚቀጥል በመሆኑ ፕሮጀክቱ የአንድ ዓመት ነው የበጀት ዓመቱ ደግሞ የሚያልቀው ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ነው በማለት ፍርድ ቤቱ የደረሰበት መደምደሚያ አግባብነት የለውም የሚል ነው፡፡

የቀረበውን ክርክር ስንመለከት በእርግጥ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9 እና አንቀጽ 10 አንድ ላይ ስናዬው አንድ የስራ ውል ለተወሰነ ጊዜ መደረጉ ብቻ የተወሰነ ጊዜ የስራ ውል እንደማያሰኘውና እንደስራው ባህሪ እየተየ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ ያስገነዘበናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ግን የስራ ውሉ ተጠሪ እንደሚከራከረው ለተወሰነ ጊዜ ስለመሆኑ ማስረዳት ብቻ ሣይሆን ስራው የፕሮጀክት ስራ መሆኑና በውጪ ድርጅት የሚደገፍ በመሆኑ የዓመት ስራ እንቅስቃሴው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታይቶ ፕሮጀክቱ ይቀጥል ሲባል ብቻ የሚቀጥል እንደሆነ የበጀት ዓመቱም የሚጠናቀቀው ታህሣስ 2001 ዓ.ም እንደሆነ ከመከራከሩም በላይ በዚህ ነጥብ ላይ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ማስረጃ ሰምቶ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

የፕሮጀክቱ የበጀት ዓመት በታህሣስ ወር ላይ እንደሚጠናቀቅ ማስረጃን የመቀበልና የመመዘን ስልጣን ያለው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ያረጋገጠው ሲሆን ተጠሪ ይሄንን የሚያስተባብል ማስረጃ ባልቀረበበት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የበጀት ዓመቱ የሚጠናቀቀው ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ነው ወደሚለው መደምደሚያ መድረሱ ወደዚህ መደምደሚያው ያደረሰውን በቂ ምክንያት ሣይገልጽ በመሆኑ መሠረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆዎችን የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም በተጠሪ እና በአመልካች መካከል የነበረው የስራ ውል ግንኙነት በተወሰነ ጊዜ በመሆኑ የውል ጊዜያቸው ከማለቁ በፊት በስራ ላይ ትብብር እንዲደረግላቸው የድጋፍ ደብዳቤ ለሚመለከተው ክፍል አመልካች መጻፉ እንደዚሁም የስራ ውሉ ከተቋረጠ በኋላ ሌሎች ሰዎችን ድርጅቱ መቅጠሩ የስራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው የሚያሰኝ አግባብ የለም ብለናል፡፡ ከስራም የተገለለው በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24/1/ መሠረት ነው ብለናል፡፡

በዚሁ መሠረት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ለተጠሪ በስራ ላይ ቢቆይ ኖሮ ይከፈለው የነበረው ደሞዝ ከታህሣስ 22 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን ይከፈለው ማለቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ውሣኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 86989 በቀን 26-09-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 56140 ጥቅምት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 64734

ሰኔ 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አለ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ካንትሪ ክለብ ዴቨሎፐር የረር ቪው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት - ነገረ ፈጅ ታማኝ የበነ - ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ በቀለ ለማ - ቀረቡ

2. አቶ ተሾመ አጫሉ - ቀረቡ

3. አቶ ባህሩ አበራ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ሲሆን በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበው በአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ በተከሣሽ ድርጅት ውስጥ በአናጢነት ሙያ ተቀጥረን 1ኛ ከሣሽ በቀን ብር 36 ፣ 2ኛ ከሣሽ ብር 39 እና 3 ከሣሽ ብር 20 እየተከፈለ በመስራት ላይ እያለን ነሐሴ 17 ቀን 2002 ዓ.ም ያለአግባብ ከስራ ላይ ያሰናበተን ስለሆነ ወደ ምድብ ስራችን እንድንመለስ ወደ ስራ የማይመልሰን ከሆነ ደግሞ በህጉ መሠረት ሊከፍለን የሚገባውን ክፍያዎች እንዲከፍለን የሚል ነው፡፡ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ መጥሪያ ደርሷቸው በሰጡት መልስ ከሣሾች ከስራ የተሰናበቱት ድርጅቱ ከመዝገብ ቤት የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ አንቀበልም በማለታቸው በህብረት ስምምነቱ መሠረት ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክር በመስማት የተከሣሽ ምስክሮች ከመዝገብ ቤት ወጪ ሆኖ ለከሣሾች የተጻፈውን ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ አንቀበልም ማለታቸውን አረጋግጫለሁ በሌላ በኩል የተከሣሾች ምስክሮች ቃል እርስ በርስ የሚቃረን በመሆኑ ማስተባበል አልቻሉም፤ ከድርጅቱ መዝገብ ቤት ተጽፎ የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ አልቀበልም ማለት ደግሞ በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 58/10/ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብት የሚችል በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የአሁን አመልካች እየሰጠ የነበረው ማስጠንቀቂያ ሣይሆን ቀደሞ በቅጥር ውላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውስጥ የተጠቀሰውን በቀን 5 ካ.ሜ የአሁን ተጠሪዎች ለመስራት የገቡትን ግዴታ ወደ 10 ካ.ሜ. ለማሻሻል የተደረገ በመሆኑ የአሁን አመልካች በራሱ ተነሳሽነት በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን የስራ ውል ስምምነት መጣሱን እንጂ በጥፋት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ባለመሆኑ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሯል፡፡ የተጠየቀውን ክፍያ በተመለከተም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ፣ የስራ ስንብት እና የካሣ ክፍያ እንዲከፍላቸው አመልካች ኃላፊነት እንዳለበት ወስኗል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በቀን 23-5-03 ዓ.ም በነገረፈጅ በኩል በተጻፈ 4 ገጽ አቤቱታ ፍሬ ሃሣብ ከድርጅቱ መዝገብ ቤት ወጪ ሆኖ ለሰራተኞች የሚሰጠውን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ አልቀበልም ማለት በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 58/10/ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ሆኖ እያለ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይሄንን በማለፍ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ታዘው የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ ፍሬ ሃሣብ ያቀረብኳቸው የሰው ምስክሮች የተባለው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተሰጠ ለተባለበት ያልነበርና እንቢ ያላልን መሆኑን መስክሮልናል ፤ አንፈርምም ያልነው ደግሞ ቀድሞ የተስማማንበት የስራ ውል በቀን 5 ካ.ሜ ሆኖ እያለ አሁን ደግሞ 10 ካ.ሜ እንድንሰራ ያዘዘን በመሆኑ ከአቅማችን በላይ በመሆኑ እምቢ ማለታችን እንጂ በጥፋተኝነት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ባለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረቡትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪዎች ከስራ የተሰናበቱት በህጋዊ መንገድ ወይስ በህገ-ወጥ መንገድ ነው? በሚል ጭብጥ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27 ስር ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ የሚችሉ ጥፋቶችን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ 5 አንቀጽ 27/1/ ስር ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰብቱ የሚችሉትን ጥፋቶች በህብረት ስምምነታቸው መደንገግ እንደሚችሉና በዚሁ መሠረት በድርጅቱ ውስጥ ስራ ላይ ያለው የህብረት ስምምነት አንቀጽ 58/10/ ከመዝገብ ቤት የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ አልቀበልም ማለት እንደ አንድ በቂ ምክንያት የተቀመጠ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የአሁን አመልካችም የሚከራከሩት ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ይሄ የህብረት ስምምነት አንቀጽ እንደሆነና የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ያለመቀበል በራሱ ከስራ ለማሰናበት በቂ መሆኑን ተከራክሯል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች የሚከራከሩት የተጻፈው ደብዳቤ ባጠፉነው ጥፋት የተሰጠ ሣይሆን በስራ ውላችን ውስጥ የተስማማንበትን በቀን 5 ካ.ሜ ለመስራት ውል የገባንበትን በመለወጥ በቀን 10 ካ.ሜ እንድንሰራ የታዘዘንበት ነው በማለት የተጠቀሰው የህግ አንቀጽ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት እንደሌለው ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመረምር የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1/ መግቢያን በምናይበት ጊዜ በሌላ አኳኋን በህብረት ስምምነቱ የተካተተ ካልሆነ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ የሚችሉ ነገሮች በዚሁ አንቀጽ ስር የተዘረዘሩት ብቻ እንደሆኑ ያመለክታል፡፡ ለህብረት ስምምነቱ መውጣት መሠረት የሆነው የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/ተ/ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ ይችላሉ ተብለው በህብረት ስምምነት የሚደነገጉት ሌሎች ጥፋቶች እንደሆነ ያመለክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይሄ ማለት ደግሞ በህብረት ስምምነት እንደምክንያት ሊደነገጉ የሚችሉት ነገሮች ጥፋትን መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት ያመለክታል፡፡

አሁን ለተጠሪዎች ከስራ መሰናበት መሠረት የሆነውን የህብረት ስምምነት አንቀጽ 58 ስንመለከትም የአንቀፁ ርዕስ ከስራ የሚያስናብቱ ከባድ ጥፋቶች በሚል ከመደንገጉም በላይ የዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 10 በተያያዘ መልኩ "ድርጅቱ ከመዝገብ ቤት የሚሰጠውን የማስጠንቀቂያ ወረቀት አልቀበልም ካለ" በማለት ይደነግጋል፡፡ ይሄንን ሁሉ አንድ ላይ ጠቅለል አድርገን ስንመለከት የስራ ስንብቱ የሰራተኛውን ጥፋት መሠረት ያደረገና የሚሰጠውም ማስጠንቀቂያ ጥፋትን መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት ያመለክታል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች እንዲቀበሉ የታዘዙትን ደብዳቤ አንቀበልም ማለታቸው በመጀመሪያ ጉዳዩን ባየው ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑ ቢታመንበትም እየተሰጣቸው ያለው ደብዳቤ ከላይ እንደተብራራው የህግ ድንጋጌዎች ጥፋትን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም ከሚለው አኳያ መታየት አለበት፡፡

በዚህ መሠረት ተጠሪዎች እንዲቀበሉ እየታዘዙ ያሉት ቀድሞ በስራ ውላቸው ውስጥ በቀን ተጠሪዎች 5 ካ.ሜ ለመስራት የተስማሙበትን አመልካች በቀን 10 ካ.ሜ እንዲሰሩ የጻፈባቸውን ደብዳቤ ስለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው በመሆኑ የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ /ሀ/ እና በአዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የህግ ስህተት ሲኖር ማረም በመሆኑ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሠረቱ አመልካችም የሚከራከረው የተጻፈው የደብዳቤ ይዘት ከዚህ የተለየ ስለመሆኑ ሣይሆን ደብዳቤውን ያለመቀበላቸው ብቻ ከስራ ለማባረር በቂ ነው ከሚለው ነጥብ አኳያ በመሆኑ አልፈነዋል፡፡

የተጻፈባቸው ደብዳቤ ይዘት ከላይ የተመለከተው በመሆኑ አመልካችም ተጠሪዎች ሲቀጠሩ የነበረው ውል በቀን 5 ካ.ሜ ለመስራት እንደተስማሙ ባላስተባበሉበት በራሱ ተነሣሽነት በውላቸው ውስጥ የተቀመጠውን የቀን የስራ መጠን በመተላለፍ በቀን 10 ካ.ሜ እንዲሰሩ ማለቱና ቀድሞ የነበረውን የስራ ውል የሚያስቀይር ጉዳይ መኖሩን እንኳ ባላስረዳበት በራሱ መጻፍና አንቀበልም ብሏል በማለት ከስራ ማሰናበቱ ከተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ/ቁ. 99340 በቀን 09-05-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ተጠሪዎችን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበተው ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ተያያዥ ክፍያዎች ለተጠሪዎች እንዲፈጸሙ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በቀን 01-06-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

እ.ከ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 66306

ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንገሤ

አመልካች ፡- እምላሉ ወረዳ ክንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ጠበቃ ሲሳይ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ መሐመድ ሰይድ አልቀረቡም

2. ሲሳይ ተስፋዬ ቀረቡ

3. መላኩ እውነቱ ቀረቡ

4. አበባ ጉዲሳ ቀረቡ

5. ስብአት አለማየሁ ቀረቡ

6. በሐይሉ ደምሴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች በሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ተከሣሽ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሾች ነበሩ፡፡ ክሱም በተከሣሽ ድርጅት ተቀጥረን እየሠራን እያለ ተከሣሽ በራሱ አነሳሽነት የሥራ ውላችንን ያቋረጠብን ስለሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍለን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ተከሣሽ በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሳሾች የተቀጠሩት ተከሣሽ ተስፋ የነጋዴዎች አክሲዮን ማህበር ከተባለው ጋር የሱቆች ህንፃ ግንባታ ለማድረግ በገባነው ውል መሠረት የሱቆች ህንፃ ለመገንባት ቢሆንም ከማህበሩ ጋር የተደረገው የሱቆች ህንፃ ግንባታ ውል በመቋረጡና ከሳሾችም የተቀጠሩት ለዚሁ ኘሮጀክት ለተወሠነ ጊዜ በመሆኑ የሚገባቸውን ክፍያ ማለትም የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እና የስንብት ክፍያ እንዲሁም የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶአቸው የሥራ ውሉ ተቋርጧል ብሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትም ተከሣሽ ከከሣሾች ጋር የነበረውን የቅጥር ውል ያቋረጠው ተስፋ ኒጋዴዎች አክሲዮን ማህበር ጋር የነበረው የሱቆች ግንባታ ውል በመቋረጡ ነው ቢልም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 12 ላይ የተመለከተውን ግዴታ አልተወጣም ። የሥራ ውሉ የተቋረጠው የኘሮጀክቱ ሥራ (የሱቆች ሕንፃ ግንባታ) በመጠናቀቁ አይደለም። ተከሣሽ ከማህበሩ ጋር ያደረገው የሱቆች ህንፃ ግንባታ ውሉ መቋረጡ ከ3ኛ ወገኖች (ከሳሾች) ጋር የነበረውን ውል እንዲቋረጥ አያደርገውም በማለት የሥራ ውሉ የተቋረጠው በህገወጥ መንገድ ነው ሲል ተከሣሽ ለከሳሾች ቀደም ብሎ ከከፈላቸው ክፊያዎች በተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና ካሣ የ6 ወር ደመወዘ እንዲከፍል ወስኗል።

የሥር ተከሣሽም በዚህ በሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች ካከራከረ በኋላ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል።

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በዋነኛነት አመልካች የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- ተጠሪዎች መያቸው አናጢነትና ግንበኝነት ሲሆን የተቀጠሩትም ተስፋ የነጋዴዎች አክሲዮን ማህበር አባላት ሱቆችን ለመገንባት አመልካች ከማህበሩ ጋር በገባው ውል መነሻ ሲሆን ይኸው የግንባታ ሥራ የማህበሩ አሠሪ እንዲቋረጠ በማዘዙ ተቋርጧል። የተጠሪዎችም የሥራ ውል በዚሁ ምክንያት ተቋርጦ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/2/ሀ/ ሠራተኞቹ በተሠማሩበት ሥራ በሙሉና በቀጥታ የሚያስቆም ሁኔታ የተከሰተ አንደሆነ አስሪው ለማሠናበት የሚችል መሆኑ ተደንግጐ እያለ ይኸንኑ ድንጋጌ በማለፍ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው ሲሉ መወሰናቸው ያለአግባብ ነው የሚል ሲሆን የሥራ ውሉ የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው በሚል መነሻም አመልካቾች ለተጠሪዎች እንዲከፍል የተባሉትን ክፍያዎች ይህ ችሎት ውድቅ እንዲያደርግ ጠይቋል።

ተጠሪዎች ለአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰጡት መልስ አመልካች በተለያዩ ክፍሎች ሠራተኞችን እየመደበ የሚያሠራ እንጂ የግንባታ ሠራዎችን ከአሠሪዎች እየተቀበለ የተቀበለውን ህንፃ ግንባታው እስከሚጠናቀቅ ብቻ ሠራተኞችን ውል በማስገባት የሚይሠራ አይደለም። ተጠሪዎች መያችን አናጢነት ሲሆን አመልካች የቀጠረን ከተስፋ ኒጋዴዎች አክሲዮን ማህበር የተቀበለው የህንፃ ግንባታ ሥራ እስከሚጠናቀቅ በሚል ብቻ አይደለም ስለሆነም በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለዋል።

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው ውል የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 4/1/ መሠረት ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሠሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሠሪው ለመሥራት በሚያደርገው ስምምነት የሥራ ውል ይመሠረታል። በአዋጁ አንቀጽ 10 ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ በሚል መዋዋል የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች የሚዘረዝር ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች በቀር የሚመሠረቱ ውሎች በአዋጁ አንቀጽ 9 በተጠቀሰው መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረጉ የሥራ ውሎች የሚቆጠሩ ናቸው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደተያዘው ጉዳዩ ስንመለስ በሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ተጠሪዎችን የቀጠራቸው አመልካች ተስፋ የነጋዴዎች አክሲዮን ማህበር ለተባለው የሱቆች ህንፃ ግንባታ ሲሆን ሥራው ሲጠናቀቀም ውሉ የሚያበቃ ነበር፡፡ በመሆኑም ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ እንደተጠቀሰው በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል በአዋጁ አንቀጽ 10 ሥር ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ ተብሎ የሚደረጉ ውሎች ውስጥ የሚሸፈን ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሱቆች ህንፃ ለመገንባት ከተስፋ ነጋዴዎች ማህበር ጋር የገባው ውል የግንባታ ውሉ ፕሮጀክት ከመጠናቀቁ በፊት ተቋርጧል፡፡ ይህ አመልካች ከተስፋ የጋዴዎች አክሲዮን ማህበር ጋር የገባው የሱቆች ህንፃ ግንባታ ውል መቋረጡ የሥራ ውሉ በሌላ ምክንያት ድርጅቱ ለዘለቀታው ሲዘጋ በህግ የሚቋረጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24/4/ የተደነገገውን የሚያሟላ ነው፡፡

ይህ ሆኖ ግለ የሥር ፍ/ቤቶች በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል የተቋረጠው በአመልካችና በተስፉ ነጋዴዎች አክሲዮን ማህበር ተደርጐ በነበረው ውል መሠረት የተጀመረው የፕሮጀክት ሥራ ሳይጠናቀቅ ነው፡፡ በማህበሩና በአመልካች መካከል የነበረው ውል መቋረጥ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረውን ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት አይሆንም በማለት ውሉ የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው ሲሉ የወሰኑት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/67044 በቀን 20/11/2002 በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጠር 96791 በቀን 22/6/2003 የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለተጠሪዎች የስንብት ክፍያና የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ በመክፈል እንደሁም የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት በመስጠት ተጠሪዎችን ያሰናበታቸው በአግባቡ ነው፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 09 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት - ነገረ ፈጅ አቶ ፈለቀ እንግዳሸት ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኃ/ማርያም ሻረው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር ክርክር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታውም የአሁን ተጠሪ የሥራ ውሉ ተቋርጦ እንዲሰናበት የተደረገው ከሕግ ውጭ ስለሆነ አሠሪው ድርጅት ወደ ሥራው እንዲመልሰው ይገባል፣ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጭ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅሞች ሊከፈሉት ይገባል በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/3/ መሠረት የቀረበ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በገደብ አሳሳ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሹ ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ ሆኖ ክሱ አሠሪው ድርጅት የሆነው የአሁኑ አመልካች ከሕግ ውጭ እኔን በወንጀል በመጠርጠር አግዶኝ እንዳልሠራ ስላደረገ ወደ ሥራ እንዲመለስ ይወስንልኝ በሚል የቀረበ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው ከሥራው እንዲታገድ የተደረገው የመንግሥት ቼክ በሀሰት ፈርሞ ከባንክ ገንዘብ ስላወጣ ነው፣ ከሥራ የሚያሰናብተው ከፍተኛ የዲሲፕሊን ጥፋት ስለፈፀመ የተወሰደው እርምጃ ትክክል ነው የሚል ክርክር ቢያቀርብም የወረዳው ፍ/ቤት ሠራተኛው በተጠረጠረበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በሕግ የተሰጠ ውሣኔ የለም፣ በመጠርጠሩ ብቻ ከሥራ ታግዷል የሚለው በሕጉ ተቀባይነት የለውም በማለት የአሁኑ አመልካች ሠራተኛውን ወደ ሥራው እንዲመልሰው፣ ደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅሞች ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊከፍለው ይገባል በሚል ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አመልካች በዚህ የወረዳው ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን በየደረጃው ላሉ የኦሮሚያ ፍ/ቤቶች ቢያቀርብም ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች በ28/12/2002 በነገረ ፈጁ አማካኝነት በተጻፈ ማመልከቻ ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመባሉ ማመልከቻው ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት ተጠሪው በ23/03/2003 የተጻፈ መልስ ሲያቅርብ የአመልካች ነገረ ፈጅም የመልስ መልስ ሰጥቶበት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩም ተመርምሯል፡፡

አሠሪው ድርጅት የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበተው የድርጅቱን ቼክ በሀሰት በመፈረም ከባንክ ገንዘብ አውጥቶ በመውሰድ ከፍተኛ ጥፋት በመፈፀሙ ነው በማለት አጥብቆ የሚከራከር ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ከጥርጣሬ በቀር ወንጀሉን ስለመፈፀሜ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስላልቀረበ የአመልካች ክርክር በሕግ ተቀባይነት የለውም ባይ ነው፡፡

በመጀመሪያ ከሥራ ዕገዳ ሆኖ በመጨረሻ ከሥራ ስንብት ሆኗል የተባለው የአሁኑ አመልካች እርምጃ ከሕግ ውጭ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ዋናውን የክርክር ጭብጥ በተመለከተ ወረዳው ፍ/ቤት ሠራተኛው በወንጀል ተጠርጥሯል ከመባል በቀር በሕግ ጥፋተኛ ስለመሆኑ ተወስኖበት የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት ማስረጃው የፍርድ ቤት የወንጀል ውሣኔ ብቻ እንደሆነ አድርጐ በመውሰድ አሠሪው ሠራተኛው ፈጽሟል ስለሚለው ጥፋት በማስረጃ አላስረዳም ወደሚል ድምዳሜ ያመራ ሆኖ ይገኛ እንጂ አሠሪው ድርጅት ሠራተኛው ፈጽሟል ስለሚለው ጥፋት በፍርድ ቤት የተሰጠ የወንጀል ውሣኔ በማስረጃነት ማቅረብ ሣያስፈልግ የሰው ወይም ሌላ የጽሑፍ ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይችላል፡፡ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ጉዳዩ ተጣርቶ ከሥራ የሚያስወጣው ጥፋት ፈጽሟል የተባለበት የዲሲፕሊን ውሣኔ መኖሩ ከታወቀ በጽሑፍ ማስረጃነት የማይቀርብበት ምክንያት የለም፡፡ በወንጀል ምርመራ የተጣራበት ማስረጃም ካለ በማስረጃነት ቀርቦ ሊታይና ሊመዘን የሚችል ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች እነዚህን ሁሉ ማስረጃዎች እንዲያቅርብ አድርጐ አጣርቶ መወሰን ሲገባው ሠራተኛው በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ የተባለበት የፍርድ ቤት ውሣኔ በማስረጃነት ካልቀረበ ከሥራ የሚያሰናብተው ጥፋት ስለመፈፀሙ ማስረዳት እንደማይችል አድርጐ የወሰነው ትክክል አይደለም፡፡

ሌሎች ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተደርጐ ሣይጣራ የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የገደብ አሳሳ ወረዳ ፍ/ቤት በፋይል ቁጥር 04168 በ23/09/2002 የሰጠው ብይን፣ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09309 በ30/10/2002 የሰጠው ትዕዛዝ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 109450 በ13/12/2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረው የገደብ አሳሳ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ሠራተኛው የአሁኑ ተጠሪ ፈጽሟል ስለሚለው ጥፋት በፍርድ ላይ በተዘረዘረው መሠረት አሉኝ የሚላቸውን ሌሎች ማስረጃዎች እንዲያቀርብ አድርገው በተገቢው መንገድ በማጣራት ከሥራ እገዳው ወይም ማሰናበቱ በሕጉ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም በሚለው ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ጉዳዩ ተመልሷል፡፡

2. የገደብ አሰሳ ወረዳ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ መሠረት እንዲፈጽም ታዟል፡፡
3. በዚህ መዝገበ በተደረገው ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተጠሰው ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኢት/መንገዶች ባለሥልጣን - ነ/ፈጅ አስመላሽ ገሠሠ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አሚናት ገበየሁ - በሌለችበት የሚታይ

ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 6083 ኀዳር 7/1997 በዋለው ችሎት የኮምቦልቻ ወረዳ ፍ/ቤት በቁ. 633/96 ጥቅምት 22/97 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ ክሱን ያቀረቡት ሟች ሀሰን ዓሊ የተባለው ልጃ በተከሣሽ መ/ቤት ከ1978 ዓ.ም. ጀምሮ በወር ብር 285 እየተከፈለው በሠራተኛነት ሲያገለግል ቆይቶ በአደረበት ሕመም በ20/8/96 ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ የሟች ወራሽ በመሆኔ የልጇን የ18 ዓመት የአገልግሎት ካሣና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ይክፈሉኝ የሚል ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39/2/3/ እና አንቀጽ 110/2/ሐ/፣ 3/ሐ/ መሠረት የሠራተኛው የዓመት ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ ተከሣሽ ለከሳሽ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ የዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ አጽንቶታል፡፡

አቤቱታው የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለበት ምክንያትም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39 መሠረት የአገልግሎት ካሣ እንዲከፈል የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ነው፡፡

ከሥር ክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው ለሥራ ውሉ መቋረጥ ምክንያት የሆነው የአመልካች ሠራተኛ የነበረው ሟች በአደረበት ሕመም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ከአሠሪው የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሚኖረው በአዋጁ አንቀጽ 39/1/ ሥር ከ/ሀ/ እስከ/ረ/ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ ነው፡፡

በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረት ሠራተኛው በሞት ምክንያት የሥራ ውሉ ቢቋረጥ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚጠየቅበት አይደለም፡፡ ሕጉ መብት አይሰጥም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ፍ/ቤቱ ክፍያው ይፈፀም ያለው በአዋጁ አንቀጽ 39/1/ መሠረት በቅድሚያ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ስለመኖር አለመኖሩ ሳያረጋግጥ በአንቀጽ /2/ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያው በአንቀጽ 110/2/ ለተመለከቱት ጥገኞች ይከፈላቸዋል የሚለውን በማየት ብቻ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 39/2/ ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ግን በአንቀጽ 39/1/ መሠረት የስንብት ክፍያ የማግኘት መብት መኖሩ የተረጋገጠ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቱ የሥራ ስንብት ክፍያው እንዲከፈል የወሰነው የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39/1/ እና /2/ ድንጋጌን በአግባቡ ባለማገናዘብ ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኮምቦልቻ ወረዳ ፍ/ቤት በቁ. 633/96 ጥቅምት 22/97 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና ይህንኑ በማጽናት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 6083 ኅዳር 7/97 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የተሻረ መሆኑንም እንዲያውቁት የዚህ ውሣኔ ቅጂ ይተላለፍላቸው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- ከማል በድሪ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ጌታቸው ምህረቱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ፋንታሁን አባተ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቢሲኒያ ባንክ አ/ማ - ቀረቡ (ነ/ፈጆ እስክንድር)

ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ውሣኔ የሰጠው የፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በስራ ላይ ለነበሩበት ጊዜ የተከፈለው የሁለት ወራት ቦነስ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የቦነስ ክፍያ ዋና አላማው ሠራተኛ በስራ ላይ በነበረበት ወቅት የሠራው ስራ ለአሠሪው ጥሩ ውጤት አስገኝቶ ከሆነ በስራ ላይ ያለው ሠራተኛ ለወደፊት ውጤታማ እንዲሆን ለማበረታታት እንጂ ስራውን የለቀቀ ሠራተኛ እንደመብት የሚጠይቀው አይደለም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም የቀረበውን ይግባኝ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች በስራ ላይ ለነበሩበት ጊዜ የተከፈለውን የቦነስ ክፍያ ለአመልካቹ ስራ በመልቀቃቸው ሊከፈላቸው አይገባም የተባለበትን ህጋዊ ምክንያት በመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ተጠሪ ተጠርቶ ቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው አመልካች ስራ ላይ በነበሩበት ወራት ለተሰራ ስራ የተከፈለው ቦነስ አመልካች ከሥራ ከተሰናበቱ በኋላ ሊከፈላቸው የሚገባ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡

አመልካች የተጠሪ መ/ቤት ሠራተኛ የነበሩና በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን ከለቀቁ በኋላ አመልካቹ በሥራ ላይ በነበሩበት ጊዜ ለተሰራ ሥራ የቦነስ ክፍያ ለተጠሪ መ/ቤት ሠራተኞቹ መክፈሉ ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ ፍ/ቤቶቹ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት የአመልካች የሥራ ውል በተቋረጠበት ጊዜ የተፈቀደ የቦነስ መብት ካለመኖሩም በላይ የቦነስ አላማው ሠራተኛው በሥራ ላይ በነበረበት ወቅት የሠራው ሥራ ለአሠሪው ጥሩ ውጤት አስገኝቶ ከሆነ ለወደፊትም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተመሳሳይ መልኩ በርትቶ ውጤታማ እንዲሆን ለማበረታታት እንጂ ስራውን የለቀቀ ሠራተኛ እንደመብት የሚጠይቀው አይደለም በማለት ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው ቦነስ የሚከፈለው በስራ ላይ ያለ ሰራተኛ ወደፊት በርትቶ እንዲሰራ ለማበረታታት ብቻ ሳይሆን ሠራተኛው በስራ ላይ በነበረበት ወቅት የሰራው ሥራ ለአሠሪው ትርፋማ ውጤት በማስገኘቱ የትርፉ ተጠቃሚ እንዲሆንም ጭምር የሚሰጥ የጥቅም ክፍያ ነው፡፡ በመሆኑም የቦነስ መብት ተጠቃሚ ለመሆን ለቦነስ ክፍያ ምክንያት ለሆነው ትርፍ ሠራተኛው አስተዋጽኦ ማድረግ አለማድረጉ ሊታይ ይገባል፡፡ በእርግጥ የሠራተኛው ሥራ ትርፋማ መሆን አለመሆኑ የሚታወቀው የበጀት አመቱ ሂሳብ ከተሠራ በኋላ በመሆኑ የቦነስ መብት የሚፈቀደው ይኸው ውጤት ከታወቀ በኋላ ነው፡፡ የሂሳቡ ውጤት የአሠሪውን ትርፋማነት ካረጋገጠ ግን ለትርፋማነቱ አስተዋጽኦ ያደረገው ሠራተኛ የቦነስ ጥቅም ተካፋይ ሊሆን ይገባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቹ በስራ ላይ በነበሩበት ጊዜ የተሰራው ሥራ ለመ/ቤቱ ትርፋማነት ምክንያት ሆኗል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን የቦነስ መብት የተፈቀደው አመልካቹ ከሥራ ከለቀቁ በኋላ ቢሆንም የቦነስ መብቱ የተፈቀደው የአመልካች በስራ ላይ በነበሩበት ወቅት ለተሠራ ሥራ በመሆኑ አመልካች የጥቅሙ ተካፋይ የማይሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ቦነስ በስራ ላይ ያለን ሠራተኛ ለማበረታታት ብቻ የሚሰጥ ነው በማለት የአመልካች የቦነስ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ሥህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16632 በ29/6/97 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37603 በ25/09/97 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በስራ ላይ ለነበሩበት ከሰኔ 24 ቀን 1995 እስከ ሰኔ 23/1996 ላለው ጊዜ ለሌሎች ሠራተኞች የተሰጠው ቦነስ እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. *48217*

ጥቅምት *03* ቀን *2003* ዓ.ም

ዳኞች - ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ ወ/ሮ አባዲት ለምለም የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፣ 1. የዛለአንበሳ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ወኪል አለምፀሐይ ግርማይ ቀረቡ

2. አቶ ብርሃን ዘረፈ በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ቤትና ቦታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአግባቡ በዛላንበሳ አስተዳደር የታደልኩትን በራሴ ተጨማሪ ገንዘብ ደግሞ የሰራሁትን በስሜ በርዕስተ መዝገብ የተመዘገበውን ቤትና ቦታ አስተዳደሩ ነጥቆ ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የሰጣቸው መሆኑን ገልፀው ገንዘቡና ቤቱ እንዲመለስላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበውም አመልካች ቦታና ገንዘብ የተሰጣቸው በጦርነት ምክንያት ቤት ስለወደመባቸው መንግስት ምትክ ቦታና ገንዘብ እንዲሰጥ በአስተላለፈው አስተዳደራዊ ውሣኔ በመሆኑና ይህም ውሣኔ ፖለቲካዊ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ እንደማይችል በመግለፅ አመልካች ክስ ለመመስርት የሚያስችላቸው ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ያሳያል በማለት ያቀረበው ክርክር ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም የአመልካች ጥያቄ በአስተዳደሩ ተጣርቶ ቤትና ገንዘብ ከመንግስት ሊያገኙ የማይችሉበት ምክንያት በመገኘቱ ውድቅ የሆነ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪም ቤትና ገንዘቡን የመንግስት አስተዳደር አካላት በሰጡት ውሣኔ መሠረት የተሰጣቸውና የተረከቡት በመሆኑ ሊከሰሱ እንደማይገባ ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶና መርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤትና ገንዘብ ለአመልካች ሊመለስላቸው እንደሚገባ ገልፆ ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ጉዳዩ ተመርምሮ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የሚያልቅ እንጂ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 30 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የአመልካች ጥያቄ ቤትና ገንዘብ ያላግባብ ተነጠቅሁ የሚል ሁኖ እያለ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻሩ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና በሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩ አስተዳደራዊ ስለሆነ በፍርድ ቤት መዳኘት የለበትም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻሩ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪዎች መጥሪያ ተልኮላቸውና መድረሱም ተረጋግጦ ሊቀርቡ ስላልቻሉ ጉዳዩ ተጠሪዎች በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በበታች ፍርድ ቤቶች ግራቀኙ ያደረጉትን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በዛላንበሳ አካባቢ በጦርነት ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለነበሩት ዜጎች ማቋቋሚያ የሚሆን መሬትና የብር 25,000.00 /ሃያ አምስት ሺህ/ ቤት መስሪያ እርዳታ ለመስጠት የተለያዩ አካላት ተወካዮች ያሉበት ኮሚቴ ማቋቋሙን መንግስት ባወጣው የችግረኛ ተረጂዎች መለያ መስፈርት መሠረት በጦርነቱ ተፈናቅለው በፕላስቲክ ዳስ የሚኖሩ 969 ተፈናቃዮች በዕዳ መሬት ተሰጥቷቸው ገንዘቡም በየደረጃው በሶስት ጊዜ እንዲሰጥ ተወስኖ ብር 7,500.00 በማቋቋሚያ ኮሚሽን መስጠቱን አመልካችም በጦርነቱ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በፕላስቲክ ዳስ የሚኖሩና ለተረጂነት የሚያሟሉ መሆኑ ተረጋግጦ መሬት ተሰጥቷቸው በስማቸው በማዘጋጃ ቤት ተመዝግቦ የመሬት ኪራይ ካርታ የዕዳት የቤት ስራ ፈቃድ የቴክኒክ አገልግሎት የችካል የይዞታ ማረጋገጫ ክፍያዎችን በሙሉ ከፍለው ከመንግስት በእርዳታ የተሰጣቸውን ብር 7,500.00 እና ከራሳቸው ብር 7000.00 ጨምረው በብር 14,500.00 የቆርቆሮ ክዳን እስኪቀረው ቤቱን ሰርተው ከጨረሱ በኃላ ኤርትራዊ ነሽ በሚል ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ነጥቆ ለሁለተኛ ተጠሪ እንዲሰጥ ማድረጉን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የተቻለው አመልካች የሚከራከሩት በመንግስት በተሰጣቸው ቦታና ገንዘብ የራሳቸውን ገንዘብ ጨምረው የገነቡት ቤትና ቦታ ያላግባብ የተነጠቁ በመሆኑ በፍርድ ኃይል እንዲመለስላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን ነው፡፡

በመሠረቱ በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍ/ቤቶች ብቻ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 79/ለ/ ተደንግጓል፡፡ የሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ ፍ/ቤቶች በማናቸውም ጉዳይ ገደብ የለሽ ስልጣን የሌላቸው መሆኑም ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሕገመንግስቱ አንቀጽ 79/ለ/ እና 37 አንድ ላይ ሲታዩ ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ለማየትና ለመወሰን ሥልጣን የሚኖራቸው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው /Justiciable matter/ ሆኖ ከተገኘ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 “ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡" በሚል ከተደነገገው "…. ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል….." የሚለው እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 4 በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም በህግ ካልተገለፀ ክሱን ተቀብሎ ለማከራከር ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ብቻ ነው በሚል መደንገጉ በፍርድ ሊወሰን በሚችለው ጉዳይ ፍ/ቤቶች ብቸኛ ስልጣን ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ማየት የሚችሉት ጉዳዩ በፍርድ የሚያልቅ ሲሆንና በሌላ አኳኋን እንዲታይ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካች ጥያቄ ቤትና ቦታዬን ያላግባብ ተነጠቅሁ የሚልና በፍርድ ኃይል የንብረት መብቻው እንዲከበርላቸው የሚጠይቅ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ጉዳይ በፍርድ እንዳያልቅ የሚከለክል ሕግ የሌለ ሲሆን ጉዳዩ አስተዳደራዊ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያትም የለም፡፡ ጉዳዩን እንዲዳኝ በሕግ ተለይቶ ስልጣን የተሰጠው አካልም የለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው /Justiciable matter/ ጉዳይ እንጂ በአስተዳደር የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በአስተዳደር የሚያልቅ ነው በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መሻሩና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ውሣኔ ማጽደቁ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 23281 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 25845 ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም በአብላጭ ድምጽ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ጥያቄ ያላግባብ ቤትና ቦታዬን ተነጠቅሁኝ የሚል በመሆኑ በፍርድ ሊወሰን የሚችል እንጂ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የሚያልቅ አይደለም ብለናል፡፡
3. ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚችል በመሆኑ የስር የዞን ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሣኔ የግራቀኙን ማስረጃዎችንና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን በመመርመር በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ሥሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- እነ አቶ ከድር ኃሌጅንሶ /አስራ ሁለት ሰዎች/- ጠበቃ አማን ቡልቡላ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመሬት ይዞታ ካሣ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታህሣሥ 13 ቀን 1998 ዓ.ም በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ በክሱ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው 6666 ካሬ ሜትር የሆነው የእርሻ መሬት ይዞታ የነበራቸው መሆኑን፣ አመልካች በዚሁ የእርሻ መሬት ላይ ጥቅምት 05 ቀን 1997 ዓ.ም ካምፕ ያሰፈረበት መሆኑን፣ እያንዳንዳቸው በመሬቱ ላይ በሄክታር ሰላሣ ኩንታል ስንዴ የሚያገኙ መሆኑን፣ በወቅቱ የአንድ ኩንታል ስንዴ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ መሆኑን ገልፀው የአምስት ዓመት ምርት በጠቅላላው ብር 240,000.00 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ እንደሚያወጣ ጠቅሰው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 7 እና 8 መሠረት ካሣውን እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ተጠሪዎች የመሬቱን ባለይዞታ መሆናቸውን የሚያሣይ ማስረጃ ስላላቀረቡ ለመክሰስ የማይችሉ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ካምፑ የሰፈረበትን መሬት የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት የተረከበ መሆኑን፣ ካምፑ ከሰፈረሰበት መሬት ውስጥም 20794.5 ካ.ሜትር ላይ ብቻ መኖሩን የሚመለከተው አካል አረጋግጦ በአዋጅ ቁጥር 80/89 እና 401/96 መሠረት ተገቢው ካሣ መከፈሉን፣ በቀሪው 79,205.5 ካ.ሜትር ላይ ግን መሬቱ ባዶ ስለሆነ የወረዳ አስተዳደርም ሆነ የቀበሌ አስተዳደር ያነሱት የካሣ ጥያቄ ሣይኖር መሬቱን የተረከቡ መሆኑንና በዚሁ ይዞታ ላይ የቀረበው ክስ በተጨባጭ ማስረጃ ተደግፎ ያልቀረበ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪዎችን ምስክሮችን ከሰማ እና መሬቱ እህል የሚያበቅል መሆን ያለመሆኑን ከሚመለከተው አካል ማጣራት ከአደረገ በኋላ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ ለካሣው በአዋጅ ቁጥር 401/96 መሠረት ኃላፊነት አለበት የሚል ምክንያት በመስጠት ለክሱ መሠረት የሆነውን የገንዘብ መጠን አመልካች እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ የካቲት 03 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪዎች በአከራካሪው የመሬት ይዞታ መብት ያላቸው ስለመሆኑ ሣያረጋግጡ እና መሬቱ በተወሰደበት ሰዓትም በይዞታው ላይ ምንም ሰብል በሌለበት ሁኔታ የአምስት ዓመት ካሣ ይከፈላቸው ተብሎ የተወሰነው ከሕጉ ውጭ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪዎች በይዞታው ላይ መብት ወይም ጥቅም የነበራቸው ስለመሆኑ የተረጋገጠ መሆን አለመሆኑ እና ከአዋጅ ቁጥር 401/96 አኳያ ካሣ ይከፈል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡በዚህም መሠረት ተጠሪዎች በወኪሎቻቸው አማካኝነት ሐምሌ 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የጽሑፍ መልስ የሰጡ ሲሆን የአመልካች ነገረፈጅ በበኩላቸው ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች ክሱን የመሠረቱት የእርሻ መሬት ይዞታችን በአመልካች ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ተወስዶ ካሣ ስላልተከፈለን ሊከፈለን ይገባል በሚል መሆኑን፣ አመልካችም ተጠሪዎች ክስ ለመመሥረት የሚያስችላቸው መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑንና ለክሱም በአጠቃላይ ሕጋዊ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመጥቀስ የተከራከሩ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች ተጠሪዎች ክስ ለመመሥረት መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በሚል ያቀረበው ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉበትን አግባብ ይህ ችሎት ለመመርመር የሚችል መሆን ያለመሆኑን ስንመለከተው ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች በይዞታው ላይ መብት የነበራቸው መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጣቸውን መሠረት በማድረግ የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረጉ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ አመልካች የማስተባበያ ማስረጃም ከሚመለከተው አካል አላቀረበም፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ይዞታውን ተጠሪዎች ቀበሌ አስተዳደሩ በፃፈው አንድ ደብዳቤ እና የግብር ካርኒዎች ብቻ ሊያረጋግጡ አይገባም የሚል እንድምታ ያለውን ክርክር በማቅረብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቀበሌ አስተዳደሩ የፃፈው ደብዳቤና የግብር ካርኒ ይዞታን ለማረጋገጥ አግባብነት የሌለው ማስረጃ ነው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሠረት የለም፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤት ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግሥት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ ፍሬ ጉዳዩን ለማጣራት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር አልፈነዋል፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ሌላውና ዋናው ነጥብ ተጠሪዎች ካሣ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ከአዋጅ ቁጥር 401/96 መንፈስና ይዘት ውጪ ነው የሚለው ሲሆን ይህ ችሎት ይህንኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክርክር ነጥብ ከሕጉ ጋር አሣምዶ ተመልክቷል፡፡ አመልካች የተጠሪዎች የእርሻ መሬት ይዞታ ወሰደ ተብሎ የተረጋገጠው ጥቅምት 05 ቀን 1997 ዓ.ም ሲሆን ተጠሪዎች ክሱን የመሠረቱት ታህሣሥ 13 ቀን 1998 ዓ.ም ነው፡፡ እንዲሁም አመልካች ወሰደ የተባለው መሬት በወቅቱ እህል ማብቀል የሚችል መሆን ያለመሆኑ በሚመለከተው አካል ከመረጋገጡ ውጪ በአመልካች ሲወሰድ የስንዴ አዝመራ የነበረበት አለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በባዶ የእርሻ ይዞታ መሬት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት የተባለው መሬቱ ወደፊት ሊዘራበትና ሊመረትበት የሚችል ነው በሚል ምክንያት መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ እና ከአጠቃላይ የክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ እንግዲህ ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ አግባብነት ያለው ሕግ የትኛው ነው? በዚሁ ሕግ መሠረትስ አመልካች ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት? ወይንስ የለበትም? የሚለው ጥያቄ መታየት ያለበት ነው፡፡

አመልካች የተጠሪዎችን የእርሻ ይዞታ መሬት መወሰዱ በተረጋገጠበት ጥቅምት 05 ቀን 1997 ዓ.ም ስራ ላይ የነበረውና ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አዋጅ ቁጥር 401/96 ነው፡፡ ተጠሪዎች ክስ የመሠረቱት ታህሣሥ 13 ቀን 1997 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ወቅት ስራ ላይ ያለው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ ስለሚለቀቅበትና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 455/97 መሠረት ነው፡፡ ተጠሪዎች ከጉዳዩ አግባብነት አለው በማለት የሚከራከሩትም ክስ በመሠረቱበት ወቅት ተፈፃሚ የሆነውን ይህንኑ ሕግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አዋጅ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የተደረገው ከሐምሌ 08 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን በመሸጋገሪያ ድንጋጌም አዋጅ ቁጥር 401/96 ተፈፃሚነት በነበረበት ወቅት የተወሰዱ የመሬት ይዞታ ጉዳዮች በአዋጅ ቁጥር 455/97 መሠረት የሚታዩበት አግባብ ስለመኖሩ አላስቀመጠም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ መታየት ያለበት መሬቱ ተወሰደ በተባለበት ወቅት ስራ ላይ በነበረው አዋጅ ቁጥር 401/96 መሠረት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9/1/ መሠረት መሬት የሚወሰድበት ባለይዞታ በገንዘቡ፣በጉልበቱ፣ ወይም በፈጠራ ችሎታው ላፈራውና በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት እንዲሁም ላደረገው ቋሚ ማሻሻል ካሣ ይከፈለዋል በሚል የተደነገገ ሲሆን የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ከባለይዘታው በሚወሰደው መሬት ላይ ለሚገኝ ንብረት የሚከፈል ካሣ ንብረቱን ለመተካት ከሚያስፈልገው ወጪ ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል ሲል ደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ የምንገነዘበው አቢይ ነጥብ የካሣ መሠረትና መጠን የሚወሰነው በይዞታው ላይ ንብረት ያለ መሆኑ ሲረጋገጥ መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም መሬቱ ሲወሰድ ንብረት ያልነበረ ከሆነ ካሣ ሊከፈል ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚያገኘው በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የመሬት ይዞታው በቋሚነት የሚወሰድበት ሰው በመሬቱ ላይ ሰብል ወይም ተክል ቢኖርም ባይኖርም ተመሣሣይ መሬት ያለው ሰው የሚያገኘው አማካይ ገቢ በአዋጁ አንቀጽ 9 ከሚከፈለው ካሣ በተጨማሪ የሚከፈለው ስለመሆኑ በመርህ ደረጃ በንዑስ ቁጥር አንድ ስር ያስቀመጠ ሲሆን ዝርዝሩም በደንብ እንደሚወሰን ያሣያል፡፡ የተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌም የመሬቱ ይዞታው ለተወሰነ ጊዜ ለሚወሰድበት ሰው ወይም ለወል መሬት ባለይዞታዎች በመሬቱ ላይ ሰብል ወይም ተክል ቢኖርም ባይኖርም መሬቱ ባይለቀቅ ኖሮ ከመሬቱ ሊገኝ ይችል የነበረው ገቢ መሬቱ እስከሚመለስ ድረስ ላለው ጊዜ ታስቦ በአዋጁ አንቀጽ ዘጠኝ መሠረት ከሚከፈለው ካሣ በተጨማሪ እንደሚከፈል፣ በአንቀጽ አስር ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ከሚከፈለው ክፍያ መብለጥ እንደሌለበትና ዝርዝሩም በደንብ እንደሚወሰን ደንግጓል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ አስር ንዑስ ቁጥር አንድ እና ሁለት የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት የመሬት ባለይዞታው ለተወሰደበት ሰው ተተኪ መሬት ያልተገኘለት መሆኑን አግባብ ያለው የመስተዳድር አካል ሲያረጋግጥ ብቻ እንደሆነ ተጠቃሹ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሦስት ስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ለተጠሪዎች ካሣ እንዲከፈል የስር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት ደንቡን መሠረት በማድረግ ባይሆንም ይዞታው ምን አይነት ሰብል እና ምን ያህል መጠን ሊያስምርት እንደሚችል ከሚመለከተው የክፍሉ አካል የስር ፍርድ ቤት ማረጋገጫ እንዲቀርብለት አድርጎ ባጣራው መሠረት ነው፡፡ ተጠሪዎች ለተወሰደባቸው መሬት ይዞታ ተተኪ መሬት የተገኘላቸው ወይም የተሰጣቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፣ አመልካችም በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የለም፣ በስር ፍርድ ቤትም የሚመለከተው አካል ለተጠሪዎች ተተኪ መሬት የተገኘላቸው ስለመሆኑ የገለፀው ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በአዋጁ አንቀጽ አስር ንዑስ አንቀጽ አንድ፣ ሁለት እና ሶስት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መሰረት የመፈናቀያ ካሣ የማያገኙበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመጨረሻ የተወሰነው የመፈናቂያ ካሣ መጠን ሲታይም የተጋነነ ወይም ከክፍሉ አካል ከቀረበው ማረጋገጫ ይዘት ውጪ ነው ለማለት የሚያስችልም አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ባለይዞታ ስለመሆናቸው ተረጋግጧል እስከተባለ ድረስ በቦታው ላይ ሰብል ሣይኖር ቦታውን አመልካች መውሰዱ የመፈናቂያ ካሣ ለተጠሪዎች እንዲከፈል የሚያደርግ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 401/96 አንቀጽ 9 እና 10 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/7/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ሆኖ ስለአገኘን በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 55081

ጥቅምት 18 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሪት ራሔራ ሥነፀሐይ - ጠበቃ አስረስ ባያው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መስፍን ታምራት - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤትና የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የፍርድ ባለመብት የሆኑበትን እዳ ለማስከፈያ እንዲሆን የፍርድ ባለእዳው የተጠሪው ንብረት የሆነ ቤት እንዲሸጥላቸው አመልካች አመልክተዋል፡፡ ቤቱ በፍርድ ባለእዳው ልጅ ተማሪ ማራማዊት መስፍን ስም ስሙ ተዛውሮና ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ ቤቱን የእዳ መክፈያ እንዳይሆን ለማሸሽ ያደረጉት ድርጊት በመሆኑ በልጃቸው ተማሪ ማራማዊት መስፍን ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ንብረት ተሸጦ ፍርዱ እንዲፈፀምልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዲውል የጠየቁት ቤት በፍርድ ባለ እዳው ስም ሳይሆን በተማሪ ማሪማዊት መስፍን ስም የሚገኝ በመሆኑ አፈፃፀሙን በቤቱ ላይ ማስቀጠል አይቻልም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች የፍርድ ባለእዳ የሆነው ተጠሪ ቤቱን ለእዳ መክፈያ እንዳይሆን ለማሸሽ በማሰብ ምንም አይነት ሐብት ለሌላት አካለ መጠን ላልደረሰች ልጁ የቤቱን ስመ ንብረት በማዛወር የፈፀመው ተግባር መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የማራማዊት መስፍን ነው፡፡ ለዚህም ቤቱ የማራማዊት መስፍን መሆኑን የሚያረጋግጥ ውልና የቤቱ ክፍያ የተከፈለባቸው ወርሀዊ ደረሰኞች ስላሉ ቤቱ የፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር የተገለፀው ሲሆን ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ የሆነበትን ገንዘብ ለመክፈል ጥረት በሚደረግበት ጊዜ ቤቱ የተጠሪ ልጅ በሆነችው ህፃን ማራማዊት መስፍን ስም የተዛወረ መሆኑ የስር ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ተረጋግጧል፡፡ የቤቱ ባለቤት ናት ቤቱም በስሟ ተመዝግቧል የምትባለው ማራማዊት መስፍን ህፃን መሆኗን የስር ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ተረጋግጧል፡፡

አንድ ሰው የንብረት ባለቤት የሚሆነው በጉልበቱ በፈጠራ ችሎታው ወይም በገንዘቡ ንብረቱን ያፈራው ሲሆን እንደሆነ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ በተጠሪና በተጠሪ ባለቤት በወ/ሮ አለም ዘውዱ ዘርፉ ስም ተመዝግቦ የነበረው ቤት በህፃን ልጃቸው በህፃን ማራማዊት መስፍን ስም አዛውረው ቤቱን በህፃን ማራማዊት ስም አስመዝግበው መገኘታቸው ብቻውን ህፃን ማራማዊት መስፍን የቤቱ ባለሐብት ናት ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ በፍርድ የተወሰነበትን እዳ መክፍያ እንዳይሆን ቤቱን በራሷ መንገድ ሰርታ ባገኘችው የገቢ ምንጭ የገዛችው ስለመሆኗ ሳያረጋግጥ የንብረቱ በህፃን ልጅ ስም በማዛወር ለፍርድ ማስፈፀሚያነት ንብረቱ እንዳይውል ለማሸሽ የሞከረ መሆኑን የሚያመለክት ተግባር ነው፡፡

የፍርድ ባለእዳ የሆነ ሰው ንብረቱ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እዳይውል አካለ መጠን ባልደረሰ ህፃን ልጁ ስም እያዛወረ መልሶ ንብረቱን በሞግዚትነት የሚያስተዳድርበት የሚሸጥበትና የሚለውጥበትን ሁኔታን ህጋችን አይፈቅድም፡፡ ባለእዳው መክፈል የሚገባውን እዳ ባለመክፈል በአጭበርባሪነት የሚፈጽማቸውን ተግባራት የፍርድ ባለመብት ወይም ገንዘብ ጠያቂው የመቃወምና እዳውን ላለመክፈል ያደርገው ተግባር መሆኑን ለማሳየት በማጭበርበር የተሰራው ስራ ዋጋ እንዳይኖረውና ባለእዳው እዳውን እንዲከፍል ማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1895 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1896 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መዝገብ በተጠሪና በአመልካች ስም የነበረውን ቤት ተጠሪ በህፃን ልጁ ለማራማዊት መስፍን ስም ማዛወሩ ንብረቱ የፍርድ ማስፈፀሚያ እንዳይሆን ለማድረግ የተፈፀመ የማጭበርበር ተግባር ነው በማለት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤትና የከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. በመጀመሪያ በተጠሪና በባለቤታቸው ወ/ሮ ዓለም ዘውድ ዘርፉ በአሁኑ ጊዜ በህፃን ማሪማዊት መስፍን ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት አመልካች በፍርድ ያስወሰኑትን ገንዘብ ማስፈፀሚያ እንዲሆንና የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በሐራጅ በማሸጥ እንዲያስፈጽም ጉዳዩን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች - ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፣

1. አቶ ፀጋዩ መሠረት
2. ወ/ሮ አስናቀች ሞላ
3. አቶ ታደሰ ተንሱ
4. ወ/ሮ እቴቱ አስፋው
5. ወ/ሮ ከበደች ባሕታ
6. አቶ ሀይለሚካኤል ወልደገብርኤል
7. አቶ ፀጋዬ ዋቄ
8. ወ/ሪት ፍቅርተ ጴጥሮ
9. አቶ ሀይሌ ካሣይ
10. አቶ አስናቀ እጅጉ
11. አቶ ባልቻ ያህያ
12. አቶ አሉላ ዘሪሁን
13. አቶ ንጉሴ አለሙ
14. ወ/ሮ ቅድስት አበበ
15. አቶ ብርቁ ፈቃዱ
16. አቶ ከተማ ተክሉ
17. አቶ ገብሩ ገብርሥላሴ
18. አቶ አሰፋ መልካ
19. አቶ ግርማ ገብረስላሴ
20. አቶ ደበበ ደምሴ
21. ወ/ሮ እቴነሽ ያደቴ
22. አቶ ገረመው ቦጋለ
23. አቶ መዝይን መሐመድ
24. አቶ ክንፈ ገብሩ
25. አቶ ጌታቸው በቀለ
26. ወ/ሮ ጣይባቸው ደግፌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

27. አቶ ሰይፈ ተሾመ
28. አቶ ጌቱ ሀይሉ
29. አቶ ጌታቸው ደምሴ
30. ወ/ሮ አበራሽ ዲባባ
31. አቶ ተስፋዬ ሀይለጊዮርጊስ
32. አቶ ፍቅሬ መላ
33. አቶ አብርሃም ሀይሉ
34. ወ/ሮ ሙንትሀ አወል
35. አቶ ባርክልኝ ኑር
36. አቶ ዋናው ሀይለማርያም
37. አቶ ገብረዩሐንስ ሰባኔ
38. አቶ እንዳለው በየነ
39. ወ/ሮ ሉባባ ይልማ
40. ወ/ሪት ሙስዓለም ዳመጠው
41. የአስር አለቃ ክብረት ቱሉ
42. መቶ አለቃ ሳሙኤል ክብረት
43. አቶ ሙሉ በረዳ
44. አቶ ጌታቸው ደፍሰህ
45. አቶ ማዕረጉ ሽፋ
46. ወ/ሮ አለም ሲሳይ
47. አቶ ኤርካ ጉርሙ
48. ወ/ሮ አሰለፈች ደስታ
49. ወ/ሮ ባዩሽ ስጠኝ
50. አቶ አብራ መላ
51. አቶ ጌታቸው ካሣዬ
52. አቶ አወጣኸኝ አማረ
53. አቶ አረጋይ ቤኛ
54. ወ/ሮ አለም ተፈራ
55. አቶ ታምራት ቱሉ
56. አቶ ሀይሉ ታችበሌ
57. አቶ አበበ ተካ
58. ወ/ሮ ድጌረዳ መንግስትአብ
59. ወ/ሮ አስናቀች እሸቱ
60. አቶ አማረ ፀጋዬ
61. አቶ ተስፋዬ አበበ
62. ወ/ሮ አሰገደች ክብረት
63. ወ/ሮ ግምጃ ጉርሙ
64. አቶ ከበደ ባራኪ
65. ወ/ሮ አሰገደች ቱሉ
66. አቶ ገረመው ይርዳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

67. አቶ ጫኔ ተፈራ
68. አቶ መኮንን አሰፋ
69. አቶ ሲሳይ ግርማይ
70. ወ/ሮ ዘነበች ገብረህይወት
71. ወ/ሮ ልዑል ገባኢ
72. ወ/ሮ ጋዲሴ ሞላ
73. አቶ ካሣሁን አለሙ
74. አቶ ጣሰው ፈይሳ
75. አቶ ብርሃኑ ገብሬ
76. ወ/ሮ ቀነኔ ደባ
77. አቶ ሀብታሙ ወልደማርያም
78. ወ/ሮ ለተ ትንሣኤ
79. ወ/ሮ አስቴር ቀለታ /ወ/ሮ አስናቀች ተፈራ/

ተጠሪ - የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን - ነገረፈጅ አወቀ ታረቀኝ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የመጨረሻ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት በጠበቃቸው አማካኝነት ህዳር 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ የአሁን አመልካቾችና ሌሎች ሰዎች በድምሩ 151 ሰዎች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ አሁን ላለው የአሽከርካሪዎችና መካኒኮች የሥልጠና ማዕከል ለማስፋፋት በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስትር 130,777 ካሬ ሜትር ቦታ የካቲት 7 ቀን 1982 ዓ.ም የተሰጠው መሆኑን ገልፀው በወቅቱ በቦታው ላይ የነበሩት ሰላሣ ዘጠኝ ሰዎች የቤታቸውን ግምት ተቀብለው በተዘጋጀላቸው ቦታ እንዲዛወሩ ተወስኗል፡፡ በዚህ መሠረት ግምት የተቀበሉት ቦታውን እንዲለቁ ወይም የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ ሌሎቹም በህገወጥ መንገድ በቦታው የሰፈሩ በመሆኑ ቦታውን ለቅቀው እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካቾች የተጠሪ ክስ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በቦታው ላይ የሰፈርነው መንግስት እያወቀው በህጋዊ መንገድ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ቤታችን የተገመተው በዝቅተኛ ዋጋ ነው ስለዚህ እንደገና ተገምቶ ካሣ ሊሰጠን ይገባል የሚል ዝርዝር የመከራከሪያ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ቦታውን ተጠሪ በህዝብ አገልግሎት ስም ተቋም ለማስፋፋት በህጋዊ መንገድ የያዘው በመሆኑና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149/1/ ለእንደዚህ አይነት ሁኔታ የሚያገለግል ባለመሆኑ ተገቢነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ስማቸውን ከአንደኛ ተራ ቁጥር እስከ ስልሣ ዘጠነኛ ተራ ቁጥር የጠቀሳቸው ተከሣሾች በወቅቱ የንብረታቸው ግምት ተገምቶ ግምቱን እንዲቀበሉ በመሆኑና ምትክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቦታ ተዘጋጅቶ የተሰጣቸው በመሆኑ የተጠሪን የይዞታ መሬት የማያስረክቡበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ ቦታውን ለተጠሪ ያስረክቡ ስማቸው ከተራ ቁጥር 40 እስከ 151 የተዘረዘሩት ተከሣሾች የቤታቸው ግምት ያልወሰዱ ስለሆነ ቤቱ በፊት በነበረው ግምት መጠን በቅድሚያ በመክፈል ወይም ተመሳሳይ ቤት እንዲሰጣቸው አድርጎ ይዞታውን ማስለቀቅ ይችላል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ስልሣ ዘጠኝ የሚሆኑ አመልካቾች ይግባኝ ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ሰዎቹ በቦታው ላይ የሠፈሩት በህገወጥ መንገድ ሆኖ እያለ ካሣ እንድከፍል መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሥር ተከሣሽ የነበሩና አሁን ይግባኝ ባይ የሆኑ ሰዎች በአስተዳደር አካላት ህጋዊ ነዋሪዎች መሆናቸውና የተለያዩ ማስረጃዎች የተሰጣቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት ለሚፈርሰው ቤታቸው ተጠሪ ግምት እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው በማለት የተጠሪን መስቀለኛ ይግባኝ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የካሣውን መጠን በተመለከተ ይግባኝ ባዮችም ሆኑ ሌሎች ግለሰቦች ቤታቸው ተጠንቶ ለተወሰኑት ካሣና ምትክ ቦታ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በወቅቱ በቤቶቹ ግምት ላይ የቀረበ መቃወሚያ አልቀረበም ካሣው ለይግባኝ ባዩች ሣይከፈል የዘገየው ይግባኝ ባዮች በስምምነቱ መሠረት የክፍሉ ማዘጋጃ ቤት ወደአዘጋጀው ቦታ ለማዛወር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እና አከራካሪውን ቦታ ይዘው ለመቆየት በመፈለጋቸው በመሆኑ ጥፋቱ የይግባኝ ባዩች ነው ጥፋቱ የይግባኝ ባዩች ከሆነ መልስ ሰጭ/ተጠሪ/ በወቅቱ በነበረው ግምት መሠረት እንጂ አሁን ባለው የገበያ ዋጋ ለቤቶቹ ግምት የሚከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አቤቱታውንም ሰርዞታል፡፡ አመልካቾች ለሰበር ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አመልካቾችና ሌሎች በቦታው /ስፍራው/ የሚገኙ ከሶስት መቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ከሰላሣ አንድ ዓመት በላይ የያዙትን ይዞታ እንዲለቁ ክስ የቀረበው የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስትር ፈቅዶልኛል በማለት ነው፡፡

መንግስት አንድ ንብረት የሚወሰደው ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውና ተመጣጣኝ ካሣ ሲከፍል ብቻ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ቦታው ለህዝብ ጥቅም የሚፈለግ ስለመሆኑ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሰጠው ውሣኔ አልቀረበም፡፡ ቦታው በሊዝ የተወሰደ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሰነው ውሣኔ የለም፡፡ ስለዚህ ቦታው ለህዝብ ጥቅምና አገለግሎት የሚውል መሆኑ በተገቢው የመንግስት አካል ሣይወሰን ተጠሪ ይዞታን ለማስፋፋት በማቀድ ያቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም ተጠሪ በዚህ አይነት ሁኔታ ከንብረታችንና ከይዞታችን ለማስነሣት የሚያደርገው እንቅስቃሴ የህገመንግስቱ አንቀጽ 40/8/ ና አዋጅ ቁጥር 272/1994 ድንጋጌ ውጭ በመሆኑ ካሣውም እነዚህን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የተሰራ ባለመሆኑ የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በይግባኝ የተከራከሩት ስልሣ ዘጠኝ ሰዎች ብቻ ሲሆኑ ሰባ ዘጠኝ ሰዎች ለችሎቱ የሰበር አቤቱታ ማቅረባቸው ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም የማሰልጠኛ ተቋሙ በአገራችን የትራፊክ አደጋን ለመቀነስና የትራፊክ ደህንነትን ለማጎልበት አስፈላጊ መሆኑ በመንግስት ታምኖበት በከፍተኛ በጀትና ወጭ የተቋቋመ ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡ ተቋሙን ለማስፋፋት በአቅራቢያው ያለውን ምቹ ቦታ እንዲንወሰድ ሥልጣን ባለው አካል ውሣኔ ተሰጥቶበት የቦታው ባለይዞታ የሚያደርገን ካርታና ፕላን ተሰጥቶናል ስለዚህ አመልካቾች ቦታውን ላለመልቀቅ የሚያቀርቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት በቃል ክርክር መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካቾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሣይወሰን ቦታውንና ንብረታችንን እንድንለቅ መደረጉ ህጋዊ አይደለም በማለት በጠበቃቸው አማካኝነት በቃል ክርክር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ በፅሑፍና በቃል ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካቾች ቦታውንና ንብረቱን ለተጠሪ እንዲለቁ እንደዚሁም ተጠሪ በፊት በተሠራው ግምት መሠረት ለተጠሪዎች ካሣ እንዲከፍል በአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ከማየታችን በፊት ተጠሪ በይግባኝ ተከራካሪ የነበሩት ስልሣ ዘጠኝ ሰዎች ነበሩ አሁን ለሰበር ሰባ ዘጠኝ ሰዎች አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበውን ተቋውሞ መርምረናል፡፡ አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ነው፡፡ ከመዝገቡ ጋር ከተያያዘው የአዲስ አበባ አስተዳደር የሰበር ችሎት የውሣኔ ግልባጭ በከተማው ሰበር ችሎት አመልካች የነበሩት ስልሣ ዘጠኝ ሰዎች ሣይሆኑ ሰባ ዘጠኝ ሰዎች መሆናቸው በግልፅ ተመዝግቧል፡፡ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በአንድ መዝገብ ይግባኝ አቅርበው የተከራከሩት ስልሣ ዘጠኝ ሰዎች ሲሆኑ አሰሮቹ ሰዎች በይግባኝ የብቻ መዝገብ አስከፍተው በይግባኝ ሲከራከሩ ቆይተው ወደ ከተማው ሰበር አቤቱታ ያቀረቡና መዝገባቸው ተጣምሮ የታየ መሆኑን ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ለከተማ ሰበር ችሎት ያቀረቡትን አቤቱታ የተቀበላቸው ስለመሆኑ ለመለየት የማይቻል ቢሆንም ተጠሪ ተቃውሞ ከማቅረብ ውጭ እንዴትና በምን ምክንያት የከተማ ሰበር ችሎት ሰባ ዘጠኝ ሰዎች አመልካቾች የሆኑበትን አቤቱታ ተቀብሎ ትዕዛዝ ሰጠ የሚለውን ያላስረዳ በመሆኑ ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አልተቀበልነውም፡፡

ወደ መሠረታዊ ጉዳዩ ስንመለስ ተጠሪ ያቋቋመውን የአሸከርካሪና የቴክኒክ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም ለማስፋፋት ክርክር ያስነሣውና ስፋቱ 137,777 ካሬ ሜትር ቦታ በወቅቱ በነበረው ከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የተሰጠ መሆኑንና ተጠሪ የይዞታ የምስክር ወረቀት፣ ካርታና ፕላን በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል የተሰጠው መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ መንግስት ለህዝብ ጥቅም ተመጣጣኝ ካሣ በመክፈል የግለሰብ ሀብትና ንብረት መውሰድ የሚችል መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 8 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ መንግስት በህግ በኩል እንደአንድ ሰው የሚቆጠር መሆኑንና በመሥሪያ ቤቶቹ አማካኝነት ከተፈጥሮው ጋር የሚስማሙትን መብቶች ሁሉ ሊሠራባቸውና ሊያገኝ እንደሚችል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 394 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ የመንግስት መሥሪያ ቤት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ለህዝብ ጥቅምና አገልግሎት ያቋቋመውን ተቋም ለማስፋፋት ጥያቄውን ለጉዳዩ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን ላለው የከተማው ልማትና ቤት ሚኒስቴር አቅርቦ ቦታው ተሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም ቦታው ለህዝብ ጥቅም የተፈለገ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 394 ንዑስ አንቀጽ 2 ተጠይቆ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 396 አንቀጽ 2 መሠረት ታምኖበት በወቅቱ ሥልጣን ባለው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የተፈቀደ በመሆኑ አመልካቾች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሣይወሰን ቦታና ንብረታችንን እንድንለቅ መደረጉ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 8 የሚጥስ ተግባር ነው በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 272/1994 በመጥቀስ ከቦታው እንድንለቅ የተሰጠው ውሣኔ የአዋጁን ድንጋጌ የሚቃረን ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር ስንመለከት አመልካቾች በቦታው ላይ ያለውን ንብረት በማንሣት እንዲለቁ የተወሰነው ቦታው በህዝብ ጥቅምና ግልጋሎት የሚሰጥ ተቋም ማስፋፊያነት ለመጠቀም ነው፡፡ መንግስት አንድ የግል ንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚወስድበት ጊዜ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓት ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1460 እስከ ፍታብሔር ህግ ቁጥር 1488 ተደንግጓል፡፡ አመልካቾች የሚከራከሩበት ቦታና ንብረት ለህዝብ ጥቅም እንዲለቁ የተወሰነው በ1982 ዓ.ም በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መብታቸውን በማስከበር ከሚጠይቁ በስተቀር ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን አዋጅ ቁጥር 272/1994 በመጥቀስ ክርክር ማቅረባቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካቾች የህገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 8 በሚደነግገው መሠረት ለንብረታቸው ተመጣጣኝ ካሣ ተጠሪ እንዲከፍል አልተወሰነልንም በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ አመልካቾች ንብረት ተጠንቶና ግምቱ ተለይቶ አመልካቾች ማዘጋጃ ቤት ወደአዘጋጀው ቦታ ተዛውረው የንብረታቸውን ግምትና ዋጋ እንዲወስዱ ተጠየቀው የነበሩ መሆኑን በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በወቅቱ ለንብረቱ የተሰጠው ግምት ከንብረቱ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ አይደለም ብለው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1477/2/ በሚደነግገው መሠረት በሶስት ወር ለፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ እንደሌለ የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

አመልካቾች ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የህግ ድንጋጌ በሚደነግገው የጊዜ ገደብ ውስጥ በወቅቱ ለንብረታቸው የተወሰነላቸውን የካሣ ገንዘብ በመቃወም ለፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ የለም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች በቦታው ላይ ያለውን ንብረት እና ይዞታውን እንዲለቁ የሚመለከተው የመንግስት አካል ወስኖ ካሣወቃቸው በኃላ ወደ ተዘጋጀው ቦታ ላለመዛወርና ቦታውን ላለመልቀቅ የተለያየ ምክንያት እየፈጠሩ እስካሁን እንዳለቀቁ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በወቅቱ ተገምቶ ተጠሪ ያሣወቃቸውን የካሣ መጠን በመቃወም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1477 ድንጋጌዎች መሠረት አቤቱታ ለፍርድ ቤት በማቅረብ እንዲሻሻል መከራከር ወይም ቦታውን በመልቀቅ ግምቱን መውሰድ ሲገባቸው አስካሁን በቦታው ላይ መቆየታቸው ተገቢ አለመሆኑና ጥፋቱ የተጠሪ ሣይሆን የአመልካቾች መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች የህጉን ሥርዓት ተከትለው ቅሬታቸውን ማቅረብና ቦታውን በመልቀቅ ቦታውን ለተሰጠው የህዝብ ጥቅምና ግልጋሎት እንዲውል ማድረግ ሲገባቸው ይህንን ሣያደርጉ በመቅረታቸውን በመዘግየታቸው ምክንያት ንብረቱ በፊት ከተገመተው ግምት በላይ የሚጠየቁበት የህግ መሠረት የለም በማለት የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎት መወሰናቸው ንብረቶቹ በወቅቱ በግምታቸው ካሣ ሣይከፈል የቀረው በማን ጥፋት ነው የሚለውን ነጥብ ለማስረዳት ያቀረቡ ማስረጃዎችን በመመዘን የደረሱበት መደምደሚያ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውና ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ያገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47139

ኅዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ የሱፍ ሁሴን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አደን አብደላ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሱማሌ ብሔራዊ ክልል የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለጅጅጋ ዞን ያቀረበው ክስ ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ካሀ አብደላ የተባለችው እህቱ የአፈር ቤቶችና የከተማ ቦታ የነበራት መሆኑንና እህቱ ካሀ ከተጠሪ ውጭ ሌላ ወራሽ የሆነ የሥጋ ዘመድ የሌላት መሆኑን ገልፆ ሟች ካሀ ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ አክስቷ ወ/ሮ ከድጃ ሰምታ መጥታ ለተከሳሽ (አመልካች) ቤቶቹን እኔ እስክመጣ ድረስ በአደራ እየጠበቀ እንዲቆይ ለተከሳሽ (አመልካች) አባት ሁሴን አሰን ሰጥታዋለች፡፡ አቶ ሁሴን አሰን (የአመልካች አባት) በቀበሌ 02 ክልል ውስጥ ያሉትን የሟች ወ/ሮ ካሀ ቤትና ቦታ ይዟል፡፡ የቦታው አዋሳኝ በምስራቅ የአመኑር ቤት፣ በምእራብ መንገድ በሰሜን የአህመድ ሸፋው ቤተሰቦች በደቡብ መንገድ ሲሆን የሟች ወ/ሮ ካሃ ቤቶች ብዛት ሁለት ክፍል በአፈር ክዳን የተሰራ ቤት፣አምስት ክፍል በቆርቆሮ ክዳን የተሰራ ቤትና ስድስት መፀዳጃ ቤት ያካተተ ነው፡፡ አቶ ሁሴን አሰን ቤቶቹን እንዲያስረክበኝ ስጠይቀው ለረዥም ጊዜ ቤቶቹን ስንከባከብና ስጠብቅ ስለቆየሁ ገንዘብ ይክፈለኝ በማለቱ በሽማግሌ ብር 8000 (ስምንት ሺህ ብር) ልከፈለው ከተስማማን በኋላ የቤቱ ባለሐብት ለመሆኔ ካርታና ፕላን አለኝ በማለት ቤቱን ለመሸጥ እያስማማሁ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ቤቱን የሠራችው ሟች ወ/ሮ ከሃ አብደላ መሆኗን፣እና ተከሳሽ የያዘው ትክክለኛ ያልሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ትክክለኛ አለመሆኑ በማስረጃ ተጣርቶ እንዲወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፣የሥር ተከሳሽ የአሁን አመልካች በበኩሉ ቀደም ሲል ሟች ወ/ሮ ከሃ የግል ይዞታና ቤት የነበራት ቢሆንም በሕይወት እያለች ቤቱንና ቦታውን ለእኔ ወላጅ አባት ሁሴን ሐሰን ሰጥታዋለች ወ/ሮ ከሃ ቤቱን ለወላጅ አባቴ የሰጠች ስለመሆኑ ማስረጃ አለን፡፡ ከሳሽ (ተጠሪ) ገንዘብ እንዲከፍለኝ ያደረግሁበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስምምነት የለም በማለት የይዞታ ማረጋገጫ የባለቤትነት የምስክር ወረቀትና ሌሎች ምስክሮችን ዘርዝሮ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልስ ሰጥቷል፡፡

የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካችን የቃል ክርክር ሲሰማ ቤቱና ቦታው በመጀመሪያ የሚች የወ/ሮ ካሀ አብደላ መሆኑንና በአቅራቢያው ሚች ወራሽ ያልነበራት መሆኑን የተስማሙበት ፍሬ ጉዳይ እንደሆነ በውሣኔው የገለፀ ሲሆን፣ወ/ሮ ካሃ አብደላ በህይወት እያለች ቤቱን ለአመልካች አባት ሰጥታለች ወይስ አልሰጠችም የሚለው ነጥብ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት መሆኑን በመለየት ጭብጥ መሥርቷል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በጽሑፍ በተደረገ የስጦታ ውል ቤቱን ለአመልካች አባት የሰጠች ስለመሆኗ የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳላቀረበና አመልካች ያቀረበው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በአሁኑ ወቅት ቤቱ የአመልካች ንብረት መሆኑን የሚያስረዳ እንጅ ቤቱ የቀድሞ ባለሐብት ከሆነችውና የቤቱ ባለንብረት መሆኗ አከራካሪ ካልሆነው ሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ እንዴት ወደ አመልካች አባት እንደተዛወረ አያስረዳም፡፡ በሌላ በኩል ከሳሽ/ተጠሪ/ የሚች ካሃ አብደላን ቤት ከድጃ የተባለችው ሴት ለአመልካች አባት ተጠሪ የሚች ወራሽ እስኪመጣ በአደራ ይዞ እንዲቆይ የሰጠችው መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ የተደራደሩና አመልካች ብር 8000/ስምንት ሺህ ብር/ ከተጠሪ ለመቀበል ተስማምቶ ተጠሪ ገንዘብ የሌለው በመሆኑ መክፈል እንዳልቻለ አስረድቷል በማለት የአመልካች አባት ቤቱን የያዙት በአደራ በመሆኑ ለተጠሪ (ለሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ) ወራሽ እንዲያስረክብ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታቸውን አልተቀበለውም፡፡ አመልካች ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ወላጅ አባቴ አቶ ሁሴን አው ሐሰን 1986 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡ ወላጅ አባቴ በጅጅጋ 02 ቀበሌ የቤት ቁጥር 123-01 ቤት ውስጥ ይኖሩ የነበረ ሲሆን እኔም አባቴ በሞት ከተለዩ በኋላ እየኖርኩበት እገኛለሁ፡፡ ተጠሪ ቤቱ የእህቴ ወ/ሮ ካሃ ስለሆነ ይልቀቅልኝ በማለት ክስ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦብኝ እኔም አባቴ ለአርባ ስድስት ዓመት በቤቱ ውስጥ የኖረና በሶማሊያ ጦርነት ሰነዱ /ካርታና ፕላኑ/ በመቃጠሉ ወ/ሮ ካሃ በሕይወት እያሉ ሌላ ካርታና ፕላን አውጥተው የኖሩበት ነው በማለት ተከራክሬአለሁ፡፡ ቤቱ የአባቴ አክስት የሆነውንና የአባቴ አክስት ለአባቴ በሕይወት እያለ የሰጡት ቤት መሆኑን በህይወት ያሉት የአባቴ አክስት ባል አሊ ባድል ሣይጠየቁና ሣይመሰክሩ ለተጠሪ እንዲያስረክብ የተሰጠው ውሣኔ አባቴ የቤቱ ባለሐብት መሆኑን የሚያረጋግጥ የባለሐብትነት የምስክር ወረቀት ያለው ሆኖ እያለ አላግባብ የተሰጠ ውሣኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለዚህ ውሣኔው በሰበር እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የእህቴ የሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካች ሚች ወ/ሮ ካሃ ቤቱን ለአባቷ እንደሰጡ በመግለጽ የተከራከረ ቢሆንም ሚች ወ/ሮ ከሃ ቤቱን በስጦታ ያስተላለፉበትን ሰነድ በማቅረብ አላስረዳም፡፡ በእኔ በኩል የሚች ወ/ሮ ካሃ ወንድምና ወራሽ መሆኔን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቤአለሁ፡፡ የአመልካች አባት ቤቱ ከቀድሞ ባለንብረቷ ከወ/ሮ ካሃ በሕጋዊ መንገድ ሣይተላለፍላት የወጣው የባለሐብትነት የምስክር ወረቀት አመልካችን የቤቱ ባለሐብት ሊያደርገው አይችልም፡፡ ስለሆነም በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ በማለት ኅዳር 10 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ጎዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የአባቴ አክስት ከሆኑት ከወ/ሮ ከሃ አብደላ ለሚች አባቴ እንዲተላለፍና በሚች አባቴ ስም ካርታ ወጥቶበት እንደሚገኝ በአቤቱታዬ በሰፊው ዘርዝሬ አቅርቤያለሁ፡፡ ቤቱ በአባቴ ስም ካርታ ያለው በመሆኑ ተጠሪ ከዚህ የበለጠ የቤቱ ባለሐብት ለመሆን ማስረጃ ያላቀረቡ ስለሆነ ክርክራቸው ተገቢ አይደም የሰነድ ማስረጃ በምስክር ማቅረብ እንደማይቻል የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2005 ይደነግጋል የሚል ሰፊ ክርክር አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ክርክር የተደረገበትን ቤትና ቦታ ለተጠሪ እንዲያስረክብ የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመመስረት ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤትና ቦታ የሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በህይወት እያሉ ያፈሩት ንብረት መሆኑን አመልካችና ተጠሪ ያልተካካዱበት ፍሬ ጉዳይ እንደሆነ የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በመጀመሪያ ያፈሩት ሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ መሆናቸውን አመልካች ለዚህ ችሎት በሰጠው የመልስ መልስ ገልጿል፡፡ ስለሆነም የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤትና ቦታ ሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በህይወት እያሉ ያፈሩት ሀብት መሆኑ አከራካሪ ጭብጥ አይደለም፡፡

አከራካሪው ጭብጥ አመልካች ወ/ሮ ካሃ አብደላ ቤቱንና ቦታውን በህይወት በነበሩበት ጊዜ ለአባቴ ለአቶ ሁሴን አው ሐሰን በስጦታ አስተላልፋለት የቤቱ ባለሃብትነት ካርታና ፕላን በአባቴ ስም ሆኗል በማለት አመልካች የሚያቀርበውን ክርክር ተጠሪው በግልጽ በመካድ የአመልካች አባት አቶ ሁሴን አው ሐሰን ቤቱን ከወ/ሮ ከድጃ እኔ እስክመጣ ድረስ በአደራ እንዲጠብቅ ነው የተረከበው፣የቤቱን ባለሃብትነት ማስረጃ ያወጡት ቤቱ በስጦታ ለሺያጭ ወይም ለውርስ ከሚች ወ/ሮ ካሃ አብደላ ሣይተላለፍላቸው በተሣሣተ መንገድ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ስለሆነም ቤቱ በአሁኑ ወቅት በአመልካች አባት ስም ተመዝግቦ መገኘቱና የአመልካች አባት የቤቱ ባለሐብት መሆኑን የሚያረጋግጥ የባለሐብትነት ማስረጃ ካርታና ፕላን ያለው መሆኑ ቤቱ የቀድሞ ባለንብረት ከነበሩት ወ/ሮ ከሃ አብደላ በህጋዊ መንገድ የተላለፈለት ለመሆኑ የሚያረጋግጥና ሊስተባበል የማይችል ማስረጃ ነው ወይስ አይደም? የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአንድ የማይንቀሣቀሥ ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ማረግገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ማስረጃ የያዘ ሰው የማይንቀሣቀሰው ንብረት ባለቤት ነው ተብሎ እንደሚገመት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1195/1/ የሚደነግግ ሲሆን ይኸ የሕግ ግምት ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት መሆኑ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1195 ንኡስ አንቀጽ 2 በግልጽ ይደነገጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በአሁኑ ወቅት በአመልካች አባት ሚች አቶ ሁሴን አው ሃሰን ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን የአመልካች አባት የቤቱ ባለሐብት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ማስረጃ ያላቸው መሆኑ ቤቱ የአመልካች አባት አቶ ሁሴን አው ሐሰን ሐብት ነው ብሎ የህሊና ግምት ለመያዝ የሚያበቃ ማስረጃ ነው፡፡ ነገር ግን ይኸ ማስረጃ ጥቅሜና መብቴ ተነክቶብኛል የሚል ሌላ ሰው ቤቱ የሚች አቶ ሁሴን አው ሐሰን አለመሆኑንና የተሰጠው የባለቤትነት ማስረጃም ትክክለኛ ማስረጃ አለመሆኑን ሌላ ማስረጃ በማቅረብ ሊያፈርሰውና ሊያስተባብለው የሚችል መሆኑ በፍታብሔር ሕጉ አንቀጽ 1195 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ንብረቱ በአባቴ ስም የተመዘገበና የአባቴ ንብረት መሆኑን የሚያረጋግጥ ካርታና ፕላን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እያለ ተጠሪ ይህንን እንዲያስተባብልና በሰው ማስረጃ እንዲያፈርስ የበታች ፍርድ ቤቶች መፍቀዳቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የሕግ መሰረት የለውም፡፡

ተጠሪ ቤቱ በመጀመሪያ አውራሹ የሆነችው የሟች ካሃ አብደላ መሆኑን በማስረጃ ከማረጋገጡ በተጨማሪ ቤቱን በሕይወት እያሉ ያፈሩት ሟች ወ/ሮ ካሃ መሆናቸውን አመልካች በሥርና በዚህ ፍርድ ቤት አምኖ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ከዚህ በተጨማሪ የአመልካች አባት አቶ ሁሴን አው ሐሰን ቤቱን በአደራ ጠባቂነት ወ/ሮ ከድጃ ከተባሉ የሟችና የተጠሪ ዘመድ የተረከቡ መሆኑና አመልካች ቤት በአደራ የጠበቁበትን የድካም ዋጋ ብር 8000 (ስምንት ሺ ብር) ለመቀበል ተስማምተው የነበሩ መሆኑን ጉዳዩን በሽምልና በማየት አመልካችና ተጠሪን ያስማሙ ምስክሮች እንዳረጋገጡ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ተረጋግጧል፡፡ የአመልካች ወላጅ አባት ቤቱ ከሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በሽያጭ ውል በውርስ ወይም በስጦታ ሣይተላለፍላቸው ቤቱን በአደራ ጠባቂነት ከወ/ሮ ከድጃ ከተረከቡ በኋላ የቤቱን ስመ ሐብት ማዞራቸውንና የባለቤትነት ማስረጃ የተሰጡ መሆኑን ተጠሪ በበቂ ማስረጃ ካረጋገጠ የአመልካች አባት የቤቱ ባለሐብት ናቸው የሚለውን ግምት ለማፍረስና ለማስቀረት የሚችል ምክንያት መሆኑ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1196/ሀ/ እና /ለ/ ድንጋጌዎች ለመገንዘብ የሚቻል በመሆኑ አመልካች በዚህ በኩል ያቀረቡት ቅሬታ የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡

ቤቱ በአመልካች አባት ስም መመዝገቡና የአመልካች አባት የባለሐብትነት የምስክር ወረቀት ያላቸው መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1195/1/ መሰረት የቤቱ ባለሃብት ናቸው የሚል ግምት ሊያሣድር የሚችል ማስረጃ ቢሆንም ተጠሪ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1196 /ሀ/ እና /ለ/ የተደነገጉትን ሁኔታዎች በማስረዳት የባለቤትነት ማስረጃው ትክክል አለመሆኑን በበቂ ሁኔታ እንዳስተባበሉ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ለሟች አባቴ አቶ ሁሴን አው ሐሰን ወ/ሮ ከሃ አብደላ የቤቱን ባለሐብትነት በስጦታ አስተላልፋላቸዋለች የሚል ክርክር ከሥር ጀምሮ እስከ ሰበር ችሎት ያቀረበ ቢሆንም አመልካች ሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ቤቱን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2443 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 881 ወይም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 882 በሚደነግገው መሰረት በስጦታ የሰጧቸው መሆኑን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ እንዳላቀረቡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ አመልካች አባታቸው ቤቱን ከሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ ከላይ የተገለፁት የሕግ ድንጋጌዎች በሚደነግጉት መሰረት በስጦታ ያስተላለፉላቸው መሆኑን የማስረዳት ግዴትና ኃላፊነታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ ሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ ቤቱን ለአባቴ የሰጠችው መሆኑን አቶ አሊ ባድል የተባሉ ሰው በሚሰጡት የምስክርነት ቃል ለማስረዳት ያቀረብኩትን ጥያቄ የበታች ፍርድ ቤቶች አላግባብ ውድቅ አድርገውብኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ ድጋፍና መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም አከራካሪው ቤትና ቦታ ሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በሕይወት እያሉ ያፈሩት ንብረት መሆኑና ተጠሪም የሟች ወ/ሮ ካሃ ወራሽ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑና ለክርክር መነሻ የሆነው ቤትና ቦታ በአመልካች አባት በአቶ ሁሴን አው ሐሰን ስም ተመዝግቦ የሚገኝና አቶ ሁሴን የቤቱ ባለሐብት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ማስረጃ ያላቸው ቢሆንም አቶ ሁሴን የቤቱን ባለሐብትነት በስማቸው ያስመዘገቡትና የባለሐብትነት ማስረጃ የወሰዱት ቤቱ በሕጋዊ መንገድ ከባለሐብቷ ሟች ወ/ሮ ካሃ አብደላ በሽያጭ፣ በውርስ ወይም በስጦታ ሣይተላለፍላቸው ይልቁንም ወ/ሮ ከድጃ የተባሉ የሟች ወ/ሮ ካሃና የተጠሪ ዘመድ በአደራ እየጠበቁ እንዲቆዩ ካስረከቧቸው በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የቤቱን ስመ ሐብት በስማቸው ያዛወሩና የባለቤትነት ማስረጃ የወሰዱ መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1196/ሀ/ ና /ለ/ በሚደነግጉት መሰረት ተጠሪ በማስረጃ ያረጋገጠና ያስረዳ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡትን ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማጽደቁ ተገቢና የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሱማሌ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ሰኔ 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የካቲት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡት ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48086

ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1/ወ/ሮ አሰለፈች ወልደሚካኤል አልቀረበም

2/ ወ/ሮ ቀለመወርቅ ወልደሚካኤል አልቀረበም

ተጠሪ፡- ቶታል ኢትዮጵያ አክሲዮን ማህበር ጠበቃ አቶ ወንድየ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የአሁን አመልካች አባታችን ሟች አቶ ወልደሚካኤል ወልደማርያም በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 1 ቀበሌ 07 የቤት ቁጥር 142 የሚታወቀውንና በተለመዶ አርበኞች ቶታል ኩባንያ ለኮትንትራክት አስረክበዋል፡፡ የአባታችን የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ስለሆንን የነዳጅ ማደያው ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት ስለሆነ ቢሮውንና የነዳጅ ማደያውን እንዲያስረክቡን በማለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡

ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፣ከሣሾች ወራሽነታቸውን አላረጋገጡም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭ አርበኞች መንገድ ተብሎ የሚጠራው የቶታል ቤንዚን ማደያ ቢሮ ግምት ያነሰ ነው፡፡ በተከሣሽ /ተጠሪና/ በከሣሾች አውራሽ አቶ ወልደሚካኤል ወልደማርያም መካከል ተደርጎ የነበረው ውል የነዳጅ ማደያ ኪራይ ውል አይደለም፡፡ ከሟች አቶ ወልደሚካኤል ጋር የነበረን ውል የመሬት ኪራይ ውል ነው፡፡ ከአቶ ወልደሚካኤል በተከራየው ቦታ ላይ የቤንዚን ማደያውንና ጽ/ቤቱን የሠራው ተከሣሽ /ተጠሪ/ ነው፡፡ ኪራዩ ከ1967 ዓ.ም በፊት የተደረገ በመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 47/1967 የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት እንዲሆን የታወጀ በመሆኑ እንደዚሁም በየነዳጅ ማደያው ከመንግሥት ቦታና ቤት ተከራይተው ይሰሩባቸው የነበሩ ይዞታዎች የሚኒስትሮች ቤት መጋቢት 10 ቀን 1968 ዓ.ም ቁጥር 411/68 በተሻሻለ ደብዳቤ ግንኙነቱ ከመንግሥት ጋር እንጅ ከቀድሞ አከራዬች ጋር እንዳልሆነ የደነገገ በመሆኑ ክሱ ሕጋዊ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል የተከራይ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያዎችን ውድቅ በማድረግ አመልካች በነዳጅ ማደያውና በጽ/ቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎችና የሕግ ድንጋጌዎች እንደዚሁም ከአመልካች አውራሽ ጋር ከተደረገው የመሬት ኪራይ ውል ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪና በአመልካች አውራሽ መካከል የተደረገው የመሬት ኪራይ ውል እንጅ የነዳጅ ማደያና የጽ/ቤት ኪራይ ውል አይደለም፡፡ የኪራይ ውሉ የተደረገው ከአዋጅ ቁጥር 47/1967 በፊት በመሆኑና በዚህ አዋጅ የከተማ ቦታ የመንግሥት ሀብት የሆነ በመሆኑ እንደዚሁም የሚንስትሮች ምክር ቤት መጋቢት 10 ቀን 1968 በቁጥር 411/68 ዲፖዎች ባሉበት እንዲቀጥሉ የወሰነ ስለሆነ አመልካች ተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ተገቢ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የተከራየው መሆኑ ብቻ አይደለም፡፡ የነዳጅ ማደያውንና ቤቱን የተከራየ መሆኑን የሚያሣይ ማስረጃ አቅርበናል፡፡ በሚንስትሮች ምክር ቤት ተፃፈ የተባለው ደብዳቤ ታዓማኒነቱ ሣይረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች መቀበላቸው ስህተት ነው፡፡ ውሉ የተደረገው 1954 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ውል መሠረት የውሉ ዘመን ሲጠናቀቅ ተጠሪ የነዳጅ መቅጃ መሣሪያዎቹን ቤቱቹን አስረክቦ ለመሄድ ተዋውሏል፡፡ ተጠሪ ቦታውን ተረክቦ ቤት ሠርቷል ስለዚህ በውሉ ምዕራፍ አስር መሠረት የቤቱ ባለመብቶች እኛ ሆነን እያለ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1731/11/ በመጣስ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ የመሬት ኪራይ ውል የተፈፀመው አዋጅ ቁጥር 47/1967 ከመታወጁ በፊት ሣይሆን ውሉ ከዚህ አዋጅ በኋላ ሕጋዊ አስገዳጅነት የሌለው በመሆኑ የተከራየነው የነዳጅ ማደያ ቢሮ ሣይሆን መሬት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም በአመልካwች አውራሽና በተጠሪ መካከል በተደረገው ውል መሠረት ተጠሪ እንዲፈጽም አይገደድም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በአውራሻችን አቶ ወልደሚካኤልና በተጠሪ መካከል በ1954 ዓ.ም የተደረገው ውል የመሬት ኪራይ ውል ሣይሆን የነደጅ ማደያና ለጽሕፈት ቤት የሚሆን ቤት ኪራይ ውል ነው በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በተጠሪና በአመልካች አውራሽ መካከል በ1954 ዓ.ም የተደረገው ውል የመሬት ኪራይ ውል መሆኑን በማረጋገጥ ወስነዋል፡፡ አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የማስረጃ ተዓማኒነት እና ክብደት ሲመዝኑ ስህተት ሠርተዋል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የሰበር ችሎት ለሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባና የሰበር ችሎት ማስረጃ ታዓማኒነትና ክብደት እንዲመዝን የሚጠይቅ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በአመልካች አውራሽና አቶ ወልደሚካኤል መካከል የመሬት ኪራይ ውል የተደረገው በ1954 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ጊዜ መሬት የግለሰቦች ሀብትና ርስት እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን አቶ ወልደሚካኤል የነበረችውን ርስት መሬት ላይ ተጠሪ የነዳጅ ማደያ ድርጅትና ጽ/ቤት ገንብቶ ኪራይ እየከፈለ እንዲኖር በመጨረሻም የኪራይ ዘመኑ ሲጠናቀቅ ድርጅቱንና ግንባታውን ለቆ እንዲሄድ ተስማምተው የነበሩ መሆኑን ግራ ቀኙ በሥርና በሰበር ካደረጉት ክርክር ተገንዝበናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖም የኪራይ ውል ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት የውሉን አይነተኛ ጉዳይ በተለይም የአመልካች አውራሽ ባለመብት ሆነው የኪራዩን መሬት መንግሥት የሕዝብ ሀብት የሚያደርግ የሕግ ማዕቀፍ አዋጅ ቁጥር 47/1967 ታውጇል፡፡ በአዋጁ በባለርስትና በጭሰኛ መካከል ያለውን ግንኙነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የተቋረጠ በመሆኑ ከነሐሴ ወር 1967 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ ከአመልካች አውራሽም ሆነ በአመልካች እንዲፈጽም የሚገደድበት ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል ውል የለም፡፡ አንድ ውል በተዋዋዮች መካከል እንደ ሕግ ሆኖ አስገዳጅነት የሚኖረው ውሉ የሚቻልና የተደረገውም ሕጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ የሆነ እንደሆነ መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1678 ንዑስ አንቀጽ /ለ/ ይደነግጋል፡፡ የአመልካች አውራሽና ተጠሪ በ1954 ዓ.ም ሲዋዋሉ የውርስን መሬት ማከራየት፣ መሸጥና መለወጥ የሚቻል ቢሆንም ይህ ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 የተቋረጠና በግለሰብ ደረጃ መሸጥ ፣መለወጥ የተከለከለ በመሆኑ የውሉ መሠረታዊ ጉዳይ የማይቻልና በሕግ ያልተፈቀደ ሆኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቀድሞ የመሬት ባለርስት ከነበሩ ሰዎች መሬት ተከራይተው የነደጅ ማደያ ያቋቋሙ ድርጅቶች ግንኙነታቸው ከመንግሥት ጋር እንደሆነና መንግሥት አይቶ ውሣኔውን የሚያሣውቃቸው መሆኑን የሚኒስትሮች ምክር ቤት መጋቢት 10 ቀን 1968 በቁጥር 411/68 በዓፈው ደብዳቤ ያሣውቁ መሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ በመንግሥት የተደረገ ክልከላ ከተዋዋይ አቅም በላይ የሆነ ምክንያት መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ለ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካች አውራሽና በተጠሪ መካከል በ1954 ዓ.ም የተደረገው የመሬት ኪራይ ውል በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ተፈፃሚነቱ የተቋረጠ በመሆኑና የሚንስትሮች ምክር ቤትም ተጠሪ የመሬቱን ኪራይ በተመለከተ ግንኙነቱ ከመንግሥት ጋር እንጅ ከቀድሞ አከራይ ጋር አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን በማጣራት ተጠሪ የነደጅ ማደያውንም ሆነ በቦታው ላይ የሠራቸውን ቤቶች ለአመልካች ለማስረከብ አይገደድም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
3. ለውሣኔ አሰጣጥ እንዲጠቅም ከፊዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በትውስት የመጣው መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሻለቃ አሰፋ አየለ ደምሴ ጠበቃ አቶ ግርማ አይታገድ

ተጠሪ፡- ፍቃዱ ሙሉኔታ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ አንድ ተለይቶ የታወቀ ንብረት ተወስዶብኛል ይመለስልኝ በሚል በሁከት ይወገድልኝ ስም ክስ በቀረበ ጊዜ ለዚህ ዓይነቱ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(2) የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ለመወሰን ልንከተል የሚገባውን አተረጓጐም የሚመለከት ነው፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሰኔ 22 ቀን 1991 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ በወረዳ 17 ቀበሌ 20 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር 23803 የተሰጠኝን ስፋቱ 250 ካ.ሜትር የሆነውን ቦታ ከእነ ጅምር ቤቱ በመያዝ አለቅም ስላለ ለቆ እንዲያስረክበኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪም በተከሳሽነቱ ክርክር ያስነሳውን ንብረት ከያዝኩበት ጊዜ ጀምሮ ከሳሽ ቦታው ተወሰደብኝ በማለት ክስ እስካቀረቡበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ 13 ዓመት ያለፈው ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ነው፡፡

ቦታውን ተረክበው ግንባታ ባለማከናወናቸው በመንግስት መመሪያ ከተወሰደባቸው መንግስትን እንጂ እኔን አይጠይቁም ቦታውን በክፍሉ ቀበሌ አመልክቼ በ1978 ዓ.ም ተሰጥቶኝ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ የንግድ ፈቃድ አውጥቼ በይዞታ ሥር አድርጊያለሁ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር መልስ አቅርበዋል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የቀረበውን የሰነድና የሰው ማስረጃ ከተመለከተ በኋላ ክርክር ያስነሳውን ቦታ የአሁን ተጠሪ ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ያዙት የሚለውን ነጥብ በሚመለከት የተጠሪ ማስረጃዎች ከአመልካቹ በተሻለ ሚዛን በሚደፋ መልኩ አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህ በተጠሪ ይዞታ ሥር ንብረቱ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው (ከ1978-1991) ዓ.ም ያለው ጊዜ ሲታሰብ ከ2 ዓመት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በላይ ስለሚሆነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(2) መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል። ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች በመፅናቱ ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ ችሏል።

በሰበር ቅሬታቸውም ላይ ለይርጋ ጊዜ መነሻ ሆኖ የሚያዘው ጊዜ የትኛው ሊሆን ይገባል የሚለውን አስመልክቶ የፍሬ ነገር ዝርዝር ክርክር ካቀረቡ በኋላ የእኔ ክስ የሥራ-ነገር ጥያቄ በሚል አገላለፅ ይጥቀሱት እንጂ የባለቤትነት ጥያቄ ነው በማለት ሁከት ይወገድ በሚለው አይወድቅም ስለሆነም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149 የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት የለውም የሚል ክርክር አቅርበዋል።

ተጠሪም በጊዜው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ለመመልከት ሥልጣን ለነበረው ፍ/ቤት ክሱን ማቅረባቸው ክሳቸው የሁከት ይወገድልኝ የሚል እንደነበረ በእራሱ አስረጂ ነው እንዲሁም ክሱ የመፋለም ሳይሆን የይዞታ ስለመሆኑ ብር 2000.00(ሁለት ሺህ) መገመታቸው ክሳቸው በሁከት ይወገድልኝ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያመለክታል በማለት ለተያዘው አከራካሪ ጉዳይ አግባብነት ያለውን መልስ ሰጥቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል።

የአመልካች የክስ ምክንያት ተለይቶ የታወቀ ንብረት ተወስዶብኛል፤ ይመለስልኝ የሚል እንደመሆኑ የክሱ አቀራረብ ሥርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 226(3) እንደተመለከተው ትክክለኛ ዋጋው ተገምቶ ነገሩን አይቶ ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎበት ሊቀርብ እንደሚገባ አመላካች ነው። በዚህ መሠረት መቅረብ ሲገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 1149(1) ሁከት የተነሣበት ሰው ሁከት እንዲወገድለት መጠየቅ ይችላል ከሚለው የህግ አነጋገር "ሁከት ይወገድልኝ" የሚለውን ለይቶ በገንዘብ ሊገመት እንደማይቻል ተደርጎ መቅረቡን ያሳያል።

ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(1) ላይ ሁከት የተፈጠረበት ሰው ሁከት እንዲወገድለት፤ ይዞታው የተወሰደበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንዲመለስለት ሁለቱንም ዓይነት ሁኔታዎች ለያይቶ የደነገገ በመሆኑ የተወሰደን ነገር ለማስመለስ በሚል ዳኝነት ለመጠየቅ በተፈለገ ጊዜ ከላይ በተመለከተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 16፣ 226(3) መሠረት ትክክለኛ ዋጋው ተገምቶ ተገቢው ዳኝነት ተከፍሎበት የሥረ ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት የሚቀርብ እንጂ የተፈጠረ ሁከት እንዲወገድ ("cessation of interference") እንደሆነ ተቆጥሮ በገንዘብ የማይገመቱ አቤቱታዎች በሚቀርቡበት ሁኔታ ሊስተናገድ የሚችል እንዳልነበር ተገንዝበናል።

ይህ ዓይነቱ በክስ አቀራረብ ረገድ የሚታየው ሥነ ሥርዓታዊ ግድፈት የሥረ ነገር ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ ጉዳዩ እንዳይታይ በማድረግ ብቻ ውጤቱ የተንፀባረቀ ሳይሆን በይርጋ ደንቦች አፈፃፀም ላይ ችግርን አስከትሏል።

ከክርክሩ ዓይነት አንፃር ጉዳዩ በሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሥር ሊሸፈን የሚችል ባለመሆኑ ለዚህ ለተያዘው ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(2) የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ አግባብነት የሌለው መሆኑ እየታወቀ የክሱን ይዘት ሳይሆን የክሱን አርዕስት ብቻ በመመልከት የሥር ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሌለውን የይርጋ ዘመን ተፈፃሚ በማድረጋቸው የህግ ስህተት መፈፀማቸውን ተረድተናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠሪ ክርክር ላይ እንደተገለፀው አከራካሪ የሆነው ንብረት በተጠሪ እጅ ከገባ 13 ዓመት አልፎታል የሚል ክርክር ስለቀረበ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(2) ተጠቅሶ ሁለት ዓመት አልፎታል ቢባልም ከ10 ዓመት (ከአስር ዓመት) በላይ ያለፈው መሆኑ ከተረጋገጠ በይርጋ ቀሪ መሆኑ ስለማይቀር የተለየ ለውጥ አያመጣም እንዳይባል የተወሰደ ንብረት ለማስመለስ እና የመፋለም መብትን ለማስከበር የሚቀርቡ ክሶች (petitory actions) በይርጋ ዘመን ቀሪ ሊሆን የማይገባበትን የህግ ትንታኔ በመስጠት ከዚህ ቀደም በዚህ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 43600 በሆነው ውሳኔ የተሰጠበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1677 እና 1845 መሠረት የተቀመጠው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜም ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሆኖ አይገኝም፡፡

በሌላ በኩል የክሱ አቀራረቡ ግድፈት በሥረ ነገር ሥልጣን ረገድ ያስከተለውን ሥነ-ሥርዓታዊ ስህተት በማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የማይታለፍ የመርህ ጉዳይ እንደመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ በየትኛውም ደረጃ ሊታረም ይገባል የሚለውን መሠረት በማድረግም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡

ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው ክስ በቀረበበት ዘመን በ1991 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ይህንን መሰል የባለቤትነት ጉዳይ ተቀብለው ለማስተናገድ የሚያስችላቸው ስልጣን ያልነበራቸው መሆኑ ቢታወቅም፤ እንዲሁም ክርክሩ የተነሣው በሁለት ግለሰቦች መካከል እንደመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/95 መሠረት ሥልጣን የሌላቸው ቢሆንም በክርክር ላይ የነበሩ ጉዳዮች በምን አኳኋን መስተናገድ እንደሚኖርባቸው በሚደነግገው የተሻሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ለማሻሻል በወጣው በአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀጽ 2(3) በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 66 ሥር የሚከተለው አንቀጽ 10 ተጨምሯል ካለ በኋላ በአንቀጽ 10 ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት በመታየት ላይ የነበሩና በአዋጅ ቁጥር 361/95 በከተማ ፍ/ቤት ዳኝነት ሥልጣን ሥር የማይወድቁ ጉዳዮች በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት መታየታቸው ይቀጥላል በሚል ምላሽ ስለተሰጠው ይህም ጉዳይ ከላይ በዝርዝር እንደህጉ አነጋገር ሁከት ይወገድልኝ በሚል ሥር የማይወድቅ በመሆኑ ከጅምሩም ቢሆን በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ባይሆንም ክርክሩ ሳይቋጭ በክርክር ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ ከላይ በተመለከተው አዋጅ መሠረት አሁንም በተጀመረበት ፍ/ቤት የሚታይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ 00257 በ3/2/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ 08247 በ15/7/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የከተማው ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/መ/ቁ 09744 በ06/2/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ ዘመን ቀሪ ሊሆን የሚችል ባለመሆኑ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀሪው ጉዳይ ላይ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ይስጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት መዝገቡን መልሰናል፡፡

በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ራ/ታ ***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49200

ህዳር 1 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ጋሻው በጎሰው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አለበል መከተ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው በአማራ ክልል የላይ ጋይንት ወረዳ ፍርድ ቤት የደቡብ ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ወሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ የቦታና የባህር ዛፍ አትክልት ይዞታን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ከሳሽ ሆኖ የቀረበው የአሁን ተጠሪ ሲሆን የከሰሰውም አቶ ሲሳይ በጎሰውንና አቶ ጋሻው በጎ ሰውን ነው፡፡ ተጠሪ ከሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ሲሳይ በጎ ሰው ብር 1900 (አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ብር) ተበድሮ ቆይቶ ገንዘቡን ለመክፈል ባለመቻሉ ቦታውን ከእነ አትክልቱ በብር 1500 (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) ግምት አስረክቦኛል፡፡ ይህ ቦታ ለመንገድ ሲቀየስ ሁለተኛው ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ቦታውና ባህር ዛፍ የእኔ ነው በማለት 4,400 የባህርዛፍ ግምት እንዳይከፈለኝ ቦታው የእኔ ነው በማለት በቀበሌ አስተዳዳር በማመልከት ገንዘቡ እንዲያገ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የባህርዛፉን አላባ እንዳልቀበል ቦታውም የእኛ ነው በማለት ሁከት የፈጠሩብኝ ስለሆነ በይዞታዬ ላይ የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተከሳሾች በበኩላቸው ተከሳሽ ብር 1900 ለሲሳይ በጎ ሰው ያበደረ መሆኑን በክሱ ገልጿል፡፡ ሆኖም የብድር ገንዘቡን ከሰጠኝ አስር ዓመት ያለፈ በመሆኑ ሊጠይቀኝ አይችልም የብድር ውሉ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በወቅቱ የዕዳ መክፈያ እንዲሆን የተዋዋልኩት ቦታና ባህርዛፍ አትክልት የተበዳሪው የአቶ ሲሳይ በጎ ሰው ሣይሆን የወንድሜ የጋሻው በጎ ሰው በመሆኑ ውሉ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ሲሳይ በጎ ሰው መልስ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ አመልካች በበኩሉ በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ ሆኖ ቀርቦ ቦታውም ሆነ ይዞታው የእኔ እንጅ የአንደኛ ተከሳሽ የሲሳይ በጎ ሰው አይደለም፡፡ ወንድሜ በተዋዋለውና እኔ ባልተስማማሁበት ሁኔታ እኔ የይዞታ መሬቴንና የባህርዛፍ አትክልቴን ለከሳሽ የምለቅበት ምክንያት የለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ የቀረቡት ምስክሮችም ቦታውና ባህርዛፍ አትክልቱ የጋሻው በጎሰው ነው ነገር ግን አንደኛ ተከሳሽ ሲሳይ በጎሰው ለአሁን ተጠሪ ለሥር ከሳሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለበል መከተ ሽጦለታል በማለት የመሰከሩ መሆናቸውን በውሣኔው ገልጿል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ሁከት ፈጥሮአል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅረቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርቦ የሰበር ችሎቱ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የባህር ዛፍ አትክልቱና ቦታው የእኔ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ካረጋገጠ በኋላ የእኔን አትክልት ግምት ወንድሜ ሲሳይ በጎሰው በተዋዋለው ውልና በተበደረው ገንዘብ መነሻ የአሁን ተጠሪ እንደወሰደ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ይዞታው የአቶ ሲሳይ በጎ ሰው ነበር፡፡ በብር 1900 /አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ብር/ ተበድሮ ባለመክፈሉ ቦታውንና አትክልቱን ተረክቤዋለሁ፡፡ የይዞታ የምስክር ወረቀትም አውጥቼበታለሁ ፡፡ አሁን ግን የባህርዛፍ ግምት ለእኔ ነው የሚገባው በማለት አመልካች ሁከት የፈጠረ በመሆኑ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ክስ አቅርቤ የተወሰነው በአግባቡ ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረባቸው ምስክሮች ይዞታው የማን እንደሆነ አናውቅም ገዝቶታል ሲባል ሰምተናል በማለት የመሠከሩ ሲሆን የእኔ ምስክሮች የእኔ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ የላይ ጋይንት ወረዳ መሬት አስተዳደር ይዞታው የእኔ መሆኑን በማረጋገጥ ጽፏል ስለሆነም ይዞታው የእኔ እንጅ የሲሳይ በጎ ሰው ባለመሆኑ ተጠሪ ቦታውን በዕዳ መክፈያነት በውል ተቀብዬ ይኸርዋለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ ሁከት የፈጠረ ስለሆነ ሁከቱ ይወገድ በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የወረዳው ፍርድ ቤት በአንድ በኩል የተጠሪ ጥያቄ የቦታ ባለቤትነት ጥያቄ ባለመሆኑ የቦታ ውሉን ማጣራቱ አስፈላጊ አይደለም በማለት በውሣኔው የገለፀ ሲሆን በሌላ በኩል ቦታው የጋሻው በጎሰው ነው ነገር ግን ሲሳይ በጎሰው ለተጠሪ ለመከተ ደምሴ በገንዘብ ሲሸጠው እናውቃለን በማለት የመሰከሩ መሆኑን በውሳኔው ገልፆል፡ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ ሁከት ፈጥረዋል ወይም አልፈጠሩም የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመያ ተጠሪ የቦታው ህጋዊ ባለይዞታ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ማጣራት አስፈላጊ ነው፡፡

ተጠሪ ቦታውን አገኘሁ የሚለው የአመልካች ወንድም አቶ ሲሳይ በጎሰው ብር 1900 /አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ብር/ ተበድሮኝ ይህንን ገንዘብ ባለመክፈሉ ቦታውንና የባህርዛፍ አትክልቱን በብር 1500 /አንድ ሺ አምስት መቶ ብር/ ተገምቶ በእዳ መክፈያነት በውል አግኝቸዋለሁ በማለት የሚከራከር ሲሆን አመልካች ከሲሳይ በጎ ሰው ጋር የእዳ መክፈያ እንዲሆን የተስማማሁበት ቦታና አትክልት የእኔ ይዞታ በመሆኑ ከውል የመነጨ መብት በቦታውና በባህርዛፍ ላይ ሊኖርህ አይችልም በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

ተጠሪ ቦታውን አገኘሁ የሚለው ከማን እንደሆነ በራሱ አከራካሪ ቢሆንም ተጠሪ የቦታውን ባለይዞታ ሆንኩበት የሚለው ውል በቦታው ላይ ባለይዞታ ሊያደርገው የሚችለው ነው ወይስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም? የሚለው መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ቦታውን የፍታብሔር እዳ መክፈያነት ተረክቤአለሁ የሚለው ክርክር በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሀብት ነው ተብሎ ከተደነገገው ድንጋጌ አንፃር ስናየው መሬትን ለዕዳ በመክፈያነት በውል በማስተላለፍ መሸጥና መለወጥ የማይቻልና በዚህ አይነት መንገድ ህጋዊ የመሬት ባለይዞታ መሆን የማይቻል በመሆኑ ተጠሪ የመሬቱ ባለይዞታ ሆኘበታለሁ የሚለው ውል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1678 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ህጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ የተደረገ ባለመሆኑ ውሉ ህጋዊ ውጤት የሌለውና መብት የማያስገኝ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ምስክሮች ይዞታው የአመልካች መሆኑን ነገር ግን ወንድሙ ለተጠሪ አባት የሸጠ መሆኑን እናውቃለን በማለት የመሰከሩ መሆኑን በውሣኔው ገልጿል፡፡ ይዞታውና የባህርዛፍ አትክልቱ የአመልካች መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች ወንድሙ ሲሳይ በጎ ሰው ባደረገው ውል ሊገደድ የሚችለው አመልካች እሱን ወክሎ ውል እንዲዋዋል የሰጠው የውክልና ሥልጣን ካለና ወንድሙ ሲሳይ በጎ ሰው በዚህ በውክልና ሥልጣኑ መሠረት ውል የተዋዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አቶ ሲሳይ በጎ ሰው ውሉን የተዋዋለው ከአመልካች ባገኘው የውክልና ሥልጣን መሆኑን አላስረዳም፡፡ ስለዚህ አመልካች ባልተስማማበትና በቦታው ላይ ያለው የባህር ዛፍ አትክልት ለወንድሙ ዕዳ መክፈያ እንዲሆን ስምምነቱን ባልገለፀበት ሁኔታ ወንድሙ በተዋዋለው ውል መነሻ ቦታውንና አትክልቱን ለተጠሪ እንድለቅና በተጠሪ ላይ ሁከት እንዳይፈጥር ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በቦታዬና በንብረቱ ላይ ሁከት ተፈጥሮብኛል ብሎ ክስ ለማቅረብ በመጀመሪያ የቦታውና የንብረቱ ህጋዊ ባለይዞታ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ምስክሮች ይዞታው የአመልካች መሆኑን እንደመሠከሩና ቦታውን ከነባህርዛፉ ለተጠሪ በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ሲሳይ በጎሰው በገንዘብ ሽጦለታል የሚል የምስክረነት ቃል እንዳስመዘገቡ የወረዳው ፍርድ ቤት በውሳኔው ገልፆታል፡፡ ይሽም ተጠሪ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገውን የሚጥስ ተግባር በመፈፀምና የመሬቱ ህጋዊ ባለይዞታ ካልሆነው አቶ ሲሳይ በጎሰው መሬቱን በዕዳ መክፈያነት በውል ይገ'ለሁ በማለት የሚከራከሩ መሆኑንና የቦታው ህጋዊ ባለይዞታ የማያደርጋቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ አመልካች በተጠሪ ህጋዊ ይዞታ ላይ ሁከት ፈጥሯል በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል የላይ ጋይንት ወረዳ ፍርድ ቤት የደቡብ ጐንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በዚህ ክርክር ተሣታፊ ካልሆነውና በሥር አንደኛ ተከሳሽ በነበረው አቶ ሲሳይ በጎ ሰው በብድር ሰጥቸዋለሁ የሚለውን ገንዘብ እንድከፍለው ክስ አቅርቦ ከመጠየቅ ይህ ውሣኔ አያግደውም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች የቦታውና የአትክልቱ ሕጋዊ ባለይዞታ በመሆኑ በተጠሪ ላይ የፈጠረው ሁከት የለም በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች - የኢትዩጵያ መንገዶች ባለስልጣን - መላኩ ነገሠ ቀረበ
ተጠሪ - ጃዳ ብሩ ከጠበቃ ደጀኔ ፋይሳ ጋር ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በመንገድ ሥራ ምክንያት ለተወሰደ ንብረት ካሣ ይከፈል ዘንድ በመጠየቅ የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች እና በሞጆ ከተማ አስተዳደር ላይ ክስ የመሠረተው በሞጆ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ በ400 ካ.ሜትር ቦታ ላይ ያለኝን የንግድ ቤት በሚሠራው መንገድ ምክንያት እንደሚነሳ ነግረውኝ የንብረቱን ግምት ብር 46614 እንድወሰድ ያዘዙልኝ ቢሆንም ግምቱ ትክክል ባለመሆኑ አልወሰድኩም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ንብረቱን በግል ባለሙያ አስገምቼ ብር 119,367 ዋጋ እንዳለው አረጋግጫለሁ፡፡ በመሆኑም ንብረቱ በሶስተኛ ወገን ባለሙያ እንዲገምትልኝ እና በዚሁ መሠረት ካሣው እንዲከፈል ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ከዚሁ በተጨማሪም በተወሰደው ቦታ ምትክ ሌላ ቦታ ይሰጠኝ የሚል ጥያቄም አንስቶ እንደነበር ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ፍ/ቤቱ የሁሉንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኃላ ንብረቱን እንደገና አስገምቶ ተገኘ ባለው ውጤት መሠረት ካሣ እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የካሣው ክፍያ ጥያቄ በቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤት የሚቀርብበት አግባብ አለ ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ጭብጡን በማስመልከት ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ ባጭሩ እንዳመለከትነው አመልካች ለተጠሪ የሚከፈለውን ካሣ በማስገመት ገንዘቡን እንዲወስድ አስቀድሞ አስታውቆታል፡፡ ተጠሪ ደግሞ የካሣው መጠን አንሶአል የሚል እምነት በመያዙ በቀጥታ ለፍ/ቤት ክሱን አቅርቦአል፡፡ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የሕግ ጥያቄ የተነሳውም እዚህ ላይ ነው፡፡ ተጠሪ የካሣው መጠን አንሶአል የሚል እምነት ወይም ተቃውሞ ካለው ይህን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቃውሞውን ማቅረብ የነበረበት በምን አግባብ ነው የሚለው ጭብጥ ነው በሰበር ችሎቱ ውሣኔ የሚያሻው ሆኖ የተገኘው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ግልጽ የሆነ የመከራከሪያ ነጥብ አቅርቦአል፡፡ ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብ ያለው ሕግ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁ 455/97 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ካሣን በሚመለከት ስለሚቀርብ አቤቱታ እና ይግባኝ ተደንግጓአል፡፡ የከተማ መሬት ይዞታውን እንዲለቅ የሚደረግ ባለይዞታ በተወሰነለት የካሣ መጠን ላይ ካልተስማማ ወይም በካሣው መጠን ላይ ቅሬታ ካለው አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት በከተማው አስተዳደር ለተቋቋመው የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አስተዳደራዊ አካል ስለመሆኑም በዚሁ አንቀጽ 11/2/ ተመልክቶአል፡፡ የካሣውን መጠን በሚመለከት ለመደበኛ ፍ/ቤት ክርክር ወይም አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው በንዑስ አንቀጽ /4/ በተደነገገው መሠረት በይግባኝ ብቻ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ጉዳዩ የተነሳው በከተማ ክልል ውስጥ እንደመሆኑ ይህን በሚመለከት በተቀመጠው ድንጋጌ መሠረት ክርክሩ መታየት እንዳለበት የሚያከራክር አይደለም፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዋጁ መሠረት እንደሆነ መገንዘቡን ከውሣኔው ተመልክተናል፡፡ ይህን እየተገነዘበም ነው አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ ሊሰጥ የቻለው በመሠረቱ ፍ/ቤቶች ሊመሩ የሚገባቸው በሕጉ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ሕጉን መሠረት ያላደረገ ውሣኔ እንዲሰጡ አይጠበቅም፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደምናየው ግን ሕጉን በመተው ነው ውሣኔ የተሰጠው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22818 መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 53814 ሰኔ 4 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በካሣው መጠን ላይ በቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ማቅረብ በሕጉ አልተፈቀደም ብለናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዛፍኮ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ዜና ደባሱና አቶ

ታምሩ ወንድምአገኘሁ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ብሔራዊ መሐንዲሶች ስራ ተቋራጭ ድርጅት - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ ሆነው የተከራከሩ ሲሆን በሌላ በኩል አመልካች የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በማቅረቡ አመልካች የተከሣሽ ከሣሽ ተጠሪ የከሣሽ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ጉዳይ የግንባታ ስራ ውል አፈጻጸምና ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡

1. ጉዳዩ የተጀመረው ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ መጋቢት 4 ቀን 1984 ዓ.ም በተደረገና ሐምሌ 1 ቀን 1985 ዓ.ም በተሻሻለ ውል ለተከሣሽ የግንባታ ስራ የሰራ መሆኑንና በግንባታው ሂደት በአሰሪው የተሰጠ የስራ ለውጥ ትዕዛዝና ተጨማሪ ስራ ምክንያት ሶስት ስምምነቶችን በመፈራረም ስራውን የሰራ መሆኑን ገልጿል፡፡ ተጠሪ /ከሣሽ/ ጥር 1 ቀን 1988 ዓ.ም የምድር ቤቱንና ቤዝመንቱን ለተጠሪ ያስረከበ መሆኑንና ከአንደኛ ፎቅ እስከ አምስተኛ ፎቅ ያለውን ስራ በማጠናቀቀ መጋቢት 20 ቀን 1988 ዓ.ም ማስረከቡንና የተከሣሽ /አመልካች/ አማካሪ መሐንዲስ ብር 644,216.37 /ስድስት መቶ አርባ አራት ሺ ሁለት መቶ አስራ ስድስት ብር ከሰላሣ ሰባት ሣንቲም/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ለመጨረሻ የክፍያ ሰርተፊኬት ጽፏል፡፡ አመልካች የእሱ ተቀጣሪ በሆነው አማካሪ መሀንዲስ የተሰጠውን የክፍያ የምስክር ወረቀት በመቃወም በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተከሣሽ አማካሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሀንዲስ በክፍያ የምስክር ወረቀት የገለጻቸው ክፍያዎች ለከሣሽ ሊከፍሉት የሚገባ ክፍያዎች መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠውን የመጨረሻ ክፍያ ከነወለዱና ለመያዣና ለመልካም ስራ አፈጻጸም የተያዘውን ገንዘብ ከነ ወለዱ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ተከሣሽ ብር 2,144,107.60 /ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ አራት ሺ አንድ መቶ ሰባት ብር ከስልሣ ሣንቲም/ እንዲከፍለው ጠይቋል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ጉዳዩ በሽምግልና ሣይታይ ለፍርድ ቤት መቅረብ አይገባውም የሚል መከራከሪያ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከሣሽ 589 ቀናት የዘገየ በመሆኑ መቀጫ ገንዘብ የመክፈል ሃላፊነት አለበት ከሣሽ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ የግንባታ ስራውን አልሰራም፡፡ ከጊዜዊ እርክክብ በኋላ የተለያዩ ጉድለቶችን ለማስተካከል ወጭ አውጥቻለሁ፡፡ አማካሪ መሐንዲስ የመጨረሻ ክፍያ የማጽደቅ ስልጣን ያሌለው በመሆኑ የከሣሽ /ተጠሪ/ ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

2. አመልካች በበኩሉ አሻሽሎ ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ የከሣሽ ተከሣሽ /ተጠሪ/ የግንባታ ስራውን ሐምሌ 6 ቀን 1986 ዓ.ም በማጠናቀቅ ማስረከብ ሲገባው አምስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ቀናት ግንባታውን አዘግይቷል፡፡

   ስለሆነም የከሣሽ ተከሣሽ የግንባታ ስራ ውሉን ላዘገየበት 10% ቅጣት ብር 662,679.59 /ስድስት መቶ ስልሣ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ብር ከሀምሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ ሊከፍል ይገባዋል፡፡ የህንጻ ስራው በመዘግየቱ ህንጻውን በማከራየት አገኘው የነበረውን ገቢ ቀርቶብኛል፡፡ እንዲሁም ለባንክ የተከፈለው ወለድ የከሣሽ ተከሣሽ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡ የከሣሽ ተከሣሽ ስራውን በሚፈለገው ጥራት ደረጃ ባለመስራቱ ጉድለቱን ለማስተካከል የወጣውን ወጭ መሸፈን ይገባዋል፡፡ ስለሆነም የከሣሽ ተከሣሽ /ተጠሪ/ ብር 5,823,704.26 /አምስት ሚልዮን ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ሺ ሰባት መቶ አራት ብር ከሃያ ስድስት ሣንቲም/ ለተከሣሽ ከሣሽ /ለአመልካች/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

   ተጠሪ የከሣሽ ተከሣሽ በመሆን የህንጻ ስራው ማጠናቀቂያ ጊዜ የተራዘመው በስምምነት በመሆኑ ከህንጻ ስራው ማጠናቀቂያ ጊዜ ጋር በማያያዝ የተከሣሽ ከሣሽ ያቀረቡት የቅጣት ክፍያና የጉዳት ካሣ ክፍያ የህግ መሠረት የለውም፡፡ የከሣሽ ተከሣሽ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ስራውን ሰርቶ አስረክቧል፡፡ አለ የተባለውን ጉድለት ለማስተካከል ተገቢውን ጥረት አድርጐ በተከሣሽ ከሣሽ እንቢተኝነት የቀረ በመሆኑ በሀላፊነት ልጠየቅ አይገባም፡፡ የተከሣሽ ከሣሽ ጉድለትን ለማስተካከል አወጣሁ የሚሉትን ወጭ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ክሣቸው ሙሉ በሙሉ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

3. የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን ለማጠናከር በቃልና በጽሁፍ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች /ተከሣሽ/ የከሣሽ /የተጠሪ/ ክስን በመቃወም የቀረበውን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ በብይን ውድቅ አድርጐታል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከሣሽ /ተጠሪ/ ህንጻውን በአግባቡ ሰርተው ያስረከቡ መሆኑን በማስረጃ አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ /አመልካች/ ከሣሽ የጠየቀውን የመጨረሻ ክፍያ ብር 644,216.37 /ስድስት መቶ አርባ አራት ሺ ሁለት መቶ አስራ ስድስት ብር ከሰላሣ ሰባት ሣንቲም/ ከነወለዱ የመክፈል ሀላፊነት አለበት፡፡ ነሐሴ 29 ቀን 1984 ዓ.ም የተደረገው የግንባታ ስራ ውል ስምምነት ሀምሌ 1 ቀን 1985 ዓ.ም በተደረገው ውል ተሻሽሏል፡፡ ከዚህ በኋላ የተከሣሽ ከሣሽ /አመልካች/ መስከረም 26 ቀን 1987 ዓ.ም ግንቦት 28 ቀን 1987 ዓ.ም እና ጥር 9 ቀን 1988 ዓ.ም በሰጠው የስራ ለውጥ ትዕዛዝና ተጨማሪ የግንባታ ስራ ትዕዛዝ መሠረት የስራ ውል ማጠናቀቂያ ጊዜ ግራ ቀኙ ቃለጉባኤ በመያዝ የተስማሙ በመሆኑና የከሣሽ ተከሣሽ ስራውን በተሻሻለው የጊዜ ገደብ ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስላጠናቀቁ የከሣሽ ተከሣሽ የተከሣሽ ከሣሽ የጠየቀውን መቀጫና የጉዳት ካሣ ክፍያ የመክፈል ሀላፊነት የለበትም፡፡ ከሣሽ ለተከሣሽ ስራውን ሰርቶ ካስረከበ በኋላ የእምነበረድ ስራው የረገፈ መሆኑን የተከሣሽ ከሣሽ በተሻለ ማስረጃ አስረድቷል፡፡ ስለሆነም ጉድለት ያለበት መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠው የዕምነበረድ ስራ በካሬ ሜትር ብር 238 ታስቦ የ2040.64 ካሬ ሜትር እንደገና ለመስራት የሚያስፈልገው ብር 485,672.32 /አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሰላሳ ሁለት ሣንቲም/ የከሣሽ ተከሣሽ /ተጠሪ/ ለከሣሽ ተከሣሽ /አመልካች/ የመክፈል ሀላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም የከሣሽ ተከሣሽ ለመልካም ስራ አፈጻጸምና መያዣ ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ የእምነበረድ ስራውን ለማስተካከል የሚያስፈልገው ብር 485,672.32 ቀንሶ የተከሣሽ ከሣሽ ብር 28, 663.68 /ሀያ ስምንት ሺ ስድስት መቶ ስልሣ ሶስት ብር ከስልሣ ስምንት ሣንቲም/ ለከሣሽ ተከሣሽ ሊከፍል ይገባዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

4. አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የአመልካችና የተጠሪ ክርክር በሽማግሌ እየታየ እያለ በፍርድ ቤት መቅረቡ ተገቢ አለመሆኑን በግልጽ ያቀረብኩትን ተቃውሞ የስር ፍርድ ቤት ማለፉ የሥነ ሥርዓት ህግ ግድፈት ነው፡፡ በህግና በውል የተደነገገውን የግንባታ ስራ ውል ማጠናቀቂያ ጊዜ በተለያየ ጊዜ በተያዙ ቃለ ጉባኤዎች ተራዝሟል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የአመልካች አማካሪ መሀንዲስ በግንባታ ስራዎች መመሪያ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ የመጨረሻ ክፍያ ሰርተፍኬት ያለአመልካች ፈቃድና ስምምነት ለተጠሪ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡

የስር ፍርድ ቤት አማካሪ መሀንዲስ ከስልጣኑ ወጭ ባጸደቀው የመጨረሻ ክፍያ የምስክር ወረቀት መሠረት አመልካች ለተጠሪ ክፍያ እንዲፈጽም መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የልዩ አዋቂ ምስክርነት ቃል ሣይመዝነው ማለፉ ተገቢነት የለውም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ የተዘረዘረው ጉድለት ያለበትን ውሣኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የራሱ ወኪል የሆነው አማካሪ መሀንዲስ ያዘጋጀውን የክፍያ የምስክር ወረቀት በመቃወም ለስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አቤቱታ አቅርቦ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአማካሪ መሀንዲሱ ያዘጋጀው የክፍያ የምስክር ወረቀት ጉድለት ያሌለበት መሆኑን በመግለጽ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲፈጸምለት የአፈጻጸም ክስ አቅርቦ አመልካች ጉዳዩ መወሰን ያለበት በፍርድ ቤት ነው የሚል መቃወሚያ በማቅረቡ የአፈጻጸም መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ አመልካች ተጠሪ ክስ ሲያቀርብ ጉዳዩ በሽምግልና ሊታይ ይገባል በማለት ያቀረቡት ተቃውሞ የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካችና ተጠሪ ውል የተዋዋሉበት መሠረታዊ ጉዳይ የማይንቀሣቀስ ህንጻ ስራ ግንባታ ውል ነው፡፡ አመልካች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ልዩ የህግ ክፍል ሣይሆን ስለ ውሎች በጠቅላላው የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 24 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የግንባታው ማጠናቀቂያ ጊዜ የተለወጠ መሆኑን አምኖ መልስ ከሰጠ በኋላ አመልካች የስራ ለውጥ ትዕዛዝና የተጨማሪ ግንባታ ስራ ትዕዛዝ ለመፈጸም የሚያስፈልገው የጊዜ መጠን ላይ በመስማማት ስራው ከተከናወነ በኋላ የግንባታ ስራ ማጠናቀቂያ ጊዜው አልተራዘመም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ የግንባታ ስራ የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ ለመቀየር የሚደረግ ስምምነት በተለየ ፎርም እንዲሆን ህግ አያስገድድም፡፡ አመልካች ያቀረበው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት አረጋግጠው የወሰኗቸው ፍሬ ጉዳዮች የሚደግፍ እንጂ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆኑን የማያመላክት በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ እንዲሆንልኝ በማለት ሚያዝያ 8 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አቅርቧል አመልካች መስከረም 28 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

5. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩ አመልካችና ተጠሪ የግንባታ ስራው ስለሚጠናቀቅበት ጊዜ በመጀመሪያ ያደረጉት ስምምነት ተጠሪና የአመልካች አማካሪ መሀንዲስ በተለያየ ጊዜ ቃለ ጉባኤ በመያዝ ባደረጉት ስምምነት ተሻሽሏል በማለት አመልካች ያቀረቡት የተሻሻለ የክሣሽነት ክስ ውድቅ መደረጉ ተገቢ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1721፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1763 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1764 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ለመመርመር ጭብጥ ተይዞ ለሰበር ችሎት የቀረበ ነው፡፡ እኛም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ይህንን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

   5.1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ለሚከራከሩበት ጉዳይ ገዥነትና ተፈጻሚነት ያለው የህግ ክፍል የትኛው ነው? የሚለውን ነጥብ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ የግንባታ ስራውን የሚያጠናቀቅበት ጊዜ በህግ የተደነገገውን መሠረት በማድረግ አልተሻሻለም በማለት የሚከራከረው ስለውሎች የተደነገገውን የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች በተለይም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1721፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1763 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1764 በመጥቀስ በመሆኑ ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ከላይ የተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ ሆኖም የአመልካች ጠበቆች በስርና በሰበር ጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ያቀረቡት ክርክርና ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ ህግ አውጭው የማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውልን በተመለከተ ገዥነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸዉ በማሰብ ከደነገጋቸው ልዩ የህግ ማዕቀፎችና በህግ ስልጣን የተሰጣቸው አስፈጻሚ አካላት ስለማይቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውል አውጥተው ተፈጻሚ ካደረጓቸው የአሰራር መመሪያዎች አንጻር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የማይንቀሣቀስ ንብረት ለመስራት የሚደረግ ውል ገዥነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው በማሰብ ህግ አውጭው ከደነገጋቸው የህግ ማዕቀፎች መካከል አንደኛው በፍታብሔር ህጉ አንቀጽ 3019 እስከ አንቀጽ 3040 የተደነገገው የሚገኘው ልዩ የህግ ክፍል ነው፡፡ “ስለማይንቀሣቀስ ንብረት ስራ ውል” በሚል ርዕስ ስር የተደነገጉት እነዚህ የህግ ድንጋጌዎች የስራ “ተቋራጭነቱ ውል የተደረገው የህንጻን ስራ ለመስራት የተሰራውን ለማደስ ወይም አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ለማደራጀት የሆነ እንደሆነ ከዚህ በታች በተነገሩት ድንጋጌዎች የሚመራ ይሆናል” በማለት ህግ አውጭው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3019 ንኡስ አንቀጽ 1 በመደንገግ ለማይንቀሣቀስም ንብረት ግንባታ ስራ ውል ገዥነትና ተፈጻሚነት ያላቸዉ ልዩ የህግ ድንጋጌዎች መሆናቸዉን በግልጽ አውጇል፡፡

ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የስራ ውል አስመልክቶ የሚያቀርባቸው ክርክሮች ለጉዳዩ ገዥነትና ተፈጻሚነት ያላቸዉ ልዩ የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ሣይሆን ጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ እንዲታይለትና እንዲወሰንለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስራ ተቋራጭነት ውል ተፈጽሟል የሚባለው አሰሪውና የስራ ተቋራጩ ስለሚፈጽሙት ስራዎችና ስለ ዋጋው አከፋፈል የተስማሙ በሆነ ጊዜ እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ንኡስ አንቀጽ 1 የሚደነግግ ሲሆን የስራው ተቋራጭ አሰሪው እያወቀ ስራዎቹን ለመስራት ጀምሮ እንደሆነ ወይም ከዋጋው ላይ አስቀድሞ ገንዘብ ተቀብሎ እንደሆነ ውል ለመኖሩ በቂ ማረጋገጫ ይሆናል በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ንኡስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል። ከላይ ከተገለጹት የህግ ድንጋጌዎች የምንረዳው የግንባታ ስራ ውል በልዩ ፎርም እንዲደረግ ስለማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውል የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚያዙት ፣ መሆኑን ለመረዳት የሚቻል መሆኑን ነው።

ይሽው የአመልካችና ተጠሪ ክርክርና ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭበጥ የማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውል ልዩ ባህሪና ህግ አውጭው የማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውልን በተመለከተ ገዥነትና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸዉ በማሰብ የደነገጋቸውን ልዩ የህግ ድንጋጌዎች አግባብነት ያላቸዉ የህግ ማዕቀፎች መሠረት ያደረገ ከመሆኑ አንጻር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

የማይንቀሣቀስ ንብረት ለመስራት የሚደረግ ውል አስመልክቶ ልዩ ተፈጻሚነትና ገዥነት ያላቸዉ ደንቦች ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3019 እስከ ፍታብሔር ህግ ቁጥር 3040 የተደነገጉት ድንጋጌዎች መሆናቸውን ህግ አውጭው "ስለማይንቀሣቀስ ንብረት የስራ ውል" በሚለው ክፍል " የስራ ተቋራጭነቱ ውል የተደረገው የህንጻ ስራን ለመስራት ፣ የተሰራውን ለማደስ ወይም አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ለማደራጀት የሆነ እንደሆነ ከዚህ በታች በተነገሩት ድንጋጌዎች የሚሰራ ይሆናል" በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3019 ንኡስ አንቀጽ 1 በግልጽ ደንግጓል። ስለማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ ውል አስረጅነት በልዩ ሁኔታ የተደነገገው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ንኡስ አንቀጽ 1 የስራ ተቋራጭነት ውል አለ የሚባለው ሁለቱ ወገኖች /አሰሪውና የስራ ተቋራጩ /ስለሚፈጸሙት ስራዎችና ስለዋጋው የተስማሙ በሆነ ጊዜ እንደሆነ የሚደነግግ ሲሆን የስራው ተቋራጭ አሰሪው እያወቀ ስራዎቹን ለመስራት ጀምሮ እንደሆነ ወይም ከዋጋው ላይ አስቀድሞ ገንዘብ ተቀብሎ እንደሆነ ውል ለመኖሩ በቂ ማረጋገጫ እንደሚሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ንኡስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል።

የሚሰራውን የግንባታ ስራ አይነትና መጠን እንደዚሁም ስራው ስለሚጠናቀቅበት ጊዜ መጋቢት 4 ቀን 1984 ዓ.ም በጽሁፍ ያደረጉት የስራ ውል ሐምሌ 1 ቀን 1985 ዓ.ም ያሻሻሉት መሆኑን የስር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል። አመልካች ከዚህ በኋላ የአመልካች ወኪልና አማካሪ መሀንዲስ ከተጠሪ ጋር በመስማማትና ቃለ ጉባኤ በመያዝ የሰጣቸው የስራ ትዕዛዝ ለውጦችና ተጨማሪ የግንባታ ስራዎች ስለመኖራቸውና በአሰሪው ወኪል ለውጥ የተደረገውን ስራዎችና የስራ ትዕዛዝ የተሰጠባቸው ተጨማሪ የግንባታ ስራዎች ለማከናወን የሚያስፈልገው ተጨማሪ ጊዜ የመጀመሪያው የስራ ውል በተደረገበት ፎርም መሠረት የተደረገ ባለመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1721ን በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ከላይ ሙሉ ይዘታቸው ከተገለጸው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ድንጋጌዎች አንጻር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል። የግንባታ ስራ ውል መጠን ፣ ክፍያና የግንባታ ስራ ውል የሚጠናቀቅበትን ጊዜ ለማሻሻል አሰሪውና የስራ ተቋራጩ የተስማሙ መሆናቸውን ለማስረዳት የመጀመሪያው የስራ ውል በተደረገበት አይነት የተጻፈ ውል ማቅረብ ግዴታ እንዳልሆነ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3020 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ይዘት ፣ መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ የአሰሪው ተወካይ የሆነው አማካሪ መሀንዲስ በየዕለቱ የሚሰጣቸው የስራ ትዕዛዞች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚጽፋቸው ማስጠንቀቂያዎችና ከስራ ተቋራጩ ጋር የተስማማባቸው ስነዶች የማይንቀሣቀስ ንብረት ግንባታ ስራ ውል ልዩና ውስብስብ ባህሪ አንጻር የስራ ተቋራጩን መብትና ወይም ግዴታ ለማስረዳት ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች እንደሆኑ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ስለግንባታ ስራ አፈጻጸም ባወጣው መመሪያ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች በወኪሉ አማካኝነት በተለያየ ጊዜ ከስራ ተቋራጭ ከሆነው ተጠሪ ጋር በማስማማትና ቃለ ጉባኤ በመያዝ የሰጣቸው የስራ ለውጥ ትዕዛዞችና ተጨማሪ የግንባታ ስራ ትዕዛዞችና የለወጣቸውን ስራዎችንና ተጨማሪ የግንባታ ስራውን ለማከናወን ተጠሪ የሚያስፈልገውን ጊዜ በሚመለከት ያደረጓቸው ስምምነቶች የመጀመሪያው የግንባታ ስራ ውል በተደረገበት ፎርም መሠረት የተከናወኑ ባለመሆኑ ህጋዊ ውጤት የላቸውም በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1721 በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

5.2. አመልካች የግንባታ ስራውን እንደ እሱ ሆኖ እንዲከታተሉለት የመደበው አማካሪ መሀንዲስ በተለያየ ጊዜ ከተጠሪ ጋር በተያዘ ቃለ ጉባኤ የስራ ለውጥ ትዕዛዝ የሰጠና የተጨማሪ ግንባታ ስራ እንዲሰራ የተስማማ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በግንባታው ሂደት ለተደረገ የስራ ለውጦችና ተጨማሪ የግንባታ ስራዎች ተጨማሪ ክፍያ ሲፈጽም የቆየ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የሰጠው የስራ ለውጥና የተጨማሪ ስራ ትዕዛዝ ተጨማሪ ስራ የሚያስከትል በሆነ ጊዜ በስራው መጠን የስራ ተቋራጩ ተጨማሪ ክፍያ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3032 ንኡስ አንቀጽ 2 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ አሰሪው የስራ ተቋራጩን ሀላፊነት የሚያከብድ የስራ ለውጥ ትዕዛዝ ወይም ተጨማሪ የግንባታ ስራ በሚያዝበት ጊዜ የተለወጠውን የግንባታ ስራ ወይም ተጨማሪ የግንባታ ስራ ለመስራት ተጨማሪ ክፍያ /ገንዘብ/ ብቻ ሣይሆን ተጨማሪ ጊዜ የማያስፈልገው በመሆኑ አመልካች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1763 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥት 1764 በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር የማይንቀሣቀስ ግንባታ ስራ በአሰሪው ትዕዛዝ ስለማለውጥበት ወይም ተጨማሪ የግንባታ ስራ ትዕዛዝ በሚሰጥበት ወቅት የስራ ተቋራጩ የተቀያየረውንና በተጨማሪነት የተሰጠውን የግንባታ ስራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነ ጊዜና ገንዘብ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን በፍ.ሕ፤ቁ. 3032 የተደነገገውን በግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 4 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት የህንጻ ግንባታ ስራ ውል ሀምሌ 1 ቀን 1985 ዓ.ም ያሻሻሉት መሆኑንና ከዚህ ጊዜ በኋላ አመልካች በወኪሉ አማካኝነት በሰጠው የስራ ትዕዛዝ ለውጥና የተጨማሪ ግንባታ ስራ ትዕዛዝ ምክንያት በተለያየ ጊዜ በቃለ ጉባኤ በመስማማት የግንባታው ስራ ማጠናቀቂያ ጊዜውን ያሻሻሉት በመሆኑ ተጠሪ በውሉ መሠረት የሚከፍለው ቅጣትም ሆነ የጉዳት ካሣ የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

5.3. አመልካች አማካሪ መሀንዲሱ የመጨረሻ ክፍያ የምስክር ወረቀት የማጽደቅ ስልጣን የሌለው መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አማካሪ መሀንዲሱ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ባዘጋጀው የክፍያ የምስክር ወረቀት የተመለከተውን ገንዘብ እንዲከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት አመልካች ወኪሉ በሆነው አማካሪ መሀንዲሱ ባዘጋጀው የመጨረሻ የክፍያ የምስክር ወረቀት የዘረዘረውን ክፍያ እንዲፈጽም የወሰነው ፣ የአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አማካሪ መሀንዲስ የመጨረሻ ክፍያ በተናጠል የማጽደቅ ስልጣን አለው ከሚለው መደምደሚያ በመድረሱ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት የወሰነው አመልካች ክፍያውን አልፈጽምም የሚልበት ህጋዊ ምክንያት ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ተአማኒነት ያለው ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑንና ተጠሪ ክፍያ የጠየቀበትንና በአመልካች አማካሪ መሀንዲስ የክፍያ የምስክር ወረቀት የተዘረዘረውን ስራ በአግባቡ ያከናወነና ክፍያውም የሚገባው መሆኑን በማስረጃ ያስረዳ መሆኑን በግልጽ በማስፈር እንደሆነ የስር ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልጽ አስፍሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የግንባታ ስራውን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ለአመልካች ያስረከበ መሆኑንና ተጠሪ ለአመልካች ሰርቶ ካስረከበው ስራ ውስጥ ጉድለት የተገኘበት የእምነበረድ ስራ ብቻ መሆኑ አመልካች ባቀረበው የክሣሽ ክሣሽነት ክስ በተደረገው ክርክርና በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣኑን በመጠቀም ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ የእምነበረድ ስራውን በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ባለመስራቱ አመልካች ጉድለቱን ለማስተካከል ሊያወጣ የሚችለውን ወጭ ተጠሪ ለመልካም አፈጻጸምና ለመያዣ ካስያዘው ገንዘብ ቀንሶ እንዲያስቀር የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ አማካሪ መሀንዲሱ ባዘጋጀው የመጨረሻ የክፍያ ሰርተፊኬት የገለጸውን የስራ መጠንና ዋጋ ያለው ስራ የሰራ መሆኑን በማስረጃ እንዳስረዳ በማረጋገጥ አመልካች ተጠሪ ለሰራው ስራ ክፍያ እንዲፈጽም የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር ባስቀምጥናቸው ምክንያቶች የአመልካች ክርክር ስለማይንቀሣቀስ ንብረት ግንባታ ስራ ተፈጻሚነት ያላቸውን ልዩ የህግ ድንጋጌዎችና የአሰራር መመሪያዎች መሠረት ያላደረገ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 60720

ግንቦት 15 ቀን 2003

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሄሪያ መሐመድ ግርግቦ - ጠበቃ አምሣለ ፀሐዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሽምሱ የሱፍ ጠበቃ በሻዳ ገመቹ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከመነሻው የስም መመሳሰልን መሠረት በማድረግ በሐሰተኛ ማስረጃ የተከናወነ የማይንቀሳቀስ ንብረት / መኖሪያ ቤት / ሽያጭ ውል ላይ የተደረገን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኗ አመልካች የፍርድ ባለመብት በመሆን መብታቸውን ከአስከበሩ በሁዋላ የአሁኑ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ መታየት የጀመረ ነው፡፡

የተጠሪ የውሣኔ መቃወሚያ አቤቱታ ይዘትም፡- በወረዳ 25 ቀበሌ 04 ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 1413 የሆነውንና አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸው በፍርድ ተረጋግጦ ውሣኔ ባገኘው መኖሪያ ቤት ሐምሌ 25 ቀን 1998 ዓ/ም በውልና ማስረጃ በተደረገ የሽያጭ ውል የባለሃብትነት መብት ማቋቋማቸውንና ካርታው በስማቸው ተሰርቶላቸው ቤቱን ተረክበው ይዘው እንደሚገኙ በቤቱ ላይ አመልካች የፍርድ ባለመብት መሆናቸውንም ግንቦት 03 ቀን 2001 ዓ/ም በቤቱ ላይ ከተለጠፈው ማስታወቂያ ማወቃቸውን ገልፀው ቀድሞ በቤቱ ላይ ሚያዝያ 08 ቀን 1995 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ እንዲነሳላቸውና ባለሃብትነታቸው እንዲረጋገጥላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ አቤቱታ በሰጡት መልስም ተጠሪ ውሣኔውን ለመቃወም የማይችሉ መሆኑን የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት መሆናቸው በፍርድ የተረጋገጠና ተጠሪም ከሕግ ውጪ አግኝቼበታለሁ በሚሉት ማስረጃ መሠረት ባለሃብት ሊሆኑ እንደማይችሉ ቤቱን ከመነሻውም ባለሃብት ያልሆኑት ወ/ሮ ሄሪያ መህመድ ኢብራሂም ለአቶ ሙዲ የሱፍ በመሸጥ አቶ ሙዲ የሱፍ ለተጠሪ መሸጣቸው ተግባሩን ሕጋዊ ሊያደርግ አይችልም በማለትና ቤቱ ለተጠሪ የተላለፈበትን መንገድ ሕገ ወጥ መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ፍሬ ነገሮችን በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ተጠሪ ቤቱን በውል እና ማስረጃ ፤ ከአቶ ሙዲ የሱፍ መግዛታቸውና በስማቸውም ካርታ ተሰርቶላቸው ቤቱን ይዘው የሚገኙ መሆኑ ተረጋግጧል፤ ካርታውን የሰጠው አካል እስካልሰረዘው ድረስ ተጠሪን ባለሃብት ነው ብሎ ለመቁጠር የሚያስችል ነው የሚሉ ምክንያቶችን ይዞ ቀድሞ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአከራካሪው ቤት ባለቤት ናቸው ሲል የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁጥር 360/2/ መሠረት ሰርዞታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ጸንቷል፡፡ አሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ መስከረም 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የአመልካች ስለመሆኑና ለተጠሪ ሽያጭ ፈጸሙ የተባሉት ሰው ምንም አይነት መብት የሌላቸው መሆኑን፣ ተጠሪ የሽያጭ ውሉን የፈፀሙት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ መሆኑ በተለያዩ ጊዜአት በተሰጡት የፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች በግልፅ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ ስመ ሃብቱን በአስተዳደር አካሉ በተሰጠው ካርታ አስመዝግበዋል ተብሎ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት ናቸው ተብሎ መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና ተገቢነት የሌለው ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አቶ መዲ የሱፍ የንብረቱ ባለቤት አይደሉም ተብሎ በተለያዩ መዛግብት ተወስኖ እያለ ለአሁኑ ተጠሪ በህጋዊ መንገድ እንደተሸጠ ተቆጥሮ የቤቱ ባለሃብት ተጠሪ ናቸው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአከራካሪው ቤት ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ታህሣሥ 20 ቀን 1987 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መሆኑን አመልካች ክስ የመሰረቱትም፡- 1ኛ/ በአቶ መዲ የሡፍ ፤ 2ኛ/ በመቶ አለቃ ሲሳይ መብራቱ ፤ 3ኛ / የሥጋ ሜዳ ተራራ የመኖሪያ ቤቶች የንብረት ሥራ ማህበር ፣ 4ኛ/ በአቶ ከማል ሀምዛ እና 5ኛ/ በወ/ሮ ሄሪያ መሀመድ ኢብራሂም ላይ መሆኑን ፣ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ መርምሮ አቶ መዲ የሱፍ ቤቱን የያዙት ቤቱን ለመሸጥ ምንም መብት ከሌላቸው ሰው ስለሆነ ሽያጩ የተከናወነውም በሀሰተኛ ሰነድ በመጠቀም ስለሆነ ውሉ ሊፈፀም የሚቻል አይደለምና ፈራሽ ነው በማለት ቤቱን ለአሁኗ አመልካች እንዲመልሱ ሲል ሚያዝያ 08 ቀን 1995 ዓ/ም በዋለው ችሎት መወሰኑን ፣ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኙት የስር ተከሣሾችም ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተናጠል አቅርበው አቶ መዲ የሱፍ የተባሉት ግለሰብ ያቀረቡት ይግባኝ በመ/ቁጥር 20831 ሐምሌ 02 ቀን 1995 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውድቅ የሆነ ሲሆን አቶ ከማል ሀምዛ እና ወ/ሮ ሄሪያ መሀመድ ኢብራሂም ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንድ ላይ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ሚያዝያ 08 ቀን 1995 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ መጋቢት 05 ቀን 1999 ዓ/ም በመ/ቁጥር 21687 ቢሻርም በዚህ ውሣኔ ላይ አሁኗ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሮ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 29978 ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተመልሶለት ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤትም በመ/ቁጥር 21687 ጉዳዩን እንደገና አይቶ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ መጋቢት 23

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀን 2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት ማጽናቱን በዚህ ውሣኔ አቶ ከማል ሀምዛ እና ወ/ሮ ሄሪያ መሀመድ ኢብራም ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በጉዳዩ ላይ መሰረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በመ/ቁጥር 45100 ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት መወሰኑን ነው። ተጠሪ ቤቱ ላይ ሕጋዊ መብት አቋቋሜአለሁ የሚሉት ሐምሌ 25 ቀን 1998 ዓ/ም ከአቶ ሙዲ የሱፍ ጋር የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በቅን ልቦና በውልና ማስረጃ የተደረገና ከውሉ በሁዋላ በስሜ ካርታ ተሰርቶ ቤቱን ይገፍው የምገኝ ነኝ በሚል ምክንያት እንጂ ቤቱን ሻጭ የሠሩት የግል ሀብታቸው መሆኑን የሚያሳይ ሕጋዊ ማስረጃ አለ አመልካችም የቤቱ ባለሃብት አይደሉም በሚል ምክንያት አለመሆኑን ተንገዝበናል።

በመሰረቱ አንድ ሰው አንድን ንብረት ለሌላ ሰው በሕጋዊ መንገድ ሊያስተላልፍ የሚችለው በንብረቱ ላይ መብት ሲኖረው መሆኑ የሚታወቅ ነው። በሌላ አገላለፅ በሕግ ጥበቃ የማይደረግለት ወይም የሌለ መብት ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ አይችልም። ይህ ተቀባይነት ያለው የሕግ መርሕ ነው። የሌላ ሰው ንብረት ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ ሕጋዊ የሆነ ስልጣን ሊኖር ይገባል።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ለተጠሪ አካራካሪውን ቤት የሸጡት አቶ ሙዲ የሱፍም ሆነ ቤቱን ከመጀመሪያውኑም ለአቶ ሙዲ የሱፍ ሸጡ የተባሉት አቶ ከማል ሀምዛ እና ወ/ሮ ሄሪያ መሀመድ ኢብራሂም የአመልካችን ሕጋዊ ስምምነት ወይም ወራሽነት አግኝተው ባይሆንም የቤቱ ባለሃብት መሆናቸውን የሚያሳዩ ሐሰተኛ ሰነዶችን ይዘው የነበሩ መሆኑ ፣ አቶ ሙዲ የሱፍ ቤቱን ከገዙ በሁዋላ የቤቱን ስመ- ሀብት ከተገቢው የአስተዳደር አካል ከአገኙ በኋላ ለአሁኑ ተጠሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርበው ቤቱን የሸጡላቸው የቤቱ ስመ ሃብትም በተጠሪ ስም የተመዘገበ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሠረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሠጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማንቀሳቀስውን ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊገመት እንደሚገባ ተመልክቷል። ይህን ማስረጃ የያዘ ሰው ደግሞ ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሸጠ ተግባሩ ሕገወጥ የሚባልበት ምክንያት የለውም። አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገዶች ለሌላ ለማስተላለፍ መብት አለውና። ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ስር የተመለከተው የሕግ ግምት ፍፁም የሆነ ወይም ደምዳሜ ላይ መድረስ የሚያስችል ማስረጃ አይደለም። ግምቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ስር የተመለከቱት ሁኔዎች ስለመኖራቸው በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ ሊስተባብል የሚችል የሕግ ግምት ነው። በመሆኑም አንድ ሰው በአስተዳደር አካል የተሰጠ ካርታ በመያዙ ብቻ በካርታው የተጠቀሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሕጋዊ ባለሃብት እንደሆነ ሕጉ ግምት ቢወስድለትም ይህ ግምት ግን ካርታው የተሰጠበትን አግባብ ከደንቡ ከአሰራሩና ከስልጣኑ ውጪ እንዲሁም በማይረጋ የምስክር ወረቀት መሠረት ማስረጃው ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ የሕጉን ሕሊናዊ ግምት ማፍረስ እንደሚቻል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል። በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሣሽ የነበሩት አቶ ሙዲ የሱፍ ቤቱን የያዙትና ለየአሁኑ ተጠሪ ያስተላለፉት ሕጋዊ ካልሆኑ ሻጮች በመግዛት መሆኑና ለጉዳዩ የቀረቡት ሰነዶች ሁሉ ሕጋዊ ዋጋ የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጦ አቶ ሙዲ የሱፍ የቤቱ ባለሃብት ሊሆኑ አይችሉም ተብሎ በተለያዩ የክርክር ደረጃዎች የተወሰነ ከሆነ አቶ ሙዲ የሱፍ ለአሁኑ ተጠሪ የሸጡት ሽያጭ ሕጋዊ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም። ተጠሪ ውሉን በውልና ማስረጃ ማድረጋቸው ከመነሻው ሕገወጥ የሆነን ተግባር ሕጋዊ ሊያደርግ የሚችልበት አግባብ የለም። የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በቅን ልቦ የተደረገ ነው ተብሎም በሕግ ጥበቃ የሚደረግበት አግባብ የለም። በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሕጋዊ መብት የሌለው ሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውሉ ለገ/ር መድህን ለመሆን ግዴታ ገብቶ ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሃብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገ/ር ሳይሆን ሻጩን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2882 እስከ 2884 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 997 ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ አቶ ሙዲ የሱፍ በቤቱ ላይ መብት የሌላቸው መሆኑን ያወቁት ሐምሌ 02 ቀን 1995 ሲሆን ለተጠሪ ቤቱን በውልና ማስረጃ የሸጡት ግን ሐምሌ 25 ቀን 1998 ዓ/ም የቤቱ ባለመብት ያለመሆናቸውን እያወቁ ነው፡፡ አቶ ሙዲ ለአሁኑ ተጠሪ መድህን ለመሆን ግዴታ የገቡበት ሁኔታም የለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካች ለረ/ርም ጊዜ በክርክር ላይ በነበሩበት ሁኔታና በፍርድ መብታቸው ተረጋግጦ እያለ የክርክሩ ተሳታፊ የነበሩት ሰዎች በፍርድ መሸነፋቸውን አውቀው በአከናወኑት የሽያጭ ውል ሕጋዊ ገ/ር ናቸው ሊባሉ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት የገዙት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ከያዙት ግለሰብ ባለመሆኑ ሽያጩ የተከናወነው ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት በመሆኑና ካርታውም በስማቸው ተሰርቶ ተሰጥቷል በሚል ምክንያት ብቻ የሽያጭ ውሉ ሕጋዊ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/1/ የተከበረላቸው እና በፍትሓ ብሔር ሕጉ ስለንብረት በሚደነግጉት ድንጋጌዎች ጥበቃ የሚደረግለት የባለሃብትነት መብታቸው ከሕግ አግባብ ውጪ ስለመደረጉ በተረጋገጠዉ የሽያጭ ውል ቀሪ የሚሆንበት ምክንያት ሳይኖር የበታች ፍርድ ቤቶች የአከራካሪው ቤት ሕጋዊ ባለሃብት ተጠሪ ናቸው፡፡ በማለት የቀድሞውን ውሣኔ በመሻር የሠጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04917 ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 88537 ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአከራካሪዉ ቤት ተጠሪ ሕጋዊ መብት የላቸውም ፣ ቤቱ የአመልካች ሕጋዊ ንብረት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠ/መ/ቁ 63042

ግንቦት 1 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነገረ ፈጅ አቶ ደስታ ሊበን - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሰለሞን ነጋሽ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች የፌደራል የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የሚጣራ የህግ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታ ክርክር መነሻ የሆኑት ጉዳዮች በመጀመሪያ የታዩት በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104138 ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በቀድሞው አጠራር ወረዳ 22 ቀበሌ 07 የቤት ቁጥር 117 የሆነውንና ለሆቴል አገልግሎት የሚውል የድርጅት ቤት በወር ብር 27,942.95 /ሃያ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከዘጠና አምስት ሣንቲም/ ለመክፈል ተስማምተው በፈረሙት የኪራይ ውል መሠረት የአስራ ሁለት ወር /የአንድ ዓመት / የቤት ኪራይ መጠባበቂያ የሁለት ወር ኪራይ ፣ በድምሩ የአስራ አራት ወር ኪራይ ብር 442,288.61 /አራት መቶ አርባ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከስልሣ አንድ ሣንቲም/ ለተከሣሽ /አመልካች/ ከፍያለሁ ቤቱ የእግድ ትዕዛዝ የነበረበት በመሆኑና የቀድሞው ተከራይ ሁከት ስለፈጠረብኝ ቤቱን ለተከራየሁበት ዓላማ ማዋል አልቻልኩም፡፡ ስለሆነም አከራዩ አመልካች የከፈልኩትን ገንዘብ እንዲመለስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል አመልካች/ ተከሣሽ/ በተከራይነት ቀርቦ የአከራይነት ግዴታውን የተወጣ መሆኑን ገልፆ የኪራይ ውሉ የሚፈርስበትና ከሣሽ/ ተጠሪ/ የከፈለውን የቤት ኪራይ የምንመልስበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌደራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104138 በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታና ክርክር በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 65504 ሰምቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ከሣሽ በመሆን ተጠሪ ላይ ክስ መስርቶ በመዝገብ ቁጥር 136416 የአመልካቾችና የተጠሪን ክርክር በመስማት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 7 ቀን 2001 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች ተከራዩ /ተጠሪ/ ከሀምሌ 17 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ቤቱን ይዘው ኪራይ ያልከፈሉ በመሆኑ በውሉ መሠረት ኪራይ መቀጫና ሌሎች ክፍያዎች ብር 171,487.63/አንድ መቶ ሰባ አንድ ሺ አራት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከስልሣ ሶስት ሣንቲም/ ሊከፍል ይገባል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የኪራይ ውሉ እንዲፈርስ ክስ አቅርቦ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቤአለሁ፡፡ ተጨማሪ ኪራይ የመክፈል ሀላፊነት የለብኝም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ/ ተከሣሽ/ አመልካች/ከሣሽ/ በክሱ የጠየቀውን ብር 171,487.63 እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 82009 ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 65504 ያቀረበውን ይግባኝ ከይግባኝ መዝገብ ቁጥር 82009 ካቀረበው ይግባኝ ጋር በማጣመር መርምሮ አመልካች በቅድሚያ ክፍያነት ከተጠሪ የወሰደውን የቤት ኪራይ ብር 442,288.61/አራት መቶ አርባ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከስልሣ አንድ ሣንቲም/ ለተጠሪ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ የቤት ኪራይ ብር 171,487.63/አንድ መቶ ሰባ አንድ ሺ አራት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሥልሳ ሶስት ሣንቲም/ የመክፈል ሀላፊነት የለበትም በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104138 እና በመዝገብ ቁጥር 136416 የሰጣቸውን ውሣኔዎች ሙሉ በሙሉ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የፌደራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ታህሣሥ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በጨረታ ተወዳድረው የድርጅት ቤት ተከራይተዋል፡፡ በኪራይ ውሉ መሠረት ቤቱን አስረክበናቸዋል፡፡ አመልካች በኪራይ ውሉ መሠረት ግዴታውን ተወጥቷል፡፡ ተጠሪ በቤቱ የንግድ ፈቃድ ለማውጣት አልቻልኩም በማለቱ ቤቱን ቀበሌ በይዞታው አድርጎ ለቆየበት ጊዜ በቅድሚያ ከፍሎት የነበረውን የኪራይ ገንዘብ እንድንመልስ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተከራዩ ተጠሪ ቤቱን ለአከራዩ አመልካች መልሶ ከማስረከቡ በፊት ሊከፍለው የሚገባውን የኪራይ ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የለበትም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔና በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገውን የኪራይ ውል ይዘት ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጥር 3 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ያከራየኝ የድርጅቱ ቤት ሶስት የእግድ ትዕዛዞች ያለበት በመሆኑ የንግድ ፈቃድ ማውጣት እንደማልችል በሚመለከተው አካል ተነግሮኛል፡፡ አመልካች የእግድ ትዕዛዙን እንዲያስነሳልኝ ሁለት ጊዜ ማስጠንቀቂያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰጥቸዋለሁ፡፡ አመልካች እግዱን ያላስነሣ በመሆኑ የኪራይ ውሉ ፈርሶ በቅድሚያ የከፈልኩትን ብር 442,288.61 እንዲመልስልኝ የተሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኪራይ ውሉ ሣይታደስ አመልካች ቤቱን ይዘህ ቆይተሀል በማለት የጠየቀውን ብር 171,487.63 የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ያድርግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በፅሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ በኪራይ ውሉ መሠረት የከፈለውን የኪራይ ገንዘብ አመልካች እንዲመልስ መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ያልከፈለውን የቤት ኪራይ ለአመልካች የመክፈል ሀላፊነት ያለበትም በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚሉት ጭብጦች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ተጠሪ በተከራየውና የተረከበውን ቤት ለሆቴል አገልግሎት እንዳላውል ተፈጥረውብኛል የሚላቸውን ሁከቶችና ሌሎች ችግሮች ተጠሪ በራሱ ስም አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን በመፈፀም ሊያስወግዳቸው የሚችሉ ናቸው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ በኪራይ በውሉ መሠረት የተረከበውን ቤት ለሆቴል አገልግሎት ድርጅት ለማዋል ያልቻለው በቤቱ ላይ ሶስት የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ተሰጥቶ የነበረ በመሆኑ ንግድ ፈቃድ ማውጣት አልቻልኩም፡፡ የቀድሞው ተከራይ በየወቅቱ እያመጣ ሁከት ፈጥሮብኛል በማለት ነው፡፡

የማይንቀሣቀሥ ንብረት የኪራይ ውል ከተደረገና ንብረቱ ለተከራይ ከተላለፈ በኋላ በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎችና የሀብት ተግባራት በማስወገድ በኩል አከራዩ ብቻ ሣይሆን በተከራዩም ላይ በህግ የተጣለ ግዴታና ሀላፊነት እንዳለ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2913 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2914 ድንጋጌዎች ይዘት በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የተከራየው የማይንቀሣቀስ ንብረት የኔነው ወይም በዚሁ ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ክርክር በሶስተኛ ወገኖች ለፍርድ ቤት ክርክር ያቀረቡ በሆነ ጊዜ ተከራዩ ለአከራዩ የማሣወቅ ግዴታ እንዳለበትና አከራዩም በክርክሩም ጣልቃ ገብቶ በመከራከር ሀላፊነት ያለበት መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2913 ድንጋጌዎች በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2913 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ የሚቻለው አከራዩ በዋቢነት ቀርቦ ክርክር የማድረግ ሀላፊነት ያለበት የተከራየው ንብረት ባለሀብት ነኝ የሚል ሰው በሚመጣ ጊዜ ወይም በተከራየው የማይንቀሣቀሥ ንብረት ላይ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠው መብት አለኝ የሚሉ ሶስተኛ ወገኖች ክርክር ያነሡ በሚሆንበት ጊዜ መሆኑን "የተከራየው የማይንቀሣቀሥ ንብረት የኔ ነው ወይም በዚሁ ንብረት ላይ መብት አለኝ ብሎ ሶስተኛ ወገን ክርክር ያነሣ እንደሆነ ተከራዩ ለአከራዩ ማሳወቅ አለበት" በሚል ይዘት ካለው የፍታብሔግ ህግ ቁጥር 2913 ንዑስ አንቀፅ 1 እና እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ተከራዩ ከክርክሩ ውጭ የሚሆን ስለመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2913 ንዑስ አንቀፅ 2 ከተደነገገው ለመገንዘብ እንችላለን፡፡

በያዝነው ጉዳይ የቀድሞው የቤቱ ተከራይ ከሌሎች ሰዎች ጋር በነበረው ክርክር ምክንያት የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ተሰጥቶ የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ የተሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአመልካች ላይ የቀድሞው ተከራይ በፍርድ ቤት ክስ በማቅረቡ ምክንያት እንዳልሆነ ወይም ቤቱ የእኔ ንብረት ነው የሚል ክርክር በመቅረቡ ምክንያት እንዳልሆነ የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ የዕግድ ትዕዛዝ በፍርድ ቤት የተሰጠው የቤቱ ባለንብረት ነኝ ወይም በቤቱ ላይ ከውል ወይም ከህግ በመነጨ መብት አለኝ የሚሉ ሶስተኛ ወገኖች ክርክር በማቅረባቸው ሣይሆን ከቀድሞው ተከራይ ጋር ክርክር የነበራቸው ሰዎች የቀድሞውን ተከራይ የሆቴል ንግድ ድርጅት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲከበርላቸው ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ተጠሪ በተከራየው ቤት ላይ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2913/1/ መሠረት ከሶስተኛ ወገኖች የቀረበ ክርክር አለመኖሩ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ በቤቱ ላይ ከውል ወይም ከህግ ያመነጨ መብት የሌላቸው ሰዎች ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻ የተሰጠን የዕግድ ትዕዛዝ ማስነሳት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2914 መሠረት ቀላል የሆነ ሀብት የማስወገድ ተግባር ነው፡፡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2914 ንዑስ አንቀፅ 1 በተከራየው የማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የባለቤትነት መብት ወይም ሌላ መብት አለን በማይሉ በሶስተኛ ወገኖች አድራጎት ለሚነሳው ሁከት አከራዩ ዋስትና እንዲሰጥ የማይገደድ መሆኑን በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ይህን የመሰለውን ሁከት ለማስወገድ ተከራዩ በራሱ ስም ለመከራከር ይቻላል በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2914 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ በፍርድ ቤት የተሰጠው አመልካች ባከራየው ቤት ላይ የቀድሞው ተከራይ በነበረው የንግድ ድርጅት ላይ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ቤቱን ከአመልካች የተከራየ መሆኑንና በትዕዛዝ የተከበረው የንግድ ድርጅቱ በተከራየው ቤት ላይ የሌለ መሆኑን የዕግድ ትዕዛዙን በሰጠው ፍርድ ቤት በማመልከት የዕግድ ትዕዛዙ እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 158 መሠረት የመጠየቅና ተጠሪ በተከራየው ንብረት ላይ የተከሰቱ ቀላል ችግሮችን የማስወገድ ሀላፊነት የተከራዩ /የተጠሪ/ መሆኑን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2914 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ መሆኑን ሣያገናዝብ የፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ ቤቱን ከተከራየበትና ከተረከበበት ከሀምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ቤቱን በይዞታቸው ሥር አድርገው የቆዩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ በማለት የሚከራከር ቢሆንም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2936 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት የኪራይ ውሉ ሲያልቅ በኪራይ የያዘውን የማይንቀሣቀስ ንብረት ለአመልካች ያስረከበ መሆኑን ተጠሪ አላስረዳም፡፡ ተጠሪ ቤቱን ይዞ መቆየቱ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2968 ንዑስ አንቀፅ 1 ኪራዩን እንዳደሰ የሚያስቆጥረው ነው ስለሆነም አመልካች ከሀምሌ 18 ቀን 2000 እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ያለውን ቤት ኪራይ ተጠሪ የመክፈል ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ስለሆነም የመጀመሪያው ጭብጥ ለመወሰን የሰጠውን የተሣሣተ የህግ ትርጉም መሠረት በማድረግ ተጠሪ ውዝፍ ቤት ኪራይ የመክፈል ሀላፊነት የለባቸውም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104138 እና በመዝገቡ ቁጥር 136416 የሰጣቸው ውሣኔዎች ፀንተዋል፡፡
3. ወጭና ኪሣራን ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 13 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ ቱሌ አብዶ በሌለበት

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ ተጠሪ ለሥር የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ የሰበር አመልካች / በሥር 1ኛ ተከሣሽ / እና በሥር 2ኛ ተከሣሽ በነበረው ሁናን ሁንዴ የመንገድና የድልድይ ሥራ ድርጅት ላይ ያቀረቡት ክስ ፍሬ ቃሉ 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሽ በመካከላቸው ባደረጉት የመንገድ ሥራ ውል 2ኛ ተከሣሽ ዳከር በሚባል አካባቢ የሚገኘውንና በገማች ኮሚቴ ተገምቶ ግምት 166,115 የሆነውን የከሣሽ መጋዘን እንዲፈርስ በሰኔ ወር 2000 ዓ/ም ምልክት በማድረግ ግምቱ ሳይከፈል መጋዘኑን በታህሣሥ ወር 2001 ዓ/ም ያፈረሰ ከመሆኑም ሌላ ብር 20,000 የሚያወጣ አንድ ቤት እና ብር 15,000 የሚያወጡ ዛፎች ግምት ብር 15,000 ፣ የአንድ ክፍል ቤት ግምት 20,000 እና መጋዘኑ እንዲፈርስ ምልክት ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ለ17 ወራት ገቢ የተቋረጠ ስለሆነ በቀን ብር 350 ሂሣብ 178,500 ሆኖ በድምር ብር 379,615 ተከሣሾች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር 1ኛ ተከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካችም በሰጠው መልስ በገማች ኮሚቴ ግምት መሠረት ንብረቱ እንዲነሣ መደረጉን በማመን ከመንገድ ክልል ውጪ ላሉት የከሣሽ ንብረቶች ግን ካሣ የመክፈል ግዴታ የለብኝም ፣ በገንዘብ ልክ ተመልክቶ የሚከፈል ካሣ ዘግይቶ በመክፈል ምክንያት ለደረሰ ጉዳት መክፈል ያለበት ህጋዊ ወለድ እንጂ የተቋረጠ ጥቅም አይደለም፣ መጋዘኑ እንዲፈርስ ምልክት ቢደረግም ከሣሽ በመጋዘኑ እንዳይጠቀሙ ስለመከልከላቸው አላስረዱም፣ የዕለት ገቢን በሚመለከት ከሣሽ የመንግስት ግብር የተከፈለበትን ደረሰኝ አያይዘው አልቀረቡም፣ ቤቱ ላይ ደረሰ ለተባለውም ጉዳት መጠየቅ የሚችሉት የጥገና ወጪውን እንጂ የአዲስ ቤት መሥሪያ ግምት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር 2ኛ ተከሣሽ በበኩሉ ባቀረበው መልስ ከሣሽ የካሣ ጥያቄአቸውን ህጉ በሚፈቅደው መሠረት 1ኛ ተከሣሽን ከሚጠይቁ በስተቀር 2ኛ ተከሣሽን ሊጠይቁ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትም በሰጠው ፍርድ 1ኛ ተከሣሽ በገማች ኮሚቴ ተገምቶ የቀረበውን የመጋዘን ዋጋ ብር 166,115 እና የመጋዘኑ የዕለት ገቢን በሚመለከት የከሣሽ ምስክሮችን ከሰማ በኋላ መጋዘኑ ከፈረሰበት ከታህሣሥ 2001 ጀምሮ የ17 ወራት ብር 178,500 ፣ እንዲሁም በተጨማሪ ክስ ከተጀመረበት እስከ ግንቦት 2002 ያለውን የ7 ወር ብር 73,500 ተጨምሮ በድምሩ ብር 418,115 1ኛ ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ 2ኛ ተከሣሽ ግን የንብረት ካሣን በሚመለከት ሀላፊነት ባይኖረውም በሌሎች የካሣ ዓይነቶች ሀላፊነት የለብኝም ለማለት የማይችል መሆኑን በውሣኔው አስፍሯል፡፡

ጉዳዩን የአሁኑ የሰበር አመልካች በይግባኝ ለሥር ክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የመጋዘኑን የዕለት ገቢ በፍ/ህ/ቁ 2102 መሠረት በርትዕ ብር 75 በመወሰን የ24 ወራት ብር 54,000 ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጪው እንዲከፍል አሻሽሎ በመወሰን በሌሎች ነጥቦች ላይ ግን የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም የመጋዘኑ ባለቤት ስለመሆናቸው ተጠሪው የባለቤትነት ማረጋገጫ ወረቀት አላቀረቡም፡፡ የገማች ኮሚቴ ለመጋዘኑ ካቀረበው የግምት ውጤት ብር 166,155 በተጨማሪ በቀን በብር 75 ሂሣብ የ24 ወራት የተቋረጠ ገቢን ብር 54,000 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ የተወሰነው ህግና ማስረጃን መሠረት ያላደረገ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ለተጠሪው መጥሪያ ተልኮላቸው ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን አመልካች ለዚህ ችሎት በ28/8/2003 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ከመግለጹም በላይ ተጠሪው የሚኖሩበት ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት በቁጥር አ/አ/ቀ/ሠ/10328/03 በቀን 26/8/2003 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ተጠሪው የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑን በማረጋገጡ ክርክሩ በሌሉበት እንዲቀጥል ችሎቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በሥር ፍ/ቤት የተደረገው ክርክርና የአመልካች አቤቱታ ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ የተገለፀ ሲሆን እኛም ለመጋዘኑ ከቀረበው የግምት ገንዘብ በተጨማሪ ከመጋዘኑ የሚገኘው ገቢ ተቋርጧል በሚል የተቋረጠውን ገቢ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ከሥር ፍ/ቤት ጀምሮ ተጠሪው የመጋዘኑ ባለቤት ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ የላቸውም በማለት እንዲከፍል ከተወሰነበት የተቋረጠ ገቢ ጋር አያይዞ የሚከራከር ቢሆንም የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት በመንገድ ሥራ ምክንያት ንብረቶቻቸው ላይ ጉዳት ከደረሰባቸው ግለሰቦች መካከል አንዱ ተጠሪው ስለመሆናቸው የሶፊ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት አረጋግጧል በማለት በውሣኔው ካሰፈረው ጋር ሲገናዘብ ተጠሪው የንብረቱ ባለቤት አይደሉም በማለት የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ወደተያዘው ጭብጥ ስንመለስ አመልካች የመጋዘኑን ግምት ዋጋ እንጂ ተጠሪው አጥተዋል የተባለውን የተቋረጠ ጥቅም መክፈል አይገባኝም በማለት ያቀረበውን የመከራከሪያ ሀሣብ ለህገ-ብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን ከወጣው አዋጅ ቁጥር 455/97 አንፃር መመርመር ተገቢነት የሚኖረው ነው፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 2/1/ ለ “ ካሣ ” በተሰጠው ትርጉም መሠረት ካሣ ማለት የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ ለሚወሰንበት ባለይዞታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሬቱ ላይ ለሠፈረው ንብረት በዓይነት ወይም በገንዘብ ወይም በሁለቱም የሚከፈል ክፍያ ሲሆን የመሬት ይዞታውንም የሚለቅ ባለይዞታም በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት ወይም ማሻሻል ካሣ እንደሚከፈለው በአዋጅ አንቀጽ 7/1/ ተደንግጓል፡፡ በይዞታው ላይ ለሚገኘው ንብረት የሚከፈለውም ካሣ ንብረቱን ባለበት ሁኔታ ለመተካት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪው በመንገድ ሥራ ምክንያት የፈረሰባቸው አንድ መጋዘን ሲሆን ይኸው የመጋዘን ዋጋም በገማች ኮሚቴ ብር 166,115 ተገምቶ ቀርቧል፡፡ ይህ የመጋዘኑ ግምትም በአዋጅ አንቀጽ 7/1/2/ በተደነገገው መሠረት የፈረሰውን መጋዘን ለመተካት በሚያስችል መልኩ የቀረበ ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪው ምናልባት ይኸው የመጋዘኑ ግምት መጋዘኑን ለመተካት የሚያስችል አይደለም የሚሉ ከሆነ በአዋጅ አንቀጽ 16 በተደነገገው መሠረት ይግባኝ ማቅረብ ከሚችሉ በስተቀር መጋዘኑ ተገምቶ የግምቱን ገንዘብ እንዲወስዱ ከተወሰነላቸው በኋላ መጋዘኑ እንዲፈርስ ምልክት ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ የአጡትን ገቢ የሚጠይቁበት የህግ መሠረት የላቸውም፡፡ በሌላ አነጋገር የመጋዘኑ ግምት እንዲከፈል እስከጠየቁ ድረስ የግምቱን ገንዘብ ከሚወስዱ በስቀር ገቢ አጥቻለሁ በማለት የተቋረጠውን ገቢ ሊጠይቁ የሚችሉበት ሁኔታ የለም፡፡

የሥር ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ ለውሣኔአቸው መሠረት ባደረጉት አዋጅ ቁጥር 455/97 ሆነ አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 135/99 የንብረቱ ካሣ ለባለንብረቱ ከሚከፈል ውጪ የተቋረጠ ገቢን ለባለንብረቱ እንዲከፈል በግልጽ ባልተደነገገበት ከተጠቀሱት ህጐች ዓላማ ውጪ ለተጠሪው የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈል መፍቀዳቸው ወይም መወሰናቸው ተገቢነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን የመሩት በአግባቡ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ ቁጥሮችን ሳይከተሉ መሆኑን የክርክሩ መዝገብ ያመለክታል፡፡ ይኸውም ተጠሪው አመልካች እንዲከፍል የጠየቁት የካሣ መጠን ብር 379,615 ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤት ግን የመጀመሪያው ክስ ባልተሻሻለበት አመልካች ለተጠሪ ብር 418,115 እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይህም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182 /2/ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራካሪዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ ለመስጠት አይችልም በሚል የተደነገገውን የሚቃረን ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ቢሆን ተጠሪው ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የ17 ወሩ የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈላቸው እንዲወሰን ጠይቀው እያሉና በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት መስቀለኛ ይግባኝ ባላቀረቡበት አመልካች ባስከፈተው የይግባኝ መዝገብ በሥር ፍ/ቤት ክርክር ያልተደረገውን የ7 ወራት የተቋረጠ ገቢን በመጨመር በድምሩ የ24 ወራት የተቋረጠ ገቢን አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል በሚል መወሰኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 329/1/ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያልተነሣውን ክርክርና ያልቀረበውን አዲስ ነገር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለመቀበል አይችልም ተብሎ በግልጽ የተደነገገውን ያልተከተለ ነው፡፡ ለማጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በመንገድ ሥራ ምክንያት እንዲፈርስ የተባለው የተጠሪ መጋዘን ተገምቶ ግምቱ ከቀረበ በኋላ ይኸው ገንዘብ ለተጠሪው እንዲከፍል መወሰን ሲገባቸው የመጋዘኑን የተቋረጠ ገቢ ጭምር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የሥር የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06653 በቀን 17/10/2002 በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01670 በቀን 05/4/2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪው የመጋዘኑን የተቋረጠ ገቢ እንዲከፍል የተወሰነው የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ስለሆነም የተቋረጠውን መጋዘን ገቢ አመልካች ለተጠሪ አይከፍልም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ አመልካች የራሱን ይቻል ብለናል፡፡ ተጠሪው በዚህ ፍ/ቤት ቀርበው ያልተከራከሩ ስለሆነ የሚታዘዝላቸው ወጪና ኪሣራ የለም፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ፓዝ ፋይንደር ኢንተርናሽናል ኢትዮጲያ - ጠበቃ ኒቆዲሞስ ጌታነ-ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ መንበር አድማሱ - ቀረቡ

2. የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ - ወኪል በላይ አንተ - ቀረቡ ።።

መዝገብ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።።

ፍ ር ድ

ይህ የስበር ጉዳይ የቀረበው አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት በተከራይ እጅ እያለ በእዳ ምክንያት በተለላለፈ ጊዜ ገዥው በባለቤትነቱ ተከራይ ደግሞ በተከራይነቱ የሚኖራቸው መብት ምንድን ነው የሚለውን አስመለክቶ ግራቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር በማየት አስፈላጊውን ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው።።

የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመሰረተው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ነው የአመልካች የክስ ይዘትም ሐጂ ይማም መሀይን ከተባሉ ግለሰብ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 04 ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 1212 የሆነ ቤት ሐምሌ 11 ቀን 2002 ዓ/ም በተጻፈና እስከ መስከረም 20 ቀን 2005 ፀንቶ በሚቆይ የኪራይ ውል ተከራይቶ በመጠቀም ላይ እያለ አከራዩ ግለሰብ ከአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የወሰዱን የብድር ገንዘብ ለመክፈል ባለመቻላቸው ባንኩ ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ መሸጡን ግልጾ የኪራይ ውሉ ከአከራዩ ጋር ባላበቃበት ሁኔታ ባንኩ የተከራይነት መብቱን ለአመልካች ሳይጠብቅ ለ2ኛ ተጠሪ ቤቱን በመሸጥ ተከራዩ አመልካች ቤቱን ለ2ኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ የጻፈው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሁከቱ ሊወገድ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው።። የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ስልጣን የተጠቀመው መብት በመሆኑ ሁከት ሊባል አይችልም የሚል ሆኖ ክሱ ውድቅ እንዲሆን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ተጠሪም በሕጉ አግባብ ተጫርቶ የገዛው ንብረት በመሆኑ የሁከት ተግበር ሊባል እንደማይችል ገልፆ ተከራክሯል።። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌደራሉ መጀመሪያ ደርጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የተጠሪዎች ተግባር ሁከት ሊባል የሚችል አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አደርጎታል በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኝ ለፌዴራሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2931 እና 2933 በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 449 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታርም የሚገባው ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1933 ስር ከተመለከተው ድንጋጌ አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ የሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በዚህ መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በውሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ባቀረበው የውሐፍ መልስ የፍ/ብሕ/ቁጥር 2931 እና 2933 ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 97/90 የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው መሆኑን በመግልፅ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን 2ኛ ተጠሪም በሕጉ አግባብ የገዙት ቤት ስለሆነ ተግባሩ ሁከት ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

እንግዲህ ግራቀኙ ከሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ በጉዳዩ ላይ ያቀረቡት ክርክር እና ለሰበር ክርክርሩ መነሻ የሆኑት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔዎች ይዘት ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይህንኑ ክርክራቸውን ከስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል ፡፡

እንደመረመርነውም ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ በሆነውና ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀረበው ክስ ላይ የአሁኑን አመልካች የጠይቁት ዳኝነት በኪራይ ውል በያዝኩት ቤት የኪራይ ውሉ ዘመን ከመራዘሙ በፊት ቤቱ በሐራጅ ለ2ኛ ተጠሪ ተሸጦ ርክክብ እንዲደረግ ማስጠንቀቂያ መውጣቱ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊወገድ ይገባል የሚል ነው፡፡

አከራካሪ ሆኖ የተገኘውና የህግ ትርጉም የሚያሻው ነጥብ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ህንፃውን በጨረታ መሸጡና ቤቱን አመልካች ለቆ እንዲያስረክብ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ አመልካች በሻጭና በገዥው ላይ በመቃወሚያነት በማነሳት በፍ/ሕ/ቁ 2931 እና 2933 በተደነገገው መሰረት የኪራይ ውሉ ዘመን ሳያበቃ ቤቱን የማስረከብ ግዴታ የለብኝም ድርጊቱ ሁከት ነው ሊወገድ ይገባል በማለት ለመከራከር ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ነው፡፡

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራይ ለአሁን ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክብ ማስጠንቀቅያ መስጠቱ ሁከት አይደለም የሚለውን ምክንያት ለውሳኔው መደምደሚያ መሰረት ያደረገው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2899 አና 2932/1/ እና አዋጅ ቁጥር 97/90 ስር የተመለከተው ዓላማ ሲሆን ከላይ የተጠቀሱት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች የተፈፃሚነት ወሰን አንድ ኪራይ ውሉ ይዞታን በተከራይ እጅ አፅንቶ ለማቆየት አከራዩ በእዳ ምክንያት ንብረቱ የሚሸጥበት ከሆነ ንብረቱን የሚግዛው ሶስተኛው ወገን ንብረቱን የመረከብ ሁኔታ የኪራዩ ውሉ ዘመን ከማብቃቱ በፊት ሊጠቀምበት የመቻሉን ሁኔታ እስከመገደብ የሚደርስ ነው? የሚለውን ለይቶ ማስቀመጡ ተገቢ መሆኑን ከክርክሩ ይዘት መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የፍትሐብሔር ሕግ ደንጋጌዎች በተናጠልም ሆነ እረስ በእርሳቸው አስተሳስረን ስንመለከታቸው አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት የገዛ ሰው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1184 መሰረት በሽያጭ ውል አማካኝነት የባለቤትነት መብት በተላለፈለት ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1204 በህግ በተሰጠው የባለቤትነት መብት ተጠቅሞ ከመሸጡ በፊት በተሸጠው ንብረት ላይ በተከራይነት በይዞታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አድርገው የሚገኙት ሰዎችን በማስለቀቅ የኪራይ ውሉን ማቋረጥ የማይችል በመሆኑ በፍ/ብሕ/ቁ 1204/2/ እንደተመለከተው ገደብ የጣሉበት ድንጋጌዎች መሆናቸውን የሚያሳዩ ሲሆን ይህ የሚሆነው ደግሞ ገዥው ንብረቱን ከአከራይ ገዝቶ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

አንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ከአምስት ዓመት በላይ የተደረገ እና ይህም የኪራይ ውል ተመዝግቦ ከተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2899 እና 2931 ይህ ዓይነት የኪራይ ውል በገዥው ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችልና ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት በተከራዩ ላይ ጉዳት ደርሶ ከሆነ ውሉ እንዲፈርስና የጉዳት ኪሳራን ለመጠየቅ የሚችል መሆኑን ከሚያሳይ በስተቀር ይህ ከአምት ዓመት በላይ የሆነው የኪራይ ውል ዘመን እስከሚያበቃ ድረስ ተከራይ አከራይ ባለበት እዳ ምክንያት የአከራዩን ንብረት በሕግ አግባብ በመሸጥ እዳን ለመሰብሰብ በሕጉ ስልጣን የተሰጣቸው አካል ጨረታ በማውጣት ንብረቱን ሲሸጡና በማስታወቂያ መሰረት ቤቱን ንብረቱን የገዛው ሰው ከቀድሞው አከራይ ሳይረከብና ማናቸውንም ጥቅም የመጠየቅ መብት የለውም ማለት እንዳልሆነ ሕጎቹ ያሳያሉ፡፡

በተመሳሳይ የኪራይ ውሉ ምንም እንኳ የተመዘገበ ባይሆንም የተረጋገጠ ቀን መኖሩ ከታወቀ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2933/1/ መሰረት ገዥው የሸያጭ ውሉን ካስመዘገበበት ቀን አንስቶ ተከራዩ እስከ አምስት ዓመት ድረስ መቃወሚያ ሊያደርገው ይችላል መባሉ ንብረቱን በእዳ ምክንያት በሕጉ አግባብ የሚሸጥ አካል እና በዚሁ መሰረት ንብረቱን የገዛው ገዥ በዚህ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በንብረቱ ላይ እንደ ባለመብት ንብረቱን ሳይረከብ ይቆያል ወይም ማናቸውም ጥቅም ሳያገኝ ይቆያል ማለት አይደለም፡፡

ይልቁንም የኪራይ ውል ባልተመዘገበ ጊዜ በግዥ ባለመብት የሆነው ሰው የኪራይ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጥረዋል ተብሎ በፍ/ብሕ/ቁ 2933/1/ መደንገጉ የኪራይ ውል የመመዝገብና ያለመመዝገብ ውጤት ገዥው አስቀድሞ ንብረቱን ከመግዛቱ በፊት የተደረገውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ እና ላለማቋረጥ ያለዉን መብት የሚያመለክት እንጂ ኪራዩን ከቀድሞው ተከራይ የግድ እንዲቀጥል ወይም ንብረቱን የመረከብ መብቶች እስካለመጠየቅ ሊያደርስ የሚችል መብት ሊያሳጡ የሚችሉ ድንጋጌዎች ናቸው ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም ፡፡

ስለሆነም እንደአሁኑ ባለው ጉዳይ ተከራይ በኪራይ የያዘውን ንብረት ለአዲሱ ባለንብረት በግዥ ላገኘው ባለሀብት ለማስረከብ ይገደዳል ወይስ አይገደድም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ንብረቱን ገዥው በመረከቡ የተነሳ ተግባሩ ሁከት ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም ፡፡ የሁከት ተግባር መብት የሌለው ሰው ሌላ ሕጋዊ መብት ባለው ሰው ይዞታ ላይ የኃይል ተግባር መፈፀም ወይም መስናከል ሆኖ ሲገኝ በሕግ አግባብ እንዲወገድ የሚደረግ ወይም የሚጠይቅ እንጂ በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል ከአከራዩ በእዳነት የማፍለገውን እንቅስቃሴ ሁሉ የሚሸፈን አለመሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እና 1149 እንዲሁም ከአዋጅ ቁጥር 97/90 ዓላማ እና ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንቀጽ 6 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ የፍ/ብ/ስ/ሕ/ቁጥር 449 ድንጋጌ መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክርክር ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ባለመሆኑ የምንቀበለው አይደለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላላገኘው የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ። መዝገቡ ተዘግቷል ወደ ። መዝገብ ቤት ይመለስ ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡ - ሐሳስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. አቶ መስፍን ጀምበሩ - ቀረበ

2. የሆሳእና ከተማ አስተዳደር - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንብረት ግምት ይከፈለን ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ከቡታጅራ ሆሣዕና በሚያሰራው መንገድ ምክንያት በሆሣዕና ከተማ የሚገኙ ንብረቶቻቸው እንዲነሱ የግምት ሥራ ተሰርቶላቸው በዚሁ መጀመሪያ ግምት የከተማው አስተዳደር ንብረቶቻቸውን ያስነሳቸው መሆኑን የንብረቶቻቸው ዓይነትና ግምት ምን ያህል እንደሆነ ዘርዝረው አመልካች ካሣ እንዲከፍለን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሠረቱት የተናጥል ክስ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ ለመንገድ ሥራው የዲዛይን ለውጥ ማድረጉንና በተለወጠው ዲዛይን መሠረትም ንብረቶቹ መነሳት የማያስፈልጋቸው በመሆኑ ኃላፊነት እንደሌለበት የተነሱ ወይም እንዲፈርሱ የተደረጉ ንብረቶች በአዋጅ ቁጥር 455 አንቀጽ 3(1) እና 4(1) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን ሥርዓት ባልተከተለ መልኩ የተከናወነ በመሆኑ ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑን እንዲሁም አዋጁን ባልተከተለ መንገድ የራሱን ሥራ ለመስራት ንብረቶችን አስነሳ የተባለው የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ይታዘዝለት ዘንድ በመግለፅ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪዎችን ክርክር በተለያዩ መዛግብት መርምሮ የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ወደ ክርክሩ ይግባልኝ የሚለውን የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎ አመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለፅ ተጠሪዎች በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ወስኖላቸዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይኸው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ መዛግብትን በአንድ ላይ በማጣመር መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቦ ይህ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ (የሆሳእና ከተማ አስተዳደር) ለክርክሩ የግድ ተካፋይ ሊሆን የሚገባው ወገን ሁኖ አያለ መታለፉ ያላግባብ ነው በሚል ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር ይኸው ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ጉዳዩ እንደገና ታይቶ እንዲወሰን ለስር ፍርድ ቤት መልሶለት የሥር ፍርድ ቤትም የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካችን ለጉዳዩ ኃላፊ በማድረግ የሆሳዕና ከተማ አስተዳደርን ግን ከኃላፊነቱ ነፃ አድርጎ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ በድጋሚ የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሕዳር 13 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፉት 5(አምስት) ገፅ የሠበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ጉዳዩ የዳኝነት ሳይከፈልበት መታየቱ ያላግባብ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ያየው ከስልጣኑ ውጪ መሆኑንና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከተላከለት ውጪ ሶስተኛ ወገንን ጨምሮ ውሳኔ መስጠቱ የስነ ሥርዓት ግድፈት ያለበት መሆኑን በመጀመሪያ መንገዱ ሊሰራበት በታሰበው ስፋት መሠረት የተሠራው ግምት እጅግ የተጋነነ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው ለከተማ አስተዳደሩ አመልካች ከገለጸለት በኋላ አስተዳደሩም ይህንን አውቆ የዲዛይን ክለሳ እና በዚህም መሠረት የግምት ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀድሞው ዲዛይን መሠረት ተነስቷል የሚባል ንብረት ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ባልዋለበትና በህጉ አግባብ ላልተነሳ ንብረት ካሣ ለመክፈል ህጋዊ ግዴታ የሌለበት መሆኑን በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሙሉ በሙሉ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው የጽሁፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሠበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ለተጠሪዎች ካሳ ይክፈል የተባለበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩን እንደሚከተለው አይቶታል፡፡

ክርክሩ ሲጀመር በተራ ቁጥር አንድ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በተናጠል ክሳቸውን አቅርበው ጉዳያቸው የታየ ሲሆን በይግባኝ ደረጃ የተጣመሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ያየውም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ስልጣን በመወከል መሆኑንና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለበት ወገን ሁሉ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይገባ የነበረ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 322/95 እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ በመ/ቁጥር 54577 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጉዳይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመልሶ እንዲታይ ውሳኔ ሲሰጥ ይግባኙ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መታየቱ ላይ ያስቀመጠው ትችት ባለመኖሩና ክርክሩ ከወሰደው ጊዜ እንዲሁም ከሥነ ስርዓት አላማ ስንነሳ በይግባኝ አቀራረብ ሥርዓቱ ላይ የተፈጸመውን ስህተት አልፈነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በመጀመሪያ መንገዱ ሊሰራበት በታሰበው ስፋት መሰረት የተሰራው የንብረቶች ግምት ባልተለመደ ሁኔታ እጅግ የተጋነነ በመሆኑ እንደማይቀበለው ለከተማ አስተዳደሩ ገልጾና አሳውቆ የዲዛይን ክለሳና የግምት ሥራ ተጠናቅቆ ከአለቀ በኋላ ንብረቶቹ እንዲነሱ ወይም እንዲፈርሱ ለተደረገው ሁኔታ አመልካች ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሌለበትና ይህንን ድርጊት የከተማው አስተዳደር ለራሱ ሥራ ሲል ስለአከናወነው ኃላፊነት ሊወስድ ስለሚገባ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ሊታዘዝ ይገባል በማለት የሥነ ሥርዓት ጥያቄ አንስቶ ይህ ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 43424 የከተማው አስተዳደር ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ለጉዳዩ ኃላፊነት ያለበት ወገን እንዲለይ ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡ በዚህም መሰረት የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ሰምቶ አመልካች የዲዛይን ክለሳ ከማድረጉ በፊት የ1ኛ ተጠሪዎች ንብረቶች ተገምተው በአስቸኳይ እንዲፈርሱ መደረጉን፣ ይህንኑ ስራ ሲመሩ የነበሩት የአመልካች መስሪያ ቤት ሰራተኛም የ1ኛ ተጠሪዎች ንብረቶች እንዲፈርሱ ያደረጉ መሆኑን እንዲሁም የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር የመንገዱ ዲዛይን ክለሳ ስለመኖሩ ያወቀው የ1ኛ ተጠሪዎች ንብረቶች እንዲፈርሱ ከተደረገ በኋላ ስለመሆኑና ከ1ኛ ተጠሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ንብረታቸው የፈረሰባቸው ሰዎች ካሳ በአመልካች መከፈሉ በአመልካች መከላከያ ምስክሮች ጭምር መረጋገጡን ምክንያት በማድረግ አመልካችን ለጉዳዩ ኃላፊ አድርጓል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም ኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆን/መሆኗ የተከበረለት/ላት መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 40(1) ስር በግልፅ ደንግጎ የምናገኘው ጉዳይ ነው፡፡ የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40(7) ድንጋጌም ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬቱ ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለው ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬቱ ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን እንደሚያካትት የተደነገገ ሲሆን የዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ ስምንት ደግሞ የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሁኖ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል በሚል ተቀምጧል፡፡ ይህንኑ ተከትሎ የወጣው አዋጅ ቁጥር 455/97 ደግሞ ለህዝብ ጥቅም ትርጉም አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት የህዝብ ጥቅም ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሕዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የከተማ ልማትን በቀጣይነት ለማጎልበት አግባብ ያለው አካል በመሪ ፕላን ወይም በልማት እቅድ የሕዝብ ጥቅም ብሎ የሚወስነው ነው በሚል በአንቀፅ 2(5) ስር ይዞ እናገኛለን፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪዎች ይዞታቸው አመልካች ለሚያሰራው መንገድ የተወሰደባቸው መሆኑና ንብረቱ የፈረሰውም የመንገዱ ዲዛይን ክለሳ ከመደረጉ በፊት በአመልካች ባለሙያ ግፊት መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ይህ ተቀባይነት በሌለው ሁኔታ የተረጋገጠ ስለሆነ ሕጋዊ አይደለም በማለት የሚያቀርበው ክርክር በግልፅ የማስረጃ ጉዳይ መሆኑን የምንገነዘበው ሲሆን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የበታች ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር በማስረጃ የተደገፈ አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3/ሀ) እና 25/1988 አንቀፅ 10 የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈፀም ማረም በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ አሳማኝ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጉዳይ የሚመለከተው ሁኖ አላገኘውም፡፡ እንዲህ ከሆነ የ1ኛ ተጠሪዎች ይዞታ ቦታ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ሲወሰድና በቦታው ላይ የነበሩት ንብረቶች በአመልካች ባለሙያ ጭምር ግፊት ተደርጎ እንዲነሱና እንዲፈርሱ ከተደረገ በኋላ የዲዛይን ክለሳ ሲደረግ ንብረቶቹ የማይነሱ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ብቻ በመመስረት አመልካች የካሳ ገንዘቡን ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀፅ 3(1 እና 2) እንዲሁም ከአንቀፅ 4(1) ድንጋጌዎች ከላይ ከተጠቀሱት የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር ተደምረው ሲታዩ የአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 03332 ግንቦት 05 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ት ታሪክ ጌታቸው

ተጠሪዎች፡- 1ኛ ወ/ሮ አልጋነሽ ተጠምቀ

2ኛ ወ/ሮ ልዕልቲ በላይ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ለቀረበው ክርክር መነሻ ሆኖ የተገኘው የሚች አቶ ጌታቸው በላይ ንብረት የሆነ በመቀሌ ከተማ የሚኝ 325 ካሬ ሜትር የቦታ ይዞታ ያለውን ቤት የሚች ልጅና ህጋዊ ወራሽ የሆነችው የአሁኗ አመልካች እያለች አቶ በላይ በየነ የተባሉት ሰው እና የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ወ/ሮ አልጋሽ ተጠምቀ የሚቹ ወራሾች እኛ ነን ብለው ፍ/ቤት በመቅረብ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀው የወራሽነት ማስረጃ በመውሰድ የሚችን ቤት ስም ባለሃብትነት በሥማቸው ካዛወሩ በኃላ ልጃቸው ለሆነችው ለአሁኗ 2ኛ ተጠሪ ወ/ሮ ልዕልቲ በላይ ብር 50,000 በመሸጥ አስተላልፈው በሥሟ እንዲመዘገብ አድርገው መገኘታቸው ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበችው ክስ የሚቹ የአቶ ጌታቸው በላይ ልጅና ህጋዊ ወራሽ መሆኗን 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች በማይመለከታቸውና ያለአግባብ የሚችን ቤትና ቦታ ተሻሽጠውና አዛውረው እንደሚገኙ በመዘርዘር እንዲያስረክቧት ጠይቃለች፡፡ አቶ ጌታቸው በላይ በ1986 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ስለመሆናቸውና ሚች ባደረጉት ኑዛዜ ስለልጅቱ አስተዳዳሪ ለወላጆቻቸው በሰጡት መሠረት የአሁኗ አመልካች የስድስት አመት ዕድሜ ሲሞላት 2ኛዋ ተከሣሽ ወደ ደሴ ከተማ መጥታ ልጅቷን ወደ መቀሌ ከተማ በመውሰድ ከእነርሱ ጋር ስትኖር ቆይታ ዕድሜዋ ለአካለመጠን ሲደርስ ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ፍ/ቤት ቀርባ የሚቹ ህጋዊ ወራሽ ስለመሆኗ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንደተሰጣት በክሱ ላይ ተገልጿል፡፡ አመልካች በክሷ ቤት ብቻ ሳይሆን ሌሎች የጠየቀቻቸው ነገሮች ነበሩ፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች የነበሩት የይርጋ የመቃወሚያና ሌሎች የፍሬ ነገር ክርክሮች ያቀረቡ ሲሆን ቤቱን ገዝታለች የተባለችው 3ኛዋ ተከሣሽ የነበረችው የአሁኗ 2ኛ ተጠሪ በበኩሏ 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች ቤቱን በይዞታቸው ሥር ለ10 አመት አቆይተው በብር 50,000 ሸጠውልኝ ንብረቱ በሚመለከተው የሕግ ክፍል በፍትሐብሄር ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1723 መሠረት ተመዝግቦ በቅንነት የገዛሁትን መልሺ ተብዬ ልገደድ አይገባም በማለት ተከራክራለች፡፡ የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን፣ የግራ ቀኙን ክርክሮች እና ማስረጃዎችን መርምሮ ክሱ በ10 አመት ይርጋ ይታገዳል በሚል ለተነሣው ክርክር ከሣሽዋ የአካለመጠን ዕድሜ በመድረስ የመክሰስ ችሎታ እንዳገኘች በ30/10/2000 ዓ.ም ክሱን ያቀረበች ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብሎ ውድቅ ካደረገው በኋላ የክሱን ዋና ፍሬ ነገር በተመለከተም ቤቱ የሚቹ የአቶ ጌታቸው በላይ ንብረት መሆኑ በቀረበው የጽሑፍ ማስረጃ ተረጋግጧል 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች ከሣሽዋን በሞግዚትነት እያሳደጓት ባለበትና የመውረስ መብት ባልነበራት ወቅት ወራሾች ሣይሆኑ ተሯሩጠው የሚች ወራሽ ስለመሆናቸው በማስወሰን ቤቱን ለልጃቸው ለ3ኛዋ ተከሣሽ ሸጠው መገኘታቸው በሕግ የሚደገፍ አሻሻጥ አይደለም፣ የራሣቸው ያልሆነውን ንብረት መሸጥ በሕጉ አይፈቀድም፣ ሽያጩ በሕጉ ውጤት የለውም ፈራሽ ነው፤ ያገኙት ወራሽነትና ያደረጉት ሽያጭ ቅንነት የጎደለው የማይገባ ብልጽግና ለማግኘት የተፈፀሙ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣ 3ኛዋ ተከሣሽም ንብረቱን የገዛችው ቅንነት ከሌላቸውና በቤቱ ላይ መብት ከሌላቸው ወራሾች ነው፣ ራሷም ብትሆን ቤቱን በቅንነት የገዛች ባለመሆኑ ሽያጩ ተቀባይነት የለውም በማለት በክሱ ላይ አዋሳኞቹ የተጠቀሰውን በውስጡ 8 ክፍል መኖሪያ፣ ሽንት ቤትና ማዕድ ቤት የያዘ የቦታ ስፋቱ 325 ካሬ ሜትር የሆነውን ቤት 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች ለከሣሽዋ ለአሁኗ አመልካች ሊያስረክቧት ይገባል ብሎ ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በዚህ የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ያቀረቡ ቢሆንም መርምሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚተችበትና የሚጣራ ነገር የለውም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት የሚያስቀርብ አይደለም ብሎ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

እንደገና የአሁኑ ተጠሪዎች በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት አይቶት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ቀርበው ክርክሩ ከተሰማ በኃላ ሰበር ሰሚው ችሎት በበኩሉ መርምሮ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ከባለቤቷ ጋር ሆና ሚቹ ልጃችን ወራሽ የለውም፣ ወራሾቹ እኛ ነን ብለው ቤቱን ወደ ሥማቸው በማዛወር ለአሁኗ 2ኛ ተጠሪ በብር 50,000 ሸጠው ስለተገኙ በህጋዊ መንገድ የገዙትን ቤት ሊያስረክቡ አይገባም፣ ቤቱን በመሸጥ ጥቅም ያገኘችው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ብር 50,000 ክሱ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ ተከፍሎ እስኪያልቅድረስ 9% ወለድ ጨምራ ለአሁኗ አመልካች ትክፈል የሚል ውሣኔ በመስጠት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ሽሮታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) መሠረት የቀረበ ሲሆን ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ ተብሎ በመወሰኑ ማመልከቻው ለአሁኑ ተጠሪዎች ተልኮ ቀርበው ክርክሩ እንዲሰማ ተደርጓል፡፡ በሁለቱም በኩል ቀርበው የተከራከሩት በየባለጉዳዮቹ የተወከሉት ጠበቆች ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት የአመልካች ጠበቃ ቤቱ ለ2ኛዋ ተጠሪ ተሸጧል የተባለበት ውል በተንኮል የተደረገ ስለሆነ ሊፀና አይገባም፣ ሻጮችም በቤቱ ላይ ህጋዊ መብት የላቸውም፣ በትክክል በሚታይበት ጊዜ ሁለተኛዋ ተጠሪ ቤቱን ሆነ ብላ ነው የገዛችው፣ ገንዘቧን ማግኘት አለባት ከተባለም ማግኘት ያለባት ከሸጡላት ወላጆቿ ነው፡፡ ውሉ ፈርሶ ቤቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለአመልካች መስጠት አለባቸው፣ ይህ እንኳን ቢታለፍ በክሱ ላይ የቤቱ ግምት ብር 120,000 ተብሎ ስለቀረበ እነርሱ የተሻሻጡበት ብር 50,000 ይከፈላት የተባለው ያለአግባብ ነው ብለው በመዘርዘር ተከራክረዋል። የተጠሪዎች ጠበቃ በበኩላቸው 1ኛዋ ተጠሪ 10 አመት በሙሉ በቤቱ ሲገብሩበት ቆይተው ይዞታቸውን መሸጣቸው ህጋዊ ነው፣ ገዢዋም ብትሆን ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በሥማቸው ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት መግዛቷ ህገ ወጥ አያሰኝም። በቦታው ላይ 5 ክፍል ቤት ሠርታበታለች፣ ይዞታው ሁሉ ተለውጧል፣ ሽያጩ በአግባቡ ስለሆነ ሊፈርስ አይገባም፣ ብር 120,000 ነው የቤቱ ግምት ያሉት በክሱ እንዲከፈላቸው የጠየቁት ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ በመሆኑ ሊፀና ይገባል የሚሉትን ክርክሮች አቅርበዋል። የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሮቹ ይዘት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ሲሆን ጉዳዩም ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ እንደሚከተለው ተመርምሯል።

ለክርክሩ መነሻ ሆኖ የተገኘው ቤት የአሁኗ አመልካች አባትና አውራሽ የሆኑት የሟቹ የአቶ ጌታቸው በላይ ንብረት መሆኑና 1ኛዋ ተጠሪ የአሁኗን አመልካችን አባቷ እንደሞቱ ገና የ6 አመት ህፃን ልጅ እያለች ወስዳት አብራቸው እየኖረች ባለበት ወቅት የሟች ልጅ መሆኗን እያወቀች 1ኛ ተከሣሽ ከነበረው ከአቶ በላይ በየነ ጋር በመሆን የሟች ወራሾች እኛነን ብለው ለፍ/ቤት በማመልከት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው አድርገው የሟቹን ቤት የባለሃብትነት ሥም በራሣቸው ሥም በማዛወር ልጃቸው ለሆነችው ለአሁኗ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን በመሸጥ በሥሟ እንዲዛወር ማድረጋቸው፣ በሥር ፍ/ቤት በተደረጉ ክርክሮችና በቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው።

ከወላጆቿ ቤቱን ገዝታለች የምትባለው የአሁኗ 2ኛ ተጠሪም የአሁኗ አመልካች የሟች የአቶ ጌታቸው በላይ ልጅ ስለመሆኗና ቤቱም ቀደም ሲል የሟቹ ንብረት መሆኑን አላውቅም አትልም።

የአሁኗ አመልካች አብራቸው እየኖረችና እንደ ሞግዚትም ሆነው እያሳደጓት እያሉ አካለመጠን ያልደረሰችውን ልጅ የአባቷን የውርስ ሀብት ጠብቀው በሥርዐት እንዲተላለፍላት ማድረግ ሲገባቸው ሆነ ብለው አካለመጠን ባልደረሰችው ልጅ ላይ ጉዳት ለማድረስና መብቷን ለማሳጣት፣ ለራሣቸው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት የፈፀሙት ድርጊት መሆኑን ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች መረዳት ይቻላል።

በእንዲህ አይነት መንገድ አካለመጠን ላልደረሰችው ልጅ በሕጉ አግባብ በውርስ ሊተላለፍለት የሚገባውን ንብረት አሳዳጊዎቿ የነበሩት ሰዎች የሟቹ ወራሾች እኛ ነን ብለው የወራሽነት ማስረጃ በመውሰድ ቤቱን ለገዛ ልጃቸው ሸጥዋል ተብሎ መገኘቱ በሕጉ የሚኖረው ውጤት ምንድ ነው? ቤቱ ለህጋዊ ወራሿ እንዲለቀቅ የማይደረግበት የሕግ ምክንያት አለ ወይንስ የለም የሚለውን በተመለከተም የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2884(1) ላይ የተመለከተው ድንጋጌ የተሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል የሻጩ ሀብት ሣይሆን የቀረ እንደሆነ የመነቀልን የአላፊነት ዋስትናን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ያስረዳል። እነዚህ የመነቀልን የአላፊነት ዋስትና የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ደግሞ የአንድን ነገር ባለሃብትነት ማስተላለፍን ስለሚመለከቱት ውሎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መካከል ከፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2282 - 2285 የሚገኙ ናቸው። ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የተሸጠው ነገር ሌላ ሰው በነበረው መብት ምክንያት ይለቀቅልኝ በሚል ለሚቀርበው ጥያቄ ለገዢው መድን የሚሆነው ሻጩ ነው። የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2284(2) የተሸጠው ነገር ለይለቀቅልኝ ባዩ በሚለቀቅበት ጊዜ በውላቸው ላይ ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ ሻጩ በሸያጩ የተቀበለውን ዋጋ ለገዢው የመመለስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የሚደነግግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው። ድንጋጌዎቹ ለማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭም የሚያገለግሉ ናቸው። ከላይ የተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2884 ድንጋጌ እና በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2884(2) እንዲሁም በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2285 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተያይዘው በአንድነት ሲታዩ የተሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል የሻጩ ሀብት ሣይሆን የሌላ ሰው ሀብት ሆኖ ከተገኘ ገዢው እንደሚነቀል ወይም እንዲለቅ የሚደረግ ስለመሆኑ የሚጠቅሱ ናቸው። ገዢው በሕጉ ያለው መፍትሄ ሻጩን መጠየቅ ነው።

በሌላም በኩል አንድ ሰው አንድን ንብረት በሽያጭ ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ የሚችለው በንብረቱ ላይ ትክክለኛ ህጋዊ ባለመብት ሲሆን ወይም በሕጉ አግባብ የንብረቱ ህጋዊ ባለመብት የሆነው ሰው የመሸጥና የመለወጥ ሥልጣን ሰጥቶት ሲገኝ ነው። የሌላውን ሰው ንብረት ንብረቱ ነው ብሎ መሸጥ ከሕጉ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ህገ ወጥ ነው። ሕገወጥ ውል ደግሞ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1716 መሠረት ፈራሽ ነው። ገዢው ከንብረቱ የሚነቀለው ወይም ለህጋዊ ባለመብቱ እንዲለቅ የሚደረገውም በዚህ ምክንያት ነው።

በቀረበው ጉዳይም የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ እና ክሱ ሲቀርብ 1ኛ ተከሣሽ የነበሩት አቶ በላይ በየነ የአሁኗ አመልካች የሚቹ የአቶ ጌታቸው በላይ ልጅ መሆኗን እየወቁና ወስደዋት በማሣደግ ከእነርሱ ጋር አብራቸው እየኖረች እያለ እኛ ነን የሚች ወራሾች ብለው ማስረጃ በመውሰድ በውርስ ለአመልካች ሊተላለፍ የሚገባውን ቤት በሥማቸው በማዛወር ከልጃቸው ከ2ኛዋ ተጠሪ ጋር አድርገናል የሚሉት የመሻሻጥ ውል ከዚህ የተለየ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም። በወቅቱ አካለመጠን ካልደረሰችው የሚች ልጅ ንብረቱን ለማሸሽ ወላጆችና ልጅ ያደረጉት የሚችን ቤት መሻሻጥ ውል ህጋዊ ሊሆን አይችልም።

የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁኗ አንዳኛ ተጠሪ እና አቶ በላይ በየነ ወራሾች ነን ብለው የቤቱን ሥመ ባለሃብትነት በሥማቸው በማዛወር ለልጃው ለአሁኗ 2ኛ ተጠሪ በብር 50,000 ከሸጡላት ቤቱን ለአሁኗ አመልካች ማስረከብ የለባትም፣ ቤቱን ሸጣ ጥቅም ያገኘችው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ስለሆነች ገንዘቡን ትመልስላት ያለውም ሥመ ባለሃብትነቱን በሥማቸው ማዘወራቸው ውሉን ህጋዊ ሊያደርገው ስለማይችል ተቀባይነት የለውም።

2ኛዋ ተጠሪ ለቤቱ ዋጋ ብር 50,000 ለሻጮች ከፍላ ከሆነ በሕጉ መሠረት እንዲመልሱላት መጠየቅ ይኖርባታል።

በሕጉ 2ኛዋ ተጠሪ ቤቱን ለህጋዊ ባለመብቷ ለመልቀቅ ትገደዳለች።

ሲጠቃለል ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁኗ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን በህጋዊ መንገድ የገዛችው ስለሆነ ለአሁኗ አመልካች ልታስረክብ አይገባም፣ ቤቱ ተሸጧል የተባለበትን ዋጋ ብር 50,000 የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ትክፈል በሚል የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህ ጉዳይ የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ አግባብነት ያለው በመሆኑ የሚሻርበት የሕግ ምክንያት የለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 31069 በ18/02/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(2) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 30843 በ05/09/2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 6429 በ26/08/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 56011

መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሳሙኤል ታደሰ አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- ወ/ት እጥፍ ወርቅ ኃይለማርያም አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የአፈፃፀም ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር የቀረበ ነው፡፡ ክርክሩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት አመልካች የፍርድ ባለዕዳ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ የአመልካች ንብረት የሆነ የኮንደሚኒየም ቤት ያለ በመሆኑ ቤቱ ተሸጦ በፍርድ የተረጋገጠለትን ገንዘብ ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ እንዲከፈል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 በሠራተኛ ሠፈር ሣይት የህንፃ ቁጥር 01 የቤት ቁጥር 52-Bs-2506 የወለል ቁጥር 002 የቤቱ ስፋት 43.37 ካሬ ሜትር የሆነውን ኮንደሚኒየም ቤት በሐራጅ በመሸጥ ለፍርድ ቤት ባለመብት ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺ ብር/ በታህሣሥ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከ አለቀ ድረስ ከሚታሰብ ከአሥራ ሁለት በመቶ ወለድ ጋር እንዲከፈል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙ ፍሬ ነጥብ የሌለው መሆኑን በመግለፅ ሰርዞታል፡፡

አመልካች ግንቦት 9 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት በፍርድ የተወሰነብኝን ገንዘብ ለመክፈል የአንድ ወር ጊዜ እንዲሰጠኝ ያቀረብኩትን ጥያቄ አለመቀበሉ የፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 186/2/ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኮንደሚኒየም ቤቱ አምስት ዓመት ሣይሞላው ለዕዳ መክፈያነት እንዲሸጥ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ የአዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 14/2/ እና አንቀፅ 21 እንደዚሁም የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 404/ሰ/ የተደነገገውን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ዕዳውን ያለመክፈል የተለያየ ሰበብ እየፈጠሩ አጉላልተውኛል፡፡ አዋጅ ቁጥር 19/97 የቤቱ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚሰጠው ዕዳው ተከፍሎ ሲያልቅ መሆኑን ከሚደነግግ በስተቀር ገንዘብ የተበደረና የኮንደሚኒየም ቤት ያለው ሰው ዕዳው ቤቱ ተሸጦ እንዳይከፈል አይከለክልም፡፡ ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተገቢ ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ያሰናብተኝ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ታህሣሥ 22 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የፍርድ ባለዕዳ መሆናቸው በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በሰበር የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ ባለዕዳ መሆኑ በፍርድ የተረጋገጠበት ሰው በፍርድ የተወሰነበትን ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ የማይከፍልበት በአፈፃፀም ወቅት ሊያነሣው የሚችለው መከራከሪያ ያለው ስለመሆኑ አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲያስረዳ ፍርድ ቤቱ እድል የሚሰጠው መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 378/1/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በፍርዱ መሠረት ፈፅሞ ከሆነ ፍርዱን የፈፀመ መሆኑን በፍርዱ መሠረት ያልፈፀመ ከሆነ ያልፈፀመበትን ምክንያት ሲጠየቅ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለመፈፀም ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን የአመልካችን ተጨማሪ ጊዜ ይሰጠኝ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የፍርድ አፈፃፀሙ በአመልካች ንብረት ላይ የሰጠው ትዕዛዝ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠኝ ይገባ ነበር በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ አመልካች ለፍርድ አፈፃፀምና ለአመልካቿ እዳ መክፈያ ይሆን ዘንድ የኮንደሚኒየም ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ የአዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 2 እና አንቀፅ 21 የሚጥሱና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ስንመረምረው ከላይ የተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ጠቅላላ ዋጋውን ከፍሎ ያጠናቀቀ የኮንደሚኒየም ቤት ባለሃብት የሆነው ሰው ክፍያ ያጠናቀቀበትን የኮንደሚኒየም ቤት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሸጦ ለፍርድ ማስፈፀሚያ እንዳይሆን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች ሆነው አላገኘናቸውም፡፡ የአዋጅ ቁጥር 19/94 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ የመጀመሪያው ፖራግራፍ ቃል በቃል ሲነበብ “ገዢው ጠቅላላ ዋጋውን ከፍሎ ቢያጠናቅቅም ቤቱን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ የሚቻለው ቤቱን ከገዛ በኋላ አምስት ዓመት ሲሞላው ብቻ ይሆናል” በማለት የሚደነግግ ሲሆን የአዋጁ አንቀፅ 21 ከአዋጁ ጋር የሚቃረን የተለመደ አሠራር ወይም ህግ በዚህ አዋጅ በተሸፈነ ጉዳዮች ተፈፃሚነት የለውም በማለት የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡

የአዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 14/2/ የኮንደሚኒየም ቤት ዋጋ ከፍሎ ያጠናቀቀ ባለሃብት ቤቱን የመሸጥ የመለወጥና ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ መብቱን በተሟላ ሁኔታ ተግባር ላይ የሚያውለው ከአምስት ዓመት በኋላ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ድንጋጌው የኮንደሚኒየም ቤት ባለሃብት የሆነው ሰው በራሱ ፈቃድና ፍላጎት ቤቱን በሽያጭ ወይም በስጦታ ስለሚያስተላለፍበት ሁኔታ የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የቤቱን ዋጋ አጠቃሎ የከፈለ የኮንደሚኒየም ቤት ባለሃብት እንዲከፍል በፍርድ የተወሰነበት የሌላ ሰው ዕዳ ያለበት በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ዕዳው ተጠቃልሎ የተከፈለውን የኮንደሚኒየም ቤት በሀራጅ ተሸጦ ለፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን ትዕዛዝ ከመስጠት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚከለክል ወይም ሥልጣናቸውን የሚገድብ የህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ አመልካች የጠቀሱት የአዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 21 ዋጋው ተጠናቅቆ የተከፈለውን የፍርድ ባለዕዳ የኮንደሚኒየም ቤት ፍርድ ቤቶች በሀራጅ ተሸጦ ለፍርድ ማስፈፀሚያ ከማድረግ የሚገደብ ይዘት ያለው ድንጋጌ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የፍርድ ማስፈፀሚያ ይሆን ዘንድ በሀራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሰጡበት የኮንደሚኒየም ቤት በህግ ለሌላ ሰው እንዳይሸጥ ክልከላ የተደረገበት ነው በማለት የአዋጅ ቁጥር 19/77 አንቀፅ 14/2/ እና አንቀፅ 21 ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 404/ሰ/ ጋር በማጣመር ያቀረቡት ክርክር የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ግብ ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍርድ ቤት በማፅናት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 8 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49428

ኅዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ከበቡሽ ልሳነርቅ } የቀረበ የለም

2. ወ/ሮ መና ገብረ አጋይስት }

ተጠሪ፡- 1. አቶ ፀዳሉ አዳነ የቀረበ የለም

2. የጐንደር ከተማ አገ/ጽ/ቤት- ከክርክር ውጪ ሆኗል፡፡

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የቤት ሽያጭ ውልን አፈፃፀም የተመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ ነው፡፡ የዳኝነት ጥያቄውም ጥር 9 ቀን 1989 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ከ1ኛ አመልካች የገዛውን ቤት ስመ ሐብት እንዲያዛውርለት እና ካርታ በስሙ እንዲሰራለት ማዘጋጃ ቤቱ ተጠይቆ ፈቃደኛ ስላልሆነ በፍርድ ሃይል ተገዶ ይፈጽምልኝ የሚል ነበር፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ ያከራከረው የከተማ ነክ ፍ/ቤት ማዘጋጃ ቤቱ አስተዳደራዊ ተግባሩን እንዲያከናውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የአመልካቾችን መቃወሚያ ባለመቀበል ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360/2/ መሰረት አጽንቷል፡፡

አመልካቾች በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለከተማው ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ አልተቀበለም፡፡

የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቀርቦለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕግ ስሕተት የለውም በማለት አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ የጐንደር ከተማ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የዳኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውንና ተጠሪ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተደረገ የሽያጭ ውል በማቅረብ ስም ይዛወርልኝ፤ ካርታ ይሰራልኝ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለው ወይንስ የለውም? የሚለውን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ ጥር 27 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ በይዘቱ ሲታይ የ1ኛ ተጠሪ ክስ በይርጋ ያልታገደ ስለመሆኑ፣የተጠየቀው ዳኝነትም በሕግ የተመሰረተ ውል መሰረት ያደረገ ስለመሆኑና የጐንደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን አለው በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና በግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር የተያዘውን ጭብጥ መሰረት አድርገን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የመጀመሪያው ጭብጥ የጐንደር ከተማ ፍ/ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣንን በተመለከተ ነው፡፡ በመሰረቱ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በሕግ የሚወሰን መሆኑ እሙን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው በግዥ ውል የተላለፈለትን መብት መሰረት በማድረግ የከተማው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥን የሚመለከት ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡

በአማራ ብ/ክ/መ/በወጣው አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ደንብ ቁጥር 12/2000 በተደነገገው መሰረት ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ክርክር የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን እንዳላቸው ተመልክቷል በማለት ጉዳዩን የተመለከቱት የሥር ፍ/ቤቶች የወሰኑት ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን እንደተሰጣቸው በሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት በመሆኑ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሥልጣን መሰረት የለውም የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ ውልን በመያዝ ክስ የማቅረብ መብት አለውን? የሚለውን በተመለከተ ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው 1ኛ ተጠሪ በግዥና ሽያጭ ውል ያገኘውን መብት መሰረት በማድረግ 2ኛ ተጠሪ ስም የማዛወር ግዴታ እና ካርታ የመስጠት ተግባር አልተወጡም በሚል መነሻ ክስ አቅርቧል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 33945 በሰጠው ውሳኔ እንደተመለከተው ገዥ በሽያጭ ውሉ መሰረት ስም ይዛወርልኝ ጥያቄን መሰረት በማድረግ ሻጭ ላይ የሚያቀርበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም፡፡ ይልቁንም ይህ ተግባር የአስተዳደር አካል ተግባር ነው በሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪን የከሰሰው የአስተዳዳር ተግባር አልተወጣልኝም በሚል ነው፡፡ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የሰበር መዝገብ ውሳኔ መረዳት የሚቻለውም አስተዳደሩ በሕግ የተሰጠውን ተግባር ካልተወጣ ገዥ መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ የሚገበው በአስተዳደር አካሉ ላይ ስለመሆኑ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የሚቻል ሆኖ አላገኘውም፡፡ በመሆኑም የ1ኛ ተጠሪን የዳኝነት ጥያቄ መሰረት በማድረግ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በሕግ አተገባበር ወይም አፈፃፀም ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ለዚህም ወሳኔው ባለበት ሁኔታ ሊፀና ይገባል ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በጐንደር ከተማ ነክ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00449 በ01/07/2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ፣የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00226 የሰጠው ትእዛዝ እና የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 01571 በ29/10/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ይህ ውሳኔ 2ኛ ተጠሪ የሚያቀርቡትን የሽያጭ ውል መነሻ ያደረገ የመብት ጥያቄ የሚገድብ አይደለም፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ የካቲት 3 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 57045

ጥር 25 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች ፦ ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፦ የልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ፅ/ቤት -

ምርመራና ክስ ኤክስፐርት አቶ ሰይፉ ይፍሩ ቀረቡ

ተጠሪ፦ አቶ ተስፋዬ አሰፋ - ጠበቃ አዜብ ገ/ወልድ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 406 በሆነው ቤት ውስጥ ከወላጅ እናታቸው ወ/ሮ አበበች ፍሰሃ ጋር ሲኖሩ እናታቸው በ28/05/1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ከሌሎች ተወላጆች ጋር ወራሽነታቸውን አረጋግጠው የቤቱን ኪራይ በራሳቸው ስም እንዲዞር በማድረግ በቤቱ በመገልገል ላይ እያሉ አመልካች ያላግባብ ከቤቱ እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ የሰጣቸውና ይህም ተግባር ሁከት መሆኑን ገልፀው ሁከቱ እንዲወገድ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ለተጠሪ ሳይሆን ለወ/ሮ ቀለሟ ታየ በመሆኑ ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት በአማራጭ ደግሞ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 406 የሆነውን ቤት ለቀው እንዲያስረክቡ ማስጠንቀቂያ የተሠጠው የሟች አበበች ፍሰሀ ልጅ ለሆኑት እና በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 967 የሆነ የቀበሌ ቤት በስማቸው ላለው ለወ/ሮ ቀለሟ ታዬ ሲሆን አንድ ግለሰብ ሁለት የመንግስት ቤት ሊይዝ ስለማይችል ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን ተገቢ ነው፣ ተጠሪ ወራሽነት ያገኙትም ያላግባብ ነው፣ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ አበበች ፍሰሀ ልጅ ሳይሆኑ የሟች እህት ልጅ ሁነው የሚኖሩትም በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 የቤት ቁጥር 779 በሆነው ቤት ውስጥ ከእናታቸው ከወ/ሮ ይመኙሻል ፍሰሀ እና ከአባታቸው ከአቶ አሰፋ አባተ ጋር ነው በማለት ክሱ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በአመልካች በኩል የቀረቡትን የክርክር ነጥቦች ውድቅ አድርጎ በአመልካች የተሠጠው ማስጠንቀቂያ ይዘቱ ተጠሪ በቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ እንዳይኖሩ የሚያደርግ በመሆኑ ተግባሩ ሁከት ነው በማለት ሁከቱ እንዲወገድ፣ የተለያዩ ወጪዎች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል። በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል። የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት ወስኗል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ነው።

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሰኔ 08 ቀን 2002 ዓ.ም የጻፉት የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በአከራካሪው ቤት በወራሽነት የኪራይ መብት አግኝቼአለሁ የሚሉት በተጭበረበረ መንገድ መሆኑ ተገልፆ ቀበሌ የሚያስተዳድረውን ቤት እንዲለቁ ማስጠንቀቂያ መፃፉ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ ሊወሰድ የማይገባው በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች ተግባር ሁከት ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሕጋዊ መሆኑን በመዘርዘር ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል ግንኙነቱ ተጠሪ የሚባለው በአመልካችና ተጠሪ እናቱ ናቸው የሚሏቸው ወ/ሮ አበበች ፍሰሃ ባደረጉት የቤት ኪራይ ውል መሆኑን፣ ተጠሪ ሚቿ ያላቸው የተከራይነት መብት በፍርድ ቤት ተረጋግጦ በተሰጣቸው የወራሽነት ማስረጃ ተላልፎልኛል በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም አመልካች ይኸው የወራሽነት ማስረጃ የተገኘው በተጭበረበረ መንገድ ነው በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው። በመሆኑም የክርክሩ ይዘት የሚያሳየው ክርክሩ መሰረት ያደረገው የኪራይ ውሉን መሆኑን ነው። አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ ሊጽፍ የቻለውም ቤቱ ያላግባብ ተይዟል በሚል ነው።

በመሰረቱ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊቀርብ የሚችለው ይዞታውን በእውን በሚያዘው ሰው አጠቃቀም ላይ ችግር ወይም መሰናክል ሲፈጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያል። ባለይዞታው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ ይዞታውን በግልፅ ሁኔታ የያዘው መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ጉዳይ ነው። በባለይዞታውና ሁከቱን ፈጠረ በተባለ ሰው መካከልም የተፈጠረው ግንኙነት ካለ ግንኙነቱ የሚገዛበት የሕግ አግባብ ተለይቶ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የአከራካሪው ቤት ባለቤት መሆኑ የሚያከራክር ሳይሆን ተጠሪ ወራሽ ነኝ ካሉ ከተጠሪ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ደግሞ የአከራይና የተከራይ ነው። ይህ ግንኙነት በመጀመሪያ የተፈጠረው በቀጥታ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሳይሆን በአመልካችና ተጠሪ አውራሼ ናቸው በሚሉት በሟች ወ/ሮ አበበች ፍሰሃ መካከል ነው። አመልካች ደብዳቤውን ሊፅፍ የቻለው ተጠሪ ቤቱን በሕጉ አግባብ የተከራዩት አይደለም በማለት መሆኑን ከክርክሩ ሂደት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። እንዲህ ከሆነ ተጠሪ ሰፊ የሆነ የባለቤትነት መብት ካለው አመልካች ጋር ሊከራከሩ የሚችሉት በሕጉ አግባብ የተደረገ የኪራይ ውል መኖሩን በማሳየት በውሉ መሰረት መብታቸው እንዲጠበቅላቸው እንጂ የሁከት ይወገድልኝን ክስ በማቅረብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሆን አይችልም፡፡ ተጠሪ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ የወራሽነት ማስረጃ መያዛቸውም አመልካች ማስረጃውን በቅድሚያ እንደያሰርዝ የሚያስገድደው ካለመሆኑም በላይ ማስረጃው ዋጋ የለውም የሚለውን ተቃውሞ በማናቸውም የክርክር ደረጃ ከማቅረብ የሚከለክለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ የሚገዛው የኪራይ ግንኙነትን በሚገዙት ድንጋጌዎች ሆኖ እያለ አመልካች ማስጠንቀቂያ መላፉን በመመልከት ብቻ ተግባሩ ሁከት ነው በማለት የደረሱበት ድምዳሜ በአመልካችና በተጠሪ መካከል አለ የተባለውን ግንኙነት ስለሁከት አጠቃላይ ይዘትና በዚህ ረገድ በፍርድ ቤት ስለሚጠየቀው መፍትሔ ከባለቤትነት መብት አድማስ ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ መጻፉ ሁከት ሊባል የሚችል አይደለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት ሕጋዊ የኪራይ ውል አለ የሚሉ ከሆነ ይህንኑ መሰረት በማድረግ መብታቸውን ከሚያስከብሩ በስተቀር በአመልካች ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉምሩክ /ቀረጥ/ ግብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 53749

ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ - ነ/ፈጅ እመቤት ባዩ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አዱኛ አበሉ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያላግባብ የተከፈለ ቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባሁኑ አመልካች ላይ ሐምሌ 04 ቀን 1998 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ ከቱርክ አገር ሶስት ማሽነሪዎችን ሰኔ 09 ቀን 1995 ዓ.ም በህጋዊ መንገድ ወደ አገር ማስገባታቸውን ለማሽነሪዎች የተሳሳተ ቁጥር 85489000 የሆነ የታሪፍ ኮድ እንዲሰጣቸው ተደርጎ የዋጋቸውን 40% ብር 40,514.02 እንዲከፍሉ መደረጉን ይህንኑ ገንዘብ እቃውን ለመረከብ ሲሉም መክፈላቸውንና እቃዎቹ በትክክለኛ የታሪፍ መጠን ተቀርጠው በአብላጫ የከፈሉት እንዲመለስላቸው አመልክተው የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን መስከረም 04 ቀን 1996 ዓ.ም ለአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ በጻፈው ደብዳቤ በትክክለኛ የታሪፍ መደብ እንዲስተናገዱ በሚል ማሳወቁን በትክክለኛው ኮድ ሊከፍሉ ይችሉ የነበሩት የገንዘብ መጠንም የዋጋውን 5% ብር 12,510.42 መሆኑን ዘርዝረው በአብላጫ የተከፈለው ብር 28,003.06(ሃያ ስምንት ሺህ ሶስት ብር ከዜሮ ስድስት ሳንቲም) ከወለድ እንዲሁም ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካችም በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 55 መሰረት በአብላጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስን መመለስ የሚቻለው እቃው ወደ አገር ውስጥ ከገባበት በስድስት ወር ውስጥ የታወቀ የሆነ እንደሆነ እንጂ እንደተጠሪ እቃው መስከረም 27 ቀን 1995 ዓ.ም አስገብቶ እቃውንም ህዳር 13 ቀን 1996 ዓ.ም አውጥቶ ከወሰዱ በኋላ አይደለም ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃዎችን በመመርመር ተጠሪ በአብላጫ የተከፈለ ቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄ ያቀረቡት በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 55 ስር በተመለከተው የስድስት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ አይደለም በማለት ክሱን በይርጋ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የጠቀሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌ ክፍያ ላይ ስህተት ሲፈጠር የሚፈፀም እንጂ ያላግባብ ለተከፈለ ክፍያ የሚሆን አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለክሱ መሰረት የሆነውን የገንዘብ መጠን ክሱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ (9%) ዘጠኝ በመቶ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ይርጋውን በተመለከተ አመልካች ያቀረበው ክርክር የታለፈው ከአዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለ አንቀጽ 55፣ 53 ድንጋጌዎች ውጪ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የትኛው ነው የሚለውን ነጥብ ለመለየት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ ተጠሪም በጠበቃቸው ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ አንድ ገፅ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ይርጋ መደበኛው ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም ሐምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ አመልካች አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው አንቀጽ 53 እና 55 መሰረት አድርጎ ያቀረበው የይርጋ ክርክር የመታለፉ አግባብነት ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ክሱን ሊመሰርቱ የቻሉት ያላግባብ የከፈልኩት የቀረጥ ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ ጥያቄው በስድስት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበና በሕጉ አግባብ የተፈፀመ መሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የዋጋ ኢንቮይስ ውድቅ የሆነበት ቀረጥ ከፋይ ቅሬታ ካለው በአዋጅ ቁጥር 60/1989 አንቀጽ 53 መሰረት ለተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አቅርቦ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ የሚችል ሲሆን በዚሁ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ቅሬታ ካለው ብቻ ወደሚመለከተው ፍርድ ቤት መሄድ የሚችል መሆኑን ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አከራካሪ ስለሆኑ ጉዳዮች በሚለው በእቃዎች ዋጋ አተማመን፣ በታሪፍ አሰያየምና አመዳደብ እንዲሁም በታሪፍ ልክ ላይ ተቃውሞ የቀረበ እንደሆነ የተቃውሞ ነጥብ ከተመዘገበ በኋላ የጉምሩክ ሹም በሚወስነው መሰረት ቀረጡ እንደሚከፈል በተቃውሞ የተከፈለው ቀረጥ ጉዳዩ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ በባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ እንደሚሰጥበት ባለጉዳዩ በውሳኔው ካልተስማማ በውሳኔው አለመስማማቱን ገልፆ በሰላሳ ቀናት ውስጥ በፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ያለበት መሆኑን አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል፡፡ ይህ ስርዓት ሳይፈፀም በቀጥታ በፍ/ቤት ክስ የሚመሰረትበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከተጠቀሰው ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በሕጉ ላይ የተመለከተው የስነ ስርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄ ነው፡፡ ይኸው የስነ ስርዓት ጉዳይም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት ባግባቡ መፈፀም አለበት፡፡ ይህ ለአስተዳደራዊ ውሳኔም የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎም ይታሰባል፡፡

በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለከፋዩ ሊመለስ እንደሚገባ አዋጁ በአንቀፅ 55 ስር በግልፅ ደንግጓል፡፡ ይህንኑ ያሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 15 ድንጋጌ ደግሞ ቀረጡ ተመላሽ የሚደረገው ስህተቱ መኖሩን ባለሥልጣኑ እንዳወቀ ወይም ባለቤቱ ጥያቄ እንዳቀረበ ይሆናል በሚል ካስቀመጠ በኋላ ቀረጡ ተመላሽ የሚደረገው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አጠናቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ውጪ ሀገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወራት ውስጥ ስህተቱ የታወቀና ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ነው በማለት ፍጹም የሆነ የይርጋ ጊዜ ደንግጓል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ቀሪ የቀረጥ ክፍያ መኖሩን አረጋግጠው ክፍያው እንዲፈፀምላቸው የጠየቁት እቃው ወደ አገር ከገባ ከአንድ አመት አስራ አንድ ወራት በኋላ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች መስሪያ ቤት ሹም በብልጫ የተከፈለ ቀረጥ እንዲመለስላቸው በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 53 መሰረት ጥያቄ አቅርበው ተገቢ ውሳኔ ተሰጥቶ ክሱን ፍርድ ቤት የመሰረቱ ሳይሆን ቀረጡ በስህተት መከፈሉን ተገንዝበው ስህተቱ ተስተካክሎ በብልጫ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስላቸው አቤቱታ አቅርበው ተገቢው እንዲፈፀም እናት መስሪያ ቤት ለቅርንጫፍ መስሪያ ቤት የፃፈውን ደብዳቤ መሰረት አድርገው መፍትሔ ሳያገኙ ሲቀሩ በፍርድ ቤት ክስ መስርተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጥያቄያቸውን በአዋጁ መሰረት እቃውን ከውጪ ከአስገቡ በኋላ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ አላቀረቡም፡፡ ይህም የሚያሳየው የአመልካች ጥያቄ በሕጉ የተገደበ መሆኑን ሲሆን አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 55 መሰረት ያነሱት እና የተጠቀሙበት ተቃውሞ አለመኖሩን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ክስ የመሰረቱበትን የቀሪ ቀረጥ ክፍያ ጥያቄ በተጠሪዎች በኩል በአዋጁ አንቀጽ 53(1) መሰረት ተቃውሞ ቀርቦ ተገቢው ለውጥ ባልተደረገበት ሁኔታ እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 55 መሰረት በስድስት ወር ጊዜ ያልቀረበ የቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ ባለመኖሩ በፍርድ ቤት ክስ መመስረታቸው በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤቶች መሻሩ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የአዋጁን ቁጥር 55 ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 59693 መጋቢት 17 ቀን 2001 ተሠጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 45757 ታህሳስ 27 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 73056 ሐምሌ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የተጠሪ የቀረጥ ይመለስልኝ ጥያቄ በስድስት ወር ይርጋ የታገደ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢት/ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሙሉእመቤት ኃ/ሚካኤል - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የተጠሪን መኪና ያለአግባብ ይዟል ተብሎ መኪናውን እንዲመልስና የተቋረጠ ገቢ ብር 9944.44 እንዲከፍል የተሰጠው ውሣኔ እንዲታረም አመልካች ስላመለከተ ነው፡፡

የጉዳዩ አጀማመር ባጭሩ ሲታይ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ የሠሌዳ ቁጥር 3-01017 አ.አ የሆነ መኪና አመልካች ያለአግባብ ይዞ በቁጥጥር ሥር አቆይቷል፡፡ መኪናውን እንዲለቅ እና መኪናው በመቆሙ የተቋረጠ ገቢ ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ ሲሉ ተጠሪ ያቀረቡትን ክስ የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ መኪናው እንዲመለስ እና የተቋረጠ ገቢ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን መጠን አመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች በውሣኔው ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዟል፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በሕግ የተሰጠውን ተግባር ሲያከናውን ይዞ ያቆየውን መኪና አስረክብ መባሉ እና የተቋረጠ ገቢ እንዲከፍል መወሰኑ ከአዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 73 እና 78 አኳያ ሊመረመር የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ የተጠሪ ጠበቃ ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ በይዘቱም ተጠሪ በመንግሥት ፈቃድ ከውጪ ሀገር ያስገቡት መኪና ስለመሆኑ ገልጸው ይህ መኪና ለንግድ ሥራ እንዲውል የፌዴራል የመንገድና ትራንስፖርት ባለሥልጣን ፈቅዶላቸው እየሰሩበት ስለመሆኑና ይህም በአመልካች አውቅናና ስምምነት ለመሆኑ ዘርዝረው በመግለጽ መኪናው መያዙ ሕገ ወጥ ተግባር ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ክርክሩን አጠናክሮ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተ ሲሆን እኛም በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካች በሥር ፍ/ቤት አጥብቆ የተከራከረው ተጠሪ ከቀረጥ ነፃ ለግል አገልግሎት ከውጪ ሀገር ያስገቡትን መኪና ተገቢው ቀረጥ ሳይከፈልበት ለንግድ ሥራ አውለውት በመገኘታቸው ድርጊቱ በሕግ የተከለከለ በመሆኑ ይህንኑ ለማጣራት በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መኪናውን በቁጥጥር ሥር ያዋለ ስለመሆኑ እና ይህም በሕግ የተቀበለው ሃላፊነት በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ ነው፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያና ሥልጣንና ኃላፊነትን የተመለከተው አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 368/95 እንደተሻሻለው አንቀጽ 73/1/ እንደሚያመለክተው ከቀረጥ ነፃ የገባ እቃ ለሌላ አገልግሎት ማዋል ሕገወጥ ተግባር አለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህንንም ተግባር እንዳይፈጸም ለመከላከል እንዲሁም ተፈጽሞ ሲገኝ መመርመር እና ሕጋዊ ውሣኔ የማሰጠት ኃላፊነት ለጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጠ ስለመሆኑ የጉምሩክ አዋጅ ይዘት ያመለክታል፡፡

ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 368/95 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 78 ላይ እንደተደነገገው የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ የተገኙ እቃዎችን እና ማጓጓዣዎችን አግባብ ያለው የመጨረሻ ውሣኔ አስኪሰጥባቸው ድረስ መያዝና በቁጥጥር ማዋል ይቻላል በማለት ተደንግጓል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ይህንኑ በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የተንቀሳቀሰ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪም መኪናውን ከቀረጥ ነፃ ለግል አገልግሎት ከውጪ ሀገር ያስገቡ ስለመሆኑ አምነው ነገር ግን መኪናው ለንግድ ሥራ እንዲውል የተደረገው በፌደራል የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ፈቃድ እና በአመልካች እውቅናና ስምምነት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

እንግዲህ ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር አንፃር መኪናው ለተጠሪ ሊመለስ ይገባል ወይንስ አይገባም? አመልካች መኪናውን በመያዙ የተቋረጠ ገቢ ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይንስ የለበትም የሚሉት ጭብጦች ውሣኔ ከማግኘታቸው በፊት ተጠሪ መኪናውን በምን ሕጋዊ አግባብ ለንግድ ሥራ አገልግሎት እንዲውል አደረጉት? ይኸው ከቀረጥ ነፃ የገባው መኪና ለንግድ ሥራ አገልግሎት ሲንቀሳቀስ በመልካች መያዙ ሕጋዊ አካሄድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው መሠረታዊ ጭብጥ ምላሽ የሚያሻው መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

የሥር ፍ/ቤት እነዚህን ጭብጦች ከግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ አንፃር ከሕጉ በማገናዘብ ሳይመረምር አመልካች የተጠሪን መኪና ያለፍርድ በቁጥጥር ሥር ማድረጉና መወረሱ ተገቢ አይደለም ከሚል የተሣሣተ ድምዳሜ ደርሷል፡፡ በመሠረቱ አመልካች የተጠሪ መኪና ተወርሷል የሚል ክርክርም አላቀረቡም፡፡

ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ በተደነገገው አግባብ የግራ ቀኙን ክርክር መሠረት በማድረግ ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ በአግባቡ በማጣራት ውሣኔ መሰጠት እየተገባው አመልካች መኪናውን እንዲመልስ እና የተቋረጠ ገቢ ለተጠሪ እንዲከፍል በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እና በከፍተኛው ፍ/ቤትም ይኸው ውሣኔ መጽናቱ ተገቢውን የክርክር አመራር ሥርዓት ያልተከተለ እና ከሕጉ ጋር በአግባቡ ያልተገናዘበ ሆኖ ስላገኘው ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም በክርክር አመራር ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 137829 ሰኔ 24 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83090 መጋቢት 2 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የተጠሪ መኪና ሊመለስ ይገባል? ወይንስ አይገባም? የተቋረጠ ገቢ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይንስ የለበትም? የሚለውን ጭብጥ ከመወሰኑ በፊት ተጠሪ ከቀረጥ ነፃ ያስገቡትን መኪና ለንግድ ሥራ አገልግሎት ያዋሉት በሕግ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም? አመልካች የተጠሪን ድርጊት ለመመርመር ሲል መኪናውን መያዙ ተገቢ ነው ወይንስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች ከግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ አንፃር መርምሮ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፤ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 50375

ህዳር 13 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፡- ሙሉአመቤት ውባየሁ ቀረበች

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ለተብርሃን አድሐኖም፡- ጠበቃ ተሰማ አበበ - ቀረበ

2. ሴፍ ትራንዚት ኃ/የተ/የግል ማህበር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በቀረ ይፈለጋል የተባለውን ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል የቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው አመልካች 1ኛ ተጠሪ ከውጪ ሃገር ላስመጣቻቸው የአገለገሉ የፊያት መኪና ኢንጅኖች መክፈል የነበረባት ቀረጥና ታክስ ብር 526,654.25 ሆኖ ሳለ ብር 28,218.18 ብቻ ስለከፈለች ቀሪውን ትከፍል ዘንድ ይወሰንልኝ፡፡ 2ኛ ተጠሪም ወኪል በመሆኑ የጋራ ሃላፊነት አለበት ይባልልኝ በማለት ክሱን አቅርቦአል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ካሰማ በኋላ፣ 1ኛ ተጠሪ ላስመጣቻቸው ኢንጅኖች ልትከፍል የሚገባት ቀረጥና ታክስ ብር 28,218.18 ነው በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ህዳር 4 ቀን 2002 ዓ.ም. በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ስለቀረጡ እና ታክሱ አከፋፈል በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም በግራቀኙ ወገኖች በዚህ ረገድ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በአመልካች ክስ እንደተገለጸው 1ኛ ተጠሪ የከፈለችው ብር 28,218.18 ብቻ ሲሆን፣ መክፈል የነበረባት ግን ከዚህ እጅግ ከፍያለ እንደሆነ በኋላ በተደረገው የኦዲተሮች ምርመራ እንደተረጋገጠ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ቀረጥና ታክሱ ኢንጅኖቹን ስትረከብ የከፈለችው ብቻ እንደሆነ እና ይህም በሕጉ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ ተከራክራለች፡፡ 2ኛ ተጠሪም ቀረጥና ታክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊጠየቅ የሚገባው የዕቃው ባለቤት እንጂ ወኪል አይደለም የሚል የመከራከሪያ ነጥብ አንስቶአል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የ1ኛ ተጠሪን ክርክር እንዳለ የተቀበለ ሲሆን፣ የሰጠው ምክንያትም አመልካች ለቀረጥና ታክሱ አተማመን መሠረት ያደረገው ሕግ ያገለገሉ የመኪና ሞተሮችን/ኢንጅኖችን/ አያጠቃልልም የሚል እንደሆነ ከውሳኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ሕግ የቅድመ ጭነት ምርመራ ሥርዓት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.173/91 በአንቀጽ 6(1) የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ/ክስ/ ውድቅ ያደረገው ለድንጋጌው ትርጉም በመስጠት እና ለክርክሩ መነሻ የሆኑ ያገለገሉ ኢንጅኖች በድንጋጌው አይሸፈኑም በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ድንጋጌውን ወደ መተርጎም የገባው ኢንጅኖቹ በኤስ ጂ ኤስ ኩባንያ የቅድመ ጭነት ምርመራ ተደርጎላቸው ዋጋም ወጥቶላቸው የገቡ በመሆኑ መቀረጥ ያለባቸው ኩባንያው በሰጠው ዋጋ መሠረት ነው በማለት ተከሣሽ በመከራከርዋ እና አመልካች /የሥር ከሣሽ/ ደግሞ ኢንጅኖቹ አሮጌ /ያገለገሉ/ በመሆናቸው የቅድመ ጭነት ምርመራ እንዳይደረግባቸው ሕጉ ይከለክላል የሚል መከራከሪያ በማቅረቡ ነው፡፡ በእርግጥም አከራካሪው ነጥብ የሕግ ጭብጥ በመሆኑ በዚህ ረገድ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሚፈታ ነው የሚሆነው፡፡

ማንኛውም ወደ ኢትዮጵያ የሚላክ ዕቃ በማንጓጓዣ ላይ ከመጫኑ በፊት የቅድመ ጭነት ምርመራ እንደሚደረግበት ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ በአንቀጽ 4(1) ተደንግጎአል፡፡ የቅድመ ጭነት ምርመራ ሽፋን የእቃውን ዋጋ እና የምንዛሬውን ተመን ትክክለኛነት፣ ጥራት፣ ብዛት፣ የአስተሻሸግ ሁኔታ እና የታሪፍ ምደባ የሚመለከት እንደሚሆንም በአንቀጽ 5 ተመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአንቀጽ 4 መሠረት የሚደረገው የቅድመ ጭነት ምርመራ ተፈጻሚ የማይሆንባቸው ዕቃዎች እንዳሉ ‹‹ልዩ ሁኔታዎች›› በሚል በተደነገገው በአንቀጽ 6 ተመልክተዋል፡፡ የቅድመ ጭነት ምርመራ አይደረግባቸውም የተባሉት ዕቃዎች በአንቀጽ 6(1) በዝርዝር የተመለከቱ ሲሆኑ፣ ያገለገለ ተሽከርካሪንም አጠቃለው የያዙ ናቸው፡፡ እንግዲህ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ወይም አነጋገር ከውጪ ሃገር ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው የአገለገለ ተሽከርካሪ ወይም መኪና በአንቀጽ 4 እንደተደነገገው አይነት የቅድመ ጭነት ምርመራ አይደረግበትም ማለት ነው፡፡ ተሽከርካሪው ወይም መኪና ሊሸከረከር ወይም አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው ሞተር ወይም ኢንጅን ሲኖረው እንደሆነም የሚዘነጋ አይደለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከውጪ ሃገር ያስገባቻቸው ኢንጂኖች የፊያት መኪና ኢንጅኖች እንደሆኑ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በፊያት መኪኖች ተገጥመው ሥራ ላይ የሚውሉ ናቸው ማለት ነው፡፡ እውነታው ይህ ከሆነም ሕግ አውጪው በአሮጌ ወይም ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች (ፊያት መኪኖችን ጨምሮ) ላይ የቅድመ ጭነት ምርመራ አይደረግም እያለ ባገለገሉ ሞተሮቻቸው/ኢንጅኖች/ ላይ ግን የቅድመ ጭነት ምርመራ ይደረግባቸዋል የሚል ተቃራኒ ሃሳብ ይዞ ሕጉን ያወጣል ብሎ ማሰብ ምክንያታዊ አይሆንም፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ኢንጅኖቹ በአዋጁ አንቀጽ 6(1) አይሸፈኑም ለማለት የበቃው በዝርዝሩ ውስጥ ያገለገሉ የመኪና ሞተሮች በሚል አልተመለከተም በማለት ነው፡፡ በመሠረቱ ሕግ አውጪው ሕጉን በሚተገብረው/በሚተረጉመው/ አካል በትርጉም ሊደረስበት የሚችለውን ነጥብ በሙሉ እየዘረዘረ ያወጣል ብሎ በጥቅሉ ማሰብ ተገቢም፤ ምክንያታዊም አይሆንም፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወይም መኪኖች በግልጽ እስከተመለከቱ ድረስ የመኪኖቹን/የተሽከርካሪዎቹን/ ዋነኛ አካል /አንቀሳቃሽ/ የሆነው ሞተር ተለይቶ ነው የሚታየው ወደሚለው መደምደሚያ መድረስ ትክክል አይሆንም፡፡ ሕጉም መተርጎም ያለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያትን መሠረት በማድረግ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለድንጋጌው የሰጠው ትርጉም ከዚህ አንፃር ሲታይ በምክንያት ላይ ወይም ምክንያታዊ በሆነ የሕግ አተረጓጎም ስልት ላይ በመመሥረት የተሰጠ ነው የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

በመቀጠል የተመለከትነው አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ከተባለ በምን አይነት አግባብ ሊታረም ይገባል የሚለው ነው፡፡ ከላይ በዝርዝር እንዳየነው የሥር ፍ/ቤቶች ክሱ ተቀባይነት የለውም እሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሳቸው እና ለዚህ ድምዳሜአቸው መሠረት ያደረጉት ለሕጉ የሰጡት ትርጉም በመሆኑ ወደ ፍሬ ነገሩ ክርክር ገብተው ስለቀረጥና ታክሱ መጠን በተመለከተ ውሳኔ አልሰጡም፡፡ ከዚህ የተነሳም ፍሬ ነገሩን በሚመለከት ከመጀመሪያው ክርክር ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 113733 ታህሣስ 8 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 76484 ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ኢንጅኖች በአዋጁ አንቀጽ 6(1) የሚሸፈኑ በመሆናቸው የቅድመ ጭነት ምርመራ አይደረግባቸውም ብለናል፡፡

3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ ሊከፈል በሚገባው ታክስ እና ቀረጥ መጠን ከግራ ቀኝ ወገኖች የሚቀርብለትን ክርክር ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.343(1) መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡

4. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዘቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች - 1. ዘቴዊንስ ባር እና ሬስቶራንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠ/ውብሸት ክብሩ -ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፅጌ ወልደ ገለቱ

ተጠሪ - የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ነ/ፈ ገብረእግዚአብሔር ሁናቸው - ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን በመተላለፍ የተፈፀመ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡

ሥር ፍ/ቤት ክስ የቀረበው በተጠሪ በኩል ሲሆን የክሱ ምክንያት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እና 55 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 22/1/ እና 50/ለ-1/ የተመለከተውን በመተላለፍ በ30/07/2001 ዓ.ም ከቀኑ 10፡50 ሰዓት ላይ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቾች እና የ1ኛ አመልካች የነበሩት በሥር ፍ/ቤት ከ3-5 የነበሩት ተከሣሾች በተከሰሱበት ድርጊት ጥፋተኞች ናቸው በማለት 1ኛ አመልካች ብር ስልሳ ሺህ 2ኛ አመልካች ብር ሃያ ሺህ እና 1 ዓመት እስራት ከ3-5 ያሉት ተከሣሾች ብር አሥር ሺህ እና 1 ዓመት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ግራቀኙ ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት በሁለቱም ወገን የቀረበውን ይግባኝ ተቀብሎ ካከራከረ በኃላ መዝገቦቹን በማጣመር በመ/ቁ 82648 ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔውም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ በማፅናት በቅጣት ረገድ ዐ/ሕግ ያቀረበውን ቅሬታ መነሻ በማድረግ የእስራት ቅጣቱን በማሻሻል 2ኛ አመልካች እና ከ3-5 የነበሩት ተከሣሾች እያንዳንዳቸው በሁለት ዓመት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካቾች ጠበቃ ታህሣሥ 8 ቀን 2002 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዝርዝር በመንቀፍ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ አመልካቾች በነፃ እንዲሰናበቱ እንዲወስን ጠይቀዋል፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ አቤቱታ ተመርምሮ ሁለተኛ ተጠሪ ጥፋተኛ ተብለው የተሰጠው ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 285/94 56/1/ እና/3/ አንፃር አግባብነቱ በሰበር ሊመረመር ይገባል ተብሎ ተጠሪ ቀርቦ ክርክሩን እንዲያሰማ ተደርጓል፡፡ በዚሁ አግባብ ሚያዝያ 7 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግራቀኙ ክርክር ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው 2ኛ አመልካች ጥፋተኛ ናቸው ተብለው እንዲቀጡ የተወሰነው የ1ኛ አመልካች ስራአኪያጅ ሆነው ሲሰሩ ድርጅቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን በመተላለፍ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት በመፈፀሙ የአዋጁን አንቀጽ 56/1/ እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ እና 55/ለ-1/ ተላልፈዋል ተብለው ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የ1ኛ አመልካችን ሃላፊነትና ተጠያቂነት አረጋግጠው ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ እዚህ ፍ/ቤት ላይ አጥብቀው የተከራከሩት 2ኛ አመልካች የ1ኛ አመልካች /ድርጅቱ/ ሥራ አስኪያጅ ቢሆኑም ድርጊቱ ሲፈጸም በቦታው እንዳልነበሩና በድርጊቱ አፈፃፀም ላይ ስምምነትም ሆነ እውቀት አልነበራቸውም እንዲሁም ይህ ስህተት እንዳይፈጸም ሥራ አስኪያጁ /2ኛ አመልካች/ ተገቢውን ትጋትና የአሰራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስደዋል በሚል በአዋጁ አንቀጽ 56/3/ መሠረት በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል የሚል ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው አንቀጽ 56/1/ አንቀጽ 22/1/ እና አንቀጽ 50/ለ-1/ ድንጋጌዎች ይዘት እንደሚያመለክተው አንድ የንግድ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው እሱ የሚመራው ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዘጋቢ ሆኖ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ማከናወኑ ሲረጋገጥ ይኸው ጥፋት በሥራ አስኪያጁ እንደተፈፀመ ተቆጥሮ ተጠያቂ እንደሚሆን ነው፡፡

ስለሆነም የድርጅቱ ሃላፊነት ከተረጋገጠ የሥራ አስኪያጁ ሃላፊነት የሕግ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ መንዘብ ይቻላል፡፡ ሥራ አስኪያጁ ከዚህ የሕግ ግምት ሃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችለው በአዋጅ አንቀጽ 56/3/ ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ጥፋቱ የተፈፀመው ሥራ አስኪያጁ ሳያውቅት ወይም ሳይስማሙበት እንደዚሁም ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈጸም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመተውን ጥንቃቄና ተገቢውን ትጋትና የአሰራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ወስዶ የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ 2ኛ አመልካች የ1ኛ አመልካች ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሲሰሩ ድርጅቱ ሽያጭ በሚያከናወንበት ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ወዲያውኑ ተጠቃሚው እንዲያገኝ በማድረግ ተገቢው አሰራር ተዘርግቷል በማለት የተከራከሩ ቢሆንም በዚህ ረገድ በሥር ፍ/ቤት ክርክር እና ማስረጃ ቀርቦበት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ስለመኖሩ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ አያመለክትም፡፡

በእርግጥ በወቅቱ 2ኛ አመልካች በቦታው አልነበሩም ቢባልም ከፍ ሲል እንደተመለከትነው በሕጉ ግምት የሚወሰድበት ጥፋት በመሆኑ 2ኛ አመልካች በቦታው ያልነበሩ መሆኑ በራሱ ከሃላፊነት ነፃ ሊያደርጋቸው የሚችል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል 2ኛ አመልካች በፍሬ ነገር ደረጃ ሥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤት ተረጋግጧል ሲሉ የሚከራከሩበት ጉዳይ ድርጊቱ በተፈፀመ ጊዜ መብራት ጠፍቶ ነበር የሚል ቢሆንም በማኑዋል የሚሰራ ደረሰኝ እንደነበራቸው ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም 2ኛ አመልካችን አስመልክቶ እዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ የአዋጁን አንቀጽ 56/3/ ይዘት በመዘርዘር በጠበቃቸው የተከራከሩ ቢሆንም በዚህ ረገድ በሥር ፍ/ቤት በዝርዝር ክርክር ተደርጐበት እና በማስረጃ ተረጋግጦ የቀረበ ፍሬ ነገር ባለመኖሩ ሥራ አስኪያጁ በሕጉ አግባብ እና መንፈስ መሠረት በተጠቃሹ ድንጋጌ መሠረት ነፃ ሊሆኑ የሚችሉበት ምክንያት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡

በመሠረቱ የዚህ ሰበር ችሎት ሃላፊነትና ተግባር በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠ ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ አተገባበር ወይም አተረጓጐም ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ማረም እንጂ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ክርክር የማጣራት ሥራ እንዳልሆነ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/3-ሀ/ እና ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ላይ የቀረበው ክርክር የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ እንጂ በሕግ ረገድ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚያሰኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለዚህም የሥር ፍ//ቤት 2ኛ አመልካችን ጥፋተኛ አድርጐ የቅጣት ውሣኔ መወሰኑ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 82648 ህዳር 21 ቀን 2002 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔን በማሻሻል የሰጠው ፍርድ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/2/ለ-2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የሰሜን ምስራቅ ጉምሩክ ሜሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ

ተጠሪ፡- በረከት አሰፋ - በሌሉበት የሚታይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሕግ ውጭ የተያዘው መኪናዬ ይለቀቅልኝ፣ በመኪናው ሰርቼ ላገኝ እችል የነበረው የቀን ገቢ ብር 700,00 ተሰልቶ ይከፈለኝ በማለት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ የመሠረተውን ክስ መነሻ አድርጎ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጠው መልስም ድርጊቱ ሕጉ በሰጠው ስልጣን መሠረት የተፈፀመና ኃላፊነት የሚያስከትል መሆኑንና ተቋረጠ የተባለው ገቢም ሕጋዊ ስለመሆኑ በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ከመከራከሩም በተጨማሪ መኪናውን የያዙት የአመልካች መሥሪያ ቤት ሰራተኞች ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ይታዘዙለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በሁዋላ አመልካች መኪናውን እንዲለቅ፣ እንዲሁም መኪናው በአመልካች ተይዞ በመቆየቱ ምክንያት ተጠሪ የቀን ገቢ የተቋረጠባቸው መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ብር 105, 000.00 /አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ ለተጠሪ አመልካች እንዲከፈል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማትም ይግባኙን ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የአመልካች አድርራት በአዋጅ ቁጥር 60/1989 መሠረት የተፈቀደ ሁኖ እያለና የተጠሪ የመኪና ገቢም በተገቢው መንገድ ግብር ሲከፈልበት የነበረ መሆኑ ሣይረጋገጥ የተቋረጠ ገቢ አመልካች ለተጠሪ ብር 105,000.00 /አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍል መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በጉምሩክ ተይዞ የቆየው መኪና የቤት መኪና መሆኑ ሣይካድ ተጠሪ ገቢ አጥቷል ተብሎ አመልካች ብር 105,000.00 ይክፈል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ በዚህ ፍርድ ቤት ጥሪ በተገቢው መንገድ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በስር ፍርድ ቤት የተደረገውን የግራ ቀኙን ክርክርና በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ ከአመልካች የሰበር አቤቱታና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተጠሪን መኪና ይዞ በቁጥጥር ስር ሊያውል የቻለው መኪናዋ ኮንትሮባንድ እቃ የጫነውን መኪና ፊት ለፊት በመሆን አጅባ ትጓዝ ስለነበረ በኮንትሮባንድ ድርጊት ተሣትፎ አድርጋለች በሚል ጥርጣሬ ነው በማለት አመልካች የሚከራከር መሆኑና የተያዘችው የተጠሪ መኪና የቤት መኪና መሆኗ መረጋገጡን ነው፡፡

የአመልካች መ/ቤት ስልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 60/1989 በአንቀጽ 6 እና 58 ስር ተዘርዝሯል፡፡ እነዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች የሚያሣዩት የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የጉምሩክ ባለሥልጣንና ሹም የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት በዝርዝር መቀመጣቸውን ነው፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 368/1995 ደግሞ ኮንትሮባንድ ማለት ሕጎችንና በሕግ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ወደ ጉምሩክ ክልል ዕቃዎችን በማስገባት ወይም ከጉምሩክ ክልል በማስወጣት፣ በሕጋዊ መንገድ የመጡትን በሕገ ወጥ መንገድ መልሶ ማስገባት መያዝ፣ ማከማቸት፣ ማዘዋወር ማስተላለፍ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ለማድረግ መሞከር እና እንደዚህ ላሉ ድርጊቶች መተባበርን እንደሚጨምር በአንቀጽ 2/28/ተርጓሜ ሠጥቶበታል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው አመልካች ተግባሩን ሕጋዊ ነው ብሎ ሲከራከር በተለይ መሠረት ያደረጋቸው የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6/5/ እና 58/1/ለ/ ድንጋጌዎችን ነው፡፡ አንቀጽ 6/5/ ሙሉ ይዘቱ ሲታይ ባለሥልጣኑ “በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል፣ ይከላከላል፣ በዚሁ ሁኔታ የሚንቀሣቀሱ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ይይዛል፤ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል” በማለት ሲደነግግ አንቀጽ 58/1/ለ/ ደግሞ ወደ አገር እንዳይገቡ ወይም ከአገር እንዳይወጡ የተከለከሉ፣ ገደብ የተደረገባቸው ወይም ቀረጥ እንዳይከፈልባቸው በማሰብ የተደበቁ ዕቃዎች በፍተሻ ሲገኙ ዕቃዎችን የመያዝ እንዲሁም እንደሁኔታው ማጓጓዣውን የማጓጓዣውን ኃላፊ ወይም የዕቃውን ባለቤት ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ሥር የማቆየት ስልጣንና ኃላፊነት የጉምሩክ ባለሥልጣን ያለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የጉምሩክ ባለሥልጣን በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሣቀሱ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ፣ በሕገ ወጥ መንገድ መገልገያ የሆኑ መጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ በሕገ ወጥ መንገድ መገልገያ የሆኑ መጓጓዣዎችን ጭምር ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ስር የማቆየት ስልጣን በሕጉ የተሰጠው መሆኑን ነው፡፡ እነዚህን ተግባራት የሚያከናውነው ግን ኮንትሮባንድ ተብሎ በሕግ የተሰጠው ትርጓሜ ተሟልቶ ሲገኝ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ማንኛውም የዕቃ እንቅስቃሴ ኮንትሮባንድ ስለመሆኑ አሣማኝ እና በቂ ምክንያት ሣይኖረው ባለሥልጣኑ መ/ቤት እንዲይዝና እንዲቆጣጠር ሕጉ ስልጣን ተሠጥቶታል ተብሎ አይታሰብም፡፡ እንዲሁም እቃው ኮንትሮባንድ ስለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረውም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ዕቃውን የመያዝ ስልጣን ያለው መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ይዘት ያሣያል። የኮንትሮባንድ ድርጊት ደግሞ የኮንትሮባንድ እቃ ነው የተባለውን ጭኗል በተባለ መኪና ብቻ ይፈፀማል ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ ሕጋዊ ምክንያት የለም። ድርጊቱ ወንጀል እንደመሆኑ መጠን የአድራጊዎች ተሣትፎም የተለያየ ደረጃና መልክ ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል። በመሆኑም የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በሕጉ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ሲወጣ ኮንትሮባንድ ስለመሆኑ የጠረጠረውን ዕቃ የጫነ መኪና ከመያዝ ባለፈ በቂና አሣማኝ ጥርጣሬ እስካለው ድረስ የኮንትሮባንድ ወንጀሉ ተሣታፊ ነው የሚለውን መኪና ሁሉ በመያዝ በቁጥጥር ሥር የማዋል ሥልጣን አለው። የሥር ፍርድ ቤት የኮንትሮባንድ እቃ ያልጫነ መኪናን አመልካች መያዙ ሕገወጥ ነው በማለት ሙሉ በሙሉ መደምደሙ ለአመልካች በሕግ ተለይቶ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ከኮንትሮባንድ ወንጀል አፈፃፀምና የተሣትፎ ሁኔታ ጋር ያልተገናዘበ ሁኖ አግኝተናል። ስለሆነም አመልካች መኪናውን መያዙ ሙሉ በሙሉ ሕገወጥ ተግባር ነው መባሉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው። ይሁን እንጂ የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በቂና አሣማኝ ጥርጣሬ ኑሮት እቃውን መያዝ ይችላል ማለት ተገቢና ምክንያታዊ ባልሆነ ጊዜ እቃውን ይዞ የመቆየት ስልጣን አለው ወደሚለው ድምዳሜ አያደርስም። በመሆኑም መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነቱንና ተግባሩን ሲወጣ በጥርጣሬ የያዘውን እቃ ተገቢና ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ አጣርቶ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት። በጥርጣሬ የያዘውን ንብረት ምክንያታዊ ለሆነ ጊዜ ከያዘና ስልጣን ያለው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አጣርቶ የተያዘው ንብረት እንዲለቀቅ ውሣኔ ከሰጠ በሁዋላ ባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ወዲያውኑ ከለቀቀ ተገቢና ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ንብረቱ በመቆሙ የታጣውን ገቢ እንዲከፍል የሚገደድበት የሕግ አግባብ የለም። የጊዜው ተገቢነትና ምክንያታዊነትም እንደ ጉዳዩ ባህርይና ከባቢያዊ ሁኔታዎች እየታየ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ነው። በጥርጣሬ የተያዘው እቃ ከምክንያታዊ ጊዜ በላይ መያዙ ከተረጋገጠ ግን አመልካች በሕግ አግባብ ኃላፊ የማይሆንበት ምክንያት የለም።

እጃችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች የተጠሪ መኪና የተያዘው የኮንትሮባንድ እቃ ጭኗል በሚል ጥርጣሬ ሣይሆን የኮንትሮባንድ እቃ የጫነ መኪናን አጅቦ ሲሄድ ነበር ሲሆን ጉዳዩ ሲጣራ ቆይቶ መኪናው እንዲለቀቅ በፍርድ ቤት ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ከሰጠ በሁዋላ መኪናው ወዲያውኑ ተለቋል፤ እንዲሁም ጉዳዩ እስከሚጣራና በፍርድ ቤት ውሣኔ ጉዳዩ እስከሚያልቅ ድረስ መኪናው በአመልካች ተይዞ የቆየው ለአምስት ወራት መሆኑ ተረጋግጧል። ይሁን እንጂ አመልካች የተጠሪን መኪና የያዘው የኮንትሮባንድ እቃ የጫነ መኪና አጅቦ ሲሄድ ነው በሚል ምክንያት ሲሆን ይህንኑ ምክንያት በማጣራት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰደበትን ምክንያት በስር ፍርድ ቤት አላስረዳም። መኪናው ከተያዘበት ምክንያትና ከባቢያዊ ሁኔታዎች ስንነሣም ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ከሦስት ወራት ጊዜ በላይ ሊወሰድ ይችላል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ምክንያት የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል። በመሆኑም አመልካች የተጠሪን መኪና ከሶስት ወር ጊዜያት በላይ ያለበቂ ምክንያት ይዞ ለቆየባቸው ጊዜያት / ለሁለት ወር ጊዜያት/ ተግባሩ ሕገ ወጥ በመሆኑ ኃላፊ የማይሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም።

አመልካች የተጠሪን መኪና ለሁለት ወራት ይዞ መቆየቱ ሕገወጥ ነው ከተባለ ቀጥሎ እልባት ማግኘት ያለበት ጉዳይ የካሣ መጠን ነው። ተጠሪ መኪናውን የቤት መኪና መሆኑን ጠቅሰው በኪራይ ብር 700.00 /ሰባት መቶ ብር/ በቀን ያገኙ እንደነበር ገልፀው የአምስት ወራት ገቢ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፣ አመልካች ደግሞ ገቢው ሕጋዊ መሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ተከራክሯል። የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪን ክርክር ሙሉ በሙሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቀብሏል፡፡ ይሁን እንጂ የቤት መኪና በኪራይ ገቢ ሊያስገኝ እንደሚችል የሚታመን ቢሆንም የኪራይ ገቢ ግን ሕጋዊነቱ መረጋገጥ አለበት፡፡ ሕጋዊነቱ የሚረጋገጠው ደግሞ ከሚመለከተው አካል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ፤ የንግድ ስራ ፈቃድ ሲቀርብ ወይም በዚህ ረገድ ተገቢ ማስረጃ ቀርቦ ሕጋዊነቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የተጠሪ የኪራይ ገቢ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድን መሠረት አድርጎ የተገኘ ስለመሆኑ ሕጋዊ ማስረጃ አልቀረበበትም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህንኑ ሣያረጋግጥ የተጠሪ መኪና በኪራይ መንገድ ገቢ ታስገኝ ነበር በማለት መደምደሙ ገቢ ተቋርጦብኛል የሚል ወገን በተገቢው መንገድ የማስረዳት ግዴታ አለበት በሚል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 የተቀመጠውን የሕግ መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ መኪናቸውን በቀን በብር 700.00 /ሰባት መቶ ብር/ አከራይተው ገቢ ያስገኙ ነበር የሚለው የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የተጠሪ መኪና በሕጋዊ ንግድ በመሰማራት ተገቢውን ግብር ተጠሪ የከፈሉባት ስለመሆኑ ስላልተረጋገጠ ገቢ ተቋርጧል ለማለት አይቻልም በማለት ያቀረበው ክርክርም ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም የተጠሪ መኪና የቤት መኪና መሆኗ እና በአመልካች ደግሞ ለሁለት ወራት ያህል ያለ በቂ ምክንያት በቁጥጥር ስር መዋሏ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ ላይ ሙሉ በሙሉ የጥቅም ማጣት አልደረሰባቸውም ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለምና፡፡ ተጠሪ ለራሣቸውም ሆነ ለቤተሰባቸው የትራንስፖርት አገልግሎት መኪናውን እንደሚጠቀሙ የሚታመን ሲሆን መኪናው በአመልካች ቁጥጥር በመዋሉ ምክንያት ደግሞ ለወጪ እንደሚዳረጉ እሙን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ሙሉ በሙሉ ያጡት ጥቅም የለም ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ ይሁን እንጂ መኪናውን ባለመገልገላቸው የደረሰባቸው እርግጠኛ ወጪ ይህ ነው ብሎ ለመደምደም መነሻ የሚሆን ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ሆኖም ስለ ጉዳቱ ምን ያህል ኪሣራ እንደሚከፍል በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ዳኞቹ የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎችንና ተጎጂውም ያደረገውን ጥንቃቄ አመዛዝነው በመገመት የኪሣራውን ልክ በርትዕ ሊወስኑ እንደሚችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ያጡት ጥቅም በርትዕ ሊወሰን የሚገባው ሁኖ በመገኘቱ ይህ ችሎት ተጠሪ ለሁለት ወራት ያህል ያጡት ጥቅም ለእያንዳንዱ ወር ከብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በላይ ሊሆን እንደማይችል ገምቷል፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ኃላፊነትን በተመለከተ የሰጡት ውሣኔ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 60/1989 መሠረት የተሰጠውን ስልጣን ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ሲሆን የካሣ መጠኑም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ሁኔታዎችና ስለካሣ መጠን አወሳሰን የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ድንጋጌዎችን መሠረት ያላደረገ እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሣሣይ ጉዳዮች ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር የማይጣጣም ሁኖ ስለአገኘነው ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአማራ ክልላዊ መንግሥት ደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20751 ታህሣሥ 04 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 467/2001 ጥር 05 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የተጠሪን መኪናን የያዘው በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን ሲያከናውን ቢሆንም መኪናውን ይዞ የቆየው ተገቢና ምክንያታዊ ነው ሊባል ከሚቻለው ጊዜ በላይ በመሆኑ ከሶስት ወራት ጊዜያት በላይ መኪናውን ይዞ ለቆየባቸው ለሁለት ወራት የተቋረጠ ገቢ የማይከፈልበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው የሁለት ወር የቀን ገቢ በብር 200 /ሁለት መቶ ብር/ ሲታሰብ የሚመጣው ብር 12,000.00 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ ነው ብለናል፡፡
   መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59851

የካቲት 11 ቀን 2003 ዓ/ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ዓለሙ ጋባ - ጠበቃ ወልደስላሴ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐቃቤ ሕግ ሽመልስ አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር ተያይዞ የተነሳን የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- 1ኛ፡- አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው አንቀፅ 22(1) እና 50(ለ-1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13 ክልል ውስጥ በሚገኝ ቁጥሩ 081 በተሰጠውና በንግድ ፈቃድ ቁጥር 02/1/3/01096/98 የሚሠራ የዓባይ ዙሪያ ሆቴል ተብሎ በሚጠራው ቤት ጥር 14 ቀን 2002 ዓ/ም ከቀኑ 8፡00 አከባቢ የአንድ ለስላሳ እና ሻይ ግብይት በብር 5.25 ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሠኝ በሠራተኞቸው አማካይነት በመሸጣቸው ተከሰዋል የሚል ሲሆን ሁለተኛው ክስ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እንደተሻሻለው አንቀፅ በአንቀጽ 50(መ-1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በድርጅቱ ውስጥ በባልሥጣኑ እውቅና የተሰጠበት የሽያጭ መመዝገቢያ መሥሪያ ከህዳር 25 ቀን 2002 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 24 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ ባለው ጊዜ ገዝቶ የመጠቀም ግዴታ የተጣለበት ቢሆንም በሆቴሉ ውስጥ በባለስልጣኑ መሥሪያ ቤት እውቅና ያልተሰጠውንና "ናን ፊስካላይዝድ ማሽን" ሲጠቀሙ ተገኝተዋል የሚል ነው፡፡ አመልካችም እንደ አቃቤ ክስ ድርጊቱን ያለመፈጸማቸውን በመግለፅ ክሱን ክደው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ አሉኝ ያላቸውን የሰው ምስክሮችን አስቀርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ምስክሮችን አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕጉን ማስረጃዎችን ያላስተባበሉ መሆኑን በመግለፅ ቃላቸውን ውድቅ ከአደረገ በኋላ አመልካችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማድረግ በ1ኛ ክስ በሁለት አመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራትና በብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ብር)፣ በሁለተኛው ክስ ደግሞ በአንድ አመት እሥራት በድምሩ በሦስት አመትና በስድስት ወር እስራትና በብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ብር) እንዲቀጡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተላለፈባቸው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ከተቀበለና ግራ ቀኙን ከአከራከሩ በሁዋላ በአመልካች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመቀበል የእስራት ቅጣት ውሳኔውን ግን ወደ ሁለት አመት እሥራት ዝቅ አድርጎ የገንዘብ መቀጮውን ደግሞ እንዳለ በመቀበል የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ነሐሴ 27 ቀን 2002 ዓ.ም. የተፃፈ ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ፡- የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የወሰኑት በሕጉ አግባብ አቃቤ ሕግ ባላስረዳበትና ተጨማሪ ማስረጃዎችም ቢሆኑ አመልካች ደረሠኙን እንዲታተም ለማድረግ እንዲሁም ማሽኑን ለማስገባት ተገቢውን ጥረት ሲያደርግ የነበረ መሆኑን ባረጋገጡት ሁኔታ ስለሆነ የጥፋተኝነት ውሳኔው ሊሻር የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆኑ በመ/ቤቱ የተገለፀለት ደብዳቤ እጁ ከገባ ከታህሳስ 13 ቀን 2002 ዓ.ም. ጊዜ ጀምሮ መ/ቤቱ በሰጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ደረሠኞችንና የሂሳብ መኪና ለማስገባት ተገቢውን እንቅስቃሴ ሲያደርጉ መቆየቱ በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋገጦ እያለ ጥፋተኛ ተብለው መቀጣታቸው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ በመታዘዙ ተጠሪ ቀርቦ አመልካች ጥፋተኛ ተብለው ሊቀጡ ይገባል በሚል የተሰጠው ውሳኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው ሙሉ በሙሉ ሊጸና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ጠበቃም ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አመልካች ጥፋተኞች ተብለው መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሲሆን ቅጣት ጋር ተያይዞ የቀረበው ክርክር በዚሁ ጭብጥ እልባት የሚያገኝ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609 እንደተሻሻለ አንቀፅ 22(1) እና 50(ሉ-1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ማከናወናቸውን ተጠሪ በሕጉ አግባብ አስረድቷል ወይስ አላስረዳም?፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609 እንደተሻሻለ 50(መ-1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት እውቅና ውጪ የሽያጭ መኪና ይዘው ተገኝተዋል? ወይስ አልተገኙም? የሚሉትን ጥያቄዎችን በማንሳት በስር ፍርድ ቤት በአቃቤ ሕጉ ማስረጃዎችና በአመልካች ማስረጃዎች ጭምር ከተረጋገጡት ፍሬ ጉዳዮች እና አግባብነት ካላው ሕግ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡ አመልካች የተከሰሱት 1ኛው ክስ፡- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 55 እና በአዋጅ ቁጥር 609 እንደተሻሻለ አንቀፅ 22(1) እና 50(ሉ-1) በመተላለፍ ሆቴል ድርጅቱን በወኪልነታቸው በሚያስተዳድሩበት ጊዜ ሽያጭ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሠኝ አከናውነዋል በሚል ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት የተጠሪ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ይኸው ተረጋግጧል፡፡ አመልካችም እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሚያቀርቡት ክርክር ግብይቱ በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተከናውኗል የሚል ክርክር ሳይኖራቸው አጥብቀው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚከራከሩት በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በተሰጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ደረሠኞችንና የሂሳብ መኪና ለማስገባት ተገቢውን እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበረ መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት አመልካች በውክልና የሚያስተዳድሩትን የሆቴል ድርጅት በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የመዘገበው ከጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑና የምስክር ወረቀት መስጠቱን፣ ግብይቱ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሠኝ የተከናወነው ደግሞ ጥር 14 ቀን 2002 ዓ/ም መሆኑ በአቃቤ ሕጉ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ግብር ከፋይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋይነት ተመዘገበ የሚባለው ደግሞ ከተመዘገበበት ቀን ወይም ምዝገባው ከሚጸናበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3(1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 22(1) ድንጋጌ ሲታይም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋይነት የተመዘገበ ማንኛውም ሰው ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ለሚያድርገው ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለተጠቃሚው ወዲያውኑ መስጠት እንደአለበት አስገዳጅነት ባለው ኃይለቃል ደንግጎ እናገኛለን፡፡ ሕጉ በተገቢው ጊዜ ደረሠኝ ሳያሳትም ግብይት ያከናወነ ግብር ከፋይ ጥረት እያደረገ ቢቆይና ግብይቱን ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ከአከናወነ ተጠያቂነት የሌለበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ድግንጋጌ የለውም፡፡ አመልካች ተገቢውን ጥረት ሲያደርጉ የነበረ መሆኑን ተረጋግጧል የሚሉት በመከላከያ ምስክሮችና በሠነድ ማስረጃዎቻቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ደረሠኙን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ያላሳተሙበትን ሕጋዊ ምክንያት ያላስረዱ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን ከውሳኔው ተገንዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት በተሰጠው ሥልጣን የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የደረሱበትን ድምዳሜ የሚያጣራበት ወይም ማስረጃውን የሚመዝንበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ደረሠኙን እንዲዘጋጅ ሳያደርጉ ወይም ያላዘጋጁት ከራሳቸው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ ስለመሆኑ ባላስረዱበት ሁኔታ በ1ኛ ክስ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሕጋዊ የሽያጭ መኪና ሳይጠቀሙ ከሕግ ውጪ በሆነ ሁኔታ (ከባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት እውቅና ውጪ) ናን ፊሲካላይዝድ የሚባል የሽያጭ መኪና ይዘው መገኘታቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ተጠሪ አመልካች ከሕዳር 25 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ታህሳስ 24 ቀን 2002 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ እውቅና የተሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ ያለመጠቀማቸውን አስረድቷል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 5፣ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 64፣ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 117 መሠረት ደግሞ ለጉዳዩ ደንብ የማውጣት ሥልጣን ያለው አካል ተለይቶ የተቀመጠ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ ደንብ ቁጥር 139/1999 ወጥቷል፡፡ በዚህ ደንብ ደግሞ ለጉዳዩ አፈፃጸም መመሪያ ባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት መመሪያ ለማውጣት የሚችልበት አግባብ ያለ ስለመሆኑ አንቀጽ 22 የሚያስቀምጥ ሲሆን ደንቡን ተከትሎ ደግሞ መመሪያ ቁጥር 46/1999 ተብሎ የሚጠቀስ መመሪያ በሥራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህም መሠረትም ተጠሪ መሥሪያ ቤት ግብር ከፋይ የሆነውና አመልካች በውክልና የሚያስተዳድሩት የሆቴል ድርጅት ሕጋዊውን የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ገዝቶ እንዲጠቀም በሚገባ ያሳወቃቸው ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የተገለፀላቸው ጊዜ አልፎ ሕጋዊውን የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ሳይጠቀሙ ሕጋዊ ያልሆነውን ሲጠቀሙ መገኘታቸው ከተረጋገጠ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 በአዋጅ ቁጥር 609 እንደተሻሻለው በአንቀጽ 50(መ) መሠረት ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል፡፡ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገቢውን ጥረት ሲያደርጉ ነበር፣ መሳሪያውን ገዝተው እንዲጠቀሙ የተሠጣቸውና የወንጀል ድርጊቱ ተፈፀመ የተባለበት የጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም. መቀራረብ ሲታይ የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም የሐሳብ ክፍሉ አልተሞላም ለማለት የሚያስችልበት ምክንያት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አመልካች በሁለተኛው ክስም ጥፋተኛ ተብለው መቀጣታቸው የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

በአመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195((2(ለ-2)) መሠረት ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48628

ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ በርሄ ሐጐስ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የስር ከሣሽ /ያሁን የሰበር አመልካች/ በስር ተከሣሽ /በሰበር ተጠሪ/ ያቀረበው ክስ ተከሣሹ ንብረትነቱ የራሱ በሆነው ኮድ3-29644 አይሱዙ የጭነት መኪና 56 ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ጭኖ ከጨርጨር ወደ መቀሌ ከተማ በ26/4/2001 ዓ.ም ምሽት 3፡30 ሲጓዝ እጅ ከፍንጅ በመያዙ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/1/ ተላልፎ በመገኘቱ ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሣሹም ፍ/ቤት ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉ ሲጠየቅ ወንጀሉን አለመፈጸሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የስር የትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከቀረቡት የግራ ቀኙ ማስረጃዎች አንጻር ከመረመረ በኋላ ከሣሹ ጠቅሶ ክስ ያቀረበበትን የወንጀል አንቀጽ 64/1/ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 113/2/ መሠረት ለውጦ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 ስር ጥፋተኛ ነው በማለት ተከሣሹ በ3 ዓመት ቀላል እስራትና በ5000 ብር መቀጮ እንዲቀጣ ፣ የተያዘው 56 ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ለመንግስት ገቢ እንዲሆንና መኪናው ለተከሣሽ እንዲመለስ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የይግባኝ ባዩን /የስር ከሣሽን/ ይግባኝ በመሠረዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/1/ ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡

በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ ቅር የተሰኘው የአሁኑ አመልካችም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 ያሻሻለው አዋጅ ቁጥር 365/95 አንቀጽ 64/4/ ተጠሪው በራሱ መኪና በህግ የተከለከለውን 56 ቦንዳ ጭኖ በመገኘቱ ክስ ተመስርቶበትና በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ተጠቅሶ ክስ ከቀረበበት የህግ አንቀጽ መንፈስ ወጪ መኪናው ለተጠሪ ይመለስ ተብሎ የተወሰነው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የተፈጸመው የህግ ስህተት ታርሞ መኪናው ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሰበር ቅሬታው ተጠሪው በሰጠው መልስ አመልካች በ24/6/2001 ዓ.ም ለስር ትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ወንጀሉ ብቻ የሚመለከት እንጂ አሁን ቅሬታ የቀረበበት መኪና ይወረስልኝ በሚል አይደለም፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም በተጠሪ አሸከርካሪነት 56 ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ጭኖ የተያዘው መኪና ለመንግስት ገቢ ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ጠቅሶ ክስ ያቀረበበትን አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ ከግራ ቀኙ ማስረጃዎች አንጻር ሲመረመር ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የለውም በሚል በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 ስር ጥፋተኛ ነው ብሏል፡፡ በዚህ አንቀጽ ጥፋተኛ የተደረገ ሰው ደግሞ የተያዘበት ዕቃ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊከፍል ከሚገባው ጠቅላላ የቀረጥና የታክስ ሂሣብ በማያንስ የገንዘብ መቀጮና ከሶስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን የስር ፍ/ቤት እንዳረጋገጠው ያሁኑ የሰበር ተጠሪ ንብረትነቱ የራሱ በሆነው አይሱዙ የጭነት መኪና የተጠቀሰውን የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ እጅ ከፍንጅ ተይዟል፡፡ በዚህ የወንጀል ድርጊትም በአዋጁ የማጓጓዝ ሀላፊነት የሚያስከትለውን ግዴታ በመጣሱ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያለው እንደ ስር ፍ/ቤቶች አተረጓጐም አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 ሣይሆን የተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 64/4/ ነው፡፡ የተጠሪው ድርጊት በአንቀጽ 64/4/ የሚሸፈን ከሆነ ደግሞ የሚወረሰው በኮንትሮባንድ የተያዘ ዕቃ ብቻ ሣይሆን የዕቃው ማጓጓዣ /መኪና/ ጭምር ነው፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አመልካችን ጠቅሶ ክስ ያቀረበበትን የህግ ቁጥር ያለአግባብ በመለወጥ ጥፋተኛ ነው በማለት የቅጣት ውሣኔ ያስተላለፉበት የህግ ቁጥር የማጓጓዣ ሀላፊነት ግዴታ ጥሶ ለተገኘው ለመጓጓዣው ባለቤት ተፈጻሚነት የሌለው በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የስር የትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 10/12117 በቀን 24/10/2001 በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት በመ/ቁ 33108 በቀን 06/12/2001 ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽለዋል፡፡
2. የሰበር ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ ስር ጥፋተኛ ነው ብለን ወስነናል፡፡ ቅጣትን በሚመለከት የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በ3 ዓመት ቀላል እስራትና በ5000 /አምስት ሺህ/ መቀጮ ተጠሪው እንዲቀጣ የወሰነው በአግባቡ በመሆኑ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ተጠሪው ጥፋተኛ የተደረገበት አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ የኮንትሮባንድ ዕቃ የጫነው ማጓጓዣ ጭምር እንዲወረስ የሚደነግግ በመሆኑ በተጠሪ አሽከርካሪነት የተያዘው የተጠሪ ኮድ 3-29644 አይሱዙ የጭነት መኪና ተወርሶ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ወስነናል፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

እ.ከ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 57100

ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጅማ ቅ/ጽ/ቤት ነገረ ፈጅ - ምህረቱ ቁምላቸው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ አዳለ ሰይድ

2. ፍሮሚሲስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ካቀረበው የቀደምትነት ባለመብት ክርክር ጋር የተያያዘው ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግስት በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ድርሻው እንዲሰጠው በመክሰስ ካስወሰነ በኋላ በአፈጻጸም መዝገብ የ2ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነው ክሊንክ ተሸጦ የአፈጻጸም ድርሻ እንዲሰጠው በታዘዘው መሠረት ሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ገዢ ባለመቅረቡ የፍርድ ባለመብት /1ኛ ተጠሪ/ ንብረቱን ለመረከብ ጥያቄ አቅርቦ እያለ የአሁን አመልካች ጣልቃ ይግባ፡፡ የአሁን አመልካች በ09-2-2002 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ 508,564.67 ብር የግብር እዳ ከአፈጻጸም ተከሣሽ /ከአሁን 2ኛ ተጠሪ/ ላይ ስላለን በግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት የቅድሚያ መብት ስላለን የቅድሚያ መብታችን እንዲከበር የሚል ነበር፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች /የአሁን አመልካች/ ከላይ እንደተመለከተው ያመልክቱ እንጅ በአዋጅ ቁ. 286/2002 አንቀጽ 78/1/ መሠረት የባለዕዳውን መያዝ የሚችለው ንብረት አፈጻጸም ላይ ከሌለ እና በዋስትና ያልተያዘ ከሆነ በመሆኑና ከላይ የተጠቀሰው ንብረት ደግሞ በአፈጻጸም ላይ ስላለ የጉምሩክ ጽ/ቤት የቀደምትነት መብት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ብሎ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት አጽንቶታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን በቀን 08/10/2002 ዓ.ም በ2 ገጽ በተጻፈ ማመልከቻ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት አመልካች ለግብር ዕዳ ሲጠየቅ ዋስትና ከተሰጣቸው አበዳሪዎች /ባንኮች/ ተከትሎ የቅድሚያ መብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው ስለመሆኑ እየታወቀ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የሌለውና በሶስተኛ ወገን የሚገኙቱን ንብረቶች ለማስለቀቅ የተደነገገውን የአዋጁን አንቀጽ 78/1/ በመጥቀስ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ 1ኛ ተጠሪ በቀን 20-4-2003 ዓ.ም በ3 ገጽ እና 2ኛ ተጠሪ ተወካይ በቀን 20-4-2003 ዓ.ም በ2 ገጽ በመጻፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሰጡት መልስ ፍሬ ሃሣብ በአጭሩ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ጥያቄ የዘገዬና ንብረቱንም በጊዜያዊነት እንዲያስተዳድር ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ የቀረበ ከመሆኑም በላይ የቀድምትነት መብት አይገባውም የሚል ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች አቅርቦት የነበረው የቀደምትነት መብት ውድቅ ተደርጐ የተወሰነው ውሣኔ አግባብ ባለመሆኑ ተሽሮ የአመልካች የቀደምትነት መብት እንዲከበር በማለት መልሷል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

በግራ ቀኝ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል አመልካች በአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት በሌላው ሰው ገንዘብ ጠያቂነት በተያዘ ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት አለው ወይስ የለውም የሚል ጭብጥ በመሆኑ ከዚሁ አኳያ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሁለተኛ ተጠሪ /ፎሮምሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር/ በገንዘብ ጠያቂነት ወይም ድርሻውን ለማስከራል እንደሆን አላከራከረም፡፡ በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተጠሪ /ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ላይ/ ያቀረበው የአፈጻጸም ክስ በሚመለከተው ንብረት ላይ ቀድሞ በዋስትና ያልተሰጠው ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡

ይሄንን መሠረታዊ ሃሣብ ይዘን የአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

“ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር ተከፋይ ከሚሆንበት አንስቶ ተከፍሎ እስካለቀበት ጊዜ ድረስ ግብር የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሃብት ላይ ባለስልጣኑ ከማናቸውም ሌሎች ዕዳዎች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል፡፡” የሚል ነው፡፡

ከዚህ አንቀጽ በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው ከአመልካች ሊቀድም የሚችለው በዋስትና ቀድሞ የተያዘ ከሆነ ብቻ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በተመለከተው አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 78/1/ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነቱን ስንመረምር የግብር ከፋይ ንብረት የሆነ በሌላ ሶስተኛ ወገን ሲገኝና በግብር አስገቢው ባለስልጣን እንዲያስረክበው ሲጠየቅ የማስረከብ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑና የማያስረክብበት አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለው በአፈጻጸም ላይ ስለመሆኑ በመግለጽ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡ ይሄ አንቀጽ ከተያዘው ጉዳይ ጋር በቀጥታ አግባብነት ያለው ባይሆንም አንቀፁ ሊደነግግ ያሰበው ንብረቱን ለመረከብ ሲፈልግ መከተል ያለበትን ስነ ሥርዓት ከመደንገግ አኳያ በመሆኑ የቀደምትነት መብትን ቀሪ የሚያደርግ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ በአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት አመልካች ያቀረበው የቀድምትነት መብት በዚሁ አንቀጽ መሠረት ታይቶ መወሰን ሲገባው ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለውን የአዋጁን ሌላ አንቀጽ በመጥቀስ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉና የይግባኝ ሰሚውም ፍርድ ቤት ይሄንን ሣያስተካክል ውሣኔውን ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግስት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 10/86 በቀን 18-2-2002 ዓ.ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 89407 በቀን 05-9-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች የጠየቀው የግብር ዕዳ በአዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/ መሠረት ከአንደኛ ተጠሪ የቀደምትነት መብት አለው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አለ. መሀመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐቃቤ ህግ ገብረሚካኤል ወልዴ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አንተነህ ካሣዬ - አልቀረቡም

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን አመልካች በአሁኑ ተጠሪና በሌላ የእቃው ባለቤት በተባለ ግለሰብ ላይ በቀረበው ክስ የወንጀል ህግ ቁ 32/1/ሀ/ እና የገቢዎችና ጉምሩክ አዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 91/2/ በመተላለፍ የጉምሩክ ስነ - ሥርዓት ያልተፈፀመባቸውን የተለያዩ አልባሣት ባጠቃላይ ለመንግስት ሊከፍል የነበረው ቀረጥ እና ታክስ 26,576 ብር ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-04051 ደሕ የሆነ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለቤትና ሹፌር በመሆኑ የተከሠሠ ሆኖ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በተከሠሠበት የህግ አንቀጽ ጥፋተኛ አድርጎታል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የደቡብ ክልል የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በተከሠሠበት አንቀጽ ጥፋተኛ ካደረገው በኋላ የአሁኑ ተጠሪ በ7/ ሰባት/ ዐመት ፅኑ እሥራት እና በ5000/አምስት ሺህ / ብር እንዲቀጣ በመወሰን ከላይ የተመለከተው ተሽከርካሪ ለባለቤቱ እንዲመለስ ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ያስቀርባል በማለት ሲመለከተው ከቆየ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 195/2/ ለ/ 2/ መሠረት አፅንቶታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በቀን 21/5/2003 ዓ.ም በ2 ገፅ በመፃፍ ያቀረበው የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ፡- ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት አዋጅ ቁ 622/01 አንቀጽ 91/2/ ስንመለከት የእሥራትና የገንዘብ መቀጫው ሊጣል የሚችለው ወንጀሉ የተፈፀመበት ዕቃና መሣሪያ እና የወንጀሉ ፍሬ መወረሱ እንደተጠበቀ መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ፣ ተጠሪ ደግሞ የመኪናው ባለቤትና በወቅቱ ሹፌር መሆኑን ራሱም ከማመኑ በተጨማሪ በማስረጃም የተረጋገጠ ሆኖ ሣለ ዕቃውን ሲያጓጉዝ የነበረው የተጠሪ መኪና እንዲወርስ መታዘዝ ሲገባው መታለፉ ያለአግባብ በመሆኑ፣ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 104/1/ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሠጠ ተጨማሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትዕዛዝ መስጠት ሣያስፈልግ ዕቃው ወይም ማንጓጕው እንዲወረስ ይደረጋል በማለት የደነገ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ የሠጡ ቢሆንም ተሽከርካሪው እንዲወርስ ባለማዘዛቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀሙ በመሆኑ፣ ተጠሪ በቀጥታ በወንጀሉ ተሣታፊ በመሆኑ መኪናውን ከመወረስ የሚያስቀር አግባብ ሣይኖር የሥር ፍ/ቤቶች መኪናው ለባለቤቱ ይመለስ በማለት የሠጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ግንቦት 08 ቀን 2003 ዓም በ4 ገፅ ፅፎ ያቀረበው የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካች የጠቀሳቸው የህግ አንቀጾች የተገለፀው ተሽከርካሪ እንዲወርስ የሚደነግግ አይደለም ፣ በተጠቀሰው አዋጅ 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ዕቃና መሣሪያ የሚለው በእንግሊዝኛው /goods & equipment / ተብሎ የተተረጎመ በመሆኑ መኪናን አይጨምርም፣ የተላለፍኩት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ባለመኖሩ መኪናው ሊወረስ አይገባም ፣ የቀረበው ክስ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 91/2/ በመሆኑ እና በአዋጅ አንቀጽ 104/1/ መሠረት መኪናው እንዲወርስ የቀረበብኝ ክስ ሣይኖር የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ስለሌለው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም፡- በወንጀል ክሱ የተመለከተውን የኮንትሮባንድ ዕቃ ስታጓጉዝ የተገኘችው የተጠሪ መኪና ልትወርስ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግንተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት እንደሚከተለው ተመርምሮአል፡፡ ተጠሪ ስያሽከረክረው የነበረው መኪና ኮድ ቁ 3-04051 ደሕ የሆነ የህዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ የራሱ የግል ንብረት የሆነ መሆኑ፣ ሁለተኛ ተከሣሽ በነበረና በመኪናው የተሣፈረ ሰው የተጫነ የኮንትሮባንድ ዕቃ ለመንግስት ሊከፈል የሚገባ ታክስ እና ቀረጥ ከ21,791.66 ብር ያልተከፈለበት ሲያጓጉዝ በፖሊሶች መያዝ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጠው ከመሆኑም አልፎ የጥፋተኝነት ውሣኔ እና ቅጣት በተጠሪ ላይ የተጣለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚሁ ፍርድ ቤት የተሠጠው የጥፋተኝነት ፍርድ እና ቅጣት ስለመለወጡ በተጠሪ በኩል የተመለከተ ነጥብ የለም፡፡

የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁ 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የህግ ስህተት ማረም በመሆኑ ማስረጃን የመቀበል እና የመመዘን ሥልጣን የበታች ፍርድ ቤቶች ሥልጣን በመሆኑ በዚህ ረገድ /በፍሬ ነገር / በበታች ፍርድ ቤት የተደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይሄ ከሆነ ደግሞ በተጠሪ ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት ውሣኔ በተሽከርካሪው መወረስ አለመወረስ ጋር ተያይዞ የሚያስከትለው ውጤት ምን እንደሆነና የበታች ፍርድ ቤቶች መኪናው ለባለቤቱ /ለተጠሪ/ ይመለስ ማለታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የኮንትሮባንድ ወንጀል በአዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ወንጀሉ የተፈፀመበት ዕቃ ፣መሣሪያ እንደዚሁም የወንጀሉ ፍሬ የሚወረስ መሆኑ እና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2/1/ ሥር ዕቃ ለሚለው ቃል ተንቀሣቃሽ ንብረት /መኪና/ በመጨመር ከመደንገጉም በላይ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 104/1/ መሠረት ደግሞ የተሽከርካሪ ባለቤትና ሹፌር ሆኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ሲያሽከረክር በተፈፀመ የኮንትሮባንድ ወንጀል ጥፋተኛ መባሉ ተጨማሪ ትዕዛዝ መስጠት ሣያስፈልግ ወይም ተጠሪ እንደሚከራከረው በአመልካች ላይ ሌላ ክስ ማቅረብ ሣያስፈልግ መንገዣቸው እንዲወረስ መታዘዝ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሄ ከሆነ ጉዳዩን በመጀመሪያ የወንጀል ክሱን የተመለከተው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሲሠጥ ወንጀሉ የተፈፀመበትን የተጠሪ ተሽከርካሪ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማዘዝ ሲገባው ለባለቤቱ ይመለስ ማለቱ የአዋጁን ግልፅ ድንጋጌ ፣ ዓላማና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔ/ብ/ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ 39555 በቀን 24/3/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 12612 የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 195/2/ መ/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. በተጠሪ ስመንብረት ተመዝግቦ የሚገኘው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-04051 ደሕ የሆነች ህዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ የኮንትሮባንድ ወንጀል የተፈፀመበት ተሽከርካሪ በመሆኗ በመንግስት እንድትወርስ በማለት ታዟል፡፡
3. ተጠሪ የተሠጠውን ውሣኔ እንዲያውቀው በአርባ ምንጭ ማረሚያ ቤት በኩል ይተላለፍላቸው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 58266

ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ደሴ - ከጠበቃቸው በላቸው ታደሰ ጋር - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የጉምሩክ ዐ/ሕግ ታደለ ተስፋዬ - ቀረቡ

መዘገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በዚህ በተያዘው ጉዳይ በሁለት ተከሣሾች ላይ ክስ አቅርቦባቸው የነበረ ሲሆን 1ኛ ተከሣሽ ያሁኗ አመልካች ናት፡፡ የክሱ ፍሬ ቃልም ተከሣሾች የወ/ሕ/ቁ/32/1/ሀ/ እና የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው አንቀጽ 73/1/ሀ/ለ/ በመተላለፍ 1ኛ ተከሣሽ በዲክላራሲዮን ሴሪ ቁጥር 31701 ተመዝግቦ ከቀረጥ ነፃ ያስገባችውን የሴለዳ ቁጥሩ ኮድ 2.76388 አ.አ ሱዚኪ መኪና ለ2ኛ ተከሣሽ አሳልፋ በመስጠት እንዲሁም አቶ ጥላሁን አበበ የተባለው ግለሰብ ከወጋገን ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ ለተበዳሪው ገንዘብ መኪናውን በዋስትና በማስያዝ በህግ ከተፈቀደው ውጪ ለሌላ ሰው አገልግሎት እንዲውል አድርጋለች፤ 2ኛ ተከሣሽ መኪናውን እያሽከረከረ የካቲት 06 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ 6፡00 ብሔራዊ ትያትር አካባቢ በመገኘቱ ሁለቱም ተከሣሾች ከቀረጥ ነፃ የገባውን መኪና አለአግባብ ሲገለገሉ ተገኝቷል የሚል ነው፡፡

1ኛ ተከሣሽ ወንጀሉን አለመፈፀሟንና ጥፋተኛ አለመሆኗን ክዳ በመከራከሯ የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የከሳሽንና የ1ኛ ተከሳሽን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተከሳሿ ከቀረጥ ነፃ የገባውን መኪና መብቱ ከተሰጠበት ፈቃድ ውጪ ለሌላ ሰው አገልግሎት እንዲውል ማድረጓ በበቂ ማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ተጠቅሶ ክስ በቀረበባት አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው አንቀጽ 73/1/ሀ/ ሥር ጥፋተኛ ናት ሲል በመወሰን በመኪናው ላይ የሚፈለገውን ቀረጥ ብር 100,489.37 /አንድ መቶ ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ከሰላሣ ሰባት ሳንቲም/ መቀጮ እንድትቀጣ በሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-76388 አ.አ የሆነው መኪናም ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ እንዲሁም በ6 ወር እሥራት እንድትቀጣና የእሥራቱ ቅጣት ቢፈፀሙ በምታስተዳድራቸው ልጆች ላይ ከሚደርሰው ጉዳት አኳያ የእሥራቱ ቅጣት ተገድቦ ለተከሣሽ የፈተና ጊዜ ቢሰጥ ፍ/ቤቱ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል በማለት ስለመልካም ጠባይ ብር 5000 /አምስት ሺህ/ ዋስትና ስታቀርብ ቅጣቱ ሳይፈፀም ታግዶ እንዲቆይ ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሣሽዋም በሥር የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ብታቀርብም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/195/2/ለ/2/ መሠረት የሥር የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታም በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ሲሆን በዋናነት የዘረዘራቸው የቅሬታ ነጥቦች አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለው አንቀጽ 73/1/ከቀረጥ የገባ ዕቃ ለሌላ ሰው ያስተላለፈ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት እንዲውል ያደረገ ሰው የሚጠየቅበት ሕግ ሲሆን "ማስተላለፍ" የሚለው ቃል በአዋጁ ትርጉም አልተሰጠውም ፡፡ በመሆኑም በፍ/ሕ/ቁ 1186/1/ ንብረት የገዛ ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘው ወይም በኑዛዜ የተሰጠው ሰው ንብረቱን እጁ ባደረገ ጊዜ የተላለፈ ይሆናል በሚል ስለሚደነግግ እንደሁም ስለመያዣ በፍ/ሕ/ቁ/ 2834/1/ በመያዣ ውል ውስጥ በዕቃው ላይ ባለመብት የሚሆነውን ለይተው ካልተዋዋሉ በቀር አስያዥ በመያዣነት ለሰጠው ዕቃ ባለቤት ሆኖ ይቆያል የሚል በመሆኑ አመልካች መኪናውን በተባሉት መንገዶች ይዞታውንም ሆነ ባለቤትነት መብት ያላስተላለፍኩ ስለሆነ በወንጀል ሕግ መከሰስ አይገባኝም ነበር፣

- መኪናው ከባንክ ለተሰጠው ብድር ለብር 90,000 በዋስትና የተያዘ ቢሆንም ለመኪናው ያልተከፈለ ገንዘብ ደግሞ ብር 100,489.73 በመሆኑ በልዩነትም ብዙ የሚተርፍ ገንዘብ በመኖሩ አመልካች የጉምሩክ ቀረጥ ለማስቀረት አስቤ ያደረግኩት ነገር ባለመሆኑ ድርጊቱ በወንጀል ሕግ ቁጥር 23 መሠረት የወንጀልን ድርጊት ከሚያቋቁሙት ግዙፍ ተግባራት የሐሳብ ክፍሉን አላሟላም

በመሆኑም ወንጀል በሌለበት ቅጣት አይኖርም፡፡

- መኪናውን ስያሽከረክር የነበረው የእህቱ ልጅ / 2ኛ ተከሣሽ የሆነው/ ሲሆን በጊዜው አይኔን አሞኝ ስለነበር እንዲይዝልኝ ያደረግኩ በመሆኑ ይኸው ድርጊት "ማስተላለፍን" አያሟላም
- ከቀረጥ ነፃ የገባው መኪና አለአግባብ ተገለገለ ቢባል እንኳን የጉምሩክ መ/ቤት መመሪያ ቁጥር 46/2002 አንቀጽ 7 መሠረት የቀረጥና የታክስ 25% መቀጫ በማስከፈል መኪናው ለአመልካች መመለስ ሲገባው እንዲወረስ ማድረጉ ሕግን የሚቃረን ነው የሚሉ ናቸው

ለሰበር ቅሬታ ተጠሪው በሰጠው መልስ የቀረጥ ነፃ መብት ያለተጠያቂነትና ያለገደብ የተሰጠ አይደለም፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 60/89 እና 368/95 እንደተሻሻለ አንቀጽ 73 ከቀረጥ ነፃ የገባን መኪና መብቱ ከተሰጠበት አላማ ውጪ አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ የተከለከለና የወንጀል ሀላፊነትን የሚያስከትል ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ከአዋጅ ቁጥር 60/89 እና አዋጅ ቁጥር 368/95 እንደተሻሻለው አንቀጽ 73/2/ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 98/2/ የተደነገገውን በመተላለፍ መኪናውን እንዲያሽከረክር ላልተፈቀደለት ሰው አሳልፋ ሰጥታለች፡፡ ይኸው የሥር 2ኛ ተከሣሽም መኪናውን ሲያሽከረክር መገኘቱን በሥር ፍ/ቤት ባቀረብነው ማስረጃ አረጋግጠናል፡፡ ከዚህ ሌላ አመልካች ከቀረጥ ነፃ የገባውን መኪና ለባንክ መያዣነት በመስጠት የብድር አገልግሎት አግኝታለች፡፡ አመልካች ይደግፈኛል በማለት የጠቀሰችው የጉምሩክ መመሪያ ቁጥር 46/2002 ሥራ ላይ የዋለው ከግንቦት 13 ቀን 2002 ጀመሮ ሲሆን አመልካች ጥፋተኛ ነው ተብላ ውሣኔ ከተሰጠ ከአንድ ዓመት በኋላ የወጣ በመሆኑ አግባብነት ያለው አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቶ መዝገቡ እንዲዘጋ ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም የሥር ፍ/ቤቶች የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አመልካችን ጥፋተኛ በማድረግ የቅጣት ውሳኔ ያስተላለፈባት በአዋጅ ቁጥር 60/89 እና 368/ 95 እንደተሻሻለ አንቀጽ 73/1/ሀ/ ሲሆን አንቀጹም ማንኛውም ሰው ከቀረጥ ነፃ፣ በቅናሽ ቀረጥ ወይም በጊዜያዊነት ከቀረጥ ነፃ የገባን ዕቃ አዋጁን በሚቃረን መልኩና የቀረጥ ነፃ መብት ከተሰጠበት ምክንያት ውጪ መጠቀም እንደማይችል ይናገራል፡፡ በተጠቀሰው ሕግ አንቀጽ 73/1/ሀ/ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ዕቃዎችን፣ የገዛ ፣የተቀበለ፣ ያስተላለፈ ፣ የተገለገለ፣ አሳልፎ በሌሎች ሰዎች ግልጋሎት እንዲውል ያደረገ ሰው ደግሞ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 በፊደል “ለ” በተዘረዘሩት ቅጣቶች የሚቀጣ ይሆናል፡፡

አመልካችም ከቀረጥ ነፃ ያስገባችውን መኪና በአዋጁ መሠረት መጠቀም ሲገባት ለሥር 2ኛ ተከሣሽ አሳልፋ መስጠቷንና ይኸው ተከሣሽም ሲያሽከረክር መገኘቱን እንዲሁም በዋስትና አስይዛ ከባንክ ብድር ማግኘቷን በሥር ፍ/ቤት የፍሬ ነገር ክርክር በሚደረግበት ጊዜ መረጋገጡን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ያመለክታል፡፡

በመሆኑም በሥር ፍ/ቤት አመልካች አዋጁን በሚቃረንና የቀረጥ ነፃ መብት ከተሰጠበት ምክንያት ውጪ መሥራቱን በማረጋገጥ በአዋጅ ቁጥር 60/89 እና 368/95 እንደተሻሻለ አንቀጽ 73/1/ ሥር ጥፋተኛ ናት ሲል በሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

ቅጣትን በሚመለከት የሥር ፍ/ቤት አመልካች ለመኪናው ሊከፈል በሚገባ የቀረጥ ሂሳብ መጠን በገንዘብ መቀጮና በ6 ወር እሥራት እንድትቀጣና መኪናውም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የወሰነው መሠረታዊ የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችን የተከተለና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/181633 በቀን 12/10/2001 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ እና በተጠቀሰው መዝገብ በቀን 15/10/2001 ዓ/ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/195/2/ለ/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/82371 በቀን 18/8/2002 የሰጠው ፍርድ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/195/2/ለ/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 60400

12/11/2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሞያሌ ቅርንጫፍ ተወካይ አቶ ዳሉ አብዶ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ኤፍታታ እና ቢ ኤም ኤም ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ከሣሽ የነበረ ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱም ከሣሽ ባለኝ የውጪ ንግድ ፈቃድ መሠረት 400 ኩንታል ቦሎቄ ግምቱ ብር 300,000 የሚሆነውን ወደ ኬኒያ ለማሻገር እንዲያስችለኝ ተከሣሽ መ/ቤት ተገቢውን የጉምሩክ ሥርዓት እንዲፈጽምልኝ በ13/04/2002 ዓ/ም ከቀኑ በግምት ከ7፡00 - 8፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ መኪናው እንደጫነ ወደ ተከሣሽ መ/ቤት ሳቀርብ ተከሣሽም በ15/4/2002 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ያልተሟሉ ነገሮች ማለትም የባንክ ፈቃድ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ የመሳሰሉትን አሟልቼ እንድቀርብ በማስታወቁ ከሣሽም ከተጠየቁት ነገሮች ውስጥ የባንክ ፈቃድ ብቻ አለመያዜን በመግለፅ መኪናው እንደጫነ በማቆም ወደ አዲስ አበባ የተመለስኩ ሲሆን ተከሣሽም በመሃሉ ኮንትሮባንድ ነው በሚል ከመኪናው በማራገፍ ስለከለከለኝ በፍ/ህ/ቁ 2028 እና 2031 መሠረት የጉዳቱን ዋጋ (9%) እና የጠበቃ አበል 10% እንዲከፍል ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሣሽም ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ ቦሎቄውን ወደ ተከሣሽ መ/ቤት ያቀረበውም የጉምሩክ ሥርዓት ለማስፈፀም ሲሆን ምርቱን ወደ ውጪ ለመላክ ፈቃድ ያለው ከመሆኑም ሌላ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ በጊዜው የነበረው ቢሆንም እነዚህን ነገሮች ብቻ መያዝ በቂ ባለመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 12 እና 13 ሥር የተገለፁ ነገሮች ሁሉ ተሟልተው መቅረብ ያለባቸው ሆኖ እያለ ከሣሽ በህጉ መሠረት ሳያሟላ ቦሎቄው በጉምሩክ ጠረፍ ውስጥ ገብቶ ስለተገኘ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2/42/ እና 9/1/ ሥር የተጠቀሰው መሠረት ኮንትሮባንድ ነው በሚል ተከሣሽ መያዙ በአግባቡ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ያከራከረው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትም በሰጠው ውሣኔ ተከሣሽ የያዘው ንብረት /ቦሎቄ / የተከለከለ ካለመሆኑም ሌላ ከሣሽ ህጋዊ በሆነ ሁኔታ የላኪነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፈቃድ ኖሮት የንግድ ሥራውን የሚያከናውን ሆኖ እያለ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለመፈፀም ያልተሟሉ ነገሮች ካሉ እንዲሟሉ ከማድረግ በቀር ቦሎቂውን ኮንትሮባንድ ነው ብሎ ተከሣሽ መያዙ ያለአግባብ ነው በማለት የተያዘው 400 ኩንታል ቦሎቂ ለከሣሽ እንዲመለስ ብሏል፡፡

የአሁኑ የሰበር አመልካችም በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርብም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዝጋቱ አመልካች በሥር ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

አመልካች በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡- ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2/17/ ፣ 12/4/ እና 13/1/ መሠረት አስፈላጊ ከሆኑ ሠነዶች አንድም ሳያመጣ የጉምሩክ ጠረፍ አቋርጦ ወጥቶ እያለ የተያዘውን ቦሎቂ ኮንትሮባንድ አይደለም መባሉ ህግን መሠረት ያደረገ አይደለም ፣ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን ዕቃ ከጉምሩክ ጠረፍ ማቋረጥ ይችላል መባሉ ተገቢነት የለውም፣

የአመልካች ጽ/ቤት የጉምሩክ ጠረፍን በማቋረጥ ከጉምሩክ ክልል ውጪ ከኬኒያ ድንበር 100 ሜትር በማይደርስ ርቀት የሚገኝ ሲሆን የጉምሩክ ሥነ ሥርዐት በአንድ ዕቃ ላይ መፈፀሙንና አለመፈፀመን የሚረጋገጥበት ቦታ እንጂ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የሚፈፀምበት ባለመሆኑ አመልካች መ/ቤት ተጠሪው ያልተሟሉ ሠነዶችን እስኪሚያመጣ ድረስ መጠበቅ ነበረበት መባሉ ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው ለሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ በማንኛውም መስፈርት በህጋዊ መንገድ ወደ ውጪ ሊላክ የነበረው ቦሎቂ ኮንትሮባዱ ነው ሊባል የሚችልበት ሁኔታ ስለሌለ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የቀረበ ሲሆን እኛም ተጠሪው ወደ ውጪ ሊልክ በአመልካች የተያዘው ቦሎቂ ኮንትሮባንድ ባለመሆኑ አመልካች ይመልስ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ? ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ተጠሪው ወደ ውጪ ሊልክ የነበረውን ቦሎቂ ኮንትሮባንድ ነው በማለት በዋናነት የሚከራከረው በአዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 2/17/ ፣ 12/4/ እና 13/1/ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ተጠሪው አሟልቶ ባለመገኘቱ ነው፡፡ እነዚህን አመልካች አልተሟሉም የሚላቸውን ሁኔታዎች ከመመርመራችን በፊት በተጠቀሰው አዋጅ ስለኮንትሮባንድ ወንጀል የተደነገገውን የአንቀጽ 91/1/ ይዘት መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ በተጠቀሰው አንቀጽ መሠረት ማንኛውም ሰው በአዋጅ ቁጥር 622/2001 ወይም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚያስፈጽማቸውን ሌሎች ህጐች ወይም በእነዚሁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ የተከለከሉ፣ ገደብ የተደረገባቸው ወይም የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመባቸውን ዕቃዎች ወደ ጉምሩክ ክልል ካስገባ ወይም ከጉምሩክ ክልል ካስወጣ ወይም በህጋዊ መንገድ የወጡ ዕቃዎችን በህገወጥ መንገድ መልሶ ካስገባ ወንጀሉ የተፈፀመባቸው ዕቃዎችና መሳሪያዎች እና የወንጀሉ ፍሬ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጮና ከሰባት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል ይላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ ድንጋጌ መንፈስ መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ዕቃ ኮንትሮባንድ ነው ለማለት ዕቃው ወደ ጉምሩክ ክልል እንዳይገባ ወይም እንዳይወጣ በህግ የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ሊሆን ይገባል፡፡ እንዲሁም ከድንጋጌው መገንዘብ እንደሚቻለው የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ማስገባት ወይም ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት ዕቃው ኮንትሮባንድ እንዲባል የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የኮንትሮባንድ ወንጀልን የሚያቋቁም ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ድንጋጌው በህጋዊ መንገድ እንኳን የወጡ ዕቃዎችን በህገወጥ መንገድ ወደ ጉምሩክ ክልል ማስገባት እንደኮንትሮባንድ ወንጀል እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡

ይህንኑ የአንቀጽ 91/1/ መንፈስ ይዘን የአመልካችን ክርክር ስንመለከት አመልካች የተጠሪን ቦሎቄ የያዘው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ባለመፈፀሙ ሲሆን የያዘውም በጽ/ቤቱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ወደ ጉምሩክ ጽ/ቤት በመምጣቱ ኮንትሮባንድ ነው ተብሎ እንደሚወሰድ አንቀጽ 91/1/ አይገልጽም፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ዕቃው ኮንትሮባንድ ነው ሊባል የሚችለው ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ወደ ጉምሩክ ክልል ሲገባ ወይም ከጉምሩክ ክልል ሲወጣ ነው፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 2/7/ መሠረትም የጉምሩክ ክልል ማለት የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ነው፡፡ በመሆኑም ዕቃው ኮንትሮባንድ ነው ለማለት አመልካች ተጠሪው በህገ ወጥ መንገድ ቦሎቄውን ከኢትዮጵያ ግዛት /ከጉምሩክ ክልል/ ሲያስወጣ መያዙን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን በአግባቡ ባላስረዳበትና እንዲሁም በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁኑ አመልካች ተጠሪው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለማስፈፀም ወደ አመልካች ጽ/ቤት ቦሎቄን ጭኖ እንደመጣ ፣ በጊዜው ተጠሪው የላኪነት ንግድ ፈቃድ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር / TIN/ ይዞ እንደነበር በማመን ሲከራከር ከቆየ በኋላ በሰበር ደረጃ የክርክሩን ጭብጥ በመቀየር ተጠሪው ከጉምሩክ ጠረፍ አቋርጦ ሲወጣ ተይዟል በማለት መከራከሩ እርስ በርሱ የሚጋጭ ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ጠቅሶ የተከራከረባቸው የአዋጅ ድንጋጌዎች ማለትም 2/17/ ፣ 12/4/ እና 13/1/ የተጠሪው ቦሎቄ ኮንትሮባንድ ነው ብሎ ላቀረበው ክርክር የሚረዱ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የአዋጅ አንቀጽ 2/17/ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ትርጉም የሚደነግግ ሲሆን አንቀጽ 12/4/ እና 13/1/ ደግሞ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በሚፈፀምበት ወቅት መሟላት የሚገባቸውን ሁኔታዎች ወይም ፎርማሊቲዎች የሚደነግጉ ናቸው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ወይም ፎርማሊቲዎች ተጠሪው አሟልቶ ካልተገኘ ደግሞ የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት በውሣኔው እንዳሰፈረው እንዲያሟላ ከሚደረግ ውጪ ቦሎቄውን ኮንትሮባንድ ነው ብሎ መውረስ ህግን የተከተለ አሠራር አይደለም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ቦሎቄውን ኮንትሮባንድ ነው በማለት የያዘው ያለአግባብ ነው በማለት ለተጠሪው እንዲመልስ በሰጡት ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05017 በቀን 14/12/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የሥር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 105644 በቀን 02/13/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች የወረሰውን 400 ኩንታል ቀይ ቦሎቄ ወይም በጨረታ የሸጠውን የቦሎቄ ዋጋ ለተጠሪ እንዲመልስ መወሰኑ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ ለሥር ፍ/ቤት ተላልፎ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - ባህር ዳር ቅርንጫፍ አቶ ዮሱፍ አብራ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ትዕግስት ጥላሁን - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ብሔራዊ ክልል የሰሜን ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት በሰበር ተጣርቶ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አራት መቶ ኩንታል ባቄላ ወደ ሱዳን ለመላክ የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ አሟልታ ባቄላውን ወደ ሱዳን ሳጓጉዝ ተከሣሹ ተጨማሪ ሰላሣ ኩንታል ባቄላ አግኝቻለሁ በሚል ሰበብ የያዘብኝ ስለሆነ ባቄላውን ዋጋ ሱዳን በምሸጥበት ዋጋ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች አራት መቶ ኩንታል ባቄላ የጉምሩክ ሥርዓት የተፈጸመበት ቢሆንም ይህንን ሸፋን በማድረግ ሰላሣ ኩንታል ባቄላ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ሣያሟሉ ወደ ሱዳን ለማሻገር ሲሞክሩ ተይዘዋል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ንብረቱን መያዝና መወረስ እንደምንችል በህግ የተደነገገ በመሆኑ የከሳሽ ክስ የህግ መሠረት የለውም፡፡ የባቄላውን ዋጋ መክፈል አለባችሁ የሚባል ከሆነም ባቄላው በሀራጅ የተሸጠ በመሆኑ በሀራጅ በሸጥንበት ዋጋ እንጅ ከሣሽ በጠየቁት መሆን የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ ወደ ሱዳን በመጓጓዝ ላይ ከነበረው ጭነት ውስጥ ሰላሣ ኩንታል ባቄላ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ሣይፈጸምበት ያገኘ ቢሆንም የጉምሩክ ፎርማሊቲ የተፈጸበትን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ መያዝና መውረስ አልነበረበትም በማለት አመልካች ብር 362,346.23 የባቄላው ዋጋና የሌሎች ወጭዎች ብር 21,236.23 አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያወጡትን ያተለያዩ ወጭዎች በማለት የወሰነውን ብር 21,236.23 ተገቢ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ብር 362,346.23 ለተጠሪ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የካቲት 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ 400 ኩንታል ባቄላ ሱዳን ወስደው ለመሸጥ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ካሟሉ በኋላ 430 ኩንታል ወደሱዳን ሲወስዱ መገኘታቸው በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የጉምሩክ ፎርማሊቲ የተሟላበትንና የጉምሩክ ፎርማሊቲ ያልተሟላበትን ባቄላ መያዝና መውረሳችን በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 በተደነገገው መሠረት የፈጸምነው ህጋዊ ተግባር ሆኖ እያለ አላግባብ በልጽጓል ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች የባቄላውን ዋጋ እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

አመልካች የመኪናውን ዋጋ ይመልስ ቢባል እንኳን ባቄላው በሀራጅ የተሸጠበትን ብር 141,556.95 መሆን ሲገባው በዶላር ሂሣብ በማስላት እንድንከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የጠበቃ አበልና ወጭና ኪሣራም አላግባብ ተወስኖብናል በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ወደ ውጭ እንዲልክ 168 ኩንታል ባቄላ ቀሪ አለኝ ይህ ከሆነ አመልካች የሰላሣ ኩንታል ታክስና ቀረጥ በማስከፈል ከተፈቀደልኝ 168 ኩንታል መቀነስ ሲገባው መውረሱ ህጋዊ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በስር ያላቀረበውን አዲስ ክርክር በሰበር ደረጃ ያቀረበ ስለሆነ ክርክሩ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 329/1/ መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በሚል ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 12 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ ዝርዝር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የቀረበው ክርክርና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች አላግባብ በልጽጓል በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2163 መሠረት በማድረግ አመልካች የአራት መቶ ኩንታል ባቄላ ዋጋ በዶላር ምንዛሬ ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አራት መቶ ኩንታል ባቄላ ወደ ሱዳን ለመላክ የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ አሟልተው ባቄላውን ወደ ሱዳን በሚያጓጉዙበት ጊዜ በጉምሩክ የመጨረሻ ጣቢያ ላይ ሲፈተሽ አራት መቶ ሰላሣ ኩንታል ባቄላ ተጭኖ መገኘቱን በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ያልተሟላበት ሰላሣ ኩንታል ባቄላ ተጠሪ የጫነች መሆኗ ስላልተረጋጠና ለዚህ ተጠያቂው ሹፌር ስለሆነ አመልካች ተጠሪ የጉምሩክ ቀረጥ የከፈለችበትንና አራት መቶ ኩንታል ባቄላ መወረሱ የህግ መሠረት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የህግ ትርጉም አዋጅ ቁጥር 60/89 መሠረታዊ ዓላማና አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ይዘት ያገናዘበ መሆኑን መርምረናል፡፡

ተጠሪ ወደ ሱዳን ለመላክ ከጫኑት ዕቃ ውስጥ አራት መቶ ኩንታል ባቄላ ተገቢው የጉምሩክ ሥርዓት ፎርማሊቲ የተሟላበት ሲሆን ከዚህ ጋር ተቀላቅሎ የተጫነው ሰላሣ ኩንታል ባቄላ ተገቢው የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ ሣይሟላ የተጫነ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ተጠሪ የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ አሟልተው ከጫኑት አራት መቶ ኩንታል ጋር በመቀላቀል ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ለማስወጣት ሲሞክሩ በመጨረሻው የጉምሩክ ጣቢያ በተደረገ ፍተሻ የተያዘ መሆኑን ነው፡፡ ከተጠሪ የጉምሩክ ሥርዓት አሟልተው ከጫኑት አራት ኩንታል ባቄላ ጋር ተቀላቅሎ የተያዘው ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ሊወጣ ሲል የተያዘ ዕቃ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 28 ኮንትሮባንድ ማለት ህጐችንና በህግ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ወደ አገር ውስጥ ለመግባት የመጀመሪያውን ከአገር ለመውጣት የመጨረሻውን የጉምሩክ ጣቢያ በማለፉ ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ማስወጣት እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ማድረግ መሞከር ወይም መርዳት ወይም እነዚህን የንግድ መጠን ያላቸውን ዕቃዎች መያዝ መሸጥ ማስተላለፍና በእነዚህ ዓይነት ድርጊቶች መተባበርን ጨምሮ መሆኑ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ተጠሪ ወደ ሱዳን አገር ለመላክ የጫኑት ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ተሟልቶ የተጫነ ዕቃና በኮንትሮባንድ ከአገር ለማውጣት የተጫነ ዕቃ አቀላቅሎ የያዘ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች በኮንትሮባንድ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር የመከላከልና በዚህ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎችንና መጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 5 ተሰጥቶታል፡፡ አመልካች የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ በማሟላት ተጠሪ የጫኑት አራት መቶ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ለማስወጣት ከተጫነው ሰላሣ ኩንታል ባቄላ ጋር ተቀላቅሎ ሲያገኘው በህጋዊ መንገድ ከአገር እንዲወጣ የተፈቀደውን ዕቃና በኮንትሮባንድ ሊወጣ የነበረውን ዕቃ መውረሱ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ህጋዊ ስልጣን ሥር የሚወድቅ ተግባር ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ መታየት ይገባዋል፡፡ ለዚህም ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት አዋጅ ቁጥር 60/89 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 ማንኛውም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወደ አገር የሚያስገባውን ወይም ከአገር የሚያስወጣውን ዕቃ በሚመለከት ቀረጥ እንዲቀንስ እንዳይከፈል ወይም እንዲመለስ የተከለከለ ገደብ ወይም ቁጥር የተደረገበት ዕቃ እንዲገባ እንዲወጣ ወይም እንዲተላለፍ በማሰብ ለባለስልጣን በጽሁፍ በቃል በአካል እንቅስቃሴ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም በሚያቀርበው ወይም በሚያደርገው የጉምሩክ ዲክላራላሲዮን ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ ዋጋቸው ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ የሆኑ ሰነዶች ያቀረበ ሰነዶችን የደለዘ የፋቀ አስመስሎ የሰራ ወይም ማናቸውም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት ዕቃና ለማጭበርበሩ በሽፋንነትና ከለላነት ያገለገሉት ዕቃዎች ውርስ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊከፈል ከሚባው ቀረጥና ታክስ በማያንስ የገንዘብ መቀጮና ከአስራ አምስት እስከ ሀያ አምስት በሚደርስ እስራት ሁለቱንም በማጣመር ይቀጣል በሚል መንገድ የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 67 በማሻሻል ደንግጓል፡፡

የጉምሩክ ቀረጥ ሣይከፍል ዕቃ ወደ ውጭ ለማሳለፍ በማሰብ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ያልተሟላበትን የኮንትሮባንድ ዕቃ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከተሟላበት ዕቃ ጋር ቀላቅሎ ጭኖ መገኘት ከላይ በተገለጸው የህግ ድንጋጌ መሠረት የማጭበርበር ድርጊት እንደተፈጸመ ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም የሚለው በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 ማናቸውንም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ የሚለው የአማረኛው ቅጅ እና በእንግሊዝኛው ቋንቋ “do any mischievous act” በሚል መንገድ ከተገለጸው አንጻር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በህጋዊ መንገድ ወደ ውጭ እንዲላክ ከተዘጋጀ ዕቃ ጋር በህጉና በመመሪያው መሠረት የጉምሩክ ቀረጥ ያልተከፈለበት የኮንትሮባንድ ዕቃ ቀላቅሎ በመጫን የጉምሩክ የመጨረሻ ኬላ ለማለፍ መሞከር የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 አማረኛው ቅጅ ማናቸውም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ በሚል መንገድ በገለጸውና የእንግሊዝኛው ቅጅ “do any mischievous act” በሚል መንገድ ከገለጻቸው የማጭበርበር ድርጊቶች ውስጥ የሚካተት ህገ ወጥ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በህጋዊ መንገድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደ ሱዳን ለመላክ የጉምሩክ ሥርዓትና ፎርማሊቲ ያሟሉበትን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ በሽፋንነትና በከለላነት በመጠቀም ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ውጭ እንዲወጣ የማድረግ ተግባር የተፈጸመ መሆኑን ያረጋገጠው አመልካች በኮንትሮባንድ ከአገር ውጭ ሊወጣ የነበረውን ሰላሣ ኩንታል ባቄላ ብቻ ሣይሆን ይህንን ባቄላ በኮንትሮባንድ ለማስወጣት በሽፋንነትና ከለላነት ያገለገለውን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ መውረሱ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 ገ/ኮነት ባለው ሁኔታ በደነገገው መሠረት የኮንትሮባንድ ወንጀል ለመፈጸም በሽፋንነትና በከለላነት ያገለገለውን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ የወረሰ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2163 ድንጋጌዎች በመጥቀስ አመልካች በህግ በተደነገገው መሠረት የወረሰውን ዕቃ ዋጋ በወቅቱ በነበረው የዶላር ምንዛሬ ታስቦ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 60/89 እና አዋጅ ቁጥር 368/95 መሠረታዊ አላማና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ያሟሉት አራት መቶ ኩንታል ባቄላ ተቀላቅሎ የተጫነውን ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ለማስወጣት በሽፋንነትና ከለላነት ያገለገለ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ አንድ ላኪ ዕቃ ወደ ውጭ ለመላኩ የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ ካሟላ በኋላ ዕቃውን ከመነሻው እስከ መድረሻው በመጓጓዝ ሂደት ሊከበሩ የሚገባቸው ሥርዓቶች በአዋጅ ቁጥር 60/89 ከአንቀጽ 16 እስከ አንቀጽ 18 ተደንግጓል፡፡ የዕቃው ላኪ እነዚህ ህጋዊ ሥርዓቶችና ደንቦችን ባከበረ ሁኔታ ከመነሻው እስከ መድረሻው ዕቃው የተጓዝ መሆኑን የማረጋገጥ ሀላፊነት እንዳለበትና ይህንን ግዴታውን በአግባቡ ሣይወጣ ቀርቶ ቀረጥ ያልተከፈላቸውና የተደበቁ ዕቃዎች ተቀላቅለው ከተጫኑ የዕቃው ባለቤት በሀላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 58 ንኡስ አንቀጽ 1/ለ/ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው ተጠሪ ህጋዊ ቀረጥ የከፈለበት አራት መቶ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ዕቃ ለማስተላለፍ በሽፋንነትና በከለላነት በማያገለግልበት ሁኔታ በጥንቃቄ ከመነሻው እስከ መድረሻው እየተጓዝ መሆኑን የመከታተል ህጋዊ ግዴታና ሀላፊነት አለባቸው ተጠሪ ይህንን ሀላፊነታቸዉ ሣይወጡ ቀርተው ዕቃው የኮንትሮባንድ ዕቃ ለማሳለፍ በሽፋንነትና በከለላነትና ያገለገለ መሆኑን አመልካች ካረጋገጠ አመልካች በኮንትሮባንድ ከአገር ሊወጣ የነበረውን ዕቃ ብቻ ሣይሆን በኮንትሮባንድ ዕቃ ለማሳለፍ በከለላነትና ሽፋንነት ያገለገለውን ዕቃ ለመያዝና ለመውረስ እንደሚቻል በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 የተደነገገ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በኮንትሮባንድ ከአገር ሊወጣ የነበረውን ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በተጠሪ የተጫነ መሆኑ ስላልተረጋገጠ አመልካች ህጋዊ ቀረጥ የተከፈለበትን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ ለመውረስ የሚችልበት ህጋዊ መሠረት የለውም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ሰላሣ ኩንታል ባቄላ በኮንትሮባንድ ከአገር ለማስወጣት በሽፋንነትና ከለላነት ያገለገለውን የተጠሪን አራት መቶ ኩንታል ባቄላ የወረሰው በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 5 እና በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሆኖ እያለ አላግባብ በተጠሪ ንብረት በልጽጓል በማለት የአራት መቶ ኩንታል ባቄላ ዋጋ በወቅቱ በነበረው የዶላር ምንዛሬ ሂሣብ እንዲከፍል የሰሜን ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል የሰሜን ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 65 በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 22 መሠረት የወረሰውን የአራት መቶ ኩንታል ባቄላ ዋጋ ለተጠሪ የመመለስና የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የሚሌ ገቢዎችና ጉምሩክ - ዓ/ህግ ግርማ መርሃ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ደረጀ ከፍያለው ሲማ - ከጠበቃ በላቸው ታደሰ ጋር - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ከተከሰሰበት የኮንትሮባንድ ወንጀል በነፃ የተሰናበተ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104/3/ሀ መሠረት ተሽከርካሪው እንዲወረስ በስር ፍ/ቤቶች አለመወሰናቸው የሕግ ስህተት ነው በሚል እንዲታረም ጠይቋል፡፡

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ የቀረበው በአመልካች በኩል ነው፡፡ የክሱ መነሻም ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-15475 ኦሮ. ቅጥቅጥ አይሱዙ የሕዝብ ማመላለሻ መኪና ከሐረር ወደ አ/አ ሲጓዝ አዋሽ ጉምሩክ ፍተሻ ላይ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን የኮንትሮባንድ እቃ ጭኖ በመገኘቱ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/1/ መሠረት ሾፌሩ፣ ረዳቱ እና 3ኛ ተከሳሽ /ባለንብረቱ/ በኮንትሮባንድ ወንጀል ተከሰዋል፡፡ የአፋር ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የስር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጥፋተኛ ናቸው ብሎ የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ 3ኛ ተከሳሽ /ባለንብረቱ/ የአሁኑ ተጠሪን ጥፋተኛ የሚያሰኝ ድርጊት አልፈፀመም በማለት ከክሱ በነፃ አሰናብቷል፡፡ የፊደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረቱ ይኸው ሆኖ ተጠሪው ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ቢባልም የኮንትሮባንድ እቃ የጫነው /ያጓጓዘው/ መኪና እንዲወርስ ሊወሰን ይገባ ነበር የሚል ነው፡፡ የሰበር ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ ስለንብረቱ መወረስ ወይም አለመወረስ ትዕዛዝ አለመሰጠቱ ተገቢነት ከተጠቀሰው ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር ተጠሪ እንዲቀርብ አዝዟል፡፡

ተጠሪው ነሐሴ 17 ቀን 2002ዓ.ም ባቀረበው የጽሑፍ መልስ በጉምሩክ ሕግ ገደብ የተደረገበት ወይም ቀረጥ ያልተከፈለበት እቃ የተጫነው በሹፌሩ እና በረዳቱ እንጂ በተጠሪ አለመሆኑን እንዲሁም የእቃ መደበቂያ /ሽግ/ ተሰራ የተባለው ለክሪክ፣ ለሸራና ለጎማ በተሰራ መያዣ መሆኑና ድርጊቱ የተፈፀመው ከተጠሪ እውቀትና ፍላጎት ውጪ መሆኑ ተረጋግጦ በነፃ መሰናበቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅሶ መኪናውም ሊወረስ እንደማይገባ ተረጋግጦ እንዲመለስለት በስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ መሰጠቱ በአግባቡ ነው በማለት በስር ፍ/ቤት ውሳኔ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

የአመልካች ዓ/ህግ በሰጠው የመልስ መልስ መኪናው እንዲመለስ የተሰጠው ትዕዛዝ አለአግባብ ነው ሲል አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደመርመርነውም የተጠሪ ከቀረበበት የኮንትሮባንድ ወንጀል ክስ በነፃ የተሰናበተ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ዓ/ህግ አጥብቆ የተከራከረው ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው የሕዝብ ማመላለሻ መኪና የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን እቃ ጭኖ መገኘቱ ተረጋግጦ ሹፌሩና ረዳቱ ጥፋተኞች ተብለው የተቀጡ ስለሆነ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104/3/ መሠረት መኪናው /ማንጓጓው/ እንዲወረስ ዓ/ህግ ያቀረበውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በማየት መወረስ ነበረበት የሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ሲል የያዘው ጭብጥ ስለማንጓጓው መወረስ ወይም አለመወረስ የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይሰጥበት የማለፉን አግባብነት ለማጣራት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ በሰጠው መልስ መኪናው ለተጠሪ እንዲመለስ ፍ/ቤቱ ከውሳኔው አስቀድሞ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ጠቅሷል፡፡ ዓ/ህግ በመልስ መልሱ ላይ ይህንን ሳይክድ መኪናው እንዲመለስ የተሰጠው ትዕዛዝ የአዋጁን አንቀጽ 104/3/ ይቃረናል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው መኪናው እንዲመለስ በስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለመሰጠቱ ግራ ቀኙ የተማመኑበት መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህም የሰበር ችሎቱ ውሳኔ የሚሻ ጉዳይ መኪናው ለተጠሪ እንዲመለስ መታዘዙ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ከክርክሩ መረዳት የተቻለው ተጠሪ የመኪናው ባለንብረት ቢሆንም ከወንጀል ድርጊቱ በነፃ የተሰናበተ መሆኑን ነው፡፡ ተከሳሽ በነፃ የተሰናበተ እንደሆነ ንብረቱ ሊወረስ የሚቻልበት ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 104/3/ሀ/ ስር በተለየ ሁኔታ (exceptional situation) ተመልክቷል፡፡ ይኸውም ስለድርጊቱ አፈፃፀም ሁኔታ የሚያስረዳ አጥጋቢ ማስረጃ መቅረቡንና ፍ/ቤቱ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው (Where the court is satisfied) ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ አንፃር በዚህ መዝገብ የቀረበውን ክርክር ስንመለከት ሹፌሩና ረዳቱ ጥፋተኛ ሆነው የተቀጡት በመኪናው ለክሪክ እና ሽራ፣ ጎማ መፍቻና ሌሎች መሰል እቃዎች ማስቀመጫ ተብሎ ከሹፌሩ ወንበር ጋር ተያይዞ በተሰራ ክፍል ውስጥ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት እቃ ደብቀው በማንገዛቸው ስለመሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡

በስር ፍ/ቤት የቀረበው እና የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ተጠሪ መኪናው ላይ ያሰራው የእቃ ማስቀመጫ ክፍል ከፍ ሲል ለተጠቀሰው አገልግሎት እንጂ ለሕገ ወጥ ዓላማ ነው ሊያስብል የሚያስችል አይደለም ተብሎ በወንጀሉ አፈፃፀም ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሐሳብ ነበረው ሊያሰኝ የሚችልበት ሁኔታ እንደሌለ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ የተነሳ በሕጉ አነጋገር የተጠሪ ንብረት የሆነው መኪና እንዲወረስ ለማድረግ ፍ/ቤቱን ሊያሳምን የሚችል ማስረጃ በአመልካች በኩል ያልቀረበ ስለመሆኑ መረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ አንፃር የተጠሪ መኪና ሊወረስ አይገባም ሲል የስር ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠው ውሳኔ በሕግ ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ባለበት ሁኔታ ሊፀና ይገባል ብለናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአፋር ብ/ክ/መ/ ገብረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01206 በ17/05/2002ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፊደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 89430 በ24/09/2002ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ሰኔ 17 ቀን 2002ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 65330

ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡-ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር

ተጠሪ፡-1. አቶ ተክሌ ጋርደው

2. አቶ ሐይማኖት አባተ

3. አቶ ታረቀኝ ወልዴ

4. አቶ ተሾመ አረጋይ

5. አቶ አብነት ደምሰው

6. አቶ አቡኪያ ቤኛ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር00944/2002 ሚያዚያ 15 ቀን 2002 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ውሳኔ ባግባቡ ነው ሲል በፍ/ይ/መ/ቁጥር 55990 ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው፡፡

ለሰበር አቤቱታው ምክንያነት የሆነው ጉዳይም አገልግሎትና የእድሜ መስፈርቱን የማያሟሉ ሰራተኞች ከስራ ሲሰናበቱ የመልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ እንዲያገኙ ሲደረግ በክፍያው ላይ የስራ ግብር ሊቀነስ ይገባል ወይስ አይገባም በሚለው ላይ የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤትም ሆነ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስራ ግብር ሊቀነስ አይገባም በማለት ውሳኔ በመስጠታቸው ነው፡፡በዚህ መሰረት በቀረበው አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለው ይህንኑ ነጥብ ለማጣራት ሲሆን አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ ተመርምሯል፡፡ ለዚህም ስለገቢ ግብር የሚደነግገውን የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 መመልከቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገቢ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 10(1) ስር በግልፅ እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ የገቢ ግብር ይከፍላል በማለት ተቀምጧል፡፡ ከግብር ክፍያ ነጻ የሆኑትን አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 13 ላይ በዝርዝር ሲገልጽ አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ጉዳይ አይነት በግልፅ ከስራ ግብር ነፃ ስለመሆኑ አይጠቅስም፡፡ ይህ አንቀፅ ከግብር ክፍያ ነፃ የሆኑትን ከዘረዘራቸው ውስጥ ማናቸውንም አይነት የጡረታ ጥቅም፣ወይም በተቀባዩ ሰው ላይ በደረሰ የአካል ጉዳት ካሳ ወይም በሌላ ሰው ላይ በደረሰ የሞት አደጋ የሚሰጥ የካሳ ክፍያ የሚሉት ይገኙበታል፡፡የካሣ ክፍያ ሲባልም በሕጉ ላይ በግልፅ እንደተመለከተው በደረሰ የአካል ጉዳት ወይም በደረሰ የሞት አደጋ የሚሰጥ የካሳ ክፍያ የሚመለከት እንጂ ማናቸውንም የካሳ ክፍያ ሁሉ ከግብር ነጻ መሆኑን የሚጠቅስ አይደለም፡፡በመሰረቱ የስራ ግብር የሚከፈለው ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 10(1) በግልፅ ያሰፈረው ሲሆን አዋጁ ገቢን አስመልክቶ በሰጠው የትርጉም ክፍል ላይ ገቢ ማለት ማናቸውም የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን በመደበኛነት የተገኘ ባይሆንም ከማናቸውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት በማናቸውም መልክ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው በስሙ የተያዘለትን ወይም የተቀበለውን ጥቅም ሁሉ እንደሚጨምር እንዲሁም ግብር የሚከፈልበት ገቢ ማለት ደግሞ በአዋጁና በአዋጁ መሰረት በሚወጡት ደንቦች መሰረት ማናቸውም ወጪ እና ሌሎች ተቀናሽ ሂሳቦች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው የገቢ መጠን መሆኑ አዋጁ በአንቀጽ 2(10) እና 1(11) አስፍሯል፡፡ በመሆኑም ለተጠሪዎች ይከፈል የተባለው የመቋቋሚያ ክፍያ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት አላገኘንም፡፡በዚህም መሰረት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 14 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሸበል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ብናልፈው ነጋ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐቃቤ ህግ ተወዳጅ ሲማ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀርቦ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አመልካች ያቀረባቸውን ሶስት መሠረታዊ ክርክሮች ውድቅ በማድረግ ወስኗል አመልካች የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ተጠሪ የተጨማሪ እሴት ታክስ በግምት መወሰኑን ፣ ተጠሪ አመልካች ቅጣት እንዲከፍል መወሰኑና የተጨማሪ እሴት ታክስ ከመዝገቡ በፊት የሽያጭ ታክስ የተከፈለበትን አለመቀነሡን በመቃወም ያቀረብኩትን የህግ ክርክር አልፎብኛል በማለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ በመዝገብ ቁጥር 43485 ከመረመረ በኋላ ተጠሪ አመልካች እንዲከፍል በግምት የወሰነውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 12/1/ የሚጥስ ነው በማለት ሽሮታል፡፡ ተጠሪ አመልካች የተለያዩ ቅጣቶች እንዲከፈል የሰጠው ውሣኔ የህግን ድንጋጌ የተከተለ አይደለም በማለት በግልፅ ሽሮታል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በሽያጭ ታክስ መልክ ገቢ የሆነው ገንዘብ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ሊቀነስልኝ ይገባል በማለት ያቀረበውን ክርክር በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሶ ልኮለታል፡፡

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ውሣኔ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43985 ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ጉዳዩን አጣርቶ መስከረም 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችን በማስቀረብ ተገቢውን ማጣራትና ምርመራ ካደረገ በኋላ አመልካች ታህሣሥ 23

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀን 1995 ዓ.ም የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሆንም የተጨማሪ እሴት ታክስ ያስታወቀው ነሐሴ 13 ቀን 1995 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህን ጊዜ በቅፅ 202 ያስታወቀው የሰኔ ወር 1995 እንቅስቃሴን እንጅ በህጉ መሠረት ሊመለስለት የሚገባውን የሽያጭ ታክስ በመዘርዘር የሽያጭ ታክሱ እንዲመለስለት ጥያቄ አላቀረበም፡፡ ስለሆነም አመልካች በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና ደንብ ቁጥር 79/95 መሠረት ማስታወቅና ጥያቄ ማቅረብ በሚገባበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ያሳወቀ በመሆኑ በሽያጭ ታክስ የከፈልኩት ይቀነስልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመዝገብ ቁጥር 72906 ከሰማ በኋላ የጉባኤውን ውሣኔ ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካች መቶ ፐርሰንት ግብር አልከፈለም በማለት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 ድንጋጌ ጠቅሶ ሰርዞታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሥራ ላይ ከመዋሉ ከስድስት ወር በፊት ተገዝተው በነበሩ ዕቃዎች የከፈለውና በህጉ አግባብ ሊቀናነስለት የሚገባውን የሽያጭ ታክስ ተጠሪ ሲያቀናንስለት ከቆየ በኋላ እንቢተኛ ሆኗል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሽያጭ ታክስ የተከፈለውን እንዲቀናነስልን የምንከራከር ሆኖ እያለ መቶ ፐርሰንት ግብር ሣይከፍል የቀረበ ይግባኝ በመሆኑ ይግባኙ አይታይም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ስለሆነም በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንዲከፍላቸው የሚፈልገው ገንዘብ የግብር ገንዘብ በሌለበት ሁኔታ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሥራ ላይ ከመዋሉ ከስድስት ወር በፊት የከፈልኩት የሽያጭ ታክስ እንዲቀናነስልኝ ያቀረብኩትን ጥያቄ መቶ ፐርሰንት ግብር ከፍለህ አልቀረብክም ብሎ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ አደረገብኝ በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ አይደለም አመልካች ብር 9,652,121.44 ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍል ተጠሪ የሰጠውን የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው አፅንቶታል፡፡ ስለሆነም አመልካች ይህንን የግብር ገንዘብ መቶ ፐርሰንት ሣይከፍል ይግባኙ እንደማይታይለት በመግለፅ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 285/94 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ጥያቄው የይቀናነስልኝ ጥያቄ በመሆኑ መቶ ፐርሰንት የሚከፈል ግብር የለም፡፡ ይኸም ቢታለፍ አመልካች ግብሩን ከፍሎ እንዲቀርብ ሊደረግ ይገባው ነበር ታህሣሥ 20 ቀን 2003 ዓ.ም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? በማለት ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ ከስድስት ወራት በፊት በአመልካች እጅ በነበሩት ዕቃዎች ላይ ተከፍሎ የነበረው የሽያጭ ታክስ ሊቀናነስልኝ ይገባል በማለት የሚከራከረው ተጠሪ ወስኖ ካሣወቀው የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብርና በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ከፀደቀው የግብር ውሣኔ መሆኑን በሥርና በዚህ ፍርድ ቤት በግራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀኙ ከተደረገው ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በተጨማሪ እሴት ታክስ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በተሰጠ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ሥርዓት በግብር ይግባኝ አዋጅ ቁጥር 286/94 አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 285/94 በአንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4 በግልፅ ይደንግጋል፡፡

የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሣኔ የህግ ስህተት አለበት የሚል ቅሬታ ያለው ግብር ከፋይ ይግባኙን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት የሚያቀርበው በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የተወሰነበትን የግብር ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ሲከፈል መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 112 ንዑስ አንቀፅ 4 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች በግብር ይግባኝ ጉባኤ እንዲከፍል የተወሰነበትንና የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ሙሉ በሙሉ የከፈለ መሆኑ ይግባኙን ለይግባኝ ሰሚው ችሎት ለማቅረብ በህግ የተደነገገ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ የአመልካች ጥያቄ የሽያጭ ታክስ ከተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲቀናነስልኝ የቀረበ ነው በሚል ምክንያት በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የተወሰነበትን የተጨማሪ እሴት ግብር ሙሉ በሙሉ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማያያዝ የቀረበውን ይግባኝ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4 እና በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 112 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገውን ቅድመ ሁኔታ ሣይሟላ የቀረበ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት መሠረዙ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና ምንም አይነት የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው፡፡

አመልካች ለይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኙን ከማቅረቡ በፊት በህግ የተጣለበትን ቅድመ ሁኔታ ያሟላ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች በህጉ የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ሣያሟላ የይግባኝ መዝገብ አስከፍቶ ያገኘው ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ቅድመ ሁኔታውን አሟልቶ እንዲመጣ ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች ቅድመ ሁኔታውን አሟልቶ የሚመጣ መሆኑን ለመጠባበቅ ቀጠሮ ሰጥቶ እንዲጠባበቅ የሚያስገድደው የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ይግባኝ ባይ ይግባኙን ለማቅረብ ሚሟላት የሚገባውን ቅድመ ሁኔታ ሣያሟላ ይግባኝ እንዳቀረበ ከተረዳ የህጉ የተደነገገውን ግዴታ ሣያሟላ ይግባኝ ባይ ያቀረበውን ይግባኝ በመሰረዝ መዝገቡን መዝጋት እንደሚችል ከአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4 እና ከአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 112 ንዑስ አንቀፅ 4 ድንጋጌዎች የጣምራ ንባብ መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይግባኙን ለይግባኝ ሰሚው አቅርቦ ለማሰማት በህግ የተደነገገውን ቅድመ ሁኔታ ያሟላ መሆኑን የማስረዳተና የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት አመልካች በህጉ የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታና ግዴታ ሣይፈፅም ያቀረበውን ይግባኝ ይግባኝ ሰሚው ተቀብሎ አለመሰማቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ በሰበር ችሎት የተጠቀሱት የደንብ ቁጥር 79/95 አንቀፅ 5 ፣ አንቀፅ 8 እና አንቀፅ 9 አመልካች ከፍያዋለሁ የሚለው የሽያጭ ግብር ከተጨማሪ እሴት ታክስ ግብሩ ሊቀናነስለት ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን መሠረታዊ ጭብጥ በመወሰን ሒደት ግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ የሚገቡ የህግ ድንጋጌዎች ናቸው በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጭብጥ ማለትም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የተወሰነበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሙሉ በሙሉ ሣይከፈል ያቀረበው ይግባኝ በህግ የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ የሚያሟላ አይደለም ብሎ ይግባኙን መሰረዙ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች ሆነው አላገኘናቸውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀጽ 4 እና አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 112 ንዑስ አንቀፅ 4 ድንጋጌዎችን ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ፀንቷል።
2. በዚህ መዝገብ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል። መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጭ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ዱላ ያሲን - ከጠበቃ መላኩ ገ/ሥላሴ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አበበች እሸቱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች አንደኛ ተከሳሽ አቶ አማረ ዘውዴ ሁለተኛ ተከሳሽ አዋሽ ኢንሹራንስ አክስዮን ማህበር ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ንብረቱ የሆነችውና የሰሌዳ ቁጥር 3-47351 የሆነ አይሱዙ የህዝብ ማመላለሻ መኪና ሀምሌ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ከሱልልታ ወደ አዲስ አበባ ተሳፋሪዎች ጭኖ ሲጓዝ በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛው ተከሳሽ በሆነው አቶ አማረ ዘውዴ የአንደኛ ተከሳሽ ማለትም የአመልካች ንብረት የሆነውን ኮድ 3-27054 በደረሰበት ግጭት በተሣፋሪዎችና በአሽከርካሪው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን መኪናው በወቅቱ ብር 132,000(አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ብር) ግምት ያለው መኪና ወድሟል፡፡ መኪናውን አስጠግኖ ሥራ እንዲጀምር ለማድረግ 28,000 (ሀያ ስምንት ሺህ ብር) ወጥቷል፡፡ ስለሆነም ለመኪና የወጣው 160,000 እንደዚሁም ከሀምሌ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 8 ቀን 2001 ያለው የተቋረጠ ገቢ በቀን 250(ሁለት መቶ ሀምሣ ብር) በድምሩ 190,000 እና ወደፊት በክርክሩ ሒደት የሚደርስ ጉዳት እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ በክርክሩ ጣልቃ የገባው አዋሽ ኢንሹራንስ የመኪናዋ ግምት ብር 132,000 ነው በማለት ያቀረቡት ግምት ተገቢነት የለውም፡፡ ስለዚህ የአገልግሎት ዘመኑ ተቀንሶ በመንገድ ትራንስፖርት ይገመት ከዚህ በተረፈ በወቅቱ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) እንዲቀበሉ ጠይቀናቸው እንቢ ያሉ በመሆኑ ከዚያ በኋላ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም በጣልቃገቡ የተነሱትን የመከራከሪያ ነጥቦች አንስተው ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ጣልቃገብ ግምቱን በተመለከተ ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ በማድረግ መኪናውን አገልግሎት ላይ ለማዋል ብር 25,000 ወጭ ተደርጓል፡፡ መኪናው በደረሰበት አደጋ ውሣኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቋረጠ ገቢ ብር 81,420 የቀረ በመሆኑ መከፈል አለበት፡፡ መኪናው ለተጠበቀበት ብር 7080 ተከሳሾች ይክፈሉ በአጠቃላይ 245,500 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) አመልካችና ጣልቃ ገብ እንዲከፍሉ ከዚህ ውስጥ ብር 100,000(መቶ ሺህ ብር) ጣልቃ ገቡ አዋሽ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ቀሪውን አንደኛ ተከሳሽ (አመልካች) ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ መኪናው የ1985 ዓ.ም ሞዴል በመሆኑ ግምቱ 132,000 እንደማያወጣ ያቀረብኩትን ክርክር የሥር ፍርድ ቤት አላግባብ አልፎብኛል፡፡ መኪናዋን አስነስቼ ያቆምኳት ስሉልታ ፖሊስ ጣቢያ አንስቶ ወስዶ ለጥበቃ ገንዘብ አውጥቻለሁ በማለት ተጠሪ ላቀረቡት ክስ እኔ ሀላፊ መባሌ ተገቢነት የለውም፡፡ መኪናው ሙሉ በሙሉ ወድሟል ተብሎ ሙሉ ግምቱን ክፈሉ ብሎ የሥር ፍርድ ቤት ከወሰነ በኋላ ለመስታወት ለወንበር ለጋራዥ ኪራይ ያወጡትን ገንዘብ ክፈሉ ብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ መኪናው በወር ሰላሣ ቀን አይሠራም ስለዚህ ኪሣራው ወሩን ሙሉ እንደሚሠራ ተደርጎ መታሰቡ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ክስ የቀረበበት ብር 190,000 ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ዳኝነት ከጠየቁት በላይ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው መኪናውን ከገዛሁት በኋላ ወንበር መስታወት ስላልነበረው ይህንን በማስተካከል ብር 25,000 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) አውጥቻለሁ፡፡ አሁን ንብረቱን በፊት ባለው ዋጋ ለመተካት የሚቻል አይደለም መኪናው ላይ ጉዳት በመድረሱ ገቢ መቋረጡ የሚካድ አይደለም፡፡ ስለዚህ ለተቋረጠ ጥቅም አመልካች ካሣ እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመኪናው ሙሉ ዋጋ ገምተው ከጠየቁ በኋላ ለእያንዳንዱ የመኪና አካል ካሣ መጠየቃቸው በአግባቡ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመኪናውን ቅሪት እንድንወስድ ፍርድ ቤቱ ያልወሰነልን ወይም የቅሪት አካል ዋጋ እንዲቀነስልን ማድረግ ሲገባው ይህንን አለማድረጉ ተገቢ ባለመሆኑ ሰበር ችሎቱ እንዲወስንልን በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራ ቀኙ መካከል የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የወሰኑት የካሣ መጠን ስለካሣ አወሳሰን የተደነገጉትን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በጭብጥነት የያዝነውን መሠረታዊ ጉዳይ ለመፍታት የሥር ፍርድ ቤት መኪናዋ ለአገልግሎት ለመብቃት ተጠሪ አወጣሁ ያሉትን ወጭ አመልካች እንዲከፍሉ መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ተጠሪ ለመኪናዋ ማስጠበቂያ አወጣሁ ያሉትን ወጭ አመልካች ለተጠሪ እንዲተኩ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? መኪናዋ ላይ ጉዳት በመድረሡ ተጠሪ ያቀረባቸውን ገቢና የደረሰባቸው ጉዳትና አመልካች ሊከፍሉት የሚገባውን የካሣ መጠን ለማስላት የተከተለው ስልት ህጋዊ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች በዝርዝር ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የበታች ፍርድ ቤቶች ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር 3-47351 ተሳፋሪዎች ጭኖ ሲንዝ በአመልካች መኪና የግጭት አደጋ ስለደረሰበት ሊጠገን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማይችል ሁኔታ የወደመ መሆኑን በውሣኔያቸው ገልፀዋል፡፡ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጥ የነበረው የተጠሪ ንብረት የሆነው መኪና አደጋው ሲደርስበት ሙሉ ዋጋውና ግምቱ 132,000 (አንድ መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ ብር) እንደሆነ ተጠሪ በክሳቸው የገለፁ ሲሆን አመልካች ግምቱ የተጋነነ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ሆኖም የሥር ፍ/ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የመኪናውን ጠቅላላ ዋጋ ብር 132,000 (አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ብር) በመገመት ተጠሪ ያቀረቡት ክስ የተጋነነ አይደለም በማለት አመልካችና ጣልቃገብ ተከራካሪው መኪናው አደጋ ሲደርስበት የነበረውን ግምት ብር 132,000(አንድ መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ለመኪና ወንበር የመስታወትና የቴክኒክ ዋጋ ብር 25,000 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) አመልካች ከመኪናው ግምት በተጨማሪ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 ለደረሰ ጉዳት የሚከፈለው ካሣ በተበዳዩ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን እንዳለበት የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ ያልተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ብር 25,000 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) መኪናዋን ከገዛችት በኋላ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንድትሰጥ ለማድረግ ለወንበርና ለመስታወት ያወጣሁት ነው በማለት በይግባኝና በሰበር ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም መኪናው አደጋ የደረሰበት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ባለበት ወቅት ነው፡፡ መኪናው አደጋ በደረሰበት ጊዜ የሚያወጣው ወቅታዊ ግምት ብር 132,000(አንድ መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ ብር) ነው በማለት ተጠሪ ያቀረቡትን ግምት አመልካች ተቃውመው ፍርድ ቤቱ የተለያዩ ማስረጃዎችን ከመረመሩ በኋላ መኪናዋ የግጭት አደጋ በደረሰበት ጊዜ ወቅታዊ ግምት ዋጋው ብር 132,000(አንድ መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ ብር) ስለሆነ አመልካች ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ መኪናው ከመገጨቱ በፊት ተጠሪ ለእያንዳንዱ የመኪና አካል በተናጠል ከፍየዋለሁ የሚሉትን ገንዘብ በመደመር አመልካች ብር 25,000 (ሀያ አምስት ሺህ ብር) እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ በተጠሪ መኪና ከደረሰው ጉዳት በላይ አመልካችን ካሣ እንዲከፍሉ የሚያስገድድና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪ መኪና ያስጠበቁበት ብር 7080 (ሰባት ሺህ ሰማንያ ብር) ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጡትን ውሣኔ በተመለከተ ተጠሪ ለመኪና መጠበቂያ ከፍያለሁ ያሉትን ገንዘብ ወጭ ያደረጉት አደጋ ከመድረሱ በፊት መኪናቸውን ለማስጠበቅ ያወጡትን ገንዘብ በመደመር የጠየቁት መሆኑን ወይም ገንዘቡን የከፈሉት የመኪናውን ቅሪት ለማስጠበቅ መሆኑን ሣያጣሩ ውሣኔ የሰጡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ መኪናቸው ከመገጨቱ በፊት የመኪናቸውን ደህንነት ለማስጠበቅ የከፈሉትን ገንዘብ አመልካች እንዲተኩላቸው የመጠየቅ መብት የላቸውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የመኪናዋ ቅሪት አካል ሱልልታ ፖሊስ ጣቢያ ያስቀመጡት መሆኑን በማለዕ ያቀረቡትን ክርክርና የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በግልዕ በመካድ መልስ አልሰጡበትም፡፡ ጉዳቱ የደረሰ መሆኑንና በጉዳቱ የደረሰ ኪሣራ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ካሣ እንዲከፈለው የሚጠይቀው ሰው እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2141 ይደነግጋል፡፡ ተጠሪ ለመኪናው ማስጠበቂያ አወጣሁ ያሉት ወጭ መቼና በምን ሁኔታ እንዳወጡትና በተለይም ወጭውን ያወጡት በአደጋው ምክንያት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ (Burdon of Presentation of Evidence) ባልተወጡበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪ ለመኪና መጠበቂያ አውጥቻለሁ ያሉትን ብር 7080(ሰባት ሺህ ሰማኒያ ብር) እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2141 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 ድንጋጌን መሠረት ያላደረገና ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የተጠሪ መኪና በግጭቱ ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ በመሆኑ ምክንያት አመልካች በቀን ብር 230(ሁለት መቶ ሰላሣ ብር) ስሌት አደጋው ከደረሰበት ህምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እስከሰጠበት ህምሌ 3 ቀን 2001 ዓ.ም ተጠሪ የቀረባቸው ገቢ ብር 81,420 (ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ሀያ ብር) እንዲከፍሉ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መኪናው በዓመት ውስጥ ለጥገናና ለሰርቪስ የሚቆምበትን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሰጠ ውሣኔ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሥር ፍርድ ቤት በጣልቃገብነት ተከራካሪ የነበረው አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) ጉዳቱ እንደደረሰ ተጠሪ በመድን ፖሊሲው መሠረት ብር 100,000 (መቶ ሺህ ብር) እንዲቀበሉ ጠይቋቸው የነበረ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ይህንን የሚያስተባብል ክርክርና ማስረጃ ከሥርም ሆነ ከዚያ በኋላ በተደረገው ክርክር ያላቀረቡ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ተጠሪ ይህንን ገንዘብ በቅንነት በመቀበል ቀረብኝ የሚሉትን ገንዘብ ከአመልካች መጠየቅ የሚችሉበት እድል በኢንሹራንስ ድርጅቱ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተበዳይ ላይ ለደረሰ ጉዳት የሚከፈለው ካሣ ለቅን ልቦና ተቃራኒ በሆነ አኳኋን ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡ ተጠሪ አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) ከአመልካች ጋር ያለውን የመድን ውልና በውሉ ላይ ያለውን ጣሪያ መሠረት በማድረግ እንዲቀበሉት የጠየቃቸውን ብር 100,000(አንድ መቶ ሺህ ብር) በቅንነት ቢቀበሉ ገቢ በመቋረጡ ምክንያት የደረሰባቸውን ኪሣራ ሊያስቀሩት ወይም ሊቀንሱት የሚችሉበት አቅም ይፈጥርላቸው ነበር፡፡ ተጠሪ ይህንን ባለማድረጋቸውና ወደ ክርክር መግባት የማይፈልገውን አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) በጣልቃ ገብ ተከራካሪነት እንዲጠራ የሚያስገድድና ስድስት ወር የፈጀ ክርክር ከአመልካች ጋር ለማድረግ ተገደዋል፡፡ ሌላ ሰው ኃላፊ በሆነበት ድርጊት ወይም አደጋ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱን ለማስቀረት ወይም የጉዳቱን መጠን ቀላል ለማድረግ ግዴታና ሀላፊነት እንዳለበት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 2 ተበዳዩ በማስተዋል ቢሠራ ኖሮ የደረሰበትን ጉዳት ሊያግደው ወይም ሊያቀለው የሚችል ሲሆን በደረሰበት ጉዳት መጠን በሙሉ ካሣ ለመጠየቅ አይችልም በማለት በግልፅ ደንግጎታል፡፡ ተጠሪ በግጭቱ ጉዳት የደረሰበት መኪና ጠቅላላ ዋጋ ብር 132,000 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ከዚህ ውስጥ አዋሽ ኢንሹራንስ ለመክፈል ሙሉ ዝግጁነቱን ያሣየበትን ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ተቀብለው ቢሆን ኖሮ ከዚህ ገንዘብ ሌላ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ በመሥራት ወይም በዚህ ገንዘብ አነስተኛ መጠን ያለው ሌላ መኪና በመግዛት ወይም ተጨማሪ ገንዘብ ተበድረው አደጋ የደረሰበትን መኪና ምትክ በመግዛት በአደጋው ምክንያት የተቋረጠባቸውን የገቢ መጠን ለመቀነስ እየቻሉ ገንዘቡን ለመቀበል እንቢተኛ በመሆናቸው ምክንያት ኪሣራውን ለማስቀረት ወይም ሊያቀሉት እንዳልቻሉ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ከላይ የጠቀስነውን የህግ ድንጋጌ ግምት ውስጥ ሣያስገቡ ተጠሪ በአደጋው ምክንያት የተቋረጠባቸውን ገቢ አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ እስከሰጠበት ጊዜ ድረስ ያለውን በሙሉ አስበው የሰጡት ውሣኔ የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) አደጋው እንደደረሰ እንዲቀበሉ የጠየቃቸውን ብር 100,000 (መቶ ሺህ ብር) ቢቀበሉ ኖሮ መኪናው በአደጋ በመውደሙ ምክንያት ሊያገኙት የነበረው ገቢ ከሶስት ወር በላይ ተቋርጦ የሚቀጥልበት ሁኔታ እንደማይኖር የነገሮችን ተራ ሁኔታዎችና ተጠሪ ተገቢውን ጥረት ያላደረጉና የቅንልቦና ጉድለት ያለባቸው መሆኑን በማገናዘብ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097(2) ወስነናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ ለቀረባቸው ጥቅም መክፈል የሚገባው የካሣ መጠን በቀን ብር 230(ሁለት መቶ ሠላሳ ብር) ሒሳብ የዘጠና ቀን ቀሪ ገቢ በድምሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብር 20,700(ሀያ ሺህ ሰባት መቶ ብር) ብቻ መሆን ይገባዋል በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) አሻሽለን ወስነናል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና በተራ ቁጥር 2 በተገለፁት ነጥቦች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የካሣ አወሳሰን መርሆችን መሠረት ያላደረጉና ተገቢነት የሌላቸው በቁጥር 3 የተመለከተው ነጥብ ደግሞ ተጠሪ በመኪናው መውደም ምክንያት የተቋረጠባቸውን የገቢ መጠን ለመቀነስ ወይም ለማቅለል የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት በቅን ልቦናና በአስተዋይነት ያደረጉት እንቅስቃሴ የሌለ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ያልሰጡና ውሣኔያቸው በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና ሊሻሻል የሚገባው ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የካሣውን መጠን በተመለከተ የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪ መኪና አደጋ በደረሰበት ወቅት የነበረውን ግምት ብር 132,000(አንድ መቶ ሠላሳ ሁለት ሺህ ብር) ይክፈል ከዚህ ውስጥ በሥር ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የሆነው አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) ብር 100,000(አንድ መቶ ሺህ ብር) ይክፈል በማለት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ተጠሪ ለመኪናው ወንበር መስታወትና የማስጠገኛ ያወጡትን ብር 25,000(ሀያ አምስት ሺህ ብር) እንደዚሁም ተጠሪ መኪናውን ለማስጠበቅ ያወጡትን ብር 7080(ሰባት ሺህ ሰማኒያ ብር) እንዲከፍሉ በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ ክፍል ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከላይ የተገለፀውን ብር 32,080 (ሰላሣ ሁለት ሺህ ሰማኒያ ብር) ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ወስነናል፡፡
4. የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ መኪናቸው ከጥቅም ውጭ በመሆኑ ምክንያት ተጠሪ ለተቋረጠባቸው ገቢ ብር 81,420(ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ሀያ ብር) አመልካች እንዲከፍል በማለት የሰጡትን ውሣኔ አሻሽለን አመልካች በቀን ብር 230(ሁለት መቶ ሠላሳ ብር) ታስቦ የዘጠና ቀናት የተቋረጠ ገቢ ብር 20,700(ሀያ ሺህ ሰባት መቶ ብር) ብቻ የመክፈል ሀላፊነት አለበት ብለናል፡፡
5. በአጠቃላይ በዚህ ውሣኔ መሠረት አመልካች ለተጠሪ የሚከፍሉት በሁለተኛ ተራ ቁጥር እንዲከፍሉ የተወሰነባቸውን ብር 32000 እና በተራ ቁጥር 4 የተወሰነባቸው 20,700 በድምሩ ብር 52,700(ሀምሳ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ብር) ብቻ ነው ብለናል፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 52595

ታህሳስ 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ነገረ ፈጅ መና ህብስቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ሻሎም ተስፋዬ
2 ርግዓእት ገብረእየሱስ
3. ብርቱካን ገብረእየሱስ
4. ራዓዋ ገብረእየሱስ

አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የክርክሩ መሠታዊ ጉዳይ አመልካች እንደስላሴ ከተማ ቀበሌ 02 ህንፃ ሠርቶ እንዲያስረክበው በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳች ለነበሩት አቶ አዲሱ አብርሀ በህንፃ ሥራ ውል ሠጥቷል፡፡ በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ አዲስ አብርሀ የአንደኛ ተጠሪን ባለቤትና ስማቸው ከሁለተኛው ተራ ቁጥር እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር የተገለፀውን ተጠሪዎች ወላጅ አባት አቶ ገብረእየሱስ አባይን ቀጥሮ ሥራ በመሥራት ላይ እያሉ አቶ ገብረእየሱስ ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በግንባታ ላይ ካለው ህንፃ ላይ ወድቀው በደረሰባቸው ጉዳት ወደ ሆስፒታል ከተወሰዱ በኋላ ነሐሴ 22 ቀን 2001 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪዎች አመልካች በግንባታ ላይ የሚገኘው ጅምር ህንፃ ባለቤት በመሆናቸው አቶ አዲሱ አብርሀ የሚች የአቶ ገብረእየሱስ አባይ ቀጣሪ በመሆናቸው በሚች መሞት ምክንያት ለደረሰብን ጉዳት ብር 154,200 /አንድ መቶ ሀምሣ አራት ሺ ሁለት መቶ ብር/ እንዲከፍሉን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ሚች ህንፃውን ለመሥራት የተዋዋለው ሥራ ተቋራጭ ሠራተኛ በመሆናቸውና ከህንፃው ወድቀው ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ በኋላፊነት የሚጠየቀው የሚች አሠሪ እንጅ እኔ አይደለሁም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ አመልካችና የሚች አሠሪ በአንድነትና በነጠላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለጉዳቱ ሀላፊ ናቸው በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ አዲሱ አብርሀና አመልካች በአንድነትና በነጠላ ለተጠሪዎች /ከሳሾች/ ብር 36,000 /ሰላሣ ስድስት ሺ ብር/ የዳኝነትና ሌሎች ወጭዎችን በቁርጥ ፍርድ ቤቱ ወስኖ ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የህንፃው ባለቤት ከውል ውጭ በሀላፊነት ሊጠይቅ የሚቻለው ህንፃው ለሚያደርሰው ጉዳት ብቻ መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2077 ተደንግጓል፡፡ ህንፃው በአሠራር ጉድለት ፈርሶ ወይም የህንፃው ክፍል የሆነ ነገር ወድቆ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ከላይ በተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ መሠረት ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ይኖርብናል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሚች የኮንትራክተሩ ሠራተኛ ናቸው፡፡ ሚች ሥራ እየሠሩ እያለ ከህንፃው ላይ ወድቀው ለደረሰባቸው ጉዳት ህንፃውን ለተቋራጭ ሠጥቶ እየሠራ ያለው አመልካች በኃላፊነት የሚጠይቅበት የህግ አግባብ ሣይኖር ለደረሰው ጉዳት ሀላፊነት አለባችሁ ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ሚች የሞተው ከህንፃው ላይ ወድቆ ነው፡፡ ሚች የወደቀው ህንፃው የተሠራበት ቶንዲኖ ብረት በመታጠፉ ምክንያት ነው፡፡ አመልካች በውሣኔው መሠረት ድርሻውን ከፍሏል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በሚች አቶ ገብረእየሱስ አባይ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሚች አቶ ገብረእየሱስ አባይ ለሞት የተዳረጉት የአመልካችን ህንፃ የሥራ ተቋራጭ ሆኖ የሚሠራው የሥራ ተቋራጭ ሠራተኛ ሆነው ህንፃውን እየሰሩ እያሉ ከህንፃው ላይ ወድቀው ነው፡፡ የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ሚች ህንፃውን ከሚሰራው ኮንትራክተር ጋር በነበራቸው ውል መሠረት ህንፃውን ሲሰሩ ወድቀው ለደረሰባቸው የሞት አደጋ አመልካች ኃላፊ የሚሆነው በየትኛው የሕግ ድንጋጌ መሠረት እንደሆነ አልጠቀሱም በአመልካችና በሚች መካከል የውል ግንኙነት የሌለ በመሆኑ አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ የሚሆነው ከውል ውጭ በሚመጣ ኃላፊነት የሕግ ድንጋጌዎች አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚደነግጉ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

አመልካች እየተሠራ ያለው ጅምር ህንፃ ባለቤት መሆኑ አልተካደም፡፡ የአንድ ህንፃ ወይም ቤት ባለቤት ከውል ውጭ ኃላፊ የሚሆንበት መሠረታዊ መርህ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2077 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ይዘት "የአንድ ህንፃ ባለሀብት ወይም ለይዞታ ሕንፃው ሊደርስ ይችላል ተብሎ ያልታሰበ ድንገተኛ ነገር ቢደርስም ይኸ ህንፃ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ ነው" የሚል ነው፡፡ ሚች በመገንባት ያለው ህንፃ በመፍረሱ ወይም የህንፃው አንድ ክፍል በመደርመሱ ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው የሞት አደጋ ያጋጠማቸው ሰው አይደሉም፡፡ ሚችን የሞት አደጋ ያጋጠማቸው ህንፃውን የሚሠራው ኮንትራክተር ሠራተኛ ሆነው ህንፃውን በመሥራት ላይ እያሉ ከህንፃው ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመውደቃቸው ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2077 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ አይደለም፡፡

ሟች አመልካች የሚያሠራውን ህንፃ በውል የመሥራት ግዴታ ካለበት የሥራ ተቋራጭ ጋር ባላቸው የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት በሥራ ላይ እያሉ ወድቀው የሞት አደጋ ደርሶባቸዋል፡፡ ይኸም በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ስለሚሰጡ ክፍያዎች በሚለው በምዕራፍ ሶስት ሥር የሚሸፈንና የሚተዳደር እንጅ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2077 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሚወድቅ አይደለም፡፡ በመሆኑም የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በሟች አቶ ገብረእየሱስ አባይ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሀላፊ ስለሆነ ለተጠሪዎች ካሣ መክፈል አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልል የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች ካሣ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሣስ 15 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነገረ ፈጅ አቶ አያሌው አለማየሁ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ወልዱ ገብረሥላሴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነው፡፡ የጉዳዩ መነሻ የጉዳት ካሣ ጥያቄ ነው፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሦስተኛው ተከሣሽ የነበሩት አቶ ሣህለ ሀብተማርያም በተቋራጭነት የሚሠሩትን በስር የሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩትን የአቶ ታከለ ገብሬ ባለሁለት ፎቅ ህንፃ በመሥራት ላይ እያሉ በሚሠሩበት ቦታ የሚያልፈው ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር አደጋ አድርሶባቸዋል፡፡ በአደጋው ምክንያት ሁለት እጆቻቸው መቆረጡና ሁለት ጭናቸው ላይ ጉዳት መድረሱ በየካቲት 12 ሆስፒታል የህኪሞች ቦርድ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በአደጋ በደረሰባቸው ጉዳት 100% /አንድ መቶ ፐርሰንት/ የመሥራት ችሎታቸውን እንዳጡ በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

አመልካች በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት ካሣ እንዲከፍሏቸው አመልካችን በአንደኛ ተከሳሽነት የቤቱን ባለሀብት አቶ ታከለ ገብሬን በሁለተኛ ተከሣሽነት አሠሪያቸውን አቶ ሣህለ ሀብተማርያምን በሦስተኛ ተከሳሽነት ከሰዋል፡፡ አመልካችና ሌሎቹ ተከሣሾች በኃላፊነት አንጠየቅም የሚሉባቸውን ምክንያቶች በማንሣት ተከራክረዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በደረሰው አደጋ በኃላፊነት መጠየቅ ያለበት አንደኛ ተከሣሽ/አመልካች/ ነው በማለት ተጠሪ ለዘጠኝ ዓመት /ወደፊት/ የሚያገኘው ገቢ በቀን 50 ብር /ሀምሣ ብር/ እና በዓመት ውስጥ 200 /ሁለት መቶ/ የሥራ ቀናት የሚያገኘውን የተቋረጠበትን ገቢ ብር 50 × 200 ቀናት × 9 ዓመት አስልቶ 90,000 /ዘጠና ሺህ ብር/ የሞራል ካሣ ብር 1,000 /አንድ ሺህ ብር/ በድሩ 91,000 /ዘጠና አንድ ሺህ ብር/ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በዓመት ሁለት መቶ ቀን ብቻ ይሠራል በሚል ሒሳብ ካሣው መሠላቱ ተገቢ አይደለም በማለት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ይግባኝ አጣምሮ በማየት ለአደጋው አመልካች ብቻ ኃላፊ መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ በስር ፍርድ ቤት ሦስተኛ ተከሣሽ በይግባኝ ሦስተኛ መልስ ሰጭ የነበሩት የአመልካች አሠሪ አቶ ሣህለ ሀብተማርያም ለደረሰው ጉዳት ከአመልካች ጋር ኃላፊነት አለበት፡፡ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በዓመት ተጠሪ 200 ቀናት ብቻ ነው የሚሠሩት ማለቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ በዓመት ውስጥ 300 ቀን መሥራት ይችላል፡፡ በማለት የ300 ቀናት በቀን 50 /ሀምሣ ብር/ ሒሣብ የዘጠኝ ዓመት ብር 112,500 /አንድ መቶ አሥራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ እና የሞራል ካሣ ብር 1,000 /አንድ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 113,500 /አንድ መቶ አሥራ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር/ አመልካችና በከፍተኛው ፍ/ቤት ሦስተኛ መልስ ሰጭ የነበሩት አቶ ሣህለ ሀብተማርያም እንዲከፍሉ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የኤሌክትሪክ መስመሩ ጉዳት እያደረሰ የማሠራው ህንፃ ቁመት እየጨመረ ሄዶ ወደ ኤሌክትሪክ መስመሩ በመጠጋቱና ተጠሪ ይዘውት በነበረው ፊሮ ብረት የኤሌክትሪክ መሥመሩን በመንካታቸው ነው፡፡ ተጠሪ መስመሩ ካልተነሣ ሥራውን ማቆም ይገባቸው ነበር፡፡ ስለዚህ ለደረሰው ጉዳት የህንፃው ባለቤትና የተጠሪ አሠሪ እንጂ እኛ ኃላፊ መባላችን መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በማናቸውም መንገድ ወይም ህዝብ በብዛት በሚገኝበት ሥፍራ የሚዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመር የአደጋ መከላከያ ሊኖራቸው እንደሚገባ በኤሌክትሪክ ደንብ ቁጥር 49/91 አንቀጽ 35 እና አንቀጽ 41 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ይህን ኃላፊቱን በአግባቡ አልተወጣም ስለዚህ በወቅቱ ለደረሰው ጉዳት የመካስ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ ይህንን ሥራ በሚሠሩበት ወቅት በአካባቢው በሚያልፈው የኤሌክትሪክ መስመር በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ሁለት እጆቻቸው የተቆረጡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በሰበር ደረጃ አደጋው የደረሰው ተጠሪ ከፍተኛ መስመር ይተላለፍበት የነበረውን የኤሌክትሪክ መስመር በፊሮ ብረት ስለነካ ነው፡፡ ጥፋቱ የተጠሪ በመሆኑ ኃላፊ ልንሆን አይገባም በማለት በሰበር አቤቱታው ገልጿል፡፡ ሆኖም ይህ አመልካች በሰበር ያቀረበው ክርክር ለስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ የፍሬ ጉዳይ መከራከሪያና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329/1/ የሚቃረን በመሆኑ ሥርዓቱን ጠብቆ የቀረበ መከራከሪያ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በወቅቱ አደጋው የደረሰው በተጠሪ ጥፋት ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ መሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና በከፍተኛ ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች በስር ፍ/ቤት ማስረጃ የማቅረብና ክርክሩን የማስረዳት ግዴታውን በአግባቡ ሳይወጣ በሰበር ያቀረበው ክርክር ለሰበር ችሎት በህገመንግሥቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 የተሰጠውን ሥልጣን ከግንዛቤ ያላስገባና ህጋዊ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንድ ሰው የሚፈነዱ ወይም መርዝ የሚሆኑ ቅመማት ሥራ ላይ በማዋል ወይም በማከማቸት ወይም ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር በመዘርጋት ወይም መሬትን የተፈጥሮ መልክ በመለወጥ ወይም በተለይ አደገኛ የሆነ የኢንዱስትሪ ሥራ በማካሄድ ይህ ሥራው በሌላው ሰው ላይ አደጋ ያደረሰ እንደሆነ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069/1/ የሚደነግግ ሲሆን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ተግባራትን በመፈፀም በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰው መንግሥትም ቢሆን ወይም ሥራውን እንዲሠራ በባለሥልጣን የተፈቀደለት መሥሪያ ቤት ቢሆንም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ደንብ ተፈፃሚ የሚሆን መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ አመልካች ከላይ በተገለፁት የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ለደረሰው ጉዳት የኤሌክትሪክ መስመሩ ባለሀብት በመሆኑ ብቻ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካች በጉዳቱ ካደረሰው ጉዳት በኃላፊት የማይጠይቀው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2086 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚደነግገው መሠረት ጉዳቱ የደረሰው በሙሉ ወይም በከፊል በተበዳዩ ጥፋት መሆኑን በማስረጃ በማስረዳትና በማረጋገጥ ነው፡፡ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ አለመሆኑን ለማስረዳትም በመጀመሪያ የኤሌክትሪክ መሥመሩን የሚንስትሮች ምክር ቤት ስለ ኤሌክትሪክ ሥራዎች ባወጣው ደንብ ቁጥር 49/1991 አንቀጽ 35 ስለ ኤሌክትሪክ መስመሮችና መሣሪያዎች ደህንነት የደነገገውን በሚያሟላ ሁኔታ ተዘርግቶ የነበረ መሆኑንና በዚሁ ደንብ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በስር ሁለተኛ ተከሣሽ በነበረው ግቢ ከምድር በላይ ዘርግቶት የነበረው መስመር የአደጋ መከላከያ ፕላስቲክ ተሸፍኖ የነበረ መሆኑንና ተጠሪ ጥፋት የሆነ አደጋ የሚያስከትል ተግባር በመፈፀሙ ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234/1/ እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 223 መሠረት ከመከላከያ መልስ ጋር ዘርዝሮ በማቅረብና የሠነድ ማስረጃዎቹን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 339/1/ በሚደነግገው መሠረት በማቅረብ የማስረዳት ግዴታውን መወጣት አለበት፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከላይ በተገለፀው መሠረት አደጋው የደረሰው በተጠሪ ጥፋት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑና የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069 ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ በመሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤትና ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔና ለጉዳቱ የወሰነው የካሣ መጠን መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ይህ ፍርድ ቤት ሐምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አለምነው አበበ አካሌ - ቀረበ

ተጠሪ፡- ህብረት ኢንሹራንስ አ/ማ - ቃልኪዳን ንጉሴ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በመኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት መነሻ በማድረግ የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ በወቅቱ ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ አመልካችን የከሰሰው የመድን ዋስትና በገባለት የደንበኛው መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት ነው፡፡ አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የሥረ ነገር ክርክር አቅርቦአል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎአል በዚህ መሠረትም አመልካች በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል የወጣውን ወጪ ብር 5,500 ከእነ ሕጋዊ ወለዱ ጋር እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ የተደረገው በሕጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ክርክሩ ሊነሣ የቻለው አመልካች በተጠሪ የመድን ዋስትና የተገባለትን መኪና በመግጨት ጉዳት አድርሶአል በመባሉ ነው፡፡ ገጭቶ ጉዳት ያደረሰው መኪና የአመልካች ንብረት ከመሆኑም በላይ ሲሸከረከር የነበረውም በራሱ ማለትም በአመልካቹ እንደሆነ አላከራከረም፡፡ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች የይርጋ መቃወሚያ ያነሣው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2143/1/ የተቀመጠውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ክሱን የሰማው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃሚያው ሣይቀበል የቀረው ለይርጋው መቃወሚያ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ድንጋጌ በንዑስ ቁ./1/የተመለከተው ሣይሆን፣ በንኡስ ቁ. /2/ ያለው ነው በማለት ነው፡፡ ጊዜው ከዚህ ድንጋጌ አንፃር እየታየ ሲሰላም የክስ ማቅረቢያ ጊዜው አልፎአል ሊባል አይችልም እሚል መደምደሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ደርሶአል፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው አቤቱታ የይርጋ መቃወሚያውን በሚመለከት ያነሣው ዋነኛ የመከራከሪያ ነጥብ በወንጀል ተከሰሼ አልተቀጣሁም፡፡ ስለዚህም በንኡስ ቁ. /2/ የተመለከተው ድንጋጌ ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ጉዳት ሊደርስ የቻለው በአመልካች ጥፋት አይደለም የሚል በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ ይልቁንም ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ጥፋት ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሶአል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ነው ከተባለ ደግሞ ድርጊቱ በወንጀልም የሚያስከስስ /የሚያስቀጣ/ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ድርጊቱ /ጉዳቱ/ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት በወንጀል ሕጉ በተደነገገው መሠረት እንደሚሆን ከላይ በተመለከተው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2143/2/ ተደንግጎአል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው ደግሞ ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑ ከሚታይ በቀር የድርጊቱ ፈፃሚ ተከሶ መቀጣት እግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም በወንጀል አልተከሰስኩም ወይም አልተቀጣሁም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት ያለው አይደለም በመጨረሻም የሥር ፍ/ቤቶች የይርጋውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረጋቸው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 158634 ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 94803 ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡን ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ይልማ ደጀኔ - ጠበቃ አቶ ስሜነህ ተክሉ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መዲና ዲታም - ጠበቃ አቶ ዘካሪያስ ምንተስኖት - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርበው ተከሣሹ /አመልካች/ የሻንሲ ቁጥር 8991 የሆነ ተሣቢ መኪና በውል ገዝተን ነበር፡፡ ተከሣሽ የገዛውን የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነ ተሣቢ መኪና ዴክላራሲዮን ትክክለኛነት አረጋግጣለሁ በማለት የሌሎች ተሣቢ መኪኖች ማለትም የሻንሲ ቁጥሩ 8951 እና የሻንሲ ቁጥሩ 8793 ተሣቢ መኪና ዴክላራሲዮን ከከሣሽ ወስዷል፡፡ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል ቀሪ ሆኖ ተከሣሽ በቅድሚያ ክፍያነት የከፈለውን ብር 50,000 /ሀምሣ ሺ ብር/ ከከሣሽ ተቀብሎ ወስዷል፡፡ ተከሣሽ የሶስቱን ተሣቢ መኪኖች ዲክላራሲዮን እንዲመልስ ቢጠየቅ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ተከሣሽ የተሣቢ መኪኖቹን ዴክላራሲዮን ባለመመለሱ ከሣሽ በተሣቢ መኪኖቹ ሰርተው የሚያገኙት ገቢና ጥቅም ቀርቶባቸዋል፡፡ መኪኖቹ ከቆሙበት ከሐምሌ 22 ቀን 1999 ዓ.ም ክስ እስከ ቀረበበት ጥር 6 ቀን 2000 ዓ.ም የአንድ ተሣቢ የወር ገቢ ብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ የሶስቱ ተሣቢ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺ ብር/ ሂሣብ የአራት ወር ከሃያሰባት ቀን ብር 147,000 /አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺ ብር/ እና መኪኖቹን ለማስጠበቅ የወጣ ብር 22,500 /ሃያ ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር/ በድምሩ ብር 169 500 /አንድ መቶ ስልሣ ዘጠኝ ሺ አምስት መቶ ብር/ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ የአሁን አመልካች በተከሣሽነት ቀርበው የሻንሲ ቁጥር 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል ቀሪ አልሆነም፡፡ ተከሣሽ ከከሣሽ ብር 50,000 /ሀምሣ ሺ ብር/ የወሰድኩት የመኪናው ቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ተመልሶልኝ ሣይሆን ከከሣሽ ጋር ባለኝ የግል ግንኙነት የሰጡኝ ነው፡፡ እኔ የተቀበልኩት የተሣቢ መኪና ዲክላራሲዮን የለም፡፡ ለክስ ሀላፊነት የለብኝም፡፡ አንድ ተሣቢ መኪና በወር ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

10,000 /አስር ሺ ብር/ ገቢ አያስገኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል አልፈረሰም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ተከሣሽ የሻንሲ ቁጥሩ 8951 እና 8993 የሆኑትን ተሣቢዎችና የገዛውን ተሣቢዎች ዴክራላሲዮን ይዞ ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከሣሽ በመኪናዎቹ ሊያገኙ ይችሉት የነበረው ጥቅም ቀርቶባቸዋል፡፡ ጉምሩክና የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን በሰጠው መረጃ መሠረት የሁለቱ ተሣቢ መኪናዎች የቀረ ገቢ ብር 99,290.80 /ዘጠና ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ብር ከሰማኒያ ሣንቲም/ ለተሣቢ መኪኖቹ ማስጠበቂያ የወጣ ብር 12,800 /አስራ ሁለት ሺ ስምንት መቶ ብር/ በድምሩ ብር 112090.80 /አንድ መቶ አስራ ሁለት ሺ ዘጠና ብር ከሰማኒያ ሣንቲም/ ከነ ወለዱ ተከሣሽ ለከሣሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነውን ተሣቢ መኪና አመልካች ለመግዛት ያደረገው ውል ፈራሽ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ በይግባኝ ይታይልኝ፡፡ የሁለቱ ተሣቢ መኪኖች የቀረ ገቢ የአንደኛው በወር ብር 10,000 /አስር ሺ ብር/ የሁለቱ ብር 20,000 /ሃያ ሺ ብር/ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረብኩትን ማስረጃ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገብኝ አላግባብ ነው በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሶስት ተሣቢ መኪና ዴክላራሲዮን ወስደሀል በዚህም ጉዳት አድርሰሀል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በሚል መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ ላይ አመልካች የሰጡትን መልስና ክርክር ከተቀበለና አመልካች ባቀረቡት መስቀለኛ ይግባኝ ላይ ግራቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካችን መስቀለኛ ይግባኝ የህግ መሠረት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ውድቅ አድርጐታል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪን ይግባኝ ክርክር በመቀበል የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ሽያጭ ውል እንዳይፈጸም ችግር የፈጠረው የአሁን አመልካች መሆኑን ከዘረዘረ በኋላ ተጠሪና አመልካች የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነውን ተሣቢ በተመለከተ ያደረጉት የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሉ ፈራሽ አይደለም በማለት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሻንሲ ቁጥራቸው 8951 እና 8793 ከሆኑ ሁለት ተሣቢዎች የቀረ ገቢ የአንዱ በወር ብር 10,000 የሁለቱ ተሣቢ ብር 20,000 /ሃያ ሺ ብር/ ሂሣብ መያዝ ይገባዋል በማለት አመልካች ከሐምሌ 22 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ጉዳዩ በይግባኝ ውሣኔ እስከተሰጠበት ታህሣስ 22 ቀን 2002 ዓ.ም ታስቦ ብር 480,000 /አራት መቶ ሰማኒያ ሺ ብር/ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የካሣ ውሣኔ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የሰጠው ውሣኔ የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ዴክላራሲዮን ወስዷል ተብሎ ጥፋተኛ መባሉና ካሣ እንዲከፍል መወሰኑ የተሣቢ መኪና ሽያጭ ውሉ አፈጻጸም ጋር ለማቀላጠፍ አመልካች የሰራውን ስራ የሚያሣይና ሰነድ መስጠት የተጠሪ ግዴታ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል ተጠሪ በበኩላቸው ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ሐምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሣቢዎቹ የወር ገቢን በተመለከተ ከግል የትራንስፖርት ድርጅት የተሰጠውን መረጃ መሠረት በማድረግ መወሰኑና የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን መረጃ ተቀባይነት የለውም በማለት መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውንና ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት በመጀመሪያ አመልካች የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነውን ተሣቢ መኪና ከተጠሪ ለመግዛት የተዋዋልኩት ውል እንዲፈርስ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የህግ መሠረት የለውም በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነውን መኪና ተጠሪ ለአመልካች ለመሸጥ የተዋዋሉት ውል ፈራሽ አልሆነም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በግልጽ ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡

ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ይህንን ውሣኔ በመቃወም ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪና አመልካች የሻንሲ ቁጥሩን 8991 የሆነ ተሣቢ መኪናን በተመለከተ ያደረጉት የሽያጭ ውል አመልካች አፈጻጸሙን አስቸጋሪና ከባድ ያደረገው በመሆኑ ፈራሽ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነውን ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል ሊጸናና ህጋዊ ውጤት ሊኖረው ይገባል ወይስ ፈራሽ ሊሆን ይገባል የሚለውን ጭብጥ ማዕከል በማድረግ አመልካችና ተጠሪን አከራክሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡ ይኸውም በመሆኑ አመልካች የተሣቢ መኪናውን ሽያጭ ውል በተመለከተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ የሚገባቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ይህንን የይግባኝ ስርዓት ሣይጨርሱ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ብሎ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በሰበር እንዲታይላቸው ያቀረቡት አቤቱታ ጉዳዩን አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የመስጠት ስልጣን ባለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ ያልታየና የመጨረሻ ውሣኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3 /ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተደነገገውን መስፈርት የማያሟላ በመሆኑ በሰበር ችሎት ቀርቦ ለመታየት የሚችል ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው በውል ያልገቧቸውንና የመኪናዎቹን ዴክላራሲዮን ይዞ ለመቆየት የሚያስችላቸው ከውል ወይም ከህግ የመነጨ መብት ሣይኖራቸው ንብረታቸው የተጠሪ የሆኑ ሁለት ተሣቢዎች ዴክላራሲዮን ይዞ ቆይቷል፡፡ አመልካች የሻንሲ ቁጥራቸው 8793 እና 8951 የሆኑ ተሣቢ መኪኖች አላግባብ በመያዙና ለተጠሪ ለመመልስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ጥፋት በሆነ ድርጊት ተጠሪ ሁለቱን መኪኖች አስፈላጊ ፎርማሊቲ በማሟላት ወደ ስራ አሰማርተው ሊያገኙ የነበረው ጥቅም እንዲቀር ምክንያት ሆኗል ተብለው ነው፡፡ አመልካች ዴክላሲዮኖቹን አላግባብ በመያዝ ጥፋት ስለመፈጸማቸውና በዚህ ምክንያት ተጠሪ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ለጉዳቱ አላግባብ ሀላፊ ተብያለሁ በማለት ያቀረቡትን የሰበር ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች ለተጠሪ መክፈል የሚገባውን የካሣ መጠን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የካሣ ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በማሻሻል ውሣኔ የሰጠውን የካሣ ውሣኔ በተመለከተ ይግባኝ ስለሚቀርብበትና ተቀባይነት ስለሚያገኝበት ሁኔታ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ መሆኑ ወይም አለመሆኑ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪ ሁለት መኪናዎች ወደ ስራ ቢሰማሩ ያስገኙ የነበሩትን የገቢ መጠን ከመወሰኑ በፊት ተሣቢ መኪናዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በስራ ተስማርተውና ገቢ አስገኝተው የማያውቁ በመሆኑ የካሣውን መጠን ተሣቢዎቹ ሰርተው ወይም ተከራይተው ያስገኙትን ገቢ ለመወሰን የማይቻል መሆኑ የካሣው መጠን አወሣሰን ላይ ችግር የፈጠረ መሆኑን በውሣኔው ገልጿል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተሣቢ መኪናዎቹ ሰርተው ወይም ተከራይተው የሚያስገኙት ገቢ በማይታወቅበት ሁኔታ የሻንሲ ቁጥራቸው 8951 እና 8793 የሆኑት ተሣቢ መኪኖች የተመረቱበትን ዘመንና የመሸከም አቅማቸው ተመሣሣይ የሆኑ ተሣቢ መኪኖች አማካኝ አመታዊ ገቢ ምን ያህል እንደሆነ የኢትዮጵያ ጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ መረጃ ማግኘቱ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት መረጃው እንዲላክለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ ጉምሩክና ገቢዎች ባለስልጣን በስር ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከተመረተ /ከተፈበረከ/ አስራ አምስት ዓመት ያልሞላው ተሣቢ አማካኝ አመታዊ ገቢ በ 36,888 /ሰላሣ ስድስት ሺ ስምንት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር/ እንደሆነና ከተመረተ /ከተፈበረከ/ ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሆነው ተሣቢ መኪና ገቢ 31,355 /ሰላሣ አንድ ሺ ሶስት መቶ ሀምሣ አምስት/ መሆኑን በጽሁፍ አረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ተሣቢ መኪኖች ከተመረቱ አስራ ስምንት ዓመት በላይ የሆናቸው ለመሆኑ የጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን የሰጠውን ማረጋገጫ መሠረት በማድረግ አመልካች ለተጠሪ መክፈል ያለበትን የካሣ መጠን ወስኗል፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሀላፊ የሆነው ከውል ውጭ ጥፋት በሆነ ድርጊት የሁለቱን መኪናዎች ዴክላራሲዮን አላግባብ ይዞ አልመልስም በማለቱ ምክንያት ነው፡፡ ከውል ወጭ ሀላፊ የሆነ ሰው ለተጐጂው የሚከፍለው የካሣ መጠን በመርህ ደረጃ ይግባኝ የማይቀርብበት እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 ስለኪሣራ ጥቅም አከፋፈል በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች የተወሰነ ፍርድ ላይ ለበላይ ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ማለት አይቻልም በማለት በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ የካሣ ውሣኔ በሰጠው ፍርድ ቤት ውሣኔ ላይ ይግባኝ የሚፈቀደው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ልዩና የተጠበቁ ሁኔታዎች ሲኖሩ ነው፡፡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 የተደነገጉት ልዩና የተጠበቁ ሁኔታዎች ሶስት ሲሆኑ እነርሱም፡-

/ሀ/ ዳኞች ሊገምቱት የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ አላግባብ በመያዝ ውሣኔ ሰጥተው እንደሆነ ወይም ሊገምቱት የሚገባቸውን ትክክለኛውን መንገድ ትተው ያላግባብ የሆነውን አገማመት መንገድ ይዘው የተገኙ እንደሆነ

/ለ/ በዳኞች የተወሰነው የኪሣራ ገንዘብ ልክ በግልጽ ከአእምሮ ግምት ውጭ የሆነና የተወሰነውም በማዳላት ወይም በዝንባሌ መሆኑ እርግጥ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/ሐ/ በዳኞች የተወሰነው የጉዳት ካሣ በሒሣብ መሣሣት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን አጣርቶ የላከለትን ዓመታዊ አማካኝ ገቢ መሠረት በማድረግና ተሣቢዎቹ ወደ ስራ ተሰማርተው የማያውቁና ለካሣ ውሣኔ መነሻ የሚሆን እርግጥኛ ገቢ የሌላቸው መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት የወሰነው የኪሣራ /የካሣ ውሣኔ/ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 ከተደነገገው በተለየ ሁኔታ በይግባኝ ሊታይ የሚችልበት ልዩ ምክንያትና ሁኔታ ያለ መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ድንጋጌዎች አንጻር የሰጠው ምክንያትና ትንታኔ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የወሰነው የካሣ ውሣኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ከተደነገጉትና ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት የሚያስችሉ ልዩ ሁኔታዎች የትኛውን ድንጋጌ የስር ፍርድ ቤት እንደተላለፈ ሣይገጽና ሣያረጋግጥ የካሣውን መጠን በይግባኝ አይቶ ማሻሻሉ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 መሠረታዊ መርህ የሚጥስና ህግ አውጭው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 በመደንገግ ሊያሣካ የሚፈልገውን መሠረታዊ ግብና ዓላማ የማያሣካ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የተጠሪ ሁለት ተሣቢዎች ወደ ስራ ተሰማርተው ገቢ አስገኝተው የማያውቁ ከተመረቱ ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሆናቸው በተጠሪ ተሣቢ መኪኖች የመሸከም አቅምና እድሜ የሚገኙ ተሣቢዎች በአመት የሚያስገኙት የተጣራ ገቢ ብር 31,355 /ሰላሣ አንድ ሺ ሶስት መቶ አምሣ አምስት ብር መሆኑን የኢትዮጵያ ጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን አጣርቶ የሰጠውን ማስረጃ መነሻ በማድረግ በመሆኑ በጉዳዩ ሊገመቱ የሚገባቸውን የነገሩን አካባቢ ሁኔታዎች በአግባቡ በመያዝና ትክክለኛውን መንገድ በመከተል የካሣ መጠኑን ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ያሣያል፡፡

በሌላ በኩል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጣራ ሁለት ተሣቢ መኪኖች የተመረቱበትን ዘመን የመኪኖቹን ጭነት የመሸከም አቅምና መኪኖቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ሰርተው የማያውቁ በመሆኑ መኪኖቹ ሊያስገኙት የሚችሉትን እርግጠኛ ገቢ ለመወሰን ችግር እንዲፈጠር ከግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባ የኢትዮጵያ ጉምሩክና ገቢዎች ባለስልጣን የላከውን መረጃ ያለ በቂ ምክንያት ውድቅ በማድረግ የግል የትራንስፖርት ድርጅት የጻፈውን አስተያየት ብቻ መነሻ በማድረግ አንድ ተሣቢ በወር ብር 10,000 /አስር ሺ ብር/ የተጣራ ገቢ ያስገኛል፤ ሁለቱ ተሣቢዎች በወር ብር 20,000 /ሃያ ሺ ብር/ የተጣራ ገቢ ያስገኛሉ በማለት የስር ፍርድ ቤት የወሰነውን የካሣ መጠን በመሻሻል አመልካች ለተጠሪ ብር 480,000/ አራት መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች የተደነገጉት ልዩና የተጠበቁ ጉድለቶች የሚታዩበትና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ከጅምሩ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የካሣ መጠን በይግባኝ ለማየትና ለማሻሻል የሚያስችሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 የተደነገጉ ጉድለቶች ያሉበት መሆኑን ሣያረጋግጥ ጉዳዩን በይግባኝ በማየትና የኢትዮጵያ ጉምሩክና አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን አጣርቶ የላከውን መረጃ ወደ ጐን በመተው የግል የትራንስፖርት ድርጅት የተጻፈውን አስተያየት መሠረት በማድረግ የካሣውን መጠን መወሰን ነበረበት በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔን በማሻሻል የሰጠው የካሣ ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. አመልካት ተጠሪ የሻንሲ ቁጥሩ 8991 የሆነው ተሣቢ መኪና በተመለከተ ያደረጉት የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 መሠረት በይግባኝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሣይታይና ሣይወሰን በሰበር ቀርቦ መታየት የሚችል ባለመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡
2. የሻንሲ ቁጥራቸው 8951 እና 8793 የሆኑ ተሣቢ መኪኖች በአመልካች ጥፋት ምክንያት ባለመስራታቸው አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባዋል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ጉዳዩን አይቶና አሻሽሎ የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2152 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2153 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 የሚጥስ ሆኖ በመገኘቱ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ብር 112090.80 /አንድ መቶ አስራ ሁለት ሺ ዘጠና ስምንት ብር ከሰማኒያ ሣንቲም/ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አጽንተናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ በየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44427

መጋቢት 09 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- አቶ ለገሠ ጥቀሌር - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር - ነ/ፈጅ ጌታሁን ወርቁ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው የአሁን አመልካች የተጠሪ ባንክ አ/ማህበር ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በማለፍ በፈፀመው ተግባር ምክንያት በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ያለበት ኃላፊነት ምንድን ነው? የሚለውን ግራቀኙ ባሉበት አከራክሮ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች የተጠሪ የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ እያገለገሉ በነበሩበት ጊዜ ከተሰጣቸው ሥልጣን በላይ በማለፍ ስርዎት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ለተባለ ድርጅት ብር 2,899,984.25 (ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አራት ከ25/100) የሆነ የብድር ገንዘብ ያለምንም ዋስትና ብድር እንዲፈቀድለት በወሰኑት መሠረት ይኸው የብድር ገንዘብ ለተበዳሪው መለቀቁንና ተበዳሪውም በገባው ግዴታ መሠረት በብድር የወሰደውን ገንዘብ ሊመልስ አለመቻሉ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን፤ ይህም ከሥልጣኑ በላይ በማለፉ ብድር እንዲለቀቅ የሚያደርግ ውሣኔ የመስጠት ተግባር ባንኩ በብድር የተወሰደውን ገንዘብ መልሶ ለመሰብሰብ ያላስቻለውና በዚህም ሳቢያ ጉዳት የደረሰበት ስለመሆኑም አላከራከረም፡፡ ይህንኑ በብድር የተሰጠውን ገንዘብ በሙሉም ሆነ በከፊል ተጠሪ ሰብስቧል የሚል ክርክርም አልቀረበም፡፡

አመልካች የተጠሪ ባንክ የሥራ ኃላፊ መሆኑ፤ የሥራ ኃላፊነቱን ሲያከናውን በተሰጠው ሥልጣን ክልል ውስጥ መሆን እንደሚገባው ከባንኩ የበላይ ውሳኔ ሰጭ አካል የገንዘብ ጣሪያ ተበጅቶ ኃላፊነት መረከቡን፤ ይህንኑ የሥልጣን ወሰን በመተላለፍ ተግባር ፈፅሞ በቀጣሪው ባንክ ላይ የገንዘብ ጉዳት አድርሶ መገኘቱ የተረጋገጡ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ሆነው እስከተገኙ ድረስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2524 እንደተመለከተው አመልካቹ በፈፀመው ተገቢ ያልሆነ ተግባር ምክንያት በአሠሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አስረጂ ነው፡፡

በተጠሪ ላይ ለደረሰው የገንዘብ ጉዳትም ይህ የአመልካቹ ተግባር ቀጥተኛ መንስኤ መሆኑን ከሚያመለክት በቀር ለብድሩ አለመመለስ ምክንያት የሆነ ሌላ ጉዳይ ስለመኖሩ ሳይገለፅ፤ ሳይረጋገጥ በብድር የተሰጠው ገንዘብ ሳይመለስ መቅረቱ በዚህ በአመልካች ተግባር ምክንያት ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል አይደለም፤ በምክንያቱና በውጤቱ መካከል ቅርብ የሆነና በቂ ግንኙነት አለ ማለት አይቻልም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ትንታኔ ከላይ በፍሬ ነገር ረገድ ላይ የተረጋገጠውንና በጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በውል ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዚህም ምክንያት በተጠሪው ላይ ለደረሰው የገንዘብ ጉዳት አመልካች ኃላፊ መሆኑን ጠቅሶ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በተጠሪው ላይ የደረሰው የጉዳት ልክ ምን ያህል ነው የሚለውንም ነጥብ በተከታይ እንዳየነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2524(2) አስቦ ወይም በቸልተኝነት ወይም ባለመጠንቀቅ በአሠሪው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሠራተኛው ኃላፊ መሆኑ ከታወቀ በአሰሪው ላይ የደረሰውን ጉዳት አስልቶ እንዲከስ ለማድረግ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ህግ መሠረት ልናደርግ ይገባል ይህ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ተገቢ ያልሆነው የአመልካች ተግባር የተፈፀመውና ጉዳቱ የደረሰው አመልካችና ተጠሪ ካደረጉት የቅጥር ውል የመነጨ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1676(1) እንደተመለከተው የግራ ቀኙን ውል በሚገባው ልዩ የውል ደንብ ውስጥ ደረሰ የሚባለውን የጉዳት ዓይነትና መጠን የሚያመለክት ዝርዝር ህግ ካልተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1790(2) እና 2090 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት የጉዳት ልክ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ከዚህም አንፃር ይህንን ጉዳይ ስንመለከተው አመልካች ከሥልጣኑ በላይ በፈፀመው ተግባር ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት የገንዘብ ሲሆን መጠኑም የብድር ገንዘቡ በአግባቡ ተሰጥቶ ቢሆን ኖሮ ባንኩ ማስመለስ ይቻል የነበረው ነገር ግን ሳይመለስ የቀረው እንጂ ከዚህ ያነሰ ወይም የበዛ ሆኖ አይታይም በዚህ ሁሉ ምክንያት የግራ ቀኙን ጉዳይ በይግባኝ ተመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የኃላፊነቱን እና የጉዳት መጠኑን አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም በኢትዮጵያ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት አንድ የመጨረሻ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታረም የሚችለው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ብቻ መሆኑን በማየት የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 37856 ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የሰበር ክርክር ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ ስላላገኘነው ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ከዚህ በፊት በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
   በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ወጭና ኪሣራ ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ራ/ታ ***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59698

መጋቢት 6 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገብረ ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሚኪያስ ከበደ ከጠበቃ ገ/ክርስቶስ ኪዳነ ማርያም ጋር - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ምስራቅ ንጉሴ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ አልማዝ ገብረብርሀን } ጠበቃ ተስፋዬ ደጉ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር የቀረበ በመሆኑ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች አመልካች ከአቶ ከበደ ታዬ ጋር በመሆን እያንዳንዳችን አምስት አምስት ሰው በኮንደሚኒየም ቤት እንዲያገኙ እድል የተሰጣቸው መሆኑን በመግለፅ አንደኛ ተጠሪ /አንደኛ ከሣሽ/ ከዘጠኝ ዘመዶቼ ሰብስቤ የሰጠሁትን ብር 185,000/አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ብር/ ሁለተኛ ተጠሪ /ሁለተኛ ከሣሽ/ ከዘመድ ሰብስበው የሰጡትን ብር 210,000/ሁለት መቶ አስር ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 395,000 /ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ብር / ወስደዋል፡፡ ስለሆነም በማታለልና በማጭበርበር የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት አመልክተዋል፡፡ አመልካችና በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት አቶ ከበደ ታዬ ተጠሪዎች / ከሣሾች/ ክስ ያቀረቡባቸው በይሆናል እና በግምት ነው ማስረጃ የላቸውም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን ምስክሮችና በአመልካችና በአቶ ከበደ ታዬ ላይ የተጀመረውን የፖ/ሊስ የወንጀል ምርመራ መዝገብ አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አመልካች ብር 395,000 /ሶስት መቶ ዘጠኛ አምስት ሺህ ብር / የወሰደ መሆኑን በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን በመግለፅ አመልካች ለተጠሪዎች ብር 395,000/ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ብር/ እንዲመልስና አቶ ከበደ ታዬ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 130,000 አቶ ከበደ ታዬ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካችን በተመለከተ የተሰጠው ውሣኔ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ነሐሴ 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች ገንዘብ ለእኔ የሰጡ መሆኑን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አላቀረቡም ፍርድ ቤቱ ለፖሊስ የተሰጠን ቃል አላግባብ በማስረጃነት በመጠቀምና በፖሊስ ተፅዕኖ የደረሰብኝ መሆኑን ለማስረዳት እየጠየቅሁ እያለሁ አላግባብ ብር 395,000 ለተጠሪዎች እንድመልስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ኮንደሚኒየም ቤት አሰጣችኋለሁ በማለት የማታለል ክስ ያቀረብንበትን ገንዘብ የወሰደ መሆኑን በማስረጃ አስረድተናል፡፡ አመልካችም ለፖሊስ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27/1/ በሰጠው የተከሣሽነት ቃል ብቻ ሣይሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 ለፍርድ ቤት በሰጠው የእምነት ቃል አረጋግጧል፡፡ ይኸ ማስረጃ በፍታብሔር ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በሥር ያላነሳውን አዲስ ክርክር በማቅረብ ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

አመልካች ታህሣሥ 20 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪዎች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ የጠቀሱትን ገንዘብ ለተጠሪዎች እንዲመለስ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለዉ ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪዎች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ የሆኑት አቶ ከበደ ታዬ፣ ቤቱ ለልማትና ኢንቨስትመንት የፈረሰበት ሰው ዘጠኝ ዘጠኝ ሰው ኮንደሚኒየም ቤት እንዲያገኝ ማድረግ እንደሚችል በመንግስት ውሣኔ የሰጠበት በመሆኑ ገንዘብ አሰባሰባችሁ አምጡ በማለት ከአንደኛ ተጠሪ ብር 185,000 ከሁለተኛ ተጠሪ ብር 210,000 የራሳቸውን ድርሻና ከዘመድ ያሰባሰቡትን ከወሰዱ በኋላ ሌሎችን ሰዎች በመቁጠር የተወሰነውን ገንዘብ የመለሱ መሆኑንና ብር 395,000 የሚፈለግባቸው መሆኑን የሚያስረዱ የሰው ምስክሮች አቅርበዋል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች ገንዘቡን ለእኔ የሰጡ መሆኑን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አላቀረቡም የበታች ፍርድ ቤቶች በህግ በኩል ተቀባይነት የሌለውን የሰው ምስክር በመስማት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

አንድ ሰው የሌላውን ሰው የሥራ ድካም ወይም በሌላው ሰው ሀብት በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ እንደሆነ አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሀብቱ ወይም በጉልበቱ ለደከመው ሰው የመመለስና የመካስ ግዴታ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 በመሠረታዊ መርህነት ተደንግጓል፡፡ አመልካች የኮንደሚኒየም ቤት ታገኛላችሁ ለኮንደሚኒየም ቤት የሚከፈል ነው በማለት ከተጠሪዎች ገንዘብ በመውሰድ ያልመለሰና ያለበቂ ምክንያት በገንዘቡ የተጠቀመ መሆኑን ተጠሪዎች በምስክር አስረድተዋል፡፡ ከሣሽ ተከሣሹ በንብረቱ ወይም በገንዘቡ አላግባብ የበለፀገና የተጠቀመ መሆኑን የሰነድ ማስረጃ ብቻ በማቅረብ ማስረዳት ያለበት መሆኑን የሚደነግግ ግልፅ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ የአንድ ማስረጃ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑ የሚወሰነው በህግ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪዎችን በማታለል ከተጠሪዎች ገንዘብ የወሰደ መሆኑን በምስክርና በሌላ ማስረጃ እንዲያስረዱ የበታች ፍርድ ቤቶች መፍቀዳቸው ተገቢ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ተቀብሎ የወሰደ መሆኑን በማታለል ወንጀል በተደረገበት ምርመራ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 መሠረት ለፖሊስና ለፍርድ ቤት በማመን ቃላቸውን የሰጡ መሆኑን በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በማስረጃነት ከቀረበው የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ተረጋግጧል፡፡ በማለት በሥርና በሰበር ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ለፖሊስ የሰጡት የተከሣሽነት ቃል በፖሊስ በደረሰብኝ ተዕዕኖ የተሰጠ ነው በማለት በሰበር አቤቱታቸው ከመግለፃቸው በስተቀር ከተጠሪዎች ገንዘብ ተቀብለው የወሰዱ መሆኑን በማመን ለፖሊስና ለፍርድ ቤት ቃል አልሰጠሁም በማለት በግልፅ ክደው አልተከራከሩም፡፡ አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 27 እና አንቀፅ 35 የተሰጠው የዕምነት ቃል የተጠሪዎችን ክስ ለማስረዳት የማይችልና ተገቢነት የሌለው ማስረጃ ነው በማለት ለሰበር በሰጠው የመልስ መልስ ያቀረበው ክርክር በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 235/2/ መሠረት በመሸሸ መልክ የተሰጠና እንደታመነ ሊቆጠር የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ገንዘቡን ከተጠሪዎች ተቀብሎ የወሰደ መሆኑ በፖሊስና በፍርድ ቤት ከሰጠው የዕምነት ቃል እንዳረጋገጠ በሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተገልያል፡፡ አንድ ሰው ባለዕዳ መሆኑን ያመነ እንደሆነ ዕዳው የታመነለት ሰው ባለዕዳው ዕዳውን ያመነበትን ምክንያት የማስረዳት/የማረጋገጥ / ግዴታ የሌለበት መሆኑን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2019 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም ተቃራኒ ማስረጃ ከሌለ በስተቀር ባለዕዳው ዕዳ እንዳለበት በማመን የሰጠው የዕምነት ቃል በአእምሮ ግምት በሚገባ/ በአግባቡ / የተሰጠ ቃል ነው ተብሎ የሚቆጠር መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2019 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡

አመልካች ለፖሊስ የተከሣሽነት ቃሌን ስሰጥ ከተጠሪዎች ገንዘብ ተቀብዬ ወስጃለሁ በማለት ቃሌን የሰጠሁት ፖሊስ ባደረሰብኝ ተዕዕኖ ምክንያት ነው በማለት በሰበር አቤቱታው የገለፀ ቢሆንም ይህንን ክርክሩን የሚያስረዳ ማስረጃ ለሥር ፍርድ ቤት አላቀረበም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የተጠሪዎች ዕዳ እንዳለበት በማመን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 የሰጠው የእምነት ቃልን ለማስተባበል የሚችል ተቃራኒ ማስረጃ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2019 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት አላቀረበም፡፡ ስለሆነም አመልካች በሰበር ደረጃ ያነሣው ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሣና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329/1/ን የሚጥስ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የፖሊስን የምርመራ መዝገብ በማስቀረብ በምርመራ መዝገቡ የሰጠሁት የተከሣሽ ቃል በማስረጃነት መጠቀሙ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ቅሬታ አቅርቧል፡፡ ሆኖም በፍታብሔር ጉዳይ ፖሊስ ያጣራውን የምርመራ መዝገብ አስቀርቦ እንዳያይ የሚከለክል የማስረጃ ህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በህግ ተቀባይነት የሌለውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ የበታች ፍርድ ቤቶች ወስነውብኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ በማስረጃ ህግ መሠረት ተቀባይነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመቀበልና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 ፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2164 /1/ እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2019 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. የሰበር ችሎት ታህሣሥ 13 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 64590

ሚያዝያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሊ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች ፡- ሜሪስቶኻስ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ - ጠበቃቸው አቶ ኃይልዩ ሳህለ

ተጠሪ ፡- ወ/ት ሠናይት ዓለማየሁ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በሰበር ተጠሪ ክሳሽነት ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ፍሬ ቃሉ በተከሳሽ ድርጅት /በሰበር አመልካች/ ምርመራ ተደርጐልኝ "ኖርኻላንት" የተባለ የወሊድ መከላከያ መደኃኒት በክንድ እንዲቀበር ከተደረገ በኃላ መድኃኒቱ ህመም ስላስከተለብኝ ተከሳሽ በራሱ የህክምና ባለሙያዎች መድኃኒቱ እንዲወጣ ሲያደርግ በባለሙያዎቹ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ባለመደረጉ የተነሣ መድኃኒቱ የተቀበረበት እጄን ለማያቋርጥ ህመምና ስቃይ የዳረገኝ ከመሆኑ ሌላ በጡትና በጀርባዬ ላይ ባስከተለው የመሸማቀቅ ህመም የተነሣ የጀርባ ህመም፣ የፊት ማበጥ እና የልብ ህመም አስከትሎብኛል፡፡ ህመሙም በመወሳሰቡ የደም ዝውውር ስርዓት ላይ ችግር በማስከተል የደም ቱቦ በመዘጋቱ እጄ እየመነመነ በመምጣት ሥራዬን መሥራት እንዳልችል በማድረጉ ህክምናውን በውጪ ሀገር እንድከታተል ሌሎች የህክምና ተቋማት ያረጋገጡልኝ ስለሆነ ተከሳሽ ላደረሰብኝ ጉዳት ሀላፊ ነው ተብሎ እንዲወሰንበትና ታይላንድ ሀገር ሄጂ ለመታከም፡-

- ለህክምና ወጪ ብቻ ብር 192,881
- ለደም ሥርዓት ማስተካከያ ቀዶ ጥገና ብር 114,699
- ለደም ምርመራ ኤክስሬይ /x-ray/ እና ላቦራቶሪ ምርመራ ብር 22,100
- ኤም.አር ምርመራ ብር 13,377
- ታይላንድ ደርሶ መልስ የአውሮኘላን ትኬት ብር 14,000
- የ10 ቀን የሆቴል ወጪ ብር 6,500
- ለ10 ቀን የሆስፒታል አልጋ ወጪ ብር 159,949
- ለህክምና ተጨማሪ ወጪ መጠባበቂያ ብር 100,000
- ታይላንድ ባንኮክ የታክሲ፣ የፖስፖርት እና ሌላ ወጪ ብር 13,400
- ለአስታማሚ ትራንስፖርት ሆቴል፣ የጉዞ ሠነድ ወጪ ብር 34,780

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- በጉዳቱ ምክንያት ሥራ በማቆሜ ያጣሁትን ብር 632 ክስ እስከቀረበበት ሐምሌ 2001 ታስቦ ብር 22,752
- የሞራል ካሣ ብር 1,000

በድምሩ 694,918 ብር /ስድስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንት/ ተከሳሽ እንዲከፍለኝ እንዲወሰንበት የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሽም በሰጠው መልስ አንድ ሀኪም ብሎም ሆስፒታል በሙሉ ሀላፊነት የሚጠየቀው የሞያ ደንብ ተጥሶ ሲገኝ ሲሆን ይኸው ደንብ ተጥሶ በመሰራቱ ምክንያት በከሳሽ ላይ ጉዳት ስለመድረሱ አላስረዳችም፣ ከሳሽ በውጪ ሀገር ለመታከም የሚያስችላትን ሰርትፍኬት ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በማስረጃነት አላቀረበችም በውጪ ሀገር ህክምና ያስፈልጋታል ቢባል እንኳን የዚህ ዓይነት ህክምና በቅርብ በኬኒያ ወይም ህንድ ሀገር የሚሰጥ በመሆኑ ታይላንድ ሀገር ለመታከም የጠየቀችው ያለአግባብ ነው፡፡ ከሣሽ ለህክምና የጠየቀችው ብር 192,881 በማስረጃ ያልተረጋገጠ ከመሆኑ ሌላ ለምርመራ በማለት ልዩ ልዩ ወጪዎችን መጠየቋ ተገቢነት የለውም፣ በሆስፒታል ለ10 ቀናት እንደምትቆይ በመጥቀስ የጠየቀችው ገንዘብም ቢሆን ከ2 ቀን በላይ በሆስፒታሉ ስለማትቆይ በጣም የተጋነነ ነው ለአስታማሚ በሚል የጠየቀችውን ገንዘብ ተከሣሽ መክፈል አይገባውም ፣ የደረሰባት ጉዳት የግል ሥራዋን የሚከለክላት ስለመሆኑም ማስረጃ አላቀረበችም፣ የሞራል ካሣም ቢሆን ተከሳሽ ለከሳሽ መክፈል የለብኝም ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን የመረመረው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትም የከሳሽ የህክምና ወጪዎች በትክክል ለማወቅ የሚያስችግር ናቸው በማለት በርትዕ ተከሳሽ ለከሳሽ ብር 300,000 ሊከፍል ይገባል ብሏል፡፡

በዚህ በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የሥር ተከሣሽ ይግባኝ በፍትሀብሄር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሲዘጋ በከሳሽ የይግባኝ መዝገብ ላይ ክርክር ተካሂዶ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔን በማሻሻል መልስ ሰጪ /ተከሳሽ/ ለይግባኝ ባይ በሥር ፍ/ቤት ቀደም ሲል የተወሰነላትን ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ/ የተቀበለች ስለሆነ ይኸው የተቀበለችው ገንዘብ የሚታሰብ ሆኖ ብር 694,918 /ስድስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንት/ እንዲከፍላት በሚል ወስኗል፡፡

በዚህ በጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የዘረዘራቸው ነጥቦችም፡- በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት /ሊከፈላት የሚገባው የካሣ መጠን/ ሊታወቅ የሚችል ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች የካሣ መጠኑን በርትዕ መወሰን አይገባቸውም፣ በርትዕት የሚወሰን የካሣ መጠን አነስተኛ መሆን ይገባዋል፣ ለተጨማሪ የካሣ ክፍያ የብር ተመን መውረድን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት እንደምክንያት መውሰዱ ተገቢነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ለስበር አቤቱታ ተጠሪዋ በሰጠች መልስ አመልካች ለደረሰብኝ ጉዳት በሥር ፍ/ቤቶች ሀላፊነት እንዳለበት ተወስኖ እስከ ሰበር ድረስ በመ/ቁ. 58041 ቅሬታውን አቅርቦ ጉዳዩን የመረመረው የፌ/ሰበር ሰሚ ችሎትም በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመም በሚል አቤቱታውን ውድቅ ያደረገበት ስለሆነ የካሣን መጠን በሚመለከት ያቀረበውን ክርክር የሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ባለመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯለች፡፡

አመልካችም ለተጠሪዋ መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክሩን በማጠናከር አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ ከላይ በተገለፀው አኳኋን የቀረበ ሲሆን እኛም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው የካሳ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር የአመልካች የህክምና ድርጅት ለተጠሪ ህክምና ባደረገላት ወቅት በተፈጠረው ችግር የተጠሪዋ ጤና ላይ ጉዳት የደረሰ በመሆኑ ይህም የደረሰባት ጉዳት በሀገር ውስጥ በህክምና ለማዳን የሚቻል ባለመሆኑ ታይላንድ ሀገር ሄዳ እንድትታከም ተወስኗል፡፡ ነገር ግን ለዚህ ቅሬታ ዋና መነሻ የሆነው ለህክምናና ለተለያዩ ወጪዎች ጠቅላይ ፍ/ቤቱ አመልካች ለተጠሪዋ የህክምናና ልዩ ልዩ ወጪዎች በርትዕ ከፍ አድርጐ መወሰኑ ነው፡፡

በእርግጥ በመርህ ደረጃ በጉዳቱ ምክንያት ተበዳዩ የሚካሰው ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ኪሣራ በመክፈል መሆኑን የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090 የሚደነግግ ሲሆን ለጉዳቱ ሀላፊ የተደረገው ሰውም ሀላፊነቱ ያመጣውን ጉዳት በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ተመዛዝኖ መክፈል ይኖርበታል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን የጠ/ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለደረሰው ጉዳት ካሣ ለማስክፈል እንደ አማራጭ የወሰደው ርትዕን ነው፡፡ ለዚህም በምክንያትነት ከተጠቀሱት ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ ተጠሪዋ ያቀረበቻቸው ለህክምናው ወጪ ያስፈልጋሉ የተባሉት ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት የህክምናው ወጪ ከፍተኛ ነው፣ ለተጠሪዋም አስታማሚ የሚያስፈልጋት ሲሆን ወጪውም ምን ያህል እንደሆነ ከወዲሁ ለማወቅ የሚያስቸግር ነው፣ በመላው ዓለም እየታየ ያለውም የዋጋ ንረት ለተጠሪዋ ህክምና ወጪ የራሱ የሆነ ሚና ይኖረዋል፣ የብር ምንዛሪ መውረዱ ተጠሪዋ ለህክምና ያስፈልገኛል በማለት በጠየቀችው የገንዘብ መጠን ላይ መዋዠቅን ያስከትላል የሚሉ ናቸው፡፡

በፍትሃብሄር ህጉ አንቀጽ 2102 ዳኞች ስለደረሰው ጉዳት ኪሣራን በርትዕ እንዲወሰኑ መብት የተሰጠውም በግልጽና በትክክል የኪሣራውን መጠን ለመወሰን አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ነው፡፡ ከዚሁ አንፃር የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ በርትዕ ከዚሁ አንፃር የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ በርትዕ ለማስከፈል የጠቀሳቸው ምክንያቶች የቀረቡትን ማስረጃዎች እና በአሁኑ ጊዜ በዓለም እየታየ ያለውን የዋጋ ንረት ያገናዘቡ በመሆናቸው ይህ ችሎትም የሚቀበለው ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሣት ያለበት አመልካች ዳኞች የጉዳት ካሣን በርትዕ ሊወሰኑ የሚችሉት ልዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነው በማለት የተከራከረው በአግባቡ ቢሆንም ርትዕን መሠረት አድርገው ዳኞች ካሣ ሊወሰኑ የሚችሉት የካሣ መጠን ለመቀነሥ እንጂ ከፍ ለማድረግ አይደለም ሲል የተከራከረው ግን ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ፍ/ቤቱ በርትዕ ሊወስንም ሊገመቱ የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያለአግባብ ስለመያዙ ወይም ሊገመቱ የሚገባቸውን ትክክለኛውን መንገድ በመተው ያለአግባብ የሆነውን የአገማመት መንገድ ስለመያዙ አመላካች ነገር የለም፡፡ የተወሰነውም የካሣ ልክ በግልጽ ከአእምሮ ግምት ውጪ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም ከዚህ በላይ በተገለጹት የህግ ምክንያቶች የተነሣ በጠ/ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 58732 በቀን 15/04/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያልተገኘበት በመሆኑ ፀንቷል፡፡
2. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ማለትም በሰበር ደረጃ የተደረገውን ክርክር በሚመለከት አመልካችና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- አቶ በቀለ ወልቻም - ጠበቃ አቶ አለሙ ገ/ህይወት

ተጠሪ ፡- አቶ ጥበቡ ጦና - ጠበቃ አቶ ታደሰ ሲሳይ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ንብረትነቱ የአመልካች በሆነና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-03593 /ደ.ህ/ በሆነ የህዝብ ማመላለሻ መኪና በመሳፈር ነሐሴ 6 ቀን 2001 ዓ.ም እየተጓዘ እያለ የአመልካችን መኪና ያሽከረክር የነበረው አቶ ወንድወሰን ሽታ ከተፈቀደለት የፍጥነት ወሰን በማለፍ በማሽከርከሩ መኪናው ተገልብጦ የቀኝ እግሬ ተቆርጧል፡፡ የተከሣሽ /አመልካች/ ሹፌር የነበረው አቶ ወንድወሰን በሀዋሣ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በሶስት ወር እስራት እንዲቀጣ ተወስኖበታል፡፡ የደረሰበኝ ጉዳት 60% /ስልሳ ፐርሰንት/ የመሥራት አቅሜ እንደቀነሰ በጥቁር አንበሳ የሀኪሞች ቦርድ ተረጋግጧል፡፡ አደጋው ከመድረሱ በፊት ብር 658 /ስድስት መቶ ሃምሣ ስምንት ብር/ በየወሩ ተቀጥሬ ስሰራበት ከነበረው ሚዛን ተፈሪ ሆስፒታል ይከፈለኝ ነበር፡፡ በአደጋው ምክንያት ለህክምና ያወጣሁትን ወጭና ሌሎች ወጭዎች ተከሣሽ መተካት ያለበት ሲሆን የተቋረጠ ጥቅምና ገቢዬን የመክፈል ሀላፊነት ያለበት ስለሆነ ብር 348,247.22 /ሶስት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሰባት ብር ከሀያ ሁለት ሣንቲም/ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ የሰላሣ አምስት ዓመት ደመወዝ ያለምንም ቅንስናሽ እንዲከፈለው ያቀረበው ጥያቄ ተገቢ አይደለም፡፡ የደመወዝ ጭማሪ አገኝ ነበር በማለትና የጡረታ ገንዘብ በማለት ያቀረበው ጥያቄም የህግ መሠረት የለውም፡፡ እስከ 80 ዓመት እኖራለሁ ብሎ አስልቶ የጠየቀው የካሣ ገንዘብ ተገቢ አይደለም፡፡ የህክምና ማስረጃ የአካል ጉዳት እንደደረሰበት እንጅ 60% የከሣሽ የመስራት አቅም እንደቀነሰ አያረጋግጥም፡፡ የስር ፍርድ ቤት በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተከሣሹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሀላፊ ነው ወይስ አይደለም? ተከሣሽ ጉዳቱን የመካስ ሀላፊነት አለ ቢባል ሊከፈል የሚገባው ካሣ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጭብጦች መስርቷል፡፡ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተከሣሽ /አመልካች/ በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሀላፊነት የለብኝም የሚል ክርክር አላቀረቡም፡፡ ተከሣሽ ለጉዳቱ ሀላፊ የሚሆነው በንግድ ህግ ቁጥር 599 በተደነገገው መሠረት መሆን አለበት በማለት ወስኗል፡፡ የካሣውን መጠን በተመለከተ ከሣሽ አደጋው ሲደርስ እድሜው ሰላሣ ዓመቱ ነው፡፡ ወደፊት ጡረታ እስኪወጣ ሰላሣ ዓመት ይቀረዋል፡፡ የከሣሽ ደመወዝ በወር ብር 658 ሲሆን የገቢ ግብር ብር 51.20 ሲቀነስለት የተጠሪ ገቢ 606.80 ነው፡፡ የዚህ ስልሣ ፐርሰንት ገቢ እንደቀረበት ተደርጐ የካሣው መጠን መሰላት ይገባዋል በማለት ተከሣሽ /አመልካች/ ብር 131,068.80 /አንድ መቶ ሰላሣ አንድ ሺ ስልሣ ስምንት ብር ከሰማኒያ ሣንቲም/ የተቋረጠ ጥቅም ስለሆነ ሊከፍል ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለህክምናና ሌሎች ወጭዎች የወጣ ብር 7604.34 /ሰባት ሺ ስድስት መቶ አራት ብር ከሰላሣ አራት ሣንቲም/ እና የህሊና ጉዳት ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ ተከሣሽ /አመልካች/ ለከሣሽ /ተጠሪ/ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር ችሎቱ የስር ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት መኪናው በድንገት በመገልበጡ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች አጓዥ በመሆኑ ለተጠሪ ልከፍለው የሚገባው የካሣ መጠን የንግድ ህግ ቁጥር 597ን መሠረት በማድረግ ሊወሰን ሲገባው የንግድ ህግ ቁጥር 599 መሠረት ተደርጐ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የሰላሣ ዓመት ገቢ እንደተቋረጠበት ተደርጐ ካሣው መሰላቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት እግሩ ላይ በመሆኑ ሌላ ስራ ሰርቶ ገቢ ማግኘቱን የሚከለክለው አይደለም፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ሰኔ 3 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በንግድ ህግ አንቀጽ 597 የተደነገገው የካሣ መጠን አጓዙ በተጓዡ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት እስከ ምን ድረስ ካሣ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት የሚደነግግ መሠረታዊ መርህ ሲሆን የንግድ ህግ ቁጥር 599 በመርህ ከተደነገገው በላይ አጓዡ ለተጓዡ ካሣ እንዲከፍል የሚገድቡትን ልዩ ሁኔታን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው የአመልካች ሰራተኛ ከተፈቀደለት በላይ በፍጥነት በማሽከርከሩ አደጋው የደረሰ መሆኑ ተረጋግጦ በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በወንጀል የተቀጣ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የንግድ ህግ አንቀጽ 599 መሠረት በማድረግ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ የካሣውም መጠን ቢሆን በማስረጃ በማጣራት የተሰጠ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካች ሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለውን የካሣ መጠን የንግድ ህግ አንቀጽ 599 መሠረት በማድረግ ማስላታቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከላይ የተያዘውን ጭብጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመወሰን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎችን ይዘትና ትርጉም እንደዚሁም ድንጋጌዎቹ ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

1. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የንግድ ህግ ቁጥር አንቀጽ 587 በሚደነግገው መሠረት የአጓጓዥና የመንገደኛ ግንኙነት መኖሩን አመልካችና ተጠሪ በስር ፍርድ ቤትና በሰበር ባቀረቡት ክርክር የሚተማመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሰው ለመጓጓዝ የተደረገ ውል መኖሩን አመልካችና ተጠሪ የሚስማሙበት ነጥብ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪ ዋጋ ከፍለው ሲጓዝቡበት የነበረውን የትራንስፖርት መኪና ባለሀብት ሲሆኑ ተጠሪው መንገደኛ ናቸው፡፡ አጓዡ መንገደኛውን በመልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ስለ ምቾቱና ስለ ጉዞው በውሉ የተወሰነውን ጊዜ አክብሬ እንደተወሰነው እመድረሻ ስፍራ የማድረስ ግዴታ እንዳለበት የንግድ ህግ አንቀጽ 588 ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የአጓዡን የትራንስፖርት መኪና በሀላፊነት ተረክቦ የመኪናውን ደህንነትና ብቃት አረጋግጦ በትራፊክ ደንብና ሥርዓት አክብሮ የማሽከርከር ሀላፊነት ያለበት አሽከርካሪ /ሹፌር/ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች የመንገደኛውን መልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ምቾት በመጠበቅ መንገደኛውን ከመነሻው እስከ መድረሻው የማድረስ ሀላፊነታቸውን ካልተወጡ አጓዡ በንግድ ህግ ቁጥር 588 የተጣለበትን ህጋዊ ግዴታ እንዳልተወጣ የሚቆጠር መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አጓዡ ይህንን ህጋዊ ሀላፊነቱን በአግባቡ ካልተወጣ መንገደኛው በጉዞው ላይ ስለሚደርስበት መዘግየትና በጉዞው ጊዜ ወይም በሚሣፈርበት ወይም በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል ማጉደል ወይም የህይወት ማለፍ አጓዡ ሀላፊ እንደሚሆን የንግድ ህግ አንቀጽ 595 በግልጽ ይደነግጋል፡፡

   የንግድ ህግ አንቀጽ 595 አጓዡ መንገደኛው በጉዞ ጊዜ በሚሣፈርበትና በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል መጉደል ወይም ህይወት ማለፍ አጓዡ በሀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን በመሠረታዊ መርህነት የሚደነግግ ሲሆን ፣ አጓዡ ከሀላፊነት ነጻ የሚሆንባቸዉን ልዩ ሁኔታዎች የሀላፊነቱን መጠንና አጓዡ በህግ ከተደነገገው መጠን በላይ በሀላፊነት ሊጠይቅ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎች በንግድ ህጉ ተካተዋል፡፡
2. የመጀመሪያ በንግድ ህግ አንቀጽ 595 ከተደነገገው ሀላፊነት አጓዡ ነጻ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚደነግገው የንግድ ህጉ አንቀጽ 596 ነው፡፡ በንግድ ህግ አንቀጽ 596 አጓዡ በመንገደኛው ላይ የአካል መጉዳት ወይም የሞት አደጋ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ከፍተኛ ሀይል መሆኑን ፣ ወይም ጉዳቱ የደረሰው በሶስተኛ ሰው ጥፋት መሆኑን ወይም በመንገደኛው ጥፋት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ አጓዡ ከሀላፊነት ነጻ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ አጓዡ በንግድ ህግ ቁጥር 596 መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻሉ በመንገደኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት አጓዡ በሀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑንና የሀላፊነቱ መጠን ለአንድ መንገደኛ ከብር 40,000 /አርባ ሺ ብር/ እንደማይበልጥ የንግድ ህግ አንቀጽ 597 በግልጽ ይደነግጋል፡፡

ሆኖም በንግድ ህግ አንቀጽ 597 የተደነገገው የሀላፊነት መጠን አጓዡ በንግድ ህግ አንቀጽ 596 የተደነገጉትና ከሀላፊነት ነጻ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታና መንገደኛው በንግድ ህግ አንቀጽ 599 በሚደነግገው መሠረት አጓዡ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑን እያወቀ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ባልቻለበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአመልካች ንብረት የሆነውን የትራንስፖርት መኪና ያሽከረክር የነበረው የአመልካች ሰራተኛ የመኪናው ሹፌር ከተፈቀደለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍጥነት በላይ በማሽከርከሩ መኪናው የተገለበጠና ተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑ የአመልካችን መኪና ያሽከረክር የነበረው ሹፌር በሀዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 21372 በወንጀል ተከስሶ የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በፍርድ ጥፋተኛ መሆኑ ተረጋግጦ በሶስት ወር እስራት የተቀጣ መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ በንግድ ህግ ቁጥር 588 በሚደነግገው መሠረት የመንገደኛውን መልካም ይዞታ ደህንነትና ምቾች በመጠበቅ መንገደኛውን የማጓጓዝ ሀላፊነቱን አጓዡ የሚወጣው አጓዡ ራሱ የመኪናው አሽከርካሪ ከሆነ አጓዡ፣ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች አማካኝነት ሲሆን አጓዡ የመኪናው አሽከርካሪ ካልሆነ መኪናውን በሀላፊነት ይዞ በሚያሽከረክረው ሹፌር ፣ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች በኩል መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በተመሣሣይ ሁኔታ በንግድ ህግ ቁጥር 599 በተደነገገው መሠረት አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑን እያወቀ አጓዡ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን መንገደኛው የሚያስረዳው አጓዡ የመኪናው አሽከርካሪ ከሆነ እሱ ራሱ መኪናውን ሲያሽከረክር ወይም ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች በፈጸሙት ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡ አጓዡ መንገደኛው የተሣፈረበትን መኪና የማያሽከረክር በሆነ ጊዜ መኪናውን አጓዡ በሀላፊነት ተረክቦ ሲያሽከረክር የነበረው ሰው ፣ ረዳቱ ወይም ሌላ የአጓዡ ሰራተኛ አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑን እያወቀ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡

በንግድ ህግ አንቀጽ 599 “አጓዡ የተፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት” የሚለው ሀረግ አጓዡ በግሉ የፈጸመውን ተግባር ወይም ጉድለት የሚመለከት ሣይሆን የአጓዡ ሰራተኞች አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጠር እንደሚችል እያወቁ የፈጸሙትን ተግባር ወይም ጉድለት የሚያካትት ነው፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ድንጋጌ ይዘት ህግ አውጭው ከውል ውጭ ስለሚደርስ ሀላፊነት “አንድ ሰራተኛ ስራውን በሚሰራበት ጊዜ ሀላፊነትን የሚያስከትል ጥፋት የሰራ እንደሆነ በፍታብሔር በሀላፊነት የሚጠየቀው አሰሪው ነው” በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2130 የደነገገውን መሠረታዊ መርህ በሚያካትት ሁኔታ መተርጐምና የህጉ ድንጋጌ ተግባራዊ እንዲሆን ካልተተረጐመ የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ህግ አውጭው የሰጠውን ግብ የሚያሣካ አይሆንም፡፡

ከዚህ አንጻር ስንመለከተው አደጋው የደረሰው የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር ከተፈቀደለት ፍጥነት በላይ ማሽከርከሩ አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑ በቂ የሙያ ዕውቀትና ክህሎት እያለው ከተፈቀደለት ፍጥነት በላይ በማሽከርከሩ መሆኑን ተጠሪ ስላስረዳ የበታች ፍርድ ቤቶች የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ለጉዳዩ ተፈጻሚ ማድረጋቸው ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በተጠሪ አካል ላይ ጉድለት ያደረሰው አደጋ የተከሰተው የአመልካች ሰራተኛ የሆነውና መኪናውን ያሽከረክረው የነበረው ሹፌር የትራፊክ ደንብና ስርዓት በመጣስ መኪናውን ከተፈቀደለት ፍጥነት በላይ በማሽከርከር በፈጸመው ተግባር መኪናው የተገለበጠ መሆኑን ተጠሪ በበቂ ማስረጃ እንዳስረዳ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው በላይ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በንግድ ህግ አንቀጽ 599 መሠረት በንግድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው የሀላፊነት መጠን በላይ ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት የሰጡት የህግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢና የህግ ስህተት ያሌለበት በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

3. አመልካች በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው የሀላፊነት መጠን በላይ ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት እንዳለበት የንግድ ህግ አንቀጽ 599ን መሠረት በማድረግ የበታች ፍርድ ቤቶች መወሰናቸው ተገቢ ነው የሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሰናል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚነሣው የህግ ጥያቄ አመልካች ለተጠሪ በንግድ ህግ አንቀጽ 599 መሠረት ሊከፍለው የሚገባው ምን ያህል ነው የካሣው መጠንስ እንዴት ነው የሚሰላው የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 597 ጉዳት የደረሰበት መንገደኛ ገቢ በጉዳቱ ምክንያት የደረሰበትንና ወደፊት የሚደርስበት ኪሣራ ከብር 40,000 በላይ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳን አጓዡ ለአንድ መንገደኛ የሚከፍለውን የካሣ መጠን በብር 40,000 መለወጥ እንደሌለበት የሚደነግግና የሀላፊነቱን መጠን የሚወሰን ድንጋጌ ነው፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ከላይ ለተገለጸውና የሀላፊነቱን መጠን ከሚወሰነው አንቀጽ 597 በልዩ ሁኔታ የተደነገገ ድንጋጌና መንገደኛው ከአጓዡ ከብር 40,000 በላይ ካሣ ለመጠየቅና ለማግኘት የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡

በግንድ ህግ ቁጥር 599 ድንጋጌ መሠረት ለመንገደኛው ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት አጓዡ ለመንገደኛው የሚከፍለው የካሣ መጠን ለመወሰን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2092 የተደነገጉት የካሣ አከፋፈል መርሆች አግባብነት ያላቸው ናቸዉ፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባውን የካሣ መጠን የወሰነው ከላይ የጠቀስናቸውን መሠረታዊ የካሣ አከፋፈል ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ በአደጋው ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት ለመታከም ያወጣውን ወጭና ሌሎች አስፈላጊ ወጭዎች በማስረጃ በማረጋገጥ ለተጠሪ እንዲከፈል የንግድ ህግ አንቀጽ 599ን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 ጋር አጣምሮ በመተርጎም የወሰነ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት አመልካች አደጋው ሲደርስበት ያገኝ ከነበረው የወር ደመወዝ ለገቢ ግብር የሚከፍለውን በመቀነስ ፣ ተጠሪ ከሚያገኘው የወር ደመወዝ ስልሣ ፐርሰንቱን ብቻ አመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የጡረታ መገለያ እድሜው እስኪደርስ ያገኝ የነበረው የተጣራ ገቢ ስልሣ ፐርሰንቱን ብቻ አመልካች እንዲከፍል የንግድ ህግ አንቀጽ 599ን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2092 ጋር አጣምሮ በመተርጎም የካሣውን መጠን የወሰነ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የስር ፍርድ ቤት የንግድ ህግ አንቀጽ 599 አግባብነት ካላቸው የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች ጋር በማጣመር ተግባራዊ ያደረጉ መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ማጽናታቸው ተገቢና የህግ ስህተት ያሌለበት በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው የአካል መጉደል ካሣ የሚከፍለው በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ድንጋጌዎች መሠረት ሣይሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 599 መሠረት ነው በማለት የካሣውን መጠን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2092 መሠረታዊ መርሆች በመጠቀም መወሰናቸው ተገቢና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሚያዝያ 21 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፤ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች ፡- ወ/ሮ አስናቀች ወ/ማርያም - ጠበቃ ኪሩቤል ኃ/ማርያም - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- አቶ አለማየሁ አህመድ - ቀረቡ፡፡

ፍ ር ድ፤

ለሠበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ፣ የስር 3ኛ ተከሣሽ የነበሩት የሠ/ቁ 3-03657 የሆነ መኪና ሲያሽከረክሩ ምናሴ ከበደ የተባለውን ልጃቸውን ገጭተው በመግደላቸው በወንጀል ተከሠው ተፈርዶባቸዋል፡፡ መኪናውን የሥር 2ኛ ተከሣሽ ገዝተው የባለቤትነት ስሙ በስማቸው ባይተላለፍም በይዞታቸው ሥር ነበር፤ የአሁኑ ተጠሪም የመኪናው የባለቤትነት ስም በስማቸው በመሆኑ የመኪናው ባለቤት ናቸው፡፡ በመሆኑም ሶስቱም ተከሣሾች ለደረሠው አደጋ ኃላፊነት ስላለባቸው የጉዳት ካሣ ይክፈሉኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሠምቶ የአሁኑ ተጠሪ መኪናውን ለሥር 2ኛ ተከሣሽ ሸጠው ኃላፊነቱ ለ2ኛ ተከሣሽ የተላለፈ በመሆኑ ሊጠየቁ አይገባም በማለት የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች ብቻ ለደረሠው ጉዳት ሃላፊ በመሆናቸው የጉዳት ካሣውን ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካችም ተጠሪ ሃላፊ ሊሆኑ አይገባም በማለት በተሠጠው ውሣኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ቅሬታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ የሠበር ችሎትም ጉዳት ያደረሠው መኪና የባለቤትነት ስም በተጠሪው ስም በመሆኑ ተጠሪው በሃላፊነት ሊጠየቁ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ መልስ ማግኘት ያለበት ጭብጥ የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለሃብትነት ወደ ሌላ ሰው ተላለፈ የሚባለው መቼ ነው? መኪኖች እና ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ከውል ውጭ ባሉ ግንኙነቶች ለሚያደርሱት ጉዳት በኃላፊነት የሚጠየቀው ማነው? የሚለው ይሆናል፡፡ ለተያዘው ጭብጥ መልስ ለመስጠት የተንቀሳቃሽ ንብረት ባለሃብትነት የሚተላለፍበትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መንገድ የሚመለከቱትን የህጉ ድንጋጌዎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው። በተለይ በዚህ ጉዳይ ክርክር የተነሣበት ሃብት መኪና በመሆኑ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ልዩ ከሆኑ አንዳንድ የሚንቀሣቀሱ ንብረቶችን በሚመለከት የተደነገጉትን የህግ ድንጋጌዎች መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል።

በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1186 "ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሣቃሽ ንብረቶች ባለሀብትነት ንብረቱን በመግዛት ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘው ወይም በኑዛዜ የተሰጠው ሰው ንብረቱን እጁ ባደረገ ጊዜ የተላለፈለት ይሆናል" በማለት ይደነግጋል። በዚህ የህግ ድንጋጌ መሠረትም የአንድ የሚንቀሣቀስ ንብረት ባለሃብት ለመሆን ሌላ ተጨማሪ ሁኔታ ማሟላት ሣያስፈልግ ንብረቱን በመግዛት ወይም በሌላ አኳኋን ንብረቱን አግኝቶ በእጅ በማድረግ ብቻ ባለሀብት ሊሆን የሚቻል መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ሆኖም ይህ ድንጋጌ ልዩ የሆኑ አንዳንድ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን ባለሀብትነት ለማስተላለፍ በተለይ የተመለከቱትን የሕግ ድንጋጌዎች የማያጠቃልል መሆኑን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1186(2) ላይ በግልጽ ተመልክቷል። በዚህ መሠረት የምዝገባና የባለሀብትነት ማስተላለፊያ ስርዐትን በመከተል ብቻ ባለሀብትነት ከሚተላለፍባቸው ግዙፍነት ካላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች መካከል መኪና እና ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ዋንኞቹ ስለመሆናቸው በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን ለመቆጣጠርና ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 256/1960 ተከትሎ የወጣውን እና የተለያዩ ክፍሎቹ በየጊዜው የተሻሻሉትንና እንደአግባብነቱ ተፈጻሚነት ያለውን የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 360/1961ን መመርመሩ አስፈላጊ ነው።

በቅድሚያ የፍጥነት ወሰኑ በሰዓት ከ20 ኪሎ ሜትር የማይበልጥ ልዩ ተሽከርካሪ መሣሪያዎች በስተቀር ማናቸውንም ባለሞተር ተሽከርካሪ የማስመዝገብ ግዴታ በአስገዳጅነት በሕጉ የተጣለ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 256/1960 አንቀጽ 6 "ን" እንደአግባብነቱ ካሻሻለው እና የሚኒስቴሩን መ/ቤት በአዲስ ካቋቋመው አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 21 መረዳት ይቻላል።

ባለሞተር ተሽከርካሪን ከማስመዝገብ ግዴታ ጋር ተያይዞ ማንም ሰው በደንብ ቁጥር 360/1961 አንቀጽ 6 መሠረት የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር አያስፈልጋቸውም ተብለው ከተመለከቱት ተሽከርካሪዎች ውጭ ያሉ ተሽከርካሪዎችን ለአገልግሎት ከተላለፉበት ጊዜ ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር እንዲሰጠው ለአዋጅ አስፈጻሚ መ/ቤት ማመልከቻውን ማቅረብ የሚገባው መሆኑን በደንቡ ቁጥር 7 ላይ ተመልክቷል። በማንኛውም መንገድ ተሽከርካሪው ለአገልግሎት የተላለፈለት ሰው በስሙ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር እንዲሰጠው ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋርም የንብረቱን ባለሀብትነት ያገኘበትን አግባብ የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ማቅረብ የሚገባው መሆኑ ተመልክቷል። በዚህ መሠረት የተሽከርካሪው ባለሀብትነት የተገኘው ከቀድሞው ባለቤት ላይ ከሆነ የቀድሞውን ባለቤት የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር፣ ወይም ማመልከቻው የሚመለከተው ከዚህ በፊት በውጭ አገር የተመዘገበን ተሽከርካሪ እንደሆነ በተባለው አገር የተሰጠ የባለንብረት መታወቂያ ሰነድ ወይም የተሽከርካሪውን ባለንብረትነት ለማወቅ ለሚኒስቴሩ መ/ቤት አስፈላጊ ናቸው የሚባሉትን ማናቸውንም ሰነዶችና መረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ የሚገባ መሆኑን በደንቡ ቁጥር 7 (1) እና (3) ላይ ተደንግጓል። ይህ የደንቡ ክፍል በአዲስ የተገዙትን፣ በውጭ አገር አገልግሎት ሰጥተው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትን እና በአገር ውስጥ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ከአንዱ ወደ ሌላው በተለያየ ምክንያት ሲተላለፉ ተሽከርካሪው ለአገልግሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተላለፈለት ሰው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር እንዲሰጠው ከማመልከቻው ጋር በማያያዝ ሊያቀርብ የሚገባቸው ሰነዶች የትኞቹ እንደሆኑ የሚያመለክቱ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በአገር ውስጥ የሠራ ተሽከርካሪ ለአገልግሎት ከአንዱ ወደ ሌላው ሲተላለፍ የተላለፈለት ሰው የአስተላለፈውን የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር እንዲረከብና ሁለቱ ወገኖች በደብተሩ ውስጥ የሚገኘውን የባለንብረትነት መታወቂያ ገጽ በሚገባ ሞልተው እና ፈርመው ማቅረብ የሚገባቸው መሆኑን በደንቡ ቁጥር 8 እና 11(1) ላይ ተመልክቷል። በመጨረሻም የሚኒስቴሩ መ/ቤት ማመልከቻው እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን ካረጋገጠ ማመልከቻ አቅራቢው የተሽከርካሪው ባለቤት ነው እንዲባል አንድ የባለንብረት መታወቂያ ደብተር የሚሰጠው መሆኑን በቁጥር 9 ላይ ተመልክቷል።

ከፍ ብለው ከተመለከቱት የደንቡ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ነገር ቢኖር፣ የፍጥነት ወሰናቸው በደንቡ ላይ የተመለከቱት ተሽከርካሪዎች ከአንዱ ወደ ሌላ በሽያጭ፣በስጦታ ወይም በሌሎች መንገዶች ተላልፈው ሲገኙ እንደ አብዛኛዎቹ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ዋጋ ሰጥቶ ንብረቱን በእጅ በማድረግ ብቻ የባለሀብትነት መብት የማይተላለፍ መሆኑን፤ ይልቁንም ልዩ የሆኑትን እነዚህን ግዙፍነት ያላቸውን ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ባለሀብት ሆኖ ለመገኘት ሻጭ እና ገዥ ወይም ስጦታ አድራጊና ስጦታ ተቀባይ ከሚያደርጉዋቸው የተሳኩ የውል ስምምነቶች ባሻገር ከፍ ብለው በደንቡ በተመለከተው እንኳን የተሽከርካሪውን ባለሀብትነት ከአስተላላፊው ወደ ተላለፈለት ሰው የሚዘዋወርበት ስርዓት በሚኒስቴሩ መ/ቤት መጠናቀቅ የግድ መሆኑን ነው። ሌላው ቀርቶ ባለንብረትነቱ የታወቀለት ሰው ተሽከርካሪው ከጥቅም ውጭ ሆኖ በወላለቀና ጨርሶ በወደመ ጊዜ እንኳን ይህንኑ ሁኔታ በ30 ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ መ/ቤት አሳውቆ በስሙ የተመዘገበው የባለቤትነት ደብተር እንዲሰረዝና ከመዝገብ እንዲፋቅ ካላስደረገ በቀር ባለሃብቱ ስሙ በመታወቂያ ደብተሩ ላይ የተመዘገበው ሰው ሆኖ እንደሚቀጥል ከደንቡ ቁጥር 42 እስከ 45 እና በቁጥር 11(2) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመመርመር መረዳት ይቻላል።

ባለሞተር ተሽከርካሪዎች በሰው ልጆች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ውስጥ የሚኖራቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ የመሆኑን ያህል እነዚህ ማሽኖችና ተሳቢዎች በጉዳናዎች ላይ በሚሽከረከሩበት ጊዜ በሰውና በንብረት ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት የጉዳት መጠን የዛኑ ያህል ከፍተኛ በመሆኑ እነዚህ ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ወደ አገር ውስጥ ሲገቡም ሆነ በቴክኒክ ረገድ ብቃት ኖራቸው በጉዳናዎች ላይ ሲሽከረከሩ፤ እንዲሁም በተለያዩ ሁኔታዎች ንብረቶቹ ከአንዱ ወደ ሌላው ሲተላለፉም ሆነ ከአገልግሎት ውጭ ሆነው ጨርሶ ሲወድሙ ልዩ የምዝገባና የቁጥጥር ሥርዐት እንዲደረግባቸው ማድረጉ ማህበራዊ ደህንነትን ከመጠበቅ አኳያ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ አገሮች ባለሞተር ተሽከርካሪዎች እና ተሳቢዎቻቸውን ከሞላ ጎደል ተመሣሣይነት ባላቸው ልዩ ደንቦች እንዲመሩ የሚያደርጉ መሆኑን የተለያዩ አገሮችን ልምድ በመዳሰስ ለመረዳት ተችሏል።

የመኪና እና ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለሀብትነት የሚገኘው ከፍ ብለን በገለጽነው ሥርዐት ብቻ መሆኑ ከታወቀ በመቀጠል ሊነሳ የሚገባው ጭብጥ የባለሀብትነት ዝውውር ሥርዐቱ ደንቡ በሚጠይቀው አኳኋን ሳይከናወን አንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ከሻጭ ወደ ገዥ ወይም ከስጦታ አድራጊ ወደ ስጦታ ተቀባይ ይዞታው ተላልፎ በነበረበት ጊዜ መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት አድርሶ ቢገኝ ኃላፊው ንብረቱ በስሙ የሚገኘው ሰው ነው? ወይስ ንብረቱን በእጁ አድርጎ ሲገለገልበት የነበረው ሰው? የሚለው ይሆናል። እነዚህን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጭብጦች ለመመለስ እንድንችል መዝገቡን አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር መመርመሩ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የአሁኑ አመልካች ክሳቸውን ሲመሰርቱ የስር 3ተኛ ተከሳሽ የነበረው ሾፌር የሠ/ቁ. 3-03657 የሆነውን መኪና እያሽከረከሩ ጉዳት በማድረሳቸው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንዲባሉ፤ የስር 2ተኛ ተከሳሽ ጉዳት ያደረሰውን መኪና ገዝተው በይዞታቸው ሥር እያለ ጉዳት በማድረሱ 2ኛ ተከሳሽም ኃላፊ እንዲባሉ፣ የመኪናው የባለቤትነት ስም ደግሞ በስር 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት በአሁኑ ተጠሪ ስም በመሆኑ ተጠሪው የመኪናው ባለቤት በመሆናቸው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንዲሆኑ ጠይቀዋል፡፡ ከመዝገቡም የስር 3ተኛ ተከሳሽ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ መሆኑን፣ ጉዳት ያደረሰውን መኪና የሥር 2ተኛ ተከሳሽ ገዝተው የተረከቡ መሆኑን ነገር ግን የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተሩ በአሁኑ ተጠሪ ስም መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

በዚህ መሠረት ለጭብጦቹ ምላሽ ለማግኘት በቅድሚያ በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ የሚገኙትን ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መፈተሹ አግባብነት ይኖረዋል፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) መሠረት የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው ንብረቱ ተሰርቆ በነበረበት ጊዜ ለደረሰው አደጋ ከተጠያቂነት ነጻ ከሚሆን በስተቀር መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለመንዳት ባልተፈቀደለት ሰው እንኳን ተነድቶ ጉዳት አድርሶ ቢገኝ የመኪናው ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡ የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት ከውል ውጭ በሚደርሱ ኃላፊነቶች ውስጥ በፍትሐብሔር ሕጉ አጥፊ ሳይሆን አላፊ ከሚባሉት ምድቦች ውስጥ የሚመደብ በመሆኑ መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው ላደረሰው ጉዳት ባለቤቱ ኃላፊ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ስሙ በባለቤትነት ያልተመዘገበ መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለግል ጥቅሙ ሲገለገልበትና ሲጠቀምበት የነበረው ሰው መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው በእጁ በነበረበት ጊዜ ለደረሰው ጉዳት ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናል ማለት አለመሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2082(1) መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መነሻነት በአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ሰው የመኪናውን ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪውን ባለቤት ወይም በንብረቱ ተገልጋይ የነበረውን ማንኛውም ሰው በአንድነትም ሆነ በተናጥል ክሶ ለደረሰበት ጉዳት ካሣ ለመጠየቅ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) እና 2082 (1) መሠረት መብት ያለውን ያህል የመኪናው ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት ተብሎ የሚታወቀው ሰው የንብረቱ ባለቤት በመሆኑ ብቻ ተበዳይን ተገዶ ከካሰ በኋላ መኪናውን በእጁ አድርጎ ሲገለገል የነበረውን ማንኛውም ሰው የከፈለውን ገንዘብ እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 2083 (1) ተመልክቷል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ነገር ደንቡ የሚጠይቀውን የመኪና ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪ የባለቤትነትን የማስተላለፍ ሥርዐት ባልተከናወነበት ጊዜ ሁሉ በመኪናው ወይም በባለሞተር ተሽከርካሪው ለሚደርስ አደጋ ስሙ በባለቤትነት የሚታወቀው ሰው የንብረቱ ባለቤት በመሆኑ ብቻ የሚጠየቅ መሆኑን እና ንብረቱን በማናቸውም መንገድ በእጁ አድርጎ ለግል ጥቅሙ ሲገለገልበት የነበረ ሰው ለደረሰው ጉዳት ምንግዜም የመጨረሻው ኃላፊነት የማይቀርለት መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው ። ከዚህ ሌላ ስለባለቤቱ ወይም ስለሌላ ሰው ሆኖ በአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ይሰራ የነበረ ታዛኝ መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው ጉዳት አድርሶ የተገኘው በራሱ ጥፋት ምክንያት ካልሆነ በቀር እንደ ባለቤቱ ወይም እንደ ንብረቱ ተገልጋይ ሰው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደማይሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2082(2) ይደነግጋል። በዚህ ጉዳይ ግን የሥር 3ተኛ ተከሳሽ የነበረው ሾፌር በወንጀል ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በፍትሐብሄር ሕግ ቁ. 2082(2) መሠረት ለጉዳቱ ኃላፊ ነው መባሉ ተገቢ ነው።

ባጠቃላይ የአሁኑ ተጠሪ ጉዳት ያደረሰውን ተሽከርካሪ በሽያጭ ለስር 2ተኛ ተከሳሽ ለነበሩት ሰው በማስተላለፋቸው ብቻ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2324(1) በተመለከተው አኳኋን የጉዳት ኃላፊነቱ ሙሉ በሙሉ ወደ ገዢው ብቻ ተላልፏል ለማለት አይቻልም። መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ልዩ የምዝገባና የባለሃብትነት ስም ዝውውር የሚሻ ንብረት በመሆኑ እንደአብዛኛዎቹ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ዋጋ ሰጥቶ ንብረቱን በእጅ በማድረግ ብቻ ባለሃብትነት የሚተላለፍ አይደለም። በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2267(2) በተደነገገው መሠረት አንዳንድ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን የሚመለከቱ ልዩ ሕጎች ውስጥ የሚገኙ ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ ስለሽያጭ በተጻፉ ደንቦች አይነኩም በማለት የተደነገገውም የህንኑ የሚያጠናክር ነው።

በመሆኑም የተሽከርካሪው የባለሃብትነት ስም ዝውውር ደንቡ በሚጠይቀው አግባብ ባልተጠናቀቀበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤቶች የአሁኑ ተጠሪ ተሽከርካሪውን ለሥር 2ተኛ ተከሳሽ በሽያጭ አስተላልፏል በሚል ብቻ ተጠሪ ኃላፊ ሊሆኑ አይገባም ብለው መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ሆኖ አግኝተነዋል።

ው ሣ ኔ

1. የመኪናው ባለኃብትነት በስሙ የሚታወቀው በስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በንብረቱ አማካኝነት ለደረሰው የሞት አደጋ ንብረቱን ለግል ጥቅሙ ሲገለገልበት ከነበረው ከሥር 2ተኛ ተከሳሽ እና ስለ 2ተኛ ተከሳሽ ሆኖ በመኪናው ይሰራበት ከነበረው እና በጥፋቱ ኃላፊ ከተባለው ከሥር 3ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነት ኃላፊ ናቸው ብለናል።
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በልጃቸው ሞት ምክንያት እንዲከፈላቸው የተወሰነውን ብር 71,887.50 /ሰባ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ከስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በተጨማሪ የአሁኑ ተጠሪ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ ተወስኗል። ተጠሪ የከፈሉትን የጉዳት ካሣ ከሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ለመጠየቅ ይችላሉ።
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በ5/8/97 በመ/ቁ 03696 በሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የካቲት 8 ቀን 1998 በቁጥር 40410 በሰጠው ትዕዛዝ ላይ የአሁኑ ተጠሪ ከተጠያቂነት ነጻ ናቸው በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል ብቻ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል።
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 25 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- አቶ አብራር ሳቢር - ጠበቃ ቸርነት ወርዶፋ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ አለምፀሐይ ወሰኔ - በሌሉበት የሚታይ ነው

2. ጥበቡ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ አበበ ምትኩ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ የሰሌዳ ቁጥር 2-37663 ሀይሉክስ ቶዮታ መኪና፣ ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች የሆነች ባለቤታቸውን (አቶ አብርሃም አክሊልን) በአቶ ዘነበ ብርሃኑ ጥቅምት 25 ቀን 1996 ዓ.ም በመነዳት ላይ እያለች ሸረራ በተባለ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ክልል ውስጥ ስትደርስ መንገዱን በመልቀቅ ሮጣ ከእንጨት ላይ በመጋጨት በአቶ አብርሃም ላይ ጉዳት በማድረሷ አቶ አብርሃም በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ታህሳስ 03 ቀን 1996 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን፣ በሕይወት እያሉም የፍራፍሬ ንግድ ስራ ሰርተው ገቢ ያስገኙ እንደነበር፣ ሚች እድሜአቸው 32 ዓመት እንደነበር፣ በሚያገኙት ገቢም ተጠሪን ያስተዳድሯቸው እንደነበርና የገቢ መጠኑንም ጭምር በመግለጽ በጉዳቱ ምክንያት ብር 134,400.00(አንድ መቶ ሰላሳ አራት ሺህ አራት መቶ ብር) ገቢ የተቋረጠባቸው መሆኑን፣ ለህክምናና ለቀብር ወጪ ማውጣታቸውን የሕሊና ጉዳትም የደረሰባቸው መሆኑን ጠቅሰው በጠቅላላው ብር 138,400(አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ብር) በክሱ ምክንያት ካወጡት ወጪና ኪሳራዎች ጋር አመልካች እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመኪናዋ ባለንብረት ቢሆኑም መኪናዋን ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በኮንትራት ሰጥተው በነበሩበት ወቅት ጉዳቱ መድረሱን ገልጸው ኃላፊነት የለብኝም በማለት የተከራከሩ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪም ወደ ክሱ እንዲገባ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክሱ እንዲገባ ትእዛዝ ሰጥቶ ተጠሪም ቀርቦ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የአሁኑን አመልካች በመኪናው ባለንብረትነቱ ለጉዳቱ ኃላፊ ሲያደርግ 2ኛ ተጠሪን ግን ከክሱ ነጻ አድርጎታል፡፡ የጉዳት መጠኑን በተመለከተም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በርትዕ ብር 40,000.00(አርባ ሺህ) ሊሆን ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ለጉዳቱ ኃላፊ፣ 2ኛ ተጠሪን ደግሞ ነፃ በማድረግ የሠጠውን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የጉዳት መጠኑን ብቻ ብር 25,000.00(ሃያ አምስት ሺህ ብር) እንዲሆን በማሻሻል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ ተብለው መወሰኑም ሆነ ለ1ኛ ተጠሪ ካሳ ይከፈል ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095፣ 2082፣ 2089 እና 2102 ድንጋጌዎች ውጪ ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ኃላፊነትን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ ሕጋዊነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው 2ኛ ተጠሪ ቀርቦ በጠበቃው አማካኝነት ጥቅምት 11 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሱን የሰጠ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ግን በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2082(2) እና 2089 ድንጋጌዎች አንፃር ለይቶ ለመወሰን ሲባል ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት አብርሃም አክሊል ንብረትነቱ የአመልካች በሆነች ሃይሉክስ ቶዮታ መኪና ተሳፍረው ሲሄዱ በደረሰው አደጋ ምክንያት ከዚህ አለም በሞት የተለዩ መሆኑን፣ መኪናው ጉዳቱን ባደረሰበት እለት በ2ኛ ተጠሪ እጅ የነበረ መሆኑ፣ መኪናው ወደ ሁለተኛ ተጠሪ እጅ ሊገባ የቻለውም በኪራይ ስለመሆኑ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች 2ኛ ተጠሪን ለጉዳቱ ኃላፊነት የለበትም በማለት ሊወስኑ የቻሉት 2ኛ ተጠሪ ሲገለገልበት አልነበረም በሚል ምክንያት ሳይሆን መኪናው ጉዳቱን ባደረሰበት ጊዜ ይሽከረከር የነበረው በአመልካች በተቀጠረ ሹፌር በመሆኑና መኪናውን የመቆጣጠር ኃላፊነት የሹፌሩ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) መሠረት የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው ንብረቱ ተሰርቆ በነበረበት ጊዜ ለደረሰው አደጋ ከተጠያቂነት ነፃ ከሚሆን በስተቀር መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለመንዳት ባልተፈቀደለት ሰው እንኳን ተነድቶ ጉዳት አድርሶ ቢገኝ የመኪናው ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡ የአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት ከውል ውጭ በሚደርሱ ኃላፊነቶች ውስጥ በፍትሐብሔር ሕጉ አጥፊ ሳይሆን አላፊ ከሚባሉት ምድቦች ውስጥ የሚመደብ በመሆኑ መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው ላደረሰው ጉዳት ባለቤቱ ኃላፊ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ስሙ በባለቤትነት ያልተመዘገበ መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለግል ጥቅሙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲገለገልበትና ሲጠቀምበት የነበረው ሰው መኪናው ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው በእጁ በነበረበት ጊዜ ለደረሰው ጉዳት ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናል ማለት አለመሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2082(1) መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መነሻነት በአንድ መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ሰው የመኪናውን ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪውን ባለቤት ወይም በንብረቱ ተገልጋይ የነበረውን ማንኛውም ሰው በአንድነትም ሆነ በተናጠል ክሶ ለደረሰበት ጉዳት ካሣ ለመጠየቅ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081(1) እና 2082(1) መሠረት መብት ያለውን ያህል የመኪናው ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት ተብሎ የሚታወቀው ሰው የንብረቱ ባለቤት በመሆኑ ብቻ ተበዳይን ተገዶ ክሳሰ በኋላ መኪናውን በእጁ አድርጐ ሲገለገል የነበረውን ማንኛውም ሰው የከፈለውን ገንዘብ እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2083(1) ተመልክቷል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች የተከሰሱት የመኪናው ባለንብረት በመሆናቸው ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ወደ ክሱ እንዲገቡ የተደረገውም መኪናውን ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜ ሲገለገልበት ነበር በሚል ምክንያት ሁኖ ይኸው ስለመሆኑም በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ 2ኛ ተጠሪ መኪናውን ሲገለገልበት የነበረ መሆኑ ከታወቀ የመኪናውን አሽከርካሪ ባለንብረቱ መቅጠሩ መታወቁ መኪናውን ሲገለገልበት የነበረን ሰው ከኃላፊነት ነጻ ሊያደርገው የሚችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2082 ድንጋጌ በመስፈርትነት ያላስቀመጠው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳቱን ያደረሰውን መኪና ሲገለገልበት የነበረው 2ኛ ተጠሪ መሆኑ ከተረጋገጠ የመጨረሻ ኃላፊነቱን (ultimate liability) ሊወስድ የሚገባው ይኸው ተጠሪ ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ለክሱ ኃላፊ፣ 2ኛ ተጠሪን ከክሱ ነጻ በማድረግ ውሳኔ መስጠታቸው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2081፣ 2082(1) እና 2083 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሚች በፍራፍሬ ንግድ ስራ ላይ የነበሩ መሆኑና ሲያገኙ የነበሩት የገቢ መጠን ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካችም ሆነ ጣልቃ ገብ የነበረው 2ኛ ተጠሪ በዚህ ረገድ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ማስረጃ የሚያፈርስ የመከላከያ ማስረጃ አለማቅረባቸው በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳቱ ምክንያት በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረባቸውን ጥቅም በተጠሪ ማስረጃ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ ተጠሪዋ የሚገባቸውን የካሳ መጠን በርትዕ በመለየት ወስነዋል፡፡

ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋጥ ሲሆን የካሳ አተማመን፣ መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣ 2091፣ 2092፣ 2095 እና 2102 ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሁኖ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች በሚሰጡት የካሣ መጠን ላይ ይግባኝ የሌለው መሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2152 ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኙ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 ስር ተገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ለ1ኛ ተጠሪ ይከፈል የተባለው ካሳ መጠን ብር 25,000.00(ሃያ አምስት ሺህ ብር) የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ አመልካችን ኃላፊ በማድረግ ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሲሆን በካሳ መጠኑ ግን ሊነቀፍ የሚችል ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 2ኛ ተጠሪ ጉዳቱን ያደረሰውን መኪና ሲገለገልበት የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2082(1) መሰረት ለጉዳቱ ኃላፊ ነው ብለናል፡፡
3. ለ1ኛ ተጠሪ ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ) የጉዳት ካሳ ሊከፍላቸው የሚገባው አመልካች ሳይሆኑ 2ኛ ተጠሪ (ጥበብ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር) ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልድ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ከበደ ዓለሙ - ቀረበ

ተጠሪዎች ፡- 1. ፀሐዬ ዘሙይ

2. ሱልጣን ካሕሣይ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ በሰበር ችሎቱ እንዲወሰን የተያዘው ጭብጥ የቤት ኪራይ ውልን መነሻ ባደረገው ክስ የተጠየቀው የገንዘብ ክፍያ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2024/መ/ የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የሰጠው ውሣኔ በሕጉ አግባብ ነው ወይ? የሚል ነው፡፡ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ሲሆን፣ ተጠሪዎችን የከሰሰው በሕግ አግባብ እና በኤጀንሲው የኪራይ መመሪያ መሠረት የኪራይ ውል ሣይኖራቸው በቤቱ የተገለገሉ በመሆናቸው ያለአግባብ በበለፀጉበት መጠን ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎችም ለክሱ በሰጡት መልስ በእነሱ እና በአመልካች መካከል የኪራይ ውል ወይም ግንኙነት እንደሌለ በመግለጽ የመክሰስ መብት የለውም እንደዚሁም ገንዘቡ የተጠየቀው በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ስላልሆነ ክሱ ሊስተናገድ አይገባም በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የክሱን ሥረ ነገር በሚመለከትም ቤቱን የያዝነው ከቀድሞው ተከራይ የንግድ መደብሩን በመግዛት ነው፡፡ ቤቱ በአሁኑ ጊዜ ፈርሶአል የሚሉትን የመከራከሪያ ነጥቦች በማንሣት ክሱ ውድቅ ይደረግላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት ክርክሩን የመረመረ ሲሆን፣ በመቀጠልም የክፍያ ጥያቄው በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2024/መ/ መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የሥር ፍ/ቤቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠየቀው ገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት የህሊና ግምት የወሰዱት ሕጉን በአግባቡ በመተርጎም ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን መሠረት በማድረግ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የአመልካች እና የተጠሪዎች ግንኙነት በኪራይ ውል ላይ የተመሰረተ ላለመሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካች ተጠሪዎችን የከሰሰው የውል ግዴታ አልተወጡም ወይም በገቡት የኪራይ ውል መሠረት ኪራይ አልከፈሉም በማለት እንዳልሆነም ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ክስ የመሠረተው ተጠሪዎች ቤቴን ያለአግባብ ይዘው ከህግ ውጪ በልጽገዋል በማለት ነው፡፡ በእርግጥ የጠየቀውን ገንዘብ ያሰላው ቤቱን በማከራየት አገኝ ነበር ባለው መጠን ነው፡፡ ተጠሪዎችም በቤቱ አልተገለገልንም የሚል ክርክር አላነሱም፡፡ ይልቁንም ከአመልካች ጋር የውል ግንኙነት የለንም በማለት ገንዘቡን መክፈል የለባቸውም እንዲባልላቸው የተከራከሩት በመሆኑም እነዚህን ፍሬ ነገሮች ደምረን ጉዳዩን ስንመለከተው ክርክሩ ከኪራይ ክፍያ ጋር የሚያያዝበት ምክንያት የለም፡፡

የሥር ፍ/ቤቶች ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢነት አለው በማለት የጠቀሱት የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2024 የሚገኘው “ ስለውሎች በጠቅላላው “ በሚል በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 12፣ በምዕራፍ 7 በክፍል 3 ሥር ሲሆን፣ ክስ የቀረበበት ገንዘብ በሁለት ዓመት እንደተከፈለ የሚያስቆጥር የህሊና ግምት የሚወሰድባቸውን አግባቦችም በዝርዝር ያመለክታል፡፡ የህሊና ግምት ከሚወሰድባቸው የክፍያ ጥያቄዎች አንዱ የቤት ኪራይ እንደሆነም በንኡስ ቁጥር /መ/ ተመልክቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ የኪራይ ገንዘብ እንደሆነ ከላይ በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2024 ለክርክሩ አወሳሰን የሚጠቀስ ወይም አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል በውል ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የለም፡፡ ይህም ሆኖ ግን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚያስችል ምክንያት አለው፡፡ ቤቱን ያለዋጋ ሲጠቀሙ ቆይተዋል፡፡ ይህን የመሠለ ግንኙነት የሚገዛው ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነት እና ያለአግባብ ስለመበልፀግ በሚል በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13 በምዕራፍ 2 ሥር ባሉት ድንጋጌዎች ነው፡፡ የሌላ ሰው ሐብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አለአግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠን ለባለሐብቱ ኪሣራ መክፍል እንዳለበት ከፍ ሲል በተጠቀሰው በምዕራፍ 2 ሥር በሚገኘው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2162 ተመልክቶአል፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ተጠሪዎች የአመልካች ንብረት በሆነው ቤት አልተገለገልንም የሚል ክርክር የላቸውም፡፡ አመልካች አስልቶ ባቀረበው የገንዘብ መጠንም ተቃውሞ አላነሱም የገንዘብ መጠኑ የተሰላው የንግድ ሥራ የሚካሄድባቸው ቤቶች ለሌላ ሰው በንግድ ሽያጭ ውል ሲተላለፉ ኪራይ ለመተመን በኤጀንሲው በወጣው መመሪያ መሠረት ነው፡፡ ይህም ማለት ቤቱ በተጠሪዎች በመያዙ ምክንያት አመልካች የወሉን ገቢ ነው የጠየቀው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በቤቱ መገልገላቸው እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካች ቤቱን ባለው መመሪያ መሠረት አከራይቶ ሊያገኝ ይችል የነበረውን ገንዘብ ያክል የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች እነዚህን ሁኔታዎች ሣያገናዝቡ ሕጉን ተከትለው ጉዳዩን ሣይመረምሩ በመወሰናቸው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 130183 ሐምሌ 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 84627 ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 138,122.19 /አንድ መቶ ሠላሣ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሁለት ብር ከአሥራ ዘጠኝ ሣንቲም/ ለአመልካች በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 38117

ሐምሌ 9 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዩ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ብርሃኑ ፈይሳ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ናይል ኢንሹራንስ /አ.ማ/

2. አቶ ሰለሞን አህመድ በሌሉበት ታይቷል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ በመዝገብ ቁጥር 15427 ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 5984 መጋቢት 11 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በማመልከታቸው ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በከፍተኛው ፍርድ ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ንበረትነቱ የአንደኛው ተጠሪ የሆነ ሱዙኪ ቪታራ መኪና በሁለተኛው ተጠሪ በማሽከርከር ላይ እያለ የካቲት 6 ቀን 1996 ዓ.ም ከቀኑ በግምት ስድስት ሰዓት ሲሆን በአንጦሰላናጠራ ወረዳ መኪ ከተማ ከትምህርት ቤት ፊት ለፊት መንገዱን በመሳት የአስራአንድ ዓመት ታዳጊ ወጣት የሆነውን ልጁን ዮሐንስ ብርሃኑን በመግጨት የሞት አደጋ አድርሶበታል፡፡ በልጁ መሞት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰብኝ ሲሆን ልጁ አስራ ስምንት ዓመት ከሞላው በኋላ ለእኔ ሊያደርግልኝ የነበረ ድጋፍ እንክብካቤና የገንዘብ እርዳታ ቀርቶብኛል፡፡ ስለዚህ ታዳጊ ወጣት ብርሃኑ ፈይሳ ቢኖር ኖሮ እድሜው አካለ መጠን ሲደርስ ሊያደርግልኝ የሚችለው ድጋፍ እንክብካቤና የገንዘብ ድጋፍ የቀረብኝ በመሆኑ አንደኛ ተከሳሽ /ተጠሪ/ የመኪናው ባለቤት በመሆኑ ሁለተኛው ተጠሪ /ተከሳሽ/ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ዩሐንስ ብርሃኑን ለሞት የዳረገ በመሆኑ ብር 76,800 /ሰባ ስድስት ሺ ስምንት መቶ ብር/ ካሣ እንዲከፍሉኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው በተናጠል የመከላከያ መልስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በህፃኑ መሞት ምክንያት አመልካች በክሱ የገለፁትን ያህል ወደፊት የሚገኝ ጥቅም የቀረባቸው መሆኑን በማረጋገጥ አላቀረቡም፡፡ ሟች ህፃን ብርሃኑ ፈይሳ ራሱን በመርዳት ለአባቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እገዛ ማድረግ የሚችል ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለም፡፡ ስለዚህ ከሳሽ /አመልካች/ ለደረሰባቸው የህሊና ጉዳት የሞራል ካሣ ከሚጠይቁ በስተቀር የቀረባቸው ጥቅም ስለመኖሩ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ጥያቄአቸው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ህፃን ብርሃኑ ፈይሳ ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ በአንድነትና በነጠላ አላፊነት አለባቸው በማለት ኃላፊነቱን በሚመለከት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የካሣውን መጠን በተመለከተ ከሳሽ /አመልካች/ በልጃቸው መሞት ምክንያት የቀረባቸው ጥቅም ያለ መሆኑንና ለወደፊቱም የሚቀርባቸው ጥቅም ስለመኖሩ ያላረጋገጡ ስለሆነ ጥያቄአቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ በአደጋው ምክንያት ልጃቸው በመሞቱ ለደረሰባቸው የህሊና ጉዳት ካሣ ብር 800 /ስምንት መቶ ብር/ አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም አሻሽሎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ልጁ ብርሃኑ ፈይሳ በደረሰበት የመኪና አደጋ በመሞቱ ልጁን ለማሳደግና ለማስተማር ያወጣሁት ወጭ ፍሬ አልባ ከመሆኑ በተጨማሪ ከትምህርት ቤት መልስ ያደርግልኝ የነበረው እገዛና ይሰጠኝ የነበረው ግልጋሎት ተቋርጦብኛል፡፡ እኔ ሚች ታዳጊ ወጣት ብርሃኑ ፈይሳ ከትምህርት ቤት መልስ ከብቶችን በመንከባከብና በሌሎች የእርሻ ሥራዎች የሚያደርግልኝን እገዛ ከሌላ ሰው ለማግኘት በቀን አስር ብር /10 ብር/ እከፍላለሁ፡፡ ልጁ በህይወት ቢኖር ኖሮ በእውቀቱና በጉልበቱ ሠርቶ ሊያገኝ የሚችለው ገቢ እየጨመረ እንደሚሄድና ሌላ የሌለኝ በመሆኑ በእሱ መሞት ምክንያት ከፍተኛ ችግርና ኪሣራ እንደሚገጥመኝ የታወቀ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 559/2000 ተሸክርካሪ በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት የሚገባው የመድን ዋስትና መነሻው ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን መነሻ በማድረግ አለመወሰናቸውና በህፃን ብርሃኑ ፈይሳ መሞት ምክንያት የደረሰብህና ለወደፊትም የሚደርስብህ ጉዳት የለም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ሁለተኛ ተጠሪ መጥሪያው በፍርድ ቤት ቅጥር ጊቢ ተለጥፎ ያልቀረበ በመሆኑ ጉዳዩ ተጠሪዎች በሌሉበት እንደሚታይ ችሎቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ህፃን ብርሃኑ ፈይሳ በመሞቱ የደረሰባቸው እርግጠኛ ጉዳት ያለ መሆኑንና ህፃን ብርሃኑ ፈይሳ ለሌላ ሰው የሚከፍሉትን በቀን የአስር ብር ወጭ ይሸፍንላቸው እንደነበር ወደፊትም ያለጣሪ መቅረታቸው ራሱን የቻለ ጉዳት እንደሆነ በቃል ክርክር አስረድተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካች በጽሁፍና በቃል ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች እድሜው አስራ አንድ የሆነው ልጃቸው የሞት አደጋ ስለደረሰበት የደረሰባቸው እርግጠኛ ጉዳትና የቀረባቸው ጥቅም አለ ወይስ የለም? አመልካች በህፃኑ መሞት ምክንያት ወደፊት ሊያገኙ ይችሉ የነበሩት ጥቅም ቀርቶባቸዋል ወይስ አልቀረባቸውም? የሚሉት ነጥቦች የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ አርሶ አደር መሆናቸውን ከመዝገቡ ውስጥ ያሉት ፍሬ ጉዳዮች ያሳያሉ፡፡ በእርሻ ሥራ ውስጥ ሚች የሚያደርግላቸው እገዛና የሚሰጣቸው ግልጋሎት እንደነበር ተጠሪዎች በግልጽ ክደው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልተከራከሩም፡፡ ይሽም ተጠሪዎች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234/1/ ሠ መሠረት በአመልካች በኩል የተነሱትን ነጥቦች እንዳመኑ የሚያስቆጥር ነው፡፡ ሟች ለአመልካች ከትምህርት ቤት ሲመለስና በእረፍት ቀናት የተለያዩ አገልግሎቶች እገዛ ያደርግላቸው የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ በሟች መሞት ምክንያት የደረሰበት ጉዳት የለም ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የአስራ አንድ አመት ልጃቸው በደረሰበት የመኪና አደጋ በመሞቱ ልጃቸው ወደፊት የሚሰጣቸው የጉልበትና ሌሎች እገዛዎች የተቋረጠ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች የአስራ አንድ ዓመት ልጃቸው በደረሰበት የመኪና አደጋ በመሞቱና ከልጃቸው ያገኙት የነበሩት የእርሻ ሥራ ድጋፍና እገዛ ተቋርጦባቸዋል፡፡ አመልካች ይህንን እገዛ ወደፊት ሊያገኙ የሚችሉ የነበረ ቢሆንም ወደፊት ከልጃቸው ሊያገኙት የሚችሉት እገዛና ድጋፍ ተቋርጦባቸዋል፡፡

ስለዚህ አመልካች የካሣ ጥያቄ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2090 እና በፍታብሐር ሕግ ቁጥር 2091 የሚሸፈን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የካሣው መጠንም መወሰን ያለበት አመልካች ልጃቸው ቢኖር ሊያገኙት የሚችሉትን ጥቅም መሠረት በማድረግ ሳይሆን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2095 ንዑስ አንቀጽ 2ን መሠረት በማድረግ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች የደረሰባቸውንና ወደፊት ሊደርስባቸው የሚችለውን እርግጠኛ የጉዳት መጠን ለማረጋገጥ ባይቻልም እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ዳኞች ፍትህንና ርትዕን መሠረት በመድረግ እንደሚወስኑ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2092/1/ የሚደነግግ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች በዚህ ድንጋጌ መሠረት የአመልካችን ጥያቄ ተቀብለው ውሣኔ አለመስጠታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የሞራል ካሣ ብር 800 /ስምንት መቶ ብር/ ብቻ ይከፈላቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

የካሣውን መጠን በተመለከተ ርትዕና ፍትህን መሠረት በማድረግ እንዲወስኑ ጉዳዩ ለሥር ፍርድ ቤት ቢመለስ የሚያስከተለውን ወጭና በአመልካች ላይ የሚደርሰውን መጉላላት ታሳቢ በማድረግ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ እንዲከፍሉ በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2092/2/ መሠረት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠዎች የሥር ፍርድ ቤት የወሰነውን የሞራል ካሣ 800 እና በዚህ ፍርድ ቤት የተወሰነውን ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ/ በድምሩ 12,800 /አስራ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ብር/ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች ይክፈሉ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 3 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ዓለማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ጉና ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ - ጠበቃ ጥላዬ ተገኝ ቀረበ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. ቡሬ ባጉና የማዕድን ውሃ ፋብሪካ

2. ሞሃ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ አ/ማ - ጠበቃ ተፈራ ደንበል - ቀረበ፡፡

3. የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ታምራት አባተ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአፈፃፀም ሂደት የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የአፈፃፀም መዝገቡ የተከፈተው የአሁኑ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ለማስፈፀም ነው፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ክርክሩ ውስጥ የገቡት የአፈጻጸም ሂደቱ የእኛን መብት ነክቶአል በማለት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው አመልካች በፍርድ ባለመብትነቱ በ1ኛ ተጠሪ ፋብሪካ ላይ የአፈጻጸም ትዕዛዝ አሰጥቶ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፋብሪካው የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በ1ኛ ተጠሪ ላይ ላሰጠው ውሳኔ ማስፈጸሚያነትይውል ዘንድ በፋብሪካው ላይ የሐራጅ ማስታወቂያ አስቀድሞ አውጥቶ እንደነበር እና በዚህ ጨረታም 3ኛ ተጠሪ ተወዳድሮ በማሸነፍ ፋብሪካውን እንደገዛ፣ በመቀጠልም 3ኛ ተጠሪ ፋብሪካውን ለ2ኛ ተጠሪ እንደሸጠው፣ 2ኛ ተጠሪም ዋጋውን ከመክፈሉም በላይ፣ ፋብሪካውን በስሙ አስመዝግቦ ባለቤት እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም እነዚህን ሁኔታዎች በተጨባጭ ካረጋገጠ በኋላ፣ አመልካች የ1ኛ ተጠሪ ፋብሪካ ነው በማለት አሰጥቶት የነበረውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲቋረጥ ወስኖአል፡፡ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2001 ዓ.ም. በጻፈው ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ/ትዕዛዝ/ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ አቤቱታ አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ክርክሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰምተናል፡፡ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት የቀረቡት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሲሆኑ፣ 1ኛ ተጠሪ በጥሪው መሠረት ባለመቅረቡ ክርክሩ የተሰማው በሌለበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ለወደፊቱ የሚሰጥ ፍርድን ማስፈጸም ይቻል ዘንድ ለዋስትና ሲባል የተከበረ ንብረት በሌላ እዳ ምክንያት በተሸጠ ጊዜ ቀደም ሲል ንብረቱን ያስከበረው ወገን የሚኖረው መብት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ አግባብነት ካለው ሕግ አኳያ ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራቀኝ ወገኖች በዚህ ረገድ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ /ትዕዛዝ/ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ፋብሪካው የተሸጠው ፍ/ቤት በሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ መሠረት ነው፡፡ በወቅቱ የፍርድ ባለመብት የነበረው ግብር አስገቢ የሆነው የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ወይም መሥሪያ ቤት ነው፡፡ አመልካች ንብረቱን አስከብሬ /በፍ/ቤት የእግድ ትዕዛዝ አሰጥቼ/ ነበር የሚለው ፋብሪካው ከመሸጡ በፊት ነው፡፡ ሆኖም ከፋብሪካው ይፈለግ የነበረው የግብር ዕዳ በመሆኑ እና የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ከማናቸውም ሌሎች ባለዕዳዎች የቀድምትነት መብት እንዳለው በገቢ ግብር አዋጅ ቁ. 286/1994 አንቀጽ 80/1/ በመደንገጉ ፋብሪካው የግብር ዕዳውን ለመክፈል ሲባል መሸጡ ተገቢ ነው፡፡ አመልካችም በዚህ ጊዜ የነበረው መብት ከሺያጩ ገንዘብ ላይ ተራፊ ካለ መብቱን አስረድቶ መውሰድ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ፋብሪካውን የመከተል ወይም ከገዛው ወገን ላይ ወስዶ ማሸጥ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ፋብሪካውን የገዛው ከ3ኛ ተጠሪ ላይ ነው፡፡ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በግብር ዕዳው ምክንያት በወጣው ጨረታ ተወዳድሮ በማሸነፍ ፋብሪካውን ገዝቶአል፡፡ በዚህም የፋብሪካው ባለቤት ሆኖ ነበር፡፡ በዚህ መልክ ያገኘውን የባለቤትነት መብት መሠረት በማድረግም ነው ፋብሪካውን ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠው፡፡ በመሆኑም አመልካች በ3ኛ ተጠሪ ላይ ያልነበረውን መብት በ2ኛ ተጠሪ ላይ ሊኖረው አይችልም፡፡ ሲጠቃለል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር በዚህ ረገድ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.51946 ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ.ቁ.45060 ግንቦት 21 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ-ሥ ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪራቸውን ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኅዳር 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ አስካለ ደግለኝ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ብዙነሽ ደግለኝ - ቀረቡ

3. አቶ ደረጃ ደግለኝ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ የትምወርቅ ታደሰ - በሌሉበት ይታያል

2. አቶ በድሩ የሱፍ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች የፍርድ ባለእዳዎች (የአፈፃፀም ተከሳሾች) አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት (የአፈፃፀም) ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የወረዳው ፍርድ ቤት ባወጣው የሀራጅ ማስታወቂያ መሰረት በጨረታ በመካፈል በብር 32,000 (ሰላሣ ሁለት ሺ ብር) አሸናፊ በመሆን ቤት ገዝቷል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት ከቤቱ ሽያጭ ዋጋ የአንደኛ ተጠሪ ድርሻ 16,100(አስራ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ብር) መሆኑንና አንደኛ ተጠሪ ድርሻዋን እንዲከፍላት አድርጓል፡፡ ቀሪው ብር 16,100(አስራ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ብር) የአመልካቾች ድርሻ መሆኑንና አመልካቾች ድርሻቸውን ለመውሰድ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በሞዴል 85 ተይዞ እንዲቆይና በጠየቁ ጊዜ እንዲሰጣቸው ትእዛዝ ሰጥቶ የአፈፃፀም መዝገቡን ዘግቷል፡፡ በዚህ የአፈፃፀም ትእዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከሐራጅ ሽያጩ በፊት ቤቱ ብር 40,000 መገመቱን አንደኛ ተጠሪ በእርቅ ብር 20,000 ለመውሰድ ተስማምታ እያለ በእርቅ ስምምነቱ መሰረት እንዲፈጸመላት የአፈፃፀም ክስ ስታቀርብ ቤቱ በብር 28,047.50(ሃያ ስምንት ሺ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አርባ ሰባት ብር ከሃምሣ ሣንቲም) ግምት መነሻ ለጨረታ እንዲቀርብና በብር 32,200 እንዲሸጥ ማድረጉ ስህተት ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ ሽሮታል፡፡

በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት የቤቱ የጋራ ባለሐብት የሆነችው አንደኛ ተጠሪና ቤቱን በሐራጅ ተጫርቶ የገዛውና የቤቱን ሙሉ ዋጋ ለወረዳው ፍርድ ቤት ገቢ ያደረገው ሁለተኛው ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፍርድ ባለእዳዎች የአፈፃፀም ክሱና መጥሪያው ደርሷቸው በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረባቸው ቤቱ በሃራጅ እንዲሸጥ የወሰነ መሆኑን በመግለጽ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ የወረዳው ፍርድ ቤት ትእዛዝ የሰጠው በእርቅ ውሣኔው መሰረት የማይፈጽመውን ምክንያት በቀነ ቀጠሮው ቀርበው ባለማስረዳታቸውና በሌሉበት የተሰጠውን ትእዛዝ በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 ሣያስነሱ አዲስ ክርክር በይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ማቅረባቸው የሕግ ድጋፍ የሌለው መሆኑን በመዘርዘር የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡ አመልካቾች መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አንደኛ ተጠሪና ሟች አባታችን የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት እንድናካፍላት አንደኛ ተጠሪ ክስ አቅርባ ቤቱ በብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ ተገምቶ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ልንከፍላት በሽማግሌ ታርቀን እርቁ በፍርድ ቤት ተመዝግቧል፡፡ ከዚህ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ያቀረበችው የአፈፃፀም ክስና መጥሪያ ሣይደርሰን በብር 28,047.50 ለሐራጅ ቀርቦ በብር 32,200 መሸጡ ተገቢነት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ሐራጅ በሚከናወንበት ወቅት ቤቱን ለማስቀረት ጠይቀን በወረዳው ፍርድ ቤት ተከልክለናል፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሐራጅ ሽያጩ የፍትሐብሔር የሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎችን ያልተከተለ መሆኑን በማረጋገጥ የወረዳውን ፍርድ ቤት ትእዛዝ በመሻር የሰጠውን ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ መጥሪያው በፍርድ ቤት ግቢ ተለጥፎ ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ ሰኔ 11 ቀን 2002 ዓ.ም ባቀረበው መልስ አመልካቾች ለወረዳው ፍርድ ቤት በፍርድ ቤት በፀደቀው የእርቅ ስምምነት መሰረት የማይፈጽሙበትን ምክንያት እንዲያስረዱ በተሰጠው ቀነ ቀጠሮ ቀርበው ባለማስረዳታቸውና በሂደቱም ሐራጁን ለማስቆም ወይም ለማሳገድ ያደረጉት እንቅስቃሴ ሣይኖር በሕጉ መሰረት ተጫርቼ ከገዛሁና ሙሉ ዋጋውን ከከፈልኩ በኋላ በሥር ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን ክርክር በማንሣት ሐራጁ እንዲሰረዝ የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ ድጋፍና መሰረት የለውም ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 ለአፈፃፀም ክርክር ተፈፃሚነት እንዳለው በመቁጠር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉም ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር የቀረበ መሆኑን በመገንዘብና የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ የሚሻርበት ህጋዊ ምክንያት አለ? ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ በመመሥረት ጉዳዩን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካቾችና አንደኛ ተጠሪ በመጀመሪያ በፍርድ ቤት የተከራከሩበት በኋላም የእርቅ ስምምነት አድርገውና በፍርድ ቤት አጸድቀው የጨረሱት መሰረታዊ ጉዳይ የአመልካቾች ወላጅ አባትና የአንደኛ ተጠሪ የጋራ ሐብት የሆነውና በሃራጅ የተሸጠው ቤት ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ አመልካቾች በገቡትና በፍርድ ቤት በፀደቀው የእርቅ ስምምነት መሰረት ብር 20,000(ሃያ ሺህ ብር) እንዲከፍሏት የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስና መጥሪያ አልደረሰንም በማለት አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የገለፁ ቢሆንም የአፈፃፀም ክስና መጥሪያው ደርሷቸው በቀነ ቀጠሮው በፍርድ ቤት በፀደቀው የእርቅ ስምምነት መሰረት የማይፈጽሙበትን ምክንያት ባለማስረዳታቸው የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካቾች አባትና አንደኛ ተጠሪ የጋራ ሐብት የሆነው ቤት በሐራጅ እንዲሸጥ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች የፍርድ ቤቱ መጥሪያና አንደኛ ተጠሪ ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ የደረሳቸው መሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተረጋገጠና በውሣኔውም በግልጽ ያሰፈረው በመሆኑ አመልካቾች የአፈፃፀም ክስና መጥሪያው አልደረሰንም በማለት ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢና ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 መሰረት ማስነሳት ነበረባቸው የሚል ትችት በውሣኔው ውስጥ አስፍሯል፡፡ የአፈፃፀም ክስና መጥሪያው ደርሶት የፍርድ ባለእዳው ሣይቀርብ በሚቀርበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ሥርአት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 70/ሀ/ ድንጋጌን መሰረት የሚያደርግ አይደለም፡፡ ስለሆነም የፍርድ ባለእዳው ባለመቅረቡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 መሰረት ለማስነሣት የሚቻልበት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለፍታብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 በአፈፃፀም ክርክር የፍርድ ባለእዳው በሌለበት የተሰጠውን ትእዛዝ ለማስነሣት እንደሚያገለግል በመቁጠር የሰጠው የሕግ ትርጉም ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 78ን አላግባብ የጠቀሰና የተረጉመ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የአፈፃፀም ክርክር ስለሚመራበት ሥርአት የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ስንመለከት የአፈፃፀም ክስ ማመልከቻውና የፍርድ ቤቱ መጥሪያ የደረሰው የአፈፃፀም ተከሳሽ ወይም የፍርድ ባለእዳ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ቀነ ቀጠሮ በመቅረብ ፍርዱን ፈጽሞ ከሆነ ፍርዱን መፈፀሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ወይም ፍርዱን የማይፈጽምበት ምክንያት ካለው ይህንኑ ምክንያቱን ለፍርድ ቤቱ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ የፍርድ ባለእዳው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ ከላይ በተገለፀው መንገድ ካላስረዳ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም አስፈላጊ መስሎ የታየውን ትእዛዝ መስጠት እንዳለበት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 386/2/ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አንደኛ ተጠሪ ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስና መጥሪያ ከደረሳቸው በኋላ አመልካቾች ፍርድ ቤቱ በያዘው ቀነ ቀጠሮ ያልቀረቡ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካቾች አባትና የአንደኛ ተጠሪ የጋራ ሐብት የሆነው ቤት በሐራጅ ተሰጦ አንደኛ ተጠሪ ድሻዋን እንድትወስድ የሰጠው ትእዛዝ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 386/2/ ንመሰረት ያደረገና ጉድለት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት ለፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 78 የተሣሣተ ትርጉም የሰጡ ቢሆንም ስህተቱ በውጤት ደረጃ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የደረሱበትን መደምደሚያ ውሣኔ ሊያስለውጥ የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች የቤቱ በሐራጅ መሸጥ የቤት ግምትና ሌሎች ነጥቦችን በማንሣት የወረዳው ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ትእዛዝ ከመሰጠቱ በፊት በመቅረብ አልተከራከሩም፡፡ አመልካቾች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የእርቅ ስምምነት መሰረት የማይፈጽሙበትን ምክንያት በቀነ ቀጠሮው ቀርበው አላስረዱም የወረዳው ፍርድ ቤት ቤቱ በባለሙያ ተገምቶ ለጨረታ እንዲቀርብ ማድረጉ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 423ና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካቾች የጨረታው ሒደት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 445 የተደነገጉ ተግባራት የተፈፀሙ መሆኑን ያላስረዱ በመሆኑ የእርቅ ስምምነት ያደረግንበት የቤት ዋጋ ቤቱ በሐራጅ ለሁለተኛ ተጠሪ ከተሸጠበት የበለጠ ነበር የሚል ምክንያት በማቅረብ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ያቀረቡት ጥያቄ የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ በማጽናት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማጽደቁ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 13 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ኮሎኔል ግርማ ኃይለሥላሴ - ወኪል ስርጉት በላይ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አስማማው መንግሥቱ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሁለት የፍርድ ባለመብቶች መካከል አንዱ የፍርድ ባለእዳን ንብረት ቀድሞ ተረክቧል ሊባል የሚችልበትን የሥነ ሥርዓት አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በአስከፈቱት የአፈፃፀም መዝገብ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻና ይዘትም የሚከተለው ነው፡፡ አመልካች አቶ ፍስሐ ወረታ የተባሉት ግለሰብ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አ.አ ቅርንጫፍ ለከባድ የጭነት መኪና መግዣ ብር 291,100.00/ ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር/ ሲበደሩ ዋስ በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ በድሮው አጠራር ወረዳ 16 ቀበሌ 12 / ባሁኑ አጠራር የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13/14/ ክልል ውስጥ የሚገኝ ቪላ ቤታቸውን በመያዣ ሰጥተው የነበረ ሲሆን ዋናው ተበዳሪ የብድር ገንዘቡን መክፈል ባለመቻላቸው ባንኩ ከአሁኑ አመልካች የያዘውን መያዣ በመሸጥ አመልካች የዋናውን ተበዳሪ እዳ ዋናውን ገንዘብ ከእነ ወለዱ ጨምረው ብር 316,300.00 /ሶስት መቶ አስራ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ብር/ ለባንኩ ከፍለዋል፣ ባንኩም ይህንኑ አረጋግጦ ለአመልካች ደረሰኝ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች በአቶ ፍስሐ ወረታ ላይ በዋስትናቸው የከፈሉትን ገንዘብ እንዲተኩላቸው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ለባንኩ የከፈሉትን ገንዘብ ዋናው ተበዳሪ እንዲተካላቸው ፍርድ አግኝተዋል፡፡ ይህንኑ ፍርድ መሠረት በማድረግ የአፈፃፀም መዝገብ ከፍተው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መመልከት ጀምሮ የፍርድ ባለእዳ የሆኑትን ግለሰብ /አቶ ፍስሐ ወረታ/ እንደፍርዱ እንዲፈጽሙ፣ ወይም የማይፈጽሙበትን ምክንያት ካለ ይህንኑ እንዲያስረዱ ተደርጎ ባለእዳው ለአመልካች ገንዘቡን ሊተኩላቸው ወይም ንብረት ካለ እንዲጠቀሙ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የአሁኑ አመልካች የአቶ ፍስሐ ወረታን ንብረት አፈላልገው አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት እንዲገልፁ ተደርጎ አመልካች የፍርድ ባለእዳ ባለቤት በሆኑት ወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ስም የተገዛ ቤት ነው የሚሉትን ለፍርድ ቤቱ ገልፀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም አመልካች የጠቆሙት ቤት በወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ስም የሚታወቅ መሆኑን የሚመለከተው አካል አጣርቶ ለፍርድ ቤቱ ውጤቱን እንዲልክ ፍርድ ቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትእዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩ ይመለከተዋል የተባለው የየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19 አስተዳደር ጽ/ቤት ቤቱ በእርሱ በኩል የማይታወቅና ማህደር የሌለው በመሆኑ እንደፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ለመፈፀም የማይችል መሆኑን ገልጿል፡፡ የአሁኑ አመልካች ቤቱ የፍርድ ባለእዳው ባለቤት ለመሆኑ ማስረጃ አለኝ በማለትም ግንቦት 11 ቀን 1994 ዓ.ም ተደርጓል ያሉትን የሽያጭ ውል አቅርበዋል፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መመርመሮ አለ የተባለው የሽያጭ ውል በሕጉ አግባብ የተደረገ አይደለም፣ የባለእዳው ባለቤት በሻጮች ስም ተተክተው የተመዘገቡና ባለሀብት ስለመሆናቸው አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት አለ በተባለው ቤት አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም ሲል የአመልካችን አፈፃፀም የፍርድ ባለእዳ ንብረትን አፈላልገው ባቀረቡ ጊዜ የማንቀሣቀስ መብታቸውን በመጠበቅ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው አመልካችና አቶ ፍስሐ ወረታ ከተከራከሩ በሁዋላ ቤቱ የጨረቃ ቤት በመሆኑ ብቻ በሐራጅ ከማሸጥ የሚከለክል ሕግ የለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ትእዛዝ ሽሮ አፈፃፀሙ አመልካች አለ ባሉት የአቶ ፍስሐ ወረታ ባለቤት ቤት ላይ እንዲቀጥል በመ/ቁጥር 55873 ህዳር 19 ቀን 2000 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በሁዋላ የአሁኑ ተጠሪ አፈፃፀሙ ይቀጥልበት የተባለው የወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ቤት ከተጠሪ በነበረባቸውና በፍርድ ቤት በተረጋገጠው እዳ ምክንያት የተረከቡትና የርክክቡ ስምምነትም በፍርድ ቤት የተመዘገበበት ነው በማለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ እንዲሰርዝላቸው የተቃውሞ አቤቱታቸውን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበው ከአሁኑ አመልካች ጋር እንዲከራከሩ ከተደረገ በሁዋላ ተጠሪ ከአመልካች ቀድመው አከራካሪውን ቤት በእዳ ምክንያት ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል የተረከቡት መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የቀድሞውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360/2/ መሠረት በመሠረዝ ታህሣሥ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሣኔ ሰጥቶታል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚሁ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈፃፀሙ በቤቱ ሊቀጥል አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

በበኩላችን አመልካች ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈው ማመልከቻ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መሠረት በማድረግ ለተጠሪ ጥሪ አድርገን ክርክሩን በፅሑፍ ሰምተናል፣ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው የተባሉትን የበታች ፍርድ ቤቶችን ዋና መዛግብትም በማስቀረብ የክርክሩን አጠቃላይ ሂደት ተመልክተናል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች የፍርድ ባለእዳ ባለቤት ስለመሆናቸው በማረጋገጥ አፈፃፀሙ በቤቱ እንዲቀጥል ያቀረቡት አቤቱታ የአሁኑ ተጠሪ በቤቱ ላይ ቅድሚያ መብት አላቸው ተብሎ ውድቅ የተደረገው ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 7405 በሆነው መጋቢት 09 ቀን 1994 ዓ.ም ክስ የመሠረቱ ሲሆን ሐምሌ 12 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሊፈፀም የሚችል ፍርድ በአቶ ፍስሐ ወረታ ላይ ያስፈረዱ መሆኑን፣ ይኸው ፍርድ እንዲፈፀምላቸው ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ ማመልከቻ አቅርበው የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 23051 ማስከፈታቸውን፣ አፈፃፀሙን፣ የያዘው ፍርድ ቤትም ለፍርድ ባለእዳ እንደፍርዱ እንዲፈጽሙ፣ የማይፈጽሙበት ምክንያት ካለም ቀርበው እንዲያስረዱ ትእዛዝ ሰጥቶ የፍርድ ባለእዳ የሆኑት አቶ ፍስሐ ወረታ ፍ/ቤት ቀርበው እንደፍርዱ ለመፈፀም የማይችሉ መሆኑን ከመግለጽ ውጭ እንደፍርዱ ላለመፈፀምያቀረቡት ምክንያት የሌለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ፍ/ቤቱ ገልጾ አፈፃፀሙ ከቀጠለ በሁዋላ የአሁኑ አመልካች የፍርድ ባለእዳ ንብረትን በማፈላለግ አሁን አከራካሪ የሆነው ንብረት እንዲከበርላቸው አቤቱታ አቅርበው አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤትም የፍርድ ባለመብት የሆኑት የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር የሌለው የፍርድ ባለእዳ ባለቤት በሆኑት የወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ስም የሚገኝ ቤት ተከብሮ እንዲቆይ በማለት ጥቅምት 08 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቶ እንደትእዛዙ እንዲፈጽም ለክፍሉ ቀበሌ ትእዛዙን ሲልክ የክፍሉ ቀበሌ ቤቱ የለም በማለት ጥቅምት 16 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ ገልጿል፡፡ ፍርድ ቤቱን የፍርድ ባለመብት የሆኑት የአሁኑ አመልካች ማስረጃ ካላቸው እንዲያቀርቡ እና የፍርድ ባለእዳውም አስተያየት እንዲሰጡበት ከአደረገ በሁዋላ የፍርድ ባለመብት በቤቱ ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ያቀረቡት አቤቱታ ቤቱ የጨረቃ ቤት ነው ስለተባለ ተቀባይነት የለውም በማለት ሚያዚያ 17 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በአከራካሪው ቤት ባለመብት ሁኜበታለሁ የሚሉበት መንገድ የመነጨው በሁለት መዛግብት ሲሆን አንዱ፡- በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 43327 መስከረም 20 ቀን 1997 ዓ.ም በወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ላይ በመሠረቱት ክስ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ሚያዚያ 09 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሣሽ የነበሩት ወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ለአሁኑ ተጠሪ ብር 23,752.55 /ሐያ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሣ ሁለት ብር ከአምሣ አምስት ሣንቲም/ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ አስወስነው ይኸው ፍርድ እንዲፈፀምላቸው ሰኔ 09 ቀን 1998 ዓ.ም የተፃፈ የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው የአፈፃፀሙ ጉዳይ በፌዴራሉ የመ/ደ/ፍ/ቤት መ/ቁጥር 71496 በሆነው ተከፍቶ አሁን እያከራከረ ባለው ቤትም ተጠሪ የእግድ ትእዛዝ ታህሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በፍርድ ቤት አሰጥተው ጉዳዩ እየታየ ባለበት ሂደት ግራ ቀኙ ወገኖች ጉዳዩን ግንቦት 25 ቀን 1999 ዓ.ም አቅርበው ፍርድ ቤቱ በእርቅ ስምምነቱ መሠረት አፈፃፀሙ ማለቁን ተገንዝቤአለሁ በማለት የአፈፃፀሙን መዝገብ ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ዘግቶታል፡፡ ሌላው ተጠሪ በወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ላይ ፍርድ ያገኙ ስለመሆኑ ያሣያል የተባለው ጉዳይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 85943 የታየው ሲሆን ተጠሪ ክስ የመሠረቱት መጋቢት 24 ቀን 1999 ዓ.ም ሁኖ ጉዳዩ ሲታይ ቆይቶ ግራ ቀኙ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ጉዳዩን በስምምነት ጨርሰናል በማለት ስምምነቱ በፍርድ ቤቱ እንዲፀድቅላቸው አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም በስምምነቱ መሠረት ወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ለአሁኑ ተጠሪ ብር 52,769.73 /ሃምሣ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ስልሣ ጠዘኝ ብር ከሰባ ሶስት ሣንቲም/ በመክፈል መዝገቡ እንዲዘጋላቸው ግራ ቀኙ መስማማታቸውን ገልፀው አቤቱታ አቅርበዋል፣ ስምምነቱም ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ተረጋግጧል የሚል ምክንያት በመያዝ ስምምነቱን በማጽደቅ ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 25 ቀን 1999 ዓ.ም ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ጋር አድርጌአለሁ የሚሉት የእርቅ ስምምነት ቤቱን ለሁሉም እዳዎች ስለመረከቤ ያረጋግጣል የሚሉት ነው፡፡ ይህ ችሎትም ከላይ ከተጠቀሱት መዛግብት በፍሬ ነገር ደረጃ በተረጋገጡት ነጥቦች መሠረት ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡

በመሠረቱ ፍርድ እንደፍርዱ መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 378 እና ተከታዩቹ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሣያል፡፡ በአንድ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ላይ አፈፃፀሙን የቀጠሉ ተራ የፍርድ ባለመብቶች ካሉም ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 403 ድንጋጌ መሠረት ምላሽ ሊያገኝ እንደሚችል ሕጉ ያሣያል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 85943 ተሰጠ የሚሉት ትእዛዝ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ጋር ያደረጉትን ስምምነት ለሕግ እና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን በማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ አጽድቆታል የሚሉት ሲሆን ፍርድ ቤቱ የመዘገበው ትእዛዝ የሚያሣየው ወ/ሮ አበበች ለአሁኑ ተጠሪ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ የከፈሉ መሆኑን እንጂ ለሚፈለግባቸው ገንዘብ አሁን እያከራከረ ያለውን ቤት ለማስረከብ ተስማምተው፣ ስምምነቱም ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም ተብሎ የተመዘገበ አለመሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በመ/ቁጥር 71496 ባስከፈቱት የአፈፃፀም መዝገብ ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ትእዛዝም ቢሆን እርቁን የመዘገበ ሣይሆን አፈፃፀሙ በእርቅ መሠረት መፈፀሙ ተረጋግጧል በማለት የፍርድ አፈፃፀም መመሪያ የያዘውን አፈፃፀም ሂደት እንዲያቆም የተደረገበት ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው አሁን እያከራከረ ያለውና ባለሀብትነቱ የወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ስለመሆኑ የተረጋገጠውን ቤት ቅድሚያ ያስከበሩት የአሁኑ አመልካች መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በመ/ቁጥር 85943 ላይ በስር ፍርድ ቤት ባሰጡት ትእዛዝ ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል የሚፈልጉት ገንዘብ የተከፈላቸው መሆኑን መዘገቡ በግልጽ ያሣያል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በመ/ቁጥር 71496 የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ለመውሰድ ያደረጉት ጥረት ስለመኖሩ በማረጋገጥ ይህንኑ ያፀደቀ ሣይሆን አፈፃፀም መቋጨቱን ያረጋገጠበት ነው፡፡ በመ/ቁጥር 71496 የተከፈተው የአፈፃፀም መዝገብ ሲሆን የሚያወሣውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የሚገኘውንና ግንቦት 25 ቀን 1999 ዓ.ም በተጠሪና በወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል መካከል ተደረገ የተባለውን የእርቅ ስምምነት ሲሆን በመ/ቁጥር 85943 ለፍርድ ቤቱ ቀረበ የሚባለው ደግሞ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ተደረገ የተባለው ስምምነት ሁኖ ወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ለተጠሪ እዳቸውን የከፈሉ መሆኑን የተረጋገጠበት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አከራካሪውን ቤት በእዳ ምክንያት ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል ሙሉ በሙሉ ተረክቤአለሁ የሚሉት መክፈሉ በተረጋገጠበት ገንዘብ ጭምር በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡ በሌላ አገላለጽ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ከአመልካች ቀድመው ወስደዋል ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ መክንያት የለም፡፡ ሌላው ተጠሪ በዚህ የሰበር ደረጃ የሚያቀርቡት ክርክር አከራካሪውን ቤት ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል በመረከብ ባሁኑ ጊዜ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ሸጬአለሁ የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የክርክር ነጥብ በተጠሪ ሊነሣ የሚችልበት እና ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በአጠቃላይ አከራካሪው ቤት ላይ ተጠሪ ከአመልካች አስቀድመው በእዳ ምክንያት ወስደዋል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ በእያንዳንዱ መዝገብ ላይ ሲደረግ የነበረውን አጠቃላይ የክርክር ሂደት ከጊዜ ቅደም ተከተሉና በተለያዩ ጊዜአት ሲሰጡ የነበሩትን ትእዛዝ ይዘት በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ስለፍርድ አፈፃፀም የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 55873 ታህሣሥ 24 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35155 ሐምሌ 16 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 23035 ሚያዚያ 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡ በዚህም መሠረት አፈፃፀሙን እንዲቀጥል የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ታዝዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ተጠሪ ከወ/ሮ አበበች ወ/ሚካኤል የሚፈልጉትን ገንዘብ ከመጠየቅ ይህ ፍርድ አያስቀርም ብለናል፡፡
4. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1- አቶ ብርሀን ገ/እግዚአብሔር

2- ወ/ሮ አልጋነሽ ገ/እግዚአብሔር

3- ወ/ሮ ዝማም ገ/እግዚአብሔር

4- ወ/ሮ ሙሉ ገ/እግዚአብሔር

5- ወ/ሮ አልማዝ ገ/እግዚአብሔር

6- ወ/ሪት ገነት ገ/እግዚአብሔር

7- የአቶ አበበ ገ/እግዚአብሔር ወራሾች

/ወ/ሪት ትክሻዬ አበበ ና አቶ ዮሐንስ አበበ

1ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር ለተጠቀሱት ጠበቃ አቶ ደስታ በርሄ ቀረቡ

8- ወ/ሪት ሊንዳ ገ/እግዚአብሔር - ቀረቡ

9- ወ/ሮ ምዕላል ገ/እግዚአብሔር

10- ወ/ሮ ፅጌወይኒ ገ/እግዚአብሔር

11- አቶ ሀይሉ ገ/እግዚአብሔር

12- አቶ ግዛቸው ገ/እግዚአብሔር

ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ቀረቡ

የተጠቀሱት ወኪል አንደኛ ተጠሪ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ለታይ ገ/ጊዮርጊስ ጠበቃ አቶ ደረጀ ወረቁ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በቦሌ ክፍለ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 17 ቀበሌ 24 የቤት ቁጥር 166 ሥር የመኖሪያ ቤትና መጋዘን ያሉ ሲሆን መኖሪያ ቤቱ የአመልካቾች አውራሽና የተጠሪ የጋራ ሃብት መሆኑ በፍርድ የተወሰነ ሲሆን መጋዘኑ የአመልካቾች አውራሽ የግል ንብረት መሆኑ ተወስኗል፡፡

አመልካቾችና ተጠሪ የሚከራከሩት በግቢው ውስጥ የሚገኘው ባዶ ቦታ የመኖሪያ ቤቱ ነው ወይስ የመጋዘኑ ነው በሚለው ነጥብ ላይ ነው፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው የሥር ፍርድ ቤት የቦሌ ክፍለ ከተማ ቦታው በባለሙያ እንዲታይ ካደረገ በኋላ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ቦታ የሚጠቃለለው ወደ መኖሪያ ቤቱ መሆኑን ወይም ወደ መጋዘኑ መሆኑን ወይም መኖሪያ ቤቱና መጋዘኑ የየራሳቸው ይዞታ ካላቸው የይዞታቸውን ስፋት ምን ያህል መሆኑን ለይቶ የእስኬች ማብራሪያ እንዲልክ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ቦታ ለመጋዘን ይሁን ለመኖሪያ ቤቱ ለማሳወቅ የሚችገር እንደሆነና ቀደም ሲል በነበረው ካርታ ይዞታው ተለይቶ ያልተቀመጠ መሆኑንና ለአመልካቾች አውራሽ 1973 ዓ.ም ቦታው የተሰጣቸው የመኖሪያ ቤት በመሥራት እንዲገለገሉበት መሆኑን በመግለፅ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የቀረበለትን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ባዶ ቦታው ወደ መኖሪያ ቤቱ እንዲጠቃለልና አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሠኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡

አመልካቾች ፍርዱን የሚያስፈፅመው ፍርድ ቤት ተጨማሪ ማብራሪያ መጠየቅ አልነበረበትም መጋዘኑ ኤል ሼኘ በመሆኑ ቦታውን ለአመልካቾች ማስረከብ ነበረበት፡፡ መጋዘኑ የተሠራው 1973 ዓ.ም ሲሆን የመኖሪያ ቤቱ የተሠራው 1978 ዓ.ም ነው፡፡ ተጠሪ በመ.ቁ 723592 ባቀረቡት ክስ ቦታው የመጋዘኑ አካል መሆኑን በማመን ገልፀው እያለ በፍርዱ መሠረት ባዶ ቦታውን በእጅ ማስረከብ ሲገባው ከመኖሪያ ቤቱ ጋር እንዲጠቃለል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ህዳር 24 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው መጋቢት 2 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በባለሙያ በኩል እንዲጣራ በማድረግ የሰጠው ትዕዛዝ የህግ ስህተት የለበትም በመዝገብ ቁጥር 723592 የአጥር ግንባታ የተገነባበትን ግምት ከሚጠይቅ ውጭ ስለቦታ የቀረበ ክርክርና የተሰጠ ውሣኔ የለም፡፡ የአመልካቶች አቤቱታ የበታች ፍርድ ቤቶች መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀመ መሆኑን የማያሣይ ከመሆኑም በላይ ፅውነታውን የሚያንፀባርቅ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች መጋቢት 17 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት የመኖሪያ ቤቱና መጋዘኑ ከተሠራበትና በአንድ ካርታ በተጠቃለለው ይዞታ ቦታ ላይ የሚገኘው ባዶ ቦታ የመኖሪያ ቤቱ ነው ወይስ የመጋዘኑ ነው በሚለው ነጥብ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ባዶ ቦታ በመጋዘኑ ሊጠቃለል እንደሚገባ ውሣኔ እንደተሰጠበት በማንሣት የሚከራከሩ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 30811 ውሣኔ የሰጠው መጋዘኑ የአመልካች አውራሽ የግል ንብረት መሆኑን እንጅ በግቢው የሚገኘው ባዶ ቦታ ከመጋዘኑ ጋር ሊጠቃለልና ለአመልካቾች ሊሰጥ የሚገባው መሆኑን አልወሰነም፡፡ በሌላ በኩል በመዝገብ ቁጥር 723592 ተጠሪ ከጋብቻ በኋላ አጥር በማጠር ወለል ሊሾ በማድረግ ያወጡትን ገንዘብ ጠይቀው ውሣኔ የተሰጠበት ሲሆን የባዶ ቦታ ክርክር አቅርበው የተወሰነ ውሣኔ የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ቦዶ ቦታ ከዚህ በፊት በፍርድ ያልተወሰነ በመሆኑ ፍርዱን በማስፈፀሙ ሂደት ቦታው መጠቃለል ያለበት ከመኖሪያ ቤቱ ጋር ነው ወይስ ከመጋዘኑ ጋር የሚለው ጥያቄ ሲነሳ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቦታውን በማየት ካርታውን በመመርመር መግለጫ እንዲሰጥበት አድርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ቦታው የመጋዘኑ ነው ወይም የመኖሪያ ቤቱ ነው ብሎ ለመለየት ያልተቻለና በካርታውም ላይ ያልተመለከተ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል የአመልካቾች አውራሽ በ1973 ዓ.ም ቦታውን የተመሩት ለመኖሪያ ቤት አገልግሎት መሆኑን የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ያረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ ከመኖሪያ ቤቱ ጋር እንዲጠቃለል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ፍርዱን የሚያስፈፅመው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የሚገምተውን ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣን ያለው መሆኑን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 392 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ድንጋጌ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአመልካቾች አውራሽ ቦታውን የመኖሪያ ቤት ለመሥራት የተመሩት መሆኑን ከክፍሉ አስተዳደር የቀረበለትን ማረጋገጫ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቦታው ወደ መኖሪያ ቤቱ እንዲጠቃለል የሰጠውን ትዕዛዝ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማፅናቱ ስለፍርድ አፈፃፀም በተለይም የፍታብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ 392 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ የተሰጠና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር/መ/ቁ. 63754

ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አለ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- አቶ ዓለም ባህታ - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ኑኑሽ ሸህምሉ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ አመልካች ተሰጠ የተባለውን የፍርድ አፈጻጸም አደናቅፎአል በማለት የፌ/የመ/ደረጃ/ፍ/ቤት በአምስት ወር እስራት እንዲቀጣ መወሰኑና ይሄው ውሣኔ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመጽናቱ የቀረበ ቅሬታ ነው፡፡

አመልካች በተፈረደበት የፍርድ አፈጻጸም ማሰናከል ቅጣት ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ያለውን ታህሣስ 14 ቀን 2003 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ቅሬታ ያመለከተ ሲሆን መሠረታዊ ፍሬ ሃሣቡ አመልካች አፈጻጸም በማሰናከል ከዚህ በፊት በ5 ወራት የእስራት ቅጣት የተቀጣ ሲሆን ይሄ ውሣኔ ይግባኝ ቀርቦበት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 73402 የተሻረ ሆኖ እያለ አዲስ ፍሬ ነገር ሣይኖር እንደገና በዚህ ጉዳይ ፍርድ አሰናክሏል በማለት ቅጣት መጣሉ ያለአግባብ ነው አመልካችም የፈጸሙት የማሰናከል ተግባር ባለመኖሩ እና አመልካቹ ላይ የተጣለውም ቅጣት የከበደ በመሆኑ የተሰጠው ቅጣት እንዲሻርልን በማለት የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ በተጠሪ ጠበቃ በኩል በመጋቢት 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡- ቀድሞ የተቀጣበት የፍርድ አፈጻጸም ማሰናከል ጉዳይ ከአሁን ጋር የማይገናኝ በመሆኑና በውሣኔ ያለቀ ጉዳይ የማይባል በመሆኑ ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የፍርድ ማሰናከል ተግባር ተፈጽሟል እና የተጣለበት ቅጣትም የከበደ ባለመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራ ቀኙ የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም በዚህ ጉዳይ ላይ መፍትሄ ማግኘት ያለበት፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. አመልካች የተቀጣበት የፍርድ አፈጻጸም የማሰናከል ኃላፊነት በፊት ከተቀጣበት ምክንያት የተለየ ተግባር በመፈጸም ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ጋር በማገናዘብ መታየት ያለበት በመሆኑ
2. የተፈጠረ የፍርድ ማሰናከል ተግባር አለ ወይስ የለም? እንዲሁም፡-
3. የተጣለው የእስራት ቅጣት አግባብነትን በመመልከት መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

በዚሁ መሠረት ወደ መጀመሪያው ጭብጥ ስንመለስ አሁን ለዚህ ክርክር መነሻ ከሆነው ቅጣት በፊት አመልካች በፍርድ ማሰናከል ተግባር ኃላፊ ተብለው በአምስት ወር እስራት የተቀጡ የነበርና ጉዳዩ በይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ በመዝገብ ቁጥር 73402 የተሻረ መሆኑን ግራቀኙ አልተካካዱም፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ቀድሞ ከተጣለው ቅጣት በኋላ አዲስ የማሰናከል ተግባር ስላልተፈጠረ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት አዲስ ኃላፊነት ሊጣል አይገባም በማለት የአመልካች ጠበቃ ሲከራከሩ በተጠሪ በኩል ደግሞ በቀድሞው የፍርድ ማሰናከል ተግባር ኃላፊ የተደረጉበት ምክንያት ከአሁኑ ጋር የተለየ በመሆኑ ጉዳዩ በውሣኔ የተቋጨ ነው ለማለት የማይችል ባለመሆኑና በሁለቱም ጊዜ ሊያዝ የሚገባው ጭብጥ የተለያየ በመሆኑ ውሣኔ ያገኘና የተቋጨ ጉዳይ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም የሚል ነው፡፡

አሁን እየቀረበ ካለው ክርክር አኳያ ጉዳዩን ስንመረምረው የቀድሞው የፍርድ ማሰናከል ኃላፊነት በአመልካች ላይ የተወሰነው ለፍርድ አፈጻጸም እንዲውል የታገደው የሰሌዳ ቁ. 3-27755 የሆነ መኪና አመልካች በቃለ መሀላ ስር ሆነው መኪናውን ገዝተው እንዳላቸው ከገለጸ በኋላ መኪናውን በወ/ሮ ደብራቱ ውክልና ነው የገዛሁት በማለታቸው እንደሆነ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ያስረዳል፡፡ በአሁኑ ጉዳይ ግን በሌላ ችሎት ተጠይቀው ከላይ የተጠቀሰውን መኪና ከአቶ ተስፋዬ ሞላ የገዙት መሆኑን እንደገና የገለጸ ሲሆን በዚህ መሠረት እንዲፈጽሙ ሲጠየቁ ግዢውን አፍርሸያለሁ ያፈረስኩትም ስመንብረቱን ወደ ራሴ ስም ማዛወር ስላልቻልኩ ነው ከሻጭ ወኪል 100.000 /አንድ መቶ ሺህ/ ብር ተቀብዬ መኪናውን መልሼለታለሁ የተቀበልኩትንም ገንዘብ ተጠቅሜበታለሁ በማለት በማቅረቡ እንደሆነ ተረድተናል፡፡ከዚህ መረዳት የሚቻለው አሁን ለቀረበው ጉዳይ አመልካች ገዝቶ የነበረውን መኪና የተሰጠው እግድ ሳይነሣ መኪናውን ለሻጭ በመመለስ የገዛበትን ገንዘብ መልሶ የተቀበለ ሲሆን ገንዘቡንም ተጠቅሜበታለሁ ማለቱ ከቀድሞ ጉዳይ ጋር አንድ ዓይነት ጭብጥ የሚያዝበት ባለመሆኑ ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል አይችልም ብለናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ በመኪናው ላይ የተላለፈው እግድ ሣይነሣ አመልካች መኪናውን ገዝቶ እያለ ስመ ንብረቱ ወደ እሱ ያለመዞሩን አጋጣሚ በመጠቀም መኪናውን ለሻጭ በመመለስ የገዛበትን ገንዘብ መቀበሉን ገልጿል፡፡ መልሶ በተቀበለው ገንዘብ ላይ አፈጻጸሙ እንዳይቀጥል /እንዳይከፍል/ ደግሞ ተጠቅሞበታል ወይም ገንዘቡ የለም ማለቱ የፍርድ ባለዕዳው ለአፈጻጸሙ የታገደውን መኪና ከማሸሹም በላይ ቢያንስ የተቀበለውን ገንዘብ እንኳ ለዕዳው አለማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 389/1/ /ሀ/ /ለ/ መሠረት ያለበቂ ምክንያት ፍርዱን ላለመፈጸም ከመንቀሣቀሱ በላይ ፍርዱ ያልተፈጸመው አመልካች ፍቃደኛ ባለመሆኑ ብቻ የተለያዩ መሰናክሎችን በመፍጠሩ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም አመልካች የፍርዱን አፈጻጸም አላሰናከልኩም በማለት ያነሱት ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ 389 /1/ /ለ/ መሠረት እስከ 6 /ስድስት/ ወር ሊደርስ በሚችል እስራት ሊቀጣ እንደሚችል ስለሚደነግግ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት የጉዳዩን አጠቃላይ ሂደት በማመዛዘን በ 5 ወራት እስራት የቀጣው መሆኑ ሲታይ የከበደ ቅጣት ነው የሚያሰኝ ባለመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ባጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች የፍርድ አፈጻጸም አደናቆፎአል በማለት የሰጡት የእስራት ቅጣት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ/ቁ. 89236 በቀን 26-01-2003 ዓ.ም እና የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ/ቁ. 115299 በቀን 13-5-02 ዓ.ም በዋሉት ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች የፍርድ አፈጻጸም አደናቅፈዋል በማለት የተላለፈባቸው የ5 ወራት የእስራት ቅጣት በአግባቡ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት የካቲት 16 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ለሚመለከተው ይጻፍ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራቀኙ ላይ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- አቶ ቀደመ ተሾመ - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ ፡- አቶ ኢብራሂም ሐመዱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምርን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 159867 በቀን 30/3/2002 የሰጠውን ፍርድ በአፋር ብ/ክ/መ/ የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና እንዲያስፈፅም በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲያስፈጽምላቸው የአሁኑ የሰበር አመልካች የአፈፃፀም ክስ ሲያቀርቡ ከፍተኛው ፍ/ቤት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ ሂሳብ ሳይጣራ የተሰጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ለማስፈፀም ይቸገራል በማለት ባለመቀበል ፍርድ በመስጠቱና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በማፅናቱ ነው፡፡

የአሁኑ የሰበር አመልካችም በሥር ፍ/ቤቶች ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱትም የቅሬታ ነጥብ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 152121 የተሰጠው ፍርድ የአፈፃፀም ተከሳሾችን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ከሆነ በይግባኝ ወይም በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ በተቀመጠው መሠረት መቃወሚያዎችን በማቅረብ ስህተቱ እንዲታረም ከሚያደርጉ በስተቀር እንዲፈፀም የቀረበውን ፍርድ ሂሳብ ሳይጣራ የተሰጠ ፍርድ ነው በሚል በመተርጎት ለማስፈፀም የሚያስቸገር ነው መባሉ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

ለሰበር አቤቱታው የአሁኑ ተጠሪ /የሥር 2ኛ የአፈፃፀም ተከሳሽ/ በሰጡት መልስ በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍርድ እና ትዕዛዝ ላይ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም የሥር ፍ/ቤቶች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ ባልተጣራና ባልተመረመረ ሂሳብ የተሰጠ በመሆኑ በውክልና አፈፃፀሙን ለመቀጠል የሚያስቸግር ነው ያሉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 371/1/ መሠረት ፍርድ የሚያስፈጽመው ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤት ወይም ፍርዱን እንዲያስፈፅም የታዘዘ ፍ/ቤት ነው፡፡ ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን እንዲያስፈፅም ለሌላ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሰጠ ጊዜም እንዲያስፈፅም የታዘዘው ፍርድ ቤት ስለ ፍርዱ ትክክለኛነት ወይም በግልባጮች ላይ ስለሰፈረው ነገር ሌላ መግለጫና ማብራሪያ ሳይጠይቅ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ማስፈፀም እንዳለበት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 373/2/ ይደነግጋል፡፡ ፍርድ እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍ/ቤትም ፍርዱን የፈረደው ፍ/ቤት ማረጋገጫ እንዲልክለት የሚጠይቀው የፍርዱ ወይም የትዕዛዙ ወይም የግልባጩ ትክክለኛነት የሚያጠራጥር ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ካለው ብቻ ነው፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን ፍርዱን እንዲያስፈፅም የታዘዘው የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዚህ በላይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 373/2/ ከተደነገገው ውጪ ፍርዱን የፈረደው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በአግባቡ ሂሳብ ሳይጣራና ሳይመረመር የተሰጠ ነው በማለት በመተቸት ማብራሪያ መጠየቁና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይኸንኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሥር የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአፈ/መ/ቁ 1917 በቀን 02/11/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 2155 በቀን 21/6/2003 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የሥር የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የሰጠውን ፍርድ እንዲያስፈፅም በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት እንዲያስፈፅም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ ክርክሩን መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ኡልባሬ ሰማን - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የአፈጻጸም ክርክር ነው፡፡ የክርክሩ አመጣጥ አመልካች ከአቶ ሁሴን መሐመድ ጋር የነበረውን የብድር ውል አቶ ሁሴን መሐመድ በብድር ውሉ መሠረት ያልፈጸሙ መሆኑን ገልጾ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የብድር ውሉን በተመለከተ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቀርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል አቶ ሁሴን መሐመድ ብር 601154.55 /ስድስት መቶ አንድ ሺ አንድ መቶ ሀምሣ አራት ብር ከሀምሣ አምስት ሣንቲም/ ለአመልካች እንዲከፍሉ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህንን ፍርድ ለማስፈጸም የአፈጻጸም ክስ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ክስ አቅርቧል፡፡ የአመልካች የአፈጻጸም ክስ የቀረበለት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሆነውና በአቶ ሁሴን መሐመድ ሚስት በወ/ሮ ከድጃ አወል ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቁጥሩ 425 የሆነ ቤት ተሸጦ ለፍርድ ማስፈጸሚያ እንዲሆን በአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 59328 መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ንብረቱ የሚገኝበት የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሻሸመኔ ከተማ በዲዳ ቦቂ ቀበሌ የሚገኘውንና ቁጥሩ 425 የሆነውን ቤት በመሸጥ ፍርዱን እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠረት በማድረግ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሻሸመኔ ከተማ በዲዳ ቦቂ ቀበሌ የሚገኘውና በወ/ሮ ከድጃ አወል ስም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመዝግቦ ያለውን ቁጥሩ 425 የሆነው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ሰጥቶ የሀራጅ ማስታወቂያ ወጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁን ተጠሪ የሀራጅ ማስታወቂያ የወጣበትን ቤት ከወ/ሮ ከድጃ አወል ሀምሌ 6 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ ውል ገዝተው በእጃቸው አድርገው እየተጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽና የቤቱን የሀራጅ ሽያጭ በመቃወም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 418 መሠረት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ቤቱን የገዙት በመሆኑ ለፍርድ ማስፈጸሚያ ሊሸጥ አይገባውም በማለት ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቀረበ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በመሻር ቤቱ ተሸጦ ለፍርድ ማስፈጸሚያ ሊውል ይገባዋል በማለት ውሣኔ ሰጠ፡፡

ተጠሪ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቀረቡ፡፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር ሰምቶ ብይን የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍርዱን እንዲያስፈጽም በሰጠው የውክልና ስልጣን ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሰጠው ብይን የሚቆጠር በመሆኑ ይግባኝ መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሌለውን የይግባኝ ስልጣን በመጠቀም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሻሩ ተገቢ አይደለም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች ጥር 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 374 /1/ን በመተርጉም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 372 /ሐ/ ድንጋጌን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፍርዱን በውክልና የሚያስፈጽም ፍርድ ቤት የሚሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሚኖረውን ውጤትና በትዕዛዝ ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ያገናዘበ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራክሮ ውሣኔ ሊሰጥበት የማይችለውን የተጠሪን ጣልቃገብነት ጥያቄ በመቀበል የሰጠው ውሣኔ ከስልጣኑ ወሰን ያለፈ ነው፡፡ ስለሆነም የውክልና ስልጣኑን በማለፍ የሰጠውን ትዕዛዝ በይግባኝ አይቶ የማረም ስልጣን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው በማለት ሚያዝያ 17 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ በአፈጻጸሙ ሂደት ያቀረቡትን የጣልቃ ገብነት ጥያቄ በመቀበል የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ፍርድ ለማስፈጸም የዳኝነት ስልጣን ስላለው ፍርድ ቤትና ፍርድ የማስፈጸም መሠረታዊ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ፍርዱን ሌላ ፍርድ ቤት እንዲያስፈጽም ስለሚችልበት ሁኔታ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን በሰባተኛው መጽሀፍ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የተሰጡትን ፍርዶች ስለማስፈጸም የሚደነግጉ የሥነ ሥርዓት ህጐች ተደንግገዋል፡፡ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ሰባተኛ መጽሐፍ ማለትም ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 371 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥዓርት ህግ ቁጥር 455 የተደነገጉትን የሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ ግዛት የተሰጠን ፍርድ የማስፈጸም ስልጣን ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ወይም ፍርዱን እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት መሆኑን በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ፍርድ የሚያስፈጽመው ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ወይም እንደፍርዱ እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት ነው በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 371 ንኡስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ፍርዱን ያልሰጠው ፍርድ ቤት በሌላ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሣኔ ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መስጠት የሚችል ስለመሆኑና ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ያልሰጠው ፍርድ ቤት አፈጻጸሙን ተከታትሎ እንዲያስፈጽምለት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 372 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ያልሰጠው ሌላ ፍርድ ቤት ውሣኔውን ተከታትሎ እንዲያስፈጽምለት ትዕዛዝ በሚያስተላልፍበት ጊዜ አብሮ ሊገልጻቸውና ሊልካቸው የሚገቡ ጉዳዮች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 373 የተደነገገ ሲሆን

“ፍርዱን አስፈጻሚው ፍርድ ቤት ስለፍርዱ አፈጻጸም የሚሰጠው ትዕዛዝና በትዕዛዙም ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ ያለው ስልጣን ዋናውን ፍርድ ከወሰነው ፍርድ ቤት ስልጣን ጋር እኩል ሆኖ ይቆጠራል በማለት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 374 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ድንጋጌዎች ፍርድን በሰጠው ፍርድ ቤት ውሣኔውን ተከታትሎ እንዲያስፈጽምለት ለሌላ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመስጠት ስለሚችልበት ሁኔታ ትዕዛዙን የሚሰጠው ፍርድ ቤት ሊያሟላቸው ስለሚገቡ ሥነ ሥርዓቶችና ፍርድ እንዲያስፈጽም በሌላ ፍርድ ቤት የታዘዘው ፍርድ ቤት በአፈጻጸም ሂደት ስላለው ስልጣን የሚደነግጉ ተያያዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም አመልካች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 372 ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 374/1/ ጋር ተያያዥነት የሌለውና ራሱን የቻለ ድንጋጌ ነው በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጹትን ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. አመልካች ውሣኔውን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም የታዘዘ ፍርድ ቤት ሊወስናቸው የሚችላቸው ጉዳዮች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 የተደነገጉት ብቻ ናቸው፡፡ በአፈጻጸም ክርክር የሚቀርብ የጣልቃገብነት ጥያቄ ተቀብሎ የማከራከርና የመወሰን ስልጣን ፍርዱን በውክልና የሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ያለው ስለመሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 ያልተደነገገ በመሆኑ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የሰጠው ብይን ከተሰጠው የውክልና ስልጣን ውጭ ነው በማለት ሰፊ ክርክር አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖም ይህ የተጠሪ ክርክር የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ባህሪና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ የአመልካች ክርክር ፍርድ እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ሰባተኛ መጽሐፍ በምዕራፍ አንድ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ማለትም ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 371 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 455 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ፍርዱን የማስፈጸም ስልጣን እንዳለው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 371 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ ግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ በመሆኑ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 በመሠረታዊ ባህሪው ፍርድ እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች ምንምን እንደሆኑ የሚያመላክት ድንጋጌ /indicative provision of law/ እንጂ ፍርድን እንዲያስፈጽም የታዘዘው ፍርድ ቤት የሚያቸውን ጉዳዮች በሙሉ የሚዘረዝር ድንጋጌ /conclusive provision of law/ አለመሆኑ ነው፡፡ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 ድንጋጌዎችን አመላካች የህግ ድንጋጌ መሆኑን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 418 ንኡስ አንቀጽ 1 በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር የመቃወም አቤቱታ ሲቀርብ ወይም በዚሁ ንብረት ላይ ቀዳሚ መብት አለኝ የሚል ተቃዋሚ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያ ያቀረቡት ወይም እንዲያዝ በታዘዘው ንብረት ላይ ተቀዳሚ መብት አለን የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ክርክር ተካፋይ ባይሆኑም በያዝነው ንብረት ላይ መብት እንዳላቸው በመቁጠር የሚያቀርቡትን መቃወሚያ አቤቱታ ተቀብሎ መመርመር አለበት በማለት አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ህግ አውጭው የደነገገውን ድንጋጌና ከዚህ በላይ ባለው ንኡስ ቁጥር የተነገረው መቃወሚያ ወይም አቤቱታ የሚቀርበው በጽሁፍ ሆኖ ፍርድን ለሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ነው በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 418 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪን በአፈጻጸሙ ጣልቃ በመግባት ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በመመርምር ውሣኔ የሰጠው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 418 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2ን መሠረት በማድረግ በመሆኑ አመልካች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 375 በመጥቀስ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

3. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሻሸመኔ ከተማ በዲዳ ቦቂ ቀበሌ የሚገኘውንና በወ/ሮ ከድጃ አወል ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቁጥሩ 425 የሆነውን ቤት በሀራጅ በመሸጥ ፍርዱን እንዲያስፈጽም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 372 ንኡስ አንቀጽ /1/ሐ/ እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 373 የተደነገገውን ስርዓት በማሟላት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ፍርዱን የሚያስፈጽመው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤቱ የፍርድ ባለዕዳው ባለቤት የወ/ሮ ከድጃ አወል ሣይሆን የእኔ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡትን የጣልቃገብነት ክርክር በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 371 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 418 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ መሠረት መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይኸ ውሣኔ የኦሮሚይ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሰጠው ትዕዛዝ ጋር እኩል በመሆኑ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የሚቀርበውን ይግባኝ የማየት ስልጣን ያለው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሣይሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥርዓት ህግ ቁጥር 374 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍርድ እንዲያስፈጽም ያዘዘው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በይግባኝ አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተገለጹትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ነው በማለት ወስነናል፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59301

ግንቦት 04 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- መምህርት አታቱ ከበደ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ስቴኘስ አት.ኢዱኬሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር - በሌለበት የሚታይ ነው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት አድርጎ የቀረበን የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በስቴኘስ ትምህርት ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከስቴኘስ ት/ቤት ጋር በመምርነት ስራ ከመሰከረም 1998 ዓ/ም ጀምሮ የስራ ውል ግንኙነት በመመስረት እስከ ጥቅምት 23 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ በወር ብር 1,050.00 እየተከፈላቸው ሲሰሩ ቆይተው ከህግ ውጪ በተከሳሽ እንደተሰናበቱ ገልጸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲክፍሉቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የማያሳይ ነው፡፡ የስር ተከሳሽ ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካች ተቀጠርኩበት በሚሉበት ጊዜ ስቴኘስ ት/ቤት በሌላ ሰው ስም የነበረ መሆኑን ገልጾ በጠየቁበት ዘመን በስቴኘስ ት/ቤት እንዳልሰሩ ክሱም ሊቀርብ የሚገባው ስቴፕስ አት ኢዱኬሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር በመሆኑ እንዲሻሻል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የገለጸ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ስቴፕስ አት ኢዱኬሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር የፈረሰና የተዘጋ መሆኑን ተረጋግጦ በድርሻቸው መልስ እንደሚሰጡ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የባልና ሚስት የጋራ ንብረት የነበረው ትምህርት ቤት ጋብቻው ፈርሶ ሲከፋፈል አመልካች ወደ ሴትየዋ ሄደው መስራቱን መቀጠላቸው መረጋገጡንና ከዚህ በሁዋላም ሴትየዋ አመልካችን አላሰናበትኩም የሚል ክርክር የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ለአመልካች የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ዘርዝሮ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ተጠሪ ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ስቴኘስ አት ኢዱኬሽናል የተባለ ትምህርት ቤት የንግድ ፈቃዱ መሰረዙ መረጋገጡን በመግለፅ አመልካች ክሱን ከትምህርት ቤቱ ስራ አስኪያጅና ከሌሎች ባለአክሲዮኖች ተነጥለው ሊከሰሱ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበትን ትምህርት ቤትና ስራውን ሲያሰራ የነበረን ትምህርት ቤት ከጋብቻው መፍረስ በሁዋላ የንግድ ፈቃዱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሰርሿል ከተባለው የስቴኘስ አት ኢዱኬሽናል ትምህርት ቤት ጋር አንድ አድርጎ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ የክስ አቅራረቡንና በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ሁኔታ ባግባቡ ሳያገናዝብ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ድርጅት መደበኛ ስራውን እያከናወነ አይደለም የሚለውን ብቻ በመያዝ ሊከሰስ አይችልም በሚል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ድርጅት መጥሪያው ተልኮለት ሊቀበል አለመቻሉ ተረጋግጦ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገርና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ክስ የመሰረቱት ስቴኘስ ት/ቤት በሚል ሲሆን ይህ ትምህርት ቤት ሊከሰስ እንደማይገባ ፣ አመልካች ስራውን የጀመሩት ስቴኘስ አት ኢጁኬሽናሉ ኃ.የተ.የግል ማህበር ጋር ሆኖ ይህ ትምህርት ቤት በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክርክር ምክንያት የተከፋፈለ በመሆኑ ክሱ ሊቀርብ የሚገባው በዚህ ትምርት ቤት መሆኑን የስቴኘስ ት/ቤት ባለቤት ተብለው የተከሰሱት ግለሰብ ጠቅሰው መከራከራቸውን፣ የስር ፍርድ ቤት የባልና ሚስት ንብረት የተከፋፈለ ቢሆንም የአሁኗ አመልካች የመምህርነት ስራውን የሴትዬዋ /ማዳም ፑሽ ፖላታ/ ንብረት በሆነው ስቴኘስ ት/ቤት መቀጠላቸው መረጋገጡን፣ ይህ ትምርት ቤትም አመልካችን አላሰናበትኩም የሚል ክርክር የሌለው መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋገጦ ለአመልካች የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው የወሰነ መሆኑን ፣ ይህ ውሳኔ በየትኛውም እርከን በሚገኝ ፍርድ ቤት አለመለወጡንና ለስር ፍርድ ቤት የአፈጻጸም አቤቱታ ቀርቦለትም በመ/ቁጥር 16902 በሆነው የአፈጻጸም መዝገብ ተከፍቶ የፍርድ ባለእዳ የሆነው ስቴኘስ ት/ቤት ፍርዱን እንዲፈጽም ትዕዛዝ መሰጠቱን፣ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ዋናው ፍርድ እንዲፈጸም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኝ ቀርቦለት አመልካችንና ስቴኘስ አት.ኢዱኬሽናል ኃ.የተ.የግል ትምህርት ቤት የተባለውን በይግባኝ ባይነት አከራክሮ ይኸው ድርጅት የንግድ ፈቃዱ መሰረዙ ተረጋግጧል፣ ስራውን ባቆመ ድርጅት ስራ አሰኪያጅ የነበረ በመሆኑ ብቻ ተጠያቂ መሆን የለባቸውም በሚል ምክንያት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ እንግዲህ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ባይ የተጠቀሰው ድርጅት እና የስር ፍርድ ቤት በዋናው ክርክር ኃላፊ አድርጎ አፈጻጸሙን የቀጠለበት ድርጅት የተለያዩ መሆናቸውን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍርድ ሊፈጸም የሚገባው እንደፍርዱ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች የተመለከቱትና አፈጻጸምን የሚገዙ ድንጋጌዎች ያሳዩናል፡፡ ስለሆነም አንድ የፍርድ አፈጻጸም የሚመራው እንደፍርዱ ነው፡፡ አንድ ፍርድ እንደፍርዱ የማይፈፀመው ፍርዱ በይግባኝ ሥርዓት የተለወጠ የሆነ እንደሆነ ወይም ፍርዱን ለመፈፀም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 386 መሰረት ሕጋዊ ምክንያቶች ያሉ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ ነው፡፡ ፍርዱ ተለውጧል ሊባል የሚችለውና ለአፈጻጸም መሰረት ሊሆን የማይችለው ደግሞ ዋናው ክርክር ላይ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው በማለት ሳይሆን ዋናው ክርክር ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ/ሰበር ስርዓት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በማስለውጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሻረው የንግድ ስራውን ባቆመ ድርጅት ስራ አስኪያጁ ብቻውን ሊጠየቅ አይችልም በሚል ምክንያት ሲሆን ይህ ምክንያት ይዘቱ ሲታይ ከዋናው ፍርድ ይዘት ውጪ የሆነ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዋናው ክርክር ጊዜ ቀርቦ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያጣና በሥርዓቱ መሰረት በበላይ ፍርድ ቤት ያልተለወጠ በመሆኑ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በዋናው ክርክር የተሠጠውን ፍርድ በአፈፃፀም መዝገብ የሚሸርና አፈጻጸም ከሚመራበት ስርዓት ውጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ስለአፈጻጸም የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 93697 ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16902 የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡ በመሆኑም ይኸው ፍርድ ቤት በዚሁ አፈጻፀም መዝገብ በጀመረው መሰረት አፈጻጸሙን በመቀጠል እንደዋናው ፍርድ እንዲያስፈጽም ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች - ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች - 1. ወ/ሮ ይሕደጋ ሳሙኤል - አልቀረቡም

2. ወ/ሮ አልጋነሽ ሳሙኤል "

3. ወ/ት ዘነበሽ ሳሙኤል - ቀረቡ

ተጠሪዎች - 1. ወ/ሮ አሰፋ ሳሙኤል

2. ወ/ሮ አስካል ሳሙኤል

3. ወ/ሮ በላይነሽ ሳሙኤል

4. አቶ ሞገስ ሳሙኤል

5. አቶ ሙሉ ሳሙኤል

6. ወ/ሮ ንግስቲ ሳሙኤል

7. ወ/ሮ ምልእተ ሳሙኤል

8. ወ/ት ዓይንምሽት ሳሙኤል

9. ወ/ሮ ሃና ሳሙኤል

10. አቶ ሰለሞን ሳሙኤል

11. ወ/ሮ ርግበ ሳሙኤል

12. ወ/ሮ ደሞዝ ሳሙኤል

አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአመልካቾች እና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የውርስ ንብረት ክፍያ አፈፃፀም ክርክር በፍርድ አፈፃፀም መዝገብ ላይ ሰኔ 29 ቀን 2000 ዓ.ም ትዕዛዝ ተሰጥቶ የአፈፃፀም መዝገቡ ከተዘጋ በኃላ የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78/1/ መሠረት አቤቱታ በማቅረባቸው ይህንኑ የሥር ፍ/ቤቶች ተቀብለው ትዕዛዝ መስጠታቸውን በመቃወም አመልካቾች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በአፈፃፀም በተያዘ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78 መሠረት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ መደረጉ በአግባቡ መሆን /አለመሆኑን ድንጋጌው ተፈፃሚነት አለው ቢባል እንኳን በጉዳዩ ላይ ትዕዛዝ ከተሰጠ ከአንድ ዓመት በኃላ የቀረበ አቤቱታ ተቀባይነት ማግኘቱ በሥነ ሥርዓት ሕግ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ አኳያ የታየ መሆን /አለመሆኑን እንዲሁም ተጠሪዎች ቀደም ሲል ቀርበው የሚፈለገውን ገንዘብ ከፍለው ንብረቱን ለማስቀረት ዳኝነት ጠይቀው ውሣኔ ያረፈበት ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የተጠሪዎች የመከራከር መብት አልተጠበቀም ማለት ይቻላልን? የሚሉት ነጥቦች ሊመረመሩ የሚገባቸው ሆኖ ስለተገኙ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

የተጠሪዎች ጠበቃ ሚያዚያ 4 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ በይዘቱም ተጠሪዎች የተለያየ ቦታ ይኖሩ እንደነበር ጠቅሰው በሥር ፍ/ቤት ቀድሞ የተሰጠው ትዕዛዝ እንደማያውቁትና የቤቱ ስመሀብት በአመልካቾች እንዲመዘገብ የተደረገው በ22/06/2001 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ መሆኑን እና እነሱም ይህንን ያወቁት በ15/10/2001 ዓ.ም እንደሆነና ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ያቀረቡትም በ26/10/2001 ዓ.ም ስለመሆኑ ዘርዝረው አቤቱታ ያቀረቡት ጉዳዩን ባወቁ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ እንደሆነ ተከራክረዋል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78/1/ ተፈጻሚነት በተመለከተ ጉዳዩ በአፈፃፀም ላይ ያለ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ አመሳስሎ በመተርጐም መቀበሉ አግባብ ነው በሚል እንዲሁም ቀደም ሲል በአፈፃፀም ሂደት ተጠሪዎች ፍርድ ቤት ቀርበው ክርክር እንዳላቀረቡ ጠቅሰው የሥር ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲፀና አመልክተዋል፡፡

አመልካቾች ክርክራቸውን አጠናክረው የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እልባት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳዩ ተጠሪዎች ቀደም ሲል በአፈፃፀም ክርክር እንዲቀርቡ ተደርጓል ወይንስ አልተደረገም? ቀርበው እንዲከራከሩ አልተደረገም ከተባለ በአፈፃፀም ጉዳይ ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 78 ተፈፃሚነት አለው ወይንስ የለውም? ተፈፃሚነት አለው ከተባለ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ተፈጻሚነትን በተመለከተ የሥር ፍ/ቤት ከአንድ አመት በኋላ መቀበሉ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም የሚሉትን በየተራ እንመለከታለን፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቾች አጥብቀው የተከራከሩት ተጠሪዎች ቀደም ሲል በአፈፃፀም ክርክር ላይ ቀርበው የውርስ ንብረት በዓይነት ለማስቀረት እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው ተቀባይነት አጥተዋል፡፡ በሂደቱም ተከራካሪ የነበሩ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት መዝገብ ተረጋግጧል የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ከዚህ ፍሬ ነገር አንፃር መርምረናል፡፡ የአክሱም ከተማ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05063 ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ በሆነው ፍርድ ላይ እንዳረጋገጠው ከተጠሪዎች ውስጥ 1ኛ - 4ኛ፣ 6ኛ፣ 8ኛ - 10ኛ እና 12ኛ ተጠሪ በአፈፃፀም ክርክር ላይ በተለያዩ ቀናት ችሎት ቀርበው የበኩላቸውን ክርክር ያቀረቡ ስለሆነ ነው የተቀሩት ተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጐላቸው እንዳልቀረቡ ፍርድ ቤቱ የአፈፃፀም መዝገብ አስቀርቦ መርምሮ እንዳረጋገጠ በውሣኔው አሰፍሯል፡፡ በዚህም መነሻ መሠረት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78/1/ መሠረት የአፈፃፀም መዝገቡ በ19/10/2000 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ተዘግቶ ካደረ በኃላ ተጠሪዎች በ26/10/2001 ዓ.ም ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ሲል ውሣኔ የሰጠው፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪዎች ቀደም ሲል ቀርበው የተከራከሩ መሆኑን ፍሬ ነገር በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን አንዳችም ምክንያት ሳይሰጥ ሽሮታል፡፡

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪዎች ቀደም ሲል የበኩላቸውን ክርክር አቅርበው ተቀባይነት አጥቶ ያደረ ሆኖ ሳለ እንደአዲስ አቤቱታ ማቅረባቸው አግባብ እንዳልሆነ ነው፡፡ በመሠረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ ክርክሮች በተወሰነ ደረጃ እና ጊዜ እንዲቋጭ ማስቻል እንጂ ጉዳዩች ያለገደብ በሙግት ላይ ተንጠልጥለው እንዲቆዩ ማድረግ አይደለም፡፡ በዚህም የተከራካሪ ወገኖችን እንዲሁም የፍርድ ቤቱን ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ያለአግባብ ብክነት ማስቀረት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይም ቀደም ሲል ስለውርስ ንብረት ክፍያ አፈፃፀም በ19/10/2000 ዓ.ም ትዕዛዝ ተሰጥቶ ካበቃ በኃላ ተጠሪዎች ከአንድ አመት በኃላ በ26/10/2001 ዓ.ም እንደ አዲስ ተከራካሪ ወገን አቤቱታ ማቅረባቸው እና በሥር ፍ/ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ ከሥነ ሥርዓት ሕጉ ዓላማና መንፈስ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል አይደለም፡፡

ስለሆነም ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው አብዛኛው ወገን በጉዳዩ ላይ የበኩላቸውን ክርክር ያቀረቡ ሆነው ሳለ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78/1/ አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡ የተቀሩት ሶስት ተጠሪዎችም ቢሆኑ ክርክሩ የውርስ ንብረት ክፍያን የሚመለከት እንደመሆኑና የሁሉም ተጠሪዎች መብት በአንድ መስመር የተወሰነ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ ከአብዛኞቹ የተለየ ክርክርና መብት አላቸው የሚባልበት ሁኔታ አልተጠቀሰም፡፡ ስለሆነም የከፍተኛው ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር በአክሱም ወረዳ ፍ/ቤት ደረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 78/1/ መሠረት ሊስተናገዱ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡

ስለዚህም ጉዳዩ በመጀመሪያው ጭብጥ ብቻ እልባት ያገኘ በመሆኑ ወደተከታዮቹ ነጥቦች መግባትና መመርመር አስፈላጊ አይደለም፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182/3/ የመጀመሪያ ዐረፍተነገር ይዘት ይህንኑ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሣኔ ከሥነ ሥርዓት አኳያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ብ/ክ/መ የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15276 በ9/2/2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 35416 በ14/03/2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአክሱም ከተማ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05063 በ13/12/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ላይ የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ግራቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 26 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡ - ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡ - 1. አቶ ስለሺ ወርቅነህ - ጠበቃ ግሩም አየለ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ብርቅነሽ መኮነን
3. ወ/ሮ ራሄል መኮነን } አቶ የውሴፍ አእምሮ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡ - 1. አቶ ሁሪሳ ደመሳ - ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ለማ

2. ወ/ሮ ሰውነት ፈቃዱ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልካቾች ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ እንዲሰረዝላቸው አመልካቾች ያቀረቡት ጥያቄ በየደረጃው ያሉ የክልል ፍርድ ቤቶች ህጋዊ መሠረት የለውም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ይዘት አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ ገንዘብ አበድሮ ያልተከፈለው መሆኑን በመግለጽ ክስ አቅርቦ ሁለተኛ ተጠሪ ከአንደኛ ተጠሪ የተበደሩትን ገንዘብ እንዲከፍሉ በፍርድ ተወስኖባቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሁለተኛ ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳ ሆነው አንደኛ ተጠሪ በአስከፊቱት የአፈፃፀም መዝገብ ተከራክረው ንብረትነቱ የሁለተኛ ተጠሪ ነው የተባለ ቤት በሀራጅ የሚሸጥ መሆኑ በበኩልቻ ጋዜጣ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ ቤቱ ተሸጦ ለሁለተኛዋ ተጠሪ እዳ መክፈያነት እንዲውል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ቤቱ ከተሸጠና የአፈፃፀም መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ ለሁለተኛ ተጠሪ እዳ መክፈያነት የተሸጠው ቤት የሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት ሣይሆን የአንደኛ ተጠሪ፣ የሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የጋራ ንብረት ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ጋር በመሆን ህዳር 26 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ውል ለአንደኛ አመልካች የሸጡትና አንደኛ አመልካችም በውሉ መሠረት ብር 82,640.29

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(ሰማንያ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ አርባ ብር ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም) ቤቱን ከባንክ መያዣነት ለማስለቀቅ የከፈሉ መሆኑን የቤቱን ስመ ሀብት ወደ ወራሾቹ ለማዛወር ብር 31,884.42 (ሰላሳ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰማንያ አራት ብር ከአርባ ሁለት ሳንቲም) የከፈለ መሆኑን ብር 16,799 ለወራሾቹ የከፈለ መሆኑን በመግለጽ ንብረቱ ላይ የተደረገው የሀራጅ ሽያጭ እንዲሰረዝላቸው ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልክተዋል፡፡

አንደኛ ተጠሪ ቤቱ በሀራጅ የሚሸጥ መሆኑ ማስታወቂያው በቤቱ ላይ ያልተለጠፈ መሆኑን በማመን የሀራጅ ማስታወቂያው በጋዜጣ የወጣ በመሆኑ የሽያጩን ሥርአት ለማሰረዝ የሚያበቃ ምክንያት አይደለም፡፡ ቤቱ የፍርድ ባለዕዳዋ የሁለተኛ ተጠሪ ንብረት እንደሆነ በክፍሉ አስተዳደር ተረጋግጧል፡፡ ሽያጩ እንዲሰረዝ ጥያቄው የቀረበው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447(1) በተደነገገው የሁለት ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ በአምስት ወሩ ነው፡፡ አመልካቾች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418 መሠረት ጣልቃ መግባት የሚችሉት ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት ነው፡፡ አንደኛ አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 መሠረት ቤቱን የገዛ መሆኑን ያቀረበው ማስረጃ ስለሌለ የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ ለማመልከት የሚያስችል መብት የለውም በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ (የፍርድ ባለዕዳዋ) በበኩሏ ከአንደኛው ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ገንዘብ ተበድሬ መክፈል ስላልቻልኩኝ ቤቱ ተሸጦ ተከፍሏል፡፡ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከእዳ ቀሪ ከሆነው ገንዘብ ድርሻቸውን እንዲሰጣቸው ከሚጠይቁ በስተቀር ሽያጩ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ አይችሉም፡፡ ቤቱ ከተሸጠና ገንዘቡ ከተከፈለ በኋላ ሁለት ወር አልፎታል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን አቤቱታና የተጠሪዎችን መልስ ከመረመረ በኋላ

1. የጨረታው ማስታወቂያ በተሸጠው ቤት ላይ ተለጥፏል ወይስ አልተለጠፈም?
2. የጨረታ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣ የሀራጅ ማስታወቂያው በሚሸጠው ቤት ላይ መለጠፍ ነበረበት በማለት አቤቱታ አቅራቢዎች (አመልካቾች) የሚያቀርቡት ክርክር ትክክል ነው ወይስ አይደለም?
3. አቤቱታ አቅራቢዎች የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ ጥያቄ ያቀረቡት ህጉ በሚፈቅደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ነው ወይስ አይደለም?
4. የአንደኛው አቤቱታ አቅራቢ (አመልካች) ቤቱን ለመግዛት ያደረገው ውል በህግ ፊት ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም?
5. በፍርድ አፈፃፀም ሂደት መብታችንና ጥቅማችንን ያሳያል የሚሉ ሰዎች የጣልቃ ገብነቱን ጥያቄ መቼ ማቅረብ አለባቸው? የሚሉትን ጭብጦች መስርቷል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤቱ የሀራጅ ማስታወቂያ በቤቱ ላይ ያልተለጠፈ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ሆኖም የሀራጅ ማስታወቂያው በጋዜጣ የወጣ በመሆኑ የሀራጅ ማስታወቂያው በሚሸጠው ቤት ላይ አለመለጠፉ የሀራጅ ሽያጩን ለመሰረዝ የሚያበቃ ምክንያት አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካቾች ሽያጩ እንዲሰረዝላቸው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447(1) የተደነገገው የሁለት ወር የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ ስለሆነ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አራተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አንደኛው አመልካች የሁለተኛ ተጠሪ፣ የሁለተኛና የሶስተኛ አመልካች የጋራ ሀብት የሆነውን ቤት በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 1723 መሠረት የገዛ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በቤቱ ላይ የተደረገውን ሽያጭ እንዲሰረዝለት ለመጠየቅ የሚያስችለው መብት የለውም በማለት ብይን የሰጠ ሲሆን አምስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ በአፈፃፀም ሂደት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት ጣልቃ መግባት የሚቻለው ፍርዱ ከመፈፀሙና ንብረቱ ከመሸጡ በፊት በመሆኑ የአመልካቾች ጥያቄ ሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌው መሠረት አልቀረበም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የፍርድ ባለዕዳ (ሁለተኛ ተጠሪ) ባመነችው መሠረት ድርሻቸውን ከሚጠይቁ በስተቀር ሽያጩ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካቾችን ይግባኝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ አድርጐታል፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 6 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛ አመልካች ከሁለተኛዋ ተጠሪና በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑት ሄኖክ መኮነን እና ራሄል መኮነን የጋራ ንብረት የሆነ ቤት በቡራዩ ከተማ ነበራቸው፡፡ ይህንን የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት ህዳር 26 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ውል አንደኛው አመልካች የገዛው ሲሆን ውሉ በምዕራብ ሸዋ ዞን ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ የፍርድ ባለመብት ነው የተባለው አንደኛው ተጠሪ በሽያጭ ውሉ ላይ በምስክርነት የፈረሙ ሲሆን ለሽያጭ ውሉ መልካም አፈፃፀም ለሻጮች ሀላፊ እሆናለሁ በማለት የዋስትና ግዴታ ገብቷል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 15876 በመጀመሪያ ለእኔ ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ ብዙ ገንዘብ ገዥ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡ ሲሆን ከዚህ በኋላ ክሳቸውን በማሻሻል ውሉ ይፍረስልኝ የሚል ክስ አቅርበው ነበር፡፡ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሁለተኛ ተጠሪን ክስ በመቃወም በክርክሩ ጣልቃ ከገቡ በኋላ መዝገቡ የዳኝነት ሳይከፈል የተከፈተ በመሆኑ ሁለተኛ ተጠሪ የዳኝነት ክፍለው እንዲቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቶ የዳኝነት ስላልከፈሉ የዳኝነት ሲከፈል መዝገቡ እንደሚንቀሳቀስ ገልፆ ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም መዝገቡን ዘግቶ አሰናብቶናል፡፡

ከዚህ በኋላ ሁለተኛ ተጠሪ ክርክራቸው የማያዋጣቸው መሆኑን በመለየት በቤቱ ሽያጭ ላይ በምስክርነት የፈረሙትና ለአፈፃፀሙ ዋስ ከሆኑት አንደኛ ተጠሪ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ለሁለተኛ ተጠሪ እንዳበሩ የሚገልጽ ሁለት የብድር ውል በማዘጋጀት በፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርበው አስፈርደውና የአፈፃፀም ክስ አቅርበው የሀራጅ ማስታወቂያው ቤቱ ላይ ሳይለጠፍ ሀራጅ እንዲከናወን በማድረግ የአንደኛ ተጠሪ የአክስት ልጅ ቤቱን በሀራጅ እንዲገዛው አድርገዋል፡፡ እኛ ቤቱ በሀራጅ የተሸጠ መሆኑን ያወቅነው ከአምስት ወር በኋላ የአንደኛ ተጠሪ የአክስት ልጅ ቤቱን በፍርድ ቤት በወጣ ሀራጅ ስለገዛሁት ልቀቁ ብሎ ሲጠይቀን ነው፡፡ በአንደኛ ተጠሪና በሁለተኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የብድር ውል ሀሰተኛ የብድር ውል መሆኑን ፖሊስ በወንጀል እንዲያጣራልን ጠይቀን የብድር ውሉ በሀሰት የተዘጋጀ የብድር ውል መሆኑን በፖሊስ ምርመራ የተረጋገጠ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447(1)፣ ድንጋጌ ይዘትና ተጠቃሽና ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሁኔታና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418ን አላግባብ በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለአመልካች የሰበር አቤቱታ አንደኛ ተጠሪ ህዳር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ባቀረበው መልስ አመልካቾች ለሥር ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን አዲስ መከራከሪያ በሰበር ያቀረቡ ስለሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 329 መሠረት ውድቅ ይደረግልኝ፡፡ አመልካቾች አቤቱታቸውን ያቀረቡት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418 ን በመጥቀስ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ ድንጋጌ በአፈፃፀም ጣልቃ መግባት የሚችለው ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት ነው በማለት የሰጠው ትርጉም ስህተት የለውም፡፡ የሀራጅ ማስታወቂያው ቤቱ ላይ አለመለጠፉ የሀራጅ ሽያጩን ለማሰረዝ የሚያስችል ምክንያት አይደለም፡፡ አመልካቾች ጥያቄያቸውን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447(1) በተደነገገው የጊዜ ገደብ አላቀረቡም፡፡ ስለሆነም የሀራጅ ሽያጩ የህጉን ሥርአት ተከትሎ የተፈፀመ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ህዳር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርበዋል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የጨረታ ማስታወቂያው ቤቱ ላይ አለመለጠፉ የሀራጅ ማስታወቂያው በጋዜጣ የወጣ በመሆኑ የሀራጅ ሽያጩን ለመሰረዝ የሚያበቃ አይደለም፡፡ አመልካቾች ጥያቄያቸውን በህግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ አላቀረቡም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች አቤቱታቸውን ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው፣ በምዕራብ ሸዋ ዞን ውልና ማስረጃ የተደረገውን ውል ሁለተኛ ተጠሪ የሚያውቁት አይደለም፡፡ የብድር ውሉ በሀሰት የተደረገ ነው ይበሉ እንጂ በፍርድ ቤት ውሣኔ የተረጋገጠ ነው፡፡ ቤቱን የገዛው የክርስትና ልጅ ነው ለሚሉት የክርስትና ልጅ መሆኑን ማስረጃ አላቀረቡም የክርስትና ልጅ እንዳይገዛ ህጉ አይከለክልም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447 እና ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች ሲተረጉሙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሰሩ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል በማለት ታህሣሥ 15 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራ ቀኙ የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት አመልካቾች የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት በአግባቡና ለጉዳዩ ተጠቃሽና ተፈፃሚ መሆን የሚገባቸውን የፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ በአፈፃፀም የተሸጠው በቡራዩ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ቤት የማን ንብረት ነው? የሚለውን መለየት አስፈላጊ ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአፈፃፀም እንዲሸጥ ያደረገው ቤት የሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት አለመሆኑን ሁለተኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በሠበር ለዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር ያመኑት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ በአፈፃፀም በሀራጅ የተሸጠው ቤት የሁለተኛ አመልካች፣ የሶስተኛ አመልካች፣ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆኑት ሄናክ መኮንንና ራሄል መኮንን እና የሁለተኛ ተጠሪ የጋራ ሀብት የነበረ ነው፡፡ በቤቱ ላይ ሁለተኛ ተጠሪ ድርሻ የነበራቸው ቢሆንም ይህንን ድርሻቸውን ቤቱ በአንደኛ አመልካች እንዲሸጥ በሰጡት ፈቃድና ስምምነት መሠረት ሸጠዋል የሚለው ነጥብ በሥር ፍርድ ቤት የቀረበና ውሉ የህጉን ፎርም አላሟላም በማለት የታለፈ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ውሉ በምዕራብ ሸዋ ዞን ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑን በመግለጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላቀረበው ክርክር ምዕራብ ሸዋ ዞን የተደረገውንና የተመዘገበውን ውል አላውቀውም በማለት ሁለተኛ ተጠሪ በመሸሸ መልክ መልስ የሰጡ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ ከሌሎች የቤቱ የጋራ ባለሀብቶች ጋር በመሆን ቤቱን ለአንደኛ አመልካች አልሸጥኩም በማለት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) መሠረት አልተከራከሩም፡፡ ከዚህ የምንረዳው ቤቱ የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት የሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት እንዳልሆነና ሁለተኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ ያላቸውን መብት ከሌሎች የጋራ ባለሀብቶች ጋር በመሆን ለአንደኛ አመልካች ለፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የሆነውን የብድር ገንዘብ ከአንደኛ ተጠሪ ከመበደራቸው በፊት የሸጡ መሆኑን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት እንዳመኑ የሚቆጠር ነው፡፡ በአፈፃፀም የተሸጠው ቤት የፍርድ ባለዕዳዋ ካልሆነና የፍርድ ባለዕዳዋ በቤቱ ላይ የነበራቸው የጋራ ንብረት ባለቤትነት መብት ከሌሎች ባለሀብቶች ጋር በመሆን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1266 በሚደነግገው መሠረት ለአንደኛ አመልካች የሸጠች መሆኑን ክዳ ባልተከራከረችበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447(1) የተደነገገው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ነው አቤቱታ ያቀረባችሁት በማለት የሰጡት ብይን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አንደኛ አመልካች ንብረቱ የጋራ ባለሀብት ከሆኑ ሰዎች ቤቱን የገዛው መሆኑን ሁለተኛ ተጠሪ በግልጽ ክደው አልተከራከሩም፡፡ በአፈፃፀም የተሸጠው ቤት የጋራ ባለሀብት የሆኑት ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች አንደኛ አመልካች ቤቱ ላይ በባንክ የሚፈለገውን እዳ በመክፈልና የማዘጋጃ ቤትን ዕዳ በመክፈል ቤቱን ነፃ ያደረገ መሆኑንና ከሁለተኛ ተጠሪና ከሌሎች የጋራ ባለሀብቶች በሙሉ ፈቃድና ስምምነት ገብቶ ቤቱን ይዞ የሚገኝ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የሁለት ወር ጊዜ ገደብ በአፈፃፀሙ ሂደት ተከራካሪ የነበሩት የፍርድ ባለዕዳው ወይም የፍርድ ባለመብቱ ወይም በሀራጅ ጨረታው ተሳትፎ ቤቱን የገዛው ሰውና ለአፈፃፀሙ ሙሉ እውቀት የነበራቸው ሌሎች በጉዳዩ ይገባናል የሚሉ ሰዎች የሀራጅ ጨረታውን ለማስፈረስ በቂ ምክንያት ካላቸው ሽያጩ እንዲሰረዝላቸው በሁለት ወር ውስጥ ማመልከት ያለባቸው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ በአፈፃፀም በሀራጅ በተሸጠው ቤት ላይ መብት ያለውን ሶስተኛ ወገን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የሁለት ወር ጊዜ ገደብ ውስጥ አላመለከትክም ብሎ አቤቱታውን ውድቅ ለማድረግ በመጀመሪያ ቤቱ በፍርድ ምክንያት እግድ የተሰጠበት መሆኑና ሀራጅ ማስታወቂያ የወጣበት መሆኑን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በቤቱ ላይ የተሰጠፈ መሆኑን ማረጋገጥ የግድ የሚያስፈልግ መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሁለተኛ ተጠሪ የግል ሀብት ያልሆነው ቤት የሀራጅ ማስታወቂያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት በቤቱ ላይ አልተሰጠፈም፡፡ ይኼም በመሆኑ ቤቱን ከሁለተኛ ተጠሪና ከሌሎች የቤቱ የጋራ ባለሀብቶች ገዝቶ የያዘው አንደኛ አመልካችና ቤቱን ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር በመሆን ለአንደኛ አመልካች የሸጡት የቤቱ የጋራ ባለሀብት የሆኑት ሁለተኛ እና ሶስተኛ አመልካቾች ቤቱ በሁለተኛ ተጠሪ እዳ ምክንያት እግድ የተሰጠበትና የሀራጅ ጨረታ የወጣበት መሆኑን ለማወቅ የሚያስችላቸው ሁኔታ አልነበረም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ አውጪው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 423 የተደነገገውን ሁኔታ አሟልቶ በጋዜጣ እንዲወጣ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገገው በተጨማሪ የሀራጅ ማስታወቂያው በሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ቤት ላይ እንዲለጠፍ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 የደነገገበት የራሱ የሆነ መሠረታዊ ምክንያት አለው፡፡ ይኸው የእግድ ትእዛዝ የተሰጠበት ወይም የሀራጅ ማስታወቂያ የወጣበት የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ መብት ያላቸው ሰዎች ንብረቱ የእግድ ትእዛዝ የተሰጠበት ወይም ለሀራጅ ማስታወቂያ የወጣበት መሆኑን በመገንዘብ በአፈፃፀሙ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418 መሠረት ጣልቃ ገብተው መብታቸውን እንዲያስከብሩ ለማድረግ ንብረቱ የጋራ ባለሀብቶች በሆነ ጊዜ የንብረቱ የጋራ ባለሀብቶች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 443 የተጠበቀላቸውን መብት እንዲያስከብሩ ንብረቱ በሀራጅ የሚሸጥ መሆኑን እንዲያውቁት ለማድረግና በመጨረሻም የሀራጁን ሂደት በመከታተል በሂደቱ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 445 የተደነገጉት ሕገ ወጥና የማጭበርበር ተግባራት ከተፈፀሙ የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ለማመልከት እንዲችሉ ነው፡፡ ህግ አውጭው ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች የማሳካት ሀሳብና ፍላጐት ባይኖረው ኖሮ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያውና በማይንቀሳቀስ ንብረት በፍርድ በተወሰነ እዳ ምክንያት የእግድ ትእዛዝ ሲሰጥ በማይንቀሳቀሰው ቤት ላይ እንዲለጠፍ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 አይደነግግም ነበር፡፡ ስለሆነም የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያው በሚሸጠው ቤት ላይ አለመለጠፍን እንደ ቀላል የሥነ ሥርአት ግድፈት በመቁጠር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጓሜ ከላይ በዝርዝር የተገለፀውንና ህግ አውጭው ሊያሳካቸው የሚፈልጋቸውን ግቦች ያላገናዘበ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. በአፈፃፀም በተያዘው ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ሰው ፍርድ ከመፈፀሙ በፊት አለኝ የሚለውን ክርክር ማቅረብ እንደሚገባው የፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚደነግገው የሀራጅ ሽያጩ ከመፈፀሙ በፊት ፍርድ ቤቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚሰጠውን እግድ ትእዛዝና የሀራጅ ማስታወቂያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚለጠፍ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከላይ የተገለፀውን ሥርአት የሚሟላ መሆኑንና የሀራጅ ሽያጩ እየተካሄደ መሆኑን የማያውቁ ወይም ማወቅ የሚገባቸውን ሰዎች የሚመለከትና በእነርሱ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡

የሀራጅ ማስታወቂያው በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሣይለጠፍ የያዙት የማይንቀሳቀስ ንብረት በአፈፃፀም ምክንያት የእግድ ትእዛዝ በሌላ ወይም የሀራጅ ማስታወቂያ የወጣበት መሆኑን ሳያውቅ በሌላ ሰው እዳ ምክንያት የያዙት ንብረት በሀራጅ የተሸጠባቸው ሰዎች በምን መንገድና መቼ የሀራጅ ሽያጭ እንዲሰረዝላቸው ለማመልከትና በንብረት ላይ አለን የሚሉትን የንብረት ባለቤትና ሌሎች ተዛማጅ መብቶች ለማስከበር ይችላሉ? የሚለው ነጥብ የያዝነውን ጉዳይ ለመወሰን መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት በሀራጅ ከተሸጠ በኋላ በንብረቱ ላይ መብት ያለው ሰው ንብረቱን ለገዢው እንዲያስረክብ ሲጠየቅ ንብረቱን መልቀቅ አይገባኝም በማለት አቤቱታውን ሊያቀርብ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 1 የሚደነግግ ሲሆን እንደዚህ በሚሆን ጊዜ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ በመያዝ መስማት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ሂደት አመልካች ንብረቱን የያዘው በራሱ መብትና ከሌላ ሰው በተላለፈለት መብት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳው ንብረቱ እንዲመለስለት ለመወሰን እንደሚቻል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝላቸው የጠየቁት አንደኛ አመልካች ከሁለተኛ ተጠሪ /የፍርድ ባለዕዳ/ እና ከሌሎቹ ባለሀብቶች ገዝቶ የያዘውን ቤት በሀራጅ ከፍርድ ቤት ትእዛዝ ስለገዛሁት ልቀቅልኝ በማለት ገዥው ሀራጁ ከተከናወነ በኋላ ከአምስት ወር በኋላ ሲጠይቀው መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን አቤቱታ የፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 453 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ማስተናገድና ውሣኔ መስጠት ሲገባው ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 418 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 ን በመጥቀስ የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት ይህንን ውሣኔ ማጽናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

4. በሁለተኛ ተጠሪ ዕዳ ምክንያት በፍርድ አፈፃፀም በሀራጅ የተሸጠው ንብረት ሁለተኛ ተጠሪ ከሌሎቹ የቤቱ የጋራ ባለሀብቶች ጋር በመሆን ለአንደኛ አመልካች የሸጡት የሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የፍርድ ባለመብት በመሆን በቤቱ ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ያደረገው አንደኛ ተጠሪ ሁለተኛ ተጠሪና ሌሎቹ የጋራ ባለሀብቶች ይህንን ቤት ለአንደኛ አመልካች የሸጡ መሆኑን ሙሉ እውቀት እንዳለውና በምስክርነት በሽያጭ ውሉ ላይ እንደፈረሙ በመግለጽ አመልካቾች በአቤቱታቸው የገለጹ ሲሆን አንደኛ ተጠሪ ይህንን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) መሠረት በግልጽ በመካድ ያልተከራከረ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት እንዳመነ የሚቆጠር ነው፡፡ የፍርድ ባለመብት ነኝ የሚለው አንደኛ ተጠሪ በእዳ ምክንያት የሚሸጠው ቤት የፍርድ ባለዕዳዋ ሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት እንዳልሆነና ቤቱ የጋራ ሀብት መሆኑን እያወቀና የጋራ ባለሀብቶቹም ቤቱን ለአንደኛ አመልካች የሸጡ መሆኑን እያወቀ ንብረቱ የፍርድ ባለዕዳዋ የሁለተኛ ተጠሪ የግል ንብረት እንደሆነ አድርጐ ባቀረበው የአፈፃፀም ማመልከቻ መነሻ አመልካቾች ቤቱ ለሀራጅ መቅረቡን ለማወቅ በማይችሉበት ሁኔታ የሀራጅ ሽያጩ መከናወኑ የአመልካቾችን መብት በጠቅላላውና ቤቱን ከሁለተኛ ተጠሪና ከሌሎቹ የጋራ ባለሀብቶች ስምምነት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1266ን መሠረት በማድረግ ገብቶ የተለያዩ የቤቱን እዳዎች ከፍሎ ቤቱን በይዞታው ሥር አድርጐ የሚገኘውን የአንደኛውን አመልካች መብት የሚጎዳ የማጭበርበር ተግባር የተፈፀመበት የሀራጅ ሽያጭ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ሀራጁን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ቀሪ በማድረግ ቤቱን አንደኛ አመልካች እንደያዘ እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት ሲገባቸው ሀራጅ ሽያጩ መሠረት ቤቱን እንዲያስረክብ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያከናወነው የሀራጅ ሽያጭ ማጭበርበር የተፈፀመበትና የህጉን ሥርአት ያልተከተለና የፍርድ ባለዕዳ ያልሆኑትን የአንደኛ አመልካችንና የሌሎች አመልካቾችን መብት የሚጎዳ በመሆኑ የሀራጅ ሽያጩ ሊሠረዝ ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

ሃ/ዓ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የቦሌ ክ/ከ/ገቢዎች መምሪያ ነ/ፈጅ ታደሰ አንዳርጌ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ መዓዛ ሽፈራው - ጠበቃ ወርቅነሽ መንግሥቱ - ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ስብለ ከፈለኝ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ አቤቱታ የቀረበው በተጠሪዎች መካከል የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የቀዳሚነት መብት ይፈጽምልኝ ሲል አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች ባለመቀበላቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ይታረምልኝ በማለት አመልካች ስለጠየቀ ነው፡፡

አመልካች ለሰበር ችሎቱ ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ሲታይ 1ኛ ተጠሪ በኮንስትራክሽን ሙያ የተሰማሩ ነጋዴ ስለመሆናቸው፣ አመልካችም በአዋጅ ቁጥር 286/94 እና 285/94 መሠረት የንግድ ትርፍ ገቢ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ከ1997 እስከ 2000 ዓ.ም. ያለባቸው የመንግሥት እዳ ብር 405,070.88 እንዲከፍሉ ማስታወቂያ ደርሷቸው ባለመክፈላቸው በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለማስፈጸም እንደሚችል፣ 1ኛ ተጠሪ በተጨማሪ እሴት ታክስ የሰበሰቡት ገንዘብ ብር 40,140.63 ቄምር መታገዱን በመግለጽ ይህንኑ ለማስፈጸም ያቀረበውን የጣልቃ ገብነት አቤቱታ የሥር ፍ/ቤት አለመቀበሉ ስሕተት ነው ተብሎ እንዲታረም በሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ የተደረገው በሕጉ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አሏል፡፡

1ኛ/ ተጠሪ በ24/06/2002 ዓ.ም. ባቀረበው የጽሁፍ መልስ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በነበረው ክርክር ንብረቶቹ በመታገዳቸው የመንግሥት እዳ /ግብር/ ለመክፈል አለመቻሉን ገልፆ በዚህም ምክንያት የሥራ ፈቃዱም እንዳልታደሰ በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲታረም ጠይቋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሏ በ18/5/2002 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርባለች፡፡ ይዘቱም የአመልካች አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 418 መሠረት ተቀባይነት እንደሌለው ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈለገው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግብር ገንዘብ መጠን በ1999 እና 2000 ዓ.ም. የተከፋፈለ በመሆኑ ተጠሪዋ ደግሞ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራት ግንኙነት በ1999 ዓ.ም. የተቋረጠ በመሆኑ የጋራ እዳ ሊባል እንደማይገባ በዚህም ምክንያት የጋራ ሀብት ሊያዝ እና ሊፈፀምበት እንደማይገባ በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤት ትእዛዝ እንዲፀና ጠይቃለች፡፡

አመልካች ክርክሩን በማጠናቀር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው በ1ኛ ተጠሪ እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የንብረት ክፍፍልን በተወሰነው መሠረት አፈፃፀሙ በ2ኛ ተጠሪ አመልካችነት መዝገብ ተከፍቶ በሂደት ላይ ባለበት ሁኔታ ግራ ቀኙ ንብረቱን ከመከፋፈላቸው በፊት ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈለግ ግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ በቀዳሚነት ለማስፈጸም አመልካች አቤቱታ ያቀረበ ስለመሆኑ ነው፡፡

አመልካች ለአቤቱታው መሠረት ያደረገው መሠረታዊ ሕግ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና አዋጅ ቁጥር 286/94ን ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 32/1/ እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 80/1/ ላይ እንደተደነገገው ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ወይም ግብሩ ተከፍሎ እስከአለቀበት ጊዜ ድረስ ታክስ ወይም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ሀብት ላይ ባለሥልጣኑ ከማናቸውም ሌሎች እዳዎች የቀደምትነት መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡ በዚህ ረገድ የሕጉ አገላለጽ ግልጽ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በተጠሪዎች መካከል ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ መወሰኑን ተከትሎ የፍርድ ባለመብት የሆነችው 2ኛ ተጠሪ ባስከፈተችው የአፈፃፀም መዝገብ በ2ኛ ተጠሪ ስም አለ የተባለን ሀብት ያስከበረች ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ በፍርድ ባለእዳ ጥያቄ የታገደና የተከበሩት የ2ኛ ተጠሪ ሀብቶች አንድም በዓይነት አልያም ተሸጠው ለፍርድ ባለመብት የሚከፈል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም ንብረቱ ለፍርድ ባለመብት ከመከፈሉ በፊት አመልካች በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መብቱን ለማስከበር እና ለማስፈጸም አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረቡ ሲታይ ከሕግ የመነጨ መሠረት ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች በአፈፃፀም በተያዘ ንብረት ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 418 ጠቅሶ አቤቱታ ማቅረቡም ቢሆን በሥነ ሥርዓት ሕጉ እንደተደነገገው የቀዳሚነት መብቱን መሠረት /መነሻ/ ምክንያት ማስረዳት የሚጠበቅበት እንጂ በዋናው ውሣኔ እንዲከራከር አያስገድደውም፡፡

ስለሆነም አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው የሕጉን ዓላማና ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል 2ኛዋ ተጠሪ የጋራ አፈፃፀም አይመለከተኝም የሚል ክርክር በዚህ ሰበር ችሎት በአማራጭ አቅርባለች፡፡ በመሠረቱ ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈለገው የተከሣሽ እና የግብር እዳ የግል ወይንስ የጋራ? የሚከፈለውስ ከግል ሀብት ወይንስ ከጋራ ሀብት የሚሉት እና ተያያዥ ጭብጦች በሥር ፍ/ቤት ተመርምሮ ውሣኔ ያልተሰጠባቸው ስለሆነ በዚህ ሰበር ችሎት የሚመረመርበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም በዚህ ረገድ ጉዳዩ እልባት ሊያገኝ የሚገባው የሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ክርክር እና ማስረጃ መሆን እንዳለበት ታምኗል፡፡

ስለሆነም አመልካች ያቀረበውን የቀዳሚነት መብት ይከበርልኝ ጥያቄ የሥር ፍ/ቤት ሳይቀበል መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በማረም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 140988 በ05/08/2001 ዓ.ም. የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ትዕዛዝ በመ/ቁ. 81055 ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም. በማጽናት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካችን አቤቱታ ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መዝገቡን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀም ችሎት መልሰናል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ካ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስከረም 26 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ አሰገደች የእናቶች እና የሕጻናት ሆስፒታል - ጠበቃ ብስራት መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር - ነ/ፈጅ እድገት ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአስፈጻሚ አካል ውሳኔ ይሰረዝልን ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ አመልካቾች በሕጉ አግባብ የመከራከር መብት ሳይጠብቅላቸውና ጥፋታቸውም በአግባቡ ሳይረጋገጥ የሙያ ሥነ ምግባር ጉድለት ፈፅመዋል ተብሎ ድምዳሜ መደረሱም ሆነ የተጣለው ቅጣት ሕጉን ያልጠበቀ ከመሆኑም በላይ የውሳኔው ሀሳብ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤት ያቀረበው አካል ሥልጣን የሌለው በመሆኑ ከሕግ ውጪ የተሰጠው ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ውሳኔው በሕጉ አግባብ የተሰጠ በመሆኑ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በሁዋላ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ ሕጉን መሰረት አድርጎ የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት የአመልካቾችን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ ሕጉን ተከትሎ የተሰጠ አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ውሳኔን ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሠጠው ውሳኔ ተሸሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ሰኔ 04 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ሰባት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የአመልካቾች የመከላከል መብት በሕግ አግባብ ሳይጠበቅና ውሳኔው ሥልጣን በሌለው አካል የተሰጠ ሆኖ እያለ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ አይሰረዝም ተብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የሕክምና ሥነ ምግባር ጉድለት ተፈፅሟል? ወይስ አልተፈፀመም? የሚለውን ጉዳይ የጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚመረምርበት ጊዜ ከተራ ቁጥር ሁለት እስከ ስድስት የተዘረዘሩት አመልካቾች ስለጉዳዩ ሙሉ የመከራከርና የመሰማት መብታቸው ታልፎ በመታየቱ የተነሳ በየጉዳዩ ውጤት ላይ ለውጥ ያስከትላል ወይስ አያስከትልም? እንዲሁም በዚህ ጉዳይ በፍትሐብሔሩ የካሣ ጥያቄ ቀርቦ አመልካቾች በፍርድ ኃላፊነት የለባቸውም በሚል በነጻ የተሰናበቱ ከመሆኑ አኳያ ጉዳዩን ለማየት ይቻል ዘንድ በሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት ተጠሪ ቀርቦ ሐምሌ 15 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ አመልካች ፈቃድ ተሰጥቶት የሚሰራ የጤና ተቋም ሁኖ ሌሎች አመልካቾች ደግሞ 1ኛ አመልካች ተቋም ውስጥ የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች መሆናቸውን በ1ኛ አመልካች ውስጥ ህክምና ሲሰጣቸው የነበሩት ወ/ሮ የኔነሽ ደምሰው ለሕልፈት መዳረጋቸውን ለህልፈት የተዳረጉትም ከህክምና ሙያ ሥነ ምግባር ጉድለት ጋር የተያያዘ ነው የሚል አቤቱታ ለተጠሪ ሲቀርብለት የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጉዳዩን ሲያጣራ ቆይቶ የካቲት 8 እና 11 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጋቸው ስብሰባዎች በ1ኛ አመልካች ላይ የስድስት ወር የፈቃድ እገዳ በዶ/ር አሰገደች ላቀው ላይ የአንድ ዓመት የስራ ፈቃድ እገዳ፣ በዶ/ር ጌታቸው ተፈራ እና በሲስተር አበባ ኪዳኔ ላይ የስድስት ወር የስራ ፈቃድ እገዳ፣ በሲ/ር ወጋየሁ አለሙና በአቶ አረፋይኔ ገ/እግዚአብሔር ላይ ከፍተኛ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤና ቅጣት ውሳኔ አስተላልፎ ተጠሪ መስሪያ ቤት የኮሚቴውን ውሳኔ ተቀብሎ ማጽደቁን ነው፡፡

አመልካቾች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉበት አንዱ ምክንያት ለ1ኛ አመልካች በተላከው መጥሪያና ክስ ሌሎች አመልካቾች ቀርበው ለኮሚቴው መልስ ሰጥተው አልተከራከሩም፣ አልተሰሙም በማለት እና ይህ አካሄድ የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎችን መማክርት ጉባኤ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 16 ስር የተመለከተውን ያላሟላ ነው የሚል ነው፡፡ ይኸው የተጠቀሰው ደንብ ድንጋጌ የሙያ ሥነ ምግባር ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባርን ያስቀመጠ ሲሆን በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አንድ ስር የጤና ሙያ የሚጠይቀው ሥነ ምግባር ባለመከበሩ በባለሙያ ላይ የሚቀርብ ክስን ተቀብሎ ምርመራ እንደሚያካሂድና እንደሚያጣራ የደነገገ ሲሆን የአንቀጹ ንኡስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ በንዑስ ቁጥር አንድ መሰረት የሚቀርበውን ክስ ለማየት በቂ ማስረጃ መኖሩን ካረጋገጠ መልሱን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይዞ እንዲቀርብ በመግለጽ ክሱን ክስ ለቀረበበት ባለሙያ ይልካል በሚል አስቀምጧል፡፡ እንግዲህ ንዑስ ኮሚቴው ሊከተለው የሚገባውን ሥርዓት ሕጉ ከላይ በተመለከተው መልኩ ያስቀመጠው ሲሆን ይህ ስነ ስርአት የባለሙያውን የመሰማት መብት የሚያስጠብቅ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ምላሽ የሚይስፈልገው ነገር ይህ ሥነ ሥርአት በሕጉ መንፈስ መሰረት አልተጠበቀም ለማለት ይቻላልን? የሚለው ነው፡፡ የአመልካቾች ጠበቃ የሚከራከሩት በሕጉ መሰረት ለአመልካቾች ክሱና ማስረጃው ደርሷቸው መልስ ሳይሰጡና መልሳቸው ሳይመረመር ውሳኔ ተሰጥቷል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ 1ኛ አመልካች ክሱ ደርሶት በጹሑፍ መልስ የሰጠበት፣ ሌሎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች ደግሞ በጽሑፍ መልስ ባያቀርቡም ቀጠሮ ተሰጥቷቸው ጉዳዩን በያዘው ንዑስ ኮሚቴ ፊት ቀርበው ቃላቸውን የሰጡ ስለመሆኑ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ይህ ችሎትም የስር ፍርድ ቤትን ዋና መገገብ አስቀርቦ ይህንኑ ተመልክቷል። በመሆኑም 1ኛ አመልካች ክስና ማስረጃ አልደረሰኝም በማለት የሚያቀርበው ክርክር እውነትነት የሌለው በመሆኑ የሥነ ሥርዓት ግድፈት አለበት ለማለት የማይቻል ሲሆን ሌሎች አመልካቾችን በተመለከተ ደግሞ ምንም እንኳ አመልካቾች በፁሑፍ ክስና ማስረጃ ደርሷቸው ወደ ክርክሩ ሂደት ባይገቡም በንዑስ ኮሚቴ ፊት ቀርበው ግን ተገቢውን ቃላቸውን የሰጡ በመሆኑ እነኚህ አመልካቾች አልተደመጡም ወይም የመሰማት መብታቸው ተነፍጓል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም። ከሁሉም በላይ ጉዳዩን ሲመለከት የነበረው አካል ሲያካሂዳቸው የነበራቸው ስብሰባዎች በርካታ ጊዜ የተደረጉ፣ በተገቢ ባለሙያዎች አስተያየት የተሰጠበት የነበረ መሆኑን የአስተዳደር ውሳኔ አካሄድና ይዘት ከማሳየቱም በላይ የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ውሳኔ የሚያስተላልፉበት ጥብቅ የሆነ የክርክር ሥርዓትን ጠብቀው ነው ለማለት የማያስደፍር መሆኑን በኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎችን መማክርት ጉባኤ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 16 ስር የተመለከቱት አጠቃላይ የስነ ስርአት ደንቦች አስገዳጅ የሆነ ሥርዓት አለመሆናቸው የድንጋጌዎቹ ይዘታቸውና አቀራረፃቸው የሚያስገነዝብ መሆኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ በአመልካቾች የመሰማት ወይም የመደመጥ መብት ላይ መሰረታዊ የመብት መጣበብ ወይም ግድፈት ያስከተለ ሁኔታ ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል አይደለም። በመሆኑም አመልካቾች ክሱን የመከላከል መብት አልተከበረም በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም።

ሌላው ከዚሁ ነጥብ ጋር ተያይዞ በአመልካቾች የቀረበው ቅሬታና በዚህ ችሎትም እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ አመልካቾች በፍትሐብሔር የካሣ ጥያቄ ቀርቦ አመልካቾች በፍርድ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ በነፃ መሰናበታቸው የመከላከል መብታቸው ቢከበር ኑሮ ሊያስከትል ይችል የነበረው ውጤት ነው። በእርግጥ አመልካቾች በፍትሐብሔር የካሣ ጥያቄ በመደበኛው ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦባቸው የመከላከያ ማስረጃ አሰምተው ክሱ ውድቅ ሁኖ በነፃ የተሰናበቱ መሆኑን በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 51700 ግንቦት 03 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ የሚያሳይ ሲሆን ይህ ውሳኔ ለማስረጃነት በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ሲሆን በዚህ ሰበር ችሎትም በመከራከሪያነት የቀረበው የመከላከል መብት ቢጠበቅ ሊከተል ይችል የነበረውን ውጤት ያሳያል በሚል እምነት በመሆኑ እና ይህ ችሎት ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው አመልካቾች የመሰማት መብታቸው ተነፍጓል ለማለት አይቻልም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰ በመሆኑ የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር የካሣ ጥያቄ ላይ የሠጠው ውሳኔ በአመልካቾች ላይ ተጠሪ ለወሰደው እምርጃ አመልካቾች የመሰማት መብት ቢከበርላቸው ኑሮ የተለየ ውጤት ሊያስከትል ይችል ነበር ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ሊሆን የሚችል ሁኖ አልተገኘም። በአጠቃላይ ተጠሪ በሕጉ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ለመወጣት በሕጉ በተዘረጋለት ሥርዓት መሰረት የሰጠው ውሳኔ እንጂ ከሕጉ ውጪ የተሰጠ ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም። በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥረ 47731 ግንቦት 23 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል። ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 32282

መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

በላቸው አንሺሶ

ዓለ. መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች ፡- ሚ/ር ካርሎ ካስቴሊ

ተጠሪ ፡- የወ/ሮ ዘውዴ ደሚኪኮ ውርስ አጣሪ አቶ ታምራት ኪዳነ ማርያም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43181 ጥቅምት 7 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና ከውሣኔው በፊት ባቀረብኩት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ላይ የሰጠው ብይን እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 28021 ግንቦት 2 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ሀምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የወ/ሮ ዘውዴ ዶሜንኮ የውርስ አጣሪ ሆነው ወ/ሮ ዘውዴ ዶሜንኮ በአሜሪካን አገር በእንግሊዘኛ ቋንቋ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ፌብሪዋሪ 6 ቀን 2005 ዓ.ም በአደረጉት ግልፅ ኑዛዜ የተሾሙ መሆኑን በመግለፅ የአሁን አመልካች ከሚች ወ/ሮ ዘውዴ ዶሚኒኮ ጋር መስከረም 29 ቀን 1990 ዓ.ም በተደረገ የኪራይ ውል በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 23 ቀበሌ 13 የቤት ቁጥር 1822 በወር ብር 6500 (ስድስት ሺ አምስት መቶ ብር) ለመክፈል ተስማምተዋል ስለዚህ የኪራይ ገንዘቡን እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስረክቡ በማለት አቶ ታምራት ኪዳነማርያም ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ አመልካች አቶ ታምራት ኪዳነማርያም በውርስ አጣሪነት ተሹሜበታለሁ የሚሉት ኑዛዜ በውጭ አገር የተደረገ በኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤት ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም ስለዚህ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ሥልጣን ስለሌለው ክስ ሊያቀርብብኝ አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ግንቦት 28 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ብይን ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ በማከራከር አመልካች ተጠሪ ክስ ያቀረበበትን ቤት ለውርስ አጣሪው እንዲያስረክብ የቤቱን ኪራይ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሥር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስህተት የለም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል። አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በውጭ ቋንቋ ተዕፈው ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ሰነዶች በኢትዮጵያ ቆንጺላ ጽ/ቤቶች ተረጋግጠው ካልገቡ በስተቀር ውጤት እንደማይኖራቸው የሰነዶች ምዝገባ አዋጅ 334/95 አንቀፅ 2 አንቀፅ 26 እና አንቀፅ 27(1)ን አጣምሮ በማንበብ ለመገንዘብ እየተቻለ በኢትዮጵያ ቆንጺላ ባልተረጋገጠና ሚች ወ/ሮ ዘውዴ አሜሪካን አገር አድርገውታል ተብሎ በቀረበ ኑዛዜ የውርስ አጣሪ ሆኖ ተሹሟል በሚል ምክንያት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ሥልጣን ሣይኖረው ያቀረበውን ክስ ተቀብሎ ማስተናገዱና ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሥለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል። ተጠሪ በበኩሉ ሚች ወ/ሮ ዘውዴ ዶሚኒኮ በውጭ የኢትዮጵያ ቆንጺላ ጽ/ቤቶች አለመረጋገጡ ሰነዱን ህጋዊ ውጤት እንዳይኖረው የሚያደርግ ምክንያት አይደለም። ህጋዊ ውጤት እንዲኖራቸው የግዴታ መመዝገብና መረጋገጥ የሚገባቸው ሰነዶች ዝርዝር በአዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀፅ 5 ተደንግጓል። የኑዛዜ ሰነድ ህጋዊ ውጤት ለማግኘት መመዝገብና መረጋገጥ ያለበት ሰነድ ስለመሆኑ በአንቀፅ 5 አልተደነገገም። ስለሆነም አመልካች ሚች ዘውዴ ዶሜንኮ በአሜሪካን አገር ያደረጉት ግልፅ ኑዛዜ ሰነድ የመመዝገብና የማረጋገጥ ሥልጣን ባላቸው የኢትዮጵያ ቆንጺላ ጽ/ቤት ያልተረጋገጠ ስለሆነ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል። አመልካችና ተጠሪ በፅሑፍ ካደረጉት ክርክር በተጨማሪ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቷል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን የሚችን ወራሾች በመወከል በአመልካች ላይ ክስ ያቀረበውና የውርስ አጣሪ ሆኜ ተሹሜአለሁ የሚለው ሰው የውርስ አጣሪ ሆኖ የተሾመበት የወ/ሮ ዘውዴ ዶሜንኮ በውጭ አገር አድርገውታል የተባለው ግልፅ ኑዛዜ ሰነድ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

መዝገቡን እንደመረመርነው ሚች ወ/ሮ ዘውዴ ዶሜኒኮ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ፌብሪዋሪ 6 ቀን 2005 ዓ.ም በአሜሪካን አገር ሆነው በእንግሊዘኛ ቋንቋ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 881 መሠረት ባደረጉት ግልፅ ኑዛዜ ክስ የቀረበበትን ቤት በኤርትራ ግዛት አሥመራ ከተማ ውስጥ የእየሱስ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ደቂ ገብሩ ለሚገኝና አብርሀበሀታ አይነስውራን ትምህርት ቤት ሙሉ የባለቤትነት መብቱ እንዲዛወር የተናዘዙ መሆኑንና ይህንንና ሌሎች የኑዛዜ ቃሎችን እንዲያስፈፅም አቶ ታምራት ኪዳነማርያም በውርስ አጣሪነት የሾሙ መሆኑን የሚገልፅ ሰነድ ነው። ተጠሪ የሚከራከሩት ይህ ኑዛዜ በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 ሰነድ በሚለው ትርጉም ሥር የሚወድቅ ቢሆንም ሰነዱ በውጭ አገር የኢትዮጵያ ቆንጺላ ጽ/ቤቶች አለመመዝገቡና አለመረጋገጡ ህጋዊ ውጤት አያሳጣውም። ምክንያቱም "ኑዛዜ" ካልተረጋገጠና ካልተመዘገበ ህጋዊ ውጤት ከማይኖራቸው ሰነዶች አንደኛው አለመሆኑን ከአዋጁ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ መረዳት የሚቻል በመሆኑ የሚል ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንን አተረጓጎም በመከተል ሚች በውጭ አገር አድርገውታል የተባለው የኑዛዜ ሰነድ ህጋዊ ውጤት አለው ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል።

በእኛ በኩል ተጠሪ ያቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ወ/ሮ ዘውዴ ዶሜንኮ ኢትዮጵያ ውስጥ ያደረጉት የኑዛዜ ሰነድ ቢሆን ከላይ የተሰጠው የህግ ትርጉም ተገቢነት ያለው ነው። ሆኖም ተጠሪ ያቀረበው ሚች ኢትዮጵያ ውስጥ ያደረጉትን የኑዛዜ ሰነድ ሣይሆን በአሜሪካን አገር ፊፅመውታል የተባለውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኑዛዜ ሰነድ በሌላ አነጋገር የውጭ አገር ሰነድ (Foreign document) ነው፡፡ አንድ ሰነድ የውጭ አገር ሰነድ (Foreign document) የሚባለው በውጭ አገር ተዕፎ ተዘጋጅቶ ከውጭ አገር የተላከና ወደ አገር ውስጥ የገባ ሲሆን ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ በውጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤቶች ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበ የውጭ አገር ሰነድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ቢቀርብ ህጋዊ ውጤት ይኖረዋል ወይ? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 334/1995 በውጭ አገር የተደረጉ ሰነዶች በአዋጁ መሠረት ካልተመዘገቡና ካልተረጋገጡ ህጋዊ ተቀባይነትና ውጤት አይኖራቸውም በማለት ያስቀመጠው ራሱን የቻለ ግልፅ ድንጋጌ የለም፡፡ አዋጁ ስለ “ውጭ ሰነዶች” መረጋገጥና ህጋዊ ውጤት ስለሚያገኙበት ሁኔታ ከላይ በተገለፀው መንገድ በግልፅ ያልደነገገ ቢሆንም በውጭ አገር ተደርጓል ተብሎ የቀረበ ኑዛዜ በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ወይም ቆንጲላ ጽ/ቤቶች ባይረጋገጥም በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ፊት ሲቀርብ ህጋዊ ውጤት ይኖረዋል ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከውጭ አገር የሚገቡ የመንግስትም ሆነ የግል ሰነዶች ትክክለኛነታቸው በኢትዮጵያ ኤምባሲ ጽ/ቤቶችና በውጭ በሚገኙ የኢትዮጵያ ቆንጲላ ጽ/ቤቶች እየተረጋገጡና እየተመዘገቡ መግባት ያለባቸው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 1 “በውጭ አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንጲላ ጽ/ቤቶች ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ሰነዶችን ያረጋግጣሉ” በሚል መንገድ የደነገገና ይኸም ድንጋጌ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ መሆኑን በድንጋጌው የእንግሊዘኛ ቅጅ “Ethiopian Embassies and Consular offices shall authenticate documents entering in to Ethiopia” በማለት ከውጭ አገር የሚገቡ ሰነዶች ትክክለኛነት በኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤት ትክክለኛነታቸው መረጋገጥ ያለበት መሆኑ አስፈላጊና የግድ መፈፀም የሚገባው ተግባር መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ነው፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የውርስ አጣሪ ሆኜ ተሾሜበታለሁ የሚለው በውጭ አገር ሚች አድርገውታል የተባለው የኑዛዜ ሰነድ የአዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት አሜሪካን አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ትክክለኛነቱ ተረጋግጦና ተመዝግቦ የመጣ ሰነድ አይደለም፡፡ ሰነዱ በህጉ በአስገዳጅነት የተቀመጠውን መስፈርት ማለትም በውጭ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤት ትክክለኛ ሰነድ መሆኑ ተረጋግጦና ተመዝግቦ ያልቀረበ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት ሊሰጠው ስለማይገባ ተጠሪ የውርስ አጣሪ ሆኜ ተሾሜበታለሁ በማለት ያቀረበው ሰነድ አመልካችን በፍርድ ቤት ክስሶ ለመከራከር የሚያስችለው ሰነድ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ክስ ለማቅረብ ሥልጣን አግኝቼበታለሁ በማለት ያቀረበው ኑዛዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገ ሣይሆን በውጭ አገር ተደረገ ተብሎ የቀረበና ኑዛዜው የሚች ወ/ሮ ዘውዴ ዶሜንኮ ትክክለኛ የኑዛዜ ቃል ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በአሜሪካን አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበና ይኸም በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን ሣያገናዝቡ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በመቀበል አከራካሪውን ውሣኔ መስጠታቸው ከላይ የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌ ይዘት መንፈስ ዓላማና የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43181 ጥቅምት 7 ቀን 1999 የሰጠው ውሣኔና ግንቦት 28 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ብይን ሙሉ ለሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ግንቦት 2 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
3. ሚች ወ/ሮ ዘውዴ ዶሜንኮ በአሜሪካን አገር አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ ትክክለኛነት አሜሪካን በሚገኘው በኢትዮጵያ ኤምባሲ ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የሌለውና ተጠሪን ክስ ለማቅረብ የሚያስችል አይደለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 44226

ታህሳስ 15 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. ሕብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ
2. አቶ እየሱስወርቅ ዛፉ
3. አቶ ወርቅሸት በቀለ ደምሴ

ጠበቃ እስራኤል ተክሌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአመልካች የወጣውን መመሪያ ሕጋዊነት አስመልክቶ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪዎች የሕብረት ባንክ ባለ አክሲዮኖች መሆናቸውን፣ በ1952ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ የአክሲዮን ማህበር አስተዳደር ለማህበረተኞች እንጂ ለሌላ ሊሰጥ እንደማይችል በአንቀጽ 347/1/ ላይ የተገለፀ፣ ከባለ አክሲዮኖች መካከል በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ማለትም በባለ አክሲዮኖች እንደሚመረጡ በአስተዳደሪነት መመረጥ የሚችለው ለሶስት አመት እንደሆነ ሆኖም ግን የኩባንያው መመስረቻ ጽሑፍ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ እስካልከለከለው ድረስ በድጋሚ ለምርጫ መቅረብ እንደሚችል በአንቀጽ 350 ስር መደንገጉን፣ የህብረት ባንክ መመስረቻ ጽሑፍም በድጋሚ መመረጥን እንደሚፈቅድ፣ የባንኩ መተዳደሪያ ደንብም በድጋሚ መመረጥን የሚከለክል ድንጋጌ የሌለው መሆኑን፣ 1952ዓ.ም የወጣው የንግድ ሕግ የአንድ ኩባንያ ዳይሬክተር በሌላ ኩባንያ ውስጥ በዳይሬክተርነት እንዲያገለግል የሚከለክል ድንጋጌ የሌለው መሆኑን፣ አዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986 ስለባንክ ጉዳዮች መውጣታቸውንና ለአመልካች መመሪያ የማውጣት ስልጣን የሰጡት ቢሆንም በንግድ ሕጉ ስለ ዳይሬክተሮች የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ለውጥ ያላደረጉ ወይም ገደብ ያላደረጉ ወይም ሌላ ወገን ገደብ እንዲያስቀምጥ ስልጣን ያልሰጡ መሆኑን፣ አመልካች ባንክ የስልጣኑ ምንጭ ሁለት አዋጆች ሆነው እያለ የባንክ ስራ ፍቃድና ቁጥጥር የተሻሻለ የአዲስ ባንክ የስራ ፍቃድና የዳይሬክተሮችና የዋና ስራ አስፈፃሚ ሹመት ማጽደቂያ መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ/39/2006 የሚል በእግሊዝኛ የተፃፈ መመሪያ አውጥቶ በመመሪያው ላይ በአንቀጽ 5.1.4 እና 5.1.5 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ገደብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚጥሉና ከንግድ ሕጉ፣ ከሕብረት ባንክ የመመስረቻ ጹሑፍ ጋር ፍፁም የሚጋጩ መሆናቸውን ዘርዝረው አመልካች ያወጣው መመሪያ እንዲታገድና በስራ ላይ እንዳይውል እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፣ አመልካች ሕገ ወጥ መመሪያ አላወጣም፣ መመሪያው የባለ አክሲዮኖችን የመመረጥና የመምረጥ መብት አላስቀረም የሚሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 83/86 እና 84/86 መመሪያ የማውጣት ስልጣን የተሰጠው ቢሆንም መመሪያ የሚወጣባቸው ጉዳዮች በአዋጆቹ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ብቻ በመሆኑ እና በሌሎች ህጎች በተለይም ከመመሪያው በላይ በሆኑ አዋጆች የተሰጡትን መብቶችና የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የማይቃረን መሆን የሚገባው ስለሆነ የተሻሻለው አዲስ የባንክ ሥራ ፈቃድና የዳሬክተሮች፣ የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሹመት ማጽደቂያ መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ /39/2006 ላይ በአንቀጽ 5.1.4 እና 5.1.5 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሕጋዊ አይደሉም የሚል ምክንያት በመስጠት እነዚህ ድንጋጌዎች ተሽረዋል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 04 ቀን 2001ዓ.ም በፃፉት አምስት ገጽ አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባው መሆኑንና አከራካሪው መመሪያም የሕግ አወጣጥ ስርዓቱን መስረት አድርጎ የወጣና ከንግድ ሕጉም በላይ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮም ለሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ጥቅምት 17 ቀን 2002ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ አመልካች ባወጣው የተሻሻለ አዲስ የባንክ ስራ ፈቃድና የዳይሬክተሮች፣ የዋና ስራ አስፈፃሚ ሹመት ማጽደቂያ መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ /39/2006/ ስር የተመለከቱት አንቀጽ 5.1.4 እና 5.1.5 ድንጋጌዎች ሕጋዊ አይደሉም ተብሎ መሻሩ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

በመሠረቱ ሕግ የማውጣት ስልጣን በስልጣን ክፍፍል መርህ መሠረት የሕግ አውጪው አካል ስለመሆኑ እሙን ነው፡፡ በሕግ አውጪው የመንግስት አካል የሚወጡ ሕጎች ቀዳማዊ /Primary legislations/ ተብለው የሚታወቁ ሲሆን ሌሎቹ እንደአሰፈላጊነታቸው አግባብ ባለው አካል የሚወጡ የበታች ሕጎች /Subsidiary legislations/ ተብለው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ሕግ አውጪው የመንግስት አካል በተለያዩ ቴክኒካዊ፤ ሙያዊና ማህበራዊ ምክንያቶች ቀዳሚውን ሕግ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ዝርዝር ሕጎች ያስፈልጋሉ ብሎ ባመነ ጊዜ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው አካል የበታች ሕጎችን እንዲያወጣ ስልጣን መስጠት የተለመደና ተቀባይነት ያለው አሰራር ነው፡፡ ይህ አሰራር በሕግም በምክንያትም የተደገፈ እና የዳበረ ልምድ ስለመሆኑ የታወቀ ነው፡፡ አሁን በተግባር ሥራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ ያለው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 14/88 አንቀጽ 2/1/ እንደሚያመለክተው ሕግ የሚላቸው አዋጅ ደንብና መመሪያዎችን ነው።

ክርክሩ በተነሳበት ወቅት ተፈፀሚነት የነበረው አዋጅ ቁጥር 83/1986 ሲሆን ይህ አዋጅ ለገንዘብና ለባንክ አዋጅ የተደነገገ ሲሆን በዚህ ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከዚህ አዋጅ በፊት የተቋቋመ ሲሆን ባለበት እንዲቀጥል የደነገገ እና ስለ ባንኩ ዓላማዎች፣ ስልጣን እንዲሁም ተግባር በዝርዝር ተመልክቷል። እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 84/1986 ደግሞ ለባንክ ስራ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ነበር። በዚህ አዋጅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክ፣ የኢንሹራንስና የአነስተኛ ገንዘብ ተቋማትን በተመለከተ ለመስራት የሚፈለጉ ሰዎችን ፈቃድ እንዲሰጥ፣ ከፈቃዱ በኋላ ቁጥጥር እንደሚያደርግ፣ ለፈቃዱ አሰጣጥ በቅድሚያ ሊሟሉ የሚችሉ ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ ያሳያል። አዋጅ ቁጥር 83/1986 አንቀጽ 61 ድንጋጌ ሲታይም ባንኩ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካትና ይህንን አዋጅ በሚገባ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት እንደሚችል ሕግ አውጪው ስልጣን ሰጥቶታል። አዋጁ በአንቀጽ 6 ስር የባንኩ ዓላማዎች የተረጋጋ የገንዘብ ሁኔታ መፍጠር፣ የአገሪቱ ገንዘብ አስተማኝ እንዲሆን ማድረግ፣ አስተማማኝ የፋይናንስ አቅም እንዲኖር ማድረግ እንዲሁም ለኢኮኖሚ እድገት አመቺ የሆኑ የክፈዲትና የምንዛሬ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ መጣር መሆናቸውን ደንግጓል። እነዚህን ዓላማዎችን ለማስፈፀምም ብሔራዊ ባንክ ስልጣንና ተግባሩ በአዋጁ አንቀጽ 7 ስር ተመልክቷል። አዋጁ በአንቀጽ 60/2/ ስር ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም በሚል ደንግጓል። አዋጅ ቁጥር 84/1986 አንቀጽ 36 ደግሞ መመሪያ የማውጣት ስልጣንን ለአመልካች ሰጥቶታል። በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 35 ስር ከአዋጁ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም በማለትም ተደንግጓል።

እንግዲህ አመልካች በሕግ ኃላፊነትና ተግባሩ ተለይቶ የተሰጠው ሲሆን ይህንኑ ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣትና ሕጉን ለማስፈፀም መመሪያ የማውጣት ስልጣን በሕግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986 የተሰጠው መሆኑን ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። የባንኮችን ሥራ የመቆጣጠር ተግባርና ኃላፊነት ደግሞ እንደማንኛውም ቁጥጥር የማድረጊያ ስርዓት ሊፈፀም የሚችለው የፋይናንስ ተቋሞችንና የባንኮችን ተግባርና ኃላፊነት አስቀድሞ በሕግ በመወሰን፣ ይህንኑ ተግባርና ኃላፊነታቸውን ስራ ላይ የሚያውሉበትን ደንብ እንዲኖራቸው በማድረግ እና በአመራራቸውም ላይ በተለያየ ሕጋዊ መንገዶች ቁጥጥር በማድረግ ስለመሆኑ ይታመናል። የባንኮችን ስራ የመቆጣጠር ስራ ለጉዳዩ የተለየ እውቀትና ልምድ ያለውን ተቋም /አካል/ ባለሙያ የሚያስፈልግ መሆኑ እሙን ነው። ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት በሰፊው የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው መሆኑም ይታወቃል። በ1952ዓ.ም በወጣው የንግድ ሕግ የአንድ ኩባንያ ዳይሬክተር በሌላ ኩባንያ ውስጥ በዳይሬክተርነት እንዲያገለግል የሚከለክል ድንጋጌ የሌለው መሆኑና አጠቃላይ ስለ ዳይሬክተሮች የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነታቸው የነበረው ኩባንያና ከፋይናንስ ተቋማት ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች የንግድ ማህበራትም ላይ ጭምር መሆኑ ይታወቃል። ሕግ አውጪው ባንክና የፋይናንስ ተቋማትን በተወሰነ ደረጃ በተለየ የሕግ ማዕቀፍ እንዲገዙ አድርጓል። በ1952ዓ.ም የወጣው የንግድ ህግ በሕጎች አወጣጥ ደረጃ አዋጅ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986ዓ.ም ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው ሕጎች ናቸው። በአዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986 በሚሸፈኑ ጉዳዮች የንግድ ሕጉ የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑ ከሕጉቹ አወጣጥ ቅደም ተከተልና ደረጃ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። አዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986 ከንግድ ሕጉ እኩል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደረጃ ያላቸው በመሆኑና በኋላም የወጡ በመሆኑ በገንዘብና በባንክ እንዲሁም ስለ ባንክ ስራ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመቆጣጠር ቀዳሚ ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን ከሕጎች አተረጓጎም ደንብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አዋጆቹ ከንግድ ሕጉ ቀድመው የሚፈፀሙ ናቸው ከተባለ አመልካች ያወጣው መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ /39/2006 እነዚህ አዋጆቹን መሠረት አድርጎ የወጣ በመሆኑ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ከንግድ ሕጉ በላይ የሚፈፀም ይሆናል፡፡ የስር ፍ/ቤት ሕጎቹ የወጡበትን ስርዓት፣ ሕጉቹ የሚፈፀሙትን ጉዳይ እና በአፈፃፀም ደረጃ ያላቸውን እርከን በአግባቡ ሳይለይ አመልካች ባወጣው መመሪያ ውስጥ የተካተቱት አንቀጽ 5.1.4 እና 5.1.5 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ሊኖራቸው አይገባም በማለት እንዲሻሩ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 93620 ጥር 02 ቀን 2000ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64552 ታህሳስ 09 ቀን 2001 የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 83/1986 እና 84/1986 መመሪያውን የማውጣት ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ የተሻሻለው አዲስ የባንክ ስራ ፈቃድና የዳይሬክተሮች፣ የዋና ስራ አስፈፃሚ ሹመት ማጽደቂያ መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ /39/2006 አንቀጽ 5.1.4 እና አንቀጽ 5.1.5 ከ1952ቱ የንግድ ሕግ ጋር የሚጋጭ ነው ተብሎ ሊሻር የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሳስ 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ተስፋዬ ምንዳገኝ - ቀረበ

ተጠሪ፡- ንጋቱ ወ/ስንበት - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ የሚች ወ/ሮ ፀሐይ በቀለ ባል ነኝ በማለት የሰጠው ውሳኔ የባልና ሚስት ግንኙነት (ጋብቻ) ሳይኖር የተሰጠ በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች መቃወሚያውን ያቀረበው ተጠሪ የሚች ባል መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ ለሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በመቃወሚያ ሥረ ነገር ላይ ገብቶ ሳያከራክር ተጠሪን መልስ እንዲሰጥ ሳያደርግ አመልካች መቃወሚያውን ለማቅረብ የሚያስችል መብት የለውም በማለት ሳያስተናግደው ቀርቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ትዕዛዙን በመቃወም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች በተሰጡት ውሳኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል በማለት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርብም፤ የሰበር ችሎቱ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው አመልካች ተጠሪ በሰጠው የባልነት ውሳኔ ላይ መቃወሚያ የማቅረብ መብት የለውም በማለት የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች መቃወሚያ ሊያቀርብ የቻለው ተጠሪ ሐሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ በተሰጠው የባልነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በመጠቀም የጡረታ አበል እንዲከፈለው በማስወሰኑ እና ይህን ውሳኔ መሠረት በማድረግም አበሉን መውሰድ በመጀመሩ ነው፡፡ በእርግጥም ተጠሪ የሚች ባል ነው ተብሎ የጡረታ አበል እንዲከፈለው ከተወሰነ አመልካች በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም ይገደዳል፡፡ ከዚህ ግዴታ ነፃ ሊሆን የሚችለው ተጠሪ የሚች ባል ነው የተባለበትን ውሳኔ ከመሠረቱ ማሻር ሲችል ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መቃወሚያ ያቀረበውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች መቃወሚያውን ሳያስተናግዱ የቀሩት ተጠሪ የሚች ባል ነው በመባሉ መብቱ (የአመልካች) ተነክቶአል ሊባል አይችልም የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነ ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡

በሕግ መሠረት የጡረታ አበል የሚከፈላቸው ሰዎች አበሉን የሚያገኙ ከአመልካች ኤጀንሲ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ አመልካች አበሉን መክፈል ያለበት ሕጉን መሠረት በማድረግ ብቻ እንደሆነም አያከራክርም፡፡ ይህ ሁኔታ ከሌላ አቅጣጫ ሲታይ ደግሞ አመልካች በሕግ የተመሠረተ መብት ለሌለው ሰው አበሉን አልከፍልም የማለት መብት አለው ማለት ነው፡፡ አመልካች በዚህ በያዝነው ጉዳይ እያለ ያለውም ይኸው ነው፡፡ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሳኔ (ክፈል የሚል) በመኖሩ ግን በራሱ ሥልጣን መክፈል ማቆም ያስችግረዋል፡፡ በመሆኑም ለአበሉ ክፍያ መሠረት ሆኖአል ያለውን ውሳኔ ለመቃወም ቀርቦአል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.358 እንደተደነገገው ቀደም ሲል ለተሰጠው ውሳኔ መሠረት በሆነው ክርክር ተካፋይ ያልነበረ ሰው ውሳኔው እንዲሻርለት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ (ውሳኔ) መብቱን የሚነካበት እንደሆነ ነው፡፡ ፍርዱ መብቱን የሚነካበት ከሆነ ደግሞ በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ የመሆን በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተረጋገጠለት መብት አለው ማለት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ሕጋዊ መሠረት የሌለውን የጡረታ አበል የመክፈል ግዴታ የለበትም ወይም ደግሞ አልከፍልም የማለት መብት አለው የሚል መነሻ ተይዞ ነው መቃወሚያው የቀረበው፡፡ በእርግጥም አመልካች መብቱን ማስከበር የሚችለው በክርክሩ ውስጥ በመግባት የበኩሉን ክርክር በማቅረብ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች መቃወሚያውን ባለማስተናገዳቸው ክርክሩን ለማቅረብ አልቻለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የተከተሉት አካሄድ ሕጉንና የሥነ ሥርዓት ደንቦቹን የተከተለ አይደለም፡፡ የሰጡት ውሳኔም በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ የካ-1624/98 መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ.ቁ 10067 ህዳር 4 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የይግባኝ ሰሚው ሰበር ችሎት በመ.ቁ 12586 የካቲት 4 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበለትን መቃወሚያ በመቀበል እና ተጠሪ በመቃወሚያው ሥረ ነገር ላይ የሚሰጠውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መልስ በመስማት ግራቀኝ ወገኖቹን በማከራከር ተገቢውን ይወሰን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.341(1) መሠረት ወሰነናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

ራ/ታ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡ - ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

አለ. መሐመድ

አመልካች፡ - የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ወኪል ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡ - አቶ ታዬ በዛብህ ፊኖ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው በቀጥታ ለፍ/ቤት በቀረበ ክስ መነሻ ፍትህ ሚኒስቴር ለአሁኑ ተጠሪ የጥብቅና ፈቃድ በመስጠት እንዲመዘግባቸው በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10(3) መሠረት የቀረበ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠኝ የሚል ጥያቄ ለፍትህ ሚኒስቴር አቅርበው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለሚሰሩ ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ በሚመለከት በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 21 መሠረት በጥብቅና ገምጋሚ ኮሚቴ ተመርምሮ የተሰጠው የውሣኔ ሃሳብ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 26 መሠረት ለሚኒስትሩ ቀርቦ የጥብቅና ፈቃድ እንዳይሰጣቸው ተብሎ በመወሰኑ በአዋጅ አንቀጽ 29(1) በሚደነግገው መሠረት የጥብቅና ፈቃድ ጠያቂው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበው ክርክሩ ከተሰማ በኋላ ፍ/ቤቱ መርምሮ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ “2” መሠረት በሕጉ ጉዳይ ላይ ውሣኔ በመስጠት መታየት ይገባዋል ባለው ፍሬ ነገር ላይ ሚኒስትሩ አይቶ በ30 ቀን ውስጥ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብሎ የመለሰው ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ሚኒስትሩ ከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ባለመሆን ለ40 ቀናት ውሣኔ ሳይሰጥበት በማቆየት የጥብቅና ፈቃድ እንዳላገኝ ስላደረገ ክልከላው ተወግዶ የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጠኝ ይታዘዝ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 314(1) መሠረት በቀጥታ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ በዚህ የክልከላ ይወገድ ክስ ተከሳሽ የሆነው የፍትህ ሚኒስቴር ወኪል ቀርበው ጉዳዩን ገምጋሚ ኮሚቴ ተመልክቶ ውሣኔ እንዲሰጥበት አስተላልፈናል የሚል መልስ እንደሰጡ ተመዝግቦ ፍ/ቤቱ መርምሮ ፍትህ ሚኒስቴር ጉዳዩን ለማየት ፈቃደኛ መሆኑን ከመግለጽ በቀር ክልከላው የማይወገድበት ምክንያት ስለመኖሩ ስላላስረዳ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 314(2) መሠረት ክልከላው ተወግዶ ለከሣሹ የጥብቅና ፈቃድ በመስጠት ይመዝግባቸው በሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም ከፍተኛው ፍ/ቤትም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው በዚህ ምክንያት የቀረበ ሲሆን ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ ተብሎ ስለታዘዘ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪው ታህሣሥ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፣ የአመልካቹ አቤቱታ ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም የሚሉባቸውን ምክንያቶች ገልፀው አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተጠሪው በኩል የተሰጠውን መልስ በማስመልከት የመልስ መልስ እሰጣለሁ ካለ ይቅረብ የተባለ ቢሆንም ከመዝገቡ እንደሚታየው ያቀረበው የመልስ መልስ የለም፡፡

ሰበር ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ያቀረቡት የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠኝ ጥያቄ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለሚሰሩ ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ በሚመለከት በተለይ በወጣው በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 20፣21 እና 26 መሠረት ታይቶ ሚኒስትሩ የጥብቅና ፈቃድ እንዳይሰጥ ብሎ በሰጠው ውሣኔ ላይ ፈቃድ ጠያቂው በተጠቀሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29(1) መሠረት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ክርክሩ ከተሰማ በኋላ ፍ/ቤቱ መርምሮ የሕግ ጉዳይ ነው ባለው ነጥብ ላይ ውሣኔ በመስጠት በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ “2” መሠረት በቀሪው ፍሬ ነገር ላይ ሚኒስትሩ አጣርቶ በ30 ቀን ውስጥ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብሎ መልሶት ሚኒስትሩ ውሣኔ ሳይሰጥበት ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ እያለ ተጠሪው ሚኒስትሩ በተባለው 30 ቀን ውስጥ ውሣኔውን ባለመስጠቱ ምክንያት የአሁኑ አመልካች ያደረገብኝ የጥብቅና ክልከላ ይወገድ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.314(1) መሠረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡት በሕጉ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም? የአሁኑ ተጠሪ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት ፍትህ ሚኒስቴር በ30 ቀን ውስጥ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ሳይሰጥ ቢቀርና ቢያዘገየው ምን ማድረግ አለባቸው? የሚሉት ጥያቄዎች ሲታዩ፡ -

በፌዴራል ፍ/ቤቶች ለመስራት የሚቀርብ የጥብቅና ፈቃድ መስጠትና ምዝገባ ጥያቄን በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 19 መሠረት አይቶ የመወሰን ስልጣን የተሰጠው ለፍትሕ ሚኒስቴር ነው፡፡

በመጀመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 20 እና 21 መሠረት የአመልካቹን የጥብቅና ፈቃድ ጥያቄ አይቶ ማስረጃዎቹን በመመርመር ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም እንዳይሰጠው ለሚኒስትሩ የውሣኔ ሃሣብ የሚያቀርበው የጥብቅና ገምጋሚ ኮሚቴ ነው፡፡ በአንቀጽ 26 ላይ እንደተመለከተው የጥብቅናው ፈቃድ ይሰጥ ወይንስ አይሰጥ የሚለውን የመጨረሻውን ውሣኔ የሚሰጠው ሚኒስትሩ ነው፡፡ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የሚኖረው ከዚህ የሚኒስትሩ ውሣኔ በኋላ በአዋጅ አንቀጽ 29 መሠረት በይግባኝ ደረጃ ብቻ ነው፡፡ የመጀመሪያውን ይግባኝ የሚያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ሚኒስትሩ የጥብቅና ፈቃድ እንዳይሰጥ በማለት በሰጠው ውሣኔ መነሻ በቀጥታ ለፍ/ቤት የሚቀርብ ክስ አይኖርም፡፡ በሕጉ ይግባኝ እንዲባልበት ብቻ የተፈቀደ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአሁኑም ጉዳይ ተጠሪው አዋጁን በተከተለ መንገድ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠኝ ጥያቄ ለፍትሕ ሚኒስቴር አቅርበው ታይቶ ሚኒስትሩ የጥብቅና ፈቃድ እንዳይሰጥ የሚል ውሣኔ በመሰጠቱ በሕጉ በተፈቀደው የይግባኝ ሥርዓት በመጠቀም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ክርክሩ ተሰምቶ ፍ/ቤቱ መርምሮ በሕጉ ጉዳይ የራሱን ውሣኔ ሰጥቶበት በቀሪ ፍሬ ነገር ላይ ራሱ ፍትህ ሚኒስቴር አይቶ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት የመለሰው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ወደ ፍትህ ሚኒስቴር የመለሰው በ30 ቀን ውስጥ አይቶ ውሣኔ እንዲሰጥበት ነው፡፡ ሆኖም ፍትሕ ሚኒስቴር ከፍተኛው ፍ/ቤት በአጭር ጊዜ ውስጥ ታይቶ እንዲወሰን በመፈለግ ውሣኔው በ30 ቀን ውስጥ አይቶ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት ባዘዘው መሠረት ሳይፈጽም ቆይቷል፡፡ ጉዳዩም ገና በእንጥልጥል ላይ ስለሚገኝ ውጤቱ ምን እንደሚሆን አይታወቅም፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ሁኔታ ምን ማድረግ ይችላሉ? በሕጉ ክስ ማቅረብ ይችላሉ ወይ? የሚለውን በተመለከተ ከፍ ሲል እንደተገለፀው በቀጥታ ክስ ለፍ/ቤት ቀርቦ የሚታይ ጉዳይ አይደለም፡፡ የጥብቅና ክልከላ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 29(1) መሠረት ሥልጣኑ ለሚመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ ቀርቦ ታይቶ የሚወሰን እንጂ ክልከላ ይወገድ በሚል በቀጥታ ለፍ/ቤት አቤቱታ የሚቀርብበት ባለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.314 ድንጋጌ በእንዲህ አይነቱ ጉዳይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡ ተጠሪ የአሁኑ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንደገና ጉዳዩን አይቶ ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት ባለመፈለግ የሚያዘገየው ከሆነ በውሣኔው መሠረት እንዲፈፀምላቸው ማመልከት ያለባቸው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በውሣኔው መሠረት እንዲፈጸም ሊያስገድደው የሚችለውም ይኸው ውሣኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ መንገድ በመጠየቅ በጥብቅና ፈቃድ ጥያቄው ላይ ውሣኔ እንዲሰጥ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች የጥብቅና ፈቃድ ክልከላ አድርጉብኛል በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.314(1) መሠረት ክልከላው ይወገድ በሚል በቀጥታ ለፍ/ቤት የክስ አቤቱታ ያቀረቡት በሕጉ አግባብ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሥር ፍ/ቤትም የጥብቅና ፈቃድ ጉዳይን በተመለከተ በተለይ በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/1992 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት ታይቶ የሚወሰንና ለፍ/ቤትም የሚቀርበው በይግባኝ ደረጃ ብቻ መሆኑ እየታወቀ የጥብቅና ፈቃድ ክልከላ ተደርጓል በሚል ምክንያት በቀጥታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.314 መሠረት የቀረበውን ክስ በመቀበል የአሁኑ አመልካች ለተጠሪው የጥብቅና ፈቃድ በመስጠት እንዲመዘግባቸው በሚል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.166328 በ25/8/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 94250 በ27/09/2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 9 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐሳስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን - ሠላማዊት ሀይሉ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ከበደ ወዳጆ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በወሮጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ለሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ አመልካች (ተከሳሽ) በጅማ ገነት ወረዳ ውስጥ የገጠር መንገድ ሲጠግን አላግባብ በእርሻ መሬት ይዞታዬ በመግባት የተለያዩ ቋሚ አትክልቶች የሰብል ምርትና ሣር ቤት አውድሞብኛል፡፡ ተከሳሽ በቆፈረው ጉድጓድ በሬ ገብቶ ስለሞተብኝ የበሬውንም ዋጋ እንዲከፍለኝ በማለት በአጠቃላይ የጉዳቱን መጠን ብር 71950 ብር በመገመት ካሳ እንዲከፈለው ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የይርጋ ጊዜው አልፏል፡፡ ሥራ ያሠራሁት በክልሉ አዋጅ ቁጥር 11/88 በተሰጠኝ ሥልጣንና ሀላፊነት መሠረት ነው፡፡ ከሳሽ አሉ የሚሏቸው ንብረቶች በቦታው ላይ አልነበረም፡፡ የበሬ ዋጋ ልንከፍል አንገደድም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች (ተከሳሽ) በተጠሪ ይዞታ ሥር የነበሩ ግምታቸው ብር 7,850 (ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሀምሳ ብር) ያላቸው የተለያዩ ተክሎች አውድሟል፡፡ የከሳሽ(ተጠሪ) በሬ ተከሳሽ ከቆፈረው ጉድጓድ ገብቶ የሞተ ስለሆነ ብር 2,500 (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) በጠቅላላው ብር 10,350 (አስር ሺ ሶስት መቶ ሀምሳ ብር) አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይዞታው የተጠሪ ይዞታ መሆኑ በተጠሪ ይዞታ ላይ ያለው ተክል ላይ አመልካች አላግባብ ጉዳት እንዳደረሰ የተረጋገጠ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች ለተጠሪ ብር 7,750 (ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) እንዲከፍል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው፡፡ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የበሬ ዋጋ ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረበ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ጳጉሜ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2143ን በመጥቀስ ያቀረብነውን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው አላግባብ ነው፡፡ በመሬቱ ላይ አትክልትና ንብረት እንደሌለ ተረጋግጦ እያለና በአዋጅ በተሰጠኝ ሥልጣን መሠረት መንገድ የጠገንኩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ካሣ እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የጠቀሳቸው የይርጋ ድንጋጌዎች ማለትም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149(1) እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2143 በእኔና በአመልካች መካከል ባለው ክርክር ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡ አመልካች በህጋዊ ይዞታዬ ላይ በነበሩት ቋሚ አትክልቶች ላይ ጉዳት ማድረሱ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ለህዝብ ግልጋሎት የሚሰጥ የመንገድ ጥገና ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት የተጠሪን ይዞታና በተጠሪ ይዞታ ላይ ያሉ የተለያዩ ተክሎች ላይ ጉዳት ስላደረሰ ካሣ እንዲከፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ከውል ውጭ የሚደርስ ሀላፊነትን የሚመለከት ክስ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ጥያቄ አመልካች ይዞታውን ለህዝብ ጥቅምና ግልጋሎት የሚውል መንገድ ለመጠገን ከወሰደ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 8 መሠረት በይዞታው ላይ ለነበረው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ በመሬቱ ላይ የነበሩትን ተክሎች ዋጋ ይክፈለኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ በህገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 8 መሠረት ለተወሰደ ንብረት ካሣ እንዲከፈላቸው ተጠሪ የመጠየቅ መብት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2143 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው የሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ የማይገደብ መሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42629 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጠሪ ክስ በሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ አይታገድም በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢና መሠታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ በይዞታ መሬቱ ላይ ነበሩ ከሚላቸው የተለያዩ አይነት ቋሚ ዛፎችና አትክልቶች ጠቅላላ ግምት ከብር 60,000(ስልሣ ሺህ ብር) በላይ እንደነበርና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣናቸውን ተጠቅመው በተጠሪ ይዞታ ላይ የነበሩትና በአመልካች ጉዳት የደረሰባቸው ተክሎችና ዛፎች ግምት 7,750 (ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ይህንን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል ወስነዋል፡፡ አመልካች በቦታው ላይ ምንም አይነት ንብረት የለም በማለት በሰበር አቤቱታው የሚከራከር ቢሆንም ይህ የአመልካች ክርክር የፍሬ ነገር ክርክር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች የካሣውን መጠን በተመለከተ ያቀረበው አቤቱታ ለሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የቀረበና ሕጋዊ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ጥቅምት 26 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጉስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካቾች፡- 1. ኤርሰዴ ንግድ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ አብዱርማን መሀመድ - ቀረቡ

2. አቶ ፀደቀ ማርቆስ - ጠበቃ አቶ ዳንኤል ወ/ጊዮርጊስ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐ/ሕግ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁን ተጠሪ ለሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረባቸው ሁለት የወንጀል ክሶችን ሲሆን 1ኛ ክስ በሥር 1ኛ ተከሳሽ /በአሁን 1ኛ አመልካች/ ላይ የቀረበ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ቃልም ተከሳሹ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ እና የቡና ጥራት ቁጥጥር እና ግብይት አዋጅ ቁጥር 602/2000 አንቀጽ 14/3/ እና 15/3/ በመተላለፍ የቡና ላኪነት ፈቃድ አውጥቶ በቡና ግብይት ሥራ ላይ ተሠማርቶ ሲንቀሳቀስ በአንድ የምርት ዘመን ከጨረታ ማዕከላትና ከኢት/የምርት ገበያ የገዛውን ቡና የሚቀጥለው የምርት ዘመን ከመድረሱ በፊት በሚመለከተው ገበያ አቅርቦ መሸጥ ሲገባው መጋቢት 23 እና 30/2001 የቡና ክምችቶ ቆጠራ በተደረገበት ወቅት በድርጅቱ መጋዘኖች ከተገኘው 203,577 ኪሎ ግራም ውስጥ ለኤክፖርት የተዘጋጀ 101,580 ኪ.ግ የከረመ ቡና ለገበያ ሳያቀርብና ለሚመለከተው አካል ሳያሳውቅ ቡና አከማችቱ በመገኘቱ ተከሷል የሚል ሲሆን፣ 2ኛ ክስ በሥር 2ኛ ተከሳሽ /በአሁኑ 2ኛ አመልካች/ ላይ የቀረበ ነው፡፡ 2ኛ የሥር ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 602/2000 አንቀጽ 14/3/ እና 15/3/ ሥር በ1ኛ ክስ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት በመፈፀሙ ተከሷል የሚል ነው፡፡

የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከቀረቡት ማስረጃዎች አንፃር በመመርመር በሰጠው ፍርድ 1ኛ ተከሳሽን ክስ በቀረበበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ እና በአዋጅ ቁጥር 602/2000 አንቀጽ 15/3/ ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት በብር 40,000 እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በመሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 15/3/ ሥር ጥፋተኛ ሆኖ በ1 ዓመት ቀላል እሥራት እና በብር 30,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚሁ በፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ የሥር ተከሳሾች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሥር የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች ካከራከረ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤትን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካቾች በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

የተጠሪ ክስ አቀራረብ ከአዋጅ ቁጥር 602/2000 አንቀጽ 15/3/ አባባል ጋር ተጣጥሞ ባለመቅረቡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130/1/ መሠረትም የአመልካቾችን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ያቀረብነውን ተቃውሞ የሥር ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ያለአግባብ ነው፤

- የወንጀሉ አፈፃፀም ከጥርጣሬ በፀዳ መልኩ ሳይረጋገጥ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ መሠጠቱ ተገቢነት የለውም፤
- ከረመ የተባለው ቡና የምርት ዘመኑ ሳያልፍ ጥር 10 ቀን 2001 ዓ/ም ተሸጦ የውል መፈፀሚያው ቀን የክፍያ ማረጋገጫ የቀረበበት ቀን ተደርጐ መወሰዱ ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ለሰበር አቤቱታ ተጠሪው በሰጠው መልስ አመልካቾች ክሱ ተጠቅሶ የቀረበብንን የአዋጅ ቁጥር 602/2000 አንቀጽ 15/3/ ዝርዝር ሁኔታን አያሟላም በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130/1/ እና 119 መቃወሚያ በማቅረብ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ጠይቀን ታልፎብናል ያሉትን በሚመለከት የሥር ፍ/ቤት ምላሽ እንድንሰጥበት በጊዜው ጠይቆን አመልካቾች ቡናን ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ ፈቃድ አውጥተው የሚንቀሣቀሱ እንደመሆናቸው መጠን ቡናን ለማገበያየት ፈቃድ ካለው አካል የገዙትን ያልተዘጋጀ ቡና ለኤክስፖርት በሚመጥን መልኩ አዘጋጅተው ወደ ውጪ ሀገር ከሚልኩ በስተቀር ቡናውን ለሌላ አላማ ሊያውሉት እንደማይችሉና የተከማቸውም ቡና ለግብይት የሚውል መሆኑን አስረድተናል፡፡ አመልካቾች የሸያጩ ጊዜ ከማለፉ በፊት ሽያጩ ተከናውኗል ያሉትም ቢሆን ገዥ ነው የተባለው ኩባንያ የግዥ ማረጋገጫ የላከው የካቲት 26 ቀን 2001 መሆኑን አመልካቾች ያልካዱት ሲሆን ይህም የሚያሳየው ሽያጩ የተጠናቀቀው የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ/ም መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ ቁጥር 602/2000ን ተከትሎ የወጣው መመሪያ ላይ ላልታጠበ ቡና የተመለከተው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የተከናወነ ሽያጭ ነው፡፡ በማለት የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግና የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

አመልካቾች በሰጡት የመልስ መልስ ክርክራቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡ የግራቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን የቀረበ ሲሆን እኛም በሥር ፍ/ቤቶች የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪ በመጋቢት 23 ቀን 2001 እና መጋቢት 30/2001 ዓ/ም በአመልካቾች መጋዘን ባደረገው ቆጠራ 42,646 ኪሎ ግራም የከረመ ያልታጠበ ቡና ተከማችቶ የተገኘ ሲሆን ተጠሪዎች ግን ተከማችቶ ተገኝቷል የተባለው ቡና በጀርመን ሀገር የሚገኘው ሀምቡርግ የተባለው ኩባንያ ጥር 10 ቀን 2001 ዓ/ም በቃል በተደረገ ስምምነት መግዛቱንና የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ/ም የስምምነት ደብዳቤ መላኩና ቡናውም ሳይጫን የዘገየው ገዥው ተግባሩን ባለመወጣቱ ምክንያት ነው በሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከራክሯዋል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪዎች ቡናው በመጋዘናቸው ተከማችቶ የቆየ ስላለመሆኑ ክደው አልተከራከሩም፡፡

ይህ የከረመው ቡና ያልታጠበ እስከሆነ ድረስ ኢዲስ አመት ከገባ ከየካቲት 01 ቀን እስከ ሚቀጥለው ጥር 30 ድረስ ወደ ገበያ ወጥቶ መሸጥ የነበረበት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት የፍሬ ነገርን ክርክር በሚያጣራበት ጊዜ የተጠሪ ምስክሮች ቀርበው ሙያዊ ምስክርነት የሰጡ ሲሆን ቡናው በተለያዩ ችግሮች ለገበያ ካልቀረበ ደግሞ ለሚመለከተው አካል የማስታወቅ ግዴታ አመልካቾች ያለባቸው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 602/2000 እና ይኸንኑ አዋጅ ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 159/2001 እንዲሁም የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ያወጣው መመሪያ ይደነግጋሉ፡፡

በመሆኑም ቡናው ስለመክረሙ በሕጉ በተጣለባቸው ግዴታ መሠረት አግባብ ላለው የመንግስት አካል አመልካቾች እስካላሳወቁ ድረስ የተጠቀሰባቸውን የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ ጥሰው ተገኝተዋል በማለት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው በአግባቡ ስለሆነ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 160177 በቀን 07/8/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 91949 በቀን 21/10/2002 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለባቸው በመሆኑ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ /ለ-2/ ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 2 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ መልኩ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ነገረፈጅ ተስፋዬ ከርጋ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡-1. አቶ ወልዱ በየነ ቀረቡ፡፡

2. አቶ ታምሩ አያለው - ቀረቡ፡፡

3. አቶ አየለ ዋቀዮ } በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ተወካይነት ቀረቡ፡፡

4. አቶ ተስፋዬ በዳዳ }

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የደሞዝ ጨማሪን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በበታች ፍ/ቤት ከሣሾችና አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱ የቀረበው በኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግሥት የምሥረቅ ኦሮሚያ አሰሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን ቀርቦ የነበረው ክስ በጡረታ እድሜያችን የጡረታ አበል ያገኙ የነበረና ተከሣሽ በኮንትራት ሲቀጥረን በጡረታ በምናገኘው ክፍያ ላይ 291 ብር ጨምሮ ይከፍለን የነበረና የጡረታ ደብተራችንም የተመለሰ መሆኑ ይሁን እንጂ የጡረታ እና ዋስትና ባለሥልጣን ከሐምሌ 1999 ዓ.ም ጀምሮ ጭማሪ ቢያደርግም የአሁን ተከሣሽ በደሞዛችን ላይ እንዲጨምርልን ስንጠይቅ መልስ ሣይሠጠን ቆይቶ ከጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ ግንቦት 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን ብቻ ከፍሎናል፡፡ ስለዚህ ከሐምሌ 1 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ18 ወር ውዝፍ እንዲከፍል የሚል ነበር፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሣሽ በበኩሉ በሠጠው ክሣሾች በጡረታ ላይ የነበሩ ቢሆንም በግልፅ ውል በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 4 መሠረት ተቀጥረው እንደማንኛውም ሠራተኛ የሚመለከታቸውን ደሞዝና ጥቅማጥቅም እያገኙ ነው፣ ማህበርዊ ዋስትና በኑሮ ውድነት ምክንያት ደሞዝ ሲጨምር እኛም መጨመር እንዳለብን የተደረገ ስምምነት የለም፡፡ እንዲሁም ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆናል በማለት ተከራክሯል፡፡

ቦርዱ ከላይ እንደተመለከተው ከክርክር በኋላ የቀረበው ክስ የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁን ተጠሪዎች ቅር በመሠኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብለው ፍ/ቤቱ ከክርክር በኋላ የአሁን አመልካች ከሐምሌ 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ መንግሥት በጨመረው መሠረት ለአሁን ተጠሪዎች ሊከፍላቸው ይገባል በማለት የቦርዱን ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ ከዚሁ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሲሆን በ03/13/2003 2 ገጽ በተፃፈ አቤቱታ መንግሥት የሰጠውን ጭማሪ አስቀምጦ በውላችን ውስጥ የካተተ ነገር ባለመኖሩ ልንከፍል አየገባም፡፡ በተጨማሪም ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት አመልክቷል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በ29/03/2003 ዓ.ም 2 ገጽ ላይ ጽፈው ባቀረቡት መልስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ በመሆኑ እንድፀና የሚል ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች የመልስ መልስ እንድያቀርብ በተቀጠረበት ባለመቅረቡ መዝገቡ ለምርመራ አድሯል፡፡

በግራ ቀኙ የተደረገው የክርክር ሂደቶች ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረበውን ቅሬታ ከተያዘው ጭብጥና ከሚመለከታቸው ሕጎች ጋር መርምሮአል፡፡ እንደመረመርነውም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል የክፍያውን አግባብነት በግራ ቀኙ መካከል ከተመሠረተው የሥራ ውል አኳያ ለመመርመር ነው፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን ከዚህ አኳያ መርምሮታል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የአሁን ተጠሪዎች በጡረታ ላይ የነበሩ ሰዎች ሆነው የቅጥር ውል ከአሁን አመልካች ጋር የፈፀሙ ስለመናቸው አላከራከረም፡፡ ይሄ የሥራ ውል ግንኙነት በመፈጠሩ ምክንያት የጡረታ ደብተራቸውን ለሚመለከተው የመንግሥት አካል የመለሱ መሆናቸውን ተጠሪዎች ራሣቸው አመልክተዋል፡፡ በግራ ቀኙ የሥራ ውል ውስጥ አመልካች ለአሁን ክስ ምክንያት የሆነውን ክፍያ ለመክፈል የገባው ግዴታ ያለመኖሩን አመልካች የተከራከረ ሲሆን ተጠሪዎችም በውላቸው ውስጥ የተቀመጠ ግዴታ ስለመኖሩ ያነሱት ነገር ካለመኖሩም በላይ እንደዚህ ዓይነት ግዴታ በመካከላቸው ያለመኖሩን የበታች ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል አንድ ጡረታ የወጣ ሰው ተመልሶ ብቀጠር እንደማንኛውም ተቀጣሪ ሠራተኛ ማግኘት ያለበትን ክፍያ ከመጠየቅ ባለፈ ለጡረተኞች የክፍያ ጭማሪ በማደረጉ ብቻ አመልካች የተደረገውን ጭማሪ እንድከፍል የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች መንግሥት ለጡረተኞች ያደረገውን የደመወዝ ጭማሪ ለተጠሪዎች እንዲከፍል በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/93661 በ29/10/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምሥራቅ ኦሮሚያ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በቁጥር 664/01/2002 በ26/6/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች ጡረታኝነታቸውን በመተው የሥራ ቅጥር ውል ከአመልካች ጋር ከፈፀሙ በኋላ መንግሥት ለጡረተኞች በኑሮ ውድነት ምክንያት ደሞዝ ጨምሯል በሚል አመልካች ጭማሪውን እንዲከፍል ለመጠየቅ የሚያስችል ከውል ወይም ከህግ የሚመነጭ መብት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ላይ የደረሰውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልስናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐሳስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- አቶ ባልቻ ወ/ፃድቅ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ግርማ ቀለታ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ቃረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ያቀረበ ነው አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት የጥበቅና ግልጋሎት አሰጣጥን በሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ከወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ ጋር በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የነበረኝን የፍታብሔር ክርክር ለመከታተልና ጉዳዩን እስከሰበር ችሎት ድረስ እኔን በመወከል ሊከራከሩልኝ ከተጠሪ ጋር ውል ተዋውለናል፡፡ ከሳሽ በውል ከተስማማነው ብር 2,000 /ሁለት ሺ ብር/ ውስጥ ብር 1,000 /አንድ ሺ ብር/ ለተከሳሽ ከፍያለሁ፡፡ ተከሳሽ ተገቢውን የጥብቅና አገልግሎት ያልሰጡኝ በመሆኑ የከፈልኩትን ገንዘብ ከነኪሣራው እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ የማህበራዊ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች ብር 2,000 /ሁለት ሺ ብር/ ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የተዋዋለው በአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለመከራከር እንጂ በይግባኝና በሰበር ለመከራከር አይደለም በማለት የማህበራዊ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለከተማው ሰበር ችሎት አቅርቦ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ጋር ያደረግሁት የጥብቅና አገልግሎት ውል ተጠሪ እኔ ከወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ ጋር ባለኝ የፍታብሔር ክርክር በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር ሊቆሙልኝ መሆኑ በውሉ ተገልፆ እያለ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ውሣኔ በይግባኝ ያየው የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት ውሉ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብቻ ለመከራከር የተደረገነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ውሉ በአዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የጥብቅና ግልጋሎት ለመስጠት የተደረገ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ማቅረቡ የማይጠቅማቸው መሆኑን መክሬአቸዋለሁ፡፡ አመልካች ከሙያ አንፃር የማያዋጣውንና የማላምንበትን ጉዳይ ይግባኝ ካላቀረብክ በማለት ያቀረቡት ክስ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥ በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገው የጥብቅና አገልግሎት ውል ስምምነት “እኔ ውል ሰጭ ከወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ ጋር በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስላለኝ የቦታ ክርክር ጉዳይ ውል ተቀባይ ባላቸው የጥብቅና ሙያ ጉዳዬን እስከ መጨረሻ ድረስ ሊከራከርልኝ ለዚህ አገልግሎታቸው ብር 2,000 /ሁለት ሺ ብር/ ልከፍላቸው የተስማማን ሲሆን” በሚል መንገድ በተራ ቁጥር 1 የአመልካችን ግዴታ የሚገልፅ ሲሆን በተራ ቁጥር 2 “እኔም ውል ተቀባይ በተራ ቁጥር 1 ላይ በተገለፀው መሠረት የውል ሰጭው ጉዳይ እስከመጨረሻ ድረስ ልከራከርላቸው ተስማምተን በቅደሚያ ብር /አንድ ሺ ብር/ ተቀብያለሁ” በሚል መንገድ የተጠሪን ግዴታ የሚገልጽ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል በተደረገው ውል ውስጥ “እስከመጨረሻ ድረስ ሊከራከሩልኝ” የሚለውና “እስከ መጨረሻ ድረስ ልከራከርላቸው” የሚለው ቃል ተጠሪ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብቻ ለመከራከር የውል ግዴታ እንደገቡ በማድረግ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1732 እና የጥብቅና አገልግሎት በደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀፅ 8/2/ የተደነገገውን ያላገናዘበና የአተረጓጎም ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህ “እስከ መጨረሻ ድረስ” ልከራከርላቸው በማለት ተጠሪ የገቡት ውል ይዘት አመልካች ከሙያ አንፃር የሚያዋጣ ከሆነ ይግባኝ አቅርቦ የመከራከርና በሰበር አቤቱታ አቅርቦ መከራከረን የሚጨምር በመሆኑ በዚህ በኩል የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው በሰበር ችሎት የሰጡት ትርጉም ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም ተጠሪ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብቻ ለመከራከር ነው በጥብቅና አገልግሎት ውሉ የተስማማሁት በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ አልተቀበልነውም፡፡

የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን ውል ሲተረጉሙ ስህተት የሰራ ሲሆን ተጠሪ ያቀረበው ሁለተኛ መከራከሪያ ስንመለከተው ፍርድ ቤቶቹ የደረሱበትን መደምደሚያ የሚያስለውጥ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ ከሙያ አንፃር አመልካች ከህግ አንፃር ማድረግ የሚገባቸውን የማስረዳትና ግልፅ የማድረግና የማማከር ግዴታና አከራካሪ ጉዳይ በሌለበት ክስና ክርክር ያለማቅረብ ግዴታ እንዳለበት በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 28 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በአመልካችና በወ/ሮ እታገኘሁ በሻህ መካከል በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የነበረው ክርክር የቦታ ይዞታ ክርክር ሲሆን በጉዳዩ አመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርበው ነበር፡፡ በክርክሩ ሂደት ክርክር የተነሳበት ቦታ የማናቸው ይዞታ እንደሆነ አጣርቶ እንዲገልፅ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳዳር ተጠይቆ ተከሳሽ ወ/ሮ እታገኘሁ የአመልካችን ቦታ አልፎ እንዳልያዘ እና በተቃራኒው አመልካች የወ/ሮ እታገኘሁን ህጋዊ ይዞታ አልፎ የያዘ መሆኑን በማረጋገጡ የአመልካች ክስ ውድቅ መሆኑን የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00076 ሀምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ከሰጠው ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ባይ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ከሙያ አንፃር እንደማያዋጣ የምክር አገልግሎት ከሰጠ ለአመልካች የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡ አመልካች የተጠሪን ምክር ወደጎን በመተው ይግባኝ አቅርቦ ይግባኙ የተሠረዘበት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ተገቢ የሆነ የሙያ ግልጋሎትና ምክር ለአመልካች የሰጠ በመሆኑ በውጤት ደረጃ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ምክንያቱ ተለውጦ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች ፡- 1. ወ/ሮ ሮዛ አባተ

2. አቶ ጌትነት አባተ

3. አቶ በላይ አባተ

4. አቶ ዮሐንስ አባተ ጠበቃ አቶ አበበ አሣመረ - ቀረቡ

ተጠሪ፡ - የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነገረፈጅ ሚካኤል ጌታቸዉ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/06/07 የሚገኝና ቁጥሩ 832 የሆነና በርካታ ክፍሎችን የያዘ ህንጻ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶና ተረክቦት እስከ ህዳር 1992 ዓ.ም እያከራየ ሲጠቀምበት የኖረ መሆኑን ከገለጸ በኋላ ህንጻውን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሰጠው ውሣኔ መሠረት ህዳር 24 ቀን 1992 ዓ.ም አስረክቤያቸው ነበር፡፡ ሆኖም ቤቱን ተከሣሾች እንዲከራዩ ውሣኔ የተሰጠው በሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑን በማረጋገጥ ተከሣሾች ለከሣሽ ቤቱን እንዲያስረክቡ ሀምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ወስኗል፡፡ ከሣሽ ከህዳር 1992 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን በማከራየት ያገኘው የነበረው ጥቅም ተቋርጦበታል፡፡ ተከሣሾች የተቋረጠውን ጥቅም /ኪራይ/ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ በማሰብ እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት በአመልካቾችና በሌሎች አራት ሰዎች ላይ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካቾች በተከሣሽነት ቀርበው ከሣሽ አላግባብ በልጽጋችኋል በማለት ያቀረበው ክስ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ከሣሽ ከሀምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም በኋላ ያለውን ኪራይ ከሚጠይቅ በስተቀር በውሣኔ ባለመብት ሆነን ቤቱን ከያዝንበት ከህዳር 1992 ዓ.ም ጀምሮ ኪራይ እንድንከፍል ያቀረበው ጥያቄ የህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት የለውም፡፡ተከሣሾች ቤቱን ከተረከብን በኋላ ብር 1,630,000 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰላሣ ሺ ብር/ በማውጣት ቤቱን ያሣደስን በመሆኑ ሊቻቻልልን ይገባል የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተከሣሾች ከሣሽ ቤቱን ካስረከበበት ህዳር 12 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን እስከተረከበበት ድረስ ባሉት 117 ወራት /አንድ መቶ አስራ ሰባት ወራት/ ቤቱን አከራይቶ ሲያገኝ የነበረውን ገንዘብና የተጨማሪ እሴት ታክስ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተደምሮበት ለከሣሽ የመክፈል ሀላፊነት አለባቸው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካቾችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች መስከረም 14 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ዳኝነት ከጠየቀበት ገንዘብ በላይ እንድንከፍል ወስኖብናል፡፡ አመልካቾች ቤቱን ለማሣደስ ከብር 1,630,000 እንዳወጣን በመግለጽ ያቀረብነውን የመቻቻል ጥያቄ በመቃወም ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይኸም ተጠሪ የአመልካቾችን ክርክር እንዳመነ የሚያስቆጥረው መሆኑ በፍታብሔር ሥነ-ሥነዓት ህጉ ተደንግጐ እያለ በተጠሪ በታመነው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ሣይሰጥበት ማለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የከፊል አገልግሎት ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት አገልግሎት አይደለም፡፡

ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፈል የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም ተጠሪ ቤቱን በፊት ከሚያከራይበት በተሻለ ዋጋ ያከራየው ቤቱን እኛ ከተረከብን በኋላ ስላሳደስነው ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች በእኛ በኩል የቀረቡ መከራከሪያዎችን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ታህሣስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራ ቀኙ የቀረበው የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካቾች ቤቱን በኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ውሣኔ ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ ቤቱን ለተጠሪ እንዲመልሱ እስከተወሰነበት ሀምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ተጠሪ ቤቱን በማካራየት ሊያገኝ ይችል የነበረውን ገቢ እንዲከፍሉ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በህጋዊ ውሣኔና ፍርድ ንብረት የተረከበ ሰው ባለመብት የሆነበት ውሣኔ ሲሰረዝ ወይም ሲሻር በኢትዮጵያ ህግ ያለበት ሃላፊነትና ግዴታ ምንድነው? የሚለውን ነጥብ መመለስ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 ይዘት ትርጉምና የተፈጻሚነት ወሰን አስመልክቶ ሰፊ የህግ ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጉዳይ ለመወሰን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 349 ድንጋጌዎች አግባብነት ያላቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 349/1/ ጉዳዩን በመጀመሪያ አይቶ የወሰነው ፍርድ ቤት ውሣኔ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተለወጠ ወይም የተሻረ ሲሆን በተለወጠው ወይም በተሻረው ፍርድ መሠረት የተወሰደ ንብረት የሚመለስበትና የተከራካሪ ወገኖች መብት እንዲስተካከል ፍርድ ቤቱ ተስማሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስሎ የታየውን ትዕዛዝ መስጠት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 349 ንኡስ አንቀጽ 2 በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 349 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን ለማስፈጸም ፍርድ ቤቱ የተወሰደ ገንዘብ እንዲመለስ ወለድ እንዲከፈል ፣ ኪሣራ እንዲወሰን ፣ ካሣና ያላግባብ የተወሰደ ጥቅም እንዲከፈል ወይም በፍርዱ መሻሻል ወይም መለወጥ ምክንያት የተካራካሪ ወገኖች መብትን ለማስተካከል ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችል መሆኑን ይደነግጋል፡፡

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 349 በመጀመሪያ ጉዳዩን ባየው ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሚለወጥበት ወይም በሚሻርበት ጊዜ ተፈጻሚ እንደሚሆን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 349 የመጀመሪያ ውሣኔ ወይም ፍርድ በይግባኝ ሲሻርና ሲለወጥ ብቻ ሣይሆን የመጀመሪያውን ውሣኔ የሰጠው ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ስልጣን በህግ የተሰጠው አካል የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 6 እና ሌሎች የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደገና አይቶ ቀደም ብሎ የሰጠውን ውሣኔ በሚያሻሽልበት ወይም በሚሽርበት ጊዜ ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ እንደሆነ የድንጋጌውን ርዕስ አቀራራጽና መሠረታዊ ግብና ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ቤቱን ለአመልካቾች እንዲያስረክብ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ወስኖ የነበረው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 6 መሠረት እንደገና በማየት ከዚህ በፊት የሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሰርዞታል፡፡

የኤጀንሲውን ውሣኔ የማስፈጸም ስልጣን የፍ/ቤት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 193/92 ተደንግጓል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ የማስረከብ ብቻ ሣይሆን ተጠሪ ቤቱን እያከራየ ያገኘ የነበረውን ጥቅም እንዲተኩ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 349 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2ን መሰረት ያደረገ በመሆኑ አመልካቾች ቤቱን በህጋዊ ውሣኔ ከተረከቡን በኋላ ተጠሪ ያቀረቡትን የቤት ኪራይ እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው ነው በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

አመልካቾች ቤቱን እስከሚያስረክቡበት ጊዜ ድረስ ያለው ሂሣብ ታስቦ እንዲከፈለው በግልጽ የዳኝነት ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ አመልካቾች ተጠሪ ከጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ በላይ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

2. አመልካቾች ቤቱን ከተረከብን በኋላ ቤቱን ለማደስ ያወጣነው ገንዘብ ሊቻቻልልን ይገባል በማለት ለስር ፍርድ በተጠሪ ለቀረበባቸዉ ክስ መልስ ሲሰጡ እንደተከራከሩ ከስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን የመቻቻል ጥያቄ በጭብጥነት በመያዝ ውሣኔ እንዳልሰጠበት ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የመቻቻል ጥያቄ ተጠሪን የከሣሽ ተከሣሽ አመልካቾችን የተከሣሽ ከሣሽ የማድረግ ውጤት ያለው እንደሆነ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 236 ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ በዚህ መንገድ የሚቀርቡ ክርክሮች በዳኝነት ታይተው ውሣኔ የሚሰጥባቸው በመጀመሪያ የዳኝነት ተከፍሎባቸው ሲቀርቡ እንደሆነ ከፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 215 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ አመልካቾች ቤቱን ከተረከቡት በኋላ ብር 1,630,000 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰላሣ ሺ ብር/ በማውጣት እንዳሣደሱ በመግለጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመቻቻል ጥያቄ ያቀረቡት ከላይ የጠቀስነው የሥነ-ሥርዓት ህግ በሚደነግገው መሠረት የዳኝነት ገንዘብ ከፍለውና ሥርዓቱን አሟልተው ስለ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካቾች የዳኝነት ገንዘብ ሣይከፍሉና ሥርዓቱን ሣያሟሉ ያቀረቡትን የመቻቻል ጥያቄ በጭብጥነት ሣይዙና ውሣኔ ሣይሰጡበት ማለፋቸው የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 67280

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- የኢ.ፌ.ዲ. ፍትሕ ሚኒስቴር - ዐ/ህግ አልጋነህ ተሾመ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. አቶ ተስፋዬ በርሄ - ቀረቡ

2. አቶ በለጠ ታፈሰ - ቀረቡ

3. ወ/ሪት ሕይወት ሲሳይ - ቀረቡ

4. አቶ ተሾመ አንጀሎ - የቀረበ የለም

5. አቶ መኳንንት ደግነት - ቀረቡ

በሰ/መ/ቁጥር 67275፣ 67276፣ 67277 እና 67281 የቀረቡት ጉዳዮች በዚህ መዝገብ በተያዘው ጭብጥ ተጠቃለው እንዲታዩ የተደረገ በመሆኑ መዛግብቱን አንድ ላይ አጣምረን መርምረን ተከታዩ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ለሚሠሩ ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 11/2/ ሥር በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ለጥብቅና ሙያ ፈቃድ የሚሰጥበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

ይህ አቤቱታ የቀረበው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ለተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ያለፈተና የጥብቅና ፈቃድ እንደማይሰጣቸው ባሳወቀው ውሣኔ ቅር በመሰኘት በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 29(1) መሠረት ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በተለያዩ መዛግብት አከራክሮ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሠጠውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪዎች ያለፈተና የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጣቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሟልና ሊታረም ይገባዋል በማለት ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውና ዲግሪ ከመያዛቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፊት የሥራ ልምድ ያላቸው ቢሆንም ከዲግሪ በኋላ የአምስት ዓመት የሥራ ልምድ የሌላቸው በመሆኑ በፌደራል ማናቸውም ፍርድ ቤት ለመከራከር የሚያስችል የጥብቅና ፈቃድ የመግቢያ ፈተና ለመቀበል አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀፅ 11(2) የግድ የሚላቸው ሆኖ እያለ ከዲግሪ በፊት ያለው የሥራ ልምድ ሊቆጠር ይገባል ተብሎ ትርጉም መስጠቱ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሠበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ የፅሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሠበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሠበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 21 ቀን 1996 ዓ.ም ከሮያል ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማ፣ ሚያዝያ 02 ቀን 2000 ዓ.ም ከሮያል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሕግ ባችለር ዲግሪ የተመረቁ ሁነው በሥራ ልምድ ረገድ ደግሞ ከግንቦት 01 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 1995 ዓ.ም፣ ከታህሳስ 01 ቀን 1997 ዓ.ም እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ነገረ ፈጅ፣ ከሐምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 03 ቀን 2002 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ዐቃቤ ሕግ ሁነው ያገለገሉ መሆኑን፣ 2ኛ ተጠሪ (አቶ በለጠ ታፈሰ) በበኩላቸው ሐምሌ 07 ቀን 1982 ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሕግ ዲፕሎማ፣ የካቲት 04 ቀን 2000 ዓ.ም ደግሞ ከሮያል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሕግ ባችለር ዲግሪ የተመረቁ ሁነው በሥራ ልምድ ረገድም ከሰኔ 14 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 21 ቀን 1987 ዓ.ም በኢትዮጵያ የቸርቻሮ ንግድ ድርጅት ኮርፖሬሽን ውስጥ በነገረ ፈጅነት፣ ከጥር 15 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥር 14 ቀን 1988 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ የቤት እና የቢሮ ዕቃዎች ድርጅት ውስጥ በነገረ ፈጅነት፣ ከታህሳስ 10 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 6 ቀን 1989 ዓ.ም ድረስ በእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን ውስጥ በነገረ ፈጅነት፣ ከሐምሌ 10 ቀን 1989 ዓ.ም እስከ መስከረም 27 ቀን 1984 ዓ.ም ድረስ በነገረ ፈጅነት፣ ከመስከረም 28 ቀን 1984 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1996 ዓ.ም የሕግ አማካሪ ቢሮ ተጠባባቂ ሓላፊ፣ ከነሐሴ 06 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም የሕግ አገልግሎት ተጠባባቂ ኃላፊ፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 08 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ የሕግ አገልግሎት ኃላፊ በመሆን በውሃ ሥራዎችና ኮንስትራክሽን ድርጅት ውስጥ የሠሩ መሆኑን፣ 3ኛ ተጠሪ (ሕይወት ሲሳይ) ደግሞ ሐምሌ 11 ቀን 1994 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሕግ ዲፕሎማ፣ እ.ኤ. አቆጣጠር ጁላይ 22 ቀን 2010 ደግሞ ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ በሕግ ባችለር ዲግሪ የተመረቁ ሲሆን በሥራ ልምድ ደግሞ ከነሐሴ 16 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ዐቃቤ ህግ ሁነው ያገለገሉ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን፣ 4ኛ ተጠሪ (አቶ ተሾመ አንጀሎ) ደግሞ በትምህርት ዝግጅት እ.ኤ.አ. ኖቬንበር 11 ቀን 2004 ዓ.ም ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሕግ ዲፕሎማ፣ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 01 ቀን 2009 ደግሞ ከአልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሕግ ባችለር ዲግሪ ያላቸው ሁነው በሥራ ልምድ ረገድም ከየካቲት 01 ቀን 1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 01 ቀን 1999 ዓ.ም በአማራ ክልል ውስጥ ዐቃቤ ሕግነት፣ ከሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 03 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በኢ.ፌ.ድ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር አቃቤ ሕግ ሁነው የሠሩ መሆኑ መረጋገጡን፣ 5ኛ ተጠሪ (አቶ መኳንንት ደግነት) በበኩላቸው ነሐሴ 16 ቀን 1993 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማ፣ ጳጉሜ 01 ቀን 2001 ዓ.ም ደግሞ ከሮያል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሕግ ባችለር ዲግሪ የተመረቁ መሆኑንና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሥራ ልምድ ረገድም ከታህሳስ 01 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ደግሞ የዐቃቤ ሕግ ረዳት፣ ከጥር 01 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ በዐቃቤ ሕግ ደረጃ አምስት፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በዐቃቤ ሕግ ደረጃ አራት፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ጥር 30 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ደግሞ በዐቃቤ ሕግ ደረጃ ሦስት የሠሩ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን ነው። ተጠሪዎች ያለፈተና የጥብቅና ፈቃድ ሊሰጠን ይገባል በማለት የሚከራከሩት የሥራ ልምዳቸው መያዝ ያለበት ከዲግሪ በሁዋላ ሳይሆን በፊት ያለውም ጭምር ነው በሚል ሲሆን አመልካች ደግሞ የሚከራከረው የሥራ ልምድ ሊያዝ የሚገባው ከዲግሪ ምረቃ በሁዋላ ያለውን ጊዜ ነው በሚል ተገንዝበናል።

ከላይ እንደተጠቀሰው የአመልካች ጥያቄ ያለፈተና ለማናቸውም የፌደራል ፍርድ ቤቶች የጥብቅና ፍቃድ ማግኘት የሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 11 (2) በተመለከተው ሁኔታ ሆኖ ይህ ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 8 እና 9 ለተመለከቱት ድንጋጌዎች ልዩ ድንጋጌ ነው በሚል ነው።

በአዋጅ ቁጥር 199/92 የፌደራል የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቷል። በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 8 (1) በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት የሚቻልባቸው ሁኔታዎች በግልፅ የተዘረዘሩ ሲሆኑ እነዚህም በሕግ ዲፕሎማ ያለው፣ የኢትዮጵያ መሠረታዊ ሕጐችን ማወቅ እንዲሁም አግባብነት ባለው ሙያ ቢያንስ 5 ዓመታት ልምድ ያለው ወይም በሕግ ዲግሪ የተመረቀ፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ሕጐችን የሚያውቅና በሙያው ቢያንስ የሁለት ዓመት ልምድ ያለው፣ ለፍትህ ሥራ አካሄድ መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣ ለደረጃው የሚሰጥን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ያለፈ፣ ምግባረ ብልሹነትን በሚያመላክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፣ የሙያ ኃላፊነት መድህን ዋስትና መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረበ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚሉ ሲሆኑ ለፈቃዱ መሰጠት ፈተና መቀመጥንና ማለፍን የግድ የሚል መሆኑ የአዋጁን አንቀፅ 8 ከአዋጁ አንቀፅ 11(1) ጋር አጣምረን በማንበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። የፌደራል ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት ደግሞ በአዋጁ አንቀፅ 9 ሥር የተመለከቱትን መስፈርቶች ማሟላት ቅድመ ሁኔታ ነው። በዚህ ድንጋጌ መሠረት የፌደራል ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ የሚሠጠው በሕግ ዕውቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም በሕግ ዲግሪ የተመረቀ፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ሕጐችን የሚያውቅና በሙያው ቢያንስ አምስት ዓመት ልምድ ያለው፣ ለፍትህ ሥራ አካሄድ መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣ ለደረጃው የሚሠጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ያለፈ፣ ምግባረ ብልሹነቱን በሚያመላክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣና፣ የሙያ ኃላፊነት መድህን ዋስትና መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ ላቀረበ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ነው። በአዋጁ አንቀፅ 8 እና 9 ድንጋጌዎች የጥብቅና ፈቃድ ደረጃውን የሚለዩ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሁኖ ፈቃዱ የሚሠጠው ለደረጃው የሚሠጠውን ፈተና ላለፈ ኢትዮጵያዊ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባሉ። በሌላ በኩል አዋጁ ያለፈተና የጥብቅና ፈቃድ የሚሠጥባቸውን ሁኔታዎች ለይቶ አስቀምጧል። ከእነዚህም በአዋጁ አንቀፅ 10 ሥር የተመለከተው የፌደራል ልዩ የጥብቅና ፈቃድ አንዱ ሲሆን ሌላው በአዋጁ አንቀፅ 11 (2) ሥር የተመለከቱ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ኢትዮጵያዊያን የሚመለከተው ነው። የአዋጁ አንቀፅ 11 ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ በአዋጁ አንቀፅ 8 እና 9 ሥር የተመለከቱትን መስፈርቶችን የሚያሟላ ማናቸውም ኢትዮጵያዊ የጥብቅና ፈቃድ የሚሠጠው የፈተና መመዘገቢያ ክፍያ ፈፅሞ የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ሲወስድና ፈተናውን ሲያልፍ መሆኑን የሕጉ መንፈስ ያስገነዝባል። የዚህ ንዑስ አንቀፅ ድንጋጌ ከተጠቀሰው አንቀፅ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ጋር ተጣምሮ ሲነበብም ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ጠያቂዎች በኢትዮጵያ ከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የትምህርት ተቋማት ውስጥ ቢያንስ በረዳት ፕሮፌሰርነት ወይም የመጀመሪያ ዲግሪ ኖሮት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ከዚያ በላይ በዳኝነት ወይም በዐቃቤ ሕግነት ወይም በታወቁ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በሕግ አማካሪነትና በነገረ ፈጅነት ቢያንስ አምስት ዓመት ያገለገለ ማንኛውም ሰው ሥራውን በለቀቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፈቃድ ማመልከቻ ካቀረበ የጥብቅና መግቢያ ፈተና እንዲወስድ አይገደድም በሚል በኃይለ ቃል የተቀመጠ ሲሆን ይህ ድንጋጌ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ክርክር ያስነሣው የሥራ ልምዱ ሊቆጠር የሚገባበትን ጊዜ አስመልክቶ ነው፡፡ አመልካች የሥራ ልምዱ ሊቆጠር የሚገባው ከዲግሪ ምርቃት በኋላ ነው በሚል የሚከራከር ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው የሚከራከሩት በዲግሪ ከመመረቃቸው በፊት የነበራቸው የሥራ ልምድ ሊያዝ እንደሚገባ ሕጉም ያሣያል፣ የአመልካች የቆየ አሠራርም ያስረዳል ይህ ሠበር ሰሚ ችሎትም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል በሚል ነው፡፡ እኛም የአከራካሪውን ድንጋጌ አቀራረፅ ይዘትና መንፈሱን አይተናል፡፡ በዚህም መሠረት የድንጋጌው የአማርኛው ቅጂ ፡-

" በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሕግ ቢያንስ በረዳት ፕሬፌሰርነት ወይም የመጀመሪያ ዲግሪ **ኖሮት** በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ከዚያ በላይ በዳኝነት ወይም በዐቃቤ ሕግነት ወይም በታወቁ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና በልማት ድርጅቶች በሕግ አማካሪነት እና በነገረ ፈጅነት ቢያንስ ለአምስት ዓመት ያገለገለ ማንኛውም ሰው ሥራውን በለቀቀ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፈቃድ ማመልከቻ ካቀረበ የጥብቅና መግቢያ ፈተና እንዲወስድ አይገደድም፡፡ " በሚል የተቀመጠ ሲሆን የድንጋጌው የእግንሊዝኛ ቅጂ ደግሞ፡-

"Any person who has taught law in Ethiopian higher educational institutions at least as an assistant professor or has served, holding degree in law, at least for five years as a judge or public prosecutor in federal first instance court or above, or as a legal consultant and attorney in known government organs and public enterprises **may not be** required to take an examination, where he applies for a license within a period of one year from the termination of his employment." በሚል የተቀመጠ ነው፡፡

ከላይ የተመለከቱትን መስፈርቶችን የሚያሟሉ ፈቃድ ጠያቂዎች ከፈተና ነጻ እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያት ሲታይም የሥራ ፀባይ በሙያው የዳበረ ልምድ የሚያስጨብጣቸውና ስለ ፍርድ ቤቶችም አሠራር በቂ እውቀት ለማግኘት በበቂ ሁኔታ የሚያስችላቸው መሆኑን በመታመኑ ስለመሆኑ የአዋጁ ሐተታ ዘ ምክንያት ያሣያል፡፡ ከላይ ከተመለከቱት የድንጋጌው አማርኛ እና እንግሊዝኛ ቅጂዎች ውስጥ እንደ ቅደም ተከተላቸው ....**ኖሮት** .... እና Holding a degree in law ..... የሚሉት ቃላትና ሐረግ ሲታዩ የሥራ ልምድ ዲግሪ ኖሮት እና ከዚህ ጊዜ በኋላ መቆጠር እንዳለበት ለትርጉም በማይጋብዝና ትርጉሙን በማያሻማ ሁኔታ ከትምህርት ዝግጅቱ በሁዋላ ያለው ጊዜ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ድንጋጌው በአቀራረፁ፣ በይዘቱና በመንፈሱ ሲታይ ግልፅ በመሆኑ ድንጋጌው ግልፅ እስከሆነ ድረስ ትርጉም የማያስፈልገው መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጐም ደንቦች የሚያሣዩን ጉዳይ ሲሆን ግልፅነት የለውም፣ ትርጉም ያስፈልገዋል ቢባል እንኳን ድንጋጌው በአዋጁ በአንቀፅ 8 እና 9 ጋር ከተቀመጡት ድንጋጌዎች እና የጥብቅና ሙያ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ አንፃር የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶችን ከፍ በማድረግ በዚህ አገልግሎት ዘርፍ ለሚሠማሩ ባለሙያዎች የብቃት ደረጃ ከሚሠጡት አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ለማድረግ ከሚለው የአዋጁ ዓላማ ጋር ተዛምዶ መተርጎም ያለበት ነው፡፡ የተጠቀሰው አዋጁ በአንቀፅ 8 እና 9

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥር የሚሠጠው የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈቃድ የትምህርት ዝግጅቱንና የሥራ ልምዱ መስፈርቶች ራሣቸውን ችለው የተቀመጡ መሆኑን የሚያሣይ ሲሆን የአገልግሎት ዘመኑ መቆጠር ያለበት በዲፕሎማ ወይም በዲግሪ ከተመረቁበት ጊዜ ጀምሮ አለመሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች አቀራረፅና ይዘት መሠረት የትምህርት ዝግጅቱና የሥራ ልምዱ ራሣቸውን ችለው የቆሙ መስፈርቶች ሁነው እኩል ዋጋ ያላቸው ሲሆን እነዚህን መስፈርቶችን የሚያሟላ ፈቃድ ጠያቂ ለደረጃው የሚዘጋጀውን ፈተና ማለፉ ከተረጋገጠ የጥብቅና ሙያ ፈቃድ እንደሚሰጠው ከአንቀፅ 11 (1) ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀፅ 8 እና 9 የተቀመጡት ድንጋጌዎች የሥራ ልምድ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ ኖሮት በሚል ያስቀመጡ ሣይሆን የሥራ ልምዱ ከትምህርት ዝግጅት ጋር በፊትም ቢሆን እንኳን ከትምህርት ዝግጅቱ እኩል ዋጋ የሚሠጠው መሆኑን ለያይተው የሚገልፁ በመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 11 (2) ሥር ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር አንድ ናቸው ሊባል የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ሕግ አውጪው የትምህርት ዝግጅቱንና የሥራ ልምዱን ለያይቶ እኩል ዋጋ በአንዱ አንቀፅ ከሰጠ በሁዋላ በተከታዩ ድንጋጌ ተመሣሣይ መንፈስ ያለው አንቀፅ ያስቀምጣል ማለት ትርጉም አልባ ከመሆኑም በላይ የሕጎችን ዐውደ ንባብ (contextual interpretation) **ትርጓሜ** ያልተከተለ፤ አዋጁ ውጤት እንዲኖረውና በአዎንታዊ መንገድ ታይቶ ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል የአተረጓጎም መንገድ ሆኖ አይገኝም፡፡ አንድ ድንጋጌ ግልፅነት የሚጎድለው መሆኑ ከታመነበት የድንጋጌው ትክክለኛ ትርጉሙ የሕጉን አጠቃላይ ድንጋጌዎችን በማየት ሊተረጎም እንደሚገባ ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀፅ 11 (2) ሥር የተመለከተው ድንጋጌ በአዋጁ አንቀፅ 8 እና 9 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እና ከሌሎች የአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ለተያዘው ጉዳይ ልዩ ድንጋጌ ሲሆን ጉዳዩ መገዛት ያለበትም በዚሁ ልዩ ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡ የሥር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአዋጁን አንቀፅ 11(2) ድንጋጌ ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በግልፅልነቱ በመቀበል ወይም ልዩ ድንጋጌ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ውጤት ባለው መልኩ በመተርጎም ተግባራዊ ማድረግ ሲገባው በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ የሚተገበረውን የሥራ ልምድ አያያዝ አሠራር በመመርኮዝ የሥራ ልምዱ ከዲግሪ ምርቃት በሁዋላ ሊሆን አይገባም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የድንጋጌውን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሰው ከአዋጁ አላማ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ በዋቢነት የጠቀሰውና በሠ/መ/ቁጥር 37375 ይህ ሠበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉምም በመዝገቡ የሰበር አመልካች የነበሩት ግለሰብ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ መግቢያ ፈተና ለመውሰድ እንዲፈቀድላቸው ቢያመለክቱም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የአመልካች ጥያቄና ማስረጃ በማገናዘብ በሰጠው ውሣኔ አመልካች ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓ.ም በሕግ ዲፕሎማ ከተመረቁ በኋላ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሠጣጥ እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀፅ 8/1/ መሠረት በሙያው 5 ዓመት ያላገለገሉ ናቸው በማለት የአመልካች ጥያቄን ሳይቀበለው በመቅረቱ በድንጋጌው የተመለከተው የሥራ ልምድና የትምህርት ዝግጅት እኩል ዋጋ ያላቸው የተለያዩ መስፈርቶች ከሚሆኑ በስተቀር ሁለቱም አንድ ጊዜ እንዲሟሉ ሕጉ የግድ አይልም፤ የሠበር አመልካቹ ለፈተና እንዲቀመጡ ሊፈቀድላቸው ይገባል ተብሎ የተሰጠ ትርጉም ነው እንጂ በአዋጁ አንቀፅ 11(2) ሥር የተመለከቱትን መስፈርቶች ተመልክቶ ትርጉም የሰጠበት መዝገብ አይደለም፡፡ በመሆኑም አንድ የሠበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉም በማናቸውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድደው ተመሣሣይ ለሆኑ ጉዳዮች ነው፡፡ የተያዘው ጉዳይ ይህ ሠበር ሰሚ ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሰ/መ/ቁጥር 37375 ን ከሰጠው የሕግ ትርጉም ጋር ተመሣሣይነት የሌለው በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የሰ/መ/ቁጥር 37375 ለውሣኔው በዋቢነት መጠቀሱ አግባብነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪዎች ለጠየቁት የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ በሕጉ የተመለከቱትን መስፈርቶች አላሟሉም በማለት አመልካች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች መስፈርቱን እንዳሟሉ በማድረግ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ውሣኔ በመሻሩ በሕጉ አተረጓጎምና አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 98707፣ 99105፣ 99561፣ 99563 ታህሳስ 14 ቀን 2003 ዓ.ም፣ በመ/ቁጥር 99156 ታህሳስ 19 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥተው በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀኑት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ያሳወቀው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሣኔ ግልባጩ ከሠ/መ/ቁ 67275፣ 67276፣ 67277 እና 67281 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/ም.ፋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 55238

መጋቢት 9 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድማ

አመልካቾች፡- 1. የየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር - ነገረ ፈጅ ፍፁም ካሣዬ ቀረቡ

2. ወ/ሮ አልማዝ ተረፈ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሕድአት ፍስሀዕዬን ከጠበቃ አቶ ሚሊዬን አበራ ጋር ቀረቡ

አንደኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 55238 ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የተደረገውን ክርክርና ሁለተኛ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 55153 ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ የተደረገውን ክርክር በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 11/5/ መሠረት በማጣመር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካቾች በተናጠል ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 29861 የአሁን ተጠሪ አመልካች የአሁን አመልካቾች ተጠሪዎች ሆነው ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ ጉዳዩን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደገና አይቶ እንዲወሰን ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራቀኞችንን ክርክር በመስማት ህዳር 24 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ መጋቢት 28 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ የአሁን ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግንቦት 22 ቀን 1994 ዓ.ም ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው ሁለተኛ አመልካች አዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 314 የሚገኘውን ቤቱን ከታህሣሥ 23 ቀን 1991ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ ብር 3,000/ሦስት ሺ ብር/ ኪራይ ለመክፈል ተስማምተው ተከራይተውታል፡፡ በውላችን መሠረት ያልከፈሉኝ ብር 117,000 /አንድ መቶ አሥራ ሰባት ሺ ብር/ የቤት ኪራይ ያለባቸው ስለሆነ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ፡፡

አንደኛው አመልካች ህግና መመሪያ ሣይከተል ቁጥሩ ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ቤት ለሁለተኛ አመልካች ነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ሸጧል፡፡ አመልካቾች በአንድነትና በነጠላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉና ቤቱንም ለቅቀው እንዲያስረክቡኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ቤቱን ለሁለተኛ አመልከች የሸጠው ቤቱ የኤርትራዊያን ንብረት መሆኑ በወቅቱ በተቋቋመው አጣሪ ኮሚቴ ተጣርቶ ስለቀረበለት መሆኑን ገልጾ የተጠሪ ክስ ተገቢ አይደለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ሁለተኛ አመልካችም መንግስት ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሠረት በህጋዊ መንገድ የገዛሁ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ የሚፈርስበትም ሆነ ቤቱን የምለቅበት ምክንያት የለም፡፡ የቤት ኪራይ ለተጠሪ ወኪል ከፍያለሁ የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች ለሁለተኛ አመልካች የተጠሪን ንብረት የሸጠው ከህግ ውጭ ነው፡፡ ስለዚህ ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ ያስረክቡ፡፡ የቤት ኪራይ ከነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን በአንድነትና በነጠላ አመልካቾች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት በመዝገብ ቁጥር 07632 ታህሣሥ 28 ቀን 97 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፣፣ አመልካቾች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው የከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 36844 ሀምሌ 12 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ሽሮታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት በመዝገብ ቁጥር 26905 የካቲት 2 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ስርዞታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር ችሎቱ የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመሻር የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 79183 አለ የሚሉትን የሚስትነትና የልጆቻቸውን የወራሽነት ማስረጃ በማስቀረብና ተገቢውን በመፈፀም እንደዚሁም ተገቢነት አላቸው የሚላቸውን ማስረጃዎች ሁሉ በማስቀረብ በግራ ቀኙ የመከራከሪያ ነጥቦች ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት በሰበር መዝገብ ቁጥር 29861 ጥር 14 ቀን 2001 ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጥር 14 ቀን 2001ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ጉዳዩን በማንቀሣቀሥ አጣርቶ እንዲወሰንላቸው የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሠረት መዝገቡን በማንቀሣቀሥ ሊቀርቡ ይገባቸዋል የሚላቸውን ማስረጃዎች በማስቀረብ 24-3-2002 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ ለመክሰስ የሚያስችል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም; አመልካቾች ክስ የቀረበበትን ቤት ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ወይስ አይገባም; ተጠሪ ክስ ያቀረቡበትን የኪራይ ገንዘብ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም; አመልካቾች ተጠሪ የጠየቁትን የቤት ኪራይ የመክፈል ሀላፊነት አለባቸው ወይስ የላበቸውም; የሚሉትን ጭብጦች መሥርቷል፡፡

ክርክር የተነሳበት ቤት በብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ስም የተመዘገበ ነው፡፡ ተጠሪ የሚች ብርጋዴር ጄኔራል ገብርአብ ወልዳይ ሚስት መሆናቸው በሥር ፍይል መዝገብ ቁጥር 79/83 ተረጋግጦ በፍርድ ተወስኗል፡፡ የቤቱ ስመ ሀብት በብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ስም የተመዘገበ ቢሆንም ተጠሪ ቤቱን በጋብቻ ያፈሩት የጋራ ሀብታቸው በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሥልጣን ባለው የመንግስት አካል የተሰጣቸው በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 470/94 አንቀፅ 5/4/ መሠረት ክስ ማቅረብ ይችላሉ በማለት ወስኗል፡፡ ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አንደኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ቤቱን ለሁለተኛ አመልካች የሸጥኩት የክልል 14 መስተዳድር ጽ/ቤት መጋቢት 15 ቀን 1992ዓ.ም በቁጥር አመ/አአ 73/6/53 በፃፈው ደብዳቤና ባወጣው መመሪያ መሠረት ነው በማለት የሚከራከር ቢሆንም መመሪያው በወቅቱ በመንግስት ውሣኔ ከአገር እንዲወጡ የተደረጉት ኤርትራዊያን ንብረት በጨረታ የሚሸጥበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ ብርጋዴር ጀኔራል ገብረአብ ወልዳይ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ግንቦት 23 ቀን 1983 ዓ.ም መሆኑና በኢትዮጵያ ውስጥ የተቀበሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ብ/ር ጀኔራሉ የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ወታደራዊ ባለሥልጣን የነበሩና ተጠሪ አሁንም ከኢትዮጵያ መንግስት ጡረታ በሚች ስም እየተቀበሉ መሆናቸው ተገልጿል፡፡ የቤቱ ባለንብረት ኢትዮጵያዊ ሆነው እያለ በተሣሣተ መረጃ አንደኛ አመልካች ቤቱ የኤርትራዊና በመንግስት ውሣኔ ከአገር እንዲወጡ የተደረጉ ሰው ንብረት እንደሆነ በመቁጠር ለሁለተኛው አመልካች የፈፀመው ሽያጭ ፈራሽ ነው፡፡

ስለዚህ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ የማስረከብ ግዴታና ሀላፊነት አለባቸው በማለት ወስኗል፡፡ ሦስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17068 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት ሁለተኛ አመልካች ከመጋቢት 20 ቀን 1992 በፊት የነበረውን የቤት ኪራይ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2024 መሠረት እንደተከፈለ የሚገመት በመሆኑ ሁለተኛ አመልካች ከመጋቢት 20 ቀን 1992 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 26 ቀን 1993 ዓ.ም ያሉትን አሥራ ስምንት ወራት ኪራይ ብቻ በብር 3,000 ተሰርቶ ብር 54,000 ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አራተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ከነሐሴ 28 ቀን 1993ዓ.ም ጀምሮ ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን የያዙት በሽያጭ ውል በመሆኑ ለተጠሪ ኪራይ የመክፈል ሀላፊነት የለባቸውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አንደኛ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን የሚጣራ ፍሬ ነጥብ የለውም በማለት በመዝገብ ቁጥር 89888 መጋቢት 28 ቀን 2002 በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 ሠርሿል፡፡ ሁለተኛ አመልካች በበኩላቸው ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙ የሚጣራ ነጥብ የለውም በማለት በመዝገብ ቁጥር 88806 መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አንደኛው አመልካች የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 89888 የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ቤቱን ለሁለተኛ አመልካች የሸጥነው መንግስት የኤርትራዊያን ንብረት እንዲሸጥ ባወጣው መመሪያ መሠረት ነው፡፡ ተጠሪ ሽያጩ ሲከናወን ኢትዮጵያዊ የነበሩ መሆኑን አላስረዱም፡፡ ተጠሪ ኢትዮጵያዊ ባለመሆናቸው በባንክ የተቀመጠውን ገንዘብ ከሚጠይቁ በስተቀር የቤት ሽያጩ ውሉ እንዲፈርስ መጠይቅ አይችሉም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በወቅቱ ያልወጣውን አዋጅ ቁጥር 270/94 በመጥቀስ መወሰኑ የህግ ስህተት አለበት በማለት ሚያዚያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የተከራከረ ሲሆን ሁለተኛ አመልካች በበኩላቸው የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 88806 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የሚች ብ/ር ጀኔራል ገብረአብ ሚስት ቢሆኑም ኤርትራዊ ዜግነት ያልያዙ እንደነበሩ ባላሥረዱበት ሁኔታ መንግስት ባወጣው መመሪያ መሠረት የገዛሁትን ቤት እንዳስረክብ መወሰኑ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የቤቱ ስመ ሀብት በገዥዎ በሁለተኛ አመልካች ስም የተዛወረና ውሉ የተፈፀመ በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ ኢትዮጵያዊ ስለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቱን ከገዛሁ በኃላ ከብር 500,000 በላይ ወጭ በማድረግ የግንባታ ሥራ አከናውኛለሁ፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሰበር ችሎቱን ትዕዛዝ በመከተል አጣርቶ አልወሰነም፡፡ የውጭ ዜጋ ንብረቱን ለኢትዮጵያዊ እንዲያስተላለፍ ማስገደድ እንደሚችሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 390 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 391 የተደነገገ በመሆኑ አንደኛ አመልካች ቤቱን ለእኔ ለመሸጥ ሥልጣን አለው ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በመሻር የተፈፀመውን የህግ ስህተት እንዲያርሙልኝ በማለት ከዚህ መዝገብ ጋር በተጣመረው በሰበር መዝገብ ቁጥር 55153 ሚያዚያ 8 ቀን 2002ዓ/ም ዕፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ አመልካቾች በተናጥል ባቀረቡት መልስ ቤቱ የሚች ብ/ር ጀኔራል ገብረአብ ወልዳይ ቤት ነው፡፡ ሚች የኢትዮጵያ የጦር መኮንንና ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ መንግስት የጡረታ አበል እየከፈለኝ መሆኑን በቂ ማስረጃ አቅርቤለሁ፡፡ እኔም የሚች ሚስት መሆኔን በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች የኤርትራዊ ንብረት ነው ከሚሉት ውጭ ቤቱ በመንግስት ውሣኔ ከአገር የተባረሩ ኤርትራዊ ንብረት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ስለሆነም አንደኛ አመልካች ለሁለተኛ አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል ምክንያትና ሥልጣን ሣይኖረው ሚች ብ/ር ጀኔራል ገብረአብ ወልዳይ በመንግስት ውሣኔ ከአገር የተባረሩ ኤርትራዊ ናቸው በሚል ምክንያት ቤቱን መሸጡ የተረጋገጠ ስለሆነ ሽያጩ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ መሠታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ስኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በተናጠል የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

አመልካቾችና ተጠሪ ከዚህ በፊት ያደረጉት ክርክር ያለፈበት ሂደትና ጉዳዩ የተመለሰለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔና ግራቀኙ በተጣመሩት መዝገቦች በሰበር ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አንደኛ አመልካች በቀድሞው ወረዳ 16 ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 314 ለሁለተኛ አመልካች ለመሸጥ ያደረገው ውል ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም; የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ የሆነው የቤት ቁጥር 314 አንደኛ አመልካች ነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ለመሸጥ ህጋዊ መሠረት ያደረገው የክልል 14 መስተዳድር ጽ/ቤት መጋቢት 15 ቀን 19992ዓ.ም በቁጥር አመ/አስ 73/6/53 ያፃፈውን ደብዳቤና በመንግስት ከአገር እንዲወጡ የተደረጉ ኤርትራዊያን ንብረት ስለሚሸጥበት ሁኔታ የወጣውን መመሪያ ነው፡፡ መመሪያው አስተዳደሩ በመንግስት ውሣኔ ከአገር እንዲወጡ የተደረጉ ኤርትራዊያን ንብረት እንዲሸጥ ሥልጣን የሚሰጥ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ተጠሪ የሚከራከሩበትን ቤት ለሁለተኛ አመልካች የሸጠው ቤቱ በስማቸው የተመዘገበው አቶ ገብረአብ ወልዳዊ ከአገር የተባረሩ ኤርትራዊ ናቸው በማለት እንደሆነ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች በማስረጃነት ያቀረበው ሰነድ ጭምር ተረጋግጣል፡፡

አንደኛ አመልካች ከአገር የተባረሩ ኤርትራዊ ናቸው በማለት ቃለ ጉባኤ ይዞ ንብረታቸው እንዲሸጥ የወሰነባቸው ብርጋዴል ጀኔራል ገብረአብ ወልዳዊ ኤትርራዊ ዜግነት የሌላቸው ኢትዮጵያዊ የጦር መኮንን እንደነበሩና ግንባት 23 ቀን 1983 ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ይህም አንደኛ አመልካች በህግ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ ከሁለተኛ አመልካች ጋር የቤት ሽያጭ ውል ያደረገ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል ተጠሪ የሚች ብርጋዴር ጀኔራል ገብረአብ ወልዳይ ሚስት መሆናቸውንና የኢትዮጵያ መንግስት የጡረታ አበል እስካሁን ድረስ የሚከፍላቸው መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በመንግስት ውሣኔ ከአገር የተባረሩ ኤርትራዊ መሆናቸውን አመልካቾች ለበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የሌላ አገር ዜግነት ያላቸው መሆኑን የሚያስረዳ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የመታወቂያ ካርድ የተሰጣቸው መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ" የሚል መታወቂያ የሚሰጠው አንድ ሰው በአዋጅ ቁጥር 270/1994 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2ን ለሚያሟላ የውጭ አገር ዜጋ መሆኑ በደንብ ቁጥር 101/96 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደንግጋል፡፡ የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራን ዜግነት መርጦ የያዘ ሰው "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ" የሚለውን ትርጉም የማይሸፍን ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 270/94 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ "የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጋ" መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የመታወቂያ ካርድ ከኢፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋገጡ በመሆኑ የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራ ዜግነት መርጠው ይዘው ያልነበረ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነው፡፡ ስለሆነም አንደኛ አመልካች በህግ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ ንበረትነቱ የኢትዮጵያዊው ብርጋዴር ጀኔራል ገብረአብ ወልዳይና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑት የተጠሪን ንብረት ለሁለተኛ አመልካች ለመሸጥ ነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም ያደረገው የሽያጭ ውል ፈራሽና ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ህገ መንግስቱ ለግል ንብረት ባለቤትነት በአንቀጽ 40/1/ የሰጠውን ጥበቃና ዋስትና መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች ቤቱን ከመግዛታቸው በፊት ያሉትን አስራስምንት ወራት የቤት ኪራይ ሁለተኛ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጠው ውሣኔም በሁለተኛ አመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገውን የኪራይ ውል መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አንደኛ አመልካች በዚህ መዝገብ የሸጠውና ክርክር ያቀረበበት ኢትዮጵያዊ ዜግነት የነበራቸውን ብርጋዴል ጀኔራል ገብረአብ ወልዳይንና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑትን የተጠሪን የጋራ ሀብት መሆኑ ስለተረጋገጠ ይህ የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17986 አከራክሮ ውሣኔ ከሰጠበት ጉዳይ ጋር ተመሣሣይነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በሰበር መዝገብ ቁጥር 17986 የተደረገው ክርክርም ሆነ የሰበር ችሎቱ የሰጠው ውሣኔ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ይህንን መዝገብ በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች ነሐሴ 28 ቀን 1993ዓ.ም ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ በመሆኑ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠውን ውሣኔ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛ አመልካች ቤቱን ከገዛሁ በኃላ ከብር 500,000/አምስት መቶ ሽ ብር/ በላይ ወጭ በማድረግ የግንባታ ሥራ አከናውኛለሁ በማለት በሰበር አቤቱታቸው ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ ሁለተኛ አመልካች ቤቱን ከተረከቡ በኃላ ያደረጉት ግንባታ ስለመኖሩ በሥር ፍርድ ቤት አንስተው ያልተከራከሩ መሆኑን የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 07632 በማስቀረብ ለመረዳት ችለናል፡፡ ሁለተኛ አመልካች በሥር ያልተከራከሩበትን አዲስ ፍሬ ጉዳይ በሰበር ደረጃ ማንሳታቸው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ የሚጥስ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በመንግስት ውሣኔ ከአገር እንዲወጡ የተደረጉ ኤርትራዊያን ንብረትን ለመሸጥ ያወጣውን መመሪያ ይዘትና የተፈፃሚነት ወሰን ያገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 07632 ህዳር 24 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 88806 እና በመዝገብ ቁጥር 89888 መጋቢት 28 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 01 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- - ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ሻምበል ተሾመ ደምሴ - ጠበቃው ያለለት ተሾመ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ሕግ ገበያው ስማቸው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ መ/ቤት የዲስኘሊን ኮሚቴ የሰጠው የዲስኘሊን ውሣኔ ሲሆን ውሣኔውም ለተጠሪ መ/ቤት የበላይ ሀላፊ ቀርቦ ይፈፀም በመባሉ ምክንያት ለከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ በአሁኑ አመልካች ይግባኝ ጠያቂነት ቀርቦ ከፍተኛው ፍ/ቤትም መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዝጋት ይግባኝ ባዩን በማሠናበቱ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ለዲስኘሊን ኮሚቴ ውሣኔ መነሻ የሆነውን አቤቱታ ለተጠሪ መ/ቤት ያቀረቡት ወ/ሮ ዮላንዳ ካፑሲ ሲሆኑ የአቤቱታውም ፍሬ ቃል ከአቶ ሩፋኤል ዶልጋውዲ ከተባለው ጋር ባልና ሚስት ሆነን ከቆየን በኋላ በመካከላችን በተፈጠረው አለመግባባት በፍ/ቤት ጉዳያችን እየታየ ባለበት ወቅት ባለቤቱ የጋራ ሃብታችንን በሙሉ በእጁ በማድረጉ የንብረት ክፍፍሉ እስከሚደረግ ድረስ ለወደፊት ከንብረቱ ከሚደርሰኝ የሚታሰብ በየወሩ ብር 10,000 እንዲከፍለኝ ተወስኖልኝ ሲከፍለኝ ከቆየ በኋላ ተጠሪው /የአሁኑ አመልካች / የባለቤቱ ጠበቃ በመሆናቸው ለፍ/ቤቱ የካቲት 02 ቀን 1999 ዓ/ም በሰጡት የመልስ መልስ እኔ “ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ግሩፕ” የሚባል የግል ድርጅት ሳይኖረኝ እንዳለኝ በማስመሠል ሐሰተኛ የቢዝነስ ካርድ በማዘጋጀት አቅርበው በፈፀሙት ህገወጥ ድርጊት ከፍተኛ እንግልትና ጉዳት ያደረሱብኝ ስለሆነ በዲስኘሊን ኮሚቴ ይጠየቅልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተጠሪውም /የአሁኑ አመልካች/ በሰጡት መልስ የአቤቱታ አቅራቢዋ ባለቤት የቢዝነስ ካርዱን ስለሰጣቸው ለፍ/ቤቱ እንዳቀረቡ ገልፀዋል፡፡

የሥር የዲስኘሊን ኮሚቴውም የአሁኑ አመልካች የፌዴራል ፍ/ቤቶች የጠበቆች ሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 29/2/ እና አንቀጽ 56/4/6/ ላይ የተደነገጉትን የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች ጥሰዋል በማለት በብር 10,000 /አሥር ሺህ / እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠሪ መ/ቤት የዲስኘሊን ኮሚቴ ውሣኔና በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ያሉ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- የተጠሪ የዲስኘሊን ኮሚቴ ለውሣኔው መሠረት ያደረጋቸው ድንጋጌዎች ላይ ያሉት ነጥቦች ስለመኖራቸው አልተረጋገጠም ፣
- የዲስኘሊን ኮሚቴው ማስረጃዬን ሳይሠማና ሳይመረምር ውሣኔ መስጠቱ ያለአግባብ ነው፣
- በደንበኛዬ ትክክለኛ መሆኑ ተገልጾ የተሰጠኝ ሰነድ ሀሰተኛ መሆን አለመሆኑን የማጣራት ግዴታ የሌለብኝ ሆኖ ሣለ ጥፋተኛ መባሌ ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ለአመልካች የሰበር አቤቱታ ተጠሪው በሰጠው መልስ ለሥር የዲስኘሊን ኮሚቴ አቤቱታው እንዲታይ የጠየቁት ግለሰብ የንግድ ድርጅት ያላቸው ስለመሆኑ ምንም አይነት ህጋዊ ሠነድ ከአመልካች ደንበኛ ሳይቀርብላቸውና በቢዝነስ ካርዱ የተመለከቱት ዝርዝር ሁኔታዎችን በአግባቡ ሳያረጋግጡ አመልካች ካርዱን ለፍ/ቤቱ በማቅረብ ለግለሰቧ የሚከፈለው ቀለብ እንዲቋረጥ ማድረጋቸው ከቅን ልቦና ውጪ የፈፀሙት መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሣለ አመልካች የሠነዱን ሀሰተኛነት አላውቅም ያሉት ከተጣለባቸው ሙያዊ ግዴታ አንፃር ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች በሰበር ቅሬታቸው ማስረጃቸው ያልተሰሙ መሆናቸውን ቢገልጹም የተጠሪ የዲስኘሊን ኮሚቴ 7 የአመልካች ማስረጃዎችን አቅርቦ የሰማ በመሆኑ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት የዲስኘሊን ኮሚቴውም ሆነ የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በውሣኔያቸው የፈፀሙት የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም አመልካች በተከሰሱበት የዲስኘሊን ክስ ጥፋተኛ ናቸው ተብለው በገንዘብ የተቀጡት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የተጠሪ መ/ቤት የዲስኘሊን ኮሚቴ ውሣኔ እንደሚያመለክተው አመልካች ጠበቃ ሆነው ሲከራከሩ የነበሩት የወ/ሮ ዩላንዳ ካፑሲ ባለቤት ወክሎአቸው ሲሆን አመልካች የተባለውን የቢዝነስ ካርድ ያገኙት ከደንበኛቸው መሆኑን እና ለፍ/ቤቱ ግለሰቧ የንግድ ድርጅት እንዳላቸው ካርዱን በማቅረብ ጭምር የገለጹት ይኸው ደንበኛቸው በሰጡት መረጃ መሠረት ነው ብሏዋል፡፡ ይበሉ እንጂ ደንበኛው ያቀረባቸውን ማስረጃዎች ባለሙያው /ጠበቃው/ እንዳለ ተቀብሎ ለፍ/ቤት ማቅረብ አለበት? ወይስ የለበትም የሚለውን ነጥብ መመለስ ተገቢነት ያለው ይሆናል፡፡ ለዚህም በመጀመሪያ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 92/1/ን መመልከት የሚገባ ሲሆን የተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ስለማናቸውም ጉዳይ የሚቀርብ አቤቱታ በሌላ ሁኔታ እንዲቀርብ የሚያዝ ድንጋጌ ከሌለ በቀር በአቤቱታው ማመልከቻ ላይ የተገለፀው ነገር አቤት ባዩ ወይም ነገሩን የሚያውቅ ሌላ ሰው በአቤቱታው ግርጌ ይህ የቀረበው አቤቱታ እውነት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ይላል፡፡ ከዚህ ከህጉ መንፈስ መረዳት እንደሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ያቀረበው አቤቱታ እውነት ስለመሆኑ የማረጋገጥ የህግ ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ ቢሆን ደንበኛቸውን በመወከል ግለሰቧ የንግድ ድርጅት ያላቸው ስለመሆኑ አመልካች ካርዱን ጭምር ይዘው ለፍ/ቤት የቀረቡ ሲሆን ይህ አለ የተባለው የንግድ ድርጅት ስለመኖሩ ደግሞ አስቀድሞ በእርግጠኝነት ሊያውቁ ይገባ ነበር፡፡

ይህ ሆኖ ሣለ አመልካች በእርግጠኛነት የሚያውቁትን ጉዳይ ብቻ ክርክሩን ለያዘው ፍርድ ቤት ማቅረብ ሲገባቸው የቢዝነስ ካርዱን ሐሰተኛ መሆንና አለመሆን የማጣራት ግዴታ የለብኝም ያሉት ከተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ህግ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 3 በመርህ ደረጃ ማንኛውም ጠበቃ በተለይም ለደንበኛው፣ ለሌሎች የህግ ሙያተኞችና ተከራካሪ ወገኖች፣ ለፍርድ ቤት፣ ለሙያው እና በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ያለበትን የሙያ ሃላፊነት በቅንነት፣ በታማኝነት እና በእውነተኛነት መውጣት እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን በደንቡ አንቀጽ 29/2/ ደግሞ ማስረጃን ማሳሳት ወይም ሌሎች ሰዎች ይህን መሠል አድራጐት እንዲፈጽሙ መምከር ወይም መርዳት የተከለከለ ተግባር እንደሆነ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በደንቡ አንቀጽ 56/4/ ሆን ብሎ ፍርድ ቤትን የሚያሳስት ወይም የተጋነነ ጽሁፎችንና ንግግር ማድረግ ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 56/6/ እንደተደነገገው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ማስረጃ አግባብነት እንዳለው አስመስሎ ማቅረብ የማይፈቀዱ ድርጊቶች እንደሆኑ ተጠቅሰዋል፡፡

ይህ ሆኖ ሣለ አመልካች ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 92/1/ ውጪ እና ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ በሚቃረን መልኩ የደንበኛቸው ባለቤት የነበሩት ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ማሩኝ የሚባል የንግድ ድርጅት ሳይኖራቸው አላቸው በማለት በሐሰት የተዘጋጀ የቢዝነስ ካርድ ለሥር ፍ/ቤት በማቅረብ ፍ/ቤቱን በማሳሳት ከቅን ልቦና ውጪ ለግለሰቧ እንዲከፈላቸው ተወስኖ የነበረውን ቀለብ እንዲቋረጥ ማድረጋቸው በተጠሪ የዲስኘሊን ኮሚቴ በማስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ አመልካችንም ባቀረቡአቸው የመከላከያ ማስረጃዎች ማስተባበል ባለመቻላቸው ጥፋተኛ ተደርገው የቅጣት ውሣኔ የተላለፈባቸው እንዲሁም የተጠሪው የዲሲኘሊን ኮሚቴ ውሣኔ በይግባኝ ቀርቦ መጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የተጠሪ መ/ቤት የዲስኘሊን ኮሚቴ በ14/05/2002 ዓ/ም ባደረገው ስብሰባ የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 90784 በቀን 26/04/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች የመቀጮ ገንዘብ ብር 10,000 /አሥር ሺህ / ለመንግስት ገቢ እንዲያደርጉ የተወሠነው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች ፦ ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

አመልካች፦ እነ አቶ ግርማይ ካሕሳይ - ጠበቃ ዜና ደባሱ - ቀረቡ

ተጠሪ፦ አቶ ሥዩም ታደሰ ሐጎስ - ወኪል ሂሩት ታደሠ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ እጣው ከመድረሱ በፊት አባልነትን ያቋረጠ የእቁብ አባል ለእቁብ የከፈለው ገንዘብ ይመለስልኝ የሚል ጥያቄ ሲያቀርብ ኃላፊነት ያለበትን ወገን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች እና ቀድሞ የእቁቡ ሰብሳቢ ነበሩ በተባሉ በአንድ ግለሰብ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ተጠሪ አመልካቾች በኃላፊነት በሚሰሩትና በየሳምንቱ በሚጣል እቁብ ውስጥ ማህበርተኛ ሁነው በመመዝገብ 63,300.00(ስልሳ ሦስት ሺህ ሶስት መቶ ብር) መክፈላቸውን፣ ይሁን እንጂ እቁቡ ሳይጠናቀቅ መክፈል ማቆማቸውን፣ ለአመልካቾች የከፈሉት ገንዘብ እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቅርበውም ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ ብር) ከፍሏቸው ቀሪውን ብር 33,300.00(ሰላሳ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ብር) እቁቡ ሲጠናቀቅ እንደሚከፍሏቸው አመልካቾች የፈረሙላቸው መሆኑን፣ ሆኖም ለመክፈል አመልካቾች ከፈረሙላቸው በኋላ ቀሪውን ገንዘብ እንዲከፍሏቸው ተጠሪ ጥያቄ ቢያቀርቡላቸውም አመልካቾች ያልፈፀሙላቸው መሆኑን ገልፀው ለእቁቡ ከፍለው ያልተመለሰላቸውን ብር 33,000.00 (ሰላሳ ሶስት ሺህ ብር) በአንድነትና በነጠላ ከእነ ሕጋዊ ወለዱ እንዲሁም ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት ግለሰብም ክሱ በቀረበበት ወቅት ከእቁቡ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑንና ጉዳዩ የሚመለከተው የአሁኑን አመልካቾችን መሆኑን ገልፀው በራሳቸው ላይ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን የተከራከሩ ሲሆን የአሁኑ አመልካቾችም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችንና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በመከራከሪያነት ያቀረቡት ነጥብም ተጠሪ አመልካቾችን ለመክሰስ ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ መብት የሌላቸው መሆኑን፣ በእቁቡ መተዳደሪያ ደንብም አመልካቾች ያለባቸው ኃላፊነትም የተጠሪን ክስ አይነት አለመሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ የተከራከሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የአመልካቾችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ በማድረግ በዋናው ጉዳይ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የስር 1ኛ ተከሳሽን ክክሱ ነጻ ሲያወጣ፣ የአሁኑ አመልካቾችን ግን ገንዘቡን ለመክፈል መፈረማቸው ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ለክሱ ኃላፊ አድርጎ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ከተለየዩ ወጪና ኪሣራ ጋር በአንድነት እና በነጠላ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር.337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለተጠሪ የእቁቡን ገንዘብ ለመክፈል ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ ሳይኖርባቸው በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በእቁቡ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 7.4 ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካቾች በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የጎደለውን የእቁብ አባል ክስ መስርተው እየተከራከረ መሆኑ ከታወቀ ከዚህ በማለፍ የመክሰስ ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ በደንቡ ተሸፍኗል? ወይስ አልተሸፈነም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ያለውን አሰራርና ልምድ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት የፅሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ተጠሪ አባል ሁነው ገንዘብ መክፈላቸው በተረጋገጠው የእቁብ ማህበር ውስጥ በኃላፊነት ቦታ የሚሰሩ መሆኑ፣ ተጠሪ ለእቁቡ ከከፈሉት ገንዘብ ውስጥ ብር 30,000.00 ተመልሶላቸው ቀሪ ብር 33,000.00 ያልተከፈላቸው መሆኑን፣ ይህንኑ ቀሪ ገንዘብ ደግሞ አመልካቾች ለተጠሪ ለመክፈል በፊርማ ያረጋገጡላቸው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡ ነጥቦች መሆናቸውን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾች ግዴታ ምንጩ የክፍያ ሰነዱ ላይ የተቀመጠው ፊርማቸው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪን ክርክር ያላስተባበሉ መሆኑንም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልፅ ያሳያል፡፡ አመልካቾች ለተጠሪ ገንዘቡን እንከፍላለን በማለት ግዴታ መግባታቸው ከተረጋገጠ የማይጠየቁበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሲሆን ከኃላፊነት ነጻ ያደርገናል በማለት የሚጠቅሱት የእቁቡ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 7.4 ሙሉ ይዘቱ ሲታይም ሙሉ በሙሉ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ያለባቸው የእቁቡ ፀሐፊና ዋናው ተቆጣጣሪ መሆናቸውን የሚጠቅስ ሁኖ አግኝተናል፡፡ 1ኛው አመልካች የእቁቡ ፀሐፊ፣ ሁለተኛው አመልካች ደግሞ የእቁቡ ተቆጣጣሪ የመሆናቸው ጉዳይ ደግሞ በሚገባ የተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡ አመልካቾች ራሳቸው በፊርማቸው አረጋግጠው በሰጡት የሰነድ ማስረጃ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ከመረጋገጡም በላይ ከላይ እንደተጠቀሰው የእቁቡ መተዳደሪያ ደንብም ቢሆን ይዘቱ ሲታይ ከተጠያቂነትና ኃላፊነት ነፃ የማያደርጋቸው ሲሆን አመልካቾች ግዴታውን ባልተወጣው የእቁቡ አባል ላይ ክስ መመስረታቸው በውጤት ደረጃ ተጠሪ አመልካቾችን እንዳይጠይቁ የሚያደርግ አይደለም፡፡ ግዴታውን ባልተወጣው ግለሰብ ላይ አመልካቾች ክስ መመስረታቸውን በስር ፍርድ ቤት ገልፀው ይኸው ተረጋግጦ ጥያቄአቸው ውድቅ መደረጉ ወይም ግዴታውን አልተወጣም የተባለው ግለሰብ ተጠሪ በመሰረቱት ክስ ውስጥ የክርክሩ ተካፋይ ያለመሆኑ ጉዳዩ በአንድ ላይ ቢታይ የክርክሩን አመራር ተገቢ ያደርገው ነበር ከሚባል በስተቀር ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በሚኖራቸው መብት፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች ደግሞ ለተጠሪ በሚወጡት ግዴታ ለሚመለከተው ሰው የተወጡትን ግዴታ እንዲተካላቸው ለመጠየቅ ከሚኖራቸው መብት አንፃር ሲታይ የመብት መጣበብን ሊያስከትል ይችላል ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የሌለው በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 54567

የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች ፦ ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፦ የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት - ዓ/ህግ መቅጫ ለገሠ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፦ 1. የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አ.ማ - ነ/ፈጅ ኃይለእየሱስ ደምሴ - ቀረቡ፡፡

2. ሮማን ገብሩ - የቀረበ የለም፡፡

3. ማሩ አላምረው - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍትሐብሔር ክርክር ሂደት በፍርድ ቤት የታገደ ንብረት እግዱ ተግባራዊ በሆነበት ጊዜ ተሸጦ ሲገኝ እግዱን ያሰጠውና የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን ስላለው መፍትሔ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በአመልካች ጠያቂነት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ የተደረጉ ናቸው፡፡ የስር ከሳሽ የክስ ይዘትም አቶ ብርሃኑ ታርቆ የተባሉ ግለሰብ በከሳሽ ድርጅት በቋሚ ሰራተኛነት ተቀጥረው ከ1988 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ በገንዘብ ያዥነት ሲሰሩ በነበረበት ጊዜ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በመዘንጋትና አጋጣሚውን በመጠቀም ብር 28,794.70 /ሃያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና አራት ብር ከሰባ ሳንቲም/ በማጉደላቸውና ለግል ጥቅም በማዋላቸው ይህንን ገንዘብ እንዲከፍሉ ለምዕራብ ጎጃም መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ በመመስረት የመ/ቁጥር 2312 ተከፍቶ ተከሳሽ አቶ ብርሃኑ ታርቆ ተጠርተውና በጉዳዩ ላይ ተከራክረው የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው ፍርድ ቤት መጋቢት 08 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቶ ብርሃኑ ታርቆን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ዋናውን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለዱና ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍል ውሣኔ መስጠቱን፣ ለዚህ ፍርድ ማስፈፀሚያ ይሆን ዘንድ የአቶ ብርሃኑ ታርቆን ቤት የፍርድ ባለመብት የሆነው ድርጅት በዋናው ክርክር ጊዜ እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ አሰጥቶ ለባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የእግድ ትዕዛዙን ያደረሰ ቢሆንም እግዱ ተጥሶ ቤቱን የፍርድ ባለዕዳው ሽጦ መገኘቱን ገልጾ ማዘጋጃ ቤቱ የፍርዱን ገንዘብ እንዲተካለት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም በቤቱ ላይ እግድ መሰጠቱን ሳይክድ ሁኔታው የተከሰተው በሰራተኞች ጥፋት መሆኑን ገልጾ መስሪያ ቤቱ ኃላፊነት እንደሌለበት፣ ሰራተኞቹም ወደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሩ እንዲገቡለት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም በአሁኑ አመልካች ጥያቄ መነሻነት በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ተደርጐ ባቀረቡት መከራከሪያ ለጉዳዩ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በሁዋላ የአሁኑን አመልካች ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለ1ኛ ተጠሪ የፍርዱን ገንዘብ ያህል እንዲከፍል በማለት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን ግን በነፃ በማሰናበት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙንና የሰበር አቤቱታውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም ጥፋቱ ሰራተኛ የሆኑት የ2ኛ እና የ3ኛ ተጠሪዎች ሁኖ እያለ መስሪያ ቤት የሆነው አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ መባሉ ተገቢነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ኃላፊነት አለበት ቢባል ደግሞ የኃላፊነት መጠኑ ሊሆን ይገባ የነበረው ቤቱ የተሸጠበት የገንዘብ መጠን እንጂ 1ኛ ተጠሪ በፍርድ ከአቶ ብርሃኑ ታርቆ እንዲከፈለው የተወሰነውን መጠን ያህል ሊሆን አይገባም የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ ተብሎ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለ1ኛ ተጠሪ ይክፈል ተብሎ የመወሰኑ ሁኔታ ተገቢነት ያለው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ ተጠሪ ከአቶ ብርሃኑ ታርቆ የሚፈልገው የገንዘብ መጠን በፍርድ የተረጋገጠ ሲሆን በዋናው ክርክር ጊዜ ደግሞ የአቶ ብርሃኑ ታርቆ ንብረት የሆነውን ቤት በፍርድ ቤት በማስከበር የእግዱን ትዕዛዝ ለአሁኑ አመልካች አድርሶ ባለበት ሁኔታ የቤቱ ባለቤትና የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት ግለሰብ ቤቱን ለሌላ ሰው ራሳቸው ሸጠው በመገኘታቸው 1ኛ ተጠሪ ፍርዱን ሊያስፈጽም የሚችለውን የአቶ ብርሃኑ ታርቆን ንብረት ሊያገኝ ያልቻለ መሆኑን፣ እንዲሁም የቤቱ ሽያጭን በተመለከተ ተገቢ ነው የሚለውን ክርክር 1ኛ ተጠሪ አቅርቦም እስከ መጨረሻው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን፣ የአሁኑ አመልካች ሃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከረውም እግዱ ለመስሪያ ቤቱ መድረሱን በመካድ ሳይሆን ተግባሩ የተፈፀመው ሰራተኛ በሆኑት የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጥፋት ነው በማለት መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው የእግድ ትዕዛዙ ደርሶት እያለ ይህንኑ ጥሶ ቤቱ እንዲሸጥ አድርጐአል፣ የሰራተኞች ጥፋት ስለመኖሩም አላስረዳም በሚል ምክንያት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ አጥብቆ የሚከራከረው ጥፋቱ በሰራተኞች የተፈፀመ እንጂ በመስሪያ ቤቱ የተፈፀመ ነው ሊባል የሚችል አይደለም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የአመልካች ሰራተኛ በሆኑት የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የተፈፀመ ጥፋት ስለመኖሩ አመልካች ያላስረዳ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ይህ ድምዳሜ የማስረጃውን ታዓማኒነት መሰረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን ደግሞ ይህ ችሎት ሊመረምር የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የእግድ ጥሰት ተግባር የተፈፀመው በሰራተኞች ጥፋት መሆኑን አመልካች ካላስረዳ ደግሞ ራሱ ሃላፊነት የማይወስድበት ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍርድ ቤት እግድ ትዕዛዝ አለማክበር በሕግ ላይ በትክክል ተገልጾ የተደነገገውን ልዩ ደንብና ሥርዓት መጣስ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2028፣2035 እና 2126 መሠረት ኃላፊነትን የሚያስከትል ተግባር ነውና፡፡ በመሆኑም አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃን ከሕጉ ጋር ያገናዘበ እንጂ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው አመልካች የሚከራከርበት ነጥብ የካሳ መጠኑን በተመለከተ ሲሆን በዚህ ረገድ አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ኃላፊነት መጠኑ ሊሆን የሚገባው ቤቱ በእርግጠኝነት የተሸጠበት ዋጋ እንጂ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከአቶ ብርሃኑ ታርቆ ላይ የሚፈልገው የፍርድ ገንዘብ መጠን አይደለም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቤቱ በጨረታ ሳይሆን ከዚህ ውጪ የተሸጠ በመሆኑ በትክክል በምን ያህል ዋጋ እንደተሸጠ ተረጋግጧል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ቤቱ የተሸጠው በገበያ ዋጋ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ደግሞ አመልካች የኃላፊነት መጠኑን የሚቃወምበት ሕጋዊ ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የሌለ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 04 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሰናይት ተመስገን - ጠበቃ አልታዬ ወ/አማኑኤል - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እጥፍወርቅ በቀለ - ጠበቃ አስናቀ ከፋለ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኗ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ ክሱ ታህሣሥ 09 ቀን 1993 ዓ.ም የተፃፈ ሁኖ አመልካች የሚች አባታቸው የአቶ ተመስገን በቀለ ወራሽ መሆናቸውን በመግለጽ ሚችና ተጠሪ (በስር ተከሳሽ) በውርስ የተላለፈላቸውን በወረዳ 23፣ቀበሌ 13፣የቤት ቁጥር 1597/ለ/ እና /ሀ/ እንዳላቸውና ይህም መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ የቦታ መለያ ውል ድርሻ ድርሻቸውን ተከፋፍለው ከቆዩ በኋላም ሚች ከሞቱ ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ የሚችንም ድርሻ ጠቅልለው በመያዙ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ብር 30100.00(ሰላሳ ሺህ አንድ መቶ ብር) የኪራይ ገቢ እንዳገኙና የሚች የተለያዩ ቁሳቁሶችንም እንደያዙ በመዘርዘር ተጠሪ ክስ የቀረበበትን የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍሉ እና ቁጥሩ 159/ለ/ የሆነውን እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው ዘንዳ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ለማስረጃነትም የሰነድና የሰው ምስክሮችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ክሱ ያለ ማስረጃ የቀረበ ነው፡የውርስ ክፍፍል አላደረግንም፣እንዲያ ቢሆን ኑሮ ሌሎች ወንድሞቻችን በተካፈሉ ነበር፣ መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም የተደረገው የአጥር መለያ ጊዜአዊ ስምምነት ነው፣ ከሳሽን ባለቤትና ባለቦታ የሚያደርግ ካርታ ወይም ደብተር አላቀረቡም፣ክስ የቀረበበትን ቤት ተረክቤ የማስተዳድረው ሆኖ ሳለ ኪራይ ልጠየቅ አይገባም፣የቤት ቁጣቁስ አልተረከብኩም፣ቤቱን ግን ሚች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ተረክቤ አስተዳድራለሁ፣ የቤት ቁጥር 1597/ለ/ እና /ሀ/ ሚች 600 ካ. ሜትር የቦታ ስፋት ጋር እናቴ ሐምሌ 3 ቀን 1957 የሰጡኝና ቤቱም በራሴ ገንዘብ የተሰራ በመሆኑ የግል ቤቴ ነው፣ካርታና ደብተር ለመቀበልም በመጠባበቅ ላይ እገኛለሁ በማለት ዘርዝረው የአመልካች ክስ ያለምንም ሕጋዊ ማስረጃ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡ ለማስረጃነትም የሰነድና የሰው ምስክሮችን ዘረዝረው አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን ከመመረመረ በሁዋላ ከ600 ካ.ሜትር ውጪ ያረፈውና መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም በአጥር የተለየው አከራካሪው ቤት ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1597/ለ/ ወይም 1597/2/ በሚል የሚታወቀው ቤት የሚች አቶ ተመስገን በቀለ በመሆኑ ቤቱን የሚች ወራሽ ለሆኑት የአሁኗ አመልካች ተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል፣ የኪራይ ገንዘብና የቤት ቁሳቁስን በተመለከተ የቀረበው ክስ ግን በማስረጃ የተደገፈ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል። የአሁኗ ተጠሪ ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ በተወሰነው የውሳኔ ክፍል፣ የአሁኗ አመልካች ደግሞ የቤት ኪራይ ገንዘብንና የቤት ቁሳቁስን በተመለከተ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ባለመስማማት የየራሳቸውን ይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ እና ተገቢው መጣራት ተደርጉ የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎች ከቀረቡ በሁዋላ የይግባኝ መዛግብቱ ተጣምረው ጉዳዩ ከተመረመረ በሁዋላ አመልካች ያቀረቡት ይግባኝ ውድቅ ሲደረግ የተጠሪ ተቀባይነት አግኝቶ አከራካሪው ቤት የተጠሪ እንጂ የአመልካች አውራሽ አይደለመ ተብሎ ተወስኗል። አመልካች ቤቱ የተጠሪ ነው ተብሎ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት አንድ ገጽ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- አከራካሪው ቤት የአውራሻቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ይግባኙን የሰማው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመተው እና በይግባኝ ጊዜ ከሥነ ሥርአቱ ውጪ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ አድርጉ እንዲሁም የተጨማሪ ማስረጃዎችን ይዘት ባግባቡ ባላገናዘበ መልኩ ማስረጃውን መዝኖ የስር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ውሳኔው ተሽሮ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታቸው ተመርምሮ ተጠሪ አቶ ተመስገን በቀለ ከሞቱ በሁዋላ ያዙት የተባለውና ከይዞታቸው 600 ካ.ሜትር ውጪ ያለ እንዲሁም መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት የተለየው በቀድሞው ወረዳ 23፣ቀበሌ 13 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 1597/ለ/ ወይም 1597/2/ የሆነውን ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም የተባለው በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ክርክሮችንና ማስረጃዎችን ይዘት ባገናዘበ መልኩ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጉ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ታህሣሥ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ዳኝነት የጠየቁበት ቤት የአውራሻቸው የሚች አቶ ተመስገን በቀለ መሆኑን ገልጸው ሲሆን ተጠሪ ቤቱን ሚች በሕይወት እያሉ ሲኖሩበት የነበረና ከሕልፈተ ሞታቸው በሁዋላ ተረክበው ማስተዳደር የጀመሩት መሆኑን እንዲሁም መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም የተደረገው ስምምነት መኖርን ሳይክዱ ቤቱን የሰሩት ሚች ሳይሆኑ ተጠሪ በግል ገንዘባቸው የሰሩት የግል ንብረታቸው መሆኑንና ምንጩም ሐምሌ 03 ቀነ 1957 ዓ.ም የተሰጣቸው የስጦታ ወሉ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን፣የግራ ቀኙ ምስክሮች በስር ፍርድ ቤት ቀርበው መሰማታቸውን ነው። የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደጋቸው ምክንያቶች የተጠሪ ቤት በ600 ካ.ሜትር ቦታ ላይ ማረፉ በቀረበው ካርታ ተረጋግጧል፣በቀበሌው የቤት ቁጥር 1597/ለ/ በሚል የሚታወቅ ቤት ከካርታው ክልል ውጪ ያለና ተጠሪ እና የአመልካች አባት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም የይዞታ ስምምነት ያደረጉበት የአመልካች አውራሽ ቤትና ይዞታ በመሆኑ የተጠሪ ይዞታ አይደለም፣ በ1992 ዓ.ም በቤት ቁጥር 1597/2/ የተሰጠው የግብር ሂሳብ ማስታወቂያ የአመልካች አባት ካፈሩት በኋላ ለተጠሪ መመዝገቡን የሚያስገነዝብ ነው፣ ማስታወቂያው ለአመልካች አባት ይዞታው በ1980 ዓ.ም መሰጠቱንና የተጠሪ ይዞታ ከሆነው ከ600 ካ.ሜትር ውጪ መሆኑን ያሳያል የሚሉ መሆናቸውንም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የቤት ቁጥር 1597/ለ/ ወይም 1597/2/ የሆነውን ተጠሪ ለአመልካች እንዲያስረክቡ ሲል የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሻረው በ28/2/92 ዓ.ም በተወሰደ የቦታ ልኬት የቦታ ስፋት ልዩነት መገኘቱ ለአመልካች አውራሽ ለቤት ቁጥር 1597/ለ/ የይዞታ ማረጋገጫ ሊሆን እንደማይችል፣ የግብር ማስተወቂያው ለአመልካች አባት በወርስ የተላለፈላቸው ሃብት ስለመኖሩና ለዚሁ የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ተደርጐ ሉወሰድ የማይችል መሆኑን፣ መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም ተደረገ የተባው ስምምነትም የድንበር መለያ ስምምነት እንጂ የውርስ ሃብት ድርሻ ክፍፍል የተደረገበት አለመሆኑን፣ ቤቱን የአመልካች አባት በውርስ ወይም በስጦታ አግኝተውት ባለሃብት ስለመሆናቸው የቀረበ የማስረጃ የለም፣ የአመልካች አባት በ30/05/1982 ዓ.ም ለሚኖሩበት ሰርቪስ ቤት ቁጥር እንዲሰጥ ጠይቀው በኮሚቴ 1597/ለ/ የሚል ቁጥር መስጠቱና ውሃና መብራት መግባቱም የይዞታ ማስረጃ ሊሆን እንደማይችል፣ የንፋስ ስልክ ላፍቶ አስተደደር ጽ/ቤት ጎዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ ለአመልካች አባት በጠየቁት መሰረት ከመፈቀዱ ውጪ የቦታ ይዞታ በተጠሪና በባለቤታቸው አቶ ከበደ ወ/ጊዮርጊስ ስም ብቻ መሆኑና በ1967 ዓ.ም የቤት ቁጠር ሲሰጥም የተሰጠው ቁጥር 1597 ሆኖ በተጠሪና በባለቤታቸው ስም መሆኑን ማረጋገጡን፣የክፍሉ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ታህሣሥ 06 ቀን 1998 ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ የይዞታው አመጣጥ ተጠሪ ከእናታቸው በስጦታ ያገኙት መሆኑና በማህደር ውስጥ የቤት ቁጠር 1597 የሚል ከመሆኑ ውጪ በ/ሀ/ እና በ/ለ/ የተለየ ቤት ቁጥር የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩን እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ይዞታው በካርታ ቁጠር 05/203/11862/00 በተጠሪ፣ በግዛቸው በከበደና በትዝታ አበበ መመዝገቡን ማረጋገጡን፣ተጠሪ ከ1968-1992 ዓ.ም ድረስ በቤት ቁጥር 1597/2/ ግብር ስለመክፈላቸው ማስረጃ ማቅረባቸውን፣ የካቲት 17 ቀን 1998 ዓ.ም የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ለፍርድ ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ በተጠቀሰው ካርታ ውስጥ የቤት ቁጥር 1597/ለ/ የሚል ቤት አለመኖርንና በግቢው ውሥጥ የቤት ቁጠር 1579/2/ ራሱን የቻለ ቤት እንደሚገኝ ሪፖርት የቀረበለት መሆኑን ማረጋገጡን፣የአመልካች ምስክሮች የአመልካች አባት ቤት ሲሰራ አየን ባሉበት ግቢ ውስጥ ሌሎች ቤቶች መኖራቸውን፣የተሰራው ቤት፣የቤት ቁጥር እና ቦታው የማን እንደሆነ እንደማያውቁ የመሰከሩ ናቸው፣በተጠሪ፣በግዛቸው ከበደና ትዝታ አበበ ስም የተመዘገበ የቤት ቁጥር 1597 ካርታ ይዞታ 666 ካ.ሜትር መሆኑ ተረጋግጧል የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ ነው፡፡

እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ያጣሩት ነጥብና ማስረጃውን በመመዘን የደረሱበት ድምዳሜ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት ጉዳዩን እንዲመረምር ጉዳዩ ለችሎቱ ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ በዚህ ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር ሲያደርጉ የተጠሪ ጠበቃ የተያዘው ጭብጥ የማስረጃ ጉዳይ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው አይደለም በማለት ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ በእርግጥ ይህ ሰበር ችሎት ሊመለከተውና ማረም የሚገባው ጉዳይ የማስረጃን ጉዳይ ሳይሆን በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

10 ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሰበር ችሎት እንዲመለከተው የተያዘው ጭብጥ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ይዘት ባግባቡ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር እንጂ የማስረጃውን ክብደት ወይም ታአማኒነት ለመመርመር ተብሎ አይደለም፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩትም በጉዳዩ ላይ የቀረቡት የሰው ምስክሮች አከራካሪው ቤት በሚች አባቱ የተሰራ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሁነው እያለ እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘትም ይህንኑ የሚደግፍ ሁኖ እያለ በአግባቡ ሳይታይ ታልፏል በሚል ነው፡፡ በመሆኑም ሊነሣ እና ሊታይ የሚገባው ጭብጥ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የቀረቡት ማስረጃዎችን ይዘት መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚል ሲሆን ለክርክሩ የቀረቡት ማስረጃዎች ይዘት ወይም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነጥብ ከሕጉ ጋር በአግባቡ ተዛምዶ አልታየም የሚለው ቅሬታ የሕግ ነጥብ እንጂ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት ባለመሆኑ የተጠሪ ጠበቃ ጉዳዩ የማስረጃ ምዝና ስለሆነ በሰበር ችሎቱ የሚታይ አይደለም በማለት ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ቀጥለን ተጠሪ ከ600 ካ.ሜትር ውጪ ያለውንና በመጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም በተደረገው ስምምነት በአጥር የተለየውን ቁጥሩ 1597/ለ/ ወይም 1597/2/ በሚል የሚታወቀውን ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ተመልክተናል፡፡ አከራካሪው ቤት በአመልካች አባት የተሰራ ስለመሆኑ የአመልካች ምስክሮች ማረጋገጣቸውን የበታች ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት ፍሬ ነገር ነው፡፡ ተጠሪ ለአመልካች ክስ መልስ ሲሰጡ ቤቱ በገንዘባቸው የተሰራ መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ሲሆን ምስክሮቻቸው ቤቱ በተጠሪ የግል ገንዘብ የተሰራ መሆኑን አስረድተዋል ወደሚለው ድምዳሜ የስር ፍርድ ቤቶች አልደረሱም፡፡ በመሆኑም ቤቱ በአመልካች አባት የተሰራ መሆኑ በሰው ምስክሮች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የአመልካች አባት የቦታውና የቤቱ ባለሃብት ስለመሆናቸው የሚያሳይ ማስረጃ የለም ተብሎ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ድምዳሜ የተያዘው የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን ይዘት በመመርመር ነው፡፡ አከራካሪው ቤት ተጠሪ ከእናታቸው በስጦታ ባገኙት ቦታ የተሰራ መሆኑ የተካደ አይደለም፡፡ ሆኖም ዋናው ነገር በቦታው ላይ ያለውን ቤት የሰራው ሰው ተጠሪ ወይስ? የአመልካች አባት? የሚለው ነው፡፡ ይህ ፍሬ ጉዳይ ደግሞ አመልካች ባቀረቧቸው የሰው ምስክሮች በሚገባ መረጋገጡን ሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት ነው፡፡ በሕጉ አግባብ የሚታወቀው ቦታ ቀድሞ የነበረው ስፋት እንደነበር፣ ስፋቱ በሁዋላ እየተቀነሰ ግብር ሲገበርበት የነበረ መሆኑም በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሚመለከታቸው አካላት ተገቢው ማብራሪያ ማስረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ እነዚህ አካላት የቦታውን አመጣጥ፣ በቦታው ላይ በማህደር የሚታወቀው ቤት ቁጥር ስንት እንደሆነ፣ ካርታው በማን ስም እንደተመዘገበ እና ስፋቱ ስንት እንደሆነ መግለጫ መስጠታቸውን መሰረት በማድረግ አከራካሪው ቤት የአመልካች አውራሽ ስለመሆኑ ማስረጃ የለም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ቤቱን ማን ሰራው? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ፣ለጉዳዩ አወሳሰን ቁልፍ የሆነውን ፍሬ ነገርን በተመለከተ የቀረቡትን ማስረጃዎችን ይዘት ባግባቡ ሳይመረመር ነው፡፡ ተጠሪ ቦታውን በስጦታ አገኘሁ ከማለት ውጪ ቤቱን በግል ገንዘባቸው የሰሩት መሆኑን አላስረዱም፡፡ መሬት የኢትዮጵያ ህዝቦችና የመንግስት ብቻ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/3/ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል ሕገ መንግስቱ በተጠቀሰው አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ ስር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት መሆኑ/መሆኗ በሕግ የተከበረለት መሆኑ የተደነገገ ሲሆን የግል ንብረት በጉልበት፣ በፈጠራ ችሎታ ወይም በካፒታል የሚፈራ ስለመሆኑና ጥበቃም የሚደረግለት መሆኑን ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው መሬት የመንግስት እና የሕዝብ ብቻ መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጉልበት፣ በፈጠራ ችሎታ ወይም በካፒታል የተፈራ ንብረት በሕግ ጥበቃ የተደረገ መሆኑ እንዲሁም በሕጉ አግባብ የተገኘ የመሬት ባለይዞታነት የሕግ ጥበቃ የሚደረግለት መሆኑን ነው። በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1204 እና 1026 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎችም የባለቤትነት መብት የሕግ ጥበቃ ያለው መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። በሕጉ አግባብ የተፈራ ንብረት ደግሞ ለሚች ወራሾች በውርስ ሊተላለፍ የሚችል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826/2/ ድንጋጌ ያስገነዝባል።

ተጠሪ ቦታውን በስጦታ ከእናታቸው ያገኙት ነው ቢባልም ባዶ ቦታውን የአመልካች አውራሽ ይዘው ቤት ሲሰሩ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1178 እና 1179 መሠረት ተቃውሞ ያሰሙ ስለመሆኑ በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር የለም። ተጠሪ በሕጉ አግባብ በተሰጣቸው ካርታ ውስጥ አከራካሪው ቤት ተሰርቷል ቢባል እንኳ ቤቱ በአመልካች አውራሽ ጉልበትና ገንዘብ ስለመሰራቱ እንዲሁም ተጠሪ በወቅቱ ተቃውሞ የነበራቸው አለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የቦታው ካርታ አንድ ነው፣ ግብርም በዚሁ ካርታ መሠረት ስለመገበሩ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ብቻ ቤቱ የተጠሪ ነው ሊባል የሚችል አይደለም። ተጠሪ ከአመልካች አባት ጋር መጋቢት 22 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት ሲታይም የድንበር መለየት ጉዳይን የሚመለከት ቢሆንም በቦታው ላይ ሁለት ቤቶች እንደነበሩ፣ የአመልካች አባት ይዘውት የነበረው ቤት ተጠሪ ከያዙት ከ600 ካ.ሜትር ውጪ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሲሆን ስምምነቱ የውርስ ክፍፍል ስለመሆኑ የማያሳይ ቢሆንም አከራካሪው ቤት በአመልካች አባት አልተሰራም ለማለት ግን የሚያስችል አይደለም። ተጠሪ ቤቱን ከአመልካች አባት ሞት በኋላ መረከባቸውን በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክርክር ገልፀዋል፤ ሆኖም ቤቱ የግላቸው ንብረት ስለመሆኑ ግን አላረጋገጡም። በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪው ቤት በአመልካች አባት የተሰራ መሆኑ ስለመረጋገጡ ተቀብሎ እያለ የውርስ ድርሻ ክፍፍል የተደረገበት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት ቤቱ የአመልካች አባት የግል ንብረት አይደለም ማለቱ በሚመለከታቸው አካላት የተሰጠው የሰነድ መግለጫ ማስረጃም የቦታውን አመጣጥና በቦታው ላይ ያሉ ቤቶች በሕጉ አግባብ የተሰጠውን መለያ ቁጥር ከሚገልጽ በስተቀር ቤቱ በማን ተሰራ የሚለውን ጥያቄ በግልጽ ምላሽ ባልሰጠበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ መሻሩ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ይዘት ከላይ ከተጠቀሱት የሕገ መንግስት እና የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል። በዚህም ምክንያት ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 46403 ጥቅምት 21 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42971 የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት በከፊል ተሽሯል።
2. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01180 መጋቢት 29 ቀን 1998 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348/1/ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል።
3. ተጠሪ ከአቶ ተመስገን በቀለ ሞት በሁዋላ የያዙትንና ከተጠሪ ይዞታ /600 ካ.ሜትር/ ውጭ ያለውንና መጋቢት 22 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት ድንበሩ የተለየውን በቀድሞ ወረዳ 23 ቀበሌ 13 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 1597/ለ/ ወይም 1597/2/ የሆነውን ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ብለናል።
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐቃቤ ሕግ ታደሰ ተስፋዬ - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- አይንሸምስ ሁሴን አብደላ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ክርክር በወንጀል ክስ ምክንያት በኤግዚቢትነት ተይዞ የቆየውና በኋላ ከወንጀሉ ክስ በነፃ ለተሰናበቱት ለአሁኑ ተጠሪ ይመለስ የተባለው የአፈር ወርቅ ይዞት በቆየው አካል በአሁኑ አመልካች ተሸጦ ከተገኘ ለወርቁ ባለቤት ሊከፈል የሚገባው ተሸጧል የተባለበት ዋጋ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ 2512 ግራም የአፈር ወርቅ በህገወጥ መንገድ ደብቆ ሊያሣልፍ ሲል ተይዟል ተብሎ በቀረበበት የወንጀል ክስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክርና ማስረጃዎቹን መርምሮ ወንጀሉን መፈፀሙ ተረጋግጧል ብሎ ጥፋተኛ በማድረግ በኤግዚቢትነት የተያዘው የአፈር ወርቅም እንዲወረስ ወስኖ የነበረ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር ከክሱ በነፃ እንዳዲሰናበት ፣ በኤግዚቢትነት ተይዞ የቆየው የአፈር ወርቅም ለአሁኑ ተጠሪ እንዲመለስለት ወስኗል፡፡

ይህ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ይግባኝ ተብሎበት የተለወጠ ባለመሆኑ ኤግዚቢቱ ይመለስልኝ የሚለውን ጥያቄ የአሁኑ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው ሲሆን የአሁኑ አመልካች ቀርቦ ሲጠየቅ የአፈር ወርቁን በወቅቱ በነበረው ዋጋ እክፍላለሁ የሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አመልካች የአፈር ወርቁን ዋጋ እከፍላለሁ ያለውን ቢቀበሉትም የሚከፈለው በወቅቱ በነበረው ዋጋ ነው በሚለው ላይ ሣይስማሙ ቀርተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የአሁኑ አመልካች ገንዘቡን የምከፍለው በወቅቱ በነበረው ዋጋ ነው ያለው ተገቢ አይደለም በማለት ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ዋጋው ታስቦ ለአሁኑ ተጠሪ መክፈል ይገባዋል የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ትዕዛዝ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራቀኙ እንዲቀርቡ አድርጐ በጉዳዩ ላይ ካከራከረ በኋላ መርምሮ በሰጠው ፍርድ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ አመልካች የአፈር ወርቁን ዋጋ መክፈል ያለበት በወቅቱ በነበረው ዋጋ መሠረት ሣይሆን በኋላ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በነበረው የገበያ ዋጋ መሠረት ነው በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የቀረበ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ተብሎ በመታዘዙ ማመልከቻው ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ በጽሑፍ በሰጠው መልስ የአሁኑ አመልካች በወቅቱ የአፈር ወርቁ የተሸጠበትን ዋጋ እከፍላለሁ በማለት የጠየቀው ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም፣ ወርቁን በአይነት መመለስ ካልቻለ በጊዜው በወጣው የብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው ዋጋ መሠረት መክፈል ይኖርበታል በማለት ተከራክሯል፡፡ በተጠሪ በኩል በጽሑፍ የተሰጠው መልስ ለአመልካች የተሰጠ ቢሆንም ከመዝገቡ እንደሚታየው በጽሑፍ ያቀረበው የመልስ መልስ የለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ሲሆን ይህ የሰበር ችሎቱም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ ተጠሪ መክፈል የሚገባው የኤግዚቢቱ የአፈር ወርቅ ዋጋ በወቅቱ ሽጫለው የሚልበትን ዋጋ ነው ወይንስ በኋላ ፍ/ቤት ወርቁን መመለስ አለበት የሚል ትዕዛዝ በሰጠበት ጊዜ የነበረውን ዋጋ ነው? የሚለውን ዋናውን የክርክር ጭብጥ በተመለከተ፡-

የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ.ም ተጽፎ ባቀረበው የሰበር ማመልከቻው ላይ በኤግዚቢትነት ተይዞ የቆየውን የአፈር ወርቅ ሊሸጠው የቻለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑን ተጠሪ በወንጅሉ ጥፋተኛ በማድረግ መጋቢት 22 ቀን 1997 ዓ.ም ወርቁ እንዲወረስ በማለት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መሆኑንና ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወርቁ እንዳይሸጥ የሚል ትዕዛዝ ያስተላለፈው ወርቁ በውርስ ውሣኔው መሠረት እንዲሸጥ ከተደረገ በኋላ ሰኔ 15 ቀን 1997 ዓ.ም እንደሆነ የገለጹ ሲሆን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን ገልጿል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ይህንን በሚመለከት በጽሐፍ ባመጣው መልስ ላይ የአሁኑ አመልካች ወርቁን የሸጠው መቼ ነው? ከፍ/ቤቱ ዕግድ በኋላ ወይንስ በፊት? የሸጠውስ በምን ያህል ነው? የሚለውን በሚስጥር ይዞ ስለማቆየቱና ክርክሩም በማስረጃ የተደገፈ እንዳልሆነ ገልጿል ከማለት በቀር አመልካች ወርቁን የሸጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዳይሸጥ የሚል የዕግድ ትዕዛዝ ከሰጠና ከደረሰው በኋላ ነው በሚል በግልጽ ያቀረበው ክርክር የለም በግልጽ ያልተካደ ፍሬ ነገር ደግሞ በሕጉ እንደታመነ የሚቆጠር ነው፡፡

አመልካች በኤግዚቢትነት ይዞ የቆየውን የአፈር ወርቅ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወርቁ እንዳይሸጥ በማለት የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት አሰቀድሞ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪን በወንጀሉ ጥፋተኛ በማድረግ ወርቁ ይወረስ ብሎ በሰጠው የውርስ ውሣኔ መሠረት የሸጠው መሆኑ የታመነ ሆኖ ከተገኘ አመልካች ለተጠሪ ለመክፈል የሚገደደው በወቅቱ ወርቁን የሸጠበትን ዋጋ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ ተጠሪን ከወንጀል ክሱ በነፃ በማሰናበት ወርቁ ይመለስለት ብሎ ባዘዘበት ጊዜ በነበረው የገበያ ዋጋ መከፈል አለበት በሚል የቀረበው ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1ኛ) የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ/43191 የካቲት 29 ቀን 2002

ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና

2ኛ) የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ. 90395 ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ

ተሻሽሎ የአሁኑ አመልካች በኤግዚቪትነት ተይዞ የቆየውን 2512 ግራም አፈር ወርቅ በወቅቱ የሸጠበትን ዋጋ ለአሁኑ ተጠሪ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

3ኛ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

4ኛ) በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኅዳር 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ አቶ ሰናይ ልዑልሰገድ(ሁለት ሰዎች) - ጠበቃ መኮንን ሰመ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ትእግስት ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር አመልካች የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች ሲሆኑ የአቤቱታቸው ይዘትም ባጭሩ፡- ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ልዑል ሰገድ መዘምር ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውንና የሟቹን ንብረት የአሁኑ ተጠሪዎች ይዘው እንደሚገኙ ገልፀው ተጠሪዎች ተጠርተው ቀርበው የውርስ አጣሪ እንዲሾምና ውርሱ ተጣርቶ ሲቀርብ አስፈላጊው ውሳኔ እንዲሰጣቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአመልካቾችን አቤቱታ መርምሮ ውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው በማለት መዝገቡን በትእዛዝ ዘግቶታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ የካቲት 04 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የውርስ ማጣራት ጉዳይ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥረ ነገር ሥልጣን ነው ተብሎ መወሰኑ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 35657 ከሰጠው የሕግ ትርጉም አኳያ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበው ሚያዝያ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸው ላይም የሰበር ችሎቱ በመ/ቁጥር 35657 የሰጠው ትርጉም በመ/ቁጥር 36205 የተለወጠና መለወጡም ባግባቡ መሆኑን ገልጸው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ይህ ችሎት አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 እና ስለውርስ አጣሪ በ1952 ዓ.ም በወጣው በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ የተካተቱትን ድንጋጌዎችን በመመርመር ውርስ አጣሪን የመሾም ሥልጣን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ መሆኑን በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኘውን ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁ. 35657 ጥቅምት 13 ቀን 2001 ዓ.ም፣በሰ/መ/ቁ. 42015 ኅዳር 29 ቀን 2002 ዓ.ም፣በሰ/መ/ቁ. 51329 ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ የሕግ ትርጉም አለመለወጡንም ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 51329 ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በግልጽ አረጋግጧል፣ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ እንደሚችል የደነገገ ቢሆንም በዚሁ አግባብ ቀድሞ የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁ. 36205 አልተለወጠም፡፡ በተያዘው ጉዳይም የስር ፍርድ ቤቶች ይህ ሰበር ችሎት ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ በሕጉ አግባብ ባልተለወጠበት ሁኔታ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ሳይቀበሉ መቅረታቸው ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ማንኛውም ፍርድ ቤት አንድ ጉዳይ ሲቀርብለት ጉዳዩን የማየት ሕጋዊ ስልጣን ያለው መሆኑን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ስልጣኑ የሆነውን ጉዳይ ደግሞ ከሕጉ አግባብ ውጪ በሆነ ምክንያት አልተመለከትም ሊል አይችልም፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/ለ/ሸ/ እና አዋጅ ቁጥር 408/96 መሰረት የወራሽነት የምስክር ወረቀት ከመስጠት በስተቀር ውርስ እንዲጣራ አጣሪውን የመሾም የስረ ነገር ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ ተገልፆ በዚህ ሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ መሰረት ባልተለወጠበት ሁኔታ የከተማው ፍርድ ቤት ውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን አለው ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. በ21/11/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83998 ታህሳስ 28 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. የውርስ አጣሪ የመሾም የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው ብለናል፡፡
3. የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ የሚቀርበውና ውርስ አጣሪውንም መሾም በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር ስለሚወድቅ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ እንዲመለከት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 341 መሰረት ተመልሶለታል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

<u>የልዩነት ሐሳብ</u>

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ የማልስማማ በመሆኑ የምለይበትን ሐሳብ እንደሚከተለው አሰፍራለሁ፡፡

በእኔ እምነት የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን አላቸው፡፡ የተሻሻለው የአዲስ አበባ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 ንኡስ አንቀጽ 1/ሸ/ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን በመመርመር ውሣኔ የመስጠት ስልጣን እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ወራሽ የሆነው ሰው የሟች የኑዛዜ ወይም የሕግ ወራሽ መሆኑንና ከውርስ የሚደርሰውን ድርሻ የሚይዝ እንደሆነ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 996 ተመልክቷል፡፡ ይህንን ለማወቅ የግዴታ የውርስ አጣሪ መሾምና በሟች መሞት ምክንያት የማይቋረጡ መብትና ግዴታዎቹን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ሕግ አውጭ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጡ ሥልጣን ሲሰጥ ለወራሽነት የምስክር ወረቀት ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ሁሉ የመፈፀም ሥልጣን እንዲሰጣቸው ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው ነው ስለሆነም በዚህና ከዚህ በፊት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35654 በገለጽኳቸው ምክንያቶች አብላጫው ድምጽ ከሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ዓብዱል መሐመድ - ጠበቃ አሰፋ መኮንን - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘበናይ ኃይሌ - ቀረበች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውልን መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው ተጠሪ ናት፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው ከሚች እህቱ በኑዛዜ የወረስኩትን ቤት ከሕግ ውጪ ይዞ ስለሚገኝ ለቆ ያስረክበኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የሥረ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ መቃወሚያዎቹ ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚያስችል መብት የላትም እንዲሁም ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚሉ ሲሆን፣ ሥረ ነገርን በተመለከተም ቤቱ ከወ/ሮ ንጋቷ /ሚች/ በብር 250000 በውል ገዝቼዋለሁ፡፡ ከዋጋው ውስጥ ብር 240000 በመክፈል ቤቱን ተረክቤአለሁ፡፡ ከሣሽም ጉዳዩን /ውሉን/ ለማስፈጸም ብር 40000 ከኔ ወስዳለች የሚሉትን ነጥቦች ማንሳቱን ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቦ ተጠሪ በውሉ መሠረት የማስፈጸም ግዴታ ያለበት በመሆኑ የቤቱን የባለቤትነት መብት እና ካርታ በስሜ እንድታስተላልፍ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ስለመጠየቁ ከመዝገቡ አረጋግጠናል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የሁለቱንም ወገኖች ክርክር መርምሮአል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችን ክርክር ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ በማለት ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 22 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ አቤቱታ አቅርቦአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው አመልካች ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ለሕጉ የተሰጠው ትርጓሜን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረትም አመልካች እና ተጠሪ በጭብጥነት የተያዘውን ነጥብ በሚመለከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት መቃወሚያ ያቀረበው ከሚች ጋር በተደረገው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ገንዘቡን ከፍዬ ቤቱን ተረክቤያለሁ የሚልበትን ጊዜ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው በ1988 ዓ.ም. ሆኖ ተጠሪ ክስ የመሠረተችው ደግሞ በ2001 ዓ.ም. ነው፡፡ ተጠሪ ክሱን የመሠረተችው የሽያጭ ውሉን ሳታስፈርስ እንደሆነም መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1168 በተደነገገው መሠረት ለ15 ዓመት ግብር በተከታታይ ከፍሎ ቤቱን ስለመያዙ አላስረዳም የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነም ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቤቱን ይዞ የሚገኘው አመልካች ላቀረበው የይርጋ መቃወሚያ አወሳሰን ተገቢነት አለው በማለት የጠቀሰው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1168 “ስለግል ሃብት” በተመለከተ በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕግ በአንቀጽ 7 ሥር ነው የሚገኘው፡፡ የዚህ አንቀጽ አንደኛው ክፍል የሆነው ምዕራፍ 1 ሀብት ስለሚገኝበት ሁኔታ፣ ሀብትን ስለማስተላለፍ እንዲሁም ሀብት ስለሚቀርበት እና ስለ ሀብትነት ማስረጃ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቶ የያዘ ሲሆን፣ ከፍ ሲል የተጠቀሰው ቁ. 1168 በተለይ የሚገኝበት የምዕራፉ ክፍል 1 ደግሞ ሀብት ስለሚገኝበት ሁኔታ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዞአል፡፡ በዚህ መሠረትም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው በንብረቱ ላይ የባሃብትነት መብት የሚያገኝበት ሁኔታ በቁጥር 1168 ተደንግጎአል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተቀመጠው መርህ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት በይዞታው ሥር ያደረገው ሰው የዚህኑ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ አሥራ አምስት /15/ ዓመት በስሙ ከከፈለ የንብረቱ ባለቤት እንደሚሆን ነው የሚያመለክተው፡፡ በመሆኑም የማይንቀሳቀሰውን ንብረት የያዘው ሰው ንብረቱን እንዲለቅ ሲከሰስ ድንጋጌውን በመጥቀስ ሊከራከር የሚችለው በድንጋጌው የተመለከቱትን ሁኔታዎች አሟልቶ በመያዙ የንብረቱ ባለሃብት መሆኑን ለማረጋገጥ እንጂ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ለማለት አይደለም፡፡ የይርጋ መርህ ክስን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት በመሆኑ ንብረትን በመያዝ ወይም ባለይዞታ በመሆን የባለሃብትነት መብት ከሚገኝበት መርህ ወይም አግባብ የተለየ ነው፡፡ ስለዚህም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168/1/ የተመለከተውን ድንጋጌ ለይርጋው መቃወሚያ አወሳሰን መሠረት ማድረጉ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመቀጠል የተመለከትነው አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የሚደረግበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አመልካች ቤቱን የያዘው ከሚች ወ/ሮ ንጋቷ ሃይሌ (ተጠሪ አውራሼ ናት የምትላት) ጋር በ1988 ዓ.ም ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ነው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግንዛቤ እንደተወሰደበት ከውሳኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በሌላ በኩል ግን የሺያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 በተደነገገው መሰረት በውል አዋዋይ ፊት ያልተመዘገበ በመሆኑ ለአመልካች የሚሰጠው መብት የለም፤በሻጭም ሆነ በወራሽ (ተጠሪ) ላይም የሚያስከትለው ግዴታ የለም፤ በአጠቃላይ ውሉ ሕጋዊ ውጤት የለውም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ፍ/ቤቱ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጐአል፡፡ በእርግጥ ፍ/ቤቱ የይርጋውን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው ከላይ በተገለጸው ምክንያት በመሆኑ ውሉ በሕጉ የተቀመጡትን የፎርም ሁኔታዎች (መስፈርቶች) አያሟላም ከሚለው ትችቱ ጋር አላያያዘውም፡፡ ይሁንና ትችቱ የሽያጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል መደረጉን ስለሚያመላክት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ በመወሰን ረገድ ጠቃሚ ፍሬ ነገር ነው።

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪ በክስዋ ያቀረበችው የዳኝነት ጥያቄ አመልካች ቤቱን ያስረክበኝ የሚል ነው። አመልካች ደግሞ ተጠሪ ቤቱን ልትረከብ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው የሥረ ነገር ጭብጥ ከመታየቱ በፊት ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባው የይርጋ መቃወሚያ አቅርቦአል። በመሆኑም ተጠሪ የአመልካችን የይረጋ መቃወሚያ ውድቅ ታስደርግ ዘንድ በቅድሚያ ይጠበቅባታል። አመልካች ቤቱን የያዘው በውል እንደመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው ወይም ተሰርዞአል ሳይባል እንዲሰቅ የሚደረግበት አግባብ የለም። በእርግጥ አመልካች በመከራከሪያነት ያቀረበው ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 በተደነገገው መሰረት አልተደረገም ተብሎአል። የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ውል በጽሑፍ እና ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ወይም በፍ/ቤት ካልተደረገ ውጤት እንደማይኖረው የተጠቀሰው ድንጋጌ ያመልክታል። በሌላ በኩል ደግሞ በሕጉ የተመለከተውን የአፃፃፍ ሥርአት አለመከተል የሚያስከትለው ውጤት ምን እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808/2/ ተደንግጐአል። በዚህም መሰረት ይህን የመሰለ ውል የሚፈርሰው ከተዋዋዮቹ አንዱ ወይም ማናቸውም ጥቅም ያለው ሰው ሲጠይቅ እንደሆነ ሕጉ ያመለክታል። ይህም የሚያስገነዝበን የአፃፃፍ ሥርአትን ያላሟላ ነው የተባለው ውል በሕጉ በተመለከቱት ሰዎች እንዲፈረስ ጥያቄ እስካልቀረበበት ድረስ ከጅምሩ ፈራሽ ነው ሊባል እንደማይችል ነው። ውሉ እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄም በጊዜ የተገደበ ነው። የአፃፃፍ ሥርአቱን ያልተከተለ ውል እንዲፈረስ ጥያቄው መቅረብ ያለበት በአሥር /10/ ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808/2/ እና 1845 ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መንፈስ እና ይዘት መገንዘብ ይቻላል።

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው መስከረም 12 ቀን 88 ሆኖ ተጠሪ ክስ የመሰረተችው ደግሞ ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም እንደሆነ መዝገቡ ያመለክታል። ይህም ማለት ክሱ የቀረበው ውሉ ከተደረገ ከ13/ አሥራ ሦስት/ ዓመት በኋላ ነው ማለት ነው። ክሱን የሰማው ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሰረት አድርጐ ባለማየቱ ከተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ችሎአል። ከፍ ሲል እንደገለጽነው ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት ያላቸው ድንጋጌዎች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808/2/ እና 1845 በመሆናቸው አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ ውድቅ የሚሆንበት ምክንያት የለም። ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጐም ረገድ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39406 ጥቅምት 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 87347 ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል።
2. ተጠሪ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ብለናል።
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቶአል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጎንደር 08 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ብርሃኔ ተሰማ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ታምራት አያኔ - ጠበቃ ወረደ ወ/አማኑኤል - ቀረቡ

2. የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

በሌሉበት የሚታይ ነው፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1225 ስር የተመለከተውን ንውጽውጽታን /Nuisance/ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፊደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች የስር ከሣሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ ክሱም የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ ሆኖ ይዘቱም ባጭሩ በመኖሪያነት በተሰጣቸው ቦታ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ የገነቡት ቤት ያላቸው ሆኖ ይኸው ተጠሪ በመኖሪያ ቤታቸው ላይ የብየዳ ሥራ በመስራታቸው ጎረቤት በሆኑት አመልካች ላይ የድምጽ ብክለት ሁከት መፍጠራቸውን፣ 2ኛ ተጠሪም የብረታ ብረት ብየዳ ሥራ በኢንዱስትሪ ዞን መስጠት ሲገባው ያላግባብ ፈቃዱን መስጠቱን ገልፀው የተፈጠረው የድምጽ ሁከት ሊወገድላቸው፣ የሥራ ፈቃድም እንዲሠረዝ እንዲደረግ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪም ጉዳዩን በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ሊታገድ እንደሚገባውና የብይዳ ማሽኑ ዝቅተኛ ድምጽ ያለው መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪም የሥራ ፈቃዱን የሰጠው በሕግ አግባብ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የታገደ ነው፣ 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ ደግሞ የሰጠውን ፈቃድ የሚሰርዘው ራሱ እንጂ ፍርድ ቤት አይደለም ሲል የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፊደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ሁከቱ በክፍሉ ደንብ አስከባሪ ትእዛዝ መሠረት ቆሞ ቀይቶ እንደገና ሲፈጠር ክስ ያቀረበ ሆኖ እያለ በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ይታገዳል ተብሎ መወሰኑ የሕግ ግድፈት ያለበት ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ ተገቢው ውሣኔ እንዲሰጥበት ይደረግ ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም አመልካች የተፈጠረው ሁከት ለተወሰነ ጊዜ ከተወገደ በኋላ እንደገና ሁከቱ በመጀመሩ ምክንያት የቀረበው ክስ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው 1ኛው ተጠሪ ሲቀርቡ 2ኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የአመልካች የሰበር ቅሬታ ነጥብ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሣ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊነሳ አይገባም፣ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ መወሰኑም ባግባቡ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊመመርመር ይገባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሮታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ጐረቤት ሆነው በሚኖሩበት አካባቢ 1ኛ ተጠሪ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ወስደው የብረታ ብረት ብየዳ ሥራ እንደሚሰሩና በስራው ወቅት ጥቅም ላይ የሚውለው ማሽን በሚያሰማው ድምጽ አመልካች ሁከት ተፈጥሮብኛል የሚሉ መሆኑን ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ የብየዳ ሥራውን ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ የሚሰሩት መሆኑን በመግለጽ የሚከራከሩ መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1225 ስር በባለቤትነት መብት ያለመጠን መገልገልን የሚደነግገው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149 ስር ከተመለከተው በይዞታ ላይ ሁከት ስለመፍጠር እጅጉን የተለየ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1225 ስር የተመለከተው ጉዳይ በሰፊ የባለቤትነት መብት ላይ በህጉ ከተመለከቱት ገደቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ ባለቤቱ ድርጊቱን የሚፈጽመው ወይም ሥራውን የሚፈጽመው በራሱ ንብረት ወይም ቤት ውስጥ ቢሆንም የድርጊቱ ወይም የሥራው ውጫዊ መገለጫዎች ሌላውን ጐረቤት ወይም ባለቤት፣በሌላ ሕጋዊ አግባብ ተጠቃሚ የሆነውን ሰው እንዳይረብሽ፣ እንዳያውክ ወይም በማናቸውም መልኩ ከተገቢው በላይ የሆነ ችግርን እንዳያስከትል በማድረግ መብቱን በልክ ባለቤቱ ይጠቀም ዘንድ ህጉ ያበጀው፣ የባለቤትነት መብትን አጠቃቀም አድማስን የሚወሰን ሥርአት ስለመሆኑ ከአንቀጽ 1226 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ጋር አዛምደን በምናነብበት ጊዜ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1149 ስር የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የክርክሩ ባህርይ የሚያሳየው የአመልካች ጥያቄ በይዞታቸው ላይ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድላቸው ሳይሆን የማሽኑ ድምጽ የፈጠረባቸው ረብሻ እንዲወገድላቸው ነው፡፡ የማሽኑ ድምጽ ሥራው እስከተሰራ ድረስ የሚቀጥል መሆኑም ግልጽ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የብየዳው ሥራ ከተጀመረ በኋላ የጊዜ ማለፍ ሁኔታ መኖር በድምጽ ሁከት ተፈጥሮብኛል በማለት ክስ ለማቅረብ የሚገድብ አይደለም፡፡ ዋናው ቁልፉ ነገር ድምፁ ከመጠን በማለፉ ረብሻ መፍጠሩን ማረጋገጥ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1225 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ዓይነተኛ ዓላማውም ባለሐብቱ በመብቱ በሚገለገልበት ጊዜ የጐረቤቱ ርስት ጥቅም የሚቀንስበትን ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚጐዳበትን ማናቸውንም ከመጠን ያለፈ ነገር ከመስራት መከላከል ነው፡፡ አንዱ የተፈጠረ የድምጽ ብክለት እንዲቀጥል የሚደረገበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ተከራካሪ ወገኖች የጠቀሱትን ድንጋጌ ብቻ በመያዝ ለፍሬ ጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ በመያዝ ውሳኔ መስጠት የዳኝነት አካሄድ የሚፈቅደው አይደለም፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በመለየት ዳኝነት መስጠት የፍርድ ቤት የእለት ተእለት የስራ ድርሻ እንጂ የተከራካሪ ወገኖች አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ የጉዳዩ ይዘት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1225 እና 1226 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን የሚመለከት ሆኖ እያለ በይዞታ ላይ ሁከት ሲፈጠር የይርጋ ጊዜን የሚመለከተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡

2ኛ ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠውን ውሣኔ ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው ተጠሪ ስለንግድ ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ በወጣው አዋጅ መሰረት መሟላት ያለባቸው ነገሮች ሲሟሉ ፈቃድ የመስጠት በጎላም ጉድለት ካገኘ የማገድና የመሰረዝ ሥልጣን አለው እንጂ የከተማውን የቦታና መሬት አጠቃቀም የመወሰን ሥልጣን የለውም በሚል ምክንያት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የስር ፍርድ ቤት ይርጋን አስመልክቶ የሰጠውን ውሳኔ ስህተት ነው የሚሉበትን ምክንያት ከመዘርዘር ውጪ 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ቅሬታቸውን አልዘረዘሩም፡፡ በሌላ በኩል ይህ ችሎት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/89 ሲመለከተው የንግድ ፈቃዱን የተሰጠው ሰው በሌላ ሰው ላይ በስራ በሚፈጥረው ረብሻ የንግድ ፈቃድ የሰጠው አካል ሊሰርዘው የሚገባ ስለመሆኑ የማይደነግግ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 10 ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት መደምደሚያ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ/ቁጥር 12960 ሰኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 69348 ጎዳር 24 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. የአመልካች ጥያቄ በይርጋ የሚታገድበት ምክንያት ስለሌለ 1ኛ ተጠሪ በሚሰሩት የብየዳ ሥራ የሚሰማው ድምጽ ከመጠን በማለፍ ወደ አመልካች መኖሪያ ዘልቆ ሁከት የሚፈጥር መሆን ያለመሆን፣ለመከላከል ያደረጉት ነገር መኖር ያለመኖሩን፣ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1225 ድንጋጌ አኳያ በመመልከት ጉዳዩ ላይ ተገቢው ውሳኔ እዲሰጥበት ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. 2ኛውን ተጠሪ በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 25 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች ፦ ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፦ 1. የልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07/14 አስተዳደር ፅ/ቤት ነ/ፈጅ ሠይፉ ግርማ ቀረቡ

2. በልደታ ክ/ከተማ የመሬት ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥና ይዞታ አስተዳደር ፅ/ቤት ነ/ፈጅ ሠይፉ ግርማ ቀረቡ

ተጠሪ ፦ አቶ ታሪኩ ዑርጌሣ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በወረዳ 03 ቀበሌ 47 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና ቁጥሩ 04613 የሆነ ቤት ተጠሪ በጨረታ አሸንፈው የገዙት መሆኑን፣ ቤቱ በእርጅና ምክንያት ሊፈርስ በመድረሱ በጊዜአዊነት በላሜራ እንዲያድሱ መስከረም 15 ቀን 2002 ዓ/ም የእድሳት ፈቃድ ተፈቅዶላቸው ቤቱን ሰርተው ሲጨርሱ የተሠጠው የጊዜአዊ ግንባታ ፈቃድ ከመመሪያ ውጪ ነው በማለት ግንባታውን እንዲያፈርሱ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑን ገልጸው ተግባሩ ሁከት በመሆኑ እንዲወገድ ዳኝነት ሊሰጥ ይገባል በማለት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የእድሳት ፈቃድ የተሰጠበት መንገድ ከሕግ ውጪ ነው በመሆኑም ግንባታው እንዲፈርስ ማስጠንቀቂያ ተፅፏል፣ ይህ ደግሞ ሕጋዊ ተግባር እንጂ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የግንባታ ፈቃዱ የተሰጠው ከመመሪያው ውጪና በስህተት መሆኑ ስለተረጋገጠ እና የአመልካቾች እርምጃ ሕጋዊ እንጂ ሁከት ሊባል አይችልም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የግንባታ ፈቃዱ ለተጠሪ መሰጠቱ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ በቅን ልቦና የገነቡት ግንባታ የሚፈርስበት ምክንያት የለም፤ የአመልካቾች ተግባር ሁከት ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም የግንባታ ፈቃዱ የተሰጠው ከመመሪያ ውጪ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአመልካቾች ተግባር ሁከት ነው ተብሎ መወሰኑ የአመልካቾችን ኃላፊነት እና ተግባር ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለተጠሪ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሕጋዊ መንገድ ባለንብረት ሁነውና ከመንግስት አካል ጊዜአዊ ፈቃድ ወስደው የገነቡት ግንባታ እንዲፈርስ ማስጠንቀቂያ መጻፍ ሁከት ነው ተብሎ መወሰኑ ምንም የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ውሳኔው ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የተሠጣቸው ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከዓላማው ውጪ በስህተት የተሰጠ መሆኑ በሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነጥብ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት የተባፊውን ማስጠንቀቂያ ሁከት ነው ወደሚለው ድምዳሜ ሊደርስ የቻለው ተጠሪ በተሰጣቸው ጊዜያዊ የግንባታ ፈቃድ መሰረት በቅን ልቦና ግንባታ ከአከናወኑ ለስህተቱ ኃላፊነት መውሰድ ያለበት ፈቃዱን የሰጠው አካል ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሠረቱ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ይዞታውን ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈጸምን ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ወይም ንብረቱ እንዲመለስለት ሕጉ ከሚጠብቃቸው መንገዶች አንዱ አማራጭ የይዞታ ክስ ማቅረብ (Possessory Action) ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1149(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ መቅረብ የሚችለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ ከሆነው ነገር በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረው ነው፡፡ እንዲሁም የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም አይነት መብት በሌለው ሰው ላይ ስለመሆኑም የድንጋጌው መንፈስ ያስረዳል፡፡ የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅራቢ በማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ንብረቱ በይዞታው ስር የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የኃይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጢር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ነው፡፡ የሁከት ተግባር የሚኖረው ባለይዞታ የሆነ ሰው በይዞታው ስር በሚገኘው ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ሲሆንበት ወይም ረብሻ ሲፈርጥበት ነው፡፡ እንግዲህ የሁከት መፍጠር ድርጊት ትርጓሜና ይዘቱ ከላይ የተመለከተው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እስከ 1149 ድረስ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርበው ሰው ንብረቱ በእርሱ ግልፅ ቁጥጥር ስር መሆኑንና በዚህ ንብረት እንዳይገለገልበት ተከሳሹ ረብሻ የፈጠረበት ወይም መሰናክል የሆነው ስለመሆኑ ከተከሳሽ በተሻለ ማስረጃ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም፤ አንድ ባለይዞታ ይዞታውን ከሕጋዊ አካል ከወሰደ በኋላ ይዞታው የተሰጠበት አግባብ ከሕግ ውጪ መሆኑ ከተረጋገጠ ይኸው ስህተት እንዲስተካከልና ሕጋዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሆን ለማድረግ የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ በተሳሳተ መንገድ በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅን ልቦና አድሮበት ለኪሳራ የተዳረገ ሰው ደግሞ በሕጉ አግባብ ተገቢውን ኪሳራ ለመጠየቅ ይችል ይሆናል ከሚባል በስተቀር ቀድሞ በስህተት የተሰጠ ፈቃድ ወይም ሌላ ውሳኔ ጸንቶ ሊኖር ይገባል ብሎ ሊጠይቅ የሚችልበትና ፍርድ ቤትም ይህንኑ ሊቀበል የሚገባበት አግባብ አይኖርም፡፡ አንድ የአስተዳደር አካል የሰጠው ውሳኔ ወይም የወሰደው እርምጃ ሕገ ወጥ መሆኑን ከአረጋገጠ ይኸው ውሳኔ እንዲስተካከል የማድረግ ኃላፊነትና ተግባር አለውና፡፡ በመሆኑም ለተጠሪ የተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ከመመሪያው ዓላማ ውጪ መሆኑ በመረጋገጡ ይህንኑ ሕጋዊ ያልሆነ መመሪያ መሰረት በማድረግ የተሰራ ግንባታ እንዲፈርስ ለተጠሪ የተፃፈው ማስጠንቀቂያ አስተዳደራዊ ኃላፊነትንና ተግባርን ለመወጣት የተደረገ ነው ከሚባል በስተቀር የሁከት ተግባር ሊሆን የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የአመልካቾች ተግባር ሁከት ነው በማለት የከተማው መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩና የከተማው ሰበር ሰሚው ችሎትም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ማጽናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12735 መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 13339 ሚያዝያ 28 ቀን 2002 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 18533 የካቲት 02 ቀን 2002 ዓ/ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. አመልካቾች በተጠሪ ላይ የፈጠሩት ሁከት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 54121

ህዳር 01 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች ፡- ሲ.ኤ.ኤስ - ኮንሰልቲንግ ኢንጂነርስ ሳልዝጊተር ጂ.ኤም.ቢ.ኤች ጠበቃ ፍቃዱ ሞላ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ካሳሁን ተወልደብርሃን ጠበቃ ፈቃዱ አስፋው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክር የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ የስር ከሳሽ ክስ ይዘት ሲታይም ከአመልካች ድርጅት ጋር የመሰረቱት የቅጥር ውል ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካቹ የስራ መሪ መሆናቸውንና የግራ ቀኙ ስምምነት ጉዳዩ በጀርመን ሕግ እንደሚዳኝ የሚገልጽ መሆኑን በመጥቀስ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ዳኝነት ስልጣን የሌለው መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ የስራ መሪ ስለመሆናቸው አልተረጋገጠም ብሎ ከደመደመ በኋላ በቅጥር ስምምነቱ ላይ ጉዳዩ በጀርመን ሕግ እንደሚታይ መስማማታቸውን ገልጾና የግለሰብ የአለም አቀፍ ሕግ የሚያስነሳ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2/ሀ/ መሠረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው ሲል ክሱን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲያቀርቡ አመልካችም ተጠሪ የስራ መሪ አይደሉም ተብሎ የተሰጠው ብይን ላይ መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ተጠሪ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መሆኑን፣ ተጠሪ የስራ መሪ ስለመሆናቸው ግን አለመረጋገጡን ገልጾ የስር ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341 መሠረት ተመልሶለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 14 ቀን 2002ዓ.ም በፃፉት የሰበር ማመልከቻ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ ጉዳዩ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ የሚያስነሳ ስለሆነ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመልክቶ ብይን ይስጥበት ተብሎ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ይኸው ትዕዛዝ በይግባኝ መሻሩ ያላግባብ መሆኑን ማስረጃ ሳይሰማ ተጠሪ የስራ መሪ አይደሉም ተብሎ መወሰኑም ተገቢነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታቸውም ተመርምሮ ክሱን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማየት አለበት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው መስከረም 21 ቀን 2003ዓ.ም በተፃፈ አራት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል። የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ጥቅምት 15 ቀን 2003ዓ.ም የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የሚገዛው ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሠረት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ነው ብሎ ጉዳዩን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን እንዲመለከተው መመለሱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝቶታል።

ከክርክር ሒደት መገንዘብ የተቻለው ግራ ቀኙ መስከረም 20 ቀን 2001ዓ.ም ባደረጉት ስምምነት መሠረት በመካከላቸው የሚነሳው አለመግባባት በጆርመን ሕግ የሚታይ መሆኑን መስማማታቸውን፣ በመካከላቸው የነበረው ግንኙነትም የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት መሆኑን፣ ተጠሪ ኢትዮጵያዊ ሆነው የሚኖሩትና ስራውን ለመስራት ግዴታ የገቡት በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን፣ አመልካች የውጪ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበውና ስራውን የሚሰራው በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ነው።

በመሰረቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11/2/ሀ/ ስር የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ (Private International Law) የሚመለከቱ ጉዳዮች በሚኖሩ ጊዜ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን እንደሚኖረው ተደንግጓል። አዋጁ ይህን ድንጋጌ ሲያስቀምጥ የራሱ የሆነ ምክንያት አለው ተብሎ ይታሰባል። በዚህም መሠረት ሕግ አውጪው ይህንን ድንጋጌ ያስቀመጠው አንድም ወደ ፊት በስራ ላይ የሚውለውን የአገራቱን የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ በሕግ አውጪው አካል ፀድቆ በስራ ላይ ሲውል በዚህ ረገድ የሚነሱ የህግ ክርክሮች የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን አይቶ እንዲወስን ወይም አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ለዳኝነት በቀረበ አንድ ጉዳይ ላይ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ የኢትዮጵያ ሕግ ከአመልካቹ አገር ሕግ ወይም ከሌላ አገር ሕግ ጋር ይጋጫል ወይም ይቃረናል በማለት በኢትዮጵያ ሕግ እንዳይዳኝ ወይም በራሱ ወይም በሌላ አገር ሕግ ጉዳይ እንዲታይና እንዲወሰንለት ሲያመለክት ነው። በሌላ አገላለጽ ለዳኝነት የቀረበው ጉዳይ በባህርይው ከአንድ በላይ የሆኑ የሕግ ስርዓቶችን ለጉዳዩ አወሳሰን የሚጋብዝና የየትኛው ሥርዓት ሕግ ተመራጭ ሊሆን ይገባል የሚለው ክርክር ሲነሳ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን አይቶ እንዲወሰን ከመደረጉ ውጪ በማናቸውም ሁኔታ ተከራካሪዎች የአገራቱን ሕግ በሚፃረር መልኩ ስምምነት አድርገው ሲገኙ ሁሉ ተከራካሪ ወገን ክርክር ስነሳ ብቻ የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም። ከዚህ አንፃር ግራ ቀኙ አደረጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተባሉትን ስምምነት ስንመለከት የኢትዮጵያ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሕግ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የሚያደርግ መሆኑ ሲታይ ስምምነቱ ተቀባይነት አለው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ዓላማ እና መንግስት አዋጁ ላይ ካለው ጠቅላላ ፍላጎት አንፃር የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ የመንግስትም ፍላጎት የሚንፀባረቅበት ሕግ ሲሆን ይህን አዋጅ የሚመለከቱ ስምምነቶች ሕጋዊ እና የሕዝብን ጥቅም የማይፃረሩ መሆን ይገባቸዋል፡፡ የሚኒስተሮች ምክር ቤት በደንብ ካልወሰነ በስተቀር አዋጅ ቁጥር 377/96 የውጪ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ከአዋጁ ድንጋጌ 3/3/ለ/ ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የወጣ ደንብ የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ አዋጅ ቁጥር 377/96 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግ ጥያቄን ስምምነቱን መሠረት አድርጎ ያስነሳል ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ለጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈፃሚነት እንዳለው በመግለጽ ጉዳዩን ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መመለሱ ምንም የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ የስራ መሪ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ነጥብ በሰበር ችሎት እንዲታይ በጭብጥነት ያልተያዘ በመሆኑና ከአመልካች የመልስ መልስ ክርክር ላይም ያልተነሳ በመሆኑ መመልከቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1/ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 82430 የካቲት 8 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2/ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው ብለናል፡፡

3/ ለክርክር የወጣን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 2 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- የእንግሊዝ ህጻናት አድን ድርጅት - ጠበቃ ጥላዬ ተገኝ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ገአስ አስማን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የተጀመረ ነው፡፡ ጉዳዩ አሰሪ የሆነው የአሁን አመልካች ሰራተኛ በሆኑት በአሁን ተጠሪ ላይ የወሰደውን የስንብት እርምጃ የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት የተወሰደብኝ እርምጃ ህገ ወጥ በመሆኑ የተቋረጠብኝ ክፍያ ተሰጥቶኝ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ ሲሉ በአመልካች ላይ ክስ መስርተዋል፡፡ አመልካች ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጐ በውሣኔው ላይ ቢገለጽም ተወካዮቹ ቀርበው በጽሁፍ መልስ የሰጡ ስለመሆኑ ግን የክርክሩ ሂደት ያሣያል፡፡ የአመልካች የመከላከያ መልስ ክርክርም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የስንብቱን ተገቢነት ይገልጻል የሚለውን መልስ አቅርቦ የተከራከረ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሣያል፡፡ ክሱ የቀረበለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዞን አራት ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ መታየቱ ፍርድ ቤቱ ክሱን አዛውሮ ከማየት ስልጣኑ አንጻር ተገቢ ነው የሚለውን ምክንያት በመስጠት በስልጣን ረገድ የተነሣውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከአለፈው በሁዋላ ዋናውን ጉዳይ በተመለከተም መርምሮ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ አመልካች ድርጅት ተጠሪን አሰናበተ ከተባለበት ከጥቅምት ወር 2001 ዓ.ም እስከ ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲሁም ከጥር 27 ቀን 2002 እስከ የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ ከቆላ አበሉ ጋር የደመወዝ ጭማሪ እንዲሁም ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን በመክፈል ወደ ቀድሞው የስራ መደብ እንዲመልሰው በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ የመመልከት ስልጣን የሌለው መሆኑን ጠቅሶ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘቱም ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመልከቱም ሆነ ጉዳዩን የመራበት ስርዓት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጉላቸው ቀርበው የጽሁፍ መልስ የሰጡ ሲሆን በመልሣቸው ላይም የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ይህም ችሎት በቅድሚያ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው አቢይ የህግ ነጥብ ላይ ብቻ በማተኮር መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዋነኛነት ሊፈታ የሚገባው የነገሩ ጭብጥ፡-

የአሰሪና ሰራተኛን ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 “ን” መሠረት አድርጐ የሚነሣውን የግል የስራ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ በማየት የመዳኘት ስልጣን የማነው? የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው? ወይስ የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት? የሚለው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ የማግኘቱ ጉዳይ ስለ ስራ ክርክር ስለ ቦርድና ስለ ፍርድ ቤት ስልጣን የሚገልጹትን የአዋጅ ቁ. 377/96 ድንጋጌዎችን ተመስርቶ ጭብጡን መመርመርን ይጠይቃል፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 ከአዋጅ ቁ. 25/1988 በኋላ የወጣ ሲሆን በአንቀጽ 136/3/ ስለ ስራ ክርክር ምንነት ትርጓሜ የሚሰጥ ድንጋጌ ከመያዙም በላይ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 147 ስለቦርድ ስልጣን የሚደነግገው ሲሆን የፍ/ቤት ስልጣንን ደግሞ የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 138/2/ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 138/1/ የተዘረዘሩትንና መሰል የግል የስራ ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን ለፍ/ቤት መስጠቱን ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ አዋጁ የስራ ክርክርን የክልልና የፌዴራል ጉዳይ ነው የሚል መለኪያ በመስጠት የስነ-ነገር የዳኝነት ስልጣን መከፋፈሉን በግልጽ አያሣይም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 322/95 “ም” ሆነ በህገ መንግስቱ መሠረት የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስራ ክርክርን አስመልክቶ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በውክልና ሊመለከት ይችላል የሚባልበት አግባብም የለም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 138/1/ ድንጋጌ መሠረት ለፍ/ቤት የሰጡትን የስራ ክርክሮችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 139/1/ /ሀ/ ደግሞ በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በስራ ክርክር ችሎት የተሰጡ ውሣኔዎች ላይ የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት የይግባኝ ስልጣን እንዳለው ያሣያል፡ በመሆኑም የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 138 መሠረት በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚታዩት ጉዳዮች ላይ የይግባኝ ስልጣን ያለው መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 139/1/ሀ/ በግልጽ ያሣያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ የስራ ውል ከህግ ውጭ የተቋረጠ ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ቀድሞው ስራ እንዲመለስ ፣ ጭማሪ ደመወዝ እንዲከፈለኝ ፣ የቆላ አበል እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች እንዲከፈሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን በይዘቱ በአዋጅ አንቀጽ 138/1/ለ/ መሠረት የሚታይ የግል የስራ ክርክር ሁኖ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ለክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት በአንቀጽ 139/1ሀ/ መሠረት አቅርቦ የሚያሣይበት ጉዳይ ነው፡፡ የአፋር ክልል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ሊመለከት የቻለው ጉዳዩን ለማየት ስልጣኑ በህጉ በግልጽ ተሰጥቶኛል በሚል ምክንያት ሣይሆን የክስ መዛወር ጥያቄ ሲቀርብ ለማስተናገድ የምችለው እኔ ነኝ በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ችለናል፡፡ ይሁን እንጂ የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ /Change of Venue/ የሚስተናገድበትን አግባብ ህጉ የዘረጋው ስርዓት ያለ ሲሆን የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለብይኑ ዋቢ ያደረገው በ1958ቱ የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 31 ስር የተመለከተው አንዱ ሲሆን ከዚህ ህግ በሁዋላ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች የወጡት የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጆችም ተመሣሣይ ይዘት ያለውን ድንጋጌ ስራ ላይ አውለው ይገኛሉ፡፡ አንድ ክስ ወደ ሌላ ስፍራ ሊዛወር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችልበትን አግባብ ከሚደነግጉት የስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ጥያቄው ከተከራካሪ ወገኖች የሚቀርብ መሆኑና ህጋዊ ምክንያቶች ተብለው በህጉ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ መሟላት ያለበት መሆኑን ነው። በተያዘው ጉዳይ ግን የአፋር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ወደራሱ ያዞረው በተከራካሪ ወገኖች የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ቀርቦለትና በህጉ ስር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎችም ተሟልተው ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሣይ መሆኑን ተገንዝበናል። በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ወደ ራሱ አዙሮ የተመለከተው ህጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ አይደለም ፣ በውጤቱም በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ እንዲመለከተው በህጉ ያልተሰጠውን ስልጣን በመውሰድ ጉዳዩን በማየት በህጉ ጥበቃ ያገኘነው የተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብት ያጣበበ ሁኖ ተገኝቷል። በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዞን አራት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00126 የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል።
2. ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ሊታይ የሚገባው በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ሊታይ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት/አግባብ የለም ብለናል።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሣቸውን ይቻሉ ብልናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 65688

ሐምሌ 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ- - አቶ እሸቱ በቀለ /ነገረ ፈጅ/ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- አቶ ንጉሴ በያን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለባንክ ብድር መያዣ የሠጠበት የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣው ከመያዙ በፊት በሽያጭ ለሶስተኛ ወገን ተላልፎና ስመ ሀብቱም ከመያዣው በኋላ ለገዥው ዙሮ ሲገኝ ያለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻና ይዘትም የሚከተለው ነው፡፡ አመልካች ለአቶ አያሌው መንገሻ የሠጠውን ብድር ተበዳሪው ባለመመለሱ ምክንያት እና ተበዳሪው በውሉ መሰረት የወሰደውን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ክስ አቅርቦባቸው ውሳኔ እንዳገኘ በውሳኔው መሰረት እንዲፈጸምለት ለምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርቦ በቅድሚያ በዋስትና የተያዘ ቤት በአገምሳ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 026 እና 96 የሆነ ተገምቶ በጨረታ በሐራጅ እንዲሸጥ አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም ቤቶቹ በሐራጅ እንዲሸጡ ትእዛዝ ሰጥቶ ከተሸጡ በሁዋላ የአሁኑ ተጠሪ ይህ ቤት አመልካች በዋስትና ከመያዙ በፊት በውል ስምምነት ገዝቼ የንብረት ባለቤትነት ስም ወደ ስሜ ተዛውሮ የሚገኝ መሆኑን ገልፀው የሐራጅ ሽያጩ ውድቅ እንዲሆንላቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ቤቱ በሽያጭ ስምምነት ለተጠሪ መዛወሩና ስም በተዛወረበት ወቅትም የአሁኑ አመልካች ያቀረበው ወይም ያነሳው ተቃውሞ የለም በሚል ምክንያት የሐራጅ ሽያጩን ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ አከራካሪው ቤት በ10/10/1988 ዓ/ም በዋስትና መያዙ ተረጋግጧል፣ ስመ ሀብቱ ለተጠሪ የዞረውም በ1992 ዓ/ም ውስጥ ነው የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3059(1) ድንጋጌ የቅድሚያ መብት አለው በማለት ሽያጩ ሊቀጥል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ተጠሪ ቤቱን በ01/10/1988 ዓ/ም ገዝተው ሲገቡ ከነበረበት ከአስር ቆርቆሮ ወደ አንድ መቶ ቆርቆሮ በማሳደግ ግንባታ ያከናወኑ መሆኑ መረጋገጡን፣ ስመ ሃብቱ ሲዞርም በቤቱ ላይ እዳና እገዳ የሌለው መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚመለከተው ቀበሌ አስተዳደር መገለጹን እንዲሁም ተጠሪ ቤቱን የገዙት ከባለእዳው ጋር ተመሳጥረው ለማሸሽ ነው አለመባሉን በምክንያትነት ይዞ ቤቱ ከተሸጠ በኋላ በመያዣነት ተይዞ ብድር በባለእዳው መወሰዱን ከክርክሩ ሂደት መገንዘቡን ጠቅሶ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠውን ውሳኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ቤቱን በ01/10/1988 ዓ/ም ገዛሁ ቢሉም ስመ ሀብቱ የዞረው በ1992 ዓ/ም ሁኖ አመልካች ቤቱን በመያዣ የያዘው በ10/10/1988 ዓ/ም መሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች የቅድሚያ መብት የለውም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተምርምሮም ክርክር የተነሳበት ቤት ተጠሪ አመልካች በመያዣ ከመያዙ በፊት ነው የተገዛው ተብሎ ለተጠሪ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ቤቱን ገዛሁ የሚሉት ጊዜ በ01/10/1988 ዓ/ም ሁኖ ስመ ሀብቱ የዞረው በ1992 ዓ/ም መሆኑን፣ ስመ ሀብቱ ሲዞርም በቤቱ ላይ እዳና እገዳ የሌለው መሆኑን የክፍሉ ቀበሌ ማረጋገጡና ተጠሪ አስር ቆርቆሮ ቤት ገዝተው ባሁኑ ጊዜ አንድ መቶ ቆርቆሮ በማድረግ ይዘው የሚጠቀሙበት መሆኑን፣ ተጠሪ ቤቱን ይዘው ግንባታ ሲያከናውኑም አመልካች ያነሳው ተቃውሞ የሌለ ሁኖ ሽያጩን ያከናወኑትም ከባለእዳው ጋር ተመሳጥረው ስለመሆኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክርክር ያላቀረበበትና ይህንኑ የሚያሳይ ሁኔታም አለመኖሩን፣ ቤቱ እንዲታገድ በ10/10/1988 ዓ/ም ቀበሌው ሰጠ የተባለው የአመልካች የሰነድ ማስረጃም ቀበሌው በሁዋላ ስመ ሀብቱ ወደ ተጠሪ ሲዞር በቤቱ ላይ እዳና እገዳ የሌለ መሆኑን በ25/2/1992 ዓ/ም ከገለፀበት ማስረጃ አንፃር ሲታይ ተጠሪ ቤቱን እዳና እገዳ እያለ ገዝተዋል ለማለት የሚያስችል አለመሆኑን የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍሬ ነገርን ሲያጣራና ማስረጃን ሲመዘን ያረጋገጣቸውና ለውሳኔው መሰረት ያደረጋቸው ምክንያቶች መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በግልፅ መረዳት የሚቻለው በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመያዣ ውል በአከራካሪው ቤት ላይ አለመደረጉን ፍርድ ቤቱ ፍሬ ጉዳዩን በማጣራትና ማስረጃውን በመመዘን የደመደመው ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ አመልካች በቤቱ ላይ የመያዣ ውሉን በሕጉ አግባብ ስለማቋቋሙ ሊታመን በሚችል ማስረጃ አለማስረዳቱን የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያስገነዝብ ሁኖ አግኝተናል፡፡ አመልካች ቤቱን በመያዣነት የያዘው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3051(2) ድንጋጌ መሰረት በቅን ልቦና ነው ለማለት የሚያስችል ፍሬ ነገርም በክርክሩ ሂደት አለመረጋገጡን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪ አመልካች በመያዣ ከመያዙ በፊት ነው የተገዛው ተብሎ ሐራጁ በቤቱ ሊቀጥል አይገባም ተብሎ የተወሰነው ፍሬ ነገሩና ማስረጃው ተመዝኖ በመሆኑና ይህ ፍሬ ነገርና ማስረጃ ምዘና ጉዳይ ደግሞ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 51557 ሕዳር 24 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የቀበሌ 10 ባለአደራ ቦርድ - ወኪል ታደሰ ሃብቱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዳንኤል አድርሴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክርክርን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10/11/12 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና አመልካች የሚያስተዳድረውን የሥጋ መሸጫ ቤት ሐምሌ 01 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ የኪራይ ውል በወር ብር 500.00(አምስት መቶ) ተከራይተው እየከፈሉ በመስራት ላይ እንዳሉ አመልካች በወቅቱ በአቢይ ጾም ምክንያት የሥጋ ቤቱ ለሁለት ወር ስለሚዘጋ ኪራይ እንዲቀንስላቸው ተጠሪ ማመልከታቸውን፣ አመልካችም ይህንኑ ተቀብሎ በወር ብር 105(አንድ መቶ አምስት ብር) ቅናሽ ተደርጐላቸው እየከፈሉ ባለበት ሁኔታ ባለአደራ ኮሚቴ በአዲስ ኮሚቴ ተተክቶ ለአዲሱ ኮሚቴም ሁኔታውን ተጠሪ ገልፀው በመነጋገር ላይ እንዳሉ የተጠሪ ጥያቄ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ያልሰሩትን የኪራይ ክፍያ ከእነወጪው ብር 2010.00(ሁለት ሺህ አስር ብር) መጋቢት 24 ቀን 1999 ዓ.ም የከፈሉ ቢሆንም አመልካች የኪራይ ውሉን መጋቢት 22 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በማቋረጥ ስጋ ቤቱን እንዲያስረክቡ መጠየቁን ገልጸው ድርጊቱ ሁከት ስለሆነ ሁከቱ ይወገድልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ በኪራይ ውሉም ግዴታቸውንም በወቅቱ ባለመወጣታቸው የኪራይ ውሉ እንዲቋረጥ መደረጉን ገልፆ ሁከት ሊባል ስለማይገባ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር አመልካች ድርጊቱን የፈጸመው የኪራይ ውልን መሰረት በማድረግ በመሆኑ አድራጐቱ ሁከት ነው ሊባል የሚችል አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጐታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ አመልካች ለመክሰስም ሆነ ለመከሰስ ሕጋዊ ሰውነት የሌለው አካል ነው የሚል ምክንያት በመያዝ የበታች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ወኪል መጋቢት 01 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚልበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ቦርዱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ በ1988 ዓ.ም የወጣው መመሪያ የሚያሳይ ሁኖ እያለ ሕጋዊ ሰውነት የለውም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ ተጠሪ ቀርበው ሚያዚያ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በጠበቃቸው አማካኝነት በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ አመልካች ሕጋዊ ሰውነት የሌለው መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑና መመሪያ የሚባለውም በአመልካቹ በራሱ የወጣ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የሰበር ቅሬታው ሕጋዊ መሰረት የሌለው ስለሆነ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡፡ አመልካች በበኩሉ ሰኔ 23 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች የሕግ ሰውነት የለውም ተብሎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ ባግባቡ ነውን? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም ዓላማው በ1988 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሰረት ተዘርዝሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 361/95 በአንቀጽ 14 ስር በተመለከተው መሰረት የከተማው ምክር ቤት አዋጅ የማውጣት ስልጣን ያለው ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 10/3/ሐ/ ስር የቀበሌ ሥልጣን አካላት ስር የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ አንዱ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ የከተማው ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 14/1/ረ/ እና 66/2/ መሰረት በተሰጠው ስልጣን ክሱ ሲመሰረት ስራ ላይ የነበረውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1995 አውጥቷል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52 ስር በቦርድ ወይም በምክር ቤት (ካውንስል) ስለሚመሩ ማዘጋጃ ቤታዊ ያልሆኑ አስፈፃሚ አካላት የሚደራጁበት ሁኔታ ተመልክቷል፡፡ ይህ አዋጅ የሻረው አዋጁን የሚቃረን ማናቸውንም አዋጅ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ ስለመሆኑ በአንቀጽ 54 ስር በግልጽ አመላክቷል፡፡ ይህም ቀድሞ በመመሪያ የተቋቋመ የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ ሕልውናው እንዲያከትም የተደረገ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘትና የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ ካለው አጠቃላይ ዓላማ እንዲሁም ከሚመራበት አሰራር ስንነሳ የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ የሕግ ሰውነት ያለው መሆኑን ፍርድ ቤት በራሱ ጊዜ ግንዛቤ የሚወስድበት ጉዳይ(ጉዳዩ የሕግ ጉዳይ በመሆኑ) ሆኖ አግኝተናል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ውድቅ ያደረገው አመልካች ክስ ለማቅረብ ወይም ለመክሰስ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 397 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሕግ ሰውነት ያለው መሆኑን ፍርድ ቤቱ የራሱን ግንዛቤ(judicial notice) የሚወስድበት ስለመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ሕግ መርሆዎች የሚያስገነዝቡት ነጥብ እንጂ ተከራካሪ ወገን ለፍርድ ቤት ሕጉን ለማስረጃነት እንዲያቀርብ የሚገደድበት ሁኔታ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች የሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰውነት የሌለው በመሆኑ ሊከሰስ ወይም ሊከስ የሚችል አይደለም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ከላይ የተጠቀሱትን ሕጐች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም የተጠሪን የክስ አቀራረብ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላው በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ነጥብ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ ያስተላለፉት ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ በእርግጥ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ ጭብጥ መስርቶ የሰጠው ውሳኔ የለም፡፡ ነገር ግን የከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ሥልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ እና ይህም የሕግ ጥያቄ ከፍትሓብሔር ሥነ ሥርአት ህጉ አላማም አንፃር በዚህ ችሎት ቢታይ ተገቢ ሁኖ በመገኘቱ ጉዳዩን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት መመለሱ አስፈላጊ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ተጠሪ ክሱን የመሰረቱት አመልካች ሁከት ፈጠረብኝ፣ሊወገድልኝ ይገባል በሚል ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጠው መልስ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት የኪራይ ውልን መሰረት ያደረገ መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ስላልተወጡ ተገቢውን መፈጸሙን ገልጾ ተግባሩ ሁከት ሊባል የሚገባው አይደለም በሚል ተራክሮ የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ የአመልካችን ክርክር በመቀበል የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን ሲመለከተው አመልካችና ተጠሪ ግንኙነታቸው ውል እስከሆነ ድረስ የአመልካች ጥያቄም በውሉ መሰረት እንዲፈጸም የሚል በመሆኑ ተጠሪ የአመልካችን እርምጃ ሁከት ነው በማለት ክስ የሚመሰርቱበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140፣1148 እና 1149 ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ መብታቸውን ሊያስከብሩ፣ የሚችሉት ውላቸውን መሰረት በማድረግ እንጂ በሁከት ይወገድልኝ ክስ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች ተግባር ሁከት አይደለም በሚል ምክንያት የተጠሪን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው ምንም የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 08792 ታህሣሥ 02 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለመክሰስም ሆነ ለመከሰስ ሕጋዊ ሰውነት አለው ብለናል፡፡
3. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02754 ሐምሌ 01 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመ/ቁጥር 07713 ሕዳር 09 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት እ ዛ ዝ

ይህ ችሎት ሚያዝያ 06 ቀን 2002 ዓ.ም ሰጥቶት የነበረው እግድ ተነስቷል ይባፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ቤ/ኃ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሣሥ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ አቶ ጌትነት የኔው - ቀረቡ

ተጠሪ፣ አቶ ኢዩብ ቢንያም ወ/ቢኒያም ዮሐንስ - ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ሁከት ይወገድልኝ ሲል አመልካች ያቀረበውን ክስ የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ እንደክሱ አቀራረብ ከወሰነ በኃላ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ይታገዳል ሲል መሻሩን በመቃወም አመልካች በዚህ ሰበር እንዲታረም ስላመለከተ ነው፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በድሬደዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፍርድ ቤቱም የድሬደዋ ከተማ መሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ስለጉዳዩ አጣርቶ መግለጫ እንዲያቀርብ ካደረገ በኃላ በዚሁ መነሻ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ክልል ገብቶ ሁከት ፈጥሯል ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የድሬደዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ ሥር ተከሣሽ /ተጠሪ/ በአከራካሪው ይዞታ ላይ የግንብ አጥር የሰራው በ1987 ዓ.ም መሆኑን አመልካች ደግሞ ክስ ያቀረበው ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን በማመልከት የአመልካች ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149/2/ መሠረት በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም ባሻገር በፍሬ ነገር ረገድም በይዞታ ላይ ክርክር ሲነሳ ይዞታውን በእጁ አድርጐ በእውነት የሚያዝበት ባለይዞታ ቅድሚያ እንደሚሰጠው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1144/2/ ይደነግጋል በማለት ይዞታው የተጠሪ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በአመልካች በኩል የቀረበው የይዞታ ማረጋገጫ ውድቅ ተደርጐ ተጠሪ አከራካሪውን ቦታ ቀደም ሲል ይዞት ነበረ በሚል ይዞታው ለተጠሪ እንዲፀና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ህዳር 29 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል በይዘቱም አከራካሪው ይዞታ 52 ካ.ሜ የተባለው የአመልካች ይዞታ ሳይሆን ተጠሪ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በእጁ አድርጐ የሚያዝበት ስለመሆኑ በመጥቀስ አመልካች በይዞታው ሥር በሌላ ቦታ ሁከት ተፈጥሮብኛል በማለት ያቀረበው ክስ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

አመልካች ክስ ባቀረበበት ይዞታ ላይ ባለመብት ስለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር 02473 መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ስለመሆኑ ይኸው ማስረጃ ሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ስለመሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ አመልካች በዚሁ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው ይዞታ ስፋት 180 ካ.ሜ ሆኖ ከዚህ ውስጥ 52 ካ.ሜ በተጠሪ የተያዘ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡

ተጠሪ ይህንን ይዞታ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ይገዋለሁ ይበል እንጂ የቀበሌው አስተዳደር የተጠሪ ይዞታ እና የተሰራው ግንባታ ሕገወጥ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1140 እና 1144/2/ ተጠቅሶ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ሲታይ ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ ይዞ በእጁ በማድረጉ ለሕገወጥ ተግባር ሕጋዊ ሽፋን እንደመስጠት ያህል መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

የፍ/ብ/ሕጉ ዓላማ በሕግ አግባብ ባለይዞታ ለሆነው ወገን ጥበቃ ለማድረግ እንጂ ሕገወጥነትን ለማበረታታት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1146/1/ እንደሚያስገነዝበን በስውር ወይም በሚያሻማ አኳኃን የተደረገው ይዞታ ማንኛውንም መብት አይሰጥም፡፡

ስለዚህም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን ለመሻር መሠረት ያደረገው የሕግ ድንጋጌ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በዚህ አከራካሪ ይዞታ ባለመብት ስለመሆኑ በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም ሆኖ ክስ የመሠረተው ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑ ሲታይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149/2/ መሠረት የሁለት ዓመት ጊዜ አልፎበታል የሚባልበት ሁኔታ የለም፡፡

በመሆኑም አመልካች ከተጠሪ የተሻለ መብት ያለው መሆኑን ከአስተዳደር አካል የተሰጠውን የምስክር ወረቀት መሠረት አድርጐ ያቀረበው ክስ መታየት የሚገባው ይህንኑ ማስረጃ ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ ይዞታውን በእጁ ካደረገበት ጊዜ ሊሆን አይገባም፡፡

ባጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከሕጉ ጋር በአግባቡ ሳያገናዝብ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 00514/2002 ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የድሬዳዋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01098 ሰኔ 28 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገው ክርክር ግራቀኙ የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎችን /ከቅጽ 8 - 10 / ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ቅጽ - 8

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት				1
1	ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2)	33945	አቶ ሣልህ ሁሴን እና ደግፌ ደርቤ	ጥቅምት 20/2001	2
2	ማንኛውም ክርክር ሊወሰን የሚገባው በቀረበው ማስረጃ እና በህጉ መሰረት ብቻ ስለመሆኑ	36848	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና መኮንን ግርማይ (ሦስት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	5
3	በክርክር ሂደት ተቃዋሚ ወገን መጠራት ያለበት ምስክር ከመሰማቱ በፊት ስለመሆኑ	35946	እነ አቶ ማማሸ ወ/ስላሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሰብለ ወንድይራድ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 27/2001	7
4	መጥሪያ ለምስክር እንዲደርስ በሚል ፍ/ቤቶች ሊልኩ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103	36479	ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ኃይሉ ወልዱ	ጥቅምት 25/2001	9
5	በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የተወሰነበት ተከራካሪ ፍ/ቤት ህጉን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78	36412	ተስፋሁን ዋኘው እና በጃክ አግሮ ኮሜርሻል ኢንተርፕራይዝ	ጥቅምት 13/2001	12
6	የቃል ክርክር ለመስማት እና የጽሁፍ መልስ ለመቀበል በሚል ፍ/ቤቶች በአንድ ቀጠሮ ሁለት ተግባራትን ለማከናወን የሚሰጡት ትዕዛዝ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ ስለመሆኑ	36380	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ታረቀኝ ገ/ዓዲቅ	ጥቅምት 18/2001	16
7	የበላይ ፍ/ቤቶች ውሣኔን ወደጐን በመተው በሥር ፍ/ቤቶች የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ	37725	እነ በቀለ ድሪብሣ (ሁለት ሰዎች) እና የምክር በሪሁን	ጥቅምት 6/2001	18
8	በግልፅ የቀረበን ክርክር በተቆጠረ ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ እንዲጣራ/እንዲነጥር/ ሣይደረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	37105	ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር እና ሰለሞን አበበ ኮከብ	ጥቅምት 25/2001	21
9	ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን አስቀርተዋል /ትተዋል/ ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢያዊ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በተረዱበት ደረጃ እርስ በርሳቸው ስምምነት	37678	ድራጋዶስ ጄ ኤንድ ፒ.ጆይንት ቬንቸር እና ሳባ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር	ህዳር 18/2001	23

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ባደረጉ ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 350(1) እና (2)				
10	በሥር ፍ/ቤት ዳኝነት ያልተጠየቀበት ጉዳይ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ታይቶ ሊወሰን የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1), 182(2)	37762	ገወኔ ኢንተርኘራይዝ ኃ/ተ/የግ/ማህበር እና አቶ የሱፍ ይማም	ታህሣሥ 9/2001	26
11	ከሥራ ውል ጋር በተያያዘ የሚጠየቁ ክፍያዎች ሳይነጣጠሉ በአንድ ላይ መቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4), 5	38601	የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና ወ/ሮ ከድጃ ሳቢር	ታህሣሥ 14/2001	30
12	• ክርክር ከሚካሄድበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ መብትና ጥቅም እንዳለ የተረጋገጠ እንደሆነ በክርክር ጣልቃ ለመግባት በቂ ምክንያት ስለመሆኑ • በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ጥያቄ (ተቃውሞ) አለማቅረብ ሚስት/ባል የሆነን ወገን የጋራ ነው በሚለው ንብረት ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚያግድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41	37742	ወ/ሮ አልማዝ ጐንፌ ኦሪቲ እና ወ/ሮ ፀሐይ ሊበን	ታህሣሥ 7/2001	32
13	በአንድ መንግስታዊ መዋቅር ሥር የሚገኙ ሁለት ራሳቸውን የቻሉና የህግ ሰውነት ያላቸው ተቋሞች የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቁ አካላት በመሆናቸው ብቻ እንደ አንድ መቆጠር የሌለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 አዋጅ ቁጥር 1/1995,18/1997,2/1995,4/2000	37502	የአዲስ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ህግ ጉዳዬች ቢሮ እና እነ ወ/ሮ የኃላሸት ገመዳ ቤኛ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 2/2001	34
14	ፍ/ቤቶች ለክርክር ፍትሐዊነት ተገቢ ነው ብለው ሲያምኑ ማናቸውንም አይነት ማስረጃ አስቀርበው መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 145,345,327/3/	29861	ወ/ሮ ህጽአት ፍስሐጽዬን እና እነ ወ/ሮ አልማዝ ተረፈ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 14/2001	37
15	የክርክር ዋነኛ ጭብጥ በሆነ ጉዳይ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሣኔ ፍ/ቤት በድጋሚ “ስህተት ለማረም” በሚል ምክንያት ሊለውጥ ወይም ሊያሻሽል ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208	37303	ኤ.ሲ.ዲ አይ/ቮካ-ኢትዮጵያ እና እነ ሃይደር አሊ (ስምንት ሰዎች)	ጥር 26/2001	41
16	ዳኝነት የሚጠየቅበት መብትና ጥቅም በግልጽ ተለይቶ ያልተመለከተበት አቤቱታ የክስ ምክንያት እንደሌለው የሚቆጠር በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33, 231	38419	የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 አስ/ጽ/ቤት እና አቶ ያሲን ጀማል	የካቲት 5/2001	43
17	ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ክርክር መሠረት በማድረግ አግባብነት ያለውን ጭብጥ ሳይመሰርቱ የሚሰጡት ውሣኔ ህጋዊ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ	37391	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ ስዩም ማሞ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 3/2001	46
18	በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች በሚሰጠው ውሣኔ ጥቅማቸው /መብታቸው/ ሊነካ የሚችል የሆነ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.40	39540	ናስ ፋድስ የድ/ዳ/ጨ/ጨ/ፋብሪካ ተከራይ እና እነ ስንዱ ደጀኔ (ዘጠና ሦስት ሰዎች)	የካቲት 26/2001	48
19	አንድ ጉዳይ ከዚህ ቀደም በፍርድ ያለቀ ነው		ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ	መጋቢት	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5	36780	እና አቶ ገ/ኪዳን እንግዳ	3/2001	51
20	ነዋሪነታቸው በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሣ ክርክርን የክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት የሚገኘው ወይም ውል የተደረገው በአንደኛው ክልል እንኳን ቢሆን የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(2)	36460	መሐመድ ሰዓዳይ ረኛ እና እነ አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ ፈረጀ (ሰባት ሰዎች)	መጋቢት 24/2001	59
21	በተከራካሪ ወገኖች የተጠየቀን ዳኝነት አስመልክቶ ግልጽ ፍርድ አለመስጠት ስህተት ስለመሆኑ	39144	አቶ ልዑልሰገድ ቦኔ እና ኢትዮ ሴዘር ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር	መጋቢት 24/2001	62
22	የቀረበበትን ክስ ያመነ ተከሣሽ ባመነው መሠረት ውሣኔ ለመስጠት የሚከለክል በቂ የህግ ምክንያት እስከሌለ ድረስ ውሳኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ	38597	እነ ጋሻው መንግስቱ ካሣ (ሁለት ሰዎች) እና ናይል ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሚያዝያ 6/2001	65
23	በአንድ ዘንግ የሚመደቡ ተከራካሪዎች እና አንድ ጭብጥ ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች ተጣምረው እንዲታዩ ያለማድረግ መሠረታዊ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 11(5)	40024	ሽራተን አዲስ እና እነ አቶ እያሱ መገርሣ	ሚያዝያ 29/2001	67
24	የሥር ፍ/ቤቶች የፈፀሙትን ሥህተት ለማረም በሚል በሥር ፍ/ቤት ተከራካሪ ከነበሩ ወገኖች መካከል አንዱ ወገን ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሌላኛው ወገን ሳይጠራና ሳያከራክር ውሣኔ መስጠት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1)	34504	አቶ አበባው የሺድንበር እና አቶ ካሣ በቀለ	ሚያዝያ 6/2001	71
25	በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣን ክርክር መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 329(1), 182(2)	37761	ገብረመስቀል ንጉሴ እና አዲስ ልብስ ስፌት አ.ማ	ሚያዝያ 20/2001	73
26	ክስ በሚሰማበት የቀጠሮ ዕለት የይግባኝ ባይ አለመቅረብ ጋር በተያያዘ መዝገብ ሊዘጋ የሚችለው መልስ ሰጪው ይግባኙን ሙሉ በሙሉ ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ	38181	የኢትዮጵያ መንግዶች ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ወንድይፍራው (ሁለት ሰዎች)	ግንቦት 4/2001	76
27	ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገን ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የሚጠቅም ያልሆነ እንደሆነና የሰው ምስክር በተጨማሪነት የቆጠረ እንደሆነ ፍትሐዊ የሆነ ውሣኔን ለመስጠት የምስክሮችን ቃል መስማት ያለበት ስለመሆኑ	42706	ላየን ሴኩሪቲ ኩባንያ እና አቶ ጥላሁን ገ/እግዚአብሔር	ግንቦት 25/2001	78
28	በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መለወጥ ወይም መሻሻል ተከትሎ ማናቸውም ተከራካሪ ወገኖች ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚሰጥ ትዕዛዝ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ እንጂ የግድ የሚሰጥ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349(1)	37741	አቶ መኮንን ዘውዴ እና እነ አቶ ተሾመ ሽፈራው (ሦስት ሰዎች)	ሰኔ 4/2001	80
29	ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ጉዳይ ለማስተናገድ ስልጣን	38452	የአ.አ ከተማ ቤቶች ኤጀንሲ	ሰኔ	82

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9(2)		እና አቶ አለም ገብሩ	11/2001	
30	አንድን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማንሣት ስልጣን የለኝም ያለ ፍ/ቤት ጉዳዩ በበላይ ፍ/ቤት ታይቶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ እንዲያከራክር ጉዳዩ የተመለሰለት እንደሆነ ሌላ ተጨማሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለማየት አልችልም ማለት የማይገባው ስለመሆኑ	39014	አለሙ መግራ እና እምነቱ እንዳሻው ህንፃ ተቋራጭ	ሰኔ 23/2001	84
31	የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈበት ተከራካሪ ወገን የሚያቀርበው የማስፈቀጃ ማመልከቻ በበቂ ምክንያት የተደገፈ መሆን/አለመሆኑን ፍ/ቤቶች በጥሞና መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 326(1)	38145	ወ/ሮ አያልነሽ ዘገየ እና አቶ ተስፋዬ ደምሴ	ሰኔ 30/2001	86
32	አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃነት የሚጠቅሳቸው ምስክሮች፣ ሰነዶች ወይም ሌላ አስረጂዎች (የሙያ) ማስረጃው በፍ/ቤቱ በኩል በጭብጥነት ተይዞ ከሚፈታው ፍሬ ነገር ጋር አግባብነት ያለው እና በህግ ተቀባይነት ያለው እስከሆነ ድረስ ቀርቦ መሰማት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111, 249 እና 257	38683	የትምህርት መማሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት እና አቶ ሣህሉ ወ/ማርያም	ሰኔ 25/2001	88
33	ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአግባቡ ሳይመረምሩ እና ለውሣኔያቸው በቂ ምክንያት ሣይሰጡ መሻር የማይችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1)	38844	የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን እና ጋድ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህ	ሰኔ 25/2001	90
34	ተከራካሪ ወገኖች በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲቀርብላችው የሚጠይቁት ማስረጃ የተያዘውን ጉዳይ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ዕልባት ለመስጠት የሚያስችል እስከ ሆነ ድረስ ጥያቄውን ፍ/ቤቶች ሊቀበሉት የሚገባ ስለመሆኑ	36979	ቤዛ አማካሪ መሀንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ሚስተር ሸሬሃሪ ብራማቫሪ ጐፓል	ሐምሌ 23/2001	94
35	ሦስተኛ ወገኖች በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር እንዲገቡ የሚያስፈልግበት ሁኔታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43	41544	ሰላም የህዝብ ማመላለሻ (አ.ማ) እና ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ	ሐምሌ 8/2001	96
አስራና ሰራተኛ					98
36	የኘሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀፅ 2/ስ/	35197	አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና ኤፍሬም ንዋየማሪያም	ጥቅምት 13/2001	99
37	ለኘሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች የተቀጠሩበት የኘሮጀክት ሥራ ሲጠናቀቅ የሥራ ውላቸው የሚቋረጥ ስለመሆኑ	35621	ሰንሻይን ኮንስትራክሽን እና እነ አቶ ፍቃዱ ገቢሣ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	102

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10/1//ሠ//ሀ/				
38	በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 ባልተሸፈነ ጉዳይ ላይ በአሠሪና በሠራተኛ መካከል የተደረገ የህብረት ስምምነት መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ	36692	አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት እና ተስፋዬ መኮንን	ጥቅምት 25/2001	104
39	ሠራተኞች ለሚፈፅሙት ጥፋት በህብረት ስምምነት የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች የተቀመጡ በሆነ ጊዜ አሰሪው በሠራተኛው የተፈፀመውን ጥፋት ክብደት በመመዘን ይመጥናል የሚለውን ቅጣት መወሰን የሚችል ስለመሆኑ	37027	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት አስለፈች ደስታ	ጥቅምት 11/2001	106
40	አንድ ድርጅት እንደስራው ፀባይ በህግ ከተደነገገው ማዕቀፍ ሳይወጣ/ሳይጥስ/ የሥራ ሰዓቱን ማሻሻል ስለመቻሉ አዋጅ 377/96 አንቀፅ 61/1/	36518	ሜታ አቦ ቢራ አ.ማ እና እነ ሳሙኤል ተፈራ (አራት ሰዎች)	ጥቅምት 4/2001	108
41	የአሰሪ ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደል ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1/ተ/	35484	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና አቶ ደረጀ ማሞ	ህዳር 25/2001	110
42	አሰሪ ሠራተኛውን በሣምንት ዕረፍቱ ሥራ እንዲሰራ ለማድረግ የሚችል ስለመሆኑ	37815	አለማየሁ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ እና አቶ አብዮት በፈቃዱ	ህዳር 2/2001	112
43	በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ “የሥራ ቀናት” የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(3)	36377	የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና ተሾመ ኩማ	ህዳር 2/2001	114
44	የኘሮቪደንት ፈንድ ወይም/ እና የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ	37048	የሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ሣህሉ ምትኩ	ህዳር 2/2001	116
45	በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ መውጣት በራሱ አንድን ሠራተኛ ወደ ቀድሞ ሥራ ለመመለስ መብት የሚሰጥ ስላለመሆኑ	37256	አዲስ አበባ የምግብ አዳራሽ አስተዳደር እና ወ/ሮ የውብዳር ጥላሁን	ህዳር 4/2001	119
46	ለአምስት ተከታታይ ቀናት በሥራ ገበታ ላይ ያለበቂ ምክንያት አለመገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ስለመሆኑ	37402	የንኮማድ ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ ቡሽራ በቀለ	ህዳር 11/2001	122
47	ከሥራ ጋር በተገናኘ በሚፈፀም ድርጊት መነሻነት በሠራተኛው ላይ በፖሊስ የሚደረግ ምርመራ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ	37573	የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና አቶ መሐመድ አደን	ህዳር 16/2001	125
48	የሥራ ውል በስምምነት ተቋረጠ ለማለት የሚቻለው ስምምነቱ በፅሁፍ የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ	37575	ቃሊቲ ባሌስትራ ማምረቻ እና ብርሃኑ ልደት ወልዴ	ህዳር 2/2001	127
49	በአሰሪ በተደረገ የሥራ ዝውውር ቅሬታ አድሮብኛል በሚል ምክንያት ከሥራ መቅረት የህግ ድጋፍ የሌለው ስለመሆኑ	37778	አዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪ አከፋፋይ አ.ማ እና አቶ ካሣሁን ከበደ	ህዳር 4/2001	129
50	በአሰሪና በሠራተኛ መካከል የሥራ ውል ግንኙነት አለ ለማለት የሚቻልበት አግባብ	03171	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና ወ/ት ትርሲት ደገፋ	ህዳር 16/2001	132
51	አዲስ መዋቅርን ተግባራዊ ያደረገ	36210	አቃቂ መለዋወጫ	ህዳር	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ተቋም/ድርጅት/ ሠራተኞቹን “ራሱ ባወጣው መስፈርት” መሰረት ሊመድብ ስለመቻሉ		ዕቃዎችና መሣሪያዎች አ.ማ እና አቶ ኃይለ ሳልቫቶር	2/2001	136
52	• አንድ ሠራተኛ በአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበት የሚችልበት አግባብ • በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ “የአሰሪ ንብረት” በሚል የተገለፀው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1//ሸ/	34669	አድማስ ኮሌጅ እና ሠለሞን ሙሉአለም	ታህሣሥ 2/2001	138
53	የተረከበው የአሠሪ ንብረት የጠፋበት ሰራተኛ ንብረቱን ለማል ጥቅሙ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ያዋለው ያለመሆኑን ካላስረዳ በቀር የንብረቱ መጥፋት ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)(ቀ) 14(2)(ለ)(2)	39118	ደሣለኝና ቤተሰቡ ኃላ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ በፈቃዱ በላይ	ታህሣሥ 23/2001	141
54	በህብረት ስምምነት ወይም በሌላ አካኋን የተወሰነ የሥራ ውል የሚቋረጥበት ምክንያት ካለ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ያልተመለከተ ቢሆንም ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 3787/96 አንቀፅ 27/1/	36591	ማታዶር አዲስ ጎማ አ.ማ እና ደረጀ ኡመታ	ታህሳስ 14/2001	144
55	የሥራ መሪ በሆነ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት መስራት ግለሰቡን የሥራ መሪ ከመሆን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 3/2/ /ሐ/	36894	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ሙላት ታረቀኝ	ታህሳስ 30/2001	146
56	ለተወሰነ ጊዜ በተደረገ የሥራ ውል ግንኙነት ለሠራተኛው የሚከፈል የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸው ባስቀመጡት መልክ የሚፈፀም ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 35/2/	37201	ማታዶር አደስ ጎማ አክሲዮን ማህበር እና እነ አቶ ኤልያስ በቀለ (አስራ አራት ሰዎች)	ታህሣሥ 30/2001	148
57	የጥበቃ ሥራን የሚሠራ ሠራተኛን በተመለከተ የሥራ ውሉ ያለአግባብ ተቋርጧል በሚል ሲወሰን በአሠሪውና ሠራተኛው መካከል ሊኖር የሚገባው ከፍተኛ መተማመን የሚሻክር በመሆኑ ሰራተኛው ወደ ሥራ እንዲመለስ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43	37454	ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል እና ከበደ ሰይፉ	ታህሣሥ 16/2001	151
58	ወደ ሥራ እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ የሥራ ክርክሮችን የሚወስነው አካል ሠራተኛው አግባብነት ያላቸውን ክፍያዎች ተከፍሎት ከሥራ እንዲሰናበት ሊወሰን የሚችለው በመጀመሪያው ፍርድ መሠረት ያልተፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/	38255	አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አለምሰገድ ኃይሉ	ታህሣሥ 23/2001	154
59	የሥራ ውሉን በፍቃዱ የቋረጠ ሠራተኛ የህብረት ስምምነት የሚፈቅድለት ከሆነ	37551	አቶ ድካምየለህ ጥበቡ እና አርሾ የህክምና	ታህሣስ 9/2001	157

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ኘሮቪደንት ፈንድና የሥራ ስንብት የማግኘት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ		ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር		
60	የስራ ውል የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው ተብሎ በተወሰነ ጊዜ የስራ ውሉ የተቋረጠበት ወገን/ሠራተኛ/ ሊወሰኑለት የሚገቡ ክፍያዎች	34476	ኮመላ በጅማ እና ብሔራዊ አስጭኚና ጉዞ ወኪል	ታህሳስ 2/2001	160
61	አንድ የሥራ ዘርፍ የአሠሪው ቋሚ ሥራ ቢሆንም በዚሁ ዘርፍ ሠራተኞችን ለተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ቀጥሮ ሊያሰራ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሐ)	40305	የኢትዮጵያ ፖልኘና ወረቀት አ.ማ እና እነ አቶ ታመነ ጫላ	ታህሣሥ 21/2001	163
62	አንድ ሠራተኛ ይሰራው የነበረ የሥራ መደብ መሰረዝ ወይም አለመኖር ለሥራ ውሉ መቋረጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1) (መ)	40804	ዳንዲቦሩ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና እነ ተክሉ ኡርጌ ኢደኤ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 26/2001	165
63	አንድ ሠራተኛ ወደ ሥራ ሲሄድና ከሥራ ወጥቶ ወደቤቱ ሲመለስ አሰሪው በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ሲጠቀም አደጋ የደረሰበት መሆኑ ከተረጋገጠ ሦስተኛ ወገኖች ለአደጋው ያደረጉት አስተዋፅኦ መኖር አሰሪው የጉዳት ካሣ ላለመክፈል እንደመከላከያ ሊሆነው ስላለመቻሉ እና የጉዳት ካሣው በጉዳት የተነሣ ህይወቱን ላጣው ሠራተኛ ጥገኞች የሚከፈልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 95/2/, 96/1/, 98/2/, 97/1/, 107/1//ሐ/, 110/ 112	36194	ዶ/ር ማንደፍሮ እሸቴ እና ፍሬድሪክ ኤቨርት ሲቲፍቱንግ	ጥር 28/2001	167
64	በድርጅት ውስጥ በተደረገ የመዋቅር ማሻሻያ የሥራ መደብ የተሰረዘ እንደሆነ የሥራ መደብ የተሰረዘበትን ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚቻልበት አግባብ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1)(መ)	38811	ርሆቦት ሆሊ ሴቪየር ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ አማረ አድማሱ	የካቲት 17/2001	173
65	በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለ የሥራ መደብ በሌላ 3ኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የስራ ውል ለማቋረጥ ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 28	38435	ኤስ.ኦ.ኤስ የህፃናት መንደር እና እነ አቶ ከበደ ኩምሣ (ስድስት ሰዎች)	የካቲት 17/2001	175
66	ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል የሚቋረጠው ማስጠንቀቂያ በመሰጠት ስለመሆኑ	38023	የመንግስት ቤቶች ኤጅንሲ እና ብርሃኑ ደስዬ	የካቲት 17/2001	178
67	በአሰሪያቸው ላይ ክስ አቅርበው ያስፈረዱ ሠራተኞች የአሰሪውን ንብረት በዋስትና ከያዙ ባለገንዘቦች ይልቅ የቅድሚያ ክፍያ መብት ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 167 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀጽ 2857(1) አዋጅ ቁ. 186/94 አንቀጽ 80 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ- መንግስት አንቀፅ 13(2)	40921	አቢሲንያ ባንክ (አ.ማ) እና አብዱ አህመድ (ሁለት መቶ ስልሣ ስድስት ሰዎች)	የካቲት 26/2001	180
68	የአንድ ሠራተኛን ድርጊት ከባድ ቸልተኝነት ነው ለማለት የሥራውን ባህሪ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ	41115	ሜድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ ሞገስ ሽፈራው	የካቲት 26/2001	183
69	አሠሪ የአንድን ሠራተኛ ደሞዝ እና ሌሎች		ሙገር ሲሚንቶ	መጋቢት	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ጥቅማጥቅም ሣይነካ በተመሳሳይ የሥራ መደብ ላይ አዛውሮ ሊያሠራ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 13(2) እና (7)	40938	ኢንተርኘራይዝ እና አቶ ኃይሉ መንግስቱ	24/2001	186
70	አንድ ሠራተኛ የአሠሪው ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደሉ የተረጋገጠ እንደሆነ አሠሪው ሠራተኛውን በፍ/ብሔር ክሶ ገንዘቡን የማስመለሱ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)	42292	የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ከበደ አቡነቱ	መጋቢት 24/2001	188
71	በአሠሪው ወደሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሠራ የተደረገ ሠራተኛ ዝውውሩን በወቅቱ ሣይቃወም የተዛወረበት የሥራ ገበታ ላይ ለ5 ተከታታይ ቀናት የቀረ እንደሆነ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27 (1)(ለ)	41623	አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ሣሙኤል ኪዳኔ	መጋቢት 8/2001	191
72	• ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛን ከሥራ የማገድ ተግባር ሠራተኛን እንደማሰናበት የማይቆጠር ስለመሆኑ • አሠሪው ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛው ለታገደበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፍል የሚደረግበት አግባብ • ከሥራ ያለአግባብ ታገድኩኝ በሚል የቀረበን ክስ በማስተናገድ ላይ ያለ ፍ/ቤት በክርክሩ ሂደት ሠራተኛው ከሥራ የተሰናበተ መሆኑን ካወቀ የተያዘው ጭብጥ እንዲሻሻል እና ጭብጡ እንዲስተካከል በማድረግ ጉዳዩን ማየት ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(4)	41411	ሙሉመል ዳቦ መጋገሪያ ድርጅት እና አቶ በለጠ ተገኝ	ግንቦት 11/2001	193
73	• አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ከጉዳቱ በኋላ የቀድሞ ስራውን መስራት መቀጠሉ ብቻ አሰሪውን የጉዳት ካሣ ከመክፈል ነፃ የማያወጣው ስለመሆኑ • በሥራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተገናኘ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ውስጥ የተመለከተውና “የመስራት ችሎታ” የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ እና የጉዳት ካሣ መጠንና ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 109, (1) እና (3) , 107, 99(1), 102(3) አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 33	43370	የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና አቶ ጌታቸው ገድሌ	ግንቦት 12/2001	196
74	• የድርጅት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የአሰራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሠራተኛ ቅነሣ የሚደረግበት አግባብ • ቅነሣ የሚደረግበትና ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ	42752	እነ ወ/ት ማሜ አሠፋ (ሰላሳ ስድስት ሰዎች) እና ብሔራዊ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል(NTO)	ግንቦት 12/2001	199

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(2)(ሐ), 29(3)				
75	በሠራተኛ እጅ የሚገኙ የአሠሪ ንብረቶች መመለስ ወይም አለመመለስ ጉዳይ ሠራተኛው የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚያነሣቸውን ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ለማስተናገድ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 36, 38	39464	ሐረር ቢራ አክሲዮን ማህበር እና አቶ አብዱልቃድር አብዱረዛቅ	ግንቦት 25/2001	202
76	ቀድሞ ይሰራበት የነበረን የሥራ መደብ በመሰረዙ ምክንያት ሠራተኞችን በማሰናበት ፋንታ በክፍያ አነስተኛ ወደሆነ ሌላ የሥራ መደብ እንዲሰሩ ያደረገ አሠሪ ለሠራተኞቹ በቀድሞው ደመወዝ መሠረት እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	41786	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ አቶ አሰፋ አቤቦ (ሦስት ሰዎች)	ግንቦት 26/2001	204
77	በጥበቃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ እንዲጠብቅ የተሰጠው የአሰሪ ንብረት የጠፋ እንደሆነ ሰራተኛው ለንብረቱ መጥፋት አስተዋጽኦ ያለማድረጉን ማረጋገጥ ካልተቻለ በስተቀር በሃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ	39650	የየረር በር ምስራቅ ፀሐይ ቅዱስ ዑራኤል ቤ/ክ እና እነ ቁስ ሰፊነው ደሣለኝ	ግንቦት 27/2001	207
78	በተጭበረበረ ማስረጃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የማጭበርበር ድርጊቱ የታወቀ/የተደረሰበት/ ከሆነ ማጭበርበሩ የተከሰተው ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ተቆጥሮ ሊያስናብተው የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1) (ሐ)	39543	የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ በረከት ተ/ማርያም	ግንቦት 4/2001	209
79	ለኘሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቅነሣ በሚካሄድበት ወቅት አሰሪው በአዋጅ ቁ.377/96 ላይ የተመለከተውን የሠራተኞች ቅነሣ ሥነ-ሥርዓት መከተል የማይጠበቅበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30(1)	39042	ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ጀማል መሐመድ	ግንቦት 26/2001	211
80	የሥራ መደብ ዝውውርን በመቃወም ቅሬታን በማሰማት ላይ መሆን በስራ ቦታ ላይ ላለመገኘት እንደ በቂ ህጋዊ ምክንያት የሚወሰድ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ)	38189	ሮፓክ ኢንተርናሽናል ኃላ/የተ/የግል ማህበር እና ይደርሳል አእምሮ	ግንቦት 27/2001	213
81	አሠሪ የሥራ መሪ የሆነን ሠራተኛውን ያሰናበተው ያለበቂ ምክንያት ቢሆንም እንኳን ተገቢ የሆነ ካሣ ለመክፈል ከሚገደድ በስተቀር ሠራተኛውን ወደ ሥራ እንዲመልስ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ	37982	የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና አቶ ታደሰ ዘነበ	ሰኔ 16/2001	216
82	ለሥራ ማስኬጃነት የተቀበሉትን የአሰሪ ገንዘብ አጉድሎ መገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)	41720	የእንጨት መሠንጠቂያና መገጣጠሚያ ድርጅት እና ረዲ እንዳለ	ሰኔ 9/2001	219
83	የሥራ ውል የተቋረጠው በህጉ አግባብ ነው ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ የማይከፈል ስለመሆኑ	39861	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ሣምሶን በለጥካቸው	ሰኔ 18/2001	221
84	በቃል ከሥራ ተሰናበትኩ በሚል ክስ	43610	ናይኮ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር	ሐምሌ	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የሚያቀርብ ሠራተኛ አሰሪው ከሥራ ያሰናበተው ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ		እና አቶ ሰለሞን ተሰማ	21/2001	224
85	አሠሪ የሆነ ወገን የሥራ ቅልጥፍናን፣ ውጤታማነትን፣ የኢንዱስትሪ ሰላምን ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድን ሠራተኛ የተቀጠረበትን ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በጠበቀ ሁኔታ አዛውሮ ለማሰራት የሚችል ስለመ ሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 2 (1), 4	44033	መንበረ ፓትሪያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና አቶ ይበልጣል አጥናፉ	ሐምሌ 22/2001	226
86	በህግ ወይም በሕብረት ሥምምነት የተመለከተው የጡረታ እድሜ ሣይደርስ በመንግሥት መመሪያ በጡረታ እንዲገለሉ የተደረጉ ሠራተኞችን በተመለከተ አሰሪ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ለመክፈል የማይገደድ ስለመሆኑ	42906	የኢትዮ-ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ እና እነ ትዕግስት ማሞ (ሰማንያ አንድ ሰዎች)	ሐምሌ 21/2001	228
87	የኮንስትራክሽን ሥራ የሚሰራ ድርጅት የሥራው መጠን በቀነሰ ጊዜ ሠራተኞችን ለማሰናበት የማስጠንቀቂያና ሌሎች የቅነሳ ሥነ-ሥርዓቶችን ሳይከተል ቅነሳ ለማካሄድ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30	42075	አፍሪካዊት የህንፃ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና እነ አቶ እንድሪስ ዓሊ	ሐምሌ 16/2001	231
88	የሥራ ውል □ንደተቋረጠ የጡረታ አበል ለማግኘት መብት ያለው ሠራተኛ የሥራ ስንብት የማይከፈለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39 አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2) (ሰ)	39808	ናዝሬት ማሙና ፋብሪካ እና ዘውዴ ኃ/ማርያም	ሐምሌ 21/2001	233
89	የሥራ መሪ ከሠራተኛ ሊለይ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3, አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2	42901	የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና ወ/ሮ ንግስት ለጥይበሉ	ሐምሌ 21/2001	235
90	በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በሚካሄድ የሥራ ክርክር የሚያዘው ጭብጥ አሰሪው ገንዘብ ይከፈለኝ በሚል በሠራተኛው ላይ ክስ ባቀረበ ጊዜ ከሚያዘው ጭብጥ ጋር አንድ አይነት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ	39471	ኤርሚያስ ሙሉጌታ እና በክልቻ ትራንስፓርት አ/ማ	ሐምሌ 29/2001	237
91	በሃይማኖት ተቋም ውስጥ መንፈሳዊ(ሃይማኖታዊ) አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ የሚሸፈን ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	18419	ሐመረወርቅ ቅ/ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና እነ ዲያቆን ምህረት ብርሃን(ስድስት ሰዎች)	ግንቦት 4/1998	239
ቤተሰብ					242
92	የውርስ ሀብት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክስ የግዴታ ውርስ ከተጣራ በኋላ መቅረብ የሌለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1)	34703	እንዳሻው ፍቃዱ እና እነ ወንድማገኝ ፍቃዱ(ሰባት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	243
93	ኑዛዜ ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም በሚል የሚያቀርቡት የመቃወም አቤቱታ	36604	ወ/ሮ ፅጌ መንግስቱ እና እነ አቶ ወንድይራድ	ጥቅምት	245

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ኑዛዜው በተነበበ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973		መንግስቱ(ሁለት ሰዎች)	25/2001	
94	ከጋብቻ በፊት የግል የነበረን ንብረት መነሻ በማድረግ በጋብቻ ጊዜ በግብይት የተገኘ ንብረት የግል ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው በፍ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 58(2), 57, 62(2)	37275	ሻ/ባሻ ገዛኸኝ ድልነሣው እና ወ/ሮ ተዋበች ደመቀ	ጥቅምት 18/2001	247
95	ግልፅ ኑዛዜ ህጋዊ እንዲሆን መሟላት ያለበት ፎርማሊቲ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882	36777	አቶ ወንድም አገኘ ዘውዱ እና እነ አቶ ታፈሰ ወንድአፈራሽ (ሶስት ሰዎች)	ጥቅምት 25/2001	251
96	ህፃናትን ማዕከል ያደረጉ ክርክሮች የልጆችን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ መስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ	35710	ወ/ሮ እፀገነት እሸቱ እና ወ/ሮ ሰላሚዊት ንጉሴ	ታህሣስ 16/2001	253
97	የስጦታ ውል የተፈፀመው ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ከሆነ ይኼው ግለሰብ እንደ ምስክር ተደርጐ ባይፃፍም ምስክር ተደርጐ ሊቆጠር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443,881,882	37562	አቶ ሣሙኤል ፈረንጅ እና አቶ ግርማ ታፈሰ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 28/2001	258
98	ጋብቻ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው በህግ አግባብ ተፈፅሟል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 28(3)	41896	ወ/ሮ ታደለች ዋለልኝ እና እነ ወ/ሮ አዲስዓለም ፀጋ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 26/2001	261
99	የሚች እዳን ለመክፈያ በአፈፃፀም ሊያዝ የሚገባው በውርስ የተገኘውን ሀብት እንጂ የወራሾች የግል ሃብት ስላለመሆኑ	38691	አቶ ለገሰ ቢራቱ እና አቶ ደረጀ ጅማ ገርግሶ	የካቲት 24/2001	263
100	የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሣይኖር የጋራ የሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት በሌለኛው ተጋቢ የተሸጠ እንደሆነ ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ 6 ወር ውስጥ እንዲሁም በማናቸውም ሁኔታ ደግሞ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየት ስለመቻሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 69(2)	38126	ዲያቆን ኃይለጊዮርጊስ ወንድምሲያምረኝ እና እነ ወ/ሮ የሺ ተፈሪ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 22/2001	266
101	በኑዛዜ የተገኘ ንብረት በ10 (አሥር) ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተጠየቀ በስተቀር በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ	38152	የወ/ሮ ገነት ዳምጤ ወራሾች እና እነ አቶ ይልማ አስፋው	ሚያዝያ 29/2001	268
102	የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ ከመረመረ በኋላ የጉዳዩን ጭብጥ በመያዝ ወደ ሥር ፍ/ቤት የመለሰው እንደሆነ አስቀድሞ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ፍርድ እንደሌለ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ	37313	እነ አቶ መሐሪ ተ/ማሪያም (ሁለት ሰዎች) እና የወ/ሮ ገነት መኮንን ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	ግንቦት 18/2001	271
103	ወራሽ የሆኑ ወገኖች የሚያቀርቧቸውን ተገቢነት ያላቸው ማስረጃዎች በሙሉ አሰባስቦ በመስማት ያልተከናወነ የውርስ ማጣራት ሪ□ርት በህግ አግባብ የተከናወነ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241, 270 እና 345	42525	እነ አቶ አብዱልዋሲቅ አርጋው እና ወ/ሮ አልዋያ አባበሊስ	ግንቦት 27/2001	274
104	የተናዛዡ ህጋዊ ንብረት ባልሆነ ነገር ላይ		ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ	ሰኔ	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የተደረገ ኑዛዜ በፍ/ቤት ቢፀድቅም እንኳን የኑዛዜ ሰነዱ ዋጋ የማይኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 865	32817	እና እነ ወ/ሮ ቱቱ ዘውዴ(ሦስት ሰዎች)	11/2001	277
105	የገበያ ዋጋን መሠረት ያላደረገና የግንባታ ዋጋ ግምት ላይ ብቻ ተመርኩዞ የሚደረግ የውርስ ሀብት ክፍፍል ፍትሐዊ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ	40510	ቴዎድሮስ መንበሩ እና ገ/ህይወት ታደሰ	ሰኔ 23/2001	281
106	ጋብቻ በሁለት የተለያዩ ሥርዓቶች የተፈፀመ ቢሆንም አንድ ጊዜ በህግ አግባብ የተደረገ ፍቺ በቂና ሙሉ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 75(ሐ)	40781	ፍቅረስላሴ ካህሣይ እና ወ/ሮ ሮማን ታደሠ	ሐምሌ 30/2001	283
107	በውርስ ሃብት ክፍፍል ላይ ተወላጅ የሆነ ሰው ከሩብ በላይ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ክፍፍሉ እንዲቀር ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 11/22,913,1060,1037-1051,942	18394	ወ/ሮ ዝናሽ በቀለ ማንደፍሮ እና ወ/ሮ ሐረገወይን በቀለ	መጋቢት 21/1999	286
ውል					290
108	የደረሰው ወይም ይደርሣል ተብሎ የሚጠበቀው ኪሣራ በጉዳት ኪሣራ ሊካስ የሚችል በሆነ ጊዜ ውሉን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776	35472	አቶ መሐመድ ካሣሁን እና አቶ ሰለሐዲን ኑር	ጥቅምት 6/2001	291
109	የፍ/ብ/ህ/ቁ.1723"ን" መስፈርት አላሟላም በሚል ውል እንዲፈርስ የተደረገ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1815	34803	መ/ር መኳንንት ወረደ እና እነ መስከረም ዳኛው (አራት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	294
110	ከአንቺሎነት ውል ጋር በተያያዘ ለሚኖር የጉዳት ሃላፊነት ካሣ ሊወሰን የሚችልበት አግባብ የንግድ ህግ ቁጥር 595, 596, 597 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790, 2090, 2091, 2092, 2141, 2102	32854	ወ/ሪት ማርታ አድማሱ እና እነ አቶ በረከት ሰብስቤ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 20/2001	307
111	የተከራዩትን ቤት ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት ለውል ማፍረስ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ	36520	የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ይብራህ ግርማይ	ጥቅምት 27/2001	310
112	መሐይምነትን ወይም ዓይነስውርነትን መሠረት በማድረግ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ አቤቱታ በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719,1845	29363	ወ/ሮ ወርቅነሽ አምዴ እና አቶ ጥላሁን አርምዴ	ህዳር 18/2001	313
113	የማይንቀሣቀስ ንብረት የሽያጭ ውል ተደረገ የሚባለው በውል ውስጥ ያሉ ወገኖች በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የሽያጭ ውሉን ከተፈራረሙበት ቀን ጀምሮ እንጂ የአስተዳደር ጉዳዩች ተጣርቶ የመስሪያ ቤቱ ማህተም ካረፈበት ቀን አንስቶ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723(1), 2015(ሀ)	36740	አቶ አብዱልዋሐብ ኢብራሂም እና እነ ወ/ት መሰለች ከፍያለች (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 23/2001	316
114	በማኅበር በመደራጀት የተሠራ ቤትን ለሶስተኛ ወገን ከማስተላለፍ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚነሣ	36294	ወ/ሮ ሠናይት ገነሜ ገንታ	ህዳር	319

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ክርክርን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1723		እና እነ በቀለ ገመዳ ዳኖ (ሁለት ሰዎች)	9/2001	
115	በአሰሪ ወይም በ3ኛ ወገን ወጪ ትምህርትን ተከታትሎ ለማገልገል በሚል የተገባን ውል (ስምምነት) የጣሰ ሰው ግዴታውን በአማራጭ ሊወጣ የሚችል ስለመሆኑ	33473	ወ/ሮ ሃርሌማ ሰለሞን እና የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ	ህዳር 16/2001	322
116	የዕቃ አስተላላፊነት ሃላፊነትና ተግባር ዕቃን የማጓጓዝና የማስረከብ ሥራን የሚያካትት ስለመሆኑ	32571	አቶ ሚፍታህ ከድር እና የባህር ትራንዚት አገልግሎት	ታህሣሥ 9/2001	326
117	ክርክር የሚካሄድበት ጉዳይን አስመልክቶ በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ የሌለ እንደሆነ ስለ ውሎች በጠቅላላ በሚለው ክፍል የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677፣1845	34940	ወ/ሮ ሐጅራ አብሮ እና አቶ ሐሺም ሐጂ አሊዬ	ታህሣስ 28/2001	329
118	• ፍ/ቤት የቀረበለትን የውል ይሰረዝልኝ፣ ጥያቄ ወደጐን በመተው የውል የፎርማሊቲን የተመለከተ ጭብጥ በማንሣትና ምክንያቱን በመለወጥ ውሣኔ መስጠት የማይገባው ስለመሆኑ • በፍ/ብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሰረት ጭብጥ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ	32299	እነ አቶ ሰለሞን ከተማ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ሴንትራል ቬኑ /የተ/የግል ማህበር (አራት ሰዎች)	ጥር 7/2001	331
119	በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161 የንግድ ሕግ ቁ. 124	34586	አቶ አያሌው ድልነሳው እና እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሽዋረግ (አራት ሰዎች)	ጥር 28/2001	336
120	በውል ግንኙነት ውስጥ የራስን ግዴታ ሳይወጡ ሌላው ወገን ግዴታውን አልተወጣም በሚል የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1757	39568	አቶ ሽንቁጤ ተ/ማርያም እና አቶ ገብሬ ጐንጤ	መጋቢት 24/2001	339
121	የማይንቀሳቀስ ንብረት ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጐት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ያላሳወቀ እንደሆነ ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት የመጠየቅ መብቱ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731(1), 1732, 1789 እና 1845	38935	እነ አቶ ወልደዓዲቅ ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ስንታየሁ አያሌው	መጋቢት 3/2001	343
122	በፍ/ብሔር ጉዳዮች የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1846	36756	አቶ ፀጋዬ ምትኩ እና እነ ወ/ሮ አበበች ምትኩ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 17/2001	348
123	ለብድር በዋስትና መልክ የተሰጠን ንብረት ለተበዳሪው መመለስ ብድሩ እንደተከፈለ የሚያስቆጥር ስለመሆኑ	41571	ማህደር አእምሮ እና ላእከ ገ/መድህን	ሰኔ 2/2001	351
124	በህግ ፊት በማይፀና ውል አማካኝነት የተሣሠሩ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ይመለሱ	39336	ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ	ሐምሌ	354

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በሚል ውሣኔ መስጠት የሚቻለው መመላለሱ አንደኛውን ወገን በእጅጉ የሚጐዳ ወይም ለሌላኛው ያልተገባ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችል አለመሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ		እና እነ አዱኛ እጅጉ (ሁለት ሰዎች)	7/2001	
125	በፍ/ቤት በንብረት ላይ የሚሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ክፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ተቋቁሟል ለማለት የሚያበቃ ስለመሆኑ	39170	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ክንዴ አፍራሶ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2001	357
126	የባለዕዳውን ዕዳ ለባለገንዘብ የከፈለ ወገን በባለገንዘቡ መብቶች ላይ በመዳረግ (subrogation) ባለገንዘቡ የነበረውን መያዣን መሰረት ያደረገ የቀዳሚነት መብት ሊሰራበት የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1968 - 1974	39778	ሕብረት ባንክ አ/ማ እና አቢሲኒያ ባንክ አ/ማ	ሐምሌ 30/2001	361
127	ፈራሽ የሆነን የስጦታ ውል ተከትለው የተሰሩ ስራዎችን ቀሪ ማድረግና ተዋዋዬችን ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የሚቻለው በቅን ልቦና የተዋዋለ 3ኛ ወገን መብትን የማይጐዳ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 1815,1816,1817	41116	ፍሌንስቶን ኢንጅነሪግ እና እነ ወ/ት ሐና ተስፋዬ (ስድስት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2001	368
128	የአክስዮን ድርሻ በመያዣነት እንደተሰጠ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2863 - 2874	39256	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ሞሣ ነጋሽ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2001	371
129	በብድር የተሰጠን ገንዘብ እጥፍ ለመቀበል በሚል የሚደረግ የብድር ስምምነት የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ	43372	አቶ ደረሱ አለሙ እና አቶ ሙሊሣ ወርቁ	ሐምሌ 22/2001	379
130	ስልጣን ያለው የአስተደደር አካል የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነቱን አውቆለት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ከሰጠው ሰው ጋር የተደረገ የንብረቱ የመያዣ ውል የተሰጠው የምስክር ወረቀት የተሰረዘ ቢሆን እንኳን መያዣ ተቀባዩ በቅንልቦና አለመሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የፀና ሆኖ የሚቀጥል ስለመሆኑ	41388	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ከፍያለው ሞልቶት (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2001	381
131	የማይንቀሣቀስ ንብረት ገዥ ውል እንዲፈፀምለት ሻጭን የመጠየቅ መብቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 384(ሀ), የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2892(3)	39725	እነ ወ/ሮ አለምሸት ካሣሁን (ሦስት ሰዎች) እና አቶ ሽመልስ እንዳለ	ሐምሌ 23/2001	384
132	የማይንቀሣቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚደረግ የስጦታ ውል የማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም በህግ የፀና ውል ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443, 881, 1723(1)	39803	አቶ አለሽኝ ገ/ሀይወት እና እነ እማሆይ አጢነሽ በቀለ (ሦስት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2001	387
አፈፃፀም					390
133	በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ተካሄዶ ሽያጭ	31963	አቶ አብዱልሐኪም	ጥቅምት	39

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የተፈፀመ እንደሆነ ሽያጩ ሊፈርስ የሚችለው በአሻሻጥ ሥርዓቱ የተካሣ መብት ወይም ጥቅም ያለው ሰው ላይ ቀጥተኛ ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 445		ሁሴን እና እነ አቶ ቀነኒ ሁንዴ (ሁለት ሰዎች)	20/2001	1
134	የፍርድ ባለመብት ባለመቅረቡ የተዘጋ የአፈፃፀም መዝገብ ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ10(አሥር) ዓመት ይርጋ ካልታገድ በቀር ሊንቀሳቀስ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384	35018	በዛብህ አበበ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ጥቅምት 18/2001	394
135	• የፍርድ አፈፃፀም ክርክር የሚጀመረው የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን በፍርዱ መሰረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378/1/ • የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ወይም የአፈፃፀም የውክልና ስልጣን ለተሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371,372	21359	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ተገኝ ማንደፍሮ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 28/2001	396
136	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥሮች 358 እና 418 ተፈፃሚ የሚሆኑበት አግባብ	32143	መሐመድ አስማኤል ተርቢ እና መሐመድ አህመድ ኑር	ጥቅምት 18/2001	400
137	የአንድ ንብረት ወቅታዊ ዋጋ ማለት ንብረቱ ለጨረታ ሽያጭ ቀርቦ የሚያወጣው ዋጋ ስለመሆኑ	37503	አቶ ወልደዮሐንስ ኃብተየስ እና ወ/ሮ ያምሮት ሸዋረጋ	መጋቢት 24/2001	402
138	የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ሊሸጥ የሚችልበት ሥነ- ሥርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 426,428(2)	39175	ወ/ሮ በለጡ ጋሼ እና እነ አንዱአለም ቴድሮስ (ሦስት ሰዎች)	መጋቢት 24/2001	404
139	በቀጥታ ክስ ወቅት የተገመተ የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቅት በአይነት ካልተገኘ እና የንብረቱ ዋጋ በልጦ ከተገኘ አፈፃፀሙ ሊሆን የሚገባው ንብረቱን በአይነት ለመተካት በሚያስችል የወቅቱ ዋጋ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378, 392	39485	የህፃን ሠላማዊት ቴድሮስ ሞግዚት እና መምህር ሚካኤል ግደይ	መጋቢት 17/2001	407
140	በህግ አግባብ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ የሞራል ወይም የህሊና አስተሳሰብን መሠረት በማድረግ ብቻ ዋጋ አልባ ሊደረግ የማይችል ስለመሆኑ	38041	ታደሠ ገ/መስቀል እና እነ ሙሉጌታ ዘካርያስ (ሰባት ሰዎች)	መጋቢት 22/2001	410

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ወንጀል				1
1	በወንጀል ጉዳይ የክስ ሂደት የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ ሊመዘን የሚገባ ስለመሆኑ	35697	የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ከበደ ወርቅነህ	ጥቅምት 20/2001	2
2	• በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ የተሻሻሉና የተሰወጡ ሁኔታዎች ከነባሩ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ጋር በቀጥታ ተጣምረው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባ ስለመሆኑ • በወ/ሕ/ አንቀጽ 543(3) የተከሰሰ ሰው የዋስ መብት የሚከለከል ስለመሆኑ የወ/ሕግ አንቀፅ 543 የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 63	35695	የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና አቶ ተመስገን አዲስ	ህዳር 11/2001	5
3	በተወሰነበት ፍርድ ላይ ይግባኝ እንደሚል ፍላጐቱን አሳውቆ እያለ ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት በኩል በተከሰተ መጓተት የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ፍርደኛ የሚያቀርበው የማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ	39722	ግርማ ሃይሌ እና ዐቃቤ ህግ	ታህሣሥ 23/2001	7
4	የዳኝነትን ሥራ በማከናወን ወቅት የሚፈፀሙ ስህተቶች እና ጥፋቶች ሁሉ ዳኛን በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ሊያስጠይቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 214/74	33075	አቶ ብርቁ ገላነው እና የአማራ ብ/ክ/መ/የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ጥር 19/2001	9
5	አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉ የሚቋቋምበት ህጋዊ፣ ግዙፍዊና፣ ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2	38161	እነ ጀሚላ መሐመድ ሐጉስ እና የፌዴራል የመ/ደ/ዐ/ህግ	የካቲት 19/2001	11
6	በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ንብረት የሆነ ንግድ መደብር ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የንግድ መደብሩን በውስጡ ከያዘው ሸቀጦች በመለየት (በመነጠል) የሚሰጡት ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ	44594	የፌ/ሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ እና እነ ካፋ መሐመድ (አራት ሰዎች)	ሐምሌ 15/2001	13
7	በወንጀል ጉዳይ በእስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሰው የእስራት ቅጣቱን ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ወይም እንዲለቀቅ ሊደረግ የሚችለበት አግባብ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 82,192,194	46382	እነ ዳንኤል ገ/ዮሐንስ (አራት ሰዎች) እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ	ሐምሌ 28/2001	16
8	አንድ ተከሣሽ በተፈፀመ ወንጀል ላይ ተካፋይ ነበር ለማለት ተከሣሹ በሙሉ ፈቃዱና ዕውቀቱ በወንጀል ድርጊቱ ተሣታፊ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32, 33, 630, 25	44031	ወ/ሮ ፈለቀች ኃ/ንብርኤል እና የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ	ሐምሌ 30/2001	19
9	ከተሸከርካሪ ጋር በተያያዘ በድንገተኛ አደጋ ለሚከሰት የሰው ህይወት መጥፋት አሽከርካሪው በቸልተኝነት ወንጀል በማድረግ ሊጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 59(1), 543(2) እና (3)፣57 (2)	42703	ፋሲል ብርሃኑ እና ዓቃቤ ሕግ/የኦሮሚያ ክልላዊ ብሔራዊ መንግስት/	ሐምሌ 22/2001	22
	ንብረት				27
10	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ካርታ በማቅረብ ብቻ የሚረጋገጥ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195	36320	ወ/ሮ ዘውዴ ገ/ስላሴ እና ወ/ሮ ህይወት ባህታ	ጥቅምት 18/2001	28
11	የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተገናኘ የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው ንብረቱን ለመገንባት የወጣው ወጪ (BooK value) ብቻ ሣይሆን ንብረቱ	35003	አቶ አሸናፊ አብዱልቃድር እና እነ ወ/ሮ ሽቶ አብዱራሂም	ህዳር 9/2001	30

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በወቅቱ ለገበያ ቀርቦ ሊያወጣ የሚችለው ዋጋ (market value) ጭምር ስለመሆኑ		(አራት ሰዎች)		
12	አንድ ተከራካሪ ተገቢነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅርቧል ለማለት ለክርክር መንስኤ የሆነው ንብረት በእጅ አድርጎ መገኘትና በዚሁ ንብረት ላይ በእውነት ለማዘዝ እንዲችል የንብረቱ አያያዝ ያልተጭበረበረና በማናቸውም መንገድ ህገ-ወጥ በሆነ ሁኔታ ያልተገኘ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1)	36645	ረዳት ሳጂን አያኖ አንጀሎ እና እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጫሌቦ	ህዳር 11/2001	32
13	የጋራ ንብረትን ለመካፈል በሚደረግ ሽያጭ የጋራ ባለንብረት የሆነ ወገን የቅድሚያ ግዥ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1261(2), 1386 — 1409	37297	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አታለም ተስፋ	ታህሣሥ 2/2001	36
14	የጋራ ሀብት የሆነ ንብረት በመያዣ የተያዘ በመሆኑ የቅድሚያ መብት ያለ ቢሆንም የጋራ ባለሀብት የሆነ ወገን ንብረቱ በግልፅ ጨረታ ቀርቦ የሚያወጣውን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ግማሽ በመክፈል ማስቀረት የሚችል ስለመሆኑ	37298	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ዋቅጂራ	ታህሣስ 2/2001	39
15	የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታን ለማቅረብ አቤቱታ አቅራቢው ክርክር የቀረበበት ንብረት ባለሀብትነቱን ሳይሆን ባለይዞታነቱን ብቻ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ	38228	ሐጂ መሐመድ አወል ረጃ እና እነ አቶ ዲኖ በሸር (ሁለት ሰዎች)	ታህሣስ 7/2001	41
16	ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንፃ የሰራ ሰው የህንፃው ባለሀብት ሊሆን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179	36638	በላይ አበበ እና እነ አበራሽ ዋቅጅራ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 21/2001	43
17	በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያለው ባንክ በንብረቱ ላይ ሊኖረው የሚችለው የመብት አድማስ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3088/1/, 3110/ሐ/	36013	ወ/ሮ ዘምዘም ኑሩ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ታህሣሥ 21/2001	46
18	የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን የሁከት ተግባር ፈጽሟል ከሚባለው ሰው የተሻለ የይዞታ መብት ያለው መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149	39940	ወ/ሮ ነጂባ ነጋሽ እና ወ/ሮ ዚያዳ ዩታሞ	ግንቦት 27/2001	50
19	ንብረትነታቸው የመንግስት የሆኑ ቤቶችን በተመለከተ የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ መንግስትን ወክሎ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2)	38169	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የወ/ሮ ንጋቷ ዘለቀ ወራሽ አቶ እሸቱ ቦጋለ	ግንቦት 12/2001	52
20	የይዞታ መብት ፍፁም ስላለመሆኑ እና በህግ አግባብ ይዞታው የተወሰደበት ሰው ተገቢ የሆነ ካሣ የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1), (2) አዋጅ ቁ. 7/1986 አንቀጽ 2(5), 21, 22, 24, 23 በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ- መንግሥት አንቀጽ 40 (8) አዋጅ ቁ. 455/1997	39539	የአዲስ አበባ አስተዳደር ግብርና ቢሮ እና እነ አቶ አበበ ዓባይ(ዘጠኝ ሰዎች)	ሐምሌ 30/2001	54
21	ከህግ የሚመነጭ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብትነትን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ	38666	የኢትዮጲያ ልማት ባንክ እና ባላንባራስ ተስፋዬ ገ/እየሱስ	ሐምሌ 9/2001	57
ከውል ውጭ ኃላፊነት					60
22	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 2143 ላይ የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የቀረበው የይርጋ ድንጋጌ የሞት ጉዳትን የሚያካትት ስለመሆኑ	34544	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ፋጤ ዓሊ	ጥቅምት 11/2001	61
23	ማንም ሰው ሥራው በሚያደርሰው ጉዳት ምክንያት ጥፋት ባይኖርበትም ከውል ውጭ ሃላፊነት ሊከተልበት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066- 2089(2069(1))	33201	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና ሼል ኢትዮጵያ	ጥቅምት 27/2001	63
24	ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው (ልጅ) ሃላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሰራ እንደሆነ ወላጆች በፍ/ብሔር	31721	ወ/ሮ ብዙነሽ ኃ/ዮሐንስ እና	ጥቅምት	65

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በሃላፊነት ሊጠየቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2125, 2124		ወ/ሮ ስንታየሁ እሸቱ	25/2001	
25	የጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባር ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው በህጉ መሠረት ሊሟሉ የሚገቡትን ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ እንጂ በማናቸውም ጥርጣሬ ምክንያት የግለሰብን ንብረት በመያዝ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.60/89 አንቀጽ 6, 58 አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 2(28) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26(1) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1193(1),(2), 2027, 2035, 2054, 2118	31171	አብልሃሚድ የሱፍ እና የምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት	ጥቅምት 27/2001	67
26	ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ ከሆነና ጉዳቱ በተጎጂው የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ካሣ ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ	35034	እነ ወ/ሮ ጥሩቀለም ደሴ እና እነ ወ/ሮ ጽጌ ከፍያለው	ጥቅምት 6/2001	70
27	ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት የሰው ህይወት የጠፋ እንደሆነና ለጉዳቱ መንስኤ (ምክንያት) የሆነው ወገን ሃላፊነት የተረጋገጠ ከሆነ በጠፋው የሰው ህይወት የተነሣ ጉዳት የደረሰበት ሰው የሞተው ሰው ምን ያህል ጥቅም ያስገኝለት እንደነበር ወይም ምን ያህል ተጨማሪ ዕድሜ ሊኖር እንደሚችል ያላስረዳ ቢሆንም እንኳን ፍ/ቤት የጉዳት ካሣውን በርትዕ ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102	34314	ወ/ሮ ግምጃ ጎበና እና እነ አቶ ወንድወሰን ወልዴ (ስድስት ሰዎች)	ህዳር 11/2001	73
28	የጉምሩክ ባለሥልጣን ያለአግባብ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ ለሚያቆየው ንብረት በባለንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ	31704	አቶ አማረ መጃ እና የድሬዳዋ ለጋር ጉምሩክ	ጥር 29/2001	76
29	በጥቅም ላይ ባልተመሰረተ ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ የሚሄድ ተሣፋሪ ላይ ለሚደርስ አደጋ የመኪናው ባለቤት ካሣ የመክፈል ሃላፊነት የማይኖርበት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089	38457	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ተመኘሁ እንደሻው	ሰኔ 2/2001	79
የዳኝነት ስልጣን					81
30	የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ውስጥ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1) (ሸ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996(1)	35657	እነ ወ/ሮ እመቤት መክብብ እና አቶ በድሉ መክብብ	ጥቅምት 6/2001	82
31	የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ለክርክር መነሻ የሆነው ክስ በገንዘብ ሊተመን የማይችል የመብት ጥሰትን የተመለከተ በሆነ ጊዜ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 50(1), 39	36338	ገ/መስቀል ደመወዝ እና ወ/ሮ አፀደ መኮንን	ጥቅምት 25/2001	86
32	የቅኔ መምህርነት ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ሥራ በመሆኑ በሥራ ክርክር ችሎቶች ሊስተናገድ የሚችል ስላለመሆኑ	34440	መንበረፓትሪያክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና መጋቢ ሚስጢር መዝገቡ በላይነህ	ጥቅምት 6/2001	88
33	የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የቤት ባለቤትነት ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ረ)	33841	አቶ አስጨናቂ ረጋሣ እና እነ አቶ ገዛኸኝ ነጋሽ (ስድስት ሰዎች)	ጥቅምት 6/2001	91
34	በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ በወታደርነት በግብልጋል ላይ የሚገኙ የሠራዊት አባላት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ	33368	ሻምበል አሰፋ በላይ ዘገየ እና	ህዳር 9/2001	93

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወንጀል አቤቱታዎችን ለማስተናገድ ወታደራዊ ፍ/ቤቶች ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.27/88, አዋጅ ቁ. 343/94 አንቀፅ 2(9),26(1)		ወታደራዊ አቃቤ ህግ		
35	የአ.አ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች በከተማው አስተዳድር ሥር ካሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን ብቻ ለማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ	34788	የሚች አቶ ሰለሞን ሳሙኤል ወራሾች እና ማርታ ሰለሞን (2 ሰዎች)	ህዳር 2/2001	96
36	በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በፍርድ ቤት ቀርቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ስላለመሆኑ	31906	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የአቶ መርስኤ መንበሩ ወራሾች	ህዳር 4/2001	99
37	በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ከተወረሱና በቀላጤ ከተያዙ ቤቶች ውጭ ያሉ ቤቶችን አስመልክቶ የሚነሣ የቤት ክርክር ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች ማየት የሚችሉ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ.47/67 አዋጅ ቁ. 110/87	37281	አቶ አበበ ዓሊ እና እነ የዐ8 ቀበሌ ገ/ማህበር (ሦስት ሰዎች)	ታህሣሥ 16/2001	103
38	በውጭ አገር የሚገኝ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክርን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማስተናገድ ስለመቻሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 37, አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ(4)	37339	ወ/ሮ ንግስት ኃይሌ እና አቶ ለገሠ ዓለሙ	ጥር 28/2001	106
39	ወደ ቀድሞ የሥራ መደብ እንድመለስና ለመደቡም የተሰጠው ልዩ ጭማሪ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ የወል ሥራ ክርክር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ142(1) (ሀ)	37016	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ተስፋዬ ማሞ	የካቲት 3/2001	109
40	ከጉምሩክ ፖሊስ አባላት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን ለመደበኛ የሥራ ክርክር ችሎቶች ያልተሰጠ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 368/96 , አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 8(2) , መመሪያ ቁ.4/1996	39085	የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ር አስረሳኝ ወርቅነህ (ሰማንያ ሰባት የጉምሩክ ፖሊሶች)	የካቲት 3/2001	111
41	ቀደም ብሎ የተሰጠን የፍች ውሣኔ ወደጉን በመተው አዲስ የተደረገን ጋብቻ ህገ ወጥ ነው ማለት የማይቻል ስለመሆኑ	38745	እነ ወ/ሮ ሣሊያ ኢብራሂም (ሁለት ሰዎች) እና ሐጂ ሰማን ኢሣ	መጋቢት 10/2001	113
42	የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የይዞታ ክርክርን ማስተናገድ የማይችሉ ስለመሆናቸው	36677	ወ/ሮ ሻምሺ የኑስ እና ወ/ሮ ኑሪያ ማሚ	ሚያዝያ 30/2001	116
43	የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀሎ እና ወለድ ላይ የሚቀርብ ይግባኝን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ስለመሆኑ	37866	መሉጌታ አባይ እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን	ግንቦት 19/2001	119
44	የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶችም ሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳዮችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን በህግ ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ	41608	እነ መላቱ አንበርብር እና ወ/ት ታመነች ዮሴፍ መና	ሐምሌ 22/2001	121
	ባንክና ኢንሹራንስ				123
45	ዕቃዎችን ለሚያጓጉዝ የጭነት መኪና የተገባ የመድን ዋስትና ጋር በተያያዘ በመኪናው ላይ ተሣፍሮ ሲሄድ ለነበረና አደጋ ለደረሰበት ሰው መድን ሰጪው የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ	42139	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ብያን ኡመር	ሰኔ 30/2001	124
46	ኢንሹራንስ ሰጪ በውሉ መሠረት ክፉፀመ በኋላ በተሸሸገ ወይም በሀሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ አጋጥሚል በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባለው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የንግድ ህግ 674(1),(2)	42309	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሰኔ 30/2001	126

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውክልና					128
47	አደራ ተቀባይ የሆነ ወገን በአደራ የተቀበለውን ዕቃ መመለስ ያለበት ለአደራ ሰጪው ወይም ይቀበልልኝ ብሎ ላመለከተው ሰው ስለመሆኑ	38289	ወ/ሮ ነጂሃ ድዋሌ ዋይስ እና አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ	ሰኔ 23/2001	129
48	መንግስታዊ የሆነ ተቋም በሚከሰስበትም ሆነ በሚከስበት ክርክር የሚቀርብ ሰነድ የኘሮቶኮል ቁጥር እንዲሁም ስለአቤቱታው ጽሁፍ ትክክለኛነት በሚመለከተው ኃላፊና በወኪሉ መፈረም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 80, 92, 93 እና 92(3)	43875	በወላይታ ዞን የቦዲቲ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና አቶ ወንድሙ ኃይሌ	ሐምሌ 16/2001	131
49	የዕቃ አስተላላፊ አካል እንደ አንዥር ሆኖ የሚቆጠረው ከወደብ የተረከበውን ዕቃ በራሱ ማጓጓዣ ካጓጓዘ ብቻ ስለመሆኑ ደንብ ቁ.37/90 አንቀጽ 2(1), 3(6),(7) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2251 የንግድ ህግ .ቁ. 683(3)	37799	የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሐምሌ 29/2001	134
50	በወኪል በኩል የሚፈፀም የመኪና ጭነት ውል በአስጫኝ እና በመኪናው ባለቤት መካከል እንደተደረገ የሚቆጠር ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 566 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2251	34621	ኒያላ ኢንሽራንስ አ/ማ እና አቶ ሐጎስ ገ/መድህን	ሐምሌ 30/2001	136
የንግድ ሕግ					140
51	የንግድ ድርጅት በህግ አግባብ ለባለመብቶች ሊከፋፈል የሚችልበት ሁኔታ የንግድ ህግ ቁጥር 127	33954	ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ እና አቶ ዘውዱ ቢረዳ	ጥቅምት 20/2001	141
52	የእሽሙር ማህበር መፍረስ በንብረት ክፍፍል ረገድ የሚያስከትለው ውጤት	33470	ወ/ሮ እጅጋየሁ ታደሰ እና መገርሳ ጉደታ	ህዳር 2/2001	144
53	የጋራ ሀብት የሆነ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደሌላ ማናቸውም ንብረት ባለበት ሁኔታ በዓይነት ሊከፋፈል ወይም ደግሞ በሃራጅ ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 542	34945	ወ/ሮ መስታወት በላቸው እና አቶ ለገሠ ሣህሉ	ህዳር 2/2001	146
54	የንግድ መደብርን የተከራየ ወገን ይህንኑ የንግድ መደብር ለሌላ ሶስተኛ ወገን ያለአከራዩ ፈቃድ ማከራየት ስለመቻሉ የንግድ ህግ ቁጥር 145	31264	ወ/ሮ እመቤት መኮንን እና ወረዳ 20 ቀበሌ 29 አስ/ጽ/ቤት	ጥር 5/2001	148
55	በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161 የንግድ ሕግ ቁ. 124	34586	አቶ ያለው ድልነሳው እና እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ (አራት ሰዎች)	ጥር 28/2001	151
56	ቼክን አስመልክቶ ክስ በቀረበ ጊዜ የተከሰሰው ወገን የቀረበበትን ክስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት የሚያቀርበው ምክንያት ፈቃድ ሊያሰጥ የሚችል መሆን ያለመሆኑን አግባብነት ካላቸው ህግጋት አኳያ መታየት ያለበት ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 717 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 284, 285	43315	ብራንድ ኒው የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል እና አቶ መስፍን ታደሰ	ግንቦት 18/2001	154
አእምሯዊ ንብረት					156
57	አንድን የሥነ-ጥበብ(ኪነ-ጥበብ) ሥራ ያለባለቤቱ ፈቃድ ኦርጅናሉ ወይም ቅጅው ለህዝብ እንዲታይ ማድረግ የኮፒ ራይት ህግ ጥሰት የሚያስከትል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1791, 1771(1), 1790, 2090-2123 አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀፅ 7	42253	መምህር ሙሉ ኃይለሥላሴ እና ዘመናዊ ማተሚያ ቤት	ሐምሌ 8/2001	157

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ					160
58	የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዋቅር ባልተዘረጋባቸው ክልሎች የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ወክለው/ተክተው/ ክርክሮችን ማስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 139/1//ለ/,154/1/,153,140	21214	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ለማ ኩማ (ሦስት ሰዎች)	ህዳር 4/2001	161
59	• የጡረታ መዋጮ በመዘግየቱ ምክንያት በአዋጅ ቁ. 345/95 መሠረት ተጨማሪ ክፍያ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ እና አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 7(3), 52(1),56 • የጡረታ መዋጮ በ2 ዓመት ውስጥ እንደተከፈለ የህግ ግምት ሊወሰድበት የሚችል የክፍያ ዓይነት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ሠ)	35391	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና አንበሣ ጫማ አ/ማ	ህዳር 25/2001	163
60	የጥብቅና ፈቃድን ለማግኘት በህጉ የተቀመጡት መስፈርቶች ራሣቸውን ችለው መታየት ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 8(1)	37375	አቶ ሸምሱ ከድር አህመድ እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር	ህዳር 11/2001	166
61	በክባድ የወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ እና በራሣቸው ወጪ ጠበቃ ለማቆም ያልቻሉ ግለሰቦች በተመለከተ ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት የግለሰቦችን በጠበቃ የመወከል ህገ-መንግሥታዊ መብት መከበሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 13 (1)	37050	ሻምበል ሁሴን አሊ እና የሱማሌ ክልል ዐ/ሕግ	ታህሣሥ 30/2001	168
62	ከዘር የወረደ ርስት ነው በሚል የመሬት ባለቤት ለመሆን የሚቀርብ ክስ ህገ-መንግስታዊ ያልሆነና ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	38237	አቶ በርገና ሽፈራው እና እነ አቶ አብራሃም ሽፈራው(አራት ሰዎች)	ታህሣሥ 21/2001	171
63	በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍ/ብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት ለመወሰድ ብቃትና አግባብነት ያለው ስለመሆኑ	37184	የሰሜን ቀጠና ጉምሩክ እና እነ ቂስ ብርሃን ንዋይ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 9/2001	174
64	የመንግሥት መሥሪያ ቤት በጨረታ አማካኝነት የሽያጭ ውል አካሄዷል ተብሎ ሊገደድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1688(2), 3167(1), 1688(2), 3168	37163	የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን እና ህያብ ገ/መድህን ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ	ታህሣሥ 23/2001	179
65	አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ምንነት፣ የሚደረጉበት መንገድና ለአፈፃፀም የሚቀርቡበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3318, 3324, 3325, 3346, 1731 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 315, 319, 350, 357	38794	አቶ መኩሚል መሐመድ እና አቶ ሚፍታህ ከድር	መጋቢት 24/2001	182
66	አስተዳደራዊ የሆኑ መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ ካርታ እንዲሰጥ የሚወሰን ውሣኔ ተገቢ ስላለመሆኑ	39529	ቦሌ ክ/ከተማ የመሬትና ልማት አስተዳደር እና እነ ወ/ሮ ግምጃ በዳኔ (ስድስት ሰዎች)	ግንቦት 11/2001	186
67	ግምቱ ከብር 10,000 ብር በላይ ለሆነ የአፈፃፀም ክስ ሊከፈል የሚገባው ዳኝነት 25 ብር ብቻ ስለመሆኑ የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ. 177/1945 አንቀጽ 2(ሠ)	40752	እነ ወ/ሮ ኤክራም መሃመድ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘኪ መሐመድ	ሐምሌ 28/2001	189
68	ከፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ሠራተኞች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር ምንም እንኳን ሥራው የሚካሄደው በክልሎች ቢሆንም ወይም ሠራተኞቹ የክልል ነዋሪዎች ቢሆኑም ገቢ የሚደረገው ለፌዴራሉ መንግስት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 96(3) አዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ5(2)(ሐ) ደንብ ቁ. 109/96	40133	የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን እና በሶማሌ ብ/ክ/መ የፊደልቱ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ገቢዎች ጽ/ቤት	ሐምሌ 2/2001	191

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አሰሪና ሰራተኛ				195
69	የማንባታ ዕቃዎች እጥረት አጋጥሟል በሚል የሚደረግ የሥራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 26,28,30	41385	ጊጋ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና እነ ተረፈ ዘርጋው (ስድስት ሰዎች)	ጥቅምት 3/2002	196
70	የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት አድርጉ ከሚቀርብ ክርክር ጋር በተገናኘ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሣይሰጥ ከተጠየቁት ዳኝነት መካከል ወደ ሥራ የመመለስ ጉዳይ ላይ ብቻ ውሣኔ ከተሠጠና ሠራተኛው ወደ ሥራ መመለስ ላይፈልግ ቢቀር ቀድሞ ዳኝነት በጠየቀባቸው ነገር ግን ውሣኔ ባላረፈባቸው ነጥቦች ላይ ዳኝነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3)	42361	ወ/ት ትዕግስት ንጉሴ እና ኤስ.ኦ.ኤስ ኢንፋንት ኢትዮጵያ	ጥቅምት 5/2002	198
71	በትርፍ ሰዓት በሌላ መሥሪያ ቤት ሰርተሃል በሚል ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ 377/96 አንቀፅ 27	42818	አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ እና ወ/ር ሙሉታ ገዳ	ጥቅምት 10/2002	200
72	አሰሪ በግልፅ ባልፈቀደበት ሁኔታ በሁለት ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ መስራት ሠራተኛውን የማታለል ተግባር እንደፈፀመ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ)	41767	የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና አቶ አድማስ ደምሳቸው	ህዳር 8/2002	202
73	አሰሪ የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት እና መለኪያ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ በሠራተኞቹ መካከል በክፍያ ረገድ ልዩነት ማድረግ ስለመቻሉ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 14(1)(ረ) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት 42(1)(መ)	42923	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ነጃት አባስ	ህዳር 22/2002	204
74	ሥራውን በገዛ ፈቃዱ የሚለቅ ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት የሚችለው ቢያንስ የ5 ዓመት አገልግሎት ያለው እንደሆነ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(ሸ)	44410	ወ/ሮ ላይላ ረዲ እና ድሬ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግል ማህበር	ጎዳር 01/2002	207
75	በአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ "በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት" ወይም "በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" በሚል የተቀመጠው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 95/2/,97,96	47807	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ ፈንታው (ሁለት ሰዎች)	ታህሳስ 06/2002	210
76	አሰሪ ሠራተኞቹን በማስተዳደር ረገድ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች በራሱ አነሣሽነት ሊያርም የሚችል ስለመሆኑ	45889	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን እና ሳሙኤል ቁለቦ	ታህሣሥ 20/2002	213
77	በክርስትና ሃይማኖት ተቋም ውስጥ በዲያቆንነት ሥራ ከማገልገል ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የሥራ ክርክር ጉዳዮች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ሊስተናገዱ የማይችሉ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	47806	የሆህተሰማይ ቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና ዲያቆን አያሌው አዲሱ	ታህሣሥ 20/2002	215
78	በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኟቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት መብት የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10	47469	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ስዩም ገብረዓዲቅ(ሃያ ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 15/2002	217
79	በሥራ ክርክር ጉዳይ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853 ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 164(3) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853,1852	47784	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አለምፀሐይ አያና	ታህሣሥ 20/2002	220
80	በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት የሥራ ግንኙነት በአንቀፅ 30 መሠረት ሲቋረጥ አሰሪ ማስጠንቀቂያ	49057	አስመላሽ እና ልጆቹ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል	ጥር 5/2002	223

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 30, 28(2)		ማህበር እና ዮሐንስ እሸበል		
81	የጡረታ መብት ያለው እና መደበኛ የጡረታ ዕድሜው ደርሶ የተሰናበት ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/2(ሰ) እና (ሸ)	46276	ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት እናእነ ኃይሌ ይማም (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 11/2002	225
82	• አንድ ድርጅት ለመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኞች የስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው የሚገባ ስለመሆኑ • ድርጅት ለዘለቄታው እንዲቆም የሚያደርግ ሁኔታ ሲከሰት ማስጠንቀቂያ ለሠራተኞች መሰጠት ያለበት ስለመሆኑ	42985	ውድ መጣስ ኑሮ አስመጪና ላኪ ድርጅት እና እነ አቶ ሁነኛው ሰጠ (አስራ አንድ ሰዎች)	የካቲት 25/2002	227
83	የጠብ አጫሪነት ኃይለ ቃልና ዛቻ አዘል ንግግር በሥራ ቦታ ላይ ማድረግ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ረ)	49958	ግዬን ትራቭልና ቱርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ዳንኤል አስፋው	የካቲት 12/2002	229
84	በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ለሠራተኛው ጥገኞች ስለሚከፈል ካሣ፣ ካሣው የሚከፈልበትና የሚሰላበት ሁኔታ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 110	40529	የህፃን ዮናታን ነጋ ተሻገር ጠ/ጥ/ጋቡ ጌጤ እና አቶ ለገሠ አበራ	የካቲት 10/2002	231
85	በአሰሪና ሰራተኛ በኩል በአጠቃላይ ለፕሮጀክት ሥራ በሚል የተደረገ የሥራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አንቀጽ 10(1)(ሀ) መሰረት የተደረገ እንደሆነ ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሀ)	48648	የፃልቂ የትምህርትና የተቀናጀ የልማት ማህበር እናእነ አቶ ታጠቅ ደጀኔ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 24/2002	234
86	ሠራተኞችን ለማበረታታት በሚል የሚደረግ የደመወዝ (ጥቅማጥቅም) ጭማሪን መሠረት በማድረግ ጭማሪውን የሚፈቅደው መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ የሚጠይቀው መብት የሌለ ስለመሆኑ	47825	የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ) እና እነ አቶ ዘርዓየሁ ሰሜ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	236
87	አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ ከሚፈፅመው ጥፋት ጋር በተያያዘ ከሥራ ታግዶ ሊቆይ ስለሚችልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	47535	የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት እና አቶ እንግው ላቀው	መጋቢት 20/2002	238
88	• የአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አሰሪና ሰራተኛ ስምምነት ሊያደርጉባቸው የሚችሉበት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ጥፋትንና ጥቅምን በተመለከተ የተለያየ አቋም የያዘ ስለመሆኑ • አሰሪና ሠራተኛ በህብረት ስምምነታቸው ውስጥ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በሚል የተስማሙበት ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 134(2), 27(1)(ሸ)	49750	በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/01 የመዝናኛ ክበብ እና አቶ ማስረሻ ሁሴን	መጋቢት 30/2002	240
89	አሠሪ የሠራተኛውን የሥራ ውል ያቋረጠበትን ምክንያት በፅሁፍ አለመግለፅ ብቻ ስንብቱ ህገ- ወጥ ነው ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2)	49797	አልሀበሽ ሹገር ሚልስ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ተገኔ ገ/ሃዋሪያት	መጋቢት 30/2002	242
90	በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ውስጥ "እንደ ጥፋቱ ክብደት በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር መፈፀም" በሚል የቀረበው አባባል (አነጋገር) ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ)	50009	የአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል እና አቶ ዮናስ ጥላሁን	መጋቢት 6/2002	244
91	አሠሪና ሠራተኛ የሥራ ውል መቋረጥ ጋር በተያያዘ በሥራ ውሉ ላይ የሚያመለክቱት ሁኔታ የአሰሪና	50205	የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት	መጋቢት 20/2002	246

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሠራተኛ ህጉን እስካልተፃረረ ድረስ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ		እና አቶ ምናለ በሪሁን		
92	የሥራ ውል በተቋረጠ ጊዜ አሰሪው ከሠራተኛው በህግ አግባብ የሚፈልገው/ የሚጠይቀው ዕዳ ያለ እንደሆነ ለሠራተኛው የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት ከመስጠት ባሻገር የሥራ መልቀቂያ (ክሊራንስ) ለመስጠት የማይገደድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀፅ 78 (1),87	48476	የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና አቶ ደረጀ መኮንን	ሚያዝያ 12/2002	248
93	ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የሚደርስበትን ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ወይም ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት በማለት ለመለየት የሚቻልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 101 (2)	49273	አቶ ደረጀ ውለታው እና ዋሊያ ሌዘርና ሌዘር ኘሮዳክትስ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሚያዝያ 27/2002	250
94	• አንድ ሰው በአፈፃፀም ሊገደድ የሚችለው በህግ አግባብ የተፈረደ ፍርድ ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ • በግልፅ ፍርድ ያላረፈበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378	50148	እነ አቶ ወርቁ ደረጀ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ አባርኪሮ ሁመድ	ሚያዝያ 4/2002	252
95	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ከሠራተኛው ጋር ያለው ግንኙነት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቢመለስ ችግር ውስጥ እንደሚወድቅ በአሠሪው ስለተገለፀ ብቻ ሠራተኛው ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት በሚል የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/	49931	የጎሽና እርግብ መለስተኛና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር እና አቶ ተሰማ ኃይሉ	ሚያዝያ 21/2002	254
96	የድርጅት መዋቅራዊ ለውጥ ያደረገ ተቋም በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መሠረት ሠራተኞቹን አዲስ በሚያወጣው የሥራ መደብ ላይ ተመርኩዞ የሥራ ምደባ ሊያከናውን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28	50838	ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ኘሮጀክት እና እነ አቶ አማረ አበራ (ሰባት ሰዎች)	ሚያዝያ 12/2002	256
97	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪ ሠራተኛው የፈፀመውን ድርጊት መሠረት አድርጐ ለማሰናበት የሚችለው የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት የሆነው ነገር መከሰቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ ሰላሳ ቀናት ውስጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3)	45746	ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ በለጠ ጫላ	ሚያዝያ 6/2002	258
98	ሠራተኛ የተረከባቸውን ንብረቶች አላስረከበም ወይም አጉድሏል በሚል የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚጠይቃቸውን ተገቢ ክፍያዎች ሊጠይቅ አይችልም በሚል በአሠሪው የሚቀርብ ክርክር ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 36,37,38	44405	ፊንፊኔ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ደጃ ደምሴ ጎበና	ግንቦት 19/2002	260
99	ወደ ሥራ እንዲመለስ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነና በአሰሪው ችግርም ሆነ በሠራተኛው ፍላጐት በፍርዱ መሠረት ወደ ሥራ ለመመለስ ሠራተኛው ያልፈለገ ከሆነ ሠራተኛው የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ በምትክነት በሰጠው መብት መሠረት በመመለሱ ፈንታ ካሣ እንዲከፈለው አፈፃፀሙን ለያዘው ችሎት ጥያቄውን ባቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3)	53064	አቶ ደሬሳ ኮቱ እና የአምቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን	ግንቦት 17/2002	263
100	በድርጅት ውስጥ የተከሰተ ተጨባጭ ችግርን ለመቅረፍና የድርጅቱን ትርፋማነት ለማስቀጠል በሚል በተመሳሳይ ሙያና ደረጃ ላይ ካሉ ሠራተኞች መካከል ተለይቼ ወደ ሌላ የሥራ መደብ ስለተዛወርኩኝ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ	50182	የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት እና አቶ አበበ ተፈራ ይልማ	ግንቦት 13/2002	265
101	የሥራ ውል የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ ነው በሚል ክርክር በቀረበ ጊዜ ይህንኑ የማስረዳት	44218	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና	ግንቦት 13/2002	267

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሽክም የሚኖር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 9		እነ አቶ ታጁ አባጋሮ (ሃያ አንድ ሰዎች)		
102	አንድ አሰሪ በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበትን ሰራተኛ ወደ ውጭ አገር ልኮ ስለሚያሳክምበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 124,105	46363	ሚሊኒ ኮንስትሩቶሪ ኤስ.ፒ.ኤ እና አቶ ትግሉ ፍሬህይወት	ግንቦት 19/2002	270
103	• ከአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጋር በተገናኘ ሁለቱ ወገኖች አዋጅ ቁ. 377/96 "ን" ወደ ጐን በማድረግ በሌላ አገር ህግ ለመዳኘት ስምምነት ያደረጉ በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ህግ ጥያቄን ያስነሳል በሚል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑ • አዋጅ ቁ. 377/96 የውጭ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ የበጐ አድራጐት ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/3/ /ለ/	50923	ፋውንዴሽን አፍሪካ እና አቶ አለሙ ታደሰ	ግንቦት 19/2002	273
104	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚነሣው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚሰላው የሥራ ቀናትን ብቻ በማስላት ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 163(2)	51912	የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና ወ/ሮ ሶፋኒት አጥናፉ	ሰኔ 7/2002	276
105	• በአሰሪ የተፈፀመው የሥራ ስንብት ህጉ ወጥ ቢሆንም ከሥራ ግንኙነቱ ፀባይ የተነሣ ከፍተኛ ችግር የሚፈጠር በሆነ ጊዜ ሠራተኛውን ወደ ሥራ ከመመለስ ይልቅ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ • የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀፅ 43(3) በአንድ በኩል የሠራተኛን የሥራ ዋስትና በሌላ በኩል ደግሞ የኢንዱስትሪን ሰላም በማመዛዘን ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ	55189	አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል እና አቶ ዘላለም መንግስቱ	ሰኔ 30/2002	279
106	በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ‹‹... ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት...›› በሚል የተመለከተው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3)	53358	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ ጥላሁን ኩማ	ሰኔ 18/2002	281
107	አንድ የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9,10	43160	እነ እንደገና ተሾመ (ሁለት ሰዎች) እና ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ነቀምቴ ቅርንጫፍ	ሰኔ 22/2002	283
108	በማናቸውም ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኛው ያልወሰደው የዓመት እረፍት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 77(5) ,24(2)	52459	እነ ወ/ሮ ሙሉ ታደሰ እና አለሙ መራ ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ብረታ ብረት ሥራድርጅት	ሐምሌ 16/2002	285
109	በክረምት ወቅት የማስተማር ሥራ እንዲሠራ የሚያዝ ግልፅ ደንብ ወይም መመሪያ የሌለ እንደሆነ ወይም አስተማሪው በክረምት ወራት ለማስተማር የገባው የውል ግዴታ (ስምምነት) በሌለ ጊዜ በክረምት ወቅት ሥራን ለመስራት ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ከሥራ ሊሰናበት የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 13(1)	45170	የቅድስት ማሪያም አፀደ ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እና መ/ት ሲሳይ ሙሉጌታ	ሐምሌ 8/2002	287
የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት					289
110	በክርክር የማድ ተካፋይ ሊሆኑ የሚገባቸው ወገኖች እና የፍ/ቤት ሚና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 39,(1),40(2)	43424	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና እነ አቶ መስፍን /ስምንት ሰዎች/	ጥቅምት 10/2002	290
111	የቃል ክርክር እንዲሰማ በተቀጠረበት ዕለት ግራ ቀኝ የሆኑ ወገኖች ያልቀረቡ እንደሆነ መዝገቡ መዘጋት ያለበት ስለመሆኑ	43410	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል	ህዳር 30/2002	293

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 69(2)				
112	አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ይህንን ፍሬ ነገር በማንኛውም የማስረጃ ዓይነት ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ	47551	ንግድ ማተሚያ ድርጅት እና አቶ ካሱ መላት	ታህሣሥ 6/2002	295
113	ጣልቃ በመግባት በክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጠይቆ የተፈቀደለትና የጣልቃ ገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባው ይህን ባለመፈፀሙ መብቱ ከተሰረዘበት በኋላ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41,358	40229	ወ/ሮ ኸይሮ መሐመድ እና እነ ወ/ሮ መዲና በያን (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 15/2002	297
114	በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ተከራካሪ ወገን ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አቤቱታው ሊሰተናገድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 78,69,72	43731	ሲ.ጂ.ሲ.አቪርሲስ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ሊሚትድ እና ሰለሞን እንዳለ	ታህሣሥ 8/2002	299
115	• በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 መሠረት መዝገብ ሊዘጋ የሚችልበት አግባብ • ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ዳኝነት የሚጠይቁበትን ፍሬ ነገር በአግባቡ ከገለፁ ትክክለኛውን የህግ ድንጋጌ አለመጥቀሳቸው መብታቸውን የሚያስቀር ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280,69(2), 70(መ), 71(2)	39581	አቶ ውብሸት ካሣዬ እና የኢትዮጵያ ማዕድን ሃብት ኮርፖሬሽን	ጥር 25/2002	302
116	ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሷቸውን የሰው ማስረጃዎች ሊሰሙ (ሊቀይሩ) የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223/2/,234	45984	ኘሮፌሰር ረዳ ተ/ኃይማኖት እና አቶ ልመንህ ተፈራ	ጥር 26/2002	304
117	የክርክር ጭብጥ የሚመሰረተው ከላሽ የሚያቀርበውን ክስና ማስረጃ በተከሳሽ የቀረበውን የመከላከያ መልስና ማስረጃ እንዲሁም ፍ/ቤቱ የቃል ምርመራ ሲያደርግ የሚያገኘውን ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241,248	47252	ወ/ሮ ፑሽፓላት ጆሴፍ እና አቶ ሠይፈ ጎሣዬ	የካቲት 26/2002	307
118	ዳኝነት እንደገና እንዲታይ (Review of judgement) በሚል የሚቀርብ አቤቱታ አስቀድሞ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የተባለበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ ውድቅ ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)(ሀ),(ለ)	43821	ወ/ሮ ትርሃስ ፍስሀዬ እና ወ/ሮ ዘነበች በሪሁን	ጥር 5/2002	310
119	ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ላይ በተሰጠ ትእዛዝ/ብይን ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6(3)(4)	42871	የቀድሞ ወረዳ 07 ቀበሌ 32 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ጆሮ ዋቅጅራ	ጥር 12/2002	315
120	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 421 መሠረት ክስ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418,421	37214	አቶ ተስፋዬ አለሙ እና እነ ሐጂ ይማም መዝይን(ሦስት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	318
121	በፍ/ብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ	44634	አቶ ታዬ ሆሳዕና እና ወ/ሮ መሠረት ወልደየስ	የካቲት 22/2002	320
122	ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው ክስ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ በቂ በሆነ ማስረጃ በተገነዘቡ ጊዜ ክሱን ሊዘጉት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280	45371	የገነተ-ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማህበር በኮር ሰንበቱ እና እነ አቶ ማሞ ተሠማ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 8/2002	322
123	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216 መሠረት በድጋሚ ክስ እንዳይቀርብ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216(3)	36776	መብራቱ፣ተ/ማሪያም፣ገ/ማሪያም የሸርክና ማህበር እና አቶ መብራቱ ዓንዳይ	መጋቢት 7/2002	324
124	ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር በዋናው ጉዳይ ላይ የራሱን ውሣኔ ካሣለፈና የበላይ የሆነ	44545	ክፍሉ መሓሪ እና	መጋቢት 7/2002	326

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ፍ/ቤት ደግሞ የይግባኝ ውሳኔውን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በደፈናው በማፅናት የሚሰጠው ውሣኔ የተከራካሪ ወገን የይግባኝ መብት የሚያጣብብና የሥነ-ሥርዓት ህግ ደንብን የሚጥስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341,342,343		በላይ ከመላ		
125	የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘ ባለገንዘብ ባንክ መብቱ በይርጋ እስካልታገደ ድረስ የያዘውን ንብረት በጨረታ ለመሸጥ የሚገደድበት ተሰይቶ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 97/90 አዋጅ ቁ. 216/92 አንቀፅ 2 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394 - 449	44883	አቶ ፊንታ ምህረቱ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	መጋቢት 8/2002	328
126	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ	39799	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ ገነት ስዩም	መጋቢት 21/2002	331
127	• በተከራካሪ ወገኖች የሚቆጠሩ ማስረጃዎች ሳይሰሙ የሚቀሩት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የሌላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ • ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች የቆጠሩትን ማስረጃ ሳይሰሙ ወደ ጉን በመተው አቤቱታቸውን በበቂ ማስረጃ አላስረዱም በሚል የሚደርሱበት መደምደሚያ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ	43845	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ጌታይዳ ኃ/የተ/የግል ማህበር	መጋቢት 20/2002	334
128	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208 መሠረት በሥር ፍ/ቤት የተደረገ እርማትን መነሻ በማድረግ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ለመለወጥ የሚያስችለው የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 208,209,320,(1) ,348(1)	44931	ወ/ሮ ሰዓዳ ኢድሪስ እና አቶ ረሺድ ቡባ	መጋቢት 20/2002	337
129	የፍ/ቤትን ክብርንና የዳኝነት ሥርዓቱን መልካም አመራር ለማስጠበቅ ሲባል የማንኛውም ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ በችሎት ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 480	48237	ወ/ሮ ሰኢዳ ሁሴን ይመር ተጠራ፡የለም	መጋቢት 6/2002	339
130	ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ ተከሳሽ የሆነን ወገን በሌለበት ባለዕዳ የሚያደርግ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ተከሳሹ በአግባቡ ስለመጠራቱ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 97, 95(3)	50022	5 ብራዘርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ዓብደላ ኢብሮ ዩሴፍ	መጋቢት 29/2002	341
131	የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በውሳኔው ወቅት ንብረቱን በእጁ አድርጉ የሚገኘው ወገን የንብረቱን ስመ ሐብት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን አዛውሮ ሲገኝ ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት ስለሚገባው አካሔድ	45038	እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጓዱ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ አስረስ አህመድ	መጋቢት 23/2002	343
132	• ሐሰተኛ ቃል ተሰጥቷል በሚል ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 መሠረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሊሰጥ የሚችልበት አግባብ • በአንድ የወንጀል ድርጊት ነፃ የተባለ ሰው እንደገና ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጉ የሚቀጣበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 የወንጀል ህግ ቁ. 452(1)	43005	እነ አቶ አውግቸው እርገጤ (ሦስት ሰዎች) ተጠራ፡የለም	ሚያዝያ 19/2002	345
133	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 መሠረት ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ለሰጠ ፍ/ቤት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6	45839	ወ/ሮ ይርጋለም ከበደ እና እነ ወ/ሮ ፅጌ ሚካኤል (አምስት ሰዎች)	ሚያዝያ 5/2002	348
134	በፍ/ብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 256, 345, 327	39853	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር (ሁለት ሰዎች)	ሚያዝያ 21/2002	350
135	አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ እንደሆነ በሰበር ችሎት	41526	ትራንስ አፍሪካ ትራንስፖርት አ.ማ	ግንቦት 2/2002	353

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(3), አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10		እና ሙሉ ኤሌክትሮኒክስ ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር		
136	ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ የተሰማሙና ይዜንኑም ስምምነት ለፍ/ቤት በማቅረብ ያስፀደቁ በሆነ ጊዜ ስምምነቱ እንደ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተቆጥሮ መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277	52752	እነ ከድር ሐጂ ሁሴን (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ አሚን ዑስማን (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 16/2002	355
137	ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው አቤቱታ የክስ ምክንያት አለው ወይም የለውም ብሎ ለመወሰን በክስ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሽ የሆነው ወገን የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ህግ ይፈቅድለታል ወይስ አይፈቅድለትም የሚለውን ጥያቄ መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ	45247	አቶ ደጀኔ በላቸው እና አቶ ነስሩ አወል	ሰኔ 17/2002	358
138	ሁለት ሰዎች ተጣምረው በተከሰሱ ጊዜ አንደኛው ወገን ጉዳዩ በሌለበት ከታየ በኋላ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተፈቀደለት እንደሆነ ሌላኛው ተከሳሽ አስቀድሞ ያነሳቸውን መቃወሚያዎች በድጋሚ ልታነሣና ልትከራከር አትችልም ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	49857	ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ፋንታ እና ወ/ሮ በላይነሽ ወ/ኪዳን	ሰኔ 30/2002	361
139	በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሽ ቀርቦ ክርክሩን ባሰማ ጊዜ ስለመሆኑና ድንጋጌው የካሣ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 235(2),83	48632	አቶ ሙልሳ በየቻ እና አቶ ደበሌ በየቻ	ሰኔ 14/2002	363
140	ክስ የቀረበበት ወገን ክሱን ለማስተባበል የሚቆጥራቸው ማስረጃዎችን ተቀብሎ አለመስማት የመከላከል ህጋዊ መብትን የሚያጣበብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ5 223, 234, 137, 249, 256	49660	እነ መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ት/ቤት (ሁለት ሰዎች) እና መምህር ሲሳይ ደጀኔ	ሰኔ 22/2002	365
141	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1) መሠረት በድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀደመው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑና የተከራካሪ ወገኖች አንድነት በመኖሩ ብቻ ሣይሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	52525	ወ/ሮ የትምወርቅ ሰብስቤ እና አቶ ሽዋረጋ ደመቀ	ሰኔ 29/2002	368
142	የሥር ፍ/ቤት በመቃወሚያ ላይ የሰጠውን ውሣኔ የሚለውጥ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠ እንደሆነ በግራ ቀኝ ወገኖችን በኩል የሚቀርቡ የፍሬ ነገር ክርክሮችንና ማስረጃ በአግባቡ ለመስማት ብሎም የተከራካሪዎችን ይግባኝ መብት ላለማጣበብ ሲባል ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለስ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341(1)	43331	አቶ ገመቹ ቡቻላ እና አቶ በቀለ ኩማ (ቡቻላ)	ሐምሌ 19/2002	370
143	ስልጣን ለሌለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብና ክርክር ማካሔድ የይርጋ ጊዜን የሚያቋርጥ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም የሰበር ችሎት በተቃራኒው የሰጠው የህግ ትርጉም የተሰወጠ ስለመሆኑ።።) አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 138, 147, 164(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9, 23,(1) (ለ) ,231,(1)(ለ), 278(3) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 (ለ),1852(1) አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀፅ 2(4)	36730	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አማረ ገላው	ሐምሌ 30/2002	372

https://t.me/ethiopianlegalbrief

144	• በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከሣሽ ለሆነ ወገን ከፍ/ቤት የሚላከውን መጥሪያ ለተከሳሹ ሊደርስ የሚችልበትን የተሻለ አማራጭ መንገድ በመለየት ሊላክ የሚገባ ስለመሆኑ • የመኖሪያ አድራሻው በግልፅ ለሚታወቅ ተከሳሽ ፍ/ቤቱ የሚልከውን መጥሪያ በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ብቻ እንዲለጠፍ በማድረግ ተከሳሹ አልቀረበም በሚል በሌለበት ጉዳዩ እዲታይ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ • መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው ያልተደረገ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሣኔ እንዲነሣለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 105(1), 78,	50376	ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ገሰሰ እና በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/08 አስተዳደር ጽ/ቤት	ሐምሌ 12/2002	378

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
		ቤተሰብ			1
1	በጋብቻ ውል ላይ ባልና ሚስት "መተዳደሪያችን" ነው በሚል ያመለከቷቸው ንብረቶች የጋራ ንብረት ተደርገው የሚቆጠሩ ስለመሆናቸው	38544	አቶ ብሩክ ኃ/እየሱስ እና ወ/ሮ ፋናዬ አበበ	ጥቅምት 5/2002	2
2	• በጋብቻ ላይ የተደረገ ጋብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው (void ab initio) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ • የጋብቻ ውል ተጋቢዎች ንብረታቸውን በተመለከተ ጋብቻው የሚያስከትለውን ውጤት ስምምነት የሚያደርጉበት ሰነድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 42,44,33,11	39408	አርጋው አባቹ እና የወ/ሮ አስቱር አበጋዝ ወራሾች (ስድስት ሰዎች)	ጥቅምት 24/2002	5
3	የውርስ ሀብትድርሻ ክፍፍል ጥያቄ በይርጋ የሚታገድበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080(3)	40418	ተስፋዬ ሞላ እና እነ እሸቱ ምነ (ሦስት ሰዎች)	ጥቅምት 10/2002	7
4	አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43	42682	እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ በላይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ	ጥቅምት 10/2002	9
5	ፀንቶ ባለ ጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት በጋብቻ ውስጥ ባል የሆነው ወገን ስለመሆኑና የዚህን ሰው አባትነት ለመቃወም የሚቻልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 144,126,167,168,173	40624	እነ ወ/ሮ መብራት ታደሰ (አራት ሰዎች) እና አቶ ኤፍሬም ዘውዴ	ጥቅምት 12/2002	11
6	የጋራ የሆነን የውርስ ሀብት ከፍቃዱ ውጪ እንዲሸጥ የተደረገበት ወራሽ ከሽያጩ ዋጋ ድርሻውን ለማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1266,1060(1)	41857	አሕመድ ሑሴን እና እነ ወ/ሮ የኔዓለም ተመስገን (ሦስትሰዎች)	ጥቅምት 24/2002	14
7	አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43	42682	እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ	ጥቅምት 10/2002	17
8	ከጋብቻ በፊት የግል የነበረ ንብረት በተጋቢዎች የጋብቻ ውል መነሻነት የጋራ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ	42766	እነ ወ/ት ሠናይት ኃ/ማሪያም እና ወ/ሮ አበበች ወርቁ	ጥቅምት 10/2002	19
9	ልጅነትን በማረጋገጥ በፍ/ቤት የሚሰጥ ውሣኔ የህግ ግምት የሚፈጥር እንጂ አስገዳጅነት ያለው እና የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ መወሰድ የሌለበት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,155,156,157	42648	ወ/ሮ ዘነበች በያን እና ወ/ት ብርቅነሽ ከበደ	ታህሣሥ 6/2002	21
10	አባትነት በህግ አግባብ ሊታወቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126,1(1),(2),128(1),130(2),125,106(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 35(2)	44612	ወ/ሮ ዘውዴ ወ/ጊዮርጊስ እና ወ/ት ኤልሣቤጥ ኪዳኔ	ጥቅምት 10/2002	23
11	• በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት አግባብ • የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1),1000(2),1060,1062	38533	እነ ወ/ሮ ጽጌ ወልደመስቀል (ስድስት ሰዎች) እና አቶ ስዩም ክፍሌ	ህዳር 8/2002	27
12	ልጅነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 156,168,158,169	42569	እነ የዳግማዊ ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ (ሁለት ሰዎች) እና የሃና ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ	ታህሣሥ 212002	30
13	ኑዛዜ ሊተረጐም የሚገባው ቃላቶቹና መልዕክቱ ግልፅ		አቶ ሐይለራጉኤል ደበላ እና	ታህሣሥ	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ማይሆን ሲቀር ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 810(2)	47487	እነ ወ/ሪት አለምፀሐይ ፊለገ (ሁለት ሰዎች)	27/2002	33
14	የስጦታ ውል ሊተረጐም የሚገባው በውሉ ውስጥ የሚገኝን አንድ ሃረግ ነጥሎ በማውጣት ላይሆን የውሉን አጠቃላይ ይዘት በመመልከት ስለመሆኑ	41893	ወ/ሮ ዮዲት ኃይሉ እና እነ ወ/ሪት ገነት አረጋይ (ሦስት ሰዎች)	ታህሣሥ 21/2002	36
15	የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3)	47957	እነ አቶ ተፈሪ ሐጐስ (ሦስት ሰዎች) እና አቶ ተስፋይ ገ/እግዚአብሔር	ጥር 5/2002	39
16	• የስጦታ ውል ገደብ ያለበት ወይም ግዴታ የተጣለበት እንደሆነ በውሉ ውስጥ የተመለከተው ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ፈራሽ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ • በፍ/ብ/ህ/ቁ. 244(1) ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ በስጦታ ውል ውስጥ የተመለከተ ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ውሉ እንዲፈርስ ሲጠየቅ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2452(1),2464(1),2441(1)	42346	እነ አቶ ፍስሐ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ አለምነሽ ፍስሐ	የካቲት 9/2002	41
17	የጉዲፈቻ ስምምነት የሕፃናትን ጥቅምት ለማስጠበቅ ሲባል ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 195(2)	44101	ሚስስ ፍራንሲዊስ ፖስተር እና እነ ሚ/ር ዱክማን ቬኖ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 24/2002	44
18	የውርስ ንብረት በሆነ ቤት ላይ ድርሻ አለን የሚሉ ወገኖች ንብረቱን ህጋዊ የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ይዞ ከነበረ ሰው በመግዛት ስመ ሀብቱን ወደራሱ ስም አዛውሮ የሚገኝን ሰው ለመጠየቅ የማይችሉ ስለመሆኑ	46527	ወ/ሮ ገነት በቀለ እና ወ/ሮ ትዕግስት አሰፋ	የካቲት 24/2002	48
19	ከውርስ ጋር በተያያዘ በቤት ላይ ህጋዊ መብት የሌለው ሰው ሽያጭ አከናውኖ ሲገኝ ትክክለኛው ባለሃብት መብቱን ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገዥ ማይሆን ሻጩን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 997,2882, 2884,1060(1),1266	47378	አቶ አለማየሁ ከተማ እና እነ ወ/ሮ ላቀች አይተንፍሱ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 24/2002	50
20	ኑዛዜ በፍ/ቤት መፅደቁ በንብረት ላይ ያለ የባለቤትነት መብትን የሚያረጋግጥ ስላለመሆኑ	42482	እነ አቶ ፍሬዘውድ ተካ ጐጂ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሰለሞን ኃ/ማሪያም	የካቲት 3/2002	53
21	የልጆች ቀለብ አከፋፈል ሁኔታ ጋር በተያያዘ ክፍያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ	45819	አቶ ካሣ ፋንታ እና ወ/ሮ አስካዳር ግጨው	የካቲት 12/2002	55
22	በትዳር ወቅት የተወሰደ ብድር የአንደኛው ተጋቢ ፈቃድ የሌለበት ቢሆንም ፈቃዱን ያልሰጠው ተጋቢ የብድር ስምምነቱ እንዲፈርስ ያላደረገ እንደሆነ ወይም ደግሞ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን ማስረዳት ያልቻለ ከሆነ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(መ)	45202	አቶ ድንቁ ወርዶፋ እና ወ/ሪት ኤደን ድንቁ ወርዶፋ	መጋቢት 8/2002	57
23	በተጭበረበረ መንገድ ወራሽነትን አሳውጆ የውርስ ንብረት አካል የሆነን ቤት ስመ ሃብት ወደ ራሱ አዙሮ የሚገኝ ሰው ጋር የሽያጭ ውል በተደረገ ጊዜ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሚል ትክክለኛ ወራሾች የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2882, 2884, 997	45370	እነ አቶ ዳንኤል አበበ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 21/2002	61
24	የስጦታ ውል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ 10 (አስር) ዓመታት ውስጥ ለአፈፃፀም ያልቀረበ እንደሆነ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676(1),1845	42691	አቶ አደፍርስ በቀለ እና አቶ ይቁም በቀለ	መጋቢት 22/2002	64
25	• በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት አግባብ • የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ	44237	እነ ወ/ሮ መሉሸዋ ቦጋለ (አራት ሰዎች)	መጋቢት 20/2002	66

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1)1002,1060,1062		እና አቶ መስፍን ቦጋለ		
26	ሞግዚት የሆነ ሰው በሞግዚትነት የሚያስተዳድራቸውን ልጆች ሀብት የሆነን ንብረት ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ ሲል ሊሸጠው የሚችል ስለመሆኑ የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ቤተሰብ ህግ አንቀፅ 292	46490	እነ ወ/ሮ ቦጋለች ደባልቄ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ መሠረት በለጠ	መጋቢት 21/2002	69
27	በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የተደረገ የሽያጭ ውል በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አለመፍረሱ ስለሚያስከትለው ውጤት	51295	አቶ ዮሐንስ ጡእማይ እና ወ/ሮ ምህረት ገብሩ	መጋቢት 6/2002	72
28	ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ባለስልጣን ፊት የሚደረግ ኑዛዜ በህግ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አሟልቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 882	49851	ወ/ሮ ታሪካ አበበ የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞግዚት ተጠሪ፡የለም	ሚያዝያ 4/2002	75
29	ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ የሆነ ሰው እና ከህግ ውጪ ከውርስ የተነቀለ ያለኑዛዜ ወራሽ የውርስ ሃብትን ሊከፋፈሉ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ 939(3) ,850,,911(1) 912(1)	43069	አቶ አማረ ረታ እና አቶ ሰለሞን ካሣዬ	ሚያዝያ 6/2002	78
30	የጉዲፈቻ ውል እንዲፈርስ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 195(1),(2)	52691	እነ ቤተ ዛታ ችልድረንስ ሆም አሶሴሽን (ሦስት ሰዎች) ተጠሪ፡የለም	ሚያዝያ 22/2002	81
31	ኑዛዜ መኖሩን የማስረዳት ሸክም (ግዴታ) የተጠቃሚዎች ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896,897	53279	ወ/ሮ ትእግስት ግርማ የእነ አቤል ወርቁ ሞግዚት እና አቶ ኤፍሬም መንግስቱ	ሰኔ 8/2002	84
32	በኑዛዜ የውርስ ሀብት ክፍፍል መደረግ ጋር በተያያዘ ወራሽ የሆነ ወገን ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ሀብት መጠን ከአንድ አራተኛ በታች እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ኑዛዜውን እንዲፀና በማድረግ የተናዛዡን ፍላጐት ማክበርና መጠበቅ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 910, 913 1123(1)	50901	ወ/ሮ እልፊ ኃይሌ እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ደበሌ (ሦስት ሰዎች)	ሰኔ 10/2002	87
33	በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ለማስረዳት የሚችሉት በግንኙነቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 98,99,106	46613	ወ/ሮ ኑኑ ሸህሞሎ እና ወ/ሮ አሰገደች ጫኔ	ሰኔ 24/2002	91
34	በተከራካሪ ወገኖች ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ ፍ/ቤቶች በግልፅ በመቀበል ወይም ባለመቀበል ውሣኔ ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ	51866	ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለማየሁ እና ወ/ሮ አሳለች ደበበ	ሐምሌ 2/2002	94
35	ከኮንዶሚኒየም ቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ከጋብቻ በፊት በአንደኛ ተጋቢ በተደረገ ምዝገባ የተነሣ የቤት ዕጣው የወጣው ብሎም የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው በጋብቻ ወቅት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ለቤቱ መገኘት ምክንያት የሆነው ተጋቢ ቤቱ የግል መሆን አለበት በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(2)	51893	እንዳልካቸው ዘለቀ እና ወ/ሮ ብዙዓለም መንግስቱ	ሐምሌ 8/2002	96
36	በፍ/ቤት የተሰጠ የኑዛዜ ወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የውርስ ሃብት ማጣራት ሳይደረግ የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ሊሰረዝ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	50836	ወ/ሮ ቅድስት ተካ እና ወ/ሮ የኔነሽ ተካ	ሐምሌ 13/2002	99
37	ከውርስ ሃብት ክፍፍል ጋር በተያያዘ ተጠቃሚው በኢንሹራንስ ውል ላይ ባልተገለፀበት ጊዜ የሚች ባል	44561	ወ/ሮ ገነት በላይ	ሐምሌ	101

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ወይም ሚስት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ከወራሾች ጋር ሊካፈሉ የሚችሉበት አግባብ የንግድ ህግ ቁጥር 705,701(1)(ሀ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 827		እና አቶ ያፈት ተክሉ	28/2002	
38	ከውርስ ሃብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የውርስ ሃብቱን በእጅ አድርጐ በመገልገል ላይ ያለ ተከራካሪ የሆነ ወራሽ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት በጋራ ይዞ የቆየ ሰው ላይ የሚያነሳው የውርስ ጥያቄ በይርጋ ታግዷል ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	44025	እነ ወ/ሪት ፀሐይ ሐይሌ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ ፈልቃ ቤኛ	ሐምሌ 22/2002	110
39	ወራሽ የሆነ ወገን በውርስ ሃብት ክፍፍል ድርሻው ላይ ከሩብ የበለጠ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለፅ አውራሽ ባደረገው ኑዛዜ መሠረት ክፍፍል እንዳይፈፀም መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1123(1)	47622	ወ/ሮ ትዕግስት ነጋሽ እና እነ ወ/ሮ መንበረ ስላሴ ተሾሌ (አምስት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2002	112
40	የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3)	45587	እነ ወ/ሮ አተረፈች ዘውደ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘውዱ ወሰኔ	ሐምሌ 29/2002	115
41	በተዘዋዋሪ መንገድ ተወላጅን ከውርስ ያለ በቂ ምክንያት መንቀል የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 938,842,915	42546	አቶ ተስፋልደት ኪዳኔ እና እነ ወ/ሮ ዘሀቡ ይመር (ሦስት ሰዎች)	ሐምሌ 28/2002	118
	ውል				123
42	በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ እስከ አሥር ዓመት ድረስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058	44800	አቶ አብዱራዛቅ ሐሚድ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ጥቅምት 05/2002	124
43	ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትና የመተማመን ግንኙነት መሠረት በማድረግና ጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ልቦና ሊተረጐም የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1732(1)	42897	አቶ አየለ ሐብተየስ እና እነ ሚ/ር ኖቼራ ጃካርሎ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 10/2002	127
44	ለጨረታ ማስከበሪያ በሚል የሚያዝ ገንዘብ ጨረታውን ባዘጋጀው አካል ሊወሰድ የሚችለው ተወዳዳሪው ጨረታውን ባሸነፈው መጠን ሆኖ በጨረታው መሠረት ውል ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ	40947	አቶ መዝገቡ መድህኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር	ህዳር 15/2002	131
45	ተከራካሪ ወገኖች ባላነሱበት ሁኔታ ፍ/ቤት የውል አፃፃፍ ሥርዓትን (ፎርማሊቲን) መሠረት በማድረግ በግራ ቀኝ ወገኖች መካከል የተካሄደን ውል ፈራሽ ነው በሚል የሚሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1808(2)	43825	የህፃን ኮከቤ ተረፈ ሞግዚትና አስተዳዳሪ እና እነ አቶ አያሌው ካሳዬ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 6/2002	133
46	• የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) ለባንኮችና ለደንበኞቻቸው መብት ልዩ ጥበቃ የሚያደርገው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2473(2) ድንጋጌን ዋጋ በሚያሳጣ መንገድ ተፈፃሚ ሊሆን የማይገባ ስለመሆኑ • የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) በባንኮችና በሌሎች አበዳሪ ተቋማት እና ደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተፈፃሚነት የሌለው የህግ ድንጋጌ ስለመሆኑ • ባንኮች ለደንበኞቻቸው ያበደሩትን የብድር ወለድ ያልተከፈለ መሆኑን በሰው ምስክር፣ የሰነድና ሌላ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(1) ስር የተደነገገውን የህሊና ግምት ለማስተባበል የሚችሉ ስለመሆኑ	29181	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ልየው ቸኮል (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 20/2002	135
47	በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2024/፫/ መሰረት እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችለው በብድር የተሰጠ ገንዘብ ሳይሆን የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ ክፍያ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024	35758	እነ አቶ ገብረመድኅን አየናቸው (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሰብስቤ ኃይሌ	ታህሣሥ 20/2002	142
48	የወለድ አግድ ውል ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው		እነ አቶ ፈታኒ ባየህ		

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መቋቋምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በመከተል የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑና በዚህ መሰረት ያልተደረገ መሆኑ ውሉን ፈራሽ ሊያደርገው የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3118,3045,3052	45422	(ሰባት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ አስራት ባየህ (ሦስት ሰዎች)	ጥር 13/2002	147
49	የስልክ አገልግሎት ከማግኘት ጋር በተያያዘ በአገልግሎት የክፍያ መጠን ላይ በአገልግሎት ሰጪውና በአገልግሎት ተቀባዩ መካከል አለመግባባት በተፈጠረ ጊዜ የተጠየቀው የአገልግሎት ሒሳብ በእርግጥም ስልኩን በይዞታው ስር አድርጎ የሚጠቀምበት ወገን በተገለገለው መጠን የተመዘገበ ስለመሆኑ በባለሙያ እንዲጣራ በማድረግ እልባት መስጠት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732	48967	አቶ ሳዲቅ ሐሰን እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2002	151
50	መዋዕለ ነዋይን በማፍሰስ ግንባታን ለማካሄድ የከተማ ቦታን ከመንግስት ተረክቦ ግንባታን በተገቢው ጊዜ ለማጠናቀቅ አለመቻል ሊያስከትል የሚችለው ውጤት የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ደንብ ቁ. 41/97 አንቀፅ 8(3) የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ አዋጅ ቁ. 51/94	46052	ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ እና የቦንጋ ማዘጋጃ ቤት ከፋ ዞን	ጥር 19/2002	154
51	ከቤት ኪራይ ውል ጋር በተያያዘ የኪራይ ውልን ለማቋረጥ በቂ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ተከራይ የሚፈፅማቸው የግንባታ አይነቶች የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2953,2954,1732	46394	ወ/ሮ ስንቂ መስፍን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	የካቲት 11/2002	157
52	ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች ወለድን አስመልክቶ በውላቸው ካመለከቱት ሃሳብ ውጪ የራሱን ስሌት መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1731,2478	45559	የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ) እና እነ የአቶ ኃይሉ ፈይሳ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	160
53	ከሽያጭ ጋር በተያያዘ ውል ሲመሰረት ጉድለት የነበረበት መሆኑ ቢረጋገጥም ከውሉ መመስረት በኋላ በተሸጠው ንብረት ላይ ተዋዋይ ወገኖች ተጨማሪ ግንባታ ያካሄዱና ወደ ነበሩበት ለመመለስ አዳጋች ሁኔታ ያለ መሆኑ ከታመነ ውሉ ሊፀና የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1)	47800	ወ/ሮ እመቤት ደርበው እና አቶ ታደሰ ሰዳማ	የካቲት 25/2002	162
54	ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር የኪራይ ውል አከራይ የሆነ ወገን ለተከራይ ማስታወቂያ በመስጠት ምክንያቱን መግለፅ ሳያስፈልገው የኪራይ ውሉን ሊያቋርጥ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966(1)	40336	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የወ/ሮ አሰገደች ካሣሁን ወራሽ ሄኖክ ሣሙኤል	መጋቢት 22/2002	164
55	በሌላ ሰው ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠንና ባደረሰው ጉዳት መጠን ኪሣራ ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162	43381	ወ/ሮ ፎዚያ ሁሴን እና አቶ ውብሸት ተ/ወልድ	መጋቢት 10/2002	166
56	ከሳሽ የሆነ ወገን ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ በአንድ ላይና በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ለመክሰስ የሚችል (የሚገባው) የነበረ ቢሆንም ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ቀንሶ ያቀረበው በፍ/ቤት ፈቃድ የሆነ እንደሆነ የቀረው መብት ላይ በድጋሚ ክስ ለመመስረት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4)	43992	እነ አቶ ይልማ አንበሴ (አራት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ እመቤት መንገሻ (አምስት ሰዎች)	መጋቢት 6/2002	168
57	ከሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ የሚያቀርበው የውል ይፍረስልኝ ክስ ገዥ ውል እንዲፈፀምልኝ በሚል ሊያቀርብ የሚችለው አቤቱታ ላይ የሚቆጠረውን የይርጋ ጊዜ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,1851	43636	ወ/ሮ አልማዝ ተሰማ እና እነ አቶ በየነ ወ/ሚካኤል (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 22/2002	173
58	የኪራይ ውልን መሠረት በማድረግ ቤትን የያዘ ወገን የኪራይ ውሉን በቅድሚያ ሣያስፈርስ የባለቤትነት ጥያቄን መሠረት በማድረግ በኪራይ ውሉ አልገደድም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	46947	አቶ ዘነበ ኃ/ማሪያም እና እነ ወ/ሮ አባይነሽ ዘለቀ (ሦስት ሰዎች)	መጋቢት 7/2002	175

https://t.me/ethiopianlegalbrief

59	ከእጅ በእጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ገዢ የሸያጩን ዋጋ የከፈለበትን ደረሰኝ ይዞ መገኘቱ የገዛውን ንብረት እንደተረከበ የሚያሳይ የመጨረሻ (conclusive) ማስረጃ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2266,2278(1) እና (2)	45545	ወ/ሮ ሸዋዬ ኑርዬ እና ምን አዩ ኃ/የተ/የግል ማህበር	መጋቢት .22/2002	178
60	በፍ/ብሔር ጉዳይ ህጋዊ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ዋስትና የሚደረግበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1922	47971	ወ/ሮ ጅቦኒ ቱና እና ወ/ሮ ብርቂ ኢርክታ	ሚያዝያ 5/2002	181
61	ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ ተከራይ የሆነ ወገን የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ በህግ የተጣለበት እንደሆነ አከራይ የሆነው ወገን ይህንኑ ክፍያ ለመፈፀም ይቻል ዘንድ ተከራዩን ለመጠየቅ ስለመቻሉ አዋጅ ቁ. 308/95 አንቀፅ 2(3,5,7,8,9,12),6	48358	አቶ ብርሃነ ንብረሐይሉ እና አንሲዩን ኮንትር ላፋም	ሚያዝያ 7/2002	183
62	• አንድ ሰው ብድሩን አለመክፈሉን አምኖ በሚከራከርበት ሁኔታ የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 2024(ረ) ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ • 2024(ረ) ዋና ብድርን ሣይሆን ለብድር የሚከፈል ወለድን የሚመለከት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ረ)	44691	አቶ ሸባባው ወሌ እና አቶ ሙሉጌታ ዓባይ	ሚያዝያ 8/2002	186
63	አንድ ውል ህግን የሚፃረር /የሚቃረን/ ነው በሚል እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845	48094	እነ ሙና እንድሪስ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ግንቦት 10/2002	188
64	በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት አሰሪው ሠራተኛው በውጭ አገር ትምህርቱን እንዲከታተል ለማስቻል የሚያስፈልጉ ወጭዎችን ደመወዝን ጨምሮ ለመክፈል ሠራተኛው ደግሞ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ አሠሪውን ለማገልገል ውል ገብቶ ሠራተኛው ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለ በሆነ ጊዜ አሠሪው የጉዳት ኪሣራ የመጠየቅ / የመክፈል/ መብት ያለው ስለመሆኑ	49453	የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት እና አቶ ተፈሪ ማሞ	ግንቦት 19/2002	192
65	የሽያጭ ውል በህግ የተቀመጠውን የአፃፃፍ ሥርዓት ባለመከተሉ ፈራሽ ሲሆን ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ወገን ንብረቱን ለውጦ ወይም በንብረቱ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ባወጣው ወጪ መጠን ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1818	49326	ወ/ሮ እታፈራሁ ኃ/ማሪያም እና እነ መምህር በቀለ ታችበሌ (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 28/2002	195
66	በፍ/ብሔር ጉዳይ (ክርክር) የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1846	42700	የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ	ሐምሌ 12/2002	198
67	የአቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024 ሥር በተመለከተው የህሊና ግምት የሚሸፈን ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024	46019	የአቶ ደሣለው ፋንታ ወራሾች እነ ሙሉጌታ ደሣለው እና አየለ ደበላ	ሐምሌ 20/2002	202
68	አንድ የስጦታ ውል በኃይል ወይም በተንኮል ተግባር ተደርጓል በሚል ስለሚፈርስበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2442(3),1698,1699,1704,1706	49900	እነ ወ/ሮ ሐመልማል ዓለሙ(ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ሀረገወይን ዘለቀ	ሐምሌ 19/2002	206
አፈፃፀም					210
69	የውርስ ንብረት በጨረታ እንዲሸጥ ለማድረግ መነሻ ዋጋን ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1083,1084	43888	አቶ ፀሐይ ወንድም እና እነ አቶ አያለው መለስ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 23/2002	211
70	አንድ ተጋቢ በግሉ ያመጣው ዕዳ ከሌለኛው ተጋቢ የጋራ ንብረት እንዲከፈል የሚደረገው ዕዳውን ያመጣው ተጋቢ ዕዳውን ለመክፈል አለመቻሉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የደቡ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ እና የፌዴራል መንግስት የተሻሻለው	39837	አቶ ስመንጉስ አሰፋ እና መ/ት ምህረት ክበበው	ግንቦት 3/2002	213

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የቤተሰብ ህግ				
71	አንድ ንብረት በፍርድ አፈፃፀም የተነሣ ሊያዝ የሚችለው በተሰጠው ፍርድ ባለዕዳ የሆነው ወገን ሃብት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ	46143	ወ/ሮ ድልበኔ ራሕመቶ እና እነ የባህር ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት(ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2002	215
	ወንጀል				217
72	የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የንግድ ድርጅት ሠራተኛ፣ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ድርጅቱ በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦባቸው ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 56(1)(3) አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀፅ 50(ለ)(1),22(1) የወንጀል ህግ አንቀፅ 23(3),34(1)	48850	እነ አቶ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ (ሦስት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ታህሣሥ 8/2002	218
73	በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የፈፀመው የግድያ ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1) (ሀ) ሥር የሚያስጠይቅ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)(ሀ),84,86	45927	የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ እና መሰረት መኮንን	ጥር 19/2002	221
74	በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ክስ በዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተሟልቶ አለመቅረብ የከሳሽ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ መዘጋት በቀረበው ወንጀል ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ ከመሆን የሚያግደው ስላለመሆኑ	45572	ወ/ሮ ዘነበች ሽብሩ እና ፌ/ዐ/ህግ	የካቲት 26/2002	224
75	ህጋዊ መካላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የሰው መግደል ተግባር በወንጀል ህግ ቁጥር 541(ሀ) የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 540, 541	43501	እነ ረዳት ሳጅን ሽጋ ተካ ሞላ (ሦስት ሰዎች) እና የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ	መጋቢት 15/2002	225
76	በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 እና 567 መሰረት አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543,567	44235	ቁስ ጌታቸው ተሾመ እና ዓቃቤ ሕግ	መጋቢት 28/2002	229
77	አንድ ሰው የማታለል ተግባር ፈፅሟል በሚል በወንጀል ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ የወንጀል ህግ ቁጥር 692(1)	46189	ሐረገወይን ተፈራ እና ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	ሚያዝያ 20/2002	232
78	ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ የዘወትር ፀባይ መልካም የነበረ መሆኑ በተናጠል (በራሱ) ቅጣትን ለማቅለል የሚያስችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 82(1) (ሀ)	53612	እነ አቶ ፍስሐ ዓባይ(ሁለት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ዓ/ህግ	ሚያዝያ 25/2002	234
79	በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ወንጀለኛው በይቅርታ የተለቀቀ መሆኑ አስቀድሞ የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ እንዳልነበረ የሚያስቆጥር (በሪከርድነት እንዳይያዝ የሚያደረግ) ስላለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 230	41248	ቡርቁሶ ዋቆ እና ዐቃቤ ሕግ	ሰኔ 23/2002	237
80	በሥር ፍ/ቤት የተሰጠ የቅጣት ውሣኔ ላይ አነሰ ወይም በዛ በሚል በግልፅ ይግባኝ ባልተጠየቀበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅጣትን ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ውሣኔ ሊሰጥ የማይገባ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(መ)	48617	ተስፋዬ አደላ እና ዐቃቤ ሕግ	ሰኔ 18/2002	239
81	• ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተከራካሪ ወገኖች የማስረዳት ሸክማቸውን ተወጥተዋል ለማለት የሚቻልበት አግባብ • በፍ/ቤት ፊት ቃለ- መሃላ በመፈፀም የተሰጠ የምስክር ቃል እውነት ነው በሚል የሚወሰደው ግምት ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ	51706	አቶ ግርማ ትኩ እና የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ሐምሌ 21/2002	242

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111				
	ንብረት				251
82	የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041,3052	38681	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እማሆይ ፀሐይቱ አምበሉ	ጥቅምት 3/2001	252
83	ለረጅም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ሥር የነበረ ቤትን ይለቀቅልኝ በሚል አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ አግኝቶ ባለመብትነቱን ሳያረጋግጥ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 47/67	45161	እነ እናኑ ጀንበሬ (ሁለት ሰዎች) እና የደሴ ከተማ ቀበሌ 03 ጽ/ቤት	ታህሣሥ 24/2002	255
84	የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው (ቀሪ ሆኗል) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677,1845,1206,1188-1192	43600	ዳዊት መስፍን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ጥር 05/2002	257
85	የአዋጅ ቁጥር 47/67 በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠን ካርታ መሰረት በማድረግ ክሥ ለመመስረት የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67	48699	አቶ አምሣለ ጀመሪ እና አቶ ፍርዱ ገበያሁ	ሚያዝያ 21/2002	262
86	በአንድ ቤት ውስጥ ሲኖር ያልነበረ ወይም ቤቱን በእጁ አድርጐ ሲያዝበት ያልነበረ ሰው የሚያነሣው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149	43081	አቶ ሣሙኤል ጦኖሮ እና እነ ወ/ሮ አይሻ አርጌሳ (አራት ሰዎች)	ግን ቦት 6/2002	266
87	በሃይል ቤቱ ተይዞብኛል እንዲለቀቅልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206,1149	42861	ወ/ሮ አጤነሽ አበበ እና አቶ ማንተጋፋቶት አጥላው	ሰኔ 28/2002	268
88	• አንድን ንብረት በአደራ ለማስተደደር (ለመጠበቅ) የተረከበ ወገን አደራ ሰጪው ንብረቱ እንዲመለስ በጠየቀው ጊዜ ወዲያውኑ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ • ንብረትን በአደራ የሰጠ ወገን ንብረቱ እንዲመለስለት ከመጠየቅ ጋር በተያያዘ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ (ይርጋ)የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2781 (1)(2),2779, 2989(1)	48048	ወ/ሮ ንብርኤላ ኒካላ ቶማስ ናክሶ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ሐምሌ 22/2002	270
89	ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የጉዳት ኪሣራን ጉዳት ለሚደርስበት ወገን በመክፈል የመንገድ መተላለፊያ (servitude right) መብት ሊከበር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1221	48783	ወ/ሮ ሶፊያ ሁሴን እና እነ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 27/2002	273
	ከውል ውጭ ኃላፊነት				276
90	የጉዳት ኪሣራ የሚከፈለው ጉዳት ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090,2091	39601	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ገዛኸኝ መንግስቱ	ጥቅምት 5/2002	277
91	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ገቢ ያልነበረው መሆኑ በርትዕ ሊከፈለው የሚገባውን ካሣ የሚያስቀር ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102	42962	አቶ አየለ አድማሱ እና አቶ አጀቡ ሹሜ	ታህሣሥ 28/2002	279
92	በወንጀል ጉዳይ ተከሳሾ ጥፋት የሌለበት መሆን በራሱ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍትሐብሔር ከቀረበ ክስ ነፃ ለመውጣት እንደ በቂና የመጨረሻ መስፈርት የሚወሰድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149	43843	ዶ/ር ተስፋነሽ በላይ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ	መጋቢት 21/2002	289
93	ለተወሰነ ጊዜም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት በሥራ ወቅት በሌሎች ሰዎች	45735	አቶ ደረጀ ቸርነት እና	መጋቢት 21/2002	285

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አሠሪ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2130, 2131, 2132		ወ/ሮ ሕይወት የኃላሸት		
94	በአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ችሎት ሠራተኛው የፈፀመው ድርጊት ከሥራ ለማሰናበት በቂ አይደለም ተብሎ መወሰኑ አሰሪው በሠራተኛው ላይ በፍ/ብሔር ጉዳይ ሊያቀርብ የሚችለውን ክስ የሚያስቀር የመጨረሻ ፍርድ /ውሣኔ/ ስላለመሆኑ	44588	የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና እነ ኃይለየሱስ ቱኪ (አራት ሰዎች)	ሚያዝያ 4/2002	290
95	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ህይወቱ ካለፈ ሰው ጋር በተገናኘ የሚከፈለው የጉዳት ካሣ መብቱን የሚጠይቀው ሰው ዕድሜ ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ በመሆኑ የተነሣ ብቻ ካሳው ሊከፈለው አይገባም ለማለት የሚያስችል የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2095/1/	50225	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ት ዝናሽ አሰፋ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 5/2002	293
					295
	የዳኝነት ስልጣን				
96	የአ.አ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ደብተርን ለመሰረዝ የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ	34665	እነ አቶ ናትናኤል ዘውገ (ሁለት ሰዎች)እና እነ ወ/ሮ እግዜሩ ገ/ህይወት(ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት1 2/2002	296

97	የከተማ ቦታ ያለአግባብ ተወስዶብኝ በሊዝ ለሌላ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የቦታውን መውሰድ ውሣኔ ለሰጠው አካል በቅድሚያ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑና በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ያለበትና ይኸው አካል የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 272/1994	46220	የደቡብ ክልል የሐዋሣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና የሐዋሳ ደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ገዳም	ጥር 18/2002	298
98	በውጪ አገር ሕግ መሰረት የተቋቋመና በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገበ የንግድ ድርጅት ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊዳኝ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 27(1), አዋጅ 25/88 አንቀጽ 11(2)(ሀ)	42928	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ድራጋዶስ ኮንስትራክሽን	ጥር 12/2002	300
99	በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለባለገንዘቡ ሊመለስ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 53(1),55	42866	ብርሃነ ጥዑም እና የጉምሩክ ባለስልጣን	መጋቢት 20/2002	302
100	የሥራ መደብ ወይም እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የወል የሥራ ክርክርን የሚመለከት ስለመሆኑ	48111	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ቂጤሳ ገብሬ	ሚያዝያ 13/2002	305
101	በውድድር አሸንፌ ያገኘሁትን የሥራ መደብ እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ የሥራ ክርክር የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የሚታይ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	52600	የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር እና አቶ ተስፋዬ ኃይሌ	ሚያዝያ 12/2002	308
102	የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በከተማው የሚገኝ ቤት ባለቤትነቱ የማን ነው ከሚል ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚነሣ ክርክርን ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 416/19 አንቀፅ 33	47134	የድሬዳዋ አስተዳደር ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ፋንታዬ ምትኩ	ግንቦት 6/2002	310
103	• የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከ5000 ብር በታች የሆነ ጉዳይን በሙሉ ተቀብሎ ለማስተናገድ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች በሕግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ	52041	የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክ/አ/ማህበር እና የኢት/መድን ድርጅት	ሰኔ 29/2002	313

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• የሥራ-ነገር ሥልጣን በሕግ ባልተሰጠው የዳኝነት አካል (ፍ/ቤት) የተሰጠ ፍርድ የማይፀና ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(6),5(9) አዋጅ ቁ. 361/95				
104	በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ጋር በተያያዘ የሚነሣ ክርክርን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 5(6)	43912	አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና እነ የአቶ ኢብራሂም መ·ሣ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 15/2002	315
105	በሰዎች ወይም በሚንቀሳቀስ ሀብት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስን ለማስተናገድ የግዛት ክልል ሥልጣን ስለሚኖረው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 27	48018	አቶ ተከተል ዘካሪያስ እና እነ ወ/ሮ አስቴር ታደሰ(ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 7/2002	317
106	በሽሪአ ፍ/ቤት በሚካሄድ ክርክር ላይ ጣልቃ ገብቶ መከራከር በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ስምምነትን እንደመስጠት የሚያስቆጥር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 188(92) አንቀፅ 5(1)	45806	አቶ ፍፁም በረታ እና እነ ወ/ሮ ሶፊያ ዱላ(አራት ሰዎች)	ሐምሌ 8/2002	319
107	• በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ እጅግ አስፈላጊ የህዝብ አገልግሎት ድርጅቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ተቋማት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ጥያቄን የያዘ የውል የሥራ ክርክር ካልሆነ በስተቀር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ለማስተናገድ የሥረ- ነገር ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ • መሰል ጉዳዮችን ለማየት በህግ ስልጣን የተሰጠው በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰየም ቦርድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 466/97 አንቀፅ 2(2) አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 142(1)(ሀ),(2),(3),136(2)	49152	የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር እና የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት	ሐምሌ 7/2002	324
ባንክና ኢንሹራንስ					328
108	በብድር ለተሰጠ ገንዘብ በመያዣነት የተያዘ ንብረት መድን የተገባለት ሆኖ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ አበዳሪው ንብረቱን በመያዣ የያዘበት ብድር ዋጋ ዋስትና ከተገባለት የገንዘብ መጠን ያነሰ እንኳን ቢሆን መድን ሰጪው እንዲከፍለው ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2858	38572	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ጥቅምት 17/2002	329
109	ባንክ በመያዣ መልክ የያዘውን የተበዳሪ ንብረት በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት በመሸጥ ላይ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ በተበዳሪው ላይ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ ዕዳው እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ	44164	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ሐሰን ኢብራሂም	ታህሣሥ 8/2002	332
110	የኢንሹራንስ ውልን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 674(1),754(1)	46778	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ	የካቲት 24/2002	336
111	የመድን ሰጭ ኃላፊነት በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 665(2)	46808	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና ወ/ሮ ጫልቱ ሚደግሳ	ሚያዝያ 6/2002	339
112	ለአንድ ንብረት መድን የገባ ሰው በንብረቱ ላይ የደረሰው ጉዳት ሙሉ ውድመት ሊባል የሚችል ቢሆንም ካሣ ሊከፈለው የሚችለው ጉዳት በደረሰ ጊዜ ዕቃው ከሚያወጣው ዋጋ ሳይበልጥ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 678	48698	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አቶ ሣሙኤል አለሙ	ግንቦት 19/2002	341
113	መድን ሰጪ የሆነ ወገን በመድን ገቢው እግር በመተካት ባለዕዳ የሆነ ወገን ላይ ጥያቄ ባነሣ ጊዜ ባለዕዳው ከመድን ገቢው ጋር የሚፈጠር አለመግባባትን ከፍርድ ቤት ውጪ በሽምግልና ለመጨረስ የተስማማን በመሆኑ መድን ሰጪው በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ ሊጠይቅ አይችልም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ	39902	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ	ሰኔ 18/2002	344

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የንግድ ህግ ቁ. 683(1)				
114	አስቀድሞ የተደረገ ነገር ግን ባለመታደሱ ምክንያት የተቋረጠ (ያበቃ)ን የመድን ውል መሠረት በማድረግ ሊጠየቅ የሚችል የጉዳት ካሣ ስላለመኖሩ የንግድ ህግ ቁ. 666(2) እና (3)	52910	አቶ አንዳርጌ ታደሰ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሐምሌ 28/2002	347
	ጉምሩክ(ግብር)ታክስ				349
115	• የንግድ ቤቶችን የማከራየት እንቅስቃሴ ከታክስ ነፃ ከሆኑ ግብይቶች የማይመደብ ስለመሆኑ • የንግድ ቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 8	39574	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ወ/ሮ ምልእተ ፀጋ ቢዘን (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 3/2002	350
116	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያልተከፈለን ቀሪ ቀረጥ ሊያስከፍል የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ.60/89 አንቀፅ 57(1),48,53(1)	45882	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ እጅጋየሁ አራምዴ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 6/2002	352
117	የጉምሩክ አዋጅን በመተላለፍ ከሚፈፀም የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ የኮንትሮባንድ ተግባር ሃይልን በመጠቀም ወይም ከሌሎች ጋር በማበር የተፈፀመ እንደሆነ አዋጅ ቁ. 60/89 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ	44862	አሸናፊ አበበ እና የጉምሩክ ባለስልጣን	ጥር 5/2002	355
118	የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ክስ ሊቀርብበት የሚገባውና ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲሱ የወንጀል ህግ ሣይሆን የጉምሩክ አዋጆች መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89	48693	ነኢማ አወል እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ጥር 5/2002	357
119	የንግድ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው የድርጅቱን አስተዳደራዊ ሥራ ለሌላ ሰው የወከለ መሆኑ ድርጅቱ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት በመፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ በተባለ ጊዜ ከሚቀርብበት የወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የማያደርገው ስለመሆኑ	54061	አቶ መስፍን ሽፈራው እና የኢትዮጵያ ገቢዎች ባለስልጣን	ሚያዝያ 26/2002	359
120	• የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባሩን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ባለማከናወኑ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ • የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ግዴታውን ለመወጣት ሲንቀሳቀስ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐት ከሚቆየው ንብረት ጋር በተያያዘ የተቋረጠ ጥቅም ወይም የጉዳት ካሣ ሊከፍል የሚችልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ 60/98 አንቀጽ 6(5), 58,74 አዋጅ ቁ 368/95 አንቀጽ 78	49889	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና አቶ ዛኪ ሰይድ	ሰኔ 28/2002	361
121	የግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜና ስሌቱ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 43(1)	48621	አቶ አብደላ ሁሴን ከለር ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን	ሰኔ 30/2002	365
	ውክልና				368
122	ባንክ በሐዋላ ለማድረስ የተቀበለውን ገንዘብ ለተገቢው ሰው አልደረሰም በሚል ኃላፊነት አለበት ሊባል የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር ሳይከተል የቀረ እንደሆነ ወይም መጭበርበሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ	48269	አቶ ሽረፈዲን አብደ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	የካቲት 24/2002	369
123	ወኪል የሆነ ሰው የውክልና ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ የራሱን ወይም ከራሱ ጋር ቤተሰባዊ ወይም ሌላ ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር ያለው ሰውና የወካዩ ጥቅም ሊጋጭ	50440	አቶ ሃብቱ ወልዱ እና እነ ወ/ሮ መሰሉ ደስታ	ግንቦት 16/2002	371

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የሚችልበት አጋጣሚ እንዳይፈጠር መከላከል ያለበት ወይም በተፈጠረ ጊዜ አስቀድሞ ለወላዩ ማሳወቅ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)2198,2208,2209		(ሁለት ሰዎች)		
የንግድ ሕግ					375
124	• የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ • በግለሰቦች መካከል በውል የሚፈጠር የሽርክና ማህበር የንግድ ሕግ በሚያዘው መሰረት አይነቱ ተለይቶ ተመዝግቦ የማይገኝ በሆነ ጊዜ እንደ የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ የንግድ ሕግ ቁጥር 211,212,219	46358	ወ/ሮ ብርሃን ፀጋዬ እና እነ አቶ ሚካኤል ፋስሐ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	376
125	ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ሰዎች ማህበሩን ሲያስተዳድሩ በሰሩት ያልተገባ ስራ ምክንያት በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት አግባብ የንግድ ሕግ ቁጥር 580	39608	ወ/ሮ አስቱር አርአያ እና እነ ወ/ሮ አምሳለ በላይ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 11/2002	378
አእምሯዊ ንብረት					381
126	አንድን መፅሐፍ ከተፃፈበት ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የተረጐመ ሰው እንደ ድርሰት አመንጪ ተቆጥሮ የሞራልና የቁሣዊ ጉዳት ሊወሰንለት ስለመቻሉ አዋጅ ቁ.410/96 አንቀፅ 2(2),6(1)	44520	አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት እና ዶ/ር ጌታሁን ሽብሩ	ጥቅምት 10/2002	382
ልዩ ልዩ					385
127	ለዋስትና የተያዘ ገንዘብን የአስያዡን ማንነትን ማረጋገጥ እስከተቻለ ድረስ ገንዘቡን ያስያዘበት ደረሰኝ ኮፒን ያቀረበ እንኳን ቢሆን የተያዘው ገንዘብ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ	53459	አቶ ማሞ ገ/ማሪያም ተጠራ፡የለም	ሚያዝያ 12/2002	386
128	• በአስፈፃሚ አካላት የሚወጡ የተለያዩ መመሪያዎች በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው የወጡ ወይም በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ አለመሆናቸው ህጋዊ ውጤት እንዳይኖራቸው የሚከለክል ስላለመሆኑ • አዋጅን መሠረት በማድረግ የወጡ መመሪያዎችን የሚፃረር ድርጊት መፈፀም በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 83/86 አንቀፅ 39(2),1, 2, 59(1)(ሸ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁ. ሲቲጂ 001/97	43781	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና አቶ ዳንኤል መኮንን	ሐምሌ 14/2002	388
129	• የሕግ ክርክሮችን በሰበር ማየት /ማስተናገድ/ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠ ስልጣን (power) ስለመሆኑ • በግልግል ዳኝነት (arbitration) የታየ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተዋዋይ ወገኖች የይግባኝ መብትን ለማስቀረት የሚያደርጉት ስምምነት ጉዳዩን በሰበር ችሎት ከመታየት የማያግድ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ።።) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3 (ሀ), አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 (4), አዋጅ ቁጥር 25/88, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 350(2) 351 እና 356	42239	ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ እና ዳን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ	ጥቅምት 20/2003	393

https://t.me/ethiopianlegalbrief



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች



ቅጽ- 12

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች ቅጽ- 12

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ - 12

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/ ሥር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ እነዚህን የሰበር ውሣኔዎች አሣትሞ ማሠራጨት ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኃላፊነት እንደሆነም ተመልክቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሠጠባቸውን የሰበር ውሳኔዎች ማሣተም የተጀመረ ሲሆን ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህም ከቅፅ 5 እስከ ቅፅ 10 ያሉትን አሣትመን አሠራጭተናል፡፡ እነሆ አሁን ደግሞ ቅፅ 11 እና ቅፅ 12 የሰበር ውሣኔዎች ሊታተሙ በቅተዋል፡፡ ይህም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሠጠባቸው የሰበር ውሳኔዎቻችንን የማሣተሙ ሥራ ወቅቱን የጠበቀና ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲሆን የምናደርገው ጥረት ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን ያሣያል፡፡

ባለፉት እትሞች መልእክቴ እንደገለፅሁት እነዚህ ፍርዶች ምንም እንከን የላቸውም የሚባሉ እንዳልሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በፍርድ ቤቶቻችን በየትኛውም ደረጃ ላይ ባለን ዳኞች በአንፃራዊነት የልምድም ሆነ የብቃት ውስንነቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ እነዚህ እጥረቶች በሰበር ፍርዶችና ውሳኔዎች ላይ አልፎ አልፎ ቢታዩ ሊገርመን አይገባም፡፡ የብዙ ዓመታት ተሞክሮ ያላቸው ሀገሮች ልምድም የሚያሣዩን ይህንኑ ነውና፡፡

የሀገራችን ፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ወጥና ተገማች እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የሰበር ውሣኔዎች ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ይህን አጠናክሮ ለመቀጠልና ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን በሰበር ውሣኔዎቻችን ላይ

በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሠማሩ የሕግ ምሁራንና ተማሪዎች ገንቢ አስተያየቶችን እና ትችቶችን ሊሠጡበት ይገባል፡፡

እነዚህ አስተያየትና ትችቶች ከሌሎች በተመሣሣይ ጎዳና ካለፉ ሀገሮች ከምናገኛቸው ልምዶች ተደምረው አቅማችንን በማሣደግ የተጣለብንን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት ጉልበት ስለሚሆኑን የሙያው ባለቤቶችና መላው ህብረተሰባችን ለጥረታችን መሣካት የሚጠበቅባቸውን ሀገራዊ ኃላፊነት እንዲወጡ በአክብሮት እየጠየቅሁ ውሳኔዎቻችንን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረ ገፅ ላይ ማግኘት የሚቻል መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ2003 ዓ.ም. የሰበር ችሎት

የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ውል				
1.	አግባብነት ካለው የመንግስት አካል ፈቃድ ሳይኖር የከርሰ ምድር ቁፋሮ ሥራን ለመስራት የሚደረግ ውል ህጋዊና አስገዳጅ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058/1/ እና /2,/ 1632/2/	54249	ጌታሁን አበበ ቦጋለ እና ሐሰን ገአስ ሁመድ	ጥቅምት 16/2003	
2.	በህግ አግባብ ተመዝግቦ የሚገኝ የመያዣ ውል ተጠቃሚ የሆነ ወገን በህግ የተቀመጠው ጊዜ ከማለፉ በፊት ውሉ እንዲታደስለት ከጠየቀ የንብረቱ አስያዥ ፈቃድ መኖሩ ሳይረጋገጥ ውሉ ሊታደስና ሊመዘገብ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058/1/ እና /2,/ 1632/2/	40109	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ ተክሌ ዋከኔ	ጥቅምት 01/2003	
3.	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ በፍርድ ሃይል የኪራይ ውል እንዲዋዋል የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ	42150	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ አቶ ዳንኤል ካሣ /ሀያ ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 29/2003	
4.	ውልን በተመለከተ በህግ የተቀመጠውን ፎርም አልጠበቀም በሚል አቤቱታ ለማቅረብ ስለሚችለው ሰው /ወገን/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808/2/	47617	ቄስ ገ/ሚካኤል አለምነው እና ወ/ሮ መልኬ ደምሴ	ህዳር 30/2003	
5.	የዋስትና ግዴታን ቀሪ ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1925/2/	49041	የአ/አ ከተማ አስተዳደር ዋና አዲተር መ/ቤት እና አቶ ኤሣው መዓዛ /ሦስት ሰዎች/	ህዳር 02/2003	
6.	ከመኪና ሽያጭ ጋር በተገናኘ ሽያጩ ከመከናወኑ በፊት በነበረ የፍ/ቤት እገዳ መነሻነት ገዢው በባለቤትነት መብቱ መገልገል ሳይችል ቢቀር በሻጩ ላይ የሚኖር ኃላፊነትና የጉዳት ካሣውን በመወሰን በኩል የገዢው ተነሳሪ ግዴታ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2341/2/ 2281, 2336, 2329, 2360, 1802, 1790	52106	እነ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ታደሰ አደራ	ህዳር 13/2003	
7.	እቃን ለመግዛት በጨረታ ማስታወቂያ ያወጣ ድርጅት ተወዳዳሪዎች በጨረታ ላይ ከተነገረው የተለየን ዕቃ በማቅረብ ከተወዳደሩ በኋላ ድርጅቱ ተወዳዳሪ የሆነው አካል በጨረታ ሰነዱ ላይ ሞልቶ ያቀረበውን እቃ መሰረት በማድረግ ውል የተዋዋለ እንደሆነ ይህንኑ ውል ለመፈፀም የሚገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1695/2/	53968	እነ የምስራቅ ወለጋ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ፀጋዬ ነጋ	ህዳር 13/2003	
8.	በማህበር አባላት ስምምነት የሚወጣ ደንብን አስመልክቶ በማህበሩ አባላት መካከል ብሎም በማህበሩ እና በአባላት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን እልባት ለመስጠት በፍትሐብሔር ህጉ ውስጥ ስለ ውሎች በጠቅላላው የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676/1/	54312	አቶ ሃይሉይ ተክላይ እና ውቁር የጨው አምራቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	ህዳር 28/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

9.	ውል ጋር በተያያዘ ተዋዋይ የሆነ ወገን ውሉን የፈፀምኩት ተገድጀና ከፍላገሩቱ ውጭ ነው በሚል የሚያደርገውን ክርክር ዳኞች (ፍ/ቤቶች) የዚህን ተዋዋይ ወገን እድሜ፣ ጾታ፣ የተዋዋይ ወገኖችን ልዩ ግንኙነት እና አጠቃላይ ተያያዥነት ያላቸው አኳኋኖች ጭምር መሰረት በማድረግ መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1706/1,1678/ሀ/,1809	55311	ወ/ሮ ብርሃኔ አጥናፉ እና ኢንስፔክተር ዮሃንስ ተሲላ	ህዳር 11/2003	
10.	ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው ሊፈጠር የሚችለውን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት ለመፍታት ከተስማሙ በኋላ አንደኛው ወገን ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ሌላኛው ተዋዋይ ስምምነቱ እንዲፈፀም ለፍ/ቤት የሚያቀርበው አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/, 231	56368	ዶ/ር ሰለሞን ነጋሽ እና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ	ህዳር 01/2003	
11.	የመያዣ ውል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተደርጐ ለማስረጃነት ዋናውን ሰነድ ማቅረብ ባልተቻለ ጊዜ የዋናው ሰነድ ግልባጭ ስለመሆኑ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተረጋግጦ የቀረበ የዋናው ሰነድ ኮፒ እንደ በቂ ማስረጃ ሊወሰድ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2011, 2008, 2009	56682	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አንዋር አብዱራህማን /ስምንት ሰዎች/	ህዳር 14/2003	
12.	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/ረ/ እና 2023 ለውሃ ፍጆታ ክፍያ ተፈፃሚነት የሌላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2023, 2024/ረ/	48857	የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 አስተዳደር ጽ/ቤት	ታህሳስ 12/2003	
13.	• የተሸጠለትን ነገር የተረከበ ገዢ የሸያጩን ዋጋ ወዲያውኑ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • ገዥ ለሻጭ /በሽያጭ/ ለማስረከብ በውል ከተስማማው መካከል የተወሰነውን ክፍል ያስረከበ መሆኑና ሻጭም በተረከበው መጠን ክፍያ ያልፈፀመ መሆኑ ለውሉ መፍረስ በቂ ምክንያት ሊሆን ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2278	49635	ሂጦስ የገበሬዎች የህብርት ስራ ማህበር እና የምስራቅ ዱቄት ፋብሪካ	ጥር 23/2003	
14.	አንድን ዕቃ በውል የተረከበ ሰው የተረከበው ዕቃ ጉድለት አለው በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በአንድ ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2291, 2292, 2298/1/	55229	ወ/ሮ መሃዳ ይመር እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአርሲ ቅርንጫፍ	ጥር 09/2003	
15.	• የግንባታ ሥራን ለመንግስት ለመስራት ጨረታውን ያሸነፈ ሥራ ተቋራጭ ሥራውን ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሥራ ተቋራጭ /ሰው/ በህጋዊ መንገድ ሊለቀቅ ወይም ሊያስተላልፍ የሚችልበት አግባብ • ከአሰሪ ጋር ያልተደረገና ከሥራ ተቋራጭ ጋር የተደረገ የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውልና የሚኖረው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3202/1/ እና /2/ 3205, 3206, 3244/1/, 2107	56252	ተስፋዬ አበበ ሥራ ተቋራጭ እና ማዕረገ ወርቁ ሥራ ተቋራጭ	ጥር 24/2003	
16.	• ውሎችን ህገ ወጥ ናቸው ወይም በህግ የተቀመጠውን መስፈርት አላሟሉም (Unlawful contracts or illegal contracts) በሚል ለመለየት የሚቻልበት አግባብ እና የሚያስከትሉት ውጤት • በመያዣ ተይዟል በሚል ባለንብረት በሆነ ባንክ በሐራጅ ንብረቱ የተሸጠበት ሰው ባንኩ ንብረቱን ለመሸጥ መብት የለውም በሚል /ውሉ እንዲፈርስ/ የሚያቀርበው የመቃወም አቤቱታ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ	43226	ጌታ ትራዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	የካቲት 7/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 446,447 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 6 አዋጅ ቁ. 216/92				
17.	የከተማ ቦታ ውልን መሰረት በማድረግ በሊዝ የሚሰጥበትና ውሉ ሊቋረጥ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 272/94 አንቀጽ 15/1/ /ለ/, 16	54596	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ እና ወ/ሮ ላቀች መንግስቱ	የካቲት 09/2003	
18.	ውልን መሰረት በማድረግ ቀብድ የተቀበለ ወገን የቀብዱን አጠፌታ በመክፈል ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1885/2/	56794	አቶ ሳህሉ ሙሉጌታ እና እነ አቶ ሰለሞን ኤፍሬም /ሦስት ሰዎች/	የካቲት 07/2003	
19.	• ተዋዋይ ወገኖች ውል ባለመፈፀሙ አንዳቸው ለሌላቸው መቀጮ /ገደብ/ እንዲከፈል በማለት የሚደርሱበት ስምምነት ተፈፃሚ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ • በውል በተወሰነ የገንዘብ ቅጣት ላይ የሚታሰብ የወለድ ክፍያ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1891, 1892/1/, 1889	58258	ወ/ሮ ዮርዳኖስ ሃጉስ እና ወ/ሮ ሀይማኖት ተፈራ	የካቲት 21/2003	
20.	የእውቀት ሥራ /ግሊጋሎት/ ውልን አሰሪ የሆነ ወገን በተናጠል ለማቋረጥ የሚችለው ባለሙያው ሥራውን ሙሉ በሙሉ አጠናቅቆ ለአሰሪው ከማስረከቡ በፊት ስለመሆኑና ባለሙያው ሥራውን አስመልክቶ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው የሙያውን ደንቦች በመጣስ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2637/2/, 2636/2/ና/1/	60469	ኮከብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ እና ሙሉ አለም የስራ አመራር አማካሪዎች	የካቲት 21/2003	
21.	ከመንግስት አስተዳደር መ/ቤት ጋር የሥራ ውል ያደረገ ወገን እንደውሉ ለመፈፀም ባልቻለ ጊዜ የአስተዳደር መ/ቤቱ ተዋዋዩ ለውል ማስከበሪያ (contract security) በሚል ካስያዘው ገንዘብ ላይ ውሉ ባለመፈፀሙ የደረሰበትን የጉዳት ኪሣራ መቀነስ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 430/97 አንቀጽ 43 የመንግስት የግዢ መመሪያ ቁ. 117/5/ /ሀ-ሐ/	60951	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ካንትሪ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ግንቦት 19/2003	
22.	• በሃዋላ የተላከን ገንዘብ ባንክ ለዕዳ ማስመለሻ በሚል ያለፍርድ መያዝ የማይችል ስለመሆኑ • በፍትሐብሔር ግንኙነት እዳን ለማቻቻል ስለሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1838/1/, 1840, 1841	64203	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ መሐመድ ሙሳ /አራት ሰዎች/	ግንቦት 15/2003	
23.	አንድን ስልጠና በአሰሪው ትብብር በውጪ አገር ተከታትሎ በምትኩ አገልግሎት ለመስጠት የተስማማ ሠራተኛ አስቀድሞ በውል የገባውን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ ሌላ /ተጨማሪ/ ስልጠና መጀመሩ በውሉ መሰረት ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን የሚያሳይና በኃላፊነት የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731	46574	ሐዋሳ ዩኒቨርስቲ እና እነ ዮናስ ካሣ /ሁለት ሰዎች/	መጋቢት 09/2003	
24.	• ከመኪና ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ ከመኪናው ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶችን ለገዢ አሟልቶ ያስረከበ መሆኑ ከተረጋገጠ ገዢ ስመ ሃብቱ በስሜ አልተዛወረም በሚል ምክንያት ብቻ ውሉ እንዲፈርስ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ • ከመኪና ጋር በተገናኘ ስመ ሃብቱን ለማዞር አስፈላጊ ሁኔታዎችን አሟልቶ ስም እንዲዛወርለት ጥያቄ አቅርቦ መብቱ ሊረጋገጥለት ያልቻለ ሰው በሚመለከተው አካል ላይ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ መብቱን ለማስከበር የሚችል ስለመሆኑ	56569	አቶ ዳዊት አሰፋ እና አቶ ተሻለ ደስታ	መጋቢት 23/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

25.	• በጽሁፍ እንዲደረጉ በህግ የተደነገጉ የውል አይነቶች ህጋዊና የተሟሉ ናቸው ለማለት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች /መስፈርቶች/ • የቤት ሽያጭ ውል ምስክር ሳይኖርበት በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በመደረጉ ብቻ ህጋዊና የሚፀና ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723/1/, 1727/2/, 2877	57356	ወ/ሮ መሠረት በቀለ እና ወ/ሮ ኤልሳ ሶሞኔላ	መ/ጋቢት 22/2003	
26.	ከግንባታ ሥራ ውል ጋር በተያያዘ የግንባታ ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ለባለቤት ወይም ለወኪሉ ስለመሆኑ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ክትትልና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 17, መመሪያ ቁ. 1/97	55359	አቶ ተድላ ማሞ ጌታቸው እና እነ አቶ ፍስሐ ሱመር /ሁለት ሰዎች/	ሚያዝያ 21/2003	
27.	• ተዋዋይ ወገኖች ውል ለማድረግ ነፃ ቢሆኑም ህግ የወሰናቸውና የከለከላቸውን ነገሮች ባለመገንዘብ /ባለማክበር/ የሚደረጉ ውሎች የማይፀኑ እና የማይፈፀሙ ስለመሆናቸው • በመንግስትና በህዝብ መሬት ላይ ግለሰቦች አንዱ ሰጪ ሌላው ደግሞ ተቀባይ በመሆን የባለቤትነት መብት ሊመሰርቱ የማይችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716	58157	አቶ ዮሐንስ ታደሰ እና ወ/ሮ አማረች መንገሻ	ሚያዝያ 06/2003	
28.	ህጋዊ ባልሆነ የቤት ሽያጭ ውል አማካኝነት የተሰጠን ገንዘብ ለማስረዳት ህጉ የደነገገው ልዩ የማስረጃ አይነት የሌለና በማናቸውም ማስረጃ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472, 2001, 2019, 1808/2/, 1815, 2162, 2164	58636	እነ አቶ ተሾመ ካሣ እና አቶ ቤዛ ኩሉ አዳም	ሚያዝያ 19/2003	
29.	• የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች በመያዣ (pledge) ለሌላ ሰው ተሰጥተዋል ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ እና ውጤቱ • መኪና በመያዣነት ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2825, 2832, 2830, 1186/2/, 2828, 1727, 2930, 2027, 2028, 2054	43582	ራፒድ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ ድርጅት እና ኦርቢስ ንግድና ቴክኒክ ክፍል ሊሚትድ	ሰኔ 28/2003	
30.	ጥሬ ገንዘብን በአደራ ከመስጠት ጋር በተያያዘ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ገንዘቡ በአደራ መልክ መሰጠቱን ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚችል ማስረጃ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2742 2782 2779	60204	አቶ ታደሰ ደምሬ እና አቶ ጌታሁን ለቻሞ	ሰኔ 14/2003	
31.	አንድን ሥራ ለሥራ ተቋራጭ የሰጠ የመንግስት መ/ቤት በራሱ ጥፋት ጉዳት አድርሶ ከሆነ ወይም የሥራ ተቋራጩን ሥራ መደበኛ አፈፃፀም ከባድ ያደረገበት እንደሆነ ለሥራ ተቋራጩ ኪሣራ የመክፈል ኀላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3259	61110	አል ናይል ቢዝነስ ግሩፕ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን	ሰኔ 28/2003	
32.	የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ ወደ ነበርንበት እንድንመላለስና የከፈልኩት ገንዘብ ይመለስልኝ በሚል ክስ መስርቶ ፍ/ቤት ጥያቄውን በህግ ፊት የሚፀና ውል የለም በማለት ውድቅ ያደረገበት ወገን ያለአግባብ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስልኝ በማለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለውና ህጋዊ ስለመሆኑና በመጀመሪያው ክስ ተጠቃሎ መቅረብ የነበረበት ነው ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1815, 1880/2/, 2001-2019, 2162, 2164 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216/2/3/	62134	እነ ጣና ወ/ሰማያት እና ወ/ሮ አልማዝ አሰጋሽኝ	ሰኔ 28/2003	
33.	• የጠፋ ዕቃን ላገኘ ወይም ሌላ ነገር ለፈፀመ ሰው ሽልማት ይሰጠዋል ተብሎ በተሰጠፈ /በተነገረ/ ማስታወቂያ ወይም በአደባባይ ሊታወቅ በሚችል ሌላ አይነት ማስታወቂያ መሰረት ዕቃውን አግኝቶ የመጣ ወይም የተባለውን ሥራ የፈፀመ እንደሆነ የተሰፋ ቃሉን የሰጠው ሰው የተገለፀውን ሽልማት /የገባውን ቃል/ የመፈፀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • በውል የተገባ ግዴታ ፍፁም የማይቻልና የማይሞከር ነው ለማለት ተዋዋይ ወገን ብቻ ሳይሆን	62146	ወ/ሪት ፍሬወይኒ ቴዎድሮስ እና ተርካንሬ ፕሮሞሽንና የማስታወቂያ ስራ ድርጅት	ሐምሌ 12/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ማንም ሰው ሊፈጽመው የማይችለው ግዴታ መሆን ያለበት ስለመሆኑ • በአንድ ከተማ የሚገኝና መጠኑ ተለይቶ የታወቀ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በሽልማት መልክ ለመስጠት በውል የተገባ ግዴታ ሊፈፀም የማይችል ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1715, 1741-1762, 1714, 1711, 1736, 1734, 1689				
34.	የደንበኛን ጉዳይ /ክርክር/ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ ሙያዊ አገልግሎት ለመስጠት የጥብቅና የውክልና ስልጣን የተሰጠው ጠበቃ በውል የገባውን ግዴታ በተገቢው ጊዜና ትጋት ለመወጣት አለመቻል በኃላፊነት የሚያስጠይቅና ለቅጣት የሚዳርግ ስለመሆኑ ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 8/2//ለ/ 3 አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 24/3/ /ሐ-3/	66210	አቶ ተስፋዬ ጉላ እና የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚ/ር	ሐምሌ 29/2003	
35.	• ከቤት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ የስም መዛወር የሚፈፀመው በመንግስት አስተዳደር ፊት እንጂ ሻጭ ነው የተባለው ወገን ሊፈጽመው የማይችልና ከህግ ወይም ከውል ይመነጫል ሊባል የማይችል ግዴታ ስለመሆኑ • የስም ይዛወርልኝ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ	33945	አቶ ሳልህ ሁሴን እና ደግፌ ደርቤ	ጥቅምት 20/2001	
36.	ስለ አስፈላጊ አደራ እና የማስረጃ አይነት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2782,2800,2802,2472	64887	አቶ አደም የሱፍ እና አቶ አብዱሠላም መ/ሐመድ	ሐምሌ 29/2003	
37.	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1810/2/ ላይ የተመለከተው የይርጋ ገደብ ተፈፃሚ የሚሆነው ውል በፈቃድ ጉድለት ወይም በችሎታ ማጣት የተነሳ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1810	48012	አቶ ኡመር ከድር እና አቶ በዳዳ ሰቦቃ /ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 03/2003	
38.	ተዋዋይ የሆነ ወገን ወይም ጥቅም ያለው ማናቸውም ሰው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከህግ ውጪ ነው ወይም ለህሊና ተቃራኒ ነው ወይም ለውሉ አፃፃፍ የተደነገገው ፎርም አልጠበቀም የሚል መከራከሪያ ምክንያት በማቅረብ ወሉ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808/2/	43379	አበበ አበጋዝ እና ጥሩነሽ ተክሌ	ታህሳስ 25/2003	
39.	የንግድ መደብር ሽያጭ ውል በግዴታ እንዲፈፀም ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2330, 2329, 1778/	44873	አቶ ሰሚር ሱሩር እና እነ ወ/ሮ ስንዱ ዱባለ	ጥር 13/2003	
40.	• በብድር ከተወሰደ ገንዘብ አከፋፈል ጋር በተያያዘ ብድር መክፈያ ጊዜው የዘገየ እንደሆነ ለአበዳሪው በኪሣራ መልክ የሚከፈለው ህጋዊ ወለድ ብቻ ስለመሆኑና ከዚህ ህጋዊ ወለድ በተጨማሪ በመቀጫ መልክ ለመክፈል የሚደረግ ስምምነት ፈራሽ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2006/2/, 2005/1/, 2489, 1889	59882	ወ/ሮ አሰገደች ዘርጋው እና አቶ አየለ ንዳኔ	የካቲት 21/2003	
	ወንጀል				
41.	• ከ13 ዓመት እስከ 18 ዓመት ድረስ ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኝ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ • ድርጊቱን የፈፀመው ሠው ዕድሜ በዚሁ የእድሜ ክልል መገኘት የወንጀል ተጠያቂነቱን የማያስቀር ስለመሆኑ የወ/ህ/ቁ. 626/1/, 211/1/, 48-56	46412	የሐረሪ ክልል ዓቃቤ ሕግ እና ቦና አህመድ አሚን	ጥቅምት 30/2003	
42.	ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖር ሰዎችን ወደ ውጪ አገር በመላክ ወንጀል የተከሰሰን ሰው ጥፋተኛ ነው ለማለት እና ቅጣት ለመጣል የሚቻልበት አግባብ የወንጀል ህግ ቁ. 598/1/ /2/	54839	አቶ ኢምራን ጉደሣ አብዲ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	ጥቅምት 30/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

43.	በህጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የገባ የውጭ ምንዛሪን በህግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ከአገር ይዞ ለመውጣት መሞከር የሚያስከትለው ኃላፊነት /ውጤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.67/ሀ/	47935	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ወ/ሮ እየሩሳሌም ወንዴ	ህዳር 30/2003	
44.	ከዋስትና መብት ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤቶች የተከሳሽን የዋስትና መብት ለመንፈግ የተከለሰባቸውን የወንጀል ክሶች ብዛትና ከባድነት መነሻ ሊያደርጉ ስለመቻላቸው የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.67/ሀ/	59304	እነ አቶ አያሌው ተሰማ /ሦስት ሰዎች/ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ህዳር 15/2003	
45.	በወንጀል የተከሰሰ ሰው የዋስትና መብት እንዲከበርለት ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ትዕዛዙ ተነስቶ ዋስትናውን ሊከለከል ስለመቻሉ የወ/መ/ሥ/ህ/ቁ. 74	59855	ወ/ሮ ሊዊዛ ሮርቤታ እና አቃቤ ሕግ	ህዳር 28/2003	
46.	በሚያሽከረክረው መኪና ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ የነበረ ሰው ወድቆ ለህልፈተ ህይወት የተዳረገበት ሾፌር በወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/ ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/	52075	አቶ ጌቱ ብርሃኑ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	ታህሳስ 26/2003	
47.	• በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ ፍርድ የተሰጠበት ተከሳሽ የሚያቀርበው የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ • በይግባኝ ደረጃ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተሰጠ የጥፋተኝነት ፍርድ እንደመጨረሻ ውሣኔ ተቆጥሮ በሰበር እንዲታረም ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 193/2/, 197-202, 160, 164, 163, 195/2/ /ሀ/ የወንጀል ህግ ቁ. 522, 526 አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 9, 10 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/	57632	ሰማኸኝ በለው እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	ታህሳስ 25/2003	
48.	ዓቃቤ ሕግ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተጠረጠረና ምርመራ የተደረገበትን ሰው ተከሳሽ ከሚሆን ይልቅ ምስክር ቢሆን የተሻለ ነው ብሎ ካመነ ይህንኑ ለማድረግ የሚከለክለው ህግ የሌለ ስለመሆኑ	57988	ዮርዳኖስ አባይ አሰፋ እና የፌዴራል አቃቤ ሕግ	ጥር 10/2003	
49.	• ከወንጀል ጉዳዮች የክስ ሂደት ጋር በተገናኘ ዓቃቤ ሕግ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ተግባራትና ኃላፊነቶች • የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ በሆነ ወገን ላይ ቅጣት ሊጥሉ ስለሚችሉበት ሥርዓት /አግባብ/ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 136/1/, 148/1/ ,149	47755	የፌዴራል አቃቤ ህግ እና አቶ ሚፍታህ ኑረዲን	ግንቦት 05/2003	
50.	• በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የወንጀል ቁጥር 540 ወይም 541ን መሰረት በማድረግ ጥፋተኛ አድርጐ ለመወሰን የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀምን እንዲሁም መነሻ ሁኔታዎች በአግባቡ መመልከት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ • የወንጀል ህግ ቁጥር 78 "ን" ተፈፃሚ ለማድረግ ሊሟሉ ስለሚገባቸው መስፈርቶች • ህጋዊ መከላከልን በማለፍ የተፈፀመ የነፍስ ግድያ በወንጀል ህግ ቁጥር 541 የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 78, 540, 541	57446	ሃለቃ ገ/እግዚያብሔር ኃይሉ እና የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ	ግንቦት 19/2003	
51.	የወንጀል እና የፍ/ብሔር ክሶች ተጣምረው ሊታዩ የሚችሉት በወንጀል ህግ ቁጥር 101 አግባብ ብቻ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 101	59045	የስልጤ ዞን ምርመራና ክስ ዓ/ሕግ እና እነ አቶ ጌታቸው አስራት /አምስት ሰዎች/	ግንቦት 16/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

52.	በወንጀል ድርጊት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ ሰው ከጉዳቱ በኋላ ተጐጂውን ወደ ህክምና ቦታ የወሰደው መሆኑ ብቻ በድርጊቱ የተፀፀተ መሆኑን ያሳያል በሚል ቅጣትን ከመነሻው በታች በመወረድ ቀልሎ እንዲወሰን ለማድረግ የሚያስችል ስላለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 543/3/, 59/1/, 575/2/, 82/1/ የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁ. 279/56 አንቀጽ 35	62332	አቶ ዘለቀ ካሣዬ እና የፌዴራል ዓ/ሕግ	ግንቦት 29/2003	
53.	በወንጀል ተከሳሾ የቀረበ ተጠርጣሪ በፍ/ቤት በሰጠው የእምነት ቃል መሰረት ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ከተጣለበት በኋላ በተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የማይችል ስለመሆኑ	63741	አቶ መሐመድ ሰኢድ አሊ እና የፌዴራል ዓ/ሕግ	ግንቦት 15/2003	
54.	ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ እውነታ የተጠቀሰውን ወንጀል የሚያቋቁም መሆን አለመሆኑ ጉዳይ የህግ ጭብጥ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊመረመር የሚችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 675/1/	64813	ያሲን አሕመድ መሐመድ እና የፌዴራል ዓ/ሕግ	ግንቦት 17/2003	
55.	• የመወሰን ስልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ብቻ ያላቸው ሰዎች /ሰራተኞች/ በወንጀል ጉዳይ በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት አግባብ • የተቀጠረበትን የሙያ ሥራ በጥንቃቄና በአግባቡ አለመፈፀም በአዋጅ ቁ. 214/74 በስልጣን ያለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ያስጠይቃል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ	43049	አረጋኸኝ መርዕድ እና የፌ/ስ/ፀ/መ/ኮ/ዓ/ህግ	ግንቦት 26/2002	
56.	አንድ ተከሳሽ በወንጀል ህግ ቁጥር 427/3/ መሰረት የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በሚል ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ የወንጀል ህግ ቁጥር 427/1/, /3/	55047	አቶ ነብይ በድሩ ሸፋ እና የፌዴራል ሥ/ፀ/መ/ኮሚሽን ዓ/ህግ	መጋቢት 05/2003	
57.	ፍ/ቤት በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው በተመለከተ አስቀድሞ የፈቀደውን የዋስትና መብት በራሱ አነሳሽነት ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት አዲስ ነገር ተከስቷል ብሎ ካመነ ዋስትናው እንዲነሳ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 74	61275	አቶ ኤልያስ ገረመው እና የኢት/ገ/ን/ባ/ዓ/ህግ	ሚያዝያ 18/2003	
58.	• በክሳድ የሰው መግደል ወንጀል ተከሰሶ ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ ተከሳሽ ስለሚጠየቅበት አግባብ • የተመሰረተበት ክስ በዓቃቤ ሕግ በኩል እንደክሱ አመሰራረት ያልተረጋገጠበት ቢሆንም ተከሳሹ የቀረበው ማስረጃ ከቀረበበት ክስ ባነሰ የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ተከሳሹ በነፃ እንዲሰናበት ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የማይኖር /የሌለ/ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 32/1/ /ሀ-ለ/, 539/1/ /ሀ/, 84, 86, 40, 445, 88 የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 113/2/ የወንጀል ህግ ቁጥር 40, 445	45595	የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ህግ እና እነ ኢዮስያስ አበራ ገ/ሚካኤል /አምስት ሰዎች/	ሰኔ 17/2003	
59.	• በወንጀል ተከሰሶ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበት ተከሳሽ ላይ የሚጣለውን የቅጣት አይነትና መጠን ለመወሰን ፍ/ቤቶች በህጉ ውስጥ ተካትተው የሚገኙትን የቅጣት ማቅለያ እና ማክበጃ ምክንያቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚችሉበት አግባብ • የሞት ቅጣት ሊተላለፍ የሚችልበት አግባብ የወንጀል ህግ ቁጥር 117, 32/1//ሀ-ለ/, 539/1//ሀ/, 84/1//ሀ-ሠ/, 183, 179, 180, 182, 88/2/, 87/1/	47831	እነ መስታወት ጌታነህ /አራት ሰዎች/ እና የፌዴራል ዓቃቤ ህግ	ሰኔ 03/2003	
60.	“የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት” በሚል በወንጀል ህጉ ውስጥ የተመለከተውን የወንጀል	67947	አቶ አዱኛ አንበሎ	ሰኔ 15/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ድርጊት ለማቋቋም ቼኩ ለክፍያ ባንክ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን /ያለመኖሩ/ ማረጋገጥ ብቻ በቂ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 693/1/		እና የፌዴራል አቃቤ ህግ		
61.	• በህጉ በጠቅላላ የቅጣት ማቅለያነት የተመለከተን ምክንያት ወንጀሉን ለማቋቋም የቀረበ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች ይህንን ምክንያት እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያነት ሊጠቀሙበት የማይችሉ ስለመሆኑ • ፍርድ ቤቶች በህጉ ለዳኞች የሚሰጠውን አመዛዝኖ ቅጣትን የመወሰን ስልጣን ሲጠቀሙ በቅጣት አወሳሰን ረገድ ህጉ ያስቀመጣቸውን መሰረታዊ መርሆዎች ሊጥሱ የማይገባ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 82/2/, 189,86, 180, 179, 182, 184, 82/1/, 88/2/	59356	የፌዴራል ዓ/ህግ እና በሪሁን ፍቃዱ	ሰኔ 03/2003	
62.	በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ክስ ከቀረበበት ሰው ጋር በተገናኘ በሚካሄድ የቅድመ ክስ ሂደት ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት እንደቀረበው የወንጀል አይነት በመመርመር ወደ ዋናው ክስ የመሰማት ሂደት እንዲገባ በሚል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 419 አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 36/1//2/	57938	እነ አቶ አደም አብዱ /ሁለት ሰዎች/ እና የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ህግ	ሐምሌ 14/2003	
63.	• በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የሚያቀርበውን ጥያቄ ፍ/ቤቶች ተከሳሹ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊጣልበት የሚችለውን የቅጣት ጣሪያ መነሻ በማድረግ ውሣኔ ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ • ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ በእስራት ሊያስቀጣ የሚችል በሆነ ጊዜ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ሊፈቀድ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 4/1/ አዋጅ ቁ. 239/93 አንቀጽ 2 አዋጅ ቁ. 236/93 የወንጀል ህግ ቁጥር 676/1/	63344	የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/የ/ሥ/ፀ/መ/ኮሚሽን እና እነ ላሉ ሰይድ አከልታ	ሐምሌ 28/2003	
64.	ውልን /ስምምነትን/ መሰረት ባደረገ ግንኙነት አንድን ንብረት ወስዶ በውሉ መሰረት ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው የአምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል የወንጀል ክስ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 23/2/, 24, 57, 58	65054	ብሩክ ሚካኤል እና የፌዴራል ዓ/ህግ	ሐምሌ 14/2003	
65.	• ዓቃቤ ህግ በወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የሚያቀርበው የወንጀል ክስ የወንጀሉን ዝርዝር ሁኔታ መያዝ እንዳለበት በተለይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል ክሱ ወንጀሉንና ሁኔታውን መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ • አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር የወንጀል ተካፋይ ሆኗል የሚባለው በወንጀሉ አፈፃፀም የግዙፍ ተግባር የሃሳብና የህግ ሁኔታዎችን መተላለፍ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 112 የወንጀል ህግ ቁ. 32/1/ 23/2/	57644	መ/ር አወት ተካ እና የትግራይ ዓ/ህግ	ሐምሌ 25/2003	
66.	ተጨማሪ ማስረጃን ከመቀበል ጋር በተያያዘ በወንጀል ህግ ቁጥር 143/2/ ሥር የተመለከተው ድንጋጌ ፍ/ቤቱ ለፍትህ አሰጣጥ ተገቢ ነው ብሎ ሲያመን ትዕዛዝ ሊሰጥበት የሚችል ስለመሆኑ በፈቃጅነት (permissive) የተቀመጠ አንጂ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ ስላለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 143/2/	66767	አቶ ተስፋዬ ተሾመ እና የፌዴራል ዓ/ህግ	ሐምሌ 28/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

67.	በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው የሚያነሳው የጤና ችግር ከዋስትና መብት አኳያ ሲታይ ስላለው ህጋዊ ጥበቃ	68407	ወ/ሮ ውልታ ደሳለኝ እና የኦሮሚያ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ህግ	ሐምሌ 14/2003	
68.	• ወንጀልና የወንጀል ቅጣት የእያንዳንዱን ጥፋተኛ ግላዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ውሣኔ ሊሰጥባቸው የሚገባ ስለመሆኑ • የጉምሩክ ህግን በመተላለፈ ጥፋተኛ የተባሉ ሰዎች /ተከሳሾች/ ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በእያንዳንዱ ጥፋተኛ ላይ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 41, 32/1/ሀ/ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 73/1/ አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/	48956	እነ ወ/ሮ ፍኖተ ፃድቅ አበራ እና የጉምሩክ ዓ/ህግ	መጋቢት 10/2002	
69.	አንድ ሰው በወር ደመወዝ ከሚያገኘው ገቢ ውጪ ሌላ ህጋዊ የገንዘብ ምንጭ እንዳለው ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታ በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብትና ንብረት ባለቤት መሆኑ ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ ይዞ በመገኘት የሙስና ወንጀል የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 419	58514	አቶ ሃንካራ ሃርቃ ሃያሞ እና የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዓ/ህግ	ጥር 09/2003	
70.	የንግድ ፈቃድ መብትን መጣስ በአዋጅ ቁ. 501/98 መሰረት የወንጀል ተጠያቂነትን ስለሚያስከትልበት አግባብ	69899	እነ ዮሴፍ ሀይሉ ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	ሐምሌ 29/2003	
71.	በአሽከርካሪነት ሥራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በሌላ ሰው ላይ የሞት አደጋ ያደረሰ ሰው በወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/ የሚጠየቅ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 543/1/, /2/, /3/, 59/1/ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 113	55649	ኤልያስ ዲጋ እና የፌዴራል ዓ/ሕግ	መጋቢት 06/2003	
72.	የወንጀል ክስ ቀርቦ ተከሳሹ እንዲከላከል በሚል በፍ/ቤት ብይን የተሰጠ መሆኑ ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ እንደተሰጠበት በመቁጠር የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ	59537	አዝዚር ኢብራሂም እና የቤ/ጉ/ክ/ስ/ፀ/ሙስና ኮሚሽን	ሚያዝያ 19/2003	
73.	አንድ የወንጀል ድርጊት በአርግጥም ተጀምሯል /ተፈጽሟል/ ለማለት የሚቻለው የተደረገው ተግባር በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ ወንጀሉን ለመፈፀም ወደታሰበለት ግብ ለማድረስ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲቻል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 27/1/ 540 555/ሀ//ለ/	63727	ፋሲል ታምራት እና የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ ከሳሽ	ሰኔ 13/2003	
	ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት				
74.	በፍ/ቤቶች ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ትዕዛዝ የተሰጠው ተከራካሪ ወገን ጥሪ ተልኮለት ቀርቦ መልሱን አልሰጠም በሚል ምክንያት ክስርክሩ ውጪ እንዲሆን የሚሰጥ ትዕዛዝ በክርክሩ ውስጥ ያሉ ሌሎች ወገኖችን መብት የሚያጣብብና የሥነ-ሥርዓት ህግን የሚጥስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70, 41/3/, 199	53844	የወ/ሮ ቅድነሽ አነስታል ወራሾች /ሦስት ሰዎች/ እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ስራና ከተማ ልማት ቢሮ	ጥቅምት 18/2003	
75.	በፍርድ ለሌላ ሰው የተላለፈ ንብረት የእኔ ነው በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418, 421, 455	50835	እነ አቶ ምናሴ ኢትሶ /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ፋንታዬ ተረፈ	ጥቅምት 16/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

76.	• የግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንደ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድ ሁልጊዜ ጥብቅ የሆነ የሙግት ሥርዓትን ተከትሎ ጉዳዩን ማየት የሌለበት ስለመሆኑ • የግልግል ጉባኤ ጉዳዩን ለማየት ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ያህል ሊወስን ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 318/5/, 317/1/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3345	52942	አቶ ገብሩ ኮሬ እና አቶ አመዲዮ ፌዶሬቼ	ጥቅምት 18/2003	
77.	ተከራካሪ ወገኖች የሚሟገቱበት ጉዳይ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ይህ እንዲፈፀም ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/	48608	ወጋገን ባንክ አ.ማ እና አቶ ሃብቶም ረዘነ	ህዳር 02/2003	
78.	• ተከራካሪ ወገኖች እንዲሰሙላቸው የሚቆጥሯቸው የሰው ማስረጃዎች የማስረዳት ብቃት ሊታወቅ የሚችለው ቃላቸው ከተሰማ በኋላ ስለመሆኑ • የተቆጠሩ ማስረጃዎች የማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት መርህ (relevancy and admissibility) ካልከለከለ በስተቀር በዝርዝር ሊሰሙ የሚገባ ስለመሆኑ • በሰው ማስረጃነት የተቆጠረ ኦዲተር በኦዲት ሪፖርት ላይ ከተመለከተው ውጪ /የተለየ/ ሊያስረዳ አይችልም በሚል ምክንያት ሊሰማ አይገባም ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ	49502	የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት እና እነ መርዕድ ተፈራ /ስድስት ሰዎች/	ህዳር 01/2003	
79.	• መጥሪያ በጋዜጣ ጥሪ ሊደረግ የሚገባው ሌሎች አግባብነት ያላቸው የመጥሪያ አላላክ መንገዶች ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ ከተከናወኑ በኋላ ስለመሆኑ • መጥሪያ በአግባቡ ደርሷል ለማለት የሚላክለት ሰው ስም በተሟላ ሁኔታ ተገልጾ መላክ ያለበት ስለመሆኑ • መጥሪያ በህጉ አግባብ እንዲደርሰው ሳይደረግ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ወገን ትዕዛዙ እንዲነሳለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 94-110, 7870/ሀ/	53113	እነ ወ/ሮ አበበች በጅጋ /ሁለት ሰዎች/ እና ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ	ህዳር 03/2003	
80.	በዋናው ክርክር ላይ በተሰጠ ፍርድ መብቱ የተነካበት ሰው በፍርድ አፈፃፀም ወቅት መብቱ ከተነካበት ሰው በተለየ ሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ማቅረብ የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418, 419	53607	የምጥን መንደር መኖሪያ ቤቶች የህብረት ስራ ማህበር እና እነ ወ/ሮ ባየች አይገምት /ሦስት ሰዎች/	ህዳር 14/2003	
81.	አስቀድሞ የተሰጠን ውሣኔ ለማስነሳት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችል ወገን በክርክሩ መግባት የሚገባው ሆኖ ነገር ግን ተካፋይ ያልነበረ እንደሆነ ባልተካፈለበት ክርክር የተሰጠውን ፍርድ መቃወም የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 41	42714	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፍትህና ህግ ጉዳዮች ቢሮ እና እነ የሽቀጣ ሽቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት /ሦስት ሰዎች/	ህዳር 08/2003	
82.	ከሳሽ የሆነ ወገን ያቀረበው ክስ ውድቅ በተደረገበት ሁኔታ ተከሳሽ የዳኝነት ክፍያውን ለከሳሽ እንዲከፍል የሚደረግበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 215, 462	46281	ወ/ሮ አበባዬ አቢ ደራወርቅ እና ይገረም ፊዬ	ታህሳስ 28/2003	
83.	• ልዩ ዕውቀትና ክህሎትን መሰረት በማድረግ አንድ ጉዳይ ተመርምሮ የተሰጠ የሙያ አስተያየት ሊስተባበል የሚችለው በጉዳዩ ላይ የተሻለ የሙያ እውቀትና ክህሎት ባለው ባለሙያ ጉዳዩን መርምሮ በሚሰጠው አስተያየት ስለመሆኑ • አንድን ሰው ለማጓጓዝ ውል የተዋዋለ ሰው በጉዞ ወቅት በተጓዡ ላይ ለደረሰ ጉዳት ሊከፍል የሚገባው የካሣ መጠን ከብር 40,000 መብለጥ የሌለበት ስለመሆኑ	47960	አቶ ታከለ ባልቻ እና ወ/ሮ አዜብ ፀጋዬ	ታህሳስ 12/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• የጉዳት ካሣ መጠኑ ከብር 40,000 ሊበልጥ የሚችለው በንግድ ህግ ቁ. 599 የተመለከተው መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/ የንግድ ህግ ቁ. 597/1/				
84.	• የበላይ ፍርድ ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሊሽር የሚችለው ህጋዊና በቂ ምክንያት ሲኖረው ብቻ ስለመሆኑ • በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች የበላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ለማድረግ የሚችለው የማይቀበልበትን ምክንያት በውሣኔው ላይ በግልጽ በማስፈር እንጂ በደፈናው "በተገቢው አልተረጋገጡም" የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ስላለመሆኑና በዚህ መልክ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 341 እና ተከታዮቹ	58540	ኪድስ ሊንክ ኢንተርናሽናል እና ሲስተር ገነት ወንድሙ	ጥር 27/2003	
85.	ሁለት ተከራካሪ ወገኖች አንደኛው በሌላኛው ላይ የፍርድ ባለመብት ሆነው የአፈፃፀም አቤቱታው በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በቀረበ ጊዜ በፍርድ የበለለው ገንዘብ በመቻቻል እንዲፈፀም በሚል በአንድ ፍርድ ቤት ተጠቃሎ እንዲታይ ለማድረግ የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት ያለውና ህጋዊ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 397	57378	ወ/ሮ አስቱር አርአያ እና ወ/ሮ አምሳለ ፀሐይ	ጥር 23/2003	
86.	በባንክ በኩል ከተላከ ገንዘብ ጋር በተገናኘ በአግባቡ ለተላከለት ሰው አልደረሰውም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በላኪው ወይም በተላከለት ሰው ስም ክስ ቀርቦ ከተወሰነ በኋላ በሌላኛው /በላኪው/በተላከለት/ሰው/ ስም የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥህ/ቁ. 5 የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	51223	ዳሸን ባንክ አ.ማ እና ወ/ሮ ሀመልማል መኮንን	የካቲት 24/2003	
87.	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 አቤቱታ እንዲያቀርብ ተፈቅዶለት ክርክር ተካሂዶ ውሣኔ የተሰጠበት ወገን በድጋሚ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447 "ን" መሰረት በማድረግ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 447, 354	53421	ወ/ሮ ወርቅነሽ ዋሴ እና አቶ ባንተይርጋ ወርቁ	የካቲት 22/2003	
88.	በመጀመሪያ በቀረበ የክስ መከላከያ መልስ ያልተካተተን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መልስ እንዲሻሻል በሚል ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት ተካትቶ ሲቀርብ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91, 244 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1856	55973	ወ/ሮ አዐደ ኤዶ እና አቶ ትኩ ዋቅሹም	የካቲት 21/2003	
89.	• ሌሎች ሰዎች ተከራካሪ በሆኑበት ጉዳይ ንብረትን አስመልክቶ በፍርድ ቤቱ የተሰጠ የማገጃ ትዕዛዝ ይነሳልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ሰው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሰረት ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ • አንድ ክርክር መጀመሩን ያወቀ ወገን የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከውሣኔው በኋላ የሚያቀርበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሰረት ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 153/3/, 418-421	56795	አቶ መብረክ ከድር እና እነ ሚስተር ኑዋምባ ሲርር /አምስት ሰዎች/	የካቲት 21/2003	
90.	ፍርድ ቤቶች ከውሣኔ ሊደርሱ የሚገባው የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት፣ የመከላከል ብሎም በእኩልነት መርህ የመዳኘት መብት በጠበቀ መልኩ ስለመሆኑ	52546	እነ አቶ በቀለ አማረ /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ብዙነሽ ግርማ	ታህሳስ 13/2003	
91.	ክስ ለመስማት ቀጠሮ ከተሰጠ በኋላ ያልቀረቡ ከሳሾችን ክክርክሩ ውጪ እንዲሆኑ በማለት ትዕዛዝ	55078	ማበርፋይድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ታህሳስ	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የሰጠ ፍ/ቤት /ችሎት/ በራሱ ተነሳሽነት አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ በማንሳት ክሱ ውጪ የሆኑትን ከሳሾች የክሱ አካል በማድረግ የሚሰጠው ውሣኔ ከሥነ ሥርዓት ህግ ውጪ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73, 74, 78		እና እነ አሸናፊ አለሙ /ዘጠኝ ሰዎች/	25/2003	
92.	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 377 ተፈፃሚ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ	52193	የኮንስትራክሽን እና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ እና እነ ወ/ሮ መድሀኒት ሃይሉ /ሁለት ሰዎች/	ታህሳስ 27/2003	
93.	ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል የተደረገበት ተከሳሽ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያለመቅረቡን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ የመከራከር መብት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 72, 78/1/	61846	ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል እና ወሮ ፋጡማ አስማን	ግንቦት 29/2003	
94.	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 እና 418 መሰረት በተሰጠ ፍርድ ላይ ተቃውሞ የሚቀርብበት ሥርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 359, 418, 222, 223, 137/3/	55842	የኦሮሚያ ክተሞች ፕላን ኢንስቲትዮት እና እነ አቶ ካሣ ጭርሳ /አራት ሰዎች/	መጋቢት 23/2003	
95.	በፍ/ብሔር ክርክር ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ /ጭብጥ/ ለማስረዳት የሚቀርብን የሙያ ምስክርነት (expert witness) ውድቅ በማድረግ ባለሙያ ባልሆኑ ምስክሮች የተሰጠ የምስክርነት ቃልን ሊቀበል የሚችለው ይህን ለማድረግ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/	65930	የሱ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና እነ አቶ ደጀኔ በቀለ /ሁለት ሰዎች/	ሰኔ 14/2003	
96.	ከኢትዮጵያ ውጪ በሚገኝ ፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች እውቅና ሊሰጠው ወይም ተቀባይነት ሊኖረው የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 456-461	59953	ወ/ሮ አለምነሽ አበበ እና አቶ ተስፋዬ ገለሰ	ሰኔ 02/2003	
97.	• በህግ የተቀመጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንዲፈቀድ የሚቀርብ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ • ይግባኙ በጊዜው ሊቀርብ ያልቻለው የባለጉዳዩ ጠበቃ፣ነገረፈጅ ወይም ወኪል የሆነው ሰው ባለመቅረቡ ወይም ከነዚህ ሰዎች ጋር በተያያዘ በተከሰተ ጉድለት መሆኑ ከታወቀ የማስፈቀጃ አቤቱታው በበቂ ምክንያት የተደረገ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 326/2/ /1/ 323/2/ 325	57360	አፍሪካ ኢንሹራንስ አ.ማ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ሐምሌ 15/2003	
98.	በአንድ በመካሄድ ላይ ባለ የፍርድ ቤት ክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጥያቄ አቅርቦ በብይን ውድቅ የተደረገበት እና በሌላ መዝገብ ክስ መስርቶ መብቱን እንዲያስከብር በሚል ትዕዛዝ የተሰጠበት ወገን በዚህ ትዕዛዝ መሰረት አዲስ መዝገብ በማስከፈት ወይም በሌላ መዝገብ በመግባት የክርክር ተሳታፊ ከመሆን የሚያግደው ነገር የሌለ ስለመሆኑ ወይም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	62173	ወ/ሪት ቤተልሄም ታደሰ እና እነ ወ/ሮ ሃና ታደሰ /ሦስት ሰዎች/	ሐምሌ 11/2003	
99.	ግልጽነት የጐደለው ክስ /አቤቱታ/ በቀረበ ጊዜ ክሱ በተከራካሪዎች አነሳሽነት ወይም ፍ/ቤቱ በራሱ ክሱ እንዲሻሻል ሳይደረግ በደፈናው የቀረበን የይግባኝል ጥያቄ ላይ የሚሰጥ ፍርድ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91/1/	63699	አፔኖ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅት እና አቶ ጥሩነህ ይመር	ሐምሌ 15/2003	
100.	ፍ/ቤቶች በባንክ ለተሰጠ ብድር መያዣነት የተሰጠ ንብረትን በአዋጅ ቁ. 97/90 ባንኩ ሲረከበው በብድሩ ገንዘብ እና በንብረቱ ወቅታዊ የዋጋ ግምት መካከል ያለውን ልዩነት ማስላት አስፈላጊ	61227	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና	ሐምሌ 14/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	መሆኑን ባመኑ ጊዜ ይህንን ለማድረግ ልዩ የሂሳብ አዋቂ (expert witness) በመመደብ ለጉዳዩ እልባት ሊሰጡ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1//2/		እነ አቶ ኃይሉ አምቦ /ሁለት ሰዎች/		
101.	• በፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ የእግዱ ትዕዛዝ ተጥሶ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት በተደረገ የሽያጭ ውል ለሦስተኛ ወገን በተላለፈ ጊዜ ሊኖር ስለሚችል ውጤት • እግዱ ተጥሶ በተከናወነው ተግባር መብቱ የተጎዳበት ሰው የእግዱን ትዕዛዝ በጣሰው ወይም እንዲጣስ ምክንያት በሆነው አካል ላይ ተገቢውን አቤቱታ በማቅረብ መብቱን ለማስከበር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 156 አዋጅ ቁ. 334/95 አንቀጽ 15/2/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1204, 1206, 1184, 1185, 1195	61637	ዶ/ር አልሑሴን በድልገዋድ እና እነ ወ/ሮ ገነት ሐድጉ /ሁለት ሰዎች/	ሐምሌ 11/2003	
102.	በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት እውቅና ካልተሰጠው በስተቀር በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የቀረበ አቤቱታ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ	54632	ወ/ሮ ራውዳ መሙሜ እና አምባሳደር አብደላ አብድራህማን	ግንቦት 29/2003	
103.	የኤክስፐርት ማስረጃ ሙሉ እምነት ሊጣልበት የሚችል ማስረጃ ስላለመሆኑ	43453	አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ዘነበወርቅ ከበደ /ሁለት ሰዎች/	ህዳር 15/2002	
104.	የባለሙያ ማስረጃ ፍፁም ስላለመሆኑና ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ተገናዝቦ ብቃቱና ተአማኒነቱ ሊመዘን የሚገባ ስለመሆኑ	14981	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ ሀዋ መሐመድ	ግንቦት 04/1998	
105.	በህግ /ፍርድ/ ኃይል የተወሰደ ንብረት ሊመለስ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349/1/	44238	አቶ ማሞ ደምሴ /ሦስት ሰዎች/ እና እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሄር /ሦስት ሰዎች/	ጥር 09/2003	
106.	ከሀራጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447 እና 453 ትርጉምና ሊፈፀሙ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447, 453	56130	ሊሲ ታነሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና እነ መኳ አስፋው /ሦስት ሰዎች/	ጥር 26/2003	
107.	• ክስ ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት ለመቅረብ ያልቻለው በቂ ሊባል በሚችል እክል /ችግር/ ምክንያት መሆኑን ያስረዳ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲነሳለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ • "በቂ ምክንያት" በሚል የሰፈረው ሃረግ ሊተረጐም የሚገባው ተከሳሹ ቀና ልቦና ያለው መሆኑንና የተለያዩ አግባብነት ያላቸው ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ህ/, 72, 78/1/	54080	እነ አቶ ላል ሮላንድ ቻፕ ማን እና አቶ ዜና ወ/ማሪያም	ጥቅምት 19/2003	
108.	የልዩ አዋቂ ምስክሮች በፍ/ቤት የሚሾመበት፣ የመ.ያ ግዴታቸውን የሚያከናውኑበት እና ፍ/ቤቶችም የሚቀርበውን መ.ያዊ ምስክርነት ሊቀበሉ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136	44522	ጭላሎ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አፍሪካ ኢንጂነርስ ኮንስትራክሽን	ታህሳስ 15/2003	
109.	ክስ የቀረበበት ጉዳይ ለቃል ክርክር /ለመስማት/ በተቀጠረበት ዕለት ከሳሽ የሆነ ወገን በመቅረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 መሰረት የተዘጋ መዝገብን መነሻ በማድረግ በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 74/2/	58487	ወ/ሮ አባይነሽ ገ/ህይወት እና ወ/ሮ እታገኝ ደሳለኝ	መጋቢት 22/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

110.	በፍ/ቤት በተሰጠ ፍርድ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የተቀመጠው የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትና የቀን አቆጣጠር ስሌት ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 323/2/	59085	ወ/ሮ ብርሃኔ አዱላ እና ግርማ አብዲሳ	መ.ጋቢት 05/2003	
111.	ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ሳይሰጥ በማለፍ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ ሠ, 234	59294	አቶ በቀለ ጃፋር እና እነ ወ/ሮ ሙስነሽ ማሞ	መ.ጋቢት 19/2003	
112.	አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ጋር በተያያዘ “ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ” በሚል የተቀመጠው ሃሬግ ትርጉም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 244/2/	62330	አቶ አዱኛ አጃው እና ቀስቀስ አየነው	ሚ.ያዝያ 03/2003	
ባንክና ኢንሹራንስ					
113.	በባንክ ከተቀመጠ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ትክክለኛው ገንዘብ አስቀማጭ ከሆነ ሰው ውጭ ለሆነ ሰው ገንዘብ ወጪ ተደርጐ የተከፈለ እንደሆነ ባንኩ በሃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረገ ወይም የባንኩን የተለመደ አሰራር ሳይከተል የሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ	41535	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ ግሎሪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር /አራት ሰዎች/	ጥቅምት 03/2003	
114.	በንግድ ህጉ የመድን ሰጪን ግዴታና ኃላፊነት በተመለከተ የቀረቡ ድንጋጌዎች መድን ሰጪው ከመድን ገቢው ጋር አንዳንድ ኃላፊነቶችን ለማስቀረት በሚል ከተስማሙባቸው ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝበው ሥራ ላይ መዋል ያለባቸው ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 664/1/	50199	ግሎባል ኤንሹራንስ ኩባንያ እና አቶ አያሌው ወርቁ	ታህሳስ 27/2003	
115.	• ባንኮች ላበደሩት ገንዘብ በመያዣነት የያዙትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በዕዳ መክፈያነት በሐራጅ ለመሸጥ የተሰጣቸውን ስልጣን በተግባር ሲያውሉ ህግን በመተላለፍ በባለዕዳው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂነት ያለባቸው ስለመሆኑ • በመያዣነት የተያዘውን ንብረት በሐራጅ ለመሸጠም የፍርድ ቤት ውሣኔ ወይም ፈቃድ የማያስፈልጋቸው ስለመሆኑ • አበዳሪ የሆነ ባንክ በአዋጅ ቁ. 97/90 የተሰጠውን ስልጣን /መብት/ ትቷል (waive) ሊባል ስለሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394-449 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3, 6	65632	ህብረት ባንክ አ.ማ እና አቶ አሊ አብዱ	ሐምሌ 13/2003	
116.	መድን ገቢ የሆነ ወገን ጉዳት የደረሰበትን መድን የተገባለት ንብረቱ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ሊጠገንለት /ሊካስ/ ያልቻለ መሆኑን በተረዳ ወቅት በዚህ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የጉዳት ኪሣራ ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1802	47076	አፍሪካ ኢንሹራንስ /አ.ማ/ እና ወ/ሮ ጣይቱ አመዴ	መስከረም 25/2003	
117.	ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለን ተበዳሪ ንብረት አበዳሪ ባንክ በአዋጅ ቁ. 97/90 በንብረቱ ግምት ከተረከበ በኋላ ቀሪውን ዕዳ በተመለከተ የሚያቀርበው ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1846	56010	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ ቃድሮ ኑራ	ሐምሌ 29/2003	
የዳኝነት ስልጣን					
118.	• የሊዝ ውል እንዲቋረጥ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ እና ሊከተል የሚችለው ውጤት	54697	አዲስ ኢንተርናሽናል አካዳሚ	መስከረም	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• የሊዝ ውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ በአ.አ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የሚታይ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀጽ3/2/ አዋጅ ቁ. 272/94 አንቀጽ 2/7/, 15/1/ /ለ/		እና እነ አቶ ሃይማኖት አበበ /ዘጠኝ ሰዎች	24/2003	
119.	• ከአዋጅ ውጪ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተወስዶብኛል በሚል በቀረበ አቤቱታ መነሻነት የፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በህጉ አግባብ የሚሰጠው ውሣኔ እንደ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊቆጠር የሚችልና ለአፈፃፀም የሚቀርብ ስለመሆኑ • አንድን ጉዳይ የማየት ስልጣን ከፍርድ ቤት ውጪ ለሆነ አካል የተሰጠ በመሆኑ በዚህ አካል እየታየ ባለበት ተመሳሳይ ወቅት በፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 110/87 አዋጅ ቁ. 193/92 አዋጅ ቁ. 572/2000 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 8	48316	ወ/ሮ ዘነቦች ተመስገን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ጥቅምት 04/2003	
120.	• የፌዴራል ጉዳይን በውክልና ስልጣን ተመልክቶ በክልል ፍርድ ቤት ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ መሰረት በማድረግ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ ስለሚቻልበት ሁኔታ /አግባብ/ • የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ በሚነሳ ክርክር ላይ እንደ ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ብሎም በይግባኝ ደረጃ ባለ ክርክር ደግሞ እንደ ፌዴራል ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ የፌዴራል ጉዳዮችን ለማስተናገድ የሚያስችል የውክልና ስልጣን ያለው ስለመሆኑ • አዋጅ ቁ. 322/95 የተወሰኑ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በህገ መንግስቱ ተሰጥቷቸው የነበረውን የፌዴራል ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸው የማስተናገድ የውክልና ስልጣንን ብቻ የሚያስቀር እንጂ በይግባኝ ያላቸውን ስልጣን ጭምር የሚያስቀር ስላለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/2/, /5/ አዋጅ ቁ. 322/95	54577	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ሰለሞን ያቆብ	ህዳር 01/2003	
121.	የአ.አ. ከተማ አስተዳደር ማንበራዊ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ተቋማት ተከራካሪ የሆኑበትንና የገንዘብ መጠናቸው ከ5000 ብር ያልበለጠ የፍ/ብሔር ጉዳዮችን ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አዋጅ ቁ. 25/88	56118	የኢትዮጵያ ቴሌ ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ወርቅነሽ ወ/ማርያም	ህዳር 16/2003	
122.	በውጭ አገር መንግስት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት የዳኝነት ስልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 12/1/ የወንጀል ህግ ቁ. 263, 71	55299	ዓለም ገብሩ እና የትግራይ ዓቃቤ ህግ	መጋቢት 19/2003	
123.	• የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁ. 67/89 ሥር የተደነገጉ የወንጀል ድርጊቶችን የተመለከቱ ክርክሮችን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ • ያለ ንግድ ፈቃድ በመነገድ ወንጀል የተከሰሱ ሰዎችን በተመለከተ የቀረበ ክርክርን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ • ሺሻ ጋር በተገናኘ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ወንጀሎችን አይቶ ለመወሰን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 46	56893	የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አቤቱታና ምርመራ ክስ አቀራረብ ንዑስ የስራ ሂደት እና እነ ወ/ሪት ፍሬህይወት ፍቃዱ /አስራ ሁለት ሰዎች/	መጋቢት 22/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41/2/, 52				
124.	• የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማው አስተዳደር ለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ፣ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ • የሁከት ይወገድልኝ ክስ ከከተማው መሪ ፕላን ጋር እስካልተያያዘ ድረስ በከተማው ፍ/ቤቶች የሥረ ነገር ስልጣን ሥር የሚወድቅ ስላለመሆኑ • የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖር የሚሰጥ ፍርድ እንዳልተሰጠ የሚቆጠርና ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለው ስለመሆኑ • ከቤት ይዞታ ጋር በተገናኘ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የተሰጣቸው ስልጣን ሁከት ይወገድልኝ በሚል የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄን መሰረት ባደረገ መልኩ ሲቀርብ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41/1//4//ረ/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9 231 /1/ /ለ/	64703	ሻምበል ለታይ ገ/መስቀል እና በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ጽ/ቤት	ሐምሌ 29/2003	
125.	• የፖለቲካ ተሿሚ የሆነ ሰው ከሥራ ኃላፊነቱ መነሳቱን ተከትሎ ያለውን ቅሬታ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅን መሰረት በማድረግ ለአስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩን አቅርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ • ፍ/ቤቶች በዚህ መልኩ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 12/2/ የቤንሻንጉል ብ/ክ/መ/የሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ቁ. 29/95 አንቀጽ 71	63417	አቶ ትዕዛዙ አርጋው እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ ም/ቤት	ሐምሌ 15/2003	
126.	• የኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ከአዋጅ ውጪ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ የቀረበን ጉዳይ አከራክሮና አጣርቶ የመወሰን ስልጣን በህግ የተሰጠውና ከፍ/ቤት ውጪ ያለ የዳኝነት አካል ስለመሆኑ • ውሣኔውን ለማስፈፀምም አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚችልና የሚሰጠውን ትዕዛዝ ለማስፈፀምም ማንኛውም የመንግስት አካል ተገቢውን ትብብር ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 110/87 አንቀጽ 74/ሐ/ 7 4 /ሐ/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371/1/ አዋጅ ቁ. 146/91 አንቀጽ 26/2/ 28/2/	63627	ሼህ አሸራቅ ሰይድ እና የቡታጅራ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር	ሐምሌ 14/2003	
127.	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) አዋጅን በመተላለፍ የሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮችን ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 52/4/ /5/ 41/2/ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 96 አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 49 የወንጀል ህግ ቁ. 349/1/	59723	አብዱልፈታህ መሐመድ እና ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት	ሰኔ 16/2003	
128.	• የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በሚመለከት የሚነሳውን ክርክር የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ • ከንግድ ምልክት ጋር በተያያዘ አንድ ድርጊት ያልተገባ የንግድ ውድድር ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/2/ /ሀ/, 11, 15	55162	ዩኒሊቨር ፒ.ኤል.ሲ./ፖርት ስንላይት ሚራል ማርሲ ሳይድ እና ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻ እና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	የካቲት 22/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 501/98 የንግድ ህግ ቁ. 133				
129.	• አንድን ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ለሌላ የዳኝነት አካል ከሆነ ፍ/ቤቶች ጉዳዮን የማየት ስልጣን የማይኖራቸው ስለመሆኑ • የፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በሚል በኤጀንሲው የተረጋገጠ ጉዳይን ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለሌላ የዳኝነት አካል የተሰጠ ነው በሚል ክርክር እስካልቀረበ ድረስ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆናቸው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1//ለ/, 9/2/, 244/3/ እና 328/3/ አዋጅ ቁ. 110/87 አዋጅ ቁ. 47/67	37964	እነ አቶ መሐመድ ሁሴን የእነ አቶ መሐመድ ሁሴን ወራሾች /ሦስት ሰዎች/ እና እነ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ /ሁለት ሰዎች/	ጥር 27/2003	
130.	• በአስተዳደራዊ ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ እንዲያገኙ በህግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን በተመለከተ ፍ/ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ • የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ከሥራ የተሰናበተ ሰራተኛ በየትኛውም የፍርድ አካል ውሣኔ ወደ ሥራ የመመለስ መብት የማይኖረው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 578/2000 አንቀጽ 19/1/ /ለ/ ደንብ ቁ. 155/2000 አንቀጽ 37/1/ /2/	51790	እነ ወልዳይ ዘሩ /ስልሳ አንድ ሰዎች/ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ህግ	ግንቦት 16/2003	
131.	• የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በተመለከተ የሚነሳ ክርክርን የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ • የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/2/ /ሀ/, 3, 15 አዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 49	47682	አም.ኤ ሸሪፍ ኃ.የተ.የግ.ማህበር እና ታደሰ ኃ.የተ.የግ.ማህበር	መጋቢት 06/2003	
	የንግድ ህግ				
132.	በቼክ ላይ የተፃፈለትን ገንዘብ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ክፍያ ያልጠየቀበት ሰው ወይም በይዞታው እያለ የታገደበት እንደሆነ ይህንኑ ቼክ እንደ ተራ ሰነድ በማስረጃነት በማቅረብ ያላግባብ የመበልፀግ ክስ ሊመሰርት የሚችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 799	40173	አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ አብዱልቃድር ጁሃር	ጥቅምት 05/2003	
133.	የሐዋላ ወረቀት በይርጋ ስለሚታገድበት አግባብ የንግድ ህግ ቁ. 817/1/ /2/, 825	48242	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ቦጋለ መስቀሌ /ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 04/2003	
134.	የአክስዮን ማህበር መሥራቾችና የአክሲዮን ድርሻ መብት ጋር በተያያዘ በሚቀርብ አቤቱታ ላይ የንግድ ህግ ቁ. 416/2/ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 416/2/	52269	እነ አቶ ከድር ሀድ ሁሴን /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ጁሀር አልይ	ጥቅምት 17/2003	
135.	• ቼክ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የፍትሐብሔር ክስ ለቼኩ መፃፍ /መውጣት/ ምክንያት ከሆነው ውል ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባ ስለመሆኑ • ውልን መሠረት በማድረግ የተፃፈ ቼክ ሌላው ወገን የውል ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም	55077	ወ/ሮ ጥሩወርቅ ዘገኑ እና አቶ ግደይ አብርሃ	ህዳር 28/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በሚል ምክንያት ብቻ ቼኩን የፃፈው ወገን በቼኩ ከመጠየቅ ነፃ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ሕግ ቁጥር 717				
136.	በባህር ላይ በሚደረግ የዕቃ ማጓጓዝ ለደረሰ ጉዳት የሚከፈል የጉዳት ካሣ አወሳሰን የባህር ህግ ቁ. 198/1/ /3/	52667	ኒያላ ኢንሹራንስ አክስዮን ማህበር እና የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ	ታህሳስ 12/2003	
137.	• የአክስዮን ማህበር አባል በመሆን የሚገኝ መብትና ጥቅም ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችልበት አግባብ • ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለአክሲዮን የሆነ ሰው ላለበት የግል ዕዳ አክሲዮኖቹ /በወቅቱ የገበያ ዋጋ/ ተሸጠው እንዲከፈል ለማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 522-524	57288	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አሸብር ታደሰ /አምስት ሠዎች/	መጋቢት 19/2003	
138.	በባህር ላይ በሚደረግ የዕቃ ማጓጓዝ ለሚደርስ ጉዳት የአጓጓዡ የኃላፊነት አድማስ የባህር ህግ ቁ. 196, 138, 205, 197, 180/3/	56480	የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሰኔ 14/2003	
139.	• የአክስዮን ማህበር ወይም የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ድርጅቱ የሚያገበት ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ በድርጅቱ ስም በሚያወጣው/ በሚሰጠው/ ቼክ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ • የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ በንግድ ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ወይም የኩባንያውን መተዳደሪያ ደንብ በመጣስ መስራቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ከድርጅቱ ጋር በአንድነት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በተናጠል ሊጠየቅ ስለመቻሉ የንግድ ህግ ቁ. 530	57932	ተክሉ ካሣ ገብረየስ እና ማርኮ ባርዚ	ሰኔ 30/2003	
140.	የንግድና ኢንዲስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ሥራ ፈቃድ ለመስጠት የቀረበው የንግድ ስም ቀደም ሲል ከተመዘገቡ የንግድ ስሞች ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች አለመሆኑን እንዲሁም ለመልካም ጠባይ ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 16/2/ 14 20 አዋጅ ቁ. 376/96 የንግድ ህግ ቁ. 137,138	58931	የንግድና ኢንዲስትሪ ሚኒስቴር እና ታይገር ሎጀስቲክ እና የንብረት ጥበቃ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሐምሌ 15/2003	
141.	• ከቼክ ጋር በተያያዘ "የግል ግንኙነት" በሚል የተቀመጠው ሀረግ ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ • በቼክ የሚገደዱ ሰዎች ላይ አውጭው ክስ ለማቅረብ የሚችለው ቼኩ ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ • በቼክ በተከሰሰና ሰነዱን ይዞ በመጣው ሰው መካከል ያለን "የግል ግንኙነት" በመቃወሚያነት ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ • ቼክ የሚሰጥበት ምክንያት በሰጪውና በተቀባዩ የሚወሰን እንጂ በህጉ የተዘረዘረ ባለመሆኑ ቼኩን የፃፈው ሰው ቼኩን የሰጠሁት ለዋስትናነት ነው በሚል ቼኩን ይዞ በመጣው ሰው ላይ "የግል ግንኙነትን" መሠረት በማድረግ የሚያቀርበው መቃወሚያ ቼክ በዋስትና ሊሰጥ የማይችል ነው በሚል ውድቅ ሊደረግበት የማይገባ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 717/1/-/3/, 855, 881/1/, /ሀ/, 854, 640,868,752,850,827 - 840	24435	ሀጂ መሃመድ አደም እና አቶ ፍፁም ግርማ	የካቲት 04/2000	
142.	• ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባል የሆነ ሰው ከአባልነቱ ለመውጣት የሚችልበት ብሎም ማህበሩ ሊመሰረትና ሊፈርስ የሚችልበት አግባብ • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ /ረ/ ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በሽምግልና ስምምነት ከመፋታት ጋር ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብ	50537	ሲ/ር መአዛ ዮሴፍ እና ዶ/ር ዮሴፍ ደነቀው	ግንቦት 02/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የንግድ ህግ ቁጥር 510/2/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ /ረ/				
143.	• በንግድ ህጉ ቁጥር 683 “ወኪሎች” በሚል የተመለከተው የእቃ አስተላላፊነት ሥራን ለጥቅም የሚሰሩ ወገኖችን የማያካትት ስለመሆኑ • መድን ሰጪው ክስ ሊያቀርብባቸው የማይችላቸው ወገኖች ከመድን ገቢው ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸውና ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለመድን ገቢው ጥቅም የሚሰሩ ወገኖችን ስለመሆኑ የንግድ ሕግ ቁ. 683/3/	49295	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ የቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን /ሁለት ሰዎች/	መጋቢት 22/2003	
	አእምሯዊ ንብረት				
144.	የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክት እና የንግድ ስምን አስመልክቶ ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት የህብረተሰቡን ግንዛቤ በሚያዛባና ያልተገባ የንግድ ውድድር እንዲይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መሆን ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/1/, /2//ሀ/, እና /ሐ/ አዋጅ ቁ. 501/98 አዋጅ ቁ. 320/95 አንቀጽ 6/1/	57179	ኢትዮ ሴራሚክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና እነ የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/	የካቲት 22/2003	
145.	• የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በሚሰጣቸው ውሣኔዎች ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ያለው መብት ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ማቅረብ ነው እንጂ የቀጥታ ክስ ማቅረብ ስላለመሆኑ • የፌ/ጠፍ/ቤት ሦስት ዳኞች በሚሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው ትዕዛዝ /ውሣኔ/ አስገዳጅ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/1/ አዋጅ ቁ. 25/88 አዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 6, 17, 36, 49 አዋጅ ቁ. 320/95 አዋጅ ቁ. 410/96	59025	የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረቶች ጽ/ቤት እና አቶ ጥበበ አየለ	ግንቦት 19/2003	
	ውክልና				
146.	• አንድ ሰው ለሌላ ሰው በሰጠው ፍፁም የውክልና ስልጣን መሰረት የተከናወነውን ተግባር ለማፍረስና መከራከሪያው ሊያደርገው የሚችለው ወሳዩ ራሱ ስለመሆኑ • የወካይ ወራሾች ወኪሉ የውክልና ስልጣን ወሰኑን ሳያልፍ የስራውን ተግባር የሚቃወሙበት ህጋዊ መሰረት ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2189/1/ እና /2/	38721	ካፕቴን ዮናስ ሕሉፍ እና እነ አቶ እስጢፋኖስ ኪዳኔ /አራት ሰዎች/	ህዳር 27/2003	
147.	የውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ቀርቦ ካልተረጋገጠና ካልተመዘገበ በስተቀር ህጋዊ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 334/95 አንቀጽ 5/1//ለ/	59568	አቶ ቴዎድሮስ ተስፋዬ እና አቶ መሉ አርጌ /ሁለት ሰዎች/	ሚያዝያ 05/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ጌታሁን አበበ ቦጋለ - ጠበቃ ገመዳ ጎንፋ - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ሐሰን ገአስ ሁመድ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ውልን መነሻ በማድረግ የተጠየቀውን የገንዘብ ክፍያ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአፋር ብ/ክ/መ/ በዞን አንድ /የአውሲረሲ/ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪው በመልካች ላይ ክስ የመሠረተው የከርሰ ምድር ቁፋሮ ሥራ በጋራ ለመሥራት ውል የተዋዋልን ሲሆን፣ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ሥራውን መጀመር ሲገባው ይህን አላደረገም፡፡ በመሆኑም ውሉን በማፍረሱ ግዴታ የገባበት ብር 200.000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ውሉ በስህተት የተደረገ ነው፡፡ ስህተቱም የሁለቱ ወገኖች ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም የክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ውሉን ሰርዞአል የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሠማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በመሻር አመልካችን ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች እንደ ውል አፍራሽ በመቁጠር ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር እና አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ክርክሩን በመጀመያ ደረጃ የሰማው የአውሲረሲ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪን ክስ ወድቅ ያደረገው ለክሱ መሠረት የተደረገው ውል ተከሣሽን ለማስገደድ የሚችል ሕጋዊ ውል አይደለም እሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ እንደሆነም ከውሳኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ የከርሰ ምድር ቁፋሮ ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖረው ውሉን እንደተዋዋለና በዚህ ምክንያት የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ውሉ ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው እንዳደረገው በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠም ተመልክተናል፡፡ ይግባኙን የሰማው የአፋር ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲሆን ውሉ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ስለመሠረዙ ግንዛቤ እንደወሰደ በውሣኔው አመልክቶአል፡፡ በከፍተኛው ፍ/ቤትም የተሰጠውን ውሣኔ የሻረውም ውሉ በቢሮው አልተሰረዘም በማለት ሳይሆን፣ ውሉ በክልሉ ፍትሕ ቢሮ ፊት የተደረገ ነው፡፡ ተዋዋይ ወገኖችም ወደውና ፈቅደው ያደረጉት ነው፡፡ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮው ውሉን የመሠረዝ ሥልጣን የለውም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው የከርሰ ምድር ቁፋሮ ለማድረግ በቅድሚያ ከሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ወይም መሥሪያ ቤት ፈቃድ ሊኖር ይገባል፡፡ የመሬት ይዞታ እና በመሬት ውስጥ ያሉት ማዕድናት የመንግሥት እና የሕዝብ ሃብቶች እንደመሆናቸው /የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ /3/ ይመለከተዋል/ ከመንግሥት በግልጽ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር የከርሰ ምድር ቁፋሮ ለመሥራት ግለሰቦች ቢዋዋሉ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ውል ተዋውለዋል ሊባል አይችልም፡፡ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በዚህ ረገድ የሚመለከተው አካል አይደለም አልተባለም፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረውን ውል ሰርጓጆሁ ያለውም በዚህ ምክንያት ማለትም ከቢሮው የተሰጠ ፈቃድ ስለሌለ ነው፡፡ በአጠቃላይ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ተደርጎአል የተባለው ውል ተግባራዊ ሊሆን ይችል የነበረው ፈቃዱ ተሰጥቶ ቢሆን ነበር፡፡ ውሉ በዚህ ምክንያት ተግባራዊ ሊሆን ካልቻለ ደግሞ ለውሉ አለመተግበር አመልካች ብቻውን ኃላፊ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የአፋር ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 1098 ጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. በአፋር ብ/ክ/መ/ የዞን አንድ /አውሲረሲ/ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1220 የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
   ስለዚህም አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል አይገደድም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 1 ቀን 2003

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጲያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ አክሊሉ ተስፋዬ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተክሌ ዋከኔ -- ዋከኔ ቶላ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የመያዣ ውል የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ክስ የቀረበው በተጠሪ ነው፡፡ የክሱ ምክንያት በአበዳሪ /አመልካች/ እና ተበዳሪ በአቶ ሽፈራው ቡሎ መካከል በ24/12/1987 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል የቤት ቁጥር 870 የሆነውን መኖሪያ ቤት ለብድር አከፋፈል ዋስትና መያዣ ያደረገ መሆኑን ጠቅሶ የብድር ውሉም ሆነ የመያዣ ውሉ ሳይታደስ አሥራ ሦስት /13/ ዓመት ስለሆነ የመያዣ ውሉ በፍ/ብ/ሕግ/ ቁጥር 3058 መሠረት ቀሪ ሆኖ አመልካች የያዘውን የቤቱን ካርታና ፕላን እንዲመልስ እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡

አመልካች ሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ክርክር ታህሳስ 19 ቀን 1988 የተፈረመው የመያዣ ውል ጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም ለነቀምቴ ከተማ አስተዳደር በተፃፈ ደብዳቤ ለቀጣይ 10 ዓመት እንዲታደስ የተደረገ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን ያከራከረው የምሥራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለ ውሉ መታደስ ከማዘጋጃው መግለጫ ከጠየቀ በኋላ ውሉ የታደሰው ከሳሹ /ተጠሪ/ በሌለበት ነው በማለት ይህ የዋሱን ሃላፊነት የሚለወጠው ያለእሱ እውቅና የተደረገ ነው በሚል የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1928/2/ን በመጥቀስ የመያዣ ውሉ እንደታደሰ አይቆጠርም በማለት የመያዣ ውሉ ሳይታደስ 10/አሥር/ ዓመት አልፎበታል በሚል ተጠሪ የዋስትና ሃላፊነት የለበትም ሲል ፈርዷል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር ተሰኝቶ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ነ/ፈጅ ለሰበር የቀረበው አቤቱታ ይዘት ባጭሩ አመልካች ለሰጠው ብድር ተጠሪ መያዣ መስጠቱን፣ የመያዣ ውል ከሰው ዋስትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተለየ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ባለመገንዘብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1928/2/ን ጠቅሰው መወሰናቸው ስሕተት ስለመሆኑ እና የመያዣ ውሉ የተጠሪን ስምምነት ሳይጠይቅ ሊታደስ መቻሉን የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 3058/2/ ድንጋጌ ባለማገናዘብ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲሻር አመልክተዋል፡፡ የሰበር ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የተጠሪን ስምምነት ሳያገኝ ውሉ መታደሱ ተቀባይነት የለውም ሲሉ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ሲባል ተጠሪ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቀርበው ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ የክርክራቸው ይዘትም ማዘጋጃ ቤቱ የመያዣ ውሉን አላደሰም የሚልና ቀርበው ስምምነት ያልሰጡ መሆኑን ጠቅሰው የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው ሆኖ እኛም ጉዳዩን ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት ውሳኔ የሚያስፈልገው ጭብጥ የመያዣ ውልን ለማደስ የተጠሪው ስምምነት አስፈላጊ ነው ወይስ አይደለም; የሚለው ነው፡፡ከመዝገቡ መረዳት እንደቻለው አመልካች ለአቶ ሽፈራው ቡሎ ለሰጠው ብድር ተጠሪ በነቀምት ከተማ ቀበሌ 04 ክልል የሚገኘው ቁጥሩ 870 የሆነ መኖሪያ ቤቱን በዋስትና መያዣ መስጠቱን አላከራከረም፡፡

የመያዣ ውሉም በክፍሉ አስተዳደር ተመዝግቦ የቆየ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የመያዣ ውል ተመዝግቦ ካለ ለቀጣይ አሥር ዓመት ያህል ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 3058/1/ ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ይህ ጊዜ ከማለፉ በፊት ለተጨማሪ ጊዜ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ውሉን ማደስ አስፈላጊ እንደሆነም የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 3058/2/ ይጠቅሳል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመያዣ ውሉ እንዲታደስ የአሥር ዓመት ጊዜ ከማለፉ በፊት አመልካች ለክፍሉ መሬት አስተዳደር /ማዘጋጃ ቤት/ በደብዳቤ ያሳወቀ ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህንን ፍሬ ነገር ካረጋገጠ በኋላ የመያዣ ውሉ እንዲታደስ የአስያዡ ፈቃድ አልተገለፀም በሚል ምክንያት መያዣ ውሉ እንደታደሰ አይቆጠርም በማለት ውሉን ውጤት አልባ ማድረጉን ተረድተናል፡፡

የመያዣ ውል ከተመዘገበ ይህው ውል እንዲታደስ ጥያቄ የሚቀርበው በመያዣ ውሉ መብት ተጠቃሚ በሆነው ወገን መሆኑን መረዳት አዳጋች አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 3058/2/ መንፈስ መረዳት የሚቻለውም ይኸው ሀሳብ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ይበልጥ ግልፅ የሚሆነው የመያዣ ውል ከመዝገብ ሊሰረዝ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች እና የሥልጣኑን ጉዳይ አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1632/2/ ጋር በማገናዘብ ሲታይ ነው፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡት የተመዘገበው መብት ጊዜ ተወስኖለት የተደረገ እንደሆነ ጊዜው ሲያበቃ ይኸው እንዲሰረዝ አቤቱታ ሊቀርብ ሳያስፈልግ ባለሥልጣኑ ከመዝገብ መሠረዝ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል በተመዘገበው መብት ተጠቃሚ የሆነው ወገን ይኸው የተወሰነ ጊዜ ከማለፉ በፊት እንዲታደስለት ከጠየቀ ውል እንዲታደስ መመዝገብ የሚችል መሆኑን ያመለክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከእነዚህ ድንጋጌዎች አቀራረፅና ይዘት መረዳት የሚቻለው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል አንዱ ከተመዘገበ ይህንኑ ውል የማደስ ተግባር ለመፈጸም የአስያዡ ፈቃድ እንደገና መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የሚያሣይ አንቀጽ አለመሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች የመያዣ ውሉ እንዲታደስ ለማዘጋጃ ቤቱ በሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄ ማቅረቡ እስከተረጋገጠ እና ማዘጋጃ ቤቱም ይህንኑ መፈፀሙ እስከታመነ ጊዜ ድረስ ተጠሪ ውሉ እንዲታደስ ፈቃዱን አለመግለፅ የመያዣ ውሉን ጊዜ ሊያራዝም አይችልም በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ የሕጉን መንፈስና ይዘት በአግባቡ ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህም የመያዣ ውሉ የአሥር አመት ጊዜ አልፎበታል ከዚያ በኋላም አልታደሰም በማለት የተጠሪን ክስ ተቀብለው የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምሥራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 13190 በ4/7/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64740 በ4/11/2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የመያዣ ውል ለተጨማሪ 10 ዓመት ጊዜ የታደሰ በመሆኑ የተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፍ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. *42150*

ጥቅምት *29* ቀን *2003* ዓ.ም

ዳኞች፦ ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች - የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ወንድወሰን ጥሩነህ ቀረቡ

ተጠሪዎች - እነ አቶ ዳንኤል ካሣ /ሃያ ሁለት ሰዎች/ - ቀረቡ

- የ22ኛ ተጠሪ ጠበቃ ይሁን ፀሐይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኪራይ ውል ይሞላልን ጥያቄን መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪዎች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁኑ አመልካች ላይ የካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች የሚያስተዳድራቸውን የመንግስት ቤቶች ያለውል በቁልፍ ሽያጭ ወይም በውክልና በመያዝ ከሶስት እስከ አስር አመት ድረስ በቤቶቹ ቤተሰብ አፍርተው እየኖሩ እንደሚገኙ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር የስራ አመራር ቦርድ 94ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ በተጠሪዎች ሁኔታ የሚኖሩ ግለሰቦች ሕጋዊ ተከራይ እንዲሆኑ ውሣኔ ማሳለፉን፣ የተጠሪዎች ሁኔታ ውሣኔ ያረፈበት በመሆኑ የኪራይ ውል አመልካች እንዲያስሞላቸው ቢጠይቁ ከሰባት መቶ ሁለት ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የሌላችሁ በመሆኑ ውል አላስሞላችሁም በማለት የመለሳቸው መሆኑን ተጠሪዎች ከእነዚህ ሰባት መቶ ሁለት ከተባሉ ግለሰቦች ጋር ሲመዘገቡ አቅርቡ የተባሉትን ማስረጃ ሲያቀርቡ ቆይተው በአመልካች ድርጅት አስተዳደራዊ ችግር ባለመመዝገባቸው ሁሉንም ዜጋ እኩል ያላስተናገደና ተጠሪዎችን የጎዳ መሆኑንና የአመልካች ድርጅት ድርጊት ኢፍትሐዊና አድሎ ያለበት በመሆኑ ሊታረም እንደሚገባው ገልፀው ጥቅምት 03 ቀን 1998 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠቃሚ መሆናቸው እንዲረጋገጥ በኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች በኩል የተከሰተው አፈፃፀም ችግር የተጠሪዎችን በሕግ ፊት በእኩል የመታየት ሕገ መንግስታዊ መብት የጣሰና የመልካም አስተዳደር መርህን ያልተከተለ አሰራር ነው ተብሎ በአመልካች ቤቶች ላይ ሕጋዊ ውል እንዳይሞሉ የተደረገው ክልከላ ተነስቶ በቦርዱ ውሣኔ መሠረት ሕጋዊ ውሉ እንዲሞላ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት የሌላቸው መሆኑን ተጠሪዎች ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች በመባል ውል እንዲሞሉ ከተፈቀደላቸው ሰዎች መሐል ስማቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደማይገኝ በተደረገው 105ኛ ስብሰባ በኤጀንሲው ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች በመባል ከሚታወቁት ባለጉዳዩች በቀር ሊስተናገዱ እንደማይገባ በመወሰኑ የተጠሪዎችን ጉዳይ ማስተናገድ እንደማይቻል፣ ተጠሪዎች ከፊሉ ከመጋቢት 04 ቀን 1997 ዓ.ም በፊት ጉዳያቸው ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ 94ኛ ስብሰባ በተደረገው ውሣኔ መሠረት ሊስተናገዱ የማይገባ ከፊሉ ደግሞ ውዝፍ ኪራይ ባለመክፈላቸው ምክንያት ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ በአንድነት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት እንደሌለው እንዲሁም ውል አመልካች ሊዋዋል የሚችለው በሙሉ ፍላጎት እንጂ ተገዶ አለመሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በመመርመር የአመልካችን ክርክር በከፊል ውድቅ አድርጐ የአሁኑ ተጠሪዎች ጥቅምት 03 በቀን 1998 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠቃሚዎች በመሆናቸው በውሣኔው መሠረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሲል ወስኗል በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ ታህሣሥ 03 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮም አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የኪራይ ውል ማድረግ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ነጥብ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ የግራቀኙ የቃል ክርክርም ጥቅምት 23 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰምቷል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ አመልካች በቤቶቹ ላይ ውል አስሞልቷቸው የተከራይነት መብት እንዲረጋገጥላቸው ሲሆን ለጥያቄው መሠረት ያደረጉትም የአመልካች ቦርድ ውሣኔ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው መሆኑን አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ያላቸውን ሌሎች በርካታ ሰዎችን የኪራይ ውል እንዲሞሉ ሲያደርግ ተጠሪዎሪችን በሕገ መንግስቱ የተጠበቀላቸውን የእኩልነት መብት ግንዛቤ ውስጥ ባላስገባ መልኩ አድሎ ፈጥሯል የሚሉትን ምክንያቶችን መሆኑን ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪዎች ተመሳሳይ ሁኔታ ያላቸው ሰዎች የኪራይ ውል እንዲሞሉ ተደርጓል የሚሉት ለተጠሪዎች መብት የማይሰጥ መሆኑንና የቀድሞው የቦርድ ውሣኔ በሌላ ውሣኔ መተካቱን እንዲሁም የኪራይ ውል መደረግ ያለበት በተዋዋይ ወገኖች ሙሉ ፈቃድ እንጂ በግዴታ አለመሆኑን ጠቅሶ የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ የህግ ወይም የውል መሠረት የለውም በማለት መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍ/ቤቶች ብቻ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 79/1/ ተደንግጓል የሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ ፍ/ቤቶች በማናቸውም ጉዳይ ገደብ የለሽ ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሕገመንግስቱ አንቀጽ 79/1/ እና 37 አንድ ላይ ሲታዩ ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ለማየትና ለመወሰን ሥልጣን የሚኖራቸው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው /Justiciable matter/ ሆኖ ከተገኘ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 “ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡" በሚል ከተደነገገው "..... ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል..." የሚለው፤ እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 4 በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም በህግ ካልተገለፀ፤ ክሱን ተቀብሎ ለማከራከር ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ብቻ ነው በሚል መደንገጉ በፍርድ ሊወሰን በሚችለው ጉዳይ ፍ/ቤቶች ብቸኛ ስልጣን የሌላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ማየት የሚችሉት ጉዳዩ በፍርድ የሚያልቅ ሲሆንና በሌላ አኳኋን እንዲታይ በሕግ እስካልተወሰነ ጊዜ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ነው ሊባል የሚችለው ደግሞ የክርክሩ መሠረት በሕግ ጥበቃ ያገኘ መብት ወይም ግዴታ ሲሆን ወይም ለመብቱ ወይም ግዴታው መሠረት የሚሆን ውል መኖሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የመሠረቱት ሕጋዊ ውል የሌላቸው መሆኑን ራሳቸው ክሱን ሲመሠርቱም ቢሆን አረጋግጠው የቀረቡት ጉዳይ ሲሆን አመልካች የሚያስተዳድረውን ቤት የኪራይ ውሉ ከተጠሪዎች ጋር እንዲገባ ይደረግላቸው ዘንድ ዳኝነት የሚጠይቁት አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ያላቸውን ሰዎች ኪራይ እንዲሞሉ በቦርድ ተወስኖ በቁጥር ሰባት መቶ የሆኑት ሰዎች የውሣኔው ተጠቃሚ ሲሆኑ ተጠሪዎች ላይ አድሎ በመፈፀም በቦርዱ ውሣኔ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማድረጉ ከመንግስት መስሪያ ቤት የማይጠበቅ ነው በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ አመልካች የራሱ የሆነ ሕጋዊ ስልጣን ያለው፣ የመንግስት ቤቶችን የማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠው ሲሆን እንደማንኛውም ባለሃብት ቤቶቹን ለፈለገው ሰው የማከራየት ሕጋዊ መብት ያለው አካል መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የራሱን ሥርዓት በመዘርጋት የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች ለሕብረተሰቡ በተከራይነት እንዲጠቀሙ የሚያደርግ መሆኑ ይታመናል፡፡ ኪራይ ደግሞ ውል ከሚባሉት ሕጋዊ ተግባራት አንዱ ሲሆን በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት የኪራይ ውል የውል አመሰራረት መሠረታዊ ነጥቦችን አሟልቶ መገኘትን የግድ ይላል፡፡ ለውል አመሰራረት መሠረታዊ ነጥቦች ናቸው ከሚባሉት መካከል ደግሞ አንዱ የመዋዋል ነፃነት /Freedom of contract/ ነው፡፡ የመዋዋል ነፃነት ሲባልም ተዋዋይ ወገኖች በሙሉ ፈቃዳቸውና ፍላጎታቸው ውል የማድረግ መብት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ሕግ ጥበቃ የሚያደርገው በሕጉ አግባብ የተመሰረተን ውል እንጂ ከመነሻው ተዋዋይ ወገኖች በግድ በውል ግዴታ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግን አለመሆኑን ነው፡፡

የተጠሪዎች ጥያቄ ሲታይም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25፣ 41፣ 89 እና 90 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መንፈስ የሚጠቅስ ቢሆንም አመልካች በሕጉ ከተሰጠው ሥልጣን እና ተግባር እንዲሁም ከውሉ አመሰራረት መሠረተ ሃሳቦች አንፃር ሲታይ የተጠሪዎች የእኩልነት እና መጠለያ የማግኘት መብት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተያያዘ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ከተጠሪዎች ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ያላቸውን ሰዎች የኪራይ ተጠቃሚነት ወሰነ የተባለው የአመልካች መስሪያ ቤት የስራ አመራር ቦርድ የተጠሪዎች ጥያቄ ከሰባት መቶ ሰዎች ጋር ተመሳሳይ አለመሆኑን በ105ኛው መደበኛ ስብሰባ አረጋግጦ የወሰነ ሲሆን ተጠሪዎች ጉዳዩ ተመሳሳይ ነው፣ ወይም ተመሳሳይ እንዳይሆን በአመልካች የአስተዳደር ችግር ተፈጥሯል የሚሉ ከሆነም ጥያቄውን ማቅረብና መስተናገድ ያለባቸው በፍርድ ቤት ክስ በመመስረት ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች ጥያቄ በሕግ አግባብ የተቋቋመ የኪራይ ውል አፈፃፀም ጋር የተገናኘ ባለመሆኑ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር በፍርድ ኃይል የኪራይ ውል እንዲዋዋል የሚደረግበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሲሆን ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የማይችል ሆኖ እያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የበታች ፍርድ ቤቶች ክሱን በመቀበል ውሣኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 84204 ሕዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 61531 ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያቋቁሙት ሕጋዊ የኪራይ ውል በሌለበት ሁኔታ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የኪራይ ውል ለማድረግ በፍርድ ኃይል የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሃሣብ ልዩነት

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ አመልካቾችና ተጠሪዎች በዚህ መዝገብ የተከራከሩበት ጉዳይ /ጭብጥ/ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም አመልካቾችን በፍርድ ለመጠየቅ የሚያስችላቸው ተጠሪዎች ከውል የመነጨ ወይም በህግ ዕውቅናና ጥበቃ የተሰጠው መብት የላቸውም በማለት አብላጫው ድምፅ በሰጠው የህግ ትርጉምና ውሣኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ ለልዩነት ምክንያት የሆኑኝን ነጥቦች ከዚህ ቀጥሎ ገልጫለሁ፡፡

1. አብላጫው ድምፅ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰበት የመጀመሪያው ምክንያት ጉዳዩ በፍርድ የሚያልቅ /Justiciable matter/ አይደለም በማለት ነው፡፡ “ፍትህ የማግኘት መብት” በአገራችን የማናቸውም ሰው መሠረታዊ መብት መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 37 የተደነገገ ሲሆን ማናቸውም ሰው በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዩችን ለፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል የማቅረብና ፍትህ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን በሕገመንግስቱ አንቀጽ 37/1/ ተደንግጓል በእኔ እምነት ይኸ ህገመንግስታዊ ድንጋጌ በተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ፍርድ ቤት ወይም ሌላ የዳኝነት ሥልጣን በህግ የተሰጠው አካል በፍትህ ጠያቂው ወይም አቤቱታ አቅራቢው የቀረበለትን ማመልከቻና ማስረጃ ለማመልከቻው መልስ የመስጠት ግዴታ ያለበት የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰው የሚሰጠውን መልስና ማስረጃ በመቀበል በመስማትና በመመርመር ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ውሣኔ ሊያስተላልፍባቸው የሚችሉ ጉዳዩች በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዩች ወይም /Justiciable matter/ እንዲሆኑና ማናቸውም ሰው ለፍርድ ሰጭ አካል በማቅረብ ለመጠየቅና የእሱን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ የሚያደርግ ወይም ለጥያቄው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ዕውቅናና ጥበቃ የሚሰጥ ውሣኔ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን የሚደነግግ እና ሰፊ ትርጉምና ማዕቀፍ ያለው ድንጋጌ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ አንድ ጉዳይ በፍርድ የሚያልቅ ጉዳይ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን የህገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መንግስቱ አንቀጽ 13/2/ በሚደነግገው መሠረት አገራቱ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችና የሌሎች አገሮች ፍርድ ቤቶች ተሞክሮና ልምድና ለዳኝነት የቀረበውን ጉዳይ መሠረታዊ ባህሪ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

አንድ ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ነው የሚባለው የክርክሩ መሠረታዊ ባህሪ በፍርድ ለመጨረስ አመች የሆነ ሲሆንና ተከራካሪዎቹ የሚከራከሩበት ጉዳይ ንድፈ ሃሳባዊ ወይም ምናባዊ የፈጠራ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ሣይሆን በነባራዊ ዕውነታና ተጨባጭ በሆነ ችግር ወይም ክስተት መሠረት ያደረገ የመብት ወይም የሃላፊነት ጥያቄ ሲሆን እንደሆነ በህግ መዝገብ ቃላት “Justiciable matter“ ለሚለው ቃል ከተሰጡት ትርጉም ለመረዳት የሚቻል ሲሆን በህገመንግስቱ አንቀጽ 37 የተደነገገው ፍትህ የማግኘት መብት አገራችን ካፀደቃቻቸው ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀፅ 1 እና የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብት ቻርተር አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና ትርጉም ጋር በተጣጣመ መንገድ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ነው፡፡ በተለይም የህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 የተደነገገው ፍትህ የማግኘት መብት የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብት ቻርተር “Every individual Shall have the right to have his cause heard. This comprisises the right to appeal to competent national organs against acts of violating his fundamental rights as recognized and guaranteed by conventions, laws, regulations and custom in force“ በማለት በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ከተደነገገው ድንጋጌ ጋር በተጣጣመ መንገድ ግንዛቤ ሊያዝበትና ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ነው የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

ከዚህ አንፃር ስመረምረው አመልካችና ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ጉዳይ ተጠሪዎች በተከራይነት ወይም ተከራዩችን በመወከል ለረዥም ጊዜ ይዘው ሲጠቀሙባቸው የነበሩና ንብረትነታቸው የአመልካች የሆኑ ቤቶች የአመልካቹ ድርጅት ሥራ አመራር ቦርድ በ94ኛ መደበኛ ስብሰባው ባሣለፈው ውሣኔ መሠረት በሙሉ ተከራይነት የመያዝና ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል የመዋዋል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? አመልካች የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ 94ኛ መደበኛ ስብሰባ ያሣለፈውን ውሣኔ ሲያስፈፅም ተጠሪዎችን በእኩል ደረጃ ከሌሎች በተመሳሳይ ውሣኔ ተጠቃሚ ከሆኑ ሰዎች በመለየት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ በማስፈፀም ሂደት የፈፀመው አድሎ አለ ወይስ የለም? የሚለው ጭብጥ ነው ይህ ክርክር በመሠረታዊ ባህሪው የፖሊሲ ጥያቄ የማያስነሣና ፖለቲካዊ የሆነ ጉዳዩችን ያላካተተ በተቃራኒው የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርዱ የሰጠው ውሣኔ አመልካች ያለአድሎ ወጥነት ባለው ሁኔታ አስፈፅሟል ወይስ አላስፈፀመም ተጠሪዎች በሥራ አመራር ቦርድ 94ኛ መደበኛ ስብሰባ በሰጠው ውሣኔ ተጠቃሚ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚሉትን ነጥቦች የማጣራትና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመመርመርና በመመዘን ውሣኔ ሊሰጥበት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ድርጅት የመንግስት የልማት ድርጅት መሆኑ አመልካችና ተጠሪዎች የሚከራከሩበትን ጉዳይ “በፍርድ የማያልቅ ጉዳይ” “non Justiciable matter“ አያደርገውም፡፡ ስለሆነም የተጠሪዎችን ክስ በመቀበል በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመዘን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መስጠታቸው ጉዳዩ በመሠረታዊ ባህሪው በፍርድ የሚያልቅ / Justiciable matter/ በመሆኑ ትክክል ናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በሚል ምክንያት ከሙያ ባልደረቦቼ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

2. ሁለተኛው ነጥብ ተጠሪዎች አመልካችን በፍርድ የሚጠይቁበት ከህግ ወይም ከውል የመነጨ መብት የላቸውም በማለት አብላጫው ድምፅ የሰጠው ትርጉም በተለይ አመልካች ከተቋቋመበት ዓላማና መሠረታዊ ባህሪ አንፃር መታየት ያለበት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች የአመልካችን ቤት የያዙት አመልካች በህጋዊ መንገድ ላከራያቸው ሰዎች ገንዘብ በመክፈልና የተከራይ ተከራይ በመሆን ወይም የተከራዩቹ ወኪል በመሆን እንደሆነ በበታች ፍርድ ቤቶች በተጠሪዎችና በአመልካች በኩል ከተደረገው ክርክርና ፍርድ ቤቶቹ ከደረሰቡት መደምደሚያ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በግለሰቦች መካከል የተደረገው የቤት ኪራይ ውል ወይም የቤት ተከራይ የሚያደርገው አከራይ ውል ወይም በግለሰብና በአንድ የንግድ ድርጅት መካከል የሚደረግ የቤት ኪራይ ውልና የተከራይ አከራይ ውል እና የኪራይ ውሉን ተፈፃሚነት በተመለከተ ተከራዩ በወኪል ስለሚፈፅማቸው ተግባራት በአራከዩና በተከራዩ ወይም በአከራዩና የተከራይ ተከራይ በሆነው ሰው መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ወይም በአከራዩ እና በተከራዩ ወኪል መካከል አለመግባባት ቢፈጠር አለመግባባቱን አግባብነት ያላቸውን ስለቤት ኪራይና ስለእንደራሴነት የሚደነግጉትን የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ እልባት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የተጠሪዎች ጥያቄ በፍታብሔር ህጉ ስለ እንደራሴነትና ስለቤት ኪራይ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ የማይወሰንበት ዋነኛው ምክንያት አመልካች የመንግስት ልማት ድርጅት መሆኑና አመልካች የተቋቋመበት ዋናው ዓላማ እንደማንኛውም የግል የንግድ ድርጅት ያሉትንና የሚሰራቸውን ቤቶች ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርብለት ሰው እያከራየ ገንዘብ መሰብሰብ ሣይሆን የመንግስት መሠረታዊ የፖሊሲ ሃሳብና መመሪያን መሠረት በማድረግ ያለውን የቤት እጥረት ለማቃለል የተቋቋመ መሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 59/1968 ና በአዋጁ ከተደነገገው የድርጅቱ መሠረታዊ ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚችሉ ግልፅ የአሠራር ሥርዓቶችን በመቀየስ የቤት ኪራይ ግልጋሎት የሚሰጥባቸውን መመዘኛዎች በማውጣት መመዘኛውን ለሚያሟሉ ሰዎች በቅደም ተከተል ክፍት ቤት ሲኖረው የማስተናገድ ግዴታና ሃላፊነት አለበት፡፡ አመልካች በሕዝብና በመንግስት ሃብት የተቋቋመ የልማት ድርጅት በመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በህገመንግስቱ አንቀጽ 13/2/ መሠረት በአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብት ቻርተር አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀጽ 3 “Every individual Shall have the right to access to public property and service in strict equality of all persons before the law“ በማለት ከሚደነግገው ድንጋጌ ጋር በተጣጠመ መንገድ ግልፅ የሆነ አሰራርና መመዘኛ መሠረት በማድረግ መመዘኛውን የሚያሟላ በቅድም ተከተል የማስተናገድና እኩል ግልጋሎት የመስጠት ግዴታ ይኖርበታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

አመልካች ቤት በኪራይ ማግኘት የሚፈልጉ ሁሉንም ዜጎች ጥያቄ ለማስተናገድ አቅም የሌለው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም አመልካች ያሉትን ቤቶች የሚያከራይበትንና የተከራዩ ሰዎችንም የሚያስለቅቅበትን ግልፅ የሆነ መስፈርትና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋትና የአሠራር ሥርዓቱ ቤት እንዲከራዩ የሚፈቅድላቸውና መመዘኛ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰዎች በቅድም ተከተል በእኩል ደረጃ የኪራይ ግልጋሎት እንዲያገኙ የማድረግ የመመዘኛ መስፈርቱን የማያሟሉ ሰዎች ያገኙት የነበረውን የኪራይ ግልጋሎት የማቋረጥ ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህም ማለት አመልካች የኪራይ ውል ሲዋዋልም ሆነ የኪራይ ውሉን ሲያቋረጥ ግልፅ የሆነ የአሠራር ሥርዓትና የመመዘኛ መስፈርቶችን የመጠቀምና በቅደም ተከተል መስፈርቱን የሚያሟሉትን በእኩል ደረጃ የማስተናገድ ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች እንደማንኛውም የግል የንግድ ድርጅት የመዋዋል ነፃነት /Freedom of contract/ አለኝ በማለት የሚያቀርበው ክርክር ድርጅቱን መሠረታዊ ባህሪና የተቋቋመበትን ዓላማ እንደዚሁም የህገመንግስቱን አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የህገመንግስቱ አንቀጽ 13/2/ መሠረት በማድረግ በአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብት ቻርተር አንቀጽ 13 /3/ በማክበር አገራቱ የገባችው ቃልኪዳን ጋር የሚጣጣም ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በህገመንግስቱ አንቀጽ 12 ንዑስ ቁጥር 1 እና 2 የተደነገገውን የግልፅነትና የተጠያቂነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርህ አገልግሎቱን በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሊያከብርውና ሊመራበት የሚገባው ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከላይ የገለፅኳቸውን መሠረታዊ ሃሰቦች ይህ የአመልካችና የተጠሪዎች ክርክርና በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ ስመረምረው አመልካች የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ከተጠሪዎች ቤት በያዙበት ተመሳሳይ ሁኔታ ቤት ይዘው የሚገኙና ተመሳሳይ መስፈርት የሚያሟሉ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች የያዙትን ቤት በቋሚነት ተከራይተው ለመኖር እንዲችሉ በመፍቀድ የኪራይ ውል ተዋውሏል፡፡ ተጠሪዎች የሥራ አመራር ቦርዱ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያወጣቸውን መስፈርቶች የሚያሟሉና አመልካች በቦርዱ ውሣኔ ለመፈፀም ባለመፈለጉ ብቻ ተጠሪዎች እንደ ሌሎቹ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች የኪራይ ግልጋሎት የማግኘት መብታቸውን በእኩል ደረጃ ሳይከበርላቸው የቀረ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ያለበቂ ምክንያት ተጠሪዎች እንደሌሎቹ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ መከልከሉ ከላይ የጠቀሳቸውን የህገመንግስት ድንጋጌዎች የሚጥስና የድርጅቱን ተፈጥሯዊ ባህሪና ዓላማ የሚቃረን አድሏዊ የሆነ አሠራር ነው፡፡

አመልካች የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠሪዎች ከሌሎቹ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች ጋር በእኩል ደረጃ ማስተናገድና ግልጋሎት እንዲያገኝ ማድረግ ሲገባው ተጠሪዎችን ያለበቂ ምክንያት ሲያጉላላ ቆይቶ ከአንድ ዓመት በኃላ የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ጥቅምት 10 ቀን 1999 ዓ.ም በ105ኛ መደበኛ ስብሰባው ያስተላለፈውን ውሣኔና መስፈርት አያሟሉም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው አይደለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የሥራ አመራር ቦርዱ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የድርጅቱን ቤቶች የተከራይ ተከራይ በመሆን ወይም የተከራይ ወኪል በመሆን ይዘው ለረዥም ጊዜ የኖሩ ሰዎች በህጋዊ ተከራይነት የአመልካችን ግልጋሎት የሚያገኙበትን መስፈርትና መመዘኛ የሚያሟሉ ሆነው እያለ ተጠሪዎችን ከሌሎቹ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች ጋር በእኩል ደረጃ አለማስተናገዱ ህጋዊ አይደለም ተጠሪዎችን ከሌሎቹ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች ጋር በእኩል ደረጃ ማስተገድ ይኖርበታል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም የሚል እምነት ስላለኝ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል / Justiciable matter/ በመሆኑና የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ተመሳሳይ መመዘኛና መስፈርት የሚያሟሉ ሰባት መቶ ሁለት ሰዎች የሥራ አመራር ቦርዱ ጥቅምት 3 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት አስተናግዶ ተጠሪዎችን የቤት ኪራይ ግልጋሎት እንዳያገኙ ያለበቂ ምክንያት የከለከላቸው መሆኑን በማጣራትና በማስረጃ በማረጋገጥ አመልካች አገልግሎቱን ለተጠሪዎች በእኩል ደረጃ እንዲሰጥ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም የሚል እምነት ስላለኝ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 47617

ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ቂስ ገ/ሚካኤል አለምነው - ጠበቃ ታደሰ ወ/ጊዮርጊስ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መልኬ ደምሴ ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ከሕግ ውጪ የተያዘብኝ ቤት ይለቀቅልኝ በማለት ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሠረተችው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ በተጠሪ ክስ እንደተገለጸው አመልካች ቤቱን አለቅም ያለው ከተጠሪ አውራሽ ላይ በውል ገዝቼ ነው የያዝኩት በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ይህን ሁኔታ በማወቅዋም ውሉ በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት /ፎርማሊቲ/ አሟልቶ የተደረገ አይደለም የሚል የመከራከሪያ ነጥብ በክስዋ አንስታለች፡፡ በመጨረሻም የጠየቀችው ዳኝነትም ውሉ በሕግ ውጤት የለውም እንዲባል እና አመልካችም ቤቱን እንዲያስረክቢት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የስረነገር የመከራከሪያ ነጥቦችን አንስቶአል፡፡ ከመቃወሚያዎቹ አንዱ ክሱ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1000 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል ሆኖ ሥረ ነገርን በሚመለከትም ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም፡፡ የገዛሁት ጅምር ቤት ስለነበር በእንጨት ተሰርቶ የነበረውን ጅምር በማፍረስ ህንፃ ሠርቻለሁ፡፡ እንደከሳሽ ጥያቄ ቤቱን አስረክብ ብባል የማስረክበው የገዛሁትን ሳይሆን በራሴ ገንዘብ የሠራሁትን ህንፃ ነው የሚሉትን መከራከሪያዎች አቅርቦአል፡፡ ይህን የመሰለ ክርክር የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአንድ በኩል ለይርጋ መቃወሚያው አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1000 በወራሾች መካከል ለሚነሳ ክርክር ነው አግባባነት የሚኖረው በማለት በሌላ በኩል ደግሞ የሺያጭ ውሉ በተደረገበት እና ክሱ በቀረበበት መካከል ያለው ጊዜ ሰባት ዓመት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1845 ከተቀመጠው የጊዜ ወሰን አንፃር ሲታይ ይርጋው አላለፈም የሚል ምክንያት በመስጠት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በሥረ ነገር ረገድ የቀረበው ክርክር የሽያጭ ውሉ በፍ/ሕ/ቁ. 1723 የተመለከተውን መስፈርት ወይም /ፎርም/ አያሟላም የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ውድቅ አድርጐታል፡፡ በእርግጥ አመልካች በቤቱ ላይ ወጪ አድርጌአለሁ ካለ ወጪው እንዲመለስለት ስለ አላግባብ መበልፀግ በሚመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የመጠየቅ መብቱ ተጠብቆአል የሚል ትችት በውሳኔው መጨረሻ ላይ አስፍሮአል፡፡ በመጨረሻም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በክሱ የተመለከተውን ቤት አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክብ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 17 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው አመልካች የገዛሁትን ጅምር ቤት በመገንባት ህንፃ ሠርቻለሁ በማለት ያቀረበው ክርክር እና ማስረጃ የመታለፉ አግባባነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምንመለከተው ክርክሩ የተነሳው በወራሾች መካከል ባለመሆኑ እና ክሱም የቀረበው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 የተመለከተውን የይርጋ ወሰን ከማለፉ በፊት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ በመረጋገጡ አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው፡፡ ወደ ጉዳዩ ሥረ ነገር ስንመጣ ተጠሪ ቤቱን ልረከብ የምትለው የቤት ሺያጭ ውሉ ሕጋዊ አይደለም ወይም የተደረገው ከሕግ ውጪ ነው በማለት እንደሆነ ነው የምንገነዘበው፡፡ ውሉ ውጤት የለውም ለማለት የሰጠችው ምክንያትም በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1723 የተመለከተውን የውል አጻጻፍ ፎርም አያሟላም በማለት ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ አራተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 12 በምዕራፍ 3 ሥር ስለግዴታዎች መቅረት በሚመለከት ዝርዝር ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል፡፡ የዚህ ምዕራፍ ክፍል 1‘ም’ ውሎችን ስለመሰረዝና ስለማፍረስ በሚል የተደነገገ ሲሆን በዚህ መዝገብ ለያዝነው ጉዳይ አወሳሰን ተገቢነት ያለው በዚህ ክፍል ሥር ከተካተቱት ድንጋጌዎች አንዱ የሆነው በቁጥር 1808 የተመለከተው ድንጋጌ እንደሆነም እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንኡስ ቁ(2) እንደተመለከተው ውሉ ለውሉ አጻጻፍ የተደነገገውን ፎርም አልጠበቀም የሚል መከራከሪያ ያለው ተዋዋይ ወገን ወይም ማንኛውም ከውሉ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ጥቅም ያለው ሰው ውሉ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በእርግጥ ተጠሪ ውሉ ይሰረዝልኝ የሚል ክስ ባትመሰርትም የውሉን መኖር ተገንዝባ ለውሉ አጻጻፍ የተደነገገውን ፎርም አልጠበቀም የሚል መከራከሪያ አንስታለች፡፡ አመልካች ደግሞ ውሉ ሳይነካ በራሴ ጥረት እና ገንዘብ የሠራሁትን ቤት ይገፍ መቅረት አለብኝ በማለት ተከራክሮአል፡፡ በዚህ ምክንያትም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል ወይስ አይገባም በሚለው ነጥብ ላይ ውሳኔ ከመስጠት በፊት ውሉ የሚሰረዝ ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ውሳኔ መስጠት አግባብ ይሆናል፡፡ በዚህ አካሄድ በመጨረሻ ውሉ ይሰረዛል የሚባል ቢሆን እንኳ አመልካች ቤቱን አስረክበህ ሂድ የሚባልበት አግባብ ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሕግ/ቁ 1815 (1) እንደተደነገገው ውል ሲሰረዝ ወይም ሲፈርስ ተዋዋዮቹ በተቻለ መጠን ውሉ ከመደረጉ በፊት እንደነበሩት ሁኔታ እንዲመለሱ የግድ ነው፡፡ በዚህ መንገድ መፈፀም ካልተቻለም በፍ/ብ/ሕግ ቁ1817 የተመለከተውን ደንብ መከተል እንደሚገባ ሕጉ ያመለክታል፡፡

ጉዳዮን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የፌዴራል መጀመያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት ከጅምሩ ውል እንደሌለ በመቁጠራቸው የውልን መፍረስ ወይም መሠረዝ ተከትሎ ስለሚኖረው ውጤት በተመለከተ ውሳኔ ሊሰጡ አልቻሉም ተጠሪ ልረከብ የምትለው ቤት እኔ የሰራሁት ነው የሚለው የአመልካችን ክርክር በጭብጥነት ይዘው በማስረጃ ሳያጣሩ ያለፉትም በዚህ ምክንያት ነው የሚመስለው፡፡ እንደ ሕጉ ከሆነ ግን ክርክሩ የውል መፍረስ ወይም መሠረዝንም የሚመለከት በመሆኑ ቀጥሎ ስለሚመጣው ውጤት በተመለከተ ተገቢውን መወሰን ይቻል ዘንድ በእርግጥ ቤቱ አመልካቹ የሠራው ነው? ቤቱ በጅምር የነበረ ነው ከተባለስ አመልካች ምን ያህሉን ሠራ፣ ወዘተ የሚሉትን ነጥቦች አስቀድሞ በማስረጃ ማንጠር አስፈላጊ ነው የሚሆነው፡፡ ይህ ሁኔታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕጉ አግባብ ውል ይፈርሳል ወይም ይሰረዛል የሚል ውሳኔ ቢሰጥ ሊከተል ስለሚገባው ውጤት ወሳኝ ሚና የሚኖረው የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን በዚህ አግባብ አልመሩም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተገባበር /አተረጓጐም/ ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 08007 ሚያዝያ 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 80087 ሐምሌ 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ሠርቼ ያጠናቀቅሁት እኔ ነኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር ተጠሪ ከምታቀርበው ክርክር ጋር በማገናዘብ እንዲያጣራ በመቀጠልም በፍሬ ነገር ረገድ ያጣራውን መሠረት በማድረግ በአጠቃላይ የክርክሩ ውጤት ላይ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49041

ጎንደር 2 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ሻገረ ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአ/አ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት ነ/ፈጅ ማህሌት ዳዊት ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ኤሣው መዓዛ
2ኛ. አቶ ዘርሁን መላኩ
3ኛ. ወ/ሮ ተስፋነሽ ተሰማ
} ጠ/መስፍን ደምሴ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የዋስትና ግዴታን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ክስ የቀረበው በአመልካች በኩል ነው፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ ሲታይ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ ሁኖ ለ7 ዓመታት ያህል ትምህርት እንዲከታተል እና ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ ለ6 ዓመት ያህል ለማገልገል ግዴታ ገብቶ ለ5 ዓመታት ያሕል ትምህርቱን ከተከታተለ በኋላ ባልታወቀ ምክንያት ትምህርቱንና ሥራውን ስላቋረጠ ለትምህርት የወጣውን ወጪ እንዲተካ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች (ተጠሪዎችም) ለዚሁ ውል አፈፃፀም እስከ ብር 50,000 ድረስ የዋስትና ግዴታ የገቡ ስለሆነ ክስ የቀረበበትን ብር 29,497.03 ባልተነጣጠለ ሃላፊነት እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ የመረመረው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ(ተጠሪ) ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል ሲወስን፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ መሰረት አስቀድመው አስቀርተዋል በሚል ክሱ በነሳ እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በፍርድ አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ የሰጡት ትርጉም መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1925/2/ መሰረት ከዋስትና ግዴታቸው ነፃ ናቸው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጠበቃ የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ በይዘቱም ተጠሪዎች የገቡት ግዴታ ወደፊት ይደርሳል ተብሎ ለሚታሰብ ሁኔታ ስለመሆኑ ጠቅሶ ይህ ሃላፊነት ከመድረሱ በፊት የዋስትና ግዴታቸውን ማውረዳቸው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ የሚሸፈን ስለመሆኑ በመግለጽ በዝርዝር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የዚህ ሰበር ችሎት ውሳኔ የሚያሳየው ነጥብ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ አውርደዋል ተብሎ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 125/2/ ተጠቅሶ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር ላይ እንደተረዳነው 1ኛ ተጠሪ በአመልካች እስፖንሰርንት ከፍተኛ ትምህርት ተከታትሎ አጠናቆ ሲመለስ ለ6 ዓመት ለማገልገል፣ ይህንን ካልፈፀመ ደግሞ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ያወጣውን የትምህርት ወጪዎች ሊተካ የውል ግዴታ የገባ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም 1ኛ ተጠሪ በውል የገባውን ግዴታ ካልፈፀመ እስከ ብር ሃምሣ ሺህ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለመክፈል የዋስትና ግዴታ መፈረማቸውም አላከራከረም፡፡

በዚሁ አግባብ አመልካች ይህንኑ ውለታ መነሻ በማድረግ 1ኛ ተጠሪ እንደውሉ ግዴታውን ባለመፈፀሙ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ብር 29,497.03 እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት በመጠየቁ የሥር ፍ/ቤትም 1ኛ ተጠሪን ሃላፊ በማድረግ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ ውል የገቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ መሰረት የዋስትና ግዴታቸውን አስቀድመው አውርደዋል በሚል ክሱ በነሳ አሰናብቷቸዋል፡፡

የሥር ፍ/ቤት ለውሳኔው ምርኩዝ ያደረገው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ ወደፊት ስለሚሆን ወይም በአንድ ዓይነት ሁኔታ ስለሚመጣ ግዴታ ዋስ ስለመሆን አስመልክቶ የዋስትና ግዴታው ለስንት ጊዜ እንደሚረጋ በስምምነቱ ያልተመለከተ እንደሆነ የዋናው እዳ ተጠያቂነት ከመድረሱ በፊት ዋሱ ዋስትናውን ሊያስቀር እንደሚችል ያመለክታል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መረዳት የሚቻለው ዋናው ግዴታ ወደፊት ሊደርስ ወይም ላይደርስ በሚችል ሁኔታ ላይ (uncertain event) የተመሰረተ በሆነ ጊዜ ዋሱ ዋናው ግዴታ ከመድረሱ በፊት የዋስትና ግዴታውን ማስቀረት የሚችልበት አግባብ ስለመኖሩ ነው፡፡

የዚህ ድንጋጌ መንፈስ ዋናው ግዴታ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ሊፈጸም የሚችል ስለመሆኑ ከይዘቱ መረዳት ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች ግዴታ 1ኛ ተጠሪ ከሥራ ውጪ ሆኖ ትምህርት እንዲከታተል መፍቀድ እና ለትምህርቱም አስፈላጊውን ወጪ መሸፈን ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ትምህርቱን ተከታትሎ እንዳጠናቀቀ በውሉ ለተመለከተው ጊዜ ያሕል ለአመልካች አግልግሎት መስጠት አሊያም ለትምህርት የወጣውን ወጪ መተካት ስለመሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የዋናው ውል ግዴታ ወደፊት በሚደርስ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ እርግጠኛ ያልሆነ (uncertain event) ሁኔታ ላይ የተንጠለጠለ ነው ተብሎ በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1925 ሥር የሚሸፈን አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው ዋና ግዴታ ወደፊት ሊደረስ ወይም ላይደርስ የሚችል ሁኔታ (conditional) ነው የማይሰኝ ነው ከተባለ ደግሞ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ መሰረት የዋናው ግዴታ ተጠያቂነት ከመድረሱ በፊት አስቀርተዋል ተብሎ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች 2ኛ ና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ የ1ኛ ተጠሪ ግዴታ ከመድረሱ በፊት ቀሪ ሆኗል በሚል ምክንያት ተጠሪዎች አላፊነት የለባቸውም ሲል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1925/2/ በመጥቀስ የሰጠው ፍርድ የድንጋጌውን ይዘትና መንፈስ በአግባቡ ያላገናዘበና የግራ ቀኙን የውል ግዴታ በውል ያላመነ ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 110168 በ01/09/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 70425 በ16/10/2000 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በገቡት የዋስትና ግዴታ ውል መሰረት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለአመልካች የመክፈል ግዴታ አለባቸው ብለናል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤት በዚሁ መሰረት ያስፈጽም፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር ነ.ፈ.ጅ አቶ ብርሃኑ ልኪሣ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ታደሰ አደራ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ አንድ የተሸጠ የሚንቀሣቀስ ንብረት ከመሸጡ በፊት በነበረ የፍ/ቤት ዕገዳ ምክንያት ገዥው በባለቤትነት መብቱ መገልገል ሣይችል ቢቀር በሻጩ ላይ ሊኖር የሚችለው ኃላፊነት ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ በሚመለከት በሻጭና በገዥ መካከል በተነሣው የሕግ ክርክር ላይ ያተኮረ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ባጭሩ፡

ሳምሶን ነጋሽ በሚባል ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ፊያት የጭነት መኪና ሚያዚያ 28 ቀን 1998 ዓ.ም በብር 58,000.00 ሸጦልኛል፡፡ ሆኖም የፍ/ቤት ዕግድ ስላለበት የንግድ ፈቃድ፣ ቦሎ እና ታርጋ በማውጣት እንደባለቤት በንብረት አገልግሎት ማግኘት አልቻልኩም ጥቅም ተቋርጦብኛል፡፡ ስለሆነም የተቋረጠ ጥቅም በወር 7000.00 /ሰባት ሺህ ብር/ እንዲከፍለኝና ስመሐብትነቱንም ወደ እኔ ይዙርልኝ የሚል ክስ አቅርቦበታል፡፡

የአሁን አመልካችም በተከሣሽነት ቀርቦ ባለቤትነትን የሚያረጋግጡ ሰነዶችንና ሊብሬውን አስተላልፈናል፡፡ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የዕግድ ትእዛዝ ያስነሳን ሲሆን በወረዳው ፍ/ቤት የነበረውን ግን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለማሰነሣት አልቻልንም የሚለውንና ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ መረዳት እንደሚቻለውም በዕገዳ ምክንያት መኪናው ያለሥራ አልቆመም፤ ዕግድ ያለበት መሆኑንም እያወቀ ስለገዛ ኃላፊነት የለብንም የሚሉትን ከኃላፊነት ጋር የተያያዙ ክርክሮችን ካቀረበ በኋላ ስለተቋረጠ ጥቅም መጠን አስመልክቶ ደግሞ የተቋረጠው ጥቅም መጠን በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አይታመንም በማለት ግልጽ መልስ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተቋረጠ ስለተባለው ጥቅም ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ይችል ዘንድ ከበከልቻ ትራንስፖርት አክሲዩን ማህበር ማረጋገጫ እንዲቀርብ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ፣

ተከሣሽ የአሁን አመልካች ለተቋረጠ ጥቅም ኃላፊነት አይኖርብኝም ሲል ያቀረባቸው ምክንያቶች ተቀባይነት የላቸውም የተቋረጠ ጥቅምን በሚመልከት የትራንስፖርት አክሲዮን ማህበሩ ከሣሽ ከገለፀው መጠን በላይ ሆኖ ስለተገኘ ከሣሹ ያቀረበውን መጠን የሰሌት መነሻ በማድረግ የሽያጭ ውሉ ከተደረገበት ሚያዚያ 28 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ስመ ሀብትነቱ ወደ ከሣሽ ዞሮ ሥራ እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ በወር 7000.00 /ሰባት ሺህ ብር/ ተከሣሽ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ

የሽያጭ ውሉ ከተደረገበት ከሚያዚያ 28 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት ግንቦት 23 ቀን 1994 ዓ.ም የተሰጠ የፅግድ ትእዛዝ መኖሩን ከተረጋገጠ ሻጭ ቀድሞውኑ የፅግድ ትእዛዝ እንዳለበት ያውቃል፡፡ ስመሀብት የማዛወር ግዴታ ባይኖርበትም ይህንን ፅገዳ እያወቀ መሸጡ፡ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው በሽያጭ ውል ላይ ሻጭ አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ ያደርጋል በሚል መገለፀ በሻጭ ላይ ያለውን ከሕግ የመነጨ ግዴታን የሚያስቀር አይሆንም መኪናው ስለመቆሙ አልተረጋገጠም ቢልም ስመሐብትነቱ በገዥው ስም እስካልዞረ ድረስ ያለስራ እንደቆመ ይቆጠራል ስለሆነም ኃላፊ ነው መባሉ ተገቢ ሲሆን፤ የደረሰውን የጉዳት መጠንንም ቢሆን በገለልተኛ ወገን የተረጋገጠው ከሣሹ ከጠየቀው በልጦ በመገኘቱ የተነሣ በከሣሽ በኩል የቀረበው መጠን መወሰዱ ስህተት አይደለም የሚሉትን መነሻ በማድረግ ውሣኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር ቅሬታ የቀረበውም በእነዚህ በየደረጃው የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው ይታረምልን በሚል ሆኖ የመከራከሪያ ነጥቡም በሥር ፍ/ቤቶች አቅርቧቸው ከነበረው በይዘቱ የተለዬ አይደለም፡፡

ተጠሪም በኃላፊነትም ሆነ በጉዳት ካሣ መጠን ረገድ የሰጠው ዳኝነት ሕግን መሠረት ያደረገ ነው ስሚለው ክርክሩ ውሉን አብራርቶ አቅርቧል፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2341/2/ ላይ በተመለከተው መሠረት ከኃላፊነት ለመዳን ሲል ገዥው በንብረቱ ላይ የፅገዳ ትእዛዝ ያለበት መሆኑን እያወቀ ገብቷል የሚለውን ክርክር ያቅርብ እንጂ ይህ ክርክር ለሻጭ ጠቃሚ የሚሆነው ገዥው ተከስተ ባለው ጉድለት ሣቢያ የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በሚል ክስ የቀረበበት እንደሆነ ስለመሆኑ በንዑስ ቁጥር 1 ላይ ተመልክቷል፡፡ የገዥ የአሁን ተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ውል ይፍረስልኝ የሚል ሣይሆን ሻጭ ግዴታውን ከኪሣራ ጋር ይፈጽም የሚል ስለሆነ ቀጥተኛ አግባብነት የለውም፡፡ ገዥው የሚጠይቀው ዳኝነት አስገድዶ ማስፈፀምም ይሁን የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ይህ የሻጭ መከራከሪያ ነጥብ በሁለቱም ዓይነት ዳኝነቶች ያገለግላል እንኳ ቢባል ገዥ የአሁኑ ተጠሪ ንብረቱን በገዛበት ጊዜ በፍ/ቤት በተሰጠ ዕገዳ ምክንያት ሻጩ የእኔ ነው ከሚሉ ሦስተኛ ወገኖች መብት ሁሉ ነፃ የሆነ መኪና ለገዥው ማስረከብ የማይችል መሆኑን ያውቅ ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም በዚህ ነጥብ ላይ ማስረጃችንም አልታየልንም የሚል የሰበር ክርክርም የለውም፡፡ ገዥ ያውቅ ነበር በሚል በአባባል ደረጃ ከመግለጽ አልፎ ይህንን አባባል በማስረጃ አስደግፎ ማስረዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም በዚህ ሰበር ደረጃም ቢሆን ገዥ ያውቅ ነበር በሚል ብቻ ተወስኖ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

እንዲሁም አመልካች አከራካሪ የሆነው የዕግድ ትእዛዝ በእሷ መዝገብ ላይ ስላልተሰጠ፤ የወረዳው ፍ/ቤትም ስለእግድ ጉዳይ ሲጠየቅ ዕግድ የለም በሚል ስለአረጋገጠ እና ገዥውም ዕገዳ ያለበት መሆኑን አስቀድሞ የማረጋገጥ ግዴታ ነበረበት የሚሉትን ነጥቦች በመጠቀስ ኃላፊነት የለብኝም ሲል ያቀረባቸው ክርክሮች ሻጩ የተሸጠው ንብረት ላይ የማያስነካ መብት ለገዥው ለማስተላለፍ አስፈላጊ ተግባሮችን ለመፈፀም ግዴታ ይኖርበታል በሚል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2281 እንዲሁም ውጤቱ የውል ማፍረስን ጉዳይ የሚመለከት ቢሆንም የገዥውን መብት በሚነካ ጉድለት ምክንያት ሻጭ የእኔ ነው ከሚሉ ሦስተኛ ወገኖች መብት ሁሉ ነፃ የሆነ ነገር ለገዥው የማስረከብ ግዴታ አለበት በሚል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2341 የተጣለበትን ከሕግ የመነጨ ግዴታ ያገናዘቡ ክርክሮች ባለመሆናቸው የሕግ መሠረት የላቸውም፡፡

አከራካሪው መኪና በፍ/ቤት ዕግድ ምክንያት ያለ ሥራ ቆሟል ወይስ በሥራ ላይ ነበረ የሚለውን ጉዳይ አስመልክቶ አመልካች በሰበር ደረጃ የተብራራ ክርክር ያቀረበ ቢሆንም ይህ የፍሬ ነገር ጉዳይ ለሥር ፍ/ቤት በማስረጃ ተደግፎ ሊያጥር የሚችል እንጂ የሕግ ክርክርን የሚያስነሳ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት አመልካች በሸጠው ንብረት ላይ አስቀድሞ በነበረ የፍ/ቤት ዕገዳ ምክንያት በገዥው ላይ ደረሰ ለተባለው የጥቅም መቋረጥ ኃላፊ ነው በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሆኖም በዚሁ በሻጭ የግዴታ ጉድለት በገዥው ላይ ደርሷል የተባለውን የጉዳት መጠን በሚመለከት የተሰጠው ውሣኔ በተጓዳኝ ገዥ እንዲህ ያለ ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜ እርሱም በተቻለ መጠን ሊደርስ የሚችለውን ለይቶ የመቀነስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር ተካቶ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የመኪና ሽያጭ ውል የተደረገው ሚያዚያ 28 ቀን 1998 በሕግ ገዥው ጉዳት ደረሰበኝ ካሣ ይከፈለኝ ሲል ክስ ያቀረበው ደግሞ መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም ነው፡፡ ጉድለት ያለበት ንብረት ወይም ደግሞ ሙሉ የባለቤትነት መብት ለመገልገል የሚያስችል ጉድለት ያለበት ንብረት የተረከበ ገዥ ያለው የማስተካከያ መብት በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 2336 ቀጥሎ ባሉት ድንጋጌዎች ተቀምጧል፡፡ ገዥው ወዲያውኑ ክስ አቅርቦ ውሉን ማስፈረስ ወይም ደግሞ ከቁጥር 2329 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች የተጓደለው ነገር ተሟልቶ ይፈፀም ዘንድ ወዲያውኑ መጠየቅ ከዚህ ጋር ጎን ለጎንም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2360 እንደተመለከተው ከላይ ከተመለከቱት የሕግ መፍትሄዎች በሻጭ ግዴታ መጓደል ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት በገንዘብ አስልቶ መጠየቅ እንደሚገባው ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ ገዥው ይህንን በሕግ በተሰጠው መብቱ ሳይገለገል ለአንድ ዓመት ያህል እንደቆዩ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይህንንም ማድረግ መብቱ የሆነውን ያህል ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በመቀነስ ረገድ ከባከነው ጊዜ አንፃር ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1802 እንደተመለከተው ግዴታው ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር የደረሰውን የጉዳት ልክ አወሳሰን ከተያዘው ጉዳይ አንፃር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1790፤1802 የተመለከተውን መሠረት በማድረግ ሊወሰን ሲገባ ይህንን በገዥው በኩል የታየው የጥንቃቄ ጉድለት ሳይታይ የሽያጩ ውል የተደረገበትንና ዕግዱ የተነሣበትን ጊዜ መነሻ በማድረግ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተመለከተው ድንጋጌ ብቻ በማየት ውሣኔ መስጠቱ በሥር ፍ/ቤቶች በጉዳት ካሣው አወሳሰን ረገድ ስህተት መፈፀማቸውን ተገንዝበናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በመ/ቁ. 05183 21/6/2000 በመ/ቁ. 64263 በ22/04/02 የሰጡትን ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ አሻሽለን ወስነናል፡፡

2. አመልካች በተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡

3. የተከሰተውን ጉዳት በጊዜው እንዲስተካከል ማድረግ ሲገባ ይህን ካልፈፀመ ከተያዘው ጉዳይ አንፃር ጊዜ በረዘመ ቁጥር የጉዳቱ ስሌት በዚሁ ልክ እያደገ እንደሚሄድ ማወቅ ሲገባው ይህንን ሣያደርግ ያሳየውን የጥንቃቄ ጉድለት ሁሉ በማየት ለደረሰበት የጉዳት ልክ በርትዕ ብር 21,000.00 /ሃያ አንድ ሺህ/ ብር ይከፈለው ብለናል፡፡

በሥር ፍ/ቤት የተወሰነው ወጭና ኪሣራ ስሌቱ መሠረት ይኸው የጉዳት ገንዘብ ይሁን፤ በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ስለተሰጠው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች - ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች - 1. የምሥራቅ ወለጋ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ነገፈጅ አቶ በቀለ መንገሻ ቀረቡ

2. የምስራቅ ወለጋ ዞን ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ነገረፈጅ ድንቀለም ይኖሩ

ተጠሪ፣ አቶ ፀጋዬ ነጋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የምስራቅ ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ስላመለከቱ ነው ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛው አመልካች በአዲስ ዘመን ባወጣው ጨረታ ተሣትፌ በማሸነፌና ሌሎች ፎርማሊቲዎችን በማሟላት ለጤና ኬላ የሚውሉ መሣሪያዎችን ሳቀርብ ተከሣሹ ዋጋቸውን ሊከፍል ውል ተዋውለናል፡፡ ሆኖም ተከሣሹ /አንደኛ አመልካች ሀምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረግነው ውል መሠረት ላቀረብኩለት አስራ አራት ፍሪጅ ዋጋውን ከነተጨማሪ እሴት ታክሱ እንዲከፍለኝ ጠይቄ እስካሁን ያልከፈለኝ በመሆኑ ብር 340,621.96 /ሶስት መቶ አርባ ሺ ስድስት መቶ ሃያ አንድ ብር ከዘጠና አንድ ሣንቲም/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ተጠሪ ክስ አቅርቧል፡፡ አንደኛ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ፍሪጁን ተረክቦ ለሁለተኛው ተጠሪ ያስረከበ መሆኑን ከገለፀ በኃላ ገንዘብ ያልከፈልነው ተጠሪ ያቀረበው ፍሪጅ በጨረታ ተወዳድሮ ያሸነፈበት ሣይሆን ሌላ አይነት ፍሪጅ በማቅረቡ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው አመልካች በጨረታው ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆኖ ቀርቦ ተጠሪው “Cibir Type “ የሚባል ፍሪጅ ማቅረብ ሲገባው “Zero applience“ የተባለ ፍሪጅ ነው ያቀረበው ሊከፈለው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተጠሪ ባቀረበው የጨረታ ሰነድ “Zero applience“ የሚባለውን ፍሪጅ በመሞላት የተወዳደረ በመሆኑ በውሉ አስፈላጊው ሪፍሪጅሬተር የሚል አሻሚ ቃል ያለ በመሆኑ ተጠሪ ለማቅረብ የተስማማው “Zero applience“ የተባለውን ፍሪጅ ነው ይህንን ፍሪጅ በውሉ መሠረት ያቀረበ በመሆኑና አስራ አራት ፍሪጅ ከሣሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/ተጠሪ/ ያስረከበ ስለሆነ ብር 340,621.95 ብር አመልካቾች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል አንደኛ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የአንደኛ አመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል አመልካቾች የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 7 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በጨረታው ያቀረበው ስፔስፊኬሽንና አመልካቾች እንድንረከበው የጠየቀው ዕቃ አንድ አይነት አይደሉም ከዚህ በተጨማሪ በዋጋ ማቅረቢያው ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት መሆኑን ሣያሣውቅ ከነተጨማሪ እሴት ታክሱ የዕቃውን ዋጋ እንድንከፍል ተወስኖብናል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ፍርድ ቤቶች በየደረጃው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል ተጠሪ በበኩሉ የአመልካቾች አቤቱታ የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ የሰበር አቤቱታቸውን በመሰረዝ የሰበር ችሎት እንዲያሰናብተኝ የሚል ይዘት ያለው መልስ ያቀረበ ሲሆን አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካቾች ተጠሪ ያቀረበውን አስራ አራት ፍሪጅ በሙሉ ባለቤትነት በመቀበል ለተጠሪ የፍሪጁን ዋጋ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር እንዲከፍሉ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ የሥር ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ የደረሱበትን መደምደሚያ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በጨረታ ሰነድ ሞልቶ ያቀረበው “Zero applience“ የሚባለውን ፍሪጅ መሆኑን ሁለተኛው አመልካችም “Zero applience” የሚባለው ፍሪጅ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት የሚችልና ከተያዘው በጀት ጋር ዋጋው ተመጣጣኝ መሆኑን ገልፆ ለጨረታ ኮሚቴው ደብዳቤ የፃፈ መሆኑን በመዘርዘር ተጠሪ የተዋዋለው “Zero applience“ የተባለው ፍሪጅ በመሆኑና ይህንኑ ፍሪጅ በቁጥር አስራ አራት ያስረከበ በመሆኑ የፍሪጁን ዋጋ ከነተጨማሪ እሴት ታክስ አመልካቾች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አመልካቾች ከተጠሪ ጋር ውል የተዋዋሉት “Zero applience“ የሚባለውን ፍሪጅ ለመግዛት መሆኑን በመግለፅ ትዕዛዝ ሰጥቷል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ በውሉ የተገለፀውን ዕቃ ያቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አንደኛ አመልካች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ለጨረታ የወጣው “Cibir Type“ የተባለውን ፍሪጅ ለመግዛት ነው የሚል ክርክር ያቀረበ ቢሆንም ተጠሪ በጨረታ ሰነዱ ሞልቶ ያቀረበው “Zero applience“ የሚባለውን ፍሪጅ ለማቅረብ እንደሆነ በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ይህም ተጠሪ በሀራጅ ማስታወቂያው የተገለፀውን ፍሪጅ ሣይሆን ሌላ አይነት ፍሪጅ ለተጠሪ ለማቅረብ የጨረታ ሰነዱን ሞልቶ ሲያቀርብ አዲስ ድርድር እንዲደረግ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1694 መሠረት ሀሳቡን እንደገለፀ የሚያስቁጥር ሲሆን የጨረታ ኮሚቴው የሁለኛውን አመልካች ሃሳብና ስምምነት ከተቀበለ በኃላ ተጠሪን የጨረታው አሸናፊ መሆኑን በማረጋገጥ ውል መዋዋሉ ተጠሪ ያቀረበውን አዲስ ድርድር የተቀበለና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1695 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ውል የተዋዋሉ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም ተጠሪ የጨረታ ሰነዱን የሞላው “Zero applience “ የሚባለውን ፍሪጅ መሆኑና አመልካቾችም ይህንኑ አውቀውና አምነውበት ተጠሪን ዕቃውን እንዲያቀርብ ውል የተዋዋሉ መሆኑና ተጠሪ በውሉ መሠረት አሥራ አራት “Zero applience“ ፍሪጅ ማስረከቡን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች ይህ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ተገቢነት የለውም በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካቾች ተጨማሪ እሴት ታክስ እንድንከፍል መወሰኑ አላግበብ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የአዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋጌዎች እንደተሻሻለው ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ውል መሠረት የተረከቧቸውን አስራ አራት ሪፍሪጅሬተሮች ዋጋ ከነተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍሉ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኅዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ኃይላይ ተክላይ - ጠበቃ አቶ ገ/አምላክ ገ/ጊዮርጊስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- መቀር የጨው አምራቾች ኃላ/የተወ/የግል ማህበር ጠበቃ አቶ መሉጌታ ገብሩ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በተጠሪ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16 ላይ ስለ ውዝግብ አፈታት በሚል የተቀመጠው የደንብ ክፍል በማህበሩ አባላት መካከል የተነሣን ክርክር ብቻ ለመሸፈን ታስቦ የተቀረፀ ነው ወይስ በአባሉና በማህበሩ መካከል የሚነሳውንም ውዝግብ ሊጨምር የሚችል ነው? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ጋር በተያያዘ የአንቀፁ የተፈፃሚነት ወሰን በሚመለከት አግባብነት ያለውን ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች የማህበሩ አባል በማህበር ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ሲሆን ይዘቱም ማህበሩ በንግድ ሕግ ባለበት ኃላፊነት መሰረት የማህበሩን የሂሳብ ሚዛን ለአባላት አላቀረበም፤ ትርፍና ኪሣራም አላሳወቀም፡፡ በመሆኑም ማህበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያደረገውን እንቅስቃሴ የሚያሳዩ የሂሳብ ሪፖርት እንዲያቀርብ ትርፍና ኪሣራ ታይቶ ድርሻዬ ይሰጠኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16 ላይ ማህበር ነክ አለመግባባት በግልግል እንደሚታይ የተደነገገ ሲሆን ይህ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

የአሁኑ አመልካችም የፍ/ቤቱን ሥልጣን አስመልክቶ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በግልግል እንዲታይ የተስማማነው በማህበርተኞች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን እንጂ በማህበሩ ላይ የቀረበውን ክስ የሚመለከት አይደለም፡፡ ስለሆነም ሥልጣኑ የፍ/ቤት ነው በሚል ይዘት ማስተባበያውን በቃል ክርክር አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም በማህበርተኞች መካከል የሚነሱ ማህበር ነክ አለመግባባቶች የሚለው የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ በማህበሩና በማህበርቶኞች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን ሁሉ የሚመለከት በመሆኑ በግልግል ከሚታይ በቀር ፍ/ቤቱ ክርክሩን ለማየት ሥልጣን የለውም የሚል ዳኝነት ሰጥቶበታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤትም በዚሁ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ብይን አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም ክርክር ያስነሳው ጉዳይ በፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመለየት በሥር በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16 የተመለከተውን የደንብ ክፍል በአግባቡ አልተረጐሙትም፤የሚል ሆኖ በምክንያትነትም ክርክሩ የተነሣው በማህበርተኞች መካከል ሳይሆን በማህበርተኛ እና በማህበሩ መካከል ስለሆነ ደንቡ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ጉዳዩ በፍ/ቤት ሊታይ የሚችል ነው፡፡ በሚል የተጠቀሰው ይገኝበታል፡፡

እንዲሁም ወጭና ኪሣራን አስመልክቶ የአሁን ተጠሪ አቅርቦት የነበረው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ከተደረገ ተረቺ በመሆኑ የወጭና ኪሣራ መብታችን ሳይጠበቅ በአንፃሩ በሥልጣን ምክንያት የእኛን ክስ ውድቅ ሲያደርግ ለተጠሪ መብቱን መጠበቁና በተመሳሳይ መንገድ የእኛን መብት መንፈጉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 463 የተመለከተውን ድንጋጌ የሣተ የሕግ ስህተት ነው የሚለውንም ቅሬታ አቅርቧል፡፡

ተጠሪም የሥር ፍ/ቤቶች ሥልጣንን አስመልክቶ የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን ለማስረዳት የበኩሉን መልስ ዘርዝሮ ያቀረበ ሲሆን፤አመልካችም በመልሱ መልስ ላይ የጠበቃውን በጥብቅና ለመከራከር ያለውን የውክልና ሥልጣን የፀና አይደለም ስለሆነም መልሱ ዋጋ ያለው ባለመሆኑ የክርክሩ አካል ሊሆን አይገባም የሚለውን ሁሉ ጨምሮ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ለትርጉም መነሻ የሆነው፤በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16 ውዝግብ ለመፍታት በሚል ርዕስ በማህበርተኞቹ መካከል የሚነሱ ማህበር ነክ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ የፍ/ብሔር ህግና የሥነ-ሥርአት ሕግ ስለግልግል በተመለከተው ደንብ መሰረት ይወስናል፡፡ ውሳኔው አስገዳጅና የመጨረሻ ነው “በሚል ከተቀመጠው አንቀጽ” በማህበርተኞቹ መካከል የሚነሱ ማህበር ነክ አለመግባባቶች …” የሚለው ሐረግ በቀጥተኛው የሐረግ ትርጉም (literal meaning) የሚገደብ ነው ወይስ የተነሳው አለመግባባት ማህበር ነክ መሆኑ እስከተገለፀ ድረስ ከማህበሩ የሚመነጭ ማህበር ነክ አለመግባባት በማህበርተኞቹ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን በማህበሩና በማህበርተኞቹ መካከል አለመግባባት መነሳቱ አይቀሬ በመሆኑ “በማህበርተኞች መካከል” የሚለው ሐረግ በስፋት ታይቶ ሊተረጐም ይገባል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ስለሚያስነሳ ለትርጉም በር በማይከፍት ሁኔታ የተቀረፀ አንቀጽ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የትርጉም ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሚመራበት ደንብ የመነጨ በመሆኑ እና ይህ ደንብም በማህበርተኞች ስምምነት የሚወጣ በመሆኑ እንደማናቸውም በሕግ ፊት የፀና ውል እንደሚተረጐመው ይህም ደንብ ስለውሎች በጠቅላላው ሕግ በተቀመጠው የመነሻ_አተረጓጐም መርህ ሊታይ የሚችል ከመሆኑም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በላይ ይህን መሰል ደንብ ለመተርጎም ሊመራን የሚችል የተለየ ሕግ እስከሌለ ድረስ የስምምነት ዓይነት ምንም ይሁን ምን ስለውሎች በጠቅላላው የተመለከቱት ደንቦች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1676/1/ የተመለከተ በመሆኑ ጭምር ነው።

በመሆኑም ማህበር ነክ አለመግባባት በማህበርተኞች መካከል ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በማህበሩና በማህበሩ አባላት መካከል ጭምር የሚነሳ በመሆኑ አንቀጹን ቃል በቃል ካየነው በማህበሩና በማህበርተኞች መካከል ከማህበሩ የመነጨ አለመግባባት የተነሣ እንደሆነ እንደሌትና በማን ይታያል? የሚል ጥያቄ ከተነሣ በክፍተትነት የሚቀር በመሆኑ ይህንኑ በሚመለከት ጥያቄ ቢነሳ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1734 እንደተመለከተው በዚህ ነጥብ ላይ የማህበሩ አባላት የሐሳብ አንድነት (common interest of the members) ምን ሊሆን ይችላል? እንዲሁም ማህበር ነክ አለመግባባት የሚል ጠቅላላ አነጋገር በዚሁ አንቀጽ ላይ ተጠቅሶ እያለ ከማህበሩ ሊመነጭ የሚችለውን የአለመግባባት ዓይነት ወሰን የሚያጠብ "በማህበርተኞች መካከል" የሚል ቃል ቢገኝም ማህበርተኞቹ ማህበር ነክ አለመግባባት የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ የነበራቸው ሐሳብ ምን ነበር? የሚለውን ሁሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1735 ከተመለከተው አንፃር ማየት የሚያስፈልግ በመሆኑ ይህ ክርክር ያስነሳው አንቀጽ ከነዚህ ማዕዘኖች አኳያ ታይቶ ሊተረጎም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል።

የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ዝርዝር ይዘቱን ማየት እንደሚቻለው ማህበር ነክ ጉዳዮችን በተሟላ አኳኋን እንዲሸፈን ተደርጐ የተቀረፀ ሲሆን፤በስተመጨረሻ ከዚህ መሰል መተዳደሪያ ደንብ ሊመነጭ የሚችልን ውዝግብ እንዴት መፍታት እንደሚቻል አስቀድሞ ለማየት የደንቡ አካል በማድረግ በአንቀጽ 16 ላይ ከማህበሩ የመነጨን ማናቸውም ውዝግብ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፍትህ የማግኘት መብቱ በሕገ-መንግስቱም ሆነ አከራካሪ በሆነው በንግዱ ሕጉ ላይ የተከበረ መሆኑ እየታወቀ ውዝግቡ በሕግ መሰረት በግልግል እንዲታይና ይህም በግልግል ታይቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን በመግለጽ ማካተታቸው ማናቸውም ጉዳይ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ እንዲያልቅ ሐሳብ የነበራቸው መሆኑን የደንቡ ይዘት እና አቀራረጽ ስለሚያስረዳ፤

እንዲሁም ከማህበሩ የሚመጩት ውዝግቦች በማህበርተኞች መካከል ወይም በማህበሩና በአባላቱ መካከል ሊሆን እንደሚችል እየታወቀ የውዝግቡን ዓይነት በሁለት በመክፈል በማህበሩና በአባላት መካከል ከሆነ ግን ወደ ፍ/ቤት እንዲሄድ አስበው ነው ለማለት የተለዩ የግምት መነሻ የሆኑ ምክንያቶች ባለመገኘታቸው፤

በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16 ላይ ማህበር ነክ ውዝግብ የሚለው አባባል በማህበሩና በአባላቱ መካከል ጭምር ሊነሳ የሚችልን ክርክር ሁሉ የሚያጠቃልል ሊሆን ይገባል በሚል የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት በውል አተረጓጐም ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም።

በሌላ በኩል የዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ትርጉም ለመስጠት መነሻ ያደረገው በአመልካች የሰበር አቤቱታ እና በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ትርጉም መሰረት በማድረግ እንጂ የተጠሪን መልስ በመመርኮዝ ባለመሆኑ፤

እንዲሁም ስለተጠሪ ሆኖ ለመከራከር ለጠበቃው የውክልና ሥልጣን ሰጡ የተባሉት ሥራ አስክያጅ በማህበሩ ቃለ ጉባኤ ተሰጥቷቸው የነበረው የሥራ ዘመን አልቋል እንጂ በሌላ ሥራ አስኪያጅ ተተክተዋል በማለት ባለመሆኑ፤ ይልቁንም አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ በግልጽ እስካሁን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድረስ በሌላ ሥራ አስኪያጅ የአለመተካታቸውን የሚያስረዳ በመሆኑ ከጥብቅና ውክልና ጋር በተያያዘ ያነሱት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለወጭና ኪሣራ ጉዳይ ማን እንደሚከፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 እንደተመለከተው ለይቶ ለመወሰን ሥልጣኑ የፍ/ቤቱ በመሆኑና ይህንኑ ሥልጣኑን በዘፈቀደ የተጠቀሙበት ለመሆኑ ጠቋሚ እና አስረጂ በሆነ አኳኋን የቀረበ ክርክር ባለመሆኑ ወጭና ኪሣራ ማን ይክፈል የሚለውን በመወሰን ረገድም የሕግ ስህተት የተፈፀመ ሆኖ ስላላገኘው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁ. 6204 በ27/6/2001 እና በመ/ቁ. 79390 በ22/4/2002 የሰጡትን ብይን እና ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 መሰረት አጽንተናል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም ብለናል፡፡
   ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. *55311*

ህዳር *17* ቀን *2003* ዓ.ም

ዳኞች - ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች - ወ/ሮ ብርሃኔ አጥናፉ ጠበቃ መኮንን አራጋው ቀረቡ

ተጠሪ - ኢንስፔክተር ዩሐንስ ተሲላ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም ባቀረበው የክስ ማመልከቻ እና በተከሣሽ ማለትም በአሁን አመልካች መካከል በነበረን የተለየ ግንኙነት ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ በብድር እንድሰጣት ጠይቃኝ አበድራያታለሁ፡፡ ተከሣሽ ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የብድር ውል የፈረመች ሲሆን እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺ ብር/ ቀሪውን ብር 100,000 /መቶ ሺ ብር/ እስከ ሚያዚያ 5 ቀን 2002 ዓ.ም ሊከፍሉ ተስማምተዋል፡፡ በውሉ መሠረት ያልከፈሉ በመሆኑ በብድር የወሰዱትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርባ ከከሣሽ ጋር እንደባልና ሚስት በመሆን አብረን ስንኖር መግባባት ስላልቻልን ለመለያየት ስንወሰን ገንዘብ ካልሰጠሽኝ በስተቀር በማለት በእኔና በንብረቴ ላይ አደጋ እንደሚያደርስ ስላስፈራራኝ ገንዘብ ሣልበደር በግዳጅ ገንዘብ እንደተበደርኩ አድርጌ ፈርሜለሁ ስለሆነም ከከሣሽ /ተጠሪ/ የተበደርኩት ገንዘብ ስለሌለ እንድከፍል የምገደድበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለት ምስክሮችን ሰምቷል፡፡ አንደኛው ምስክር በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ሲከራከሩ እንደነበር ከዚያም ሣይስማሙ በመቅረታቸው ከጠበቃ ጋር ሄደው ሲጮሁ እንደነበርና አመልካች የእኔ ድርሻ ስተጠሪ እንዳይደርሰው ስትል እንደነበርና ተጠሪ የአንቺ ድርሻ እንዳይደርሰኝ ፈርሚ ሲል የነበረ መሆኑንና በመጨረሻ አመልካች ብር 200,000 ከተጠሪ ተበድራለሁ በማለት እንደፈረመች በመቅረቱ ተጠሪ ለአመልካች ብር 200,000 እንዳልሰጣት የመሰከረ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልፅ ያሰፈረ ሲሆን ሁለተኛው ምስክር አመልካችና ተጠሪ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደነበር የብድር ውል በተፈራረሙበት ቀን አመልካች ተጠሪን ከድርሻየ ጋር እንድትደርስ ስትል ተጠሪ አብረን ያፈራነውን ንብረት ድርሻየን እንዳገኝ ነው በማለት ይናገር እንደነበር ከዚያ በኃላ አመልካች የብድር ውል የፈረሙለት መሆኑን በመግለፅ እንደመሰከረ ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን እንደባልና ሚስት በኖርንበት ጊዜ ያፈራነውን የጋራ ንብረት ስጭኝ በማለት ሲጠይቅ የነበረ መሆኑንና አመልካች ከተጠሪ በደረሰባት ግፊትና ተፅዕኖ የተበደረችው ገንዘብ ሣይኖር ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ተበደሬለሁ ብላ የፈረመች መሆኑ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 በተደነገገው ሁኔታ የተደረገ ውል በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የለውም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል የክልሉ ጠቅላይ ፍድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በፈረመችው ብድር ውል መሠረት ተጠሪ ክስ ያቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ የመክፈል ግዴታ አለባት በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

አመልካች ሚያዚያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ እኔና ተጠሪ እንደባልና ሚስት በነበረን ግንኙነት አብረን የኖርን ሲሆን አስራ አንድ ዓመት የሆናት መክሊት ዩሐንስን ወልደናል፡፡ ሆኖም በመካከላችን በነበረው አለመግባባት ግንኙነታችንን ለማቋረጥ ስንወስን ገንዘብ ካልሰጠሽኝ በማለት በሥራው ምክንያት መንግስት ባስታጠቀው መሣሪያ በተለያየ ጊዜ እያስፈራራ ስላስቸገረኝ በብድር የወሰዱትት ገንዘብ ሣይኖር ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ እንደተበደርኩ በመግለፅ በፍራቻ ፈርሜለሁ ገንዘብ በወቅቱ ያልተበደርኩ መሆኔን በውሉ ላይ በምስክርነት የፈረሙት የተጠሪ ሁለት ምስክሮች ለሥር ፍርድ ቤት አስረድተዋል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ያላግባብ ተጨማሪ ማስረጃ በመቀበል የሰጠውና ህግን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በይግባኝ ሰሚው ችሎት የተፈፀመውን የህግ ስህተት ሣያርም ማለፉ ተገቢ ባለመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ውሉን ሲፈፅሙ የሀይል ተግባር የተፈፀመባቸው መሆኑን አላስረዱም አመልካች የፍታብሔር ህግ ስለብድር በሚደነግገው መሠረት ገንዘብ በብድር የወሰዱ መሆኑ በውሉ ሰነድ የተረጋገጠ በመሆኑ ብድሩን ላለመክፈል የሚያቀርቡት ክርክር የህግ ድጋፍና መሠረት የለውም፡፡ ስለዚህ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲያደርግልኝ የሚል ይዘት ያለው መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ ማስፈራራትና ዛቻ የፈፀመው ውሉ በተፈረመበት ቀን ሣይሆን ከዚያ በፊት አመልካች ላይ ከዚያ በፊት ሥነ ልቦናዊ ተፅኖ የሚያሣድሩ ተግባራትን በመፈፀም ነው አመልካች ያልተማርኩ በመሆኔና ተጠሪ የፖሊስ መኮንን በመሆኑ እኔን ስጋት ላይ የሚጥል ተግባር ሲፈፅም የቆየ ሲሆን ውሉ በሚፈረምበት ወቅትም በእኔና በአመልካች መካከል ጭቅጭቅ የነበረ መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ውሉን በሙሉ ፈቃድና ፍላጎቱ ያላደረግሁት በመሆኑ ልገደድበት አይገባም በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራቀኙ መካከል የተደረገው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በአመልካችና በተጠሪ መካከል ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም ያደረጉት የብድር ውል ህጋዊ ውጤትና አስገዳጅነት አለው ወይስ የለውም የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመመለስ አንድ ውል ህጋዊ ውጤት የሚኖረው በምን መንገድ ሲፈፀም ነው የሚለውን ነጥብ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በህግ ፊት የፀናና ህጋዊ ውጤት ሊኖረው የሚችለው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678 የተደነገጉትን ሶስት መሠረታዊ ሁኔታዎችን ሲያሟላ መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678 “የሚፀና ውል ነው ለማለት ሶስት ሁኔታዎች ያስፈልጉታል” በማለት ሁኔታዎቹን ከ”ሀ” እስ “ሐ” በዝርዝር ደንግጓል፡፡ በህግ ፊት የፀና ውል ለማቋቋም አስፈላጊ ከሆኑ ሁኔታዎች አንደኛ ውሉ ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል የተደረገና ተዋዋዩቹ ጉድለት በሌለው ሁኔታ የተስማሙበት ሲሆን እንደሆነ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1678 /ሀ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ብድር የወሰዱ መሆኑን በመግለፅ ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጣሪያ ምስክርነት ጠርቶ ቃላቸውን የተቀበላቸው ጠበቃ ባዘጋጁት የብድር ውል ላይ በማጣሪያ ምስክሩ ቢሮ ውስጥ መፈረማቸውን አልካዱም፡፡ አመልካች የሚከራከሩት በወቅቱ ብር 200,000 እንደተበደርኩ በሚገልፀው ሰነድ ላይ የፈረምኩት በሙሉ ፍላጎቴና ፈቃዴ አይደለም፡፡ ከተጠሪም ውሉን በምፈርምበት ጊዜም ሆነ ከዚያ በፊት በብድር የወሰድኩት ገንዘብ የለም ፡፡ ብድሩን የፈረምኩት ተጠሪ ሰነዱን ካልፈረምኩ በህይወቴና በንብረቴ ላይ የማይቀር አደጋ ወይም ጉዳት የሚያደርስብኝ መሆኑን በመግለፅ በተለያየ ጊዜ የማስፈራራትና የማስገደድ ተግባራትን ስለፈፀመብኝ ነው በማለት ነው፡፡

የማስገደድ ወይም የሀይል ሥራና ተግባር ስለተፈፀመበት አንድ ሰው አንድን ውል ለመዋዋል የተስማማ በሆነ ጊዜ ለውሉ የሰጠው ስምምነት ጉድለት ያለበት ስምምነት ተደርጎ እንደሚወስድና በህግ ፊት የፀና መብትና ግዴታ ለማቋቋም የማይችል ስለመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678/ሀ/ እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1809 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማንበብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አንደኛው ተዋዋይ ወገን ሌላውን ተዋዋይ ወገን ራሱን ወይም ወላጆቹን ወይም ተወላጆቹን ወይም ባልን ወይም ሚስትን ከባድና የማይቀር አደጋ በህይወቱ በአካሉ በክብሩ ወይም በንብረቱ እንደሚያመጣበት ያሳመነው በመሆኑ ምክንያት ውሉን ለመዋዋል የተስማማ እንደሆነ ውሉን በማፍረስ በቂ ምክንያት እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ እዚህ ላይ ሌላውን ወገን ውል እንዲፈፅም የሚያስገድደው ሰው የማስገደድ ተግባሩን የፈፀመውና ሌላውን ተዋዋይ ወገን ስጋት ላይ የሚጥሉ ተግባራትን የፈፀመው ውሉ በሚፈፀምበት ዕለት ወይም ከዚያ ውሉ ከተፈፀመበት ዕለት በፊት ሊሆን እንደሚችል ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የጣምራ ንባብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛው ተዋዋይ ሌላውን ተዋዋይ ወገን በውሉ ካልተስማማ በህይወቱ ወይም በንብረቱ ላይ የማይቀር አደጋ የሚያደርስበት መሆኑን ለማሳመን የሚችሉ የተለያዩ የማስገደጃና የማስፈራሪያ ተግባራትንና ዘዴዎች በመጠቀም በአእምሮው ተደላድሎ የነበረው ተዋዋይ ወገን ሌለው ተዋዋይ ከባድና የማይቀር አደጋ ሊያደርስብኝ ይችላል በሚል ስጋት ውሉን እንዲዋዋል ለማድረግ የሚችልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ውሉ ከመደረጉ በፊት የተፈፀሙ መሆኑን አለመሆኑን አንደኛ ተዋዋይ ወገን ሌላው ተዋዋይ ከባድና የማይቀር አደጋ ሊያደርስብን ይቻላል በሚል ስጋት ለውሉ ስምምነቱን የሰጠ መሆኑን ዳኞች በመገደድ ስምምነቱን የሰጠውን ሰው እድሜውን ዖታውንና አካኃኑን በማመዛዘን ውሣኔ መስጠት እንደሚገባቸው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ከተጠሪ ብር 200,000 መበደራቸውን የሚገልፅ ውል ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የፈረሙት በእርግጥ ከተጠሪ ተበድረው የወሰዱት በውሉ መጠኑ የተገለፀው ገንዘብ ስላለ ነው? ወይስ ተጠሪ የማይቀርና ከባድ አደጋ በህይወታቸውና በንብረታቸው የሚያደርስባቸው መሆኑን እንዲያምኑና ስጋት ላይ እንዲወድቁ ለማድረግ የሚችሉ የተለያየ ተግባራትና ዘዴ በመፈፀሙ ነው? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ልዩ ግንኙነትና ባህሪ የአመልካችን ዕድ የትምህርት ደረጃና የተጠሪውን ግላዊ ሁኔታና እና ሥልጣንና ኃላፊነት መመርመርና መመዘን እንደሚያስፈልግ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ እንችላለን፡፡

ከላይ ያስቀመጥናቸውን መሠረታዊ ሁኔታዎች ስንመዝን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጣሪያ ምስክርነት የሰማቸው ሁለት ሰዎች አመልካች በተጠሪ ምንም አይነት የማስገደድ ተግባር ሣይፈፀምባቸው እኛ ባለንበት የብድር ውሉን ፈርመዋል በማለት ውሉ በተፈረመበት ወቅት ብቻ ስለነበረው ሁኔታ የሰጡትን የምስክርነት ቃል መሠረት በማድረግ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች አልተገደዱም የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱ ከላይ የጠቀስነውን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ያልመዘነና ያልመረመረ መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሉ ከመፈፀሙ በፊት በተጠሪና በአመልካች መካከል የነበረውን ግንኙነትና የተጠሪ ምስክሮች አመልካችና ተጠሪ ወደ ሁለተኛው የማጣሪያ ምስክር ቢሮ ከመሄዳቸው በፊት ሲለዋወጡት የነበረው ሃሳብና ንግግርን መመዘንና መመርመር ይገባው ነበር አመልካችና ተጠሪ እንደባልና ሚስት አብረው ለረዥም ጊዜ የኖሩ እና የአስራ አንድ ዓመት ሴት ልጅ ወልደው ያሣደጉ መሆናቸው በግራቀኙ የተካደ ፍሬ ጉዳይ አይደለም እንደባልና ሚስት በመተማመን የኖሩት አመልካችና ተጠሪ በመካከላቸው በተፈጠረው አለመግባባት ግንኙነታቸውን ለማቋረጥ ለየብቻቸው ለመኖር ሲወስኑ በመካከላቸው አለመግባባትና ቅሬታ ተፈጥሮ የነበረ በመሆኑ የብድር ውሉ ተፈረመ በተባለበት ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የዕርቅ ስምምነት ውል አድርገው የነበሩ መሆኑና በውሉም በጋራ በቆየንበት ጊዜ የተፈራ የጋራ ሀብት በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘነው ንብረት የለም በማለት ተስማምተው የነበረ መሆኑ አመልካችና ተጠሪ ካቀረቡት ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ወደ ሁለተኛው የፍርድ ቤት የማጣሪያ ምስክር ቢሮ ከመሄዳቸው በፊት የእኔን ድርሻና ንብረት እንዳትወስድ እያለች አመልካች ትናገር የነበረ መሆኑና አመልካች ብር 200,000 ተበድሬያለሁ ብላ ከመፈረሟ በፊት ይከራከሩና ሃሳብ ይለዋወጡ የነበሩት ስለብድር ገንዘብ ሣይሆን ስለጋራ ንብረት እንደነበር የከፍተኛው ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃላቸውን የሰማቸውና የሰጡትን የምስክርነት ቃል ተዓማኒነት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልፅ አስፍሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ብር 200,000 ተበድሬአለሁ ብላ ከመፈረሟ ውጭ በዕለቱ ተጠሪ በብድር የሰጣት ጥሬ ገንዘብ ቼክ ወይም ሐዋላ የሌለ መሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቃላቸውን የሰማቸው የተጠሪ ምስክሮችና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰማቸው የማጣሪያ ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡

ተጠሪ መርማሪ ፖሊስ በመሆኑ አመልካችን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሰማቸው የማጣሪያ ምስክሮች ፊት ውሉን ፈርሚ ብሎ ለማስገደድ የሚሞክርበት ሁኔታ የለም ምክንያቱም ተጠሪ ድርጊቱ በህግ ፊት የሚያስተለውን ህጋዊ ውጤት ጠንቅቆ የሚያውቅ ከአመልካች የተሻለ የህግ ዕውቀትና ግንዛቤ ያለው በመሆኑ ከአመልካች ጋር እንዳባልና ሚስት ስንኖር ያፈራነው የጋራ ሀብት አለ ብሎ በህግ ፊት ተከራክሮ ለመፍታት የሚያስችለው ማስረጃ አለመኖሩን በመረዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የብድር ውል እንዲፈፅሙ ያደረገ መሆኑን ከላይ ከገለፅናቸው ሁኔታዎች ለመገንዘብ ይቻላል የብድር ውሉ አመልካች ከሚኖሩበት ከተማ ውጭ መደረጉ የአመልካችን ክርክር የሚያጠናክር ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ውሉን ስትፈርም ተጠሪ አላስገደዳትም ወይም አላስፈራራትም የሚለውን የማጣሪያ ምስክሮች ቃል በመስማት ብቻ አመልካች የብድር ውሉን ተጠሪ እንድትፈፅም አላስገደዳትም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706/3/ በሚደነግገው መሠረት ውሉ ከመፈረሙ በፊት አመልካችና ተጠሪ ያደረጉትን የዕርቅ ስምምነት እንደዚሁም ወደ ሁለተኛው ማጣሪያ ምስክር ቢሮ ከመሄዳቸው በፊት ሃሳብ እየተለዋወጡ ሲከራከሩ የነበሩት በብድር ስለተወሰደ ገንዘብ ሣይሆን አብረው ሲኖሩ በጋራ ያፈሩት ንብረት አለ ወይም የለም በሚለው ነጥብ ላይ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ አመልካች የማስፈራራትና የማስገደድ ተግባራት የተፈፀመባት መሆኑን አላስረዳችም በማለት ያቀረበውን ክርክር ስንመለከተው አመልካች የብድር ውሉ በህግ ፊት የማይፀናና ፈራሽ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ እንዳለባቸው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2001 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ቢሆንም በህግ ፊት የሚፀናና ጉድለት የሌለበት የብድር ውል ያለ መሆኑን ለማስረዳት ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2001 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ያቀረባቸው ምስክሮችና በአጠቃላይ ሌሎች የአካባቢ ሁኔታዎች አመልካች ከተጠሪ ብር 200,000 በሙሉ ፍላጎትና ፈቃዳቸው ያልተበደሩና በተቃራኒው ተጠሪ አብረን ስንኖር ያፈራነው የጋራ ገንዘብ ያለኝ በመሆኑ በብድር መልክ ድርሻየን ፈርሚ በማለት የተለያዩ የማስገደጃና የማስፈራራት ተግባራትን በመፈፀም የብድር ስምምነቱን እንዲፈርሙ ያደረጉ መሆኑን የሚያረጋግጡ መሆናቸውን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገጉትን ሁኔታዎች በማመዛዘን ከድምዳሜ ላይ የደረሰ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ በኩል ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ አመልካች የብድር ውሉን ለማፍረስ በሁለት ዓመት ያልጠየቁ መሆኑን ገልፆ የተከራከረ ቢሆንም ይኸ የተጠሪ ክርክር ውሉን ለመፈፀም እንቢ ለማለት የማይፈልገው ወገን ውሉ የማይረጋ መሆኑን በማናቸውም ጊዜ መቃወሚያ ሊያደርገው እንደሚችል በግልፅ የሚደነገግውን የፍታብሔር ህገ ቁጥር 1809 መሠረት ያላደረገ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት እና ሰበር ችሎት በአመልካችና ተጠሪ በመካከላቸው የነበረውን ልዩና ጥብቅ ግንኙነት አመልካችና ተጠሪ በመካከላቸው የነበረውን ግንኙነት ለማቋረጥ ያደረጉትን ስምምነትና ውሉ የአመልካች መኖሪያ በሆነው ቢሸፍቱ ከተማ ሣይሆን የተጠሪ መኖሪያና የሥራ ቦታ በሆነው አዳማ ከተማ የተደረገ መሆኑን የአመልካችን ዕድና የትምህርት ደረጃና የተጠሪን የትምህርት ደረጃ ሙያና ስልጣንና ሀላፊነት እንደዚሁም የብድር ውሉን ከማፀፋቸው በፊት ሲከራከሩበት የነበረውን መሠረታዊ ጉዳይ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1706 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው መሠረት ሣያመዛዝኑ አመልካች ለተጠሪ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ከነወለዱ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሰበር ችሎት እና የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንተነዋል፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ ግንቦት 16 ቀን 2000 ዓ.ም የተፈራረሙት የብድር ውሉ ተጠሪ በሙሉ ፈቃዳቸው ስምምነታቸውን ያልሰጡበት ጉድለት ያለውና በህግ ፊት የማይፀናና ውጤት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች - ዶ/ር ሰሎሞን ነጋሽ ዶ/ር ዘውድነህ በየነ ቀረበ

ተጠሪ - የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ መላት ያዛቸው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ሰበር ችሎት እንዲወሰን ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ቀደም ሲል በተደረገው ውል መሠረት የግልግል ዳኛ በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲመረጥ አመልካች አቅርቦት የነበረውን ጥያቄ የሚመለከት ነው አመልካች ጥያቄውን ያቀረበው ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ፍ/ቤቱ ተጠሪን አስቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ከማድረጉ በፊት ጥያቄው በፍ/ቤት የሚስተናገድ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 231 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ መዝገቡን ዘግቶአል ጉዳይ በይግባኝ የቀረበለት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበት ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 14 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ለአመልካች ክስ መሠረት የሆነው በሁለቱ ወገኖች መካከል የተደረገ ውል መሆኑ እስካላከራከረ ድረስ እንደውሉ ጉዳዩ በግልግል ያልቅ ዘንድ የፍ/ቤትን እገዛ በመጠየቅ የቀረበው ክስ በማያስከስስ ነገር ላይ የቀረበ ነው በማለት ሳይስተናገድ የመቅረቱን አግባብነት ለመመርመር ነው በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ትዕዛዝ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተው በመሃከላቸው የተደረገውን ውል መነሻ በማድረግ ነው ውሉ ነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገ የማማከር አገልግሎት የመስጠት እንደሆነም በክርክሩ ተመልክቶአል በሌላ በኩል ደግሞ የውሉን አፈፃፀም በሚመለከት በመሃከላቸው አለመግባባት ቢፈጠር እና አለመግባባቱን በድርድር መፍታት ካልተቻለ ሁለቱ ወገኖች በሚያቋቁሙት የግልግል ዳኝነት እንደሚታይ ስምምነት ስለመደረጉ ግራቀኝ ወገኖች አልተካካዱም አመልካች ወደክስ ያመራው ተጠሪ በውሉ መሠረት ለመገዛት ፈቃደኛ አልሆነም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ሲሆን የጠየቀው ዳኝነትም ተጠሪ በውሉ በገባው ግዴታ መሠረት የግልግል ዳኛ እንዲመርጥ ይገደድልኝ የሚል ነው፡፡

እንደሚታየው አመልካች እና ተጠሪ በመሃከላቸው ያቋቁሙትን መብት እና ግዴታ የሚገዛ ውል አድርገዋል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1731 እንደተደነገገው በሕጉ አግባብ የተቋቋመ ውሉች ባቋቋሙዋቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው ከሣሽ የሆነው ወገን ተጣሰብኝ የሚለውን መብት ለማስከበር ዳኝነት የሚጠይቀው የመብቱን ምንጭ ወይም መሠረት ውል ወይም ህግ እንደሆነ በማረጋገጥ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 33/2/ አነጋገር ከሣሽ ከተከሣሽ ላይ የሚጠይቀውን ጥቅም ወይም መብት በማረጋገጥ አቤቱታውን ያቀርብ ዘንድ ይጠበቅበታል ሲባልም የመብቱ መሠረት ሕግ ወይም ውል መሆኑን በግልጽ ማሳየት አለበት ማለት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪ ይፈጽምልኝ የሚለው ግዴታ መሠረቱ ውሉ እንደሆነ አሳይቶአል ተጠሪም ለአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ እንደገለጸው ስለውሉ መደረግም ሆነ ስለይዘቱ የሚክደው ነገር የለም፡፡ ክርክሩ ተከሣሽ የመንግስት መሥሪያ ቤት በመሆኑ ጉዳዩን በግልግል እንዲጨርስ በሕግ አይገደድም የሚል እንደሆነም ከዚሁ መልሱ ይዘት ተገንዝበናል፡፡

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የክሱን መዝገብ የዘጋው ተጠሪን ሳያስቀርብ እንደሆነ ከላይ ተገልጾአል፡፡ መዝገቡን ሊዘጋ የቻለውም አመልካች የክስ ምክንያት የለውም በማለት ነው ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤትም በተመሳሳይ ሁኔታ ይግባኙን ሰርዞአል በመሆኑም ይህ የሰበር ችሎት በዚህ ደረጃ ሊያይ የሚገባው አመልካች ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት የተሰጠው ትዕዘዝ አግባብነት ያለው ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ በመሆኑ ተጠሪ በግልግል ዳኝነት ጉዳዩን እንዲጨርስ የሚለውን የሥረ ነገር ክርክር የምንመረምርበት አግባብ የለም፡፡ ወደያዝነው ጭብጥ ስንመለስም አመልካች በክሱ ላይ የገለጸው ጉዳይ /ነገር/ የክስ ምክንያት የሌለው /የማያስከስስ/ ነው የሚባል ባለመሆኑ አቤቱታ የቀረበበት ትዕዛዝ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 39576 ሚያዚያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና በአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ 29491 ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. አመልካች ውሉን መሠረት በማድረግ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ሳይስተናገድ መቅረቱ በአግባቡ አይደለም ብለናል፡፡ ስለዚህም የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን ለተጠሪ እንዲደርስ በማድረግ እና ግራቀኝ ወገኖች በክሱ ስረ ነገር የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኃላ ተገቢውን ይወሰን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 341/1/ መሠረት ወስነናል፡፡

3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 56682

ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ አንዋር አብዱራማን

2ኛ አብዱልቃድር አብዱራማን

3ኛ መሐመድ አብዱራማን

4ኛ ከሊፍ አብዱራማን

5ኛ አይሻ አብዱራማን

6ኛ ሂቦ አብዱራማን

7ኛ ሳሚያ አብዱራማን

8ኛ ናሬሳ አብዱራማን

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ ግራ ቀኙ ከቀጠሮ በፊት ካቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ጋር መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ግራ ቀኙ የመያዣ ውል አደራረግ ሥርዓትን አስመልክቶ ያቀረቡትን የህግ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁኑ ተጠሪዎች አባታችን ሳያውቀው በድብቅ የተደረገ የመያዣ ውል ስለሆነ ያስረክብልን ይሰረዝልኝ ይለቀቅልን የሚል ክስ በአሁን አመልካች ላይ በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት በማቅረባቸው ሲሆን የአሁን አመልካችም ባንኩ ለዮሴፍ አብርሃም ለሰጠው የብድር ገንዘብ ከአባታቸው ጋር ሐምሌ 14 ቀን 1987 ዓ.ም በተደረገ የመያዣ ውል መነሻ እንጂ ከሳሾች እንደሚሉት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ይህ አከራካሪ የሆነ የመያዣ ውል በኦሮሚያ ከተማ አስተዳደር ተመዝግቦ እንደማይገኝ የከተማው አስተዳደር ምንም ዓይነት ማስረጃ እንደሌለ አረጋጋጧል፡፡ አከራካሪ በሆነው የመያዣ ውል ላይ የተቀመጠውን ፊርማ የአባታቸው ስለ መሆኑ ማረጋገጥ እንዳይቻል ባንኩ የአሁን አመልካች ማገናዘብያ የሚሆን የተለያዩ ማስረጃ ለማቅረብ አልቻለም፡፡ ዋናውን የመያዣ ውል ማቅረብ ባለመቻሉ ያቀረበው ኮፒ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2011 ሥልጣን ባለው አካል ፊት ካልተረጋገጠ ተቀባይነት የለውም፡፡

ስለሆነም የመያዣ ውሉ በፍ/ብ/ስ/ሕ/ቁ 1723 መሠረት በአዋዋይ ፊት ያልተረጋገጠ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3052 መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ ስላልተመዘገበ አደራረጉ የሕግ መስፈርትን አላሟላም በመሆኑም ውድቅ ነው፡፡ ካርታው ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ የተጠሪዎች አባት በህይወት እያሉ እኔ ሳላውቀው ካርታ ይዞብኛል በማለት ከአሁን አመልካች ጋር ስለተከራከረ የመያዣ ውል ምዝገባ ሥርዓት አስፈላጊ አልነበረም በህይወት እያሉ በመያዣ ውሉ ላይ አልፈረምኩም በማለት ስለተከራከሩ ዋናው አከራካሪ ነጥብ ፊርመዋል ወይስ አልፈረሙም የሚለው ነበር ይህንን ነጥብ ለመለየት የአሁን አመልካች ዋናውን ሰነድ አላቀረበም የእራሱን ሰነድ በሥርዓት መያዝ ግዴታው ነው ያቀረበው ኮፒ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቻልበት መንገድ የለም፡፡ የሚለውን ተችቶ በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ወሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከዚህ በላይ በአጭሩ እንደተገለፀወው በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ነው ያቀረበውም ምክንያት ዋናው የመያዣ ውል ሊገኝ ባይችልም ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ኮፒ አቅርበናል፡፡ በዚህ ሰነድ ላይ የሰፈረን ፊርማ መካድ እንደማይቻል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2011 ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ በአግባቡ አልተተረጐመም የሚለውን ነው፡፡

ተጠሪዎችም ለዚህ የሰበር ቅሬታ መልሳቸውን በጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን በግራ ቀኙ መካከል ለተነሣው አከራካሪ ነጥብ መነሻ የሆነውን የኮፒ ሰነድ ጉዳይን አስመልክቶ የአሁን አመልካች በሰበር ቅሬታው ላይ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተረጋገጠ ኮፒ አቅርቤያለሁ ለሚለው ክርክር ዋናውን ቅጅ ማቅረብ እንደማይቻል በዚህ ሰበር ደረጃም አረጋግጧል፡፡ ቢኖረው ኖሮ በሚመለከተው ማዘጋጃ ቤት ይቀመጥ ነበር እራሱም ዋናውን መያዝ ነበረበት ይህ ሁሉ ሳይሆን በሰጡት ሰነድ ይወሰንልኝ ማለቱ አግባብ አይደለም በማለት ተከራክረዋል ፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነውም በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ እንዳደረጉት ክርክር የአሁን አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ጉዳዩን ለማስረዳት ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተረጋገጠ ኮፒ አቅርቦ እንደነበር የሚያስረዳ ሲሆን ይህንንም የሚያጠናክረው በሥር በሁለቱም ደረጃ በተደረገው ክርክር አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2008 መሠረት አከራካሪ የሆውን የመያዣ ውል ሰነድ ኮፒ አቅርቦ እንደነበረ በሁለቱም ውሳኔዎች ተመዝግቦ የመገኘቱ ጉዳይ ነው፡፡ የዚህን ክርክር ያስነሳው የመያዣ ውል ዋናው ኮፒ ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ተጠሪዎች ሦስተኛ ወገን ናቸው እንኳ ቢባል ይህ የመያዣ ውል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት እስከተረጋገጠ ድረስ የሰነዱን ይዘቱና ፊርማን ጨምሮ በማናቸውም መንገድ ቢሆን ሊቃወሙት እንደማይችሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2009 ላይ ተመልክቷል ይህ ዋናው ሰነድ መቅረቡ ቀርቶ የዚህ ሰነድ ትክክለኛ ቅጅ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተረጋግጦ ከቀረበ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2011 እንደተመለከተው በማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዋጋነቱ እንደ ዋናው የተረጋገጠ የመያዣ ሰነድ የሚያገለግል እንጂ ክርክር የቀረበለት ፍ/ቤት ዋናውንና ቅጂውን ሁለቱንም በማስቀረብና በማስተያየት ቅጅው ያለውን የማስረጃ ዋጋ የሚመረምርበት የህግ አግባብ የለም በዚህ መንገድ የማረጋገጥ ተግባሩ አይከናወንም፡፡ ዋናውና መሠረታዊ የሆነው ጉዳይ ለማስረጃነት የቀረበው ኮፒ ከዋናው ጋር በማገናዘብ ሥልጣን ባለው አካል ፊት ትክክለኛ ግልባጭ ስለመሆኑ በኮፒው ላይ ተገልፆ የመገኘቱ ሁኔታ ነው፡፡

በመሆኑም የመያዣ ውል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተደርጎ ለማስረጃነቱ ዋናው ሰነድ ባልተገኘ ጊዜ በምትኩ ኮፒ ሲቀርብ የዚህ የዋናው ሰነድ ግልባጭ ስለመሆኑ እራሱ ሰነዱ ሥልጣን በተሰጠው አካል ማረጋገጫ ተደርጉበት የሚናገርሆኖ ከተገኘ ከላይ በተጠቀሰው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2011 መሠረት በእራሱ በቂ ማስረጃ ሆኖ እያለ ለዚህ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተረጋግጦ የቀረበን ኮፒ ብቸኛው ማረጋገጫ ዋናው ሰነድ እንደሆን ተደርጎ የተሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በመ/ቁ 9452 በ19/12/2000 እና በመ/ቁ 84422 በ29/18/2002 የሰጡትን ፍርዶች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕቁ 348(1) መሠረት ሽረናል፡፡

ሐምሌ 14 ቀን 1987 ዓ.ም በተፃፈ የተደረገው የመያዣር ውል በተጠሪዎች አባት ስለመደረጉ አመልካች በህግ መሠረት ያረጋገጠ ስለሆነ ዋጋ ያለው በመሆኑ በዚሁ በአንድ ላይ የተገለፀው ንብረት ካ ርታ ለተጠሪዎች ሊለቀቅ አይችልም ብለናል፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ላደረጉት ክርክር ወጪና ኪሣራውን በየእራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48857

ታህሳስ 12 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ነ/ፈጅ ፈያራ ገለታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 አስተዳደር ጽ/ቤት የቀረበ የለም፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውሃ አገልግሎት ሂሳብ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ በቀድሞ ወረዳ 07/ቀበሌ 27 አስተዳደር በቤት ቁጥር 436 ነዋሪና ባለቤት የነበሩት አቶ ግርማ ወ/ሚካኤል በ15/07/1950 በውል ቁጥር 12085 ከአመልካች መስሪያ ቤት ጋር ባደረጉት የውል ስምምነት አገልግሎት እያገኙና የውሃ ሂሳብ ሲከፍሉ የቆዩ መሆኑን የተጠቀሰውን ቤት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ወርሶ በቀድሞው ባለሃብት እግር በመተካት የውሃ አቅርቦት አገልግሎት ሲጠቀም የቆየ ቢሆንም የህዳር ታህሳስና ከሐምሌ 1992 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 1993 ዓ.ም ድረስ የተጠቀመበትን የውሃ ፍጆታ ክፍያ አለመክፈሉን ገልጾ ብር 556.79 (አምስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከሰባ ዘጠኝ ሳንቲም) እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በመልሱም አመልካች ክስ ለመመስረት የሚያስችለው የውል ወይም የሕግ ግንኙነት የሌለው መሆኑን ክሱም በይርጋ የሚታገድ መሆኑንና ሂሳቡ ካልተከፈለ ደንበኝነቱን ሳያቋርጥ ቆይቶ ክስ መመስረቱ አግባብ አለመሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትም የተጠሪን የክርክር ነጥቦች ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ተጠሪን ለክሱ ኃላፊ አድርጐ ለክሱ መሠረት የሆነውን ገንዘብ (ብር 556.79) እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የውሃ ፍጆታ ክፍያ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ጉዳዩ በሰበር አቤቱታ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጳጉሜ 05 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ድንጋጌና የደንብ ቁጥር 31/1994 ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው እንዲሻር እና ተጠሪ የውሃ ፍጆታ ሂሳቡን እንዲከፍል ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚየሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀረቦ በነገረ ፈጁ አማካኝነት የፁሑፍ መልሱን ሰጥቷል። የአመልካች ነገረ ፈጅም የመልስ መልሱን አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ዋናው የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጉዳይ፡- የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ ለውሃ ፍጆታ ሂሳቡ(ገንዘብ) አግባብነት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል።

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብ (Legal Presumptions) የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት (not freely rebuttable or rebuttable but in a limited way) የሕግ የህሊና ግምት ነው። የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 የተለያዩ የክፍያ አይነቶችን የሚዘረዝር ሆኖ በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች (እዳዎች) በዚሁ የሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠየቁ የቀሩ እንደሆኑ ክፍያውን (እዳውን) የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ (እዳ) እንደከፈለ የሕግ ግምት እንደሚወሰድበት ያስገነዝባል። ድንጋጌው የውሃ ፍጆታ ሂሳቡን ለይቶ አላስቀመጠም።

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ ተብሎ በተጠሪ የሚጠቀሰውን በስር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘው በፍ/ሕ/ቁጥር 2024 ድንጋጌ በፊደል (ረ) ስር የተመለከተው የክፍያ ግምት ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠ ነው።

ቁ. <u>2024 በሁለት አመት የተወሰነ ጊዜ</u>

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው፡-

(ረ) በብድር ለተሰጠ፣ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ውሳኔ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ነው። የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛ ቅጂም፡-

Art. 2024 presumption of payment after two years

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(f) interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical intervals. በሚል ተቀምጧል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፖራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት አመት ያለፋቸው እዳዎች (ክፍያዎች) እንደተከፈሉ ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታይ የተዘረዘሩት ንዑስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሚወሰንባቸውን የክፍያ (እዳ) ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ በድንጌጋው ፊደል (ረ) ስር የተመለከተው ሲታይ በብድር የተሰጠ ወይም ለማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከአመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች (እዳዎች) ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው በብድር ለተሰጠ የገንዘብ ወለድ ላይ ሲሆን ዋናው የብድር ገንዘብን የማይጨምር መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና አቀራረጽ ያስገነዝባል፡፡ ምክንያቱም ድንጋጌው ዋናውን የብድር ገንዘብ የሚጨምር ቢሆን ኖሮ የብድር ገንዘብና ወለድ በማለት ያስቀምጠው ነበር እንጂ ለብቻው ነጥሎ የብድር ገንዘብ ወለድን በማለት አይጽፈውም ነበር፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ ችሎት በሰመ/ቁጥር 29181 እና የሠ/መ/ቁጥር 35758 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ አግባባነት የሚኖረው ለብድር ገንዘብ ወለድ እንጂ ለዋናው የብድር ገንዘብ አይደለም፣ የውሃ ፍጆታ ሂሳብም ብድር ባለመሆኑ ከመነሻውም ድንጋጌው አግባባነት ሊኖረው አይችልም፡፡

ሌላው ስለክፍያ ግምት የሚያወሳው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 ሲሆን ይህ ድንጋጌ የስድስት ወር ጊዜ ማለፉ ክፍያው እንደተፈጸመ ያስቆጥራል በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የስድስት ወር ማለፍ ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥርባቸው ሁኔታዎችን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የወርሃዊ የውሃ ፍጆታ ሂሳብ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2022 ድንጋጌ ሲታይም የተከፈለው እዳ ወለዶችን ወይም በተወሰነው ጊዜ የሚከፈሉትን ሌሎች የክፍያ ድርሻዎችን የሚመለከት እንደሆነ የተከፋዩን አይነት ለይቶ ሳይገልጽ ለአንዱ የክፍያ ደረሰኝ የሰጠ ባለገንዘብ ያለፈውንም ድርሻ እንደተቀበለ ይቆጠራል በማለት በንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ያስቀመጠ ሲሆን ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በዚህ ድንጋጌ መሠረትም ሊታይ የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው ተጠሪ ለክርክሩ መሠረት ያደረገው የደንብ ቁጥር 31/1994 አንቀጽ 19(1) ድንጋጌን ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በክፍያ ምክንያት የውሃ አቅርቦት ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ደንበኛው የአገልግሎት ክፍያ ካልፈጸመ የደንበኝነት ውሉ ተሰርዞ ደንበኛው ለዋስትና ያስያዘው ተቀማጭ ገንዘብ ለአመልካች መስሪያ ቤት ገቢ የሚደረግበትን አግባብ ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌው በአመልካችና በደንበኛው መካከል ስለሚኖረው የወደፊት ግንኙነትና አመልካች ሊወስደው ስለሚችለው እርምጃ ከሚያሳይ በስተቀር ደንበኛው ለተጠቀመበት የውሃ አገልግሎት ያልተከፈለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሂሳብ ካለ አመልካችን ለመጠየቅ አይችልም የሚል መንፈስ የለውም፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለው ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የውሃ ፍጆታ ሂሳብ ከመሰረቱ ብድር አይደለም፣ የብድር ባህሪም የለውም፡፡ የውሃ ፍጆታ ሂሳብ አመልካች ለህብረተሰቡ በሚያቀርበው አገልግሎት መሠረት የሚከፈል ሲሆን መሰረቱም ውል ነው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረበው በክሱ ላይ በተመለከተው ቤት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት እያስተዳደረው በመሆኑ በቤቱ ለተጠቀመበት ውሃ ተጠሪ ክፍያ እንዲፈጽም ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱን በተጠቀሰው ሕግ ተረክቤ አላስተዳድርም የሚል ክርክር የሌለው ሲሆን በቀድሞው ባለቤት ስም የገባው የውሃ ቆጣሪ ሲነሳም ችግሩ እንደደረሰበት ገልጾ ቆጣሪው እንዲመለስለት ጠይቆ ቆጣሪው የተመለሰለት መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ክርክር ከአመልካች ጋር የውሃ አቅርቦት ውል አልፈፀምኩም የሚል ሲሆን ከላይ እንደተመለከተው በስር ፍርድ ቤት ቤቱን በሕግ ተረክቦ የሚያስተዳድረው መሆኑ ካለመካዱም በተጨማሪ የውሃ ቆጣሪውን አመልካችን ጠይቆ መውሰዱ የተረጋገጠ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 235 መሠረት ጉዳዩ እንደታመነ የሚቆጠር ነው፡፡ በመሆኑም የውሃ አቅረቦቱ ተጠሪ ቤቱን በሕግ አግባብ ተረክቦ የሚያስተዳድረው እስከሆነ ድረስ መብትና ግዴታው በሕግም ሆነ በውል ለተጠሪ መተላለፉ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ ለውሃው ፍጆታ የማይጠየቅበት አግባብ የለም፡፡ ክፍያውን ስለመክፈሉ ደግሞ ተጠሪ ገልፆ የተከራከረው ነገር የለም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ተጠሪ የክፍያ ግምት ተጠቃሚ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለውሃ ፍጆታ አገልግሎት ሂሳብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) እና የደንብ ቁጥር 31/1994 ድንጋጌዎችን መሠረት ማድረጋቸው ያላግባባ በመሆኑ እና ተጠሪም በሕጉ አግባባ ለሚያስተዳድረው ቤት የውሃ ፍጆታ ክፍያውን ለመክፈል ከሕግና ከውል የመነጨ ግዴታ ያለበት በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03172 ሚያዝያ 05 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 10318 ሐምሌ 17 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/09 ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2602 ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
3. የውሃ ፍጆታ ሂሳብ ይከፈለን ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2022 መሠረት የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበበት ከሆነ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር በተመለከተው የሕሊና ግምት የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡
4. ተጠሪ ብር 556.79 (አምስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከሰባ ዘጠኝ ሳንቲም) ለአመልካች እንዲከፍል ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ሂጦስ የገበሬዎች የህ/ሥ/ማህበር - የቀረበ የለም

ተጠሪ ፡- የመሥራቅ ዱቄትና ፋብሪካ - "

መዝገቡ የተቀጠረው ለጉዳዩ አወሳሰን እንዲረዳ ይቅረብ የተባለው የሥር የመጀመሪያ ደረጃ መዝገብ ቁጥር 6059 አለመቅረቡን አስመልክቶ ተገቢውን ትዕዛዝ ለመስጠት በሚል ነበር፤ ይሁን እንጂ ይኸው መዝገብ ዘግይቶም ቢሆን የቀረበ ስለሆነ ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ግራ ቀኙ እንደአደረጉት የስንዴ ሽያጭ ውል ሳይፈፀም የቀረው በየትኛው ተዋዋይ ወገን ጉድለት ነው የሚለውን ነጥብ በውሉ ከተመለከተው የሻጭና የገዥ መብትና ግዴታ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ግራ ቀኙ ስለጉዳዩ ካቀረቡት ክርክርና ማስረጃ አንፃር ለይቶ ከሚያስከትለው ውጤት ጋር ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች የሂጦስ ገበሬዎች የህ/ሥ/ማህበር ያቀረበው ክስ ሲሆን፤ ይዘቱም

ታህሳስ 26 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገ የስንዴ ግዥና ሽያጭ ውል መሠረት በየጊዜው ለማስረከብ ከገባነው 4000(አራት ሺህ) ኩንታል ስንዴ ውስጥ እስከ ጥር 27 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ በድምሩ 1020(አንድ ሺህ ሃያ) ኩንታል አስረክበናል፡፡ ለዚሁ ለተረከበው ገዥ ዋጋውን አልከፈለም፡፡ እኛም የማስረከቡን ተግባር በማቆም ክፍያ እንዲፈፅም ብንጠይቀው እንደጥያቄው ባለመፈፀሙ ርክክቡ ዘገየ፡፡ የስንዴም ዋጋ በነዳጅ ዋጋ ጭማሪ የተነሣ ጨመረ፡፡ ይህንም የስንዴ ዋጋ ጭማሪ እራሱ በሰጠን ማስታወቂያ ጭምር አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በእራሱ የክፍያ ግዴታ ባለመፈፀም ተግባር ውሉ ቀሪ ሆኖ ላስረከብነው የስንዴ ዋጋ ብር 168,300(አንድ መቶ ስድሳ ስምንት ሺህ ሦስት መቶ ብር) ከእነ ወለዱ ጋር ይክፈል የሚል ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በተከሳሽነት የሰጠው መልስ የክፍያ ጥያቄ አቅርቦ አልተከለከለም፡፡ ውሉ ከተደረገበት ስንዴውን እስከሚያስረክብበት ድረስ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ አልተደረገም ለማስረከብ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አልቻልኩም በማለት የገለፃቸው ምክንያቶች በህጉ መሠረት እንደአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች አይቆጠሩም፡፡ ስለሆነም ስንዴውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማቅረብ እንቢተኛ ሆኖ ያስረከበውን ስንዴ ዋጋ ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት መልሷል፡፡

እንደገናም የተከሳሽ ከሳሽ ሆኖ ተከሳሽ እንደውሉ ለማስረከብ በገባው ግዴታ መሠረት ባለማስረከቡ ባልተረከብነው 2980 ኩንታል ልክ የስንዴ ዋጋ በዚያው ጭማሪ የብር 447,000(አራት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ብር) በልዩነት ጉዳዩ ደርሶብናል፡፡ ስለሆነም ቀሪውን 2980 ኩንታል ያስረክበን፤ ወይም ይህንኑ የዋጋ ልዩነት በጉዳት ኪሣራ ይክፈለን የሚል አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የአሁን አመልካች ለዚሁ የተከሳሽ ከሳሽ አቤቱታ የሰጠው መልስ ፍሬ ቃል

ለማስረከብ የገባሁት ስንዴ እኔ የማመርተውን ሳይሆን ከማህበሩ አባላት ወይም ከአርሶ አደሩ በግዥ የሚገኘውን ነው፡፡ ለተረከበው የስንዴ ዋጋ ባለመክፈሉ ምክንያት የስንዴ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት የቀሪውን የማስረከብ ተግባር እንዲያቆም ተገዷል፡፡ በውሉ አንቀጽ 13 አንደኛው ወገን የገባውን ግዴታ ሳይፈፅም ቢቀር ወይም ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ውሉን ማፍረስ ይቻላል፡፡ ለተረከበው 1020 ኩንታል ስንዴ በወቅቱ ክፍያ ለመፈፀም ባለመቻሉ ጊዜው ተራዘመ ጊዜው ሲራዘም የስንዴ ዋጋና የነዳጅ ዋጋ በመጨመሩ ለዚሁ ጭማሪ ምክንያት የሆነው እራሱ የተከሳሽ ከሳሽ ነው፡፡ ስለሆነም ለውሉ መፍረስ ምክንያት የሆነው እራሱ በመሆኑ በተከሳሽ ከሳሽነት ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡ የጠየቀውም የጉዳት ኪሣራ መጠን በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ የአሁን ተጠሪ የተረከበውን 1020(አንድ ሺህ ሃያ) ኩንታል ስንዴ ዋጋ ክፍያ ያልፈፀመ መሆኑን ስላመነ ዋጋውን ብር 168,300.00(አንድ መቶ ስድሳ ስምንት ሺህ ሦስት መቶ ብር) ከጥር 20 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለከሳሽ ይክፈል፤

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ቀሪውን ስንዴ ላለማስረከብ በምክንያትነት የጠቀሰው የስንዴና የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ናቸው በሚል ስለመሆኑ እራሱ ለተከሳሽ በ10/6/97 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ አስረጂ በመሆኑ ምክንያት ከክፍያ መዘግየት ጋር የሚያያዝ አይደለም፤ በተጨማሪም የክፍያ መዘግየት ለውል ማፍረስ ምክንያት የሚሆነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1788 እንደተመለከተው የክፍያው መዘግየት የውሉን መሠረታዊ ስምምነት የነካ ሲሆን ነው፡፡ በውላቸው አንቀጽ 8 ላይም የክፍያ መዘግየት የውሉን መሠረታዊ ስምምነት የሚነካ መሆኑ አልተመለከተም፡፡ ስለሆነም የክፍያ መዘግየት ውሉን ያፈርሳል የሚለውን ክርክር ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፤ በውሉ መሠረት ቀሪውን 2980(ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ) ኩንታል ስንዴ ያስረክብ፤ ወይም ደግሞ በአሁን ጊዜ ለአንድ ኩንታል ብር 150.00(አንድ መቶ ሃምሣ ብር) ስለመጨመሩ በቀረበው መረጃ መሠረት ለ2980 ኩንታል ብር 447,000.00(አራት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ብር) ተከሳሽ ለከሳሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ወሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች ያቀረበው የይግባኝ ክርክር በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለዚህ የሰበር መዝገብ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ሁለቱም ወገኖች በዚህ በሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ ባጭር ባጭሩ በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡትን ለመግለፅ ከተጠቀሰው በይዘቱ የተለየ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርመረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች በከሳሽ ለውሉ መፍረስ ምክንያት የሆነው ገዥ መሆኑ ታውቆ ውሉ ይፍረስ ላስረከቡት ስንዴ ዋጋ ይክፈለኝ በሚል እና የአሁን ተጠሪም በተከሳሽ ከሳሽነት እንደ ውሉ ቀሪውን ስንዴ ያስረክበኝ፤ የማያስረክብ ከሆነ በሻጭ ጉድለት ምክንያት የስንዴ ዋጋ በመጨመሩ የተነሳ የታየውን የዋጋ ጉድለት በጉዳት ኪሣራ ይክፈለኝ በሚል ይከራከሩ እንጂ ሁለቱንም ወገኖች የሚያከራክራቸውን ነጥብ ለይቶ ለጉዳዩ ውሳኔ ለመስጠት አከራካሪው ነጥብ አንድ ነው፡፡ ይኸውም

እንደ ውሉ ሊፈፀም ያልቻለው በየትኛው ተዋዋይ ወገን ጉድለት የተነሣ ነው የሚለው ነው፡፡ ከዚህም ጭብጥ በመነሳት በታመነው እና የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ ከውላቸው አንቀጾች እና አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደተመለከትነው ፡-

የአሁን ተጠሪ በሁለት ተከታታይ ጊዜ ለተረከበው 1020(አንድ ሺህ ሃያ ኩንታል) ስንዴ ዋጋ ያለመክፈሉን የካደው ጉዳይ አይደለም ስላልጠየቀኝ እንጂ ጠይቆ ክፍያ አልተከለከለም የሚል ክርክር ያቀርብ እንጂ በውሉ እንደተመለከተው በየጊዜው ለሚረከበው ስንዴ ዋጋውን የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ከመሆኑ በቀር የመክፈል ግዴታው በክፍያ ጥያቄ ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሻጭ በየጊዜው የተባለውን የስንዴ መጠን የማስረከብ ግዴታ ያለበትን ያህል ተጠሪም በገዥነት በየጊዜው ለሚረከበው የስንዴ መጠን ዋጋውን የመክፈል ተነፃፃሪ ግዴታ አለበት፡፡ ይህም የሻጭና የገዥ እንደቅደም ተከተሉ በየጊዜው የተሸጠውን ነገር የማስረከብና ዋጋውን የመክፈል ግዴታቸው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በውላቸው ላይ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ይህ በየጊዜው ለሚረከበው ስንዴ ዋጋ የመክፈል ግዴታ መዘግየቱ ካላከራከረ የገዥ ብቸኛ ግዴታ በሽያጭ ለተረከበው ስንዴ ዋጋ መክፈል እንደመሆኑ መጠን ይህ የክፍያ መዘግየት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1784 በተደነገገውም ቢሆን የውሉን መሠረታዊ ስምምነት የነካ ነው ከሚባል በቀር የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ትርጉም የሚከተል አይደለም፡፡ እንደውሉ አነጋገር ክፍያ የመፈፀም ግዴታ በየጊዜው በሚደረገው ርክክብ መሠረት እንጂ ገዥ ክፍያ ሳይፈፀም በውል ማብቂያ ጊዜ አጠቃሎ የመክፈል መብት ያለው ይመስል ከፊል ክፍያ የውሉን መሠረታዊ ስምምነት ሊነካ አይችልም ወደ ሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በተለይም ሻጭ የሚሸጠውን ስንዴ ከማህበሩ አባል ከሌሎች አርሶአደሮች በመሰብሰብ በሽያጭ የሚያስተላልፍ መሆኑን ገልፆ ሲከራከር ለዚህ ማስተባበያ ክርክር ተጠሪ አለማቅረቡ በየጊዜው ለሚደረገው ርክክብ በወቅቱ ክፍያ የማግኘት መብትና ክፍያ የመፈፀም ግዴታ የውሉ መሠረታዊ የስምምነት ክፍል መሆኑን አመላካች ነው፡፡

በውላቸው አንቀጽ 8 ላይ ገዥው በየጊዜው ለሚረከበው ስንዴ ዋጋውን የመክፈል ግዴታ ያለበት በመሆኑና አንደኛው ወገን የገባውን ግዴታ ሳይፈፅም በቀረ ጊዜ ለውል ማፍረሻ ምክንያት እንደሆነ በውሉ አንቀጽ 13 ላይ የተመለከተ በመሆኑ የገዥ ግዴታ አለመፈፀም ምን ውጤት እንደሚያስከትል በውላቸው ላይ የተቀመጠ ሲሆን፤ ይህ ስለመሆኑ በውላቸው በግልፅ አልሰፈረም እንኳ ቢባል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2278 እንደተመለከተው የተሸጠን ነገር የተረከበ ገዥ የሸያጩን ዋጋ ወዲያውኑ የመክፈል ግዴታ ያለበት በመሆኑና የሸያጩ ዋጋ ያልተከፈለው ሻጭ የተሸጠውን ነገር ሳያስረክብ በእጁ የማቆየት መብት የሚሰጠው ለመሆኑ የዚሁ ድንጋጌ ግልባጭ ንባብ ስለሚያስረዳ በተለይም ግራ ቀኙ ከያዙት ውል አንፃር ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ባለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2351(1) እንደተመለከተው ሻጭ በተከታታይ ለሁለት ጊዜ የተሸጠውን ስንዴ ሲያስረክብ በተጓዳኝ ገዥ የክፍያ ዋጋውን አለመክፈሉን እንዳረጋገጠ፤ በተከታይ ለሚያስረክባቸውም ነገሮች ስለመክፈሉ ተገቢውን ስጋት የሚያሳድርና በዚህም የተነሣ ውሉን የማፍረስ መብት የሚሰጠው እንጂ ተጠሪ እንደሚለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገዶ ቀሪውን ስንዴ እንዲያስረክብ ወይም ደግሞ ይህንኑ የማስረከብ ግዴታ የማይዋጣ ከሆነ የዋጋ ልዩነትን የመክፈል ግዴታ የሚጥልበት አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ግራ ቀኙ እንደገቡት የሽያጭ እና ግዥ ውል እንዳይፈፀም ምክንያት የሆነውን የግዴታ መጓደል የፈፀመው ገዥ እንጂ ሻጭ ያለመሆኑ ግራ ቀኙ ባቀረቡት ክርክር ማስረጃ ማረጋገጡን የሥር ፍ/ቤት ተቀብሎ ሆኖም ይህ የክፍያ ግዴታ አለመሟላት ዋናውን የስምምነት አካል የነካ አይደለም በሚል መነሻ ለውሉ መፍረስ ሻጭን ኃላፊ በማድረግ የሰጠው ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች አፈፃፀም በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁ 6059 በ8/8/2000 እና በኮ/መ/ቁ 68877 ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ እና ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
2. የግራ ቀኙ የሽያጭ ውል በገዥ በኩል የሚጠበቀውን የክፍያ ግዴታ ባለመፈፀም ምክንያት መፍረሱ ስለተረጋገጠ ሻጭ የአሁን አመልካች በሽያጭ ላስረከበው 1020(አንድ ሺህ ሃያ) ኩንታል ስንዴ ዋጋ ብር 168,300.00(አንድ መቶ ስድሳ ስምንት ሺህ ሦስት መቶ ብር) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ገዥ /የአሁን ተጠሪ/ ይክፈል ብለናል፡፡
3. ለስንዴው ሽያጭ እና ግዥ ውል መፍረስ ምክንያት ሆኖ የተገኘው ገዥ ለተረከበው 1020 ኩንታል ዋጋ ክፍያ በጊዜው ባለመክፈሉ የተነሣ በመሆኑ እንጂ በሻጭ በኩል በታየ የግዴታ አለመፈፀም ምክንያት ባለመሆኑ ሻጭ የአሁን አመልካች ለገዥው ለአሁን ተጠሪ ቀሪ ስንዴውን የማስረከብም ሆነ ቢያስረክብ ታዩ የተባለውን የዋጋ ልዩነት በጉዳት ኪሣራ መልክ የመክፈል ግዴታ የለበትም ብለናል፡፡

በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የሥር ፍ/ቤቶች መዝገቦች በመጡበት ሁኔታ ይመለሱ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/55229

ጥር 09 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ መሐዳ ዑመር

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአርሲ ቅርንጫፍ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበውን ጉዳይ በተመለከተ በመጀመሪያ ያየው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዕዳውን ሳይከፍል ከቀረ የገበሬ ማህበር ተረክቦ ለእኔ ያስተላለፈልኝ ማሽን ጉድለት የሌለበት መሆን ሲገባው ከጉድለቱ ጋር ስላስተላለፈልኝ ተከሣሹ ባንክ ከእኛ የወሰደውን ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ መመለስ ይገባዋል በሚል ባቀረቡት ክስና ክርክር መሠረት ተከሣሹ ገንዘቡን ለከሣሽ መመለስ ይገባዋል በማለት የወሰነ ሲሆን በባንኩ /በአሁኑ ተጠሪ/ የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ጉዳዩ ቀርቦለት የተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ ባንኩ የክስ መቃወሚያ አድርገው ያቀረበውን የይርጋ ክርክር የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሳያየው አልፎ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ መክፈል አለበት ብሎ የወሰነው ያለአግባብ ነው፡፡ ከተነሣው የይርጋ ክርክር አንፃር ሲታይ ክሱ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

የአሁኗ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ሊያቀርቡ የቻሉ ቢሆንም ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው በዚህ ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ክሱ በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሚያዚያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ገልፀው አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ በመባሉ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በተጠሪው በኩል በጽሑፍ በቀረበው መልስ ላይ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥተውበት ተከራክረዋል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በይግባኝ ያላነሳውን የይርጋ ክርክር እራሱ በማንሳት ውሣኔ ሰጥቷል በሚል የገለፁትን በተመለከተ ከዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ የይርጋው ክርክር መቅረቡን ውሣኔው ስለሚያስረዳ ተቀባይነት የለውም፡፡

በአሁኑ ተጠሪ በኩል የይርጋ ክርክር መቅረቡ ስለተረጋገጠ የአሁኗ አመልካች በተጠሪው ላይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል የተባለው በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ሲመረመር፡-

የአሁኗ አመልካች ተጠሪው ለእኔና ለባለቤቴ መጭመቂያ ማሽን አስተላለፈልን የሚሉት ነሐሴ 14 ቀን 1985 ዓ.ም. በተደረገ ውል ሲሆን ተጠሪው ከሌላ ገበሬ ማህበር በዕዳ ምክንያት የተረከበውን ማሽን ስለዋጋው አከፋፈል በውሉ ላይ በማመቻቸት ከፍለን የራሳችን በማድረግ እንድናስቀረው አስተላለፈልን በማለት የሚገልጹት ሽያጭ እንጅ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ አመልካች በውል ተላልፎልኛል የሚሉትን ማሽን እንደተረከቡ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2291 መሠረት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲመረመር በማድረግ ጉድለት ያለበት ሆኖ ከተገኘ በዚሁ ሕግ ቁጥር 2292 መሠረት ለተጠሪው ማስታወቅ ነበረባቸው፡፡ ካስታወቁ በኋላም በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2298/1/ ላይ በተገፀው መሠረት ክስ ማቅረብ ይችሉ የነበረው ካስታወቁበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ክስ ካላቀረቡ ዕቃው ጉድለት ያለበት ነው ብለው የመክሰስ መብታቸውን ያጣሉ፡፡ አመልካች በማሽኑ ላይ ጉድለት ስለመኖሩ በሕጉ መሠረት በአጭር ጊዜ ለተጠሪው አስታውቀው በተወሰነው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ ቀርቶ የፊፀሙት አንድም ነገር ሣይኖር ከአሥራ ሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ ተጠሪው ያስረከበን ማሽን ጉድለት ስላለበት የከፈልነውን ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ ይመልስልን የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡ አሥር ዓመት ወደሚለው የይርጋ ክርክር መሄድ ሳያስፈልግ አመልካች ማሽኑን እንደተረከቡ በአጭር ጊዜ እንዲመረመር አድርገው ጉድለት ያለው ስለመሆኑ ለተጠሪው በማሳወቅ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማሽኑ ጉድለት ያለበት ነው የሚለውን ክስ ያላቀረቡ ስለሆነ የመክሰስ መብታቸውን አጥተዋል፡፡

የይርጋው ጊዜ ተቋርጦ ቆይቷል በሚል ያነሱትን ክርክር በሚመለከት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በሚያይበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት ክርክር ያላቀረቡ ሲሆን የይርጋው ጊዜ ተቋርጦ ቆይቷል የሚለውን ክርክር ያነሱት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ላይ ነው፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በሥር ፍ/ቤት ያልቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329 መሠረት ሊታይ የሚችል አይደለም ብሎ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ ፈጽሟል የሚባለው የሕግ ስህተት የለም፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ የአሁኗ አመልካች ተጠሪው አስተላልፎልን የነበረው ማሽን ጉድለት ስላለበት የከፈልነውን ገንዘብ ብር 40,000 ይመልስልን በሚል ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 56252

ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ተስፋዬ አበበ ሥራ ተቋራጭ - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ማዕረጉ ወርቁ ሥራ ተቋራጭ - ጠበቃ ተካ ዳባ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ በምዕራብ አርሲ ዞን በገደብ አሣሣ ወረዳ ጥጆ ዋቄንጥረ ከሚባለው ሥፍራ የሚሰራውን የጤና ኬላ ለመገንባት በጨረታ ተወዳድሮ አሸንፏል፡፡ ተጠሪ ይህንን ግንባታ ራሱ ለማከናወን ስላልፈለገ ህንፃውን እኔ ሙሉ በሙሉ እንድሠራለት በተወካዩ በኩል ተዋውሏል፡፡ እኔም ለተጠሪ ኮሚሽን ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ ከፍዬ ውሉን በተዋዋልንበት ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. የግንባታ ቦታውን አስረክቦኝ ሥራውን ሠርቻለሁ፡፡ ሆኖም ተጠሪ ለተሠራው ሥራ ከምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ የተከፈለውን ብር 240,000 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ ከተቀበለ በኋላ ለእኔ መስጠት ሲገባው ራሱ የወሰደ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የእኔ ወኪል የዚህ አይነት ውል ለመዋዋል ሥልጣን የለውም፡፡ አመልካች የውክልና ሥልጣን ከሌለው ሰው ጋር አደረግሁ የሚለው ውል ህግን የሚቀረን ነው፡፡ አመልካች ህንፃውን አንድም ቀን አልሠራም፡፡ የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በራሱም ሆነ በወኪል አማካኝነት በራሱ ለመገንባት ተጫርቶ ያሸነፈውን የህንፃ ሥራ ውል ለአመልካች አሣልፎ የመስጠት ሥልጣን የለውም፡፡ በውሉ ላይ አሠሪው የህንፃው ባለቤት የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ አልተስማማም፡፡ ስለሆነም አመልካች /ከሣሽ/ ያቀረበው ክስ ህጋዊ መሠረት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በጨረታ ተወዳድሮ ያሸነፈውን ጤና ኬላ ሠራተኛ ቀጥሬና የሚያስፈልገውን የግንባታ ዕቃ አሟልቼ እንድሠራ በወኪሉ አማካኝነት ውል በመፈረምና ብር 50,000 /ሀምሳ ሺህ ብር/ ኮሚሽን በመቀበል ተዋውሏል ውሉን ስንዋዋል የአሠሪው የምዕራብ አርሲ ጤና መምሪያ ተቆጣጣሪ መሀንዲስ የነበረ ሲሆን ተቆጣጣሪ መሐንዲሱ ባለበት የግንባታውን ቦታ ተረካክበናል፡፡ ለስራው በተሰጠው ንድፍና ቢል ኦፍ ኳንቲቲ መሠረት ስራውን የሠራሁት እኔ ስሆን አሠሪውም የተሠራውን ሥራ ሲያፀድቅ ቆይቷል፡፡ ሠራተኛ ቀጥሬ የግንባታ ዕቃዎችን በራሴ ወጭ አቅርቤና አሟልቼ የሠራሁትን ሥራ ለአሰሪው በማስረከብ የክፍያ ሰርተፍኬት የተቀበለው ተጠሪ ወኪሉ የግንባታውን ሥራ ለሌላ ለማሳለፍ ስልጣን የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር በመቀበል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ስለግንባታ ሥራ ውል የተደነገጉ መሠረታዊ የአሠራር መመሪያን የሚፃረርና የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ውሉ ሥልጣን በሌለው ተወካይ በኩል የተደረገ ነው፡፡ አመልካች የግንባታ ሥራውን የሠራ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን ያላቀረበ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተገኃግሟል፡፡ ስለዚህ አመልካች ክርክሩን በማስረጃ በአግባቡ ሣያስረዳ በሰበር አቤቱታው አዲስ ክርክር ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ጥቅምት 22 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ በሰበር አቤቱታው ያነሣቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ለግንባታ አስፈላጊ የሆነውን የግንባታ ዕቃ በማሟላትና ሠራተኛ በመቅጠር ለሠራሁት ሥራ ተጠሪ ክፍያውን ሊሰጠኝ ይገባል በማለት የቀረበው ክስ የህግ ድጋፍ እና መሠረት የለውም በማለት የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ በአግባቡ ለመወሰን በመጀመሪያ በአመልካችና በምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ እንደዚሁም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጓል የተባለውን ውል መሠረታዊ ባህሪና በህግ የሚያስከትለውን ውጤት መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ የወጣውን ጨረታ በማሸነፍ ተጠሪ በገደብ አሰሳ ወረዳ ጥጃዋቂንጥራ ከሚባለው ሥፍራ ላይ በአሠሪው በተሰጠው ንድፍና ኘላንና ቢል ኦፍ ኳንቲቲ መሠረት የጤና ኬላ ሠርቶ ለማስረከብ የግንባታ ሥራ ውል ተዋውሏል፡፡ ይህም በአሠሪው /የምዕራብ አርሲ ዞን የጤና መምሪያ/ እና በሥራ ተቋራጩ /ተጠሪ/ መካከል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3244 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት የመንግስት የሥራ ውል የተዋዋሉ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች በእኔና በተጠሪ መካከል ተደርጓል የሚለው ውል ተጠሪ በጨረታ ያሸነፈውን የህንፃ ሥራ ሙሉ ለሙሉ ለእኔ በመልቀቅ ሥራውን እንድሠራና ዋጋው መጨረሻ ለእኔ ሊከፈል ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ተዋውለናል የሚል ክርክር ያቀርባል፡፡ ይህ የአመልካች ክርክር በአሠሪው /በምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ/ ፈቃድና ዕውቅና ተጠሪ የህንፃውን ሥራ ለእኔ አስተላልፎልኛል የሚል ይዘት ያለው አይደለም፡፡ የግንባታ ሥራ ውል በአሠሪው ዕውቅናና ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው የሚለቀቅበት ወይም ለንዑስሥራ ተቋራጭ የሚሰጥበት ሁኔታ ማለትም “Nominated Assignment or Nominated sub contract” የሚደረግበት ሁኔታ እንዳለና በእኛ አገር አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ጋር የተደረገን የሥራ ውል ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው ለመልቀቅ ወይም ለንዑስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥራ ተቀራጭ ለመስጠት የአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ፈቃድ አስፈላጊ እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3202 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ሙሉ ዕውቅናና ፈቃድ የህንፃ ሥራ ውሉን ለሌላ ሰው በሚለቀቅበት ጊዜ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3205 የተደነገገው ውጤት የሚያስከትል መሆኑን በአስተዳደሩ ሙሉ ዕውቅናና ፈቃድ ሥራው ለንዑስ ሥራ ተቋራጭ የተሰጠ ሲሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3206 የተደነገገውን ውጤት የሚያስከትል መሆኑ ተደንግጓል፡፡ የአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ተቋራጩ ሥራውን ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው እንዲለቅ ለመፍቀድ ወይም ሥራውን በከፊል ለንዑስ ሥራ ተቋራጭ እንዲሰጥ ለመፍቀድ የሚችለው ውሉን ለመዋዋል ሥልጣን ባለው ባለሥልጣን በኩል መሆን እንዳለበት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3202 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው አመልካች ከተጠሪ ጋር ውል የተዋዋልኩት የአሠሪው /የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ/ ተቆጣጣሪ መሀንዲስ ባለበት ስለሆነ የህንፃ ሥራ ውሉን ለተጠሪ ለመልቀቅ የተስማማው በአሠሪው ዕውቅናና ፈቃድ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍና መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ውሉ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በአግባቡ ተደርጓል ወይስ አልተደረገም የሚለው ጭብጥ ወደፊት የሚታይ ሆኖ በአመልካችና ተጠሪ መካከል ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ተደርጓል ተብሎ የአመልካች መከራከሪያ የሆነው ውል በባህሪው ከአሠሪው ማለትም የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ከሆነው የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ ፈቃድ ውጭ የተደረገ የህንፃ ሥራን የመልቀቅ ውል / Unnominated Assignment of Contract of work / ነው፡፡ ተቋራጩ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3202 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት ሣይፈቅድለት የህንፃውን ሥራ ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው ቢለቅ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን ጥያቄ መልስ ማግኘት ያለበት ነው፡፡ የሥራ ተቋራጩ ከአሠሪው ፈቃድ ውጭ ሥራውን ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው ቢለቅ ወይም ለንዑስ ሥራ ተቋራጭ ቢሰጥ፣ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3205 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3206 የተደነገጉትን ህጋዊ ውጤቶች በተቋራጩና በሌላ ሶስተኛ ወገን መካከል የሥራ ውልን ለመልቀቅ ወይም ንዑስ የሥራ ውል ለመዋዋል የተደረገው ውል በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ላይ ግዴታ የሚያስከትልበት አይደለም፡፡ የአስተዳደሩ መስሪያ ቤት መብቱን የሚጠይቀውም ሆነ ግዴታውን የሚወጣው ለሥራ ተቋራጩ ሲሆን የአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ግንኙነት ከሥራ ተቋራጩ ጋር ብቻ የሚወሰን መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3205 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3206 የተቃርኖ ንባብና ትርጉም “ Acontrario reading and Interpretation “ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ተቋራጩ አሠሪ የሆነው የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ሣይፈቅድለት ሥራውን ለመልቀቅ ያደረገው ውል ወይም ለንዑስ ተቋራጭ ጋር ያደረገው ንዑስ የሥራ ውል በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ላይ መከራከሪያና መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3204 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በተቃራኒው የሥራ ተቋራጩ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱ ሣይፈቅድለት የሥራ ውሉን ለሌላ ሰው ለመልቀቅ በመዋዋሉ ወይም ንዑስ የስራ ውል መዋዋሉ እንደ ጥፋት ተቆጥሮ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱ ውሉን ለማፍረስ የሚያስችለው በቂ ምክንያት እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3204 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ይደነግጋል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አሰሪው የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3202 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ሣይፈቅድ ተጠሪና አመልካች ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. አደረጉት የተባለው ውል አመልካች በአሠሪው በምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ ላይ በቀጥታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መከራከሪያ አድርጎ ሊያነሣው የማይችል መሆኑ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3204 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሠሪው የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ የሥራው ተቋራጭ ከሆነው ከተጠሪ ጋር አድርጎት የነበረውን የህንፃ ሥራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችለው በቂ ምክንያትና ጥፋት እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3204 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የአሠሪው ፈቃድና ስምምነት አለመኖር ከላይ ከተገለፀው ሁኔታ አልፎ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጓል የተባለውን ውል በመካከላቸው አስገዳጅነትና ምንም አይነት ህጋዊ ውጤት የማያስከትል ውል አያደርገውም፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጓል የተባለውን ውል በመካከላቸው አስገዳጅነትና ምንም አይነት ህጋዊ ውጤት የማያስከትል ውል አያደርገውም፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለው ውል ላይ አሠሪው /የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ/ ፈቃድና ስምምነቱን አለመስጠቱ ውሉ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ምንም አይነት መብትና ግዴታ የማይፈጥር ፈራሽና ውጤት አልባ ያደርገዋል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የህግ ትርጉምና ውሣኔ ከላይ በዝርዝር ያየናቸውን ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ እና የሚያስከትሉትን ህጋዊ ውጤት ያላገዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የጤና ኬላው ህንፃ አሠሪ የሆነው የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ ከሥራ ተቋራጩ ተጠሪ ጋር በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3244 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ያደረገውን ህንፃ ሥራ ውል የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3204 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት አላፈረሰም፡፡ በአንፃሩ አሠሪው የተሠራውን የጤና ኬላ በመረከብ ለሥራ ተቋራጩ/ተጠሪ/ የክፍያ ሰርተፊኬት በመሥራት ብር 240,000 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ የከፈለ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ የህንፃ ሥራውን ለአመልካች ለመልቀቅ ከአሠሪው ፈቃድ ውጭ ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. አድርጎታል የተባለው ውል አመልካች በማናቸውም መልኩ አሠሪውን የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ ለመጠየቅ የማያስችለው ቢሆንም ውሉ መኖሩና በአግባቡ መፈጸሙ ከተረጋገጠ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የህግ አስገዳጅነት ያለው ነው፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ጋር የጤና ኬላ ህንፃ ሥራ ውሉን ለመልቀቅ የተደረገ ህጋዊ ውል ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. አላደረግሁም፡፡ የእኔ ተወካይ ይህንን ውል የተዋዋለው ከተሰጠው የውክልና ሥልጣን ውጭ ነው በማለት በሥር ፍርድ ቤት የተከራከረ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ምክንያት የአመልካችን ክስ ውድቅ ለማድረግ ጠቅሶታል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ተወካይ ከውክልና ሥልጣኑ ውጭ ነው የተዋዋለው የሚለውን የህንፃ ሥራ የመልቀቅ ውል ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2107 ድንጋጌዎች መሠረት የማፅደቅ ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ጭብጥ የበታች ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር ማስረጃና የግንባታ ሥራን ልዩ ባህሪ መሠረት በማድረግ ጭብጥ መመሥረትና መወሰን ይገባቸው የነበረ መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን መሠረታዊ ጭብጥ ሣይመሠርቱና ውሣኔ ሣይሰጡበት አልፈዋል፡፡ ይህንን ጭብጥ በአግባቡ ለመወሰን፣ አመልካች ለተጠሪ በኮሚሽን መልክ ከፍየዋለው የሚለው ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ ተጠሪ ተቀብሏል ወይስ አልተቀበለም? ተጠሪ የግንባታ ሥፍራውን ሙሉ በሙሉ ለአመልካች አስረክቦ ነበር ወይስ አልነበረም? ለጤና ኬላው ግንባታ የሚያስፈልገውን ሠራተኛ በመቅጠርና ለግንባታው አስፈላጊ የሆነውን ዕቃ በማሟላት ግንባታውን ያከናወነው አመልካች ነው ወይስ አይደለም? አመልካች የሠራው የግንባታ ሥራ አለ ከተባለ ተጠሪ አመልካች የሠራውን ሥራ አሠሪው የምዕራብ አርሲ ዞን ጤና መምሪያ እንዲረከበው በማድረግ ክፍያ እንዲፈፀምለት አሠሪውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠይቋል ወይስ አልጠየቀም የሚሉት ነጥቦች ፍርድ ቤቱ በተከራካሪ ወገኖች የሚቀርቡ ማስረጃዎችንና እውነቱን ለማውጣት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 145/1/ በማስቀረብ ጭምር በማጣራት ውሣኔ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች ናቸው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመወሰን አስፈላጊ የሆኑትን ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ሣይመሰርትና ፍሬ ጉዳዩን ሣያጣራ ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. የተደረገውን ውል የተዋዋለው የተጠሪ ወኪል ከሥልጣኑ ውጭ የፈፀመው ተግባር ነው የሚለውን ነጥብ ብቻ በማየት የሰጠው ውሣኔ በውሉ መሠረት አመልካች ግዴታውን ፈፅሞና የግንባታ ሥራ ሠርቶ ከሆነ ውጤቱ ምን ይሆናል ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄ እልባት ያልሰጡ በመሆኑ ውሣኔው መሠታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪውን የጤና ኬላ የሰራው ማን ነው? የሚለውንና ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥናቸውን ነጥቦች ዙሪያ አመልካችና ተጠሪ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በመቀበልና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሸ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ጌታ ትራዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርቦ በሥር ተከሣሽ የነበረው ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ዱቄት ፋብሪካን ለመሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ አውጥቶ ነበር፡፡ በሐራጅ ማስታወቂያው መሠረት ተወዳድሬ ጨረታውን በማሸነፌ ታህሣሥ 23 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ ሽያጭ ውል ፋብሪካውን በብር 42,500,100.99/አርባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ አንድ መቶ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ ገዝቻለሁ፡፡ አከፋፈሉን በተመለከተ ብር 10,625,025.50 /አስር ሚሊየን ስድስት መቶ ሃያ አምስት ሺ ሀያ አምስት ብር ከሀምሣ ሣንቲም/ ተከፍሏል፡፡ ቀሪው ብር 31,825,025 /ሠላሣ አንድ ሚሊየን ስምንት መቶ ሃያ አምስት ሺ ሀያ አምስት ብር/ ተከሣሽ በሚሰጠው ብድር ለመክፈል የካቲት 17 ቀን 1993 ዓ.ም ከተከሣሽ /ተጠሪ/ ጋር የብድር ውል ተዋውለናል፡፡ ከተከሣሽ /ተጠሪ/ ለተወሰደው ብድር ከሣሽ ሠላሣ ሠባት መኪናዎችን በመያዣ ውል አስይሏል፡፡ ሆኖም የፋብሪካው ሽያጭ የባንኩን አሻሻጥ ደንብ የተከተለ አይደለም በማለት የባንኩ ኢንስፔክተሮች ሐምሌ 23 ቀን 1993 ዓ.ም ባቀረቡት ሪፖርት ፋብሪካው በተጠሪ በመያዣነት ያልተያዘ መያዣውም የተመዘገበ አይደለም ተብሎ የተከሣሽ /ተጠሪ/ ድርጅት ሥራ አስኪያጆችና የከሣሽ /አመልካች/ ድርጅት በወንጀል ተከሰው የከሣሽ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በነፃ ተሰናብተዋል፡፡ ስለዚህ የሽያጭ ውል የማይፀናና ውል ለመዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገ በመሆኑ የብድርና የመያዣ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም፡፡ ሽያጩ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት ያለው የተሸጠው ንብረት ባለቤት የሆኑት አስር አለቃ ወ/ሃይማኖት ስርቋ እንጅ ከሣሽ /አመልካች/ ክስ የማቅረብ መብት የለውም፡፡ ከሣሽ /አመልካች/ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስልኝ በማለት ጥያቄ ያቀረበው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ ቁጥር 447/1/ የተደነገገው የሁለት ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ ነው። ጥያቄው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1810 የተደነገገው የሁለት ዓመት የይርጋ ገደብ ካለፈ በኋላ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል።

አመልካች ተጠሪ/ ተከሣሽ/ ፋብሪካ የሸጠልን በመሆኑና የሸጠልኝ የፋብሪካ ላይ ሽያጭ ውል ሊፈፀም የማይችል በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት አለኝ። ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለው የሚል ሰፊ ክርክር አቅርቧል።

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማና ያቀረቡትን የጽሑፍ ክርክርና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ክስ ተቀብሎ የማከራከርና ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አለው። ከሣሽ /አመልካች/ ክስ ለማቅረብ መብት አላቸው በማለት ብይን የሰጠ ሲሆን በተጠሪ በኩል የቀረበውን የሁለት ወር የይርጋ ጊዜ መቃወሚያ በመቀበል በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ባንክ በመያዣ ሲሸጥ ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 394-449 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚነት እንዳላቸው ይደነግጋል። ከሣሽ መብት የሌለውን ንብረት ነው የሸጠልኝ በማለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 446 መሠረት ሽያጩ እንዲሰርዝ የሚያቀርቡት ጥያቄ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447/1/ የተደነገገው የሁለት ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል። አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧዋል። ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በድምጽ ብልጫ አጽንቶታል።

አመልካች ታህሣሥ 1 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ከተጠሪ ጋር የተደረገው የፋብሪካ ሽያጭ ውልና የመያዣ ውሉ ቀሪ እንዲሆንና የጠየቅሁት የባንክ ኢንስፔክሽን ተጠሪ ንብረቱን የሸጠው የመያዣ መብት ሣይኖረው ነው በማለት በጽሑፍ የሰጠውን ማረጋገጫ በማስረጃነት በመያያዝ ነው። ውሉ ሕግን የሚቃረን ውል ከሆነ በይርጋ የማይታገድ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለሕግ ተቃራኒ የሆነ ውል ቀሪ እንዲሆን የሚቀርብ ጥያቄ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን ሣይገነዘብ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው።በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 344 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 449 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ለጉዳዩ ተፈፃሚ የሚሆኑት በመጀመሪያ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የመያዣያ መብት ሲኖረው ነው። ተጠሪ በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት ሣይኖረው የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ሆነ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አብላጫው ድምጽ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447/1/ን በመጥቀስ የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት። ስለዚህ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል።

ተጠሪ በበኩሉ ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ለአመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የዱቄት ፋብሪካውን የሸጥነው የፋብሪካው ባለቤት ለሆኑት አስር አለቃ ወልደሀይማኖት ስቋር የሰጠነው ብድር ባለመከፈሉና የፋብሪካውን ሕንፃ በመያዣነት በክልል 14 መስተዳድር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ አስመዝግበን ስለያዝነው ነው። ማሽነሪዎቹንና ተሽከርካሪዎቹን በተመለከተ በመያዣነት የያዛቸው አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በሰጠን ውክልና መሠረት ሸጠናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለዚህ አመልካች በዚህ በኩል የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ አይደለም ይህም በመሆኑ ለጉዳዩ የአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 በሚደነግገው መሠረት ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 339 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 449 የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚነት አላቸው፡፡ ስለሆነም የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ሆነ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ግራ ቀኙ ለሰበር ችሎት በጽሑፍ ካቀረቡት ክርክር በተጨማሪ ችሎቱ የአመልካችንና የተጠሪን የቃል ክርክር ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰማ ሲሆን የቃል ክርክሩ ወደ ጽሑፍ ተቀይሮ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ የአመልካችና ተጠሪ የቃል ክርክር በይዘቱ በጽሑፍ ካቀረቡት ክርክር ጋር ተመሣሣይነት ያለው ሲሆን አመልካች ሕገወጥ የሆነ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በጊዜ ገደብ አይታገድም የሚል መሠረታዊ የሕግ መርህ አለ፡፡ለምሣሌ በዚህ ዘመን የባሪያ ንግድ አይፈቀድም፡፡ ባሪያ ነግዳለሁ ብሎ ተዋውሎ ቢገኝ በሁለት ዓመት ይርጋ ታግዷል ሊባል አይችልም የሽያጭ ውሉ ሕገወጥ ስለሆነ፡፡ በዚህ ጉዳይም ተጠሪ የሱ ያልሆነውንና በአዋጅ ሊሸጠው የማይችለውን መሸጥ አይችልም፡፡ አንድ ውል ሕገወጥ ውል ነው የሚባለው በሕግ የተከለከለ ሲሆን ነው፡፡ ስለዚህ የይርጋ ክርክርና የይርጋ የሕግ ድንጋጌዎች በዚህ ጉዳይ ተጠቃሽነትም ሆነ ተፈፃሚነት የላቸውም የሚል ይዘት ያለው ሰፊ ክርክር አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የሸጥነው በመያዣ የያዝነውን ንብረት ነው ገዥ ፋብሪካውንም ተረክበው እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ውሉ ሕገወጥ ነው መባሉ ተገቢ አይደለም የሚል ይዘት ያለው መልስ በቃል ክርክር ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራ ቀኙ በኩል የቀረበው የጽሑፍና የቃል ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካች ጥያቄ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447/1/ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔና የሕግ ትርጉም ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው መሠረታዊ ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች ከተጠሪ ጋር የተደረገው የፋብሪካ ሽያጭ ውል ሕገወጥ የሆነ ውል /unlawfull contract/ ነው፤ ሕገ ወጥ የሆነ ውል ቀሪ ለማስደረግ የሚቀርብ ክስ በማናቸውም ጊዜ ለመቅረብ ይችላል፡፡ ሕገወጥ የሆነ ውል ቀሪ ለማድረግ በሚቀርብ ክስ ላይ በፍታብሔር ሕግም ሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የተደነገገው የጊዜ ገደብ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የላቸውም በማለት ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የዱቄት ፋብሪካ ሽያጭ ውል ሰውን ከመሸጥና ከባሪያ ንግድ ጋር በማመሣሰል ያቀረበው ክርክር ተገቢና ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሀ/ ሕገ ወጥ ውል /unlawfull contract/ ማለት በሕግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ የሕግ ክልከላ ያለበት ውል ማለት ነው፡፡ አንድ ውል ሕገወጥ ውል ነው የሚባለው ተዋዋዮቹ የተዋዋሉበት መሠረታዊ ጉዳይ ዓላማ በመሠረታዊና ሞራላዊ ይዘቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት በማድረግ መብትና ግዴታ እንዲፈጥሩበት በሕግ ያልተፈቀደ ወይም በሕግ ክልከላ የተደረገበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ለምሣሌ አመልካች እንዳለው በሕገ መንግሥቱም ሆነ በአገሪቱ የወንጀል ሕግ እንደዚሁም በዓለም አቀፍ የወንጀል ሕግ ማንኛውንም ሰብዓዊ ፍጡር በግዴታ አገልጋይነት መያዝ ወይም በሰው መነገድ የተከለከለ በመሆኑ ሰውን በግዴታ አገልጋይነት ለመያዝ ወይም በሰው ለመነገድ የተደረገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል በመሠረታዊ ባህሪውና ሞራላዊ ይዘቱ ሕገወጥ ውል /unlawfull contract/ ነው፡፡ አንድ ውል የተመሠረተበት መሠረታዊ ጉዳይ “object of contract” በሕግ ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜ ውሉ በሕግ ፊት እንደሌለና ምንም አይነት ሕጋዊ ውጤት የማያስከትል /void contract/ ነው፡፡ አንድ ውል በማናቸውም ሰው ወይም አካል ፈቃድና ስምምነት ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ የማይቻልና በማናቸውም መንገድ ለማስተካከልና ሕጋዊ ውጤት እንዲያገኝ ለማድረግ የማይቻል በሆነ ጊዜ ውሉ ከጅምሩ በሕግ ፊት እንዳልተደረገና እንደሌለ “Null or void contract” እንደሚሆን በዘርፉ ከተደረጉ ጥናቶች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በእኛ አገር የሕግ ሥርዓት አንድ ውል የፀና ውል ለመሆን ማሟላት ከሚገባው አንደኛው መሠረታዊ ነጥብ ውሉ ሕጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ የተመሠረተ መሆን የሚገባው እንደሆነ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1678 ንዑስ አንቀጽ /ለ/ ይደነግጋል፡፡ ይህንን ነጥብ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1678 ንዑስ አንቀጽ “ለ” የእንግሊዝኛው ቅጅ “The object of the contract is sufficiently defined and is possible and lawful” በማለት ከአማርኛው ቅጅ በተሻለ አገላለጽ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የውሉ መሠረታዊ ባህሪና ጉዳይ በሕግ ያልተፈቀደና ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜ ማለትም ውሉ ሕገወጥ /unlawful contract/ በሆነ ጊዜ በሕግ ፊት ውጤት እንደማያስከትል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1716 ተደንግጓል፡፡ በውጤት ደረጃ ዳኞች የውሉ መሠረታዊ ዓላማ ሕገወጥ መሆኑን ከውሉ ቃል ወይም ውሉ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ተዋዋይ ካቀረበው ጽሑፍ በተረዱበት በማናቸውም ጊዜ ውሉ እንዲፈፀም የቀረበላቸውን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግና አንቀበልም ለማለት የሚችሉ መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1718 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የውሉ መሠረታዊ ዓላማ ወይም ጉዳይ በሕግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲያገኙት ዳኞች ሕገወጥ /unlawful/ የሆነው ውል በቀረበላቸው በማናቸውም ጊዜ ሕጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ለመወሰን እንደሚችሉና ሕገወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በሕጉ የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል ከላይ ከተጠቀስናቸው የሕግ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ለ/ ውሉ ሲደረግ በጠቅላላ የውል ሕግና በልዩ የውል ሕግ ድንጋጌዎች ወይም በሌሎች ህጎች የተደነገገውን መስፈርት የማያሟላና ጉድለት ያለበት ሆኖ መገኘቱ ውሉ የሕጉን መስፈርት የማያሟላ “illegal contract” ያደርገዋል እንጅ ውሉን ሕገወጥ ውል /unlawfull contract/ ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም፡፡

ከባለሀብቱ በቂ የሆነ የውክልና ሥልጣን ሣይኖረው ወይም ንብረቱን ለመሸጥ የሚያስችል መብት በሌለው ሰው የተደረገ የሽያጭ ውል፣ ውሉ በሕግ የተደነገጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን የማያሟላ ነው የዚህ ጉድለት ውሉን በፍርድ ቤት እንዲፈርስ መቃወሚያና ክርክር ሊቀርብበት የሚችል /invalid contract/ የሚያደርግ አይደለም፡፡

በሕገወጥ ውል /unlawful contract/ እና የሕጉን መስፈርት ሣያሟላ በተደረገ ውል /illegal contract/ መካከል በጽንሰ ሀሣብ ደረጃ ሰፊ ልዩነት እንዳለ በሥነ ሕግ ዙያ በተደረጉ ጥናቶች ብቻ ሣይሆን በብላክስ ሎው መዝገበ ቃላት ውስጥ “The principal distinction between the terms of lawful and legal is the former contemplates the Substance of a law, the latter the form of law.. To say an act “lawful” implies that it is authorized, sanctioned or at any rate not forbidden by law. To say it is “legal” implies that it is done or performed in accordance with the forms and usage of law, or in a technical manner;

https://t.me/ethiopianlegalbrief

in this sense illegal approaches the meaning of invalid" በሚል መንገድ ተገልጸ እናገኘዋለን፡፡

ከላይ የተገለጸውን የሕግ ጽንሰሀሳብ እና የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የዱቄት ፋብሪካ ሽያጭ ውል በመሠሪታዊ ባህሪው ሞራላዊ ይዘቱና ዓላማው በሕግ ክልከላ የተደረገበት ሕገወጥ ውል /unlawfull contract/ ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሀብቱን በሽያጭ የማስተላለፍ የውክልና ሥልጣን በባለሀብቱ ባልተሰጠው ሰው ወይም ንብረቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ በማይችል ሰው ቢሸጥ ውሉን በመሠረታዊ ባህሪው በሞራላዊ ይዘቱና ዓላማው ሕገ ወጥ ውል /unlawfull contract/ አያደርገውም፡፡ በአንጻሩ ይህ ጉድለት መኖሩ ቢረጋገጥ ውሉ ባለሀብትነትን በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደነገጉትን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የማያሟላ "Illegal or invalid contract" የሚያደርገው ጉድለት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ፋብሪካውን የሸጠልኝ ንብረቱ ላይ ሕጋዊ የመያዣ መብት ሣይኖረውና ንብረቱን በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ለመሸጥ የሚያስችል መብት ሣይኖረው ነው፡፡ ስለዚህ ውሉ ሕገወጥ ውል /unlawfull contract/ በመሆኑ ከጅምሩ ውሉ እንደሌለ የሚቆጠር /null or void contract/ ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክርም ከሕጉ መሠረታዊ ሀሣብ ጋር የማይሄድ ነው፡፡ የውል ሕግ ወይም ሌሎች የሕግ ማዕቀፎች የደነገጉትን መስፈርት ሣያሟላ የተደረገ ውል በሙሉ /null or void contract/ና ሕገወጥ ውል ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አይቻልም፡፡

አንድ ውል ከጅምሩ እንዳልተደረገ /null or void contract/ የሚቆጠረው በማናቸውም መንገድ ሕጋዊ ውጤት ለማስገኘት የማይችልና ጉድለቱ ሊስተካከል የሚችልበት ምንም ዓይነት አማራጭ ወይም መንገድ የሌለ ሆኖ ሲገኝ መሆኑን "An instrument or transaction which is wholly in effective, in operative and incapable of ratification and which thus has no force or effect so that nothing can cure it" በሚል መንገድ ተገልፃ የምናገኘው ሲሆን የውሉን ጉድለት በማቃናት ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ የሚቻልበት መንገድና ሁኔታ ሲኖር ውሉ (null or void contract) ሣይሆን ጉድለት ያለበትና ፈራሽ ሊሆን የሚችል ውል "voidable or invalid contract" እንደሚሆን Variable exists when an imperfection or detect can be cured by an actor confirmation of him who could take advantage of it" በሚል መንገድ በብላክስ ሎው እና በሌሎች ጽሑፎች የተሰጡ ትንታኔዎችን በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በእኛ አገር የህግ ሥርዓት አንድን ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ መብት ወይም የውክልና ሥልጣን በሌለው ሰው ሽያጭ ሲፈፀም የንብረቱ ባለቤት ሽያጩን ካፀደቀውና ከተቀበለው ውሉ በሕግ ፊት የፀናና ውጤት ያለው እንደሚሆን ከፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2190- 2192 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሽያጭ ሊያስተላልፈው የሚችለው የባለሀብትነት መብት ከሌለው ሰው ንብረት የገዛ ገዥ ንብረቱ የእኔ ሀብት ነው የሚል ሶስተኛ ወገን ሲመጣበት ሻጭ በዋቢነት /መድንነት/ እንዲቀርብለት ለመጠየቅ እንደሚችልና የሽያጭ ውሉን ለማፍረስ የሚያስችለው በቂ ምክንያት እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875፣የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2884፤ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2342 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማንበብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ በሽያጭ ሂደቱ ፈፅሞታል በማለት የሚዘረዝራቸው ጉድለቶች በተጠሪ ሙሉ በሙሉ የተካደና በፍርድ ያልተረጋገጠ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ጉድለቱ መኖሩ ቢረጋገጥም እንኳን አመልካች እንደሚለው ውሉን ከጅምሩ ሕገ ወጥ ውል/unlawfull contract/ ና ከጅምሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳልተደረገ የሚያስቆጥር (null or void contract) የሚያደርግ ሣይሆን የሽያጭ ውሉን ጉድለት ያለበትና በፍርድ ቤት መቃወሚያና ክርክር ሊቀርብበትና ፈራሽ ሊሆን የሚችል ውል መሆኑን (voidable or invalid contract) የሚያሣዩ መሆናቸውን ከላይ ከዘረዘርነው የሕግ መሠረተ ሀሣብ የፍታብሔር ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል በመሠረታዊ ባህሪው በሞራላዊ ይዘቱና ዓላማው ከሰው ከመነገድ ጋር የሚነፃፀርና ሕገወጥ ውል /unlawful contract/ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በሽያጭ ውሉ ላይ አመልካች ሉሉ በማለት የሚዘረዝራቸው ጉድለቶች ውሉን ከጅምሩ እንዳልተደረገና ሕጋዊ ውጤት የሌለው /null or void contract/ የሚያደርጉ አይደለም፡፡ አመልካች የሚዘረዝራቸው የሕግ ጉድለቶች መኖራቸው ቢረጋገጥ እንኳን ውሉን ጉድለት ያለበትና በፍርድ ቤት ሊፈርስ የሚችል /voidable or invalid Contract/ ሊያደርግ የሚችል ጉድለት ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በጽሑፍና በቃል ባቀረቡት ክርክር የሽያጭ ውሉ ሕገወጥ የሆነ ውል/unlawful contract/ በመሆኑ ከጅምሩ እንዳልተደረገ መቆጠር የሚገባው(null or void contract) ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር ከላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች አልተቀበልነውም፡፡

2.የሽያጭ ውሉ ሲደረግ በተጠሪ በኩል አልተሟሉም በማለት አመልካች የሚያነሣቸው የሕግ መከራከሪዎች በተጠሪ የተካዱና በፍርድ ያልተረጋገጡ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ ጉድለቶቹ ሙሉ በሙሉ እውነት መሆናቸው ቢረጋገጥ እንኳ ውሉን ለማፍረስ ምክንያት የሚሆኑ /avoidable contract) የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1718 በግልጽ እንደተመለከተው ዳኞች ሕጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ገልፀው አንድ ውል ተፈፃሚ እንዲሆን የሚቀርብን ጥያቄ ውድቅ የሚያደርጉት ውሉ ሕገ ወጥ ውል /unlawfull contract/ ሆኖ ሲያገኙት ነው፡፡ ውሉን በፍርድ ቤት ተከራክሮ ለማፍረስ የሚቻል /invalid contract/ ከሆነ ውሉ ጉድለት አለበት የሚለው ወገን ውሉን ለማስፈረስ ጥያቄውን የሚያቀርብበትን የጊዜ ገደብ ሕግ አውጭው በሕግ ይደነግጋል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች የዱቄት ፋብሪካውን የሸጥኩት በአዋጅ ቁጥር 97/1990 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 216/92 በተደነገገው መሠረት ለብድር በመያዣነት የያዝኩትን ንብረት ነው፡፡ የሽያጩ ሥርዓትም በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 እና 5 የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 423 በሚደነግጉት መሠረት ሐራጁን ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ማስታወቂያ በማውጣት የተከናወነ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ባወጣው የሐራጅ ሽያጭ ስርዓቱ ተሣትፈው አሸናፊ በመሆን አመልካች የዱቄት ፋብሪካውን የያዙ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ተጠሪ በሐራጅ ንብረት ሲሸጥ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 394 እስከ አንቀጽ 449 የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ተጠሪ ባወጣው ሐራጅ ሽያጭ ተሣትፎ ያደረገው ውል እንዲፈርስለት የሚጠይቀው ተጠሪ ንብረቱን በአግባቡ በመያዣነት ያልያዘ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት ንብረቱን የመሸጥ መብት ሣይኖረው ነው የሸጠልኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ንብረቱን ለመሸጥ የሚያስችለው መብት በዱቄት ፋብሪካው ላይ እንዳለው በመግለጽ የሚከራከር ሲሆን ተጠሪ ንብረቱን ለአመልካች የሸጠው በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት ንብረቱን ለመሸጥ የሚችልበት መብት እያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች የሐራጅ ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስለት ጥያቄ ያቀረበው በሕግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ መወሰን ያስፈልጋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስለት የሚጠይቀው ተጠሪ የንብረቱን ባለሀብትነት በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚያስችለው መብት የለውም በማለት መሆኑን በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡ በተሸጠው ንብረት ላይ የፍርድ ባለእዳው መብት የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ሽያጩ እንዲፈርስለት ገዥ ማመልከት እንደሚችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 446 ይደነግጋል፡፡ አመልካች ተጠሪ ንብረቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚያስችል መብት የለውም የሚል በመሆኑ የአመልካች ክርክር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 446 ድንጋጌ ሥር የሚታቀፍ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 446 የተደነገገውን መሠረት በማድረግ የሐራጅ ሽያጭ እንዲፈርስለት የሚጠይቅ ገዥ ውሉን ለማስፈረስ ጥያቄውን ከሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ እንዳለበት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች ውሉ እንዲፈርስ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ያልጠየቀ በመሆኑና ከስድስት ዓመት በኋላ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ሕገወጥ ውል /unlawfull contract/ አለመሆኑን ከግንዛቤ ያስገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ውሣኔው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ከጅምሩ እንዳልተደረገና እንደሌለ የሚቆጠር /void contract/ ሣይሆን በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊፈርስ የሚችል /voidable or invalid contract/ ነው የሚል ይዘት ያለው መቃወሚያና ክርክር በአመልካች የቀረበበት መሆኑና የአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 446 እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው መሆኑን በማገንዘብና የእነዚህን ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ መሠረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ብይንና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ይህ ውሣኔ ተጠሪ የሸጠለትን የዱቄት ፋብሪካ የእኔ ነው ባይ ሰው የመጣበት እንደሆነ አመልካች ተጠሪ በዋቢነት እንዲቀርብለት ከመጠየቅ የሚገድበው አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
4. የከፍተኛው ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 54596

የካቲት 09 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ ጽ/ቤት ነ/ፈጅ ተስፋዬ ዘውዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ላቀች መንግሥቴ - ጠበቃ ዶ/ር ንዋይ ዘርጌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሊዝ ውል አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በአሁኑ አመልካችና በሌሎች ሁለት የመንግሥት ተቋማት ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፤ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13 ክልል ውስጥ የሚገኙ ቁጥራቸው 1055 እና 1056 የሆኑ ቤቶች ያረፉበትንና ስፋቱ 3139 ካ.ሜትር የሆነ ቦታ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካቲት 20 ቀን 1992 ዓ.ም በተፈረመ የሊዝ ውል ቦታውን ወስደው በእለቱ የቦታ ይዞታ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸው ቦታው በከፊልም ቢሆን በእጃቸው እንዳለ የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ አቤቱታ ቀርቦበት ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በሊዝ ቦርዱ ውሣኔ ከተሰጠ በሁዋላ በመንግሥት ቤቶች እና በፍትህ ሚኒስቴር አመልካችነት የሊዝ ውሉ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል እንዲሰረዝ ጥያቄው ለሊዝ ቦርድ ቀርቦ የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ ከሕግ ውጪ ቦርዱ መወሰኑን ገልፀው በሊዝ ውሉ የመጠቀም መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የሊዝ ውሉ ሊሰረዝ የቻለው በአዋጅ ቁጥር 20/1997፣ 34/2000 እና 272/1994 መሠረት መሆኑን ጠቅሶ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንደሌለው እና የዳኝነት ጥያቄውም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ በስር ፍርድ ቤት እንደየቅደም ተከተላቸው ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተከሣሽ የነበሩት የፍትህ ሚኒስቴርና የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ አቤቱታ ለማቅረብ በሕጉ አግባብ ሥልጣንና መብት ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የሊዝ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ከተወሰነ በሁዋላ እንደገና ታይቶ መሠረዙ ከአዋጅ ቁጥር 20/1997 አንቀጽ 5/11/ ድንጋጌ ውጪ ነው፣ ተጠሪ በቦታው ላይ ግንባታውን ያላከናወኑት ቦታው ሙሉ በሙሉ ነፃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኖ ሣይረከቡት በመቅረታቸው ከመሆኑም በላይ የሊዝ ውሉ ሊፈፀም ይገባል ተብሎ በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ አግኝቶ ባለበት ሁኔታ የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ መደረጉ ያላግባብ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 272/1994 አንቀጽ 15/ለ/ መሠረትም የሊዝ ውሉን ለመሠረዝ የሚያስችል የሕዝብ ጥቅም ስለመኖሩ ተረጋግጧል ለማለት አይቻልም የሚሉትን ምክንያቶች በመያዝ ተጠሪ በሊዝ ውሉ የመጠቀም መብታቸው ሊጠበቅላቸው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረፈጅ መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ስምንት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም ባጭሩ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 34/2000፣ 272/1994፣ 455/97፣ 555/2000 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 27604 እና 46052 የሰጣቸውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞችን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ አመልካች መወሰኑ ተገቢነት የለውም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰጠቱ ከአዋጅ ቁጥር 272/1994 እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 27604 ከሰጠው የሕግ ትርጉም ጋር ተገቢነቱን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ጥር 05 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ሰባት ገጽ ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመልሣቸው መሠረታዊ ይዘትም በጉዳዩ ላይ የተለያዩ ክርክሮች ቀርበውበት በፍርድ ቤት ውሣኔ ተጠሪ የሊዝ ውል መብት የተረጋገጠላቸው ከመሆኑም በላይ በዚህ በውሉ ጊዜ ግንባታውን ያላከናወኑትም ቦታው ሙሉ በሙሉ ነፃ ሁኖ ባለመረከባቸው መክንያት በመሆኑና ይህም በፍርድ ቤት ውሣኔ ጭምር የተረጋገጠ መሆኑን፣ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 34/2000 ተብሎ የሚጠቀሰው ሕግም በሕግ አግባብ የታወጀ ስለመሆኑ የሚያመላክት ነገር በሌለበት ሁኔታ የአመልካች እርምጃ በዚሁ አዋጅ መሠረት የተከናወነ ነው በማለት ክርክር መቅረቡ እውነት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረፈጅም ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፉት አራት ገጽ የመልስ መልስ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ለበርካታ ጊዜያት በጉዳዩ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ የፍርድ ባለመብት የሆኑ ከመሆኑም በላይ የሊዝ ቦርዱም ጉዳዩን ተመልክቶ የሊዝ ውሉ ሊሰረዝ እንደማይገባ በቃለ ጉባዔ ቁጥር 6/2000 አረጋግጦ ከወሰነ በሁዋላ የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የሊዝ ውሉን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሠረዙ አግባብ መሆኑን ገልፆ የቀድሞውን ውሣኔ ሽሮ ቦታው ለመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እንዲሸጥ የወሰነ መሆኑን ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ የሊዝ ቦርዱ የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊ ነው በማለት የሚከራከሩት አዋጅ ቁጥር 34/2000 “ን”

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት ያደረገ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ አዋጅ በሕጉ አግባብ የታወጀ አይደለም በማለት ተጠሪ ለአቀረቡት ክርክርም አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ያልታወጀ መሆኑን በመልስ መልሣቸው ላይ የአመልካች ነገረፈጅ አምነው አዋጅ አለ ለማለት ይቻላል በማለት የሚከራከሩት ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ በአስተዳደሩ አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት ለሚመለከታቸው አካላት በደብዳቤ ተልኳል፤ ተገልጿል የአስተዳደሩ የሕግ አወጣጥ ስርዓትም ለየት ያለ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም አለ የተባለውን አዋጅ ኮፒውን አስቀርቦ የተመለከተ ሲሆን የአመልካች ነገረ ፈጅ እንደአረጋገጡት በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነገር የሌለው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 20/1997 አንቀጽ 5/11/ መሠረት ቦርዱ በሊዝ ውል ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ የሚነሣ ቅሬታን መርምሮ ተገቢነት ካለው ውሣኔውን ለአንድ ጊዜ ብቻ ማሻሻል እንደሚችል በግልጽ የተደነገገ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ በቃለ ጉባዔ ቁጥር 6/2000 በቀድሞው ውሣኔ ላይ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ የቀድሞውን ውሣኔ መሻሻል እንደሌለበት የወሰነ ሲሆን የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠ የተባለው የሊዝ ውልን የሚሰርዝ ውሣኔ አዋጅ ቁጥር 20/1997 አንቀጽ 5/11/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚሰርዝ በሕጉ የወጣ አዋጅ በሌለበት ሁኔታ ነው፡፡ አዋጁ ቁጥር 34/2000 ተብሎ የሚጠቀሰው ሰነድ በሕጉ አግባብ የወጣና ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ ሲሆን አዋጁ በስራ ላይ ውሏል ቢባል እንኳ የሊዝ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ውሣኔ ከተሰጠ በሁዋላ በድጋሚ የሊዝ ውሉ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ቀርቦ ውሉ እንዲሰረዝ የተሰጠው ውሣኔ አዋጁ ተፈፃሚነት አለው ከተባለበት ከአንድ ቀን በሁዋላ መሆኑ ከውሉ አፈፃፀም ሁኔታ ጋር ያለው ተገቢነቱ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ተጠሪ በሊዝ ውሉ መሠረት ቦታውን ሙሉ በሙሉ እንዲረከቡ ይወሰንላቸው ዘንድ ጥያቄ አቅርበው ከስር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቦታውን እንዲረከቡ ውሣኔ ተሰጥቷቸው በጉዳዩ ላይ የፍርድ ባለመብት በመሆን በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 92111 የአፈፃፀም ጥያቄው አቅርበው ያልተፈፀመላቸው መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መረጋገጡ ተጠሪ በሊዝ ውሉ መሠረት በአንድ ዓመት ከስድስት ወር የጊዜ ገደብ ሕንፃውን የመገንባት ግዴታቸውን ያልተወጡት በራሣቸው ችግር ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት አለመኖሩን የሚያሣይ ነው፡፡ ሌላው የአመልካች ነገረፈጅ አጥብቆ የሚከራከሩት የሊዝ ውሉ በአዋጅ ቁጥር 272/1994 አንቀጽ 15 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የሊዝ ውሉን የመሠረዝ ስልጣን የአስተደደር አካል የሆነው የሊዝ ቦርድ ነው፣ ፍርድ ቤቶች ሊመለከቱ አይገባም በማለት ነው፡፡ በመሠረቱ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37/1/ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሣየው ጉዳይ ነው፡ ከዚሁ የሕገ መንግሥት ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ፍርድ ቤቶች አንድ ጉዳይ /አቤቱታ/ ተቀብለው ውሣኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ /አቤቱታ/ ተቀብለው ውሣኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ መሆኑን ነው፡፡ በሕግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍርድ ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ሥልጣን ስለሌለው በሕጉ መሠረት ለአንድ አስተዳደር አካል ቀርቦ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወይም ለአስተዳደር መቅረብ የሚገባውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ሊያስተናግደውም ሆነ አከራክሮ ውሣኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ለአንድ የመንግሥት አካል በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሰጡት ሕጎች መጠበቅና መከበር ያለባቸው ሲሆን የዳኝነት አካል ስልጣንም በሕግ የተወሰነ ስለሆነ ሕግ የተመርጎም ስራው በሕጉ በተመለከተው አድማስ የሚመራ ይሆናል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4 ድንጋጌ የሚያሣየውም ፍርድ ቤቶች በሌላ ሕግ በግልጽ በታገዱ ጉዳዮች ላይ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በአስተዳደራዊ ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በሕግ ተለየተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ /ክርክር/ መሠረት ያደረገው ከአመልካች ጋር ባደረጉት የሊዝ ውል የተሰጠውን ቦታ የሊዝ ውሉ ከውሉ አፈፃፀም መሠረታዊ ባህርያትና ከሕግ ውጪ ተሰርዞ ቦታው ለመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እንዲሰጥ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው። አዋጅ ቁጥር 272/1994 የሊዝ ቦታ የሚሰጥበትና ውሉ የሚቋረጥበትን አግባብ ዘርግቷል። የአዋጁ አንቀጽ 15፣16 እና 17 ድንጋጌዎች ሲታዩ የሊዝ ውል የሚቋረጥበትንና ካሣ የሚከፈልበትን አግባብ፣ ጉዳዩን ሊመለከቱ የሚችሉ ወገኖችንና የይግባኝ አቀራረብን ሥርዓት ደንግገው እናገኛለን።

በተያዘው ጉዳይ የሊዝ ውል እንዲቋረጥ ተደርጓል የሚባለው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ነው በሚል ምክንያት በመሆኑ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸው የአዋጅ ቁጥር 272/94 ድንጋጌዎች አንቀጽ 15/1/ለ/ እና 16 ናቸው። የአንቀጽ 15/1ለ/ ድንጋጌ የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ለሌላ ስራ ወይም አገልግሎት እንዲውል ሲወሰን ሊቋረጥ እንደሚችል የተመለከተ ሲሆን በአንቀጽ 16/1/ ደግሞ አግባብ ያለው አካል ለሕዝብ ጥቅም ይውላል ተብሎ በሚወስነው መሠረት ለሚመለከተው አካል የማስለቀቂያ ትእዛዝ ወይም ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ በመስጠት የሚገለገለውን የከተማ ቦታ ማስለቀቅና መረከብ እንደሚችል አስቀምጧል። የአዋጁ አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ሲታይም በአንቀጽ 16 መሠረት የማስለቀቅ ትእዛዝ የደረሰው ወይም ትእዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ወገን የካሣም ሆነ ማንኛውንም ለፍርድ ሊቀርብ የሚገባው ሌላ አቤቱታ ከዝርዝር ምክንያቱ እና ማስረጃው ጋር ትእዛዙን ለሰጠው አካል የማቅረብ መብት አንዳለው ያስገነዝባል። በዚህ መልኩ ቀርቦ የታየ ጉዳይም በአንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ስር የተመለከተውን ተገቢ ዳኝነት የሚሰጥበት ሲሆን በውሣኔው የማይስማማ ሰው ለጉባዔው ይግባኙን ማቅረብ እንደሚችል በአንቀጽ 18/1/ ስር ተደንግጎ ያለ ከመሆኑም በላይ ይህ አካል የሚሰጠው ውሣኔ ካሣ አነሰኝ ወይም ካሣ በዛብኝ ወይም ካሣ ተከለከልኩ በሚል ክርክሮች ላይ ካልሆነ በስተቀር በሕግም ሆነ በፍሬ ነገሮች ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ስለመሆኑ የጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሦስት ድንጋጌ ያሣያል። ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው በሊዝ የተሰጠ ቦታን የሚመለከተው አካል ማስለቀቅ የሚችለውና ጉዳዩ ላይ ጉባዔው የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ እና በፍርድ ቤት ሊቀርብ የማይገባው ቀድሞ የቦታ ማስለቀቁ እርምጃ የተወሰደው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ነው። አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 2/7/ ስለሕዝብ ጥቅም ትርጉም አስቀምጧል። በዚህም መሠረት የሕዝብ ጥቅም ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሕዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የከተማ ልማትን በቀጣይነት ለማጎልበት አግባብ ያለው አካል በመሪ ፕላን ወይም በልማት እቅድ የሕዝብ ጥቅም ብሎ የሚወስነው ነው በሚል ትርጓሜ የተቀመጠ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 455/97ም ተመሣሣይ ይዘት ያለውን ትርጉም በአንቀጽ 2/5/ ስር ይዞ እናገኛለን።

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ጉዳዩ ከሕዝብ ጥቅም ጋር የተገናኘ ነው በሚል ያቀረበው ክርክር በበታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያላገኘው የሊዝ ውሉ የተሰረዘበት መንገድ ሕጉ ከደነገገው ስርዓት ውጪ ነው ከሚል ምክንያት በተጨማሪ ቀድሞውንም ቢሆን የሊዝ ውሉ የሚሰርዝበት ምክንያት የለውም ተብሎ በመወሰኑ፣ በአዋጅ ቁጥር 555/2000 ስር ለመንግሥት ቤቶች የተሰጠው ስልጣንም ጉዳዩን የማይማለከተው መሆኑን፣ በአዋጅ ቁጥር 471/1998 መሠረት ለፍትህ ሚ/ር የተሰጠው ስልጣንም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል አቤቱታ ማቅረብ የሚችል መሆኑን ቢያሣይም በተያዘው ጉዳይ ግን ከሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የበላይነት መርህ ጋር በሚጋጭ መልኩ የፍርድ ቤትን ውሣኔ ውጤት ሊያሣጣ የሚችል ሁኖ ተገኝቷል በሚሉት ምክንያቶች መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ከላይ እንደተመለከተውም ተጠሪ በተለያዩ የክርክር መስመሮችና ደረጃዎች በሕጉ አግባብ በተቋቋመ የሊዝ ውል የቦታው ሕጋዊ ባለይዞታ መሆናቸው ተረጋግጦላቸዋል፡፡ ስለሆነም የፍርድ ቤት ውሣኔ ስለአለ ብቻ ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ንብረት አይወሰድም ለማለት የማይቻል ቢሆንም ከተያዘው ጉዳይ ልዩ ባሕርይ አንፃር ሲታይ ግን የአመልካች እርምጃ ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ የተወሰደ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው የአመልካች ነገረፈጅ አጥብቀው የሚከራከሩትና ሰበር ችሎቱ እንዲመለከተው የተያዘው ጭብጥ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 27604 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር ስላለው ተገቢነት የሚመለከት ነው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 27604 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የቦታ ምስክር ወረቀት ይሰጠኝ ጥያቄን በሚመለከት የተነሣን ክርክር መሠረት ያደረገ ሲሆን በችሎቱ የተሰጠው ትርጉምም እንዲህ አይነት የቦታ ወይም ይዞታ ይሰጠኝ ጥያቄዎችን በመቀበል እየመረመረ ለቦታ ጥያቄዎች ቦታ የመመደብ፣ የይዞታ ምስክር ወረቀት የመስጠት የከተማው አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት እንጂ በፍርድ የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም የሚል ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ክስ የመሠረቱት ከሊዝ ውል አፈፃፀም ጋር የተያያዘ እንጂ የቦታ ወይም የይዞታ ይሰጠኝ ጥያቄ አይደለም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄና የአመልካች ክርክር በመ/ቁጥር 27604 በተያዘው ጉዳይ ካለው ፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ሙሉ በሙሉ ግንኙነት አለው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ምክንያቱም የተጠሪ ክስ መሠረቱ የሊዝ ውል ሆኖ ውሉ ተጥሷል በሚል ዳኝነት የጠየቁ ስለመሆኑ የሚያሣይ ነውና፡፡ ሌላው የአመልካች ነገረፈጅ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 46052 የሰጠው የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ሲታይም የሊዝ ውሉን ከከተማው አስተዳደር ጋር አደረጉ የተባሉት ግለሰብ ቦታውን ሙሉ በሙሉ ተረክበው በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ባለማከናወናቸው የሊዝ ውሉ የተሰረዘ ስለመሆኑ ስለሚያሣይ ሲሆን አሁን በእጃችን ባለው ጉዳይ ግን መሠረታዊ ክርክሩ የሊዝ ውሉ ያላግባብ ተሰርሧል የሚል ቢሆንም ቦታውን ተጠሪ በከፊል በመረከባቸው ምክንያት በገቡት ግዴታ መሠረት ግንባታውን ሊያከናውኑ ያልቻሉ መሆኑ በፍርድ ቤት ውሣኔ ጭምር የተረጋገጠ በመሆኑ በመ/ቁጥር 46052 ከተያዘውና የሊዝ ውሉን ከከተማው አስተዳደር ጋር አደረጉ የተባሉት ግለሰብ ቦታውን ሙሉ በሙሉ ተረክበው በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ባለማከናወናቸው የሊዝ ውሉ የተሰረዘ ስለመሆኑ ከሚያሣይ ውሣኔ ጋር በፍሬ ነገር ደረጃ ጉልሕ ልዩነት ያለበት በመሆኑ የመ/ቁጥር 46052 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ነው ተብሎ ለዚህ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/4/ መሠረት የሚጠቀስበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም የተጠሪ ጥያቄ የአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ ጽ/ቤት በሊዝ የተወሰደ ቦታን ከሕግ ውጪ የሊዝ የምስክር ወረቀትን በመሠረዝ ሕገ ወጥ እርምጃ ወስዷል በማለት በዚህ ውል ያገኙት የንብረት መብታቸው /የኢ.ፌ.ዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/6 ይመለከታል/ በፍርድ እንዲጠበቅላቸው የሚጠይቅ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊስተናገድ የሚገባው እና ውሣኔ የሚሰጥበት ጉዳይ ሁኖ ክርክሩ ሲጀመር የክርክሩ ተሣታፊ ከነበሩት አካላት ማንነት አንፃር ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መቅረቡም ሆኖ የአመልካች ክርክር ውድቅ ሁኖ ተጠሪ በሊዝ ውሉ የመጠቀም መብታቸው እንዲጠበቅ በማለት የተሰጠው ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 272/94፣ 20/1997፣ 555/2000፣ ከአዋጅ ቁጥር 471/1998 ድንጋጌዎች እንዲሁም ከውል አፈፃፀም መሠረታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርሆዎች ጋር ተጣምዶ ሲታይ ሕጋዊ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት በውሣኔው ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 66717 ጥር 27 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 46194 ጥር 07 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 07 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሳህሉ ሙሉጌታ - ጠበቃ ወንድም ጌታሁን ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሰለሞን ኤፍሬም
2. አቶ ጌታቸው ኤፍሬም — አቶ ደረጀ ወርቁ ቀረቡ
3. አቶ መስፍን ኤፍሬም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪዎች ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች አመልካች ታህሣስ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. በተጻፈ የሽያጭ ውል በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/12 የሚገኙ ቁጥራቸው 595 እና 596 የሆነ ቤቶች በብር 1,330,000 /አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሠላሳ ሺህ ብር/ ለመሸጥ ተስማምቶ ብር 206,000 /ሁለት መቶ ስድስት ሺህ ብር/ ቀብድ ተቀብሏል፡፡ ተከሣሽ /አመልካች/ የቤት ሽያጭ ውሉን መሠረዙን በደብዳቤ የገለፀ ሲሆን እኛም በሽያጭ ውሉ መሠረት ቤቱን እንዲያስረክበን ማስጠንቀቂያ ሰጥተነዋል፡፡ ተከሣሽ/አመልካች/ ቤቱን ተገድዶ እንዲያስረክበን እንዲወስንልን ይህ ቢታለፍ በውሉ የተቀመጠውን የገደብ መቀጫና የቀብዱን ገንዘብ አጠፌታ አድርጎ እንዲመልስ ይወሰንልን በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከከሣሾች/ተጠሪዎች/ ጋር በሕጉ አግባብ ያደረግሁት የቤት ሽያጭ ውል የለም፡፡ ተጠሪዎች/ከሣሾች/ ያቀረቡት ውል በውል አዋዋይ ፊት ወይም በፍ/ቤት መዝገብ ሹም ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ከረቂቅነት አልፎ ሕጋዊ አስገዳጅነት የሌለው በመሆኑ የከሣሾች/ተጠሪዎች/ ክስ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የቃልና የጽሑፍ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በከሣሾች/ተጠሪዎች/ እና በአመልካች/ተከሣሽ/ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለውም? ተከሣሽ/አመልካች/ የቤት ሽያጭ ውሉን ተገድዶ መፈፀም አለበት ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦችና ሌላ ሦስተኛ ጭብጥ ከመሠረተ በኋላ በከሣሾችና/በተጠሪዎች/ና በአመልካች/ተከሣሽ/ መካከል ሕጋዊ አስገዳጅነት ያለውና የፀና የቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሽያጭ አለ በማለት ስለ ቀብድ የተደነገጉ የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎችና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰበር መዝገብ ቁጥር 36887 መሠረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተከሣሽ/አመልካች/ የቤት ሽያጭ ውሉን በፍርድ ተገዳዶ ይፈፅም ከሣሾች/ተጠሪዎች/ ቀሪውን የቤቱን ዋጋ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቀርቧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ግንቦት 16 ቀን 1992 ዓ.ም. በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውል አዋዋይ ወይም በፍ/ቤት መዝገብ ሹም ፊት ያልተረገ ውል ሕጋዊ አስገዳጅነትና የፀና ውል ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21448 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ከተጠሪዎች ጋር ያደረግሁት የቤት ሽያጭ ውል የለም እንጅ አለ ቢባል እንኳን ተጠሪዎች በውሉ አደራረግ ወቅት የተለያዩ ተዕዕኖ ያደረጉ በመሆናቸውና ጉድለት የሌለ በመሆኑ አላግባብ የገደብ መቀጮና ቀብዱ አጠፊታ ሆኖ እንዲከፈል ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢ አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ውሉ እንዲፈፀም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ጥር 4 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ አመልካች ቤቶቹን አልሸጥኩም የሚል ክርክር አላቀረቡም፡፡ አመልካች የሸያጭ ውሉን መኖሩን አምኖ በሚከራከርበት ሁኔታ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ በመጥቀሱ ብቻ የውሉ አስገዳጅነት እንደማይቀር የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት የሕግ ትርጉም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36887 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉምና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1883 ድንጋጌን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተገቢነት የለውም፡፡ የሸያጭ ውሉን አመልካች እንዲፈፅሙ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔም የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ በሥር ስለ ቀብድና መቀጮ የተሰጠ ውሣኔ በሌለበት ሁኔታ አመልካች የሰበር አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የፀና የቤት ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለም? በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የፀና የቤት ሽያጭ ውል አለ የሚባል ቢሆን የአመልካች ግዴታና ኃላፊነት ምንድን ነው? የሚሉትን ጭብጦች መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ታህሣስ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. በተጻፈ የቤት ሽያጭ ውል በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/12 የቤት ቁጥር 595 እና የቤት ቁጥር 596 በብር 1,330,000 /አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሠላሳ ሺህ ብር/ እንደገዙና አመልካች ከቤቶቹ ዋጋ ብር 206,000 /ሁለት መቶ ስድስት ሺህ ብር/ ቀብድ እንደወሰዱ ለሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክሥ ማመልከቻ ገልጸዋል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በቀብድ መልክ ወስደዋል በማለት የገለፁትን ብር 206,000 /ሁለት መቶ ስድስት ሺህ ብር/ አልወሰድኩም በማለት በግልፅ ክደው ያልተከራከሩ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህም አመልካች ከተጠሪዎች የቤት ሽያጭ ቀብድ ገንዘብ የተቀበሉ መሆኑን እንዳመኑ እንደሚቆጠር በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1/ሠ/ እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን መነሻ በማድረግ ብር 206,000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/ሁለት መቶ ስድስት ሺህ ብር/ መቀበላቸውን በግልፅ ክደው ያልተከራከሩና ይህም የቀብድ ገንዘብ መቀበላቸውን እንዳመኑ ከላይ በተገለፁት የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የሚቆጠር ነው፡፡ አንዱ ወገን ለአንዱ ወገን ቀብድ መስጠቱ በማያከራክር ሁኔታ ውሉ መደረጉን እንደሚያረጋግጥ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1883 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በሥር ክርክሩን አይቶ የወሰነው የከፍተኛ ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36887 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በተዛባ መንገድ በመረዳት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ አድርጓል በማለት አመልካች ሰፊ ክርክር አቅርበዋል፡፡ በእኛ በኩል የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን የወሰነው በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በጽሑፍ የተደረገውን የሽያጭ ውል ብቻ መሠረት በማድረግ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የፀና የቤት ሽያጭ ውል አለ ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው በመካከላቸው ተደርጓል የተባለውንና ይህንኑ ፎርም አላሟላም የሚል ክርክር በቀረበበት የጽሑፍ ውል ላይ ብቻ በመመራት እና በመመልከት ሣይሆን ተጠሪዎች ለአመልካች የቀብድ ገንዘብ የከፈሉ መሆኑንና አመልካችም የቀብድ ገንዘቡን ከተጠሪዎች የተቀበሉ መሆናቸውን ማመናቸው በሕግ በኩል ያለውን ውጤት በመመዘን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የቀብድ ገንዘብ መቀበላቸውን ያልካዱና የቀብድ ገንዘብ እንደተቀበሉ የሚቆጠር በመሆኑና ይህም የቤት ሽያጭ ውሉ መደረጉን በማያከራክር ሁኔታ እንደሚያረጋግጥ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1883 በግልጽ የተደነገገ መሆኑን አመልካች ውሉን በተናጥል ያፈረሰ መሆኑን በመግለጽ ማስጠንቀቂያ የጻፈ መሆኑን ክዶ ያልተከራከረ መሆኑን በማገናዘብ የሥር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በዚህ መዝገብ ያለውን ልዩ ሁኔታ የቀብድ ገንዘብ ክፍያ የሽያጭ ውሉ መኖሩን በማረጋገጥ በኩል የሚኖረውን የአስረጅነት ዋጋ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1883 የተደነገገውን መሠረት ያደረገና የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የሥር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን እንዲፈጽም የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ሲሆን ይህንንም ለመወሰን በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል መሠረታዊ ባህሪና አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መመርመር ያስፈልጋል፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች ታህሣስ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የቤቱ ሻጭ የተባሉት አመልካችና የቤቱ ገዥ የሆኑት ተጠሪዎች ቀብድ የተቀባበሉበት ውል መሆኑ በሽያጭ ውሉ በግልፅ የተመለከተ መሆኑን ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ከተጠሪዎች የቀብድ ገንዘብ የተቀበሉ መሆኑን በማመን ተጠሪዎች የውል ግዴታቸውን ስላልተወጡ ውሉን በተናጠል ያፈረሱ መሆኑን በመግለፅ ጥቅምት 22 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ለተጠሪዎች አሳውቀዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ተጠሪዎች የከፈሉትን ቀብድ በመልቀቅ ውሉን የማፍረስ መብታቸውን ቀሪ ያደረጉ መሆኑና በተመሣሣይ ሁኔታ አመልካች የተቀበሉትን የቀብድ ገንዘብ አጠፊታ በመክፈል ውሉን የማፍረስ መብታቸውን ቀሪ ያደረጉ ስለመሆኑ በአመልካችም ሆነ በተጠሪዎች የቀረበ ማስረጃ እንደሌለ ከሥር ፍ/ቤትና በሰበር ከተደረገው ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በውላቸው ሌላ ስምምነት ከሌለ በቀር ቀብድ የተቀበለው ወገን የተቀበለውን ቀብድ አጠፊታ በመክፈል ውለታውን ማፍረስ እንደሚችል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1885 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ይህን የሕግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ውሉን የማፍረስ መብታቸውን ቀሪ የሚያደርግ ተቃራኒ ስምምነት ያደረጉ መሆኑን ተጠሪዎች እስካላስረዱ ድረስ አመልካች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1885 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን በማሟላት የሽያጭ ውሉን የማፍረስ መብት አላቸው፡፡ ተጠሪዎች አመልካች የሽያጭ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ ካልሆኑ በአማራጭ የቀብዱን ገንዘብ አጠፊታ አድርገው እንዲከፍሉ እንዲዋሰንላቸው ያቀረቡት ክስ አመልካች ቀብዱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጠፊታ በመክፈል ውሉን የማፍረስ መብታቸውን ቀሪ የሚያደርግ ተቃራኒ ስምምነት ያላደረጉ መሆኑን የማያመላክት ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤትና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የቀብድ ገንዘብ የተከፈለበት ውል በመሆኑ ውሉን በማፍረስ በኩል አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች ያላቸውን መብትና ውሉን ሲያፈርስ በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት ከግንዛቤ ውስጥ ሣያስገቡ አመልካች ቤቶቹን ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡና የሽያጭ ውሉን እንዲፈፅሙ የሰጡት ውሣኔ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1885 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም የከፍተኛው ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን እንዲፈጽምና ቤቶቹን እንዲያስረክብ የሰጡትን ውሣኔ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት በማሻሻል አመልካች ከተጠሪዎች የተቀበለውን ቀብድ ብር 206,000 /ሁለት መቶ ስድስት ሺህ ብር/ አጠፊታ አድርጎ ብር 412,000 /አራት መቶ አሥራ ሁለት ሺህ ብር/ ለተጠሪዎች በመክፈል የሽያጭ ውሉን ማፍረስ ይችላል በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1885 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
4. አመልካች ከተጠሪዎች የተቀበለውን የቀብድ ገንዘብ አጠፊታ ማለትም ብር 412,000 /አራት መቶ አሥራ ሁለት ሺህ ብር/ ለተጠሪዎች ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ. 58258

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጉስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ዮርዳኖስ ሐጉስ አልቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ሐይማኖት ተፈራ ጠበቃ አቶ ፋንታሁን አባተ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ጉዳይ ተዋዋይ ወገኖች በውላቸው የወሰኑት መቀጫ/ገደብ/ እንዲፈፀም የሚያስገድድ ሆኔታ መኖር አለመኖሩን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1889-1895 ካሉት ድንጋጌዎች አንፃር መመርመርን የሚጠይቅ ነው፡፡

ለክርክሩ መነሻ ሆኖ የተገኘው የካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገ የቤት ኪራይ ውል ነው፡፡ በዚህ ውል የአሁኗ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ ካልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ አዲስ የሆነ ቤት ለትምህርት ቤት አገልግሎት ይውላል ተብሎ ለአሁኗ ተጠሪ በወር ብር 10,000 የኪራይ ሂሣብ ለ5 ዓመት ለማከራየት ተስማምተዋል፡፡ የቅድሚያ ክፍያ ብር 60,000 ከተከራይዋ ወስደዋል፡፡ በኪራይ ውሉ አከራይ ቤቱን አጥረው ነሐሴ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ለተከራይዋ ለማስረከብ ግዴታ ገብትዋል፡፡ በውሉ መሠረት ባይፈጽሙ መቀጮ/ገደብ/ ብር 50,000 ለመክፈል ተስማምተዋል፡፡

በኪራይ ውሉ መሠረት ቤቱን አጥረው ሊያስረክቡኝ አልቻሉም ማስጠንቀቂያም ተጽፎላቸው በውሉ መሠረት ሣይፈጽሙ ቀርተዋል ቤቱንም ለታሰበለት አገልግሎት ለማዋል ስላልተቻለ ውሉን አፍርሰዋል ስለዚህ በቅድሚያ የተቀበሉትን ብር 60,000 ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም ቤቱን ባለማስረከብ ውሉን ስላፈረሱ በውሉ ላይ የተወሰነውን መቀጫ/ገደብ/ ብር 50,000 አከራይዋ የአሁኗ አመልካች ሊከፍሉኝ ይገባል በሚል ወደ ፍርድ ቤት ክስ ያመሩት ተከራይ የሆኑት የአሆኗ ተጠሪ ናቸው፡፡ ተከሣሽዋ የአሁኗ አመልካች ክሱ ደርሷቸው በሰጡት መልስ የውል ግዴታዬን ለመወጣት በመንቀሳቀስ ላይ እያለሁ የቀለሉ መስተዳድር ያጠርኩትን አጥር አፍርሶብኛል እንዳላጥርም ከልክሎኛል ውሉ ሣይፈፀም የቀረው በተከሣሽ ጥፋት አይደለም ቤቱም ለትምርት ቤት አገልግሎት ሊውል አይችልም ተብሏል፡፡ ውሉ በእኔ ጥፋት ስላልፈረሰ ገደብና ወለድ ሊከፍል አይገባም ኪሣራ በሌለበት ገደብና ወለድ በክሱ የተጠየቀው ያለ አግባብ ነው፡፡ ውሉ እንደማይፈፀም ከታወቀ በኃላ ከሣሽ ገንዘባቸውን እንዲወስዱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚሉትን ክርክሮች አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክሱን የግራቀኙን ክርክሮችና ማስረጃዎች መርምሮ በሰጠው ፍርድ አከራይዋ ቤቱን እንዳላጠሩ የቀበሌ መስተዳድር ከልክሎኛል የሚለውን ለማሰረዳት ያቀረቡት ቀበሌው የፃፈው ደብዳቤ ከይዞታቸው ውጪ የያዙት የመንግሥት መሬት መኖሩን የሚያስረዳ ነው፡፡ ከራሣቸው የካርታ ይዞታ ውጭ ያለ ቦታ አጥረው ለከሣሽ ለማስረከብ መንቀሳቀሳቸው ህጋዊ አይደለም በዚህ ምክንያት ለከሣሽ ማስረከብ የነበረባቸውን ቤት ሣያስረክቡ መቀረታቸው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በውሉ መሠረት ሣይፈጽሙ ቀርተዋል ሊባል አይችልም አንድ የትምህርት ቢሮ ተወካይ ማህተም በተደረገበት ደብዳቤ መፃፃፍ ሣይሆን በቃሉ ቤትና ቦታው ለትምህርት ቤት አገልግሎት ሊውል አይችልም ብሉ ክልክሏል የተባለውም ተቀባይነት የለውም አከራይ የዉል ግዴታቸውን ባለመፈፀማቸው ምክንያት የኪራይ ውሉ ፈርሷል፡፡ በቅድሚያ የተቀበሉትን ብር 60,000 ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ /9%/ ጋር እና በኪራይ ውሉ መሠረት ባለመፈፀማቸው በውሉ ላይ የተስማሙበትን ብር 50,000 ፍርዱ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሣሽዋ ለአሁኗ ተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኗ አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርበው ያስረቀርባል ተብሎ ግራቀኙ ቀርበው ክርክሩ ከተሰማ በኃላ ከፍተኛው ፍ/ቤትም መርምሮ በሰጠው ፍርድ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ምክንያት አልተገኘም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የአሁኗ አልካች በኪራይ ውሉ ላይ የተመለከተውን መቀጫ ብር 50,000 ፍርዱ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለአሁኗ ተጠሪ እንዲከፍሉ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የቀረበ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመወሰኑ ማመልከቻው ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት የተጠሪ ጠበቃ በጽሑፍ በሰጡት መልስ ውሉ ሣይፈጽም የቀረው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው የሚያሰኝ ነገር አለመኖርን ውሉ እንዳይፈፀም ያደረጉት አመልካች ራሣቸው እንደሆኑ ፣ በውሉ ወሉን አፍራሹ ወገን መቀጫ ብር 50,000 ለመክፈል ግዴታ ስለመግባቱ እና አመልካችም በውሉ መሠረት ሣይፈጽሙ መቅረታቸው በውሉ የተወሰነውን መቀጫ በክሱ እንዲከፍሉ ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤት በሕጉ አግባብ አይቶ እንዲከፍሉ ስለመወሰኑ በመዘርዘር ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በተጠሪ በኩል በተሰጠው መልስ ላይ የመልስ መልስ መስጠት አያስፈልገኝም ብለዋል፡፡

ጉዳዩም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በአሁኗ አመልካችና ተጠሪ መካከል የካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በጽሑፍ የቤት ኪራይ ውሉ ተደርጓል፡፡ አመልካች የቤቱ አከራይ ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ተከራይ ናቸው፡፡ ተከራይ ቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውሉ የተከራዩት ለትምርት ቤት አገልግሎት ሊጠቀሙበት ነው። ተከራይ ለቤቱ ኪራይ በየወር ብር 10,000 የሚከፍሉ ሆኖ በቅድሚያ ብር 60,000 ለአከራይ ከፍለዋል። ቤቱ በተከራይዋ በኩል ለተፈለገበት ለትምህርት ቤት አገልግሎት እንዲውል ከነቦታ ይዞታው መታጠር ያለበት ስለመሆኑ በውሉ አምነውበት አከራይዋ አጥረው ለማስረከብ ግዴታ ገብተዋል። ውሉን የካቲት 19 ቀን 2000ዓ.ም ተፈራርመው ማስረከቢያው ከ5 ወር በኃላ ነሐሴ 1 ቀን 2000ዓ.ም እንዲሆን የተሰማሙትም በዚህ ጊዜ ውስጥ አከራይ የአጥሩን ሥራ ለማጠናቀቅ እንዲችሉ ታስቦ ነው።

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2900 አከራይ ያከራየውን የማይንቀሳቀስ ሀብት ከተጨማሪ ዕቃዎቹና በውሉ መሠረት ወይም በሀብቱ ተፈጥሮ መሠረት ለተመደበበት ጉዳይ ሊያገለግል በሚችልበት ሁኔታ አሟልቶ ለተከራዩ ማስረከብ እንዳለበት ደንግጓል።

በዚህ ጉዳይ ቤት አከራይ የሆኑት የአሁኗ አመልካች ቤቱ በውሉ ለተመደበበት ጉዳይ ሊያገለግል በሚችልበት ሁኔታ አጥረውና አሟልተው በውሉ በተወሰነው የማስረከቢያ ግዜ ለተከራይዋ ለአሁኗ ተጠሪ ሣያስረክቡ ቀርተዋል።

አመልካች በኪራይ ውሉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አሟልተው ቤቱን ለተከራይ የማስረከብ ግዴታቸውን ባለመፈፀማቸው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1784 መሠረት ውሉ ቀሪ እንዲሆን ተደርጓል።

አመልካች በውሉ መሠረት ሊፈጽሙ ባለመቻላቸው ውሉ ቀሪ መሆኑ ከተረጋገጠ በውሉ ላይ የተወሰነውን መቀጫ /ገደብ/ ብር 50,000 ለተከራይዋ ለአሁኗ ተጠሪ ለመክፈል ይገደዳሉ ወይንስ አይገደዱም; የሚለውን ዋናውን የክርክር ጭብጥ በተመለከተም አመልካች በውሉ መሠረት ያልፈፀምኩት የቀበሌ መስተዳዳር ቤቱን እንዳላጥር በመከልከሉና ያጠርኩትንም በማፍረሱ ስለሆነ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም አመልካች ራሣቸው በጽሑፍ ማስረጃነት ለፈዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት የቀበሌ መስተዳድር የፃፈው ደብዳቤ እንዳያጥሩ የተደረገው ከይዞታቸው ውጭ የመንግሥት ቦታን ጨምረው በመከለል በመያዛቸው ምክንያት መሆኑን እንደሚያስረዳ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሚያሣይ በመሆኑና አመልካችም በስር አቤቱታቸው ላይ ቀበሌው ይህንን አላለም በሚል የገለጹት ነገር ስለሌለ በሕጉ ከአቅም በላይ የሚል ትርጉም የሚሰጠው አይደለም። ሁለተኛውን ምክንያት በሚመለከት ቤትና ቦታው ለትምርት ቤት አገልግሎት ሊውል የሚችል አይደለም ተብሏል የሚለውን የፈዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከቀበሌው የትምህርት ቢሮ በጽሑፍ ተገልጾ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩንና ተወካዩ በቃል ተናግሯል የተባለው በቂ አለመሆኑን በማለጽ ሣይቀበለው ስለቀረ በሰበር ደረጃ የሚመረመር አይደለም። ስለዚህ የአሁኗ አመልካች በውሉ መሠረት ያልፈፀምኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም። ለውሉ መፍረስ ተጠያቂ የሚሆኑት አመልካች ናቸው።

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1889 አንደኛው ወገን ግዴታውን ያልፈፀመ እንደሆነ ወይም አጓድሎ ወይም አዘግይቶ የፈፀመ እንደሆነ የሚከፈለውን መቀጮ ተዋዋዮች አስቀድመው በውላቸው ለመወሰን እንደሚችሉ ያስረዳል።

በተያዘው ጉዳይም በዚሁ ሕግ መሠረት የአሁኗ አመልካች በውሉ መሠረት ግዴታቸውን ካልፈፀሙ መቀጮ ብር 50,000 ለመክፈል ተስማምተዋል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1891 ባለገንዘቡ መቀጫ /ገደብ/ ሊቀበል የሚገባው ውሉ ባለመፈፀሙ ኪሣራ ለመጠየቅ በሚችልበት ጊዜ ሁሉ እንደሆነ ይገልፃል፡፡

ከዚህ ሌላ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1892/1/ ላይ የተመለከተውም ሲታይ ባለገንዘቡ ኪሣራ ባይደረስበትም የተዋዋለው መቀጫ/ገደብ/ ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ የሚደነግግ ነው፡፡

አመልካች ተጠሪዋ በውሉ አለመፈፀም ምክንያት የደረሰባቸው ኪሣራ ስለሌለ መቀጫ ሊከፈላቸው አይገባም በሚል ያቀረቡት ክርክርም ከፍሲል በተጠቀሰው ድግጋጌ መሠረት ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡

በሕጉም መቀጫውን ለመቀነስ የሚያስችል ምክንያት አልተገኘም፡፡

በመሆኑም የአሁኗ አመልካች በውላቸው የተወሰነውን መቀጫ /ገደብ/ ብር 50,000 ለአሁኗ ተጠሪ እንዲከፍሉ በመወሰኑ የሚታይበት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

በሌላ በኩል ግን እንደ ውሉ ባለመፈፀሙ በተወሰነው የቅጣት ገንዘብ ላይ ህጋዊ ወለድ ታስቦ እንዲከፈልበት የተወሰነው በሕጉ የሚደገፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከፍርዱ በኋላም ቢሆን በመቀጫ ገንዘብ ላይ ህጋዊ ወለድ /9%/ ታስቦ እንዲከፈል መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ መታረም የሚገባው ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14189, በ22/10/2001, በመቀጫው ብር 50,000 ላይ ወለድ 9% እንዲከፈልበት የወሰነው እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 84660, በ28/10/2002 ይህንኑ ያፀናበት ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎ የአሁኗ አመልካች የመቀጫውን ገንዘብ ብር 50,000 ያለ ወለድ ለአሁኗ ተጠሪ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
2. በዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 60469

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ኮከብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ - ጠበቃ ነቅዓጥበበ በየነ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ሙሉ ዓለም የሥራ አመራር አማካሪዎች - ሙሉሸዋ ወልደ ማርያም ሥራ አስኪያጅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ሲሆን ተጠሪም በበኩሉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በአመልካች ላይ አቅርቧል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት መሠረታዊ ጉዳይ የሙያ ሥራ አገልግሎት ውል አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ የድርጅቱን መዋቅር ለማስጠናት ያወጣሁትን ጨረታ አሸናፊ በመሆን የድርጅቱን መዋቅር በስልሣ ቀን ውስጥ ሰርቶ ለማስረከብ ታህሣሥ 4 ቀን 1999 ዓ.ም የውል ግዴታ ገብቷል፡፡ ተጠሪ በውሉ መሠረት ብር 8,625 /ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሀያ አምስት ብር/ ከአመልካች የቅድሚያ ክፍያ ተቀብሎ ወስዷል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ጥናቱን በወቅቱና በጥራት ሰርቶ ያላስረከበ ሲሆን ከአመልካች የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ በማካተት ሠርቶ አላስረክብም፡፡ ስለዚህ በቅድሚያ ክፍያነት የወሰደውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ መሰረቷል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ በውላችን መሠረት ጥናቱን ሰርተን ሁለት ጥራዝ ለአመልካች አስረክበናል፡፡ ስለዚህ የአመልካች/ከሳሽ/ ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በአመልካች ላይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ የተጠሪ የተከሳሽነት ክስ ይዘት ከአመልካች/ከከሳሽ/ ጋር ባደረግነው ውል መሠረት ጥናቱን አጠቅቀን አስረክበናል፡፡ ስለሆነም ያልከፈለን ቀሪ ክፍያ ብር 20,125 /ሀያ ሺህ አንድ መቶ ሀያ አምስት ብር/ ለመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ያስያዝነውን 2,250 /ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሀምሣ ብር/ የጉዳት ካሣ በርትእ 10,000/አስር ሺ ብር/ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል የተከሳሽ ከሳሽነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በሥር በከሳሽ ተከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪ ሥራውን በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ያላጠናቀቀና ያጠናውም ጥናት በተሰጠው ቢጋር መሠረት ያልተሰራና ከድርጅቱ የተሰጠውን ማሻሻያ መሠረት በማድረግ አስተካክሎ ባለማቅረቡ ቀሪውን ክፍያ ለመፈፀም አልገደድም፡፡ አስር ሺህ ብር ተጠሪ የጠየቀው ከህግ ውጭ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል ያቀረበውን ክስና ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር እንደዚሁም በተጠሪ በኩል ያቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስና አመልካች በከሳሽ ተከሳሽነት ያቀረበውን ክርክር እንደዚሁም ግራ ቀኙ የየበኩላቸውን ክርክር ለማስረዳት ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች ከመረመረ በኃላ አመልካች ጥናቱ እስከ ሰኔ 7 ቀን 1999ዓ.ም ተጠሪ ጥናቱን አጠናቆ እንዲያቀርብ ደብዳቤ የፃፈ መሆኑንና ተጠሪ ሰኔ 11 ቀን 1999ዓ.ም ሁለት ጥራዝ ጥናት ለአመልካች መላኩ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች የጥናቱን ማስረከቢያ ጊዜ ለማራዘም በፃፈው ደብዳቤ መሠረት ተጠሪ ጥናቱን ያሰረከበ በመሆኑ አመልካች በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተጠሪ ጥናቱን ሰርቶ አላስረከበም በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ ጥናቱን አጠናቅቆ ያስረከበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ ያቀረበው ጥናት ጉድለት ያለበት ነው በማለት የሚከራከር ቢሆንም ጥናቱ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ በማስረጃ ስላላስረዳ አመልካች በቅድሚያ ክፍያ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ያቀረበው ክስ ተገቢ አይደለም በማለት የወሰነ ሲሆን የተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በተመለከተ የሙያ ግልጋሎት ክፍያው ብር 29,750 መሆኑ በውሉ በግልፅ የተመለከተ በመሆኑና ተጠሪ ለመልካም ሥራ አፈፃፀም 2,250 /ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሀምሣ ብር/ ያስያዘ መሆኑ ስለተረጋገጠ እንደዚሁም ተጠሪ ጥናቱን በውሉ መሠረት ሰርቶ ያስረከበ ስለሆነ ቀሪ ያገልግሎት ክፍያ 20,125 /ሀያ ሺህ አንድ መቶ ሀያ አምስት ብር/ ለመልካም ሥራ አፈፃፀም የተያዘው ብር 2,250 /ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሀምሣ ብር/ ከህጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ የመክፈል ሀላፊነት አለበት፡፡ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ስላልተረጋገጠ ብር 10,000 የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅረቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚነቀፍበት የፍሬ ጉዳይ ወይም የህግ ስህተት የሌለ መሆኑን በመግለጽ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች መስረከም 13 ቀን 2003 ዓ.ም ተጠሪ አመልካች በሰራው ቢጋር መሠረት ድርጅቱን ከኃላቀርነት ወደ ዘመናዊ አሠራር የሚያሸጋግር ጥናት ለማቅረብ የውል ግዴታ የገባ ቢሆንም የተጠሪ ጥናት አስራ ሁለት የሚደረሱ ጉድለቶች እንዳሉበት በአመልካች የሥራ አመራር ቦርድ ያደረገውን ውይይት ቃለ ጉባኤ በማስረጃነት አቅርበን እያለ የሥር ፍርድ ጥናቱ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ አያስረዳም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ ህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከተጠሪ ጋር ያደረግነውን የሙያ ግልጋሎት ውል በማናቸውም ጊዜ በተናጠል የማፍረስ ሥልጣን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2637 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጎ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን ድንጋጌ በመተለለፍ ውሉ የተፈፀመ በመሆኑ ቀሪ ክፍያ ለተጠሪ ይከፈለው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጥናቱን ሙሉ በሙሉ አጠናቅቄ ለአመልከች ማስረከቤን የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ አረጋግጧል፡፡ አመልካች በጥናቱ ላይ ከሙያ አንፃር ጉድለት ያለ መሆኑን ያላስረዳ ሲሆን ቀሪውን የሙያ አገልግሎት ክፍያ ላለመክፈል ያቀረበው መከራከሪያ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ የሚል ይዘት ያለው መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በውሉ መሠረት ግዴታውን ስለተወጣ አመልካች ቀሪውን የሙያ አገልግሎት ክፍያ ይክፈል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዘ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ይህንን መሠረታዊ ጭብጥ ለመወሰንና በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገውን ውል ልዩ ባህሪና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎችን ይዘት መንፈስና ዓላማ ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የሙያ ግልጋሎት ውል በማናቸውም ጊዜ በተናጥል የማፍረስ መብት አለኝ በማለት የሚከራከረው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2637 ንዑስ አንቀጽ 1 በመጥቀስ ነው፡፡

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2637 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ አሠሪው በማናቸውም ጊዜ ውሉን ማፍረስ ይችላል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው መቼ ነው የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የዕውቀት ሥራ ለመስራት ከአሠሪው ጋር ውል የተዋዋለ ሰው የዕውቀት ሥራውን ሙሉ ለሙሉ አጠናቆ ለአሠሪው ካስረከበ በኃላ በአሠሪውና የዕውቀት የሥራ ውሉን በሠራው ሠው መካከል የሚነሳው ክርክር የዕውቀት የሥራ ውሉን የሠራው ሰው ፣ የሙያ ሥራውን በልምድና የሙያ ሥራ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ የአመልካችን ጥቅም በሚያረጋግጥ አኳኃን የሙያ ሥራውን ከልብ ስርቷል ወይስ አልሰራም; የሙያ ሥራውን የሠራው ሰው የዕውቀት ሥራውን የሙያውን ደንቦች በጠበቀና በሚያሟላ ሁኔታ ፈፅሟል ወይስ አልፈፀመም የሚሉት ነጥቦች መሆናቸውን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2636 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2636 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይችላል፡፡ ስለሆነም አሠሪው በተናጠል የዕውቀት ግልጋሎት ውሉን ለማቋረጥ የሚችለው የዕውቀት የሥራ ውሉን የተዋዋለው ሰው የዕውቀት ሥራውን ሙሉ በሙሉ አጠናቅቆ ለአሠሪው ከማስረከቡ በፊት እንደሆነ ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎችና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2637 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የሙያ ሥራ ለመሥራት የተዋዋለው ሰው የሙያ ሥራውን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ለአሠሪው ካስረከበ በኃላ የኪነጥበብ ደንቦችን ማለትም የሙያውን ደንቦች በማፍረስ ጥፋት መፈፀሙ ካልተረጋገጠ በቀር በኃላፊነት እንደማይጠየቅ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2636 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልጽ የተደነገገ ሲሆን የፍ/ህ/ቁ.2632 ንዑስ አንቀጽ 2 የእንግሊዘኛው ቅጅ “He shall not be liable to his client, unless he commits an error, having regard to the rules of his profession” በሚል መንገድ ከአማርኛው ቅጅ በቀላልና ግልፅ በሆነ አገላለፅ ደንግጐታል፡፡ ተጠሪ ጥናቱን ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ለአመልካች ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም ሁለት ጥራዝ የጥናት ሰነድ ያስረከበ መሆኑ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች በውሉ መሠረት ቀሪውን የሙያ ግልጋሎት ክፍያ የማይከፍልበት በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን በተለይም ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2636 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የውል ግዴታውን ያልተወጣና ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2636 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት የሙያውን ደንብ ያልጠበቀና የዕውቀት ሥራው ስህተት ያለበት መሆኑን የማስረዳት ግዴታ (Burdon of proof) አለበት፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪ ያቀረበው የጥናት ሰነድ በድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ታይቶ ጉድለት የተገኘበት መሆኑን የሚያሣይ ቃለ ጉባኤ በማስረጃነት ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበ መሆኑን በመግለፅ የሚከራከር ቢሆንም ይህ ማስረጃ በተጠሪ ተጠንቶ የቀረበው ሁለት ጥራዝ የጥናት ሰነድ ሙያዊ ጉድለትና ስህተት ያለበት መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳልሆነ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም አመልካች በተጠሪ ተሠርቶ በቀረበው የጥናት ሰነድ ላይ ተፈፅመዋል የሚላቸውን የሙያውን ደንብና አሠራር የሚጥሱ ጥፋቶች የማስረዳት ሸክሙን (Burdon of proof) ካልተወጣ ተጠሪ ለሰጠው ሙያዊ ግልጋሎት መክፈል የሚገባውን ቀሪ ክፍያ እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2634 ንዑስ አንቀፅ 2ን መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ተጠንቶ የቀረበው ሰነድ ሙያዊ ጉድለት ያለበት መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በማጣራት እንዲወሰንላቸው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለፅነው ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 60951

ቀን 19/9/2003

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች - የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ነገረ ፈጅ አቶ ሳሙኤል ተገኔ፣ ቀረቡ

ተጠሪ - ካንትሪ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ፣ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አመልካች በስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነው፡፡ ክሱም ለመንገድ ስራ የሚያገለግሉትን የተለያዩ የአስፖልት ውጤቶችን እስከ ተከሳሽ ሳይቶች ድረስ ለማቅረብ ተከሳሽ መ/ቤት ያወጣውን ጨረታ ተወዳድሬ በማሸነፍ የሥራ አፈፃፀም ዋስትና (contractual security) የጠቅላላ ሥራ ዋጋ 10% ብር 9,559,525.37 ከወጋገን ባንክ የተሰጠ ዋስትና አስይዤ ስለእቃውም አቅርቦት ከተከሳሽ መ/ቤት ጋር እንደ አውሮፖ አቆጣጠር ሰፕቴምበር 20/2007 ውል የገባን ሲሆን ከሳሽ ከገባሁት ግዴታዎች የአስፖልት ውጤቶችን አቅርቤ Ac 60/70 ተብሎ ከሚታወቀው የአስፖልት አይነት ማቅረብ ከሚገባኝ 8.276 ሜትሪክ ቶን ውስጥ 3,829.5 ሜትሪክ ቶን ብቻ አላቀረብኩም፡፡ ምክንያቱም በውሉ ይደርሳሉ ተብሎ ያልተገመቱ ጉዳዮች ውሉን በከፍተኛ ሁኔታ በማናወጣቸዉ ሲሆን ከተከሳሽ ጋር በመወያየት በቅድሚያ የተቀበልኩትን 10,224,989.13 ብር ተመላሽ በማድረግ ውሉ ተቋርጧል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ መ/ቤት ለመልካም አፈፃፀም ዋስትና ካስያዝኩት ፋይናንሻል ጋራንቲ ቦንድ ውስጥ ላላስረከብኩት የአስፖልት ውጤት መጠን ብር 3,557,729.34 በመቁረጥ ቀሪውን ገንዘብ እንደሚመልስልኝ ገልጿል፡፡ ስለሆነም ተሰካሽ ብር 3,557,729.34 ያስቀረብኝና ለተከሳሽ ባቀረብኳቸው የአስፖልት ውጤቶች ብር 497,735 ኪሣራ የደረሰብኝ በመሆኑ የተጠቀሰው ገንዘብ ወጪና ኪሳራ ተጨምሮ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ለክሱ ተከሳሽ የሰጠው መልስ ከሳሽ ኪሳራ ገጥሞኛል ይበል እንጂ ደረሰብኝ የሚለው ኪሣራ አስቀድሞ ሊገመት የሚችል ነው፡፡ ተከሳሽ መ/ቤት ለሚሰራው እና ለሚያስጠግነው መንገድ በእቅድ የሚሠራ በመሆኑና ከሳሽም ማቅረብ የሚገባውቸውን የአስፖልት ውጤቶች በግዜ ካለማቅረቡ የተነሳ በተከሳሽ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡ Ac 60/70 ከተባለው የአስፖልት ውጤት ውስጥ 3829.5 ሜትሪክ ቶን እስካሁን ድረስ አላቀረበም፡፡ ተከሳሽም ለደረሰበት ጉዳት ከሳሽ ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ ብር 3,557,927.34 መውሰዱ አግባብነት አለው ይህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለሚደርሰው ጉዳት እንደሚውል በውላችን የተስማማነው ጉዳይ ነው፡፡ በውሉ ምክንያት ኪሳራ ብር 497,735 ደርሶብኛል በማለት እንዲከፈለው የጠየቀውም ቢሆንም ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም በውላችን በማናቸውም ሁኔታ የዋጋ ማስተካከያ እንደማይደረግ ተስማምተናል በማለት የከሳሽ ክስ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ከሳሽ ለማቅረብ የውል ግዴታ ከገባው የአስፓልት ውጤት ውስጥ 3829.5 ሜትር አለማስረከቡን አምኗል፣ ውሉም በግራ ቀኙ ስምምነት የተቋረጠ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፣ ከሳሽ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ናቸው በማለት የዘረዘራቸው ምክንያቶች በፍ/ህ/ቁ 1792/2/አንፃር ሲታዩ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ናቸውየሚባሉ አይደሉም፣ተከሳሽ በደብዳቤ እንደገለፀው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ቀንሶ ያስቀረው ከሳሽ ያስረከበውን እና ያላስረከበውን መጠን በማመጣጠን ሲሆን ይህን ተከሳሽ በራሱ መወሰኑ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ የተከሳሽ መ/ቤት ኪሳራ ደርሶበታል ቢባል እንኳን በፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ከሚያስወስን በስተቀር የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ለደረሰበት ኪሣራ መቀነስ የለበትም ሲል ቀንሶ ያስቀረውን የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ብር 3,557,927.34 ለከሳሽ እንዲመልስ ሲወስን ከሳሽ በተጨማሪ ኪሣራ ገጥሞኛል ሲል የጠየቀውን የኪሳራ ገንዘብ ብር 497,735 ተከሳሽ ሊጋራ አይገባውም ብሏል፡፡

የሥር ተከሳሽ በሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም ሲል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት አጽንቷል፡፡

በሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አመልካች መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት የቅሬታ ነጥቦች ለዚህ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሣቸውም ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የመንግስት የግዥ ስርአት ለመወሰን የወጣው የአዋጅ ቁጥር 430-97 ሆኖ እያለ ፍ/ቤቱ አግባብነት የሌለውን የፍትሃብሔር ህግ ቁጥር 1790/1/ እና 1799 ለውሳኔው መሰረት ማድረጉ ተገቢነት የለውም፣ ለውሳኔው አግባብነት አለው እንኳን ቢባል የበሰለ የጉዳት ካሳ (liquidated Damages) በተመለከተ በውሉ ጠቅላላ ክፍልና ልዩ ሁኔታ አንቀጽ 27 የተስማማንበት ጉዳይ ስለሆነ የፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1894 እንደተደነገገው አመልካች ስምምነት በተደረሰበት ጉዳይ ላይ የጉዳቱን ልክ ሆነ መጠን የማስረዳት ሀላፊነት የለበትም፡- ስለሆነም ተጠሪው ካስያዘው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ በስምምነቱ መሰረት ቆርጦ የመውሰድ መብት አለው፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ ይህንኑ ገንዘብ አመልካች በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ማስወሰን አለበት የተባለው በፍ/ህ/ቁ 1731፤ በውሉ አንቀፅ 18/2/ እና በመንግስት እቃ ግዢ መመሪያ አንቀፅ 11/14/2 መሰረት ተቀባይነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ለሰበር አቤቱታ ተጠሪው በሰጠው መልስ ከአመልካች ጋር የነበረው ውል በመቋረጡ ላስረከበው እቃ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚከፈለውን ካሳ ስምምነት ያላደረገ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ያልቀረበውን እቃ በተመለከተ የካሳ መጠን አመልካች ክስ አቅርቦ ከሚያስወስን በቀር ጉዳት መኖሩንም ሆነ የካሳውን ልክ ራሱ ወስኖ ሊወስድ እንደማይችል የሰጡት ውሳኔ በፍ/ህ/ቁ 3200 መሰረት ህጋዊ ነው፣ አመልካች ተጠሪ በውሉ አንቀፅ 27 መሰረት የተስማሙትን ዘግይቶ ለቀረበ ዕቃ የሚከፈል መቀጫን እንጂ ውሉ በመቋረጡ ላልቀረበ ዕቃ የሚደርስ ጉዳትን በተመለከተ አይደለም፣ ተጠሪ ላስረከበው ዕቃ የተረጋገጠ ጉዳትም ቢሆን ኪሳራ ሊከፍል አይገባም፣ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውሉ አንቀፅ 27 መሰረት ሊከፍለኝ የሚገባውን መቀጫ በውሉ አንቀፅ 18 መሰረት ከዉል ማስከበሪያ ላይ የመቀነስ መብት አለኝ በማለት ያቀረበው ቅሬታ የህግ መሰረት የለውም በማለት የሥር ከፍ/ፍ/ቤትም ሆነ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት አመልካች ከዘረዘራቸው የቅሬታ ነጥቦች አንፃር የፈፀሙት የህግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የቀረበው ሲሆን እኛም ተጠሪው ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ ባልፈፀመው የውል ግዴታ መጠን አመልካች ቀንሶ ማስቀረቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ለዚህ ለተያዘው ጭብጥ ከአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 430/97፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሐምሌ 1997 ባወጣው የመንግስት ዕቃ ግዥ መመሪያ በአመልካችና ተጠሪ መካከል በተደረገው ውል መሰረት ተጠሪው ለመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ ባልተፈፀመው የውል ግዴታ መጠን የመቀነስ መብት አለኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪው ግን አመልካች ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ከተያዘው ገንዘብ ውስጥ በራሱ ስልጣን ቀንሶ ለማስቀረት አይችልም ሲል ተከራክሯል፡፡ ተጠሪው ለዚህ ክርክር አግባብነት አለው በማለት በዋናነት የጠቀሰውም የፍ/ብ/ህ/ቁ 3200 ነው፡፡ የተጠቀሰው የፍ/ብ/ህ/ቁ 3200 ከአስተዳደር መ/ቤቶች ጋር የሚደረገውን ውል የሚመለከት ሲሆን ድንጋጌው በመርህ ደረጃ የቅድሚያ ልዩ መብት እንደማይኖር የሚናገር ነው፡፡ በዚሁ ህግ መሰረትም የአስተዳደር መ/ቤቱም ተዋዋዩ ውሉን ባለመፀሙ የሚያስቀጣ ጥፋት አድርጓል በማለት በገዛ ራሱ አንድ ውሳኔ ለማድረግ ወይም በተዋዋዩ ግዴታ አለመፈፀም ወይም ለመፈፀም በመዘግየቱ ምክንያት የሚፈለግበትን ኪሣራ ልክ በገዛ ራሱ ለመወሰን አይችልም፡፡

ይሁን እንጅ ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው የመንግሰት የግዥ ሥርአትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 430/97 እና የመንግስት የግዢ መመሪያ እንዲሁም ግራ ቀኙ የገቡት ውል እንጅ የተጠቀሰው የፍትሀብሔር ህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በህግ አተረጓጎም ረገድ ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ የፍ/ህጉ አጠቃላይ ህግ ሲሆን የመንግስት የግዥ ሥርአትን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 430/97 ልዩ ህግ በመሆኑ ከግዥ ጋር ተያይዞ ለሚነሳ ክርክር ተፈፃሚ የሚሆነው ይኸው አዋጅ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 430/97 አንቀፅ 43 ስለ ውል ማስከበሪያ (contract security) የሚደነግግ ሲሆን አቅራቢው በውሉ መሰረት ባለመፀሙ በግዥ ፈፃሚው አካል ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚውል ማስከበሪያ ለግዥ ፈፃሚው አካል መስጠት አለበት ይላል፡፡ የግራ ቀኙ ተዋዋዮችም ይህንኑ አስገዳጅነት ያለውን የህግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ በውላቸው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ያካተቱ ሲሆን ተጠሪው በውሉ መሰረት ማስረከብ የሚገባውን Ac 60/70 የተባለውን የአስፋልት ውጤት ቀንሶ በማስረከቡ በአመልካች ላይ ጉዳት መድረሱን ክርክሩ ያመለክታል፡፡ ይህ በመሆኑ አመልካች በውሉ አንቀፅ 18/2/ እንደተጠቀሰው በውሉ መሰረት ተጠሪው ግዴታውን ባለመፈፀሙ የተነሳ ለተፈጠረው ጉድለት መያዣ ከነበረው ከመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ቀንሷል፡፡ ሐምሌ1997 የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ያወጣው የግዥ መመሪያ አንቀፅ 11/5/ም ቢሆን አቅራቢው ዕቃውን አጠናቅቆ ባለማስረከቡ ርክክቡ ባልተፈፀመበት ግዢ ላይ በየቀኑ 0.1 ወይም 1/1000 መቀጫ እንደሚከፍል ይናገራል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመሪያው መቀጫ የውሉን ዋጋ 10% የሚበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ግዥ ፈፃሚው ውሉን የመሰረዝ መብት እንዳለው እና የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በግዥ ፈፃሚ ስራ ላይ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ግዥ ፈፃሚው የመቀጫውን መጠን 10% ሳይጠብቅ ውሉን መሰረዝ እንደሚችል ጭምር በቁጥር 11.7/5/ /ለ//ሐ/ ይገልፃል፡፡

በመሆኑም ከአዋጁ አንቀፅ 43፣ ከመመሪያው ቁጥር 11.7/5/ /ሀ-ሐ/ እንዲሁም ከውሉ አንቀፅ182፣27.1 ይዘት አንፃር ሲታይ አመልካች ለመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ከተያዘው ገንዘብ ባልተፈፀመ ውል ግዴታ መጠን ቀንሶ መውሰዱ አግባብነት አለው፡፡ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የሚያዘውም አቅራቢው በውሉ መሰረት ግዴታውን ባለመፈፀም የተነሳ ግዥ ፈፃሚው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተገቢውን መቀጫ አቅራቢው ከዚሁ ገንዘብ እንዲከፍልና ውሉን አክብሮ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ግዴታውን እንዲፈፅም ታስቦ ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች ለመልካም ስራ አፈፃፀም ተጠሪው ያስያዘውን ገንዘብ ራሱ ቀንሶ የአስፋልት ውጤቱ ባለመቅረቡ የተነሳ ለተፈፀመው ጉድለት ማስቀረት አይችልም በማለት በስር ፍ/ቤት የተወሰነዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 79497 በቀን 30/4/2002 በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 52052 በቀን 24/1/2003 የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

2. ተጠሪው ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ካስያዘው ገንዘብ አመልካች ቀንሶ ያስቀረውን ብር 3,557,929.34 /ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ አምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ከሰላሳ አራት ሳንቲም /ለተጠሪው ሊመልስ አይገባም ብለናል፡፡

3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ አመልካችና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሂአ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 15 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፦ የኢት/ንግድ ባንክ አልቀረበም

ተጠሪዎች ፦ 1. አቶ መሐመድ ሙሳ

2. ወ/ሮ ሐሊማ ሃብቤ

3. ወ/ሮ ነኢማ ዩያ

4. ወ/ሮ ሽኩር ዋቃዩ

ተወካይ አቶ መሐመድ ሙሣ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ተጠሪዎች በስር ክፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሾች ሲሆኑ አመልካች 2ኛ ተከሳሽ፣ እንዲሁም የኢት/መንገዶች ባለሥልጣን 1ኛ ተከሳሽ፣ የሚጨታ ከተማ አስተዳደር ደግሞ 3ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ክሱም በሚጨታ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ በ1226 ካሬ ሜትር ላይ የሰፈረውን ግምቱ 250,000 ብር የሚያወጣውን የከሳሾች ቤት 1ኛ ተከሳሽ በብር 162,306 ብቻ በመገመት ይህንኑ ገንዘብ 1ኛ ተከሳሽ ለ2ኛ ተከሳሽ ሰጥቶ 2ኛ ተከሳሽም ከከሳሾች ጋር ምንም ዓይነት የዋስትናም ሆነ የብድር ውል ሳይኖር ገንዘባችንን የያዘብን ሲሆን 3ኛ ተከሳሽ ደግሞ የተለያዩ መብታችንን የሚጋፉ ደብዳቤዎች የሰጠ ስለሆነ ተከሳሾቹ የቤታችንን ግምት ብር 250,000 ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍሉ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

የሥር 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በስር ፍ/ቤት በተደረገ ክርክር ከክሱ የወጡ ሲሆን የ2ኛ ተከሳሽ መልስ 1ኛ ከሳሽ በ23/7/1986 ዓ.ም ከባንኩ ጋር በተደረገ ውል ብር 40,000 ተበድሮ ባለመክፈሉ የተነሳ ወለድ ተጨምሮበት ብር 71,398.67 እዳ አለበት፣ እንዲሁም ወንድሙ ሶፍያን ሙሳ የተባለው ከባንኩ ጋር በተደረገ ውል ገንዘብ ሲበደር ከሳሽም የአንድነትና ነጠላ ዋስትና የገባ ሲሆን ከተበዳሪው የሚፈለገው ብር 19,583.53 በመሆኑ ከሳሽ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ ስላለበት በአጠቃላይ ከ1ኛ ከሳሽ ብር 90,583.59 የሚፈለግበት በመሆኑ ይህው ገንዘብ ተቀንሶ ቀሪውን ብር 71,727.27 ከሳሾች እንዲወስዱ ቢነገራቸውም ለመውሰድ ፈቃደኞች አይደሉም የሚል ሲሆን 1ኛ ከሳሽ የፈረመውን የብድር ውል እና የዋስትና ሠነድ አያይዞ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የመረመረው የስር ከፍተኛ ፍ/ቤትም ባንኩ በብድር ውሉ አንቀጽ 15 መሠረት በርሱ ዘንድ የተቀመጠውን ገንዘብ ለሚፈለገው የብድር እዳ እንዲቻቻል ከሚያደርግ ውጪ በሐዋላ አገልግሎት የተላከውን በእንቅስቃሴ የሚገኘውን ገንዘብ ለእዳው ማቻቻል አይችልም በማለት 1ኛ ተከሳሽ ማለት የኢት/መንገዶች ባለሥልጣን የላከውን የከሳሾች ገንዘብ ብር 162,306.90 ይመልስ በማለት ፈርዷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በበኩሉ ክርክሩ በይግባኝ ቀርቦለት ከመረመረ በኋላ ቤቱ በዋስትና የተያዘ ስለመሆኑ ውሉ የሚያመለክት አይደለም፡፡ ይግባኝ ባይ /ያሁን አመልካች/ ውሉን መሠረት አድርጐ ክስ አቅርቦ እዳውን ማስከፈል ከሚችል በቀር የመ/ሰጪዎችን ገንዘብ መያዙ አግባብነት የለውም፡፡ በስር ከፍተኛ ፍ/ቤትም ቢሆን ስለ ብድር ውል አንቀጽ 15 የሰጠው ትርጉም አግባብ ሆኖ አላገኘሁም በማለትና የውሳኔውን ድምዳሜ በመቀበል ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጪዎች የያዘውን ገንዘብ ይመልስ መባሉ የሚነቀፍ አይደለም ተብሏል፡፡

በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ቅር የተሰኘው የአሁን ሰበር አመልካችም ባቀረበው ቅሬታ አመልካች በግልጽ ከተጠሪዎች ጋር ባደረገው የብድር ውልና የአንድነትና የነጠላ ዋስትና ውል መሠረት ገንዘቡ ባለመከፈሉ ዕዳውን ለማቻቻል በማንኛውም መልኩ በባንኩ ዘንድ በባለእዳዎች ስም የተቀመጠውን ገንዘብ መውሰድ የሚችል ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች ለተጠሪዎች እዳ ገቢ የተደረገውን ገንዘብ አመልካች እንዲመልስ መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ብሏል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከአመልካች ጋር የተፈራረምነው የብድርም ሆነ የአንድነትና የነጠላ ዋስትና ውል የለም፣ በፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 1832 እና 1833 መሠረትም የእዳ ማቻቻያ የሚያስደርጉ ምክንያቶች የሉም በማለት የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጐ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተገለፀው የቀረበ ሲሆን እኛም አመልካች ለተጠሪዎች የቤት ግምት የተላከውን ገንዘብ ለእዳ ማቻቻያነት መያዙ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በፍታብሔር ህጋችን እዳን ለማቻቻል የሚቻለው በሶስት መንገዶች ሲሆን 1ኛው መንገድ በፍታብሔር ህግ አንቀጽ 1838/1/ እንደተጠቀሰው ባለእዳውን እንዲቻቻልለት መፈለጉን ለባለገንዘቡ ሲያስታውቅ ወይም ባለእዳው እዳው እንዲቻቻልለት ስምምነቱን ሲገልጽ ነው፡፡ 2ኛው የማቻቻያ መንገድ ደግሞ ሁለቱ ወገኖች በውል ፈቃዳቸውን ሲገልጹ መሆኑን የፍ/ህ/ቁ 1840 ያመለክታል፡፡ 3ኛው የእዳ ማቻቻያ መንገድ ደግሞ በፍ/ህ/ቁ 1841 መሠረት በፍ/ቤት የሚደረገው ማቻቻያ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የማቻቻያ መንገዶች አመልካች ጠቅሶ የሚከራከረው የእዳ ማቻቻያ መንገድ ማለትም የብድሩንና የዋስትና ውሎች ሲሆን ውሎቹም በፍ/ህ/ቁ 1731 መሠረት በመካከላቸው ህግ ሆነው ይገዛሉ በሚል ነው፡፡ በዚህም መነሻ ለእዳው ማቻቻያነት ገንዘቡ የተያዘው ተገቢ ነው ይላል፡፡

የአመልካች እና ተጠሪዎች የእዳ ማቻቻያ ክርክርን ለመወሰን የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መሠረት ያደረገው ተያይዞ የቀረበለትን የብድር ውል አንቀጽ 15 ነው፡፡ ይህ የተጠቀሰው የውሉ አንቀጽ “ተበዳሪው በዚህ ውል ላይ የተገለፀውን ማናቸውንም ግዴታ ያልፈፀመ እንደሆነ በባንኩ ዘንድ ያስቀመጠውን ገንዘብ ወጪ በማድረግ ለእዳው ለማቻቻል ባንኩ መብት አለው” ይላል፡፡ ይህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውል ድንጋጌ የሚናገረው በባንኩ ዘንድ ባለእዳው ያስቀመጠውን ገንዘብ ነው፡፡ አመልካች ግን 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ባንኩ ያስቀመጠውን ገንዘብ ሳይሆን በስር 1ኛ ተከሳሽ የተላከለትን ገንዘብ ነው፡፡ በተጠቀሰው የውል አንቀጽም በባንኩ ከተቀመጠ ገንዘብ ውጪ በሌሎች መንገዶች የተገኙ የባለዳውን ገንዘቦች ለእዳው ማቻቻያነት የሚያዙ ወይም ገቢ የሚደረጉ ስለመሆናቸው አልተገለፀም፡፡ በመሆኑም አመልካችና ተጠሪ የገባነው ውል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1731 መሠረት አስገዳጅ ነው በሚል ብቻ በውሉ ውስጥ ባልተካተተ ጉዳይ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ አመልካች ለእዳው ማቻቻያ ማድረጉ የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡ በመሆኑም በስርፍ/ቤት አመልካች የያዘውን ገንዘብ ለተጠሪዎች ይመልስ በሚል በተሰጠ ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15734 በቀን 25/10/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔና የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 106858 በቀን 25/4/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለባቸው ስለሆኑ ፀንተዋል፡፡
2. ይህ ውሳኔ አመልካች ከተጠሪዎች የሚፈለግባቸው እዳ ካለ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ የማስወሰን መብቱን የሚያስቀርበት አይሆንም፡፡
3. አመልካች የያዘውን የተጠሪዎች ገንዘብ እንዲመልስ ተወስኗል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸው ይችሉ፡፡
5. ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ በመ/ቁ 17488 ተጀምሮ የነበረው አፈፃፀም እንዲታገድ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
6. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 9 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አመልካች ፡- ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ - ይሁንልኝ ቡሎ ቀረበ

ተጠሪዎች ፡- 1. ዮናስ ካሣ አልቀረበም

2. ወ/ሮ በለጡ አጎታለም ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ሰበር መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ለትምህርት (ለስልጠና) የተደረገው ወጪ በውሉ መሠረት ይመለስልኝ በማለት አመልካች የመሠረተውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው 1ኛ ተጠሪ በውሃ (ወተር) ኢንጂነሪንግ የማስትሬት ዲግሪ ትምህርቱን በአመልካች ድጋፍ እና ትብብር ፈቃድ ወደ ቤልጂየም ሀገር ሄዶ እንዲማር እና ተምሮ ሲመለስም ለተማረበት ሁለት ዓመት ሦስት እጥፍ ማለትም ስድስት ዓመት አመልካችን ለማገልገል፣ ይህን ማድረግ ካልቻለ ደግሞ ለትምህርት የወጣውን እና ለቤተሰቡ የተከፈለውን ደመወዝ በጠቅላላው ብር 190,470.00 ለአመልካች እንዲከፍል ስምምነት ተደርጎአል፡፡ 2ኛ ተጠሪም 1ኛ ተጠሪ ግዴታውን ባይወጣ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ገንዘቡን ለመክፈል ግዴታ ገብታለች፡፡ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ በገባው ግዴታ መሠረት ተመልሶ ለማገልገል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህም ሁለቱም ተጠሪዎች ገንዘቡን ይከፍሉ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው አመልካች ክሱን የመሠረተው፡፡ ክሱ የቀረበለት የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ተጠሪዎች የሰጡትን መልስ ካየ በኋላ፣ 1ኛ ተጠሪ በአሁኑ ጊዜ በመማር ላይ እንደሆነ ማስረጃ ቀርቦልኛል የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ሰርዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የተሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ትዕዛዝ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 4 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኝ ወገኖች የተገባውን ውል መሠረት ያደረገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ጭብጡን ግራቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ግራ ቀኝ ወገኖች ካቀረቡት ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው ለክሱ መነሻ የሆነው ውል በግራቀኙ መካከል ስለመደረጉ እና 1ኛ ተጠሪም ወደቤልጅየም ሃገር ሄዶ የማስተርስ ዲግሪውን ስለማግኘቱ አልተካደም ወይም አከራካሪ አልሆነም፡፡ ተጠሪዎች ክሱን የተቃወሙት 1ኛ ተጠሪ የማስተርስ ዲግሪውን ካገኘ በኋላ ወደ አሜሪካን ሃገር በመሄድ ለፒ.ኤች. ዲግሪ ትምህርት በመቀጠል ላይ ስለሆነ በውሉ መሠረት ተመልሶ አመልካችን ሊያገለግል አልቻለም በሚል ገንዘቡን እንዲከፍል አይገደድም የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን በተጠሪዎች የቀረበውን የመከራከሪያ ነጥብ እንዳለ በመቀበል ነው ክሱን ውድቅ ያደረጉት፡፡ አመልካች 1ኛ ተጠሪ የቀጠለውን ትምህርት ጨርሶ ሲመለስ ክሱን ማንቀሳቀስ ይችላል በማለትም ነው ክሱን የሰረዙት፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ የተሰጠውን ውሳኔ የተቃወመው በመሃከላችን የተደረገውን ውል እና ሕጉን መሠረት ያደረገ አይደለም በማለት ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው እና እንደምንገነዘበው ክርክሩ ሊወሰን የሚገባው በግራቀኝ ወገኖች የተደረገውን ውል እና አግባብነት ያለውን ሕግ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ከሁሉ በፊት የውሉን ይዘት እንደዚሁም ውሉ ለተዋዋይ ወገኖች የሰጠውን መብት እና የጣለውን ግዴታ መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡ በክርክሩ እንደተገለጸው አመልካች 1ኛ ተጠሪን በማስተርስ ዲግሪ ለማስተማር ግዴታ የገባ ሲሆን፣ ተጠሪዎች ደግሞ በውሉ ለተመለከቱት ዓመታት አመልካችን ለማገልገል፤ ይህ ካልተፈጸመ ደግሞ ለትምህርቱ የወጣውን ወጪ ለአመልካች ለመተካት ግዴታ ገብተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በውሉ መሠረት ትምህርቱን ጨርሶ የማስተርስ ዲግሪውን ያገኘ ቢሆንም፤ ወደ አገሩ በመመለስ ለአመልካች አገልግሎት አልሰጠም ወይም ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ይህም ማለት ውሉ በሰጠው መብት የተጠቀመ (ትምህርቱን የተማረ) ሲሆን፣ ግዴታውን ግን አልፈጸመም፡፡ የፒ.ኤች ዲግሪ ትምህርት እንዲቀጥል የሚያስችለው ተጨማሪ ስምምነትም ከአመልካች አላገኘም፡፡

በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሙዋቸው ሰዎች ላይ ሕግ ስለመሆናቸው በፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1731 በተቀመጠው ድንጋጌ ተመልክቶአል፡፡ ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ ወይም ከዚሁ በመውጣት በፍ/ቤት ሊተረጎሙ እንደማይችሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1733 ተደንግጎአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መሠረት የሆነው ውል ግልጽ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ተመልሶ አመልካችን ለማገልገል ግዴታ የገባው የማስተርስ ዲግሪውን ካገኘ በኋላ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ትምህርቱን ጨርሶ ዲግሪውን እንዳገኘ ተረጋግጠኦል፡፡ በመሆኑም የማገልገል ግዴታውን መወጣት የሚችለው በኋላ የጀመረውን የፒ.ኤችዲ ድግሪ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ ነው ለማለት የሚቻልበት የውልም ሆነ የሕግ አግባብ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ወደሌላኛው ጫፍ (ትምህርቱን ጨርሶ ከተመለሰ በኋላ ክሱ ይቀጥል ወደሚለው) የሄዱት ግልጽ የሆነውን ውል ግልጽ ሆኖ ከሚታየው በመውጣት እንደሆነ ነው መገንዘብ የቻልነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በመ.ቁ 03288 ጥር 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 64401 መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በጉዳዩ ሥረ ነገር ገብቶ አመልካች ባቀረበው የክፍያ መጠን ላይ ክርክር እንዲሰማ፤ በመጨረሻም ተገቢውን ይወስን ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.341(1) መሠረት ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 56569

መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- አቶ ዳዊት አሠፋ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ተሻለ ደስታ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ጭብጥ ተመሥርቶ ለሰበር የቀረበ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ የመኪና ሽያጭ ውልን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሣሽነት ቀርበው ተከሣሽ /አመልካች/ ለከሣሽ /ተጠሪ/ና በሥር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ለነበሩት ወ/ሮ ደብራቱ በየነ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-07999 አ.ሮ የሆነውን መኪና በብር 250,000 /ሁለት መቶ ሀምሣ ሺ ብር/ ሸጠዋል፡፡ ከመኪናው ዋጋ ውስጥ ገዥዎች ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ የከፈልን ሲሆን ሻጭ /አመልካች/ ውል ክፍል ቀርበው ውሉን ባለመዋዋላቸው የመኪናው ባለሀብትነት ሊተላለፍልን አልቻለም፡፡ የመኪናው ባለሀብትነት ለገዥዎች ባለመዛወሩ መኪናውን ለማስመርመርና ቦሎ ማድረግ ስላልተቻለ ከመጋቢት 2000 ዓ.ም. ጀምሮ መኪናው ሥራ አልሰራም ስለሆነም ከሣሽና ጣልቃ ገብ በወር ብር 8000 /ስምንት ሺ ብር/ ገቢ ያጣን በመሆኑ ብር 20000 ጨምረው ተከሣሽ እንዲከፍሉ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሣሽነት ቀርበው ሻጭ የሽያጭ ውሉን በአግባቡ ፈፅሜአለሁ፡፡ የመኪናውን ይዞታ ለገዥዎች አስተላልፈዋል፡፡ የመኪናውን ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ለገዥዎች አስተላልፈዋል፡፡ የመኪናውን ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ለገዥዎች ሰጥተዋል፡፡ የመኪናውን ስመሀብት የማዞር የእኔ የሻጭ ግዴታና ሀላፊነት አለመሆኑ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተከራክረን ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡ ውሉ እንዲፈርስ የቀረበው ክስ የህግ መሠረትም የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የመኪናውን ሻጭ የሆነው ተከሣሽ /አመልካች/ የመኪናውን ባለሀብትነት ለገዥዎች /ተጠሪ/ ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆነውን የመኪና ሽያጭ ውል በውል አዋዋይ ፊት ለመፈረም ፈቃደኛ አይደለም ስለዚህ ተከሣሽ ግዴታውን ያልፈፀመ በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባዋል፡፡ ተከሣሽ /አመልካች/ ከሣሽና /ለተጠሪና በሥር ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ለሆኑት ለእያንዳንዳቸው ብር 112,500 /አንድ መቶ አሥራ ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር/ በድምሩ ብር 250,000 /ሁለት መቶ ሀምሣ ሺ ብር/ ይክፈል፡፡ ከሣሽ /ተጠሪና/ ጣልቃ ገብ መኪናውን ለተከሣሽ /ለአመልካች/ ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 121731 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅረበዋል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሻጭ /ይግባኝ ባይ/ መኪናውን የሚመለከቱ አስፈላጊ ሰነዶችን ለገዥዎች /ለመልስ ሰጭዎች/ አስረክቧል፡፡ መኪናውን ለገዥዎች አስረክቧል የመኪናውን ባለሀብትነት ወደ ገዥዎቹ የማዛወር ኃላፊነት የሻጭ /ይግባኝ ባይ/ እንዳልሆነ ከዚህ በፊት ግራ ቀኙ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባደረጉት ክርክር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 ውሣኔ ሰጥቶበታል የመኪና ሽያጭ ውል በውል አዋዋይ ፊት እንዲደረግ የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ሻጭ /ይግባኝ ባይ/ የመኪና ሽያጭ ውሉን አሟልቶ የፈፀመ ስለሆነ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ግንቦት 25 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45360 ሚያዝያ 29 ቀን 2002 ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የወሰነው ከዚህ በፊት ተጠሪ የመኪናውን ሽያጭ ውል እንዲፈፅም ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተከራክረን ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 የሰጠውን ውሣኔ የሚሽርና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አንድ ውል የማይፈፀመው ውሉ ሣይፈፀም የቀረ ወይም ውሉ ሊፈፀም የማይችል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ አመልካች ከሶስት ዓመት በፊት የሽያጭ ውሉን ፈፅሜአለሁ፡፡ ስለዚህ የመኪናው ባለሀብትነት ወደ ገዥዎች አላዛወርክም በማለት ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ መኪናው የቆመው ለፍርድ ማስፈፀሚያነት ስለተያዘ ነው የመኪናው ዲኘሪሼሽን ዋጋና ገዥዎች በመኪናው በመጠቀም ሊሰበስቡት የነበረው ገቢ ሣይታሰብ መኪናውን በመውሰድ ገንዘባቸውን ይክፈላቸው በማለት የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ እኔና አመልካች ከዚህ በፊት የተከራከርንበት ጭብጥ የሚያስነሳው የህግ ጥያቄ አሁን ከምንከራከርበት ጉዳይ የተለየ በመሆኑ አመልካች ጉዳዩ ከዚህ በፊት የተወሰነ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ የሽያጭ ውሉ አልተፈፀመም፡፡ አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2281 የተጣለባቸውን ግዴታ አልተወጡም፡፡ መኪናውን ያሣገዱትም አመልካች ናቸው ስለዚህ ውሉ ፈርሶ ወደ ነበርንበት እንድንመለስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በቅንነት የሸጥኩት መኪና በገዥዎች ሥም እንዲዛወር የካቲት 12 ቀን 1999 ዓ.ም. ከተጠሪ ጋር በመሆን በፅሑፍ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ጽ/ቤት ማመልከቻ አቅርቤአለሁ፡፡ የመኪናውንም ክሊራንስ ለተጠሪ አስረክቤአለሁ፡፡ ስለዚህ በእኔ በኩል የሚፈፀም የሚገባኝን ማናቸውንም ግዴታ ተወጥቼ እያለ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ፈርሶ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይህንን ጭብጥ ለመመለስ በመጀመሪያ ተጠሪ ከዚህ በፊት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43008 ባቀረበው ክስ መነሻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሰኔ 23 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ በማየት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ በይግባኝ በማየት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 የሰጠውን ውሣኔ ይዘት መመልከቱ አስፈላጊ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ መዝገብ ቁጥር 35601ን በማስቀረብ ተመልክተናል፡፡

ተጠሪና አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43008 የተከራከሩት ሻጭ አመልካች መኪናውን ከዕዳና እገዳ ነፃ በማድረግ ስም እንዲያዛውሩ በማለት ተጠሪ በመክሰሳቸውና አመልካች መኪናው ከዕዳና እገዳ ነፃ መሆኑን የካቲት 29 ቀን 1999 ከጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09/15 እና ከኢንሹራንስ ማስረጃ በማምጣት የሰጠ መሆኑን በማንሣት ተከራክሮ የአመልካች ማስረጃ ተዓማኒነት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የወሰነ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው ከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሻጭ የሸጡትን መኪናና ሊብሬ ለገዥዎች አስተላልፈዋል ስሙ እንዲተላለፍላቸውም ለሚመለከተው አካል የተለያዩ ደብዳቤዎችን አቅርበዋል የመኪናው ዕዳ እስከ የካቲት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የተከፈለ ለመሆኑም ማጣሪያ አቅርበዋል፡፡ የመኪና ሽያጭ ውል የተለየ ፎርም የለውም የመልስ ሰጭዎች ጠበቃ እንደገለፁት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 መሠረት የመድረግ ግዴታ የለበትም የመኪና ሽያጭ ውል ከተደረገ በኋላ ስመሀብቱ የሚተላለፍበት ሁኔታ በህግ ማስታወቂያ ቁጥር 360/6/ ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የሽያጭ ውሉና ሊብሬው ሲቀርብለት የሚመለከተው የመንገድ ትራንስፖርት ስመሀብቱን በገዥው ስም ያዛውራል ሻጭ በህግ ለመንግስት መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ስም የማዛወር ግዴታ ሊወስዱ አይችሉም የሚል ዝርዝር ምክንያት በመስጠት ተጠሪ አመልካች የመኪናውን ስም ያዛውርልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት የሌለውና ሻጭ (አመልካች) መኪናውን በማስረከብ ስም እንዲዛወርላቸው ደብዳቤ በማስገባት፣ የመኪናው ዕዳ መከፈሉን ማረጋገጫ በማቅረብ ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን በውሣኔው ውስጥ በግልፅ በማስፈር ውሣኔ የሰጠ መሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 57891 ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማየት ለመረዳት ችለናል፡፡ ተጠሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይዘቱ ከላይ የተገለፀውን የከፍተኛው ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠውን ውሣኔ ያፀናው መሆኑን በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 35601 ግንቦት 6 ቀን 2000 ዓ.ም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከሰጠው ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 35601 ያፀናው ውሣኔ መሠረታዊ ይዘት የመኪናው ሻጭ የሆኑት አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2274 በተደነገገው መሠረት የሸጡትን መኪና ለገዥዎች ያስረከቡ መሆኑንና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2281 በተደነገገው መሠረት የተሸጠውን መኪና ባለሀብትነት ለገዥዎች (ለተጠሪና በሥር ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ለነበሩት) ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን የፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት በእሳቸው በኩል መፈፀም የሚገባቸውን ተግባራት ሙሉ በሙሉ የፈፀሙና ቀሪው ሥራ ሥልጣን ያለው የአስተዳደር ክፍል መሆኑን በማረጋገጥ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 ውሣኔ ሰጥተውበታል፡፡

ተጠሪ ከላይ ቁጥራቸው በተገለፀው መዛግብት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሣኔ ግልባጭ የመኪናውን ስመሀብት ከሻጭ ወደገዥ የማዛወር ሥልጣን ላለው አካል በማቅረብ የመኪናው ስመሀብት እንዲዛወርላቸው መጠየቅና አስፈላጊም ከሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል ላይ ክስ በማቅረብ መብታቸውን ማስከበር ይገባቸዋል፡፡ ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታቸውን ሙሉ በሙሉ አሟልተው የፈፀሙ መሆኑ በፍርድ የተረጋገጠላቸውን አመልካችን በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታውን አሟልቶ ያልፈፀመ ስለሆነ ውሉ ፈርሶ ወደነበርንበት እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት መክሰሳቸው የህግ መሠረት የለውም፡፡ ይህን ክስ በመቀበል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 121731 ውሉ እንዲፈርስ የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 45360 የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን በማፅናት የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረታዊ ድንጋጌ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ አሁን በቀረበው ክስና በፊት ከአመልካች ጋር ተከራክረው ውሣኔ ያገኘው ጉዳይ መካከል ግኑኝነት የሌለው የተለያዩ ጭብጦች መሆናቸውን በማንሣት የተከራከሩ ቢሆንም አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታቸውን አሟልተው ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም? የሚለውን ነጥብ በመመርመር አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታቸውን አሟልተው የተወጡ መሆኑን በመግለፅ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 ውሣኔ ሰጥተውበታል ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታውን ስላልተወጣ ውሉ ፈርሶ ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት በመዝገብ ቁጥር 45360 የሰጠው ውሣኔ ከዚህ በፊት የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበትን ጭብጥ በድጋሜ በማየት የተሰጠው ከዚህ በፊት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የተሰጠ ውሣኔ በመሆኑ ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም አመልካች በሽያጭ ውሉና ስለ ሽያጭ ውል በተደነገጉት የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ግዴታቸውን አሟልተው የተወጡ መሆኑንና ቀሪው ሥራ ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግስት አካል መሆኑን በማረጋገጥ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57891 የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35601 የሰጠው ውሣኔ በሰበር ታይቶ ሣይሻሻል ወይም ሣይሻር አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግዴታውን አሟልቶ ያልፈፀመ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባዋል በማለት ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በመቀበል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5(1)ን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 121731 ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማፅናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45360 በሚያዝያ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 73449 መጋቢት 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሸ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ *57356*

መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች - ወ/ሮ መሠረት በቀለ ጠበቃ አቶ ታየ ገብረመድህን ቀረቡ

ተጠሪ - ወ/ሮ ኤልዛ ሶሞኔላ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት ስለቀረበ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ/ከሣሽ/ ተከሣሽ/አመልካች/ አውሊያቸውን ተለማምነው በጠና ታሞ የነበረውን ባለቤቴን እንደሚያድኑት ገልፀው የሸያጭ ውል የተደረገ በማስመሰል በድሬደዋ ከተማ በካርታ ቁጥር 1813 የተመዘገበውን ቤት በነፃ በስጦታ ወስደዋል ውሉ ህገወጥ በመሆኑ እንዲፈርስ ይህ የሚታሰፍ ቢሆን ውሉ በአስገዳጅነት ማሚላት እንዳለባቸው በህግ የተደነገገውን መስፈርት የማያሚላ በመሆኑ እንዲፈርስልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርበው ውሉ በሙሉ ፈቃድና ስምምነት ከሣሽ ቤታቸውን የሸጡልኝ በመሆኑ ውሉ ለህግ ተቃራኒ አይደለም፡፡ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ በመሆኑ አስገዳጅ መስፈርቶችን የሚያሚላ ውል በመሆኑ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ ከሣሽ /ተጠሪ/ እና ተከሣሽ /አመልካች/ ሰኔ 25 ቀን 1996 ዓ.ም ያደረጉት ውል ተዋዋዮቹ ብቻ የፈረሙበት ሰነድ ነው፡፡ በውልና ማስረጃ የተደረገ ቢሆንም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በሁለት ምስክሮች የተፈረመ አይደለም ስለዚህ ውሉ እንደረቂቅ የሚታይና ፈራሽ ነው በማለት ከሣሽ /ተጠሪ/ ከተከሣሽ የወሰዱትን ብር 23,000 /ሃያ ሶስት ሺህ ብር/ ለተከሣሽ ይመልሱ ተከሣሽ /አመልካች/ በድሬዳዋ ከተማ በካርታ ቁጥር 4813 በ800 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን የድርጅት ቤት ተከሣሽ /ተጠሪ/ ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በድፊዳዋ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ፊት የተደረገ ነው፡፡ ውሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723/1/ የተደነገገውን ፎርማሊቲ ያሟላል፡፡ ውሉ በፅሑፍ የተደረገ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2877 የተደነገገውን ፎርማሊቲ ያሟላል ውሉ በሁለት ምስክሮች አለመፈረሙና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727/2/ የተደነገገውን ፎርማሊቲ አላሟላም በማለት ውሉ እንዲፈርስ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ቤቱን ከገዛሁ በኃላ ከብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ ብር በላይ ወጭ በማድረግ የማስፋፊያ ግንባታ አድርጌለሁ ስለዚህ ውሉ ፈርሶ ወደነበራችሁበት ተመለሱ በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ጥር 13 ቀን 2003 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ባለሥልጣን ውሉን ተቀብሎ ከመመዝገቡ ውጭ ውሉን ስንፈራረም አላየም ውሉን መንደር ውስጥ ነው የተፈራረምነው በውሉ ላይ ምስክሮች እንዲኖሩ ያልተደረገው አመልካች እኔን በውሉ ላይ ያስፈረሙኝ አውሊያው አዞሻል የሚልና ሌሎች የማስፈራሪያ ቃሎችን በመጠቀም ያስፈረሙኝ በመሆኑ ነው፡፡ ውልና ማስረጃ መደረጉ የምስክሮችን ፊርማ አስፈላጊነት ቀሪ አያደርግም ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል አመልካች ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የተጠሪ ባለቤት ከዚህ ዓለም በሞት የተለያት ጥር 13 ቀን 1995 ዓ.ም በመሆኑና ተጠሪ ቤቱን የሸጡልኝ ሰኔ 25 ቀን 1996 ዓ.ም ተጠሪ አመልካች አሰፈራርታኝ ነው የፈረምኩት በማለት ያቀረቡት ክርክር ዕውነትነት የሌለውና በክፉ ልቦና የቀረበ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ውል በሁለት ምስክሮች ፊርማ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ውሉ ፈርሶ ተዋዋዬች ወደነበሩበት ይመለሱ በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አንድን ውል የፀና ውል ለማድረግ ከሚያስፈልጉ ሶስት መሠረታዊ መስፈርቶች አንደኛው የውሉ አፃፃፍ በህግ የታዘዘ በሆነ ጊዜ ውሉ በህጉ የተመለከተውን ልዩ ፎርም በሚያሟላ ሁኔታ መደረጉ እንደሆነ በፍታብሐር ህግ ቁጥር 1678/ሐ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪና አመልካች ያደረጉት የማይንቀሳቀሥ ንብረት ሽያጭ ውል ነው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውሉ በፅሑፍ ሊደረግ የሚገባው መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2877 “የውሉ ፎርም” በሚል ርዕስ ሥር ተደንግጓል፡፡ ህጉ በግልፅ የሚያስገድድ በሆነ ጊዜ ውሉ በህጉ የታዘዘውን ልዩ ፎርም ማሟላት የሚገባው መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1719 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ሲሆን ውሉ በፅሑፍ እንዲደረግ በህግ የተደነገገ ግዴታ ሲኖር ልዩ በሆነ አሰራር ተገልፆ በውሉ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ውሉን መፈረም እንዳለባቸው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ውሉ በፅሑፍ እንዲሆን ህግ የሚያስገድድ በሆነ ጊዜ በፅሑፍ በተደረገው ውል ላይ ተዋዋዬች መፈረማቸው ብቻውን ህጉ የፀና ውል እንደማያደርገው በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተረጋገጠ አይፀናም በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ደንግጓል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ውሉ መደረጉን የሚያረጋግጡ ምስክሮች አካለመጠን ያልደረሱና ያልተከለከሉ መሆን እንደሚገባቸው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1729/1/ ተደንግጓል፡፡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723/1/ መሠረት የማይንቀሳቀሥ ሽያጭ በውል አዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ፊት እንዳደረገ የተደነገገው በፍታብሐር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1729

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን አስገዳጅ ፎርም ህግ አውጭው ለማስቀረት ወይም ለመተካት በማሰብ አይደለም፡፡ በአንፃሩ የማይንቀሳቀሥ ንብረት በውል አዋዋይ ፊት ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ፊት ሲደረግ ውሉን የሚያዋውለው ባለሥልጣን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678 የተደነገጉት ሶስት መሠረታዊ ሁኔታዎች መሟላታቸውንና በተለይም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገጉት ፎርማሊቲዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ተዋዋዩች ውሉን እንዲፈራረሙ ያደርጋል የሚል ሀሳብ ስለነበረው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪና አመልካች ሰኔ 25 ቀን 1996 ዓ.ም ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1678 /ሐ/ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2877 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን አስገዳጅና ልዩ የውል ፎርም የማያሟላ በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባዋል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ቤቱን ከገዙ በኃላ ከፍተኛ የሆነ የማስፋፊያ ግንባታ ሥራ እንደሰሩ በሰበር አቤቱታቸው በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም አመልካች ይኸንን ለሰበር ችሎት ያቀረቡትን መከራከሪያ ለሥር ፍርድ ቤት አንስተው ያልተከራከሩበትና በሰበር ደረጃ የቀረበ አዲስ የፍሬ ጉዳይ ክርክር መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ግልባጭ ተገንዝበናል በመሆኑም አመልካች ቤቱን ከገዙ በኃላ ተጨማሪ ግንባታ እንደገነቡ በማንሣት በሰበር ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሣና የፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 329 ንዑስ አንቀጽ 1ን በሚጥስ መንገድ ለሰበር ችሎት የቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ ህጋዊ መሠረትና ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸውን መሠረታዊና አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪና አመልካች ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት መስከረም 26 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. ግራቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚያዝያ 21 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ተድላ ማሞ ጌታቸው ጠበቃ አቶ ጌታቸው በለጠ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1- አቶ ፍስሐ ሱመር ቀረቡ

2- አቶ ስዩም ተክለማርያም አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አንድ በኩል አመልካች ከሣሽ ተጠሪዎች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች የተከሣሽ ከሣሾች አመልካች የከሣሽ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር መስከረም 27 ቀን 1996 ዓ.ም የግንባታ የሥራ ውል እንደተዋዋለና ለሥራው ብር 715,625/ የሰባት መቶ አሥራ አምስት ሺ ስድስት መቶ ሃያ አምስት ብር/ ለመክፈል የተስማማ መሆኑን ተጠሪዎች በሶስት ጊዜ ክፍያ ብር 322,345.75 /ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ሺ ሶስት መቶ አርባ አምስት ብር ከሰባ አምስት ሣንቲም/ የወሰዱ መሆኑን ገልፆ ተጠሪዎች የግንባታ ሥራውን ከጀመሩ በኋላ ብር 94,905.40 /ዘጠና አራት ሺ ዘጠኝ መቶ አምስት ብር ከአርባ ሣንቲም/ ዋጋ ያለው ሥራ ከሠሩና ብር 6068.40 ዋጋ ያለው የግንባታ ዕቃ በቦታው በመተው ሥራውን አቁመዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ከወሰዱት ክፍያ ውስጥ ሥራ ላይ ያላዋሉትን ብር 221,369.95 /ሁለት መቶ ሃያ አንድ ሺ ሶስት መቶ ስልሣ ዘጠኝ ብር ዘጠና አምስት ሣንቲም/ ከነወለዱ ሊመልሱልኝ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግንባታው በወቅቱ ባለመጠናቀቁ ቤቱን ለመሥራት የሚጠይቀው ተጨማሪ ወጭ ብር 335,012.70 /ሶስት መቶ ሰላሣ አምስት ሺ አስራ ሁለት ብር ከሰባ ሣንቲም/ ሊከፍሉ ይገባል፡፡ ግንባታው በመዘግየቱ ብር 71,562.50 መቀጫ የመክፈል ሀላፊነት አለባቸው፡፡ በአጠቃላይ ተከሣሾች /ተጠሪዎች / ብር 637,623.88 /ስድስት መቶ ስላሣ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከሰማኒያ ስምንት ሣንቲም/ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በተከሣሽነት ቀርበው ከሣሽ /አመልካች/ ያቀረበው ክስ ተገቢ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግንባታ ሥራው በወቅቱ ያልተጠናቀቀው ከሣሽ የግንባታ ፈቃድ የሌለው በመሆኑና ግንባታውን እንድናቆም የቀበሌ አስተዳደር ስላስገደደን ነው፡፡ የዋጋ ጭማሪውም በዚህ ምክንያት የደረሰ ነው፡፡ የግንባታውን ሰማኒያ አምስት ፐርሰንት አጠናቀናል፡፡ ከሣሽ ግምቱ ብር 100,000 የሆነ የግንባታ ዕቃ ወስዷል፡፡ ስለሆነም የከሣሽ ክስ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

2. ተጠሪዎች በበኩላቸው የግንባታውን ሰማኒያ አምስት ፐርሰንት የሠራን ሲሆን ከሣሽ ሊከፍለን የሚገባውን የሶስተኛ ዙር ክፍያ አልከፈለንም ከሣሽ የግንባታ ዕቃ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት የመጣውን የዋጋ ለውጥ የመሸፈን ግዴታ ያለበት ቢሆንም የዋጋ ለውጡን አልከፈለንም ከዚህ በተጨማሪ ከሣሽ ለዕቃ ኪራይ የከፈልነውን በቦታው የነበረውና የወሰደውን የግንባታ ዕቃ ዋጋ በድምሩ ብር 33,594.56 /ሶስት መቶ ሰላሣ ሶስት ሺ አምስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከሀምሣ ስድስት ሣንቲም/ ሊከፍለን ይገባል በማለት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሣሽ ከሣሽነት ቀርቦ ተከሣሾች/ ተጠሪዎች/ የሠሩት የግንባታ ሥራ አስራ አራት ፐርሰንት ብቻ ስለሆነ ተጨማሪ ክፍያ የጠየቁት አላግባብ ነው፡፡ ከሣሾች የዋጋ ጭማሪ ክፍያና የግንባታ ዕቃ ዋጋ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአመልካችን ክስና የተጠሪዎችን የመከላከያ መልስ እንደዚሁም የተጠሪዎችን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስና የአመልካችን የከሣሽ ተከሣሽነት ክርክርና ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ በመስማትና በመመርመር የግንባታ ፈቃድ የማውጣት ኃላፊነት ያለባቸው ተከሣሾች /ተጠሪዎች/ በመሆናቸው ለግንባታው መዘግየት በሀላፊነት የሚጠየቁት ተከሣሾች /ተጠሪዎች/ ናቸው፡፡ ስለተሠራው የግንባታ ሥራ መጠን የተሻለ ማስረጃ ያቀረበው ከሣሽ /አመልካች/ በመሆኑ ተጠሪዎች/ ተከሣሾች/ በቅድሚያ ክፍያ ከወሰዱት ገንዘብ ውስጥ ብር 221,369.95 ለከሣሽ /አመልካች/ ሊመልሱ ይገባል፡፡ የግንባታ ሥራው በወቅቱ ላለመጠናቀቁ ሀላፊነት ያለባቸው ተጠሪዎች ስለሆኑ በግንባታው መዘግየት ለተከሰተው የዋጋ ጭማሪ የተከሣሽ ከሣሾች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተጠሪዎች ብር 556,382.65 / አምስት መቶ ሃምሣ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሠማኒያ ሁለት ብር ከስልሣ አምስት ሣንቲም/ ለአመልካች ከሣሽ ይክፈሉ በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

3. ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የግንባታ ፈቃድ የማውጣትና ኘላኑን የማፅደቅ ሀላፊነት ያለበት ተዋዋይ ወገን ማንኛቸው እንደሆኑ አመልካች ተጠሪዎች ያደረጉት የግንባታ ሥራ ውል አይገልፅም፡፡ ተጠሪዎች የግንባታ ፈቃድ ለማውጣትና ኘላን ለማፀደቅ በውሉ በግልፅ ሀላፊነት ያልወሰዱ ከመሆኑና የግንባታ ፈቃድና ኘላን የሚሰጠው ለባለቤቱ ወይም ለህጋዊ ወኪል ብቻ እንደሆነ የየካ ክፍለ ከተማ የመሠረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት የግንባታ ፈቃድ ክትትልና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 17 እና የመመሪያ ቁጥር 1/97ን በመጥቀስ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት በፅሑፍ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች የአመልካች ወኪል መሆናቸው አልተረጋገጠም ስለዚህ ግንባታ ፈቃድ የማውጣትና ኘላን የማፅደቅ የአመልካች ሀላፊነት ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪዎች በኘላኑ መሠረት የተከናወነውን የግንባታ ሥራ በማረጋገጥ ክፍያ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት መሆኑ አመልካችና ተጠሪዎች መስከረም 27 ቀን 1996 ዓ.ም ባደረጉት ውል አንቀፅ 3 በግልፅ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ለተጠሪዎች የከፈለው የመጀመሪያ ክፍያ የግንባታ ሥራውን ለማስጀመር ሁለተኛው ክፍያ ደግሞ ሥራው የተሠራ መሆኑ ተረጋግጦ የተከፈለ መሆኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 221,369.95 የመመለስ ግዴታ የለባቸውም፡፡ አመልካች የግንባታ ፈቃድ ባለማውጣቱና ኘላን ባለማፀደቁ ምክንያት የግንባታ ሥራው በመዘግየቱ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጣን የግንባታ ዕቃ ዋጋ ጭማሪ ተጠሪዎች ለአመልካች የመክፈል ግዴታ ያለባቸውም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ የተጠሪዎችን የከሣሽነት ክስ በተመለከተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ይወስን በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

4. አመልካች ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች አመልካች ጋር የቤት ግንባታ ውል የተዋዋሉት የግንባታ ፈቃድ አውጥተውና ኘላኑን አፀድቀው በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ግንባታውን ጨርሰው ለአመልካች ለማስረከብ ነው ተጠሪዎች የግንባታ ፈቃድ ሣይኖርና ኘላን ሣይፀድቅ ቤቱ ሊገነባ እንደማይችል ያውቃሉ፡፡ የግንባታ ፈቃድ ሣይወጣና ኘላኑ ሣይፀድቅ ሥራ መጀመራቸው ጥፋት ነው፡፡ ስለዚህ ለግንባታው መዘግየት ተጠሪዎች ሀላፊነት ያለባቸውም በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የወሰዱትን ገንዘብ የሚመጥን የግንባታ ሥራ ሠርተዋል ወይስ አልሠሩም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኞችን ክርክርና ማስረጃ በመመዘንና በማጣራት መወሰን ሲገባው በገለልተኛ ባለሙያ ተገምቶ የቀረበውን ማስረጃ ውድቅ በማድረግ ክፍያው የተፈፀመው ለተሠራው ሥራ መጠን ነው በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ለውሉ መዘግየት ሀላፊ መሆናቸውንና የግንባታ ዕቃ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት የመጣውን ልዩነት መክፈል ሀላፊነት ወስኖ እያለ የተጠሪዎችን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ውሣኔ አልሰጠበትም በማለት ጉዳዩን መመለሱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪዎች ታህሣሥ 1 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጡት መልስ ስለግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ አቀራረብ አሰጣጥና ቁጥጥር በወጣው አዋጅ ቁጥር 316/79 ግንባታ ፈቃድ የሚጠየቀው ሲፈቀድም የሚሰጠው ለባለቤቱ ወይም ለወኪሉ ስለመሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ ነጥብ በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ የሚመለከተው አካል ግልፅ ምላሽ በፅሑፍ ሰጥቶ እያለ ይህንን በማለፍ የከፍተኛው ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ በይግባኝ ሰሚው ችሎት መሻሩ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች የግንባታ ፈቃድ ያወጡት ከአንድ ዓመት በኋላ በመሆኑ ግንባታው በመዘግየቱ ምክንያት ለደረሰው የግንባታ ወጭ ጭማሪ ተጠሪዎች የመክስ ሀላፊነት የለብንም፡፡ የግንባታ ሥራውን ዋጋ ክፍያ የወሰድነው የተሠራው ሥራ መጠንን በተመለከተ አሠሪው /አመልካች/ እና የሥራ ተቋራጮች የሆኑት ተጠሪዎች ጥር 28 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ መተማመኛ ተፈራርመው በመሆኑ የምንመልሰው ገንዘብ የለም፡፡ ተጠሪዎች 85% እንደሠራንና አመልካች ለሠራነው ሥራ ክፍያ ያልፈፀመ በመሆኑን ገልፀን ያቀረብነው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ሣያጣራና ሣይወሰን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያለፈው በመሆኑ ጉዳዩን ይግባኝ ሰሚው ችሎት መመለሱ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ ሁለት ገፅ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ይዘት በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ ማለትም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች የግንባታ ፈቃድ የማውጣትና ኘላን የማስፀደቅ ሀላፊነት የሌለባቸው በመሆኑ ግንባታው በመዘግየቱ ምክንያት የግንባታ ዕቃ ዋጋ በመጨመሩ የደረሰውን የዋጋ ጭማሪ ለመክፈል ሀላፊነት የለባቸውም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተለያየ መደምደሚያ ላይ የደረሱበትን ምክንያት መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ግንባታ ፈቃድ የማውጣትና ኘላን የማስፀደቅ ሀላፊነት አለባቸው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው አመልካችና ተጠሪዎች የግንባታ ሥራ ውል ለመዋዋል ሲነጋገሩ ተጠሪዎች የግንባታውን ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግስት አካል በማውጣትና ኘላኑን በማስፀደቅ ግንባታውን በስድስት ወር ውስጥ አጠናቅቀው ለማስረከብ ለአመልካች ገልፀውላቸዋል በማለት የአመልካች ምስክሮች ቃል ለሰጡት የምስክርነት ቃል ታዓማኒነትና ክብደት ያለው ማስረጃ መሆኑን በመግለፅና ተጠሪዎች የግንባታ ፈቃድ ሣይኖር ሥራ መጀመራቸው ከሙያቸው አንፃር ሲታይ ጥፋታቸው ነው በማለት መሆኑን በውሣኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ አመልካችና ተጠሪዎች መስከረም 27 ቀን 1996 ዓ.ም የተዋዋሉት የግንባታ ሥራ ውል ተጠሪዎች የግንባታ ፈቃድ የማውጣትና ኘላን የማስፀደቅ ሀላፊነት ያለባቸው መሆኑን አይገልፅም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግንባታ ሥራ ፍቃድ የሚሰጠው ለንብረቱ ባለቤት ወይም ለህጋዊ ወኪሉ ብቻ መሆኑ አግባብነት ባላቸው የህግ ማዕቀፎችና የአሠራር መመሪያዎች ተመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች የአመልካች ወኪሎች ስለመሆናቸው የቀረበ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ ተጠሪዎች የግንባታ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚችሉ አይደለም፡፡ ስለሆነም የግንባታ ሥራ ፈቃድ ባለመውጣቱ ምክንያት የግንባታ ሥራ ለመዘግየቱም ሆነ በዚህ ምክንያት ለተከሰተው የዋጋ ለውጥ ተጠሪዎች በሀላፊነት አይጠየቁም በማለት ነው፡፡

ከዚህም የምንረዳው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችና ተጠሪዎች መስከረም 27 ቀን 1996 ዓ.ም በፅሑፍ ያደረጉትን የግንባታ ሥራ ውል ይዘትና አግባብነት ባላቸው የህግ ማዕቀፎች መሠረት የግንባታ ሥራ ፈቃድ ማውጣት የሚችለው ማንኛው ወገን ነው የሚለውን ነጥብ መሠረት ማድረግ ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ነው፡፡ የአንድ ሰው ግዴታ ሀላፊነት ከውል ወይም ከህግ የሚመነጭ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ሲደራደሩ የግንባታ ፈቃድ ለማውጣትና ኘላኑን ለማስፀደቅ እንደሚችሉ እንደገለፀ በአመልካች ምስክሮች የተገለፀ ሲሆን አመልካችና ተጠሪዎች ያደረጉት የግንባታ ሥራ ውል ስምምነት ውስጥ ተጠሪዎች የግንባታ ሥራ ፈቃድ ለማውጣትና ኘላኑን አፅድቀው ሥራ ለመጀመር በግልፅ ያልተዋዋሉም መሆኑን ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘዘን የሥር ፍርድ ቤት የፈፀመውን ስህተት በይግባኝ አይቶ የማረም ሥልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የግንባታ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የግንባታ ሥራ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥና የፀደቀ ኘላን መኖሩን የማረጋገጥ ሙያዊ ሀላፊነት አለባቸው በማለት የወሰነው ውሣኔ የግንባታ ፈቃድ አሠጣጥ ክትትልና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 17 እና ከመመሪያ ቁጥር 1/97 አንፃር ሲታይ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ የግንባታ ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ለባለቤቱ ወይም ለወኪሉ ብቻ መሆኑን በማረጋገጥ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤት በህግ አተረጓጎም ረገድ የፈፀመውን ግድፈት እንዳረመ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የግንባታ ሥራ ፈቃድ የማውጣት ሀላፊነት ያለበት ማን ነው? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ መፍታት ያስፈለገው የግንባታ ሥራ ፈቃድ ባለመውጣቱ ምክንያት ለግንባታ ሥራው መዘግየትና የግንባታ ዕቃዎች ባሣዩት የዋጋ ጭማሪ ምክንያት የወጣውን ተጨማሪ ወጭ የመሸፈን ሀላፊነት ያለበት አመልካች ነው ወይስ ተጠሪ ነው የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግንባታ ሥራ ውሉ በግልፅ ተጠሪዎች ግዴታ ያልገቡበትንና ከላይ በተገለፁት አግባብነት ባላቸው የህግ ማዕቀፎችና የአሠራር መመሪያዎች የአመልካች ወይም የአመልካች ህጋዊ ወኪሎች ተግባርና ሀላፊነት መሆኑ የተደነገገውን ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት የግንባታ ሥራው የዘገየ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡

ተጠሪዎች ከውል ወይም ከህግ የመነጨ የግንባታ ሥራ ፈቃድ የማውጣትና ኘላን የማስፀደቅ ሀላፊነት የሌላባቸው በመሆኑ የግንባታ ሥራው የግንባታ ሥራ ፈቃድ ባለመወጣቱ ምክንያት ለመዘግየቱና የግንባታ ሥራው በመዘግየቱና ምክንያት ለተከሰተው የግንባታ ዕቃ ዋጋ ጭማሪ ተጠያቂ የሚሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያሌለበት በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪዎች የሠሩት የግንባታ ሥራ መጠንና ከአመልካች የወሰዱትን የገነዘብ መጠን ተመጣጣኝ መሆኑን በማጣራት መወሰን ሲገባው ተጠሪዎች ለአመልካች የሚመልሱት ገንዘብ የለም በማለት መወሰኑ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በሰበር በጭብጥነት የተያዘ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፌደራል ጠቅለይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 221,369.95 እንዲመልሱ በማለት የሰጠውን ውሣኔ የሻረው ተጠሪዎች ለገነቡት የግንባታ ሥራ አመልካች ክፍያ ስለሚፈፅምበት ሁኔታ በግንባታ ሥራ ውሉ የተስማሙበትን የውል ሀይለ ቃልና አመልካች ተጠሪዎች ጥር 25 ቀን 1996 ዓ.ም በመተማመን የተፈራረሙበትን ሠነድ ይዘት ታሳማኒነትና ክብደት በመመዘን እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን ውሣኔ የተሰጠበት በመሆኑና የሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን የሌለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 የተደነገገ በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን መመለሱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግለፅ አመልካች የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የከሣሽን ክስና ማስረጃ በመቀበል ተጠሪዎች በሀላፊነት ይጠየቃሉ ብሎ ስለወሰነ የተጠሪዎችን የተከሣሽ ከሣሽነት ጥያቄ በጥቅሉ ውድቅ አድርጎባቸው የነበረ መሆኑን ውሣኔው ያሣያል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪዎች ለአመልካች ክስ ተጠያቂ አይደሉም በማለት ወስኖ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ ይህም በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከዚህ በፊት በዝርዝር አጣርቶ ያልወሰነውን የተጠሪዎች የተከሣሽ ከሣሽነት ጥያቄ አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን መልሶታል፡፡ ይህ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ከመሆኑም በላይ ገና በሂደት ላይ ያለና የመጨረሻ ውሣኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወሰን ይግባኝ ሰሚው ችሎት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

ከላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 58157

ሚያዚያ 06 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- አቶ ዮሐንስ ታደሰ - ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አማረች መንገሻ ጠበቃ አቶ ምክሩ ወ/አረጋይ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች ለሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ፍሬ ቃሉ ተከሳሽ /ያሁን ተጠሪ/ የአደረግነውን የወሰን ምልክት ስምምነት በመጣስና በውላችን በተስማማንበት መሠረት ባለመፈፀም ከፍ/ቤት የተሰጠ ትዕዛዝ ሳይኖር ሀሰተኛ የአጥር ፈቃድና ህገ ወጥ የይዞታ ማረጋገጫ በመያዝ አጥሬን በማፍረስ፣ የወሰን ምልክት በማጥፋትና ቀደም ሲል ከወ/ሮ ይርግዱ ሳሙኤል ወራሾች ከነ ወልደየስ አምባዬ በግዥ ካገኘችው ቦታ አልፋ በንብረቶቼ ላይ ጉዳት ያደረሰችና አዲስ አጥር ስላጠረች በህገ ወጥ መንገድ ያጠረችውን አጥር አፍርሳና የራሴን ያፈረሰችውን አጥር መልሳ በመሣጠር ቀደም ሲል በገባነው ውል መሠረት እንደትፈጽም ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሳሽም በሰጠችው መልስ ይዞታው የከሳሽ ስለመሆኑ ማስረጃ ስለሌለው ክስ የማቅረብ መብት የለውም፣ በዚህ ጉዳይ ለአምስት ተደጋጋሚ ጊዜያት በተለያዩ መዛግብት ክስ ሲያቀርብ የቆየ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 መሠረት ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል፣ ከሳሽ እነደሚለው ሣይሆን ቦታውን ያጠርኩት ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርና ከሥራና ከተማ ልማት ጽ/ቤት በተሰጠኝ ፈቃድ ሲሆን ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ታጥሮ ያለ የግል ይዞታዬ ነው፣ በንብረቱም ላይ ያደረስኩት ጉዳት የለም፡፡ ነገር ግን ዛፍ ተቆረጠብኝ ለሚለው ዛፉ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ ታውቆ የደን ሚኒስቴር እና ፖሊስ ያስቆረጡ ስለሆነ አይመለከተኝም፣ ከዕርቅ ስምምነት ውጪ ስለመሥራቴም ከሳሽ ያቀረበው ማስረጃ ካለመኖሩም ሌለ ከሳሽ የተከሳሽን ይዞታ 2x4 ሜትር የሆነውን አልፎ በመያዝ በጉልበት እየተጠቀመበት ስለመሆኑ የካርታ ቁጥሩ ጀ አይ ኤስ 5556 የሆነ ያረጋግጣል በማለት የከሳሽ ክስ ውድቅ ተደርጎ ኪሣራ ከፍሎ መዝገቡ እንዲዘጋ አመልክታለሁ ብላለች፡፡

የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ በ24/10/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ፍርድ በአዋጅ ቁጥር 361/95 መሠረት ካርታ የመስጠትና የመሠረዝ ሥልጣን የክፍለ ከተሞች ነው፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ካርታው የተሰጣት ያለአግባብ ነው የሚል ከሆነ ካርታውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠውን ክፍል እንዲሰርዝ ከሚጠይቅ ውጪ ጥያቄውን ለፍ/ቤት ማቅረብ የለበትም በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ አድርጐበታል፡፡ ከሳሽ አላአግባብ ተከሳሽን በመክሰሱ ምክንያት ለወጣው የጠበቃ አበል ብር 10,000/አሥር ሺህ/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

በዚሁ በሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁኑ አመልካች ለሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በማጽናት ለሥር መ/ሰጪ የወጪና ኪሣራ የመጠየቅ መብት ጠብቆላታል፡፡ በዚሁ መሠረት የሥር መልስ ሰጪ የወጪ ዝርዝር ጥያቄ ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርባ በመዝገብ ቁጥር 82975 በቀን 24/12/2002 በተሰጠ ፍርድ ብር 6,000/ስድስት ሺህ/ ይግባኝ ባይ /ያሁን አመልካች/ ለመልስ ሰጪ /ለአሁኗ ተጠሪ/ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

የሰበር አመልካችም የሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገሩም ሆነ በወጪ ዝርዝር ላይ በሰጡት ውሣኔ ቅር በመሰኘት አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ በዋነትም አመልካች የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦች፡-

እኔ ለሥር ፍ/ቤት ያቀረብኩት ክስ እንደውሉ እንዲፈፀምልኝ ሆኖ ሳለና ካርታ ይሠረዝልኝ በሚል ተቀጥሮ ክሱ ውድቅ መደረጉ፣ እንዲሁም በሥር መ/ደ/ፍ/ቤት ብር 10,000 የጠበቃ አበል እንድከፍል መወሰኑና ከፍተኛ ፍ/ቤትም ድጋሚ ኪሣራ እንድከፍል መወሰኑ ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡ ተጠሪዋ በጠበቃ አማካይነት በሰጠችው መልስ አመልካች የተጠሪው ይዞታ 500 ካ.ሜ ሲሆን 900 ካ.ሜ ካርታ ድንበሩን በመግፋት ያወጣችው ህገ ወጥ ካርታ ይሠረዝልኝ በማለት በተደጋጋሚ የሚከራከር ሲሆን ህገ ወጥም ሆነ ህጋዊ ካርታን ለማሠረዝ የሚቀርበው አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 361/95 ሥልጣኑ የክፍለ ከተማ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ አይደለም፣ አመልካችና ተጠሪ ቦታን በሚመለከት ያደረግነው ስምምነት የለም፣ አለ ቢባል እንኳን ከ1985 ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ድረስ በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1727 መሠረት በምስክሮች ፊት ያልተረጋገጠ፣ በውል አዋዋይ ቀርቦ ያልተመዘገበና ተጠሪ ያልፈረምኩበት በአመልካች ብቻ የቀረበ ውል ተቀባይነት የለውም በማለት በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ወጪና ኪሣራ የመጠየቅ መብት ተጠብቆ መዝገቡ እንዲዘጋ ጠይቃለች፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን የቀረበ ሲሆን እኛም የሚከተሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

1. ውሉ ሊፈፀም የሚችል ነው ወይስ አይደለም;
2. አመልካች በሁለቱም የሥር ፍ/ቤቶች እንዲከፍል የተወሰነበትን የጠበቃ አበል በሙሉ መክፈል አለበት ወይስ የለበትም;

1ኛን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ይፈፀምልኝ በማለት ከክሱ ጋር አይይዞ ያቀረበው ሚያዝያ 04 ቀን 1991 ዓ.ም አመልካችና ተጠሪ በቀድሞ አጠራር በወረዳ 17 ቀበሌ 14 አስተዳደር ጽ/ቤት ስምምነታቸውን የገለጹበት ማመልከቻ ሲሆን ፍሬ ቃሉም የአሁኑ አመልካች እና ይዞታውን ላሁኗ ተጠሪ ሸጠዋል የተባሉት እነ ወልደየስ አምባዬ የሚፈጽሙትን የወሰን መግፋትና የፍርድ ቤት ክስ በመተው ከአስፋልት መንገድ ጀምሮ ነባር አጥር ታጥሮ በኘላን ታይቶ የተነሣው የወ/ሮ ይርገዱ ሣሙኤል የካርታ ቦታ ኘላን የወሰን ድንጋይ ከታች በአቶ ደስታ መሐመድ አጥር መሠረት ቀጥታ ሆኖ የፈረሰው የአመልካች ነባር አጥር በነበረበት መሠረት ድንበራችን መሆኑን ለቀበሌ እናረጋግጣለን የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተዋዋይ ወገኖች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት ያላቸው ሲሆን ሕግ የወሰናቸውንና የከለከላቸውን ነገሮች ግን ሊያከብሩ እንደሚገባ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716 ይደነግጋል፡፡ ህግ የወሰናቸውንና የከለከላቸውን ነገሮች ባለመገንዘብ ወይም ባለማክበር የሚደረጉ ውሎች የማይፀኑና የማይፈፀሙ ናቸው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት በከተማ መሬት ነው፡፡ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት ደግሞ የመንግስትና የሕዝብ ብቻ መሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 40/3/ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በመንግሥትና በህዝብ መሬት ላይ ግለሰቦች አንዱ ሰጪ ሌላው ተቀባይ በመሆን የባለቤትነት መብት ሊመሠርቱ አይችሉም፡፡

በሌላ በኩል የሚያከራክረው ቦታ የከተማ ቦታ እስከሆነ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 11/2//ሰ/ መሠረት ተጠሪዎች የአመልካችን ይዞታ አልፋ ስለመያዟ በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት በሕግ መሠረት ለማስተዳደር ሥልጣን ለተሰጠው የከተማው አስተዳዳር ማመልከት ነበረበት፡፡ ይህን መብቱን ለመጠየቅ ደግሞ አመልካች ተጠሪዋ አልፋ ይዛብኛለች በሚለው ቦታ ላይ የባለይዞታነት መብት ያለው ስለመሆኑ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ካርታ ሊኖረው ይገባል፡፡

ተጠሪም በህገ ወጥ መንገድ የባለ ይዞታነት ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቷታል ለሚለውም ህገ ወጥ መሆኑንና አለመሆኑን መመርመርና ህገ ወጥነቱ ሲረጋገጥ መሠረዝ የሚችለው ይኸንኑ ማስረጃ ለመስጠት በህግ መብት የተሰጠው የከተማው አስተዳደር አካል መሆኑን ከዚህ በፊት ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 22719 ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በአመልካች የአ/አ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተተኪ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለሥልጣንና በተጠሪ አቶ ነጋሽ ዱባለ መካከል በተደረገው ክርክር ከሰጠው የህግ ትርጉም መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሰበር ችሎቱም የሚሰጠው የህግ ትርጉም በተመሣሣይ ጉዳዮች ላይ በየትኛውም ፍ/ቤት የአስገዳጅነት ባሕሪ ያለው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ስለሚደነግግ የሥር ፍ/ቤት ይኸንኑ የህግ ትርገም መሠረት በማድረግ ካርታ ማሰጠትም ሆነ ማሠረዝ የፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም በሚል የወሰነው ከዚህ በላይ በተገለጹ ምክንያቶች የተነሣ አመልካች እንዲፈፀምለት ያቀረበው ውል የማይፈፀምና ካርታ የማሰጠትም ሆነ የማሠረዝ ሥልጣን የፍ/ቤት ሳይሆን የአስተዳደር መሥሪያ ቤት በመሆኑ በውሣኔው ላይ ይህን ጭብጥ በሚመለከት የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

2ኛው ጭብጥ የጠበቃ አበልን በሚመለከት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ነው፡፡ በመ/ደ/ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ለተጠሪ የጠበቃ አበል ብር 10,000/አሥር ሺህ/ ፣ በከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ደግሞ ብር 6,000.00 /ስድስት ሺህ/ እንዲከፍል ተወስኖበታል፡፡ በጠቅላላው አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነበት ብር 16,000/አሥራ ስድስት ሺህ ብር/ ነው፡፡

ለሥር መ/ደ/ፍ/ቤት የሥር ከሳሽ /አመልካች/ ክሱን በ24/03/2001 ዓ.ም ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዋም ፍ/ቤት ቀርባ ለክሱ መልስ የሰጠችው በ4/07/2001 ዓ.ም መሆኑንና ፍ/ቤቱም የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም በሚል የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው በ24/10/2001 መሆኑን የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡ ተጠሪዋ ፍ/ቤት ቀርባ ክርክር ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ በጉዳዩ ፍርድ እስከተሰጣት ጊዜ ተጠሪዋ ጠበቃዋ ፍ/ቤት የተመላለሡበት ጊዜ አጭር ነው፡፡ ፍርዱም ብዙም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለውሣኔ የሚረዱ ማስረጃዎችን መመርመር ሳያስፈልግ በሥር ነገር ሥልጣን መዝገቡ የተዘጋበት ነው፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤትም ቢሆን ያስቀርባል በሚል ካከራከረ በኋላ በፎርም የፍትሐብሔር ሥ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ን በመጥቀሥ የሥር መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የተጠሪ ጠበቃ በፍ/ቤት ቀጠሮዎች በዚህ ጉዳይ ለብዙ ጊዜ በመመላለስ ተጉላላቷል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

በመሆኑም ጠበቃው ዕውቀቱን ሥራ ላይ ለማዋል ላበረከተው አስተዋጽኦ እንዲከፍለው የተወሰነው የጠበቃ አበል ከሰጠው አገልግሎት አንፃር ሲታይ ከፍ ብሎ ተገኝቷል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2635 'ም' ከመጠን በላይ የሚደረገውን የሥራ ዋጋ ዳኞች ሊቀንሱ እንደሚችሉ የተደነገገውም ተዋዋይ ወገኖች ለሙያው ሥራና ተግባር እንዲሁም ክብር ተቃራኒ የሚሆን የሥራ ዋጋ ስምምነት እንዳያደርጉ ለመከልከል ታስቦ ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ የቀረበውን የወጪ ዝርዝር ጥያቄ በሚመረመሩበት ጊዜ የቀረበውን የወጪ ዝርዝር ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የፍትሃብሔር ሕግ ድንጋጌና ሌሎች አግባብነት ካላቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. ድንጋጌዎች አንጻር መርምረው መወሰን አለባቸው፡፡ ይህ ታልፎ አመልካች ከፍ ያለውን የጠበቃ አበል እንዲከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/መ/ቁ. 132135 በቀን 24/10/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች የጠበቃ አበል ብር 10,000 /አሥር ሺህ/ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔና የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ኮ/መ/ቁ. 82975 በቀን 24/12/2002 አመልካች ብር 6,000/ስድስት ሺህ/ እንዲከፍል የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች በሁለቱም ፍ/ቤቶች ለወጣው የጠበቃ አበል ብር 2,000/ሁለት ሺህ/ ለተጠሪ እንዲከፈል ወስነናል፡፡
2. አመልካች እንደውሉ ይፈፀምልኝ በማለት ያቀረበው ውል ሊፈፀም የሚችል አይደለም ብለናል፡፡
3. የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 132135 በቀን 24/10/2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት ካርታ የማሠረዝ ክስ የፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም በማለት የሥር ከሳሽን ክስ ውድቅ ያደረገውና ከፍተኛው ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 82975 በቀን 09/10/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ን በመጥቀስ ያፀናው በአግባቡ ስለሆነ አጽንተናል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ አመልካችና ተጠሪ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚያዝያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- እነ አቶ ተሾመ ካሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ቤዛ ኩሉ አዳም የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሽያጭ ምክንያት ተከፈለ የተባለ ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቶች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- አመልካቾች ከመኖሪያ ቤታቸውና ከይዞታቸው በመቀነስ በግምት 270 ካ.ሜትር የሆነና ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤት ብር 40,000/ አርባ ሺህ/ ሸጠውላቸው ብር 10,000.00 /አስር ሺህ / በውሉ እለት የከፈሏቸው መሆኑን ብር 20,000.00/ሃያ ሺህ ብር/ ደግሞ አመልካቾች ቤቱን አድሰው ለተጠሪ ሲያስረክቡ እንዲከፈላቸው የተስማሙ ቢሆንም አመልካቾች ቤቱን ባለማደሳቸው ተጠሪ በራሳቸው ገንዘብ እንዲያድሱ ስምምነት ላይ በመደረሱ ምክንያት ተጠሪ ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ/ ወጪ በማድረግ ቤቱን አድሰው የተረከቡ መሆኑን ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ ብር 51,000.00/ሃምሳ አንድ ሺህ ብር/ ወጪ በማድረግ ደረጃውን የጠበቀ አምስት ክፍል ቤት የሰሩ መሆኑን ተጠሪ በአመልካች ላይ የቤት ሽያጭ ውሉን በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ቀርበው እንዲያስመዘግቡ በፍርድ ቤት ክስ መስርተው ክርክሩ ሲካሄድ ቆይቶ ፍርድ ቤት በሕግ ፊት የሚፀና ውል የለም በማለት ውሣኔ መስጠቱን በመዘርዘር በማይጸና ውል የተወሰደውና ለግንባታ የወጣው ወጪ በድምሩ ብር 81,000.00/ሰማንያ አንድ ሺህ ብር / እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች በበኩላቸው ተጠሪ ወደ ቤቱ የገቡት በኃይል መሆኑን በተጨማሪነት የገነቡት ግንባታም አለመኖሩን የሽያጭ ውሉም የተጭበረበረ መሆኑን በውሉ ደረሰኝነት ብር 10,000.00 ብቻ መቀበላቸውን ገልፀው ይኸው ገንዘብ ተከፍሏቸው ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ሊደረግ ይገባል ሲሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውንና ተያያዥ ጭብጦችን በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮችን ቃል መርምሮ አመልካቾች ለተጠሪ ብር 61,000.00 ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የቤት ሽያጭ ስለመኖሩ በሕግ መሠረት በጽሑፍ የተደረገና በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ፊት የተፈረመ የቤት ሽያጭ ውሉ በሌለበት ሁኔታ ለቤቱ እድሳት የወጣ ገንዘብ ለተጠሪ ሊመለስላቸው ይገባል መባሉ እንዲሁም ተጠሪ ተጨማሪ ግንባታ አከናወንኩ የሚል ክርክር ሳይኖራቸውና በማስረጃም ባልተደገፈበት መንገድ ለብር 61,000.00/ስልሳ አንድ ሺህ ብር / ሃላፊ ተደርገን ውሣኔ መሰጠቱ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በማይፀና ረቂቅ ውል አመልካቾች የተቀበሉትን ብር 10,000.00 እንዲመልሱ ከመደረጉ በተጨማሪ ተጠሪ የግንባታ ፈቃድ እንኳን ሳይኖራቸው ሰራሁት ለሚሉት ቤት የምስክሮች ቃል ብቻ መሠረት ተደርጎ አመልካቾች ለተጠሪ የግንባታ ወጪ እንዲከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ከአላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ፡- አመልካቾች ለተጠሪ ገንዘቡን እንዲመልሱ ተብሎ የተወሰነው በሕጉ ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ መሠረት ባደረገ መንገድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክስ የመሰረቱት አመልካቾች ቤት ሽጠውልኝ የተወሰነ ገንዘብ ከፍዬአለሁ የተወሰነውንም የአመልካቾችን ግዴታ ለመወጣት ስል ወጪ አድርጌ ቤቱን በመረከብ ተጨማሪ ግንባታ አከናውኜ ባለበት ሁኔታ በፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር በሕግ ፊት የሚጸና ውል የለም ስለተባለ ገንዘቡ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት መሆኑን በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ የለም የሚለው ክርክርም በፍርድ ቤት ታይቶ ሕጋዊ የሆነ የቤት ሽያጭ ውል የሌለ መሆኑ መረጋገጡን ነው፡፡ የቤት ሽያጭ ውል የሌለ መሆኑ የተረጋገጠው ተጠሪ አመለካቾች የቤት ሽያጭ ውሉን ውል አዋዋይ ፊት ቀርበው ሊያስመዘግቡልኝ ይገባል በማለት በመሰረቱት ክስ አመልካቾች በሕግ ፊት የሚጸና ውል የለም በማለት በመከራከራቸው ምክንያት መሆኑንም ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ጉዳይ ያቀረቡትም የቤት ሽያጭ ውል የለም ተብሎ ውሣኔ ከተሰጠ በሁዋላ ሲሆን አመልካቾች ገንዘቡን ስለመቀበላቸው ያቀረቡትና ያሰሙት ማስረጃ የሰው ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡ አመልካቾችም የሰው ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የውሣኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾችን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው ገንዘቡን ከተጠሪ ስለመቀበላቸው ተጠሪ በተገቢው ማስረጃ አስረድተዋል አመልካች ግን በምስክሮቻቸው ሊያስተባብሉ አልቻሉም በሚል ምክንያት ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ የተመለከቱት ነጥቦች በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡት ሲሆን አመልካች የስር ፍርድ ቤት የስነ ሥርዓት ግድፈት ፈጽሟል በማለት የሚያቀርቡት አንዱ ነጥብ ተጠሪ ሕጋዊ የሆነ ቤት ሽያጭ ውል አለ በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ሳያገኝ በቤት ሽያጭ ውል የተከፈለው ገንዘብ እንዲመለስ ተብሎ መወሰኑ ለጉዳዩ መቅረብ ከሚገባው ማስረጃ አይነት አንፃር ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የቤት ሽያጭ ውልን አስመልክቶ ክርክሩ የቀረበበት አግባብ በተጠሪ በኩል የቀረበው የቤት ሽያጭ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውል አዋዋይ ፊት እንዲመዘገብ የሚል ክስ በመቅረቡ በመሆኑና በሕጉ አግባብ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የለም ተብሎ ድምዳሜ የተደረሰ በመሆኑ ተጠሪ በሽያጩ ምክንያት ለአመልካቾች የሠጡትን ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት ጥያቄ ከማቅረብና በማናቸውም ማስረጃ ከማስረዳት የማይከለክል መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1808/2/ ፣ 1815 ፣ 2001 እስከ 2019 እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 እና 2164 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን የማስረጃ አይነት መሠረት በማድረግ መቃወሚያ የሚቀርብበት ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩትና በዚህ ሰበር ችሎት እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ በጉዳዩ ላይ የቀረበው ማስረጃ በሕጉ ስላለው ተቀባይነት ነው፡፡ ተጠሪ ሕጋዊ አይደለም በተባለው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ለአመልካቾች ከፍያለሁ የሚሉት የገንዘብ መጠን ብር 10,000.00/አስር ሺህ ብር / ሲሆን ሌላው ብር 51,000.00 ከቤቱ ርክክብ በሁዋላ ለተደረገ ግንባታ የወጣ ወጪ ነው፡፡ አመልካቾች ለጉዳዩ የቀረበው ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ነው የሚሉት ይህንኑ የገንዘብ መጠን በሰው ማስረጃ ሊረጋገጥ አይገባም ተጠሪ በማስረጃም ክርክራቸውን አላስደገፉም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት የብድር ውል ሳይሆን ሕጋዊ ያልሆነ የቤት ሽያጭ ውል ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በሰው ምስክር ሊረጋገጥ አይገባም ተብሎ በአመልካቾች የቀረበው ክርክርም ሆነ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ጉዳዩ መገዛት ያለበት ስለሽያጭ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በተለይ በመመልከት ወይም ስለጠቅላላው ውል የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በማየት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች በጠቅላላው የውል ሕግ ሲሆን በዚህ የውል ሕግ አንድን ነገር ለመግዛት ገንዘቡን የከፈለ ሰው ግዥው ሕጋዊ አይደለም ተብሎ ውሣኔ ከተሰጠው ገንዘቡ እንዲመለስለት ጥያቄ ቢያቀርብና ክሱን በሰው ምስክር ቢያስረዳ የሰው ምስክሮች ቃል ተቀባይነት የለውም ሊባል እንደማይችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2001 እስከ 2019 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረቧቸውን የሰው ምስክሮች ቃል በመቀበል ውሣኔ መስጠቱ ከላይ ከተመለከቱት የጠቅላላ ውል ሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ሕጋዊ እንጂ የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ በቦታው ላይ ግንባታውን ያከናወኑት በአመልካቾች በኩል ተቃውሞ እየቀረበ ባለበት ሁኔታ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ ሲሆን የግንባታ ፈቃድ ሳያወጡ ግንባታው መከናወኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1178 እና 1179 ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ የተጠሪን የግንባታ ወጪ ይተካልኝ ጥያቄን ህጋዊ አይደለም ለማለት የሚያስችል አይሆንም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶቹ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ራፒድ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ ድርጅት - ጠበቃ አብዱወሀብ ረቢ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ኦርቢስ ንግድና ቴክኒክ ክፍል ሊሚትድ - ጠበቃ ግርማ ስላሴ አርአያ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመኪና ሽያጭ ውል ጋር ተያይዞ የተነሳውን መኪናና ሊብሬ ልረከብ እንዲሁም የተቋረጠ ጥቅም ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡-አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 3-07539 እና 3-09190 የሆኑ ሁለት መርቸዲስ ከባድ የጭነት ገልባጭ መኪናዎችን በ15-10-1993 ዓ.ም በተፈረመ የሽያጭ ውል ከተጠሪ ላይ በብር 1,620,000.00 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሺህ ብር) ገዝቶ አብዛኛውን ገንዘብ ከከፈለ በሁዋላ ቀሪውን ብር 486,000.00 በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ለማጠናቀቅ ይችል ዘንድ ቀናቸው ወደፊት ተደርጎ የተፃፉ ሁለት ቼኮችን ለተጠሪ በመስጠት ሁለቱን መኪኖች የተረከበ መሆኑን ፣ አመልካች ገዝቶ የተረከባቸው መኪኖች 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) ኪሎ ሜትር ከመንዛቸው ወይም አመልካች ከተረከባቸው ከአንድ አመት በፊት ቴክኒካል የሆነ ብልሽት ስለገጠማቸው ተጠሪ በውሉ መሰረት መኪኖቹን ለመጠገን ባለበት ግዴታ መሰረት መኪኖቹን ለጥገና ከጋራዡ ገብተው ተገቢው ጥገናም የተደረገላቸው መሆኑን ፣ ተጠሪ ለጥገና ከተረከባቸው ሁለቱ መኪኖች ውስጥ የሰ.ቁጥር 3-09190 አ.አ የሆነውን መኪና ጠግኖ ለአመልካች ሲያስረክብ የሠሌዳ ቁጥር 3-07539 የሆነውን መኪናና የሁለቱን መኪኖች ሊብሬ ለአመልካች መልሶ ለማስረከብ ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘቱንና ለዚህ ተግባሩም የሰጠው ምክንያት ቀናቸው ወደፊት ተደርጎ በአመልካች በኩል የተጻፉት ቼኮች የመክፈያ ጊዜ የደረሰ ስለሆነ በቼኮቹ ላይ የሰፈረውን ገንዘብ ሳይከፈለኝ ሊብሬዎቹንም ሆነ መኪናውን አላስረክብም የሚል መሆኑን ፣ ሊብሬዎቹና መኪናው እንዲመለስለት አመልካች ማስጠንቀቂያ የሰጠ ቢሆንም ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆኑን ፣ ተጠሪ በቼኮቹ ላይ የሠፈረው ገንዘብ እንዲከፈለው በፍርድ ቤት ክስ መስርቶም ያስወሰነ መሆኑን ፣ ተጠሪ አንዱን መኪና ከእነ ሊብሬው እንዲሁም ሌላኛውን መኪና ሊብሬ አላግባብ በመያዙ ምክንያት የሠ/ቁጥር 3-07539 አ.አ የሆነው ገልባጭ መኪና ለጥገና በተጠሪ ጋራዥ ከገባበት ከሚያዝያ 06 ቀን 1995 ዓ/ም ጀምሮ በስር ፍርድ ቤት ክስ እስከ ቀረበበት እስከ ታህሳስ 15 ቀን 1997 ዓ/ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድረስ እንዲሁም የሰ/ቁጥር 3-09190 የሆነው መኪና ሊብሬ በተጠሪ በመያዙ ምክንያት ለስምሪት ከከተማው ለመውጣት የሚያስችለውን ፈቃድ አጥቶ ለዘጠኝ ወራት ያህል ስራ በማቆሙ ምክንያት በድምሩ ብር 1,402,741.00 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ አርባ አንድ ብር) ገቢ ያጣ መሆኑን ዘርዝሮ ሊብሬውንና የተያዘውን መኪና ለአመልካች እንዲያስረክቡ ፣ የተቋረጠውን ጥቅምም እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሳሽነቱ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ ነጥቦችንና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ ያነሳው ነጥብ አመልካች ክስ የመሰረተው ቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ስለመሆኑ የሚገልፅ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የመኪኖቹን ዋጋ ቀሪ ሂሳብ ለመክፈል የተጠሰው ቼክ ካልተከፈለ ተጠሪ መኪኖቹን ወዲያውኑ በእጁ አስገብቶ ለሕዝብ በሐራጅ ለመሸጥ ይችላል በሚል በግራ ቀኙ መካከል ውል መደረጉን ፣ ሊብሬውንም በመያዣነት ተይዞ አመልካች ክላውዶ ለማስደረግ ሲፈልግ ሲሰጠው የነበረ በመሆኑ በገቢ መቋረጥ ላይ ተጠሪ የፈፀመው ድርጊት የሌለ መሆኑንና ሌሎች ነጥቦችን በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለተከው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረበውን መከራከሪያ ነጥብ ውድቅ አድርጎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ መኪኖቹንና ሊብሬዎቹን በሕግ አግባብ በመያዣነት የያዛቸው መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የአመልካችን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ወሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ/ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ፤ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በሕግ አግባብ የተደረገ የመያዣ ውል በሌለበት ሁኔታ የተሠጠ ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2825 ፣ 2828 ፣ 2830 እና 2846 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው፡-በአመልካችና በተጠሪ መካከል በሕግ አግባብ የተደረገ የመኪኖች የመያዣ ውል አለ ወይስ የለም? የሚለው ሲሆን ሌሎች ነጥቦች ከዚሁ ነጥብ ጋር ተያይዘው ምላሽ ሊሰጣቸው የሚገባቸው ናቸው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ/ም የሁለት መኪኖች ግዥ ውል ማድረጋቸውን ፣ የመኪኖቹ ዋጋ ብር 1,620,000.00 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሓያ ሺህ ብር) ሁኖ ገዥው ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ አብዛኛውን ከፍሎ ብር 486,000.00 (አራት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺህ ብር) የቀረበትን ይህንኑ ገንዘብም በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ለማጠናቀቅ ይችል ዘንድ ቀናቸው ወደፊት ተደርጎ የተፃፈ ሁለት ቼኮችን ለሻጭ በመስጠት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መኪኖቹን ሰኔ 08 ቀን 1994 ዓ/ም ገዥው ተረክቦ የመኪኖቹን ሊብሬም በዚሁ ቀን መረከቡን ፣ መኪኖቹ በተጠሪው ጋራዥ ሚያዚያ 06 ቀን 1995 ዓ/ም መግባታቸውን ፣ ከዚህም በሁዋላ ለቀሪው እዳው መክፈያነት በአመልካች ለተጠሪ የተሰጡት ቼኮች ውስጥ 1ኛው የሚመነዘረው ሰኔ 02 ቀን 1995 ሲሆን ሁለተኛው ቼክ ደግሞ ሰኔ 30 ቀን 1995 ዓ/ም ሁኖ በእነዚህ ጊዜያት ለባንክ ቀርበው በቂ ስንቅ የላቸውም ተብሎ በመመለሳቸው ምክንያት ተጠሪ በአመልካች ላይ ቼኮቹን መሰረት አድርጎ ክስ መስርቶ የፍርድ ባለመብት መሆኑ መረጋገጡን ፣ ይህ ሁኖ እያለም ተጠሪ ለጥገና የገቡትንና ለአመልካች ከሸጣቸው መኪኖች ውስጥ የሰ/ቁጥር 3-0990 የሆነውን መኪና ሊብሬ ፣ የሰ/ቁጥር 3007539 የሆነውን መኪና ደግሞ ሊብሬውንና መኪናውን በመያዝ ለአመልካች ሊሰጥ ፈቃዳኛ ሊሆን ያልቻለ መሆኑን ፣ ይህ መብት ከሽያጭ ውሉ ያገኘው ስለመሆኑ ተጠሪ ጠቅሶ የሚከራከር ሲሆን አመልካች ደግሞ በሕግ አግባብ የተደረገ የመያዣ ውል የለውም በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው።

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2825 ስር በግልጽ እንደተመለከተው የሚንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ መያዣ ፣ (Pledge) መሰረተ ሐሳብ በዋናነት የአንድን ተንቀሳቃሽ ንብረት ይዞታ አሳልፎ በመስጠት ዋስ መሆን የሚቻልበት የግዴታ ዓይነት ነው። የዚህ አይነት ዋስትና (ፕሌጅ) አንድ ሰው ለራሱ ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገን ለሚገባው ግዴታ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይችላል። የዚህ አይነት ዋስትና ተፈጻሚነት ያለው በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ መሆኑ ከማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ (Mortgage) መለያ መንገዱ መሆኑም የሚታወቅ ነው። በመሆኑም በመርህ ደረጃ ፕሌጅ ሊመሠረት የሚችለው የሚንቀሳቀሰውን ንብረት በማስተላለፍ ስለመሆኑ በዚህ ረገድ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በግልፅ የሚያሳዩን ነጥብ ነው። የድንጋጌዎቹ ቅርጽ ፣ ይዘትና መንፈስ የንብረቱ ይዞታ ካልተላለፈ ፕሌጅ አልተቋቋመም ሊባል ሁሉ እንደሚችል ያስረዳል። የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2832 በሕጉ ላይ ተገልጾ ካልተፈቀደ በቀር በመያዣ ተሰጥቶ ተይዘዋል የተባለው ዕቃ ከባለዕዳው እጅ ሳይወጣ በመያዣ እንደ ተሰጠ ሆኖ ሊቆጠር እንደማይችል መደንገጉም ከላይ የተነሳውን ምክንያት የሚያጠናክር ነው። በሕግ ከተፈቀደው በቀር መያዣው በባለዕዳው እጅ ይሆናል ብለው ቢዋዋሉ እንኳን ውሉ እንደማይጸና ጨምሮ ሕጉ ደንግጓል። ሆኖም ሕጉ ሲፈቅድ በልዩ ሁኔታ /As an exception/ የንብረቱ ይዞታ ሳይተላለፍ ፕሌጅ ሊመሠረት የሚችልበት የሕግ አግባብ አለ። ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2830 ላይ የተመለከተው ሲሆን ፣ በተለይ በዕቃው ለማዘዝ የሚያስችሉት ሰነዶች ከተሰጡት ባለገንዘቡ መያዣውን እጅ እንዳደረገ ያህል ይቆጠራል። እንደዚህ ዓይነት ንብረቶች ባለቤትነታቸው ያለምዝገባ ወረቀት (Title deed) ሊተላለፍ ስለማይችል የንብረት ይዞታ መተላለፍ ሳያስፈልግ ፕሌጅ ሊፈጸም ይችላል። እነዚህ ዓይነት ዋስትና ሊሰራባቸው የሚችሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1186(2) የተጠቀሱት ፣ ልዩ ተንቀሳቃሽ ፣ ንብረቶች ፣ እንደ ፣ መኪናና ፣ የአክሲዮን ፣ የዕቃ ፣ ማከማቻ ፣ ደረሰኝ ፣ ዓይነት ፣ ንብረቶች ፣ ናቸው። ንብረቱን ለባለገንዘቡ ከማስተላለፍ (Dispossession) በተጨማሪ የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በሕጉ በተቀመጠው የአሠራር ሁኔታ ፎርም መሠረት ካልተፈጸመ በሕግ ፊት የጸና አይሆንም። ይህ የፎርም መስፈርት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2828 ላይ የተደነገገ ሲሆን ፣ ዋስትና የተሰጠበት ግዴታ ከፍተኛው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን በግልጽና በጥንቃቄ በመያዣው ውል ውስጥ መመልከት ይገባዋል። ይህ ካልሆነ ግን ውሉ ፈራሽ እንደሚሆን ሕጉ በግልጽ ደንግጓል። በተጨማሪም የመያዣው ውል ከብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በላይ የሆነ እንደሆነ ውሉ በጽሑፍ ካልተደረገና ይኸውም እርግጠኛ ቀን ካገኘበት ዘመን ጀምሮ ካልሆነ በቀር አይጸናም። ስለዚህ ከብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በላይ የሆነ የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በጽሑፍ እንዲፈጸም ሕጉ በአስገዳጅ ሁኔታ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው። ከዚህም በተጨማሪ እንዲህ ዓይነት የመያዣ ውል በጽሑፍ እንዲደረግ ሕጉ ግዴታ ካስቀመጠ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1727 መሠረት በውሉ ፣ ግዴታ ፣ ያለባቸው ፣ አስያዡና ፣ መያዣ ፣ ተቀባዩ ፣ መፈረም ፣ እንዳለባቸውና ፣ ሁለት ፣ ምስክሮች ፣ ፊትም ፣ መረጋገጥን የግድ ይሏል ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ካልተሟላ ውሉ በሕግ ፊት የሚፀና አለመሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎችን ፣ በአንድ ላይ ስናነብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል(Pledge) አቋቁሜአለሁ በማለት ተከራክሮ የበታች ፍርድ ቤቶችም ውሉ መያዣ ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ምክንያት ሊሰጠው የሚችለው አይደለም በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ/ም በተደረገው ውል ለውሉ መያዣነት የተያዙት የማይንቀሳቀሱት ንብረቶች አሁን ክርክር ያስነሱ ስለመሆኑ ፣ የዋስትናው መጠን ምን ያህል እንደሆነ በግልፅ ያልተመለከተ ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሉ መያዣ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት "ገዥው ግዴታውን የማያከብር ሁኖ ሲገኝ ወይም ቼኩ ክፍያ ሳይፈጸምበት ከተመለሰ ያልተከፈለው ውዝፍ ሂሳብ በሙሉ ወዲያውኑ ተገቢ ሂሳብና ተከፋይ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜም ሻጩ ወዲያውኑ መኪናውን በእጁ አግብቶ ያላአንዳች ሌላ አይነት አሰራር መኪናውን ለሕዝብ በሐራጅ የመሸጥ ስራውን ይቀጥላል፡፡" በሚል በውሉ ውስጥ የተቀመጠውን ዐረፍተ ነገር በመያዝ ነው፡፡ ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው በሽያጭ ውሉ ውስጥ የመያዣ ውሉ በግልጽ የተጠቀሰና በሥርዓቱ መሰረት የተደረገ የመያዣ ውል አይደለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ ከመኪናዎቹ ውስጥ አንዱን በውሉ ባለው ግዴታ መሰረት ለጥገና ሲገባ የያዘው መሆኑ ሲታይ የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2828 እና 2930 ድንጋጌዎችን ባከበረ መልኩ ተደርጓል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ ተጠሪ በአንድ በኩል የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል ያለው መሆኑን ጠቅሶ ከመኪኖቹ አንዱንና የሁለቱን መኪኖች ሊብሬ በይዞታው ስር ያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለእዳው መክፍያ እንዲውል የተሰጠውን ቼክ መሰረት በማድረግ ክስ አቅርቦ የፍርድ ባለመብት መሆኑ ሲታይ የመኪናው ሽያጭ ውል ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ/ም ሲደረግ መያዣውን አስመልክቶ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ሐሳብ ግልፅነት የሌለው መሆኑን የሚጠቁም ሲሆን በቼኩ ላይ በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ መብቱን ከውሉ መደረግ በሁዋላ ማስከበሩ ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1734 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይ የመያዣ ውል ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ/ም በተደረገው ውል መሰረት ያለመቋቋሙን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች የመኪኖቹን ሊብሬ ለተጠሪ መስጠቱ ያልተካደ ፍሬ ነገር ሲሆን ይህ መሆኑ ተጠሪ መኪኖቹን በራሱ ስልጣን እንዲሸጥ መብት የሚሰጠው ሳይሆን መኪኖቹ እዳው ከመከፈሉ በፊት ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፉና የተጠሪን ቅድሚያ መብት የሚያስገኝ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ የሚንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ ውል በመኪኖቹ አቋቁሜአለሁ በማለት አንዱን የአመልካች መኪና በቁጥጥር ስር ማዋሉን ከውሉ የመነጨና ሕጋዊ ጥበቃ ሊደርግለት የሚገባው እርምጃ አይደለም፡፡ አመልካች ሊብሬውን ለመያዣነት መስጠቱን በክርክሩ ሂደት ያረጋገጠው ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪ በመኪኖቹ ሊኖረው የሚችለው መብት ሊብሬውን በመያዝ የቅድሚያ መብት ማስከበር ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ መኪናውን ይዞ ቁጥጥር ስር ያደረገው በመያዣ ውሉ መሰረት ነው በማለት የደረሱበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2825 ፣ 2828 እና 2830 እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1727 ድንጋጌዎችን ባገናዘበ መልኩ ሁኖ ስላላገኘን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው ተጠሪ የአመልካችን መኪኖች በራሱ ይዞ ቁጥጥር ስር ለማዋል የሚችልበት በሕግ አግባብ የተደረገና በሕጉ መሰረት ጥበቃ የሚደረግለት የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል የለም ከተባለ መኪናውን ለጥገናው በቂና ተገቢ ጊዜ ነው ከሚባለው ምክንያታዊ ጊዜ በላይ ከሕግ ውጪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመያዙ በአመልካች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም መኪኖቹ ወደ ተጠሪ ጋራዥ የገቡት ለጥገና ነው የሚለው ፍሬ ነገር የተረጋገጠ ቢሆንም ለጥገናው ጊዜ ያስፈልግ የነበረው ጊዜ ምን ያህል ነው ፣ ከሕግ ውጪ የተያዘው የሠሌዳ ቁጥር 3-07539 የሆነውን መኪና በወቅቱ ተጠግኖ ለአመልካች ቢሰጥ ኑሮ ይገኝ የነበረው ሕጋዊ ገቢ ምን ያህል ነው የሚለው እና ሌላ ከገቢ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ክርክር በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤት ያልነጠረ በመሆኑ በዚህ ችሎት መቋጫ ሊሰጠው የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ለመኪናው ጥገና የሚያስፈልገውን ምክንያታዊ ጊዜ በተገቢው መንገድ በማጣራት እንዲያረጋግጥና ከዚህ ጊዜ ውጪ ላለው የመኪና መያዝ ደግሞ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027 ፣ 2028 እና 2054 ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ አመልካች ሊያገኝ ይችል የነበረውን የገቢ መጠን በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ሊወስነው የሚገባ ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ አመልካች የመኪኖቹን ሊብሬ ተጠሪ በመያዙ ምክንያት ጥቅም ተቋርጧል ለሚለው ክርክር የስር ፍርድ ቤት አመልካች በፈለገ ጊዜ ሊብሬውን እየፈረመ ወስዶ ይመለስ የነበረ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠ ቢሆንም ሊብሬው በመያዙና የሰ/ቁጥር 3-09190 የሆነው መኪና ክላውዶ ባለመደረጉ በአመልካች ላይ ደርሷል በማለት አመልካች በጠየቀው ዳኝነት ላይ ግልፅ ውሳኔ አልሰጠበትም፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በሕግ አግባብ የተቋቋመ የሚንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል አለ የሚል ድምዳሜ የስር ፍርድ ቤቱ በመድረሱ ምክንያት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደተመለከተው በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመያዣ ውል ባይኖርም ሊብሬዎቹን አመልካች ለተጠሪ አሳልፎ መስጠቱ ተጠሪ የቅድሚያ መብቱን ለማስከበር የሚያስችለው ይሆን የነበረ ሁኖ በየጊዜውም ሊብሬውን ለአመልካች አሳልፎ ይሰጥ የነበረ መሆኑን ተጠሪ በምስክሩ ማረጋገጡን ፣ አመልካች ሊብሬውን በየጊዜው እየፈረመ ያለመውሰዱን ከመግለጽ ውጪ በተገቢው ማስረጃ በማስገደፍ ክርክሩን ያለማቅረቡን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰ/ቁጥር 3-09190 መኪና ሊብሬው በተጠሪ ለአመልካች በየጊዜው ይሰጥ የነበረ መሆኑን እንደተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመውሰድ በሕግ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ካለ ብቻ ማረም ስልጣኑ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌ መገንዘብ የምንችለው ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የሰ/ቁጥር 3-09190 የሆነ መኪና ሊብሬ በተጠሪ በመያዙ ምክንያት ጥቅም ተቋርጦብኛል በማለት ያቀረበው ክርክር በተገቢው ማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘውም፡፡ እንዲሁም የመኪኖቹን ሊብሬ በተመለከተ አመልካች ለተጠሪ በራሱ ፈቃድ አሳልፎ መስጠቱ የተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ አመልካች ቀሪ እዳውን ለተጠሪ እስካልከፈለው ድረስ ተጠሪ ሊብሬዎቹን በዚህ የክርክር ደረጃ እንዲመልስ የሚያስገደደው ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች ጥያቄ የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ተጠሪ መኪኖቹ ላይ የቅድሚያ መብት እንዲኖረው ከሚያደርግ በስተቀር መኪኖቹን በራሱ ሥልጣን በመያዝና ቁጥጥር ስር በማዋል ራሱ እንዲሸጥ መብት የሚያጎናፅፍ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የሠሌዳ ቁጥር 3-07539 የሆነውን የአመልካች መኪና ለጥገና ከሚያስፈልገው ምክንያታዊ ጊዜ ውጪ በመያዙ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን የጉዳት መጠኑ በስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባ ሁኖ የሰ/ቁጥር 3-09190 የሆነውን መኪና ሊብሬ በመያዙ በአመልካች ላይ ጉዳት ደርሷል ፣ ሊብሬዎቹን ተጠሪ ሊመልስ ይገባል በማለት አመልካች ለአቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ግን ተጠሪ ኃላፊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ ሁኖ ስለአገኘነው የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊሻሻል የሚገባው ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35917 ጥቅምት 21 ቀን 1999 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28219 ህዳር 15 ቀን 2001 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ/ም የተደረገው የመኪኖች ሽያጭ ውል ተጠሪ መኪኖቹን በራሱ ሥልጣን በመያዝና ቁጥጥር ስር በማዋል ራሱ እንዲሸጥ መብት የሚያጎናፅፍ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህም ምክንያት የሥሌዳ ቁጥር 3-07539 የሆነውን የአመልካች መኪና ለጥገና ከሚያስፈለገው ምክንያታዊ ጊዜ ውጪ በመያዙ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን የጉዳት መጠኑ በስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ ለመኪናው ጥገና የሚያስፈልገው ምክንያታዊ ጊዜ ምን ያህል እንደሆነ እና ለጥገናው ከሚያስፈለውገው ምክንያታዊ ጊዜ ውጪ መኪናው ሊያስገኝ ይችል የነበረው ገቢ መጠን ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰምቶና በተገቢው መንገድ አጣርቶ ተገቢውን ሊወስንበት ይገባል በማለት በዚሁ ነጥብ ላይ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1)መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ተጠሪ የሥሌዳ ቁጥር 3-07539 የሆነውን የአመልካች መኪና ለአመልካች ሊመልስና ሊያስረክብ ይገባል ብለናል፡፡
5. የሰ/ቁጥር 3-09190 የሆነውን መኪና ሊብሬ በመያዙ በአመልካች ላይ ጉዳት ደርሷል በማለት አመልካች ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
6. አመልካች ሊብሬውን ለክላውዶ የሚያስፈልገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ ከሚሰጥ በስተቀር እዳው እስከሚከፈለው ድረስ ሊብሬዎቹን ተጠሪ ለአመልካች እንዲያስረክብ አይገደደም ብለናል፡፡
7. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ 60204

ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ታደሰ ደሞሬ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጌታሁን ለቻሞ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገንዘብ ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ ሕዳር 26 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፋው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ሰኔ 05 ቀን 1997 ዓ/ም ለአመልካች ብር 180,000.00(አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ) ለጊዜው በአደራ አስቀማጭነት መኪና ተገዝቶ አብረው ለመጠቀም ተነጋግረው የሠጡ መሆኑን ገልፀውና በዚህ አጋጣሚ ወደ አመልካች እጅ ገንዘቡ ከገባ በሁዋላ ገንዘቡን ለመመለስ አመልካች ሲጠየቁ ሊመልሱ ያልቻሉ መሆኑን ጠቅሰው ገንዘቡን ከእነ ወለዱ እንዲመልሱላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ተጠሪ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ በአደራ ያልሰጧቸው መሆኑን ገልጸውና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች በተጠሪ በኩል ያልቀረቡባቸው መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን በመመርመር አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ከነሕጋዊ ወለዱ(9%) ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 04 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፉት በ2/ሁለት/ገፅ የሠበር ማመልከቻ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ በአደራ የሠጡ መሆኑ እየተገለጸ ለጉዳዩ መቅረብ የሚገባው ማስረጃ ሳይቀርብ በሰው ምስክሮች ቃል ለክሱ ኃላፊ ተደርገው መወሰኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2782፣2472 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2471 እስከ 2489 ድረስ የተደነገጉትን የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቶች ፣ እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 248 ስር ስለጭብጥ አመሰራረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደነገገውን ሥርዓት ባላገናዘበ መልኩ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው።

የሠበር አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ለአመልካች ብር 180,000.00(አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር) በአደራ መስጠታቸው ስለተረጋገጠ ይክፈሉ ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 እና 2782 ድንጋጌዎች አንፃር ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሠበር ችሎቱ ሊቀርብ ይገባዋል በመባሉ ነው። በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ሕዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ 2/ሁለት/ ገፅ ማመልከቻ፡- ገንዘቡ በአደራ ለአመልካች ተሰጠ ተብሎ ክሱ ሲመሰረት የተገለፀው የአገላለፅ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር አደራ ተብሎ አልተረጋገጠም ፣ ገንዘቡ ለአመልካች የተሰጣቸው መኪናውን በጋራ ገዝቶ ለመጠቀም በሚል ሃሳብ ሁኖ ይኸው ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ምንም አይነት የሕግ ግድፈት የሌለበት በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ መልሳቸውን ሠጥተዋል። አመልካችም ታህሳስ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ገፅ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሠጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ እና የቃል ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመውም አመልካች ለክርክሩ መነሻ ለሆነው ገንዘብ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 እና 2782 ድንጋጌዎች አንፃር ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል።

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ግዴታ ከውል ወይም ከህግ ከሚመነጭ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው። ክስ አቅራቢው ወገን ደግሞ ይህንኑ በአግባቡ በመለየትና በመግለጽ የሚጠይቀውን ዳኝነት በዝርዝር የማቅረብ እንዲሁም የማስረዳት ግዴታ አለበት። በተያዘው ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ መሀከል የተፈጠረው ግንኙነት ምን እንደነበረ ከላይ በተመለከተው መልኩ የጥሬ ገንዘብ አደራ ሲሆን አመልካች በክስ አቤቱታቸው በዝርዝር ለይተውና ገልፀው ለተጠሪ ገንዘቡን በአደራ የሰጡ መሆኑን በማሳየት ክሱን መስርተዋል ፣ ክርክርም አድርገዋል። ስለሆነም ተጠሪ ከአመልካች ጋር አለኝ የሚሉትን ግንኙነት በሕጉ አግባብ ሊቀርብ በሚገባው ማስረጃ የማስረዳት ግዴታ ይኖርባቸዋል። ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ አመልካች ከተጠሪ ወሰዱ የተባሉት በአደራ ሲሆን አመልካች ደግሞ ይኸው ግንኙት ከተጠሪ ጋር የለኝም በማለት ተከራክረዋል። ስለሆነም የተጠሪ ክርክር መሠረት ያደረገው አደራ ስለመሆኑ ተገንዝበናል። እንግዲህ ግንኙነቱ አደራ ነው ከተባለ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክርም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በመመልከት ሊስተናገድ የሚገባው ይሆናል።

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ግንኙነት ዓይነት የተለያየ ሲሆን እያንዳንዱ ግንኙነት የሚቋቋምበት ፣ ግንኙነቱ ክርክር ቢያስነሣ ተከራካሪዎቹ የሚለያዩባቸውን ነጥቦችን ለማስረዳት መቅረብ ያለበት የማስረጃ ዓይነት በህጉ የተወሠነ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ግንኙነቱ ክርክር ሲያስነሣ ተከራካሪዎቹ የሚለያዩባቸውን ነጥቦች የማስረዳት ሸክም በተከራካሪ ወገኖች በሚቀርበው የክርክር ይዘት አግባብነት ባለው ህግ የተወሰነ ነው። በሌላ አገላለፅ የፍትሐብሔር ግንኙነቶች ክርክር ሲያስነሱ በምስክር ወይም በተለየ ማስረጃ መረጋገጥ ያለባቸው መሆኑ በህግ ተለይተው ተመልክተዋል። በመሆኑም ለእያንዳንዱ የፍታሐብሔር ግንኙነት የማስረዳት ሸክም ያለበት ወገን በቀጥታ አግባብነትና ተፈፃሚነት ባለው በፍትሐብሔር ህጉ በታዘዘው የማስረጃ ዓይነት ማረጋገጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለበት፡፡ አደራ የፍታሐብሔር ግንኙነት የሚቋቋምበት አንዱ ተግባር ነው፡፡ይህ ተግባር ክርክር ሲያስነሣ የግንኙነቱን መኖር ማስረዳት የሚቻልበትን መንገድ ህጉ ለይቶ ወስኗል፡፡ የአደራ ጉዳይን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የፍታሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች ቁጥር 2779 እና ተከታዬቹ ናቸው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2782(1) ድንጋጌ የገንዘብ አደራ ሁኖ ሲገኝ ሊቀርብ የሚገባውን የማስረጃ አይነት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472"ን" በማጣቀስ ምላሽ ይሠጣል፡፡ በዚህም መሰረት ለአደራ ተቀባዩ የተሰጠው እቃ ጥሬ ገንዘብ የሆነ እንደሆነ አደራ ተቀባዩ እንዲገለገልበት ፣ ተፈቅዶለት ከሆነ ስለእንደዚህ ያለው ጉዳይ የአላቂ ነገርን ብድር የሚመለከቱ ደንቦች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም በአደራ የተሰጠው እቃ አደራ ተቀባዩ እንዲገለገልበት የተፈቀደለት ገንዘብ ከሆነ ይህ ግንኙት የሚገዛው የአላቂ ነገር ብድርን በሚመለከቱ ደንቦች ይሆናል ማለት ነው፡፡ አደራ ሠጪው አደራ ተቀባዩ በገንዘቡ እንዲገለገልበት በግልፅ ሊፈቅድለት የሚችል ሲሆን ግልፅ ስምምነት ባይኖርም ገንዘቡ ለአደራ ተቀባዩ የተሰጠው ሳይታሸግና ሳይዘጋበት ከሆነ ተቀባዩ እንዲገለገልበት እንደተሰጠው የሚቆጠር መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2782(2) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ተጠሪ ለአመልካቹ የሰጡት ጥሬ ገንዘብ ሲሆን ገንዘቡን ተጠሪ አሸገው ወይም ዘግተው ለአመልካች የሰጡ መሆኑንም የተነሳ ክርክር የሌለ በመሆኑ አመልካቹ ገንዘቡን እንዲገለገሉበት በተጠሪ እንደተፈቀደ የሚቆጠር ነው፡፡ እንዲሁም ተጠሪ ገንዘቡ ለመኪና መግዣ ተሰጠ ይበሉ እንጂ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር 180,000.00(አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር) ቆጥረው ለአመልካች በአደራ የሰጡ ስለመሆኑ ማስረጃ አቅርቤ አሰማለሁ በማለት ባቀረቡት ክርክር ማስረጃዎቹን አቅርበው በአደራ የሰጡ ስለመሆኑ ማስመስከራቸውን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ በግልፅ የሚያሳይ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የሚገዛው የአላቂ ነገር ብድርን በሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሕግ ደንቦች መሆኑ ግልፅ ይሆናል፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣም የፍ/ህ/ቁ 2472(1) በብድር የተሠጠ ገንዘብ ከብር 500.00/አምስት መቶ ብር/ በላይ ሲሆን የብድሩን ውል በጽሁፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሃላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት አይቻልም በማለት የሚደነግግ ሲሆን ለብድር ውሉ ሌላ ማናቸውም ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ ደግሞ የተጠቃሹ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ በአስገዳጅ ሁኔታ ደንግጓል፡፡ ስለሆነም ከብር 500.00 በላይ የሆነ የገንዘብ ብድር ውል ለማስረዳት ተቀባይነት ያለው ማስረጃ በጽሁፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ እምነት ቃል ወይም መሃላ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ማስረጃዎች ውጪ ሌሎች የማስረጃ ዓይነቶች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑ በህጉ ተለይቶ መቀመጡን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ጉዳይ የተጠሪ ክርክር ብር 180,000.00 ለአመልካች ለጊዜው በአደራ ስጥቼው ነው የሚል ሆኖ ይህንኑ በተመለከተ በህጉ አግባብ ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ዓይነት የማቅረብ ግዴታ የተወጡ ሁነው አልተገኙም፡፡ ተጠሪ ጉዳዩን ለማስረዳት ያቀረቡት የሰው ማስረጃዎችን ሲሆን የሰው ማስረጃ ደግሞ ለጉዳዩ ተቀባይነት ያለው(Admissible) ማስረጃ አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ሊመልሱ ይገባል ወደ ሚለው ድምዳሜ የደረሱት ተቀባይነት የሌላቸው ማስረጃዎች የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመያዝ በፍ/ህ/ቁ 2782 ፣ 2472(1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተቀመጠውን ሁኔታ ባላገናዘበ መልኩ ነው፡፡ ሲጠቃለልም ተጠሪ ገንዘቡን ለአመልካች ሠጠሁ የሚሉበትን ምክንያት ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ዓይነት /admissible evidence/ በማቅረብ ያላስረዱ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 12455 ግንቦት 21 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 82022 ሐምሌ 04 ቀን 2002 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348 (1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000.00/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ ሊከፍሉ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በክርክሩ ሂደት የወጡትን ወጪዎችንና ኪሣራዎችን ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አል ናይል ቢዝነስ ግሩኘ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጠበቃ አቶ ዓለማየሁ ተፈሪ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ነገረ ፈጅ ብርሃነ ደስታ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ በመዝገብ ቁጥር 81664 ያቀረበውን ክስና አመልካች በተጠሪ ላይ በመዝገብ ቁጥር 85281 ያቀረበውን ክስ በማጣመር በመዝገብ ቁጥር 81664 በማየት ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

1. ተጠሪ በአመልካች ላይ በመዝገብ ቁጥር 81664 በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ከሣሽ ለሚያሠራው የመንገድ ሥራ አገልግሎት የሚሰጡ አስር የውሃ ጉድጓዶች እንዲቆፈርለት አመልካች /ተከሣሽ/ ጋር ህዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም ውል ተዋውለናል፡፡ ውሉ ሁለት ክፍል ያለው ሲሆን በውሉ የመጀመሪያ ክፍል ተከሣሽ በደገሀቡር አካባቢ ጥልቀታቸው ሁለት መቶ ሀምሣ ሜትር የሚሆኑ ሁለት ጉድጓዶችን በመቆፈር በአንድ መቶ አምስት ቀናት በማጠናቀቅ ለከሣሽ ግንቦት 15 ቀን 1999 ዓ.ም ለማስረከብ ተስማምቷል፡፡

በውሉ ሁለተኛው ክፍል ተከሣሽ ከደገሀቡር እስከ ቀብራደሀር ከቀብራደሀር እስከ ሰላዩ ባለው ቦታ ጥልቀታቸው ሁለት መቶ ሀምሣ የሆኑ ስምንት ጉድጓዶች ቆፍሮና አጠናቅቆ በመቶ ሰማኒያ ቀን ውስጥ ማለትም ግንቦት 29 ቀን 1999 ዓ.ም ለከሣሽ ለማስረከብ ተስማምቷል፡፡ ተከሣሽ ቆፍሮ ያጠናቀቀው ሁለት ጉድጓድ ሲሆን እነርሡም ቢሆኑ በውሉ መሠረት የተሠሩ አይደሉም፡፡ ተከሣሽ ያለከሣሽ ፈቃድ ሥራውን ለንዑስ ተቋራጭ በመስጠቱ ውሉ ተቀርጧል፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ በገባው የውሀ ጉድጓድ ቆፋሮ ሥራ ውል መሠረት ግዴታውን ያልፈፀመ በመሆኑ ከከሣሽ የወሰደውን ብር 1,838,592.27/አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ሺ አምስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሃያ ሰባት ሣንቲም/ እንዲመልስ እንዲወሰንልኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስራ ውሉን በአግባቡ ባለመፈፀሙ ምክንያት ከሣሽ ጨረታ አውጥቶ ሥራውን ለሌላ ተቋራጭ ሰጥቷል፡፡ ሥራው ለሌላ ተቋራጭ ሲሰጥ ብር 2,708,219/ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ስምንት ሺ ሁለት መቶ አሥራ ዘጠኝ ብር/ ከበፊተኛው ውል ብልጫ ያለው ገንዘብ ለመክፈል ተገድደናል፡፡

ስለዚህ ተከሣሽ ይህንን በልዩነት የተጠየቅነውን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልን እንዲሁም ተከሣሽ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ሥራው ለዘገየበት አንድ ፐርሰንት በየቀኑ መቀጫ ለመክፈል የተስማማ በመሆኑ ብር 1,057,070.93/አንድ ሚሊዮን ሀምሣ ሰባት ሺህ ሰባ ብር ከዘጠና ሶስት ሣንቲም/ የመክፈል ከውል የመነጨ ግዴታ አለበት፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ በድምሩ ብር 5,603,532.52/አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሶስት ሺ አምስት መቶ ሰላሣ ሁለት ብር ከሀምሣ ሁለት ብር ከሀምሣ ሁለት ሣንቲም/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ተገቢ ናቸው የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡

አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ ሥራውን በወቅቱ ያላስረከበና ሥራው እንዲጀመር ሁኔታዎችን ያላመቻቸ በመሆኑ ተከሣሽ መቀጫ እንዲከፍል ያቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም፡፡ ተከሣሽ በውሉ መሠረት በውሉ ክፍል አንድ የተገለፁትን ሁለት ጉድጓዶች በወቅቱ ቆፍሮ አጠናቅቋል፡፡ በውሉ ሁለተኛው ክፍል ከተገለፁት ጉድጓዶች አንድ ጉድጓድ ቆፍሯል፡፡ ሶስተኛው ጉድጓድ ሁለት መቶ ሃምሣ ሜትር ጥልቀት ተቆፍሯል፡፡ ውሃ ላይ ለመድረስ አስተላለፊ ቱቦ እንዲገባለት ተከሣሽ ለከሣሽ ሃሣብ ያቀረበለት ቢሆንም አልተቀበለውም፡፡ የዲዛይን ሥራ ለንዑስ ተቋራጭ የሰጠነው ከሣሽ አውቆትና ፈቃደኛ በመሆኑ ነው፡፡ ሰባት ጉድጓዶች አልተሠሩም፡፡ ሰባት ጉድጓዶች ያልተሠሩት በወቅቱ በአካባቢው የፀጥታ ችግር ስለነበረና ከሣሽ ሥራውን በቅርበት የሚከታተል ክፍያ የሚያፀድቅ መሀንዲስ ባለመመደቡ ነው፡፡ አመልካች ውሉን ያፈረሰው በራሱ ምክንያትና ጥፋት በመሆኑ ለተጨማሪ ዋጋ ክፍያ እንዲሸፍን ያቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት የተከራከረ ሲሆን ተገቢ ነው የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡

2. በመዝገብ ቁጥር 85285 አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ከሣሽ/አመልካች/ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ከተከሣሽ ጋር በነበረኝ የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ውል መሠረት በውሉ ክፍል አንድ የተመለከቱትን ሁለት ጉድጓዶች ሙሉ በሙሉ ቆፍሬ አጠናቅቄያለሁ፡፡ በውሉ ሁለተኛ ክፍል ከተገለፁት ስምንት ጉድጓዶች አንድ ጉድጓድ በውሉ መሠረት ቆፍሬአለሁ፡፡ ተከሣሽ ለሠራሁት ሥራ ክፍያ ያልፈፀመልኝ ሲሆን በወቅቱ ኢንጅነር አልመደበም፡፡ ተከሣሽ የውሉ ጊዜ ካለቀ ከስድስት ወር በኋላ የመደበው ኢንጅነር ሥራው በአግባቡ አልተሠራም በማለቱ ክፍያ ለመፈፀም ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ኢንጅነሩ ጋር እንድንነጋገር ያቀርብነውን ጥያቄ ተከሣሽ አልተቀበለውም፡፡ ስለሆነም ከሣሽ ለቆፈርኳቸው የሶስት ጉድጓዶች ዋጋ ብር 2,776,728.22 /ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም/ ተከሣሽ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ፡፡ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ከሣሽ ብር 1,838,298.12 ቅድሚያ ክፍያ ወስጃለሁ፡፡ ስለዚህ ተከሣሽ ብር 938,435.95/ዘጠኝ መቶ ስላሣ ስምንት ሺህ አራት መቶ ስላሣ አምስት ብር ከዘጠና አምስት ሣንቲም/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ የሥራ ኘላንና ኘሮግራም ሣያወጣ ሥራውን ጀምሯል፡፡ ከሣሽ ሁለት ጉድጓድ የቆፈረ ቢሆንም በውሉ መሠረት በአግባቡ አልተሠሩም፡፡ ተከሣሽ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ አለመመደቡ ከሣሽ ሥራውን በውሉ መሠረት እንዳይሠራ የሚያደርግ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም፡፡ ውሉ የተቋረጠው በከሣሽ ጉድለት ነው ስለዚህ ከሣሽ ያቀረበው ክስ የህግ መሠረት የለውም በማለት መልስ አቅርቧል፡፡

3. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሁለቱ መዝገቦች በተከራካሪዎች የተቆጠሩ ምስክሮችን ከሰማና በግራ ቀኙ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ውሉ የተቋረጠው በሥራ ተቋራጩ/አመልካች/ ጥፋት ምክንያት በመሆኑ አሠሪው /ተጠሪ/ ሥራውን በሌላ ሥራ ተቋራጭ ለማሠራት ያወጣውን ተጨማሪ ክፍያ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት አለበት፡፡ ሥራ ተቋራጩ/አመልካች/ ለሥራው መዘግየት ሊከፍል የሚገባውን የመቀጫ ገንዘብ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ አሠሪው/ተጠሪ/ በክሱ የገለፀውን የመቀጫ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል፡፡ አመልካች የቆፈራቸው ሁለት ጉድጓዶች በውሉ መሠረት ያልተሠራ መሆኑን አሠሪው/ተጠሪ/ የገለፀ በመሆኑ ሥራ ተቋራጩ በቅድሚያ ከወሰደው ገንዘብ እንዲቀናነስለት ያቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም፡፡ ስለዚህ አመልካች ከተጠሪ የወሰደውን ቅድመ ክፍያ ሙሉ በሙሉ ለተጠሪ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ብር 5,603,532.52/አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ስላሣ ሁለት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም/ ለተጠሪ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በአካባቢው በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት ነው ቀሪዎቹን ጉድጓዶች ያልቆፈርኩት በማለት ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አመልካች በፅሑፍ ላቀረበው ጥያቄ ምላሽ አለመስጠቱና ሥራውን የሚከታተል መሀንዲስ ባለመመደቡ ለውሉ በአግባቡ አለመፈፀምና መቋረጥ አስተዋፅኦ እንዳበረከተ በመዘርዘር አመልካች ለመዘግየቱ ሊከፍል ከሚገባው የመቀጫ ገንዘብ ግማሹን ማለትም 528,520.47/አምስት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አስር ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ እንዲከፍል በማለት አሻሽሎ ወስኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የሁለት ጉድጓድ ዋጋ በውሉ መሠረት ለአመልካች የመክፈል ግዴታ አለበት በማለትም ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ሥራውን ለሌላ የሥራ ተቋራጭ ሲሰጥ የተጠየቀውን የዋጋ ብልጫ ማለት ብር 2,708,219 አመልካች ሙሉ በሙሉ ሊከፍል ይገባዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

5. አመልካች ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ለውሉ በአግባቡ አለመፈፀም የአመልካች ጥፋት ብቻ ሣይሆን የተጠሪም ጥፋትና አስተዋፅኦ እንዳለበት በማረጋገጥ የመቀጫው ገንዘብ በግማሽ እንዲቀነስ ከወሰነ በኋላ ተጠሪ ለሌላ ተቋራጭ ሥራውን ሲሰጥ ተጠይቂአለሁ የሚለውን አብላጫ የሥራ ዋጋ ሙሉ በሙሉ አመልካች እንዲሸፍን መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ ከሌላ የሥራ ተቋራጭ ጋር ውል መዋዋሉ ብቻውን ሥራውን ለማሠራት ተጨማሪ ገንዘብ የተጠየቀና የከፈለ መሆኑን የሚያስረዳ አይደለም፡፡ በውሉ መሠረት የመቀጫ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ከተወሰነ በኋላ በውሉ አለመፈፀም ምክንያት ተጨማሪ የጉዳት ካሣ አመልካች እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በሥራ ውሉ መሠረት የተወሰኑ ጉድጓዶችን ቆፍሮ አስረክቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች ምንም አይነት ሥራ እንዳልተሠራ አድርጎ በማስላት ያቀረበውን የካሣ ጥያቄ በመቀበልና አመልካች የሠራውን ሥራ ሣያቀናንስ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ጥቅምት 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በበኩሉ ጥር 19 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በሥራው መዘግየት የሚከፈለው የመቀጫ ገንዘብ በሥራ ውሉ ላይ በግልፅ የተወሰነና ተጠሪ ውሉ ባለመፈፀሙ ለደረሰበት እርግጠኛ ጉዳት ከሚጠይቀው ገንዘብ የተለየ ነው፡፡ አመልካች የውል ግዴታውን ባለመፈፀሙ የተቋረጠው የቀሪ ጉድጓድ ሥራ ሌላ ተጫራች እንዲያጠናቅቀው ተጠሪ የሰጠው አመልካች ጋር በተደረገው ውል ሣይሰሩ ለቀሩት 7/ሰባት/ ጉድጓዶች ብቻ ነው፡፡ በአመልካች የተሠሩት በሁለተኛው ጨረታ አልተካተቱም በመሆኑም አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሠራሁትን ሥራ ግምት ውስጥ ሣያስገባ ካሣ እንዲከፍል ወስኖብኛል በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች መቀጫው ከተቀነሰ ጉዳቱንም እኔ ብቻ እንድከፍል መወሰኑ ስህተት ነው በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የፍርድ ቤቱ ሥልጣንን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የካቲት 4 ቀን 2003 ዓ/ም በተፃፈ የመልስ መልስ የዋጋ ልዩነት የታየው በወቅቱ ባለው የዋጋ ንረት ምክንያት በመሆኑ አመልካች ተጠያቂ ሊሆን አይገባውም፡፡ የዋጋ ልዩነቱን አመልካች ይክፈል እንኳን ቢባል ተጠሪ ለውሉ አለመፈፀም አስተዋፅኦ ያለው መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ችሎት ያረጋገጠ በመሆኑ እንደሀላፊነቱ መጠን ኪሣራው ሊቀነስ ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የቀሪዎቹን ሰባት የውሃ ጉድጓዶች ሥራ ለሌላ የሥራ ተቋራጭ በጨረታ አወዳድሮ ሲሰጥ የተጠየቀውን ተጨማሪ ገንዘብ አመልካች ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የያዝነውን ጭብጥ በአግባቡ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ህዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም አድርገውት የነበረውን የውሃ ጉድጓድ ሥራ ውል አፈፃፀም ለማስረዳት ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ የደረሰባቸውን መደምደሚያዎችና አመልካችና ተጠሪ በሰበር ደረጃ የማይካካዱባቸውን ነጥቦች በዝርዝር ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

6.1 የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረግኩትን የሥራ ውል በአግባቡ ያልፈፀምኩት በአካባቢው የፀጥታ ችግር የነበረ በመሆኑና ተጠሪ በውሉ መሠረት ተቆጣጣሪ መሀንዲስ ባለመመደቡ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ለውሉ መዘግየትም ሆነ ቀሪው የውሉ ክፍል አለመፈፀም ምንም አይነት ተጠያቂነት ስለሌለብኝ የመቀጫ ገንዘብም ሆነ ኪሣራ ለተጠሪ የመክፈል ሀላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበውን ክርክር ሙሉ በሙሉ አልተቀበለውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለሥራ ውሉ አፈፃፀም መዘግየትና መቋረጥ የአመልካች ጥፋትና አስተዋፅኦ ያለበት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣኑን በመጠቀም እንዳረጋገጠ በውሣኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡ በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥራ ውሉ በአግባቡ አለመፈፀምና ለውሉ መቋረጥ አመልካች ብቻ ሣይሆን በተጠሪ በኩል የተፈፀመ ጥፋትና አስተዋፅኦ ያለ መሆኑን በተለይም አመልካች በሥራ ውሉ መሠረት ተቆጣጣሪ መሃንዲስ እንዲመድብለት በተደጋጋሚ በፅሑፍ ላቀረበለት ጥያቄ ተጠሪ መልስ ያልሰጠ መሆኑን በማስረጃ እንዳረጋገጠ በውሣኔው ገልፆል፡፡ በሌላ አገላለፅ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው የውሀ ጉድጓድ ሥራ ውል አፈፃፀም ለመዘግየቱም ሆነ ለውሉ መቋረጥ አመልካችና ተጠሪ የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያበረከቱ መሆኑን በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን በውሣኔው አረጋግጧል፡፡ በዚህ ምክንያት ለውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራ ውሉ መክፈል የሚገባውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመቀጫ ገንዘብ ሙሉውን ሣይሆን ግማሹን /ሃምሣ ፐርሰንቱን/ ብቻ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት አለበት በማለት የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ብር 1,057,070.93 የመቀጫ ገንዘብ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች ግማሹን ብቻ ማለትም ብር 528,510.47 የመቀጫ ገንዘብ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት አለበት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሚከራከረው ለውሉ አለመፈፀምና መዘግየት የተጠሪ ጥፋትና አስተዋፅኦ እንዳለበት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ከተረጋገጠ፣ ውጤቱ የመቀጫ ገንዘብ በመቀነስ ብቻ የሚወሰን አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሥልጣኑ የዳኞች በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የመቀጫውን ገንዘብ በመቀነስ ብቻ መወሰኑ ተገቢ ነው የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ በእኛ በኩል አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን ይህንን መሠረታዊ ነጥብ የፍታብሔር ህጉ የመንግስት ሥራዎችን በተቋራጭ ስለማሥራት የተደነገጉትን ልዩ የህግ ድንጋጌዎችና ሌሎች አግባብነት ካላቸው የህግ ማዕቀፎች መሠረት በማድረግ መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አንድን ሥራ ለሥራ ተቋራጭ የሰጠ የመንግስት መሥሪያ ቤት በራሱ ጥፋት ጉዳት አድርሶ እንደሆነ ወይም ተቋራጩ ውሉን ለጊዜው እንዳይፈፅም አግዶት እንደሆነ የሥራ ተቋራጩ ኪሣራ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3259 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡ ከሁሉም በላይ የሥራው አሠሪ የሆነው የመንግስት መሥሪያ ቤት ጥፋት ወይም የመብት መተላለፍ ባያደርግም አድራጎቱ የሥራ ተቋራጩን ሥራ መደበኛ አፈፃፀም ከባድ ያደረገበት እንደሆነ ለሥራ ተቋራጩ ኪሣራ የመክፈል ሀላፊነት እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3259 ንዑስ አንቀፅ 3 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ በሥራ ውሉ መሠረት ሥራውን የሚከታተል መሀንዲስ ባለመመደቡና አመልካች በፅሑፍ ለጠየቃቸው ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ ባለመስጠቱ ለሥራ ውሉ መዘግየትና ለውሉ አለመፈፀም የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዳበረከተ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ህጋዊ ዉጤትም በመቀጫ ገንዘብ ብቻ የሚወሰን እንዳልሆነና ተጠሪ ለአመልካች ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት መሆኑን ከላይ የተጠቀሱትን ልዩ የህግ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 85295 በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተጠሪ ለውሉ አፈፃፀም መዘግየትና ለውሉ መቋረጠ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረከተ ስለሆነ ኪሣራ ወይም ካሣ ሊከፍለኝ ይገባል የሚል የዳኝነት ጥያቄ አላቀረበም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በተጠሪ በኩል ተፈፅሟል የሚላቸውን ጥፋቶችና ጉድለቶች በመዘርዘር ተጠሪ ላቀረበው የኪሣራ ጥያቄ ሀላፊ ልሆን አይገባኝም በማለት የተከራከረ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤትና ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለውሉ በአግባቡ አለመፈፀምና መዘግየት የተጠሪ ጥፋትና አስተዋፅኦ አለበት በማለት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ከደመደመ በኋላ የዚህን መደምደሚያውን የአመልካችን የመከላከያ መልስ ህጋዊ ውጤት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3259 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አለመመዘኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካች የሥራ ውሉ በመዘግየቱና ባለመፈፀሙ የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፍል ተወስኖብኛል፡፡ ይህ ከሆነ ለተጠሪ ኪሣራ የመክፈል ሀላፊነት የለብኝም በማለት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፍል መወሰኑ ውሉ ባለመፈፀሙ ተጠሪ የደረሰበትን ኪሣራ ከመክፈል ነፃ አያደርገውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ይህም የአመልካችና የተጠሪ ክርክር የመንግስት ሥራዎችን ለመሥራት ስለመቋረጥ ከተደነገጉት ልዩ ድንጋጌዎችን አንፃርና መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በተለይም የአመልካች ክርክር ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3261

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎችን አንፃር መሠረት በማድረግ መታየት ያለበት ሲሆን ከሥራ ውጭ የተደረገው ሥራ ተቀራጭ ሥራው ለአዲስ ተቋራጭ በጨረታ የተሰጠ ሲሆን አዲሱ የሥራ ውል በመሥሪያ ቤቱ የሚያስከትለውን ከባድ የሆነውን ወጭ መቻል እንዳለበት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3261 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅና አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለሥራው መዘግየትና አለመፈፀም መቀጫ እንድከፍል የተወሰነ ስለሆነ ቀሪው ሥራው ለሌላ ሥራ ተቋራጭ ሲሰጥ ተጠሪ የደረሰበትን ኪሣራ የመክፈል ግዴታ ያለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀውን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደገለፅነው ተጠሪ የሥራ ውሉ ለመዘግየቱና ውሉ በአግባቡ ላለመፈፀሙ ላደረገው አስተዋፅኦ የመቀጫ ገንዘብ በመቀነስ ብቻ የሚወሰን ሣይሆን ተጠሪን ተጨማሪ ሀላፊነት የሚያስከትልበት ስለመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3259 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል ለውሉ አለመፈፀምና መዘግየት ጥፋትና አስተዋፅኦ ያበረከተ መሆኑ የተረጋገጠበት አመልካች ተጠሪ ሥራውን ለሌላ ተቋራጭ ሲሰጥ የወጣውን ወጭ የመጋራት ወይም መሸፈን ግዴታ እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3261 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ተጠሪ ሥራውን ለሌላ ሥራ ተቋራጭ ሲሰጥ የደረሰበትን ኪሣራ ሙሉ በሙሉ እንዲሸፍን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3261 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የሚገደደው ለሥራ ውሉ መዘግየትና አለመፈፀም ተጠሪ ያበረከተው አስተዋፅኦ አለመኖሩ ሲረጋገጥ እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3259 ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3261 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ የጣምራ ይዘት ተፈፃሚነትና ውጤትን በማገንዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ለውሉ አለመፈፀምና መዘገየት ብቸኛ ተጠያቂና ሀላፊ አለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣኑን በመጠቀም ካረጋገጠ በኋላ በውሉ አለመፈፀም ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሰውን ኪሣራ ሙሉ በሙሉ አመልካች እንዲሸፍን የተሰጠው ውሣኔ ከላይ የተገለፁትን የህግ ድንጋጌዎች ይዘትና ድንጋጌዎቹ በአንድ ላይ ሲፈፀሙ የሚያስከትሉትን ውጤት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች ሊከፍል የሚገባው ተጠሪ ቀሪውን ሥራ ለሌላ ተቋራጭ ሲሰጥ የደረሰበትን ኪሣራ ማለትም ብር 2,708,219/ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ስምንት ሺ ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር / ሣይሆን የዚህን ግማሽ/ሀምሣ ፐርሰንት / በሌላ አነጋገር ብር 1,354,109.50 /አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃምሣ አራት ሺ አንድ መቶ ዘጠኝ ብር ከሀምሣ ሣንቲም / ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡

6.2 አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ኪሣራው ለተጠሪ እንዲከፈል የወሰነው አመልካች ምንም አይነት ሥራ እንዳልሠራ በመቁጠርና አመልካች ሠርቶ ለተጠሪ ያሥረከባቸውን የተወሰኑ ሥራዎች ከግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባና ሒሳቡን ሣያቀናንስ ነው በማለት ክርክር በሰበር አቤቱታው አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ለዚህ ሰበር ችሎት ጥር 19 ቀን 2003 ዓ.ም በፅሑፍ በሰጠው መልስ ጨረታ ወጥቶ ለሌላ የሥራ ተቋራጭ የተሰጡትን የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ መጠን በተመለከተ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ካቀረበው ክርክር የተለየ መልሥ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ለሰበር ችሎት በሰጠው መልስ በተራ ቁጥር 3 ላይ ለሌላ የሥራ ተቀራጭ በጨረታ የተሰጠው የሰባት /7/ ውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ መሆኑንና ይህም በአመልካች የቁፋሮ ሥራ የተሠራላቸውን የውሃ ጉድጓዶች እንደማይጨምር በመግለፅ ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህም የተጠሪ ክርክር አመልካች በሥራ ውሉ መሠረት ጥልቀታቸው ሁለት መቶ ሃምሣ ሜትር የሆነ የሶስት የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ሠርቻለሁ በማለት አመልካች ከሥር ጀምሮ ያቀረበውን ክርክር በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት እንዳመነ የሚያስቆጥረው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ሁለት የውሀ ጉድጓድ በመቆፈሩ እንጅ ሶስት የውሀ ጉድጓድ በውሉ መሠረት የቆፈረ መሆኑን አላስረዳም በሚል ምክንያት ተጠሪ ለአመልካች ሁለት የውሀ ጉድጓድ የቆፈረበትን ዋጋ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሣኔ ተጠሪ በሰበር ካቀረበው ክርክር አንፃር በመመዘንና በማሻሻል ተጠሪ አመልካች ሶስት የውሃ ጉድጓድ የቆፈረበትን ዋጋ በውሉ መሠረት የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

6.3 በሥር ፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር በተሰጠው ውሣኔ መሠረት አመልካች ለተጠሪ ሊመልስ የሚገባው በቅድመ ክፍያ የወሰደውን ገንዘብ ያለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ውሣኔና በዚህ ሰበር ችሎት በተሰጠው ውሣኔ መሠረት አመልካች ለተጠሪ መክፈል የሚገባው የመቀጫ ገንዘብና ኪሣራ /ካሣ/ እንዳለ በውሣኔው ተገልፆል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አመልካች ለሠራው የሶስት ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ በውሉ መሠረት ተገቢውን ዋጋ እንዲከፍል ይህ ሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በውሣኔው አመልካች ከተጠሪ እንደዚሁም ተጠሪ ከአመልካች የሚጠይቁት የገንዘብ ዕዳ ያለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ዕዳውን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 236 መሠረት በማቻቻል ተራፊ ገንዘብ የሚጠይቀውና በዚህ ፍርድ የፍርድ ባለመብት የሚሆነውን ወገን ለመለየት ፍርዱ ለአፈፃፀም ምቹ በሚሆንበት መንገድ ለመስጠት ይቻል ዘንድ ጉዳዩን በዝርዝር ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ሀ/ አመልካች ለተጠሪ መክፈል ያለበት ገንዘብ</u>

- አመልካች ከተጠሪ ብር 1,838,292.27 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከሃያ ሰባት ሣንቲም/ በቅድሚያ ክፍያ የወሰደ መሆኑን ያልካደና በማመን የተከራከረ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ የመመለስ ግዴታና ሀላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
- አመልካች ለሥራ ውሉ መዘግየትና ለውሉ አለመፈፀም በከፊል ሀላፊነት ያለበት መሆኑን በማረጋገጥ ለተጠሪ ብር 528,520.47 /አምስት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አስር ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ ለተጠሪ እንዲከፍል ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ውሣኔ መሠረት የመክፈል ሀላፊነት አለበት፡፡
- ተጠሪ ለውሉ መዘግየትና አለመፈፀም የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደረገ መሆኑ በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ስለተረጋገጠ አመልካች በሥራ ውሉ መሠረት ያልሠራውን ቀሪ ሰባት የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ተጠሪ ለሌላ ተቋራጭ ሲሰጥ ከደረሰበት ኪሣራ ግማሹን ብቻ አመልካች የመሸፈን ሀላፊነት እንዳለበት ይኸ ሰበር ችሎት የይግባኝ ሰሚውን ውሣኔ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ብር 1,354,109.50/አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃምሣ አራት ሺህ አንድ መቶ ዘጠኝ ብር ከሃምሣ ሣንቲም/ ለተጠሪ ካሣ ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ብር 3,720,918.09 /ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃያ ሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንት ብር ከዜሮ ዘጠኝ ሣንቲም/ የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለ/ <u>ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ገንዘብ</u>

አመልካች ሶስት የውሃ ጉድጓዶችን በውሉ መሠረት የሠራ መሆኑን ተጠሪ በማረጋገጡ አመልካች የሶስት ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ዋጋ ለአመልካች የመክፈል ሃላፊነት እንዳለበት በዚህ ችሎት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሶስቱን ጉድጓዶች ለሠራበት ተጠሪ በውሉ መሠረት ሊከፍለው የሚገባው ብር 2,776,728.22/ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም/ እንደሆነ በሥር ፍርድ ቤት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ዋጋው በውሉ መሠረት ተሰልቶ የቀረበ አይደለም የሚል ክርክር አላቀረበም፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ከላይ መጠኑ የተገለፀውን ገንዘብ ለአመልካች የመክፈል ሃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ለተጠሪ ከሚከፍለው ብር 3,720,918.09 /ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃያ ሺ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንት ብር ከዜሮ ዘጠኝ ሣንቲም/ ውስጥ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ብር 2,776,728.22 /ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም/ ተቀንሶ ፣ /ተቻችሎ/ የሚቀረውን ብር 944,189.87/ዘጠኝ መቶ አርባ አራት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ ሰባት ሣንቲም/ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች መክፈል ያለበት ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ ከላይ በውሣኔው በተገለፀው መሠረት ከተቀናንሶ የቀረውን ብር 944,189.89 /ዘጠኝ መቶ አርባ አራት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ ሰባት ሣንቲም / አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች - እነ ጠና ወ/ሰማያት - ከጠበቃ ሀይሉ አግዘው ጋር - ቀረቡ
ተጠሪ - ወ/ሮ አልማዝ አሰጋኽኝ - ከጠበቃ አሰፋ ንጉሴ ጋር - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሽያጭ ምክንያት ተከፈለ የተባለ ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- አመልካቾች የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል መመዘኛና መስፈርት ባላሟላ ሰነድ ቤት ሽያጭ ውል ተዋውለዋል በማለት ነሐሴ 20 ቀን 1997 ዓ/ም በተጻፈ ከተጠሪ ላይ ብር 80,000.00 (ሰማኒያ ሺህ ብር) መቀበላቸውን ፣ ይህ ረቂቅ ውል እንጂ የሚፀና ውል ባለመሆኑ ተጠሪ ያገኙት ቤት ወይም ጥቅም የሌለ መሆኑንና ገንዘቡንም ሊመልሱላቸው ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጸው ያላግባብ የተወሰደባቸውን ገንዘብ ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ከታሰበው ብር 24,300.00 ሕጋዊ ወለድ ጋር በድምሩ ብር 104,300.00 (አንድ መቶ አራት ሺህ ሶስት መቶ ብር) ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካቾች በበኩላቸው ተጠሪ በጉዳዩ ላይ ክስ አቅርበው የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ በድጋሚ ክስ ለማቅረብ የማይችሉ መሆኑን ፣ ጉዳዩም ያላግባብ መበልፀግ ነው የሚል በመሆኑ በሁለት አመት ይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ ገልፀው በእነዚህ የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ ነጥቦች ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አመልካቾች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱትን የይርጋ ጊዜ የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ ያላግባብ የተወሰደ ገንዘብ ይመለስልኝ የሚል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(1) መሰረት የሚገዛ ነው በማለት በሁለት አመት የይርጋ ጊዜ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ጉዳዩ በሁለት አመት የይርጋ ጊዜ የማይታገድ መሆኑን በመግለፅ በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤት የተያዘውን ምክንያት በመሻር ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የአስር አመት የይርጋ ጊዜ ነው በማለትና ክሱ የቀረበውም ይኸው ጊዜ ሳይልፍ መሆኑን አረጋግጦ እንዲሁም አከራካሪውን ገንዘብ አመልካቾች ከተጠሪ መቀበላቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤት መረጋገጡን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ ብር 80,000.00 (ሰማኒያ ሺህ ብር) ከግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር አመልካቾች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የይርጋው ጊዜ ወደ አስር አመት ተብሎ መተርጎሙም ሆነ ተጠሪ የቤት ሽያጭ ስለመኖሩ አለመኖሩ በነበረው ክርክር አጠቃልለው ማቅረብ ይችሉ የነበረውን ክርክር ነጥለው በኋላ አቅርበው ተቀባይነት ማግኘታቸው ክስን ነጣጥሎ ማቅረብ የማይቻል መሆኑን የሚደነግገውን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 216 ድንጋጌን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተጠሪ ቀደም ሲል ክስ አቅርቦ ባስወሰነበት መዝገብ አጠቃልለው ማቅረብ የነበረባቸውን ነጣጥለው አቅርበዋል በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ተቃውሞ መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ከአላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ፡- አመልካቾች ለተጠሪ ገንዘቡን እንዲመልሱ ተብሎ የተወሰነው በሕጉ ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ መሰረት ባደረገ መንገድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካቾች ላይ መጀመሪያ ክስ የመሰረቱት ውል እንዲፈርስና ገንዘባቸው ተመልሶላቸው ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ የሚል ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሉ ረቂቅ ስለሆነ የክስ ምክንያት የለውም በማለት መዝገቡን መዝጋቱን ፣ ለአሁኑ ክርክር መሰረት የሆነውን ክስ ተጠሪ የመሰረቱት በረቂቅ ውሉ መሰረት የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስላቸው መሆኑን ፣ ቤቱ ከአመልካቾች እጅ ያልወጣና በተጠሪ እጅ ያልገባ መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪ አመልካቾች ቤት ሸጠውልኝ ብር 80,000.00 ከፍዬአለሁ ፣ ውል ይፍረስልኝ፤ወደ ነበርንበት እንድንመለስ ይደረግ የሚል ጥያቄ አቅርበውም ውሉ ረቂቅ በመሆኑ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሰጠቱ ምክንያት ሁለተኛ ክስ ሊያቀርቡ የቻሉት በፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር በሕግ ፊት የሚጸና ውል የለም (ረቂቅ ነው) ስለተባለ ያላግባብ የተከፈለ ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት መሆኑን ፣ በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ የለም የሚለው ክርክርም በፍርድ ቤት ታይቶ ሕጋዊ የሆነ የቤት ሽያጭ ውል የሌለ መሆኑ መረጋገጡን ከክርክሩ ሂደት በግልጽ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ጉዳይ ያቀረቡትም የቤት ሽያጭ ውል የለም ተብሎ ውሳኔ ከተሰጠ በሁዋላ ሲሆን አመልካቾች ገንዘቡን ስለመቀበላቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾችን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው ገንዘቡን ከተጠሪ ስለመቀበላቸው ተጠሪ በተገቢው ማስረጃ አስረድተዋል ፣ አመልካቾች ግን አላስተባበሉም በሚል ምክንያት ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ የተመለከቱት ነጥቦች በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡት ሲሆን አመልካቾች የስር ፍርድ ቤት የስነ ሥርዓት ግድፈት ፈጽሟል በማለት የሚያቀርቡት አንዱ ነጥብ ተጠሪ ሕጋዊ ያልሆነ የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ፣ ወደ ነበርንበት እንድንመለስ ይወሰንልኝ በማለት ክስ ሲያቀርቡ ገንዘቡን ያላግባብ ለአመልካቾች የከፈሉ መሆኑን ገልጸው ገንዘቡ እንዲመለስላቸው በአማራጭ ዳኝነት መጠየቅ ሲገባቸው እና ተጠሪ ቀደም ሲል በተመሳሳይ ጉዳይ ክስ ሲመሰርቱ ይህንኑ ክስ አጠቃልለው ሊከሱ ሲገባ ቀንሰው ባስቀሩት ገንዘብ ላይ ድጋሚ ክስ እንዳይመሰርቱ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216 ይከለክላቸዋል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚል መቃወሚያ አቅርበው መታለፉን ነው። በመሆኑም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ በተያዘው መሰረት የተጠሪ ክስ በተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ወይ? የሚለውን ጭብጥ ፍ/ቤቱ መርምሯል። ለዚህ ይረዳ ዘንድ ድንጋጌውን መመልከቱ ተገቢ ነው። የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 216 በአጠቃላይ ስለ ክስ አቀራረብና አገላለፅ የሚመለከት ድንጋጌ ነው። በተለይ ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 2 እና 3 ነው። የንዑስ ቁጥር 2 የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር አንድ ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ እንደሚገባ የሚናገር ሲሆን ንዑስ ቁጥር 3 ደግሞ አንድ ከሳሽ ሊከስበት ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረው ሃብት ምክንያት እንደገና ሌላ ክስ ለማቅረብ እንደማይፈቀድለት ይገልፃል። በመሆኑም ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን ማቅረብ ሲችል ሆነ ብሎ **ቀንሶ ባስቀረው** ሃብት ላይ ግን ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ እንደማይችል ከድንጋጌዎቹ መረዳት ይቻላል።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ የቤት ሽያጭ ውልን አስመልክቶ ክርክሩ የቀረበበት አግባብ በተጠሪ በኩል የቀረበው የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ፣ ወደነበርንበት እንድንመለስ ይደረግልኝ የሚል ክስ በመቅረቡ በመሆኑና በሕጉ አግባብ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የለም ፣ ዉሉ ረቂቅ ስለሆነ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜ ላይ የተደረሰ በመሆኑ ተጠሪ በሽያጩ ምክንያት ለአመልካቾች የሠጡትን ገንዘብ ሊመለስልኝ ይገባል በማለት ጥያቄ ከማቅረብና በማናቸውም ማስረጃ ከማስረዳት የማይከለክል መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1808(2) ፣ 1815 ፣ 2001 እስከ 2019 እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 እና 2164 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ በክስ አቀራረብ ሥርዓት ላይ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ስርዓት ግድፈት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል አይደለም። ተጠሪ ቀድሞ ከመሰረቱት የክስ ይዘትና ከጠየቁት ዳኝነት አንፃር ውሉ ረቂቅ በመሆኑ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተሰጠው ውሳኔ አኳያ ሲታይ የሽያጭ ገንዘቡን ሆነ ብለው ትተዋል ፣ ወይም በክሱ ሊጠቃለል የሚችል ሀብት ቀንሰው አስቀርተው ሌላ ጊዜ ክስ መስርተዋል ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የለም። በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም። በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል።
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 62146
ሐምሌ 12 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሪት ፍሬወይኒ ቴዎድሮስ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ተርካንፌ ፕሮሞሽን የማስታወቂያ ስራ ድርጅት - ጠበቃ ነፃነት ጌታሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውል ይፈፅምልኝ ጥያቄን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ሚያዚያ 07 ቀን 2002 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የደቡብ ክልል ሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የሚሳተፉበትን የደቡብ ሚስስ ቱሪዝም የቁንጅና ውድድር በኮንሶ ልዩ ወረዳ ካራት ከተማ መስከረም 09 ቀን 2001 ዓ/ም እንደሚያዘጋጅና ተወዳዳሪዎች እንዲመዘገቡ ባወጣው ማስታወቂያ መሰረት መመዝገባቸውን ፣ በማስታወቂያውም ላይ በውድድሩ አሸናፊ ለሆነች ወጣት በክልሉ ርዕሰ ከተማ ሐዋሳ መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ፣ በክልሉ በሚገኙ ታላላቅ ኮሌጆች ውስጥ ነፃ የትምህርት እድል እና የብር 5000.00(አምስት ሺህ) የገንዘብ ስጦታ ለመስጠት አመልካች በሚኖሩበት የዳውሮ ዞን በፋክስ የማስታወቂያ ደብዳቤ ቃል መግባቱን ፣ በውድድሩም አመልካች ተወዳድረው አንደኛ በመውጣት የደቡብ ሚስስ ቱሪዝም ማዕረግ ያገኙ መሆኑን ፣ ተጠሪ በገባው ቃል መሰረት በኮሌጅ የነፃ የትምህርት እድሉን እና ብር 5000.00 ለአመልካች የሰጣቸውና አመልካችም የተቀበሉ ሁኖ የቤት መስሪያ ቦታ ግን በገባው ቃል መሰረት ያልፈፀመላቸው መሆኑን ዘርዝረው ተጠሪ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው ፣ ቦታውን መስጠት የማይችል ከሆነ ደግሞ በወቅቱ በነበረው የከተማው የሊዝ ዋጋ ተመን መሰረት የሁለት መቶ ካሬ ሜትር ዋጋ ብር 360,000.00 (ሶስት መቶ ስልሳ ሺህ ብር) እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም በማስታወቂያው ላይ የተገለፀው እድል የሚለው ቃል የሚያመላክተው የሥጦታ ተስፋ ቃል እንጂ ሽልማት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥ 2435 መሰረት ግዴታ የሚጥል አይደለም ፣ የስጦታ ተስፋ ቃል በሕግ ፊት ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ፎርማሊቲውንም የጠበቀ አይደለም ፣ የውሉ ጉዳዩ በግልፅ ያልተመለከተና የሚቻል ውል ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1714 መሰረት ሕጋዊነት የለውም ፣ እንዲሁም መሬት የመንግስትና የሕዝብ በመሆኑ ልገደድበት አይገባም በማለት ክሱ ውድቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ማስታወቂያው የሚያሳየው የስጦታ ተስፋ ቃል መሆኑን ፣ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2435 መሰረት ግዴታ የሚጥል አለመሆኑን ፣ የውሉ ጉዳይም በሕዝብና በመንግስት መሬት ላይ የተደረገ በመሆኑ ተጠሪ ሊፈፀመው የሚችለው አይደለም ፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1689(1) ለጉዳዩ አግባብነት የለውም የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ የአመልካችን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በማስታወቂያው ላይ ከገለፃቸው ሽልማቶች መካከል ሁለቱን ፈጽሞ እያለ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ለመሸለም ቃል አልገባሁም በማለት ያቀረበው ክርክር በበታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱ የውል አተረጓጐም ደንቦችን ስለውል አፈፃጸም የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በይዘቱ በስር ፍርድ ቤት ከአቀረበው መከራከሪያ ነጥብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ክርክር ያቀረበ ሲሆን አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀለው አመልካች በተጠሪ በተደረገው ጥሪ መሰረት ተወዳድረው የደቡብ ሚስስ ቱሪዝም ማዕረግ ማግኘታቸው ፣ በጥሪው ጊዜም ለአሸናፊ ሊሰጡ የሚገባቸው ሽልማቶች መገልፃቸው የተረጋገጠ ሲሆን ከሽልማቶች መካከል በክልሉ በሚገኙ ታላላቅ ኮሌጆች መካከል የነጻ ትምህርት እድልና ብር 5000.00 (አምስት ሺህ ብር) ተጠሪ ለአመልካች የፈጸመላቸው ሽልማቶች መሆናቸው ተረጋግጠዋል፡፡ አሁን ግራ ቀኙን እያከራከሩ ያለው የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ከሽልማቶች መካከል የሚገኝ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ረገድ አጥብቆ የሚከራከረው በማስታወቂያው ላይ "በሐዋሳ ከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እና በክልል የሚገኙት ታላላቅ ኮሌጆች ውስጥ ነጻ የትምህርት እድል---"በሚል ከተቀመጠው አረፍተ ነገር ውስጥ እድል የሚለው ቃል የስጦታ የተስፋ ቃል እንጂ ሽልማት አይደለም ፣ የስጦታ የተስፋ ቃል ደግሞ አስገዳጅ ግዴታ የማይጥል ነው በማለት ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ የተጠሪን ክርክር ተቀብለዋል፡፡ ይህን የስር ፍርድ ቤቶችን ድምዳሜ በፍ/ሕ/ቁጥር 2427 ስር ከተመለከተው የስጦታ ትርጓሜ አንፃር ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስጦታ ማለት አንድ ወገን ተዋዋይ ማለት ሰጪ ተቀባይ ተብሎ ለሚጠራው ለሌላ ሰው ችሮታ በማድረግ አሳብ ከንብረቶቹ አንዱን የሚለቅበት ወይም ግዴታ የሚገባበት ውል ስለመሆኑ የተመለከተ ሲሆን በተቀባዩ በኩል የሚገባ ግዴታ የለም፡፡ በሌላ አነጋገር ስጦታ በስጦታ ሰጪ ለስጦታ ተቀባዩ በችሮታ(gratuitously) የሚደረግ ውል ነው፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ያደረጉት ውል ግን አመልካች የቁንጅና ውድድሩ አሸንፈው የደቡብ ሚስስ ቱሪዝም ማዕረግ ከአገኙ ሽልማቱን ተጠሪ የሚሰጣቸው መሆኑን የሚገልፅ በመሆኑ የውሉ ጉዳይ ሲታይ አንዱ ተዋዋይ ለሌላኛው አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ለመስጠት የተስማማበትና በሕጉ አግባብ የተቋቋመ መሆኑን የሚስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ከመነሻው ጉዳዩ በስጦታ ውል የሚሸፈን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆን ያለመሆኑን ግራ ቀኙ ከአቋቋሙት ውል የግራ ቀኙን ግዴታ በመለየት ስጦታ መሆን ያለመሆኑን ሳይለዩ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2435 ድንጋጌን ለውሳኔአቸው ዋቢ ማድረጋቸው አግባብነት ያለውን ሕግ በመለየት ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ ፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1689 ሲሆን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ መሰረት የጠፋ እቃ ላገኘ ወይም ሌላ ነገር ለፈጸመ ሰው ሽልማት ይሰጠዋል ተብሎ በተለጠፈ ማስታወቂያ ወይም በአደባባይ ሊታወቅ በሚችል ሌላ ዐይነት ማስታወቂያ ወጥቶ ቃል ከተሰጠ በኋላ የጠፋውን ዕቃ አግኝቶ ቢያመጣ ወይም እንዲፈጽም የተባለውን ስራ ፈጽሞ ቢገኝ ይህን ያደረገው ሰው የወጣውን ማስታወቂያ ሳይውቅ ቢቀርም የተሰጠውን የተስፋ ቃል እንደተቀበለ እንደሚቆጠር የተደነገገ ሲሆን በአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ቃል ሰጪውም በበኩሉ የሠጠውን የተስፋ ቃል የመፈጸም ግዴታ እንዳለበት በኃይለ ቃል ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ሌላ ነገር መፈፀም በሚል ከተቀመጠው ሐረግ መረዳት የሚቻለው የውድድር አሸናፊንም የሚያካተት መሆኑን ሲሆን ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ ይኸው ድንጋጌ እንጂ የስጦታ ውልን በሚመለከት የተቀመጡት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች አይደሉም፡፡

ሌላው የበታች ፍርድ ቤቶች ለውሳኔው መሰረት ያደረጉት የግራ ቀኙ ሐሳብን የሚመለከት ነው፡፡ በመሰረቱ በውል ውስጥ የተጠቀሱት ቃላትና ድንጋጌዎች ግልጽ ባልሆኑ ጊዜ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1732 ፣ 1735-1738 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር በሰፈሩት ደንቦች መሰረት መተርጎም የተፈቀደ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ደንቦች የፍ/ሕ/ቁጥር 1734 እና 1736 ሲሆኑ ተዋዋዮች ውላቸውን ከመዋዋላቸው አስቀድሞ ወይም ከተዋዋሉ በኋላ የነበሩበትን ሁኔታዎች ፣ የፈጸሙትን ተግባር በማመዛዘንና ሐሣባቸው ምን እንደነበር ለማወቅ መሞከር እና የውሎችን ቃሎች አንዱን ከአንዱ ጋር እያዛመዱ በመመልከት ለውሉ ጉዳይ አግባብ ያለውን ትርጉም በመስጠት አዎንታዊ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች በተጠሪ በኩል የቀረበው የውል አቀባበል ማስታወቂያ በ19/12/2000 ዓ/ም የተጻፈ መሆኑን የገለፀ ሲሆን ተጠሪም ይህንኑ ደብዳቤ ስለመኖሩ ሳይክድ አጥብቆ የሚከራከረው በይዘቱና መንፈሱ ላይ ነው፡፡ ለክርክሩ መሰረት የሆነው የደብዳቤው ክፍል " **....አሸናፊ የሆነች ወጣት በክልሉ ርዕስ ከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እና በክልሉ የሚገኙት ታላላቅ ኮሌጆች ውስጥ ነጻ የትምህርት እድል ሲኖራት የብር 5000.00 (አምስት ሺህ ብር) ገንዘብ ሽልማትም ታገኛለች**" በሚል የተቀመጠ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚሁ የደብዳቤ ይዘት የነፃ ትምህርት እድልና የብር 5000.00 ሽልማት ለአመልካች በተጠሪ የተፈጸሙ ግዴታዎች ናቸው፡፡ ተጠሪ በደብዳቤው **<u>....እድል ሲኖራት...</u>** የሚለው ሐረግ አመልካች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ሽልማት ይሰጣታል ወይም ታገኛለች የሚል ግልጽ የሆነ የተስፋ ቃል የለም ፣ ቃሉ መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ልታገኝ የምትችልበት ሁኔታ መኖሩን ከሚያመላክት አልፎ በእርግጠኝነት ይህ ቦታ በሽልማት የሚሰጥ መሆኑን አያሳይም በማለት ተከራክሮ የስር ፍርድ ቤቶችንም ይሕንኑ የተጠሪን ክርክር ተቀብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ እንደተመለከተው የውል ቃሎች ግልፅነት የሚጎድላቸው ከሆነ ሕጉ የአተረጓጎም ደንቦችን ያስቀመጠ ሲሆን ዳኞቹም ይህንኑ የአተረጓጎም ደንብ ሊከተሉ እንደሚገባ የግድ ይላል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የነጻ ትምህርቱን የሰጠውና ብር 5000.00 የከፈለው ከውሉ በሁዋላ ሲሆን ይህን ግራ ቀኙ ከውሉ በሁዋላ የፈጸሙትን ተግባር በማመዛዘንና ሐሣባቸውን ምን እንደነበር ለማወቅ ሲሞክር ተጠሪ ለአመልካች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ለመሸለም የተስፋ ቃል መስጠቱን የሚገልፅ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ለአመልካች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ለመሸለም የገባው ግዴታ የለም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1734 እና 1736 ድንጋጋጎችን መሰረት ያላደረገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ሽልማት ቃል አልተገባም ለማለት በምክንያትነት የያዙት ጉዳይ የውሉን ጉዳይና ሊፈፀም የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከታው ነጥብ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የውል ጉዳይ የሚያሳየው ተዋዋይ ወገኖች ለመፈጸም የገቡትን ግዴታ ሲሆን ይህ የሚቋቋመው ግዴታም አንዱ ተዋዋይ ለሌላኛው አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ለመስጠት አለበለዚያ አንድን ማድረግ ይችል የነበረውን ከማድረግ ለመቆጠብ የሚስማማበት ነው፡፡ ይህ የተባለው ነገር እንዲደረግለት የሚፈልገው ሌላኛው ወገንም በበኩሉ ሌላ ግዴታ ይገባል፡፡ ይህ ግዴታ የሚያሳየው የውሉን ጉዳይ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1711 ላይ እንደተመለከተው ሕግ ከከለከለው በስተቀር ተዋዋዮቹ ሁሉ የሚዋዋሉትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት አላቸው፡፡ የውል ጉዳይ አወሳሰን ከመዋዋል ነጻነት(Freedom of Contract)ጋር በእጅጉ በቀጥታ የተገናኘና ለተዋዋዮች ግላዊ ምርጫ የተተወ ስለመሆኑ የጠቅላላ ውል ዕንሰ ሐሳቦች የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ተዋዋይ ወገኖች የራሳቸውን መብትና ግዴታ ገልፀው የሚፈልጉትን ባግባቡ ለይተው ካመለከቱ በመካከላቸው በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ውል ተመስርቷል ለማለት የሚቻል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1715 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚሳየን ጉዳይ ሲሆን ግዴታዎቹ በትክክልና በሚበቃ ሁኔታ ሊገለፁ እንዲሚገባም የዚሁ ድንጋጌ ይዘት ያስረዳል፡፡ እንዲሁም የአንደኛው ተዋዋይ ወገን ግዴታ ሊፈፅሙት ፍጹም የማይቻልና የማይሞከር ጠባይ ያለው ሆኖ ከተገኘ ፈራሽ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1714 የተመለከተው ድንጋጌ የሚያስገነዝብ ሲሆን ይኸው ድንጋጌ ፍፁም የማይቻልና የማይሞከር ጠባይ ያለው ግዴታ ሲባል ተዋዋይ ወገን ብቻ ሳይሆን ማንም ሰው ሊፈፅመው የማይችለው ግዴታ መሆን እንዲሚኖርበት የሚያስረዳ ሲሆን ሊፈጸም እስከቻለ ድረስ አስቸጋሪነቱ ግዴታውን ሊያፈርሰው እንደማይችል የተጠቃሹ ድንጋጌ መንፈስና ይዘት በግልጽ ያሳያል፡፡ ውል ሕጋዊ ውጤት ያለው ተግባር እንደመሆኑ መጠንም እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን በውሉ የተጣለበትን ግዴታ መፈፀም የሚገባው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1740 እስከ 1762 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የበታች ፍርድ ቤቶች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በእርግጠኝነት በተጠሪ እጅ የሚገኝ መሆኑ ፣ ስፋቱ እና አቀመማጡ የተለየ እና የታወቀ መሆኑ በትክክል እና በግልጽ በሚበቃ መልኩ አልተመለከተም በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1714(1)ን በመጥቀስና ተጠሪ የከተማ ቦታን በስጦታም ሆነ በሽልማት የመስጠት ስልጣንም ሆነ ችሎታ የለውም በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1715 ድንጋጌ ጋር በማዛመድ ውሉ በሕግ ግዴታን የሚፈጥር አይደለም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ሲታይ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታዎች በከተሞች ለሰዎች የሚሰጡበትን ስርዓት ፤ የማዘጋጃ ቤትን ስልጣንና የሊዝ ሕጎችን ፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1711፣1713፣1714 እና 1715 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ መሬት የመንግስትና የሕዝብ መሆኑ በፌዴራልም ሆነ በክልል ሕግጋተ መንግስታት የተደነገገ ሲሆን በከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታዎች ለሰዎች የሚሰጡበትና ስራው የሚያከናውነው የክፍሉ ማዘጋጃ ቤት መሆኑን ስራ ላይ ያሉት ሕጎች የሚሳዩን ሲሆን መጠኑን በተመለከተም ሕግና ሥርዓት የተዘረጋለት ጉዳይ ነው፡፡የከተማ ቦታን የመስጠት ስልጣን የከተማው ማዘጋጃ ቤት ስልጣን መሆኑ በሕጉ በተደነገገበት ሁኔታ ተጠሪ ቦታ ለአመልካች እሸልማለሁ ብሎ የገባው ቃል ስልጣኑ ሲኖረው የሚፈጽመው ግዴታ መሆኑን አውቆ ያደረገው ሳይሆን ቦታ የሚገኝበትን ሥርዓት ተከትሎ ለአመልካች ለማስረከብ ግዴታ መግባቱን የሚያሳይ ነው፡፡ የከተማ ቦታ ከሚገኝባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ የሊዝ ስርዓት ነው፡፡ ቦታ በሊዝ የሚገባው ደግሞ በሕጉ ፣ ደንቡና በመመሪያው መሰረት ተመንና የውሉ ጊዜ ወጥቶለት ነው፡፡ ተጠሪ የቦታ ሽልማት ውሉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በወቅቱ በነበረው የሊዝ ተመንና በሕጉ አግባብ በሊዝ ገዝቶ የሚፈጸመው ጉዳይ እንጂ ፍጹም የማይቻልና የማይሞከር ጉዳይ አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የመሬቱን አቀማመጥና ተይዞ የሚገኝበትን ሁኔታ እንዲሁም ቦታ በሽልማት የመስጠት ስልጣንን በምክንያትነት በመያዝ በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ውል የለም ብሎ መደምደሙ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1715 ድንጋጌ አንፃር ሲታይ ሕጋዊ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በከተማ የመኖሪያ መስሪያ ቦታ የሚገኝበትን የሕግ ስርዓት እያወቀ ያደረገው ውል መሆኑ እየታወቀ በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት አይችልም በማለት መደምደም በተዋዋዮች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትንና የመተማማን ግንኙነት መሰረት በማድረግና በጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል ውሎች በቅን ልቦና ሊተረጎሙ ይገባል ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1732 ስር የተደነገገውን ድንጋጌ ውጤት አልባ የሚያደርግ ነው፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1689(1) ድንጋጌ ሁኖ እያለ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2435 ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የደረሱበት ድምዳሜ የውል አተረጓጎም ደንቦችንና የውል ውጤትን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 08045 ሰኔ 30 ቀን 2002 ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 44079 ጥቅምት 10 ቀን 2003 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተቋቋመው የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ውል ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካች በሐዋሳ ከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በሕጉ አግባብ ገዝቶ እንዲሰጣት ወይም ውሉ ሲደረግ በነበረው የከተማ የሊዝ ዋጋ መሰረት አንድ መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ሊገዛ ይችል የነበረውን ዋጋ በሊዝ ሕጉ ፣ ደንቡና መመሪያው መሰረት አስልቶ ለአመልካች እንዲከፍል ብለናል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 66210

29/11/ 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ ጎላ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ ተጠሪ መ/ቤት የዲሲፕሊን ኮሚቴ የሰጠው የዲሲፕሊን ውሣኔ ለተጠሪ መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ቀርቦ ይፈፀም በመባሉ ምክንያት አመልካች ይግባኛቸውን በደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 29 መሰረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ከፍተኛው ፍ/ቤትም መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዝጋት አመልካችን በማሰናበት በመወሰኑ አመልካች በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን ስለአቀረቡ ነው፡፡

ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሣኔ መነሻ የሆነውን አቤቱታ ለተጠሪ መ/ቤት ያቀረቡት አቶ ጽጌ ጌታነህ ሲሆኑ የአቤቱታውም ፍሬ ቃሉ ከአዲስ አበባ ቴኒስ ክለብ ጋር በተፈጠረው ያለመግባባት ክለቡን በሕግ ፊት አመልካች አቅርበው እንዲፋረዱላቸው አመልካችን ጠይቀው አመልካችም ፈቃደኛ ሆነው የጥብቅና ሙያ ውል እንደአደረጉና አመልካች ለሚሰጧቸው አገልግሎትም ብር 2,000.00 ለመክፍል፣ አከፋፈሉም በቅድሚያ ብር 1,000.00፣ ቀሪው ብር 1,000.00 ደግሞ ጉዳዩ እንደተከናወነ እንደሚሆን ተስማምተው ቅድሚያ ክፍያውን አመልካች ተቀብለው አመልካች እንደስምምነቱ ሳይፈፅሙ ለእንግልት የዳረጓቸው መሆኑን ገልጸው የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸውና የተወሰደባቸው ገንዘብ እንዲመለስላቸው መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ክሱን ሊያቀርቡ ያልቻሉት አስተዳደራዊ መፍትሔዎችን ለመጨረስ ተገቢውን ሲያደረጉና ክለቡ ሕጋዊ ሰውነት ስለሌለው በፍርድ ቤት ሊከሰስ የሚችል አለመሆኑን እንዲሁም ክሱ የሚቀርበው አስተዳደራዊ መፍትሔዎች ሲያልቁ በመሆኑ በዲስፕሊን ሊያስጠይቃቸው የማይችል መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ የሥር የዲሲፕሊን ኮሚቴውም የአሁኑ አመልካች የፌዴራል ፍ/ቤቶች የጠበቆች ሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 8/2/ለ/ የተደነገገውን የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች በመጣስ የደንበኛቸውን በአፋጣኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትህ የማግኘት መብት ጎድተዋል፣ ይህም ሕብረተሰቡ ለሌሎች የሕግ ባለሙያዎች ያለውን እምነት የሚሸረሽር ነው የሚለውን ምክንያት በመስጠት በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 24(3(ለ(3)) መሰረት በብር 10,000 /አሥር ሺህ/ እንዲቀጡ የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ ኃላፊ ያቀረበ ሲሆን የበላይ ኃላፊውም የኮሜቴውን የውሳኔ ሀሳብ አጽድቀውታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ከግል ተበዳይ ጋር በተደረገው የጥብቅና ውል መሰረት ሙያው የሚጠይቀውን እየፈጸመ ያሉ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በጉዳዩ ላይ ክስ ሳያቀርቡ ዘግይተዋል ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የዲስፕሊን ግድፈት ፈፅመዋል ተብሎ ብር 10,000.00 እንዲቀጡ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ተይዞ ለሰበር ችሎቱ ጉዳዩ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም አመልካች በዲሲፕሊን ግድፈት ሊጠየቁ የቻሉት ከግል ተበዳይ ጋር ባደረጉት የጥብቅና ውልና ተገቢ ያልሆኑ ተግባራትን መፈፀማቸው በመረጋገጡ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በፅሑፍ መልሱን አቅርቧል፡፡ አመልካችም የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም አመልካች በተከሰሱበት የዲስፕሊን ክስ ጥፋተኛ ናቸው ተብለው በገንዘብ የተቀጡት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሰረቱ የጥብቅና ሙያ ለእውነት፣ ለፍትህ እና ለሕግ የበላይነት መስፍን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑ እሙን ሲሆን ይህንን ግብ ላይ ለማድረስ ደግሞ ሙያው ከባለሙያው የሙያ ኃላፊነቱን በታማኝነት፣ በቅንነት፣ በታታሪነትና በብቃት እንዲወጣ የሚጠይቀው ጉዳይ ይሆናል፡፡ ይህንኑ ግዴታ ያለመወጣት ደግሞ ምግባረ ብልሹነት ሲሆን ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ምዝገባና ፍቃድ አሰጣጥ አዋጅ ቁጥር 199/92 መግቢያው እንዲሁም አንቀጽ 30 ስር ለተመለከቱት ድንጋጌዎች እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 3፣8(2(ለ)) እና ሌሎች ድንጋጌዎች ይህንኑ ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡና ተጠያቂነት መቼ ሊከተል እንደሚችል የሚያሳዩ ድንጋጌዎችን ይዘው እናገኛለን፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ሲመጣ አመልካች የዲስፕሊን ግድፈት ፈጽመዋል የተባሉት ከአቶ ጽጌ ጌታነህ ጋር ባደረጉት የጥብቅና ውክልና ስልጣን መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ወስደው ጉዳያቸውን በተገቢው ጊዜ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት አቅርበው ሳያስወስኑ አዘገይተዋል ተብለው ሲሆን ይህ ስለመሆኑ የዲሲፕሊን ኮሚቴው በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን አመልካችም ቢሆኑ ጉዳዩን አስተዳደራዊ መፍትሔ እንዲሰጥበት ለማድረግ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ በማቅረብ እየተከታተሉት ያለና ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድም አቶ ጽጌ ጌታነህ እንዲከሰስላቸው የሚፈልጉት አካል ሕጋዊ ሰውነት የሌለው በመሆኑ የተቸገሩ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ከአቶ ጽጌ ጌታነህ ጋር ያደረጉት የጥብቅና ውል ይዘት ሲታይም እኔ አገልግሎት ተቀባይ ከአዲስ አበባ ቴንስ ክለብ ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የክለቡ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ከጥቅምት 23 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ያገደኝ በመሆኑ አገልግሎት ሰጪው አቶ ተስፋዬ ጎላ ጥሩነህ ባላቸው የጥብቅና ሙያ ከስራ አስኪያጅ ኮሚቴው ጋር ተከራክረው የእኔን የክለብ አባልነት መብቴን እንዲያስጠብቁልኝ የሚል ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የደንበኛቸውን ጉዳይ በፍርድ ቤት ክስ ለመመስረት ያልቻሉበት ምክንያት በጉዳዩ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስተዳደራዊ መፍትሔ ለማግኘት ነው የሚል የሚገኝበት ሲሆን ይህ ምክንያት ጉዳዩን ለመጨረስ አንዱ አካሄድ ነው ቢባልም አስተዳደራዊ መፍትሔ ለማግኘት ሲባል ግን ጉዳዩ በፍርድ ቤት በተገቢው ጊዜ ክስ ሳይቀርብበት እንዲቆይ የሚያደርግ አይደለም፡፡ የስር የዲስፕሊን ኮሚቴውም አስተዳደራዊ መፍትሔ መፈለግ ተገቢነቱን አምኖ አመልካችን ከተጠያቂነት ሊድኑ አይችሉም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አመልካች በትጋትና በታማኝነት ጉዳዩን ያልተከታተሉ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል በማለት ሲሆን አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት የማስተባበያ ማስረጃ የሌለ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ሌላው አመልካች በምክንያትነት የሚያቀርቡት ነጥብ ደንበኞቸው እንዲከሰስ የሚፈልጉት አካል ሕጋዊ ሰውነት የሌለው መሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ምክንያት ጠበቃው የሙያው ስነ ምግባሩን መሰረት በማድረግ በሙያው ሕጋዊ ነው የሚለውን አስተያየት የማቅረብ ሙያዊ ነፃነት ያለው መሆኑ ቢታወቅም ይህንኑ ነፃነቱን ደግሞ የደንበኛውን ፍላጎት ማዕከል በአደረገ መልኩ ሊወጣው የሚገባው ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ ደንበኛቸው እንዲከሰስ የሚፈልጉትን አካል ከሰው ይኸው አካል የሕግ ሰውነት ያለው መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲወሰን ማድረግ የሚችሉት ነጥብ በመሆኑ ክስ ላለማቅረብ እንደ በቂ ሕጋዊና ሙያዊ ምክንያት ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ከደንበኛቸው ጋር ያደረጉት የጥብቅና ውክልና ስልጣን ሰነድ ይዘቱ ሲታይ አመልካች ክሱን በተገቢው ጊዜ በፍርድ ቤት እንዲያቀርቡና የደንበኛቸውን መብት እንዲያስጠብቁ ግዴታ የሚጥልባቸው መሆኑና አመልካች ይህንኑ ግዴታቸውን በተገቢው ጊዜና በትጋት ሳይወጡ ቀርተው ጉዳዩን ያዘገዩ መሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የዲስፕሊን ኮሚቴውና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተስማሙት ጉዳይ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፕብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ የሚነቀፍበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረገጋጠው ነጥብ ከላይ የተጠቀሰው ከሆነ አመልካች በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 8(2(ለ)) እና አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24(3(ሉ-3)) ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ ተብለው በብር 10,000.00(አስር ሺህ) መቀጣታቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 33945

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ሣልህ ሁሴን ቀረቡ

ተጠሪ፡- ደግፌ ደርቤ ከጠበቃ ጣሰው ማሞ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡

አመልካች ግንቦት 05 ቀን 1997 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ተጠሪ በስማቸው ተመዝግቦ የሚታወቀውንና በቀድሞው አጠራር ከፍተኛ 09 ቀበሌ 07፣ በአሁኑ አጠራር በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘውን ቁጥሩ 207 እና 206 የሆነ ቤት በመያዣነት አስይዘው ብር 120000.00 /አስራ ሁለት ሺህ/ ተበድረው ቤቱን እንዳስረከቧቸው፤ በስምምነቱ ወቅት የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥና መለወጥ ችግር ስለነበር ገንዘቡ የ10 ዓመት መክፈያ ጊዜ ተወስኖለት ኅዳር 20 ቀን 1990 ዓ.ም. ማብቃቱን፤ ኅዳር 20 ቀን 1980 ዓ.ም. በተዛፈ የብድርና የዋስትና ውል ቤትን መሸጥና መለወጥ በመንግሥት ሲፈቀድ አመልካች ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ ለተጠሪ በመጨመር ከወሰዱት ብር 120000.00 ጋር ተደምሮ በብር 170000.00 /አስራ ሰባት ሺህ ብር/ ቤቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ ተጠሪ ውል መፈረማቸውን፤ የቤቱን የእድሣት ወጪዎችም አመልካች እንዲሸፍኑ ተጠሪ ፈቃዳቸውን በውሉ የገለጹላቸው ሆኖ ተጠሪ ከወሰዱት የቤቱ መያዣ ብድር ጋር የእድሣት ወጪ ሲደመር ድምሩ ብር 18787.90 /አስራ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሠማኒያ ሰባት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ መሆኑን፤ የቤት ሽያጭም ከ1982 ዓ.ም. ጀምሮ በመንግሥት መፈቀዱን ዘርዝረው ተጠሪ በስምምነቱ መሠረት የብድሩን ገንዘብ በወቅቱ ካለመመለሣቸውም በላይ የቤቱን ስመ ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ በአማራጭ የገቡትን ግዴታ ስላልፈፀሙላቸው አመልካች ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ ለተጠሪ ጨምረውላቸው የቤቱ ስም በአመልካች እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ለማስረጃነትም የጽሑፍና የሰው ምስክሮችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች የክስ ማመልከቻና ማስረጃ ለተጠሪ እንዲደርስ ተደርጎም ተጠሪ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ፍ/ቤቱም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካችን ክስና ማስረጃ መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ ውል የመያዣ ውል ሣይሆን የወለድ አገድ ውል ነው፤ ውሉ በተደረገበት ወቅት የወለድ አገድ ግንኙነት የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 47/67 ስለነበር ይኸው አዋጅ የወለድ አገድ ውልን የሚከለክል በመሆኑ ውሉ ሕገወጥ ስለሆነ ፈራሽ ነው፤ ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ይመለሱ፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ያስረክቡ፤ ተጠሪ ከአመልካች የወሰዱትን ገንዘብና የቤት ማደሻ ብር በገቡት ውል መሠረት ለከሣሽ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶች ጎዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ቀርበው ባልተከራከሩበት እና የተጠየቀ ዳኝነት በሌለበት ሁኔታ ቤት እንዲረከቡ መወሰናቸው ያላግባብ በመሆኑ ውሣኔው ተሽሮ ጎዳር 20 ቀን 1980 ዓ.ም. በውል ያገኙት መብት ተጠብቆ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በጉዳዩ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ የተሠጠውን ውሣኔ የሕግ አግባብነት ለማጣራት ተጠሪ እንዲቀርብ ተደርጎ ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት፣ የፍ/ሕ/ቁ. 1815 ድንጋጌን ያገናዘበ፣ የአመልካች ጥያቄ ግን በፍ/ሕ/ቁ 2851 ድንጋጌ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የመልስ መልስ ማመልከቻ ተጠሪ ወደ ዋናው ጉዳይ ገብተው ለመከራከር ሥነ ሥርዓቱ የማይፈቅድላቸው መሆኑን ገልፀውና የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ይህንኑ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጭብጦች፡-

1ኛ/ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ከጠየቁት ዳኝነት በተለየ ሁኔታ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? እና

2ኛ/ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም? የሚሉት ሁነው ተገኝተዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች ከተጠሪ ጋር ተደርጓል በሚሉት ስምምነት አከራካሪውን ቤት ተረክበው በይዞታቸው ሥር አድርገው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ ሲሆን የጠየቁት ዳኝነትም ቀሪውን ብር ለተጠሪ ጨምረው የቤቱ ስመንብረት እንዲዛወርላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ነው፡፡ ይህንኑ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የአሁኑ ተጠሪ ፍ/ቤት ቀርበው ክስር ያልተከራከሩበት ሆኖ የስር ፍ/ቤት ግን የውሉን ሕጋዊነት በራሱ ጊዜ በማንሣት ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የስር ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው የአሁኑ አመልካች በግልጽ ባላመለከቱት እና ባልጠየቁት ዳኝነት ላይ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182/2/ ድንጋጌ ሥር የተመለከተውን የመጀመሪያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደረጃ ፍ/ቤት የዳኝነት አሠጣጥ የስልጣን አድማስ በግልጽ የሚዛረር ነው። የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በይግባኝ ሠሚነቱ ስልጣን የስር ፍ/ቤትን የውሣኔ አሠጣጥ ማረም ሲገባው በተመሣሣይ ምክንያት ተቀብሎ ማጽናቱ የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓቱን ያላገናዘበ ነው። የስር ፍ/ቤት ስለውሉ ሕጋዊነት ክርክር ባልተነሣበት ሁኔታ በራሱ ጊዜ ማንሣቱም የክርክር አመራር ስርዓቱ በሚፈቅድለት ሁኔታ አይደለም። ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሣይቀርቡ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ከተወሰነ በኋላ አሁን በሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም። ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሣይቀርቡ ታይቶ በተሰጠው ውሣኔ ለበላይ ፍ/ቤት ሊያቀርቡ የሚችሉት ክርክር ከስር ክስ ተያይዘው የቀረቡትን የከሣሽን ማስረጃዎች አግባብነት፣ ተቀባይነት እና ጥንካሬ ያገናዘብ መሆን ያለመሆኑን መሠረት በማድረግ ብቻ የተወሰነ ነው። ስለሆነም ተጠሪ በዚሁ የክርክር ደረጃ ያነሱት ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል። በዚህም መሠረት የስር ፍ/ቤት የውሣኔ አሠጣጥ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ መሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል።

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- በመጀመሪያው ጭብጥ እንደተገለፀው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ስመ ንብረቱ እንዲዞርላቸው ይወሰን ዘንድ ነበር። የስር ፍ/ቤትም የዚህኑ ጥያቄ አግባብነት በመመርመር ውሣኔ መስጠት እየተገባው ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ ውሣኔ ሰጥቷል። የአመልካች ጥያቄ ተገቢነት ያለው መሆን ያለመሆኑን የስር ፍ/ቤት በጭብጥነት ይዞ በሕጉ አግባብ የሰጠው ውሣኔ ባይኖርም ከተጠየቀው ዳኝነት ይዘት በሰበር ችሎቱ ከዚህ በፊት በተመሣሣይ ጉዳይ ከተሰጠው የሕግ ትርጓሜና ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ዓላማ አኳያ ሲታይ በዚህ ችሎት ለጉዳዩ እልባት መስጠቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም መሠረት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የሚያስከስስ ሊሆን ይችላል አይችልም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል።

ከአመልካች ክስና ክርክር ማረጋገጥ የተቻለው ከተጠሪ ጋር በተደረገው ስምምነት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ተረክበው ለረጅም ጊዜያት በይዞታቸው ስር አድርገው የሚገኙ መሆኑን፣ ቤቱን የሚመለከቱ አስፈላጊ ሰነዶችም በተጠሪ እጅ ይገኛሉ ተብሎ በክሱ አለመገለጹንና የዳኝነት ጥያቄ ያልቀረበበት መሆኑን በተጠሪ በኩል መፈፀም አለበት የተባለው የቤቱ ስመ ንብረት ማዞር ብቻ መሆኑን ነው። የስም ዝውውር ተግባር የሚፈፀመው በመንግሥት አስተዳደር ክፍል ፊት እንጂ ሻጭ ነው የተባለው ወገን ሊፈጽም ይገባል ተብሎ ከሕግ ወይም ከውል ያመነጫል ሊባል የማይችል ግዴታ ነው። የስም ዝውውር ጥያቄ የሚስተናገደው የባለ ሀብትነት የምስክር ወረቀት በሚሠጥ የመንግሥት አስተዳደር አካል ገዢው ውልና አስፈላጊ ሠነዶችን ይዞ ሲቀርብ እንጂ በፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ዳኝነት የሚሰጥበት አይደለም። አንድ ክስ ሊቀርብ የሚገባው የክስ ምክንያት ሲኖረው ሲሆን የክስ ምክንያትም ተከሣሽ ለከሣሽ ሊፈጽመው የሚገባው ግዴታ መኖሩ ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚችለውን ጥያቄ አወንታዊ ምላሽ መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ሲረጋገጥ የሚታወቅ ነው። በዚህም መሠረት አመልካች ተጠሪ የስም ዝውውሩን እንዲፈጽሙ ይወስንልኝ ብለው ዳኝነት መጠየቃቸው በተጠሪ በኩል ሊፈፀም የሚገባ የሕግ ወይም የውል ግዴታ የሌለ መሆኑን ስለሚያሣይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231/1/ሀ/ መሠረት ፍሬ ነገሩ የማያስከስስ ነው ተብሎ መወሰን ያለበት ሆኖ ተገኝቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13295 ጥቅምት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 51107 ጎዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የስም ዝውውር ጥያቄ ታይቶ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው እያለ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ ውሉ ሕገወጥ ነው ተብሎ ቤቱን እንዲያስረክቡ መባሉ የዳኝነት አሰጣጥ ሥርዓትን የተከተለ አይደለም ብለናል፡፡
3. የአመልካች የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የሚያስከስስ ምክንያት የለውም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 3 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ዑመር ከድር ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1/ አቶ በዳዳ ሰቦቃ

2/ ወ/ሮ አበበች ተካ ጠ/ሰለሞን ሀብቴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የቤት ሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪዎች ጅምር ቤት ከ1057 ካ.ሜ. ይዞታ ጋር ሸጠውለት ሳለ ክ/ከተማው ቦታውን ለልማት የወሰደ መሆኑን ጠቅሶ ሽያጭ የተፈፀመው የሻጮች ይዞታ ባልሆነ ቦታ ላይ ነው ሲሉ ሽያጩ ዋጋ የለውም ተብሎ ወደነበሩበት እንዲመለሱ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪዎች የይርጋ ክርክር በማቅረባቸው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሽያጭ ውል ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በላይ ይሆናል በማለት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810/2/ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕግ 244/2/ሠ እና 245 በመመረኮዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይህንኑ ብይን አጽንቷል፡፡

የአመልካች ጠበቃ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት አቤቱታ ውስ በሕጉ አላግባብ ያልተፈፀመ ስለመሆኑ እና ተጠሪዎች መብት የሌላቸውን ቦታ የሸጡላቸው መሆኑን ዘርዝረው የሥር ፍ/ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን ትክክለኛ ጭብጥ ሣይዝ የሰጠው ብይን እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

ሰበር ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ በዚህ ጉዳይ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810/2/ ተፈፃሚነትን አስመልክቶ ለመመርመር ሲል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

የተጠሪዎች ጠበቃ በ14/5/2002 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ የአመልካች ክስ ውል ማሰረዝ ይሁን ማፍረስ ግልጽነት የሚጎድለው ስለመሆኑ ጠቅሰው ተጠሪዎች ያደረጉት የሽያጭ ውል ዋጋ የለውም እንዲባልና ወደነበርንበት እንመለስ የሚለውም ውሉ ከተደረገ ከ9 ዓመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810 በይርጋ ቀሪ መደረጉ በአግባቡ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሆኖ እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው በግራ ቀኙ መካከል ነሐሴ 12 ቀን 1990 ዓ.ም በተደረገ ውል ተጠሪዎች ጅምር ቤት ለአመልካች መሸጣቸው እና በዚሁ አግባብም በግራ ቀኙ መካከል በውሉ መሠረት የተፈፀመ ስለመሆኑ ነው፡፡

አመልካች ውሉ ዋጋ የለውም ተብሎ ግራ ቀኙ ከውሉ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ እንዲወስን ዳኝነት የጠየቀው ለአመልካች የተሸጠው ይዞታ የሻጮች አልነበረም በሚል መነሻ ስለመሆኑም የሥር መዝገብ ያስረዳል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የውሉ ጉዳይ ሕጋዊነት አከራካሪ ሆኖ የቀረበ መሆኑን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1711 በግልጽ እንደተደነገገው የውለታው ጉዳይ /Object of the Contract/ የመወሰን መብት የተዋዋዮች ቢሆንም በሕግ የተወሰኑ ወይም የተከለከሉ ጉዳዮች የተጠበቁ መሆናቸውን ያስገነዝባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያቀረበው ክስ መሠረት ያደረገው ተጠሪዎች የሸጡት ቤትና ይዞታው የራሣቸው አይደለም በሚል ነው፡፡

ስለዚህ የውለታው ጉዳይ ተጠሪዎች ሕጋዊ ባለይዞታ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው በፍሬ ነገር ክርክር እና ማስረጃ የሚጣራ በመሆኑ በዚህ ደረጃ የምንመረምረው አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810/2/ን በመመርኮዝ ክሱን በይርጋ ደንብ ስለዘጋው የዚህን አቋም አግባብነት ብቻ እንመረምራለን፡፡

ውል የማፍረስ /invalidation/ መነሻ ምክንያቶች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1808 ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም ውሉ አመሠራረት ላይ የፈቃድ ጉድለት መኖር ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ ችሎታ ማጣት፤ የውለታው ጉዳይ ሕገወጥነት ወይም ኢምራላዊነት ወይም የውሉ አቀራረጽ /ፎርም/ በሕግ የተደነገገውን ሥርዓት አለመጠበቅ የሚሉ ናቸው፡፡

ከእነዚህ ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሌላው መነሻ ውሉ እንዲፈርስ ጥያቄ በማንና መቼ መቅረብ እንዳለበትም በሕጉ ተመልክቷል፡፡

ከዚሁ አንፃር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810 ሥር እንደተመለከተው የውሉ መፍረስ ምክንያት ከተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ ጉድለት ወይም ችሎታ ማጣት ጋር የተያያዘ ከሆነ ውሉ እንዲፈርስ ጥያቄ መቅረብ ያለበት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን እንዳለበት ያመለክታል፡፡

የጊዜውም አቆጣጠር ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ ወይም አካለመጠን ከደረሰ ጊዜ ጀምሮ መሆኑንም ተመልክቷል፡፡ ይህ የድንጋጌው ይዘት ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ምክንያቶች የተወሰኑትን ብቻ ለይቶ ያስቀመጠ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1808/1/ ድንጋጌ ይዘት ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810/1/2/ የተመለከተው የጊዜ ገደብ የሚያገለግለው ውሉ በፈቃድ ጉድለት ወይም በችሎታ ማጣት መነሻ እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄን በሚመለከት ብቻ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ ሌላ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1808/2/ ሥር የተዘረዘሩትን ምክንያቶች መነሻ በማድረግ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1810 መሠረት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብ ሕጉ አላስገደደም፡፡ ስለዚህም የውለታው ጉዳይ ሕጋዊነትን አስመልክቶ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810 መሠረት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ አልቀረበም ሲል የሥር ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የደረሰበት ድምዳሜ የሕጉን ይዘት በአግባቡ ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የውለታውን ጉዳይ ሕጋዊነት አስመልክቶ የሚያቀርብ ክስ የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810 ሥር የሚሸፈን ሣይሆን እንደማናቸውም የውል ጉዳዮች ክርክር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 በተደነገገው የአሥር ዓመት ጊዜ የሚታይ ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ መካከል የሽያጭ ውል የተደረገው ነሐሴ ወር 1990 ዓ.ም ሲሆን ክስ የቀረበው ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ጊዜው ሲሰላ ደግሞ አሥር ዓመት /10/ እንዳላለፈው ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም የውለታው ጉዳይ ሕጋዊነትን አስመልክቶ አመልካች ያቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1810/2/ መሠረት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ አልቀረበም በሚል የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ብይን ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13325 መስከረም 28 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 72117 በ02/11/2001 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡
3. ክሱ የአሥር ዓመት ይርጋ ጊዜ አላለፈበትም ብለናል፡፡
4. ስለሆነም በግራ ቀኙ የቀረበውን የፍሬ ነገር ክርክር መርምሮ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መዝገቡን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሳስ 25 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- አበበ አበጋዝ ቀረበ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ጥሩነሽ ተክሌ ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ቀደም ሲል በቤት ላይ ተደርጎ የነበረው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ በተወሰነው መሠረት ቤቱን ያስረክቡኝ፣ የአሁኑ አመልካችም ቤቱን ይዞ ስለሚገኝ እስኪያስረክበኝ ድረስ ኪራይ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ተጠሪ በአሁኑ አመልካች እና ሃይሉ ታደሰ በተባለ ግለሰብ ላይ ያቀረበችውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የተከሳሾቹን መልስ ካየ እና ክርክሩን ከሰማ በኋላ በወቅቱ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ለቆ ለተጠሪ እንዲያስረክብ፤ በውሉ መፍረስ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት 2ኛ ተከሳሽ የነበረውን ሃይሉ ታደሰን ከሶ የመጠየቅ መብት አለው በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ ፍ/ቤቱም ቀደም ሲል ተሰጠ የተባለው ውሳኔ የስር ከሳሽ ቤቱን እንድትረከብ የሚያስችላት አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 3 ቀን 2001ዓ.ም በዓፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ከክርክሩ አነሳስ እና ቀደም ሲል ተሰጥቶ ነበር ከተባለው ውሳኔ አንፃር ሲታይ ያለው አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና በየደረጃው የተሰጡትን ውሳኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል። ከዚህም በቅድሚያ መገንዘብ የቻልነው ተጠሪ በ2ኛ ተከሳሽነት ተመዝግቦ የነበረው ሃይሉ ታደሰ የተባለው ሰው ሚስት እንደሆነች እና ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ከኔ ፈቃድ ውጭ ነው የተሸጠውና የሸያጭ ውሉ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ተጠሪ ባልዋን ጨምራ መክሰስዋን ነው። ይህን የመሰለውን ክስ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣ ውሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 የተመለከተውን መስፈርት አያሟላም፤ በሕግ ፊት የፀና አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ክሱ የክስ ምክንያት የለውም የሚል ውሳኔ እንደሰጠም ተመልክተናል። ተጠሪ ቤቱን ልረከብ፤ ኪራይም ይከፈለኝ በማለት አዲስ ክስ የመሠረተችውም ከዚህ በኋላ ነው።

እንደምንመለከተው በአመልካች እና በተጠሪ ባለቤት መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በማለት ተጠሪ ክስ ብትመሠርትም ክስዋ የክስ ምክንያት የለውም በሚል ትዕዛዝ ነው የተዘጋው። ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ለክሱ መነሻ የሆነው ውል ሊፈርስ የሚገባው ነው ወይም አይደለም? በሚለው የሥረ ነገር ጭብጥ ላይ ክርክር ተደርጎ ውሳኔ አለመስጠቱን ነው። በእርግጥ ቀደም ሲል ቀርቦ በነበረው ክስ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ተወስኖ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ አመልካች ይግባኝ ባይነት ጉዳዩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ክርክር ከተካሄደበት በኋላ ተሽሮ ክርክሩ እንደገና ተሰምቶ ይወሰን ዘንድ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶአል። ከዚህ በኋላም ነው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክሱ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ክሱን ሳያስተናግድ መዝገቡን የዘጋው። በዚህ ላይም ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ይግባኝ አላለም።

ቀደም ሲል እንዳየነው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የክስ ምክንያት የለም በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ ከጅምሩ የቤት ሽያጭ ውል የለም እንደማለት ነው በሚል እሳቤ ነው አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክብ በማለት የወሰኑት። የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን የክስ ምክንያት የለም በመባሉ ተጠሪ ቤቱን ልትረከብ ችላለች ማለት አይቻልም የሚል አስተሳሰብ ነው የያዘው። በእርግጥ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጠሪን የውል ይፍረስልኝ ክስ የክስ ምክንያት የለውም ለማለት የሰጠው ምክንያት ውሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 የተመለከተውን መስፈርት /ፎርም/ ያላሟላ እና ከጅምሩ ውል ሳይኖር የውል ይፍረስ ክስ ሊቀርብ አይችልም የሚል ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል። የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ይህን አካሄድ በመከተሉ ነው በአመልካች እና በተጠሪ ባለቤት መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ሊሆን የሚገባው ነው ወይም አይፈርስም? በሚለው የሥር ነገር ጭብጥ ላይ ክርክር ሳይሰማ ተጠሪ ቤቱን ትረከብ ዘንድ የወሰነው።

ለፍ/ቤት የቀረበ የፍትሐብሔር ክስ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም? ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚያገኙት ወይም የሚወሰኑት ፍ/ቤቱ ወደ ክሱ ሥረ ነገር ከመግባቱ በፊት ነው። ይህንንም የሚያደርገው ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና 231/1/ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ዋነኛው ጉዳይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች አግባብ የክስ መዝገብ ሲዘጋ ወይም ክስ አይስተናገድም ሲባል ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ሥረ ነገር ላይ ጭብጥ ይዞ በማከራከር ያልወሰነ መሆኑን ነው። ይህ ሁኔታ ከያዝነው ጉዳይ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው በአመልካች እና በተጠሪ ባለቤት መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ይፈርሳል ወይስ አይፈርስም? የሚለው ነጥብ የክሱ ሥረ ነገር ጭብጥ ነው። ይህ የሥረ ነገር ጭብጥ በየትኛውም ደረጃ በተደረገው ክርክር ተይዞ በተከራካሪዎች መካከል ንጥጥር አልተደረገበትም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም ምንም የተደረገ ውል የለም የሚለው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት መደምደሚያ የሕግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለፀው የቤት ሽያጭ ውል ስለመኖሩ አላከራከረም፡፡ ለዚህም ነው ተጠሪ የውል ይፍረስልኝ ክስ የመሠረተችው፡፡ "የግዴታዎች መቅረት "በሚለው በፍትሐብሔር ሕጉ አራተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 12 በምዕራፍ 3 ሥር" ውሎችን ስለመሰረዝና ስለማፍረስ" የሚል ክፍል አለ፡፡ በዚህ ክፍል ሥር ከተቀመጡት ድንጋጌዎች አንዱ በሆነው በቁ.1808/2/ እንደተመለከተው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከሕግ ውጭ ነው ወይም ለሕሊና ተቃራኒ ነው ወይም ለውሉ አጻጻፍ የተደነገገውን ፎርም አልጠበቀም የሚል መከራከሪያ /ምክንያት/ ያለው ተዋዋይ ወይም ማንኛውም ጥቅም ያለው ሰው ውሉ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ ውሉ መፍረስ አለበት የሚል እምነት ስላላት የውል ይፍረስ ክስ መስርታለች፡፡ ውሉ የሚፈርስበት የሕግና የፍሬ ነገር ምክንያት አለ ወይስ የለም የሚለው የሥረ ነገር ክርክር በዝርዝር የሚታየው ክሱ በቀረበለት ፍ/ቤት እንደሆነም ግልጽ ነው፡፡ በእርግጥም ውሉ የሕጉን ፎርም አልጠበቀም የሚል ክርክር የሚነሳ ቢሆን የሚታየው ከፍ ሲል ከጠቀስነው ድንጋጌ አንፃር ነው፡፡ በዚህ አግባብ ውሉ ፈራሽ ነው ካልተባለ ደግሞ ተጠሪ በቀጥታ ቤቱን ትረከብ ዘንድ መወሰን የሚቻልበት አካሄድ የለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ቤቱ ተሸጦአል መባሉን በመቋወም ክስ እስከ መሠረተች ድረስ ክርክሩ እስከመጨረሻው ድረስ ተኪዶ ሳይታይ ከወዲሁ ልትሰናበት አይገባም፡፡ ነገሩን አጠቃለን ስንመለከተው የሥር ፍ/ቤቶች ወደ ድምዳሜ የደረሱት ክርክሩ መመራት ባለበት አግባብ ሳይመሩ ተገቢም ጭብጥ ሳይዙ ነው ለማለት ችለናል፡፡ ይህ ደግሞ ከሕጉ አተገባበር አንፃር ሲታይ መሠረታዊ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 01887 መጋቢት 20 ቀን 96ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 31308 ሐምሌ 22 ቀን 2000ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 40132 ጥር 4 ቀን 2001ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በቅድሚያ ለተጠሪ የክስ መነሻ የሆነው ውል ይፈርሳል ወይስ አይፈርስም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ፤ ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡትን የሕግና የፍሬ ነገር ክርክር ከሰማ በኋላ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 13 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሰሚር ሱሩር - ጠበቃ በፀሎት መኮንን ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ስንዱ ዱባለ - አልቀረቡም

2. አቶ መርሀፅድቅ ድጋፌ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በአዲስ አበባ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/08 በቤት ቁጥር 441 በንግድ ፈቃድ ቁጥር 03/01/3/00/69/95 የሚያካሂዱትን የንግድ ድርጅት በብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ተጠሪዎች ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የውል ስነድ ሽጠውልኛል ተጠሪዎች ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) በቼክ ተቀብለው ወስደዋል፡፡ ቀሪውን ብር 160,000(መቶ ስልሳ ሺህ ብር) የንግድ ድርጅቱን ሽያጭ በውልና ማስረጃ ፈርመውና ባለሀብትነቱን ተጠሪዎች ሲያስተላልፉ ሊከፈላቸው ተስማምተናል፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች (ተከሳሽ) በውሉ መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ሣይሆኑ በመቅረታቸው ተከሳሾች (ተጠሪዎች) የሸጡት ድርጅት ከዕዳና ዕገዳ ነፃ አድርገውና ማናቸውም አስፈላጊ ፎርማሊቲ አጠናቀው እንዲያስረክቡና መቀጫውንም እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው ከሳሽ (አመልካች) በውሉ ላይ አልፈረሙም ውሉም ሲደረግ አልነበሩም፡፡ የቅድሚያ ክፍያው በወቅቱ አልተፈፀመም፡፡ ውሉ በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡ ከሳሽ የበኩላቸውን ግዴታ እንዲወጡ በደብዳቤ ተጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ውሉ መፍረሡን አሣውቀናቸዋል፡፡ ከሳሽ ውሉን በግድ የማሣወቅ ሀሳብ ያላቸው መሆኑን አስቀድመው ያላሣወቁን በመሆኑ ውሉ በግዴታ ይፈፀምልኝ በማለት ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አመልካች በውሉ ላይ በወኪላቸው በአቶ ሰብሀ ሱሩር አማካኝነት የፈረሙ ስለሆነ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ውል አለ፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዕፈው የሰጧቸውን ቼክ ባንክ ወስደው መንዝረዋል፡፡ ስለዚህ የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውል ተዋዋዮች ስምምነታቸውን የሰጡበት ውል ነው፡፡ ውሉ በዕሑፍ የተደረገ ስለሆነ በህጉ የተቀመጠውን ፎርም ያሟላ ነው፡፡ ሆኖም ከሳሽ አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2331 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ውሉ በግዴታ እንዲፈፀምለት የሚያስገድድ ስለመሆኑ ለሻጭዎች (ተጠሪዎች) ያልገለፀ በመሆኑና ውሉ የተለየ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን ያላስረዳ በመሆኑ የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውሉ እንዲፈፀምለት ከሳሽ (አመልካች) የመጠየቅ መብት የለውም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የህግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች መጋቢት 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች የንግድ ድርጅቱን የሚያስረክቡት እስከ ህዳር 28 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ነው፣ የአመልካች ወኪል ተጠሪዎች ገንዘቡን ተቀብለው የንግድ ድርጅቱን እንዲያስረክቡ በምስክሮች ፊት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ውሉን አፍርሠናል በማለት ደብዳቤ የፃፉት መጀመሪያም ያሰቡበት ጉዳይ ነው፡፡ የውሉ መፈፀሚያ የጊዜ ገደብ ስለሚታወቅ ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ አልነበረም፡፡ የተከፈለው ብር 40,000 አላግባብ በዝምታ ታልፏል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሉን በግዴታ ለመፈፀም ለመጠየቅ አመልካች አይችልም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በቃል ባቀረቡት ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ውሉ በግዴታ ለመፈፀም ልዩ ጥቅምና ፍላጎት ያላቸው መሆኑን አለማስረዳታቸውንና ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም ለመጠየቅ የሰጡት ማስጠንቀቂያ አለመኖሩን በማረጋገጥ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በቃል የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የዕሑፍና የቃል ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውል በግድ እንዲፈፀም አመልካች ለመጠየቅ አይችሉም በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ውሉ በግዴታ አይፈፀምም ቢባል አመልካች ለተጠሪዎች የከፈሉት ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) በተመለከተ ውሣኔ ሣይሰጡ ማለፋቸው ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች መፈታት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመፍታት የሽያጭ ውልን በግዴታ ስለመፈፀም የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና አላማ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመርህ ደረጃ ገዥ ሻጭ የሽያጭ ውሉን በግድ እንዲፈፅምለት ለመጠየቅ የሚችለው ውሉ ልዩ የሆነ ጥቅም የሚያስገኝለት ሆኖ ሲታየው እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2329 ይደነግጋል፡፡ ገዥው በሽያጭ ውሉ ላይ ልዩ ጥቅም አለው የሚባለውና የሽያጭ ውሉን ሻጭ በፍርድ ሀይል ተገድዶ እንዲፈፅም ፍርድ ቤቶች ለመወሰን የሚችሉት የሽያጭ ስምምነት የተደረገበት ዕቃ በልማድ ምትክ ሊገዛበት የማይቻል የሆነ እንደሆነ ወይም የተባለውን ምትክ ለመግዛት ገዥው ላይ ከፍ ያለ ወጭና ችግር የሚያስከትልበት የሆነ እንደሆነ መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2330 ይደነግጋል፡፡ አመልካች የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውሉ ልዩ ጥቅም የሚያስገኝላቸው መሆኑንና የንግድ ድርጅቱ ምትክ ሌላ የንግድ ድርጅት መግዛት የማይችሉ ስለመሆናቸው ወይም ሌላ የንግድ ድርጅት ለመግዛት ቢሞክሩ ከፍተኛ ወጭና ችግር የሚያስከትልባቸው ስለመሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት በክሳቸው እንዳልገለፁ ማስረጃ በማቅረብም እንዳላስረዱ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ አረጋግጧል። አመልካች የሽያጭ ውሉ በግድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2329 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2330 የተደነገጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን የማስረዳት ግዴታ ያለባቸው ሲሆን አመልካች ይህንን ግዴታቸውን ያልተወጡ መሆኑን በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ውለታን በግድ ስለመፈፀም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1778፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2329 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2330 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም።

ከዚህ በተጨማሪ የንግድ መደብር ሽያጭ ውሉ እስከ ህዳር 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሚፈፀም ስለመሆኑ የአመልካችና ተጠሪዎች ባደረጉት ውል የተገለፀ ቢሆንም የሽያጭ ውሉ በግዴታ እንዲፈፀምለት የሚፈልግ ገዥ ውሉ በግዴታ እንዲፈፀምለት የማስገደድ ሀሳብ ያለው መሆኑን ለሻጭ ካልገለፀ ውሉን በፍርድ ሀይል ተገድዶ ሻጭ እንዲፈፅም ቢደረግ መብቱን እንደሚያጣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2330 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል። አመልካች በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማስጠንቀቂያ ያልሰጠ መሆኑንና ይልቁንም ተጠሪዎች ውሉን አፍርሰናል በማለት ቀድመው ለአመልካች በፅሑፍ ያሣወቁ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል። ከዚህ በተጨማሪ በአመልካችና በተጠሪ ውል ላይ የተገለፀው የጊዜ ገደብ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2331 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን ጥብቅ መሥፈርት የሚያሟላ አይደለም። ይኸም በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውሉ በግዴታ እንዲፈፀምላቸው አመልካች የመጠየቅ መብት የላቸውም በማለት የሰጡት ውሣኔና የደረሱበት መደምደሚያ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል።

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በቼክ ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) ለተጠሪዎች የከፈሉና ሁለተኛው ተጠሪ ቼኩን በገንዘብ መንዝረው ከባንክ የወሰዱ መሆናቸው በሥር ፍርድ ቤት አንስተው አመልካች የተከራከሩበት ሲሆን ተጠሪ ይህንን በመካድ የሰጡት መልስ የለም። ስለሆነም አመልካች ብር 40,000 የከፈሉ መሆኑን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 235 መሠረት ያመኑ መሆኑን ግራቀኙ ካደረጉት ክርክር ለመገንዘብ ችለናል። የሽያጭ ውሉ በግዴታ ሊፈፀም አይገባውም ከተባለ ተከራካሪዎች ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ማድረግና ለውሉ አለመፈፀም ኃላፊ የሆነው ተዋዋይ ሌላኛው ተዋዋይ ወገን የደረሰበትን ኪሣራ የመተካት ኃላፊነት እንደሚኖርበት ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1815 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1790 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል።

አመልካች ውሉ በግዴታ የማይፈፀም ከሆነ በአማራጭ ውሉ ባለመፈፀሙ የደረሰበትን የኪሣራ መጠን በመግለፅ ተጠሪዎች ኪሣራ እንዲከፍሉት የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የለም። በዚህ በኩል አመልካች ያልጠየቁት ዳኝነት በመሆኑ በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ ተጠሪዎች የሚከፍሉት ካሣ የለም። ሆኖም ተጠሪዎች ከአመልካች በቼክ ተቀብለው የወሰዱትን ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) ለአመልካች የመመለስ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1815 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ የተደነገገ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ከአመልካች የወሰዱትን ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍሉ አለመወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም ይህንን የውሣኔ ክፍል ብቻ በማሻሻል ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታና ሀላፊነት አለባቸው በማለት ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውሉን በግዴታ እንዲፈፅሙ አይገደዱም በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) ይክፈሉ በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59882

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አሰገደች ዘርጋው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አየለ ንዳኔ ጠበቃ አቶ ዘነበ አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር ማመልከቻ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ ተከሳሽ /አመልካች/ መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል ስምምነት ብር 105,000 /አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ ወስደዋል፡፡ ተከሳሽ /አመልካች/ የተበደሩትን ገንዘብ እስከ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ሊከፍሉ በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልከፈሉ ቅጣት ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ ጨምረው ሊከፍሉ ተስማምተዋል፡፡ ተከሳሽ የብድር ገንዘቡን በውሉ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ያልከፈሉ በመሆኑ ብር 135,000 /አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ብር/ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀረበው ከከሳሽ /ተጠሪ/ ጋር የብድር ውል ያደረግሁ መሆኑ አይካድም፡፡ ሆኖም ከሳሽ /ተጠሪ/ ውሉን ካስፈረሙኝ በኃላ የውሉን ኮፒ ላምጣ ብሉው ገንዘቡን ሣይሰጡኝ በመሰወራቸው ጉዳዩን በሽምግልና ስከታተል ቆይቼ አሁን በወንጀል ከስሽ መያዣ ወጥቶባቸዋል፡፡ ስለሆነም ከሳሽ /ተጠሪ/ የብድር ውሉ ገንዘቡን ተቀብያለሁ ብዬ ከፈረምኩ በኃላ ገንዘቡን ሣይሰጠኝ የተሰወረ በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ተደርጎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተከሳሽ /አመልካች/ ብር 105,000 በብድር ከከሳሽ /ተጠሪ/ የወሰዱ መሆኑን በመግለፅ መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገው የብድር ውል ላይ ፈርመዋል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ /አመልካች/ በውል ወስጃለሁ ብለው በፅሑፍ ያረጋገጡትን ገንዘብ ተጠሪ /ከሳሽ/ ያልሰጠኝ መሆኑን በሰው ምስክር ላስተባብል በማለት ያቀረቡት ክርክር የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2005/1/ እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2006 ድንጋጌዎችን የሚቃረን በመሆኑ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ውሉ በተንኮል የተደረገ አይደለም ውሉ ለሞራልና ለህግ ተቃራኒ አይደለም፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ /አመልካች/ የተበደሩትን ብር 105,000 በውሉ የተስማሙትን የቅጣት ገንዘብ ብር 30,000 በድምሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

135,000 /አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ብር/ ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይከፈሉ በማለት ወሰኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል አመልካች ነሐሴ 17 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በእኔና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል በተንኮል ላይ የተመሠረተና ተጠሪ ግዴታቸውን ያልተወጡበት ውል ነው፡፡ በውሉ የተገለፀውን ገንዘብ ያልሰጡኝ መሆኑን በምስክሮች ለማስረዳት ያቀረብኩት ጥያቄ የበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1704 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009/1/ን ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካችና እኔ ያደረግነው የብድር ውል ገንዘቡን መውሰዳቸውን ያረጋግጣል፡፡ አመልካች ተዋዋይ እንጅ ሶስተኛ ወገን ባለመሆናቸው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009 በጉዳዩ አግባብነት የለውም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የፍታብሔር ህግ አንቀፅ 2005 እና አንቀፅ 2006ን መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ህዳር 29 ቀን 2003 ዓ.ም በፅሑፍ ባቀረቡት መልስ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ታህሣሥ 14 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ተጠሪ ውሉ መፈረሙን እንጂ ውሉ መፈፀሙን አላስረዳም፡፡ እኔ ውሉ ከተፈረመ በኃላ የብድር ገንዘቡን ያለሰጠኝ መሆኑን በማስረጃ ለማስተባበል ያቀረብኩት ጥያቄ አላግባብ ተከልክያለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ብር 105,000 /አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ የብድር ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም; የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ብር 30,000/ሰላሣ ሺህ ብር/ እና ወለድ ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚሉት ጭብጦች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ከተጠሪ ብር 105,000/አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ በብድር ከተጠሪ ተቀብለው የወሰዱ መሆኑን አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት የብድር ውል አረጋግጠው ፈርመዋል፡፡ አመልካች ውሉ በተንኮል የተደረገ ነው፡፡ ተጠሪ ከፈረምኩለት በኃላ በውሉ ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ አልሰጠኝም፡፡ ውሉ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ ፈራሽ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች ከተጠሪ በውሉ የተገለፀውን ገንዘብ ለመበደር ወደውና ፈቅደው የብድር ውል ስምምነት ያደረጉ መሆኑንና በብድር ውሉ ላይ የፈረሙ መሆኑ በአመልካች የተካደ ፍሬ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህ የምንረዳው አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የብድር ውል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1698 በተደነገገው መሠረት መሠረታዊ ስህተት የሌለበት በመሆኑና ውሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1704 በሚደነግገው መሠረት በተንኮል የተደረገ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ያልቀረበበት በመሆኑ አመልካች ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የአመልካች ክርክር በባህሪው የብድር ውል ስምምነት ሲደረግ ውሉ ጉድለት አለበት የሚል ሣይሆን ተጠሪ በብድር ውሉ መሠረት የብድር ገንዘቡን አልሰጠኝም በውሉ የተገለፀውን ግዴታውን አልተወጣም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች የብድር ገንዘቡን የተቀበሉ መሆኑን በነፃ ፈቃዳቸው አንብበው ተስማምተው በፊርማቸው ያረጋገጡ መሆኑን መጋቢት 19 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2000 የተደረገው የብድር ውል አስረጅ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ገንዘብን አልተቀበልኩም በማለት የሚያቀረቡት ክርክር ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ያደረጉት ውል አመልካች በውሉ ሰነድ የተገለፀውን ገንዘብ ከተጠሪ ተቀብለው የወሰዱ ስለመሆኑ ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ መስረጃ እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2005 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ በመሆኑና አመልካች በብድር ውሉ ላይ ከተጠሪ ገንዘብ የተቀበሉ መሆኑን የሚገልፀውን ህግ በሰው ምስክር ወይም በህሊና ግምት ማስረጃ በማቅረብ ለማስተባበል እንደማይፈቅድላቸው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2006 ንዑስ አንቀፅ 2 አስገዳጅ ድንጋጌ የተደረገገ በመሆኑ አመልካች ገንዘቡን ያልተቀበልኩ መሆኑን በምስክር እንዳላስረዳ የበታች ፍርድ ቤቶች አላግባብ ከለከሉኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የህግ መሠረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች በብድር ውሉ ገንዘብ እንደተቀበሉ የሚገልፀውን ሀይለ ቃል ለመቃወም የሚችሉት ተጠሪ ቃለ መሀላ እንዲፈፅም በመጠየቅ እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2006 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ተጠሪ ቃለ መሀላ እንዲፈፅምላቸው ያቀረቡት ክርክር ያሌለ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ አመልካች የተበደሩትን ብር 105,000 /መቶ አምስት ሺህ ብር / ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ ከላይ የተገለፁትን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካችን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በብድር የወሰዱትን ገንዘብ እስከ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ለመመለስ የብድር ገንዘቡን እስከ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ካልመለሱ መቀጫ ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ ብር/ ለተጠሪ ለመክፈል ተስማምተዋል፡፡ አንደኛው ወገን ግዴታውን ያልፈፀመ ወይም አጉድሎ ወይም አዘግይቶ የፈፀመ እንደሆነ የሚከፍለውን መቀጮ ተዋዋዬቹ አስቀድመው በውላቸው ለመወሰን እንደሚችሉ በመሠረታዊ መርህነት በፍታሔር ህግ ቁጥር 1889 ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ከዚህ ጠቅላላ መርህ የሚገድቡ በልዩ ሁኔታ የተደገነጉ ድንጋጌዎች ተዋዋዬች የሚያደርጉትን የመቀጫ ስምምነት መጠን የሚገደቡና የሚከለክሉ በሆነ ጊዜ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1889 ድንጋጌ ተጠቃሽና ተፈፃሚ የሚሆንበት ምክንያት የሌለ መሆኑን ተቀባይነት ካለው የህግ ድንጋጌዎች አተረጓጎም ለመረዳት ይቻላል፡፡ የብድር ገንዘብ አመላለሱን አስመልክቶ ተበዳሪው የብድር ገንዘቡን በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ከመክፈል የዘገየ እንደሆነ ለአበዳሪው በኪሣራ መልክ የሚከፍለው በፍታብሔር ህጉ በተደነገገው መሠረት የወለድ ገንዘብ እንደሆነ በፍታብሐር ህግ ቁጥር 2489 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ ሲሆን በህግ ከተፈቀደው የወለድ መጠን በላይ ተበዳሪው መቀጫ እንዲከፈል የሚደረግ ስምምነት ፈራሽ እንዲሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2489 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች በተጠሪ በብድር የወሰዱትን ገንዘብ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ካልመለሱ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ ለተጠሪ ለመክፈል ያደረጉት ስምምነት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2489 ንዑስ አንቀፅ 2 አስገዳጅ ድንጋጌን የሚጥስና ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በመቀጫ መልክ በተጠሪ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ ለመክፈል ያደረጉት ስምምነት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1889 ከተደነገገው ጠቅላላ መርህ በተለየ ሁኔታ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2489 ንዑስ አንቀፅ 2 ክልከላ የተደረገበት መሆኑን ሣያገናዝቡ የሰጡትና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ አመልካች በብድር ውሉ መሠረት ገንዘቡን በወቅቱ ባለመመለሳቸው መቀጫ ለተጠሪ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ እንዲከፍሉ በወሰኑት የበታች ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች በተደራቢነት አመልካች የዋናውን ብድርና የመቀጫ ገንዘቡ ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ መሠረት የሌለውና የአመልካችና የተጠሪን የብድር ውል ስምምነት መሠረታዊ ይዘትና የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ብር 105,000 /አንድ መቶ አምስት ሺህ ብር/ የሆነውን የብድር ገንዘብ ብድሩ መመለስ ካለበት ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ ሆኖም አመልካች ለተጠሪ መቀጫ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2489 ንዑስ አንቀፅ 2 አስገዳጅ ድንጋጌን የሚጥስና መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌን በመጥቀስ በብድር ውሉ ላይ ገንዘብ ተቀብያለሁ በሚል አገላለፅ የተፃፈው ቃል ሀሰተኛ መሆኑን በምስክር ለማስተባበል ያቀረቡት ጥያቄ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009 ንዑስ አንቀፅ 1 ይዘትና ተፈፃሚነት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በውል ሰነድ የተፃፈን ቃል ሀሰተኛ መሆኑን በማናቸውም አይነት ማስረጃ ለማስተባበል ሰነዱን የፃፈው ወይም የተቀበለው የመንግስት መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን አለመሆኑን በውሉ ላይ የተፃፈውን ቃል ለማስተባበል ጥያቄ ያቀረበው ሰው የውሉ ተዋዋይ ሣይሆን ሶስተኛ ወገን ተከራካሪ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ በግልፅ ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳዩ የአመልካችና የተጠሪ ውል በመንግስት መሥሪያ ቤት ባለስልጣን የፃፈው ወይም የተቀበለው ሰነድ አለመሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በውሉ ውስጥ ያለውን ቃል ሀሰተኛነት ለማስተባበል የጠየቁት አመልካች የብድር ውሉ ተዋዋይ ወገን እንጂ ሶስተኛ ወገን ተከራካሪ አይደሉም፡፡ ስለሆነም አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2009 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ የውሉን ቃል ሀሰተኛነት በምስክር ለማስረዳት ያቀረቡት ጥያቄ የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤት ብር 30,000 /ሠላሣ ሺህ ብር/ መቀጮና ለዚህ የመቀጮ ገንዘብ ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሰጡት የውሣኔ ክፍል ብቻ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ሊሻሻል የሚገባው ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ብር 105,000 /መቶ አምስት ሺህ ብር/ ከሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለተጠሪ ይክፈሉ በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች የመቀጫ ገንዘብ ብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ እና ይህ የመቀጫ ገንዘብ የሚወልደውን ወለድ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታና ኃላፊነት የለባቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የሐረሪ ክልል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ ፡- ቦና አህመድ አሚን - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ እድሜአቸው አስራ ሦስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ ሕዳር 07 ቀን 2000 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 4፡00 ስዓት በሚሆንበት ጊዜ በሐረሪ ክልል በቀበሌ 19 ልዩ ስሙ ንደ ጎቤ ተብሎ በሚጠራ ስፍራ የግል ተበዳይ የሆነችውን የ15 ዓመት ሕፃን ዘሙ አህመድን በመኖሪያ ቤት ውስጥ በር ዘግቶባት መብራት አጥፋቶ አፏንና አፍንጫዋን በማፈን እንዳትጮህ በማድረግ ለመከላከል በማትችልበት ሁኔታ ውስጥ ካደረገ በሁዋላ አስገድዶ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈፀሙ በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620 ስር የተመለከተውን ተላልፏል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በሁዋላ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ገልጾ ስለድርጊቱ አፈፃፀም ግን የክህደት ቃል ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አቃቤ ሕግ እንደክሱ ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅረቦ ከአሰማ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመው በኃይል ተግባር ሳይሆን በግል ተበዳይ መልካም ፈቃድ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ተጠሪን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 መሠረት በነፃ አሰናብቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በሁዋላ ተጠሪ የግል ተበዳይ ላይ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀማቸው በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች መረጋገጡን እንደስር ፍርድ ቤት አባባል ተቀብሎ ድርጊቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕግ አንቀጽ 620 ስር የሚሸፈን መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ ተጠሪ እድሜው 16 አመት የግል ተበዳይ ደግሞ እድሜዋ 15 አመት መሆኗንና እንደዚህ አይነት ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ ምን መሆን እንዳለበት የወንጀል ሕጉ ምንም የሚሰጠው ምላሽ የሌለ መሆኑ በመጥቀስ እና በማመሳሰል ደግሞ ተጠያቂነትን ማስከተል እንደማይቻል ሕጉ በአንቀጽ 2(3) ስር ያስቀመጠው መርህ መሆኑን በዋቢነትይዞ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪን በነፃ በማሰናበት የሠጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ ተገቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን በመቀበል አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ነው፡፡

አመልካች አቃቤ ሕግ ሚያዝያ 28 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ሦስት ገጽ የሰበር አቤተታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2(3)፣ 56፣211 እና 626ን እንዲሁም የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር 113(2) ድንጋጌዎችን መንፈስና ይዘት ያላገናዘበ መሆኑን በመዘርዘር ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 626(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መተላለፉ ተረጋግጧል ተብሎ እንዲከላከል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጉለት ቀርቦ መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም በጠበቃው አመካኝነት በተጻፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪው የወንጀል ተጠያቂነት የሚከተልበት አይደለም ተብሎ ከክሱ ነፃ መባሉ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ እድሜዋ አስራ አምስት አመት ከሆናት ሕፃን ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀሙ መረጋገጡን ሁለቱም የስር ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ የተጠሪ ጠበቃ በዚህ ችሎት ባቀረቡት የፁሑፍ መልስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ መሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም ይህ ችሎት በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ለመመልከት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት ስልጣን የሌለው በመሆኑ የተጠሪ ጠበቃ ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ተጠሪ ከግል ተበዳይ ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈፀመ በተባለበት ጊዜ እድሜው አስራ ስድስት አመት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከወንጀሉ ነፃ ነው የተባለውም የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 626(1) የግል ተበዳይና የድርጊቱ ፈፃሚ እድሜው በአስራ ሶስት አመትና በአስራ ስምንት አመት ክልል ውስጥ ከሆኑ ሕጉ ምላሽ አይሰጥም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የድንጋጌው አቀራረጽ ሲታይ ማንም ሰው ተቃራኒ ጾታ ካላትና እድሜዋ ከአስራ ሦስት ዓመት በላይ ሆኖ አስራ ስምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ይህችው ልጅ እንዲህ አይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንድትፈጽም ያደረገ እንደሆነ በሚል የተቀመጠ ሲሆን “ማንም ሰው....የሚለው የሕጉ አገላለጽ የወንጀል ሐላፊነትን በተመለከተ የተደነገጉትን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችን ማለትም ከአንቀጽ 48 እስከ 56 ድረስ የተመለከቱትን ግንዛቤ ውሰጥ ባስገባ መልኩ መታየት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 56 ድንጋጌ በተለይም ሲታይም እድሜአቸው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ ከ18 ዓመት በታች ያሉ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች ከተጠያቂነት የሚድኑ አለመሆኑን የሚያሳይ ሆኖ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እድሜው ሲታይ ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የሚሆንበት ህጋዊ ምክንያት የለም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 626(1) ስር የተቀመጠው ድንጋጌ ትኩረት የሚያደርገው የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ወይም እንድትፈጽም ማድረግ የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ አስራ ሶስት አመት በሆናትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስራ ስምንት አመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረገ ወንድ እድሜው በዚሁ የእድሜ ክልል መገኘት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 211(1) መሠረት ታይቶ የግል ተበዳይን ተጠያቂነት ከማያመጣ በስተቀር ተጠሪን ከወንጀሉ ነፃ የሚያደርገው አይደለም፡፡ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙ ወንድና ሴት እድሜያቸው በአስራ ሶስት አመትና በአስራ ስምንት አመት መካከል መገኘት ሁለቱንም የወንጀል ተጠያቂነት ያስቀርላቸዋል ብሎ መደምደም የሕጉ አላማ አይደለም፡፡ በዚህ እድሜ መካከል ያሉት ሕፃናት ተገቢ ላልሆነ ድርጊት እንዳይጋለጡ መከላከል የሕጉ አላማ ነው ተብሎም ይታመናል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2(3)ን የጠቀሰው ያለቦታው ሆኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ እድሜዋ አሥራ አምስት አመት ከሆናት ሕፃን ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀሙ ተረጋጋጧል ከተባለና ድርጊቱ በአቃቤ ሕጉ የክስ ማመልከቻ ስር ከተጠቀሰው ድንጋጌ ያነሰ ሁኖ ከተገኘ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113(2) መሠረት ተጠሪ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 56 እና 626(1) ድንጋጌ አንጻር እንዲከላከል መደረግ ነበረበት፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪን ሳይከላከል የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም በማለት የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 56፣211 እና 626(1) ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም የወንጀል ሕጉን ዓላማ ያላገናዘበ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ሀ) መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በ1996ቱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 626(1) ስር በተመለከተው ሁኔታ ድርጊቱን መፈጸሙን አቃቤ ሕጉ ያስረዳ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ መከላከያ ካለው እንዲያቀርብ አድርጉና ማስረጃዎቹን ሰምቶ ተገቢውን እንዲወሰን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ሀ) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- አቶ ኢምራን ጉደሣ አብዲ ጠበቃ ገዛኸኝ ፍቅሬ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ነጥቦች የፌዴራል ዐ/ሕግ በአመልካች ላይ ያቀረባቸው ሁለት የወንጀል ክሶች ናቸው፡፡ ዐቃቤሕግ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2) የተመለከተውን በመተላለፍ ሴቶችን ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል ህጋዊ ፈቃድ ሣይኖረው ሰኔ 22 ቀን 2001 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03/02 ክልል ውስጥ ወ/ሮ መቅደስ ንጉሴን ኩዌት ከሚባል ሀገር በሠራተኝነት እልክሻለሁ ብሎ ብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ ተቀብሎ ልኳት በሣምንት አንድ ቀን ጽዳት ትሠሪያለሽ ተብላ ከተቀጠረች በኋላ ሥራው በጣም ስለከበዳት ወደ አገሯ ለመመለስ ስትጠይቅ ሁለት ወር ከአስር ቀን የነፃነት መብቷ በአንድ ክፍል ውስጥ በመገደብ ሰብዓዊ ክብር አጥታ ለከፍተኛ እንግልት የተዳረገች በመሆኗ ዜጐችን ያለ ፈቃድ ወደ ውጭ የመላክ ወንጀል ፈጽሟል፡፡

እንደዚሁም በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ ከነበረው ሰው ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)ሀ እና አንቀጽ 692(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ከከፈተው ጽ/ቤቱ ውስጥ እነ ሀያት መሐመድ የተባሉትን አስራ ሁለት የግል ተበዳዮች ብር 6000 እስከ 6500 ብር ኩዌት ዱባይና ሣውዲአርቢያ እልካችዋለሁ በማለት ሀሰተኛውን ነገር እውነት አስመስለው ገንዘብ ተቀብለው የወሰዱና የግል ተበዳዮችን ያልላካቸው በመሆኑ የማታለል ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቀርቧል፡፡

አመልካች የተለያዩ የክስ መቃወሚያዎችን አቅርቦ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገበት ሲሆን በሁለቱም ክሶች ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንደኛውን ክስ ለማስረዳት የግል ተበዳይን ለምስክርነት አስቀርቦ ያስመሰከረ ሲሆን በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ በመቀበል አመልካችን ወደ ኩዌት አገር እንደላካትና እና አመልካች ከነገሯት በላይ የከበደ ሥር እንድትሰራ ስለተደረገች ይህንኑ ለአመልካች መናገሯን በኋላም መሐመድ ሩዜን የሚባል ኤጀንሲ 475 ዶላር ደመወዟን ቀምቶ ሁለት ወር ከአስር ቀን በአንድ ክፍል እንድትቆይ እንዳደረጋትና ነፃነቷን እንዲገደባት በመጨረሻ ቡታ ጋር አፈነዳለሁ ብላ ቢላ ይዛ በመጋበዟ ወደ አገሯ አሳፍረው እንደላኳት የመሠከረች ሲሆን ሌሎች ሁለት ምስክሮች የምስክሯን ቃል የሚያጠናክር የምስክርነት ቃል እንደሰጡ ከሥርፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ ሁለተኛውን ክስ ለማስረዳት አስራ አንድ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ መሆኑንና ምስክሮቹም የግል ተበዳዩች እንደሆኑ አመልካችና በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው የማነ ወይም አሚር ገብረማርያም እያንዳንዳቸው ዱባይ ሣውዲአረቢያ ኩዌት እንልካችኋለን በማለት ብር 6000 እስከ 6500 የተቀበላቸው መሆኑን መሥክረዋል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠውብይን መሠረት አንደኛውን ክስ በተመለከተ በህግ በተሰጠኝ ፈቃድ ትኬት ቆርጬ ከመስጠት ውጪ የግል ተበዳይን ወደ ውጭ አልላኩም በሁለተኛው ክስ የተመለከተውን ተግባርም ያልፈፀምኩ ስለመሆኔ ያስረዳልኛል በማለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃቸውን ከመዘነ በኋላ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ሁለት ክሶች የተጠቀሰውን የወንጀል ተግባር አመልካች የፈፀመ መሆኑን በበቂ ማስረጃ አስረድቷል፡፡ የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ ታዓማኒነት የሌለውና የተጠሪን ክስ የሚያስተባብል አይደለም በማለት አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2) እና አንቀጽ 692(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት በአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 17,000 /አሥራ ሰባት ሺህ ብር/ እንዲቀጣ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለበት ነው በማለት ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ አመልካች ሚያዚያ 1 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ላቀረበብኝ አንደኛ የወንጀል ክስ በአስር ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ወስኖብኛል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በወንጀል ህግ ቁጥር 598(2) የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሟል በማለት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተተ አለበት፡፡ ምክንያቱም የግል ተበዳይ በህይወት ወይም በአካሏ ላይ የደረሰባት ጉዳት ያለ ስለመሆኑ በሰጣቸው የምስክርነት ቃል አልገለፀችም አየር በማይገባበትም ቤት ተቆልፊ ነበር ያለችውም ስልክ እየደወለች ዘመዶቿን ታገኝ የነበረ በመሆኑ በህጉ ድንጋጌ የተገለፀውን ፍሬ ጉዳይ ያልተሟላ መሆኑን ያሣያል፡፡ ስለዚህ በወንጀል ህግ አንቀጽ 598(1) ጥፋተኛ መባል ሲገባኝ በፍሬጉዳይ ደረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2) ጥፋተኛ ተብዬ የተጣለብኝ ቅጣት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የግል ተበዳይ ለሰባ ቀናት በውጪ አገር ሰብዓዊ ክብሯ ተጥሶ በአንድ ክፍል ውስጥ ተቆልፎባት የቆየች መሆኑን የመሰከረች በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598(2) የተመለከተው ሁኔታ ተሟልቷል ስለዚህ የአመልካች ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2)ን የተላለፈ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በፍሬ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ ደረጃ አመልካች የተጠሪ አንደኛ ምስክርና የግል ተበዳይ የሆነችው ወ/ሮ መቅደስ ንጉሴ ፈቃድ ሣይኖረው ለቤት ሠራተኛነት ወደ ኩዌት የላከ መሆኑን የግል ተበዳይ ኩዌት ሄዳ ሥራ ከጀመረች በኋላ አሠሪዎቿ ከባድ ሥራ ያለእረፍት እንድትሠራ ያስገደዷት መሆኑን በመጨረሻም ሥራውን ለቅቃ ስትወጣ መሀመድ ሩዜን የሚባል ኤጀንሲ የወር ደመወዟን 475 ዶላር በመውሰድ በቂ አየርና ምግብ ልታገኝ በማትችልበት ሁኔታ ለሁለት ወር ከአስር ቀን ነፃነትና መብቷን በመገደብ በአንድ ክፍል ውስጥ እንድትቀመጥ አስገድዷት መሆኑንና በመጨረሻም ከዚህ ክፍል እንድትወጣ የማይፈቀድላት ከሆነ ስሊንደር እንደምታፈነዳ ቢላ ይዛ ስትናገር ወደ አገሯ የላኳት መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬጉዳይ በየትኛው የወንጀል ህግ ድንጋጌ በህላፊነት እንደሚያስጠይቅ ለመወሰን አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ይዘት መመርመር ያስፈልጋል፡፡

እኛም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 598 ድንጋጌዎች መርምረናል፡፡ ማንም ሰው ፈቃድ ሣይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ህግ ወጥ መንገድ ኢትዮጵጳያዊ ዜጋን ለሥራ ወደ ውጪ አገር የላከ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ሊደረስ በሚችል ጽኑ እሥራት እና ከሀያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ እንደሚቀጣ" የወንጀል ህግ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ አንድ ሰው ጥፋተኛነህ ተብሎ የሚቀጣው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተዘረዘሩት የማክበጃ ምክንያት አንደኛው ያልተሟላ ሲሆን መሆኑን ከህጉ ድንጋጌ አንቀጽና ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሆኖም አንድ ሰው ፈቃድ ሣይኖረው ወይም በማናቸውም ህገ ወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገር የላካት ኢትዮጵያዊት ሰብአዊ መብቷ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የደረሰባት እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እስከ ሀያ አመት የሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከሀምሣ ሺ ብር የማይበልጥ መቀጮ እንደሚሆን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ አመልካች የግል ተበዳይዋ በአካሏ ወይም በህይወቷ ላይ የደረሰባት ጉዳት ስለሌለ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 ጥፋተኛ መባሌ የህግ ስህተት አለበት በማለት ይከራከራል፡፡ ሆኖም የወንጀል ህግ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 የተላከችው "ኢትዮጵየዊት የሰብአዊ መብቷ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የደረሰባት እንደሆነ" በሚል መንገድ የተደነገገ ሲሆን አጥፊው በዚህ የህግ ድንጋጌ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ፍርድ የሚሰጠው የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ መደፈር ደርሶባት እንደሆነ ወይም በህይወቷ ላይ ጉዳት የማድረሥ መከራ ተደርጐ እንደሆነ ወይም በህይወቷ ላይ ጉዳት ደርሶባት እንደሆነ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የማድረስ የሙከራ ወንጀል ተፈጽሞባት ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት ደርሶባት እንደሆነ መሆኑን ከህጉ ድንጋጌ ይዘትና አቀራረጽ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 አንድ ሰው በህላፊነት የሚጠይቀው ከላይ ከተዘረዘሩት አንደኛው ወደ ውጭ በላካት ኢትዮጵያዊት ላይ መፈፀሙ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው የግል ተበዳይ የሆነችው አንደኛ የተጠሪ ምስክር መሐመድ ሩዜን በሚባል ኤጀንሲ በአንድ ክፍል ውስጥ ታግታና የነፃነትና የመንቀሣቀሥ መብቷ ተገድቦ ለሰባ ቀናት የቆየች መሆኑና በዚህም ወቅት ከፍተኛ የሆነ የሥነ ልቦናና የአካል መጎሳቆል ጉዳት ደርሶባት የነበረ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የግል ተበዳይ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የማድረስ ሙከራ ያልተፈፀመባት ወይም ጉዳት ያልደረሰባት ቢሆንም በነፃነት የመንቀሣቀሥና ወደ አገር የመመለስ መብቷ በአንድ የንግድ ድርጅት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሰባ ቀናት ያህል ተገድቦ በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ እንድትቆይ የተገደደችና ሰብአዊ መብቷ የተጣሰ መሆኑ ስለተረጋገጠ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ተጠሪ ባቀረበው አንደኛ ክስ የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 598 ንዑስ አንቀጽ 2 በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጡት ፍርድና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2(-2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ፍርድ የፀና መሆኑን በማወቅ ተከታትሎ እንዲየስፈጽም ለማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - ግርማ ወልደማሪያም ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እየሩሣሌም ወንዴ ጠበቃ አቶ የሺጥላ አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተከሣሽ ተጠሪ ከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ ከአሜሪካን አገር ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ 12,500 የአሜሪካን ዶላር ይዘው የመጡ መሆኑን በደኅራላሪስዮን ቁጥር ሲ-5-7119 ሐምሌ 29 ቀን 1999 ዓ.ም እንዳስመዘገቡ ገልፀው ጥቅምት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ወደዱባይ ሊሄዱ ሲሉ 2500 የአሜሪካን ዶላር ብቻ የመለሱልኝ ሲሆን 10,000 የአሜሪካን ዶላር አስቀርተዋል፡፡ ስለዚህ ዶላሩን በአይነቱ ወይም በኢትዮጵያ ብር ምንዛሬ እንዲከፍል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች አንድ ኢትዮጵያዊ ከ45 ቀናት በላይ የውጭ ገንዘብ መያዝ አይችልም ለጊዜያዊ ጉብኝት የመጣ ሰው ቢሆንም እንኳን ያመጣውን የውጭ ምንዛሬ ይዞ እንዲወጣ የሚፈቀድለት በአንድ መቶ ሰማኒያ ሶስት ቀናት ውስጥ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ 10,000 የአሜሪካን ዶላር ይዘው እንዳይወጡ መከልከሉ ተገቢ ነው ሆኖም ዶላሩን በኢትዮጵያ ብር መንዝሮ የማይከፍልበት ምክንያት የለም በማለት 10,000 የአሜሪካን ዶላር የካቲት 18 ቀን 2001 ዓ.ም በነበረው የምንዛሬ ተመን መሠረት በኢትዮጵያ ብር መንዝሮ ከየካቲት 18 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች የይግባኝ ቅሬታ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ቦሌ ቅርንጫፍ በላከው መመሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ በጊዜያዊነት ለጉብኝት የመጡ ወይም ለንግድ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ሰዎች ለጊዜው በእጃቸው የያዙትን የውጭ ምንዛሬ ለጉምሩክ አስመዝግበው ማስረጃ ከያዙ ለአንድ መቶ ሰማኒያ ሶስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ይዘውት የመጡትን የውጭ ምንዛሬ ይዘው ለመውጣት ፈቃድ አያስፈልጋቸውም የሚል በመሆኑ የተጠሪ ዶላር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተያዘው በዚህ መመሪያ መሠረት ነው፡፡ ስለዚህ የተያዘው ዶላር በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዲከፈላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው 10,000 ዶላሩን ጉምሩክ በሰጠኝ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ /Temporary Receipt for Deposit/ ቁጥሩ 176828 ገቢ ያደረግሁት በመያዣ ስም መሆኑንና ደረሰኙም ከአንድ መቶ ሰማኒያ ቀን በኋላ እንደማያገለግል ይገልፃል፡፡ ስለዚህ አመልካች በሕጋዊ መንገድ አሣውቀው ያስገቡትን ዶላር እንዳይወጣ ከሚከለክል በስተቀር የሚወርስበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን መመሪያ በመጣስ ዶላሩን ሊያወጡ ሲሉ የተያዘ በመሆኑ የመውረስ ሥልጣን አለን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ተጠሪ ከአሜሪካን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የግል ንብረታቸው የሆነውን 12,500 /አሥራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ/ የአሜሪካን ዶላር አመልካች እንዲያውቀው በዲክራላሲዩን ያስመዘገቡ እና በጊዜያዊ የመያዣ ማስቀመጫ ደረሰኝ 176828 ያስያዙ መሆኑን በግራ ቀኙ ክርክር ተገልፆአል፡፡ ተጠሪ ከአሜሪካን አገር ይዘው የመጡትንና ለአመልካች በግልጽ ያሣወቁትን ዶላር ከመቶ ሰማኒያ ቀን በኋላ ይዘው ለመውጣት የሞከሩ መሆኑንና አመልካች የብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ ያለ ፈቃድ አንድ ሰው ለንግድ ወይም ለጉብኝት ወደ አገር ይዞት የገባውን ዶላር ከመቶ ሰማኒያ ሶስት ቀን በኋላ ይዞ መውጣት የማይፈቀድለት መሆኑን በመግለጽ 10,000 የአሜሪካን ዶላር ተጠሪ ይዘው እንዳይወጡ የከለከለና ዶላሩን የያዘ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ተጠሪ ለመንግሥት አሣውቀው ይዘው የገቡትን 10,000 የአሜሪካን ዶላር ከአንድ ዓመት ከአራት ወር በኋላ ያለ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ይዘው መውጣት እንደማይችሉ በመግለጽ መከልከሉ ተገቢነት ያለው ተግባር ቢሆንም ተጠሪ የውጭ ምንዛሬውን ይዘው የመወጣት መብታቸውን ከሚያጡ በስተቀር ዶላሩ በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዳይሰጣቸውና በሕጋዊ መንገድ ከአገራቸው ይዘውት የመጡትን ገንዘብ እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ የወንጀል ተግባር ያልፈፀሙ በመሆኑ ገንዘቡን በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዲከፈላቸው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኅዳር 15 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

አመልካች፡- 1. አቶ አያሌው ተሠማ
2. አቶ ጌታቸው አጎናፍር
3. ዶ/ር መሐሪ መኮንን

ጠበቆች፡-
1. ታምሩ ወንድምአገኘሁ ቀረቡ፡፡
2. ደሣለኝ ዓለሙ ቀረበ፡፡
3. ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓቃቤ ሕግ

1. እሸቱ ወ/ሰማያት
2. ወንድወሰን ደሣለኝ
3. አውግቸው ክብረት

ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ድርጊት ተፈጽሟል በሚል የቀረበውን ክስ ተከትሎ የተነሣውን የዋስትና ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ በጉዳዩ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሣሽ የሆነው የተጠሪው ባለሥልጣን ዓቃቤ ሕግ በአመልካቾች ላይ ክስ መስርቷል፡፡ በአሁኑ 1ኛ አመልካች ላይ አስራ አንድ ክሶች በሁለተኛ አመልካች ላይ አምስት ክሶች በአራተኛ አመልካች ላይ ስድስት ክሶች መመስረታቸውን የሥር ፍርድ ቤት ብይን ይገልፃል፡፡ አመልካቾች የዋስትና ጥያቄ ያቀረቡት በክሶቹ የተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች የዋስትና መብት የሚያስነፍጉ አይደሉም በማለት ሲሆን ዓቃቤ ሕግ ደግሞ ይህንኑ የአመልካቾችን ጥያቄ የተቃወመው በአመልካቾች ላይ የተመሠረተው ክስ ከአስራ አምስት ዓመታት በላይ ሊያስቀጣ ይችላል፤ አመልካቾች በዋስ ቢለቀቁ ግዴታቸውን አክብረው ፍርድ ቤት አይቀርቡም ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ይችላሉ፤ ምስክሮችን በመግዛት ወይም በማባበል ወይም አስረጂ የሚሆኑበትን ያጠፋ ይሆናል በሚሉ ምክንያቶችና የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 63፣ 67/ሀ/፣ /ለ/ እና /ሐ/ በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ ከዚህም በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ከሁለቱም ወገኖች የቀረበውን ክርክር መርምሮ አመልካቾች የተከሰሱባቸው የወንጀል ክሶች ከባድ ተደራራቢ በመሆናቸው አመልካቾች የዋስትና መብታቸው ቢከበርላቸው ግዴታቸውን ሊያከብሩ ይችላሉ የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እምነት ሊያሳድሩ የሚችሉ አይደሉም የሚል ምክንያት በመስጠትና የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67/ሀ/ን ብቻ በዋቢነት በመጥቀስ የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

እኛም የአመልካቾች ጠበቆች ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም. ጽፈው ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን በጽሁፍ እንዲያደርጉ አድርገናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ሲያደርግ በምክንያትነት የያዛቸው ነጥቦች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67/ሀ/ ሥር የተመለከተውን ነጥብ የማቋቋሚያ ነጥብ መሆን አለመሆናቸውን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የአመልካቾች ጠበቆች እና ዓቃቤ ሕግ ያቀረቡትን የጽሁፍ ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የተጠቀሱባቸው ድንጋጌዎች በራሳቸው ዋስትና የሚከለክሉ አለመሆናቸውን የተቀበሉት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም አመልካቾች ዋስትና ይፈቀድ ዘንድ ክሱን ለሚያየው ፍርድ ቤት ጥያቄ /አቤቱታው/ አቅርበዋል፡፡

በመሠረቱ የዋስትና መብት በሕገ መንግሥት ጥበቃ ከተደረጉለት የተያዙ ሰዎች መሠረታዊ መብቶች አንዱ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6/ ሥር የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው “መሠረታዊ” መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ይኸው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የዋስትና መብት መሠረታዊ የሆነ ሕገ መንግሥታዊ መብት ቢሆንም ፍጹም መብት ሳይሆን በሕጉ አግባብ ሊነፈግ የሚችል ነው፡፡ ስለሆነም የዋስትናው ጥያቄ ተቀባይነት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ላይ ውሣኔ የሚሰጠው ፍርድ ቤት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረገድ አግባብነት ያለውን ልዩ ሕግ መሠረት አድርጎ ጉዳዩን ሊመዝነውና ተገቢውን ውሣኔ ሊሰጥ እንደሚገባ ግልጽ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ያቀረቡት የዋስትና ጥያቄ የተስተናገደው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67 መሠረት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻ ለመቀበል የማይቻልባቸውን ሁኔታዎችን አስቀምጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ ያልተቀበሉት በተጠቀሰው ድንጋጌ ፊደል “ሀ” ሥር የተመለከተውን ሁኔታ በመጥቀስ ነው፡፡ በእርግጥም ድንጋጌው በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች አመልካቾች የሚፈጽሙ የማይመስሉ እንደሆነ ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ እንደሚቻል ያሳያል፡፡ እዚህ ላይ ሊስተዋል የሚገባው ዋናው ጉዳይ ግን ድንጋጌውን በመተግበር ረገድ ፍርድ ቤቱ ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባው የሚገባው ምክንያት ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ለመከልከል ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች በተጠቀሰው ድንጋጌ በግልጽ አልተመለከቱም፡፡ እንዲህ ከሆነ አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም የማይመስል ነው ተብሎ ግምት የሚወሰደው በቂና ሕጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆን ይገባል ተብሎ የሚታመን ሲሆን ምክንያቶች በቂና ሕጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከተለያዩ ከባባዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባሕርይ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ነጥብ ነው ተብሎ የሚታሰብ ነው፡፡ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67 ድንጋጌ አቀራረጽና ይዘት በጠቅላላው ሲታይ ፍርድ ቤት የዋስትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብትን የሚነፍግባቸውን ሁኔታዎች የሚያስገነዝብ ሲሆን ምክንያቶቹን ፍርድ ቤቶች ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር እየተመለከቱ ሊመዘኗቸው የሚገባቸው ናቸው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት በዋስትና ቢወጡ የዋስትናውን ግዴታ አክብረው ይገኛሉ ለማለት የሚቻል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ግምት መሠረቱ በአመልካቾች ላይ የተመሠረቱት የክሶች ብዛትና የወንጀሎች ከባድነትና ሊያስከትሉ የሚችሉት ውጤት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ወንጀሎቹ ከባድና ተደራራቢ መሆናቸውን ለግምቱ መነሻ አድርጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ በእነዚህ ምክንያቶች ላይ በመመስረት ዋስትናውን ነፍጎአል፡፡ ይህን ምክንያት ለግምቱ መነሻ እንዲያደርግ ደግሞ በሕጉ የተከለከለ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ሕጉ ለፍርድ ቤቱ ስልጣን የሰጠው ስለመሆኑ የሚታመን ከሆነ የሥር ፍርድ ቤት ሕጋዊ ምክንያት መሠረት ሳያደርግ ውሣኔ የሰጠ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የተሰጠው ሥልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ ማረም ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19/6/ እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ሕግ 67/ሀ/ መሠረት የሰጡት ውሣኔ ሕጉ የሰጣቸውን ሥልጣን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር በሕጉ አተረጓጎምና አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 91837 ሚያዝያ 19 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 55696 ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. የጸናው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 75/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሊዊዛ ፎርቤታ የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- ዓቃቤ ህግ የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የዋስትና መብት ይከበርልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካችና በሌሎች ሦስት ግለሰቦች ላይ በመሰረተው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ክሱ በፍርድ ቤት መታየት ከቀጠለ በሁዋላም አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ጉዳይ የዋስትና መብት የማይከለክል በመሆኑ የዋስትና መብታቸው ተከብሮላቸው ቆይቷል፡፡ ከዚህ በሁዋላም ዓቃቤ ሕግ የተፈቀደውን የዋስትና መብት ሊያስነሳ የሚችል አዲስ ነገር መገኘቱን ገልጾ ለአመልካች የተከበረላቸው የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 74 መሰረት እንዲነሳ አመልክቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሲመለከት የነበረው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ ለአመልካች የተከበረላቸውን የዋስትና መብት የሚያስነሳ ፍሬ ነገር ተገኝቷል የሚል ምክንያት በመያዝ ቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ በመቀየር የአመልካችንና የሌሎችን ተከሳሾች የዋስትና መብት ነፍጓል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካችና ሌሎች አብሯቸው የተከሰሱና የዋስትና መብት በማክበር የተሰጠው ትዕዛዝ የተነሳባቸው ሰዎች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት በድጋሚ የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሮ የዋስትና መብት ተከብሮላቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ አቃቤ ሕግ አመልካችና ሌሎች አብሯቸው የተከሰሱ ሰዎች የዓቃቤ ህግ ምስክር የሆነውን ሰው ሌላ ሰው ልከው አስፈራርተዋል፣ የዋስትና መብት በማክበር የተሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 74 መሰረት ተነስቶ ጉዳያቸውን ማረሚያ ቤት ሁነው እንዲከታተሉ ሲል ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተስፈራራ የተባለውን የዓቃቤ ህግ ምስክር በችሎት አስቀርቦ በመስማትና ምስክሩ በጉዳዩ ላይ በተከሰሱ ሰዎች መስፈራራቱን መመስከሩን በማረጋገጥ ቀድሞ የአመልካችን የዋስትና መብት በማክበር የሰጠውን ትዕዛዝ በማንሳት ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሁነው እንዲከታተሉ ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ጠበቃ ነሐሴ 20 ቀን 2002 ዓ.ም. በጻፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተስፈራራ የተባለው የአቃቤ ሕግ ምስክር አመልካች በላኩት ሰው የተስፈራራ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የዋስትና መብቱ አዲስ ነገር ተገኝቷል ተብሎ መነሳቱ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ሕዳር 13 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ በመልሱም ላይ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ሥነ-ሥርዓቱን ጠብቆ ያለመሆኑንና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝ በማስረጃ በተረጋገጠ ፍሬ ነገር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ገልፆ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲሆን ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ተስፈራራ የተባለው የዓቃቤ ሕግ ምስክር በዋናው ጉዳይ ላይ የምስክርነት ቃሉን ሰጥቶ ያበቃ መሆኑን በመጨመር የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ሥነ ሥርዓቱን ጨርሶ የቀረበ መሆን ያለመሆኑን ስንመለከተው የአመልካች የዋስትና መብት መጀመሪያ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከተሰጠ በኋላ አዲስ ነገር ተገኝቷል በሚል ምክንያት በአቃቤ ሕግ አቤቱታ አቅራቢነት በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የስር ፍርድ ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 74 ድንጋጌን መሰረት በማድረግ የሰጠውን ትዕዛዝ የተሻረ ቢሆንም አቃቤ ህጉ ለዚሁ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አዲስ ነገር ተገኝቷል በሚል በድጋሚ የአመልካች የዋስትና መብት እንዲነሳ አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ምስክር ሰምቶ በአቃቤ ሕግ በኩል የተገለጸው ፍሬ ጉዳይ በማስረጃ መረጋገጡን በመያዝ የአመልካችን የዋስትና መብት በማክበር የሰጠውን ትዕዛዝ አንስቶታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው በውጤት ደረጃ ሁለቱም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ ተመሳሳይ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ መቅረቡ ሥነ ሥርዓቱን ሳይጠብቅ ነው ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አለተገኘም፡፡

አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት የዋስትና መብት የማይከለከል ሲሆን የዋስትና መብታቸው ከተከበረላቸው በኋላ ሊከለከል የቻለው የዓቃቤ ሕግ ምስክርን በሌላ ሰው አስፈራርተዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ዋስትና የተፈቀደለት ሰው በዋስ ከወጣ በኋላ አዲስ ነገር ከተገኘ ፍርድ ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በስልጣኑ ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት በዋስትና ወረቀት የተለቀቀው ሰው የተለቀቀበትን ሁኔታዎች (ግዴታዎች) እንደገና ተመልክቶ የተለቀቀው ሰው አዲስ ዋሶችን እንዲያመጣ ወይም በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ለማዘዝ የሚቻል ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 74 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ የአመልካችን የዋስትና መብት በማክበር የተሰጠው ትእዛዝ በስር ፍርድ ቤት እንደገና የታየውም በአቃቤ ሕግ ምስክር ላይ የማስፈራራት ተግባር ፈፅመዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ምስክሩ የተስፈራራ ስለመሆኑ ደግሞ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ በዚህ ረገድ የአመልካች ጠበቃ አጥብቀው የሚከራከሩት ምስክሩ በአመልካች በቀጥታ ወይም አመልካች ራሳቸው በላኩት ሰው ስለመስፈራራቱ አልተረጋገጠም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው የአመልካች ጠበቃ ክርክር የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን ፍሬ ነገርን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ባለመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የአመልካች ጠበቃ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በዚህም መሰረት የአቃቤ ሕግ ምስክር መስፈራራቱ ከተረጋገጠ ምክንያቱ እንደአዲስ ነገር መገኘት የሚታይ ሲሆን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 67(ለ) እና (ሐ) ድንጋጌዎች መንፈስ ጋር ተዳምሮ ሲታይ ለአመልካች የተከበረውን የዋስትና መብት እንደገና ለማንሳት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡

ሌላው የአመልካች ጠበቃ በዚህ ችሎት በመልስ መልሳቸው ላይ ያነሱት ክርክር ተስፈራራ የተባለው ምስክር በጉዳዩ ላይ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተው ጉዳዩ አብቅቷል የሚለው ሲሆን ይህ ነጥብ በዚህ ችሎት የተነሳ አዲስ ነጥብ ሲሆን ችሎቱ መመርመር ያለበት የስር ፍርድ ቤቶችን የውሳኔ ግልባጭ መሰረት በማድረግ በሕግ አተረጓጎም ወይም አተገባበር ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት የሚያስችል የክርክር ነጥብ አይደለም፡፡ የአመልካች ጠበቃ ተስፈራራ የተባለው ምስክር በጉዳዩ ላይ መስክሮ ጉዳዩ አብቅቷል የሚሉ ከሆነም አዲስ ነገር መገኘቱን መሰረት በማድረግ የዋስትና መብቱን ለከለከለው ፍርድ ቤት ጥያቄአቸውን ከሚያቀርቡና በሚሰጠው ትእዛዝም ቅሬታ ካላቸውም ተዋረዱን ጠብቀው የይግባኝ ቅሬታቸውን ወይም የሰበር አቤቱታቸውን ከሚያቀርቡ በስተቀር በዚህ ችሎት ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 72(2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፤

ዘቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ጌቱ ብርሀኑ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ህግ - ወርቅነህ ዘነበ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የበታች ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ግንቦት 22 ቀን 1998 ዓ.ም ከጧቱ ሁለት ሠዓት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/03 የሰሌዳ ቁጥር 3-17408 አ.አ የጭነት መኪና ከአየር ጤና ወደ ቃሊቲ አቅጣጫ በማሽከርከር ላይ እንዳለ ገብሬል ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ሲደርስ ከመኪናው ላይ አሣፍሮት የነበረው ታምራት ሰማኸኝ ከመኪናው ወድቆ በመሞቱ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ በመከራከሩ ተጠሪ ሁለት ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ሟች አመልካች የቆመለት መስሎት ለመውረድ ሲሞክር አመልካች መኪናውን በማሽከርከሩ ሟች ወድቆ የሞተ መሆኑንና አመልካች ከላይ የተጫነው ሰው ሁኔታ በስፖኪ ሣያይና ሣያረጋግጥ ማሽከርከሩ በሙያው ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ያላደረገ መሆኑን ያሳያል በማለት መስክረዋል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2ን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ቀላል እስራትና በብር 4500 መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ አልተቀበለውም፡፡

አመልካች ጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተጠሪ ምስክሮች ቃል በአይናቸው ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይን የመሰከሩ ሳይሆኑ የራሳቸውን ሀሳብ የገለፁ ናቸው፡፡ አመልካች ሟችን በሚያሽከረክረው መኪና ላይ አልጫነም ሀላፊነት ወስጄ ያልጫንኩትን ሰው ህይወት ደህንነት ጥንቃቄ ላደርግ አልችልም ስለዚህ የአመልካች ድርጊቱ በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚሸፈን አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሟች ተጠሪ ሲያሽከረክረው ከነበረው መኪና ላይ ወድቆ የሞተ መሆኑን በማስረጃ አስረድተናል፡፡ አመልካች ሟችን አለመጫኑን በመከላከያ ማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ የአመልካች አድራጎት የትራንስፖርት ደንብ ቁጥር 279/56ን የሚጥስና በሙያው ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ የሟች ህይወት ለህልፈት የበቃ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በፊፀመው ጥፋት የሆነ ቸልተኝነት ከሚያሽከረክረው መኪና ላይ አሣፍሮት የነበረው ሟች ታምራት ሰማኸኝ የሞት አደጋ የደረሰበት መሆኑን ተጠሪ በቂ ማስረጃ በማቅረብ ያረጋገጠ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የከፍተኛው ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የተጠሪን ማስረጃ ለመከላከል ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት ፈፅመውታል የሚለውን ስህተት ይህ ሰበር ችሎት እንዲያርምላቸው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ አመልካች ከመኪናው ላይ አሳፍሮት የነበረው ሟች ከመኪናው እየወረደ እያለ መኪናውን ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ በማሽከርከሩ ሟች ከመኪናው ላይ ወድቆ ለህልፈት የተዳረገ መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የአመልካች አድራጎት በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገውን መሥፈርት የሚያሟላ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(1/ለ-2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ውሣኔው የፀና መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሣስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሰማኸኝ በለው - ባለቤቱ ነኝ ብለው ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - ወርቅነህ ዘነበ ቀረቡ

መዝገቡ የቀረበው ለምርመራ ሲሆን መርምረን በአብላጫ ድምፅ ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በአመልካች ላይ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 48189 መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ምክንያት በመግለፅ አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ሲሆን ተጠሪ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግም የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ በሕግ መሠረት የተሰጠ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡

አመልካች በሰበር ሰሚው ችሎት እንዲታረምለት የሰበር አቤቱታ ያቀረበበት የጥፋተኝነት ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 193/2/ መሠረት የአሁን አመልካች በመልስ ሰጭነቱ ተጠርቶ ሊቀርብ ባለመቻሉ ምክንያት በሌለበት ይግባኙን በመስማት በመሆኑ በዚህ አኳኋን የተሰጠን የጥፋተኝነት ውሣኔ ይህ ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር የማረም ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለው የሥልጣን ጉዳይ በቅድሚያ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለጉዳዩ አወሳሰን እንዲረዳ የጉዳዩን አመጣጥ ባጭሩ ለመግለፅ ያህል ለዚህ ለሰበር መ/ቁ. 57632 መነሻ የሆነው ውሣኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ከ/ቁ. 20464 ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው ፍርድ ሲሆን ይዘቱም፡-

ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ በወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ሟች አርቲስት ግሩም ተስፋዬን በግፍ ገድሏል፣ ህይወቱ እንዲያልፍ አድርጓል በማለት የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ከእነ ሙሉ የወንጀል ዝርዝሩ በቀረበው ክስ መነሻ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ቀርቦ እንዲከራከር ተጠርቶ ሊቀርብ ያልቻለ፣ በጋዜጣም ቢጠራ ያልቀረበ መሆኑን በማየት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 163/1/ መሠረት ጉዳዩን ተከሣሹ በሌለበት እንዲታይ ካደረገ በኋላ፣ ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ እንደ የወንጀል ክሱ አቀራረብ ተከሣሹ የወንጀሉን ድርጊት ሆን ብሎ አስቦ የፈፀመ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመሆኑ አላረጋገጠም፡፡ ስለሆነም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 163/3/ መሠረት ክሱ ነፃ ነው የሚል ፍርድ የተሰጠበት ነው፡፡

በዚህ ፍርድ ላይ የአሁን ተጠሪ ቅር ተሰኝቶ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ለዚህ የሰበር መዝገብ ምክንያት የሆነውን በወ/ይ/መ/ቁ. 48189 መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የአሁን አመልካች በሌለበት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

በዚሁ ፍርድ ላይ የአሁን አመልካች በሌለበት ሊታይ የቻለበትን ምክንያትም እንደሚከተለው አስፍሮታል፡፡

ተከሣሽ የሆነው የአሁኑ አመልካች በመልስ ሰጪነት እንዲቀርብ የይግባኙ ማመልከቻና መጥሪያ ምርመራውን ባጣራው የፖሊስ ክፍል በኩል እንዲደርሰው ተልኮ የአ/አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን የትራፊክ መቆጣጠሪያና ምርመራ መምሪያ መልስ ሰጭ ከኢትዮጵያ ውጭ ሄዷል የሚል ጥቆማ እንደደረሰው በመግለፅ ያላገኘው መሆኑን በጽሑፍ በማሳወቁና መዝገቡም ሲታይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም መልስ ሰጭ ተፈልጐ ባለመገኘቱ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጐለት ባለመቅረቡ ክሱ በሌለበት የታየ ሆኖ በመገኘቱ እንደገና ተጨማሪ በጋዜጣ ጥሪ ማድረግ ሳያስፈልግ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 193/2/ መሠረት ይግባኙ መልስ ሰጭ በሌለበት ታይቶ እንዲወሰን ተበይኗል፡፡

በዚህ መሠረትም የሥር ፍ/ቤት ፍርድና የይግባኝ ባይ ዐቃቤ ሕግ ቅሬታ ከህጉ ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ፡-

በይግባኝ የቀረበለት መዝገብ ከአሁን አመልካች ጉዳይ ጋር በተያያዘ ለሦስተኛ ጊዜ የቀረበ መሆኑንና የአመጣጡንም ሂደት እንደሚከተለው ገልፆታል፡፡

በመጀመሪያ የአሁን አመልካች በተባለው ጊዜና ቦታ ሟችን በቸልተኝነት ገድሏል በሚል የወ/መ/ሕ/ቁ. 526/1/ ተጠቅሶ በቀረበበት ክስ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሣሹን መከላከል ሳያስፈለገው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 141 መሠረት በብይን በማሰናበቱ የተነሣ የይግባኝ ክርክር ቀርቦበት በወ/ይ/መ/ቁ. 26293 ታህሣስ 16 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሥር ፍ/ቤት የተሰማው ማስረጃ ተከሣሹ እንዲከላከል የሚያበቃ መሆኑን ጠቅሶ ይከላከል ሲል መመለሱን፡፡

በዚህ መሠረት መዝገቡ ከተመለሰ በኋላ ዐቃቤ ሕጉ የድርጊቱ አፈፃፀም በቸልተኝነት የተፈፀመ ሳይሆን ሆን ብሎ የፈፀመው መሆኑን ስለተረዳን ክሱን እንድናሻሽል ይፈቀድልን በማለት ጥያቄ ቢያቀርብም የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንን ጥያቄ ባለመቀበል የተከሳሹን ቃል በመከላከያ ማስረጃነት ተቀብሎ ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተከሣሹ የአሁን አመልካች በወ/መ/ሕ/ቁ. 526/1/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ድርጊቱን የፈፀመ መሆኑን አረጋግጦ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ለዚሁ ጥፋት በብር 3000.00 /ሦስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በዚህ ውሣኔ ለሁለተኛ ጊዜ በወ/ይ/መ/ቁ. 36932 በክስ ማሻሻል ጥያቄው ላይ አተኩሮ የይግባኝ ክርክሩን ሲያቀርብ በዚህ መነሻ መልስ ሰጭ የነበረው የአሁን አመልካች እንዲቀርብ ተፈልጎ ሊገኝ ባለመቻሉ እንዲሁም በጋዜጣ በተደረገው ጥሪ ባለመቅረቡ የይግባኝ ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌለበት ስምቶ ዐቃቤ ሕግ ከፍርድ በፊት የክስ መሻሻል ጥያቄ ለማቅረብ የሥነ-ሥርዓቱ ሕጉ አይከለክለውም ከፍርዱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ክስ የማሻሻል መብቱን የሥር ፍ/ቤት ሳይቀበለው መቅረቱ አግባብ አይደለም በማለት ቀደም ሲል የሰጠውን የጥፋተኝነት እና የብር 3000.00 /ሦስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ ቅጣት ውሣኔ ሽሮ ተዘጋጅቶ በሚቀርበው አዲስ ክስ መሠረት ጉዳዩ እንዲታይ መልሶታል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ መሠረት ያንኑ የከ/መ/ቁ. 20464 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ በዚሁ መዝገብ ላይ ተሻሽሎ የቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ቀርቦ ባለው የመከራከር መብት እንዲከራከር ተጠርቶ ያለመቅረብ እና በጋዜጣ ጥሪም ተደርጐለት አለመቅረቡን በማየት ክላይ በመግቢያው ላይ እንደተገለፀው ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የአሁን አመልካች በክሱ ላይ የተገለፀውን ድርጊት እንደ ተከሰሰበት ድንጋጌ ሆን ብሎ የፈፀመው ለመሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም፡፡ ስለሆነም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 163/3/ መሠረት በነፃ ይሰናበታል በማለት ለመጨረሻ ጊዜ በጉዳዩ ላይ ፍርድ የሰጠ መሆኑን ጠቅሶ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ሥልጣኑ የዚህኑ ፍርድ አግባብነት እንደሚከተለው መርምሮ የእራሱን ፍርድ መልስ ሰጭ የነበረው የአሁን አመልካች በሌለበት በአብላጫ ድምፅ ሰጥቷል፡፡

የድርጊቱ ሆን ተብሎ የተፈፀመ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው የሰውና የሠነድ ማስረጃ ሊያረጋግጥ አልቻለም፡፡ በሌላ በኩል ይህ የአሁን አመልካች በዚሁ ድርጊት የተነሣ በቸልተኝነት ጥፋተኛ ተብሎ የብር 3000.00 /ሦስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ ተቀጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ክክስ ማሻሻል ጥያቄ ጋር በማያያዝ ይግባኝ የጠየቀበት ዐቃቤ ሕግ እንጂ ተከሣሹ አይደለም፡፡ ስለሆነም ድርጊቱ የተፈፀመው ሆነ ተብሎ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጉዳይ ከሚያከራክር በቀር የድርጊቱ ፈፃሚ ተከሣሹ መሆኑ የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም ማስረጃው በወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ በተመለከተው መሠረት ጥፋተኛ ለማድረግ ደካማ ሆኖ ቢገኝም የፈፀመው አድራጐት በቸልተኝነት የግድያ ወንጀል ነው ለማለት በቂ ሆኖ ስለተገኘ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 113/2/ መሠረት በወ/ሕ/ቁ. 526/2/ የተመለከተውን ተላልፎ የተገኘ ጥፋተኛ ነው ሊባል ስለሚገባው የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ሀ/ መሠረት ተሰርዞ በወ/ሕ/ቁ. 526/2/ ጥፋተኛ ነው ካለ በኋላ ከዐቃቤ ሕግ በኩል ከቀረበው የቅጣት አስተያየት አንፃር በማየት የአሁን አመልካችን በአራት ዓመት እሥራት እንዲቀጣ በማለት ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡

የይግባኝ መዝገቡ በዚህ አኳኋን ከተቋጨና ከተዘጋ በኋላ የአሁን አመልካች የይግባኝ ክርክር በቀጠሮ ጊዜ ውጪ ሀገር ነበርኩኝ ክሱ ስለመቀጠሉ አላወቅኩም መጥሪያም አልደረሰኝም የሚሉትን ምክንያቶች በመጥቀስ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ ውድቅ ሆኖ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ይደረግለት ዘንድ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 197 አቤቱታ በማቅረቡ በዚህ መነሻ ዐቃቤ ሕግ እንዲቀርብ አድርጎ ጉዳዩን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 201 መሠረት ከሰማ በኋላ የወንጀል ክሱ ተሻሽሎ በወ/ሕ/ቁ. 522/1/ሀ/ መሠረት በከባድ ወንጀል ክስ ሲታይ ሊቀርብ ባለመቻሉ ጥሪ ተደርጐም ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት መወሰኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጀመሪያው ክስ በነፃ ከተሰናበተ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው የይግባኝ መነሻ በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀርቦ ተከራክሯል፡፡ ይከላከል ተብሎ መዝገቡ ከተመለሰ በኋላም በከፍተኛው ፍ/ቤት በጠበቃ ታግዞ ተከራክሯል፡፡

በዚሁ የወንጀል ጉዳይ ከአንዱም ሁለቱ በይግባኝ ሰሚውና በሥር ፍ/ቤቶች በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ለመቅረብ ስላልቻለ በሌለበት ተፈርዷል፡፡

ከአገር ወጥቷል ለተባለ ሰው መጥሪያ በግንባር ማድረስ ስለማይቻል ጥሪው በጋዜጣ መደረጉ ሥነ-ሥርዓታዊ ነው፡፡

ወደ ውጭ አገር ለምን እንደሄደና ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ምን ይሠራ እንደነበርና ለምን ወደ አገር ውስጥ ሳይመለስ የቆየበትን ምክንያት እንኳን አልገለፀም፡፡

በቀረበበት በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እየቀረበ ሲከራከር ከቆየ በኋላ ክሱ ወደ ከባድ ወንጀል ከተቀየረበት ጊዜ ጀምሮ ከአገር መውጣቱና ክርክሩ በከፍተኛው ፍ/ቤት ሲቀጥል ያን ያህል ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ሳይመለስ መቆየቱ በተሻሻለው ወንጀል ምክንያት የዋስ መብቱ ስለማይፈቀድ ታስሮ ክርክሩን የሚቀጥል መሆኑን በመረዳት ከፍርዱ ሂደት መሸሹን ስለሚያመለክት ባለቤቱ በየቀጠሮው እየቀረበች ጉዳዩን ትከታተል ነበር፤ ለዚህም ማስረጃ አለኝ በማለት ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ክርክር አለመካዱ ሁሉ ሲታይ አመልካች በዚህ መዝገቡ ቀርቦበት የነበረውን የወንጀል ይግባኝ ክርክር አያውቅም ነበር ለማለት አያስችልም፡፡ ስለሆነም ከከባድ የወንጀል ክስ በመሸሽ አገር ጥሎ በመውጣት ሳይመለስ በመቅረቱ ምክንያት በሌለበት ሊታይ የቻለ ሆኖ ስለተገኘ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ የሚሆንበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ይህን ሲመስል አመልካቹ ይህን የሰበር አቤቱታው ያቀረበው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እኔ በሌለሁበት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ እና የቅጣት አወሳሰን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚልበትን በክርክር አካሄድ ተፈፀመ የሚላቸውን የሥነ-ሥርዓት ጉድለቶችን በቸልተኝነት ወንጀል ተፈፀመ ለማለት በሕግ የሚጠይቀውን ሟሟያ የመሳሰሉትንና በቅጣት አጣጣል ረገድ እንደ ሕጉ አልተፈፀመም የሚላቸውን በመጥቀስ የተከራከረ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ ፍርድ ተከሳሽ /ይግባኝ ባይ/ በሌለበት ታይቶ የተሰጠ መሆኑ ሲታወቅ እርሱ ባለበት ክርክሩ ታይቶ እንዲወሰን የማድረግ መብቱን ሳያስጠብቅ በቀጥታ ያንኑ በሌለበት ታይቶ የተሰጠውን ውሣኔ በሰበር ለማሳረም የሚያስችል ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጥያቄ ሊያስነሳ ችሏል፡፡

የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/3/ እና ይህንኑ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ተከትሎ ከወጣው ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 የሚመነጭ በመሆኑ እንደ ሕገ መንግሥቱ እና አዋጁ ሥልጣን ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ከሌላው ተከራካሪ ወገን በክርክር መልክ ባይቀርብለትም በእራሱ መርምሮ የመለየት ግዴታ አለበት፡፡ ከዚህም አንፃር ይህንኑ ጉዳይ ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የሥልጣን ምንጭ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ የተመለከተው ድንጋጌ ሲሆን ይዘቱም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል የሚል ነው።

ከዚህም ድንጋጌ "... የመጨረሻ ውሣኔ ..." የሚለው ሀረግ አንድ ጉዳይ በሀገሪቱ በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች ታይቶ እንዲወሰን ከታች ወደ ላይ ስንት የክርክር ደረጃ ማለፍ አለበት። ስንት የክርክር ደረጃ ሊፈቀድ ይገባል የሚለውን አስመልክቶ በወጣው ሕግ መሠረት የክርክሩ ደረጃውን አሟጦ የጨረሰ መሆኑን የሚያመለክት ነው። የዚሁ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌን አፈፃፀም አስመልክቶ በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 እና 10 የተመለከተውም የመጨረሻ ውሣኔ ማለት በፍ/ቤቶች አደረጃጀት አንፃር አንድ ጉዳይ ከታች ወደ ላይ እስከምን ያህል ደረጃ መዝለቅ ይችላል የሚለውን መሠረት በማድረግ የተቀመጠ የክርክር ደረጃ ወሰን መሆኑን እስረጂ ነው።

አሁን የተያዘውን አንድ የወንጀል ጉዳይ ተከሣሽ በሌለበት ታይቶ ፍርድ በተሰጠ ጊዜ በዚህ ፍርድ ላይ ይግባኝ የማሰማት መብት ያለው መሆኑንና አለመሆኑን አስመልክቶ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 202 የተመለከተው ድንጋጌ ከላይ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 እና 10 የተመለከተውን የክርክር ደረጃ ወሰን የሚያመለክት ሳይሆን የተለየ ዓላማ ያለው ነው።

በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ አንድ ፍርድ ተከሣሽ በሌለበት ታይቶ ከተፈረደ በኋላ ፍርደኛው ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 197 ቀጥሎ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ፍርዱ ውድቅ ሆኖ የመከራከር መብቱ እንዲጠበቅለት ያቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ውድቅ እንዲሆን ከተደረገ ይግባኝ ማለት አይቻልም። ነገር ግን ስለተፈረደበት ቅጣት ብቻ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ከተወሰነበት ቀን አንስቶ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ማለት አይከለክልም በማለት በጥፋተኝነት ውሣኔው ላይ ይግባኝ ማለት እንደማይቻል በግልፅ ተደንግጓል።

በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ ይነሳ ለማለት በምክንያትነት የሚቀርቡት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 199/ሀ/ እና /ለ/ የተመለከቱት የመጥሪያ አደራረስ እና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለመቅረብ አለመቻል ናቸው። እነዚህን ምክንያቶች ማስረዳት የቻለ ፍርደኛ ፍርዱን ውድቅ አድርጎ እንደገና እርሱ ባለበት ክርክሩ እንዲሰማ የማድረግ መብት ያለው ሲሆን ከእነዚህ ሁለት ምክንያቶች አንደኛውን ለማስረዳት ያልቻለ ተከሣሽ ወይም ፍርደኛ ከፍትህ ርቆ ወይም ሸሽቶ የነበረ (considered as a convicted perform who was actually seeking to evade justice) መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

ከወንጀል ጉዳዮች የትኞቹ ተከሣሽ በሌለበት ሊታዩ የሚችሉ ስለመሆኑ በሌለበት እንዲታይ ከመደረጉ በፊት ስለሚፈፀመው ሥርዓት በመዘርዝር አንድ የወንጀል ክስ ጉዳይ ተከሣሽ በሌለበት እንዲታይ ማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 160 እስከ 164 መደንገጉም ጥሪ ተደርጎለት አለመቅረቡ ቢታወቅም በወ/ሕ/ቁ. 1 እንደተመለከተው የተከሣሽ አለመቅረብ የወንጀልን ሕግ ግብ አፈፃፀም ሊያሰናክል የሚችል እና ሕጉም ተገቢ ባልሆነ ምክንያት ወደ ሕግ ሊቀርቡ የማይችሉን ያለማበረታት ቀዳሚ ግብ ያለው መሆኑንና በዚህም የተነሣ ተጐጂዎች ከሚፈልጉት ፍትህ የማግኘት መብት አንፃር ታይቶ የተዘረጋ ሥርዓት ሲሆን፤ በአንፃሩ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 2/ሀ//1/ እንደተደነገገው የተከሰሰ ሰው ካለው መሠረታዊ መብት አንዱ የመሰማት መብት እንደመሆኑ መጠን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 13/2/ እንደተመለከተው ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋት አንዱ በሆነው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/እ.ኤ.አ. 1966/ አንቀጽ 14/3/መ/ ተከሣሽ ባለበት የመዳኘትና እራሱን የመከላከል መሠረታዊ መብት ያለው በመሆኑ እና ይህም በማናቸውም ምክንያት በሌላ ሕግ ሊገደብ ስለማይችል በዚህ መብቱ ለመገልገል እንዳይችል ጥሪ በሚገባ ያልተደረገላቸው ከሆነ ጥሪ ቢደረግላቸውም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በክርክሩ ጊዜ መቅረብ ያልቻሉ ወገኖች ካሉ ይኸው ከላይ በተቀመጠው ሕገ መንግሥታዊ መብት መጠቀም እንዲችሉ ሥርዓቱ በወ/ሕ/ቁ. 197-202 ተዘርግቷል፡፡

ስለሆነም ከእነዚህ ምክንያቶች አንዱን ያላስረዳ ፍርደኛ ፍርዱን ውቅድ የማስደረግ መብት ያለው ሲሆን ይህንን ለማስረዳት ያልቻለው ግን በሕገ መንግሥቱ በተሰጠው በሕግ መሠረት የመዳኘት መብት /The right to fair trial) ለመጠቀም ሳይፈልግ ከሕግ ለመራቅ ያቀደ ከሕግ ርቆ የቆየ በመሆኑ ግምት የሚወሰድበት ስለሆነ በተሰጠው የቅጣት ውሣኔ ላይ ካልሆነ በቀር በተሰጠው ጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት የሌለው መሆኑን በመግለፅ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 202 ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 202 መሠረት በጥፋተኝነቱ ውሣኔ የይግባኝ መብት አይኖረውም በሚል መደንገጉ ከላይ ከተቀመጠው ምክንያት አንፃር የመከራከር መብቱን የነፈገ እንጂ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም መባሉ ፍርዱን የመጨረሻ አድርጎታል የሚል ትርጉም ለመስጠት የሚቻል አይደለም፡፡

ስለ ወንጀል ይግባኝ ጉዳይ አስመልክቶ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 193/2/ በዐቃቤ ሕግ ይግባኝ መነሻ በነፃ የተሰናበተውን ተከሣሽ ጉዳይ በሌለበት እንዲታይ ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን መደንገጉም በይዘቱም ሆነ በዓላማው የመጀመሪያ ደረጃ ክስን ተከሣሽ በሌለበት እንዲታይ ከማድረግ ተለይቶ የሚታይ ስለሆነ መልስ ሰጭ በሌለበት የተሰጠውን ፍርድ እርሱ ባለበት ክርክሩ እንዲታይ ፍርዱን ውድቅ ካላደረገው በቀር በሌለበት ታይቶ የተሰጠውን ፍርድ እንደመጨረሻ ፍርድ ተቆጥሮ በሰበር እንዲታረም ለማድረግ የሚያስችል መብት አይሰጥም ፍርዱም እንደመጨረሻ ፍርድ ስለማይቆጠር ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር የማረም ሥልጣን የለውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በአሁን አመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ የተቋጨ እንጂ በሰበር ሊታይ የሚችል ጉዳይ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በቅጣት ውሣኔ ረገድ የሰበር ጉዳዩን መመርመር የሚቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር እንደተመለከትነውም በቅጣት አጣጣል /አወሳሰን/ ረገድ የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፈፀመው የሕግ ስህተት አልተገኘም፡፡

ስለሆነም የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን የጥፋተኝነት ውሣኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/3/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 እና 10 እንዲሁም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 202 መሠረት ከክርክሩ ደረጃ ወሰን አንፃር በማየት እንደተቀመጠ የመጨረሻ ውሣኔ ሆኖ ባለመገኘቱ ይህ ሰበር ችሎት ለማየት ሥልጣን የሌለው በመሆኑ በሰበር ሊታረም የሚችል አይደለም፡፡

የቅጣት አወሳሰኑም ቢሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡ በዚህም መነሻ የሚተለውን ውሣኔ በአብላጫ ድምፅ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ከ/ቁ. 20464 ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ የተሻረ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 48189 መጋቢት 30 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2002 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሠረት በተለየም ምክንያት ቢሆን አፅንተናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የልዩነት ሀሳብ</u>

ስማችን በአራተኛውና በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተገለፀው ዳኞች አብላጫው ድምፅ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኙን አይቶ አመልካች በሌለበት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ አመልካች የሰበር አቤቱታ እንዲያቀርብ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚፈቀድ አይደለም በማለት በሰጠው የሕግ ትርጉምና በደረሰበት መደምደሚያ ያልተስማማን በመሆኑ በሀሳብ ተለይተናል፡፡ ከሥራ ባልደረቦቻችን የተለየንበት የመጀመሪያው ምክንያት ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አሻሽሎ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 አመልካች በሌለበት አይቶ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በሌለበት ሁኔታ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገገው ሥርዓት በጠቅላላውና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 በልዩ ሁኔታ ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ድንጋጌ እንደሆነ አድርጎ በመተርጎም አብላጫው ድምፅ በሰጠው ውሣኔ የማንስማማ በመሆናችን ሲሆን ሁለተኛው ለጉዳዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በጠቅላላውና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር አንቀጽ 202 ንዑስ አንቀጽ 3 በልዩ ሁኔታ ለያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚነት አላቸው የሚባል ቢሆን እንኳ እነዚህ ድንጋጌዎች አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ፍርድ ላይ ተፈፅሟል የሚለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በሰበር ታይቶ እንዲታረምለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከመጠየቅ የሚገድብ አይደለም የሚል አቋም ያለን በመሆኑ ነው፡፡

1. ከላይ ለልዩነታችን ምክንያት አድርገን በመጀመሪያ የገለፅነውን ነጥብ ለመረዳት በመጀመሪያ በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ፍርድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምፅ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩ ያለፈበትን ሂደት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ጉዳይ በተደጋጋሚ ለሦስት ጊዜ ያህል በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የታየና በተለያየ ጊዜ የተለያየ ውሣኔ የሰጠበት ሲሆን በይግባኝም በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለሦስት ጊዜ ያህል የታየና የተለያዩ ውሣኔዎች የተሰጠበት መሆኑን መዛግብቱን በመመርመር ለመርዳት ችለናል፡፡

አመልካችና ተጠሪ በዚህ መዝገብ የሚከራከሩበት ጉዳይ መነሻ ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሚያዚያ 14 ቀን 1995 ዓ.ም. ጽፎ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ይዘትም ተከሣሹ/አመልካች/ በ1949 ዓ.ም. የወጣውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 526 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ ሐምሌ 7 ቀን 1994 ዓ.ም. በግምት ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ሲሆን የመለያ ቁጥር 2-72538 አ.አ. የሆነ መኪና ባለመጠንቀቅና ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲያሽከረክር የመኪናውን መንገድ ወደ ቀኝ በመልቀቅ ባምቢስ ድልድይ ውስጥ ገብቶ በመገልበጡና በአደጋው በመኪናው ውስጥ ተሣፍሮ የነበረው አቶ ግሩም ተስፋዬ ላይ የሞት አደጋ ያደረሰበት በመሆኑ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ አመልካች/ተከሣሽ/ ሚያዚያ 14 ቀን 1995 ዓ.ም. ጽፎ ተጠሪ ያቀረበውን የወንጀል ክስ አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት በመከራከሩ ተጠሪ ክሱን ያስረዱልኛል የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ የተጠሪ ማስረጃ አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ መሆኑን በአጥጋቢ ሁኔታ አላስረዳም በማለት አመልካች የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 20464 ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ የከፍተኛው ፍ/ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሠረት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይገባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የተጠሪንና የአመልካችን ክርክር በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 26293 ከሰማ በኋላ ተጠሪ ሚያዚያ 14 ቀን 1995 ዓ.ም. ያቀረበውን የወንጀል ክስ በአጥጋቢ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሣሽን/አመልካችን/ በነፃ ማሰናበቱ ተገቢ አይደለም በማለት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር የከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ በመስማት ጉዳዩን እንዲወስን በማለት ታህሣስ 16 ቀን 1999 ዓ.ም. በመወሰን ጉዳዩን ለከፍተኛው ፍ/ቤት መልሶ ልኮታል፡፡

በዚህ ውሣኔ መሠረት የከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን ማየት ቀጥሏል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለው በመሆኑ ፍ/ቤቱ የክሱን ቃል እንዲሰማው የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በቸልተኝነት ሳይሆን አስቦና ሆነ ብሎ ሚችን የገደለው መሆኑን የሚያስረዳ አዲስ ማስረጃ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 522 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ክሳችንን አሻሽለን እንድናቀርብ ይፈቀድልን በማለት አመልክተዋል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ የወንጀል ክሱን ለማሻሻል ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በብር 3000 /ሦስት ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ ጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም. ውሣኔ ሰጥቶ አመልካች የገንዘብ መቀጮውን የከፈለ መሆኑን ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል፡፡

ተጠሪ ያቀረብነውን የወንጀል ክስ በማሻሻል ለማቅረብ ያቀረብነውን ጥያቄ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ለማሻሻል ጥያቄ ያቀረብንበትንና ሚያዚያ 14 ቀን 1995 ዓ.ም. ጽፈን ያቀረብነውን የወንጀል ክስ መሠረት በማድረግ የሰጠው የጥፋተኝነት የቅጣት ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለሁለተኛ ጊዜ የይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ አመልካች ይግባኙ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኙ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበ በመሆኑ ይግባኙን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ጉዳዩን መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት አይቶ ተጠሪ ከፍርድ በፊት የወንጀል ክሱን የማሻሻል መብት ያለው መሆኑ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ተደንግጎ እያለ የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ክሱን ለማሻሻል ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በመሻር የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አሻሽሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያቀርበውን የወንጀል ክስ በመቀበልና ክርክሩን በስማት እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን ለሁለተኛ ጊዜ መልሶ ልኮለታል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ መሠረት ተጠሪ አመልካች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 522 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ ሚች ግሩም ተስፋዬ ላይ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም. አሻሽሎ ያቀረበውን የወንጀል ክስ በመቀበል ጉዳዩን ለሦስተኛ ጊዜ ለመስማት ተጠሪና አመልካች /ተከሣሽ/ እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም አመልካች ባለመቅረቡ መጥሪያው በጋዜጣ እንዲወጣ ካደረገ በኋላ ወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው መሠረት ተከሣሽ/አመልካች/ በሌለበት በ(default) የተጠሪን ማስረጃና ክርክር በመስማትና በመመርመር ተጠሪ የወ/መ/ሕ/ቁ. 522/1/ በመጥቀስ ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም. አሻሽሎ ባቀረበው የወንጀል ክስ መሠረት አመልካች ከባድ የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ አጥጋቢ ማስረጃ አላቀረበም በማለት ተከሳሽ /አመልካች/ን ተሻሽሎ ከቀረበው የወንጀል ክስ በነፃ እንዲሰናበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 163 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሠረት ወስኗል፡፡

ከላይ በአጭሩ የገለጽነው ክርክሩ ያለፈባቸው ሂደቶች ተከሣሽ/አመልካች/ በሌለበት (default) ክሱ ታይቶ ጉዳዩን በመጀመሪያ ባየው የከፍተኛው ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ያለ መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ተጠሪ ያቀረበው የተሻሻለ የወንጀል ክስ ተከሳሹ/አመልካች/ በሌለበት (default) በከፍተኛው ፍ/ቤት የታየ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት አመልካች በነፃ እንዲሰናበት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በነፃ እንዲሰናበት ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲታረም ለማድረግ ዐቃቤ ሕግ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 181 እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 185 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በማቅረብ ጉዳዩ በይግባኝ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ በእኛ እምነት የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት (default) በማየት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ባለመኖሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ 160 እና ተከታዮቹ አንድ ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠውን ፍርድ ውድቅ እንዲደረግለት ስለሚያመለክትበትና ጉዳዩ ፍርዱን በሰጠው ፍ/ቤት በድጋሚ ስለሚታይበት ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በጠቅላላውና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 202 ንዑስ አንቀጽ 3 በልዩ ሁኔታ ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች አይደሉም፡፡

2. ከፍተኛው ፍ/ቤት ተከሣሹ በሌለበት (default) ተጠሪ ያቀረበውን የተሻሻለ የወንጀል ክስ በማየት አመልካች/ተከሣሽ/ በክርክሩ ተሣታፊ ያልነበረ ቢሆንም ከቀረበበት ክስ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ፍርድ በመሻር በአመልካች ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሰጠው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት አይቶ ለመወሰን የተከተለው ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 የተደነገገውን ልዩ ሥርዓት (special procedure in cases of default) አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት አንቀጽ 181 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያቀረበውን ይግባኝ በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭው ባለመቅረቡ የተከተለው ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን (absence of a resepondant to the appeal) ሥርዓት ነው፡፡ በእኛ እምነት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ 163 በተደነገገው የdefault procedure እና በይግባኝ መልስ ሰጭ በሚቀርበት ጊዜ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሚከተለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መካከል ሠፊና መሠረታዊ ልዩነት አለ፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 የተደነገጉት የ(default procedure) ጉዳዩን በመጀመሪያ የሚያየው ፍ/ቤት አሥራ ሁለት ዓመትና ከዚህ በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ የወንጀል ክሶችን ተከሣሹ በሌለበት አይቶ ለመወሰን የሚከተለውን ልዩ ሥርዓት የሚደነግግ ሲሆን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 በማናቸውም ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር በመሰኘት ተከሣሹ ወይም ዐቃቤ ሕግ ያቀረቡት ማናቸውም ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ ካልቀረበ ተፈፃሚ የሚሆን ሰፊ ሥርዓት ነው፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 በጥቅል አገላለጽ የተደነገገና በበርካታ ጉዳዮች ሰፊ ተፈፃሚነት ያለው ሥርዓት ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ ሥርዓት መሠረት አይቶ የሰጠው ውሣኔ መልስ ሰጭ ውድቅ እንዲሆንለትና ይግባኙ መልስ ሰጭ ባለበት ታይቶ እንዲወሰን ማመልከቻ የሚያቀርብበት ሥርዓት አይደለም፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የቀረበለትን ይግባኝ መልስ ሰጭ በሌለበት አይቶ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት የሰጠው ፍርድ እንዲሰረዝና ውድቅ እንዲሆን በማድረግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 መሠረት በማድረግ መጠየቅም ሆነ ማመልከት አይቻልም፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገገው ሥርዓት ጉዳዩን ተከሣሹ በሌለበት (default) በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው መሠረት አይቶ የተሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ውድቅ ለማስደረግ የሚያገለግል እንጂ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኙን መልስ ሰጭ በሌለበት አይቶ የወሰነውን ውሣኔ በድጋሚ አይቶ ውድቅ ለማስደረግ የሚያገለግል ሥርዓት አይደለም፡፡ ስለሆነም አብላጫው ድምፅ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኙን አመልካች/መልስ ሰጭ/ በሌለበት አይቶ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የሰጠውን ፍርድ ለማሰረዝ አግባብነትና ተፈፃሚነት እንዳላቸው አድርጎ በሰጠው ትርጉም ያልተስማማን በመሆኑ በሀሳብ ተለይተናል፡፡

3. የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚከተሉት ሁኔታዎች ሁሉ ተፈፃሚነት ያለው ሥርዓት ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ ሥርዓት መሠረት መልስ ሰጭ በሌለበት ይግባኙን አይቶ የሰጠው ውሣኔ ላይ የተፈፀመ የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት ሊታረም የሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው የይግባኝ ሥርዓት በመጠቀምና ይህ የይግባኝ ሥርዓት በሌለበት ሁኔታ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረም በመጠየቅ መሆን አለበት የሚል እምነት አለን፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ይግባኙ መልስ ሰጭ በሌለበት ታይቶ የሚወሰነው፡-

- ተከሣሽ የወንጀል ክሱን በመጀመሪያ በሚሰማበት ጊዜ ቀርቦ ተከራክሮ የሥር ፍ/ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሊወስን፣ ተከሣሹ የጥፋተኝነቱን ውሣኔ ወይም የቅጣቱን ውሣኔ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔውን በመቃወም ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭው /ዐቃቤ ሕግ/ ያልቀረበ በሆነ ጊዜ፣
- ተከሣሹ የተወሳሰቡትን የወንጀል ድርጊት የፈፀመና ጥፋተኛ መሆኑን በማመን ክሱን ለሚሰማው ፍ/ቤት በሰጠው የዕምነት ቃል መሠረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተሰጠበት በሆነ ጊዜና ተከሣሹ የቅጣት ውሣኔውን በመቃወም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 185 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ/ዐቃቤ ሕግ/ ያልቀረበ በሆነ ጊዜ፣

- ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት የወንጀል ክሱንና ክርክሩን ተከሣሹ በሌለበት (default) በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 መሠረት አይቶ በተከሣሹ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሰጠ ሲሆንና ተከሣሹ በሌለበት የተሰጠውን ፍርድ ለማሰረዝ ያቀረበው ማመልከቻ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 201 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት ከታየ በኋላ ማመልከቻው በአንቀጽ 202 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተቀባይነት ያላገኘ ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠውን የቅጣት ውሣኔ በመቃወም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ /ዐቃቤ ሕግ/ ያልቀረበ ሲሆን፣
- ተከሣሽ ባለበት ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤት ተከሣሽ ለጊዜው እንዲለቀቅ ወይም በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ዐቃቤ ሕግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 181 እና አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ/ተከሣሹ/ ያልቀረበ ሲሆን፣
- ተከሣሽ ባለበት ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤት በተከሣሽ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የወሰነ ሲሆንና ዐቃቤ ሕግ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ ወይም የቅጣት ውሣኔ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔውን በመቃወም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 181 እና አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ/ተከሣሽ/ ያልቀረበ ሲሆን፣
- የወንጀል ክሱን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት የወንጀል ክሱን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው መሠረት ተከሣሹ በሌለበት (default) በማየት ተከሣሹ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ዐቃቤ ሕግ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 181 እና አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ/ተከሣሽ/ ያልቀረበ ሲሆን፣
- የወንጀል ክሱን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ተከሣሹ በሌለበት ያየው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ ወይም የቅጣት ውሣኔ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመቃወም ዐቃቤ ሕግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 181 እና አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 2 ያቀረበው ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚሰማበት ጊዜ መልስ ሰጭ/ተከሣሽ/ ያልቀረበ ሲሆን፣
- ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መልስ ሰጭ ባለበት ወይም በሌለበት ይግባኙን አይቶ በሰጠው ፍርድ ላይ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ሁለተኛ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻል በሆነ ጊዜ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሣሹ ያቀረቡትን ይግባኝ ለማሰማት በተያዘው ቀነ ቀጠሮ መልስ ሰጭ ሳይቀርብ ሲቀር በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 አንቀጽ 2 ተፈፃሚነት አለው።

4. ከላይ በተገለፁት ሁኔታዎች ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መልስ ሰጭው በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኙን መርምሮ በወንጀለኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች በአንደኛው የተመለከተውን ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት ተከሣሹ አመልካች በሌለበት የወንጀል ክሱን በማየት ተከሣሽ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠው ፍርድ ላይ ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት ሰምቶ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር በአመልካች ላይ የጥፋተኝነትና የጥፋት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በማየት የሰጠውን ፍርድ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ጉዳዩን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 በተደነገገው ሥርዓት መሠረት አይቶ ፍርዱን ውድቅ እንዲያደርግለት ያቀረበው ማመልከቻ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይግባኙን መልስ ሰጭ በሌለበት አይቶ የሰጠውን ፍርድ ውቅድ እንዲያደርግለት አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ያቀረበውን ማመልከቻ በመቀበል የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በቂ ምክንያት ያላቀረበ በመሆኑ ፍርዱ አይሰረዝም በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 2ን በመጥቀስ ሰኔ 7 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የለውም፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በማናቸውም ምክንያት የቀረበለትን ይግባኝ መልስ ሰጭ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 ሰምቶ የሰጠው ፍርድ ውድቅ እንዲደረግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ለመመልከት የሚፈቅድ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መልስ ሰጭ በሌለበት አይቶ የሰጠው ፍርድ ላይ የተፈፀመ የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የሚታረምበት ሥርዓት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው መስፈርት የተሟላ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ የተዘረጋውን የይግባኝ ሥርዓት በመጠቀም ነው፡፡ ጉዳዩ ከላይ በተገለፀው የሕግ ድንጋጌ የተዘረጋውን መሥፈርት የማያሟላ ሲሆን ወይም በዚህ መዝገብ እንደተያዘው ጉዳዩን ለሁለተኛ ጊዜ በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሌለ ጊዜ ስህተቱ የሚታረመው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተዘረጋውን የሰበር ሥርዓት በመጠቀም ነው፡፡

ከላይ ከደረስንበት መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ከዚህ በፊት በሰፊው ከገለፅናቸው ምክንያቶች በተጨማሪ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 አቀራረፅ እና የቃል በቃል ንባብ መገናዘብ አለበት የሚል እምነት አለን፡፡ "የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሥልጣን" የሚል ርዕስ ያለው የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 "የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሚከተሉትን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል"

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሣኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች፣
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ የተለየ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች በማለት ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት አይቶ በነፃ እንዲሰናበት በተሰጠው ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ወስኗል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት የሰበር አቤቱታ ለማቅረብ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኙን በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መልስ ሰጭ ባለበት አይቶ ውሣኔ መስጠቱ በመስፈርትነት አልተደነገገም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት መልስ ሰጭ በሌለበት ይግባኙን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰምቶ በሰጠው ውሣኔ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ከሻረ ወይም ካሻሻለ መልስ ሰጭ ያለው ብቸኛ አመራጭ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ መሆኑን የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አሻሽሎ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ተከሳሹ/አመልካች/ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው መሠረት አይቶ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሣሹ/አመልካች/ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 192 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በማየትና የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት በመሻር በአመልካች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የሚያይ ሌላ ችሎት ወይም ፍ/ቤት የለም ይህም በመሆኑ አመልካች ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን በሌለበት አይቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኝ ለማቅረብ አይችልም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች/መልስ ሰጭ/ በሌለበት ይግባኙን በማየት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በይግባኝ የማይታይ ወይም ከሰበር ውጭ በሌላ መንገድ ሊታይም የማይችል የመጨረሻ ውሣኔ ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት አይቶ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሊወስን ፈፅሞታል የሚለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በሰበር ታይቶ እንዲታረምለት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎቱ እንዳይታይ የሚገድብ ወይም የሚከለክል ግልፅ የሆነ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ በዚህ በኩል አብላጫው ድምፅ ጉዳዩ በሰበር የሚታይና የሚታረም አይደለም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በጉዳዩ የተሰጠ “የመጨረሻ ውሣኔ” የለም በማለት ሲሆን በእኛ በኩል ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበትና በሰበር ሊታይ የሚችል ውሣኔ በመሆኑ ተጠሪ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ያቀረበለት ይግባኝ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በማየት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት በሰጠው ፍርድ ላይ ተፈፅሟል የሚለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በሰበር ታይቶ እንዲታረምለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የሰበር አቤቱታ እንዳያቀርብ የሚገድብ ወይም የሚከለክል የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ በዚህ በኩል አብላጫው ድምፅ ጉዳዩ “የመጨረሻ ውሣኔ” አላገኘም በማለት የሰጠውን የሕግ ትርጉም ከላይ በዝርዝር በገለጽነው ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡

5. አብላጫው ድምፅ ጉዳዩ በሰበር የሚታይ አይደለም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ መሆኑን በመዘርዘር ነው፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አቀራረፅና የቃል በቃል ንባብ “ማመልከቻው ፍ/ቤቱ ሣይቀበል ቀርቶ ውድቅ እንዲሆን በመወሰኑ ይግባኝ ማለት አይቻልም ነገር ግን ስለተፈረደበት ቅጣት ብቻ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ከተወሰነበት ቀን አንስቶ በአሥራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ቢል አይከለከልም” የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ድንጋጌ የወንጀል ክስ ተከሣሹ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በማየት ወንጀል ክሱን ተከሣሹ በሌለበት (default) ያየው ፍ/ቤት በተከሣሽ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሰጠ በሆነ ጊዜ ብቻ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ድንጋጌ ነው፡፡ ድንጋጌው ሁለት ደንቦች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው የወንጀል ክሱ በሌለበት የታየ ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ እንዲሆንለት ያቀረበው ማመልከቻ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 201 በተደነገገው ሥርዓት ከታየ በኋላ ማመልከቻው ተቀባይነት የለውም ተብሎ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተወሰነበት ተከሣሽ የሥር ፍ/ቤት አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ማለት የማይችል መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ሁለተኛው ደንብ በሌለበት የወንጀል ክሱ ታይቶ ፍርድ የተሰጠበት ተከሣሽ ፍርድ ውድቅ እንዲደርግለት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ያቀረበው ማመልከቻ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አቤቱታው ተቀባይነት ያላገኘ ተከሣሽ ፍ/ቤቱ ክሱን በሌለበት አይቶ በሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔን በመቃወም ይግባኝ ለማቅረብ የማይችል መሆኑንና በቅጣት ውሣኔ ላይ ብቻ ይግባኝ የማለት መብት ያለው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ የሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 202 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ገዥ ደንብ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 181 በወንጀል ፍርድ ላይ ይግባኝ ስለሚቀርብበት ሁኔታ ከደነገገው ጠቅላላ መርህ በልዩ ሁኔታ የተደነገገ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የወንጀለኛ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 በይዘቱም ሆነ በሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 185 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ጋር ተመሣሣይነት ያለውና በሌለበት የወንጀል ክስ ታይቶ የተሰጠን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ውድቅ ለማስደረግ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ያላገኘ ተከሣሽ በቅጣት ውሣኔው ላይ ብቻ ይግባኝ ማለት እንደሚችል ግልጽ የሚያደርግ ነው፡፡

የቀረበበትን የወንጀል ክስ በሙሉ በማመኑ ምክንያት በዕምነቱ መሠረት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 134/1/ መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው የቅጣት ውሣኔውን በመቃወም ካልሆነ በስተቀር በጥፋተኝነቱ ውሣኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደማይቻል የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 185 ንዑስ አንቀጽ 1 ከደነገገው በተጨማሪ ተከሣሽ የጥፋተኝነት ውሣኔውን በመቃወም ይግባኝ የማያቀርብበት ሁኔታ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ በአምስተኛው መጽሐፍ በሁለተኛው አንቀጽ ተከሣሹ በሌለበት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 ታይቶ የተሰጠውን ፍርድ ውድቅ ለማድረግ በሚቀርብ ማመልከቻ ላይ ብቻ ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡ ድንጋጌው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ አምስተኛው መጽሐፍ አንደኛ አንቀጽ የወንጀል ፍርድ በይግባኝ ስለሚታረምበት ሁኔታ ከአንቀጽ 181 እስከ አንቀጽ 196 በደነገገው ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት የሌለው በመሆኑ አብላጫው ድምፅ ጉዳዩ በሰበር የሚታይ አይደለም በማለት የተሰጠው ትርጉም ተገቢ ሆኖ አልታየንም፡፡

6. በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በጠቅላላውና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነትና ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 5 ዘርዝረናል፡፡ አብላጫው ድምፅ እንደተረጎመው እነዚህ ድንጋጌዎች ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኙን መልስ ሰጭ በሌለበት በማየት በሰጠው በጥፋተኝነትና በቅጣት ውሣኔ ላይ ተፈፃሚነት አላቸው የሚባል ቢሆን እንኳን የሰበር ችሎቱ አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ ከመስጠት እነዚህ ድንጋጌዎች በጠቅላላው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 ሁኔታ የሚከለክሉ ወይም የሚገድቡ አይደሉም፡፡

ለዚህም የመጀመሪያው ምክንያት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 ያሉትን ድንጋጌዎች ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መልስ ሰጭ በሌለበት አይቶ በሰጠው ፍርድ ላይ የማመሳሰል የሕግ አተረጓጎም ዘዴን በመጠቀም ተፈፃሚ ሲሆኑ ጥብቅና ጠባብ የሆነ ትርጉም ሊሰጣቸው የሚገባ መሆኑ ነው፡፡ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድነጋጌዎች የሙግት ሂደትን በአግባቡ ለመምራትና የተከሣሹን መሠረታዊ መብቶች የሚከበሩበትን ሥርዓት የሚደነግጉ ናቸው፡፡ ስለሆነም አንድ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ በሚተረጎምበት ጊዜ ሠፊና የተለጠጠ ትርጉም በመስጠት መሠረታዊ መብቶችንና ነፃነቶችን በሚያሣጣ መንገድ ሊተረጎም አይገባውም፡፡ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎችን በጥብቅና በጠበበ መንገድ በመተርጎም በህገ መንግሥቱ እና በሌሎች የሕግ ማዕቀፎች የተደነገጉ የስህተት ማረሚያ ሥርዓቶች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ የማያሠናክል ወይም አላስፈላጊ ገደብ በማይጥል መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል የሚል እምነት አለን፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 202 ንዑስ አንቀጽ 3 ተከሣሹ በሌለበት የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ይግባኝ እንዳያቀርብ ገደብ የሚጥል ነው፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 181 እስከ እስከ አንቀጽ 196 የተደነገገው የይግባኝ ሥርዓት የሰበር ችሎት በሚጠቀምበት ጊዜ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተዘረጋውን የሰበር ሥርዓት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ የማያጣብብና ዜጎች መሠረታዊ የሕግ ሥህተት አለበት የሚሉትን የመጨረሻ ውሣኔ በሰበር እንዲታረምላቸው የመጠየቅ እድላቸውን በማያጣብብ ሁኔታ መተርጎምና ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡

ሁለተኛው ምክንያት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተዘረጋው የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማና ግብ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ማናቸውም የመጨረሻ ውሣኔ በሰበር ታይቶ ሊታረም የሚችልበትን እድል በመፍጠርና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ በሰበር አይቶ በማረም በአገሪቱ ውስጥ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎምና ተፈፃሚነት እንዲቀር ማድረግ ነው፡፡ ሌላው የሰበር ዓላማ ህጋዊ ያልሆነ ውሣኔ እንዳይፀና ማድረግ ሲሆን ከይግባኝና ከሌሎች ሥርዓቶች የተለየ መሆኑን ይህ የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42239 ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም. በሰባት ዳኞች በተሰየሙበት በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አቋም የያየዘበት ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መልስ ሰጭ/አመልካች/ በሌለበት በማየትና የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት በመሻር በሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ላይና የአመልካችና የተጠሪ ክርክር ባለፈባቸው ሂደቶች ተፈፅሟል የሚለው የሕግ ስህተት እንዲታረምለት አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ መመርመር የሰበር ሥርዓት ከተዘረጋበት መሠረታዊ ዓላማና ግብን መሠረት ያደረገ ሆኖ እያለ ጉዳዩ ለሰበር ቀርቦ እንዳይታይ የሚከለክል የሕግ ድንጋጌ በሌለበት ጉዳዩ በሰበር የሚታይ አይደለም መባሉ ተገቢ ነው የሚል እምነት የለንም፡፡

7. አብላጫው ድምፅ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 199/ሀ/ እና /ለ/ን በመጥቀስ አመልካች ከፍትህ ርቆ ወይም ሸሽቶ የነበረ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 2 ይግባኙን በሌለበት አይቶ የሰጠው ፍርድ ውድቅ እንዲደረግለት ያቀረበውን አቤቱታ ያልተቀበለው መሆኑን በመግለጽ የሰጠው ምክንያት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ክርክር ያለፉበትን ረዥምና ውስብስብ ሂደት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመጥቀስ ያቀረበው የወንጀል ክስ ሲሰማ አመልካች ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ተከራክሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቱ በብይን በነፃ አሰናብቶታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲያቀርብ አመልካች በይግባኝ ሰሚው ችሎት ቀርቦ ተከራክሮ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን መከላከያ ሰምቶ እንዲወስን የሰጠውን ውሣኔ በማክበር በከፍተኛው ፍ/ቤት ቀርቦ ከተከራከረ በኋላ የከፍተኛው ፍ/ቤት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 526 ንዑስ አንቀጽ 1ን የተላለፈ ጥፋተኛ ነው በማለት የወሰነበትን የገንዘብ መቀጮ ከፍሏል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 526 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ የሰጠው ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ክሱን የማያስረዳ ማስረጃ ስላቀረበ የአመልካችን መከላከያ ሰምተህ ወስን በማለት የሰጠውን ፍርድ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የወንጀል ክስ ከተጀመረበት 1995 ዓ.ም. ጀምሮ የከፍተኛው ፍ/ቤት ጥር 13 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አመልካች እስከፈፀመበት ጊዜ ድረስ ረዥም ጊዜ አመልካች በክርክር የቆየ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ተጠሪ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 119 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ውጭና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ በክሱ በጠቀሰው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ሰምቶ የከፍተኛው ፍ/ቤት እንዲወስን በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 26293 የሰጠውን ፍርድ በማያስለውጥ ሁኔታ ተጠሪ አቅርቦት የነበረውን የወንጀል ክስ በመተው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 522 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመጥቀስ ክሱን ለማሻሻል ያቀረበውን ጥያቄ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውድቅ ያደረገው በመሆኑ ተጠሪ ይግባኝ አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን የተሻሻለ ክስ ተቀብሎ አከራክሮ እንዲወስን በሰጠው ውሣኔ መሠረት የተሻሻለው ክስ ሲሰማ አመልካች ያልቀረበ መሆኑን በመዝገቡ የተደረገው የክርክር ሂደት ያሣያል፡፡ ይህ ሂደት አመልካች ከፍትህ ርቆና ሸሽቶ የኖረ መሆኑን አያሣይም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 26293 የሰጠውን ፍርድ በሚለውጥና የሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 119 ከሚደነግገው ሥርዓት ውጭ ተጠሪ ክሱን እንዲያሻሽል በመፍቀዱ ምክንያት በክርክሩ ሂደት ችግሮች የተፈጠሩ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱን ግብ ለማሣካት የሚቻለው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 22 እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የህጋዊነት መርህ በሚያከብር ሁኔታ የፍትህ አካላቱ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ነው የሚል እምነት አለን፡፡ ሰበር በወንጀል ጉዳይ በተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ በህገ መንግሥቱና በወንጀል ሕጉ የተደነገጉ መሠረታዊ መርሆች መከበራቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ነው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በሌለበት የሰጠው ፍርድ ላይ አለ በማለት በሰበር አቤቱታው የገለፃቸው የሕግ አተረጓጎም የወንጀል ሕጉን ግብ የማያሣካ ነው የሚል እምነት የለንም፡፡

8. አብላጫው ድምፅ የአመልካች ጉዳይ በሰበር የሚታይ አይደለም በማለት የሰጠውን ውሣኔ ለማጠናከር የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አገራቱ ያፀደቀችውን የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 3/መ/ በዋቢነት ጠቅሷል፡፡ በእኛ በኩል ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 በጠቀሳላውና ንዑስ አንቀጽ 3/መ/ በልዩ ሁኔታ በአቀራረቡም ሆነ በይዘቱ የወንጀል ክስ ተከሣሽ ባለበት መታየት ያለበት መሆኑን የሚደነግግና በወንጀል የተከሰሰ ሰው ሊከበርለት የሚችል ሰፊ መብት ያለው መሆኑን በዝርዝር የሚደነግግ እንጅ የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ በማናቸውም መንገድ የሚያጣብብ ይዘት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ የተጠቀሰው የሲቪልና የፖለቲካ መብት ቃል ኪዳን ስምምነት ድንጋጌ መተርጎም ያለበት መብትን በሚያሣጣ ወይም በሚያጣብብ መንገድ መሆን አይገባውም፡፡ ይህ ድንጋጌ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች መብት በሚያሣጣ ወይም በሚያጣብብ መንገድ ሊተረጎም የማይገባው መሆኑን ዓለም አቀፍ ህብረተሰብ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 1948 ዓ.ም. ባወጀው የሰብዓዊ መብቶች ሁለንተናዊ መግለጫ /The Universal Decleration of Human Rights) አንቀጽ 30 የደነገገውን የአተረጓጎም መርህ መሠረት ባደረገ ሁኔታ ትርጉም ሊሰጠው ይገባዋል የሚል እምነት አለን፡፡

በአጠቃላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 8 በተጠቀሱት ምክንያቶች የሰበር ችሎት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታና ተጠሪ ያቀረበውን መልስና ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የሰጠውን ውሣኔ በመመርመር መዝገቡ ለሰበር ሲቀርብ በተያዘው ጭብጥ መሠረት ውሣኔ እንዳይሰጥ የሚከለክለው ሕግ በሌለበት ሁኔታ ጉዳዩ በሰበር የሚታይ አይደለም በማለት አብላጫው ድምፅ በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማን በመሆናችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. *57988*

ጥር *10* ቀን *2003* ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ ዩርዳኖስ አባይ አሰፋ የቀረበለት የለም

ተጠሪ፣ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የአሁኗ አመልካች በተከሰሰችበት የስርቆት ወንጀል በክሱ ላይ ተላልፋለች ተብሎ በተጠቀሰባት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 665/1/ መሠረት ጥፋተኛ ተብላ በ2 ዓመት ቀላል እሥራትና በብር 2500 የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በሚል በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 80/3//ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10/3/ መሠረት የቀረበ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ቀርቦለት የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በጥፋተኝነቱም ሆነ በቅጣት አወሳሰኑ ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ግንቦት 5 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ይታይ በመባሉ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት አድርጓል ተጠሪው በጽሑፍ የሰጠው መልስ ለአመልካች ጠበቃ ደርሷቸው በጽሑፍ የመልስ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡

እንደመረመረውም የአሁኑ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 665/1/ን በመተላለፍ የስርቆት ወንጀል ፈጽማለች ተብላ የተከሰሰችው ከሌሎች ዋና የወንጀል አድራጊዎች ጋር በመሆን ቀን የግል ተበዳይዋ ቤት ገብተው ቁምሣጥን በመስበር በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ የተለያዩ የወርቅ ጌጣጌጦች እና ሌሎች ቁሳቁሶችን ሰርቀው ወስደዋል በሚል ምክንያት መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

የአሁኗ አመልካች ክሱን ክዳ ብትከራከርም ዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች አቅርቦ አስረድቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዐቃቤ ሕግ ካቀረባቸው ማስረጃዎች መካከል አንዱ የጽሑፍ ሲሆን የጽሑፍ ማስረጃውም የአሁኗ አመልካች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 35 መሠረት ፍ/ቤት ቀርባ የስርቆቱን ድርጊት ስለመፈፀሟ በማመን ሰጥታለች የተባለው ቃል ነው፡፡ ይህንንም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 44948 በ14/11/2001 ዓ.ም በሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ ላይ ገልጾታል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በሰበር አቤቱታቸው ላይ እንዲህ አይነት የጽሑፍ ማስረጃ አልቀረበባትም አላሉም፡፡ ሚስጥር ሰለሞን የተባለችው የግል ተበዳይ ልጅ ከአሁኗ አመልካች ጋር በዚሁ የስርቆት ወንጀል አንደኛ ተከሣሽ መሆኗን ተከሳ እያለ የዐቃቤ ሕግ ምስክር እንድትሆን ተደርጐ ቀርባ ዐቃቤ ህግ በእርሷ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ በማንሣት ምስክር እንድትሆን አድርጓል ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ወንጀሉን ፈጽሟል ተብሎ ምርመራ ተጣርቶበት ክስ እንዲቀርብበት የተደረገው ሰው ተከሣሽ ከመሆን ይልቅ ምስክር መሆኑ ይጠቅመኛል ብሎ ዐቃቤ ሕግ በእርሱ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ ማንሣት ምስክር እንዲሆን ማድረግን የሚከለክለው ሕግ ስለሌለ በዚህ ጉዳይ በ1ኛም ተከሣሽ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ በማንሣት ምስክር አድርጐ ማቅረቡ የሚጥሰው ሕግ የለም፡፡ በአሁኗ አመልካች ላይ የቀረበባት ማስረጃ ምስክሯ ብቻ ሣትሆን ከፍ ሲል እንደተገለፀው የፅሑፍ ማስረጃም ቀርቦባታል አመልካች ወንጀሉን መፈፀሟ ተረጋግጦባታል የተባለው በእነዚህ ሁለት ማስረጃዎች ስለሆነ የአመልካች ጠበቃ ምስጥር ሰለሞን ክሱ ሣይነሣላት በተከሣሽነት ደረጃ እንዳለች እርሷ ብቻ ቀርባ እንዳመሰከረችባት አድርገው የገለጹት ትክክል አይደለም፡፡

የአሁኗን አመልካች በሚመለከት በማስረጃ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ስለሥርቆት ወንጀል የሚያሣዩ አይደሉም በሚል የተነሣውን ክርክር በተመለከተም በማስረጃ የተረጋገጡበት ፍሬ ነገሮች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 665 ላይ የተመለከተውን የስርቆት ወንጀል በሚገባ የሚያቋቁሙ ሆነው ስለተገኙ በዚህ የሕግ አንቀጽ መሠረት ጥፋተኛ በመባሏ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም፡፡

የተወሰነባትን ቅጣት በሚመለከት ፍ/ቤቱ በርካታ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መኖራቸውን በቅጣት ውሣኔው ላይ ከገለፀ በኃላ ሁለተኛውን አማራጭ እስከ አምስት አመት የሚደርሰውን የጽኑ እሥራት ቅጣት በመተው የቀላል እሥራቱን ቅጣት በመከተል በ2 ዓመት ቀላል እሥራት እንድትቀጣ መወሰኑ ዕድሜዋ 17 አመት ነው የተባለውን ግምት ውስጥ ያስገባ የሚባል እንደሆነ እንጂ ያለአግባብ ከብዶባታል የሚያሰኝ አይደለም፡፡ በመሆኑም በቅጣት አወሳሰኑም ረገድ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ተወሰኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ለ/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 47755

ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፣ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ዐቃቤ ሕግ ወርቅነህ ዘነበ ቀረበ

ተጠሪ፣ አቶ ሚፍታህ ኑረዲን ጠበቃ ግርማ ደጀኔ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪና በዚህ ክርክር ተካፋይ ባልሆኑ ሌሎች ሁለት ሰዎች ላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አንቀጽ 346 የተመለከተውን በመተላለፍ በተጠሪ በተመዘገበ የንግድ ድርጅት /ሱቅ/ ውስጥ ተጠሪ ፈቃድ ሣይኖረው የውጭ አገር ገንዘብ በመመንዘርና የዘጠኝ የውጭ ሀገር ገንዘብ አስማችቶ የተገኘ ሲሆን ሌሎች ተከሣሾች የወንጀሉ ሥራ ተካፋይ በመሆናቸው የውጭ አገር ገንዘብ በህገወጥ መንገድ የመመንዘር ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ካቀረበው የወንጀል ክስ ጋር በተጠሪ ሱቅ ውስጥ

1. የኢትዮጵያ ብር 1,275,159 /አንድ ሚሊዬን ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሺህ ብር አንድ መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር/
2. የአሜሪካን ዶላር 6,042 /ስድስት ሺህ አርባ ሁለት የአሜሪካን ዶላር/
3. የአውሮፖ ህብረት ዩሮ 920 /ዘጠኝ መቶ ሃያ ዩሮ/
4. የእንግሊዝ ፖውንድ 40 /አርባ የአንግሊዝ ፖውንድ/
5. የአረብ ኢምሬት 205 /ሁለት መቶ አምስት AED/
6. የሳውዲ አረቢያ ሪያል 2,261 /ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ስልሣ አንድ ሪያል/
7. የስዊዝ / CHF/ 1400 /አንድ ሺህ አራት መቶ የስዊዝ CHF/
8. የካታር ገንዘብ 7.00 /ሰባት የካታር ገንዘብ/
9. የካናዳ ዶላር 2.00 /ሁለት የካናዳ ዶላር በኢግዚቢትነት የተያዘ መሆኑን ከአቀረበው የወንጀል ክስ ጋር በመዘርዘር አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም ብለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የተጠሪን የመከላከያ ማስረጃ ሰምቷል የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተጠሪ በወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አንቀጽ 346 የተመለከተውን በመተላለፍ በህገወጥ መንገድ የውጭ አገር ገንዘብ የመነገድ ወንጀል ፈፅሟል በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኃላ አመልካችና ተጠሪ የቅጣት ውሣኔ አስተያየት እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ሊያርምና ሊያስተምር የሚችል የቅጣት ውሣኔ እንዲሰጥለትና በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተገኙት የውጭ አገር ገንዘቦች ውርስ ሆነው ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት የቅጣት አስተያየት አቅርቧል፡፡ ተጠሪም 4 ገጽ የቅጣት አስተያየት በፅሑፍ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ከመረመረ በኃላ ተጠሪ በሁለት ዓመት ፅኑ እስራትና በብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ ብር/ እንዲቀጣ ወስኖ የፅኑ እስራት ቅጣቱን በሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ እንዲገደብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዙት የውጭ አገር ገንዘቦች በመንግስት እንዲወረሱ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወርስ ትዕዛዝ ማይሰጥ ማለፉ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 346 እና አንቀጽ 48 የሚጥስ ነው ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ ትዕዛዝ ማይሰጥ በዝምታ ማለፉ ተገቢ ባለመሆኑ በይግባኝ ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የይግባኝ ቅሬታ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሣኔና ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሀምሌ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ያነሳቸውን የቅሬታ ነጥቦች በማንሣት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ተጠሪ በህገወጥ መንገድ የውጭ አገር ገንዘብ የመመንዘር ወንጀል የፈፀመ መሆኑ ተረጋግጦ ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ ስለዚህ የወንጀሉ ድርጊት የሥራ ፍሬ የሆነውና በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረሱ ትዕዛዝ ማይሰጥ የሥር ፍርድ ቤት በዝምታ ማለፉና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሚያዚያ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባደረግነው ክርክር ከተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ብር እንዲወረስ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት አላመለከተም፡፡ በተቃራኒው አመልካች እንዲወረስ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት የሚፈልገው የውጭ አገር ገንዘቦችን ብቻ መሆኑንና በተጠሪ ሱቅ የተያዘውን ገንዘብ እንደማይጨምር በግልፅ አስተያየት ሰጥቷል፡፡ ስለዚህ በስር ያልተከራከረበትን ፍርድ ቤቱ አለፈብኝ በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሚያዚያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ግራቀኙ በፅሑፍ ካደረጉት ክርክር በተጨማሪ ችሎቱ ሀምሌ 15 ቀን 2002 ዓ.ም የግራቀኙን ክርክር ሰምቷል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ የተገኘው የኢትዮጵያ ብር እንዲወረስ አስተያየት መስጠቱን በማንሣት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወርስ በሥር ፍርድ ቤት አልተከራከረም፡፡ አመልካች የመወረስ ትዕዛዝ የኢትዮጵያን ብር እንዲጨምር እንደማይፈልግ በመግለፅ ነው አስተያየት የሰጠው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ግራቀኙ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በሰጠው የቅጣት አስተያየት በተለይም በተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሱቅ ውስጥ ስለተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ አመልካች ባቀረበው ክርክር ይዘት ላይ ሰፊ ልዩነት ያላቸው በመሆኑ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ሶስተኛ የወንጀል ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር ከመቅረፀ ድምፅ ያቀረቡትን ካሴት እንዲልክ ችሎቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 124880 ያደረጉት ክርክር የተቀረፀን ካሴት በፖስታ በማሸግ ህዳር 8 ቀን 2003 በተፃፈ መሸኛ ልኳል፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡትን የቅጣት አሰተያየትና ክርክር የተቀረፀበትን ካሴት ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም በቴፕ ሪከርደር ሰምቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ብር እንዲወረስ ትዕዛዝ ሣይሰጡ ማለፉ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን ጭብጥ ለመወሰን አመልካች የተጠሪ ሱቅ ውስጥ ስለተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበውን አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ትክክለኛ ይዘት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና ለሰበር ችሎት የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተገኘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ ትዕዛዝ ሣይሰጥ በዝምታ ማለፉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 346 እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 98ን የሚጥስ መሆኑን በመጥቀስ በሰፊው የሚያቀርበውን ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ በማንሣት እንዳልተከራከረ በመቅረፀ ድምፅ ከተቀዳው የአመልካች የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኃላ አመልካች የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣቡን እንዲያቀርብ እድል ሲሰጠው ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ሊያርምና ሊያስተምር የሚችል የቅጣት ውሣኔ እንዲሰጥለት የጠየቁ መሆኑንና በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተገኙ የውጭ ገንዘቦች እንዲወረሱ ውሣኔ እንዲሰጥለት የጠየቁ መሆኑን በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ ያቀረበው የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ እንደሌለ ተገንዝበናል፡፡ በተቃራኒው አመልካችን በመወከል ለችሎቱ የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ያቀረቡት ዐቃቤ ሕግ በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዙት የውጭ ገንዘቦች እንዲወረሱ ያቀረቡት የውሣኔ ሃሣብ እንደተጠበቀ ሆኖ የመወረስ ትዕዛዙ በተጠሪ ሱቅ የተያዘውን የኢትዮጵያ ገንዘብን የማይጨምር መሆን እንዳለበት በግልፅ አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ያቀረበ መሆኑን ችሎቱ በትዕዛዝ አስቀርቦ ከሰማውና በመቅረፀ ድምፅ የተቀረፀው የቅጣት አስተያየትና ይህንን አስተያየት በፅሑፍ በመገልበጥ በሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ጋር ከተያያዘው ሰነድ ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በወንጀል ክሱ በኤግዚቢትነት ዘርዝሮ ያቀረበውና ከተጠሪ የንግድ ሱቅ ውስጥ የተገኘው 1,275,159 /አንድ ሚሊዩን ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሺህ አንድ መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር/ ተጠሪ ጥፋተኛ ከተባለበት የወንጀል ድርጊት ጋር ግንኙነት አለው የሚልበትን ምክንያት በመግለፅ ይህ የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ የውሣኔ ሃሣብና ክርክር በሥር ፍርድ ቤት አላቀረበም፡፡ አመልካች ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው የመውረስ ትዕዛዝ በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘውን የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲጨምር ክርክር የማያቀርብ መሆኑን የውሣኔ ሃሳቡን በግልፅ አስመዝግቧል አመልካች የተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዙት የውጭ ገንዘቦች እንዲወረሱና የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዳይወረስ በግልፅ የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ከቀረበ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ ውሣኔ ሣይሰጥ አልፎብኛል በማለት ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሰበር ችሎት ያቀረበው ክርክር ምንም አይነት የህግ መሠረት የሌለውና በሙግት ሂደት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ነፃና ገለልተኛ ሆነው የመምራት የመመርመርና የመመዘንና ውሣኔ የመስጠት ህገመንግስታዊ ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ክርክር ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

የአገሪቱን ህዝብና የፌዴራሉን መንግስት በመወከል በጉዳዩ ተከራካሪ ሆኖ የቀረበው አመልካች በክስ መክፈትና በመሰማት ሂደት ያለበት ግዴታና ሃላፊነት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ሊፈፅመው ስለሚገባው ተግባር በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 148 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ፍርድ ቤቱ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኃላ አመልካች ፍርድ ቤቱ ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ሊመረምራቸው አስፈላጊም ከሆነ በማስረጃ አረጋግጦ ውሣኔ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦችና ክርክሩን ሊያስረዱለት የሚችሉ ማስረጃዎችን በመዘርዘር የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ የማቅረብ ሃላፊነት እንዳለበት በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ያቀረበውን የቅጣት አሰተያየትና የውሣኔ ሃሣብ ከተቀበለና ተጠሪም የአመልካችን የቅጣት አሰተያየት የውሣኔ ሃሣብ መሠረት በማድረግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 4 ያቀረበውን ክርክር ከተቀበለ በኃላ ጉዳዩን ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በመመዘን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ግልፅ ክርክርና የውሣኔ ሃሣብ ያላቀረበበትን በተቃራኒው በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዘው የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ ክርክር የማያቀርብ መሆኑን በግልፅ አስተያየቱን ያስመዝገበበትን ጉዳይ የኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወረስ የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በዝምታ አልፎብኛል በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ከላይ የተደነገጉትን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያላደረገና አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ ስለተገኘው የኢትዮጵያ ገንዘብ ያቀረበውን የውሣኔ ሃሣብ ትክክለኛ ይዘት የማያንፀባርቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ሱቅ ውስጥ የተያዙት የውጭ አገር ገንዘቦች ብቻ እንዲወረሱ የሰጠው ውሣኔ በወንጀለኛ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አመልካች ያቀረበውን የቅጣት አስተያየትና የውሣኔ ሃሣብ መሠረት ያደረገና ምንም አይነት የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሀምሌ 24 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይባፍ፡፡
3. ከበታች ፍርድ ቤቶች የመጡትን መዝገቦችና ከሥር ፍርድ ቤት የመጣው ካሴት ይመለስ፡፡
4. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አደነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- ሃለቃ ገ/እግዚአብሔር ኃይሉ -ጠበቃ ፈቃዱ ያሚ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ - በሌለበት የሚታይ ነው፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት የበታች ፍ/ቤቶች በሠጡት ጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡

አመልካች የተከሰሱት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ በቀን 02/06/2001 ዓ.ም ከምሽቱ 2፡30 ሰዓት ላይ የደን ጠባቂ ሆኖ ሲሰራ መንግስት ባስታጠቀው ክላሽ ጠመንጃ ሶስት ጥይት ተኩሶ ሟች አቶ ግደይ ትኩእ የተባሉትን መትቶ ገድሎታል በሚል ሲሆን አመልካች ስለድርጊቱ አፈፃፀም ክደው በመከራከራቸው ዐቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስጃዎችን በማቅረብ አስምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቶ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን በማረጋገጣቸው በዐቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብለው በ20 /ሃያ አመት/ ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኖባቸዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለትግራይ ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የሰጠውን የጥፋተኛነት ውሳኔ በማጽናት ቅጣቱን ብቻ በማሻሻል 15/ አስራ አምስት ዓመት/ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ጉዳዩ በሰበር አቤቱታ የቀረበለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በሚል ምክንያት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት ያላግባብ ከመሆኑም በላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ድንጋጌም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ያላገናዘበ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው ፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መታየት ያለበት መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና የሥር መዝገብ ውሳኔ ይዘት ከመረመረ በኋላ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ምላሽ የሚያሻው የሕግ ጥያቄ ሆኖ ያገኘው አመልካች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወ/ሕ/ ድንጋጌ አንቀጽ 540? ወይንስ 541? የሚለውን ነው፡፡ የህንኑ ለመፍታት የጉዳዩን አፈፃፀም እና መነሻ ሁኔታዎች በአጭሩ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ፍሬ ነገር ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት ቀን ሌሊቱን አመልካች ደን ለመጠበቅ ተቀጥረው ባለበትና መሳሪያውንም ለዚሁ አላማ ለማዋል በያዙት ሁኔታ የስር አቃቤ ሕግ ምስክሮችና ሟቹ ወደ ደኑ በመሄድ ዛፍ በመቁረጥ ላይ እያሉ በተፈጠረው አለመግባባት አመልካች ሁለት ጥይቶችን ከተኮሱ በኋላ ሶስተኛውን ጥይት በመተኮስ ሟችን በመምታት ለሕልፈት የዳረጉት መሆኑ በክርክሩ ሂደትና በአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል ጭምር ከተነገረው የአመሰካከር ይዘት መስፈሩን ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የተከሰሱበትን ወንጀል ስለመፈጸማቸውም አምነው ክደው የሚከራከሩት የአፈጻጸሙን ሁኔታ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ እንግዲህ አጠቃላይ የወንጀሉ አፈፃፀም ሁኔታ ይህንን የሚመስል ሲሆን አመልካች ለወንጀል ድርጊቱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት እስከዚህ ችሎት አጥብቀው የተከራከሩ ቢሆንም ስለወንጀሉ አፈፃፀም እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን የሚታይ ባለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር እንዳለ በመቀበል በህግ ረገድ የሚኖረውን ውጤት ብቻ መመልከቱ ተገቢ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን በሚከተለውን መልኩ አይተናል፡፡

አመልካች የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት በሕዝብ ደን ላይ አደጋ ለመከላከል እንደሆነ ከፍ ሲል የተመለከተውን ፍሬ ነገር እና ከወንጀሉ አፈፃፀም ከባቢያዊ ሁኔታ መረዳት ይቻላል፡፡

ድርጊቱ ወንጀል ነው ቢባልም በሕግ በተመለከተ ልዩ ሁኔታ በሕግ በተፈቀዱ ድርጊቶች የማያስቀጡ እና ይቅርታ የሚያሰጡ ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተመለከተውን ድንጋጌ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ማየት ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ለተያዘው ጉዳይ ቀጥታና አግባብነት ያለውን የወንጀል ሕግ ድንግጋጌ ቁጥር 78 እንመለከታለን፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት የራሱን ወይም የሌላውን ሰው መብት ሕገወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ሕገ ወጥ ጥቃት ለማዳን ጥቃቱ እንዳይደርስ ለማድረግ ሌላ መንገድ ሳይኖር ከሁኔታው መጠን ባለመለፍ የተፈፀመ ድርጊት አያስቀጣም ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተከሳሹ ከቅጣት ነፃ የሚሆነው ሕገወጥ ጥቃት በራሱ ወይም በሌላው ሰው መብት ላይ የተሰነዘረ ወይም በእርግጠኛነት ሊደርስ የሚችል ጥቃት ስለመኖሩ ይህንንም ለማስወገድ ወይም ለመከላከል ሌላ አማራጭ የሌለው ስለመሆኑ እና የወሰደው የመከላከል ወይም ጥቃቱን የማስወገድ እርምጃ ከተሰነዘረው ጥቃት ጋር ተመጣኝ ኃይል የተጠቀመ መሆኑን ማስረዳት ሲችል ብቻ ነው፡፡ ይህንኑ የሕጉን መንፈስ እና ይዘት መሰረት አድርገን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት በስር አቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል የተረጋገጠው ፍሬ ነገር በሕዝብ ደን ሟችና የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በሌሊት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰዓት የዛፍ መቁረጥ ተግባር መፈፀማቸው አመልካችም ለደኑ ጥበቃ ከመንግስት የታጠቁትን መሣሪያ በወቅቱ ይዘው በጥበቃ ላይ የነበሩ ስለመሆኑ አመልካች ደኑን ለማስከበር ያደረጉትን ጥረት በሚች ጥቃት ተሰንዝሮባቸው የነበረ ስለመሆኑ እና በደኑ ላይ አደጋ ሲሰነዘር አመልካች ሚች ከሁለት ጥይት ተኩስ በኋላ በሶስተኛው ጥይት የመቱት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ ፍሬ ነገር የሚያስገነዝበን በደኑ የተቃጣ ሕገወጥ ጥቃት ስለመኖሩ ነው፡፡ ይህንን ጥቃት ለማስወገድ አመልካች ተኩሰው ሰው መግደላቸው እና ማቁሰላቸው ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ተከትሎ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች የተሰነዘረውን ጥቃት ለማስወገድ ሌላ አመራጭ ያልነበራቸው ስለመሆኑ እና የወሰዱት አማራጭም ተመጣጣኝ ስለመሆኑ አስረድተዋል ወይ? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቧቸው መከላከያ ማስረጃዎች የሉም፡፡ አመልካች ሕገወጥ ጥቃትን ለማስወገድ እርምጃ ስለመውሰዳቸው የተመለከተ ቢሆንም እርምጃው ሌላውን አማራጭ የጨረሱ ስለመሆኑ እና ተመጣኝ ስለመሆኑ ለማስረዳት ያልቻሉ ስለሆነ በወ/ሕግ አንቀጽ 78 የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት አሟልተዋል ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ ስለዚህም ድርጊታቸው ሕገወጥ ጥቃትን ለማስወገድ ነው የሚያስብል መነሻ ቢኖረውም የፈፀሙት የነፍስ ግድያ ወንጀል በሕጉ ከተመለከተው መጠን በማሳለፍ መሆኑን መገንዘብ ችለናል፡፡

ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ደግሞ ከቅጣት ነፃ የማያደርግ ስለመሆኑ የወ/ሕ ድንጋጌ ቁጥር 79/1/ ያመለክታል፡፡ ይልቁንም ይህ አድራጎት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስለመሆኑ የዚህ ድንጋጌ ቁጥር 79/1/ ይገልፃል፡፡ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ከተረዳን የአመልካች ድርጊት ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚገባው በየትኛው የወ/ሕጉ ድንጋጌ ነው የሚለውን መሠረታዊ ጭብጥ ወደ ማየት ስንመለስ የአመልካች ድርጊት ህጋዊ መከላከልን ከመጠን ማሳለፍ መሆኑን መሠረት በማድርግ የወ/ሕጉ ልዩ ክፍል በዚህ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆን ድንጋጌ እንዳለው እንረዳለን፡፡ ይኸውም በወ/ሕጉ አንቀጽ 541/ሀ/ ሥር ከተመለከቱት የድንጋጌው ማቋቋምያ ምክንያቶች አንዱ ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የነፍስ ግድያ ወንጀል እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው የወ/ሕጉ አንቀጽ 79/1/ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አድርጐ በገለፀው አኳኋን አንቀጽ 541/ሀ/ ሁለተኛው ሐረግ ደግሞ ወንጀሉን ለማቋቋም እንደሚችል ደንግጓል፡፡

እንዲህ አይነት ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ ደግሞ በወ/ሕጉ አንቀጽ 82/2/ እንደተደነገገው ድርጊቱን ለማቋቋም የተደነገገው ልዩ ክፍል ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ ይህንን ለማለት የወንጀል ሕጉን ድንጋጌ ቁጥር 82/2/ እና 84/2/ ይዘት እና አቀራረጽ አገናዝቦ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች የፈፀሙት የወንጀል ድርጊት የወ/ሕጉን አንቀጽ 540 የሚያቋቁም ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የድርጊቱን አፈፃፀም ከባቢያዊ ሁኔታና ምክንያት በአግባቡ ባለማገናዘብ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን መረዳት ችለናል፡፡

ስለሆነም አመልካች የፈፀሙት የወንጀል ድርጊት የሕዝብ ደን ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን ሕገወጥ ጥቃት ለማስወገድ እና ለመከላከል ቢሆንም ድርጊቱ የተፈፀመው ሌሎች አማራጮችን ሁሉ አሟጠው ሳይጨርሱ መሆኑን አፈፃፀሙ ሲታይ ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን በማሳለፍ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የድርጊቱ አፈፃፀም የወ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 541/ሀ/ን የሚያቋቁም ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለዚህም አመልካች በ540 ሥር ጥፋተኛ መባላቸው አግባብ ሆኖ ስላላገኘው ይህንኑ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበትን ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2/ መሠረት ለውጠን አመልካች በወ/ሕግ ቁጥር 541/ሀ/ ሥር ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ አመልካች በዚህ ፍ/ቤት ጥፋተኛ የተባሉበት አንቀጽ አስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እንደሚያስቀጣ ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ በመሠረቱ ቀላል እስራት በመደቡ የሚጣለው ከአሥር ቀን እስከ ሦስት ዓመት የሚደርስ ስለመሆኑ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106/1/ ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ቀላል እስራት ቅጣት ከዚህ መደብ ጣሪያ ከፍ ብሎ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችለው በዚሁ አንቀጽ ሥር የተመለከቱት ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ስለመሆኑም ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ በማገናዘብ አመልካች ላይ ሊፈፀም የሚገባውን ቅጣት እንደሚከተለው ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ032878 ሚያዝያ12 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በ195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በዚሁ መሠረት አመልካች በወ/ሕግ 541/ሀ/ ድንጋጌ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የግድያ ወንጀል የፈጸሙ ጥፋተኛ ናቸው ብለን ወስነናል፡፡
3. አመልካች በዚህ ጉዳይ እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በአመስት /5/ ዓመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ ብለናል፡፡
4. የጥፋተኝነት አንቀጽ እና ቅጣቱ የተሻሻለ መሆኑን እንዲያውቀው የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ማረሚያ ቤቱ በዚህ ችሎት በተሻሻለው ቅጣት መሠረት እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የስልጤ ዞን ምርመራና ክስ ዐቃቤ ህግ ቃሲም ባደ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. አቶ ጌታቸው አስራት - ቀረቡ

2. አቶ አመነ ድሪባ - ቀረቡ

3. አቶ ሰንበቶ ጃራ - አልቀረቡም

4. አቶ ፋንታሁን ዘውዴ - አልቀረቡም

5. አቶ አድነው ያዕቆብ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በዳሎቻ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ለወረዳው ፍ/ቤት የወረዳው መርማሪ ከሣሽ ዐቃቤ ህግ ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 686 ንኡስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ በዳሎቻ ከተማ 01 ቀበሌ ልዩ ስሙ ሰሊም ሰፈር ከሚባለው አንደኛ ተከሣሽ ለመኖሪያ ቤት የተፈቀደለትንና የሰራውን ቤት አላግባብ ለመሰረተ ክርስቶስ አማኞች በመጸለያነት እንዲጠቀሙበት በመስጠቱ በርካታ የእምነት ተከታዮች ተሰባስበው ከግንቦት 22 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ ሁለት ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት ከፍተኛ ጩኸት በማሰማትና በድምጽ ማጉሊያ መሣሪያ በመጠቀም የሁከት ማድረስ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች ክሱን ክደው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ዐቃቤ ህግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ዐቃቤ ህግ በክሱ የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 113 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት በመለወጥ ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 815 ንኡስ አንቀጽ 1

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከተውን የደንብ መተላለፍ ጥፋት የፈጸሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው በብር 80 /ሰማኒያ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ተጠሪዎቹ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የክልሉ መርማሪ ከሣሽ የሰጠው አስተያየትና የቀረበውን ክርክር ተቀብሎ ከመዘነ በኋላ የክልሉ መርማሪ ከሣሽ የተጠሪዎችን የሰበር አቤቱታ በመደገፍ የተከራከረ መሆኑን በውሣኔው በገጽ 9 ካሰፈረ በኋላ የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር በወረዳው ፍ/ቤት በትዕዛዝ የተዘጋው የጸሎት ቤት እንዲከፈት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በዳሎቻ ወረዳ ፍ/ቤት የወረዳው መርማሪ ከሣሽ ያቀረበው የወንጀል ክስ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 02395 ቀርቦና ክርክር ተደርጉበት ፍ/ቤቱ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በተጠሪዎች ላይ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን የወንጀል ይግባኝ የስልጤ ዞን በመዝገብ ቁጥር 05761 በማየት የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

ተጠሪዎች የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡት የወንጀል ሰበር አቤቱታ በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 ሲታይና ክርክርና አስተያየት የተደረገበት እንደሆነ በየደረጃው የተከፈቱትን መዛግብትና አመልካች ያቀረበውን ክርክር ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከአንደኛው ተጠሪና ከአምስተኛው ተጠሪ ጋር የከተማዋን ፕላን መከበር ማዕከል ያደረገ ክስ የፍታብሔር ክርክር ለዳሎቻ ወረዳ ፍ/ቤት አቅርቦ ጉዳዩ ከወረዳው ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 02428 ክርክር ከተደረገበት በኋላ አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ የመኖሪያ ቤት እንዲገነቡ በተሰጣቸውና በሰሩት ቤት ከመኖሪያነት ውጭ ለሆነ አገልግሎት ማዋል የሌለባቸዉ መሆኑ ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ የፍታብሔር ይግባኝ ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአንደኛና የአምስተኛ ተጠሪን የፍታብሔር ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 05607 በማየት የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የህግም ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የሌለ መሆኑን ገልጾ ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ የወረዳው ፍ/ቤት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 02428 የሰጠውን ውሣኔ የዞኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት በፍታብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 05607 ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑን በመግለጽ ራሱን የቻለ የሰበር አቤቱታ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ሲመረምር ከቆየ በኋላ የፍታብሔሩን ጉዳይ የወንጀሉ ጉዳይ ከሚታይበት የሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 ጋር በማጣመር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከህግ ውጭ ሁለቱን መዛግብት በማጣመርና አግባብነት የሌላቸዉን የህግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች በበኩላቸው ጥር 9 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በወንጀሉ መዝገብም ሆነ በፍታብሔር መዝገብ የሚነሣው ክርክርና የሚያዘው ጭብጥ ተመሣሣይ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት ሁለቱን መዛግብት በማጣመር መርምሮ ውሣኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ አመልካች የመኖሪያ ቤት በመስራት እንድትገለገሉበት በተፈቀደ ቦታ ላይ ለአምልኮ አገልግሎት አውለዋል በማለት ያቀረበው ክስ በህገመንግስቱ የተረጋገጠልንን የሀይማኖትና የእምነት ነጻነት የሚጋፋ ነው፡፡ አገሪቱ ኋላ ቀር አገር በመሆኑ የመኖሪያ ሰፈር የኢንዱስትሪ ሰፈር የሚባል የሌላት ሲሆን ቤተክርስቲያንና መስጊዶችን በመኖሪያ ቤት ውስጥ ማግኘት የተለመደ ነው፡፡ ስለዚህ በመኖሪያ ሰፈር ለጸሎትና የአምልኮት ማከናወን አይቻልም በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ በመልስ መልሱ ከተማዋ እድገቷን የምትመራበት ፕላን አለ፡፡ በከተማዋ ፕላን መሠረት መስጊዶች ፣ ቤተክርስቲያንና የጸሎት ቤቶች መገንባት ሲያስፈልግ የሚገነቡበት ቦታ ተለይቷል፡፡ በፕላኑ መሠረትም የጸሎት ቤት መገንቢያ ቦታ ተሰጥቷቸው እያለ የመኖሪያ ቤታችን ተቀይሮ የጸሎት ቤት ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 36352 እና የፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 35808 ጋር በማጣመር ተጠሪዎች የፈጸሙት የሁከት ተግባር የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው በወረዳው ፍ/ቤት በወንጀል ተከሣሽ የነበሩት ሶስቱም ተጠሪዎች የነበሩ መሆኑንና ተጠሪዎች በወረዳው ፍ/ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 02395 በዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁ. 05761 ይግባኝ ባይ በመሆን የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ በመሆኑና የወረዳውና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከላይ ቁጥራቸው በተገለጸው ሁለት መዛግብት የሰጡትን የወንጀል ፍርድ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡ ስለዚህ የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡትን የወንጀል ፍርድ በመቃወም በክርክሩ ተሣታፊ የሆኑት አምስቱም ተጠሪዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የመኖሪያ ቤት ለመስራት የተፈቀደላቸውን ቦታና ለመኖሪያነት የሰሩትን ቤት ለአምልኮት አገልግሎት ለዘላቂነት እንዲውሉ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ከዚህ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት የፍታብሔር ክስ የመሠረተው የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነው፡፡ የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ክስ ያቀረበው በአምስቱ ተጠሪዎች ላይ ሣይሆን በአንደኛ ተጠሪና በአምስተኛው ተጠሪ ላይ ብቻ ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት በማዘጋጃ ቤቱ የቀረበውን የፍታብሔር ክርክር በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 02428 በማየት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 05607 በማየት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አንደኛና አምስተኛ ተጠሪዎች የወረዳውና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር አቤቱታቸው በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ሲመለከት የቆየ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍታብሔር ክርክር ከወንጀል ክርክር ጋር ሊጣመር የሚችልበት መሠረታዊ ሁኔታ በወንጀል ህግ አንቀጽ 101 የተደነገገ ሲሆን የፍታብሔር ክርክሩ የወንጀል ሰለባ የሆነ ሰው የሚያቀርበው የካሣ ጥያቄ በሆነ ጊዜ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ እንዲወሰንለት ማመልከት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፍታብሔር ክርክር በወንጀሉ ጉዳት ደርሶብናል የሚሉ ሰዎች ካሣ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወንጀል የሚደረገው ክርክርና በፍታብሔር በሚደረገው ክርክር የሚያዘው ጭብጥና የሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደዚሁም የማስረጃ አመዛዘን ሥርዓቱ የተለያየ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወንጀል መዝገብና በፍታብሔሩ መዝገብ ተከራካሪ የሆኑት ሰዎች የተለያዩ ናቸው፡፡

በፍታብሔር መዝገብ ተከራካሪ የሆነው የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሲሆን አመልካች የሚከራከረው የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤትን በመወከል ነው፡፡ የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሚከራከረው ከአምስቱ ተጠሪዎች ጋር ሣይሆን ከአንደኛውና ከአምስተኛው ተጠሪ ጋር ብቻ ነው፡፡ በወንጀሉ መዝገብ ከስር ጀምሮ የመርማሪ ከሣሽና በአምስቱ ተጠሪዎች ተከራካሪ መሆናቸውን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና አንደኛና አምስተኛ ተጠሪ በፍታብሔር የሚከራከሩበትን የሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 አመልካችና ተጠሪዎች ከሚከራከሩበት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 36352 ጋር በማጣመር ማየቱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 101 መሠረታዊ የህግ ድንጋጌ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

2. ተጠሪዎች ከግንቦት 22 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ጸሎት እንዲደረግ ሁኔታዎችን በማመቻቸት በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ የድምጽ ሁከት የመፍጠር የደንብ መተላለፍ ጥፋት ፈጽመዋል በማለት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልጾ አመልካች አስተያየትና ክርክር ያቀረበ መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 በሰጠው ውሣኔ በግልጽ አስፍሯል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የደንብ መተላለፍ ጥፋት እንዳልፈጸሙ የክልሉ ሰበር ችሎት በሰጠው አስተያየትና ባቀረበው ክርክር የተከራከረ በመሆኑ ተጠሪዎች በወንጀሉ ጥፋተኛ ተብለው የተወሰነባቸውን ቅጣት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሻረው አግባብ ነው በማለት የቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሻረው የአመልካችን ክርክርና አስተያየት መሠረት በማድረግ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የወንጀሉን ጉዳይ በተመለከተ በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር የሰጠውን ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 195 ንኡስ አንቀጽ 2/ለ/1 መሠረት አጽንተናል፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ክርክር የያዘውን የሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ከወንጀል መዝገብ ቁጥር 36352 ጋር በማጣመር አይቶ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የወንጀሉን ጉዳይ በተመለከተ በመዝገብ ቁጥር 36352 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በዳሎቻ ወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 02395 የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔና የስልጤ ዞን በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 05761 የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪዎች ከቀረበባቸው የወንጀል ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አንደኛ ተጠሪና አምስተኛ ተጠሪ የዳሎቻ ወረዳ ፍርድ ቤት ከዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ጋር የነበራቸውን የፍታብሔር ክርክር በማየት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 02428 የሰጠው ውሣኔ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 05607 ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ያቀረቡትን ክርክር የወንጀሉ ጉዳይ ከሚታይበት የሰበር መዝገብ ቁጥር 36352 አጣምሮ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተሽሯል፡፡
3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪና አምስተኛ ተጠሪ በሰበር መዝገብ ቁጥር 35808 ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አመልካች የዳሎቻ ከተማ ማዘጋጃ ቤትን በመወከል ያቀረበውን ክርክር የወረዳ ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍታብሔሩን ጉዳይ በተመለከተ የሰጡትን ውሣኔና ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጓቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 391/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ የወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ/ቁ. 62332

ቀን 29/9/ 2003 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- አቶ ዘለቀ ካሣዬ - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- የፌዴራል ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን በፌ/ከ/ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረው በቸልተኝነት ሰው በመግደል የሚል ነበር፡፡ ዐቃቤ ሕጉ አቅርቦት የነበረው ክስ ተከሳሽ /የአሁን አመልካቹ / የትራንሰፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁ . 279/56 አንቀጽ 35 እና የ1996 ዓ/ም ወ/መ/ህግ አንቀጽ 543 /3/ የተመለከተውን ተላለፎ የሚያሽከረክረው ታርጋ ቁ 1-10432 አ/አ የሆነውን መኪና ታህሳስ 20/01 ዓ/ም ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ በዬሐንስ ቤተክርስቲያን ልዩ ስሙ ሰባራ ባቡር እየተባለ በሚጠራው አካባቢ በእግረኛ ማቋርጫ ዜብራ ላይ ቅድሚያ ባለመስጠት ተክሉ ጌታሁን የተባለውን በቸልተኝነት ገጭቶ ገድሎአል የሚል ነበር ፡፡

ክሱን የሰማው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኖ ግን ጥፋቱ ያለመሆኑን ስለካደ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ በወ/መ/ሕግ አንቀፅ 59/1/ /ሀ/ እና 543/3/ ስር ጥፍተኛ ነው በማለት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ በአንድ አመት ከ6 ወር ፅኑ እስራትና ብር 10,000 / አስር ሺህ/ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የፌ/ዐቃቤ ሕግ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅረቦ ፍ/ቤቱም ካከራከረ በኃላ ቅጣቱ በአምስት አመት ፅኑ እስራት ከፉ አድርጉ የወሰነ እና የገንዘብ መቀጮውን ባለበት ያልተነሳ መሆኑን ወስኗል ፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በጠበቃው አማካኝነት ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ/ም 3 ገፅ ማመልከቻ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የተለያዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በማቅረባችን የከፍተኛው ፍ/ቤት ከግምት አስገበቶ ቅጣት የቀለለና ከመነሻው ዝቅ ብሎ መቅጣቱ ግልፅ ሆኖም እያለ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጉጅን ወደ ሕክምና ቦታ መውሰድ በሕግ ማለትም በወ/መ//ሕግ ቁ . 575/2/ ሥር የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣቱ እንጅ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ዐ/ሕግ በቀን 10/6/2003 ዓ/ም በ2 ገፅ መልስ ስጥቷል ፡፡ የመልሱ ፍሬ ሀሳብ የተባለው የቅጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማቅለያ መክንያት ቅጣቱን ከመነሻው ዝቅ የሚደርግ ባለመሆኑ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡

የአመልካች ጠበቃ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን በአቤቱታውም የቀረበውን ክርክር ከተያዘው ጭብጥና አግባበነት ካላቸው ሕጉ ጋር በማገናዘብ መርመሮታል ፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ጉዳይ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ከመነሻ ቅጣት / አምስት ዓመት ፅኑ እስራት / በታች የሚቀጣበት ምክንያት የለም የማለቱን አግባብነት በመመልከት መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ በዚሁ መሰረት በሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል አመልካች ግጭቱን ካደረሰ በኋላ ማለትም የሐኪም ዕርዳታ እንድታገኝ ማደረጉ በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 82/1/ /ሠ/ መሰረት ቅጣቱን ሊያቀለው የሚገባ ነው ወይስ አይደለም ? የሚል በመሆኑ ችሎቱም ከዚህ ጭብጥ አኳያ ብቻ በመመልከት መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ በመሠረቱ አንድ ጉዳት የደረሰበት ሰው ወይም በአደጋ ላይ የሚገኘውን ሰው አለመርዳት የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል መሆኑ በወ/መ/ሕግ ቁ 575 ሥር የተደነገገ ከመሆኑም በላይ ጉዳቱን ያደረሰው ተከሳሽ ራሱ በሆነበት ጊዜ ደግሞ የበለጠ የወንጀል ኃላፊነት የሚጥል ስለመሆኑ ከወ/መ/ ሕግ ቁጥር. 575 /2/ ሥር መረዳት ይቻላል ፡፡ ይሄንን ኃላፊነት ያልተወጣ ተከሳሽ ለዚህም ተጨማሪ የወንጀል ኃላፊነት በተደራራቢነት ሊጠየቅ እንደሚችልና አመልካች ወደ ሕክምና ማዕከል ማድረሱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣቱን የሚያመለክት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 82/1/ /ሠ/ መሰረት ተከሳሽ በእዉነት የተፀፀተ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲገነዘብ ቅጣት ሊያቀልለት እንደሚችልና በእውነት ስለመፀፀቱ ከመገልጫዎቹ አንዱ በደል ለደረሰበት ሰው አስፈላጊውን እርዳታ ማድረጉ ሊሆን እንደሚችል ተቀምጧል ፡፡ ይሄ ማለት ግን ተከሳሽ ተበዳይን ወደ ሕክምና ማዕክል ማድረሱ ብቻ በፈፀመው ድርጊቱ በእውነት ተፀፅቷል የሚያሰኝ ሳይሆን ጉዳዬን በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በይግባኝ ያየው ፍርድ ቤት አጠቃላይ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በማመዛዘን የሚደርስበት መደመደሚያ ነው፡፡

አመልካች ተበዳይን ወደ ሕክምና ማዕክል ማድረሱ አጠቃላይ የክሱን ሂደት ከግምት በማስገባት አመልካች በእውነት ተፀፅቷል የሚያሰኝ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው ነጥብ የማስረጃ ምዘና በመሆኑና የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን ደግሞ በሕግ መንግስቱ አንቀፅ 10 መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት ማረም እንደመሆኑ መጠን የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ተበዳይን ለሕክምና ማዕከሉ ማድረሱ ሌላ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአመልካች ላይ የተጣለውን ኃላፊነት መወጣቱን እንጂ ቅጣቱን ለማቅለል የሚያበቃ አይደለም ማለቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘንም፡፡ በዚሁ መሰረት ቀጥሎ የተመለከተው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 54154 በቀን 24.2.2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/2/ /መ/ መሰረት ፀንቷል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመልስ ፡፡

ሰ/ረ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ መሐመድ ሰይድ አሊ - ጠበቃ እሸቱ ዓሊ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - በሌሉበት የሚታይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ወንጀል ህግ አንቀጽ 27 እና 593ን በመተላለፍ በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ወደ ውጪ አገር ለመላክ መሞከር ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካችም ፍርድ ቤት ቀርበው የአቃቤ ሕግ የክስ ቻርጅ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሲጠየቁ የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸውን በዝርዝር በማመናቸው በእምነታቸው መሠረት በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበበት አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ተብለውና የቅጣት አስተያየት ቀርቦ ከተመዘገበ በኋላ በቅጣት መመሪያው መሠረት በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እና በብር 100 (አንድ መቶ) እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ብቻ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195 /2/መ/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም አመልካች ድርጊቱን እንደአመኑ ተደርጎ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመለኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን ቅሬታ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ ከድርጊቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም አንዲሁም አመልካች ላይ ከተጣለው የቅጣት መጠን አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት ኢትዮጵያዊያኑን ከሕግ ውጪ ወደ ውጭ አገር ሊልኩ ሲሉ ተይዘዋል በሚል ሲሆን ይህንኑ ደርጊት መፈፀማቸውን በዝርዝር አምነዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ድርጊቱን በዝርዝር ማመናቸውን መሠረት በማድረግም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 134/1/ መሠረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጠቷል፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት ጉዳዩን በዝርዝር ማመናቸው ተረጋግጦ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በእምነቱ መሠረት በሚሰጠው የቅጣት ውሳኔ ሕጋዊነት ላይ ይግባኝ ማለት ከሚቻል በስተቀር በእምነት መሠረት በሚሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ የማይችል ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 185/1/ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል ፡፡ አመልካች ይህንኑ በመገንዘብም ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርቡ በስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ አለማቅረባቸውን በሰበር አበቱታቸው በግልጽ የገለፁት ከመሆኑም በላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ይህንኑ በሚገባ ይረጋገጣል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጠር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የተሰጠው ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር ማረም ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ያቀረቡት ቅሬታ የእምነት ቃላቸው በዝርዝር የተሰጠ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት ከተመዘገበው ይዘት ውጪ በመሆኑና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ካለው ሥልጣን አንፃር ሲታይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ በሕጉ አተገባበርና በውጤት ደረጃ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/መ/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ያሲን አሕመድ መሐመድ አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ባምላኩ አንዳርጌ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በሥር ፍ/ቤቶች የተላለፈበትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ቅሬታ ስላነሳ ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች የተከሰሰው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) የተመለከተውን በመተላለፍ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ ነው፡፡ ድርጊቱም ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) የሚያወጣ ቆርቆሮ ገዝቼ አመጣለሁ በማለት ከግል ተበዳይ ገንዘቡን የወሰዱና ቆርቆሮውን ግን ሳያመጣ መቅረቱን የሚያመለክት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ድርጊቱን አለመፈጸሙን በመግለጽ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኋላም ክሱን የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መጀመሪያ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን ሰምቶ አመልካች ሊከላከል ይገባል የሚል ብይን ሰጥቶአል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃ የሰማ ሲሆን በመጨረሻም አመልካች በዐቃቤ ህግ ክስ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት የፈጸመ መሆኑን አረጋግጫለሁ በማለት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የጥፋተኝነት ውሳኔውን እንዳለ በማፅናት በሥር ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የአንድ ዓመት ከሁለት ወር ጽኑ እስራት ወደሰባት ወር ቀላል እስራት ዝቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 25 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ዐቃቤ ሕግ (ተጠሪ) ባቀረበበት ክስ መሠረት ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራቀኝ ወገኖች ይህን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ በዝርዝር እንዳመለከትነው በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት አልፈጸምኩም በማለት አመልካች ቢከራከርም፤ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት ግን ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በማስረጃ አረጋግጦአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው ፍ/ቤትም እንደዚሁ የተሰማውን ማስረጃ በመመዘን በድርጊቱ መፈጸም እርግጠኛ ሆኖአል፡፡ እንደሚታየው ድርጊቱ ተፈጽሞአል ወይስ አልተፈጸመም የሚለው የፍሬ ነገር ጭበጥ በመሆኑ የሚነጥረው (የሚጣራው) በማስረጃ ነው፡፡ የፍሬ ነገር ጭብጥን በማስረጃ የማጣራት እና የተሰማውን ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን በዚህ መልክ በመምራት መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡ በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተው ድርጊት በአመልካች መፈጸሙን በማረጋገጣቸውም ድርጊቱ ከተጠቀሰው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ጋር አገናዝበው የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡

በበኩላችንም እንደምናየው አመልካች በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት ፈጽሞአል ወይስ አልፈጸመም የሚለውን የፍሬ ነገር ጭብጥ የማጣራት ሥልጣን ለሰበር ችሎቱ የተሰጠ ባለመሆኑ በዚህ ደረጃ የምንመረምረው አይደለም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ በክሱ በተጠቀሰው ድንጋጌ የተመለከተውን ወንጀል ያቋቁማል ወይ የሚለው ነጥብ ግን የሕግ ጭብጥ በመሆኑ ተመልክተነዋል፡፡

አመልካች የተከሰሰው በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 675(1) የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፎ ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ድንጋጌው የሚለው

“ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽናግ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማሰገኘት በማሰብ፣ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ፣”

ጥፋተኛ ተብሎ በሕጉ የተመለከተውን ቅጣት ይወስንበታል ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች የግል ተበዳይ ለቆርቆሮ መግዣ በማለት የወሰደውን ገንዘብ ወስዶ አስቀርቶአል፡፡ ገንዘቡ ቆርቆሮውን አልገዛበትም ወይም ለሰጠው የግል ተበዳይ አልመለሰም፡፡ ይህ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦበታል፡፡ ገንዘቡን አስካልመለሰ ወይም ለተባለው አገልግሎት ስለማዋሉ እስካላስረዳ ድረስ ደግሞ በድንጋጌው የተመለከተውን ወንጀል ፈጽሞአል ለማለት ነው የሚቻለው፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካች የፈጸመው በማስረጃ የተረጋገጠበት ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁም ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የምንልበት ምክንያት የለም፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ 102615 ጥር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቶአል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

ራ/ታ ***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።***

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አረጋሽኝ መርዕድ - ጠበቃ ግሩም አየለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 34393 የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ እያለ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዕናቱ ተገቢ ባለመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ጥር 24 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካችና በሌሎች አራት ሰዎች ላይ የሙስና ወንጀል ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው የክስ ይዘትም አመልካች የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የህግ ኤክስፐርት ሆኖ በሚሠራበት ጊዜ ንብረትነቱ የወ/ሮ ኤስሚንግ አግኑያ የሆነውንና በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 20 ቀበሌ 29 ቁጥሩ 214 የሆነውን መኖሪያ ቤት በከፍተኛው ፍርድ ቤት አራተኛ ተከሳሽና አምስተኛ ተከሳሽ የነበሩትንና ክሳቸው የተቋረጠውን አቶ አብዲሣ ሁሪሣና አቶ ሳምሶን ጋርቮልድ አላግባብ ብልፅግና እንዲያገኙ በማሰብ የአባታችን ቤት አላግባብ የተወረሰብን ስለሆነ ይመለስልን በማለት ለኤጀንሲው ያቀረቡትን አቤቱታ የሚያረጋግጥ የይዞታ የምስክር ወረቀት መብራትና ውሀ ያስገቡበት ውልና የቤት ሥራ ፈቃድ ሣያቀርቡ በቀበሌ ፍርድ ሸንጎና በምስክር የተረጋገጠ ስለሆነ እንዲመለስላቸው የሚል የውሣኔ ሀሳብ በሥር አንደኛና ሶስተኛ ተከሳሾች ለነበሩት የፕራይቬታይዜሽን የሥራ ኃላፊዎች በማቅረብ በወንጀል ህግ 33 እና 32(1)ሀ እና በተሻሻለው ልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ 214/74 አንቀፅ 23 የተደነገገውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት በሥልጣን አላግባብ የመገልገል ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ነው፡፡

አመልካች ወንጀሉን አልፈፀምኩም ብለው የተከራከሩ ቢሆንም ከላይ መለያው የተገለፀውን ቤት በሚመለከት በሳምሶን ጋርቮልድ ስም ሁለት ሺህ ካሬ ሜትር ካርታና ፕላን፣ በወ/ሮ ኤስሚንግ አግኑያን ስም አንድ ሺህ ካርታና ፕላን በማስረጃነት ቀርቦ የአዲስ አበባ ከተማ ልማት ቢሮ ተጠይቆ ቢሮው ቤቱ ያረፈው በወ/ሮ ኤስሚንግ አግኑያን ቦታ ላይ እንደሆነ አረጋግጦ መግፉን፣ ቤቱ የገባው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውሀና የመብራት ቢል የወ/ሮ ኤስሚንግ አግኑያን ስም መሆኑን እንደሚያረጋግጥና አመልካች የውሣኔ ሀሳብ ለማቅረብ የምስክርነት ቃላቸውን ያሰማቸው ምስክሮች ቤቱ ከአዋጅ ውጭ የተወረሰ መሆኑን ለማስረዳት የቀረቡ ቢሆንም የተጠሩበትን ጭብጥ የሰጡት ምስክርነት የሌለ መሆኑና ከመጡበት ጭብጥ ውጭ ቤቱ የሳምሶን ጋርልቮልድ ነው በማለት መመሥከራቸውንና ይህንን መነሻ በማድረግ አመልካች ቤቱ ለሳምሶን ጋልቮልድ ወራሾች እንዲመለስ የውሣኔ ሀሳብ በሥር አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሽ ለነበሩት የኤጀንሲው ሀላፊዎች ማቅረባቸው በዐቃቤ ህግ አንደኛ ምስክርና በሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል በማለት አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ብይን ሰጥቶ፣ አመልካች ከአንደኛና ሶስተኛ ተከሳሾች ጋር በጋራ ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አመልካች በዐቃቤ ህግ ክስ የተጠቀሰውን ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቶ አመልካች በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በከፍተኛው ፍርድ ቤት በተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)ለ(2) መሠረት አፅንቶታል፡፡

አመልካች ለሰበር አቤቱታው የውሣኔ ሀሳብ ያቀረቡት የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ከሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር ከአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የተላፈውን ደብዳቤና ማህደር በማየት ነው፡፡ ካርታው እውነተኛ መሆኑ ተረጋግጧል ይህ የተሣሣተ ከሆነ ፍርዱ እንዲታረም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 6 ከሚጠየቅ በስተቀር እኔ በወንጀል መጠየቁ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠያቂም የምሆን ከሆነ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ 420(1) የሙያ ግዴታን ጥሰሀል በሚል መሆን ሲገባው በሥልጣን አላግባብ ተገልግሏል ተብዬ ጥፋተኛ መባሌ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ወንጀል መሥራቴን ከተገቢው ጥርጣሬ ውጭ አላስረዱብኝም፡፡ ምስክርነት መስማት በአዋጅ ቁጥር 110/87 እና በመመሪያ ቁጥር 001/88 የተፈቀደ ነው በወንጀል ሊያስጠይቀኝ አይገባም ስለዚህ የህግ አስተያየት ስለሰጠሁ ብቻ ወንጀል ሠርተሀል ተብዬ የተወሰነብኝ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ቤቱ በሥር አራተኛና አምስተኛ ተከሳሽ ለነበሩ ሰዎች እንዲመለስ የውሣኔ ሀሳብ የቀረበው ማስረጃ ሣይቀርብለትና ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ ነው፡፡ ስለሆነም በግብረአበርነት መከሰሳቸውና ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ ነው፡፡ የዐቃቤ ሕግ በሰውና በዕሐፍ ማስረጃ አመልካች ተገቢውን ማጣራት ማድረግ የነበረባቸው መሆኑን አስረድተዋል በአጠቃላይ አመልካች በሰበር ያቀረቡት የህግ ሣይሆን የፍሬ ጉዳይ ክርክር በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድ እንዲፀናልን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ፈፀመ የተባለው አከራካሪው ቤት በተመለከተ በአራተኛና አምስተኛ ተከሳሽ በነበሩት ሰዎች በኩል ያቀረቡትን ማስረጃዎች በማገናዘብ የሙያ አስተያየትና የውሣኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡ አመልካች አከራካሪው ቤት ለአራተኛና ለአምስተኛ ተከሳሾች ቢመለስ የህግ ድጋፍ ያለው ነው የሚል የውሣኔ ሀሳብ ከማቅረብ ውጭ በጉዳዩ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣንና ኃላፊነት የለውም፡፡ ይኸም በመሆኑ አመልካች በዐቃቤ ህግ ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተዘረዘሩትን ስህተቶች የፈፀመው በሥር አራተኛና አምስተኛ ተከሳሽ የነበሩትን አላግባብ ለመጠቀምና ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና እንዲያገኙ ነው ወይስ እንደማንኛውም ባለሙያ የሙያ ሥራውን በሚሰራበት ወቅት ተገቢውን የሙያ ትጋት እና ጥንቃቄ ባለማድረጉ ነው የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ አመልካች ለመኖሪያ ቤቱ የሙያ ግልጋሎት ሲሰጥ ሊመራባቸው በሚገቡት የሕግ ማዕቀፎች ማለትም አዋጅ ቁጥር 110/87 እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈጸም ከወጣው መመሪያ 001/88 ከሚፈቅዱት ውጭ በመውጣት በሥር አራተኛና አምስተኛ ተከሳሾች የነበሩትን ሰዎች ጥቅም ለማስገኘት ሲል የፈፀመው ተግባር ያለ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ አመልካች የሚመራባቸውን የህግ ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግ ተገቢውን ሙያዊ ማጣራት ሲያደርግ ሁሉንም ማስረጃዎች በአግባቡ ያላገናዘበ በተለይም የአራተኛና አምስተኛ ተከሳሾች ቤት ነው የተባለው ሰው በተመለከተ ካርታና ፕላን የቀረበለት ቢሆንም የመብራትና የውሀ ቢል በግል ተበዳይ ወ/ሮ ኤስሚንግ አግኑያን ስም የሆነበትን ትክክለኛ ምክንያት ሣያገናዝብና ሣያጣራ የውሣኔ ሀሳብ በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሳሽ ለነበሩት የመምሪያ ኃላፊውና ለአንደኛ ተከሳሽ ማቅረቡ ነው፡፡ የመወሰን ሥልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ብቻ ያለባቸው ሰዎች ግልፅ በሆነ ሁኔታ አንድን ሰው ለመጥቀም ወይም ራሳቸውን ለመጥቀም በማሰብና ኃላፊዎቻቸውን ለማሣሣት የፈፀሙት ጉልህ ተግባር መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ በሥልጣን አላግባብ የመገልገል ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው ሊጠየቁ አይገባም፡፡ ስለሆነም አመልካች የሙያ ተግባሩንና ሥራው በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመፈፀሙ ምክንያት በመንግስትና በግል ተበዳይ ላይ ዐቃቤ ህግ በክሱ የገለፀው ጉዳት ቢኖርም አመልካቹ ጥፋተኛ መባል የሚገባው በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 214/74 አንቀጽ 23(1)ሀ መሆን ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ አንፃር የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምፅ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔና የጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

አመልካች የፈፀመው የተቀጠረበትን የሙያ ሥራ በጥንቃቄና በአግባቡ አለመፈፀም ወንጀል ነው፡፡ ይህ ወንጀል ከሶስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እንደሚያስቀጣ በአዋጅ ቁጥር 214/74 አንቀፅ 25 ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ከአዋጅ ቁጥር 214/74 በኋላ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የተደነገገ በመሆኑና በወንጀል ህጉ የሥራ ሀላፊነትን አለመወጣት ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑ በወንጀል ህግ አንቀፅ 420 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ በመሆኑና በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 2 ወንጀሉ ከተፈፀመ በኋላ የወጣው የወንጀል ህግ ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚ እንደሚሆን የሚደነግግ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2/ እና በህገ መንግስቱ አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በመለወጥ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀፅ 420 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ የሥራ ሀላፊነትን ያለመወጣት ወንጀል ፈፅሟል በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

የቅጣቱን መጠን በተመለከተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቅጣቱን አቅልሎ ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች ያሉ መሆኑን በቅጣት ውሣኔው የመዘገባቸውን ነጥቦችና አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት የወንጀል ህግ አንቀፅ 420 ንዑስ አንቀፅ 1 ከስድስት ወር በማይበልጥ እሥራት የሚያስቀጣ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና በወንጀል ህግ አንቀፅ 88 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የአመልካችን ግላዊ ሁኔታዎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሶስት ወር እስራት እንዲቀጣ በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)ለ2 መሠረት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በማሻሻል ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የሥራ ሀላፊነትን ባለመወጣት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በሶት ወር እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 5 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ነብይ በድሩ ሸፋ ጠበቃ ማርቆስ ወ/ሰንበት - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ሥ/ፀ/መ/ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ ዋልተ ንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 66890 የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 51161 ማፅናቱ በሰበር የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ጭብጥ ተይዞ በመቅረቡ ነው፡፡

በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካችና በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው አቶ ቶውፊቅ ሹፌ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሠ/ እና /ለ/ በአንቀጽ 427 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ግብረ አበር በመሆን የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን መረጃና ክትትል ሠራተኛ የሆነውን አቶ ሰለሞን ታደሠን በሥራው ኃላፊት ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ በማሰብ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ባለመክፈል የማታለልና የሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ለመያዝ ይደረግባቸው የነበረውን ምርመራና ክትትል እንዲቋረጥ አድርግልን በማለት መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ከፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ህንፃ ቢሮ ቁጥር 207 ድረስ በመግባት ብዛቱ አሥራ አምስት እሽግ የሆነ እያንዳንዱ አሥር ሺህ ብር የያዘ በሁለተኛው ተከሣሽ አማካኝነት ለአቶ ለለሞን ታደሠ የሰጡ በመሆናቸው በግብረአበርነት በመላ ሀሳባቸውና አድራጎታቸው ሙሉ ተካፋይ በመሆን የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ግራ ቀኙ የቅድመ ክስ ክርክር እንዲያደርጉ ካደረገ በኋላ የተማመኑበት ነጥብ የሌለ በመሆኑ የተጠሪን ምስክሮች ሰምቷል፡፡

የመጀመሪያው የዐቃቤ ሕግ ምስክር የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የክትትል ሠራተኛ መሆኑን ገልፆ፣ መጋቢት 17 2000 ዓ.ም. ከጧቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን ሁለተኛ ተከሣሽ አቶ ቶፊቅ ሹሬ አቶ ታደሠ ከሚባል ሰው ጋር ከቢሮ ድረስ መጥተው ሁለተኛ ተከሣሽ የአጎቱ ልጅ አንደኛው ተከሣሽ በኮሚሽኑ ምርመራ እየተደረገበት ነው፡፡ ቤተሰብ እየተጨነቀ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአንደኛው ተከሣሽ ላይ የተጀመረውን ክትትልና ምርመራ አቋርጥልን ለአንተም ትጠቀማለህ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ እንሰጥሀለን፡፡ ሁለተኛ ተከሣሽ 18/07/2000 ብሩን ይዞ እንዲመጣ ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ቀጠርኩት፣ ሁለተኛ ተከሣሽ ብር ይዞ እንደሚመጣና በአንደኛ ተከሣሽ ላይ የሚደረገው ምርመራና ክትትል እንዲቋረጥለት እንደሚፈልግ፣ ይህ ከሆነ አንደኛ ተከሣሽ ከተቀበለለት እንደሚመጣ ለኮሚሽነሩና በየደረጃው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎችና የሥራ ባልደረቦች ሪፖርት አደረግሁ፡፡ ከሁለተኛ ተከሣሽ ጋር ሣደርግ የነበረውን ንግግር በመቅረፀ ድምፅ ቀረፅኩ፡፡ ሁለተኛ ተከሣሽ 18/07/2000 ብሩን በፌስታል ይዞ መጥቶ ዘበኞች አናስገባም ሲሉ እንዲያስገቡት ነገርኳቸው፡፡ አሥራ አምስት ባለ አሥር ሺ ብር ጥቅል ገንዘብ አመጣ ንግግራችንን ቀረፅኩት፡፡ አንደኛ ተከሣሽ ምርመራው የሚቋረጥለት ከሆነ እንደሚመጣ ነገረኝ፡፡ መጋቢት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት አንደኛ ተከሣሽን ይዞ ለመምጣት ተቀጣጠርን፡፡ 21/07/2000 ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ይዞት መጣ፡፡ አንደኛ ተከሣሽ 21/07/2000 ዓ.ም. ከሁለኛ ተከሣሽ ጋር ቢሮዬ ድረስ መጥቶ በጉምሩክ ማጭበርበር እንደተከሰሰ ለእኔ ብር 150,000 የላከልኝ መሆኑን ምርመራውና ክትትሉ ከተቋረጠለት ወደፊት ውለታ እንደሚውልልኝና ሌሎች ዝርዝር ነገሮችን አወራ፡፡ እኔም በመቅረፀ ድምፅ ቀረፅኩት፡፡ ከዚያ በኋላ ወጥተው ሲሄዱ አንደኛ ተከሣሽና ሁለተኛ ተከሣሽ በቁጥጥር ሥር ዋሉ፡፡ ገንዘቡ በኃላፊዎች ትዕዛዝ ባንክ ገቢ ሆኗል በማለት መሥክሯል፡፡ ሌሎቹ ምስክሮች ሁለተኛ ተከሣሽ በፌስታል ገንዘብ ይዞ ሊገባ ሲል በመፈተሽ አናስገባም ብለው በአንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ትዕዛዝ ገንዘቡን ይዞ የገባ መሆኑንና አንደኛና ሁለተኛ ተከሣሾች አንደኛ ዐቃቤ ሕግ ምስክር ጋር ቀጠሮ አለን ብለው ከገቡ በኋላ ሲወጡ የያዟቸው መሆኑን መስክሯል፡፡ አመልካች በ18/07/2000 አገር ውስጥ ያልነበሩ መሆኑን በማስረዳት ፓስፖርት ያቀረቡ መሆኑን ከበታች ፍ/ቤት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ /አመልካች/ በሁለተኛ ተከሣሽ በኩል ሲደራደሩ ቆይተው የዐቃቤ ሕግ አንደኛ ምስክር የሆነው የኮሚሽኑ የክትትልና ምርመራ ሠራተኛ በሥራ ኃላፊነት ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ብር 150,000 በሁለተኛ ተከሣሽ በኩል ከሰጡ በኋላ መጋቢት 27/2000 ዓ.ም. በግንባር ከሁለተኛው ተከሣሽ ጋር ከአንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጋር በመቅረብ ገንዘቡን የላኩት እሳቸው መሆናቸውንና ወደፊትም ውለታ እንደሚውሉለት መግለፃቸውና ገንዘቡ ከጉምሩክ ቀረጥ በማጭበርበር የተገኘ መሆኑን ያረጋገጡ መሆናቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/1/ እና /3/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሙስና ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው ብሎ አመልካች በሰባት ዓመት ፅኑ እሥራትና በብር አሥር ሺህ ብር መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙ የሚጣራ ሕግ ወይም የፍሬ ነገር ነጥብ የሌለው መሆኑን ገልፆ የአመልካችን ይግባኝ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/1/ መሠረት ሠርዞታል፡፡ አመልካች በኮሚሽኑ እንደሚፈለግ መጥሪያ በተጻፈበት መጋቢት 12 ቀን 2000 ዓ.ም. ከአንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጋር ሁለተኛው ተከሣሽ ጉቦ ለመቀበል ተደራድረዋል በተባለበት መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም.፣ ሁለተኛ ተከሣሽ ገንዘቡን ለአንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሰጥተዋል በተባለበት መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ አልነበሩም ስለዚህ በወንጀሉ ተካፋይ ነው ተብሎ የተሰጠብኝ የጥፋተኝነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ጉቦ ተቀባይ ሣይኖር ጉቦ የመስጠት ወንጀል ሊፈፀም ስለማይችል አንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጉቦ ተቀባይ ነው ባልተባለበት ሁኔታ ጉቦ የመስጠት ወንጀል ፈፅመሀል ተብዬ ጥፋተኛ መባሌ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉምሩክ ቀረጥ ባለመክፈል ወንጀል ተጠርጥሮ ክትትል ይደረግበት የነበረው ወንጀል ክስ በተመሠረተበት ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቱ በዚህ ጉዳይ የጥፋተኝነት ውሣኔ ወስኖ የቅጣት ውሣኔውን እንዲያቆይልን ያቀረብነውን ጥያቄ ባለመቀበል ቅጣት መወሰኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 63 እና አንቀጽ 184 ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ መባል አይገባኝም እንጂ ጥፋተኛ እንኳን ብባል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 27/1/ እና በአንቀጽ 427/1/ መሆን ሲገባው ወይም በአናሣው ድምፅ ውሣኔ መሠረት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/1/ ጥፋተኛ መባል ሲገባኝ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/1/ እና /3/ ጥፋተኛ ነው በማለት የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ አመልካችና በሥር ፍ/ቤት ሁለተኛ ክሣሽ የነበረው ሰው ያሰቡትን ውጤት ያላገኙ ቢሆንም ጉቦ የመስጠት ወንጅሉን ሙሉ በሙሉ ፈፅመው አጠናቀዋል፡፡ ስለዚህ ወንጀሉ የሞራላዊ ግላዊና ሕጋዊ መስፈርቶችን በማያሟላ መልኩ የተፈፀመ ሆኖ እያለ ሙከራ ነው እንዲባል የቀረበው የሰበር አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ከአሥራ ሦስት ሚሊዮን ብር በላይ የቀረጥ ማጭበርበር ፈፅሞ ይደረግበት የነበረው ክትትል እንዲቋረጥለት ለማድረግ የፈፀመው ድርጊት በአዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2/9/ በተሰጠው “ከባድ ሙስና” ትርጉም የሚካተት ነው፡፡ ስለዚህ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/1/ ጥፋተኛ መባል ይገባኝ ነበር በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ የቅጣት ውሣኔውን በተመለከተ አመልካች ያቀረቡት መከራከሪያ የበታች ፍ/ቤቶች መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን የሚያሣይ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች ክርክርና አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን የሚያረጋግጥ ባለመሆኑ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥር 26 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ የመልስ መልስ አመልካች ከመጋቢት 2 ቀን እስከ መጋቢት 19 ቀን 2000 በአገር ውስጥ ስላልነበረ በወንጀሉ ተካፋይ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ የኮሚሽኑ ሠራተኛ ጉቦ የመቀበል ወንጀል ከፈፀመ አመልካች ጉቦ የመስጠት ወንጀል ፈፅሟል በማለት ለማጠቃለል አይችልም፡፡ የወንጀል ሕጉ ቅጣት ተጠቃልሎ የሚወስንበትን ሁኔታ ያስቀመጠ ስለሆነ አመልካች በሌላ ወንጀል ተከስሶ እያለ በዚህ መዝገብ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ተገቢ አይደለም የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ፍርድ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የጉምሩክ ቀረጥ የማጭበርበርና የሙስና ወንጀል ፈፅሟል በሚል ምክንያት ተጠርጥሮ በፌዴራል ሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ክትትል እና ምርመራ እየተደረገበት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በኮሚሽኑ የሚደረግበት ክትትል እንዲቋረጥለት ለማድረግ የኮሚሽኑ የክትትልና የምርመራ ባለሙያ የሆነውን አንደኛ የተጠሪ ምስክር ጋር በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ በሆነው አቶ ቶውፊቅ በኩል መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ገንዘብ ለመስጠት ሀሳብ ያቀረበ መሆኑን፣ ከዚያም በኋላ በስልክ አንደኛውን የተጠሪ ምስክር በስልክ ካነጋገረና ገንዘብ በሁለተኛው ተከሣሽ በኩል እንደሚልክ ከነገረው በኋላ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. 150,000 /አንድ መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ በመላክ ገንዘቡ ለአንደኛ የተጠሪ ምስክር ከተሰጠ በኋላ በኮሚሽኑ የሚደረገው ክትትልና ምርመራ ተቋርጧል በሚል ዕምነት መጋቢት 21 ቀን 2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓ.ም. ከአንደኛው የተጠሪ ምስክር ቢሮ ድረስ ከሁለተኛው ተከሣሽ ጋር የመጣና ገንዘቡን የላከው እሱ መሆኑን ወደፊትም ውለታ እንደሚውልለት ካረጋገጠለት በኋላ ሁለቱም በቁጥጥር ሥር የዋሉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንደኛው የተጠሪ ምስክር ከአመልካቾች ጋር በስልክና በአካል ያደረጋቸው ንግግሮች በመቅረፀ ድምፅ የተቀዳ መሆኑን መሥክሯል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በወንጀሉ ሥራ በመላ ሀሳቡ ሙሉ ተካፋይ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የከፍተኛው ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡

አንድ ሰው ጉቦ የመስጠት ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ጥቅም ወይም ጥጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ ሆኖ በተገኘ ጊዜ እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ አመልካች በመላ ሀሳቡና ድርጊቱ ሙሉ ተካፋይ በመሆን የተጠሪ አንደኛ ምስክር የሆነው የክትትልና የምርመራ ሠራተኛ በአመልካች ላይ የሚደረገውን ክትትል እንዲያቋርጥ ለማድረግ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ በመደለያነት ያቀረበ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከውጭ አገር የገባሁት መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ነው በማለት ፓስፖርቱን በማስረጃነት ያቀረበ ቢሆንም አንደኛው የተጠሪ ምስክር በአመልካች ላይ የሚያደርገውን ክትትል ቢያቆም የሚጠቀምና ገንዘብ የሚሰጠው መሆኑን በሁለተኛው ተከሣሽ በኩል ሀሳብ ካቀረበበት መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ አመልካችና ሁለተኛ ተከሣሽ ጋር ከሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ቢሮ እስከተያዘበት መጋቢት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/ለ/ በሚደነግገው መሠረት በመላ ሀሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊት በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ መሆኑ በተጠሪ ማስረጃና አንደኛው የተጠሪ ምስክር ጋር በስልክ ካደረጋቸው ንግግሮችና በሁለተኛ ተከሣሽ በኩል ከፈፀሙ ተግባራትና መጋቢት 21 ቀን 2000 አንደኛው የተጠሪ ምስክር ጋር ካደረጋቸው ንግግር ከፈፀማቸው ተግባራት የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካች የሙስና ወንጀል ክትትል ሠራተኛ የሆነው አንደኛ የተጠሪ ምስክር የሚያደርገውን ክትትል እንዲያቋርጥለት የሚፈልገውና የተጠረጠረበት ወንጀል ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያለው የጉምሩክና ቀረጥ ገንዘብ የማጭበርበር ወንጀል ፈፅሟል በሚል ምክንያት መሆኑ በተጠሪ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች አንደኛውን የዐቃቤ ሕግ ምስክር ለመደለል ያቀረበው የገንዘብ መጠንም ከፍተኛ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ የአመልካች አድራጎት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚሸፈን መሆኑን “ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ጥቅም ወይም ስጦታ ከፍተኛ እንደሆነ ወይም ድርጊቱ በመንግሥት ወይም በህዝብ ወይም ግለሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎ እንደሆነ” የሚለውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/3/ ድንጋጌ ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ጥፋተኛ መባል የሚገባኝ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 427/1/ መሆን ይገባዋል በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች ለአንደኛው ተጠሪ ማድረግ የሚገባውን የወንጀል ክትትል እንዲያቆምለት ብር 150,000 /አንድ መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የወንጀሉን ድርጊት የፈፀመ በመሆኑ ጥፋተኛ መባል የሚገባኝ በሙከራ ወንጀል መሆን ይገባዋል በማለት ያቀረቡት ክርክር በወንጀል ህግ ቁ. 27/4/ እና /3/ ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ጋር የሚጣጣም ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች የቅጣት አወሳሰኑን በተመለከተ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን የሚያመላክት አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ በዘረዘርነው ምክንያት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/ለ/ እና አንቀጽ 427/1/ እና /3/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የሙስና ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጡት የቅጣት ውሣኔ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 23 እና ሌሎች መሠረታዊ መርሆችና ከላይ የገለፅናቸውን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የተሰጠና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ፍርድ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. ፍርዱ የፀና መሆኑን እንዲያውቀው ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ይጻፍ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 61275

ሚያዝያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ኤልያስ ገረመው - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የኢት/ገ/ን/ባ/ዐ/ህግ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አመልካች በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት 3ኛ ተከሣሽ የነበረ ሲሆን ፍ/ቤቱም የቀረበለትን የዋስትና ጥያቄ ከመረመረ በኋላ አመልካች ለብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ/ የሚበቃ ዋስትና እንዲያቀርቡ በመ/ቁ 167550 በቀን 18/10/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ብይን የሰጠ ሲሆን የስር ከሣሹ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 74ን በመጥቀስ አዲስ ነገር የተገኘ ስለሆነ ቀደም ሲል የተፈቀደው የዋስትና መብት እንዲነፈግ በማመልከቱ ፍ/ቤቱም የስር ከሣሽን አቤቱታ በመቀበል የተፈቀደው ዋስትና ቀሪ እንዲሆንና አመልካች /የስር 3ኛ ተከሣሽ/ በማረሚያ ቤት ሆኖ ክርክሩን እንዲቀጥል ማዘዙን የስር ፍ/ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡

የሰበር አመልካችም የተፈቀደለትን ዋስትና በመከልከሉ ምክንያት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም የስር መ/ደ/ፍ/ቤት የፈቀደውን ዋስትና እንደገና መከልከሉ ተገቢ አይደለም ሐምሌ 7/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በዋስ እንዲወጣ አዟል፡፡ ይሁን እንጂ ያሁን ተጠሪ አዲስ ነገር ተገኝቷል በማለት የአመልካች የዋስትና መብት እንደገና እንዲነፈግ በመጠየቁ ከፍተኛው ፍ/ቤትም አዲስ ነገር መገኘቱንና አለመገኘቱን ለማጣራት ማስረጃ የሰማ ሲሆን ለማስረጃነት የቀረበውም የማስፈራራት ድርጊት ተፈጽሞበታል የተባለው ሰው ነው፡፡

የስር ከፍተኛ ፍ/ቤትም የቀረበውን ምስክር ቃል ከመረመረ በኋላ የተጠሪን አቤቱታ በመቀበል በመ/ቁ 96273 በቀን 12/12/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተፈቅዶለት የነበረውን ዋስትና ከልክሏል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ በከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን የዘረዘራቸውም ዋና ዋና የቅሬታ ነጥቦች፣

አመልካች የተከሰሰበት ወንጀል ዋስትናን አያስከለክልም፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 74 መሠረት አዲስ ነገር ተገኝቷል በሚል በቀረበው አቤቱታ መነሻ ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን የሰጠው የተጠሪ ምስክር ለቀረበለት መስቀለኛ ጥያቄ ሲመልስ ማን እንዳስፈራራው እንደማያውቅ ተናግሮ እያለ አዲስ ነገር ተገኝቷል በሚል የተፈቀደው ዋስትና መነፈጉ ተገቢነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 መሠረት አዲስ ነገር የተገኘ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በማንኛውም ጊዜ በዋስትና ላይ የሰጠውን ውሣኔ መሻር ይችላል፣ ፍ/ቤቱም አዲስ ነገር ስለመገኘቱ ማስረጃ ሰምቶ አረጋግጧል፣ በማስረጃ ዙሪያ በሰበር ደረጃ ክርክር ሊደረግ አይገባም፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ህግን መሠረት ያደረገ ስለሆነ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተገለጸው አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት የፈቀደውን ዋስትና አዲስ ነገር ተገኝቷል በሚል በሰጠው ትዕዛዝ መከልከሉ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚያሰኝ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህግ-መንግስት አንቀጽ 19/6/ በተደነገገው መሠረት የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት ያላቸው ሲሆን በህግ በተደነገጉ ሁኔታዎች ግን ፍ/ቤት ዋስትናን ላለመቀበል ይችላል፡፡ ዋስትና ከተፈቀደ በኋላም ቢሆን አዲስ ነገር የተገኘ እንደሆነ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 መሠረት ፍ/ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን በስልጣኑ ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት ተከሣሹ በዋስትና ወረቀት የተለቀቀበትን ሁኔታዎች እንደገና ለማየት ይችላል፡፡ በዚሁ መሠረት ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በዋስትና ከተለቀቀ በኋላ የከሣሽ ምስክር የሆነውን ግለሰብ ማስፈራራቱን ምስክሩ ለስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሰጠው የምስክርነት ቃል መመልከት ይቻላል፡፡

አመልካች በዋስትና ከተለቀቀ በኋላ የፈጸመው ድርጊት ደግሞ አዲስ ድርጊት ስለሚሆን ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 ከተቀመጡት ሁለት አማራጮች ማለትም ተከሣሽ አዲስ ዋስ እንዲያመጣ ወይም በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ይደረጋል ከሚሉት ሁለተኛውን አማራጭ በመውሰድ የዋስትና መብቱን በመከልከል ማረፊያ ቤት እንዲቆይ አድርጓል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የቀረበው የተጠሪ ምስክር ለቀረበለት መስቀለኛ ጥያቄ ማን እንዳስፈራራው እንደማያውቅ ተናግሯል በማለት የተከራከረውም ቢሆን በዚህ በሰበር ደረጃ መጣራት የሌለበት የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

በአጠቃላይ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ 59855 በቀን 28/3/2003 ዓ.ም በአመልካች ወ/ሮ ሊዊዛ ፎርቤታ እና በተጠሪ ዐ/ሕግ መካከል በተደረገው የዋስትና ክርክር ችሎቱ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ /ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃ መመዘን ባለመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታይ አይገባም በማለት እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 መሠረት አዲስ ነገር ሲገኝ የተፈቀደው ዋስትና ሊከለክል ስለመቻሉ የሰጠው ትርጉም በዚህ በተመሣሣይ ጉዳይ አስገዳጅነት ስላለው በዚህ በተያዘውም ጉዳይ በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የስር ክፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 96273 በቀን 12/12/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሐምሌ 7 ቀን 2002 ዓ.ም ለአመልካች ተሰጥቶት የነበረውን የዋስትና ፈቃድ ትዕዛዝ በማንሣቱ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
2. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ሕግ-አቶ ደሳላኝ ደንገላ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1.ኢዮሲያስ አበራ ገ/ሚካኤል-አልቀረበም፡፡-የሁሉም ጠበቃ አቶ ጎበና እጅጉ ቀረቡ፡፡

2. ለአለም አበራ ገ/ሚካኤል-ቀረቡ፡፡

3. ወ/ሮ ትርንጎ ወ/ሚካኤል -ቀረቡ፡፡

4. አብያለው አበራ ገ/ሚካኤል-ቀረቡ፡፡

5. መላኩ ግዛው ማሩ-ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 54215 ከሆነው ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሰው ግድያ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ የመሰረተው ክስ ይዘት ሲታይም በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ፣ለ)) እና 539(1(ሀ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ሟች አቶ የማነ መስፍንና ሟች የትናየት ጌቱ ጥር 12 ቀን 1999 ዓ/ም በነገሌ ወረዳ ላንጋኖ በቀለ ሞላ ሆቴል ልዩ መዝናኛ ስፍራ ውስጥ እያሉ 1ኛ ተጠሪ ሟች የትናየት ጌቱ እጮኛዬ ሆና እያለች ከሟች የማነ መስፍን ጋር ወደ መዝናኛ ሥፍራው ሄዳለች በማለት ከሌሊቱ ወደ 6፡00 አከባቢ ሲሆን ከአዲስ አበባ እስከ መዝናኛ ቦታው በመሄድ በዚያው ሆቴል አልጋ በመያዝ ሟቾችን አይታቸው ከለያቸው በኋላ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ ቁጥር ስማቸው ለተጠቀሱት ተጠሪዎች ደውሎ ሟቾችን መግደል እንደሚፈልግ ነግሯቸው፣እነዚህ ተጠሪዎች በእለቱ ከሌለቱ 8፡00 አከባቢ ላይ ተሰባስበው በመወያየት ሲጓዙ አድረው፣ ጥር 13 ቀን 1999 ዓ/ም ከጥዋቱ 12፡30 ሲሆን ወደ ሆቴሉ ሲደርሱ አቶ አበራ ወ/ሚካኤል ፈቃድ ያወጡበትንና ቁጥሩ 678309 የሆነ ኮልት ሽጉጥ ባልታወቀ ሁኔታ ወደ ሆቴሉ በድብቅ ካስገቡና ከ1ኛ ተጠሪ ጋራ ከተመካከሩ በሁዋላ በዚሁ እለት ከጠዋቱ 1፡30 ሲሆን 1ኛ ተጠሪ(ኢዩሲያስ አበራ) ሟቾች ያሉበትን የሆቴሉ አልጋ ቁጥር 9 በአልጋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኩል ያለውን መስኮት በመስበር በመግባት፣2ኛ ተጠሪ(ለአለም አበራ) ደግሞ በበር ገብቶ 1ኛ ተጠሪ በክሱ በተጠቀሰው ሽጉጥ ተኩሶ ሟቾችን የተለያየ አካላቸውን በመምታት ሲገድላቸው 2ኛ ተጠሪ አብሮ ገብቶ በሃሳብ ሲረዳው የነበረ ሲሆን ከ3ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ደግሞ ወንጀሉ በሚፈጸምበት ወቅት በጋራ እነሱን ልኳቸው የወንጀሉን ውጤት በሆቴሉ ቁጥር 9 እና 8 መካከል ቆመው ሲጠባበቁ የነበሩ ከመሆኑም በላይ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ከሕግ ተጠያቂነት ራሳቸውንም ሆነ 1ኛ ተጠሪን ለማስመለጥ አስበው ወንጀሉ የተፈፀመበትን ሽጉጥ 2ኛ ተጠሪ በሆቴሉ አልጋ ቁጥር 9 ክፍል ውስጥ በጃኬት ጠቅልሎ ይዞ ለ4ኛ ተጠሪ ሲሰጥ ይኸው ተጠሪም ለ3ኛ ተጠሪ በማቀበል በመጡበት መኪና ውስጥ እንዲቀመጥ የደበቁ መሆኑን ዘርዝሮ በአጠቃላይ ተጠሪዎች አስበው፣ተባብረው፣ተረዳድተውና የወንጀሉን ውጤት በመቀበል በቅናት ተነሳስተው ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ሁለት ሰዎችን በግፍ ገድለዋል የሚል ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ 1ኛ ተጠሪ የወንጀል ሕጉን 808(ሀ) ድንጋጌን በመጣስ የተከሰሰ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ተጠሪዎች ክሱ ደርሷቸው በግልጽ ችሎት ከተነበበላቸውና እንዲረዱት ከተደረገ በሁዋላ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ 1ኛ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኖ መብቱን ጠብቆ የተከራከረ ሲሆን ሌሎች ተጠሪዎች ግን የድርጊቱን አፈጻጸም ክደው ተከራክረዋል፡፡ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎችም ድርጊቱን እንደአቃቤ ሕግ የክስ አመሰራረት ስለመፈፀማቸው በዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተረጋግጦባቸዋል ተብሎ እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃዎችን አሰምተዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ክስ መሰረት የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቶ 1ኛውን ተጠሪ በ18(አስራ ስምንት አመት)፣3ኛዋን ተጠሪ(ትርንጎ ወ/ሚካኤልን) ደግሞ በ15(አስራ አምስት አመት) ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲወሰን 2ኛ፣4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎችን ግን ክሱን ተከላክለዋል በማለት በነፃ አስተናብታቸዋል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች በ1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ በተሠጠው የቅጣት ውሳኔ፣በሌሎች ተጠሪዎች ላይ የተሠጠው የነፃ መለቀቅ ውሳኔ ላይ እንዲሁም የአሁኑ 1ኛና 3ኛ ተጠሪዎች በጥፋተኝነት ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በተለያዩ መዛግብት አቅርበው ጉዳዩ ከታየ በሁዋላ የአሁኑ አመልካች እና የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ይግባኝ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ ሲሆን የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ይግባኝ ግን ተቀባይነት አግኝቶ ክርክር ከተደረገበት በሁዋላ 3ኛ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀማቸው በሚገባ አልተረጋገጠባቸውም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በነጻ እንዲሰናበቱ ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካችና የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው የአሁኑ አመልካች አቤቱታ ተቀባይነት ሲያጣ የ1ኛ ተጠሪ አቤቱታ ግን ተቀባይነት አግኝቶ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ 1ኛ ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙ የተረጋገጠበት ቢሆንም ድርጊቱ ሊሸፈን የሚገባው በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ሳይሆን ተራ የሰው ግድያ ወንጀል በሚያስጠይቅበት ድንጋጌ ነው ተብሎ ድንጋጌው ዝቅ ተደርጎለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በሁዋላ ቅጣቱም 16(አስራ ስድስት አመት) እንዲሆን ተድርጎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በሰ/መ/ቁጥር 45595 በሆነው የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው በ1ኛ ተጠሪ ላይ በስር ፍርድ ቤት የተጣለው ቅጣት ተገቢነት የለውም፣ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎችም ከክሱ በነጻ መሰናበታቸው ያላግባብ ነው በሚል ሲሆን በሰ/መ/ቁጥር 54215 የቀረበው የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ ይዘትም ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድርጊቱ በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 540 የሚሸፈን ነው ተብሎ የተሠጠው የሕግ ትርጉም ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡በሁለቱም መዛግብት የቀረቡት የአቃቤ ሕግ የሰበር አቤቱታ ቅሬታ ነጥቦች ተመርምረውም በሰበር ችሎት ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጠበቃቸው አማካኝነት የተጻፈ የጹሑፍ መልስ አቅርበዋል፡፡የመልሳቸው መሰረታዊ ይዘትም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሲቀርብ በሁለቱም መዛግብት የተያዙትን ጭብጦች በሚከተለው መልኩ መርምሯቸዋል፡፡

<u>1ኛ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት የሕግ ድንጋጌና በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው የቅጣት መጠን ተገቢ መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ፡-</u>

1ኛ ተጠሪ የተከሰሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ለ)፣(ሀ)) እና 539(1ሀ) የስር የተመለከተውን በመተላለፍ የትናየት ጌቱ እና የማነ መስፍን የተባሉትን ሰዎች በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ በግፍ ገድሏል በሚል ሲሆን ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኖ ኃላፊነት የለብኝም፣ኃላፊነት አለብህ ከተባለም ቅጣትን ሊያቀልሉ የሚችሉ ሁኔታዎች በተገኙ ጊዜ የሰው መግደል ወንጀል ሊያስጠይቅ በሚችለው ድንጋጌ መሰረት ነው በማለት መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡አቃቤ ሕግ በበኩሉ የድርጊቱ አፈፃፀም በቅናት እና በጨካኝነት የተፈፀመ ስለመሆኑ ያሳያሉ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡1ኛ ተጠሪ ራሱ በሰጠው ቃልም ሆነ በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በፍሬ ነገር የተረጋገጠው ነጥብ የሚያሳየው ሟች የትናየት ጌቱና ተጠሪ ትዳር ሊመሰርቱ ስምምነት ተድርጎ ጋብቻው ሊፈፀም ሶስት ወራት ያህል በቀሩበት ጊዜ ውስጥ ጥር 12 ቀን 1999 ዓ/ም ከሟች የማነ መስፍን ጋር ወደ ላንጋኖ መዝናኛ በመሄድ በመዝናናት ላይ የነበሩ መሆኑን ተጠሪ ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ ሌሊቱን ሄዶ መኖራቸውን አረጋግጦና አጠቃላይ ሁኔታውን ከተመለከተ በሁዋላ በበነጋው ላይ ግን ተጠሪዎችን ከአገኘ በሁዋላ ሟቾች ወደ ተኙበት አልጋ በመስኮት በመግባት ሟቾችን በወቅቱ በያዘው ሽጉጥ ተኩሶ መግደሉ ነው፡፡ተጠሪ ድርጊቱ የተፈፀመው በንዴትና በብሥጭት ነው፣ራሴን ለመከላከል ነው በማለት ያቀረበውን መከራከሪያ ሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች ያልተቀበሉት ጉዳይ ሲሆን የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የ1ኛ ተጠሪ ድርጊት በግፍ ሰው የመግደል ወንጀል ሊያቋቁም የሚችል አይደለም ወደ ሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ ከሟች የትናየት ጌቱ ጋር እጮኛ ሁኖ ጋብቻ ሊመሰርት ሶስት ወር በቀረው ጊዜ ውስጥ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀሟ መረጋገጡና ተጠሪ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ላንጋኖ እስኪደርስ ድረስ ሰው ለመግደል ሀሳብ ያለው ስለመሆኑ በዐቃቤ ሕግም ሆነ በፈፀመው ድርጊት የተረጋገጠ አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሰረቱ የሰው ግድያ ወንጀል በወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በመዘጋጀት ሲፈፀም ወይም በአንቀጽ 84 ወይም 86 ስር የተመለከቱት አክባጅ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ስለመሆኑ ተጠቃሹ ድንጋጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግልጽ ያሳያል፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች በየራሳቸው መቆም የሚችሉ ነጥቦች ስለመሆናቸው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ሚኾችን የገደለው ሚች የትናየት ጌቱ ፍቅረኛው ሁና ለጋብቻ ዝግጅት እየተደረገ ባለበት ጊዜ ከሚች የማነ መስፍን ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ስትፈፅም አረጋግጬአለሁ በማለት ሲሆን ድርጊቱን የፈፀመውም ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ ሂዶ ሲሆን ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ ሲሄድም የሌላ ሰው መሣሪያ ይዞ መሆኑ፣ላንጋኖ መዝናኛ ሲደርስም ሚቺ ከሌላ ሰው ጋር መሆኗን ከአዲስ አበባ በሄደበት እለት አረጋግጦ እዚያው ላንጋኖ መዝናኛ አድሮ ጥዋት ላይ የአሁኑ ተጠሪዎች ከቦታው ከደረሱለት በሁዋላ ሚቾች ወደ ተኙበት አልጋ በመስኮት ገብቶ ነው፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ ቀድሞውኑም ከአዲስ አበባ ሲነሳና እስከ ላንጋኖ ሌሊቱን በመንዝ ሲደርስ ሰውን ለመግደል ሀሳብና ቅድመ ዝግጅት ያለው ስለመሆኑ በራሱ አረጋጋጭ ሲሆን ይህ ቅድመ ዝግጅቱን አያረጋግጥም ቢባል እንኳ ተጠሪ እዚያው አድሮ ሌሎች ሰዎች ወደ ቦታው ከደረሱ በሁዋላ ድርጊቱን መፈጸሙ ከላንጋኖ መዝናኛ ከደረሰ በሁዋላ ሁኔታውን አይቶና ተገንዝቦ፣አጠቃላይ ሁኔታዉን አውጥቶና አውርዶ ከአሰበና ሊከተል የሚችለውን ውጤት ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ዝግጁ ከሆነ በሁዋላ ሲሆን በቅፅበት ደም ሊያፈላ የሚችል ሁኔታ ሲያልፍና መንፈሱ ሲረጋጋ የፈፀመው ድርጊት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡እነዚህ ፍሬ ነገሮች 1ኛ ተጠሪ የግድያ ወንጀሉን አስቦበትና ቀድሞ ተዘጋጅቶበት በጭካኔ ወይም በአደገኛነት በተለይም በማንአለብኝነት የፈፀመው ስለመሆኑ ያሳያሉ ከሚባሉ በስተቀር በእለታዊ ፀብ እና አለመግባባት ምክንያት የፈፀመው ድርጊት ነው ለማለት የሚያስችሉ አይደሉም፡፡አንድ ሰው እጮኛው የሆነችውና ጋብቻ ለመፈፀም በዝግጅት ላይ ያለች ሴት ጋብቻው ከመፈፀሙ በፊት ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅማለች ብሎ ከሴቷ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈፀም ነበር ከተባለው ሰው ጋር ይገኙበታል እስከተባለው ቦታ ድረስ ሌሊቱን ረኸርም ጉዞ በመንዝ ከደረሰና ሁኔታውን ከተመለከተ በሁዋላ ቀላል የማይባል ሰዓት አሳልፎ ሕግና ሥርዓት ባለበት አገር ሁለት ሰዎችን በአንድ ላይ አከታትሎ መግደሉ በማንአለብኝነት፣በቂምና በቅናት መንፈስ ክቡሩን የሰው ሕይወት አጥፍቷል ከሚባል በስተቀር በማናቸውም መመዘኛ ግድያውን ተራ የሰው ግድያ ወንጀል ሊያደርግ የሚችል አይደለም፡፡በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአቃቤ ሕጉ ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር ማገናዘብ ሲገባው ያለሕጋዊና በቂ ምክንያት በ1ኛ ተጠሪ ላይ በአቃቤ በኩል ተጠቅሶ የቀረበውን ድንጋጌ መቀየሩ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት 1ኛ ተጠሪ ለፈመው የሰው ግድያ ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 539(1(ሀ)) ስር እንጂ በአንቀጽ 540 ስር ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በ1ኛ ተጠሪ ላይ በወ/ሕ/ቁጥር 539(1ሀ) ስር የሠጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀየረው ያላግባብ ሁኖ ስላገኘነው በ1ኛ ተጠሪ (ኢዮስያስ አበራ) ላይ በወ/ሕ/ቁጥር 540 ስር የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሰረት ለውጠን ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 539(1ሀ) ስር ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡

<u>2ኛ. በሌሎች ተጠሪዎች(ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ በተጠቀሱት) ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ፡-</u>

ሁለተኛ ተጠሪ(ለአለም አበራ) በስር ፍርድ ቤት በነፃ የተሰናበተ ሲሆን ለውሳኔው የስር ፍርድ ቤት መሰረት ያደረገው ምክንያትም ተጠሪው የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ አልተረጋገጠም፣በመከላከያ ምስክርም ወደ ቦታው የሄደበትን ምክንያት አስረድቷል በሚል ምክንያት ነው፡፡2ኛ ተጠሪ በአቃቤ ሕግ የተከሰሰው ለ1ኛ ተጠሪ ግብረ አበር በመሆን በድርጊት አፈጻጸሙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሳትፏል በሚል ምክንያት ሲሆን በድርጊት አፈፃጸሙ የነበረው ተሳትፎን በተመለከተም ሚኞች ወደ ተኙበት አልጋ 1ኛ ተጠሪ በመስኮት ሲገባ 2ኛ ተጠሪ በአልጋው በር በኩል ገብቷል፣ድርጊቱ ከተፈጸመ በሁዋላም በበር በኩል ወጥቷል በማለት በክሱ ላይ ገልጿል።ይህንኑ የተጠሪን የወንጀል ድርጊት ተሳትፎ ለማረጋገጠም የሰው ምስክሮችን ያቀረበ ሲሆን 1ኛው የአቃቤ ምስክር በወቅቱ በቦታው ላይ የነበረ መሆኑን ገልፆ ሁለት ሰዎች ሲሯሯጡ እንደነበርና አንዱ ሚኞች ወደ ተኙበት አልጋ በበር ሲገባ ሌላው በመስኮት መግባቱን መመልከቱን በአከባቢ ማስረጃነት የመሰከረ ሲሆን 3ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር 2ኛ ተጠሪ ሚኞች ከተኙበት አልጋ ውስጥ ጥይት ከተተኮሰ በሁዋላ በበር በኩል ጃኬቱን ይዞ መውጣቱን መስክሯል።ሌሎች የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በሰጡት ቃልም 2ኛ ተጠሪ ድርጊቱ በተፈፀመበት ቦታ የነበረ መሆኑንና 1ኛ ተጠሪን ሌሎች ሰዎች ለመያዝ ሲሞክሩም እንዳይያዝና ጉዳት እንዳይደርስበት ጥረት ሲያደርግ የነበረ መሆኑን አረጋግጠዋል።እንግዲህ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነጥብ ሲታይ 2ኛ ተጠሪ ሚኞች በተገደሉበት ጊዜና ቦታ በመገኘት 1ኛ ተጠሪ በመስኮት ሲገባ እሱ ደግሞ በቤርጎው በር በመግባት ጥይት ከተተኮሰ በሁዋላ እንደገና በቤርጎው በር ሩጦ የወጣና ጃኬትም ለሌላ ሰው ያቀበለ መሆኑ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪን በቦታው የነበሩት ሌሎች ሰዎች ከተኩሱ በሁዋላ ቁም ሲሉትም ይህንኑ ይከላከል የነበረ መሆኑ ነው።እነዚህ ፍሬ ነገሮች ሲታዩ ደግሞ 2ኛ ተጠሪ ሚኞችን ራሱ በቀጥታ ተኩሶ መግደሉ ባይረጋገጥም ሚኞችን ለህልፈት የዳረገውን የተኩስ ተግባር 1ኛ ተጠሪ ሲፈፅም ከዚሁ ተጠሪ ጋር ተባብሮ ሚኞች ወደ ተኙበት አልጋ በበር በኩል መግባቱም ሆነ ከተኩሱ በሁዋላ በበር ሩጦ መውጣቱ በመላ ሀሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሠጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ መሆኑን የሚያስገነዝቡን ናቸው። የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪን ነጻ ያደረገበት ምክንያት ድርጊቱን ስለመፈፀሙ አልተረጋገጠም፣በመከላከያም አስረድቷል በሚል ነው።ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰው በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በአግባቡ ባለመያዝ በደፈናው የ2ኛ ተጠሪ የድርጊቱ ተሳትፎ አልተረጋገጠም በማለት ነው። አንድ ፍርድ ቤት በሕግ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎችን ውድቅ ሊያደርግ የሚገባው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነገር ሙሉ በሙሉ በመመዘን እንጂ ከማስረጃዎቹ ውስጥ የተወሰነውን ፍሬ ነገር ብቻ በመያዝ ሊሆን እንደማይገባው ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ሕግ ፅንሰ ሀሳቦች የሚያስገነዝበን ሐቅ ነው።በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በ2ኛ ተጠሪ ላይ የድርጊቱን ተሳትፎ አላረጋገጡም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ እንዲከላከል ትዕዛዝ ከሰጠ በሁዋላ ሁሉም የአቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል አንድ ባንድ ባለማየት ነው።ተጠሪው በመከላከያ ማስረጃ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አስተባብሏል የሚለው ድምዳሜም ተጠሪው ወንድሙ የሆነው 1ኛ ተጠሪ ያለበትን ሁኔታ ለማየት ከአዲስ አበባ ወደ ላንጋኖ መሄዱ ተመስክሯል በሚል ምክንያት ነው።ሆኖም የ2ኛ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ ያረጋገጠው ይኸው ፍሬ ነገር ተጠሪው ላንጋኖ ከደረሰ በሁዋላ የነበረውን የድርጊት ተሳትፎን የሚያስተባብል አይደለም።በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪ(ለአለም አበራ ገ/ሚካኤል) የወንጀል ድርጊቱን በመላ አሳቡና አድራጎቱ የወንጀሉ ድርጊት የሚሰጠውን ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ መሆኑ በአቃቤ ሕግ የአከባቢና የአይን ምስክሮች ተረጋግጦበት እያለ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመተው ተጠሪውን የስር ፍርድ ቤት በነጻ ማሰናበቱም ሆነ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች አለመታረሙ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው 2ኛ ተጠሪ ላይ የተሰጠውን የነጻ መለቀቅ ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት ለውጠን 2ኛ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ለ)) እና 539(1(ሀ)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብለናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌላው በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው የሰበር ቅሬታ በ3ኛ ተጠሪ(ትርንጎ ወ/ሚካኤል) ላይ የተሰጠውን ውሳኔ የሚመለከት ነው፡፡የስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ በተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌ ጥፋተኛ በማድረግ በአስራ አምስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት ደግሞ ተጠሪ በግድያው ወንጀል የነበራቸው ተሳትፎ አልተረጋገጠም በማለት ሙሉ በሙሉ በነጻ እንዲሰናበቱ አድርጓል፡፡ይህ ችሎትም ጉዳዩን ሲመለከተው ማስረጃን የመመዘንና ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአቃቤ ሕግን ማስረጃ ዝርዝር ይዘት በመመልከት 3ኛ ተጠሪ በግድያው ወንጀል የነበራቸው ተሳፍቶ አልተረጋገጠም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሷል፡፡አቃቤ ሕግ ደግሞ የተጠሪ የወንጀል ተሳትፎ በማስረጃ የተረጋገጠ ነው በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ይሁን እንጂ አቃቤ ሕግ ክሱን ሲመሰርት 1ኛ ተጠሪ ሟቾችን እንደሚገድል ለ3ኛ ተጠሪ ስልክ ደውሎላቸው ይህንኑ ሰምተው ሌሊቱን በመኪና ሲጓዙ አድረው ድርጊቱ ወደተፈጸመበት ቦታ በመድረስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከተመካከሩ በሁዋላ ድርጊቱ መፈፀሙን፣ድርጊቱ ሲፈፀምም በቦታው ላይ 3ኛ ተጠሪ ቁመው ውጤቱን ሲጠባበቁ የነበሩ መሆኑን የጠቀሰ ቢሆንም ይህ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ አለማረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የሚያስገነዝብ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም 3ኛ ተጠሪ ወደላንጋኖ የሄዱበትን ምክንያትና ከሄዱ በሁዋላ ስለግድያው የነበራቸውን ተሳትፎ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በግድያ ወንጀሉ 3ኛ ተጠሪ ተሳትፎ የነበራቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሷል፡፡ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ድምዳሜ የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም አቃቤ ሕግ 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ በከባድ የግድያ ወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል በማለት ያቀረበው ቅሬታ የመሰረታዊ ሕግ ስህተትን መመዘኛ የሚያሟላ ሁኖ ባለማግኘታችን አልፈነዋል፡፡ሆኖም 3ኛ ተጠሪ ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ የነበሩ፣ተኩስ ከተሰማ በሁዋላም የወንጀል ድርጊቱ ከተፈፀመበት ቤርጎ ውስጥ በሌላ ሰው ወጥቶ የተሰጣቸውን ጃኬት ተቀብለው መኪና ውስጥ በማስገባት ቆልፈው በኋላ መኪናው ተከፍቶ ጃኬቱ ሲታይ ሽጉጥ መገኘቱ በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑ ሲታይ 3ኛ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ? ወይስ በተረጋገጠባቸው መጠን አግባብነት ባለው የሕግ ድንጋጌ ሊጠየቁ ይገባቸዋል? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡በመሰረቱ አንድ ሰው በአቃቤ ሕግ በኩል የተመሰረተበት ክስ እንደክሱ አመሰራረት ሳይረጋገጥ ቢቀርም የቀረበው ማስረጃ ከቀረበው ክስ ያነሰ የወንጀል ድርጊት በተከሳሽ መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሳሹ በተመሰከረበት የወንጀል ድርጊት የማይጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ 3ኛ ተጠሪ የግድያ ወንጀል ከተፈጸመ በኋላ ሽጉጡ የተጠቀለለበትንና የተሰጣቸውን የግድያ ወንጀል ከተፈጸመበት ቤርጎ የወጣውን ጃኬት ተቀብለው ከመኪና ውስጥ መደበቃቸው የተረጋገጠ ሲሆን ይህም ወንጀል ከተደረገ በሁዋላ ሆነ ብለው ወንጀል አድራጊው ከመከሰስና ከመቀጣት እንዲያመልጥ የረዱት መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ ሲሆን አድራጎቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 መሰረት በአንቀጽ 445 ስር ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው፡፡በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 3ኛ ተጠሪን በግድያ ወንጀል ሊጠየቁ አይገባም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰበት መንገድ የማስረጃ ምዘና ሁኖ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚችል ባይሆንም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ስለመፈፀማቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠውንና ወንጅሉ ከተደረገ በኋላ ወንጀል አድራጊውን መርዳትን በተመለከተ የተደነገገውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ 3ኛ ተጠሪን ጥፋተኛ ያለማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግኝተናል፡፡ስለሆነም 3ኛ ተጠሪ በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ የቀረበባቸውን ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113(2)መሰረት በመለወጥ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 እና 445 ስር የተመለከተውን የተላለፉ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

ሌላው በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ቅሬታ በስር 4ኛ ተከሳሽ(አብያለው አበራ) ላይ የተሰጠውን የነጻ መለቀቅ ውሳኔ የሚመለከት ነው፡፡አቃቤ ሕግ ይህ ተጠሪም በግድያው ወንጀል ሊጠየቅ የሚገባ መሆኑን ጠቅሶ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት ይህንኑ ተጠሪ ከግድያ ወንጅሉ ያስናበቱት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመዘን ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡በመሆኑም ከላይ እንደተጠቀሰው ይህ ችሎት በሕግ ከተሠጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ በዚህ ረገድ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ይሁን እንጂ 4ኛ ተጠሪ በግድያ ወንጅሉ የነበረው የተሳትፎ ሁኔታ አልተረጋገጠም የተባለው ማስረጃ ተመዝኖ ቢሆንም ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ ተገኝቶ ድርጊቱ ከተፈጸመበት የቤርጎ ቁጥር ከድርጊቱ በሁዋላ ወዲያውኑ የወጣውንና ድርጊቱ የተፈጸመበት ሽጉጥ መጠቅለሉ የተረጋገጠበትን ጃኬት ድርጊቱ ከተፈጸመበት ቤርጎ ከወጣው ሰው ተቀብሎ ለ3ኛ ተጠሪ መስጠቱ በአቃቤ ሕግ የአይንና የአካባቢ ማስረጃ የተረጋገጠበት ሲሆን ይህንኑ ፍሬ ነገር ላለመቀበል የሚያስችል ምክንያት የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ስለሆነም 4ኛ ተጠሪ(አብያለው አበራ) ወንጀል ከተደረገ በሁዋላ ወንጀል አድራጊውን በመርዳት ወንጀል መጠየቅ ሲገባው ከዚሁ የወንጀል አድራጎቱ ሁሉ ነፃ መደረጉ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመተው በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን 4ኛ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 እና 445 መሰረት ጥፋተኛ ሊሆን የሚገባው ነው ብለናል፡፡

5ኛ ተጠሪን (መላኩ ግዛው ማሩን) በተመለከተ የቀረበውን የአቃቤ ሕግን ቅሬታ ስንመለከተው ደግሞ ይህ ተጠሪ ከድርጊቱ ሙሉ በሙሉ ነፃ የተባለው በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ተመዝነው ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ከግድያው ባነሰ የወንጀል ድርጊት ሊያስጠይቀው የሚችል የወንጀል ተሳትፎ ስለመኖሩ የክርክሩ ሂደት የማያረጋግጥ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

3. ቅጣትን በተመለከተ

1ኛውን ተጠሪ በግፍ ሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ያሉት የበታች ፍርድ ቤቶች ያስተላለፉት የቅጣት መጠን አስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት ነው፡፡አቃቤ ሕግ ይህ ቅጣት ተገቢ ያለመሆኑን በመጥቀስ ለበላይ ፍርድ ቤቶች ይግባኙን ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ሁለት ሰው በግፍ መግደሉ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)ሀ)) ስር ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው እድሜ ልኩን በፅኑ እስራት ወይም በሞት ነው፡፡በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ “የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው” በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወሰነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኝነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሰን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ከላይ እንደተገለጸው ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2)፡ስር፡የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤አመዛዝኗልም፡፡ተጠሪ ሪኮርድ ያልቀረበበት መሆኑም ያለፈ የሕይወት ታሪኩ መልካም የነበረ መሆኑን እንደሚሳይ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82(1(ሀ)) መሰረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሲሆን ከዚህ ውጪ 1ኛ ተጠሪ የተለየና ልዩ የሆነ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የለውም፡፡ የቅጣት መጠኑንም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 179(ሀ) መወሰኑ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ሲጠቃለልም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪን ተጠያቂ ያደረጉበት ድንጋጌ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገና በምክንያትም የተደገፈ ቢሆንም በቅጣት ረገድ ግን ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ሊያስቀጣ ከሚችለው የቅጣት መጠንና ከቅጣት ዓይነተኛ ዓላማ አንፃር ሲታይ ተገቢ ባለመሆኑ በተጠሪ ላይ የተጣለው የአስራ ስምንት ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችንና የቅጣትን ዓላማ ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ አድራጎት በከባድ የሰው መግደል ወንጀል የሚሸፈንና የቅጣት መጠኑም ከእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሊወርድ የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

3ኛ ተጠሪን በተመለከተ ይህ ችሎት ጥፋተኛ ያደረጋቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 40 እና 445 ስር ሲሆን ቅጣቱ ሊተላለፍ የሚገባውም በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሊቀጣ የሚችለው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ነው፡፡ ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን በማመዛዘን ሲሆን ይህ ችሎትም 3ኛና 4ኛ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ያስመዘገቡትን የቅጣት አስተያየት ከድርጊቱ አፈጻጸም ጋር አገናዝቦ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት 3ኛ ተጠሪ በጉዳዩ የታሰሩት ማንኛውም ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ በሶስት አመት ቀላል እስራት ሊቀጡ የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በበታች በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊሻሻል የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14431 ሚያዚያ 01 ቀን 2000 ዓ/ም የተሰጠ ውሳኔ ፣ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 65733 ጳጉሜ 04 ቀን 2000 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ ፣ በዚሁ ችሎት በመ/ቁጥር 64223 ህዳር 02 ቀን 2001 ዓ/ም የተሠጠው ውሳኔ ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 31426 የካቲት 18 ቀን 2001 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም በዚሁ ችሎት በመ/ቁጥር 74006 ታህሳስ 19 ቀን 2002 ዓ/ም የተሠጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 1ኛ ተጠሪ (ኢዮስያስ አበራ) ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539(1(ሀ)) ሲሆን ቅጣቱም እድሜ ልኩን ጽኑ እስራት እንዲሆን ተወስኗል ፣ 3ኛ ተጠሪ የፈጸሙት ድርጊት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 445 ስር የሚሸፈን ሁኖ ቅጣቱን በተመለከተ በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ በሶስት አመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ በማለት ወስነናል፡፡
3. 5ኛ ተጠሪ (መላኩ ግዛው)ን በተመለከተ በነፃ መሰናበቱ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. በ1ኛ ተጠሪ ላይ ቅጣቱ ተሻሽሎ የተወሰነ መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረ/ቤቱ ይገለፅለት ብለናል፡፡ይፃፍ፡፡

ከተባለ በኋላ በ2ኛ እና በ4ኛ ተጠሪዎች ላይ ቅጣት ለመወሰን ይቻል ዘንድ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመጠየቅ ግራ ቀኙ ያቀረቡት የቅጣት አስተያየት በመቅረጸ ደምፅ ተቀርጿል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. ግራ ቀኙ ያቀረቡት የቅጣት አስተያየት ከመቅረፀ- ደምጽ ወደ ፅሑፍ ተቀይሮ ከመዝገቡ ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡
2. የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ ተገቢውን ቅጣት ለመወሰን ለሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ተቀጥሯል፡፡
3. 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችን የአራዳ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ አቆይቶ ለሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ችሎት እንዲያቀርባቸው ታዝዟል፡፡ ማስረያ ዋራንት ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ሕግ ዐ/ህግ ደሣለኝ ደንገላ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1.ኢዮስያስ አበራ ገ/ሚካኤል-አልተጠራም

2. ለአለም አበራ ገ/ሚካኤል-ቀረቡ፡፡

3. ትርንጎ ወ/ሚካኤል-ቀረቡ፡፡

4. አብያለው አበራ ገ/ሚካኤል-ቀረቡ፡፡

5. መላኩ ግዛው -አልተጠራም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው በ2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ላይ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ተብሎ ነው፡፡በዚህም መሰረት ጉዳዩን መርምረን ተከታዩን የቅጣት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ቅ ጣ ት

2ኛ ተጠሪ ለአለም አበራ ጥፋተኛ የተባለው በግፍ ሰው መግደል ወንጀል በሚያስጠይቅበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1ሀ) ስር ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው እድሜ ልኩን በፅኑ እስራት ወይም በሞት ነው፡፡

ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 88(2) መሰረት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአፃፀሙን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን መገንዘብ ይቻላል፡ በዚህ መሰረት ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም፡፡ 2ኛ ተጠሪ ሪከርድ ያልቀረበበት መሆኑም ያለፈ የሕይወት ታሪኩ መልካም የነበረ መሆኑን እንደሚያሳይ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ይህ ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82(1(ሀ)) መሰረት የቅጣት ማቅላያ ምክንያት ሲሆን ከዚህ ውጪ 2ኛ ተጠሪ የተለየና ልዩ የሆነ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የለውም፡፡ የቅጣት መጠኑንም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 179(ሀ) መወሰኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ሲጠቃለልም 2ኛ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ሊያስቀጣ ከሚችለው የቅጣት መጠንና ከቅጣት ዓይነተኛ ዓላማ አንፃር ሲታይ ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በጉዳዩ ላይ የታሰረው ጊዜ የሚታሰብለት ሁኖ በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ሁኖ አግኝተናል፡፡ 4ኛ ተጠሪን በተመለከተ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ሊያስቀጣ የሚችለው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ነው፡፡ በተጠሪው ላይ ሊተላለፍ የሚገባውን የቅጣት መጠን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 88(2) ስር ከተመለከቱት ሁኔታዎች እና ከቅጣት አላማዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡ በዚህም መሰረት 4ኛ ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በጉዳዩ ላይ የታሰረው የሚታሰብለት ሁኖ **በ3 (ሶስት) አመት ቀላል** እስራት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. 2ኛ ተጠሪ ለአለም አበራ ገ/ሚካኤል በጉዳዩ ላይ የታሰረው የሚታሰብለት ሁኖ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ደግሞ በጉዳዩ ላይ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሁኖ እያንዳንዳቸው በሶስት አመት ቀላል እስራት የተቀጡ መሆኑን አውቆ የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ከአራዳ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በመረከብ በእያንዳንዳቸው ላይ በተላለፈው ቅጣት መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም፡፡ የማሰሪያ ዋራንት ይጻፍ፡፡
2. መዝገቡ ያለቀለት በመሆኑ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. መስታወት ጌታነህ ከማረ/ቤት - ቀረበች

2. ግርማ ገዛኽኝ - አልቀረቡም

3. ባዩ ጌታነህ ከማረ/ቤት - ቀረበ

4. በለጠ አስፋ ከማረ/ቤት - ቀረበ

} ለሁሉም ጠበቃ ወንድወሰን ተ/ማርያም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ፌዴራል አቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች ላይ የመሠረተው የወንጀል ክስ በሁለት ምድብ የተከፈለ ሲሆን 1ኛው ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/ህ/አንቀጽ 32(1(ሀ)(ለ))እና 539(1ሀ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካቾች በሙሉ ሐሳባቸውና አድራጎታቸው በወንጀሉ ስራና በሚሰጠው ዉጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ተበዳዮች ጌታነህ ወ/ማሪያም እና ደስታ ወ/ማሪያም የተባሉት በጥቅምት ወር 1985 ዓ/ም በኢ.ሕ.አ.ዲ.ግ ታጋዮች 1ኛ/ ጌታነህ ወ/የስ ፣ 2ኛ/ መኮንን ጌታነህ ፣ 3ኛ/ በቀለች ወ/አረጋይ የተባሉ ቤተሰቦቻችንን አስገድለውብናል በሚል ቂም በቀል ተነሳስተው ቤት ንብረታቸውን በእሳት አውድመው ከአገር እንዲሰደዱ ካደረጓቸው በኋላ እንደገና በፍርድ ቤት ከሰዋቸው በነዛ ሲሰናበቱ 1ኛዋ አመልካች በተሰጠው የፍርድ ውሳኔ የበቀል ጥማቷ ባለመርካት ከአስር አመት በላይ ተበዳዮቹ የሚኖሩበትን ቦታ ለማወቅ በግብረአበሮቿ አማካኝነት ስትከታተል ቆይታ በ2ኛው አመልካች አማካኝነት ቤታቸውን ካገኘች በኋላ በተጨማሪም የተበዳይን ወንድሞች ቤት ጭምር ራሷ ፈልጋ በማግኘት ከቤታቸው ድረስ እየሄደች ስታጠና ቆይታ የወንጀሉን ሥራ መሪ ተዋናይ በመሆን 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾችን ከደብረ ብርሃን ፣ 2ኛ አመልካችን ከአዲስ አበባ በማሰባሰብ የአከባቢው ሰው በስራ የሚሰማራበትንና ጭር የሚልበትን አመቺ ጊዜ አጥንተው ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ/ም ከጠዋቱ ከ4፡00 እስከ 6፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 ክልል ወደሚገኘው የሟቾች መኖሪያ ቤት በመሄድ ዘመድ ነን ብለው ሕፃናቱን በር ካስከፈቱ በኋላ ጨካኝታቸውንና አደገኛነታቸውን እንዲሁም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነውረኝነታቸውን በሚገልፅ አስቃቂ ሁኔታ፡- 1ኛ/ ህፃን ፍቅረተ በቀለ እድሜዋ 12 አመት የሆነችውን ፣ 2ኛ/ ሕፃን ሐና በቀለ እድሜዋ 8 አመት የሆነችውንና 3ኛ ሕፃን ነጻነት በቀለ እድሜዋ 1 አመት ከ8 ወር የሆነችውን ከሚች ሕፃን ፍቅረተ በቀለ ጀርባ እንደታዘለች ሶስቱንም ሕጻናት በዱላ ጭንቅላታቸውን እና መላ ሰውነታቸውን እየተፈራረቁ ቀጥቅጠው በግፍ ገድለዋል የሚል ሲሆን 2ኛው ክስ ደግሞ ሁሉም አመልካቾች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669(3(ለ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካቾች ሕገ ወጥ ብልፅግና ለራሳቸው ለማግኘት በማሰብ በቡድን ተደራጅተው በ1ኛው ክስ ላይ በተገለጸው ጊዜና ስፍራ በክሱ ላይ የተመለከተውን የግፍ ግድያ ወንጀል ከፈጸሙ በሁዋላ ንብረትነቱ የአቶ በቀለ ወ/ማሪያም የሆኑ፡- ባለ 14 ኢንች ኤልጂ (LG) ቴሌቭዥን ፣ ሶስት ጋቢዎች ፣ አንድ ሰማያዊ ሽራ ላስቲክ እና አንድ አሮጌ የማዳበሪያ ከረጢት ሰርቀው በመውሰዳቸው ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካቾች ክሱን ክደው በመከራከራቸውም ዐቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ከዚህም በኋላ የአመልካቾች የመከላከል መብት ተጠብቆላቸው የመካለከያ ማስረጃዎችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካቾች የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ያላስተባበሉ መሆኑን ዘርዝሮ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን ቃል ውድቅ ያደረገ ሲሆን አመልካቾችን በዐቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሰው በቀረቡባቸው ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ በማድረግ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በቅጣት ረገድም የአሁኗ 1ኛ አመልካችን (መስታወት ጌታነህን) በሞት ፣ ሌሎች አመልካቾችን ደግሞ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል በድምፅ ብልጫ ወስኗል፡፡ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው የጥፋተኝነም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ በሌላ በኩል ዐቃቤ ሕግ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተራ በተጠቀሱት አመልካቾች ላይ የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ሕጋዊነት የለውም ፣ ያነሰ ነው በሚል ምክንያት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የአመልካቾችን የድርጊት አፈጻፀም ከሕጉ ጋር በመመርምር አመልካቾች ሊቀጡ የሚገባው በሞት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን የቅጣት ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በጥፋተኝነት እና በቅጣት ውሳኔው ላይ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ድርጊቱን አመልካቾች ስለመፈጸማቸው በወንጀል ሕግ የማስረጃ ምዘና መርህ ባልተረጋገጠበት ሁኔታና በፖሊስና በፍርድ ቤት አመልካቾች ሰጡ የተባሉት የእምነት ቃል በኃይል የተገኘ ሁኖ እያለ የወንጀል ድርጊቱን ፈጽማችኋል ተብሎ የመከላከያ ማስረጃዎችን እንድናቀርብ ብይን መሰጠቱ ያላግባብ ከመሆኑም በላይ የመከላከያ ማስረጃዎች ቃል ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው ፣ የቅጣቱ ውሳኔም ሕጉን የተከተለ ሳይሆን የተጋነነ ነው በማለት ውሳኔው እንዲታረም ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች እያንዳንዳቸው በሞት እንዲቀጡ ተብሎ የተወሰነው የቅጣት ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ሶስቱን ህፃናት ለሕልፈተ- ሕይወት ዳርገዋል ፣ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ በግፍ የሰው ግድያና በከባድ የስርቆት ወንጀል ጥፋተኛ የተባሉበት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 27(2) ለፖሊስ ፣ በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 35 ደግሞ ለፍርድ ቤት ሰጡ በተባሉት የእምነት ቃል ፣ የድርጊቱን አፈጻጸም መርተው ሲያሳዩ በተነሱት ገላጭ ማስረጃና በጠንካራ አካባቢ የሰው ምስክሮች ቃል ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልፅ ተጠቅሷል፡፡ የአመልካቾች የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ የተደረገውም አመልካቾች የእምነት ቃሉን የሠጡት በኃይል ስለመሆኑ ለማስረዳት እምነት ሊጣልበት የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ድርጊቱን ፈፀሙ በማለት ድምዳሜ ላይ የደረሱት አመልካቾች እያንዳንዳቸው በድርጊቱ አፈጻጸም ላይ የነበራቸውን ቀጥተኛ ተሳትፎ በሚገባ አቃቤ ሕግ አስረድቷል ፣ በመከላከያ ማስረጃዎቻቸውም አልተደገፉም በሚል ነው፡፡የአመልካቾች ጠበቃ ከሚከራከሩባቸው ነጥቦች ውስጥ የአመልካቾችን የድርጊት ፈጻሚነት በተገቢው መንገድ አቃቤ ሕግ በማስረጃ ያለማስደገፉንና የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አመልካቾች በመከላከያ ምስክሮች የማስተባበላቸው ሁኔታን የሚመለከቱ ነጥቦች የሚገኙ ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች ተገቢውን የማስረጃ ምዘና መርህ ተከትለው አመልካቾችን ጥፋተኛ ያደረጉ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳየን ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ከዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ተመዝነው መሆኑን ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘን ጉዳይ ማረም የሚችለው በውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ይህ ሰበር ችሎት ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም የአመልካቾች ጠበቃ አጥብቀው የሚከራከሩባቸው ነጥቦች የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን መሰረት ያደረጉ ሳይሆን የፍሬ ነገርንና የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው በዚህ ችሎት ሊታዩ የሚችሉ ሁነው አላገኘናቸውም፡፡በመሆኑም አመልካቾች የእምነት ቃላቸው በመገደድ የተገኘ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ባልቻሉበት ሁኔታና በራሳቸው ምሪት ወንጀሉ የተሰራበትን ቦታና የአፈጻጸሙን ሁኔታ ስለማሳየታቸው በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ ባለበት የክርክር ሂደት እንዲሁም ወንጀሉ በአመልካቾች ስለመፈጸሙ ደግሞ በበርካታ ጠንካራ የአካባቢ ማስረጃዎች ተደግፎ በቀረበበት መንገድ አመልካቾች የአቃቤ ሕግ ማስረጃ በሕጉ መመዘኛ የሚያሟላ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ አመልካቾች ለድርጊቱ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የተወሰነው ወንጀሉ መሰራቱ ወይም መፈጸሙና ተሰራ ወይም ተፈጸመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በአመልካቾች መፈጸሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑና ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚያሟላ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ወደዋናው ጭብጥ ስንመለስም የአመልካቾች መሠረታዊ ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ያስተላለፉት የሞት ቅጣት የቅጣት አወሣሠኑን በተመለከተ የወንጀል ህጉ ያስቀመጣቸውን መርሆዎች ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ እኛም ይህንኑ ቅሬታ ከህጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ “የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወሰነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን ፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስንና የቅጣት አወሣሰን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሠን መመሪያ (Manual) እንደሚወጣ የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡

ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንረዳው አቢይ ነጥብ ቅጣቶች መወሠን ያለባቸው የህጉን መንፈስ በመከተል ዓላማዎችንና ግቦቹንም ተፈፃሚ በማድረግ ሀሣብ መሆኑን ነው፡፡ የህጉን መንፈስ ከመተግበር አኳያ ወንጀለኛውን ማዕከል የማድረግ ፅንሰ ሀሣብ አጽንኦት የተሠጠው ጉዳይ ነው፡፡ ዳኞች በፅንሰ ሀሣቡ መሠረት የተሠጣቸውን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣን (Discretion) በስራ ላይ ሲያውሉ ሠብአዊ ክብርን ከማስጠበቅ ዓላማ ጋር መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ ህግ አውጪው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 87/1/ ስር የተመለከቱትን መሠረት በማድረግ ዳኞች የቅጣት ውሣኔ በምን መንገድ መወሠን እንደሚገባቸው በአንቀጽ 88 ስር አስቀምጧል፡፡ በወንጀል ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ስንመለከትም ዳኞች ከተሠጣቸው የቅጣት ክልል ሣይወጡ የአጥፊውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት እንዲወስኑ ህጉ ስልጣን የሠጣቸው መሆኑ ነው፡፡ ዳኞች አጥፊውን በተመለከተ ከግምት ውስጥ ሊያስገቧቸው የሚገባቸው በርካታ የአጥፊ ፡ ሁኔታዎች ቢኖሩም የቅጣት አወሣሠናቸው መሠረት የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን /degree of individual guilt/ ስለመሆኑ የአንቀጽ 88/2/ ድንጋጌ ይዘትና አቀራረፅ ያስረዳል፡፡ አንቀጽ 88(2) በመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል አድራጊውን የአደገኛነት መጠን መሠረት በማድረግ ዳኞች ቅጣት እንዲወስኑ ማድረጉና ይህንን ሲወስኑም በድንጋጌው የተመለከቱትን የወንጀሉን አፈፃፀም የአጥፊውን ያለፈ የህይወት ታሪኩንና የኑሮ ሁኔታ ከግምት በማስገባት በማመዛዘን ለወንጀሉና ለወንጀለኛው የሚገባውን የቅጣት መጠን እንዲወስኑ መደንገጉ የቅጣት ውሣኔዎችንና እርምጃዎችን እየተራራቁ እንዳይወሠኑ የማድረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ከመታሠቡም በተጨማሪ ችግሩ የሚቀረፍበትና የሚቀነስበትን ሥርዓትም ህጉ ዘርግቷል፡፡ ዳኞች ቅጣት ሲወስኑ በህጉ አንቀጽ 88(2) ለአጥፊው ተገቢ ነው ያሉትን ቅጣት ከወሠኑ በኋላ በህጉ የተመለከቱትን የማቅለያና የማክበጃ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ከፍ ወይም ዝቅ ለማድረግ የሚችሉ ስለመሆኑ ህጉ ያሣያል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ በአንቀጽ 84(1) ከፊደል (ሀ) እስከ ፊደል (ሠ) ድረስ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን ካስቀመጠ በኋላ በአንቀጹ ንዑስ ቁጥር ሁለት ስር በንዑስ ቁጥር አንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስር የተመለከቱት የማክበጃ ሁኔታዎች በህጉ ልዩ ክፍል ተካተው ሲገኙ በድጋሚ በማክበጃነት ዳኞች እንዳይጠቀሙ ያሣስባል፡፡ ስለሆነም የህጉ አንቀጽ 84 ደግሞ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን የዘረዘረ ሲሆን ዳኞች የህጉን አንቀጽ 183 ባገናዘበ መልኩ ቅጣት የሚያከብዱባቸውን ሁኔታዎች ያሣያል፡፡ ዳኞች ቅጣትን የሚቀንሱትም ሆነ የሚያከብዱት ተገቢ ሁኖ ሲገኝ ስለመሆኑ የአንቀጽ 179 እና 183 ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ አንቀጽ 179 የቅነሣውን ገደብ የሚያሣይ ሲሆን ከዚህ መደበኛ ቅነሣ በተጨማሪ ልዩ ቅነሣ ለማድረግ እንደሚቻልም ህጉ በአንቀጽ 180 ስር አስቀምጧል፡፡ በህጉ አንቀጽ 86 ቅጣትን በማቅለልም ሆነ በማክበድ ረገድ ከህጉ አንቀጽ 179፣182 እና ውጪ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥማቸው ዳኞች ምክንያታቸውን በመግለፅ ቅጣቶችን ለመቀነስ ወይም ለማክበድ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ግንቦት 09 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ በሆነው የቅጣት መመሪያ ውስጥ የተቀመጠው የቅጣት አወሳሰን ሥርዓት እንደተጠበቀ ሁኖ ከላይ ስለቅጣት አወሣሰን በህጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሲታዩ የሚያስገነዝቡን ዓቢይ ነጥብ ቅጣቶችን በመጣልና እርምጃዎችን በመውሠድ ረገድ ዳኞች **አመዛዝነው የመወሠን ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው**፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት ግዙፍነት ባላቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ሲሆን የግድያ ወንጀሉ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 32(1(ሀ)(ለ)) እና 539(1ሀ)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በቂም ፣ ጨካኝነት ፣ ነውረኝነት ፣ አሰቃቂና አደገኛነትን በሚያሳይ ሁኔታ ምንም የማያውቁ ጨቅላ ሕጻናትን በግፍ ገድለዋል ተብሎ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው እድሜ ልኩን በጽኑ እስራት ወይም በሞት ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ፍርድ ቤት ቅጣት ሲወስን ሊከተላቸው የሚገባቸው የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች በሕጉ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ ያስተላለፈው የሞት ቅጣት ስለመሆኑም ከላይ ገልፀናል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ በተደነገገው ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይገባ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 15 ስር በጎይለ ቃል የደነገገው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ ከባድ ወንጀል መፈጸሙ በተረጋገጠበት ሰው ላይ የሞት ቅጣት ማስተላለፍ የሚፈቀድ መሆኑን ሕገ መንግስቱ አስቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል የሞት ቅጣት ሊተላለፍ የሚገባበትን አግባብ የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 117 ስር ድንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ መሰረት የሞት ቅጣት የሚወሰነው ወንጀሉ ፍጻሜ ያገኘ ሁኖ እጅግ በጣም ከባድ በመሆኑና ወንጀለኛውም በተለይ አደገኛ በመሆኑ ለወንጀሉ ቅጣት እንዲሆን በሕጉ በግልጽ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ እንዲሁም ለወንጀለኛው ቅጣትን የሚያቀልለት ምክንያት በታጣ ጊዜ እድሜው ቢያንስ አስራ ስምንት አመት የሞላው ሁኖ ሲገኝ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ እድሜ ልኩን በፅኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ ነው፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሞት ቅጣቱን ለመወሰን የቻለውም ድርጊቱን ለመፈጸም ያነሳሳቸውን ምክንያት ፣ ድርጊቱን ለመፈጸም ለረዥም አመታት ሲደረግ የነበረውን ቅድመ ዝግጅትና እና ድርጊቱ የተፈጸመባቸው ምንም የማያውቁና ከማንኛውም ሰው እንክብካቤ የሚሹ ሶስት ጨቅላ ህጻናት ላይ መሆኑን እንዲሁም የአፈጻጸሙን ዘግናኝነትና አስቃቂነት ከአመልካቾች አደገኛ ባህርይና ቅጣቱ ለሌላው ማህበረሰብ ሊያስተላልፈው ከሚችለው መልዕክት በመነሳት ከመሆኑም በላይ ለአመልካቾች በሕጋዊ ማቅለያነት ሊያዙ የሚችሉ ምክንያቶች የሌሉ መሆኑን በመረዳት መሆኑን ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተያዘው ምክንያትና የተደረሰው ድምዳሜ በቅጣት አወሳሰን ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ የቅጣት አወሳሰን መሰረታዊ መርሆዎችን ያልተከተለ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም በአመልካቾች ላይ የተጣለው የሞት ቅጣት የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ ግብና ዓላማ እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችን ከድርጊቱ አፈጻፀም ጋር ያገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ቁ 45475 ሰኔ 26 ቀን 2001 ዓ.ም ፣ 45693 ሰኔ 26 ቀን 2001 ዓ/ም እና በመ/ቁጥር 45640 ሰኔ 26 ቀን 2001 ዓ/ም የሰጣቸው ውሳኔዎች በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ-2) መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. አመልካቾች በሞት እንዲቀጡ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡ የሞት ቅጣቱ ተፈጸሚነት የሚኖረውም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 117(2) መሰረት በአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ከፀና በሁዋላ ይሆናል ብለናል፡፡
3. በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው የሞት ቅጣት የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለአዲስ አበባ ማረ/ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 67947

15/10/2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አዱኛ አንበሎ - ጠበቃ ሰለሞን እምሩ ከቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌደራል ዐቃቤ ሕግ ወርቅነህ ዘነበ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ በፌ/የከፍተኛ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን ቀርቦ የነበረው ክስ፡-

1ኛ ክስ ተከሣሽ በ1996 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ የቢ.ኤ.ኦሜጋ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ ማህበር ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ይሰራ በነበረበት ወቅት በባንክ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ያለመኖሩን እያወቀ በ05/2/01 ዓ.ም ከዳሸን ባንክ ጥቁር አንበሣ ቅርንጫፍ ወጪ ሆኖ የሚከፈል ብር 3,000,000 /ሶስት ሚሊዮን ብር / የያዘ ቁጥሩ ኤች 257/638 የሆነ ቼክ ለአቶ ፍትዊ ወልዳይ ፈርሞ ከሰጠ በኋላ በ15/7/01 ዓ.ም ቀርቦ ክፍያ ሣይፈፅሙለት በመመለሱ በፈፀመው ገንዘብ ሣይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

2ኛ ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ.ህ በአንቀጽ 693/1/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ የተጠቀሰው የንግድ ድርጅት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ይሰራ በነበረበት ወቅት በባንክ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ በ06/2/2002 ዓ.ም ከላይ ከ1ኛ ክስ በተመለከተው ዳሸን ባንክ ቅርንጫፍ ወጪ ሆኖ የሚከፈል ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ ብር/ የያዘ ቁጥር ኤች 257/680 የሆነ ቼክ በ1ኛው ክስ ስማቸው ለተጠቀሰው ግለሰብ ፈርሞ ከሠጠ በኋላ ቼኩ በ11/07/01 ዓ.ም ለባንክ ቀርቦ በቂ ገንዘብ የለውም ተብሎ ክፍያ ሳይፈፀምለት በመመለሱ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ በማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

3ኛ ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/ህግ አንቀጽ 302/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የሌላውን ሠው መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት አስቦ በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 12/13 ክልል ልዩ ቦታው ዳሚና ሩፋ ህንፃ ላይ ከሚገኘው ቢ.ኤ ኦሜጋ ኃ/የተ/የግ ማህበር ውስጥ የማህበሩ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሠራ በእጁ የነበረ ለሥራ አስኪያጅ አቶ በላይነህ ሰርጉአለም ብቻ የሚፈረም የዳሸን ባንክ ጥቁር አንበሣ ቅርንጫፍ ቼክ ውስጥ ሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 4፡00

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰዓት ሲሆን TF 4948565 የሆነ ቼክ የግል ተበዳይ በላይነህ ሰርጉአለም ፊርማን አስመስሎ ፊርሞ ከማህበሩ ገንዘብ ጠያቂ ለነበረው ሞክሮ ጀነራል ኮንተራክተር 225,477.38/ሁለት መቶ ሃያ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከሠላሣ ስምንት ሣንቲም/ እንዲከፍል ለተወካዩ አቶ ኤልያስ ማሞ ከሠጠው በኋላ ቀኑ ይርዘም ቢቻል ሲለው በ17/8/08 የሚለውን እላዩ ላይ በ15/8/08 በሚል አስተካክሎ ለማረጋገጥ በላዩ ላይ የግል ተበዳዩን ፊርማ አስመስሎ ከቀኑ በላይ ፊርሞ በመስጠት በፈፀመው ሃሠተኛ ሠነድ በመፍጠር ሌላው እንዲገለገልበት ማድረግ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች የቀረበባቸውን ክሶች አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚሁ መሠረት ከሣሽ (ዐ/ሕግ) አሉኝ ያለውን የሠውና የሠነድ ማስረጃ በማቅረብ አሠምቷል፡፡ ተከሣሽ/አመልካች/ መከላከያውን እንዳያቀርብ በተሠጠው መብት መሠረት የሰነድና የሠው ማስረጃ አቅርቦ አሠምቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ክስ ተደራራቢ ወንጀል ነው ማለት ስለማይቻል በአንድ አንቀጽ ሥር በወ.መ.ሕግ ቁ 693/1/ ሥር ጥፋተኛ በማድረግ ሶስተኛውን ክስ በክሱ በተመለከተው አንቀጽ 382/1/ ሥር ጥፋተኛ በማለት የጥፋተኛነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ ጥፋተኛ በተባሉበት ሁለቱ አንቀጾች ሥር በ1 ዓመት ከ4 ወር ፅኑ እሥራት እንዲቀጡ ከወሰነ በኋላ በሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ ገድቧል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት አመልካችም ሆኖ ተጠሪ ይግባኙ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የአመልካች ቅሬታ ውድቅ ሲደረግ የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ግን ተቀባይነት አግኝቶ በዐቃቤ ሕግ በቀረባቸው ሶስቱም ክስ ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ ከሠጠ በኋላ ለ1ኛው ድርጊት 4 ዓመት ፅኑ እሥራት ፣ ለሁለተኛ ድርጊት 1 ዓመት ፅኑ እሥራት እና ለ3ኛው ድርጊት 1 ዓመት ፅኑ እሥራት ሆኖ ባጠቃላይ በ6 ዓመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጣና በ1ኛ ና 2ኛ ድርጊቶች በተጨማሪ የገንዘብ መቀጮ ባጠቃላይ 11,000/አሥራ አንድ ሺህ ብር/ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን አመልካች ይግባኝ ያቀረበበት የመዝ.ቁ 55773 ንም በመጨመር የቀረበ ነው፡፡ የቅሬታው ፍሬ ሃሣብ በ1ኛ እና 2ኛ ክስ ሥር የተጠቀሰው አቶ ፍትዊ ወልዳይ ላይ የተፈፀመ የማታለል ተግባር የሌለ መሆኑን አቶ ፍትዊ ወልዳይ ለድርጅቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችንና ቢሮ ሲያከራዩ ድርጅቱ ከደንበኞቹ ገንዘብ ሰብስቦ እስኪሠጣቸው ድረስ ሁለቱ ቼኮች በዋስትና መልክ የተሠጠ እንጅ ባንክ ቤት ሄደው እንዲመነዝሩት አይደለም፣ ተበዳይ የተባሉትም ቼኮቹ በቂ ስንቅ እንደሌላቸው የሚያውቁ ስለመሆኑ ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል፣ ቼክ ደግሞ በዋስትና ሊሠጥ የሚችል ሠነድ ስለመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁ 24435 የህግ ትርጉም የሠጠበት በመሆኑ፣ አመልካች ቼኮቹን በፈረሙበት ወቅት ከዋና ሥራ አስኪያጅ በተሠጣቸው ውክልና መሠረት ሲሆን ለባንክ በቀረበበት ጊዜ ግን ውክልናቸው በመውረዱ ተከታትለው ሃሣቡን ማስተካከል የማይችሉ በመሆኑ፣ ቼኩ ለክፍያ ቀርቦ ሊመለስ የቻለው በቂ ስንቅ የለውም በማለት ሣይሆን ሂሣቡ በመዝጋቱ በመሆኑ እና ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል ቢባል እንኳ 1ኛ እና 2ኛ ክስ በአንድ የወንጀል የመሥራት ሃሣብ የተሠራ በመሆኑ እንደሁለት የተለያዩ ወንጀሎች መታየት የለባቸውም የሚል ሲሆን፣ ሶስተኛውን ክስ በተመለከተ የተጠቀሰው ቼክ በአቶ በላይነህ ሠርጉአለም ያልተፈረመ ስለመሆኑ በቴክኒክ ምርመራ ከመረጋገጥ አልፎ በአመልካች ስለመፈረሙ አልተረጋገጠም፣ የሠነድ ማስተካከያ አድርገዋል ቢባል እንኳ የነበረን ዕዳ ከመክፈል አኳያ እንጅ ሀሰተኛ ሠነድ ለመፍጠር ባለመሆኑ በቸልተኝነት አደረጉ ቢባል እንኳ እንደሚያስቀጣ ባለመደንገጉ ጥፋተኛ የሚያደርግ አይደለም ፣ ቼኩ የተሠጠው የድርጅቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትክክለኛ ዕዳ ለመክፈል እንጅ ድርጅቱን ለመጉዳት ወይም አመልካች ራሱን ወይም ሌላውን ለመጥቀም ያደረገው ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የሚባል ከሆነ እንኳ ከዚህ በፊት ወንጀል ፈፅመው ሪከርድ የሌለባቸው በመሆኑ፣ የቤተሰብ ኃላፊ መሆናቸው፣ አጠቃላይ የጉዳዩ አፈፃፀም እና ያበረከቱት አስተዋጽኦ ታይቶ ቅጣቱ ተሻሽሎ በገደብ እንዲለቀቁ በማለት የቀረበ ነው፡፡

ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ዐቃቤ ሕግ መልስ እንዲሠጥበት ታዞ በቀን 06/10/03 6 ገፅ የጽሑፍ መልስ አቅርበል፡፡ የመልሱ ፍሬ ሃሣብ የቀረበው ቅሬታ የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተትን የማይመለከት በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎት የማይታይ በመሆኑ ውድቅ ሆኖ እንዲሠናበት ፣ በ1ኛ እና 2ኛ ክስ ሥር ማታለሉ ከተከፋይ አቶ ፍትዊ ወልዳይ አካያ ብቻ የሚታይ ከሆነ መታለል የለም ብሎ መከራከር ይቻላል ሆኖም በወ.መ.ሕግ ቁ 692 ሥንመለከት በቼኩ መታለል መፈፀሙን ለማስረዳት ብቸኛው መመዘኛ ቼኩ ለክፍያ ሲቀርብ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን ማረጋገጥ በቂ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የግል ተበዳይ ጠየቀም አልጠየቀም የህጉ አላማና ፍላጎት የሕዝብን ጥቅም ከማስከበር አኳያ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ክርክር አይደለም፣ የተሠጠውም ቼክ በዋስትና የተሠጠ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር የለም፣ ሶስተኛው ክስ ሥርም ፊርማውን ከሥራ አስኪያጁ ጋር አመሣስሎ የፈርመው ተበዳይን ለመጉዳት እንደሆነ ግልፅ በመሆኑ እና የተሠጠው የጥፋተኝነትም ሆኖ ቅጣት የሚነቀፍ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲሠናበት በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በቀን 10/10/2003 ዓ.ም 3 ገፅ የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሠረት መፍትሔ ማግኘት ያለባቸው ጭብጦች፡-

1. በ1ኛ እና 2ኛ ክስ ሥር የአመልካች በወ.መ.ሕግ አንቀጽ 693/1/ ሥር ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ከአጠቃላይ የቼኩ አሠጣጥ ሂደት አኳያ በመመርመር
2. በ3ኛ ክስ ሥር በተጠቀሰው አንቀጽ የወ/መ/ሕ/ቁ 382/1/ ሥር ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነትና አጠቃላይ ቅጣት አጣጣሉን በመመልከት አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ወደ ተያዙት ጭብጦች ስንመለስ፡- 1ኛ እና 2ኛውን ክስ በተመለከተ በእርግጥ በወ.መ.ሕ.ቁ 692/1/ ሥር ስለማታለል የተሠጠውን ትርጉም በምናይበት ጊዜ “…….የማይገባ ብልፅግና ለራሱ ለማስገኘት ወይም ለሌላ ሠው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር ፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሠወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሠው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም ፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታሎ የራሱን ወይም የሶስተኛ ወገን የንብረት ጥቅም የመጉዳት አድራጎት እንዲፈፀም ያደረገ እንደሆነ……” በሚል ይደነግጋል፡፡

አሁን በቀረበው ክርክር ላይም የቀረበው ክርክር የተፈፀመ የማታለል አድራጎት የለም፣ ቼኩ በሚሠጥበት ጊዜ በቂ ስንቅ እንደሌለው ተበዳዩም ያውቅ ነበር ገንዘብ ከደንበኞች ተሰብስቦ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እስኪሠጠው ድረስ ለመያዣር የተሠጠ እንጅ ባንክ ቤት ቀርቦ እንዲመነዘር አይደለም የሚል ከመሆኑ አኳያ ተበዳይን መሠረት ያደረገ ማታለል የተፈፀመ ስለመሆኑ ከላይ ከተመለከተው የሕግ ድንጋጌ አኳያ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የወ.መ.ሕግ ቁ 693/1/ን በምንመለከትበት ጊዜ ርዕሱ " የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት" የሚል ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ሥር የተደነገገው 693/1/ ማንም ሰው ቼክ በሚያወጣበት ወይም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ያለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ /የሰጠ / እንደሆነ በሚል ተደንግጓል፡፡ ይሄንን ስለቼክ የሚደነግገውን የወንጀል አንቀጽ ስንመለከት በወንጀለኛ መቀጫ ሕግ ቁ 692/1/ ሥር ከላይ የተመለከተውን የወንጀሉን አፈፃፀም ከግል ተበዳይ/ተታሎአል/ ከሚባል ግለሰብ አኳያ ያልታዬ መሆኑን ነው፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ በተለይም የቼክ ሠነድ ለአምጭው ወድያውኑ የሚከፍል እና በንግድ ሕጉ ከተቀመጡት ውስን መቃወሚያዎች ውጪ ሊቀርቡበት የማይገባ በመሆኑ በቼክ አውጪው ላይ ኃላፊነት የጣለ ይመስላል፡፡ ይሄም ማለት ከላይ የተመለከተው የወ.መ.ሕግ ንባብ አንድ ቼክ ያወጣ /የሠጠ/ ሰው በቂ ስንቅ መኖርን ማረጋገጥ እንዳለበትና ቼኩ በተሠጠበት ጊዜ ወይም ለክፍያ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ ያለመኖሩ ብቻ የተጠቀሰውን የወንጀል ኃላፊነት እንደተቋቋመ የሚቀበለው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አኳያ የግል ተበዳዩ በየትኛውም ተቋም በወንጀል ክስ ያልመሠረተ መሆኑ ሆኖም ግን ቼኩን ለክፍያ ሲያቀርበው በቂ ገንዘብ የለውም ተብሎ መመለሱ እስከተረጋገጠ ድረስ ሕግ አውጪው ደግሞ ቼክን በተመለከተ የተደነገገዉ የማታለል ወንጀል እስከ ተሟላ ድረስ ከኃላፊነት ነፃ ሊያደርገው አይችልም ፡፡

በሌላ በኩል ቼኩ የተሠጠው ለባንክ ቀርቦ እንዲመነዘር ሣይሆን ለዋስትና የተሠጠ ነው በማለት የቀረበውን ክርክር ስንመለከተው ከዚህም ጋር ተያይዞ ከዚህ በፊት ይሄ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ 24435 በሆነ መዝገብ ቼክ በዋስትና መያዝ እንደሚቻል የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል በማለት ተያያዥ ክርክር ቀርቧል፡፡ ይሄንን በተመለከተ ቀድሞ የሕግ ትርጉም ተሠጥቶበታል የተባለው መዝገብ አንድ ቼክ ለክፍያ ሲቀርብ /ገንዘብ ስጠየቅ ለቀረቡበት ከሚችሉት መቃወሚያዎች አንድ የግል ግንኙነት /personal Relation/ መኖር ስለመሆኑ በፍትሕብሔር ክርክር ላይ የተያዘ አቋም እንጅ አሁን እየታየ ካለው የወንጀል ኃላፊነት አኳያ ቀጥታ ግንኙነት ያለው ባለመሆኑ ፣ የተባለውም የግል ግንኙነት ከላይ ከተመለከተው የወንጀል ኃላፊነት አኳያ አላፊነቱን ቀሪ የሚያደርግበትን አግባብ ያስረዳ /ያመለከተ/ባለመሆኑ አልፈነዋል፡፡

የአመልካች ኃላፊነት መታየት ያለበት በወ/መ/ሕግ ቁ 693/1/ ወይስ 693/2/ ሥር የሚለውን በተመለከተ ባንክ ቤት የነበረው ሂሣብ የተዘጋው በተደጋጋሚ በቂ ስንቅ ሣይኖር ቼክ በመሠጠቱ ባለው መመሪያ መሠረት የሂሣብ ቁጥሩ መዝጋቱን ያመለከተና ይሄንንም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጡት በመሆኑ በቸልተኝነት የተሠጠ ነው የሚያሠኝ አይደለም ፡፡

1ኛ እና 2ኛው ክስ የተሠራው በአንድ የወንጀል ሐሣብ ነው በሚል የተነሣውን ክርክር በተመለከተ የተፈፀመው በአንድ ቀን ልዩነት ከመሆኑም በላይ የተሠጠበት ዓላማም ለተለያዩ ይሄውም የድርጅቱን ደረጃ ለማሣደግና ለዕዳ መክፈያ በሚል በመሆኑ በአንድ የወንጀል ሃሣብ የሚያሠኝ ሣይሆን በወ.መ.ሕግ ቁ 62 መሠረት በአዲስ ሃሣብ እንደሠራው ይቆጠራል፡፡

ሶስተኛውን ክስ በተመለከተ በቼኩ ላይ የተፈረመው ፊርማ የተበዳይ አለመሆኑ በቴክኒክ ምርመራ የተረጋገጠ በመሆኑ ፈራሚው ማን ሊሆን ይችላል? የሚለው ነጥብ መታየት አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚሁ መሠረት ቼኩን የተቀበለው ሰው ለፍርድ ቤት ቀርቦ በሠጠው የምስክርነት ቃል ቼኩን የሠጠው አመልካች እንደሆነ ፣ ቀድሞ የተፈረመበት እንደሆነና ቀኑ እንዲያጥርለት አመልካችን እንደጠየቀና በጠየቀው መሠረት ቀኑን አሣጥሮ ፖራፍ አድርጎበት የሠጠው መሆኑን መስክሯል፡፡ በዚህ ቼክ ላይ የቴክንክ ምርመራ ሲደረግ ቢያንስ ፖራፍ የተደረገው እንኳ የአመልካች ፊርማ ስለመሆኑ ያልተመለከተ በመሆኑና የበታች ፍ/ቤትም አመልካች የተበዳዩን ፊርማ አስመስሎ ፈርሟል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ይሄ ደግሞ የማስረጃ ምዘና በመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና አዋጅ ቁ 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማረም እንጂ ማስረጃን መመዘን ባለመሆኑ በሌላ በኩል አመልካች የተበዳዩን ፊርማ አመሣስሎ ፈርሟል ወይስ አልፈረመም? የሚለው ደግሞ የማስረጃ ምዘና በመሆኑ ነው፡፡

ባጠቃላይ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሠጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ቅጣትን በተመለከተ የአመልካች ቀድሞ ባህርይ መልካም መሆኑ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑና በበርካታ ማህበራዊ አገልግሎቶች ተሣታፊ መሆኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተላለፈ በመሆኑ ከዚህም አኳያ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የተላለፈበት የጥፋተኝነት ውሣኔና ቅጣት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ መሠረት ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 55773 በቀን 20/5/2003 ዓ.ም እና በመዝ.ቁ 55897 በቀን 30/6/2003 እና ሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠው ፍርድ እና ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ቁ 195/2/ /ለ/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የሠጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ የሚነቀፍበት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ፌዴራል ዐቃቤ ህግ - ዐ/ህግ አበባው መንግስቱ ቀረበ፡፡

ተጠሪ ፡- በሪሁን ፍቃዱ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ የመሰረተው የወንጀል ክስ ተጠሪ በ1996 ዓ/ም በወጣው የወ/ህ/አንቀጽ 540 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ መስከረም 15 ቀን 2002 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 8፡30 ሲሆን በቂ/ክ/ከተማ ቀበሌ 02/03 ልዩ ቦታው "ኤልሲባር" አካባቢ ሚች ከድር አብዱልቃር ያሽከረክር ከነበረው መኪና ሲወርድ ልትገጨን ነው እንዴ በማለት የሟችን ግንባር በቦክስ መትቶ ከጣለው በሁዋላ በወደቀበት ግንባሩንና ሆዱን ደጋግሞ በመረጋገጥ በብርጭቆ ጭንቅላቱን በመምታት ለከፍተኛ ጉዳት በመዳረግ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሕይወቱ እንዲያልፍ በማድረጉ ተራ የሆነ ሰው ግድያ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም የዐቃቤ ሕጉን ክስ በመካዱ ዐቃቤ ሕግ እንደክሱ ሊያስረዱ የሚችሉ ማስረጃዎች ያሉት መሆኑን ገልጾ ማስረጃዎቹ ከተሰሙ በሁዋላ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ድርጊቱን መፈፀሙ ተረጋግጦበታል በሚል ምክንያት እንዲከላከል አድርጎ የመከላከያ ምስክሮች እንዲያሰማ መብቱን ጠብቆለት የመከላከያ ማስረጃዎቹን አሰምቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃዎቹ ያላስተባበለ መሆኑን ዘርዝሮ የመከላከያ ማስረጃዎቹን ቃል ውድቅ ከአደረገ በሁዋላ ተጠሪን በዓቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ በ3/ሦስት/ አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ በተጠሪ ላይ በተላለፈው የቅጣት ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቁጥር 3-9590/02 በቀን 11-12-2002 ዓ.ም በተፃፈ 5/አምስት/ ገፅ የሰበር አቤቱታ የበታች ፍርድ ቤቶች በቅጣት አወሳሰን ረገድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ፈፅመዋል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ጥፋተኛ ከተባሉት ድንጋጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መነሻ ቅጣት ወርዶ ቅጣት መሰጠቱ የወ/መ/ሕ/ቁጥር 189/1/ ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም ተጠሪ ጥፋተኛ ከተባሉበት ድንጋጌ መነሻ ቅጣት ዝቅ ተደርጎ በሦስት ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት መቀጣታቸው ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አኳያ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የበታች ፍርድ ቤቶች የቅጣት አወሳሰን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሚች ከድር አብዱልቃድር ያሽከረክር ከነበረው መኪና ሲወርድ "ልትገጪን ነው እንዴ?" በማለት የሟችን ግንባር በቦክስ መትቶ ከጣለው በሁዋላ በወደቀበት ግንባሩንና ሆዱን ደጋግሞ በመረጋገጥ በብርጭቆ ጭንቅላቱን በመምታት ለከፍተኛ ጉዳት በመዳረግ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ህይወቱ እንዲያልፍ ማድረጉ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ለወንጀል ድርጊቱ መፈፀም ወይም መሰራቱ እንዲሁም ድርጊቱን የፈጸሙት ወይም የሰሩት ተጠሪ መሆናቸው በሚገባ መልኩ እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 ስር በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት የተረጋገጠ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት በመገንዘብ በቅጣቱ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ሕጋዊነት ተመልክተናል፡፡

የአመልካች መሠረታዊ ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ከሚያስቀጣው ድንጋጌ መነሻ ቅጣት ዝቅ በማለት የሰጡት የሦስት አመት ፅኑ እስራት ቅጣት በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮችና የቅጣት አወሳሰኑን በተመለከተ የወንጀል ህጉ ያስቀመጣቸውን መርሆዎች ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ እኛም ይህንኑ ቅሬታ ከህጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ "የወንጀል ህግ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለ ወንጀሎችና ስለ ቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለበቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምንጊዜም ሰብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሳዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለ ቅጣታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የሃሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስንና የቅጣት አወሳሰን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ (manual) እንደሚወጣ የሚያስገነዝቡን ናቸው።

ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንረዳው አቢይ ነጥብ ቅጣቶች መወሰን ያለባቸው የህጉን መንፈስ በመከተል ዓላማዎችና ግቦቹንም ተፈፃሚ በማድረግ ሀሣብ መሆኑን ነው። የህጉን መንፈስ ከመተግበር አኳያ ወንጀለኛውን ማዕከል የማድረግ ፅንሰ ሀሣብ አፅንኦት የተሰጠው ጉዳይ ነው። ዳኞች በፅንሰ ሀሣቡ መሠረት የተሰጣቸውን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣን (Discretion) በስራ ላይ ሲያውሉ ሰብአዊ ክብርን ከማስጠበቅ ዓላማ ጋር መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ ህግ አውጪው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 87 እና 1 ስር የተመለከቱትን መሠረት በማድረግ ዳኞች የቅጣት ውሣኔ በምን መንገድ መወሰን እንደሚገባቸው በአንቀጽ 88 ስር አስቀምጧል። በወንጀል ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ስንመለከትም ዳኞች ከተሰጣቸው የቅጣት ክልል ሳይወጡ የአጥፊውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት እንዲወስኑ ህጉ ስልጣን የሰጣቸው መሆኑ ነው። ዳኞች አጥፊውን በተመለከተ ከግምት ውስጥ ሊያስገቡዋቸው የሚገባቸው በርካታ የአጥፊ፣ ሁኔታዎች ቢኖሩም የቅጣት አወሳሰናቸው መሠረት የሚያደርገው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን /degree of individual guilt/ ስለመሆኑ የአንቀጽ 88/2/ ድንጋጌ ይዘትና አቀራረፅ ያስረዳል። ይህም በሕጉ አግባብ የወጣውና ከግንቦት 09 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ እንደተጠበቀ ሁኖ በቅጣት አወሳሰን ወቅት ዳኞች ሰፊ ስልጣን ያላቸው መሆኑን ጠቋሚ ነው። አንቀጽ 88/2/ በመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል አድራጊውን የአደገኛነት መጠን መሠረት በማድረግ ዳኞች ቅጣት እንዲወስኑ ማድረጉና ይህንን ሲወስኑም በድንጋጌው የተመለከቱትን የወንጀሉን አፈፃፀም የአጥፊውን ያለፈ የህይወት ታሪኩን እና የኑሮ ሁኔታ ከግምት በማስገባት በማመዛዘን ለወንጀለኛው የሚገባውን የቅጣት መጠን እንዲወስኑ መደንገጉ የቅጣት ውሣኔዎችንና እርምጃዎችን እየተራራቁ እንዳይወስኑ የማድረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ከመታሰቡም በተጨማሪም ችግሩ የሚቀረፍበትና የሚቀነስበትን ሥርዓትም ህጉ ዘርግቷል። ዳኞች ቅጣት ሲወስኑ በህጉ አንቀጽ 88/2/ ለአጥፊው ተገቢ ነው ያሉትን ቅጣት ከወሰኑ በኋላ በህጉ የተመለከቱትን የማቅለያና የማክበጃ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ከፍ ወይም ዝቅ ለማድረግ የሚችሉ ስለመሆኑ ህጉ ያሳያል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ በአንቀጽ 82/1/ ከፊደል /ሀ/ እስከ ፊደል /ሠ/ ድረስ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ካስቀመጠ በኋላ በአንቀጹ ንዑስ ቁጥር ሁለት ስር በንዑስ ቁጥር አንድ ስር የተመለከቱት የማቅለያ ሁኔታዎች በህጉ ልዩ ክፍል ተካተው ሲገኙ በድጋሚ በማቅለያነት ዳኞች እንዳይጠቀሙ ያሳስባል። የህጉ አንቀጽ 84 ደግሞ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን የዘረዘረ ሲሆን ዳኞች የህጉን አንቀጽ 183 ባገናዘበ መልኩ ቅጣት የሚያከብዱባቸውን ሁኔታዎች ያሳያል። ዳኞች ቅጣትን የሚቀንሱትም ሆነ የሚያከብዱት ተገቢ ሁኖ ሲገኝ ስለመሆኑ የአንቀጽ 179 እና 183 ድንጋጌዎች ያሳያሉ። አንቀጽ 179 የቅነሣውን ገደብ የሚያሳይ ሲሆን ከዚህ መደበኛ ቅነሣ በተጨማሪ ልዩ ቅነሣ ለማድረግ እንደሚቻልም ህጉ በአንቀጽ 180 ስር አስቀምጧል። በህጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 86 ቅጣትን በማቅለልም ሆነ በማክበድ ረገድ ከህጉ አንቀጽ 179፣ 182 ውጪ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥማቸው ዳኞች ምክንያታቸውን በመግለፅ ቅጣቶችን ለመቀነስ ወይም ለማክበድ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ እነዚህ ስለቅጣት አወሳሰን በህጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሲታዩ የሚያስገነዝቡን አቢይ ነጥብ ቅጣቶችን በመጣልና እርምጃዎችን በመውሰድ ረገድ ዳኞች አመዛዝነው የመወሰን ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ እንግዲህ ህጉ ለዳኞች የሰጠውን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣን ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታና በሕጉ የሰፈረውን የቅጣት አጣጣል መርህ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ዐ/ህግ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ቅሬታ ስንመለከተው ከመነሻው ቅጣቱ እንዲወርድ የተደረገው ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሳይኖርና እና የቅጣት ማቅለያው አለ ቢባል እንኳ የወንጀሉ ማቋቋሚያ የሆነው ነገር ስለመሆኑ ጠቅሶ መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ቅጣቱን ሲጥል በማቅለያነት የያዘው ድርጊቱ በድንገተኛ አጋጣሚ መፈጸሙን፣ በተጠሪ ላይ ሪኮርድ ያለመቅረቡንና በወቅቱ የነበረው ያልተገባ የሚች መኪና አነዳድ የፈጠረው ጫና ነው የሚሉትን ምክንያቶችን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ የተከሰሱትና ጥፋተኛ የተባሉት ተራ በሆነ የሰው ግድያ ወንጀል ሲሆን ድርጊቱ በድንገት የተፈፀመ ነው የሚለው ምክንያት ተጠሪ የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት የሚያቋቁም ነው ከሚባል በስተቀር በቅጣት ማቅለያነት በድጋሚ ሊወሰድ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠውን የወንጀሉን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ፍ/ቤቱ ይዞ በቅጣት ማቅለያነት መወሰዱም የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 82/2/ ስር ያስቀመጠውን መርህ የሚጻረር ሲሆን ይኸው ሕግ በአንቀጽ 86 ስር ለዳኞች የሰጠውን ስልጣንም መሰረት ያደረገ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ፍርድ ቤቱ በወንጀል ህጉ ቁጥር 540 ስር የተመለከተውን መነሻ ቅጣት ተገቢ መስሎ ሲታየው በህጉ አንቀጽ 108/1/ የተመለከተውን የዕኑ እስራት ቅጣት መነሻ ሳይወርድ ማቅለል የሚችል ስለመሆኑ የአንቀጽ 179/ሐ/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህ በህጉ ለዳኞች ከተሰጠው ስልጣን አኳያ ተገቢነት ያለው ውሳኔ ተሰጥቷል ሊባል የሚችለው በጠቅላላ ወይም ልዩ ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ስር የሚወድቁና የወንጀሉ ማቋቋሚያ ያልሆኑ ማቅላያ ምክንያቶች መገኘታቸው ሲረጋገጥ ነበር፡፡ በተያዘው ጉዳይ ድርጊቱ በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ ነው የሚለው ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የወንጀል ድርጊቱ መቋቋሚያ ከሚሆን በስተቀር በወ/መ/ሕጉ አንቀጽ 82/2/ እንደተመለከተው በድጋሚ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝ የሚችል አይደለም፡፡ በዚህ ምክንያት የቅጣት ማቅለያ አይሆንም እንጂ ይሆናል ቢባል እንኳ ተጠሪ ሚችን ለሕልፈተ - ሕይወት ሲዳርግ የድርጊቱ አፈፃፀም ከባድ የነበረ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልፅ የሚያሳይ በመሆኑ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉት ድንጋጌ ሊያስቀጣ ከሚችለው መነሻ ቅጣት መውረድም ሆነ መነሻ ቅጣቱን ለመጣል የሚያስችል ሕጋዊና በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ ስለሆነም ድርጊቱ በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈጸመ ነው የሚለው ምክንያት በቅጣት ማቅለያነት መወሰዱ ከድርጊቱ አፈፃፀም አንጻር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች በህጉ ለዳኞች የሚሰጠውን አመዛዝኖ የመወሰን ስልጣንን ሲጠቀሙ በቅጣት አወሳሰን ረገድ ህጉ ያስቀመጣቸውን መሠረታዊ መርሆዎች በተለይም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 82/2/ እና 189 ስር የተመለከቱትን፤ ጥሰው መገኘታቸውን የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ የወንጀል ሪኮርድ የሌለባቸው መሆኑም ቅጣቱን ከመነሻው ለመውረድ የሚያስችል አይደለም፡፡ ሲጠቃለልም በተጠሪ ላይ የተጣለው ቅጣት የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ ግብና ዓላማ እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ከድርጊቱ አፈጻጸም ጋር ያገናዘበ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 87623 ሚያዝያ 22 እና 26 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 56605 ሐምሌ 09 ቀን 2002 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2//መ/ መሠረት ተሻሽሎ ተጠሪ ሊቀጣ የሚገባው በጉዳዩ ላይ የታሰረው የሚታሰብለት ሁኖ በአስር አመት ጽኑ እስራት ነው በማለት ወስነናል፡፡
2. ውሳኔው የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማ/ቤቱ ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 14/2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1- አቶ አደም አብዱ } የቀረበ የለም

2- አቶ ጀማል አሊ }

ተጠሪ፡- የፌደራል ሥነ - ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ

ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካቶች በተከሠሡበት የሙስና ወንጀል የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን የቅድመ ክስ ክርክር ሂደት ከሠማ በኋላ ወደ ዋና ክስ እንዲገባና የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች እንዲሠሙ የመወሰኑን እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይሄንኑ ትዕዛዝ የማፅናቱን አግባብነት ለመመርመር የቀረበ ነው፡፡

አመልካቾች ቅሬታቸውን ከሌሎች 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ከነበሩት እና ጉዳያቸው አያስቀርብም ከተባሉት ጋር ያቀረቡ ሲሆን ሰኔ 23 ቀን 2002 ዓ.ም በ3 ገፅ በተፃፈ አቤቱታ የአሁን አመልካቾችን የሚመለከተው ክፍል ፍሬ ሃሣብ ከሣሽ የአሁን አመልካቾችን ከገቢያቸው በላይ ንብረት አፍርተዋል በማለት ስለተከሣሾቹ የያዘው የሀብት ማስረጃ ሣይኖር በወ/መ/ሕግ ቁ 419/ለ/ መሠረት ክስ ማቅረቡ ያለአግባብ ነው በሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በቀን 21/4/2003 ዓ.ም በሁለት ገፅ የሠጠው የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካቾች የሉሲ አንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር አባል ብቻ ሣይሆኑ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ውስጥ ባላቸው ኃላፊነት በመጠቀም ማህበሩ ያለአግባብ ጨረታዎቹን እንዲያሸንፍ አድርገዋል፡፡ ከገቢያቸው ጋር ያልተመጣጠነ ንብረት አፍርተዋል በማለት የከሰሰ ሲሆን ወደ ክሱ ሲገባ በማስረጃ ነጥሮ የሚወጣ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ወደ ዋና ክስ እንድንገባ መወሰኑ በአግባቡ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሠረት የወንጀል ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው ፍርድ ቤት የቅድመ ክሱን ክርክር በመስማት ወደ ዋናው ክስ ተገብቶ ምስክር እንዲሠማ መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ መሠረት በሙስና ወንጀሎች ላይ የቅድመ ክስ ዝግጅት የሚመራበት አግባብ በአዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 35 እስከ 41 ድረስ የተዘረዘሩ ሲሆን ሂደቱ ውስጥ ማለፍ አስገዳጅ ያልሆነና እንደ ክሱ ዓይነት ታይቶ የክሱ ጭብጦችና ማስረጃው ዝርዝር ውስብስብ በመሆኑ የፍርድ ሂደቱን ሊያራዝምና ሊያወሳስብ ይቻላል ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲገምት ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 35 በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

የቅድመ ክስ ዝግጅት ዓላማ ለክሱ አወሣሠን ሊረዱ የሚችሉ ጭብጦችን ለመለየት ፣ ባለጉዳዮች ጭብጦችን እንዲረዱ ማድረግ ፣ የክሱን ሂደት ለማፋጠንና ችሎቱ አካሄዱን ለመምራት እንዲችል ለማስቻል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 36/1/ ሥር የተዘረዘረ ሲሆን የማስረጃዎች ተቀባይነት ላይ እና መደበኛው ክስ ከመጀመሩ በፊት ውሣኔ ሊያገኙ በሚገባቸው የህግ ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ የሚሠጥ ስለመሆኑ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 36/2/ ሥር ተደንግጓል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ከገቢያቸው በላይ ንብረት አፍርተዋል በማለት የተከሠሡ በመሆኑ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት የቅድመ ክሱን ሂደት ካዳመጠ በኋላ ወደ ዋና ጉዳዩ ተገብቶ ምስክሮች ይሠሙ በማለት ትዕዛዝ መስጠቱ በአመልካቾች ላይ ከቀረበው ክስ አኳያ ሲታይ የተከሠሱበት ጉዳይ በማስረጃ የሚጣራ ከመሆኑ አኳያ ተፈፀመ ሊባል የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡ በተጨማሪም በዚህ ቅድመ ክስ ዝግጅት ሂደት ውስጥ መታለፍ ራሱ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ የተቀመጠ ባለመሆኑና ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን ውስብስብነት እየተመለከተ የሚወሰነው ጉዳይ በመሆኑ የቀረበው የወንጀል ክስ በማስረጃ እንዲጣራ መታዘዙ ቅሬታ የሚቀርብበት ሊሆን አይገባም ብለናል፡፡ በዚሁ መሠረት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ዋና ክስ ተገብቶ ምስክሮች ይሠሙ በማለት የሠጠው ብይን እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 54774 ሰኔ 11 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 85874 መጋቢት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሣኔ በተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 40 መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የቅድመ ክስ ዝግጅት ሂደት እንደተጠናቀቀ በወንጀል ክሱ የተመለከቱት ነጥቦች ላይ ምስክሮች እንዲሠሙ መታዘዙ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 63344

ሐምሌ 28 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡- 1. ላሉ ሰይድ አከልታ - አልቀረቡም

2. ከማል ሁሴን ዳልቦ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የዋስትና ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪዎች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 676 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የአምነት ማጉደልና የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦባቸዋል፡፡

ተጠሪዎች የዋስትና መብታቸው ተጠብቆ ክርክሩን እንድንቀጥል ይፈቀድለን በማለት አመልክተዋል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የተከሰሱበት የሙስና ወንጀል ከአምስት ዓመት እስከ ሀያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ የተደነገገ በመሆኑና ከአስር ዓመት በላይ በሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው የዋስ መብት እንደማይፈቀድለት በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 የተደነገገ በመሆኑ በዋስትና ወረቀት ሊለቀቁ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4ን በመጥቀስ ተጠሪዎች በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከራከሩ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ከአስር ዓመት በላይ በሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል የተከሰሰ የሚለው ሀረግ አስር ዓመት ዝቅተኛው የቅጣት መነሻ ወይም ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያን መሠረት በማድረግ እንደሚወሰን ግልጽነት የጐደለው ነው፡፡ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ ዝቅተኛው መነሻ አምስት ዓመት ከፍተኛው ጣሪያ ሀያ አምስት ዓመት በመሆኑ ተጠሪ ሌላ ዋስትና የሚያስከለክል ተጨማሪ ምክንያት ያላቀረበ ስለሆነ በዋስትና ወረቀት ሊለቀቁ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ታህሣስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ከአርሶ አደር በደረሰኝ የሰበሰቡትን ገንዘብ አንደኛ ተጠሪ ብር 382,895.01 ለመንግስት ገቢ ሣያደርጉ ከባድ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸሙ መሆናቸዉን ሁለተኛው ተጠሪ ከሰበሰቡት ግብር ብር 333,940.91 ለመንግስት ገቢ ባለማድረጋቸዉ ከባድ የዕምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የወንጀል ህግ አንቀጽ 676 ንኡስ አንቀጽ 1ን በመጥቀስ ክስ አቅርበናል፡፡ ከአስር ዓመት በላይ በሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ተከሣሽ በዋስትና ወረቀት የማይለቀቅ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ይህንን ድንጋጌ በተመሣሣይ መንገድ በመተርጉም ተጠሪዎች በዋስ እንዲለቀቁ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሷቸው በቀነ ቀጠሮው መልስ ይዘው ያልቀረቡ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ተጠሪዎች በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቁ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን የአዋጅ 434/97 አንቀጽ 4 መሠረታዊ ይዘትና የዚህን ድንጋጌ ተግባራዊ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ ፍርድ ቤቶች ሊከተሏቸው የሚገባቸዉ የህግ አተረጓጐም መሠረታዊ መርሆችን ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ 1 በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይቻላል፡፡ ሆኖም የተከሰሰበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው የዋስትና መብት ለተከሣሽ ፍርድ ቤቶች ሊፈቅዱ የማይችሉበትን ሁኔታ አስገዳጅ በሆነ መንገድ የሚደነግግ ነው፡፡

ድንጋጌው ከአስር ዓመት በላይ በሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስትና ወረቀት መለቀቅ እንደማይፈቀድለት ይደነግጋል፡፡ ተከሣሹ የከሰሰበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ መሆኑን ወይም ከአስር ዓመት በላይ በእስራት የማያስቀጣ መሆኑን ለመወሰን ፍርድ ቤቶች ተከሣሹ የተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ የሚደነግገውን ዝቅተኛውን የመነሻ ቅጣት ነው መሠረት የሚያደርጉት ወይም ተከሣሹ በተከሰሰበት ወንጀል በህጉ የተደነገገውን ከፍተኛውን የቅጣት ጣሪያ የሚለውን ነጥብ ለመተርጐም በመጀመሪያ የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ምግባርና ልዩ የማስረጃ ህግ በልዩ ሁኔታ መደንገግ ያስፈለገበትን ምክንያትና የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግን በማወጅ ህግ አውጭው ሊያሳካው የፈለገውን ግብ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ ህግ አውጭው የሙስና ወንጀል ያለውን ልዩ ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት ሙስናን ለማጋለጥ ሙስናን ለመመርመርና የሙስና ክስን ውጤታማ ለማድረግ በማሰብ የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ በመሆኑ በአዋጅ መግቢያ ላይ ግልጽ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የአዋጁ ድንጋጌዎች ትርጉምና ተግባራዊ አፈጻጸም ይህንን የህግ አውጭውን መሠረታዊ ግብ የሚያሣካ በሚሆንበት መንገድ መተርጐምና ስራ ላይ ማዋል ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት የሚባው አተረጓጐም መርህ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሁለተኛ ደረጃ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ድንጋጌ በልዩ ሁኔታ አሁን ያለውን ቅርጽና ይዘት እንዲኖረው ተደርጐ የተደነገገበትን መሠረታዊ ምክንያት ማየት ያስፈልጋል፡፡ አዋጅ ቁጥር 434/97 በአዋጅ ቁጥር 236/93 እና አዋጅ ቁጥር 239/93 የታወጀውን የፀረሙስና ልዩ የሥነ ሥርአት ሕግ የማስረጃ ህግ ለማሻሻል የወጣ የህግ ማእቀፍ ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 በአዋጅ ቁጥር 239/93 አንቀጽ 2 በሙስና ተጠርጥሮ የተያዘ ማናቸውም ሰው የዋስትና መብት አይኖረውም በማለት የተደነገገውን ለማሻሻል ታስቦ የተደነገገ ድንጋጌ ነው፡፡ ድንጋጌው ዓላማ ሁሉንም በሙስና ወንጀል የተከሠሱ ሰዎች የዋስ መብት በህግ ከመከልከል ይልቅ የተከሠሱበት ወንጀል የሚያስከትለውን ከፍተኛውን የቅጣት ጣሪያ መሠረት በማድረግ በቀላል የሙስና ወንጀል የተከሰሰና ከአስር ዓመት በታች በሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል የተከሰሱት በዋስትና የሚለቀቁበትና የዋስትና መብታቸው የሚጠበቅበትና በከባድ ሙስና ወንጀሎች የተከሰሱትና የተከሰሱበት ወንጀል ከዓስር አመት በላይ የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከራከሩ ለማድረግ ታስቦ የወጣ ድንጋጌ መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 434/97 ሀተታ ዘምክንያት በግልጽ የሚያሳይ በመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 434/97 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ከዚሁ አንፃር መተርጉምና ተፈፃሚ መሆን የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ድንጋጌ ውጤታማ በሚሆንበት መንገድ መተርጐምና ሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 404 ንዑስ አንቀጽ 4 የሙስና ወንጀል እንደሆኑ የተዘረዘሩት የወንጀል ድንጋጌዎች በአብዛኛው ዝቅተኛው የመነሻ ቅጣት ከአስር ዓመት በታች እንደሆነ የድንጋጌዎቹን ይዘትና የሚያስከትሉትን አነስተኛ ቅጣትና ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ዝቅተኛ የቅጣት መነሻ በማድረግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ትርጓሜ ድንጋጌውን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ተፈፃሚ የማያደርግና ህግ አውጭው የፀረሙስና ልዩ የሥነ ሥርዐትና የማስረጃ ህግን በማውጣት ለማሳካት የሚፈልገውን ግብ የማያሳካና ህግ አውጭው ድንጋጌውን ሲያወጅ የነበረውን መሠረታዊ ሀሳብ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በዝርዝር ባስቀመጥናቸው ምክንያቶች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ ለወንጀል የሚደነግገውን ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያ ሣይሆን ዝቅተኛውን የቅጣት መነሻ መሠረት በማድረግ መተርጐም አለበት በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

2 ተጠሪዎች የተከሰሱበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 676 ንኡስ አንቀጽ 1 እስከ ሀያ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ በዋስትና ወረቀት ሊለቀቁ አይገባም በማለት በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች :- *ብሩክ ሚካኤል የቀረበ የለም*

ተጠሪ :- *ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ የቀረበ የለም*

መዝገቡ ተመረምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በወንጀል የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ የተጀመረ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት በማሰብ ጥቅምት 02 ቀን 2002 ዓ/ም በግምት ከቀኑ 4፡00 ሰዓት ሲሆን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09 ውስጥ ካለው ኒያላ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ድርጅት ውስጥ የድርጅቱ ንብረት የሆነውን አንድ ቱርቦ ቻርጀር ግምቱ ብር 46,000.00(አርባ ስድስት ሺህ ብር) እና አንድ ፒስተርን ሪንግ ግምቱ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) በአጠቃላይ ግምቱ ብር 56,000.00(አምሳ ስድስት ሺህ ብር) የሚያወጣ ንብረት ሊጠግን መጥቶ ንብረቶችን ከዚሁ ስለማይጠገኑ በራሴ ድርጅት ጠግኜ አመጣቸዋለሁ ብሎ ከወሰደ በሁዋላ ሳይመለስ የቀሩ በመሆኑ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ነው፡፡ አመልካችም ክሱ ደርሶትና ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረደረ በሁዋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ የክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ ካሰማ በሁዋላ አመልካች የመከላከል መብታቻው ተጠብቆላቸው የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አሰምተዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በመከላከያ ምስክሮቻቸው የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ አልቻሉም በሚል ምክንያት ክስ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ በአንድ አመት ከስድስት ወር እስራት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሲጸና ቅጣቱን በተመለከተ ደግሞ የቅጣት መመሪያውን ያላገናዘበ ነው በሚል ምክንያት ወደ ሰባት ወር ቀላል እስራት ዝቅ ተደርጎ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ የፍትሓ ብሔር ጉዳይ ከሚሆን በስተቀር በወንጀል የሚያስጠይቅበት አግባብ የለም ፣ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እንደክሱ አላስረዱም ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው የመቀጣታቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም መጥሪያው መድረሱ ተረጋግጦ ያልቀረበ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) በግልፅ ደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች የሚመለከት ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደምተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ አንቀፅ 24 ፣ 57 እና 58 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት ሁኔታዎችን የሚመለከቱ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች መውሰዳቸው የተረጋገጠውን እቃ ወደ እጃቸው ያስገቡት ለጥገና በሚል ምክንያት ሲሆን ይህም ከንብረቱ ባለቤት ከሆነው ድርጅት ፈቃድ ያገኙ እንደነበር ፣ ከንብረቱ ባለቤት ከሆነው ድርጅት ውስጥ ሊጠገን ባለመቻሉ ምክንያት ወደራሳቸው ድርጅት ወስደው ለመጠገን ጥያቄ ሲያቀርቡም ድርጅቱ ፈቅዶላቸው አመልካች ንብረቶቹን እንደወሰዱ በአቃቤ ክስና ማስረጃዎች የተገለፀና የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን አመልካችም ግዴታዬን ተወጥቼአለሁ ከማለት በስተቀር ከንብረቱ ባለቤት ድርጅት ጋር የጥገና ውል የነበራቸው መሆኑን የሚክዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ እንግዲህ የንብረቶቹ ባለቤት የሆነው ድርጅት ንብረቶቹን ለማስጠገን መስማማቱ ከተረጋገጠና ለጥገና የሄዱት ንብረቶች ተጠግነው ካልተመለሱ ከአመልካች የሚጠይቁት ጉዳይ ፍትሓ ብሔራዊ መፍትሔ ወይም ውልን መሰረት ያደረገ እንደሚሆን ግልፅ ነው፡፡ በውል መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ ተዋዋይ ወገን እምነት አጉድሏል ተብሎ በወንጀል የሚጠየቅ ስለመሆኑ ስለእምነት ማጉደል የሚደነግጉት የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችም ሆነ ሌሎች ድንጋጌዎች አያሳዩም፡፡ በመሆኑም በሕግ አግባብ ወንጀል ነው ተብሎ ያልተጠቀሰ ድርጊት በወንጀል የማያስጠይቅ መሆኑን ከወንጅል ሕግ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በግልፅ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡በዚህም መሰረት አመልካች ለጉዳዩ በወንጀል ጥፋተኛ የተባሉት የፍትሓ ብሔር ይዘት ባለው ጉዳይ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የወ/መ/ሕ/አንቀጽ 23(2) እና 675(1) ድንጋጌዎችን የጣሰ ሁኖ በመገኘቱ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 25870 ሕዳር 16 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ፣ ይኸው ፍርድ ቤት ሕዳር 23 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 101571

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 04 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-1)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡

2. አመልካች በወንጀል የሚጠየቁበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት አመልካች በሌላ ወንጀል የማይፈለጉ ከሆነ ካሬውኑ ከእስር እንዲፈታቸው ታዝሟል፡፡ መፍቻ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- መምህር ዓወት ተካ - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ ፡- የትግራይ ዐቃቤ ሕግ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ብሔራዊ ክልል የምሥራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የዞኑ ዐቃቤ ሕግ አመልካች በአንደኛ ተከሳሽ ስሙን በመመዝገብ በሥር ፍርድ ቤት አብረው ክስ ከቀረበባቸው ሌሎች ሦስት ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ጳጉሜ 2 ቀን 1998 በአዲግራት ከተማ ቀበሌ 01 ዞን 4 ዓለም መስፍን ሆቴል ፊት ለፊት ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት አቶ ፅጌ ባህታን በድንጋይ አናቱንና ሌላውን ሰውነቱን መትተው የገደሉት ስለሆነ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ዐቃቤ ሕግ በጠቀሰው ቀንና ሰዓት አብረውት ከተከሰሱት ሦስት ሰዎችና ክስ ካልቀረበበት ኃይለማርያም አብርሀ ከተባለ ልጅ አህዋ ሆቴል ከተባለው ሆቴል ሲጠጡ ቆይተው ወደ ቤት በመሄድ ላይ እያሉ ዓለም መስፍን ሆቴል ሲደርስ መዚቃ ሰምቶ ቀድሞ ከዓለም መስፍን ሆቴል ሲደርስ ሚች ከሆቴሉ ውስጥ ሲወጣ በር ላይ አግኝቶት ሚች ሂድ አንተ ምናባህ ብሎ እንደገፋው፣ አመልካችም ሚች ወታደር ስለመሰለው ምን አደረግሁህ ጋሼ እንዳለውና ሚች አከታትሎ መትቶት ከአስፋልት ላይ እንደጣለውና መነሳት እንዳልቻለ አመልካችም ኡኡ ብሎ እንደጮኸና ከዚያ በኋላ ሚችን በድንጋይ ማን እንደመታው እንዳላየና ተፈንክቶ ስለነበር ተነስቶ እየተንገዳገደ እንደሄደ በመግለፅ በሚች ግድያ ተካፋይ አይደለሁም ወንጀሉን አልፈፀምኩም በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ አመልካችና ሌሎቹ ተከሳሾች ዋና ወንጀል አድራጊና የወንጀል ተካፋይ በመሆን ሚችን መግደላቸውን ያስረዳልኛል በማለት አምስት ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ካቀረባቸው ምስክሮች ውስጥ ዐቃቤ ሕግ በአራተኛው ተራ ቁጥር የማስረጃ ዝርዝር ላይ ስሙን የገለፀው ምስክር ሥራው ፖሊስ መሆኑን ገልፆ በሥር ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁለተኛ ተከሳሽ እና አራተኛ ተከሳሽ ለፖሊስ ቃል ሲሰጡ የሰማ መሆኑንና ሟች አመልካችን ወድቀው ሟች ከላይ በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው አመልካች ከታች ሆነው እንዳገኟቸውና ሁለተኛ ተከሳሽ ሟችን በድንጋይ አናቱን የመታው መሆኑንና አራተኛ ተከሳሽ በእግሩ ሟችን የመታው መሆኑን ሲናገሩ ሰምቻለሁ አንደኛ ተከሳሽ /አመልካች/ መናገሩን አላስታውስም በማለት መስክሮ ተመልሷል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ ዝርዝሩ ስሙ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የጠቀሰው ምስክር ሥራው ፖሊስ መሆኑን ገልፆ በሥር ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሰዎች ስለወንጀሉ አፈፃፀም ለፖሊስ ቃላቸውን ሲሰጡ የሰማ መሆኑን በዝርዝር መስክሮ የተመለሰ ነው፡፡ ለፖሊስ የተሰጠን ቃል የመሰከረው የዐቃቤ ሕግ ሶስተኛ ምስክር ሁሉም በጠቡ ተሳታፊ መሆናቸውን የመሰከሩ መሆኑንና ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች በድምፅና በምስል በተቀረፀ ካሴት የሰጡት ቃልና ከአዲግራት ሆስፒታል የተሰጠ ማስረጃ በማስረጃነት የቀረበ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች በወረዳ ፍርድ ቤት የሰጡት የእምነት ቃል ሶስት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች በቀዳሚ ምርመራ ፍርድ ቤት የሰጡት የምስክርነት ቃልና በማስረጃነት እንደቀረበ የዞኑ ፍርድ ቤት በውሣኔው ገልጿል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ሌሎች ተከሳሾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ብይን ሰጥቶ የአመልካችና የሌሎቹን ተከሳሾች መከላከያ ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሥር ሶስተኛ ተከሳሽ የነበረው በነፃ እንዲሰናበት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በሥር ሁለተኛ ተከሳሽና አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሰዎች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 540ን በመተላለፍ የሰው መግደል ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት አመልካች በሰባት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ አፅንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በአብላጫ ድምፅ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዐቃቤ ሕግ እኔን ሟችን በመግደል ወንጀል የከሰሰኝ ቢሆንም ዐቃቤ ህግ ያቀረበው የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ በወቅቱ ሟች እኔን መሬት ላይ ጥሎ እየደበደበኝ እያለ ኡኡታ የሰማሁ መሆኑንና በሥር ሁለተኛ ተከሳሽና አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሟችን የመቱት መሆኑንና እኔም ከወደቅሁበት ተነስቼ መሄዴን የሚያስረዱ ናቸው፡፡ ሟች መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበኝ የኡኡታና የጩኸት ድምፅ ማሰማቴ በወንጀሉ ድርጊት ተካፋይ ወይም ግብረ አበር የነበርኩ መሆኑን አያስረዳም፡፡ ስለሆነም በወንጀሉ ድርጊት የተሳተፍኩ መሆኔን የሚያሳይ ምንም ዓይነት ማስረጃ ተጠሪ አቅርቦ ባላስረዳበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብዬ መቀጣቴ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በፅሑፍ መልሱን እንዲያቀርብ መጥሪያ ከደረሰው በኋላ በፅሑፍ መልሱን ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ እንዲታለፍ ችሎቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ሟችን በመግደል ወንጀል ጥፋተኛ ነው ተብሎ የተወሰነበት የቅጣት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ዐቃቤ ህግ /ተጠሪ/ ባቀረበው ማስረጃ አመልካች የወንጀሉ ሥራ ዋና ወንጀል አድራጊ /ተካፋይ/ አባሪ ወይም ረዳት መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነቱን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1.በተጠሪ ማስረጃ ምስክሮች ስለ አመልካች ያረጋገጡትን ፍሬ ጉዳይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታህሳስ 2 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በመጨረሻው ገፅ በአንደኛው ፓራግራፍ "አንደኛ ተከሳሽ ከሟች ጋር ወድቆ ሲመታ እንደነበረ በምስክሮች የተመሰከረ ሆኖ ነገሩ በመጀመሪያ መነሻው ተከሳሽ ነው ወይስ ሟች ያስነሳው የሚለው ባይታወቅም ሟች ተከሳሹን ጥሎ ይመታው እንደነበር ተከሳሽም እየተመታ እንደነበር ምስክሮችን ሰምቶ ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦና ተረድቷል በሚል መንገድ በአጭሩ ገልፆታል፡፡ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረባቸው የምስክሮች ቃልና የሰነድ ማስረጃዎች ሟች አመልካችን ጥሎ እየደበደበው እያለ አመልካች የኡኡታና የጫጫታ ድምፅ ያሰማ መሆኑንና የአመልካች የጩኸት ድምፅ በሰሙትና ከአመልካች ጋር አብረው ያመሹት በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች ሟች ከላይ አመልካች ከታች ሆነው ሟች አመልካችን እየደበደበ እንዳለ ሟችን መሐል ራሱን በድንጋይ እንደመቱት የሚያረጋግጡ መሆናቸው የሥር ፍርድ ቤት ስለ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ይዘት በውሣኔው በክርክር ከገለፀው ፍሬ ጉዳይ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ሟች መሬት ላይ ጥሎ እየደበደበው እያለ የኡኡታና የጩኸት ድምፅ በማሰማቱና የአመልካችን ጩኸት ሰምተው የመጡት ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች በቦታው የደረሱና ሟችን በድንጋይ የመቱት መሆኑን እንጂ ተጠሪ ዐቃቤ ሕግ አመልካች ሟችን ለሞት ያበቃው ድርጊት ሌሎቹ ተከሳሾች ሲፈፅሙ በተግባር ወይም በመላ ሃሳቡ ተካፋይ የነበረ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ ዐቃቤ ሕግ በወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የሚያቀርበው የወንጀል ክስ የወንጀሉን ዝርዝር ሁኔታ መያዝ እንዳለበት በተለይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል ክሱ ወንጀሉንና ሁኔታውን መግለፅ ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 112 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከት ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ አመልካች በወንጀሉ ድርጊት በምን ሁኔታ እንደተሳተፈ የሚገልፅ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችና ከአመልካች ጋር የተከሰሱት ሌሎች ሰዎች በወንጀሉ ሥራ ያደረጉትን ተሳትፎና በወንጀሉ ተካፋይ ናቸው የሚልበትን ምክንያት በመዘረዘርና ክሱን እንዲያሻሽል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 119 መሠረት ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው የአመልካች የወንጀል ተሳትፎና ተካፋይነት በዝርዝር የማይገልፀውን የወንጀል ክስ ተቀብሎ ማከራከሩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 112 ድንጋጌን መሠረታዊ ግብ ሳይከተል ክርክሩን የመራው መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ተጠሪ በወንጀል ክሱ በገለፀው ስፍራና ጊዜ ሟች አመልካችን መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው አመልካች የኡኡታና የጩኸት ድምፅ ያሰማ ከመሆኑ ውጭ አመልካች ሟችን ለመግደል የሃሳብ ወይም የድርጊት ተካፋይ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ አንድ ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት በኃላፊነት የሚጠየቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 /ከሀ-ሐ/ በተደነገጉት መሠረት በወንጀሉ ሥራ ተካፋይ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 /ከሀ-ሐ/ በተደነገገው መሠረት ሟችን ለሞት ያበቃውን ድብደባ ሌሎቹ ተከሳሾች ሲፈፅሙ ተካፋይ የነበረ መሆኑ ተጠሪ አላስረዳም፡፡ በተለይም አመልካች ሟችን ሀሳብና አድርጉቱ እንደዚሁም በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ኃላፊነቱን /Burden of proof/ የተወጣ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሣኔያቸው አላረጋገጡም፡፡ በአንፃሩ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች ጓደኞች የነበሩት ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሽ ሟችን በድንጋይ ሲደበድቡት አመልካች የሟች ጥቃት ሰለባ ሆኖ መሬት ላይ ወድቆ ሟች እየደበደበው የነበረና አመልካችም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኡኡታና የጩኸት ድምፅ እያሰማ እንደነበር ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ማስረጃ ይዘት በማጠቃለል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሣኔው ካሰፈረው ለመረዳት ችለናል፡፡

አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር የወንጀል ተካፋይ ሆኗል የሚባለው በወንጀሉ አፈፃፀም የግዙፍ ተግባር፣ የሃሳብና የሕግ ሁኔታዎች በመተላለፍና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት በወንጀሉ ድርጊት ተሳታፊ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 በጣምራ በማንበብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ ሰው ጥቃት እየተፈፀመበት ከመሬት ላይ ወድቆ እየተደበደበ ያለ ሰው የጩኸትና የኡኡታ ድምፅ ማሰማቱን በወንጀልነት የሚፈርጅ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ አመልካችን ሟች መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው የጩኸትና የኡኡታ ድምፅ ከመስማቱ ውጭ ሁለተኛና አራተኛ ተከሳሾች ሟችን እንዲገድሉት ያነሳሳ ወይም የወንጀሉ አባሪ ስለመሆኑ አያሳይም፡፡ በአጠቃላይ አመልካችን ሟች በመሬት ላይ ጥሎ እየደበደበው እያለ የጩኸትና የኡኡታ ድምፅ ማሰማቱ የወንጀል ግዙፍ ተግባር አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ሟችን የመግደል ሃሳብ የነበረው ወይም በመላ ሃሣቡ አድራጎቱ የሚሰጠውን ውጤት የራሱ በማድረግ በወንጀሉ ተካፋይ መሆኑን ተጠሪ በቂ ማስረጃ በማቅረብ እንዳላስረዳ ከሥር ፍርድ ቤት የውሣኔ ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ኡኡታና ጩኸት ማሰማቱ ለሟች መሞት ያስከተለ ተግባር ነው ብሎ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በምክንያትና በውጤት መካከል ግንኙነት እንዳለ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ሟች አመልካችን መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው የጩኸትና ኡኡታ ድምፅ ባያሰማ ኖሮ፣ ሟችን በድንጋይ ደብድበው የገደሉት ሌሎቹ ተከሳሾች ከቦታው አይደርሱም ነበር፡፡ ሌሎቹ ተከሳሾች ጩኸቱን ሰምተው መጥተው ሟች አመልካችን እየደበደበው ባያገኙት ኖሮ ሟችን በድንጋይ አይደበድቡትም ነበር የሚል ሕጋዊ መሠረት የሌለው መነሻ በመያዝ አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ እና አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ሟችን ለመግደል በተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ተካፍሏል በማለት የሰጠው ውሳኔ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 23/1/ ንዑስ አንቀጽ 2፣ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1፣ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎትም ከላይ በዝርዝር የተገለፀውና የሕግ ስህተት ያለበትን የከፍተኛ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ማረምና ማስተካከል ሲገባቸው ውሣኔውን በአብላጫ ድምፅ ማፅናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አነስተኛ ድምፅ አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ እና አንቀፅ 540 በመተላለፍ ሳይሆን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 571 በመተላለፍ ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑን የገለፀው ሃሳብ ተገቢነት ያለው መሆኑን መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 571 “ ማንም ሰው አስቦ ሌላውን ሰው በቅርብ ለሚደርስ የሞት አደጋ ያጋለጠ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ወይም ከሶሶት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ይቀጣል” በሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠው ሟች አመልካችን ከመሬት ጥሎ ሲደበድበው አመልካች የኡኡታና ጩኸት ድምፅ ያሰማ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች ሟችን ሆን ብሎና አስቦ ለሞት አደጋ ለማጋለጥ የጩኸትና ኡኡታ ድምፅ ያሰማ ስለመሆኑ ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ማስረጃ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ አመልካች ሟችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሞት አደጋ ለማጋለጥ በማሰብ የፈፀመው ተግባር መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 571 የተዘረዘረውን የወንጀል ድርጊት የፈፀመ ስለመሆኑ በበቂ ማስረጃ ባላስረዳበት ሁኔታ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 571ን በመተላለፍ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በሥር ፍርድ ባቀረበው የወንጀል ክስ በገለፀው ስፍራና ጊዜ ሟች ከመሬት ላይ ጥሎ ሲደበድበው አመልካች የኡኡታና ጩኸት ድምፅ ከማሰማቱ ውጭ አመልካች ሟች በሌሎች ተከሳሾች በድንጋይ ሲደበደብ በወንጀሉ ዋና አድራጊነት /ተካፋይነት/ በአነሳሽነት፣ ወይም በአባሪነት የተሳተፈ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነቱን አልተወጣም፡፡ ተጠሪ አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት ወይም ከተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ውጭ የሆነ በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የፈፀመ መሆኑን በበቂ ማስረጃ እንዳላስረዳ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ስላቀረበው ማስረጃ ይዘት በውሣኔው ካስፈረው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ አመልካች ሟችን ለህልፈት ባበቃው ድርጊት በመላ ድርጊቱ፣ ወይም ሃሣቡ ተሳታፊ መሆኑን በበቂ ማስረጃ ካላስረዳ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ቁ. 141 መሠረት በነፃ ማሰናበት ሲገባው አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ በማድረግ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሣኔ ማፅናቱ ከላይ የተገለፁትን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈፅመዋል በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልል የምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ እንደዚሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ፍርድ በማፅናት የሰጡት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2 /ለ/ -1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ ይሰናበታል በማለት በወንጀለኛ ሕግ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2/ለ/ -1 መሠረት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 28 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- አቶ ተስፋዬ ተሾመ - ጠበቃ ሲሳይ ኃይሉ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- የፌደራል ዓቃቤ ሕግ - ማርታ በቀለ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን በፌ/ከፍተኛ ፍርድ በተጠሪ ቀርቦ የነበረው የክስ ይዘት ተከሣሽ/የአሁን አመልካች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ደ.ሪ የወንጀል ሕግ ቁ.692(1) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማሰገኘት አስቦ የግል ተበዳይ ወይንሸት ወርቁ የከባድ መኪና ካምፒዮ እንደተሸጠለት በወ/ሮ አልማዝ ከበደ የከባድና ቀላል መኪና ዕቃ መለዋወጫ ሱቅ ውስጥ አስቀምጣ እንዳለ ተከሣሽ ወደ ሱቁ ውስጥ የሠሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2.35215 አ.አ በሆነ መኪና እያሽከረከረ በመምጣቱ መጀመሪያውኑም ከግል ተበዳይ ጋር የከባድ መኪና ካምፒዮ በብር 45,000 ለመግዛት ከመስማማቱ በኋላ ብር ላምጣ ብሎ መሄዱን እንጂ የግል ተበዳይ ከላይ የተመለከተውን ዕቃ ውሰድ ሳትለው ወ/ሮ አልማዝም የግል ተበዳይ የታለች ብላ ስትጠይቀው ከኋላዬ ናት ከፊትና ኋላ ሆነን ነው የመጣነው በማለት አሳሳች ነገር በመናገር የከባድ መኪና ካምፒዮን ይዞት በነበረው መኪና ውስጥ ጭኖ በመጥፋቱ በፈፀመው የማታለል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

በቀረበው ክስ ላይ አመልካች በመካድ የተከራከረ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት ክሱ በቀረበበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት በመወሰን የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል በአንድ ዓመት ከስድስት ወር የእስራት ቅጣት እንዲቀጣ በማለት ወሰኗል፡፡ አመልካች በተሠጠው ውሣኔ ቅር በመሠኘት ይግባኙን ለፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ በማፅናት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው አቤቱታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን አመልካች በጠበቃቸው በኩል መጋቢት 12 ቀን 2003ዓ.ም የተፃፈ የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ዋናው የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የሆነው የተከለከለ የወንጀል ድርጊት ስላልተሟላ ድርጊቱ የማያስከስስ በመሆኑ፣ ዓ/ሕግ ያቀረባቸው የሰው ምስክሮች አመልካች ከጥርጣሬ ውጭ የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመ ስለመሆኑ የማያረጋግጡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ፣ አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ያቀረባቸው የሠውና ሰነድ ማስረጃዎችን በአግባቡ ያልተመለከቱት በመሆኑ እና አመልካች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.143(2) እና በሕገ-መንግስቱ በተሠጠኝ የመከላከል መብት መሠረት ያቀረብኩትን ተጨማሪ ማስረጃ ያለመቀበላቸው ያለአግባብ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤት የፈፀሙት መሠረታዊ የህግ ስህተት ታርሞ አመልካች በነፃ እንዲሠናበት የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ መልስ የሰጠ ሲሆን በቀን 22/9/2003 ዓ.ም በ3 ገፅ የተፃፈ የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካች የፈፀማቸው ተግባር ሕጉ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ስንመለከት በወንጀል ሕጉ የተቀመጠውን የወንጀል አላፊነቱን የሚያቋቁሙትን ተግባራት የሚያሟላ በመሆኑ፣በዓቃቤ ህግ የቀረቡት ማስረጃዎች የተፈፀመውን ወንጀል በአግባቡ ያረጋገጡ በመሆኑና አመልካች በመከላከያ ምስክሮቹ ያላስተባበለ በመሆኑ እና ተጨማሪ የማስረጃ ጥያቄ በተመለከተ የመከላከልን መብት በተመለከተ ቀድሞ በመከላከያዎች ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰ ባለመሆኑ እና ፍርድ ቤቱ የተጠየቀው ተጨማሪ ማስረጃ ነገሩን ለማዘግየት ሣይሆን ለፍትሕ አሠጣጡ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሚፈቅድ በመሆኑ በባሕርይው ፍቃጅ እንጂ አስገዳጅ ባለመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደተመረመረውም በመጀመሪያ ደረጃ የቀረቡት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ስለመፈፀሙ አላስረዱም እና አመልካች ያቀረባቸው ማስረጃዎች በአግባቡ አልታየልኝም የሚሉትን ነጥቦች ስንመለከት ማስረጃን መመዘን ጉዳዩን በመጀመርያ የተመለከተው እና በይግባኝ የያዘው የፍርድ ቤት ሥልጣን በመሆኑ እና የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በአዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲፈፀም ማቃናት በመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን መደምደሚያ መቀበሉ አግባብነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት መታየት ያለባቸው አመልካች የጠየቀው ተጨማሪ ማስረጃ መታለፍ እና በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው ነጥቦች አመልካች ጥፋተኛ የተባለውን የወንጀል ኃላፊነት ስለ ማቋቋሙ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች ተይዘው ይሄ ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የመጀመረያውን ጭብጥ በተመለከተ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የችሎት ሂደት ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካች የሰውና የሠነድ መከላከያ ምስክሮችን /ማስረጃዎቹን/ ካጠናቀቀ በኋላ የካቲት 26 ቀን 2002ዓ.ም በዋለው ችሎት የተጨማሪ የባለሙያ ምስክር የጠየቁ መሆኑ ተመዝግቦ የማስረጃው ዝርዝርና ምን እንደሚያስረዱለት ሲያቀርብ ለትክክለኛ ፍትሕ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም የሚለው ይታያል በማለት መዝገቡ ለውሣኔ የተቀጠረ መሆኑ፣ ለውሣኔ በተቀጠረበት መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተከሣሽ ጠበቃ በቀን 10/7/2002 ዓ.ም በተፃፈ ተጨማሪ የባለሙያ ምስክር የተጠየቀ መሆኑ ተገልፆ አስፈላጊ ሲሆን የሚታዘዝ መሆኑ ተገልጾ አሁንም መዝገቡ ለውሣኔ የተቀጠረ መሆኑን፣ በቀጠሮው ሚያዝያ 18 ቀን 2002ዓ.ም በተመሣሣይ መልኩ የተቀጠረ መሆኑን በመጨረሻውም ለአሁኑ ቅሬታ ምክንያት የሆነው ፍርድ መሠጠቱን መመልከት ይቻላል፡፡ በዚሁ በስተመጨረሻ በተሰጠው ፍርድም የተጨማሪ ማስረጃ ጉዳይ የተነሣ ሲሆን ከሂደቱ ፍርድ ቤት ያለፈው መሆኑን ተረድተናል በማለት ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ሂደት መገንዘብ የሚችለው መጀመሪያውኑ የተጨማሪው ማስረጃ የመራለት ችሎት ወደ ፊት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ትዕዛዝ ይሰጥበታል በማለት ሲቀጥር መቆየቱ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጨረሻም ፍርድ የሠጠው ችሎት የተጨማሪ ማስረጃ ጉዳይ በማንሣት እንደታለፈ ይቆጠራል ማለቱ ጉዳዩን የተመለከተውና የቀረበውን ጥያቄ ያለመቀበሉን ያመለክታል፡፡

ፍርድ ቤቱ የተጨማሪ ማስረጃን ጥያቄ አልተቀበለውም የሚል መደምደሚያ ላይ ከተደረሰ የታለፈበትን አግባብ ወይም መታለፉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ ተጨማሪ ማስረጃ የተጠየቀው የባለሙያ ምስክርነት ሲሆን በወቅቱ የያዝኩት መኪና የከባድ መኪና ካምፒዮ መጫን የማይችል ስለመሆኑ ያረጋግጣል በማለት ነው፡፡ተጠሪ የሙሉ አመልካች ይዞት የነበረው የቤት መኪና የከባድ መኪና ካምፒዮ መጫን መቻሉ ወይም ያለመቻሉ በጭብጥነት ያልተያዘ ጉዳይ በመሆኑ እና መሸከም እንደሚችል ለማንም ሰው ግልፅ በመሆኑ የተለየ የባለሙያ ምስክርነት የማያስፈልገው በመሆኑ ቢታለፍ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ችሎቱም የግራቀኙን ክርክር ሲመለከተው አጠቃላይ ክርክሩና የምስክር ሂደቱ አመልካች ከግል ተበዳይና ከዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ጋር የተባለውን የከባድ መኪና ካምፒዮ በእጅ ለማስገባት የተጠቀመባቸውን ስልቶች ወይም ዘዴዎች ላይ ያተከረ እንጂ የመኪናው ዓይነት እና በተለይም አመልካች ይዘውት የመጡት መኪና ዝርዝር ይዘት ወይም የመሸከም አቅም በተመለከተ ጭብጥ ተይዞ በስፋት የተኪደበት አይደለም፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ቀድሞ በጭብጥነት ያልተያዘ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ከወ/መ/ሕግ ቁ.143(2) ሥር እንደተመለከተው ተጨማሪ ማስረጃ ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትሕ አሠጣጥ ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን እንጅ አስገዳጅ ካለመሆኑ ጋር ተደምሮ ሲታይ መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚያሠኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ መሠረት አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ስርዓት ህግ እና በህገ መንግስቱ የተሠጡትን መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ የመከላከል መብቱን የተጠቀመበት በመሆኑ እና ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል ደግሞ አስገዳጅ ሣይሆን ፍርድ ቤቱ ለፍትሕ አሠጣጥ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሚሠጥ /የሚፈቀድ/ በመሆኑ በመታለፍ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚያሠኝ ነገር የለም ብለናል፡፡

ወደ ሁለተኛው ጭብጥ ስንመለስ የተረጋገጠው ፍሬ-ነገር አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበትን የወንጀል ህግ ኃላፊነት ሊያቋቁም ስለመቻሉ መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የግል ተበዳይና አመልካች በደላላ ከተገናኙ በኋላ የከባድ መኪናውን ካምፒዮን ያስቀመጠችበት ድረስ በማምጣት የግል ተበዳይ ለአመልካች ካሣየችውና ዋጋውን ከተነጋገሩ በኋላ አመልካች ገንዘቡን ይገፍ እመጣለሁ በማለት ሲሄድ ተበዳይም እስከዚያ የግል ጉዳይ ቦታ ለመድረስ እንደወጣች፣ አመልካች ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተመልሶ የመጣ መሆኑ፣ የዓቃቤ ሕግ ምሥክሮች የግል ተበዳይስ ብለው ሲጠይቁት ከኋላዬ ነች አብረን ነው የመጣነው፣ ፓርክ ለማድረግ መኪና እያዞረች ነው፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታ እየፈለገች ነው፣ እስከዚያ ይጫን ፣ይዘን እንጥፋ በማለት የተለያዩ የማሣመኛ ቃላቶችን በመጠቀም ዕቃውን አስወጥቶ በመጫን የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የራሳቸውን ሱቅ ሥራ ለመሥራት መለስ ሲሉ ይዞ የጠፋ መሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጧል፡፡ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከወ/መ/ሕግ ቁ.692(1) አኳያ ሲታይ አመልካች የማይገባ ብልፅግና ለራሱ ወይም ለሌላ ሠው ለማስገኘት ቀድሞ ከግል ተበዳይ ጋር የመምጣቱን አጋጣሚ በመጠቀም የግል ተበዳይ ከእሱ ጋር ሣትመጣ አብራው እንደመጣች በማስመሠል የባለ ሱቆቹን የተሣሣተ እምነት በመጠቀም፣ ትክክለኛውን ነገር በመደበቅ ካምፒዮኑን ይዞ በመጣው መኪና ላይ ከጫነ በኋላ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች በሌላ ሥራ መጠመድ አጋጣሚ በመጠቀም ይዞት የሄደ በመሆኑ በሕጉ የተቀመጠውን ወንጀል ሕጉ ሥር የወንጀል ኃላፊነቱን የሚያረጋጡ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የተፈፀመው ድርጊት የወንጀል ኃላፊነቱን የሚያቋቁሙ በመሆኑ ስለተረጋገጠ በዚህ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ በአግባቡ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖ አልተገኘም፡፡ የተላለፈበት ቅጣትም የግራቀኙን የቅጣት አስተያየትና አጠቃላይ የቅጣት አጣጣል ሥርዓቶች የተከተለ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተው ውሣኔ ተሠጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.58613 የካቲት 29 ቀን 2ዐዐ3ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.80841 በቀን 12/11/2002 ዓ.ም እና በቀን 15/11/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ፍርድ እና ውሣኔ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በተከሠሠበት የማታለል ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የተጣለበት ቅጣት በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በትውስት የመጣው የመዝ.ቁ.80841 ወደ መጣበት ይመለስ መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- ወ/ሮ ውልታ ደሳለኝ - ጠበቃ ግርማ ሚደቅሣ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ የስነ ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ ማንደፍሮ ናታአ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የዋስትና አቤቱታ ሲሆን የቀረበው በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በክልሉ የስነ ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ በሙስና ወንጀል ከሌሎች 11 ሰዎች ጋር በተከሰሱበት መዝገብ በካንሰር በሽታ መታመማቸውን ገልፀው ውጪ አገር ሂደው ለመታከም ዋስትና እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡት ጥያቄ በተከሰሱበት ወንጀል ዋስትና አይፈቀድም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር የቀረበ ነው፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ እንደተመለከተው በመወሰኑ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደዚሁም ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በማፅናታቸው ሲሆን በቀን 15-9-2003 ዓ.ም በ3 ገፅ የቀረበ የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ባደረብኝ የጉበት ካንሰር በሽታ በአገር ውስጥና ውጪ ስታከም የቆየሁ መሆኑ እየታወቀ፣ በተሰጠኝ በሐኪሞች ቦርድ መሠረት ውጪ አገር ሄጄ እንድታከም ተወስኖ እያለ በቁጥጥር ሥር በመሆኔ መሄድ ያልቻልኩ መሆኑ እየታወቀ፣ በጤንነት ምክንያት ችሎት ቀርቤ መከራከር ያልቻልኩ በመሆኑ፣ ዋስትና ያስከላክላል በማለት የተጠቀሰብኝ አንቀፅ የሕክምና እድል የማግኘት መብቴን የማይነፍገኝ እንጂ የሚነፍገኝ ቢሆን እንኳን የአዋጁ ድንጋጌ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 21 እና 15 እንደዚሁም አንቀፅ 9 ጋር ታይቶ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ ተሽሮ ውጪ አገር ሄጄ መታከም እንድችል እንዲፈቀድልኝ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ በቀን 02-10-2003 ዓ.ም በ4 ገፅ የሰጠው የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካች ዋስትና የተከለከሉት የተከሰሱበት የሙስና ወንጀል ዋስትና የማይፈቅድ በመሆኑ፣ በበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ጥያቄ የዋስትና ጥያቄ እንጂ ሕክምና የማግኘት መብት ባለመሆኑ ሁለቱ ጥያቄዎች ደግሞ መቅረብ ያለባቸው በተለያዩ ሁኔታዎች በመሆኑ አሁን የቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም፣ የበታች ፍርድ ቤቶችም ውሣኔ የሰጡት የቀረበው የዋስትና ጥያቄ ተቀባይነት አለው? ወይስ የለውም? በሚለው ነጥብ ላይ በመሆኑ አሁን እየተነሳ ያለው በህይወት የመኖር መብት ጋር ተያይዞ የሕገ-መንግስቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ በመጥቀስ የቀረበው ክርዳዩ ጋር ተያያዥነት የለውም፣ የቀረበው ጉዳይ ከሕገ መንግስቱ ጋር ተያያዥነት አለው ቢባል እንኳ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግስት አንቀጽ 19 ለተከሰሱ ሰዎች በመርህ ደረጃ የዋስትና መብት የሚፈቅድ ቢሆንም በልዩ ሁኔታ ግን ዜጐች እንደ ወንጀሉ ሁኔታ ዋስትና ሊከለከሉ እንደሚችሉ የሚደነግግ በመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የቀርበው አቤቱታ የዋስትና መብትን መሠረት ያደረገ ነው? ወይስ የህክምና የማግኘት መብቱን ነው? በሁለቱ ጉዳይ መከተል የሚገባው ሥርዓት አንድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች ተይዞ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የሙስና ወንጀል እየታየ ያለበት ችሎት ቀርቦ የነበረው አቤቱታ አመልካች በካንሰር በሽታ እየታመሙ መሆናቸውን ገልፀው የዋስትና መብታቸው ተጠብቆ ውጪ አገር ሂደው ለመታከም እንዲቻሉ በሚል የቀረበ ሲሆን ችሎቱም ሰጥቶት የነበረው ትዕዛዝ ዋስትናን በተመለከተ የተሰሱበት ወንጀል ዋስትና አያስጠብቅም፡፡ ሕክምናን በተመለከተ ግን በፖሊስ ክትትል ሥር ሆነው ለመታከም የሚያግድ ነገር የለም በሚል ነበር፡፡ ይሄ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት ቀርቦ ፀድቋል፡፡

አሁን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው ቅሬታ “…. የተከሰሰሸበት የወ.መ.ሕ.ቁ. 407/2/ በአዋጅ ቁ. 434/1997 አንቀጽ 4/1/ መሠረት የዋስትና መብት አይፈቅድም በሚል ምክንያት የውጭ አገር የህክምና ጥያቄን በትእዛዝ እና ውሣኔ ውድቅ አድርገውብኛል፡፡” በሚል ነው፡፡ ከዚኑ ፍርድ ቤት ጀምሮ ሲጠየቅ የነበረውን የዋስትና ጥያቄ በተመለከተ አመልካች የተከሰሱበት የወንጀሉኛ መቀጫ ሕግ አንቀጽ 407/2/ን ስንመለከት ከ7 ዓመት ፅኑ እስራት እስከ 15 ዓመት ፅኑ እስራት ሊያስቀጣ የሚችል አንቀጽ በመሆኑና አመልካች በካንሰር በሽታ መታመማቸው በራሱ ከተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 4/1/ አኳያ ሲታይ ለዋስትና ጉዳይ ከግምት የሚገባበት አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም በዚህ አዋጅ አመልካች የተከሰሱበት አንቀጽ ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል ከሆነ በዋስትና መልቀቅ እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩል የተሰጠው ትዕዛዝ ወይም ደግሞ የዋስትና ጥያቄ ውድቅ መደረጉ የአመልካችን ሕክምና የማግኘት መብት ብሎም በህይወት የመኖር ሕገ-መንግሥታዊ መብቷን ተቀባይነት አሳጥቷል ወይ? የሚለውን ነጥብ ስንመለከት በመጀመሪያ ደረጃ በሕግ ጥላ ሥር ያለ ተከሣሽ የመታከም መብት የማይገደብበትና ከዚህ አኳያ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት የተቀመጡት መሠረታዊ መብቶች እንደ ማንኛውም ዜጋ የሚከበርላቸው ስለመሆኑ በሕገ መንግሥቱና አገሪቷ ካፀደቀቻቸው አለም አቀፍ የሰበአዊ መብት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የዋስትናውን ጥያቄ ውድቅ ሲያደርጉ በሌሎች ሕጎች የተመለከቱትን የመታከም መብቷን ውድቅ ያላደረጉና አሁንም ቢሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላትን የመጠየቅ መብታቸውን የሚነካባቸው ባለመሆኑ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ የተከሰሱበት ወንጀል ዋስትናን አያስጠብቅም በማለት ያቀረብኩትን የመታከም መብቴን ውድቅ አድርገውብኛል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አግባብነት የለውም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም አመልካች በበታች ፍርድ ቤት አቅርበውት የነበረው አቤቱታ የዋስትና ጥያቄ የነበረ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች የተከሰሱበት ወንጀል ዋስትና ይከለክላል በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ በመሆኑና ጉዳዩን የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ የመታከም መብታቸውን የሚነካ ባለመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም ከላይ በተመለከተው መሠረት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ብሔ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ. 129766 በቀን 05-09-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 122550 በቀን 02-9-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 03345 በቀን 08-7-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በአዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 4/1/ እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 75/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች የተከሰሱበት ወንጀል የዋስትና መብት አያስጠብቅም መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 48956

መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ ፍኖተ ፃድቅ አበራ
2. አቶ ሳመሶን አበራ
} ከጠበቃ ማሩ ባዘዘው ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- የጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ የቀረበ የለም ከተባለ በኋላ መከንን አየለ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰምተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የቀረበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአንደኛ አመልካችና በሁለተኛ አመልካች እያንዳንዳቸው ለመኪናው ሊከፈል የሚገባ የነበረውን የቀረጥና የታክስ ግምት ብር 332,005.19 (ሶስት መቶ ሰላሣ ሁለት ሺህ አምስት ብር ከአሥራ ዘጠኝ ሣንቲም) እንዲቀጣ የመወሰንን ህጋዊነትና አግባብነት ለማጣራት ተብሎ ነው፡፡ አመልካቾች ፍርድ ቤቱ በሁለታችን ላይ የጣለው የገንዘብ ቅጣት ለመኪናው ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እጥፍ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 73ን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ አመልካቾች ወንጀል በመፈፀማቸው ጥፋተኛ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ስለዚህ ቅጣት የሚወሰነው በአንዳንዳቸው ላይ በመሆኑና የበታች ፍርድ ቤቶች በእያንዳንዳቸው ላይ በህጉ የተመለከተውን ዝቅተኛ የገንዘብ ቅጣት እያንዳንዳቸው እንዲከፍሉ የተሰጠው ውሣኔ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን ስንመረምረው አመልካች በወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 60/89 እንደተሻሻለ አንቀጽ 73(1) በመተላለፍ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች መሆናቸውን ተረድተናል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ በእስራትና በገንዘብ መቀጮ በጣምራ የሚያስቀጣ ወንጀል ነው፡፡ ቅጣት የሚወሰነው የእያንዳንዱን ጥፋተኛ ግላዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነና ወንጀልና የወንጀል ቅጣት ግላዊ መሆናቸውንና ከአንዱ ወደ ሌላው የማይተላለፍ መሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 41 ከተደነገገው መሠረታዊ መርህ ለመረዳት የሚቻል ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶችም የገንዘብ መቀጮ የወሰኑት በአንደኛ አመልካች ላይ ያሉትን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችና በህጉ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የገንዘብ መቀጮ መነሻ በማድረግና በማገናዘብ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በሁለተኛ አመልካች ላይ የገንዘብ መቀጮ የወሰኑት በሁለተኛው አመልካች ላይ ያሉ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን መነሻ በማድረግና በማገናዘብ ነው፡ ስለሆነም እያንዳንዳቸው ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የህግ ድንጋጌ በወቅቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመንግሥት ይከፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ ገንዘብ መነሻ በማድረግ ፍርድ ቤቱ ሊወሰን የሚችል መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

ወንጀል በመፈፀሙ የሚወሰነው የገንዘብ ቅጣት በወንጀል ሕጉ የቅጣት አወሳሰን መርሆችን መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ በወንጀል ጥፋተኛ በተባሉ ሰዎች ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በፍታብሔር መንግሥት ሣይከፈለው የቀረበን ቀረጥና ታክስ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል ለማድረግ ከሚቀርብ ክስና ከሚሰጥ ውሳኔ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች እያንዳንዳቸው ለመክፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ መከፈል ያለበት ገንዘብ ለፈፀሙት ወንጀል በመቀጫነት እንዲከፍሉ የሰጡት ውሣኔ የወንጀል ህጉን መሠረታዊ የቅጣት አወሳሰን መርሆች የተከተለና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሠረት አጽንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ፍርድና ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ፍርዱ የፀና መሆኑን አውቆ እንዲያስፈጽም ለሚመለከተው ክፍል የውሣኔው ግልባጭ ይተላለፍ

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 9 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሐንካራ ሐርቃ ሃያሞ

ተጠሪ፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ

መርዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የአሁኑ አመልካች በወንጀል የተከሰሱበትን ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ባለቤት ሆኖ መገኘት ጉዳይ በሚመለከት በይግባኝ ደረጃ ቀርቦለት የተመለከተው የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው የጥፋተኛነት ፍርድ እና የቅጣት ውሣኔ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበውን ክርክር በመጨረሻ ያየው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 39818 በ22/10/2002 የጥፋተኛነቱም ሆነ የቅጣት ውሣኔው እንዲሁም የንብረት መወረስ ውሣኔው በአግባቡ ስለሆነ ፀንቷል በሚል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10(3) መሠረት የቀረበ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሐምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው በመባሉ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በ08/03/2003 ጽፎ ባቀረበው መልስ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ምንም አይነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ አመልካች ለሰበር ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ በሥር ፍ/ቤት የህግ ስህተት ተፈጽሟል ብለው የገለጿቸው ምክንያቶች ስለማስረጃ ምዘናና ከጥፋተኛነቱ ውሣኔ በኋላ ስላሉ ጥቃቅን ፍሬ ነገሮች የሚመለከቱ እንጅ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያስረዱ አይደሉም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲህ አይነት የማስረጃ እና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በሕጉ የማየት ስልጣን የለውም በማለት የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሆኖ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአመልካች ጠበቃ በኩልም የመልስ መልስ መቅረቡን መዝገቡ ያሳያል፡፡

ይህ ችሎትም የአሁኑ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በእጃቸው ገብቶ ተገኝቷል ተብለው በወንጀል የተከሰሱባቸውን ጉዳዮች በሚመለከት በሥር ፍ/ቤት ታይቶ በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ሲመረምር መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ በተለይ ቅጣቱን በተመለከተ የአሁኑ አመልካች በመንግሥት ሥራ ላይ ሆነው ከብር 182 የወር ደመወዝ ተነስተው በጭማሪና በዕድገት ብር 928 የወር ደመወዝ ላይ ደርሰው በዚህ መጠነኛ ደመወዝ ራሣቸውን ሲያስተዳድሩ እንደቆዩና ባለቤታቸውም ሌላ ህጋዊ ገቢ እንዳልነበራቸው እየተገለፀ ምንጩ ያልታወቀ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በእጃቸው ገብቶ መገኘቱና ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረት ባለቤት ሆነው መገኘታቸው ነገሩን ከባድ ስለሚያደርገው በዚሁ በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው እስከ አምስት አመት ከሚደርሰው የጽኑ እስራት ቅጣት በአራት አመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ መወሰኑ ያለአግባብ ቅጣቱ ከብዶባቸዋል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በመ/ቁ 39816 በ22/10/2002 የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ፀንቷል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. ዮሴፍ ሀይሉ ጠቅላላ ንግድ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ አቶ መላኩ ወልደማሪያም- ቀረቡ

2. አቶ ዮሴፍ ሃይሉ - ጠበቃ አቶ መላኩ ወልደማሪያም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ህግ ዓቃቤ ሕግ አቶ ሲሳይ ተድላ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካቾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 15 የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ እና አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመተላለፍ አምድሁን ጠቅላላ ንግድ ኃላፊነቱ የግል ማህበር ብቸኛ አስመጭና አከፋፋይ የሆነበትንና ኮሪያ አገር ያለው ኦርዮን ኮርፖሬሽን የንግድ ድርጅት የሚጠቀምበትን “ORIQN” የሚል የንግድ ምልክት ያለበትን 639 ካርቶን ማስቲካዎች በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 የቤት ቁጥር 479 አከማችቶ የተገኘ በመሆኑ ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠውን የንግድ ምልክት በማስመሰል ተጠቃሚውን ለማሳሳት የሚናችል ዕቃ የመያዝና የመሸጥ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡

አመልካቾች የወንጀል ተግባር አልፈፀምንም በማለት በመከራከራቸው ተጠሪ “ORION” የሚለው የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑና አምድሁን ጠቅላላ ንግድ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ብቸኛ አስመጭና አከፋፋይ መሆኑንና አመልካቾች ይዘው የተገኙት ማስቲካ “ORION” ከሚለው ማስቲካ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት የጽሑፍና የሰው ማስረጃ አቅርቧል፡፡ አመልካቾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ብይን ሰጥቶ አመልካቾች ORIQN የሚለው ማስቲካ ህብረተሰቡ ለይቶ የሚያውቀውና መሳሳትና መሳከር የማይፈጥር መሆኑን ያስረዱልናል በማለት የሰው ምስክሮች አቅርበው አስመስክረዋል እንደዚሁም ማስቲካውን ከቻይና አገር በባንክ በኩል በተከፈተ ሌተር ኦፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሬዲት ዋጋ ከፍለው ማስገባታቸውና የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ አሟልተው ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ መሆኑን ያሳያሉ ያሉቸውን የሰነድ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረና ከመከሩ በኋላ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመተላለፍ ህጋዊ ጥበቃ ባለው የንግድ ምልክት ላይ ወንጀል የፈፀሙ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከሰማ በኋላ አንደኛ አመልካች በብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ሁለተኛው አመልካች በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን አመልካቾች ይዘው የተገኙት 639 ካርቶን ማስቲካና 23,000 ፖኬት ማስቲካ ወደ ገበያ እንዳይሰራጩ ይወገዱ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካቾች ሰኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፈው የሰበር አቤቱታ የንግድ ምልክቱ አላግባብ ጥቅም ላይ ውሎበታል የተባለው ድርጅትና በአገር ውስጥ ያለው ብቸኛ አከፋፋይ “ORION” የሚለውን የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ያስመዘገቡት አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት ነው፡፡ ይህንን የንግድ ምልክት አዋጅ ቁጥር 501/98 ወጥቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በአዋጅ አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት ከአሥራ ስምንት ወራት ውስጥ አላስመዘገቡም፡፡ የግል ተበዳይ በአዋጅ በተደነገገው መሠረት ሳያስመዘግቡ ለአራት ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠው የንግድ ምልክታችንን አላግባብ ተጠቅመዋል በማለት ክስ ለማቅረብ የሚችሉበት ሁኔታ የለው፡፡ ስለሆነም “ORION” የሚለው የንግድ ምልክት አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት መመዝገቡ የአዋጁን አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 48 እና አንቀጽ 29 አንቀጽ 2 መሥፈርት የሚያሟላና ሶስተኛ ወገኖች በሃላፊነት የማያስጠይቅና ውጤት የሌለው ሆኖ እያለ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች ለማጭበርበርና ተጠቃሚውን ለማሳሳት ሆነ ብለንና አስበን የፈፀምነው ተግባር የለም፡፡ ስለዚህ ማስቲካ ከቻይና አገር በማስገባታችን በወንጀል የሚያስጠይቀን አይደለም እንጅ በወንጀል የምንጠየቅ ከሆነም በቸልተኝነት መሆን ሲገባው ሆነ ብለንና አስበን እንደፈፀምን ተቆጥሮ ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው መልስ ORION የሚለው የንግድ ምልክት የተመዘገበና ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠው መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 320/95 ሥልጣን የተሰጠው የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በጽሑፍ አረጋግጧል፡፡ አመልካቾች ተጠቃሚውን የሚያሳስትና የማይሳክር እንደዚሁም በአገር ውስጥ የተመዘገበና ህጋዊ ጥበቃ የሌለው QRIQN የሚል የንግድ ምልክት የለው ማስቲካ በአገር ውስጥ ሚያሰራው ተገኝተዋል፡፡ አመልካቾች QRIQN የሚለውን ማስቲካ ከቻይና አገር በባንክ በተከፈተ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የውጭ ምንዛሬ ተፈቅዶላቸው ከፍለው ማስመጣታቸውና ማስቲካውን የጉምሩክ ቀረጥና ፎርማሊቲ አሟልተው ወደ አገር ውስጥ ማስገባታቸው አድራጐታቸው ወንጀል መሆኑን የሚያስቀረው ባለመሆኑ የአመልካቾች ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 42 ንዑስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 1ን በመተላለፍ ህጋዊ ጥበቃ በተሰጠው የንግድ ምልክት ላይ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች በወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑባቸው የወንጀል ህግ መርሆዎች የየራሳቸው ልዩ ባህሪያት ያላቸው በመሆኑ በዚሁ አንፃር ጉዳዩን ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. አንደኛ አመልካች የንግድ ድርጅት ሲሆን ሁለተኛ አመልካች የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 501/98 በህግ ወለድ ሰዎች ላይ የወንጀል ሀላፊነትና ተጠያቂነትን የሚደነግግ የህግ ማዕቀፍ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ አከራካሪ በመሆኑ በመጀመሪያ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሁለተኛው አመልካች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ተገቢነትን ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አንድ ሰው ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ተጠያቂ የሚሆነው የግዙፍ ተግባር የህግና የሃሳብ ሁኔታ ተሟልተው ሲገኙ እንደሆነ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ሁለተኛ አመልካች የተከሰሱትና ጥፋተኛ የተባሉት በአዋጅ ቁጥር 501/98 ህጋዊ እውቅናና ጥበቃ የተሰጠውን የንግድ ምልክት የሚጐዳ ተጠቃሚውን የሚያሳስትና የሚያሳክር ተግባር ሆን ብለውና አስበው ፈጽመዋል ተብለው እንደሆነ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ ሁለተኛውን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌን በመተላለፍ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ በመጀመሪያ “ORIQN” የሚል የንግድ ምልክት ያላቸውንና በኮሪያ አገር የሚመረቱ ምርቶች ብቸኛ አስመጭ ነኝ የሚለው “አምደሁን ጠቅላላ ንግድ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር “ORION” የሚለው የንግድ ምልክት የአዋጅ ቁጥር 501/98 ህጋዊ ጥበቃና እውቅና ለማግኘት የሚያስችለውን የህግ ሁኔታ /ህጋዊ መስፈርት/ ያሟላ ለመሆኑ ተጠሪ በቂ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታና ሃላፊነቱን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

ይህንን ነጥብ ለማጣራት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን መዝገብ አስቀርበናል፡፡ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከዛፈው የሰነድ ማስረጃ እንደተረዳነው ጽ/ቤቱ ORION የሚለውን የንግድ ምልክት ለመመዝገብ የቀረበውን አቤቱታ በአዲስ ዘመንና በሄራልድ ጋዜጣ አውጥቶ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ የንግድ ምልክቱን መጋቢት 12 ቀን 1998 ዓ.ም በመመዝገብ የምዝገባ ሰርተፊኬት ሰጥቷል፡፡ ጽ/ቤቱ በሰጠው የምዝገባ ሰርተፍኬት የንግድ ምልክቱ እስከ መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም ህጋዊ ጥበቃ እንደሚኖረው የሚገልጽ ቢሆንም ORION የሚለው የንግድ ምልክት ከተመዘገበ በኋላ አዋጅ ቁጥር 501/98ን ህግ አውጭው በማወጅ፣ አዋጁ ከሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቀመጡ የንግድ ምልክቶች ይህ አዋጅ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በአስራ አምስት ወራት ጊዜ ውስጥ መመዘገብ ይኖርባቸዋል በሚል መንገድ በመደንገድ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የንግድ ምልክት ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት አቅርበው በማስመዝገብ የባለሃብትነት ሰርተፊኬት አግኝተው የነበሩ ሰዎች አዋጁ ወጥቶ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ባሉት አሥራ አምስት ወራት የማስመዝገብ ግዴታና ሃላፊነት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

ይህ የአዋጁ ድንጋጌ ፈቃጅነት ያለው የህግ ድንጋጌ ያለመሆኑን ከድንጋጌው አቀራረጽ፣ መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይም የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጅ “Trade marks deposited before the entry into force of this proclamation shall be submitted for registration with in eighteen month beginning from the entry in to force of this proclamation” በሚል መንገድ የተቀረፀና የተደነገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት የንግድ ምልክት ያስመዘገበ ማናቸውም ሰው ህግ አውጭው በአዋጁ የሰጠውን ጥበቃና ከለላ ለማግኘትና አዋጁን መሠረት በማድረግ የመብት ጥያቄ ለማቅረብ በመጀመሪያ ህግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 501/98 የደነገጋቸውን አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች በመፈፀም ህጋዊ ሁኔታዎችን አሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ ህግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 501/98 አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ የደነገጋቸው ድንጋጌዎች በአዋጁ መሠረት መብታቸው እንዲከበርላቸው የሚጠይቁ የህግ ወይም የተፈጥሮ ሰዎች ብቻ ሳይሆን አዋጁን የማስፈፀም ሥልጣንና ሀላፊነት በተሰጠው የመንግስት አካል ማለትም የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ላይ ገዥነትና አስገዳጅነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይኸም በመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ጽ/ቤቱ ለግል ተበዳይ ለስድስት ዓመት ህጋዊ ጥበቃ እንዳለው በመግለጽ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ሠቶት በነበረው የምዝገባ ሠርተፍኬት ላይ የበላይነትና ገዥነት ያለውና የግል ተበዳይ የንግድ ምልክቱን አዋጁ ወጥቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በአሥራ ስምንት ወራት ውስጥ እንደገና እንዲያስመዘግብ የሚያስገድድ ድንጋጌ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የግል ተበዳይ የንግድ ምልክቱን አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከመጋቢት 12 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም የሚያገለግል የምዝገባ ሰርተፍኬት ተሰጥቶት የነበረ መሆኑን የሚያስረዱ የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ ከዚህ ውጭ ተጠሪ በአዋጁ ቁጥር 501/98 ህጋዊ ጥበቃና ከለላ ለማግኘት ህግ አውጭው በአዋጁ አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን አስገዳጅ መሥፈርት ያሟላና በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 45 እና አንቀጽ 16 የተደነገጉትን ህጋዊ ሥርዓቶች በማሟላት በአስራ ስምንት ወራት ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ይኸም በመሆኑ የግል ተበዳይ አምዱሁን ጠቅላላ ንግድ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኢትዮጵያ ግዛት ብቸኛ አስመጭና አከፋፋይ ነኝ የሚለው “ORION” የሚለው የንግድ ምልክት በአዋጅ ቁጥር 501/98 ህጋዊ ጥበቃና ከለላ ለማግኘት ህጋዊ ሁኔታዎችን ያሟላ መሆኑን ተጠሪ በበቂ ማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ ሁለተኛውን አመልካች በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነው ህጋዊ ሁኔታ ማለትም ከአዋጅ ቁጥር 502/98 በፊት የነበረው ምዝገባና ሠርተፍኬት አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 በአስገዳጅነት በደነገገው የጊዜ ገደብ ማለትም አዋጁ ወጥቶ ሥራ ላይ መዋል ከጀመረበት ቀን አንስቶ በአስራ ስምንት ወራት ውስጥ የንግድ ምልክቱን ያስመዘገበ መሆኑ በበቂ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ሶስተኛ ወገኖችን በአዋጅ ቁጥር 501/98 ለንግድ ምልክቱ የተሰጠውን ህጋዊ እውቅና እና ጥበቃ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽመዋል ብሎ ለመክሰስም ሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ብሎ ለመቅጣት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚደነግገውና ወንጀል ለማቋቋም አስፈላጊ በመሆናቸው ከሚዘረዝራቸው አስፈላጊ ጉዳዮች ሁለተኛ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት ያሟላና ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠው የንግድ ምልክትን የሚጥስ ግዙፍ ተግባር የፈፀመ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ሸክሙን ሳይወጣ የግል ተበዳይ አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት የንግድ ምልክቱ መመዝገቡን ብቻ በመመልከት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 1 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት ያላሟላና ህጋዊ ጥበቃ የተሰጠውን የንግድ ምልክት የሚጥስ ግዙፍ ተግባር የፈፀመ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ሸክሙን ሳይወጣ የግል ተበዳይ አዋጅ ቁጥር 501/98 ከመውጣቱ በፊት የንግድ ምልክቱ መመዝገቡን ብቻ በመመልከት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 አስገዳጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የህግ ድንጋጌ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2ን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የአንደኛው አመልካች የወንጀል ተጠያቂነት ሁለተኛው ፓራግራፍ ከተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአንደኛው አመልካች ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ሁለተኛ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት በማሟላት የተመዘገበ “የንግድ ምልክት”ን የሚጐዳ የወንጀል ተግባር የፈፀመ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ይኸ ሰበር ችሎት አረጋግጧል፡፡ ይኸም በመሆኑ አንደኛ አመልካች በወንጀል በሃላፊነት የሚያስጠይቅ ተግባር ፈጽሟል ከሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ በወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ሁለተኛው ፓራግራፍ የተደነገገውን ሁኔታ የማያሟላ በመሆኑ በአንደኛ አመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ቀሪ የሚሆን እንደሆነ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 ሁለተኛው ፓራግራፍ መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ የገለጽነው ምክንያት እንደተጠበቀ ሆኖ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአንደኛ አመልካች ላይ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጸ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በማለት የወሰኑት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሚያስነሳው የህግ ጥያቄ አለ፡፡ ይኸውም የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሁሉም የወንጀል ድርጊቶች ተጠያቂና ሀላፊ እንደማይሆን የወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 “በህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የመንግስት አስተዳደር አካላትን ሳይጨምር በህግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ አነሳሽነት ወይም በአባሪነት በወንጀል ሊቀጣ ይችላል” የማለት የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው ይህንኑ የሚደነግግ ግልጽ የህግ ድንጋጌ በሚኖርበት ጊዜ ብቻ እንደሆነ ገሸርነት ያለውን መርህ በግልጽ ያስቀመጠ በመሆኑ ነው፡፡

ህግ አውጭው በወንጀል ህጉ ወይም በሌሎች የህግ ማዕቀፎች ለምሳሌ በወንጀል ህጉና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በወንጀልነት የተፈረጀው አድራጐት የህግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት የተፈፀመ ሲሆን የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል የሚጠየቅ ስለመሆኑ በግልጽ የሚደነግግ ድንጋጌ በማወጅ ህግ ወለድ ሰዎች በወንጀል ተጠያቂና ሀላፊ የሚሆኑበትን ሥርዓት እንደሚዘረጋ አግባብነት ያላቸውን የህግ ማዕቀፎች ይዘትና አቀራረጽ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 501/98 የተደነገገውን የተላለፈ የንግድ ህግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂና ሃላፊ የሚሆኑ መሆኑን የሚደነግግ ግልጽ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1 “ማንኛውም ሰው” የሚለው አገላለጽ የተፈጥሮ ሰውና የህግ ሰውነት ያላቸውን ድርጅቶች የሚያካትት ስለሆነ አንደኛ አመልካች በወንጀል መጠየቁ ተገቢነው በማለት ያቀረበው ክርክር በወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መሠረታዊ መርህ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ አንደኛ አመልካች ላይ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የወንጀል ህግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረታዊ መርህን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው የህግ ምክንያቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/1 መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል።
2. ሁለተኛ አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ የተሰናበተ በመሆኑ ከእስር እንዲለቀው ለማረሚያ ቤት ይፃፍ።
3. አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች የወንጀል ሃላፊነትና ተጠያቂነት የሌለባቸው በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አንደኛ አመልካች ከቻይና አገር ያስገባው 639 ካርቶንና 23,000 ፓኬት QRIQN የሚል የንግድ ምልክት ያለው ማስቲካ እንዲወገድ የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።
4. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተያዘውና አመልካቾች ከቻይና አገር ያስገቡት ማስቲካ እንዲለቀቅ ወስነናል።
5. ይኸ ውሣኔ መብቱ ተጥሷል የሚል ወገን ህጋዊ ሁኔታዎችን በማሟላት ህጋዊ ጥበቃና ከለላ እንዲሰጠው ጥያቄ ከማቅረብ የሚገደብ አይደለም በማለት ወስነናል።
6. በትውስት የመጣው መዝገብ ይመለስ ነው።

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 06 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ኤሊያስ ዲጋ ጉዳይ የውብነሽ ማንደፍሮ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ አሻሽሎ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ክሱም በሁለት ምድብ የተከፈለ ሆኖ የ1ኛው ክስ ይዘትም ፡- አመልካች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በአሽከርካሪነት ሙያው የሌላውን ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለበት ጥር 20 ቀን 2000 ዓ/ም ከቀኑ 11፡20 ሲሆን የሰሌዳ ቅጥሩ 3-41980 አ.አ መኪና ይዞ ከቦሌ አየር መንገድ ወደ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ እያሽከረከረ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ቦታው ቦሌ ሚካኤል ከተባለ ቦታ ሲደርስ ግልፅ የሆነ ደንብ ተላልፎ ሰው በማይጫንበት አይሱዚ የጭነት መኪና የእቃ መጫኛ ላይ ተጭኖ የነበረውን ጋሻው ተሾመ የተባለውን ሰው ከመኪናው ላይ ጥሎ ሕይወቱ እንዲያልፍ በማድረጉ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ሲሆን 2ኛው ክስ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ከመኪናው ወድቆ ጉዳት የደረሰበትን ሰው አፋጣኝ ህክምና እንዲያገኝ ሳያደርግ ከወደቀበት ጥሎት በመሄድ በአደጋ ላይ ያለን ሰው ባለመርዳቱ በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 575(2(ሀ)) ስር የተመለከተውን ተላልፏል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም የክስ ማመልከቻው ደርሶት ክሱን እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ገልፆ የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን የክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በሁዋላ አመልካች የወንጀል ድርጊቶችን ስለመፈፀሙ አቃቤ ሕግ በማስረጃዎቹ ያስረዳበት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ታምኖበት ይህንኑ እንዲያስተባብል ዕድል ተሰጥቶት አመልካች በሌላ የመከላከያ ማስረጃ ያሰማ ሲሆን የሥር ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ያላስተባበለ መሆኑን በመጥቀስ በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሰው በቀረቡት ሁለቱም ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ አድርጎ ወስኗል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም በ1ኛው ክስ በስድስት አመት እና በብር 10,000.00 በሁለተኛው ደግሞ በስድስት ወር ጽኑ እስራትና በብር 1000 በድምሩ በስድስት አመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 11,000.00 (አስራ አንድ ሺህ ብር) አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/1/ መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሚያዚያ 29 ቀን 2002 ዓ/ም በተጻፈ አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፤ አመልካች የወንጀል ድርጊቶቹን ስለመፈፀሙ ዐቃቤ ሕግ በሕጉ አግባብ አላስረዳም፣ የመከላከያ ማስረጃው ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው በማለት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ እንዲሰረዝ ወይም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/2/ ነው ተብሎ የቅጣት ውሳኔው አመልካች የታሰረበትን ጊዜ በቂ በማድረግ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ የጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በ1ኛው ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ ስር ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ባግበቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት የሚታይ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ምላሽ ከመስጠታችን በፊት ግን የአመልካች ጠበቃ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ፈፅሟል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተደረሰው ድምዳሜ ከማስረጃ አረዳድና አፈፃፀም አንፃር ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ ከዚህ ሰበር ችሎት ሥልጣን አንፃር ያለውን ተገቢነት ተመልክተናል፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን በማናቸው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ይህንኑ ማረም ነው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለውም የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በሰበር ችሎቱ ስልጣን ስር የማይወድቅ መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ጠበቃ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የማስረጃ አረዳድና አፈፃጸም ግድፈት ተፈፅሟል፣ ይህም የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 23/4/ የሚፃረር ነው በማለት በሰበር ማመልከቻው ላይ የዘረዘሩ ቢሆንም በዚህ ረገድ የቀረበው የቅሬታው አጠቃላይ ይዘት ሲታይ ግን የማስረጃ ምዘናን ጉዳይ የሚመለከት በመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አላግኝነውም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ባለመሆኑ አልፈነዋል፡፡

ወደዋናው ጭብጥ ስንመለስ አመልካች በ1ኛው ክስ ጥፋተኛ የተባለው እቃ በሚጫንበት መኪና ሰው ጭኖ ሲሄድ ሰው ውድቆ እንዲሞት አድርጓል፣ ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(3) ስር የተመለከተውን የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦችን የሚያሟላ ነው በሚል ነው፡፡

በሰበር ችሎት ከላይ የተጠቀሰው አጠቃላይ የክርክሩ ሂደት አግባብ ካላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና የአመልካች ጠበቃና ተጠሪ ለዚህ ችሎት በጽሑፍ ካቀረቡት ክርክር እንዲሁም የስር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ በማስቀረብ ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡ በበታች ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገርና ከተወሰነው ውሣኔ አንፃርም አመልካችን በወንጀል ጥፋተኛ ለማለት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 543/3/ የተጠቀሱት መስፈርቶች ተሟልተዋል? ወይስ አልተሟሉም? የሚለውን ነጥብ አጣርቷል፡፡ አመልካቹ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቀጣ በመሆኑ በሕጉ ችልተኝነት የሚያቋቁሙ መስፈርቶች መሟላት አለመሟላታቸውን ተመልክቷል። ይህ ችሎት በዋናነት የመረመረው የሕግ ነጥቡን ብቻ ቢሆንም የሕጉን አግባብነት በትክክል ለመመዘን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በቅደሚያ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

ጉዳዩ በሥር ፍ/ቤት ሲታይ አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 3-41980 አ.አ መኪና ይዞ ከቦሌ አየር መንገድ ወደ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ እያሽከረከረ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ቦታው ቦሌ ሚካኤል ከተባለ በታ ሲደርስ የእቃ መጫኛ ላይ ተጭኖ የነበረውን ጋሻው ተሾመ የተባለውን ሰው ከመኪናው ላይ ወድቆ ሕይወቱ እንዲያልፍ ማድረጉ በክሱ ተገለጿል። ይሁን እንጂ መኪናው የእቃ መጫኛ ሆኖ እያለ ሟችን አመልካች ያሳፈረው ስለመሆኑ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ስለመነገሩ የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር የለም። በሌላ አገላለጽ ሟችን አመልካች አሳፍሮት ሲጓዝ እንደነበር የሚያሳይ የፍሬ ነገር ድምዳሜ የለም። ይህ በፍርዱ ሂደት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2/ በግልፅ ተደንግጓል። እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል። ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸው ነጥቦች ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉትን ደግሞ እንደየቅደምተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ ናቸው።

በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ሟች በመኪና ግጭት እንዲሞት ማድረጉ በፍሬ ነገር ደረጃ አመልካችን ሊያስጠይቅ የሚችለው በየትኛው ድንጋጌ ነው? የሚለው ነው። አመልካቹ በዓቃቤ ሕግ ክስ የመሰረተበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/"ን" በመተላለፍ ጋሻው ተሾመን ገድሏል በማለት ነው። በዚህ የሕግ ድንጋጌ አንድ ሰው ተጠያቂነት የሚከተልበት የሌላ ሰውን ሕይወት ፣ጤንነት ወይም ደኅንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ሕክሙና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ፣ ወይም ወንጀሉን የፈፀመው ግልፅ የሆነ ደንብ /መመሪያን/ ተላልፎ እንደሆነ ወይም የሚያስክሩ ወይም የሚያፈዙ ንጥረ ነገሮችን ወይም መጠጦችን በመውሰዱ እራሱን ከኃላፊነት ነጻ በሚያወጣ ሁኔታ ውስጥ ካስገባ በኋላ በችልተኝነት ሰው የገደለ እንደሆነ ስለመሆኑ በሕጉ ተመልክቷል። የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ከላይ የተመለከቱት ሲሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የተጠቀሰውን ሕግ የሚያቋቁሙ መሆን አለመሆናቸው ለማረጋገጥ ሕጉ ችልተኝነት አለ የሚለው ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል።

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57 በግልፅ እንደሰፈረው "ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በችልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆንም" በአንዳንድ ሰው "የፈፀመው ድርጊት በሕግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈፀመ ወይም የደረሰ ሆኖ ሲገኝ በወንጀል ሕግ ሊፈረድበት አይገባውም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 57/2/ ይደነግጋል። ከዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕጉ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ክሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ድርጊቱ የተፈፀመው ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት መሆኑን ነው፡፡ ድርጊቱ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑ ማስረጃ ካላቀረበ ወይም ድርጊቱ ከአቅም በላይ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በተከሣሽ በኩል ከቀረበ የተከሰሰውን ሰው በወንጀል ሕግ ጥፋተኛ ብሎ መፍረድ ከሕጉ መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ቸልተኛ ነበር? ወይስ አልበረም? የሚለው ጥያቄ በወንጀል ሕጉ በአንቀፅ 59 የሰፈረውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ የዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ አንድ አሁን ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው በመሆኑም የሕጉን ይዘት እንዳለ ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው፡፡ ይኸውም፡- ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለው፡-

ሀ) ድርጊቱ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም በሚል ግምት ወይም ባለመማዘዘን፣ ወይም

ለ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እያቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ነው፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው ውጤቱን እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ደግሞ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ውጤቱን ማወቅ ይችል ነበር ማለት ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም ቸልተኝነት አለ ለማለት ሕጉ የሚጠቀምበት ዋነኛ መስፈርት የተከሰሰው ሰው በድርጉቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ነው፡፡ ድርጊቱን የፈፀመው ሰው የነበረው ዕውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚባው ዕውቀትና ግንዛቤ የሚመዘነው የሰውዬው ዕድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ ፣ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃውን ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነም የሕጉ አንቀፅ 59/1/ ይደነግጋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የሚከራከረው ሟችን ለእቃ ጭነት በሚያገለግለው መኪና እያወቀ ያልጫነው መሆኑንና ተሳፍሮ ያለ መሆኑንም ማወቅ ይችል የነበረ ስለመሆኑ አቃቤ በፍሬ ነገር ደረጃ ያላረጋገጠው መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን ይህ ያለመረጋገጡ ደግሞ ደንብ ቁጥር 279/1956 አንቀጽ 46/1/ ስር የተመለከተውን ጥሷል ለማለት አያስችልም በማለት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ሟች አመልካች ሲያሽከረክር በነበረው የአይሱዚ መኪና ተገጭቶ ከዚህ አለም በሞት መለየቱ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን ይህ ድርጊት አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ መሠረት ሊያስጠይቅ የሚችለው በአሽከርካሪነት ስራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 59/1/ የተገለፀውን ያሟላና የትራፊክ ደንቡን መጣሱ የተረጋገጠ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑንም በክርክሩ ሂደት አመልካች ሟችን በአይሱዚ መኪና በአንቀጽ 543/3/ ሥር ስለቸልተኝነት የተመለከተውን መመዘኛ በሚያሟላ መልኩ የጫነው መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 543/3/ ሥር ጥፋተኛ ሊባል የሚችልበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡ ይልቁንም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ አመልካች በአሽከርካሪነት ስራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቆርቶ ሟችን በመግጨት ለሕልፈት የዳረገው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ሲሆን ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/2/ ሥር ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/3/ ሥር ጥፋተኛ የተባለው ባለተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘን አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/113/2/ መሠረት በመለወጥ ድርጊቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/2/ ሥር የሚሸፈንና የሚያስጠይቅ ነው ብለናል፡፡

ሌላው አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ የተባለው የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 575/2/ሀ/ ሥር ሲሆን አመልካች በአሽከርካሪነት ሥራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ ሟችን ከገጨ በኋላ እርዳታ ሳያደርግለት መሸሹ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም ፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በ1ኛ ክስ ላይ አመልካች ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው ድንገጌ መለወጥ ያለበት መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ከዚሁ ተያይዞ መታየት ያለበት በዚህ ረገድ ሊጣል የሚገባው የቅጣት መጠን ነው፡፡ አመልካች ሊቀጣ የሚገባው በዚህ ችሎት ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2/ መሠረት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሊቀጣ የሚገባው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደረስ በሚችል ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ እስከ ስድስት ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ነው፡፡ ቅጣት ደግሞ ሊጣል የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88/2/ ሥር የተመለከቱትን ነጥቦችን በማመዛዘን ነው፡፡ እኛም አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያስመዘገባቸውን የቅጣት ማቅላያ ምክንያቶች (ሪኮርድ የሌለበትና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑን) ከድርጊቱ አፈጻጸምና ከቅጣት ዓላማ እንዲሁም ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው ሲገኙ ቅጣት ከሚጣልበት አግባብ (ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/1/ለ/) ጋር በበገናዘብ ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በሁለቱም ጉዳዮች ሊቀጣ የሚገባው የእስራት መጠን በጠቅላላው አራት አመት ቀላል እስራት ሆኖ የገንዘብ መቀጮው ደግሞ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90 ይዘትና መንፈስ አንጻር ሲታይ በድምሩ ብር 7000.00 (ሰባት ሺህ) ሊሆን የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊሻሻል የሚገበው ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ ቁጥር 70094 የካቲት 03 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፍደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 53779 መጋቢት 29 ቀን 2002 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2) እና 575(2(ሀ)) ሥር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የተላለፈ ጥፋተኛ ነው በማለት በጉዳዩ ላይ የታሰረው ጊዜ የሚታሰብለት ሆኖ በጠቅላላው በአራት አመት ቀላል እስራትና በብር 7000.00 (ሰባት ሺህ) እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ተሻሽሎ በተወሰነው ውሳኔ መሠረት ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማረሚያ ቤቱ ትዕዛዝ ይድረሰው ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

እ/ብ ***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59537

ሚያዝያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አነዚር ኢብራሂም - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የቤ/ን/ክ/ሥ/ፀ/ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ አቶ አብዮት አልቦሮ ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ትዕዛዝ ሰጥተናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ከሳሽ ነበር፡፡ የሥር ከሳሽም በአመልካች (በሥር ተከሳሽ) ሁለት ክሶችን አቅርቧል፡፡ 1ኛ ክስ ተከሳሹ ቀደም ሲል በክልሉ የሥራ አመራር ተቋም ሀላፊ የነበረ ሲሆን ከዚሁ ከተጠቀሰው ተቋም ወደ ክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ከተዛወረ በኋላ የሥራ አመራር ተቋም በጀት በሆነው በስልክ መስመር ቁጥር 0911254789 በህገ ወጥ መንገድ ተጠቅሞ ብር 4,674.32 የመንግሥት ገንዘብ ወጪ ሆኖ እንዲባክን በማድረጉ በሥልጣን ያለአግባብ በመገልገል በወ/ህ/ቁ 407/1ሐ/ የተመለከተውን ተላልፏል የሚል ሲሆን፤ 2ኛ ክስ ደግሞ ተከሳሹ በሥራ አመራር ተቋም ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በሚሠራበት ወቅት በሥራ አጋጣሚ በትውስት በእጁ የገቡትን የመንግስት ንብረቶች እንዲመልስ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ጠፍተውብኛል በማለት ያለአግባብ በንብረቶቹ ለመጠቀም አስቦ የሰወራቸው በመሆኑ በወ/ህ/ቁ/አ 413 (1ለ) የተደነገገውን የመሰወርና የወውሠድ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ተከሳሹም ፍ/ቤት ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ወንጀሉን አለመፈፀሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የከሳሽ ማስረጃዎችን ከሰማ በኋላ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 141 መሠረት ተከሳሹን በብይን በነፃ አሰናብቷል፡፡

በተከሣሹ በነፃ መለቀቅ ቅር የተሰኘው የሥር ከሳሽም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ 01966 በቀን 24/02/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195(1) መሠረት የይግባኝ ባዩን ይግባኝ ባለመቀበል አሠናብቷል፡፡ ይሁን እንጂ አነስተኛው ድምፅ መልስ ሰጪው በሥር ፍ/ቤት ሳይከላከል በነፃ መሠናበቱ ያለአግባብ በመሆኑ መከላከል አለበት ብሏል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የከፍተኛውን ፍ/ቤት ብይን በማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የአሁኑ ተጠሪ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም በመ/ቁ 02083 በቀን 19/11/2002 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ፍርድ ክሳሽ (ይግባኝ ባይ) በሁለቱም ክሶች አስረድቶ እያለ አልተመሠከረበትም በሚል በነፃ መለቀቁ ያለአግባብ ነው በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 142(1) መሠረት እንዲከላከል ወስኗል፡፡ የሰበር ችሎት አነስተኛው ድምጽ ደግሞ ተጠሪው (የሥር ተከሳሽ) ሊከላከል አይገባም ብሏል፡፡

በክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ያለው የአሁን አመልካችም ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ቅሬታ በቀረቡብኝ ሁለት ክሶች የተጠሪ ምስክሮች የወንጀሉን ድርጊት አለመፈፀሜን በሚገባ በማረጋገጥ መስክረው እያሉ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ፍርድ እንዲከላከል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ስህተቱ ታርሞ የአብላጫው ድምጽ ፍርድ ተሽሮና አነስተኛው ድምጽ መካላከል የለበትም ያለው ፀንቶልኝ በነፃ እንድሰናበት ይወሰንልኝ ብሏል፡፡

ለዚህ የሰበር ቅሬታ ተጠሪው በቁጥር 01/2003 በቀን 02/05/2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም አንድ ተከሳሽ ወይም ይግባኝ ባይ ወይም የሰበር አቤቱታ አቅራቢ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 184(መ) እና 195 መሠረት የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሣኔ ባልተሰጠበት ይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ አይችልም፡፡ አመልካች የሚያነሣቸው ነጥቦች በመከላከያ ማስረጃዎች የሚረጋገጡ እንጂ በሰበር አቤቱታው ባቀረበው ሁኔታ የሚታመንበትና ተቀባይነት የሚያገኝበት አይደለም፡፡ በሁለቱም ክሶች ተጠሪ ባቀረባቸው የሰውና የጽሁፍ ማስረጃዎች ከተገቢው ጥርጣሬ በላይ የተመሠከረበት በመሆኑ የሥር ሰበር ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ተጠሪው ለሰበር ችሎት ለሰጠው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የቀረበ ሲሆን እኛም ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን የመመርመር ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10(2) ሆነ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3) ሀ መሠረት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ማንኛውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ያለው መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን በሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት አመልካች የቀረቡበትን ክሶች ይከላከል መባሉ በጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶበታል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

ስለሆነም የሰበር አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለመቅረብ ብቁ ባለመሆኑ ውድቅ አድርገን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ እንዲሆን ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ፋሲል ታምራት - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- የሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ ከሣሽ - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን የተጀመረው በአዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በመግደል ሙከራ ክስ በአመልካች ላይ ባቀረበው መሠረት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ በአጭሩ፡- ተከሣሽ የወ/መ/ሕ/ቁ. 27 እና 539 /1/ /ሀ/ በመተላለፍ በቀን 06-9-2002 ዓ.ም ከምሽቱ በ4፡00 ሰዓት በሀዋሳ ከተማ መሀል ከተማ ክልል ጸሐይ ሆቴል ፊት ለፊት ባለው አስፋልት መንገድ ላይ አቶ ተስፋአብ ለተሞ ወደሚያሽከርክረው መኪና ተጠግቶ ምስራቅ ሆቴል ልታሰዬኝ ትችላለህ? በማለት ካልተያዘው ተጠርጣሪ ጋር ካነጋገሩት በኋላ ያልተያዘው የግል ተበዳይ እንዳይከላከል ክልሎ ሲያመቻች ተከሣሹ የግል ተበዳዩን በኋይል አንገቱን ሊወጋው ሲል ዞር በማለቱ ቀኝ ጉንጩን ወግቶ የፊት ለፊት 3 ጥርስ ከታች መንጋጋ 5 ጥርሶቹን በሣንጃ ወግቶ ያወላላቀበት በመሆኑ በፈጸመው የመግደል ሙከራ ተከሷል የሚል ነበር፡፡

ተከሣሽ የቀረበበትን ክስ በመካድ ሲከራከር የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው ከተሰሙ በኋላ የተከሣሽም መከላከያ ምስክር እንዲቀርቡ ታዘው ከተሰሙ በኋላ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ ወደ 555 /ሀ/ /ለ/ በመለወጥ ጥፋተኛ መሆኑን ፍርድ በመስጠት በ8 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ፍርድ ቤቱ በሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ እና ቅጣት ላይ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ ጠይቆ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካከራከረ በኋላ ተከሣሽ ጥፋተኛ መሆን ያለበት በወ/መ/ሕ/ቁ. 27 እና 540 መሆን አለበት በማለት ቅጣቱንም በ12 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታውን አቅርቦ ችሎቱም በትዕዛዝ የበታች ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ፍሬ ሃሣብ የተላለፈበት የጥፋተኝነት ውሣኔና ቅጣት ያለአግባብ በመሆኑ ተሽሮ በነጻ እንዲሰናበት ፣ ይሄ ካልሆነ ደግሞ የተላለፈበት ቅጣት ተሻሽሎ እስከአሁን የታሰረው በቂ ሆኖ እንዲለቀቅ ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ቀርቦ በሰጠው መልስ የተላለፈበት የጥፋተኝነት ውሣኔና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅጣት በአግባቡ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይሄ ችሎትም የቀረበውን ክርክር ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡

በዚሁ መሠረት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች ጥፋተኛ መባል ያለበት በከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወይስ? በመግደል ሙከራ የነበረ በመሆኑ ይሄ ጉዳይ ከዚሁ አካያ ታይቶ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ አመልካች በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ስላልተረጋገጠብኝ በነጻ ልሰናበት ይገባኛል በማለት የተከራከረውን በተመለከተ በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ እና ቅጣት ያንሣል በማለት ይግባኝ ያለው ከሣሽ ዐቃቤ ህግ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ምክንያቱም በከፍተኛው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ አመልካች ይግባኝ ስለማቅረቡ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠበትን አንቀጽ በተመለከተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በዐቃቤ ህጉ ክስ ውስጥ የተመለከተውን የወ/መ/ሕ/ቁ. 27 እና 539 /1/ /ሀ/ ወደ ወ/መ/ሕ/ቁ. 555 /ሀ/ /ለ/ የቀየረው እውነት ለመግደል ሃሳብ ቢኖረው ደጋግሞ በመውጋት ሃሳቡን ከግቡ ለማድረስ ይችል ነበር በሚል ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ አመልካች ጥፋተኛ መሆን ያለበት በወ/መ/ሕ/ቁ. 27 እና 540 ስር መሆን አለበት ወደሚል መደምደሚያ የደረሰው አመልካች በያዘው ሣንጃ የተበዳይ አንገት ላይ ለመውጋት የሰነዘረ መሆኑና ተበዳይ በድንገት ዞር በማለቱ ጉንጩ ላይ በመውጋት ከወጋ በኋላ ደግሞ ሣንጃውን ነቅነቅ በማድረግ ባጠቃላይ 8 /ስምንት/ ጥርሶቹን ያረገፈ በመሆኑ እና መጀመሪያ እንደሰነዘረው አንገቱን ቢወጋ ኖሮ የተበዳይ በህይወት የመትረፍ አጋጣሚ ጠባብ የነበረ መሆኑ ስለመረጋገጡ በማስረዳት መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

ይሄንን የይግባኝ ሰሚ ችሎት መደምደሚያ ከወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 27/1/ ሁለተኛ ምዕራፍ ጋር ስናመሣዝን... “ወንጀሉ እንደተጀመረ የሚቆጠረው የተደረገው ተግባር በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ ወንጀሉን ለመፈጸም ወደ ታሰበበት ግብ ለማድረስ የተደረገ በሆነበት ጊዜ ነው” ይላል፡፡

በእርግጥም አመልካች ቀድሞ አስቦ ሣንጃውን በሰነዘረው መሠረት ተበዳይ ዞር ባይልና በቀጥታ አንገቱን ቢያገኘውና ቢወጋው ኖሮ ሞትን ሊያስከትል እንደሚችል መገመት አያስቸግርም፡፡

አንገት ላይ በሣንጃ መውጋት ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወ/መ/ሕ/አንቀጽ 24/1/ ሁለተኛ ምዕራፍ ላይ እንደተመለከተው በነገሮች የታወቀ ወይም የተለመደ ሂደት In the normal course of things...” ሞትን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ በውጤቱና ምክንያቱ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት አለ የሚያሰኝ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባጠቃላይ ከላይ የተመለከቱትንና ሌሎችንም የድርጊቱን አፈጻጸም ሂደቶች ከግምት በማስገባት የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ጥፋተኛ መባል ያለበት በመግደል ሙከራ ስር ነው በማለት በወ/መ/ሕ/ቁ. 27 እና 540 ስር ጥፋተኛ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የተላለፈበት ቅጣትም ከወንጀሉ አፈጻጸም እና ጥፋተኛ ከተባለበት አንቀጽ አኳያ ሲታይ በተመሣሣይ መልኩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደ/ብ/ብ/ሕ/ብሔ/ክ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 45137 በቀን 09-3-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 43913 በቀን 06-01-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ ወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ለአመልካች የውሣኔው ግልባጭ በሀዋሳ ማረሚያ ቤት በኩል ይድረሰው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍታብሔር ሥነ - ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 53844

ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- አቶ ውጅራ ንዳ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. አቶ ታደሰ መኮንን ጠበቃ ይመኑ ገ/ፃድቅ ቀረቡ

2. አዲስ ዘመን 83 የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ሊቀመንበር ኪሮስ አምደየሱስ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ አንደኛ ተጠሪ ከሳሽ በመሆኑን ተከራክረዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሥር ተከሳሽ የሆኑት አመልካች እኔ በሊቀመንበርነት የምመራው አዲስ ዘመን 83 የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበር አለ በማለት ብር 20,000 /ሀያ ሺህ ብር/ ተቀብለው በመውሰድ በልጽገውበታል፡፡ ተከሳሹ /አመልካች/ ማስጠንቀቂያ ብጽፍላቸውም መልስ አልሰጡኝም ስለሆነም ከእኔ የወሰዱትን ብር 20,000 /ሀያ ሺህ ብር/ ከነወለዱ እንዲከፍሉ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች ገንዘቡን ለእኔ በግሌ አልሰጠኝም፡ ገንዘቡን የከፈለው ለቤት ሥራ ማህበር ሲሆን ገንዘቡን ለማህበሩ የከፈለ ስለመሆኑ ደረሰኝ ተሰጥቷል፡፡ እኔ ገንዘብ የተቀበልኩት በወቅቱ የማህበሩ ገንዘብ ያዥ በመሆኔ ነው፡፡ ስለዚህ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ አልቀረበም በማለት አመልካች ብር 20,000 /ሀያ ሺህ ብር/ ከግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አንደኛ ተጠሪን በአንደኛ መልስ ሰጭነት ሁለተኛ ተጠሪን በሁለተኛ መልስ ሰጭነት ስማቸውን በመጥቀስ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ገንዘቡን እኔ በግለሰብነቴ ሣይሆን የማህበሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘብ ያዥ ስለሆንኩ የተቀበልኩት መሆኑን ማስረጃ በማቅረብ ተከራክሬአለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛው ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ጠይቆ ገንዘቡ ለማህበሩ ገቢ መሆኑንና ገንዘቡ እኔን የማይመለከተኝ መሆኑን በጽሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ ይህንን ሁሉ በማለፍ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሁለተኛው ተጠሪ አለኝ የሚለውን የሰነድ ማስረጃ በማያያዝ በክርክሩ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆኖ እንዲገባ ያመለከተ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት ማህበሩ ህጋዊ ህልውና የሌለው መሆኑን በማረጋገጥ ጥያቄውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ ስለዚህ አመልካች ያቀረበው አቤቱታ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች ብር 20,000 /ሀያ ሺህ ብር/ የከፈለ መሆኑን ለማስረዳት የቀረበው በአዲስ ዘመን 83 የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበር ሥም የታተመ የገንዘብ መሠብሰቢያ ደረሰኝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማህበሩ የራሱ የሆነ ማህደር ያለው ስለመሆኑ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ቡራዩ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤትና የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ማህበራዊ ማደራጃና ማስፋፊያ መምሪያ የፃፋቸው ደብዳቤዎች ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛ ተጠሪ ገንዘቡ የተከፈለው መሆኑንና ክርክሩ አመልካችን ሳይሆን በቀጥታ እሱን የሚመለከተው መሆኑን ገልፆ በሥር ፍርድ ቤት ታህሣሥ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ያመለከተ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤትን መዝገብ በማስቀረብ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛው ተጠሪ የከሳሽን /የአንደኛ ተጠሪን/ ክስና ማስረጃ ወስደው መልስ እንዲያቀርቡና በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ከፈቀደ በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ ጥር 13 ቀን 2001 ዓ.ም በነበረው ቀነ ቀጠሮ መልስ ይዘው ባለመቅረባቸው የሁለተኛ ተጠሪን ጣልቃ ገብነት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 199 መሠረት ሠርዣርዋለሁ በማለት ትእዛዝ የሰጠ መሆኑን ችሎቱ አስቀርቦ የሥር ፍርድ ቤት መዝገብና አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ካቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት የተከተለው የክርክር አመራር ሥርዓትና በመጨረሻም ውሳኔ ሲሰጥ የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመመሥረት ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ታህሣሥ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ያቀረቡትን አቤቱታ በመቀበል በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ታህሳስ 10 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረቡት የጣልቃ ገብነት አቤቱታ አመልካች ገንዘቡን የተቀበለው የማህበሩ ገንዘብ ያዥ በመሆኑና ማህበሩም ገንዘቡ ገቢ የተደረገለት በመሆኑ ከሳሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ ስለማህበር አባልነትና ተመላሽ ገንዘብ መክሰስም ሆነ መከራከር ካለበት ከማህበሩ ጋር መሆን አለበት የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ለአንደኛ ተጠሪ በሥር ከሳሽ ክስና ማስረጃ ይዘው እንዲቀርቡ በተቀጠረበት ቀን ካልቀረቡ የሁለተኛ ተጠሪን መልስ የመስጠት መብት በማለፍ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ህጋዊ ህልውና አለህ በክርክሩ ጣልቃ እንድትገባ ተፈቅዷል ያለውን አካል ከክርክር ውጭ እንዲሆን የሰጠው ትእዛዝ የአመልካችን መብት የሚያጣብብና አንድ በክርክር ተካፋይ የሆነ ሰው መልሱንና ማስረጃውን ባያቀርብ ፍርድ ቤቱ በሌለበት ክርክሩን ሰምቶ የሚወሰን መሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 70 የተደነገገውን የሚጥስና የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛ ተጠሪ ሕጋዊ ህልውና እንዳለውና በክርክር ጣልቃ መግባት እንደሚችል የሥር ፍርድ ቤት ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ ህጋዊ ህልውና እንደሌለውና አንደኛ ተጠሪ በማህበሩ ስም የታተመ ደረሰኝ ተቀብሎ ለከፈለው ብር 20,000 /ሀያ ሺህ ብር/ አመልካች በግሉ ተጠያቂነት አለበት በማለት መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፍርድ ቤቱ የማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ ታህሳስ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ከሰጠው ትእዛዝ ጋር የሚቃረንና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ሁለተኛ ተጠሪና በአንደኛ ተጠሪ መካከል የቀረበውንና የሚቀርበውን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. ከሥር ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ ይመለስ
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ምናሴ ኢትሶ ጠበቃ አሰፋ ንጉሴ ጋር ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሸዋዬ በዳሶ ጠበቃ አሰፋ ንጉሴ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፋንታዬ ተረፈ ጠ/ጌታቸው እንግዳ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ አመልካቾች ተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ያላአግባብ የፍርድ ባለመብት የሆኑበት ቤት ይለቀቅልኝ ክስ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ባለማገኘቱ ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤት አመልካቾች ከሳሾች ነበሩ፡፡ የክሱ ምክንያትም ባልና ሚስት የሆኑት የሥር ተከሳሾች በቤቱ ላይ መብት ሳይኖራቸው የባልና ሚስት ንብረት በማስመሰል በፍርድ አፈፃፀም የተረከቡትን ቤት እንዲያስረክቡ /እንዲመልሱ/ ይወሰንልን የሚል ነበር፡፡

የአሁኗ ተጠሪ ሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ ሆነው የሰጡት መልስ ቤቱ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ መሆኑ ተረጋግጦ በመ/ቁ. 45803 በ16/7/98 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ በክፍፍል ያገኙት ንብረት መሆኑን ገልፀው የከሳሾች ጥያቄ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149 መሰረት በይርጋ ቀሪ ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከሳሾች ቤቱን የያዙት በፍርድ ስለመሆኑ ከሳሾች ያመኑት ጉዳይ ስለመሆኑ ጠቅሶ በሐሰት ማስረጃ ያገኙት ነው የሚሉ ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6/1/ መሰረት ከሚጠይቁ በስተቀር ክስ ለማቅረብ አይችሉም በሚል ጥያቄያቸውን ሳይቀበል ቀርቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6/1/ን በመጥቀስ በውሳኔው ያመለከተውን የከሣሽ መብት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንደሌለው ተችቶ ከሳሾች መብታቸውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ከሚጠይቁ በስተቀር አዲስ ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ ምክንያት በመለወጥ አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡፡ የቤት ቁጥር 260 የባልና ሚስት ሐብት ነው ተብሎ እንዲከፋፈሉ በመ/ቁ. 45803 ውሳኔ መስጠቱን እንዳወቁ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት አቤቱታ አቅርበው ውሳኔ ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ ነው በሚል ውድቅ የተደረገባቸው መሆኑን ጠቅሰው አዲስ ክስ የቀረበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421 መሰረት ስለመሆኑ ገልፀው የሥር ፍ/ቤቶች ፍትህ የማግኘት መብታቸውን በሚጐዳ ሁኔታ የሰጡት ውሳኔ እንዲታረም ጠይቀዋል፡፡

የሰበር ችሎቱም አቤቱታቸውን መርምሮ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 እና 358 ጠቅሰው የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ በይዘቱም የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቾችን የዳኝነት ጥያቄ ቀደም ሲል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ውድቅ መደረጉን ተገንዝበው መወሰናቸው በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው የአሁኑ ተጠሪ እና ባለቱቷ መካከል የነበረ ጋብቻ በፍች እንዲፈ|ርስ መወሰኑን ተከትሎ የንብረት ክፍፍል ክርክር ተደርጐ በተሰጠ ውሳኔ መሰረት በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቀበሌ 04 የቤ/ቁ. አዲስ የሆነ በ400 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያለ ቤት ተጠሪዋ በፍርድ አፈፃፀም የተረከበች መሆኑን ተከትሎ ይህ ቤት የባልና ሚስቱ ሳይሆን የአመልካቾች ነው ሲሉ አመልካቾች ክስ ማቅረባቸው ተመልክቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት ተጠሪና ባለቤቷ በሐሰተኛ ማስረጃ ቤቱን አገኙ የሚሉ ከሆነ የከሳሾች (አመልካቾች) ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6/1/ መሰረት ሊታይ የሚገባ እንጂ አዲስ ክስ መቅረብ አይችልም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

በመሰረቱ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህ የሥነ ሥርአት ሕጉ ድንጋጌ ተከራካሪ በነበሩ ወገኖች መካከል እንጂ ሦስተኛ ወገን ሊጠቀምበት እንደማይችል ጠቅሷል፡፡ በዚህ ረገድ የ3ኛው ፍ/ቤት የውሳኔው ምክንያት ተገቢነት ያለው እንደሆነም መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን አመልካቾች አዲስ ክስ ከማቅረባቸው በፊት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት በዋናው መዝገብ ላይ አቤቱታ አቅርበው ውሳኔው ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ ጥያቄ ነው ተብሎ ውድቅ የተደረገባቸው መሆኑ በግልጽ ተጠቅሶ እያለ ከፍተኛው ፍ/ቤት መልሶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት መብታቸውን ማስከበር ይችላሉ ያለው እርስ በርሱ የሚጋጭ አቋም መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአንድ ንብረት ላይ መብት አለኝ፣በክርክሩ ሂደት አልተካተትኩም በሚል ምክንያት መብቱ ተነክቷል የሚል ወገን መብቱን ሊያስከብር የሚችልበትን ሥርአት ሕጉ በየደረጃው ዘርግቷል፡፡

ለዚህም ተጠቃሽ የሚሆኑት ውሳኔው ከመፈጸሙ በፊት ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት፤ውሳኔው በአፈፃፀም ሂደት ላይ ሆኖ ንብረቱ ያለአግባብ ተይዞብኛል የሚል ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 418 መሰረት መብቱን ማስከበር የሚችልበት አግባብ ተደንግጓል ከዚህ ባለፈ በንብረቱ ላይ የተሻለ መብት አለኝ የሚል ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 421 አልያም እንደነገሩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/አንቀጽ 455 መሰረት ክስ መሥርቶ መብቱን ማረጋገጥ እንደሚችል ተመልክቶ እናገኛለን፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ጥያቄ ያቀረቡበት ንብረት በፍርድ ለ1ኛ ተጠሪ የተላለፈ ስለመሆኑ በክርክር ሂደት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካቾች ይህ ንብረት የባልና ሚስቱ ሳይሆን የአመልካቾች ነው ሲሉ ያቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 455 በተደነገገው አግባብ ሊስተናገድ የሚችል ስለመሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እንደማናቸውም ጉዳዮች በማስረጃ ተጣርቶ ውሳኔ ሊይገኝ የሚገባው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

ስለሆነም አመልካቾች በንብረቱ ላይ ያላቸውን መብት ለማረጋገጥ ያቀረቡትን ክስ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 እና 358ን በመጥቀስ ውድቅ ማድረጋቸው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው እና የጉዳዩን ደረጃ እና የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12351 በ29/5/01 የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 78780 ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄን ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መዝገቡን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 18 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ገብሩ ኮሬ ጠበቃ ወልደስላሴ ብርቱ

ተጠሪ፡- አቶ አመዲዮ ፈዬራቼ ከጠበቃ መስፍን ጌታቸው ጋር ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በውሉ መሠረት የግልግል ዳኛ ጉዳዩን እንዲመለከት ይወሰን ዘንድ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ቀርቦ በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት ጉባኤው ተቋቁሞ ጉዳዩን ማየት ከጀመረ በኋላ ጉባኤው የአባላቱን አበል በተመለከተ ትዕዛዝ ሲሰጥ በአበሉ መጠን ቅሬታ ያለው ወገን ሊከተለው የሚገባውን ሥነ ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩ በግልግል ጉባኤ እንዲታይና ጉባኤው እንዲቋቋም ለፊዬራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት ያሁኑ ተጠሪ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የሽምግልና ዳኛ እንዲሾም ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት ፍ/ቤቱ አንድ ሰብሳቢ ዳኛ ግራ ቀኙ ደግሞ አንድ አንድ የሽምግልና ዳኛ መርጠዋል፡፡ በፍርድ ቤቱ የተሾሙት ሰብሳቢ ዳኛ በግራ ቀኙ ከተሾሙት ዳኞች ጋር በመሆን ስራ ከመጀመራቸው በፊት ስለአበል ክፍያ አተማመን ይረዳቸው ዘንድ የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር እንዲቀርብ አድርገዋል፡፡ ከዚህም የሽምግልና ጉባኤ አባላት አበል ብር 60,000.00 (ስልሳ ሺህ ብር) እንዲሆንና ግማሹ ቅድሚያ እንዲከፈል ለግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ተገልጾላቸዋል፡፡ ተጠሪ ይህ ሲገለጽላቸው አበሉ ከአቅም በላይ የሆነባቸው መሆኑን ገልፀው ቀነ ቀጠሮ በጉባኤ ከተሰጣቸው በኋላ አባላቱ ጉዳዩን ለማየት የማይችሉ መሆኑንና የተጠሪን በቀነ ቀጠሮ አለመቅረብ በመጥቀስ መዝገቡን ዘግተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ ሌላ የሽምግልና ጉባኤ እንዲቋቋምላቸው /እንዲሾምላቸው/ እና የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸው ለስር ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍ/ቤቱም የግልግል ጉባኤው አበሉ ቀድሞ ካልተወሰነ ራሱ መወሰን እንደሚችል፣ ይህም በስራ ሒደት እንደተሰጠ ትዕዛዝ እንደሚቆጠር በትዕዛዙ ቅሬታ ያለው ወገን ማሳረም የሚችለው በይግባኝ እንጂ ሌላ ጉባኤ እንዲቋቋም በማድረግ አለመሆኑንና ተጠሪ እንዲከፈል ትዕዛዝ የተሰጠበትን የጉባኤ አባላት አበል በመክፈል መዝገቡን ከማንቀሳቀሳቸው ውጭ ሌላ የግልግል ዳኛ እንዲተካ ጥያቄ ማቅረብ የለባቸውም በሚል ምክንያት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 318/5/፣ 317/1/ እና 319/1/ ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ተጠሪ ሌላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኛ ተተክቶ መዝገቡ ይንቀሳቀስልኝ ሲሉ ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በዋላ የስር ፍ/ቤት ብይን ተሽሮ የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አነጋግሮ ምትክ የሽምግልና ዳኝነት ጉባኤ እንዲያቋቁም በሚል ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 15 ቀን 2002ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የሽምግልና ጉባኤ አበል በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ክስ ለማቅረብ ከሚጠየቀው የዳኝነት ገንዘብ የተለየ ነው፡፡ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ የተከፈተው መዝገብ የተዘጋው በአበል ያለመክፈል ብቻ አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች ዘርዝረው ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የሽምግልና ጉባኤው የአበል መጠንን አስመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ በስራ ሒደት እንደተሰጠ ውሳኔ ስለማይቆጠር ተጠሪ ይግባኝ ማለት አያስፈልጋቸውም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው ሐምሌ 19 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ 3 ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በ8/02/03 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ የግልግል ዳኝነት የሚቋቋምበት አይነተኛ ዓላማ ተከራካሪዎቹ ወገኖች ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት በመሄድ የሚያጠፉትን ጊዜና ገንዘብ ለማስቀረት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ጉባኤው የሚቋቋመውም በተከራካሪ ወገኖች ስምምነት ሲሆን ተከራካሪዎቹ ባላቸው የመዋዋል ነፃነት ጉዳያቸውን ከፍርድ ቤት ውጪ በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የሚስማሙት ሁኔታ መኖሩ በራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ የተቋቋመው ጉባኤ ጉዳያቸውን በተገቢው ጊዜና በአነስተኛ ወጪ ለመወሰን ይችላል የሚል እምነት ኑሯቸው ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በሕጉ አግባብ በተደረገ የግልግል ስምምነት መሠረት የግራ ቀኙ ጉዳይ /ክርክር/ የግልግል ዳኛ መመልከት ከጀመረ በኋላ ሊከተል የሚገባው ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት ስለመሆኑ የፍ/ህ/ቁጥር 3345 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 317/1/ ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ የግልግል ዳኛ ክርክሩን መምራት ያለበት በተቻለ መጠን የመደበኛ ዳኝነት አካሄድን ተከትሎ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መንፈስ የግልግል ዳኝነት አካሄድ የመደበኛ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድን መከተል ያለበት ቢሆንም እንደመደበኛ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድ የጠበቀ ወይም ሁል ጊዜ ጥብቅ የሙግት ሥርዓትን ተከትሎ ሊሆን የማይገባ መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 318/5/ ድንጋጌ ሲታይ የግልግል ጉባኤ ጉዳዩን ለማየት ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ያህል መወሰን የሚችል መሆኑን ያሳያል፡፡ ጉባኤው ይህንን አይነት ትዕዛዝ ጉዳዩ መታየት ከመጀመሩ በፊት ወይም በኋላ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን ድንጋጌው ያስገነዝባል፡፡ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ጉባኤው ተከራካሪ ወገኖች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይሰማሙበትን የአበል መጠን እንዲከፍልሉ የሚል ትዕዛዝ ቢሰጥ በትዕዛዙ ላይ ተቃውሞ ያለው ተካራካሪ ወገን ያለው መፍትሔ ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡ አንድ ሰው በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ጉዳይን ፍርድ ቤት ይዞ ሲቀርብ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መክፈል ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 215፣ ከ467 እስከ 479 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ የዳኝነት አገልግሎት መክፈል የማይችል ሰው ክስ ለማቅረብ የሚችልበት አግባብ ስለመኖሩም ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ አንድ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ለመክፈል የማይችል ሰው በደሃ ደንብ ክስ ለማቅረብ የሚችል ሲሆን ለመክፈል አቅም እያለው ክስ ያቀረበ መሆኑ ከተረጋገጠ ግን መዝገቡ እንደሚዘጋ፣ የተዘጋ መዝገብ ደግሞ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ/ገንዘቡን/ ለመክፈል ዝግጁ እስከሆነ ድረስ የሚንቀሳቀስለት መሆኑን የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡

የግልግል ጉባኤ ከሚቋቋምበት ዋነኛ ዓላማ፣ ጉባኤው ሊከተለው ከሚገባው ሥርዓት እና ስለ ዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የተመለከቱት ደንቦች መሠረት ሲሆኑ አንድ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይለት የተስማማ ሰው በአካሄዱ ቅሬታ እያለው ጉዳዩ በተቋቋመው ጉባኤ እንዲታይ ማድረግ ተገቢነት አለው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ጉባኤው ጉዳዩን ለማየት ከመጀመሪያውኑ አበሉን መወሰን የሚችል ሲሆን በዚሁ ደረጃ የሚሰጠው ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ የክርክሩ አካል አይደለም ለማለት የማይቻል ቢሆንም በተያዘው ጉዳይ ከላይ ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮችና የሕጉ ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በአመልካች መብት ላይ መሠረታዊ የመብት መጣበብ ያስከተለ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ጉዳዩ በምትክ የጉባኤ አባላት እንዲታይ ማድረግ በአመልካች መብት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ውጤት የሌለው ከመሆኑ አንፃር ስንመለከተው በውጤት ደረጃ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ውጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህዳር 2 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወጋገን ባንክ (አ.ማ) - ኤፍሬም ፈቃዱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሀብቶም ረዘነ ከጠበቃ ፊሊጶስ አይናለም ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ በብድር የተወሰደ ገንዘብን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ በብድር የወሰዱትን ብር 200,000 እና ይህ የብድር ገንዘብ የሚወልደው ወለድ በድምሩ 306,185.16 (ሶስት መቶ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ብር ከአስራ ስድስት ሣንቲም) እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርበው አመልካች መኪና ሸጧል እንደዚሁም ወለዱ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2024(ረ) ይታገዳል የሚሉ መከራከሪያዎችን ያቀረቡ ሲሆን በዋነኛነት እዳዬን ሰርዞልኛል ምክንያቱም በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በደረሰብኝ ጉዳት ለመክፈል እንደማልችል ተረጋግጧል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ በማስረጃነት የጠቀሱት የውስጥ መዛግፊያ ነው፡፡ እዳው አልተሠረዘም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አመልካች ተጠሪ የተበደሩትን ብድር የሰረዘላቸው በመሆኑ ዕዳውን ተጠሪ (ተከሳሽ) የመክፈል ሀላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነሐሴ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተጠሪ ዕዳ ለጊዜው በተንጠልጣይ ሂሳብ እንዲቆይ (written off) አደረግን እንጅ እዳው የተሰረዘ መሆኑን ለተጠሪ አልገለፅንለትም፡፡ አንድ ዕዳ በተንጠልጣይ ሂሳብ መያዝ (written off) እና አንድን የብድር ዕዳ ሙሉ በሙሉ መሠረዝ የተለያዩ ናቸው፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን ለማስረዳት ያቀረብናቸውን ማስረጃዎች በተሟላ መልኩ አላየልንም፡፡ ባንኩ ለተጠሪ ያበደረውን ብድር ሙሉ በሙሉ ምህረት አላደረገም፡፡ ተጠሪ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት የተበደሩትን ብድር እንዳይከፍል የፈጠረባቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰናክል የለም ስለዚህ ተገቢውን ማጣራት ሣያደርግና ሙያዊ በሆኑ ነገሮች የባለሙያ አስተያየት ሣይሰማ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት እኔ በምኖርበት አካባቢ ጦርነት የነበረ መሆኑና በጦርነቱም ውድመት የደረሰ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ዕውቅና ሊሰጠው የሚገባው ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ብድር ሲያበድር በመያዣነት ይዞት የነበረውን ተሽከርካሪ በራሱ ፈቃድ በግንቦት ወር 1997 ዓ.ም ነፃ በማድረግ ለቆታል፡፡ ይህም ዕዳውን በምህረት መልክ መሠረዙን የሚያሣይ ነው፡፡ በባንኮች ዝርዝር ፖሊሲና ፕሮሲጀር መሠረት ሁለት አይነት የብድር ዕዳ ሥረዛዎች መኖራቸውን ለመረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው “written off” የሚባለው ሲሆን ሁለተኛው ለዘለቄታው ተበዳሪውን ላለመጠየቅ የሚደረግ የዕዳ ሥረዛ ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ያደረገው ሁለተኛውን አይነት የዕዳ ስረሳ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ እኔ ያደረክሁት (written off) እንጅ ለዘለቄታው ተበዳሪው ብድሩን እንዳይከፍልና እንዳይጠየቅ ምህረት አላደረግሁም በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በዕሑፍ የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ችሎቱም የአመልካችንና የተጠሪን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ በቃል ክርክሩም አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት አመልካች የተጠሪን ዕዳ በተንጠልጣይ ሒሳብ እንዲያዝ (written off) ነው ያደረገው ወይስ ተጠሪ በዕዳው እንዳይጠየቅ ለዘለቄታው እዳውን በመሰረዝ ምህረት አድርጎለታል በሚለው ነጥብ ላይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እኛም በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነውን ይህንን ጭብጥ በአግባቡ ለመፍታት አመልካችና ተጠሪ የሚያቀርቡትን ማብራሪያና ደጋፊ ጽሑፎችን መመልከቱ ብቻ በቂ እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡

አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ነጥብ የባንኮች የዕዳ አመዘጋገብ እና የዕዳ ሥረዛን “ፕሮሲጀርና” አሰራር የሚመለከትና የሙያ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነጥብ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎች የሚከራከሩበት ጉዳይ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሆኖ በሚያገኝበት ሠዓት የልዩ አዋቂ ምስክር በመሰየም ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ማድረግ እንደሚገባው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አመልካች ግንቦት 12 ቀን 1997 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ዕዳውን ከእኔ በማናቸውም ጊዜ ላለመጠየቅ ሙሉ በሙሉ በመሠረዝ ምህረት አድርጎልኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር የባንክ ባለሙያዎችን በመመደብና አስፈላጊም ከሆነ ከብሔራዊ ባንክና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስለ ባንኮች የዕዳ አመዘጋገብና የእዳ ሥረዛና የምህረት ፕሮሲጀር ተገቢው ሙያዊ ማብራሪያ እንዲሰጥ በማድረግ አመልካች የተጠሪን ብድር በተንጠልጣይ ሒሳብ ነው የመዘገበው (written off) ነው ያደረገው ወይስ አመልካች የተጠሪን ዕዳ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ላይጠይቅ ሙሉ በሙሉ በመሠረዝ ምህረት አድርጓል የሚለውን ጭብጥ መወሰን ሲገባቸው በጉዳዩ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማብራሪያ ሣይሰሙ አመልካች የተጠሪን ዕዳ ሰርዟል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል የምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪን የብድር ዕዳ በተንጠልጣይ ሒሳብ ነው የያዘው (written off) ነው ያደረገው ወይስ ዕዳውን በማናቸውም ጊዜ ላይጠይቅ ሙሉ በሙሉ በመሰረዝ ምህረት አድርጓል በሚለው ነጥብ ላይ የልዩ አዋቂ በመመደብና በማስመርመር የልዩ አዋቂ የሚያቀርበውን ሙያዊ አስተያየት ከሰማ በኋላ እንድወሰን ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 49502

ህዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ የኢት/ያ የእህል ንግድ ድርጅት አልቀረቡም

ተጠሪዎች፣ 1ኛ. መርዕድ ተፈራ

2ኛ አያሌው መኮንን ቀረቡ

3ኛ ስለሺ ኃ/ሚካኤል ቀረቡ

4ኛ ወ/ሪት ዙልፋ ከድር አልቀረበችም

5ኛ አቶ ጣሰው ነገሥ ቀረቡ

6ኛ አቶ አሰፋ ቱሉ ጠበቃ አቶ ወንድአወክ አየለ ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁን አመልካች ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6ኛ የተጠቀሱት ሠራተኞቹ በሥራቸው ምክንያት የብር 154,334.67/100 የገንዘብ ጉድለት አድርሶውብኛል በማለት እያንዳንዱ ሠራተኛ ኃላፊ ሊሆን ይገባዋል የሚልበትን ምክንያት በመጥቀስ ገንዘቡን እንዲተኩለት ባቀረበው ክስ መነሻ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቻለሁ በማለት ተጠሪዎች ኃላፊ ሊሆኑ የሚገባበት ምክንያትና ማስረጃ አልተገኘም በማለት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነትን አላገኘም፡፡

አመልካች የጉዳዩ አካሄድ እንደ መሣት አመራር ሥርዓቱ ባለመከናወኑ ምክንያት ተገቢውን ዳኝነት አላገኘም የሚለውን የመከራከሪያ ነጥብ በዋነኛነት በመጥቀስ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎችም በሥር የተሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም የሚሉበትን ምክንያት ከመግለፅ ጋር ውሣኔው እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል እንደተመለከትነውም የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ከቀረበው የአዲት ምርመራ ውጤት በተጨማሪ የአዲት ምርመራ ሥራውን ያከናወኑት ባለሙያዎች ሙያዊ የምስክርነት ቃል እንዲሰጡለት በማስረጃነት የቆጠራቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑንና ነገር ግን እነዚህ የሰው ማስረጃዎች ሳይሰሙ ታልፎ ውሣኔ በመስጠቱ ፍትህ እንደተጓደለበት ገልፆ ቅሬታ ሲያቀርብ፤

በተጠሪዎች በኩል በሰበር ከቀረበው ክርክር መካከል እነዚህ አዲተሮች ከአዲት ምርመራ ሰነዱ በተለዩ ምን ሊያስረዱ ይቻላሉ? አንደኛውም አዲተር ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል ለመስማት የሚቻልበት መንገድ የለም በማለት ከመከራከራቸው ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በእርግጥም የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ማስረጃዎች በሙሉ አለመሰማቱን አረጋጋጭ ነው፡፡

አመልካች በሰው ማስረጃነት የሙያ ምስክርነት እንዲሰጡለት የጠቀሳቸው አዲተሮች ሳይሰሙ የታለፈበት ምክንያት ምን እንደሆነ በውሣኔው ላይ ተገልፆ ባይገኝም ከላይ እንደተመለከተው የምስክርነት ቃል አለመስጠታቸውን ከውሣኔው ይዘት መረዳት ችለናል፡፡

እነዚህ የሙያ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ጉዳዩን በማስረዳት ረገድ የሚኖረው የማስረዳት ብቃትም ሆነ አግባብነት ቃላቸውን ከሰጡ በኃላ የሚታወቅ በመሆኑ ተጠሪዎች በሰበር ደረጃ ባቀረቡት ክርክር እንደገለፁት የአዲት ምርመራ ውጤቱን ከያዘው ሰነድ የተለየ አያስረዱም ብሎ ከወዲሁ መደምደም የማይቻል ከመሆኑም በላይ አንድ ተከራካሪ ወገን ያቀረበውን ክርክር ለማስረዳት የማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት መርህ ካለገደው ወይም ካልከለከለው በቀር ዘርዝሮ ያቀረበውን የማስረጃ በዓይነትም ሆነ መጠን የማስረዳት መብት ያለው በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የእነዚህን ምስክሮች የሙያ ምስክርነት ቃል ሳይቀበል በዝምታ አልፎ ውሣኔ መስጠቱ የሙግት አካሄድ ሥርዓትን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም እንዲሁም ጉድለቱ በጥፋት ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑን ለማስረዳት የግምት መነሻ ይሆናል የተባለውና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 ከፖሊስ ኮሚሽን የቀረበ የተባለው በቁጥር 272179 የተሰየመው ሰነድ ቀርቦ ስለመታየቱም ሆነ ታይቶ ተቀባይነትን አጥቶ ስለመሆኑ የውሣኔው ይዘት የሚያስረዳው ነገር እንዳሌለ ተረድተናል ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ከውሣኔ ለመድረስ አመልካች ያቀረበውን ክርክር በማስረጃ የማስረዳት መብቱን ሙሉ በሙሉ ጠብቆ ያከናወነ ስለመሆኑ የውሣኔው ይዘትም ሆነ በሰበር ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ስለማያስረዳ የጉዳዩ አካሄድ ሙሉ የክርክር አመራር ሥርዓትን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 01217 በ10/11/2000 እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 72047 በሐምሌ 07 ቀን 2001 የሰጠው ዳኝነት ተሽሯል፡፡

2. የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 01217 የተመዘገበውን መዝገብ እንደገና አንቀሳቅሶ በአመልካች በኩል ማመልከቻው ላይ የጠቀሰውን ጉዳይ ለማስረዳት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 መሠረት አስቀድሞ ዘርዝሮ ያቀረበውን ማስረጃ በሙሉ ሰምቶና አይቶ በጉዳዩ ላይ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህዳር 03 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ አበበች በጅጋ - ጠበቃ አፈወርቅ ደጀኔ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሰብለወንጌል አበበ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ - ጠበቃ ፋንታሁን አበራ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት የተሠጠ ውሳኔ ተነስቶ ተከሳሹ ባለበት የሚታይበትን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አግባብን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ የቤት ሽያጭ ውል ተደርጓል የተባለው እንዲፈርስና ቤቱንም እንዲረከቡ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በመሰረቱት ክስ የአሁኑ አመልካቾች በሌሉበት ታይቶ አመልካቾች በቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 13 ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 1099 የሆነ ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የሚል ውሳኔ ተጠሪ አግኝተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካቾች ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ክርክሩ ባሉበት እንዲታይላቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች የስር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ለ1ኛ አመልካች የጋዜጣ ጥሪ የተደረገው ያላግባብ መሆኑን 2ኛ ተጠሪም በሚኖሩበት ቤት መጥሪያው ተለጥፏል የተባለው ባግባቡ አለመሆኑን ዘርዝረው መጥሪያው በአግባቡ ደርሷል ለማለት ስለማይቻል መጥሪያው እንደአልደረሰ ተቆጥሮ በሌለንበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ክርክሩ ባለንበት እንዲካሄድ ይደረግልን የሚል ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ተጠሪ በአመልካቾች አቤቱታ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ ክርክሩን መርምሮ የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች ይግባኝን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 02 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ለ1ኛ አመልካች የጋዜጣ ጥሪ የተደረገው የመጥሪያ አደራረስ ቅደም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከተልን ባልጠበቀ ሥነ ሥርዓት በመሆኑና ይህም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስለመጥሪያ አደራረስ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን የሚፃረር በመሆኑ አመልካች በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም ተብሎ የተወሰነው ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ትእዛዝ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች ወደ ጉዳዩ ገብተን እንከራከር በሚል ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ የሆነው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም መጥሪያው ለአመልካቾች የደረሰው በሥነ ሥርዓቱ የተቀመጡትንና የሰበር ችሎቱም የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ባገናዘበ መልኩ መሆኑን በማረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የ1ኛ አመልካች ጠበቃም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው አቤቱታ ያቀረቡት መጥሪያ በተገቢው ስርዓት ቅደም ተከተሉን ተከትሎ አልደረሰም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው መጥሪያውን አመልካች ቤት ድረስ ተዟዙ እማኞች ባሉበት ማግኘት ሳይቻል ቀርቷል፣ ይህም ብቻ ሳይሆን መጥሪያው በአመልካች ቤት ላይ ተለጥፎ ነበር፤ ሊቀርቡ ባለመቻላቸው በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸዋል፡፡ ይህም ሆኖ ሳይቀርቡ ቀርተዋል፣ አንድ ሰው በአካል ተፈልጎ ካልተገኘ በመኖሪያው ላይ መጥሪያ ተለጥፎ እና በጋዜጣ ተጠርቶ ካልቀረበ መጥሪያው እንደደረሰው እንደሚቆጠር በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል፣ አመልካች ታምሜ ወደ ሌላ ቦታ ሄጀ ነበር በማለት የገለፁት ከ10/11/2001 ዓ.ም በኋላ ሲሆን ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተወሰነው ከመሄዳቸው በፊት ነው ስለዚህ መጥሪያው ደርሷቸው እንደነበር ፍርድ ቤቱ ስለተረዳና በቂ ምክንያትም ስላላቀረቡ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ችሎትም የስር ፍርድ ቤት ዋናውን ጉዳይ የመራበትን የኮ/መ/ቁጥር 148744 አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ መዝገቡ ሲታይም አመልካች መልሳቸውን ከመዝገቡ ጋር በ17/10/2001 ዓ.ም እንዲያያይዙ እና በ19/10/2001 ዓ.ም ለቃል ክርክር እንዲቀርቡ በ02/10/2001 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱን፣ የክፍሉ ቀበሌ ደንብ አስከባሪዎች ነን የሚሉ ሁለት ግለሰቦች በ09/10/2001 ዓ.ም በዓፉትና ማህተም በሌለው ደብዳቤ ቁጥር 1099 ወደሆነው ቤት ሄደን ነበር፣ ወ/ሮ አበበች በጅጋ በቤቱ ውስጥ እንደማይኖሩና የት እንደሚኖሩም የሚያውቅ ሰው አለመኖሩን ጠይቀን የተረዳን መሆናችንን እናረጋግጣለን በማለት ለፍርድ ቤቱ ማረጋገጫ የላኩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ መገኘቱን የተጠሪ ጠበቃ በ16/10/2001 ዓ.ም በተጻፈ የቃለ መሐላ ማመልከቻ አንደኛ አመልካች በቤቱ ውስጥ አይኖሩም በሚል መጥሪያ ለማድረስ አለመቻሉን ገልጸው በጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲጠሩላቸው መጠየቃቸውን 1ኛዋ አመልካች በጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲጠሩ ታዝዞም በ8/11/2001 ዓ.ም ስላልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ መታዘዙን ክሱ ቤት ለመረከብ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 36(4) መሰረት ቤቱን የያዘውን ሰው በተከሳሽነት መካተት አለበት ተብሎ የተሻሻለው ክስ እንዲቀርብ ታዞ ይኸው የተሻሻለው ክስ ለአመልካቾች ተልኳል ተብሎ መመዝገቡን የተላከው መጥሪያ ከስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት መዝገብ ሲታይም በከሳሽ የፍርድ ባለመብት ዶ/ር ተስፋዬ አካሉና በተከሳሽ የፍርድ ባለእዳ ወ/ሮ ሰብለወንጌል ታደሰ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የሚያወሳ መሆኑንና "ሰዎችን ስላሳገኘን በቤቱ በራፍ ላይ የለጠፍን መሆኑን እንገልፃለን" የሚል ይዘት የያዘ ሁኖ የ1ኛዋን አመልካች ስም ግን የሚጠቅስ አለመሆኑን መጥሪያው በመኖሪያ ቤቷ ላይ ተለጥፏል የተባለችው ሁለተኛ አመልካች ወ/ሮ ሰብለወንጌል ታደሰ በሚል ስም ሲሆን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሰረት ጥያቄውን አልቀበልም ያለው ወ/ሮ ሰብለወንጌል አበበ በሚል መዝግቦ መሆኑን ከመዝገቡ ተረጋግጧል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ዋናውን ጉዳይ ከመራበት መዝገብ ከተረጋገጡት፣ ከላይ ከተገለፁት ፍሬ ነገሮች በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው አንደኛ አመልካች በቅድሚያ በአካል ሊሰጣቸው የሚገባን መጥሪያ ባግባቡ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ እና በማትኖርበት ቤት ላይም ቢሆን የሷን ስም የሚጠራ መጥሪያ በተገቢው አካል ተለጥፏል ለማለት የማይቻል መሆኑን እንዲሁም ሁለተኛዋን አመልካች በተመለከተ ደግሞ የአባቷ ስም ተለውጦ የፍርድ አፈፃፀም መጥሪያ እንጂ ከተጠቃሹ ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው መጥሪያ አለመለጠፉ በሚገባ መረጋገጡን ነው፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣ፤ በመሰረቱ የመጥሪያ አሰጣጥ ዘዴና ቅደም ተከተሉ እንዲሁም መጥሪያው ለማን እንደሚሰጥ የሚመለከተው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ክፍል ዓይነተኛ ዓላማ ከሆኑት መካከል አንዱ ተከራካሪ ወገኖችን እኩል የመከራከር መብት እንዲኖራቸው በማድረግ ጉዳዩን ፍትሐዊ በሆነ አኳኋን ለመወሰን ማስቻል መሆኑን ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ መጥሪያ የሚደርስበትን ተገቢ መንገድና ለማን መድረስ እንዳለበት ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ መጥሪያ በተገቢው መንገድ ደርሶት ተከራካሪ ወገን ካልቀረበ ወይም መጥሪያን አልቀበልም ካለ ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ስርዓትም በሕጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህም ድንጋጌዎች መካከል አንዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 70(ሀ)፣ 103፣ 104፣ 105፣ 106 እና 107 ስር የተመለከተው ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩ ታይቶ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው መጥሪያው በአግባቡ የደረሰው መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ ወይም ሊገኝ ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ ወይም ሊገኝ ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌዎቹ መጥሪያው በትክክል ያልደረሰው መሆኑ ከተረጋገጠ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ የማይታዘዝ ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 70(ሀ) ድንጋጌ ስር ላይ "መጥሪያው በትክክል መድረሱ" የሚለው ሐረግ መኖሩም የሚያሳየው ስለመጥሪያ አሰጣጥና አደራረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 94 እስከ 110 ድረስ የተመለከቱት ሁኔታዎች በአግባቡ መሟላታቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ ከተሰጠውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሰረት መፍትሔ መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት መፍትሔ ሊጠየቅ የሚችለው አቤቱታ አቅራቢው በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ የጥሪው ትዕዛዝ "በሚገባ ያልደረሰው" መሆኑን በመጥቀስ ይህንኑ ማረጋገጥ ሲችል ነው፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው አንድ ሰው የመከራከር መብቱን እንደተወው የሚቆጠረው መጥሪያው በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓትና ቅደም ተከተል መሰረት ደርሶት ክርክር ያለው መሆኑን እያወቀ ሳይቀርብ ሲቀር ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትሎ አማራጭ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት ከፈጸመ መጥሪያው ለተከሳሹ እንደደረሰ እንደሚቆጠርና በቂና ሕጋዊ ምክንያት ካለው ብቻ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የሚፈቀድ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማንኛውም ውሳኔ መሰጠት ያለበትም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት መጥሪያው መድረሱ በሚገባ የተረጋገጠና የተከሳሽ የመከራከር መብት የተጠበቀ መሆኑ ሲታወቅ ሊሆን ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ከላይ ከስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የሚያሳዩት 1ኛ አመልካችን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ወደ ጋዜጣ ጥሪ የሄደበት አካሄድ ቅድሚያ ሊፈጸም የሚገባውን ሥርዓት በአግባቡ አሟጦ ሳይጨርስና ተገቢ ያልሆነ መግለጫ ስለቀረበለት ከመሆኑም በላይ ክሱ ተሻሽሎ ከቀረበ በኋላም ቢሆን የአመልካቿ ስም ተጠቅሶ መጥሪያው መላኩ ሳይረጋገጥ ነው፡፡ የሁለተኛዋ አመልካችም የአባት ስም ተለውጦ የፍርድ አፈፃፀም መጥሪያ እንጂ ከዋናው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው መጥሪያ ያልተለጠፈላቸው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በግልፅ ያሳያል፡፡ የጋዜጣ ጥሪና በተከሳሽ መኖሪያ ላይ በአግባቡ መጥሪያ እንዲለጠፍ ማድረግ ውጤታቸው መጥሪያው እንደደረሰ የሚያስቆጥር የሚሆነው ተከሳሽ መገኘት አለመቻሉ በሚገባ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተገለፁትና በስር ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 148744 የተረጋገጡት ፍሬ ጉዳዮች ለአመልካቾች መጥሪያው እንደሕጉ አነጋገር በሚገባ ያልደረሳቸው መሆኑን የሚያረጋግጡ ሁነው አግኝተናል፡፡ ይህ በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካቾች ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቶ ገብተን እንከራከር ሲሉ ያቀረቡትን ጥያቄ በበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ የሆነው በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕጉ ስለመጥሪያ አደራረስ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ከመከራከር መብት ጋር ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ትእዛዙ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 148744 ህዳር 08 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 86844 ህዳር 23 ቀን 2002 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች በሌሉበት ታይቶ የተሠጠው ውሳኔ ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ የሆነው ስለመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ከመከራከር መብት ጋር ባላገናዘበ መልኩ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካቾች በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 78(2) መሰረት ተነስቶ ባሉበት እንዲታይ ብለናል፡፡
4. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አመልካቾች ባሉበት በመመልከት የግራ ቀኙን ጉዳይ ሠምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የምጥን መንደር መኖሪያ ቤቶች የህብረት ሥራ ማህበር ጠበቃ ዜና ደባሱ ቀረበ

ተጠሪዎች ፡- 1. ወ/ሮ ባየች አይገምት - በሌሉበት

2. ወ/ሮ ሸዋሰገድ አይገምት - በሌሉበት

3. ወ/ሮ ሃና መኰንን - ከጠበቃ ይልማ አቻሜ ጋር ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በሁከት ይወገድ ክስ መነሻነት ክርክር ተካሂዶ የተሰጠውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የተጀመረውን የአፈጻጸም ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው የአሁኑ አመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ መስርቶ ክርክር ከተደረገ በኋላ፣ የፍርድ ባለመብት ሆኖአል፡፡ በውሳኔው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ ሁከት የፈጠሩ መሆናቸውን ስለመረጋገጡ ተመልክቶአል፡፡ አመልካች የአፈጻጸም መዝገቡን ያስከፈተው በውሳኔው መሠረት የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ይዞታውን ለቀው እንዲወጡላት ትዕዛዝ ለማሰጠት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 3ኛ ተጠሪ አፈጻጸም በተጠየቀበት ቦታ ይዞታ ያለኝ እኔ ነኝ በማለት መቃወሚያ በማቅረብዋ የክርክሩ ተካፋይ ልትሆን ችላለች፡፡ አፈጻጸሙን የጀመረው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ በመቀበል እንደውሳኔው እንዲፈጸም ትዕዛዝ ሰጥቶ የነበረ ሲሆን የአሁንዋ 3ኛ ተጠሪ ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ ትዕዛዙ ተሽሮአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ክርክሩ በዚህ ደረጃም ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም የሰበር ችሎቱ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 3 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ የተሰማው እነሱ በሌሉበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደረገው የሥር ፍ/ቤቶች የ3ኛ ተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል የመወሰናቸውን አግባብነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ ባጭሩ እንዳመለከትነው ለአፈጻጸሙ መሠረት የሆነው ውሳኔ በተሰጠበት ክርክር ተጠሪ ተከራካሪ ወገን አልነበረችም፡፡ አመልካች በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው በሕጋዊ መንገድ በያዝኩት መሬት ላይ ሁከት ፈጥረውብኛል፡፡ ስለዚህም ያለ አግባብ የያዙትን መሬት ለቀው ይወጡ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ተጠሪዎች (ተከሳሾች) ስፋቱ በካሬ ሜትር ተለክቶ ለአመልካች በተሰጠው መሬት ውስጥ ገብተዋል በሚል ምክንያት ከሕግ ውጪ የያዙትን መሬት እንዲለቁ ወስኖአል፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን የመሰለ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው መሬቱ በአመልካች የተሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡ 3ኛ ተጠሪ ክርክሩ ውስጥ የገባችው ከዚህ በኋላ ብቻ ሳይሆን መቃወሚያዋን ያቀረበችውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የአፈጻጸም ክርክር በቀጠለበት መዝገብ ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ከሰጡአቸው ውሳኔዎች ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል የሰጡት ውሳኔ እንዳየነው ክርክር የተነሳበት መሬት ለተጠሪ የተሰጠ ነው ወይም የተጠሪ ይዞታ ነው የሚል እንድምታ ያለው ነው፡፡ ይህ ውሳኔ በይዙቱ ሲታይ በአመልካች እና በ1ኛና በ2ኛ ተጠሪዎች መካከል በተነሳው ክርክር መነሻነት የተሰጠውን ውሳኔ የሚሽር ነው፡፡

ጉዳዩ የፍትሐብሔር ክርክርን የሚመለከት በመሆኑ የሚመራው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የክስ አቀራረብን፣ የክርክር አመራርን፣ አወሳሰን እና አፈጻጸምን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዞአል፡፡ በዋናው ክርክርም ሆነ በአፈጻጸም ሂደት መብታችን ተነክቶአል የሚሉ ሦስተኛ ወገኖች መቃወሚያ የሚያቀርቡበት እና መብታቸውን የሚያስከብሩበት ሥርዓት በዚሁ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተካቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሦስተኛ ተጠሪ ለጉዳዩ ሦስተኛ ወገን በመሆንዋ እና መብቱ በአፈጻጸሙ ሂደት ተነክቶአል ብላ በማመንዋ በአፈጻጸም ደረጃ ባለው ክርክር ላይ መቃወሚያ ማቅረብ የሚያስችለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418ን መሠረት በማድረግ ክርክሩ ውስጥ ገብታለች፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም መቃወሚያው የቀረበበትን ሥርዓት በትክክል ቢገነዘቡም፤ አፈጻጸሙ የቀጠለበት መሬት የማን ይዞታ ነው ወይም በመሬቱ ላይ የተሻለ መብት ያለው የትኛው ወገን ነው የሚል የንጥጥር አይነት ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ ፍ/ቤቶቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418 መሠረት የቀረበውን መቃወሚያ ለመወሰን የተከተሉት አካሄድ አግባብነት ያለው ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ የሚሆነውም እዚህ ላይ ነው፡፡

በዋናው ክርክርም ሆነ በአፈጻጸም ሂደቱ መብታችን ተነክቶአል ብለው የሚያስቡ ሦስተኛ ወገኖች መቃወሚያቸውን የሚያቀርቡበት ሥርዓት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ስለመዘርጋቱ ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ በዋናው ክርክር የሚሰጠው ውሳኔ እና በውሳኔው መሠረት ለማስፈጸም የሚደረገው ሂደት የተለያዩ በመሆናቸው በሚቀርቡት መቃወሚያዎች ላይ የሚሰጡት ውሳኔዎችም የተለያዩ ናቸው፡፡ መቃወሚያ አቅራቢው መብቱ የተነካው በአፈጻጸም ሂደቱ ከሆነ ከአፈጻጸም ሂደቱ ጋር የተያያዘ መፍትሄ ነው የሚሰጠው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418 መሠረት በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.419 ተመልክቶአል፡፡ በዚህ መሠረት መቃወሚያው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ በአፈጻጸም የተያዘው ንብረት በከፊል ወይም በሙሉ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ከዚህ አልፎ በአፈጻጸም የተያዘው ንብረት ለአንዱ ወይም ለሌላው ተከራካሪ ወገን ይገባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚል ዳኝነት አይሰጥም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ በዋናው ክርክር የተሰጠውን ውሳኔ የሚሽር ወይም የሚያሻሽል ውሳኔ አይሰጥም፡፡ የዚህ አይነት ውሳኔ መስጠት የሚቻለው ዋናውን ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ ሲቀርብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እራሱን የቻለ የአቀራረብ ሥርዓት እና የክርክር አመራር ሂደት ያለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተገቢው ድንጋጌም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.358 የተመለከተው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ 3ኛ ተጠሪ በዚህ ቁጥር 358 መሠረት ወይም ዋናውን ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ አላቀረበችም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ግን ዋናውን ውሳኔ የሚሽር ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም ፍ/ቤቶቹ የሰጡት ውሳኔ (አቤቱታ የቀረበበት) በሕጉ አተገባበር/አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ.09838 መስከረም 27 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 11818 የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በቀድሞው ውሳኔ መሠረት የተጀመረው አፈጻጸም የሚቆምበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42714

ጎንደር 8 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፍትሕና ሕግ ጉዳዮች ቢሮ - ተስፋዬ ዘመድኩን ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. የሽቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ገ/ማርያም ዋዩሮ ቀረበ

2. አመሃ ጥበቡ ቀረበ

3. በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የቤቶች ማስተላለፍ ጽ/ቤት - ሽምሱ ስሩር ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከቤት ባለቤትነት መብት ጋር ተያይዞ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የሆነው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ በማቅረቡ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ ክስ አቅርቦ ከተከራከሩ በኋላ፣ ክስ ያቀረበበትን ቤት እንዲረከብ ውሣኔ አሰጥቶአል፡፡ አመልካች መቃወሚያ ያቀረበው ቤቱ ከጅምሩ የአስተዳደሩ ሲሆን ዋጋ ተቀብሎ ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፈው በመሆኑ ቀደም ሲል የተሰጠው ውሣኔ መብቴን ይነካል በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን ከመረመረ በኋላ፣ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በዳፊው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች መብቴ ተነክቶአል በማለት ያቀረበው የመቃወሚያ ክርክሩ ሣይሰማ ውድቅ መደረጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች ባቀረበው መቃወሚያ መሠረት የክርክሩ ተካፋይ በመሆን ሊያቀርበው ይችል የነበረውን የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር እንዲያሰማ አልተደረገም፡፡ በሰበር አቤቱታው እንደገለፀው በጉዳዩ ያገባኛል የሚለው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 2/95 እና በአዋጅ ቁ. 4/2000 /እንደተሻሻለ በአንቀጽ 29 መሠረት የተቋቋመ የአስተዳደሩ አስፈፃሚ አካል በመሆኑ ነው፡፡ በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 29/3/ መሠረት የከተማውን አስተዳደርና የነዋሪዎችን መብትና ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር መብት የተሰጠው መሆኑንም በክርክሩ ገልጾአል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 በተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት መቃወሚያ ያቀረበው ለክርክሩ መሠረት ከሆነው ቤት ጋር በተያያዘ ያለውን የከተማውን አስተዳደር የነዋሪዎች መብትና ጥቅም ለማስከበር በሚል እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡

አስቀድሞ የተሰጠውን ውሣኔ ለማስነሣት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችል ወገን በክርክሩ ውስጥ መግባት የሚገባው ሆኖ ነገር ግን ተካፋይ ያልነበረ፤ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድም መብቱን የሚነካበት የሆነ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 ተደንግጎአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች በአስተዳደሩ የአስፈፃሚ አካልነቱ ሊያስጠብቀው የሚገባው የአስተዳደሩና የነዋሪዎች መብትና ጥቅም እንዳለ በመግለጽ መቃወሚያውን አቅርቦአል፡፡ መቃወሚያው የቀረበለት ፍ/ቤት ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ በተደነገገው መሠረት ክርክሩን አልሰማም፡፡ አቤቱታውን ውድቅ ያደረገው ቀደም ሲል በተሰጠው ውሣኔ መብቱ ከተነካ "በሕግ አግባብ ውሣኔውን ከሚያስለውጥ በቀር ... በዚህ ረገድ ሊያቀርበው የሚችለው የመቃወም አቤቱታ ... የለም" የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡ ይህን አይነቱ አካሄድ አግባብ ያለውን የሥነ ሥርዓቱን ድንጋጌ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ አይደለም፡፡ አመልካች ቀድሞ በተሰጠው ውሣኔ መብቱ ተነክቶአል ማለቱ እስከተረጋገጠ ድረስ ውሣኔውን ለማስለወጥ የሚችለው መቃወሚያውን በማቅረብ ነው በፍ/ቤቱ ግንዛቤ ሣያገኝ ቀርቶአል የምንለውም ይህ ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሥነ - ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 71179 ህዳር 10 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 75281 ጥር 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የመቃወሚያ አቤቱታ ተቀብሎ በጉዳዩ ሥረ ነገር ግራ ቀኝ ወገኖችን አከራክሮ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፣ ወ/ሮ አበባዬ አቢ ደራ ወርቅ ጠበቃ ተስፋዬ ርቀቱ ቀረበ

ተጠሪ፣ ይገረም ፈዬ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመር የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ከተወሰነ በኃላ ክሱን ሲመሠረት የከፈለውን የዳኝነት ገንዘብ ተጠሪ ትተካለት የተባለው በአግባቡ ነው ወይ? የሚል ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ተጠሪ ክስ የመሠረተው ብር 30,000 ግምት ያለው ባህር ዛፍ ቆርጣ ስለወሰደችብኝ ገንዘቡን ትከፍለኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው አመልካች ለክሱ በሰጠችው መልስ ክሱን በመካድ የተከራከረች ሲሆን ፍ/ቤቱም የአመልካችን ክርክር በመቀበል የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ይግባኙን ለሚሰማው የበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ለክሱ ምክንያት የሆነው ባህርዛፍ ስለመቆረጡ በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ አትከፍልም በማለት በአንድ በኩል ሲወስን በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ለዳኝነት የከፈለውን ብር 1718.50 አመልካች ትተካለት ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር በጭብጥነት ከተያዘው ነጥብ አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየው ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተቀባይነትን አላገኘም፡፡ ክሱ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በመደረጉም በክሱ የተመለከተውን ብር 30,000 አመልካች ልትከፍልህ አይገባም ተብሎ ተወስኖአል፡፡ ለዳኝነት ተከፈለ የተባለው ብር 1718.50 ሊከፈል የቻለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 215 መሠረት ነው በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተለየ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክሶች ሁሉ ዳኝነት ሊከፈልባቸው እንደሚገባ በተጠቀሰው ቁጥር 215/1 አመልክቶአል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የቻልነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የከሣሹ ወገን እንደሆነ ነው በእርግጥ በክርክር ወቅት ወይም ክርክሩን ለማካሄድ የሚወጡ ወጪዎች ስለወጪና ኪሣራ በሚመለከት በተደነገገው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በስምንተኛው መጽሐፍ ሥር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር እየታዩ በየትኛው ተከራካሪ ወገን እንደሚሸፈኑ በፍ/ቤቱ ውሣኔ የሚሰጥበት ሁኔታ እንዳለ ይታወቃል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ ቁ 462 እንደተመለከተው በሌላ አኳኋን በግልፅ ካልተደነገገ በቀር በክሱ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሣራ የትኛው ወገን ሊከፍለው እንደሚገባ ፍ/ቤቱ ተገቢ በመሰለው ሁኔታ ሊወሰን ይችላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ያለአግባብ በአመልካች ላይ ክስ መመስረቱ ተረጋግጦ ጥያቄው ውድቅ እንዲሆን ከመወሰኑ አልፎ በአመልካች በኩል የተፈጸመ ኪሣራ ሊያስከፍል የሚችል ድርጊት /ጥፋት/ ስለመኖሩ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ አልተመለከተም ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ለተጠሪ ኪሣራ የምትከፍልበት የሕግ አግባብ አይኖርም ሕግ ሳይፈቅድ ረቺ የሆነውን ወገን ለተረቺ ኪሣራ እንዲከፍል መወሰን ደግሞ ሕጉን በተሳሳተ ሁኔታ መተረጎም ወይም መተግበር ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በጋምቤላ ሕዝቦች ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ28/07/2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የዳኝነት ገንዘቡን እንድትተካ የምትገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ 47960

ታህሣሥ 12 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ታከለ ባልቻ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አዜብ ፀጋዬ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሱማሌ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ዕቃንና ሰውን በየብስ ለማጓጓዝ በተደረገ ውል ምክንያት ለደረሰ ጉዳት ሊከፈል የሚገባውን የካሣ መጠን የሚመለከት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት የመለያ ቁጥሩ 2612 የሆነ ሻርኘ የፎቶና የፊልም ማባዣ ማሽን ከሻርኘ ጀኔራል ትሬዲንግ ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ገዝቼ ንብረትነቱ የተከሳሽ/የአሁኑ አመልካች/ የሆነ የመለያ ቁጥሩ 3-12334 አይሱዙ መኪና እኔንና ዕቃውን ጅጅጋ እንዲያደርስ ተዋውለን ዕቃውን ጭኖ ወደ ጅጅጋ ስንጓዝ ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. ከአዋሽ አስር ኪሎ ሜትር ዕርቀት ከምትገኘው "መድን" ተብሎ ከሚጠራው መንደር አካባቢ መኪናው በመገልበጡ የፊልምና የፎቶ ማሽን ወድሟል፡፡ ስለሆነም በአደጋው ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር ማሽኑ በመውደሙ የደረሰብኝን ኪሣራ እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአደጋው እግሬን የተሰበርኩ በመሆኑ ለደረሰብኝ ጉዳት ካሣ ብር 30,000/ሠላሳ ሺህ ብር/ ለህክምና ያወጣሁትን ብር 40,000/አርባ ሺህ ብር/ እና በመታመሜ ምክንያት የቀረብኝን ገቢ ብር 30,000/ሠላሳ ሺህ ብር/ በድምሩ ተከሣሽ/የአሁኑ አመልካች/ ብር 300,000/ሦስት መቶ ሺህ ብር/ እንዲከፍለኝ በማለት ተጠሪ ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርበው ማሽኑ እየሠራ ነው፡፡ ከሣሽ/ተጠሪ/ ለህክምና ብር 40,000/አርባ ሺህ ብር/ ያወጡ መሆኑን ያቀረቡት ማስረጃ የለም ማሽኑ አዲስ ወይም ያገለገለ መሆኑ አልተረጋገጠም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት የዕቃና ሰው መጓጓዝ ውል መሠረት ከሳሽ/ተጠሪ/ ማሽኑን ጭነው ወደ ጅጅጋ ሲሄዱ አደጋው የደረሰ መሆኑን ተከሳሽ/አመልካች/ ያመኑ መሆኑንና የሚያከራክረው መሠረታዊ ጭብጥ የካሣው መጠን መሆኑን በውሣኔው ከገለፀ በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥሩ 2612 የሆነው ሻርኘ የፎቶና የፊልም ማባዣ ማሽን ተጠሪ ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የገዙት መሆኑን የሚያረጋግጥና ማሽኑ የወደመ መሆኑን በመግለፅ ሻጩ ሻርኘ ጀኔራል ትሬዲንግ ማሽኑን ካየ በኋላ በፅሑፍ እንዳረጋገጠ በመጥቀስ፣ ጉዳቱ በድንገተኛ አደጋ የደረሰ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ ይክፈል ለህክምና፣ ለጉዳት ካሣና ተጠሪ ለቀረበት ገቢ ብር 54,00/ሃምሣ አራት ሺህ ብር/ ተከሳሽ ለከሳሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሻርኘ ጀኔራል ትሬዲንግ ማሽኑን ከተረከበና ካየ በኋላ በማሽኑ ላይ የደረሰበት ጉዳት የለም ብለው በቃል ሲናገሩ ሰምተናል የሚል የአመልካችን ሁለት ምስክሮች ቃል ሰምቷል፡፡ ከዚያ በኋላ አመልካች ማሽኑ ጉዳት አልደረሰበትም ስለዚህ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ እንድከፍል የሰጠው ውሣኔ አላግባብ ነው በማለት ውሣኔውን አሻሽሎ አመልካች ለተጠሪ ብር 25,000/ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ለህክምና ለደረሰባት ጉዳት ካሣ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የፎቶና የፊልም ማባዣ ማሽኑ ብልሽት እንደደረሰበት የቀረቡት ማስረጃ ሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርበው የምስክርነት ቃል በሰጡ ሁለት ምስክሮች አረጋግጫለሁ፡፡ አደጋው የደረሰው ሹፌሩን ሽፍቶች ሊያስገድዱት መሀል መንገድ ውስጥ በመግባታቸውና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በመሆኑ ለደረሰው ጉዳት ሃላፊ ነህ መባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት የወሰነው የካሣ መጠን የንግድ ህግ ቁጥር 597ን የሚቃረን ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንዳለ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ማሽኑ የወደመ መሆኑ በፅሑፍ ከተገዛበት ድርጅት የተሰጠን ማስረጃ እያለ ስለ ማሽኑ ምንም አይነት ሙያ በሌላቸው ሁለት ምስክሮች ቃል አስተባብያለሁ በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት የላኑሱትን መከራከሪያ ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ነው አደጋው የደረሰው በማለት የቀረቡት ክርክር በህግ በኩል ተቀባይነት የሌለውና በማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ሰኔ 20 ቀን 2002 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የካቲት 1 ቀን 2002 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ለተጠሪ መክፈል ያለበት የካሣ መጠን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ውሣኔ ለመስጠት ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ዋጋ ያለውን ሻርኘ የፎቶና የፊልም ማባዣ ማሽን ከአዲስ አበባ ወደ ጅጅጋ ለማድረስ ዋጋ ከፍለው በአመልካች ንብረት በሆነው መኪና ላይ የጫኑ መሆኑና ንብረትነቱ የአመልካች የሆነው መኪና የመገልበጥ አደጋ የደረሰበት ስለመሆኑ አመልካችና ተጠሪ የማይካካዱበት ነጥብ ነው፡፡ ይኸም አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪን ዕቃ በየብስ ትራንስፖርት በማጓጓዝ፣ ከመድረሻው ሥፍራ ማለትም ጅጅጋ ከተማ ለማድረስ፣ ተጠሪ በበኩላቸው የትራንስፖርት ግልጋሎት ክፍያ ለመክፈል ውል የነበራቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። አደጋው ከደረሰ በኋላ በአመልካች መኪና ላይ ተጭኖ የነበረውን ማሽን ተጠሪ ከገዙበት ሻርኘ ጀኔራል ትሬዲንግ ወስደው ለማሣየት በመስማማት የፎቶና የፊልም ማባዣዮያ ማሽኑን ለሻርኘ ጀኔራል ትሬዲን ወስደው ያስረከቡ መሆኑ በተጠሪም ሆነ በአመልካች በኩል በቀረበው ክርክር ተገልጿል።

የከፍተኛ ፍርድ ቤት አደጋው ስለደረሰበት ማሽን ዋጋ፣ እና አጠቃላይ ባህሪይ በማሽኑ ላይ ስለደረሰው ጉዳይ የሚያውቀው ሻርኘ ጀኔራል ትሬዲንግ ማሽኑ በአደጋው ምክንያት በደረሰበት ጉዳት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ የወጣ መሆኑን በፅሑፍ የሰጠውን ማረጋገጫ በመቀበል፣ አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ/ እንዲከፍል ወስኗል። የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሻርኘ ጀኔራል ትሬዲንግ በማሽኑ ላይ ስለደረሰው ጉዳት ማሽኑን ከመረመረ በኋላ የሰጠው የሙያ አስተያየት ታዓማኒነት የለውም የሚል ከሆነ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136(1) በሚደነግገው መሠረት ስለማሽኑ ልዩ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በመመደብ እንዲመረመር ማድረግ ይገባው ነበር። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ስለ ማሽኑ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ድርጅት ማሽኑን ከአደጋው በኋላ መርምሮ በፅሑፍ የሰጠውን የሙያ ማረጋገጫ ማሽኑን ለሻርኘ ጀኔራል ትሬዲንግ ስናደርስ ማሽኑ ደህና ነው በማለት የድርጅቱ ሠራተኞች ሲናገሩ ሰምተናል የሚሉ ስለ ማሽኑ ልዩ ዕውቀትና ሙያ የሌላቸው ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመቀበል በሻርኘ ጀኔራል ትሬዲንግ በማሽኑ ላይ ስለደረሰው ጉዳት የቀረበውን የሙያ ማረጋገጫ ውድቅ ማድረጉ፣ ልዩ ዕውቀትና ክህሎትን መሠረት በማድረግ አንድ ጉዳይ ተመርምሮ የተሰጠ የሙያ አስተያየትን ለማስተባበል የሚቻለው በጉዳዩ የተሻለ የሙያ ዕውቀትና ክህሎት ያለው ባለሙያ ጉዳዩን መርምሮ በሚያቀርበው የሙያ አስተያየት "ነው" የሚለውን የማስረጃ ህግ መርህና የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136(1) ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘትና መንፈስና ዓላማ ጋር የማይጣጣም ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሙያ ምርመራ በማድረግ የቀረበን ማረጋገጫ መሠረት በማድረግ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሻርኘ ጀኔራል ትሬዲንግ ሠራተኞች ማሽኑ ደህና ነው በማለት ሲናገሩ ሰምተናል የሚሉ ሁለት ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግ መሻሩ ስህተት ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ ስላገኘነው አመልካች በዚህ በኩል ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም።

አመልካች አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ለሥር ፍርድ ቤት ያልቀረበና በይግባኝና በሰበር ደረጃ ያላነሱት በመሆኑ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም የመለያ ቁጥሩ 2612 የሆነው የተጠሪ ማሽን ጅጅጋ ለማድረስ ዋጋ ተቀብሎ ከጫነ በኋላ የማሽኑ ደህንነት በተጠበቀበት ሁኔታ ያላደረሰና መንገድ ላይ በደረሰው አደጋ ማሽኑ መሉ በሙሉ ከአገልግሎት ውጭ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ እንዲከፍል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማፅናቱ ዕቃን በየብስ ትራንስፖርት ስለማጓጓዝ የወጡትን የንግድ ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ በመሆኑ የአመልካችን ክርክር አልተቀበልነውም።

2. አመልካችና ተጠሪ የዕቃ ማጓጓዣዮያ ውል ብቻ ሣይሆን ተጠሪን ከአዲስ አበባ እስከ ጅጅጋ ለማጓጓዝ አመልካቹ ተስማምቶ እየተጓዙ እያለ መኪናው በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ በተጠሪ ላይ ሃያ ኘርሰንት(20%) ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ በኢትዮ ተቢብ ሆስፒታል በተሰጠ የፅሑፍ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው ውስጥ ገልጿል። አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ለደረሰባቸው ጉዳት የህክምና ወጭ በሚል ብር 9,000/ዘጠኝ ሺህ ብር/ ለአመልካች የከፈሉ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሊከፍል የሚገባውን የካሣ መጠን ያሰላው ከውል ውጭ የሚደርስ ሃላፊነት ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው የካሣ መጠን መሰላት የሚገባው በንግድ ህግ አንቀፅ 597 ድንጋጌዎች መሆን ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በንግድ ህግ አንቀፅ 597 ንዑስ አንቀፅ 1 አንድ ሰውን ለመጓጓዝ ውል የተዋዋለ ሰው በጉዞ ወቅት በሰውየው ላይ ለደረሰው ጉዳት መክፈል የሚገባው የካሣ መጠን ከብር 40,000/አርባ ሺህ ብር/ መብለጥ እንደሌለበት ይደነግጋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ብር 9,000/ዘጠኝ ሺህ ብር/ ለህክምና ወጭ እንዲሆን የሰጡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ ከላይ በጠቀስነው የህግ ድንጋጌ መሠረት አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉት የሚገባው ቀሪ የካሣ ገንዘብ ብር 31,000/ሠላሳ አንድ ሺህ ብር/ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በንግድ ህግ ቁጥር 597 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ሣያሻሽል ተጠሪ በአመልካች መኪና ሲጓጓዙ ለደረሰባቸው ጉዳት አመልካች ካሣ ብር 54,000/ሃምሣ አራት ሺህ ብር/ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ይህንን የውሣኔ ክፍል በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት በማሻሻል፣ አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት ሊከፍል የሚገባው ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 9,000/ዘጠኝ ሺህ ብር/ የከፈሉ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች የሚቀርበት የብር 31,000/ሠላሳ አንድ ሺህ ብር/ ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በገለፅናቸው ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በተጠሪ ማሽን ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000/አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር/ ይክፈል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት የሚከፍለውን የካሣ መጠን በማሻሻል አመልካች ለተጠሪ ከዚህ በፊት ከከፈለው ብር 9,000 /ዘጠኝ ሺህ ብር/ በተጨማሪ ብር 31,000/ሠላሳ አንድ ሺህ ብር/ ብቻ ሊከፍል የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው ብር 211,000/ሁለት መቶ አሥራ አንድ ሺ ብር/ ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ብር 211,000/ሁለት መቶ አሥራ አንድ ሺህ ብር/ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፤

ዘቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ኪድስ ሊንክ ኢንተርናሽናል - ጠበቃ ቶማስ ገ/አብ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ሲስተር ገነት ወንድሙ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሠረት ያደረገ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር የመሠረቱት የስራ ቅጥር ውል ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም የስራ ቅጥር ውሉ የተቋረጠው የአመልካች እናት ድርጅት በመክሰሩ ምክንያት መሆኑን በመግለጽ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ብሎ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ካናዳ የሚገኘው የአመልካች ድርጅት እናት መስሪያ ቤት ስለመክሰሩ የአመልካች ድርጅት በማስረጃዎች አረጋግጠዋል፣ የተጠሪ ምስክሮች ቃል ግን ይህንኑ የአመልካች ማስረጃዎች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር የሚያስተባብል አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ተጠሪ ሊከፈላቸው የሚገባው የስራ ስንብት ክፍያና የ29 ቀናት የዓመት ፈቃድ ክፍያ ብቻ እንዲከፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የስራ ስንብቱ ከሕግ ውጪ የተከናወነ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ከሰጠው ክፍያ አይነት በተጨማሪ የካሣ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የስራ ስንብቱ ሕገወጥ ነው የተባለው በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ከስራ መሰናበት የነበረባቸው በቅነሣ መልክ መሆን ይገባው ነበር ተብሎ የስራ ስንብቱ ከሕገ ውጪ ነው በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመረመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ ባቀረቡት ክርክር በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ የሻረው የአመልካች ድርጅት ጠቅላላ ስራ መዘጋቱ በበቂ ማስረጃ አልተረጋገጠም፣ ስራው እየቀዘቀዘ ነው እንዳይባል ደግሞ በቅነሣ መልክ ስንብቱን አላከናወነም በማለት መሆኑን ነው፡፡ ከሁሉም በላይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው አመልካች ድርጅት ማዕከል ውስጥ በወቅቱ አንድ ህፃን ብቻ መቅረቱ በግራ ቀኙ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ የአመልካች ድርጅት እናት መስሪያ ቤት በመከሰር ላይ ያለ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በሚገባ ማረጋገጡን የውሣኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ የስር ፍርድ ቤትን ድምዳሜ ውድቅ ያደረገው በተገቢው መንገድ ሣይረጋገጥ የተያዘ ድምዳሜ ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ድምዳሜ ውድቅ ያደረገው በደፈናው በተገቢው ሣይረጋገጥ ነው በሚል ከመሆኑ ውጪ ተገቢ ያልሆነበትን፣ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት የአመልካች ማስረጃዎች የሰጡት ቃል ተቀባይነት የማይኖርበትን ህጋዊ ምክንያት ሣይጠቅስ ነው፡፡ የበላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሊሽር የሚችለው ሕጋዊና በቂ ምክንያት ሲኖረው ስለመሆኑ ስለ ፍርድ አሰጣጥ የሚደነግጉት ከቁጥር 341 ጀምረው ያሉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ ያለሕጋዊ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ በበላይ ፍርድ ቤት ሊሻር አይገባም፡፡ በመሠረቱ የበላይ ፍርድ ቤት በበታች ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችንም የማይቀበልበትን ምክንያት በግልጽ ጽፎ ውድቅ ማድረግ እንጂ በደፈናው በተገቢው አልተረጋገጡም በማለት ሊያልፈው አይገባም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የደረሰበትን ድምዳሜ ያልተቀበለበት አግባብ የዳኝነት አካሄዱን ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሕጋዊ አይደለም ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም ከተባለ ደግሞ የተሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊነት መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተቀጠሩበት ስራ መቀዝቀዙን በሚገባ ያረጋገጠ ሲሆን አንድ አሰሪ ስራው በመቀዝቀዙ ምክንያት ሰራተኛውን ሊያሰናብተው የሚችልበት አግባብ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ተዘርግቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይም የተጠሪ ስንብት በአዋጁ አንቀጽ 24/4/ መሠረት ሕጋዊ እንጂ ሕገ ወጥ ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አመልካች ተጠሪን በቅነሣ ሥርዓት ያሰናበታቸው መሆኑን አላስረዳም በማለት የያዘው ምክንያት የሕግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነገር ተጠሪ ጋር በተመሣሣይ ሁኔታ ተቀጥረው ስራ በመስራት ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ስራውን እየሰሩ ስለመሆኑ የተረጋገጠበት ሁኔታ የለምና፡፡ በአጠቃላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሻረው በሕጉ አግባብ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓትም ሆነ የመሠረታዊ ሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87901 ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58407 ታህሣሥ 07 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 57378

ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ አስቱር አርአያ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ አምሳለ በላይ - ጠበቃ ሽመልስ ሄይስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ወ/ሮ አምሳለ በላይ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም. በተሰጠ ውሣኔ በዶ/ር አለኸኝ መኮንንና በወ/ሮ አስቱር አርአያ ላይ ገንዘብ በማስወሰን የፍርድ ባለመብት የሆንኩበት ይፈፀምልኝ ብለው ባስከፈቱት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 92421 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም. የፍርድ ባለመብት በሌላ መዝገብ ባለዕዳ ሆነው በመ/ቁ. 63974 በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀሙ እየታየ ስለሆነ በዚህ ችሎት የተሰጠው ፍርድ ተቻችሎ እንዲፈፀም የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻው ከትዕዛዙ ጋር ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለ8ኛ ችሎት ይተላለፍ በሚል የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም በዚሁ ትዕዛዝ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፍዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 56661 ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም. ይግባኝ የተባለበት ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲፈፀም አፈፃፀም የተጠየቀበት የገንዘብ ፍርድ እና በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀም የተጠየቀበት የገንዘብ ፍርድ ተቻችሎ እንዲፈፀም ለከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበውና ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይተላለፍ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ገልፀው አቅርበዋል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ተብሎ በመታዘዙ ማመልከቻው ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ቀረበው መልስ እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን በተጠሪዋ በኩል በጽሑፍ የቀረበው መልስም ለአመልካች እንዲደርሳቸው ተደርጐ በጽሑፍ የመልስ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ጉዳይ በአንድ በኩል የአሁኗ ተጠሪ በአሁኗ አመልካች እና በሌላ አንድ ሰው ላይ ገንዘብ በማስወሰን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አፈፃፀም የጠየቁበት ፍርድ በሌላም በኩል የአሁኗ አመልካች በአሁኗ ተጠሪ ላይ ብቻ ገንዘብ በማስወሰን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀም የጠየቁበት ፍርድ መቻቻል ሊደረግበት እንዲችል ለከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበው የአፈፃፀም ጥያቄ ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተላልፎ ይታይ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት መኖር አለመኖሩ ሲመረመር፡-

በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 397/1/ ላይ እንደተመለከተው በዚህ ጉዳይ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች በየበኩላቸው ክስ አቅርበው አንዱ በአንዱ ላይ የፍርድ ባለገንዘብ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን ሁለቱም እንደፍርዱ እንዲፈፀምላቸው ለፍ/ቤት የአፈፃፀም ማመልከቻና ለማቅረብ የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍተዋል፡፡ ልዩነት የታየው የአሁኗ አመልካች የአፈፃፀም ማመልከቻውን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው የአፈፃፀም መዝገብ ማስከፈታቸው እና የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ የአፈፃፀም ማመልከቻውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረብ የአፈፃፀም መዝገብ ያስከፈቱ ሆኖ መገኘታቸው ላይ ቢሆንም ፍርዱ በአንድ ፍ/ቤት ዘንድ ሊፈፀም የሚችል ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ በመረዳት ፍርዱ መቻቻል ሊደረግበት እንዲችል አፈፃፀሙ በአንድ ፍ/ቤት እንዲታይ በአሁኗ ተጠሪ በኩል የቀረበው የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበው የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ አድርጓል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ያቀረቡበት ፍርድ ገንዘቡን የአሁኗ አመልካችና ሌላው የፍርድ ባለዕዳ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ስለመቻቻሉም ጥያቄ አፈፃፀሙን በዝርዝር በማየት የሚወሰነው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሌላው ላይ ያስወሰነው በፍርድ የበሰለ ገንዘብ በመቻቻል መፈፀም እንዲችል የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ ማድረጉ የሕግ ስህተት ያለበት አይደለም፡፡

የአሁኗ አመልካች የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1838 እና 1839ን በመጥቀስ ማቻቻል እንዲደረግ ባለዕዳው የሚፈልግ መሆኑ መረጋገጥ አለበት በሚል ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተም በፍርድ የበሰለው የገንዘብ ዕዳ መቻቻል አፈፃፀም የሚመራው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 397 መሠረት ስለሆነ ወደ ፍትሐብሄር ሕጉ ድንጋጌዎች የሚወሰድ ጉዳይ አይደለም፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 397/1/ የሚጠይቃቸው ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ ሆነው ከተገኙ ማቻቻሉ መፈፀም ይኖርበታል፡፡ በዚህ ጉዳይ መቻቻሉ እንዲፈፀም በሕጉ ላይ የተመለከቱት መሠረታዊ የሆኑት ነገሮች ተሟልተው ስለሚገኙ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡

ሌላው አመልካች የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ባቀረቡበት ፍርድ ገንዘቡን እንድከፍል የተወሰነው በእኔ ላይ ብቻ ሣይሆን በዶ/ር አለሽኝ መኮንንም ላይ ስለሆነ እኔ በተጠሪዋ ላይ ካስፈረድኩት ገንዘብ ጋር መቻቻል ሊደረግበት አይችልም በሚል ያነሱትን የተቃውሞ ክርክርም በሚመለከት በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነ መሆኑን ተጠሪዋ በጽሑፍ በአቀረቡት መልስ ላይ የገለፁት ሲሆን አመልካችም በጽሑፍ በሰጡት የመልስ መልስ ላይ በአንድነትና በነጠላ ይከፈል መባሉን አልካዱም፡፡ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነ ሆኖ ከተገኘ የፍርድ ባለመብቷ በሕጉ የአንደኛው የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ብቻ ተሸጦ ወይም አፈፃፀሙ በአንደኛው የፍርድ ባለዕዳ ላይ ብቻ ቀጥሎ ገንዘቡ እንዲከፈላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡ መቻቻሉም በተመጣጣይ መንገድ ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች በተጠሪዋ ላይ ብቻ አስፈርደው የአፈፃፀም ማመልከቻ ያቀረቡበት ገንዘብ የአሁኗ ተጠሪ አመልካችና ሌላ ሁለተኛ ሰው በአንድነትና በነጠላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይክፈሉ ተብሎ ተወስኖ አፈፃፀም ከጠየቁበት ገንዘብ ጋር እንዲቻቻል ከተደረገ በኋላ አመልካች በሕጉ ያላቸው መፍትሄም ሆነ አማራጭ ሁለተኛው የፍርድ ባለዕዳ በድርሻቸው ያለውን ገንዘብ እንዲተኩላቸው መጠየቅ ስለሆነ ተጠሪ በእኔና በሌላ ሁለተኛ ሰው ላይ በፍርድ ያስወሰኑት ገንዘብ እኔ በተጠሪዋ ላይ ብቻ ካስወሰንኩት ገንዘብ ጋር መቻቻል እንዲፈፀም ሊደረግ አይገባም በሚል ያቀረቡት ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም፡፡

አመልካች የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲያቀርቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 386 መሠረት ለእኔም ማመልከቻው ተልኮልኝ ቀርቤ መልስ እንድንሰጥ መደረግ ሲገባው ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን የመሰማት መብቴን አልፎ መቻቻል እንዲደረግ የተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይተላለፍ ያለው ያለአግባብ ነው ብለው የገለጹትን በተመለከተም አሁንም ቢሆን ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚቃወሙበት የሕግ ምክንያት ስለመኖሩ ያስረዱት ነገር ስለሌለ በፍርድ ተወስኖ ባለቀ ጉዳይ ላይ እንደገና መልስ እንድሰጥ መደረግ ነበረበት የሚለው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ሁለት ፍርዶች በማቻቻል እንዲፈፀሙ በማድረጉ ሂደት ሊያነሱት የሚገባ ጥያቄ ካለ ማቅረብ የሚገባቸው የአፈፃፀሙን ጉዳይ በማየት ላይ ለሚገኘው ፍ/ቤት ነው፡፡

በአጠቃላይ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሌላው ላይ በፍርድ ያስወሰኑትን ገንዘብ የአፈፃፀም ጥያቄዎች በአንድ ፍርድ ቤት ታይተው በማቻቻል እንዲፈፀሙ የአሁኗ ተጠሪ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበውት የነበረው የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የሌለ ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 56661 ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 51223

የካቲት 24 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ዳሽን ባንክ ነገረ ፈጅ ትንሳኤ ተፈራ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ሀመልማል መኮንን ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ታደሠ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በግራ ቀኙ ከተነሣው ክርክር አንፃር በማየት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 የተመለከተውን ሥነ-ሥርዓታዊ ድንጋጌ አፈፃፀምን በሚመለከት በሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠውን ትርጉም አግባብነት ለማየት በሚል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 126261 በአሁን አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ፡-

ከወ/ሮ ፅዮን መኮንን በዳሽን ባንክ መሣለሚያ ቅርንጫፍ ብር 55,907.02 የተላከልኝን ገንዘብ ባንኩ ለሌላ ግለሰብ ከፍሏል፡፡ ይህም ክፍያ የሥራ ግዴታውን በአግባቡ ካለመወጣቱ የተነሣ የተፈፀመ ስለሆነ ሊከፍለኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም በተከሣሽነት ቀርቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244/2/ መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በማስቀደም በዚህ ጉዳይ ወ/ሮ ፅዮን መኮንን ከሰውን የድሬዳዋ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ እንደሌለብን በመግለፅ ወስኖ አሰናብቶናል፡፡ የአሁን አመልካች ጥያቄ ከወ/ሮ ፅዮን መኮንን የመነጨ ስለሆነ አስቀድሞ ዳኝነት ባገኘው ጉዳይ ላይ ዳግመኛ ክስ ማቅረብ እንደማይቻል ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ስለተደነገገ ክሱ ውድቅ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም ይህንኑ ክርክር በማስረጃነት ከቀረበው ከመ/ቁጥር 23357 ፍርድ ይዘት ጋር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ እንደ አመልካች ክርክር አስቀድሞ ውሣኔ ባገኘ ጉዳይ ዳግመኛ የቀረበ ክስ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በአካያው ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ጉዳዩን ተመልክቶ በሁለቱም መዝገቦች ያሉት ተሟጋቾች የተለያዩ ናቸው፣ የመብታቸውም ጥያቄ እራሱን የቻለ ነው እንዲሁም ጭብጡም የተለያየ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 የተመለከተው ድንጋጌ ለዚሁ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚል ትርጉም ከሰጠ በኋላ በዋናው ጉዳይ ዘልቆ የአሁን አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ ጋር ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በሁለተኛ የይግባኝ ደረጃ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አከራካሪ የሆነውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ክርክርም ሆነ በዋናው ጉዳይ የተሰጠውን ውሣኔ መርምሮ በተመሳሳይ አተረጓጎም ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበውም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ጋር በተያያዘ በግራ ቀኙ ለተነሣው ክርክር ይግባኝ ሰሚዎች ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የሰጡት ትርጉም አግባብነት በሚለው ነጥብ ላይ ግራ ቀኙን በሰበር አድምጦ አስፈላጊውን ትርጉም ለመስጠት በሚል ነው፡፡

በዚህ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ በፍሬ ነገርም ሆነ ስለ ሕጉ ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍ/ቤቶች ካቀረቡት በይዘቱ የተለየ ባለመሆኑ በዚህ ፍርድ ላይ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ዓይነት ከላይ ባጭሩ የመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የወ/ሮ ሀመልማል ክስ በኮ/መ/ቁ. 126261 በሆነው መዝገብ ከመቅረቡ በፊት ገንዘቡን በሃዋላ ለወ/ሮ ሀመልማል መኮንን ላኩ የተባሉት ወ/ሮ ፅዮን መኮንን ይህንኑ ገንዘብ ብር 55,907.02 በሃዋላ ለወ/ሮ ሀመልማል እንዲከፍልልኝ ግዴታ ገብቶ ገንዘቡን ከተቀበለ በኋላ ለተላከለት ሰው አልከፈለም ስለዚህ ገንዘቡን ይመልስልኝ በማለት በአሁን አመልካች ላይ ክስ አቅርበው ገንዘቡን አስተላላፊ ነው የተባለው ባንክ ገንዘቡን በማስተላለፍና ለተላከለት ሰው ክፍያን በመፈፀም ረገድ ካለበት የሥራ ግዴታ አንፃር ያደረገው ተግባር ሁሉ ታይቶ ተከሣሽ ግዴታውን በመወጣት በኩል ተግባሩን በአግባቡ ፈፅሟል፡፡ ገንዘቡን የመመለስ ግዴታ የለበትም ተብሎ በመ/ቁ. 23357 ተወስኗል፡፡

ይህ ውሣኔ ከተሰጠ ከሦስት ወር ተኩል በኋላ ደግሞ እንደገና ገንዘቡ ተላከላቸው የተባሉት የአሁን ተጠሪ ከወ/ሮ ፅዮን የተላከልኝን ብር 55,907.02 ባንኩ ለእኔ መክፈል ሲገባው ለሌላ ግለሰብ ከፍሏል ይክፈለኝ በማለት ክስ አቅርበውበታል፡፡

በዚህም ሁለተኛ ክስ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጭብጥ ገንዘብ አስተላላፊው በገባው ግዴታ መሠረት ገንዘቡን ለተላከለት ሰው ለመክፈል የሚጠበቅበትን ተግባር አከናውኗል ወይስ አላከናወነም? የሚለው በመሆኑና የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት በተሳሳተ መንገድ ወደ ፍሬ ነገሩ ጉዳይ ዘልቀው በመገባታቸውም የተነሣ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው አከራካሪ ነጥብ ይህው ስለመሆኑ የወሣኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ስለሆነም በመ/ቁ. 23357 ሆነ በመ/ቁ. 126261 የተነሣው የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጭብጥ ተመሳሳይ ነው፡፡ ተከራካሪ ወገኖችም የተለያዩ ሰዎች ይሁን እንጂ የወ/ሮ ሀመልማል ገንዘብ የመጠየቅ መብት የሚመነጨው ከገንዘብ ላኪዋ በመሆኑና ገንዘብ ላኪዋ ባቀረቡት ክስ ረቺ ሆኖ በተገኙ ጊዜ እንዲሁም ገንዘብ ተቀባይ የፍርዱ ተጠቃሚ የሚሆኑ ወገን ናቸው፡፡ ተመሳሳይ ዳኝነት ከአንድ ተከሣሽ የሚጠይቁ ወገኖች በመፈራረቅ የተለያዩ ክስ በማቅረብ በተከሣሹ ላይ አላስፈላጊ እንግልት እንዳያደርሱ በማሰብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ በአንቀጽ 5/1/ ላይ ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ለማቅረብ እንደማይችሉ ተደንግጓል፡፡ የእነዚህ ለመጀመሪያው ጉዳይ ተከራካሪ ከሆኑት ወገኖች መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች እጣ ፈንታ በመጀመሪያው የክስ ውጤት ላይ የተወሰነ ውሣኔውም ጎጂ ከሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለአስከተለው ኃላፊነት በቅድሚያ በተከራከረው ወገን ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር እንጂ ዳግመኛ ክስ በዚያው በአንድ ተከሣሽ ላይ እንዲቀርብ የተፈቀደበት ሥርዓት አይደለም፡፡

በዚህም የሕግ ይዘትና የሕጉ መሠረተ ሀሳብ መነሻ በሁለቱም ጉዳዮች በከሣሽነት የተሰየሙት ወገኖች ተመሳሳይ ወገኖች እንደሆኑ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

ከሁሉም በላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 የተቀመጠው ድንጋጌ ክርክሮችን ሥርዓት ባለው መንገድ እንዲመሩ በማድረግ በተቻለ ፍጥነት በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጭ ታይተው እንዲቋጩ በማድረግ ረገድ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ የያዘውን ዓላማ ተከትሎ የተዘረጋ ሥርዓት እንደመሆኑ መጠን አንድ አስቀድሞ የተሰጠ ፍርድ ወደ ፊት ለሚነሱት ክርክሮች ያለውን ውጤት ለይቶ ደንግጓል፡፡ ይህንንም ድንጋጌ አስመልክቶ የትርጉም ጥያቄ ከተነሣ ልንሰጠው የሚገባው ትርጉም ከዚሁ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ የራቀ ሊሆን አይገባም፡፡ ከዚህ አንፃር ለሁለቱም ጉዳዮች መነሻ የሆነው አንድ የተላከ ገንዘብ ሆኖ እያለ በሁለቱም ጉዳዮች ለተነሣው ክርክር ዕልባት ለመስጠት በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ባንኩ በአግባቡ የሥራ ግዴታውን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚለው መሆኑ እየታወቀ እና ላኪ እና ተቀባይ የሚጠይቁት ዳኝነት በይዘቱ ተመሳሳይ ሆኖ እያለ በጊዜ ቅደም ተከተል በመፈራረቅ አንድን ተከሣሽ ሁለት ጊዜ በአንድ ጉዳይ በተለያዩ ፍ/ቤት በተለያዩ ጊዜ ለሙግት በሚደረግ አካኋን የክርክሩ አንኳር ነጥብ ሲያያዝ በጭፍጫፊ የቃላት አጠቃቀም በመመራት ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 እንደተመለከተው አስቀድሞ በፍርድ እንዳለቀ ሊቆጠር የሚችል አይደለም በሚል የተሰጠው ትርጓሜ የድንጋጌውን ይዘትም ሆነ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዋነኛ ዓላማን መሠረት ያደረገ ሆኖ ስላላገኘነው ትርጉሙ መሠረታዊ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና በጠቅላይ ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁ. 74189 ጥር 25 ቀን 2001 ዓ.ም. እና በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 45987 ህዳር 09 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰጠው ፍርድ እና ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 126261 በ10/03/2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በአሁን አመልካች ላይ የቀረበውና ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ ዳግመኛ የቀረበ ሆኖ ስላገኘነው ክሱ ውድቅ ነው፡፡ ውድቅ ሊሆን በሚገባው ክስ ምክንያት ብር 55,907.02 /ሃምሣ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባት ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ ይክፈል በሚለው ፍርድ ሊገደድ አይችልም፡፡ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡ በዚህ ሰበር ክርክር ምክንያት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 53421

ቀን የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች :- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓለ. መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ ዋሴ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ባንተይርጋ ወርቁ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ፍርድን ለማስፈፀም ሲባል በተሸጠ ቤት ላይ የአሁን አመልካች ቤቱ የእራሴ ንብረት ነው፡፡ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት እንደሆነ ተቆጥሮ የተሸጠው ያለአግባብ ስለሆነ የሐራጅ ሽያጩ ፈርሶ የቤቱ ባለመብትነቱ ይረጋገጥልኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 447 (4) አንጻር ተቀባይነት ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ አቶ ባንተይርጋ ወርቁ እና ባለቤታቸው የነበሩት በዚህ ጉዳይ በፍርድ ባለዕዳነት የተሰየሙት ወ/ሮ አየሁብርሃን ወዳጆ በመካከላቸው የነበረውን ጋብቻ ካፈረሱ በኋላ በፍቺ ውጤቱ ይህ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን በወ/ሮ አየሁብርሃን ወዳጆ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው በቦራዩ ከተማ ቀበሌ ለኩ ኮታ በዕድገት የመኖሪያ ቤት ሥራ ማህበር ተደራጅተው ያፈሩት የመኖሪያ ቤት የባልና ሚስት የጋራ ሀብት መሆኑን ገልፀው እንዲካፈሉ ተስማምተው ስምምነታቸው በፍ/ቤት በመ/ቁ 12592 ሚያዚያ 11 ቀን 1986 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ መሠረት ፀድቋል፡፡

በዚህ ውሳኔ መሠረት ለማስፈፀም የአሁን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት፤ ሚስት የነበሩት ወ/ሮ አየሁብርሃን ወዳጆ ባለዕዳ በመሆን የተሰየሙበት የአፈጻጸም መዝገብ በአ/ፈ/መ/ቁ በኮ/መ/ቁ 17831 ተከፍቶ አፈጻጸሙ ቀጥሎ ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. የፍርድ ባለዕዳ ባሉበት ቤቱ ክፍት ሆኖ በመቆየቱ የፍርድ አፈጻጸም መምሪያ ባለሙያ፣ ከቀበሌና ከፖሊስ ጽ/ቤት በተገኙ አባላት አማካኝነት ቤቱ ተገመተ፡፡ ነገር ግን ግምቱ ቦታውን አላካተተም ተብሎ የመሬት አስተዳዳር የመሬቱን ዋጋ እንዲሰላ በድጋሚ ሲታዘዝ የፍርድ ባለዕዳም ቤት የላትም የሚል መልስ መስጠቱን፤ ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሁን አመልካች በሽያጭ አስተላለፈልኝ የሚሏቸው አቶ ቦጋለ ደገፋ በአፈጻጸም ይሸጥ በተባለው ቤት ላይ መብት አለኝ በማለት በዚሁ የአፈጻጸም መዝገብ ጣልቃ ገብተው በመከራከራቸው በኮ/መ/ቁ 17831 ሐምሌ 04 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አቶ ቦጋለ የማህበር ማረጋገጫ ካርታ አቀረቡ እንጂ ቤቱ የግላቸው ስለመሆኑ የሚገልፅ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብት የላቸውም በማለት አሰናብቷቸዋል፡፡ አቶ ቦጋለ በአፈጻጸም ጉዳይ የተያዘው ንብረት የእኔ ነው በማለት አቤቱታ ሲያቀርቡ የፍርድ ባለዕዳ የነበሩት እና ቤቱ በስማቸው ተመዝግቦ ይገኝ የነበሩት ወ/ሮ አየሁብርሃን ወዳጆ እኔና ባለቤቴ የነበረው የአሁን ተጠሪ የጋራ ቤት የሌለን ስለሆነ ቤቱ ለአቶ ቦጋለ ደገፋ ቢለቀቅ አልቃወምም የሚል መልስ ሰጥተው እንደነበሩ የክርክሩ አመጣጥ ያስረዳል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህ ክርክር የተነሳበትን ቤት ከፍርድ ባለመብትም ሆነ ከፍርድ ባለእዳ ጋር ግንኙነት ከሌላቸው ከአቶ ቦጋለ ነሐሴ 07 ቀን 2001 ዓ.ም. ገዝቻለው ስመ ሀብትነቱም በካርታ ቁጥር Bur/74/93/10 በ11/12/2001 ወደ እኔ ተዛውሯል፡፡ የፍርድ ባለዕዳ ሳልሆን ንብረቴ ላይ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተሰጠፈብኝ በማለት በአፈጻጸም መዘገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም. አቤቱታ ሲያቀርቡ ቤቱን ሸጠልኝ የሚሏቸው ግለሰብ አቶ ቦጋለ ደገፋ በዚህ መዝገብ ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርበው ውድቅ የተደረገባቸው መሆኑን መነሻ አድርገው አሰናብቷቸዋል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ሲያቀርቡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 87938 በ12/4/2002 በዋለው ችሎት ቤቱ በሐራጅ መሸጡን ስለተረዳሁ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት የቀረበውን አቤቱታ መርመሮ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፤ለሥር ፍ/ቤት ያመልክቱ የሚል ዳኝነት ሰጥቶበታል በሚል ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን አቤቱታ የሐራጅ ሽያጩ ፈርሶ ቤቱን ልረከብ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 መሠረት አፈጻጸሙን በያዘው ፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸውን የጉዳዩ አመጣጥ ያስረዳል፡፡

አፈጻጸሙን የያዘው ፍ/ቤትም በኮ/መ/ቁ 17831 በ27/4/2002 በዋለው ችሎት ከላይ እንደተመለከተው የጉዳዩን አጀማመር፤ በመካከል አፈጻጸሙን ያሰናከሉትን ሙግቶች ሁሉ ከጠቀሰ በኋላ ንብረቱ የፍርድ ባለዕዳዋ የነበረ ስለመሆኑ በንብረት አገማመት ጊዜ በባለቤትነት የነበራቸውን ተሳትፎ የአሁን አመልካች በዚሁ ጉዳይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ዳኝነት ጠይቀው መሰናበታቸውን ሁሉ መሠረት በማድረግ አመልካች ያቀረቡት ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም፡፡ በማለት ወስኗል፡፡

ይህም ውሳኔ የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦበት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚልበት ዋና የመከራከሪያ ነጥብ የንብረቱ ባለቤት እኔ ስለመሆኔ የቤቱ ስም ሀብትነት በእኔ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ የፍርድ ባለዕዳና የፍርድ ባለገንዘብ የተሸጠው ቤት ያልነበራቸው መሆኑን የቡራዩ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት አረጋግጠውልኛል የሚሉ ናቸው፡፡

የአሁን ተጠሪም በሥር ፍ/ቤቶች ከነበረው ክርክር አንስቶ የተሰማቸውን ነጥቦች በማድረግ ንብረት የባልና የሚስት የጋራ ሀብት ስለሆነ ለክፍፍል በአፈጻጸም እንዲሸጥ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አጀማመር እና የክርክሩ ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በቅድሚያ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ያገኘነው በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት እንዲሸጥ በተከበረ ንብረት ላይ የቀዳሚ መብት አለኝ በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት በአፈጻጸም ጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ ተከራክሮ ክርክሩ ውድቅ ከተደረገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኋላ እንደገና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 444-447 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በዚያው የአፈጻጸም መዝገብ ገብቶ ለመመርመር የሚያስችለው መብት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 ሆኖ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ባለው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 447(4) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ግብ ተመሳሳይ ሆኖ የሚለያዩበት ነጥብ ቢኖር እንዲሸጥ በተከበረው ንብረት ልዩ መብት አለኝ በሚል የቀረበው አቤቱታ መቼ ቀረበ በሚለው ላይ ነው፡፡ በቁጥር 418 አቤቱታ የሚቀርበው ከመሸጡ በፊት ሲሆን በቁጥር 447-(4)የሚቀርበው ደግሞ ከተሸጠ በኋላ መሆኑ ብቻ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ግን ተመሳሳይ ነው ይኸውም በሐራጅ ለማሸጥ የተከበረው ንብረት ወይም ደግሞ ተከብሮ የተሸጠው ንብረት የፍርድ ባለዕዳ ሳይሆን የእኔ ነው የሚል በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ከሆነ በተመሳሳይ ክርክር ነጥብ በአንድ ጉዳይ እንደ አመልካች ባለ አቀራረብ ፍ/ቤቱ ሁለት ጊዜ ሊያስተናግድ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ይህ ዓይነት አቀራረብ ክርክርን ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት ማስተናገድ ይገባል ከሚለው የሙግት አመራር አላማ ጋርም የሚጣረስ ነው በዚህም ምክንያት አፈጻጸሙን የያዘው ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445-446ን በመጥቀስ ዳኝነት የጠየቀበት ጉዳይ ቀደም ሲል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ጥያቄ ቀርቦበት ዳኝነቱ ያረፈበት ጉዳይ ስለሆነ በድጋሚ ሊታይ የሚችልበት አግባብ የለም በሚል የሰጠውን ውሳኔ መሠረት ማድረጉ በአግባቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ንብረቱ ከተሸጠ በኋላም ቢሆን በዚያው የአፈጻጸም መዝገብ ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረቡት ክርክር ይታይ እንኳ ቢባል ይህ ክርክር ያስነሰውን ንብረት አመልካች ከአቶ ቦጋለ ደገፋ ከመግዛታቸው በፊት በፍርድ አፈጻጸም ተይዞ ሻጭ የተባሉት በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ሊያዝብኝ አይገባም በማለት ተከራክረው በፍርድ ከተረቱ በኋላ ነሐሴ 07 ቀን 2002 ዓ.ም. ገዛሁ የሚል በመሆኑ ይህ ከሆነ በኋላ የተላለፈው የግኝር ተግባር አስቀድሞ የተጀመረውን የአፈጻጸም ጉዳይ ሊያቋርጠው የሚችል አይደለም፡፡ በተለይም ሻጭ የተባለው አቶ ቦጋለ በአፈጻጸም ጉዳይ ጣልቃ ገብተው በተከራከረ ጊዜ የፍርድ ባለዕዳ ንብረቱ ይለቀቅለት የእኔና የፍርድ ባለመብት የጋራ የሆነ ቤት አይደለም የሚለውን ገልፀው መከራከራቸውን እና አመልካችም ይህንኑ ቤት በግኝር አገኘሁ የሚሉት ቤቱ በአፈጻጸም ምክንያት በፍ/ቤት ከተያዘ በኋላ እንደመሆኑ መጠን ጥያቄያቸው ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 354 አንጻር ሲታይ የህግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

ስለሆነም በዚህ ሁሉ ምክንያት የአሁን አመልካች እንደአባባላቸው ቤቱን በሽያጭ አግኝተው የስመ ሀብቱም ዝውውር ወደ እርሳቸው ተዛውሮ ከሆነ ይህ ሁሉ ሥርዓት የተፈፀመው አስቀድሞ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት መሆኑ ታውቆ ፍርድ ያረፈበት፣በአፈጻጸም ተመርቶ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የተሰላፈበት፤ በሐራጅ እንዲሸጥ በሂደት ላይ እያለ የአሁን አመልካች ሽጡልኝ የሚሏቸው ሻጭ በአፈጻጸም ጉዳይ ጣልቃ ገብተው ከተረቱ በኋላ የተደረገ የግኝር ተግባር በመሆኑ በእጅ የተያዘውን የሐራጅ ሽያጭ ለማስቆም የሚያስችል መብት የሌላቸው በመሆኑ፤ እንዲሁም የአመልካች የአቤቱታ አቀራረብም ሥርዓቱን የተከተለ ሆኖ ባለመገኘቱ የሥር ፍ/ቤቶች በአሁን አመልካች አቤቱታ መነሻ የሰጠው ዳኝነት በአግባቡ የተሰጠ እንጂ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ በመ/ቁ 88606 ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠውን የመጨረሻ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1)መሠረት አፅንተናል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም መዝገቦቹ ይመለሱ
3. የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 55973

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ አፀደ ኤዶ ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ታደሠ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ትኩ ዋቅሹም ጠበቃ አቶ ይመኑ ገብረፃድቅ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1987 ዓ.ም. እንደ ባልና ሚስት ስንኖር ያፈራናቸው የጋራ ሀብት አለ፡፡ ስለሆነም የጋራ ሀብቴን እንዲያካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት አሉ የሚሉትን ንብረት ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 6 ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ ንብረቶቹን በግሌ ያፈራኋቸው ናቸው፡፡ ከሣሽ /አመልካች/ የጋራ ንብረት ስለሆነ ያካፍለኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በሥር ተከሣሽ የሆኑት ተጠሪ ቀደም ሲል በፍ/ቤቱ ያቀረቡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ያልተካተተበትና ጉዶሎ ስለሆነ መልሴን እንዳሻሻል ይፈቀድልኝ በማለት ህዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ አመልክተዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተከሣሽ /ተጠሪ/ መልሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸዋል፡፡ ተጠሪ /ተከሣሽ/ ታህሣስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ የተሻሻለ መልስ የከሣሽ /አመልካች/ የተከሣሽ /ተጠሪ/ ግንኙነት 1987 ዓ.ም. ተቋርጧል፡፡ ስለሆነም የባልና የሚስት የጋራ ንብረት ክፍያ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም የከሣሽ /አመልካች/ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ አሻሽለው ባቀረቡት መልስ ላይ ያቀረቡትን የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ በመቀበል የከሣሽ /አመልካች/ የጋራ ንብረት ክፍያ ጥያቄ በአሥር ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የጋራ ንብረት እንዲያካፍለኝ ላቀረብኩት ክስ ተጠሪ በጽሑፍ ሙሉ መልስ ከሰጡና ግራ ቀኞችን የቃል ክርክርና ምስክሮች ተሰምተው ጉዳዩ ለውሣኔ ቀጠሮ ከተሰጠው በኋላ ተጠሪ መልሱን ለማሻሻል አቤቱታ አቀረበ፡፡ የሥር ፍ/ቤት ከፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 መሠታዊ ድንጋጌ ከሚፈቅደው ውጭ ተጠሪ መልሱን እንዲያሻሽል የፈቀደ ሲሆን በተሻሻለው መልስ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ሆኖ መቅረብ የነበረበትን የይርጋ ክርክር አካትቶ አቀረበ፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኞችን ክርክር ከተጠናቀቀና ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ተጠሪ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጠው ብይን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244/1/ እና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91/1/ የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መልሴን ለማሻሻል ጥያቄ ያቀረብኩት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አካትቶ ለማቅረብ እንደሆነ ለሥር ፍ/ቤት ገልጬአለሁ፡፡ የሥር ፍ/ቤትም በዚሁ ጥያቄ አምኖበት መልሴን እንዳሻሽል ፈቅዶልኛል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ብይን የሰጠው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 17937 የሰጠውን የሕግ ትርጉም በመከተል ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች የፈፀሙት የሕግ ስህተት የሌለ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሆኖ እንድሰናበት በማለት ታህሣስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም. የተጻፈ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ በማካተት መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ መፍቀዱና በተሻሻለው መልስ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ መሠረት አድርጎ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተከሣሽ የቀረበበትን ክስ ለመቃወም የሚችልበት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ለክሱ ከሚሰጠው ዝርዝር መልስ በፊት ወይም ከመከላከያ መልሱ ጋር ማቅረብ እንዳለበትና ፍ/ቤቱም በመጀመሪያ የክሱ መቃወሚያ ላይ ከሣሽ የሚሰጠውን መልስ በመቀበል ብይን መስጠት እንደሚገባው በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 245 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ አንድ ጉዳይ በይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል የሚለው መከራከሪያ ተከሣሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት መቅረብ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተከሣሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርብው ይገባው የነበረውን የይርጋ መቃወሚያ ሣያካትት የመከላከያ መልሱን ካቀረበ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1856 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት የይርጋ መከራከሪያውን እንደተወው የሚቆጠር መሆኑን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ እና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 245 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1856 ንዑስ አንቀጽ 1 ያጣመረ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማን በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የመጀመሪያ ክስ የሚሰማው ፍ/ቤት ተከሣሽ የመከላከያ መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ የሚፈቅደው ተከሣሽ መልሱን አሻሽሎ ማቅረቡ ጉዳዩን ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው (Necessary for the Purpose of the Real Question in Dispute) መሆኑ በፍታብሔር ሥነ-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 1 ተከሣሽ በፍትብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ድንጋጌዎች መሠረት በመጀመሪያ የክስ መቃወሚያነት ያላቀረበውን በተለይም በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ መሠረት ማቅረብ የሚባውንና የተወውን የይርጋ ጊዜ ገደብ መከራከሪያ አካትቶ እንዲያቀርብ የሚፈቅድ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ድንጋጌው ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ የክሱ ወይም የመከላከያ መልሱ መሻሻል በክርክር የተያዘውን ጉዳይ ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ ባልተገኘበት ሁኔታ ፍ/ቤት ክስ ወይም መልስ እንዲሻሻል መፍቀድ የሌለበት መሆኑን የሚያስቀምጥ ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ የጽሑፍና የቃል ክርክር ካደረጉና ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸውን አቅርበው ካሰሙ በኋላ ተጠሪ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርብ ይገባው የነበረውን የይርጋ መቃወሚያ አካትቶ ለማቅረብ የመከላከያ መልሱን ለማሻሻል የቀረበውን ጥያቄ ተቀብሎ ተጠሪ የመከላከያ መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ የሰጠው ትዕዛዝ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው የመከላከያ መልስ ውስጥ በማካተት ያቀረበውን የይርጋ መከራከሪያና የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል የሰጠው ትዕዛዝ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀጽ 2/ረ/ እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1856 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244/3/ ንዑስ አንቀጽ 2 የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ከላይ የዘረዘርነው የሕግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ በይግባኝ አይቶ ማረም ሲገባው የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ የከፍተኛው ፍ/ቤት ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካች ክስ ቀሪ እንደማይሆን በመገንዘብ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 56795

የካቲት 21 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ መ·ባረክ ከድር - ጠበቃ አቶ ወንድም ጥላሁን ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ሚ/ር መ·ዋንጋ ሲ.ርል - አልቀረቡም

2ኛ. ወ/ሮ አሰለፈች ሰይድ በሌሉበት የሚታይ

3ኛ. ወ/ሪት አስቴር ጉግሳ ” ”

4ኛ. አቶ አወል ሸበሽ ” ”

5ኛ. አቶ መሐመድ ሺበሽ ወኪል አቶ መ·ሣ መሐመድ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት በንብረት ላይ የተሰጠ የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ አቤቱታ ያቀረበ ወገን በጉዳዩ ላይ ተከራክሮ ዳኝነት እንዳገኘ የሚቆጠር ወገን ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ዳኝነት የመጠየቅ መብት የለውም በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ትርጉም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመልክቶ አግባብነቱን ለማየት በሚል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ህዳር 25 ቀን 1999 ዓ.ም. በተጻፈ የክስ አቤቱታ

ከሚች ወ/ሮ አረጋሽ ሺበሽ ጋር ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ በግሪክ አገር ጋብቻ ፈጽመን እየኖርን እያለ ሚች ኢትዮጵያ መጥታ ሞታለች የእኔም ባልነት በፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ የጋራ ሀብት 1ኛ በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 13/14 የሚገኘውን ቁጥሩ አዲስ/የፋይል ቁጥር ሊዝ 06 የሆነ ቤት፣ 2ኛ በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 15 ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ ጅምር ቤት፣ 3ኛ በሚች ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ የሚገኝ መጠኑ ያልታወቀ ገንዘብ ስለአለ ግማሽ ድርሻ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቀበት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ የክስ ማመልከቻ በተጠሪነት የተሰየመ ወገን ስላልነበር ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚች ወራሾች ካሉ ቀርበው ክርክር ያደርጉ ዘንድ ጥሪ ሲያደርግ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ህዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ ከሣሽ የሚች አሠሪ እንጂ ባል አይደለም እርሱም ከሚች ቀድሞ የሞተ ስለሆነ የጥብቅና ውክልናው ዋጋ ያለው አይደለም ተጣርቶ ውድቅ ይደረግልን፤ ሚች ንብረቷን በሙሉ በኑዛዜ አስተላልፋለች፡፡ ክስ የቀረበበት ንብረት የሚች የግል ንብረቷ መሆኑንም አረጋግጣለች፡፡ ስለሆነም የጋራ ሀብት መሆኑ ሳይረጋገጥ የቀረበው ክስ አግባብነት የለውም በማለት ሲከራከሩ፤ የአሁን 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው እኛም የሚች ወራሾች ስለሆን የንብረቱ ተካፋይ ልንሆን ይገባል የሚል መልስ ጥቅምት 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በተጻፈ ሰጥተዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ደረጃ ላይ እያለ የአሁን አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 እና 205 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ ግማሽ ድርሻ ከተጠየቀበት ንብረቶች መካከል በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 13 ክልል በካርታ ቁጥር ሊዝ/06/8328/02 8388 ተመዝግቦ የሚታወቀው ቤት የሚች የወ/ሮ አረጋሽ ሺበሺ የግል ንብረት የነበረ ሲሆን ሚች ይህንኑ ቤታቸውን ለ2ኛ ተከሣሽ ለአሁን 3ኛ ተጠሪ በግልፅ ኑዛዜ አስተላልፋልኝ የአሁን ተጠሪም የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው በደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ተረጋግጦ ከተወሰነ በኋላ የቤቱ የይዞታ ማረጋገጫ ወረቀት በስማቸው መስከረም 09 ቀን 1999 ዓ.ም. ከተዛወረ በኋላ ለአሁን አመልካች በሽያጭ አስተላልፈዋል፡፡ የቤቱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታም ሆነ ንብረቱ በእጄ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የአሁን 1ኛ ተጠሪ መብት በሌለው ንብረት ላይ የዕግድ ትዕዛዝ ማሰጠቱን ስለተረዳሁ በዚሁ ንብረት ላይ የተሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ የተከበረው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት እንዲነሳ ያድርግልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በኮ/መ/ቁ. 50497 አቤቱታ በቀረበበት ዕለት ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ዕግድ የሰጠበትን ንብረት ስለመግዛታቸው በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተረጋገጠ ውል ከመቅረቡ በቀር 3ኛ ወገኖችን ለመመለስ እንዲቻል ስለመመዝገቡ አላስረዱም፡፡ ስለሆነም የዕግድ ይነሳልኝ አቤቱታ ለከሣሽ ደርሶ መልስ ይስጡበት በማለት ማዘዝ ሳያስፈልግ አቤቱታው ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶበታል፡፡

ከዚህም በኋላ ክርክሩ በከሣሽና በተከሣሾች መካከል ቀጥሎ ከተጠናቀቀ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ባልነት በአዲስ አበባ የመ/ደ/ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ የጠበቃው ውክልናም በግሪክ አገር ኢምባሲና በውጭ ጉዳይ ሚ/ር በኩል ተረጋግጦ ቀርቧል፡፡ ጉዳዩም በኢትዮጵያ ፍ/ቤትም ሆነ ሕግ መሠረት ይዳኛል፡፡ ተከሣሾች የጋራ ሀብት ናቸው የተባሉት ንብረቶች የሉም በሚል አልተከራከሩም፡፡ ስለዚህ ንብረቶቹ የጋራ ሀብት ናቸው፡፡ ግማሽ ድርሻ የመካፈል መብት አላቸው በማለት ወስኗል፡፡

ይህ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ የአሁን አመልካች ይህን ውሣኔ ለሰጠው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በ25/5/2002 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ ያላቸውን መብት ለማስከበር ዝርዝር የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር በማቅረብ ዳኝነት ሲጠይቁ ፍ/ቤቱ በኮ/መ/ቁ. 50497 የካቲት 03 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የአሁን አመልካች ከዚህ በፊት ተመሳሳይ አቤቱታ አቅርበው ይህ ፍ/ቤት ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ ውሉ በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ያልተመዘገበ ስለሆነ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ አይሆንም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት የተሰናበቱ ስለሆነ በይዘቱ ተመሳሳይ አቤቱታ በድጋሚ ማቅረባቸው አግባብ አይደለም በሚል ትዕዛዝ አሰናብቷቸዋል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይኸው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 54796 በ11/9/2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤቱ የሰጠው ብይን የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት መዝገቡን በመዘጋቱ የአሁን አመልካች ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ጥቅል ይዘቱ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የካቲት 03 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ የሰጠው ዳኝነት በንብረቱ ላይ ያለኝን የመፋለም፣ የመከራከር መብት ያለ ሥርዓቱ የነፈገኝ ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ሆኖ ዝርዝሩም፡- ከዚህ በፊት በባለቤትነቱ በንብረቱ ላይ የተሰጠው የፅኖድ ትዕዛዝ እንዲነሳልኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት አቤቱታ አቀረብኩ እንጂ ሙሉ ክርክር ያቀረብኩበት አቤቱታ አይደለም፡፡

የሚች ወ/ሮ አረጋሽ ሺበሺ ንብረት በኑዛዜ ለአሁን 3ኛ ተጠሪ ተላልፎ የ3ኛ ተጠሪ የኑዛዜ ወራሽነት በፍ/ቤት ከተረጋገጠ በኋላ የንብረት ስመ-ሀብትነት ወደ ስሚ መዞሩን፣ ከዕዳና ዕገዳ ነፃ መሆኑን በማረጋገጥ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በተደረገ ውል በግዥ የተላለፈልኝ ንብረት ነው፡፡ ይህም የሽያጭ ውል ከቤቱ ማህደር ጋር ተያይዞ የሚገኝ ሲሆን የንብረት /የይዞታ/ ማረጋገጫ ካርታ እና ንብረቱ በእጄ ይገኛል፡፡ ይህ ንብረት የጋራ ሀብት ነው እንኳ ቢባል አንደኛው ተጋቢ ያለ ሥልጣኑ ወደ ሌላ ወገን አስተላልፎ ከተገኘ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 69 የተመለከተው ድነጋጌ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ይህንኑ የሽያጭ ውል አላስፈረሰም፡፡ ከሚች ሌላ የሀብት ድርሻ ላይ በማካካሻነት ከሚጠይቁ በቀር ሀብቱን ሊከተሉ አይችሉም፡፡ በመሆኑም በሕግ መሠረት በሽያጭ ያኘሁት ሀብት ያለአግባብ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው የሚል ውሣኔ መሰጠቱን ስረዳ ስለ ጉዳዩ ዝርዝር የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር በማቅረብ የመከራከር መብቴን ያስጠበቁበት የሕግ መሠረት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 የተመለከተው ሆኖ እያለ ክርክር የማሰማት መብቴን የሚነፍግ ዳኝነት መሰጠቱ ሥነ-ሥርዓታዊ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

በዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ ተጠሪዎች ቀርበው እንዲከራከሩ ጥሪ ሲተላለፍ ከተራ ቁጥር 2 እስከ 4ኛ ድረስ የተዘረዘሩት በጥሪው መሠረት ያልቀረቡ በመሆኑ ጉዳዩ እነርሱ በሌሉበት እንዲታይ ሲደረግ 1ኛ ተጠሪ በጠበቃው አማካኝነት፡- ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. እና ጥር 25 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ አመልካች ያቀረበው ጥያቄ አርዕስቱና የሕግ አንቀጹ ተለያዩ እንጂ ይዘቱ አንድ ነው፡፡ የኑዛዜ ሠነድ የተባለው ተሽሯል፡፡ ስለሆነም በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት ሲከራከር፤

5ኛ ተጠሪ በበኩሉ ሻጯ ቤቱን በስሚ ያዞረችው የቤቱ ባለቤት ሚች ወ/ሮ አረጋሽ በኑዛዜ ሰጥተውኛል በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ኑዛዜው በፍ/ቤት ተሰርዟል፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 69 የተመለከተው ድንጋጌ የውርስ ሀብት ክፍፍልን አይመለከትም፡፡ የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም የሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመለሰ መልስ የሰጠበት ሲሆን በይዘቱ ከዚህ በፊት ካቀረበው የተለየ አይደለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት ያቀረበውን ዝርዝር የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ለሰጠው ዳኝነት መሠረት አድርጎ የያዘው ይህ አቤቱታ በይዘቱ ከዚህ በፊት በ20/11/2001 ዓ.ም. ቀርቦ ዳኝነት ከተሰጠበት በይዘቱ የተለየ አይደለም፡፡ ተመሳሳይ አቤቱታ ሆኖ ስለተገኘ በድጋሚ ሊታይ የሚችልበት አግባብ የለም የሚለውን በመንተራስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአሁን አመልካች ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ ለፍ/ቤቱ የጠየቀው ዳኝነት በጉዳዩ ላይ የክርክር ተካፋይ ሆኖ በተከራካሪነቱ አቋም ያቀረበው ክርክር ሳይሆን በሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መካከል በተነሳው ሙግት ሳቢያ በንበረቱ ላይ ጊዜያዊ የማገጃ ትዕዛዝ መሰጠቱን ተረድቻለሁ፣ ይኸው ትዕዛዝ ይነሳልኝ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት ዳኝነት የጠየቀበት ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ከፍርዱ በፊት ጊዜያዊ ማገጃ ትዕዛዝ የሰጠበት ንብረት የአመልካች ንብረት ነው ለማለት የሚያበቃውን የንብረት ምዝገባ ሥርዓት ያሟላ ባለመሆኑ በዚህ ጊዜያዊ ማገጃ ትዕዛዝ ይነሳልኝ አቤቱታ ላይ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መልስ እንዲሰጡበት ማድረግ ሳያስፈልግ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት በዕለቱ ዕለት አቤቱታው በቀርበበት አግባብ ዳኝነት የሰጠበት እንጂ የአሁን አመልካች በንብረቱ ላይ ያለውን መብት በሚያሳይ አኳኋን ሙሉ የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አቅርቦ በዚሁ ክርክር ላይም የከሣሽና የተከሣሾች ክርክር ተሰምቶ ዳኝነት የተሰጠበት ትዕዛዝ አይደለም፡፡

ይልቁንም የዚህ ትዕዛዝ መነሻ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በከሣሽነትና በተከሣሽነት በሚከራከሩበት ጉዳይ ስለሚሰጠው ፍርድ አፈፃፀም ዋስትና ይሆን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 3ኛ መጽሐፍ ምዕራፍ 5 ሥር በተመለከቱት ሁኔታዎች በአንድ ንብረት ላይ ጊዜያዊ የማገጃ ትዕዛዝ በተሰጠ ጊዜ በዚህ ትዕዛዝ ላይ ቅሬታ ያላቸው ወገኖች በሚስተናገዱበት ሥርዓት መሠረት የቀረበ ጥያቄ እና የተሰጠ ዳኝነት እንደመሆኑ መጠን ለጉዳዩም ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች በዚህ የሕግ ክፍል የሚገኙት ናቸው፡፡

ከእነዚህም ድንጋጌዎች መካከል ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ንብረት በተከበረ ወይም ታግዶ እንዲቆይ በተደረገ ጊዜ መብት አለን የሚሉ እንደአሁኑ አመልካች ያሉ ሦስተኛ ወገኖች አቤቱታ ባቀረቡ ጊዜ የአቤቱታው አግባብነት የሚመረመረው በፍርድ አፈፃፀም ላይ ያለው ንብረት የሦስተኛ ወገን መብት ያለበት መሆኑ በሚመረመርበት ዓይነትና ሁኔታ (በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418-421) በተመለከተው መሠረት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 153/3/ ተመልክቷል፡፡ ይህም ዓይነት ምርመራ በንብረቱ ላይ ሦስተኛ ወገኖች ያላቸውን መብት ለመለየት ሲባል ቀለል ያለና አጭር ሥርዓትን የሚከተል እንጂ ሙሉ የክርክር አካሄድን (Ordinary Judicial Proceeding) የሚጋብዝ ባለመሆኑ በጊዜያዊ ማገጃ ትዕዛዝ እንዲነሳ የቀረበ ጥያቄ ውድቅ በተደረገ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሠረት ለክርክሩ መነሻ በመሆነው ንብረት ላይ ክስ የማቅረብ መብትን በማይነፍግ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

በዚህም በተያዘው ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ የቀረበለትን ጊዜያዊ የንብረት ማገጃ ትዕዛዝ ይነሳልኝ ጥያቄ ብቻ እንደቀረበለት በዚህ ጥያቄ ላይ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች /ከሣሽና ተከሣሾች/ መልስ መስጠት የማያስፈልጋቸው ሆኖ አልተገኘም በማለት በአጭር ሥርዓት ተመልክቶ ትዕዛዝ የሰጠበት እንጂ አመልካች የክርክር ተካፋይ ሆኖ በጉዳዩ ላይ የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ ያላቸው ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ የተሟላ የሙግት ሥርዓትን በመከተል የተሰጠ ዳኝነት ባለመሆኑ በዚሁ ንብረት ላይ የአሁን አመልካች አለኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚለውን መብት ለማስከበር የመደመጥ መብቱ ተከብሮ ዳኝነት ማግኘት ይችል ዘንድ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚከለክለው ሥርዓት አልተገኘም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የተዘረጋው ሥርዓት አስቀድሞ በተሰጠው ውሣኔ መብቱ የሚነካበት ወገን ባለበት እንደገና ውሣኔ እንዳልተሰጠበት ተቆጥሮ እንደገና ክርክር የሚጀምርበት ሥርዓት በመሆኑ በውጤት ደረጃ አዲስ ክስ ከማቅረብ ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ ይህም ሲባል አሁን የተነሣውን ክርክር መነሻና መድረሻ መሠረት በማድረግ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ክፍል አንፃር በማየት የአሁን አመልካች ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ ያለው የመሟገት መብት የተጠበቀ ነው ለማለት እንጂ በማንኛውም ጉዳይ ቢሆን በአንድ ጉዳይ ላይ ክርክር መጀመሩን ያወቀ ወገን የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከውሣኔ በኋላ የመሟገት መብት አለው በማለት ለፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 የተለጠጠ ትርጉም ለመስጠት ተፈልጎ አይደለም፡፡ ይህ ዓይነት አተረጓጎም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግን መሠረታዊ ዓላማ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የከፍተኛው ፍ/ቤት ሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም. የቀረበለት ጥያቄ እና ለጥያቄው የሰጠው ዳኝነት ከጊዜያዊ የማገጃ ትዕዛዝ አነሳስ ጋር የተያያዘ መሆኑ እየታወቀ አስቀድሞ ሙሉ ክርክር ተደርጎበት ዳኝነት እንዳገኘ ጉዳይ በመቁጠር አመልካች በንብረቱ ላይ ያለውን መብት ለማስከበር ሲል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ያቀረበው የተሟላ የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አስቀድሞ ዳኝነት ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ በድጋሚ ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ ተቀባይነት የለውም በሚል የተሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ከፍተኛው ፍ/ቤት እንደ ቅደም ተከተሉ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 54796 በ11/9/2002 እና በኮ/መ/ቁ. 50497 ጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰጠ ትዕዛዝ እና ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች ክርክር የቀረበበትን ንብረት በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 13/14 የሚገኘውንና ቁጥሩ አዲስ የሆነውን በካርታ ቁጥር ሊዝ/06/8328/02/8388 አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት በቀረበው የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር መሠረት ጉዳዩ እንደገና ታይቶ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ሆኖ ስለተገኘ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚሁ መሠረት አከራክሮ ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት መልሰናል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ውጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ አቶ በቀለ አማረ /ሁለት ሰዎች/ 1ኛው አመልካች ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ብዙነሽ ግርማ ጠበቃ ጉታ ጫካ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ጋብቻን መሠረት ያደረገ የንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ በአርሲ ዞን ጢዮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካቾች አባት ጋር ተጋብተው ሲኖሩ ባለቤታቸው ከዚህ አለም በሚያዚያ 07 ቀን 1981 ዓ.ም በሞት መለየታቸውን በሚች ስም የተመዘገበ የጋራ ቤት እንዳላቸው ተጠሪ ቤቱን በአደራ እያስተዳደሩ አመልካቾች ድርሻቸውን እንዲካፈሉ ቢጠይቁም ሳይከፋፈሉ መቆየታቸውን አመልካቾችን በማክበር የንብረቱን ክፍፍል ሳይጠይቁ መቆየታቸውን በመግለጽ አመልካቾች ድርሻቸውን እንዲካፈሉ እና የእርሳቸውም ድርሻ እንዲሰጣቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት ክርክር ጉዳዩ በእርቅ ያለቀ መሆኑን የሚጠቅስ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ አባታቸው ቤቱን ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት የሰሩት የግል ሀብት መሆኑን ሚች ቤቱን በተመለከተ ያደረጉት ኑዛዜ አለመግባባት በመፍጠሩ ወራሾች ስለቤቱ አጠባበቅና ክፍፍል በተመለከተ ግንቦት 21 ቀን 1981 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት ማድረጋቸውንና ተጠሪ የልጆቻቸው ሞግዚት በመሆን ፈርመው እና ስምምነቱ በፍርድ ቤቱ ፀድቆ ያለ በመሆኑ ክስ ሊቀርብ እንደማይገባ በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ከአመልካቾች አባት ጋር ሚስት በመሆኑ አብረው እስከኖሩና አመልካቾች ቤቱ የአባታቸው የግል ሀብት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ እስካላቀረቡ ድረስ ሚችና ተጠሪ በጋራ የሚጠቀሙበት ቤት የጋራ ሀብት መሆኑንና ተደረገ የተባለውም የእርቅ ስምምነት በወራሾች መካከል የተደረገ በመሆኑ በተጠሪ ላይ ተፈፃሚነት የለውም የሚል ምክንያት በመያዝ ተጠሪ የቤቱ ግማሽ ድርሻ ይገባቸዋል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ የካቲት 04 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተሰራ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎች ተቆጥረው እያለ ሳይሰሙ ውሣኔ መስጠቱ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የአመልካቾች አባት እና ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት የአመልካቾች አባት የሰሩት ቤት ስለሆነ የጋራ ሊባል አይገባም በማለት አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ክርክር አቅርበው ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተሰራ ስለመሆኑ ያስረዱልናል በማለት የቆጠሯቸው ምስክሮች ሳይሰሙ የስር ፍርድ ቤቶች ቤቱ የጋራ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ አምስት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም የአመልካቾች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆንና ጋብቻው መቼ እንደተፈጸመ ገልጸው ያልተከራከሩ መሆኑን በመጥቀስ ማስረጃ ሳይሰማ ውሣኔ ተሰጥቷል የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃም በመልስ መልሳቸው ላይ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት አከራካሪው ቤት ከአመልካቾች አባት ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ የተፈራ መሆኑን ገልፀው አመልካቾች ተጠሪ የአውራሻቸው ሚስት የነበሩ መሆኑን ሳይክዱ የሚከራከሩት አከራካሪው ንብረት ተጠሪ ከሟች አባታቸው ጋር ጋብቻ ከመፈፀማቸው በፊት የተሰራ በመሆኑ የጋብቻ ውጤት አይደለም በማለት መሆኑን ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው አመልካቾች አከራካሪው ንብረት የተፈራው አውራሻቸው ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ከመመስረታቸው በፊት ነው በማለት ቢከራከሩም ተጠሪ ግን ቤቱ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአመልካቾች ክርክር እንደተገለፀው ቤቱ ከጋብቻ በፊት በአውራሻቸው ስለመፈራቱ ተጠቅሶ ይህንኑ ፍሬ ነገር ለማስረዳት ምስክሮችን ቆጥረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካቾች የቆጠሯቸው ማስረጃዎች በስር ፍርድ ቤት አልተሰሙም ፍ/ቤቱ በቂ የሆነ ማጣራትም አላደረገም፡፡

በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የተካደ ወይም ያልተማመኑበት የፍሬ ነገር ነጥብ የሚነጥረው በማስረጃ ነው፡፡ በግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የተቆጠረና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በአግባቡ መስማት አንዱና ዋነኛው የፍርድ አመራር ስርዓት መሠረታዊ መርህ ነው፡፡ በእርግጥ በተከራካሪ ወገን የቀረበ ማስረጃ ሁሉ ያለምንም ምክንያት መሰማት አለበት ማለት እንዳልሆነ የማስረጃ ደንቦች የሚያሳዩን ጉዳይ ነው፡፡ የተቆጠረው ማስረጃ ለተያዘው ክርክር አግባብነት የሌለው ሆኖ ከተገኘ ውድቅ የሚደረገው እንዲሁ በደፈናው ሣይሆን ምክንያቱን በግልጽ በጽሑፍ በማስፈር ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ 138/፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደምናየው የስር ፍ/ቤቶች ወደ ውሣኔ ያመሩት በአመልካቾች የተቆጠረውን ማስረጃ አስቀርበው ሣያዩ እና ሣይመረምሩ ነው፡፡ ማስረጃው ቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተሰራበትን ጊዜና ሁኔታ ያረጋግጣሉ የተባሉት የሰው ምስክሮች ሲሆኑ ምስክሮች የሚሰጡት ቃል ደግሞ ቤቱ የጋብቻ ውጤት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ለመፍታት አግባብነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የምስክሮችን ቃል ሳይሰማና ክብደቱን ከተያዘው ጭብጥ ጋር አገናዝቦ ሣይመረምር ብቃት ያለው ማስረጃ አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ ሊደርስ አይችልም አይገባምም፡፡ አንደ ሰው ለቀረበበት ክስ መከላከያ ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት እስካለው ድረስ ማሰማት የሕግ ስርዓቱ /Due Process of law/ የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ መብትም ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ ተቆጥሮ እያለ ማስረጃው ሳይሰማ ወደፍርድ ማምራት አይቻልም፡፡ ፍርድ ሊሰጥ የሚገባው የክርክር አመራር ሥርዓት በተገቢው መንገድ ከተሟላ በኃላ ነው፡፡ የመከላከያ ማስረጃ በሥነ ሥርዓቱ አግባብ ተቆጥሮ እያለ ይኸው ሳይሟላ የሚሰጥ ፍርድ አካሄዱ የተሟላ ነው ሊባል አይችልም፡፡ የፍርድ አካሄዱ ያልተሟላ ውሣኔ ደግሞ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

እነዚህን ሁኔታዎች ደምረን ስንመለከት ፍ/ቤቱ ወደ ውሣኔ ያመራው ምንም ዓይነት ማስረጃ ሣይሰማ እንደሆነ ነው፡፡ በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረው ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ሣያጣሩ/ሣያነጥሩ/ መወሰን ደግሞ ዋነኛው መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀም ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔም የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብት ያልጠበቀ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአርሲ ዞን ጢዮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 08970 ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 16409 ጥቅምት 21 ቀን 2001 ዓ.ም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመ/ቁጥር 71266 ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲሁም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 90774 ህዳር 14 ቀን 2002 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የጢዮ ወረዳ ፍርድ ቤት በተከፈተው መዝገብ ቁ 08970 ክርክሩ እንዲቀጥል በማድረግ እና በአመልካቾች የተቆጠሩትን ማስረጃዎች በመስማት እንዲሁም የተጠሪንም ማስረጃ የማሰማት መብት በመጠበቅ ክርክሩን መርምሮ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፣ ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች - ማበርፋይድ ኃ/የተ/የግል ማህበር

ተጠሪዎች - 1. አሸናፊ አለሙ

2. በለጠ እሸቱ

3. አብዮት ጉግሳ

4. ወንድወሰን ጌቱ

5. አባይነህ ደምሴ

6. ሰሎሞን ይገዙ

7. ኤልያስ አክመል

8. ሳህሌ ከበደ

9. እንግዳ ደበሌ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኞች መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክር በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች አመልካችን የከሰሱት የሥራ ውላችን ከሕግ ውጪ አቋርጦብናል በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪዎች ያለበቂ ምክንያት ከሥራ በመቅረታቸው ነው በማለት ተከራክሮአል ከዚህም በተጨማሪ 1ኛ፣3ኛ፣5ኛ፣ 7ኛ፣ 8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎች ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ዕለት በመቅረታቸው ምክንያት ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ ከተደረጉ በኃላ ክርክሩ ውስጥ እንዳሉ በመቁጠር መመዘገባቸው ትክክል አይደለም በማለት አመልካች መከራከሩን ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቱ በአመልካች የቀረበውን ክርክር ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች የተለያዩ ክፍያዎች እንዲያገኙ ወስኖአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም አመልካች ሚያዚያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው 1ኛ፣3ኛ፣5ኛ፣7ኛ፣8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎች ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ እነሱ ሳይጠይቁ የሥር ፍ/ቤት ትዕዛዙን በማንሳት እነሱንም በመጨመር ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው 2ኛ 4ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎችን በሚመለከት እንደውሣኔው እፈጽማለሁ በማለት የአመልካች ጠበቃ ተጠሪዎች ግን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት ተሰምቶአል፡፡

በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በዝርዝር ተመልክተናል በእርግጥም ከሣሾች ሆነው በፍ/ቤቱ መዝገብ የተመለከቱት ዘጠኙም ተጠሪዎች ቢሆኑም ክርክሩ ሊሰማ ቀነ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት የቀረቡት ግን 2ኛ 4ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች እንደሆኑ እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ይህን ሁኔታ በመገንዘብ እንደዚሁም የአመልካች ጠበቃ ያቀረበውን አቤቱታ በመስማት 1ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ፣ 7ኛ፣8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎችን /ተከሣሾችን/ ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ አድርጎ እንደነበር ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ በአንድ በኩል የሆነው የክርክሩ ሂደት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ፍ/ቤቱ ትዕዛዙን በማንሳት ተጠሪዎቹ በክርክሩ ውስጥ እንዳሉ በመቁጠር ቀሪውን የክርክር ሂደት አጠናቆ ውሣኔ እንደሰጠ ተገንዝበናል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ 7ኛ፣ 8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 73 በተደነገገው መሠረት ትዕዛዝ ሰጥቶ ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ አድርጎአል ከዚህ በኃላ ተጠሪዎቹ ክርክሩ ውስጥ እንዳሉ በማድረግ የወሰነው ደግሞ ጉዳዩን ቀጥሎ ባለው የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ /ቁ 74/ ከተቀመጠው ሥርዓት ውጪ በሆነ ሁኔታ እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪዎቹ እነሱን በተመለከተ የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲነሳላቸው አላመለከቱም ከሁሉ በላይ ደግሞ ተጠሪዎቹ በየግላቸው ከአመልካች ጋር ባላቸው የሥራ ውል መሠረት ክርክር አልተደረገም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ተጠሪዎቹ የክርክሩ ተካፋይ እንደሆኑ አድርጎ በመወሰኑ ውሣኔው ከሥነ ሥርዓት ሕጉ አተገባበርም ሆነ ለውሣኔው መሠረት ሊሆን የሚገባውን ፍሬ ነገር ከመጨበጥ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13664 ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና ይህን ውሣኔ በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 83507 የካቲት 18 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች 1ኛ፣3ኛ፣5ኛ፣7ኛ፣8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎችን በሚመለከት በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ እንዲፈጽም አይገደድም በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሣስ 27 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኮንስትራክሽንና የቢዝነስ ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ ነጋ አበበ ቀረቡ

ተጠሪ ፡-1. ወ/ሮ መድኃኒት ኃይሉ ጠበቃ መኮንን ይማም ቀረቡ

2. አቶ ጌታቸው ተሰማ

መዝገቡ በአዳሪ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን የፍርድ ባለመብት የሆነው የአሁኑ ተጠሪዎች በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የአፈፃፀም ማመልከቻ እስከዚህ ሰበር ችሎት እንዲከፈላቸው የተወሰነው ብር 1,307,607.00 /አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰባት ብር/ ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲፈጸምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪዎች አፈፃፀም መዝገብን በመቀበል እንደፍርዱ የማይፈጸምበትን ምክንያት አመልካች ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም እንደፍርዱ ፈፅሞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የአሁኑ አመልካች ቀርቦ ተጠሪዎች በ27/07/1985 እና በ07/04/1986 ዓ.ም. በተፈረሙ የብድር ውሎች ከአመልካች ላይ የወሰዱትን ገንዘብ በውሉ መሠረት ከሚያስከትለው ወለድ፣ የኢንሹራንስ ክፍያ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር ብር 858,457.38 /ስምንት መቶ ሃምሣ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሃምሣ ሰባት ብር ከሠላሣ ስምንት ሣንቲም/ እና አመልካች ሆቴል ቤቱን በጨረታ ከገዛው በኋላ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ምክንያት በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች ሆቴል ቤቱን እንዳይረከብ በማሳገድ ያላግባብ ስለተጠቀሙት አመልካች ሆቴል ቤቱን በወቅቱ ተረክቦ ቢሆን ኖሮ ከሆቴል ቤቱ ሊያገኝ የነበረውን የቤት ኪራይ ብር 604,000.00 /ስድስት መቶ አራት ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 1,460,457.38/ አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ስልሣ ሺህ አራት መቶ ሃምሣ ሰባት ብር ከሠላሣ ስምንት ሣንቲም/ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚያስከትለው ወለድ እና ከክሱ ወጪ እና ኪሣራ ጋር እንዲከፍሉት በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀጥታ ክስ ማቅረቡን በመግለጽ አፈፃፀሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 መሠረት እንዲቆምለት ወይም ገንዘቡ ታግዶ እንዲቆይለት አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አመልክቷል፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤትም አመልካች ያቀረበውን አቤቱታና እግድ ውድቅ በማድረግ አመልካች በፍርዱ መሠረት ፈጽሞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም. በጻፉት አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች የአፈፃፀም ትዕዛዝ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

ይዘቱም ባጭሩ፡-

አመልካች ከተጠሪዎች የሚፈለግ ዕዳ መኖሩን ገልፆ ቀጥታ ክስ በመመስረት ጉዳዩ እየታየ ባለበት ሁኔታ ተጠሪዎች የከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ እንዳይቆም መደረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 ድንጋጌን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የፍርድ ባለመብት በሆኑት ተጠሪዎች ላይ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ በቀጠሮ ላይ ባለበት ሁኔታ አፈፃፀሙ የመቀጠሉ አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅም የመልስ መልሳቸውን በጽሑፍ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አመልካች በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሠረተው ቀጥታ ክስ በመ/ቁጥር 64235 በሆነው ታይቶ ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም. ውድቅ መሆኑን፣ እንዲሁም በዚሁ ውሣኔ ላይ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ በመ/ቁጥር 57640 በሆነው የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መጽናቱ ተረጋግጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ፍርድ በተፈረደበት ማናቸውም ሰው ላይ ፍርድ የተፈረደለት ወገን ክስ ያቀረበበት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የገመተውን በቂ ዋስትና ወይም መያዣ እንዲሰጥ ካደረገ በሁዋላ ለክርክሩ ውሣኔ እስከሚሰጠው ድረስ አፈፃፀሙ ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው በቀድሞው ክስና በአፈፃፀሙ ጊዜ በቀረበው ክስ ተከራካሪ የሆኑት ወገኖች ተመሳሳይ መሆን እንደሚገባቸው ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ የተሰጠው የተጠሪዎችን ሆቴል ከግምቱ ውጪ ሸጧል በሚል ምክንያት ሲሆን ይህ ውሣኔ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቷል፡፡ አመልካች ከዚህ በሁዋላ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው በብድር ውሉና በሐራጅ ገዝቼዋለሁ በሚለው ቤት የቀረበትን ጥቅም በመዘርዘር ነው፡፡ አፈፃፀሙ እንዲታገድ የጠየቀውም ይህንኑ ክስ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 ዓላማ የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን አፈፃፀሙን በሚቀጥልበት ጊዜ የፍርድ ባለዕዳው በበኩሉ በፍርድ ባለመብቱ ላይ ክስ አቅርቦ ሲገኝ ምናልባት በክርክሩ ረቺ ቢሆን ፍርዱን ጎን ለጎን ለማስፈጸም እንዲቻል ለማድረግ መሆኑ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የፍርድ ባለመብት በሆኑት ተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው አስቀድሞ ታይቶ በተወሰነው ጉዳይ ሳይከፈለኝ የቀረ ዕዳ አለ፣ በጨረታ የተሸጠውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆቴል ደገሞ በጊዜው በመረከብ አከራይቼ ላገኝ እችል የነበረውን ጥቅም አስቀርተውብኛል በሚል ሲሆን ይህ አካሄድ መጨረሻ ላይ ጎን ለጎን ሊፈፀም የሚችል ፍርድ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 377 ድንጋጌ ዓላማ ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡ አመልካች ያቀረበውን ቀጥታ ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ሲመለከተው የነበረው ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፡፡ አመልካች አሁን የቀረው የመጨረሻ እድሉ ጉዳዩን በሰበር ማሳየት ነው፡፡ በሰበር ሰሚው ችሎት ጉዳዩ የሕግ ነጥብ አለበት የሚባል ከሆነም አመልካች ሥርዓቱን ጠብቆ ለተጠሪዎች የሚከፍለው ገንዘብ እንዲከበርለት ከሚጠይቅ በስተቀር አሁን የሥር ፍርድ ቤት የያዘውን አፈጻጸም ሙሉ በሙሉ እንዲቆም የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በአሁኑ ደረጃ ሲታይ ስህተት ነው ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1) በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2) በዚህ ሰበር ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 29 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ፋጡማ ኡስማን ከጠበቃ መሐመድ ሀሰን ጋር - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሠረት የሚስተናገደውን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ሽሪዓ ፍ/ቤት ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሠረት አቤቱታውን ያቀረቡት የአሁኑ አመልካች ናቸው፡፡ የአመልካች የአቤቱታ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች በከፍተኛ ሽሪዓ ፍርድ ቤት በነበረው የይግባኝ ክርክር የክርክሩ ተካፋይ መሆን ሲገባቸው ሣይከራከሩበት በቀድሞ አወቃቀር በወረዳ 08 ፣ ቀበሌ 02 ክልል ወስጥ በሚገኝና ቁጥሩ 102 በሆነው የግል የመኖሪያ ቤታቸው ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ መብታቸውን የሚጐዳ ከመሆኑም በላይ በተከሰሱበት ጉዳይ የመከላከል ህገ መንግስታዊ መብታቸውን የሚጋፋ በመሆኑ አመልካች በሌሉበት የተሰጠው ውሣኔ ተነስቶ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ይደረግላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ጋርም ከውጭ አገር የነበሩ መሆኑን የሚያሣዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘው አቅርበዋል፡ አቤቱታው የቀረበለት ከፍተኛ ሽሪዓ ፍርድ ቤትም አመልካች አቤቱታውን ያቀረቡት ጉዳዩ ውሣኔ ካገኘ ከስድስት ዓመት በሁዋላ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ የቤተሰብ እንደመሆኑ መጠን አልሰሙም ነበር ለማለትም የሚቻል አይደለም በሚል ምክንያት የአመልካች አቤቱታን ውድቅ አድርጐ ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ጠቅላይ ሽሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ በከፍተኛው ሽሪዓ ፍርድ ቤት በነበረው የይግባኝ ክርክር አመልካች በወኪላቸዉ አማካኝነት የክርክሩ ተካፋይ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡን ጉዳዩ የቤተሰብ ከመሆኑም በላይ አመልካች ይኖሩበት ከነበረው ውጪ አገር ወደ ኢትዮጵያ ሲመላለሱ የነበረ መሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት በመያዝ በይግባኙ ክርክር ውሣኔ ከተሰጠ ከስድስት ዓመት በሁዋላ ጉዳዩ ባለሁበት ይታይልኝ ተብሎ የቀረበው የአመልካች ጥያቄ በህጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበና በበቂና ህጋዊ ምክንያት ያልተደገፈ ነው በማለት የከፍተኛ ሽሪዓ ፍርድ ቤትን ብይን አጽንቶታል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህኑን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ሲታይም የክርክሩ ተካፋይ ሣይሆኑ በግል ገንዘባቸው በገዙት ቤት ላይ ተገቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያልሆነ ውሣኔ ማረፋን ገልጸው የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው ህጋዊ አለመሆኑን በመዘርዘር ውሣኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት ሊታይ የሚችልበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን ሣያረጋግጡ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሠረት ወደ ክርክሩ ለመግባት በቂ ምክንያት የላትም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጉአል፡፡ በዚህም መሠረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጉላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ ክርክር አድርገዋል፡፡ ከላይ የተመለከተው የክርክሩ አመጣጥ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ካስቀረብነው የመ/ቁጥር 51/93 እና 4640/2001 ፣ ከፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ካስቀረብነው መ/ቁጥር 68/2002 ጋር አዛምደን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ተጠሪ በሌሉበት የተሰጠው ውሣኔ ሊነሣ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ መመልከቱ ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

የፍታብሔር ክርክሮች የሚመሩት በ1958 ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ መሠረት ነው፡፡ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የክርክር አመራር ስርዓትም በዚህ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 6/1/ ድንጋጌ በግልጽ ያሣያል፡፡ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አካቶ ከያዛቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የተከራካሪ ወገኖች በክርክሩ ወቅት ያለመቅረብና ውጤቱ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መጥሪያ ተልኮለት በተገቢው መንገድ የደረሰው መሆኑ በተረጋገጠበት ተከሣሽ /መልስ ሰጪ/ ላይ ፍ/ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓት ጉዳዩ ተከሣሹ/መልስ ሰጪ በሌለበት የሚሰማበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70/ሀ/ ስር ተመልክቷል፡፡ ሌላው በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተው ሥርዓት ተከሳሹ ሊከተለው የሚገባው መፍትሔ ነው፡፡ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል የተደረገበት ተከሣሽ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ ያለመቅረቡን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 72 ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78/1/ አንድ ተከሣሽ /መልስ ሰጪ/ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሣይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሣያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠ ከሆነ ውሣኔው ወይም ትዕዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትዕዛዙ ወይም ውሣኔው እንዲነሣለት የማመልከት መብት እንዳለው ተደግንጓል፡፡ አቤቱታ አቅራቢ በዚህ መሠረት ማመልከቻ በሚያቀርብበት ጊዜ የጥሪው ትዕዛዝ በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን ወይም ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ቀርቦ መከራከሪያውን ያላሰማው ወይም መልስ ያልሰጠው በበቂ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳ እንደሆነ የተከሣሹ /የመልስ ሰጪ/ አቤቱታ ላንደኛው ወገን ተከራካሪ እንዲደርሰው ካደረገና ተገቢውን ኪሣራ ወይም መቀጮ እንዲከፍል ካዘዘ በኋላ ትዕዛዙን ወይም ብይኑን በማንሣት ክርክሩን እንደገና መስማት እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78/2/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሣያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በሌለሁበት በግል ንብረቱ ላይ ውሣኔ ተሰጥቶብኛል የሚሉት ጥር 09 ቀን 1995 ዓ.ም ሲሆን ይኸው ውሣኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ ልገባ ይገባል በማለት አቤቱታ ያቀረቡት ደግሞ ነሐሴ 19 ቀን 2001 ዓ.ም ነው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት የስር ፍርድ ቤቶች መዛግብት መገንዘብ የተቻለው ደግሞ የአሁኗ አመልካች ወ/ሮ ኑሪያ ኡስማን /የሚች ሚስት/ እና ሌሎች አምስት የሚሆኑ የሚች ጀማል ሐምዛ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸውን ገልጸው በሸሪዓ ህግ መሠረት የውርስ ንብረቱን ለመከፋፈል ንብረቱን ይዘዋል፣ የሚች ሁለተኛ ሚስት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ናቸው ባሏቸው የአሁኗ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ ከሰጠ በሁዋላ ተጠሪ የአሁን አመልካች በግል የገዛሁት ንብረቴ ነው በሚሉት ቤት ላይ የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው የስር ከሣሾች የነበሩት፤ የአሁኗ አመልካች ጭምር በወ/ሪት ቀመሪያ ጀማል አማካኝነት ተወክለው የይግባኝ ክርክሩ ተካሂዶ አከራካሪው ንብረት ላይ ተገቢ ነው የተባለ ውሣኔ የተሰጠበት መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ራሣቸው የክርክሩ ተካፋይ ባይሆኑም በህጉ አግባብ የወከሏቸው እህታቸዉ ወ/ሪት ቀመሪያ ጀማል የክርክሩ ተካፋይ የነበሩ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት መዛግብት በሚገባ ያረጋግጣሉ፡፡ ይህም የሚያሣየው አመልካች በህጉ አግባብ የክርክሩ ተካፋይ የነበሩ መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አንድ ሰው በውሣኔው ላይ የሚኖረውን ቅሬታ በይግባኝ ወይም በሰበር ስርዓት ማሣረም እንጂ ጉዳዩ በሌለሁበት ታይቷል፡፡ ባለሁበት ሊታይልኝ ይገባል በማለት አቤቱታ የሚያቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ ሲታይም አከራካሪው ንብረት የክርክሩ ምክንያት የነበረ መሆኑንና አመልካችም በህጉ አግባብ ተወክለው የነበሩ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሣይ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት የአመልካች አቤቱታ ሊስተናገድ ይገባ ነበር ሊባይ የሚችል ባለመሆኑ ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በሌለሁበት የተሰጠው ውሣኔ ይነሣልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 ስር የተመለከተውን መመዘኛ መሠረት ያደረገ ሲሆን አመልካች የግል ቤቱ ላይ ተገቢ ያልሆነ ውሣኔ ተሰጥቷል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ደግሞ በይዘቱ በዋና ጉዳይ ላይ የቀረበ በመሆኑ የክርክሩን አመራር ስርዓት ካልሆነ በስተቀር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በስረ ነገር ስልጣናቸው ስር የሆኑ ጉዳዮች የሚቀርብላቸዉን አቤቱታና ክርክር የሚወስኑት የሸሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/92 በአንቀጽ 6/1/ በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ አንድ ሰው ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ሲያቀርብና ተገቢ የተባለ ውሣኔ ከተሰጠ ሥነ ሥርዓታዊ ከሆነው ጭብጥና ጥያቄ ውጭ የሆኑት ጉዳዮች ለዚህ ሰበር ችሎት ለማቅረብ የሚቻልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አላገኘንም፡፡ በዚህም መሠረት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68/2002 ሐምሌ 28 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አንድ ተከራካሪ ወገን በህጉ አግባብ በተወከለው ሰው የክርክሩ ተካፋይ መሆኑ ከተረጋገጠ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሠረት በሌለሁበት የተሰጠ ውሣኔ ሊነሣልኝ ይገባል ለማለት አይችልም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ጥር 19 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኦሮሚያ ከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት - ነ/ፈጅ ለገሠ ለማ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. አቶ ካሣ ጭርሳ
2. አቶ ሽፈራ ሒምቤ } ቀረቡ
3. አቶ አክሊሉ ካሣ
4. የቡሌ ሆራ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ ፈቃዱ ኤሌማ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍርድን መቃወም የሚቻልበትና አቤቱታው የሚስተናግድበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ባሁኑ 4ኛ ተጠሪ ላይ ያስፈረዱት ፍርድ የአመልካችን መብትና ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ፍርዱ እንዲነሳለት ባቀረበው አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም አመልካችንና ተጠሪዎችን በአፈፃፀም መዝገቡ ላይ እንዲከራከሩ በማድረግ አመልካች ዋናውን ውሳኔ በይግባኝ ሳያሽር አፈፃፀሙን ሊቃወም አይችልም፣ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያትም የለም በማለት አፈፃፀሙ ሊቀጥል ይገባል ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትእዛዝ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የሰበር አቤቱታውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የአፈጻጸም ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ግንቦት 04 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፉት አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ አመልካች በሕጉ በተሰጠው ስልጣን ለክልሉ ከተሞች እንደየደረጃቸው ከተማ አቀፍ መዋቅራዊ ፕላን እና የአካባቢ ልማት ፕላን (City wide structure plan and local development plan) እየሰራና እያሰራ ስራ ላይ እንዲውል የማድረግና ስራ ላይ መዋሉን የመቆጣጠር ኃላፊነቱንና ተግባሩን ለመወጣት የሚችል ሁኖ እያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህንኑ ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች ከከተማው ፕላን ውጪ ቦታ ሊወስዱ አይገባም በማለት ያቀረበው የፍርድ ተቃውሞ ተቀባይነት ያጣው ያላግባብ መሆኑንና አቤቱታው የቀረበውም ዋናውን ፍርድ በመቃወም ሁኖ እያለ በአፈፃፀም መዝገብ ላይ እንደቀረበ ተደርጎ ትእዛዝ መሰጠቱ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ ዋናውን ፍርድ ሕጋዊ አይደለም በማለትም ተገቢው ክርክርና ማስረጃ ቀርቦ እያለና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 መሰረትም አግባብነት ያለው ማስረጃ በፍርድ ቤቱ እገዛ እንዲቀርብ ጥያቄ ቀርቦ እያለ ይኸው ታልፎ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊሻር አይገባም ተብሎ የተሰጠው ትእዛዝ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም በማለት ዘርዝረው የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች የፍርድ ተቃውሞ አቤቱታ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው መልሳቸውን በፅሑፍ አቅርበዋል፣ አመልካችም የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ አንድ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራበት ሥርዓት የሚገዛው በ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን እና በክልሎች ስራ ላይ ባሉት አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሆኑ እሙን ነው፡፡ የ1958ቱ የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕጋችን ከያዛቸው ስርዓቶች መካከል በፍርድ ላይ የሚቀርበው ተቃውሞ እና በፍርድ አፈጻጸም ጊዜ በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ የሚቀርበው ጣልቃ ገብነትን የሚገዙት ድንጋጌዎች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ አቤቱታዎችን የሚገዙት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 እና 418 ስር የተመለከቱት ናቸው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አንድ የክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚገባው ሰው የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ውሳኔ ተሰጥቶ ከሆነ እና ውሳኔውም ያረፈው በአንድ የክርክሩ ምክንያት በሆነ ንብረት ላይ ሁኖ ይህንኑ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገንን መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑ ከተረጋገጠ ፍርዱ ይኸው ወገን ባለበት እንዲታይና እንዲነሳለት የሚደነግግ ነው፡፡ አቤቱታው የሚቀርብበት ሥርዓትም በቁጥር 359 ስር በተመለከተው መንገድ መሆን እንደአለበት የተቀመጠ ሲሆን ይህ ድንጋጌ የመቃወሚያ አቤቱታ አቀራረብ በክስ አመሰራረት አይነት ሁኖ የማስረጃ ዝርዝር ሁሉ ይህንኑ ስርዓት ማሟላት እንደአለበት ያስገነዝባል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት የሚቀርበው አቤቱታ ደግሞ ለፍርድ ማስፈጸሚያ እንዲሆን የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት የፍርድ ባለእዳው ንብረት አይደለም፣ የራሴ ንብረት ነው የሚል ወገን አቤቱታውን የሚያቀርብበትን አግባብ የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አቤቱታ አቅራቢ የሚሆን ወገን በሕጉ አግባብ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ሲሆን ስርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበን አቤቱታ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ሊቀበል የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን በፍትሐብሔር ስነ ስርአት ስለ ክርክር አመራር የተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚያሳዩን ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች አቤቱታውን ያቀረበው በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ፍርድ መብትና ጥቅሜን ይነካል በሚል ሲሆን አቤቱታውን የስር ፍርድ ቤት ያስተናገደው ግን በፍርድ አፈጻጸም መዝገብ ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካች የፍርድ ተቃውሞ አቀራረብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 ድንጋጌን መሰረት ያደረገ ሳይሆን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358ን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአፈጻጸም መዝገብ የሚቀበልበት ሥርዓት የሌለ ሲሆን አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መሰረት በዋናው ጉዳይ የተሰጠውን ፍርድ በያዘው መዝገብ ላይ ማስተናገድ ነበረበት፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት እንደተቻለው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዳይከራከር በስር ፍርድ ቤቱ የተከለከለው በአፈጻጸም መዝገብ አቤቱታውን እንደአቀረበ ተቆጥሮ ከመሆኑም በላይ ተጠሪዎች ከፍርድ ባለእዳው ነው ከተባለው 4ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለውን ደንብ የሚጥስ አይደለም፣ ውሉ ሲመሰረትም አመልካች አልተመሰረተም፣ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ፍርድ በይግባኝም አልተለወጠም በሚል ነው፡፡ በእርግጥ እነዚህ ሁለት አካላት በአንድ መንግስታዊ መዋቅር (በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስተዳደር) ስር የሚገኙ አካላት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ የክልል መንግሥታዊ መዋቅር ስር መገኘታቸው ብቻ አከራካሪውን የመሬት ይዞታ በተመለከተ ተመሣሣይ ጥቅምን የሚወክሉ አካላት ናቸው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፤ እነዚህ ሁለት አካላት የክልሉ መስተዳድሩ የተለያዩ እርከኖች ወይም አካላት ሆነው የየራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት፣ ስልጣንና ተግባር እንዳላቸው የሚታመን ነው፡፡ ይህ ነጥብ በስር ፍርድ ቤት ግንዛቤ ውስጥ ያልገባ ከመሆኑም በላይ አመልካች በክርክሩ ቀደም ብሎ ከቀረበው ክርክር አመልካቹ የተለየ ሌላ ክርክር ሊያቀርብ አይችልም የተባለውም ቢሆን ክርክራቸው ተመሣሣይና አንድ አይነት ጥቅም የሚወክል መሆኑና አለመሆኑ የሚታወቀው አመልካቹ አግባብነት ባለው የስነ ስርዓት ድንጋጌ ያቀረበው አቤቱታ ተገቢነት ካለው መዝገብ ጋር ታይቶ፣ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ የሚያቀርበውን የክርክር አይነትና የሚወክለውን ጥቅም የአሁኑ 4ኛ ተጠሪ አቅርቦት ከነበረው ክርክር በማነፃፀር የሚታወቅ እንጂ አስቀድሞ ተመሣሣይ ክርክር አለው፣ ውሉ አግባብነት ያለውን ደንብ የሚጥስ አይደለም የሚል ግምት በመያዝ አይደለም፡፡

በመሰረቱ ከላይ እንደተጠቀሰው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የሚቀርበው አቤቱታ በቁጥር 359 ስር በተመለከተው መንገድ መቅረብ ያለበት ነው፡፡ ድንጋጌው የአቤቱታው አቀራረብ የክስ አቀራረብ ሥርዓቱን ሊከተል እንደሚገባ የሚያሳይ ሲሆን እንዲህ ከሆነ ከሣሽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222 መሠረት አዘጋጅቶ ከሚያቀርበው የክስ ማመልከቻ ጋር በክሱ መሰማት ወቅት ለጉዳዩ ማስረጃ ይሆኑኛል የሚሏቸውን የሠውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 223 ድንጋጌ የደነገገ ከመሆኑ ጋር ተጣምሮ ሲታይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የሚቀርበው አቤቱታም ይህንኑ መከተል ያለበት መሆኑ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137/3/ የሠነድ ማስረጃዎችን በተመለከተ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ወይም ከቀነ ቀጠሮ በፊት ወይም በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ ካልቀረበ በቀር ማስረጃው ሊቀርብ ወይም ይቅረብልኝ ተብሎ ሊጠየቅ እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ ይሄው ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኘው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 256 ስር በተመለከተው አኳኋን ማስረጃዎቹ ሣያቀርቡት የቀሩት ከባድና በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍ/ቤቱ ሲረዳ ብቻ ነው፡፡ የማስረጃ አቀራረብን በተመለከተ በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተው ሌላው ደንብ የይግባኝ ሠሚውን ፍ/ቤት ሥልጣን የሚመለከት ነው በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345 ድንጋጌ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በራሱ አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውም ዓይነት ሠነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ ዓይነት ማስረጃ በተጨማሪነት እንዲቀርብለት የማዘዝ ህጋዊ ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145(1) ድንጋጌም በሌላ ፍ/ቤት የሚገኝ ሠነድ የፅሁፍ ማስረጃ ወይም ፍርድ የተሠጠበት መዝገብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለውሣኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍ/ቤቱ በራሡ አነሣሽነትም ሆነ በተከራካሪዎቹ ጠያቂነት እንዲቀርብለት ማዘዝ የሚችል ስለመሆኑ ያስረዳል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው አመልካች በዋናው ጉዳይ ላይ በተሰጠው ፍርድ ላይ ያቀረበው ተቃውሞ ያላግባብ በአፈጻጸም መዝገብ ላይ ተያይዞ ጉዳዩ ከመታየቱም በላይ ዋናውን ፍርድ ለመቃወምና ለማሻር የሚያስችላቸውን ማስረጃዎች ዘርዝሮ ከማቅረቡም በተጨማሪ በፍርድ ቤቱ እገዛ መሰረት የሚቀርብለት ማስረጃ መኖሩንም ጠቅሶ እያለ ይህ ማስረጃ ሳይታይለት አቤቱታው ውድቅ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልፅ ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ በአመልካች የተጠቀሠው ማስረጃ ሳይቀርብ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በአመልካች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚያስከትለው ችግር የለውም ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርስ አይችልም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ተቃውሞ አግባብነት ባለው መዝገብ ሳይቀበልና ተገቢ ማስረጃዎችን ሁሉ ሳይመለከት ውድቅ በማድረግ መወሰኑ የክርክሩን አመራር ከላይ በተመለከቱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የተቃውሞ አቀራረብና የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች መሠረት አለመምራቱንና፣ በውጤቱም አመልካች በሕጉ የተጣለውን ኃላፊነትና ተግባሩን እንዳይወጣ የሚያደርግ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ትእዛዝ የሠጡት አመልካች አቤቱታ ባላቀረበበት ሥርዓትና አቤቱታው ሊቀርብ በማይችልበት መዝገብ ከመሆኑም በላይ የአመልካች አቤቱታ የተስተናገደው የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ድንጋጌዎች በማይደግፉት፣ የፍርድ አካሄዱ ባልተሟላ ሁኔታ በመሆኑ በእየርከኑ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሠጠው ትዕዛዞች ሙሉ በሙሉ ሊሻሩ የሚገባና የአመልካች አቤቱታ በዋናው የፍርድ መዝገብ ላይ ቀርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥ ማድረጉ አግባብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የቡሌ ሆራ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05757 የካቲት 09 ቀን 2002 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ የቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 5196 መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሠጠው ትእዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 103608 ሚያዝያ 14 ቀን 2002 ዓ.ም የሠጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የአቀረበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የሚስተናገድ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04136 በሆነው ላይ የአመልካችን አቤቱታ በመቀበልና ለተጠሪዎች እንዲደርስ በማድረግ እንዲሁም አመልካች በሕጉ አግባብ ሊቀርቡልኝ ይገባል በማለት የዘረዘራቸውን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን ሁሉ በማስቀረብ፣ በጉዳዩ ላይ ቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ የሚሻር መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 65930

14/10/2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- የሱ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ አቶ ግሩም አየለ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1- አቶ ደጆኔ በቀለ - ቀረቡ

2- አቶ አሸናፊ አብርሃም አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁን ተጠሪዎች በሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩ ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱም በተከሣሽ ድርጅት ተቀጥሬን እየሠራን ተከሣሽ ያለአግባብ የሥራ ውላችን እንዲቋረጥ ያደረገ ስለሆነ በህጉ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍለን ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሣሽም ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሾች በምርት ማምረቻ ማሽን ከመጠን በላይ ነዳጅ በመጨመርና ማሽኑ በፍጥነት እንዲሠራ በማድረጋቸው ሙቀት ጨምሮ የማሽኑ ኩሽኔታ ከመቃጠሉም በላይ በስርኩሌሽን ዩስክ ብልሽት ደርሶ በቀጣይ ፈረቃ ማሽኑ የቆመ በመሆኑ በተከሣሽ ድርጅት ላይ ባደረሱት ጉዳት የተነሣ ከሥራቸው እንዲሠናበቱ ተደርገዋል ብሏል፡፡

የሥር የፌ/የ/መደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በሰጠው ፍርድ ከሣሾች በአሠሪው ንብረት ላይ በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት እንዲደርስ ያደረጉ በመሆናቸው ውሉ እንዲቋረጥ የተደረገው በህጋዊ መንገድ ነው ብሏል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረው የሥር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ማሽኑ የተበላሸው ይግባኝ ባዮች /የሥር ከሣሾች / ለቀጣዩ ፈረቃ ተረኞች በ2፡00 አስረክበው ማሽኑም ሥራውን እያከወነ ቆይቶ 5፡30 ሲሆን የቆመ በመሆኑ እንዲሁም የማሽኑን ሁኔታ የሚቆጣጠር ኮምፕዩተር ተበላሽቶ ስለነበር ጉዳቱ የደረሰው በይግባኝ ባዮች ነው ለማለት አይቻልም ሲል ይግባኝ ባዮች ወደ ሥራቸው እንዲመለሡና መልስ ሰጪ /የአሁኑ አመልካች/ የ6 ወር ደመወዛቸውንም እንዲከፍል ፈርዷል፡፡

በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- ተጠዎች በአመልካች ንብረት ላይ ብር 2,000,000 የሚገመት ጉዳት በማድረሣቸው ምክንያት የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሥራ የተሠናበቱት በህጋዊ መንገድ ነው ሲል የወሰነውን ከፍተኛው ፍ/ቤት መሻሩ፣
- በልዩ ባለሙያዎች /Experts/ የተሰጠውን የምስክርነት ቃል ከፍተኛው ፍ/ቤት ከሙያው ወጪ ውድቅ ማድረጉ፣
- ከፍተኛው ፍ/ቤት ለተጠሪዎች ካሣ ብቻ ይከፈላቸው ማለት ሲገባው ወደ ሥራ ይመለሡ ማለቱ ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ የአመልካችና የተጠሪዎች ምስክሮች ተመሣሣይ ሥራ ያላቸውና በጊዜው ሥራ ላይ ሆነው ሁኔታውን የተመለከቱ እንጂ ለሙያዊ ምስክርነት ያስፈልጋሉ ተብለው የተጠሩ አይደሉም፡፡ ለቀጣዩ ፈረቃ ማሽኑን አስረክበን ከሄድን ከ5፡00 ቆይታ በኋላ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪዎች ተጠያቂዎች አይደለንም በማለት የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘን የግራ ቀኙን ክርክር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአመልካች ማሽን በደረሰበት ጉዳት መቆሙን ተጠሪዎችም የሚያምኑት ጉዳይ ሲሆን ዋናውና አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ግን በማሽኑ ላይ ጉዳት የደረሰው በተጠሪዎች ፈረቃ ነው? ወይስ ተጠሪዎች ለቀጣዩ ፈረቃ ሠራተኞች አስረክበው ከወጡ በኋላ ነው? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ተጠሪዎች በፈረቃቸው ወቅት ያለአግባብ ነዳጅ በመጨመርና ማሽኑም ከሚገባው በላይ ፍጥነት እንዲጨምር በማድረጋቸው በተፈጠረ ሙቀት የተነሣ በተለያዩ የማሽኑ ክፍሎች ጉዳት ደርሷል የሚል ሲሆን ጉዳቱ ግን የታወቀው ከኮምኘዩተር በተገኘው መረጃ መሠረት ሆኖ በቀጣይ ፈረቃ የሚሠሩ ሠራተኞች ሥራ ላይ ባሉበት ጊዜ ነው ብሏል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ማሽኑ በራሳቸው ፈረቃ አለመበላሸቱንና ብልሽቱም የደረሰው በቀጣዩ ፈረቃ በመሆኑ ለደረሰው ጉዳት ሃላፊነት የለብንም ሲሉ ይከራከራሉ፡፡

የሥር የፌ/የ/መደ/ፍ/ቤትም ከግራ ቀኙ የቀረበውን የፍሬ ነገር ክርክር ለማጣራት ማስረጃዎችን የሰማ ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረቡት ልዩ ዕውቀት ያላቸው /Experts / ምስክሮች ሲሆኑ በተጠሪዎች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ደግሞ ልዩ አዋቂዎች ያልሆኑ በቀጣዩ ፈረቃ ሲሠሩ የነበሩ የማሽኑ ኦፕሬተሮች ናቸው፡፡

ልዩ አዋቂዎች የሚባሉት በትምህርት ፣ በሥልጠና እና በልምድ ዕውቀት ያካበቱ ሰዎች ሲሆኑ እነዚህን ሰዎች ፍ/ቤቱ በሚጠራበት ጊዜ በተፈለገው ጉዳይ አግባብ የሆነ ዕውቀት ያላቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህም ሲባል የኤክስፐርት ምስክርነት ለምሳሌ በኢንጅነሪንግ /engineering/ የሚያስፈልግ ከሆነ መጣራት ያለበት በዚሁ በኢንጅነሪንግ ሙያ ዕውቀት ያለው ሰው መሆን ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም በአርክቴክቸር /architecture/ ቴክኒዮሎጂ /technology / እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ የልዩ አዋቂዎች ምስክርነት አስፈላጊነት በፍ/ቤቱ ሲታመን ወይም ተከራካሪዎቹ ቀርበው እንዲሰሙ በጠየቁ ጊዜና ፍ/ቤቱም የልዩ አዋቂዎች ምስክርነት ጉዳዩን ለማብራራት ወይም ለክርክሩ ውሣኔ አሰጣጥ ተገቢ ነው ካለ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን ልዩ አዋቂዎች ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ከዚህ በላይ የተገፀው ሁኔታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 136/1/ ሥር የተደነገገ ሲሆን የምስክርነት ቃላቸውን የሚሰጡ ልዩ አዋቂዎችም የሚሰጡት የምስክርነት ቃል በገለልተኝነት የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ የአሁኑ አመልካች ባቀረባቸው የልዩ አዋቂ ምስክሮች ገለልተኝነት /impartiality of experts/ ከተጠሪዎች በኩል የቀረበ ክርክር የሌለ ሲሆን በአንድ የፍትሃብሄር ጉዳይ ልዩ አዋቂዎች/Experts / እና ልዩ አዋቂዎች ያልሆኑ ምስክሮች ቀርበው በተሰሙ ጊዜ " In the civil context … lay evidence should not be preferred to expert evidence with out good reason " የሚለውን የማስረጃ ምዘና መርህ መከተል ይገባል፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የማስረጃ ምዘና መርህ መገንዘብ የሚቻለው ዳኞች በልዩ አዋቂዎች የተሰጠውን ምስክርነት ተቀባይነት የለውም በማለት ሊወስኑ የሚችሉት ይህንኑ የልዩ አዋቂዎችን ምስክርነት ተቀባይነት ሊያሳጣ የሚችል በቂ ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ ብቻ ነው፡፡ የልዩ አዋቂዎችን ምስክርነት ተቀባይነት ለማሳጣት በቂ ምክንያት ከሌለ ግን ልዩ አዋቂ ያልሆኑ ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት ይልቅ በልዩ አዋቂዎች የተሰጡት ምስክርነት ተመራጭነት ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ልዩ አዋቂዎች ከሰጡት ምስክርነት ልዩ አዋቂ ያልሆኑ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት አሳማኝ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ የልዩ አዋቂዎችን የምስክርነት ቃል ውድቅ በማድረግ ልዩ አዋቂዎች ያልሆኑት ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ዳኞች እንዳይቀበሉ የሚከለክላቸው የህግ መርህ የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች የልዩ አዋቂ /Experts / ምስክሮች ስለብልሽቱ የቴክኒዮሎጂ ውጤት የሆነውን ኮምፒዩተር በማንበብ በሙቀት መጨመርና ከመጠን በላይ በሆነ ፍጥነት ማሽኑ እንዲሠራ በመደረጉ የተነሣ ብልሽት የደረሰበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህን አግባብ ባለው ባለሙያ የተሰጠውን ምስክርነት ውድቅ ለማድረግ ምንም በቂ ሁኔታ ባልተገኘበት የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት ውድቅ በማድረግ ለጉዳዩ ይግባኝ ባዮች /ያሁን ተጠሪዎች/ ሀላፊት የሰባቸውም ያለውና የሥራ ስንብቱም የተደረገው በህገወጥ መንገድ በመሆኑ የ6 ወር ደመወዝ ተከፍሎአቸው ተጠሪዎች ወደ ሥራቸው ይመለሱ በሚል የወሰነው መሠረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተለ ስለሆነ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 93713 በቀን 26/04/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 62045 በቀን 11/8/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው ውል የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ነው ተብሏል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59953

ሰኔ 02 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ዓለምነሽ አበበ-

ተጠሪ ፡- አቶ ተስፋዬ ገሠሠ-

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍቺን ተከትሎ የተነሳውን የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-ከተጠሪ ጋር ከ1970 ዓ/ም ጀምሮ አብረው እንደባልና ሚስት ከኖሩ በኋላ ታህሳስ 25 ቀን 1977 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የፈጸሙት ጋብቻ ከሚያዚያ 18 ቀን 1994 ዓ/ም በፍቺ መፍረሱን፣በጋራ የሠሩትን ቤት ቁጥር 398ሀ1 የሆነን ቤት እንዲከፋፈሉ አመልካች ተጠሪን ጠይቀው ተጠሪ ፈቃደኛ ካለመሆናቸውም በላይ ከ1989 ዓ/ም እስከ 1992 ዓ/ም በወር ብር ከ800.00(ስምንት መቶ ብር)፣ከ1992 እስከ 1997 ዓ/ም ብር 900.00፣ከ1997 ዓ/ም ጀምሮ በአመት ብር 20,000.00 ተጠሪ ቤቱን እያከራዩ ገቢውን ለአመልካች ሊከፍሏቸው ያልቻሉ መሆኑን ገልፀው በቤቱ ኪራይ የሚገኘውን ገቢ እንዲያካፍሏቸውና ቤቱን በስምምነት ሽጠው ለመከፋፈል ፈቃደኛ ካልሆኑ በሐራጅ ተሸጦ እንዲከፋፈሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት በማንሳት የተከራከሩት ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ነው በሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበውን መቃወሚያ በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ጉዳዩ ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በመሆኑ ድጋሚ ክስ ሊቀርብበት የማይገባ ነው በማለትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 እና 244(2(ለ)) ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ ሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በአሜሪካን አገር የሚገኝ ፍርድ ቤት በግልፅ ዳኝነት የሰጠበት ስለሆነ ዳግመኛ ዳኝነት መጠየቅ አይቻልም በማለት መዝገቡ የተዘጋው የተሰጠው ዳኝነት ኢትዮጵያ ያላችሁንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ያጠቃልላል የማይል ሁኖ እያለ በተሳሳት ትርጉም ፍርድ አርፎበታል መባሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላግባብ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው።አቤቱታው ተመርመሮም አመልካች በኢትዮጵያ የሚገኘውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመካፈል ያቀረቡት አቤቱታ ዳግመኛ የተጠየቀ ዳኝነት ነው በማለት ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም የአሜሪካን አገር የሚገኘው ፍርድ ቤት በሁሉም የጋብቻ ውጤቶች ላይ ውሳኔ ያሳረፈ መሆኑን ጠቅሰው በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክረዋል።አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፍቺ ውሳኔም ሆነ የንብረት ውሳኔ የተሰጠው በአሜሪካ ሀገር ሜሪላንድ እስቴት ሞንትጎመሪ ካውንት ፍርድ ቤት በቤተሰብ ሕግ ቁጥር 21746 በሆነ በ25/08/94 ገቢ የሆነበት ማስረጃ መኖሩን፣ይህ ማስረጃ ግራ ቀኙ ንብረታቸውን በጋራ እርካታ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ እንደተከፋፈሉና በማንኛውም ወገን የንብረት ባለመብትነት ይገባኛል ጥያቄ ለዳኝነት እንዳይቀርብ የታዘዘ ስለመሆኑ እንደሚያሳይ፣ከዚህ በተጨማሪ ባለጉዳዮቹ የገንዘብ ነክ ፍርድን በጋራ በራሳቸው ፈቃድ እንደተው መታዘዙን እንደሚገልፅ የሰር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ መግለፁን፣በውጪ አገር የተሰጠ ውሳኔም በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ የቀረበ መሆኑን የሰር ፍርድ ቤት ማረጋገጡን ነው።እንግዲህ የሰር ፍርድ ቤት የውጪ አገር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸውንም ሆነ የንብረትና የገንዘብ ክርክራቸውን በአሜሪካን አገር ፍርድ ቤት በስምምነት ቀርበው ውሳኔ ያሰጡ መሆኑን በመገንዘብ የአመልካችን ጥያቄ ዳግመኛ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱን የውሳኔው ግልባጭ የሚያሳይ ነው።

በመሠረቱ የፍትሐብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ የክርክርን ሂደት ለማቀላጠፍና አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ ለማበጀት መሆኑ ይታመናል። የፍትሐብሔርን ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ እልባት እንዲደረግበት በማቀድ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ጽንሰ ሐሣቦች አንድ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ስር በግልጽ ተቀምጧል።በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውጤት የገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን፣በውሣኔ፣በትእዛዝ፣ወይም በጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ ለመንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው።በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አካኂን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ በአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች አሻሽለው በ08/03/2001 ዓ.ም ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ጋብቻው መፍረሱን ገልጸው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለና በጋራ የሠሩትን ቤት ቁጥር 398ሀ1 የሆነን ቤትና በቤቱ የተገኙትን ፍሬዎች እንዲከፋፈሉ አመልካች ተጠሪን ጠይቀው ተጠሪ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ በአሜሪካን አገር ተሰጠ የተባለው ውሳኔ ግራ ቀኙ ንብረታቸውን በጋራ እርካታ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ እንደተከፋፈሉና በማንኛውም ወገን የንብረት ባለመብትነት ይገባኛል ጥያቄ ለዳኝነት እንዳይቀርብ የታዘዘ ስለመሆኑ እንደሚያሳይ፣ከዚህ በተጨማሪ ባለጉዳዮቹ የገንዘብ ነክ ፍርድን በጋራ በራሳቸው ፈቃድ እንዲተው መታዘዙን እንደሚገልፅ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሮታል፡፡ ይሁን እንጂ የውጪ አገሩ ፍርድ ኢትዮጵያ ውሥጥ ያለውን ንብረት እንደተከፋፈሉ ወይም በራሳቸው ፈቃድ እንደተው የሚያሳይ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥቶበታል የሚባለው በመጀመሪያው ክርክር ላይ በአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ ሲሆን ነው፡፡በመሆኑም አንድ ጉዳይ በፍርድ አልቋል የሚለው ተቃውሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት የሚኖረው በሕጉ የተመለከቱት መመዘኛዎች መሟላታቸው በቅድሚያ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ግን ግራ ቀኙ በጋብቻ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ንብረት በተመለከተ በውጪ አገር ባለ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙ ስለመሆኑና ይህም ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ከቁጥር 456 እስከ 461 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በሚያሳዩት መልኩ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነትን ሊያገኝ የሚችልበትን ሁኔታ በግልፅ መሟላቱ ሳይረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት የአመልካችን ዳኝነት ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 118249 መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 92036 ነሐሴ 11 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን የማይንቀሳቀስ ንብረትና ፍሬውን ለመካፈል ያቀረቡት አቤቱታ ዳግመኛ የተጠየቀ ዳኝነት አይደለም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የፈደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 118249 የቀረበውን ክርክር ቀጥሎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1)መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ - ሜሮን ሰሎሞን ቀረበች

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ዮናስ ለሜሳ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የማቅረቢያው ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ ይከፈት ዘንድ እንዲፈቀድ የቀረበውን ጥያቄ መነሻ ያደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የማስፈቀጃ ጥያቄው የቀረበው ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲሆን፣ ጥያቄ አቅራቢው የአሁኑ ተጠሪ ነበር፡፡ የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ሊያልፍበት የቻለው ወይም ይግባኙን በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሊያቀርብ ያልቻለው ጉዳዩን ይዞ ሲከታተል በነበረው ነገረ ፈጁ ስህተት /ጥፋት/ እንደሆነም በማመልከቻው ላይ ገልጾአል፡፡ ፍ/ቤቱም ይህን መነሻ በማድረግ የአሁን አመልካች መልስ ሰጪን አስቀርቦ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ጊዜው ያለፈው በነገረ ፈጁ ጥፋት ነው፡፡ ነገረ ፈጁም በዚህ ምክንያት የዲሲፕሊን እርምጃ ተወስዶበታል የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት የተጠሪን ጥያቄ ተቀብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የይግባኝ ማስፈቀጃው ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ነው በሚል በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 326/2/ ከተቀመጠው ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ያቀረበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 323/2/ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ባለማቅረቡ ከፍ/ቤቱ ፈቃድ ለማግኘት ነው፡፡ ጊዜ ካለፈ በኋላ ይግባኝ እንዲከፈት ጥያቄ የሚቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 325 በተደነገገው መሠረት ሲሆን፣ ጥያቄው ተቀባይነት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ የሚመረመረው /የሚመዘነው/ ደግሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 326 መሠረት ነው፡፡ ጥያቄው ተቀባይነት አለው ወይንስ የለውም? የሚለው ነጥብ ሊወሰን የሚገባው እንደየአግባቡ በንኡስ ቁ/1/ ወይም /2/ መሠረት እንደሆነም ግልፅ ነው በንዑስ ቁ /1/ እንደተመለከተው አመልካቹ ወይም የፈቃድ ጥያቄ አቅራቢው ይግባኙን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑ ፍ/ቤቱን ማሣመን ከቻለ ይግባኙን በአሥር ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ይፈቀድለታል፡፡ በዚህ ረገድ ምክንያቱ በቂ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ፍሬ ነገር በፍ/ቤቱ የሚመዘን ከመሆን አልፎ በሕጉ የተቀመጠ የታወቀ /የተለየ/ መስፈርት የለም፡፡ በንዑስ ቁ./2/ የተቀመጠው ድንጋጌ ግን አመልካቹ ያቀረበው ምክንያት በንኡስ ቁ./1/ አባባል ሊስተናገድ የማይገባ ወይም ተቀባይነት የሌለው ነው የሚባልበትን አግባብ የሚያመለክት ነው፡፡ በፈቃድ መጠየቂያው ማመልከቻ ላይ የተገለፀው ምክንያት ይግባኙን በጊዜው ማቅረብ ያልቻለው በአመልካቹ ጠበቃ ወይም ነገረ ፈጁ ወይም በወኪሉ ያለመቅረብ እና በእነዚሁ ጉድለቶች መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ ምክንያቱ በንኡስ ቁ./1/ እንደተነገረው በቂ ነው ሊባል እንደማይገባ ድንጋጌው በግልጽ ያመለክታል፡፡ በዚህ ምክንያትም የይግባኝ ይከፈትልኝ ጥያቄው ተቀባይነት ለማግኘት አይችልም በማለት ግልጽ ድንጋጌ ሕጉ አስቀምጦአል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ ይግባኙን በጊዜው ያላቀረበው በነገረፈጅ ጉድለት ምክንያት እንደሆነ በፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻው አረጋግጦአል፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኙ እንዲከፈት የፈቀደው ነገረ - ፈጁ ሥራውን በታማኝነት እና በተገቢ የሥራና የሙያ ሥነ ምግባር አልፈፀሙም የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በእኛ እምነት ሕጉ ግልጽ ነው፡፡ የነገረፈጁን ወይም የጠበቃውን ወይም የወኪሉን በታማኝነት ሥራውን አለመሥራት ወይም አለመሥራት እንደመስፈርት ተወስዶ በሕጉ አልተቀመጠም፡፡ ለምዘና የሚቀርብ ፍሬ ነገርም አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታ በአመልካቹ /የይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄ አቅራቢው/ እና በነገረፈጁ በጠበቃው ወይም በወኪሉ መካከል ለሚነሣ የኃላፊነት ክርክር አወሳሰን አግባብነት ይኖረው እንደሆነ ነው እንጂ ይግባኙ ይከፈትልን በሚለው ወገን እና በተቃራኒው ይግባኙ ሊከፈት አይገባም በሚለው ተከራካሪ ወገን መካከል የሚነሣ አይደለም፡፡

ፍ/ቤቶችም የቀረበላቸውን ጉዳይ መወሰን ያለባቸው በሕጉ መሠረት እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ግልጽ የሆነውን ሕግ በመተላለፍ የሚሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ውሣኔው ከሕጉ አተረጓጎም /አተገባበር/ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው የሚሆነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 54164 ግንቦት 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበው የይግባኝ ይከፈት ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 326/2/ እንደተደነገገው ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ወ/ሪት ቤቱልሔም ታደሰ - ጠበቃ ዳንኤል ግርማ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ሐና ታደሰ - የቀረበ የለም

2. አቶ ተስፋዬ አበበ - የቀረበ የለም

3. አቶ ተስፋዬ ጎይቴ - ከጠበቃ መላኩ ወ/ማርያም ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሰረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ጉዳይ ነው ሊባል የሚችልበትን የሥነ ሥርዓት ሕግ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች ነሀሴ 11 ቀን 2001 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው ላይ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 ክልል ውስጥ የሚገኝና የቤት ቁጥሩ 261 የሆነውን ፣ የአመልካች ድርሻም ጭምር ያለበትን መኖሪያ ቤት ለአሁኑ 3ኛ ተጠሪ ነሀሴ 12 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የሸጡት መሆኑን ፣ ይህ የሽያጭ ውል አመልካችን የሚጎዳና ሕገወጥ መሆኑን ጠቅሰው ውሉ እንዲፈርስላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም ውሉ መደረጉን ሳይክዱ የሕጉን ፎርማሊቲን ያልጠበቀና ረቂቅ በመሆኑ ቢፈርስ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን የገለፁ ሲሆን የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በጉዳዩ ላይ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ 3ኛ ተጠሪ ላይ የውል ይፈረስልኝ ጥያቄ አቅርበው አመልካች የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ ውድቅ ያደረገባቸው መሆኑንና ውሉም ሊፈርስ አይገባም ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጭምር የፀና መሆኑን ጠቅሰው ጉዳዩ ዳግም ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ያቀረቡት የውል ይፍረስልኝ ክስ ቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ በመሆኑ ዳግም ክስ ሊቀርብበት የሚገባው አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ልግባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚለውን ጥያቄ አቅርበው አቤቱታቸው ውድቅ የሆነው 1ኛ ተጠሪ ከ3ኛ ተጠሪ ክስ በመሰረቱበት ጊዜ የጠየቁት ዳኝነት አመልካች ጣልቃ ልግባ በማለት ከጠየቁት ጋር የተለየ ምክንያት ያለው በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባም ተብሎ ሲሆን አመልካች በሌላ መንገድ መብታቸውን ከማስከበርም የማያግዳቸው መሆኑ ተገልፆ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12928 ብይን ሰጥቶ እያለ ከዚሁ ብይን ውጪ በሆነ መንገድ ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሰረት ውድቅ ነው በማለት የሰጠው ብይን በመ/ቁጥር 12928 ከሰጠው ብይን አንፃር ሲታይ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም በስር ፍርድ ቤት ከሰጡት መልስ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው መልስ አቅርበዋል ፣ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ የክርክርን ሂደት ለማቀላጠፍና አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ ለማበጀት መሆኑ ይታመናል፡፡ የፍትሐብሔርን ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ እልባት እንዲደረግበት በማቀድ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ጽንሰ ሐሣቦች አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ስራ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውጤት ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን ፣ በውሣኔ ፣ በትእዛዝ ፣ ወይም በጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ ለመንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አካኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው ፣ ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡

ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሊቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ በአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በ11/12/2001 ዓ.ም ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ድርሻቸው ባለው መኖሪያ ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል የሚጎዳቸውና ሕገ ወጥ መሆኑን ጠቅሰው ውሉ እንዲፈርስላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን እህታቸው የሆኑት የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ 3ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት የውል ይፈረስልኝ ክርክር ስርዓቱን ጠብቀው የጣልቃ ልግባ አቤቱታ አቅርበው የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ጥያቄና የ1ኛ ተጠሪ ጥያቄ የተለያዩ ምክንያቶችን መሰረት ያደረገ ነው በሚል ምክንያት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎ አመልካች በተናጠል መብቷን ማስከበር እንደሚችሉ ገልጾ አመልካችን ስለማሰናበቱ የስር ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 12928 በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚህ በሁዋላ አመልካች የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ በተናጠል ሲያቀርቡ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በ3ኛ ተጠሪ ላይ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ አቅርበው ተቀባይነት እንዳጡ ፣ የአመልካች ጥያቄም ተመሳሳይ እንደሆነና በ1ኛ ተጠሪ በቀረበው አቤቱታም የክርክሩ ተሳታፊ ሁነው ተቀባይነት እንዳጡ ተገልፆ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሰረት መዝገባቸው ተዘግቶባቸዋል፡፡ ከዚህ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው የስር ፍርድ ቤት አመልካች በ1ኛ ተጠሪ በቀረበው ክስ የክርክሩ ተሳታፊ ነበሩ ከማለት በስተቀር በመ/ቁጥር 12928 የተሰጠው ብይን ይዘቱ ምን እንደነበር በግልፅ ያልመዘገበውና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ጋር አዛምዶ ያልተመለከተው መሆኑን ነው፡፡ አመልካች የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ በሥርዓቱ መሰረት አቅርበው የስር ፍርድ ቤት በተናጠል ሊያቀርቡ የሚገባውና 1ኛ ተጠሪ ካቀረቡት ምክንያት የተለየ ምክንያት ያለው ነው በማለት ብይን የሠጠበት ጉዳይ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በዚህ ችሎት እምነት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈረስ የጠየቁት የተለያዩ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ነው ቢባልም የውል ይፍረስልኝ ጥያቄው ውጤት ግን አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ አለን የሚሉትን መብት መጠበቅ በመሆኑ አመልካች ትክክለኛውን መድረክና ስርዓት በመምረጥ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ በጣልቃ ገብነት አቅርበዋል ፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በያዘው መዝገብ አስተናግዶ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ነበረበት፡፡ ፍርድ ቤት በፈጠረው ስህተት ተከራካሪ ወገን ተቀጪ የሚሆንበትና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 መሰረት የተከበረለትን ፍትህ የማግኘት መብት የሚጣበበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ራሱ በመ/ቁጥር 12928 የሰጠውን ብይን ይዘት ባግባቡ ሳይመረምር የአመልካችን ጥያቄ ይዘት ከ1ኛ ተጠሪ ጥያቄ ይዘት ጋር መመሳሰሉን ብቻ በመመልከት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሰረት መዝጋቱ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15316 የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 92343 ነሐሴ 24 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15316 በሆነው ክርክሩን ቀጥሎ የግራ ቀኙን ፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃ በመስማት በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሃ/ዲ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አፔኖ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅት ጠበቃ አቶ በረከት ቡሽራ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጥሩነህ ይመር አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ተጠሪ ለሥር የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በተከሣሽ ድርጅት /በአሁኑ አመልካች ድርጅት/ በዘበኝነት ተቀጥሬ እየሠራሁ የቆየሁ ቢሆንም በህመም ምክንያት ሥራዬን ያቆምኩ ስለሆነ ተከሣሽ አንዳንድ ያልከፈላቸውን ክፍያዎች እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

ተከሣሽ ድርጅት በበኩሉ በሰጠው መልስ ከሣሽ በድርጅቱ ከታህሣሥ ወር 2001 እስከ ጥቅምት 2002 ለአሥራ አንድ ወራት በጥበቃ ሥራ ከቆየ በኋላ በራሣቸው ፈቃድ ከተከሣሽ ድርጅት የተሰናበቱ ሲሆን በሰጡት አገልግሎት መሠረት የስንብት ክፍያ የተከፈላቸው በመሆኑ ሌሎች የሚከፈላቸው ክፍያዎች የሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር የከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቱም በሰጠው ፍርድ ተከሣሽ የስንብት ክፍያ ለከሣሽ መክፈሉን በማረጋገጥ ሌሎች ክፍያዎችን በሚመለከት ግን ከሣሽ በግልጽና በዝርዝር ያልጠየቁና በማስረጃ አስደግፈው ያላቀረቡ በመሆናቸው ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ፍ/ቤት በበኩሉ በሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ባይ በመልስ ሰጪ ድርጅት ለአንድ ዓመት የሠሩ መሆናቸው ስለተረጋገጠ መከፈል ያለባቸው ክፍያዎች ማለትም የትርፍ ሰዓት ክፍያ የዓመት ዕረፍትና የበዓላት ቀን ክፍያ የተከፈላቸው ስለመሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ መልስ ሰጪ ሊከፍላቸው ይገባል ብሏል፡፡

በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ያለው ያሁን አመልካችም ለዚህ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪ በደፈናው አንዳንድ ያልተከፈሉኝ ጥቅማ ጥቅሞችን አመልካች እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለታቸው ብቻ የትርፍ ሰዓት የዓመት ዕረፍት እና የበዓላት ቀን ክፍያ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው መወሰኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ስለ ክስ አቀራረብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደነገጉትን መርሆዎችንና ስለማስረጃ አቀራረብ ሥርዓትን መሠረት ያላደረገ ስለሆነ ውሣኔው ሊሻር ይገባል ብሏል፡፡

ተጠሪው ለሰበር አቤቱታ መልስ ለመስጠት ባለመፈለጋቸው መብታቸው የታለፈ ሲሆን እኛም የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ለተጠሪው የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣ እንዲሁም የዓመት ዕረፍትና የበዓላት ቀናት የሠሩባቸው ታስቦ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥራ ክርክር የፍትሐብሔር ባሕሪ ስላለው ክርክሩ መመራት ያለበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት መሆን ይኖርበታል፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 222 በክስ ጽሑፍ ላይ ስለሚሠፍሩ ነገሮች የተደነገገ ሲሆን በዚሁ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር /1/ በፊደል /ረ/ አንድ ክስ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች መያዝ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ከዚህ ሌላም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 80/1/ እንደተጠቀሰው ከሣሽ የሚጠይቀውን ሁሉ ዘርዝሮ በክሱ ወይም በአቤቱታው ማቅረብ እንደሚኖርበት በማያሻማ ሁኔታ ተጠቅሷል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪው ያልተከፈሉኝን ክፍያዎች አመልካች ይክፈሉኝ ከሚል ውጪ መክፈል ያለበትን ክፍያዎች በሕጉ መሠረት በዝርዝር ግለጽ አድርገው አላቀቡም፡፡ በግልጽ በዝርዝር ባልቀረበ ጉዳይ ደግሞ ሌላኛው ወገን እንዲከራከርበት ማድረግ የተጠቀሱትን የፍትሐብሔር ሥነ ሥ/ሕ/ድንጋጌዎች መጣስ ይሆናል፡፡

ግለጽነት የጎደው ክስ ወይም አቤቱታ በቀረበ ጊዜ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 91/1/ እንደተጠቀሰው ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ከተከራካሪ ወገኖች በሚቀርበው ጥያቄ ወይም ፍ/ቤቱ በራሱ አነሣሽነት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑን ከተረዳ ክሱ ወይም አቤቱታው እንዲሻሻል ለማዘዝ ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ በያዝነው ጉዳይ በዚህ መልኩ ክሱ እንዲሻሻል አልተደረገም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ተጠሪው እንዲከፈላቸው የሚጠይቁት የዓመት ዕረፍት፣ የበዓላት ቀን እና የትርፍ ሰዓት ክፍያዎች ለየትኛው ጊዜ እንደሆኑ ተለይተው ባልቀረቡበት እንዲሁም በእነዚህ ጊዜያት ተጠሪው የትርፍ ሰዓት ሥራ እና በበዓላት ቀናት የሠሩ ስለመሆናቸው፣ የዓመት ዕረፍት ያልተጠቀመበት መኖር አለመኖሩ ማረጋገጫ ባለቀረበበት አመልካች እነዚሁኑ ክፍያዎች እንዲከፍሉ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት መወሰኑ በፍትሐብሔር ሥ/ሥ ስለ ክስ አቀራረብ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ባልተከተለ ሁኔታ ከመሆኑም ሌላ ተጠሪው ክሱን በማስረጃ ሣያስረዱ የተወሰነ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሥር የጋምቤላ ከተማና ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 10/2/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሥር የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03436 በቀን 28/10/2002 የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ የዓመት ዕረፍት፣ የበዓላት ቀናት፣ ትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያዎችን በገንዘብ ተለውጦ ሊከፍላቸው አይገባም ብለናል፡፡
4. አመልካች የዚህን ፍ/ቤት ወጪ የራሱን ይቻል፡፡
5. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

ሃ/ዲ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 61227

ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነገረ ፈጅ ክበሩ ደበበ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ኃይሉ አምቦ } አልቀረቡም

2. ወ/ሮ እታገኝ ወርቁ }

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ቀባንክ ብድር ጋር ተያያዥነት ያለው ክርክር ሲሆን የተጀመረው በደቡብ ብሔ/ብ/ሕ/ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ 1ኛው ተከሣሽ በተደረገው የብድር ውል የእህል ንግድ ለመሥራት ብር 30,000 የተበደረና 2ኛ ተከሳሽም የ1ኛ ተከሳሽ ባለቤትና ውሉ እንዲፈቅድ ስምምነታቸውን ገልፀዋል፣ ለዋስትናም በሚዛን ተፈሪ ከተማ ያለው የመጋዘን ቤትና የመኖሪያ ቤት ባንኩ በመረከብ ከዕዳቸው ላይ ቀንሷል፣ ይሄም ሆኖ በውሉ መሠረት ዋና ገንዘብ ብር 8,112.49 እና ወለድ 6,433.37 በድምሩ ብር 14,545.86 የሚፈለግባቸው በመሆኑ የቀረበ ክስ ነው፡፡ ተከሣሾች በሰጡት መልስ ከሳሽ በዕዳው ምክንያት ንብረቱን የተረከበ በመሆኑ የቀረውን ዕዳም ከፍሎ ለመጨረስ ጊዜ ይሰጠን በማለት የመለሱ በመሆኑና በቃል ክርክር ወቅት ከሳሽ ንብረቶችን በእጅ ካስገባ በኋላ ተከሣሾች ኃላፊነት መውሰድ የለብንም የሚል ክርክር ያነሱና በወቅቱ በባንክ ነገረፈጅ ቀርቦ የነበረው ክርክር ንብረቱን የተረከብን ቢሆንም ወደ ገንዘብ ተሸጦ ያልተለወጠ በመሆኑ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ ከላይ እንደተመለከተው ክርክሩ በኋላ ከሳሽ ከላይ የተመለከቱትን መጋዘንና መኖሪያ ቤት ብረከብም ወደ ገንዘብ አልተለወጠም በማለት የተነሳው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ሐምሌ 09/1994 ዓ.ም ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ በግምቱ መጠን ያለባቸው ሆኖ ተቀናሽ መሆን ይገባዋል በማለት የንብረቶቹ ግምት በአጠቃላይ ብር 41,209 ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ በማያያዝ ከሳሽ ንብረቱን እስከተረከበበት ጊዜ ድረስ በተከሣሾች ላይ ያለው ዕዳ ብር 41 /አርባ አንድ/ ብቻ በመሆኑ ውሣኔውን እስከሰጠበት ድረስ ያለውን ወለድ በማስላት ወይም በማሰብ ብር 85.28 /ሰማኒያ አምስት ብር ከሃያ ስምንት ሣንቲም/ ብቻ ይቀራል በማለት ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ አፅንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥቅምት 08 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ባንኩ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች በአዋጅ ቁ. 97/90 እና አዋጅ 216/92 መሠረት የተረከባቸውንና የተረከበበትን የንብረት ግምትም ከዕዳው ላይ በማቀናነስ ቀሪውን ዕዳ ለመጠየቅ የቀረበ ክስ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ከጭብጡ በመውጣት የሂሣብ ስሌት ውስጥ በመግባት የወሰነው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተሽሮ በክሳችን መሠረት እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በቀን 02-5-2003 ዓ.ም የሰጡት 2 ገፅ የመልስ ፍሬ ሃሣብ አመልካች መጋዘን እና መኖሪያ ቤቱን ከተረከበ በኋላ ሰባት ዓመት ቆይቶ ንብረቶቹንም እያከራዩ ሲጠቀሙ ቆይተው በተሳሳተ ስሌት ቀሪ ዕዳ አለባችሁ በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ከግራ ቀኙ የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደተመረመረውም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት ተገቢውን ማጣራት ካደረገ በኋላ የተሰጠ ውሣኔ ነው? ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ተይዞ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ ለዕዳው መክፈያ በአንደኛ ደረጃ ዋስትና የተያዙት መጋዘን ቤት እና መኖሪያ ቤት ባንኩ የተረከበው አጠቃላይ ግምታቸው ብር 41,209 ስለመሆኑ እና ሐምሌ 9/1994 ዓ.ም ባንኩ የተረከባቸው መሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካቹ ንብረቶቹን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ በንብረቱ ግምት መጠን ዕዳውን ተቀናሽ ማድረግ ሲገባው ንብረቱን ብንረከብም ተሽጦ ወደ ገንዘብ የተለወጠ ባለመሆኑ ሊቀነስ አይገባም በማለት በከፍተኛው ፍርድ ቤት በቃል ክርክር ወቅት የተነሣውን ነጥብ በተመለከተ በዚህም ችሎት ለማጣራት የአመልካች ነገረ ፈጅ ተጠይቀው በወቅቱ የቀረበው የአመልካች ተወካይ የፈፀሙት የክርክር ስህተት እንጂ ባንኩ ንብረቱን ሲረከብ በግምቱ መጠን ዕዳውን የሚቀንስ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በወቅቱ በከፍተኛው ፍርድ ቤት በቃል ክርክር ወቅት በአመልካች ነገረ ፈጅ በኩል ተነስቶ የነበረውን ክርክር ፍርድ ቤቱ ውድቅ በማድረግ ባንኩ ንብረቶቹን በዕዳው ምክንያት ከተረከበበት ቀን ጀምሮ በግምቱ መጠን ዕዳው የሚቀነስ መሆኑን የወሰነ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ላይ አከራካሪው ነጥብ አመልካቹ ለዋስትና የተያዙትን መጋዘንና መኖሪያ ቤት በተረከበበት ሐምሌ 09 ቀን 1994 ዓ.ም ወቅት በተጠሪዎች ላይ የነበረው ዕዳ ስንት የነበረ ስለመሆኑ፣ በወቅቱ የነበረው ዕዳ አመልካች ንብረቱን ሲረከብ የንብረቶቹ ግምት መጠን ከተጠሪዎች ዕዳ ላይ ሲቀናነስ ምን ያህል ዕዳ የሚቀርባቸው ስለመሆኑ እና አመልካች /ባንኩ/ ንብረቶቹን ከተረከበ በኋላ በግራ ቀኙ መካከል በነበረው ውል መሠረት የቀረው ዕዳ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ያለው ስሌት ስንት ይሆናል የሚሉት ነጥቦች እንደሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይሄንን በተመለከተ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በዋስትና የተያዙትን ንብረቶች ስረከብ የነበረው ዕዳ ተቀናንሶ ብር 41 ብቻ በተጠሪዎች ላይ እንደሚቀር ይሄው ዕዳ ውሣኔ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ በቀሪው ዕዳ ላይ ወለድ ታስቦ ብር 85.28 ብቻ እንደሚቀርባቸው ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ወደ ዕዳው ስሌት ሊገባ የቻለው በግራ ቀኙ መካከል በነበረው ክርክር በኃላፊነት መጠን ስሌት ላይ ክርክር በመፈጠሩ ምክንያት መሆኑ ከክርክሩ አጠቃላይ ሂደት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዕዳው ሒሳብ ስሌትን በተመለከተ አጠራጣሪ ሁኔታ ከተፈጠረ ዳኞች በራሳቸው የሂሣብ ስሌቱን ለመሥራት ሳያስፈልግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 136 /1/ /2/ መሠረት ልዩ አዋቂ /ኤክስፐርት/ በመመደብ እንዲሰሩት ማድረግ እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለመፈፀማቸው አሁን እየተነሣ ላለው የስሌት ስህተት አለ የሚለውን ሊያስቀር የሚችል ነው፡፡ በዚህ መሠረት ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የዕዳውን ስሌት መሥራቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ከላይ በተመለከተው በልዩ አዋቂ ማሰራት ሲገባው ፍርድ ቤቱ በራሱ ስሌት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የክርክር ማጣራት ሂደትን ከላይ እንደተመለከተው የተከተለ ባለመሆኑ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይሄንን ሳያጣራ ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብሔ/ብ/ሕ/ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 32725 በቀን 14-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 07373 በቀን 28-12-2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ በፍርድ ሐተታው በተመለከተው መሠረት በተጠሪዎች ላይ የቀረውን ዕዳ በልዩ አዋቂ /ኤክስፐርት/ እንዲጣራ ካደረገ በኋላ ተገቢ የሆነውን ውሣኔ እንዲሰጥ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 343 /1/ መሠረት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 61637

ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዶ/ር አልሑሴን በድልገዋድ - ጠበቃ 1. በሻዳ ገመቹ ቀረቡ፡

2. ጥላሁን ምትኩ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ገነት ሐድጎ ጠበቃ ንዋይ ዘርጌ ዓይናለም /ዶ/ር/ - ቀረቡ

2. አቶ ታደሰ ጥላሁን-

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍርድ ቤት እግድ የሠጠበት የማይንቀሳቀስ ንብረት እግዱ ተጥሶ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት በተደረገ ሽያጭ ውል ለሶስተኛ ወገን ንብረቱ ተላልፎ ሲገኝ ያለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻና ይዘትም የሚከተለው ነው፡፡ አመልካች አቶ ጥበቡ እሸቱ በተባሉት ግለሰብ ላይ ብር 1,598,470.00 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰባ ብር) ለማስከፈል በኮ/መ/ቁጥር 56345 በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰኔ 05 ቀን 1999 ክስ መስርተው የፍርድ ባለመብት መሆናቸውን አረጋግጠው እንደ ፍርዱ እንዲፈፀምላቸው የአፈጻጸም ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ አቅርበው አሁን ለክርክሩ መሰረት በሆነው ቤት ላይ ሐራጅ ወጥቶ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ባቀረቡት ማመልከቻ መሰረት ፍርድ ቤቱ እግድ ተሰጥቶበት የነበረ መሆኑን ተገንዝቦ የሐራጅ ማስታወቂያውን አውጥቶ አፈጻጸሙን በመምራት እንዳለ የአሁኑ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት የተቃውሞ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች የተቃውሞ ምክንያት የሆነው ነገር ለአፈጻጸሙ መሰረት የሆነውና በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 274 የሆነውን መኖሪያ ቤት በሕግ አግባብ በተደረገ የሽያጭ ውል ከአቶ ጥበቡ እሸቱ የገዙትና ስመ ሀብቱንም ወደራሳቸው ያዞሩት መሆኑን የሚገልፅ ሁኖ አፈጻፀሙ በንብረታቸው ላይ ሊቀጥል አይገባም የሚል ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ በቀረበው የተጠሪዎች አቤቱታ ላይ አመልካች መልስ እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡ አመልካች በሰጡት መልስም ዋናውን ክስ በአቶ ጥበቡ እሸቱ ላይ ሲመሰርቱ ክሱ ለቀረበለት ፍርድ ቤት ባቀረቡት የእግድ አቤቱታ መሰረት ሰኔ 06 ቀን 1999 ዓ/ም በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 274 የሆነ መኖሪያ ቤት በግለሰቡ ስም የሚታወቅ መሆኑ ተጣርቶ በማናቸውም መንገድ ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በማለት ያዘዘ ሲሆን ይኸው የእግድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትዕዛዝ ለቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ደርሶት በቤቱ ማህደር መያያዙንና ይህ የእግድ ትዕዛዝ በሕግ አግባብ ያልተነሳ መሆኑን ዘርዝረው እግዱ በተጭበረበረ መንገድ ተነስቷል ተብሎ በተገለፀበት ሁኔታና ጊዜ የተከናወነው የሽያጭ ውል ሕጋዊ ባለመሆኑ የተጠሪዎች ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም፣ አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ መቀጠል አለበት በማለት ተከራክረዋል። ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በአከራካሪው ቤት የፍርድ ቤት እግድ መተላለፉ የተረጋገጠ ቢሆንም በሕግ አግባብ ሳይነሳ እንደተነሳ ተደርጎ ትእዛዝ ተላልፎ እግዱ ተነስቷል ተብሎ በተገለጸበት ሁኔታና ጊዜ የሽያጭ ውሉ በውልና ማስረጃ ፅ/ቤት ተደርጎ ስመ ሀብቱ ሁሉ ወደ ተጠሪዎች መዛወሩን፣ እግዱ በመጣሱ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው ደግሞ እግዱን የጣሰው ወገን እንጂ ገዥ ሊሆን እንደማይገባ ዘርዝሮና የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 156፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1566 እና የአዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 15(2) እና 27(1) ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ቤቱ በሐራጅ ሊሸጥ አይገባም ሲል ወስኗል። በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

የአመልካች ጠበቃ ታህሳስ 07 ቀን 2003 ዓ.ም ተሻሽሎ በተፃፈ አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች በሕግ አግባብ አስከብረው የነበረና በሕግ አግባብ እግዱ ሳይነሳ በተጭበረበረ መንገድ የተነሳ መሆኑ በግልጽ ተረጋግጦ እያለ ሽያጩ ቀሪ ሊሆን አይገባም፣ እግዱን የጣሰው ወገን እንጂ ገዥ ተጠቂያነት የለበትም ተብሎ መወሰኑ የእግድን ዓላማና ውጤቱን ያላገናዘበና ሕጋዊነት የሌለው ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በሐራጅ እንዲሸጥ የተባለው ቤት ለሁለተኛ ተጠሪ በግዥ ተላልፏል ተብሎ ሐራጁ እንዲቋረጥ የስር ፍርድ ቤቶች የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪዎች ጥር 17 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል። የመልሳቸው ይዘትም ባጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ሽያጩ የተከናወነው እግዱ የተነሳ መሆኑ በተረጋገጠበትና በውልና ማስረጃ በተደረገ የሽያጭ ውል ሁኖ ስመ - ሐብቱም ለገዥው የዞረ በመሆኑ ሽያጩ ሕጋዊ አይደለም ሊባል የሚችልበት ምክንያት ስለሌለ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከሪያቸውን የሚያሳይ ነው። የአመልካች ጠበቃም በተጠሪዎች መልስ ላይ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል። ይህ ችሎትም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመራበትን መዝገብ ቁጥር 67884ን አስቀርቦ የክርክሩን ሂደት ተመልክቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በአቶ ጥበቡ እሸቱ ላይ የገንዘብ ይከፈለኝ ክስ ሰኔ 05 ቀን 1999 ዓ.ም መስርተው አሁን እያከራከረ ያለው እና ሌላ ቤት ሰኔ 06 ቀን 1999 ዓ/ም በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲከበር ያደረጉ መሆኑን፣ ይህ የእግድ ትዕዛዝም ለሚመለከታቸው አካላት መተላለፉ የተረጋገጠ ቢሆንም እግዱ መነሳቱን ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ስለማስተላለፉ ያሳያል የተባለ ማስረጃ በመኖሩ ምክንያት ውልና ማስረጃ ፅ/ቤት በተደረገው የሽያጭ ውል መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ/ም አከራካሪው ቤት ለተጠሪዎች መተላለፉን፣ ከዚህም በኋላ ተጠሪዎች የስመ ሃብቱን ወደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ራሳቸው አዙረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ የአመልካች ክርክር መሰረቱም የፍርድ ቤት እግድ ያለበትን ቤት በተጭበረበረ መንገድ እግዱ ተነስቷል ተብሎና እግዱ የተነሳው ከፍርድ ቤት ከወጣ ትዕዛዝ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ሽያጩ መከናወኑም ሆነ የቤቱን ስመ - ሃብት ገዢዎች ማዞራቸው ሽያጩን ሕጋዊ አያደርገውም በሚል ምክንያት ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡ እኛም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከሕጉ ጋር በሚከተለው መልኩ በማዛመድ ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ በፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ የሚሰጠው በክርክሩ ሂደት ረቺ የሚሆነው ወገን ለፍርድ አፈጻጸም ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲያስችለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ደግሞ ሊከበር የሚገባ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ፍርድ ደግሞ ሊፈጸም የሚገባው በፍርድ ባለእዳውና በሕግ አግባብ እንዳይያዙ ከሚጠቀሱት ንብረቶች/መብቶች ውጪ ባሉት የፍርድ ባለእዳ ንብረቶች/መብቶች ስለመሆኑ በቁጥር 378 ተከታዮቹ በተመለከቱት የፍትሐ ብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ሰው በሕግ አግባብ ለሌላ ሰው ሊያስተላለፍ የሚችለው መብትም በሕግ አግባብ ገደብ ያልተደረገበትንና ያለውን መሆኑ እሙን ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የስር የፍርድ ባለእዳ የሆኑት አቶ ጥበቡ አከራካሪውን ቤት የሸጡት በፍርድ ቤት የተላለፈው እግድ በፍርድ ቤቱ መነሳቱን አረጋገጠው ባይሆንም የፍርድ ቤቱ የእግድ ትዕዛዝ የተነሳ መሆኑን የሚያሳይና ከፍርድ ቤቱ የወጣ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ በቤቱ ማህደር ተያይዞ በመገኘቱ ሲሆን እግዱን የጣሰው አካል ማን እንደሆነም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ አይደለም፡፡ የፍርድ ቤቱ እግድ የተነሳ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ሽያጩም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ሽያጩ ሲከናወን አቶ ጥበቡ እሸቱ የአከራካሪው ቤት ባለሃብት ሲሆኑ በዚሁ ሰፊው መብታቸው ደግሞ በሕግ ያልተገደቡ መብቶቻቸውን መጠቀም የሚችሉ መሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1204፣1206፣1184 እና 1185 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊቆጠር እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ከላይ የተገለጹትን ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ጋር አጣምረን ስንመለከት የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸው እስካልተረጋገጡ እና ሌሎች ሕጋዊ ክልከላዎች እስከሌሉ ድረስ ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሸጠ ተግባሩ ሕገ ወጥ የሚባልበት ምክንያት የለውም፡፡ አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገዶች ለሌላ ለማስተላለፍ መብት አለውና፡፡ በዚህ መንገድ መብቱ የተላለፈለት ሰውም በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በቤቱ ላይ እግድ ማሰጠታቸው የተረጋገጠ ቢሆንም ከዚህ በሁዋላ ደግሞ እግዱ መነሳቱ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች እግዱ ከፍርድ ቤት በወጣ ትዕዛዝ የተነሳ አይደለም በማለት ከመከራከራቸው ውጪ ለእግዱ መጣስ ወይም የይነሳልኝ ጥያቄው የቀረበው ወይም እግዱ ስለመነሳቱ የሚገልጸው ደብዳቤ ጋር ተጠሪዎች ያላቸው ግንኙነት ስለመኖሩ ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ አለመኖሩን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ ከሻጭ ጋር የመመሳጠር ሁኔታ ስለመኖሩ ያልተረጋገጠበትና የተለየ ግንኙነት የሌለው ሰው በቤቱ ላይ እግድ መነሳቱን የሚያሳይ ማስረጃ ከሚመለከተው የቤቱ ማህደር አይቶና ይህን ማስረጃ በመመልከት ንብረቱን ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የሚገዛ ገዥ ሽያጩን ያከናወነው ከሕግ ውጪ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በቤቱ ላይ ሕጋዊ መብት የሌለው ሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሃብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገዥ ሊሆን አይገባም፡፡ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ በሕጋዊ ተግባር መብት ያገኘ ሰው ከራሱ እውቅና ውጪ ለተፈፀመ ሕገ ወጥ ተግባር ተጠያቂ ማድረግ የግብይት ሥርዓቱንም ጭምር ዋስትና የሚያሳጣው ይሆናል፡፡ ከሁሉም በላይ የፍርድ ቤት እግድ ተጥሶ ሲገኝ ኃላፊነት ሊወስድ የሚገባው የእግድ ትዕዛዙ እንዲጣስ ምክንያት የሆነ ተግባር የፈፀመ አካል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 156 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤትም በሕግ የባለቤትነት መብት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸውን ንብረቶች ለማስተላለፍ የሚዘጋጁ ሰነዶች ከመዘጋጀታቸው በፊትም ሰነድ አረጋጋጩ ንብረቱ በመያዣነት ያልተሰጠ ወይም በፍርድ ቤት ያልታገደ መሆኑን ሊያረጋግጥ እንደሚገባ አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 15(2) ድንጋጌ በጎይለ ቃል አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት የገዙት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ከያዙት ግለሰብ ሆኖ ሽያጩም የተከናወነው ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ሲሆን በዚህ ጊዜም የፍርድ ቤቱ እግዱ ስለመነሳቱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከቤቱ ማህደሩ ጋር በመገኘቱ በመሆኑ የአከራካሪው ቤት ሽያጭ ውል ቀሪ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ በሕግ አግባብ በተፈጸመ የሽያጭ ውል ያቋቋሙት የባለሃብትነት መብት ያላቸው መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች ያላቸው መፍትሄ የእግዱን ትእዛዝ በጣሰው አካል ላይ ተገቢውን ጥያቄ በተገቢው አካል አቅርበው የደረሰባቸው ጉዳት ካለ መብታቸውን ማስከበር እንጂ አፈጻጸሙ በአከራካሪው ቤት እንዲቀጥል ማስደረግ ሊሆን አይገባም፡፡ አመልካች በሰ/መ/ቁጥር 21270 እና 29269 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት አለው በማለት ያቀረቡት ክርክርም በተጠቀሱት መዛግብት ላይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ከመያዣ ቀዳሚ መብት ጋር የተያየዘ በመሆኑና በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ደግሞ በፍርድ ቤት የተሰጠ እግድ ከገዥው እውቅና ውጪ ተነስቷል ተብሎ ማረጋገጫ በመቅረቡ እግድ የተላለፈበት የማይንቀሳቀስ ንብረት በውልና ማስረጃ ፅ/ቤት በተደረገ የሽያጭ ውል ለሶስተኛ ወገን ተሸጦ ቢገኝ ውሉ በሕግ ስለሚኖረው ጥበቃ የሚመለከት በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት አስገዳጅ የሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉሞች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው አይደሉም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች ክርክር የምንቀበልበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሌላው የአመልካች ጠበቆች የሚከራከሩበት ነጥብ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአከራካሪው ቤት ላይ የተደረገው ሽያጭ ሕጋዊ የሚሆንበት አግባብ የለም፣ በማለት ሐራጁ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ከሰጠ በሁዋላ ችሎቱ ላይ የነበሩት ዳኛ ሲለወጡ በሽያጭ ውሉ ላይ ክርክር ተደርጎ የቀድሞው ትዕዛዝ ተመሳሳይ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎት ቀሪ እንዲሆን መደረጉ ሥነ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት ነው፡፡ እኛም ይህንኑ ክርክር መሰረት አድርገን የስር ፍርድ ቤትን መዝገብ አስቀርበን ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪዎች በአከራካሪው ቤት ላይ ሕጋዊ መብት አለን በማለት ወደ ክርክሩ የገቡትና በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ተደርጎ የሽያጭ ውሉ ሕጋዊ ነው ተብሎ ውሳኔ የተሰጠው ሕዳር 11 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት እንጂ ከዚህ ቀን በፊት በነበረው የክርክር ሂደት አለመሆኑን አረጋግጠናል፡፡ አንድ ሰው በሕግ አግባብ የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነበት ሁኔታ የተሰጠ ብይን ይኸው ሰው መብት አለኝ በሚል ሥርዓቱን ጠብቆ ሲቀርብ ሌላ ወገን ተከራክሮ ተገቢ ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል በሚል ምክንያት ብቻ በሌላ ወገን ላይ የተሰጠ ትእዛዝ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል የሚል ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ሁለት ጊዜ የተለያየ አቋም መያዙ ስነ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት የሚቀርበው ቅሬታ እውነትነትና ሕጋዊ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ስለእግዱ መጣስ ተጠሪዎች ያደረጉት ድርጊት አለመኖሩንና የሽያጭ ውሉም እግዱ በተነሳበት ሁኔታና ጊዜ በተገቢው አካል ዘንድ የተከናወነ መሆኑን በማረጋገጥ የሠጡት ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 67884 ሕዳር 11 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 51156 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡፡

2. በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 274 የሆነውን መኖሪያ ቤት ላይ የተደረገው ሽያጭ ውል ሊፈረስ አይገባም፣ አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ ሊቀጥል አይገባም ብለናል፡፡

3. አመልካች በእግዱ መጣስ ተግባር የደረሰባቸው ጉዳት ካለ የሚመለከተውን አካል በመክሰስ መብታቸውን ከማስከበር ይህ ውሣኔ አያስቀርም ብለናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ራውዳ መሜ - ጠበቃ አበራ ማረኝ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አምባሳደር አብደላ አብዱራህማን - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ በአጭሩ በመካከላችን የነበረው ጋብቻ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 64296 ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ፈርሷል፡፡ የጋራ ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ተከሳሽ ካናዳ ቶሮንቶ ከተማ 4725 የቤት ቁጥር 1614 የሆነውን ኮንዶምኒየም ተከሳሽ እንዲወስዱና በአ/አበባ ን/ስል/ላ/ክ/ከተማ ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 1775 የሆነውን ደግሞ ከሣሽ እንድወስድ የሚል ሃሳብ አቅርቤ ተከሳሽ ከሣሽ ያልተሳተፍኩበትን በካናዳ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በማቅረብ ለፍ/ቤቱ በማመልከታቸው በከፍተኛው ፍ/ቤት እንዲታይ የሚል ውሣኔ በመሰጠቱና በይግባኝም በመጽናቱ የቀረበ ነው፡፡ የተባለው የካናዳ ፍ/ቤት ውሣኔ ከሳሽ በሌለበት የተሰጠ የጋራ ንብረቱን በሙሉ ለአንደኛ ወገን የሚሰጥና የካናዳን ሕገ መንግስት የሚፃረርና ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ከላይ ባቀረብኩት የክፍፍል ሃሳብ መሰረት እንዲወሰን በሚል ጠይቋል፡፡

ክሱ ለተከሳሽ ደርሶ በሰጡት መልስ የከሳሽና የተከሳሽ ጋብቻ ከመፍረሱም በላይ የካናዳ ፍ/ቤት ሰኔ 23 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቀረበበት የንብረት ክርክር የካናዳውም ሆነ በአ/አበባ የሚገኘው ቤት ለተከሳሽ እንዲሰጥ የተባለ በመሆኑ አሁን የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት የካናዳ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት አፈፃፀም የማቅረብ መብቱ ተጠብቆ የደረሰው ኪሣራ እንዲከፈለኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ከክርክር በኋላ የፍች ውጤት መታየት የሚገባው ጋብቻ በተመሰረተበት ሀገር ህግ በመሆኑ እና በካናዳ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ሁሉንም ንብረት ለአንድ ወገን ብቻ የተደረገ በመሆኑ በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 34 መሠረት ባልና ሚስት በፍች ውጤት ላይ ያላቸውን እኩል ህገ መንግስታዊ መብት የሚነካ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት እኩል እንዲከፋፈሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርዱ ቤቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 337 መሠረት አጽንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በ2 ገጽ በዓፉት ማመልከቻ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ የቅሬታው ፍሬ ሃሳብ በዚህ ጉዳይ ቀድሞ በካናዳ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ እያለ በማለፍ የበታች ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ እንድሻርልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በጠበቃ በኩል ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ 2 ገጽ መልስ በካናዳ ተሰጠ የተባለው ፍርድ ያልተከራከርኩበትና የአንደኛውን ተከራካሪ ወገን መብት የሚስጥ መሆኑን ፍ/ቤቱ በመገንዘብ ውድቅ ያደረገው በመሆኑ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም በግራ ቀኙ የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሠረት በግራ ቀኙ መካከል ያለው ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሣኔ መፍረስ ተከትሎ ያለው የንብረት ክፍፍል ክስ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ተይዞ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ይሄንን ጉዳይ ስንመረምረው አመልካች ቀድሞ በፍርድ አልቋል የሚሉት በካናዳ ፍርድ ቤት ተሰጠ የተባለውና በኢትዮጵያም ሆነ በካናዳ የሚገኙትን መኖሪያ ቤቶች ለአመልካች ወስኗል የተባለውን ፍርድ ነው፡፡

አንድ የውጭ ሃገር ፍርድ ከአገራችን የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት እይታ አኳያ ሲታይ የክሱ መጀመር ወይም ከተወሰነ በኋላ ለአፈፃፀም ቢቀርቡ ያላቸው ተቀባይነት በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 8/2/ እና በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ ወይም ብይን ስለሚፈፀምበት ሁኔታ የሚደነግገው ከአንቀጽ 456 አስከ 461 ሥር የተደነገጉት ናቸው፡፡ የመጀመሪያውን አንቀጽ ማለትም አንቀጽ 8/2/ በምናይበት ጊዜ በውጭ አገር ክስ መጀመሩ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ከመመልከት እንደማያግደው የሚያመለክት በመሆኑ በዚሁ እናልፈዋለን፡፡ ከላይ በሁለተኛ ደረጃ የተመለከቱትን የህግ ድንጋጌዎች በምናይበት ጊዜ አንድ የውጭ ሃገር ፍርድ የመጨረሻ ውሣኔ ተሰጥቶበት መቅረቡ ብቻ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ሊያስገኝለት የማይቻል ስለመሆኑና የተለያዩ መመዘኛዎችን ማሟላት እንዳለበት ይደነግጋሉ፡፡ የተመለከተው ፍርድ ደግሞ በሥነ ሥርዓት ሕጉ ላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች ያሟላል ወይስ አያሟላም ማለት ደግሞ የሚቻለው የተሰጠው ፍርድ ይጠቅመኛል ወይም መብት ያጐናጽፈኛል ባይ የአፈፃፀም ማመልከቻ ከላይ በተጠቀሱት የሥነ ሥርዓት ሕጐች መሠረት ብታቀርብ ኖር እንጂ ለቀረበባቸው ክስ እንደመከራከሪያ በማቅረብ አይደለም፡፡

በመሆኑም በካናዳ ፍርድ ቤት ተሰጠ የተባለው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 456 እስከ 416 በተመለከተው አግባብ ተቀባይነቱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካችም ይሄንን ባለፍፀሙበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 መሠረት የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ ነው በማለት የቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ከዚህ አኳያ የተነሳውን ተቃውሞ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለመሆነም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 51738 የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 71195 ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ያላቸውን የጋራ ንብረት በኢትዮጵያ የፌዴራል ቤተሰብ ህግ መሠረት እኩል ይካፈሉ መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በግራ ቀኙ ላይ በዚህ ችሎት ለደረሰው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43453

15/3/2002 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሠ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች ፡- አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት ነ/ፈጅ ፋሲካ በለጠ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ዘነበወርቅ ከበደ } ጠበቃ ይፍሩ ወ/ጻዲቅ

2. አቶ ኢብራሂም አብዱጃቢር }

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪዎችና በሥር 3ኛ ተከሣሽ ላይ በቀረበው ክስ የሠ.ቁ. 3-15306 የሆነውን የከተማ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ንብረትነቱ የ1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች የሆነ መኪና በ3ኛ ተከሣሽ አማካይነት ሲሽከረከር በፈጸመው ጥፋት በከሣሽ አውቶቡስ ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ ከሣሽ አውቶቡሱን ብር 43,392.55 ወጭ አድርጎ ከማሰራቱም በላይ መኪናው ለጥገና በመቆሙ ብር 68,742.52 ከሣሽ ገቢ ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ በመሆኑም ተከሣሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ብር 112,149.67 ከነወለዱ እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች ቀርበው 1ኛ ተከሣሽ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ገልጸው አደጋው የደረሰው በ3ኛ ተከሣሽ ጥፋት ሳይሆን የከሣሽን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሾፌር በፈፀመው ጥፋት ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተጠየቀውም የካሳ መጠን የተጋነነ ነው በማለት መልስ ሠጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች /የአሁን ተጠሪዎች/ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበው አደጋው የደረሰው የከሣሽን መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሹፌር ጥፋት ስለሆነ የእኛ ንብረት በሆነው የሠ.ቁ. 1-01766 መኪና ላይ ጉዳት የደረሰ ስለሆነ ለእጅ ዋጋ፣ ለመለዋወጫና የተቋረጠ ጥቅም በድምሩ ብር 16,900 የከሣሽ ተከሣሽ እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሣሽ ተከሣሽም ጉዳቱ የደረሰው በተከሣሽ ተከሣሾች ሹፌር ጥፋት ስለሆነ ካሣ የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት መልስ ሠጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሠማ በኋላ ከሣሽ በማስረጃነት ያቀረበው የፖሊስ የምርመራ መዝገብ በአደጋው ቦታ በተነሳው ንላን መሠረት ጥፋቱ የ3ኛ ተከሣሽ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል ተከሣሾች ያስሟቸው ምስክሮች አደጋው የደረሰው የተከሣሾች መኪና በቆመበት የከሣሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መኪና መትቶ በመግጨቱ መሆኑን በቦታው ተገኝተው በዓይናቸው እንዳዩ ገልጸዋል፡፡ የከሣሽ ማስረጃ የፖ/ሊስ ምርመራ ሪፖርት ከአደጋው በኋላ ከነበረው ሁኔታ የተዘጋጀ በመሆኑ እና የተከሣሾች ማስረጃ ደግሞ በቦታው የነበሩ ሰዎች ቃል ስለሆነ ፍ/ቤቱ በተከሣሾች ማስረጃ ላይ የበለጠ እምነት ጥሎ አደጋው የደረሰው የከሣሽን መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሾፌር ጥፋት ስለሆነ ከሣሽ ኃላፊ ነው ካለ በኋላ የካሳ ክፍያውን መርምሮ ተከሣሾች በአደጋው ምክንያት ብር 9,600 ጥቅም ተቋርጦብናል ቢሉም ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም ነገር ግን መኪናው የታክሲ አገልግሎት የሚሰጥ እንደመሆኑ መጠን ገቢ ሊቋረጥ እንደሚችል ስለሚታመን በርትዕ ብር 2,000 ሺህ እንዲከፍል ለእጅ ዋጋና ለመለዋወጫ የተከፈለን በተመለከተ ተከሣሾች ማስረጃ ያቀረቡ ስለሆነ ይህንኑ ጨምሮ በጠቅላላው ብር 10,300 ከወጭና ኪሣራ ጋር ከሣሽ ለ2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ተከራክረው ፍ/ቤቱ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ 2ኛ ተጠሪ በትራፊክ ፖ/ሊሱ ኘላን ላይ ጥፋታቸውን በማመን በሰነዱ ላይ በፈረመበት ሁኔታና የተሽከርካሪው ባለቤት ናቸው የተባሉትም ጥፋቱን በመቀበል በካሳው መጠን ላይ ከአመልካች ጋር ለመደራደር ጥያቄ ማቅረባቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋት የፈፀመው የአመልካች ሾፌር ነው ተብሎ መወሰኑ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረው በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ በተጠሪዎች በኩል የቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክሱ ተቀብሎ ውሣኔ የሰጠው ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ተጠሪዎች ያሰሟቸው ምስክሮች አደጋው የደረሰው የተጠሪዎች መኪና በቆመበት የአመልካች መኪና መጥቶ በመግጨቱ መሆኑን በቦታው ስለነበሩ በዓይናቸው እንዳዩ የገለጹ ስለሆነና በአመልካች በኩል የቀረበው የባለሙያ ሪፖርት የተጠሪዎችን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር ጥፋት መፈጸሙን ቢያረጋግጥም የምስክሮቹ ቃል ይበልጥ ዕምነት የሚጣልበትና ክብደት የሚሰጠው ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በማስረጃ ዓይነቶች ክፍፍል የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት ሊቀርብ የሚችሉት ማስረጃዎች ቀጥተኛ ማስረጃ /direct evidence/ ወይም የአካባቢ ማስረጃዎች /circusmstantial evidence/ ተብለው፣ ሊመደቡ የሚችሉ ሲሆን ምስክሮች በስሜት ሕዋሳታቸው አማካይነት የተፈለገው ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖሩ እናውቃለን በማለት የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ቀጥተኛ ማስረጃ ተብሎ ይወሰዳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአካባቢ ማስረጃ የሌሎች ፍሬነገሮችን መኖር ወይም አለመኖር በማስረዳት ለክርክሩ ግምት መውሰጃ መሠረት የሆነውን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር በተዘዋዋሪ መንገድ ለማስረዳት የሚቀርብ ማስረጃ እንደሆነ በመስኩ ከዳበረው ሥነ ሕግ /Jurisprudence/ መገንዘብ ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ክሱን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ አደጋው ከደረሰ በኋላ በአደጋው ሥፍራ በተገኘ ባለሙያ /ኤክስፐርት/ አማካይነት የተዘጋጀ የባለሙያ ሪፖርት ነው፡፡ የባለሙያ ሪፖርት የኤክስፐርት ማስረጃ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ሲሆን አንድ ኤክስፐርት የሚሰጠው ቃል በፍ/ቤት እንዲረጋገጥ የተፈለገውን ጉዳይ በቀጥታ አይቻለሁ ወይንም ጉዳዩ በቀጥታ ሊረጋገጥ የሚችልበት በማንኛውም የስሜት አካሎች አማካይነት ተረድቻለሁ በማለት ሳይሆን በሙያው ሊረጋገጡ የሚችሉትን ነገሮች ተመራምሮ ውጤቱን ወይም ግኝቱን የሚገልጽ ስለሆነ የኤክስፐርት ማስረጃ በአካባቢ ማስረጃ ሥር ሊመደብ እንደሚችል ከዳበረው ሥነ-ሕግ መረዳት ይቻላል፡፡ የኤክስፐርት ማስረጃም ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ይህን ማስረጃ ሳይጠረጥረው ባለበት ሁኔታ የሚቀበለው ሣይሆን እንደማንኛውም ማስረጃ የሚመዘን ነው፡፡

የተጠሪዎች መኪና ቆሞ ባለበት በአመልካች መኪና የተገጨ ስለመሆኑ ተጠሪዎች የቆጠሯቸው ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበው የባለሙያ ሪፖርት ጥፋቱ የተጠሪዎችን መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሹፌር የተፈጸመ መሆኑ ቢረጋገጥም የባለሙያ ማስረጃ የኤክስፐርት ማስረጃ እንደመሆኑ መጠን ኤክስፐርቱ መጨረሻ ላይ የሚደርስበት መደምደሚያ /ግኝት/ ሙያዊ አስተያየት /opinion/ እንጂ ፍሬ ነገር /fact/ ሊሆን አይችልም፡፡ የኤክስፐርቱ የሚደርስበት የመጨረሻ አስተያየት ከሚኖረው ሙያዊ ዕውቀት አድማስ ከሚታገዘበት መሣሪያና ከመሳሰሉት ጋር የተሟላና ሙሉ ዕምነት የሚጣልበት ማስረጃ /conclusive evidence/ ሊሆን ስለማይችል በዓይን ምስክሮች የተነገረን ፍሬ ነገር ለማስተባበል የሚያበቃ አቅም አይኖረውም፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም ቀደም ሲል በሰበር መ.ቁ. 14981 የኤክስፐርት ማስረጃ ሙሉ ዕምነት ሊጣልበት የሚችል ማስረጃ እንዳልሆነ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ ከዚህም ሌላ የኤክስፐርት ማስረጃ በማስረጃነት በቀረበ ጊዜ ይበልጥ ተቀባይነት የሚኖረው ከቀጥተኛ ማስረጃ ጋር በተጣጣመ ጊዜ እንጂ ቀጥተኛ ማስረጃውን በሚሻረር ጊዜ የበለጠ ክብደት የሚሰጠው ለቀጥተኛ ማስረጃው ስለሆነ የኤክስፐርት ማስረጃው ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል መገንዘብ ስለሚቻል የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በቀጥተኛው ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ጥፋት የተፈጸመው የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር በነበረው ሹፌር አማካይነት ነው ሲል የደረሰበት መደምደሚያ ከማስረጃ አቀራረብ መሠረታዊ መርህ አኳያ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

በሌላ በኩልም የተጠሪዎች ሾፌር ጥፋተኛ በተደረገበት በባለሙያ አስተያየቱ ላይ ፈርሞ መገኘቱ እንደዚሁም ተጠሪዎች ይህንኑ ተቀብለው ለአመልካች ካሣ ለመክፈል ተደራድረው ነበር መባሉ የኤክስፐርት ማስረጃውን ከቀጥተኛ ማስረጃው የበለጠ ተቀባይነት ሊያደርገው ስለማይችል ውጤቱን ሊቀይረው የሚችል ሆኖ አላገኘውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08549 በ28/6/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 67409 በ8/3/2001 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሸ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 04 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

አብዱልቃድር መሐመድ

ጌታቸው ምህረቱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሰ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የባለሙያ አስተያየት የመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካች ለም/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አቶ መሐመድ አብዱራህማን ከባንኩ ለወሰዱት ብድር ተጠሪ ንብረታቸውን በዋስትና ስላስያዙ ተበዳሪው በሚፈለግባቸው ዕዳ ተጠሪ በዋስትናቸው መሠረት ግዴታቸውን እንዲወጡ ጠይቋል፡፡ ተጠሪም የገቡት የዋስትና ውል አለመኖሩን በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ፍ/ቤቱም በዋስትና ሠነዱ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪዋ አለመሆኑን በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ በመረጋገጡ ተጠሪ ሊጠየቁ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በባለሙያ የሚሰጥ አስተያየት የመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) ነው ወይ? የሚለውን የሕግ ነጥብ ለመመርመር ጉዳዩን ለሰበር ችሎት አስቀርቧል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ ዋነኛው አከራካሪ የሆነው ተጠሪ ንብረታቸውን በማስያዝ የዋስትና ግዴታ የመግባታቸው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪዋ ለተሰጠው ብድር የዋስትና ግዴታ መግባታቸውን ለማስረዳት የዋስትና ሠነዱን እንዲሁም ምስክሮችን አቅርቧል፡፡ ምስክሮቹም ተጠሪ በዋስትና ውሉ ላይ የፈረሙ ለመሆኑ ባል የሌላቸው መሆኑን ከቀበሌ ማስረጃ አቀርበው እንደነበር አረጋግጠዋል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ፊርማውን የካዱ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ፊርማው በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ክፍል እንዲመረመር አድርጎ በሠነዱ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪዋ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ውጤት ለፍ/ቤቱ ቀርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ፊርማው የተጠሪ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስለቀረበ የሰው ማስረጃው ፋይዳ ከሌለው መሠማታቸው ስህተት ነው በማለት የመስክሮቹን ቃል ሙሉ በሙሉ ውቅድ በማድረግ ተጠሪን ከተጠያቂነት ነፃ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የባለሙያ አስተያየት ተቃራኒ ማስረጃ ሊቀርብበት የማይችል የመጨረሻ ማስረጃ መሆን አለመሆኑን መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአገራችን ራሱን የቻለ የማስረጃ ሕግ ባለመኖሩ በዚህ ጉዳይ በቀጥታ ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ ሊጠቀስ ባይችልም በሌሎች አገሮች ተቀባይነት ካገኘው የማስረጃ ሕግ መርህ ግን መረዳት የሚቻለው የባለሙያ አስተያየት ብቻውን ለመቆም የሚችል ወይም በተቃራኒ ማስረጃ ሊስተባበል የማይችል ሳይሆን ይልቁንም ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ተገናዝቦ ብቃቱና ተአማኒነቱ ሊመዘን የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን በባለሙያ አስተያየቱ መሠረት የሚያቀርበው የሣይንሳዊ ጥናትና ምርመራ ውጤትን ቢሆንም ሣይንስ በራሱ ፍፁም እርግጠኛነት የሌለውና ሙሉ እምነት የሚጣልበት አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ የባለሙያ አስተያየት ብቻ እንደበቂ ማስረጃ ተቆጥሮ ሌሎች ማስረጃዎችን ያለበቂ ምክንያት ተቀባይነት ማሳጣቱ ወደ ተሣሣተ መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችል ይሆናል፡፡

በተያያዘው ጉዳይም ቢሆን ፍ/ቤቱ የቀረበለትን የፖሊስ ምርመራ ውጤት ብቻ ተቀብሎ የምስክሮቹ ቃል ተቀባይነት ወይም ተአማኒነት ሊያጣ የሚገባበትን በቂ ምክንያት ሣይገልፅ የምርመራ ውጤቱ በመቅረቡ ብቻ በደፈናው የሰው ማስረጃ ፋይዳ የለውም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ስህተት መሆኑን ተረድተናል፡፡

በሌላ በኩል ፍ/ቤቱ ከግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች እንዲሁም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ጠቃሚ ነው የሚለውን ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር የሚችል ቢሆንም የጠሪን ምስክሮች እንዲቀርቡ በማድረግ የምስክርነት ቃላቸውን ከሰማ በኋላ የባለሙያ አስተያየት በመቅረቡ ብቻ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 207 መሠረት የምስክርነት ቃሉን ውድቅ ማድረጉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አካሄድ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም የተጠቀሰው የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ ክስ ሲቀርብ ወይም በክሱ ውስጥ ከደንብ ውጪ የሆነ ተግባር ሲፈፀም ስህተቱን ለማረም የተቀመጠ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ምስክሮቹ በአመልካቹ የተቆጠሩ በመሆናቸው ቀርበው መሰማተቸው ስህተት አልነበረም፡፡ በአመልካች ባይቆጠሩ እንኳን ፍ/ቤቱ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ጠቃሚ ናቸው ብሎ ካመነ እንዳይሰሙ የሚከለክል ሥርዓት የለም /የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 ይመለከታል/፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ምስክሮቹ የሰጡት ምስክርነት ተአማኒነት የለውም ካለ ይህንኑ ገልፆ ውድቅ ከሚያደርገው በቀር ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የሥነ-ሥርዓት ድነጋጌ መሠረት በማድረግ የሰው ማስረጃውን ውድቅ ማድረጉ ስህተት ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች የባለሙያ አስተያየቱን እንደመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) አድርገው በመውሰድ የሰው ማስረጃውን ውድቅ በማድረጋቸው የሕግ ስህተት ፈጽመዋል፡፡

ው ሣ ኔ

3. የም/ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24190 ግንቦት 28/1995 የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00894 ታህሣስ 13/1996 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
4. ተጠሪ በዋስትና ባስያዙት ንብረት ግምት ልክ ለሚፈለገው የዕዳ መጠን ተጠያቂ ናቸው፡፡
5. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ በመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 09 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ማሞ ደምሴ ወኪል ወ/ት አዲስ ማሞ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር
2. ወ/ሮ ታየች ብርሃኑ } በሌሉበት
3. ወ/ሮ ከበቡሽ በጅጋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 መሠረት የሚቀርበውን የተወሰደ ነገር የማስመለስ ጥያቄንና አፈፃፀሙን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ በሐረር ከተማ ቀበሌ 14 ውስጥ የቤት ቁጥር 700 የሆነ መኖሪያ ቤትን በሚመለከት ክርክር ላይ የነበሩ መሆኑንና ክርክሩም በመ/ቁጥር 84/88 ታይቶ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቤቱን የአሁኑ አመልካች ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲያስረክቡ የሚል ውሳኔ ተስጥቶ ፍርዱ እንዲፈፀም በመ/ቁጥር 14/90 በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ቤቱን አመልካች ያስረከቡ ቢሆንም በቀጥታ ክስ ላይ በተሰጠው ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ በጉዳዩ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በመ/ቁጥር 5390 ጥር 29 ቀን 1999 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ መሻሩን በመግለፅ ቤቱን ተጠሪዎች መልሰው እንዲያስረክቡ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ ጉዳዩ ቀደም ብሎ በፍርድ ያለቀ ነው፣ አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም (ባለቤት አይደሉም)፣ ቤቱን በሕግ አግባብ በተደረገ የሽያጭ ውል ከባለቤቶቹ ገዝቼ ቤቱን በመረከብ ስመሃብቱን በማዛወር እየተጠቀምኩ የምገኝ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የ3ኛ ተጠሪን ክርክር ባለመቀበል ውድቅ አድርጎ ቤቱን ለአሁኑ አመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህም በኋላ 3ኛ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ መዛግብት የቀረቡትን ክርክሮችና የተሠጡትን ውሳኔዎችን ይዘት በመመርመር ለአሁኑ አመልካች መብት የሚሰጥ ውሳኔ አለመሰጠቱን እና የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ቤቱን በሕግ አግባብ መግዛታቸውን በመግለፅ የበታች ፍርድ ቤቶችን ብይን ሽሮ አመልካች ቤቱን የሚረከቡበት አግባብ የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 04 ቀን 2001 ዓ.ም በተጻፈ ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስ ጥያቄ ቀርቦ በበላይ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ተጠሪዎች ይግባኝ ብለው ተቀባይነት ባላገኙበት ሁኔታ 3ኛ ተጠሪ ቤቱን በሕግ አግባብ ገዝተዋል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ ሊሻር ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪዎች በተገቢው መንገድ ጥሪ ሲደረግ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ሳይቀርቡ በመቅረታቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ግን ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም 3ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ላይ የመልስ መልሳቸውን በጽሑፍ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን በበታች ፍርድ ቤቶች ከተደረጉት ክርክሮችና ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እንዲሁም አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡ ለዚሁ ጭብጥ ምላሽ ለመስጠት ይቻል ዘንድም በጉዳዩ ላይ የተደረጉትን ክርክሮችን በእየእርከኑ ባሉት ፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ውሳኔዎችን መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች ከአቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር (ከአሁኑ 1ኛ ተጠሪ) ጋር ያደረገው የቤት ሽያጭ ውል እንዲጸድቅላቸው ስመ ሀብቱ እንዲዞርላቸው ይወሰን ዘንድ በጊዜው ለነበረው ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤቱም ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ አድርጎ ባለመቅረቡ ውሉን በማፅደቅ ስመ ሀብቱ በአሁኑ አመልካች እንዲዞር ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በዚህ ውሳኔ መሰረት ከመፈፀሙ በፊት ቤቱን ሸጠ የተባለው ግለሰብ፣ የግለሰቡ ሚስት(ወ/ሮ ታየች ብርሃኑ) እና የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ፍርዱን በመቃወም አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የተቃውሞ አቤቱታቸውን በመቀበል ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የቤት ሽያጭ ውሉ ሻጭ የሆኑትን ግለሰብ (አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር) ሚስት ወ/ሮ ታየች ብርሃኑ ፈቃድ የሌለበት በመሆኑ ፈራሽ ነው በሚል የቀድሞውን ውሳኔ በመሰረዝ ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸውን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት ባያገኙም የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ጉዳዩ ከታየ በኋላ አመልካች መጀመሪያውኑ የቤት ሽያጭ ውል ይፅደቅልኝ በማለት ለአውራጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ነው በሚል ምክንያት መዘጋት ሲገባው ጉዳዩ መታየቱ ያላግባብ ነው በሚል ምክንያት በበታች ፍርድ ቤቶች የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አመልካች ውሉ በፍርድ ቤት ውሳኔ ይጽደቅልኝ በማለት ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት ቤቱን ተረክበው የነበሩ ሲሆን ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ የአሁኑ 1ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና 2ኛ ተጠሪዎች ቤቱን አመልካች ያስረክበን በሚል ጥያቄ አቅርበው ፍርድ ቤቱ አመልካች ቤቱን ለእነዚህ ተጠሪዎች እንዲያስረክቡ በማለት ግንቦት 26 ቀን 1989 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቶ በዚህ ውሳኔ መሰረት የአፈጻጸም መዝገብ ተጠሪዎች አቅርበው አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች መስከረም 20 ቀን 1990 ዓ.ም አስረክበዋል፡፡ ከዚህም በኋላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በጋራ ሁነው ለአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ሰኔ 17 ቀን 1984 ዓ.ም በተደረገና ሐምሌ 22 ቀን 1984 ዓ.ም በፍርድ ቤት በተመዘገበ የሽያጭ ውል ቤቱን ሸጠው 3ኛ ተጠሪ ቤቱን በመረከብ ስመ ሀብቱን ሁሉ አዙረው መጠቀም ቀጥለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ግንቦት 26 ቀን 1989 ዓ.ም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያገኙት ፍርድ በአሁኑ አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦበት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ የስረ ነገር ሥልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ ነው በሚል ምክንያት የተሻረ ሲሆን የአሁኗ 3ኛ ተጠሪም በዚህ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቀርቦበት ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን ችሎቱ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ችሏል፡፡ ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ የአሁኑ አመልካች አከራካሪው ቤት ላይ የስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤት የተሻረ ስለሆነ ተጠሪዎች በፍርድ ኃይል የተረከቡትን ቤት መልሰው ያስረክቡኝ በሚል ጥያቄ ያቀረቡት፡፡

በመሰረቱ የተወሰደ ነገር ለማስመለስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349(1) መሰረት አቤቱታ የሚቀርበው ይግባኝ የተባለበት ፍርድ ወይም ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተለወጠ ወይም የተሻሻለ የሆነ እንደሆነ ሲሆን ይኸው ሲረጋገጥ ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ነገሩን በመጀመሪያ ደረጃ ላየው ፍርድ ቤት ሲያመለክት የተሻሻለው ወይም የተለወጠው ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ክርክር የተነሳበት ነገር ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ እንዲችል በመጀመሪያው ፍርድ መሰረት የተወሰደው ንብረት ወይም ገንዘብ ለባለመብቱ እንዲመለስ ወይም የተከራካሪዎቹ ወገኖች መብት በይግባኙ ፍርድ መሰረት እንዲስተካከል ተስማሚ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ፍርድ ቤቱ መስጠት ያለበት መሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ ተጠቃሹ የንዑስ ቁጥር 3 ድንጋጌ ስር አቤቱታው የሚቀርብበትን ሥርዓት አስቀምጧል፡፡ ይኸውም ለማስመለስ የሚቻለውን ሀብት ወይም ለማስተካከል የሚቻለውን መብት ለማስፈጸም ሌላ የክስ መዝገብ መክፈት አስፈላጊ አለመሆኑ በሕጉ ተመልክቷል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349(1) መሰረት የተወሰደን ንብረት ለማስመለስ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሠጠው ውሳኔ በይግባኝ መሻሻል ወይም መለወጥ እና ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት ይመለስልኝ የሚለው አቤቱታ አቅራቢ የንብረቱ ባለመብት መሆን መረጋገጥ ስለመሆናቸው ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ነጥብ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ቤቱን ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በግዥ አግኝቼአለሁ፣ እነዚህ ተጠሪዎች ቤቱን የተረከቡበት ፍርድ በበላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል ቢሉም አመልካች በየትኛውም የክርክር መስመር ወይም ደረጃ የአከራካሪው ቤት ባለንብረት መሆናቸው ተረጋግጦ የተሰጠ ፍርድ የሌለ መሆኑን ከላይ የተመለከተው የክርክሩ አመጣጥ በግልፅ ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 መሰረት አቤቱታ የሚያቀርበው ወገን ደግሞ የንብረቱ ባለመብት የሆነ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ የአሁኗ 3ኛ ተጠሪ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ውሳኔ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የስረ ነገርን ስልጣን መሰረት ባደረገ ምክንያት በመሻሩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ተቀባይነት ያለማግኘታቸውም የአሁኑን አመልካች የአከራካሪው ቤት ሕጋዊ ባለንብረት ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ ይልቁንም 3ኛ ተጠሪ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት ናቸው ከተባሉት ከአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች (ባልና ሚስት) ቤቱን ከአመልካች ከተረከቡ በኋላና አመልካችም በየደረጃው በነበሩት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቶች ክርክር ሲያደርጉ በቤቱ ላይ በሕጉ አግባብ የእግድ ትዕዛዝ ባላሰጡበት ሁኔታ ስልጣን ባለው አካል ፊት በሕጉ አግባብ በተደረገው የሽያጭ ውል ቤቱን ገዝተውና ተረክበው እንዲሁም ስመ ሀብቱን በማዛወርና ለውጦችንም በማድረግ ለበርካታ ጊዜያት የሚጠቀሙበት መሆኑ መረጋገጡ ሦስተኛ ወገን የሆኑት ግለሰብ እጅ የገባን ንብረት አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349ን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ጥያቄ የማቅረብ መብት የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች በሕጉ አግባብ ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት ግንኙነት ካለና በዚህ ግንኙነት መሰረት ወጪ ያደረጉት ገንዘብ ካለም እነዚህን ተጠሪዎች ከሚጠይቁ በስተቀር ቤቱን ከ3ኛ አመልካች ሊወስዱ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮችንና የትኛው ወገን ከቀድሞ ባለቤቶች ጋር ሕጋዊ ግንኙነት መስርቷል ከሚለው ጥያቄ ምላሽ እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 ድንጋጌ መንፈስና ይዘት ጋር ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር ሊነቀፍ የሚችልበትን መሰረታዊ የሕግ ነጥብ አላገኘንም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01169 ታህሳስ 07 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 56130

ጥር 26 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡ - ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ሊሲ ታነሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አብይ ስንታየሁ /ስራ አስኪያጅ/ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ መዓዛ አስፋው - አልቀረቡም፡፡

2. አቶ ክብሮም ሙሉ - አልቀረቡም፡፡

3. አቶ አየለ ኮሮሶ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪዎች ከድል የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር ተከራክረው የፍርድ ባለመብት መሆናቸውን ገልፀው የአፈፃፀም መዝገብ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከፍተዋል፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳው የሚገኝበት የምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በባለዕዳው ስም የሚገኘውን ንብረት በማሸጥ ብር 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ ለፍርድ ባለመብቶቹ እንዲያስከፍል በማለት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 371 እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 392/1/ሀ መሠረት ውክልና ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ አፈፃፀሙ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀጥሏል፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ንብረት እንደሚሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ አውጥቷል፡፡ በሀራጅ ማስታወቂያው መሠረት ሽያጭ ፈጽሟል፡፡ ስለ ሽያጭ ሒደቱም ውክልናውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ሪፖርት አድርጓል፡፡ አመልካች በዕዳ የተሸጠው የእኔ ንብረት ነው ሽያጩ የተከናወነው የካቲት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ነው፡፡ እኔ በማይመለከተኝ ዕዳ ንብረቴ መሸጡን ያወቅሁት ገዥው ስመ ንብረቱን ለማዛወር እንቅስቃሴ ሲያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝልኝ በማለት አመልክተዋል የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ውድቅ አድርጐታል፡፡ የመጀመሪያው አቤቱታው መቅረብ ያለበት በውክልና ቤቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላሸጠው ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆን አለበት በማለት የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 374 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመጥቀስ የወሰነ ሲሆን፣ ሁለተኛው አቤቱታው ሽያጩ በተከናወነ በሁለት ወር ውስጥ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አቤቱታው አልቀረበም በማለት ነው። አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ይግባኝ ፍሬ ነጥብ የሌለው መሆኑን በመግለጽ በፍታብሔር የሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል።

አመልካች ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የጨረታ ማስታወቂያው የፍርድ ባለዕዳውን ስም በግልጽ መያዝ ሲገባው "የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር" በሚል ስያሜ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ወጥቷል። የፍርድ ባለዕዳው በትክክል ባልተገለፀበት ሁኔታ የእኛ ንብረት ላይ የሃራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ያወጣ መሆኑን አውቀን ልንከታተል እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447/1/ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ሀራጁ እንዲሰረዝ ለማመልከት የምንችልበት ሁኔታ የለም። ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ጥያቄያችንን ተቀብለው ሁኔታውን አጣርተው መወሰን ሲገባቸው ባለዕዳ ባልሆንበት ፍርድ ንብረታችን እንዲሸጥ መደረጉና ሽያጩ ይፀናል ማለታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክተዋል።

ተጠሪዎች በበኩላቸው ጥያቄው መቅረብ ያለበት በውክልና ንብረቱን በሸጠው ፍርድ ቤት መሆን ይገባዋል። ይህንንም በተለያዩ ምሁራን የተፃፉ የህግ ትንታኔዎችን በማየት ለመገንዘብ ይቻላል። የምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሸጥ የታዘዘው በተለይ በአዋሳኝ የተገለፀው ቦታ የአመልካችን ንብረት አይደለም። የተሸጠው የባለዕዳው ንብረት ነው። አመልካች በስም ስህተት የእኔ ንብረት ነው የተሸጠው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢ አይደለም በሀራጅ የተሸጠው ንብረት በእነ አዜብ ሙሉ አውራሽ በአቶ ሙሉ በአቶ ደረጃ ደመቀና በአቶ ስለሺ ሀይሌ በተቋቋመው ድል የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥር የተያዘ ነበር። ይህ የንግድ ማህበር ሳይፈርስ እንደፈረሰ በማስመሰል ሊሲ ታነሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚል ስም ይዘነዋል እያሉ የሚያቀርቡት ክርክር የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክረዋል። አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ሀራጁን እንዲያስፈጽም ለተወከለው ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥና የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄውን አላቀረበም በማለት የሰጡት ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የህግ ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች እልባት ማግኘት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል።

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመወሰን በዚህ መዝገብ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የተከተለውን አሠራርና የህጉን ድንጋጌ ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሞጆ ከተማ የሚገኘው የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ይዞታና ንብረት በማሸጥ ለፍርድ ባለመብቶች ብር 250,000 /ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር/ እንዲከፍል ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውክልና ሰጥቷል። የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥቅምት 3 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውክልና መሠረት "የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር" ንብረት በጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲወጣ በማድረግ ንብረቱን በሀራጅ ሸጧል። የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ንብረቱን በሀራጅ የካቲት 14 ቀን 2001 ዓ.ም ከሸጠው በኋላ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረቡ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን አቤቱታ ከተቀበለ በኋላ ስለ ሀራጁ አካሄድ ጉዳዩን በውክልና ያስፈፀመው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማብራሪያ እንዲሰጠው ታህሳስ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥር 20 ቀን 2002 ዓ.ም አምስት ገጽ ማብራሪያ ልኮለታል። የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማብራሪያ ከደረሰው በኋላ የካቲት 2 ቀን 2002 ዓ.ም አመልካች አቤቱታውን ማቅረብ ያለብህ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ቤት ፍርድ ነው በማለት ወስኗል።

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ይህንን ብይን መስጠት የነበረበት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማብራሪያ እንዲሰጠው ከመጠየቁ በፊት አመልካች አቤቱታውን ወዲያውኑ እንዳቀረበ መሆን ነበረበት። የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ተቀብሎ ጉዳዩን ለማጣራት ረጅም ጊዜ ከወሰደ በኋላ አመልካች ወደ ምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ እንዲያቀርብ መወሰኑ ተገቢ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዋቢነት የጠቀሰው የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 374 ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀሙ በውክልና የሚያከራክረው ፍርድ ቤት የስልጣን ወሰንን የሚገልጽ እንጅ የሃራጅ ሽያጭ ተከናውኖ ካለቀ በኋላ ጉዳዩን በውክልና ካስፈፀመው ፍርድ ቤት ሙሉ ማብራሪያ የተሰጠው ወካዩ ፍርድ ቤት የሀራጅ ሽያጩ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ሲቀርብለት ጉዳዩን እንዳያከራክር እና ውሣኔ እንዳይሰጥ የሚከለክል ድንጋጌ አይደለም። ድንጋጌም ሁለቱም ፍርድ ቤቶች እኩልና አቻ ስልጣን ያላቸው መሆኑን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው። ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ተቀብለው ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን እንደሌላቸው በመግለጽ የሰጠውን ብይን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የሁለት ወር የጊዜ ገደብ በአፈፃፀም ክርክሩ ተሳታፊ የነበረ የፍርድ ባለመብት፣ የፍርድ ባለዕዳ ወይም በሀራጅ ንብረቱን የገዛው ሰው የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ በሁለት ወር ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት የሚደነግግ የህግ ድንጋጌ ነው። ይህ ድንጋጌ የፍርድ ባለዕዳ ያለሆኑ የሦስተኛ ወገን ንብረት በሀራጅ በተሸጠ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የሀራጅ ጨረታ ማስታወቂያው በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 423 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ያሟላ በሆነ ጊዜና የሀራጅ ማስታወቂያው በሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 414 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 425 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት የተለጠፈ መሆኑ ሲረጋገጥና የንብረቱ ባለሀብት ነኝ የሚለው ሰው የሀራጅ ሽያጭ በንብረቱ ላይ እየተካሄደ መሆኑን የሚያውቅ ወይም ማወቅ የሚገባው ሆኖ ሲገኝ ነው።

በያዝነው ጉዳይ የፍርድ ባለዕዳ የሆነው ድል የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን በጋዜጣ የወጣው የሀራጅ ማስታወቂያ "የቆዳ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የግል ማህበር" በሚል ስያሜ መሆኑንና የሀራጅ ማስታወቂያው በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 423 በሚደነግገው መሠረት የፍርድ ባለዕዳውን ስም በትክክል የሚገልጽ አለመሆኑ ተረጋግጧል። ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ንብረቱ ነው የሚለው የማይንቀሳቀስ ንብረት በሃራጅ እየተሸጠ መሆኑን ለማወቅ የሚችልበት ሁኔታ የነበረ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት አላጣራም። የሀራጅ ማስታወቂያው በህጉ የተደነገገውን መስፈርት የማያሟላ በሆነበት ሁኔታ የሀራጅ ሽያጩ በፍርድ ባለዕዳው ድል የቆዳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ንብረት ላይ ሳይሆን በእኔ ንብረት ላይ ነው የሚለው የሚለውን የአመልካች ጥያቄ ለመወሰን አግባብነት ያለው የህግ ድንጋጌ የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447/1/ ሳይሆን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ድንጋጌ ነው፡፡

አመልካች የፋብሪካውን ስመ ንብረት ሐራጅ አሸናፊ ሆኖ ወደ ገዛው ሰው ለማዛወር የሚደርገውን እንቅስቃሴ በመቃወም ንብረቱ የፍርድ ባለዕዳው ሳይሆን የእኔ ሀብት ስለሆነ ልለቅ አይገባኝም የሚል አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቅጽ 1 ይደነግጋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካች አቤቱታ ለፍርድ ባለመብትና ንብረቱን ለገዛው ሰው እንዲደርስ በማድረግና ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ቀነ ቀጠሮ በመያዝ ማከራከር እንዳለበት የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚደነግግ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተገቢ ነው የሚለውን ውሣኔ የማሰጠት ግዴታና ሀላፊነት አለበት፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታና ማስረጃ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በመቀበል የግራ ቀኙን ክርክር በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በመስማት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት መወሰን ሲገባው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀጽ 1 በመጥቀስ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታና ማስረጃ እንደዚሁም የተጠሪዎችን መልስና ማስረጃ በመቀበልና የሚያቀርቡትን ክርክር በመስማት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 453 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 19 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- እነ አቶ ላሪ ሮላንድ ቻፕማን ጠበቃ ከድር ቡሎ ቀረበ

ተጠሪ ፡- አቶ ዜና ወልደማሪያም የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካቾች በስር ፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሌለንበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ክርክሩ ባለንበት ይታይልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው በሚል በጠበቃቸው አማልካኝነት መጋቢት 15 ቀን 2002ዓ.ም የተፃፈ ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታቸውን ስላቀረቡ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው ሐምሌ 13 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ ሶስት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም ላይ መጥሪያ በአግባቡ ደርሶ ተገቢው ሰው ለክርክር ሳይቀርብ በመቅረቱ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ ውሳኔ የተሰጠ ስለሆነ እና በፍርዱ መሠረት ከፊሉም የተፈፀመ በመሆኑ የፍርድ አፈፃፀሙን ለማጓተት የቀረበ አቤቱታ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን የሚገባው መሆኑን ገልፀው የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጓቸውን የጽሁፍ ክርክሮች ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደሚታወቀው የፍትሐብሔር ክርክሮች የሚመሩት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት ነው፡፡ ይኽው የሥነ ሥርዓት ሕግ አካቶ ከያዛቸው ጉዳዩች ውስጥ አንዱ የተከራካሪ ወገኖች በክርክሩ ወቅት ያለመቅረብና ውጤቱ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መጥሪያ ተልኮለት በተገቢው መንገድ የደረሰው መሆኑ በተረጋገጠበት ተከሳሽ ላይ ፍ/ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓት ጉዳዩ ተከሳሹ በሌለበት የሚሰማበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70/ሀ/ ስር ተመልክቷል፡፡ ሌላው በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከተው ሥርዓት ተከሳሹ ሊከተለው የሚገባው መፍትሔ ነው፡፡ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል የተደረገበት ተከሳሽ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያለመቅረቡን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 72 ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78/1/ አንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠ ከሆነ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትዕዛዙ ወይም ውሳኔው እንዲነሳለት የማመልከት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ ተከሳሽ የጥሪው ትዕዛዝ በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን ወይም ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ቀርቦ መከራከሪያውን ያላሰማ ወይም መልስ ያልሰጠው በበቂ ምክንያት መሆኑን ለፍርዱ ቤቱ ያስረዳ እንደሆነ ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ የተሰጠው ብይን ወይም ትዕዛዙ እንደሚነሳለትና ክርክሩ እንደገና እንደሚሰማለት ይደነግጋል፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው ተከሳሽ በቀነ ቀጠሮ ያልቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳው ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የተሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ብይን በማንሳት ክርክሩ ተከሳሹ ባለበት እንዲቀጥል ማድረግ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ የድንጋጌው ዓላማም የተከሳሹን የመከራከር መብት ለመጠበቅ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡ በመሆኑም ተከሳሹ ቀና ልቦና ያለው መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በቂ ምክንያት የሚለው የድንጋጌው ሐረግ መታየትና መተግበር ያለበት የተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተከሳሹን የመከራከር መብት በሚጠበቅ መልኩ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስመንለስም አመልካቾች በቀጠሮው ቀን ስላለመቅረባቸው ያቀረቡት ማስረጃ የቤተሰብ ጤና ችግር መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የሥር ፍ/ቤትም ይህ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም ወደሚለው ድምዳሜ አልደረሰም፡፡ የስር ፍ/ቤት በቀደመው ቀነ ቀጠሮ የቀረቡትን የአመልካቾችን ጠበቃ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ለመቆም የሚያስችል የጥብቅና ፈቃድ የላቸውም በማለት ተገቢውን ፈቃድ አሚልተው እንዲመጡ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቶ ጠበቃቸው አልቀረቡም፡፡ አመልካቾቹም በቤተሰባቸው የጤና መታወክ ችግር ምክንያት በተለዋጩ ቀነ ቀጠሮ አልቀረቡም፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካቾችን ጉዳዩ ባለንበት ይታይልን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በጠበቃ መወከል ትችሉ ነበር በሚል ምክንያት ነው፡፡ በመሠረቱ በጠበቃ መወከል ግዴታ ሳይሆን መብት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ከላይ እንደተገለፀው የአመልካቾች ቤተሰብ የጤና ችግር በወቅቱ መድረሱን ያረጋግጣል የተባለውን የህክምና ማስረጃ ተቀባይነት ሰጥቶ በጠበቃ መወከል ትችሉ ነበር በሚል ምክንያት አመልካቾች በሌሉበት እንዲታይ የተሰጠውን ትዕዛዝ ሳያነሳ መቅረቱ የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ዓላማንና የአመልካቾችን የመከራከር መብት ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የአመልካቾች ጠበቃ ተገቢውን ፈቃድ አልያዙም በሚል ምክንያት አመልካቾችን መወከል አይችሉም ተብሎ ከተሰናበቱ በኋላና አመልካቾችም በቤተሰብ የጤና መታወክ ችግር ምክንያት በተለዋጩ ቀጠሮ አለመቅረባቸው ተረጋግጦ እያለ በተከራካሪ ወገን ፈቃድ ላይ የተመሰረተውን በጠበቃ የመወከል መብት እንደ አማራጭ በመውሰድ አመልካቾች ወደ ክርክሩ ሊገቡ አይገባም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 33470 ጥር 12 ቀን 2002ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 89198 ጥር 28 ቀን 2002ዓ.ም የፀናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ የሆነው አመልካቾች ያቀረቡት ማስረጃ ተቀባይነት ያለው መሆኑና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78/2/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ከመከራከር መብት ጋር ባላገናዘበ መልኩ ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካቾች ተከሳሽ ሆነው በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ አመልካቾች ባሉበት ክርክሩን አቅርበው ግራ ቀኙ ባለቡት ጉዳዩ እንደገና በስር ፍ/ቤት ታይቶ ይወሰን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78/2/ መሠረት ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሣሥ 15 ቀን 2003

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ጭላሎ ሥራ ተቋራጭ የተወሰነ የግል ማህበር አልቀረበም

ተጠሪ፡- አፍሪካ ኢንጅነርስ ኮንስትራክሽን ጠበቃ አቶ ተሰማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የማሽነሪ ኪራይ ውል አፈፃፀምን የተመለከተ ነው ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ከሣሽ በመሆን አንድ ግሬደር በሰዓት ሁለት መቶ ሃምሣ ብር ላንድሮለር በሰዓት ሁለት መቶ ብር አንድ ዶዘር በሰዓት አራት መቶ ብር ሊከፍል የአሁን አመልካች /ተከሣሽ/ የወሰደ መሆኑን ገልፆ ያልተከፈለ የማሽነሪ ኪራይ ብር 1,327,500.00/አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ያለበት ስለሆነ እንዲከፍለኝና ማሽነሪዎቹን እንዲያስረክበኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ /ተጠሪ/ የጠየቀው ማሽነሪዎቹ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በዝናብና በጎማ አለመኖር ለቆመበት ሰዓት በመሆኑና የሠሩበት ሠዓት በሹፌሮቹ ተረጋግጦ የቀረበ ባለመሆኑ ክሱ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሣሽ /ተጠሪ/ ያቀረበውን ክስ የሚያስረዳ ማስረጃ ያቀረበ በመሆኑና አመልካች /ተከሣሽ/ የኪራይ ገንዘብ ትክክል አይደለም በማለት ከሚከራከር በስተቀር ክርክሩን የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሒሣቡ በባለሙያ ተጣርቶ መቅረብ እንዳለበት በማመን አመልካች አንድ ባለሙያ ተጠሪ አንድ ባለሙያ እንዲመርጡና ሒሣቡን ሁለቱ ባለሙያዎች በጋራ አጣርተው እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሁለቱ ባለሙያዎች በጋራ ሒሣብ እንዲያጣሩ የተሰጡትን ትእዛዝ ወደ ጎን በመተው አመልካች የመረጠው ባለሙያ ሒሣቡን ለብቻው በማጣራት አመልካች ለተጠሪ ያልከፈለው ብር 54,267.17 /ሀምሣ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሥልሣ ብር ከአሥራ ሰባት ሣንቲም/ ነው በማለት የሒሣብ ሪፖርት ለብቻው ያቀረበ ሲሆን በተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመረጡት ባለሙያ በበኩላቸው አመልካች በተጠሪ ያልከፈለው ቀሪ ሒሣብ ብር 1,327,005 /አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሃያ ሰባት ሺህ አምስት ብር/ አለበት በማለት የብቻውን የሒሣብ ሪፖርት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካች የተመረጠው ባለሙያ ያቀረበው ጥቅል የሒሣብ ሪፖርት መሆኑና በተጠሪ በኩል የተመረጡት ባለሙያ ዝርዝር የሒሣብ ሪፖርት ያቀረቡ መሆኑን በመግለጽ በተጠሪ የተመረጠው ባለሙያ ያቀረበው የሒባብ ሪፖርት አሣማኝነት አለው በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት አመልካች ለተጠሪ ብር 1,327,005 እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የኪራይ ሒሣቡ በባለሙያ ሣይጣራ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰጠቱ በአግባቡ መሆኑን በማመን ሒሣቡ በባለሙያ እንዲጣራ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በባለሙያዎቹ ሒሣቡን በጋራ በማጣራት የሚስማሙባቸውን ሒሣብ ተስማምተው የተለያዩበትን ሒሣብ የልዩነታቸውን ምክንያት በመግለጽ በጋራ ማቅረብ ሲገባቸው ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከሰጠው ትእዛዝ ውጭ ለየብቻ ሠርተው ካቀረቡት ሪፖርት ውስጥ የአንደኛውን ባለሙያ ሪፖርት በመተው ሌላውን ተቀብሎ የሰጠው ውሣኔ ስለ ልዩ አዋቂ ምስክር የተደነገገውን የማያሟላና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በቃል ክርክር ባቀረቡት መልስ ችሎት ሒሣቡን በዝርዝርና በሚያሣምን ሁኔታ ሠርቶ ያቀረበለትን ባለሙያ በመቀበል ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በጋራ ሒሣቡን እንዲያጣሩና ሪፖርት እንዲያቀርቡለት ትእዛዝ የሰጣቸው ባለሙያዎች ለየብቻ ሒሣብ በማጣራት ያቀረቡትን ሪፖርት በመቀበል የአንደኛውን ባለሙያ የሒሣብ መግለጫ ውድቅ በማድረግና የሌላውን ትክክለኛ ነው በማለት ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ እልባት ለመስጠት በአገራችን የሕግ ሥርዓት ልዩ አዋቂ ምስክር በፍርድ ቤቱ የሚሾምበትን ምክንያት በዝርዝር ማየት ያስፈልጋል፡፡ የኮመንሎው የሕግ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች ተከራካሪዎች ልዩ አዋቂ ምስክሮቻቸውን በራሣቸው የማቅረብና በተከራካሪዎች ምርጫና ክፍያ የማይቀርበው ልዩ አዋቂ ምስክር የቆጠራቸውን ተከራካሪ ሊረታ የሚችልበትን ሁኔታ ከሙያ አንፃር አቀነባብረው የሚያቀርቡ የሲቪል ሎው በሚከተሉ አገሮች የልዩ አዋቂ ምስክር የሚመድበው በፍርድ ቤት ሲሆን የልዩ አዋቂ ምስክሩ በማናቸውም ተከራካሪ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ከሙያ አንፃር ማጣራት የሚገባውን ነገር አጣርቶ ለፍርድ ቤቱ የሚያቀርብና የሙያ አበልም የሚታሰብለት በፍርድ ቤቱ በኩል እንደሆነ የሕግ ሥርዓቱን የሚከተሉ የሥነ ሥርዓት ሕግጋት በማየት ለመረዳት ይችላል፡፡

የአገራችን የሕግ ሥርዓት የሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓት የሚከተሉ አገሮች የሚከተሉትን መሠረታዊ መርህ የሚያራምድ ሲሆን አከራካሪ ጉዳይ የሚያጣሩ ልዩ አዋቂዎች /ባለሙያዎች/ ጉዳዩን አጣርተው እንዲቀርቡ የሚሾመው ፍርድ ቤቱ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሚሾማቸው ልዩ አዋቂ ምስክሮች ከተከራካሪዎቹ አንደኛውን ለመደገፍ ሣይሆን ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ትእዛዝ የሙያ ሥነ ምግባር የሚጥልባቸውን ግዴታ ተከትለው ገለልተኛ ሆነው ፍሬ ጉዳዩን በመመርመር ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለባቸው፡፡ በፍርድ ቤቱ የተመደቡ ልዩ አዋቂ ምስክሮች የሙያ ምግባር የሚጥስ ወይም ገለልተኛ በመሆን ከሙያ አንፃር ጉዳዩን መርምረው ማቅረባቸው አከራካሪ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በሌላ ባለሙያ እንዲጣራ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ባለሙያዎቹን ሲመድብ ነፃና ገለልተኛ የሆኑ ባለሙያዎች በመምረጥ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136/1/ መሠረት ባላቸው ልዩ የሒሣብ እውቀት ሒሣቡን መርምረው መመደብ ሲገባው አመልካች የራሱን ባለሙያ እንንዲያቀርቡ ማድረጉ ተገቢነት አልነበረውም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ባለሙያዎቹ በጋራ ሒሣቡን ሠርተው እንዲያቀርቡ የሰጣቸውን ትእዛዝ ባለሙያዎቹ አላከበሩም፡፡ ባለሙያዎቹ የፍርድ ቤቱ ልዩ አዋቂ ምስክር ሆነው ከተሰሙ በኋላ ከሁሉም በላይ ለፍርድ ቤቱ ትእዛዝና መመሪያ ተገዥ በመሆን የሙያ ሥራቸውን ማከናወን አለባቸው የልዩ አዋቂ ሒሣብ አጣሪዎች የችሎቱ ትእዛዝና በመመሪያ መጣስ አመልካች የመደበው ባለሙያ የአመልካችን ክርክር በመደገፍ የሒሣብ ሪፖርት ተጠሪ የመረጠው ባሉሙያ ተጠሪን በመደገፍ የሒሣብ ሪፖርት አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሁለቱም ምስክሮች ችሎቱ ከሰጣቸው ትእዛዝና መመሪያ ውጭ ሒሣቡን በተናጠል ሠርተው ሲያቀርቡለት የሁለቱንም ሪፖርት ውድቅ በማድረግ ሂሣቡ በሌላ ባለሙያ ወይም አዲት ለማድረግ በተቋቋሙ ሕጋዊ ድርጅት በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠት ነበረበት፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጣቸው ትእዛዝና መመሪያ ተመርተው ሒሣቡን ያላጣሩ መሆኑን እያወቀና ችሎቱ ከሰጣቸው ትእዛዝ ውጭ ሁለቱም ባለሙያዎች በተናጠል የመሰላቸውን ሁለት የሂሣብ መግለጫ ካቀረቡለት በኋላ በአመልካች በኩል የተመረጠው ባለሙያ የቀረበው ጥቅል ሒሣብ ስለሆነ አሣማኝ አይደለም ከተጠሪ የተመረጠው ባለሙያ ያቀረበው ዝርዝር ሪፖርት ስለሆነ አሣማኝ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ስለ ልዩ አዋቂ አመዳደብና አሠራርና የተዘረጋውን ሥርዓትና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ድንጋጌን የሚቃረን በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ብቃት ያለው ገለልተኛ የሒሣብ ባለሙያ ወይም ፈቃድ ያለው የኦዲት ድርጅት በመመደብ ሒሣቡ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 58487

መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ አባይነሽ ገ/ህይወት - ወኪል ወ/ት ትዕግስት ደመወዝ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ እታገኝ ደሣለኝ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ክርክር በፍትሐብሔር ክስ ክርክሩ ሊሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ከሣሽ ወገን አልቀረበም ተብሎ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ተከሣሽ ተሰናብተዋል በተባለበት ጉዳይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74/2/ መሠረት እንደገና ክሱ እንዲታይ ሣይጠየቅ በቀጥታ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኙ ቀርቦ ሊታይ የሚችል ስለመሆን አለመሆኑ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው ደቡብ ጐንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ ከሣሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች ናቸው፡፡ ተከሣሾች የነበሩት ደግሞ ሀብታሙ ጌትነት እና የአሁኗ ተጠሪ ናቸው፡፡

1ኛው ተከሣሽ ሀብታሙ ጌትነትና የአሁኗ ተጠሪ እናትና ልጅ ናቸዉ፡፡ ከሣሽ ሁለቱን እናትና ልጅ በአንድነት የከሰሷቸው ልጅየው ሰርቆ ወስዷል የተባሉትን የተለያዩ የወርቅ ጌጣጌጦች ዋጋ ብር 13,490 እንዲከፍሏቸው ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ልጃቸው ሰርቋል በተባለው ወርቅ ጉዳይ ገንዘቡን ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ የተከሰሱት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2125 መሠረት ሃላፊነት አለባቸው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ሁለቱ ተከሣሾች ክሱ ደርሷቸው በጽሁፍ መልስ ሰጥተው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ክርክሩ ሊሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ከሣሿ የአሁኗ አመልካች ባለመቅረባቸውና የአሁኗ ተጠሪም በጽሁፍ በሰጡት መልስ ሃላፊ ልሆን አይገባም ብለው ክደው በመከራከራቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ጋር በማገናዘብ መርምሮ የአሁኗ ተጠሪ ሃላፊነት የለባቸውም ወደሚለው ጭምር የገባ ቢሆንም በእርሳቸው ላይ ክሱ አይቀጥልም ብሎ አሰናብቷቸዋል፡፡ በመጨረሻም ፍርድ በሚለው የተወሰነውና መዝገቡም ሣይዘጋ የቆየው አንደኛው ተከሣሽ በጽሁፍ በሰጠው መልስ ወንጀሉን ስለመሠረቱ ማመኑ በፍትሐብሔር የቀረበበትን ክስም እንዳመነ ይቆጠራል ተብሎ በመወሰዱ ሲሆን በተሰጠው ፍርድም በክሱ ለተጠየቀው ገንዘብ ሃላፊነት አለበት ተብሎ ተወስኗል፡፡ የአሁኗ አመልካች 2ኛዋ ተከሣሽ የአሁኗ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ታይቶ ከክሱ እንዲሰናበቱ የተደረገበትን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርድ በመቃወም በቀጥታ ለአማራ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርበው ፍ/ቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግራ ቀኙ እንዲቀርቡ አድርጐ ክርክሩን ከሰሙ በኋላ መርምሮ በሰጠው ውሣኔ የአሁኗን ተጠሪ በሚመለከት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጨረሻ አጠቃሎ በሰጠው ፍርድ ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ከሣሿ ስላልቀረቡና ተከሣሿም በጽሁፍ በሰጡት መልስ ክሱን ስለካዱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ታይቶ ተሰናብተዋል ስላለው ያነሣው ነገር ሣይኖር በቀጥታ ወደ ሃላፊነቱ ክርክር በመግባት በወቅቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ለሰረቀው ወርቅ በፍትሐብሔር በኩል ስላለው ሃላፊነት የልጁ እናት የአሁኗ ተጠሪ በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 2125/1/ መሠረት ሃላፊነት አለባቸው ብሎ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 13,490 ለአሁኗ አመልካች ሊከፍሉ ይገባል በሚል ወስኗል፡፡

ቀጥሎ ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ክርክሩን መርምሮ በሰጠው ፍርድ የደቡብ ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኗ ተጠሪ በሚመለከት የክሱን መዝገብ የዘጋው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ስለሆነ ከሣሽም የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.74/2/ መሠረት የክሱ መዝገብ ይከፈትልኝ የሚል ጥያቄ ሣያቀርቡ በቀጥታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ያቀረቡት ትክክል አይደለም፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ወደ ፍሬ ነገሩ መግባት አልነበረበትም፤ ይግባኙን መቀበሉም የስነስርዓት ህጉን የተከተለ አይደለም በማለት በዚሁ ስነስርዓት ምክንያት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የአማራ ክልላዊ መንግስት የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ መሠረት የቀረበ ሲሆን ጉዳዩም ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው በመባሉ ግራ ቀኙ እንዲቀርቡ ተደርጐ መልስ እና የመልስ መልሱን በጽሁፍ በመለዋወጥ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡

ጉዳዩም ከህጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የደቡብ ጐንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት የአሁኗን ተጠሪ በሚመለከት የክሱን መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ነው የዘጋው ለማለት ይቻላል አይቻልም? የአሁኗን ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ነው ያሰናበታቸው የሚባል ሆኖ ከተገኘስ ከሣሽዋ የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74/2/ መሠረት የመዝገብ ይከፈትልኝ ጥያቄ ሣያቀርቡ በመጨረሻ በተሰጠው ፍርድ መነሻ በቀጥታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረቡ ስነስርዓት ህጉን የተከተለነው የሚባል ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን በተመለከተ፡-

ከሣሽ የሆኑት የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ክርክሩ በቃል ሊሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሣይቀርቡ መቅረታቸውንና ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ በጽሁፍ በሰጡት መልስ ሃላፊ ልሆን አይገባም ብለው ክሱን ሙሉ በሙሉ በመካድ መከራከራቸውን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጨረሻ የሰጠው ፍርድ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የቀረበው ኮፒው የሚያስረዳ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዚህ ፍርድ ላይ የአሁኗን ተጠሪ ክዶ የመከራከር ሁኔታ የተመለከተው የአሁኗ አመልካች ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረባቸው ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ጋር በማያያዝ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በፍርዱም ላይ የጀመረው ከሣሽ ለቃል ክርክር ስላልቀረቡ መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ተመርምሯል በማለት ነው፡፡ ቀጥሎም 2ኛዋ ተከሣሽ በጽሁፍም ሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቃል ሃላፊ ልሆን አይገባም ብለው ስለመከራከራቸው ከሣሽ ደግሞ በቃል ክርክሩ ላይ ቀርበው በዚህ ላይ ተቃውሞ እንዳላቀረቡ በመግለጽ 2ኛዋ ተከሣሽ ሃላፊነት የለባቸውም ብለናል በማለት ከክሱ አሰናብቷቸዋል፡፡ ከዚህም የአጻጻፍና የአገላለጹ ሁኔታ እንጅ 2ኛዋን ተከሣሽ የአሁኗን ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያሰናበታቸው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ መዝገቡ ወዲያውኑ ያልተዘጋው 1ኛ ተከሣሽ ክሱን አምኗል ተብሎ በመቀጠሉና ፍ/ቤቱም ውሣኔ ሊሰጥበት በማቆየቱ ነው፡፡ የአሁኗን ተጠሪ በሚመለከት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት የክሱ መዝገብ ተዘግቷል ለማለት የሚቻል ሆኖ ስለተገኘ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት የሰበር ክርክር ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ተጠሪን በተመለከተ የክሱ መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ተዘግቷል የሚባል ሆኖ ከተገኘ ከሣሽዋ የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74/2/ መሠረት ጥያቄ በማቅረብ እንደገና መዝገቡ ተከፍቶ ነገሩ እንዲቀጥል ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

አመልካች ይህንን ሣይፈጽሙ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት በተሰናበቱበት ላይ በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ የሚያስችላቸው ስነስርዓት የለም፡፡ የአማራ ክልላዊ መንግስት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔም ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ው ሣ ኔ

1ኛ/ የአማራ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 0469 ሐምሌ 5 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 05 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ብርሃኔ አዱላ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ግርማ አብዲሣ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለመመርመር ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 323(2) የተደነገገውን ድንጋጌ አፈፃፀም ከግራ ቀኙ ክርክር አንፃር ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ባቀረበቺው የአፈፃፀም ክስ መነሻ የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 01161 መጋቢት 27 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ዳኝነቱን በትዕዛዝ መልክ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ላይ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝተው ሚያዝያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ትዕዛዝ የተሰጠበት የመዝገብ ግልባጭ እንዲሰጣቸው ስለመጠየቃቸውና በጥያቄው መሠረት ግንቦት 11 ቀን 2002 ዓ.ም ግልባጩ እንደተሰጣቸው ትዕዛዙን በሰጠው ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 01161 ግንቦት 11 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሸኚ ላይ ከተዘረዘረው መረዳት ችለናል፡፡

እንዲሁም ይህ ግልባጭ ከደረሳቸው በኋላ ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ ዝርዝር የይግባኝ አቤቱታ አዘጋጅተው ይግባኙን እንዳቀረቡ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በአፈ/ይ/መ/ቁ 00978 ሰኔ 03 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከሰጠው ዳኝነት ተገንዝበናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ለይግባኙ ምክንያት የሆነው ዳኝነት መቼ ተሰጠ፤ ይግባኝ ባይ ቅሬታ እንዳላቸው ገልፀው ግልባጭ እንዲሰጣቸው መቼ ጠየቁ፤ በጥያቄው መሠረት የመዝገቡን ግልባጭ ፍ/ቤቱ መቼ ሰጣቸው፤ ግልባጩ ከተሰጣቸው በኋላ የይግባኝ ቅሬታ አዘጋጅተው ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መቼ አቀረቡ፤ የሚለውን አስመልክቶ ለማረጋገጥ ማስረጃ ሆነው የቀረቡት በፍ/ቤቶች የተሰጡት ማረጋገጫዎች ከመሆናቸውም በላይ ተጠሪ ይህንን ለማስተባበል የሚያስችል የተለየ ክርክር አላቀረበም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የአመልካች የይግባኝ መዝገብ እንደቀረበለት ለይግባኙ ምክንያት የሆነው ዳኝነት የተሰጠበትን መጋቢት 27 ቀን 2002 ዓ.ም እና የይግባኝ ቅሬታ የቀረበበትን ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም በፍሬ ነገር ረገድ የቀረቡትን ጊዜዎች መነሻ በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323(2) የተመለከተው የሁለት ወር የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበ የይግባኝ መዝገብ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶ አሰናብቷል። የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ዳኝነት የይግባኝ አቤቱታን አቀራረብ ጊዜን አስመልክቶ ከተቀመጠው ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ሲል የበኩሉን ዳኝነት ሰጥቶበታል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል።

ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323(2) ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መቅረብ የሚገባው ይግባኝ የሚባልበት ጉዳይ በተፈረደ በ60 ቀን ውስጥ ነው በማለት ተደንግጓል። የዚህን ድንጋጌ አነጋገር በቀጥታ ከወሰድን በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ይግባኝ የሚባልበት ፍርድ በተፈረደ በ60 ቀን ጊዜ ውስጥ መሆን ይኖርበታል ወደሚለው መደምደሚያ የሚያደርሰን በመሆኑ ተከራካሪው ወገን ግልባጭ በመጠየቅና በማግኘት ረገድ ያሳየው ጉድለት ሳይኖር ፍ/ቤቶች ባላቸው አሠራር ምክንያት የባከነውን ጊዜ ሁሉ በስሌት ውስጥ የሚያስገባ ሆኖ ስለሚገኝ ድንጋጌው ትርጉም የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል።

ድንጋጌው ሥነ ሥርዓታዊ እንደመሆኑ መጠን ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌዎችን ሥራ ላይ በምናውልበት ጊዜ ትርጉም ካስፈለገ በተለይ የሥነ ሥርዓት ህግ ግብን መሠረት በማድረግ ውጤታማ እና ትርጉም ባለው አኳኋን ተግባራዊ ፋይዳውን በማየት ሌሎች መሠረታዊ ህጎችን ከምንተረጉምበት መደበኛ የአተረጓጎም ዘዴ በተለየ ሁኔታ ልንተረጉም ስለሚገባ ይህ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323(2) ድንጋጌ በግልፅ የተቀመጠ ስለሆነ ትርጉም ሳያስፈልገው እንዳለ በሥራ ላይ ሊውል ይገባል የሚያሰኝ አይደለም።

ስለሆነም ፍርድ እንደተፈረደበት ይግባኝ እንደሚጠይቅ ገልፆ የይግባኝ መጠየቂያ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ የመዝገብ ግልባጭ እስኪሰጠው ድረስ ያለው ጊዜ ለይግባኝ ማቅረቢያ ተብሎ ከተሰጠው 60 ቀን ስሌት ውስጥ ሊካተት አይገባውም።

ይህ በፍ/ቤት አሠራር ምክንያት የባከነው ጊዜ ከይግባኝ ጥያቄው አቅም ውጭ የሆነና እንደበቂ ምክንያት ስለሚቆጠር የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዳለፈበት በይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አማካኝነት ይግባኙ እንዲቀርብ ያድርግ የሚለውን መስመር መከተል ይኖርብናል እንዳይባል ከላይ እንደተጠቀሰው አስቀድሞ ውጤቱ ለሚታወቅ ጉዳይ ትርጉም አልባ የሆነ ሥርዓት እንዲፈፀም ለማድረግ ብቻ ከሚሆን በቀር ተግባራዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ አይገኝም።

ስለሆነም ይህ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 323(2) የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ይሰላ ከተባለ ፍርዱ በተፈረደበት ቀን እና ይግባኝ ጠያቂው የይግባኝ አቤቱታ ሊያቀርብ እንደሚፈልግ ገልፆ የመዝገብ ግልባጭ በጠየቀበት ጊዜ መካከል የባከነውን ጊዜ፣ የመዝገብ ግልባጭ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ የይግባኝ አቤቱታውን አዘጋጅቶ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እስካቀረበበት ድረስ የባከነውን ጊዜ በማስላትና በመደመር 60 ቀን ማለፉ እና አለማለፉ እንዲለይ በማድረግ ሊሆን ይገባል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህም አንፃር አሁን በእጅ ያለውን ጉዳይ ስንመለከት ፍርዱ ከተፈረደበት ከመጋቢት 27 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የይግባኝ መጠየቂያ ለፍ/ቤቱ እስከቀረበበት እስከ ሚያዝያ 18/2002 ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ 21 ቀናት ያለፉ እንዲሁም ግልባጩ በአመልካች እጅ ከደረሰበት ከግንቦት 11 ቀን ጀምሮ የይግባኝ ቅሬታ ተዘጋጅቶ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እስከቀረበበት እስከ ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ 21 ቀናት ብቻ በድምሩ 42 ቀናት ብቻ ያለፉ እንጂ በህጉ የተቀመጠውን የ60 ቀን ጊዜ የተላለፈ ሆኖ ባለማግኘታችን የአመልካች የይግባኝ ጉዳይ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በሚል የጋምቤላ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ሰሚው ችሎት የሰጡት ዳኝነት ድንጋጌውን በመተርጎም ረገድ ትክክለኛውን የትርጉም መስመር የተከተለ ሆኖ ስላላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የጋምቤላ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአፈ/ሰ/መ/ቁ 00005 ሐምሌ 01 ቀን 2002 ዓ.ም እና ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በአፈ/ይ/መ/ቁ 00978 በ03/10/2002 ዓ.ም የሰጡትን ትዕዛዞች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ሽረናል፡፡
2. የአመልካች የይግባኝ አቤቱታ የማሰማት መብታቸው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜውን ያለፈ ሆኖ አልተገኘም፡፡
3. የአመልካችን የይግባኝ ጉዳይ ተቀብሎ እንደ ሥርዓቱ ማየት ይቀጥል ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ወደ ጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
4. ይህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 19 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች ፦ ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፦ አቶ በቀለ ጃፋር - ቀረቡ

ተጠሪ ፦ እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ ማሞ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክርን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ናቸው፣ ተከሣሽ ደግሞ አመልካች ነበሩ። ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘቱ ሲታይ የእናታችንን የውርስ ሀብትና ይዞታ አመልካች ይዞ ስለሚገኝ እንዲለቅልን ይወስንልን የሚል ሲሆን የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል። በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት የውርስ ሀብት ይገባናል ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የውርስ ሀብቱን ያልያዙ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤትም በአመልካች በቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ብይን ሳይሰጥ በማለፉ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅረበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት በአመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን ሳይሰጥ ማለፉ ሥነ ስርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመውን የስነ ስርአት ግድፈት በማረም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ብይን እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሶታል። ከዚህም በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የአመልካች ማስረጃ እንዲሰሙ ያዘዘ መሆን ያለመሆኑን ማብራሪያ እንዲሰጥና ትእዛዙንም አመልካች አድርሰው ማብራሪያውን እንዲያቀርቡ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች ይህንኑ ትዕዛዝ አልፈፀሙም፣ ይልቁንም ቀድሞ ዘርዝረው ያላቀረቡትን የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር አቅርበዋል በማለት መዝገቡን ዘግቶታል። በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ነሐሴ 11 ቀን 2002 ዓ.ም. በዓፋት ሦስት ገፅ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ብይን ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የፅሑፍ መልሳቸው ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ወሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች ተጠሪዎች ባቀረቡባቸው የውርስ ንብረት ይልቀቅልን የዳኝነት ጥያቄ የይርጋ ክርክር አንስተው የሥር ፍርድ ቤት በዚሁ ላይ ብይን ሳይሰጥ በማለፉ የበላይ ፍርድ ቤት በአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢው ብይን እንዲሰጥ ለስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከመለሰለት በሁዋላ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን ለመስጠት ማስረጃ መስማት እንደአለበት የስር ፍርድ ቤት አምኖ ተገቢ ነው ያለውን ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰው ይግባኙን ተመልክቶ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢው መጣራት ተደርጎ ብይን ሊሰጥበት ይገባል በማለት ውሣኔ የሰጠው የበላይ ፍርድ ቤት ተገቢው መጣራት ተደርጓል ሲል ማስረጃ ተሰምቶ መሆን ያለመሆኑን ማብራሪያ እንዲሰጥበት፣ ይህንኑም አመልካች ተከታትለው እንዲያስፈፅሙ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች ይህንኑ ትዕዛዝ ሳያስፈፅሙ አዲስ የማስረጃ ዝርዝር አቅርበዋል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት ያደረገው የጊዜ ማለፍ ሲሆን ይህ የጊዜ ማለፍ ደግሞ ተጠሪዎች ካቀረቡት ክስ ባሕርይ እና ክስ ከተመሰረተበት ጊዜ አንፃር ታይቶ አግባብነት ባለው ሕግ ምላሽ የሚሰጠው ከመሆን ውጪ የተከሣሽ ማስረጃ ሊሰማ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለው ነው፡፡ ተጠሪዎች የጊዜውን ማለፍ አምነው የይርጋ ጊዜውን ሊያቋርጡ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያት ያላቸው ስለመሆኑ ጠቅሰው ተከራክረው አመልካች ይህንኑ ሊያስተባብል የሚችል ክርክርና ማስረጃ ያላቸው ስለመሆኑ ጠቅሰው መከራከራቸውን የሚያሳይ የክርክር ሂደትም የለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን እንዲሰጥ ይግባኙን የተመለከተው የበላይ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲሰጥም በጊዜው ማለፍ ላይ ማስረጃ እንዲሰማ ብሎ የገለፀው ነገር የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካች በኩል የይርጋ ጊዜ አልፏል በሚል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው መሆን ያለመሆኑን የክሱን አይነትና ክሱ የቀረበበትን ጊዜ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማዛመድ ብይን የሚሰጥበት ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት የሰው ማስረጃ መቅረብ አለበት ያለበት አግባብ ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖረው መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ይህ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244/2/ሠ/ እና 234 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም አላማቸውን ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ የአመልካችን የመከራከር መብት ያጣበበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ከተመለሰለት በሁዋላ መዝገቡን የዘጋበት ሥርዓት መሰረታዊ የሆነ የሥነ ስርዓት ሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12832 ጥር 06 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00520 መጋቢት 09 ቀን 2002 ዓ.ም.፣ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 103687 ሐምሌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

03 ቀን 2002 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሸሯል፡፡

2. አመልካች ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የተጠሪዎችን የክስ አይነትና ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለውን ሕግ መሰረት በማድረግ ተገቢው ብይን ከሚሰጥበት በስተቀር የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲሰማ የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. የሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ጉዳዩን ከዚህ በፊት ባላዩት ዳኛ እንዲታይ በማድረግና በአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢውን ብይን በመስጠት ጉዳዩን እንዲዳኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሰረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ለአደረጉት ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሸ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚያዚያ 03 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ዋልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካች፡- አቶ አዱኛ አጃው የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- ቀስቅስ አየነው የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የከብቶች ግምት ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ስሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪና ለጉዳዩ ዋስትና ገብተውላቸዋል በሚሏቸው ግለሰብ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የስር ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- የግላቸው የሆኑት ሶስት ከብቶች ጠፍተውባቸው ተጠሪን ጠርጥረው በሽማግሌ ሲጠይቋቸው በቤተክርስቲያን ለመማማል ፈቃደኛ ከሆኑ በኋላ እንደገና አልምልም፣ ወስጄአለሁ በማለት አምነው መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት መሰረት ብር 8000.00 (ስምንት ሺህ ብር) ለመክፈል መስማማታቸውን፣ ተጠሪ ይህንኑ ባይከፍሉ ደግሞ በስር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት አቶ ባበዩ ሲሳይ የተባሉት ግለሰብ የዋስትና ግዴታ መግባታቸውን፡ ሆኖም በውሉ መሰረት ገንዘቡ ያልተከፈላቸው መሆኑን ዘርዝረው የከብቶቹ ግምት የሆነው ብር 8000. (ስምንት ሺህ ብር) እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ጉዳዩ ቀድሞ በማህበራዊ ፍ/ቤት ቀርቦ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ገልጸው ክሱ በድጋሚ ሊቀርብ እንደማይገባ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ውሉን በሃይል የፈረሙ መሆኑን ገልፀው ሕጋዊ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪን መከራከሪያ ውድቅ አድርጎ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ብቻቸውን እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ ይግባኛቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩ ቀድሞ የማሕበራዊ ፍርድ ቤት ቀርቦ ያለቀ ነው በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም ለክሱ መሠረት የሆነው የመስከረም 25 ቀን 2000 ዓ.ም ውል ሆኖ እያለ በ1998 ዓ/ም በቀበሌ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቷል ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የአመልካች ክስ በቀበሌ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መዝገንዘብ የተቻለው አመልካች ለክሳቸው መሰረት ያደረጉት መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ.ም ተደረገ የተባለውን ውል ሲሆን የቀበሌ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ውሳኔ ስለመስጠቱ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተገለፀው በ1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለው ስምምነት መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገ ውል ስለመኖሩ ሳይክዱ በኃይል የተደረገ ነው በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ይህንኑ እንዲያስረዱ እድል ተሰጥቷቸው በቀነ ቀጠሮው እለት ችሎት ሳይቀርቡ የቀሩ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ ከመዘገበው ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ የክርክርን ሂደት ለማቀላጠፍና አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ ለማበጀት መሆኑ ይታመናል፡፡ የፍትሐብሔርን ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ እልባት እንዲደረግበት በማቀድ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ጽንሰ ሐሳቦች አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በ1958ቱ የፍትሓ ብሔር ሥነ ስርዓት ሕጋችን ውስጥ በቁጥር 5 ድንጋጌ ስር በግልጽ ተቀምጦ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን፣ በውሣኔ፣ በትእዛዝ፣ ወይም በጊዜያዊ አግልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ ለመንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ሥር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ፡- ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው ፣ቀደም ሲል የነበረው ክርክር አሁን በክርክር ተሳታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተለለፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡

ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው፡፡ “ … ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ …” የሚለው ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች በሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንደሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በ15/07/2000 ዓ.ም ለሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መሠረት ያደረጉት ከተጠሪ ጋር መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ/ም ተደረገ የተባለውን ውል ሲሆን ይህ ውል በ1998 ዓ.ም ቀበሌ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ሊቀርብ እንደማይችል የጊዜው ቅደም ተከተል በራሱ አስረጂ ነው፡፡ ተጠሪ መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ/ም የተደረገውን ውል ስለመኖሩ የካዱት ሳይሆን ውሉ በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት አይገባም ያሉትን የኃይል ተግባር ጠቅሰው ቢከራከሩም በማስረጃ ያረጋገጡት ፍሬ ነገር አለመኖሩን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በአቤቱታ ጽሑፋቸው የገለፁትና የዘረዘሩት ፍሬ ነገር በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ቀርቦ ነበር ከተባለው ጉዳይ ጋር ሲነፃፀር የተለየ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ነው ሲል የበታች ፍ/ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ ባግባቡ ባለመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 4248 ጥቅምት 11 ቀን 2003 ዓ.ም የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 25638 ታህሳስ 06 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 25316 ጥቅምት 03 ቀን 2003 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348(1) መሰረት ጽንቷል፡፡
3. አመልካች መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የአቤቱታ ጽሑፍ (ክስ) መሠረት ያደረጉት መስከረም 25 ቀን 2000 ዓ.ም ተደረገ የተባለውን ውል በመሆኑ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ጉዳይ አይደለም ብለናል፡፡
4. ተጠሪ ብር 8000.00 (ስምንት ሺህ ብር) ከመጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፈሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ ዘጠኝ ከመቶ /9%/ ወለድ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባንክና ኢንሹራንስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 41535

ጥቅምት 3 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ተሾመ መኩሪያ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. ግሎሪ የኃላነቱ/የተ/የግል ማህበር -ጠበቃ ዓብደላ ዓሊ ቀረቡ

2. ማታዶር አዲስ ጎማ - ማርዬ ማንደፍሮ ቀረቡ

3. ኩሪፍቱ ኃ/የተ/የግል ማህበር

4. ብርሃነ በርሀ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የኔ ባልሆነ ሐሰተኛ ፊርማ እና ማህተም መሠረት ተደርጎ ከኔ የባንክ ሂሣብ ላይ ገንዘብ ወጪ ሆኖብኛል በማለት 1ኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የሁሉንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከእነወለዱ ለ1ኛ ተጠሪ ይክፈል በማለት በአንድ በኩል ሲወስን፤ በሌላ በኩል ደግሞ 4ኛ ተጠሪ ገንዘቡን ለአመልካች ይተካለት በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በውሣኔው ባለመስማማት ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልባቸውን ምክንያቶች በመግለጽ ውሣኔው ይታረምለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት የቀረቡት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ብቻ ሲሆኑ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ክርክሩ የተሰማው በሌሉበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ገንዘቡ ከባንክ ወጪ ሊሆን የቻለው የ1ኛ ተጠሪ ሠራተኛ በሆነው 4ኛ ተጠሪ ሆኖ ሣለ አመልካች ለገንዘቡ መውጣት ኃላፊ ነው መባሉ አግባብ ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረትም ግራ ቀኝ ወገኖች ጭብጡን በማስመልከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ከተሰጠው ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ለክሱ ምክንያት የሆነው ገንዘብ በተጭበረበረ መንገድ ከባንክ ሊወጣ የቻለው የ1ኛ ተጠሪ ሠራተኛ በሆነው በ4ኛ ተጠሪ አማካይነት ነው፡፡ 4ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪን ምክትል ሥራ አስኪያጅ ፊርማ እና የኩባንያው /1ኛ ተጠሪ/ ማህተም አስመስሎ በተዘጋጀ ሲፒዮ እና የክፍያ መጠየቂያ ለባንኩ /አመልካች/ እንዳቀረበ፣ ይህን ሰነድ ያቀረበው በሁለት የተለያሉ ጊዜያት ማለትም የብር 420,000 ክፍያ የታዘዘበት የመጀመሪያው በጃንዋሪ 8 ቀን 2005 /እ.ኢ.አ/ ታህሣሥ 30 ቀን 97 ዓ.ም/፤የብር 347,206.63 ክፍያ የታዘዘበት ሁለተኛው ደግሞ በማርች 17 ቀን 2005/እ.ኢ.አ. መጋቢት 8 ቀን 97 ዓ.ም/ እንደሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ ክፍያዎቹም የተፈፀሙት እንደዚሁ እንደአመጣጡ ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ ክሱን የመሠረተው ታህሣሥ 25 ቀን 99 ዓ.ም ሆኖ ለገንዘቡ በተጭበረበረ መንገድ መውጣት ኃላፊነት መውሰድ ያለበት ባንኩ ነው በማለት የተከራከረውም የሚጠበቅበትን ጥንቃቄ አላደረገም፡፡ የሰነዶቹን ትክክለኛነት ሣያረጋግጥ እና እኔን /ከሣሽን/ ሣያሣውቅ ከፍሎአል የሚሉትን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ገንዘቡን ለታዘዘላቸው ወገኖች እንዲተላለፍ/ እንዲከፈል/ ያደረግሁት የባንኩን የተለመደ አሠራር እና ሥርዓት በመከተል ተገቢውን ጥንቃቄ ከወሰድኩ በኋላ ነው፡፡ በሰነዶቹ ላይ ያለው ፊርማ እና ማህተም ትክክል አለመሆኑን ለመጠራጠር ወይም ለማወቅ የምችልበት የተለየ ሁኔታ አልነበረም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሕጉ እና በተለመደው አሠራር መሠረት ለ1ኛ ተጠሪ የባንክ ወርሃዊ የሂሣብ መግለጫ እየላከለት እና ከሂሣቡ ላይ ገንዘቡ መቀነሱን ሲያሣውቀው እንደቆየ፤ ይህም ሁኔታውን ለማወቅ የሚያስችለው ሆኖ ሳለ 1ኛ ተጠሪ ግን የራሱ ሠራተኛ ላይ ጥንቃቄ አለማድረጉን በመግለፁም ተከራክሮአል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተደረገው የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ተጠቃሎ ሲታይ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም “ተከሣሽ ባንክ ለክሱ መሠረት የሆነውን ሲፒዮ በከሣሽ ስም ሲዘጋጅ እና ክፍያ ሲፈፀም ተገቢውን የተለመደ የባንክ አሰራር ተከትሎአል አልተከተለም?” የሚል ጭብጥ በመያዝ ክርክሩን መርምሮአል፡፡ በውሣኔው ላይ በግልጽ እንዳመለከተው ከቀረበለት ማስረጃ አንፃር አመልካች /ባንኩ/ ተገቢውን የተለመደ የባንክ አሠራር አልተከተለም፣ ገንዘቡን የከፈለው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ እና ቅን ልቦናን ተከትሎ አይደለም እሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ አልቻለም፡፡ አመልካችን ኃላፊ በማድረግ ሊወስን የቻለው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ. 25306 በሰጠው ውሣኔ የገንዘቡ አደራ ጠባቂ የሆነው ባንክ አደራ አስቀማጭ የሆነው ባለሂሣብ ሣይጠይቅ ወይም ሕጋዊ ትእዛዝ ሣይሰጥበት ገንዘቡ በተጭበረበረ መልኩ ወጪ ከሆነ የተጭበረበረው አደራ አስቀማጩ ባለሂሣብ ሣይሆን፣ አደራ አስቀማጩ ባንክ ነው በማለት ለሥር ፍ/ቤቶች ገዢ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶአል በማለት እና ከሣሽ በተከሣሽ ባንክ ካለው ሂሣቡ ውስጥ ያለእሱ ትእዛዝ እና እውቅና ወጪ እንደሆነበት ሰነዱን በማስመርመር አረጋግጦአል የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡

ቀደምሲል እንደተገለፀው ለባንኩ የቀረቡት ሰነዶች በማስመሰል የተዘጋጁ እንጂ እውነተኛ አይደሉም ስለተባሉ ነው 1ኛ ተጠሪ ወደ ክስ ያመራው በመሆኑም አከራካሪ የሚሆነው እና በውሣኔ እልባት ማግኘት ያለበት ሰነዶቹ የተጭበረበሩ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ሣይሆን፣ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰነዶቹን መሠረት በማድረግ ክፍያ የፈፀመው የባንኩን የተለመደ አሠራር ሣይከተል እና ተገቢውን ጥንቃቄ ሣያደርግ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ ይህ ነጥብ የፍሬ ነገር ጭብጥንም የሚመለከት በመሆኑ የሚነጥረው በማስረጃ ነው፡፡ ጭብጡን በማስረጃ የማንጠር ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ተገቢውን ጥንቃቄ ሣያደርግ ወይም የባንኩን የተለመደ አሠራር ሣይከተል ገንዘቡ እንዲከፈል አድርጎአል እሚል መደምደሚያ ላይ አልደረሰም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ኃላፊ ሊያደርገው የሚችል ጥፋት ወይም የሕግ /የሥርዓት/ ጥሰት አልፈፀሙም ማለት ነው፡፡

በመቀጠል የሚታየው የሰበር ችሎቱ ሰጠው የተባለው የሕግ ትርጉም ነው፡፡ በሰበር መ.ቁ. 25306 የተሰጠውን ውሣኔ አስቀርበን ተመልክተነዋል፡፡ በመጀመሪያ የተገነዘብነው በዚህ መዝገብ /ቁ.25306/ የነበረው ክርክር እና የተያዘው ጭብጥ አሁን በያዝነው ጉዳይ ከተነሣው ክርክር እና ጭብጥ የተለየ እንደሆነ ነው፡፡ በሰበር መ.ቁ. 25306 ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ሣይኖር ውሣኔ እንደተሰጠ በማስመሰል እና የተጭበረበረ የፍ/ቤት ትእዛዝ በማቅረብ ገንዘብ ከባንክ ወጪ ሆኖአል የሚል መነሻ ያለው ነው፡፡ ተከሣሾች የነበሩትም ፍ/ቤት እና ባንክ ናቸው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የተገነዘብነው እና ዋናው ቁም ነገር ደግሞ የሰበር ችሎቱ በተጭበረበረ መንገድ ከባንክ ገንዘብ ወጪ በሆነ ቁጥር ያለምንም ምክንያት ባንኩ ኃላፊ ይሆናል የሚል የሕግ ተርጉም አለመስጠቱን ነው፡፡ እንደሚታወቀው ክርክሮች የሚወሰኑት እንደ የግል ባህሪያቸው እየታየ ነው፡፡ በአንድ ጉዳይ የተነሣውን ክርክር እልባት ለመስጠት የተሰጠ ውሣኔ በሌላ ጉዳይ ለተነሣው ክርክርም እልባት ለመሰጠት ያስችላል ብሎ ሙሉ በሙሉ መደምደም ትክክልም ተገቢም አይደለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወደ ድምዳሜ የደረሰው የሰበር ችሎቱ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው የፍሬ ነገር እና የሕግ ምክንያት በዝርዝር ሣይመለከት እንደሆነ ነው በበኩላችን መገንዘብ የቻልነው፡፡ በመሆኑም የሰበር ችሎቱ በሰጠው የሕግ ትርጉም ነው በሚል አመልካችን ኃላፊ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ቀደም ሲል ተሰጠ በተባለው ውሣኔም ሆነ በሰበር ችሎቱ እምነት ባንክ በተጭበረበረ መንገድ ለወጣ ገንዘብ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው የተለመደውንና ተገቢውን የባንክ አሠራር ሣይከተል ወይም ተገቢውን ጥንቃቄ ሣያደርግ ከፍሎ ከተገኘ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ባንኩ / አመልካች/ ገንዘቡን የከፈለው አሠራሩንና ሥርዓቱን ተከትሎ ነው፡፡ ስለዚህም አመልካችን ኃላፊ በማድረግ የተሰጠው ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 51654 ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 38080 ህዳር 8 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ እንዲከፍል የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ የቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሳስ 27 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ አያሌው ወርቁ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመድን ውልን የተመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ በመሠረቱት ክስ ነው፡፡ የተጠሪ የክስ ምክንያት አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው የተጠሪ ንብረት የሆነ ታርጋ ቁጥር 3-10953 የሆነ መኪና የመኪናው ሹፌር ረዳት የነበረው አቶ በሪሁን ገ/ሚካኤል ፈቃድ ሳይሰጠው ቁልፍ ሰርቆ ለማሽከርከር ሲሞክር መኪናውን ከቴሌኮሙንኬሽን ፖል ጋር በማጋጨት ጉዳት ስላደረሰበት ለጥገና እና ሌሎች ወጪዎች የወጣ በድምሩ ብር 146,998.50 አመልካች እንዲከፍል እንዲወሰን የሚል ሲሆን በአመልካች በኩል ስር ፍ/ቤት የቀረበው ክርክር ለመኪናው የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑን አምኖ መኪናው ላይ ጉዳት የደረሰው ረዳቱ መንጃ ፈቃድ ሳይኖረው ሲያሽከረክር በመሆኑ እና ይህም በመድን ውሉ ክፍል 1 እና 2 መድን ሰጪን በሃላፊነት የማያስጠይቅ ስለመሆኑ እና ረዳት የመኪናውን ቁልፍ ሰርቋል ሊባል አይችልም በሚል ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ መድን ሰጪ በመድን ውል ማግለያ አንቀጽ መሠረት ከሃላፊነት ሊድን የሚችለው የሹፌሩ ረዳት መኪናውን ያሽከረከረው ተጠሪ /ከሳሽ/ አውቀውና ፈቅደው ስለመሆኑ አመልካች ማስረዳት ሲችል ብቻ ነው፤ ነገር ግን በዚህ ረገድ አመልካች /ስር ተከሳሽ/ አላረጋገጠም በማለት ሃላፊነት አለበት ሲል ወስኗል፡፡ እንዲሁም ጉዳት የደረሰው በተጠሪ ሠራተኛ ጥፋት ስለሆነ በንግድ ሕግ አንቀጽ 664/1/ መሠረት አመልካች ለደረሰው ጉዳት መድን የመሰጠት ሃላፊነት አለበት ብሏል፡፡ በዚሁ አግባብ ክስ የቀረበበት ገንዘብ እንዲከፍል ፈርዷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳት ያደረሰው ሰራተኛ የመንጃ ፈቃድ አለው ወይስ የለውም? እና የመድን ፖሊሲ ክፍል 1ና2 ማግለያ ሁኔታ በአግባቡ ተተርጉሟል ወይስ አልተተረጎመም የሚሉትን ነጥቦች ለመመርመር ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪ ጠበቃ መጋቢት 15 ቀን 2002ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅረበዋል። በይዘቱም ሲታይ የመኪናው ሹፌር ረዳት ተጠሪ ሳይፈቅዱና ሳይስማሙ የመኪናውን ቁልፍ ሹፌሩ ደብቆ ካስቀመጠበት አንስቶ ለማሽከርከር ሲሞክር አደጋ የደረሰ ስለመሆኑ በመግለጽ ለደረሰው አደጋ የማግለያ አንቀጹ ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደማይገባ እንዲሁም በንግድ ህግ አንቀጽ 664/1/ መሠረት አመልካች ሃላፊ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል። አመልካች አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል። የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ነው።

እኛም ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ መሠረት አድርገን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ለተጠሪ መኪና የመድን ሽፋን መስጠቱ አላከራከረም። የተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው በሹፌሩ ረዳት እንደሆነም ተረጋግጧል። የሹፌር ረዳት መኪናውን ለማሽከርከር የሚያስችለው የመንጃ ፈቃድ እንደሌለውም በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል።

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ክስ ሲያቀርብም ሆነ እዚህ ሰበር ችሎት ሲከራከር የሹፌር ረዳት የመኪናውን ቁልፍ ሰርቆ ነበር መኪናውን ሊያሽከረክር የሞከረው በማለት ነው። እነዚህን በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጡትን እና የቀረቡት ክርክሮች መሠረት በማድረግ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመድን ውል ክፍል 1 እና 2 በአግባቡ ተተርጉሟል ወይስ አልተተረጐመም የሚለውን እንደሚከተለው መርምረናል።

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመድን ውል ፖሊሲ ለክፍል 1ና2 ልዩዎች በሚል "ኩባኒያው ለሚከተሉት ማንኛቸውም ክፍያ የመክፈል ሃላፊነት አይኖርበትም" በሚለው ርዕስ ስር በንዑስ አንቀጽ ሁለት ------ በመድን ገቢው ወይም በመድን ገቢው እውቅናና ስምምነት በሌለ ግለሰብ ከፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን ወይም በሌላ ሕግና ደንብ ለማሽከርከር ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በአስካሪ መጠጦችና እጾች ተፅዕኖ ስር ሆኖ ሲሽከረክር በሚፈጠርና በሚደረስ አደጋ፣ ጉዳት፣ ብልሽትና ኃላፊነት በማለት ያመለክታል።

አመልካች በዚህ የማግለያ አንቀጽ መሠረት ሃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል። የተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው በሹፌሩ ረዳት ሲሽከረክር መሆኑ ተረጋግጧል። የሹፌሩ ረዳት መንጃ ፈቃድ የለውም። ከፍ ሲል በተጠቀሰው የማግለያ አንቀጽ መኪናው መንጃ ፈቃድ በሌለው ሰው ሲሽከረክር ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ መድን ሰጪው ሃላፊነት እንደሌለበት ተጠሪ ፈቅዶ ውል ገብቷል። በሌላ በኩል መኪናውን ያሽከረከረው ረዳት የተጠሪ እውቅናና ስምምነት ሳይኖር ስለመሆኑ ለማስረዳት ተጠሪ ስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የፍሬ ነገር ክርክር የመኪናውን ቁልፎ ረዳቱ ሰርቆ ነበር የሚል ሲሆን እንደ ክርክሩ አቀራረብ የመኪናው ቁልፍ በረዳቱ የተሰረቀ ስለመሆኑ ተጠሪ በማስረጃ አላረጋገጠም።

ተጠሪ እንደክሱ አቀራረብ ፍሬ ነገሩ ስለመኖሩ ማስረዳት ግዴታ እንዳለበት የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 2001/1/ ይዘት ያመለክታል። ተጠሪ የማስረዳት ግዴታውን ባልተወጣበት ሁኔታ ረዳቱ መኪናውን ያሽከረከረው በተጠሪ እውቅናና ስምምነት ስለመሆኑ አመልካች አላስረዳም ሲል የስር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ከተጠቀሰው ሕግ መንፈስና ይዘት ጋር የሚጣጣም አይደለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም መኪናው ከተጠሪ ፈቃድና ስምምነት ውጪ ተሰርቆ በረዳቱ ይሽከረከር የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪ ሳያስረዳ በተቃራኒው አመልካች የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት የስር ፍ/ቤት የወሰደው አቋም የስር ከሳሽ /ተጠሪ/ የማስረዳት ሸክምን ያለአግባብ ወደ ተከሳሽ /አመልካች/ ያስተላለፈ ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ነው ለማለት ችለናል፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤት ለውሳኔው ምርኩዝ ያደረገው የንግድ ሕግ ቁጥር 664/1/ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ ይዘት መሠረት መድን ገቢው ሃላፊ የሚሆንባቸው ሰዎች ባደረጉት ጥፋት ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት መድን ሰጪው መድን የሚሆን ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ መኪናው ላይ ጉዳት የደረሰው መንጃ ፈቃድ በሌለው የሹፌሩ ረዳት መኪናው ሲሽከረከር ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ መኪናው በማንኛውም ሰው ቢሆን መንጃ ፈቃድ በሌላው ሰው ሲሽከረከር ጉዳት ከረደሰበት መድን ሰጪው ሃላፊነት እንደሌለበት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ማግለያ አንቀጽ ላይ በግልጽ የተመለከተ ስለመሆኑ ከፍ ሲል ተመልክተናል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው በመኪናው ላይ ጉዳት ያደረሰው የተጠሪ ተቀጣሪ በሆነ ሠራተኛ ቢሆንም በማግለያ አንቀፁ መሠረት ረዳቱ መንጃ ፈቃድ የሌለው በመሆኑ ብቻ እንኳ አመልካች መድን የመስጠት ሃላፊነት የሌለበት መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ መንጃ ፈቃድ የሌለው ሰው ባለሞተር ተሽከራካሪ ማሽከርከር እንደማይችል ይልቁንም ድርጊቱ በወንጀል ጭምር እንደሚያስጠይቅ በሕግ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ሕጉ በዚህ መልክ ሲደነገግ ጥበቃ ሊያደርግ የፈለገው ለባለ ንብረቱ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰቡ /ለሕዝብ/ አጠቃላይ ደህንነትም ጭምር እንደሆነ መገንዘብ አዳጋች አይደለም፡፡ በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ጋር ስናያይዘው የተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት የደረሰው ሚያዝያ 6 ቀን 1999ዓ.ም ሲሆን በዚህ ጊዜ ሥራ ላይ የነበረው የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀጽ 22 ላይ እንደተደነገገው ያለመንጃ ፈቃድ ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት እንደማይፈቀድ እና ባለንብረቱም ይህንን መፍቀድ እንደሌለበት በግልጽ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡

በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 29 እንደተመለከተው አዋጁንና አዋጁን ለማስፈፀም ተብሎ የወጡትን ደንቦች የተላለፈ ሰው የወንጀል ሕግ መሠረት እንደሚሰማ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም ጉዳት አደረሰ የተባለው የሹፌሩ ረዳት በተጠሪ ስር የሚሆን ሰው ነው በሚል ምክንያት አመልካች የመድን ሃላፊነት አለበት ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የማግለያ አንቀፁን የውል ድንጋጌ መንፈስ በአግባቡ ያላገናዘበና በሌሎች ሕጎች ለሕዝብ ጥቅም ተብለው የተደነገጉትን ሕጎች ዓላማና ግብ ያላጤነ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ተችሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 127331 ታህሳስ 3 ቀን 2001ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 76377 ነሐሴ 25 ቀን 2001ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የመክፈል ሃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 65632

ሐምሌ 13 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ሕብረት ባንክ /አ.ማ/ - ነገረ ፈጅ ንጉሴ ኪዳኔ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- አቶ ዓሊ አብዱ - ጠበቃ አቶ ደምሴ ልዑልሰገድ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በፍርድ የተወሰነላቸው ገንዘብ እንዳለ በመግለፅ ወሐቢይ መሐመድ የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል፡፡ በአፈፃፀሙ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ የሰሊጥ ማበጠሪያ ማሽን ድርጅት መጋዘን የተያዘ በመሆኑ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ በሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅቱ መጋዘን የብድር መያዣ በመሆኑ የቀዳሚነት መብት አለኝ፡፡ ሌሎች የፍርድ ባለመብቶች የሰሊጥ ድርጅቱ ሲሸጥ ከእኔ የተረፈ ገንዘብ ከተገኘ በተረፈው ላይ ብቻ ነው ፍርድ የማስፈፀም መብት ያላቸው የሚል ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ ተቀብሎ የሀራጅ ማስታወቂያው በሬድዮና በቴሌቪዥን እንዲነገር ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ የሀራጅ ማስታወቂያው ሳይነገር የቀረ መሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያሳያል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በመያዣነት የያዘውን የሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅት መጋዘን ሸጦ ቀሪ ገንዘብ ከተገኘ ለሌሎች የፍርድ ባለመብቶች ለማከፋፈል እንዲችል ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሰጥለትና መያዣውን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሐራጅ ለመሸጥ የተጀመረው አፈፃፀም እንዲቆም ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ በመቀበል አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መያዣውን እንዲሸጥ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በመያዣ የያዘውን የሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅት መጋዘን እንዲሸጥ እድል ተሰጥቶት ጨረታ ማስታወቂያ ካወጣ በኋላ የተወው በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መያዣውን በራሱ የመሸጥ መብቱን ትቷል፡፡ ስለሆነም የሐራጅ ሥርዓቱ መከናወን ያለበት አፈፃፀሙን በጀመረው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኩል እንጂ በአመልካች በኩል መሆን የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የካቲት 15 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች መያዣውን የመሸጥ መብቱን ከፈቃዱ ለቋል በሚል የተሳሳተ የሕግ ትርጉም በመስጠት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መያዣውን በመሸጥ ብድራችንን የመሰብሰብ መብታችንን የሚያሳጣ ውሣኔ ወስኗል፡፡ ይኸም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅቱን ለመሸጥ የመጀመሪያ ሐራጅ እንዲወጣ ካደረገ በኋላ አመልካች መያዣውን በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንዲሸጥ በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሻረው ባግባቡ ነው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፤ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች መያዣውን የመሸጥ መብቱን በፍላጎቱ ትቶታል፡፡ ሁለተኛ መያዣውን በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ለመሸጥ ያቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የፍርድ ባለዕዳ የሆኑትን የተጠሪ ሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅት መጋዘኖች በመያዣነት የያዘ መሆኑ አመልካችና ተጠሪ የሚካሳዱበት ነጥብ አይደለም፡፡ የመንግስትም ሆኑ የግል ባንኮች ለአበደሩት ብድር ዋስትና እንዲሆን የያዙትን የማይንቀሳቀስ ንብረት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በሐራጅ በመሸጥ ለአበደሩት ብድር መክፈያነት ሊያውሉ የሚችሉበት ሥልጣንና ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 97/90 በሕግ አውጭው ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሕግ አውጭው በአገሪቱ የሚገኙ ባንኮች በውል የያዙትን የመያዣ ንብረት ራሳቸው በሐራጅ ሸጠው ዕዳቸውን ለመሰብሰብ የሚያስችላቸው ሥልጣን የሰጠበት ዋነኛው ምክንያት የገንዘብ ተቋማቱ መያዣውን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማሸጥ ያበደሩትን ገንዘብ ለማስመለስ በሚጥሩበት ጊዜ የተለያዩ ችግሮች ስለሚያጋጥሟቸውና በዚህ ምክንያት ዕዳቸውን ለመሰብሰብና መያዣውን በወቅቱና በዋጋቸው ለመሸጥ የማይችሉ በመሆናቸው መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 97/90 መግቢያ ላይ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ሕግ አውጭው የገንዘብ ተቋማቱ በመያዣ የያዙትን ንብረት በሐራጅ ሲሸጡ በፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ከአንቀፅ 394 እስከ አንቀፅ 449 ያሉትን ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው የመከተል ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን በአዋጁ አንቀፅ 6 ከመደንገጉም በላይ በሽያጭ ሂደቱ ሕግን በመተላለፍ ሽያጩን ቢፈፅም ባንኩ በባለ ዕዳው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂነት ያለበት መሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 7 በግልፅ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም አመልካች በመያዣነት የያዘውን የተጠሪ ሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅት መጋዘን በራሱ በሐራጅ የመሸጥና ዕዳውን የመሰብሰብ መብት ያለው መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀፅ 3 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ይህንን በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን ለመጠቀም የፍርድ ቤት ውሣኔም ሆነ ፈቃድ አያስፈልገውም፡፡ አመልካች ከዚህ በፊት መያዣውን የመሸጥ መብቱን በፈቃዱ ትቶታል የሚለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክንያት ሕግ አውጭው ከጅምሩ አዋጅ ቁጥር 97/90 በማወጅ ባንኮች መያዣቸውን ለመሸጥ የሚያስችላቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት የሰጠበትን መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በመያዣነት የያዘውን የተጠሪን የሰሊጥ ማበጠሪያ ድርጅት መጋዘን በአዋጅ ቁጥር 97/90 ራሱ መሸጥ አይችልም፡፡ የሐራጅ ሽያጩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኩል ይፈፀም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ /አ.ማ/ ነ/ፈጅ ሜሮን ሰለሞን ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ጣይቱ አመዶ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት ለመሸፈን የተደረገ የመድን ውል ነው፡፡ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው የክስ ማመልከቻ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-27956 አ.አ የሆነ ኤፍ ኤስ አር አይሱዚ መኪና እንዳላቸውና መኪናው በአደጋ ምክንያት ጉዳት በደረሰበት ተከሳሹ /አመልካች/ እስከ ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ ብር/ የመድን ሽፋን ለመስጠት በመስማማቱ ተጠሪ የአረቦን ክፍያ ሲከፍሉ የቆዩ መሆኑን የተጠሪ መኪና ህዳር 10 ቀን 1999ዓ.ም በመውደቁ ተጠሪ አመልካች መኪናውን እንዲያስጠግን ወዲያውኑ ያሳወቁ መሆኑን ሆኖም አመልካች ሙሉ በሙሉ ሊተካ የሚገባውን የመኪናውን አካል በአዲስ ለመተካት ባለመፈለጉና መኪናው ሳይጠገን 198 ቀናት የቆየ በመሆኑ የመኪናውን አካል እንዲተካና መኪናውን ለመጠገን ከሚያስፈልገው ምክንያታዊ ጊዜ በላይ የቆመ በመሆኑ በቀን ብር 1500 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ሒሳብ አመልካች ውሉን ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰብኝን ጉዳት ካሳ /የቀረ ገቢ/ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ መኪናው አዲስ እቃ ተገዝቶ ካልተተካለት በማለት ተጠሪ /ከሳሽ/ በፈጠሩት ችግር ምክንያት ሳይጠገን የቆየ በመሆኑ ኃላፊነቱ የከሳሽ /ተጠሪ/ ነው፡፡ በመድን ፖሊሲው መሠረት የተቋረጠ ጥቅም የመክፈል ኃላፊነት የሌለብን በመሆኑ የከሳሽ ጥያቄ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃና ክርክር ከሰማ በኋላ መኪናው ሳይጠገን ለመቆየቱ የአመልካች /የተከሳሽ/ ጥፋትና ኃላፊነት ነው በማለት ከደመደመ በኋላ ተከሳሽ /አመልካች/ በመድን ውሉ መሠረት የከሳሽን መኪና ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ባለማስጠገኑ ምክንያት ከሳሽ /ተጠሪ/ ያቀረቡትን ገቢ የመሸፈን ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም የመኪናውን መጠን የሚያስፈልገውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘብ ብር 139,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ብር/ እና መኪናው ፍርድ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ያስገኝ የነበረው ገቢ በቀን በብር 1500 ታስቦ ብር 588,000 /አምስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺ ብር/ እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሁለት ጭብጦችን መስርቷል የመጀመሪያው ጭብጥ የከፍተኛው ፍ/ቤት አመልካች መኪናውን ለማስጠገን አስፈላጊ የሆነውን ብር 139,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ብር/ ለተጠሪ ይክፈል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ሁለተኛው ጭብጥ መኪናውን ለማስጠገን የሚፈጀው ምክንያታዊ ጊዜ ምን ያህል ነው የሚል ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛው ፍ/ቤት አርባ አምስት ቀናት ብቻ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት መኪናውን ለማስጠገን የሶስት ወራት ጊዜ ይፈጃል ከዚህ በተጨማሪ መኪናው በቀን የሚያስገኘው ገቢ ብር 1300 እስከ ብር 1500 ስለሆነ ሒሳቡ መሰላት ያለበት በዝቅተኛው መጠን በብር 1300 መሆን አለበት በማለት ካሻሻለ በኋላ መኪናው ከየካቲት 6 ቀን 1999ዓ.ም ጀምሮ በቀን ብር 1300 /አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር/ እየታሰበ ጉዳዩ በይግባኝ ውሳኔ እስካገኘበት ግንቦት 26 ቀን 2001ዓ.ም ድረስ ይከፈል በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች ሰኔ 24 ቀን 2001ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የክስ ማመልከቻ ከማቅረባቸው በፊት አመልካች የመኪናውን አካል እንዲቀይርልኝ የማይቀይር ከሆነ መኪናው ሙሉ ውድመት እንደደረሰበት ተቆጥሮ የመድን ውሉ ሙሉ ገንዘብ ብር 300,000 /ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ይክፈለኝ የሚል እንደሆነ ለአመልካች በጽሑፍ በሰጡት ማስጠንቀቂያ አሳውቀዋል፡፡ በዚህ መሠረት የመኪናውን ጋቢና ስፖንዳ በማስቀየር ወይም በማስጠገን የሚስተካከል ስለመሆኑ በባለሙያ አስጠንተን ሊጠገን የሚችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች መኪናውን ለመጠገን እና ለማስተካከል ከሚያስፈልገው በላይ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ተጠሪ መኪናውን ለማስጠገን ከሚያስፈልገው በላይ እንዲካስ የሚያደርግና መሠረታዊ መርህ የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ በሁለተኛ ደረጃ አመልካች መኪናው ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ተጠሪ የቀረበትን ገቢ የመክፈል ኃላፊነት እንደሌለበት በመድን ፖሊስው በግልጽ ተገልጾ እያለ የእኛን ምስክሮች ሳይሰማ ተጠሪ ጉዳቱን የመቀነስ ኃላፊነታቸውን የተወጡ መሆን አለመሆኑን ሳይመዝን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802ን በመጣስ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ለመኪናው ማስጠገኛ ከሚያስፈልገው በላይ እንዲካስ ወስነዋል በማለት የቀረበው አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች ፍሬ ጉዳዩን በማጣራትና በማስረጃ በማረጋገጥ የደረሱበትን መደምደሚያ የሚመለከት በመሆኑ የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበትና የሚታይ ነጥብ አይደለም፡፡ በእኔ በኩል የጠየቅሁት መኪናው ላይ አደጋ በመድረሱ ምክንያት የቀረብኝን ገቢ /Consequential loss/ እንዲከፍለኝ ሳይሆን አመልካች መኪናውን አስጎትቶ ወስዶ በማቆም በመድን ውሉ መሠረት በምክንያታዊ ጊዜ ውስጥ አሰርቶ ማስረከብ ሲገባው መኪናውን አሰርቶ ባለማስረከቡ የደረሰብኝን ኪሳራ የሚመለከት በመሆኑ የአመልካች ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በጸሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተጎዳውን የመኪና ክፍል በአዲስ ለመተካት የሚያስችል ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔና አመልካች መኪናውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለማስጠንቱ ተጠሪ ያቀረባቸውን ጥቅም በሙሉ ይክፈል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ መስርተናል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በተጠሪ መኪና አካል ላይ የደረሰው ጉዳት በጥገና የሚስተካከል ሳይሆን አዲስ እቃ ገዝቶ በመተካት ሊስተካከል የሚችል መሆኑን በገለልተኛ ባለሙያ እንደተረጋገጠና ጉዳቱ በጥገና ሊስተካከል የሚቻል ነው በማለት ሐሳብ የሰጡት የአመልካች ኤክስፐርቶች መሆናቸውን በመግለጽ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት አዲስ እቃ በመግዛትና በመተካት ሊስተካከል የሚችል ጉዳት ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳቱን ለማስተካከል አስፈላጊ የሆነውን ብር 139,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ብር/ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት የወሰነው ፍሬ ጉዳዩን በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ፍሬ ጉዳዩን በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፀንቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ማስረጃ በመመዘን ሐደት ሰርተውታል የሚለውን ስህተት የማጣራትና የማረም ስልጣን ይህ ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ያልተሰጠው በመሆኑ አመልካች መኪናው እንዲጠገንና እንዲስተካከል ለማድርግ ብር 139,000 ለተጠሪ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ በመኪናው የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ከሚያስፈልገው መጠን በላይ ነው በማለት ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ አመልካች በመድን ውሉ መሠረት ባለመፈፀሙና መኪናውን ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ አስጠግኖ ባለመስጠቱ የቀረብኝ ገቢ ክርክሩ እስከተቋጨበት ጊዜ ድረስ ያለው ታስቦ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ይህ የተጠሪ ጥያቄ ተጠሪ መኪናቸው በአደጋው ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ምክንያት ያቀረባቸውን ጥቅም አመልካች እንዲከፍላቸው የቀረበ የ /Consequential loss/ ጥያቄ በመሆኑና የዚህ አይነት ጥያቄ በመድን ውሉ እንደማይሸፈን ግልጽ የፖሊሲ ድንጋጌ ያለ በመሆኑ ተገቢ አይደለም በማለት አመልካች ተከራክሯል፡፡ በእኛ በኩል እንደተረዳነው ተጠሪ የጠየቁት መኪናው በአደጋው በመጎዳቱ ምክንያት ያቀረባቸውን ጥቅም አመልካች እንዲሸፍንና እንዲከፍላቸው አይደለም፡፡ የተጠሪ ክስ መሠረታዊ ይዘት አመልካች መኪናውን ከወደቀበት ካነሳ በኋላ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ መኪናውን አስጠግኖ የማስረከብ የውል ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች ይህንን የውል ግዴታውን በወቅቱ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰብኝን ኪሳራ እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ከመድን ፖሊሲው ድንጋጌ ውጭ /Consequential loss/ እንድንከፍል ተወስነብን በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የተጠሪ ክርክር ውልባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰብኝ ኪሳራና ጉዳት በውሉ መሠረት ግዴታውን ያልፈፀመው አመልካች ይክፈለኝ የሚልና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1790 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1791ን መሠረት ያደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ሆኖም እዚህ ላይ ሊታይ የሚገባውና የበታች ፍ/ቤቶች በአግባቡ ያላዩዋቸው መሠረታዊ የህግ ነጥቦች አሉ፡፡ ይኸውም አመልካች በመድን ውሉ መሠረት መኪናውን በምክንያታዊ ጊዜ ውስጥ በማስጠገን የማያስረክባቸው መሆኑን ካወቁ ተጠሪ መኪናው ተጠግኖ ለስራ ባለመሰማራቱ ምክንያት የሚያደርሰውን ኪሳራ/ጉዳት/ ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ግዴታ አለባቸው ወይስ የለባቸውም? ተጠሪ ጉዳቱን ለመቀነስ አስፈላጊውን ጥረት ካላደረጉ ሊከፈላቸው የሚገባው የካሳ መጠን ምን ይሆናል የሚሉት ናቸው፡፡

ሌላቸው ተዋዋይ ወገን የውል ግዴታውን ያልፈፀመለት ሰው ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የሚደረሰውን የጉዳት ኪሳራ የመቀነስ ግዴታ እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 ተደንግጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 "የጉዳት ኪሳራን የመቀነስ ግዴታ" በሚል ርዕስ ስር በንዑስ አንቀጽ 1" ውል አልተፈፀመልኝም የሚለው ወገን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የሚደርሰው ኪሳራ ያነሰ እንዲሆን ተገቢ የሆነውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት ይኸውም ይህንን የሚያደርገው ጥንቃቄ አስቸጋሪና ብዙ ወጭ እንዲያደርግ የማያስገድደው ሲሆን ነው" በማለት ይደነግጋል፡፡ ጉዳት የደረሰበትን መኪና ለመጠገን አስፈላጊ የሆነው ምክንያታዊ ጊዜ ሶስት ወር/ዘጠና ቀናት/ እንደሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በማረጋገጥ ወስኗል፡፡ የተጠሪ መኪና ጉዳት የደረሰበት ህዳር 3 ቀን 1999ዓ.ም በመሆኑ አመልካች በመድን ውሉ መሠረት መኪናውን ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ያስጠግነዋል ብለው መጠበቅ ያለባቸው እስከ የካቲት 10 ቀን 1999ዓ.ም ነው፡፡ ተጠሪ ከየካቲት 11 ቀን 1999ዓ.ም በኋላ አመልካች መኪናውን በመድን ውሉ መሠረት ባለማስጠገኑ ምክንያት የሚደርሰውን የኪሳራ /ጉዳት/ ለመቀነስ የበኩላቸውን እንቅስቃሴ ማድረግና መኪናውን በሶስት ወር ውስጥ በግል ወጫቸው አስጠግነው ወደ ስራ እንዲሰማራ የማድረግ ህጋዊ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስም ሆነ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ እስከተወሰነበት ግንቦት 26 ቀን 2001ዓ.ም ድረስ መኪናውን በግል ወጭ ለማስጠገንና መኪናው ተጠግኖ ለስራ ባለመሰማራቱ ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ያደረጉት እንቅስቃሴ የለም፡፡ ይህም ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጣለባቸውን የጉዳት ኪሳራን የመቀነስ ግዴታ ያልተወጡ መሆኑን ያሳያል፡፡

ተጠሪ መኪናው ባለመጠገኑ ምክንያት የሚደርስባቸውን ኪሳራ መኪናውን በራሳቸው ወጭ በማስጠገን ለመቀነስ እየቻሉ ይህንን ግዴታቸውን ካልተወጡ የሚከፈላቸው የኪሳራ መጠን እንዲቀንስ አመልካች ለመከራከር የሚችል መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 ንዑስ አንቀጽ 2 "ይህንን ጥንቃቄ በቸልተኝነት ሳያደርግ ቢቀር ውሉን ያልፈፀመው ሰው የሌለውን ወገን ችልታ መከራከሪያ አድርጎ ኪሳራው እንዲቀንስለት ለመጠየቅ ይችላል" በማለት በግልጽ ይደነግጋል፡፡ አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802ን በመጥቀስ የተከራከረ ሲሆን የበታች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መኪናው በመድን ውሉ መሠረት አስጠግኖ ባለማስረከቡ ተጠሪ የደረሰባቸውን ኪሳራ ለመቀነስ ያደረጉት እንቅስቃሴ አለመኖሩንና የጉዳት ኪሳራ የመቀነስ ግዴታቸውን ተጠሪ ያልተወጣ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የካሳውን መጠን መወሰን ሲገባቸው መኪናውን ለማስጠገን ከሚያስፈልገው ምክንያታዊ ጊዜ ከየካቲት 8 ቀን 1999ዓ.ም ጀምሮ ጉዳዩ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እስከተወሰነበት ግንቦት 26 ቀን 2001ዓ.ም ድረስ በየቀኑ 1300 /አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር/ እየታሰበ አመልካች ለተጠሪ ካሳ እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802 የተደነገገውን የጉዳት ኪሳራን የመቀነስ ግዴታ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ መኪናውን ለማስጠገን አመልካች ከሚወስድበት ምክንያታዊ ጊዜ ማለትም ከየካቲት 11 ቀን 1999ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 10 ቀን 1999ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ መኪናውን በግሉ በማስጠገን መኪናው ያለስራ በመቆሙ ምክንያት የሚደርስበትን ኪሳራ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802/1/ መሠረት መቀነስ ሲገባው ይህንን ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ ኪሳራ የሚከፈለው ጉዳዩ በይግባኝ ውሳኔ እስካገኘበት ጊዜ ድረስ ሳይሆን በራሱ ወጭ መኪናውን በማስጠገን ኪሳራውን ለመቀነስ የሚያስፈልገው ምክንያታዊ ጊዜ ማለትም የሶስት ወር ወይም የዘጠና ቀናት ብቻ መሆን ይገባዋል በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወሰነውን የካሳ መጠን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1802/2/ እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1/ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

2/ አመልካች ለመኪናው ማስጠገኛ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተወሰነውን ብር 139,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ብር/ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ከሰጠበት የካቲት 3 ቀን 2000ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡

3/ አመልካች መኪናውን ባለማስጠገኑ ተጠሪ ለደረሰባቸው ጉዳት የዘጠና ቀናት ገቢ በቀን በብር 1300 /አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር/ ታስቦ ብር 117,000 /አንድ መቶ አስራ ሰባት ሺህ ብር/ ጉዳዩ በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ ካገኘበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይክፈል ብለናል፡፡

4/ በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 56010

ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

ተጠሪዎች፡- 1. ቃድሮ ኑሬ

2. ወ/ሮ ይባ ሄቦ

3. ቱሪ ዋሪቱ

4. ወ/ሮ ሃጆ ዱቤ

5. ከድር ቢፍቱ

6. ወ/ሮ ሽምሲያ ዓብዱልቃድር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የክርክሩን መነሻ በብድር የተሰጠን ገንዘብ ለማስመለስ የቀረበ ክስ ሆኖ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲወሰን ተይዞ የቀረበው ጭብጥ ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ ክሱ /ክርክሩ/ የጀመረው በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በክሱ እንደተመለከተው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከባንኩ ገንዘብ በብድር የወሰዱ ናቸዉ፡፡ ሌሎች ተጠሪዎች ደግሞ ለብዱሩ አመላለስ የዋስትና ግዴታ ገብተዋል፡፡ ብድሩ የተወሰደው በ24-7-88 ዓ.ም በተፈረመው ውል እንደሆነ መመለስ የነበረበት በ24-7-89 ዓ.ም መሆኑን ተበዳሪዎች ገንዘቡን ለመመለስ ባለመቻላቸው አመልካች በዋስትና የያዘው የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ቤት በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት አስገምቶ ሐራጅ ማወጣቱን ፣ የሐራጅ ማስታወቂያ ከማውጣቱ በፊትም በ19-5-92 ዓ.ም ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ ጽፎ የነበረ መሆኑን በወጣው የሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት ቤቱን የሚገዛ ሰው ባለመገኘቱ አመልካች በቀረበው ግምት ብር 52,525.10 ቤቱን መረከቡን በመጨረሻም አመልካች በቀሪ የሚፈለገውን ገንዘብ ይከፈለው ዘንድ በ21-2-2001 ዓ.ም ክስ መመስረቱን ክሱን የሰማው ፍ/ቤት በሰጠው ብይን ላይ በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ለክሱ በሰጡት መልስ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦች አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ወደሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከማለፉ በፊት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጐአል። ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤትም ብይኑ ጉድለት የለበትም ብሎአል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው።

እኛም አመልካች ግንቦት 10 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። በመቀጠልም በጭብጥነት የተያዘውን ነጥብ ግራ ቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

እንደምንመለከተው ተጠሪዎች የብድሩን ገንዘብ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለመክፈላቸው አመልካች በ92 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአቸዋል። ሆኖም በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረትም ገንዘቡን ሊከፍሉ ባለመቻላቸው በዋስትና በያዘው ቤት ላይ በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት የሐራጅ ማስታወቂያ ያወጣ ቢሆንም ቤቱን የሚገዛ ሰው ባለመገኘቱ ለጉዳዩ አፈጻጸም አግባብ ባለው የሥነ -ሥርዓት ህግ መሠረት ቤቱን በግምቱ ልክ ተረክቦአል። አመልካች ቤቱን የተረከበው ሚያዝያ 20 ቀን 96 ዓ.ም ስለመሆኑም በተጠሪዎች መልስ ጭምር ተረጋጋጦአል። አመልካች ቤቱን ቢረከብም በዚህ ረገድ ተከፈለ ሊባል የሚችለው ዕዳ በተጠሪዎች ላይ የሚፈለገውን አጠቃላይ ዕዳ የሚሸፍንለት ሆኖ ባለማግኘቱ ቀሪው ዕዳ እንዲከፈለው በመጠየቁ ክስ መስርቶአል። አመልካች ቤቱን በግምቱ ልክ ተረክቦ ቀሪ ዕዳ የሚፈልግ መሆኑን ባረጋገጠበት ጊዜ እና ክስ በመሰረተበት ቀን /ጊዜ/ መካከል ያለው ጊዜ ሲታሰብ አስር ዓመት አልሞላም። የስር ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ስለመገንዘባቸው ከተሰጠው ብይን ይዘት ለመገንዘብ ችለናል። ይህም ሆኖ የይርጋውን ጊዜ ያሰሉት ብድሩ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በመሆኑ የአስር ዓመትን የይርጋ ጊዜ መሠረት በማድረግ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው አልፎአል እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል።

በበኩላችን እንደምናየው አመልካች በዋስትና የያዘውን ቤት በአዋጅ ቁ. 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሸጦ ለብድሩ መክፈያ ከማድረጉ በፊት ያልተከፈለ ቀሪ የብድር ገንዘብ የሚኖር ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ይችል ነበር ለማለት አይቻልም። በመጀመሪያ ማድረግ የነበረበትም በመያዣነት የያዘውን ቤት ሸጦ ገንዘቡን መሰብሰብ እንደመሆኑ አመልካቹ ይህንኑ ፈጽሞአል።

ተጠሪዎችን ቀሪ የብድር ገንዘብ ይክፈሉኝ በማለት ሊከስ የሚችለው በእርግጥም ያልተከፈለ ቀሪ ዕዳ መኖሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከያዘ በኋላ ነው። የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም በውሉ የሚሰጠው መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 1846 ተደንግጐአል።

አመልካች ለብድር ገንዘቡ አመላለስ ዋስትና እንዲሆን የያዘውን ቤት በግምቱ ልክ ከተረከበ በኋላ ቀሪ ዕዳ እንደሚፈልግ እርግጠኛ የሆነው ከሚያዝያ 20 ቀን 96 ዓ.ም በኋላ ነው። በመሆኑም በተጠሪዎች ላይ ክስ መመስረት የሚችለው ከዚህ በኋላ ነው። የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረውም ከሚያዝያ 20 ቀን 96 ዓ.ም ጀምሮ ስለሆነ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ያለው ሲታሰብ ጊዜው አላለፈበትም። የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ከዚህ አንጻር ሲታይም በህጉ አተረጓጐም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው። ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 04301 መስከረም 21 ቀን 2002 የሰጠው ብይን እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 77420 መጋቢት 7 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ብለናል፡፡ በመሆኑም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን በተጀመረው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በክሱ ስረ ነገር ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች የሚያቀርቡለትን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሠረት ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡-1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነ/ፈጅ ተስፋዬ ዘመድኩን ቀረበ

የመሬት ልማት አስተዳደር ባለስልጣን

2. የቂርቆስ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት

አስተዳደር ጽ/ቤት

ተጠሪ፡- ድንቅ ስራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ሞላ ዘገዬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሊዝ ውልን መሰረት አድርጐ ለአንድ ሰው የተሰጠ ቦታ ለሌላ ሰው ሲሰጥ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው አካል የትኛው ነው? የሚለውን የሕግ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ማህበር ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/19 በተለምዶ ባንቢስ አጠገብ ስፋቱ 1194 ካ.ሜ የሆነ ቦታ ላይ ሕንፃ ለመስራት ቦታውን ከአሁኑ 2ኛ አመልካች ጋር የሊዝ ውል በመፈረም ቦታውን በመረከብ ስራ ከጀመረ በሁዋላ 1ኛ ተጠሪ ከመስከረም 25 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ምንም ዓይነት የቦታ ጥያቄ እንዳያስተናግድ ታግዶ ሳለ፣አስፈላጊውን መረጃዎች ሳይቀርቡለት ከተጠሪ መሬት ጋር አጐራባች ለሆኑት የሆቴል ዲልፖል ባለቤት ለሆኑት ለአቶ ዳመና ሲማ ቦታውን እንዲወስዱ፣ተጠሪ ቦታውን እንዲያስረክብ መወሰኑን፣አመልካቾች በሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣን ውጪ ተጠሪ በሊዝ ውል መሰረት የወሰደውን የልማት ቦታ በመቀማት ለሌላ ግለሰብ ለመስጠት የወሰኑትን እንዲያርሙ ቢጠየቁ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመግለጽ ከዚህ አድርጐታቸው እንዲቆጠቡ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችንና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ በሚል ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረቡትን የአመልካቾችን መከራከሪያ ነጥቦችን በመመርመር ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅሬታውን አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን የማየት ሥረ ነገር ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ነገረ ፈጅ ሚያዝያ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶችም ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ስር የማይወድቅ የአስተዳደር አካሉ ሥልጣን ነው በማለት መከራከራቸውንና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ እንዲታረም ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስረ ነገር ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪ መስከረም 04 ቀን 2003 ዓ.ም በጠበቃቸው አማካኝነት በተፃፈ ሦስት ገጽ ማመልከቻ የጽሁፍ መልሱን አቅርቧል፡፡ የአመልካቾች ነ/ፈጅም መስከረም 14 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመልጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀረብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ፣በቀድሞው አጠራር በወረዳ 15 ቀበሌ 34 ክልል ውስጥ በተለምዶ አጠራር ባምቢስ አጠገብ ስፋቱ 1194 ካ.ሜትር ቦታ ለማልማት በቅድሚያ ሰኔ 28 ቀን 1996 ዓ.ም ከአዲስ አበባ አስተዳደር የመሬት አስተዳዳር ባለስልጣን ጋር በተፈረመ ጊዜያዊ መተማመኛ ውል ቀጥሎም መስከረም 25 ቀን 1998 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ከተማ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር በተፈረመ የከተማ ቦታ የሊዝ ውል አድርገው ቅድሚያ የሊዝ ክፍያ ተከፍሎ ካርታ እና የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሁኖ እያለ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን አልተወጡም ወይም የውሉ ጊዜ አብቅቷል ባልተባለበት ሁኔታ እንዲሁም ለመንግስት ልማት የሚፈለግ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ መሬቱን አመልካቾች ከተጠሪ ነጥቀው ለሆቴል ዲሊኦፖል ባለቤት ግለሰብ ለመስጠት ደብዳቤ የፃፉላቸው መሆኑን ጠቅሰው የአመልካቾች እርምጃ ከሕግ ውጪ ነው በማለት ተጠሪ የሚከራከሩ መሆኑን፣አመልካቾች በበኩላቸው ይህ ለተጠሪ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሊዝ ቦርዱ ከተጠሪ ጋር የነበረው የሊዝ ውል እንዲቋረጥ በመወሰኑ መሰረዙን ገልፀው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊዳኝ የማይችል መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ተጠሪ ጉዳዩ የሊዝ ውል እንጂ የአስተዳደር ውል ባለመሆኑ መዳኘት ያለበት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው የሚለውን ክርክር፣አመልካቾች ደግሞ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ይታያል ከተባለም መታየት ያለበት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ነው የሚል ክርክር በስር ፍርድ ቤት አቅርበው የነበሩ መሆኑንም ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1/ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳየው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚሁ የሕገ መንግስት ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ፍርድ ቤቶች አንድን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ(አቤቱታ) ተቀብለው ውሳኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ መሆኑን ነው፡፡ በሕግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍርድ ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን ስለሌለው በሕጉ መሰረት ለአንድ አስተዳደር አካል ቀርቦ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወይም ለአስተዳደር መቅረብ የሚገባውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ሊያስተናግደውም ሆነ አከራክሮ ውሳኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ለአንዳንድ የመንግስት አካላት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሰጡት ሕጐች መጠበቅና መከበር ያለባቸው ሲሆን የዳኝነት አካል ስልጣንም በሕግ የተወሰነ ስለሆነ ሕግ የመተርጐም ስራው በሕጉ በተመለከተው አድማስ የሚመራ ይሆናል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.4 ድንጋጌ የሚያሳየውም ፍርድ ቤቶች በሌላ ሕግ በግልጽ በታገዱ ጉዳዮች ላይ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በአስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በሕግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ(ክርክር) መሰረት ያደረገው ከአመልካቾች ጋር ባደረጉት የሊዝ ውል የተሰጠውን መሬት ከሕግ ውጪ ተወስዶ ለሌላ ግለሰብ እንዲሰጥ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ በዚህ መልኩ የሚቀርበውን የዳኝነት ጥያቄ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ እልባት የሚሰጥበት መሆኑን ወይም ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባው መሆኑን የሚደነግግ ሕግ አለ በሚል በአመልካቾች የሚቀርበው ክርክር መሰረት ያደረገው አዋጅ ቁጥር 272/1994 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ የሊዝ ቦታ የሚሰጥበትና ውሉ የሚቋረጥበት አግባብ ተዘርግቷል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 15፣16 እና 17 ድንጋጌዎች ሲታዩ የሊዝ ውል የሚቋረጥበትንና ካሳ የሚከፈልበትን አግባብ፣ጉዳዩን ሊመለከቱ የሚችሉ ወገኖችንና የይግባኝ አቀራረብን ሥርዓት ደንግገው እናገኛለን፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሊዝ ውል እንዲቋረጥ ተደርጓል የሚባለው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ነው በሚል ምክንያት በመሆኑ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸው የአዋጅ ቁጥር 272/94 ድንጋጌዎች አንቀጽ 15/1/ለ/ እና 16 ናቸው፡፡ የአንቀጽ 15/1/ለ/ ድንጋጌ የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ለሌላ ስራ ወይም አግልግሎት እንዲውል ሲወሰን ሊቋረጥ እንደሚችል የተመለከተ ሲሆን በአንቀጽ 16/1/ደግሞ አግባብ ያለው አካል ለሕዝብ ጥቅም ይውላል ተብሎ በሚወስነው መሰረት ለሚመለከተው አካል የማስለቀቂያ ትእዛዝ ወይም ማስጠንቀቂያ በጹሑፍ በመስጠት የሚፈልገውን የከተማ ቦታ ማስለቀቅና መረከብ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡ የአዋጅ አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ሲታይም በአንቀጽ 16 መሰረት የማስለቀቅ ትእዛዝ የደረሰው ወይም ትእዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ወገን የካሣም ሆነ ማንኛውንም ለፍርድ ሊቀረብ የሚገባው ሌላ አቤቱታ ከዝርዝር ምክንያቱ እና ማስረጃው ጋር ትእዛዙን ለሰጠው አካል የማቅረብ መብት እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ በዚህ መልኩ ቀርቦ የታየ ጉዳይም በአንቀጹ ንኡስ ቁጥር ሁለት ስር የተመለከተው ተገቢ ዳኝነት የሚሰጥበት ሲሆን በውሳኔው የማይስማማ ሰው ለጉባኤው ይግባኙን ማቅረብ እንደሚችል በአንቀጽ 18/1/ ስር ተደንግጐ ያለ ከመሆኑም በላይ ይህ አካል የሚሰጠው ውሳኔ ካሣ አነሰኝ፣ ወይም ካሣ በዛብኝ ወይም ካሳ ተከለከልኩ በሚሉ ክርክሮች ላይ ካልሆነ በስተቀር በሕግም ሆነ በፍሬ ነገሮች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ስለመሆኑ የተጠቀሰው አንቀጽ ንኡስ ቁጥር ሦስት ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው በሊዝ የተሰጠ ቦታን የሚመለከተው አካል ማስለቀቅ የሚችለውና ጉዳዩ ላይ ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍርድ ቤት ሊቀርብ የማይገባው ቀድሞ የቦታ ማስለቀቁ እርምጃ የተወሰደው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 2/7/ ስር ለህዝብ ጥቅም ትርጉም አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት የሕዝብ ጥቅም ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሕዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የከተማ ልማትን በቀጣይነት ለማጐልበት አግባብ ያለው አካል በመሪ ፕላን ወይም በልማት እቅድ የሕዝብ ጥቅም ብሎ የሚወስነው ነው በሚል ትርጓሜ የተቀመጠ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 455/97ም ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ትርጉም በአንቀጽ 2/5/ ስር ይዞ እናገኛለን፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ጉዳዩ ከሕዝብ ጥቅም ጋር የተገናኘ በሚል ያቀረቡት ክርክር በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያላገኘው መሬቱ ሊሰጥ የታሰበው ሆቴል ለሕዝብ ጥቅም የሚለውን ትርጉም በሚያሟላ መልኩ የሚታወቅ ስለመሆኑ አላስረዱም በሚል ነው፡፡ ይህ ግልጽ የማስረጃ ጉዳይ መሆኑን የምንገነዘበው ሲሆን ፍሬ ነገርን የማጣራትና የማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካቾች ክርክር በማስረጃ የተደገፈ አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እ 25/1988 አንቀጽ 10 የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈፀም ማረም በመሆኑ የአመልካቾች ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ አሳማኝ ነው? ወይስ አይለም? የሚለውን ጉዳይ የሚመለከተው ሆኖ አላገኘውም፡፡ በተለይ አመልካቾች የተጠሪ ቦታ የሚወሰድ መሆኑን የገለፁት ተጠሪ በሊዝ በወሰዱት ቦታ ላይ የፈለጉትን ግንባታ ቢያካሂዱ በስተጀርባ ያለውን የአቶ ዳመና ሲማ ንብረት የሆነውን ዲሊኦፖል ሆቴል ስለሚጋረድ በሆቴሉ ሥራ ላይ እንቅፋት ይፈጥራል በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ቦታው ላይ የተሻለ ልማት የሚካሄድ መሆኑን፣በከተማው መዋቅራዊ ፕላን ቦታ ላይ የሚካሄደውን ግንባታ ለሆቴሉ ለመስጠት ማስፈለጉን አመልካቾች ያላረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን በሊዝ አዋጅና ደንብ መሰረት የገባውን ውል ባለማክበሩ ወይም መሬቱ መንግስት ለሚያካሄደው የልማት ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በቀር መሬት በሊዝ የተከራየ ሰው የሊዝ ዘመኑ ከማለቁ በፊት መሬቱ የማይወሰድበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 3/2/ ከመደንገጉ ጋር ተዳምሮ ሲታይ የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ጉዳዩ በፍርድ ቤት የሚታይ ነው ከተባለ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የትኞቹ ናቸው የሚለው ነጥብም ምላሽ የሚያስፈልገው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ይህንኑ ነጥብም ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝተናል፡፡ ይህንኑ ነጥብ ለመመለስ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ይዘቱ ምን እንደሆነ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ተጠሪ የአመልካቾችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው በማለት የሚከራከሩት ከሊዝ አዋጁና ደንብ ውጪ የተፈጸመ ነው በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካቾች ጋር የሊዝ ውል ያላቸው መሆኑና ተያያዥ ማስረጃዎችም ያላቸው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ አመልካቾች ደግሞ የተጠሪ የሊዝ ውል እንዲቋረጥ ተደርጐ ካርታና የይዞታ ምስክር ወረቀት መሰረዙን ገልጸው የሚከራከሩ መሆኑን የክርክር ሂደቱ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ተጠሪ ከአመልካቾች ያገኙት የሊዝ ቦታ ምስክር ወረቀት የተሰረዘው በአግባቡ ውሉን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው ወይም ከውሉና አግባብነት ካላቸው ሕጐች ውጪ ነው? የሚለው ነው፡፡

የከተማው አስተዳደር ካርታ የመስጠት፣የመሰረዝ፣የማሻሻል፣የማምከን፣ የማገድ እና አሻሽሎ የመስጠት ሙሉ ስልጣን ያለው ቢሆንም የሊዝ ውልን መሰረት አድርጐ የተሰጠውን ካርታና የምስክር ወረቀት መልሶ ከሕግ ውጪ ሰርዞ ሲገኝ በእርምጃው ላይ ቅሬታ ያለው ወገን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን ለፍርድ ቤት እንዲያቀርብ የሚከለክልበት ስርዓት የሌለ ስለመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አግልግሎት አካላት ስልጣንና ኃላፊነትን ለመደንገግ የወጣው፣ክርክሩ ሲጀመርም ሆነ ከተጀመረ በኋላ በስራ ላይ ያለው ሕግ ያሳያል፡፡ ይልቁንም የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሀ/ እና/መ/ ድንጋጌዎች ሲታዩ የተያዘውን ጉዳይ አይነት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ተቀብሎና አከራክሮ ለመወሰን የስረ ነገር ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በአማራጭ ባቀረቡት ክርክርም ይህንኑ ደግፈው ሲከራከሩ የነበሩ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቀርቦ ሊታይ ይገባል ሲባል የተያዘው ጭብጥ ሰበር ችሎቱ ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር ለማየት ተብሎ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶባቸዋል ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉት መዛግብት የመ/ቁጥር 17712 እና በመ/ቁጥር 27604 በተያዘው ጉዳይ ካለው ፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ሙሉ በሙሉ ግንኙነት አላቸው ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የተጠሪ ክስ መሰረቱ የሊዝ ውል ሆኖ ውሉ ተጥሷል በሚል ዳኝነት የጠየቁ ናቸውና፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ ጥያቄ የክፍለ ከተማው አስተዳደር ከሕግ ውጪ በሊዝ የተወሰደ ቦታ ለመውሰድ ካርታና የምስክር ወረቀት በመሰረዝ ሕገ ወጥ እርምጃ ወስዷል በማለት በሊዝ ውል ያገኙት የንብረት መብታቸው (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/6/ ይመልከቷል) በፍርድ እንዲጠበቅላቸው የሚጠይቅ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊያስተናግድ የሚገባው እና ውሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ በመሆኑ እና መታየት ያለበትም በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች በመሆኑ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜም ከአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሀ/ እና/መ/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ህጋዊ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት በውሳኔው ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 48336 ጥር 04 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት እ ዛ ዝ

ይህ ችሎት ሐምሌ 14 ቀን 2002 ዓ.ም ሰጥቶት የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 04 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘነበች ተመስገን - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ መሠረት አበራ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ከቀኛዝማች ተመስገን ዳልኬሮ መስከረም 20 ቀን 1960 ዓ.ም በተደረገላቸው የስጦታ ውል በወረዳ ሶስት ቀበሌ 47 ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 790 የሆነ ቤት ተሰጥቷቸው ሥጦታው ፀድቆና ቤቱ ያላግባብ የተወሰደ መሆኑ ተረጋግጦ በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ሕዳር 20 ቀን 1970 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ እንዲመለስላቸው የታዘዘ ቢሆንም ተጠሪ ቤቱ ሊመለስላቸው ያልቻለ መሆኑን ገልፀው ቤቱ እንዲመለስላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ አመልካች ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን ቤቱን ከሀያ አመት በላይ በእጁ አድርጎ የሚያስተዳድረው እና ግብርም የከፈለበት በመሆኑ ክሱ በይርጋ እንደሚቋረጥ ጉዳዩ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እየታየ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም የአመልካች ክስ በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መሆኑን ገልጾ መዝገቡን ቢዘጋውም የአሁኗ አመልካች በዚሁ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ያለው መደበኛ ፍርድ ቤት ነው በሚል ምክንያት ቀደም ብሎ የተሰጠው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ ጉዳዩ ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ተመልሶለታል፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን እንደገና መርምሮ የአሁኑ ተጠሪ ያቀረባቸውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገር ደረጃም የአመልካችን ክርክር ተቀብሎ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪ ለአመልካች እንዲያስረክብ ሲል ወስኗል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ አመልካች ጉዳዩን ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቅርበው ጉዳዩ እየታየ ባለበት ሁኔታና ውጤቱ ሳይታወቅ በፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስ መመስረታቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 8 ድንጋጌ አኳያ ተገቢነት የለውም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ መሆኑ ተረጋግጦ ከተወሰነ በኋላ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንደመደበኛ ፍርድ ቤት የማይቆጠር ሁኖ እያለ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 8 ተጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ ስነ ስርአቱን የጠበቀ ስላልሆነ ሊለወጥ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ የተጠሪ ነገረ ፈጅ ቀርበው ጥር 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የፁሑፍ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች አከራካሪው ቤት ይመለስልኝ ጥያቄን በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ የመሰረቱበት ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቤቱታቸውን አቅርበው ጉዳዩ እየታየ መሆኑን አልካዱም፤ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት አቤቱታቸው በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቢቀርብም ይኸው አካል እንደ መደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ አይገባውም ባሁኑ ጊዜም ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለኝም በማለት አቤቱታቸውን ያልተቀበለው መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ወገን ጉዳዩን ማቅረብ ያለበት ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 110/87 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 193/92 እና 572/2000 ያሳያሉ፡፡ ይህ አካል ጉዳዩ ሲቀርብለት በሕጉ አግባብ የሚሰጠው ውሳኔ እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊቆጠር የሚችልና ለአፈፃፀምም የሚቀርብ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ አካል በሕግ ተለይቶ በተሰጠው ጉዳይ ላይ የዳኝነት ሥልጣን ያለው አካል ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 110/87 ስለኤጀንሲው ስልጣንና ተግባሩ በአንቀፅ 4 ስር በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን የዚሁ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ፊደል “ለ” ከአዋጁ ውጪ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ የቀረቡለትን የመብት ጥያቄዎችና ሁኔታዎች በአዋጁ መሰረት ይመረምራል፣ ለምርመራው አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን ከማናቸውም የመንግስት ወይም የግል መስሪያ ቤት፣ ድርጅት ወይም ተቋም እንዲሁም ከማንኛውም ግለሰብ ለማግኘት የምስክር ቃል ለመቀበል ወይም የፅሁፍ ማስረጃን እንዲያቀርብለት ለማዘዝ እንደሚችል የተገለፀ ሲሆን በዚሁ ንኡስ ድንጋጌ ፊደል “ሐ” ስር ደግሞ ከአዋጁ ውጭ የተወሰደን ንብረት ባለቤትነት በተመለከተ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ መረጃዎችን እያጣራ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፣ ውሳኔው እንዲፈፀም አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል በሚል ተደንግጓል፡፡ ሌላው በአዋጁ አንቀፅ 9 ስር ከአዋጁ የማይቃረን ህግ ወይም መመሪያ ተፈጻሚነት እንዳለው በሚያስገነዝብ መልኩ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው ይኸው አካል ጉዳዩን ሲመለከት የተለያዩ የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ሥርዓቶችን ሊከተል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችል መሆኑና አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ሊመራ የሚችል መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው የየትኛው አካል ነው የሚል ክርክር ቀርቦ ባለበት ሁኔታ አንድ ጉዳይ ለሁለት የዳኝነት አካላት የሚቀርብበት አግባብ የለም፡፡ አንድ ጉዳይ በተመሳሳይ ጊዜ በሁለት የዳኝነት ሥልጣን ባላቸው አካላት መቅረብ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ድንጋጌ አላማን የሚፃረር ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ሳያልቅ በፍርድ ቤት መቀጠሉ ያላግባብ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ በአግባቡ ነው፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ታይቶ ተገቢው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አመልካች ለሚመለከተው ፍርድ ቤት በሕጉ አግባብ ክርክራቸውን ከመቀጠል የማይገድብ መሆኑን የተገነዘብን ሲሆን አመልካች በአሁኑ ወቅት የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቤቱታቸውን ያልተቀበለው መሆኑን በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃ የገለፁ ስለሆነ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ለስር ፍርድ ቤት ክርክራቸውን ከመቀጠል በስተቀር የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት የሚያስችል ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58727 ሕዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመ/ቁጥር 44907 ሰኔ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያቀረቡት አቤቱታ እልባት አግኝቶ ከሆነና እልባት የተሰጠበት አግባብም በፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ከሆነ ይህ ውሳኔ ክርክራቸውን በስር ፍርድ ቤት ከመቀጠል የሚያግዳቸው አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 54577

ህዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢት/ያ መድን ድርጅት - ነገረፈጅ ክንፉ ታደለ ቀረበ

ተጠሪ፡- አቶ ሰለሞን ያዕቆብ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ የቻለው አንድ የፌዴራል ፍ/ቤቶች የሆነን ጉዳይ በሕገ መንግሥቱ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት በክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ በታዩ ጊዜ የይግባኝ ክርክሩን ተመልክቶ ለመወሰን የይግባኝ ሰሚነት ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው ወይስ የዚያው ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት? ለሚለው የሕግ ጥያቄ አግባብነት ያለው የሕግ ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ ከውል ውጪ በሚደርስ ኃላፊነት ክስ ምክንያት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የገንዘብ ክርክር የአሁን አመልካች በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለትም የአላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ከመረመረ በኋላ ኃላፊ የሆነውን ወገን ለይቶና የካሣ መጠኑን ወስኖ የአሁን አመልካች በገባው የዋስትና ሽፋን መሠረት ለተጠሪ ይክፈል በማለት በመወሰኑ ምክንያት የኢት/ያ መድን ድርጅት ኃላፊነትና የካሣ መጠኑን አስመልክቶ በተሰጠው ውሣኔ ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ በዚህም የይግባኝ ቅሬታ መነሻ የአሁን መልስ ሰጭ ቀርቦ እንዲከራከር ሲደረግ በመጀመሪያ ደረጃ ያቀረበው የይግባኝ ክርክር የፍ/ቤቱን የይግባኝ ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡

ከውሣኔው ግልባጭ ይዘት እንደምንረዳው ለክርክሩ መሠረት ያደረገው ከዚህ ቀደም በተመሣሣይ ጉዳይ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መ/ቁ. 20465 ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ በክልል ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣን የታዩ ጉዳይ በይግባኝ ተቀብሎ የማስተናገድ ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እንጂ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አይደለም በማለት የወሰነ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 454/97 መሠረት ይህም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ጉዳይ ተቀብሎ ለማየት የሚያስችለው ሥልጣን የለውም የሚለውን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የይግባኙ ጉዳይ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ በሚመለከት የሚከተለውን ዳኝነት ሰጥቷል፡

ክርክር ባስነሣው ጉዳይ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የሁለት የተለያዩ ክልል ኗሪ ናቸው። በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/2/ መሠረት ጉዳዩ የፌዴራል ነው የፌዴራል የሆነውን ጉዳይ የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣኑ ተመልክቶ ከወሰነ ክሱ የሚታይበትን ክልል ጨምሮ በአምስቱም ክልሎች ተሰጥቶ የነበረው የውክልና ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተነሣ ስለሆነ በዚህ መንገድ በተሰጠው ውሣኔ ላይ የሚቀርበውን የይግባኝ ክርክር ተቀብሎ ለማስተናገድ ሥልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንጂ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አይደለም የሚለውን ትንታኔ ምርኩዝ በማድረግ በሥልጣን ረገድ የቀረበውን የመከራከሪያ ነጥብ በኮ/መ/ቁ. 67947 ሚያዚያ 05 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውድቅ አድርጎታል።

የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ የማየት ሥልጣን አለኝ ሲል በሰጠው ውሣኔ የአሁን መልስ ሰጭ ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማቅረባቸው ይህ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በመ/ቁ.46679 በ04/5/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተመሣሣይ ጭብጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 20465 ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትርጉም መሠረት የአላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባገኘው የውክልና ሥልጣን ተመልክቶ ውሣኔ በሰጠበት የፌደራል ጉዳዩ የሚቀርበውን የይግባኝ ክርክር ተመልክቶ የመዳኘት ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ስለሆነ የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረቡ ተገቢ አይደለም። ስለሆነም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ከሚያቀርብ በቀር ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብ አይችልም በማለት ውሣኔውን ሽሮታል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔውን ለመሻር መሠረት ያደረገው የሰበር ሰሚ ውሣኔ ለዚህ ጉዳይ ተዘማጅነት የለውም። በዚህ ጉዳይ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የተለያዩ ክልል ኗሪ በመሆናቸው ጉዳዩ የፌዴራል ነው የፌዴራል የሆነን ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚከለክለው ሕግ የለም ስለሆነም ከጉዳዩ ጋር ተገቢነት የሌለውን የሰበር ውሣኔ ጠቅሶ የሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው።

በዚህ የሰበር ቅሬታ መነሻ መልስ ሰጭ ቀርቦ በሥር ፍ/ቤቶች አቅርቦት የነበረውን ክርክር በማጠናከር ውሣኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ከይግባኝ ስልጣን ጋር በተያያዘ የተነሣውን የሕግ ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 አኳያ የፌዴራል ጉዳይ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተካደ ነጥብ አይደለም።

አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የአላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣኑ ተመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ሊቀርብ የሚገባውን የይግባኝ ክርክር ተቀብሎ የማስተናገድ ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው ወይስ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ በኢት/ያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ራፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80፤ 78/2/ እና አንቀጽ 78/2/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከትሎ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 322/95 ጋር በማጣቀስ ሊሰጥ የሚገባውን የሕግ ትርጓሜ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 78/2/ እንደተደነገገው ክርክር የተነሣበትን ክልል ጨምሮ በአምስቱም ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመደራጀቱ በአዋጅ ቁጥር 322/95 ተደንግጓል፡፡

በዚሁ አዋጅ መሠረት የተደረገው አደረጃጀት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ብቻ የተወሰነ እንጂ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ጨምሮ ያደራጀ ባለመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 78/2/ ሁለተኛ ክፍል ላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በክልሎች እንዲደራጅ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ካልተወሰነ ለክልል ፍ/ቤቶች የተሰጠው የውክልና ሥልጣን እንደፀና የሚዘልቅ መሆኑ በመደንገጉ፣ በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 80/4/ እንደተመለከተው የእነዚህ ክልሎች የከፍተኛ ፍ/ቤቶች በፌዴራል ጉዳይ እንደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሆነው በዳኝነት የማየት የውክልና ሥልጣናቸው የተነሣ አይደለም ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በአንድ በኩል በእነዚህ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተደራጀ መሆኑን ጠቅለል ባለ መልኩ ብቻ በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተደነገገ በመሆኑ የተነሣ፤ በሌላ በኩል ከላይ እንደተገለፀው የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች በፌዴራል ጉዳይ ላይ የተሰጣቸው ሕገ መንግሥታዊ የውክልና ሥልጣን እንደፀና ያለ ለመሆኑና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/5/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በውክልና የማየት ሥልጣን ያለው መሆኑ፣

እንደ አሁኑ ባለው ጉዳይ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ሥልጣኑ ተመልክቶ ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ ተቀብሎ ለማስተናገድ ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ወይስ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ነው? የሚለውን ጥያቄ ያስነሣል፡፡

በእነዚህ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ብቻ ተለይቶ በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተደራጀ እንደመሆኑ መጠን የዚህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥልጣን ወሰን በይግባኝ ተመልክቶ የመወሰንን ሁሉ የሚጨምር ስለመሆኑና አለመሆኑ በሕጉ በግልጽ ሊሰፍር ይገባ እንደነበረ የክርክሩ ይዘት ያስረዳል፡፡

ይሁን እንጂ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፌዴራል ጉዳይ ላይ ያለው የውክልና ሥልጣን ጠቅለል ባለመንገድ በሕገ - መንግሥቱ አንቀጽ 80/2/ ላይ ይቀመጥ እንጂ በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 80/2/ እና 80/5/ እንደቅደም ተከተሉ በመጀመሪያ ደረጃ በሚነሳ የክርክር ጉዳይ እንደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ ባለክርክር ደግሞ እንደ ፌዴራል ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ መመለከት እንደሚችል ዘርዘር ባለ ሁኔታ ያለው የውክልና ሥልጣን አይነት ተለይቶ ተቀምጧል፡፡

በመሆኑም የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፌዴራል ጉዳይ በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 80/2/ የተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን አሁንም ያልተነካና በዚህ መንገድ ታይቶ በሚሰጥ ውሣኔ ላይ ይግባኙ ለማን ይቀርባል የሚለውን ጥያቄ የአዋጅ ቁጥር 322/95 ጥቅል አነጋገር ጥያቄ የሚያስነሣ ቢሆንም፤ እንዲሁም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው የውክልና ሥልጣን በሁለት የክርክር እርከን ዓይነት ተለይቶ በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 80/2/ እና 80/5/ በግልጽ የተሰጠ እስከሆነ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተደራጀው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሥልጣን የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕገ- መንግሥቱ አንቀጽ 80/2/ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀርቡትን የፌዴራል ጉዳይ ክርክሮችን ተቀብለው እንዲያስተናግዱ ተሰጥቷቸው የነበረውን ሥልጣን የወሰደ፤ የተካ እንጂ ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በሕገ - መንግሥቱ አንቀጽ 80/5/ መሠረት በይግባኝ ያላቸውን ሥልጣን ሁሉ ያስቀረ አይደለም ብሎ ለመተርጎም የሚያበቁ በቂ መነሻዎች ናቸው፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በክልሎች የተደራጀ መሆኑ በአዋጁ በግልጽ እስከተደነገገ ድረስ በይግባኝ ደረጃ ያለውን ሥልጣን ሁሉ የሚጨምር ነው እንዳይባል ከአንድ የፌዴራል ጉዳይ የሚመነጭን የመጀመሪያ ደረጃ ክርክር በክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲታይ አድርጎ የይግባኙን ጉዳይ ለማከራከር በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/5/ መሠረት የውክልና ሥልጣን የተሰጠው መሆኑ እየታወቀ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትን ወደ ጎን ትቶ ወይም አስቀርቶ ይግባኙ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ ይገባል የሚለው መደምደሚያ ትርጉም አልባ ከመሆኑም በላይ የሕጎችን ዐውደ ንባብ ትርጓሜ ያልተከተለ፤ አዋጁ ውጤት እንዲኖረውና በአዎንታዊ መንገድ ታይቶ ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል የአተረጓጎም መንገድ ሆኖ አይገኝም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የአላባ ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት ተመልክቶ ውሣኔ በሰጠበት የፌዴራል ጉዳይ ላይ የአሁን አመልካች ቅሬታ ካለው የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከሚያቀርብ በቀር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ ለማየት የሚያስችለው ሥልጣን የለውም ሲል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 46679 በ04/5/2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰ/መ/ቁ. 46679 በ04/5.2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2/ የሰበር አመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 56118

ኅዳር 16 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኢት/ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ አቶ ዓለምሰገድ ፍትህአወቅ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ ወ/ማርያም በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአ/አበባ ከተማ ማኅበራዊ ፍ/ቤቶች አመልካች የኢትዮጵያ ኤሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ተከራካሪ የሆነበትን ጉዳይ ተመልክተው ለመወሰን የሚያስችል ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለውን ጭብጥ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ ለመተርጎም ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ የስልክ አገልግሎት ክፍያና የስልክ ቀፎ እንዲመለስለት አመልካች ክስ መሥርቷል፡፡ በክሱ የተካተተውም የገንዘብ መጠን ከብር 5000.00 በታች በመሆኑ ለአዲስ አበባ ከተማ ማኅበራዊ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ሁለቱንም ወገኖች ካከራከረ በኋላ የመጨረሻ ወርሃዊ ክፍያ ስለመፈፀሙ ደረሰኝ ከቀረበ ከዚህ ወር በፊት ላሉት አገልግሎቶች ተገቢው ክፍያ እንደተፈፀመ ይቆጠራል የሚለውን መሠረት አድርጎ ወስኖበታል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ በማጽናት ስላሰናበተው የሰበር አቤቱታውን ለአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡

ይኸው ሰበር ሰሚው ችሎትም ወደ ጉዳዩ ዘልቆ ከመግባቱ በፊት ክሱ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ቀርቦ ሊታይ የሚገባው ነው ወይስ አይደለም? የሚለው የሥልጣን ጉዳይ በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው ነጥብ መሆኑን ጠቅሶ የአሁን አመልካች በፌዴራል መንግሥቱ የተመዘገበ አካል ነው፡፡ ይህን መሰል ወገን ተከራካሪ የሆነበትን ጉዳይ ተመልክተው የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ ሥር ተመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም የፌዴራል የሆነውን ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ተመልክተው ለመወሰን ከሕግ የመነጨ ሥልጣን የላቸውም በማለት በየደረጃው የተሰጠውን ውሣኔ ሽሮ አሰናብቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ ከላይ የተጠቀሰው ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 361/95 ለማኅበራዊ ፍ/ቤቶች የተሰጣቸውን ሥልጣን ያገናዘበ አይደለም በሁለቱም አዋጆች ላይ ሥልጣንን በሚመለከት ግጭት አለ እንኳ ቢባል አግባብነት ያለውን አተረጓጎም ልንከተል ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ከዚህ ቅደም ተከተል አንፃር ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 361/95 እንጂ አዋጅ ቁጥር 25/59 አይደለም፡፡ ስለሆነም የሕግ ስህተቱ ይታረምልን በማለት ነው፡፡

እኛም በዚህ የሰበር ቅሬታ መነሻ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የፌዴራል ፍ/ቤቶች የወል የፍትሐብሔር ሥልጣንን በሚደነግገው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ መሠረት በጉዳዩ የተካተተው የገንዘብ መጠን ምንም ይሁን ምን በፌዴራል መንግሥቱ የተመዘገበ የንግድ ድርጅት ወይም ማኅበር ተከራካሪ የሆነበትን ማናቸውም ጉዳይ ተቀብለው ለማስተናገድ ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ ከሥልጣን ጋር በተያያዘ ሥራ ላይ የሚገኘው የሕግ ዘርፍ ይህ ብቻ ቢሆን ኖሮ ይህ ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር ሊወድቅ የሚቻል ስለመሆኑ ባላከራከረ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችን ለማደራጀት በወጣው አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50 ላይ ደግሞ ተከራካሪ ወገን ማንም ይሁን ማን እስከ ብር 500ዐ.00 ሊደርስ የሚችለውን የገንዘብ ክርክር ጉዳይ በአ/አበባ ከተማ ሥር እስከተነሣ ድረስ የአ/አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለመወሰን ሥልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ ከላይ ከፍ ሲል በአዋጅ ቁጥር 25/85 የተመለከተውን ድንጋጌ ከዚሁ አዋጅ ይዞታ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል፡፡ በሁለቱም አዋጆች መሠረት አሁን የቀረበውም ጉዳይ ለየትኛው የፍ/ቤት አደረጃጀት ሊቀርብ ይገባዋል? የጉዳዩ ባለቤት ማን ነው? የሚል ጥያቄ ከተነሣ አንድ ወጥ የሆነ ምላሽ አያገኝም፡፡ በሁለቱም ሕጎች መካከል ቅራኔ እንዳለ እንረዳለን፡፡ ይህም ከሆነ ጉዳዩን ተቀብሎ ለማስተናገድ ሥልጣን የሚኖረው በአንደኛው መስመር የተደራጀው ፍ/ቤት ሊሆን ስለሚገባው ይህንኑ ለይቶ ለመወሰን ተገቢውን የሕግ አተረጓጎም ዘዴ መከተል የግድ ይላል፡፡ ከእነዚህም የአተረጓጎም ዘዴዎች መከተል አንዱ አንድን ጉዳይ ይሸውም ክርክር ያስነሳውን ጉዳይ ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው የትኞቹ ፍ/ቤቶች ናቸው የሚለውን አስመልክቶ በእኩል ደረጃ በሚገኙ ሕጎች /አዋጆች/ በተለያዩ ሁኔታ ደንግገው ከተገኙ ከጊዜ ቅደም ተከተል አንፃር በኋላ የወጣው ሕግ ከፊተኛው በልጦ ተፈፃሚነት ይኖረዋል የሚለው የትርጉም መርህ በመሆኑ ጉዳዩ በአዋጁ ቁጥር 361/95 ሥር የሚታቀፍ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በተለይም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ ድንጋጌ መሠረት ይህን መሰል ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥር እንደሚወድቅ እየታወቀ ሕግ አውጪው ዘግይቶ ሥልጣንን የገንዘብ መጠን ወሰን አበጅቶ በሌላ አነስተኛ የፍርድ መድረክ ሥር ቀርቦ እንዲታይ ማድረጉ በክርክር ምክንያት የሚወጣው ወጪና የሚባክነው ጊዜ ክርክሮች ከያዙት የገንዘብ መጠን ጋር የተመጣጠነ ሊሆን እንደሚገባው ታሳቢ በማድረግ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ሥልጣን ቀንሶ ለመስጠት ሲባል የወጣ ሕግ መሆኑን ያመለክታል በተለይም ይህንኑ የትርጉም መስመር ይበልጥ የሚያጠናክረው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ተፈፃሚ ከሚሆንበት ከድሬደዋ ከተማ ጋር በተያያዘ የድሬዳዋ ከተማ ቻርተርን ለማቋቋም በወጣው በአዋጅ ቁጥር 416/96 አንቀጽ 41 ሥር ስለ ቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሲደነግግ ከተላላፊ የገንዘብ ሰነዶች እና ከኢንሹራንስ ጉዳይ በቀር ሌሎች ግምታቸው እስከ ብር 250ዐ.00 ድረስ ያሉትን ገንዘብ ነክ ክርክሮች ለማየት ሥልጣን ያላቸው የማኅበራዊ ፍ/ቤቶች ናቸው በማለት ከዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀድሞ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 ሥር የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን ለመለየት መነሻ ከሆኑት 10 ንዑስ ጉዳዮች መካከል ተላላፊ የገንዘብ ሰነድና የኢንሹራንስ ጉዳዮች ሊያስነሱ ከሚችሉት የተወሳሰበ የሕግ ጥያቄ አንፃር ሁለቱን ብቻ በመለየት የፌዴራል ሆነው እንዲቀሩ በሌሎች ጉዳዮች የሚነሳው ክርክር ግን ግምቱ እስከ ብር 2500.00 እስካልበለጠ ድረስ ከፌዴራል ፍ/ቤቶች ወጥተው በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ ማንበራዊ ፍ/ቤቶች እንዲታዩ መደረግ በገንዘቡ መጠን ትይዩ የሚታይበትን ፍ/ቤት እና የክርክር ደረጃ ለመለየት ሆን ተብሎ የወጣ ሕግ መሆኑን አስረጂ ነው፡፡

የአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50 ይዘት ከዚሁ ተለይቶ የሚታይ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም ከሥልጣን አደላደል አንፃር የሕግ ጥበቃ የተደረገለት የአሁን አመልካች ሥልጣን አለው በማለት በቀበሌ ማንበራዊ ፍ/ቤት የቀረበው ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች እንጂ በአ/አበባ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በሚል የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ትርጓሜ ሕጎቹ ከወጡበት ዘመን አንፃርም ሆነ የሕግ አውጪውን ሃሣብ ከመፈለግ አንፃር ሊሰጥ የሚገባውን የሕግ አተረጓጎም ዘይቤ ያልተከተለ ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 12124 በ12/6/2002 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ሽረናል፡፡
2. ክርክር ያስነሳው ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ከአዲስ አበባ የቀበሌ ማንበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን የሚጀምር ስለሆነ ከቀበሌ ማንበራዊ ፍ/ቤት ጀምሮ በየደረጃው የተሰጡትን ውሣኔዎች በማገናዘብ ለአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ መነሻ የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮ ተገቢውን ፍርድ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ወስነናል፡፡

በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ስላስለከተለው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 55299

መጋቢት 19 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ዓለም ገብሩ አልቀረቡም (ማ/ቤት ስለሆኑ)

ተጠሪ ፡- ትግራይ ዐቃቤ ህግ አልቀረቡም VC ስለማይሠራ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው የትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ስሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ስለቀረበ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለዞኑ ዐቃቤ ህግ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች ከሌሎች ግብረአበሮቹ ጋር በመሆን በወንጀል ህግ 32/3/ አንቀፅ 671 /1/ /ሀ/ /ሰ/ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት አስበው በቡድን የጦር መሣሪያ በመያዝ በህዳር ወር 2000ዓ.ም ከቀፍታ ወረዳ ሁመራ ወደ ሀገረ ኤርትራ በመሻገር ከሁለት ኤርትራውያን ሰባት መቶ ዶላር /700 ዶላር/ በመዝረፍ የዘረፉ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

በኢፌድሪ የወንጀል ህግ አንቀፃ 27/1/ 32/1/ /ሀ/ /ለ/ ከሌሎች ግብረአበሮቹ ጋር ቡድን በመፍጠር ትጥቅ ይዘው ከሁመራ ወደ ሀገረ ሱዳን ሐምዳይት ከሚባል ቦታ ለዘረፋ ከሄዱ በኃላ በሱዳን ወታደሮች ተኩስ ተከፍቶባቸው ስለሸሹ የመዝረፍ ሙከራ ወንጀል ፈፅሟል፡፡ ከ1994ዓ.ም እስከ 1999ዓ.ም ብዛቱ ያልታወቀ ማር ቅቤ በርበሬና ሽሮ ይዞ ከሁመራ በህገወጥ መንገድ ወደ ሱዳን ሐምዳይት የወሰዱ በመሆኑ በተደጋጋሚ የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀፅ 66/1/ን በመተላለፍ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅሟል፡፡ ይህንን ወንጀል በ2000ዓ.ም ዕቃዎችን በህገወጥ መንገድ ወደ ሱዳን በመወሰድ በህገወጥ መንገድ ኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅሟል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀፅ 481/1/ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ 1800 ጥይት በአራት ብር ከሀምሣ ሣንቲም ገዝቶ በአምስት ብር ሸጧል፡፡ ከሌሎች ጋር በመሆን ቁጥሩ 7862 የሆነ ሁለት እግሯ ከላሽን ጠመንጃ ደብቆ በማስቀመጡ ተከስሷል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡ አመልካች የወንጀሉን ድርጊት አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ዐቃቤ ህግ ከሳሽ መደበቁንና በሥር ስድስተኛ ተከሳሽ ከነበረው ሰው ቤት የተገኘ መሆኑን እናውቃለን የሚሉ፣ ምስክሮችንና አመልካች ለፖሊስ ቃሉን ሲሰጥ ሰምተናል የሚሉ ምስክሩችን በማቅረብ አስመስክሮአል አመልካች ለፖሊስ ቃል የሰጠሁት በተፅዕኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው በማለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከመዘነ በኃላ አመልካች የተከሰሰበትን አራት ወንጀሎች የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ብሎ በአሥር ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ፍርድ ሰጥቷል። አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል። ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል። አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት የሰበር ሥልጣን የለኝም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል።

አመልካች ሚያዚያ 4 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የወንጀል ክሱ የቀረበውን የታየው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን በሌለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው። ክሱ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መታየት ያለበት እና በክልል ደረጃ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መታየት ነበረበት። ስለዚህ በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት። ዐቃቤ ህግ በወንጀል ህግ አንቀፅ 18 /1/ሀ እና አንቀፅ 19/3/ የተቀመጡትን ሁኔታ ሣያሟላ ያቀረበውና ለፖሊስ በተፅዕኖ ከሰጠሁት የተከሳሽነት ቃል ውጭ ሌላ ማስረጃ ያላቀረበበት ሆኖ እያለ ጥፋተኛ ተብዬ የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል። ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 17 ቀን 2003ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ከኢትዮጵያ ግዛት ውጪ በፈፀመው ወንጀል በኢትዮጵያ ፍርድ ቤትም መከሰሱም ሆነ ጥፍተኛ ተብሎ መቀጣቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ጥፋተኛ ከተባለባቸው አራት ወንጀሎች መካከል አንደኛው ወንጀል በኤርትራ ግዛት ክልል ውስጥ ገብቶ ሰባት መቶ የአሜሪካን ዶላር ከሁለት ኤርትራዊያን ዘርፏል የሚል ሲሆን ሁለተኛው በሱዳን ግዛት ክልል ሐምዳይት ከተባለ ቦታ መሣሪያ ታጥቆ ከግብረአበሮቹ ጋር በመሄድ የዘረፋ ወንጀል ለመፈፀም ሲሞክር በሱዳን መከላከያ ሀይል ተኩስ ተከፍቶበት የተመለሰ በመሆኑ የዘረፋ ወንጀል ለመፈፀም ሞክሯል የሚል ነው። እነዚህ ሁለት ወንጀሎች በኢትዮጵያ ግዛት ክልል ውስጥ ወይም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዜጋ ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች አይደሉም። እነዚህ ሁለት ወንጀሎች የሱዳን ግዛት ክልልና በሱዳናዊ ዜጎች ላይ የተፈፀመ የዘረፋ ሙከራ ወንጀልና በኤርትራ ግዛት ክልል ውስጥ በኤርትራዊያን ላይ የተፈፀመ የዘረፋ ወንጀሎች መሆናቸውን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል። እነዚህ ወንጀሎች አመልካችና ግብርአበሮቹ የሌላውን ሉዓላዊ መንግስት የግዛት ክልል በመጣስ የተፈፀሙ መሆኑን የወንጀል ህጉን አንቀፅ 263 እና አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የወንጀል ህግ አንቀፅ 71 በጣምራ በማየት ለመረዳት ይችላል።

በአዋጅ ቁጥር 25/1988 በውጭ አገር መንግስት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት የዳኝነት ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን ከአዋጁ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 1 እና የአዋጁን አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 2 በጣምራ በማየት ለመገንዘብ ይችላል። በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሆነ በግልጽ ይደነግጋል። ይህም የትግራይ ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በኤርትራ ግዛት ክልልና በሱዳን ግዛት ክልል ፈፅሟቸዋል የተባሉ የወንጀል ክሶችን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ነው። ከቀረቡለት ክሶች ሁለቱን የወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሶች የማየት የዳኝነት ስልጣል የሌለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ህግ በጉዳዩ የመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን በህገ መንግስቱ በተሰጠው በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 110 መሠረት ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው ጉዳዩን ለማት የዳኝነት ሥልጣን ሣይኖረው የቀረበለትን የወንጀል ክስ በማየት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ሥልጣን ሣይኖረው ጉዳዩን በማየት በአመልካች ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በይግባኝ ሣያርምና ሣያስተካክል ማዕናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ፍርድ ተሽሯል፡፡

2. ይህ ውሣኔ ዐቃቤ ህግ የዳኝነት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት የወንጀል ክሱን ከማቅረብ የሚገድበው አይደለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አቤቱታ ምርመራና ክስ አቀራረብ ንዑስ ሥራ ሒደት

ተጠሪዎች ፡-

1. ወ/ሪት ፍሬህይወት ፍቃዱ
2. ወ/ሮ ሰላም ጥላሁን
3. አቶ ረዘነ ብሥራት
4. አቶ እስራኤል ቶላ
5. ወ/ሪት አጃኤባ አህመድ
6. ወ/ሪት ትዕግስት ጌትነት
7. ወ/ሪት ሰላማዊት ስዩም
8. አቶ ታደሰ ግርማ - ጠበቃ ፍሬው ካሣሁን ቀረቡ
9. ወ/ሪት ዘበናይ ተሻገር
10. ወ/ሪት ሰሚራ ጀማል
11. ወ/ሪት ሀይማኖት ዓለሙ
12. አቶ አብርሀም ታደሰ

አመልካች በመዝገብ ቁጥር 56893 ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ አስረኛው ተራ ቁጥር በተጠቀሰው ተጠሪዎች ላይ የቀረበው የሰበር አቤቱታና የተደረገውን ክርክር አመልካች በመዝገብ ቁጥር 56894 ስማቸው ከአስራ አንደኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ተራ ቁጥር ከተጠቀሰው ተጠሪዎች ጋር ካደረገው ክርክር ጋር በማጣመር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 10 የተጠቀሱት ተጠሪዎች በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 13165 ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ በመመርመር የሰጠው ውሣኔና ስማቸው አስራ አንደኛና አሥራ ሁለተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 13138 ያቀረቡትን ይግባኝ በመመርመር የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በሁለት መዛግብት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበው አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት ስለቀረበ ነው።

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው። በሥር ፍርድ ቤት አመልካች በሁሉም ተጠሪዎች ላይ መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም. ዕፎ የወንጀል ክስ አቅርቧል። የአመልካች የወንጀል ክስ ይዘትም ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 4 የተጠቀሱት ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 28/1/ለ አንቀፅ 33 እና አንቀፅ 46/3/ መጋቢት 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በተደረገው ፍተሻ ጫት ሲያስቅሙና ሺሻ ሲያስጨሱ ከነሺሻ ዕቃው የተገኙ በመሆኑ ከተፈቀደላቸው ንግድ ፈቃድ ውጭ የመነገድ ሕግ የመጣስ ተግባር ፈፅመዋል። ስማቸው ከተራ ቁጥር 5 እስከ ተራ ቁጥር 12 የተጠቀሱት ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀፅ 21(1) እና አንቀፅ 46(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ጫት በማስቃምና ሺሻ በማስጨስ ገንዘብ እየሰበሰቡ የተገኙ በመሆኑ ያለንግድ ፈቃድ በመነገድ የህግ መጣስ ተግባር ፈፅመዋል የሚል ይዘት ያለው ነው። ተጠሪዎች ጥፋተኝነታቸውን ያመኑ በመሆኑ የአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተከሰሱበትን ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል። የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በተናጠል ያላቸውን የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ እያንዳንዱን ተጠሪ ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ ነው በሚለው በአስራትና በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል።

ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 10 የተጠቀሱት ተጠሪዎች የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የይግባኝ መዝገብ ቁጥር 13165 ያቀረቡ ሲሆን አስራአንደኛና አሥራሁለተኛ ተጠሪ ይግባኛቸውን በመዝገብ ቁጥር 13138 አቅርበዋል። የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሁለቱ መዝገቦች ተጠሪዎችና አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 67/89 የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን አስመልክቶ የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳይ የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 67/89 ሆነ በሌላ ህግ አልተሰጣቸውም። ስለሆነም የወንጀል ክሱ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል። አመልካች የሰበር አቤቱታውን በሁለት መዛግብት ለአዲስ አበባ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን የከተማው ሰበር ችሎት የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት የሌለበት መሆኑን በመግለፅ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል።

አመልካች በተጣመሩት መዛግብት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 41(2)ሀ የከተማው ፍርድ ቤቶች የፋይናንስ መሰል ድርጊቶች ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት ሥልጣን እንዳላቸው ደንግጓል። ይህ ድንጋጌ የአዲስ አበባ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ህግን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማስከበርና የመቆጣጠር ሥራ በሚሠሩበት ጊዜ ያጋጠማቸውን የህግ ጥሰት በከተማው ፍርድ ቤቶች ክስ አቅርቦ ለማስቀጣት በሚችሉበት መንገድ መተርጎም ይገባዋል፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አንደኛ ሶስተኛና ስምንተኛ ተጠሪዎችና አስራ አንደኛና አሥራ ሁለተኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ አዋጅ ቁጥር 67/89ን በመተላለፍ የተፈፀመ የወንጀል ጉዳይ የማየት ሥልጣን የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች አይደለም፡፡ በህግ በግልፅ ባልተደነገገ ወንጀል መክሰሳችንም ሆነ ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን የህጋዊነት መርህን የሚጥስ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የሰበር ችሎቱ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሌሎቹ ተጠሪዎች በሌሉበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡ አመልካች በህግ ረገድ ያለውን ክፍተት የሰበር ችሎት ህጉን በመተርጎም ተገቢውን ማስተካከያ ሊያደርግ ይገባዋል የሚል ይዘት ያለው የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የዕሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በተጠሪዎች ተፈፀመ የተባለውን ወንጀል ለማየትና ለመወሰን የሚያስችል የዳኝነት ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን ጭብጥ ለመወሰን የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣንን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 41 ንኡስ አንቀጽ 2 የከተማው የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን በአዋጅ አንቀጽ 52 በተመለከቱት የፋይናንስ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ወንጀሎችን አይተው እንደሚወስኑ የሚደነግግ ሆኖ አግኝተዋል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የተከሰሱበት ጉዳይ የደንብ መተላለፍ ተግባር እንደሆነ በማድረግ የሚከራከር ቢሆንም አዋጅ ቁጥር 67/89 የተደነገጉ የወንጀል ሃላፊነት የሚያስከትሉ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሞ መገኘት እንደወንጀሉ ክብደት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ እስራትና በገንዘብ መቀጮ የሚያስቀጣ መሆኑ የአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 46 ድንጋጌዎችን በማየት ለመገንዘብ የሚቻል በመሆኑ አመልካች ተጠሪዎች የተከሰሱት በደንብ በመተላለፍ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ህጋዊ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪዎች የተከሰሱትና በሥር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብለው የቅጣት ውሣኔ የተወሰነባቸው በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በአዋጅ አንቀጽ 52 በተመለከቱት በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ጉዳዮች የሚመለከቱ ወንጀሎችን ፈፅመዋል ተብለው እንዳልሆነ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ ይዘትና የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ከሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪዎች የተከሰሱትም ሆነ በሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የተሰጠባቸው በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 46 እና ሌሎች ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅመዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 67/89ን በመተላለፍ የተፈጸሙ ወንጀሎች የማየትና ዳኝነት ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 67/89 እና በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 አልተሰጣቸውም፡፡ ህግ አውጭው የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች የዳኝነት ሥልጣን እንዲኖራቸው ሀሣብና ፍላጐቱ ቢኖረው ኖሮ ጉዳዩን የማከራከርና የመወሰን ሥልጣን ያላቸው መሆኑን በህግ ማዕቀፎቹ በግልፅ በመደንገግ የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቶች ናቸው ብሎ ግልፅ ያደርገው ነበር፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዋጅ ቁጥር 67/89ን በመተላለፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት የዳኝነት ሥልጣን ለአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ያልተሰጣቸው ሆኖ እያለ አመልካች ይህ የሰበር ችሎት በትርጉም የዳኝነት ሥልጣን ለአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ነው ብሎ እንዲወሰንለት ያቀረበው አቤቱታ የህግ አተረጓጎም መርህን የሚጥስና ህግ ከውጭው አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 የደነገገበትን መሠረታዊ ዓላማ የማያሟላ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እና የከተማው ሰበር ችሎት የከተማው ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 67/89ን በመተላለፍ የተፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የላቸውም በማለት የወንጀል ክሱ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 110ን መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና የከተማው የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ተጠሪዎች ፈፅመውታል የሚለውን ወንጀል የማየት የዳኝነት ሥልጣን ላለው አካል የወንጀል ክሱ እንዲቀርብ ከማድረግ ይኼ ውሣኔ አያግደውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 64703

ሐምሌ 29 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ሻምበል ለታይ ገ/መስቀል - ጠበቃ ሣህሉ ሀብቴ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የወረዳ 1 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ቴዎድሮስ ጸሀዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14640 ታህሳስ 14 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይሻርልኝ በማለት ጥር 05 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች በማቅረባቸው ነው፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ አመልካች ነሀሴ 12 ቀን 2002 ዓ/ም ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፅፈው ያቀረቡት ክስ ሲሆን ይዘቱም ተጠሪ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 067 የሆነውን ቤት በወር ኪራይ እየከፈልን በመኖር ላይ እንዳለን ከቀድሞ ባለቤቱ ጋር አብሮ መኖር ስላልቻልን በመ/ቁጥር 142006 በሆነው ሚያዚያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጋብቻችን እንዲፈርስ ውሳኔ ተሰጥቷል ፣ እንዲሁም ከፍቺው በኋላ የወለድናቸውን ልጆች ለማሳደግ የሞግዚትነት ስልጣን የተሰጠኝ በመሆኑ በባለቤቴ ስም ተመዝግቦ የነበረውን የመንግስት ቤት ኪራይ ተጠቃሚነት በስሜ ዞሮ እንድጠቀምበት ከፍቺው ጋር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሠጠ በመሆኑ የፍርድ ቤቱን የውሳኔ ግልባጭ ለተጠሪ በማድረስ የስም ዝውውሩን በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ የኮንዶሚኒየም ቤት ከቀድሞ ባለቤትሽ ጋር የደረሰሽ በመሆኑ ቤቱን እንድትለቂ የሚል ማስጠንቀቂያ በተጠሪ የተሰጣቸው መሆኑንና ለባለቤታቸው የኮንዶሚኒየም ቤት የደረሳቸው መሆኑን ከፍቺው በሁዋላ የተረዱ መሆኑን ገልፀው በተጠሪ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድላቸው ፣ የቤቱ የኪራይ ስምም እንዲዞርላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም የመንግስት ቤት ኪራይ ተጠቃሚነትን የኮንዶሚኒየም ቤት በባለቤታቸው ስም ትዳር ፅንቶ ባለበት ጊዜ ደርሶአቸው እያለ ሊጠይቁ እንደማይገባ ገልፆ ተግባሩ ሁከት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለተከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን መርምሮ የአመልካች ተግባር እንደሁከት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተግባር ሊቆጠር የሚችል አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጓል። በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የአመልካች ተግባር ሁከት ነው ተብሎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል። ከዚህም በኋላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል። የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የኮንዶሚኒየም ቤት ለቀድሞ ባለቤታቸው መድረሱን ያወቁት ከፍቺው በኋላ ሁኖ እያለ ኮንዲሚኒየም መድረሱን በመገናኛ ብዙሃን በግልጽ የእጣ አወጣጥ ስነ ስርዓት የተደረገና በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ለሕዝብ ይፋ የሆነ ጉዳይ በመሆኑ የሕግ ግምት የሚወሰድበት ጉዳይ ነው ተብሎ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ግራ ቀኙ በጽሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በክሱ የጠየቁት ዳኝነት የተከራይነት ስም እንዲዞርላቸው የሚመለከት ብቻ ሳይሆን የተጠሪ ማስጠንቀቂያ መስጠት የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊወገድ ይገባል የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ጭምር ነው። የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የሰበር ሰሚ ችሎትም የተጠሪ ተግባር ሁከት ነው በማለት ዳኝነት ሰጥተዋል።

ተጠሪ ደግሞ ቤቱን ለማስለቀቅ ለአመልካች የሰጠው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ተከራክሯል። ከዚህ አንፃር ስንመረምረው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ስልጣንና ሐላፊነት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በአንቀጽ 41 የተዘረዘረ ሲሆን የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ንብረትነቱ የከተማው አስተዳደር የሆነ ቤት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን እንዳለው በአዋጅ አንቀጽ 41(1)(ረ) በግልጽ ተደንግጓል። ከዚህም የምንረዳው የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማው አስተዳደር ለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ ፣ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው።

ሆኖም ክርክር የተነሳበት ቤት የከተማው አስተዳደር ነው? ወይስ የሌላ ግለሰብ? ወይም ድርጅት? የሚል መሰረታዊ ክርክር ያለበት ከሆነ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ይህንን የቤት ባለቤትነት ጥያቄ አስመልክቶ በከተማው አስተዳደርና በሌሎች ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በዳኝነት አይተው ለመወሰን የሚያስችል የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 (1) (ረ) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል። በያዝነው ጉዳይ የቤቱን ሕጋዊ ባለቤትነት አስመልክቶ በአመልካች በኩል ክርክር የቀረበበት ሳይሆን የተጠሪን ባለቤትነትን በማመን በቤቱ ላይ የተከራይነት መብታቸው እንዲረጋገጥላቸው በፍርድ ቤት ውሳኔ ተሰጥቶ እያለ አመልካች ለተጠሪ በትዳር ጊዜ የኮንዶሚኒየም ቤት በባል ስም ደርሷቸዋል ተብሎ ቤቱን እንዲለቁ የተሰጣቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊወገድ ይገባል በማለት በመሆኑ የጉዳዩ መሰረታዊ ጭብጥም የተጠሪ ተግባር ሁከት ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ የቤት ይዞታ አይደለም እንጂ ነው ቢባል እንኳ የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የቤት ይዞታ ክርክርን በተመለከተ የዳኝነት ስልጣን በሕጉ የተሰጣቸው ሁከት ይወገድልኝ በሚል የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄን መሰረት ባደረገ መልኩ ሲቀርብ አይደለም፡፡ የቦታ ይዞታ ክርክርን በተመለከተም የዳኝነት ሥልጣን ለፍርድ ቤቶቹ በሕጉ የተሰጠው ከከተማው መሪ ፕላን አፈፃጸም ጋር በተያያዘ እንደሆነ አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41((ሀ)) ይይደነግጋል ፣ እንዲሁም በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 18552 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1)መሰረት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ስለሆነም የሁከት ይወገድልኝ ክስ ከከተማው መሪ ፕላን ጋር እስካልተያያዘ ድረስ በከተማው ፍርድ ቤቶች የስነ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከማየቱ በፊት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም በማናቸውም የክርክር ደረጃ ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሳው የሚገባው ጉዳይ መሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 (1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን በሌለው ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ደግሞ በመርህ ደረጃ እንዳልተሰጠ የሚቆጠር ነው፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ሣይኖራቸው ጉዳዩን ሰምተውና አከራክረው የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 07101 መስከረም 05 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14292 ጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14640 ታህሳስ 14 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖራቸው የተሰጡ ውሳኔዎች በመሆናቸው ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄን ሥልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይም አካል አቅርበው ተገቢውን ዳኝነት የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሣኔ አይገድብባቸውም ብለናል፡፡
3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- አቶ ትዕዛዙ አርጋው - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ ም/ቤት - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች ለሥር የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የአሁኑ ተጠሪ /የሥር ተከሳሽ/ በሕገ ወጥ መንገድ ከሥራዬ በማገዱ ምክንያት ያልከተፈለኝ ውዝፍ ደመወዝ ብር 114,788 እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

የሥር ተከሳሽም በዋናነት ሁለት መቃወሚያዎችን አቅርቧል፡፡ መቃወሚያዎቹም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የለውም፣ የከሳሽ ክስ በይርጋ ይቋረጣል የሚሉ ናቸው፡፡

የሥር ፍ/ቤት ተከሳሽ ያቀረቧአቸውን የመቃወሚያ ነጥቦች ከመረመረ በኋላ ከሳሽ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኛ በመሆናቸው በክልሉ የሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ቁጥር 29/95 አንቀጽ 71 መሠረት ክሱ መቅረብ ያለበት ለአስተዳደር ፍ/ቤት እንጂ ለመደበኛ ፍ/ቤት ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም ሲል የከሳሹን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡፡

የሥር ከሳሽም ለክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩን ያቀረቡ ሲሆን የአስተዳደር ፍ/ቤቱ በአስተዳደር መ/ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ የተሰጠ ውሣኔ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከፀደቀ በኋላ በይግባኝ የሚቀርቡ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን ያለው ሲሆን የይግባኝ ባይ ቅሬታም ይኸንኑ ሥነ ሥርዓት ሳይጠብቅና በአሰሪው መ/ቤት የተሰጠ የዲስፕሊን ኮሚቴ ውሣኔ በሌለበት በ3ኛ ወገን /በክልሉ ም/ቤት/ ውሣኔ ከሥራ የተሰናበቱ በመሆናቸው የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት ክሱን ሳይቀበል ቀርቷል፡፡

የአሁን አመልካችም በክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት በተሰጠ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም መልስ ሰጪውን መጥራት ሳይስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡ የአሁኑ አመልካችም በሥር የአስተዳደር ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ችሎት ብይን ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የሰበር አቤቱታቸውን ለሥር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ብይን አጽንቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም በሥር የአስተዳደር ፍ/ቤትና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ብይንና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በሚል ሲሆን በዋናነት የጠቀሱትም የቅሬታ ነጥብ፣ ተጠሪው አመልካችን ከሥራ አግዶ ካቆየ በኋላ ማሰናበቱ አግባብ ባለመሆኑ ጉዳዩን አከራክሮ እንዲወስኑ በሚል ለአስተዳደር ፍ/ቤትም ሆነ መደበኛ ፍ/ቤቶች ክስ ባቀርብም አለመቀበላቸው አመልካች ፍትሕ እንዳላገኝ የሚያደርግ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች የክልሉ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ሆነው በሹመት በሚሰሩበት ወቅት በታማኝነት ማገልገል ሲገባቸው በፀረ ልማትና አፍራሽ በሆኑ ተግባራት ላይ ተሰማርተው በመገኘታቸው በተሰጠው የፖለቲካና የአስተዳደር ውሣኔ ከሥራቸው እንዲሰናበቱ የተደረገው በአግባቡ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገው ክርክር ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም በሥር የአስተዳደር ፍ/ቤት ብይንም ሆነ በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች ብይንና ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ? ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከቀረበው ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ቀደም ሲል የመንግስት ሠራተኛ በመሆናቸው በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት የሚተዳደሩ ቢሆንም የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ተመርጠው በተሰጣቸው ሹመት መሠረት የክልሉ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ በመሆን እየሰሩ ፈጽመዋል በተባሉት ፀረ ልማትና አፍራሽ ተልዕኮ ከሥልጣናቸው ወይም ከሹመታቸው የሾሟቸው አካል አንስቶአቸዋል፡፡

ይህ በመሆኑ ቀደም ሲል ሲሰሩበት ከነበረው የመንግስት መ/ቤት ለቀው በተሰጣቸው ሹመት ላይ እያሉ በተወሰደባቸው የፖለቲካ እርምጃና የአስተዳደር ውሣኔ ከሥራቸው በመነሳታቸው ጉዳይ በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት ሊታይ የሚገባ መሆን አለመሆኑን መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

በክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሠረት ለአስተዳደር ፍ/ቤት በይግባኝ የሚቀርበው ጉዳይ አስቀድሞ መታየት ያለበት ሰራተኛው በሚሰራበት የመንግስት መ/ቤት ውስጥ በተቋቋመው የዲስፕሊን ኮሚቴ ነው፡፡ አመልካች ግን ከፍ ተብሎ እንደተገለፀው የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ በመሆናቸው በሥራቸው ያሉ የመንግስት ሠራተኞች የዲስፕሊን ግድፈት ሲፈጽሙ የመ/ቤቱ የዲስፕሊን ኮሚቴ ውሣኔን ሊያፀድቁ ሊያሻሽሉ ወይም ውድቅ በማድረግ እንደገና እንዲታይ የማድረግ ሥልጣን ያላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ራሳቸውን እንደ ሠራተኛ በመቁጠር የፖለቲካ ውሣኔን ለአስተዳደር ፍ/ቤት የሚያቀርቡበትና ጉዳያቸውን በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ እንዲታይ የሚጠይቁበት ሁኔታ የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል ተጠያቂነት አንዱ የመልካም አስተዳደር ማዕቀፍ ሲሆን በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ሕገ መንግስት አንቀፅ 12/2/ ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን በግልጽ የተደነገገ ሲሆን ተጠያቂነቱ ለሕግ እና ለመረጠው ሕዝብ ጭምር ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ አመልካች የቢሮው ኃላፊ በነበሩበት ወቅት ፈጽመዋል ለተባሉት ድርጊቶች የሕዝብ ውክልና ያለው የክልሉ ም/ቤት ከሥልጣናቸው ወይም ከሹመታቸው አንስቷል፡፡ ይህን የፖለቲካ ውሣኔ አመልካች በፍ/ቤት ለማስለወጥ ማቅረባቸው ያለአግባብ ሲሆን የፖለቲካ ውሣኔዎችን /political actions/ ፍ/ቤቶች ተቀብለው አከራክረው ተገቢውን ፍርድ ለመስጠት የዳኝነት ሥልጣንም አይኖራቸውም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የለንም ሲሉ በሰጡት ብይንም ሆነ ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የክልሉ የአስተዳደር ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ/አስ/ፍ/ቤት 17/02/2001 በቀን 30/04/2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01721 በቀን 19/05/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01732 በቀን 30/03/2003 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረቡትን ክስ ለማየት የዳኝነት ሥልጣን የለንም ሲሉ የወሰኑት በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሼህ አሸራቅ ሰይድ - ጠበቃ ዝኑር አብዱልወሀብ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የቡታጅራ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር - አበበ ነጋሽ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል የጉራጌ ዞን የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔውን እንዲያስፈፅምለት የሰጠው ውክልና ነው፡፡ ኤጀንሲው ሕዳር 17 ቀን 2002 ዓ.ም በተባለና ቁጥር 05/1506/88/8402/2002 በሆነ ደብዳቤ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 371 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አማካኝነት እንዲፈፀም ስለመጠየቅ የሚል ርዕስ ያለውና በይዙቱም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በጉራጌ ዞን ቡታጅራ ከተማ ልዩ ከፍተኛ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 112 የሆነ መኖሪያ ቤት ከሼህ አሸራቅ ሰይድ ከአዋጅ ውጭ የተወሰደባቸው በመሆኑ እንዲመለስላቸው መስከረም 7 ቀን 2002 ዓ.ም በቁጥር 05/1506/339/2000 የተሰጠውን ውሣኔ ለሚመለከታቸው አካላት አሳውቀናል፡፡ ሆኖም በኤጀንሲው ውሣኔ መሠረት ያልተፈፀመላቸው መሆኑን ባለጉዳዩ ካቀረቡት ማመልከቻ ስለተረዳን በአዋጅ ቁጥር 146/9/ እና አዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ውሣኔያችንን ፍ/ቤቱ እንዲያስፈፅምልን የሚል መሆኑን የሥር ፍ/ቤቱ በውሣኔው አስፍሮታል፡፡ ከዚህ ደብዳቤ ጋር ኤጀንሲው ቤቱ እንዲመለስ የሰጠውን የውሣኔ ግልባጭ እንደላከ ከገለፀ በኋላ ተጠሪ በመቃወሙ ኤጀንሲው በቡታጅራ አካባቢ ፍ/ቤት ውሣኔውን እንዲያስፈፅምለት የሰጠው ውክልና ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው የሚላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ከዘረዘሩና ከተረጐሙ በኋላ የኤጀንሲውን ውሣኔ የማስፈፀም ሥልጣን ያለው የሚኒስቴሮች ምክር ቤትና ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንጂ ፍርድ ቤት የኤጀንሲውን ውሣኔ የማስፈፀም ሥልጣን የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲያይላቸው አመልካች አመልክተው ይግባኛቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች ለክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል፡፡

አመልካች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 371 በሰጣቸው ውክልና መሠረት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ በውሣኔው መሠረት የማይፈፀምበትን ምክንያት በመጠየቅ ውሣኔውን ማስፈፀም ወይም ሌላ ተገቢ ነው የሚለውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው በአዋጅ ቁጥር 146/9 እና በአዋጅ ቁጥር 110/87 ድንጋጌዎች የተዛባ ትርጉም በመስጠት ሥልጣኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩ እንጂ የፍርድ ቤት አይደለም በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማፅናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ፍርድ ቤት ግለሰቦችን እንጂ የአስተዳደር አካላትን በአፈፃፀም የማስገደድ እና የኤጀንሲውን ውሣኔ እንዲያስፈፅም እንዲያደርግ ኤጀንሲውን መወከል አይችልም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ሥልጣን የለንም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በሰጠው የአፈፃፀም ውክልና መሠረት የኤጀንሲውን ውሣኔ የማስፈፀም ሥልጣን ፍርድ ቤቱ የለውም በማለት የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረታዊ ባህርይ መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የኤጀንሲው ሥልጣንና ኃላፊነት በተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች የተዘረዘረ ሲሆን በያዝነው ጉዳይ አግባብነት ባለው አዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 4/ሐ/ ከአዋጅ ውጭ የተወሰደን ንብረት ባለቤትነት በተመለከተ ከቀረቡት ጥያቄዎች መረጃዎችን እያጣራ ተገቢውን ውሣኔ እንደሚሰጥና ውሣኔውም እንዲፈፀም አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወስድ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አዋጅና የሕግ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ንብረት ከአዋጅ ውጭ የተወሰደ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጉዳይ የማጣራት ማስረጃ የማሰባሰብና የመመዘን ንብረቱ ከአዋጅ ውጭ የተወሰደ ነው ብሎ ሲያምን ለባለቤቱ እንዲመለስ የመወሰን ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 110/87 ለኤጀንሲው የተሰጠው መሆኑን ነው፡፡ ይህ በሕግ ለኤጀንሲው የተሰጠው ሥልጣን ተራ ሕግ የማስፈፀም ሥልጣን አይደለም፡፡ ለኤንጀሲው በዚህ አዋጅ የተሰጠው ሥልጣን ይህን ልዩ ጉዳይ በማየትና በማስረጃ በማጣራት ውሣኔ የመስጠት ወይም የዳኝነት ሥልጣን ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ አንድ ሰው በፍርድ የሚያልቅ ጉዳይ በፍ/ቤቱ ወይም በሌላ የዳኝነት ሥልጣን በሕግ ለተሰጠው አካል አቅርቦ የማስወሰን እና ፍትሕ የማግኘት መብት እንዳለው አንቀጽ 37 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ኤጀንሲው ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ አከራክሮና አጣርቶ የመወሰን ሥልጣን በሕግ ተሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም ኤጀንሲው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ አገላለፅ ከፍ/ቤት ውጭ ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ አከራክሮ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን በሕግ የተሰጠው የመንግስት አካል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ከአዋጅ ውጭ የተወሰደ ንብረት ለባለቤቱ እንዲመለስ የመወሰን ብቻ ሳይሆን ውሣኔውንም ለማስፈፀም አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 74/ሐ/ ተሰጥቶታል፡፡ በፍርድ ቤት ወይም በሕግ ዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል የተሰጠው ውሣኔ የሚፈፀመው ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት /ወይም/ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም እንደ ፍርዱ እንዲያስፈፅም በታዘዘው ፍርድ ቤት እንደሆነ ከፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 371 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማናቸውም የመንግስት ተቋም ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 110/87 የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል ተገቢውን ትብብር የማድረግ ግዴታ ያለበት መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 7 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 146/1991 አንቀፅ 26 /2/ ፍርድ ቤቶች ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን ለባለቤታቸው እንዲመለሱ ኤጀንሲው የሰጠውን ውሣኔ የማስፈፀምና በንብረቱ ላይ ያለውን ባለይዞታ እንዲለቅ ለመወሰን እንደሚችሉ ነገር ግን ይዞታው ወይም ንብረቱ የእኔ ነው ወይም በህግ መሰረት የተወሰደ ነው የሚል መቃወሚያ ቢቀርብላቸው ሊያስተናግዱ እና አከራክረው ሊወስኑ እንደማይችሉ ይደነግጋል፡፡ በሌላ አነጋገር የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 87 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማን በሚያሳካ መንገድ የአዋጅ ቁጥር 110/87 እና የአዋጅ ቁጥር 146/91 አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች መተርጎምና ስራ ላይ መዋል ያለባቸው ሲሆን ፍርድን ስለማስፈፀምና ፍርድ እንዲፈፀም ውክልና ስለመስጠት ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 371 ጀምሮ ያሉት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 እና የሥነ ሥርዓት ሕጉ ከታወጁ በኋላ የወጡ ልዩ የህግ ማዕቀፎች አዋጅ ቁጥር 110/87 እና 146/91 ለማስፈፀም በሚያግዝ መልኩ መተርጎምና ሥራ ላይ መዋል ይገባቸዋል፡፡

2. ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይቬሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አከራካሪው ቤት አመልካች ከአዋጅ ውጪ የተወሰደባቸው መሆኑን በማጣራት ቤቱ ለአመልካች እንዲመለስ የወሰነበትን የውሳኔ ግልባጭ በማያያዝ፣ ውሳኔውን እንዲያስፈፅምለት ለቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ህዳር 17 ቀን 2002 በተፃፈ ደብዳቤ ውክልና ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በስህተት ነው ቤቱ የተመለሰው የሚል መቃወሚያ ማቅረቡንና የመንግስት አካላት የኤጀንሲው ውሳኔ ከደረሳቸው በኋላ አለመፈፀማቸውን መነሻ በማድረግ የኤጀንሲውን ውሳኔ የማስፈፀም ሥልጣን የለኝም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

በመሰረቱ ተጠሪ የኤጀንሲው ውሳኔ የተሳሳተ ነው ወይም በተሳሳተ ማስረጃ መሠረት የተሰጠ ነው ካለ የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 6 በሚደነግገው መሠረት አቤቱታውን ውሳኔውን ለሰጠው ኤጀንሲ አቅርቦ ከሚያሳርም በስተቀር አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት መቃወሚያ መቅረብ የማይችል መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 146/91 አንቀፅ 28(2) ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል መንግስት በህግ በኩል እንደ አንድ ሰው የሚቆጠር መሆኑና በክልል በዞንና በወረዳና በከተማ አስተዳዳሮችና በገጠር ቀበሌዎች ያሉ የመንግስት አካላት ከተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ጋር የሚስማሙ መብቶች ያሏቸውን ግዴታዎች ያሉባቸው መሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 394 እና 395 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ስለሆነም የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪም ሆነ ሌላ በዞኑ የሚገኝ የመንግስት አካል በኤጀንሲው ውሳኔ መሠረት የማይፈፅመበትን ህጋዊ ምክንያት በመስማት ተገቢውን ትዕዛዝ የመስጠት ስልጣን እያለው በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 የተደነገገውን ፍትህ የማግኘት መብት፣ ከአዋጅ ቁጥር 146/9/ አንቀፅ 28/2 እና ከአዋጅ ቁጥር 110/87

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደዚሁም አግባብነት ያላቸው የስነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ለማስፈፀም የሚያስችል ሥልጣን እንደሌለው አድርጎ የሰጠው ትርጉምና ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ማፅናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጉራጌ ዞን ቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

2. የጉራጌ ዞን የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ ፕራይቬታዜሽንና የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲን ውሳኔ የማስፈፀም የዳኝነት ሥልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡

3. የጉራጌ ዞን ቡታጅራ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በማሰማት ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59723

ሰኔ 16 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አብዱልፈታህ መሐመድ - ጠበቃ ጥበቡ ተስፋዬ - ቀረበ

ተጠሪ፡- ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፍትሕ ጽ/ቤት የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በገቢ ግብር አዋጅ ቁ 286/94 አንቀጽ 96 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ 285/94 አንቀጽ 49 እንደዚሁም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 349/1/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ተፈጽሞአል በማለት ተጠሪ ባቀረበው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሣሽ የነበረውን የአሁኑ አመልካችን ጥፋተኛ ነው ብሎአል፡፡ በዚህ መሠረትም በአመልካች ላይ ተገቢ ነው ያለውን ቅጣት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቅጣቱ አወሳሰን ላይ ባለመስማማት ተጠሪ ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ችሎቱ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን የቅጣት ውሣኔ በመሻር አመልካች በስድስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ነሐሴ 24 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ የሚቀርቡ የወንጀል ክሶችን ለማየት ሥልጣን አላቸው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጭብጥ ግራ ቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር ፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው አመልካች የተከሰሰው በሁለት የተለያዩ አዋጆች የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ ነው፡፡ አዋጆቹ የተለያየ ስያሜ እና ተግባር ያላቸው ሲሆኑ ፣ የመጀመሪያው የገቢ ግብር አዋጅ ፤ ሁለተኛው ደግሞ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ናቸው፡፡ የዳኝነት ሥልጣን ጥያቄ ያስነሳው የተጨማሪ እሴት ታክስን መሠረት በማድረግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበው ክስ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተነሳው ጥያቄ መታየት ያለበት የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን በሚመለከት ከተደነገገው የቻርተሩ/የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ 361/95 አንቀጽ 41 አንፃር ነው፡፡ በተጠቀሰው አንቀጽ 41/2/ የፍ/ቤቶቹ የወንጀል /የደንብ መተላለፍ የዳኝነት ሥልጣን በዝርዝር ተቀምጦአል፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ድንጋጌ በፊደል /ሀ/ ሥር የተመለከተው ሲሆን፣ ይዘቱም ፍ/ቤቶቹ በቻርተሩ አንቀጽ 52 በተመለከቱ የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ በሚነሱ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ሥልጣን ያላቸው መሆናቸውን ይገልጻል፡፡

የቻርተሩ አንቀጽ 52 የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ሥልጣን በዝርዝር የሚያመለክት ሆኖ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /4/ እና /5/ም ለተያዘው ክርክር አግባብነት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ንኡስ አንቀጽ /4/ የከተማው አስተዳደር በራሱ የሚወሰነው እና የሚሰበሰበው የንግድ ትርፍ /የገቢ / ግብር ፣ የኤክሳይዝ ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ብቻ እንደሆነ ሲያመለክት ፤ ንኡስ አንቀጽ /5/ ደግሞ በከተማው ከሚኖሩ ግለሰብ ነጋዴዎች እና በከተማው ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰበሰበው የፌዴራል መንግስት እንደሆነ እና በመጨረሻ ታክሱ የሚሰጠው ለከተማው አስተዳደር መሆኑን ያመላክታል፡፡ እነዚህን ድንጋጌዎች አንድ ላይ አድርገን ስንመለከት መገንዘብ የምንችለው የተጨማሪ እሴት ታክስን የመሰብሰብ ሥልጣን ለከተማው አስተዳደር በሕግ አለመስጠቱን ነው፡፡ ታክሱን የመሰብሰብ ሥልጣን ካልተሰጠው ደግሞ ታክሱን የመክፈል ግዴታ ያለባቸውን ሰዎች የመከታተል፣ በታክስ ሕጉ አፈጻጸም ረገድ ጥፋት ፈጽመዋል የሚባሉትንም የመክሰስ ሥልጣን ተሰጥቶታል ሊባል አይችልም፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ከታክሱ አሰባሰብ ወይም ደግሞ ከታክሱ አዋጅ አፈጻጸም ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ሊከታተላቸው የሚገባው ታክሱን የመሰብሰብ ሥልጣን የተሰጠው የፌዴራል መንግስቱ ነው፡፡ ይህን የማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንደመሆኑ የወንጀል ክሱ መቅረብ ያለበት በባለሥልጣኑ ዓቃቤ ሕግ ነው፡፡

ጉዳዩ የፌዴራል መንግስቱ ሥልጣን ነው ከተባለም ክሱ መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ፍ/ቤት ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በመተላለፍ ተፈጽሞአል የተባለውን ወንጀል በሚመለከት የቀረበላቸውን ክስ ያዩት በሕጉ ሥልጣን ሳይሰጣቸው ነው ለማለት ችለናል፡፡ ፍ/ቤቶቹ በአዋጅ ቁ 361/95 አንቀጽ 52/4/ እና /5/ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች የተረጎሙበት አግባብ ትክክል አይደለም፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 30746/02 ሚያዝያ 5 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 13473 ሰኔ 8 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 13785 ነሐሴ 14 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽለዋል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ 285/94ን በመተላለፍ በሚቀርቡ የወንጀል ክሶች ላይ የዳኝነት ሥልጣን የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡ በዚህ መሠረትም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ላይ በመመሥረት በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ ብቻ ተሽሮአል፡፡ መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 55162

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ዩኒሊበር ፒ.ኤል.ሲ.ፐርት ሰንላይት ዊራል ሜርሲ ሳይድ - ጠበቃ ተሾመ ገ/ማርያም - ቀረበ

ተጠሪ፡- ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግል/ማህበር - ጠበቃ አድማሱ መአዛ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተፈጽሞብኛል በማለት አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ለንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ጽ/ቤት ሆኖ ኮሚሽኑም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ከሣሽ /የአሁኑ አመልካች/ ያቀረበውን ጥያቄ ተቀብሎአል፡፡ በዚህ መሠረትም ተጠሪ በንግድ አሰራር አዋጅ ቁ.329/95 አንቀፅ 10/2/ሀ/ የተደነገገውን በመተላለፍ አመልካች የሚጠቀምበትን የንግድ ምልክት አስመስሎ በመለጠፍ ምርቱን መሸጡን እንዲያቆም፤ ለዚህ ድርጊቱም በአዋጁ አንቀፅ 26/1/ መሠረት ብር 10,000/አስር ሺህ ብር/ መቀጫ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱም የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ጉዳዩን ለማየት /ለመዳኘት/ ስልጣን የለውም በማለት ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡አመልካች ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ ስህተቱ ይታረምለትም ዘንድ ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሠማው ጉዳይ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ስልጣን ስር አይወድቅም የተባለው በህጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኙ ወገኖች ያሠሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና የተሰጡትን ውሣኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በቅድሚያ ልንገነዘብ የቻልነው አመልካች ክስ የመሰረተው የንግድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምልክት ምዝገባና ጥበቃ መብትን ለማስከበር ወይም የንግድ ምልክት ባለቤትነት መብትን ለማረጋገጥ ሣይሆን ፣ ከህግ አግባብ ውጪ ተፈጽሞብኛል ያለውን የማይገባ የንግድ ውድድር እንዲገታለት /እንዲቆም/ እና ተጠሪም ለዚህ ድርጊቱ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድበት በመጠየቅ እንደሆነ ነው፡፡ ክሱን የሰማው የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽንም የቀረበለት የዳኝነት ጥያቄ የተፈጸመውን እና በመፈጸም ላይ ያለውን ያልተገባ የንግድ ውድድር እንዲቆም፣ ተጠሪም በአዋጁ መሠረት እርምጃ ይወሠድበት የሚል እንደሆነ በመገንዘቡ የንግድ ምልክት ጥበቃን /አዋጅ ቁ. 501/98/ በሚመለከት የሚነሣውን ክርክር የመዳኘት ስልጣን የለህም በማለት ከተጠሪ ቀርቦለት የነበረውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በጉዳዩ ስረ ነገር ላይ አከራክሮ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የስር ከሣሽ /አመልካች/ ክስ የንግድ ምልክት ባለቤትነት ማዕከል ያደረገ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ጉዳዩ በኮሚሽኑ የዳኝነት ስልጣን ስር አይወድቅም በማለት ወስኖአል፡፡

የኮሚሽኑ ውሣኔ እንዳየነው የተመሰረተው በንግድ አሰራር አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10 እና 15 በተቀመጡት ድንጋጌዎች ላይ ነው፡፡ አመልካችም ክሱን የመሰረተው በእነዚህ ድንጋጌዎች እና ያልተገባ የንግድ ውድድርን በሚመለከት በንግድ ህግ ቁ. 133 የተቀመጠውን ድንጋጌ በመጥቀስ ነው፡፡ ተጠሪ የፈጸመው እና እየፈጸመው ነው ያለውን ድርጊትም በዝርዝር በመግለጽ አቅርቦታል፡፡ የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በሚመለከት የሚነሣውን ክርክር የመዳኘት ስልጣን ያገኘው በአዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 15 መሠረት ነው፡፡

በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ/ እና /ሰ/ እንደተመለከተው ኮሚሽኑ ከማንኛውም ወገን የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች የአዋጁ ድንጋጌዎችን የመተላለፍ ድርጊት ተፈጽሞአል በሚል እስከቀረቡ ድረስ አቤቱታዎቹን የመመርምር እና በመጨረሻም እንደአግባቡ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና /ወይም የቅጣት ውሣኔ የመስጠት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ረገድ አግባብነት ያላቸው ማለትም ለአቤቱታው መቅረብ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉት የአዋጁ ድንጋጌዎችም ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድርን በተመለከተ ዝርዝር ነገሮችን የያዘው አንቀጽ 10 ፣ ገበያን በበላይነት ያለአግባብ ስለመጠቀም በሚል የተደነገገው አንቀጽ 11 ‘ን’ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአዋጁን ዓላማ በዝርዝር ያስቀመጠው አንቀጽ 3 ‘ንም’ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የአዋጁ ዓላማ :-

/1/ ለነጻ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ስራዎች እንዳይፈጸሙ በመከላከልና በማስወገድ ተገቢ የንግድ ውድድር እንዲሰፍን ለማድረግ እና

/2/ በንግድ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች አቅርቦት እና ስርጭት ላይ ገደብ የሚፈጥሩ ድርጊቶችን በመከላከልና በማስወገድ የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡

በሚል በዝርዝር ተቀምጦአል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪ በአዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/2//ሀ/ የተቀመጠውን ድንጋጌ ስለመተላለፉ በአመልካች ክስ ተገልጾአል፡፡ የድርጊቱ አፈጻጸም ምን እንደሚመስልም በክሱ በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ የተጠቀሰው አንቀጽ 10/2/ሀ/ በሌላው የንግድ ድርጅት ወይም በንግድ ድርጅቱ ተግባሮች፣ በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ድርጊት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ሆኖ እንደሚቆጠር ያመለክታል፡፡ ተጠሪ ፈጽሞታል ወይም እየፈጸመው ነው ተብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአመልካች ክስ የተነገረውም ይኸው በድንጋጌው የተመለከተው ድርጊት ነው፡፡ የአመልካች የክስ መነሻ ተጠሪ እኔ የምጠቀምበትን የንግድ ምልክት አመሣስሎ በመለጠፍ ምርቱን እየሸጠ ነው የሚል ነው በአጠቃላይ የአመልካች በአዋጅ ቁ. 329/95 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የመተላለፍ ድርጊት ተፈጽሞብኛል በሚል ብቻ የሚያቆም ሣይሆን፣ ተፈጸሙ የሚላቸው ድርጊቶች ከህጉ ጋር ያላቸውን ግንኙነት /አግባብነትም/ በግልጽ እና በዝርዝር የሚያሣይ ነው፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ መብት አከባበር አንጻር የሚታይ ነው /አዋጅ ቁ 501/98/ ለማለት የቻለው ተጠሪ የአመልካችን የንግድ ምልክት አመሣስሎ በመለጠፍ ምርቱን እየሸጠ ነው የሚለውን በአመልካች ክስ የተቀመጠውን አባባል አጉልቶ በማውጣት እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በበኩላችን እንደምንገነዘበው በተያዘው ጉዳይ የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ስልጣን አለው ወይም የለውም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በዋናነት መታየት ያለበት የክሱ አጠቃላይ ይዘት እና የተጠየቀው ዳኝነት ነው፡፡ ሌላው በመቀጠል መታየት ያለበት ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ብቻ ሣይሆኑ፣ ተመሣሣይነት ያለው ዕቃም ለገበያ እያቀረቡ ናቸው፡፡ አመልካች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተፈጽሞብኛል የሚለውም ተጠሪ የሱ ያልሆነውን የንግድ ምልክት /አመልካች ባለቤት የሆነበትን/ አመሣስሎ በሚሸጠው ምርት መያዣ ዕቃ ላይ በመለጠፍ እየሸጠ /ለገበያ እየቀረበ/ ነው በማለት ነው፡፡ ድርጊቱ ያልተገባ ውድድር ነው እየተባለ ያለውም አመልካች ከሚያቀርበው ምርት ጋር ማደናገርን አስከትሉአል ስለተባለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ሆኖ በመታየቱ ነው፡፡ በመሆኑም በክሱ አቀራረብ ወይም በክርክር ሂደት ስለንግድ ምልክት በመነሣቱ ጉዳዩ የንግድ ምልክት ባለቤትነት መብት ወይም ምዝገባና ጥበቃን የሚመለከት ነው ማለት አይችልም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የደረሱበት መደምደሚያ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ጉዳዩ በንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡

በመጨረሻም ተጠሪ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያለበትን ምክንያት አይተናል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ እንደተመለከተው የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽንን የዳኝነት ስልጣን በሚመለከት ብቻ ነው ተጠሪ ቅሬታውን ያሰማው፡፡ ከዚህ ባለፈ ኮሚሽኑ በስረ ነገር አጣርቶ በደረሰው መደምደሚያ ላይ ክርክር /ይግባኝ/ አላቀረበም፡፡ በመሆኑም ከዚህ በኋላ በስረ ነገር ላይ የሚደረግ ክርክር የለም፡፡ ጉዳዩ በህጉ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመውን መሠረታዊ ስህተት ማረም ከዚሁ የሚቋጭ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 67927 ሚያዝያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46554 የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ የመሰረተው ክስ በንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ብለናል፡፡ ስለዚህም ኮሚሽኑ በን.አ.አ.ኮ/1-2-58 መጋቢት 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ጸንቶአል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

በላቸው አንሺሶ

አሊ መሐመድ

አመልካች - የአቶ መሐመድ ሁሴን ወራሾች

1. አቶ ዓሊ መሐመድ
2. ዶ/ር ዘምዘም መሐመድ ሁሴን } ጠበቃ አቶ ወንድሜነህ ዳኘው ቀረቡ
3. ወ/ሮ ሮዛ መሐመድ ሁሴን

ተጠሪዎች - 1. የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ.ፈ.ጅ አቶ ደስታ ሊበን

2. አቶ ኃይለስላሴ ገ/መድህን አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው በተደረገው ምርመራ መሠረት ተገቢውን ለመሥራት ሲሆን በዚሁ መሠረት የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የግራቀኙን ጉዳይ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለማየት ሥልጣን የላቸውም በጉዳዩም ላይ ቢሆን የአሁን አመልካቾች ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በሚል ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ አግባብነት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

ይህንን ጉዳይ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለማስተናገድ የሚያስችላቸው ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? እንዲሁም አመልካቾች በጉዳዩ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚሉትን ሁለት አከራካሪ ነጥቦች ለመለየት ከእነዚህ ጭብጦች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የፍሬ ነገርም ሆነ የህግ ክርክሮች በእነዚህ ጭብጦች ላይ ከታች ባሉት ፍ/ቤቶች በየደረጃው የሰጡት ውሣኔዎች እና ግራቀኙም በጉዳዩ ላይ በሰበር ደረጃ ያቀረቡትን ክርክር ባጭር ባጭሩ ለመጥቀስ ያህል የአሁን አመልካቾች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በከሣሽነት ያቀረቡት የክስ አቤቱታ የአውራሻችን ንብረት የሆነው በኪራይ ቤቶች አስተደደር ድርጅት በቁጥር 785 በቀበሌው ቁጥር 786 ከሚታወቀው ቤት ውጭ ሌላ ቤት ስላልነበራቸው አዋጅ ቁጥር 47/67 በወጣበት ጊዜ በቅጽ 004 ተረክበው እያለ ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩበት ጊዜ በ1970 ዓ.ም አስረክባችሁ እንደገና ትጠይቃላችሁ በሚል በማስገደድ ቅጽ 003 እንዲሞላ አድርገው እንደ አዋጁ ያልተወረሰውን ንብረት ወስደውብናል ይህንኑ የንብረት ባለቤትነት መብት ለማስከበር ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ጥያቄ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብናቀርብም እነዚህን ቅጾች መነሻ በማድረግ ጉዳዩ በእኔ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በማለት አሰናብቶናል ስለሆነም በአዋጁ መሠረት ያልተወረሰውን ንብረት በጥንቃቄና በኃይል ወስዶ ከህግ ውጭ ለ3ኛ ተጠሪ አሳልፎ የሰጠ ስለሆነ ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ያለውን የቤት ኪራይ ብር 390,000 ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን ደግሞ የመጠየቅ መብታችንን ከማስጠበቅ ጋር ንብረቱን እንዲያስረክቡ ይድረግልን የሚል ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ የቤቱ ባለቤት ስለመሆናቸው ማስረጃ ያላቀረቡ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የመክሰስ መብት የላቸውም ቅፅ 004 ከተሞላ በኃላ መልሰው በቅፅ 003 አስረክበዋል፡፡ ቅጽ 004 እንደቋሚ የባለቤትነት ማስረጃም አያገለግልም፡፡ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በቅፅ 003 በትርፍነት ተሞልቶ ማስረከባቸውን አረጋግጦ አቤቱታውን አልተቀበለውም፡፡ በመሆኑም ቤቱ ሊመለስላቸው አይገባም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የአሁን 2ኛ ተጠሪም በበኩሉ ከከሣሾች ጋር የውል ግንኙነት ስለሌለኝ እኔን የመክሰስ መብት የላቸውም ጉዳዩን ማየት የሚችለው ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ኤጀንሲው በሰጠው ውሣኔ ቅር ከተሰኙ ለኤጀንሲው ሥራ አመራር ቦርድ ያቀርባሉ እንጂ ፍ/ቤቱ ሊመለከት አይችልም ቤቱ በአዋጅ የተወረሰ ነው በአዋጁ መሠረት ተገቢውን ካሣ ከሚጠይቁ በቀር እኔን ከቤቱ ለማስወጣት የሚያስችል መብት የላቸውም የንግድ ድርጅቱንም በህግ አግባብ ገዝቻለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክሱ የቀረበበት የከፍተኛው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ ፍ/ቤት አይደለም በሚል የቀረበውን ክርክር አስመልክቶ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ከአዋጅ ውጭ በትዕዛዝና በቀላጤ የተወረሱ ንብረቶችን እንጂ ከሣሽ ያቀረቡትን ከህግ ውጭ ቤት ተወርሶብኛል የሚልን ጥያቄ ለመመልከት ሥልጣን የሌለው በመሆኑ ተቃወሚቸው ተቀባይነት የለውም፡፡

ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት ቤቱ በተወረሰበት ወቅት ሌላ ቤት የሌላቸው መሆኑን 1ኛ ተከሣሽ የአሁን 1ኛ አመልካች በ18/10/72 ዓ.ም ለከሣሾች የኪራይ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ከባፈው ደብዳቤ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የከሣሾች አውራሽ ክስ የቀረበበትን ቤት ሌላ ቤት ስለሌላቸው በአዋጁ መሠረት ቤቱ ተፈቅዶላቸዋል ተብሎ በ21/3/68 ዓ.ም ቅፅ 004 የሞሉ ሲሆን በሌላ በኩል በ1970 ዓ.ም ቤቱ ትርፍ ነው ተብሎ ቅፅ 003 ተሞልቷል፡፡ ነገር ግን በዚሁ ቅፅ 003 በተሞላበት ፎርም ላይ ክስ የቀረበበት ቤት ትርፍ ነው ተብሎ ከተሞላው ቤት ሌላ የመረጡት ቤት አልተገለፀም ይህም ከሣሾች አንድ ቤት ብቻ ያላቸው መሆኑን ያመለክታል ተከሣሾች ከሣሾች ቤቱን በቅፅ 003 ሞልተው ቤቱ በትርፍነት ተወርሷል በማለት ይከራከሩ እንጂ አዋጁን አስፈፃሚ እንደመሆናቸው መጠን የአዋጁን መንፈስ የሚቃረኑ ከሆነ ህገወጥ ናቸው የማይባሉበት ምክንያት አይኖርም ተከራይ ነኝ የሚለው የአሁን አመልካች ድርጅቱን ከ1ኛ መልስ ሰጭ ተከራይቼ እየተገለገልኩበት እገኛለሁ የሚለው ክርክሩ ክርክር ከተነሳበት ቤት ጋር የሚገናኝ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በመሆኑም ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች በአዋጁ መሠረት ሊወረስ የሚገባው ትርፍ ቤት ከሆነ ብቻ ስለሆነ ቅጽ 003 ተሞልቶ ተወርሷል የሚለው ክርክር ህጋዊ መሠረት ስለሌለው እና ከህግ ውጭ መወረሱን ስለሚያስረዳ ተከሣሾች ቤቱን ሊመልሱ ይገባል ቤቱ በኪራይ ያስገኘውን የገንዘብ መጠን አስመልክቶ የቀረበ ክርክር ስለሌለም ከብር 390,000 /ሶስት መቶ ዘጠኝ ሺህ/ ጋር ለከሣሾች ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪዎች በተናጠል ያቀረቡትን የይግባኝ መዝገብ አጣምሮ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 24633 የካቲት 28 ቀን 2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዋለው ችሎት ከሣሾች በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ሥልጣን ላለው ለፕራይቬይታይዜሽን ኤጀንሲ ቤቱ እንዲመለስላቸው ጠይቀው ቤቱ በቅጽ 003 ተሞልቶ በመሰረዙ ምክንያት ጥያቄያቸው ተቀባይነት ማጣቱን የክስ ማመልከቻቸው እያስረዳ ሥልጣን ያለው አካል ውሣኔ ያሰፈረበትን ነጥብ ቤቱ ከህግ ውጭ የተወረሰ ነው በማለት ከፍተኛው ፍ/ቤት መወሰኑ በሌለው ሥልጣን ነው፣

ከዚህም በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ቤቱ ትርፍ ነው አይደለም ሊወረስ ይገባል አይገበም? ብሎ የመወሰን ሥልጣን ያለው የሥራና ከተማ ቤቶች ሚ/ር ስለመሆኑ በአዋጁ ተጠቅሶ እያለ ከሣሾች ትርፍ ቤት ሳይኖራቸው የተወረሰባቸው ያለአግባብ ነው ማለቱ በሌለው ሥልጣን በመሆኑ እንዲሁም ቤቱ ከተወረሰ በኃላ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ሆነ ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 292/18 መሠረት ቤቱ እንዲመለስላቸው በወቅቱ አጠራር ለሥራና ቤቶች ሚ/ር አመልክተው እንዲመለስላቸው ተወስኖ ውሣኔው በሚ/ሩ የፀደቀበትን ማስረጃና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195/1/ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነታቸውን ለማወቅ የተሰጣቸው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ስላላቀረቡ ከሣሾች ከመነሻውም ቢሆን ክስ በቀረበበት ሐብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያላቸው መሆኑን ስላላረጋገጡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/መሠረት በቤቱ ላይ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም፡፡

ስለሆነም በእነዚህ ነጥቦች ላይ ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መቀበል ሲገባው አልፎ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካቾች በዚህ የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተፈፅሟል የሚሉትን የህግ ስህተት ለማሳየት ዝርዝር የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ሲሆን ፍሬ ቃሉም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በቤቱ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት የላቸውም በማለት የሰጠው ውሣኔ ያቀረብነውን የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃ መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡

እንዲሁም የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ማስረጃዎችን አጣርቶ ቅጽ 003 የተሞላው ከህግ ውጭ መሆኑን በኤክስፐርቶች ካረጋገጡ በኃላ ቤቱ ሊመለስ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ሆኖም የኤጀንሲው ሥራ እስኪያጅ ቅጽ 003 በህግ አግባብ ያልተሞላ ቢሆንም ሰነዱ ህጋዊነት አለው ወይስ የለውም የማለት ሥልጣን ለኤጀንሲው አልተሰጠውም ስለዚህ ሰነዱ በህግ ውጤት የለውም ቤቱ ሊመለስ ይገባል ለማለት አይችልም ከማለት ውጭ ቅፅ 003 በህግ አግባብ የተሞላ እና ቅጽ 004ን የሻረ ነው አላለም ስልጣን የለኝም ማለት በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ተሰጠ ማለት አይደለም ስለሆነም ማንኛውም ሰው በህገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን መብት ያለህግ የግል ንብረቱን ማጣት የለብኝም በማለት መብቱን ማስከበር የሚችለው በፍ/ቤት ዳኝነት በመጠየቅ በመሆኑ ኤጀንሲው የመጨረሻ ውሣኔ ባልሰጠበት ጉዳይ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ፍ/ቤት የማየት ሥልጣን አለው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም በየፊናቸው ለሰበር አቤቱታው መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ በይዘቱም በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እና በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡትን መልስና ቅሬታ የሚያጠናክር የጠቅላይ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ዳኝነት ትክክለኛነት የሚያስገነዝብ በመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካቾችም በመልስ መልሳቸው በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የቀረበውን የሚያብራራ እና የሚያጠናክር ነው፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህንን ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት ተመልክቶ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በሚል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ዳኝነት በማስቀደም ተመልክተናል፡፡

በኢት/ያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀጽ 37 እንደተደነገገው አንድን ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ለሌላ የዳኝነት አካል ከሆነ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የላቸውም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል መቅረብ የሚገባው ጉዳይ ለፍ/ቤቶች በቀረበ ጊዜ ጉዳዩ በየትኛው የክርክር ደረጃና በየትኛውም የፍ/ቤት እርከን ቢገኝም በሥልጣን ምክንያት ክርክሩ ሊቋረጥ እና ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ ይኸው ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ሆነ በዝርዝር ህጉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 231/1/ /ለ/፣ 9/2/፣ 244/3/ እና 328/3/ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ከፍ/ቤቶች ሥልጣን አንፃር መመርመሩ አግባብ ቢሆንም ይህ ጉዳይ ቀደም ሲል ለፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ የታየና ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ ስለሆነ ፍ/ቤቶች ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያስችላቸው ሥልጣን የለውም በሚል የሰጠው ዳኝነት ስለጉዳዩ ግራቀኙ በፍሬ ነገር ረገድ ያቀረቡትን ክርክር መሠረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም ይኸውም ለዚሁ ውሣኔ እንደመነሻ ያደረገው ጉዳዩ ለፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ውሣኔ ያገኘ ስለመሆኑ የከሣሾች የክስ ማመልከቻ በግልፅ ያስረዳል የሚለውን በመያዝ ነው ይሁን እንጂ የከሣሾች የክስ ማመልከቻ ክሱ ቀርቦለት የነበረው የፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መምሪያ ቤቱ በአዋጁ መሠረት ያልተወረሰ መሆኑን አረጋግጦ እንዲመልስልን የወሰነልን ቢሆንም ዋና ስራ አስኪያጅ ጉዳዩ በኤጀንሲው ሥልጣን ሥር የማይወድቅ መሆኑን ጠቅሶ ሥልጣን የለኝም ብለናል የሚለውን የሚጠቅስ እንጂ እንደይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ የሚናገር አይደለም፡፡

አመልካቾችም ይህንኑ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ በመንቀፍ በሰበር አቤቱታቸው ገፅ 4 የመጨረሻ ክፍል ላይ ኤጀንሲው ጉዳዩን ተመልክቶ ውሣኔ የሰጠበት ጉዳይ ሳይሆን ሥልጣን የለኝም በማለት ነው ያሰናበተን በማለት ላቀረቡት ቅሬታ 1ኛ መልስ ሰጭ በሰጠው መልስ ገፅ 3 የመጨረሻ ክፍል የፐራይቨታይዜሽን ኤጀንሲም ቢሆን ይህን የማጣራትም ይሁን ትክክለኛነቱን ወይም ህገ ወጥነቱን የመመርመር ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለፅ መዝገቡን ዘግቶታል ቤቱ የተወረሰው ከአዋጁ ውጭ ነው በማለት ቤቱ እንዲመለስላቸው በኤጀንሲው የተሰጠ ውሣኔ የለም በማለት ጉዳዩ በኤጀንሲው በኩል ቀርቦ ክርክር ተደርጐ ማስረጃ ተመርምሮ ተገቢውን ዳኝነት ያረፈበት ሳይሆን ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የዘጋው መሆኑን ሁሉ አረጋግጧል ይህ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ በኤጀንሲው ታይቶ ዳኝነት ያረፈበት ጉዳይ ነው የሚለውን መነሻ አድርጎ ጉዳዩን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የማየት ሥልጣን አልነበረውም በማለት የሰጠው ዳኝነት የግራቀኙን ክርክር መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ የተነሣ የተሳሳተ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 110/87 እንደተመለከተው ጉዳዩ በፐራይቬታዜሽን ኤጀንሲ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም ተብሎ መመለሱ ከተረጋገጠ እና አሁንም ቢሆን ይህን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን ሥልጣኑ ለሌላ የዳኝነት አካል የተሰጠ ነው የሚል የህግ ክርክር እስካልቀረበ ድረስ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ይህንኑ ጉዳይ በፍ/ቤት ቀርቦ እንዳይታይ የሚከለክል አይደለም በዚህ ረገድ የሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት ሥልጣኑን አስመልክቶ የሰጠው ትርጓሜ የግራቀኙን ክርክር ይዘት ካለማገናዘብም ሆነ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

እንዲሁም ትርፍ ቤት ነው ወይስ አይደለም? ሊወረስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውንም ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት አዋጁን ለማስፈፀም ሥልጣን በተሰጠው አካል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚታይ በቀር የፍ/ቤቶችን ዳኝነት የሚጠይቅ ጉዳይ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም በሚል በሁለተኛ ደረጃ የሰጠውንም ትርጉም እንደተመለከትነው ከሣሾች ያቀረቡትን የክርክር ይዘት ያገናዘበ አይደለም የከሣሾች የክስ መነሻ አውራሻችን አዋጅ ቁጥር 47/67 በወጣበት ጊዜ ከዚህ ክርክር ካስነሳው ቤት ሌላ ትርፍ ቤት የሌላቸው መሆኑን በማረጋገጥ አዋጁን ለማስፈፀም ሥልጣን በተሰጠው አካል ተረጋግጦ በ21/03/68 ዓ.ም ቅፅ 004 ተሞልቶ ቤቱ ሳይወረስ በአባታችን ባለቤትነት ዘልቆ ቆይቷል በባለቤትነት መብታቸውም እየተገለገሉበት እያለ በ1970 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ምክንያት በማድረግ እኛን ወራሾችን ከቤት አስመጥተው እንደተወረሰ አድርገው ቅጽ 003 በመሞላት ያልተወረሰን ንብረት ተወስዶብናል በማለት ቤቱን ለማስመለስ አዋጁን ለማስፈፀም ሥልጣን የተሰጠው አካል ያደረገውን የፈቃድ ተግባር መነሻ በማድረግ የሚከራከሩ መሆኑን ያገናዘበ አይደለም በእነዚህ ፍሬ ነገሮች በመመሥረት የቀረበው የቤት ይመለስልኝ አቤቱታ ከመነሻውም በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም ከሚል መደምደሚያ ለመድረስ የሚያስችል የህግ መሠረትም አላገኘንበትም ከዚህም ነጥብ አንፃር ቢሆን ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ተቀብለው ለመወሰን የሚያስችል ሥልጣን የላቸውም የሚለው ትርጉም ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሶስተኛውና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ ለመሻር በምክንያትነት የጠቀሰውን የክስ ምክንያት የላቸውም የሚለውንና የዳኝነት አግባብነት የአሁን አመልካቾች በክስ ማመልከቻቸው ላይ ከገለፁት የክስ ምክንያት እና የማስረጃ ዝርዝር ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል፡፡

አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ ማመልከቻና የማስረጃ ዝርዝር ላይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በፊት ሀብትነቱ የአባታቸው የአውራሻቸው የነበረ መሆኑን አዋጁ እንደወጣም በአዋጁ መሠረት ትርፍ ቤት የሌላቸው መሆኑ ሥልጣን በተሰጠው አካል በቅፅ 004 ተረጋግጦ ህዳር 21 ቀን 1968 ተሞልቶ ተሰጥቷቸው በባለቤትነት በይዞታቸው እያለ በ1970 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን በ1970 ዓ.ም የቤቱ ባለቤት ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለዩ በተደራቢ ቅፅ 003 የአሁን 1ኛ ተጠሪ እንደተረከበው ጠቅሰዋል ይህም ስለመሆኑ በየደረጃው የተሰጠው ውሣኔም ያስረዳል፡፡

እንዲሁም አመልካቾች በክስ ማመልከቻቸውና በሰበር ደረጃ በተደረገው ክርክር እንደገለፁት በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የተደረገው ክርክርና ማስረጃ ከተሰማ በኋላ መምሪያው የሰጠው ውሣኔ በሥልጣን ምክንያት ቀሪ ይሁን እንጂ የቤቱ አወራረስ እንደ አዋጁ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አስመልክቶ የኤጀንሲው ኤክስፐርቶች አረጋግጠው መምሪያው እንዲመለስ አድርጎ ነበር ለሚለው ክርክራቸው ተጠሪውም ይህ ውሣኔ የመ/ቤቱ የበላይ ውሣኔ አይደለም ተፈፃሚነት የለውም የተቋም ውሣኔ እንደሆነ አይቆጠርም በሚል ተከራክሩ እንጂ በፍሬ ነገር ረገድ ሐሰት ነው አልተባለም የሚል ማስተባበያ አላቀረቡበትም ስለጉዳዩ በሌላ የዳኝነት ሰጭ አካል በተደረገ ክርክር የተረጋገጠ ጉዳይ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ክርክር በቀረበ ጊዜ ያለው ተቀባይነት ምን ያህል ነው? የሚለው አከራካሪ ነጥብ እንዳለ ሆኖ አሁን ለተያዘው የመክሰስ መብት አላቸው ወይስ የላቸውም የሚለውን ለመለየት ግን አግባብነት ያለው በመሆኑ እነዚህ ፍሬ ነገሮችና የከሣሾች የማስረጃ ዝርዝር በጉዳዩ ላይ ክስ የማቅረብ መብት ያላቸው ለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ አንፃር ሊታዩ በቂ መነሻዎች ናቸው፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መብትና ግዴታን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚረዳ መሣሪያ እንደመሆኑ ክስ የሚያቀርብ ወገን ክስ የሚያቀርብበት ጉዳይ ከህግ በመነጨ መብት የተደገፈ ተከሣሹም መብቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማሟላት በህግ ግዴታ የተጣለበት መሆኑን ሊያሳይ ይገባዋል በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና /3/ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተገቢ ያልሆነ ክስ እንዳይቀርብ መገደቢያዎች ከመሆኑ አንፃር ስታይ በዚህ ጉዳይ ከሣሾች በጉዳዩ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያላቸው ስለመሆኑ በክሳቸው የገለፁት የክስ ዝርዝር እና ማስረጃ አረጋግጭ ናቸው ጉዳዩን ለማስረዳት በብቸኝነት መቅረብ የሚገባው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ነው ለማለትም አያስችልም፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በተመሳሳይ ጉዳይ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ተመልክቶ ከዚህ በፊት የመክሰስ መብት የለም በሚል ስለተረጋገጠው በዚያው አንፃር ይታይልን በማለት በሰበር መ/ቁ 14094 በአመልካች የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና በአቶ ሰለሞን ወረደ መካከል የነበረውን ጉዳይ በመጥቀስ ሁለተኛ አመልካች ያቀረበውን ክርክር ተመልክተናል፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላለ ፍ/ቤት የአስገዳጅነት ባህሪ የሚኖረው ጉዳዮች በፍሬ ነገር እና በማስረጃ አቀራረብ ተመሳሳይ ሆነው በተገኙ ጊዜ ለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 454/97 አስረጂ ነው በሰበር መ/ቁ 14094 በተነሳው ጉዳይ ቤቱን በውርስ ይገባኛል ሲል ክስ ያቀረበው ወገን ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በፊት የነበረን ካርታና የቤት ሥራ ፈቃድ መሠረት በማድረግ የቀረበ ከመሆኑ በቀር በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ሊወረስ የማይገባበትን ምክንያት አዋጁን መሠረት በማድረግ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም ከአዋጁ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የህግ ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ለመሆኑ መነሻ የሚሆኑ የፍሬ ነገሩና የማስረጃ ጉዳይ የቀረበበት አይደለም በክርክርና በማስረጃ ረገድ ሁለቱም የተለያዩ ናቸው ስለሆነም በተመሳሳይነት የሚወሰንበት አግባብ አላገኘንበትም በዚህ ሁሉ ምክንያት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ለመመልከት የሚያስችለው ሥልጣን የለውም በሚል እና በጉዳዩም ቢሆን አመልካቾች ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም በሚል የሰጠው ትርጉም የግራቀኙን የክርክር ይዘትና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ባለማገናዘብ የተሰጠ ትርጉም በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ 24633 የካቲት 28 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ክስ ባቀረቡበት ጉዳይ ክስ የማቅረብ መብት አላቸው ጉዳዩንም ተመልክቶ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው በሥልጣኑ ስር የሚወድቅ ሆኑ በመገኘቱ ነው ብለናል፡፡
3. ጉዳዩ የሚያስከስስ እና በስር ፍ/ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ ሆነ በሥልጣን ምክንያት ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚቋጭ ስላልሆነ በቀሪው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ሥልጣኑ ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 341 መሠረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙ ላደረሱት ክርክር ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- 1. እነ ወልዳይ ዘሩ (61 ሰዎች) - ጠበቃ ዳንኤል ብርዬ ቀረቡ

2. አቶ ቴዎድሮስ ይልማ - የቀረበ የለም

3. አቶ አማረ ተረፈ - “ “

4. እነ አቶ ጀማል አህመድ (ሶስት ሰዎች) - የቀረበ የለም

5. አቶ ትግስቱ ጥላሁን - የቀረበ የለም

6. አቶ ቀዳማዊ ረታ - የቀረበ የለም

7. እነ አቶ አሰለፈው ገድፍ (ሁለት ሰዎች) የቀረበ የለም

8. እነ አሸናፊ አማረ (ሁለት ሰዎች) - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ እስከዳር አዘዘው ቀረቡ፡፡

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በመ/ቁጥር 51789፣ 51792፣ 51794፣ 51798፣ 53301፣ 53460 እና 57247 ከቀረቡት ጉዳዮች ጋር ተመሳሳይ የሕግ ጥያቄ ያለበት በመሆኑ መዝገቦችን አንድ ላይ አጣምረን በመመርመር ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/ መሠረት ሠራተኛን በልዩ ሁኔታ ከሥራ ስለማስናበት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረቡት የአሁኑ አመልካቾች ናቸው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ ይዘት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እየተገበረ ባለው የመሠረታዊ አሰራር ሂደት ለውጥ ምክንያት ምደባ ሳያገኙ የቀሩ በመሆኑ እረፍት እንዲወስዱ መደረጉንና ለአስራ አንድ ወራት ደመወዝ ሲከፍላቸው ቆይቶ ሐምሌ 01 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸው ተቋርጦ ከስራ መሰናበታቸው ከሕግ ውጪ መሆኑን ገልፀው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ ይህ የማይሆን ከሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከስራቸው የተሰናበቱበትን ምክንያት በአግባቡ በመግለፅ የአመልካችን የመሰማት መብት ተግባራዊ በማድረግ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ የይግባኝ አቤቱታውን ማቅረባቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በተደረገለት ጥሪ መሠረት የአሁኑ ተጠሪ ቀርቦም እርምጃው በአዋጅ ቁጥር 578/2000 አንቀፅ 19/1/ለ/ እና በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/ መሠረት የተከናወነ በመሆኑ ተገቢ ነው በማለት የአመልካች ይግባኝ ውድቅ እንዲሆን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የአስተዳደር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካቾችን ይግባኝ በድምጽ ብልጫ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን በተለያዩ መዛግብት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/337 መሠረት ይግባኛቸው ተሰርዞባቸዋል የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ ሲሆን የአቤቱታቸው መሠረታዊ ይዘትም አመልካቾች የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ያረጋገጠልን የመደመጥ መብት ሳይከበር የተሰጠ የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ጉዳያቸው ባግባቡ እንዲጣራ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካቾች የተሰናበቱት በሕጉ አግባብ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/ እና /2/ አንጻር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት በተወሰኑ መዛግብት ሲያሰሙ በተወሰኑ መዛግብት ደግሞ የጽሑፍ ክርክር ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች መስሪያ ቤቱ በአዲስ መልክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተብሎ ሲዋቀር የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የሰራተኞችን መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37/1/"ን" በመጥቀስ አመልካቾችን ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ሲሆን አመልካቾች ይህ የተጠሪ እርምጃ ሕጋዊ አይደለም፣ በሕገ መንግስቱ የተከበረውን የመሰማት መብት የሚጥስ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1/ ድንጋጌ በግልፅ የሚያሳየው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚሁ የሕገ መንግስት ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ፍርድ ቤቶች አንድን ጉዳይ (አቤቱታ) ተቀብለው ውሳኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ መሆኑን ነው፡፡ በህግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍርድ ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን ስለሌለው በሕጉ መሠረት ለአንድ አስተዳደር አካል ቀርቦ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ወይም ለአስተዳደር መቅረብ የሚገባውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ሊያስተናግደውም ሆነ አከራክሮ ውሳኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡ ለአንዳንድ የመንግስት አካላት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የሚሠጡት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጎች መጠበቅና መከበር ያለባቸው ሲሆን የዳኝነት አካል ስልጣንም በሕግ የተወሰነ ስለሆነ ሕግ የመተርጎም ስራው በሕጉ በተመለከተው አድማስ የሚመራ ይሆናል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4 ድንጋጌ የሚያሳየውም ፍርድ ቤቶች በሌላ ህግ በግልጽ በታገዱ ጉዳዮች ላይ አስራክሮ የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በአስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በህግ ተለይተው የተቀመጡት ጉዳዮችን ፍ/ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 79/1/ እና 37 ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩ ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ለማየትና ለመወሰን ሥልጣን የሚኖራቸው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው (Justiciable matter) ሆኖ ከተገኘ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አዋጅ ቁጥር 578/2000 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን ያቋቋመ ሕግ ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 19/1/ለ/ ድንጋጌ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ቢኖርም የባለስልጣኑ ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይመራል በሚል በኃይለ ቃል ተደንግጎ ይገኛል ፡፡ በዚሁ ሥርዓት መሠረትም የሚኒስሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 ያወጣ ሲሆን በዚህ ደንብ አንቀጽ 37/1/ ስር በደንቡ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢሆንም ዋና ዳይሬክተሩ በሙስና የተጠረጠረውንና እምነት ያጣበትን ማንኛውንም ሠራተኛ መደበኛውን የዲሲፕሊን እርምጃ አፈጻጸም ሥርዓት ሳይከተል ከሥራ ማሰናበት እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ከላይ በተመለከተው ስርዓት መሠረት ከስራ የተሰናበተ ሰራተኛ በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ስራ የመመለስ መብት እንደማይኖረው አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የሚተዳደሩት አዋጅ ቁጥር 578/2000 “ን” ተከትሎ በወጣው ደንብ ቁጥር 155/2000 መሠረት እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በደንቡ አንቀፅ 37/1/ መሠረት የሥራ ስንብት ቢፈፀም በዳኝነት በፍ/ቤት እንደማይታይ በተጠቀሰው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በመርህ ደረጃ ሕግ የማውጣት ሥልጣን በሥልጣን ክፍፍል መርህ መሠረት የሕግ አውጪው አካል ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሕግ አውጪው የመንግስት አካል የሚወጡ ሕጎች ቀዳሚዊ (primary legislations) ተብለው የሚታወቁ ሲሆን ሌሎቹ እንደአስፈላጊነታቸው አግባብ ባለው አካል የሚወጡ ሕጎች የበታች ህጎች (subsidiary legislations) ተብለው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ሕግ አውጪው የመንግሥት አካል በተለያዩ ቴክኒካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ምክንያቶች ቀዳሚውን ሕግ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ዝርዝር ሕጎች ያስፈልጋሉ ብሎ ባመነ ጊዜ ተገቢ ነው ላለው አካል የበታች ሕጎችን እንዲያወጣ ሥልጣን ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡ ይህ አሰራር በሕግም በምክንያትም የተደገፈ እና የዳበረ ልምድ ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 155/2000 ሕግ አውጪው በሰጠው ስልጣን መሠረት የወጣ ሲሆን በደንቡ አንቀጽ 37 መሠረት ደግሞ ሰራተኛው ከስራ የሚሰናበትበትን አግባብ ደንግጓል፡፡ በመሆኑም ወደ ስራ የመመለስ ወይም የመደመጥ መብት በፍርድ የሚያልቅ ጉዳይ አለመሆኑን የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አንድ ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችለው ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካቾች የተሰናበቱት ሕግ አውጪው በዘረጋው ሥርዓት መሰረት ሲሆን አመልካቾች ከጠየቁት ዳኝነት አንጻር (ወደ ስራ መመለስ ወይም የመደመጥ መብት መከበር) ሲታይ ጥያቄው በፍርድ ሊያልቅ የሚችል (justiciable matter) አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም የአስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት የአመልካቾችን የይግባኝ ቅሬታ በአብላጫ ድምፅ ውድቅ ማድረጉ በአመልካቾች ከተጠየቀው ዳኝነት (ወደ ስራ እንድንመለስ ወይም የመደመጥ መብታችን ይጠበቅልን ከሚለው) አንፃር ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 578/2000 አንቀጽ 19/1/ለ/ እና ከሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 37(1 እና 2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም አላማን የተከተለና ለአስተዳደር አካሉ በሕጉ አግባብ የተሰጠውን ስልጣን (executive prerogative) ያከበረ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 00827/2001 ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ/ም ጳጉሜ 02 ቀን 2001፣ በይ/መ/ቁጥር 00831/2001 ነሐሴ 18 ቀን 2001 ዓ/ም በይ/መ/ቁጥር 00839/2001 ነሐሴ 26 ቀን 2001 ዓ.ም፣ 00833/2001 ነሐሴ 26 ቀን 2001 ዓ.ም፣ በይ/መ/ቁ 00826/2001 ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም እና በይ/መ/ቁጥር 00828/2001 ነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ/ም እና በይ/መ/ቁጥር 00830/2001 መጋቢት 08 ቀን 2002 በአቶ አሸናፊ አማረና በአቶ አወቀ ተሻለ ጉዳይ ተሰጥተው በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀኑት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ተጣምረው እንዲታዩ ከተባሉት መዛግብት ጋርም ይያያዝ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 6 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች - ኤም. ኤ. ሸሪፍ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ ይማጅ ዩኒስ - ቀረቡ

ተጠሪ - ታይስ ኃ/የተ/የግል ማህበር - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የማይገባ የንግድ ውድድር ተፈጽሞአል በማለት የአሁኑ ተጠሪ የመሠረተውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ለንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ጽ/ቤት ሲሆን፣ ኮሚሽኑ ከሣሽ እና በወቅቱ ተከሣሾች የነበሩት የአሁኑን አመልካች እና አቶ መሐመድ አደም የተባለውን ግለሰብ አከራክሮአል፡፡ በመጨረሻም ተከሣሾች ከከሣሽ የንግድ ምልክት ጋር ተመሣሣይነት ያለውን ምልክት በመጠቀም ምርታቸውን ሲሸጡ ተገኝተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ተጠቃሚውን ህብረተሰብ ግራ የሚያጋባና የሚያደናግር ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከሣሾች ድርጊቱን እንዲያቆሙ፣ 1ኛ ተከሣሽ የነበረው /የአሁኑ አመልካች/ ብር 15,000 መቀጫ እንዲከፍል፣ 2ኛ ተከሣሽ የነበረው ግለሰብ ደግሞ በማስጠንቀቂያ እንዲታለፍ በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ኮሚሽኑ ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ሥልጣን የለውም በማለት ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ በበኩሉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ጉዳዩን ያየው በንግድ አሠራር አዋጅ ቁጥር 329/95 በተሰጠው ሥልጣን ነው የሚል ምክንያት በመስጠት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቀርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በሕጉ አግባብ የተሰጠ ነው ወይ? በሚለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በሆኑም ግራ ቀኝ ወገኖች በጭብጡ መሠረት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና የተሰጡትን ውሣኔዎች ይዘት በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በቅድሚያ ልንገነዘብ የቻልነው ተጠሪ ክስ የመሠረተው የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ መብትን ለማስከበር ወይም የንግድ ባለቤትነት መብትን ለማረጋገጥ ሳይሆን፣ ከሕግ አግባብ ውጪ ተፈጽሞብኛል ያለውን የማይገባ ውድድር /የንግድ ውድድር/ እንዲገታለት እና አመልካችም ለዚህ ድርጊቱ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድበት በመጠየቅ እንደሆነ ነው፡፡ ክሱን የሰማው የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽንም ባቀረበለት የዳኝነት ጥያቄ የተፈፀመውን እና በመፈፀም ላይ ያለውን ያልተገባ የንግድ ውድድር እንዲቆም፤ አመልካችም በአዋጁ መሠረት እርምጃ ይወሰድበት የሚል እንደሆነ በመገንዘቡ የንግድ ምልክት ጥበቃን /አዋጅ ቁ. 501/98/ በሚመለከት የሚነሳውን ክርክር የመዳኘት ሥልጣን የለህም በማለት ከአመልካች ቀርቦ የነበረውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በጉዳዩ ሥረ ነገር ላይ አከራክሮ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የሥር ከሣሽ /የአሁኑ ተጠሪ/ ክስ የንግድ ምልክት ባለቤትነትን ማዕከል ያደረገ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ጉዳዩ በኮሚሽኑ የዳኝነት ሥልጣን ሥር አይወድቅም በማለት ወስኖአል፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ባለመስማማቱ በአዋጅ ቁ. 329/95 እና በአዋጅ ቁጥር 501/98 መካከል ያለውን ልዩነት በዝርዝር በማመልከት ጉዳዩ በንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡

በበኩላችንም እንዳየነው የኮሚሽኑ ውሣኔ የተመሠረተው በንግድ አሠራር አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10 እና 15 በተቀመጡት ድንጋጌዎች ላይ ነው፡፡ ተጠሪም ክሱን የመሠረተው በእነዚህ ድንጋጌዎች የተመለከተውን መሠረት በማድረግ ሲሆን ተፈፀመ ወይም እየተፈፀመ ነው ያለውን ድርጊትም በዝርዝር ገልጾ አቅርቦታል፡፡ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በሚመለከት የሚነሳውን ክርክር የመዳኘት ሥልጣን ያገኘው በንግድ አሠራር አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 15 መሠረት ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ እና /ሰ/ እንደተመለከተው ኮሚሽኑ ከማንኛውም ወገን የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች የአዋጁ ድንጋጌዎችን የመተላለፍ ድርጊት ተፈጽሞአል በሚል እስከቀረቡ ድረስ አቤቱታዎቹን የመመርመር እና /ወይም የቅጣት ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ረገድ አግባብነት ያላቸው ማለትም ለአቤቱታ መቅረብ መሠረት ሊሆኑ የሚችሉት የአዋጁ ድንጋጌዎችም ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድርን በተመለከተ ዝርዝር ነገሮችን የያዘው አንቀጽ 10፣ ገበያን በበላይነት ያለ አግባብ ስለመጠቀም በሚል የተደነገገው አንቀጽ 11"ን" መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአዋጁን ዓላማ በዝርዝር ያስቀመጠው አንቀጽ 3 "ንም" መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የአዋጁ ዓላማ፡-

1) ለነፃ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ሥራዎች እንዳይፈፀሙ በመከላከልና በማስወገድ ተገቢ የንግድ ውድድር እንዲሰፍን ማድረግ እና
2) በንግድ ዕቃዎች አገልግሎቶች አቅርቦት እና ሥርጭት ላይ ገደብ የሚፈጥሩ ድርጊቶችን በመከላከልና በማስወገድ የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡

በሚል በዝርዝር ተቀምጦአል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀጽ 10/2/ሀ/ የተቀመጠውን ድንጋጌ ስለመተላለፉ በተጠሪ ክስ በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ የድርጊቱ አፈፃፀም ምን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚመስልም በክሱ ተገልጾአል፡፡ በዚህ ረገድ የተጠቀሰው አንቀጽ 10/2/ሀ/ በሌላው የንግድ ድርጅት ወይም በንግድ ድርጅቱ ተግባሮች በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ድርጊት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ሆኖ እንደሚቆጠር ያመለክታል፡፡ አመልካች ፈጽሞታል ወይም እየፈጸመው ነው ተብሎ በተጠሪ ክስ የተነገረውም ይኸው በድንጋጌው የተመለከተው ድርጊት ነው፡፡ የተጠሪ የክስ መነሻ አመልካች እኔ የምጠቀምበትን የንግድ ምልክት አመሳስሎ በመጠቀም ምርቱን ለገበያ እያቀረበነው የሚል ነው፡፡ በአጠቃላይ የተጠሪ ክስ በንግድ አሠራር አዋጅ ቁ. 329/95/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የመተላለፍ ድርጊት ተፈጽሞብኛል በሚል ብቻ የሚያቆም ሳይሆን ተፈጸመ /እየተፈጸመ ነው/ የሚለው ድርጊት ከሕጉ ጋር ያለውን ግንኙነት /አግባብነት/ም በግልጽ በዝርዝር የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ጉዳዩ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ መብት አከባበር አንፃር በማየት ነው ኮሚሽኑ ሥልጣን የለውም በማለት እየተከራከረ የመጣው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም አመልካች የተጠሪን የንግድ ምልክት አመሳስሎ በመጠቀም ምርቱን ለገበያ እያቀረበ ነው የሚለውን በተጠሪ ክስ የተቀመጠውን አባባል ብቻ አጉልቶ በማውጣት ጉዳዩ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁ. 501/98 አንፃር ነው መታየት ያለበት እሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ እንደቻለ ከውሣኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በእርግጥም የክርክሩ አነሳስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወደያዘው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ከሆነ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የሚኖረው የንግድ አሠሪር አጣሪ ኮሚሽን ሳይሆን የፌዴራል መደበኛ ፍ/ቤት እንደሆነ ከአዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 49 መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁንና ወደ ድምዳሜ ከመደረሱ በፊት የተያዘውን ክርክር አጠቃላይ ይዘት እና ተጠሪ በክሱ የጠየቀውን ዳኝነት በአግባቡ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በበኩላችን እንደምንገነዘበው በተያዘው ጉዳይ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በዋናነት መታየት ያለበት የተጠሪ የክስ ምክንያት /መነሻ/ እና በመጨረሻ የተጠየቀው ዳኝነት ነው፡፡ ሌላው በመቀጠል መታየት ያለበት ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ በንግድ ሥር ላይ የተሰማሩ ብቻ ሳይሆኑ ተመሣሣይነት ያለው ዕቃም ለገበያ እያቀረቡ ናቸው የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተፈጽሞብኛል የሚለውም አመልካች የሱ ያልሆነውን የንግድ ምልክት /ተጠሪ ባለቤት የሆነበትን/ አመሳስሎ በመጠቀም ምርቱን ለገበያ እያቀረበ /እየሸጠ/ ነው በማለት ነው፡፡ ድርጊቱ ያልተገባ ውድድር ነው እየተባለ ያለውም ተጠሪ ከሚያቀርበው ምርት ጋር ማደናገርን አስከትሎአል ስለተባለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ሆኖ በመታየቱ ነው፡፡ በመሆኑም በክርክር ሂደት ወይም በክሱ አቀራረብ ስለ ንግድ ምልክት በመነሳቱ ጉዳዩ የንግድ ምልክት ባለቤትነት መብት ወይም ምዝገባ ጥበቃን የሚመለከት ጉዳይ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር መቀበሉ ትክክል አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ግን የጉዳዩን ይዘት ከሕጉ ጋር ያገናዘበ የሕግ መሠረት ያለው ነው፡፡ ጉዳዩ በእርግጥም በንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ነው፡፡

በመጨረሻም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣንን በመሚመለከት የተነሳውን ክርክር ከወሰነ በኋላ በሥረ ነገር ረገድ ያለውን ክርክር በሥር ፍ/ቤት እንዲታይ አለማድረጉ ተገቢ ነው ወይ? የሚለውን ነጥብ ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ የመጨረሻ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንደመሆኑ ከንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ጀምሮ የተካሄደውን ክርክር ነው የመረመረው፡፡ በአጣሪ ኮሚሽኑ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔዎችም በዚህ ሂደት ይመረመራሉ፡፡ በእርግጥ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ትኩረት አድርጎ የወሰነው በዳኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥልጣን ረገድ የተነሳውን ክርክር ብቻ በመያዝ በመሆኑ ወደ ጉዳዩ ሥረ ነገር አልገባም፡፡ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ግን በሥረ ነገር ረገድ የተነሳውን ክርክር ጭምር በመመርመር ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በተመሣሣይ ሁኔታ በሁለቱም ነጥቦች ላይ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ ለዚህም ነው የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱን በግልጽ በውሣኔው ላይ የገለጸው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 እንደተደነገገው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በተባለበት መዝገብ ውስጥ የሰፈረው ማስረጃ በቂ ነው የሚል ግምት ከያዘ የነገሩን ጭብጥ በማሻሻል ወይም በመለወጥ ተገቢ መስሎ የታየውን የመጨረሻ ፍርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሆነውም ይኸው ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነቱ ከንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን ጀምሮ የተደረገውን ክርክር የተሰማውን ማስረጃ በመመርመር የመጨረሻ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የንግድ አሠራር አጣሪ ኮሚሽን በመቃወሚያውም ሆነ በጉዳዩ ሥረ ነገር ላይ የሰጠው ውሣኔ ትክክል ሆኖ ስላገኘውም ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ በመሆኑም ውሣኔው በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41022 ሚያዚያ 26 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቶአል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

ብርሃኑ አመነው

ሡልጣን አባተማም

አመልካች ፡- አምባሰል የንግድ ሥራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የቀረበ የለም

ተጠሪ ፡- አቶ አብዱልቃድር ጁሀር የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ያለአግባብ መበልፀግ በሚል መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አቤቱታ ስለቀረበበት ነው፡፡

የክርክሩ አጀማመር ሲታይ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገ የሰሊጥ ሽያጭ ውል መነሻ ተጠሪ ለአመልካች የገንዘብ ክፍያ የሰጠው ቼክ ከፋይ ባንክ ዘንድ ቀርቦ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑ ተረጋግጦ በቼኩ መሠረት በአመልካች በኩል ቀርቦ የነበረው ክስ በንግድ ሕግ ቁጥር 881 መሠረት በይርጋ ጊዜ ገደብ ቀሪ በመባሉ በንግድ ሕግ ቁጥር 799 መሠረት ተጠሪ በአመልካች ሀብት ያለአግባብ በልጽጓል በሚል መነሻ ብር 2,448,250 ከጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 14% ወለድ ጋር እንዲከፍል እንዲወስን ሲል አመልካች ክስ መመሥረቱን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ክሱን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከተው የአማራ ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡ ለብይኑ የሰጠው ምክንያትም በአንድ በኩል አመልካች ቀደም ሲል በቼክ መነሻ ያቀረበው ክስ በይርጋ ታግዷል ከተባለ በኋላ ይህንኑ ቼክ መሠረት አድርጎ ያለአግባብ መበልፀግ በሚል የክስ ምክንያት በንግድ ሕግ ቁጥር 799 መሠረት ክስ ማቅረቡ ቀድሞ ከቀረበው ክስ ጋር ተመሣሣይ በመሆኑ ፍ/ቤት በይርጋ ቀሪ ነው ባለው ጉዳይ እንደገና ክስ ማቅረቡ ተገቢነት እንደሌለው፣ በሌላ በኩል ክስ የቀረበበት ገንዘብ መክፈያ ጊዜ ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም ሆኖ ክስ የቀረበው ጥር 25 ቀን 1999 ዓ.ም መሆኑን በመጥቀስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት 10 /አሥር ዓመት/ ጊዜ አልፎበታል የሚሉ ናቸው፡፡

አመልካች በዚህ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የሥር ፍ/ቤት ለንግድ ሕግ አንቀጽ 799 የተሣሣተ ትርጉም እንደሰጠ፣ የክሱ አቀራረብ ጊዜን በተመለከተ በመ/ቁ. 50554 ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ላይ ሥልጣኑ በውክልና ለአማራ ብ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠ መሆኑን ጠቅሶ ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም በብይን መዝገቡን የዘጋ ስለሆነ የይርጋ ጊዜው አቆጣጠር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1851/2/ መሠረት ተቋርጧል፤ ከዚህም በተጨማሪ የቼኩ መክፈያ ቀን የካቲት 20 ቀን 1989 ዓ.ም ቢሆንም ቼክ ቆርጦ ከሰጠ በኋላ ተጠሪው ከዚሁ በቼክ ከተሰጠው ገንዘብ ውስጥ ሚያዝያ 21 ቀን 1989 ዓ.ም ብር 70,000 /ሰባ ሺህ ብር/ እና ሰኔ 10 ቀን 1989 ዓ.ም ብር 60,000 /ስልሣ ሺህ/ ለአመልካች የከፈለ መሆኑን በመጥቀስ ይርጋ ጊዜው መታሰብ ያለበት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መሆን እንዳለበት በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ብይን እንዲሻር አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ አመልካች አለአግባብ መበልፀግን መሠረት በማድረግ ያቀረበው ክስ በንግድ ሕግ ቁጥር 799 መሠረት በድጋሚ የቀረበ ነው ሲል የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትርጉም እና ብያኔ ተገቢነትን ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ይ/ባይም በቼክ ክስ ቀርቦ በይርጋ ከታገደ በኋላ በንግድ ሕግ ቁጥር 799 ሌላ ክስ እንዲቀርብ መፍቀድ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 አኳያ የተከለከለ ስለመሆኑ የክፍያ ጊዜንም በሚመለከት ክፍያ የሚፈፀመው ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም ሆኖ ክስ የቀረበው ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም በመሆኑ የአሥር /10/ ዓመት ጊዜ ያለፈ ስለመሆኑና በመ/ቁ. 50554 የቀረበውን ክስ ፍ/ቤቱ ሥልጠን የለኝም በሚል የተዘጋ ስለሆነ በሰበር መ/ቁ. 16648 በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ይርጋ ማቋረጫ ምክንያት ሊሆን አይችልም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

የአመልካች ጠበቃ አቤቱታውን አጠናክሮ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተ ነው፡፡ ችሎቱም የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ከሕጉ አገናዝቦ መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ውሣኔ እንዲሰጥበት የተያዙት ጭብጦች ሁለት ናቸው፡፡ እነዚሁኑ በየተራ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የመጀመሪያው ጭብጥ የሥር ፍ/ቤት የንግድ ሕግ ቁጥር 799 አፈፃፀምን አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም አግባብ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በተመለከተ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው ተጠሪ ለአመልካች ቆርጦ የሰጠው ቼክ ለባንክ ቀርቦ በቂ ስንቅ የለውም ከተባለ በኋላ ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍል እንዲወስን አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ መሥርቶ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ የቼኩ የክፍያ ቀን የካቲት 20 ቀን 1989 ዓ.ም ሆኖ በቼኩ ክስ የቀረበው ነሐሴ 21 ቀን 1989 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በንግድ ሕግ ቁጥር 881 መሠረት የስድስት /6/ ወር የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ ነው በሚል በመ/ቁ. 11774 በ4/10/96 ውሣኔ መሰጠቱን ከዚያም በኋላ ያለአግባብ መበልፀግ በሚል የክስ ምክንያት ለቼኩ መሰጠት ምክንያት የሆነውን ውል እና ያልተከፈለ ቼክ ማስረጃ በማድረግ አመልካች በመ/ቁ. 50554 በ19/3/99 ዓ.ም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ማቅረቡን እና ፍ/ቤቱም የተጠሪን መልስና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቃወሚያ ከተቀበለ በኋላ በ23/5/99 ዓ.ም ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ ጠቅሶ በብይን መዝገቡን መዝጋቱን ነው።

ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ አመልካች በአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ክስ የመሠረተው የክሱ ምክንያትና ይዘትም ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ከመ/ቁ. 50554 ጋር ተመሣሣይና አንድ ነው።

በዚህ መልክ የቀረበውን ክስ የተመለከተው የአማራ ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ላለመቀበል የሰጠው ምክንያት በቼክ ክስ ቀርቦ በይርጋ ቀሪ ነው ከተባለ በኋላ ይህንኑ የክስ ምክንያትና የገንዘብ መጠን መሠረት በማድረግ ያለአግባብ መበልፀግ የሚል ክስ ማቅረብ እንዲቻል የንግድ ሕግ ቁጥር 799 ድንጋጌ የሚፈቅድ አይደለም የሚል ነው።

የዚህ ዓይነት ድምዳሜ የሕጉን ይዘትና ግላማ ያገናዘበ መሆን ወይም አለመሆኑን ለመረዳት የድንጋጌውን ይዘት እንመለከታለን።

የአንቀጽ 799ን ይዘት ከማየታችን በፊት ግን አጠቃላይ ስለቼክ የተመለከቱ ጉዳዮችን በአጭሩ እንዳስሣለን።

በመሠረቱ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትእዛዝ የያዘና ቼኩም እንደቀረበ የሚከፈል ስለመሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር 827/ሀ/ እና 854 ሥር ተመልክቷል።

እንዲሁም ቼኩ የወጣበት ቀን ከግምት ሣይገባ ቼኩ ከተፃፈበት ቀን አንስቶ በሚከተሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለክፍያ መቅረብ እንዳለበት አልፎም በቼኩ አውጭውና ሌሎች ተገዳጆች ላይ አምጪው ክስ ለመመሥረት የሚችለው ቼኩን ለማቅረብ ከተወሰነው ጊዜ ባሉት ቀጣይ ስድስት ወራት ጊዜ ስለመሆኑ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ ቁጥር 854 እና 881/1/ ይዘት ያስገነዝባሉ። እነዚህ ጥያቄዎች የሚቀርቡት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 640 እና 868/ሐ/ በተመለከተው መሠረት የቼኩ አውጪና ሌሎች የጀርባ ፊርማና እሺ ባይ በቼኩ ለተመለከተው ገንዘብ አከፋፈል ኃላፊ መሆናቸው የተደነገገውን ተከትሎ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል።

እነዚህን የሕጉ ድንጋጌዎች ተከትሎ ክፍያ ያልተፈፀመ እንደሆነ የአምጪው መብት ምን ሊሆን ይገባል የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ምላሽ የሚሰጠን የንግድ ሕጉ አንቀጽ 799 ነው። ይህ ድንጋጌ ስለሐዋላ ወረቀት በተመለከተ የተደነገገው ክፍል ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም በቼክ ላይም ተፈፃሚነት እንዳለው የንግድ ሕጉ አንቀጽ 886 በግልጽ ያመለክታል።

ስለሆነም የንግድ ሕጉ አንቀጽ 799ን ይዘት ለመረዳት ይቻል ዘንድ እንጠቅሣለን።

<u>799፡ ያላግባብ ስለመበልፀግ የሚቀርብ ክስ፡-</u> 799/1/ በሐዋላ ወረቀት ላይ የተመሠረቱት ግዴታዎቸቸው ጊዜያቸው በማለፉ ወይም በይርጋ ምክንያት የቀሩ ቢሆኑም እንኳ አውጪውና እሺ ባዩ ሕግ በማይፈቅደው አኳኋን ያለአግባብ በመበልፀግ ባገኙት ጥቅም መጠን ለአምጪው ኃላፊዎች ናቸው" ይላል።

ድንጋጌው ንዑስ ቁጥሮች ቢኖሩትም ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ይኸው ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ ድንጋጌ በግልፅ መረዳት የሚቻለው በቼኩ የተመለከተው ክፍያ ሣይፈፀም ጊዜ ያለፈበት እንደሆነ ወይም በይርጋ ቀሪ ነው የተባለ እንደሆነ የቼኩ አምጪ የቼኩ አውጪ ወይም እሺ ባይ ያለአግባብ በበለፀጉበት መጠን ኃላፊ ስለመሆናቸው ነው፡፡

ይህ ድንጋጌ ግልጽ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህንኑ ግልጽ የሆነውን የሕጉ ድንጋጌ ከንግድ ሕግ ቁጥር 881/ረ/ በማጣቀስ የሰጠው ትርጓሜ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

አንድ የሕግ ድንጋጌ ግልጽ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ትርጓሜ እንደማያሻው የሕግ አተረጓጎም መርህ ያስረዳል፡፡ ስለሆነም ቼኩን መሠረት አድርጎ በሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ክፍያ ያልተጠየቀበት ወይም በይዞታ የታገደ የሆነ እንደሆነ ይህንኑ ቼክ እንደተራ ሰነድ በማስረጃነት በማቅረብ ያለአግባብ መበልፀግ በሚል የክስ ምክንያት መክሰስ የሚቻል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ አመልካችም የዚህን የንግድ ሕግ ቁጥር 799 መሠረት በማድረግ ክስ የመሠረተ ስለመሆኑ ከመዝገቡ ይዘት መረዳት ተችሏል፡፡

ስለዚህም ክሱን በመጀመሪያ የተመለከተው የሥር ፍ/ቤት የንግድ ሕግ ቁጥር 799ን አስመልክቶ የተሣሣተ ትርጉም የሰጡ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች በመ/ቁ. 50554 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ የይርጋ ጊዜ ያቋርጣል ወይንስ አያቋርጥም? የሚለው ነው፡፡

በዚህ ረገድ የአማራ ብ/ክ/ጠ/ፍ/ቤት ለውሣኔው የሰጠው ምክንያት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት መ/ቁ.50554ን የዘጋው ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝ በሚልም ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት የቀረበው ክስ የይርጋ ጊዜን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም በሚል ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡

አመልካች የይርጋ ጊዜው በከፍተኛው ፍ/ቤት በቀረበ ክስ ምክንያት ስለመቋረጡ እና የጊዜውም ስሌት ቼኩ ሊከፈል ከሚገባበት የካቲት 20 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ መታሰብ እንዳለበት አጥብቆ ተከራክሯል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የተጠሪ ጠበቃ በሰጡት መልስ የይርጋ ጊዜ መታሰብ ያለበት ከጥር 10 ቀን 1989 ጀምሮ ስለመሆኑ ጠቅሰው ይህ ደግሞ ክስ እስከቀረበበት ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም የአሥር ዓመት ጊዜ ያለፈው መሆኑና ሥልጣን በሌለው ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ማቋረጫ ምክንያት ሊሆን እንደማይገባ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መ/ቁ. 16648 ታህሣሥ 20 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

እኛም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ከሕጉ አገናዝበናል፡፡ በመሠረቱ የክፍያው ጊዜ ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም ስለመሆኑ የሥር ፍቤት በውሣኔው አረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች በመ/ቁ. 50554 በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመሠረተው ክስ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለውም ሲል ክሱን መዝጋቱ የይርጋ ጊዜ ያቋርጣል ወይንስ አያቋርጥም የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 36730 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ማገናዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በመ/ቁ. 16648 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በመለወጥ በመ/ቁ. 36730 አስገዳጅ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በይዘቱም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ሥልጣን የለኝም በሚል ክሱን ቢዘጋውም የይርጋ ጊዜ ማቋረጫ ሊሆን እንደሚባ ለዚህም የሕግ መሠረቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥልጣን ጉዳይ መለየት በዋነኛነት የፍ/ቤቱ ኃላፊነት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር አንቀጽ 9፣ 23/1/ለ እና 231/1/ለ ድንጋጌዎችን እንዲሁም ሕገ መንግሥታዊ መብት የሆነውን ፍትህ የማግኘት መብት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ስለሆነም የዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለዚህ ጉዳይም ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/4/ን ይዘት መሠረት በማድረግ ስንመለከተው የሥር ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1851/ለ/ ጠቅሶ የሰጠው ውሣኔ አግባብነት የለውም፡፡

በመሆኑም አመልካች በመ/ቁ. 50554 ያቀረበው ክስ ህዳር 19 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሆን ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በብይን የዘጋው ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ክሱ የ10 ዓመት ጊዜ ገደብ ጥር 10 ቀን 1999 ዓ.ም ቢሆንም አመልካች አስቀድሞ ህዳር 19 ቀን 1999 ዓ.ም በመ/ቁ. 50554 የመሠረተው ክስ የይርጋ ጊዜውን አቋርጧል፡፡

ስለሆነም አመልካች በአማራ ብ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም የመሠረተው ክስ በይርጋ ጊዜ ያልታገደ መሆኑን ከፍ ሲል ከተመለከቱት መዛግብትና የሰበር ችሎቱ ውሣኔ ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ችለናል፡፡ ሲጠቃለል አመልካች ያቀረበው ያለአግባብ መበልፀግ የክስ ምክንያት ቀደም ሲል በቼክ ክስ ቀርቦበት በይርጋ የታገደ ነው በሚል እና ክሱም የአሥር ዓመት የይርጋ ጊዜ አልፎበታል ሲል የአማራ ብ/ክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ብይን እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንኑ ማጽናቱ ከፍ ሲል በዝርዝር በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 113000ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 34738 ግንቦት 22 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካችን ክስ ተቀብሎ በፍሬ ነገር ረገድ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መዝገቡን ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 48242

ጥቅምት 4 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት - ጽጌረዳ ተሻገር ቀረበች

ተጠሪዎች፡- 1. ቦጋለ መስቀሌ
2. ሚሊዮን ቦጋለ

} ጠበቃ ብሥራት መኮንን ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፍዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት በመ.ቁ. 65456 ግንቦት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ጉዳዩ 1ኛ ተጠሪ ያለበትን የብር 107,440 ዕዳ ለመክፈል እንዲያስችለው በ2ኛ ተጠሪ አማካይነት የቃል ኪዳን ሰነድ ፈርሞ ቢሰጠኝም በገባው ቃል መሠረት አልከፈለኝም በማለት አመልካች የመሠረተውን ክስ መነሻ ያደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ 2ቱም ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ዕዳውን እንዲከፍሉ ወይም ፍ/ቤቱ ኃላፊነቱ የማን እንደሆነ ለይቶ ገንዘቡ እንዲከፈለው እንዲወስንለት ሰለመጠየቁም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ተጠሪዎችም ለክሱ በሰጡት መልስ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ በውክልና ሰነዱ ላይ ያለው ፊርማ የ2ኛ ተጠሪ አይደለም፡፡ ስለዚህ በቀረበው ክስ በኂላፊነት ልንጠየቅ አይገባም በማለት በጋራ ሲከራከሩ፤ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በተለይ ባቀረበው ክርክር በውክልና ሠርተሃል እየተባልኩ ለገንዘቡ አከፋፈል ተጠያቂ የምሆንበት ምክንያት የለም ብሎአል፡፡ ከዚህ በኂላ ፍ/ቤቱ 2ኛ ተከሣሽ ፊርማውን በመካዱ ፊርማው እንዲመረመር ቢታዘዝም፤ ከሣሽ ዋናውን ሰነድ ሊያቀርብ አልቻለም የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 4 ቀን 2001 ዓ.ም በዓፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም ይህን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው አመልካች ዋናውን የውክልና ሰነድ አላቀረበም በማለት ክሱ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በሌላም በኩል ተጠሪዎች ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ መቃወሚያችን ውድቅ በመደረጉ በሕጉ አተረጓጐም መሠረታዊ ስህተት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተፈጽሞአል በማለት መስቀልኛ አቤቱታ በማቅረባቸው በዚህ ረገድም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ክርክሩን አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪዎች ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት አቅርበውት የነበረው መቃወሚያ የሥር ፍ/ቤቶች ያልተቀበሉት ቢሆንም፤ተጠሪዎች ግን መቃወሚያው ውድቅ የተደረገው ከሕጉ ውጪ ነው በማለት እየተከራከሩ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የንግድ ሕግ ድንጋጌ መሠረት አድርገው ወስነዋል የሚል የመከራከሪያ ነጥብም አንስተዋል፡፡ አመልካች ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የንግድ ሕግ ቁ. 817/1/ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተወሰነው የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ሦስት ዓመት ሲሆን ክሱ የቀረበው ደግሞ ይህ ጊዜ ከማለፉ በፊት በመሆኑ የተጠሪዎች የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡

ለክሱ መነሻ የሆነው የቃል ኪዳን ሰነድ ተፈርሞ በተሰጠበት ጊዜ እና ክሱ በቀረበበት ጊዜ መሐል ያለው ጊዜ ሲታይ የሦስት ዓመት ጊዜ አለማለፉ እርግጥ ነው፡፡ አከራካሪ የሆነው የይርጋው መቃወሚያ ለመወሰን ተገቢ የሆነው ድንጋጌ የትኛው ነው? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ የተሰፋ /ለመክፈል ቃል የሚሰጥበት/ ወረቀትን ወይም ሰነድን በሚመለከት በንግድ ሕጉ አራተኛ መጽሐፍ በአንቀጽ 2 ሥር ያሉት ድንጋጌዎች አግባብነት እንደሚኖራቸው በንግድ ሕግ ቁ. 825 በመመልከቱ ተጠሪዎች ወደ ቁ. 817 በመሄድ እና አግባብነት ያለው ድንጋጌ ንዑስ ቁ. /2/ እንደሆነ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ለዚህ ክርክራቸው ምክንያት ያደረጉት የሰነዱ አውጪ ነን፤ በሰነዱ አውጪ ላይ የሚቀርበውን ክስ በሚመለከት ግልጽ ድንጋጌ ያለው በንዑስ ቁ. /2/ ላይ ነው የሚል ነው፡፡

ለተያዘው የይርጋ ክርክር አወሳሰን ተገቢነት አለው በማለት በግራ ቀኝ ወገኖች የተጠቀሰው የንግድ ሕግ ቁ. 817 የሃዋላ ወረቀትን መሠረት በማድረግ የሚቀርበው ክስ በይርጋ ቀሪ ስለሚሆንበት ሁኔታ የሚደነግግ ነው፡፡ ንዑስ ቁ. /1/ ክሱ በሦስት ዓመት ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ሲያመለክት፤ ንኡስ ቁ. /2/ ደግሞ ክሱ በአንድ ዓመት ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ እዚህ ላይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት የጊዜዎቹ መርዘም ወይም ማጠር ሣይሆን፣ በሁለቱ ድንጋጌዎች /ንኡስ ቁጥሮች/ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ የመጀመሪያው ክሱ በእሺ ባዩ ላይ የሚቀርብ እንደሆነ ገልጾ መቅረብ ያለበት ከመክፈያው ቀን አንሰቶ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ሁለተኛው ማለትም ንኡስ ቁ. /2/ ደግሞ ክሱ የሚቀርበው በጀርባ በፈረሙ ሰዎችና በአውጪ ላይ መሆኑን በአንድ በኩል ሲገለጽ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሐዋላ ወረቀቱ / ሰነዱ/ በሚገባው ጊዜ እንቢታ ማስታወቂያ የተደረገበት ወይም “ያለኪሣራ የሚመለስ” የሚል ቃል ያለበት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ እነዚህ በንኡስ ቁ./2/ የተጨመሩ ሁኔታዎች በንኡስ ቁ./1/ የሉም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች የተከሰሱት የሰነዱ አውጪ በመሆናቸው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ሰነድ መሠረት ግንኙነት የተፈጠረው በተጠሪዎች እና በአመልካች መካከል ብቻ እንደሆነ ግን ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በሰነዱ የተመለከተውን ገንዘብ ለመክፈል”እሺ” ባዮች ተጠሪዎች እንደሆኑም መታወቅ አለበት፡፡ በሰነዱ ላይ በንግድ ሕግ ቁ. 817/2/ የተመለከቱት ሁኔታዎች አለበት አልተባለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ከእነሱ ውጪ ሌላ ሰው ያለ ይመስል የይርጋ መቃወሚያችን መታየት ያለበት በንኡስ ቁ./2/ መሠረት ነው በማለት መከራከራቸው አግባብ አይደለም፡፡ በመሆኑም ክሱ የቀረበው በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ ነው በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመቀጠል የተመለከትነው አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት የተያዘውን ጭብጥ ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው በ2ኛ ተጠሪ የተካደው በውክልና ማስረጃ ላይ ያለውን ፊርማ ለማስመርመር አመልካች ዋናውን የውክልና ሰነድ ለማቅረብ አልቻለም በማለት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የውክልና ማረጋገጫ ሰነድ የሚመለከተው ወካዩንና ተወካይን ብቻ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ጉዳይ ወካይም ተወካይም አይደለም፡፡ በመሆኑም የውክልናው ሰነድ ዋናውን አቅርብ ሊባል የሚገባው ወካይ ወይም ተወካይ እንጂ ሦስተኛ ወገን የሆነውን አመልካችን አይደለም፡፡ በሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ፍ/ቤቱ የውክልናውን ዋና ሰነድ አመልካች ማቅረብ አልቻለም ከማለት አልፎ ውክልናውን አረጋግጦ ሰነዱን ከሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተጠሪዎች መካከል የውክልና ግንኙነት የለም የሚል ማረጋገጫ አላገኘም፡፡ ይልቁንም ዋናው የውክልና ሰነዱ የሚገኘው በተጠሪዎች ዘንድ እንደሆነ የሚመለከተው መንግሥታዊ አካል እንደገለፀለት በአመልካች ክርክር ተመልክቶ እያለ ይህንኑ በዝምታ ማለፉን ነው የተገነዘብነው ከሁሉ በላይ ደግሞ ተጠሪዎች ዋናውን ሰነድ በማቅረብ የማስረዳት ሸክማቸውን ሣይወጡ የማስረዳት ሸክሙን ወደአመልካች በማዞር ወደብይን በማምራቱ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት መፈፀሙን ነው መገንዘብ የቻልነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 75930 ታህሣሥ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 65456 ግንቦት 17 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

2/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው ተጠሪዎች የውክልና ስልጣኑን በተመለከተ የማስረዳት ሸክማቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ መሆኑን ተገንዝቦ ወደ ክሱ ሥረ- ነገር በመግባት ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የማይከፍሉበት አግባብ አለ ወይስ የለም በሚለው ጭብጥ ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች ካከራከረ በኋላ ተገቢውን ይወሰን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸው ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 52269

ጥቅምት 17 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- 1. አቶ ከድር ሀጅ ሁሴን አልቀረቡም

2. ሊስ ኮሌጅ አክሲዮን ማህበር አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ጁሀር አልይ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ የአክሲዮን ድርሻን የሚመለከት ነው፡፡ተጠሪ 148,000 /አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ ብር/ ዋጋ ያለው አክሲዮን ባለቤት እንዳልሆንኩ የወሰኑበት ውሣኔ ተሰርዞ የአክሲዮን ባለመብት መሆኔ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ይህንን ገንዘብ ተጠሪ በአይነት ወይም በገንዘብ ገቢ አላደረገም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ብር 100,000, የከፈሉ መሆኑ በመመሥረቻ ጽሑፍ የተገለፀ ሲሆን ብር 95,000 የከፈሉ ስለመሆኑ ደግሞ ሉሲ ኮሌጅ አክስዮን ማህበር የሰጣቸው ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ይህንን ድርሻ በቃለ ጉባዔ እንዳልተከፈለ ለመቀየር መሞከራቸው ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ የአክሲዮን ማህበሩ ሲቋቋም ከጠቅላላ ካፒታል ብር 100,000 ከዚያ በኋላ ብር 95,000 መክፈላቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህንን መብት ለማሻሻል የተሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ተጠሪ ክስ ያቀረበው ውሣኔ ከተላለፈ በኋላ አንድ ዓመት አሣልፎ ነው፡፡ እኛ ያነሣነውን የይርጋ መቃወሚያ አላግባብ ውድቅ ተደርጎብናል፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የአክሲዮን ማህበር ቃለ ጉባዔ ጉዳዩን በአጀንዳነት ይዞ ያስተላለፈው ውሣኔ የለም፡፡ የእኔን አክሲዮን ድርሻ ዝቅ አድርጎ በቃለ ጉባዔው መመዝገቡ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት የለም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ በተመለከተም የራሱን የመከራከሪያ ነጥብ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ለመመሥረቻ ጽሑፍና በአክሲዮን ሼር ሰርቲፊኬት የተገኘውን መብት በማስመልከት ዝቅ ለማድረግ የአክሲዮን ማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ የተሰጠው ውሣኔ በአንድ ዓመት ይርጋ ይገደባል በማለት ያቀረቡትን ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ያለፉት በመዝገቡ ዋና የመከራከሪያ ጭብጥ የሆነውን ነጥብ አጠቃላይ ባህሪና የንግድ ሕግ ቁጥር 359/1/ ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓለማ በማገናዘብ መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡

ተጠሪ በዚህ መዝገብ ያቀረቡት ክስ የባለአክስዮኖች ጉባዔ የሰጠው ቃለ ጉባዔ እንዲሻሻልን ወይም ቀሪ እንዲሆን ሣይሆን በመሠረታዊነት የአክሲዮን ማህበሩ መሥራችነታቸውና ለአክሲዮን ማህበሩ በተረጋገጠ ማስረጃ ክፍያ የፈፀሙባቸው የአክሲዮን ድርሻ የሚጎዳ ተግባር ባአክሲዮን ማህበሩ እየተፈፀመ ስለሆነ ይህንን መብታቸውን ለማስከበር ነው፡፡ በዚህ መንገድ የሚቀርብ ክስ በንግድ ሕግ ቁጥር 416/2/ የሚሸፈንና ቀሪ የሚሆን አይደለም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኅዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ጥሩወርቅ ዘገኑ - ጠበቃ አቶ በጋሻው ኃ/ገብርኤል ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- አቶ ግደይ አብርሃ - ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ወረደ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በቼክ ምክንያት የተነሣን ክርክር የሚመለከት ሆኖ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቼክ ቼኩን ለመስጠት ምክንያት ከሆነውና ግራ ቀኙ የካቲት 09 ቀን 2001 ዓ.ም. ካደረጉት ውል አንፃር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በመለየት የሥር ፍ/ቤት የሰጡትን ዳኝነት አግባብነት ለማየት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

ምንም እንኳ የአሁን አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በዋስትና በተሰጠውና ፊርማው የእኔ ባልሆነ ቼክ በሚል እንደ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር ያቅረቡ እንጂ ይኸው ቼክ በእርሳቸው ለተጠሪ የተሰጠ ስለመሆኑ ከሥር ፍ/ቤት ጀምሮ የተደረገው ክርክርና የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ አስረጅ ናቸው፡፡

ሆኖም ለቼኩ ምክንያት የሆነው ግራ ቀኙ የካቲት 09 ቀን 2001 ዓ.ም. ከግንባታ ሥራ ጋር በተያያዘ ያደረጉት ስምምነት ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

አከራካሪ የሆነውና የሥር ፍ/ቤቶችን ዳኝነት አግባብነት ለማየት ያስፈለገው ቼኩ በክፍያ ሰነድነቱ ብቻ ተለይቶ የሚታይ ነው ወይስ ለቼኩ መሰጠት መነሻ ከሆነው የግራ ቀኙ ስምምነት ጋር የሚለውን ከንግድ ሕግ ቁጥር 717 አንፃር ለማየት በሚል ነው፡፡

ይህንን ጉዳይ በሚመለከት የሥር ፍ/ቤት መመርመር ሳያስፈልገው ቼኩ በላዩ ላይ የያዘውን የገንዘብ መጠን እና ከቼኩ መስጠት በኋላ አመልካች በተለያየ ጊዜ የፈፀሙትን ክፍያ አቀናንሶ ቀሪውን ብር 180,000.00 /አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ/ ብር ከሀጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

ሆኖም ለዚህ ቼክ ምክንያት የሆነው የግራ ቀኙ ያደረጉት ውል መሆኑን የአሁን አመልካች በመከላከያነት ያቀረቡት ሲሆን ተጠሪ ይህንኑ የካዱት አይደለም ይህም ከሆነ ከቼኩ በስተጀርባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው የስምምነት ጉዳይ ከቼኩ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤት በቼኩ ላይ ብቻ ተወስኖ የሰጠው ዳኝነት በንግድ ሕግ ቁጥር 717 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በዚሁ መሠረት የተሰጠው ዳኝነት አግባብ አለመሆኑን ጠቅሰው ቼኩ ከውሉ ጋር ተጣቅሶ ሊታይ ይገባዋል የሚለውን ክርክር በሚመለከት አመልካች ቼኩ የተሰጠው ተጠሪ እንደውሉ ግዴታውን የሚፈጽሙ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን ተጠሪ በውሉ መሠረት ግዴታቸውን አልተወጡም፣ ሥራው ግድፈት አለበት ይህንኑ ከግንባታ ፈቃድ ውጭ የሚለውን አላስተካከለም በማለት ያቀረብኩት ሳይታይልኝ ታልፏል በማለት ላቀረቡት ክርክር ተጠሪ በተራው በውሉ መሠረት የግንባታ ሥራው ተፈጽሞ የአማካሪ መሐንዲሱ ባለበት በ22/6/2002 አመልካች ፈርመው ተረክበዋል፡፡ ለዚህም በማስረጃነት ሰነዱ ቀርቧል በማለት መልስ ሲሰጥ አመልካች ለዚሁ ማስተባበያ የሚሆን የፍሬ ነገር ክርክር ጎዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ ልስ ያቀረቡ ሲሆን የክርክሩ ይዘት ቼኩ ዋጋ እንዳይኖረው የሚያደርግ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ እንደ አባባላቸው ከሆነም እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት እራሱን የቻለ አቤቱታ እንዲያቀርቡ ከሚረዳ በቀር ክርክር ያስነሳውን የቼክ ጉዳይ ከንግድ ሕግ ቁጥር 717 አንፃር እንዲታይ በማድረግ በዚህ ነጥብ ላይ በሥር ፍ/ቤት ታይቶ ውሣኔ እንዲሰጥበት ለማድረግ የሚያበቃ ክርክር አይደለም፡፡ ይኸው ጉዳይ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ሥር ፍ/ቤት ለመመለስ የሚቻልበት ምክንያት ካልተገኘ ደግሞ የሥር ፍ/ቤት ይህንኑ ማጣራት ሳያስፈልገው በቼኩ ላይ ተመርኩዞ ውሣኔ መስጠቱ ከውጤት አንፃር የሕግ ስህተት ፈጽሟል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ይህንን ሁሉ በማየት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የከፍተኛው ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በክ/መ/ቁ. 144516 በ28/9/2001 ዓ.ም. እና በመ/ቁ. 85254 የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጡትን ፍርድ እና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንተናል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ክርክር ሁኔታ እስከሚታወቅ ድረስ የሰበር መ/ቁ. 55077 አፈፃፀሙ ታግዶ እንዲቆይ በሚል ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 52667

ታህሳስ 12 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ ነ/ፈጅ ዕዮን በላይ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ በባህር ላይ እቃ ሲጓጓዝ ለደረሰ ጉዳት የካሳ አከፋፈልን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ የደንበኛቸው ንብረት የሆነና የመድን ሽፋን የሰጠባቸውን ሀምሳ ሳጥን መስታወት ክቻይና በመጫን ጅቡቲ ወደብ ለማድረስ በተዋዋለው ውል መሠረት ጅቡቲ ወደብ ካደረሳቸው አምሳ ሳጥን መስታወት ውስጥ አስር ሳጥን መታወት ላይ በአኗኗር ችግር ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል፡፡ እኔ ለደንበኛየ የመስታወቱን ዋጋ ብር 101,465 /አንድ መቶ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሳ አምስት ብር/ የከፈልኩ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ ተከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ እንዲተካ ውሳኔ ይሰጥልኝ ለማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ የእቃዋቹን ደህንነት በማረጋገጥ ያልጫንኩ በመሆኑ ሐላፊነት የለብኝም፡፡ ለእቃዎቹ ጉዳት ሐላፊ ነህ የምባል ከሆነ የእቃዎቹ ዋጋ ስለማይታወቅ በጥቅል ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ ብቻ ታስቦ እንዲከፈለው ይወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በእቃው ላይ ጉዳት የደረሰው በኮንቴነሩ ላይ በተደረገው ደካማ አያያዝ በመሆኑን በሰርቬይ ሪፖርት የተረጋገጠ በመሆኑ ተከሳሽ /ተጠሪ/ በእቃዎቹ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሐላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የካሳውን መጠን በተመለከተ የእቃው ዋጋ ያልታወቀ በመሆኑ በባህር ህግ አንቀጽ 198 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለአንድ ሳጥን ብር 500 /አምስት መቶ ብር ሒሳብ ለአስሩ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች የካቲት 8 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የአመልካች ደንበኛ ለተጠሪ የጭነት ትዕዛዝ የሰጠው የእቃውን ትክክለኛ ዋጋ፣ ከባንክ "በሌትር ኦፍ ክሬዲት" ክፍያ የተፈፀሙትን ሰነድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመግለጽና ስነድን በማያያዝ ነው፡፡ ለመስተዋቱ 21,499.94 የአሜሪካን ዶላር የተከፈለ መሆኑን ተጠሪ ያውቃል፡፡ ተጠሪም በሰጡት ቢል ኦፍ ሌዲንግ የኤል ሲ ቁጥር /L/C No.NIB /HGB/ 044/2007/ ክፍያ የተፈፀመበት እቃ መሆኑን ገልጿል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እቃውን ሲጭኑ በባንክ በኩል በተከፈተ "ኤል ሲ" ለእያንዳንዱ መስተዋት ምን ያህል የውጭ ምንዛሬ እንደተከፈለት ያውቅ ስለነበር ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የባህር ህግ 198 ንዑስ አንቀጽ 3 ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የባህር ህግ ቁጥር 198 ንዑስ አንቀጽ 2ን በመጥቀስ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የአመልካች ደንበኛና የእኛ ግንኙነት በባህር ላይ እቃ ማጓጓዣን የሚመለከት ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች የባህር ህጉን መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአመልካች ደንበኛ ለተጠሪ የሚጭነው እቃ በውጭ ምንዛሬ በባንክ በኩል ክፍያ የተፈፀመበትን የኤል.ሲ ዶክመንት የሰጠውና ተጠሪም ለአመልካች ደንበኛ በሰጠው የባህር እቃ መጫኛ ሰነድ /ቢል ኦፍ ሌዲንግ/ ለእቃዎቹ በባንክ በኩል ክፍያ የተፈፀመበትን የኤል. ሲ ቁጥር ማለትም /L/C No.NIB /HGB/ 044/2007/ የጠቀሰ መሆኑን አመልካች በሰበር አቤቱታው የገለፀ ሲሆን ተጠሪ ለአመልካች የሰጠሁት /ቢል ኦፍ ሊዲንግ/ ለእቃው የአመልካች ደንበኛ በንብ ባንክ በኩል የውጭ ምንዛሬ የከፈለበትን "ሌተር ኦፍ ክሬዲት" ቁጥር አይጠቅስም፣ የባንክ ሌተር ኦፎ ክሬዲት ሰነድ ከጭነት ማዘጋጀው ጋር አልተሰጠንም የሚል መልስ አላቀረበም፡፡ ይህም የአመልካች ደንበኛ በንብ ባንክ በኩል ለእቃዎቹ በውጭ ምንዛሬ የከፈልኩትን የሌተር ኦፍ ክሬዲት ለተጠሪ የቀረበለት መሆኑን እንዳመነ የሚያስቆጥረው መሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት 234 ንዑስ አንቀጽ 1 /ሠ/ የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ የአመልካች ደንበኛ የሆነውን አምሳ ሳጥን መስታዎት ስጭን የእያንዳንዱ ሳጥን መስታወት ዋጋ በነጠላና የእቃው ዋጋ በጥቅል ስለማላውቀው ለእቃው መክፈል የሚገባኝ ካሳ በጥቅል ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ መሆን ይገባዋል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የአመልካች ደንበኛ በተጠሪ የጭነት ትዕዛዝ ለሰጠበት እቃ የተከፈለው ዋጋ በውጭ ምንዛሬና በንብ ባንክ በኩል በተከፈተ ሌተር ኦፊ ክሬዲት እንደሆነ ይህንንም ተጠሪ በቢል ኦፍ ሌዲንግ ላይ የገለፀ መሆኑ ያልተስተባበለና ያልተካደ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ለእቃው በባንክ በኩል በውጭ ምንዛሬ ክፍያ የተፈፀመበትን ሰነድ ተጠሪ የማያውቀውና በባህር ማጓጓዣያ ሰነድ ላይ የባንኩን "ሌተር ኦፍ ክሬዲት ቁጥር" የተገለፀው ከሆነ የባህር ህግ አንቀጽ 198 ንዑስ አንቀጽ 1 ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ አይደለም፡፡ ለዚህ ጉዳይ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ በባህር ህግ አንቀጽ 198 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ተጠሪ ለእቃዎቹ በንብ ባንክ በኩል በተከፈተ "ሌተር ኦፍ ክሬዲት" የተከፈለውን የውጭ ምንዛሬ ክፍያ አውቆና "የሌተር ኦፍ ክሬዲቱን" ቁጥር ለአመልካች ደንበኛ በሰጠው "ቢል ኦፍ ሊዲንግ" የእቃ መጫኛ ሰነድ ገልጾ እያለ የባህር ህግ ቁጥር 198 ንዑስ አንቀጽ 1ን በመጥቀስ የእቃው ዋጋ ስለማይታወቅ የአንድ ሳጥን መስታዎት ዋጋ ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ ሒሳብ ተጠሪ ለአመልካች ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሳኔና ከፍተኛው ፍ/ቤት ሳያርም ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካች ደንበኛ በንብ ባንክ በኩል በከፈቱት "ሌተር አፍ ክሬዲት" በእቃዎቹ የከፈሉትን ዋጋ በማጣራትና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች አስቀርቦ በመመርመር ተጠሪ ለአመልካች ሊከፈለው የሚገባውን የካሳ መጠን እንዲወስን ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሶ/በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 57288

መጋቢት 19 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ሰለሞን ፍቅሬ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. አቶ አሸበር ታደሰ ቀረቡ

2. ሽብሩ አራርሶ
3. ጌታቸው ገልቹ ጠበቃ አዲስ ወልዴ ቀረቡ
4. ጥሩነሽ ዲያሶ
5. ወርቁ ፍንጢ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ መብት አለን ባዮች አቤቱታ የሚያቀርቡበትንና አቤቱታው የሚመረመርበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች የፍርድ ባለመብት በመሆን ባሁኑ 1ኛ ተጠሪ ላይ በፍርድ ባለእዳነታቸው የአፈፃጸም ማመልከቻ በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአስከፈተ በሁዋላ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በፍርድ ያገኘው ገንዘብ እንዲፈፅምለት አቤቱታ አቅርቦና የፍርድ ባለእዳውም ፍርዱ የማይፈጸምበትን ምክንያት ያላስረዱ በመሆኑ የፍርድ ባለመብት የሆነው አመልካች ከአክሲዮን ማህበሩ ንብረት ንብረቱ ተገምቶ የባለእዳው ድርሻ በጨረታ ተሸጦ ለእዳው ገቢ እንዲሆን አፈፃጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አመልክቶ አፈፃጸሙ በቀጠለበት ሁኔታ የአሁኑ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች አፈፃጸሙ በአክሲዮን ማህበሩ ሊቀጥል የማይገባበት ምክንያት ዘርዝረው አፈጻጸሙ እንዲቆም ከላይ በተጠቀሰው ስነ ስርዓት መሰረት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት በእነዚህ ተጠሪዎች የቀረበውን ተቃውም ለአመልካችና ለፍርድ ባለእዳ(የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ) እንዲደርስ አድርጎአል፡፡አመልካችና የፍርድ ባለእዳም የተቃውሞ አቤቱታ አቅራቢዎች ተቃውሞ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑንና የተቃውሞ አቤቱታውም የቀረበው የአፈጻጸም ሂደቱን ለማስናከል ስለመሆኑ ጠቅሰው አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የተቃውሞ አቤቱታ አቅራቢ የሆኑት የአሁኑ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የአክሲዮን ማህበሩ አባል መሆናቸውን መስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም የማህበሩ አባላት ከአካሄዱት ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ላይ መረዳት ይቻላል በሚል ምክንያት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አልፎ በዋናው ጉዳይ ላይ ብይን ሰጥቷል፡፡ በዋናው ጉዳይ ላይ የሠጠው ብይንም ሰላም እሸት የተባለ ፋብሪካ በአንድ አባል ድርሻ ምክንያት ሊሸጥ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ፋብሪካው የጋራ ንብረት ነው፣የ1ኛ ተጠሪ እዳ የግሉ ሀኖ በግሉ የሚጠየቅበት እንጂ የማህበሩ አባለት ሁሉ የሚጠየቁበት ጉዳይ አይደለም፣ለግለሰብ እዳ ደግሞ መያዝ የሚቻለው የባለእዳውን ድርሻ ብቻ ስለመሆኑ በንግድ ሕጉ ተመለክቷል የሚሉትን ምክንያቶችን በመዘርዘር ንብረቱ በጨረታ ሊሸጥ የሚገባው ሀኖ አልተገኘም፣ሆኖም የቀረበው የፋብሪካ ግምት ብር 582,637.20 (አምስት መቶ ሰማኒያ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር ከሃያ ሳንቲም) መነሻ ሀኖ ለማህበሩ አባላት ተከፋፍሎ የፍርድ ባለእዳው በፋብሪካው ያላቸውን ድርሻ የማህበሩ አባላት ለፍርድ ባለመብት ሰጥተው ፋብሪካውን ሊያስቀሩት ይገባል በማለት የጨረታ ሂደቱ እንዲቆም ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች ሕጋዊ የማህበሩ አባላት ናቸው ተብሎ የተወሰነው ተቀባይነት ባለው ማስረጃ አይደለም፣የማህበሩ አባላት ቁጥርም አራት እንጂ አምስት አይደለም፣የፋብሪካው የመሃንዲስ ግምት መነሻ ተደርጎ የፍርድ ባለእዳ ድርሻን የማህበሩ አባላት ለአመልካች ከፍለው ፋብሪካውን ያስቀሩ ተብሎ መወሰኑንም የወቅቱን የገበያ ዋጋ ባላገናዘበ መልኩ ከመሆኑም በላይ የአመልካችን ፍርድ ይፈጸምልኝ መብቱን የሚያጣብብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያስችላቸው መብት አላቸው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውንና ተያያዥ ነጥቦችን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው መልሳቸውን በጽሑፍ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በቅድሚያ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ጠበቃ የአመልካች ክርክር በፍሬ ነገር ላይ የተመሰረተ እንጂ በሕግ ስህተት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው አይደለም በማለት ያቀረቡትን ተቃውሞ ተመልክተናል፡፡ይህ ሰበር ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ሥልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙ ሲረጋገጥ ማረም መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለውም ሰበር ችሎቱ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክርን መሰረት ያደረገ ጉዳይ መመልከትና ማረም የማይችል መሆኑን ነው፡፡ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ክርክር እያቀረበ ያለው ለጉዳዩ የቀረበው ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ነው፣የአከራካሪው ንብረት የጋራ ባለሃብቶች እነማን እንደሆኑ በሕጉ አግባብ ሊቀርብ የሚችል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ አይደለም በሚል እንጂ ማስረጃው ታዓማኒነት የሌለው ነው በሚል አይደለም፡፡እንዲህ ከሆነ ለጉዳዩ በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠ ማስረጃ መቅረብ ያለመቅረቡና የንብረቱ የጋራ ባለሃብቶች እነማን ናቸው? የሚለው ጥያቄ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን በሕገ መንግስቱ ፣በንብረትና በንግድ ሕጎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ባላቸው አዋጆች መሰረት ታይቶ ምላሽ የሚያገኝ የሕግ ጥያቄ በመሆኑ በሰበር ችሎት የሚታይ ስለሆነ በዚህ ረገድ የቀረበው ተቃውሞ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ በቀዳሚነት የተያዘው ጭብጥ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያስችላቸው መብት አላቸው ሲል የስር የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰነው ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን ውድቅ ያደረገው ተጠሪዎች የማህበሩ አባል ስለመሆናቸው ማህበሩ መስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም ከአደረገው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ተገንዝቤአለሁ በሚል ምክንያት መሆኑን በውሳኔው ላይ በግልፅ አስፍሯል፡፡አከራካሪው ፋብሪካ በአክሲዮን የተቋቋመ ኃላ.የተ.የግል ማህበር መሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ነው፡፡አክሲዮን ማህበሩ ሲቋቋም ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ ከተጠቀሱት ተጠሪዎች ጋር በመሆን አባል የነበሩት አቶ ጸጋዬ ሐጎስ የተባሉ ሰው መሆናቸው ያላከራከረ ሲሆን ግራ ቀኙ እየተከራከሩ ያሉት የማህበሩ የጋራ ባለሃብቶች ቁጥር፣አቶ ጸጋዬ በማህበሩ ያላቸው የአክሲዮን መጠንና ለ4ኛ እና ለ5ኛ ተጠሪዎች አክሲዮናቸውን ማስተላለፍ አለማስተላለፋቸው እንዲሁም እነዚህ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ከአቶ ጸጋዬ የገዙት የአክሲዮን መጠን፣ይኸው የአክሲዮን ማስተላለፍ ሁኔታ በሕጉና በማህበሩ መመስረቻ ፁሑፍና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተከናወነ መሆን ያለመሆኑን ጉዳይ ነው፡፡

በመሰረቱ የአክሲዮን ድርሻ አንድ የተፈጥሮ ወይም ሕግ ወለድ ሰው ካፒታሉ አስቀድሞ በታወቀ በአክሲዮን በተከፍለና ለዕዳውም ንብረቱ ብቻ ዋስትና በሆነ የአክሲዮን ማህበር ውስጥ ያሉትንና በባለቤትነት የያዛቸውን አክሲዮኖች ብዛትና ዋጋ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አንድ ባለአክሲዮን በአክሲዮን ማህበሩ ውስጥ በባለቤትነት የያዛቸው አክሲዮኖች የራሣቸው ልዩ ባህሪና ውጤት ያላቸው ግዙፍ ያልሆኑ ሃብቶች ናቸው፡፡ በአገራችን ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸው ሁለት አይነት አክሲዮኖች የራሣቸው ልዩ ባህሪና ውጤት ያላቸው እንዳሉ የንግድ ሕግ ቁጥር 325 (1) ይደነግጋል፡፡

የመጀመሪያው አይነት አክሲዮኖች “ለአምጭው ተብሎ የተፃፈባቸው አክሲዮኖች ናቸው፡፡ ለአምጭው ተብሎ የተፃፈበት አክሲዮን እንደማንኛውም ተላላፊ የንግድ ሰነዶች ናቸው፡፡ ለአምጭው ተብሎ የተፃፈባቸውን አክሲዮኖች ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ እንደማንኛውም ተላላፊ የንግድ ሰነድ የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰነዱን /ሼር ሰርተፊኬቱን/ አሳልፎ በመስጠት ያለአንዳች አይነት አሰራር /ፎርማሊቲ/ ማከናወን እንደሚቻል ከንግድ ሕግ ቁጥር 340(1) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛዎቹ አይነት አክሲዮኖች የባለአክሲዮኑ ስም የተፃፈባቸው አክሲዮኖች ናቸው፡፡ የባለአክሲዮኑ ስም የተፃፈበቸው አክሲዮኖች እንደማንኛውም ተላላፊ የንግድ ሰነድ የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰነዱን /ሼር ሰርተፊኬቱን/ አሳልፎ በመስጠት ብቻ ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ አይቻልም፡፡ ስም የተፃፈባቸውን አክሲዮኖች ለማስተላለፍ አክሲዮኖቹ ለሌላ ሰው የተላለፉ መሆኑን በአክሲዮን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኘው የአክሲዮን መዝገብ ማስመዝገብ አስፈላጊ እንደሆነ ከንግድ ሕግ ቁጥር 341 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ክርክር የቀረበበት የንግድ ድርጅት አይነቱ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን የዚህ አይነት ማህበር አክሲዮኖች ለሌላ ሰው የሚተላለፉበት አግባብ በንግድ ሕጉ ከቁጥር 522 እስከ 524 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡የን/ሕ/ቁጥር 522 በተለይ ሲታይም የአክሲዮኖቹ መተላለፍ በጹሑፍ የተረጋገጠ መሆን እንዳለበት፣መተላለፉም በአክሲዮኖቹ መዝገብ ላይ ካልተጻፈ በቀር ለማህበሩና ለሶስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል በሕጉ በአስገዳጅነት ተደንግጓል፡፡የን/ሕ/ቁጥር 523 በመተዳደሪያ ደንቡ ተቃራኒ ቃል ከሌለ በቀር አክሲዮኖች በማህበተኞቹ መካከል ያለገደብ ሊተላላፉ የሚችሉ መሆኑን፣አክሲዮን ለባእድ ሰው የሚተላለፍበትን አግባብም የተወሰነ ስለመሆኑ ያሳያል፡፡የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር ሶስት ደግሞ ማህበርተኞቹ አክሲዮኑ እንዲተላለፍ የተስማሙበት ውሳኔ በንግድ መዝገብ ላይ እንዲመዘገብ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ኃይለ ቃል ባለው አገላለፅ አስቀምጧል፡፡እንግዲህ በህጉ ረገድ ኃላ.የተ.የግል ማህበር የአክሲዮን ድርሻ የሚተላለፍበት አግባብ በግልፅ ከተቀመጠ የአንድ የማህበሩ አባል የአክሲዮን ድርሻ ለሌላ መተላለፍ አለመተላለፉ መረጋገጥ ያለበት በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በሚያሳይ ማስረጃ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ የአቶ ጸጋዬ የአክሲዮን ድርሻ ለ4ኛ እና ለ5ኛ ተጠሪዎች መተላለፉን ያሳያል የተባለው መስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም የማህበሩ አባላት ያደረጉት ቃለ ጉባኤ ነው፡፡ሆኖም ይኸው ማህበረተኞቹ የተሰማሙበት ውሳኔ በንግድ ሕግ ቁጥር 523(3) አግባብ በንግድ መዝገብ ላይ እንዲመዘገብ የተደረገ መሆን ያለመሆኑን የስር ፍርድ ቤት በተገቢው መንገድ አላረጋገጠም፡፡ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የአክሲዮኑ መተላለፍ የማህበሩን መመስረቻ ጹሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ባገናዘበ መልኩ የተከናወነ መሆኑን ገልጸው ቢከራከሩም የመስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም ቃለ ጉባኤ ግን በሕጉ አግባብ እንዲመዘገብ የተደረገ ስለመሆኑ ተረጋግጧል የሚል ክርክር በዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስ ላይ ያነሱ ሲሆን አመልካች ደግሞ ይህ እውነትነት የሌለው መሆኑን ጠቅሶ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡እንዲህ ከሆነ የስር ፍርድ ቤት ቃለ ጉባኤውን በሕጉ አግባብ የተመዘገ መሆኑን ሳያጣራ ማስረጃነቱን ዋጋ ሰጥቶ ውሳኔ መስጠቱ የፍርድ አካሄዱን የተሟላ ባደረገ መልኩ አይደለም፡፡በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚገለጸው እንደተጠበቀ ሁኖ ቃለ ጉባኤው በማስረጃነቱ ሕጋዊ ዋጋ ሊሰጠው የሚችለው በማህበርተኞቹ ስምምነት የተደረሰበት በመሆኑ ብቻ ሳይሆን በንግድ መዝገብ መመዝገቡም በሚገባ ሲረጋገጥ ነው፡፡አንድ ፍርድ ቤት በተከራካሪ ወገኖች የሚቀርበውንና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በመቀበል ፍትሓዊ ዳኝነት መስጠት ያለበት መሆኑን በፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ላይ ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል እንዲሁም ስለፍርድ አሰጣጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ሐቅ ሲሆን አግባብነት ያለው ማስረጃ ሳይቀርብና ጉዳዩ በአግባቡ ሳይጣራ የሚሰጠው ውሳኔ የፍርድ አካሄዱን የተሟላ የማያደርግና በዳኝነት አሰጣጥ ሥርዓት ተቀባይነት የሌለው አካሄድ ነው፡፡በመሆኑም ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የተከራካሪ ወገኖች ሲሆን ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ መቅረብን ማረጋገጥና ወደ እውነት መድረስ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ራሱ በማስረጃ አቀራረብ ረገድ ተካራካሪ ወገኖችን ማገዝና ተገቢውን ማጣራት ማድረግ ያለበት መሆኑ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓቱ የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም መስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም የማህበሩ አባለት አደረጉ የተባለው ቃለ ጉባኤ የተመዘገበ መሆን ያለመሆኑ በተገቢው መንገድ ሳይጣራ ቃለ ጉባኤው መኖሩ ብቻ በመረጋገጡ ይኸው የሰነድ ማስረጃ እንዳለ የማስረጃነት ዋጋ በበታች ፍርድ ቤቶች መሰጠቱ በማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝነተናል፡፡በዚህም ምክንያት ይህ ሰነድ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደገና ተጣርቶ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ እንዲታይ ማድረጉ ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡

በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት አጣርቶ የሚደርሰው ውጤት ከዚህ በፊት የደረሰበትን ድምዳሜ የማያስለውጠው ከሆነ የስር ፍርድ ቤት የፋብሪካውን የመሃንዲስ ግምት መነሻ ተድርጎ በማህበሩ አባላት እንዲከፋፈልና የፍርድ ባለእዳውን ድርሻ የሥር ተቃውሞ አቅራቢ የሆኑ የማህበሩ አባላት ለአመልካች ከፍለው ፋብሪካውን እንዲያስቀሩ ተብሎ የጨረታው ሂደት እንዲቆም የመደረጉን አግባብነትም ከወዲሁ መመልከቱ አስፈላጊ ሁኖ አግኝተናል፡፡የስር ፍርድ ቤት የፍርድ ባለእዳው አክሲዮን ድርሻ በማህበሩ አባላት ለአመልካች እንዲከፋፈልና ፋብሪካውን እንዲያስቀሩ ብሎ መወሰኑ ማህበሩ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደመሆኑ መጠን ሊቋቋም የሚችለው የመቀራረብና የመተማመን ሁኔታዎች ባላቸው ሰዎች መካከል ነው የሚለው እሳቤ ሲያዝ ከዚሁ የማህበሩ ልዩ ባሕርይ አንፃር ሲታይ ተገቢ ነው ቢባል እንኳ የፋብሪካ ዋጋ ሊሆን የሚችለው ግን የመሐንዲሱ ግምት ሳይሆን የወቅቱ የገበያ ዋጋ ነው፡፡በመሆኑም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባል የሆነ የአንድ የማህበር አባል የግል እዳ ከአለበት አክሲዩኑ ለእዳው እንዳይሸጥ የሚከለክል ሕግ የሌለ መሆኑ ከን/ሕ/ቁጥር 522፣523 እና 524 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡እነዚህ ድንጋጌዎች ከማህበሩ ልዩ ባሕርይ አንፃር የአንድ የማህበሩ አባል አክሲዮን ሲሸጥ ቅድሚያ መብት ለማህበሩ አባላት እንዲሰጥ ከሚያሳዩ በቀር የማህበሩ አባላት አክሲዩኑን ወይም የማህበሩ ንብረት በመሐንዲስ ግምት መሰረት እንዲያስቀሩት መብት የሚሰጡ አይደሉም፡፡የአንድ ንብረት ሕጋዊ ባለቤት መሆኑ የተረጋገጠ ሰው ንብረቱ በእዳ ምክንያት ሲሸጥ የወቅቱን የገበያ ዋጋ እንዳያገኝ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም፡፡የፍርድ ባለእዳ ንብረት በጨረታ የሚሸጥበት አግባብ በፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርኣት ሕጋችን የመደንገጉ አንዱ ዓላማም የንብረቱን የገበያ ዋጋን በማረጋገጥ የፍርድ ባለመብትና የፍርድ ባለእዳን መብት ለመጠበቅ ነው፡፡የአንድን ንብረት የመሐንዲስ ግምት እንደትክክለኛ የገበያ ዋጋ መውሰድ የማይቻል ሲሆን በመሐንዲሱ ግምት ብቻ ንብረቱ እንዲሸጥ ማድረግ የንብረቱ ባለቤትን መብት ከማጣበቡም በላይ የንብረቱ ግምት ከፍርድ ባለእዳው ከሚፈለገው ገንዘብ ያነሰ ከሆነ የፍርድ ባለመብትን መብት ጭምር የሚያጣብበት አጋጣሚ ሰፊ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የፋብሪካውን ግምት መነሻ በአደረገ መልኩ ፋብሪካው ለማህበርተኞቹ እንዲከፋፈልና የፍርድ ባለእዳውን ድርሻ ተጠሪዎች ከፍለው ፋብሪካውን ያስቀሩ በማለት የደረሰበት ድምዳሜም ሕጋዊ መሰረት የሌለው ነው፡፡በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ዝርዝር ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03309 የካቲት 26 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77893 መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ክርክር ያስነሳው ማህበር አባላቱ ስንት እንደሆኑ፣እንያንዳንዱ አባል ያለውን የአክሲዮን ብዛት፣4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የማህበሩ አባል መሆን ያለመሆናቸውን፣በሕጉ አግባብ ተቀባይነት ያለው ቃለ ጉባኤ መኖር ያለመኖሩን(የመስከረም 18 ቀን 1999 ዓ/ም ቃለ ጉባኤ በሕጉ አግባብ መመዝገብ አለመመዝገቡን)፣እነዚህ ተጠሪዎች አባል ሁነው ከሆነም እያንዳንዳቸው የገዙት የአክሲዮን ብዛት ስንት እንደሆነ እና ሌሎች ለጉዳዩ ፍትሓዊ አወሳሰን አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ጭብጦችን በመያዝና ማጣራቶችን በማድረግ አመልካች ተጠሪዎች ጣልቃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመግባት የሚችሉ አይደሉም በማለት ያቀረበውን ተቃውሞ እንዲመረምርና ተገቢ ነው ያለውን ብይን እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት ለጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መለሰንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ለአደረጉት ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ - አ.ማ ጠበቃ ማረን ወንዴ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ተመስገን ማሞ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ባህር ላይ በሚደረግ የእቃ ጉዞ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበትን ወገን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ መጋቢት 25 ቀን 1999 ዓ/ም የመሰረተው ክስ ይዘት ፣ ንብረትነቱ የደንበኛው የቻይና የኤሌክትሪክ ዋየርና ኬብል አስመጪና ላኪ ድርጅት የሆነው ኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ከቻይና ሻንጋይ ወደብ በጅቡቲ ይርጋለም ዲላ ሀገረ ማርያም ፕሮጀክት ድረስ ተጓጉዞ እስኪመጣ ድረስ ለሚያጋጥም አደጋ በፖሊሲ ቁጥር ኤስ ኤን141 ኤም አር ኦኤ/10776102 የባህር ላይ ጉዞ የመድን ሽፋን መስጠቱን ፣ አመልካች እቃውን ከቻይና ሻንጋይ ወደብ አጓጉዞ ጅቡቲ ለማድረስ ግዴታ መግባቱን ፣ አመልካች እቃውን ለተጠሪ ደንበኛ ከማስረከቡ በፊት ጅቡቲ ወደብ ላይ በሚራገፍበት ወቅት የመድን ሽፋን የተሰጠው የኤሌክትሪክ ኃይል ማስለተላለፊያ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ክሬኑ ተበጥሶ ከባህር ውስጥ መውደቁንና ፣ አመልካች እቃውን አደጋ እንደደረሰ ወዲያውኑ ከባህር እንዲወጣ ማድረግ ሲገባው ከባድ በሆነ ቸልተኝነት በባህር ውስጥ ሳይወጣ ለስድስት ሰዓታት በባህር ውስጥ መቆየቱን ፣ በዚህም ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ በባለሙያዎች መረጋገጡን ፣ ተጠሪም ባለበት የመድን ግዴታ መሰረት ለተጎዳው እቃ እና ጥገናውን ለማከናወን አስፈላጊ ከሆኑ ወጪዎች ጋር በድምሩ ብር 253,827.04 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ሰባት ብር ከዜሮ አራት ብር) ወጪ አድርጎ ደንበኛውን መካሱን ፣ አመልካች ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል ቢጠየቅም ኃላፊነትን በማመን ከብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በላይ እንደማይከፍል ማሳወቁን ገልፆ አመልካች ኃላፊነት አለበት ተብሎ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብና ሌሎች ወጪዎችን እንዲተካ እንዲወሰንለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የተጠሪ ክስ በሁለት አመት ይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ አመልካች በውሉ መሰረት ጅቡቲ ወደብ እቃውን በማድረስ የማጓጓዝ ግዴታውን የተወጣና ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ፣ እቃውን ለማራገፍ ጥቅም ላይ የሚውለውን ክሬን የአመልካች በማስመሰል አመልካችን ኃላፊነት አለበት በማለት ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማቅረቡ አግባብነት የሌለው መሆኑን ፣ የክሬኑን ብቃት የማረጋገጥ ኃላፊነት የባለሃብቱ እንጂ የአመልካች አለመሆኑን ፣ አመልካች የሌላ ሰው ንብረት ባደረሰው ጉዳት ሊጠይቅ እንደማይችልና ሊጠየቁ የሚገባቸው የጅቡቲ ወደብ አስተዳደርና/ወይም ትራንዚት አገልግሎት አ.ማ እና ወይም ፔይድ(PAID) የተባለው ጫኝና አራጋፊ ድርጅት መሆኑን ፣ አመልካች ሊከሰስ አይገባውም እንጂ ኃላፊነት አለበት ቢባል እንኳን ተጠሪ የጠየቀውን ተመዛዛኝ ያልሆነ(non-equivalent) ኪሳራ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ፣ የቀረበው ገንዘብ መጠንና ማስረጃዎቹ ሕጋዊነት የጎደላቸውና ተቀባይነት የሌላቸው ሲሆን ተጠሪ ስራዎችን አጫርቶና አወዳድሮ በአነስተኛ ዋጋ አለማሰራቱ ተገቢ አለመሆኑን ፣ አመልካች ብር 500 ለመክፈል የፃፈው ደብዳቤ ግዴታውን እንዳመነ እንዳማያስቆጥረው መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ወድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካችን ለክሱ ሃላፊ በማድረግ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ብር 253,827.04 ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ ከመቶ) ወለድ እና ለክሱ ከወጡ የተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ባጭሩ፡- ክሱ በሁለት አመት ይርጋ የታገደ ከመሆኑም በላይ አመልካች እቃውን ከቻይና ሻይንጋይ ወደብ በማጓጓዝ ጅቡቲ ወደብ ማድረሱ ተረጋግጦ እያለና ይህም በውሉ ያለውን ግዴታውን መውጣቱን የሚያሳይ ሁኖ እያለ በክሬን ችግር ደረሰ ለተባለው አደጋ ኃላፊ ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱ በባህር ሕግ ቁጥር 138፣196፣197 ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ለክሱ ኃላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በፅሑፍ በሰጠው መልስ አመልካች እቃውን ለማስረከብ በውሉ ግዴታ ገብቶ እንደውሉ ያልፈፀመ መሆኑና በባህር ሕጉ ቁጥር 138፣196 እና 197 ድንጋጌዎች መሰረት ኃላፊቱን ያልተወጣና ኃላፊነቱንም በጽሑፍ ያመነ በመሆኑ ለክሱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍበት አግባብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካችና ተጠሪ በጽሑፍ ያቀረቡት ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተጠሪ ደንበኛ ንብረት የሆነውን የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ከቻይና ሻንጋይ ወደብ ጅቡቲ አጓጉዞ ለማድረስ ውል መግባቱንና ጅቡቲ ወደብ ማድረሱን ፣ እንዲሁም ይኸው እቃ ከመርከቡ በመውረድ ላይ እያለ ክሬኑ ተበጥሶ ውሃ ውስጥ ወድቆ የቆየና ጉዳትም የደረሰበት መሆኑን ያልካደው ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ደንበኛ የማጓጓዣ ሰነድ(Bill of lading) መረከቡም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ አመልካች ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው ባለበት የመድን ውል ለደንበኛው በንብረቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ ከከፈለ በኋላ ገንዘቡ እንዲተካለት ነው፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ኃላፊነት የለብኝም በማለት ሲሆን ለዚህ በቅድሚያ የሚያቀርበው ክርክር የይርጋ ጊዜ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ አመልካች ያነሳው ክርክር አመልካቹ ታህሳስ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ከፃፈው ደብዳቤ ይዘትና በይርጋው ጊዜ አቆጣጠር ላይ ሊያስከትለው ከሚችለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውጤት አንፃር ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ታህሳስ 07 ቀን 1998 ዓ/ም የጻፈው ደብዳቤ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በማመን የኃላፊነት መጠኑ ግን ከብር 500.00(አምስት መቶ ብር) በላይ ሊሆን እንደማይችልና ይህንኑ የገንዘብ መጠን ተጠሪ ከአመልካች የፋይናንስ መመሪያ እንዲወስድ የገለፀ መሆኑን እንዲሚያሳይ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች እዳውን ማመኑ ተጠሪ ከደንበኛው ካለው ግንኙነት ፣ እንዲሁም አመልካች ከተጠሪ ደንበኛ ካለው ግንኙነት አንፃር በሕጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ያልተቋረጠ መሆኑን የባህር ሕግ ቁጥር 203 ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1851 ጋር አዳምሮ በማንበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑን አመልካች ይርጋን መሰረት በማድረግ የሚያቀርብ የኃላፊነት ክርክር ታህሳስ 07 ቀን 1998 ዓ/ም ከፃፈው ደብዳቤ ይዘት አኳያ ሊታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያውን ከቻይና ሻንጋይ ወደብ ጅቡቲ አጓጉዞ ለማድረስ ውል የገባና በውሉ መሰረትም ጅቡቲ ወደብ ያደረሰ በመሆኑ እቃው ከመርከብ በክሬን ሲወርድ ለደረሰበት የመውድቅ አደጋ ኃላፊነት የለብኝም በሚል ሲሆን ይህንም በምክንያት የሚያስደግፈው ክሬኑ የራሱ ንብረት ያለመሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡

በመሰረቱ በባህር ላይ እቃ አመላለሽ ያለበትን ኃላፊነት በተመለከተ የባህር ሕጉ በቁጥር 196 ስር ያስቀመጠ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት እቃ አመላላሽ ሁለት ዋና ዋና ግዴታዎች አሉት፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ አንድን መርከብ በሙሉ በመከራየት(ቻርተር ፓርቲ) እቃን የሚያጓጉዝ ባለመርከብ ስላለበት ግዴታ የባህር ሕጉን ቁጥር 138 በማጣቀስ የሚደነግግ ሲሆን የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ በመርከቡ ላይ የተጫኑትን እቃዎች በጥንቃቄና በሚገባ ለመጫን ፣ ለአጠባበቃቸው በሚገባ አቀማመጥ እንዲደረደሩ፣ ስለጉዞዋቸው ፣ ስለ ጥበቃቸው ፣ ስለ መልካም አያያዛቸውና ስለ ማራገፉ መልካም አፈፃፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን በአስገዳጅ ሁኔታ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም አጓዡ በሕጉ የተጣሉበትን እነዚህን ግዴታዎች ካልተወጣ ሃላፊነት ያለበት መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያስረዳል፡፡ በጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ውስጥ አመላላሹ አላፊነት የለበትም ተብሎ የተደረገው ውል የማይፀና ስለመሆኑም የባህር ሕግ ቁጥር 205 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ የአመላላሹ መከላከያ ሊሆኑ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች በባህር ሕጉ ቁጥር 197 ስር የተመለከቱት ምክንያቶች ናቸው፡፡ ከላይ የተመለከቱት የባህር ሕግ ድንጋጌዎች የአመላላሽን አላፊነት ሊያስከትሉና ቀሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች የሚደነግጉ ሲሆን አላፊነትን በተመለከተ ቀሪ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ አመላላሽ እቃውን በአግባቡ ማስረከቡን መረጋገጡ ስለመሆኑም ያስገነዝባሉ፡፡ የእቃው እርክክብ ተፈጽሟል የሚባለው ደግሞ መቼና በምን ሁኔታ ሲፈጸም እንደሆነም ድንጋጌዎቹ በተለይ ከባህር ሕጉ ቁጥር 180(3) ጋር ተዳምረው ሲነበቡ ያሳያሉ፡፡ በዚህም መሰረት በጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ የተረጋገጠ የማመላለሻ ውልን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች የሚጸኑት በተለይ በመርከብ ላይ በተጫኑት የንግድ እቃዎች የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን በመሰለ ሌላ አይነት ሰነድ በተረጋገጡ የጭነት ማመላለሻ ውሎች ብቻ መሆኑ ፣ የመርከብ መከራየት ውል ሰነድ ባለው ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን ፣ ነገር ግን መርከቡ የተከራየው በኪራይ ሰነድ(ቻርተር ፓርቲ) የሆነ እንደሆነ የሚሰጠው የጭነት የማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን የመሳሰለው ሌላ ሰነድ በአመላላሹና በሰነድ አምጪው መካከል ያለው ግንኙነት ከሚመራበት ጊዜ አንስቶ በዚሁ በሚሰጠው የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ላይ ድንጋጌዎቹ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ፣ የሚፀኑትም እቃዎቹ ከመርከብ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ እስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ የተጠቀሰው ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሶስት በተለይ ሲታይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

".....ከመርከቡ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ እስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ ነው።" በሚል በኃይል ቃል ማስቀመጡ አመላላሹ በማራገፍ ሂደት ለሚከሰቱ ጉዳቶቹም ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በግልጽ የሚሳይ ነው። ከሁሉም በላይ በአመልካችና በተጠሪ ደንበኛ መካከል የተደረገው የማጓጓዣ ውል አንቀፅ 4(1(i) እቃዎቹን ማጓጓዝ ፣ መጫን ፣ ማራገፍ ፣ ማከማቸትና መጋዘን ማስቀመጥ ስራዎች ለሌሎች ወገኖች በውል አሳልፎ የመስጠት መብት እንዳለው በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ መሆኑ እነዚህ ግዴታዎች የአመልካች ጭምር መሆናቸውን የሚያሳይ ሲሆን ይኸው ውል በአንቀጽ 5(ሀ(i)) ላይም የአጓጓዡን ሃላፊነት ሲዘረዝር እቃዎቹ በባህር ላይ በሚጓዙበት ወቅት የአጓጓዡ ኃላፊነት የማራገፉ ስራ እስከተፈፀመ ድረስ እንደሚዘልቅ በግልፅ መደንገጉን ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከርበት ነጥብ ሲሆን በአመልካች በኩል የማስተባበያ ክርክር ካለመቅረቡ አንፃር ሲታይ የአመልካች ኃላፊት እቃውን በጥንቃቄ የማራገፍ ግዴታን ሁሉ የሚያጠቃልል መሆኑን የሚያስገነዝብ ሁኖ አግኝተናል። በአጠቃላይ አመልካች አጓጓዥነቱንና እቃው ከመርከብ ወደ ውሃ በመውደቅ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ሳይክድ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር በበቂ ማስረጃና ሕግ ያልተደገፈ መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው መሆኑን የተገነዘበን በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አልተገኘም። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 85940 ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71281 የካቲት 25 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል።
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 57932

ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ተክሉ ካሣ ገብረየስ - ጠበቃ ስንታየሁ ባህሩ - ቀረበ

ተጠሪ ፡- ማርኮባርዚ - በሌለበት

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በመዝገቡ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ቼክን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ሲሆን ፣ የአሁኑ ተጠሪ እና ማባ /maba/ ኂ/የተ/የግ/ማህበር የተባለ ድርጅት ደግሞ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ ክሱ በሁለት ቼኮች የታዘዘውን ብር 219,000 አልተከፈለኝም እና ሁለቱም ተከሣሾች ገንዘቡን ይከፍሉኝ ዘንድ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ እንደሆነ የቼኩ አውጪ ማህበሩ መሆኑን ቼኮቹ ወደ ታዘዘው ባንክ ሲወሰዱ የማህበሩ /2ኛ ተከሣሽ/ ሂሣብ የተዘጋ መሆኑን መገለጹም በክሱ ተመልክቶአል፡፡ ተከሣሾች በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸዉ ክርክሩ በሌሉበት ታይቶ መወሰኑንም የስር ፍ/ቤቶች ከሰጡት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ካየ በኂላ የአሁኑ ተጠሪን ክሱ በነጻ በማሰናበት 2ኛ ተከሣሽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከእነወለዱ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የተጠሪን ክሱ በነጻ መሰናበት በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ሲሆን ፣ ፍ/ቤቱም ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሐምሌ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡

ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ባለመቅረቡ ክርክሩ የተሰማው በሌለበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው ተጠሪ የኩባንያው /በስር 2ኛ ተከሣሽ/ ስራ አስኪያጅ ቢሆንም ፣ ፈርሞ ለሰጠው ቼክ በኃላፊነት አይጠየቅም የመባሉን አግባብነት ከንግድ ህግ ቁ. 530 አንጻር ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡

በዚህ መሠረትም ከስር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ክስ የመሰረተው በቼኩ አውጪ ኩባንያ ላይ ብቻ ሣይሆን ቼኩን ፈርሞ በሰጠው የኩባንያው ስራ አስኪያጅ /ተጠሪ/ ላይ ጭምር ነው፡፡ በሰበር አቤቱታ ማመልከቻው ላይም እንደገለጸው ስራ አስኪያጁን አጣምሮ የከሰሰው በስራ አስኪያጅነቱ ብቻ ሣይሆን የኩባንያው የባንክ ሂሣብ መዘጋቱን እና ለቼኩ ክፍያ የሚሆን ኩባንያው የሚያዝበት ገንዘብ እንደሌለ እያወቀ ሆነ ብሎ ቼኩን ፈርሞ በመስጠት ጥፋት ፈጽሞአል በማለት ጭምር ነው፡፡ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሣኔው እንዳመለከተው ቼኮቹ ባንክ ቀርበው ሊከፈሉ ያልቻሉት የኩባንያው የባንክ ሂሣብ በመዘጋቱ ምክንያት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን ለማለት የቻለው ባንኩ የሰጠው ማረጋገጫ በአስረጂነት ቀርቦለት ከዚሁ በማረጋገጡ እንደሆነም ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቱ ተጠሪ በስራ አስኪያጅነቱ ለፈረመው ቼክ ሃላፊ አይሆንም እሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱን ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው የቼኮቹ ባለቤት /አውጪ/ የሆነው ኩባንያ የባንክ ሂሣብ ስለመዘጋቱ ባቀረበው ማስረጃ ተረጋግጦአል፡፡ ኩባንያው ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ቢሆንም ስራውን የሚያንቀሣቅሰው በስራ አስኪያጅ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ አመልካች ቼኮቹ በስራ አስኪያጁ ተፈርመው በተሰጡበት ጊዜ ሁሉ ኩባንያው የሚያዝበት ገንዘብ በባንክ ሂሣቡ እንዳልነበረ አስረድቻለሁ በማለት የተከራከረ ሲሆን ፣ ተከሣሾቹ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቀርበው አልተከላከሉም፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ የኩባንያው ሂሣብ መዘጋቱን እያወቀ ነው ቼኮቹን ፈርሞ የሰጠው የሚለው የአመልካች ክርክር እውነት አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ የሚደረስበት ምክንያት እንደሌለ ነው የተረጋገጠው ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ ጥፋተኛ ወይም ስህተት ፈጽሞአል ማለት ነው፡፡

የኩባንያ ስራ አስኪያጅ በንግድ ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ወይም የማህበሩን /ኩባንያውን/ የመተዳደሪያ ደንብ በመጣስም ቢሆን በስራ አስኪያጅነታቸው በሰሩዋቸው ጥፋቶችም ፣ ስህተቶችም ቢሆን በማህበሩ እና በሶስተኛ ወገኖች ፊት በየራሣቸው ወይም በአንድነት ሣይከፋፈል እንደነገሩ ሁኔታ ሀላፊዎች እንደሚሆኑ በንግድ ህግ ቁጥር 530 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የኩባንያ /ማህበር/ ስራ አስኪያጅ የሆነው ተጠሪ ኩባንያውን ለመምራት ስልጣን ያለው /የነበረው/ ሰው እንደሆነ በመረጋገጡ እና ጥፋትም በመፈጸሙ ለፈረማቸው ቼኮች በሃላፊነት የማይጠየቅበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ ይልቁንም በተጠቀሰው የንግድ ህጉ ድንጋጌ እንደተመለከተው እሱም በግሉ ሃላፊ ነው የሚሆነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጡትን እውነታ ከህጉ ጋር አገናዝበው ባለማየታቸው ተጠሪን ነጻ በማድረግ የደረሱበት መደምደሚያ የተሣሣተ ሲሆን ችሎአል፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 16058 ታህሣስ 27 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 89973 ሚያዝያ 5 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪም ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የመክፈል ሃላፊነት አለበት በመሆኑም ተጠሪ እና ማባ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲከፈል የወሰነውን ገንዘብ በአንድነት እና በነጠላ ይክፈሉ በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 58931

ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- የንግድ ኢንዲስትሪ ሚኒስቴር - ነ/ፈጅ ዮናስ ከበደ ቀረበ

ተጠሪ ፡- ታይገር ሎጂስቲክ እና የንብረት ጥበቃ ኃ.የተ.የግል ማህበር - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአመልካች መስሪያ ቤት በአዋጅ ቁጥር 67/89 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 376/96 መሰረት የሚሰጣቸው የንግድ ስራ ፈቃድ ጉዳዮች ውድቅ የሚደረጉበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ ክሱ የተመሰረተውም ባሁኑ አመልካችና ታይገር ሴኩሪቲ ኃ.የተ.የግል ማህበር በተባለ ድርጅት ላይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ላይ የመሰረተው የክስ ይዘት ባጭሩ፡- ድርጅቱ ታይገር ሎጅስቲክና የንብረት ጥበቃ(Tiger Logistic and property Protection) በሚል የንግድ ስያሜ ከአመልካች መስሪያ ቤት የንግድ ስራ ፈቃድ ቁጥር ኢ.አይኤ(ኦኤል) 2047/08 በቀን 02/05/2000 ዓ/ም በሕጋዊ መንገድ ተሰጥቶት እየተንቀሳቀሰ ባለበት ሁኔታ በዚሁ ተመሳሳይ ስም ታይገር ሴኩሪቲ በሚል አላማ ላይ የተሰማራ ድርጅት ፈቃድ ወስዶ በአዋሳ ከተማ ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር(Unfair trade Competition) በማድረግ በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 14(4(ሀ)) ስር ከተመለከተው መንፈስ ውጪ የተጠሪን ድርጅቶችን ደንበኞች በማደናገር የድርጅቱን ገቢ እየቀነሰ እንደሚገኝ ፣ አመልካች መስሪያ ቤትም ሁኔታውን እንዲያርም ተጠይቆ ተገቢውን ምላሽ ያልሰጠና ተመሳሳይ የንግድ ስያሜ የተሰጠው የሥር ሁለተኛ ተከሳሽም ጉዳዩን በድርድር ሊፈታው የማይችል መሆኑንና በአመልካች መስሪያ ቤት ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ፍላጎት ያለው መሆኑን ገልጾ ሁኔታው እንዲታረምና እንዲሰረዝ እንዲወሰን እንዲሁም ኪሳራው በቀርጥ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስም የንግድ ስራ ፈቃድ የተሰጠበትን አሰራር በአዋጅ ቁጥር 67/89 እንዲሁም ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 376/96 የተከተለ መሆኑን ፣ ለተጠሪ ድርጅትና ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ የተሰጠው የንግድ ስራ ፈቃድ ተመሳሳይ ላልሆኑ ስራዎች የተሰጠ መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ሁለተኛ ተከሳሽም ቀድሞ የንግድ ስራ ፈቃድ የወሰደው ራሱ መሆኑና ተጠሪ ከተሰጠው የንግድ ስራ ፈቃድ ውጪ እየሰራ የሚገኝ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ክሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ሕጋዊ አይደሉም በማለት ውድቅ አድርጎ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የንግድ ድርጅቱን ስያሜ እንዲቀይር ፣ የአሁኑ አመልካችም የስር ሁለተኛ ተከሳሽን የንግድ ድርጅት ስያሜ እንዲሰርዝ ፣ ሁለተኛ ተከሳሽም ታይገር የምትለዋን ስያሜ እንዳይጠቀም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች መስሪያ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) ስር የተደነገገ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ከዚሁ ድንጋጌ ውጪ በሆነ መንገድ የንግድ ድርጅቱ ስያሜ እንዲሰረዝ መወሰናቸው ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የንግድ ስያሜ ተመሳሳይ ስለሆነ እና ያልተገባ የውድድር ስሜት እየፈጠረ ስለሆነ ይቀየር መባሉ ከአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) ድንጋጌ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ ቀርቦ አመልካች የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የሆነው ድርጅት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ተቀብሎ በተቀመጠበት ሁኔታ የሰበር አቤቱታውን ማቅረቡ ተገቢ ያለመሆኑንና በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔም ምንም የሕግ ስህተት የሌለበት መሆኑን በመዘርዘር መልሱን የሠጠ ሲሆን አመልካች ደግሞ በሕጉ አግባብ የተሰጠውን ስልጣን በመጠቀም ለፈፀመው ድርጊት የስር ፍርድ ቤት የሠጠውን የሕግ ስህተት በሕግ አግባብ ማሳረም መብቱ መሆኑን ዘርዝሮና የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 20 መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ የመስጠት ስልጣን ያለው ሲሆን ይህንኑ ስልጣን ተግባራዊ ሲያደርግ የሚያስፈልጉትንና ሊከተላቸው የሚገባቸው ስርዓቶች በአዋጅ ቁጥር 67/89 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 376/96 ስር ተደንግገው እናገኛለን፡፡ አዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 14 የንግድ ስም ለማስመዝገብ መሟላት ስላለባቸው ነገሮችና ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ስም ቀደም ሲል ከተመዘገበበት የንግድ ስሞች ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች አለመሆኑን ወይም ለመልካም ጠባይ ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ አለመሆኑን በአዋጁ አግባብ አለው በተባለው ባለስልጣን ከተረጋገጠ በሁዋላ የንግድ ስሙ የሚመዘገብ ስለመሆኑ በአመልካቹ ወጪ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ በማድረግ ሊመዘግብ የሚችልበትን አግባብ አዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 14(4) ድንጋጌ ደንግጎ ያለው ጉዳይ ሲሆን ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 376/96 ደግሞ የንግድ ስም ከዳታ ቤዝ ተጣርቶ የጋዜጣ ማስታወቂያ ሳያስፈልገው እንደሚመዘገብ ያስገነዝባል፡፡ የአሁኑ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረውም የአሁኑ ተጠሪ ታይገር ሎጂስቲክስ እና ንብረት ጥበቃ ኃ.የተ.የግል ማህበር የሥራ መስክ በላቀ ደረጃ የሎጂስቲክ ፣ የንብረት ጥበቃ ስልጠና እና የምክር አገልግሎት የሆነው እና የውጪ ኢንቬስቱር 70% ድርሻ የያዘ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ዋና ምዝገባ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው መሆኑን ፣ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የተሰማራበት የንግድ ስራ መስክ በደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዲስትሪ ቢሮ የተሰጠው የንግድ ስራ ፈቃድ ለሀገር ውስጥ ባለሀብት በተፈቀደ “ የጥበቃ ሥልጠና ” እና “የጥበቃ አገልግሎት” በመሆኑ አመልካች ሁለቱን የንግድ ማህበራት የተሰማሩበት የንግድ ስራ ጠባይ ፈጽሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለመመሳሰሉንና በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) የንግድ ስም መዝገብ የመግባት ውጤት ተገቢውን ማጣራት ከአደረገ በሁዋላ ምዝገባውን መፈፀሙን ነው፡፡ እንግዲህ በሕጉ የተዘረጋው ስርዓት ከላይ የተመለከተው ከሆነ እና አመልካች ተግባሩን ሕጋዊ ነው የሚልባቸው ምክንያቶች እነዚህ ከሆኑ በሕግ ረገድ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) ስር የተደነገገውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ምዝገባውን መፈጸም አለመፈፀሙን ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ በንግድ ሕጉ ቁጥር 137 እና 138 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የንግድ ስም ቀድሞ የተመዘገበ መሆኑ ብቻውን በንግድ ስራ ጠባዩ ፈፅሞ ለማይመሳሰል የንግድ ስራ እንዳይመዘገብ ሊከለክል አይችልም በማለት በአስገዳጅ ሁኔታ የተደነገገ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ አመልካች እንደተገለፀው ተጠሪ የንግድ ስራ የወሰደበት ስራ እና የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የንግድ ስራ የማይመሳሰሉ መሆናቸውን በሕጉ መሰረት በተሰጠው ስልጣን ማጣራቱን ገልፆ የተከራከረ ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች የአሁኑ ተጠሪ እና የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የንግድ ድርጅት ስም ይመሳሰላል ወደሚለው ድምዳሜ ከመድረሳቸው ውጪ ስራው አይመሳሰልም በማለት በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር ተቀባይነት የሌለበት መሆኑን የሚያሳይ ሕጋዊ ምክንያት በውሳኔአቸው ላይ አልገለፁም፡፡ በመሆኑም አንድ የአስተዳደር አካል ድርጊት ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ከሕግ ውጪ መሰራቱ ተረጋግጦ እንጂ ያለሕጋዊ ምክንያት ሊሆን አይገባም፡፡ ያለሕጋዊ ምክንያት ተግባሩን ተገቢ አይደለም ብሎ እንዲስተካከል በማለት መወሰን በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ባግባቡ እንዳይተገበር የሚያደርግ ጭምር ነው፡፡ በሌላ በኩል የስር ሁለተኛ ተከሳሽ በጉዳዩ ላይ ስርዓቱን ጠብቆ ይግባኝ ያለማቅረብ የአመልካችን አቤቱታ አቀራረብ ሕጋዊ አይደለም ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ምክንያቱም አመልካች በሕጉ ተለይቶ የተሰጠውን ሥልጣን ባግባቡ ማከናወኑን እና አንድ ወጥ አሰራር ያለ መሆኑን ማረጋገጥ የራሱ ኃላፊነት ነውና፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) ስር የተመለከተውን መመዘኛ መሰረት ማድረግ ሲገባው የውል ስም የሆነውን ታይገር የሚለውን ቃል ብቻ በመመልከት የተጠሪ የንግድ ስያሜና የስር ሁለተኛ ተከሳሽ ስያሜ የሚመሳሰልና ያልተገባ ውድድር የሚፈጥር ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 141884 ሚያዚያ 08 ቀን 2001 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81997 ግንቦት 04 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀጽ 16(2) እና አዋጅ ቁጥር 376/96 መሰረት ሲታይ ሕጋዊ ነው ብለናል፡፡ አመልካች የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የንግድ ድርጅት ስያሜን እንዲሰርዝ የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 04 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች ፡- ሀጂ መሐመድ አደም

ተከሣሽ ፡- አቶ ፍፁም ግርማ

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሚተላለፍ ሠነድ ላይ የግል ግንኙነትን መሠረት በማድረግ የሚቀርብን መቃወሚያ ይመለከታል፡፡ ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበው አቤቱታ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ለተጠሪ 0574420 የሆነ ብር 55,000 ሺህ የያዘ ቼክ የሰጡ ቢሆንም ለክፍያ ለባንክ ሲቀርብ በቂ ገንዘብ የለም ተብሎ ተመልሶላቸዋል፡፡ አመልካች ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 25,000 ከፍለው ብር 30,000 ይቀርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ይህንኑ ገንዘብ ከወለዱ ጋር ይክፈሉኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ቀርበው ቼኩ የተሰጠው በተጠሪና በአቶ ሙሣ መሐመድ መካከል ለነበረው አለመግባባት የሽምግልና ጉባኤ ባቀረበው ሃሣብ መሠረት ለሁለቱ ተከራካሪዎች መተማመኛ እንዲሆን በመሆኑ ክሱን ለመከላከል እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ቼክ ግልጽ የሆነ የክፍያ ትዕዛዝ ብቻ የሚይዝ በዚህ ትዕዛዝ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈፀምበትና ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በአውጪው ላይ የክፍያ ሃላፊነት የሚፈጥር የገንዘብ ሰነድ እንጂ የዋስትና ሰነድ ስላልሆነ ለመከላከል ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ገንዘቡን ከወለድ ጋር እንዲከፍሉ ወስኖባቸዋል፡፡

አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታም ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን ይህ ችሎትም ክሱ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው መሆን አለመሆኑን እንዲሁም አመልካች ክሱን ሊከላከሉ የሚገባቸው መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ይግባኙ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ያደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ በነዚህ ነጥቦች ላይ ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ክሱ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም የሚለውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ቼኩን ለተጠሪ የሰጡት ጥር 30 ቀን 1997 ዓ.ም. መሆኑን ከመዝገቡና ከግራ ቀኙ የቃል ክርክር ጭምር መረዳት ተችሏል፡፡ ቼክ የወጣበት ቀን ከግምት ሳይገባ በቼክ ላይ ከተፃፈው ቀን አንስቶ በሚከተሉት 6 ወራት ውስጥ እንዲከፈል መቅረብ እንዳለበት በንግድ ሕግ ቁጥር 855 ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚሁ ሕግ ቁጥር 881/1/ ሥር ደግሞ በቼክ የሚገደዱ ሰዎች ላይ አምጪው ክስ ማቅረብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችለው ቼኩን ለማቅረብ የተወሰነው ጊዜ ካለፈ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ድረስ መሆኑ ተመልክቷል። በመሆኑም አምጪው ክስ ማቅረብ የሚችለው ቼክ ከተፃፈበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በተያዘው ጉዳይ ቼክ የተፃፈው ጥር 30/1997 መሆኑ በግራ ቀኙ ያልተካደ ሲሆን ክስ የቀረበው ደግሞ ታህሣሥ 10/1998 መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ቼኩ ተጽፎ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ቀን 1 ዓመት አያልፍም። ቼኩ ተጽፎ ከተሰጠ ጀምሮ ለባንክ እንዲከፈል እስከቀረበበት ድረስ 6 ወር አልፏል እንዳይባል ደግሞ ቼኩ የተሰጠው ጥር 30/1997 መሆኑና ለክፍያ የቀረበው ሐምሌ 29/1997 መሆኑን ግራ ቀኙ ተማምነዋል። በመሆኑም ከጥር 30/1997 እስከ ሐምሌ 29/1997 ዓ.ም. 6 ወር ስለማያልፍ በንግድ ሕጉ ቁጥር 855 ሥር የተመለከተው የይርጋ ጊዜም ቢሆን ስለማያልፍ አመልካች ይርጋን አስመልክቶ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም።

በመቀጠል አመልካች ክሱን ሊከላከሉ ይገባል አይገባም የሚለውን ነጥብ እንመለከታለን።

በመሠረቱ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትዕዛዝ የያዘና ቼኩም እንደቀረበ የሚከፈል መሆኑ በን/ሕ/ቁ. 827/ሀ/ እና 854 ሥር ተመልክቷል። በመሆኑም ቼኩ የታዘዘለት ሰው /አምጪው/ ቼኩን ይዞ እንደቀረበ ቼኩ ሊከፈል ይገባዋል። አውጪውም ሆነ የጀርባ ፈራሚዎቹ ለቼኩ አከፋፈል ኃላፊዎች በመሆናቸው /የን/ሕ/ቁ. 640 እና 868 /ሐ/ ይመለከታል/ ቼክ ባልተከፈለ ጊዜ ተጠያቂዎች ይሆናሉ። ቼክ እንደ ገንዘብ ወደተለያዩ ሰዎች በቀላሉ ሊተላለፍ የሚችል ባህሪ ስላለው የቼክ አከፋፈል ላይ ማንኛውም መቃወሚያ ሊቀርብ አይችልም። ሕጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ጉዳዮች ካልሆነ የቼክ ክፍያ በማንኛውም ምክንያት ሊቆምና ሊታገድ አይችልም። ነገር ግን የተወሰኑ ሁኔታዎች ባጋጠሙ ጊዜ አውጪው ወይም ፈራሚዎቹ ቼክ ሊከፈል የማይገባበትን መቃወሚያ ሊያነሱ ይችላሉ። በመሆኑም አግባብነት ያላቸው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በመቃወሚያነት እንዲቀርቡ የፈቀድዋቸውንና የከለከሉዋቸውን ጉዳዮች ለመለየት የሕጉን ድንጋጌዎች እንዳለ መመልከቱ ጠቃሚ ነው። በዚህ ረገድ ለዚሁ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች የንግድ ሕጉ አንቀጽ 717 እና 850 ሲሆኑ የአንቀጽ 717 ይዘት የሚከተለው ነው።

<u>717 መቃወሚያ</u>

1. ዕዳ ከፋዩ ሰነዱን በያዘው ሰው በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ በተመሠረቱት፣ በሰነዱ አሳባፍ ፎርምና እንዲሁም በሰነዱ ላይ በተፃፉት ቃሎች ካልሆነ ሌላ መቃወሚያ ሊያቀርብበት አይችልም።

2. እንዲሁም ፊርማን በማስመሰል የተሰራ፣ ችሎታ ወይም ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ሥልጣን ባለመኖሩ ወይም ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው የተነሱትን መቃወሚያዎች ለማቅረብ ይችላል።

3. አምጪው ይህን ሰነድ ባገኘበት ጊዜ ዕዳ ከፋዩን ለመጉዳት እያወቀ ያደረገው ካልሆነ በቀር ከዚህ በፊት ሰነዱን ይዘው ከነበሩት ሰዎች ጋራ በግል ግንኙቶች ላይ በተመሠረቱ ክርክሮች ዕዳ ከፋዩ ሰነዱን የያዘውን ሰው ሊቃወመው አይችልም።

<u>717 Defenses</u>

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1/ The debtor may only set up against the holder of the instrument defenses based on their personal relations. Defenses of form and those based on the text of the instrument.

2/ He may set up defenses based on falsification of signature, lack of capacity or power of representation at the time of issue of the instrument or on the absence of the necessary conditions for bringing the proceeding.

3/ The debtor may not set up against the holder of the instrument defenses based on his personal relations with previous holders unless the holder in acquiring the instrument has knowingly acted to the detriment of the holder.

ከዚህ ሕግ ድንጋጌ ይዘት ሕጉ ለሚተላለፉ ሰነዶች የሚሰጠው ጥበቃ እንደተጠበቀ ሆኖ ተዘርዝረው በተገለፁ ሁኔታዎች በነዚህ ሰነዶች የተከሰሰ ሰው አንዳንድ መቃወሚያዎችን በማቅረብ ከእዳው ራሱን ነፃ ማድረግ እንደሚፈቅድ መገንዘብ ይችላል፡፡ የግል ግንኙነት መቃወሚያ ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች አንዱ ሲሆን ከዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር አንድና ሶስት መገንዘብ እንደሚቻለው ሕጉ የግሉ ግንኙነት መቃወሚያ ሊሆኑ የሚችልበትንና የማይችልበትን ሁኔታ ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ ላይ በዕዳ ከፋዩና ሰነዱን በያዘው ሰው መካከል ያለው የግል ግንኙነት በመቃወሚያነት ሊቀርብ የሚችል ሲሆን በዕዳ ከፋዩና /በተከሣሹ/ ቀድመው ሰነዱን ይዘው በነበሩ ሰዎች መካከል ያለ የግል ግንኙነት ግን በመርህ ደረጃ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡ በመሆኑም የግል ግንኙነት ምን ማለት ነው? የሚለው ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ የግል ግንኙነት እንደመቃወሚያ መቅረብ የሚችለው ይኸው የግል ግንኙነት በከሣሹና በተከሣሹ መካከል ያለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ቼክም ሆነ ሌሎች የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች በንግድ ልውውጥ ሂደት የመተላለፍ ባሕርይ ያላቸው በመሆኑ ከከሣሹና ከተከሣሹ በተጨማሪ ሌሎች ሰዎች በሂደት በፊርማ አስተላልፈዋቸው ወይም ተቀብለዋቸው ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ሂደት የሚኖረው የግል ግንኙነት አንድ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ቼኩን ፈርሞ ባስተላለፈና በተቀበለ ሰው መካከል በርካታ የግል ግንኙነቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከነዚህ በርካታ የግል ግንኙነቶች /Personal relations/ መካከል ሕጉ በመቃወሚያነት እንዲቀርብ የሚፈቅደው በተከሣሹና ሰነዱን ይዞ በመጣው ሰው መካከል ያለውን የግል ግንኙነት ብቻ ነው፡፡ ተከሣሹ ሰነዱን ይዞ ከመጣው ሰው ሣይሆን ቀድመው ሰነዱን ይዘው ከነበሩ ሰዎች ጋር የነበረውን የግል ግንኙነት እንደመቃወሚያ በማቅረብ ክፍያውን አልፈጽምም እንዲል ሕጉ አይፈቅድለትም፡፡ ይህ መሠረታዊ መርህ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 717 /1 እና 3/ ላይ ብቻ ሳይሆን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 752 እንዲሁም አንቀጽ 850 የተካተተ ነው፡፡ ቼክን የሚመለከተው አንቀጽ 850 በተለይ “አምጪው ቼኩን ሲያገኝ ያውም ባለዕዳውን ለመጉዳት ካላደረገ በቀር በቼኩ መሠረት የተከሰሱት ሰዎች ከአውጪው ጋራ ወይም በፊት አምጪ ከሆኑት ጋራ በግል ግንኙነታቸው ላይ በተመሠረቱት ልዩነቶች አምጪውን ሊቃወሙት አይችሉም” በማለት በቼክ የተከሰሰ ሰው መቃወሚያ ሊሆነው የሚችለው ከአምጪው /holder/ ወይም ቼኩን ከያዘው ሰው ጋር ያለው የግል ግንኙነት እንጂ ከቼኩ አውጪ /drawer/ ወይም ቼኩን ቀድመው ይዘው ከነበሩ ሰዎች /previous holders/ ጋር ያለውን የግል ግንኙነት እንዳልሆነ ይደነግጋል፡፡ የንግድ ሕግ አንቀጽ 850 የእንግሊዝኛው ትርጉም “ Persons sued on a cheque cannot set up against the holder defenses founded on their personal relations with the drawer or with previous holder. unless the holder in acquiring the cheque has knowingly acted to the detriment of debtor” በሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጉ የግል ግንኙነት በመቃወሚያነት የሚቀርብበት ሁኔታ ሌሎች መቃወሚያዎች ከሚቀርቡበት ሁኔታ ልዩነት አበጅቷል። ይህን ልዩነት የንግድ ሕጉን አንቀጽ 717 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በመመልከት መገንዘብ የሚቻል ነው። ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው ሕጉ በግል ግንኙነት ያስቀመጠው ዓይነት ገደብ በሌሎች መቃወሚያዎች ላይ አላስቀመጠም። አንቀጽ 717 በመቃወሚያነት የሚቀበላቸው ሌሎች ጉዳዮች /የሰነዱ አፃፃፍ፣ በሰነዱ የተፃፉ ቃሎች ምክንያት የሚነሱ መቃወሚያዎች /717/1/ ወይም በማስመሰል የተሰራ ፊርማ፣ ችሎታ ወይም ሥልጣን አለመኖር፣ ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ ሁኔታዎች አለመሟላት /717/2// የግድ በአምጪውና በተከሰሰው ሰው መካከል ብቻ የሚነሱ መሆናቸውን የሚገልጽ ድንጋጌ የለውም ይልቁንም እነዚህ ጉዳዮች መኖራቸውን ባረጋገጠ በማንኛውም ተከሣሽ ሊነሱ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም በ717 ከተገለጹት መቃወሚያዎች መካከል የግል ግንኙነት /Personal relation/ ከሣሹንና ተከሣሹን ብቻ የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ ሌሎች መቃወሚያዎች ግን ሌሎችን በሂደቱ ላይ የነበሩትን ሰዎች የሚመለከት እንኳን ቢሆን በቃወሚያነት ማንሳት ይቻላል። በሌላ አነጋገር ሌሎቹ መቃወሚያዎች ቼኩን ተከትለው የሚሄዱ ሲሆን፣ የግል ግንኙነት ግን በሁለቱ /ከሣሽና ተከሣሽ/ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ነው። በመሆኑም በአንቀጽ 717 የሚታዩት መቃወሚያዎች ሁለት ገጽታ ያላቸው ናቸው። በአንድ በኩል ማንኛውም በቼክ የተከሰሰ ሰው ሊያነሳቸው የሚችል፣ አምጪውም ቢሆን እነዚህ መቃወሚያዎች አንተን የሚመለከቱ አይደሉም ሊል የማይችልባቸው በመሆናቸው ሰነዱ እስካለ ድረስ እሱን ተከትለው የሚሄዱ በሌሎች የሕግ ሥርዓቶችና በሕግ ጽንሰ ሃሣብ real defense በመባል የሚታወቁ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰነዱ ይመለከታቸዋል ከሚባሉ ሰዎች መካከል የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ካልሆኑ በቀር ሌሎቹ እንዲያነሱዋቸው የማይፈቀዱ በሕግ ሳይንስና በሌሎች የሕግ ሥርዓቶች Personal defense /in personal defense/ በመባል የሚታወቁ መቃወሚያዎች ናቸው። መቃወሚያዎችን /defense/ ብቻ ሳይሆን መብቶችን Personal እና Real ወይም rights in personal እና rights in rem/ ብሎ መከፋፈል በሁሉም የሕግ ሥርዓቶች ያለ በኛም የሕግ ሥርዓት በተለያዩ ሁኔታዎች የተካተተ ነው።

በመሆኑም በንግድ ሕጉ የተለያዩ አንቀጾች በተለይም በአንቀጽ 717፣ 752 እንደሁም 850 የተገለፀውና የግል ግንኙነትን የሚመለከተው መቃወሚያ ሊታይ የሚገባው ከዚህ አንፃር ነው። ቼክ ለአምጪው የሚከፈል የንግድ ልውውጥን ለማቀላጠፍ ተብሎ የተዘጋጀ ሰነድ መሆኑ እሙን ነው። የአፈፃፀሙ ሂደት የንግድ ሂደትን እንዳያውክና እንዳያስተጓጉል መደረግ እንዳለበትም እሙን ነው። በሌላ በኩል ግን ቼክ የሚሰጠው በአመዛኙ በንግድ ልውውጥና በግብይት ሂደት በመሆኑ ይህን ታሳቢ በማድረግ ሕጉ ያስቀመጣቸውን መቃወሚያዎች በአግባቡ ማስተናገድ ተገቢ ነው።

በቼክ የተከሰሰ ሰው ከሌሎች በቼኩ ከተጠቀሙ ወይም ካስተላለፉ ሰዎች ጋር ያለውን የግል ግንኙነት ማንሣት ባይፈቀድለትም ከአምጪው ጋር ያለውን የግል ግንኙነት ግን ማንሳት ይፈቀድለታል። የግል ግንኙነት ምንድነው የሚለው ደግሞ ሊተረጎም የሚገባው ከላይ ከተመለከትነው፣ የንግድ ሕግን ዓላማ የሚያሳካና ከተለመደው አተረጓጎም አንፃር እንጂ ከዚህ ባፈነገጠ መንገድ ሊሆን አይገባውም። በመሆኑም የግል ግንኙነት ማለት ከሚመለከታቸው ሁለት ሰዎች ውጪ በሌሎች ሰዎች ሊነሳ የማይችል ግንኙነትን ለማመልከት እንጂ ከንግድና ከግብይት ውጪ የሚከሰቱ ግላዊ ግንኙነቶች ለማመልከት የተቀመጠ ነው ተብሎ ሊተረጎም አይገባውም። የግል ግንኙነት /Personal relation/ በተለምዶ in personal በመባል የሚታወቀውን ከሕግ ወይም ከውል የሚመነጭ በሁለት ሰዎች መካከል የተፈጠረ ግንኙነት ማለት ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ሕጉ አንቀጽ 850 በቼክ የተከሰሱ ሰዎች ቼኩን ካዘጋጀው /አምጪው/ ወይም ቼኩን ቀድመው ይዘው ከነበሩት ሰዎች /Personal holder/ ጋር የነበረውን የግል ግንኙነት ቼኩን ይዞ በመጣ ሰው /holder/ ላይ እንዳያነሳ ከሚከላከል በቀር ተከሣሹ ቼኩን ካመጣው ሰው ጋር ያለውን የግል ግንኙነት እንዳያነሳ የሚከለክል አይደለም፡፡ ይልቁንም ለሁሉም ሰነዶች ተፈፃሚነት ያለውና ከላይ የተመለከትነው አንቀጽ 717/1/ በሁለቱም መካከል ያለ የግል ግንኙነት መቃወሚያ ሊሆን እንደሚችል በግልጽ ያስቀመጠው ነው፡፡ ይህ የሕግ ይዘት በቼክ የተከሰሰ ሰው በቼኩ ላይ የተገለፀውን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ላለመክፈል መብት የሚሰጠውን ከውል የመነጨ ግንኙነት እንደመከላከያ እንዲያቀርብ የሚፈቅድለት ነው፡፡ ቼክ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጠው ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ግዴታን ለመፈፀም /in consideration/ እንደመሆኑ ለግዴታው መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን በማስመልከት መከላከያ እንዲሆኑ መፍቀድ ተገቢም ነው፡፡ ይህ አሠራር የሁለቱም ወገን ማስረጃን ለመመዘን ዕድል በመስጠት እውነት እንዲወጣ ከማገዙም ባሻገር የተለያዩ ክሶች እንዳያቀርቡ ስለሚያደርግ ወጪ ቆጣቢም ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው የንግድ ሕጉ አንቀጽ 827/840 እንዲሁም 854 ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈፀምበትና ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በአውጪው ላይ የክፍያ ኃላፊነት የሚፈጥር የገንዘብ ሰነድ እንጂ የዋስትና ሰነድ አለመሆኑን ይደነግጋል በማለት ነው፡፡ በመሠረቱ እነዚህ የተጠቀሱት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ቼክ በዋስትና ሊሰጥ የማይችል መሆኑን አይደነግጉም፡፡ ቼኩ የሚሰጥበት ምክንያት በሰጪውና በተቀባዩ የሚወሰን እንጂ በሕጉ የተዘረዘረ አይደለም፡፡ ሕጉ ቼክ ላምጪው ወዲያው የሚከፈል መሆኑን መግለፁ ደግሞ መከላከያና መቃወሚያ የማይቀርብበት ሰነድ ነው ማለት አይደለም፡፡ የሕጉ ዓላማ ይህ ቢሆን በማያሻማ ሁኔታ በ717 በተዘዋዋሪ መንገድ ደግሞ በአንቀጽ 850 መቃወሚያ የሚቀርብባቸውን ሁኔታዎች አይደነግግም ነበር፡፡

በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ተከሣሽ ያቀረቡትን መቃወሚያ አልቀበልም ያለው ከሕጉ ድንጋጌ ውጪ በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ቼኩ በዋስትና የተሰጠ መሆኑን በመገለፁ የአሁን አመልካች ከከሳሽ ጋር የዋስትና ውል ግንኙነት ያላቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ ውል ደግሞ በመካከላቸው የግል ግንኙነት መኖሩን ስለሚያሳይ በመቃወሚያነት መቅረብ የሚችል ነው፡፡ የቀረበው መቃወሚያ የተጠየቀውን ገንዘብ ላለመክፈል በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑ የሚታወቀው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን በአግባቡ ካከራከረ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት መቃወሚያውን ተቀብሎ ክርክሩን ሊያስተናግድ የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 62028 የካቲት 28/98 የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 45409 በ22/7/98 የሰጠው ትዕዛዝ በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች መከላከያቸውን አቅርበው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

<u>የሁለተኛው ዳኛ የሐሣብ ልዩነት</u>

በዚህ ጉዳይ በሰበር መ/ቁጥር 24435 እና በሰበር መ/ቁጥር 26438 አከራካሪ የሆኑት ጭብጦች፣

1ኛ/ በንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ የተደነገገው በዕዳ ከፋዩና ሰነዱን በያዘው ሰው መካከል ያለውና በሕጉ መሠረት መቃወሚያ እንዲቀርብበት የሚፈቀደው ግንኙነት የዋስትና ግንኙነትንም ይጨምራል? ወይንስ አይጨምርም?

2ኛ/ ይኸው በቁጥር 717/1/ የተፈቀደው የግል ግንኙነት /Personal relations/ መቃወሚያ ገደብ ሊኖረው ይገባል? ወይንስ አይገባም? የሚሉት ናቸው፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተም፣</u>

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 መሠረት የዋስትና ግዴታ ማለት ዋስን ባለዕዳውንና ባለገንዘቡን የሚያካትት ግዴታ ነው፡፡

በንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ መሠረት መቃወሚያ እንዲቀርብበት የሚፈቀደው ግንኙነት ግን በዕዳ ከፋዩና ሰነዱን በያዘው ሰው <u>በሁለቱ መካከል</u> ባለው የግል ግንኙነት ላይ ብቻ የሚመሠረት ነው፡፡

ስለሆነም፣ በዋስ፣ በባለዕዳውና በባለገንዘቡ የሦስትዮሽ የጋራ ግንኙነት ላይ የሚመሠረተው የዋስትና ግንኙነት በተቃጠሸ ሕግ ውስጥ የሚካተት አይደለም፡፡

የዚህን ምክንያት ከያዝነው ጉዳይና ከሕጉ አንፃር እንመልከት፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቹ በቼክ የቀረበባቸውን ክስ ለመከላከል በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁጥር 62028 የሰጡት ምክንያት የሚከተለው ነው፡፡ ይኸውም፣ ተጠቃሹን ቼክ ለከሳሹ /ለአሁን መልስ ሰጭ/ የሰጠሁት መክፈል ያለብኝ ዕዳ ኖሮ ሣይሆን በከሣሽና በአቶ ሙሣ መሐመድ /ልጃቸው መሆኑ ነው/ መካከል ለነበረው አለመግባባት የሽምግልና ጉባኤ ባቀረበው ሃሣብ መሠረት ለሁለቱ ተከራካሪዎች <u>መተማመኛ</u> እንዲሆን እንጂ ለክፍያ የተሰጠ ቼክ አይደለም የሚል ነው፡፡

አመልካቹ በማስፈቀጃ ማመልከቻው በገለጹት መሠረት <u>በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት</u> የቀረበባቸውን የቼክ ክስ ለመከላከል የሚፈልጉት በራሣቸውና በመልስ ሰጭው <u>በሁለቱ</u> መካከል ባለው የግል ግንኙነት ላይ ተመሥርተው ሣይሆን በሣቸው፣ በልጃቸውና በመ/ሰጪው መካከል ባለው የሦስቱ የጋራ ግንኙነት ውስጥ ለመተማመኛ የተሰጠ ቼክ መሆኑን በማስረዳት ነው፡፡ በአመልካቹና በመልስ ሰጪው መካከል ባለው የሁለቱን የግል ግንኙነት በተመለከተ ግን ቼኩን ዕዳ ኖሮብኝ ለክፍያ የሰጠሁት አይደለም ብለዋል፡፡

የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤቱ ቼክ በአውጪው ላይ የክፍያ ኃላፊነትን የሚፈጥር የክፍያ ሰነድ እንጂ የዋስትና ሰነድ ባለመሆኑ ተከሣሹ ክሱን ለመከላከል ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ የተከሰሱበትን የገንዘብ መጠን ይከፍላሉ ብሎ ወስኗል፡፡

ሕጉን በተመለከተም፣ በተጠቃሹ የንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ መሠረት መከላከያ እንዲቀርብበት የሚፈቀደው በሁለቱ፣ በዕዳ ከፋዩና ሰነዱን በያዘው ሰው የግል ግንኙነት ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተወሰነ መሆን ስለሚገባው፣ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 በተደነገገው መሠረት ዋስትና ከዋስትና ሰጪውና ከዋስትና ተቀባዩ የግል ግንኙነት ሰፋ ብሎ ባለዕዳውንም የሚጨምር የሦስት ወገኖች ግንኙነት በመሆኑ፣ በንግድ ሕግ ቁጥር 840 መሠረት አውጪው ዋስ የሚሆነው ለቼኩ አከፋፈል በመሆኑ፣ /The drawer guarantees payment/ ከዚህ <u>የዋስትና</u> ኃላፊነት ለመዳን የሚፃፈው ቃል ሁሉ እንዳልተፃፈ የሚቆጠር በመሆኑ፣ /any provision by which the drawer releases himself from this guarantee shall be of no effect/ ተብሎ የተደነገገ በመሆኑ የአመልካቹ /አውጪው/ ዋስትና ለአምጪው /ለመልስ ሰጪው/ መሆን ሲገባውና አውጪው ሦስተኛ ወገን ለሆነው ልጃቸው ሰጥቻለሁ የሚሉት ዋስትና መተማመኛ ወዘተ እንዳልተፃፈ መቆጠር ሲገባው፣ በድምጽ ብልጫው ተቀባይነት ማግኘቱ ተገቢ ባለመሆኑ ተለይቻለሁ፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

በዚህ ጭብጥ ላይ ተከራካሪዎቹ ወገኖች ዕዳ ከፋዩና ሰነዱን የያዘው ሰው መሆናቸው አከራካሪ አልሆነም ልዩነቱ ያለው በንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ በተደነገገው መሠረት በዕዳ ከፋዩና ሰነዱን በያዘው ሰው መካከል ያለው የግል ግንኙነት /personal relation/ ምን ያሕል ሰፋ ብሎ መተርጎም አለበት? የሚለው ላይ ነው፡፡

ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 39902 ጎዳር 8/97 የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የፍሬ ነገር ክርክሩ ደግሞ፣ በአመልካቹ በአቶ ሰለሞን ታደሰና በመልስ ሰጭው በአቶ ሽኩር ብርሃን መካከል ያለው የሴቶች ቦርሣን የንግድ ንግግነት የሚመለከት ነው፡፡ አመልካቹ አከራካሪ በሆነው ቼክ ላይ የተፃፈው 83,760 ብር እንዲከፈላቸው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ክስ ሲያቀርቡ መ/ሰጪው ለመክላከል እንዲፈቀድላቸው የጠየቀው፣ በሁለቱ መካከል የሴቶች ቦርሣ ንግድ የነበረ መሆኑን በመግለጽ ሲሆን እነዚህ አመልካቹ የሸጡላቸው ቦርሣዎች ወደሀገር ውስጥ በኮንትሮባንድ የገቡ ናቸው ተብሎ ከመ/ሰጪው ጋር ከሚሠሩት ከአቶ ሥራጅ ኢብራሂም እጅ የተወረሱና አቶ ሥራጅም ኮንትሮባንድ ይዘህ ተገኝተሃል ተብሎ በደንብ መተላለፍ ተከሰው በዋስትና ስለተለቀቁ ለተወረሰ ዕቃ ገንዘቡን ልከፍል አይገባኝም የሚል ነው፡፡ መ/ሰጭው እንዲከላከሉ ከተፈቀደላቸው በኋላ አቶ ሥራጅ ኢብራሂምንና ሌሎች በሽምግልናው ላይ ነበሩ የተባሉ ግለሰቦችን ቃል በምስክርነት እንዲያሰሙ ተደርጎ መ/ሰጪው ዕዳውን ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

የአመልካቹ ጠበቃ በሰበር አቤቱታ ማመልከቻ ቼኩን ከዕቃ ሽያጩ ጋር ተጠቅሶ መስጠቱን የሚመለከት የሽያጭ ውል በሌለበት ሁኔታ የቼክ ክስ በምስክር የሚስተባበል ከሆነ በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት የሚመራ መሆኑ ቀርቶ ከመደበኛው የብድርና አደራ ግንኙነት ደረጃ በታች መሆኑን /የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2472ትን ይመለከቷል፡፡/ ስለሚያሳይ ሊታይም የሚገባው ነው ብለዋል፡፡

ሕጉን በተመለከተም፣ የአብዛኛው ድምጽ አስተያየት፣ ቼክ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጠው ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ግዴታን ለመፈጸም /in consideration/ የሚሰጥ በመሆኑ ለግዴታው መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን በማስመልከት መከላከያ እንዲሆኑ መፍቀድ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡

በአነስተኛው ድምጽ አስተያየት ግን፣ በንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ መሠረት በግራ ቀኙ መካከል ያለው የግል ግንኙነት ለመከላከያነት ሊፈቀድ ይገባል ቢባልም የግል ግንኙነቱ በጣም ሰፋ ተደርጎ መተርጎም የለበትም የሚል ነው፡፡ ቼኩን ባመጣው ባለገንዘብና ቼኩን ባወጣው ባለዕዳ መካከል ያለው የግል ግንኙነት /ቤተሰባዊ፣ የንግድና ሌሎችም ተመሣሣይ ግንኙነቶች/ በጠባቡ መታየት አለበት፡፡ አመልካቹ በቼኩ እንዲከፈላቸው ክስ ሲያቀርቡ መ/ሰጪው የሸጠልኝ ዕቃ ሦስተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰው እጅ ከገባ በኋላ ኮንትሮባንድ ነው ተብሎ ስለተያዘ በቼኩ መክፈል የለብኝም የሚለውን ክርክሩን መቀበል የግል ግንኙነታቸውን በጣም ሰፋ አድርጎ መተርጎም ነው፡፡ ይህን የግል ግንኙነት መከላከያ በጣም ሰፋ አድርጎ መተርጎም ደግሞ፣ በንግድ ሕግ ቁጥር 840 የቼኩ አውጪ ለአከፋፈሉ ዋስ ነው፡፡ አውጪውን ከዚህ ዋስትና ኃላፊነቱ ለመዳን የሚፃፈው ቃል ሁሉ እንዳልተፃፈ ይቆጠራል ተብሎ ከተደነገገው ጋር የሚጋጭ ነው፡፡

የግል ግንኙነት ትርጉሙ በጣም የሚጠብ ከሆነም በንግድ ሕግ ቁጥር 717/1/ ላይ የተሰጠውን የመከላከል ፈቃድ የሚነሣ እንዳይሆን በሁለቱ ወገኖች መካከል ባለው <u>የጠበቀ</u> ግንኙነት ላይ ብቻ መፈቀዱ ባግባቡ ይመስለኛል፡፡

ስለዚህ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 62028 የካቲት 28/98 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሳይኖርበት በመሻሩ፣ በኮ/መ/ቁጥር 39902 ጎዳር 8/97 በዚሁ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ከመሠረታዊ የሕግ ስህተቱ ጋር እንዲፀና በመደረጉ ስላልተስማማሁ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 02 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አለ. መሀመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ሲ/ር መዓዛ ዮሴፍ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ዶ/ር ዮሴፍ ደነቀው ጠበቃቸው አቶ ሙሉቀን ሊበን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ የሰበር ተጠሪ ለሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ፍሬ ቃሉ ከተከሣሽ /ያሁኗ የሰበር አመልካች / ጋር ጐፋ ንብርኤል ከፍተኛ ክሊኒክ ኃ/የተ/የግል ማህበር አቋቁመን በድርጅቱ መመስረቻ ጽሁፍ ከተገለፀው ካፒታል በተጨማሪ የህክምና መሳሪያዎችን በመግዛት በሁለት ቦታዎች የክሊኒክ ሥራ እየሠራን ቆይተን ከጊዜ በኋላ ከተከሣሽ ጋር ተግባብተን መሥራት ያልቻልንና ተከሣሽ ከሣሽን ከማህበር በማግለል ድርጅቱን ይዘው ለብቻቸው እየተጠቀሙ ስለሆነ ማህበሩ በፍ/ቤት ውሣኔ ፈርሶ የንብረት አጣሪ ተሹሞ የሚገባኝ ድርሻ እንዲከፈለኝ አመለክታለሁ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሣሽም የክስ መቃወሚያና በፍሬ ነገር ላይ በአማራጭ መልስ አቅርበዋል፡፡ ያቀረቡት የክስ መቃወሚያም ከሣሽ ከማህበሩ ለመውጣት ባቀረቡት ተደጋጋሚ ጥያቄ መሠረት ጉዳዩ በሽማግሌዎች ሲታይ ቆይቶ ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገው ስምምነት ከሣሽ በዓይነት ያዋጡትን ንብረትና ብር 60,000 /ስድሣ ሺህ ብር/ ወስደው ጉዳዩ በሽምግልና ያለቀ በመሆኑ ከማህበሩ ከወጡ በኋላ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም ስለሌላቸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡

ተከሣሽ በፍሬ ነገሩ ላይ በአማራጭ በሰጡት መልስ ከከሣሽ ጋር ማህበሩን አቋቁመናል የማህበሩም ካፒታል ማህበሩ ሲቋቋም ብር 40,000/አርባ ሺህ ብር/ ሲሆን ከሣሽና ተከሣሽ እያንዳንዳችን ብር 20,000 ማምጣት የሚጠበቅብን ቢሆንም ከሣሽ ገንዘብ አልያዘኩም በማለታቸው ሌላ ጊዜ ይከፍላሉ በማለት በእምነት የከሣሽ ድርሻ ብር 20,000 እንደተከፈለ ተደርጐ በመመስረቻ ጽሁፍ ተሞልቷል፡፡ ሆኖም ገንዘቡን ሳይከፍሉ ቀርተዋል፡፡ በከሣሽ ተደጋጋሚ ጥያቄ ምክንያት ሽማግሌዎች ተመርጠው ጉዳዩን ሲያዩ ከቆዩ በኋላ በ24/10/98 ዓ/ም በተደረገው ስምምነት መሠረት 60,000 ብር እና በአይነት ንብረት ወስደው ከወጡ በኋላ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ ተከሣሽ እንቢተኛ በመሆን ድርጅቱን በግላቸው እየተጠቀሙ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ሐሰተኛ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመተዳዳሪያ ደንባችን የአንዱ ማህበርተኛ ከማህበሩ መውጣት ማህበሩን አያፈርሰውም በሚል የተስማማን ስለሆነና ከሣሽም ድርሻቸውን ወስደው ከማህበሩ የወጡ በመሆናቸው ማህበሩ ፈርሶ ሂሣብ አጣሪ ተሹሞና ሂሣቡ ተጣርቶ ድርሻዬ ይከፈለኝ ያሉትም የሚቻል አይደለም በማህበሩም ምንም አይነት ድርሻ የላቸውም፡፡ ማህበሩ በከሣሽ ጥያቄ እንዲፈርስ ውሣኔ የሚሰጥ ከሆነ ደግሞ ከሣሽ ከማህበሩ እወጣለሁ ብለው የወሰዱትን ብር 60,000 እና ሌሎች በዓይነት የወሰዱአቸውን ንብረቶች እንዲመልሱና ለማህበሩ ጽ/ቤት ኪራይ ብር 114,000 እንዲሁም ከሣሽ የፈረሙበት የማህበሩ ዕዳ ብር 207,536.85 በድምሩ ብር 321,536.85 ከግል ገንዘቤ እየከፈልኩ ስለምገኝ እንደማህበሩ ዕዳ እንዲቆጠር፣ የማህበሩ አባል ተከሣሽ ብቻ ስለሆንኩኝ በንግድ ህግ ቁጥር 511/1/ መሠረት የማህበሩ አባላት ቁጥር ከ2 በታች ስለሆነ ማህበሩ በፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፈርስ እጠይቃለሁ ብለዋል፡፡

የሥር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትም አጣሪ በመሾም የማህበሩ ንብረት እንዲጣራ ካደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር ከሣሽ ለማህበሩ ባዋጡት የገንዘብ መጠን ድርሻቸው ሲሰላ 36.63 ከመቶ ስለሚሆን በጠቅላላው 83,081.04 ብር ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍሉና ማህበሩም በንግድ ህግ አንቀጽ 511/1/ መሠረት እንዲፈርስ ወስኗል፡፡

ይህ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ በአሁኗ የሰበር አመልካች ይግባኝ ጠያቂነት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቀርቦ ክርክር ከተካሄደበት በኋላ ከፍተኛው ፍ/ቤትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር የተሰኙት የሰበር አመልካችም ባቀረቡአቸው የቅሬታ ነጥቦች፡-

- ጉዳዩ በሽምግልና ታይቶ ውሣኔ አግኝቷል በሚል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244/2/ረ/ መሠረት ያቀረብኩትን መቃወሚያ የሥር ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ያለአግባብ ነው፣
- ማህበሩ ይፈርሣል ከተባለም ወደ ነበርንበት ልንመለስ ሲገባ ተጠሪው ብር 60,000 እና የህክምና መገልገያዎች እንዲሁም የጽ/ቤት ዕቃዎችን ከማህበሩ ወስደው ወጥተው ባሉበት በተጨማሪ ብር 83,081.04 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ያለአግባብና የሽምግልና ስምምነቱን ያላገናዘበ ነው፣
- በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 17/2/ መሠረት አንድ ማህበርተኛ ከማህበሩ በመውጣቱ ምክንያት ማህበሩ እንደማይፈርስ ተገልጾ እያለ ከስምምነታችን ውጪ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም፣
- ማህበሩ ከፈረሰ ተጠሪውና አመልካች ለማህበሩ ዕዳ ብር 321,536.85 በጋራ ተጠያቂዎች መሆን ሲገባንና ተጠሪውም ዕዳውን ባላስተባበሉበት የሥር ፍ/ቤቶች በምን ምክንያት ዕዳውን እንዳለፉ በውሣኔያቸው አልጠቀሱም ከዚህ ሌላ ማህበሩ ሲፈርስ ትርፍና ኪሣራ ሳይለይ ለተጠሪው ብር 83,081.04 አመልካች እንዲከፍል ሲወሰን የአመልካች ድርሻ ምን እንደሆነ ሳይወሰን ታልፏል፣ ሂሣቡን ያጣሩት ሰዎች ቀደም ሲል ጉዳዩን በሽምግልና ከማየታቸው ውጪ በሂሣብ አጣሪነት እንዲሠሩ አመልካች ሳልፈቅድ ፍ/ቤቱ እንዲያጣሩ ያደረገ ሲሆን ምንም አይነት የሂሣብ ሞያ የሌላቸው ናቸው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የፈፀሙት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የሰበር ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- አመልካች ለአጣሪዎች ያላቀረቡአቸውን ክርክሮች ሪፖርቱ ለሥር ፍ/ቤት ከቀረበለት በኋላ ያቀረቡ በመሆናቸው ተጠሪ አግባብነት ያላቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማስተባበያ ማስረጃዎች በማቅረብ እንዳልከላከል ያደረገ ከመሆኑም ሌላ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 329 መሠረት ተቀባይነት የለውም፣ የሂሣብ አጣሪዎች የሂሣብ ዕውቀት የላቸውም በሚል የቀረበው ክርክርም ቢሆን ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም አጣሪዎች የተለየ ሞያ ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያስገድድ ህግ የለም፡፡ አጣሪዎቹ የተሾሙትም አመልካች ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ቀርበን ባመለከትነው መሠረት ነው፡፡ ጉዳዩ በሽምግልና የተጠናቀቀ ነው ላሉትም ስምምነቱ የማህበሩን መፍረስ የሚመለከት ካለመሆኑም በላይ አንድ የማህበር አባል በሀገሪቱ ህግና በማህበሩ ደንብ መሠረት ማህበሩ እንዲፈርስና ከንብረቱ ድርሻው እንዲከፈለው የመጠየቅ መብቱን የሚያስቀር ወይም የሚያሣጣ አይደለም፡፡ ተጠሪው በማህበሩ ባለኝ 50% ድርሻ ታስቦ ሊከፈለኝ የሚገባውን ገንዘብ በህግ የመጠየቅ መብት ቢኖረኝም ለሰላም ሲባል አነስተኛ ቀመር ተቀብያለሁ፡፡ የማህበሩ ካፒታል ብር 40,000 ሲሆን እኔም ድርሻዬን በሙሉ ከፍያለሁ፣ የከፈልኩ ስለመሆኔም አጣሪው አረጋግጧል፡፡

የማህበሩ ሀብት እና ዕዳ ተጣርቶ ቀደም ሲል ከተቀበልኩት የካሣ ክፍያ በተጨማሪ ብር 83,081.04 የሚገባኝ መሆኑን አጣሪዎች በማረጋገጣቸው ፍ/ቤቱም ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ማህበሩ ያለበት ዕዳ ፣ ሀብት እና ሁለቱም የማህበሩ አባላት ከማህበሩ ካፒታል በተጨማሪ ገቢ ያደረግነው ገንዘብ ተመዛዝኖ ነው፡፡

አጣሪዎች ሂሣቡንም የሠሩት እስከ 24/10/1998 ባለው ጊዜ ብቻ ሲሆን ከዚህ ከተጠቀሰው በኋላ የተገኘው ሀብትም ሆነ የመጣው ዕዳ በ24/10/98 አመልካችና ተጠሪ ባደረግነው ስምምነት መሠረት እንዲሰላ በፍ/ቤትም ሆነ በአጣሪዎች ዘንድ የተስማማን በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ ተጠሪን የሚጠቅም ወይም በሀላፊነት የሚያስጠይቅ ነገር የለም ሲሉ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለመኖሩን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የቀረበ ሲሆን እኛም የሚከተለውን ጭብጦች ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

- የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በፊት በሽምግልና ተጠናቅቋል ወይስ አልተጠናቀቀም?
- አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ የተወሰነባቸውን ገንዘብ ሊከፍሉ ይገባል ወይስ አይገባም?

የመጀመሪያውን ጭብጥ በሚመለከት፡- አመልካች የሚከራከሩት ጉዳዩ በሽምግልና ሲታይ ቆይቶ ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ/ም ስምምነት የተደረሰ በመሆኑና ተጠሪዉም በዚሁ ስምምነት መሠረት ብር 60,000 ፣ የህክምና መሣሪያዎች እና ሌሎች የጽ/ቤት ቁሳቁሶችን ወስደው ከማህበሩ የወጡ በመሆናቸው በተጠናቀቀ ጉዳይ ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት ለክርክራቸውም የጠቀሱት የፍትሃብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁ 244/12/ረ/ ነው፡፡

በእርግጥ የተጠቀሰው የፍብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244/2/ረ/ ክስ የተነሣበት ነገር በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተፈፀመ ከሆነ ወይም ለዕርቅ የተቀጠረ ከሆነ ክሱን መቃወም እንደሚቻል የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች እንደሚሉት በእርግጥ የግራ ቀኙ ክርክር በሽምግልና ታይቶ በስምምነት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለመወሰን ሰኔ 24 ቀን 1998 በግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የተፈረመ ቃለ ጉባኤና ብር 60,000 ለተጠሪ የተከፈለበትን ሠነድ ይዘት ተመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቃለ ጉባኤውም አመልካችም ሆነ ተጠሪ ለማህበሩ የተለያዩ ወጪዎችን ማውጣታቸውን የሚገልጽ ሲሆን የሰበር አመልካች ግን ከተጠሪው የበለጠ ወጪ ማውጣታቸውን ይገልጻል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቃለጉባኤ ድርጅቱ ከተቋቋመ በኋላ፣ በሥራ ሂደት ወይም በመጀመሪያ አካባቢ በድርጅቱ የተፈሩ ወይም የተገዙ ቋሚ ዕቃዎችን በሚመለከት እስከ 24/10/98 ድረስ ተከፍሎ ያልተጠናቀቀ ዕዳ እና የተከፈለው ተሰልቶ ለተጠሪ የሚገባ ክፍያ ያዋጡት መጠን በመቶኛ ተሠልቶ እንዲሰጣቸው ያልተከፈለ የተጠሪ ደመወዝ እንዲከፈላቸው በቅድመ ክፍያ የተከፈለው የቤት ኪራይ ገንዘብ ቅድመ ክፍያ የተፈፀመበት ወራት ተሰይቶ የተጠሪ ድርሻ እንዲመለስላቸው እና ተጠሪው ድርሻቸውን በማስተላለፍ ከማህበሩ ስለሚወጡ ካሣ ብር 60,000 አመልካች እንዲከፍሉ ማህበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 24/10/1998 በማህበሩ ላይ ያለውን ዕዳ በተመለከተ ድርጅቱን በማስቀረት ይዘው የሚያዙት አመልካች በሚያቀርቡት እና በተጠሪው ምትክ በሚገባ ግለሰብ ይሸፈናል የሚሉትንና ባጠቃላይ ከተራ ቁጥር 1-9 የተጠቀሱትን ነጥቦች ያካተተ ነው፡፡

አመልካች ግን ለተጠሪው ብር 60,000 /ስልሳ ሺህ ብር/ የተከፈላቸው በመሆኑንና በአይነት የህክምና መሣሪያዎችን ወስደዋል በሚል ነው አጥብቀው እየተከራከሩ ያሉት ብር 60,000 ለተጠሪ የተከፈለበት ሠነድም ቢሆን ሌሎች ክፍያዎች በቃለጉባኤው በተገለፀው መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን በግልጽ ይናገራል፡፡ ይህ ሆኖ ሣለ አመልካች ቃለጉባኤው ተጠሪው ከማህበሩ የሚደርሣቸውን አጠቃላይ ድርሻ ያላስቀመጠና ገና ሂሣብ ተጣርቶ የሚፈፀም መሆኑን እየገለፀ ባለበት ብር 60,000 /ስልሳ ሺህ ብር/ እና የህክምና መሣሪያዎችን በአይነት ተጠሪው ወስደው በስምምነት ተጠናቅቋል ሲሉ ያቀረቡት መቃወሚያ ከፍትሃብሄር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 244/2/ረ/ መንፈስ ውጪ በመሆኑ ያለአግባብ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ በማድረጋቸው የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

2ኛን ጭብጥ በሚመለከት፡- አጣሪው ጥቅምት 21 ቀን 2001 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ሸኚነት በ24/10/2000 ዓ/ም የተዘጋጀ ቃለጉባኤ /ሪፖርት / ለሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ሪፖርቱም መሠረት ያደረገው ቀደም ሲል ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ የማጣራቱ ሥራ ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገውን የሽምግልና ስምምነት መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት በገለፀው መሠረት ነው ብሏል፡፡

ይህ ችሎትም እንደተረዳው በ24/10/98 ዓ/ም በተደረገው የሽምግልና ስምምነት መሠረት አጣሪው የማጣራቱን ሥራ አከናውኗል፡፡ የማጣራቱ ሥራም የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ያቀረቡአቸውን ማስረጃዎች ጭምር በመመዘን የተሰራ ስለመሆኑ ሪፖርቱ ያመለክታል፡፡

ለድርጅቱ ሥራ በብድር የተገዙና ዕዳቸው ተከፍሎ ያልተጠናቀቁ ቋሚ ዕቃዎችን በሚመለከትም እስከ ሽምግልና ስምምነት ድረስ መከፈሉ በማስረጃ የተረጋገጠ ተጠሪው ባዋጡት ድርሻ መጠን ተሰልቶ ገንዘብ እንዲሠጣቸው በብድር ተገዝቶ ክፍያው የተጠናቀቀው ፎቶ ሜትር የተባለው የህክምና መሣሪያ ክፍያው የተጠናቀቀው የሽምግልና ስምምነት ከተደረገበት ቀን በፊት መሆኑ በመረጋገጡ ለተጠሪው ባዋጡት መጠን ድርሻቸው እንዲሰጥ የተወሰነ ሲሆን ሌሎች ዕቃዎችን በሚመለከት የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በ10/6/99 ዓ.ም የተፈራረሙበት ደረሰኝ ከተጠሪው በኩል በመቅረቡ ተጠሪው ባዋጡት የገንዘብ መጠን ተሰልቶ ድርሻቸው እንዲከፈል ተወስኗል፡፡ ያሁን አመልካችም እነዚህን በ10/6/99 ዓ/ም በተደረገው ውል የተዘረዘሩትን ንብረቶች እንዲያስቀሩ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቤት ኪራይም ቢሆን የአጣሪው ሪፖርት እንደሚያመለክተው ኪራይ ከ23/4/98 እስከ 23/4/99 ድረስ ብር 39,000 የተከፈለ ሲሆን ተጠሪው ከሰኔ 24 ቀን 1998 ጀምረው ከድርጅቱ ስለተሰናበቱ ከሐምሌ 1998 - ታህሣሥ 99 ዓ.ም ያለው የ6 ወራት ታስቦ ባዋጡት መጠን ድርሻቸውን አመልካች እንዲከፈሉ ሲደረግ ይህም ክሊኒክ ቁጥር 1 የተባለውን የሚመለከት ነው፡፡ ቁጥር 2 የተባለውን ክሊኒክ በሚመለከት ደግሞ ከመስከረም 19 ቀን 1998 ዓ/ም እስከ መስከረም 19 ቀን 1999 ድረስ የ12 ወር ብር 24,000 የቤት ኪራይ የተከፈለ ሲሆን ከአመልካች ጋር የተገለገሉበት እስከ 24/10/1998 ዓ/ም በመሆኑ ሐምሌና ነሐሴ 1998 የ2 ወር በቅድሚያ የተከፈለ በወር በብር 2000 ሂሣብ ተጠሪው ባዋጡት የገንዘብ መጠን ተሰልቶ ድርሻቸውን አመልካች እንዲከፈሉ መወሰኑን ሪፖርቱ ያመለክታል፡፡ ለዚሁ ለቁጥር 2 ክሊኒክ ተጨማሪ ግንባታ ቅድመ ክፍያ ብር 30,000 እንደተከፈለ ተቆጥሮ ከመስረከም 19 ቀን 1998 - ሰኔ 24 ቀን 1999 ድረስ ለ9 ወራት አመልካችና ተጠሪ በጋራ የተጠቀሙበት ስለሆነ የ51 ወራት በወር በብር 500 ሂሣብ ተጠሪው ባዋጡት መጠን ድርሻቸውን እንዲያገኙ ተብሏል፡፡

ደመወዝን በሚመለከት አጣሪው ከመቼ ጀምሮ መከፈል እንዳለበት በግልጽ የተቀመጠ ነገር የግራ ቀኙ አከራካሪዎች ባለማቅረባቸው የተነሣ አመልካች ድርጅቱ ሥራውን ከጀመረበት ቀን አንስቶ ከ2 ወር በኋላ መሆን አለበት ያሉትን አጣሪው በመቀበልና ድርጅቱ ሥራ የጀመረው 17/4/1999 በመሆኑ ከየካቲት 18 ቀን 1997 — 24/10/98 ድረስ የ16 ወራት ደመወዝ ማናቸውም የመንግስት ግብር ተቀንሶና ቀደም ሲል ተጠሪው በብድር የወሰዱት ብር 37,000 ተቀናሽ ተደርጐ የሚደርሣቸውን ድርሻ አመልካች እንዲከፍሉ በሚል በሪፖርቱ ገልጿል፡፡

እንግዲህ እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ልዩ ልዩ ክፍያዎች ናቸው ተጠቃልለው ብር 83,081.04 ሳንቲም የሆኑት አጣሪው በዚህ ዓይነት በጥልቀት የቀረቡለትን ማስረጃዎች በመመርመር አግባብነት ያላቸውን በመቀበልና አግባብነት የሌላቸውን በመጣል የተጠቀሰውን ገንዘብ የሰበር አመልካች እንዲከፍሉ በሪፖርት የገለፀውና የሥር ፍ/ቤቶች በየደረጃው የቀረበላቸውን ጉዳይ በመመርመር ገንዘቡን አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የወሰኑት፡፡

አመልካች ብር 60,000 በ24/10/98 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት መክፈላቸውን በመግለጽ ያቀረቡት የመከራከሪያ ሀሣብም ቢሆን ብር 60,000 / ስልሳ ሺህ / የተከፈለው ካሣ በሚል ስለሆነና በዚሁ ስምምነት ሌሎች ሂሣቦች ለወደፊት ተሰልቶ የሚቀርቡና ክፍያ የሚፈፀምባቸው መሆኑ የተገለፀ በመሆኑ በስሌቱ መሠረት እንዲከፍሉ የተጠየቁትን ገንዘብ መክፈል አይገባኝም ማለታቸው ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የማህበሩን ዕዳ በሚመለከት ምንም ሳይባል ታልፏል ያሉትም ቢሆን የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ሰኔ 24 ቀን 1998 ዓ/ም በተፈራረሙት ቃለ ጉባኤ ገጽ 6 በቁጥር “7 ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ይህ ውል እስከ ተደረገበት እለት ድረስ በድርጅቱ ላይ ያለውን ዕዳ በተመለከተ ድርጅቱን በማስቀረት ይዘው የሚጓዙት አመልካች በሚያቀርቡትና በተጠሪው “ሼር” ምትክ በሚገባው ግለሰብ የሚሸፈን ይሆናል” ተብሏል፡፡ በዚህ መልክ ስምምነት ላይ የተደረሰ ከሆነ ደግሞ እንደገና አመልካች ተጠሪው ለማህበሩ ዕዳ ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል ያሉት ከተፈረመው ስምምነት ጋር የሚጋጭ ይሆናል፡፡

የማህበሩን መፍረስ በሚመለከት አመልካች ባቀረቡት ክርክር ተጠሪ ድርሻቸውን ይዘው ከማህበሩ የወጡ በመሆናቸው በተጠሪው ጥያቄ መነሻ ማህበሩ ሊፈርስ አይገባም ካሉ በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማህበሩ አባላት ከሁለት በታች በመሆኑ እንዲፈርስ ጠይቀዋል የሥር ፍ/ቤትም ማህበሩ እንዲፈርስ የወሰነው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የክርክር ሃሣብ መነሻ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የመሠረቱት ማህበር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን ማህበሩ ሊመሠረት የሚችለው ደግሞ በንግድ ህግ አንቀጽ 510/2/ እንደተጠቀሰው ማህበርተኛው ከሁለት ያላነሠና ከአምሣ ያልበለጠ ከሆነ ነው፡፡

በዚህ በተጠቀሰው ማህበር ደግሞ አባላቱ አመልካችና ተጠሪ ብቻ ሲሆኑ ተጠሪው ከማህበሩ ከተሠናበቱ አመልካች ብቻ ይቀራሉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በህጉ ከተጠቀሰው አነስተኛ ቁጥር በታች በመሆኑ መፍረሱ የግድ ነው፡፡

በመሆኑም የሂሣብ አጣሪ ያቀረበውን ሪፖርት መነሻ በማድረግ የሥር የመ/ደ/ፍ/ቤት ከውሣኔው በፊት ተጠሪ የተቀበሉትን ብር 60,000/ስድሳ ሺህ/ እና በሂሣብ አጣሪ ተሠልቶ የቀረበውን ብር 83,081.04 /ሰማንያ ሶስት ሺህ ሰማንያ አንድ ከዜሮ አራት ሳንቲም/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉና የንግድ ማህበሩም እንዲፈርስ የሰጠውን ውሣኔ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ያፀናው በአግባቡ ስለሆነ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሥር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በክ/ቁ 26095 በቀን 01/7/2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 78493 በቀን 10/03/2003 በዋለው ችሎት የሰጡት ፍርዶች ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ቀደም ሲል ከከፈሉት ብር 60,000/ስድሳ ሺህ/ በተጨማሪ ብር 83,081.04/ሰማንያ ሶስት ሺህ ሰማንያ አንድ ከዜሮ አራት ሳንቲም/ እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ አመልካችና ተጠሪ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ናሆም ሸዋንግዛው ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1- የቻይና ዋንቦ ኢንጂሪንግ ኮርፖሬሽን ጠበቃ ዱቺ ፈለቀ ቀረቡ

2- ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጠበቃ መኮንን ሽፈራው ቀረቡ

የሰ/መ/ቁጥር 49321 የሆነ መዝገብ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመድን ውልን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በሰ/መ/ቁጥር 49295 በአመልካች በ2ኛ ተጠሪና በአቶ ዮናስ ተስፋዬ ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአሁኑ አመልካች የመድን ዋስትና የተሰጠው የ1ኛ ተጠሪ ኤሌክትሪክ ትራንስፎርመር ንብረትነቱ የአቶ ዮናስ ተስፋዬ በሆነ ተሸከርካሪ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ አስጫኝነት ከጅቡቲ ወደብ ተጭኖ ወደ ደብረ ብርሃን ሲሄድ መኪናው የመገልበጥ አደጋ ደርሶበት በትራንስፎርመሩ ላይ ከባድ ጉዳት መደረሱን ገልፆ የአሁኑ አመልካች በመድን ውሉ መሠረት የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ወኪል ሁኖ በማስጫኑ የስር ሶስተኛ ተከሣሽ የነበሩት ግለሰብ /አቶ ዮናስ ተስፋዬ/ ደግሞ አጓዥ በመሆኑ ኃላፊነት እንደአለባቸው ጠቅሶ ለደረሰው ጉዳት ብር 2,223,293.80 /ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም/ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በስር ከሣሽ በኩል ለቀረበበት ክስ በሰጠው መከላከያ መልስ ፡- ከከሣሹ ጋር የመሰረተው የመድን ዋስትና ውል የባህር መድን ዋስትና ውል በመሆኑ ጉዳዩ የሚገዛው በባሕር ሕጉ እንጂ በንግድ ሕጉ አለመሆኑን በትራንስፎርመሩ ላይ ጉዳት የደረሰው ተሽከርካሪው መጫን ከሚችለው አቅም በላይ በመጫኑ ይህም የተደረገው በከሣሹ ወኪል በሆነው ታብትራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በመሆኑና ወኪል ያደረገው ወካዩ እንዳደረገው ስለሚቆጠር እንዲሁም በመድን ውሉ ላይ በግልፅ መድን ሰጭውን ከኃላፊነት ነፃ የሚያደርገው እንደሆነ ገልጾ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለብኝም በንግድ ሕጉ መሠረትም የእምቢታ ማስታወቂያ በሰባት ቀናት ውስጥ ለመድን ሰጪው ያለመገለፁ የመዳረግ መብቱን ያሳጣው በመሆኑም መድን ሰጪው ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን እንዲያሳይ እንዲሁም የኃላፊነት መጠኑም ቢሆን የተጋነነ እና በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መጠኑን ጠቀሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ታብትራ ኃላ.የተ.የግል ማህበር በበኩሉ ከተከሣሾች ጋር ተጣምሮ መክሰስ የሌለበት መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከረ ሲሆን በኃላፊነት ረገድ ደግሞ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሠረት በውሉና በሕጉ አግባብ ግዴታውን የተወጣ መሆኑን ገልጾ ክሱ ውደቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ሶስተኛ ተከሣሽ የነበሩት ግለሰብ /አቶ ዮናስ ተስፋዬ / በበኩላቸው ከአንድ አጓዥ በሚጠበቅ መልኩ ትራንስፎርመሩን ጭነው ለስር ከሣሽ ያስረከቡ መሆኑንና በጊዜውም በሕጉ አግባብ መሠረት የእቢታ ማስታወቂያ /Protest/ ሳይፃፍላቸው ከስምንት ወራት በሁዋላ ጉዳቱ ደርሷል በማለት ጥያቄ መቅረቡ ሕጋዊ አለመሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በሁዋላ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የባሕር ሕጉ መሆኑን ጠቅሶ የኢትዮጵያ መድን ድርጅትንና አቶ ዮናስ ተስፋዬን ከኃላፊነት ነጻ ሲያደረጋቸው ታብታራ ኃ/የተ/የግል ማህበርን ለጉዳዩ ኃላፊ በማድረግ በከሣሽ የተጠየቀውን ገንዘብ ያህል እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የስር ከሣሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅትና አቶ ዮናስ ተስፋዬ ከኃላፊነት ነፃ መባላቸው ያለአግባብ ነው በማለት ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ደግሞ ኃላፊነት የለብኝም በማለት በየፊናቸው ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ መዛግብቱ ተጣምረው ታይተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ የንግድ ሕጉ ሁኖ የስር ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ከኃላፊነት ነፃ መደረጉ ያላግባብ ነው ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ከመድን ሰጪና ከአቶ ዮናስ ተስፋዬ ጋር ተጣምሮ መክሰሱም ያላግባብ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለክሱ መሠረት የሆነውን ገንዘብ ለከሣሽ /ቻይና ወንቦ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን /እንዲከፍል መድን ሰጪው ገንዘቡን ለከሣሽ ከፍሎ የስር ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተከሣሾችን የመክሰስ መብቱ የተጠበቀ መሆኑ ተገልጾ ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በሁለት መዛግብት ነው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 49295 አመልካች የሆነው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሲሆን የሰበር ተጠሪ የሆኑት የስር ከሣሽና የስር ሁለተኛ ተከሣሽ ናቸው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 49321 አመልካች የሆነው የስር ከሣሽ ሲሆን የሰበር ተጠሪ የሆነው ደግሞ የስር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ነው፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነገረ ፈጅ መስከረም 11 ቀን 2002 ዓ/ም በጻፋት ስምንት ገፅ የሰበር አቤቱታ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ፡- ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የባህር ሕግ ሁኖ እያለ ከውሉ መሠረታዊ ይዘት ውጪ የንግድ ሕጉ ተፈፃሚነት አለው መባሉ ያላግባብ ከመሆኑም በተጨማሪ መድን ድርጅቱ የስር ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾችን በመክሰስ የመዳረግ መብቱን ሊያስከብር ይችላል ተብሎ መወሰኑ ከስነ ሥርዓት ውጪ ከመሆኑም በላይ በውጤት ደረጃ የመድን ድርጅቱን መብት ሊያስጠብቅ የሚችልበት ከሕግም ሆነ ከውል የመነጨ ምክንያት የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ውሣኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የቀረበው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የባህር ሕጉ ሳይሆን የንግድ ሕጉ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመረር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደረገ ሲሆን ተጠሪ የሆኑት የስር ከሣሽና የስር ሁለተኛ ተከሣሽ ቀርበው የፅሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የስር ከሣሽ የሆነው ድርጅት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ መስረከረም 18 ቀን 2002 የተፃፈ ሁኖ መሰረታዊ ይዘቱ የስር ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ድርጅት /ታቭትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር / ከስር ተከሣሾች ጋር ተጣምሮ መከሰስ የለበትም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ያለግባብ ነው የሚል ሲሆን ይኸው አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙም ግራ ቀኙ የጽሑፍና የቃል ክርክር እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 37799 ከሰጠው የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

1. <u>**በኢትዮጵያ መድን ድርጅትና በቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን መካከል ያለውን የመድን ዋስትና በተመለከተ ተፈፃሚነት ስላለው ሕግ፡-**</u>

መድን ሰጪ የሆነው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ጋር የመድን ውል ያለው ስለመሆኑ ሳይክድ ጉዳዩ ሊገዛ የሚገባበትን ሕግ ለይቶ ክርክር አቅርቧል፡፡ በመድን ሰጪ በኩል ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰው ሕግ የባህር ሕጉ ነው፡፡ መድን ገቢ የሆነው የቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ደግሞ በንግድ ሕጉ ጉዳዩ ሊገዛ የሚችል ነው በማለት ምክንያቶችን ጠቅሷል፡፡ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ ያደረጉትን የመድን ውል እንደተመለከተው የባህር ጉዞ ፖሊስ የሚባል መሆኑን ከሰነዱ የተገነዘበ ሲሆን በኢንሹራንስ ውል ላይ በተራ ቁጥር 1.4 እስከ 7 ከተዘረዘሩት የአደጋ መንስኤዎች በስተቀር የጉዞው ሽፋኑ እቃው ከሚመጣበት የቻይና ሀገር እስከ እቃው የሚደርስበት የኢትዮጵያ ግዛት ደብረ ብርሃን ድረስ ለሚደርስ ማንኛውም ጉዳት ስለመሆኑ በውሉ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ ደግሞ እቃው በሰሌዳ ቁጥር 3-26454 ኢት ተሳቢ ቁጥር 3-02979 ኢት የጭነት መኪና ከጅቡቲ ወደብ ተጭኖ በመሬት ሲጓጓዝ በአፋር ብሔራዊ ክልል ኤሊዳር ከተማ መኪናው ተገልብጦ የመድን ዋስትና በተገባለት እቃ ላይ ጉዳት መድረሱ ሲሆን የመድን ውሉ በአንቀጽ 19 ስር ኢንሹራንሱ የሚገዛው በኢትዮጵያ ሕግና ልማድ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የመድን ውሉ ይዘት ከላይ በተመለከተው መልኩ ስለመሆኑ ግልፅ ማስተባበያ ክርክር ሳያቀርብ የውሉን ርዕሰና የባህር ኢንሹራንስ መሰረታዊ ባህሪያትን እንዲሁም የዓለም አቀፍ ልምድን መሠረት አድርጎ ክርክር አቅርቧል፡፡ በእርግጥ የባህር ኢንሹራንስ መሠረታዊ ባህርይ ሲታይ ኢንሹራንሱ የሚገባው በባህር ላይ ለሚደርስ አደጋ ላይ፡፡ የባህር ሕጉ አንቀፅ 292/1/ ሲታይም ግባቸው ሕጋዊ ለሆነው የገንዘብ ግምት ዋጋ ላላቸውና ሊደርስ የሚችል የባህር አደጋ ለሚያስፈራቸው ነገሮች ሁሉ ኢንሹራንስ ሊደረግላቸው እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን የዚሁ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ በባህር አደጋ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ካልሆነ በቀር ማንም ሰው በኢንሹራንስ የሚገኘውን ጥቅም ለመጠየቅ አይችልም በማለት ይገልፃል፡፡ የባህር ሕጉ ስለኢንሹራንስ ውል የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የሚያስቀምጠው አንቀጽ ሰባት ምዕራፍ አንድ በቁጥር 288 ስር ዋናው ዓላማ በባህር የሚደርሰውን አደጋ ወይም ከዚሁ ጋር ተጨማሪ የሆኑትን አደጋዎችም ለማረጋገጥ ቢሆን እንኳ ማንኛውም የኢንሹራንስ ውል በዚሁ ክፍል በተደነገጉት ውሣኔዎች ይመራል በማለት ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የባህር ሕጉ ተፈፃሚነት የሚኖረው በባህር አደጋ ሲደርስ ስለመሆኑ ነው፡፡ የባህር አደጋ የሚባለው ደግሞ በባህር ላይ ዘረፋ እና የመሳሰሉ ሁነው የባህር ክልል ውስጥ የሚደርሱ አደጋዎች ናቸው፡፡ የባህር ሕጉ ከመግቢያው ጀምሮ ሲታይ የባህርን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚገዛ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት የባህር ሕጉ ድንጋጌዎችና የሕጉ መግቢያ ይዘትና መንፈስ ሲታይ የባህር ሕግ የተፈፃሚነት አድማሱ የባህርን ጉዳይ ለሚመለከቱ ጉዳዮች ነው፡፡ ለክርክሩ አግባብነት ያላቸው የባህር ሕጉ ድንጋጌዎች ይዘታቸውና መንፈሳቸው ከላይ የተመለከተው ሲሆን የንግድ ሕጉ አንቀጽ 655 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ሲታይም ለጉዳዩ ጭብጥ አወሳሰን ምላሽ የሚሠጥ ሁኖ ይገኛል፡፡ ይህ ድንጋጌ ስለኢንሹራንስ የተመለከቱት የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች የተፈፃሚነት ወሰንን የሚያሳይ ሲሆን በንዑስ ቁጥር አንድ በንግድ ሕጉ ስለኢንሹራንስ የሚደነግገው አንቀጽ ሶስት ተፈፃሚ የሚሆነው በመሬት ፣ በወንዝና በአየር ለሚደርሱ አደጋዎች መሆኑን ሲጠቅስ የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ በንግድ ሕጉ ስለኢንሹራንስ የተመለከተው አንቀጽ በባሕር ሕግ የሚተዳደረውን የባህር ኢንሹራንስን የማይመለከት ስለመሆኑ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው የውሉ አርዕት የባህር ኢንሹራንስ ነው ተብሎ በተዋዋይ ወገኖች መገለጹ ውሉ በባህር ሕጉ እንዲገዛ ፍላጎት ስላላቸው በዚሁ መልኩ ውሉ መገዛት ያለበት ሳይሆን የውሉ ይዘትና አደጋው የደረሰበት ቦታ በራሱ ውሉ የሚገዛበትን የሕግ አግባብ ለመለየት የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የተዋዋይ ወገኖች ፍላጎት ከውሉ አጠቃላይ ይዘት ታይቶ ውላቸው የሚገዛበት ሕግ መለየቱ የውል አተረጓጎም ደንቦች የግድ የሚሉት ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን የሠጠው የመድን ውል በአርስት ደረጃ የባህር ጉዞ ፖሊሲ /Marine insurance / በሚል የተጠቀሰ ቢሆንም የውሉ አንቀጽ 1 እና 19 ይዘት ሲታይ ግን በውሉ በግልፅ ከተገለሉት አደጋዎች ውጪ በመሬት ላይ ለሚደርሱ ሌሎች አደጋዎች ሁሉ መድኑ የተገባ በመሆኑ በባህር ሕጉ ቁጥር 288 ፣ 292 እና በመግቢያው ላይ እንዲሁም በን/ሕ/ቁጥር 655 ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት ሲታይ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ሕግ የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ የቀረበው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው የሕግ ትርጉም መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

2. **ኃላፊነትን በተመለከተ፡-** የቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ሊከስ የቻለው በመድን ውሉ መሠረት ሲሆን ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበርን ደግሞ የእቃ ማጓጓዝ ውልን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽንና በታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር የተደረገው ውል እቃውን በማጓጓዝ ደብረ ብርሃን ከተማ ለማድረስ ሲሆን በውሉ አንቀጽ 3.6 ላይ እቃው ሲጓጓዝ በመንገድ ላይ ለሚደርስበት ማንኛውም ጉዳት ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ኃላፊነት ለመውሰድ ስለመሆኑ ቻይና ዋንቦ በዚህ ስበር ችሎት ባቀረበው ክርክር ላይ ጠቅሷል፡፡ ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ባቀረበው ክርክርም ከቻይና ዋንቦ ጋር የመጓጓዣ ውል መፈራረሙን ሳይክድ ስራውን በስር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሣሽ ለነበረው ለአቶ ዮናስ ተስፋዬ የሰጠ መሆኑን ይህም ግለሰብ በራሱ አሽከርካሪ እቃውን አስጭኖ ሲያመጣ ጉዳቱ የደረሰ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ እንግዲህ የቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን ከታብተራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር ያደረገው ስምምነት ሲታይ የትራንዚት አገልግሎትና የትራንስፖርት ስምምነት የሚል ስለመሆኑ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውሣኔው ላይ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ግንኙነቱ የሚገዛውም በደንብ ቁጥር 37/1990 ነው፡፡ በዚህ ደንብ አንቀጽ 2/1/ ስር እቃ አስተላላፊ በአገር ውስጥ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ እቃ ተቀባይነት ወይም እቃ ላኪነት በመወከል የጉምሩክ የወደብ ወይም ሌሎች ስርዓቶች አስፈፅሞ ገቢ ወይም የወጪ እቃዎችን ወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ የሚያደርግ ሲሆን እቃን የማጓጓዝና የማስረከብን ስራም እንደሚጨምር ተቀምጧል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ጠቅላላ ይዘት ሲታይም እቃ አስተላላፊው ስራውን የሚያከናውነው እቃ ላኪዎችን ወይም ተቀባዮችን በመወከል ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን የሚያስገነዝብ ቢሆንም በደንቡ አንቀጽ 3/6/ እና 7 ድንጋጌዎች ስር ያሉት ሁኔታዎች ሲታዩ ደግሞ የእቃ መጓጓዝ ተግባሩ እንዴት ሊከናወን እንደሚገባ ያመላክታሉ፡፡ በደንቡ አንቀጽ 3/6/ ድንጋጌ ስር እቃ አስተላላፊ የራሱን የትራንስፖርት አገልግሎት ካለው የእቃ ማጓጓዙን ተግባር የሚያከናውነው እንደ አጓዥ ሁኖ እንጂ በውልክና አለመሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ግን የራሱ ትራንስፖርት ከሌለው ወይም ባለእቃው የራሱን ማጓጓዣ ካላቀረበ እቃ አስተላላፊው ማጓጓዣ ተከራይቶ እቃውን እንደሚያጓጉዝ በደንቡ አንቀጽ 3 ንዑስ ቁጥር ሰባት ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ በአንቀጹ ንኡስ ቁጥር ስድስት እንደተመለከተው የማጓጓዝ ስራውን እንደ አጓዥ ሆኖ እንደሚሰራ አያስቀምጥም፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው እቃ አስተላላፊ ስራውን ሁሉ የሚያከናውነው በውክልና ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር የማጓጓዝ ተግባሩን ያስፈጸመው በአቶ ዮናስ ተስፋዬ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ሲሆን ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር የማጓጓዝ ተግባሩን ያከናወነው በውክልና ተግባሩ እንጂ ራሱ በሰራው የማጓጓዝ ስራ አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ታብትራ ኃላፊነቱ የሚኖረው በደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀጽ 12 ስር በተመለከተው ሁኔታ ነው፡፡ በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ስር እቃ አስተላላፊ ወይም የመርከብ ወኪል ተግባሩን ባለማከናወኑ ጥፋት ቢፈጽም በተለይም እቃው ቢጠፋበት ቢጎድልበት ወይም እቃውን በወቅቱ ባያስረክብ ተጠያቂ የሚሆን መሆኑ የተቀመጠ ሲሆን የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጂም፡ “ the Frieght forwarder shall be liable for defaults in the performance of his duties, in particular he shall be liable for loss of or shortage of or damage to the goods or delay in delivery of the goods.” የሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ለጉዳቱ በመድን ውሉ መሠረት ኃላፊ በማድረግ ካሳውን ለቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን ከፍሎ ታብትራን ኃ.የተ.ግል ማህበር ወይም አቶ ዮናስ ተስፋዬን በን/ሕ/ቁጥር 683/3/ መሠረት እንዲጠይቅ መብቱን የጠበቀለት መሆኑን ውሣኔው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ በቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽንና በታብትራ ኃ.የተ.የግል ማህበር መካከል ያለው የእቃ ማጓጓዝ ተግባር የሚፈጸመው በውክልና ግንኙነት /እቃ አስተላላፊነት ነው፡፡/ በዚህ መልኩ ለሚፈፀም ተግባር እቃ አስተላላፊ የሚጠየቀው ደግሞ በደንቡ አንቀጽ 12/2/ ስር በተመለከተው ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት እቃ አስተላላፊ ተግባሩን በጥንቃቄ ማከናወን እንደአለበት የተቀመጠ ሲሆን የጥንቃቄው መለኪያ ሲታይም እቃ አስተላላፊው በገባው ውል ግዴታ መሠረት እቃውን በማጓጓዝ ለባለንብረቱ የማስረከብ ኃላፊነትን የሚሸፍን መሆኑ በድንጋጌው ከሰፈሩት አመላካች ነጥቦች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አንድ እቃ አስተላላፊ እቃዎችን አጓጉዞ ለባለንብረቱ ካላስረከበ በሕጉ አግባብ ኃላፊነቱን የሚያስቀሩ ሁኔታዎችን እስካላስረዳ ድረስ ጥፋት እንደፈፀመ የሚቆጠር መሆኑን የተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ በን/ሕ/ቁጥር 683/3/ ስር ወደ ተመለከተው ድንጋጌ ስንመለስ ደግሞ፡- ሌላ ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም በክፋት ያደረጉት ካልሆነ በቀር ኢንሹራንስ ሰጪው በኢንሹራንስ ገቢው ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወኪሎች ፣ ሰራተኞች ወይም ከእርሱ ጋር ዘወትር አብረው በሚኖሩት ሰዎች ላይ ኢንሹራንስ ሠጪው በምትክነት ክስ ለማቅረብ እንደማይችል ተቀምጧል፡፡ የድጋጌው የእንግሊዝኛ ቅጂም “Notwithstanding any provision to the contrary, the insurer may not claim against the ascendants, descendants, agents or employees of the insured person nor against persons living with him, unless such persons have acted maliciously..” በማለት ይደነግጋል፡፡

የዚህ ድንጋጌ አቀራራጽና ይዘት ሲታይ ኢንሹራንስ ሰጪ ክስ ሊያቀርብባቸው የማይቻላቸው ወገኖች ከኢንሹራንስ ገቢው ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸውና ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለኢንሹራንስ ገቢው ጥቅም በሚሰሩ ወገኖች ላይ መሆኑን የሚስገነዝብ ነው፡፡ ስለሆነም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እነዚህ ወገኖች ከወካዩ ጋር ካላቸው የጠበቀ ግንኙነትና ስራቸውን የሚያከናውኑት ደግሞ ለወካዩ ጥቅም እስከሆነ ድረስ በደንብ ቁጥር 37/90 ስለእቃ አስተላላፊ ከተሰጠው ትርጉም ጋር እኩል ተደርገው ሊወሰዱ የሚገባ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የእቃ አስተላላፊነት ተግባር የሚከናወነው በውክልና ስልጣን መሠረት ቢሆንም እቃ አስተላላፊው ለእራሱ ጥቅም የሚሰራ ነውና፡፡ በመሆኑም እቃ አስተላላፊነት በን/ሕ/ቁጥር 683/3/ ስር “ወኪሎች” በሚል ከተዘረዘሩት ወገኖች ስር ሊካተት የሚችል አይደለም፡፡ በን/ሕቁጥር 683/3/ ስር የተመለከቱት ወገኖች የሚፈፅሙት ተግባር የመድን ሰጪውን በምትክነት እንዲገባና ሃላፊነቱን እንዲወስዱ የሚያደርገው ተግባሩ በክፋት የተደረገ/Have acted maliciously/ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህም የጥፋቱ አፈፃፀም መለኪያው በደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀጽ 12 ስር ከተመለከተው የወኪሎች ተግባር ጥፋት ጋር ሲነጻጸር የጠበቀ መሆኑን የድንጋጌው አቀራረፀ ያሳያል፡፡ ይኸውም አንድ ድርጊት በክፋት የተፈጸመ ነው የሚባለው ምንም ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር በአንድ ሰው መብት እና ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ ሆነ ተብሎ ሲፈፀም መሆኑ ታዋቂው የሄኔሪ ብላክስ የሕግ መዝገብ ቃላት “Malicious Act is an intentional, wrongful act performed against another without legal justification .” በማለት ከሰጠው ትርጉም የምንገነዘበው ሲሆን ከደንብ ቁጥር 37/90 አንቀጽ 12 ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጥፋት ደግሞ ከውል አፈጻጸም ጋር ተያይዞ ግዴታ ሳይፈጸም ሲቀር የሚነሳና ኃላፊነት የሚያስከትል፣ ሕጉም ምክንያቶችን አመልካችነት ባለው ሁኔታ የጠቀሰ በመሆኑ ጥፋቱ የሚፈፀመው ሰፋ ባሉ አጋጣሚዎች መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው መዝገበ ቃላት ጥፋትን ሲተረጎም “Default is the omission or failure to perform a legal or contractual duty.” በማለት ያስቀመጠው ሲሆን ይህም ትርጉም ጥፋቱ ከውል አፈጻጸም ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነው በማለት የገለፅነውን አባባል የሚያጠናክር ነው በመሆኑም የፊዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በን/ሕ/ቁጥር 683/3/ መሠረት ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበርን ለመጠየቅ ይችላል ብሎ ሲወሰን መሰረት ያደረገው ሕግ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 37799 ላይ የእቃ አስተላላፊ በክፋት ለፈጸመው ተግባር ካልሆነ በስተቀር የሚጠየቅበት አግባብ የለውም በማለት የን/ሕ/ቁጥር 683/3/ “ን” መሠረት በማድረግ የሰጠው ትርጉምም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ሕግ መሠረት በማድረግ የተሰጠ ሁኖ ስለአገኘነው በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/2/ መሠረት መለወጥ ያለበት ነው፡፡

ሌላው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ካሣውን ከፍሎ ታብትራ ኃ/የተ/የግ ማህበርን እንዲጠይቅ ውሣኔ የተሠጠበትን የክርክር ሂደት አግባብነቱን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በእነዚህ ወገኖች መካከል የሚነሳው ክርክር የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 37/90 ሲሆን የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን በሰጠው የመድን ውል መሠረት በእቃ አስተላላፊው ላይ የሚያቀርበው ክርክር እቃው አቅም በሌለው መንገዣ ላይ በመጫኑ ጉዳቱ መድረሱን የሚያሳይ ሲሆን ታብትራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ደግሞ በክሱ ውስጥ ተሳታፊ የሚሆንበት ወይም በጣምራ የሚከሰስበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ በመከራከሩ ይህንኑ የእቃ አስተላላፊ ክርክር የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት እንዳለ ተቀብሎ በስር ፍርድ ቤት የክሱ አመሰራረትም ሆነ የክርክሩ አመራር ስነ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ታብትራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው መልስም የመከራከር መብቱ መጣበቡን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተገንዝቦ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ መሆኑንና በጭብጥ አመሰራረትም ሆነ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካለው ድንጋጌ አንጻር አንድ ተከሣሽ ሌላ ተከሣሽ ለሰጠው መከራከሪያ መልሱን የሚሰጥበት አግባብ በኢትዮጵያ የሙግት አመራር ሥርዓት ውስጥ የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ እኛም እንደተመለከትነው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን ላይ የሚያነሳው ክርክር የመድን ውሉንና የንግድ ሕጉን መሠረት ያደረገ ቢሆንም ቻይና ዋንቦ ከእቃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስተላላፊው ጋር የሚያቀርበውን ክርክር ደግሞ መድን ድርጅቱ በውሉ በሚያገኘው የመዳረግ መብት በእቃ አስተላላፊው ላይ ከማቅረብ የሚከለክለው ሕግ የለም፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም መድን ድርጅቱ እቃ አስተላላፊውንና አጓዡን የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀለት ነው ያለው በእነዚህ ወገኖች የቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን ሊያነሳ የሚችለውን ክርክር ሁኖ እነዚህ ወገኖች ደግሞ ለመድን ድርጅቱ ጥያቄ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን የሚያሳይ ክርክር ሊያቀርቡ የሚችሉት በቻይና ዋንቦ ላይ ወይም ታብትራ ከአቶ ዮናስ ተስፋዬ ላይ ፣ ወይም ዮናስ ተስፋዬ ደግሞ በታብትራ ላይ ሊያነሱ የሚችሉትን ክርክር ነው፡፡ ለጉዳዩ አወሳሰን ደግሞ ከመድን ውሉ ጀምሮ ሁሉም ወገኖች በመካከላቸው ያደረጉት ስምምነት አግባብነት የሚኖረው ይሆናል፡፡ የመዳረግ መብት አጠቃላይ ዕንሰ ሀሣብ ሲታይም የመጨረሻ ኃላፊነት ያለውን ወገን በመለየት ካሣውን የከፈለው ወገን ገንዘቡ እንዲተካለት ማድረግ ነው ፡፡ ፍርድ ቤቶች በመድን ውሉ መሠረት ኃላፊነት ያለው ወገን ኃላፊ የማሆንበትን ምክንያት ገልፆ የሚከራከር ከሆነ ይህንኑ እንዲያስረዳ እድል መስጠት አለባቸው፡፡ እንዲሁም በክርክሩ ውስጥ የሚገባ ወገን ካለና ኃላፊነቱ የማን እንደሆነ እንዲለይ ከሣሽ ጥያቄ ከአቀረበም ይህንኑ በተገቢው መንገድ በመመራት ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ይገባቸዋል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁጥር 36/5/ ፣ 39 ፣ 40 ፣ እና 43 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስም ይህንኑ የሚያሳይ ነው፡፡ ግልፅ የሆነ ክርክር ቀርቦ ባለበት ሁኔታ እነዚህ ድንጋጌዎች በአግባቡ ሳይተገበሩ የሚሰጠው ውሣኔ በክርክር አመራር ስርዓት ተቀባይነት አለው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የመድን ውሉ መኖሩን ሳይክድ ኃለፊነት የሌለበት መሆኑን ጠቅሶ የሚከራከረው መድን የተገባለት እቃ ላይ ጉዳት የደረሰው አቅም በሌለው መኪና ላይ በመጫኑ ምክንያት ነው የሚል ክርክር ሲሆን ይኸው ተግባር እቃ አስተላላፊውን በደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀፅ 12/2/ መሠረት ሊያስጠይቅ የሚችል መሆን ያለመሆኑ ፣እቃ አስተላላፊው አጓዡ /አቶ ዮናስ/ ኃላፊነት ያለው መሆን ያለመሆኑን ሊያስረዳ የሚችል መሆን ያለመሆኑ አጓዥ የተባሉት አቶ ዮናስ ተስፋዬ ለጉዳቱ የማይጠየቁበት የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር ያለ መሆን ያለመሆኑ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጭብጦች መለየት ያለባቸው የኢትየጵያ መድን ድርጅት ካሣውን ለቻይና ዋንቦ ኮርፖሬሽን ከከፈለ በኋላ ሳይሆን አሁን በቀረበው ክርክር መሆኑን የክርክሩ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ የታብትራ ኃ/የተየግል ማህበር ጠበቃ አንድ ተከሣሽ ላቀረበው ክርክር ሌላው ተከሣሽ መልስ እንዲሰጥበት የሚያስችል የክርክር ስርዓት በኢትዮጵያ የሙግት አመራር ሥርዓት የለም፣ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሣኔም ይህንኑ ያገናዘበ ነው በማለት ለሰበር ችሎት በሰጡት መልስ ላይ ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ የፍትሓ ብሔር ክርክር ላይ በክርክር አመራር እና እውነትን በማውጣት ረገድ የፍርድ ቤት ሚና ሲታይ እጅጉን ከፍተኛ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39 ፣ 40 ፣ 91 ፣ 136 ፣ 241 ፣ 246 ፣ 247 ፣ 248 ፣ 256 ፣ 265 ፣266፣ 272 እና ሌሎች በርካታ በዋቢነት የሚጠቀሱ ድንጋጌዎች ያሉ በመሆኑ አንድ ተከሣሽ በሚያቀርበው ክርክር ላይ ሌላው ተከሣሽ መልስ /ክርክር / እንዲያቀርብበት ማድረግ ሥርዓቱ የሚደግፈው አይደለም ሊባል የሚችል አይሆንም፡፡ ዋናውና ቁልፉ ነገር የተከራከሪ ወገኖች የመከራከር መብት መጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የታብትራ ጠበቃ ያቀረቡትን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ባቀረበው ክርክር ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበርም ሆነ አቶ ዮናስ ተስፋዬ ክርክር እንዲያቀርቡ አድርጎ ሙግቱን አለመመራቱን በማረም ጉዳዩን እንደገና እንዲመለከተው ማድረግ ሲገባው መድን ድርጅቱን ከወዲሁ ለጉዳቱ ኃላፊ በማድረግ ሌላ ክስ አቅርቦ መብቱን ሊያስከብር ይችላል በማለት የሰጠው ውሣኔ የመድን ድርጅቱ የመድን ውሉንም ሆነ በደንብ ቁጥር 37/1990 እንዲሁም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የሚያቀርበውን ክርክር ከወዲሁ ዋጋ ሊያሳጣ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ከክርክሩ ይዘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገዝበናል፡፡ በዚህም ምክንያት ኃላፊነቱን በተመለከተ የተሰጠው ውሣኔ የክርክር አመራር ስርዓቱ በአግባቡ ሳይከናወን የተሰጠ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ጉዳዩ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ክርክር ምክንያቶች መሠረት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ ተሸሮ ክርክሩ እንደገና መመራት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1- በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39888 ሰኔ 25 ቀን 2001 ዓ/ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2- የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔም ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡
3- ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37799 ላይ በደንብ ቁጥር 37/1990 መሠረት በራሱ ማንጓጠጥ እቃ የማያስተላላፍ ሰው ለመድን ሰጪ ሊጠይቅ የሚችለው በን/ሕ/ቁጥር 683/3/ መሠረት የክፋት ተግባር የፈፀመ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው በማለት የሰጠው የህግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/2/ መሠረት ተለውጦ እንደዚህ አይነት ግንኙነት ሊገዛ የሚገባው በደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀጽ 12/2/ በተመለከተው ሁኔታ ነው ብለናል፡፡
4- የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች/ታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ዮናስ ተስፋዬ /በኢትዮጵያ መድን ድርጅት በቀረበው ክርክር ተገቢ ነው የሚሉትን ክርክር እንዲያቀርቡ አድርጎ እንዲሁም እነዚህ ተከሣሾች እርስ በራሳቸው የሚያቀርቡት ክርክር ካለም በመቀበል እና ማስረጃ ካላቸውም ከሰማ በሁዋላ ጉዳዩን ከደንብ ቁጥር 37/1990 አንቀጽ 12 እንዲሁም አቶ ዮናስ ተስፋዬ ከታብትራ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚገዛውን ውልና ሕግ በመለየት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
5- በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አምሮዊ ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- ኢትዮ ሴራሚክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡- 1. የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ነገረ ፈጅ አቶ አጥናፉ ደምሴ ቀረቡ

2. ኦቮርጊጋ ቴክኖሎጅ ሊሚትድ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች አንደኛ ተጠሪ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ በማየት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አንደኛ ተጠሪ ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረበውን የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ በመቀበል ሁለተኛ ተጠሪ በአራት ማዕዘን ውስጥ ዙሪያውን በአስር ኮከቦች የተከበበ " ETHIO CEMENT " የሚለው የንግድ ምልክት ለመመዝገብ የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ ዓለም አቀፍ ምድብ ያለው የሲሚንቶ ምርት ግልጋሎቱ በአራት ማዕዘን ውስጥ ዙሪያውን በአስር ኮከቦች የተከበበና መካከሉ " ETHIO CEMENT " የሚል ፅሑፍ ያለበት የንግድ ምልክት በአንደኛው ተጠሪ እንዲመዘገብለት ቁጥሩ 1912 በሆነ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ የንግድ ምልክቱን ከመመዝገቡ በፊት መቃወሚያ የሚያቀርብ ወገን ካለ መቃወሚያውን እንዲያቀርብ መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም. በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ማስታወቂያ አውጥቷል፡፡ አመልካች "ኢትዮ ሲሚንቶ" በሚለው የንግድ ሥም የኢንቨስትመንት ፈቃድ በማውጣት የሲሚንቶ ፋብሪካ ለማቋቋም ጥረት እያደረገ መሆኑን በመግለፅ ሁለተኛ ተጠሪ እንዲመዘገብለት ያቀረበው የንግድ ምልክት ከአመልካች የንግድ ስም ጋር አንድ አይነት በመሆኑና ሁለቱም ድርጅቶች የሲሚንቶ ምርት ለተገልጋዩ የሚያቀርቡ በመሆናቸው ተጠቃሚውን የሚያደናግር በመሆኑ የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብ አይገባውም የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ኢትዮ ሲሚንቶ /ETHIO CEMENT/ የሚለው ሀረግ የአመልካች የንግድ ስም መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያቀረበለት መሆኑን ገልፆ ሆኖም አመልካች ይህንን ሀረግ በንግድ ምልክትነት ስላላስመዘገበ፣ የሁለተኛ ተጠሪ የንግድ ምልክት ETHIO CEMENT የሚለው ሀረግ ብቻ ሣይሆን ዙሪያውን ያሉት ኮከቦች አካል ሆኖ ያቀረበ በመሆኑና አመልካች " ETHIO CEMENT " የሚለውን ሀረግ ከሌላ ሊመዘገብ ከሚችል ምልክት ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስመዝገብና መጠቀም ስለሚችል የአመልካች መቃወሚያ የህግ መሠረት የለውም በማለት፣ ሁለተኛ ተጠሪ እንዲመዘገብለት የጠየቀውን የግንድ ምልክት በመመዝገብ ዕውቅናና ጥበቃ ሰጥቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ በተሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔው የይግባኝ ቅሬታ የቀረበበት አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረቡትን መልስና የአመልካችን የመልስ መልስ ከሰማ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ውሣኔ ሲሰጥ ያቀረባቸውን ምክንያቶች በመቀበል አንደኛ ተጠሪ በአራት ማዕዘን ውስጥ በአስር ኮከቦች የተከበበ " ETHIO CEMENT " የሚል ፅሑፍ ያለበት የንግድ ምልክት የሁለተኛ ተጠሪ ንብረትና የንግድ ምልክት መሆኑን በማረጋገጥ መመዝገቡ የአመልካችን መብትና ጥቅም ስለማይነካ የንግድ ምልክቱ አይሰረዝም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ለሁለተኛ ተጠሪ በንግድ ምልክትነት የተመዘገበው " ETHIO CEMENT " የሚለው ሀረግ የአመልካች የንግድ ስምና መጠሪያ ሆኖ አግባብነት ባላቸው አካላት ተመዝግቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሁለተኛው ተጠሪን የንግድ ምልክት ሲመዘግብ አመልካች በንግድ ስሙ አምርቶ ፅፎ ለገበያ የሚያቀርበውን የሲሚንቶ ምርት ሁለተኛ ተጠሪ የንግድ ምልክት አድርጎ ለተገልጋዩ በሚያቀርበው የሲሚንቶ ምርት ላይ በንግድ ምልክትነት እንዲጠቀምበት ፈቃድ ሰጥቷል፡፡ ይህ ተጠቃሚውን ህብረተሰብ የሚያሣስትና የሚያደናግር ሲሆን የአንደኛ ተጠሪ ውሣኔ የንግድ አሠራር አዋጅ 329/95 እና የንግድ ምልክት ጥበቃና አሠራር አዋጅ 501/1998 መሠረታዊ ግብና ዓላማ በሚያሣካ መንገድ ተጣጥመው ሥራ ላይ እንዲውሉ የሚያደርግ አይደለም፡፡ ስለሆነም እኔ በንግድ ስምና መጠሪያነት የምገለገልበትን " ETHIO CEMENT " ሁለተኛ ተጠሪ የንግድ ምልክት አድርጎ እንዲጠቀም አንደኛ ተጠሪ የሰጠው ዕውቅና የአዋጅ ቁጥር 329/1995 ድንጋጌዎች እና የአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀፅ 5 እና ሌሎች ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ የንግድ ስም በአንድ ድርጅት መጠሪያነት የሚያገለግል ሲሆን ዓላማው አንደኛውን የንግድ ድርጅት ከሌላው የንግድ ድርጅት ለመለየት ነው፡፡ የንግድ ስም የሚመዘገበው በንግድ ሚኒስትር ወይም በክልል ንግድ ቢሮዎች ነው፡፡ የንግድ ምልክት የአንድን ሰው ምርት ወይም አገልግሎት ከሌላው ሰው ለመለየት የሚያገለግል ነው፡፡ የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚያደርገውና የሚመዘገበው በአዋጅ ቁጥር 501/1998 ሲሆን ይህንን ተግባር አንደኛ ተጠሪ እንዲያከናውን በአዋጅ ቁጥር 320/1995 ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ የንግድ ድርጅቶች የንግድ ስያሜያቸውን በንግድ ምልክትነት በማስመዝገብ ወይም በመጠቀም ባለቤት መሆን እንደሚቻል አዋጅ ቁጥር 501/98 በአንቀፅ 5/1/ እና በአንቀፅ 7/2/ በግልፅ የተደነገገ ቢሆንም አመልካች የንግድ ስማቸውን በንግድ ምልክትነት አላስመዘገቡም፡፡ አንደኛ ተጠሪ ጥበቃ የሰጠውና የመዘገበው ለኮከቦቹ እንጅ " ETHIO CEMENT " ለሚለው ሀረግ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሰበር አቤቱታው የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሆኖ እንድሰናበት በማለት ታህሣሥ 13 ቀን 2003 ዓ.ም. በፅሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ የንግድ ስምና የንግድ ምልክት የተለያዩ ናቸው፡፡ አመልካች ሲሚንቶ አምርቶ መሸጥ ስላልጀመረ በሚያመርተው ሲሚንቶ ላይ የሚያስቀምጠው የንግድ ምልክት ምን እንደሆነ ገና አልታወቀም፡፡ እኔ የአመልካችን የንግድ ስያሜ በንግድ ምልክትነት አልተጠቀምኩም፡፡ አመልካች ምርት ማከፋፈል አልጀመረም ስለዚህ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመሠረዝ እንዲያሰናብተን በማለት ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪና ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተጠሪ እንዲመዘገብለት ያቀረበው "የንግድ ምልክት" አመልካች የንግድ ስሙን በንግድ ምልክትነት ስላላስመዘገበ ወይም የንግድ ስሙ የሚያመርተውን የሲሚንቶ ምርት ለተጠቃሚው ማቅረብ ያልጀመረ በመሆኑ መቃወሚያ ሊያቀርብበት አይችልም በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መመርመር ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን አመልካችና ተጠሪ ለማምረትና ለመስጠት የሚፈልጉትን አገልግሎት አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች በተለይም ከንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 በአዋጅ ቁጥር 328/1995 እንደተሻሻለ አግባብነት ያላቸውን የንግድ ህግ ድንጋጌዎች የንግድ አሠራር አዋጅ ቁጥር 329/1995 ከአንደኛው ተጠሪ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 320/1995 እና ከአዋጅ ቁጥር 501/1998 ድንጋጌዎች ማገናዘብና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተከተለውን የህግ አተረጓጎም ተገቢነት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በአዋጅ ቁጥር 67/1989 በአዋጅ ቁጥር 329/1995 እንደተሻሻለው በአንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረትና የንግድ ህግ አንቀፅ 135 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግጉት መሠረት "ኢትዮ ሲሚንቶ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር" በሚል የንግድ ስም ተመዝግቦ የሲሚንቶ ማምረቻ ፋብሪካ በማቋቋምና ሲሚንቶ በማምረት ለአገር ውስጥ ገበያና በተሻሻለው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁ. 328/1995 አንቀፅ 32 መሠረት ምርቱን ወደ ወጭ አገር ለመላክ የሚችል የንግድ ድርጅት ስለመሆኑ አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ ካቀረባቸው ማስረጃዎችና በይግባኝ እና በሰበር ካቀረበው ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ይህንን ተግባሩን ሲያከናውን በንግድ ህጉና በንግድ ሥራ አዋጅ 329/1995 መሠረት ተገቢው ጥበቃ የሚሰጠው ሲሆን በንግድ ሥራ አዋጅ ቁ. 329/1995 እና በሌሎች ህጎች የተደነገጉትን ግዴታና ሀላፊነቶች በአግባቡ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ይህም በመሆኑ አመልካች ፋብሪካውን በመገንባት ያመረተውን ሲሚንቶ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ሲያቀርብ በንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 21 በተደነገገው መሠረት ስለ አመረተው ምርት መግለጫ የመለጥፍ ግዴታ አለበት፡፡ በምርቱ ላይ የሚለጥፈው መግለጫ በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገውን መያዝ እንደሚገባውና በተለይም አመልካች የሲሚንቶ ምርቱን አሸጎ ለገበያ ሲያቀርብ በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ /3/ በሚደነግገው መሠረት የፅቃውን የተጣራ ክብደት፣ የፋብሪካው ወይም የአሻጊው ስምና አድራሻና ፅቃው አገልግሎት መስጠት የሚያበቃበትን ቀን እና ፅቃው የተመረተበትን ቀን በምርቱ ላይ የመፃፍ ግዴታና ሀላፊነት እንዳለበት ከላይ ከተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም የምንረዳው አመልካች የፋብሪካውን ግንባታ አጠናቅቆ የሲሚንቶ ምርት በማምረት ለገበያ ሲያሠራጭ ሲሚንቶውን ያመረተው “ኢትዮ ሲሚንቶ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር“ መሆኑን በመግለፅ የመለጠፍ ህጋዊ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በግልፅ የተደነገገ መሆኑ ነው፡፡ አመልካች ከዚህ በፊት የሲሚንቶ ምርት በንግድ ስሙ በመጠቀም ያላሰራጨ ቢሆንም ምርት ሲጀምር የንግድ ስሙንና አድራሻውን አሸጎ በሚያቀርበው የሲሚንቶ ምርት ላይ የመግለፅ /የመፃፍ/ ህጋዊ ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡

በሌላ በኩል ሁለተኛው ተጠሪ የሚሠራው ሥራ የሲሚንቶ ምርት ስርጭት ጋር የተገናኘ መሆኑ ሁለተኛው ተጠሪ ለአንደኛ ተጠሪ ባቀረበው አቤቱታ የተገለፀ ሲሆን፣ ሁለተኛው ተጠሪ በአራት ማዕዘን ውስጥ ሆኖ በአስር ኮከቦች የተከበበና /ETHIO CEMENT/ የሚለው ሀረግ ያለበት የንግድ ምልክት አንደኛ ተጠሪ ብቸኛ ባለሀብትና ተጠቃሚ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲመዘገብለት፣ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ይህ የሁለተኛው ተጠሪ የንግድ ምልክት በአራት ማዕዘን ምስል ውስጥ በአስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኮከቦች መካከል የሚፃፍ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ መሠረት አመልካች በሚያመርተውና አሸን በሚሸጠው የሲሚንቶ ምርት ላይ መግለፅ ህጋዊ ግዴታው ከሆነው የአመልካች የንግድ ስም / ኢትዮ ሲሚንቶ/ በእንግሊዝኛው " ETHIO CEMENT " PRIVATE LIMITED ጋር አንድና ተመሣሣይ ነው፡፡ ተጠሪ በንግድ ምልክትነት በሚያመርተውና በሚያሰራጨው የሲሚንቶ ምርት ላይ እንዲለጥፍ በአንደኛ ተጠሪ የተመዘገበለት የንግድ ምልክት አመልካች በህግ ተገድዶ በምርቱ ላይ መግለፅ ከሚገባው የንግድ ስያሜ ጋር የሚመሳሰል ተመሣሣይ " ETHIO CEMENT " የሚል ሀረግ ያለው ነው፡፡

የንግድ ሥራ አዋጅ መሠረታዊ ዓላማ ለነፃ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ሥራዎች እንዳይፈፀሙ በመከላከልና በማስወገድ ተገቢ የንግድ ውድድር እንዲሰፍን ማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ በዚህ አዋጅ መሠረት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ማለት በንግድ ሥራ ኡዲት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ተወዳዳሪን ለማጥፋት ያለመ ማንኛውም ድርጊት ወይም ተግባር ሁሉ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር እንደሆነ እንደሚቆጠር በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 1 በመርህ ደረጃ የተደነገገ ሲሆን፣ በሌላው የንግድ ድርጅት ወይም በንግድ ድርጅቱ ተግባሮች በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ ማደናገርን ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ድርጊትና የአንድ ድርጅት ወይም የድርጅቱን ተግባሮች በተለይም ድርጅቱ ከሚያቀርበው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ የሕዝብ ግንዛቤን ያዛባ ወይም ሊያዛባ የሚችል ማናቸውም ድርጊት ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ውድድሮች እንደሆኑ በአዋጅ አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/ እና /ሐ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

በተመሣሣይ ሁኔታ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ መሠረታዊ ግብ ፅቃ በማምረት እና በማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎችን መልካም ስም እና ዝና መጠበቅና በተመሣሣይ ፅቃዎችና አገልግሎቶች መካከል መሣከርን ማስወገድ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 501/1998 መግቢያ በመጀመሪያው ፓራግራፍ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንደኛ ተጠሪ የፖተንትና የንግድ ምልክት የምዝገባ ወረቀት ማመልከቻዎችን ተቀብሎ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅን መሠረታዊ ግብና ዝርዝር ድንጋጌዎች እንደዚሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መመርመር ወይም እንዲመረመር የማድረግ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 320/95 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አንደኛ ተጠሪ " ETHIO CEMENT " የሚል ሀረግ ያለበትን የንግድ ምልክት እንዲመዘግብለት ሁለተኛ ተጠሪ ሲጠይቀው "ኢትዮ ሲሚንቶ" በእንግሊዝኛው " ETHIO CEMENT " በሚል የንግድ ስም የሚጠራው አመልካች በሚያመርተውና አሸን በሚሸጠው ሲሚንቶ ላይ ይህንን የንግድ ስሙን የመፃፍና የመግለፅ ግዴታና ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 329 በአንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ የተጣለበት መሆኑንና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በአንድ በኩል በአራት ማዕዘን ምስል ውስጥ ሆኖ በአስር ኮከቦች መካከል የተፃፈ " ETHIO CEMENT " የሚል ሀረግ ያለው የንግድ ምልክት ያለበት ሲሚንቶ በሁለተኛው ተጠሪ የሚቀርብ መሆኑና በሌላ በኩል " ETHIO CEMENT " ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚለው የአመልካች የንግድ ስም የተፃፈበት የሲሚንቶ ምርት ሊቀርብለት የሚችል መሆኑን የማገናዘብ ሀላፊነት አለበት፡፡

እነዚህ ሁለት ምርቶች ለተጠቃሚው በሚቀርቡበት ጊዜ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ የወጣበትን መሠረታዊ ዓላማ በሚፃረር መንገድ በሁለተኛው ተጠሪና የአመልካች ምርት መካከል መሣከርን የሚፈጥርና በአዋጅ ቁጥር 329/95 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/ እና /ሐ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክልከላ የተደረገበት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ምክንያትና መንስኤ የሚሆኑ በመሆኑ አንደኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 320/95 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን አግባብነት ያላቸውን ህጎች ሣይመረምር የአመልካችን የንግድ ስም በውስጡ የሚያካትተውን የሁለተኛ ተጠሪ የንግድ ምልክት ተቀብሎ መመዝገቡ ህግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 329/95 እና በአዋጅ ቁጥር 501/98 በንግድ ሥራ ለተሰማራው ሰውም ሆነ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ለመስጠት ያሰበውን ህጋዊ ጥበቃና ዋስትና በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ ለማድረግ የማያስችል የህግ አረዳድና አተገባበር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛው ተጠሪ የአመልካች የንግድ ስም የተካተተበትን የንግድ ምልክት በመመዝገብ የሰጠው ዕውቅና ከላይ በዝርዝር ይዘታቸው፣ መሠረታዊ ዓላማና ግባቸው የዘረዘርናቸውን ተያያዥነት ያላቸው የህግ ማዕቀፎችና ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረት ያላደረገ፣ እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 320/95 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት አግባብነት ያላቸውን ሌሎች የህግ ማዕቀፎችና ድንጋጌዎች ሣይመረምርና ሣያገናዝብ የሰጠው ውሣኔ በመሆኑ በይግባኝ ሊታረም የሚገባው ሆኖ እያለ በይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት መዕናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አንደኛ ተጠሪና በከፍተኛው ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረበውና የአመልካችን የንግድ ስም የሚያካትተውን የንግድ ምልክት እንዲመዘገብ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ሁለተኛ ተጠሪ የአመልካችን የንግድ ስም " ETHIO CEMENT " የሚለውን ሀረግ ከንግድ ምልክቱ በማውጣትና በሌላ በመተካት የንግድ ምልክቱን ሠርቶ ካላቀረበ በስተቀር የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብና ህጋዊ ጥበቃ ሊሰጠው አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሸ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59025

ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረቶች ጽ/ቤት -ነ/ፈጅ አጥናፉ ደምሴ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ጥበበ አየለ - ጠበቃ ታገል ጌታሁን ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአመልካች መስሪያ ቤት በአዋጅ ቁጥር 501/98 መሠረት በሚሰጡት ውሰኔዎች ቅሬታ ያለበት ወገን አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚገባበትን ፍርድ ቤት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት ተጠሪ ናቸው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ላይ የመሰረቱት የክስ ይዘት ባጭሩ፡- RISING የሚለውን የንግድ ምልክት እንዲመዘግብልኝ አመልክቼ ማመልከቻዬን ያላግባብ ያልተቀበለኝ ስለሆነ የንግድ ምልክቱን እንዲመዘግብልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ማየት እንደማይችል ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥብን ውድቅ አድርጓል በፍሬ ጉዳዩ ላይም ተጠሪ የንግድ ምልክቱ እንዲመዘገብላቸው ሲል ወስኗል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው አመልካች መስሪያ ቤት በፍርድ ቤት ሊከሰስ እንደሚችል አዋጅ ቁጥር 501/98 ይደነግጋል በሚል ምክንያት ነው ፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የአመልካች መስሪያ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17 ስር የተደነገገ ሆኖ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ደግሞ ይግባኙን ማቅረብ ያለበት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 49 ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተሰጠው የይግባኝ ስልጣን ድንጋጌዎች ጋር አጣምሮ በማንበብ መረዳት የሚቻልና በጉዳዩ ላይ በስራ ላይ የነበሩትና ሌሎች ተዛማጅ ሕጎችም ሆነ ያለው አሰራር አየመልካች መስሪያ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይቀርብ የነበረ አሁንም እየቀረበ ያለ መሆኑን በግልጽ የሚያሳዩ ሁነው እያለ ጉዳዩን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ቀጥታ ክስ መመልከቱ ተገቢነት የለውም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመርምሮም በስር ፍርድ ቤት የቀረበውን የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ ተቀብሎ የተጠሪን የንግድ ምልክት እንዲመዘግብ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ አስተናግዶ ፍርድ የሰጠበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 320/1995 ፣ 501/98 እና 25/1988 አንፃር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የጽሁፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል። ተጠሪ በጽሁፍ መልሳቸው በተመሳሳይ ጉዳይ በመ/ቁጥር 56938 በሰበር ችሎት የአመልካች የሰበር ቅሬታ ለሰበር ችሎቱ አያስቀርብም ተብሎ መዘጋቱን ፣በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/2/ ስር ይግባኝ የሚለው ቃል መቀመጡ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተቀመጠውን የይግባኝ ቃል ትርጉም በመያዝ ሳይሆን ቅሬታ በሚል ቃል መንፈስ ነው የሚሉትንና ሌሎች ነጥቦችን በማንሳትና በዋቢነትም አግባብነት አላቸው ያሏቸውን ሕጎችና ድንጋጌዎችን በመጥቀስ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል። አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። አንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያሰፈልገው አቢይ ነጥብ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን አለው? ወይስ የለውም የሚለው ሆኖ አኝቶታል።

በመሠረቱ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 320/1995 አንቀጽ 6/1/ መሠረት የንግድ ምልክት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎችን በመቀበል አግባብ ባለው የአእምሯዊ ንብረት ሕግ መሠረት ምርመራ በማካሄድ ውሳኔ የመስጠትና በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 36 መሠረት በተመዘገበ የንግድ ምልክት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን በማየት ፈራሽ የማድረግ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በግልፅ ያስገነዝባሉ። የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ሲታይም የአመልካች መስሪያ ቤት ስለንግድ ምልክቱ ምዝገባ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል አስቀምጧል። የአዋጁ አንቀጽ 49 ሲታይ ደግሞ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤትን ያሳያል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በአዋጁ አንቀጽ 47 መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ የተመለከቱ ጉዳዩችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችንና ተዛማጅ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የሚኖራቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በሚል የሚደነግግ ነው። እንግዲህ በሕጉ ረገድ ያለው የውሳኔ አሰጣጥና የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ሕጉ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት (The right to Appeal) እንዳለው በግልፅ ከማስቀመጡ ውጪ ይግባኙ በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች በየትኛው እርከን ለሚገኝ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ ግልጽና አሻሚነት በሌለው አነጋገር አያስቀምጥም። እንዲህ በሆነ ጊዜ ሕጉን መተርጎም ተገቢ ይሆናል።

የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ርእሱ ሲታይ አማርኛው “ይግባኝ የማቅረብ መብት” በሚል የተቀመጠ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጂ ደግሞ “The right to Appeal” በሚል የተቀመጠ ነው። እንግዲህ ሕጉ በይዘቱና በቅርጹ ይህን የሚመስል ከሆነ ይግባኝ የሚለው የሕጉ አገላለፅ ለየትኛው ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩ መቅረብ ያለበት የሚለውን ጥያቄ ይፈታ ዘንድ የይግባኝ ትርጉሙንና የአቀራረብ ሥርዓቱን በአጠቃላይ ማየቱን፣ የአመልካች መስሪያ ቤትን ለማቋቋም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወጣውን ሕግና ለመስሪያ ቤቱ ስልጣን የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሕጎች የሚያስቀምጡትን የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት መመልከቱና ግንዛቤ መውሰዱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ታዋቂው የ“ Black’s Law Dictionary” ይግባኝ የሚለውን ቃል ሲተረጎም A proceeding undertaken to have a decision reconsidered by bringing it to a higher authority, especially, the submission of a lower court’s or agency’s decision to a higher court for review and possible reversal. በሚል ያስቀምጣል፡፡ ከዚሁ መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ በበታች አካል የተሰጠ አንድ ፍርድን ወይም ውሳኔን በመቃወም ለበላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረብ የስር ፍርዱ /ውሳኔ/ እንደገና የሚታይበትን ወይም እንዲጣራ የሚደረግበትን ወይም ሊለወጥ የሚችልበትን ሥርዓት የሚያመላክት መሆኑን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 320/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ሲታይም በፍትሓብሔር ወይም በሌሎች ሕጎች ውስጥ በሌላ ሁኔታ እንዲፈጸም የሚያዝ ድንጋጌ ከሌላ በቀር ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤት በተወሰነበት የመጨረሻ ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችሉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የይግባኝ ትርጉም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪ የነበረና በተሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን ይህንኑ ቅሬታውን ለበላይ ወይም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ የበታች ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ እንዲሻሻል ፣ እንዲለውጥ ወይም በጠቅላላው ውድቅ እንዲሆንና ዳኝነቱ ለእሱ እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 ደግሞ የይግባኝ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17/1/ ድንጋጌ ስለንግድ ምልክት ምዝገባ ዕ/ቤቱ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ብሎ ሲያስቀምጥ “የመጨረሻ ውሣኔ” የሚለው ሐረግ አቀራረቡና ይዘቱ የሚያሳየው በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት መሆኑን እንጂ ቀጥታ ክስ የሚቀርብበት አለመሆኑን መገንዘብ የሚቻል መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም አመልካች የተቋቋመው አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈፅም ወይም ተፈፃሚነታቸውን የሚከታተል እንዲሁም አስፈላጊውን አቅም በመገንባት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጥ መንግስታዊ አካል ማቋቋሙ በማስፈለጉ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 320/95 በመግቢያው ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሆን የዚሁ አዋጅ አንቀፅ 2 ደግሞ “አእምሮአዊ ንብረት” እና “ፓተንት” የሚሉትን ቃላት ትርጉም አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት አእምሯዊ ንብረት ማለት የሰው ልጅ አእምሮ ውጤት በሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ያለ ሕጋዊ መብት ሲሆን ፓተንትን፣ የንግድ ምልክትን፣ የምስክር ወረቀትንና ኮፒ ራይትን እንደሚጨምር በአዋጁ አንቀፅ 2/1/ ድንጋጌ የተቀመጠ ሲሆን ፓተንት ማለት ደግሞ የፈጠራ ስራን ለማስጠበቅ የሚሰጥ መብት ሲሆን በፈጠራ በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ በአዋጅ ቁጥር 123/87 መሠረት በፈጠራ በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዳስትሪያዊ ንድፍ የሚሰጠውን የአስገቢ ፓተንት የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትና የኢንዱስትራያዊ ንድፍ የምዝገባ የምስክር ወረቀትን እንደሚጨምር በአንቀጽ 2/2/ ስር በግልፅ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ይህ መስሪያ ቤት ከሚያስፈጽማቸው ሕጎች መካከል አንዱ አዋጅ ቁጥር 410/1996 ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/9/ እና 15/ ድንጋጌዎች ሲታዩም በአዋጁ በሚገዙ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የመመልከት ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስለመሆኑ በግልፅ ያሳያሉ፡፡፡ በሌላ በኩል የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያል ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 ስር የይግባኝ ስልጣኑ የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስለመሆኑ አንቀፅ 2/1፣ እና 54 ድንጋጌዎች በአንድ ላይ ሲነበቡ የሚያሳዩት ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ሆኖ አግኝተናል፡፡ እነዚህ ሕጎች በአመልካች መስሪያ ቤት ይፈጸማሉ ተብለው ከተጠቀሱት ሕጎች መካከል ሲሆኑ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ይግባኙ የሚቀርበው በግልፅ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት መሆኑን ያሳያሉ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አመልካች መስሪያ ቤትን ያቋቋመው አዋጅ ቁጥር 320/1995 መስሪያ ቤቱን ለማቋቋም ያስፈለገበትን ሲገልፅ አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈፅም ወይም ተፈፃሚነታቸውን የሚከታተል አካል ማቋቋም በማስፈለጉ መሆኑን በግልፅ ያስፈረ ሲሆን ይህ ምክንያት አመልካች መስሪያ ቤት ተመሳሳይ የአእምሯዊ ንብረት ጉዳዮችን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው አካል ከመሆኑ ተዳምሮ ሲታይ ጽ/ቤቱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ይታያሉ፣ ወይም በተወሰኑት ይግባኝ በተወሰኑት ደግሞ ቀጥታ ክስ ይቀርብባቸዋል ብሎ መደምደም የአመልካች መስሪያ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ውጤት ያለው ማድረግ ያስችላል ተብሎ የማይታሰብ መሆኑን አመልካች መስሪያ ቤት የሚያስፈጽማቸው ሕጎች አውደ ንባብ (contextual interpretation) የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑ አመልካች መስሪያ ቤት በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሠረት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን በሕግ የተሰጠው መብት ይግባኝ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ መመስረት አይደለም፡፡ በሕጉ የተዘረጋው ሥርዓት ይግባኝ ከሆነ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በጉዳዩ ላይ የይግባኝ ሥልጣን ያለው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የተጠሪ ጠበቃ በሰ/መ/ቁጥር 56938 በቀረበው ተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር ችሎቱ አጣሪ ችሎት በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ መወሰኑን ገልፀው ይህ ጉዳይም በተመሳሳይ መልኩ ሊስተናገድ እንደሚገባው ያቀረቡትን ክርክር ስንመለከተውም ሦስቱ ዳኞች የሚሰጡት የሰበር ትዕዛዝ /ውሳኔ/ አስገዳጅነት የሌለው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2/1/ ድንጋጌ በግልፅ የሚያሳይ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው አይሆንም፡፡ በመሆኑም በሰ/መ/ቁጥር 56938 የተሰጠው ትዕዛዝ ይህን ጉዳይ በተመሳሳይ መንገድ ለመወሰን የሚያስገድድ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪ ጠበቃ ክርክርን አልፈነዋል፡፡

ሲጠቃለልም የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀፅ 6፣17፣36፣እና 49 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ከይግባኝ ትርጉምና አመልካች መስሪያ ቤት ከተቋቋመበት አላማና አመልካች መስሪያ ቤት የሚያስፈፅማቸው ከአዋጅ ቁጥር 501/98 ውጪ ያሉት ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሕጎች ከዘረጉት የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት አንጻር ሲታይ በንግድ ምልክት ምዝገባ ጉዳይ ላይ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት በይግባኝ ሥርዓት የማስከበር እንጂ በቀጥታ ክስ የሚስተናገድ አለመሆኑን ፣ ይግባኙ መቅረብ ያለበት ደግሞ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን የሚያስረዳ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ ለማየት አይችልም ተብሎ በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አዋጅ ቁጥር 501/98 አመልካች መስሪያ ቤት ሊከሰስ እንደሚችል ይደነግጋል በሚል በደፈናው ውድቅ ማድረጉና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወሰነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 153240 በ13/4/2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 89864 በ03/10/2002 ዓ/ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የንግድ ምልክት ምዝገባ አቤቱታ ላይ አመልካች በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውክልና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፣ ተሻገር ገብረስላሴ

ብርሀኑ አመነው

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ካፕቴን ዩናስ ህሉፍ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ እስጢፋኖስ ኪዳኔ - ቀረቡ

2. ወ/ሪት ሄለን ኪዳኔ
3. ወ/ሮ አዜብ ኪዳኔ — አልቀረቡም
4. ወ/ሪት አስቴር ኪዳኔ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሁለት ጊዜ ቀርቦ ታይቶ ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት ክርክሩ የተጀመረው አንደኛ ተጠሪ ጥር 21 ቀን 1995 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ የአባትና የእናታቸው የጋራ ሀብት የሆነውንና በውርስ የተላለፈላቸውን በቀድሞው አጠራር በወረዳ 21 ቀበሌ 10 የሚገኘውና ቁጥሩ 383 የሆነውን ቤት የአሁን አመልካች /የሥር ተከሣሽ/ በመጀመሪያ ተከራይቶ ይኖርበት ነበር፡፡ ቤቱን እንዲለቅልኝ ብጠይቀው ገዢቸዋለሁ በማለት ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ቤቱን እንዲያስረክበኝና የቤቱን ኪራይ ክስ ካቀረብኩበት ቀን ጀምሮ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት የክስ ማመልከቻ በማቅረቡ ነው፡፡ የሥር ተከሣሽ የአሁን አመልካች ሚች አቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት ሌሎች ልጆች ስላሏቸው በክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ፡፡ ቤቱን የሚች ወኪል ከሆነችው የከሣሽ /የአንደኛ ተጠሪ/ እህት በውል የገዛሁት ስለሆነ ውሉ እንዲፈርስ በፍርድ ሣይወሰንብኝ ቤቱን ይልቀቅልኝ በማለት ክስ ሊቀርብብኝ አይገባም ውሉ መመዝገብ የሚያስፈልገው ለሶስተኛ ወገን እንጂ ለተዋዋይ ወገኖች አይደለም፡፡ አንደኛ ተጠሪ የእናቴ የጋራ ሀብት ነው የሚለውን በተመለከተ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ አይችልም የሚል ክርክርና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ አመልካች ከሚች ኪዳኔ ተስፋሀዋሪያት ወኪል ጋር መጋቢት 27 ቀን 1991 ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል በፍታብሐር ህግ ቁጥር 1923/1/ መሠረት ያልተፈፀመና እንደረቂቅ የሚታይ በመሆኑ ተከሣሽ የአሁን አመልካች ቤቱን ለአንደኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአንደኛ ተጠሪንና የአመልካችን ክርክር ሰምቶ ጥር 4 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በመቃወም የካቲት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ የተጠሪዎች ወላጅ እናት ጥቅምት 1 ቀን 1990 ዓ.ም ወላጅ አባታቸው ሀምሌ 1 ቀን 1991 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን ገልፀው በአባታቸው ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት ከአባታቸው በተሰጠ የውክልና ሰነድ አራተኛ ተጠሪ መጋቢት 27 ቀን 1991 ዓ.ም በተፃፈ ውል ለአመልካች ሽጠውላቸዋል፡፡ ስለዚህ እኛ በክርክሩ ሳንሳተፍ የሸያጭ ውሉ የእኛ መብት ያለበትን ቤት አንደኛ ተጠሪ እንዲረከብ የተሰጠው ውሣኔ እንዲሰርዝልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች በፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ መነሻ የይርጋና የውል ፎርም ክርክሮች ያቀረቡ ሲሆን የሥር ፍ/ቤት የይርጋው ክርክር በሥር ተከሣሽ /አመልካች/ ያልተነሣ በመሆኑ በፍርድ መቃወም አመልካቾች በኩል መነሳቱ ተገቢ አይደለም በማለትና ሌሎቹን የመከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ በማድረግ በተጠሪዎች አባት ወኪል አራተኛ ተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የህጉን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ ጥር 4 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠሁትን ውሣኔ የምሠርዝበት ወይም የምሽርበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝና ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 37810 በማጣመር በአንደኛ ተጠሪ በአመልካች እንደዚሁም በሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችና በአንደኛ ተጠሪ መካከል የተደረገውን ክርክር መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ቤቱን የተጠሪዎች ወላጅ አባት ለአራተኛ ተጠሪ በሰጡት ውክልና መሠረት መጋቢት 21 ቀን 1991 ዓ.ም ሸጠው ሚች ሀምሌ 1 ቀን 1991 ዓ.ም የሞቱ በመሆኑ የውሉን ፎርም አንደኛ ተጠሪ በመከራከሪያነት ሊያነሣው አይችልም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አንደኛ ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመልስ ሰጭዎችን ማለትም የአመልካችን የሁለተኛ ተጠሪ የሶስተኛ ተጠሪና የአራተኛ ተጠሪን የቃል ክርክር ለማሰማት ለሀምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቶ የአመልካች ጠበቃ በፅሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ የሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችን የቃል ክርክር መስማት ባለመቻሉ ክርክሩን ለመስማት ለታህሣሥ 3 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ቀን ይግባኝ ባዩ አንደኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች መዝገቡ እንዲዘጋላቸው በመጠየቃቸው ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችን አሰናብቷል ከዚህ በኃላ አመልካችና አንደኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ ውሉ በህጉ የተደነገገውን ፎርም አያሟላም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማፅናት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ውሉ በህጉ የተመለከተውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ አመልካች ቤቱን ለአንደኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ በማለት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት አለበት በሌላ በኩል የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አንደኛ ተጠሪ በሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ይግባኝ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ የአንደኛ ተጠሪን ይግባኝ በመሰረዝ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪን አሰናብቷቸዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ መዝገቦችን በማጣመር የወሰነ በመሆኑ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ የሽያጭ ውሉ የፀና ነው በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲፀና የቀረበና የአንደኛ ተጠሪ ይግባኝ ከተሰረዘ በኃላ እኔ ያቀረብኩትን መልስ መነሻ በማድረግ ውሉ ፎርሙን አላሟላም ብሎ መወሰኑ እርስበርሱ የሚቃረን ነው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የሰጠው ውሣኔ የህግ ሥርዓቱን ያልተከተለ በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በበኩሉ ጥቅምት 4 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ህግ በመተርጎም ረገድ የፈፀመው የህግ ስህተት የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይህ ሰበር ችሎት የሰጠውን የህግ ትርጉም ተከትሎ ነው ውሣኔ የሰጠው ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችንም ያሰናበታቸው የእነርሱ በተከራካሪነት መቀጠል የሚያመጣው የፍርድ መዛባት የሌለ በመሆኑ ነው፡፡ የአመልካች የሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ክርክር ተመሳሳይ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካች ላይ የሰጠው ውሣኔ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችን ክርክር የሚቋጭ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ጥቅምት 4 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአንደኛ ተጠሪን ይግባኝ በመሠረዝ እኛን አሰናብቶናል አንደኛ ተጠሪ ይህ ትዕዝዝ እንዲነሣ ወይም እንዲሰርዝ የሰበር አቤቱታ ያላቀረቡ በመሆኑ እኛን በተመለከተ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ውሣኔ መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ እንዲሰጥልን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ለሰበር በግራቀኙ የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪዎች የሚች ወ/ሮ ለተስላሴ ኃይሉና የሚች አቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት ልጆችና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ናቸው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ሚች አቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት በወኪላቸው አራተኛ ተጠሪ በኩል ከአመልካች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስና ቤቱን እንድረከብ በማለት ከፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ሰበር ችሎት ባቀረቡት ክርክር የሚከራከሩ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ፣ ሶስተኛ ተጠሪና አራተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ሚች አባታችን በወኪሉ አራተኛ ተጠሪ በኩል የፈፀመው የቤት ሽያጭ ውል የሚፈርሰበት ምክንያት የለም፣ውሉ አይፈርስም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እኛን በተመለከተ የመጨረሻና የፀና ነው በማለት የተከራከሩ መሆኑን ከሥር ጀምሮ እስከ ሰበር ችሎት ካቀረቡት ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በመዝገብ ቁጥር 37810 የቤት ሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባውም በማለት ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታና ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎሪች የሥር ፍርድ ቤት ውሉ ረቂቅ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም በመዝገብ ቁጥር 46139 ያቀረቡትን ይግባኝ በማጣመር በመዝገብ ቁጥር 37810 መርምሮ ውሉ ሊፈርስ አይገባም አመልካችም ለአንደኛ ተጠሪ ቤቱን የማስረከብ ግዴታ የለበትም በማለት ውሣኔ መስጠቱን ይህንን ውሣኔ በመቃወም አንደኛ ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካችን አንደኛ መልስ ሰጭ ሁለተኛ ተጠሪን ሁለተኛ መልስ ሰጭ ሶስተኛ ተጠሪ ሶስተኛ መልስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰጭ አራተኛ ተጠሪን አራተኛ መልስ ሰጭ በማድረግ የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው የነበረ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በይግባኝ በተደረገው ክርክር አንደኛ መልስ ሰጭ የነበሩት አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው የይግባኝ ባዩ አንደኛ ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታ የህግ መሠረት የለውም የሚል የዕሑፍ መልስ ሀምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያቀረቡ መሆኑንና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ መልስ ሰጭ የነበሩትን ከተራ ቁ 2-4 ተጠሪዎች የቃል ክርክር ለመስማት ቀነ ቀጠሮ በያዘበት ታህሣሥ 3 ቀን 2000 ዓ.ም አንደኛ ተጠሪ /ይግባኝ ባዩ/ ባለመቅረቡ መዝገቡ እንዲዘጋላቸው በመጠየቃቸው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎችን እንዳሰናበታቸው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 28090ን በማስቀረብ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

በዚህ መዝገብ ከፍሬ ጉዳይ፣ ከተከራካሪዎቹ መሠረታዊ ባህሪና በክርክር የያዙት አቋምና አንደኛ ተጠሪ ያቀረበው ይግባኝ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝና በሰበር አመልካች አንደኛ ተጠሪና ከሁለተኛ እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር ስማቸው የተጠቀሱ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻሩ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ለጉዳዩ አልባት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው የተጠሪዎች ወላጅ አባት አቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት ለአራተኛ ተጠሪ በስማቸው የተመዘገበ የማይንቀሣቀስ ንብረት የመሸጥ የመለወጥና ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚያስችል ልዩ የውክልና ሥልጣን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2205 ንዑስ 1 መሠረት ሰጥተው የነበረ ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም አራተኛ ተጠሪ ይህንን የውክልና ስልጣን በመጠቀም የክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት መጋቢት 21 ቀን 1991 ዓ.ም ለአመልካች የሸጡ መሆኑን ይህም አቶ ኪዳን ተስፋሐዋሪያት በህይወት እያሉ የተፈፀመ መሆኑን ግራቀኙ ካቀረቡት ክርክር ለመንዘብ ችለናል፡፡ አራተኛ ተጠሪ ለአቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት ከሰጧቸው የውክልና ሥልጣን ሣያልፉ በሚች አቶ ኪዳኔ ተስፋሐዋሪያት ስም የፈፀሙት የቤት ሽያጭ ውል በፍ/ሕግ ቁጥር 2189 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በሿሚው በሚች አቶ ኪዳኔ እንደተፈፀመ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ አራተኛ ተጠሪ መጋቢት 21 ቀን 1991 ዓ.ም ለወኪላቸው ለአራተኛ ተጠሪ በሰጡት ሥልጣን መሠረት የፈፀሙት የቤት ሽያጭ ውል የፈቃድ ወይም የፎርም ጉድለት ቢኖርበት ይህንን ጉድለት ለአራተኛ ተጠሪ የውክልና ሥልጣኑን የሰጡት አቶ ኪዳኔ መከራከሪያ ሊያደርጓቸው የሚችሉ ስለመሆን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2189/2/ ይደነግጋል፡፡

አራተኛ ተጠሪ ወኪላቸው በመሆን የፈፀማቸውን ሽያጭ የፎርም ጉድለት ያለበት ስለሆነ ይፍረስልኝ የሚል ጥያቄ ሣያቀርቡ ቆይተው አቶ ኪዳኔ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን በአንደኛ ተጠሪ በአመልካችና በሌሎች ተጠሪዎች ካደረጉት ክርክርና ባቀረቧቸው ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ አንድ ሰው ለሌላ ሰው በሰጠው ፍፁም የውክልና ሥልጣን መሠረት የተከናወነውን ተግባር ለማፍረስና መከራከሪያ ሊያደርገው የሚችለው ወካዩ ራሱ እንደሆነ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2189 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የጣምራ ንባብ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሚች አቶ ኪዳኔ ወኪላቸው አራተኛ ተጠሪ በሰጡት የውክልና ሥልጣን መሠረት የፈፀማችው የቤት ሽያጭ ውል የህጉን ፎርም አያሟላም ብለው መከራከሪያ የማድረግ መብት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2189/2/ የተሰጣቸው ቢሆንም በህይወት በነበሩበት ጊዜ ይህንን መብታቸውን አልተጠቀሙበትም አንድ ተወካይ ወካዩ ከሰጠው የሥልጣን ወሰን ሣያልፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠራው ሥራ ላይ የሚታዩ የፍቃድ ጉድለቶችን እንደመከራከሪያ አድርጎ ለማንሣት የሚችለው ወካዩ ብቻ እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2189/2/ የተደነገገ በመሆኑ ወካዩ ይህንን መብት ሣይጠቀምበት ካለፈ ወራሾቹ የሚች ወኪል የውክልና ሥልጣን ወሰኑን ሣያልፍ የሰራውን ተግባር የሚቃወሙበት ህጋዊ መሠረት የለም፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዚህ መዝገብ አራተኛ ተጠሪ የሚች አቶ ኪዳኔ ወኪል በመሆን ከተሰጣት የውክልና ሥልጣን ወሰን ሣታልፍ የፈፀመችው የቤት ሽያጭ ውል አቶ ኪዳኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2189/2/ መሠረት መከራከሪያ ሣያደርጉ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን ሣያገናዝቡ አንደኛው ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በመቀበል የቤት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስና አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክብ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ይግባኝ ሰሚው ችሎት አንደኛ ተጠሪ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ በሚሰማበት ወቅት አንደኛ መልስ ሰጭ የነበረው ተጠሪ ሀምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በፅሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቃል ክርክር ለመስማት ቀነ ቀጠሮ በያዙበት ታህሣሥ 3 ቀን 2000 ዓ.ም ይግባኝ ባይ የነበረው አንደኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ በይግባኝ ክርክሩ ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ መልስ ሰጭዎች የነበሩት ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች መዝገቡ እንዲዘጋላቸው በማመልከታቸው በእነርሱ በኩል የይግባኝ ክርክር ተቋርጦ የተሰናበቱ መሆኑን በመግለፅ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለይግባኝ በፅሑፍ መልስ የሰጠውና አንደኛ መልስ ሰጭ የነበረው አመልካች በይግባኝ ይግባኝ ባይ የነበረው አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ በመቃወም መልስ የሰጠ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይግባኙ በሚሰማበት ቀን ይግባኝ ባይ ካልቀረበና መልስ ሰጭዎች ቀርበው በፅሑፍም ሆነ በቃል የሰጡት መልስ ይግባኝ ባይ ያቀረበውን ቅሬታ የሚደግፍ ካልሆነ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 32/2/ እና በፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 73 በሚደነግገው መሠረት ይግባኙን ሙሉ በሙሉ በመሠረዝ ሁሉንም መልስ ሰጭዎች ማሰናበት ይገባዋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች አንደኛ መልስ ሰጭ በመሆን በፅሑፍ የሰጠው መልስ የአንደኛ ተጠሪን የይግባኝ ቅሬታ የሚነቅፍ ሆኖ እያለ የአንደኛው ተጠሪ በሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበው የይግባኝ ክርክር እንዲቋረጥና ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች እንዲሰናበቱ ያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል የአመልካችን መልስ መነሻ በማድረግ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሻሩ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 32/2/ና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 73 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያልተከተለ ትዕዛዝና ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የዚህም ትዕዛዝና ውሣኔ ውጤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአንድና ተመሳሳይ ጭብጥ የሰጠውን ውሣኔ ለአመልካች ባደረገው የይግባኝ ክርክር መነሻ የሚሽር ለሁለተኛ ሶስተኛ አራተኛ ተጠሪዎች የአንደኛ ተጠሪ ይግባኝ የተሠረዘና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚያፀና እርሱ በርሱ የሚቃረን ውጤት የሚያስከትልና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በዘረዘርናቸው የህግ ምክንያቶች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ምክንያቱ ተለውጦ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን ቤት የማስረከብ ግዴታና ሃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- አቶ ቴዎድሮስ ተስፋዬ ጠበቃ ሰመረ አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሙሉ አርጌ ቀረቡ

2. ህፃን ሐና ሙሉ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ክልል ወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ ህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ስለቀረበ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ በሰበር መዝገብ ቁጥር 58065 ከተዘረዘሩት ንብረቶች ውስጥ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-33129 ኢት፣ የሆነው የፍሰሽ ጭነት ማመላለሻ መኪናን የሚመልከት ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ ንብረቱ የሆነውን ከላይ ቁጥሩ የተገለፀውን መኪና አንደኛ ተጠሪ እንዲሸጥ እንዲለወጥ እና እንዲያስተዳደር ውክልና የሰጠው መሆኑንና ውክልናውን ያሰረዘው መሆኑን ገልፆ ንብረቱን እንዲመልስልኝና በመኪናው ተሠርቶ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፍለኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ አመልካች በሰጠው ውክልና ሥልጣን መሠረት መኪናውን ለሁለተኛ ተጠሪ በብር 1,250,000/አንድ ሚሊዬን ሁለት መቶ አምሳ ሺህ ብር/ የሸጠው መሆኑንና ገንዘቡንም የአመልካች ወኪል ለሆኑት አቶ ታፈሰ አርጌ ያስረከበ መሆኑን በመግለፅ ተከራክራል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሥር ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆነው በመቅረብ የመኪናውን ብር 1,500,000 /አንድ ሚሊዬን አምስት መቶ ሺህ ብር/ ከፍለው የተረከቡና የሚጠበቅባቸው ቀሪ ገንዘብ ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ መሆኑን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡ አቶ ታፈሰ አርጌ በሥር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆነው ቀርበው አመልካች ገንዘብ ለመቀበል የሚያስችል ውክልና ያላቸው መሆኑን ገልፀው የመኪናውን ዋጋ ከአንደኛ ተጠሪ በመቀበል የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መተማመኛ 1,200,000 /አንድ ሚሊዬን ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ለአመልካች የሰጡት መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ሌላኛው ጣልቃ ገብ ወ/ሮ ገነት ደምሴ መኪናው የጋራ ንብረት ሆኖ እያለ ወደ አመልካች መዛወሩን በመቃወም ጣልቃ ገብ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለአንደኛ ተጠሪ የውክልና ሥልጣን ለመስጠት የውክልና ውሉ ረቂቅ የተፃፈው ህምሌ 11 ቀን 1999ዓ.ም መሆኑን የውክልና ሥልጣን የሚሰጠው ሰነድ ለውልና ማስረጃ ቀርቦ የተረጋገጠው መስከረም 28 ቀን 2000ዓ.ም መሆኑን አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ የመኪና ሽያጭ ውል ያደረገው ነሐሴ 12 ቀን 1999ዓ.ም መሆኑን በውሣኔው ካስፈረ በኃላ አንደኛ ተጠሪ አመልካች ውክልናው ሥልጣን እንደሚሰጠው በቅን ልቦና በማሰብ የውክልና ሰነድ ረቂቅ ከተፃፈ ከህምሌ 11 ቀን 1999ዓ.ም በኃላና የውክልና ሰነድ በውልና ማስረጃ ቀርቦ ሣይመዘገብ በፊት ነሐሴ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የፈፀመው የሽያጭ ውል በቅን ልቦና የተደረገ በመሆኑ የፀና ነው በማለት በድምፁ ብልጫ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የይግባኝ ውሣኔውን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ ተሰርዞባታል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎበታል፡፡

አመልካች አንደኛ ተጠሪ ለህፃን ልጁ ለሁለተኛ ተጠሪ መኪናውን የሸጠው እኔ የውክልና ሥልጣን ከመሰጠቱ በፊት ነው፡፡ ስለዚህ በመኪናነት ሥልጣን ይሰጠኛል በሚል በቅን ልቦና የፈፀመው ህጋዊ ተግባር ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያመለከተ ሲሆን አንደኛ ተጠሪ መኪናውን ሽጨ ገንዘቡን ለአመልካች ወኪል ሰጥቻለሁ፡፡ አመልካች ገንዘቡን ተቀብሏል ስለዚህ ውሉ እንዲፈርስ የሚያመለክትበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተክራክሯል፡ ሁለተኛ ተጠሪ በበኩላቸው በ1982 ዓ.ም የተወለዱና ህፃን እንዳልሆኑ በመግለፅ ንብረቱን በአግባቡ የገዛሁት በመሆኑ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅረበዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አንደኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መኪና ሁለተኛ ተጠሪ የሸጠው የውክልና ስልጣን የተሰጠበት ረቂቅ ሰነድ ከተፃፈ በኃላ በቅን ልቦና በመሆኑ የሽያጭ ውሉ የፀና ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም; የሚለው ጭብጥ መመርመር ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይህንን ጭብጥ ለመወሰን አንደኛ ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-3312927 የሆነውን መኪና የማስተዳደር የመሸጥና የመለወጥ ሥልጣኑን ያገኘበትን መንገድና መኪናውን የሸጠበትን ጊዜ እንደዚሁም አመልካች መኪናው ከተሸጠ በኃላ ፈጽሟቸዋል ለማለት አንደኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ጣልቃገብ የነበሩት አቶ ታፈሰ አርጌ ያነሱትን ክርክና ፍርድ ቤቶቹ የያዙትን ጭብጥና የሰጡትን ውሣኔ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የሌላ ሰው እንደራሴ በመሆን ሥራዎችን የመፈፀም ሥልጣን የሚገኘው ከህግ ወይም ከውል እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2179 መሠረታዊ መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ አንደኛው ተጠሪ ከላይ ቁጥሩ የተገለፀውን የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ መኪና የማስተዳደር የመሸጥና የመለወጥ የውክልና ሥልጣን ያገኘው በህግ የተደነገገን ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ሣይሆን አመልካች ወኪሉ እንዲሆን ተስማምቶ በውልና ማስረጃ አስመዝግቦና አረጋግጦ በሰጠው የውል ሰነድ መሆኑን ግራቀኙ አልተካካዱም፡፡ ግራቀኙ የሚከራከሩት አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የውክልና ሰነድ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው ረቂቁ ከተፃፈበት ከህምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ነው; ወይስ የውክልና ሰነዱ በአመልካች ከተፈረመበትና በውልና ማስረጃ ተመዝግቦና ተረጋግጦ ከተሰጠበት ከመስከረም 28 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ነው; በሚለው ነጥብ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለ ውሉ አፃፃፍ ህጉ አንድ አይነት ፎርም እንዲደርግ ያስገደደ እንደሆነ ውሉን የሚፈፀምበት ሥልጣን በዚሁ አይነት ፎርም ለወኪል ሥልጣን መስጠት እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2080 የሚደነግግ መሆኑንና ውክልና በግልፅ ወይም በዝምታ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2200 ንዑስ አንቀፅ 1 የሚደነግግ መሆኑን በመመልከት አንደኛ ተጠሪን አመልካች ረቂቁ ከተዕፈበት ሀምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እንደወከለውና አንደኛ ተጠሪም መኪናውን በቅን ልቦና የአመልካች ወኪል ነኝ በሚል ውክልና ሰነድ በውልና ማስረጃ ከመረጋገጡ በፊት ነሐሴ 12 ቀን 1999 ዓ.ም አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው የመኪና ሽያጭ ውል በተሰጠው ውክልና መሠረት እደፈፀመው የሚቆጠር ነው በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የሰበር ችሎት አፅንተውታል፡፡

ሆኖም ይህ የበታች ፍርድ ቤቱች የሰጡት ውሣኔ ስለ ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 334/1995 በአንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በአንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1/ለ/ የተደነገገውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 1 አዋጁ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ላይ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑ "የተፈፃሚነት ወሰን" በሚለው ርዕስ ሥር በግልፅ ደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤት ማስረጃ የመመዘን የመመርመርና የመቀበል ህገ መንግስታዊ ሥልጣን ያላቸው አካላት በመሆናቸው ይህንን አዋጅ የመተግበር ግዴታ ያለባቸው መሆኑ የአዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀፅ 3/1/ ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ 7 ጋር በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀፅ 5 በህግ መሠረት ካልተረጋገጡና ካልተመዘገቡ ህጋዊ ውጤት እንደማይኖራቸው ከተዘረዘሩት ሰነዶች አንደኛው የውክልና ሥልጣን መስጫ ሰነድ እንደሆነ በአንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1/ለ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች የውክልና ሰነዱን ፈርሞና በውልና ማስረጃ አስመዝግቦ እና አረጋግጦ መስከረም 28 ቀን 2000ዓ.ም ለአንደኛ ተጠሪ የውክልና ሥልጣን ከመስጠቱ በፊት አንደኛ ተጠሪ የውክልና ሰነድ ረቂቅ የተጻፈው ሀምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም ነው በማለት የፈፀመው ተግባር በወኪልነት ሥልጣኑ እንደፈፀመው የማይቆጠርና ወካዩ/አመልካች/ በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ካላፀደቀው በስተቀር አመልካችን የማያስገድድ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የህግ ትርጉምና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ረቂቅ ሰነዱን መሠረት በማድረግ አንደኛ ተጠሪ ነሐሴ 12 ቀን 1999ዓ.ም የአመልካች መኪናን ለመሸጥ ያደረገው ስምምነት ህጋዊ ውጤት የሚኖው አመልካች የመኪና ሽያጭ ውሉን በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሲያፀድቀው መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2090/1/ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካች ወኪል የሆኑት አንደኛ ተጠሪ መኪናውን የሸጡትና ገንዘቡን የአመልካች ሌላው ወኪል ለሆኑት አቶ ታፈሰ አርጌ የሰጡ መሆኑን በማንሣት ያቀረቡትን ክርክርና የአመልካች ወኪል የነበሩት አቶ ታፈሰ አርጌ መኪናው ተሸጦ ገንዘቡን ተቀብለው ለአመልካች የሰጡ መሆናቸውን በማመን ያቀረቡትን ክርክር በመመልክት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ የውክልና ሥልጣን ሣይኖራቸው የፈፀሙትን የመኪና ሽያጭ ውል አመልካች በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ መኪናው መሸጡን የተቀበለው መሆኑን የሚያሣይ ተግባራትን በመፈፀም አፅድቆታል ወይም አላፀደቀውም; የሚለውን ጭብጥ በመመሥረት በግራ ቀኙ በኩል ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የመኪናውን ሽያጭ በግልፅ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አፅድቆታል ወይስ አላፀደቀውም; የሚለውን ነጥብ ለመወሰን በአንደኛ ተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገውን ክርክርና ማስረጃ መመርመሩና መመዘኑ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ አመልካች መኪናውን አንደኛው ተጠሪ እንደሸጠው የሚያውቅና ከመኪናው ዋጋ ውስጥ 1,200,000 /አንድ ሚሊዬን ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ከአንደኛው ተጠሪ ተቀብዬ ወስጄ ለአመልክች የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፈረመ መተማመኛ ሰጥቸዋለሁ በማለት በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የሆኑት አቶ ታፈሰ አርጌ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በማጣራት በመመርመርና በመመዘን ውሣኔ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የመኪናው የሽያጭ ዋጋ ከሆነው ገንዘብ ውስጥ ብር 1,200,000 /አንድ ሚሊዬን ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መተማማኛ ተቀብሏል ወይስ አልተቀበለም; የሚለው ነጥብ አመልካች የመኪናውን መሸጥ የሚያውቅ የነበረና ዋጋውን ተቀብሎ ሲጠቀምበት የቆየ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 በሚደነግገው መሠርት በክርክሩ ተካፋይ የሆኑት ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡትን የመከላከያ መልስና የፅሑፍ ማስረጃ በመመርመር መያዝ የሚገባውን ጭብጥ ሁሉ በመያዝ ጉዳዩን አጣርተው ያልወሰኑ በመሆኑ ውሣኔያቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ክልል የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ክልል የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥር አንደኛ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የነበሩት አቶ ታፈሰ አርጌን ወደ ክርክሩ እንዲገቡ በማድረግ አመልካች አንደኛ ተጠሪ ከሸጠው የመኪና ዋጋ ገንዘብ ውስጥ ብር 1,200,000 /አንድ ሚሊዬን ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ከአቶ ታፈሰ አርጌ ተቀብሎ ወስዷል ወይስ አልወሰደም; አመልካች ገንዘቡን ተቀብሎ እንደወሰደ ቢረጋገጥ አመልካች አንደኛ ተጠሪ የውክልና ሥልጣን ሣይኖረው መኪናውን ነሀሴ 12 ቀን 1999 ዓ.ም ለሁለተኛ ተጠሪ ለመሸጥ የተስማማውን ውል እንዳፀደቀው ይቆጠራል; ወይስ አይቆጠርም; የሚለውን ጭብጥ በማጣራትና የግራቀኙን ክርክር በመስማትና ማስረጃ በመመዘን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎችን /ከቅጽ 8 - 10 / ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ቅጽ - 8

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	
	የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት				1
1	ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2)	33945	አቶ ሣልህ ሁሴን እና ደግፌ ደርቤ	ጥቅምት 20/2001	2
2	ማንኛውም ክርክር ሊወሰን የሚገባው በቀረበው ማስረጃ እና በህጉ መሰረት ብቻ ስለመሆኑ	36848	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና መኰንን ግርማይ (ሦስት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	5
3	በክርክር ሂደት ተቃዋሚ ወገን መጠራት ያለበት ምስክር ከመሰማቱ በፊት ስለመሆኑ	35946	እነ አቶ ማማሸ ወ/ስላሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሰብለ ወንድይራድ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 27/2001	7
4	መጥሪያ ለምስክር እንዲደርስ በሚል ፍ/ቤቶች ሊልኩ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103	36479	ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ኃይሉ ወልዱ	ጥቅምት 25/2001	9
5	በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የተወሰነበት ተከራካሪ ፍ/ቤት ህጉን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78	36412	ተስፋሁን ዋኘው እና በጃክ አግሮ ኮሜርሻል ኢንተርፕራይዝ	ጥቅምት 13/2001	12
6	የቃል ክርክር ለመስማት እና የጽሁፍ መልስ ለመቀበል በሚል ፍ/ቤቶች በአንድ ቀጠሮ ሁለት ተግባራትን ለማከናወን የሚሰጡት ትዕዛዝ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ ስለመሆኑ	36380	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ታረቀኝ ገ/ዓዲቅ	ጥቅምት 18/2001	16
7	የበላይ ፍ/ቤቶች ውሣኔን ወደጉን በመተው በሥር ፍ/ቤቶች የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ	37725	እነ በቀለ ድሪብሣ (ሁለት ሰዎች) እና የምክር በሪሁን	ጥቅምት 6/2001	18
8	በግልፅ የቀረበን ክርክር በተቆጠረ ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ እንዲጣራ/እንዲነጥር/ ሣይደረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	37105	ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር እና ሰለሞን አበበ ኮክብ	ጥቅምት 25/2001	21
9	ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን አስቀርተዋል /ትተዋል/ ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢያዊ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በተረዱበት ደረጃ እርስ በርሳቸው ስምምነት ባደረጉ ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 350(1) እና (2)	37678	ድራጋዶስ ጄ ኤንድ ፒ.ጆይንት ቬንቸር እና ሳባ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር	ህዳር 18/2001	23
10	በሥር ፍ/ቤት ዳኝነት ያልተጠየቀበት ጉዳይ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ታይቶ ሊወሰን የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1), 182(2)	37762	ገወኔ ኢንተርፕራይዝ ኃ/ተ/የግ/ማህበር እና አቶ የሱፍ ይማም	ታህሣሥ 9/2001	26
11	ከሥራ ውል ጋር በተያያዘ የሚጠየቁ ክፍያዎች ሳይነጣጠሉ በአንድ ላይ መቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4), 5	38601	የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና ወ/ሮ ከድጃ ሳቢር	ታህሣሥ 14/2001	30
12	• ክርክር ከሚካሄድበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ መብትና ጥቅም እንዳለ የተረጋገጠ እንደሆነ በክርክር ጣልቃ ለመግባት በቂ ምክንያት ስለመሆኑ • በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ጥያቄ (ተቃውሞ)	37742	ወ/ሮ አልማዝ ጉንፌ አራቱ እና ወ/ሮ ፀሐይ ሊበን	ታህሣሥ 7/2001	32

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አለማቅረብ ሚስት/ባል የሆነን ወገን የጋራ ነው በሚለው ንብረት ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚያግድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41				
13	በአንድ መንግስታዊ መዋቅር ሥር የሚገኙ ሁለት ራሳቸውን የቻሉና የህግ ሰውነት ያላቸው ተቋሞች የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቁ አካላት በመሆናቸው ብቻ እንደ አንድ መቆጠር የሌለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 አዋጅ ቁጥር 1/1995,18/1997,2/1995,4/2000	37502	የአዲስ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ህግ ጉዳዬች ቢሮ እና እነ ወ/ሮ የኃላሸት ገመዳ ቤኛ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 2/2001	34
14	ፍ/ቤቶች ለክርክር ፍትሐዊነት ተገቢ ነው ብለው ሲያምኑ ማናቸውንም አይነት ማስረጃ አስቀርበው መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 145,345,327/3/	29861	ወ/ሮ ህጽአት ፍስሐጽዮን እና እነ ወ/ሮ አልማዝ ተረፈ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 14/2001	37
15	የክርክር ዋነኛ ጭብጥ በሆነ ጉዳይ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሣኔ ፍ/ቤት በድጋሚ "ስህተት ለማረም" በሚል ምክንያት ሊለውጥ ወይም ሊያሻሽል ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208	37303	ኤ.ሲ.ዲ አይ/ቮካ-ኢትዮጵያ እና እነ ሃይደር አሊ (ስምንት ሰዎች)	ጥር 26/2001	41
16	ዳኝነት የሚጠየቅበት መብትና ጥቅም በግልጽ ተለይቶ ያልተመለከተበት አቤቱታ የክስ ምክንያት እንደሌለው የሚቆጠር በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33, 231	38419	የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 አስ/ጽ/ቤት እና አቶ ያሲን ጀማል	የካቲት 5/2001	43
17	ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ክርክር መሠረት በማድረግ አግባብነት ያለውን ጭብጥ ሳይመሰርቱ የሚሰጡት ውሣኔ ህጋዊ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ	37391	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ ስዩም ማሞ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 3/2001	46
18	በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች በሚሰጠው ውሣኔ ጥቅማቸው /መብታቸው/ ሊነካ የሚችል የሆነ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.40	39540	ናስ ፉድስ የድ/ዳ/ጨ/ጨ/ፋብሪካ ተከራይ እና እነ ስንዱ ደጀኔ (ዘጠና ሦስት ሰዎች)	የካቲት 26/2001	48
19	አንድ ጉዳይ ከዚህ ቀደም በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5	36780	ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ እና አቶ ገ/ኪዳን እንግዳ	መጋቢት 3/2001	51
20	ነዋሪነታቸው በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሣ ክርክርን የክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት የሚገኘው ወይም ውል የተደረገው በአንደኛው ክልል እንኳን ቢሆን የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(2)	36460	መሐመድ ሰዓዳይ ረጃ እና እነ አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ ፊረጀ (ሰባት ሰዎች)	መጋቢት 24/2001	59
21	በተከራካሪ ወገኖች የተጠየቀን ዳኝነት አስመልክቶ ግልጽ ፍርድ አለመስጠት ስህተት ስለመሆኑ	39144	አቶ ልዑልሰገድ ቦኔ እና ኢትዮ ሴዘር ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር	መጋቢት 24/2001	62
22	የቀረበበትን ክስ ያመነ ተከሣሽ ባመነው መሠረት ውሣኔ ለመስጠት የሚከለክል በቂ የህግ ምክንያት እስከሌለ ድረስ ውሳኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ	38597	እነ ጋሻው መንግስቱ ካሣ (ሁለት ሰዎች) እና ናይል ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሚያዝያ 6/2001	65
23	በአንድ ዘንግ የሚመደቡ ተከራካሪዎች እና አንድ ጭብጥ ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች ተጣምረው እንዲታዩ ያለማድረግ መሠረታዊ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 11(5)	40024	ሸራተን አዲስ እና እነ አቶ እያሱ መገርሣ	ሚያዝያ 29/2001	67
24	የሥር ፍ/ቤቶች የፈፀሙትን ሥህተት ለማረም በሚል በሥር ፍ/ቤት ተከራካሪ ከነበሩ ወገኖች መካከል አንዱ ወገን ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሌላኛው ወገን ሳይጠራና ሳያከራክር ውሣኔ መስጠት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1)	34504	አቶ አበባው የሺድንበር እና አቶ ካሣ በቀለ	ሚያዝያ 6/2001	71

https://t.me/ethiopianlegalbrief

25	በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣን ክርክር መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 329(1), 182(2)	37761	ንብረመስቀል ንጉሴ እና አዲስ ልብስ ስፌት አ.ማ	ሚያዝያ 20/2001	73
26	ክስ በሚሰማበት የቀጠሮ ዕለት የይግባኝ ባይ አለመቅረብ ጋር በተያያዘ መዝገብ ሊዘጋ የሚችለው መልስ ሰጪው ይግባኙን ሙሉ በሙሉ ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ	38181	የኢትዮጵያ መንግዶች ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ወንድይፍራው (ሁለት ሰዎች)	ግንቦት 4/2001	76
27	ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገን ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የሚጠቅም ያልሆነ እንደሆነና የሰው ምስክር በተጨማሪነት የቆጠረ እንደሆነ ፍትሐዊ የሆነ ውሣኔን ለመስጠት የምስክሮችን ቃል መስማት ያለበት ስለመሆኑ	42706	ላየን ሴኩሪቲ ኩባንያ እና አቶ ጥላሁን ገ/እግዚአብሔር	ግንቦት 25/2001	78
28	በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መለወጥ ወይም መሻሻል ተከትሎ ማናቸውም ተከራካሪ ወገኖች ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚሰጥ ትዕዛዝ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ እንጂ የግድ የሚሰጥ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349(1)	37741	አቶ መኮንን ዘውዴ እና እነ አቶ ተሾመ ሽፈራው (ሦስት ሰዎች)	ሰኔ 4/2001	80
29	ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ጉዳይ ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9(2)	38452	የአ.አ ከተማ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ አለም ንብሩ	ሰኔ 11/2001	82
30	አንድን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማንሣት ስልጣን የለኝም ያለ ፍ/ቤት ጉዳዩ በበላይ ፍ/ቤት ታይቶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ እንዲያከራክር ጉዳዩ የተመለሰለት እንደሆነ ሌላ ተጨማሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለማየት አልችልም ማለት የማይገባው ስለመሆኑ	39014	አለሙ መግራ እና እምነቱ እንዳሻው ህንፃ ተቋራጭ	ሰኔ 23/2001	84
31	የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈበት ተከራካሪ ወገን የሚያቀርበው የማስፈቀጃ ማመልከቻ በበቂ ምክንያት የተደገፈ መሆን/አለመሆኑን ፍ/ቤቶች በጥሞና መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 326(1)	38145	ወ/ሮ አያልነሽ ዘገየ እና አቶ ተስፋዬ ደምሴ	ሰኔ 30/2001	86
32	አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃነት የሚጠቅሳቸው ምስክሮች፣ ሰነዶች ወይም ሌላ አስረጂዎች (የሙያ) ማስረጃው በፍ/ቤቱ በኩል በጭብጥነት ተይዞ ከሚፈታው ፍሬ ነገር ጋር አግባብነት ያለው እና በህግ ተቀባይነት ያለው እስከሆነ ድረስ ቀርቦ መሰማት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111, 249 እና 257	38683	የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት እና አቶ ሣህሉ ወ/ማርያም	ሰኔ 25/2001	88
33	ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአግባቡ ሳይመረምሩ እና ለውሣኔያቸው በቂ ምክንያት ሣይሰጡ መሻር የማይችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1)	38844	የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን እና ጋድ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህ	ሰኔ 25/2001	90
34	ተከራካሪ ወገኖች በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲቀርብላችው የሚጠይቁት ማስረጃ የተያዘውን ጉዳይ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ዕልባት ለመስጠት የሚያስችል እስከ ሆነ ድረስ ጥያቄውን ፍ/ቤቶች ሊቀበሉት የሚገባ ስለመሆኑ	36979	ቤዛ አማካሪ መሀንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ሚስተር ሽሬሃሪ ብራማቫሪ ጉፓል	ሐምሌ 23/2001	94
35	ሦስተኛ ወገኖች በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር እንዲገቡ የሚያስፈልግበት ሁኔታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43	41544	ሰላም የህዝብ ማመላለሻ (አ.ማ) እና ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ	ሐምሌ 8/2001	96

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሰሪና ሰራተኛ					98
36	የኘሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀፅ 2/ሰ/	35197	አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና ኤፍሬም ንዋየማሪያም	ጥቅምት 13/2001	99
37	ለኘሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች የተቀጠሩበት የኘሮጀክት ሥራ ሲጠናቀቅ የሥራ ውላቸው የሚቋረጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10/1//ሠ//ሀ/	35621	ሰንሻይን ኮንስትራክሽን እና እነ አቶ ፍቃዱ ገቢሣ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	102
38	በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 ባልተሸፈነ ጉዳይ ላይ በአሠሪና በሠራተኛ መካከል የተደረገ የህብረት ስምምነት መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ	36692	አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት እና ተስፋዬ መኮንን	ጥቅምት 25/2001	104
39	ሠራተኞች ለሚፈፅሙት ጥፋት በህብረት ስምምነት የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች የተቀመጡ በሆነ ጊዜ አሰሪው በሠራተኛው የተፈፀመውን ጥፋት ክብደት በመመዘን ይመጥናል የሚለውን ቅጣት መወሰን የሚችል ስለመሆኑ	37027	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት አሰለፈች ደስታ	ጥቅምት 11/2001	106
40	አንድ ድርጅት እንደስራው ፀባይ በህግ ከተደነገገው ማዕቀፍ ሳይወጣ/ሳይጥስ/ የሥራ ሰዓቱን ማሻሻል ስለመቻሉ አዋጅ 377/96 አንቀፅ 61/1/	36518	ሜታ አቦ ቢራ አ.ማ እና እነ ሳሙኤል ተፈራ (አራት ሰዎች)	ጥቅምት 4/2001	108
41	የአሰሪ ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደል ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1/ተ/	35484	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና አቶ ደረጀ ማሞ	ህዳር 25/2001	110
42	አሰሪ ሠራተኛውን በሣምንት ዕረፍቱ ሥራ እንዲሰራ ለማድረግ የሚችል ስለመሆኑ	37815	አለማየሁ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ እና አቶ አብዮት በፊቃዱ	ህዳር 2/2001	112
43	በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ “የሥራ ቀናት” የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(3)	36377	የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና ተሾመ ኩማ	ህዳር 2/2001	114
44	የኘሮቪደንት ፈንድ ወይም/ እና የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ	37048	የሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ሣህሉ ምትኩ	ህዳር 2/2001	116
45	በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ መውጣት በራሱ አንድን ሠራተኛ ወደ ቀድሞ ሥራ ለመመለስ መብት የሚሰጥ ስላለመሆኑ	37256	አዲስ አበባ የምግብ አዳራሽ አስተዳደር እና ወ/ሮ የውብዳር ጥላሁን	ህዳር 4/2001	119
46	ለአምስት ተከታታይ ቀናት በሥራ ገበታ ላይ ያለበቂ ምክንያት አለመገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ስለመሆኑ	37402	የንኮማድ ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ ቡሽራ በቀለ	ህዳር 11/2001	122
47	ከሥራ ጋር በተገናኘ በሚፈፀም ድርጊት መነሻነት በሠራተኛው ላይ በፖሊስ የሚደረግ ምርመራ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ	37573	የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና አቶ መሐመድ አደን	ህዳር 16/2001	125
48	የሥራ ውል በስምምነት ተቋረጠ ለማለት የሚቻለው ስምምነቱ በፅሁፍ የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ	37575	ቃሊቲ ባሌስትራ ማምረቻ እና ብርሃኑ ልደት ወልዴ	ህዳር 2/2001	127
49	በአሰሪ በተደረገ የሥራ ዝውውር ቅሬታ አድሮብኛል በሚል ምክንያት ከሥራ መቅረት የህግ ድጋፍ የሌለው ስለመሆኑ	37778	አዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪ አከፋፋይ አ.ማ እና አቶ ካሣሁን ከበደ	ህዳር 4/2001	129
50	በአሰሪና በሠራተኛ መካከል የሥራ ውል ግንኙነት አለ ለማለት የሚቻልበት አግባብ	03171	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና ወ/ት ትርሲት ደገፋ	ህዳር 16/2001	132
51	አዲስ መዋቅርን ተግባራዊ ያደረገ ተቋም/ድርጅት/ ሠራተኞቹን “ራሱ ባወጣው መስፈርት” መሰረት ሊመድብ ስለመቻሉ	36210	አቃቂ መለዋወጫ ዕቃዎችና መሣሪያዎች አ.ማ እና አቶ ኃይለ ሳልቫቶር	ህዳር 2/2001	136

https://t.me/ethiopianlegalbrief

52	• አንድ ሠራተኛ በአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበት የሚችልበት አግባብ • በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ "የአሰሪ ንብረት" በሚል የተገለፀው ሐረግ ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1//ሸ/	34669	አድማስ ኮሌጅ እና ሠለሞን ሙሉአለም	ታህሣሥ 2/2001	138
53	የተረከበው የአሠሪ ንብረት የጠፋበት ሰራተኛ ንብረቱን ለግል ጥቅሙ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ያዋለው ያለመሆኑን ካላስረዳ በቀር የንብረቱ መጥፋት ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)(ቀ) 14(2)(ለ)(2)	39118	ደሣለኝና ቤተሰቡ ኃላ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ በፈቃዱ በላይ	ታህሣሥ 23/2001	141
54	በህብረት ስምምነት ወይም በሌላ አካኋን የተወሰነ የሥራ ውል የሚቋረጥበት ምክንያት ካለ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ያልተመለከተ ቢሆንም ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 3787/96 አንቀፅ 27/1/	36591	ማታዶር አዲስ ጎማ አ.ማ እና ደረጀ ኡመታ	ታህሳስ 14/2001	144
55	የሥራ መሪ በሆነ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት መስራት ግለሰቡን የሥራ መሪ ከመሆን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 3/2/ /ሐ/	36894	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ሙላት ታረቀኝ	ታህሳስ 30/2001	146
56	ለተወሰነ ጊዜ በተደረገ የሥራ ውል ግንኙነት ለሠራተኛው የሚክፈል የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸው ባስቀመጡት መልክ የሚፈፀም ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 35/2/	37201	ማታዶር አደስ ጎማ አክሲዮን ማህበር እና እነ አቶ ኤልያስ በቀለ (አስራ አራት ሰዎች)	ታህሣሥ 30/2001	148
57	የጥበቃ ሥራን የሚሠራ ሠራተኛን በተመለከተ የሥራ ውሉ ያለአግባብ ተቋርጧል በሚል ሊወሰን በአሠሪውና ሠራተኛው መካከል ሊኖር የሚገባው ከፍተኛ መተማመን የሚሻክር በመሆኑ ሰራተኛው ወደ ሥራ እንዲመለስ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43	37454	ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል እና ከበደ ሰይፉ	ታህሣሥ 16/2001	151
58	ወደ ሥራ እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ የሥራ ክርክሮችን የሚወስነው አካል ሠራተኛው አግባብነት ያላቸውን ክፍያዎች ተከፍሎት ከሥራ እንዲሰናበት ሊወሰን የሚችለው በመጀመሪያው ፍርድ መሠረት ያልተፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/	38255	አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አለምሰገድ ኃይሉ	ታህሣሥ 23/2001	154
59	የሥራ ውሉን በፍቃዱ ያቋረጠ ሠራተኛ የህብረት ስምምነት የሚፈቅድለት ከሆነ ኘሮቪደንት ፈንድና የሥራ ስንብት የማግኘት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ	37551	አቶ ድካምየለህ ጥበቡ እና አርሾ የህክምና ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር	ታህሣስ 9/2001	157
60	የስራ ውል የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው ተብሎ በተወሰነ ጊዜ የስራ ውሉ የተቋረጠበት ወገን/ሠራተኛ/ ሊወሰኑለት የሚገቡ ክፍያዎች	34476	ኩመላ በጅግ እና ብሔራዊ አስገብኚና ጉዞ ወኪል	ታህሳስ 2/2001	160
61	አንድ የሥራ ዘርፍ የአሠሪው ቋሚ ሥራ ቢሆንም በዚሁ ዘርፍ ሠራተኞችን ለተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ቀጥሮ ሊያሰራ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሐ)	40305	የኢትዮጵያ ፐልኘና ወረቀት አ.ማ እና እነ አቶ ታመነ ጫላ	ታህሣሥ 21/2001	163
62	አንድ ሠራተኛ ይሰራው የነበረ የሥራ መደብ መሰረዝ ወይም አለመኖር ለሥራ ውሉ መቋረጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1) (መ)	40804	ዳንዲቦሩ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና እነ ተክሉ ኡርጌ ኢደኤ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 26/2001	165

https://t.me/ethiopianlegalbrief

63	አንድ ሠራተኛ ወደ ሥራ ሲሄድና ከሥራ ወጥቶ ወደቤቱ ሲመለስ አሰሪው በመደበው የመንገዣ አገልግሎት ሲጠቀም አደጋ የደረሰበት መሆኑ ከተረጋገጠ ሦስተኛ ወገኖች ለአደጋው ያደረጉት አስተዋፅኦ መኖር አሰሪው የጉዳት ካሣ ላለመክፈል እንደመከላከያ ሊሆነው ስላለመቻሉ እና የጉዳት ካሣው በጉዳት የተነሣ ህይወቱን ላጣው ሠራተኛ ጥገኞች የሚከፈልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 95/2/, 96/1/, 98/2/, 97/1/, 107/1//ሐ/, 110/ 112	36194	ዶ/ር ማንደፍሮ እሸቱ እና ፍሬድሪክ ኤቨርት ሲቲፍቱንግ	ጥር 28/2001	167
64	በድርጅት ውስጥ በተደረገ የመዋቅር ማሻሻያ የሥራ መደብ የተሰረዘ እንደሆነ የሥራ መደብ የተሰረዘበትን ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚቻልበት አግባብ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1)(መ)	38811	ርሆቦት ሆሊ ሴቪየር ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ አማረ አድማሱ	የካቲት 17/2001	173
65	በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለ የሥራ መደብ በሌላ 3ኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የስራ ውል ለማቋረጥ ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 28	38435	ኤስ.ኦ.ኤስ የህፃናት መንደር እና እነ አቶ ከበደ ኩምሣ (ስድስት ሰዎች)	የካቲት 17/2001	175
66	ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል የሚቋረጠው ማስጠንቀቂያ በመሰጠት ስለመሆኑ	38023	የመንግስት ቤቶች ኤጅንሲ እና ብርሃኑ ደስዬ	የካቲት 17/2001	178
67	በአሰሪያቸው ላይ ክስ አቅርበው ያስፈረዱ ሠራተኞች የአሰሪውን ንብረት በዋስትና ከያዙ ባለገንዘቦች ይልቅ የቅድሚያ ክፍያ መብት ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 167 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀጽ 2857(1) አዋጅ ቁ. 186/94 አንቀጽ 80 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ- መንግስት አንቀፅ 13(2)	40921	አቢሲንያ ባንክ (አ.ማ) እና አብዱ አህመድ (ሁለት መቶ ስልሣ ስድስት ሰዎች)	የካቲት 26/2001	180
68	የአንድ ሠራተኛን ድርጊት ከባድ ቸልተኝነት ነው ለማለት የሥራውን ባህሪ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ	41115	ሜድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ ሞገስ ሽፈራው	የካቲት 26/2001	183
69	አሠሪ የአንድን ሠራተኛ ደሞዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅም ሣይነካ በተመሳሳይ የሥራ መደብ ላይ አዛውሮ ሊያሠራ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 13(2) እና (7)	40938	ሙገር ሲሚንቶ ኢንተርኘራይዝ እና አቶ ኃይሉ መንግስቱ	መጋቢት 24/2001	186
70	አንድ ሠራተኛ የአሠሪው ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደሉ የተረጋገጠ እንደሆነ አሠሪው ሠራተኛውን በፍ/ብሔር ከሶ ገንዘቡን የማስመለሱ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)	42292	የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ከበደ አቡነቱ	መጋቢት 24/2001	188
71	በአሠሪው ወደሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሠራ የተደረገ ሠራተኛ ዝውውሩን በወቅቱ ሣይቃወም የተዛወረበት የሥራ ገበታ ላይ ለ5 ተከታታይ ቀናት የቀረ እንደሆነ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27 (1)(ለ)	41623	አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ሣሙኤል ኪዳኔ	መጋቢት 8/2001	191
72	• ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛን ከሥራ የማገድ ተግባር ሠራተኛን እንደማሰናበት የማይቆጠር ስለመሆኑ • አሠሪው ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛው ለታገደበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፍል የሚደረግበት አግባብ • ከሥራ ያለአግባብ ታገድኩኝ በሚል የቀረበን ክስ በማስተናገድ ላይ ያለ ፍ/ቤት በክርክሩ	41411	ሙስሙል ዳቦ መጋገሪያ ድርጅት እና አቶ በለጠ ተገኝ	ግንቦት 11/2001	193

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሂደት ሠራተኛው ከሥራ የተሰናበተ መሆኑን ካወቀ የተያዘው ጭብጥ እንዲሻሻል እና ጭብጡ እንዲስተካከል በማድረግ ጉዳዩን ማየት ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(4)				
73	• አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ከጉዳቱ በኋላ የቀድሞ ስራውን መስራት መቀጠሉ ብቻ አሰሪውን የጉዳት ካሣ ከመክፈል ነፃ የማያወጣው ስለመሆኑ • በሥራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተገናኘ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ውስጥ የተመለከተውና "የመስራት ችሎታ" የሚለው ሃረግ ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ እና የጉዳት ካሣ መጠንና ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 109, (1) እና (3) , 107, 99(1), 102(3) አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 33	43370	የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት እና አቶ ጌታቸው ገድሌ	ግንቦት 12/2001	196
74	• የድርጅት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የአሰራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሠራተኛ ቅነሣ የሚደረግበት አግባብ • ቅነሣ የሚደረግበትና ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(2)(ሐ), 29(3)	42752	እነ ወ/ት ማሜ አሠፋ (ሰላሳ ስድስት ሰዎች) እና ብሔራዊ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል(NTO)	ግንቦት 12/2001	199
75	በሠራተኛ እጅ የሚገኙ የአሠሪ ንብረቶች መመለስ ወይም አለመመለስ ጉዳይ ሠራተኛው የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚያነሣቸውን ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ለማስተናገድ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 36, 38	39464	ሐረር ቢራ አክሲዮን ማህበር እና አቶ አብዱልቃድር አብዱረዛቅ	ግንቦት 25/2001	202
76	ቀድሞ ይሰራበት የነበረን የሥራ መደብ በመሰረዙ ምክንያት ሠራተኞችን በማሰናበት ፋንታ በክፍያ አነስተኛ ወደሆነ ሌላ የሥራ መደብ እንዲሰሩ ያደረገ አሠሪ ለሠራተኞቹ በቀድሞው ደመወዝ መሠረት እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	41786	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ አቶ አሰፋ አቤቦ (ሦስት ሰዎች)	ግንቦት 26/2001	204
77	በጥበቃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ እንዲጠብቅ የተሰጠው የአሰሪ ንብረት የጠፋ እንደሆነ ሰራተኛው ለንብረቱ መጥፋት አስተዋጽኦ ያለማድረጉን ማረጋገጥ ካልተቻለ በስተቀር በሃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ	39650	የየረር በር ምስራቅ ፀሐይ ቅዱስ ዑራኤል ቤ/ክ እና እነ ቄስ ሰፊነው ደሣለኝ	ግንቦት 27/2001	207
78	በተጭበረበረ ማስረጃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የማጭበርበር ድርጊቱ የታወቀ/የተደረሰበት/ ከሆነ ማጭበርበሩ የተከሰተው ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ተቆጥሮ ሊያስናብተው የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1) (ሐ)	39543	የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ በረከት ተ/ማርያም	ግንቦት 4/2001	209
79	ለኘሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቅነሣ በሚካሄድበት ወቅት አሰሪው በአዋጅ ቁ.377/96 ላይ የተመለከተውን የሠራተኞች ቅነሣ ሥነ-ሥርዓት መከተል የማይጠበቅበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30(1)	39042	ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ጀማል መሐመድ	ግንቦት 26/2001	211
80	የሥራ መደብ ዝውውርን በመቃወም ቅሬታን በማሰማት ላይ መሆን በስራ ቦታ ላይ ላለመገኘት እንደ በቂ ህጋዊ ምክንያት የሚወሰድ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ)	38189	ሮፖክ ኢንተርናሽናል ኃላ/የተ/የግል ማህበር እና ይደርሳል አእምሮ	ግንቦት 27/2001	213

https://t.me/ethiopianlegalbrief

81	አሠሪ የሥራ መሪ የሆነን ሠራተኛውን ያሰናበተው ያስበቁ ምክንያት ቢሆንም እንኳን ተገቢ የሆነ ካሣ ለመክፈል ከሚገደድ በስተቀር ሠራተኛውን ወደ ሥራ እንዲመልስ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ	37982	የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና አቶ ታደሰ ዘነበ	ሰኔ 16/2001	216
82	ለሥራ ማስኬጃነት የተቀበሉትን የአሰሪ ገንዘብ አጉድሎ መገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)	41720	የእንጨት መሠንጠቂያና መገጣጠሚያ ድርጅት እና ረዲ እንዳለ	ሰኔ 9/2001	219
83	የሥራ ውል የተቋረጠው በህጉ አግባብ ነው ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ የማይከፈል ስለመሆኑ	39861	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ሣምሶን በለጥካቸው	ሰኔ 18/2001	221
84	በቃል ከሥራ ተሰናበትኩ በሚል ክስ የሚያቀርብ ሠራተኛ አሰሪው ከሥራ ያሰናበተው ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ	43610	ናይኮ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ሰለሞን ተሰማ	ሐምሌ 21/2001	224
85	አሠሪ የሆነ ወገን የሥራ ቅልጥፍናን፣ ውጤታማነትን፣ የኢንዱስትሪ ሰላምን ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድን ሠራተኛ የተቀጠረበትን ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በጠበቀ ሁኔታ አዛውሮ ለማሰራት የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 2 (1), 4	44033	መንበረ ፓትሪያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና አቶ ይበልጣል አጥናፉ	ሐምሌ 22/2001	226
86	በህግ ወይም በሕብረት ሥምምነት የተመለከተው የጡረታ እድሜ ሣይደርስ በመንግሥት መመሪያ በጡረታ እንዲገለሉ የተደረጉ ሠራተኞችን በተመለከተ አሰሪ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ለመክፈል የማይገደድ ስለመሆኑ	42906	የኢትዮ-ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ እና አነ ትዕግስት ማሞ (ሰማንያ አንድ ሰዎች)	ሐምሌ 21/2001	228
87	የኮንስትራክሽን ሥራ የሚሰራ ድርጅት የሥራው መጠን በቀነሰ ጊዜ ሠራተኞችን ለማሰናበት የማስጠንቀቂያና ሌሎች የቅነሳ ሥነ-ሥርዓቶችን ሳይከተል ቅነሳ ለማካሄድ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30	42075	አፍሪካዊት የህንፃ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አነ አቶ እንድሪስ ዓሊ	ሐምሌ 16/2001	231
88	የሥራ ውል □ንደተቋረጠ የጡረታ አበል ለማግኘት መብት ያለው ሠራተኛ የሥራ ስንብት የማይከፈለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39 አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2) (ሰ)	39808	ናዝሬት ሣሙና ፋብሪካ እና ዘውዴ ኃ/ማርያም	ሐምሌ 21/2001	233
89	የሥራ መሪ ከሠራተኛ ሊለይ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3, አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2	42901	የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና ወ/ሮ ንግስት ለጥይበሉ	ሐምሌ 21/2001	235
90	በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በሚካሄድ የሥራ ክርክር የሚያዘው ጭብጥ አሰሪው ገንዘብ ይከፈለኝ በሚል በሠራተኛው ላይ ክስ ባቀረበ ጊዜ ከሚያዘው ጭብጥ ጋር አንድ አይነት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ	39471	ኤርሚያስ ሙሉጌታ እና በክልቻ ትራንስፓርት አ/ማ	ሐምሌ 29/2001	237
91	በሃይማኖት ተቋም ውስጥ መንፈሳዊ(ሃይማኖታዊ) አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ የሚሸፈን ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	18419	ሐመረወርቅ ቅ/ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና እነ ዲያቆን ምህረት ብርሃን (ስድስት ሰዎች)	ግንቦት 4/1998	239
ቤተሰብ					242
92	የውርስ ሀብት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክስ የማዬታ ውርስ ከተጣራ በኋላ መቅረብ የሌለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1)	34703	እንዳሻው ፍቃዱ እና እነ ወንድማገኝ ፍቃዱ(ሰባት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	243

https://t.me/ethiopianlegalbrief

93	ኑዛዜ ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም በሚል የሚያቀርቡት የመቃወም አቤቱታ ኑዛዜው በተነበበ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973	36604	ወ/ሮ ዕጌ መንግስቱ እና እነ አቶ ወንድይራድ መንግስቱ(ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 25/2001	245
94	ከጋብቻ በፊት የግል የነበረን ንብረት መነሻ በማድረግ በጋብቻ ጊዜ በግብይት የተገኘ ንብረት የግል ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው በፍ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 58(2), 57, 62(2)	37275	ሻ/ባሻ ገዛኸኝ ድልነሣው እና ወ/ሮ ተዋበች ደመቀ	ጥቅምት 18/2001	247
95	ግልፅ ኑዛዜ ህጋዊ እንዲሆን መሟላት ያለበት ፎርማሊቲ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882	36777	አቶ ወንድም አገኝ ዘውዱ እና እነ አቶ ታፈሰ ወንድአፈራሽ(ሶስት ሰዎች)	ጥቅምት 25/2001	251
96	ህፃናትን ማዕከል ያደረጉ ክርክሮች የልጆችን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ መስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ	35710	ወ/ሮ እፀገነት አሸቱ እና ወ/ሮ ሰላሚዊት ንጉሴ	ታህሣስ 16/2001	253
97	የስጦታ ውል የተፈፀመው ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ከሆነ ይኼው ግለሰብ እንደ ምስክር ተደርጉ ባይሳፍም ምስክር ተደርጉ ሊቆጠር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443,881,882	37562	አቶ ሣሙኤል ፈረንጅ እና አቶ ግርማ ታፈሰ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 28/2001	258
98	ጋብቻ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው በህግ አግባብ ተፈፅሟል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 28(3)	41896	ወ/ሮ ታደለች ዋለልኝ እና እነ ወ/ሮ አዲስዓለም ፀጋ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 26/2001	261
99	የሟች እዳን ለመክፈያ በአፈፃፀም ሊያዝ የሚገባው በውርስ የተገኘውን ሀብት እንጂ የወራሾች የግል ሃብት ስላለመሆኑ	38691	አቶ ለገሰ ቢራቱ እና አቶ ደረጀ ጅማ ገርግሶ	የካቲት 24/2001	263
100	የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሣይኖር የጋራ የሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት በሌለኛው ተጋቢ የተሸጠ እንደሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ 6 ወር ውስጥ እንዲሁም በማናቸውም ሁኔታ ደግሞ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ስለመቻሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 69(2)	38126	ዲያቆን ኃይለጊዮርጊስ ወንድምሲያምረኝ እና እነ ወ/ሮ የሺ ተፈሪ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 22/2001	266
101	በኑዛዜ የተገኘ ንብረት በ10 (አሥር) ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተጠየቀ በስተቀር በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ	38152	የወ/ሮ ገነት ዳምጤ ወራሾች እና እነ አቶ ይልማ አስፋው	ሚያዝያ 29/2001	268
102	የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ ከመረመረ በኋላ የጉዳዩን ጭብጥ በመያዝ ወደ ሥር ፍ/ቤት የመለሰው እንደሆነ አስቀድሞ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ፍርድ እንደሌለ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ	37313	እነ አቶ መሐሪ ተ/ማሪያም (ሁለት ሰዎች) እና የወ/ሮ ገነት መኮንን ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	ግንቦት 18/2001	271
103	ወራሽ የሆኑ ወገኖች የሚያቀርቧቸውን ተገቢነት ያላቸው ማስረጃዎች በሙሉ አሰባስቦ በመስማት ያልተከናወነ የውርስ ማጣራት ሪ□ርት በህግ አግባብ የተከናወነ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241, 270 እና 345	42525	እነ አቶ አብዱልዋሲቅ አርጋው እና ወ/ሮ አልዋያ አባበሊስ	ግንቦት 27/2001	274
104	የተናዛዡ ህጋዊ ንብረት ባልሆነ ነገር ላይ የተደረገ ኑዛዜ በፍ/ቤት ቢፀድቅም እንኳን የኑዛዜ ሰነዱ ዋጋ የማይኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 865	32817	ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ እና እነ ወ/ሮ ቱቱ ዘውዴ(ሦስት ሰዎች)	ሰኔ 11/2001	277
105	የገበያ ዋጋን መሠረት ያላደረገና የግንባታ ዋጋ ግምት ላይ ብቻ ተመርኩዞ የሚደረግ የውርስ ሀብት ክፍፍል ፍትሐዊ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ	40510	ቴዎድሮስ መንበሩ እና ገ/ህይወት ታደሰ	ሰኔ 23/2001	281

https://t.me/ethiopianlegalbrief

106	ጋብቻ በሁለት የተለያዩ ሥርዓቶች የተፈፀመ ቢሆንም አንድ ጊዜ በህግ አግባብ የተደረገ ፍቺ በቂና ሙሉ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 75(ሐ)	40781	ፍቅረስላሴ ካህሣይ እና ወ/ሮ ሮማን ታደሠ	ሐምሌ 30/2001	283
107	በውርስ ሃብት ክፍፍል ላይ ተወላጅ የሆነ ሰው ከሩብ በላይ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ክፍፍሉ እንዲቀር ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 11/22,913,1060,1037-1051,942	18394	ወ/ሮ ዝናሽ በቀለ ማንደፍሮ እና ወ/ሮ ሐረገወይን በቀለ	መጋቢት 21/1999	286
ውል					290
108	የደረሰው ወይም ይደርሣል ተብሎ የሚጠበቀው ኪሣራ በጉዳት ኪሣራ ሊካስ የሚችል በሆነ ጊዜ ውሉን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776	35472	አቶ መሐመድ ካሣሁን እና አቶ ሰለሐዲን ኑር	ጥቅምት 6/2001	291
109	የፍ/ብ/ሀ/ቁ.1723"ን" መስፈርት አላሟላም በሚል ውል እንዲፈርስ የተደረገ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 1723,1815	34803	መ/ር መካንንት ወረደ እና እነ መስከረም ዳኛው (አራት ሰዎች)	ጥቅምት 11/2001	294
110	ከአንቺሎነት ውል ጋር በተያያዘ ለሚኖር የጉዳት ሃላፊነት ካሣ ሊወሰን የሚችልበት አግባብ የንግድ ህግ ቁጥር 595, 596, 597 የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 1790, 2090, 2091, 2092, 2141, 2102	32854	ወ/ሪት ማርታ አድማሱ እና እነ አቶ በረከት ሰብስቤ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 20/2001	307
111	የተከራዩትን ቤት ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት ለውል ማፍረስ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ	36520	የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ይብራህ ግርማይ	ጥቅምት 27/2001	310
112	መሐይምነትን ወይም ዓይነስውርነትን መሠረት በማድረግ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ አቤቱታ በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 1719,1845	29363	ወ/ሮ ወርቅነሽ አምዴ እና አቶ ጥላሁን አርምዴ	ህዳር 18/2001	313
113	የማይንቀሣቀስ ንብረት የሽያጭ ውል ተደረገ የሚባለው በውል ውስጥ ያሉ ወገኖች በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የሽያጭ ውሉን ከተፈራረሙበት ቀን ጀምሮ እንጂ የአስተዳደር ጉዳዮች ተጣርቶ የመስሪያ ቤቱ ማህተም ካረፈበት ቀን አንስቶ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723(1), 2015(ሀ)	36740	አቶ አብዱልዋሐብ ኢብራሂም እና እነ ወ/ት መሰለች ከፍያለች (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 23/2001	316
114	በማኅበር በመደራጀት የተሠራ ቤትን ለሶስተኛ ወገን ከማስተላለፍ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚነሣ ክርክርን አስመልክቶ የፍ/ብ/ሀ/ቁ 1723 ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሀ/ቁ.1723	36294	ወ/ሮ ሀናይት ገነሜ ገንታ እና እነ በቀለ ገመዳ ዳኖ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 9/2001	319
115	በአሰሪ ወይም በ3ኛ ወገን ወጪ ትምህርትን ተከታትሎ ለማገልገል በሚል የተገባን ውል (ስምምነት) የጣሰ ሰው ግዴታውን በአማራጭ ሊወጣ የሚችል ስለመሆኑ	33473	ወ/ሮ ሃርሴማ ሰለሞን እና የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ	ህዳር 16/2001	322
116	የዕቃ አስተላላፊነት ሃላፊነትና ተግባር ዕቃን የማንገዝና የማስረከብ ሥራን የሚያካትት ስለመሆኑ	32571	አቶ ሚፍታህ ከድር እና የባህር ትራንዚት አገልግሎት	ታህሣሥ 9/2001	326
117	ክርክር የሚካሄድበት ጉዳይን አስመልክቶ በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ የሌለ እንደሆነ ስለ ውሎች በጠቅላላ በሚለው ክፍል የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 1677፣1845	34940	ወ/ሮ ሐጅራ አብሮ እና አቶ ሐሺም ሐጂ አሊዬ	ታህሣስ 28/2001	329
118	• ፍ/ቤት የቀረበለትን የውል ይሰረዝልኝ፣ ጥያቄ				

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ወደጉን በመተው የውል የፎርማሊቲን የተመለከተ ጭብጥ በማንሣትና ምክንያቱን በመለወጥ ውሣኔ መስጠት የማይገባው ስለመሆኑ • በፍ/ብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሰረት ጭብጥ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ	32299	እነ አቶ ሰለሞን ከተማ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ሴንትራል ቬኑ /የተ/የግል ማህበር (አራት ሰዎች)	ጥር 7/2001	331
119	በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161 የንግድ ሕግ ቁ. 124	34586	አቶ አያሌው ድልነሳው እና እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ (አራት ሰዎች)	ጥር 28/2001	336
120	በውል ግንኙነት ውስጥ የራስን ግዴታ ሳይወጡ ሌላው ወገን ግዴታውን አልተወጣም በሚል የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1757	39568	አቶ ሽንቁጤ ተ/ማርያም እና አቶ ገብሬ ጐንጤ	መጋቢት 24/2001	339
121	የማይንቀሳቀስ ንብረት ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጐት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ያላሳወቀ እንደሆነ ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት የመጠየቅ መብቱ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731(1), 1732, 1789 እና 1845	38935	እነ አቶ ወልደፃዲቅ ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ስንታየሁ አያሌው	መጋቢት 3/2001	343
122	በፍ/ብሔር ጉዳዮች የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1846	36756	አቶ ፀጋዬ ምትኩ እና እነ ወ/ሮ አበበች ምትኩ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 17/2001	348
123	ለብድር በዋስትና መልክ የተሰጠን ንብረት ለተበዳሪው መመለስ ብድሩ እንደተከፈለ የሚያስቆጥር ስለመሆኑ	41571	ማህደር አእምሮ እና ላእከ ገ/መድህን	ሰኔ 2/2001	351
124	በህግ ፊት በማይፀና ውል አማካኝነት የተሣሠሩ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ይመለሱ በሚል ውሣኔ መስጠት የሚቻለው መመላለሱ አንደኛውን ወገን በእጅጉ የሚጐዳ ወይም ለሌላኛው ያልተገባ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችል አለመሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ	39336	ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ እና እነ አዱኛ እጅጉ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 7/2001	354
125	በፍ/ቤት በንብረት ላይ የሚሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ተቋቁሟል ለማለት የሚያበቃ ስለመሆኑ	39170	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ክንዴ አፍራሶ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2001	357
126	የባለዕዳውን ዕዳ ለባለገንዘብ የከፈለ ወገን በባለገንዘቡ መብቶች ላይ በመዳረግ (subrogation) ባለገንዘቡ የነበረውን መያዣን መሰረት ያደረገ የቀዳሚነት መብት ሊሰራበት የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1968 - 1974	39778	ሕብረት ባንክ አ/ማ እና አቢሲኒያ ባንክ አ/ማ	ሐምሌ 30/2001	361
127	ፈራሽ የሆነን የስጦታ ውል ተከትለው የተሰሩ ስራዎችን ቀሪ ማድረግና ተዋዋዬችን ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የሚቻለው በቅን ልቦና የተዋዋለ 3ኛ ወገን መብትን የማይጐዳ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1815,1816,1817	41116	ፍሌንስቶን ኢንጀነሪግ እና እነ ወ/ት ሐና ተስፋዬ (ስድስት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2001	368
128	የአክስዮን ድርሻ በመያዣነት እንደተሰጠ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2863 - 2874	39256	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ሞሣ ነጋሽ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2001	371
129	በብድር የተሰጠን ገንዘብ እጥፍ ለመቀበል በሚል የሚደረግ የብድር ስምምነት የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ	43372	አቶ ደረሱ አለሙ እና አቶ ሙሊሣ ወርቁ	ሐምሌ 22/2001	379
130	ስልጣን ያለው የአስተዳደር አካል የማይንቀሳቀስ				

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ንብረት ባለሀብትነቱን አውቆለት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ከሰጠው ሰው ጋር የተደረገ የንብረቱ የመያዣ ውል የተሰጠው የምስክር ወረቀት የተሰረዘ ቢሆን እንኳን መያዣ ተቀባዩ በቅንልቦና አለመሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የፀና ሆኖ የሚቀጥል ስለመሆኑ	41388	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ከፍያለው ሞልቶት (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2001	381
131	የማይንቀሣቀስ ንብረት ገዥ ውል እንዲፈፀምለት ሻጭን የመጠየቅ መብቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 384(ሀ) የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2892(3)	39725	እነ ወ/ሮ አለምሸት ካሣሁን (ሦስት ሰዎች) እና አቶ ሽመልስ እንዳለ	ሐምሌ 23/2001	384
132	የማይንቀሣቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚደረግ የስጦታ ውል የማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም በህግ የፀና ውል ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443, 881, 1723(1)	39803	አቶ አለኸኝ ገ/ህይወት እና እነ እማሆይ አጢነሽ በቀለ (ሦስት ሰዎች)	ሐምሌ 2/2001	387
አፈፃፀም					390
133	በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ተካሄዶ ሽያጭ የተፈፀመ እንደሆነ ሽያጩ ሊፈርስ የሚችለው በአሻሻጥ ሥርዓቱ የተነሣ መብት ወይም ጥቅም ያለው ሰው ላይ ቀጥተኛ ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 445	31963	አቶ አብዱልሐኪም ሁሴን እና እነ አቶ ቀነኒ ሁንዴ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 20/2001	391
134	የፍርድ ባለመብት ባለመቅረቡ የተዘጋ የአፈፃፀም መዝገብ ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ10(አሥር) ዓመት ይርጋ ካልታገድ በቀር ሊንቀሳቀስ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384	35018	በዛብህ አበበ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ጥቅምት 18/2001	394
135	•የፍርድ አፈፃፀም ክርክር የሚጀመረው የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን በፍርዱ መሰረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርብ ስለመሆኑ •የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ወይም የአፈፃፀም የውክልና ስልጣን ለተሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371,372, 378/1/	21359	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ተገኘ ማንደፍሮ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 28/2001	396
136	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥሮች 358 እና 418 ተፈፃሚ የሚሆኑበት አግባብ	32143	መሐመድ አስማኤል ተርቢ እና መሐመድ አህመድ ኑር	ጥቅምት 18/2001	400
137	የአንድ ንብረት ወቅታዊ ዋጋ ማለት ንብረቱ ለጨረታ ሽያጭ ቀርቦ የሚያወጣው ዋጋ ስለመሆኑ	37503	አቶ ወልደዮሐንስ ኃብተየስ እና ወ/ሮ ያምሮት ሽዋረጋ	መጋቢት 24/2001	402
138	የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ሊሸጥ የሚችልበት ሥነ- ሥርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 426,428(2)	39175	ወ/ሮ በለጡ ጋሼ እና እነ አንዱአለም ቴድሮስ (ሦስት ሰዎች)	መጋቢት 24/2001	404
139	በቀጥታ ክስ ወቅት የተገመተ የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቅት በአይነት ካልተገኘ እና የንብረቱ ዋጋ በልጦ ከተገኘ አፈፃፀሙ ሊሆን የሚገባው ንብረቱን በአይነት ለመተካት በሚያስችል የወቅቱ ዋጋ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378, 392	39485	የህፃን ሠላማዊት ቴድሮስ ሞግዚት እና መምህር ሚካኤል ግደይ	መጋቢት 17/2001	407
140	በህግ አግባብ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ የሞራል ወይም የህሊና አስተሳሰብን መሠረት በማድረግ ብቻ ዋጋ አልባ ሊደረግ የማይችል ስለመሆኑ	38041	ታደሠ ገ/መስቀል እና እነ ሙሉጌታ ዘኽርያስ (ሰባት ሰዎች)	መጋቢት 22/2001	410

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ወንጀል				1
1	በወንጀል ጉዳይ የክስ ሂደት የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ ሊመዘን የሚገባ ስለመሆኑ	35697	የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ከበደ ወርቅነህ	ጥቅምት 20/2001	2
2	• በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ የተሻሻሉና የተሰወጡ ሁኔታዎች ከነባሩ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ጋር በቀጥታ ተጣምረው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባ ስለመሆኑ • በወ/ሕ/ አንቀጽ 543(3) የተከሰሰ ሰው የዋስ መብት የሚከለከል ስለመሆኑ የወ/ሕግ አንቀፅ 543 የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 63	35695	የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና አቶ ተመስገን አዲስ	ህዳር 11/2001	5
3	በተወሰነበት ፍርድ ላይ ይግባኝ እንደሚል ፍላጐቱን አሳውቆ እያለ ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት በኩል በተከሰተ መጓተት የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ፍርደኛ የሚያቀርበው የማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ	39722	ግርማ ሃይሌ እና ዐቃቤ ህግ	ታህሣሥ 23/2001	7
4	የዳኝነትን ሥራ በማከናወን ወቅት የሚፈፀሙ ስህተቶች እና ጥፋቶች ሁሉ ዳኛን በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ሊያስጠይቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 214/74	33075	አቶ ብርቁ ገላነው እና የአማራ ብ/ክ/መ/የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ጥር 19/2001	9
5	አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉ የሚቋቋምበት ህጋዊ፣ ግዙፍዊና፣ ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2	38161	እነ ጀሚላ መሐመድ ሐጐስ እና የፌዴራል የመ/ደ/ዐ/ህግ	የካቲት 19/2001	11
6	በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ንብረት የሆነ ንግድ መደብር ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የንግድ መደብሩን በውስጡ ከያዘው ሸቀጦች በመለየት (በመነጠል) የሚሰጡት ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ	44594	የፌ/ሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ እና እነ ካፋ መሐመድ (አራት ሰዎች)	ሐምሌ 15/2001	13
7	በወንጀል ጉዳይ በእስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሰው የእስራት ቅጣቱን ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ወይም እንዲለቀቅ ሊደረግ የሚችለበት አግባብ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 82,192,194	46382	እነ ዳንኤል ገ/ዮሐንስ (አራት ሰዎች) እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ	ሐምሌ 28/2001	16
8	አንድ ተከሣሽ በተፈፀመ ወንጀል ላይ ተካፋይ ነበር ለማለት ተከሣሹ በሙሉ ፈቃዱና ዕውቀቱ በወንጀል ድርጊቱ ተሣታፊ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32, 33, 630, 25	44031	ወ/ሮ ፊለቀች ኃ/ገብርኤል እና የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ	ሐምሌ 30/2001	19
9	ከተሸከርካሪ ጋር በተያያዘ በድንገተኛ አደጋ		ፋሲል ብርሃኑ እና ዓቃቤ	ሐምሌ	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ለሚከሰት የሰው ህይወት መጥፋት አሽከረካሪው በቸልተኝነት ወንጀል በማድረግ ሊጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 59(1), 543(2) እና (3)፣57 (2)	42703	ሕግ/የኦሮሚያ ክልላዊ ብሔራዊ መንግስት/	22/2001	22
ንብረት					27
10	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ካርታ በማቅረብ ብቻ የሚረጋገጥ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195	36320	ወ/ሮ ዘውዴ ገ/ስላሴ እና ወ/ሮ ህይወት ባህታ	ጥቅምት 18/2001	28
11	የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተገናኘ የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ተደርጐ ሊወሰድ የሚገባው ንብረቱን ለመገንባት የወጣው ወጪ (BooK value) ብቻ ሣይሆን ንብረቱ በወቅቱ ለገበያ ቀርቦ ሊያወጣ የሚችለው ዋጋ (market value) ጭምር ስለመሆኑ	35003	አቶ አሸናፊ አብዱልቃድር እና እነ ወ/ሮ ሽቶ አብዱራሂም (አራት ሰዎች)	ህዳር 9/2001	30
12	አንድ ተከራካሪ ተገቢነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅርቧል ለማለት ለክርክር መንስኤ የሆነውን ንብረት በእጅ አድርጎ መገኘትና በዚሁ ንብረት ላይ በእውነት ለማዘዝ እንዲችል የንብረቱ አያያዝ ያልተጭበረበረና በማናቸውም መንገድ ህገ-ወጥ በሆነ ሁኔታ ያልተገኘ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1)	36645	ረዳት ሳጂን አያኖ አንጀሎ እና እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጫሌቦ	ህዳር 11/2001	32
13	የጋራ ንብረትን ለመካፈል በሚደረግ ሽያጭ የጋራ ባለንብት የሆነ ወገን የቅድሚያ ግዥ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1261(2), 1386 — 1409	37297	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ እታለም ተስፋ	ታህሣሥ 2/2001	36
14	የጋራ ሀብት የሆነ ንብረት በመያዣ የተያዘ በመሆኑ የቅድሚያ መብት ያለ ቢሆንም የጋራ ባለሀብት የሆነ ወገን ንብረቱ በግልፅ ጨረታ ቀርቦ የሚያወጣውን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ግማሽ በመክፈል ማስቀረት የሚችል ስለመሆኑ	37298	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ዋቅጂራ	ታህሣስ 2/2001	39
15	የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታን ለማቅረብ አቤቱታ አቅራቢው ክርክር የቀረበበት ንብረት ባለሀብትነቱን ሳይሆን ባለይዞታነቱን ብቻ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ	38228	ሐጂ መሐመድ አወል ረጃ እና እነ አቶ ዲኖ በሺር (ሁለት ሰዎች)	ታህሣስ 7/2001	41
16	ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንፃ የሰራ ሰው የህንፃው ባለሀብት ሊሆን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179	36638	በላይ አበበ እና እነ አበራሽ ዋቅጅራ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 21/2001	43
17	በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ያለው ባንክ በንብረቱ ላይ ሊኖረው የሚችለው የመብት አድማስ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3088/1/, 3110/ሐ/	36013	ወ/ሮ ዘምዘም ኑሩ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ታህሣሥ 21/2001	46
18	የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን የሁከት ተግባር ፈጽሟል ከሚባለው ሰው የተሻለ የይዞታ መብት ያለው መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149	39940	ወ/ሮ ነጂባ ነጋሽ እና ወ/ሮ ዚያዳ ዩታሞ	ግንቦት 27/2001	50
19	ንብረትነታቸው የመንግስት የሆኑ ቤቶችን በተመለከተ የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ መንግስትን ወክሎ የመከራከር መብት ያለው	38169	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የወ/ሮ ንጋቷ ዘለቀ ወራሽ	ግንቦት 12/2001	52

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2)		አቶ እሸቱ ቦጋለ		
20	የይዞታ መብት ፍፁም ስላለመሆኑ እና በህግ አግባብ ይዞታው የተወሰደበት ሰው ተገቢ የሆነ ካሣ የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149(1), (2) አዋጅ ቁ. 7/1986 አንቀጽ 2(5), 21, 22, 24, 23 በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ- መንግሥት አንቀጽ 40 (8) አዋጅ ቁ. 455/1997	39539	የአዲስ አበባ አስተዳደር ግብርና ቢሮ እና እነ አቶ አበበ ዓባይ(ዘጠኝ ሰዎች)	ሐምሌ 30/2001	54
21	ከህግ የሚመነጭ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብትነትን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ	38666	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ባላንባራስ ተስፋዬ ገ/እየሱስ	ሐምሌ 9/2001	57
ከውል ውጭ ኃላፊነት					60
22	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 2143 ላይ የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የቀረበው የይርጋ ድንጋጌ የሞት ጉዳትን የሚያካትት ስለመሆኑ	34544	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ፋጤ ዓሊ	ጥቅምት 11/2001	61
23	ማንም ሰው ሥራው በሚያደርሰው ጉዳት ምክንያት ጥፋት ባይኖርበትም ከውል ውጭ ሃላፊነት ሊከተልበት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066- 2089(2069(1))	33201	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና ሼል ኢትዮጵያ	ጥቅምት 27/2001	63
24	ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው (ልጅ) ሃላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሰራ እንደሆነ ወላጆች በፍ/ብሔር በሃላፊነት ሊጠየቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2125, 2124	31721	ወ/ሮ ብዙነሽ ኃ/ዮሐንስ እና ወ/ሮ ስንታየሁ እሸቱ	ጥቅምት 25/2001	65
25	የጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባር ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው በህጉ መሠረት ሊሟሉ የሚገቡትን ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ እንጂ በማናቸውም ጥርጣሬ ምክንያት የግለሰብን ንብረት በመያዝ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.60/89 አንቀጽ 6, 58 አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 2(28) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26(1) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1193(1),(2), 2027, 2035, 2054, 2118	31171	አብልሃሚድ የሱፍ እና የምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት	ጥቅምት 27/2001	67
26	ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ ከሆነና ጉዳቱ በተጐጂው የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ካሣ ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ	35034	እነ ወ/ሮ ጥሩቀለም ደሴ እና እነ ወ/ሮ ጽጌ ከፍያለው	ጥቅምት 6/2001	70
27	ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት የሰው ህይወት የጠፋ እንደሆነና ለጉዳቱ መንስኤ (ምክንያት) የሆነው ወገን ሃላፊነት የተረጋገጠ ከሆነ በጠፋው የሰው ህይወት የተነሣ ጉዳት የደረሰበት ሰው የሞተው ሰው ምን ያህል ጥቅም ያስገኝለት እንደነበር ወይም ምን ያህል ተጨማሪ ዕድሜ ሊኖር እንደሚችል ያላስረዳ ቢሆንም እንኳን ፍ/ቤት የጉዳት ካሣውን በርትዕ ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102	34314	ወ/ሮ ግምጃ ጎበና እና እነ አቶ ወንድወሰን ወልዴ (ስድስት ሰዎች)	ህዳር 11/2001	73

https://t.me/ethiopianlegalbrief

28	የጉምሩክ ባለሥልጣን ያለአግባብ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ለሚያቆየው ንብረት በባለንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ	31704	አቶ አማረ መኛ እና የድሬዳዋ ሊጋር ጉምሩክ	ጥር 29/2001	76
29	በጥቅም ላይ ባልተመሰረተ ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ የሚሄድ ተሣፋሪ ላይ ለሚደርስ አደጋ የመኪናው ባለቤት ካሣ የመክፈል ሃላፊነት የማይኖርበት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089	38457	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ተመኘሁ እንደሻው	ሰኔ 2/2001	79
የዳኝነት ስልጣን					81
30	የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የውርስ አጣሪ የመሾም ሥልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ውስጥ የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1) (ሸ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996(1)	35657	እነ ወ/ሮ እመቤት መክብብ እና አቶ በድሉ መክብብ	ጥቅምት 6/2001	82
31	የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ለክርክር መነሻ የሆነው ክስ በገንዘብ ሊተመን የማይችል የመብት ጥሰትን የተመለከተ በሆነ ጊዜ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 50(1), 39	36338	ገ/መስቀል ደመወዝ እና ወ/ሮ አፀደ መኮንን	ጥቅምት 25/2001	86
32	የቅኔ መምህርነት ቀጥተኛ የሆነ መንፈሣዊ ሥራ በመሆኑ በሥራ ክርክር ችሎቶች ሊስተናገድ የሚችል ስላለመሆኑ	34440	መንበረፓትሪያክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና መጋቢ ሚስጢር መዝገቡ በላይነህ	ጥቅምት 6/2001	88
33	የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የቤት ባለቤትነት ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ረ)	33841	አቶ አስጨናቂ ረጋሣ እና እነ አቶ ገዛኸኝ ነጋሽ (ስድስት ሰዎች)	ጥቅምት 6/2001	91
34	በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ በወታደርነት በማገልገል ላይ የሚገኙ የሠራዊት አባላት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የወንጀል አቤቱታዎችን ለማስተናገድ ወታደራዊ ፍ/ቤቶች ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.27/88, አዋጅ ቁ. 343/94 አንቀፅ 2(9),26(1)	33368	ሻምበል አሰፋ በላይ ዘገየ እና ወታደራዊ አቃቤ ህግ	ህዳር 9/2001	93
35	የአ.አ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች በከተማው አስተዳድር ሥር ካሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን ብቻ ለማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ	34788	የሚች አቶ ሰለሞን ሳሙኤል ወራሾች እና ማርታ ሰለሞን (2 ሰዎች)	ህዳር 2/2001	96
36	በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በፍርድ ቤት ቀርቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ስላለመሆኑ	31906	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የአቶ መርስኤ መንበሩ ወራሾች	ህዳር 4/2001	99
37	በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ከተወረሱና በቀላጤ ከተያዙ ቤቶች ውጭ ያሉ ቤቶችን አስመልክቶ የሚነሣ የቤት ክርክር ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች ማየት የሚችሉ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ.47/67 አዋጅ ቁ. 110/87	37281	አቶ አበበ ዓሊ እና እነ የ08 ቀበሌ ገ/ማህበር (ሦስት ሰዎች)	ታህሣሥ 16/2001	103
38	በውጭ አገር የሚገኝ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክርን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማስተናገድ ስለመቻሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 37, አዋጅ	37339	ወ/ሮ ንግስት ኃይሌ እና አቶ ለገሠ ዓለሙ	ጥር 28/2001	106

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ቁጥር 25/88 አንቀፅ(4)				
39	ወደ ቀድሞ የሥራ መደብ እንድመለስና ለመደቡም የተሰጠው ልዩ ጭማሪ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ የወል ሥራ ክርክር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ142(1) (ሀ)	37016	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ተስፋዬ ማሞ	የካቲት 3/2001	109
40	ከጉምሩክ ፖሊስ አባላት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን ለመደበኛ የሥራ ክርክር ችሎቶች ያልተሰጠ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 368/96 , አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 8(2) , መመሪያ ቁ.4/1996	39085	የኢትዮትያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ር አስረሳች ወርቅነህ (ሰማንያ ሰባት የጉምሩክ ፖሊሶች)	የካቲት 3/2001	111
41	ቀደም ብሎ የተሰጠን የፍች ውሣኔ ወደጐን በመተው አዲስ የተደረገን ጋብቻ ህገ ወጥ ነው ማለት የማይቻል ስለመሆኑ	38745	እነ ወ/ሮ ሣሊያ ኢብራሂም (ሁለት ሰዎች) እና ሐጂ ሰማን ኢሣ	መጋቢት 10/2001	113
42	የሽሪዓ ፍ/ቤቶች የይዞታ ክርክርን ማስተናገድ የማይችሉ ስለመሆናቸው	36677	ወ/ሮ ሻምሺ የኑስ እና ወ/ሮ ኑሪያ ማሚ	ሚያዝያ 30/2001	116
43	የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርብ ይግባኝን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ስለመሆኑ	37866	ሙሉጌታ አባይ እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን	ግንቦት 19/2001	119
44	የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶችም ሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳዬችን ለማየት የሚያስችል ስልጣን በህግ ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ	41608	እነ ሙላቱ አንበርብር እና ወ/ት ታመነች ዮሴፍ መና	ሐምሌ 22/2001	121
ባንክና ኢንሹራንስ					123
45	ዕቃዎችን ለሚያንቀሳቅስ የጭነት መኪና የተገባ የመድን ዋስትና ጋር በተያያዘ በመኪናው ላይ ተሣፍሮ ሲሄድ ለነበረና አደጋ ለደረሰበት ሰው መድን ሰጪው የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ	42139	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ብያን ኡመር	ሰኔ 30/2001	124
46	ኢንሹራንስ ሰጪ በውሉ መሠረት ከፈፀመ በኋላ በተሸሸገ ወይም በሀሰት ቃል የቀረበ ጉዳይ አጋጥሚል በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የቀረበውን ቃል ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባለው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የንግድ ህግ 674(1),(2)	42309	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሰኔ 30/2001	126
ውክልና					128
47	አደራ ተቀባይ የሆነ ወገን በአደራ የተቀበለውን ዕቃ መመለስ ያለበት ለአደራ ሰጪው ወይም ይቀበልልኝ ብሎ ላመለከተው ሰው ስለመሆኑ	38289	ወ/ሮ ነጂሃ ድዋሌ ዋይስ እና አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ	ሰኔ 23/2001	129
48	መንግስታዊ የሆነ ተቋም በሚከሰስበትም ሆነ በሚከስበት ክርክር የሚቀርብ ሰነድ የኘሮቶኮል ቁጥር እንዲሁም ስለአቤቱታው ጽሁፍ ትክክለኛነት በሚመለከተው ኃላፊና በወኪሉ መፈረም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 80, 92, 93 እና 92(3)	43875	በወላይታ ዞን የቦዲቲ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና አቶ ወንድሙ ኃይሌ	ሐምሌ 16/2001	131
49	የዕቃ አስተላላፊ አካል እንደ አንኘር ሆኖ የሚቆጠረው ከወደብ የተረከበውን ዕቃ በራሱ ማንጓጓ ካንጓዘ ብቻ ስለመሆኑ ደንብ ቁ.37/90 አንቀጽ 2(1), 3(6),(7) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2251	37799	የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሐምሌ 29/2001	134

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የንግድ ህግ .ቁ. 683(3)				
50	በወኪል በኩል የሚፈፀም የመኪና ጭነት ውል በአስጫኙ እና በመኪናው ባለቤት መካከል እንደተደረገ የሚቆጠር ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 566 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2251	34621	ኒያላ ኢንሽራንስ አ/ማ እና አቶ ሐጎስ ገ/መድህን	ሐምሌ 30/2001	136
	የንግድ ሕግ				140
51	የንግድ ድርጅት በህግ አግባብ ለባለመብቶች ሊከፋፈል የሚችልበት ሁኔታ የንግድ ህግ ቁጥር 127	33954	ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ እና አቶ ዘውዱ ቢረዳ	ጥቅምት 20/2001	141
52	የእሽሙር ማህበር መፍረስ በንብረት ክፍፍል ረገድ የሚያስከትለው ውጤት	33470	ወ/ሮ እጅጋየሁ ታደሰ እና መገርሳ ጉደታ	ህዳር 2/2001	144
53	የጋራ ሀብት የሆነ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደሌላ ማናቸውም ንብረት ባለበት ሁኔታ በዓይነት ሊከፋፈል ወይም ደግሞ በሃራጅ ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 542	34945	ወ/ሮ መስታወት በላቸው እና አቶ ለገሠ ሣህሉ	ህዳር 2/2001	146
54	የንግድ መደብርን የተከራየ ወገን ይህንኑ የንግድ መደብር ለሌላ ሶስተኛ ወገን ያለአከራዩ ፈቃድ ማከራየት ስለመቻሉ የንግድ ህግ ቁጥር 145	31264	ወ/ሮ እመቤት መኮንን እና ወረዳ 20 ቀበሌ 29 አስ/ጽ/ቤት	ጥር 5/2001	148
55	በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161 የንግድ ሕግ ቁ. 124	34586	አቶ ያለው ድልነሳው እና እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ (አራት ሰዎች)	ጥር 28/2001	151
56	ቼክን አስመልክቶ ክስ በቀረበ ጊዜ የተከሰሰው ወገን የቀረበበትን ክስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት የሚያቀርበው ምክንያት ፈቃድ ሊያሰጥ የሚችል መሆን ያለመሆኑን አግባብነት ካላቸው ህግጋት አኳያ መታየት ያለበት ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 717 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 284, 285	43315	ብራንድ ኒው የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል እና አቶ መስፍን ታደሰ	ግንቦት 18/2001	154
	አእምሯዊ ንብረት				156
57	አንድን የሥነ-ጥበብ(ኪነ-ጥበብ) ሥራ ያለባለቤቱ ፈቃድ አርጅናሉ ወይም ቅጅው ለህዝብ እንዲታይ ማድረግ የኮፒ ራይት ህግ ጥሰት የሚያስከትል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1791, 1771(1), 1790, 2090-2123 አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀፅ 7	42253	መምህር ሙሉ ኃይለሥላሴ እና ዘመናዊ ማተሚያ ቤት	ሐምሌ 8/2001	157
	ልዩ ልዩ				160
58	የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዋቅር ባልተዘረጋባቸው ክልሎች የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ወክለው/ተክተው/ ክርክሮችን ማስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 139/1//ለ/,154/1/,153,140	21214	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ለማ ኩማ (ሦስት ሰዎች)	ህዳር 4/2001	161
59	• የጡረታ መዋጮ በመዘግየቱ ምክንያት				

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በአዋጅ ቁ. 345/95 መሠረት ተጨማሪ ክፍያ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ • የጡረታ መዋጮ በ2 ዓመት ውስጥ እንደተከፈለ የህግ ግምት ሊወሰድበት የሚችል የክፍያ ዓይነት ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ሠ) አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 7(3), 52(1),56	35391	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና አንበሣ ጫማ አ/ማ	ህዳር 25/2001	163
60	የጥብቅና ፈቃድን ለማግኘት በህጉ የተቀመጡት መስፈርቶች ራሣቸውን ችለው መታየት ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 8(1)	37375	አቶ ሸምሱ ከድር አህመድ እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር	ህዳር 11/2001	166
61	በከባድ የወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ እና በራሣቸው ወጪ ጠበቃ ለማቆም ያልቻሉ ግለሰቦችን በተመለከተ ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት የግለሰቦችን በጠበቃ የመወከል ህገ-መንግሥታዊ መብት መከበሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 13 (1)	37050	ሻምበል ሁሴን አሊ እና የሱማሌ ክልል ዐ/ሕግ	ታህሣሥ 30/2001	168
62	ከዘር የወረደ ርስት ነው በሚል የመሬት ባለቤት ለመሆን የሚቀርብ ክስ ህገ-መንግስታዊ ያልሆነና ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	38237	አቶ በርገና ሽፈራው እና እነ አቶ አብራሃም ሽፈራው(አራት ሰዎች)	ታህሣሥ 21/2001	171
63	በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍ/ብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት ለመወሰድ ብቃትና አግባብነት ያለው ስለመሆኑ	37184	የሰሜን ቀጠና ጉምሩክ እና እነ ቁስ ብርሃን ንዋይ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 9/2001	174
64	የመንግሥት መሥሪያ ቤት በጨረታ አማካኝነት የሸያጭ ውል አካሄዷል ተብሎ ሊገደድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1688(2), 3167(1), 1688(2), 3168	37163	የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን እና ህያብ ገ/መድህን ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ	ታህሣሥ 23/2001	179
65	አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ምንነት፣ የሚደረጉበት መንገድና ለአፈፃፀም የሚቀርቡበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3318, 3324, 3325, 3346, 1731 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 315, 319, 350, 357	38794	አቶ መኩሚል መሐመድ እና አቶ ሚፍታህ ከድር	መጋቢት 24/2001	182
66	አስተዳደራዊ የሆኑ መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ ካርታ እንዲሰጥ የሚወሰን ውሣኔ ተገቢ ስላለመሆኑ	39529	ቦሌ ክ/ከተማ የመሬትና ልማት አስተዳደር እና እነ ወ/ሮ ግምጃ በዳኔ (ስድስት ሰዎች)	ግንቦት 11/2001	186
67	ግምቱ ከብር 10,000 ብር በላይ ለሆነ የአፈፃፀም ክስ ሊከፈል የሚገባው ዳኝነት 25 ብር ብቻ ስለመሆኑ የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ. 177/1945 አንቀጽ 2(ሠ)	40752	እነ ወ/ሮ ኤክራም መሃመድ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘኪ መሐመድ	ሐምሌ 28/2001	189
68	ከፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ሠራተኞች የሚሰበሰብ የሥራ ግብር ምንም እንኳን ሥራው የሚካሄደው በክልሎች ቢሆንም ወይም ሠራተኞቹ የክልል ነዋሪዎች ቢሆኑም ገቢ የሚደረገው ለፌዴራሉ መንግስት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 96(3) አዋጅ ቁ. 33/85 አንቀጽ5(2)(ሐ) ደንብ ቁ. 109/96	40133	የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን እና በሶማሌ ብ/ክ/መ የፊደልቱ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ገቢዎች ጽ/ቤት	ሐምሌ 2/2001	191
አስረና ሰራተኛ					195

https://t.me/ethiopianlegalbrief

69	የማንባታ ዕቃዎች እጥረት አጋጥሟል በሚል የሚደረግ የሥራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 26,28,30	41385	ጊጋ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አነ ተረፈ ዘርጋው (ስድስት ሰዎች)	ጥቅምት 3/2002	196
70	የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት አድርጐ ከሚቀርብ ክርክር ጋር በተገናኘ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሣይሰጥ ከተጠየቁት ዳኝነት መካከል ወደ ሥራ የመመለስ ጉዳይ ላይ ብቻ ውሣኔ ከተሠጠና ሠራተኛው ወደ ሥራ መመለስ ሳይፈልግ ቢቀር ቀድሞ ዳኝነት በጠየቀባቸው ነገር ግን ውሣኔ ባላረፈባቸው ነጥቦች ላይ ዳኝነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3)	42361	ወ/ት ትዕግስት ንጉሴ እና ኤስ.ኦ.ኤስ ኢንፋንት ኢትዮጵያ	ጥቅምት 5/2002	198
71	በትርፍ ሰዓት በሌላ መሥሪያ ቤት ሰርተሃል በሚል ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ 377/96 አንቀፅ 27	42818	አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ እና ወ/ር ሙስታ ገዳ	ጥቅምት 10/2002	200
72	አሰሪ በግልፅ ባልፈቀደበት ሁኔታ በሁለት ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ መስራት ሠራተኛውን የማታለል ተግባር እንደፈፀመ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ)	41767	የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና አቶ አድማስ ደምሳቸው	ህዳር 8/2002	202
73	አሰሪ የእድገት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት እና መስኪያ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ በሠራተኞቹ መካከል በክፍያ ረገድ ልዩነት ማድረግ ስለመቻሉ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 14(1)(ረ) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት 42(1)(መ)	42923	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ነጃት አባስ	ህዳር 22/2002	204
74	ሥራውን በገዛ ፈቃዱ የሚለቅ ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት የሚችለው ቢያንስ የ5 ዓመት አገልግሎት ያለው እንደሆነ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(ሸ)	44410	ወ/ሮ ላይላ ረዲ እና ድሬ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግል ማህበር	ኅዳር 01/2002	207
75	በአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ "በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት" ወይም "በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" በሚል የተቀመጠው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 95/2/,97,96	47807	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ ፈንታው (ሁለት ሰዎች)	ታህሳስ 06/2002	210
76	አሰሪ ሠራተኞቹን በማስተዳደር ረገድ የሚፈፅማቸውን ስህተቶች በራሱ አነሣሽነት ሊያርም የሚችል ስለመሆኑ	45889	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን እና ሳሙኤል ቄለቦ	ታህሣሥ 20/2002	213
77	በክርስትና ሃይማኖት ተቋም ውስጥ በዲያቆንነት ሥራ ከማገልገል ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የሥራ ክርክር ጉዳዮች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ሊስተናገዱ የማይችሉ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	47806	የሆሀተሰማይ ቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና ዲያቆን አያሌው አዲሱ	ታህሣሥ 20/2002	215
78	በጡረታ የተገለሉና ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቋሚ ሠራተኞች የሚያገኟቸውን ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት መብት የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10	47469	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ስዩም ገብረዓዲቅ(ሃያ ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 15/2002	217
79	በሥራ ክርክር ጉዳይ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853 ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	47784	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አለምፀሐይ አያና	ታህሣሥ 20/2002	220

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 377/96 164(3) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853,1852				
80	በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት የሥራ ግንኙነት በአንቀፅ 30 መሠረት ሲቋረጥ አሰሪ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 30, 28(2)	49057	አስመላሽ እና ልጆቹ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ዮሐንስ እሸበል	ጥር 5/2002	223
81	የጡረታ መብት ያለው እና መደበኛ የጡረታ ዕድሜው ደርሶ የተሰናበት ሰራተኛ የስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/2(ሰ) እና (ሸ)	46276	ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት እናእነ ኃይሌ ይማም (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 11/2002	225
82	• አንድ ድርጅት በመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኞች የስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው የሚገባ ስለመሆኑ • ድርጅት ለዘለቄታው እንዲቆም የሚያደርግ ሁኔታ ሲከሰት ማስጠንቀቂያ ለሠራተኞች መሰጠት ያለበት ስለመሆኑ	42985	ውድ መጣስ ኑሮ አስመጪና ላኪ ድርጅት እና እነ አቶ ሁነኛው ሰጠ (አስራ አንድ ሰዎች)	የካቲት 25/2002	227
83	የጠብ አጫሪነት ኃይለ ቃልና ዛቻ አዘል ንግግር በሥራ ቦታ ላይ ማድረግ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብት ጥፋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ረ)	49958	ግዬን ትራቭልና ቱርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ዳንኤል አስፋው	የካቲት 12/2002	229
84	በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ለሠራተኛው ጥገኞች ስለሚከፈል ካሣ፣ ካሣው የሚከፈልበትና የሚሰላበት ሁኔታ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 110	40529	የህፃን ዮናታን ኑጋ ተሸገር ጠ/ጥ/ጋቡ ጌጤ እና አቶ ለገሠ አበራ	የካቲት 10/2002	231
85	በአሰሪና ሰራተኛ በኩል በአጠቃላይ ለፕሮጀክት ሥራ በሚል የተደረገ የሥራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አንቀጽ 10(1)(ሀ) መሰረት የተደረገ እንደሆነ ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሀ)	48648	የፃልቁ የትምህርትና የተቀናጀ የልማት ማህበር እናእነ አቶ ታጠቅ ደጀኔ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 24/2002	234
86	ሠራተኞችን ለማበረታታት በሚል የሚደረግ የደመወዝ (ጥቅማጥቅም) ጭማሪን መሠረት በማድረግ ጭማሪውን የሚፈቅደው መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ የሚጠይቀው መብት የሌለ ስለመሆኑ	47825	የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ) እና እነ አቶ ዘርዓየሁ ሰሜ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	236
87	አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ ከሚፈፅመው ጥፋት ጋር በተያያዘ ከሥራ ታግዶ ሊቆይ ስለሚችልበት ሁኔታ በህብረት ስምምነት ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96	47535	የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት እና አቶ እንግዉ ላቀው	መጋቢት 20/2002	238
88	• የአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አሰሪና ሰራተኛ ስምምነት ሊያደርጉባቸው የሚችሉበት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ጥፋትንና ጥቅምን በተመለከተ የተለያየ አቋም የያዘ ስለመሆኑ • አሰሪና ሠራተኛ በህብረት ስምምነታቸው ውስጥ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት በሚል የተስማሙበት ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 134(2), 27(1)(ሸ)	49750	በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/01 የመዝናኛ ክበብ እና አቶ ማስረሻ ሁሴን	መጋቢት 30/2002	240
89	አሠሪ የሠራተኛውን የሥራ ውል ያቋረጠበትን ምክንያት በፅሁፍ አለመግለፁ	49797	አልሀበሽ ሹገር ሚልስ ኃ/የተ/የግል ማህበር	መጋቢት 30/2002	242

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ብቻ ስንብቱ ህገ- ወጥ ነው ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2)		እና ተጋኔ ገ/ሃዋሪያት		
90	በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ውስጥ "እንደ ጥፋቱ ክብደት በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር መፈፀም" በሚል የቀረበው አባባል (አነጋገር) ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ)	50009	የአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል እና አቶ ዮናስ ጥላሁን	መጋቢት 6/2002	244
91	አሠሪና ሠራተኛ የሥራ ውል መቋረጥ ጋር በተያያዘ በሥራ ውሉ ላይ የሚያመለክቱት ሁኔታ የአሰሪና ሠራተኛ ህጉን እስካልተፃረረ ድረስ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀፅ 78 (1),87	50205	የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና አቶ ምናለ በሪሁን	መጋቢት 20/2002	246
92	የሥራ ውል በተቋረጠ ጊዜ አሰሪው ከሠራተኛው በህግ አግባብ የሚፈልገው/ የሚጠይቀው ዕዳ ያለ እንደሆነ ለሠራተኛው የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት ከመስጠት ባሻገር የሥራ መልቀቂያ (ክሊራንስ) ለመስጠት የማይገደድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀፅ 78 (1),87	48476	የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና አቶ ደረጀ መኮንን	ሚያዝያ 12/2002	248
93	ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የሚደርስበትን ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ወይም ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት በማለት ለመለየት የሚቻልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 101 (2)	49273	አቶ ደረጀ ውለታው እና ዋሊያ ሌዘርና ሌዘር ኘሮዳክትስ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሚያዝያ 27/2002	250
94	• አንድ ሰው በአፈፃፀም ሊገደድ የሚችለው በህግ አግባብ የተፈረደ ፍርድ ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ • በግልፅ ፍርድ ያላረፈበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378	50148	እነ አቶ ወርቁ ደረጀ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ አባርኪሮ ሁመድ	ሚያዝያ 4/2002	252
95	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ከሠራተኛው ጋር ያለው ግንኙነት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቢመለስ ችግር ውስጥ እንደሚወድቅ በአሠሪው ስለተገለፀ ብቻ ሠራተኛው ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት በሚል የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/	49931	የጎሽና እርግብ መለስተኛና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር እና አቶ ተሰማ ኃይሉ	ሚያዝያ 21/2002	254
96	የድርጅት መዋቅራዊ ለውጥ ያደረገ ተቋም በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መሠረት ሠራተኞቹን አዲስ በሚያወጣው የሥራ መደብ ላይ ተመርኩዞ የሥራ ምደባ ሊያከናውን የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28	50838	ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ኘሮጀክት እና እነ አቶ አማረ አበራ (ሰባት ሰዎች)	ሚያዝያ 12/2002	256
97	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪ ሠራተኛው የፈፀመውን ድርጊት መሠረት አድርጐ ለማሰናበት የሚችለው የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት የሆነው ነገር መከሰቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ ሰላሳ ቀናት ውስጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3)	45746	ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ በለጠ ጫላ	ሚያዝያ 6/2002	258
98	ሠራተኛ የተረከባቸውን ንብረቶች አላስረከበም ወይም አጉድሏል በሚል የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚጠይቃቸውን ተገቢ ክፍያዎች ሊጠይቅ አይችልም በሚል በአሠሪው የሚቀርብ ክርክር ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ	44405	ፊንፊኔ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ደጃ ደምሴ ጎበና	ግንቦት 19/2002	260

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 36,37,38				
99	ወደ ሥራ እንዲመለስ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነና በአሰሪው ችግርም ሆነ በሠራተኛው ፍላጎት በፍርዱ መሠረት ወደ ሥራ ለመመለስ ሠራተኛው ያልፈለገ ከሆነ ሠራተኛው የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ በምትክነት በሰጠው መብት መሠረት በመመለሱ ፈንታ ካሣ እንዲከፈለው አፈፃፀሙን ለያዘው ችሎት ጥያቄውን ባቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(3)	53064	አቶ ደሬሳ ኮቱ እና የአምቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን	ግንቦት 17/2002	263
100	በድርጅት ውስጥ የተከሰተ ተጨባጭ ችግርን ለመቅረፍና የድርጅቱን ትርፋማነት ለማስቀጠል በሚል በተመሳሳይ ሙያና ደረጃ ላይ ካሉ ሠራተኞች መካከል ተለይቼ ወደ ሌላ የሥራ መደብ ስለተዛወርኩኝ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ	50182	የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት እና አቶ አበበ ተፈራ ይልማ	ግንቦት 13/2002	265
101	የሥራ ውል የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ ነው በሚል ክርክር በቀረበ ጊዜ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም የሚኖር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 9	44218	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ታጁ አባጋሮ (ሃያ አንድ ሰዎች)	ግንቦት 13/2002	267
102	አንድ አሰሪ በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበትን ሰራተኛ ወደ ውጭ አገር ልኮ ስለሚያሳክምበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 124,105	46363	ሚሊኒ ኮንስትሩቶሪ ኤስ.ፒ.ኤ እና አቶ ትግሉ ፍሬህይወት	ግንቦት 19/2002	270
103	• ከአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጋር በተገናኘ ሁለቱ ወገኖች አዋጅ ቁ. 377/96 "ን" ወደ ጉን በማድረግ በሌላ አገር ህግ ለመዳኘት ስምምነት ያደረጉ በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ህግ ጥያቄን ያስነሳል በሚል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑ • አዋጅ ቁ. 377/96 የውጭ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ የበጎ አድራጎት ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/3/ /ለ/	50923	ፋውንዴሽን አፍሪካ እና አቶ አለሙ ታደሰ	ግንቦት 19/2002	273
104	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚነሣው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚሰላው የሥራ ቀናትን ብቻ በማስላት ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 163(2)	51912	የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና ወ/ሮ ሶፋኒት አጥናፉ	ሰኔ 7/2002	276
105	• በአሰሪ የተፈፀመው የሥራ ስንብት ህገ-ወጥ ቢሆንም ከሥራ ግንኙነቱ ፀባይ የተነሣ ከፍተኛ ችግር የሚፈጠር በሆነ ጊዜ ሠራተኛውን ወደ ሥራ ከመመለስ ይልቅ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ • የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀፅ 43(3) በአንድ በኩል የሠራተኞን የሥራ ዋስትና በሌላ በኩል ደግሞ የኢንዱስትሪን ሰላም በማመዛዘን ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ	55189	አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል እና አቶ ዘላለም መንግስቱ	ሰኔ 30/2002	279
106	በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ‹‹... ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት...›› በሚል የተመለከተው ሃረግ ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(3)	53358	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ ጥላሁን ኩማ	ሰኔ 18/2002	281

https://t.me/ethiopianlegalbrief

107	አንድ የሥራ ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተደረገ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9,10	43160	እነ እንደገና ተሾመ (ሁለት ሰዎች) እና ኒው ጀኔራሽን ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ነቀምቴ ቅርንጫፍ	ሰኔ 22/2002	283
108	በማናቸውም ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ ሠራተኛው ያልወሰደው የዓመት እረፍት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 77(5) ,24(2)	52459	እነ ወ/ሮ ሙሉ ታደሰ እና አለሙ መራ ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ብረታ ብረት ሥራ ድርጅት	ሐምሌ 16/2002	285
109	በክረምት ወቅት የማስተማር ሥራ እንዲሠራ የሚያዝ ግልፅ ደንብ ወይም መመሪያ የሌለ እንደሆነ ወይም አስተማሪው በክረምት ወራት ለማስተማር የገባው የውል ግዴታ (ስምምነት) በሌለ ጊዜ በክረምት ወቅት ሥራን ለመስራት ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ከሥራ ሊሰናበት የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 13(1)	45170	የቅድስት ማሪያም አፀደ ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እና መ/ት ሲሳይ ሙሉጌታ	ሐምሌ 8/2002	287
	የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት				289
110	በክርክር የግድ ተካፋይ ሊሆኑ የሚገባቸው ወገኖች እና የፍ/ቤት ሚና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 39,(1),40(2)	43424	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና እነ አቶ መስፍን /ስምንት ሰዎች/	ጥቅምት 10/2002	290
111	የቃል ክርክር እንዲሰማ በተቀጠረበት ዕለት ግራ ቀኝ የሆኑ ወገኖች ያልቀረቡ እንደሆነ መዝገቡ መዘጋት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 69(2)	43410	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል	ህዳር 30/2002	293
112	አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ይህንን ፍሬ ነገር በማንኛውም የማስረጃ ዓይነት ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ	47551	ንግድ ማተሚያ ድርጅት እና አቶ ካሱ ሙላት	ታህሣሥ 6/2002	295
113	ጣልቃ በመግባት በክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጠይቆ የተፈቀደለትና የጣልቃ ገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባው ይህን ባለመፈፀሙ መብቱ ከተሰረዘበት በኋላ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41,358	40229	ወ/ሮ ኸይሮ መሐመድ እና እነ ወ/ሮ መዲና በያን (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 15/2002	297
114	በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ተከራካሪ ወገን ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አቤቱታው ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 78,69,72	43731	ሲ.ጂ.ሲ.አቪርሲስ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ሊሚትድ እና ሰለሞን እንዳለ	ታህሣሥ 8/2002	299
115	• በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 መሠረት መዝገብ ሊዘጋ የሚችልበት አግባብ • ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ዳኝነት የሚጠይቁበትን ፍሬ ነገር በአግባቡ ከገለፁ ትክክለኛውን የህግ ድንጋጌ አለመጥቀሳቸው መብታቸውን የሚያስቀር ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280,69(2), 70(መ), 71(2)	39581	አቶ ውብሸት ካሣዬ እና የኢትዮጵያ ማዕድን ሃብት ኮርፖሬሽን	ጥር 25/2002	302
116	ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሷቸውን የሰው ማስረጃዎች ሊሰውጡ (ሊቀይሩ) የሚችሉበት አግባብ	45984	ኘሮፌሰር ረዳ ተ/ኃይማኖት እና አቶ ልመንህ ተፈራ	ጥር 26/2002	304

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223/2/,234				
117	የክርክር ጭብጥ የሚመሰረተው ከሳሽ የሚያቀርበውን ክስና ማስረጃ በተከሳሽ የቀረበውን የመከላከያ መልስና ማስረጃ እንዲሁም ፍ/ቤቱ የቃል ምርመራ ሲያደርግ የሚያገኘውን ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241,248	47252	ወ/ሮ ፑሽፓላት ጆሴፍ እና አቶ ሠይፈ ጎሣዬ	የካቲት 26/2002	307
118	ዳኝነት እንደገና እንዲታይ (Review of judgement) በሚል የሚቀርብ አቤቱታ አስቀድሞ በተሰጠ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የተባለበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ ውድቅ ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)(ሀ),(ለ)	43821	ወ/ሮ ትርሃስ ፍስሀዬ እና ወ/ሮ ዘነበች በሪሁን	ጥር 5/2002	310
119	ዳኝነት በድጋሚ እንዲታይ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ላይ በተሰጠ ትእዛዝ/ብይን ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6(3)(4)	42871	የቀድሞ ወረዳ 07 ቀበሌ 32 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ጆሮ ዋቅጅራ	ጥር 12/2002	315
120	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 421 መሠረት ክስ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418,421	37214	አቶ ተስፋዬ አለሙ እና እነ ሐጂ ይማም መዘይን(ሦስት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	318
121	በፍ/ብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ	44634	አቶ ታዬ ሆላዕና እና ወ/ሮ መሠረት ወልደየስ	የካቲት 22/2002	320
122	ፍ/ቤቶች ለቀረበላቸው ክስ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ በቂ በሆነ ማስረጃ በተገነዘቡ ጊዜ ክሱን ሊዘጉት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280	45371	የገነተ-ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማህበር በኩር ሰንበቱ እና እነ አቶ ማሞ ተሠማ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 8/2002	322
123	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216 መሠረት በድጋሚ ክስ እንዳይቀርብ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216(3)	36776	መብራቱ፣ተ/ማሪያም፣ገ/ማሪያም የሸርክና ማህበር እና አቶ መብራቱ ዓንዳይ	መጋቢት 7/2002	324
124	ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር በዋናው ጉዳይ ላይ የራሱን ውሣኔ ካሣለፈና የበላይ የሆነ ፍ/ቤት ደግሞ የይግባኝ ውሳኔውን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በደፈናው በማፅናት የሚሰጠው ውሣኔ የተከራካሪ ወገን የይግባኝ መብት የሚያጣብብና የሥነ-ሥርዓት ህግ ደንብን የሚጥስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341,342,343	44545	ክፍሉ መሓሪ እና በላይ ከመላ	መጋቢት 7/2002	326
125	የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘ ባለገንዘብ ባንክ መብቱ በይርጋ አስካልታገደ ድረስ የያዘውን ንብረት በጨረታ ለመሸጥ የሚገደድበት ተለይቶ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 97/90 አዋጅ ቁ. 216/92 አንቀፅ 2 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394 - 449	44883	አቶ ፈንታ ምህረቱ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	መጋቢት 8/2002	328
126	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጉም የሚችልበት አግባብ	39799	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ ገነት ስዩም	መጋቢት 21/2002	331
127	• በተከራካሪ ወገኖች የሚቆጠሩ ማስረጃዎች ሳይሰሙ የሚቀሩት ለተያዘው ጉዳይ	43845	የገቢዎችና ጉምሩክ	መጋቢት 20/2002	334

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አግባብነት የሌላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ • ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች የቆጠሩትን ማስረጃ ሳይሰሙ ወደ ጐን በመተው አቤቱታቸውን በበቂ ማስረጃ አላስረዱም በሚል የሚደርሱበት መደምደሚያ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ		ባለስልጣን እና ጌታይዳ ኃ/የተ/የግል ማህበር		
128	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208 መሠረት በሥር ፍ/ቤት የተደረገ እርማትን መነሻ በማድረግ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ለመለወጥ የሚያስችለው የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 208,209,320,(1) ,348(1)	44931	ወ/ሮ ሰዓዳ ኢድሪስ እና አቶ ረሺድ ቡባ	መጋቢት 20/2002	337
129	የፍ/ቤትን ክብርንና የዳኝነት ሥርዓቱን መልካም አመራር ለማስጠበቅ ሲባል የማንኛውም ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ በችሎት ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 480	48237	ወ/ሮ ሰኢዳ ሁሴን ይመር ተጠሪ፡የለም	መጋቢት 6/2002	339
130	ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ወደ ጉዳዩ ሥረ-ነገር ገብቶ ተከሳሽ የሆነን ወገን በሌለበት ባለዕዳ የሚያደርግ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ተከሳሹ በአግባቡ ስለመጠራቱ ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 97, 95(3)	50022	5 ብራዘርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ዓብደላ ኢብሮ ዩሴፍ	መጋቢት 29/2002	341
131	የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በውሳኔው ወቅት ንብረቱን በእጁ አድርጐ የሚገኘው ወገን የንብረቱን ስመ ሐብት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን አዛውሮ ሲገኝ ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት ስለሚገባው አካሔድ	45038	እነ ወ/ሮ አለሚቱ ጓዱ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ አስረስ አህመድ	መጋቢት 23/2002	343
132	• ሐሰተኛ ቃል ተሰጥቷል በሚል ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 መሠረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ሊሰጥ የሚችልበት አግባብ • በአንድ የወንጀል ድርጊት ነፃ የተባለ ሰው እንደገና ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጐ የሚቀጣበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 481 የወንጀል ህግ ቁ. 452(1)	43005	እነ አቶ አውግቸው እርገጤ (ሦስት ሰዎች) ተጠሪ፡የለም	ሚያዝያ 19/2002	345
133	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 መሠረት ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ለሰጠ ፍ/ቤት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6	45839	ወ/ሮ ይርጋለም ከበደ እና እነ ወ/ሮ ዕጌ ሚካኤል (አምስት ሰዎች)	ሚያዝያ 5/2002	348
134	በፍ/ብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 256, 345, 327	39853	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር (ሁለት ሰዎች)	ሚያዝያ 21/2002	350
135	አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ እንደሆነ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(3), አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10	41526	ትራንስ አፍሪካ ትራንስፖርት አ.ማ እና ሙሉ ኤሌክትሮኒክስ ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ግንቦት 2/2002	353
136	ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ የተሰማሙና ይዜንኑም ስምምነት ለፍ/ቤት በማቅረብ ያስፀደቁ በሆነ ጊዜ	52752	እነ ከድር ሐጂ ሁሴን (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ አሚን ዑስማን	ሰኔ 16/2002	355

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስምምነቱ እንደ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተቆጥሮ መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277		(ሁለት ሰዎች)		
137	ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው አቤቱታ የክስ ምክንያት አለው ወይም የለውም ብሎ ለመወሰን በክስ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሽ የሆነው ወገን የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ህግ ይፈቅድለታል ወይስ አይፈቅድለትም የሚለውን ጥያቄ መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ	45247	አቶ ደጀኔ በላቸው እና አቶ ነስሩ አወል	ሰኔ 17/2002	358
138	ሁለት ሰዎች ተጣምረው በተከሰሱ ጊዜ አንደኛው ወገን ጉዳዩ በሌለበት ከታየ በኋላ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተፈቀደለት እንደሆነ ሌላኛው ተከሳሽ አስቀድሞ ያነሳቸውን መቃወሚያዎች በድጋሚ ልታነሣና ልትከራከር አትችልም ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	49857	ወ/ሮ ፈትለወርቅ መንገሻ ፋንታ እና ወ/ሮ በላይነሽ ወ/ኪዳን	ሰኔ 30/2002	361
139	በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሽ ቀርቦ ክርክሩን ባለማ ጊዜ ስለመሆኑና ድንጋጌው የካሣ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 235(2),83	48632	አቶ መልሳ በየቻ እና አቶ ደበሌ በየቻ	ሰኔ 14/2002	363
140	ክስ የቀረበበት ወገን ክሱን ለማስተባበል የሚቆጥራቸው ማስረጃዎችን ተቀብሎ አለመስማት የመከላከል ህጋዊ መብትን የሚያጣበብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ5 223, 234, 137, 249, 256	49660	እነ መንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ት/ቤት (ሁለት ሰዎች) እና መምህር ሲሳይ ደጀኔ	ሰኔ 22/2002	365
141	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1) መሠረት በድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻለው በቀደመው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑና የተከራካሪ ወገኖች አንድነት በመኖሩ ብቻ ሣይሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	52525	ወ/ሮ የትምወርቅ ሰብስቤ እና አቶ ሽዋረጋ ደመቀ	ሰኔ 29/2002	368
142	የሥር ፍ/ቤት በመቃወሚያ ላይ የሰጠውን ውሣኔ የሚለውጥ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠ እንደሆነ በግራ ቀኝ ወገኖችን በኩል የሚቀርቡ የፍሬ ነገር ክርክሮችንና ማስረጃ በአግባቡ ለመስማት ብሎም የተከራካሪዎችን ይግባኝ መብት ላለማጣበብ ሲባል ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለስ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341(1)	43331	አቶ ገመቹ ቡቻላ እና አቶ በቀለ ኩማ (ቡቻላ)	ሐምሌ 19/2002	370
143	ስልጣን ለሌለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብና ክርክር ማካሔድ የይርጋ ጊዜን የሚያቋርጥ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም የሰበር ችሎት በተቃራኒው የሰጠው የህግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ።) አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 138, 147, 164(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9, 23,(1) (ለ) ,231,(1)(ለ), 278(3) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851 (ለ),1852(1)	36730	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አማረ ገላው	ሐምሌ 30/2002	372

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀፅ 2(4)				
144	• በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከሣሽ ለሆነ ወገን ከፍ/ቤት የሚላከውን መጥሪያ ለተከሳሹ ሊደርስ የሚችልበትን የተሻለ አማራጭ መንገድ በመለየት ሊላክ የሚገባ ስለመሆኑ • የመኖሪያ አድራሻው በግልፅ ለሚታወቅ ተከሳሽ ፍ/ቤቱ የሚልከውን መጥሪያ በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ብቻ እንዲለጠፍ በማድረግ ተከሳሹ አልቀረበም በሚል በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ • መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው ያልተደረገ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሣኔ እንዲነሣለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 105(1), 78,	50376	ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ገሰሰ እና በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/08 አስተዳደር ጽ/ቤት	ሐምሌ 12/2002	378

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
		ቤተሰብ			1
1	በጋብቻ ውል ላይ ባልና ሚስት “መተዳደሪያችን” ነው በሚል ያመለከቷቸው ንብረቶች የጋራ ንብረት ተደርገው የሚቆጠሩ ስለመሆናቸው	38544	አቶ ብሩክ ኃ/እየሱስ እና ወ/ሮ ፋናዬ አበበ	ጥቅምት 5/2002	2
2	• በጋብቻ ላይ የተደረገ ጋብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው (void ab initio) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ • የጋብቻ ውል ተጋቢዎች ንብረታቸውን በተመለከተ ጋብቻው የሚያስከትለውን ውጤት ስምምነት የሚያደርጉበት ስነድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 42,44,33,11	39408	አርጋው አባቹ እና የወ/ሮ አስቱር አበጋዝ ወራሾች (ስድስት ሰዎች)	ጥቅምት 24/2002	5
3	የውርስ ሀብትድርሻ ክፍፍል ጥያቄ በይርጋ የሚታገድበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080(3)	40418	ተስፋዬ ሞላ እና እነ እሸቱ ምነ (ሦስት ሰዎች)	ጥቅምት 10/2002	7
4	አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43	42682	እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ በላይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ	ጥቅምት 10/2002	9
5	ፀንቶ ባለ ጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት በጋብቻ ውስጥ ባል የሆነው ወገን ስለመሆኑና የዚህን ሰው አባትነት ለመቃወም የሚቻልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 144,126,167,168,173	40624	እነ ወ/ሮ መብራት ታደሰ (አራት ሰዎች) እና አቶ ኤፍሬም ዘውዴ	ጥቅምት 12/2002	11
6	የጋራ የሆነን የውርስ ሀብት ክፍቃዱ ውጪ እንዲሸጥ የተደረገበት ወራሽ ከሽያጩ ዋጋ ድርሻውን ለማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1266,1060(1)	41857	አሕመድ ሑሴን እና እነ ወ/ሮ የኔዓለም ተመስገን (ሦስትሰዎች)	ጥቅምት 24/2002	14
7	አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 43	42682	እነ ወ/ሮ ፋንታነሽ ሲሳይ (ሦስት ሰዎች) እና ሞላ ደምሴ	ጥቅምት 10/2002	17
8	ከጋብቻ በፊት የግል የነበረ ንብረት በተጋቢዎች የጋብቻ ውል መነሻነት የጋራ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ	42766	እነ ወ/ት ሠናይት ኃ/ማሪያም እና ወ/ሮ አበበች ወርቁ	ጥቅምት 10/2002	19
9	ልጅነትን በማረጋገጥ በፍ/ቤት የሚሰጥ ውሣኔ የህግ ግምት የሚፈጥር እንጂ አስገዳጅነት ያለው እና የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ መወሰድ የሌለበት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,155,156,157	42648	ወ/ሮ ዘነበች በያን እና ወ/ት ብርቅነሽ ከበደ	ታህሣሥ 6/2002	21
10	አባትነት በህግ አግባብ ሊታወቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126,1(1),(2),128(1),130(2),125,106(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 35(2)	44612	ወ/ሮ ዘውዴ ወ/ጊዮርጊስ እና ወ/ት ኤልሣቤጥ ኪዳኔ	ጥቅምት 10/2002	23
11	• በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት	38533	እነ ወ/ሮ ጽጌ	ህዳር	27

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አግባብ • የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1),1000(2),1060,1062		ወልደመስቀል (ስድስት ሰዎች) እና አቶ ስዩም ክፍሌ	8/2002	
12	ልጅነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 156,168,158,169	42569	እነ የዳግማዊ ታዲዩስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ (ሁለት ሰዎች) እና የሃና ታዲዮስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ	ታህሣሥ 212002	30
13	ኑዛዜ ሊተረጐም የሚገባው ቃላቶቹና መልዕክቱ ግልፅ ሣይሆን ሲቀር ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 810(2)	47487	አቶ ሐይለራጉኤል ደበላ እና እነ ወ/ሪት አለምፀሐይ ፈለገ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 27/2002	33
14	የስጦታ ውል ሊተረጐም የሚገባው በውሉ ውስጥ የሚገኝን አንድ ሃረግ ነጥሎ በማውጣት ሳይሆን የውሉን አጠቃላይ ይዘት በመመልከት ስለመሆኑ	41893	ወ/ሮ ዮዲት ኃይሉ እና እነ ወ/ሪት ገነት አረጋይ (ሦስት ሰዎች)	ታህሣሥ 21/2002	36
15	የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3)	47957	እነ አቶ ተፈሪ ሐጐስ (ሦስት ሰዎች) እና አቶ ተስፋይ ገ/እግዚአብሔር	ጥር 5/2002	39
16	• የስጦታ ውል ገደብ ያለበት ወይም ግዴታ የተጣለበት እንደሆነ በውሉ ውስጥ የተመለከተው ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ፈራሽ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ • በፍ/ብ/ህ/ቁ. 244(1) ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ በስጦታ ውል ውስጥ የተመለከተ ግዴታ አልተፈፀመም በሚል ውሉ እንዲፈርስ ሲጠየቅ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2452(1),2464(1),2441(1)	42346	እነ አቶ ፍስሐ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ አለምነሽ ፍስሐ	የካቲት 9/2002	41
17	የጉዲፈቻ ስምምነት የሕፃናትን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 195(2)	44101	ሚስስ ፍራንሲዊስ ፖስተር እና እነ ሚ/ር ዱክማን ቬኖ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 24/2002	44
18	የውርስ ንብረት በሆነ ቤት ላይ ድርሻ አለን የሚሉ ወገኖች ንብረቱን ህጋዊ የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ይዞ ከነበረ ሰው በመግዛት ስመ ሀብቱን ወደራሱ ስም አዛውሮ የሚገኝን ሰው ለመጠየቅ የማይችሉ ስለመሆኑ	46527	ወ/ሮ ገነት በቀለ እና ወ/ሮ ትዕግስት አሰፋ	የካቲት 24/2002	48
19	ከውርስ ጋር በተያያዘ በቤት ላይ ህጋዊ መብት የሌለው ሰው ሽያጭ አከናውኖ ሲገኝ ትክክለኛው ባለሃብት መብቱን ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጐ የገዛውን ገዥ ሣይሆን ሻጩን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 997,2882, 2884,1060(1),1266	47378	አቶ አለማየሁ ከተማ እና እነ ወ/ሮ ላቀች አይተንፍሱ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 24/2002	50
20	ኑዛዜ በፍ/ቤት መፅደቁ በንብረት ላይ ያለ የባለቤትነት መብትን የሚያረጋግጥ ስላለመሆኑ	42482	እነ አቶ ፍሬዘውድ ተካ ጐጂ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሰለሞን ኃ/ማሪያም	የካቲት 3/2002	53
21	የልጆች ቀለብ አከፋፈል ሁኔታ ጋር በተያያዘ ክፍያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ	45819	አቶ ካሣ ፋንታ እና ወ/ሮ እስካዳር ግጨው	የካቲት 12/2002	55
22	በትዳር ወቅት የተወሰደ ብድር የአንደኛው ተጋቢ ፈቃድ የሌለበት ቢሆንም ፈቃዱን ያልሰጠው ተጋቢ የብድር ስምምነቱ እንዲፈርስ	45202	አቶ ድንቁ ወርዶፋ እና	መጋቢት 8/2002	57

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ያላደረገ እንደሆነ ወይም ደግሞ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን ማስረዳት ያልቻለ ከሆነ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(መ)		ወ/ሪት ኤደን ድንቁ ወርዶፋ		
23	በተጭበረበረ መንገድ ወራሽነትን አሳውጆ የውርስ ንብረት አካል የሆነን ቤት ስመ ሃብት ወደ ራሱ አዙሮ የሚገኝ ሰው ጋር የሽያጭ ውል በተደረገ ጊዜ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሚል ትክክለኛ ወራሾች የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ህ/ቁ. 2882, 2884, 997	45370	እነ አቶ ዳንኤል አበበ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሙሉ ወልደየስ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 21/2002	61
24	የስጦታ ውል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠሩ 10 (አስር) ዓመታት ውስጥ ለአፈፃፀም ያልቀረበ እንደሆነ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676(1),1845	42691	አቶ አደፍርስ በቀለ እና አቶ ይቁም በቀለ	መጋቢት 22/2002	64
25	• በውርስ ሕግ ውስጥ የተመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች ሊተረጐሙ የሚችሉበት አግባብ • የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተ ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996,1000(1)1002,1060,1062	44237	እነ ወ/ሮ ሙሉሸዋ ቦጋለ (አራት ሰዎች) እና አቶ መስፍን ቦጋለ	መጋቢት 20/2002	66
26	ሞግዚት የሆነ ሰው በሞግዚትነት የሚያስተዳድራቸውን ልጆች ሀብት የሆነን ንብረት ለልጆቹ መልካም አስተዳደግ ሲል ሊሸጠው የሚችል ስለመሆኑ የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ቤተሰብ ህግ አንቀፅ 292	46490	እነ ወ/ሮ ቦጋለች ደባልቄ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ መሠረት በለጠ	መጋቢት 21/2002	69
27	በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የተደረገ የሽያጭ ውል በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አለመፍረሱ ስለሚያስከትለው ውጤት	51295	አቶ ዮሐንስ ጡእማይ እና ወ/ሮ ምህረት ገብሩ	መጋቢት 6/2002	72
28	ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ባለስልጣን ፊት የሚደረግ ኑዛዜ በህግ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አሟልቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 882	49851	ወ/ሮ ታሪኳ አበበ የህፃን ሮቤል ንጉሤ ሞግዚት ተጠሪ፡የለም	ሚያዝያ 4/2002	75
29	ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ የሆነ ሰው እና ከህግ ውጪ ከውርስ የተነቀለ ያለኑዛዜ ወራሽ የውርስ ሃብትን ሊከፋፈሉ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ 939(3) ,850,,911(1) 912(1)	43069	አቶ አማረ ረታ እና አቶ ሰለሞን ካሣዬ	ሚያዝያ 6/2002	78
30	የጉዲፈቻ ውል እንዲፈርስ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 195(1),(2)	52691	እነ ቤተ ዛታ ችልድረንስ ሆም አሶሴሽን (ሦስት ሰዎች) ተጠሪ፡የለም	ሚያዝያ 22/2002	81
31	ኑዛዜ መኖሩን የማስረዳት ሸክም (ግዴታ) የተጠቃሚዎች ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 896,897	53279	ወ/ሮ ትእግስት ግርማ የእነ አቤል ወርቁ ሞግዚት እና አቶ ኤፍሬም መንግስቱ	ሰኔ 8/2002	84
32	በኑዛዜ የውርስ ሀብት ክፍፍል መደረግ ጋር በተያያዘ ወራሽ የሆነ ወገን ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ሀብት መጠን ከአንድ አራተኛ በታች እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑ	50901	ወ/ሮ እልፊ ኃይሉ እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ደበሌ	ሰኔ 10/2002	87

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ካልተረጋገጠ በስተቀር ኑዛዜውን እንዲፀና በማድረግ የተናዛዡን ፍላጐት ማክበርና መጠበቅ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 910, 913 1123(1)		(ሦስት ሰዎች)		
33	በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ለማስረዳት የሚችሉት በግንኙነቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብቻ ናቸው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 98,99,106	46613	ወ/ሮ ኑኑ ሽህሞሎ እና ወ/ሮ አሰገደች ጫኔ	ሰኔ 24/2002	91
34	በተከራካሪ ወገኖች ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ ፍ/ቤቶች በግልፅ በመቀበል ወይም ባለመቀበል ወሣኔ ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ	51866	ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለማየሁ እና ወ/ሮ አባለች ደበበ	ሐምሌ 2/2002	94
35	ክሱንደሚኒየም ቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ በተደረገ ምዝገባ የተነሣ የቤት ዕጣው የወጣው ብሎም የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው በጋብቻ ወቅት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ለቤቱ መገኘት ምክንያት የሆነው ተጋቢ ቤቱ የግል መሆን አለበት በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(2)	51893	እንዳልካቸው ዘለቀ እና ወ/ሮ ብዙዓለም መንግስቱ	ሐምሌ 8/2002	96
36	በፍ/ቤት የተሰጠ የኑዛዜ ወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የውርስ ሃብት ማጣራት ሳይደረግ የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ሊሰረዝ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	50836	ወ/ሮ ቅድስት ተካ እና ወ/ሮ የኔነሽ ተካ	ሐምሌ 13/2002	99
37	ከውርስ ሃብት ክፍፍል ጋር በተያያዘ ተጠቃሚው በኢንሹራንስ ውል ላይ ባልተገለፀበት ጊዜ የሟች ባል ወይም ሚስት የኢንሹራንስ ገንዘቡን ከወራሾች ጋር ሊካፈሉ የሚችሉበት አግባብ የንግድ ህግ ቁጥር 705,701(1)(ሀ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 827	44561	ወ/ሮ ገነት በላይ እና አቶ ያፈት ተክሉ	ሐምሌ 28/2002	101
38	ከውርስ ሃብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የውርስ ሃብቱን በእጅ አድርጐ በመገልገል ላይ ያለ ተከራካሪ የሆነ ወራሽ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት በጋራ ይዞ የቆየ ሰው ላይ የሚያነሳው የውርስ ጥያቄ በይርጋ ታግዷል ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	44025	እነ ወ/ሪት ፀሐይ ሐይሌ (አራት ሰዎች) እና ወ/ሮ ፈልቃ ቤኛ	ሐምሌ 22/2002	110
39	ወራሽ የሆነ ወገን በውርስ ሃብት ክፍፍል ድርሻው ላይ ከሩብ የበለጠ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለፅ አውራሽ ባደረገው ኑዛዜ መሠረት ክፍፍል እንዳይፈፀም መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1123(1)	47622	ወ/ሮ ትዕግስት ነጋሽ እና እነ ወ/ሮ መንበረ ስላሴ ተሸሌ (አምስት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2002	112
40	የምትክ ወራሽነት ተጠቃሚዎችን ስለመለየት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842,843,844(3)	45587	እነ ወ/ሮ አተረፈች ዘውደ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘውዱ ወሰኔ	ሐምሌ 29/2002	115
41	በተዘዋዋሪ መንገድ ተወላጆን ከውርስ ያለ በቂ ምክንያት መንቀል የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 938,842,915	42546	አቶ ተስፋልደት ኪዳኔ እና እነ ወ/ሮ ዘሀበ ይመር (ሦስት ሰዎች)	ሐምሌ 28/2002	118
ውል					123
42	በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ እስከ አሥር ዓመት ድረስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058	44800	አቶ አብዱራዛቅ ሐሚድ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ጥቅምት 05/2002	124
43	ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነትና የመተማመን ግንኙነት	42897	አቶ አየለ ሐብተየስ እና	ህዳር	127

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	መሠረት በማድረግና ጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ልቦና ሊተረጐም የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1732(1)		እነ ሚ/ር ኖቼራ ጃክርሎ (ሁለት ሰዎች)	10/2002	
44	ለጨረታ ማስከበሪያ በሚል የሚያዝ ገንዘብ ጨረታውን ባዘጋጀው አካል ሊወሰድ የሚችለው ተወዳዳሪው ጨረታውን ባሸነፈው መጠን ሆኖ በጨረታው መሠረት ውል ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ	40947	አቶ መዝገቡ መድህኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር	ህዳር 15/2002	131
45	ተከራካሪ ወገኖች ባላሰቡበት ሁኔታ ፍ/ቤት የውል አፃፃፍ ሥርዓትን (ፎርማሊቲን) መሠረት በማድረግ በግራ ቀኝ ወገኖች መካከል የተካሄደን ውል ፈራሽ ነው በሚል የሚሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1808(2)	43825	የህፃን ኮከቤ ተረፈ ሞግዚትና አስተዳዳሪ እና እነ አቶ ኢየሌው ካሳዬ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 6/2002	133
46	• የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) ለባንኮችና ለደንበኞቻቸው መብት ልዩ ጥበቃ የሚያደርገው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2473(2) ድንጋጌን ዋጋ በሚያሳጣ መንገድ ተፈፃሚ ሊሆን የማይገባ ስለመሆኑ • የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2026(1) በባንኮችና በሌሎች አበዳሪ ተቋማት እና ደንበኞቻቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ተፈፃሚነት የሌለው የህግ ድንጋጌ ስለመሆኑ • ባንኮች ለደንበኞቻቸው ያበደሩትን የብድር ወለድ ያልተከፈለ መሆኑን በሰው ምስክር፣ የሰነድና ሌላ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(1) ስር የተደነገገውን የህሊና ግምት ለማስተባበል የሚችሉ ስለመሆኑ	29181	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ልየው ቸኮል (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 20/2002	135
47	በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2024/ረ/ መሰረት እንደተከፈለ ሊቆጠር የሚችለው በብድር የተሰጠ ገንዘብ ሳይሆን የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ ክፍያ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024	35758	እነ አቶ ገብረመድኅን አየናቸው (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሰብስቤ ኃይሌ	ታህሣሥ 20/2002	142
48	የወለድ አግድ ውል ህጋዊ ነው ሊባል የሚችለው የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መቋቋምን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በመከተል የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑና በዚህ መሰረት ያልተደረገ መሆኑ ውሉን ፈራሽ ሊያደርገው የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3118,3045,3052	45422	እነ አቶ ፈታኒ ባየህ (ሰባት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ አስራት ባየህ (ሦስት ሰዎች)	ጥር 13/2002	147
49	የስልክ አገልግሎት ከማግኘት ጋር በተያያዘ በአገልግሎት የክፍያ መጠን ላይ በአገልግሎት ሰጪውና በአገልግሎት ተቀባዩ መካከል አለመግባባት በተፈጠረ ጊዜ የተጠየቀው የአገልግሎት ሒሳብ በእርግጥም ስልኩን በይዞታው ስር አድርጐ የሚጠቀምበት ወገን በተገለገለው መጠን የተመዘገበ ስለመሆኑ በባለሙያ እንዲጣራ በማድረግ እልባት መስጠት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1732	48967	አቶ ሳዲቅ ሐሰን እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2002	151
50	መዋዕለ ነዋይን በማፍሰስ ግንባታን ለማካሄድ የከተማ ቦታን ከመንግስት ተረክቦ ግንባታን በተገቢው ጊዜ ለማጠናቀቅ አለመቻል ሊያስከትል የሚችለው ውጤት የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ደንብ ቁ. 41/97 አንቀፅ 8(3) የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ አዋጅ ቁ. 51/94	46052	ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ እና የቦንጋ ማዘጋጃ ቤት ከፋ ዞን	ጥር 19/2002	154
51	ከቤት ኪራይ ውል ጋር በተያያዘ የኪራይ	46394	ወ/ሮ ስንቁ መስፍን እና	የካቲት	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ውልን ለማቋረጥ በቂ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ተከራይ የሚፈፅማቸው የግንባታ አይነቶች የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2953,2954,1732		የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	11/2002	157
52	ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች ወስድን አስመልክቶ በውሳኔው ካመለከቱት ሃሳብ ውጪ የራሱን ስሌት መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1731,2478	45559	የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (አ.ማ) እና እነ የአቶ ኃይሉ ፈይሳ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	160
53	ከሽያጭ ጋር በተያያዘ ውል ሲመሰረት ጉድለት የነበረበት መሆኑ ቢረጋገጥም ከውሉ መመስረት በኋላ በተሸጠው ንብረት ላይ ተዋዋይ ወገኖች ተጨማሪ ግንባታ ያካሄዱና ወደ ነበሩበት ለመመለስ አዳጋች ሁኔታ ያለ መሆኑ ከታመነ ውሉ ሊፀና የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1)	47800	ወ/ሮ እመቤት ደርበው እና አቶ ታደሰ ሰዳማ	የካቲት 25/2002	162
54	ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚቆጠር የኪራይ ውል አከራይ የሆነ ወገን ለተከራይ ማስታወቂያ በመስጠት ምክንያቱን መግለፅ ሳያስፈልገው የኪራይ ውሉን ሊያቋርጥ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966(1)	40336	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የወ/ሮ አሰገደች ካሣሁን ወራሽ ሄኖክ ሣሙኤል	መጋቢት 22/2002	164
55	በሌላ ሰው ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠንና ባደረሰው ጉዳት መጠን ኪሣራ ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162	43381	ወ/ሮ ፎዚያ ሁሴን እና አቶ ውብሸት ተ/ወልድ	መጋቢት 10/2002	166
56	ከሳሽ የሆነ ወገን ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ በአንድ ላይና በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ለመክሰስ የሚችል (የሚገባው) የነበረ ቢሆንም ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ቀንሶ ያቀረበው በፍ/ቤት ፈቃድ የሆነ እንደሆነ የቀረው መብት ላይ በድጋሚ ክስ ለመመስረት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4)	43992	እነ አቶ ይልማ አንበሴ (አራት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ እመቤት መንገሻ (አምስት ሰዎች)	መጋቢት 6/2002	168
57	ከሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ የሚያቀርበው የውል ይፍረስልኝ ክስ ገዥ ውል እንዲፈፀምልኝ በሚል ሊያቀርብ የሚችለው አቤቱታ ላይ የሚቆጠረውን የይርጋ ጊዜ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,1851	43636	ወ/ሮ አልማዝ ተሰማ እና እነ አቶ በየነ ወ/ሚካኤል (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 22/2002	173
58	የኪራይ ውልን መሠረት በማድረግ ቤትን የያዘ ወገን የኪራይ ውሉን በቅድሚያ ሣያስፈርስ የባለቤትነት ጥያቄን መሠረት በማድረግ በኪራይ ውሉ አልገደድም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	46947	አቶ ዘነበ ኃ/ማሪያም እና እነ ወ/ሮ አባይነሽ ዘለቀ (ሦስት ሰዎች)	መጋቢት 7/2002	175
59	ከእጅ በእጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ገዢ የሸያጩን ዋጋ የከፈለበትን ደረሰኝ ይዞ መገኘቱ የገዛውን ንብረት እንደተረከበ የሚያሳይ የመጨረሻ (conclusive) ማስረጃ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2266,2278(1) እና (2)	45545	ወ/ሮ ሸዋዬ ኑርዬ እና ምን አዩ ኃ/የተ/የግል ማህበር	መጋቢት .22/2002	178
60	በፍ/ብሔር ጉዳይ ህጋዊ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ዋስትና የሚደረግበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1922	47971	ወ/ሮ ጅቦኒ ቱና እና ወ/ሮ ብርቂ ኢርክታ	ሚያዝያ 5/2002	181
61	ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ ተከራይ የሆነ		አቶ ብርሃነ ገብረሐይሉ		

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ወገን የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ በህግ የተጣለበት እንደሆነ አከራይ የሆነው ወገን ይህንኑ ክፍያ ለመፈፀም ይቻል ዘንድ ተከራዩን ለመጠየቅ ስለመቻሉ አዋጅ ቁ. 308/95 አንቀፅ 2(3,5,7,8,9,12),6	48358	እና አንሲዩን ኮንትር ላፋም	ሚያዝያ 7/2002	183
62	• አንድ ሰው ብድሩን አለመክፈሉን አምኖ በሚከራከርበት ሁኔታ የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 2024(ረ) ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ • 2024(ረ) ዋና ብድርን ሣይሆን ለብድር የሚከፈል ወለድን የሚመለከት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024(ረ)	44691	አቶ ሸባባው ወሌ እና አቶ መሉጌታ ዓባይ	ሚያዝያ 8/2002	186
63	አንድ ውል ህግን የሚፃረር /የሚቃረን/ ነው በሚል እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845	48094	እነ ሙና እንድሪስ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ግንቦት 10/2002	188
64	በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት አሰሪው ሠራተኛው በውጭ አገር ትምህርቱን እንዲከታተል ለማስቻል የሚያስፈልጉ ወጭዎችን ደመወዝን ጨምሮ ለመክፈል ሠራተኛው ደግሞ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ አሠሪውን ለማገልገል ውል ገብቶ ሠራተኛው ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለ በሆነ ጊዜ አሠሪው የጉዳት ኪሣራ የመጠየቅ / የመክፈል/ መብት ያለው ስለመሆኑ	49453	የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት እና አቶ ተፈሪ ማሞ	ግንቦት 19/2002	192
65	የሽያጭ ውል በህግ የተቀመጠውን የአፃፃፍ ሥርዓት ባለመከተሉ ፈራሽ ሲሆን ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ወገን ንብረቱን ለውጦ ወይም በንብረቱ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ባወጣው ወጪ መጠን ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1818	49326	ወ/ሮ እታፈራሁ ኃ/ማሪያም እና እነ መምህር በቀለ ታችበሌ (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 28/2002	195
66	በፍ/ብሔር ጉዳይ (ክርክር) የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ/. 1846	42700	የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ	ሐምሌ 12/2002	198
67	የእቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2024 ሥር በተመለከተው የህሊና ግምት የሚሸፈን ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2024	46019	የአቶ ደሣለው ፋንታ ወራሾች እነ መሉጌታ ደሣለው እና አየለ ደበላ	ሐምሌ 20/2002	202
68	አንድ የስጦታ ውል በኃይል ወይም በተንኮል ተግባር ተደርጓል በሚል ስለሚፈርስበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2442(3),1698,1699,1704,1706	49900	እነ ወ/ሮ ሐመልማል ዓለሙ(ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ሀረገወይን ዘለቀ	ሐምሌ 19/2002	206
አፈፃፀም					210
69	የውርስ ንብረት በጨረታ እንዲሸጥ ለማድረግ መነሻ ዋጋን ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1083,1084	43888	አቶ ፀሐይ ወንድም እና እነ አቶ አያለው መለስ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 23/2002	211
70	አንድ ተጋቢ በግሉ ያመጣው ዕዳ ከሌለኛው ተጋቢ የጋራ ንብረት እንዲከፈል የሚደረገው ዕዳውን ያመጣው ተጋቢ ዕዳውን ለመክፈል አለመቻሉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የደቡ/ብ/ህ/ክ/መ እና የፌዴራል መንግስት የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ	39837	አቶ ስመንጉስ አሰፋ እና መ/ት ምህረት ክበበው	ግንቦት 3/2002	213
71	አንድ ንብረት በፍርድ አፈፃፀም የተነሣ ሊያዝ የሚችለው በተሰጠው ፍርድ ባለዕዳ የሆነው	46143	ወ/ሮ ድልበጌ ራሕመቶ እና እነ የባህር ትራንዚት	ሐምሌ 2/2002	215

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ወገን ሃብት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ		አገልግሎት ድርጅት(ሁለት ሰዎች)		
	ወንጀል				217
72	የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የንግድ ድርጅት ሠራተኛ፣ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ድርጅቱ በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦባቸው ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 56(1)(3) አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀፅ 50(ለ)(1),22(1) የወንጀል ህግ አንቀፅ 23(3),34(1)	48850	እነ አቶ ታረቀኝ ገ/ጊዮርጊስ (ሦስት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ታህሣሥ 8/2002	218
73	በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የፈፀመው የግድያ ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)(ሀ) ሥር የሚያስጠይቅ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1)(ሀ),84,86	45927	የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ እና መሰረት መኮንን	ጥር 19/2002	221
74	በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ክስ በዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተሟልቶ አለመቅረብ የክሳሽ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ መዘጋት በቀረበው ወንጀል ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ ከመሆን የሚያግደው ስላለመሆኑ	45572	ወ/ሮ ዘነበች ሽብሩ እና ፌ/ዐ/ህግ	የካቲት 26/2002	224
75	ህጋዊ መካላከልን ከመጠን በማሳለፍ የተፈፀመ የሰው መግደል ተግባር በወንጀል ህግ ቁጥር 541(ሀ) የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 540, 541	43501	እነ ረዳት ሳጅን ሺጋ ተካ ሞላ (ሦስት ሰዎች) እና የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ	መጋቢት 15/2002	225
76	በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 እና 567 መሰረት አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543,567	44235	ቁስ ጌታቸው ተሾመ እና ዓቃቤ ሕግ	መጋቢት 28/2002	229
77	አንድ ሰው የማታለል ተግባር ፈፅሟል በሚል በወንጀል ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ የወንጀል ህግ ቁጥር 692(1)	46189	ሐረገወይን ተፈራ እና ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	ሚያዝያ 20/2002	232
78	ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ የዘወትር ፀባይ መልካም የነበረ መሆኑ በተናጠል (በራሱ) ቅጣትን ለማቅለል የሚያስችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 82(1) (ሀ)	53612	እነ አቶ ፍስሐ ዓባይ(ሁለት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ዓ/ህግ	ሚያዝያ 25/2002	234
79	በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ወንጀለኛው በይቅርታ የተለቀቀ መሆኑ አስቀድሞ የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ እንዳልነበረ የሚያስቆጥር (በሪከርድነት እንዳይያዝ የሚያደረግ) ስላለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 230	41248	ቡርቁሶ ዋቆ እና ዐቃቤ ሕግ	ሰኔ 23/2002	237
80	በሥር ፍ/ቤት የተሰጠ የቅጣት ውሣኔ ላይ አነሰ ወይም በዛ በሚል በግልፅ ይግባኝ ባልተጠየቀበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅጣትን ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ውሣኔ ሊሰጥ የማይገባ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(መ)	48617	ተስፋዬ አደላ እና ዐቃቤ ሕግ	ሰኔ 18/2002	239
81	• ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተከራካሪ ወገኖች የማስረዳት ሸክማቸውን ተወጥተዋል ለማለት የሚቻልበት አግባብ • በፍ/ቤት ፊት ቃለ- መሃላ በመፈፀም የተሰጠ የምስክር ቃል እውነት ነው በሚል የሚወሰደው ግምት ሊፈርስ የሚችል	51706	አቶ ግርማ ትኩ እና የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ሐምሌ 21/2002	242

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111				
	ንብረት				251
82	የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041,3052	38681	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እማሆይ ፀሐይቱ አምበሉ	ጥቅምት 3/2001	252
83	ለረጅም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ሥር የነበረ ቤትን ይሰቀቅልኝ በሚል አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ አግኝቶ ባለመብትነቱን ሳያረጋግጥ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 47/67	45161	እነ እናኑ ጀንበሬ (ሁለት ሰዎች) እና የደሴ ከተማ ቀበሌ 03 ጽ/ቤት	ታህሣሥ 24/2002	255
84	የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቀርብ የመፋለም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው (ቀሪ ሆኗል) ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677,1845,1206,1188-1192	43600	ዳዊት መስፍን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ጥር 05/2002	257
85	የአዋጅ ቁጥር 47/67 በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠን ካርታ መሰረት በማድረግ ክሥ ለመመስረት የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67	48699	አቶ አምሣለ ጀመሪ እና አቶ ፍርዱ ገበያሁ	ሚያዝያ 21/2002	262
86	በአንድ ቤት ውስጥ ሲኖር ያልነበረ ወይም ቤቱን በእጁ አድርጐ ሲያዝበት ያልነበረ ሰው የሚያነሣው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149	43081	አቶ ሣሙኤል ጦናሮ እና እነ ወ/ሮ አይሻ አርጌሳ (አራት ሰዎች)	ግንቦት 6/2002	266
87	በሃይል ቤቱ ተይዞብኛል እንዲለቀቅልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1206,1149	42861	ወ/ሮ አጤነሽ አበበ እና አቶ ማንተጋፋቶት አጥላው	ሰኔ 28/2002	268
88	• አንድን ንብረት በአደራ ለማስተደደር (ለመጠበቅ) የተረከበ ወገን አደራ ሰጪው ንብረቱ እንዲመለስ በጠየቀው ጊዜ ወዲያውኑ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ • ንብረትን በአደራ የሰጠ ወገን ንብረቱ እንዲመለስለት ከመጠየቅ ጋር በተያያዘ በህግ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ (ይርጋ)የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2781 (1)(2),2779, 2989(1)	48048	ወ/ሮ ንብርኤላ ኒካላ ቶማስ ናክሶ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ሐምሌ 22/2002	270
89	ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የጉዳት ኪሣራን ጉዳት ለሚደርስበት ወገን በመክፈል የመንገድ መተላለፊያ (servitude right) መብት ሊከበር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1221	48783	ወ/ሮ ሶፊያ ሁሴን እና እነ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 27/2002	273
	ከውል ውጭ ኃላፊነት				276
90	የጉዳት ኪሣራ የሚከፈለው ጉዳት ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090,2091	39601	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ገዛኸኝ መንግስቱ	ጥቅምት 5/2002	277
91	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ገቢ ያልነበረው መሆኑ በርትዕ ሊከፈለው የሚገባውን ካሣ የሚያስቀር ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102	42962	አቶ አየለ አድማሱ እና አቶ አጀቡ ሹሜ	ታህሣሥ 28/2002	279
92	በወንጀል ጉዳይ ተከሰሶ ጥፋት የሌለበት መሆን	43843	ዶ/ር ተስፋነሽ በላይ	መጋቢት	282

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በራሱ በተመሳሳይ ጉዳይ በፍትሐብሔር ከቀረበ ክስ ነፃ ለመውጣት እንደ በቂና የመጨረሻ መስፈርት የሚወሰድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149		እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ	21/2002	
93	ለተወሰነ ጊዜም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ ከውል ውጭ በሆነ ግንኙነት በሥራ ወቅት በሌሎች ሰዎች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አሠሪ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2130, 2131, 2132	45735	አቶ ደረጀ ቸርነት እና ወ/ሮ ሕይወት የኃላሸት	መጋቢት 21/2002	285
94	በአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ችሎት ሠራተኛው የፈፀመው ድርጊት ከሥራ ለማሰናበት በቂ አይደለም ተብሎ መወሰኑ አሰሪው በሠራተኛው ላይ በፍ/ብሔር ጉዳይ ሊያቀርብ የሚችለውን ክስ የሚያስቀር የመጨረሻ ፍርድ /ውሣኔ/ ስላለመሆኑ	44588	የኢትዮጵያ ኢህል ንግድ ድርጅት እና እነ ኃይለየሱስ ቱኪ (አራት ሰዎች)	ሚያዝያ 4/2002	290
95	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ህይወቱ ካለፈ ሰው ጋር በተገናኘ የሚከፈለው የጉዳት ካሣ መብቱን የሚጠይቀው ሰው ዕድሜ ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ በመሆኑ የተነሣ ብቻ ካሳው ሊከፈለው አይገባም ለማለት የሚያስችል የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2095/1/	50225	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ት ዝናሽ አሰፋ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 5/2002	293
	የዳኝነት ስልጣን				295
96	የአ.አ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ደብተርን ለመሰረዝ የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ	34665	እነ አቶ ናትናኤል ዘውገ (ሁለት ሰዎች)እና እነ ወ/ሮ እግዜሩ ገ/ህይወት(ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 12/2002	296

97	የከተማ ቦታ ያለአግባብ ተወስዶብኝ በሊዝ ለሌላ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የቦታውን መውሰድ ውሣኔ ለሰጠው አካል በቅድሚያ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑና በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ያለበትና ይኼው አካል የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 272/1994	46220	የደቡብ ክልል የሐዋሣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና የሐዋሳ ደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ገዳም	ጥር 18/2002	298
98	በውጪ አገር ሕግ መሰረት የተቋቋመና በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገበ የንግድ ድርጅት ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊዳኝ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 27(1), አዋጅ 25/88 አንቀጽ 11(2)(ሀ)	42928	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ድራጋዶስ ኮንስትራክሽን	ጥር 12/2002	300
99	በብልጫ የተከፈለ የቀረጥ ገንዘብ ለባለገንዘቡ ሊመለስ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 53(1),55	42866	ብርሃነ ጥዑም እና የጉምሩክ ባለስልጣን	መጋቢት 20/2002	302
100	የሥራ መደብ ወይም እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የወል የሥራ ክርክርን የሚመለከት ስለመሆኑ	48111	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ቂጤሳ ገብሬ	ሚያዝያ 13/2002	305
101	በውድድር አሸንፌ ያገኘሁትን የሥራ መደብ እድገት ይሰጠኝ በሚል የሚቀርብ የሥራ	52600	የኢትዮጵያ ቆዳ አክሲዮን ማህበር	ሚያዝያ	308

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ክርክር የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የሚታይ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96		እና አቶ ተስፋዬ ኃይሌ	12/2002	
102	የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በከተማው የሚገኝ ቤት ባለቤትነቱ የማን ነው ከሚል ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚነሣ ክርክርን ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 416/19 አንቀፅ 33	47134	የድሬዳዋ አስተዳደር ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ፋንታዬ ምትኩ	ግንቦት 6/2002	310
103	• የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከ5000 ብር በታች የሆነ ጉዳይን በሙሉ ተቀብሎ ለማስተናገድ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች በሕግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ • የሥራ-ነገር ሥልጣን በሕግ ባልተሰጠው የዳኝነት አካል (ፍ/ቤት) የተሰጠ ፍርድ የማይፀና ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(6),5(9) አዋጅ ቁ. 361/95	52041	የእርሻ መሣሪዎችና የቴክ/አ/ማህበር እና የኢት/መድን ድርጅት	ሰኔ 29/2002	313
104	በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ጋር በተያያዘ የሚነሣ ክርክርን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 5(6)	43912	አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና እነ የአቶ ኢብራሂም ሙሣ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 15/2002	315
105	በሰዎች ወይም በሚንቀሳቀስ ሀብት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ ለማግኘት የሚቀርብ ክስን ለማስተናገድ የግዛት ክልል ሥልጣን ስለሚኖረው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 27	48018	አቶ ተከተል ዘካሪያስ እና እነ ወ/ሮ አስቴር ታደሰ(ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 7/2002	317
106	በሸሪአ ፍ/ቤት በሚካሄድ ክርክር ላይ ጣልቃ ገብቶ መከራከር በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ስምምነትን እንደመስጠት የሚያስቆጥር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 188(92) አንቀፅ 5(1)	45806	አቶ ፍፁም በረታ እና እነ ወ/ሮ ሶፊያ ዱላ(አራት ሰዎች)	ሐምሌ 8/2002	319
107	• በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ እጅግ አስፈላጊ የህዝብ አገልግሎት ድርጅቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ተቋማት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅም ጥያቄን የያዘ የውል የሥራ ክርክር ካልሆነ በስተቀር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ለማስተናገድ የሥራ-ነገር ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ • መሰል ጉዳዬችን ለማየት በህግ ስልጣን የተሰጠው በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰየም ቦርድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 466/97 አንቀፅ 2(2) አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 142(1)(ሀ),(2),(3),136(2)	49152	የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር እና የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ድርጅት	ሐምሌ 7/2002	324
ባንክና ኢንሹራንስ					328
108	በብድር ለተሰጠ ገንዘብ በመያዣነት የተያዘ ንብረት መድን የተገባለት ሆኖ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ አበዳሪው ንብረቱን በመያዣ የያዘበት ብድር ዋጋ ዋስትና ከተገባለት የገንዘብ መጠን ያነሰ እንኳን ቢሆን መድን ሰጪው እንዲከፍለው ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2858	38572	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ጥቅምት 17/2002	329
109	ባንክ በመያዣ መልክ የያዘውን የተበዳሪ ንብረት በአዋጅ ቁ. 97/90 መሠረት በመሸጥ	44164	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና	ታህሣሥ 8/2002	332

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ላይ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ በተበዳሪው ላይ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ ዕዳው እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ		አቶ ሐሰን ኢብራሂም		
110	የኢንሹራንስ ውልን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 674(1),754(1)	46778	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ	የካቲት 24/2002	336
111	የመድን ሰጭ ኃላፊነት በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 665(2)	46808	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና ወ/ሮ ጫልቱ ሚደግሳ	ሚያዝያ 6/2002	339
112	ለአንድ ንብረት መድን የገባ ሰው በንብረቱ ላይ የደረሰው ጉዳት ሙሉ ውድመት ሊባል የሚችል ቢሆንም ካሣ ሊከፈለው የሚችለው ጉዳት በደረሰ ጊዜ ዕቃው ከሚያወጣው ዋጋ ሳይበልጥ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 678	48698	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አቶ ሣሙኤል አለሙ	ግንቦት 19/2002	341
113	መድን ሰጪ የሆነ ወገን በመድን ገቢው እግር በመተካት ባለዕዳ የሆነ ወገን ላይ ጥያቄ ባነሣ ጊዜ ባለዕዳው ከመድን ገቢው ጋር የሚፈጠር አለመግባባትን ከፍርድ ቤት ውጪ በሽምግልና ለመጨረስ የተስማማን በመሆኑ መድን ሰጪው በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ ሊጠይቅ አይችልም በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 683(1)	39902	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ ብሬ ሞሲሳ	ሰኔ 18/2002	344
114	አስቀድሞ የተደረገ ነገር ግን ባለመታደሱ ምክንያት የተቋረጠ (ያበቃ)ን የመድን ውል መሠረት በማድረግ ሊጠየቅ የሚችል የጉዳት ካሣ ስላለመኖሩ የንግድ ህግ ቁ. 666(2) እና (3)	52910	አቶ አንዳርጌ ታደሰ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሐምሌ 28/2002	347
ጉምሩክ(ግብር)ታክስ					349
115	• የንግድ ቤቶችን የማከራየት እንቅስቃሴ ከታክስ ነፃ ከሆኑ ግብይቶች የማይመደብ ስለመሆኑ • የንግድ ቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀፅ 8	39574	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ወ/ሮ ምልእተ ፀጋ ቢዘን (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 3/2002	350
116	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያልተከፈለን ቀሪ ቀረጥ ሊያስከፍል የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ.60/89 አንቀፅ 57(1),48,53(1)	45882	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ እጅጋየሁ አራምዴ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 6/2002	352
117	የጉምሩክ አዋጅን በመተላለፍ ከሚፈፀም የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ የኮንትሮባንድ ተግባር ሃይልን በመጠቀም ወይም ከሌሎች ጋር በማበር የተፈፀመ እንደሆነ አዋጅ ቁ. 60/89 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ	44862	አሸናፊ አበበ እና የጉምሩክ ባለስልጣን	ጥር 5/2002	355
118	የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ክስ ሊቀርብበት የሚገባውና ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲሱ የወንጀል ህግ ሣይሆን የጉምሩክ አዋጆችን መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89	48693	ነኢማ አወል እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ጥር 5/2002	357
119	የንግድ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው የድርጅቱን አስተዳደራዊ ሥራ ለሌላ ሰው	54061	አቶ መስፍን ሽፈራው እና የኢትዮጵያ ገቢዎች	ሚያዝያ	359

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወከለ መሆኑ ድርጅቱ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት በመፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ በተባለ ጊዜ ከሚቀርብበት የወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የማያደርገው ስለመሆኑ		ባለስልጣን	26/2002	
120	• የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባሩን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ባለማከናወኑ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ • የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሕግ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ግዴታውን ለመወጣት ሲንቀሳቀስ በቁጥጥሩ ሥር አድርጐት ከሚቆየው ንብረት ጋር በተያያዘ የተቋረጠ ጥቅም ወይም የጉዳት ካሣ ሊከፍል የሚችልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ 60/98 አንቀጽ 6(5), 58,74 አዋጅ ቁ 368/95 አንቀጽ 78	49889	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና አቶ ዛኪ ሰይድ	ሰኔ 28/2002	361
121	የግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜና ስሌቱ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 43(1)	48621	አቶ አብደላ ሁሴን ከሰር ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን	ሰኔ 30/2002	365
ውክልና					368
122	ባንክ በሐዋላ ለማድረስ የተቀበለውን ገንዘብ ለተገቢው ሰው አልደረሰም በሚል ኃላፊነት አለበት ሊባል የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ እና የተለመደውን አሰራር ሳይከተል የቀረ እንደሆነ ወይም መጭበርበሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ	48269	አቶ ሽረፈዲን አብደ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	የካቲት 24/2002	369
123	ወኪል የሆነ ሰው የውክልና ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ የራሱን ወይም ከራሱ ጋር ቤተሰባዊ ወይም ሌላ ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር ያለው ሰውና የወካዩ ጥቅም ሊጋጭ የሚችልበት አጋጣሚ እንዳይፈጠር መከላከል ያለበት ወይም በተፈጠረ ጊዜ አስቀድሞ ለወካዩ ማሳወቅ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)2198,2208,2209	50440	አቶ ሃብቱ ወልዱ እና እነ ወ/ሮ መሰሉ ደስታ (ሁለት ሰዎች)	ግንቦት 16/2002	371
የንግድ ሕግ					375
124	• የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ • በግለሰቦች መካከል በውል የሚፈጠር የሽርክና ማህበር የንግድ ሕግ በሚያዘው መሰረት አይነቱ ተለይቶ ተመዝግቦ የማይገኝ በሆነ ጊዜ እንደ የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ የንግድ ሕግ ቁጥር 211,212,219	46358	ወ/ሮ ብርሃን ፀጋዬ እና እነ አቶ ሚካኤል ፋስሐ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 25/2002	376
125	ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ሰዎች ማህበሩን ሲያስተዳድሩ በሰሩት ያልተገባ ስራ ምክንያት በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት አግባብ የንግድ ሕግ ቁጥር 580	39608	ወ/ሮ አስቱር አርአያ እና እነ ወ/ሮ አምሳለ በላይ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 11/2002	378
አእምሯዊ ንብረት					381
126	አንድን መፅሐፍ ከተባዛበት ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የተረጐመ ሰው እንደ ድርሰት አመንጪ ተቆጥሮ የሞራልና የቁሣዊ ጉዳት ሊወሰንለት	44520	አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት እና	ጥቅምት 10/2002	382

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመቻሉ አዋጅ ቁ.410/96 አንቀፅ 2(2),6(1)		ዶ/ር ጌታሁን ሽብሩ		
	ልዩ ልዩ				385
127	ለዋስትና የተያዘ ገንዘብን የአስያዡን ማንነትን ማረጋገጥ እስከተቻለ ድረስ ገንዘቡን ያስያዘበት ደረሰኝ ኮፒን ያቀረበ እንኳን ቢሆን የተያዘው ገንዘብ መመለስ ያለበት ስለመሆኑ	53459	አቶ ማሞ ገ/ማሪያም ተጠሪ፡የለም	ሚያዝያ 12/2002	386
128	• በአስፈፃሚ አካላት የሚወጡ የተለያዩ መመሪያዎች በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው የወጡ ወይም በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ አለመሆናቸው ህጋዊ ውጤት እንዳይኖራቸው የሚከለክል ስላለመሆኑ • አዋጅን መሠረት በማድረግ የወጡ መመሪያዎችን የሚፃረር ድርጊት መፈፀም በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 83/86 አንቀፅ 39(2),1, 2, 59(1)(ሸ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁ. ሲቲጂ 001/97	43781	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና አቶ ዳንኤል መኮንን	ሐምሌ 14/2002	388
129	• የሕግ ክርክሮችን በሰበር ማየት /ማስተናገድ/ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠ ስልጣን (power) ስለመሆኑ • በግልግል ዳኝነት (arbitration) የታየ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተዋዋይ ወገኖች የይግባኝ መብትን ለማስቀረት የሚያደርጉት ስምምነት ጉዳዩን በሰበር ችሎት ከመታየት የማያግድ ስለመሆኑ (ከዚህ ቀደም በሰበር ችሎት የተሰጠው የሕግ ትርጉም የተለወጠ ስለመሆኑ።) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3 (ሀ), አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 (4), አዋጅ ቁጥር 25/88, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 350(2) 351 እና 356	42239	ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ እና ዳን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ	ጥቅምት 20/2003	393

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ቤተሰብ				
1.	• ባል ሁለት ሚስቶችን በአንድ ጊዜ አግብቶ የሚኖር በሆነ ጊዜ በመካከላቸው የሚፈራ ንብረት ለተጋቢዎቹ ሊከፋፈል የሚችልበት አግባብ • ሚስቶች ጋብቻ እንደተፈፀመ ከሚቆጠርበት ጊዜ ጀምሮ ከባል ጋር ያፈሩትን ሀብት ብቻ መካፈል ስለመቻላቸው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ 213/96 አንቀጽ 62/1/	50489	ወ/ሮ ዘይነባ ከልፋ እና ወ/ሮ ከድጃ ሲራጅ	መስከረም 24/2003	
2.	የኮንዶሚንየም ቤት ለማግኘት የተደረገ ምዝገባ ከጋብቻ በፊት ቢሆንም ዕጣ የወጣው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ከሆነ ተጋቢዎቹ የመካፈል መብት የሚያገኙ ስለመሆኑ	46606	አቶ ገ/ሥላሴ ጫኔ እና ወ/ሮ አብረሽት ተጫኔ	ጥቅምት 02/2003	
3.	ወራሽ የሆነ ሰው ወራሽ ባልሆነ ሰው ላይ ንብረቱ ይሰቀቅልኝ በሚል የሚያቀርበው ክስ /አቤቱታ/ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ይርጋ የሚቆጠረው ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን አንስቶ ሳይሆን ንብረቱ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ	47201	እነ በላቸው አስፋው እና ወ/ሮ መኪያ አወል	ጥቅምት 05/2003	
4.	የጋብቻ ውል አስገዳጅ የህግ ድንጋጌን እስካልተቃረነ ድረስ በፍቺ ምክንያት የሚከተለውን የተጋቢዎች የንብረት ክፍፍል አልባት በመስጠት ረገድ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 42, 47, 73, 44	47889	እነ ወ/ሮ ሠላማዊት አስራት /አምስት ሰዎች/ እና ወ/ሮ መሠረት ዘውዴ	ጥቅምት 04/2003	
5.	በሁለት የተለያዩ ከተሞች የሚገኙ ቤቶች የጋብቻ ፍቺን ተከትሎ ለባልና ሚስት ሊከፋፈሉ የሚችሉበት አግባብ	49171	ዶ/ር ደስታ አቡኑ በለጡ እና ሲ/ር አስቱር ካሣ ወልደየስ	ጥቅምት 16/2003	
6.	የውርስ ሀብትን አስመልክቶ የሚቀርብ ክስ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ገደብ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851/ለ/ መሰረት ሊቋረጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ስለመኖራቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851	49359	ወ/ሮ ቀለሚ ወርቅነህ እና ሻምበል ጌታሁን ገብሬ	ጥቅምት 04/2003	
7.	• ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ሰዎች ግንኙነታቸው በንብረት ረገድ ያለውን ውጤት በተመለከተ በውል ሊወሰኑ ስለመቻላቸው • በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ የአላባ የመጠቀም መብት ጥቅም ተቀባዩ ሲሞት የሚቋረጥና ለወራሾቹ የማይተላለፍ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731, 1322/1/	53663	እነ አቶ ጊላጋብር ገብረህይወት /ሦስት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ አረጋሽ አብረሃ /ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 29/2003	
8.	የኑዛዜ መኖርን የማስረዳት ሸክም ስላለበት ወገንና ኑዛዜውን ለማስረዳት ሊቀርቡ ስለሚገቡ ማስረጃዎች የፍ/ብ/ህ/ቁ. 896, 897	49831	ወ/ሪት ሮማን ግዛው እና አቶ ግርማ አብርሃም	ጥቅምት 02/2003	
9.	በኑዛዜ ላይ ስለሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ እና ተፈፃሚነት ስላለው የይርጋ ደንብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973, 974	53223	እነ አቶ ሐዲስ ዓለመስላሴ እና ወ/ሮ ብሌን ዓለመስላሴ	ጥቅምት 15/2003	
10.	• የጋብቻ መኖርን አስመልክቶ ቀዳሚና ዋናው ማስረጃ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ • በማንኛውም ሥርዓት የተፈፀመ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ቀርበው ሊመዘገቡ የሚችሉና በዚህ መልኩ የሚገኘው ሰነድ የጋብቻ መኖርን ለማረጋገጥ ብቃት ያለው ስለመሆኑ • በዚህ መልኩ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የተመዘገበ ጋብቻ ውጤት አለው ለማለት የሚቻለው ምዝገባው ከተከናወነበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን የጋብቻው ሥርዓት ከተፈፀመ ዕለት	54258	ወ/ሮ ዘነበች በቀለ እና አቶ ዮናስ ፀጋዬ	ህዳር 02/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አንስቶ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/1992 አንቀጽ 28/3/				
11.	• በትዳር ወቅት የተወሰደ /በአንደኛው ተጋቢ/ ብድር ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚገመት ስለመሆኑና ከዚህ ተቃራኒ የሚከራከር ተጋቢ ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም ያልዋለ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • ደመወዝ የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ነው በሚል ሊወሰድ የሚችለው ተጋቢዎቹ በጋብቻ ባሉበት ወቅት የትዳርን ወጪ ከመሸፈን አኳያ መሆን ያለበት ስለመሆኑ • ተጋቢዎች ከህጋዊ ፍቺ በፊት ተለያይተው በቆዩባቸው ግዜያት በግል ያገኙት ደመወዝ የጋራ ነው ለማለት የሚቻል ስላለመሆኑ • በጋብቻ ወቅት የተወሰደና በፍቺ ወቅት ተከፍሎ ያላለቀ ዕዳ እንደ የጋራ ዕዳ የሚወሰድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ 213/92 አንቀጽ 62/1/	56184	ወ/ሮ ኑን ስንታየሁ ጉዝ እና አቶ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል	ህዳር 02/2003	
12.	ባል/ሚስት በጡረታ መልክ የሚያገኘውን ክፍያ ሌላ ባል/ሚስት ባገባ ጊዜ የሚቋረጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 209/55 አንቀጽ 21 አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 35/2/	52569	ወ/ሮ ሙሉወርቅ ዋቹ እና ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን	ህዳር 13/2003	
13.	• የውርስ ሃብት እንዲጣራ በሚል በንብረቱ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ ከሚች ጋር ህጋዊ ግንኙነት ባልነበረበት ሁኔታ ነው በሚል ክርክር በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቶች ይህንን እንደ ጭብጥ በመያዝ እልባት ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ • በዚህ ጉዳይ ላይ ፍ/ቤት የሚሰጠው ብይን ጊዜያዊ አገልግሎት እንዳለው ትዕዛዝ የሚወሰድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320/3/, 247/1/	46726	ነጋሲ አየለ ኢትቻ እና እነ ሳሙኤል ዮሃንስ ገ/አግዚአብሔር /ሁለት ሰዎች/	ታህሳስ 13/2003	
14.	• ጋብቻ ሳይኖር እንደ ባልና ሚስት መኖርን ማስረዳት የሚቻልበት አግባብና ይዜው ግንኙነት በህግ ጥበቃ ያለው ነው ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ • ጋብቻ ሳይኖር እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በንብረት ረገድ ውጤት ሊያስከትል የሚችለው ግንኙነቱ፡ ሦስት ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ የፀና ከሆነና በዚሁ ጊዜም የተፈራ ንብረት ያለ እንደሆነ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 106/2/, 95	50580	ዶ/ር አለልኝ መኮንን እና ወ/ሮ አስቴር አርአያ	ታህሳስ 14/2003	
15.	• ሚች ካለው ሀብት እጅግ አነስተኛ የሆነ መጠን ያለው ንብረት ለተወላጁ እንዲሰጠው የተናዘዘ እንደሆነ ተናዛዡ በተዘዋዋሪ መንገድ ተወላጁን እንደነቀለው የሚቆጠር ስለመሆኑ • የሚች ኑዛዜ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ በሆነ ጊዜም የተነቀለ ተወላጅ ከኑዛዜ ተቀባዩ ጋር እኩል ሊካፈል የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 951, 938, 939, 937, 912	54385	አቶ ፍቃዱ ሽፈራው እና አቶ ግሩም ኤድሚያስ	ጥር 27/2003	
16.	• የጋብቻ ውል በአግባቡ ተደርጎል ሊባል የሚችልበት አግባብ • የጋብቻ ውል በሚል በተጋቢዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ከነሙሉ ይዘቱ ሊታይና ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 40 እና ተከታታዮቹ 73, 46/1/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 826/2/ 2427 2428 857	56157	እነ ወ/ሮ ፀሐይ ተሰማ /ሁለት ሰዎች/ እና የህፃን አማኑኤል ወንደሰን ሞግዚት	ጥር 09/2003	
17.	አባትነት በፍርድ ሊነገር የሚችልባቸው ሁኔታዎች ላይ ሳይንሳዊ የደም ምርመራ (DNA test) በማስተባበያ ማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል ስለመሆኑና ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች በዚህ ረገድ የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች በአግባቡ ሊያስተናግዱ የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 144, 143 /ሠ/, 145	62041	ጥሩወርቅ ወርዶፋ እና ጥሩነሽ ወርዶፋ	የካቲት 11/2003	
18.	ማየት የተሳናቸው ሰዎች የሚያደርጉት ኑዛዜ በውል አዋዋይ	50971	አቶ ሃይሌ ስሙጋ	የካቲት	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ፊት ካልሆነ በስተቀር አይፀናም ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881/3/, 1728/3/, 340, 343/2/		እና ሰላማዊት ተኮላ	25/2003	
19.	ከውርስ ሃብት ጋር በተያያዘ ወራሽ የሆነና አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ላይ የይርጋ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው አካለመጠን ከደረሰበት ወይም በመብቱ መጠቀም ከቻለበት ጊዜ አንስቶ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845	57114	ወ/ሮ ሃና ፀጋዬ እና ወ/ት ጣዕመ ደስታ	ግንቦት 03/2003	
20.	በጋብቻ ውስጥ የተወለድኩ በመሆኔ ልጅነቴ እንዲረጋገጥልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ህጋዊ መሰረት ያለውና ፍ/ቤቶችም ተቀብለው በፍሬ ነገር ረገድ ሊጣሩ የሚገቡትን በማጣራት መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37/1/	57607	ኤርምያስ ኬስታንትኖስ ግሊፕትስ እና ሰለሞን ኬስታንቲኖስ ግሊፕትስ	ግንቦት 30/2003	
21.	• ኑዛዜ አድራጊ “ስታመም አላስታመመኝም ” በሚል ምክንያት ተወላጅን በኑዛዜ ለመንቀል የሚያስችለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ • ኑዛዜ በተደረገበት ንብረት ሟች መብት የሌለው በሆነ ጊዜ ሊከተል ስለሚችለው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1047, 938, 939, 915, 912	57836	ወ/ሮ አስናቀች ደሳለኝ እና የድርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን	ግንቦት 17/2003	
22.	• ኑዛዜ ህጋዊ አይደለም እንዲሻር በሚል ተቃውሞ እስከቀረበ ድረስ በየትኛውም ህጋዊ መስፈርት መሰረት ፍ/ቤት ኑዛዜውን ውድቅ ሊያደርገው ስለመቻሉ • በኑዛዜ ላይ የነበሩ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ስለሚኖረው ዋጋ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881-883	59268	ወ/ሪት ዝባድ ታዬ እና እነ ብውሸን ታዬ /ሦስት ሰዎች/	ግንቦት 03/2003	
23.	ከውርስ ጋር በተገናኘ በህግ ወራሽ የሆኑ ሰዎች ሟችን ለመውረስ ያልተገቡ ናቸው ሊባል የሚችልበት ሁኔታ ሟች በኑዛዜው ከውርስ ሊነቅላቸው ከሚችልበት ሁኔታ የተለየ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 838, 937/1/, 938/2/, /3/	49713	እነ የጥሩነሽ አየለ ወራሾች /አራት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ወጋየሁ ሠለሞን	ሚያዝያ 03/2003	
24.	• ተናዛዥ የሆነ ሰው ተወላጁ የሆነ ሰው በውርስ ሊደርሰው ከሚገባው ድርሻ ከፋብ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ለማድረግ የሰጠው ምክንያት በቂ መሆን ያለመሆኑ በዳኞች ሊመረመር የሚገባው ስለመሆኑ • “ስላልረዱኝ ወይም ስላልጠየቁኝ” የሚል ምክንያት በመስጠት ተወላጅን ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ድርሻ ሩብ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 913, 1123	55648	እነ ወ/ሮ እቴቴ ሽፈራው /ሦስት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ መንበረ ሽፈራው /ሦስት ሰዎች/	ሚያዝያ 20/2003	
25.	የልጅ አባት ነህ የተባለ ሰውን በተመለከተ የመካድ ክስ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 177/3/	61677	አቶ ፈቃደ መክብብ እና አቶ ዳንኤል ብስራት	ሚያዝያ 18/2003	
26.	ከጋብቻ በሞት መፍረስ ጋር በተገናኘ የሚቀርብ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው ጋብቻው ከፈረሰበት ዕለት አንስቶ እንጂ ወራሽነት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1846, 826/1/	59539	እነ አቶ ስዩም ወ/መስቀል /አራት ሰዎች/ እና ወ/ሪት አምሳለ ሙሉነህ	ሰኔ 29/2003	
27.	አስቀድሞ የተደረገን የጋብቻ ውል በማሻሻል የተደረገ የጋብቻ ውል ህጋዊ ተቀባይነት እንዲኖረው ፍ/ቤት ቀርቦ መጽደቅ ያለበት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 47/1-3/	60725	አቶ አብርሃ የኋላሸት እና ወ/ሮ አበባ ዘመን	ሰኔ 27/2003	
28.	ባልና ሚስት በፍቺ ወቅት የጋራ ንብረታቸውን ለመካፈል ስምምነት ላይ ያልደረሱ ከሆነና ንብረቱ በአይነት ሊካፈል የማይችል እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን ዋጋ እኩል እንዲካፈሉ መደረግ ያለበት እንጂ በእጣ እንዲካፈሉ ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 103/1/	61788	ወ/ሮ ጥሩወርቅ ለማ እና ታፈሰ ተሰማ	ሰኔ 14/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

29.	በሁለት ሰዎች መካከል የጋብቻ ሁኔታ መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያዝ ጭብጥ በሁለቱ ሰዎች መካከል ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት የመኖር ሁኔታ ስለመኖሩ ለማረጋገጥ በሚል ከሚያዘው ጭብጥ የተለየ ወይም አንድ አይነት ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92	60691	ወ/ሮ ገዛችን ገብሩ እና ወ/ሮ ዓለምነሽ በየነ	ሐምሌ 12/2003	
30.	አባትነትን /ልጅነትን/ ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ በሚቀርብ አቤቱታና ክርክር የዲ.ኤን.ኤ (DNA) ምርመራ እንዲደረግለት በመጠየቅ ክርክር የሚያቀርብ ወገን ለዚሁ የህክምና ማስረጃ የሚያስፈልገውን ወጪ የመሸፈን ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 259/1/	63195	ገረመው መ.ሚቻ እና ወ/ሮ አሰፋ ነበበ	ሐምሌ 26/2003	
31.	ጋብቻ ላይፈርስ የትዳር ግንኙነቱን ትቶ የሄደ ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት የተፈራን ንብረት የጋብቻ ውጤት ነው በማለት የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ በጋብቻ ወቅት የተፈራን ንብረት የጋራ ይሆናል በሚለው የህግ ግምት ተጠቃሚ ሊሆን የማይገባ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/1/	43988	ወ/ሮ ሰኒያ ሼላ ተማም እና እነ ወ/ሮ በላይነሽ ማቴቦ /ሁለት ሰዎች/	መስከረም 24/2003	
32.	ወደ ሌላ አገር ለሥራ በሄደበት ወቅት ህይወቱ ያለፈ ሰው ጋር በተያያዘ የማለሰቡ መደበኛ መኖሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ውርሱ በኢትዮጵያ ውስጥ መከፈት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/በ/ህ/ቁ. 826/1/	65621	እነ ወ/ሮ ታደለች መንግስቱ /አምስት ሰዎች/ እና ተጠሪ፡ የለም	ሰኔ 27/2003	
33.	• የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በሦስት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ/ • ከውርስ ሀብት ክርክር ጋር በተገናኘ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ንብረቱ በእጅ ከተደረገበት ጊዜ እንጂ ስመሃብቱ ከተዛወረበት ጊዜ አንስቶ ስላለመሆኑ /	52407	እነ ወ/ሮ ውለታ ደስታ ወ/ማርያም /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ እቱቴ ደስታ	ህዳር 24/2003	
34.	• የውርስ ሃብት አጣሪ ሪፖርት በፍ/ቤት መጽደቅ ውጤት • በፍ/ቤት የፀደቀ የውርስ ሃብት አጣሪ ሪፖርትን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 አግባብ ተቃውሞ ሊቀርብበት ይገባል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358	45905	ሚስስ ሚላን ፒሲጂ ማልጂ እና እነ ሃንድሬ ፒስ ማልጂ /ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 03/2003	
35.	ከጋብቻ በፊት አንደኛው ተጋቢ የግል መኖሪያ ቤት ኖሮት ከጋብቻ በኋላ ሌሎች ተጨማሪ ቤቶችና ግንባታዎች ተካሂደዋል በሚል ከጋብቻ በፊት በስሙ ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት በጨረታ ተሸጦ ለተጋቢዎቹ እንዲካፈል በሚል የሚሰጥ ውሣኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ	53814	እነ አቶ ነስሩ ሰማን /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ መ.ህሊሳ ኒ.ጋኒ	ጥቅምት 05/2003	
36.	በፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 መሰረት የተደረገ ግልጽ ጉዞ ላይ ያለው የተናዛዠ የጣት አሻራ በተመለከተ ክርክር በቀረበ ጊዜና በፎረንሲክ ምርመራ ለማረጋገጥ ካልተቻለ በኑዛዜው የተገኙ ምስክሮች ቀርበው እንዲመሰክሩ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881, 1677/1/, 2007/2/, 897/1/, 896	54013	ወ/ሮ አስመረት ነጋሲ እና ወ/ሮ ጽጌረዳ ስዩም	ጥር 12/2003	
37.	• በጋብቻ ውስጥ የሚወለድ ልጅ አባት ባል እንደሆነ የህግ ግምት ሊወሰድ የሚችልበት አግባብ • የዚህ የህግ ግምት የሚቋቋምበት አግባብ እና እንደ ማስረጃ ተወስዶ በፍ/ቤት እውቅና ሊያገኝ የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 126, 143	54024	አቶ ገ/ሊባኖስ ረዳ እና ወ/ሮ አዜብ አሰፋ	ጥር 10/2003	
38.	አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ሞግዚት የልጁ ሀብት የሆነን የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ ለመሸጥ የማይችል ስለመሆኑ የአ/ብ/ክ/መ/ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 69/95 አዋጅ ቁ. 83/96 አንቀጽ 294, 316 የተሻሻለው የፌ.ዲ.ራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 277/1/, 292	54827	እነ ሮም ወርቁ ተስፋዬ /አምስት ሰዎች/ እና አሰግድ ሸነገለኝ	ሚያዝያ 21/2003	
39.	አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሞግዚት የልጁ ንብረት የሆነን	54129	አቶ ክፍያለው በቀለ	ህዳር	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ በህግ ስልጣን ያልተሰጠው ስለመሆኑ		እና ወጣት ሶፊያን አብዱልቃድር	01/2003	
40.	• ከውርስ በዝምታ ወይም ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት የተነቀለ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ከጠቅላላ የኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ ሆኖ የሚችን የውርስ ሃብት ሊካፈል የሚገባ ስለመሆኑ • "በህይወቴ ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥረውብኛል" የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ተወላጅን ለመንቀል የማይቻል ስለመሆኑ • ሟች ካለው ሃብት እጅግ አነስተኛ የሆነ ንብረት /ሀብት/ ለተወላጁ በኑዛዜ የሰጠ እንደሆነ በውጤት ደረጃ ተወላጁ የተነቀለ መሆኑን መገንዘብ የሚቻልና ተወላጁ ከሌሎች የጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚዎች ጋር እኩል መካፈል ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 912, 938, 939, 915, 1014, 1123	58338	እነ አቶ ዳንኤል ጽጌ /ሁለት ሰዎች/ እና የህፃን አሳለፈ ጽጌ ሞግዚት	ሚያዝያ 06/2003	
41.	• የውርስ ሃብት አጣሪ የሆነ ሰው የሟችን ንብረት በማጣራት ረገድ ሊኖረው የሚችለው የስልጣን አድማስ • በወራሾች መካከል አንድን ንብረት በተመለከተ የውርሱ ሃብት አካል ስለመሆኑ ክርክር በተነሳ ጊዜ አጣሪው ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ በሪፖርቱ ላይ በማስፈር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍ/ቤት ማቅረብ እንጂ ማስረጃዎቹን በራሱ መዝኖ አከራካሪው ንብረት የውርሱ ሃብት አካል ነው ወይም አይደለም በማለት ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 956	66727	ወ/ሪት ዝናሽ ዘውዱ እና የወ/ሮ መድሐኒት ካሣ ወራሽ እነ ወ/ሮ ደብሪቱ ስዩም	ሐምሌ 29/2003	
42.	ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ የተፈራ ቤት በጋብቻ ወቅት እድሳት የተካሄደለት መሆኑ ብቻ ንብረቱን የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት የማያደርገው ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 42/1/, 57	45207	ወ/ሮ አየለች ከበደ እና በላቸው ዋለ	ሰኔ 16/2002	
43.	• ተወላጅ የሆነ ሰው ከውርስ ተነቅሏል ሊባል የሚችለው ተናዛዡ ንብረቱን በጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ለሌሎች ተወላጆች ወይም ሌሎች ሰዎች የሰጠ እንደሆነ ስለመሆኑ • ሟች ያለው አንድ የታወቀ ንብረት ብቻ ሆኖ ይህንኑ ከተወላጆቹ መካከል አንዱን ወይም ሁሉንም ሳያካትት ለሌሎች ሰዎች በኑዛዜ የሰጠ እንደሆነ ተነቀልኩ የሚል ወገን ኑዛዜው ላይ ተቃውሞ ሊያነሳ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 937-939, 842/2/, 915	47917	እነ ወ/ሮ መልካምሥራ አለበል /አራት ሰዎች/ እና ወ/ሮ አንለይ ሊበን	ግንቦት 05/2003	
	አሥረና ሠራተኛ				
44.	• በህብረት ስምምነት ውስጥ በሌላ አካኋን ካልተገለፀ በስተቀር የህብረት ስምምነት ከተፈረመበት ዕለት አንስቶ የሚፀና ስለመሆኑ • የህብረት ስምምነት በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ እንዲመዘገብ የሚደረገው ድርድር ተደርጉበት ከተፈረመበት በኋላ ለመሆኑ • በተደራዳሪ ወገኖች በተሟላና በአግባቡ ያልተፈረመ የህብረት ስምምነት በፍርድ ሃይል እንዲመዘገብ የሚደረግበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 124-135	54451	የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ እና የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ መ/ሰ/ማህበር	መስከረም 27/2003	
45.	አንድ ለራተኛ ለሥራ ከሚጠቀምበት መሳሪያ ብልሽት መከሰት ጋር በተገናኘ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው አሰሪው ግዴታና ኃላፊነቱን በአግባቡ የተወጣ እንደሆነ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 12/1//ሀ/	48945	አቶ አየለ አበበ እና የፊንፊኔ የደን ድርጅት	ህዳር 27/2003	
46.	የህብረት ስምምነት የሌለው አሰሪ ለራተኛው የዲሲፕሊን ጉድለት ፈጽሟል የሚልበትን ጉዳይ ለማጣራትና ለመመርመር ለራተኛውን ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ ለማገድ	53985	ዳሸን ባንክ አ.ማ እና አቶ ዘነበ ድንቁሳ	ህዳር 13/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመቻሉ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/4/				
47.	በህብረት ስምምነት ላይ ከተመለከቱ ሁኔታዎች ውጪ ሰራተኛን ያለአግባብ አዛውሮ የማሰራት ተግባር ህጋዊ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ	54326	አንበሳ ጫማ አ.ማ እና ወ/ሮ እትሁን አያሌው	ህዳር 03/2003	
48.	በስራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተያያዘ የአሰሪው ኃላፊነት በጥፋት ላይ ያልተመሰረተ (strict liability) ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96, 97	57068	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ሰናይት መጫ /ሦስት ሰዎች/	ህዳር 28/2003	
49.	ከስራ ተሰናበትኩ በማለት አቤቱታ የሚያቀርብ ሠራተኛ በእርግጥም ስለመሰናበቱ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማቅረብ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ	57541	የቻይና መንገድና ድልድይ ሥራ ድርጅት እና ግርማ ቡሽራ	ህዳር 14/2003	
50.	በአዋጅ በተቋቋመ የት/ት ተቋም ውስጥ በሚገኝና በራሱ ገቢና በጀት የሚተዳደርና ሠራተኞችን ቀጥሮ በሚሠራ ክበብ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ሊስተናገዱ የሚገባ ስለመሆኑ እና ተቋሙን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ተፈፃሚ ይሆናል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አዋጅ ቁ. 515/96 አዋጅ ቁ. ደንብ ቁጥር 61/96	46075	አቶ ንጉስ ሃዱሽ እና የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ዲን	ታህሳስ 25/2003	
51.	ከሥራ ክርክር ጋር በተገናኘ አሰሪና ሠራተኛው ያደረጉት የሥራ ቅጥር ውልን አስመልክቶ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩን የሚገዛው ከኢትዮጵያ ሌላ /ውጭ/ የሆነ አገር ህግ መሆኑንና የሥራ ቦታውም ቢሆን ከኢትዮጵያ ውጪ እንዲሆን የተስማሙ እንደሆነ ጉዳዩ በአጠቃላይ የአለም አቀፍ የግለሰብ ህግ (private international law) ጥያቄን የሚያስነሳ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው?፣ በየትኛው አገር ህግ መሰረት?፣ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ስልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 11/2/	60685	አቶ በዛብህ አሸቱ እና ሳሊኒ ኮንስትራክሽን	የካቲት 21/2003	
52.	አንድ ሰራተኛ በአሰሪው ታግዶ /የሥራ ውሉ ተቋርጦ/ በነበረበትና ባልሰራበት ዓመት አሰሪው ለሌሎች ሠራተኞች የከፈለውን የቦነስ ክፍያ ለመክፈል የማይገደድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43, 45/5/, 53	59320	ጊዮን ሆቴሎች ድርጅት እና አቶ ስለሺ አምዴ	ግንቦት 15/2003	
53.	አሰሪ ሠራተኛው ጥፋት እንደፈፀመ አውቆ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማሰናበት እርምጃ አለመውሰዱ ስንብቱን ህገ ወጥ የሚያደርገው ቢሆንም ሠራተኛውን ወደ ሥራው እንዲመልስ ላይገደድ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/	64079	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ጌትነት መኮንን	ግንቦት 17/2003	
54.	በሥራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተያያዘ የጉዳቱን አይነትና መጠን መለየት የሚቻልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 109/3/ /ሀ/ለ/ 101/2/ 100 96/1/ 99/1/	60464	የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ግርማ ወዩሳ	መጋቢት 06/2003	
55.	ከአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪው ሠራተኛው የሚጠይቀውን የገንዘብ ክፍያ በማመን የፃፈው ደብዳቤ ሠራተኛው መብቱን ለማስከበር በሚያቀርበው የክፍያ ጥያቄ ላይ የሚቆጠረውን ይርጋ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 164/3/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1852/1/	63635	አቶ ጉልላት ወልዴ እና የሸቀጦች ጅምላ	ሰኔ 27/2003	
56.	• አንድ ሠራተኛ ቦነስ ወይም ድጐማ ሊያገኝ የሚችለው ከአሰሪው ጋር በሚደረግ /በሚኖር/ ስምምነት እንጂ በህጉ አሠሪ ለሠራተኛው በቦነስ ድጐማ እንዲከፍል በአስገዳጅነት የተመለከተ ነገር የሌለ ስለመሆኑ	64758	እነ ተመስገን ገ/እየሱስ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ሰኔ 17/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• የቦነስና ድጐማ አሰጣጥና አፈፃፀምን በተመለከተ በህብረት ስምምነት የተመለከተ ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 4, 12, 13, 53				
57.	•አንድ ሠራተኛ አሰሪው በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መሰረት ሊከፍለው የሚገባውን ያልከፈለው ክፍያ መኖሩን /አንዳለ/ በተረዳ ጊዜ አሰሪውን የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ •የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት በቀጠለበት ሁኔታ ሠራተኛው በአንድ ወቅት ሊከፈለኝ /ሊጠበቅልኝ/ ይገባል በማለት ያቀረበው የመብት ወይም የክፍያ ጥያቄ በፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ በሌላ ጊዜ መብቱን ከመጠየቅ የሚያግደው ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 12 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 216	66242	ወ/ሮ ሙሉ ደምሴ እና ሸራተን አዲስ	ሐምሌ 13/2003	
58.	በአዋጅ ቁ. 147/91 መሠረት በተቋቋመ ማህበር ውስጥ ላሉ ሰራተኞች አዋጅ ቁ. 377/96 ተፈፃሚ ስለመሆኑ	59579	ወ/ሮ አሞኘሽ ገብሬ እና የአቃቂ መለዋወጫ ዕቃዎች የአጅ መሣሪያዎች አ/ማ ሠራተኞች የገንዘብና ቁጠባ ብድር ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ግንቦት 16/2003	
59.	የጡረታ መብት ያለው የመንግስት ልማት ድርጅት ሠራተኛ ሊያገኝ ስለሚገባው ካሣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 9/1/	65427	ሜታ አቦ ቢራ አ.ማ እና ወ/መድህን ቢረዳ	ግንቦት 15/2003	
60.	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ሠራተኞች እየሠሩ የሚገኙትን ሥራ በተመለከተ የሥራ ውል አላደሱም ወይም ለማደስ ፈቃደኛ አይደሉም በሚል ለማሰናበት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ	62370	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ እዮብ መለሰ /አራት ሰዎች/	ታህሳስ 26/2003	
61.	• በአዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት የሠራተኛ ማህበር ለማቋቋም የሚቻልበት አግባብ • የሰራተኛ ማህበር ለማቋቋም መብት የተሰጣቸው በአዋጅ ቁ. 377/96 የሚተዳደሩ ሰራተኞች ብቻ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 114, 115, 118, 2/4/, 113 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 42/1/ /ሀ/, 31	55731	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሰራተኛ ማህበር እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ማህበራዊ ጉዳይ ሚንስቴር	የካቲት 22/2003	
62.	• የሠራተኛ ደመወዝ ሊቀነስ የሚችለው በህግ፣ በህብረት ስምምነት፣ ወይም በሥራ ደንብ በተወሰነው መሰረት ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ብቻ ስለመሆኑ • አሰሪ የሠራተኛን ደመወዝ በራሱ ውሣኔ ሊቀንስ፣ ሊይዝ ወይም የዕዳ ማቻቻያ ሊያደርግ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 59/1/	59666	የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ አቡ ጉበና	ግንቦት 04/2003	
63.	• የደረጃ እድገት በድርጅት ውስጥ በሥራ ላይ ባለ የእድገት አሰጣጥ ስርዓት እና ደንብ መሰረት የሚካሄድ ስለመሆኑ • የደመወዝ ጭማሪ ሊገኝ የሚችለው በእድገት ወይም አሰሪው የደመወዝ ጭማሪ ማድረግ የሚችልበት አግባብ ኖሮት ሲጨመር ስለመሆኑ • በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) መሠረት የተደረገ የሥራ ምደባ የደመወዝ ጭማሪ የማያስገኝ ስለመሆኑ	64821	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃየል ኮርፖሬሽን እና አያሌው ሕብስት	ግንቦት 01/2003	
64.	ከአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በፍ/ቤት የተሰጠ ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርብ አቤቱታ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ	53527	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና አቶ በዳሶ መልካቶ	መስከረም 27/2003	
65.	ሚች ከቀበሌ ተከራይቶት የነበረን መኖሪያ ቤት ወራሽነትን በማረጋገጥ ብቻ በቤቱ ውስጥ የመኖር ህጋዊ መብት ሊገኝ የማይችል ስለመሆኑና ተቀባይነት ያለው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሊቀርብ ስላለመቻሉ	57045	የልደታ ክ/ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት እና አቶ ተስፋዬ አሰፋ	ጥር 25/2003	
66.	የመከላከያ ሰራዊት አባል ያልሆነ የመንግስት ሰራተኛ	61872	የኢትዮጵያ ፕልፕና	የካቲት	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በፍቃዱ ሥራ በለቀቀ ጊዜ የስንብት ክፍያ ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95		ወረቀት አ/ማ እና አብዱልቃድር አደም	10/2003	
67.	ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለውና በባለሃብትነት ሊያዝ የሚችልን የአሰሪ የሆነ ነገር ላይ ሠራተኛው ሆን ብሎም ሆነ በቸልተኝነት በማናቸውም ሁኔታ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/	64988	ዳሸን ባንክ አ/ማ እና አቶ ሃይሉ ሽመልስ	ግንቦት 30/2003	
68.	• የመንግስት ሰራተኞች አዋጅን መሰረት በማድረግ የሚነሳ ክርክር የሚስተናገድበት ህግና የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ • ይግባኝ ለማቅረብ ጊዜ ያለፈበትን አቤቱታ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚቻልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀጽ 76/2/ አዋጅ ቁ. 6/2000 አንቀጽ	61843	ሰይፉ ናስር እና የአ.አ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ህግ ጉዳዮች	መጋቢት 23/2003	
69.	ለተወሰነ ጊዜና ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ ጊዜው ደርሶ መሰናበቱ ምንም እንኳን ሌሎች ሠራተኞች በእሱ ምትክ የተቀጠሩ ቢሆንም ህገ ወጥ ነው ለማለት የማይችል ስለመሆኑ	57337	አድቬንቲስት የልማት ተራድኦ ድርጅት እና አቶ ገበየሁ ወ/ሚካኤል	ሰኔ 15/2003	
70.	በአሰሪና ሰራተኛ ስምምነት የሚዘጋጅ የህብረት ስምምነት ውስጥ የተካተቱ ሠራተኞን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችሉ ምክንያቶች ጥፋትን መሰረት ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1//ተ/	64734	ካንትሪ ክለብ ዴቨሎበር የረር ቪው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት እና እነ አቶ በቀለ ለማ /ሦስት ሰዎች/	ሰኔ 16/2003	
71.	የግንባታ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት ከ3ኛ ወገን ጋር ባደረገው የግንባታ ሥራው ውል መነሻነት የቀጠረውን ሰራተኛ የግንባታ ሥራው ውል በመቋረጡ ምክንያት ማሰናበቱ ህገ ወጥ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24/4/, 4/1/, 10, 9	66306	አምሳሉ ወረዳ ኮንስትራክሽን አ/ማ እነ እነ አቶ መሐመድ ሰይድ /ስድስት ሰዎች/	ሰኔ 03/2003	
72.	የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል በመጠርጠሩ የተነሳ ከሥራ ታግዶ የነበረና በኋላም የተሰናበት ሠራተኛ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ የፍ/ቤት ውሣኔ ያልቀረበ በመሆኑ ብቻ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑና ጉዳዩን በማስተናገድ ላይ የሚገኝ ፍ/ቤት የሠራተኛውን ስንብት አግባብነት ለመወሰን ማናቸውንም ማስረጃ አስቀርቦ በመመልከት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ያለበት ስለመሆኑ	59906	የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት እና ኃይለማርያም ሻረው	የካቲት 09/2003	
73.	ከሥራ ጋር ባልተገናኘ /ተፈጥሮአዊ/ ሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሥራ ስንብት ክፍያ የማይከፈል ስለመሆኑ	18495	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ወ/ሮ አሚናት ገበየሁ	መጋቢት 18/1999	
74.	• የቦነስ ክፍያ ለሠራተኛ የሚከፈለው በሥራ ላይ ያለ ሰራተኛ ወደፊት በርትቶ እንዲሰራ ለማበረታታት ብቻ ሳይሆን በሥራ ላይ በነበረበት ወቅት የሰራው ሥራ ለአሰሪው ትርፋማ ውጤት በማስገኘቱ የትርፉ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ጭምር ስለመሆኑ • የቦነስ ክፍያ ተጠቃሚ ለመሆን ሠራተኛው ድርጅቱ /ተቋሙ/ ትርፋማ ውጤት ባስገኘበት ዓመት በሥራ ላይ የነበረና አስተዋጽኦ ያደረገ መሆን ያለበት ስለመሆኑ	20869	አቶ አዲሱ አቦሴ እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/1998	
	ንብረት				
75.	ቤትና ቦታዬን ያለአግባብ ተነጠቅሁ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት ታይቶ ፍርድ ሊሰጥበት የማይችል አስተዳደራዊ ጉዳይ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37	48217	ወ/ሮ አባዲት ለምለም እና እነ የዛለአንበሳ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት	ጥቅምት 03/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4		/ሁለት ሰዎች/		
76.	የመሬት ይዞታ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በተወሰደ ጊዜ ካሣ የሚከፈለው በተወሰደው ይዞታ ላይ ንብረት የነበረ መሆኑ እንዲሁም ንብረቱን ለመተካት ከሚያስፈልገው ወጪ ጋር ተመጣጣኝነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 401/96 አንቀጽ 9/1/, 10 አዋጅ ቁ. 455/97	52496	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና እነ አቶ ከድር ኃሌጅንሶ /አስራ ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 16/2003	
77.	• አንድ ሰው የንብረት ባለቤት የሚሆነው በጉልበቱ፣ በፈጠራ ችሎታው ወይም በገንዘቡ ንብረትን ያፈራ እነደሆነ ስለመሆኑ • የፍርድ ባለዕዳ የሆነ ሰው ንብረቱ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዳይውል አስቦ አካለ መጠን ባልደረሰ ህፃን ልጁ ስም ማዞሩ ብቻ ከኃላፊነት ሊያድነው የሚያስችል ስላለመሆኑና ይህ በመሆኑም ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የለም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/2/	55081	ወ/ሪት ራሔል ሥነ ፀሐይ እና አቶ መስፍን ታምራት	ጥቅምት 18/2003	
78.	• መንግስት አንድን የግል ንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚወስድበት ጊዜ ሊከተለው ስለሚገባው ሥነ ሥርዓት • ለህዝብ ጥቅም ሲባል ንብረቱ የተወሰደበት ሰው የተሰጠው ግምት ከንብረቱ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ አይደለም በሚል ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1460-1488	50810	እነ አቶ ፀጋዬ መሠረት /ሰባ ዘጠኝ ሰዎች/ እና የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን	ጥቅምት 30/2003	
79.	የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ስመ ሃብት ይዞ መገኘት የንብረቱ ባለቤት አድርጐ የማያስቆጥር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196	47139	አቶ የሱፍ ሁሴን እና አቶ አደን አብደላ	ህዳር 30/2003	
80.	አዋጅ ቁ. 47/67 ከመውጣቱ በፊት የተደረገ የመሬት ኪራይ ውል ህጋዊ አስገዳጅነት ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 47/67	48086	እነ ወ/ሮ አሰለፈች ወልደሚካኤል /ሁለት ሰዎች/ እና ቶታል ኢትዮጵያ አክሲዮን ማህበር	ህዳር 03/2003	
81.	• ፍ/ቤቶች በሚቀርቡላቸው አቤቱታዎች ላይ ህግን ተፈፃሚ ለማድረግ የቀረበውን የክስ አርእስት ብቻ ሳይሆን ይዘት ጭምር መመልከት የሚገባቸው ስለመሆኑ • ከንብረት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149/1/ መሰረት ሁከት የተፈጠረበት ሰው እንዲወገድለት ይዞታው የተወሰደበት ሰው ደግሞ እንዲመለስለት በሚል ዳኝነት የሚጠየቀው አቤቱታ የቀረበበት ንብረት ተገምቶ ተገቢው ዳኝነት ከተከፈለበት በኋላ ስለመሆኑና በጥቅሉ የተፈጠረ ሁከት እንዲወገድ (cessation of interference) እንደሆነ ተቆጥሮ ልክ አቤቱታቸው በገንዘብ የማይገመቱ አቤቱታዎች አይነት ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑና የይርጋ ደንብ ተፈፃሚ የማይሆን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1149/2/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 16, 226/3/	49985	ሻለቃ አሰፋ አየለ ደምሴ እና ፍቃዱ ሙሉጌታ	ህዳር 28/2003	
82.	መሬት በፍ/ብሔር ግንኙነት የተፈጠረን ዕዳ ለመክፈል ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/3/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678/2/	49200	አቶ ጋሻው በጉሰው እና አቶ አለበል መከተ	ህዳር 01/2003	
83.	የከተማ መሬት ይዞታን እንዲለቅ የተደረገ ባለይዞታ በተወሰነለት የካሣ መጠን ላይ ካልተስማማ አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት በከተማው አስተዳደር ሥር ለተቋቋመ የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አካል ስለመሆኑ እና በመደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ ሊታይ የሚችለው በይግባኝ ብቻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 11/2/, /4/	57271	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና ጃዳ ብሩ	ታህሳስ 27/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

84.	• የማይንቀሳቀስ ንብረት /ህንፃ/ ግንባታ ሥራ ጋር በተገናኘ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ድንጋጌዎች • የሥራ ተቋራጭነት ውል ተፈጽሟል /አለ/ ለማለት የሚቻልበት አግባብ • የግንባታ ሥራ ውል በልዩ ፎርም መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3019-3040	47526	ዛፍኮ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ብሔራዊ መሐንዲሶች ስራ ተቋራጭ ድርጅት	ግንቦት 15/2003	
85.	• የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በቅን ልቦና የተደረገ ነው በሚል ምክንያት ብቻ በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የማይችል ስለመሆኑ • በህግ ፊት በማይፀና ሁኔታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው ይህንኑ ንብረት ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የሚያደርገው የሽያጭ ውል ህጋዊ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ • የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ መብት ከሌለው ሰው እያወቀ የሽያጭ ውል የፈፀመ ገዢ በቅን ልቦና የተደረገ ነው በሚል የሕግ ጥበቃ የሚደረግበት ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196, 2882-2884	60720	ወ/ሮ ሄርያ መሐመድ ግርግቦ እና አቶ ሸምሱ የሱፍ	ግንቦት 15/2003	
86.	ተከራይ ለሆነ ወገን በተከራየው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የባለቤትነት ወይም ሌላ መብት አለን በማይሉ 3ኛ ወገኖች አድራጐት ለሚነሳ ሁከት አከራይ ዋስትና እንዲሰጥ የማይገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2914/1/, /2/, 2913/1/, /2/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158	63042	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ሰለሞን ነጋሽ	ግንቦት 01/2003	
87.	ለህዝብ ጥቅም ሲባል ይዞታውን እንዲለቅ የተደረገ ሰው በመሬቱ ላይ የሰፈረውን ንብረት ለመተካት ከሚከፈለው ካሣ በተጨማሪ በይዞታው ላይ የነበረው ንብረት በመፍረሱ የተነሳ የተቋረጠ ገቢ /የታጠ ጥቅም/ ካሣ ሊከፈል የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀጽ 2/1//ለ/, 7/1/2/ ደንብ ቁ. 135/99	63352	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ቱሌ አብዶ	ሐምሌ 13/2003	
88.	• ተከራይ በይዞታው ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት አከራይ ባለበት ዕዳ ምክንያት ባለገንዘብ የሆነ ወገን ንብረቱን መረከቡ በተከራዩ ላይ የሁከት ተግባር ፈጽሟል የማያስብል ስለመሆኑ • የተከራዩ እና በንብረቱ ላይ መብት ያለው ባለገንዘብ የሚኖራቸው ተነፃፃሪ መብት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140 1149 2933/1/ 2899 2931 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 6	62858	ፓዝ ፋይንደር ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ እና እነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ /ሁለት ሰዎች/	ግንቦት 16/2003	
89.	ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚመለከተው የአስተዳደር አካል እንዲፈርስ መረጃ የደረሰው በመሆኑ ቤቱን ያፈረሰ ሰው የአስተዳደር አካሉ የዲዛይን ለውጥ አድርጐ ቤቱ ከፈረሰ በኋላ የማለሰቡን ይዞታ /ንብረት/ መፍረስ የማያስፈልግ መሆኑን መግለፁ ካሣ የመክፈል ግዴታውን ቀሪ የማያደርግ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 322/97 አዋጅ ቁ. 455/97 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት art. 40/2/	62293	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና እነ አቶ መስፍን ጀንበሩ /ሁለት ሰዎች/	ግንቦት 15/2003	
90.	• አንድ ሰው የሌለውን ነገር ሸጦ በተገኘ ጊዜ ገዢው በህግ ሊያገኝ ስለሚገባው መፍትሔ • በሌለ መብት መሥራት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2884/1/ /2/, 2282-2285, 1716	51034	ታሪክ ጌታቸው እና እነ ወ/ሮ አልጋነሽ ተጠምቀ /ሁለት ሰዎች/	የካቲት 22/2003	
91.	• የኮንዶሚንየም ቤትን ዋጋ አጠቃላይ የከፈለ የኮንዶሚንየም ቤት ባለቤት በፍርድ የተወሰነበት የሌላ ሰው ዕዳ ያለበት በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ቤቱ በአፈፃፀም ተሸጦ ለዕዳው መክፈያነት እንዲሆን ለማዘዝ የሚችሉ ስለመሆኑ • የኮንዶሚንየም ቤት ባለሀብት የሆነ ሰው በራሱ ፈቃድ	56011	አቶ ሳሙኤል ታደሰ እና ወ/ሮ እጥፍወርቅ ኃይለማርያም	መጋቢት 23/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ ወይም ለ3ኛ ወገን ለማስፈላለፍ የሚችለው ያለበትን የቤቱን ዋጋ አጠናቅቆ ከከፈለበት ጊዜ ጀምሮ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 19/97 አንቀጽ 21, 14/2				
92.	• በህጋዊ መንገድ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ውል ያገኘ ገዢ የሚመለከተውን የአስተዳደር አካል የስም ዝውውር እንዲፈጽምለት በፍ/ቤት ለመክሰስ የሚችል ስለመሆኑ • የሚመለከተው የአስተዳደር አካል በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት ካልተወጣ ገዥ መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ የሚገባው በዚሁ የአስተዳደር አካል ላይ ስለመሆኑ የአማራ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ. 91/96 እና ደንብ ቁጥር 12/2000	49428	እነ ወ/ሮ ከበቡሽ ልሳነወርቅ /ሁለት ሰዎች/ እና እነ አቶ ፀዳሉ አዳነ /ሁለት ሰዎች/	ህዳር 28/2003	
	ጉምሩክ /ቀረጥ/ ግብር				
93.	በስህተት ለጉምሩክ የተከፈለ ቀረጥ ተመላሽ የሚደረገው ስህተቱ መኖሩን ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወቀና ዕቃውም የጉምሩክ ስነ ስርዓትን አጠናቅቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ውጭ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ ባለው 6 ወር ውስጥ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 15 አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 53, 55	53749	የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ እና አቶ አዱኛ አበሉ	ጥቅምት 18/2003	
94.	ከቀረጥ ነፃ በሆነ መልኩ ለግል አገልግሎት እንዲውል የገባ መኪናን ለንግድ ማዋል በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/, 78	54203	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ወ/ሮ ሙሉአመቤት ኃ/ሚካኤል	ህዳር 27/2003	
95.	ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎችን አስመልክቶ ስለሚካሄድ የቅድመ ጭነት ምርመራ ሥርዓት እና በዕቃው ላይ ስለሚከፈል ግብር /ታክስ/ አዋጅ ቁ. 173/91 አንቀጽ 6/1/, 4/1/	50375	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ ለተብርሀን አድሀኖም /ሁለት ሰዎች/	ህዳር 13/2003	
96.	የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግን ተላልፏል በሚል በወንጀል የተከሰሰ ስራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው አልነበረም ወይም አያውቅም በሚል ምክንያት ከወንጀል ኃላፊነት ነፃ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 56/1/ 55 አዋጅ ቁ. 609/209 አንቀጽ 22/1/ 50/ስ//1/	51090	እነ ዘ ቲዊንስ ባርና ሬስቶራንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/ እና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን	ታህሳስ 12/2003	
97.	• የጉምሩክ ባለስልጣን ኮንትሮባንድ እንደተፈፀመበት በበቂ ሁኔታ የጠረጠረውን ተሽከርካሪ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ለሚያደርገው ማጣራት ለባለንብረቱ የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፍል የማይጠየቅ ስለመሆኑ • ባለስልጣኑ በቁጥጥሩ ሥር የሚያውላቸው ተሽከርካሪዎች የተያዙበትን ጉዳይ ለማጣራት ከሚያስፈልገው ተገቢና ምክንያታዊ ጊዜ በላይ የሆነ እንደሆነ የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ • በባለስልጣኑ ቁጥጥር ሥር የቆዩ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የተቋረጠ ገቢ ይከፈለን በሚል አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤት የተጠየቀውን ገቢ ህጋዊነት እና ትክክለኛነት በማረጋገጥ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 6/5/ 58/1//1 አዋጅ ቁ. 368/95	43996	የሰሜን ምስራቅ ጉምሩክ ሚሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና በረከት አሰፋ	ጥር 10/2003	
98.	• አንድ ግብር ከፋይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ግብር ከፋይነት ተመዘገበ የሚባለው በባለሥልጣኑ ከተመዘገበበት ዕለት ወይም ምዝገባው እንደሚፀና ከተገለፀበት ጊዜ ጀምሮ	59851	አቶ አለሙ ጋባ እና የፌዴራል ገቢዎችና	የካቲት 11/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመሆኑ • የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ተመዝጋቢ የሆነ ሰው ከተመዘገበበት ዕለት ጀምሮ ለሚያደርገው ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለተጠቃሚው ወዲያውኑ ያልሰጠ መሆኑ በወንጀል የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ • እውቅና ያልተሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ መጠቀም በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 471/98 አንቀጽ 5 አዋጅ ቀ. 285/94 አንቀጽ 64, 3/1/ኘ/2/, 22/1/ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 117 ደንብ ቁጥር 139/99 አንቀጽ 22 መመሪያ ቁጥር 46/99		ጉምሩክ ባለስልጣን		
99.	• በጉምሩክ አዋጅ ቁ. 368/95 /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 74 ሥር ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ሊጣልበት ስለሚችለው የቅጣት አይነትና መጠን • በኮንትሮባንድ ዕቃ ሲያንቀሳቅስ የተገኘ ተሽከርካሪ ሊወረስ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 60/89 አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 64/4/, 74	48628	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ሕግ እና አቶ በርሄ ሐጐስ	ግንቦት 05/2003	
100.	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አስቀድሞ በዋስትና ለሌላ ሰው ያልተሰጡ የግብር ከፋይ ንብረቶች ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/, 78/1/	57100	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጅማ ቅ/ጽ/ቤት እና እነ አቶ አዳራ ሰይድ /ሁለት ሰዎች/	ግንቦት 30/2003	
101.	የተሸከርካሪ ባለንብረትና ሹፌር በመሆን የኮንትሮባንድ ወንጀል በተሸከርካሪ በመታገዝ የተፈፀመ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የግለሰቡን የወንጀል ጥፋተኝነት ውሣኔ ተከትሎ ተሽከርካሪው እንዲወረስ ትዕዛዝ መሰጠት ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 91/2/, 2/1/	64819	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና አቶ አንተነህ ካሣዬ	ሰኔ 30/2003	
102.	ከቀረጥ ነፃ፣ በቅናሽ ቀረጥ ወይም በጊዜያዊነት ከቀረጥ ነፃ የገባን ዕቃ ህግን በሚቃረን መልኩ የቀረጥ ነፃ መብቱ ከተሰጠበት ምክንያት ውጪ መጠቀም /ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት/ የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/ /ሀ/ /ለ/ /2/	58266	ወ/ሮ አልማዝ ደሴ እና የጉምሩክ ዓ/ህግ	ሰኔ 03/2003	
103.	• አንድ ዕቃ /ንብረት/ ኮንትሮባንድ ነው ወይም የጉምሩክ ስርዓት ያልተፈፀመበት ነው በሚል በቁጥጥር ስር ሊውል የሚችልበት አግባብ • የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ማስገባት ወይም ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት ዕቃው ኮንትሮባንድ እንዲባል የሚያደርግ ስለመሆኑና የኮንትሮባንድ ወንጀልን የሚያቋቁም ስለመሆኑ • "የጉምሩክ ክልል" በሚል የተጠቀሰው ሃረግ አጠቃላይ የኢትዮጵያ የግዛት ክልልን የሚያመላክት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 2/17/, 12/4/, 13/1/, 91/1/, 2/7/	60400	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ኤፍታታ እና ቢኤም ኤም ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ሐምሌ 12/2003	
104.	በህግ አግባብ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተፈፀመበት ዕቃ/ንብረት/ የኮንትሮባንድ ዕቃን ለማሳለፍ በሽፋንነትና በክለላነት ያገለገለ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ የጉምሩክ ባለስልጣን ይህን በሽፋንነትና በክለላነት ያገለገለውን ዕቃ ለመውረስ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 6/5/ 58/1/ /ለ/ 16-18 አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 22	65656	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና ወ/ሪት ትዕግስት ጥላሁን	ሐምሌ 26/2003	
105.	የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃን በማንቀሳቀስ የተያዘ ተሽከርካሪ እንዲወረስ ላይታዘዝ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 104/3/ /ሀ/ አንቀጽ 91/1/	57243	የሚሌ ገቢዎች እና ጉምሩክ እና አቶ ደረጀ ከፍያለው	መስከረም 27/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ሲማ		
106.	• ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • በደረሰ የአካል ጉዳት ወይም በሞት አደጋ ምክንያት ከሚሰጥ የካሣ ክፍያ በስተቀር ሌሎች በማናቸውም ሁኔታ የሚከፈሉ የካሣ ክፍያዎች ከግብር ነፃ ናቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ • ከሥራ መሰናበት ጋር በተገናኘ ለሰራተኞች የሚሰጥ የመልሶ ማቋቋሚያ የድጋፍ ክፍያ የሥራ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 10/1/, 2/10/, 1/11/	65330	የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር እና እነ አቶ ተክሌ ጋረደው /ስድስት ሰዎች/	ሰኔ 30/2003	
107.	በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ግብር ከፋይ ይግባኙን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ለማቅረብ የሚችለው በጉባኤው የተወሰነበትን ግብር ይግባኝ ሙሉ በሙሉ ሲከፍል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 112/4/ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 43/4/	59711	ሸበል ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ህግ	ሰኔ 14/2003	
	ከውል ውጭ ኃላፊነት				
108.	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት በመኪና ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ የመኪናው ባለቤት በደረሰው ጉዳት የተነሳ ሊከተል የሚችለውን ኪሣራ ለመቀነስ ተገቢውን ጥረት የማድረግ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2091, 2097/1/ /2/	54021	አቶ ዱላ ያሲን እና ወ/ሮ አበበች እሸቱ	ህዳር 03/2003	
109.	የህንፃ ተቋራጭ ሠራተኛ በመሆን በሚሠራው ህንፃ ላይ ሥራውን በማከናወን ላይ እያለ ከህንፃው ወድቆ ጉዳት የደረሰበት ሰው የሚሰራውን ህንፃ ባለቤት ከውል ውጭ የሆነ ግንኙነትን መሰረት በማድረግ የጉዳት ካሣ ሊጠይቅ የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2077	52595	ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት እና እነ ወ/ሮ ሻሎም ተስፋዬ /አራት ሰዎች	ታህሳስ 15/2003	
110.	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የዘረጋቸው የኤሌክትሪክ መስመር ገመዶች ለሚያደርሱት ጉዳት ከኀላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችለው ጉዳቱ የደረሰው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በተጐጂው ጥፋት መሆኑን በማስረዳት ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2086/2/	57904	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ወልዱ ገ/ስላሴ	ታህሳስ 15/2003	
111.	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ተፈፃሚ ከሚሆነው የይርጋ ጊዜ ጋር በተገናኘ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት የሆነው ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣና ጥፋት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ አጥፊው በወንጀል ጉዳይ ክስ ያልቀረበበትና ያልተቀጣ እንኳን ቢሆን በወንጀል ህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 /1/ እና /2/	58920	አለምነው አበበ አካሌ እና ህብረት ኢንሹራንስ አ.ማ	የካቲት 22/2003	
112.	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ፍ/ቤቶች የጉዳት ካሣን አስመልክቶ የሚሰጡት ውሣኔ በይግባኝ ሊሰወጥ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2152, 2153	53598	አቶ ይልማ ደጀኔ እና ወ/ሮ መዲና ዲታሞ	ግንቦት 19/2003	
113.	የባንክ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ጥፋት ፈጽሟል በሚል በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልበት ብሎም ላደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍል ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2524/2/, 1676/1/, 1790/2/, 2090	44427	አቶ ለገሰ ጥቀኔር እና ንብ ኢንተርናሽናል አ.ማ	መጋቢት 09/2003	
114.	• አንድ ሰው የሌላውን ሰው የሥራ ድካም ወይም በሌላው ሰው ሀብት በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ እንደሆነ አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሀብቱ ወይም በጉልበቱ ለደከመው ሰው የመክስ ግዴታ ያለበት	59698	አቶ ሚኪያስ ከበደ እና እነ ወ/ሮ ምስራቅ ንጉሴ /ሁለት ሰዎች/	መጋቢት 06/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመሆኑ • አንድ ሰው ባለዕዳ መሆኑን ያመነ እንደሆነ ዕዳው የታመነለት ሰው ባለዕዳው ዕዳውን ያመነበትን ምክንያት የማስረዳት /የማረጋገጥ/ ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162 2164 2019				
115.	• በህጸምና ጉድለት ሀላፊነት ሊከተል የሚችልበትና ካሣ የሚከፈልበት አግባብ • የጉዳት ካሣን ለመወሰን የጉዳቱን ልክ በማስረጃ ለማረጋገጥ አዳጋች ሲሆን በርትዕ ለመወሰን የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090, 2102	64590	ሜሪስቶፕስ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ እና ወ/ት ሠናይት ዓለማየሁ	ሚያዝያ 18/2003	
116.	የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥ ተሽከርካሪ ተሳፋሪ በመሆን ሲጓዙ ለሚደርስ ጉዳት አንገዙ ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችልባቸው ልዩ ሁኔታዎች፣ ኃላፊ በሆነ ጊዜ የኃላፊነቱ መጠን እንዲሁም አንገዙ በህግ ከተደነገገው የጉዳት ካሣ መጠን በላይ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልባቸው ሁኔታዎች የንግድ ህግ ቁ. 595, 596, 599, 588, 597 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2130, 2092, 2091	67973	አቶ በቀለ ወልቻም እና አቶ ጥበቡ ጦራ	ሐምሌ 25/2003	
117.	• መኪና ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ልዩ የምዝገባና የባለሀብትነት ስም ዝውውር የሚያስፈልገው ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ንብረት ስለመሆኑ • የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤትነት /ባለሃብትነት/ ወደ ሌላ ሰው ተላልፏል ሊባል የሚችልበት አግባብ • መኪኖች እና ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ለሚያደርሱት ጉዳት በኃላፊነት ስለሚጠየቀው ወገን የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1186/1/ /2/, 2081/1/, 2082/2/, 2083/1/, 2267/2/, 2324/1/ አዋጅ ቁ. 256/60 አንቀጽ 6 አዋጅ ቁ. 468/97 አንቀጽ 21 ደንብ ቁ. 360/61 አንቀጽ 6 7/1/ /3/, 8, 11/1/ /2/, 42-45	24643	ወ/ሮ አስናቀች ወ/ማርያም እና አቶ አለማየሁ አህመድ	ሐምሌ 29/2000	
118.	ባለሞተር ተሽከርካሪ ከሚያደርሰው ጉዳት ጋር በተያያዘ የመጨረሻው ኃላፊነት (ultimate liability) የሚወድቀው መኪናው ሲሽከረከር የነበረው ባለቤቱ በቀጠረው ሹፌር እንኳን ቢሆን በወቅቱ በመኪናው ሲገለገል የነበረው ሰው ላይ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2082/1/, 208/1/, 2083/1/	55228	አቶ አብራር ሳቢር እና እነ ወ/ሮ አለምፀሐይ ወሰኔ /ሁለት ሰዎች/	ጥር 25/2003	
119.	ከውል ውጭ የሌላ ሰው ሃብት የሆነን ነገር በመያዝ ለተገለገለበት ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል በሚል የቀረበ አቤቱታ ጋር በተያየዘ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024 ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024	54518	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ ፀሐይ ዘመ.ይ /ሁለት ሰዎች/	የካቲት 14/2003	
120.	• ለአካለ መጠን ያልደረሱ ህፃናት ላይ ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ሲደርስ የጉዳት ካሣ መክፈል የሚገባው ስለመሆኑና የካሣ አወሳሰኑ ስሌት • በገንዘብ ለመተመን የሚያዳግት የአካል ጉዳት በደረሰ ጊዜ ካሣ በርትዕ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090, 2091, 2092/2/, 2095/2/	38117	አቶ ብርሃኑ ፈይሳ ቢፍቱ እና እነ ናይል ኢንሹራንስ /ሁለት ሰዎች	ሐምሌ 09/2001	
	አፈፃፀም				
121.	በዕዳ ምክንያት በፍ/ቤት የተከበረ ንብረት እንዲሸጥ በተደረገ ጊዜ ንብረቱን ያስከበረው ወገን የሚኖረው መብት ከሽያጭ ገንዘቡ ላይ የቀዳሚነት መብት ያላቸው ባለገንዘቦች የሚተርፍ ካለ መውሰድ ነው እንጂ ንብረቱን በሽያጭ ውል የተነሳ ባለቤት የሆነን ወገን መጠየቅ ወይም ንብረቱን የመከተል ስላለመሆኑ	48042	ጉና ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ እና እነ ቡሬ ባጉና የማዕድን ውሃ ፋብሪካ /ሦስት ሰዎች/	ጥቅምት 03/2003	
122.	የአፈፃፀም ክስና መጥሪያው ደርሶት የፍርድ ባለዕዳ ሳይቀርብ	53943	እነ ወ/ሮ አስካለ	ህዳር	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በሚቀርበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ሥርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/"ን" ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ስላለመሆኑ እና የተሰጠን ትዕዛዝም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 መሠረት ለማስነሳት የሚቻልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/, 78		ደግለኝ /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ የትምወርቅ ታደሰ /ሁለት ሰዎች/	16/2003	
123.	በአንድ የፍርድ ባለዕዳ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ ባለገንዘቦች አፈፃፀም ሊቀጥል የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403, 378	40945	ኮለኔል ግርማ ሃይለስላሴ እና አቶ አስማማው መንግስቱ	ጥር 13/2003	
124.	ፍርድን የሚያስፈጽም የአፈፃፀም ችሎት የተሰጠውን ፍርድ በአግባቡ ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የገመተውን ትዕዛዝ ለመስጠት የሚያስችል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 392/1/	62804	እነ አቶ ብርሃን ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ለታይ ገ/ጊዮርጊስ	ሰኔ 15/2003	
125.	በፍ/ብሔር ክርክር የተፈረደበት ሰው የፍርዱ አፈፃፀምን ለማሰናከል የተንቀሳቀሰ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ እስከ ስድስት ወር በሚደርስ እስራት ሊቀጣ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 389/1//ሀ//ለ/	63754	አቶ ዓለም ባህታ እና ወ/ሮ ኑኑሽ ሸህምሎ	ሰኔ 15/2003	
126.	• ፍርድን የሰጠ ፍርድ ቤት ፍርዱ በውክልና እንዲፈፀም ለሌላ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ባስተላለፈ ጊዜ በውክልና ፍርድ ለማስፈፀም ስልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ፍርድ ከሰጠው ፍርድ ቤት ማረጋገጫ እንዲላክለት ለመጠየቅ የሚችለው የፍርዱ ወይም ትዕዛዙ ግልባጭ ትክክለኛነት የሚያጠራጥር ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ካለው ብቻ ስለመሆኑ • ፍርድን በውክልና እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ የደረሰው ፍርድ ቤት ስለፍርዱ ትክክለኛነት ወይም በግልባጮቹ ላይ ስለሰፈረው ነገር ሌላ መግለጫና ማብራሪያ ሳይጠይቅ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ማስፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 373/2/ 371/1/	66988	አቶ ቀደመ ተሾመ እና አቶ ኢብራሂም ሐመዱ	ሐምሌ 25/2003	
127.	ፍርድን የሰጠ ፍ/ቤት ፍርዱ እንዲፈፀምለት ለሌላ ፍ/ቤት የውክልና ስልጣን ስለሚሰጥበት አግባብና የፍርድ አስፈፃሚ ፍ/ቤት የስልጣን አድማስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371-455	64354	አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና ወ/ሮ ኡልባሬ ሰማን	ሰኔ 13/2003	
128.	ፍርድ የማይፈፀመው ፍርዱ በይግባኝ ስርዓት የተለወጠ እንደሆነ ወይም ፍርዱን ላለመፈፀም ህጋዊ ምክንያቶች ያሉ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378, 386	59301	መምህርት አታቱ ከበደ እና ስቴፕንስ አት.ኢዲኪሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር	ግንቦት 04/2003	
129.	በአፈፃፀም ደረጃ የሚገኝ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78/1/ ያለው አግባብነት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 /1/	52110	እነ ወ/ሮ ይህደጋ ሳሙኤል /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ አሰፋ ሳሙኤል /አራት ሰዎች/	ታህሳስ 26/2003	
130.	• በክርክር ሂደት ተሳታፊ ያልነበረና ፍርድ ያልተሰጠበት ሰው ንብረት በፍርድ አፈፃፀም ሲያዝበት /በሃራጅ ሲሸጥበት/ ሊከተለው ስለሚገባው አካሄድ • በፍርድ ሊያዝ ስለሚችል ንብረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447/1/, 418, 234/1/ /ሠ/, 235/2/, 414/2/, 423, 425, 443, 453/1/ /3/	58009	እነ አቶ ስለሺ ወርቅነህ /ሦስት ሰዎች/ እና እነ አቶ ሁሪሳ ደመሳ /ሁለት ሰዎች/	ጥር 262003	
131.	ከግብርና ተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተያያዘ በአፈፃፀም ደረጃ የሚቀርብ የቀዳሚነት መብት ይከበርልኝ ጥያቄ የህግ መሰረት ያለውና ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 32/1/ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 80/1/	48997	የቦሌ ክ/ከ/ገቢዎች መምሪያ እና እነ አቶ መዓዛ ሽፈራው /ሁለት	ጥቅምት 16/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418		ሰዎች/		
	ልዩ ልዩ				
132.	በጤና ጥበቃ ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ከጤና ሥነ ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ በጤና ባለሙያዎች መማክርት ጉባኤ ክስ በቀረበባቸው ጊዜ በተገቢው መንገድ መልስ የመስጠትና የመሰማት መብታቸው ሊጠበቅ የሚገባ ስለመሆኑ የኢትዮጵያ ጤና ባለሙያዎችን መማክር ጉባኤ ማቋቋሚያ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 16/1/ /2/	56934	እነ አሰገደች የእናቶች እና የህፃናት ሆስፒታል እና የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	መስከረም 26/2003	
133.	በውጭ አገር የተደረጉ ሰነዶች (foreign documents) በኢትዮጵያ ውስጥ ህጋዊ ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 26/1/	32282	ሚ/ር ካርሎ ካስቴሊ እና የወ/ሮ ዘውዴ ደሚኪ ውርስ አጣሪ አቶ ታምራት ኪዳነ ማርያም	መስከረም 25/2003	
134.	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሻሻለ አዲስ የባንክ ስራ ፈቃድና የዳይሬክተሮች እና የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሹመትን አስመልክቶ የሚያወጣው መመሪያ ህጋዊ መሰረት ያላቸውና በተግባር ሊውሉ የሚገባ ስለመሆኑ መመሪያ ቁጥር ኤስቢቢ/39/ 2006 አንቀጽ 5.1.4 አንቀጽ 5.1.5 አዋጅ ቁ. 83/89 አዋጅ ቁ. 84/86	44226	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና እነ ህብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ /ሦስት ሰዎች	ታህሳስ 15/2003	
135.	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በህግ ከተጣለበት የጡረታ አበል የመክፈል ግዴታው ጋር በተያያዘ የአንድን ሰው ባልነት /ሚስትነት/ በማረጋገጥ የተሰጠ ውሣኔን የመቃወም መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ህ/ቁ. 358	53221	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ንጋት ወ/ሰንበት	ታህሳስ 27/2003	
136.	የጥብቅና ፈቃድ ክልከላ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ ለሚመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ ታይቶ የሚወሰን እንጂ በቀጥታ ክልከላ እንዲወገድ በሚል ለፍ/ቤት አቤቱታ የሚቀርብበት ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 29/1/	59261	የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር እና አቶ ታዬ በዛብህ ፊኖ	ጥር 24/2003	
137.	በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40/8/ መሰረት ለተወሰደ ንብረት የሚጠየቅ ካሣ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1143 እና 2143 በሁለት ዓመት ይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ	59979	የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ከበደ ወዳጆ	የካቲት 09/2003	
138.	የቡና ላኪነት ፈቃድ አውጥቶ በግብይት ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅን ጥሷል በሚል በወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ መሰረት ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 602/2000 አንቀጽ 14/3/, 15/3/ ደንብ ቁ. 159/2001 የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር መመሪያ	58008	እነ ኤርሰዴ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	ግንቦት 16/2003	
139.	በጡረታ የተገለለ ሰው በሌላ ሥራ ላይ በተቀጠረበት ጊዜ መንግስት ለጡረተኞች ያደረገውን የጡረታ ጭማሪ መሰረት በማድረግ አሰሪው የደመወዝ ጭማሪ እንዲያደርግለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	60025	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ወለዴ በየነ /አራት ሰዎች/	ግንቦት 02/2003	
140.	• ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ "እስከመጨረሻ ድረስ በመያዝ ለመከራከር" በሚል የሚያደርገው ስምምነት ጉዳዩ ሊያስኬድ የሚችል እስከሆነ ድረስ በአንድ ፍ/ቤት ሳይወሰን በይግባኝና በሰበር ደረጃ ሁሉ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ • ጠበቃ ከደንበኛ ጋር ባለው ግንኙነት ደንበኛው ማድረግ ያለበትን ነገር ከህግ አንፃር የማስረዳትና ግልጽ የማድረግ ብሎም የማማከር ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም በአንፃሩ	60353	አቶ ባልቻ ወ/ፃጽቅ እና አቶ ግርማ ቀለታ	ግንቦት 04/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አከራካሪ ጉዳይ በሌለበት ሁኔታ ክስና ክርክር ለማቅረብ የማይገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1732 ደንብ ቁ. 57/92 አንቀጽ 28, 8/2/				
141.	የፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በህግ የተሰጠውን ስልጣን መሰረት በማድረግ አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ በድጋሚ በማየት የተለየ ውሣኔ በሰጠ ጊዜ የተለወጠውን /የተሻረውን/ ውሣኔ መሰረት በማድረግ የተከናወኑ ተግባራትን ለማስተካከል ወይም የተከራካሪ ወገኖችን መብት ለማስተካከል ተገቢ የሆነ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349, 6	60508	እነ ወ/ሮ ሮዛ አባተ /አራት ሰዎች/ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ግንቦት 15/2003	
142.	በፌዴራል ፍ/ቤቶች በጥብቅና ለመስራት የሙያ ፈቃድ የሚሰጥበት አግባብ	67280	የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚ/ር እና እነ አቶ ተስፋዬ በርሄ /አምስት ሰዎች/	ግንቦት 15/2003	
143.	የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራን ዜግነት መርጦ የያዘ ሰው “የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ” ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 270/94 አንቀጽ 2/2/ ደንብ ቁ. 101/96 አንቀጽ 2/1/	55238	እነ የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ህዳት ፍስሃ ጽዮን	መጋቢት 09/2003	
144.	• ጠበቃ የሆነ ሰው ደንበኛውን ወክሎ ለፍ/ቤት የሚያቀርበው አቤቱታ እውነት ስለመሆኑ በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • ማንኛውም ጠበቃ የህግ ሙያውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሁሉ ለደንበኛው፣ ለሌሎች የህግ ባለሙያዎች፣ ለተከራካሪ ወገኖች፣ ለፍርድ ቤት፣ ለሙያው ብሎም በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ኃላፊነቱን በቅንነት፣ በታማኝነት እና በእውነተኛነት የመወጣት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 92/1/ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁ. 57/92 አንቀጽ 3 29/2/ 56/4/ /6/	67146	ሻምበል ተሾመ ደምሴ እና የፍትህ ሚኒስቴር ዓ/ህግ	ሐምሌ 01/2003	
145.	አጣው ከመድረሱ በፊት አባልነቱን ያቋረጠ የአቁብ አባል ለአቁብ የከፈለውን ገንዘብ ይመለስልኝ በሚል የኃላፊነት ጥያቄ ሊያቀርብባቸው ስለሚችሉ አካላት	55794	አቶ ለማ አበበ እና ወ/ሮ ሃና አሰፋ	ጥር 24/2003	
146.	• በፍርድ ቤት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ፀንቶ ባለበት ወቅት እግድ የተሰጠበት ንብረት ተሸጦ በተገኘ ጊዜ የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን ሊኖረው ስለሚችለው መፍትሔ • የፍርድ ቤትን የእግድ ትዕዛዝ አለማክበር /መጣስ/ ኃላፊነትን የሚያስከትል ተግባር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2028, 2035, 2126	54567	የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና እነ የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ /ሦስት ሰዎች/	የካቲት 10/2003	
147.	• በአንድ በቀረበ ክርክር ላይ የተሰጠው ውሣኔ የቀረቡትን ማስረጃዎች ይዘት ወይም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነጥብ ከሕጉ ጋር በአግባቡ ተዛምዶ አልታየም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የሕግ ነጥብ /ክርክር/ እንጂ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ተብሎ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል አይደለም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ • የሰበር ችሎት በሥር ፍ/ቤቶች የቀረበን ማስረጃ ክብደትና ተዓማኒነት ለመመርመር በህግ ስልጣን ያልተሰጠው ስለመሆኑ	44804	ወ/ሮ ሰናይት ተመስገን እና ወ/ሮ እጥፍወርቅ በቀለ	ጥቅምት 04/2003	
148.	በወንጀል ድርጊት በኢንዚብትነት ተይዞ የነበረ ወርቅ ከተሸጠ በኋላ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ከተሻረ ሻጩ አካል የወርቁን ዋጋ መክፈል ያለበት በተሸጠበት ወቅት በነበረው ዋጋ ስለመሆኑ	58822	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ሕግ እና አይንሸምስ ሁሴን	መጋቢት 05/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

149.	• የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአንድ ወቅት በአንድ ጉዳይ /ጭብጥ/ ላይ የሰጠው የህግ ትርጉም እንደተለወጠ /እንደተሻሻለ/ ሊቆጠር የሚችለው በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ በህግ አግባብ የተለየ ግልጽ ትርጉም በሰጠ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ • የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ ተቀብሎ ማስተናገድ ብሎም የውርስ አጣሪ መሾም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በህግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ/ /የሰ/መ/ቁ. 35657፣ 42015፣51329 ይመለከቷል/ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41 አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/4/	52530	እነ አቶ ሰናይ ልዑልሰገድ /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ኃይሌ	ህዳር 14/2003	
150.	የይርጋ መርህ ክስን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከትና ንብረትን በመያዝ ወይም ባለይዞታ በመሆን የባለሀብትነት መብት ከሚገኝበት መርህ የሚለይ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1168, 1808	53328	ዓብዱል መሐመድ እና ወ/ሮ ዘበናይ ኃይሌ	ጥቅምት 18/2003	
151.	• የድምጽ ብክለት ተከስቷል ለማለት የሚቻለው የሚሰማው ድምጽ ከመጠን በማለፉ በሌሎች ላይ ሁከት የሚፈጥር መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ • የድምፁ ብክለት (Nuisance) ተፈጥሮብኛልና እንዲወገድ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በሁለት ዓመት ይርጋ ታግዷል ሊባል የማይችል ስለመሆኑ • አንድ ሥራን ለመስራት የንግድ ፍቃድ የሰጠ አካል ሥራው የሚፈጥረው የድምጽ ረብሻ አለ በሚል የንግድ ፈቃዱን የሚሰረዝበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 10 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1225, 1226, 1149	42824	አቶ ብርሃነ ተሰማ እና እነ አቶ ታምራት ኪዳኔ /ሁለት ሰዎች/	ህዳር 08/2002	
152.	• የአስተዳደር አካል የሰጠው ውሣኔ ወይም የወሰደው እርምጃ ህገ ወጥ መሆኑን እስካረጋገጠ ድረስ ውሣኔውን ለማረም /እንዲስተካከል ለማድረግ/ ስለመቻሉ • በተሳሳተ መንገድ በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሣኔ ቅን ልቦና አድሮበት ለኪሣራ የተዳረገ ሰው ኪሣራ ለመጠየቅ ስለመቻሉ • በስህተት በተሰጠ የግንባታ ፈቃድ ግንባታ ያካሄደ ሰው የአስተዳደር አካሉ ስህተቱን በማረም ግንባታው እንዲፈርስ መማለጫ በሰጠ ጊዜ የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ	57044	እነ የልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 04/14 ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ታሪኩ ኡርጌሳ	ጥር 25/2003	
153.	• ለዳኝነት የቀረበው ጉዳይ በባህሪይው ከአንድ በላይ የሆኑ የህግ ስርዓቶችን ለጉዳዩ አወሳሰን የሚጋብዝና የየትኛው ሥርዓት ህግ ተመራጭ ሊሆን ይገባል የሚል ጥያቄን የሚያስነሳ እንደሆነ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የፍ/ብሔር ስልጣኑ ሊታይ የሚችል ስለመሆኑ • ተዋዋይ ወገኖች በማናቸውም ሁኔታ የአገሪቱን ህግ ወደ ጐን በማድረግ ወይም በሚዛረር መልኩ ስምምነት ስላደረጉና ክርክር ስለተነሳ ብቻ አንድ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ህግ ጥያቄን/private international law issue/ የሚያስነሳ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ • በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ካልተወሰነ በቀር አዋጅ ቁጥር 377/96 የውጭ አገር ድርጅት ሆኖ በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሚሰራ ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/3//ለ/ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 11/2/ /ሀ/	54121	ሲ.ኤ.ኤስ ኮንስልቲንግ ኢንጂነርስ ሳልዝ ጊተር ጂ.ኤም.ቢ.ኤች እና አቶ ካሣሁን ተወልደብርሃን	ህዳር 01/2003	
154.	• የክስ ይዛወርልኝ (change of Venue) ጥያቄ ከተከራካሪ ወገኖች የሚነሳ ስለመሆኑና ፍ/ቤትም ጥያቄውን ሊያስተናግድ የሚችለው በህግ የተመለከቱት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ	66945	የእንግሊዝ ህግናት አድን ድርጅት እና አቶ ገለስ አስማን	ሰኔ 02/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• የክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክሶችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸው ለማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆናቸው አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 136/3/, 138/2/, /1/, 139/1/ /ሀ/ አዋጅ ቁ. 322/95 አዋጅ ቁ. 25/88				
155.	ለብድር በመያዣነት የተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ውሉ መሰረት በህጉ አግባብ በዋስትና ከመያዙ በፊት በሽያጭ ለሦስተኛ ወገን ተላልፎና ስመ ሃብቱ ለገዢው ተላልፎ በተገኘ ጊዜ ሊኖር ስለሚችለው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3051/2/	65688	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ንጉሴ በያን	ሐምሌ 27/2003	
156.	የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 14/1//ረ/, 66/1/ አዋጅ ቁ. 2/95 አንቀጽ 52	53551	የቀበሌ 10 ባለአደራ ቦርድ እና አቶ ዳንኤል አድርሴ	መስከረም 25/2003	
157.	ይዞታን አስመልክቶ ከሚነሳ የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር ያለበት አቤቱታ አቅራቢው የይዞታ መብቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ካገኘበት ቀን ጀምሮ እንጂ አቤቱታ የቀረበበት ድርጊት መፈፀም ከጀመረበት ዕለት አንስቶ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140, 1149, 1146/1/, 1144/2/	60392	አቶ ጌትነት የኔ እና አቶ እዮብ ቢንያም	ታህሳስ 26/2003	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ - 13

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት መልዕክት</u>

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሕግ ትርጉም የተሠጠባቸው ውሣኔዎች በቀጣይ የፍርድ ቤቶች ሥራዎች ወሣኝ እንደመሆናቸው ቶሎ መሠራጨት እንዳለባቸው እሙን ነው፡፡ የሰበር ውሣኔዎችን ኮፒ ውሣኔ እንደተሠጠ ባለጉዳዮች ማግኘት የሚችሉ ሲሆን ውሣኔዎችን በአንድ ላይ ለማሣተም ግን ቀደም ሲል ይፈጅ የነበረውን ጊዜ ያህል ባይሆንም የተወሰነ ጊዜ መውሰዱ አይቀርም፡፡ ይህን የአሁኑ ዕትም ከቀደሙት 12 ቅዶች በተሻለ አጭር ጊዜ ማሣተም ተችሏል፡፡

ውሣኔዎቹን በቶሎ ተደራሽ በማድረግ ረገድ ያለውን ችግር ለመቅረፍ እየተከተልናቸው ያሉ አሠራሮች ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የሕትመት ሥራውን ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው እና ምናልባትም ውሣኔዎቹን በተለይም ለፍርድ ቤቶች ጊዜ ሣይጠፋ እንዲደርሱ ከማድረግ አንፃር እንደ ጥሩ አማራጭ ያየነው ውሣኔዎቹ እንደተሰጡ በፍርድ ቤቱ ድረ ገጽ ማለትም www.fsc.gov.et እንዲቀመጡ ማድረግና ቀጣይነቱን ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ አሰራር በአሁኑ ወቅት የኢንተርኔት አገልግሎት እስከ ወረዳ ድረስ የተዘረጋ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች በቶሎ የሰበር ውሣኔዎችን የሚያገኙ ይሆናል ማለት ነው፡፡

የተሻለ ሥራ ሰርተን ለህብረሰባችን ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት ለምናደርገው ጥረት የባለሙያዎችን አስተያየትና ድጋፍ እንፈልጋለን፡፡ የጠበቅነውን ያህል ባይሆንም ለተሠጡን ጥቂት ገንቢ አስተያየቶች እያመሰገንን ይኸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን፡፡

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ2004 ዓ.ም. የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሣኔዎች

ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
1	**የፍትሐብሔር ሥነ- ሥርዓት**				
1	በሥር ፍ/ቤት ቀርቦ የተሰጠ ውሣኔ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቀርቦ በተወሰነ መልኩ ተሻሽሎ መወሰኑ በጉዳዩ ቅር የተሰኘ ወገን ውሣኔውን አስመልክቶ ለሰበር ችሎት የሚያቀርበው አቤቱታ የመጨረሻ ፍርድ ያልተሰጠበት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የትግራይ ብ/ክ/መ/ አዋጅ ቁ.93/97 አንቀፅ 30(2)(ሀ), አዋጅ ቁ.49/94 አንቀፅ 16(ለ) እና 17	61480	አቶ ገ/አግዚአብሔር ክበደ እና ወ/ት ሠላማዊት ወ/ገብርኤል	ጥቅምት 22/2004	2
2	• የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በሰበር ችሎት የተሻረ ሲሆን በውሣኔው መብቱ የተነካ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት ለሰበር ችሎት መቃወሚያ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ፣ • መብታቸው የተነካ ወገኖች ሊስተናገዱ ስለሚችሉበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10	31264	ወ/ሮ እመቤት መኮንን እና ወረዳ 20 ቀ. 29 አ/ጽ/ቤት ተቃዋሚ አቶ አይናዲስ ገዳሙ	ህዳር 06/2004	5
3	በተከሳሽ ወይም ከሳሽ ሞት ምክንያት በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ የነበረ ክርክር በተቋረጠ ጊዜ ክርክሩ በወራሾች አማካኝነት ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታና በህጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ፣	62452	እነ የሚች ወንድሙ ደምሴ ሚስትና ወራሾች (ሶስት	ጥር 03/2004	7

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.49(1), 55(2)		ሰዎች) እና አቶ በርሄ ንስራን		
4	በንብረት ላይ በፍ/ቤት የተሰጠን የእግድ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158 መሠረት መልሶ ለማንሳት ስለሚቻልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158	71316	የኢት/ያ ንግድ ባንክ እና ለገሠ ጌታሁን	ግንቦት 9/2004	13
5	•በአንድ ጉዳይ በከሳሽነትና በተከሳሽነት በተሰየሙ ወገኖች መካከል በተካሄደ ክርክር የተሰጠ ፍርድ ጋር በተያያዘ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ወገን ወይም እርሱ ባልተካፈለበት ሁኔታ በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር መብቱ/ጥቅሙ የሚጐዳበት ሰው በክርክሩ በመግባት መብቱን በህግ አግባብ ሊያስከብር ስለሚችልበት ሁኔታ፣ • ከላይ በተመለከተውና ባልተካፈልኩበት ክርክር የተሰጠ ፍርድ ሥርዓትን ባለመከተል የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ፍርዱ ዋጋ እንዲያጣ ወይም አንዱ የተሰጠ ፍርድን ወደ ጐን በመተው በሌላ ጊዜ በሚሰጥ አዲስ ፍርድ እንዲቀየር ለማድረግ የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህቁ. 41, 358, 212	67127	አቶ አበራ ሁንዴ እና ፍንፍኔ የደን ደርጅት	ሰኔ 08/2004	16
6	በበላይ ፍ/ቤት ትዕዛዝ አንድን በነጥብ ወደ ሥር ፍ/ቤት የተመለሰ ጉዳይ አይቶ እልባት እንዲሰጥበት የተላለፈለት ፍ/ቤት የተመለሰውን ጉዳይ የበላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ መሠረት በማድረግ በአግባቡ ውሣኔ ለመስጠት ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍብ/ሥምሥ/ህ/ቁ. 343(1)	72189	አቶ ካሳዬ ያደቴ እና ሲኖር ፍራንችስኮ ቬንሲያ	ሰኔ 18/2004	20
7	•በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ ውስጥ የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች የሚታዩበት አግባብ በፍ/ብ/ህጉ በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ድንጋጌዎች ስለመሆኑ፣ • በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 መሠረት በሌለሁበት የተሰጠ ፍርድ ይነሳልኝ በሚል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በህጉ የተመለከተው የአንድ ወር ግዜ ገደብ በፍታብሔር ህጉ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስሌት መሠረት ሊሰላ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1848, 1856(2) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78, 195	76601	አቶ ሽመልሽ አማረ እና አቶ አማረ መኮንን	ሰኔ 18/2004	23

https://t.me/ethiopianlegalbrief

8	ግዜው ያለፈበት የይግባኝ አቤቱታን ማስፈቀጃ በመቀበል ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በበላይ ፍ/ቤት በተካሄደ ክርክር የማስፈቀጃ አቤቱታው ተቀባይነት ማግኘቱ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ ወሣኔ የተሰጠ እንደሆነ የስር ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ፍርድ ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 325,326,349	74785	አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ሐምሌ 03/2004	27
9	• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ በግልጽ ያልሸፈናቸውና ለፍ/ቤት የቀረቡ ጉዳዮችን አካሄድ (አሰራር) በተመለከተ ህጉ ከመውጣቱ በፊት ተጽፈው በሥራ ላይ የነበሩ አግባብነት ያላቸው ህጐች እንደ አግባብነቱ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ስለመሆኑ፣ • ክስ አቅርቦ ለከሳሽ የሚላከውን መጥሪያ ከፍ/ቤት ወጪ አድርጐ ነገር ግን ለተከሣሽ መጥሪያውን ከማድረሱ በፊት ክሱ እንዲቋርጥ ያደረገ ከሣሽ ለዳኝነቱ የከፈለው ገንዘብ በመሉ እንዲመለስለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • በፍ/ቤት ክስ የመሰረተ (ያቀረበ) ወገን የክስ መሰማቱ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ክሱን በማንሣት መዝገቡ እንዲዘጋ ያደረገ ከሆነ ለዳኝነት ከከፈለው ገንዘብ ለፍ/ቤቱ በኪሣራ ስም የሚቀነሰው ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ ሊመለስለት የሚገባ ስለመሆኑ የፍብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 232(1) (ለ) ,245(4),3,278(1) የህግ ክፍል ማስታወቂያ 177/74 አንቀጽ 11	76786	አቶ አልዩ ተክሉ እና አቶ መስፍን ስለሺ	ሐምሌ 03/2004	31
10	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 የተመለከተው የጣልቃ ገብነት ሥርዓት አፈፃፀም	77322	የደብረ ዘይት መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያ እና እነ እሌኒ ዓለማየሁ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 17/2004	34
11	በተከራካሪዎች ፈቃድ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ በህግ ስልጣን ባላቸው የሽሪዓ ፍ/ቤቶች ክርክር ተካሂዶ በፍርድ ያለቀን ጉዳይ በተመለከተ እንደ አዲስ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ሊቀርብ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.188/92 አንቀፅ 4(2), 5(4) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 78(5), 34(5)	58119	ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል እና አቶ ዓሊ በከር	ጥቅምት 21/2004	37
12	በህጉ አግባብ ሊሟላ የሚገባው የዳኞች ቁጥር ባልተሟላበት ሁኔታ የሚሰጥ ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ	73696	ወ/ሪት ሃና አበባው	ሚያዝያ	39

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	እንደተሰጠ የማይቆጠርና ህጋዊ ውጤት ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73,337		እና አቶ አብዱ ይመር	9/2004	
	አሠሪና ሠራተኛ				43
13	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሠራተኛን ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የቅጥር ሁኔታ ለመወሰን የተቋሙን ድርጅታዊ አቋም ብቻ መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 9,10	67533	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ በረከት በለጠ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 08/2004	44
14	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ አስቀድሞ በሥራ ላይ የነበረን የድርጅት መዋቅርን መሰረት በማድረግ ሆኖ ጉዳዩ ለአፈፃፀም በቀረበ ጊዜ የድርጅቱ መዋቅር የተለወጠ መሆኑ ከተረጋገጠ ፍርዱ ሊፈፀም የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.392(1),(2)	69471	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን እና አቶ ጥበቡ ተሰማ	ጥቅምት 20/2004	46
15	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ለሠራተኛ የሚከፈል የሥራ ስንብትና ካሣ ክፍያ ላይ የገቢ ግብር ሊቀነስ የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 13, 10(2), 2(10) ደንብ ቁ.78/94	61549	የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን እና ወ/ሮ ብርቂሣ አብራሂም	ህዳር 06/2004	48
16	አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ከአሰሪው ፈርሞ የተረከበው ንብረት በጠፋ ጊዜ ተጠያቂ የሚሆነው ንብረቱ በእጁ እያለ እንዳይጠፋ ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረገ ወይም ለንብረቱ መጥፋት የሠራተኛው ቸልተኝነት መኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.515/99 አንቀፅ 65	69179	የኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ ባለስልጣን እና አቶ ታሪኩ ጫኔ	ህዳር 04/2004	50
17	በህግ ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል በግልጽ በተላለፈ መመሪያ መሰረት የሠራተኛን የሥራ	69125	ወ/ሪት ሠላም	ታህሣሥ	53

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ውል ያቋረጠ አሠሪ የሥንብትና የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሚገደድበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 28, 12(1)(ሀ)		ተስፋዬ እና አልካን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	02/2004	
18	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪና የሥራ መሪ የሆነ ሰው መካከል የሚፈጠርን አለመግባባት ለመፍታት ተፈፃሚነት ያለው ደንብ (መመሪያ) በስምምነት የተዘጋጀ እንደሆነ ይሄው ደንብ ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ	60489	አቶ አምባዬ ወ/ማሪያም እና የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት	ጥር 14/2004	55
19	•ከአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ጋር በተያያዘ ሰራተኛው ከሥራ ሲሰናበት ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት አላስረከበም በሚል ሰራተኛው ሊከፈለው ከሚገባው ክፍያ ቀንሶ ለማስቀረት የሚቻለው በሰራተኛው በኩል ዕዳ ስለመኖሩ መተማመን ላይ ሲደረስ ስለመሆኑ •ሰራተኛው ከተረከበው ንብረት አለመመለስ ጋር በተገናኘ ዕዳ ስለመኖሩ በግራ ቀኙ መካከል ክርክር (አለመግባባት) ያለ እንደሆነ አሰሪው ጉዳዩን በፍ/ቤት አቅርቦ መብቱን ማስከበር ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 36-38, 59(1), 53(2)(1)	67382	እነ አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች) እና አቶ አርጋው አበበ	ጥር 04/2004	58
20	•ከአምስት አመት በላይ ያገለገለ ሰራተኛ የጡረታ መዋጮው ተመላሽ የተደረገለት መሆኑ የጡረታ አበል ተጠቃሚ እንደሆነ ተቆጥሮ የስራ ስንብት የሚያስከለክለው ስላለመሆኑ •በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ የጡረታ "አበል" በሚል የተመለከተው ሀረግ የጡረታ መዋጮ ተመላሽንም የሚጨመር ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ.345/95 አንቀፅ 2(13),(14) አዋጅ ቁ.494/98 አንቀፅ 2(1)(ሸ)	73258	እነ ወ/ሮ አበራሽ ፈይሳ (ሶስት ሰዎች) እና ጂ ሰቭን ንግድና ኢንዲስትሪ ኃ.የተ.የግል ማህበር	ጥር 16/2004	61
21	•ሠራተኛ በሥራ ቦታና በሥራ ወቅት ሆን ብሎ በራሱ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አሰሪው ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ •የአደጋ መከላከያ ደንቦችን በመጣስ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በአደንዛዥ ዕፅ አስክሮ በሥራ ላይ በመገኘቱ በሠራተኛ ላይ የደረሰ ጉዳት ሆን ተብሎ እንዳደረሰ የሚቆጠርና አሠሪው ጉዳቱን ለመካስ የማይገደድ ስለመሆኑ	67201	አቶ ምትኩ ኃይሉ እና አቶ መስፍን ጥላሁን	የካቲት 26/2004	64

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 96(ሀ)(ለ), 96(1)				
22	ከስራ ክርክር ጋር በተገናኘ በዲሲፕሊን ተከስሶ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ሠራተኛው በፊፀመው የማታለል ድርጊት ጥፋተኛ የተባለ መሆኑን መነሻ በማድረግ የተሰናበተ ሰራተኛ የዲስፕሊን ኮሚቴው አባላት በሥራ ክርክር ሰሚው አካል ፊት ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ስላልሰጡ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ) እና (መ)	73881	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን እና አቶ ተፈራ ሹና	የካቲት 27/2004	67
23	የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ የመንግስት ሠራተኛ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰና ጥፋተኛ ተብሎ በጽኑ እስራት ቅጣት በተቀጣ ጊዜ የጡረታ መብቱ የሚቋረጥ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 95/1967 አንቀጽ 34 አዋጅ ቁ. 345/1995 አንቀጽ 52(2) እና (3) አዋጅ ቁጥር 209/1955	50590	ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ በርገኔ ኢንኮ	መጋቢት 28/2004	70
24	ከሚሠራበት ድርጅት ብድር ወስዶ ከፍሎ ያላጠናቀቀ ሠራተኛ በገዛ ፈቃዱ ሥራ ሲለቅ ተከፍሎ ያላለቀው ብድር ከሚያገኘው ፕሮቪደንት ፈንድ ሊቀንስ የሚችለው ሠራተኛው ዕዳ እንዳለበት ያመነ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 59(1)	71507	ሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃ.የተ.የግል ማህበር እና አቶ ሰይፉ ተፈሪ	መጋቢት 10/2004	73
25	አንድ ሠራተኛ በአሠሪው በንብረት ላይ ጉዳት አደረሰ የሚባለው ንብረቱ የአሰሪውን ወይም ከአሠሪው ድርጅት ሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(ሸ)	74400	ግዮን ኢንዱስትሪያልና ኮሜርሺያል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ኃይሉ ናርዬ	ግንቦት 07/2004	76
26	ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች (መያዶች) በስራቸው የሚቀጥሯቸውን ሠራተኞች በተመለከተ አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ሕጎች የሚዳኙ መሆኑን በመግለጽ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ያደረጉ እንደሆነ በድርጅቶቹ እና በሰራተኞቻቸው መካከል የሚነሱ	67996	ሳሳካዋ ግሎባል 2000 ፕሮጀክት እና	ሰኔ 19/2004	79

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አለመግባባቶች በስምምነቱ መሠረት እልባት ሊያገኝ የሚገባ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 3(3)		አቶሸዋድንበር ደቻሳ		
27	በሥራ ላይ በደረሰ ጉዳት በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሠራተኛው የጉዳት ካሣ በመድን ፖሊሲ ተሸፍኖ ሲገኝ የካሣ ክፈያውን ሊጠይቁ ስለሚችሉ ወገኖች፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 110(1)(2),134(2),128,129,133 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 842, 1732, 1735, 1736, 1734	72645	የኢትዩጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ክፍለዩሐንስ ተሰማ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 03/2004	82
28	አሰሪ ሲሰራው የነበረው ሥራ በመቀነሱ ወይም በመቀዝቀዙ ምክንያት ካሉት ሠራተኞች መካከል ከአሥር ፐርሰንት በታች የሆኑትን የሥራ ውል ሚቋረጡ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሥራ ውላቸው የሚቋረጥና ሥራ የሚቀጥሉትን ሠራተኞች ለመለየት ሊከተለው ስለሚገባ አካሄድ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 28(8), 29(3)	74230	አቶ አስቻለው ጌታሁን (አስር ሰዎች) እና አልፋ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ	ሐምሌ 17/2004	90
29	•የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ ውስጥ "እንደ ጥፋቱ ክብደት በሥራ ቦታው አምቧንሮ ወይም ጠብ አጫሪነት ተጠያቂ መሆን..." በሚል የተመለከተው ሀረግ ሊተረጉምና ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ፣ • "የሥራ ቦታ" የሚለው ሀረግ አሰሪው (ተቋሙ) ለሥራና ለመኖሪያ በሚል ለሰራተኞች የሚሰጠውን ቦታ እንዲሁም ተፈፀመ የተባለውን የአምባንሮ ድርጊት ከሥራ ሰዓት መጨረሻ መሆኑንም ጭምር የሚያካትት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ረ),97,4	79105	ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ እና አቶ መዘምር መክብብ	ሐምሌ 03/2004	94
30	አሰሪ ደንብን ባልጠበቀ መንገድ ሠራተኛው ወደ ሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሰራ ተመድቦ ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ሠራተኛውን ማሰናበቱ ተገቢ ስላለመሆኑ	77113	አኪኮ ቦዲዋይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ገረመው አበበ	ሐምሌ 27/2004	97

https://t.me/ethiopianlegalbrief

31	በሥራ ላይ ንብረትንም ሆነ ህይወትን ለአደጋ የሚያጋልጥ ድርጊት መፈፀም ህገ ወጥ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1)(ቀ) 14(2)(ሀ)	79096	ሪመምበር ዘ ፕረሰት ኮሚዩኒቲ እና ዘውድነሽ ማሞ	ሐምሌ 20/2004	100
32	በሥራ ላይ ከሚደረስ አደጋ ጋር በተያያዘ አደጋው የደረሰው ከሥራ ሰዓትና ከሥራ ቦታ ውጪ ከሥራው ጋር ግንኙነት በሌለው አጋጣሚ እና ከአሰሪው ትዕዛዝ ሳይኖር እንደሆነ አሰሪው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 95, 96, 97	68138	ወ/ሮ ጥሩሰው ጥላሁን (ሶስት ሰዎች) እና ሲቪል ወርክስ አማካሪ መሃንዲሶች ኃ/የተ/የግል ማህበር	ጥር 17/2004	103
33	በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች ህግ መሠረት አንድን ጉዳት በሥራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብ (ሁኔታ) እና በጉዳቱ ሞት በተከሰተ ጊዜ የጉዳት ካሣ ለሚች ቤተሰብ የሚሰጥበት አግባብ፣ አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀጽ 47(2)(ሐ) አዋጅ ቁ. 262/94 አንቀጽ 46(2)(5)(ለ)	61717	ወ/ሮ አበበች አዱኛ በራሳቸውና በህጻን ረቂቅ ተክሉ ስም እና በስራና ክተማ ልማት ሚኒስቴር የተንዳሆ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት	ጥር 15/2004	111
34	የሠራተኞች ስንብት ተከትሎ አሰሪ የሆነ አካል የከራካሪ የሆኑ ክፍያዎችን በተመለከተ ሊያዘገይ እንደሚችልና ክፍያ በማዘግየት በሚል ሊቀጣ የሚችለው ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ሳይኖር ወይም የሚያከራክር ክፍያ ሳይኖር ያለአግባብ ያዘገየ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 37, 38, 36	74636	ኢትዮ ቴሌኮም እና ትዕግስት መሉዓለም (15 ሰዎች)	ሰኔ 21/ 2004	116

https://t.me/ethiopianlegalbrief

35	በፍርድ ቤት የተቋቋመ የውርስ አጣሪ አበል መጠን ሊወሰን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ 959, 946-1125	69153	ብርሃኑ ከፍያለው እና እነ ወ/ሮ ሮማን ይርጋ (11 ሰዎች)	ጥቅምት 06/2004	121
36	የጋብቻ ፍቺን በተመለከተ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ከሌለ በስተቀር የባልና ሚስት የጋራ ንብረትን አስመልክቶ የፍቺ ውጤት የሆነውን የክፍፍል ጥያቄ በፍ/ቤት ማቅረብ አይቻልም ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 76	61357	አቶ ፍቅሬስላሴ እሸቱ እና ወ/ሮ ዋጋዬ ጋይም	ህዳር 22/2004	124
37	በባል ወይም በሚስት ለጋራ መተዳደሪያቸው በሚል ከሚካሄድ የንግድ ሥራ ማስኬጃ ጋር በተያያዘ የተገባ ዕዳ የተጋቢዎች የጋራ እዳ እንደሆነ የሚቆጠር ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ.19 የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92, አንቀፅ 70	68190	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ እመቤት ቱርፌ	ታህሣሥ 05/2004	127
38	ከባልና ሚስት የጋራ ንብረት ጋር በተገናኘ በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ አማካኝነት ከባንክ ወጪ ተደርጉ ለ3ኛ ወገን የተላለፈ (የተሰጠ) ገንዘብ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚገመትበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 85-93	70442	አቶ በቀለ ቱፋ እና ወ/ሮ ባዩሽ እሸቱ	ታህሳስ 30/2004	130
39	የወራሾች የጋራ ሀብት የሆነን ንብረት ለመሸጥና ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለንብረቶቹ ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1262, 1060(1)	64371	ፍቅረዲን ሰይፈዲን እና እነ አበራ ለማ (አምስት ሰዎች)	ጥር 02/2004	134
40	ከባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጋር በተገናኘ በአንደኛው ተጋቢ በውርስ የተገኙ ንብረቶች (ሀብቶች) ለልማት በሚል በመፍረሳቸው የተገኘ የካሳ ክፍያ በግብይት እንደተገኘ ተቆጥሮ የግል ስለመሆኑ በፍ/ቤት አልተረጋገጠም በሚል እንደ የጋራ ሀብት ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑ	65708	አቶ አራጋው አበበ እና ወ/ሮ ራሔል	ጥር 02/2004	137

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 58, 57		ውብሸት		
41	•የጋብቻ ፍቺ ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማግሌዎች ወይም በባለሞያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሣኔው ተፈፃሚነት የሚኖረው ለፍ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነትን ሲያገኝ ብቻ ስለመሆኑ •ፍቺን እና የፍቺን ውጤት በተመለከተ ውሣኔ የመስጠትና የማፅደቅ ስልጣን የፍ/ቤት ብቻ ስለመሆኑ፣ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 83(3), 117 የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.69/95 እና አዋጅ ቁ.83/96 አንቀፅ 110(5)	69657	ወ/ሮ ሐምዚያ ሼክ ኢብራሀም እና አቶ አብዲ ኡስማኤል	የካቲት 28/2004	141
42	በጋብቻ ተሳስረው የነበሩ ሰዎች ግንኙነታቸው እስካልተቋረጠ ድረስ ለረጅም ጊዜ ተለያይተው በመኖራቸው ብቻ በመካከላቸው ያለው የትዳር ግንኙነት ፈርሷል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣	67924	ወ/ሮ ምንያ ገ/ሥላሴ እና ወ/ሪት መሠረት ዓለማሁ	መጋቢት 26/2004	144
43	ከባልና ሚስት ጋብቻና ፍቺ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የቀረበን ጉዳይ ስልጣን ያለውና ተከራካሪዎቹ ለመዳኘት ፈቃዳቸውን የገለፁለት የሽሪአ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆኑን በመግለጽ መዝገቡን የዘጋው እንደሆነ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ማስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. አንቀጽ 37(1), 34(5), 78(5),	72420	ወ/ሮ ኬሪያት ያህያ እና ሐጂ ጅሀድ ኡመር	ሚያዝያ 22/2004	148
44	የውርስ ሀብት ማጣራት ጋር በተገናኘ የንብረት አጣሪው የሟች ያለኑዛዜ ወራሾች በሚል የተጠቀሱ ወራሾች በአካባቢው በሚገኘው የመረዳጃ እድር ሰፍሯል በማለት የውርስ ድርሻ አላቸው በሚል የሚያቀርበው የውሣኔ ሀሳብ ህጋዊ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 842, 856, 962, 944(ሀ),1097,1113	71895	አቶ ሞላ ንጉሴ እና አቶ ንጉሴ ገለታ	ግንቦት 10/2004	151
45	የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጋር በተገናኘ አንድን የጋራ ንብረት በዓይነት ለመካፈል ተጋቢዎቹ ከስምምነት ላይ ለመድረስ ያልቻሉ እንደሆነና ሁለቱም የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ ያቀረቡ እንደሆነ ንብረቱ ለጨረታ ቀርቦ እንዲሸጥ በማድረግ ገንዘቡን መካፈል ያለባቸው ስለመሆኑ፣ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/መ/ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/96 አንቀጽ 103(1)	71126	ወ/ሮ ወርቅነሽ ሰብስቤ እና እነ ሻለቃ ባሻ እንደሻው (ሁለት	ሰኔ 05/2004	154

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ሰዎች)		
46	ሚች አድርጐት የነበረ ኑዛዜ በተመሣሣይ ንብረት ላይ በኋላ በተደረገና ከሞተ በኋላ ተፈፃሚነት ባለው ስጦታ የተተካ እንደሆነ ኑዛዜው በስጦታው እንደተሻረ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2428, 2443, 881, 826(2), 856, 898	72286	አቶ ኃ/ስላሴ ወርቁ እና ወ/ሮ ምስራቅ ወርቁ	ሰኔ 19/2004	157
47	በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ ስም የተመዘገበና በጋብቻ ወቅት ፅጣው የወጣ የኮንዶሚንየም ቤት ላይ ያለ መብት የቤቱ ውል ከጋብቻ መፍረስ በኋላ የተፈፀመና ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ መሆኑ (የንብረት ክፍፍል እስካልተፈፀመ ድረስ) ንብረቱን የማል የሚያስብል ስላለመሆኑ	75562	ወ/ሮ ሶፊያ መሐመድ እና አቶ መሐመድ ይመር	ሰኔ 18/2004	160
48	ፍቺን በስምምነት ለመፈፀም ለፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡ ባል እና ሚስት የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ያደረጉትን ስምምነት ፍ/ቤት ለህግና ለሞራል የማይቃረን መሆኑን በማረጋገጥ ያፀደቀው እንደሆነ ስምምነቱ ተፈፃሚ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ፣ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 80,83(3) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277(2)	74376	አቶ ብዙአየሁ ታደሰ እና ወ/ሮ ሰለሞሜ ሻወል	የካቲት 27/2004	163
49	አንድ ወንድ ሁለት ሚስቶች ጋር ተጋብቶ በሚገኝ ጊዜ የንብረት ክፍፍል ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የፌዴራል የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 102(1),86(1),62(1),63(1) የአማራ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 113(1),97(1),73(1),74(1)	45548	ወ/ሮ አሚናት አሊ እና ወ/ሮ ፋጡማ ውበት	መስከረም 24/2003	167
50	ውል አዋዋይ ወይም ዳኛ ፊት የተደረገ ኑዛዜ በህጉ የተመለከተውን የኑዛዜው መነበብ ሥርዓትን ያላሟላ ከሆነ ህጋዊ ፎርማሊቲን የሚያሟላ እንደሆነ ለመቁጠር የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 881(2), 882, 857	70057	እነ ወ/ሮ አበበች ቡልቻ (ሶስት ሰዎች) ተጠሪ፡- የለም	ህዳር 06/2004	171
	ውል				**174**
51	የፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(ረ) ድንጋጌ ከስልክ አገልግሎት ክፍያ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(ረ), 2023, 2022	61331	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን	ጥቅምት 10/2004	175

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			እና ሚ/ር ጀርመን ግናሆ		
52	ከማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ጋር በተገናኘ ሻጭ የሆነ ወገን የሸጠውን ነገር ባለሃብትነት ለገዢው የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2875, 2281,1808(2)	61913	ወ/ሮ እታለማሁ መስፍን እና አጋ አንዴ	ጥቅምት 20/2004	179
53	ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉት ውል ምንም እንኳን የተፈፀመ ቢሆንም ውሉ የ3ኛ ወገኖችን መብትና ጥቅም የሚነካ ከሆነ ይህንኑ በመግለፅ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ይወሰን ዘንድ ለፍ/ቤት አቤቱታ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1806	61808	ወ/ሮ ፀሐይ ፍቃዱ እና እነ አቶ ብቻዬ ተስፋዬ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 07/2004	181
54	አንድ ማህበር ለሰጠው ብድር የሚያገኘውን የወለድ መጠን ከመደበኛው የባንክ ማበደሪያ ወለድ መጠን ከፍ አድርጐ ለማበደር ስለመቻሉና ይኸውም ተፈፃሚ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.147/91 አንቀፅ 34(2) አዋጅ ቁ.402/96 አንቀፅ 5 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731,1678 የትግራይ ብ/ክ/መንግስት አዋጅ ቁ. 145/2000	62162	መትክል ልምዓት ሁለገብ መ/ህ/ስ ማህበር እና ቁስ ካላዩ ኪሮስ	ህዳር 21/2004	186
55	ከውል መፈፀም ጋር በተገናኘ ተዋዋይ ወገኖች ውልን በተናጠል ለመሰረዝ (unilateral cancellation of contract) ስለሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1771, 1774, 1757, 1787, 1785, 1786, 1789, 1788	57280	እነ ሴንትራል ቬኑ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (አራት ሰዎች) እና እነ አቶ ሰለሞን ከተማ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 03/2004	189

https://t.me/ethiopianlegalbrief

56	የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472 ከብድር ውጪ በሆነ ግንኙነት ከተከፈለ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ የሚሆንበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472	64397	አቶ አንዳርጌ እምሩ እና ወ/ሮ ዘሀራ መሀመድ	ጥር 01/2004	200
57	ውሎች በቃል፣ በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ግዴታ ለመግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ሊደረጉ ስለመቻላቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ.1681(1)	71375	ዳሽን የህትመትና የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ፍስሐ ይሁን	ጥር 16/2004	203
58	የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል የጠፋበት ሰው የሽያጭ ውሉ የጠፋ ስለመሆኑ ለማስረዳት በሚል የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለውና የሚቀርቡት ማስረጃዎች በተገቢው ሁኔታ ተመርምረው አሳማኝ መሆናቸው ከታወቀ (ሲረጋገጥም) ተከራካሪው የሽያጭ ውሉን በምስክሮች ለማስረዳት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው የማገባ ስለመሆኑ የፍ/ህ/ብ/ህ/ቁ 2003,2002	69208	ወ/ሮ ንፁህ በላይ እና ወ/ሮ ምንትዋብ አዳነ	መጋቢት 10/2004	206
59	በወለድ አገድ ውል መሰረት የማይንቀሣቀስ ንብረቱን ያስያዘ ተዋዋይ ወገን በውል የተገለፀው ጊዜ ካለፈ በኋላም በማናቸውም ጊዜ ዕዳውን ከፍሎ ንብረቱን ለማስለቀቅ የሚችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 3128/2/ 3117-3130	72463	እነ አቶ ንጉሴ ሀይሌ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሁሬሣ ደበል (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 26/2004	209
60	እንደ ውል አልተፈፀመልኝም በሚል የጉዳት ኪሣራ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቶች የጥያቄ አቅራቢውን ተነፃፃሪ የውል ግዴታ ግምት ውስጥ በማስገባት የጉዳት ኪሣራ ሊወሰኑ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1771, 1802	69915	ሻምበል ይኩኖ ለገሠ እና አቶ መሐመድ በሽርና ቤተሰቦቹ ጨው አምራች ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሚያዝያ 25/2004	211

https://t.me/ethiopianlegalbrief

61	በሰነድ ላይ የተመለከተ ፊርማ በተካደ ጊዜ ሰነዱ ሲፈረም የነበሩ የምስክሮችን ቃል በመስማትና በሌሎች ማስረጃዎች ፊርማው የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ /Authenticate ለማድረግ/ የሚቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472(1) እና (3)	71927	ቄስ አብርሃ በርሄ እና ወ/ሮ ብርነሽ ሕሉፍ	ሚያዝያ 10/2004	215
62	የፀና የውል ግዴታ የገባ ሰው ውሉ በፍርድ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችለው ሌላኛው ተዋዋይ ወገን ግዴታውን በአግባቡ ያልፈፀመ (ያልተወጣ) እንደሆነ ወይም የፈፀመው ፍፁም ባልሆነ አኳኋን ከሆነ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1784 1785(2),(1)	66935	አቶ ሽመልስ አበራ እና አቶ ጌታቸው አያልቁ	ሰኔ 05/2004	218
63	አንድ ቀድሞ በመያዣ የተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ካርታ ቁጥሩና የቤት ቁጥሩ ተለውጦ እንዲሁም ቀደም ሲል የነበረው ቤት ፈርሶ በቦታው ላይ አዲስ ቤት ተሠርቶና አዲስ ካርታና የቤት ቁጥር ተሰጥቶ በተገኘ ጊዜ አዲሱን ቤት በመያዣ የያዘ አበዳሪ ቀድሞ የነበረውን ቤት በመያዣ ከያዘው አበዳሪ የቅድሚያ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 3052, 3066	75902	የኮንስትራክሽን እና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ሰኔ 22/2004	224
64	• ከስጦታ አድራጊው ሞት በኋላ ተፈፃሚ የሚሆን የስጦታ ውልን በተመለከተ ስለ ኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው ስለመሆኑ፣ •የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግ ስጦታ በህጉ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ አስራርን በተከተለ መልኩ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.881, 2428, 2443, 2436	61421	አቶ ጌታቸው በየነ እና እነ የሕፃን ታቦት በቀለ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 17/2004	227
65	በአሰሪው በኩል የተመቻቸን የውጪ የትምህርት እድል ተጠቃሚ በመሆን በምትኩ ለተወሰነ ጊዜ ለማገልገል ከተደረገ ውል ጋር በተገናኘ ሠራተኛው በውሉ ያለበትን ግዴታ እንዲወጣ ከሚጠበቅበት ጊዜ በፊት ከአሰሪው ፈቃድና እውቅና ውጪ ለሌላ ትምህርት ወደ ሌላ አገር በመሄወር የመጀመሪያው ውል ውጤት እንዳይኖረው ያደረገ እንደሆነ ሠራተኛው በውሉ የተመለከተውን ግዴታ ለመፈፀም እንዳልቻለ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ	70963	ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ እና እነ አቶ ተመስገን ማጉሌ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 30/2004	231
66	• የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ውል መኖሩን በማመን ነገር ግን ውሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሠረት የተከናወነ አይደለም በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣	36887	ወ/ሮ አልጋነሽ አበበ እና እነ አቶ ገብሩ እሸቱ	ህዳር 18/2001	233

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• በፍ/ብ/ህ/ቁ.1723(1) መሠረት የሚከናወን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ምዝገባ ዓላማ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውል መኖሩን ለማስረዳት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723(1),2878		(ሁለት ሰዎች)		
67	ስለ አስፈላጊ አደራ እና የማስረጃ አይነት የፍ/ብ/ህ/ቁ.2782,2800,2802,2472	64887	አቶ አደም የሱፍ እና አቶ አብዱሠላሣ መ/ሐመድ	ሐምሌ 29/2003	236
	ወንጀል				239
68	በአንድ ጉዳይ ድጋሚ ክስ ወይም ድጋሚ ቅጣት (principle of double jeopardy) ክልክል ስለመሆኑ የተደነገገው መርህ ሊተረጐም ስለሚችልበት አግባብ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 23 የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.42(1)(ሀ)	60217	እነ ም/ኢ/ር ኃይላይ አስገለ (ሁለት ሰዎች) እና የቤ/ን/ፍ/ት/ሕ ቢሮ	ጥቅምት 15/2004	240
69	• ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የዋስትና ጥያቄን ላለመቀበል ሥልጣን (discretion) ያላቸው ስለመሆኑ፣ • ዋስትናን ለመከልከል ፍ/ቤቶች የሚሰጡት ምክንያት በቂና ህጋዊ ናቸው ሊባሉ የሚችሉበት አግባብ፣ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.67	67874	እነ አቶ ፅጌብርሃን ተሰራ (ሁለት ሰዎች) እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን	ጥቅምት 23/2004	243
70	ማዕድናትና የከበሩ ድንጋዮችን ከማዘዋወርና ለሽያጭ ከማቅረብ ጋር በተገናኘ ስለሚኖር የወንጀል ኃላፊነት፣ የወ/ህ/ቁ 346፣347፣378 አዋጅ ቁ. 52/85 አንቀጽ 53(1), (5), 26(4) ደንብ ቁ. 182/80/ አንቀጽ 30(1)(ሀ), 3(ለ) እና 4(ሐ), 38-40	60345	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና . ገዳ ፎጫ በሊ-	ሕዳር 07/2004	247

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 591/2000 አንቀጽ 26(1)(ለ)		ግለሰቦቹ (ሶስት ሰዎች)		
71	በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ ከአንድ አይነት የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ በሁለት የተለያዩ የወንጀል ክሶች የተከሰሰ ተጠርጣሪ በአንዱ የወንጀል ክስ የተመለከቱ ፍሬ ነገሮች መከሰት ጋር በተገናኘ ጥፋተኛ ለማለት ያልተቻለ እንደሆነ በሌላኛው ክስ ጥፋተኛ ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ የወ/ህ/ቁ 407(ሐ), 670, 677 የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 141, 142, 149(1)	65325	ሣጅን ታዬ ተክለኂይማኖት እና የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ	ህዳር 22/2004	256
72	• በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር ክርክሩ አግባብነትና ብቃት የሚኖረው በወንጀል ክሱ ተከሳሹ በወንጀል ፍ/ቤቱ ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነ ከሆነና ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስም በወንጀሉ ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች በፍ/ብሔሩ ጉዳይም ቀርበው የተሰሙ መሆን ያለባቸው ስለመሆኑ፣ • በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ማስረጃ ለፍትሐብሔር ጉዳይ አግባብነትና ብቃት የሚኖረው በሁለቱም ጉዳዩች የተሰሙት ማስረጃዎች አንድ አይነት ሲሆኑ ስለመሆኑ፣ • በወንጀልና በፍ/ብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች የተለያዩ ከሆነ እና በወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበበት ነጥብም ከፍ/ብሔሩ ክስ ጋር ግንኙነት የሌለው ከሆነ በወንጀል ክስ ተጠያቂ መሆን ሁልጊዜ በፍ/ብሔር ክስ ኃላፊነትን የሚያስከትል ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2149 የወንጀል ህግ ቁጥር 702(2)	46386	አቶ ሃይሉ ተስፋኡ እና አቶ ብርሃነ መብራቱ	ታህሣሥ 06/2004	259
73	ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ በመገኘት ወንጀል አንድ ሰው ተጠያቂ የሚሆነው የምዝገባ ሥርዓት የተዘረጋ እንደሆነ ብቻ ነው ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ ስላለመኖሩ የወ/ህ/ቁ.419	67411	እነ አቶ ታረቀኝ ተክሉ ገመዳ (ሶስት ሰዎች) እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን	ታህሣሥ 30/2004	262
74	በወንጀል ህግ ቁጥር 448 ስር አንድ ሰው ለፍትህ እርዳታ ለመስጠት እንቢተኛ ሆኗል በሚል ወዲያውኑ ጉዳዩን በያዘው ፍ/ቤት ለመቅጣት ስለሚቻልበት አግባብ	67777	እነ ተወልደ ብስራት (ሶስት	ታህሣሥ 04/2004	266

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወ/ህ/ቁ 448(1), (3), 23(2), 58		ሰዎች) ተጠሪ የለም		
75	በኤግዚቢትነት በፖ/ሊስ ከተያዙ ንብረቶች ጋር በተገናኘ የንብረቶቹ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ንብረቱ ይመለስለት ዘንድ በፖ/ሊስ ጽ/ቤቱ ላይ የሚያቀርበው ክስ በተገቢው ማስረጃ ተጣርቶ እልባት ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ	62504	አቶ ታደሰ ናማጋ ሀያቱ እና የፌዴራል ፖ/ሊስ ወ/ምርመራ መምሪያ ዋና ሣጅን ደምሴ ሰጠኝ	ታህሣሥ 06/2004	271
76	አንድ ሰው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 407 መሰረት በስልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ጥፋተኛ ተደርጐ ቅጣት ሊጣልበት የሚችልበት አግባብ፣ የመ/ህ/ቁ 407(1)(ሀ)	60518	አቶ ፈለቀ ሊቤ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የስነ- ምግባርና ፀረ- ሙስና ኮሚሽን	ጥር 15/2004	273
77	አንድ ሰው በወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2) መሰረት በህገ-ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ወደ ውጪ አገር ልኳል በሚል ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ ስለሚችልበት አግባብ የወ/ህ/ቁ 598(2)	71753	አቶ ወርቅነህ ዳቲ እና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	ጥር 03/2004	277
78	•የግንባታና የኮንስትራክሽን ማዕድን ማውጣት ሥራ ጋር በተያያዘ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የፀና ፈቃድ ሣይኖር ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የመግዛትና የመሸጥ ውል መፈፀም በወንጀል ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለመቻሉ •ህገ ወጥ ወይም ወንጀል ስለመሆኑ የተደነገገ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተደረጉ ውለታዎችን (ውሎችን) በህግ ኃይል እንዲፈፀሙ በሚል ለፍ/ቤት ጥያቄውን በቀረበ ጊዜ ዳኞች ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ የሚገባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1718, 1716 የወ/ህ/ቁ.353(1)(ለ) አዋጅ ቁ.52/85 አንቀፅ 53(5)	69822	ዲ - ኤም - ሲ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና አቶ ኢብራሂም ኢቲሶ	ጥር 15/2004	280

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ደንብ ቁ.182/86 አንቀፅ 39				
79	•የሥራና ሠራተኛን ማገናኘት አዋጅ ቁ.632/2002 በመተላለፍ ሊኖር ስለሚችለው የወንጀል ተጠያቂነት •ከቀረበ የወንጀል ክስ ጋር በተያያዘ የግል ተበዳይ የሆነ ሰው ቀርቦ ካልመሰከረ በስተቀር ክሱን ለማስረዳት የሚቀርቡ ሌሎች ማስረጃዎች ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማለት ብቁ አይደሉም ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.632/2002 አንቀፅ 16(1)(መ), 18(1)(ሀ), 20(2), 40(3)	71184	ዓሕመድልሃዲ ካህሳይ እና የፌዴራል ዓቃቤ ህግ	ጥር 18/2004	286
80	የመንግስት ሰራተኛ ሳይሆኑ ነገር ግን ከመንግስት ሰራተኞች ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር በህዝብና በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረስ በሙስና ወንጀል ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.434/97 አንቀፅ 7 የወ/ህ/ቁ.407(1)(ሀ),33	60542	አቶ ተክለድንግል ገ/ሚካኤል እና የፌ/ሥ/ም/ፀ/ሙስና ኮሚሽን	የካቲት 27/2004	289
81	•ከመንግስት ሰራተኞች ውጪ በሆኑ ሰዎች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችን በተመለከተ የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ክስ ሊያቀርብ ስለመቻሉ •ኮሚሽኑ የወንጀል ክስ ለመመስረት ስልጣን ከተሰጠው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ወይም ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተከሰሰ ሰው ከሙስና ወንጀሉ ጋር አንድ ላይ መከሰስ ያለበትን የወንጀል ድርጊት አንድ ላይ (አጣምሮ) ሊያቀርብ ስለመቻሉ የወ/ህ/ቁ 379(2), 375, 404(4)(3) አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀፅ 58 አዋጅ ቁ.236/93 አንቀፅ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.110	64612	እነ ሐሰን አማን መሐመድ (ሁለት ሰዎች) እና የፌ/ሥ/ፀረ-ሙስና ኮሚሽን-	የካቲት 27/2004	292
82	አንድ የወንጀል አፈፃፀም ተግባር መከራ ደረጃ ላይ ደርሷል (Attempt) ሊባል የሚችልበት አግባብ የወ/ህ/አ 32(1)(ሀ),27(1),671(1)	66856	ውድማ አበጀ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል	መጋቢት 26/2004	296
83	የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጋር በተያያዘ የክስ ቻርጅን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን በወ/ህ/አ.438	73953	ከፋለ ሰፈነ	መጋቢት	299

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በየመንግስት ሥራን ማሰናከልና የመተባበር ግዴታን መጣስ ወንጀል ሊያስጠይቅ ስለመቻሉ፣ የወ/ህ/አ.348		እና የአማራ ክልል ዓ/ህግ	13/2004	
84	በወንጀል ጉዳይ በተሰጠ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ለማቅረብ በህጉ ተለይቶ ስለተመለከተ የጊዜ ገደብ፣ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 187(2)	73264	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ አቶ አልፈድል አሻፊ (ሶስት ሰዎች)	ሚያዝያ 9/2004	302
85	•በወንጀል ፍርድ ሂደት አንድ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ወይም በክርክሩ ሂደት ተሳታፊ ሳይደረግ (ሳይሆን)(default procedure) ነው የታየው ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ • የቅጣት አስተያየት በሚሰጥበት ጊዜ ያለመቅረብ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ውሣኔ ነው ሊያስብል የማይችል ስለመሆኑ፣ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.161, 164, 197, 202, 149 (4) (1) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20(4))	76909	ወ/ሮ ፈትያ አወል እና የፌዴራል ዐቃቢ ህግ	ግንቦት 10/2004	205
86	•ማንኛውም ሰው በወንጀል ህግና ሥርዓት መሠረት ተከስሶ የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም (Principle of Double Jeopardy) በሚል የሚታወቀው የወንጀል ህግ መርህ ሊተረጐምና ሥራ ላይ ሊውል የሚችልበት አግባብ፣ • አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በድጋሚ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በአንድ ጉዳይ በድጋሚ ያለመከሰስና ያለመቀጣት መብቱ ተጥሷል በሚል ክርክር ለማቅረብ ሊሚሉ ስለሚገቡ ህጋዊ መስፈርቶች፣ • ዐቃቤ ህግ በአንድ ተከሳሽ ላይ የወንጀል ክስ ከማቀርቡ በፊት ተከሳሹ አንድ ወንጀል በመፈፀም ሀላፊ የሠራው አንድ የወንጀል ድርጊት ያስከተላቸውን ወይም ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ውጤቶች ሁለተናዊ በሆነ መንገድ በማገናዘብ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመለየትና በመጥቀስ የወንጀል ክሱን በጥንቃቄ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ 2(5), 24(1)	72304	የትግራይ ክልል አጽቢ ወረዳ ዐቃቤ ሕግ እና ተማሪ ሐጎስ ወልደሚካኤል	ሰኔ 18/2004	308

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130,131, 41, 111, 112 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህግ መንግስት አንቀጽ 23,13(2)				
87	• አንድ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ በሚል ፍ/ቤት በሚሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የሚያስችል የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ • የሙስና ክስ ከሚመራበት ሥርዓት ጋር በተገናኘ ተከሳሽ የሆነ ተከራካሪ ወገን ይግባኝ ለማቅረብ ስለሚችልባቸው ህጋዊ ጉዳዮች፣ • ለሰበር ችሎት የሚቀርቡ ማናቸውም ጉዳዮች የይግባኝ አቅራረብ ሥርዓትን ያጠናቀቁና የመጨረሻ ፍርድ የተሠጠባቸው መሆን የሚገባቸው ስለመሆኑ፣ አዋጆ ቁ. 25/88 አንቀጽ 22 አዋጆ ቁ. 434/97 አንቀጽ 36(2) 40, 55 አዋጆ ቁ. 236/93	74041	እነ አንተነህ መኮንን (አራት ሰዎች) እና የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ	ሰኔ 04/2004	313
88	አንድ ሰው በወ/ህ/አ. 675(1) የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል ሊከሰስና ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ ስለሚችልበት አግባብ፣ የወ/ህ/አ.675(1),23	74530	ጀማል መሐመድ እና የፌዴራል ዐ/ህግ	ሰኔ 22/2004	316
89	አንድ ሰው በወ/ህ/አ. 429 ጉቦ ማቀባበል የወንጀል ድርጊት ክስ ሊቀርብበትና ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችልበት አግባብ፣ የወ/ህ/አ. 429,23(4,(1),58)	78793	አቶ ብስራት ወልደመስቀል እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ሰኔ 21/2004	320
90	በፍ/ቤት የወንጀል ክስ ቀርቦ የጥፋተኝነት ውሣኔ በተሰጠበት የወንጀል ድርጊት ወንጀለኛው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘው ንብረት ለመንግስት እንዲወረስ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ 98(1)(2),	66943	እነ ታምራት ገለታ (አራት ሰዎች) እና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	ሐምሌ 18/2004	324
91	በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀሙ ለማስረዳት መቅረብ የሚገባው	75922	እነ አፈወርቅ ሌሊሳ	ሐምሌ	329

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የማስረጃ አይነት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸው ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት የሚችልና ድርጊቱ ሲፈፀም አይቻለሁ ወይም/እና ሰምቻለሁ የሚል ቀጥተኛ ማስረጃ ብቻ ነው ለማለት የሚያስችል የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 137, 141, 149		(ሁለት ሰዎች) እና የደቡብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት	04/2004	
92	አንድ የወንጀል ድርጊትን ማስረዳት ጋር በተያያዘ የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ (circumstantial evidence) በይዘቱ አንድ ክስተት ከመፈጠሩ በፊት፣ ክስተቱ ሲፈጠር ወይም ድርጊቱ ሲፈፀምና ክስተቱ ከተፈጠረ ወይም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ፣ ያሉትን አካባቢያዊ ሁኔታዎች የሚያሣይና የሚገልጽ በመሆኑ ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 137(1)	75980	ስማቸው ልንገርህ ዓለሙ እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የደቡብ ክልል ቅርንጫፍ	ሐምሌ 02/2004	322
93	የባንክ ሥራ ጋር በተገናኘ የሥራ አመራር ላይ ጉድለት በመፈፀም ስለሚደረግ ወንጀል፣ የወ/ህ/አ. 703	77989	እነ አቶ ለይኩን ብርሃኑ (አምስት ሠዎች) እና የፌዴራል ዐ/ህግ	ሐምሌ 04/2004	337
94	የወንጀል ህግ አንቀጽ 692(1)ን በመተላለፍ አንድ ሰው በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችልበት ሁኔታ፣ የወ/ህ/አ. 692,32(1)(ለ)	77592	ተካልኝ ጌታቸው እና የፌ/ዐ/ሕግ	ሐምሌ 27/2004	347
95	አንድ ወኪል ከወካዩ በውክልና ስልጣኑ የወሰደውን ንብረት ለመመለስ ፈቃደኛ ያለመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 676(2) ድንጋጌ መሰረት ሊያስጠይቀው ስለመቻሉ የወ/ህ/ቁ 676(2)	67408	አቶ ፋሲል በላይነህ እና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	ጥር 01/2004	350
96	በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው የዋስትና መብቱ በፍ/ቤት ከተከበረለት በኋላ ህጋዊ ምክንያቶችን በማቅረብ የዋስትና መብቱን በመተው ያስያዘው ገንዘብ ተመልሶለት ጉዳዩን ማረሚያ ቤት ሆኖ ለመከታተል የሚያቀርበውን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣	73569	አቶ ደረጀ ጎሳዬ እና የኢትዮጵያ	ጥር 17/2004	353

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አቃቤ ሕግ		
97	በወንጀል የተከሰሱ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በግላቸው ጠበቃ ለማቆም የማይችሉ በሆነ ጊዜ በመንግስት ወጪ የጠበቃ ድጋፍና እርዳታ ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 20(5) አዋጅ ቁ.27/88 አንቀፅ 35 አዋጅ ቁ.123/90 አዋጅ ቁ.27/885	65566	የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ እና የኦሮሚያ ክልል ዐ/ህግ	ታህሣሥ 04/2004	357
98	የሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ማስረጃ የመመዘንና የመመርመር ስልጣን የሌለው ቢሆንም በሥር ፍ/ቤቶች ወይም የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት መሰረታዊ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ስርዓትን ሳይከተሉ፣ መመስረት የሚገባቸውን ጭብጥ ሳይመሰርቱና ጭብጡን የማስረዳት ግዴታ (Buden of proof) ያለበት ተከራካሪ ወገን የማስረዳት ግዴታውን በአግባቡ እንዲወጣ ሳያደርጉና መጣራት ያለበትን (የሚገባውን) ፍሬ ጉዳይ ሳያጣሩ የሰጡትን ውሣኔ በሰበር አይቶ ለማረም ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ በወ/ህ/አ. 419	63014	እነ አቶ ወርቅነህ ከንባቶ (ሁለት ሰዎች) እና የደቡብ ክልል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ሚያዝያ 09/2004	359
	የንግድ ህግ				366
99	•በባህር ላይ እቃ አመላላሽ በእቃዎች ላይ ለደረሰ ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብ፣ •በባህር ላይ እቃን ለማመላለስ የውል ግዴታ የገባ ወገን ከእቃዎቹ መጐዳት ጋር በተያያዘ ስላለበት የኃላፊነት አድማስና ከኃላፊነት ነፃ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የባህር ህግ ቁ.196,138,205,197,180(3)	54117	ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ አ.ማ	ጥቅምት 13/2004	367
100	እቃን ከማጓጓዝ ጋር በተገናኘ ከእቃው አደገኛ (ጉዳት አድራሽ) ባህሪ የተነሣ ዕቃውን በሚያጓጉዘው ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰ ጉዳት የእቃው ባለቤት (ባለንብረት) የዕቃውን በአግባቡና በጥንቃቄ አለመታሸግ	60385	ጎልደን ሮዝ አግሮ ፋርምስ ኃ/የተ/የግ	ጥቅምት 24/2004	371

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	(አለመያዝ) ጋር በተገናኘ በኃላፊነት ሊጠየቅ ስለመቻሉ የንግድ ህግ ቁ.578(2)		ማህበር እና አቶ ሐሊፎም ተስፋ ማሪያም		
101	ከንግድ ስም አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የንግድ ሚኒስቴር በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታ በይግባኝ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ.686/2002 አንቀፅ 6, 7, 30, 2(9), 16, 61	69603	አቶ ሀብተወልድ ዘርጋው የጂትሮ የስራ አመራር የማማከር አገልግሎት ድርጅት እና እነ አቶ ሳሙኤል አሰፋ የጂትሮ ሊደርሺፕ ኤንድ ማኔጅመንት(ሁለት ሰዎች)	ህዳር 08/2004	374
102	ከንግድ ስም ወይም ምልክት ምዝገባ ጉዳይ ጋር በተገናኘ በሚመለከተው ተቋም በተሠጠ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት በይግባኝ ሥርዓት የማሳረም ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 501/98/ አንቀጽ 6,17,36,49	63454	ዳት ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ/ባለቤት ዶ/ር ጤና አብተው እና እነ የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ፅ/ቤት (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 26/2004	378
103	•ለገንዘብ እዳ የሚሰጥ ዋስትና አንድ የመድን ተቋም ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል አንዱ ስለመሆኑ፣ •በመድን ሰጪ ድርጅቶች ተዘጋጅቶ የሚሰጥ የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial	36935	አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) እና	የካቲት 27/2004	383

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	Guarantee Bond) ስለሚኖረው ውጤት •የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ ሊያሟላቸው የሚገቡ ፎርማሊቲዎች እና አቤቱታ ከማቅረብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት ስለሚኖረው የይርጋ ደንብ አዋጅ ቁ.86/86 አንቀፅ 2 የፍ/ብ/ህ/ቁ 1845, 1922(2)(3), 1725(ሀ), 1727, 1926, 1929, 1930, 1931 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀፅ 1(1), 2(1) መመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀፅ 1(3), 2(1), 3 የንግድ ህግ ቁ.36(1)(2), 121(ሰ) አዋጅ ቁ.110/90 አንቀፅ 2(2) አዋጅ ቁ.57/89 አንቀፅ 2(18)		የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ		
104	•ስለ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantee Bond) • የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ውል በባህሪው ከመድን ውል የሚለይና በፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1921, 1719, 1720, 1727, 1719(2), 1920, 1845, 1924(1), 1922(3), 1926 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁ23/2002 አንቀጽ 1(1), የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ 24/2002 አንቀጽ 1(3) የንግድ ህግ ቁ. 654(1), 657(1), 712 አዋጅ ቁ. 57/1989 አዋጅ ቁ 648/2001 አንቀጽ 2/20 አንቀጸ 2(18) አዋጅ ቁ. 110/90 አንቀጽ 2(2)	47004	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ባሌ ገጠር ልማት ድርጅት	መጋቢት 11/2004	392
105	•አንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንዲፈርስ ለመጠየቅ በቂና ህጋዊ መስፈርቶች መሟላታቸው መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፣ • የማህበር ሥራው በአግባቡ አልተመራም ከሚል ጥያቄ ጋር በተያያዘ አግባብነት ያለው አካል የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጐች መሠረት በማድረግ እንዲስተካከል ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁጥር 217, 218, 511, 543	71134	አቶ ያሬድ ሲሳይ እና አልግሪን አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሰኔ 04/2004	399

https://t.me/ethiopianlegalbrief

106	• ስለ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarangee Bond) እና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ የተከለከሉ ስለመሆኑ • የአክሲዮን ማህበራት ፕሬዚዳንት ወይም ዋና ሥራ አስኪያጅ ስላለው ስልጣን እና በህግ አግባብ ስልጣኑ ተገድቧል ለማለት ስለሚቻልበት ሁኔታ • የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ እንደ የኢንሹራንስ ፖሊሲ የማይቆጠር ስለመሆኑና በፍ/ብሔር ህጉ ስለ ዋስትና ግዴታ በተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ፡ ቁ. 24/2004 አንቀጽ 3,1(3) ቁ. 23/2004 አንቀጽ 1(1) አዋጅ ቁ. 86/86 አንቀጽ 2(4) ,6,4 32-34 አዋጅ ቁ. 87/89 አንቀጽ 2(18) አዋጅ ቁ. 110/90 አንቀጽ 2(2) የፍ/ብ/ሀ/ቁ.1725(ሀ),1727,1922(2),(3) አዋጅ ቁ. 648/2001 አንቀጽ 2(20) የንግድ ህግ ቁ.36(1)(2), 121(ሰ), 348(3), 313(1)-(7), 313(10-12), 34(1),1 09(ረ), 323(2-3), 35(1), 26, 120	40186	አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) እና ዳሸን ባንክ (አ.ማ)	የካቲት 27/2004	402
107	የአክሲዮን ማህበር ሥራ አስኪያጅ ያለአግባብ ከስልጣኔ (ከስራ አስኪያጅነቱ) ተሽሬያለሁ በሚል በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍ/ቤት ግለሰቡን ወደ ስራ አስኪያጅነቱ እንዲመለስ ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁ. 525-537	63200	እነ ጣና ኢንጂነሪንግ ኃላ/የተ/የግል ማህበር(አራት ሰዎች) እና ሚስተር አልቸዲ ዩልጋውዲዮ	ታህሳስ 30/2004	417

https://t.me/ethiopianlegalbrief

108	• የመሬት ይዞታና በመሬት የመጠቀም መብት ያለው ወገን በውል ለ3ኛ ወገን ሊያስተላልፍ ስለሚችለው የመብት አድማስ • በመሬት የመጠቀም መብት የተላለፈለት ሰው በመሬቱ ላይ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ያፈራ እንደሆነ ንብረቱን አፍርሶ (ነቅሎ) የመውሰድ መብትን ብቻ ሊያገኝ የሚችል ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(3), (4) አዋጅ ቁ.456/97 የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ.130/99 አንቀፅ 6	69291	አቶ ጀማል አማን እና ወ/ሮ ተዋበች ፈረዴ	ህዳር 08/2004	423
109	•የመሬት ባለ ይዞታ የሆነና በመሬቱ የመጠቀም መብት ያለው ሰው ለሁለት ዓመት ያህል መሬቱን በመተው ከአካባቢው ከጠፋ የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬቱ የመጠቀም መብቱ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ •በገጠር የእርሻ መሬት ላይ አርሶአደሮች ያላቸውን የይዞታና የመጠቀም መብት መደፈር ጋር በተያያዘ የሚነሣ ጥያቄ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.456/97 የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ.130/99 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(4) የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677(1)(3), 1845	69302	አቶ ሸለማ ነገሰ እና አቶ ፋይሣ መንግስቱ	ታህሣሥ 20/2004	426
110	የገጠር መሬት ባለይዞታነትን በማረጋገጥ የተሰጠ የምስክር ወረቀት የመጨረሻና የማይስተባበል ማስረጃ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የአማራ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ.133/99 አንቀፅ 24(4) ደንብ ቁ.51/99 አንቀፅ 20(4)	69821	አቶ ጥላሁን ንበዜ እና እነ አቶ መኩተ ኃይሉ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 17/2004	430
111	• በአንድ ንብረት ላይ የጋራ መብት ካላቸው ሰዎች ጋር በተገናኘ የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ፣ • የጋራ ባለሃብቶች ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዱ ካለበት ያልተከፈለ ዕዳ የተነሣ ንብረቱ የሚሸጥ ቢሆን ሌሎቹ የጋራ ባለሃብቶች ሊሸጥ ያለውን ድርሻ አስገድዶ ለመግዛት የቅድሚያ መብት ያላቸው	59504	እነ አቶ እንዳለ ወርቅነህ (ስድስት ሰዎች)	የካቲት 27/2004	433

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1289(1)(2), 1290, 1261, 1388, 1406, 1281		እና አቶ ተሸለ ቱቾ		
112	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን በማረጋገጥ ከሚሰጥ የምስክር ወረቀት (ካርታ ወይም ደብተር) ጋር በተያያዘ በአንድ ወቅት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል የተሰጠን የምስክር ወረቀት መሰረት በማድረግ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በሌላ ጊዜ ሰነዱ በአስተዳደር አካሉ መምከን የተሰጠውን ፍርድ በአንድ ጊዜና ሙሉ ለሙሉ ዋጋ የሚያሳጣ ሳይሆን ካርታው በመምከኑ የተጐዳው ወገን የአስተዳደሩን አካል እርምጃ (ውሳኔ) ክርክር ሊያቀርብበት የሚችልና ፍ/ቤቶችም የእርምጃውን አግባብነትና ህጋዊነት ሊያጣሩት የሚችሉት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1195, 1196, 1206 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(1)(2)	64014	ዶ/ር ገነት ሥዩም እና እነ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17/18 አስተዳደር ፅ/ቤት (ሶስት ሰዎች)	የካቲት 28/2004	437
113	በከሳሽነት የተሰየመ ወገን አንድ ንብረት በአንድ ህጋዊ ተግባር ሳቢያ ወደ እጁ ገብቷል በይዞታዬ ላይ እያለ ሁከት ተፈጠረብኝ በሚል የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ በእርግጥም ሁከት ተፈጥሯል አልተፈጠረም የሚል ጭብጥ በመያዝ ሊስተናገድ የሚገባ እንጂ ክርክር የተነሣበት ንብረት በከሳሹ እጅ እንዴት እንደገባ ወይም ወደ ከሳሹ እጅ ሊገባ የቻለበትን ህጋዊ ተግባር ለመመርመር የሚያበቃ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1149	70801	ዋት ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ወ/ሮ ፎዚያ ቃዲ	የካቲት 30/2004	441
114	• የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ጋር በተያያዘ የሚመለከተው የአስተዳዳር አካል አንዱ የሰጠውን የባለሀብትነት ማረጋገጫ ደብተር (የምስክር ወረቀት) በሌላ ጊዜ የሰረዘው እንደሆነ ይኼው ተግባር በፍ/ቤት ክስ ሊቀርብበት የማይችል ወይም የማይስተናገድ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ •የአስተዳደር አካል ህጋዊ ምክንያት ሣይኖረው በአንድ ወቅት የሰጠውን የባለቤትነት ደብተር ከሰረዘ ይኸው አካሄድ ህጋዊ አይደለም የሚለው ወገን በፍ/ቤት መብቱን ለማስከበር ክስ ሊያቀርብና ፍ/ቤቱም ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1195,1196	57186	ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ከፊሉ ታረቀኝ	መጋቢት 10/2004	443
115	የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ የደረሰው ሰው እዳውን ከፍሎ ያጠናቀቀ ቢሆን እንኳን እጣው ከደረሰው ቀን አንስቶ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ	65140	ወ/ሮ በላይነሽ ቢያድግልኝ	መጋቢት 10/2004	447

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የማይችል ስለመሆኑና ከዚህ ጊዜ በፊት ቤቱን አስመልክቶ የሚደረግ ውል ፈራሽ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 370/95 አንቀጽ 14(2) የአ.አ አስተዳደር አዋጅ ቁ 19/97 አንቀጽ 21 የፍ/ብ/ህ/ቁ 1678,1808(2)		እና ወ/ሮ አስቱር ገበሬ		
116	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን አስመልክቶ የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተገቢውን ስርዓት እና ደንብ በመከተል የተሰጠ መሆን ያለበት ስለመሆኑና በተመሳሳይም በአንድ ወቅት የተሰጠን የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመሰረዝ አግባብነት ያላቸውን ስርዓቶች በመከተል መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1195-1198	67011	እነ የወ/ሮ ጣይቱ ከበደ ወራሽች (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ጥሩነሽ ኃየሌ (ሶስት ሰዎች)	መጋቢት 11/2004	450
117	ከአዋጅ ውጪ የተወሰደ ንብረት ነው በሚል ንብረትን ከመንግስት አካል ያስመለሰ ወገን የንብረቱ አመላለስ አግባብነት የሌለው ሆኖ በመገኘቱ ንብረቱ ወደ መንግስት እንዲመለስ ሲወሰን ንብረቱን ያለአግባብ በእጁ ያቆየው ወገን ንብረቱ ያስገኝ የነበረውን ገቢ ወይም የታጣ ገቢ ጭምር የመክፈል ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ 572/2000 አንቀጽ 6	67631	የአቶ አሰፋ አባዲዮ ባለቤትና ወራሾች እነ ወ/ሮ ዕጌ ሽኔ (ሰባት ሰዎች) እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ሚያዝያ 24/2004	453
118	አንድ ጉዳይ ለመፈፀም (ለማስፈፀም) በሚል ምክንያት መነሻነት የሰጠሁትን ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለተሰጠበት ዓላማ አላዋለም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የአደራ ህግ ጽንስ ሀሳብን መሠረት በማድረግ ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑና ጉዳዩን ለማስረዳት የሰው ማስረጃ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣	69160	አቶ ሶሬሳ ጋሪ እና አቶ አብርሃም ፍቃዱ	ሚያዝያ 24/2004	457
119	አከራይ የሆነ ወገን ተከራይ ለሆነው ወገን ቤት እንዲለቀቅ በሚል የሚፅፈው ማስጠንቀቂያ ከአከራይና ተከራይ ውልና ግንኙነት አንፃር የሚታይ እንጂ እንደ ሁከት ተግባር የማይቆጠር ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1149(1), 2966(1)	67691	የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር እና	ታህሣሥ 16/2004	460

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ወ/ሮ አለምፀሐይ ወልዴ		
	ባንክና ኢንሹራንስ				463
120	በፎርክሎዠር ህግ መሰረት የሚከናወን ሐራጅ በፍ/ቤት የሚሰረዝበት አግባብ ስላለመኖሩና ሐራጁ በህግ አግባብ ያለመከናወኑ በባንኩ ላይ የጉዳት ካሣ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.97/90 አንቀፅ 7, አዋጅ ቁ.216/92 የፍ/ብ/ሥ/ሣ/ህ/ቁ 447(1), 423(2) የፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(1), 2027, 2028, 2035	68708	እነ የአቶ ናስር አባጃቢር አባጅፋር ሚስትና ወራሾች(ሶስት ሰዎች) እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ታህሣሥ 05/2004	464
121	ባንክ ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘውን ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ንብረቶች አሻሻጥ ቅደም ተከተል ጋር በተገናኘ አቤቱታ ሊቀርብበትና ፍ/ቤቶችም ውሣኔ ሊሰጡበት የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ97/90 አንቀፅ 7, 6 አዋጅ ቁ.216/92	70824	ወጋገን ባንክ አ.ማ እና እነ አቶ ብሩክ ጫካ (ሠባት ሠዎች)	የካቲት 27/2004	467
122	• የደረሰን ጉዳት ከመካስ ጋር በተገናኘ በንግድ ህጉ እውቅና ስለተሰጣቸው የመድን ሽፋን (የኢንሹራንስ ውል) አይነቶችና ባህሪያት • ለንብረት የሚሰጥ የኢንሹራንስ ሽፋን አደጋው በደረሰበት ጊዜ ንብረቱ የነበረውን ዋጋ ለመካስ የሚያስችል መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁ. 654(2)(3),657, 674, 675, 688, 665, 678, 681, 680	69966	አቶ በላቸው እሸቴ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሚያዝያ 10/2004	472
123	•የፍርድ አፈፃፀም ጥያቄ በህጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ የባለዕዳው ንብረት እዳውን ለመሸፈን ባለመቻሉ በከፊል ተፈጽሞ ከቆየ በኋላ የፍርድ ባለመብት የባለዕዳውን ንብረት አፈላልጐ በማግኘት አፈፃፀሙን ለመቀጠል ሲፈልግ ይርጋ ሊቆጠር ስለሚችልበት አግባብ፣ •አበዳሪ የሆነ ባንክ ከዕዳው አከፋፈል ጋር በተያያዘ በባለዕዳው ላይ የአፈፃፀም ክስ መስርቶ እንደ	74898	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ፍቃዱ	ሚያዝያ 25/2004	475

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ፍርዱ ለመፈፀም የማይችል መሆኑ የተረጋገጠ ከሆነ በሌላ ጊዜ በባለዕዳው ንብረት ላይ በፍርድ ባለመብቱ የሚቀርበው የአፈፃፀም አቤቱታ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር ስለሚጀምርበት ጊዜ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384, 329(2) አዋጅ ቁ. 97/90		ተስፋዬ (ሶስት ሰዎች)		
	ከውል ውጪ ኃላፊነት				**478**
124	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ከደረሰ ጉዳት ጋር በተያያዘ ለተጐጂው የሚከፈል የጉዳት ካሣ አከፋፈል በአንድ ጊዜ እንዲከፈል ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2154, 2095(2)	67225	አቶ ኤርሚያስ ሓይሉ የሆነስት የረር ማኔጂንግ ዳይሬክተር እና አቶ ብርሃኑ ዳምጠው	የካቲት 26/2004	479
125	በኤሌክትሪክ መስመር ምክንያት ከደረሰ የቃጠሎ አደጋ ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የጉዳት ኃላፊነትንና ካሣን ለመወሰን፣ ጉዳቱ በምን ምክንያትና ሁኔታ እንደደረሰ፣ መብራት ሀይል ጥፋት ሳይኖር ኃላፊ ሊያደርጉ የሚችሉ አደገኛ ሁኔታዎችን ስለመፍጠሩ ወይም በሥራው ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄ አለማድረጉ ወዘተ ተገቢነት ባላቸው ማስረጃዎች ማንጠር ያለባቸው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2028,2066,2069,2027 በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.246,247,259	63231	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ወልደ ሚካኤል ሻንቆ	ግንቦት 06/2004	483
126	ለጉዳት ከሚከፈል የሞራል ካሣ ጋር በተያያዘ ልጃቸውን በሞት ያጡ ወላጆች ሁለት በመሆናቸው ለእያንዳንዳቸው 1000 ብር ሊከፈል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2116(3)	69428	አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ እና እነ መሐመድ አባ አሊ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 26/2004	486

https://t.me/ethiopianlegalbrief

127	ብዙ ሰዎች በአንድ ጉዳይ ለደረሰ ጉዳት ካሣን እንዲከፍሉ የተገደዱ እንደሆነ እያንዳንዳቸው ለደረሰው አጠቃላይ ጉዳት ኃላፊ የሚሆኑ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2155(1)	68613	ሐጂ መሐመድ አመዴ እና አቶ መኮንን መስፍን	ሰኔ 18/2004	488
128	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ማንኛውንም ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍና የማከፋፈል ብሎም የመሸጥ ስራዎች በሚያከናውንበት ወቅት ሁሉ የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት የወጡ ህግጋትን በማክበር መሆን ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.86/89 አንቀፅ 13(1) ደንብ ቁ.49/91 አንቀፅ 23(2), 35	65395	አቶ ትዕዛዝ ኮሬ እና የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	የካቲት 26/2004	490
129	ከአሰሪና ሠራተኛ አገናኝ አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሰዎችን ወደ ውጪ አገር የላክ ሰው በተላኩት ሰዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ካሣ የመክፈል ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 632/2001	74111	የማህደር ኤጀንሲ ባለቤት ወ/ሮ አለምነሽ ኤርሞ እና ወ/ሪት አለም መስፍን ተወካይ ገበየ ደጉ	ሐምሌ 04/2004	495
	ጉምሩክ /ቀረጥ/ ግብር				**498**
130	በኃላፊነት ይዞት በሚገኝ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትን በመተላለፍ ዕቃን ሲያጓጉዝ የተያዘ ሰው ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብና ተፈፃሚ ስለሚሆነው የህግ ድንጋጌ አዋጅ ቁ.60/89 አንቀፅ አዋጅ ቁ.368/95 አንቀፅ 79,80(1), 81,64(4)74 ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.113(2)	54889	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና አቶ ንጉሴ ገብረዓዲቅ	መስከረም 26/2004	499
131	በጉምሩክ ወንጀል የተከሰሰ ሰው በነፃ የተለቀቀ ቢሆንም ወንጀሉ የተፈፀመበት እቃ ወይም ማጓጓዣ	64115	እነ አቶ አህመድ	ጥቅምት	502

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የሚወረሰው የጉምሩክ ህግን የመተላለፍ ድርጊት ስለመፈፀሙ ፍርድ ቤቱን የሚያጠግብ ማስረጃ ሲቀርብ ስለመሆኑና ማስረጃው አጥጋቢ ካልሆነ ብቻ ፍ/ቤት እቃውን (ማንንጥውን) እንዳይወረስ በማድረግ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ሊያዝ የሚገባው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀፅ 104(3)(ሀ), 104(3)(ለ)		ሁሴን (ሁለት ሰዎች) እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	08/2004	
132	የበጐ አድራጐት ሥራን የሚሰሩ ድርጅቶች ከቦታ ኪራይ እና የቤት ግብር ነፃ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ አዋጅ ቁ.80/68 አንቀፅ 14(ለ) የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ.36/68 አንቀጽ 8	66474	የኢትዮጵያ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን የአቃቂ አድቬንቲስት ሚሲዮን ት/ቤት እና የአቃቂ ቃልቲ ክፍል ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት	ጥቅምት 17/2004	506
133	• ህንፃን (ቤትን) በኪራይ ይዞ የሚገለገል ወገን ለአከራዩ ከሚከፍለው የኪራይ ዋጋ ላይ በህግ የተመለከተውንና ለመንግስት ገቢ ሊሆን የሚገባውን ግብር ተቀናሽ ለማድረግ ስለመቻሉና ይህንን ለማድረግም የግዴታ የፍ/ቤት ውሣኔ የማያስፈልገው ስለመሆኑ • በፍርድ የኪራይ ዋጋን ለአከራይ እንዲከፍል የተወሰነበት ተከራይ ለመንግስት የሚከፈልና ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ እንዲያስቀር የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ያለበት በመሆኑ ሙሉውን የኪራይ ዋጋ ለአከራዩ እንዲያስረክብ በአፈፃፀም ሊገደድ ስላለመቻሉ አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 91, 101, 53(1) ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀፅ 24, 2(ሸ)	69677	ዳሽን ባንክ አ.ማ እና አቶ ኑረዲን መሐመድ	ታህሣሥ 20/2004	511

https://t.me/ethiopianlegalbrief

134	የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ መወጣት ጋር በተያያዘ ታክስ ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን የመጠቀም ግዴታ የሚኖርባቸው የንግድ ፈቃድ የሥራ ዘርፍ በግልፅ ተለይቶ በተመለከተባቸው ሽያጮች ጋር በተገናኘ ብቻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.285/94 አንቀፅ 55 አዋጅ ቁ.609/201 አንቀፅ 50(መ)(2) ደንብ ቁ.139/99 አንቀፅ 5(1)(ለ) የወ/ህ/ቁ.23(2)	74753	እነ ሐበሻ የባህል ማዕከልና የስእል ጋለሪ ኃ.የተ.የግል ማህበር (ሶስት ሰዎች) እና የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዓቃቤ ህግ	ታህሣሥ 17/2004	514
135	ከታክስ/ግብር አከፋፈል ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ያለውን ቅሬታ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በይግባኝ ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜና ስሌቱን ተግባራዊ ስለማድረግ አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 107(2), 108	66350	አቶ ቴዎድሮስ ደበላ እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን የልደታ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት	ጥር 02/2004	518
136	ግብር ከፋይ የሆነ ወገን ምንም አይነት የሂሣብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደ ሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሣብ መዝገቡንና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለስልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ሊከፈል የሚገባው የግብር መጠን በግምት ሊወሰን ስለመቻሉ አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 69(1), 71	69921	አቶ አበበ ገ/አግዚአብሔር እና አራዳ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ዐቃቤ ህግ	ጥር 02/2004	521
137	•ከጉምሩክ ባለስልጣን ሹም ፈቃድ ሳያገኝ በመተላለፍ ላይ ያሉ ወይም የጉምሩክ ወደብ በደረሱ ወቅት የእቃ መያዣ ላይ የተደረገን ማሸጊያ መፍታት በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ	65041	አቶ አንዳርጌ እሸቱ እና	የካቲት 30/2004	524

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	•በጉምሩክ ወደብ በምርመራ ላይ ካሉ ዕቃዎች ለሳምፕልነት በሚል ወስዶ አለመመለስ በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀፅ 100, 95(ሀ)		የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ህግ		
138	የተጨማሪ እሴት ታክስን ተግባራዊ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 49 መሰረት በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ላይ ቅጣት ሊጣል ስለሚችልበት ሁኔታ፣ አዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 49,47,50(2) የወ/ህ/አ 2(2)	68422	እነ ጀሪኮ ሰርቪስ (ሁለት ሰዎች) እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን	መጋቢት 14/2004	527
139	ተከራይ የሆነ ወገን ለአከራይ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ ለመንግስት የሚከፈለውን ግብር ሳይቀንስ ለአከራዩ እንዲከፈል ለማስገደድ የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1716, 1718, 1711 አዋጅ 286/94 አንቀጽ 56, 91, 83	65361	ዘመነ ዮሐንስ ጀኔራል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና አቶ ዳውድ ኢብራሂም	ሚያዝያ 09/2004	532
140	•የግብር ከፋይ የሆነ ሰው ገቢውን በህጉ አግባብ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ከማሣወቅ ውጪ ደረጃውን በራሱ ሊወሰን /ሊለወጥ/ የማይችል ወይም የማይገባ ስለመሆኑ፣ •የግብር አከፋፈል ስርዓት ለግብር ከፋዩ ግልጽ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 38 ደንብ ቁ. 78/94 አንቀጽ 18,22 አዋጅ ቁ. 308/95 አንቀጽ 10(2)(ሐ) አዋጅ ቁ. 587/2001	72824	የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ፅ/ቤት እና አቶ ሚሊዮን አሰፋ	ሐምሌ 18/2004	534
141	• ለግል አገልግሎት ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባን መኪና ለብድር መያዣነት መስጠት በወንጀል ኃላፊነትን (ተጠያቂነትን) የሚያስከትል ስለመሆኑ	69602	እነ አቶ አካሉ አለሙ (ሁለት	የካቲት 06/2004	539

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• በወንጀል ጉዳይ በቅጣት መልክ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በፍ/ብሔር ጉዳይ ከሚኖረው የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት የተለየ ስለመሆኑና ቅጣቱ በእያንዳንዱ አጥፊ ላይ ለየብቻ ሊጣል የሚገባው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 73(1) አዋጅ ቁ. 60/89 አዋጅ ቁ.280/94 የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ), 41		ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ		
	ውክልና				**543**
142	• የውክልና ውሎች በጠባቡ ሊተረጐሙ የሚገባ ስለመሆኑ • "በስማችን ውል እንዲዋዋል" በሚል በደፈናው የተሰጠ ውክልና ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2181(3), 2205, 2204	50985	እነ አቶ ስሻህ ክፍሌ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ አፀደ ዱቤ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 05/2004	544
143	•ልዩ የውክልና ስልጣን ለመስጠት በተዘጋጀ ሰነድ ላይ ልዩ ውክልና ስለመስጠት በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች ያለመጠቀስ ልዩ የውክልና ስልጣን እንዳልተሰጠ የሚያስቆጥር ስላለመሆኑ •የአስተዳደር አካል የሆነ ተቋም በአንድ ወቅት የሰጠውን የፅሁፍ ማስረጃ በሌላ ጊዜ ማስተካከሉ በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት የተለያዩ ሰነድ ቀርቧል በሚል እንደማስረጃ ሰነድ ዋጋ የሚያጣበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ •በውክልና ሰነድ ላይ ለተወካይ የተሰጠው ስልጣን በይዘቱ ልዩ ውክልና የሚያመለክት ሆኖ ሰነዱ ስለ ልዩ ውልክና አስፈላጊነት የተቀመጠውን የፍ/ብ/ህ/ቁ 2208 ያለመጥቀሱ ብቻ ለተወካዩ ልዩ የውክልና ስልጣን እንዳልተሰጠ የሚያስቆጥር ስላለመሆኑ፣ •ከሰነድ ማስረጃ ተቀባይነት ጋር በተያያዘ የሚነሣ ጥያቄ የህግ ጥያቄ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2205, 2005(1), 2179, 2199, 2203, 2204	72337	ወ/ሮ ንግስቲ እምነት እና ቴዎድሮስ ተክሌ	የካቲት 26/2004	549

https://t.me/ethiopianlegalbrief

144	አንድን ተቋም ወክሎ ውል ለመዋዋል በህግ ስልጣን የተሰጠው ሥራ አስኪያጅ ስልጣኑን ለሌላ ሰው በህግ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ አስተላልፎ ውል የተደረገ እንደሆነ ተቋሙ በሥራ አስኪያጁ በራሱ በመፈረም ውል አላደረገም በሚል ምክንያት ብቻ በውሉ አንገደድም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731 2274 2214(1 2215(3),2180)	68498	አቶ ገብረ ክርስቶስ ገብረ እግዛብሔር እና ሳባ እምነበረድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	ሰኔ 07/2004	553
145	የፀና የውክልና ስልጣን ከሌለው ሰው ጋር የተደረገ ውል ከጅምሩ ፈራሽና ህጋዊ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2232(2),2015(ሀ),2005(2),1204	73291	እነ አቶ አፅብሃ ወልዳይ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ዙሪያሽ አሰግድ የክልሉ ፍትህ ቢሮ	ሐምሌ 04/2004	559
146	•የውክልና ውል ሳይኖር ወኪል ነኝ በሚል የሚደረግ ውል ህጋዊ ውጤት አግኝቶ የሚፀናበት አግባብ ስላለመኖሩ፣ • የውክልና ሥልጣኑ ከመሰጠቱ በፊት የተደረገ ውል ውክልና ከተሰጠ በኋላ ሊፀና ይችላል ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑና ወካይ የሆነ ሰው የወካዩን ድርጊት እንደተቀበለ ሊቆጠር የሚችለው በህግ የሚፀና የውክልና ውል ኖሮ ነገር ግን ወኪሉ ከተሰጠው ስልጣን በላይ ሰርቶ የተገኘ እንደሆነ ወይም የውክልና ስልጣኑ ካበቃ (ከተቋረጠ) በኋላ ወካዩን በመወከል የሰራቸውን ሥራዎች በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2190, 1678 (ሐ),1719(2),1723	74538	ወ/ሪት አሊያት ይማም ሙዘይን እና አቶ እምነቴ እንደሻው	ሐምሌ 20/2004	563
147	ወካይ የሆነ ወገን በተወካይ አማካኝነት የተደረገን ህገ ወጥ ውል እንዲፈርስ በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በአሥር አመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)(2),2198,1810,1808(1),1845	67376	እነ ወ/ሮ ንግስት ኪዳኔ (ሁለትሰዎች) እና እነ አቶ በለጠ ወልደሰማያት(ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2004	567

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዕምሯዊ ንብረት				572
148	ከቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጋር በተያያዘ የፊልም ባለቤት ለመሆን በማሰብ በባለሃብትና ፊልሙን ለመስራት በሚል በተደረገ ስምምነት መነሻነት ፊልሙን ለህዝብ ከማቅረብ ጋር ተያይዞ ጉዳዩ በፍ/ብሔር ክርክር ተደርጉበት በተሰጠ ውሣኔ መሰረት ፊልሙን በእጅ አድርጉ መገኘት በወንጀል ተጠያቂነት የማያስከትል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.410/96 አንቀፅ 7(1)(ሀ), 36(1) የወ/ህ/ቁ.23(2), 57-59	70500	ኢንጅነር አድማሱ ገብሬ እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ	ታህሣሥ 17/2004	573
149	•ከቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጋር በተያያዘ የመብቱ ተጠቃሚዎችና የመብቱ አድማስ •የቅጅ መብት እንዲከበር ለመጠየቅ መሟላት ስለሚገባቸው ነገሮችና መብቱ እንደተጣሰ የሚቆጠርበት አግባብ አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀፅ 7, 9-19, 2(6)	68369	እነ ሳሙኤል ሃይሉ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ስምረት አያሌው /ዘጠኝ ሰዎች/	ጥር 04/2004	576
	አፈፃፀም				582
150	ፍርድን ከማስፈፀም ጋር በተያያዘ በተጀመረ የአፈፃፀም መዝገብ የተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ቀርቦበት በበላይ ፍ/ቤት ትዕዛዙ ከተለወጠ የአፈፃፀም ሂደቱ መቀጠል ያለበት አፈፃፀሙን በጀመረው የበታች ፍ/ቤት ደረጃ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 371-385	64129	ኢስላሚክ ሪሊፍ ኢትዮጵያ እና አቶ መሐመድ ሠይድ	ህዳር 21/2004	583
151	•ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተገናኘ የሚንቀሳቀስ ንብረት የሀራጅ ሽያጭን አስመልክቶ ተፈፃሚነት ያላቸው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች •የሚንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የተካሄደ ጨረታ ሊፈርስ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.432-438, 445	70378	እነ አቶ ልኡልሰገድ አጥላባቸው (አራት ሰዎች) እና እነ ፍሎራ ኢኮ ፖወር ኃ/የተ/የግል	ጥር 04/2004	585

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ድርጅት (ሁለት ሰዎች)		
152	ክፍርድ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በፍ/ቤት የተሰጠን ትዕዛዝ አለማክበር ስለሚያስከትለው ውጤት፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 156, 409(1) የፍ/ብ/ህ/ቁ.400	65814	ሚ/ር ቺዛኖ ቤነኛ እና አቶ ዘውዱ ወልደሥላሤ	የካቲት 29/2004	588
153	ለባልና ሚስት በብድር ገንዘብ የሰጠ ባንክ የባልና ሚስቱ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ተወስኖ ንብረት ለመከፋፈል በአፈፃፀም ደረጃ ለሚገኝ ፍ/ቤት መብቱን ለማስከበር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 418 የሚያቀርበው የተቃውሞ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.418, 419 አዋጅ ቁ. 97/90 አዋጅ ቁ.97/90 የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 89	69385	ዳሸን ባንክ (አ/ማ) እና እነ ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 28/2004	593
154	አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው በሚል ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ክፍፍሉን በተመለከተ ጥያቄ የቀረበለት የአፈፃፀም ችሎት ንብረቱ ሰነድ አልባ ነው የሚል ምክንያትን ብቻ በመያዝ ለአፈፃፀም የቀረበውን መዝገብ በመዝጋት የሚሠጠው ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 225(2),423,392(1),371(1)	73041	ወ/ሮ ሰይዳ ደበሌ እና አቶ ሸሪፍ ሽኩር	ሰኔ 22/2004	596
	የዳኝነት ስልጣን				**598**
155	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር አስፈፃሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳዳር ባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸው የሊዝ ውሎችን መሠረት አድርጉ የሚነሱ የውል አፈፃፀምና ተያያዥ ጉዳዮችን አይቶ ለመወሰን የከተማው ፍ/ቤቶች የሥራ-ነገር ስልጣን ያላቸው (የተሰጣቸው) ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ሀ) እና (መ)	77175	አሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ኢትዮጵያ እና እነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር (ሶስት ሰዎች)	ሐምሌ 19/2004	599

https://t.me/ethiopianlegalbrief

156	ሃይማኖታዊ ከሆኑ አለመግባባቶች ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቶች የአምልኮት ሥርዓትን ሆነ ሃይማኖታዊ ህገ-ደንቦችን በመተርጐም ውሣኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 11(1)(3), 37(1)	66957	የኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን እና በኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትቤተክርስቲያን የሐዋሳ ቁጥር 2 ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የቦርድ አባላት፡-	የካቲት 26/2004	603
157	የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የከተማው አስተዳዳር የሚያስተዳድራቸውን የንግድ ቤቶች ባለቤትነትን በተመለከተ በግለሰቦች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ረ) አዋጅ ቁ. 408/96 አንቀጽ	69064	ወ/ሮ አክሊለ ገብሬ እና አቶ መለኮት ክንፈሚካኤል	ጥር 18/2004	607
	ልዩ ልዩ				**610**
158	የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች የገንዘብ መጠኑ ከብር 5000 በታች የሆኑ ማናቸውም የፍትሐብሔር ክርክር ለመመልከት ስልጣን አላቸው ተብሎ በአዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 50(1) የተመለከተው ድንጋጌ ተግባራዊ መሆን ያለበት የቀረበው ጉዳይ ልዩ ባህሪ እየታየ በጉዳዩ ላይ የሚነሣው የህግ ጥያቄ ውስብስብነት በመመዘኛነት (በመለኪያነት) ተይዞ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 50(1) አዋጅ ቁ.25/88 አንቀፅ 5(1), 6 አዋጅ ቁ.416/96 አንቀፅ 41	54990	የኢት/ቴሌኮሙ ኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ማርቆስ አበበ	ህዳር 18/2004	611

https://t.me/ethiopianlegalbrief

159	• የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት በክልል ጉዳዮች ላይ የሰጡትንና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ ለማረም ስልጣን ያለው ስለመሆኑ • የሰበር ስርዓት በባህሪው ከይግባኝ ሥርዓት የተለየ ስለመሆኑና በሰበር ደረጃ ተጨማሪ ምስክሮችንና ማስረጃዎችን አስቀርቦ መስማትና የፍሬ ነገር ጉዳዮችን ተቀብሎ ማስተናገድ አግባብነት የሌለውና ህገ-ወጥ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገመንግስት አንቀፅ 80(3)ለ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.343(1)	55273	አቶ ዘውዱ ግዛው እና ወ/ሮ አየለች ደስታ	ህዳር 18/2004	615
160	የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባለው የውክልና ስልጣኑ በዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠን ውሣኔ የለወጠው ከሆነ ጉዳዩ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ከመቅረቡ በፊት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ), (2)(4) አዋጅ ቁ.322/95 አዋጅ ቁ.25/88 አንቀፅ 9(2), 5(2)	64845	አቶ ሀብቱ ሀጋዚ እና እነ የኮምቦልቻ ግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 26/2004	618
161	የፌዴራል መንግስት ተቋማት በአጠቃላይና የከፍተኛ ት/ት ተቋማት በተለይ የራሳቸው የሆነ የእድገት አሰጣጥ፣ የቅሬታ አፈታትና አጠቃላይ አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚከናወንበት አግባብ ያለ በመሆኑ በቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩ ቀርቦ ውሣኔ የሚሰጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 515/99	73549	የዲላ ዩንቨርስቲ እና እነ አቶ የትናየት ጣፋ (ሶስት ሰዎች)	ሰኔ 22/2004	620
162	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአንድ ወቅት የሰጠውን የህግ ትርጉም በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ የተለየ የህግ ትርጉምና የተለየ አቋም መያዙ በቀደመው የህግ ትርጉም መሠረት ዳኝነት የተሰጠበት ጉዳይን እንደገና እንደ አዲስ እንዲስተናገድ ለማድረግ የማያስችል ስለመሆኑ፣	68573	እነ አቶ ጌታቸው ዳየስ /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ሩስያ ከድር	መጋቢት 12/2004	623

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 61480

ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- አቶ ገ/እግዚአብሔር ከበደው - ጠበቃ አንተነህ ተካልኝ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ት ሠላማዊት ወ/ገብርኤል - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመቀሌ ቀዳማዊ ወያኔ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ መሰረትም ሟች እናታቸው ወ/ሮ ድንቅነሽ ድምጹ ከአመልካች ጋር በባልና ሚስትነት ሲኖሩ በጋራ ያፈሯቸው የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ጠቅላላ ድምሩ ብር 426,900.00 (አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር) ከሆነው የእናታቸውን ድርሻ ግማሽ ብር 213,450.00 (ሁለት መቶ አስራ ሶስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር) እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካችም ጉዳዩ በፍርድ ቀድሞ ማለቁንና በድጋሚ ዳኝነት የማይጠይቅበት መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስተው ከመከራከራቸው በተጨማሪ የዋና ጉዳይ ክርክርም አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ተጠሪ በክሱ የጠየቁትን ግማሽ ገንዘብ ከአራት ወንድሞቻቸው ጋር እንዲወስዱ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለመቐሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማጽናት የገንዘቡን መጠን ብቻ ወደ ብር 123,450.00 (አንድ መቶ ሃያ ሶስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር) ዝቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በጉዳዩ ላይ ሁለቱ የበታች ፍርድ ቤቶች የተለያየ ውሳኔ የሠጡበት በመሆኑ በይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ከሚቀርብ በስተቀር ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት መዝገቡ ተዘግቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት አይደለም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት መዝገቡ የመዘጋቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ይህ ችሎትም በዚህ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙን በጽሑፍ እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ትእዛዝ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ክርክሩ የነበረው በሁለት በተመሳሳይ ክልል ኗሪ በሆኑ ግለሰቦች ሲሆን ክርክሩም የንብረት ግምት ክርክር መሆኑን፣ ክርክሩ የተጀመረው በወረዳ ፍርድ ቤት ሁኖ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ተገቢ ነው ያለውን ግምት እንዲከፍሉ ወስኖ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ይኸው ፍርድ ቤትም አመልካች ለክሱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑን እንዳለ በመቀበል የኃላፊነት መጠኑን ብቻ በማሻሻል መወሰኑን ነው፡፡ እንግዲህ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ሲቀርብለት የመጨረሻ ፍርድ አልተሰጠበትም በማለት መዝገቡን የዘጋው በሁለቱ የበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የተለያየ ነው በማለት ነው፡፡ እኛም የዚህኑ ትዕዛዝ ተገቢነት ተሻሽሎ ከወጣው የትግራይ ብሄራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 49/1994 አንቀፅ 16(ለ) ድንጋጌ አኳያ ተመልክተነዋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለባቸው የክልል ጉዳዮች የሰበር ስልጣን የሚኖረው በወረዳ ፍርድ ቤት ተወስነው በይግባኝ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም በጠቅላይ ፍርድ ቤት ያለቁ ጉዳዮች መሆናቸው ሲረጋገጥ መሆኑን ተጠቃሽ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ሁለት ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ተመሳሳይ ውሳኔ ከሰጡ ውሳኔው የመጨረሻ እንደሚሆንና በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን በአዋጁ አንቀጽ 17 መሰረት አዘጋጅቶ እንደሚያቀርብ ነው፡፡ በመሆኑም በክልሉ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 93/1997 አንቀፅ 30(2(ሀ)) ስር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሁኖ የበታች ፍርድ ቤቶች ተመሳሳይ ውሳኔ የሠጡበት ጉዳይ በድጋሚ ይግባኝ የሌለውና ሊቀርብ የሚችለው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ብቻ መሆኑን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ለመቅረብ ብቁ አይደለም በማለት መዝገቡን የዘጋው የበታች ፍርድ ቤቶች የተለያየ ውሳኔ በጉዳዩ ላይ ሰጥተዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካችን ኃላፊነትን በተመለከተ ሁለቱም ፍርድ ቤቶች ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ የወሰኑ ከመሆናቸውም በላይ ይግባኝ አቅራቢም የአሁኑ አመልካች የነበሩ በመሆኑና የይግባኝ መብት የተፈቀደው ከአንድ ጊዜ በላይ ስለመሆኑ የሚያመላክት የክልሉ የሕግ ማዕቀፍ በሌለበት ሁኔታ (ከይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት አንፃር) በጉዳዩ ላይ የተለያየ ውሳኔ ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበትና ሊታይ የሚችለውም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሁኖ እያለ መዝገቡ መዘጋቱ ከተሻሻለው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 49/1994 አንቀጽ 16(ለ) እና 17 ድንጋጌዎች እና ከይግባኝ መብት አንፃር መሰረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 34685 ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በጉዳዩ ላይ ሁለት የበታች ፍርድ ቤቶች ተመሳሳይ ውሳኔ የሰጡበት በመሆኑና የመጨረሻ ውሳኔ ያረፈበት በመሆኑ አመልካች ጉዳዩን ለማቅረብ የሚችሉት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ነው በማለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ተገቢውን ትእዛዝ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 31264

ህዳር 06 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- ወ/ሮ እመቤት መኮንን- ጠበቃ ነቃጥበብ በየነ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- ወረዳ 20 ቀ. 29 አ/ጽ/ቤት - አልተጠራም

ተቃዋሚ፡- አቶ ዓይናዲስ ገዳሙ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

መዝገቡ በውሳኔ ከተዘጋ በኋላ እንደገና የተንቀሳቀሰው ተቃዋሚ ሁነው የቀረቡት አቶ ዓይናዲስ ገዳሙ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደገው ክርክር መሠረት የተሰጠው ውሳኔ የእኔን መብት የሚነካ በመሆኑ ሊለወጥ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ በዚህ መሠረትም የሰበር አመልካች በቀረበው የመቃወሚያ አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጡ ተደርጎ ግራ ቀኙ በጽሁፍ ተከራክረዋል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች እና ተጠሪ በመሃከላቸው የነበረው የሆቴል ንግድ ድርጅት ቤት የኪራይ ውል ሊቋረጥ ይገባል፣ አይገባም ላይ ሲከራከሩ ቆይተዋል፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አመልች፣ተከሳሽ ደግሞ ተጠሪ የሆነው የቀበሌ አስተዳደር፣የአሁኑ የፍርድ ተቃውሞ አቅራቢና አቶ አንተሁነኝ ገዳሙ ናቸው፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተጠሪና የአሁኑ ተቃውሞ አቅራቢ ለአመልካች የንግድ ድርጅቱን እንዲያስረክቡ፣ የንግድ ድርጅቱን አከራይተው አመልካች ሊያገኙ ይችሉ የነበሩትን ገቢም እንዲከፍሉ በማለት ውሳኔ የሠጠ ሲሆን የቀበሌ አስተዳደሩ እና የአሁኑ የፍርድ ተቃውሞ አቅራቢ ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ተጠሪ የሚያስተዳድረውን ቤቱን ከፈለገው ሰው ጋር የኪራይ ውል ሊያደርግ ይችላል እንጂ ከአመልካች ጋር ኪራዩን ሊቀጥል አይገባም ተብሎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው አመልካችና ቀበሌ አስተዳደሩ ከተከራከሩ በኋላ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በመጽናቱ የአመልካች የድርጅት ቤት ተከራይነት መብት ከመረጋገጡም በተጨማሪ ድርጅቱን ቢያከራዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊያገኙ ይችሉ የነበረው ገቢ ሁሉ ታስቦ እንዲከፈላቸው የገንዘቡ መጠን ተለይቶ ተወስኖላቸዋል፡፡ እንግዲህ የአመልካች የድርጅት ተከራይነት መብት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቷል፡፡ የአሁኑ ተቃዋሚ የእኔን መብት ይነካል የሚሉትም ይህንን ውሳኔ ነው፡፡ የአሁኑ የፍርድ መቃወሚያ አቅራቢ አቤቱታውን ሊያቀርቡ የቻሉት ለአመልካች ይሰጥ የተባለው የንግድ ድርጅት ቤት በይግባኝ ሰሚው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለተቃዋሚ እንዲሆን ተወስኖላቸው አመልካች ተቃዋሚን በሚመለከት ከአሁኑ ተጠሪ ነጥለው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ሶስቱ ዳኞች በሚሰየሙበት የሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ የሰ/መ/ቁጥር 31038 በሆነው ተዘግቷል በማለት ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የተቃዋሚ አቤቱታ ወይም ክርክር በሰበር ሰሚ ችሎት ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እርሳቸውን የሚመለከት የአመልካች የሠበር አቤቱታ የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቶ እያለ አምስቱ ዳኞች የተሰየሙበት የሠበር ችሎት ደግሞ ተቃዋሚ የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ መብታቸውን የሚነካ ውሳኔ ሰጥቷል በሚል ነው፡፡ ይህም ተጣርቶ እንዲወሰንላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ የፍርድ ተቃውሞ የሚቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ስር በተመለከተው ሥርዓት ሲሆን አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ የሚወሰነው ይሆናል፡፡ የሰበር ችሎቱ ፍሬ ነገሮችን በማስረጃ የማጣራትም ሆነ ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን የለውም፡፡ በእግርጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት የሚቀርበው አቤቱታ የሚስተናገደው ለመቃወሚያው መነሻ የሆነውን ውሳኔ ለሰጠው ፍ/ቤት ነው፡፡ ይሁንና አቤቱታው የሚጣራው ወይም የሚስተናገደው ማንኛውም ክስ በሚስተናገድበት ሥርዓት በመሆኑ እና ይህም ማስረጃ መስማትንና ማስረጃውን መዝኖ ውሳኔ መስጠትን የሚጠይቅ በመሆኑ በሕግ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመውን ስህተት የማረም ስልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ለተሰጠው በዚህ የሰበር ችሎት የሚታይ አይሆንም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ክርክሩ የተጀመረውና የሰበር ችሎቱም ያፀናው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሆኑ መቃወሚያው መቅረብ ያለበት ለዚሁ ፍ/ቤት ነው ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን በዚህ ፍርድ ቤት የፍርድ ተቃውሞ አቅራቢ የክርክሩ ተካፋይ ሁነው ተረቺ የነበሩ ሲሆን በአገሪቱ የፍርድ ሰጪ አካላት የመጨረሻ አካል በሆነው ሰበር ሰሚ ችሎትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ውጤቱ ከመጽናቱም በተጨማሪ አፈጻጸሙም እንዲቀጥል በሠበር መዝገብ ቁጥር 68827 የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም ምናልባት ተቃዋሚ አለኝ የሚሉትን መብት ለማስከበር ይችሉ ዘንድ መብቴን ተጋፍቶአል በሚሉት ሰው ላይ በስመ ክስ መመስረት የሚችሉ ከሚሆን በስተቀር ቀድሞ በዚህ መዝገብ የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ለማስተናገድ የሚቻልበትን ሥርዓት ስላላገኘን ተቃዋሚ ያቀረቡትን አቤቱታ በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ የሚስተናገድ አይደለም ብለናል፡፡ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የሚች ወንድሙ ደምሴ ሚስትና ወራሾች

1. ወ/ሮ ዘውድነሽ እሸቱ
2. አቶ ደረጀ ወንድሙ
3. ወ/ሮ ብርሃኔ ወንድሙ

ጠበቃ መስፍን ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ በርሄ ንስራን - ጠበቃ ከበደ ጊሹ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 49 ድንጋጌ መሰረት ክርክሩ እንዲቀጥል አቤቱታው የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች አውራሽ አቶ ወንድሙ ደምሴ ሲሆኑ ተከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ የክሱ ይዘትም ነሀሴ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. የተጻፈና በአጭር ስርዓት እንዲታይ የቀረበ ሆኖ ዝርዝሩ፡- ተጠሪ ለሚች አቶ ወንድሙ ደምሴ ብር 440,000.00 (አራት መቶ አርባ ሺህ ብር) የያዘና በሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም. የሚከፈል ቼክ ሰጥተዋቸው አቶ ወንድሙ በሕይወት እያሉ ግንቦት 02 ቀን 1997 ዓ.ም. ቼኩን ለባንክ ሲያቀርቡ በተጠሪ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ በቂ ስንቅ የለውም ተብሎ ቼኩ የተመለሰላቸው መሆኑን ገልፀው ተጠሪ የቼኩን ዋጋ ከሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድና ብር 1480 (አንድ ሺህ አራት መቶ ሰማንያ) ኮሚሽን ጋር እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ክሱ ከተመሰረተ በኋላ መስከረም 03 ቀን 1998 ዓ.ም. አቶ ወንድሙ ደምሴ ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ሲሆን አመልካቾች መስከረም 25 ቀን 1998 ዓ.ም. ፍርድ ቤት ቀርበው ሟች መሞታቸውን በመግለፃቸው ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ወደ ክርክሩ ለመግባት እንዲችሉ ረዘም ያለ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው በጠበቃቸው አማካኝነት ለፍርድ ቤቱ አመልክተው ፍርድ ቤቱ የከሳሽ ወራሾች የወራሽነት ማረጋገጫ ባገኙ ጊዜ መዝገቡን የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትለው የማንቀሳቀስ መብታቸው ተጠብቆ ለጊዜው ተዘግቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች ሚያዝያ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. ክርክሩ እንዲቀጥል አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ክስም በስማቸው አሻሽለው አቅርበዋል፡፡ አሻሽለው ያቀረቡት ክስ ይዘቱ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ተጠሪ መከላከያ መልስ ካላቸው እንዲያቀርቡ ማስፈቀጃ እንዲያቀርቡ ተደረጎ ተጠሪ ቀርበው የመከላከያ ማስፈቀጃ አቅርበዋል፡፡ በዚህም ዋናው የቼኩ ተቀባይ ከነበሩት ከሳሾች አውራሽ ጋር የነበራቸውን የግል ግንኙነት መሰረት በማድረግ ገንዘቡ በጊዜው የተከፈለ መሆኑን ለማስረዳት እና በቼኩ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የይርጋ ክርክር ለማቅረብ ክሱን ልከላከል ብለዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ መከላከያ እንዲያቀርቡ የፈቀደላቸው ሲሆን ተጠሪ ክሱ በይርጋ እንደሚታገድና ገንዘቡም ስለመከፈሉ በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ እንዲሁም መዝገቡ በወራሾች የተከፈተው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከተውን ጊዜ ባለመጠበቅ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በን/ህ/ቁጥር 881(3) መሰረት የተነሳውን ይርጋ በተመለከተ ክሱ በአመልካቾች ወራሾች መቅረቡን፣ በአመልካቾች ክሱ የተሸሻለውም ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ስለቀረቡ የአውራሻቸውን ስም በራሳቸው እንዲተኩ እንጂ አዲስ ክስ በማቅረብ ያለመሆኑን ገልጾ የይርጋ ተቃውሞውን ሳይቀበለው የቀረ ሲሆን የሥነ-ሥርዓት ሕጉን መሰረት በማድረግ የቀረበውን ተቃውሞም ከሳሾች (የአሁኑ አመልካቾች) ቀደም ብሎ አውራሻቸው የነበሩት አቶ ወንድሙ ደምሴ ክስ በተጠሪ ላይ ከአቀረቡ በኋላ መሞታቸውን እና መዝገቡም የእነርሱን ወራሽነት እስከሚረጋገጥ ድረስ ተዘግቶ ቆይቶ ከሳሾች ወራሽነታቸውን እንዳረጋገጡ መዝገቡን ማንቀሳቀሳቸውን ገልጸው ክሱን መቀጠላቸውንና ይህም በፍርድ ቤቱ ፈቃድ የተከናወነ መሆኑን ገልጸና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕቁጥር 49(1) እና 55(3) ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ አለኝ ያሉትን መከላከያ ማስረጃ እንዲያሰሙ ቀጠሮ ተይዞላቸው የሚያሰሙት ምስክር የሌላቸውና ይህንኑ መብታቸውን የተው መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማረጋገጣቸው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ብር 440,000.00 (አራት መቶ አርባ ሺህ ብር) ቼኩ ለባንክ ቀርቦ ከተመለሰበት ከግንቦት 02 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ ከ9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድና ብር 1466.00 (አንድ ሺህ አራት መቶ ስድሳ ስድስት ብር) ኮሚሽን በመጨመር ለአመልካቾች እንዲከፍሉ፣ የክሱን ወጪ ዝርዝር የማቅረብ መብታቸውን በመጠበቅ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ አመልካቾች በወራሽነታቸው ክሱን የቀጠሉት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49(1) እና 55(3) ድንጋጌዎች ስር በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ነው ተብሎ ብይን የመስጠቱን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ በወራሽነት ክርክር ለመቀጠል ጥያቄው በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ከአንድ አመት ከስድስት ወር የማይበልጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49(1)፣55(2) እና 33(3) ድንጋጌዎች ጥምር ንባብ እንደሚያስረዳ በመዘርዘር ይኸው የጊዜ ገደብ ከአለፈ በኋላ አመልካቾች ክሱን ማቅረባቸውን ማረጋገጡን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካቾች በአውራሻቸው የቀረበውን ክስ ፍርድ ቤቱ በሰጣቸው ፈቃድ መሰረት ለጊዜው አዘግተው ወራሽነታቸውን በማረጋገጥ ክሱን የቀጠሉና የወራሽነት ማስረጃ በሕጉ አግባብ የተሰጠው ግንቦት 28 ቀን 1998 ዓ.ም. ቢሆንም መብት አለኝ በሚል ወገን ተቃውሞ በመቅረቡ ምክንያት በፍርድ ቤት ታግዶ ቆይቶ የተቃውሞ ክርክር ውድቅ ከሆነ በኋላ መጋቢት 04 ቀን 2000 ዓ.ም. የወራሽነት ማስረጃው ለአመልካቾች ሲሰጥ መዝገቡን ሚያዝያ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. ማንቀሳቀሳቸው ተረጋግጦ እያለ ቀድሞ ባለቀ ጉዳይ ላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመስርቶ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49/(1)፣55(2) እና 55(3) ድንጋጌዎች መሰረት በአንድ አመት ከስድስት ወር ይርጋ የታገደ ነው በማለት መወሰኑ ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባገኙ ጊዜ መዝገቡን እንዲያንቀሳቅሱ በፍርድ ቤት ፈቃድ መዝገቡ ተዘግቶ ከቆየ በኋላ የወራሽነት ማስረጃው በተገኘ ጊዜ ተሻሽሎ ለቀረበው ክስ ሚች የሞቱበት ጊዜ መሰረት ተደርጎ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49(1)፣ 55(2) እና 55(3) መሰረት በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49(1) ድንጋጌ መሰረት ክሱን ለመቀጠል መብት አለኝ የሚሉ ወገኖች ዋናው ከሳሽ ወይንም ከሳሾች በሞቱ በአንድ አመት ውስጥ ክሱን ለመቀጠል እንዲፈቀድላቸው ሳያመለክቱ የቀሩ እንደሆነ የተጀመረው ክርክር ውድቅ እንደሚሆን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49(2) ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል። ይህ ድንጋጌ ክሱን ለመቀጠል መብት አለኝ የሚል ወገን ክሱን ለመቀጠል እንዲፈቀድለት ማመልከቻውን የሚያቀርብበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ሲሆን ከሳሽ ወይም ከሳሾች በሞቱ በአንድ አመት ውስጥ ክሱን ለመቀጠል ሳያመለክቱ መቅረታቸው ከተረጋገጠ የተጀመረው ክርክር ቀሪ የሚሆንበትን አግባብ የሚደነግግ ሲሆን ከዚህ ጊዜ በኋላም ጥያቄው ሲቀርብ ተቀባይነት የሚገኝበት አግባብ መኖሩን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 55(2) ድንጋጌ ያሳያል። በዚህም መሰረት ከሳሹ ራሱ ወይም ከሳሽ የነበረው የሚቹ ንብረት አስተዳዳሪ ነኝ የሚል ባለአደራ ወይም የከሰረው ከሳሽ ንብረት አስተዳዳሪ የሆነ ሰው ወይም የዋናው ከሳሽ መብት ተላልፎልኛል የሚል ሰው ክሱ ቀሪ በሆነ ወይም በተሰረዘ በስድስት ወር ውስጥ የቀረበው ክስ እንዲቀጥል ወይም መሰረዙን እንዲነሳለት ለማመልከት የሚችል ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ክሱ ቀሪ የሆነው ወይም የተሰረዘው በከሳሹ ጉድለት ያለመሆኑን የተረዳው እንደሆነ ይህ ምክንያት ስላደረሰው ኪሳራ ተገቢ መስሎ የታየውን ወሰኖ የቀረው ወይም የተሰረዘው ክስ እንዲቀጥል ለማዘዝ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 55(3) ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጦታል። ይህ ድንጋጌ አቤቱታው ክሱ ቀሪ በሆነ ጊዜ ውስጥ በሚቆጠር ስድስት ወራት ውስጥ መቅረብ እንዳለበትና በበቂ ምክንያት መደገፍ እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን በቂ ምክንያት የሚለውን ሐረግ ግን መመዘኛው ምን እንደሆነ በግልጽ ያስቀመጠው ነገር የለም። ይሁን እንጂ በቂ ምክንያት አለ ወይስ የለም? የሚለው ጥያቄ አመልካቹ በተገቢው ጊዜ አስፈላጊውን ስርዓት ያልፈፀመበት ምክንያት ተገቢ የሆነ ምክንያት ስለነበረው ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን በመመልከት በፍርድ ቤቱ አዎንታዊ ምላሽ ከአገኘ በቂ ምክንያት አለ ብሎ ለመደምደም የሚችልበትን አግባብ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49 እና 55(2) እንዲሁም 55(3) ድንጋጌዎች ሲታዩ ክርክሩን ለመቀጠል የአንድ አመት ጊዜ ከአለፈ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው መሆኑንና ይህ የጊዜ ገደብ በማለፍ መዝገቡ ከተዘጋ ወይም ክሱ ቀሪ ከሆነ በኋላ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ክርክሩ እንዲቀጥል ወይም ቀሪ የሆነ ክስ እንዲንቀሳቀስ በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን አቤቱታ አቅራቢው ከገለፀ እና ፍርድ ቤቱ አቤቱታ አቅራቢው አስፈላጊውን ስርዓት ያልፈፀመበት ምክንያት ተገቢ በሆነ ምክንያት መሆኑን ከተረዳው ክርክሩ እንዲቀጥል ማድረግ የግድ የሚል መሆኑን የሚያስገነዝቡን ናቸው። ከዚህ አንፃር ሲታይ ከሳሽ በመሞቱ ምክንያት የተዘጋ መዝገብን ለማንቀሳቀስ ፍጹም የሆነ ይርጋ የአንድ አመት ስድስት ወራት ጊዜ ነው ቢባል እንኳ ፍርድ ቤት መዝገቡ ተዘግቶ የቆየበትን ጊዜ በማስላት ብቻ ጊዜውን መቁጠር ያለበት ሳይሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጊዜ ገደቡ ውስጥ ጥያቄውን ያቀረበው አቤቱታ አቅራቢ የቆየበትን ሁኔታ ሁሉ አግባብነት ካላቸው ሌሎች የመሰረታዊ ህግ ድንጋጌዎችና አንድ ሰው ከሳሽ ለመሆን መሟላት ያለባቸውን የስነ ሥርዓት ሕግ መስፈርቶች ማየትን የግድ የሚል ነው።

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ሚች ክስ መስርተው ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ መዝገቡ እንዲዘጋላቸው ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ መዝገቡን እንዲዘጋላቸው የጠየቁት የወራሽነት ማስረጃ ይዘው እስከሚቀርቡ ለጊዜው መሆኑን፣ ፍርድ ቤቱም አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃ ይዘው እንዲቀርቡና በስነ ስርአት ሕጉ መሰረት አቤቱታቸውን እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸው መዝገቡ ተዘግቶ የቆየ ሲሆን አመልካቾች የሚች አቶ ወንድሙ ደምሴ ወራሽነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በፍርድ ቤት እንዲሰጣቸው ጥቅምት 17 ቀን 1998 ዓ.ም. አቤቱታ አቅርበው ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ውሳኔ የተሰጣቸው ሚያዝያ 29 ቀን 1998 ዓ.ም. መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ይኸው የወራሽነት ማስረጃ በሌላ ወራሽ ተቃውሞ ቀርቦበት ወዲያውኑ እንዳይሰጣቸው ታግዶ ቆይቶ ማስረጃው መጋቢት 04 ቀን 2000 ዓ.ም. ከተሰጣቸው በኋላ ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም. በፍርድ ቤቱ ፈቃድ የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸው ጥያቄ ማቅረባቸው በፍሬ ነገር የተረጋገጡት ነጥቦች ናቸው። እንዲህ ከሆነ አቤቱታውን ማቅረብ የሚችሉት የወራሽነት ማስረጃ ከተሰጣቸው በኋላ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) ድንጋጌ መንፈስ የሚያሳየን ነጥብ ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ከሳሽ ወይም ተከሳሽ መሆን የሚችለው ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ለመሆን የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነውና። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49 እና 55(3) ሥነ-ሥርዓታዊ ድንጋጌዎች እንደመሆናቸው መጠንም የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው መቼ ነው? ከሚለው ጥያቄ አንጻር ጉዳዩ መታየት ያለበት ነው። ይህንኑ ጥያቄ ለመመለስ ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1846 እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 48 ድንጋጌዎችን ይዘት መመልከት ተገቢ ይሆናል። በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1846 ድንጋጌ መሰረት የይርጋ ጊዜ መነሻው በመብት መስራት የሚቻልበት ጊዜ ነው። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 48 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ ክርክሩ እንዲቀጥል የሚያስችለው መብት የማይቋርጥ ከሆነ የከሳሽ ወይም የተከሳሽ መሞት ክርክሩን እንዲቆም አያደርገውም በሚል ተቀምጧል። ከዚህ የስነ ስርዓት ድንጋጌ ውስጥ "ክርክሩ እንዲቀጥል የሚያስችለው መብት የማይቋረጥ ከሆነ" የሚለው ሐረግ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826(2) እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1986 ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ የሚታይ ነው። በዚህም መሰረት በዚህ መብት አንድ ሰው ሊሰራ ይችላል ተብሎ የሚታሰበው ተገቢውን የወራሽነት ማስረጃ ከያዘ በኋላ ነው። ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከተው አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃውን የያዙበት ጊዜ መጋቢት 04 ቀን 2000 ዓ.ም. በመብታቸው መስራት የሚችሉበት ጊዜ ነው ተብሎ መያዝ የሚገባው ሲሆን ከዚህ ጊዜ በፊት ያለፈው ጊዜ ፍርድ ቤቱ ፈቅዶና በተቃውሞ የተነሳ በወራሽነት ማስረጃ ላይ ክርክር ሲደረግ ያለፈ በመሆኑ በአመልካቾች ጉድለት እንደአለፈ ጊዜ ሊወሰድ የሚችል አይደለም። ይኸው ጊዜ ሚች ከሞቱበት ከመስከረም 4 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ ከአለው ጊዜ ጋር ተቆጥሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49፣ 55(2)፣55(3) ስር የተመለከተው የጊዜ ገደብ አልፏል ብሎ መደምደም ምክንያታዊነት ያለውና በሕግ የሚደገፍ ነው ብሎ ለማሰብ የሚቻል አይሆንም። ምክንያቱም የይርጋ ጊዜ ማለፍ አይነተኛ አላማም ዳተኛውን ተከራካሪ ወገን መቅጣት ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃውን ለማግኘት ያለፈባቸው ጊዜ በዳተኝነታቸው ያለፈ ጊዜ ነው ሊባል አይችልምና። በመሆኑም ከመጋቢት 04 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲታይ አመልካቾች አቤቱታቸውን ያቀረቡት ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም. መሆኑ በመረጋገጡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49፣55(2) እና 55(3) ስር የተመለከተው የጊዜ ገደብ አልፏል ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም። በዚህም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ቀጥሎ የተመለከትነው ኃላፊነትን የሚመለከተውን ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ የቼክ ጉዳይ ሲሆን ክሱ የቀረበው በአጭር ሥነ-ሥርዓት ሆኖ ተጠሪ በተከሳሽነታቸው የመከላከያ ማስረጃ ካላቸው ማስፈቀጃ እንዲያቀርቡ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ መከላከያ ማስረጃ እንዳላቸው ለስር ፍርድ ቤት ገልጸው ፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸው የነበረ ሲሆን ተጠሪ ግን ማስረጃ የማሰማት መብታቸውን የተውት መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማረጋገጣቸው ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ተጠሪን ክክሱ ነፃ ያደረጉት በዚህ ችሎት ተገቢነት የለውም የተባለውን የስነ ስርዓት ይርጋ መሰረት በማድረግ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩ ላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረጉ ተጠሪ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለት ከአረጋገጡት ነጥብ እና ከፍትሃ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አይነተኛ አላማ አንጻር ሲታይ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቼክ ሆኖ የመከላከያ ማስረጃ ያልቀረበበት እንደመሆኑ መጠን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከደረሰበት መደምደሚያ ውጪ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚመለከተው የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጥያቄ የሌለ በመሆኑ በዚህ ችሎት ውሳኔ የመጨረሻ እልባት መስጠቱ የሥ-ሥስርዓት ሕጉን የጠበቀ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሰረቱ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትዕዛዝ የያዘና እንደቀረበም የሚከፈል ገንዘብን ተክቶ የሚሰራ ሰነድ ስለመሆኑ ከን/ሕ/ቁጥር 827/ሀ/እና 854 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ቼክ መብቱ ከሰነዱ ተነጥሎ የማይሰራበት፣ የቼኩ አውጪውም ቼኩ ላይ ለተፃፈው ገንዘብ አከፋፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑንም ከእነዚህ ድንጋጌዎችና ከን/ሕ/ቁጥር 840፣ 868(ሐ) እና 872 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም ቼክ ባልተከፈለ ጊዜ አውጪውም ሆነ ፈራሚዎቹ ለቼኩ አከፋፈል ኃላፊዎች ይሆናሉ፡፡ ቼክ በባሕሪው ገንዘብን ተክቶ የሚሰራና በቀላሉ ወደ ተለያዩ ሰዎች ሊተላለፍ የሚችል በመሆኑም ማንኛውም መቃወሚያ ሊቀርብበት አይችልም፡፡ ሕጉ ለይቶ በአስቀመጣቸው ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር የቼክ ክፍያ በማንኛውም ምክንያት ሊቆምና ሊታገድ አይችልም፡፡ በዚህም መሰረት በን/ሕ/ቁጥር 717 እና 850 ስር የተመለከቱት መቃወሚያዎች ባጋጠሙ ጊዜ አውጪው ወይም ፈራሚዎች ቼክ ሊከፈል የማይገባበትን መቃወሚያ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት በቼክ አከፋፈል ላይ መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው እዳ ከፋዩ ሰነዱን በያዘው ሰው በሁለቱ የግል ግንኙነት ላይ በተመሰረቱት በሰነዱ አፃፃፍ ፎርምና እንዲሁም በሰነዱ ላይ በተፃፉት ቃሎች ላይ፣ ፊርማን በማስመሰል የተሰራ፣ ችሎታ ወይም ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ሥልጣን ባለመኖሩ ወይም ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው የተነሱት መቃወሚያዎችን፣ አምጪው ይህን ሰነድ ባገኘበት ጊዜ እዳ ከፋዩን ለመጉዳት እያወቀ ያደረገው ከሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በድንጋጌው ተዘርዝረው በተገለፁ ሁኔታዎች በቼክ የተከሰሰ ሰው አንዳንድ መቃወሚያዎችን በማቅረብ ከእዳው ራሱን ነፃ ማድረግ እንደሚችል ሕጉ ሥርዓቱን ዘርግቷል፡፡ በቼኩ የተከሰሰ ሰው የግል ግንኙነትን መሰረት ያደረገ መቃወሚያ ሊያነሳ የሚችለው ከአምጪው ጋር ያለውን ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ለቼኩ ኃላፊ ተብለው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠው ቼኩን አውጪ መሆናቸውና ቼኩ ባንክ ሲቀርብም በቂ ስንቅ የለውም ተብሎ በመመለሱና ተጠሪ በን/ሕ/ቁጥር 717 መሰረት አለኝ ያሉትን መቃወሚያ ሊያስረዳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችል ማስረጃ የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጦ ነው፡፡ በመሆኑም ውሳኔው ከላይ የተጠቀሱት የንግድ ሕግ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 49፣55(2) እና 55(2) ድንጋጌዎችን በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ጋር ባግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሲሆን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ግን ሕጉን የተከተለ ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77636 ጥቅምት 05 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 52763 መስከረም 26 ቀን 2003 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 57668 ጥር 08 ቀን 2001 ዓ.ም. የተሰጠው ብይንና በ6/6/2001 ዓ.ም. የተሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 71316

ግንቦት 09 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነገፈ ፈጅ ዮሴፍ ቀውዬ

ተጠሪ፡- ለገሠ ጌታሁን ጠበቃ አቶ ለገሠ ማሞ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ አንድ ፍ/ቤት በንብረት ላይ የሰጠውን የዕግድ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 158 እንደተደነገገው መልሶ ለማስነሳት የሚቻልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

በከሣሽ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በተከሣሽ አቶ ኃይሉ ሃብቴ መካከል በነበረው የብድር ገንዘብ ክርክር ከሣሽ ለፍርድ አፈፃፀም ዋስትናው ይሆነው ዘንድ በተከሣሽ እና በባለቤቱ ስም ተመዝግቦ በሚገኘው ት/ቤት ላይ ክሱ በቀረበበት ፍ/ቤት አማካኝነት ታግዶ እንዲቆይ የሚያስችል ትዕዛዝ ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲሰጥበት አድርጓል፡፡

የአሁን ተጠሪ በበኩል ህዳር 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ይህ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ንብረት ከተከሣሽ እና ከባለቤቱ ጋር በተደረገ የሽያጭ ስምምነት በግንቦት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል በብር 80,000.00 ገዝቻለሁ፡፡ ይህንንም የሽያጭ ውል ያደረግነው በሲዳማ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ነው፡፡ እንደውሉ ሻጭ ሊፈጽሙ ስላልቻሉ ለሸቢዳኖ ወረዳ ፍ/ቤት ክስ አቅርቤ ስመ-ሀብትነቱን ወደ ስሜ ለማዞር ስሞክር መታገዱን ተረድቻለሁ፡፡ ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 መሠረት በህግ አግባብ በገዛሁት ቤት ላይ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ይነሣልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የአሁን አመልካችም የዕግድ ትዕዛዙን የማይነሳበትን ምክንያት በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የሲዳማ ዞን ከፍ/ቤት አስቀድሞ የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ ለማንሳት የሚያበቃ ክርክርና ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም የዕግዱ ትዕዛዝ አይነሣም የሚል ዳኝነት ሲሰጥ፤ ይግባኝ ሰሚው የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ የሽያጩ ተግባር የተፈፀመው የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ስለሆነ የሽያጭ ውሉም በሚመለከተው አካል በመመዝገቡና በህግ የሚጠየቀውም መስፈርት ውሉ በመዝገብ መፃፍን እንጂ የስመ ሃብትነት ዝውውር በግልጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕግ እንደ ማሟያ ስላልተመለከተ ቀደም ሲል የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ሊነሣ ይገባል በማለት ሽሮታል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው የተለየ ዳኝነት ጉድለት የለበትም በማለት የአሁን ተጠሪን ሳይጠራ አመልካችን በማሰናበቱ ይህ የሰበር ክርክር ሊቀርብ ችሏል፡፡

በዚህ የሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በዕሑፍ ያቀረቡ ሲሆን በይዘቱ ከዚህ በፊት ካቀረቡት የተለየ አይደለም፡፡ የተለየው ነጥብ ቢኖር ቀደም ሲል በሻጭ ላይ ባቀረቡት ክስ መሠረት አስወስኜ የፍርድ ባለመብት መሆኔም ይታወቅልኝ የሚለው ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአሁን ተጠሪ በፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ሊነሣልኝ ይገባል ሲል ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ፤ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ሊነሣ ይገባል ለሚለው ዳኝነቱ መሠረት ሆኖ የተያዘው የአሁን ተጠሪ የት/ቤቱን የሽያጭ ውል በሲዳማ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤቱ አድርጓል፤ አስመዝግቧል የሚለውን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ፊት ውል የማድረግ ተግባር አስፈላጊነቱ ከውል አመሠራረት ጋር የተያያዘ፤ ውሉ ተደርጓል፣ አልተደረገም? የሚለውንና በውሉ ስለተካተቱት ዝርዝር ጉዳዩች (As to any terms of the contract) ወደ ፊት በተዋዋይ ወገኖች መካከል ክርክር እንዳይፈጠርና እንዳይነሣ ለማድረግ ሲባል የውል አደራረግን ሂደት የማረጋገጥ (authentication) መሆኑንና ውጤቱም በተዋዋይ ወገኖች መካከል ለሚነሳ ክርክር እልባት በመስጠት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

አንድን ንብረት በሽያጭ ውል ገዝቻለሁ፤ ስለሆነም በዚህ ንብረት ላይ ያለ እኔ ሌላ ሶስተኛ ወገን መብት የለውም በማለት ማናቸውንም ሶስተኛ ወገን ለመመለስ ግን ት/ቤቱ በሚገኝበት ሥፍራ በሚገኘው ንብረትን መዝግቦ ለመያዝ ስልጣን በተሰጠው ማዘጋጃ ቤት የምዝገባ ሥርዓቱ ሊከናወን እንደሚገባ በንብረት ህጉ እና በውል ህጉ ከተመለከቱት አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር በእነዚህ በውል አደራረግ ሥርዓት ማሟያነት በቀረበው ውልን የማረጋገጥ ተግባር እና ሶስተኛ ወገንን ለመጠበቅም ሆነ ለመመለስ እንዲያስችል የተቀመጠውን የምዝገባ ሥርዓት (registration) ምንነትና ተግባር በውል ካለማጤን በሥር ፍ/ቤት ዳኝነት የተሰጠበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

እንዲሁም የአሁን ተጠሪ በንብረቱ ላይ አስወሰኜ በፍርድ ባለመብትነት ደረጃ ላይ እገኛለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር እንደ አግባብነቱ ይኸው ንብረት ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዲውል ለማድረግ በተከበረ ጊዜ የቀደምትነትን መብት ለማስረዳት የሚያግዘው ካልሆነ በቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158 የተሰጠን የእግድ ትእዛዝ ለማስነሣት የሚያስችል አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች የዕግድ ትእዛዙ ሊነሳ ይገባል በማለት የሰጡት ትርጉም የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 67656 ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ፤ እንዲሁም የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ. 51779 መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. በአንፃሩ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19703 ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፀንቷል፡፡
3. የአሁን ተጠሪ የዕግድ ትዕዛዝ ይነሣልኝ ሲል ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የህግ መሠረት ያለው አይደለም ብለናል፡፡
4. በዚህ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አበራ ሁንዴ ከጠበቃ አቶ ደረጀ ኢተቻ ጋር ቀረቡ
ተጠሪ፡- የፊንፍኔ የደን ደርጅት ነገረ ፈጅ አቶ ዳንኤል ኢፎ - ቀረቡ
መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረት የተገኘን መብት መቃወም የሚቻልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በሱሉልታ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት በአሁን አመልካች በአቶ አበራ ሁንዴ እና በሥር 1ኛ ተከሣሽ በነበረው የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መካከል ከከሣሽ ዕውቅና ውጭ በከሣሽ ይዞታ ላይ ያደረጉት ውል/ስምምነት ይፍረስልኝ በማለት የአሁን ተጠሪ የፊንፍኔ የደን ድርጅት መጠየቁን የሚያስረዳ ነው፡፡

ተከሣሽም ቀርቦ ያነሳውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ፍ/ቤቱ ውድቅ ካደረገ በኋላ ከሣሽ የፊንፍኔ የደን ድርጅት በእኔ ይዞታ ላይ ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል ይፍረስልኝ በሚል ክስ ያቅርብ እንጂ ይዞታው የእራሱ ለመሆኑ በቀጥታ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም በኢንቨስትመንት ቢሮ አማካኝነት ለ2ኛ ተከሣሽ ለአሁን አመልካች የተሰጠው የመሬት ይዞታ የከሣሽ የፊንፍኔ ደን ድርጅት ይዞታ ለመሆኑ የሚያሳይ ካርታ የለም በሌላ በኩል የፊንፍኔ የደን ድርጅት ከክሱ ጋር አያይዞ ካቀረበው የማስረጃ ዝርዝር ውስጥ 2ኛ ተከሣሽ አበራ ሁንዴ ይህንን ክርክር የተነሳበትን የመሬት ይዞታ አስመልክቶ በሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ካስወሰነ በኋላ ከኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ቢሮ ካርታ እንዲሰጣቸው ተብሎ የተወሰነ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳቀረበ ተረድቻለሁ ስለሆነም 1ኛ የመሬት ይዞታው ባለመብት ለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ባለማቅረቡና 2ኛ ክርክር ያስነሳውን የመሬት ይዞታ አበራ ሁንዴ በውሣኔ ያገኘው መሆኑን ስለተረጋገጠ በዚህ የመሬት ይዞታ ላይ ከሣሽ የፊንፍኔ የደን ድርጅት ክስ የማቅረብ መብት ያለው ሆኖ አልተገኘም በማለት ወስኗል፡፡

በአሁን ተጠሪ በፊንፍኔ የደን ድርጅት የይግባኝ ቅሬታ አቅራቢነት መነሻ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ፤ ግራ ቀኙን የሚያከራክረው የሁከት ይወገድልኝ ጉዳይ እንደሆነ ገልፆ ተከሣሽ አበራ ሁንዴ በፊንፍኔ ደን ድርጅት የመሬት ይዞታ ላይ ሁከት ፈጥሯል ወይስ አልፈጠረም? የሚለውን ጭብጥ ለመለየት እራሱ ይግባኝ ባይ ያቀረበውን ማስረጃ ተመልክቻለሁ፡፡ እንደተመለከትኩትም በጉዳዩ ላይ የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በቁጥር ከአይኦ/ፋይ/127/2001 በ08/03/2001 ዓ.ም የተፃፈው ደብዳቤ የሚያስረዳው አበራ ሁንዴ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ይዞታ ላይ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ መስርቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ይዞታው የአበራ ሁንዴ መሆኑን አረጋግጦ ውል እንዲፈርምና የተዘጋጀለት የይዞታ ካርታ እንዲሰጠው በወሰነው ውሣኔ መሠረት በዚህ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ታዞ ፈቃድና የመሬት ይዞታውን ማረጋገጫ ካርታ እንደሰጠ የሚያረጋግጥ ነው የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ቢሮ ፈቃድና የመሬት ይዞታ ካርታ ለአበራ ሁንዴ የሰጠው ኮሚሽኑ እራሱ ሳይሆን በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ስለመሆኑ ከላይ እንደተገለፀው የእራሱ የከሣሽ ማስረጃ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በዚህ ውሣኔ ላይ ተቃውሞ ቀርቦ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ ማንኛውም አካል በፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡ አበራ ሁንዴም መሬቱን ያገኘው በፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ስለሆነ በፊንፍኔ ደን ድርጅት ላይ ሁከት ፈጥሯል ለማለት አይቻልም፡፡

ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪ የእራሴ የመሬቱ ይዞታ ከህግ ውጭ ተሰጥቶብኛል የሚል ከሆነ አስቀድሞ የተሰጠውን ውሣኔ ማሰረዝና የውሣኔውን ህገ-ወጥነት የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን አላደረገም ስለሆነም መልስ ሰጭ የነበረው የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጠረው ሁከት የለም በማለት የሥር የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁን ተጠሪ ከዚህ በላይ የተገለፀው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ላቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፋይል ቁጥር 103065 የካቲት 07 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት በፊንፍኔ ደን ድርጅት ወሰንና ቁጥጥር ስር ያለ ስለመሆኑ ተከሣሽ ክዶ ያቀረበው ክርክር ስለሌለ እንዳመነ ይቆጠራል ከዚህም በቀር የይዞታ መሬቱ የፊንፍኔ ደን ድርጅት ስለመሆኑ የሚያመለክት ማስረጃ ቀርቧል፡፡ የኢንቨስትመንት ቢሮም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ተገዶ በዚሁ መሬት ላይ ፈቃድና ካርታ ለአበራ ሁንዴ መስጠቱን እንጂ በኢንቨስትመንት ቦርድ ታይቶ የተሰጠ አለመሆኑን በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡

ስለሆነም የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ቢሮ ከአበራ ሁንዴ ጋር ተከራክሮ የተሰጠ ውሣኔ ካለ ሁለቱ ወገኖች በፈለጉት ሁኔታ ተከራክረው በተሰጠ ውሣኔ የመሬቱን ባለይዞታ ያስገድዳል የሚለው በጥርጣሬ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው የሚለውን ሁሉ መሠረት አድርጎ የኢንቨስትመንት ቢሮ እና አበራ ሁንዴ ያደረጉት ህገወጥ ውል እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ የአሁን አመልካች መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ከተለያዩ የመከራከሪያ ነጥቦች አንፃር ቅሬታውን ዘርዝሮ ለዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ተጠሪ የፊንፍኔ ደን ድርጅት ቀርቦ የበኩሉን ክርክር አቅርቧል፡፡

እኛም ግራ ቀኙ በሰበር ደረጃ ካቀረቡት ክርክር እና በሥር በየደረጃው ከተሰጡት ውሣኔዎች አንፃር ጉዳዩን እንደተመለከትነው ግራ ቀኙን ያለያያቸው ነጥቦች ከአንድ በላይ መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ ከእነዚህ ጭብጦች መካከል ለጉዳዩ አወሳሰን ለአንዱ ቀድሞ ዕልባት መስጠት ብቻ ሌላውንም ክርክር ሊያስቀር እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182/3/ እንደተደነገገው የአሁን አመልካች ክርክር ያስነሳውን መሬት በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት በይዘታው ሥር የገባ መሆኑ ከተረጋገጠ የመሬቱ ባለይዞታ ነኝ የሚለው የአሁን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ይህንኑ ይዞታ በዳኝነት ሊያስመልስ የሚችልበት ሥርዓት ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ በቅድሚያ ምላሽ የሚያሻው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአሁን አመልካች በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12536 በሆነው በቀረበው ክስ መነሻ ይህንኑ ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን የመሬት ይዞታ በሚመለከት የኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ቢሮ ጽ/ቤት ከአመልካች ጋር ውል እንዲፈፅም፤ ፈቃድ እና ካርታም እንዲሰጥ የተወሰነበት ለመሆኑና በዚህም ውሣኔ መሠረት ውሉን እንዲደረግ ፈቃድና ካርታም እንደሰጠ በየደረጃው በሶስት እርከን በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች ውሣኔ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳቀረበው የሚያነሳው ክርክር እኔ በማላውቀው ውሣኔ ልገደድበት አይገባም የሚል ነው፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰጠው ትንታኔ የተመረኮዘው ሁለት ተከራካሪ ወገኖች በፈለጉት አኳኋን በሌላ ሰው የይዞታ መብት ላይ ተከራክረው ውሣኔ ቢያስወስኑ ይህ ውሣኔ የንብረቱን ባለይዘታ ሊያስገድደው አይችልም ህግና ደንብን ተከትሎ ባልተሰጠ ውሣኔ መሠረት ኢንቨስትመንት ቢሮ ተገዶ የፈፀመው ውል እና የሰጠው ፈቃድ እና ካርታ ህገ ወጥ ነው፡፡ ይህ ህገ ወጥ ውል ደግሞ ሊሰረዝ ይገባል በሚለው ምክንያት ላይ ነው፡፡

እኛም ይህንኑ የተጠሪን ክርክር እና የሰበር ሰሚው ችሎት በሰጠው ፍርድ መነሻ ያደረገውን ትንታኔ ያለውን ህጋዊ መሠረት እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በአንድ ጉዳይ በከሣሽነትና በተከሣሽነት በተሰየሙት ወገኖች መካከል ብቻ ክርክር ቢጀመር እነዚህ ወገኖች በሚከራከሩበት ጉዳይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ወገን ካለ ክርክር መጀመሩን እንዳተረዳ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ በመግባት መብቱን የማስከበር መብት ያለው ስለመሆኑ የጉዳይ አመራር ፍትሃዊ እንዲሆንና በሥርዓት እንዲከናወን ለማስቻል ሲባል በተደነገገው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ሥርዓቱ ተዘርግቷል፡፡

ክርክሩ መጀመሩን ሳይረዳ እና ሳያውቅ ጉዳዩ በከሣሽነትና በተከሣሽነት በተሰየሙት ወገኖች መካከል የተደረገው ክርክር ተጠናቆ መወሰኑ እንኳ ቢታወቅ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ በውሣኔው መብቱ ተነክቷል የሚለው የክርክር ተካፋይ ያልነበረው ሰው ይህንኑ ውሣኔ ለመንቀፍ፤ ለመቃወም የሚችልበትም ሥርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 እና ተከታይ ድንጋጌ ተበጅቷል፡፡

በዚህ ፍርዱን በፈረደው ፍ/ቤት መብቱን ከማስከበር ጀምሮ ከታች ወደ ላይ በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች አማካኝነት ይህ መሰል ተከራካሪ ወገን እርሱ የክርክር ተካፋይ ሳይሆን የተሰጠው ውሣኔ ያስከተለበትን የፍትህ መጓደል ለማረም በሚያስችል ሁኔታ የተሟላ የማስተካከያ ሥርዓት በሀገራችን የህግ ሥርዓት ተቀምጧል፡፡

አንዱ በህግ በተቋቋመ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በጎርዮስ ክርክር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በውሣኔ እስኪቋጭ ድረስ ባለው የክርክር ደረጃ የተፈፀሙት የሥነ-ሥርዓት ጉድለቶች በእራሱ በፍ/ቤቱ የሚታረሙበትን አግባብ እና ሥርዓት ካስቀመጠ እንዲሁም በውሣኔ ከተቋጨም በኋላ እንኳ ውሣኔው በእራሱ ውሣኔውን በሰጠው ፍ/ቤት እንደገና የሚታይበትን አማራጭ፤ ከዚህም በቀር እንደሁኔታው ከታች ወደ ላይ በይግባኝ አማካኝነት የተፈፀሙ የክርክር ግድፈቶች የሚታረሙበትን ሥርዓት በበቂ ሁኔታ ከዘረጋ በኋላ በዚህ በተዘረጋው ሥርዓት አለመፈፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም በዚሁ የማስተካከያ ሥርዓት አለመመራት ምን ውጤት እንደሚያስከትል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 212 በግልፅ ተመልክቷል፡፡

በአንድ ጉዳይ የክርክር ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች እነማን ናቸው? በክርክር ተካፋይ መሆን የሚገባው ሲታለፍ በምን አኳኋን መታረም እንደሚገባው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መሠረት አንዱ በሥነ-ሥርዓት ህጉ ሽፋን የተሰጠው ጉዳይ ሆኖ ልዩ ልዩ አማራጮች ተደንግገዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ጉዳዩ ሊመራ ያልቻለ መሆኑን የተገነዘበ ወገን ክርክሩ በመታየት ላይ እያለ ጣልቃ በመግባት፤ ከተወሰነም በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ፍርዱን በፈረደው ፍ/ቤት አማካኝነት ውሣኔው ተነስቶ እንደገና በሚታይበት ሥርዓት መጠቀም እንደሚችል በህጉ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በቀር ሥርዓት ሳይከተሉ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ የሥነ-ሥርዓት ጉድለት አለበት በማለት ብቻ ውሣኔው ዋጋ አልባ ሊሆን እንደማይችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 212 ተደንግጓል፡፡

ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ክርክሮችን በዘፈቀደ ሳይሆን በሥርዓት በመምራት በአፋጣኝ እና በአነስተኛ ወጭ እንዲቋጭ ለማስቻልና የሀገሪቱ የፍ/ብሔር ፍትህ አስተዳደር ተገማች እንዲሆን ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አሁን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰጠው የህግ ትርጉም ላይ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ከሣሽና ተከሣሽ በፈለጉት አኳኋን ተከራክረው የሚሰጠው ውሣኔ በክርክሩ ተሳታፊ ያልነበረን ወገን ከቶውንም ቢሆን ሊያስገድደው አይችልም በማለት የተከተለው አተረጓጐም ሥርዓት ያልተከተለ፤ ማናቸውም ክርክር በሥርዓት ሳይሆን በዘፈቀደ እንዲከራከር በር የሚከፍት ለህግ የበላይነት ተፃራሪ የሆነ አተረጓጐም በመሆኑ የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም የአሁን አመልካች ክርክር ያስነሳውን የመሬት ይዞታ በእጁ ያደረገው በፍ/ቤት ውሣኔ መሆኑ ስለተረጋገጠ የአሁን ተጠሪ ይህ ውሣኔ መብቴን ነክቷል የሚል ከሆነ ሥርዓቱን ጠብቆ ማስለወጥ ከሚችል በቀር በዚያው ጉዳይ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ሥርዓት በሌለበትና ይህንን ለማድረግም ተጠሪ መብት የሌለው መሆኑ እየታወቀ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ያለ ሥርዓት የቀረበውን ክስ መነሻ አድርጎ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርዓታዊ ህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፋይል ቁጥር 103065 በ07/6/2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ይህ ውሣኔ የአሁን ተጠሪ በዚህ የፍርድ ሐተታ እንደተገለፀው ቀደም ሲል በመ/ቁ 12536 የተሰጠው ውሣኔ የይዞታ መብቴን ያስቀረ፤ መብቴን የነካ ነው በማለት ለመንቀፍ በሥነ - ሥርዓት ህጉ መሠረት መጠየቅና ማሳረም የሚችል ከሆነ በዚሁ ሥርዓት መሠረት ከመፈፀም በቀር በህግ በተቋቋመ ፍ/ቤት የተሰጠን ውሣኔ ሌላ አዲስ ክስ በሌላ ፍ/ቤት በማቅረብ ለማስለወጥ የሚያስችል መብት የለውም ብለናል፡፡
3. የዚህ ሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ካሳዬ ያደቴ ከጠበቃ ኮ/ል መላኩ ካሣዬ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሲኖር ፍራንችስኮ ቬንሲያን የቀረበ የለም

መዝገቡ ያደረው ለውሣኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች ከፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በአደራ የተረከባቸውን የተጠሪ ንብረቶች አልመለሰም በሚል ተጠሪ የንብረቶቹን ዝርዝር እና ግምት በመጥቀስ ባቀረበው ክስ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጀመረ ሁኖ አሁን የሚያከራክረው መቆፈሪያ ማሽን በተመለከተ ሲሆን ይሄው ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማሽኑ ተገምቶ ፍርድ እንዲሰጥበት በመለሰው መሠረት አመልካች ማሽኑ ያለበትን ቦታ ማሳየት ባለመቻሉ ከዚህ ቀደም በተሰጠው ውሣኔ መሠረት አሁንም በርትዕ ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል በመወሰኑ እና ይሄው ውሣኔ በፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመጽናቱ የተፈጸመው መሠረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉዋቸውን ነጥቦች በማንሳት ያቀረቡ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ፡- በዚህ ጉዳይ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማሽኑ ተገምቶ ውሣኔ እንዲሰጥበት በማለት ወደ ታች ፍርድ ቤት መልሶ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይሄንን ሳያከብሩ አሁንም በድጋሚ በርትዕ ውሣኔ መስጠታቸው ተቀባይነት ያለው አካሄድ ባለመሆኑ አመልካች በበታች ፍርድ ቤትም ሆነ በተለያዩ አካላት ባቀረበው አቤቱታ ሌሎች እቃዎችን እንጅ የመቆፈሪያ ማሽን ያልተረከበ ስለመሆኑ ተከራክሮ እያለ እና ሌሎቹን የተረከባቸውን ደግሞ በብር 8,000 /ስምንት ሺህ ብር/ መሸጣቸውን የተከራከሩ በመሆኑ፣ በበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረብናቸውም ሰዎች ብረታ ብረት መግዛታቸውን እና መቆፈሪያ ማሽን ያልገዙ ስለመሆኑ እና ይሄንንም የገዙትን እቃ ብር 400 /አራት መቶ ብር/ በማትረፍ የሸጡ ስለመሆኑ የገለጹ በመሆኑ ተጠሪ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ክሱ ወድቅ መሆን ሲገባው የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት እንዲታረምላቸው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ በእርግጥ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሌሎቹ እቃዎች ላይ በበታች ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተላለፈው ፍርድ በአግባቡ ስለመሆኑ በማመላከት ያጸናው ሁኖ የዚህ አከራካሪ ማሽን ግን አይነቱ ሊታወቅ እና በባለሙያ ሊገመት እየተቻለ ይሄ ሳይደረግ መታለፉ እና በርትዕ መወሰኑ አግባብነት የሌለው ነው ተብሎ ወደ ታች መመለሱ ግልጽ ቢሆንም አመልካች ማሽኑን የገዛውን ሰው ማቅረብም ሆነ ማሽኑ ያለበትን ቦታ ማሳየት ባለመፈለጋቸው፣ ያቀረቡትም ሰው ስለማሽኑ ሊጠየቁ ማሽን ያለመግዛታቸውን ሁኖም ግን ብረታ ብረት ስለመግዛታቸው ብቻ በመግለጻቸው ታልፎ የተሰጠ ውሣኔ በመሆኑ እና ንብረቶቹን ስለመረከቡ ደግሞ ፈርሞ የተረከበበት ሰነድ ስላለ አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ቅሬታቸውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች አከራካሪውን የመቆፈሪያ ማሽን ግምት በተመለከተ ወደ ድምዳሜ የደረሱት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ እልባት መስጠት ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በመጀመሪያ ደረጃ የመቆፈሪያ ማሽኖቹን በተመለከተ አመልካች አልተረከብኩም የሚል ክርክር በዚህ ደረጃ እያነሳ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡ ሁኖም ግን ኃላፊነትን በተመለከተ ከዚህ በፊት እስከ ፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገ ክርክር እልባት ያገኘ እና የፌ/ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ .ቁ 50776 ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን ወደ ፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲመልስ አሁን የሚያከራክረውን ማሽን ግምት በርትዕ ለመወሰን በባለሙያ በማስገመት ውሣኔ ሊሰጥበት የሚቻል በመሆኑ ይሄው ስርዓት ሊፈጸም ይገባል በሚል ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የመቆፈሪያ ማሽኑን አልተረከብኩም በማለት ያነሳው ክርክር ቀደም ሲል በውሣኔ በተቋጨ ጉዳይ ላይ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 5/1/ መሠረት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሁኖም ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤት አከራካሪውን ማሽን ለማስገመት ተገቢውን ትጋት አድርጓል ወይ ? የሚለውን ነጥብ መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ ጉዳዩ ወደ ታች ፍርድ ቤት ከተመለሰ በኋላ ፍርድ ቤቱ ማሽኑ ያለበትን ቦታ ወይም የገዛውን ሰው እንዲያቀርብ የተጠየቀ ሲሆን አመልካችም ማሽኑን እንደቀድሞ ሁሉ እንዳልተረከበ የተከራከረ ሲሆን የገዛውንም ሰው እንዲያቀርብ ታዞ አመልካች ያቀረበው ሰው ማሽን እንዳልገዛ እና ብረታ ብረት እንደገዛ የገዛውንም ብረታ ብረት ብር 400 /አራት መቶ ብር/ በማትረፍ እንደሸጠ ገልጧል፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤትም ይሄንኑ ምክንያት በማድረግ ቀድሞ በርትዕ ብር 200,000/ ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ተብሎ የተወሰነውን ውሣኔ በድጋሚ በመቀበል ወስኗል፡፡

ሁኖም ግን አንድ ጉዳይ በበላይ ፍርድ ቤት በነጥብ ሲመለስ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በመጣራት ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተገቢውን ትጋት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 343/1/ ድንጋጌ ይዘት እና ዓላማ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሄ አከራካሪው የመሬት መቆፈሪያ ማሽን ያገለገለ ስለመሆኑ እስከታወቀ ድረስ ፍርድ ቤቱ ዓይነቱን በተመለከተ ከግራ ቀኙ ወይም በመዝገቡ ውስጥ ካሉት ሰነዶች በመመልከት እና በመግለጽ አግባብነት ባለው ባለሙያ እንዲገመት በማድረግ ቢያንስ በርትዕ ለሚሰጠውም ውሣኔ መነሻ ነገር ማስቀረብ እየተቻለ እንደዚህ ዓይነት እና ተመሳሳይ ጥረት ሳይደረግ በደፈናው በርትዕ ቀድሞ የተሰጠውን ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በድጋሚ በመቀበል ውሣኔ መስጠቱ ከፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ችሎት የተሰጠውን ጉዳዩ የሚጣራበትን አግባብ ያልተከተለ በመሆኑ አግባብነት የሌለው የክርክር አመራር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ቀደም ሲል ከዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን መመሪያ ሳይከተሉ እና ተገቢውን ማጣራት ሳያደርጉ የደረሱበት ድምዳሜ አግባብነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 67129 ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 65277 በቀን 24/5/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪውን የመሬት መቆፈሪያ ማሽን ያገለገለ ስለመሆኑ እና ሌሎች ስለማሽኑ ከመዝገቡ እና ከክርክሩ የተገኙትን ነጥቦች ለሚመለከተው ባለሙያ በመግለጽ በወቅቱ የነበረው ዋጋ ሙያዊ ግምት እንዲቀርብ በማድረግ እና በማስገመት ቀደም ሲል በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሣኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
አለማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-አቶ ሽመልሽ አማረ - ጠበቃ ታምሩ ወልደማርያም ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አማረ መኮነን - ከጠበቃ ወልደስላሴ ብርቱ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ ውሳኔ የተሰጠበት ወገን በሌለበት ታይቶ የተሠጠው ውሳኔ እንዲነሳለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78(1) መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚያቀርበው ጥያቄ የአንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ቀን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፊዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡የስር ከሳሽ በአሁኑ አመልካች ላይ ክስ መስርተው ፍርድ ቤቱ ለአሁኑ ተጠሪ በሥርዓቱ መሰረት መጥሪያ እንዲደርሳቸው ትዕዛዝ ሰጥቶ የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽን ሊያገኙ እንዳልቻሉ ገልጸው ምትክ መጥሪያ በጋዜጣ እንዲደረግ አመልክተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የተጠሪን ጥያቄ በመቀበል አመልካችን በጋዜጣ እንዲጠሩ አድርጎ በጥሪው መሰረት አመልካች ስላልቀረቡ ጉዳዩን አመልካች በሌሉበት በማየት ዋናውን ጉዳይ ለተጠሪ ወስኗል፡፡ ከዚኅም በኋላ የአሁኑ አመልካች የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሰረት ውሳኔው ተነስቶ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩ በሕጉ የተመለከተውን የአንድ ወር ጊዜውን ጠብቆ ያልቀረበ መሆኑን ጠቅሰው አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ውሳኔው መሰጠቱን የተረዱት ጥር 30 ቀን 2003 ዓ/ም ሁኖ በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው አቤቱታ ያቀረቡት የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. በመሆኑና ይህም የአንድ ወር ጊዜ ካለፈ በሁዋላ በመሆኑ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ከዚኅም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸውን ለፊዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ውስጥ የተመለከቱት የይርጋ ጊዜዎች አቆጣጠር መታየት ያለበት በራሱ በፍትሕብሔር ስነ ሥርዓት ሕጉ መሰረት እንጂ በፍትህ ብሔር ሕጉ በተመለከቱት ድንጋጌዎች ያለመሆኑን፣ ከዚህ አንፃር ጉዳዩ ሲታይም አመልካች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መሰጠቱን ከተረዱበት ከጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የአንድ ወር ጊዜ መቆጠር ያለበት መሆኑን፣ ይህም ጊዜ እስከ የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም. ድረስ መሆኑን ገልፆ አመልካች የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. ያቀረቡት አቤቱታ በሕጉ የተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ ካለፈ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በሚሉ ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች አቆጣጠርን በተመለከተ ሕጉ የማይገልጽ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያላቸው በፍትሓብሔር ሕጉ ከቁጥር 1948 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች ናቸው፣ ከዚህ አንፃር ጉዳዩ ሲታይም አመልካች በጉዳዩ ላይ በሌሉበት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን የተረዱት ጥር 30 ቀን 2004 ዓ.ም. ከሆነ የይርጋው ጊዜ አቆጣጠር ይህንኑ ቀን መነሻ ሊያደርግ አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ተጠሪ ቀርበው በጽሑፍ በሠጡት መልስ በፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ ውስጥ ያሉት የይርጋ ድንጋጌዎች አቆጣጣር በራሱ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርኣት ሕጉ መሰረት እንጂ በፍትሀብሄር ሕጉ ሊሆን አይችልም ሲሉ የተከራከሩ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረመው የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስር የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች አቆጣጠር መታየት ያለበት በራሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሰረት ነው? ወይንስ በፍ/ብ/ህጉ በቁጥር 1848 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ነው? የሚለው ነው፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የይርጋ የጊዜ ገደቡ መቆጠር ያለበት ከመቼ ጀምሮ ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስና በሁለተኛ ደረጃ በበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በሌሉበት ጉዳዩ ታይቶ ስለመወሰኑ የተረዱት ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. መሆኑንና ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይላቸው አቤቱታቸውን ያቀረቡት የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. መሆኑን ነው፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉት ደግሞ የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ከጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78(1) ስር የተመለከተው የአንድ ወር የጊዜ ገደብ የሚያበቃው የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም. ስለሆነ እና አመልካችም ከዚህ ቀን በኋላ አቤቱታቸውን ማቅረባቸው ተቀባይነት የለውም በማለት መወሰናቸውን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ በፍትሓብሔር ስነ ሥርዓት ሕጉ ስር የተለያዩ የይርጋ ድንጋጌዎች ያሉ ሲሆን አቆጣጠራቸውን በተመለከተ ግን ግልጽ ድንጋጌዎች የሉም፡፡ በሌላ በኩል በፍትሓ ብሔር ሕጉ ስር ስላሉት የይርጋ ድንጋጌዎች የአቆጣጠር ሁኔታ ሕጉ በቁጥር 1848 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ግልፅ ስሌት አስቀምጧል፡፡ የሥነ ሥርዓት ሕጎች ዋነኛ ዓላማ ለፍ/ቤት የሚቀርቡ ክርክሮች ባነሰ ወጪ፣ በተቀላጠፈና ፍትሃዊ በሆነ ሥርዓት እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በሥነሥርዓት ህጎች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች አፈጻጸም ባንድ ጉዳይ ካሉት ተከራካሪዎች ባሻገር የሌሎች ተከራካሪዎች ጥቅም ፣ በፍርድ ቤት መኖር ያለበትን የሙግት አመራርና አጠቃላይ የሀብትና የጊዜ አጠቃቀምን የሚመለከቱ ናቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በሥነሥርዓት ሕጉ የሰፈሩ ጊዜን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ይርጋን አስመልክቶ በፍትሀብሄር ሕግ ቁጥር 1856/2/ ከሰፈረው የይርጋ ጉዳይ በተከራካሪዎች ካልተነሣ ፍርድ ቤት አይነሳም ከሚለው ሕግ የተለየ ነው፡፡በፍትሐብሔር ሕግ የሰፈረው የይርጋ ሕግ ዋነኛ ዓላማ የተዋዋዮችን ጥቅም መጠበቅ ነው፡፡ የዚህ መብት ተጠቃሚ የሆነ ተከሣሽ ይርጋውን ካላነሣም የሚጎዳው ራሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ተዋዋይ ወገን የተወውን መብት ፍርድ ቤት በራሱ አነሣሽነት እንዲያነሣው አይፈቀድም፡፡ በሥነሥርዓት ሕጉ የተቀመጡ የጊዜ ገደቦች መከበር አለመከበራቸውን ግን ፍርድ ቤቱ የመከታተል ሃላፊነት አለበት፡፡ በተከራካሪ ወገን ባይነሣ እንኳን በሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 195 እንደተደነገገው ጊዜው ካለፈ በኋላ የተከናወነው ነገር ሁሉ እንዳልተፈፀመ ሆኖ ስለሚቆጠር የሥነሥርዓት የጊዜ ገደቦች ተሟጋቾችን ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱንም ጭምር የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በሥነሥርዓት ሕጉ በግልጽ የሰፈረው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የሚቀርብን ማንኛውንም ጉዳይ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ውድቅ ማድረግ እንዲሚችል ይህ ችሎት ከላይ የተመለከቱትን ሕጋዊ ምክንያቶችን በማንሳት በመ/ቁጥር 17362 በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝን ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይህን ጉዳይ በዚህ መዝገብ ማንሳት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት በስነ ስርዓት ሕጎች ያሉት የጊዜ ገደቦች በመሰረታዊ ሕጎች ካሉት የጊዜ ገደቦች የተለዩ ናቸው በማለት የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሥነ-ሥርዓት ሕጎች የተካተቱትን የይርጋ ገደቦችን አቆጣጠር በተመለከተ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ስር ከተቀመጡት የጊዜ ገደብ አቆጣጠር አንጻር ማየትም አይቻልም የሚል ክርክር ማስነሳቱ የማይቀር በመሆኑ ይህንኑ እልባት ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሰው የአስገዳጅ የሕግ ትርጉም ምክንያቶች የሚያጠነጥኑት በስነ ስርዓት ሕጎች ያሉትን የጊዜ ገደቦች ሊነያሳ የሚችለው ፍርድ ቤት ነው? ወይስ ተከራካሪ ወገን ብቻ? በሚለው ጥያቄ በመሆኑ በሥነ-ሥርዓት ሕጉች ያሉትን የጊዜ ገደቦችንና በመሰረታዊው ሕግ ውስጥ የተካተቱትን የይርጋ ገደቦችን ባሕርይ መለየቱን የሚያሳይ ከሚሆን በስተቀር በይርጋው ጊዜ አቆጣጠር ላይም ሁለቱም ህጎች መሰረታዊ ልዩነት አላቸው ወደሚለው ድምዳሜ ሊያድርስ የሚችል አይደለም፡፡ ይልቁንም ሕጉቹ እርስ በእርሳቸው ያላቸው ትስስርና አላማቸው ሲታይ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በግልጽ ምላሽ ያላገኙትን ጉዳዮች በዋናው ሕግ አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች ምላሽ በመስጠት ሕጉቹ ውጤታማ በሆነ መንገድ ስራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ከዚህ አንጻር ሲታይ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ስለይርጋ አቆጣጠር ግልፅ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ይህንኑ የሕጉን ክፍተት መሙላት የሚቻለው ስለጊዜ አቆጣጠር በፍተሐብሔር ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን በመመልከት ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ አይነቱ አተረጓጎምም ሕጉቹ ውጤታማ በሆነ መንገድ ስራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል በመሆኑ በጠቅላላ የሕግ አተረጓጎም ደንቦችም ተቀባይነት ያለው አካሄድ ነው፡፡

አንድ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትእዛዝ ወይም ውሳኔ የተሰጠበት ወገን ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ መሰጠቱን ወይም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78(1) ድንጋጌ የሚያሳይ ሲሆን የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጅም "Any defendant against whom a decree is passed or order made ex-parte or in default of pleading; may, within one month of the day when he became aware of such decree or order, apply, to the court by which the decree was passed or order made for an order to set it aside." በሚል የተቀመጠ ሲሆን የአንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው አቤቱታ አቅራቢው ስለሁኔታው ከተረዳበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በግልጽ አያሳይም፡፡ በፍትሓ ብሔር ሕጉ ስር ባሉት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ድንጋጌዎች ግን የመጀመሪያው ቀን ለይርጋው ጊዜ መቆጠር መነሻ ሊሆን እንደማይገባ በግልጽ በቁጥር 1848 ስር ተመልክቶ ይገኛል፡፡ ይህ ድንጋጌ መሰረት ሲደረግም አመልካች ጉዳዩን ተረዳሁ የሚሉበት ጥር 30 ቀን 2003 ዓ/ም ጊዜ ለአንድ ወሩ የጊዜ አቆጣጠር መነሻ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍትሃ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ያሉት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር በፍትሐ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብሔር ሕጉ በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስሌቶች ሊመሩ የሚችሉ አይደሉም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ሕጉቹ ያላቸውን ትስስርና የትርጉሜው ውጤት በመሰረታዊ ሕጉ ጥበቃ ባገኙት መብቶች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ እንድምታ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

በፍተሐብሄር ስነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች አቆጣጠር መገዛት ያለበት በፍተሐብሔር ሕጉ በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ድንጋጌዎች አንፃር ነው ወደሚለው ድምዳሜ ከደረሰን የአመልካች አቤቱታ የአንድ ወር የጊዜ ገደብ ያለፈበት መሆን ያለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች በሌሉበት ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ መሰጠቱን የተረዱት በ30/05/2003 ሲሆን ውሳኔው ተነስቶ ባሉበት ጉዳዩ እንዲታይላቸው አቤቱታ ያቀረቡት በ30/06/2003 ዓ.ም. ነው፡፡ ከላይ በተሰጠው ትርጉም መሰረት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1848 መነሻ ሲሆን የአንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከየካቲት አንድ ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አንድ ወር ሲቆጠር ደግሞ የአመልካች አቤቱታ በይርጋ የሚታገደው ከመጋቢት 01 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ባሉት ጊዜያት ከቀረበ ነው፡፡ አመልካች ጥያቄአቸውን ያቀረቡት ግን የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ከይርጋ በመለስ ያሉት ሌሎች ሕጋዊ መመዘኛዎች በስር ፍርድ ቤት ታይተው ሊስተናገድ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 164816 ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1111116 ጥር 09 ቀን 2004 ዓ.ም የፀናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስር የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች አቆጣጠር መታየት ያለበት በራሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሰረት ሳይሆን በፍ/ብ/ህጉ በቁጥር 1848 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ነው ብለናል፡፡
3. የጊዜ አቆጣጠሩ ከዚህ አንፃር ሲታይም የአመልካች ጥያቄ የአንድ ወር የጊዜ ገደብ ያላለፈበት በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን ከይርጋ በመለስ ባሉት ሌሎች ክርክሮች ጉዳዩ ታይቶ አመልካች በሌሉበት ታይቶ የተወሰነው ውሳኔ ሊነሳ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ጭብጥ እና በሕጉ አግባብ ተከታዩ ሂደት ታይቶ ጉዳዩ እንዲወሰን ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ-ነ/ፈጅ ብርሃኑ ታደሠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ አብዱልከሪም ዳውድ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የማቅረቢያው ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ ይከፈት ዘንድ እንዲፈቀድ የቀረበውን ጥያቄ አንድ ፍርድ ቤት ተቀብሎ በበላይ ፍርድ ቤት ክርክር ሲደረግ በቆየበት ጊዜ የበታች ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሚመራው ክርክር ሳይታገድ ቆይቶ የበላይ ፍርድ ቤቱ የይግባኝ ማስፈቀጃው ተቀባይነት ያገኘው ያላግባብ ነው በማለት በስነ ስርዓቱ ላይ ውሳኔ ቀድሞ ከሰጠ እና የበታች ፍርድ ቤቱ ይህንኑ የበላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ማስፈቀጃው ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሳይመለከት በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ቢሰጥ ይኸው የበታች ፍርድ ቤት ውሳኔ ተፈፃሚነት ያለው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡የማስፈቀጃ ጥያቄው የቀረበው ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲሆን፣ ጥያቄ አቅራቢው የአሁኑ ተጠሪ ነበር፡፡ የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ሊያልፍበት የቻለው ወይም ይግባኙን በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሊያቀርብ ያልቻለው ጉዳዩን ይዞ ሲከታተል በነበረው ነገረ ፈጁ ስህተት /ጥፋት/ እንደሆነም በማመልከቻው ላይ ገልጾአል፡፡ ፍ/ቤቱም ይህን መነሻ በማድረግ የአሁን አመልካችን በመልስ ሰጪነን አስቀርቦ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ጊዜው ያለፈው በነገረ ፈጁ ጥፋት ነው፡፡ ነገረ ፈጁም በዚህ ምክንያት የዲሲፕሊን እርምጃ ተወስዶበታል የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት የተጠሪን ጥያቄ ተቀብሎአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይህ ችሎት ጊዜ ካለፈ በኋላ ይግባኝ እንዲከፈት ጥያቄ የሚቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 325 በተደነገገው መሠረት ሁኖ ጥያቄው ተቀባይነት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ የሚመረመረው /የሚመዘነው/ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 326 መሠረት መሆኑን፣ ጥያቄው ተቀባይነት አለው ወይንስ የለውም? የሚለው ነጥብ ሊወሰን የሚገባው እንደየአግባቡ በንኡስ ቁ/1/ ወይም /2/ መሠረት እንደሆነም ግልፅ ስለመሆኑ፣ በንዑስ ቁጥር 1 እንደተመለከተው አመልካቹ ወይም የፈቃድ ጥያቄ አቅራቢው ይግባኙን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑ ፍ/ቤቱን ማሣመን ከቻለ ይግባኙን በአሥር ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ እንደሚፈቅድለት፣ በዚህ ረገድ ምክንያቱ በቂ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ፍሬ ነገር በፍ/ቤቱ የሚመዘን ከመሆን አልፎ በሕጉ የተቀመጠ የታወቀ /የተለየ/ መስፈርት እንደሌለው፣በንዑስ ቁ./2/ የተቀመጠው ድንጋጌ ግን አመልካቹ ያቀረበው ምክንያት በንኡስ ቁ./1/ አባባል ሊስተናገድ የማይገባ ወይም ተቀባይነት የሌለው ነው የሚባልበትን አግባብ የሚያመለክት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌ መቀመጡን፣ይኸውም በፈቃድ መጠየቂያው ማመልከቻ ላይ የተገለፀው ምክንያት ይግባኙን በጊዜው ማቅረብ ያልቻለው በአመልካቹ ጠበቃ ወይም ነገረ ፈጁ ወይም በወኪሉ ያለመቅረብ እና በእነዚሁ ጉድለቶች መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ ምክንያቱ በንኡስ ቁ./1/ እንደተነገረው በቂ ነው ሊባል እንደማይገባ በግልጽ መደንገጉን፣ በዚህ ምክንያትም የይግባኝ ይከፈትልኝ ጥያቄው ተቀባይነት ለማግኘት አይችልም በማለት ግልጽ ድንጋጌ ሕጉ ማስፈሩን በምክንያትነት ይዞ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን መፍቀዱ ግልፁን ሕግ በሚጻረር አኳኋን ነው በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሻረው መሆኑን የሰ/መ/ቁጥር 57360 ያሳያል፡፡

ከዚህ በሁዋላም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ዋናውን ጉዳይ ሲያከራክር ቆይቶ ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ የታገደ አይደለም፣በግራ ቀኙ መካከል የተፈረመው የገንዘብ ዋስትና ቦንድ ሕጋዊ ውጤት አለው በማለት በፍሬ ነገር ደረጃ የቀረበውን ክርክር አጣርቶ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመለሰ ሲሆን ይኸው ውሳኔ የተሰጠው ከሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ውጪ ነው በሚል የአሁኑ አመልካች ውሳኔው እንዲታረም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጥቅምት 20 ቀን 2004 ዓ/ም አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይኸው ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ የሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔ መኖሩን እንዲያውቅ ያለመደረጉንና ክርክሩም እንዳይካሄድ ያለመታገዱን በምክንያትነት ይዞ የራሱን ውሳኔ መልሶ የሚሽርበት አግባብ ያለመኖሩን ጠቅሶ የአመልካችን አቤቱታ ሕዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዋናው ጉዳይ ላይ የሠጠው ውሳኔ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔን ውጤት አልባ የሚያደርግ ነው በማለት በጊዜውም የሰበር ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ ግልባጭ ለይግባኝ ሰሚው ችሎት እንዲደረሰው ለማድረግ ተገቢውን ሁሉ በሚመለከተው አካል በኩል አቅርቦ የይግባኝ ሰሚው ችሎት በክረምት ጊዜ በነበረው ስራ ዋናውን መዝገብ መርምሮ ውሳኔ በመስጠቱ ችግሩ መከሰቱን ገልፆ በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻርለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በሰጠው መልስ የአመልካች የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሕጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ ያለመቅረቡንና በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለውም በአመልካች ነገረ ፈጅ ችግር ስለመሆኑ ዘርዝሮ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማናገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት በመ/ቁጥር 60886 በሆነው የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጭብጥ ምላሽ የሚያስፈልገው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው በተጠሪ በኩል የቀረበውን የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታውን በመመርመር ተቀባይነት አለው ወደሚለው ድምዳሜ ከደረሰ በኋላ መሆኑን፣የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ፈቃጅ ውሳኔ ግን በፌዴራሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሻረ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዋናው ጉዳይ ላይ ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ መስጠቱን፣ይህ ውሳኔ የተሰጠውም ይግባኙ የማቅረቢያ ጊዜውን ጠብቆ ያልቀረበ፣ጊዜው አልፎም ይግባኙን ለማቅረብ በቂና ሕጋዊ ምክንያት የለም ተብሎ በሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ነው፡፡የሰበር ሰሚው ችሎት ስለማስፈቀጃው በሰጠው ውሳኔ ላይም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 325 እና 326 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ የተረጎመ ሲሆን በዚህ ችሎት ሕግ በመተርጎም የሚሰጠው ውሳኔም በየትኛውም እርከን በሚገኝ ፍርድ ቤት አስገዳጅ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡

የተጠሪ ነገረ ፈጅ የአመልካች ነገረ ፈጅ የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሕጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ ያልቀረበ ነው በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካች ነገረ ፈጅ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 60886 ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም. የሠጠው ውሳኔ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 57360 ከሰጠው ውሳኔ አንፃር ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሕዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም. በሰጠው ትእዛዝ ያለመሆኑን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ በዋናው ጉዳይ ላይ ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም. ውሳኔ ከተሰጠና ይህ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚል ቅሬታ ካለው አመልካች የሰበር አቤቱታውን ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ ዘጠና ቀናት ውስጥ ለሰበር ሰሚው ችሎት ማቅረብ የሚችል መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና 22 ድንጋጌዎች የሚያሳዩት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ህዳር 27 ቀን 2004 ዓ.ም. በመሆኑና በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ የተሰጠው ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም. እንደመሆኑ መጠን በሕጉ የተመለከተው የዘጠና ቀናት የሰበር አቤቱታ ማቅረቢ ጊዜ ሳያልፍ አቤቱታውን ያቀረበ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተጠሪ ነገረ ፈጅ ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስ በአንድ ፍርድ ቤት የተሠጠ ውሳኔ ስህተት አለበት የሚል ወገን በሕጉ አግባብ ቅሬታውን ለበላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ወገኖች ከተራከሩ በኋላ በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤት ከተሻረ በተሻረው ውሳኔ መሰረት የሚፈጸም ነገር ሊኖር አይችልም፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስም ይህንኑ ድምዳሜ የሚያጠናክር ነው፡፡ በበታች ፍርድ ቤት የሚደረገውን ክርክር ሳያሳግድ በበላይ ፍርድ ቤት ክርክር አድርጎ የበላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚታወቅ ድረስ መቆየትና የበላይ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተከራካሪ ወገን ከአወቀው በኋላ ለበታች ፍርድ ቤት የበላይ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሳያስታውቅ በመቆየቱ ወይም በመቅረቱ ብቻ የበላዩን ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚቃረን የበታች ፍርድ ቤት ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት እንዲኖር የሚደረግበት የስነ ሥርዓት ሕግ አግባብም የለም፡፡በመሆኑም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 ድንጋጌ መንፈስም ሆነ ከአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(1) ድንጋጌ አንፃር የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 60886 ጥቅምት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት የሌለው በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 60886 ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 60886 ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ይግባኙ እንዳይቀርብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 57360 ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ/ም ውሳኔ ከሠጠ በሁዋላ የተሰጠ በመሆኑ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአመስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አልዩ ተክሉ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ መስፍን ስለሺ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ክስ ያቀረበ ወገን ክሱን ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችል ዘንድ መጥሪያውን ለተከሳሽ ለማድረስ በፊት ክሱ እንዲዘጋለት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ክሱ በተዘጋ ጊዜ ሙሉ የዳኝነት አገልግሎት አገኛለሁ በሚል በሰበር ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ተገቢው ተቀንሶ እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት በሚል ነው፡፡

ከላይ የተመለከተውን ጉዳይ አስመልክቶ በቅድሚያ ጉዳዩን የተመለከተውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሳሽ ክሱን በተከሳሽ አድራሻ ማቅረቡ ለአፈፃፀም የተሻለ ሆኖ ስላገኙት ወጭ አድርገው የወሰዱትን መጥሪያ እና የእግድ ትዕዛዙን በመመለስ መዝገቡ እንዲዘጋላቸው እና የከፈሉትም የዳኝነት ገንዘብ እንዲመለስላቸው ጠይቀዋል፡፡ በዚህም መሠረት ፍ/ቤቱ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278/1/ መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ይሁን እንጂ ከሳሽ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ተገቢው ተቀንሶ የሚመለስበትን አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 232 እና 245 ከመደንገጉ በቀር ከሳሽ በእራሱ አነሳሽነት መዝገብ እንዲዘጋ ባደረገ ጊዜ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ሊመለስ የሚችልበትን ሁኔታ የደነገገ ሕግ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ዳኝነት ሰጥቷል፡፡

ይህንኑ ትዕዛዝ በይግባኝ የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት የከሳሹን ክስ ሕጋዊ ብቃት መርምሯል፡፡ የእግድ ትዕዛዝም ሰጥቷል፡፡ ተከሳሽም ስለጉዳዩ መከላከል እንዲፈቀደለት የሚጠይቅ ከሆነ ፈቃድ እንዲጠይቅ መጥሪያ እና የክስ ማመልከቻ ግልባጭ ተልኮለታል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የፍ/ቤቱን የፅሕፈት መሣሪያ ከሳሽ የተጠቀመ ከመሆኑም በላይ ተገቢውን የዳኝነት አገልግሎት አግኝቷል፡፡ ይህን አገልግሎት ማግኘቱ ከተረጋገጠ የፍ/ቤት ዳኝነት አገልግሎት ተሰጥቷል ማለት የሚቻለው ክሱ ከተሰማ በኋላ እንጂ ክሱ ከመሰማቱ በፊት ነው የሚለው ክርክር ከግንዛቤ እጥረት የመነጨ ነው የሚለውን ለጉዳዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት በመስጠት እና የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177/45 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ሁሉ ጠቅሶ ውሣኔውን አፅንቶታል፡፡

አመልካች በዚህ ዳኝነት ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፤ ተጠሪ በጥሪው መሠረት ቀርቦ ለመከራከር ካለመፈቀዱም በላይ በጉዳዩ ላይ ሊከራከር የሚችልበት ምክንያት ላይኖርም የሚችል መሆኑ ተጠቅሶ ክርክሩ ከአመልካች የሰበር አቤቱታ ጋር ተገናዝቦ እንዲታይ ተደርጓል፡፡ እኛም አመልካች ያቀረቡትን የሰበር መከራከሪያ ነጥብ ከላይ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የሥር ፍ/ቤቶች ዳኝነት ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ እንደገለፀው ከሳሹ ክሴን ትቼዋለሁ በማለት ተከሳሹ ቀርቦ መልስ ከመስጠቱ በፊት ወይም የጉዳዩ መሰማት ከመጀመሩ በፊት በማመልከቱ የተነሣ መዝገብ በተዘጋ ጊዜ ፍ/ቤቱ ለሚሰጠው የዳኝነት አገልግሎት ሲባል ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ውስጥ የሚቀንሰው ተቀንሶ ቀሪው የሚመለስለት ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በ1958 ዓ.ም በወጣው የፍ/ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ አልተደነገገም፡፡ በዚህ ሕግ ይህ ነጥብ በዝምታ ታልፏል፡፡ የሕግ ሽፋን አላገኘም፡፡

ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ክፍል በሆነው በአንቀጽ 3 ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ በግልፅ ለሸፈናቸው ጉዳዮች ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ተፅፈው ሥራ ላይ የነበሩ ሕጐችና ደንቦች የተሻሩ መሆኑን ከመግለፅ በቀር ሕጉ ሳይሸፍናቸው ለታለፉ ጉዳዮች የፍ/ብሔር ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ተፅፈው በሥራ ላይ የነበሩ አግባብነት ያላቸው ሕጎች እንደ አግባብነቱ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በዚህም መሠረት በ1945 ዓ.ም በወጣው የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177 አንቀጽ 11 ላይ ከሳሹ ክሱን ካቀረበ በኋላ በእራሱ ጠያቂነት ክሱን የተወው እንደሆነ አስቀድሞ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ምን ያህል ተቀንሶ ምን ያህል እንደሚመለስለት በዝርዝር የተደነገገ በመሆኑ ከላይ በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት አመልካች ያቀረበው የዳኝነት ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄ ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህም እንካ ቢታለፍ ይህ በሕግ ሽፋን ሳይሰጠው በዝምታ የታለፈውን ጉዳይ ከጉዳዩ ጋር ተመሣሣይ ይዘት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማመሳሰል ተገቢውን ትርጉም መከተል እንደሚቻልም ቋሚ ከሆኑት የሕግ አተረጓጐም ዘዴዎች አግባብነት ያለው የሕግ ትርጉም ዘይቤ አመልካች ነው፡፡

ከዚህም አንፃር ሲታይ ተከሳሽ ከመጠራቱ በፊት ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ሕ/ቁ 232/1/ሀ/ እና /ለ/ መዝገብ በተዘጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 232/1/ለ/ እንደተመለከተው ከሳሹ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ውስጥ ተገቢው ተቀንሶ ቀሪው እንዲመለስለት ሕጉ ከፈቀደ ተከሳሹ በመጠራቱ ምክንያት ተከሳሹ ሥልጣንን አስመልክቶ ባነሳው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የተነሣ መዝገብ በተዘጋ ጊዜ እንደ አግባብነቱ ከተከፈለው የዳኝነት ገንዘብ የሚቀነሰው ተቀንሶ ተራፊው እንዲመለስለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 245/4/ መደንገጉ ከታወቀ መጥሪያው ወጭ መሆኑ ቢታወቅም፣ የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም ከሳሹ ለተከሳሹ መጥሪያውን ከማድረሱ በፊት በእራሱ ጠያቂነት ክሱን መተውን ገልፆ መዝገቡን ፍ/ቤቱ በዚጋው ጊዜ ክርክሩ ከደረሰበት የክርክር ደረጃ እና ሙሉ የዳኝነት ገንዘብ የተከፈለበት ምክንያት የተሟላ ክርክር ተደርጎ ፍ/ቤቱ የተሟላ የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጥ ተከራካሪውም ይህንኑ የተሟላ የዳኝነት አገልግሎት ለማግኘት ያለውን መብት መነሻ በማድረግ የሚከፈል ለመሆኑ ከላይ የተመለከቱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 232 እና 245/4/ በግልፅ የሚያመለክቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ በዚህ ጉዳይም የከሳሹ የዳኝነት ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄ በይዘቱም ሆነ ከሕግ ግብ አንፃር ሕጉ በግልፅ ከሸፈናቸው ጉዳዮች ተመሣሣይ እንጂ የተለየ ሆኖ አይገኝም፡፡

ከዚህም አንፃር ምንም እንኳ ከሳሽ የከፈልኩት የዳኝነት ገንዘብ በሙሉ ይከፈለኝ በማለት የከፈሉትን የዳኝነት ክፍያ የማግኘት መብት ያላቸው ባይሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 232/1/ለ/ እና 245/4/ በተነገረው መሠረት ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ የሚቀነሰው ተቀንሶ ተራፊውን መልሶ የማግኘት መብት እያለው የከሳሽ ጥያቄ ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም በሚል በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው የሕግ ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 185730 በ30/9/2003 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 111729 በ4/5/2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡

2. አመልካች አስቀድሞ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ውስጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 232 በተመለከተው መሠረት ተገቢው የዳኝነት ገንዘብ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪው ይመለስልለት ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 77322

ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የደብረ ዘይት መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን - ጠበቃ አቶ ዓለሙ ደገፉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. እሌኒ ዓለማየሁ - ጠበቃ አቶ ጣባ ጨፋ ቀረቡ

2. የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፊጅ አቶ መስፍን ኮርሜሶ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 የተመለከተውን የጣልቃ ገብነት ሥርዓት አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ ሆነው ግንቦት 19 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ ውል ከአቶ ገረመው ጥላሁን እና ከወ/ሮ ልባዊት ዓለሙ ቁጥሩ 154 የሆነውንና በ800 ካ.ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት ገዝቻለሁ ሆኖም የአሁን 2ኛ ተጠሪ በውል ላገኘሁት ቤት ካርታና ፕላን በስሜ ሰርቶ ሊሰጠኝ ሲጠየቅ እምቢተኛ ስለሆነ ካርታና ፕላን በስሜ ሰርቶ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት በአሁን 2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርባለች፡፡

2ኛ ተጠሪም በቃል ክርክር ወቅት ቀርቦ ይህ ካርታና ፕላን ይሠራለት የተባለው ንብረት በቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን አካባቢ ስለሚገኝ እና ህዝብና መንግስት እንዳይጋጭ ብለን ሌላ ተለዋጭ ቦታ ለመስጠት እየተዘጋጀን በመሆናችን እንጂ እምቢተኛ ሆነን አይደለንም የሚለውን አስመዝግቦ ጉዳዩ በክርክር ላይ እንዳሉ የአሁን አመልካች በፍ/ብሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 መሰረት ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር ይፈቀድልኝ፣ በማለት ጣልቃ ሊገባ የሚችልበትን አቤቱታ ከእነማስረጃው አቅርቧል፡፡ በማስረጃነትም ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የይገባኛል መብት ያለው መሆኑን የሚያመለክት የከተማ ቦታ ባለቤትነት ማስረጃ ወረቀት አያይዞ እንደቀረበ የስር የአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም የአሁን አመልካች ጣልቃ ልገባ ይገባል በማለት ላቀረበው አቤቱታ በማስረጃነት ይህንኑ ሰነድ ያቀረበ ለመሆኑ በትዕዛዙ መግቢያ ላይ ፍ/ቤቱ መግለፁ እየታወቀ እንደገና ወረድ ብሎ ጣልቃ ልግባ ባዩ ጣልቃ እገባለሁ በማለት ለቤተክርስቲያን ህጋዊ ሰውነት ሰጭ የሆነውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ 398 እና ለአስተዳደሩ የተሰጠውን ሥልጣን ከመጥቀሱ በቀር ያቀረበው ክርክርና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ የለም የሚለውን ምክንያት በመያዝ፤ እንዲሁም ከሳሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሆነችው በውል ምክንያት ባገኘችው ካርታና ፕላን ላይ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል መብትም የለውም የሚለውን በመጥቀስና ጣልቃ ገብ ራሱን የቻለ ካርታና ፕላን አለው በአሁን 1ኛ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ከሳሽ በነበሩትና በአሁን 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ በነበሩት መካከል የተነሳው ክርክር በጣልቃ ገብ ካርታና ፕላን ላይ አይደለም። ከድሮ ጀምሮ ለሌላ አካል በተሰጠ ካርታና ፕላን ላይ መብት ያለው አይደለም፤ ከፈለገም በሌላ በኩል መብቱን ያስከብር እንጂ የሚለውን በማከል ጣልቃ ሊገባ አይገባም በሚል አሰናብቶታል።

የአሁን አመልካች ደረጃውን ጠብቆ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ጣልቃ ሊገባ እንደሚገባ በመግለፅ ይኸው ትዕዛዝ በይግባኝና በሰበር ሥርዓት እንዲታረምለት ዳኝነት ቢጠይቅም የወረዳው ፍ/ቤት ከሰጠው ዳኝነት ጋር ተመሳሳይ በሆነ ምክንያት ጥያቄው ተቀባይነትን አላገኘም። በዚህም የተነሳ የአሁን አመልካች ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል።

1ኛ ተጠሪም የጣልቃ ልግባ ባዩን አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ዳኝነት መስጠታቸውን እንጂ የህግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን አያመለክትም የሚልበትን ምክንያት በመጥቀስ ሲከራከር፤ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በአንድ በኩል ክርክር ያስነሳውን ንብረት ከአሁን አመልካች በፊት 1ኛ ተጠሪ በግዥ ያገኙት ነው የሚል፤ በሌላ በኩል የዚህ ንብረት ህጋዊ ባለይዞታ አመልካች ናት የሚል እንድመታ ያለው እርስ በእርሱ የተምታታ ሐሳብ ከሰጠ በኋላ በሁለት ግለሰቦች መካከል ባለ ክርክር 2ኛ ተጠሪ በሰበር ደረጃ ተጣርቶ ለመከራከር የሚያስችለው የህግ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመግለፅ መልስ ሰጥቷል።

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል። እንደመረመርነውም ዳኝነት ሰጭ የሆነ አካል በሥራው የሚሰጠው ማናቸውም ዳኝነት በተከራካሪ ወገኖች በማስረጃ ተረጋግጦ የቀረበ ጉዳይ ከህግ ጋር በማገናዘብ ክርክርን፤ ማስረጃንና አግባብነት ያለውን ህግ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል። ከዚህ አንፃር የአሁን አመልካች በሥር የአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ጣልቃ ገብቼ ለመከራከር ያስችለኛል የሚለውን ምክንያት ለዚሁ ምክንያቱ ደጋፊ የሆነ የከተማ ቦታ ባለቤትነት ማስረጃ ማቅረቡ እየተገለፀ፤ የወረዳው ፍ/ቤት ጣልቃ ገብ ህጋዊ ሰውነት ያገኘበትን ህግና በአስተዳደሩ የተሰጠውን ሥልጣን ከመጥቀሱ በቀር ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የለም በሚል የተሰጠው ትንታኔ/ዳኝነት ከላይ ከዳኝነት ሰጭ አካል የሚጠበቀውን መሰረታዊ የስራ ግዴታ ምርኩዝ ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም። በሌላ በኩል በሥር ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በአሁን 2ኛ ተጠሪ ላይ ላቀረቡት የክስ አቤቱታ በማስረጃነት ያቀረቡት ቤቱን በግዥ አግኝቻለሁ ያሉበትን ውል በማያያዝ መሆኑ ቢታወቅም ይህ ውል በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ሆኖ ተገኝቷል ከተባለ የዚህ ውል የአስገዳጅነት ባህሪይ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተወሰነ ለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1731 የተመለከተ በመሆኑ የውለታው ጉዳይ በሆነው ንብረት ላይ መብት አለን የሚሉትን ሌሎች ሦስተኛ ወገኖችን በንብረቱ ላይ ያላቸውን መብት ለማስከበር ሲሉ ሊያቀርቡ የሚችሉትን ክርክር ከጅምሩ ሊገደብ የሚችል አይደለም ይልቁንም ተዋዋዩ ወገን ሆነ ከነዚህ ሦስተኛ ወገኖች በየፊናቸው በሚያቀርቧቸው ክርክር እና ማስረጃ እየታየ የህግ መሰረት ያለው መሆኑንና አለመሆኑ እየተለየ ሊወሰን ከሚችል በቀር ከዚህም በቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 የተዘረጋው ሥርዓት በከሳሽና በተከሳሽ ተሰይመው በሚከራከሩበት ጉዳይ የመጨረሻ ውጤት የተነሣ በማጣት ሆነ በማግኘት ረገድ ጥቅመ/መብቱ የሚነካበት፤ ማናቸውም ወገን ሌላ ክስ ማቅረብ ሳያስፈልገው በጉዳዩ ገብቶ የክርክር ተካፋይ እንዲሆን በማድረግ ከአንድ ጉዳይ ሊመነጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችልን ክርክር በአንድ ፍ/ቤት በአንድ መዝገብ አጣምሮ በአጭር ጊዜ እና በአንስተኛ ወጭ እንዲቋጭ ለማድረግ እንዲረዳ ታስቦ የተደነገገ መሆኑ እየታወቀ የአሁን አመልካች ከፊለገ በሌላ መንገድ መብቱን ያስከብር እንጂ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ሊገባ አይገባም በሚል የተሰጠው ትርጉም የህጉን ይዘት ግብና ዓላማ መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከዚህም በቀር የአሁን አመልካች ያቀረበው ክርክር እና ማስረጃ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚያስችለው አመልካች የሆነ ክርክርና ማስረጃ ማቅረቡ አስከተረጋገጠ ድረስ የክርክር ተካፋይ በማድረግ ጉዳዩን መምራት ሲቻል የአሁን አመልካች የክርክር ተካፋይ ሆኖ በዋናው ክርክርና ሙግት ጊዜ ክርክሩን ለማስረዳት ማቅረብ በሚገባው የክርክር ጥንካሬ እና የማስረጃ ሚዛን ዓይን በመለካት የተሟላ የክርክር አመራር ሥርዓት ሳይጠበቅ ለፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 በተሰጠው የተዛባ ትርጉም የተነሣ የአሁን አመልካች በጣልቃ ገብነት የክርክር ተካፋይ ሊሆን አይገባም በሚል ከታች ወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የተሰጠው ትርጉም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 25636 በ01/11/2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ በማስከተልም በ22/11/2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ፤ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 25740 በ09/3/2003 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 117229 በ05/6/2004 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ሁሉ ተሽሯል፡፡
2. የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፤ 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆኖ ክርክር በጀመሩበት በመ/ቁ 25636 በ22/11/2002 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ በዚሁ መዝገብ ላይ የአሁን አመልካችን በጣልቃ ገብነት በመሰየም ክርክሩን እንደ አዲስ ከጅምሩ በመምራት በጉዳዩ ላይ ተገቢው ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሰረት ጉዳዩን ለአደአ ወረዳ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. የዚህ ሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሳራ ሁሉም ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡ - ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ዓሊ በከር - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጋር ተያያዥነት ያለው ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በሽሪዓ ፍርድ ቤት ውሳኔ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን በማመልከት በጋራ ያፈራናቸዉን ንብረት ተጠሪ ታካፍለኝ በማለት ተንቀሳቃሽ ንብረቶቹን ከተራ ቁጥር 1-13 ከነ ግምታቸው የዘረዘሩ ሲሆን ስፋቱ 400 ካ.ሜ የሆነ ቦታና ቤት ታካፍለኝ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ተከሣሽን በተመለከተ መልስ እንዲሰጡበት ተጠርተው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎአል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠል በተሰጠው ውሳኔ በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል የሚገኘው ቤት እንዲሁም አንድ ቴሌቪዥን ባለ 14 ኢንች እና አንድ ቴኘ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት ናቸው በማለት ከተቻለ በዓይነት እኩል ይካፈሉ፣ካልተቻለ በስምምነት ተገምቶ አንዱ ለሌላው ግምቱን ከፍሎ ያስቀር፣በዚህ ካልተስማሙ በራሣቸው ወይም በጨረታ ተሸጠው ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝዋን ለፌ/የከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካች አጥብቃ የምትከራከረው ከዚህ በፊት በሽሪዓ ፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔም ሆነ የንብረት ክፍፍል ጉዳይ የተቋጨ ሆኖ እያለ ሌላ ክስ መቅረቡ ያለአግባብ ነው፣ በሽሪዓ ፍ/ቤት በተሰጠው ውሳኔ የቤት ቁሣቁስ በተመለከተ በሠፈር ሽማግሌ ይካፈሉ ሌላ ንብረት ካለ ደግሞ በመደበኛ ፍ/ቤት ይጠያየቁ በማለት የድሬዳዋ የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪአ ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ይሄንን ውሣኔ በመቃወም ለከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ከአንድ ሻንጣ ልብስ በስተቀር ሌላ ንብረት የሌለው መሆኑ ተረጋግጦ ውሣኔ የተሰጠበት ከመሆኑም በላይ ተጠሪም የተስማማበት ስለመሆኑ በሽማግሌዎች ፊት የፈረመ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር አመልካች በቀረበባት ክስ መጥሪያ ደርሷት ቀርባ ያልተከራከረች በመሆኑ፣የጋራ ንብረት ደግሞ ለመካፈል ህጉ መብት የሚሰጠኝ በመሆኑ እና የሸሪዓ ፍ/ቤት ደግሞ በመደበኛ ፍ/ቤት የመጠየቅ መብት የሰጠኝ በመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

በዚህ የክርክር ሂደት በእርግጥም ተጠሪ እንደሚከራከረው የሸሪዓ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በአካባቢ ሽማግሌዎች እንዲከፋፈሉ እና ሌሎች ንብረቶችን በመደበኛ ፍ/ቤት የመክሰስ መብቱ እንደጠበቀ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ አመልካች የምትከራከረው በሸሪዓ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ይግባኝ በመውሰድ በከፍተኛው የሸሪዓ ፍ/ቤት ተሸሯል፡፡ በዚሁ በከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ውሣኔ መሰረት ተጠሪ ከአንድ ሻንጣ ልብስ በስተቀር የሚደርሰው ንብረት የሌለ መሆኑ ውሣኔ ተሰጥቶበታል በሚል ነው፡፡ ይሄንን አመልካች በግልፅ ያነሣችውን የክርክር ነጥብ ተጠሪ ያላስተባበለና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ብቻ በመንጠልጠል መልስ የሰጠ በመሆኑ በግልፅ እና በዝርዝር ያልተስተባበለ ነጥብ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 234/መ/ እና 235 መሰረት እንደታመነ የሚቆጠር በመሆኑ ቀድሞ በሸሪዓ ፍ/ቤት ፍርድ ያረፈበትን የንብረት ክፍፍል ጉዳይ በተመለከተ እንደ አዲስ ለመደበኛ ፍ/ቤት ማቅረብ አግባብነት አለው? ወይስ የለውም የሚለውን መመልከት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የሸሪዓ ፍ/ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78/5/ እና 188/92 መሰረት በማድረግ የተቋቋሙና እውቅና የተሰጣቸው መሆኑን ስለሚያመለክት፣በዚሁ ህገ-መንግስት አንቀጽ 34/5/ መሰረት በተከራካሪዎች ፍቃድ መሰረት የግል ወይም የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በሃይማኖት ህጎች የመዳኘት መብት የተጠበቀ በመሆኑና በዚሁ ሂደትም የተሰጡት ፍርዶች ተቀባይነት ያላቸው ስለመሆኑ ከነዚህ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት ድንጋጌዎች ይዘት፣ዓላማና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚሁ መሰረት በህግ ስልጣን በተሰጠው የሸሪዓ ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ተከራክረውበት በፍርድ ያለቀን ጉዳይ ተጠሪ በውሣኔው ቅሬታ እንኳ ቢኖረው በዚያው በሸሪዓ ፍ/ቤት መዋቅር መሰረት ቅሬታውን ለሚመለከተው የይግባኝ ወይም የቅሬታ ሰሚ ክፍል ማቅረብ ሲገባው እንደ አዲስ ጉዳይ በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5/1/ መሰረት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም የአሁን ተጠሪ ያቀረበው ክስ በሌለበት የተሰማ ቢሆንም በሂደት ግን ጉዳዩ ቀድሞ በውሣኔ ያለቀ መሆኑን እንደተረዱ የቀረበውን ክስ ወድቅ ማድረግ ሲገባቸው በቀረበው ክስ መሰረት ውሣኔ መስጠታቸው አግባብነት የሌውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 05327 ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 27905 በቀን 26-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሸሯል፡፡
2. ቀድሞ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በፍርድ የተቋጨን ጉዳይ ሁለተኛ ክስ ወይም ማንኛውም ዓይነት ሌላ ክርክር ለማቅረብ አይቻልም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 73696

ሚያዝያ 09 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሃና አበባው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዱ ይመር በሌለበት የሚታይ ነው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለብድር የተሰጠው ገንዘብ ከብር አምስት መቶ በላይ ሲሆን ለማስረዳት የሚያቀርበውን የማስረጃ አይነት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም ለአመልካች ብር 10,000.00/አስር ሺህ ብር/ አበድረው አመልካች በብድር ውሉ በተገለጸው የጊዜ ገደብ ገንዘቡን ያልመለሱላቸው መሆኑን ገልፀው የብድር ገንዘቡን ሊመለስ ይገባ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ከመቶ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ለማስረጃነትም የብድር ውሉ በወቅቱ የጠፋ በመሆኑ ለፖሊስ ያመለከቱ መሆኑን የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃና የሰው ምስክሮችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ከተጠሪ የወሰዱት የብድር ገንዘብ የሌለ መሆኑን፣ ከብር 500.00 በላይ ለሆነ የብድር ስምምነት ማስረጃነትም የሰው ምስክር ሊቀርብ የማይችል መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም ተጠሪ የብድር ሰነዱ የጠፋባቸው ስለመሆኑ በሰው ማስረጃ ማረጋገጥ እንደሚችሉ ገልፆ ተጠሪ ምስክሮችን አቅርበው ምስክሮቹ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የካቲት 07 ቀን 2002 ዓ/ም የብድር ውል ስምምነት መኖሩን፣ ሰነዱ የጠፋበት መሆኑን እንደሚያውቁ ያረጋገጡላቸው መሆኑን እንዲሁም በአመልካች በኩል የተሰሙት ምስክሮች ግን የብድር ውሉ ስለመኖሩ አናውቅም ከማለት ውጪ የተጠሪን ማስረጃ ለማስተባበል የሚችል የምስክርነት ቃል ያልሰጡ መሆኑን ገልፆ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የብድር ውል ስምምነት መኖሩ ተረጋግጧል ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ አመልካች ለተጠሪ ብር 10,000.00 ከእነ ሕጋዊ ወለዱ ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ባሉበት የሚጣራ የሕግ ነጥብ አለ በማለት ነጥቡን ለይቶ ለተጠሪ ጥሪ አድርጎላቸው የግራ ቀኙን ክርክር ለመስማት ለመስከረም 22 ቀን 2004 ዓ.ም ቀነ ቀጠሮ ይዞ ተጠሪ ሲቀርቡ አመልካች አልቀረቡም፣ የቀረቡት ተጠሪም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ክደው ተከራክረዋል በማለት የጉዳዩ ክርክር ሊሰማ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ አመልካች ስላልቀረቡና ተጠሪም ክደው ስለተከራከሩ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባው ነው በማለትና በዋቢነትም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ድንጋጌን በመስማት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን መዝገብ የዘጋው አመልካች ቀርበው እያለና ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔም ስለብድር ማስረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472 ስር የተደነገገውን ደንጋጌ ይዘት ያላገናዘበና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2003 ድንጋጌን ያለቦታው በመጠቀም የተሰጠ መሆኑን ገልፀው ውሣኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው ነጥብ በመኖር ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው በስርዓቱ መሠረት ጥሪ ተደረጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ትዕዛዝና አግባብነት ከአላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የቀረበበትን መዝገብ የዘጋበት ሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ መሆን ያለመሆኑን ነው፡፡

አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው የሕግ ነጥብ መኖሩ ታምኖበት የአሁኑ ተጠሪ በተጠሪነት የተመዘገቡበት በመሆኑ ክርክሩን ተጠሪ ባሉበት ለመስማት ተብሎ ቀነ ቀጠሮ ተይዞ መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ.ም በተያዘው ቀነ ቀጠሮ ተጠሪ ሲቀርቡ አመልካች ያለመቅረባቸው ስለመረጋገጡና ተጠሪም ክደው መከራከራቸውን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ከመዝገቡ ከአሰፈረው መረዳት የሚቻል ሲሆን ይህንኑ ምክንያት በማድረግም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ አመልካች ስላልቀረቡና ተጠሪም ጉዳዩን ክደው ስለተከራከሩ መዝገቡን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ድንጋጌን በመጥቀስ ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ዘግቶታል፡፡ ከዚህ በቀላሉ መረዳት የሚቻለው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለመስማት በያዘው ቀነ ቀጠሮ ተጠሪ ቀርበው አመልካች ያለመቅረባቸውን ፣ ችሎቱ ላይ የተሰየሙት ዳኞች ቁጥር ሶስት ከመሆናቸውም በተጨማሪ መዘገቡን ሲዘጋውም በሶስት ዳኞች ብቻ መሆኑና መዝገቡ ሲዘጋ የተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ድንጋጌም መልስ ሰጪን ሳይጠራ ይግባኙን ለመሰረዝ ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚደነግገው ቁጥር 337 መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም የፍርድ ቤት ክርክር በሕጉ አግባብ በተደነገገው የሥነ ሥርአት ሕግ መሠረት መመራት አለበት፡፡ በየትኛውም እርከን የሚገኝ ችሎትም በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠለት ሥርዓት እስከሌለ ድረስ ተፈፃሚነት ባለው የስነ ስርዓት ሕግ መሠረት ከተዘረጋው ሥርዓት አንፃር ጉዳዮችን መምራት አለበት፡፡ ጉዳዮች በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት የሚመሩትም አይነተኛ አላማም ክርክሮችን ፍትሃዊ በሆነ እና ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጭ እንዲቋጩ ማድረግ ስለመሆኑም ይታመናል፡፡ ይህንኑ የሥነ ሥርዓት ሕጉን አላማ ለማሳካት ደግሞ በሕጉ የተመለከቱትን የስነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን እንደየአግባብነታቸው መከተልን የግድ ይላል፡፡ በስነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎችን እንደየአግባብነታቸው ያለመከተል በተከራካሪ ወገኖች መሰረታዊ መብት ላይ አሉታዊ ውጤት ማስከተሉ አይቀሬ ነው፡፡ ስለሆነም በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊኖራቸው የሚገባው ለጉዳዩ አግባብነት ሲኖራቸው እንጂ በዘፈቀደ ሊሆን አይገባም። ድንጋጌዎቹ አግባብነት ያላቸው ስለመሆኑ ከመለየቱ በተጨማሪ በጉዳዩ ላይ ተገቢነት አለው የሚለውን ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ የሚሰጠው ችሎትም በሕጉ አግባብ የተመለከተው የዳኞች ቁጥር የተሟላ ሊሆን ይገባል። በሕጉ አግባብ ሊሟላ የሚገባው የዳኞች ቁጥር ሳይሟላ የሚሰጠው ትእዛዝ ወይም ውሣኔ ደግሞ እንደተሰጠ የማይቆጠርና ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው የሚገባ አይደለም።

ወደተያዘው ጉዳዩ ስንመለስ በክልሉ የሰበር ችሎት በክልሉ አዋጅ ቁጥር 153/2000 እና ይህንኑ አዋጅ በአሻሻለው አዋጅ ቁጥር 169/2002 ተደራጅቷል። በእነዚህ አዋጆች መሠረት የአመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ብለው ሶስት ዳኞች ተሰይመውበት አምስት ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት ሊታይ ይገባል ተብሎ ትእዛዝ ተሰጥቶበት አመልካችንና ተጠሪን ለመስማት ቀነ ቀጠሮ መያዙ ተረጋግጦ እያለ ጉዳዩ አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት አይደለም። ጉዳዩ አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እንዲቀርብ ከተደረገ በሁዋላ የቃል ክርክርን ለመስማት ሶስቱ ዳኞች በእለቱ ተሰይመው ሊሆን እንደሚችል የሚገመት ቢሆንም መዘገቡን ለመዝጋት ግን በዚህ የዳኞች ቁጥር የሚቻል ስለመሆኑ የክልሉን ሰበር ሰሚ ችሎት ያደራጀው የክልሉ ሕግም ሆነ ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሥነ ሥርዓት ሕጎች አያሳዩም። ስለሆነም የአመልካች የሰበር አቤቱታ የተዘጋው በሕጉ አግባብ የተመለከተውን የዳኞችን ቁጥር ባሟላ ችሎት በአለመሆኑ ትዕዛዙ እንደተሰጠ የማይቆጠርና ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው የሚገባው አይደለም።

ሌላው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ሲዘጋ መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ድንጋጌን ነው። እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅራቢን ክርክር ለመስማት ቀጠሮ ይዞ እንደነበርና የመስማቱ ዓላማም የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል አልተፈፀመበትም የሚለውን ለይቶ በተሟላ ችሎት የሚታይ መሆኑንና አለመሆን ለማዘዝ ስለመሆኑን ከመዝገቡ ግልባጭ ተረድተናል። የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበለትን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን ክርክሩን የሚመራበት የእራሱ የሆነ የጉዳይ አካሄድ ሥርዓት የለውም። የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚመራው መደበኛ ችሎቶች በሚመሩበት በ1958 ዓ.ም በወጣው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት ነው።

ይህንን መነሻ አድርገን ጉዳዩን ስናየው መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚለውን የፅሑፍ ቅሬታ በማብራራት ረገድ የሰበር አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ እንዲያሰማ ችሎቱ ቀጠሮ ከያዘ ይህን ሥርዓት ለመፈፀም የሚያዘው ቀጠሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ለመፈፀም የሰበር አቤቱታ አቅራቢ የግድ እንዲቀርብ የሚጠበቅበት አይደለም። አመልካቹ ጉዳዩን የበለጠ ለማብራት የሚጠቀምበት መብት ቀሪ ከሚሆንበት በስተቀር ችሎቱ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል ወይም አያስቀርም የሚል ትዕዛዝ ከመስጠት የማያግደው ሲሆን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 73 ድንጋጌም ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው የክርክር ደረጃ አይሆንም። ጉዳዩ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ ወደ አምስቱ የሰበር ችሎት ከቀረበ እና ክርክሩን ለመስማት ቀነ ቀጠሮ ከተያዘ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖርበት ሥርዓት የለም። በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ እንዲያሰሙ በችሎቱ ቀጠሮ ከተያዘ በኋላ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 ድንጋጌን በመጥቀስ መዝገቡን መዘጋቱም ሕጋዊ አካሄዱን የተከተለ አይደለም። በአጠቃላይ አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲያሰሙ ችሎቱ ቀጠሮ ከያዘ ይህን ሥርዓት ለመፈፀም የሚያዘው ቀጠሮ ሊሟላ የሚገባው የዳኞች ቁጥር አምስት ሁኖ እያለ መዝገቡን በሶስት ዳኞች መዝጋቱና መዝገቡን ለመዝጋት የተጠቀሰው የስነ ስርአት ሕጉ ድንጋጌም አምስት ዳኞች በተሰየሙት ችሎት ባለው የክርክር ደረጃ ተፈፃሚነት የሌለው በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01515 መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ.ም በመዝገብ መዝጋት ረገድ የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቀድሞ ያስቀርባል በተባለው መሠረት ተጠሪ ባሉበት ግራ ቀኙ በተሟላ ችሎት እንዲሰሙ እንዲደረግና ተገቢ ስርዓት መሠረት ተደርጎም ክርክሩ ተካሂዶ ተገቢው ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አምስቱ ዳኞች ወደሚሰየሙበት ችሎት መልሰናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሥሪና ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 67533

ጥቅምት 8 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮ/ን

ተጠሪዎች፡- 1. በረከት በለጠ

2. ታሪኩ ተሰማ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሰሪና ሠራተኞች መካከል የተነሣውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በአዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ሲጀመር ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የሥራ ውላችንን ከሕግ ውጪ አቋርጦብናል በማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ወደ ሥራቸው እንዲመልሳቸው፤ ይህ ካልተቻለ ደግሞ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ይከፈላቸው ዘንድ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ሥራ ለመሥራት ነው፡፡ የተሰናበቱትም በውሉ መሠረት ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በውሉ እና በሕጉ መሠረት ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በዚህ መሠረትም በሕጉ መሠረት መከፈል አለበት ያለውን ክፍያ ብቻ ተከፍሎአቸው ይሰናበቱ በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪዎች ውሣኔውን በመቃወም ለአዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ይግባኝ በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የተጠሪዎችን ክርክር በመቀበል ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ ተጠሪዎች ወደ ሥራቸው ይመለሱ በማለትም ወስኖአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የነበረ ሲሆን፣ የሰበር ችሎቱ አቤቱታ በቀረበበት ውሣኔ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል ተደርጎ የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው የመባሉን አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች እና ተጠሪዎች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገው ክርክር እና የተሰጡት ውሣኔዎች ይዘት እንዳየነው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የሥራ ውል በሚሰራው ሥራ ዓይነት እና በጊዜ የተወሰነ ነው፡፡ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ሳይሰበሰብ የቆየውን የስልክ አገልግሎት ክፍያ ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ በፍ/ቤት እየቀረቡ ለመከራከር ወይም የነገረ ፈጅነት አገልግሎት ለመስጠት ነው፡፡ ውሉ ይህ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ አለማከራከሩ የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡአቸው ውሣኔዎች ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ አመልካች ውሉን ለአንድ ጊዜ አራዝሞት እንደነበር በክርክሩ ተገልጸአል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ክስ ውድቅ ያደረገው /ውሉ በሕጉ አግባብ ነው የተቋረጠው ያለው/ የውሉን ይዘት እና የሥራው ማለቅ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይግባኙን የሰማው ፍ/ቤትም ቢሆን በውሉ ይዘት ላይ የተለየ ግንዛቤ እንዳለው አልገለጸም፡፡ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ሥራ አላለቀም እሚል መደምደሚያ ላይ አልደረሰም፡፡ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው ለማለት የበቃው አመልካችን እንደተቋም በመውሰድ ብቻ ነው፡፡ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት መለስተኛ የሕግ ባለሙያ የሚል ነው፡፡ ይህ የሥራ መደብ ደግሞ ተቋሙ እስካለ ድረስ ያለ ነው የሚል ምክንያት ነው የሰጠው፡፡

በእርግጥ አመልካች እንደተቋም አሁንም አለ፣ መኖሩም ይቀጥላል፡፡ ለክርክሩ አወሳሰን መያዝ ያለበት ጭብጥ ተጠሪዎች የተቀጠሩት በአሰሪና በሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10 መሠረት ነው ወይስ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህ ጭብጥ መፈታት ያለበትም የአመልካችን ድርጅታዊ አቋም መሠረት በማድረግ ሳይሆን፣ በሥራው አይነትም የተወሰነ ነው፡፡ በውሉ መሠረት ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ሥራ የሚያልቅ አይደለም ወይም አላለቀም አልተባለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪዎችን በሠራተኝነት ይዞ የሚቀጥልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ውሉ ለተወሰነ ሥራ የተደረገ በመሆኑ አመልካች ተጠሪዎችን ያሰናበተው በአንቀጽ 10/1 እና 24/1/ መሠረት ነው፡፡ ይግባኙን የሰማው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ከዚህ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በመ.ቁ. 09768 መጋቢት 15 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 52288 ሚያዝያ 4 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል ተደርጎ የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮፖሬሽን ደቡብ ሪጅን - ነገረ ፈጅ አየነው ዲለሌቻ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጥበቡ ተሰማ - ጠበቃ ወርቀአገኘሁ ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ክርክር ሲሆን የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በፍርድ ባለመብትነት ባቀረበው የአፈፃፀም አቤቱታ በማቅረቡ በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጀመረ ነው፡፡ ቀረቦ የነበረው የአፈፃፀም አቤቱታ በተመደብኩበት የሥራ መድብና ደሞዝ ቀድሞ በተሰጠው ፍርድ መሠረት እንዲፈፀምልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች ለቀረበው የአፈፃፀም አቤቱታ መልስ ሲሰጥ ቀድሞ የነበረው መዋቅር በመንግሥት መመሪያ የተሰረዘ በመሆኑ እንደውሣኔው መፈፀም ያልቻለ መሆኑና አዲስ በወጣው መዋቅር መሠረት ደግሞ የሚመደብበትን ቦታ እንዲጠባበቅ በማለት ተከራክሯል፡፡

የአፈፃፀም መዝገቡን የያዘው ፍርድ ቤት በአፈፃፀሙ ዙሪያ በዚሁ መልኩ ካከራከረ በኋላ የፍርድ ባለመብት (የአሁኑ ተጠሪ) ፍርድ ያገኘው የቀድሞ መዋቅር ሥራ ላይ በነበረበት ወቅትና አዲሱ መዋቅር ባልነበረበት ወቅት በመሆኑ በፍርዱ መሠረት ሊፈፀም ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ የቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 337 መሠረት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከታያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረው ለአሁኑ ተጠሪ ተሰጥቶት የነበረው ፍርድ ሊፈፅም የሚችል ፍርድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ ይሄ ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች አጥብቆ እየተከራከረ ያለው ለተጠሪ በፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ መኖሩን ሳይክድ ቀድሞ የነበረው የድርጅት መዋቅር አደረጃጀቱን ለማሻሻል በተወሰዱ እርምጃ በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 197/2003 መሠረት የፈረሰ በመሆኑ እንደፍርዱ ለመፈፀም ያልተቻለ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል የተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር ቀድሞ የነበረው የድርጅቱ መዋቅር የፈረሰ ስለመሆኑ ሳያስተባብል ውሣኔውን ከመፈፀም የሚከለክል ባለመሆኑ እንደፍርዱ ሊፈፀምልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የክርክር ሂደት አመልካች ድርጅትን በተመለከተ መንግሥት ባወጣው ደንብ መሠረት ቀድሞ የነበረው መዋቅር የፈረሰ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በተጨማሪም የመዋቅር ለውጡ ከመምጣቱ በፊት ተጠሪ በፍርድ ቤት ውሣኔ የፍርድ ባለመብት ስለመሆኑ እና ይዜው የተሰጠው የፍርድ ቤት ውሣኔ ሣይፈፀም የድርጅቱ አደረጃጀት በመንግስት መለወጡ በተመሳሳይ መልኩ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይዜ ከሆነ ደግሞ የቀድሞውን የድርጅቱን አደረጃጀት መሠረት በማድረግ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ከመፈፀሙ በፊት መንግሥት በሚያወጠው ደንብ መሠረት አደረጃጀቱ ቢለውጥ ፍርዱ ሊፈፀም የሚችልበት አግባብ ስለመኖሩ ወይም አለመኖሩ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

በክርክሩ ሂደት የታወቁትን ፍሬ ነገሮች ይዘን ወደ ህጉ ስንመለስ ቀድሞ በሥራ ላይ የነበረው የአመልካች ድርጅት አደረጃጀትና በፍርድ ቤት ለተሰጠው ፍርድና ተጠሪን የፍርድ ባለመብት ያደረገው ውሣኔ መሠረት ያደረገው መዋቅር በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በሥራ ላይ በሌለ መዋቅር መሠረት የተሰጠው ፍርድ ለተጠሪ ይፈፀም ማለት ደግሞ የማይቻል ነው፡፡ በመሠረቱ በመርህ ደረጃ የተሰጡት የፍርድ ቤት ውሣኔዎች ተፈፃሚነት የሚያገኙ ሲሆን አልፎ አልፎ ሊፈፀም የማይቻል ፍርድ ሊኖር እንደሚቻል ከፍታሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 392(1) መሠረት አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ሊፈፀም የሚቻል ውሣኔ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ማረጋገጥ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ የማይፈፀምበት አግባብ ካለ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 392(2) መሠረት ይዜንኑ በማመልከት ሊፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚቻል ያመለክታል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይም በሌለ አደረጃጀት ላይ ውሣኔ ማስፈፀም የማይቻል መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ የበታች ፍ/ቤቶች በፍርድ መሠረት ይፈፀም በማለት ትዕዛዝ መስጠታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 53298 በቀን 26-9-2003 ዓ.ም እና የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ 10229 በቀን 22-9-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በህግ አግባብ ቀሪ በሆነ አደረጃጀትን መሠረት በማድረግ ፍርድ እንዲፈፀም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ አግባብነት የለውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኦሮሚያ መንገዶች ቦለሥልጣን - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ብርቁሣ አብራሂም - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሰበታ ሐዋሳ ወረዳ ፍርድ ቤት የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አመልካች የገቢ ግብር ሣይቀንስ ለተጠሪ የሥራ ስንብትና ሌሎች ክፍያዎችን እንድንከፍል የሰጡት ውሣኔ መሠታዊ የሕግ ስህተትና ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር በነበራት የሥራ ክርክር እንዲከፈላት የተወሰነላት የስራ ስንብት የካሣና ሌሎች ክፍያዎች ግብር ተቀናሽ ሣያደረግ በደመወዟ በጥቅሉ አስቦ እንዲከፍል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪን የአገልግሎት ካሣና ግብር ሣይቀንስ በሙሉ ደመወዝ (gross income) ታስቦ ይከፈላት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቦ አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያና የአገልግሎት ካሣ ክፍያ ግብር ሣይቀነስ በሙሉ ደመወዟ አስበን እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 286/94 እና ደንብ ቁጥር 78/1994 የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ የአመልካች ክርክር የህግ መሠረት የለውም የሚል መስከረም 29 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ የገቢ ግብር ሣይቀናነስ በሙሉ ደመወዙ በማስላት የስራ ስንብት ክፍያና የአገልግሎት ካሣ ክፍያ እንዲከፈል የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ውሣኔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 10 ገቢ ማለት ማናቸውም የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን በመደበኛነት የተገኘ ባይሆንም ከማናቸውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት በማናቸውም መልክ ለግብር ከፍዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከፈለው በስሙ የተያዘለትን ወይም የተቀበለውን ሁሉ ጥቅም ይጨምራል በማለት ሰፊ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

ከላይ በተገለፀው አዋጅ አንቀጽ 10 ማናቸውም ሰው በመቀጠር ከሚያገኘው ገቢ ግብር የመክፈል ሃላፊነት እንዳለበት ማናቸውም ቀጣሪ በሚከፍለው እያንዳንዱ ክፍያ ግብሩን የመቀነስና ለመንግስት ገቢ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት የተደነገገውን መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 ከግብር ነፃ የሚሆኑ ክፍያዎች የተዘረዘሩ ሲሆን በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 3 ግብር የማይከፈልባቸው ገቢዎች በዝርዝር ተደንግገዋል ስለሆነም የስራ ስንብት ክፍያንና ካሣ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 እና በደንብ ቁጥር 78/1994 ግብር የማይከፈልባቸው ስለመሆኑ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ ስለሆነም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 በተጣለበት ሃላፊነት መሠረት ለተጠሪ ከሚከፈለው ክፍያ የገቢ ግብር በመቀነስ ለመንግስት ገቢ ለማድረግ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ ለተጠሪ በሙሉ ደመወዝ አስልቶ የሥራ ስንበት የካሣ ክፍያ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሰበታ ሐዋሳ ወረዳ ፍርድ ቤት፤ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የገቢ ግብር በመቀነሰ ለተጠሪ በፍርድ የተወሰነለትን የሥራ ስንብት ክፍያና የካሣ ክፍያ ይክፈላት በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 69179

ሕዳር 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ጨረር መካላከያ ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ኃይሉ ታደሠ ቀረበ

ተጠሪ፡- አቶ ታሪኩ ጫኔ - ጠበቃ ካሣኝ ይበልጣል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስራ ምክንያት የወጣ ንብረት ባለመመለሱ የተነሳ የንብረቱ ጉድለት በገንዘብ ይተካልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-ተጠሪ ለስራ የተረከቡትን ግምቱ ብር 23,423.39 (ሃያ ሶስት ሺህ አራት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም) የሆነ የጨረር መጠን መለኪያ(Universal survey meter- model RDS-200) እና ግምቱ ብር 53,443.85 (ሃምሳ ሶስት ሺህ አራት መቶ አርባ ሶስት ብር ከሰማኒያ አምስት ሳንቲም) የሆነ የራጅ ጥራት መለኪያ (Digital quality control sit- 1 set) መጠበቅ ሲገባቸው በቸልተኝነትና በጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት ለተገዛበት ጉዳይ ሳይውል ያጠፋ መሆኑን ገልፆ የመሳሪያዎቹን ጠቅላላ ድምር ብር 76,867.34 (ሰባ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከሰላሳ አራት ሳንቲም) እንዲከፍሉ፣ የንብረቶቹ ዋጋ ከገበያ ውስጥ ከጨመረ ይኸው ታክሎበት ገንዘቡን እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም በአመልካች መስሪያ ቤት ተቀጥረው በሚሰሩበት ጊዜ ንብረቶቹን ለስራ መረከባቸውን ሳይክዱ ንብረቶቹን ለስራ ይዘው ከሄዱበት ቦታ ላይ በመኪና ውስጥ በጥንቃቄ አስቀምጠው እያለ በስራ ቦታ ላይ በሥርቆት ምክንያት የጠፉባቸው መሆኑን ገልፀው ከአቅም በላይ ለተከሰተው የንብረት መጥፋት በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 65 እና አግባብነት ባለው የመንግስት ንብረት አስተዳደር ሕግ መሰረት ሃላፊነት የለብኝም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በሁዋላ ለክርክሩ መሰረት የሆኑት ንብረቶች ተጠሪ በስራ ላይ እያሉ በጥንቃቄ ካስቀመጡበት ቦታ በስርቆት የጠፉ መሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት በመያዝና የአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 65 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ ተጠሪ ለክሱ ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ለስራ የተረከቡትን ንብረት ያላስረከቡ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ለንብረቱ መጥፋት ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለደረሰ የንብረት መጥፋት ኃላፊ አይሆኑም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ምላሽ የሚያስፈልገው የጉዳዩ ጭብጥ ተጠሪ ከአመልካች የተረከቧቸውን እቃዎች የዋጋ ግምታቸውን ለመክፈል ይገደዳሉ? ወይስ ይገደዱም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን እቃዎች ከአመልካች ላይ የተረከቡ መሆኑን ሳይክዱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከሩት ለመስሪያ ቤቱ ስራ በሄዱበት ቦታ በስራው ቦታ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሁኖ ፣ በመስሪያ ቤቱ መኪና ውስጥ አስቀምጠው እና መኪናውን በመቆለፍ የአበል ክፍያ ለመቀበል ወደ መ/ቤቱ ሂሳብ ክፍል በሄዱበት ጊዜ እቃዎቹ ሊሰረቁ ወይም ሊጠፉ ችለዋል በማለት ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም ወደሚል ድምዳሜ መድረስ የቻለው የተረከቧቸው እቃዎች በስርቆት ምክንያት የጠፉ መሆኑ ተረጋግጧል ፣ ይህም ከተጠሪ አቅም በላይ በሆነ ምክንያት ንብረቶቹ የጠፉ መሆኑን ስለሚያሳይና በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት የነበረ መሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ፍሬ ነገርን አጣርቶና የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን መዝኖ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀፅ 65 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት ያልነበረ፣ እቃዎቹ በስርቆት ምክንያት የጠፉ ስለመሆኑ የሰር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ደግሞ ተጠሪ ኃላፊነት አለባቸው በማለት ነው፡፡ ይሁንና ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከአመልካች ጋር በፈጠረው የሥራ ውል መነሻነት ለክሱ መነሻ የሆኑትን እቃዎችን ስለመረከቡ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በተጠሪም ያልተካደም ቢሆንም ተጠሪ እነዚህን ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን እቃዎች ከአመልካች ከተረከቡ በኋላ በአሰሪው መስሪያ ቤት ወደ ታዘዙበት የስራ ቦታ ይዘው ሄደው በተገቢው ቦታና ጥንቃቄ መሰረት አስቀምጠው በነበሩበት ሁኔታ ንብረቶቹ መሰረቃቸው ወይም መጥፋታቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህንኑ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የደረሱበትን ድምዳሜ ይህ ችሎት እንዳለ ከመቀበል ውጪ የማስረጃ ምዘናን መሰረት በማድረግ ሊመረምረው የማይገባው መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ይህ ችሎት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ማረም ነው፡፡ በመሆኑም ንብረቶቹ የጠፉት በስርቆት መሆኑና ስርቆቱ ደግሞ የተፈፀመው ተጠሪ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው በነበሩበት ጊዜ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መረጋገጡን ይዘን በሕጉ አተረጓጎም ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን እንመለከታለን፡፡ ተጠሪ አከራካሪ እቃዎቹን ለአመልካች መስሪያ ቤት እስከሚያስረክቡ ጊዜ ድረስ በንብረቶቹ ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት ፣ ብልሽት ወይንም መጥፋት በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህ ችግር እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ይታመናል፡፡ አንድ ሰራተኛ ከአሰሪው መስሪያ ቤት ለስራ እቃዎቹን ሲረከብ የሚፈርመበት ዋናው ምክንያትም ይህንኑ ግዴታውን ካልተወጣ ኃላፊነት ሊከተልበት ስለሚገባው እንደሆነ ይታመናል፡፡ በሌላ በኩልም ተጠሪ ፈርሞ የተከረባቸውን እነዚህን እቃዎች እንዳይጠፉ፣ እንዳይሰረቁም ሆነ ሌላ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚጠበቅበት በሥራ ሰዓት ሲሆን ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት ከራሱ ጥንቃቄ ጉድለት ውጪ በሆነ ምክንያት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጭና በራሱ እጅ ባልነበሩበት ጊዜ የጠፉ ስለመሆኑ የማስረዳቱ ሸክም አለባቸው፡፡ ይህንኑ ግዴታውን የተወጡ ስለመሆኑ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ማስረጃን መዘነው አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ተጠሪ ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ያለመስተባበሉም በበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡ ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ሸክማቸውን ከተወጡ ወይም እቃዎቹ በስራ ላይ ቆይተው በጥንቃቄ ከተቀመጡበት ቦታ በስርቆት መጥፋታቸውን በማስረጃ ከአረጋገጡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2027 ድንጋጌ መሠረት በቸልተኝነት ጥፋት መፈጸማቸውን የማያረጋግጥ ነው፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ባለው በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 65 ስር ደግሞ አንድ የመንግስት ሰራተኛ ፈርሞ ላወጣው ንብረት መጥፋት በእዳ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው ፈርሞ ላወጣው ንብረት መጥፋት የሰራተኛው ቸልተኝነት የታየ ወይም በሰራተኛው በኩል ሆነ ተብሎ የተፈፀመ ድርጊት ያለ እንደሆነ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በሰ/መ/ቁጥር 28865 በኪራይ ቤቶች ኤጀንሲና በአቶ ካሳ ግዛው መካከል በነበረው ክርክር ህዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ለዚህ ጉዳይም አግባብነት ያለው መሆኑን ጠቅሶ የተከራከረ ሲሆን ይህ ችሎት ይህንኑ መዝገብ ሲመለከተው በመዝገቡ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ አሁን ከታያዘው መዝገብ ጉዳይ ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ነው ለማለት የማይቻል ሁኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት በጥንቃቄ አስቀምጠው ባለበት ሁኔታ በስርቆት የጠፉ ስለመሆኑ በማረጋገጥና የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከላይ ከተጠቀሰው አዋጅ ጋር በማዛመድ ተመልክቶ ተጠሪ ጥፋት መፈጸማቸውን አመልካች አላረጋገጠም በማለት ክሱን ሳይቀበል መቅረቱ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ መቀበሉ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 79143 ታህሳስ 04 ቀን 2003 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 103031 ሚያዚያ 20 ቀን 2003 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚኅ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 69125
ታህሣሥ 2 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሠላም ተስፋዬ ጠበቃ ዳንኤል ግርማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አልካን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሙሉጌታ ሀመነ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ የሥራ ውል ከህግ ውጭ ያቋረጠ በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ አመልካች የተቀጠሩት በዲኘሎማ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር ነበር፡፡ በዲኘሎማ ኮርስ እንግሊዝኛ ቋንቋ እንዳይሰጥ ከመንግሥት ትዕዛዝ የተሰጠ በመሆኑ ከሥራ የተሰናበቱ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በአዋጁ መሠረት የካሣና ሌሎች ክፍያዎች ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያለውን የሥራ ውል ያቋረጠው በህግ በተደነገገው መሠረት ነው በማለት ከወሰነ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ተጠሪ ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን ያሰናበተው በህጉ በተደነገገው መሠረት ስለሆነ የማስጠንቀቂያ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ክፈል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች በመንግስት ትዕዛዝ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለዲኘሎማ ተማሪዎች እንዳይሰጥ መከልከሉና በዚህ ምክንያት ተጠሪ የሥራ ውሉን ማቋረጡ ተጠሪን የማስጠንቀቂያ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ከመክፈል ነፃ አያደርገውም በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እኔ የሥራ መደቡን አልሠረዝኩም፡፡ የሥራ መደቡ ለዲኘሎማ ትምህርት እንደማያስፈልግ ትዕዛዝ የተሰጠው በመንግስት ነው፡፡ ስለዚህ በመንግስት ትዕዛዝ የሥራ መደቡ አላስፈላጊ የሆነ በመሆኑ የማስጠንቀቂያና የሥራ ስንብት ክፍያ የምከፍልበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ለአመልካች የሥራ ስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የመክፈል ሀላፊነት የለበትም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ድርጅት የተቀጠሩት ድርጅቱ በዲኘሎማ ትምህርት ለሚያስተምራቸው ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር እንደነበር በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በዲኘሎማ ደረጃ ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ እያስተማሩ በነበሩበት ጊዜ መንግስት በዲኘሎማ ደረጃ ለሚሰጥ ትምህርት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መሰጠት የሌለበት መሆኑን የሚገልፅ መመሪያ ማውጣቱ የሚያከራክር አይደለም፡፡

አመልካች የተቀጠሩበት የሥራ መደብ በዲኘሎማ ደረጃ ትምህርት ለሚሰጡ ተቋማት እንደማያስፈልግና አመልካች ያስተምሩት የነበረው ትምህርት ሊሰጥ እንደማይችል መንግስት መመሪያ ያወጣበት ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበታቸው ከዚህ በኋላ በተቋሙ የሚሠሩት ሥራ የለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበታቸው በራሱ አነሳሽነት አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበታቸው በህግ ሥልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል በተላለፈው መመሪያ መሠረት አመልካች የሚያስተምሩት የእንግሊዝኛ ቋንቋ በዲኘሎማ ደረጃ መሰጠት የሌለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ አስገዳጅ ትዕዛዝ ስለደረሰው ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከአቅሙ በላይ በሆነ ሁኔታ ሥልጣን ባለው አካል በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት በመሆኑ በጉዳዩ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለአመልካች የሥራ ስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ መሠረት ለአመልካች ተሠጥቷት የነበረው ሥራ ሥልጣን ያለው የመንግስት አካል ባወጣው መመሪያ መሠረት አመልካች እየሠራች ለመቀጠል የማትችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የሚሰጠው ሥራ በሌለበት ሁኔታ የሥራ ውሉ እንዲቀጥል የማድረግ ህጋዊ ግዴታ የለበትም፡፡ የሥራ ውሉ በመንግስት በወጣ መመሪያ ተፈፃሚነት ምክንያት የተቋረጠ በመሆኑ አመልካች ማስጠንቀቂያም ሆነ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 60489

ጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አምባዬ ወ/ማሪያም- የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡- የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት - ነገረፈጅ በየነ ቢቂላ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች የስራ መሪ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ከተጠሪ ድርጅት ጋር ባለው የስራ ውልን መሰረት ያደረገ ክርክር ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የአማራ ብሔ/ክል/መንግስት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ አመልካችን ከስራ ያሰናበተው ያለበቂ ምክንያት በህገ-ወጥ መንገድ በመሆኑ የስራ ውሉ ተቋርጦ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ያልተከፈለው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው ይመለስ በማለት ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ ስንብቱ ህገ-ወጥ መሆኑን በማመልከት ክፍያን በተመለከተ ግን ተፈጻሚነት ያለው የፍታሐብሔር ህጉ መሆኑን በመግለጽ የሶስት ወራት ደመወዝ በካሳ መልክ እና የሁለት ወራት ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብቻ ተፈጽሞለት እንዲሰናበት በማለት በመወሰኑ እና የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይሄንኑ ውሳኔ በማጽናቱ የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉዋቸውን ነጥቦች ያነሱ ሲሆን ነሐሴ 24 ቀን 2002 ዓ.ም. በሶስት ገጽ በተጻፈ የቀረበ የቅሬታ ፍሬ-ሃሳብ፡- የአመልካች የስራ ውል በተጠሪ አነሳሽነት በህገ-ወጥ መንገድ የተቋረጠ ስለመሆኑ በሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ ያለውን የድርጅቱን የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ በግልጽ በሚቃረን መልኩ ውሳኔ የሰጡ በመሆኑ የተሰጡት ፍርዶች ተሽረው የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቶልኝ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 59(2) መሰረት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደ ስራ እንድመለስ እንዲወሰንልኝ፣ ይህ አይቻልም የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት ቢኖር ግን በስር ፍርድ ቤቶች በማስረዳት ተያይዞ በቀረበውና በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በስራ ላይ ባለው የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 54(1)(ሀ)፣ 53(3)(ሀ)ና(ለ)፣ እንዲሁም 60(2) መሰረት የስልሳ ቀን ደመወዝ በካሳ መልክ፣ የ12 ወራት ደመወዝ የስራ ስንብት ክፍያ እና የአንድ ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ታዞ ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በሁለት ገጽ በተጻፈ መልስ የሰጠ ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- አመልካች ክስ ሲያቀርቡ የሶስት ወራት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ስራዬ ልመለስ የሚል እንጂ የስራ ስንብት ክፍያ አላቀረቡም፣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያላነሱትን ክርክር በማንሳት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲፈጸሙለት ሊጠይቅ አይገባውም፣ በተጠሪ እና አመልካች መካከል ያለው ክርክር መታየት ያለበት በፍታሐብሔር ህግ እንጂ በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መሆን የለበትም፣ የበላይ እና ገዥ የሆነው ህግ የፍታሐብሔር ህጉ የስራ መሪ ከስራ ሲሰናበት የሚከፈለው ክፍያ የሶስት ወራት ደመወዝ ብቻ ስለመሆኑ እየደነገገ እና ከዚህ በፊት የሰበር ሰሚው ችሎትም የሶስት ወራት ደመወዝ ብቻ የሚገባው ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የመተዳደሪያ ደንቡ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም የሚል ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯቸዋል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ በአመልካች ላይ የተወሰደው የስራ ስንብት እርምጃ ህገ ወጥ ነው ተብሎ ውጤቱን በተመለከተ ግን ተፈጻሚነት የሚኖረው የፍታሐብሔር ህጉ ነው በማለት የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተፈጻሚ ያለመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ የተያዘው ጉዳይ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ እልባት ማግኘት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በሚሰሩት የስራ መሪዎች ላይ ተፈጻሚነት ያለው መተዳደሪያ ደንብ ስለመኖሩ እና አመልካችም የስራ መሪ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ነጥብ አይደለም፡፡ በግራ ቀኙ መካከል ስራ ላይ ያለው ልዩ ህግ እስካለ ድረስ እና ያለው ደንብ ደግሞ ለሞራል እና ለህግ ተቃራኒ ነው ወይም ተፈጻሚነት ሊኖረው የማይገባበትን ህጋዊ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ ተፈጻሚነት የሚኖረው ይሄው ልዩ ህግ በመሆኑ ወደ አጠቃላይ የፍታሐብሔር ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያላቸውን የህግ ማዕቀፍ ፍለጋ የሚኬድበት አግባብ የለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በግራ ቀኙ መካከል ስራ ላይ ያለው መተዳደሪያ ደንብ ተፈጻሚነት ሊኖረው የማይገባ ስለመሆኑ ያቀረበው ህጋዊ ምክንያት በሌለበት፣ ወደ ፍታብሔር ህግ አጠቃላይ ድንጋጌዎች ደግሞ የሚኬደው ለዚህ ጉዳይ የተለየ ህግ በሌለበት ሁኔታ በመሆኑ፣ ከዚህ በፊት ይሄ የሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል በማለት የተነሳውም ቢሆን ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ባለመሆኑ እና ለደንቡ ተፈጻሚ አለመሆን የቀረበ ህጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ በተጠሪ በኩል በደንቡ ተፈጻሚነት ዙሪያ የተነሳው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ነው ብለናል፡፡

አመልካች ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረበውን ቅሬታ በተመለከተ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 59(2) መሰረት በህገ-ወጥ መንገድ ከስራ የተሰናበተው የስራ መሪ ወደ ስራ ለመመለስ መብት እንዳለው በግልጽ የሚያስቀምጥ ቢሆንም ፍርድ ቤቶች በስራው መልካም አካሄድ ላይ የስራ መሪው ወደ ስራው መመለስ ችግር ያስከትላል በማለት ሲያምንበት ለዚሁ ለህገ-ወጥ ስንብት ተገቢነት ያላቸው ክፍያዎች ተፈጽመውለት እንዲሰናበት መወሰንን የሚከለክል አይደለም፡፡ በዚሁ መሰረት የአመልካች ወደ ምድብ ስራው የመመለስ ጥያቄን በተመለከተ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውድቅ አድርገው ማለፋቸውን በውጤት ደረጃ ይሄም ችሎት ተቀብሎታል፡፡ በመቀጠል የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ ተጠሪ እንደሚከራከረው ክስ ሲያቀርብ የሶስት ወራት ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው እንዲመለስ እንጂ የስራ ስንብት ክፍያ አልጠየቀም በሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ክስ ሲያቀርብ ከስራ ተሰናብቶ በሶስተኛ ወሩ መሆኑ የተቋረጠው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው እንዲመለስ ቢሆንም ከላይ እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ የአመልካች ወደ ስራው መመለስ ለስራው መልካም አካሄድ ችግር ሊኖረው ይችላል ብሎ ሲያምን ከዚሁ ከህገ-ወጥ ስንብት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ክፍያዎች ተፈጽመውለት እንዲሰናበት መወሰንን የሚከለክልና ህጉም የመጀመሪያው አማራጭ (ወደ ስራ የመመለስ የዳኝነት ጥያቄ) ተቀባይነት ካጣ ወደ ሁለተኛውና ተያያዥ ክፍያዎች መፈጸም በሚቻል መልኩ የተደነገገ በመሆኑ ተያያዥ ክፍያዎች እንዲፈጸምለት ውሳኔ መስጠት ያልተጠየቀ ዳኝነት ነው የሚባልበት አግባብ የለም፡፡

ተያያዥ ክፍያዎችን በተመለከተ በደርጅቱ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ በዋለው የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 54(1)(ሀ)፣ 53(3)(ሀ)(ለ)፣ እና 60(2) መሰረት በህገ-ወጥ መንገድ ከስራ የተሰናበተ የስራ መሪ የካሳ፣ የስራ ስንብት እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ የሚደነግግ በመሆኑ በዚሁ ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት ክፍያዎች ለአመልካች ሊፈጸሙለት ይገባል ብለናል፡፡ በዚሁ መሰረት የክፍያ መጠኑን ስንመለከት አመልካች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ ሲሰራ የነበረ ስለመሆኑ እና የደመወዝ መጠኑ ደግሞ ብር 1,200 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ) ስለመሆኑ ያከራከረ ነጥብ ባለመሆኑ በዚሁ መሰረት ስሌቱን ሰርተናል፡፡ ከላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ክፍያውን ስናሰላ በደንቡ አንቀጽ 54(1)(ሀ) መሰረት የሁለት(2) ወራት ደመወዝ በካሳ መልክ 1200 x 2= 2,400 ብር (ሁለት ሺህ አራት መቶ ብር)፣ በደንቡ አንቀጽ 53(3)(ሀ)(ለ) መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ የ26 ዓመት አገልግሎት መሰረት በማድረግ ስናሰላ 1,200 + 1/3 X 1,200(26-1)= 11,200 ብር (አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) እና በደንቡ አንቀጽ 60(2) መሰረት ለማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የአንድ ወር ደመወዝ ብር 1,200 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ባጠቃላይ ተጠሪ ለአመልካች ብር 14,800 (አስራ አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር) ሊከፍለው ይገባል ብለናል፡፡

ባጠቃላይ የበታች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ተፈጻሚነት ያለው ህግ በተመለከተ በድርጅቱ ውስጥ በስራ ላይ ያለው የስራ መሪዎች ደንብ ሆኖ እያለ ያለ በቂ ህጋዊ ምክንያት ማለፉ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት የውሳኔ ክፍል በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 51756 ሰኔ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 14504 ጥቅምት 12 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት መታየት ያለበት በተጠሪ ድርጅት በስራ ላይ ባለው የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በህገ-ወጥ መንገድ አመልካችን ከስራ ያሰናበተው በመሆኑ የካሳ፣ የስራ ስንብት እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ባጠቃላይ 14,800 ብር (አስራ አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር) ለአመልካች እንዲከፍል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 67382

ጥር 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1.አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር ነ/ፈጅ ሰላማዊት ጌታቸው ቀረቡ

2. ባዜን የእርሻና ኢንዲስትሪ ልማት ኃ/የተ/የግል ማህበር

ተጠሪዎች ፡- አቶ አርጋው አበበ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ የግል የስራ ክርክር ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን ክርክር በመመልከት ተጠሪ በራሱ ፍቃድ ስራ መልቀቁን ተከትሎ የሚፈጸሙት የስራ ስንብት፣የአመት እረፍት እና ሌሎች ጥቅሞች ወርሃዊ ደመወዝን መሰረት በማድረግ ስለሚከፈሉ እና እንደ ደመወዝ የሚታዩ በመሆናቸው ከተጠሪ ላይ የሚፈለጉ የተለያዩ ዕዳዎች አሉ በማለት ለዕዳው ተብሎ ከስራ ሲሰናበት ሊቀነስበት አይገባም በማለት ውሳኔ በመስጠቱ እና ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.337 መሰረት በማጽናቱ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ ነው፡፡

አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉዋቸውን ነጥቦች በማመልከት ያቀረቡ ሲሆን በቀን 27-7-2003 ዓ.ም በሁለት ገጽ የተጻፈ የቅሬታቸው ፍሬ-ሃሳብ፡- በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 59(1) በግልጽ እንደሚደነግገው በዕዳ ሊያዝ የማይችለው ደመወዝ ብቻ ነው እንዲባልልን፤ አመልካቾች የተጠሪን ዕዳ የቀነሱት እንደፐሮቪደንት ፈንድ፣ የአገልግሎት ክፍያ እና ከመሳሰሉት ጥቅማ ጥቅሞች ላይ በመሆኑ ከተጠሪ ላይ ዕዳው መቀነሱ ተገቢ ነው ተብሎ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በአንድ ገጽ በተጻፈ የጽሁፍ መልስ የሰጡ ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- ያልተወራረደ ሂሳብ አለበት የሚለው አመልካች በመሆኑ፣ በዚህ ድርጅት ውስጥ ከአስር አመት በላይ ስሰራ ምንም ዓይነት ዕዳ የሌለብኝ እና በየወሩ ሙሉ ደመወዜ የሚከፈለኝ በመሆኑ፣ አሁን ስራ በመልቀቄ ምክንያት የአገልግሎት ክፍያ ላለመፈጸም ሒሳቡን እንዳሻቸው ሰርተው ያቀረቡት በመሆኑ፣ዕዳው በትክክል ያለብኝ ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ሳይረጋገጥብኝ አመልካች እንደፈለገው ቀንሶ እንዲሰጥ መደረግ ስለሌለበት በበታች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ እና የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ ተጠሪ አላወራረደም የተባለውን ሒሳብ አመልካቾች ለተጠሪ ከሚከፍሉት ክፍያዎች ላይ መቀነስ አይችሉም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ ጉዳዩ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ስንመረምር የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ተጠሪ ስራውን በገዛ ፍቃዱ ሲለቅ ከሚከፈልለት ክፍያ ላይ ዕዳዎች አሉበት በማለት ሊቀንስበት አይገባውም ወደ ሚለው መደምደሚያ የደረሰው ከስራ በመሰናበቱ ምክንያት ለተጠሪ የሚፈጸሙለት ክፍያዎች ከደመወዝ ጋር የተያያዙ ናቸው በማለት እና የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 59(1) ን በመጥቀስ ስለመሆኑ ከውሳኔው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ደመወዝ ማለት ምን እንደሆነ እና የትኞቹ ክፍያዎች እንደ ደመወዝ የሚቆጠሩ ስለመሆኑ በዚሁ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 53(1) ስር ደመወዝ ማለት አንድ ሰራተኛ በስራ ውሉ መሰረት ለሚያከናውነው ስራ የሚከፈለው መደበኛ ክፍያ ማለት ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ የትርፍ ሰአት ክፍያ፣አበል፣ከአሰሪ የሚከፈል ጉርሻ(ቦነስ)፣ኮሚሽን፣ሌሎች የማትጊያ ክፍያዎች እና ከደንበኞች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያዎች እንደ ደመወዝ የማይታዩ ስለመሆናቸው በዚሁ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 53(2) ስር ተደንግጓል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ አጠቃላይ ንባብ መገንዘብ የሚቻለው ደመወዝ የሚባለው በግራ ቀኙ መካከል ባለው የስራ ውል መሰረት ለተከናወነ ስራ የሚከፈል መደበኛ ክፍያ እንጂ ከዚህ ውጪ ያለውን በተለይም አሁን እያከራከረ ያለውን በስራ ስንብት ምክንያት የሚፈጸሙትን ክፍያዎች የማያጠቃልሉ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ መሰረት የበታች ፍርድ ቤቶች ለተጠሪ በስራ መሰናበቱ ምክንያት የሚፈጸሙለት ክፍያዎች እንደ ደመወዝ ይታያሉ በማለት የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 59(1)ን በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 ምዕራፍ ሶስት ዘርፍ ሁለት ከአንቀጽ 36 እስከ 38 ድረስ ያለውና የስራ ውል ሲቋረጥ ደመወዝ እና ተያያዥነት ያላቸው ክፍያዎች የሚፈጸምበትን አግባብ የሚደነግገው ክፍል ነው፡፡ አንድ የስራ ውል ሲቋረጥ የሰራተኛው ደመወዝ እና ተያያዥ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት ቀናት ውስጥ መከፈል ያለባቸው ስለመሆኑ፣ሆኖም የክፍያው ጊዜ ሊራዘም የሚችለው ከአሰሪዉ የተረከበዉን ንብረት የማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማናቸዉንም ሂሳብ በማወራረድ በራሱ ጥፋት በሆነ ምክንያት ካዘገየዉ ስለመሆኑ በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 36(1) ስር ተደንግጓል፡፡

በተጨማሪም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 37 ስር በክፍያ መጠኑ ላይ አለመግባባት ሲኖር አከራካሪ ያልሆነዉ ክፍያ ሊፈጸም የሚገባ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ግራቀኙ በተጠሪ ላይ አመልካቾች ያልተወራረደ ሒሳብ አለ በማለት በሚከራከሩበት እና ተጠሪ በበኩሉ ምንም ዓይነት ዕዳ የሌለበት እና ራሳቸዉ የፈጠሩት ነዉ በማለት በሚከራከርበት ወቅት የእነዚህ ሁለቱ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ የሚያስገነዝቡት አመልካቾች የተጠሪን ክፍያ ገንዘቡ በእጃቸዉ ስላለ ብቻ ቆርጠዉ ማስቀረት ሳይሆን በፍርድ ቤት አለ የሚሉትን ዕዳ በትክክል ያለበት ስለመሆኑ ማስወሰን የሚገባቸዉ ስለመሆኑ ነዉ፡፡ አመልካቾች ይሄንን ባልፈጸሙበት ሁኔታ እና ግራቀኙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያልተማመኑበትን ዕዳ ለተጠሪ ሊፈጸምለት ከሚገባዉ ክፍያ ላይ ቀንሶ ማስቀረቱ ከላይ የተመለከቱትን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና ተቀባይነት ያለዉ አካሄድ አይደለም ብለናል፡፡

ባጠቃላይ ተጠሪ ከስራ በመሰናበቱ ምክንያት ከሚከፈሉት ክፍያዎች ላይ በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪ የሆነዉን ሒሳብ መሰረት በማድረግ ቀንሶ ክፍያ መፈጸም አግባብነት የሌለዉ ነዉ ብለናል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም በሰጡት ዉሳኔ በስንብት ወቅት የሚፈጸሙት ክፍያዎች እንደደመወዝ ይቆጠራሉ በማለት የሰጡት ምክንያት ተቀባይነት ባይኖረዉም የደረሱበት መደምደሚያ ተቀባይነት ያለዉ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 342 መሰረት ከዉጤት አኳያ ተቀብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተዉን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ ቁ.103360መ/ቢ/ት 26 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 70595 በቀን 17-6-2003ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በተጠሪ እና አመልካቾች መካከል አከራካሪ የሆነን ዕዳ በትክክል ዕዳዉ ስለመኖሩ በፍርድ ቤት ሳይወሰንበት በስንብት ወቅት ከስንብቱ ጋር በተያያዘ ለተጠሪ ከሚፈጸሙለት ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ የሚከፈልበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በቀን 13-8-2003 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 73258

ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ አበራሽ ፈይሳ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ነገት አብዲ - ቀረቡ

3. ወ/ሮ እለፏ አበራ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጂ ሰቭን ንግድና ኢንዲስትሪ ኃ.የተ.የግል ማህበር - ነ/ፈጅ ብርሃኔ አባይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች ላይ በፈጸራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-በተጠሪ ድርጅት መጋቢት 05 ቀን 1983 ዓ.ም በተለያዩ የስራ መደቦች ላይ ተቀጥረው ሲሰሩ ቆይተው በየካቲት ወር 2003 ዓ.ም ስራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ ቢሆንም ተጠሪ የአገልግሎት ክፍያ ሊከፍላቸው ፈቃዳኛ ሊሆን ያለመቻሉን በመግለጽ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈላቸው፣ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ ደግሞ ተገቢውን ክፍያ እንዲፈጽም እንዲሁም ለ3ኛ ተጠሪ ያላግባብ የቆረጠባቸውን የስድስት አመት ከስድስት ወር እረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፍላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች በድርጅቱ ከ20 ዓመታት በላይ ማገልገላቸውን፣3ኛ አመልካችም ከ10 ዓመት በላይ ማገልገላቸውን ገልፆ አመልካቾች በጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 2 ንዑስ ቁጥር 13 እና 14 ድንጋጌዎች መሰረት የጡረታ አበል ተመላሽ ተጠቃሚ ስለሚሆኑ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም፣የታመኑ ክፍያዎች ለአመልካቾች ተሰጥተዋል፣3ኛ አመልካችም የተቆረጠባቸው የአመት እረፍት ፈቃድ የለም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፈጸራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ከማህበራዊ ዋስትና አመልካቾች የጡረታ ተሸፋኝ ለመሆን የሚያበቃ የአገልግሎት ጊዜ እና የእድሜ ጣሪያ ያሟሉ መሆን ያለመሆኑን በሚመለከት ተጣርቶ እንዲቀረብለት ትእዛዝ ሰጥቶ ይኸው አካል አመልካቾች የጡረታ ተሸፋኝ ያለመሆናቸውን ከአረጋገጠለት በሁዋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ለአመልካቾች የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል ይገባል፣ሌሎች የዳኝነት ጥያቄዎች ግን ተቀባይነት የላቸውም በማለት ወስኗል፡ተጠሪ የስራ ስንብት ለአመልካቾች ሊከፍል ይገባል ተብሎ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ባለመስማማት ይግባኙን ለፈጸራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች የጡረታ ተመላሽ ተጠቃሚ ናቸው በሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት የስራ ስንብት አገልግሎት ክፍያ አይገባቸውም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካቾች የተመለሰላቸው ራሳቸው ያዋጡት የጡረታ ገንዘብ ሁኖ እያለ የፌዴራሉ ከፍተኛ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሙሉ የጡረታ መብት ተጠቃሚ እንደሆኑ በመቁጠር የአገልግሎት ክፍያ አይገባቸውም በማለት መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀፅ 2(13)(14) እና አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 39 እና ይህንኑ ድንጋጌ ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀፅ 2(ሸ) ድንጋጌን ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች የጡረታ መዋጮአቸው ተመላሽ የተደረገላቸው በመሆኑ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ አመልካቾች የጡረታ ተመላሽ የሆነውን ገንዘብ ከወሰዱ የስራ ስንብት ክፍያ ሊያገኙ የሚችሉበት ሕጋዊ መሰረት የለም በማለት በጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋለው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከአምስት አመታት በላይ ያገለገሉና ስራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ መሆኑን፣አመልካቾች ለጡረታ መብት የሚያበቃ እድሜና ያገልግሎት ዘመን ላይ ያልደረሱ መሆኑን የሚመለከተው አካል ማረጋገጡንና አመልካቾች ራሳቸው ለጡረታ ያዋጡት 4% መዋጮ ብቻ ተመላሽ የሆነላቸው መሆኑን ነው፡፡

ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያውን መክፈል የለበኝም የሚለው የጡረታ መዋጮ የተመለሰላቸው በመሆኑ በጡረታው ሕግ መሰረት የጡረታ አበል ተጠቃሚነታቸው ተረጋግጧል የሚል የመከራከሪያ ነጥብ በማንሳት ነው፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ያለው ወይም የጡረታ መብት ያለውና በጡረታ ሕግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ እድሜ ደርሶ ከስራ የተገለለ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንደሌለው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 (ማሻሻያ) አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2)(ሰ፣ሸ) ተመልክቶአል፡፡ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥበት የስራ ስንበት ክፍያ የሚፈጸምለት ለአሰሪው አገልግሎት ስለሰጠና ሊቋቋመው የማይችል ድንገተኛ የገንዘብ ችግር እንዳይገጥመው በሚል እሳቤ መሆኑ ይታመናል፡፡ይህ ከሕጉ በስተጀርባ ያለው አስተሳሰብ ወይም ምክንያት ሲሆን በሕጉ እንደተመለከተው ሰራተኛው የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት ካለው ግን የስራ ውሉ ቢቋረጥም፤ ገንዘብ ማግኘቱን ስለሚቀጥል (ስለቀጠለ) የስራ ስንብት ክፍያው አይከፈለውም፡፡የጡረታ አበል ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚነት ካለ የስራ ስንብት የማይከፈለው ከአንድ ምንጭ(አሰሪ) ሁለት ጊዜ ገንዘብ እንዳይከፈል ለመከልከል ታስቦ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች የስራ ውሉን ያቋረጡት በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከአምስት አመታት በላይ ካገለገሉ በኋላ ነው ቢባልም፤በጡረታ ሕጉ መሰረት የጡረታ እድሜና አገልግሎት ዘመን ላይ ስለመድረሳቸውና የጡረታ አበል የሚያገኙ ለመሆኑ ተጠሪ አላስረዳም፡፡ አመልካቾች የስራ ውሉን እንዳቋረጠ የጡረታ አበል ማግኘታቸውን ይቀጥላሉ የሚል ክርክርም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆነ ማስረጃ ከሌለ ደግሞ ለስራ ስንብት መከፈል መሰረት የሆነውን በሕጉ በስተጀርባ ያለውን ምክንያት መሰረት በማድረግ የስራ ስንብቱን ክፍያ ማስከፈል የግድ ይሆናል፡፡ ሕጉ በዚህ መልክ ካልተተረጐመም ሰራተኛውን ለድንገተኛ የገንዘብ ችግር ማጋለጥ ይሆናል፡፡ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 13 እና 14 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ የሚከራከረው አመልካቾች ለጡረታ ያዋጡትን የራሳቸውን 4% ገንዘብ ወስደዋል በማለት ሲሆን አመልካቾችም ይህንኑ አይክዱም፡፡ ስለሆነም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ መሆን በሕጉ አነጋገር የጡረታ መብት ተጠቃሚነትን ያሳያል ወይ? የሚለው ጥያቄ መመለስ ያለበት ነው፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቾች ክሱን ሲመሰርቱ በስራ ላይ በነበረው በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 2(13) ስር አበል የሚለው ቃል የጡረታ መዋጮ ተመላሽንም የሚጨመር መሆኑን፣በአዋጁ አንቀፅ 21 ደግሞ ተመላሽ መዋጮ የሚሰጠው ከአስር አመት ያላነሰ፣ዛያ አመት ያልሞላ አገልግሎት ፈጽሞ በራሱ ፈቃድ ስራውን ከለቀቀ ወይም ከዛያ አመት ያነሰ አገልገሎት ፈጽሞ በአዋጁ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት ከስራ ከተሰናበተ ሰራተኛው የከፈለው አራት በመቶ 4% የጡረታ መዋጮ የሚመለስ መሆኑና በአዋጁ አንቀጽ 2(14) ደግሞ ባለመብት ማለት በአዋጁ መሰረት አበል የሚቀበል ወይም አበል ለመቀበል የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሰራተኛ ወይም ተተኪ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ይህ ድንጋጌ መታየት ያለበት ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀፅ 2(1(ሸ)) ይዘት፣መንፈስ እና ዓላማ ጋር ተጣጥሞ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 2(13 እና 14) እና 21 ድንጋጌዎች የተቀመጠውን ድንጋጌ አንድ ላይ ስንመለከተው የጡረታ መዋጮ የሚመለሰው የሰራተኛው ድርሻ ብቻ ነው፡፡የአሰሪው መዋጮ የማይከፈል መሆኑን ድንጋጌዎቹ በግልፅ ያሳያሉ፡፡ እንዲህ ከሆነ ሁለት ጊዜ ከአሰሪው ኪስ ገንዘብ ወጥቷል ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ እንዲሁም ሰራተኛው ለአሰሪው ባበረከተው አስተዋጽኦ ምክንያትና የስራ ስንብት የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን (Social Security Scheme) ተብሎ ከሚታሰብበት አግባብ አንፃር ሲታይ አመልካቾች ከተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ የማያገኙበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጡረታ አበል ተጠቃሚነት የሚለውን ሐረግ ብቻ ይዞ የአዋጁን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ዓላማ ጋር ባግባቡ ሳይመረምር አመልካቾች የስራ ስንብት ክፍያ አይገባቸውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11287 መስከረም 5 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአሰሪ ዘንድ ከአምስት አመታት በላይ አገልግሎ በራሱ ፈቃድ ስራውን የለቀቀ ሰራተኛ እድሜውና የአገልገሎት ዘመኑ የጡረታ መብት ተጠቃሚ የማያደርገው እስከሆነ ድረስ ራሱ ያዋጣውን መዋጮ ተመላሽ ሁኖለታል በሚል ምክንያት የስራ ስንብት አይከፈልም ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 64257 ሰኔ 28 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር በግራ ቀኙ የወጣውን ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- አቶ ምትኩ ኃይሉ ጠበቃ ለገሰ ማሞ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ መስፍን ጥላሁን የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው እና በስራ ላይ የደረሰን ጉዳት ካሳ መሰረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔ/ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ላልተወሰነ ጊዜ በእንጨት መሰንጠቂያ ማሽኒስትነት በወር ብር 750 /ሰባት መቶ ሀምሳ ብር/ እየተከፈለኝ በማገልገል ላይ እያለሁ በጥር 08 ቀን 2002 ዓ.ም የማሽኑ መጋዘን በግራ እጅ ላይ ባደረሰው የመቆረጥ አደጋ ሶስት ጣቶቼ ተቆርጠው ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብኛል፡፡ በዚህ የተነሳ ከዚህ በኋላ ስራ ላይ ተሰማርቼ ስራ መስራት እንዳልችል አድርጎኛል፡፡ በመሆኑም በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 109/1/ መሰረት ለደረሰብኝ ጉዳት ካሳ እና የህክምና ወጪ እንዲከፈለኝ በማለት ባጠቃላይ ብር 45,000 /አርባ አምስተ ሺህ ብር/ እንዲከፍለኝ በማለት ነው፡፡ የቀረበው ክስ ለተከሳሽ ደርሶት መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ባቀረበው መልስ አመልካች በድርጅቱ ውስጥ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ሠ/መሰረት የስራ መብዛት በሚኖርበት ጊዜ ስራው እስኪያልቅ ድረስ ብቻ ለመስራት የተዋዋለ በመሆኑ፣አመልካች ከተጠሪ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌላ ስራ ተቋራጭ ጋርም የሚሰራ በመሆኑ፣የጉዳት መጠኑንም የሚያሳይ ነገር ያላቀረበ በመሆኑ፣አመልካች ጉዳት የደረሰበት አዕምሮውን በሚገባ መቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ሰክሮ በስራ ላይ በመገኘት በመሆኑ በራሱ ላይ ሆነ ብሎ እንዳደረሰ ስለሚቆጠር፣በወቅቱ ከሳሽ ወደ ድርጅቱ ሲመጣ ሰክሮ ስለነበር ወደ ስራ እንዳይገባ በአሰሪው ጭምር ትዕዛዝ ቢሰጠውም እምቢተኛ በመሆን በመስራት ላይ እንዳለ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ፣ኃላፊነት የሌለብኝ ቢሆንም እንኳ በሰብአዊነት የህክምና ወጪውን የሸፈንኩ በመሆኑ፣ከዚያም በመዳን ወደ ስራው ተመልሶ ስራውን ሲሰራ ቆይቶ የማሽን ካፖስተሮችን በመለወጡ በፈጸመው ጥፋት ምክንያት ከስራ የተሰናበተ በመሆኑ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት እና ማስረጃ በመቀበል ከሳሽ በስራ ገበታው ላይ የተገኘው በስካር መንፈስ ስለመሆኑ እና በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ መስራት እንደሌለበት የተላለፈለትን የስራ ኃላፊውን ትዕዛዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመተላለፍ በመስራት ላይ እንዳለ የደረሰበት ጉዳት በመሆኑ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ተብሎ የማይወሰድ በመሆኑ የቀረበው የካሳ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የበታች ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348/1/ መሰረት አጽንቶታል፡፡ ሆኖም የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበለትን ቅሬታ በመቀበል የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት በግራ ቀኙ መካከል የስራ ውል ስለመኖሩ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ ያረጋገጠው ነጥብ ባለመኖሩ፣ስራው ደግሞ የአደገኝነት ጠባይ ያለው በመሆኑ እና በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2088/1/ መሰረት የኃላፊነት ደንቦችን በመጥቀስ አመልካች ከኃላፊነት ሊድን ስለማይችል የደረሰውን ጉዳት የመክስ ኃላፊነት አለበት በማለት የካሳ መጠኑን በርትህ 20,000 ብር/ሀያ ሺህ ብር/ እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ቀደም ሲል ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ በዚህ ጉዳይ አመልካች ኃላፊ ነው የመባሉን አግባብነት ከአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 96/ሀ/እና/ለ/ አኳያ ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ተመልክቶ እልባት መስጠት ተገቢነት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በመጀመሪያ ደረጃ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ያነሳውን ነጥብ በተመለከተ የአሁን ተጠሪ ራሱ ክሱን ሲያቀርብ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ስለመሆኑ እና በወር የሚያገኘውን የደመወዝ መጠን በማመልከት በመሆኑ ተጠሪ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ስለመሆኑ አከራካሪ ባልሆነበት ሁኔታ እና ተጠሪም ራሱ ክሱን ሲያቀርብ አመላክቶ ያቀረበውን ነጥብ ፍርድ ቤቱ በራሱ ማንሳቱ እና ሰራተኛ ስለመሆኑ አመልካች አላረጋገጠም ወደ የሚለው መደምደሚያ መድረሱ አግባብነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በግራ ቀኙ መካከል የተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ሰራተኛ መሆን አከራካሪ ባልሆነበት ሁኔታ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት በራሱ በማንሳት ሰራተኛ አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ መድረሱ ተቀባይነት ያለው ድምዳሜ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ-ነገሮች ስንመለከት ተጠሪ በስራ ላይ ደረሰ የተባለው ጉዳት በደረሰበት ዕለት ጠዋት ወደ ስራ ከገባ በኋላ፣የስራ ኃላፊው ለሌላ ስራ ሲወጣ ተከትሎ እንደወጣ እና የስራ ኃላፊው ተመልሶ ሲመጣ ተጠሪም ተከትሎት እንደመጣ፣በዚህን ወቅት ተጠሪ በስካር ውስጥ እንደነበር ወይም ይንገዳገድ እና የመጠጥ ጠረንም እንደነበረዉ፣ከዚህ የተነሳ አመልካች እንዳትሰራ በማለት አስጠንቅቆት እንደነበር፣ሆኖም አመልካች ለስራ ሲወጣ አስፈቅዳለሁ በማለት ለመደወል በሚል የሞባይል ስልክ በመያዝ እንደወጣ፣ተመልሶም አሰሪው ፈቅዶልኛል በማለት እምቢተኛ በመሆኑ መስራት እንደጀመረ፣ስራውን መስራት ከጀመረ ብዙም ሳይቆይ አደጋው እንደተከሰተ፣ከአደጋውም በኋላ አመልካች ወደ ተለያዩ የህክምና ቦታዎች የወሰደው እና በመዳንም ስራ የጀመረ ስለመሆኑ፣ ሆኖም ስራውን ከጀመረ በኋላ አንዲቀይር የተሰጠውን የማሽን ካፖስተሮችን በማጥፋቱ በፈጸመው ጥፋት ከስራ የተሰናበተ ስለመሆኑ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ የተረጋገጡትን ፍሬ-ነገሮች ይዘን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት በእርግጥ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 96/1/ን ስንመለከት አንድ አሰሪ በስራ ላይ በሰራተኛው ለሚደርስ ጉዳት ለመካስ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ ሆነ ብሎ በራሱ ላይ ላደረሰው ማንኛውም ጉዳት አሰሪው ኃላፊነት እንደሌለበት፣በተለይም አሰሪው አስቀድሞ በግል የሰጡትን የደኅንነት መጠበቂያ መመሪያዎች በመጣስ ወይም የአደጋ መከላለከያ ደንቦችን በመጣስ ወይም አካሉን ወይም አዕምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሰክሮ በስራ ላይ በመገኘቱ የደረሰ ጉዳት በሰራተኛው ሆን ተብሎ የደረሰ ተደርጎ ስለሚወሰድ አሰሪው ለመካስ ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 96/ሀ//ለ/ ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ተጠሪ ጉዳት በደረሰበት ቀን ሰክሮ በስራው ላይ የተገኘ ስለመሆኑ፣እንዳይሰራ ተብሎ በስራ ኃላፊውም የተሰጠውን መመሪያ በመጣስ በእምቢተኝነት ወደ ስራ በመግባት ስራ የጀመረ ስለመሆኑ እና በወቅቱም ይንገዳገድ የነበረ ስለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የደረሰው ጉዳት በስራ ላይ እንደደረሰ ተቆጥሮ ለደረሰው ጉዳት አሰሪው/አመልካች/ ኃላፊነት የለበትም በማለት በክልሉ የመጀ/ደረጃ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ አያሳይም፡፡ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም ግራቀኙ ያልተካካዱበትን እና ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ስለመሆኑ ተጠሪ ራሱ ባልካደበት ሁኔታ ሰራተኛ መሆኑ አልተረጋገጠም በሚል፣በግራቀኙ መካከል ተፈጻሚነት ያለው የህግ የአሰሪና ሰራተኛ ስለመሆኑም በላከራከረበት ሁኔታ የፍተሐብሔር ህግ ድንጋጌ በመጥቀስ እና የአመልካች ድርጅት ስራ የአደገኝነት ባሕርይ ያለው ነው በማለት አመልካች ኃላፊነት አለበት ወደ ሚለው መደምደሚያ መድረሱ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ባጠቃላይ በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ያለመሆኑ ከተረጋገጡት ፍሬ-ነገሮች እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ሆኖ እያለ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች ሰጥተውት የነበረውን ውሳኔ በመሻር አመልካች ኃላፊነት አለበት በማለት መወሰኑ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተዉን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝ/ብሔ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.51342 በቀን 22-7-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ ቁ.08825 በቀን 25-1-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የሀዋሳ ከተማ የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 00347 በቀን 15-11-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. በአሁን ተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ባለመሆኑ አመልካች የደረሰውን ጉዳት ለመካስ ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 73881

የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን ሠርክብርሃን ተክሌ ቀረበ

ተጠሪ፡- አቶ ተፈራ ሹና የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተነሳውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በይርጋ አለም ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ያኔ ከሣሽ የነበረው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ ስላቋረጠብኝ ውዝፍ ደመወዜን በመክፈል ወደስራዬ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳው ነጥብ ተጠሪ ወደ ስራ ልመለስ በማለት ያቀረቡት ክስ በሶስት ወር ይርጋ የሚታገድ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የስራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው ተጠሪ ተመድበው በሚሰሩበት በይርጋዓለም ዲስትሪክት በለኩ ቅርንጫፍ ጣቢያ በተለያዩ ጊዜያት በእዳ ምክንያት ተቆርጦ ከተመለሰ ቆጣሪ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ወደ ድርጅቱ መግባት የሚያስፈልገውን ክፍያ ለእራሱ አውሎ ከሕጉ ውጪ በሆነ መንገድ ከአስራ ሶስት በላይ የሆነ ቆጣሪ ለመግጠም በዲስፕሊን ጉድለት በሪጅኑ የዲስፕሊን ኮሚቴ አጣርቶ በሕብረት ስምምነትና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ))እና((መ)) ነው በማለት ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ለስራ የታገዱት በስራ ላይ ባጠፉት ጥፋት ነው ፣ ይህ ጥፋትም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ))((መ)) መሰረት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ነው በማለት የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ መሰረት ነው ሲል ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን ፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በይርጋዓለም ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ የአስር ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደ ስራው ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በስራ ላይ እያሉ የአመልካችን ድርጅት ጥቅም ለግል ጥቅማቸው ማውላቸውና ማጭበርበራቸው በዲስፕሊን ኮሜቴ ተረጋግጦ እያለ ይኸው ማስረጃ በቂ አይደለም ተብሎ ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው። አቤቱታው ተመርምሮም የዲሲፕሊን ኮሜቴ ውሳኔ በቂ አይደለም ተብሎ ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት የፅሑፍ መልስ የዲስፕሊን ኮሜቴ የዳኝነት ሥልጣን የሌለው አካል በመሆኑ ውሳኔው ውድቅ መደረጉ ባግባቡ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል። አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ከአላቸው ውሳኔዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረናል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክስ የመሰረቱት ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ከሕግ ውጪ ተቋርጧል በሚል ሲሆን አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ በስራ ላይ በፈፀሙት የማጭበርበርና የእምነት ማጉደል ድርጊት ምክንያት መሆኑን ገልፆ መከራከሩንና ግራ ቀኙ ወገኖች ክርክራቸውን ይደግፉልናል የሚሏቸውን ማስረጃዎችን ማቅረባቸውን ፣ የተጠሪ ምስክሮች ቃል የስራ ውሉ ከሕጉ ውጪ መቋረጡን ለማስረዳት የማይችል መሆኑ በሁለቱም ፍርድ ቤቶች ስምምነት ያገኘ ነጥብ መሆኑን ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች የተለያዩበት ነጥብ የአመልካች መስሪያ ቤት የሪጅን ዲስፕሊን ኮሜቴ ውሳኔ በማስረጃነት ስላላው ተቀባይት ላይ መሆኑን ነው። አመልካች በዲሲፕሊን ኮሜቴው የተሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በስራ ላይ የማጭበርበርና የእምነት ማጉደል ድርጊት መፈፃማቸውን እንደሚያስረዳ ገልፆ ይኸው የዲስፕሊን ኮሜቴ ውሳኔ የአመልካችን ክርክር የሚደግፍ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያሳይ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዲሲፕሊን ኮሜቴው ውሳኔ የተጠሪን የማጭበርበር ወይም የእምነት ማጉደል ድርጊት ለማስረዳት በቂ አይደለም በማለት ውድቅ ያደረገው የኮሚቴው ውሳኔ በገልለተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ አይደለም ፣ በኮሜቴው ፊት የተሰሙት ምስክሮችም በፍርድ ቤት ያልተሰሙ በመሆኑ የኮሜቴው ውሳኔ ተጠሪ የአመልካችን ጥቅም ለራሳቸው ጥቅም ማዋላቸውን ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈፀማቸውን አያሳይም በሚል ምክንያት ነው። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የኮሚቴው ውሳኔ በቂ አይደለም ተብሎ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ ነው የተቋረጠው በማለት ውሳኔ የመሰጠቱን አግባብነት ለመመርመር ነው። በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ተጠሪን ከስራ እንዲሰናበት ያደረገው ተመድበው በሚሰሩበት የይርጋዓለም ዲስትሪክት ለኩ ንዑስ ጣቢያ በተለያዩ ወቅቶች በእዳ ምክንያት ተቆርጠው ተመላሽ የተደረጉትን የኤሌክትሪክ ፍጆታ ቆጣሪዎችን ለአመልካች መግባት የነበረበት ክፍያ ለግል ጥቅሙ በማዋሉ በሕገ ወጥ መንገድ ከአስራ ሶስት የፍጆታ ቆጣሪዎች በላይ በመግጠም በአመልካች ድርጅት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰዋል በማለት ሲሆን ይህ የተጠሪ አድራጎት ስለመኖሩ የዲሲፕሊን ኮሜቴው ጉዳዩን አጣርቶ በፍሬ ነገር ረገድ አረጋግጧል። አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ይህን መሰረት በማድረግ እንደሆነም አላከራከረም። በአሰሪና ሰራተኛ መካከል ተመስርቶ የነበረውን የስራ ውል ስለሚቋረጥባቸው ሕጋዊያን ምክንያቶች በሚመለከት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 በዝርዝር ተመልክቶአል። በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት ያለው የአዋጁ አንቀጽ 27 ሲሆን፣ ይህም ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚቋረጥባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር አስቀምጦአል፡፡ ተጠሪ በአሰሪው (በአመልካች) ጥቅም ላይ በማጭበርበር ድርጊት ጉዳት ማድረሱ የዲሲፕሊን ኮሜቴ ውሳኔ በሰነድ ማስረጃነት ቀርቦ ተረጋግጧል፡፡ በዲሲፕሊን ኪሜቴ የተሰጠ ውሳኔ በስራ ክርክር ችሎት ለሚቀርብ ክርክር በዲስፕሊን ኮሚቴ ፊት ቀርበው የመሰከሩት ምስክሮች የስራ ክርክር በሚሰማው አካል ወይም ፍርድ ቤት ፊት ቀርበው ካልተሰሙ የእነዚህን ምስክሮች ቃል መሰረት በማድረግ የተሰጠ የዲስፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ በስራ ክርክር ጉዳይ የሰራተኛውን ጥፋት ለማስረዳት ለማስረጃነት ሊቀርብ አይገባም የሚባልበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ ለማስረጃነት ሊቀርብ የሚገባ ሲሆን ይኸው የሰነድ ማስረጃ በተጠሪ ማስረጃ ያልተስተባበለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የኮሚቴው ውሳኔ ተጠሪ በስራ ላይ የማጭበርበርና በአመልካች ላይ ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን የሚያረጋግጥ በመሆኑና እነዚህ ድርጊቶች ደግሞ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ከሚያቋርጡ ምክንያቶች መካከል እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) እና((መ)) ስር ተመልክተዋል፡፡ እንግዲህ ሕጉ ይህን ያሕል ግልጽ ከሆነ ከዚህ በተቃራኒ መወሰን የሚቻልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ሲጠቃለል የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተቃራኒው መወሰኑ ውሳኔው በማስረጃ አቀባበል ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23119 ጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27(1(ሐ)እና((መ)) በመሆኑ በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡ ስለዚህም የይርጋዓለም መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው በማለት በመ/ቁ. 00612 ሰኔ 09 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው የውሳኔ ክፍል በውጤት ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 50590

መጋቢት 28 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ተስፋዬ ምንዳገኝ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ በርገኔ ኢንኮ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የተወሰደ የጡረታ አበል /ገንዘብ/ ይመለስልኝ በማለት አመልካች በመሠረተው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪን የከሰሰው በጡረታ መለያ ቁጥር ወ/407216 ተመዝግቦ ከጥቅምት 1 ቀን 83 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ የጡረታ አበል ሲቀበል የቆየ ሲሆን፣ በተከሰሰበት ወንጀል በመጋቢት 23 ቀን 1995 ዓ.ም የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ተፈርዶበታል፡፡ ስለዚህ የጽኑ እስራት ቅጣት ከተወሰነበት በኋላ ከሕጉ ውጪ የወሰደው ገንዘብ /ብር 7,892.27/ ከነወለዱ ይመልስ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ የጡረታ አበሉን በኃይል አልተቀበልኩም፡፡ በወንጀል ከተፈረደብኝ በኋላ ገንዘቡን የወሰድኩት ከፋዮቹ እኔ ጋ እየመጡ ስለሰጡኝ በመሆኑ የምመልስበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የሁለቱን ወገኖች ክርክር የመረመረ ሲሆን፣ በመቀጠልም ተጠሪ በወንጀል ተከሶ ከተፈረደበት በኋላ በሥራ ላይ ያለው የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ.345/95 ተጠሪ የወሰደውን ገንዘብ ለማስመለስም ሆነ ለወደፊቱ እንዳይከፈለው ለማድረግ የሚያስችል አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ውድቅ አድርጎአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ኅዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም በዓፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ የተደረገው በአዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 52/1/ የተቀመጠውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ስለመሆን አለመሆኑ ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ከተሰጠው ውሳኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ በተከሰበበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው እና የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት በመጋቢት 23 ቀን 1995 ዓ.ም ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ቅጣቱም የእድሜ ልክ ፅኑ እሥራት እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ አመልካች ክስ የመሰረተው ሦስት ዓመት እና ከዚያ በላይ ፅኑ የእሥራት ቅጣት የተወሰነበት ተጧሪ የጡረታ መብቱን ያጣ ዘንድ በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁ.5/1967 አንቀጽ 34 ተደንግጓል የሚል መነሻ ምክንያት በመያዝ ነው፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው ተጠሪ በወንጀል ተከሶ ቅጣቱ በተወሰነበት ጊዜ ሥራ ላይ የነበረው የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ.345/1995 ሥራ ላይ ያለ አይደለም፡፡ ተፈፃሚነት የሌለው እና ተከሣሽ የተቀበለውን ገንዘብ ለማስመለስም ሆነ ለወደፊቱም እንዳይከፈለው ለማገድ የሚችልም አዋጅ አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

በበኩላችን እንዳየነው ለክርክሩ አወሳሰን በቅደም ተከተል ሊታዩ የሚገባቸው አዋጆች አዋጅ ቁ.5/1967 እና አዋጅ ቁ.345/1995 ናቸው፡፡ የመጀመሪያው "የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁ.5/1967 ዓ.ም" በሚል የወጣው ሲሆን፣ ተጧሪ የነበረ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ መብቱ የሚያጣበትን ሁኔታ በአንቀጽ 34 ደንግጎአል፡፡ ይህ አንቀጽ "የወንጀል ቅጣት" የሚል ርእስ ያለው ሁኖ ይዘቱም፡- "አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ጡረተኛ ተከሶ ጥፋተኛ መሆኑ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ሲረጋገጥና ቢያንስ የሦስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ሲወሰንበት የጡረታ መብቱን ያጣል፡፡ ወይም በመከፈል ላይ ያለውን የጡረታ አበል ይቀርበታል፡፡" የሚል ነው፡፡ ይህ አዋጅ የወጣው ቀደም ሲል የወጣውን አዋጅ ቁ.209/55 `ን' ለማሻሻል ሲሆን በዚህ መልክ የተሻሻለው አዋጅ /ቁ.ቁ.209/55/ ደግሞ ከሰኔ 1 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ በዋለው "የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ.345/1995" ተሽሮአል /ተተክቶአል/፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ምክንያት ሲታይም የቀድሞውን አዋጅ በሻረው አዲሱ አዋጅ ተጧሪ የነበረ የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መብቱን ስለሚያጣበት ሁኔታ በሚመለከት በግልጽ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም የሚል መነሻ እንዳለው መገመቱ አያስቸግርም፡፡

እንደሚታየው የቀድሞዎቹ አዋጆች ማለትም ቁ.5/67ም ሆነ ቁ.209/55 በአዋጅ ቁ.345/95 ሙሉ በሙሉ እስከተተኩ ድረስ ለተያዘው ክርክር አወሳሰን በዋቢነት ሊጠቀሱ አይችሉም፡፡ በሌላ በኩል ግን እነሱን የተካው አዲሱ አዋጅ ለክርክሩ አወሳሰን ስላለው አግባብነት በሚመለከት ሊፈተሹ የሚገባቸው ድንጋጌዎችን ስለመያዝ አለመያዙ መመልከት ተገቢ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በብዙ አዋጆች እንደሚታየው አዋጅ ቁ.345/95 'ም' የመሸጋገሪያ ድንጋጌ አለው፡፡ ይህም በአንቀጽ 52 የተቀመጠውን ሲሆን፣ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት ለተፈጠሩ ሕጋዊ ሁኔታዎች ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ሕጎችና መመሪያዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በንዑስ አንቀጽ/1/ ባስቀመጠው ድንጋጌ አመልክቷል፡፡ ቀጥለው ያሉት ንኡስ አንቀጽ /2/ እና /3/ም በተመሣሣይ ሁኔታ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት የነበሩ አሰራሮች እንደሚቀጥሉ ያመለክታሉ፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በአዋጅ ቁ.5/1967 አንቀጽ 34 የተቀመጠው የጡረታ መብት የሚታጣበት አግባብ በአዋጅ ቁ.345/95 በግልጽ አልተሻረም፡፡ ይልቁንም በአዋጁ የተፈጠሩ ሕጋዊ ሁኔታዎችም ሆኑ ሲሰራባቸው የነበሩ ሕጎችና መመሪያዎች በነበሩበት ሁኔታ ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ነው የኋለኛው አዋጅ /ቁ.345/95/ በግልጽ ያመለከተው፡፡ በወንጀል ተከሶ ሦስት ዓመት ጽኑ የእሥራት ቅጣት የተወሰነበት ተጧሪ የጡረታ መብቱን እንዲያጣ እየተደረገ እንደቆየ ግልጽ ነው፡፡ የአዋጁ አስፈፃሚ የሆነው የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ /አመልካች/ ሥራውን ሲሠራ የቆየው የአፈፃፀም መመሪያ እያወጣ እንደሆነም ማሰቡ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው እና በእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ የተወሰነበት አዋጅ ቁ.345/95 ሥራ ላይ ባለበት መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የጡረታ መብቱን እንዲያጣ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ሊደርሱ የቻሉት ሥራ ላይ የነበረው አዋጅ ቁ.345/95 በአንቀጽ 52 ያስቀመጠውን ድንጋጌ ባለመመርመራቸው እና በአግባቡ ባለመተርጎማቸው ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታው የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የወላይታ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 11964 ሰኔ 22 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 30909 መስከረም 27 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ የጡረታ መብቱን ካጣ በኋላ የወሰደው ገንዘብ ብር 7,892.27 /ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከሃያ ሰባት ሣንቲም/ ለአመልካች ይመልስ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካች፡- ሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃ.የተ.የግል ማህበር - ነ/ፈጅ ወርቆ ምራጭ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- አቶ ሰይፉ ተፈሪ - በሌለበት የሚታይ ነው

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በሚገዛው ግንኙነት ውስጥ ሰራተኛው ስራውን ከመልቀቁ በፊት የወሰደውን ብድር ሳይመልስ ስራውን በገዛ ፈቃዱ ሲለቅ አሰሪው ለሰራተኛው ሊከፍለው ከሚገባው የፕሮቪደንት ፈንድ ገንዘብ ቀንሶ ለማስቀረት የሚችልበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ሲሰሩ ከቆዩ በሁዋላ በገዛ ፈቃዳቸው ስራቸውን መልቀቃቸውን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ከዘረዘራቸው የክፍያ ዓይነቶች አንዱ የፕሮቪደንት ፈንድ ሲሆን አመልካች ለዚሁ ለተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በሰጠው መከላከያ መልስ ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆኑን ሳይክድ ለተጠሪ ብር 9,000 /ዘጠኝ ሺህ/ መስጠቱን፣ ቀሪውን በተመለከተ ግን አመልካች ለተጠሪ ብድር አበድሮት እንደነበረና ብድሩን ሙሉ በሙሉ ባለመክፈሉ በመካከላቸው ባለው ስምምነት መሰረት ያስቀረው መሆኑን ጠቅሶ ልከፍለው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ ብር 9,000 መውሰዳቸውንና ከአመልካች በብድር የወሰዱት ገንዘብ መኖሩን ያለመካዳቸው ተረጋግጧል በማለት አመልካች ከተጠሪ ለእዳ መክፈያነት ያስቀረውን የፕሮቪደንት ፈንድ ቀሪ ለመክፈል ሊገደድ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፕሮቪደንት ፈንድ ከደመወዝ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ካላቸው ክፍያዎች አንዱ መሆኑን ገልጾና ያለተጠሪ ስምምነት ደግሞ አሰሪ የሆነው አመልካች ለእዳ መክፈያነት የፕሮቪደንት ፈንድ ቆርጦ ለማስቀረት የማይችል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 59/1/ ስር የተመለከተ መሆኑን በዋቢነት ጠቅሶ አመልካች ቀሪ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ብር 11,000.00 /አስራ አንድ ሺህ ብር/ ለተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይክፈላቸው በማለት የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በድርጅቱ ሕብረት ስምምነትና በብድር ፖሊሲ መሰረት የወሰዱትን ብድር ሳይከፍሉ ስራውን በገዛ ፍቃዳቸው ከመልቀቃቸውም በላይ ብድሩ መኖሩንና ስምምነት መኖሩንም ሳይክዱ አመልካች ከፕሮቪደንት ፈንድ ቆርጦ እዳውን ማስቀረት አይችልም ተብሎ መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 59 ድንጋጌን ይዘት፣ የግራ ቀኙን ክርክርና የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በድርጅቱ የብድር ፖሊሲ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ተፅእኖ በአግባቡ ባላገናዘበ መልኩ ነው በማለት ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ከስራ ስንብቱ በፊት የነበረበትን እዳ ከፕሮቪደንት ፈንድ ላይ ሊቆረጥ/ሊቀነስ/ አይገባውም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ ከተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱትን የስራ ውል ግንኙነት ያቋረጡት በገዛ ፈቃዳቸው መሆኑን፣ የስራ ውሉ ከመቋረጡ በፊት ደግሞ በሰራተኝነታቸው ከአሰሪው በተሰጣቸው መብት መሰረት ብድር ወስደው ብድሩን እንደተጠቀሙና እዳውን ሙሉ በሙሉ ሳይከፍሉ የስራ ስንብት ጥያቄን ያቀረቡ መሆኑን፣ ብድሩ ያለባቸው መሆኑንም ደግሞ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ያመኑ መሆኑ መረጋገጡን እንዲሁም የብድሩ መሰረትም በአሰሪው ድርጅት ውስጥ ያለው የሕብረት ስምምነት እና የብድር ፖሊሲ መሆኑ አከራካሪ ያለመሆኑን ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው የአሁኑ ተጠሪ ዕዳ የለብኝም በሚል ያቀረበው ክርክር የለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የታለፈ ስለሆነ አመልካች እዳው የተጠሪ መሆን ያለመሆኑን ሌላ ክስ እንዲመሰረት የሚጠበቅበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 59/1/ በሕብረት ስምምነት በተወሰነው መሠረት ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ መቀነስ እንደሚቻል የሚያስረዳ ሲሆን የፕሮቪደንት ፈንድ ከደመወዝ ጋር ጥብቅ ቁርኝነት ያለው የክፍያ ዓይነት ነው ቢባል እንኳ ተጠሪ እዳ ያለባቸው ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት ባልካዱት ሁኔታ ሌላ ግልጽ ስምምነት የሚያስፈልግበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት የወሰዱትን የብድር ገንዘብ ሳይመልሱ በገዛ ፈቃዳቸው ስራቸውን በለቀቁበትና እዳው መኖሩንም በስራ ክርክር ችሎት ባመኑበት ሁኔታ እዳውን ከፕሮቪደንት ፈንድ ቆርጦ ለማስቀረት ሌላ ግልጽ የሆነ ስምምነት ያስፈልግ ነበር ተብሎ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ከድንጋጌው መንፈስ እና ይዘትጋር ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ሳይመልሱ ስራውን በገዛ ፈቃዳቸው በለቀቁበትና እዳውም የሚመለከታቸው መሆኑን በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር በአመኑት ሁኔታ ከፕሮቪደንት ፈንድ እዳውን ቀንሶ ለማስቀረት ግልጽ ስምምነት የለም ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 59/1/ ስር የተመለከተውን የድንጋጌውን መንፈስ ከአመልካች ድርጅት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕብረት ስምምነት እና የብድር ፖሊሲ ጋር ባለገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 107857 በ06/11/200 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 57350 በ19/08/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. አመልካች ከተጠሪው ፕሮቪደንት ፈንድ በፅዳው ምክንያት ቀንሶ የወሰደውን ገንዘብ ሊመልስ አይገባም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ለተካሄደው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪያቸውን በየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ.ቁ.74400

ግንቦት 7 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ግዮን ኢንዱስትሪያልና ኮሜርሺያል ኃ/የተ/የግል ማህበር-ነ/ፈጅ ያሬድ ወርቅዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሉ ናርዬ ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ኪዳኔ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሚስተናገደውን የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ግንኙነት ውል ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት ስለመኖሩ ሳይክድ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ ሲያሽከረክሩ በነበሩት በአመልካች ድርጅት ንብረት ላይ በግጭት ጉዳት ያደረሱ በመሆኑ ነው በማለት ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን በመመርመር ተጠሪ ጉዳት አድርሷል በማለት አመልካች የሚከራከረው የአመልካች ድርጅት እህት ኩባንያ የሆነው የግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር ንብረት በሆነው ተሽከርካሪ ላይ መሆኑ መረጋገጡን፣ ተጠሪ የስራ ቅጥር ውል የፈፀሙት ከአመልካች ጋር እስከሆነ ድረስ የአመልካች ድርጅትና የግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር ባለቤት አንድ መሆን ድርጅቶቹ የራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው እስከሆነ ድረስ በአመልካች ድርጅት ንብረት ላይ ተጠሪ ጉዳት አድርሰዋል ለማለት የማያስችል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የአመልካች እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት ደምድሞ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ከእህት ኩባንያው ለስራ ተከራይቶ ሲጠቀም በነበረው ተሽከርካሪ ተጠሪ ጉዳት ያደረሱ ሁኖ እያለ ኩባንያዎቹ የተለያየ የሕግ ሰውነት ያላቸው ናቸው በማለት ስንብቱን ሕገወጥ ነው በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪን የቀጠረውና ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ የአመልካች ድርጅት ሆኖ እያለ በአመልካች ድርጅት የደረሰ ጉዳት የለም ተብሎ ስንብቱ ሕገወጥ ነው የተለያዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክፍያዎች ለተጠሪ ይፈጸሙ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት የተጠሪ ቀጣሪ ፣ ተጠሪ ጉዳት አደረሰ የተባለበት ተሽከርካሪ ደግሞ የአመልካች ድርጅት ባለቤት የሆኑት ግለሰብ ባለቤት የሆኑበት ሁኖ ጉዳቱ ደረሰ በተባለበት ጊዜ አመልካች ድርጅት ተሽከርካሪውን ለራሱ ጥቅም በመገልገል ላይ በነበረበት ሁኔታ ተጠሪ ግጭት ያደረሱ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የህግ ሰውነት ያለው ሲሆን በዚህ ሕጋዊ ችሎታ የመከሰስም ሆነ የመክሰስ ችሎታ ይኖረዋል፡፡ አንድ የተፈጥሮ ሰው ከአንድ በላይ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበሮች ባለቤት ሁኖ መገኘት በአንዱ ድርጅት ውስጥ ያለ ሰራተኛ በሌላኛው እህት ድርጅቱ ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉደት በሌላኛው ድርጅት ውስጥ በሕጉ አግባብ የተቀጠረውን ሰራተኛ በድርጅቱ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰሃል በማለት የስራ ውሉን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ሸ/ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚስችለው ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ሸ/ መሠረት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ አሰሪው ሊያቋርጥ የሚችለው ሰራተኛው በአሰሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረሱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ከያዛቸው ቁም ነገሮች ውስጥ “የአሰሪው ንብረት” እና “ከድርጅቱ ስራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት” የሚሉት ሐረጎች ይገኙበታል፡፡ ስለዚህ ጉዳት ደርሷል ለማለት መሟላት ካለባቸው ነገሮች አንዱ ንብረቱ የአሰሪው መሆኑና በቀጥታ ከድርጅቱ ስራ ጋር የሚገናኝ መሆኑ ነው፡፡ አሰሪ ማለት ደግሞ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 4 በተመለከተው መሠረት ቀጥሮ የሚያሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ስለመሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ አንቀፅ 2/1/ ስር ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ተፈጥሯል ሊባል የሚችለው የስራ ወሉ በአዋጁ አንቀጽ 4 መሠረት ሲመሰረት መሆኑንና በዚህ አግባብ የስራ ውሉ መመስረቱ ከተረጋገጠ የስራ ውል ግንኙነት በሕጉ አግባብ የሚገዛው ይህንኑ ውል በመሰረቱት ሰዎች መካከል ብቻ ይሆናል፡፡ የስራ ውል ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈፃሚ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት መመስረቱ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ተጠሪን ማሰናበቱን ሕጋዊ ነው በማለት የሚከራከረው የግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር የሆነ መኪና ላይ በግጭት ምክንያት ጉዳት አድርሰዋል በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ ከዚህ የተሸከርካሪው ባለቤት ከሆነው ድርጅት ጋር የፈፀሙት የቅጥር ውል የሌለ ሲሆን ተሽከርካሪውን አመልካች ለስራ ምክንያት ተኮናትሮ ሲጠቀምበት የነበረ ወይም ንብረቱ ከድርጅቱ ስራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የነበረው ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ድርጅት ተጠሪ በሌላ ድርጅት ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተመሰረተውን የስራ ግንኙነት ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማቋረጥ የሚስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የስራ ውሉን ከአመልካች ጋር መመስረታቸውንና ጉዳት ደርሶበታል የተባለው ተሽከርካሪም የአመልካች ድርጅት ባለቤት የሆኑት ግለሰብ የሆኑበት ግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር መሆኑን በማረጋገጥ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 2/1/ ፣ 4 እና 27/1/ሸ/ እና በንግድ ሕጉ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማህበራት ስላላቸው ሕጋዊ ችሎታን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 55719 የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 107754 ጥቅምት 16 ቀን 2004 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ ሕገወጥ ነው ተብሎ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 05 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሳሳካዋ ግሎባል 2000 ፕሮጀክት ነ/ፈጅ ባልቻ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሽዋድንበር ደቻሳ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ተከሳሽ ከህግ ውጪ የስራ ውሌን ስላቋረጠብኝ የተለያዩ ክፍያዎችን በድምሩ ብር 93,288.338 እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪው በበኩሉ ባቀረበው የመ/ደ/መቃወሚያ ተከሳሽ ድርጅት ለትርፍ ያልተቋቋመ በመሆኑ ክሱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 3(2) (መ) መሰረት ውድቅ ሊሆን ይገባል ብሏል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 (2) መሰረት የተከሳሽ ተቃውሞ ተቀባይነት ያለው ነው በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ በመልስ ሰጪና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል የተፈጸመው ውል አንቀጽ 3(5) እንደሚገልጸው ድርጅቱ ለትርፍ ያልተቋቋመ ቢሆንም ባለሙያዎችን ሲያሰራ የቅጥር ውል የሚፈጽመው በኢትዮጵያ ህግ መሰረት እንደሆነ በውሉ በግልጽ ተጠቅሷል እንደመልስ ሰጪ ያሉ ድርጅቶች የሚመሩበትን ደንብ የሚንስትሮች ም/ቤት እስካላወጣ ድረስ ደግሞ ሰራተኞቹ የሚተዳደሩት በአዋጁ መሰረት ይሆናል፡፡ በመልስ ሰጪውና ይግባኝ ባይ መካከል በተመሰረተው የቅጥር ውል መነሻ ይግባኝ ባይ ደመወዝ እየከፈለ ሲያሰራ መቆየቱ የታመነ ሲሆን በዚሁ የቅጥር ውል መሰረት ለይግባኝ ባይ መፈጸም የሚገባውን ግዴታ አለመፈጸሙ ተገቢነት የለውም በሚል የወረዳውን ፍርድ ቤት ትእዛዝ በመሻር በፍሬ ነገሩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/343 (1) መሰረት የመለሰው ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎትም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለውም በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁኑ አመልካችም በከፍተኛውና በክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- ሲጠቃለል አመልካች ድርጅት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር እ.ኤ.አ ዲሴንበር 2008 በተፈረመ ስምምነት የተቋቋመ ሲሆን በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 2 (3)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት ለትርፍ ያልተቋቋመ ፕሮጀክት በመሆኑ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 3(2) (መ) መሰረት በዚህ አዋጅ ሊከለስ አይገባም በሚል ያቀረብነውን መቃወሚያ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ባለመቀበል ከተከራከርንበት ጭብጥ በመውጣት ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3(3)(ለ) መሰረት መርምሮ ያቀረብነውን የመ/ደ/መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ማጽናቱ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች በአዋጁ ልዳኝ አይገባም ይበል እንጂ ክልከላው በሚንስትሮች ም/ቤት በሚወጣው ደንብ ሽፋን ስለማግኘቱ ያስረዳው ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ አዋጅ መሰረት ሊከሰስ የማይችልበት ምክንያት ስለሌለው አቤቱታው የህግ መሰረት ያለው አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአመልካች ድርጅት ለትርፍ ያልተቋቋመ በመሆኑ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ስር የሚሸፈን አይደለም በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ ከፍተኛው ፍርድ ቤትና ሰበር ሰሚው ችሎት ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪው ከአመልካች ድርጅት ጋር በተደረገው የቅጥር ስራ ውል መነሻ በአመልካች ድርጅት እየሰራ መቆየቱን ገልጾ የሚከራከር ሲሆን አመልካች ድርጅትም በመካከላቸው የቅጥር ስራ ውል የለም ሲል ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ሆኖም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው ድርጅቱ ለትርፍ ያልተቋቋመ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የለውም በሚል ነው፡፡ ለዚሁ ክርክር በማስረጃነት በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው የጽሁፍ ሰነድም በአመልካችና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል በ2000 ዓ/ም የተፈረመውን የተሻሻለውን የመግባቢያ ሰነድ(Memorandum of Understanding) ነው፡፡ በዚሁ በተሻሻለው የመግባቢያ ሰነድ አንቀጽ 3 (5) ደግሞ ድርጅቱ የአገር ውስጥ ሳይንቲስቶችን፣የሰብል ምርት ልዩ ባለሙያዎችን፣ ቴክኒሽያኖችን፣የፅህፈት እና አስተዳደራዊ እንዲሁም የኦፕሬሽን ድጋፍ ሰጪ ፐርሶኔሎችን በኢትዮጵያ መንግስት አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት የምደባና የቅጥር ሁኔታዎችን እና ገደቦችን እንደሚያስቀምጥ ተመልክቷል፡፡ የመግባቢያው ሰነድ በዚሁ መልክ ከተቀመጠና በአመልካችና በተጠሪው መካከል የስራ ቅጥር ውል መደረጉ በአመልካች እስከታመነ ድረስ ለትርፍ ያልተቋቋመ የውጪ ድርጅት ቢሆንም ለጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ አዋጁ ተፈጻሚነት ሊኖረው የማይችለው በአዋጁ አንቀጽ 3(3) የተደነገገው ልዩ ሁኔታ ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ይሄውም እንደአመልካች ያሉ ድርጅቶችን በተመለከተ አዋጁ ተፈጻሚነት አይኖረውም በሚል የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ያወጣ ከሆነ ወይም ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የተወሰነ ከሆነ ነው፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ እንደአመልካች ያሉ ድርጅቶችን በሚመለከት የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ካለመኖሩም ሌላ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችም እንደ አመልካች ያሉ ድርጀቶች በሀገር ውስጥ የሚቀጥሩአቸውን ሰራተኞች በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈጻሚነት የለውም በሚል በግልጽ የተደረገ ስምምነት የለም፡፡ እንዲያውም በዚህ በሚያከራክረው ጉዳይ የስራ ቅጥር በኢትዮጵያ ህግ መሰረት ይደረጋል በሚል በስር ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበው የመግባቢያው ሰነድ ላይ መስፈሩ አዋጁ ተፈጻሚነት ያለው ስለመሆኑ የሚረጋግጥ ነው፡፡

በመሆም ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ህጋዊ ምክንያቶች የተነሳ የስር ከፍተኛ እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ድርጅት የተቋቋመው ለትርፍ ባለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈጻሚነት የለውም ሲል ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ክርክር እንዲደረግ ክርክሩን ወደ ወረዳ ፍርድ ቤት መመለሳቸው ተቀባይነት ያለው ስለሆነ በውሳኔያቸው ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/26939 በቀን 27/07/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/129113 በቀን 11/08/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348 (1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. ለተያዘው ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አግባብነት አለው ተብሎ ጉዳዩ በዚሁ አዋጅ መሰረት እንዲታይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተወሰነው ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፊጅ ማህሌት ዓለሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1.አቶ ክፍለዩሐንስ ተሰማ
2.አቶ ታምራት ተሰማ } ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሰራተኛው ጉዳት ካሳ በመድን ፖሊሲ ተሸፍኖ ሲገኝ ካሳውን ሊጠይቁ የሚችሉትን ወገኖችን ማንነት አተረጓጐም የሚመለከት ነው፡፡የተጠሪዎች ወንድም አቶ ተገኔ ተሰማ በወንጂ ስኳር ፋብሪካ ተቀጥረው በስራ ላይ እያሉ ሕይወታቸው በማለፉ አሰሪው የሆነው የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ብር 20,286.60 (ሃያ ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር ከስልሳ ሳንቲም)፣የአሁኑ አመልካች ደግሞ በስራ ላይ ለሚደረስ የሰራተኛ ጉዳት ካሳ በመድን ፖሊሲው በገባው ግዴታ መሰረት ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) ለመክፍል የመድን ፖሊሲ ሽፋን መሰጠቱን ገልጸው ይኸው ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡በአሰሪነቱ የተከሰሰው የወንጂ ስኳር ፋብሪካም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 107 መሰረት ካሳውን ለማግኘት የማይችሉ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ እንዲሆንለት የጠየቀ ሲሆን በአማራጭም የአሁኑ አመልካች ለሰራተኞች የጉዳት ካሳ የመድን ፖሊሲ ሽፋን የሰጠ መሆኑን ገልፆ ወደ ክርክሩ እንዲገባለት ጠይቋል፡፡ በዚህም መሰረት የአሁኑ አመልካች ወደ ክርክር እንዲገባ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በሰጠው መልስ ወደክርክሩ ሊገባ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑንና ተጠሪዎች ካሳውን ለመጠየቅ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአሁኑን አመልካችና የስር ተከሳሽ የሆነውን የወንጂ ስኳር ፋብሪካን ለክሱ ሃላፊ አድርጎ አመልካች ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺኅ)፣አሰሪ የሆነው ፋብሪካው ደግሞ ብር 20,286.60 (ሃያ ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር ከስልሳ ሳንቲም) እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡በዚኅ ውሳኔ አመልካችና የወንጂ ስኳር ፋብሪካው ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስኳር ፋብሪካውን ካሳውን ከመክፈል ነፃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲያደርገው የአሁኑን አመልካች ግን ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት የሰበር አቤቱታውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገበት አግባብ ስነ ስርዓቱን የተከተለ ያለመሆኑንና ተጠሪዎች የጉዳት ካሳውን ሊከፈላቸው ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔም በአመልካችና በወንጂ ስኳር ፋብሪካ መካከል የተደረገውን የሰራተኞች የጉዳት ካሳ የመድን ፖሊሲውን ይዘትና መንፈስ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 107፣110 እና 134(2) ድንጋጌዎች ጋር ያላገናዘበ መሆኑን የሚገልፅ ሁኖ አመልካች ለተጠሪዎች የጉዳት ካሳውን ሊከፍል አይገባም ተብሎ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ ካሳው ለሟች ሕጋዊ ወራሾች እንደሚከፈል የሕብረት ስምምነቱም በግልፅ የሚሳይ መሆኑን ጠቅሰው በመድን ፖሊሲው ብር 150,000.00 ለሰራተኛ መሞት እንደሚከፈል በተገለጸው መሰረት ተጠሪዎች የሟች ህጋዊ ወራሾች መሆናቸው ስለተረጋገጠ የማይከፈልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካች የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው አመልካች ለወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሰራተኞች በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የጉዳት ካሳ ለመክፈል በመድን ፖሊሲው መሰረት ግዴታ መግባቱ በድርጅቱ ወንጂ ስኳር ፋብሪካና ሰራተኞች መካከል የተደረገውን የህብረት ስምምነት መሰረት በማድረግ የሚመጣውን የሰራተኞች የጉዳት ካሳ ኃላፊነት ጭምር ያጠቃልላል? ወይስ አያጠቃልልም? የሚለውን ጭብጥ ለመፍታት ተብሎ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በክርክሩ ሂደት የተጠሪዎች ወንድም የሆኑት አቶ ተገኔ ተሰማ በስራ ላይ እንዳሉ ሕይወታቸው ማለፉም ሆነ የአሁኑ አመልካች በስራ ላይ ለሚደርስ የሞት ጉዳት እስከ ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ድረስ የመድን ሽፋን መስጠቱ ያላከራከሩ ነጥቦች መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰራተኛ በሥራ ላይ በሞት የተለዩ ስለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የሞት ጉዳት ካሣ ለጥገኞች ስለሚከፍልበት ሁኔታ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 110 ስር በዝርዝር የተመለከተ ጉዳይ ነው፡፡በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 110/1/ የተመለከተው ሊከፈል የሚገባው የክፍያ ዓይነት ሲሆን ከዚህ ውስጥ አንዱ ለጥገኞች የሚከፈል ካሣ ነው፡፡ለጥገኞች የሚከፈል ካሣ መጠን እና ጥገኞች የሚባሉት እነማን እንደሆኑ ድንጋጌው በቀጣይ ንኡስ አንቀጾች በዝርዝር አስፍሯል፡፡ የሟች ጥገኞች ብሎ ሕጉ የዘረዘራቸው የሟች ልጆች ሆነው 18 ዓመት በታች የሆኑ፣የሟች ሕጋዊ ባል ወይም ሚስት እና በሟች ሰራተኛ ድጋፍ ይረዱ የነበሩ የሟች ወላጆች መሆናቸውን አንቀጽ 110/2/ በመዘርዘር ከዚኅ ውጪ ያሉት ወገኖች የሟች ጥገኞች ያለመሆናቸውን በሚያስገነዝብ መልኩ ሕጉ መቀረፁን የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት ለሚቀርበው የሞት ጉዳት ካሳ ጥያቄ ሊያቀርቡ የሚችሉ ወገኖችን ማንነት ሕጉ ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን አሁን ለክርክሩ መሰረት የሆነው የሞት ጉዳት ካሳ ጥያቄ መሰረት አድርጓል በማለት ተጠሪዎች የሚከራከሩትም ይኸው ድንጋጌ በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መልክ የተቀረፀ መሆኑን መከራከሪያ ሳያቀርቡ ለጥያቄው ሕጋዊ መሰረት ነው በማለት የሚጠቅሱት የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 134(2) ድንጋጌን ነው።ይኸውም የሕብረት ስምምነቱ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የተሻለ መብት የሚሰጥ ከሆነ በዚሁ መሰረት የሰራተኛው መብት ሊጠበቅለት ይገባል፣ሚች ተቀጥረው ይሰሩበት የነበረው ድርጅት ህብረት ስምምነት ሰራተኛው በስራ ላይ እያለ ከሞተ የጉዳት ካሳው ለሕጋዊ ወራሾች ይተላለፋል በማለት አስቀምጧል የሚሉትን ምክንያቶችን በማንሳት ነው።

በእርግጥ የህብረት ስምምነት ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ሕግ የተሻለ ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ ይኸው ስምምነት ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 134(2) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል። የህብረት ስምምነት ማናቸውም የስራ ግንኙነቶችና የስራ ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች እንዲሁም አሰሪዎችና ማህበሮቻቸው ከሰራተኞች ማህበራት ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ሊሸፈን እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 128 ስር በግልፅ የሰፈረ ሲሆን ይህ ባአጠቃላይ እንደተጠበቀ ሁኖ የህብረት ስምምነት ይዘት በዚሁ አዋጅ ወይም በሌሎች ሕጎች ለሕብረት ስምምነት የተተዉ ጉዳዮች ስለሚወሰኑበት፣የሰራተኛ የሙያ ድህንነትና ጤንነት ስለሚጠበቅበት ሁኔታዎች፣ እንዲሁም የማህበራዊ አገልግሎቶች ስለሚስፋፉበት፣ስለሰራተኞች ተሳትፎ፣በተለይም በእድገት፣በደመወዝ፣በዝውውር፣በቅነሳ እና በዲሲፕሊን አፈጻጸም ስለሚኖራቸው ተሳትፎ፣ስለ ስራ ሁኔታ፣ ስለስራ ደንብና ስለቅሬታ አቀራረብ ስነ ሥርዓት፣ስለስራ ሰዓት ድልደላና በስራ መካከል ስለሚሰጥ እረፍት እና የሕብረት ስምምነት ስለሚሸፍናቸው ወገኖች ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ መያዝ እንደሚችል በአንቀፅ 129 ተዘርዝሯል።ከዚኅም በተጨማሪ የህብረት ስምምነት ልዩ ሁኔታዎች ሊባሉ በሚችሉትና በአዋጁ አንቀጽ 133 ስር በተዘረዘሩት ምክንያቶች እንዴት መፈፀም እንደአለበት ተጠቃሹ ሕግ ያሳያል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ለጉዳዩ አግባብነት አለው የተባለው የህብረት ስምምነት ስለተፈፃሚነት ወሰኑ በአንቀፅ 2 ስር የደነገገ ሲሆን ህብረት ስምምነቱ በድርጅቱ የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ከታቀፉት የስራ መሪዎች በስተቀር በቋሚ፣ ቁርጥና በወርሃዊ/ሲዝናል ሰራተኞች ላይ ተፈፃሚነት እንደሚሆን በተጠቃሹ ድንጋጌ ቁጥር አንድ ስር የተቀመጠ ሲሆን የህብረት ስምምነቱ ስለህብረት ስምምነቱ አተረጓጎምና ያልተጠቀሱ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚገዛ ድንጋጌም በአንቀፅ 4 ስር በግልጽ አስፍሯል። በዚህም መሰረት የሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 4(1) ድንጋጌ በህብረት ስምምነቱ ውስጥ ባሉት ድንጋጌዎች የአተረጓጎም ወይም ግልጽ ያልሆነ/ያልተጠበቁ ጉዳዮች ላይ ድርጅቱና የሰራተኛው ማህበር በውይይት መፍትሔ እንደሚፈልጉ፣ጉዳዩ በውይይት የማይፈታ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 እና ቀደም ሲል በተሻሻሉትና ወደፊትም በሚወጡት ማሻሻያ አዋጆች መሰረት እንደሚፈፀም ያስቀምጣል።እንግዲህ በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው እና ትርጉም የሚያስፈልገው ሁኖ የተገኘው ነጥብ በህብረት ስምምነቱ በአንቀጽ 40(1) ስር ስለጉዳት ካሳ ተጠቃሚዎች በሚመለከት የተቀመጠው ድንጋጌ በስራ አደጋ ለሚመጣ ኢንሹራንሽ/የመድን ዋስትና የአካል ጉድለትና ጉዳት ካሳ ተጠቃሚ የሚሆኑት የሰራተኛው ሕጋዊ ወራሾች ስለመሆናቸው ተገልፆ ከተቀመጠው ድንጋጌ ውስጥ ሕጋዊ ወራሾች የሚለው ሐረግ የትርጉም አድማሱ በውርስ ሕግ የሚታወቁትን በሕጋዊ ወራሽነት የሚታወቁትን ነው ወይስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 110 ስር የተዘረዘሩትን ብቻ ነው የሚመለከተው ለሚለው ጥያቄ የሕብረት ስምምነቱ ግልጽ የሆነ ምላሽ አይሰጥም።ይሁን እንጂ በህብረት ስምምነቱ ትርጉም ሲያስፈልግ በምን አግባብ ሊተረጎም እንደሚችል በአንቀፅ 4(1) የተመለከተ ሲሆን ትርጉሙ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 እና ቀደም ሲል በተሻሻሉትና ወደፊትም በሚወጡት ማሻሻያ አዋጆች መሰረት እንደሚፈፀም የተመለከተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ በህብረት ስምምነቱ ሕጋዊ ወራሾች የሚለው ሐረግ የሚያመላክተው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 110 ስር የተመለከቱትን የተጎጂ ሰራተኛ ጥገኞችን ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ሕጉ መዘርዝሩን ከላይ ተመልክተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 110 ስር ከተዘረዘሩት ውጪ ያሉትና በውርስ ሕጉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 842 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት ሕጋዊ ወራሾች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በስራ አደጋ ለሚመጣ ኢንሹራንስ/የመድን ዋስትና የአካል ጉድለትና ጉዳት ካሳ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ሕጋዊ አግባብ አይኖርም፡፡

አመልካችና ተጠሪ በአደረጉት የመድን ዋስትና ፖሊሲ ስር በስራ ላይ ለሚደርሱ የሞት፣ለአካል ጉዳት፣በስራ ላይ ለሚከሰት በሽታ ጉዳቶች በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የጉዳት ካሳ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ የተመለከተ ሲሆን በፖሊሲው".....if at any time the period of insurance any worker in the insured's immediate service engaged in a category of work described in the Schedule shall sustain death or bodily injury by accident or occupational disease occurring at the place assigned to him for work or arising from his work and during the time of his work by the insured in the Business and if the insured shall be liable to pay compensation for such death, bodily injury, or occupational disease under Ethiopian law,....." በሚል ከተቀመጠው አረፍተ ነገርም መገንዘብ የሚቻለው መድን ሽፋኑ በስራ ላይ ለሚደርሱ የሞት፣ለአካል ጉዳት፣በስራ ላይ ለሚከሰት በሽታ ጉዳቶች በሚገዛው የኢትዮጵያ አሰሪና ሰራተኛ ሕግ መሰረት የሚታይ መሆኑን ግራ ቀኙ ስምምነት የደረሱ መሆኑን ነው፡፡ ይህ አተረጓጎም ተዋዋይ ወገኖች በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ጉዳዩ ይታያል ብለው ሲስማሙ ሐሳባቸው ምን ነበር? የሚለውን የውል አተረጓጎም ደንብን በመከተልም የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በመሰረቱ በውል ውስጥ የተጠቀሱት ቃላትና ድንጋጌዎች ግልጽ ባልሆኑ ጊዜ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1732፣1735-1738 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር በሰፈሩት ደንቦች መሰረት መተርጎም የተፈቀደ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ደንቦች በፍ/ሕ/ቁጥር 1734፣1735 እና 1736 ሲሆኑ የተዋዋዮች፣ ሐሳብ፣ በውሉ ላይ የኢትዮጵያ ሕግ በሚለው የተቀመጠው ጠቅላላ አነጋገር በመድን ፖሊሲው ስር የተዘረዘሩት የጉዳት አይነቶችን እርስ በርሳቸው በማስተሳሰር በመድን ፖሊሲው የኢትዮጵያ ሕግ የሚለውን ሐረግ ለማስቀመጥ የፈለጉበት ሁኔታ ሐሣባቸውን ምን እንደነበር ለማወቅ መሞከር እና የውሎችን ቃሎች አንዱን ከአንዱ ጋር እያዛመዱ በመመልከት ለውሉ ጉዳይ አግባብነት ያለውን ትርጉም በመስጠት አዎንታዊ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም አንፃር የተያዘው ጉዳይ ሲታይ በመድን ፖሊሲው ስር የጉዳቶቹ አይነቶች መዘርዘራቸውና በኢትዮጵያ ሕግ አግባብ ተብሎ መቀመጡ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የሚገዛ መሆኑን በመፈለግ ውሉን ያደረጉ መሆኑን የሚያስገነዝበን ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 377/1996 ስለመሆኑ የግራ ቀኙ ፍላጎት ነበር ከተባለ ደግሞ ተጠሪዎች በአዋጁ አንቀጽ 110(2) ድንጋጌ አገላለፅ መሰረት የወንድማቸው የሞት ጉዳት ካሳ በውርስ ህጉ ሕጋዊ ወራሽ ነን፣የሕብረት ስምምነቱም የተሻለ ተጠቃሚነትን የሚሰጥ ነው በሚል የሞት ጉዳት ካሳውን የሚጠይቁበትና የሚያገኙበት ሕጋዊ መሰረት የለም፡፡ለአንድ ሰው የመብት ጥያቄ መሰረቱ ውል ወይም ሕግ ሲሆን ተጠሪዎች የሞት ጉዳት ካሳውን ለመጠየቅ ከሕጉም ሆነ ከውል የመነጨ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች ክስ መመስረታቸውም ሆነ የስር ፍርድ ቤቶች የሞት ጉዳት ካሳ ለተጠሪዎች ይገባል በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መወሰናቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) ስር የተመለከተውን መመዘኛ እና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 110፣128፣129፣134 እና በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 2 እና 4 እንዲሁም 40(1) ስር ያሉን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ከውል ሕግ አተረጓጎም ደንቦችና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌ አንፃር ያላገናዘቡ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 49598 ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ.ም ለተጠሪዎች የሞት ጉዳት ካሳ ሊከፈል ይገባል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል፣ይህንኑ ውሳኔ ክፍል በማፅናት በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11906 ነሐሴ 13 ቀን 2003 ዓ.ም፣በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 132326 በ30/12/2003 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ሟች ወንድማቸው አቶ ተገኔ ተሰማ በስራ ላይ ለደረሰባቸው የሞት አደጋ የሚቹ አሰሪ በገባው መድን ውል መሰረት የጉዳት ካሳ የሚገባቸው ሰዎች አይደሉም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሃሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በሰጠው ትርጉምና ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

1. የመጀመሪያው የልዩነቱ ምክንያት አብላጫው ድምፅ በንግድ ህጉ ስለ ኢንሹራንስ በተደነገገው ክፍል ግልፅ የሆነ መልስ የተሰጣቸውን ነጥቦች የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች ሣያገናዝብ፣ የህብረት ስምምነቱን፣ አመልካች የሰጠውን የኢንሹራንስ ፖሊሲና አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 101 ድንጋጌዎች ብቻ በመመርመር ትርጉም መስጠቱና መወሰኑ ተገቢነት የለውም የሚል ሀሳብ ስላለኝ ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪዎች በዚህ መዝገብ የሚከራከሩበትን ጉዳይ ለመወሰን ከላይ የተጠቀሱትን ሰነዶችና አዋጅ ቁጥር 377/96 መመርመር ብቻ በቂ አይደለም፡፡ አከራካሪውን ጭብጥ ለመወሰን በአገራችን የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እንዲቋቋሙ በህግ የተፈቀደበትን መሰረታዊ ዓላማ፣ አመልካች እንዲሰጥ ስለተፈቀደለት የኢንሹራንስ ሽፋን አይነትና ባህሪ እንደዚሁም አመልካች በሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን በህግ ተጠቃሚ የመሆን መብት ስላላቸው ሰዎች የሚደነግጉ የህግ ማዕቀፎችን መመርመር ያስፈልጋል የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 የተዘረዘረውን መስፈርት በማሟላት የተቋቋመ የኢንሹራንስ ኩባንያ ነው፡፡ አመልካች የሚሰጣቸው የኢንሹራንስ ሽፋኖች አንደኛው የረዥም ጊዜ የመድን ሥራ ነው፡፡ የረዥም ጊዜ የመድን ሥራ የሚባሉት፣ የሕይወት መድን ሥራ፣ በየጊዜው ገንዘብ የመክፈል ግዴታ፣ የጡረታ መድን፣ ቋሚ የጤና መድን ሥራ፣ እንዲሁም ከመድን ሰጭው በተዛመደ ሁኔታ በሰው አካል ላይ የሚደርስ አደጋ መድንና የህመም መድን የሚያካትት ስለመሆኑ በአዋጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 16 የተደነገገ ሲሆን የሕይወት መድን በንግድ ህጉ አንቀጽ 691 የተሰጠው ትርጉም የሚኖረው መሆኑን በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 15 ይደነግጋል፡፡

አመልካች ለተጠሪዎች ወንድም አቶ ተገኔ ተሰማ የሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን በሥራ ላይ ለሚደርስ ህመም፣ ዘላቂ የአካል ጉዳትና ለህይወት ኢንሹራንስ መሆኑን ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም አመልካች የሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን በንግድ ህጉ አንቀጽ 654 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው የኢንሹራንስ አይነትና የራሱ የሆነ ልዩ ባህሪ ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ የተጠሪዎች ወንድም አሰሪ የሆነው ወንጂ ስኳር ፋብሪካ የተጠሪዎች ወንድም አቶ ተገኔ ተሰማ በስራ ላይ በሚደርስበት ጉዳት ህመም ካጋጠመው ወይም ቋሚ የአካል ጉዳት ከደረሰበት፣ የወንጂ ስኳር ሰራተኛ የሆነው የተጠሪዎች ወንድም እንዲጠቀምበት፣ ሰራተኛው በሥራ ላይ በሚደርስበት ጉዳት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የኢንሹራንስ ፖሊሲው ተጠቃሚ ለሚሆኑ ሰዎች የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡ እንደሚከፈል ታሳቢ በማድረግ ከአመልካች ጋር የተዋዋለ መሆኑን የኢንሹራንስ ፖሊሲውና የህብረት ስምምነቱ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ወንጂ ስኳር ፋብሪካ በህብረት ስምምነት ከገባው ግዴታ፣ (ከውል የመነጨ) በመነሳት የተጠሪዎች ወንድም አሰሪ፣ የተጠሪዎች ወንድም በስራ ላይ ለሚደርስበት ህመምና የአካል ጉዳት ወይም በስራ ላይ ለሚያጋጥመው የሞት አደጋ አመልካች ለተጠቃሚው ወይም ለተጠቃሚዎቹ የኢንሹራንስ ገንዘብ እንደሚከፍል በማሰብ በንግድ ህግ ቁጥር 661 በገባው ውል መሰረት ለአመልካች ፕሪሚየም ሲከፍልና የበኩሉን ግዴታ ሲወጣ ቆይቷል፡፡

የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ከአመልካች ጋር ያደረገው የህይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚዎች የሠራተኛው ወራሾች እንደሆኑ በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገ ሲሆን የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ከአመልካች ጋር የኢንሹራንስ ውል የተዋዋለው ይህንን በህብረት ስምምነቱ የገባውን የውል ግዴታ ለመወጣት መሆኑ አያከራክርም፡፡ ይህ ከሆነ የተጠሪዎች ወንድም በሥራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ሲሞት አመልካች የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን ለማን መክፈል ይገባዋል የሚለውን ጥያቄ ለመወሰን፣ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መመልከት የሚጠይቅ ነው፡፡ በወንጂ ስኳር ፋብሪካ እና በአመልካች መካከል የተደረገው የህይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚዎች እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ በንግድ ህጉ አንቀጽ 702 እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 705 የተደነገገ ሲሆን በተለይ የኢንሹራንስ ፖሊሲው በንግድ ህግ ቁጥር 695 የተደነገጉትን ዝርዝር ጉዳዮች ባልያዘ ጊዜና ክርክር የሚያነሱ የሟች ባል ወይም ሚስት ወይም ልጆች የሌሉት በሆነ ጊዜ፣ የኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ የሚሆኑት የሟች ወራሾች መሆናቸው የንግድ ህግ ቁጥር 705 "ተጠቃሚው ተለይቶ ያልታወቀ እንደሆነ፣ ወይም ተሸሮ እንደሆነ ወይም በህይወት የሌለ በመሆኑ ውድቅ የሆነ እንደሆነ ስለሞት የተደረገው ኢንሹራንስ ዋናው ገንዘብ የሚከፈለው ኢንሹራንሱን ለተዋዋለው ሰው ውርስ ነው " በማለት በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ወንጂ ስኳር ፋብሪካ የተጠሪዎች ወንድም በሥራ ላይ በሞት ሲለይ የኢንሹራንሱ ተጠቃሚዎች የሟች ወራሾች እንደሚሆኑ የተገለፀው ሀሳብ በንግድ ህጉ አንቀጽ 701 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) የሟች ባል ወይም ሚስት፣ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 827 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በንግድ ህግ ቁጥር 705 መሰረት የሟችን ልጆች ወይም ሌሎች ወራሾች ተጠቃሚ እንደሆኑ የሚያደርግና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 110 አደጋው በደረሰ ጊዜ በህይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ የሚሆኑትን ሰዎች በሟች ጥገኞች ላይ የተወሰነ እንዳይሆን የሚያደርግ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠው የመድን ድርጅት በአገሪቱ ህግ የህይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ መሆናቸው የተረጋገጠላቸውን የሟች ወራሾች (ወንድሞች) ወንጂ ስኳር ፋብሪካ ለሰራተኛው በገባው የኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያቀርቡት ክርክር የኢንሹራንስ ስራ የንግድ ሥራ ብቻ ሣይሆን በአንድ አደጋ የሚደርስ ጉዳትን የመጋራትና ማህበራዊ ግልጋሎት የመስጠት ሥራ መሆኑን ያላገናዘበ ክርክር ነው፡፡ አመልካች ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ ጋር የመድን ውል ሲዋዋል፣ ውሉ ስለ ህይወት በሚደረግ የኢንሹራንስ ውል በኢትዮጵያ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች የሚያመጣበትን ኃላፊነት እያወቀ ነው፡፡ አመልካች በአገሪቱ ውስጥ የመድን ንግድ ስራ የሚሰራበት ልዩ ፈቃድ የተሰጠውም አሰሪው የመድን ውል የገባበት የሞት አደጋ የሚያደርስ ጉዳት በሰራተኛው ላይ በደረሰ ጊዜ፣ በአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 15 እና በንግድ ህጉ ድንጋጌዎች ለህይወት ኢንሹራንስ የሚከፈለውን ክፍያ ለኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚዎች በመክፈል ግዴታውንና ኃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣል በሚል ዕምነት ነው፡፡ አመልካች በህግ የተጣለበትን ኃላፊነት ለማስቀረት ወይም በቻለው አጋጣሚ ሁሉ ኃላፊነቱ እንዲጠብቅለት የሚያቀርበው ክርክርም አመልካች ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ ጋር ለተጠሪዎች ወንድም ጥቅም ከገባው የረዥም ጊዜ የመድን ሽፋን ውል ልዩ ባህሪና ውጤት ጋር የማይሄድና አስገዳጅ የሆኑትን የንግድ ህግ አንቀጽ 701 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና አንቀጽ 705 ድንጋጌዎች ውጤት አልባ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለሆነም አብላጫው ድምጽ ከላይ የተጠቀሰኳቸውን አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች ሳያገናዝብ የመድን ፖሊሲውንና የህብረት ስምምነቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 ከአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች ጋር ብቻ በማጣመር በሰጠው ትርጉምና ውሳኔ የማልስማማ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

2.ሁለተኛው የልዩነቱ ምክንያት አብላጫው ድምጽ በመድን ፖሊሲውና በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 የሟች ወራሾች (legal heirs) የሚለውን ሀሳብ የሟች ጥገኞች (Dependent) ማለት ነው በማለት የሰጠው ትርጉም የህግ አተረጓጎም መርሆዎችን የተከተለ አይደለም የሚል ነው፡፡ የሟች ወራሾች (legal heirs) "የሚለው" መሰረተ ሀሳብ በፍ/ብ/ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎችና ስለ ህይወት ኢንሹራንስ በሚደነግገው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች ውጥ የሆነ ሀሳብ እንዲያራምዱ ተደርጎ በህግ አውጭው ተገልፀዋል፡፡ አመልካች የመንገድ ንግድ ሥራ የሚሰራ የኢንሹራንስ ኩባንያ በመሆኑ የኢንሹራንስ ውል (ፖሊሲ) አዘጋጅቶ ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ ጋር የመድን ውል ከመዋዋሉ በፊት የወንጂ ስኳር ፋብሪካ የህብረት ስምምነት ውስጥ የተገለጹትን ሀሳቦች ሥራ ላይ ባሉት የኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፎች የተሰጣቸውን ትርጉም መሰረት በማድረግ የኢንሹራንስ ፖሊሲውን ያዘጋጃል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የመድን ፖሊሲው (ውሉ) በአመልካች በኩል ተዘጋጅቶ የሚቀርብ (Adhesive contract) በመሆኑ በፖሊሲው በተገለፀው ሃሳብ ላይ አከራካሪ ነገር ቢነሳ ውሉን ያዘጋጀው አመልካችን በሚጠቅም መንገድ ሳይሆን ለውል ተቀባዩ በሚጠቅም መንገድ መሆን እንዳለበት በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1738 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ ተደንግጎ እያለ የአመልካች ወራሾች (legal heirs) ብሎ ያዘጋጀው የመድን ፖሊሲ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110 የተገለፀው ጥገኞች (Dependent) ተብሎ ውሉን ላዘጋጀው ለአመልካች በሚጠቅም መንገድ መተርጎሙ ይህንን የውል አተረጓጎም መርህ የሚጥስ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ህጋዊ ወራሽ (legal heir) የሚለው ፅንሰ ሀሳብና ጥገኞች (Dependent) የሚለው ፅንሰ ሀሳብ የተለያየ ትርጓሜ ያላቸው መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ ከሟች ወራሾች መካከል የሟች ጥገኛ ተብለው ካሳ የሚያገኙት የሟች ልጆች ሆነው 18 ዓመት በታች የሆኑ፣ የሟች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህጋዊ ባል ወይም ሚስትና በሟች ሰራተኛ ድጋፍ ይረዱ የነበሩ ወላጆችን ብቻ እንደሆኑ በአንቀጽ 110 ንዑስ አንቀጽ 2 ተዘርዝሯል፡፡ ስለሆነም እጅግ ሰፊ የሆነ የህግ ትርጉምና ዕውቅና የተሰጠውን የሟች ወራሾች (legal heirs) የሚለውን ቃል ከመጠን በላይ በማጥበብ Dependent ጥገኞች የሚለውን ቃል ያሣያል ተብሎ መተርጎሙ የውሉን ዕንስ ሀሳብ ሙሉ በሙሉ የመለወጥና የመተካት ሥራ እንጅ የህግ ትርጉም ስራ ነው ብዬ የማላምን በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አብላጫው ድምጽ አግባብነት ያላቸው "የኢትዮጵያ ህጎች" የሚለውን ሀረግ ለመተርጎም መሞከሩ ተገቢነት አለው ብዬ አላምንም፡፡ አሰሪው ለሰራተኛው የገባው የህይወት ኢንሹራንስ ክፍያ አግባብነት ያለው ህግ አዋጅ ቁጥር 377/96 ብቻ አይደለም፡፡ ከላይ በዝርዝር የተገለፁት ስለ ኢንሹራንስ ሥራ ፈቃድ የወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 ስለህይወት ኢንሹራንስ ውል የሚደነግገው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎችና ለህይወት የተደረገ ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚዎች በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 827 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገጉት ድንጋጌዎች አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፎች መሆናቸው ግልፅ ሆኖ እያለ ይህንን አባባል በጠበበ ሁኔታ በመተርጎም በተሰጠው ውሳኔ አልተስማማሁበትም፡፡

3.ሶስተኛው የልዩነት ምክንያቴ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110 ሰራተኛው በስራ ላይ ጉዳት ሲደርስበት ካሣ ሊጠይቁ የሚችሉ ሰዎች የሚች ጥገኞች ብቻ እንደሆኑ ህግ አውጭው የኃላፊነት መጠኑን ያጠበበው አንድ ሰራተኛ በሥራ ላይ በሚደርስበት ጉዳት (አደጋ) ህይወት ሲያልፍ ጉዳት የሚደርስባቸው የሟች ጥገኞች ብቻ ናቸው በሚል ሀሳብ አይደለም፡፤ ነገር ግን ከጥገኞች ባለፈ በአደጋው ምክንያት ሰራተኛው በመሞቱ የተጎዱ ሌሎች የሟች ዘመዶችን ወራሾች ሁሉ አሰሪው ካሣ ይክፈል ቢባል በአሰሪው ላይ የሚያስከትለውን ጫና ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

አሰሪው ሰራተኛው በሥራ ላይ በሚደርስበት አደጋ የሚከፈል የኢንሹራንስ ውል ሲዋዋል፣ የውሉ ተጠቃሚ የሚሆኑት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110 የተዘረዘሩት ጥገኞች ብቻ ሣይሆኑ ሟች በመሞቱ የጉዳቱ ሰለባ የሆኑ የሟች ወራሾች ጭምር ናቸው፡፡ ስለዚህ አሰሪው የኢንሹራንስ ውል ሲገባ በህብረት ስምምነቱ የተጠቀሱት የሟች ወራሾችን ጭምር የኢንሹራንስ ፖሊሲው ተጠቃሚ ለማድረግ አስቦ የተዋዋሉ በመሆኑ ይህም የኢንሹራንስ ውል አሰሪው (ወንጂ ስኳር ፋብሪካ) የኢንሹራንስ ፖሊሲ ለተጠሪዎች ወንድም ባይገባ ካሣ ከሚያገኙት ሰዎች የተሻለ መብት የሚያጎናጽፉ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 134(2)ን በመጥቀስ የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. አቶ አስቻለው ጌታሁን
2. አቶ ሽመልስ ከበደ
3. አቶ ኤርሚያስ ኢያሶ
4. አቶ መላኩ ካሣ
5. አቶ ሰለሞን አባተ
6. አቶ ንጉሴ ወ/አገኘሁ
7. አቶ ዋጋሁን ተከሰተ
8. አቶ እሸቱ አሰን
9. አቶ ገረመው ገብሬ
10. ወ/ሮ ሂሩት ደምሴ

ጠበቆች አቶ አዲስ ወልደኖና
አቶ አለማየሁ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አልፋ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካቾችን ያሰናበተው በአግባቡ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች በከሳሽነት ቀርበው የተቀጠርንበት የሥራ ግዜ ሳይጠናቀቅ፣ የተመደብንበት የሥራ ባህሪ ቀጣይነት ያለው ሆኖ እያለ ተከሳሽ /አመልካች/ የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር በ2003 ዓ.ም የርቀት ትምህርት ተማሪዎችን እንዳይቀበሉ መመሪያ አውጥቷል በሚል ምክንያት የሠራተኞች አቀናነስ ሥርዓትን በተመለከተ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የተደነገገውን ሳይከተል በሕገወጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መንገድ የሥራ ውል ያቋረጠ በመሆኑ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ትምህርት ሚኒስትር ባወጣው መመሪያ አዲስ ተማሪዎች እንዳንቀበል በመመሪያ የከለከለን በመሆኑ በድርጅቱ መዋቅርና የሥራ እንቅስቃሴ በከፊል፣ በቀጥታና በዘለቂታው እንዲቀንስና እንዲቀዘቅዝ አድርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት አሁን ያሉንን ተማሪዎች ለማስጨረስ የሚያስችሉ መምህራኖችን ብቻ በማስቀረት ከሳሾችን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት አሰናብተናቸዋል፡፡ ስንብቱ ሕጋዊ በመሆኑ ከሳሾች የጠየቁትን ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ አመልካቾችን ከሥራ ያሰናበተው ስለሠራተኛ ቅነሳ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ሳይከተል በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ /አመልካች/ ለከሳሾች /አመልካቾች/ የስድስት ወር ደመወዛቸውን ይክፈላቸው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ አስራ ዘጠኝ ሠራተኞችን ከሥራ በማሰናበት የወሰደው እርምጃ ካሉት ሠራተኞች ከአስር ፐርሰንት በታች በሚሆኑት ላይ የተደረገ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 29 መሠረት የሠራተኛ ቅነሳ አለመኖሩን ያሣያል፡፡ ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ያቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ መሠረት በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች ይህ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ጥቅምት 29 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ትምህርት ሚኒስትር በ2002 ዓ.ም ያወጣው መመሪያ በጥቅምት ወር 2003 ዓ.ም ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የተባረረ ሠራተኛ ወደ ሥራው እንዲመለስና የስድስት ወር ክፍያ እንዲከፈለው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ወስኗል፡፡ ተጠሪ የሠራተኛ ቅነሳ አድርጌአለሁ ቢልም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አላደረገም፡፡ ሠራተኛ ለመቀነስ የሚያስገደድ ሁኔታ አልተፈጠረም፡፡ ተጠሪ ሠራተኛ ለመቀነስ ይገደዳል ቢባል እንኳን ቅነሳው የተሻለ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ያለንን ከሥራ በማሰናበት፣ ከእኛ በታች የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያላቸውን እንዲቀጥሉ በማድረግ በዘፈቀደ እንዲወስን የሚፈቅድለት የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ ይህም የተጠሪ የሠራተኛ አቀናነስ በዘፈቀደ የተከናወነና በግለሰብ ምርጫ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያሳያል፡፡ ተጠሪ የሥራ መደባቸንን በመመሪያው የማይነካ ሠራተኞችን ያካተተ ነው፡፡ ስለዚህ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ የካቲት 19 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በመንግስት መመሪያ መሠረት የተጠሪ ሥራ ቀንሷል፡፡ ካሉን ሠራተኞች 3-8 ፐርሰንት የሚሆኑ መምህራንና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን በሕግ አግባብ ተጠሪ ቀንሷል፡፡ የተማሪዎች ቁጥር አለመቀነሱ ከስንብቱ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ ተጠሪ ሠራተኛ ቀንሷል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡ አመልካቾች በሚሰሩበት የሥራ ክፍሎች እንደገና እንዲከፈቱ አልተፈቀደም፡፡ ተጠሪ አመልካቾችን ሲያሰናብት በሕጉ መሠረት ማስጠንቀቂያ የሰጠና መክፈል የሚገባውን ክፍያ የከፈለ በመሆኑ፣ አመልካቾች ያቀረቡት ጥያቄ የሕግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ያቋረጠው በሕግ መሠረት ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ከሥራ ያሰናበታቸው ሠራተኞች በአጠቃላይ ካሉት ሠራተኞች ቁጥር 3-8 ፐርሰንት ብቻ በመሆኑ ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ያቋረጠው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 373/96 ቁጥር 29 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የሠራተኞች ቅነሣ መሠረት እንዳልሆነ የሥር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሣኔያቸው ገልፀውታል፡፡

ተጠሪ ከትምህርት ሚኒስትር በተላለፈው መመሪያ መሠረት አዳዲስ ተማሪዎችን የማይቀበል በመሆኑ የሥራ እንቅስቃሴው የቀነሰና በዚህ ምክንያት በፊት የነበሩትን መምህራንና ሠራተኞች ይዞ ለመቀጠል ባለመቻሉ የአመልካቾችን የሥራ ውል ማስጠንቀቂያ በመስጠት በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ መሠረት እንዳቋረጠ በማንሣት የተከራከረ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይህንን የተጠሪን ክርክር በመቀበል የሥራ ስንብቱ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 ቁጥር 28 ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ መሠረት የተከናወነና ሕጋዊ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

መንግስት ባስተላለፈው መመሪያ የተጠሪ የሥራ መጠን የቀነሰና የተቀዛቀዘ ቢሆንም አመልካቾች የሚያስተምሩበት የትምህርት ክፍልና ይሰሩበት የነበረው የሥራ ክፍል ሙሉ በሙሉ ያልተዘጋና ያልተሰረዘ መሆኑንና ተጠሪ ቀደም ብሎ የተቀበላቸውን ተማሪዎች የጀመሩትን ትምህርት ለማስጨረስ የሚችሉ መምህራንና ሠራተኞች በማስቀረት አመልካቾችን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የሥራ ውሉን ያቋረጠ መሆኑን ተጠሪ በሥርም ሆነ በሰበር በግልፅ ክርክር ያቀረበበት መከራከሪያ መሆኑን ተረድተናል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካቾች የሚያስተምሩበት የትምህርት ክፍልና የሥራ ክፍል ሙሉ በሙሉ ባልተዘጋበትና ባልተሰረዘበት ሁኔታ ተጠሪ የሥራ መጠኑን መቀነሱንና ሥራው መቀዝቀዙን መነሻ በማድረግ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ለማስቀረትና ሥራ የማይኖራቸውን ሠራተኞች ለማሰናበት ውሣኔ ሲሰጥ የተጠቀመባቸው መስፈርቶች ምንድን ናቸው፡፡ ተጠሪ ሊጠቀምባቸው የሚገቡ መስፈርቶችስ ምንድን ናቸው? የሚሉት ነጥቦች ናቸው፡፡

አመልካቾች ተጠሪ እነሱን ከሥራ ለማሰናበት ሲወስን ምንም አይነት ተጨባጭነት ያለው መስፈርት ያልተጠቀመ መሆኑንና ተጠሪ በትምህርት ደረጃ በሥራ ልምድና የሥራ አፈፃፀማቸው ከአመልካቾች የሚያንሱ መምህራንና ሠራተኞችን በማስቀረት እነሱን በዘፈቀደ ከሥራ ያሰናበታቸው መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት፣ በይግባኝና በሰበር ደረጃ የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ አመልካቾችን ከሥራ ለማሰናበትና ሌሎችን ለማስቀጠል የተጠቀመባቸው ተጨባጭ መመዘኛዎች ያሉ ለመሆኑ አልተጣራም፤ አሰሪው ሲሰራው የነበረው ሥራ በመቀነሱ ወይም በመቀዝቀዙ ምክንያት ካሉት ሠራተኞች ከአስር ፐርሰንት በታች የሆኑትን የሥራ ውል ማቋረጡ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ካሉት ሠራተኞች የተወሰኑትን የሥራ ውል በዘፈቀደ እንዲያቋርጥና የተወሰኑትን የሥራ ውላቸው እንዲቀጥል ለማድረግ የማይፈቀድለት መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 28 ንዑስ አንቀጽ 8 እና የአዋጅ ቁጥር 29 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘትና ዓላማ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር ሠራተኞች የሚሰሩበት የሥራ ክፍል ሙሉ በሙሉ ባልተሰረዘበት ወይም ባልተዘጋበት ሁኔታ የአሰሪው ሥራ በመቀዝቀዙ ምክንያት ከነበሩት ሰራተኞች የተወሰነ ቁጥር ያላቸውን ሠራተኞች የሥራ ውል ማቋረጥ የግድ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አሰሪው የሚሰናበቱትንና የሚቀጥሉትን ሠራተኞች ለመለየት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገጉትን መመዘኛዎች በመጠቀም በትምህርት ክፍሉና በሥራ ክፍሉ ያሉትን ሠራተኞች አወዳድሮ ከሥራ የሚሰናበቱትንና በሥራ ላይ የሚቆዩትን ሠራተኞች በመለየት በሥራ ለማይቀጥሉ ሠራተኞች ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የሥራ ውሉን ያቋረጠ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት ከዚህ አንፃር ሲታይ፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. ተጠሪ አመልካቾች በሚያስተምሩበት የትምህርት ክፍልና በሚሰሩበት የሥራ ክፍል የሚገኙትን ሠራተኞች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 3 በተቀመጡት መመዘኛዎች መሠረት በማወዳደር የአመልካቾችን የሥራ ውል አቋርጧል ወይስ አላቋረጠም?

2. ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ማስጠንቀቂያ በመስጠት ያቋረጠው አመልካቾች በትምህርት ደረጃቸው በሥራ ልምዳቸውና በሥራ አፈፃፀማቸው አመልካቾች በሚያስተምሩበት የትምህርት ክፍልና የሥራ ክፍል የሥራ ውላቸው እንዲቀጥል ከተደረጉ ሠራተኞችና መምህራን አንሰው በመገኘታቸው ነው ወይስ አይደለም?

3. ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ያቋረጠው አመልካቾችና በሥራ እንዲቀጥሉ የተደረጉ ሠራተኞች ተመሣሣይ የትምህርት ደረጃ ፣ የሥራ ልምድና የሥራ አፈፃፀም ውጤት ኖሯቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 3 ከ/ሀ/ እስከ /ረ/ የተዘረዘሩትን ቅደም ተከተል በመጠቀም ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች በሥር ፍርድ ቤት ያልተረጋገጡና ያልተጣሩ ነጥቦች ናቸው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የአመልካቾችን የሥራ ውል ያቋረጠው በአግባቡ ነው ወይስ ከህግ ውጭ ነው ብሎ ለመወሰን ከላይ የገለፅናቸው ነጥቦች መጣራትና በማስረጃ መረጋገጥ ያለባቸው ሆኖ እያለ እነዚህን ጭብጦች በመያዝ ሣያጣሩና በማስረጃ ሳያረጋግጡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስንብቱ ህገወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያላደረገና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 3 የተያዙት ጭብጦች ለማስረዳት በግራ ቀኙ በኩል የቀረቡ ማስረጃዎችንና ክርክሮችን በመመርመርና አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ ማስረጃዎችን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 145/1/ መሠረት በማስቀረብ ተጠሪ አመልካቾችን ያሰናበተው በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥና ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወርልድ ቪዥርን ኢትዮጵያ - ጠበቃ ሜላት ወርቅ ኃይሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መዘምር መክብብ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርጎ የቀረበውን የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘት ሲታይም ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ግንኙነት ያለጥፋት የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በድርጅቱ ግቢ ውስጥ ድብደባ ፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና የጠብ አጫሪነት ተግባር በመፈፀማቸው ስለመሆኑ ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በሁዋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ በአመልካች ኤዲፒ ካምፕ እና ለሰራተኞች መኖሪያነት በተሰራው ግቢ ውስጥ /በስራ ቦታ/ የድርጅቱን ሰራተኛ በመደብደብና የዛቻ ተግባር መፈፀማቸው መረጋገጡንና ለዚህም ተጠያቂ መሆናቸውን ገልፆ የአመልካች እርምጃ ሕጋዊ ነው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ወሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ተጠሪ የድብደባ ተግባሩን የፈፀሙት ከስራ ሰዓት ውጪ በመሆኑ ድርጊቱ በስራ ቦታ ላይ እንደደረሰ የሚቆጠር አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር አመልካች ለተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤተታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ለስራ ስንብቱ ምክንያት የሆነውን የድብደባ ተግባር ስለመፈፀማቸው ከመረጋገጡም በላይ ድርጊቱ የተፈፀመው በስራ ቦታ ላይ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ድርጊቱ ከስራ ሰዓት ውጪ የተፈፀመ ተግባር ነው በሚል ጠባብ ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት እንዲቀርብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ በይግባኝ ሰሚው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገርና አግባብነት ያለውን ሕግ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው ተጠሪ አምባንሮ ፈጥሮ የስራ ባልደረባውን መደብደቡን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተቀብሎ ድብደባው የተፈፀመው ተጠሪና የግል ተበዳይ አመልካች ባዘጋጀላቸው የስራና የመኖሪያ ግቢ ካምፕ ቢሆንም ድብደባው የተከናወነው ከስራ ሰዓት ውጪና በመፀዳጃ ቤት አካባቢ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ረ)) ስር የተደነገገውን አያሟላም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ውድቅ ማድረጉና ወደ ስራው ይመልሰው የመባሉን አግባብነት ለማጣራት በሚል ነው፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ተጠሪው የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ላይ የስራ ቦታ በሆነው የአመልካች ካምፕ እና በስራ ጉዞ ላይ የድብደባ ፣ የዛቻ ተግባር መፈጸማቸውን ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑንና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቢሆን የድብደባውና የዛቻው ተግባር በተጠሪ በመፈፀሙ ረገድ ከስር ፍርድ ቤት የተለየ ድምዳሜ የሌለው መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገው ክርክርም ተጠሪ የድብደባውን ተግባር ስለመፈፀማቸው ግልፅ የሆነ የክህደት ክርክር የሌላቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የተጠሪ ድርጊት የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ረ የተደነገገውን ጥፋት አያሟላም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የአመልካች ሰራተኛ የተደበደበችው ማታ ከመሆኑም በላይ የድብደባው ተግባር የተፈጸመው አመልካች ለሰራተኞቹ በመኖሪያነት ባዘጋጀው ቦታ መጸዳጃው አከባቢ ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በሕጉ አነጋገር የስራ ቦታ እና ሰአት የሚለውን መለኪያ የሚሸፈን አይደለም በሚል ነው፡፡ አመልካች ሰዓቱም ሆነ ቦታው የስራ ቦታ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜን ተገቢነት ለመመርመር የተጠቃሹን ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ በዝርዝር መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ረ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ፡- “ እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ቦታ አምባንሮ ወይም ጠብ እጫሪነት ተጠያቂ መሆን ” ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ለማቋረጥ ከሚያስችሉ ምክንያቶች አንዱ ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ውስጥ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሐረግ "....በስራው ቦታ...." የሚለው ሲሆን ይኸው ሐረግ ሰራተኛው ስራውን በስራ ሰዓት የሚያከናውንበትን ቦታ ወይም የአሰሪውን ትዕዛዝ በስራ ላይ ሊያውል የተገኘበትን ቦታ ሁሉ የሚያጠቃልል ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 97 እና 4 ድንጋጌዎችን ይዘት በማገናዘብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ አሰሪው ስራው በሚሰራበት ካምፕ ውስጥ ለሰራተኛው በመኖሪያነት የመደበውን ቦታ እና በዚህ ቦታ ሠራተኛው ያለበትን ሠዓት ጭምር ሁሉ ሊጠቃልል እንደሚችል ከሕጉ መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ሰራተኛው በስራ ሰዓት ስራውን በሚያከናውንበት ቦታ ወይም የአሰሪውን ትዕዛዝ በስራ ላይ ሊያውል በተገኘበት ቦታ ላይ እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ቦታ አምባንሮ ወይም ጠብ እጫሪነት ድርጊት መፈፀሙ ከተረጋገጠበት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ድርጊት ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ አይነተኛ አላማም በሥራ ቦታ ሰላም እንዲሰፍን በማድረግ ምርትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምርታማነትን ለማሳደግ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው ሊተረጎም የሚገባውም ይህንኑ የድንጋጌውን ዓላማ መሰረት በማድረግ ሊሆን እንደሚገባም እሙን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን ሰራተኛ መደብደቡ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠና በተጠሪም የታመነ ፍሬ ነገር መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡ ይህ የተጠሪው ድርጊት ከተጠቀሰው ድንጋጌ አንፃር ሲታይ የጠብ አጫሪነት ድርጊት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ፍ/ቤት ተጠሪው የድብደባውን ድርጊት መፈፀማቸውን ተቀብሎ ድርጊቱ የተፈጸመው ከስራ ሰዓት ወጪ ነው በማለት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠውና ከሕጉ መንፈስና አላማ ውጪ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ የአሰሪው ወይም የሥራ ኃላፊው ትእዛዝ በማክበር ካምፑ በሚገኝበት ቦታ መኖሪያ ተሰጥቶት በመኖር ላይ ባለበት ሁኔታ በዚሁ አካባቢ በድርጅቱ ሰራተኛ ድብደባ ከተፈፀመበት የድብደባውን ተግባር የፈፀመው ሰራተኛ ተግባሩን የፈፀመው በስራ ጊዜና ቦታ አይደለም ተብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ ሕጉ ሊያሳካ ያሰበውን ፤ በስራ አካባቢ ሰላምን በማስፈን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የሚለውን አላማ ያላገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የድብደባውን ተግባር የፈፀሙ ስለመሆኑና ድብደባውን የፈፀሙትም ለስራ ጉዳይ ከተጠሪ ጋር እንዲሄዱ በአመልካች የታዘዙትን ሴት ሰራተኛ ቀኑን ሙሉ ሲያስቸግሯቸው ውለው አሰሪው በስራው ቦታ ውስጥ ባዘጋጀው የሠራተኞች መኖሪያ ቤት መፀደጃ ቤት ሰራተኛዋ ቆይተው ሲወጡ ማታ ላይ መሆኑ የተጠሪን ድርጊት ጥፋት ከባድነት አመልካች ነው፡፡ ስለሆነም የተጠሪው ድርጊት የአዋጁን አንቀጽ 27/1/ረ የተመለከተውን ጥፋት አያሟላም ሲል የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሕጉ ያስቀመጠውን የሰራተኛውን ግዴታ የሚመለከተውን ድንጋጌ እና የጥፋቱን አደገኛነት ከተጠቃሹ ድንጋጌ አይነተኛ አላማ አንፃር በአግባቡ ሳያገናዝብ መሆኑን ስለተረዳን ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 116083 ሚያዚያ 08 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 74140 ታህሳስ 26 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አኪኮ ቦዲዋይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ ጌታቸው ወንድሙ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ገረመው አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ህግ በደነገገው መሰረት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክርና በማስረጃ ከተረጋገጠው የፍሬ ነገር ጉዳይ ጋር በማገናዘብ ለይቶ ለመወሰን ሲባል ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ሥራዬን በአግባቡ እየተወጣሁ እያለ አሠሪው ወደ ሌላ የሥራ መደብ ተዛውረሃል በአዲሱ የስራ መደብ ሄደህ ሥራ በማለት በቃል ሲገልጽልኝ፤ በተዛወርኩበት ቦታ ሥራዬን በኃላፊነት በአግባቡ እንድወጣ የዝውውር ደብዳቤ ይድረሰኝ በማለት በመጠየቁ በጥበቃ ኃላፊው ተገድጄ እንድወጣ ተደርጓል፡፡ በዚህም የተነሣ የሥራ ውሉ የተቋረጠ ስለሆነ ስንብቱ ህገ-ወጥ በመሆኑ የሚገባኝ ልዩ ልዩ ክፍያ እንደ ህጉ ይፈፀምልኝ በማለት ዳኝነት ስጠይቅ፤ የአሁን አመልካች በበኩሉ ከአሰሪነቱ በመነጨ ሥልጣን ሠራተኛው በሌላ የሥራ መደብ ተዛውሮ እንዲሰራ፤ የዝውውር ደብዳቤ በቀጣይነት እንደሚደርሰው በሥራ ኃላፊው ግልፅ ትዕዛዝ ቢደርሰውም ሥራ አልጀመረም፡፡ በዚህም የተነሳ በቀድሞው የሥራ ቦታ ሊያቆያቸው የሚችል ምክንያት የሌለ መሆኑ ተገልፆ ወደ መደብ የሥራ ቦታቸው እንዲሄዱ ሲነገራቸው ሥራቸውን በፈቃዳቸው ለቀው ሄደዋል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙ የሥራ ውል የተቋረጠው በሠራተኛው ፈቃደኝነት ወይስ በአሰሪው አነሳሽነት? የሚለውን በአከራካሪ ነጥብነት ይዞ በጉዳዩ ላይ ማስረጃ ሰምቷል፡፡ በተሰማው ማስረጃ መሰረትም አሠሪው ሠራተኛውን የድርጅቱ የሥራ ቦታ በሆነ በሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሰራ በቃል መገለፁንና ሠራተኛውም ዝውውር በፅሁፍ ይድረሰኝ በማለት ሲጠይቅ እንደነበር አሰሪውም በድርጅቱ የጥበቃ ኃላፊ አማካኝነት ሠራተኛው ተገዶ እንዲወጣ ያደረገ መሆኑንና ሠራተኛውም ልብ አድርጉ እያለ ተገዶ ወጥቶ መሄዱን ከዚያም ወደ ሥራ ቦታ ሊመለስ ያልቻለ መሆኑን በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ እንደሆነ ከውሳኔው ግልባጭ ተረድተናል፡፡ ስለሆነም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ሠራተኛው ወደ ተዛወረበት ቦታ አልሄድም በሚል ምክንያት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለቋል የሚለው ክርክሩ በማስረጃው የተረጋገጠውን ጉዳይ መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ለግራ ቀኙ ክርክር መነሻ የሆነው የገዘውውር ጉዳይ እንደሆነ በማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ ሁለቱንም ወገኖች ያለያያቸው ነጥብ አይደለም፡፡ የተለያዩበት ነጥብ አመልካች እንደ አሰሪነቱ የገዘውውር እርምጃውን በቃል ትዕዛዝ አስተላልፏያለሁ፤ በቀጣይም የገዘውውር ደብዳቤ እንደሚደርሰው እየተገለፀለት ወደ ምድብ ሥራው መሄድና ሥራ መጀመር ሲገባው ይህንን አላደረገም የሚለውን በማስቀደም በሠራተኛው በኩል ጥፋት እንዳለ ለማሳየት ሲል ክርክሩን አቅርቧል፡፡

ይሁን እንጂ ሠራተኛው የተዛወረበት ክፍል ከቦታም ሆነ ከሥራ መደብ አንፃር ሲታይ ቀድሞ ተመድቦ ይሰራበት ከነበረው የሥራ አድራሻም ሆነ የሥራ መደብ የተለየ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን፤ አመልካች ለዚህ ያቀረበው ማስተባበያ ክርክር የለም፡፡ ይህም ከሆነ አሰሪው የዘውውሩን እርምጃ በቃል በማስተላለፍና የሚያስገድድ አጣዳፊ ሁኔታ መኖሩን ካላስረዳ በቀር የዘውውር እርምጃውን በቃል አስተላልፏያለሁ፤ በቀጣይም በደብዳቤ እገልፃለሁ ማለቱ የአስተዳዳሪነት ሥልጣኑን በዘፈቀደ ለማከናወን ከመሻት የመነጨ ምክንያት ነው ከሚባል በቀር የእርምጃውን ህጋዊነት አያሳይም፡፡ ተጠሪም ይህ የዘውውር ውሳኔ በቃል መሆኑ ቀርቶ በፅሁፍ ይደረግልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተዛውሮ እንዲሄድ ከተገለፀለት የሥራ አድራሻ እና የሥራ መደብ አንፃር የአንድ መ/ቤትን አግባብ የሆነ የገዘውውር አፈፃፀም ተከትሎ ያቀረበው የመብት ጥያቄ ነው የሚያሰኝ እንጂ የአሰሪውን ትዕዛዝ ላለመፈፀም ያደረገው ተግባር ሆኖ አይገኝም፡፡ በመሆኑም ለግራ ቀኙ ውዝግብ የሆነው ምክንያት አሰሪው በእራሱ በፈፀመው ያልተገባ ተግባር እንደሆነ መረዳት ችለናል፡፡

አሰሪው የወሰድኩት እርምጃ ህጋዊ መሰረት ያለው ነው በሚል ያመነበት ቢሆን እንኳ ተጠሪ ወደ አዲሱ የስራ ቦታ ሄዶ ሥራ ባለመጀመሩ ምክንያት የሥራ ደንቡ እና ህጉ በሚፈቅደው ቅደም ተከተሉ የጠበቀ አስተዳደራዊ እርምጃ መወሰድ ከሚችል በቀር ሠራተኛውን የጥበቃ ኃላፊ በሆነው አማካኝነት ከስራ ቦታ አስገድዶ እንዲወጣ በማድረጉ በእራሱ እጅ የመዳኘት ተግባሩ ሌላው ህጋዊ መሰረት የሌለው እርምጃ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም የሥራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች በሠራተኛው ፈቃድ ሳይሆን ሠራተኛው/የአሁን ተጠሪ/ ደንቡን ባልጠበቀ ዝውውር ምክንያት ለመሄድ እቸገራለሁ በማለት ተገቢው እንዲፈፀም በመጠየቁ ምክንያት አሠሪው ከሥራ ቦታው በድርጅቱ ጥበቃ ሰራተኛ አማካኝነት አስገድዶ በማስወጣቱ ህገ-ወጥ ድርጊት ሆኖ ስለተገኘ የሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ህጉ ከደነገገው ውጭ የተፈፀመ ነው በሚል የሰጡት ዳኝነት በማስረጃ የተረጋገጠውን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በስንብቱ አግባብነት ዙሪያ ክርክር ከማቅረቡ በፊት በክፍያው ጉዳይ ላይ ያነሳው ክርክርም የለውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በወሰደው ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ሳቢያ የሥራ ውሉ የተቋረጠ መሆኑን ተገንዝበው የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 115625 በ29/3/2004 ዓ.ም የሰጠውና የመጨረሻ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ከዚህ በፊት በዚህ የሰበር መዝገብ ሚያዝያ 13 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የተነሳ የደረሰውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 79096

ሐምሌ 20 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሪመምበር ዘ ፑረሰት ኮሚዩኒቲ - ጠበቃ ለሜሳ ያደታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዘውድነሽ ማሞ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት አድርጎ የቀረበን የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች የክስ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ግንኙነት ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ጠቅሰው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸውና የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የተጠሪ የስራ ድርሻ ሕጻናትን መንከባከብ ሲሆን ከምትንከባከባቸው ሕጻናት ውስጥ ፍፁም ወርቁ የሚባለውን ደብድባ ሰውነቱ እስኪላጥ ድረስ ጉዳት ማድረሷ በመረጋገጡ የተፈጸመ ስንብት በመሆኑ ሕጋዊ ስለሆነ የሚከፈላት ክፍያ የለም ሲል ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና የሰነድ ማስረጃ መርምሮ ህፃኑ መደብደቡ ቢረጋገጥም ድብደባውን የፈፀሙት ተጠሪ ስለመሆናቸው አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ብሎ አመልካች ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች ሊከፍሏቸው ይገባል በማለት የክፍያዎችን አይነትና መጠን ለይቶ ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩና ተደበደበ የተባለው ሕፃን ቀርቦ ከተሰማ በኋላ ተጠሪ ድርጊቱን መፈጸማቸው ተረጋግጧል ተብሎ ስንብቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27(2)፣14(2)(ሀ)) እና 27(1(ረ)) መሰረት ሕጋዊ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡ ከዚህ በኋላም ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በሚንከባከቡት ሕፃን ላይ በድብደባ ተግባር ጉዳት ያደረሱ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሻረው ያላአግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የአመልካች የስንብት እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍል መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል የህጻናት እንክብካቤ የሚገኝበት መሆኑንና የተጠሪ ስራም ሕጻናትን መንከባከብ መሆኑን፣ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ሊቋረጥ ችሏል በማለት አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ ፍጹም ወርቁ የተባለ ሕፃን ላይ በድብደባ ተግባር ጉዳት አድርሰዋል በሚል መሆኑንና ይህንኑ ክርክሩን ለማስረዳትም የሰነድ ማስረጃዎችን ማቅረቡን፣ የወረዳው ፍርድ ቤትና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ለድርጊቱ ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሰው ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ለማለት የቻሉት ድርጊቱን ተጠሪ ስለመፈጸማቸው አመልካች አምነዋል በማለት ያቀረበው ሰነድ ቢኖርም ተጠሪ በፍርድ ቤት ሲቀርቡ ሰነዱን ክደው የተከራከሩ በመሆኑና የህክምና ማስረጃውም ጉዳቱ በተጠሪ ስለመድረሱ ያረጋግጣል ሊባል የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት መሆኑን፣የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን ድብደባው ተፈፅሞበታል የተባለውን ሕጻን አስቀርቦ ጉዳቱ በተጠሪ የደረሰበት ስለመሆኑ በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የሻረው መሆኑን ነው፡፡

እንግዲህ ከላይ ከተገለፀው የፍርድ ቤቶች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው በሕፃኑ ላይ አካሉ ላይ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ በሁሉም ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ሁኖ ጉዳቱ በምን ምክንያት ነው የደረሰው? በሚለው ጥያቄ ላይ ግን የተለያየ ድምዳሜ ፍርድ ቤቶቹ የያዙ መሆኑን ነው፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን በሕፃኑ ላይ ጉዳቱ እንዴት ደረሰ? ለሚለው ጥያቄ ሕፃኑን በችሎት በማስቀረብ ሰምቶ ጉዳዩን በአግባቡ አጣርቶ ተጠሪ ጉዳቱን ስለማድረሳቸው አረጋግጧል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግን በወረዳው ፍርድ ቤት የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ ተጠሪ ጉዳቱን አድርሰዋል ለማለት የሚቻል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠውን የሕፃኑን ቃል በመተው ነው፡፡ይህ ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ለ)) እና በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀፅ 64(2(ሐ) እንዲሁም በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀፅ 31 የተሠጠውን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም ስልጣን ባግባቡ ያላገናዘበ ነው፡፡ የሰበር ችሎቱ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው መሆኑን ከተጠቃሽ ሕጎች ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላልና፡፡በመሆኑም ድብደባውን ማን አደረሰው የሚለው ጥያቄ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ እያለ ይኸው ፍሬ ነገር በክልሉ ሰበር ሰሚ ሳይታይ መታለፉ በህጋዊ ምክንያት ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሕፃኑን በራሱ ተነሳሽነት አስቅርቦ መስማቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 345(1) መሰረት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲል ተጨማሪ ማስረጃ ማስቀረብ እንደሚችል በሕጉ የተሠጠውን ስልጣን መጠቀሙን ያሳያል ከሚባል በስተቀር በማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ደንብ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ፈጽሟል ለማለት የሚቻልበት ምክንያት የለም፡፡የዞኑ ከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት ህጻኑ የተደበደበውና ጉዳቱ የደረሰበት በተጠሪ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የተከተለው መንገድ ሕጋዊ ነው፣ጉዳቱም በተጠሪ በተፈፀመው የድብደባ ተግባር የደረሰ ነው ከተባለ ይህ ጥፋት አንድን ሰራተኛ ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል ምክንያት መሆን ያለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ማናቸውም ሰራተኛ ሕይወትና ንብረትን ለአደጋ የሚያጋልጥ ድርጊት መፈፀም ሕገ ወጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 14(2(ሀ))ስር የተመለከተ ሲሆን በአንቀጽ 27(1(ቀ)) ስር ደግሞ በአንቀጽ 14(2) ስር የተመለከቱትን ሕገ ወጥ ድርጊቶችን መፈፀም የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡በመሆኑም ተጠሪ በሚንከባከቡት ሕፃን ላይ የድብደባ ተግባሩን መፈፀማቸው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተደረገው የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና የተረጋገጠ ሁኖ በሕፃኑ ላይ ደረሰ የተባለው ጉዳትም ሲታይም ሕይወቱን ለአደጋ ሊያጋልጥ የማይችል ነው ሊባል የሚችልበትን ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከስራ የተሰናበቱት በአዋጁ አንቀፅ 27(1(ቀ)) ድንጋጌ በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡በዚህም ምክንያት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ ለሰበር ችሎቱ በሕጉ ተለይቶ ከተሰጠው ስልጣን ውጪ ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 345 መሰረት ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ስልጣን ያላገናዘበና በውጤቱም የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ቀ)) ድንጋጌን የጣሰ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 135103 መጋቢት 24 ቀን 2004 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12443 ሕዳር 25 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ብለናል፡፡አመልካች ከተጠሪ ደመወዝ ብቻ በመቁረጥ ሲያጠራቅም የነበረ የፕሮቪደንት ፈንድ ካለ ይህንኑ ተጠሪ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊረማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 68138

ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1- ወ/ሮ ጥሩሰው ጥላሁን የቀረበ የለም

2- ወ/ሮ ቦጋለች አስፋው ቀረቡ

3- እነ ወ/ሮ ብዙነሽ ካሣ / ወ/ሮ ብዙነሽ ካሣ እና

እማኒይ ድንቁ ቢሆነኝ / ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሲቪል ወርክስ አማካሪ መሃንዲሶች ኃ/የተ/የግል ማህበር ጠበቃ ዜና ደባስ ቀረቡ

መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 68139 ፣ 68140 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሞት ጉዳት ካሣ የሚጠይቅበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች ሲሆኑ ተከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ነበር፡፡ ከሣሾች ክሳቸውን ያቀረቡት በተለያዩ መዛግብት ሲሆን በተራ ቁጥር አንድ የተጠቀሱት አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘቱ ባለቤታቸውና የተፀነሰው ልጅ አባት የሆኑት ኢንጂነር ዳዊት ኃ/ማርያም በተጠሪ ድርጅት በኮንስትራክሽን መሐንዲስትነት የስራ መደብ በወር ብር 12,675 ደመወዝና በመስክ ስራ ሲመደቡ ደግሞ በቀን 200 ብር አበል እየተከፈላቸው ለመስራት ተቀጥረው ስራውን በመስራት ላይ እንዳሉ ተጠሪ መስሪያ ቤት በሚቆጣጠረው በቀይ አፈር ቱርሚ የመንገድ ስራ ኘሮጀክት አብሯቸው እንዲሰሩ ከተመደቡት ከኢንጂነር ሉሊት ታምራት ጋር የካቲት 23 ቀን 2002 ዓ/ም በመስክ መኪና በሾፌር ወደ ኘሮጀክቱ ቦታ ሄደው የተጠሪን ስራ እየሰሩ ሳለ የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ/ም የተጠሪ ሹፌር በሚያሽከረክረው መኪና የሄዱበትን የመቆጣጠር ስራ ለማከናወን ኦሞራቴ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለውን ድልድይ ተመልክተው ሲመለሱ ደሞኮ ከተማ ሊደርሱ ሁለት ኪሎ ሚትር ሲቀር መኪናው ተንሸራቶ አሸዋ ወንዝ ውስጥ ገብቶ ለመውጣት ሲሞክር ደራሽ የጎርፍ ውሃ ደርሶ ተሽከርካሪውን ከእነ ተሳፋሪዎች ይዞ በመሄዱ የተነሳ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር ሕይወቱ ሊያልፍ እንደቻለ ገልጸው በሚስትነታቸውና ከሟች የጸነሱት ልጅ በአዋጁ መሠረት የሚገባቸው ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በተራ ቁጥር ሁለት የተጠቀሱት አመልካች ባቀረቡት ክስ ልጃቸው የሆነችው ሟች ኢንጂነር ሉሊት ታምራት በተጠሪ ድርጅት ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቀጥራ ደመወዝ 4055.50 /አራት ሺህ ሃምሳ አምስት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ እና አበል በቀን አንድ መቶ ብር እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እንዳሉ የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ/ም በስራቸው ላይ እንዳሉ በደረሰባቸው አደጋ የሞቱ መሆኑን በመግልፅ የጉዳት ካሣ እና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ በተራ ቁጥር ሶስት የተጠቀሱት አመልካቾች ደግሞ የወ/ሮ ብዙነሽ ካሣ ባለቤት የህፃን ናሆም ወላጅ አባት፣ የእማኂይ ድንቁ ቢሆነኝ ልጅ የሆኑት ሚች ኢንጅነር ደምስ ወርቁ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው በወር ብር 11,135.00 የመስክ አበል ብር 270.00 እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እንዳሉ በየካቲት 28 ቀን 2002 ዓ/ም ከእነ ኢንጂነር ዳዊት ኃ/ማርያም ጋር በደረሰባቸው አደጋ የሞቱ መሆኑን ገልጸው በሕጉ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም በውሃ አደጋ ሕይወታቸው ያለፈው መሃንዲሶች ሰራተኞቹ መሆኑን ሳይክድ አደጋው የደረሰው ከተመደቡበት የስራ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በራሳቸው ፍላጎት ስራ በሌለበት እሁድ ቀን በመሄድ ሲመለሱ የደረሰ አደጋ በመሆኑ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ ሊቆጠር አይችልም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮችን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ሟቾች ሕይወታቸው በአደጋ ምክንያት ባለፈበት ጊዜ ከተጠሪ ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የነበራቸው መሆኑን ተጠሪ ያለመካዱንና በማስረጃም መረጋገጡን ከገለጸ በሁዋላ አደጋው የደረሰው ግን ሟቾች በስራ ላይ በነበሩበት ጊዜ ሳይሆን ከስራ ቀንና ቦታ ውጪ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል ፣ አመልካቾች ሟቶች የሞቱት በስራ ላይ ሆነው ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታቸውን አልተወጡም በማለት ደምድሞ ክሱን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተናጠል አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ባለመስማማት ሲሆን አመልካቾች አቤቱታቸውን በተለያዩ መዛግብት ያቀረቡ ቢሆንም የሁሉም አመልካቾቹ የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ግን ሟቾች በተጠሪ መኪና እና ሹፌር ኦሞራቱ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለውን ድልድይ ተመልክተው ሲመለሱ ጉዳቱ የደረሰባቸው ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 95 እና 97 ስር ላይ በስራ ላይ ስለሚደርስ አደጋ የተቀመጠውን የሕጉን መንፈስ ባግባቡ ሳይመለከቱ አደጋው የደረሰው በስራ ላይ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ክሱን ውድቅ ማድረጋቸውን ከሕግ ውጪ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ በሟቾች ሞት ምክንያት ለአመልካቾች ካሣ የመክፍል ኃላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም በሁሉም መዛግብት በሰጠው የጽሑፍ መልስ ሟቾች ሰራተኞቹ መሆናቸውን ሳይክድ አደጋው በደረሰበት እለት ግን የስራ ቀን ካለመሆኑም በላይ ሟቾች ሊመለከቱት የሄዱበት ድልድይ ሟቾች እንዲሰሩ ከተመደቡበት ሳይት ውጪ በሌላ አቅጣጫ ያለና በእለቱም ሟቾቹ እንዲመለከቱት ከአሰሪው ተገቢው ትዕዛዝ ባልተሰጠበት ሁኔታ ሟቾቹ በራሳቸው ፍላጎት ሄደው ድልድዩን ተመልክተው ሲመለሱ አደጋው የደረሰ በመሆኑ አደጋው በስራ ላይ የደረሰ ነው ሊባል እንደማይችልና ኃላፊነት የለበትም ተብሎ መወሰኑ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታዎቹ መነሻ ከሆኑት ውሣኔዎች እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ሟቾች አደጋው በደረሰበት እለት በመስክ ስራ ላይ የነበሩ መሆኑን ሳይክድ አጥብቆ የሚከራከረው አደጋው የደረሰው ሟቹቹ ከተጠሪ ፈቃድና እውቅና ውጪ በሆነ ሁኔታ ተጠሪ በአማካሪነት በተቆጣጣሪ መሃንዲስነት ከሚሰራበት ቦታ ውጪ ወደአለው በኦሞራቴ ወንዝ ላይ የሚሰራውን ድልድይ ለመመልከት ሄደው ሲመለሱ አደጋው የደረሰ በመሆኑ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ አይቆጠርም በማለት መሆኑን አመልካቾች ደግሞ ሟቾች በተጠሪ ትዕዛዝ ወደ ቀይ አፈር ቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ለመስክ ስራ መሄዳቸው የተረጋገጠና ወደ ኦሞራቴ ወንዝ ድልድይ ጉብኝት የሄዱትም በተጠሪ ሹፌርና መኪና እንዲሁም በወቅቱ የመስኩ ስራ ኃላፊ ከነበሩት ሰው ጋር ጭምር በመሆኑ አደጋው በስራ ላይ የደረሰ አደጋ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋጧቸው ነጥቦች ደግሞ ሟቾች በተጠሪ ድርጅት ተቀጥረው የሚሰሩ መሆናቸውን አደጋው ደረሰ የተባለበት እለት እሁድ ሁኖ የእረፍት ቀን መሆኑን ፣ በዚህ እለት ሟቾች በተጠሪ ድርጅት መኪና ኦሞራቴ ወንዝ ላይ በሌላ ድርጅት የሚሰራውን ድልድይ ለመመልከት ሄደው ሲመለሱና ደመኮ ከተማ ለመድረስ ሁለት ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው የተሳፈሩበት መኪና አዋሽ ወንዝ ውስጥ ገብቶ የጎርፍ ደራሽ ውሃ የወሰዳቸውና ለህልፈት የዳረጋቸው መሆኑን ሟቾች ከተመደበቡት የመስክ ስራ ቦታ ውጪ ወደ ሚገኘው ወደ ኦሞራቴ ወንዝ ድልድይ ግንባታ ጉብኝት የሄዱት ከተጠሪ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ኖሮ ሳይሆን በራሳቸው ፍላጎት ስለመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት ከተሰጠው ስልጣን አንጻር ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጧቸውን ፍሬ ነገሮችን እንዳሉ በመቀበል የሚኖረው ሚና በሕጉ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ ስህተት ካለ ማረም ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በሕጉ ረገድ ያለውን ጉዳይ ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ /occupational injury/ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ /occupational disease/ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 95/2/ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 97 ደግሞ በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ማለት ማንኛውም ሰራተኛ ሥራውን በማከናወን ሳለ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ወጭ በሆነ ምክንያት ወይም ስራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ እንደሆነ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በስራ ላይ የደረሰ አደጋ ማለት ደግሞ ሰራተኛው የአሰሪውን ትዕዛዝ በስራ ላይ እና በስራ ሰዓት ሲፈጽም የደረሰበት ጉዳት ፣ ሰራተኛው ከስራው በፊት ወይም በኋላ ወይም ስራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በስራው ቦታ ወይም በድርጅቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የደረሰበት ጉዳት ፣ ሰራተኛው ወደ ስራ ቦታ ወይም ከስራ ቦታው ድርጅቱ ለሰራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው መጓጓዣ በመንገዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳት ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀፅ 97 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የአሰሪው ሓላፊነት በስራ ምክንያት ለሚመጡ ጉዳቶች የተወሰነ ስለመሆኑ ድንጋጌዎቹ ያስረዳሉ፡፡ በዚህም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት በአዋጁ የጉዳት ካሣ ለመጠየቅ የሚቻለው ጉዳቱ በስራ ምክንያት የመጣ ሁኖ በስራ ሰዓት ፣ በስራ ቦታና ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው አጋጣሚ የተከሰተ መሆኑ በሚገባ ሊረጋገጥ ይገባል ። በመሆኑም የአዋጁ አንቀፅ 96 እና 97 ድንጋጌዎች ጠቅላላ ይዘት ሲታይ ደግሞ አሰሪው በስራ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ የመከላከል እርምጃ የመውሰድ ፣ አደጋው በሕጉ በተቀመጠው ትርጉም መሠረት በስራ ላይ ከደረሰ ደግሞ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ያስገነዝባል። በአዋጁ አንቀፅ 95 ድንጋጌ መሠረት የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚያቀርበው ወገን ጉዳቱ የደረሰው በአንቀፅ 97 በተመለከተው አኳኋን በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት መሆኑንና እንደዚሁም በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ቅርብና ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት መኖሩን /proximate cause and effect relationship/ ማስረዳት እንደሚጠበቅበት ይታመናል። በሌላ በኩል የአሰሪው አላፊነት በጥፋት ላይ ያልተመሰረተ /strict/ ስለሆነ ካሣ ጠያቂው ወገን በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማሳየት ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ የጉዳት አድራሹን ወይንም የአሰሪውን የአእምሮ ሁኔታ /state of Mind/ ማስረዳት እንደማይጠበቅበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ሟቾች በተጠሪ መስሪያ ቤት ተቀጣሪ ሰራተኞች መሆናቸውና በመስክ ላይ እያሉ በደረሰባቸው አደጋ ሕይወታቸው ማለፍ እና ይኸው አደጋ የደረሰው ደግሞ በተጠሪ ተመድበው በሚሰሩበት የሥራ ቦታና ሰዐት ሳይሆን ከዚህ ውጪ በራሳቸው ፍላጎት በአካባቢው በሌላ ድርጅት የሚሰራውን የድልድይ ግንባታ ለመመልከት ሄደው ድልድዩን ተመልክተው ሲመለሱ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። አደጋው የደረሰው ከስራ ሰዓትና ከስራ ቦታ ውጪ ከስራው ጋር ግንኙነት በሌለው አጋጣሚ እና ከአሠሪው ትዕዛዝ ሳይኖር መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠ ደግሞ ተጠሪ በአሰሪነቱ ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆንበት ምክንያት የሌለ መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 95፣ 96 እና 97 ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያል። በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች የሞቱት በስራ ላይ በደረሰ አደጋ አይደለም በማለት የካሣ ክፍያ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ መወሰናቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 68011 ሕዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም በመ/ቁጥር 68045 ሕዳር 16 ቀን 2003 ዓ.ም ፣ በመ/ቁጥር 68012 ሕዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 98936 የካቲት 26 ቀን 2003 ዓ.ም. በመ/ቁጥር 99000 የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም. ፣ በመ/ቁጥር 98933 የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም. የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት በድምጽ ብልጫ ጸንቷል።
2. ሟቾች ሕይወታቸው ያለፈው በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ባለመሆኑ ለአመልካቾች የሚከፈል የካሣ ክፍያ የለም ብለናል።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሣኔ ግልባጩ ከሰ/መ/ቁጥር 68139 እና 68140 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሀሣብ ልዩነት

እኛ ስማችን በሶስተኛ ተራ ቁጥር እና በአራተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምነው ዳኞች አብላጫው ድምፅ ሚችዎች ህይወታቸው ያለፈው በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ባለመሆኑ ለአመልካቾች የሚከፈል የካሣ ክፍያ የለም በማለት በሰጠው ውሣኔ የማንስማማ በመሆኑ በሀሣብ ተለይተናል፡፡

ከአብላጫው ድምፅ የምንለይባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመጀመሪያው ልዩነታችን የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች የተጠሪን ሠራተኞችና የተጠሪ የሥራ መሪ የሆነውን ሰው አደጋው በሥራ ላይ እያሉ የደረሰ መሆኑን ያለባቸውን የማስረዳት ግዴታና ተጠሪ ሠራተኞቹ በሥራ ላይ አደጋ ያልደረሰባቸው መሆኑን ያለበትን የማስረዳት ግዴታ የተረጎመበትና የተረዱበት አግባብ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር ባደረገው የሥራ ውል ከቀይ አፈር አስከቱርሚ ያለውን መንገድ ለመገንባት የሥራ ተቋራጭነት ውል የተዋዋለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በውል የተረከበውን የመንገድ ሥራ ለማከናወን የቀጠራቸውን ሠራተኞችና የግንባታ መሣሪያዎች እንዲያስተዳድርለትና የመንገድ ሥራ ኘሮጀክቱን በበላይነት እንዲመራለት ሚች ኢንጅነር ደምሴ ወርቁን የቀይ አፈርቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አድርጎ መድቦት የነበረ መሆኑ ግራ ቀኙ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በሰበር በተደረገው ክርክር ያልተካደና የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለመንገድ ሥራ ኘሮጀክቱ በመደባት የመለያ ቁጥር 3-43639 መኪና የትራንስፖርት አገልግሎት እያገኙ እያሉ “ወራባ” ከተባለው ወንዝ በደራሽ ጎርፍ ውሀ የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም ተወስደው ህይወታቸው ካለፈው አራት ሰዎች ውስጥ አንደኛው ማለትም ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ የቀይ አፈርቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የነበረ ነው ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ እንደተሻሻለ በተደነገገው መሠረት የድርጅቱ /የተጠሪ/ ሥራ መሪ ናቸው፡፡

ሌሎቹ በአደጋው ህይወታቸው ያለፈው ሰዎች ማለትም ኢንጅነር ዳዊት ሀይለማርያም ኢንጅነር ሉሊት ታምራትና የተጠሪ ሠራተኞች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በእኛ እምነት ሚች ኢንጅነር ዳዊት እና ኢንጅነር ሉሊት የሞት አደጋ የደረሰባቸው ሥራ በመሥራት ላይ እያሉ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ኢንጅነር ዳዊትና ኢንጅነር ሉሊት ወደ “አምራቱ” ወንዝ የመስክ ሥራ ጉብኝት ለማድረግ የሄዱት በአሰሪው /በተጠሪው/ ትዕዛዝ በተሰጣቸው የሥራ ስምሪትና ትዕዛዝ መሠረት ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው ነጥብ መመለስ አለበት፡፡ የቀይ አፈር ቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ ተጠሪ በተቋራጭነት የሚሠራውን የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመሥራት አስፈላጊ ነው የሚለውን ሥራ እንዲሰሩና ከሙያቸው ጋር ተያያዥነት ያለውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ በሥሩ የሚገኙትን ሰራተኞች የማሰማራት ሥልጣን እንዳለው ይገመታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ካሉት ሠራተኞች የተወሰኑትን ብቻ ለይቶ ከመደበኛ የሥራ ቀናት ፣ ከመደበኛ የሥራ ሠዓትና ከመደበኛው የሥራ ቦታ ውጭ ለሥራ ሊያሠማራና የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት እንደሚኖረው የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ልዩ የሥራ ባህሪና በግንባታው ሥራ መስክ የዳበሩ የአሠራር ልምዶችን በተለይም ስለግንባታ አካሄድ የወጣውን የሥራ መመሪያ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ የኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ለነበረው ለኢንጅነር ደምሴ ወርቁ የሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት ሠራተኞችን ለሥራ የማሰማራትና ለሥራው አፈፃፀም ጠቀሜታ ያለው የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደረጉ ለማድረግ የሚያስችለው እንደነበር የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ከመደበኛው የሥራ ቀናት ከመደበኛ የሥራ ሠዓትና ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ የድርጅቱን ሠራተኞች ለሥራ የማሰማራትና የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣን ያልነበረው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም እንጅ ማስረጃ ቢያቀርብ እንኳን በሥራ አስኪያጅ ሥልጣን ላይ ተጠሪ የጣለውን ገደብ የኘሮጀክቱ ሠራተኞች በጠቅላላውና ሚችዎች ኢንጅነር ዳዊትና ኢንጅነር ሉሊት በግልፅ እንዲያውቁት ያደረገ መሆኑንና ሚችዎች ሥራ አስኪያጅ ከሥራ ከመደበኛ ሥራ ቀናቶች ከመደበኛ የሥራ ሠዓታቸውና ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው ውጭ እንዲሰማሩና የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ የማዘዝ ሥልጣን እንደሌለው የሚያውቁ መሆኑን የማስረዳት ግዴታና ሀላፊነት አለበት፡፡ ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት ከቀረበው ክርክርና በሰበር ከቀረበው ክርክር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ተጠሪ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ በነበረው የኢንጅነር ደምሴ ወርቁ ሠራተኞችን ከመደበኛ የሥራ ቀናቶች ውጭ ለሥራ የማሰማራት ሥልጣንና ኃላፊነቱ የተገደበ መሆኑን አላስረዳም፡፡ አንድ ሠራተኛ በሥራ ውሉና በሥራ ደንቡ መሠረት በአሰሪው የሚሰጠውን የሥራ ስምሪትና ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ሚች ኢንጅነር ዳዊትና ኢንጅነር ሉሊት የካቲት 23 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀይ አፈርቱርሚ ኘሮጀክት ውጭ “በአሞራቴ” ወንዝ ላይ በመሠራት ላይ የነበረውን ድልድይ ከቦታው ድረስ በመሄድ የሙያ የመስክ የሥራ ጉብኝት ያደረጉ መሆኑን አመልካቾች ያልካዱትና የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ሚች ኢንጅነር ዳዊትና ኢንጅነር ሉሊት ከመደበኛ የሥራ ቀናት ውጭ በእረፍት ቀናቸው ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው ውጭ የሚገኘው በአሞራቴ ወንዝ ላይ እየተሠራ የነበረውን ድልድይ ለማየት የሄዱት ተጠሪን በመወከል የመንገድ ሥራ ኘሮጀክቱን በኃላፊነት ሲመራ የነበረው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የድርጅቱን መኪና እና ሹፌር በማንቀሣቀሥና ሥራ አስኪያጅም አብሮ በመንገዝ እንደሆነ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የመስክ ጉብኝቱ የኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ሚችዎች በእረፍት ቀናቸው ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ የመሥክ የሥራ ጉብኝት ማድረጋቸው ተጠሪ በተቋራጭነት የያዘውን የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመሥራት ጠቃሚታ እንዳለው አምኖበትና አውቆት እንደዚሁም የድርጅቱ ሥራ መሪ የመስክ የሥራ ጉብኝቱ ተካፋይ ሆኖበት የተከናወነ ነው፡፡

ሚች ኢንጅነር ዳዊትና ሚች ኢንጅነር ሉሊት በደራሽ ጎርፍ ውሀ የተወሰዱት ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው ከቀይ አፈርቱርሚ ኘሮጀክት ክልል ውጭ ሣይሆን በመደበኛ የሥራ ቦታቸው በተለይም ከመኖሪያ ሠፈራቸው በሁለት ኪሎ ሜትር ዕርቀት በሚገኘው “ወራባ” በተባለው ወንዝ መሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ሚችዎች በእረፍት ቀን ከመኖሪያ ሠፈራቸው ወጥተው በአሞራቴ ወንዝ ላይ እየተሠራ የነበረውን ድልድይ ለመጎበኘት የተጓዙትና ከዚያም በኋላ ከሄዱበት የመስክ የሥራ ጉብኝት ተመልሰው በቀይ አፈርቱርሚ ኘሮጀክት ክልል ውስጥ በደራሽ ጎርፍ የተወሰዱት የተጠሪ የሥራ መሪና የመንገድ ሥራ ኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ በነበረው ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ ተግባራዊ እንዲሆን ባደረገው የመስክ የሥራ ጉብኝትና በሰጠው የሥራ ስምሪት ትዕዛዝ መሠረት ነው፡፡ ሚችዎች በእረፍት ቀናቸው የመስክ የሥራ ጉብኝት እንዲያደርጉ የኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ የሰጠው የሥራ ስምሪት በአሰሪው ማለትም በተጠሪ እንደተሰጠ የሥራ ሥምሪት ትዕዛዝና የመስክ የሥራ ጉብኝት የሚቆጠር መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ ድንጋጌዎች ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2188 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብና ህጋዊ ውጤት ለመረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች ሚች ኢንጅነር ዳዊትና ሚች ኢንጅነር ሉሊት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው መሠረት ከአሠሪያቸው /ከተጠሪ/ በእረፍት ቀናቸው ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው ውጭ እንዲያከናውኑ የተሰጣቸውን የመስክ ሥራ ጉብኝት ትዕዛዝ አከናውነው ሲመለሱ በቀይ አፈርቱርሚ ኘሮጀክት ክልል አደጋ የደረሰባቸው መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 ፣ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2188 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የማስረዳት ግዴታቸውን ተወጥው እያለ የሥር ፍርድ ቤት ሚች ኢንጅነር ዳዊትና ሚች ኢንጅነር ሉሊት በሥራ ላይ እያሉ አደጋ የደረሰባቸው መሆኑን አመልካቾች አላስረዱም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ከላይ የዘረዘርናቸውን ሁኔታዎችና የህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ሀሣብ አለን፡፡

ሚች ኢንጅነር ዳዊትና ሚች ኢንጅነር ሉሊት አሠሪያቸው /ተጠሪ/ ኘሮጀክቱን በበላይ ኃላፊነት ይመራ በነበረው ሥራ አስኪያጅ የተሰጣቸውን የመስክ ሥራ ስምሪትና የመስክ ሥራ ጉብኝት በማክበር በእረፍት ቀናቸው ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጭ የሚገኘውን “የአሞራቴ” ወንዝ ላይ የሚሰራውን ድልድይ ጎብኝተው ከተመለሱ በኋላ በቀይ አፈርቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ክልል ውስጥ በደራሽ ጎርፍ ተወሰደው የሞት አደጋ ደርሶባቸዋል ፡፡ አንድ ሠራተኛ ከሥራ ቦታው ወይም ከመደበኛ ሥራ ሠዓት ውጭም ቢሆን የአሠሪውን ትዕዛዝ ሥራ ላይ ሲያውል በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳት በሥራ ላይ የደረሰ ጉዳት እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /ሀ/ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ሚችዎች የመስክ የሥራ ጉብኝት በማድረግ በእረፍት ቀናቸው አይተውት የተመለሱት በአማራቴ ወንዝ ላይ እየተሠራ ያለው ድልድይ ከሚችዎች የመደበኛ የሥራ ቦታ ክልል ውጭ የሚገኝ መሆኑን በመመልከት ብቻ የበታች ፍርድ ቤቶች አደጋው በሥራ ላይ የደረሰ አይደለም በማለት የሰጡት ትርጉምና የደረሱበት መደምደሚያ ሚች ኢንጅነር ዳዊትና ሚች ኢንጅነር ሉሊት በኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ የተሰጣቸውን የሥራ ስምሪትና ትዕዛዝ በመፈፀም ላይ እያሉ አደጋው የደረሰ መሆኑን ያላገናዘበና የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /ሀ/ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

በመሆኑም አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካቾች ሚች ኢንጅነር ዳዊትና ሚች ኢንጅነር ሉሊት በእረፍት ቀናቸው እንዲያከናውኑ በአሠሪያቸው/ በተጠሪ/ የተዘጋጀውን የመስክ ሥራ ጉብኝት በማከናወን ላይ እያሉ “ወራባ ” ተብሎ በሚጠራው ወንዝ በገጠማቸው በደረሰ የጎርፍ ውሀ ተወሰደው የሞት አደጋ የደረሰባቸው መሆኑን የማስረዳት ግዴታቸውን የተወጡ በመሆኑ አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካቾች በሚችዎች መሞት ለደረሰባቸው ጉዳት ከአሠሪና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 110 መሠረት ተጠሪ ካሣ እንዲከፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ ፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2188 ንዑስ አንቀፅ 1 ፣ የአዋጅ ቁጥር 37796 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /ሀ/ መሠረት ያደረገ ህጋዊ ጥያቄ ነው በማለት በሀሣብ ተለይተናል፡፡

2. የተጠሪ የሥራ መሪ የነበረውና የቀይ አፈርቱርሚ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የነበረው ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ በእረፍት ቀኑ ከሌሎቹ ባለሙያዎች ጋር የመስክ የሥራ ጉብኝት አድርጎ ሲመለስ በደረሰበት አደጋ ህይወቱ ያለፈ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ሟች ኢንጅነር ደምሴ የኘሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅና የሥራ መሪ ቢሆንም ከአሠሪው ጋር ያለው ግንኙነትና ሌሎች መብቶችን በተመለከተ የሥራ ውሉንና የአዋጅ ቁጥር 377/96 አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን በተጠሪና በሟች ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ መካከል ከተደረገው የሥራ ውል ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የመንገድ ሥራ ግንባታን በኃላፊነት የሚመራ ሥራ አስኪያጅ በሌላ የሥራ ተቋራጭ በመሠራት ላይ የሚገኝ ድልድይ በአካል ተገኝቶ መጎብኘት ሙያዊ ልምድ መቅሰሙና ሌሎች ባለሙያዎችም የሙያ ልምድ የሚያገኙበትን የመስክ የሥራ ጉብኝት ማመቻቸቱ በግንባታ ኘሮጀክት የሥራ አመራር ሂደት ያልተለመደና የአመራር ጉድለትና ጥፋት መሆኑን ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ እንደሌለ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ የተጠሪ የሥራ መሪ ሆኖ የመንገድ ኘሮጀክት ሥራ በሀላፊነት ሲመራ በእረፍት ቀኑ ጭምር ሥራውን በትጋት በመፈፀም ላይ እያለ የሞት አደጋ የደረሰበት መሆኑን ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸው ዝርዝር ጉዳዮች ያሣያሉ፡፡ ስለሆነም ሶስተኛ ተጠሪዎች ሟች ኢንጅነር ደምሴ ወርቁ የተጠሪን የመንገድ ሥራ ኘሮጀክት ሥራ በትጋት ሲመራና በእረፍት ቀኑ ሲሰራ የሞት አደጋ የደረሰበት በመሆኑ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 110 መሠረት ካሣ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የሥራ ውሉን መሠረት ያደረገና ህጋዊ ጥያቄ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ሊሻርና ተጠሪ ለአመልካቾች ካሣ እንዲከፍል ሊወሰንበት ይገባል በሚል ፅምነት በሀሣብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 61717

ጥር 15 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ አበበች አዱኛ በራሳቸውና በህጻን ረቂቅ

ተክሉ ስም - ከጠበቃ ሓጎስ አብርሃ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተንዳሆ ቤቶች ልማት

ፕሮጀክት ጽ/ቤት- የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስራ ላይ በደረሰ የሞት አደጋ ምክንያት ለጥገኞች የሚከፈል ክፍያ ጋር በተያያዘ የተነሳ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት ነዉ፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ ባለቤታቸውና የህጻን ረቂቅ ተክሉ አባት የነበሩት አቶ ተክሉ አያኖ በተከሳሽ ዘንድ በጊዜያዊ ሰራተኝነት ተቀጥረው ከመጋቢት 16 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምረው ብር 6,710 የወር ደመወዝ እየተከፈላቸው ይሰሩ እንደነበረ፣ መስከረም 07 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ስራ ቦታቸው በተከሳሽ መኪና በመንገዝ ላይ እያሉ በደረሰ አደጋ መሞታቸውን፣ ተከሳሽ በህጉ መሰረት ተገቢውን ክፍያ ለመፈጸም ፍቃደኛ መሆኑን በ26-6-2000 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ገልጾ የነበረ ቢሆንም ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ.ም በባንክ በኩል ለከሳሽ የከፈለው ግን ብር 27,051 ብቻ መሆኑን፣ ተከሳሽ በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 94(2) እና አዋጅ ቁ.262/94 አንቀጽ 46 መሰረት ለሟች ተተኪዎች የሚቹን የዓመት ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ ካሳ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን፣ በዚህ መሰረት ከከፈለው ሌላ የሚቀርበትን ብር 375,549 እንዲከፍል ተጠይቆ በ22-9-2000 ዓ.ም በጻፈው መልስ ፈቃደኛ ያለመሆኑን ማሳወቁን ገልጾው ተከሳሽ ይሄንን ቀሪ የካሳ ክፍያ ከየካቲት 30 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድና ከክሱ ወጪዎች ጋር እንዲከፍል እንዲወሰንበት የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ የፍርድ ቤቱ ስልጣን ተነስቶ ውድቅ ተደርጎ የታሰፈ ስለመሆኑ ተመልክቶ በፍሬ-ጉዳዩ ላይ የተሰጠው የመልስ ፍሬ-ሃሳብ፡- በእርግጥ ሟችን በጊዜያዊ ሰራተኝነት ቀጥሯቸው በኤርታሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የኮንስትራክሽን እና ኦፊስ ኢንጅነሪንግ መምሪያ ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ እንደነበረ በመግለጽ ሟች የሞቱት ያልተፈቀደላቸውን የሠ.ቁ.3-27289 የሆነ ፎርድ ፒክአፕ መኪና እያሽከረከሩ ከአዲስ አበባ ወደ ዱብቲ ሲጓዙ በደረሰባቸው የመገልበጥ አደጋ መሆኑን፣ ሟች የተቀጠሩት ባላቸው የምህንድስና ሙያ እንጂ በሹፌርነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለመሆኑን፣ ሚች ይዘውት የነበሩውን መኪና የተረከቡት አቶ ሞገስ ጀንበሩ የተባሉ ሹፌር ቢሆኑም ሚች መኪናውን ከሹፌሩ ነጥቀው አዲስ አበባ ውስጥ ሲጠቀሙበት ከቆዩ በኋላ በራሳቸዉ አሽከርካሪነት 4 የፕሮጀክቱን ሰራተኞች ጭነው ወደ ዱብቲ ሲጓዙ መኪናዋ አቅጣጫ ስታ ከመንገድ ወጥታ መገልበጧን፣ ሚች በራሳቸው ስህተት በፈጠሩት አደጋ ተከሳሽ ተጠያቂ ስለማይሆን፣ በአገራችን ባለው የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት በሚወስኑት ህጎች እንዲሁም በአዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 47(ሐ) በተቀመጠው ትርጉም መሰረት በሚች ላይ የደረሰው ጉዳት በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ሊባል የማይችል በመሆኑ በህጉ ላይ ለተተኪዎች ይከፈላል ተብሎ የተወሰነውን ካሳ ከሳሾች የመጠየቅ መብት የሌላቸው በመሆኑ፣ ጉዳቱ በስራ ላይ የደረሰ ባይሆንም ሚች ከዚህ በፊት በቋሚነት በተለያየ ቦታ ያገለገለ መሆኑን ከግምት በማስገባት ከብር 100,000 በላይ ሰራተኞችን አስተባብሮ ለከሳሽ የከፈለ መሆኑን ገልጸ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ እና የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት ሚች የሞቱት በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን በመመርመር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በዚሁ የበታች ፍርድ ቤት የተረጋገጡት ፍራ-ነገሮች አደጋው በደረሰ ጊዜ ሚች ያሽከረክሩት የነበረው መኪና በእርግጥ ከፕሮጀክቱ ጽ/ቤት ለበዓል ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ይዘውት ያልመጡ እና ሌላ ተሽከርካሪ በመያዝ የመጡ ስለመሆኑ፣ አዲስ አበባ የሚሊንየም በዓሉን አሳልፈው ወደ ስራ ቦታ ሊመለሱ ሲዘጋጁ የስራ አስኪያጁ መኪና በመበላሸቱ ሚች ይዘውት የመጡት መኪና ለስራ አስኪያጁ ተሰጥቶ አደጋው የተከሰተበት መኪና በዚህ ሂደት ሊይዝ እንደቻለ፣ ቀድሞ ሚች ይዘውት የመጡት መኪና በኃላፊነታቸው የተሰጣቸው እና አሁን አደጋው የተከሰተበት መኪና ደግሞ ከኃላፊው ጋር በመቀያየር ሂደት ሚች እጅ የገባ ስለመሆኑ፣ ሚችም ወደ ስራ ቦታቸው ዱብቲ ሲሄዱ 4 የፕሮጀክቱን ሰራተኞች ይዘው በመጓዝ ላይ እያሉ በአደጋው ምክንያት ህይወታቸው ሊያልፍ ስለመቻሉ ናቸው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ከላይ የተመለከቱትን ፍራ-ነገሮች ካጣራ በኋላ ጉዳቱ የደረሰው በስራ ላይ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ከፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 47(2)(ሐ) አኳያ መርምሮታል፡፡ የተሰጠውም ውሳኔ የዚህ ድንጋጌ ይዘት “…….መስሪያ ቤቱ ለሰራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የማንቀሳቀሻ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳት……” ከሆነ ብቻ በመሆኑ፣ አደጋዉ የደረሰበት ሰራተኛ ይጓዝ የነበረው መስሪያ ቤቱ “…for the common use….” እየተጠቀመ ባለበት ወቅት እንጂ በዚህ ጉዳይ ሚች ለግሉ መጠቀሚያ በቀጥታ ተሰጥቶት ወይም ከሌላ ባለስልጣን ጋር ተቀያይሮ ሲያሽከረክር የደረሰን አደጋ አይመለከትም፣ አደጋውን ያደረሰው መኪና ተጠሪ ለሰራተኞች መጓጓዣ እንዲያገለግል በመደበው የጋራ መጓጓዣ ሳይሆን በስራ ኃላፊነታቸው የተነሳ እንዲጠቀሙበት በግል የተሰጣቸውን መኪና ሲያሽከረክሩ የደረሰ አደጋ በመሆኑ በስራ ላይ የደረሰ አደጋ ሊባል ስለማይችል ከሳሾች በጠቀሱት ህግ ላይ ከደረሰ ጉዳት ጋር በተያያዘ ጊዜያዊ ሰራተኛ ሲሞት ለተተኪዎች የሚከፈለውን ካሳ ተጠሪ እንዲከፍል አመልካች ለመጠየቅ መብት የላቸውም የሚል ነው፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ግራ ቀኙ ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፌ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች ጥቅምት 15 ቀን 2003 ዓ.ም በሁለት ገጽ በተጻፈ አቤቱታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉዋቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነጥቦች ያነሱ ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- ሟች አደጋው የደረሰባቸው መስሪያ ቤቱ በመደበላቸው መኪና እየተጓዙ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ በጋራ ለሰራተኞች አገልግሎት የተመደበ ካልሆነ በኃላፊነታቸው ለሟች የተመደበን መኪና ለሰራተኞች በጋራ የተመደበ ባለመሆኑ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ አይቆጠርም ወደሚለው መደምደምያ መደረሱ የድንጋጌውን ይዘት ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ በወቅቱ ሟች 4 የፕሮጀክቱ ሰራተኞችን በመያዝ ወደ ስራ ቦታቸው በመጓዝ ላይ እያለ የደረሰ አደጋ በመሆኑ የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት ታርሞ በክሳችን የተመለከተው ክፍያ እንዲፈጸምልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በቀን 17-5-2003 ዓ.ም በሁለት ገጽ በተጻፈ መልስ የሰጠ ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- ድርጅታችን በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚተዳደር ስለመሆኑ ከዚህ በፊት ይዜ የፌ/ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.38250 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ፣ በዚህ ጉዳይ የፌ/መንግስት ሰራተኞች አዋጅን መሰረት በማድረግ ውሳኔ መሰጠቱ አግባብነት የሌለው በመሆኑ፣ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በተመለከተ ደግሞ ሟች የስራ መሪ በመሆኑ ይሄንንም መሰረት በማድረግ ክስ ሊያቀርብ የማይችል በመሆኑ፣ ሟች አዲስ አበባ ካለው መኖሪያ ቤታቸው ድርጅቱ ወደ አዘጋጀላቸው ዱብቲ ወደ ሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በመጓዝ ላይ እያሉ የደረሰ አደጋ በመሆኑ በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ የማይወሰድ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት የተከራከሩ ሲሆኑ በዚሁ መልሳቸው 2ኛ ገጽ ላይ መስቀለኛ ይግባኝ በማለት የተጻፈ ሲሆን ተገቢውን ስነስርዓት በመጠበቅ የቀረበ ባለመሆኑ ታልፎአል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ ያቀረቡ ሲሆን በዚህም ላይ በሟች እና ተጠሪ መስሪያ ቤት መካከል የቅጥር ውል ሲደረግ በስራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ለሚከፈለው ክፍያ ተፈጻሚነት ያለው ህግ አዋጅ ቁ.262/94 በአዋጅ ቁ.515/99 እንደተሻሻለው ስምምነት ያለ በመሆኑ በዚሁ ስምምነት መሰረት ክፍያ እንዲፈጸምልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ የአመልካች ባለቤት(ሟች) የሞቱት በስራ ላይ በደረሰ ጉዳት አይደለም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከፌ/መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 47(2)(ሐ) አኳያ ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በግራ ቀኙ መካከል ባለው ክርክር አግባብነት ያለው የህግ ማዕቀፍ እና ጉዳዩን ለመመልከት ስልጣን ያለውን አካል በተመለከተ በበታች ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር ተጠሪ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ እና የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ በመጥቀስ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ያለመሆኑን ከመከራከር ውጪ አዋጆቹ በግራ ቀኙ ባለው ክርክር ላይ ተፈጻሚነት የሌላቸው ስለመሆኑ ያነሳው ነጥብ ስለመኖሩ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ባቀረበው ክርክር ደግሞ በአንድ በኩል የተጠሪ ጽ/ቤት ውስጥ የሚነሳው ተመሳሳይ አለመግባባት የሚታየው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ስለመሆኑ ከዚህ በፊት ይዜ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በመጥቀስ በፌ/መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ሊታይ እንደማይገባ ሲከራከር በሌላ በኩል ደግሞ ሟች የስራ መሪ መሆኑን በመጥቀስ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በዚህ ክርክር ላይ ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑን ተከራክሯል፡፡ በተጨማሪም አመልካች ቀደም ሲል ጉዳዩን ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት አቅርበው ጉዳዩን የመመልከት ስልጣን የሌለው መሆኑን በማመልከት ክሱን የዘጋ ስለመሆኑ ከክርክር ሂደቱ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ክሳቸውን ሲያቀርቡ በግራ ቀኙ መካከል ባለው የስራ ውል መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገቢው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ተገቢውን ዳኝነት በመክፈል ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ መልኩ ሚች የተቀጠረው በኮንስትራክሽንና ኦፊስ ኢንጂነር መምሪያ ኃላፊ ሆኖ በጊዜያዊነት መሆኑ ያላከራከረ በመሆኑ የስራ መሪ ሊባል የሚችል የስራ መደብ ላይ የተቀጠረ በመሆኑ በሚች እና ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው የስራ ውል ደግሞ ለህግ እና ሞራል ተቃራኒ ነው የሚል ክርክር ያልተነሳ በመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገ ስምምነት ደግሞ በተስማሙት አካላት መካከል ህግ ሆኖ የሚያገለግል ስለመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁ.1731 የሚያስገነዝበን በመሆኑ ከዚሁ በሚች እና በተጠሪ ጽ/ቤት መካከል ተደርጎ በነበረው ስምምነት መሰረት የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሰረት ተመሳሳይ አለመግባባቶች ሲከሰቱ ማለትም በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ስለመሆን አለመሆኑ ለመወሰንም ሆነ የካሳ አከፋፈልን በተመለከተ ሊፈቱ የሚገባቸው በፌ/የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሰረት መሆን እንዳለበት በግራ ቀኙ በተደረገው የስራ ውል አንቀጽ 5 ስር በግልጽ በማመልከት የስምምነታቸው አካል አድርገውታል፡፡ በዚሁ መሰረት የተረጋገጡትን ፍራ-ነገሮች ይዘን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት የበታች ፍርድ ቤቶች በሚች ላይ የደረሰው አደጋ በስራ ላይ የደረሰ አይደለም ወደሚለው መደሚደሚያ የደረሱት አደጋውን ያስከተለው መኪና ሚች ይዞት የመጣው ተሽከርካሪ የስራ አስኪያጁ መኪና በመበላሸቱ ለስራ አስኪያጁ እንዲሰጥ ተደርጎ በዚህ መቀያየር ሂደት በእጁ የገባ ስለመሆኑ እና ሚች ለሚሊኒየም በዓል የተሰጠውን እረፍት ጨርሶ ወደ ስራ ቦታው እየተመለሰ ባለበት ወቅት የተከሰተ አደጋ መሆኑን በፍራ-ነገር ተቀብለው እያለ መኪናው በጋራ ለሰራተኞች የተመደበ ባለመሆኑ በሚል ነው፡፡ የፌ/መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 47(2)(ሐ) ስንመለከት መስሪያ ቤቱ ለሰራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳት በማለት ከሚደነግግ ውጪ አንድ ሰራተኛ ባለው ኃላፊነት በግሉ ተሽከርካሪ ተሰጥቶት እየተገለገለበት ባለበት ሁኔታ የተከሰተን አደጋ አይጨምርም ማለት ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በህጉ በግልጽ ከተመለከተው የድንጋጌው ይዘት ውጪ የደረሱበት መደምደሚያ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡት ፍራ-ነገሮች ሚች ህይወቱ ሊያልፍ የቻለው በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡ ሁነው እያለ በስራ ላይ የደረሰ አደጋ አይደለም መባሉ ተቀባይነት ያለው ባለመሆኑ በሚች ላይ የደረሰው የሞት አደጋ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ብለናል፡፡

የካሳውን መጠን በተመለከተ ሚች የተቀጠረው በጊዜያዊነት በመሆኑ እና በፌ/የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ የተቀመጠውና ለጊዜያዊ ሰራተኛ ተፈጻሚነት ያለው የካሳ ክፍያ በግራ ቀኙ የስራ ውል መሰረት በተመሳሳይ ተፈጻሚነት ሊኖረው እና በዚህ የካሳ ክፍያ መጠን ላይ የተነሳ ክርክር የሌለ በመሆኑ እና ለዚህም አግባብነት ያለው ድንጋጌ የአዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 94(2) እና አዋጅ ቁ.262/94 አንቀጽ 46(2)(5(ለ)) በመሆኑ ከዚሁ አኳያ ተሰልቶ ለአመልካች የጉዳት ካሳ ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡ ግራ ቀኙ ባደረጉት የቅጥር ውል መሰረት የውላቸው አካል ባደረጉት እና በዚህ መልኩ አለመግባባት ሲፈጠር ተፈጻሚነት እንደሚኖረው በተስማሙት ድንጋጌ መሰረት የካሳውን መጠን ማስላት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በስራ ላይ በደረሰ ጉዳት የሞተው ሰራተኛ ጊዜያዊ ተቀጣሪ ከሆነ የአንድ ዓመት ደመወዙ በአምስት ተባዝቶ ለተተኪዎች በጉዳት ካሳ መልክ እንደሚከፈል ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል የሚች የወር ደመወዝ 6,710 (ስድስት ሺህ ሰባት መቶ አስር ብር) ስለመሆኑ ያከራከረ ነጥብ አይደለም፡፡ በመሆኑም (6,710 x 12)5 = 402,600 ብር (አራት መቶ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ብር) ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከዚህ የካሳ ክፍያ መጠን ውስጥ ቀደም ሲል አመልካች 27,051 ብር (ሃያ ሰባት ሺህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኃምሳ አንድ ብር) በተጠሪ መስሪያ ቤት የተከፈላቸው ስለመሆኑ ያመኑ በመሆኑ ይሄው ገንዘብ ሲቀነስ ቀሪ ክፍያ 402,600 — 27,051 = 375,549 ብር (ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር) ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የተጠሪ ድርጅት ለአመልካች 375,549 ብር (ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር) እንዲከፍል ብለናል፡፡

ባጠቃላይ በሟች ላይ የደረሰው የሞት አደጋ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በስራ ላይ የደረሰ አደጋ አይደለም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. በቀን 10-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.122319 መጋቢት 7 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በሟች አቶ ተክሉ አያኖ ላይ የደረሰው የሞት አደጋ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ድርጅት ለሟች ተተኪዎች (ለአመልካች) ብር 375,549 (ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር) እንዲከፍላቸው ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 74636

ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም

ተጠሪዎች፡-1.ትዕግስት ሙሉዓለም

2. መስፍን ምስጌ
3. እቴነሽ ወጋዬሁ
4. ከተማ ዋና
5. ዲላወርቅ ግርማ
6. ጽጌረዳ አዲሱ
7. ሰናይት ማዘንጊያ
8. ትዝታነሽ በራዩ
9. ጌትነት መሀሪ
10. አንተነህ አጋር
11. መስፍን ምትኩ
12. ሂሩት ሚደቅሳ
13. ብርቱካን በረሳ
14. መንበረ ወንድማገኝ
15 .ተስፋዬ ማሞ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

ለዚህ ለሰበር መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት በሐዋሳ ከተማ የመ/ደ/ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ተከሳሽ የድርጅቱን ምርታማነት ለማሳደግ የመዋቅር ለውጥ አድርጌአለሁ በሚል የስራ ውላችንን ሲያቋርጥ የስንብት ክፍያ ብቻ በመክፈል ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳይኖር የ15 ቀናት ደመወዝ ሳይከፍል ያዘገየ በመሆኑ ያልከፈለውን ደመወዝና በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 38 መሰረት ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ እንዲከፍልና የስራ ልምድ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠን ይወሰንል የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው መልስ ተከሳሽ በመዋቅር ለውጥ ምክንያት ሰራተኞችን ስመድብ ከሳሾች በምደባው ባለመካተታቸው ክፍያ በጠየቁት ወቅት በስራ ላይ አልተገኙም፣ የ15 ቀናት ደመወዝ አልተከፈለንም ለሚሉትም ስራ የሰሩ ስለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፣ ለከሳሾች በተሰጣቸው የስንብት ደብዳቤ ከእዳ ነጻ ለመሆናቸው ክሊራንስ በማቅረብ ክፍያ እንዲቀበሉ ከመገለጹም በላይ በማስታወቂያና በግል ስልካቸው ጭምር የተዘጋጀላቸውን ክፍያ እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ የታመነውን ክፍያ በመክፈል የሚፈለግብኝን ግዴታ የተወጣሁ ስለሆነ ስራ ስለመስራታቸው ባልተረጋገጠበት የ15 ቀናት ደመወዝና ለዚሁ አከራካሪ ለሆነ ክፍያ ክፍያ ዘግይቷል በሚል የ3ወር ደመወዝ ሊከፈላቸው ስለማይገባ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ጉዳዩን የመረመረው የመ/ደ/ፍርድ ቤትም በሰጠው ፍርድ የስራ ውሉ በተቋረጠበት ወቅት ለ15 ቀናት ከሳሾች ስራ ላይ ስለመሆናቸው መዝገቡ የሚያስረዳ ሲሆን ተከሳሽ ድርጅትም በእነዚህ ቀናት ከሳሾች ስራ ያልሰሩ ስለመሆናቸው የሚያስረዳ ማስረጃ ባለማቅረቡ እስከ ሐምሌ 06 ቀን 2003 ዓ.ም. ድረስ ሥራ ላይ የቆዩበትን የ15 ቀናት ደመወዝ ሊከፍል ይገባል በሚል የወሰነ ሲሆን፣ ለዚሁ አከራካሪ ለሆነው ክፍያ የ3 ወር ደመወዝ ክፍያ ለዘገየበት በቅጣት መልክ እንዲከፍል የጠየቁት ግን ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

በስር ከሳሾች ይግባኝ ጠያቂነት ጉዳዩን የመረመረው የከተማው ከፍተኛው ፍርድ ቤት በበኩሉ በሰጠው ፍርድ የሐምሌ ወር የ15 ቀናት ደመወዝ በሐምሌ ወር መክፈል ሲገባው ሳይከፍል በማዘግየት በነሐሴ ወር የከፈለ ስለመሆኑ የሰነድ ማስረጃዎች ስለሚያሳዩና መልስ ሰጪው ክፍያውን ለማዘግየቱ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ስለመኖሩ ስላላስረዳና ሰራተኞቹ በስራ ላይ በተባለው ጊዜ ያልነበሩ መሆን አለመሆናቸውን በበቂ ማስረጃ የማስረዳት ሸክም የመልስ ሰጪው ሆኖ እያለ ይህንኑ ስላላረጋገጠ ክፍያው ለዘገየበት የ2ወር ደመወዝ ለእያንዳንዳቸው ሊከፍል ይገባል በሚል የስር የመ/ደ/ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የይግባኝ ባዩን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን በማሰናበቱ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

ሰበር አቤቱታም አመልካች በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብ፡- በሰራተኛ ምደባና ቅነሳ መሀል ባሉት ጊዜያት ሰራተኛው በሥራ ገበታ ላይ ለመገኘቱ ጊዜ ተወስዶ ከተረጋገጠ በኋላ ለተሰናበቱት ሰራተኞች የስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና እና የዓመት ዕረፍት ክፍያ በአንድ ጊዜ ከተፈጸመላቸው በኋላ የ15 ቀናት ክፍያ አጠራጣሪና አከራካሪ በመሆኑ ምክንያት ክፍያው የቆየ ሆኖ ሳለ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ክፍያው ዘግይቷል በሚል ለተጠሪዎች የ2 ወር ደመወዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲከፈላቸው የወሰነውም ሆነ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ያጸናው የቅጣት ክፍያን ዓላማ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር በክሱ በተጠቀሱት ቀናት ተጠሪዎች ስራ አልሰሩም ከማለቱ በስተቀር በማስረጃ ማረጋገጥ ባለመቻሉ ምክንያት ክፍያ ላዘገየበት የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፍል የስር ከፍተኛና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የወሰኑት በአግባቡ ስለሆነ ይጽናልን ብለዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካች የ15 ቀናት ደመወዝ በጊዜ ባለመክፈሉ የተነሳ ክፍያ ለዘገየበት ለተጠሪዎች የ2 ወር ደመወዝ እንዲከፍላቸው የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የወሰኑት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ድርጅት ባደረገው የአሰራር ለውጥ ምክንያት ሰራተኞቹን ሲቀንስ ተጠሪዎችም ከስራ የተቀነሱ ስለመሆናቸው መዝገቡ የሚያመለክት ሲሆን በቅነሳው ምክንያት ከስራ ውጪ ለተደረጉ ሰራተኞችም የተለያዩ ክፍያዎችን ከፍሎ እንዳሰናበታቸው ገልጾ የሚከራከር ሲሆን ተጠሪዎችም ቢሆኑ በህጉ መሰረት አመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን የከፈላቸው ስለመሆኑ የሚያምኑት ጉዳይ ነው፡፡ ዋናው የሚያከራክራቸው ጉዳይ ግን የስራ ውሉ ሲቋረጥ የ15 ቀናት ደመወዝ አመልካች በህጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መክፍል ሲገባው ክፍያውን ለመፈጸሙ ነው፡፡ አመልካች ለክፍያው ለመፈጸም በስር ፍርድ ቤት እንደምክንያት የጠቀሰው ተጠሪዎቹ በእነዚህ ጊዜያት ስራ አልሰሩም የሚል ሲሆን ስራ ስለመስራታቸው የተረጋገጠ መሆኑን ደግሞ የከተማው የመ/ደ/ፍርድ ቤት በውሳኔው ገልጿል፡፡ የመ/ደ/ፍርድ ቤትም ክፍያው የዘገየ መሆኑ ቢረጋግጥም ክፍያው አከራካሪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ በመድረስ ተጠሪዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የቅጣቱን ገንዘብ ሳይቀበል ያለፈ ቢሆንም ከፍተኛው ፍርድ ቤት ግን ተጠሪዎች ስራ ያልሰሩ ስለመሆናቸው የማስረዳት ሸክም የአመልካች ነው በሚል ክፍያውን አመልካች ማዘግየቱ ስለተረጋገጠ የ2 ወር ደመወዝ እንዲከፍል ሲል ወስኖበታል፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች በተረጋገጠው ፍሬ ነገር መሰረት ደግሞ አመልካች ሌሎች ክፍያዎችን ከፍሎ የ15 ቀናት ደመወዝ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 መሰረት በ7 የስራ ቀናት ውስጥ አለመክፈሉ ግልጽ ነው፡፡ አመልካች የ15 ቀናት ደመወዝ ያልከፈለው ደግሞ ከፍያው አከራካሪ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 37 ስር እንደተመለከተው አሰሪው ያመነውን ክፍያ በመፈጸም አከራካሪ የሆነ ክፍያን እስከሚጣራ ድረስ ማዘግየት የሚችል ስለመሆኑ ከድንጋጌው መረዳት የሚቻል ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 38 መሰረትም አሰሪው በቅጣት እስከ 3 ወር ድረስ የሚደርስ የሰራተኛውን ደመወዝ ያህል ቅጣት ሊከፍል የሚገደደው ከቁጥጥር ወጪ የሆነ ምክንያት ሳይኖር ወይም በአንቀጽ 37 በተደነገገው መሰረት የሚያከራክር ክፍያ በሌለበት ከቅን ልቦና ወጪ ሰራተኛውን ለመጉዳት ተነሳስቶ ክፍያውን ማዘግየቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች የስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና ሌሎች ክፍያዎችን ሳያዘገይ ለተጠሪዎች መክፈሉን መዝገቡ የሚያመለክት ሲሆን ዘግይቷል የተባለውም 15 ቀናት ደመወዝ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ለ15 ቀናት ተጠሪዎች ስራ ባለመስራታቸው የተነሳ በህጉ በተወሰነው የጊዜ ገደብ አከራካሪው ክፍያ ሳይከፈል ቀርቷል ሲል እየገለጸ ባለበት የክፍያ ጊዜ በመዘግየቱ ብቻ እንደበቂ ምክንያት በመውሰድና አመልካች ሌሎች ክፍያዎችን ሁሉ ስለመፈጸሙ ግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባት በአንቀጽ 38 መሰረት ክፍያ ለዘገየበት ለእያንዳንዳቸው የ2 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የወሰኑት በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 37 ስለአከራካሪ ክፍያ የተደነገገውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት ያደረገ ካለመሆኑም ሌላ በአዋጁ አንቀጽ 38 የተቀመጠውን የገንዘብ ቅጣት ዓላማ ባላገናዘበ መልኩ ስለሆነ ክፍያ ለዘገየበት ለተጠሪዎች የ2 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የሰጡት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሐዋሳ ከተማ የከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/11103 በቀን13/03/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣ እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 55825 በቀን 21/03/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 (1)መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. አመልክች ለተጠሪዎች የ15 ቀናት የደመወዝ ክፍያ ላዘገየበት ለእንዳንዳቸው የ2 ወር ደመወዝ እንዲከፍላቸው የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን የውሳኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348 (1) መሰረት ሽረናል፡፡ ስለሆነም ክፍያ ላዘገየበት ለተጠሪዎች የሚከፍላቸው ክፍያ የለም ብለናል፡፡
3. የስር ፍርድ ቤቶች ለተጠሪዎች አመልካች የ15 ቀን ደመወዝ እንዲከፍላቸውና የስራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ሲሉ የሰጡትን የውሳኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል ፡፡ መዝገቡ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 69153

ጥቅምት 06 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ብርሃኑ ከፍያለው ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ሮማን ይርጋ/ 11 ሰዎች/

1. ጠበቃ ናኦድ አየናቸው/ ስለፋሲል ይርጋና ፍሬ ህይወት
2. ጠበቃ ዘውዱ ዓሊ/ ስለ 10ኛ ና 11ኛ ተጠሪዎች ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተቋቋመ የውርስ አጣሪ አበል መጠን ሊወሰን የሚችልበትን ሕጋዊ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ወ/ሮ ሮማን ይርጋ ፣ ወ/ሮ ቅድስት ይርጋ እና ወ/ሮ ቆንጂት ይርጋ አመልካች ፣ አቶ መስፍን ይርጋ ደግሞ ተጠሪ ፣ እነ አቶ ተፈሪ ይርጋ ስድስት ሰዎች ደግሞ ጣልቃ ገብ ሁነው በተካሄደው የሟች አቶ ይርጋ እንደታ የውርስ ንብረት ማጣራት ክርክር ሲሆን የውርስ ይጣልራልኝ ጥያቄ ያቀረቡት የስር አመልካቾች እነ ወ/ሮ ሮማን ይርጋ ሶስት ሰዎች ናቸው፡፡ ጥያቄው የቀረበለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የአሁኑን አመልካች የውርስ ሃብቱን ለማጣራትና ለማስተዳደር የሾሟቸው ሲሆን አመልካች የውርስ ሃብቱን አጣርተው የውርስ ሃብት ሪፖርቱን ለፍርድ ቤቱ አቅርበዋል፡፡ ሪፖርቱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በተጣራው የውርስ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡ በውርስ ሪፖርቱ ከተካዱት ጉዳዮች አንዱ የውርስ አጣሪው የስራ ዋጋ መጠንን የሚመለከት ሲሆን ውርስ አጣሪው ላጣሩት የውርስ ስራ ከጠቅላላው ንብረት 5% ይገባኛል በማለት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበው የውርስ አጣሪ ስራ ዋጋ መጠን ከተጣራው የውርስ ንብረት መጠን አንፃር ሲታይ የተጋነነ ነው፣ ከወራሽነትም የሚተናነስ አይደለም፣ ወራሾች እያንዳንዳቸው ተጠይቀውም እያንዳንዳቸው ብር 3000.00 /ሶስት ሺህ ብር/ ለመክፈል ፈቃደኞች መሆናቸው ተረጋግጧል የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ ለአመልካች እያንዳንዳቸው ብር ሶስት ሺህ ፣ በጠቅላላው ብር 30,000.00 /ሰላሳ ሺህ ብር/ እንዲከፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስቀየር ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ባጭሩ የውርስ ማጣራቱና የውርስ ንብረት ማስተዳደሩን ተግባር ለማከናወን የሚያስፈልገውን የሥራ ዋጋ አስመልክቶ ከተጠሪዎች መካከል ስምንቱ አስቀድመው በስምምት መጠንኑ የቆረጡ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ፍርድ ቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጠኑ የተጋነነ ነው በማለት መቀነሱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ፣1711 ፣ 959 ድንጋጌዎች አኳያ ጉዳዩ ያልታየ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሣኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ሊጣራ የሚገባው የሕግ ነጥብ መኖሩ ታምኖበት ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ተጠሪዎች ቀርበው የተወሰኑት ከአመልካች ጋር የ5% ስምምነት ማድረጋቸውን በማመን መልስ ሲሰጡ የተወሰኑት ደግሞ ከአመልካች ጋር ያደረጉት ስምምነት የሌለ መሆኑን በመግለፅ በእየራሳቸው በኩል ተገቢው እንዲወሰን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የስር ፍርድ ቤት የአጣሪውን የአገልግሎት ዋጋ መጠን በመቀነስ የሠጠው የውሣኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም ?የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በመሰረቱ የውርስ አጣሪ መሆን የሚችለው፡- ያለኑዛዜ ወራሽ የሆነ ሰው፣ ይህም ልጅ፣ ልጅ ከሌለ ወላጅ ፣ ወንድም እህት፣ በኑዛዜ ጠቅላላውን የሟች ንብረት እንዲወርስ ኑዛዜ የተደረገለት ሰው፣ አካለመጠን ያልደረሱ ወይም በህግ የተከለከሉ ህጋዊ ወራሾች ሞግዚት፣ በወራሾች ስምምነት የሚመረጥ ሰው፣ ወራሾች ካልተስማሙ በፍ/ቤት የሚመረጥ ውርስ አጣሪ፣ ወይም (...) በኑዛዜ የሚመረጥ የውርስ አጣሪ ነው፡፡ የውርስ አጣሪው ዋና ዋና ስራዎች ደግሞ፣ ሟቹ አንድ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግ ወራሾቹ እነማን እንደሆኑ መለየት ፣ የውርስ ሀብት ማስተዳደር፣ መክፈያቸው የደረሰውን የውርስ ሀብቶች መቀበል ፣ እዳዎችን መክፈል ፣ ሟች በኑዛዜው ያደረጋቸውን ስጦታዎች ኑዛዜው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ መክፈልና የሟች ኑዛዜ እንዲፈፀም አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ፣ ሟች ኑዛዜ ያልተወ ከሆነ የሟች ያለኑዛዜ ወራሾችን በመለየት የኑዛዜውን ድልድል እንዴት እንደሆነ ለወራሾች ማሣወቅ ፣ እና በአጠቃላይ ሌሎች ስራዎችን ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 946-1125 ድረስ ያሉትን እንደ አግባብነታቸው መስራት ነው፡፡ በዚህ መልኩ በሕጉ የተሰጡትን ስራዎች የሚያከናውን የውርስ አጣሪ የስራውን አገልግሎት ዋጋ የሚያገኝበት አግባብም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 959 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አጣሪው በሟቹ በተወሰኑት ሁኔታዎች /ውለታዎች/ መሠረት ወይም በወራሾቹ ወይም በዳኞቹ መካከል በተደረገ ስምምነት **<u>የሚሰራው ሥራ የሚያረጋግጥለት ከሆነ</u>** አንድ የአገልግሎት ዋጋ ለማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የአጣሪው የአገልግሎት ዋጋ ሊወሰን የሚችለው አጣሪው ከሟች፣ ወይም ከዳኞች መካከል በሚደርገው ስምምነት ሁኖ የሚሰራው ስራ አረጋጋጭ ሁኖ ሲገኝ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የሥምምነቱ መኖር ብቻውን አጣሪ የሚሆንበት አግባብ የሌለ ሲሆን የማጣራቱ ስራ ክብደቱ ፣ ውስብስብነቱ ከወሰደው ጊዜና ድካም አንፃር እየታየ የአገልግሎት መጠኑ የሚወሰን መሆኑንና ይህም ለፍርድ ቤቱ በሕጉ የተሰጠ ስልጣን መሆኑን የድንጋጌው መንፈስና ይዘት ከውርስ ማጣራት ስራ መሰረታዊ ዓላማ ጋር ተዳምሮ ሲታይ የሚያስገነዝበን ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

አመልካች ለክርክራቸው መሰረት ያደረጉት ስምምነቱን መኖሩንና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌን ሲሆን በእርግጥ በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ሁሉ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሕግን ያህል አስገዳኝነት ኃይል ያላቸው መሆኑን ተጠቃሹ ድንጋጌ የሚያሳየን ጉዳይ ሁኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1711 አና 959 ድንጋጌዎች ጋር ተጣምሮ ሲታይ የስምምነቱ መኖር ብቻውን ስምምነቱ ሕጋዊ ጥበቃ እንዲደረግለት የሚያደርግ ሲሆን ስምምነቱ የውርስ ማጣራቱ ስራው ክብደቱና ውስብስብነቱ እየታየ የአጣሪው የአገልግሎት ዋጋ መጠን በፍርድ ቤት የሚወሰንበት ሕጋዊ አግባብ ያለ ከመሆኑ ጭምር ሲታይ የአመልካች ክርክር ሕጋዊ መሠረት የሌለው መሆኑን የሚያስገነዝብ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስምምነቱ መኖር ያለመኖር በራሱ ክርክር ያስነሳ ከመሆኑም በተጨማሪ ከወራሾች መካከል ሁለቱ ስምምነቱ ላይ ፈቃዳቸውን ያልገለፁ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ሥልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀረበው ክርክርም ስምምነቱ መኖሩን ያመኑት የተወሰኑት ተጠሪዎች ብቻ መሆናቸው፣ የውርስ ንብረቱ ክፍፍሉ እስከሚፈፀም ድረስ እንደ አንድ የተለየ ንብረት የሚቆጠርና ሳይነጣጠል የሚቆይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1060/1/ ድንጋጌ ከተቀመጠው መርህ እና የውርስ አጣሪውን የአገልግሎት ዋጋ ለመቀነስ ፍርድ ቤት በሕጉ ስልጣን የተሰጠው ከመሆኑ አንፃር ሲታይ ከወራሾች መካከል የተወሰኑት ስምምነት ማድረጋቸው የውርስ አጣሪውን የአገልግሎት ዋጋ መጠኑን በግል ለያይቶ መወሰን የግድ አስፈላጊ ነው ብሎ ለመደምደም የማያስችል ነው፡፡ አመልካች ከውርስ ንብረቱ ተገኘ ከተባለው ብር 5,498,400.00 ውስጥ 5% ይገባኛል ያሉት የተጋነነ እና ከወራሽነት የማይተናነስ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ግምት የወሰደበት ሲሆን አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የስራውን አድካሚነት እና በራሳቸው ጥረት የተነሳ ከውርስ ንብረቱ ይፈለጋል ተብሎ በግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ተጥሎ የነበረውን የግብር መጠን ማስቀረታቸውን ፣ በንብረት ጥበቃ ወቅትም የፈፀሙትን ተግባር ሁሉ በመዘርዘርና በምክንያትነት በመጥቀስ ክፍያው የተጋነነ ነው ሊባል የሚችል አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊጣራና ሊመዘን የሚችል ካለመሆኑም በላይ በፍ/ብሕ/ቁጥር 959 ድንጋጌ መሠረት ለስር ፍርድ ቤት ከተሰጠው ፈቃድ ስልጣን አንጻር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ የአጣሪው የአገልግሎት ዋጋን በተመለከተ በተወሰኑት ወራሾችና በአጣሪው መካከል ስምምነት ቢኖርም በክርክሩ የተረጋገጡትን የተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶችን በመያዝ ፍርድ ቤት የአገልግሎት ዋጋ መጠኑን ለመቀነስ የሚችል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 959 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያሳይ በመሆኑና በተያዘው ጉዳይም በዚህ አግባብም የአጣሪው የአገልግሎት ዋጋ መጠን የተወሰነ በመሆኑ በውሣኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 06321 ሐምሌ 23 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99123 መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በፍርድ ቤት የተሾመ የውርስ አጣሪ የአገልግሎት ዋጋን በተመለከተ አጣሪው የሚሰራው ስራ የሚያረጋግጥለት መሆኑን በመመርመር ፍርድ ቤት የመቀነስ ስልጣን አለው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 61357

ሕዳር 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፍቅሬስላሴ እሸቱ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዋጋዬ ጋይም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኗ ተጠሪ በአመልካች ላይ ሚያዚያ 17 ቀን 2002 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ከአመልካች ጋር ከ22/05/1968 ዓ/ም ጀምሮ ተጋብተው ሲኖሩ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 504 የሆነውን ቤት በጋራ እንዳፈሩ እንዲሁም ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ተለያይተው በመኖራቸው የተነሳ ጋብቻቸው በራሱ ጊዜ እንደፈረሰ ገልጸው በጋብቻ ወቅት በጋራ አፈራነው ያሉትን ቤት በተመለከተ የክፍፍል ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ከተጠሪ ጋር ጋብቻ መስርተው የቆዩ መሆኑ የማይካድ መሆኑን፣ቤቱን ግን በጋብቻ ወቅት በጋራ ስለመፈራቱ ተጠሪ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ቀደም ብሎ ፍርድ ቤት ቀርቦ በነበረው ጉዳይም በፍቺ ጥያቄው ላይ የተሰጠ ውሳኔ የሌለ መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ ሳይራራቁ እየተጠያየቁ እንደሚኖሩ እንዲሁም ግራ ቀኙ ተነጋግረው በግል መፍትሄ ለጉዳዩ ለመስጠት እንደሚችሉ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮና ቤቱን በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ማጣሪያ ማስረጃ እንዲቀርብ ከአደረገ በሁዋላ አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ የመሰረቱት ጥር 22 ቀን 1968 ዓ.ም. መሆኑን፣አከራካሪው ቤት የተሰራው ደግሞ በ1974 ዓ/ም መሆኑን መረጋገጡን፣አመልካች ቤቱን ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት ወይም ተለያይተው መኖር ከጀመሩ በሁዋላ ያፈሩት ስለመሆኑ ያላስረዱ መሆኑ መረጋገጡን በመዘርዘር ቤቱ የጋራ ነው በማለት እኩል እንዲካፈሉ ሲል በሕጉ የተመለከተውን የአከፋፈል ሥርዓት በመግለጽ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካችና ተጠሪ ለረዥም አመታት ተለያይተው የኖሩ በመሆኑ የፍቺ ውሳኔ አይሰጥም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117245 ውሳኔ ከተሰጠ በሁዋላ የፍቺ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውጤት የሆነው ንብረት ላይ ግን ክፍፍሉ ይቀጥላል ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ ነው ተብሎ እንዲወስንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።አቤቱታው ተመርምሮም በአመልካችና በተጠሪ መካከል በመ/ቁጥር 117245 ላይ ጋብቻ የለም ተብሎ ተወስኖ እያለ በዚሁ ጉዳይ የፍቺ ውጤት የሆነው የንብረት ክፍፍል በተጠሪ በኩል በመቅረቡ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት የቤት ቁጥር 504 የሆነ የጋራ ሃብት ነው በማለት እኩል እንዲካፈሉ ሲል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።ከዚኅም በኋላ ተጠሪ በክርክር ላይ እንዳሉ ከዚህ አለም በሞት መለየታቸው በመገለፁ ለወራሾቻቸው በጋዜጣ ጥሪ የተደረገላቸው ቢሆንም አልቀረቡም።እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት የመ/ቁጥር 139762 ቀርቦ የግራ ቀኙ ክርክር እንዲታይ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በ22/05/1968 ዓ.ም. ጋብቻ ፈፅመው አከራካሪው ቤት በ1974 ዓ.ም. የተሰራ መሆኑን፣አከራካሪውን ቤት አመልካች ከጋብቻ በፊት የሰሩት ወይም ከተጠሪ ጋራ በስምምነት ተለያይተው መኖር ከጀመሩ በሁዋላ ያፈሩት ንብረት ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117245 በሆነው የፍቺ ጥያቄ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ ሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ግራ ቀኙ ተለያይው መኖር ከጀመሩ ረዥም ጊዜ መሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት በመያዝ ጋብቻው በራሱ ጊዜ የፈረሰ በመሆኑ የፍቺ ጥያቄ የሚቀርብበት ጉዳይ አይደለም በማለት ጥቅምት 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መወሰኑን፣ከዚህም በሁዋላ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ያሉትን አከራከሪውን ቤት ለመካፈል ይወሰንላቸው ዘንድ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በሌላ መዝገብ (በመ/ቁጥር 13972) በሆነው ለስር ፍርድ ቤት አቅርበው አመልካች እንዲቀርቡ ተደርጎ ግንቦት 07 ቀን 2001 ዓ/ም ፅፈው ባቀረቡት የመከላከያ መልስ የፍቺ ውሳኔ በሌለበት ሁኔታ የንብረት ክፍፍል የሚቀርብበት አግባብ የለም በማለት መከራከራቸውን ነው።በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት የፍቺ ውሳኔ በሌለበት ሁኔታ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱ በሕጉ ከተዘረጋው ሥርዓት ውጪ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117245 ላይ ጋብቻው በራሱ ስለፈረሰ በፍርድ ቤት የሚሰጥ የፍቺ ውሳኔ የለም በማለት መወሰኑ የጋብቻውን ውጤት ከመጠየቅ የማይከለክል ነው፣ይርጋውን በተመለከተ ደግሞ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያላነሱት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲደርሱ ሊያነሱ የሚችሉበት ሥርዓት የለም በማለት በጽሁፍ ክርክር ወቅት ተከራክረዋል።እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የስር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ በመመልከትና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ ጉዳዩን መርምረነዋል።

በመሰረቱ ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በተግባር ተጋቢዎች ተለያይተው በየፊናቸው የራሳቸውን ህይወት መኖር ከቀጠሉ ሊፈርስ እንደሚችል ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 76 ድንጋጌና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ከሰጠበት የመ/ቁጥር 20398 ውሳኔ መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው።ጋብቻ ከላይ በተመለከተው የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌ ወይም የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ከፈረሰ የጋብቻ ውጤት የሆነው ንብረት በፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ውሳኔ መፍትሔ የማያገኝበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በራሱ ጊዜ የፈረሰ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117245 ውሳኔ ማግኘቱ የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ውሳኔ ግን የጋብቻ ውጤትን በተመለከተ በፍርድ ቤት የዳኝነት ጥያቄ ከማቅረብ የሚከለክልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም የጋራ ንብረት ጥያቄ የግድ በፍርድ ቤት የፍቺ ውሣኔ ከተሰጠ በሁዋላ መቅረብ ያለበት ጉዳይ ስለመሆኑ የቤተሰብ ሕጉ አያሳይም፡፡ስለሆነም ፍቺው ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጪ በሆነ መንገድ በተግባር የተከናወነ (Defacto divorce)መሆኑ የጋብቻውን ውጤትን በተመለከተ በፍርድ ቤት ዳኝነት ከመጠየቅ የማይከለክል ሲሆን ዋናውና መታለፍ የሌለበት ነገር የክፍፍሉ ጥያቄ በሕጉ በተዘረጋው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረቡ መረጋገጡ ላይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በተግባር ፍቺ ያከናወኑ ተጋቢዎች የጋብቻውን ውጤት በተመለከተ ለፍርድ ቤት ክፍፍሉን ማቅረብ ያለባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ስር በተመለከተው የአስር አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊሆን ይገባል፡፡የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ከጋብቻ መፍረስ በሁዋላ በአስር አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ቀሪ መሆን ያለበት መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17937 በቀረበው ጉዳይ ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታልና፡፡ ይርጋውን ተመለከተ ደግሞ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው የሚለው ወገን በስርዓቱ መሰረት በግልፅ አንስቶ መከራከር የሚጠበቅበት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 234(1(ሐ)) እና 244(2(ሠ)) ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ይርጋን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሳው የማይችለው ጉዳይ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1856(2) ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የመከላከያ መልስ ሥርአቱን ጠብቀው የይርጋን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አላቀረቡም፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤት አንስተው የተከራከሩት መሰረታዊው ነጥብ የፍቺ ውሣኔ ሊሰጥ አይገባም ተብሎ በፍርድ ቤት ከተወሰነ በሁዋላ የጋብቻ ውጤት ላይ ክስ መመስረት ሕጋዊ አግባብነት የለውም የሚል ብቻ ነው፡፡ይህ ደግሞ ይርጋውን አንስተው መከራከራቸውን የሚያሳይ አይደለም፡፡ስለሆነም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ሥርአቱን ጠብቀው ያላነሱትን የይርጋ ክርክር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያነሱበት አግባብ የሌለ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

- በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 139762 ሚያዚያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 94407 ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
- ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የአምስት የማይነበብ ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ትእግስት አሰፋ ቀረበች
ተጠሪ፡- ወ/ሮ እመቤት ቱርፌ - ወኪል አደፍርሰው ዘውዴ ቀረበ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በብድር የተወሰደን ገንዘብ ለማስመለስ የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፣ ክሱ የተመሠረተው ባልና ሚስት በሆኑት አቶ አደፍርሰው ዘውዴ እና በአሁኑዋ ተጠሪ ላይ ነው፡፡ ተከሣሾች ገንዘቡን የወሰዱት ለእህል ንግድ ሥራ እንደሆነ እና በወቅቱ አጠናቀው ባለመክፈላቸው በቀሪ የሚፈለግባቸውን ገንዘብ ከእነ ወለዱ እንዲከፍሉት ይወሰንለት ዘንድ አመልካች ጠይቆአል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የተከሣሾችን የመከላከያ ክርክር ከሰማ በኋላ፣ የአሁንዋን ተጠሪ /ሚስት/ በብድር ውሉ ላይ ስለመፈረምዋ አልተረጋገጠም በማለት ከእዳው ነፃ አድርጎአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጽሞአል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ ጠይቆአል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው ተጠሪ በብድር የተወሰደውን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም የተባለው በሕጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጭብጥ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ፣ አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ የተከሰሰችው ከባለቤትዋ ጋር በመሆን እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ባለቤትዋ የሆነው አቶ አደፍርሰው ዘውዴ ዕዳው ይመለከተዋል ተብሎ በፍ/ቤት ተወስኖበታል፡፡ ተጠሪ ስትከራከር የቆየችው ባለቤቴ ገንዘቡን አልተበደረም በማለት ሳይሆን፣ በብድር ውሉ ላይ አልፈረምኩም በማለት ነው፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም በፊርማው ላይ ብቻ በመመሥረት እና ይህንኑ በላብራቶሪ አስመርምሮ የመጣለትን ውጤት እንደብቸኛ እና ፍጹማዊ የሆነ ማስረጃ በመቁጠር ተጠሪን ከእዳው ነፃ አድርጎአል፡፡ አመልካች ከፊርማው በተጨማሪ ውሉ ሲፈረም የነበሩ እማኞች በምስክርነት እንዲሰሙለት ስለመጠየቁም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ፍ/ቤቱ ግን ክሱን የሰማው ፊርማውን በተመለከተ የመጣለትን የላብራቶሪ ውጤት እንደብቸኛ ማስረጃ በመቁጠሩ ምስክሮቹን አልሰማም፡፡ በሌላም በኩል ብድሩ የተወሰደው ለንግድ ሥራ ነው፡፡ የተጠሪ ባለቤት ነጋዴ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በንግድ ሕግ ቁጥር 19 ከተቀመጠው ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ይታይልኝ በማለት ከአመልካች ለቀረበው ክርክርም ዋጋ አልሰጠም፡፡ አመልካች የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታውን ያቀረበው በማስረጃው አቀባበል እና በንግድ ሕጉ የተመለከተውን ድንጋጌ አተረጓጎም በሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪም ሁለቱን ነጥቦች መሠረት በማድረግ ክርክርዋን /መልስዋን/ አቅርባለች፡፡

እንደምናየው አቶ አደፍርሰው ዘውዴ እና ተጠሪ ባልና ሚስት ስለመሆናቸው አላከራከረም፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ በብድር የተወሰደው ለእህል ንግድ ሥራ እንደሆነ እና አቶ አደፍርሰው ዘውዴም ነጋዴ ስለመሆኑም እንደዚሁ ክርክር የተነሳበት አይደለም፡፡ ተጠሪ እዳው አይመለከተኝም የምትለው ባለቤቴ /አቶ አደፍርሰው ዘውዴ/ ከአመልካች የተበደረው ገንዘብ የለም፣ ወይም የተበደረው ለንግድ ሥራ ማስኬጃ አይደለም፤ ወይም ደግሞ ነጋዴ አይደለም በማለት ሳይሆን፣ የኔ ስምምነት እስከሌለ ድረስ ከብር 500/ አምስት መቶ ብር/ በላይ ለሆነው ብድር ተጠያቂ አይደለሁም፣ በብድር ውሉ ላይ አልፈረምኩም፣ በንግድ ሕግ ቁጥር 19 የተቀመጠው ድንጋጌ በተሻሻለው የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ተሽሮአል የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

አመልካች ከሥር ጀምሮ እየተከራከረ ያለው ተጠሪም ከባለቤትዋ ጋር በመሆን በብድር ውሉ ላይ ፈርማለች፡፡ ፊርማውን በሚመለከት ከባለሙያ የተሰጠው አስተያየት ብቻውን በብድር ውሉ ላለመስማማቷ /ላለመፈረሟ/ ብቸኛ እና የተሟላ ማስረጃ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ በብድር ውሉ ላይ አልፈረመችም የሚባል እንኳን ቢሆን በንግድ ህጉ በተቀመጠው ድንጋጌ መሠረት ዕዳው እስዋንም ይመለከታል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪን ከእዳው ነፃ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ውሣኔው ሕግን መሠረት ያደረገ አይደለም በማለት ነው፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ፍ/ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪን ከእዳው ነፃ ያደረጉት በብድር ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የእሷ ስለመሆኑ በባለሙያ ሊረጋገጥ አልቻለም በማለት እና ይህ ከባለሙያ የመጣውን አስተያየት እንደብቸኛ ማስረጃ በመውሰድ ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹ ሌሎቹን የአመልካች ማስረጃዎች አልሰሙም ወይም የባለሙያው አስተያየት ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ አልመዘኑም፡፡ የተካደን ፊርማ ለማጣራት የባለሙያ አስተያየት መጠየቁ አግባብ አይደለም የሚባል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአንድ ሰው ፊርማ በተለያዩ ምክንያቶች ሊለዋወጥ የሚችልበት ሁኔታም ስለሚኖር ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች ሳይሰሙ እንደበቂና ብቸኛ ማስረጃ ተደርጎ መወሰዱ አግባብ አይሆንም፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም እነዚህን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በሰበር መ/ቁ 14981 በሰጠው ውሣኔ ፊርማን በሚመለከት የሚቀርበው የባለሙያ አስተያየት እንደመጨረሻ ማስረጃ /conclusive evidence/ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ፊርማውን በሚመለከት ከባለሙያ የቀረበላቸውን አስተያየት ብቻ መሠረት በማድረግ መወሰናቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ይህ እንግዲህ በዚህ አግባብ የሚታይ ሲሆን ፣ ቀጥሎ መታየት ያለበት ተጠሪ በብድር ውሉ ተዋዋይ አልነበረችም ቢባልስ ከእዳው ከነጭራሹ ነፃ ነች ወይም እዳው እሷን አይመለከትም ወደሚለው ድምዳሜ ከመደረሱ በፊት ሊመረመር የሚገባው የሕግ ነጥብ የለም ወይ? የሚለው ነው፡፡

ተደጋግሞ እንደተገለጸው ብድሩ የተወሰደው ለንግድ ሥራ ማስኬጃ ነው፡፡ የሚነግደው ባል ወይም ሚስት የተዋዋለው እዳ እንደባልና ሚስት ዕዳ እንደሚቆጠር በንግድ ሕግ ቁጥር 19 ተደንግጎአል፡፡ በዚህ የንግድ ሕግ ድንጋጌ የባልና ሚስት ዕዳን በተመለከተ የተደነገገው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 659 ተጠቅሶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በፍትሐብሔር ሕጉ መጽሐፍ ተካቶ የነበረው የቤተሰብ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 213/92 በመሻሻሉ ወይም እራሱን የቻለ የተሻሻለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ በመውጣቱ በአሁኑ ጊዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 659 የተቀመጠው ድንጋጌ ስለባልና ሚስት የጋራ ዕዳን በሚመለከት ለሚቀርበው ክርክር አወሳሰን በዋቢነት ሊጠቀስ አይችልም፡፡ በንግድ ሕጉ የተቀመጠው ድንጋጌ ቁጥር 19 ግን በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ተሽሮአል፡፡ የሚባልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግም ቢሆን በአንቀጽ 70 ስለባልና ሚስት ዕዳ በሚመለከት የተደነገገ በመሆኑ ሊባል የሚችለው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 659 የተቀመጠው ድንጋጌ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 70 ተተክቶአል ነው፡፡ ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ ዕዳ ከባለዕዳው ተጋቢ የግል ሃብት ፣ የግል ሃብቱ ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሃብታቸው እንደሚከፈል በተጠቀሰው አንቀጽ 70/1/ የተመለከተ ሲሆን ፣ ዕዳው የመጣው ለባልና ሚስቱ ትዳር ጥቅም ከሆነ ደግሞ ከጋራ ሃብታቸው ፣ የጋራ ሃብታቸው ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሃብት እንደሚከፈል በንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጎአል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ዕዳ በብድር የተወሰደው ባልናሚስቱ ለሚተዳደሩበት የንግድ ሥራ ማካሄጃ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳመለከትነው የተጠሪ ክርክር ዕዳውን ያመጣው ባለቤቴ ነው ከማለት ባለፈ የንግድ ሥራው የጋራ መተዳደሪያችን አይደለም የሚል አይደለም፡፡ በበኩላችን እንደምንገነዘበው ከአመልካች ባንክ በብድር የተወሰደውን ገንዘብ የባልናሚስቱ የጋራ መተዳደሪያ ለሆነው የንግድ ሥራ እንዲውል የተወሰደ በመሆኑ የባልና ሚስቱ የጋራ ዕዳ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪን ከወዲሁ ከዕዳው ነፃ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪን የመክሰስ መብት የለውም በማለት በመ.ቁ 62817 ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና ይህን ውሣኔ በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 102296 የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ክስ የቀረበበት ገንዘብ ብር 348,024.54 /ሶስት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ሃያ አራት ብር ከሃምሣ አራት ሣንቲም/ የባልና ሚስቱ /የአቶ አደፍርሰው ዘውዴ እና የተጠሪ/ የጋራ ዕዳ በመሆኑ ተጠሪ ከዕዳው ነፃ የምትሆንበት ምክንያት የለም ብለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ገንዘቡን ከነወለዱ ተጠሪ ከባለቤትዋ አቶ አደፍርሰው ዘውዴ ጋር በመሆን እንድትከፍል ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ ውሣኔው ዛሬ ታሕሣሥ 18 ቀን 2004 ዓ.ም በችሎት ተነገረ ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሳስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ በቀለ ቱፋ - ከጠበቃ ደጀኔ ታደሰ ጋር ቀረቡ
ተጠሪ፡- ወ/ሮ ባዩሽ እሸቴ - ቀረቡ
መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት የክስ ማመልከቻ መነሻ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው በባንክ ውስጥ ከገባው ገንዘብ ውስጥ በትዳር ጊዜ ወጥቶ ለአመልካች አባት ገንዘባቸው በአመልካች የተሰጠ ሆኖ እያለ እና በኦሮሚያ ክልል ለገዳዲ ግድብ ማዞሪያ አካባቢ የሚገኙ ሁለት የመኖሪያ ቤቶች የሶስተኛ ወገን ንብረቶች መሆናቸው ተገልፆ እያለ የጋብቻ ውጤቶች ናቸው ተብለው የጋራ ንብረቶች ናቸው በማለት አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ በሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ሲሉ አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ተጠሪ የጋራ ናቸው የሚሏቸውን ንብረቶች አይነታቸውንና ብዛቸውን በመለየት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥም እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያከራክሩት ንብረቶች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መገናኛ ቅርንጫፍ በአመልካች ስም በነበረው የሂሳብ ቁጥር ውስጥ የነበረ ብር 455,485.00 (አራት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ብር) እና በኦሮሚያ ክልል ለገዳዲ ግድብ ማዞሪያ አካባቢ የሚገኙት ሁለት መኖሪያ ቤቶች ሲሆኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር በእነዚህ ንብረቶች ላይ የሰጡት መከላከያ መልስ ከጥሬ ገንዘቡ ውስጥ ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ከባንኩ በጋብቻ ጊዜ ወጥቶ የአመልካች አባት ንብረት በመሆኑ በአመልካች መሰጠቱንና በአጠቃላይ ገንዘቡ በትዳር ጊዜ የወጣ በመሆኑ አመልካች እንደማይጠየቁበት የሚገልጽ ሲሆን አሁን የሚያከራክሩትን ቤቶችን በተመለከተ ደግሞ የአመልካች አባት ለልጅ ልጆቻቸው እንዲሆኑ የገዟቸው እንጂ የአመልካችና የተጠሪ የጋብቻ ውጤት ያለመሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ደግሞ ጥሬ ገንዘቡን አመልካች ያላግባብ መውሰዳቸውን በመግለጽ ለትዳር ጥቅም ያለመዋሉን ጠቅሰው እንዲሁም ቤቶቹ የጋራ ናቸው በማለት ተከራክረዋል፡፡ እነዚህን አከራካሪ ንብረቶችን በተመለከተ ክርክሩ በዚሁ መልኩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አጣርቶ በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጎ ንብረቶቹ የጋራ ስለሆኑ ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥሬ ገንዘቡ የአመልካች አባት በመሆኑ ከባንክ በትዳር ጊዜ ወጥቶ በአመልካች የተወሰደ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች ግማሹን ለተጠሪ እንዲከፍሉ ተብሎ መወሰኑም ሆነ ቤቶቹን በተመለከተ የሶስተኛ ወገኖች ንብረቶች መሆናቸው ተገልጾ እያለ አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ መወሰኑ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎችን ከቤተሰብ ሕጉ ጋር ባላገናዘበ ሁኔታ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ እያሉ ከባንክ ወጪ የተደረገን ብር እና በሶስተኛ ወገን ስም ያለ ንብረት ይካፈሉ መባሉ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በአከራካሪ ንብረቶች ላይ የተሰጠው ውሳኔ ማስረጃውንና ሕጉን መሰረት ያደረገ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲሉ የተከራከሩ ሲሆን አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መሰረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ የፈረሰው ጥቅምት 02 ቀን 2002 ዓ.ም. እንደሆነና እንደዚሁም ለዚህ ሰበር ችሎት ለቀረበው ክርክር ምክንያት የሆነው ጥሬ ገንዘብ ከባንኩ የወጣው መጋቢት 10፣14፣16 ቀን 2001 ዓ.ም. መሆኑን ነው፡፡ ከገንዘቡ ውስጥ አመልካች ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ከባንኩ በትዳር ጊዜ ያወጡት መሆኑን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት ገንዘቡ የአመልካች አባት በመሆኑ ከባንክ አውጥተው ለአባታቸው የሰጡ በመሆኑና በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሚያዚያ 23 ቀን 2000 ዓ/ም ስምምነት ሲደረግም ገንዘቡ ከባንክ ስለመኖሩ ሳይጠቀስ መታለፉ ገንዘቡ የጋራ ንብረት ያለመሆኑን ያሳያል በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች አለ የሚሉት የሚያዚያ 23 ቀን 2000 ዓ/ም ስምምነት በግራ ቀኙ የንብረት ክርክር ላይ በታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረው የማስረጃው ክብደት ተመዝኖ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ስለሚገለጽ ይህንን ማስረጃ መሰረት አድርጎ የሚቀርበው የአሁኑ ክርክር የሚሆነው የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ከሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት በዚህ ችሎት የሚታይ ጉዳይ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የማስረጃ ምዘና መሰረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ጉዳይ አይደለምና ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች ሚያዚያ 23 ቀን 2000 ተደረገ የተባለውን ስምምነት መሰረት አድርገው ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የሚያዚያ 23 ቀን 2000 ዓ.ም. ስምምነት ተቀባይነት ያጣበት ምክንያት በዚህ ችሎት ሊታይ የሚችል አይደለም ከተባለ በጋብቻ ውጤቱ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ብዛቱ ብር 455,485.00 (አራት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ብር) የጋራ ስለመሆኑ ሚያዚያ 23 ቀን 2000 ዓ.ም. በተደረገው ስምምነት አልተገለጸም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ስምምነቱ በበታች ፍርድ ቤቶች በማስረጃነቱ ተመዝኖ ውድቅ የተደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ የለም፡፡ ሌላው አመልካች ጥሬ ገንዘቡን ከባንክ ማውጣታቸውን ሳይክዱ ለተጠሪ ላካፍል አይገባም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ገንዘቡ የሌላ ሰው በመሆኑ ከባንክ አውጥቼ ሰጥቼአለሁ የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ ነገር ግን ገንዘቡ ትዳሩ ጸንቶ ባለበት ጊዜ በአመልካች ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር የነበረና አመልካች ከባንኩ አውጥተው ለአባታቸው የሰጡት መሆኑ ያልተካደ ከመሆኑም በላይ ለትዳር ጥቅም ውሏል የሚል ክርክር አመልካች ያላቀረቡ በመሆኑ በትዳር ጊዜ የነበረ ንብረት የጋራ ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ ስለሆነ የአመልካች ክርክር ሕጋዊ መሰረት የለውም፡፡ አመልካች ገንዘቡን ለሌላ ሰው አሳልፈው መስጠታቸው እስካልተካደ ድረስ ገንዘቡ በትዳር ጊዜ ከባንክ በመውጣቱ ብቻ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕጉ ግምት የሚወስድበትን አግባብ አመልካች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ በትዳር ጊዜ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከወጣ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕጉ ግምት የሚወስደው የጋራ ንብረትን ለሌላ ሰው አሳልፎ መሰጠቱ የተረጋገጠበትን ሁኔታ ሁሉ ስላለመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 85-93 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነውና፡፡ በመሆኑም ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) አመልካች ከባንክ አውጥተው ለአባታቸው መስጠታቸውን ካለመካዳቸውም በላይ አመልካች የዚሁ ገንዘብ ባለቤት ናቸው የሚሏቸው አባታቸውም የገንዘቡ ባለቤት የሆኑበት አግባብ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ግማሹን የማይከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው ብር 55,485.00 (ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ብር) የሚመለከት ሲሆን ይህ ገንዘብም ትዳሩ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ከባንክ መውጣቱ ያልተካደ ሲሆን አመልካች ይህንኑ የገንዘብ መጠን ለሌላ ሰው መስጠታቸውን አልገለፁም፡፡ በጋብቻ የተፈራ ገንዘብ ትዳሩ ጸንቶ ባለበት ጊዜ ወጪ መሆኑ ከተረጋገጠ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የባልና ሚስትን ሃብት ስለማጣራት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀጽ 85-93 ካሉት ድንጋጌዎች አንጻር የሕግ ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡ በዚህ የሕግ ግምት ተጠቃሚ የሆነ ወገንም ንብረቱ በጋብቻ ጊዜ የተሸጠ ወይም ጥሬ ገንዘብ ከሆነ በትዳር ጊዜ የወጣ መሆኑን ካስረዳ በቂ ሲሆን ሌላው ወገን ደግሞ ጋብቻው በፍቺ በፈረሰ ጊዜ ከንብረቱ የሸያጭ ገንዘብ ወይም የጋራ የሆነ ሌላ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይንም በከፊል የሚገኝ መሆኑን ወይም ያላግባብ አንደኛው ተጋቢ ያባከነው መሆኑን በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካስረዳ የሸያጩ ገንዘብ ወይም ሌላ የጋራ የሆነ ጥሬ ገንዘብ በጋብቻ ጊዜ ለጋራ ጥቅም ውሏል የሚለውን የሕግ ግምት እንዳፈረሰ ይቆጠራል፡፡

አመልካች ለክርክሩ መነሻ ምክንያት ከሆነው ጥሬ ገንዘብ ውስጥ ብር 55,485.00 (ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አምስት ብር) በጋብቻ ጊዜ ከባንክ የወጣ መሆኑን በማስረዳት የሸያጩ ገንዘብ ለጋራ የትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕጉ ለወሰደው ግምት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩልም ተጠሪ ጋብቻው በፈረሰ ጊዜ ይኸው ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይንም በከፊል በአመልካች እጅ እንደሚገኝ ወይም አመልካች ያላግባብ የወሰዱት ስለመሆኑ ያላስረዱ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልፅ ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪ የሕግ ግምቱን ማፍረስ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም አመልካች የብር 55,485.00 (ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማኒያ አምስት ብር) ግማሽ ለተጠሪ እንዲመልሱ የሚገደዱበት ሕጋዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው አመልካች የሚከራከሩበት ነጥብ በኦሮሚያ ክልል ለገዳዲ ግድብ ዙሪያ አካባቢ ይገኛሉ የተባሉትን ሁለት መኖሪያ ቤቶችን በተመለከተ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ነው፡፡ አመልካች እነዚህ ቤቶችን ለተጠሪ ላካፍል አይገባም የሚሉት ቤቶቹ የሌላ ሶስተኛ ወገን ንብረቶች ናቸው በሚል ነው፡፡ እነዚህ ሶስተኛ ወገኖች የሚባሉት ደግሞ ከአመልካችና ከተጠሪ አብራክ የተወለዱ ልጆች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሆን ቤቶቹን ለእነዚህ ሕጻናት ገዙ የሚባሉት የአመልካች አባት ናቸው። ይሁን እንጂ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ቤቶቹ የጋብቻ ውጤት ያለመሆናቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ያላቀረቡ መሆኑን አረጋግጧል፣ በአመልካች ምስክሮችም ጭምር ያለመመስከሩንም ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ በግልፅ አስቀምጧል። ይህ ፍሬ ነገር በይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቷል። እንደዚሁም አመልካች የቤቶቹ ባለቤቶች የሚሏቸው ወገኖች ወይም በእነርሱ በሕጉ አግባብ የተወከሉ ሰዎች በሕጉ አግባብ ያቀረቡት ክርክርም የለም። በመሆኑም ቤቶቹ የሌላ ሶስተኛ ወገን ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ አመልካች ቤቶቹ የጋራ አይደሉም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝ ሆኖ አላገኘነውም። በትዳር ጊዜ በጋራ የተገኘ እና የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ ስለመኖሩ የተረጋገጠ ማናቸውም ንብረት የባልና ሚስት የጋራ ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ መሆኑን ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀፅ 63(1) ድንጋጌ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው። በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተሻሽሎ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71624 ሕዳር 15 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 103845 በ27/07/2003 በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል።
2. አመልካች የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ግማሽ ገንዘብና በኦሮሚያ ክልል ለገዳዲ ግድብ ዙሪያ አካባቢ የሚገኙትን ሁለት መኖሪያ ቤቶችን ለተጠሪ እንዲያካፍሉ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል።
3. ብር 55,485.00 (ሃምሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አምስት ብር) አመልካች ለተጠሪ ሊያካፍሉ አይገባም ብለናል።
4. በሌሎች ንብረቶች ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል።
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 64371

ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ፍቅረ ዲን ሰይፈዲን - ጠበቃ ቴዎፍሎስ ክፍለ ወንጌል ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1- አበራ ለማ

2- ወ/ሮ ጋዲሴ ለማ ቀረበች

3- ወ/ሮ ጠጅቱ ለማ

4- ፍቃዱ ለማ

5- ወ/ሮ ገላዬ ለማ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል አፈጻጸምን መነሻ ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው አመልካች ሲሆን ፣ ክሱን የመሠረተው በ6-8-2001 ዓ.ም በተደረገው የሽያጭ ውል በብር 30,000 ቤት ሽጠውልኛል ባላቸው ገላዬ ለማ እና በቀሉ ለማ በተባሉት ሰዎች ላይ ነው፡፡ በወቅቱ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኋላ በውሉ መሠረት ይፈጸም በማለት ውሣኔ ሰጥቶ እንደነበር እና በኋላ ደግሞ የአሁኖቹ ተጠሪዎች መቃወሚያ በማቅረባቸው መዝገቡ እንደገና ተንቀሳቀሶ ክርክር መስማቱን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መቃወሚያ ያቀረቡት የሽያጭ ውል የተደረገበት ቤት የእኛም የውርስ ድርሻ ያለበት በመሆኑ ከእኛ ስምምነት ውጪ የተደረገው ውል ይፍረስልን በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ ፣ የቀድሞውን ውሣኔውን አፅንቶአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን ፣ በመቀጠልም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ በመጨረሻም በወረዳው ፍ/ቤት ተቃዋሚ የነበሩት እነ አበራ ለማ ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረባቸው በዚህ ደረጃ ክርክሩ የተሰማ ሲሆን ፣ ችሎቱም የሽያጭ ውሉን በማፍረስ ግራ ቀኝ ወገኖች ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ይመለሱ በማለት ወስኖአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በበኩላችንም አመልካች ታሕሣሥ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን በማስቀረብ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የቤት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሚል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

አመልካች ከእሱ ጋር የቤት ሽያጭ ውል አድርገዋል የሚላቸውን ሰዎች የከሰሰው በሚች ወንድማቸው /አውራሻቸው/ ስም የሚገኘውን ቤት ስመሃብት እንዲያዛውሩለት ፤ ቤቱንም እንዲያስረክቡት እንዲወሰንለት ስለመሆኑ ለዚህ ሰበር ችሎት ከአቀረበው የአቤቱታ ማመልከቻ ጭምር ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 358 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መቃወሚያ ያቀረቡት ሰዎችም የሚች ወንድምና እህቶች እንደሆኑም አላከራከረም፡፡ ተቃዋሚዎቹ መቃወሚያ ያቀረቡት ውሉ የተደረገበትን ቤት ስመሃብት በአመልካች እንዲዛወር በማለት በተሰጠው ውሣኔ ላይ ቢሆንም፤ የጠየቁት ዳኝነት ግን ውሉ እንዲፈርስ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ መቃወሚያው የቀረበለት የወረዳው ፍ/ቤትም ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይፈርስም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ እንዳከራከረ እና በመጨረሻም ውሉ አይፈርስም የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ የቀድሞውን ውሣኔ እንዳፀና ከሰጠው ውሣኔ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ያሉት መቃወሚያ አቅራቢዎች ብቻ ናቸው፡፡ አመልካች የውሉ መፍረስ ወይም አለመፍረስን በሚመለከት ክርክር የሚደረግበት አግባብ ወይም ሥርዓት የለም በማለት የበኩሉን ይግባኝ አላቀረበም፡፡ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይፈርስም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ክርክሩን የሰማው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተፈጸመ የክርክር አመራር ስህተት የለም፡፡ ይህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት የሚመረምረው ከዚህ አንፃር እንጂ አመልካች መጀመሪያ አቅርቦት ከነበረው የውል ይፈጸምልኝ ወይም የስም ይዛወርልኝ ክስ አንፃር አይደለም፡፡

አመልካች የሽያጭ ውል አድርጌበታለሁ የሚለው ቤት ተመዝግቦ የሚገኘው በሻጮቹ ስም እንዳልሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ አመልካቹ ውሉን አደረግሁ የሚለው ሻጮች ሆነው የቀረቡት ሰዎች የቤቱ ባለሃብት /ሚች/ ብቸኛ ወራሾች እኛ ነን ብለውኛል፡፡ የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትም አሳይተውኛል በማለት ስለመሆኑ ከሰበር አቤቱታ ማመልከቻው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ እንደምንመለከተው ሻጭ የተባሉት ሰዎች የሚች ወንድም እና እህት ከመሆናቸው ባለፈ በውርስ ሃብቱ ላይ ክፍፍል ስለመደረጉም ሆነ ቤቱ የውርስ ሃብት መሆኑ ቀርቶ ወደ ሻጮቹ ስለመዛወሩ አመልካች አላረጋገጠም፡፡ ውሉን ያደረገው በዚህ መልክ ጥርት ያለ እና ግልጽ የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ መሠረት በማድረግ /በመያዝ/ አይደለም፡፡ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሉ ፈራሽ ነው ለማለት የቻለውም ቤቱ የወራሾች የጋራ ሃብት ነው በማለት ነው፡፡ በበኩላችንም እንደምናየው የሰበር ችሎቱ ከዚህ የተለየ መደምደሚያ ላይ መድረስ ነበረበት የምንልበት ምክንያት የለም፡፡

ውርሱ ወይም የውርሱ ሃብት የውርሱ አከፋፈል እስኪፈጸም ድረስ በወራሾቹ መካከል ሳይነጣጠል እንደሚቆይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1060/1/ ተደንግጎአል፡፡ የጋራ ወራሾች የሆኑ ሰዎች ባልተከፋፈሉት የውርስ ንብረቶች ላይ ያላቸው መብትም በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 8 ስለጋራ ባለሃብትነት፣ በአላባ ስለመጠቀም እና ስለሌሎች ግዙፍ መብቶች በማመሳከት በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት እንደሚወሰን በዚሁ ቁጥር 1060/2/ ተመልክቶአል፡፡ በዚህ አግባብ የወራሾቹ ሁሉ የጋራ ሃብት የሆነውን ንብረት ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ፤ ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለንብረቶቹ ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1262 ተደንግጎአል። በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን የተፈራረመው የጋራ ባለሃብት የሆኑትን ሰዎች ሁሉ ስምምነት ሳያገኝ ነው። ውሉ እንዲፈርስ ጥያቄ ያቀረቡት ስምምነታቸውን ያልሰጡት ሌሎች የጋራ ባለሃብቶች በመሆናቸው ውሉ እንዲፈርስ በመወሰኑ ሕጉ በአግባቡ ተተርጉሞአል ነው ማለት የሚቻለው ። በመሆኑም አቤቱታው የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የምንልበት አግባብ የለም። በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 91762 ጥቅምት 15 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቶአል።
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል።
3. የግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቶአል ይመለስ።

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 65708

ጥር 02 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አራጋው አበበ - ጠበቃ ደጉ መኮንን ጋር ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ራሔል ውብሸት - ጠበቃ ስንታየሁ በቀለ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና የሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት ግራቀኙ የጋራ እና የግል በማለት ያቀረቡትን ክርክር በመስማት ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ፣ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በቃሊቲ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ ገላን ሳይት ላይ የሕንጻ ቁ.133 ሆኖ የቤት ቁ.GA-B/33/01/11 የሆነውን ኮንደሚኒየም ቤት በተመለከተ ብቻ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ሲያዝ በሌሎቹ ሀብቶች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት በመወሰኑ አመልካች የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸው የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉዋቸውን ነጥቦች ያቀረቡ ሲሆን በቀን 14-6-2003 ዓ.ም በሁለት ገጽ የተጻፈ የቅሬታ ፍሬ-ሃሳብ፡- በተሻሻለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 57 ድንጋጌ መሰረት ከጋብቻ በኋላ ያለግብይት በውርስ የተገኙ ንብረቶች በፍርድ ቤት እስካልተገለሉ ድረስ የጋራ ንብረቶች ናቸው በማለት ውሳኔ መሰጠቱ፣በስር ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳባቸው የባልና የሚስት ንብረቶች የትኞቹ የግል የትኞቹ የጋራ እንደሆኑ ያስረዱልኛል ያልኳቸውን የሰው ምስክሮች እና በውርስ ንብረት ግምት የተገኘ ገንዘብ መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት በትዕዛዝ ይቅረብልኝ ያልኩት የጽሑፍ ማስረጃ አስቀርቦ ሳይመለከት ከፊል ውሳኔ በማለት መወሰኑ፣በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.182(2) መሰረት ዳኝነት ሳይጠየቅ የንግድ ቤት ትርፍ አመልካች ከቤት ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ልታካፍላት ይገባል በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ታዞ መልስ የሰጡ ሲሆን ሚያዚያ 3 ቀን 2003 ዓ.ም በሶስት ገጽ የሰጡት የመልስ ፍሬ-ሃሳብ፡- አመልካች በውርስ ያገኘው ንብረት የጋራ እንደተባለ በማስመሰል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፣የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰጡት ግን በውርስ ተገኘ የተባለውን ንብረት የጋራ ሀብት ነው በማለት ሳይሆን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ውስጥ የተቀመጠው ገንዘብ በውርስ ያገኘሁት ንብረት ለልማት ተብሎ ሲፈርስ መንግስት የሰጠኝ የካሳ ገንዘብ ነው ያለውን ሆኖ ነገር ግን ማስረጃ ያላቀረበበትን ገንዘብ የሚመለከት በመሆኑ፣ይህም ፍርድ ያረፈው በውርስ የተገኘን ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚመለከት ሳይሆን በውርስ ሀብት ምትክ ካሳ ሆኖ ተከፈለ በተባለው ጥሬ ገንዘብ ላይ በመሆኑ፣የውርስ ሃብት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ተገኘ የተባለውን ጥሬ ገንዘብ የግል ሀብቱ ነው በማለት ክርክር ማቅረብ የሚችለው ደግሞ በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 58 መሰረት ንብረቱ የግል ይባልልኝ በማለት በፍርድ ቤት በማስገለል ብቻ በመሆኑ፣በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ያለው ገንዘብ ቀደም ሲል በተጠሪ ስም ከተከፈተ በኋላ በአመልካች ጉትጉታ በሁለታችን ስም የተደረገና በሁለታችን ጣምራ ፊርማ ብቻ የሚንቀሳቀስ የጋራ ሀብታችን በመሆኑ፣ በሌላ በኩል የሠሌዳ ቁ. 2-95871 የሆነን መኪና በውርስ ሀብት ግምት በተገኘ ገንዘብ የተገዛ ነው በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መኪና በውርስ ነው ያገኘሁት የሚል ክርክር ያላቀረቡ በመሆኑ፣መኪናውም ጋብቻችን ጸንቶ በነበረበት ወቅት በግብይት የተገኘ በመሆኑ እና የግል ስለመሆኑም በፍርድ ቤት የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 58 በሚያዘው መሰረት ያላስወሰነ በመሆኑ እየቀረበ ያለው ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ፣የንግድ ቤትን ትርፍ በተመለከተም ባቀረብኩት የጋራ ሀብት ዝርዝር ውስጥ የጋራ ሀብታችን ነው በማለት ካቀረብኳቸዉ መካከል አንዱ እና ዋነኛዉ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

በግራቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከታያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች በውርስ ያገኘሁት ንብረት በልማት ምክንያት ፈርሶ ካሳ የተከፈለኝ ነው ያለውን ገንዘብ የጋራ ሀብት ነው የመባሉን አግባብነት እና ሌሎችንም ተያያዥነት ያላቸውን ነጥቦች ለመመርመር በሚል በመሆኑ የተያዘው ጉዳይ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በግራቀኙ መካከል አከራካሪ የነበሩ እና ውሳኔ ያገኙ እንደዚሁም በበታች ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ በርካታ የፍቺ ውጤትን የሚመለከቱ የሀብት ክርክር ያለ ሲሆን በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት እያከራከረ ያለው እና የዚህን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሚያሻው አመልካች የውርስ ሀብትን መሰረት ባደረገ የካሳ ክፍያ አገኘሁት የሚሉት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ የሚገኝ ብር 276,320 (ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ብር)፣ አመልካች ከዚሁ የውርስ ሃብት ከተገኘ ካሳ ገንዘብ ላይ ቀንሼ የገዛሁት ተሽከርካሪ ነው የሚሉት የሠሌዳ ቁ.2-95871 አ.አ. የሆነው እና ከንግድ ቤት የሚገኝን ገቢ በተመለከተ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የንግድ ቤት ትርፍ በተመለከተ ተጠሪ በግልጽ ዳኝነት ባልጠየቁበት ሁኔታ መወሰኑ አግባብነት የለውም በማለት በአመልካች የቀረበውን ክርክር ስንመለከት ተጠሪ ባቀረቡት መልስ በግልጽ ዳኝነት የጠየቁበት ስለመሆኑ ከመከራከራቸውም በላይ በፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ስንመለከት ከንግድ ድርጅቱ የሚገኘውን ገቢ ከቤት ከወጣሁበት ቀን ጀምሮ ልካፈል ይገባል በማለት ዳኝነት የጠየቁ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ ዳኝነት ሳይጠየቅበት የተወሰነ ነው በማለት ከፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.182(2) አኳያ የተነሳው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ያነሱት ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ሌላው የውርስ ሀብት መሰረት ባደረገ የካሳ ክፍያ የገዛሁት ተሽከርካሪ ነው በማለት አመልካች የሚያነሱትን ክርክር በተመለከተ ተሽከርካሪው ግራቀኙ በጋብቻ ተሳስረው ባሉበት ወቅት የተገዛ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ መኪናው በጋብቻ ወቅት የተገዛ ከሆነ ደግሞ በቤተሰብ ህጉ በግብይት ስለተገኙ ሀብቶች በሚመለከት ድንጋጌ የሚገዛ ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በተሻሻለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 58 መሰረት ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘዉ ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሽጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል በማለት በንኡስ አንቀጽ አንድ ስር ሲደነግግ በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር ሁለት ስር ደግሞ በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር አንድ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብ እና ፍርድ ቤት ሲያጸድቀው ብቻ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ተሸከርካሪው የግሉ እንዲባልለት ለፍርድ ቤት በማቅረብ ያጸደቀ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ አመልካች በህጉ በተቀመጠው መሰረት በፍርድ ቤት በጋብቻ ወቅት የተገዛው ተሽከርካሪ የግላቸው እንዲባልላቸዉ አቅርበው ያስወሰኑት ነገር በሌለበት ሁኔታ በዚህ የፍቺ ውጤት ክርክር ላይ የግል ሀብት ነው በማለት ያነሱት ክርክር አግባብነት የሌለው ነው ብለናል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች በጋብቻ ወቅት የተገዛውን የሠለዳ ቁ.2-95871 አ.አ. የሆነው ተሽከርካሪ የጋራ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡና የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ አለ የተባለውን ገንዘብ በተመለከተ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ አመልካች ከበታች ፍርድ ቤቶች ጀምሮ እየተከራከረ ያለው ገንዘቡ የተገኘው በውርስ የተላለፈልኝ ንብረት በልማት ምክንያት በመፍረሱ የተነሳ የተከፈለኝ ካሳ ነው በማለት ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ገንዘቡ የጋራችን ነው፣ቀደም ሲል በራሳቸው ስም የተከፈተ እና በኋላ ግን በአመልካች ጉትጎታ በሁላታችን ፊርማ ብቻ እንዲንቀሳቀስ ያደረግነው የጋራ ሀብታችን ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ አመልካች በበታች ፍርድ ቤት ይሄንን ያስረዱልኛል የሚሉትን ማስረጃዎች እንደቆጠሩና ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል በፍርድ ቤት ውሳኔ ያላስገለልክ በመሆኑ የሚያመጣው ለወጥ የለም በማለት ያለፋቸው ስለመሆኑ በቅሬታቸው አመላክተዋል፡፡ ችሎቱም በዚህ ነጥብ ላይ የተነሳውን ክርክር እንደመረመረው አመልካች በተጠቀሰዉ ንግድ ባንክ አለ የሚሉት በቀጥታ ከውርስ ሀብቱ የካሳ ክፍያ የተገኘ ነው በማለት በመሆኑ በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 58 መሰረት በጋብቻ ወቅት በግብይት እንደተገኘ ንብረት በመቁጠር ቀደም ሲል የግልህ ስለመሆኑ ያላስገለልክ በመሆኑ በማስረጃ እንዲጣራ የሚፈቀድበት አግባብ የለም መባሉ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም አመልካች እየተከራከሩ ያሉት በግብይት ስለተገኘው ሀብት ሳይሆን በቀጥታ ከውርስ ሀብቶች ለልማት ተብሎ በመፍረሱ ምክንያት ከተከፈለኝ ካሳ የተገኘ ነው በማለት በመሆኑ በግብይት ስለተገኙ ንብረቶች በሚመለከት በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 58 ስር የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡ የአመልካች ክርክር የሚሸፈነው ከጋብቻ በኋላ በዉርስ በግሉ ያገኘው ወገን የግል ንብረቱ ሆኖ ይቀጥላል የሚለውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 57 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ነጥብ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ በመጥቀስ አከራካሪ የሆነው ገንዘብ የውርስ ሀብት ስለመሆን ወይም አለመሆን አመልካች የማስረዳት መብት እንደሌለው በመቁጠር መታለፉ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ አመልካች በዚህ ነጥብ ላይ ለማስረዳት ማስረጃ የቆጠረ ስለመሆኑ በቅሬታውም ያመላከተ ከመሆኑም በላይ በበታች ፍርድ ቤቶችም የተጠየቀ እና ፍርድ ቤቶቹ ቀድሞ በፍርድ ቤት የግሉ ስለመሆኑ ባላስወሰነበት ሁኔታ የማስረጃዎቹ መሰማት የሚያመጣው ለውጥ የለም በማለት የታለፈ ስለመሆኑ ከውሳኔው መረዳት ይቻላል፡፡

በዚሁ መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ አለ የተባለው ጥሬ ገንዘብ የግል ሀብት ወይም የጋራቸዉ ሀብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለመሆን ወይም አለመሆን ግራቀኙ ባላቸው ማስረጃ ሊያጣራ ሲገባ ሳያጣራ ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም፡፡ አመልካች ገንዘቡ የግል ስለመሆኑ ለማስረዳት የቆጠራቸውን ምስክሮች እና እንዲቀርቡለት የጠየቃቸውን የጽሑፍ ሰነዶች በመስማት እና በማስመጣት እንደዚሁም የተጠሪን የማስተባበያ ማስረጃ በመስማት እና ፍርድ ቤቱም ለፍትሕ አሰጣጥ ተገቢ ነው የሚለውን ማስረጃ በመስማት ውሳኔ መስጠት ሲገባው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የቤተሰብ ህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ማለፉ አግባብነት የሌለው በመሆኑ እና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የተፈጸመውን ስህተት ሳያርም ማለፉ ትክክለኛ አካሄድ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች በተጠቀሰው የንግድ ባንክ ያለውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ ተገቢውን ማጣራት ሳያደርጉ የደረሱበት መደምደሚያ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ. ቁ. 103132 በቀን 7-6-2003ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 78970 በቀን 7-4-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት አከራካሪ በሆኑት የሠለዳ ቁጥሩ 2-95871 አ.አ. የሆነ እና የንግድ ድርጅት ገቢን በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ የሚገኘውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.103132 በቀን 7-6-2003ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 78970 በቀን 7-4-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት የውሳኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
3. በጋብቻ ወቅት በግብይት የተገኘ ንብረት የግል ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ካልተወሰነ በስተቀር የጋራ ሀብት ነው ተብሎ መወሰኑ እና ከጋራ የንግድ ድርጅት የተገኘ ገቢ የጋራ ነዉ መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ የሚገኘውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት እና ለፍትሕ አሰጣጡ አስፈላጊ ነው የሚለውን ማስረጃ በመስማት ገንዘቡ የጋራ ወይም የግል ስለመሆኑ በተመለከተ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ በዚህ ችሎት ውሳኔ ካገኙት ውጪ ያሉትን በተመለከተ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አልተነካም፡፡
5. በዚህ ችሎት በቀን 25-6-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረዉ የዕግድ ትዕዛዝ የሠለዳ ቁ. 2-95871 አ.አ. የሆነውን ተሸከርካሪ እና የንግድ ቤቱን ገቢ በተመለከተ ጉዳዩ እልባት ያገኘ በመሆኑ ተነስቷል፡፡
6. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 69657

የካቲት 28 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሐምዚያ ሼክ ኢብራሀም ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ ኡስማኤል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክስ የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ የአመልካች ባለቤት በነበረው በአቶ ዳውድ ዩሱፍ ላይ ያስፈረደውን ገንዘብ ለማስፈጸም ሲንቀሳቀስ በአወዳይ ከተማ የሚገኘውንና አመልካች የግሌ ነው በምትለው መኖሪያ ቤት ላይ እንዲፈጸም በመታዘዙ፣አመልካች ጉዳዩን በመጀመሪያ ለተመለከተው በኦሮሚያ ብሔ/ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ሆና በመከራከር በዚህ ንብረት ላይ ሊፈጸም የማይገባ ስለመሆኑ ትዕዛዝ ያሰጠች ሲሆን፣ተጠሪ በበኩሉ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቅረብ እና ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የአመልካች ግማሽ ድርሻ ሳይነካባት በፍርድ ባለዕዳው ግማሽ ድርሻ ላይ እንዲፈጸም ያዘዘ በመሆኑ እና የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም ይሄንኑ ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት በማመልከቷ የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በቀን 06-10-2003 ዓ.ም በሶስት ገጽ በተጻፈ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያለቻቸውን ነጥቦች በማንሳት ያቀረበች ሲሆን ፍሬ-ሀሳቡ፡-አመልካች እና የፍርድ ባለዕዳ እ.ኤ.አ. በ1993 ወይም በ1985 ዓ.ም የነበረንን ጋብቻ በሀሮማያ ወረዳ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.815 ከፈረሰ በኋላ እ.ኤ.አ. በ24-5-94 ወይም በ1986ዓ.ም 4 የሀገር ሽማግሌዎች መርጠን በተፈራረምነው የንብረት ክፍፍል ውል የአሁን አመልካች የአቶ ዳውድ ዩሱፍ ድርሻ ብር 200,000/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ሰጥቼ አሁን አፈጻጸም የቀረበበት ቤት ድርሻዬ ሁኖ ከ1986ዓ.ም. ጀምሮ የግሌ ሆኖ ስጠቀምበት የቆየሁ ስለመሆኑ በተረጋገጠበት፣የፍርድ ባለዕዳ እና የፍርድ ባለመብት የክርክሩ ምክንያት የሆነውን ውል የተፈራረሙት ጋብቻችን ከፈረሰ እና ንብረት በሸማግሌዎች ከተከፋፈልን ከበርካታ ዓመታት በኋላ በ1993 ዓ.ም ስለመሆኑ ግልጽ ሁኖ እያለ፣በፍርድ ባዕዳው እና በፍርድ ባለመብት መካከል በተፈራረሙት የመኪና ግዥ እና ሽያጭ ውል ላይ ሳልፈርም እና ንብረታችንን ቀደም ሲል ተከፋፍለን የተለያየን ስለመሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ በንብረቴ ላይ አፈጻጸም እንዲቀጥል መባሉ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ ለዕዳው መክፈያ እንዲውል የታዘዘው ቤት አሁንም በፍርድ ባለዕዳ ስም ያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ፣የአመልካች የግል ንብረት ስለመሆኑ ያቀረባቸው አንድም ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ፣በፌዴራል የቤተሰብ ህጉም የንብረት ክፍፍልን የማጽደቅ ስልጣን ያለው ሸማግሌዎች ሳይሆኑ ፍርድ ቤት ብቻ ስለመሆኑ ስለሚደነግግ፣ይፈጸም የተባለውም በራሷ ድርሻ ሳይሆን በፍርድ ባለዕዳው ድርሻ በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ የአመልካች ትዳር በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የቀድሞ ባለቤታቸው በገቡት ዕዳ መነሻ ቀደም ሲል በክፍፍል ለአመልካች በደረሰ መኖሪያ ቤት ላይ ሊቀጥል ይገባል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ቀደም ሲል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች እና በፍርድ ባለዕዳው አቶ ዳውድ ዩሱፍ ጋር ያላቸው የጋብቻ ግንኙነት በፍቺ የፈረሰበትን ጊዜ በተመለከተ አመልካች በዚህ የሰበር አቤቱታቸው ላይ እ.ኤ.አ. በ1993 ነው በማለት ያቀረቡ ሲሆን በበታች ፍርድ ቤቶች ግን አመልካችም ራሳቸው ሲከራከሩ የነበሩት በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ በፍቺ የፈረሰው በቀን 16-8-1993ዓ.ም በመዝ.ቁ.815 በኦሮማያ ወረዳ ሸሪአ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ እና የበታች ፍርድ ቤቶችም በፍሬ-ነገር ያረጋገጡት ነጥብ ይሄው በመሆኑ በዚህ የሰበር ሰሚ ደረጃ አመልካች ያነሱትን ክርክር ችሎቱ የሚቀበለው ባለመሆኑ አልፈነዋል፡፡

በዚሁ የክርክር ሂደትም በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡት ፍሬ-ነገሮች አመልካች እና የፍርድ ባለዕዳ አቶ ዳውድ ዩሱፍ በጋብቻ ተሳስረው የኖሩ ስለመሆኑ፣በግራቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻም በቀን 16-8-1993 ዓ.ም በወረዳ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በፍቺ የፈረሰ ስለመሆኑ፣የጋብቻ ፍቺ ውጤትን በተመለከተ ግራቀኙ ስምምነት ያደረጉ ሆኖ በፍርድ ቤት ግን ቀርቦ ያልጸደቀ ስለመሆኑ፣ እስከ አሁን ድረስም አከራካሪው ቤት በፍርድ ባለዕዳ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ እና በስሙም ግብር የሚከፈልበት ስለመሆኑ የተመለከቱት ነጥቦች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የፍርድ ባለዕዳ አቶ ዳውድ ዩሱፍ ለአሁኑ ዕዳ ምክንያት የሆነውን እና በባንክ ዕዳ ተይዞ እያለ ለአሁን ተጠሪ ሽጦታል የተባለውን ተሸከርካሪ የሸጠው በቀን 26-4-1993ዓ.ም ስለመሆኑ፣ለአሁን አፈጻጸም ምክንያት የሆነውን ዕዳ ተጠሪ በፍርድ ባለዕዳው ላይ ያስፈረደው ደግሞ በቀን 18-7-1995ዓ.ም ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ-ነገር ረገድ የተረጋገጡ ነጥቦች ናቸው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በፍሬ-ነገር የተረጋገጡትን ነጥቦች ይዘን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት ለአሁን ዕዳ ምክንያት የሆነው ተሸከርካሪ የተገዛው በአመልካች እና በፍርድ ባለዕዳ መካከል የነበረው ጋብቻ ከመፍረሱ ከአራት ወራት በፊት በመሆኑ፣ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለዕዳው አቶ ዳውድ ዩሱፍን በዚሁ የተሸከርካሪ ግዢ ምክንያት በመክሰስ ያስወሰነበት በአመልካች እና በአቶ ዳውድ ዩሱፍ መካከል የነበረው ጋብቻ በፈረሰ በ2ኛ ዓመቱ በቀን 18-7-1995ዓ.ም. ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ግን የፍቺ ውጤትን በተመለከተ በህግ ተቀባይነት ያለው ህጋዊ ክፍፍል ስለመፈጸም ወይም አለመፈጸም በተመለከተ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ክርክር ነጥብ ላይ አመልካች አጥብቃ የምትከራከረው በሸሪአ ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በሸማግሌዎች ዕርቅ በማድረግ የፍርድ ባለዕዳውን የአቶ ዳውድ ዩሱፍ ድርሻ በተመለከተ 200000 ብር /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ በመክፈል አከራካሪውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት የግሌ አድርጌዋለሁ በሚል ነው፡፡ ሆኖም የተደረገው የፍቺ ውጤት ስምምነት ምን ያህል የህግ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.69/1995 እና 83/1996 አንቀጽ 110/5/ እንደዚሁም የፌ/የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ213/92 አንቀጽ 83/3/፣117 ስር በግልጽ እንደተደነገው የፍቺ ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማግሌዎች ወይም በባለሙያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሳኔው ተፈጻሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ እንደሆነ፣ፍቺን እና የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት እና የማጽደቅ ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ስለመሆኑ እና ሌላ ማንኛውም አካል በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የመስጠትም ሆነ የማጽደቅ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ አስገዳጅ በሆነ ቃል ተቀምጧል፡፡ በዚህም ጉዳይ አመልካች በስምምነት የንብረት ክፍፍል ያደረጉ ስለመሆናቸው ክርክር ያቅርቡ እንጂ ለፍርድ ቤት ቀርቦ የጸደቀ ወይም የተወሰነ ስለመሆኑ ያነሱት የክርክር ነጥብ የሌለ ከመሆኑም በላይ በዚህ ነጥብ ላይ የተሰጠ ፍርድ የሌለ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤት በፍሬ-ነገር ረገድ የተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡ አንድ የፍቺ ውጤት ደግሞ በህጉ አግባብ ለፍርድ ቤት ቀርቦ እስካልጸደቀ ድረስ በሽማግሌዎች ፊት የተደረገ የንብረት ክፍፍል ስምምነት መኖሩን በማመላከት መከራከሪያ ማድረግ የማይቻል እና ህጉም ለእንደዚህ ዓይነት ስምምነት ጥበቃ የማያደርግ ስለመሆኑ ከላይ ከተመለከቱት የድንጋጌዎቹ ዓላማ፣ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የአፈጻጸም ሂደት የአመልካች ግማሽ ድርሻ ሳይነካ በፍርድ ባለዕዳው ግማሽ ድርሻ ላይ እንዲቀጥል መባሉ የሚነቀፍበት አግባብ የለም ብለናል፡፡

ባጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የሰበር ሰሚ ችሎት የተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ሂደት የአመልካችን ግማሽ ድርሻ ሳይነካ በፍርድ ባለዕዳው በአቶ ዳውድ ዩሱፍ ግማሽ ድርሻ ላይ እንዲቀጥል በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡና የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.125214 በቀን 23-9-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.93945 በቀን 26-5-2003 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበው አፈጻጸም የአመልካችን ግማሽ ድርሻ ሳይነካ በፍርድ ባለእዳዉ ግማሽ ድርሻ ላይ እንዲቀጥል መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ሰኔ 06 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ምንያ ገ/ሥላሴ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡- ወ/ሪት መሠረት ዓለማሁ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርምራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በጋብቻ ተሳስረው የነበሩ ተጋቢዎች ለረዥም ጊዜ ተለያይተው በመኖራቸው ምክንያት ይህ የትዳር ግንኙነት ተቋርጧል የሚባለው እንዴት ነው? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ አስመልክቶ የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምፅ የሰጠውን ዳኝነት ከዚህ ቀደም በዚህ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ የህግ ጥያቄ አስመልክቶ ከሰጠው ትርጉም ጋር በማገናዘብ አግባብነቱን ለመመልከት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን አመልካች በአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሚስትነታቸውን የሚያረጋግጥ ውሳኔ ካገኙ በኋላ የአሁን ተጠሪ የሚች ልጅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት ይኸው ውሳኔ መብታቸውን እንደሚነካ በማስረዳት የክርክር ተካፋይ ከሆኑ በኋላ አመልካችና ሚች አባቱ በህግ በታወቀ የጋብቻ ሥርዓት ግንኙነት አልመሰረቱም፤ ጋብቻ አለ እንኳ ቢባል አመልካች ከአስር ዓመታት በላይ ኑሯቸውን ውጭ አገር አድርገው ተለያይተው የኖሩ በመሆኑ ጋብቻው ፈራሽ ነው፡፡ በመሆኑም የተሰጠው የሚስትነት ማረጋገጫ ውሳኔ ይሰረዝልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን እንደገና አንቀሳቅሶ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በአመልካችና በሚች መካከል የጋብቻ ግንኙነት ስለመኖሩ በሁኔታ ተረጋግጧል፡፡ ምንም እንኳ አመልካችና ሚች ጋብቻቸው ባለበት ጊዜ በተለያየ ሀገር ተለያይተው መኖራቸው ቢታወቅም ጋብቻቸውን ቀሪ አያደርገውም፡፡ ምክንያቱም በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ አንቀጽ 55 እንደተመለከተው ተጋቢዎች በስምምነት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ተለያይተው መኖር እንደሚችሉና መብታቸው ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች የሚች ሚስት ናቸው በማለት የተሰጠው የሚስትነት ማረጋገጫ ውሳኔ ሊሰረዝ የሚችል አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ የአ/አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአሁን አመልካችና ሚች የጋብቻ ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን ተቀብሎ፤ ነገር ግን ሁለቱም ለ18 ዓመታት ያህል ተለያይተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመኖራቸው ምክንያት የቀጠለ የትዳር ግንኙነት እንዳልነበረ መረዳት ይቻላል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 31891 ለረዥም ጊዜ ተለያይተው ከኖሩ፤ በዚህም ጊዜ ውስጥ የባልና ሚስት ዓይነት ግንኙነት ያልነበራቸው ሰዎች ሚስትነት ወይም ባልነት ተረጋግጦ ማስረጃ ሊሰጣቸው እንደማይችል ያመለከተ ሲሆን በሌሎች የሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቦችም ተመሳሳይ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል። በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ሚችና የአሁን አመልካች ለ18 ዓመት ተለያይተው የኖሩና በዚህም ጊዜ ውስጥ የትዳር ግንኙነታቸው ባቋረጡበት ሁኔታ የአሁን አመልካች ሚስት ናቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ ሆኖ አልተገኘም በሚለው ትችቱ መነሻ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል። የአ/አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይኸው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም በማለት የአሁን ተጠሪን አስቀርቦ ሳያከራክር መዝገቡን ዘግቶታል።

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ይህንኑ ሲመስል ግራ ቀኙ ከዚህ ቀደም በስር ፍ/ቤቶች በየደረጃው ያቀረቡትን ክርክር በማጠናከር በሰበር ደረጃ የፀሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል።

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል እንደመረመርነውም የአሁን አመልካችና የተጠሪ አባት ሚች የጋብቻ ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጡት ዳኝነቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው ይህ የጋብቻ ግንኙነትታቸው ሁለቱም ተለያይተው በመኖራቸው ምክንያት ተቋርጧል ወይስ አልተቋረጠም በሚለው ጭብጥ ስር የተሰጠው የይግባኝ ሰሚው እና የሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔዎች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ አከራካሪ ነጥብ ስር በሌሎች ወገኖች ክርክር መነሻ የሰጠውን ትርጉም መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው።

የአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ምንም እንኳ የአሁን አመልካችና ሚች በተለያየ ሀገር በመኖራቸው በኑሮ የተለያዩ ቢሆኑም የጋብቻ ግንኙነታቸው ግን ሳይቋረጥ የዘለቀ መሆኑ ተረጋግጧል የሚል ውሳኔ የሰጠው በአሁን አመልካች በኩል የቀረቡትን የሰው እና የተለያዩ የሰነድና ገላጭ ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ ነው። በአኳያው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል የነበረው የጋብቻ ግንኙነት መቋረጡን አረጋግጫለሁ ያለው በአመልካች በኩል በቀረበው የሰነድ እና ገላጭ ማስረጃ ሆኖ የቀረበውን በቪዲዮ የተቀረፀውን ምስል ብቻ ምርኩዝ አድርጐ የማስረዳት ብቃቱን በመመዘን እንደሆነ የውሳኔው ግልባጭ አስረጂ ነው። ይኸውም የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርቦ ከተመለከተውና ለውሳኔው መነሻ አድርጎ ከያዘው ማስረጃ መካከል፤ በአመልካች አማካኝነት የቀረቡት የደብዳቤ ልውውጦችና ፍቶግራፎች ተጠሪዋ የአሁኑ አመልካች በውጭ ሀገር በነበረችበት ጊዜ ከሚች ጋር የነበራት ግንኙነት አለመቋረጡን ያመለክታል፤ የወረዳ 19 መረዳጃ እድር የቀረበው መግለጫ ሚች እና የአሁን አመልካች በባልና ሚስት መመዝገባቸውን አረጋግጦ በመላኩ፤ የቀረበውም የቪዲዮ ፊልም የአሁን አመልካች ከውጭ ሀገር ለሚች በምትልከው ገንዘብ ሚች ቤቱን እየሰሩ መሆኑን በማረጋገጥ የደረሰበትን ውጤት ለባለቤታቸው ለአሁን አመልካች ለመግለፅ መልዕክቱን ለመላክ የተቀረፀ ሲሆን ከዚሁ ምስል ሚች ከአሁን አመልካች ጋር የትዳር ግንኙነታቸው ያልተቋረጠ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል በሚል የማስረጃውን አግባብነትና ሚዛን የመረመረበትን ክፍል ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍ/ቤት ከዕድር የመጣው ማስረጃ የዕድሩ ማህተምም ሆነ ቁጥር የሌለው በመሆኑ ተአማኒነት ያለው ነው ብሎ ለመቀበል የሚቻል አይደለም፤ የግል ደብዳቤዎችና ፍ/ቤቱ የተመለከተው የቪዲዮ ማስረጃ የትዳር ግንኙነቱ ስለመቀጠሉ የሚያመለክት ነገር የሌላቸውና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እምነት የሚጣልባቸው ማስረጃዎች አይደሉም፡፡ ለሚች 40 ቀን መታሰቢያ የታተመው የጥሪ ወረቀትም በማንኛውም ጊዜ ሊታተም የሚችል በመሆኑ ታማኝነት ያለው አይደለም የሚለውን ትችት በመስጠት ከጋብቻ የመነጨው ግንኙነት ስለመቀጠሉ በማስረጃ አልተረጋገጠም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

በእርግጥ ይህ በፍሬ ነገርና ፍሬ ነገርን ለማስረዳት የቀረበውን ማስረጃ ታማኝነት የመመርመርና የማስረዳት አቅሙን የመመዘን ሥልጣኑ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንጂ ለዚሁ የሰበር ሰሚ ችሎት በህግ የተሰጠው ሥልጣን ባለመሆኑ በዚህ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በማስረጃ አመዛዘን ረገድ የሰጠውን ዳኝነት እንደገና ለመመርመርና፤ አግባብነቱን ለማየት የሚቻል አይደለም፡፡

ይሁን እንጂ በአሁን አመልካችና በሚች መካከል የነበረው የጋብቻ ግንኙነት በመኖሪያ ቦታ መለያየት የተነሳ ሳይቋረጥ ግንኙነቱ እንዳለ፤ እንደቀጠለ ነበር በማለት የአሁን አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ እና የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ለሰጠው ውሳኔ ምርኩዝ አድርጎ የያዘው ማስረጃ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ ትችት ባሳረፈበት የሰነድ እና ገላጭ ማስረጃዎች ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ የሚች እህት የሆኑትን እና የሚች ጐረቤትን የምስክርነት ቃል ሁሉ የያዘ ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የምስክርነት ቃል ውስጥ ሁለቱም በአካባቢው በእድር፣ እና በቤት ስራ ማህበር በባልና ሚስትነት እንደሚታወቁ፤ ሚች ሥራ ስላልነበራቸው ተጠሪዋ የቤተሰባቸውን ኑሮ ለመለወጥ ከባለቤታቸው ጋር ባደረጉት ስምምነት ወደ ውጭ አገር ሄደው ሥራ በመስራት በሚልኩት ገንዘብ ቤት መስራታቸውን ሚችም ሲታመም ገንዘብ በመላክ ታስታምመው እንደነበር እስከ ሚች ዕለተ-ሞት በትዳር ሁኔታ ውስጥ እንደነበሩ በመግለጽ ያረጋገጡበት ይገኝበታል፡፡

ስለዚህ የሰው ማስረጃ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያለው የለም፡፡ ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን ማስረጃ ከማስረጃው አግባብነት ተቀባይነት እና የማሳመን ብቃት አንጻር በማየት የማይቀበለው ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ሳይመለከተው የቀረ ካልሆነ በቀር ክርክርን በማስረዳት የቀረበን የተከራካሪ ወገን ማስረጃ በዘፈቀደ ውድቅ ማድረግ እንደማይችል ስለማስረጃ አቀባበል በተደነገጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 257፣ 258 እና 259 ተመልክቷል፡፡ ይህም የተከራካሪ ወገንን የመደመጥ መብት ለማስከበር ሲባል የተዘረጋ ሥርዓት ነው፡፡ እንዲሁም የበታች ፍ/ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በክርክርና ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን፤ የተሰማን ማስረጃ አንድ በአንድ በማገናዘብ በመተቸት፤ የሚቀበለውንና የማይቀበለውን በመለየት ዳኝነት መስጠት እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181 እና 182 በተመለከተው የፍርድ አሰጣጥ ሥርዓት ተደንግጓል፡፡ የበላይ ፍ/ቤትም ይህ ዳኝነት የፍርድ አሰጣጥ ስህተት የማስረጃ አቀባበል ሥርዓት ጉድለት መፈፀሙን የሥር ፍ/ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ የሚያስረዳና ሳይመረመርና ሳይታይ የታለፈው የማስረጃ ይዘት በመዝገቡ ላይ ሰፍሮ ከተገኘ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 242 መሰረት በዚሁ የመዝገብ ግልባጭ ላይ በመመርኮዝ አስፈላጊውን ዳኝነት መስጠት እንደሚቻልም ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም የአሁን አመልካችና የሚች የጋብቻ ግንኙነት ሳይቋረጥ እስከ ሚች ዕለተ ሞት ድረስ ግንኙነት የቀጠለ ስለመሆኑ የሥር የአ/አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰው ማስረጃ ያረጋገጠው የፍሬ ነገር ጉዳይ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ይህም ከሆነ በሀገሪቱ ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጎምና አፈጻጸም ማስፈን ይቻል ዘንድ እንደ አንድ ስልት ተቆጥሮ በወጣው በአዋጅ ቁጥር 454/97 ድንጋጌ መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው የሰጡት የህግ ትርጉም በበታች ፍ/ቤቶች የአስገዳጅነት ኃይል ወይም ባህርይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚኖረው ትርጉም በተሰጠበት እና ዳኝነት እንዲሰጥበት በቀረበው ጉዳዮች መካከል የተነሳው የፍሬ ነገርና የህግ ጥያቄ የተመሳሰለ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው።

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ አዋጅ መሰረት የተጠቀሰውንና አስቀድሞ ትርጉም የተሰጠበትን በሰበር መ/ቁ 31891 የተሰጠውን ውሳኔ ማየት እንደሚቻለው ሁለቱም ለ12 ዓመታት ተለያይተው እንደኖሩ ተጠሪም በውጭ ሀገር በመኖር ላይ እንዳለች ሌላ ባል አግብታ ትኖር እንደነበር በክርክር ደረጃ የቀረበው ሳይጣራ የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ እንደገና ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል በማለት ለሰጠው ዳኝነት እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በደፈናው የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም በሰጠባቸው "ሌሎች መዝገቦች" የሚለው አገላለጽ በሰበር መ/ቁ 14290፤ 20938 የተሰጠውን ለመጥቀስ ተፈልጐ ከሆነም ተለያይተው የኖሩ ተጋቢዎች በየፊናቸው የየራሳቸውን ህይወት ስለመጀመራቸው ሚች ሌላ ሚስት አግብተው ስለመኖራቸው ተረጋግጦ መሆኑ ሁሉ ታይቶ ትርጉም የተሰጠበት ስለሆነ በፍሬ ነገር ረገድ በአሁን አመልካች በምንያ ገ/ስላሴ እና ተጠሪ ወ/ሪት መሰረት ዓለማየሁ መካከል ከተነሳው ክርክር ጋር የሚመሳሰል አይደለም። የሚመሳሰል ባለመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 454/97 መሰረት ታይቶ ሊወሰን የሚችል አይደለም።

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ከማስረጃ አቀባበል ሥርዓትና ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አፈጻጸም ረገድ አንጻር ሲታይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም የሚከተለውንም ውሳኔ ሰጥተናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ 14194 በ26/2/2003 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ፤ በአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 14801 በ20/7/03 ዓ.ም. በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል።
2. የአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1706/00 በቀን 6/11/2002 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ ፀንቷል።

   ይህ የሰበር ክርክር ስላስከተለው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።

   መዝገቡ ተዘግቷል፤

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 72420

ሚያዝያ 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐሳስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኬሪያት ያህያ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- ሐጂ ጅሀድ ኡመር በሌለበት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት የፍቺ ውጤትን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረው በጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች ከሳሽነት ነው፡፡ አመልካች ባቀረበችው ክስ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ በጅማ ዞን የሸሪአ ፍርድ ቤት የፈረሰ መሆኑን፣ ከፍቺ በኋላ የጋብቻ ውጤትን በተመለከተ ግን በመደበኛ ፍርድ ቤት የመጠየቅ መብት ተጠብቆልኝ ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ ድርሻዬን እንዲሰጠኝ በሚል ነው፡፡ ተጠሪም መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ ጉዳዩ ከዚህ በፊት ለዚሁ የወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ውሳኔ መሰጠት ያለበት የፍቺ ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት ራሱ ስለመሆኑ በማመልከት ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ድጋሚ ሊታይ አይገባውም በሚል የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የክልሉ የወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ቀደም ሲል የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ክስ ቀርቦ ማየት ያለበት የፍቺ ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት ነው በማለት ይሄው ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠበት በመሆኑ ድጋሚ ሊቀርብ አይገባም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.5 እና 245/2/ መሰረት በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ይሄው ውሳኔ በክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የሰበር ሰሚ ችሎት ጸንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች ነሐሴ 26 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበችው አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያለቻቸውን ነጥቦች ያነሳች ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- በመካከላችን የነበረው ጋብቻ በጅማ ዞን ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከፈረሰ በኋላ የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድርሻዬን እንዲሰጠኝ ክስ አቅርቤ ውሳኔ የሰጠበት ሁኖ ተጠሪ ውሳኔው ላይ ይግባኝ በመጠየቁ የክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ለመመልከት ስልጣን የለውም በሚል ውሳኔውን በመሻር ክሱን ግን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የማቅረብ መብቴን ጠብቆልኛል፡፡ በዚሁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት ለጅማ ዞን ሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቤ ስከራከር ከቆየሁ በኋላ ጉዳዩን ለማየት አልችልም በማለት ውሳኔ በመስጠቱ ምክንያት ለከተማው የወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረብኩት ክስ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔ ሊሰጥበት ሲገባ ከዚህ በፊት የተመለከትኩት ነው በማለት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የቀረበውን የፍቺ ዉጤት ክርክር ውድቅ ማድረጉ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ ፍትሕ የማግኘት መብቴን ያጣበበ ነው በማለት እንዲታረምላት ጠይቃለች፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች ያቀረበችው የፍቺ ውጤት ክስ የሸሪዓም ሆነ የመደበኛ ፍርድ ቤት በመመልከት ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው መታለፉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 37 መሰረት ፍትሕ ከማግኘት መብት አኳያ ለመመርመር በሚል ያስቀርባል በመባሉ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎ ጉዳዩ ለውሳኔ አድሮአል፡፡

ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተቋጨ ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የፍቺ ውሳኔ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ከተሰጠ በኋላ አሁን እያከራከረ ያለውን የፍቺ ውጤት መመልከት ያለበት የትኛው ፍርድ ቤት ነው የሚለው ነጥብ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡ በእርግጥ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 78/5/ መሰረት ለሚቋቋሙት የሐይማኖት ፍርድ ቤቶች እውቅና እንደተሰጠ እና እንደሚደራጁ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ አግባብ በተቋቋሙት የሐይማኖት ፍርድ ቤቶች የተከራካሪ ወገኖችን ፈቃደኝነት መሰረት በማድረግ ሊዳኙ እንደሚችሉ በዚሁ ህገ-መንግስት አንቀጽ 34/5/ ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ግራ ቀኙ ጉዳያቸውን ለሸሪዓ ፍርድ ቤት በማቅረብ የፍቺ ውሳኔ ያገኙ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡ የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ግን አመልካች የሸሪዓ ፍርድ ቤት በመደበኛ ፍርድ ቤት መጠየቅ እንድችል መብቴን ጠብቆልኝ አሰናብቶኛል በሚል ለመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበች ስለመሆኑ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ውሳኔ የፍቺ ውጤትን ተመልክቶ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ የሰጠው ነው በማለት ያልተቀበሉት መሆኑን፣ ጉዳዩን ለተመለከተው የሸሪዓ ፍርድ ቤት የፍቺ ውጤቱን በተመለከተ ክስ ያቀረበች ስለመሆኑ፣ ሁኖም ግን የፍቺ ውሳኔ የሰጠው የሸሪዓ ፍርድ ቤት አመልካች በመደበኛ ፍርድ ቤት ቀድሞ ክስ ማቅረባቸው በዚህ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን ያመላክታል በማለት አናስተናግድም በሚል መዝገቡን የዘጉት ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው ቀድሞ የፍቺ ውሳኔ የሰጠው የሸሪዓ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል ያለውን የፍቺ ውጤት በተመለከተ ተመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት ያልፈለገ መሆኑን እና በዚህም ምክንያት መዝገቡን ስለመዘጋቱ መመልከት ይቻላል፡፡ የፍቺውን ውሳኔ የሰጠው የሸሪዓ ፍርድ ቤት የንብረት ክፍፍሉንም በተመለከተ እልባት ይሰጣል ተብሎ ቢገመትም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ይሄንን የክርክር ነጥብ በተመለከተ ለመደበኛ ፍርድ ቤት እንዲያቀርቡ መብት በመጠበቅ መዝገብ ሲዘጉ ወይንም አናስተናግድም በማለት ተከራካሪዎችን ሲያሰናብቱ ዜጎች መብታቸውን ለማስከበር ያላቸው መፍትሔ ምን እንደሆነ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት ከላይ እንደተመለከተው በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ክርክር ይዳኛል ተብሎ የተቋቋመው አካል እና ግራ ቀኙ ፈቃደኝነታቸውን የገለጹለት አካል በተለያየ ምክንያት ጉዳዩን ለመመልከት ያልፈለገ እንደሆነ ዜጎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 37/1/ መሰረት ጉዳያቸውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት የማቅረብ እና ፍትሕ የማግኘት መብት ሊጠበቅላቸው የሚገባ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መደበኛ ፍርድ ቤቶችም እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ዜጎች ጉዳያቸውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት በማቅረብ ፍትሕ የማግኘት መብታቸው ሊረጋገጥ ስለሚገባ፣ ጉዳዩን እንዲያይ የቀረበለት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አልመለከትም በማለት በብይን ተከራካሪዎችን ያሰናበተ ስለመሆኑ እየታወቀ እና ይሄ ሲሆን መደበኛ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማያስተናግዱ ከሆነ ደግሞ ዜጎች ያላቸውን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚያጣብብ በመሆኑ አግባብነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ባጠቃላይ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎች በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አላስተናግድም በማለት የዘጋውን ጉዳይ ስልጣን ያለው መደበኛ ፍርድ ቤት አላስተናግድም በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.128962 በቀን 21-10-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.18872 በቀን 02-6-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 21069 በቀን 15-4-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. መደበኛ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበችውን የፍቺ ውጤት ጥያቄ ማስተናገድ አልችልም በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለው ነው ብለናል፡፡
3. የጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበችውን የፍቺ ውጤት ክስ በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት እና በማጣራት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.341/1/መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት በአመልካች ላይ የደረሰውን ወጪና ኪሳራ የራሷን ትቻል ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሞላ ንጉሴ - ጠበቃ መሉጌታ ዘመነ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ንጉሴ ገለታ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአቀረቡት የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የአመልካች እህት ወ/ሮ አረጋሽ ሲሳይና የአሁኑ ተጠሪ በጋብቻ አብረው ሲኖሩ በጋራ ያፈሩት ንብረት መኖሩን፣ ወ/ሮ አረጋሽ ሲሳይ ከዚህ አለም በመለየታቸው ምክንያት ጋብቻው በሞት መፍረሱን ገልጸው ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብላቸው አመልካች ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ተጠሪን አስቀርቦ ተጠሪ ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር ከአቀረቡ በኋላ ፍ/ቤቱ የውርስ ንብረቱ ተጣርቶ እንዲቀርብ የውርስ አጣሪዎችን ሹሞ የውርስ አጣሪዎች ሀብቱን አጣርተው ለፍ/ቤቱ ሪፖርቱን ሲያቀርቡ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ ፍ/ቤቱ በመጀመሪያው ዙር የውርስ አጣሪዎች የውርስ ንብረቱን አጣርተው ሲያቀርቡ ሊጣሩ የሚገባቸው ነጥቦች መኖራቸውን ገልፆ እንደገና እንዲያጣሩት አድርጎ ጉዳዩ በድጋሚ ተጣርቶ ቀርቦለት ጉዳዩን መርምሮ ለወ/ሪት ሸዋዬ ንጉሴ እንዲከፈል ተብሎ በሪፖርቱ በአንድ የውርስ አጣሪ የተካተተውን የብር 21,600.00 (ሃያ አንድ ሺህ ስድስት መቶ) ክፍያን ያለመቀበሉንና የሚች ወ/ሮ አረጋሽ ሲሳይ ወራሾች የአሁኑን አመልካች ጨምሮ አምስት መሆናቸውን ዘርዝሮ በሌሎች ነጥቦች ላይ ተጣርቶ በ05/03/2002 ዓ.ም. እና በ06/07/2002 ዓ.ም. ተጣርቶ የቀረበውን ሪፖርት ፍ/ቤቱ ተቀብሎ አዕድቆታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ተሻሽሎ የሚችን ድርሻ ወራሾች እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ ተወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የሚች ወራሾች በተገቢው መንገድ ተጠርተው ባልቀረቡበት ሁኔታ ተጠሪ የሚች ወራሾች አሉ ስላሉና ከእድገት ፋና መረዳጃ እድር ውስጥ የተዘረዘሩ ሰዎች የሚች ወራሾች ናቸው ተብሎ የሚች ድርሻ ንብረት ለአምስት እንዲከፋፈል መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ወራሽ ስለመሆናቸው በሕግ አግባብ ያልተረጋገጠና በውርስ አጣሪውም ጥሪ ላልቀረቡ ሰዎች የውርሱ ተካፋዮች ናቸው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሁፍ በሰጡት መልስ የሚች ወራሾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ብቻ ሳይሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች ስማቸው የተጠቀሱት ሰዎች ሆነው በአማራ ክልል በሰሜን ወሎ ዞን ወልዲያ አካባቢ በየጂ ቀበሌ ማህበር አካባቢ በሕይወት ያሉ መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የውርስ አጣሪው ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ሪፖርት የሟች ወ/ሮ አረጋሽ ሲሳይ ወራሾች እንዲቀርቡ ጥሪ ተደርጎላቸው ከአመልካች ውጪ ያሉት ያልቀረቡ መሆኑን፣ ሟች ከአመልካች ውጪ ሌላ ወራሾች አሏቸው ተብሎ የሟችን ድርሻ ከአመልካች ጋር እኩል እንዲካፈሉ የተወሰነው ከእድገት ፋና መረዳጃ እድር ውስጥ በሟች ወራሽነት ስማቸው ተዘርዝሮ ተገኝቷል በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 956 እንደተደነገገው የአጣሪው ሥራ ሟቹ አንድ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግና በመጨረሻም ውርሱ የሚደርሳቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ፣ የውርሱን ሃብት ማስተዳደር፣ መክፈያቸው የደረሰውን የውርስ እዳዎች መክፈል እና ሟቹ በኑዛዜ ያደረጋቸውን ስጦታዎች መክፈልና የኑዛዜውን ቃል ለመፈጸም ማንኛቸውም ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎች ማድረግ ነው፡፡

የሟች ወራሾች እነማን እንደሆኑ ለመለየት የሟችን የኑዛዜና ያለኑዛዜ ወራሾችን ማጣራት የውርስ አጣሪው አቢይ ስራ ሲሆን ያለኑዛዜ ወራሾችን የመለየት ስራውን ለመተግበር ደግሞ በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 842 እስከ 856 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሰረት ሟች ልጅ ወይም ተወላጆች ያሉት መሆኑን ወይም የሟችን ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆችን እንደ የደረጃቸው መኖራቸውን መለየትን የግድ የሚል ነው፡፡ የውርስ አጣሪው ይህንኑ ስራ ሲያከናውን ሊከተላቸው ከሚገባቸው መንገዶች አንዱ የሟች ያለኑዛዜ ወራሽ ካለ በተገቢው መንገድ ጥሪ ማድረግ ነው፡፡ የሟች ወራሾችን ለመለየት ውርስ አጣሪው በመጀመሪያ ደረጃ ማድረግ ያለበት የሟች ኑዛዜን ማፈላለግ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 962(1) ስር የተደነገገ ሲሆን ይህንኑ ግዴታውን ለመወጣትም የሟች የተለያዩ ፅሁፎችን በመፈተሽ ኑዛዜ የተወ መሆን ያለመሆኑን ጥረት ማድረግን፣ ሟች በኖረበት ቦታ በሚገኙት በሕግ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጣቸው ክፍሎች ወይም ፍ/ቤት መዝገብ ቤቶች ውስጥ ሟች በሕይወት ዘመኑ ያስቀመጠው ኑዛዜ መኖሩን ማረጋገጥን ሁሉ እንደሚያስፈልግ የፍ/ሕ/ቁጥር 891 እና 962/2/ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ያስገነዝባል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሟች ጽሑፎችን ውርስ አጣሪው ይመረምራል፣ በሕግ ለማዋዋል ስልጣን ከተሰጣቸው ዘንድና በፍርድ ቤት መዝገብ ቤቶች ተገቢ የሆኑ ፍለጋዎችን እንደሚያደርግ ኃይለ ቃል ባለው አገላለፅ ሲያስቀምጡ የሚያስገነዝቡት ቁም ነገር በየትኛውም ቦታ የሚገኝ ማንኛውም ማስረጃ ቀርቦ የሟች ኑዛዜ ነው ተብሎ ዋጋ የማይሰጠው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ በተመለከቱት ቦታዎች ዘንድ የሚገኙት ሰነዶች በጥንቃቄ መፈለግ አለባቸው እንጂ ከየትኛውም ቦታ የሚቀርቡ ማስረጃዎች ሁሉ ዋጋ የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡ በዚህም መሰረት በመረዳጃ እድር መዝገብ ይገኛል የተባለው ሰነድ የሟችን ወራሾችን ለጊዜው ለመወሰን ብቃት የሌለው ማስረጃ መሆኑን ከፍ/ብ/ቁጥር 962/2/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የሟች ወ/ሮ አረጋሽ ሲሳይ ያለኑዛዜ ወራሾች ካሉ እንዲቀርቡ በተገቢው መንገድ ጥሪ የተደረገላቸው መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከአመልካች ውጪ ሌሎች ሰዎች ያለኑዛዜ ወራሾች አሉ ወደሚለው ድምዳሜ የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱት ከእድገት ፋና መረዳጃ እድር መዝገብ ውስጥ ስማቸው ተዘርዝሮ ተገኝቷል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በመረዳጃ እድር መዝገብ ውስጥ ስም ተጠቅሶ መገኘት ያለኑዛዜ ወራሽነትን ለማረጋገጥ ብቃት ያለው ማስረጃ አይደለም፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ውጪ ያሉ ሌሎች የሟች ወራሾች አሉ በማለት ይኖሩበታል የሚሉትን አድራሻ ሁሉ እየጠቀሱ እየተከራከሩ እነዚህ ሰዎች ቀርበው እስካሁን ድረስ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ያለማድረጋቸውም ተገቢነት ያለውና የክርክራቸውን እውነትነት የሚያሳይ አይደለም፡፡ የሟች ሌሎች ወራሾች ካሉም በሕጉ አግባብ አመልካችን ከሚጠይቁ በስተቀር ከወዲሁ ተጠሪ ከሟች ድርሻ ለመውሰድ ያልቀረቡትን ሰዎች በመወከል ንብረቱን እንዲይዙ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪ ሟች ከአመልካች ውጪ ሌሎች ወራሾች መኖራቸውን እየገለፁ ከመከራከራቸው በተጨማሪ ለአመልካች የሟች ሁሉም ድርሻ አይገባቸውም የሚሉበት ሌላው ምክንያት ያለኑዛዜ ወራሽ የተባሉት ነገር በጥሪው መሰረት ያልቀረቡትን ሰዎች ድርሻ ሊወስድ የሚገባው መንግስት ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 852 ስር እንደተመለከተው የሟች ውርስ ለመንግስት ሊተላለፍ የሚችለው በሕጉ አግባብ የተመለከቱት የሟች ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉ ዘመዶች ከሌለ ብቻ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው የተጠሪ ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለልም ወራሽ ስለመሆናቸው በሕግ አግባብ ያልተረጋገጠና በውርስ አጣሪውም ጥሪ ስላልቀረቡ ሰዎች የውርስ ተካፋዮች እንዲሆኑ ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 944/ሀ/፣ 962፣ ከቁጥር 842 እስከ 856 እንዲሁም 962 እና ከቁጥር 1097 እስከ 1113 ድረስ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33/2/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15035 ሚያዝያ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 94752 ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የሟች አረጋሽ ሲሳይ ድርሻ ንብረት አመልካች ለብቻቸው እንዲወስዱት ከሚደረግ በስተቀር ከሌሎች አራት ሰዎች ጋር እኩል ድርሻቸውን እንዲወስዱ የሚደረግበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. የሟች አረጋሽ ሲሳይ ወራሽ የሚሆን ሰው ካለ በሕግ አግባብ ድርሻውን ከአመልካች ከመጠየቅ ይህ ውሣኔ አያግድም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ ሰብስቤ - ወኪል ፍቅርተ እንደሻው ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ሻለቃ ባሻ እንደሻው - ቀረበ

2. አቶ እሸቱ እንዳሌ - ቀረበ

መዝገቡ ያደረው ለውሳኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ክርክር ሆኖ የፍቺ ውጤትን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ሂደት በተሸጠው የጋራ መኖሪያ ቤት ላይ አመልካች የቀደምትነት መብት ይገባኛል ጥያቄን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔ/ክል/መንግስት በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው ይሄው የክልሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀን 28-10-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ባልና ሚስት በሚሸጠው የጋራ ቤት ሽያጭ ሂደት ላይ ተጫራች ሆነው እንዲሳተፉ የፈቀደላቸው ስለመሆኑ፣ በጨረታው ሂደት ግን የአሁን 2ኛ ተጠሪ ያሸነፈ ስለመሆኑ፣ ቀደም ሲልም አመልካች ያመለከቱት የቅድሚያ መብት ጥያቄ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግን በጨረታው ሂደት ተጫራች ሆነው እንዲሳተፉ መብት የሰጠ እንጅ የቀደምትነት መብት ባለመሆኑ፣ በዚሁ ቀን ጠዋት የተሰጠው ትዕዛዝ ይዜንን ሳያገናዝብ በስህተት ስለመሆኑ በማመላከት የቀረበውን የቀደምትነት መብት ጥያቄን ውድቅ በማድረግ በጨረታው ሂደት ተሳትፎ አሸናፊ የነበረው 2ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዛ ስለመሆኑ የቀረበውን ሪፖርት በማጽደቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራቀኙን ክርክር በመስማት ይዜንኑ የክልሉ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን ቅሬታ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው አቤቱታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች ባቀረበችው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያለቻቸውን ነጥቦች በማንሳት የተከራከረች ሲሆን ፍሬ ሃሳቡ፡- ቀደም ሲል የክልሉ የወረዳ ፍ/ቤት ቤቱን ቅድሚያ እንድወስድ የሰጠውን አስገዳጅ ትዕዛዝ በመለወጥ ሌላ ትዕዛዝ መስጠቱ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ባለመሆኑ፣ ስለጋራ ባለሀብትነት ከሚመለከቱት የፍትሐብሔር ድንጋጌዎች አኳያ በቀደምትነት በግዥ ስለማስቀረት መብት ከሚመለከቱት ድንጋጌዎች አንጻር በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የሌለው በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዞ በየራሳቸው ጥቅምት 8 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ ባልና ሚስት በሚሸጠው ቤት ጨረታ ላይ እንዲሳተፉ የተደረገ እና በሂደቱ እንደማንኛውም ተሳታፊ ተሳትፈው የተሸነፉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለመሆኑ፣ 2ኛ ተጠሪ በሂደቱ አሸናፊ በመሆን ቤቱን የገዛ በመሆኑ እና 1ኛ ተጠሪም ሆነ ለአመልካች የተሰጠው ዕድል በጨረታው ላይ የመሳተፍ እንጂ የተለየ ነገር በሌለበት ሁኔታ አመልካች የምታነሳው ቅሬታ አግባብነት የሌለው ነው በማለት ተከራክሯል። አመልካች ቅሬታዋን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥታለች።

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል። እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች ያነሳችው የቀደምትነት መብት ውድቅ መደረግ ስለጋራ ባለሀብት ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አኳያ ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ቀደም ሲል ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል።

በዚሁ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች በፍቺ ውጤት አፈጻጸም ወቅት በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሆነው ቤት በጨረታ እንዲሸጥ ስለመታዘዙ፣ በዚህን ሂደት ውስጥ ሁለቱም ወገኖች የቀደምትነት መብት መጠየቃቸው፣ ሁኖም ግን ፍርድ ቤቱ በጨረታው ሂደት እንዲሳተፉ እድል በመስጠት እና ለሁለቱም ወገኖች የተለየ መብት ሳይሰጥ የጨረታው ሂደት የተከናወነ ስለመሆኑ፣ በዚህም ሂደት ባልና ሚስት ተሳታፊ የነበሩ ቢሆንም ማንኛቸውም ያላሸነፉ እና በጨረታው ተሳታፊ የነበረው 2ኛ ተጠሪ ያሸነፈ ስለመሆኑ ነው። አመልካችም ብትሆን ቀደም ሲል ጨረታው ከተከናወነ በኋላ በቅድሚያ እንድወስድ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ፍርድ ቤቱ በስህተት ነው በሚል ማስተካከያ መስጠቱ አግባብነት የለውም ከሚል በስተቀር ከላይ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በተመለከተ የምታነሳው ክርክር የሌለ ከመሆኑም በላይ ከጨረታው መከናወን በፊት የቀደምትነት መብት ከ1ኛ ተጠሪ በተለየ መልኩ ተሰጥቶኛል የሚል ክርክር የላትም።

በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በመያዝ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት ክርክሩ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን በቀጥታ ተፈጻሚነት ያለው ህግ የክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/1996 መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በዚህ የክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 103/1/ መሠረት የፍቺ ውጤትን በተመለከተ በዓይነት ለመከፋፈል አዳጋች የሆነን እና ከተጋቢዎቹ እንደኛው ወገን ለሌላኛው ለመተው መስማማት ያልቻሉ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ የሚደረግ ስለመሆኑ እና በዚሁ ድንጋጌ ስር በአሻሻጡ ሂደት ግራ ቀኙ ያልተስማሙ እንደሆነ ሽያጩ የሚደረገው በጨረታ እንደሆነ ተደንግጓል።

በዚህ ጉዳይ ደግሞ ሁለቱም ባልና ሚስት ሲቀርቡ ፍርድ ቤቱ ለሁለቱም የፈቀደው እንደማንኛውም ተጫራች በጨረታው እንዲሳተፉ የሚል እስከሆነ ድረስ እና ተሳትፈውም አሸናፊው 2ኛ ተጠሪ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካች በተለየ ሁኔታ የቀደምነት መብት ይገባኛል በማለት የምታቀርበው ክርክር አግባብነት ያለው ሁኖ አልተገኘም። የበታች ፍርድ ቤቶችም በጨረታው ሂደት ያሸነፈውን 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ይረከብ በማለት ውሣኔ መስጠታቸው በአግባቡ እና በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 439 እና ተከታዮቹ ስር መሠረታዊ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ መርህን ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያመላክት ነገር አላገኘንም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባጠቃለይ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበችውን የቀደምትነት ግኝር መብት በተመለከተ ውድቅ በማድረግ በጨረታው መሠረት አሸናፊው ወገን /2ኛ ተጠሪ/ ቤቱን እንዲረከብ በማለት ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡና የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝ ብሔ/ክል/ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ. 54623 በቀን 11/11/2003 ዓ.ም. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ. ቁ. 10567 በቀን 08/11/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የሀዋሳ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝ .ቁ.21347 በቀን 28/10/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የቀደምትነት ግኝር መብት ወድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 72286

ሰኔ 19 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ኃ/ስላሴ ወርቁ - ከጠበቃ ያሲን እድሪስ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ምስራቅ ወርቁ - ከጠበቃ ነሲቡ አልዩ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ኑዛዜን መሰረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘትም የአሁኑ አመልካች እናት ወ/ሮ የሺ ይልማ መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ በፍርድ ቤት ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ.ም. መጽደቁን ገልፀው ኑዛዜውን ሚች በእርጅና ምክንያት ጃጅተው እያለ ያደረጉት በመሆኑ፣ በኑዛዜው ሰነድ ላይ የተቀመጠው ፊርማም የሚች ባለመሆኑ፣ ኑዛዜው በሐሰት ውንጀላ አመልካችን የነቀለ በመሆኑ፣ የኑዛዜ ቃሉ በስጦታ ውሉ መተካቱም የኑዛዜ ተጠቃሚነትን ቀሪ የሚያደርግ ነው፣ የህጉን ፎርማሊቲ የጠበቀ ስላልሆነ የተጠሪ የኑዛዜ ተጠቃሚነት ሊሰረዝ ይገባል ሲሉ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለአመልካች መቃወሚያ አቤቱታ በሰጡት መልስ ሚች በሙሉ ጤንነታቸው የሚሰሩትን ተግባር በማወቅና በመገንዘብ ያደረጉት ኑዛዜ መሆኑን፣ አመልካችን ከውርሱ የነቀሉትም ይሰድባቸው፣ ያንገላታቸው፣ ያዋርዳቸው፣ ለመደብደብ ሙከራ ያደርግባቸው ስለነበር መሆኑና ይህም በኑዛዜ ሰነዱ ተጠቅሶ ከተገኘ እንደ እውነት የሚወሰድና ከውርስ ለመንቀል በቂ እና ሕጋዊ ምክንያት መሆኑን፣ የኑዛዜው ሰነድ በ24/01/2001 ዓ.ም. ስጦታ ውሉ መተካቱም እርስ በእርሱ የሚጣጣምና አመልካች ከውርስ እስከተነቀሉ ድረስ የስጦታ ውሉ ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለት መቃወሚያ ሊያነሱ እንደማይችሉ በህጉ ክልክላ የተደረገ መሆኑን ገልጸው የአመልካች የመቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ ሊሆንልኝ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙ ምስክሮችን በመስማትና ፊርማው በፎረንሲክ ፖሊስ እንዲመረመር አድርጎ ጉዳዩን መርምሮ የሮረንሲክ ምርመራ ውጤቱን በተመለከተ ፊርማውን መለየት አልተቻለም፣ ፊርማውን ማጣራት አልተቻለም የሚሉ ሐረጎች በአንድ ላይ የያዘ በመሆኑ ውጤቱ ፊርማው የሚች አይደለም ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ ማለፉን ገልፆ የፊርማውን ክርክር በዚሁ ያለፈው ሲሆን ዋናውን ክርክር በተመለከተ የኑዛዜ ሰነዱ በስጦታ ውሉ መተካቱን፣ ይህ ሆኖ እያለ ተጠሪ የኑዛዜ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጠኝ ጥያቄ ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው አግባብ እንዳልነበር፣ የአመልካች ከውርስ መነቀል ያለመነቀል በኑዛዜ ሰነዱ በፀደቀበት ሳይሆን ከስጦታ ውሉ ጋር ተያይዞ በሚነሳው ክርክር ሊታይ የሚገባው መሆኑን በምክንያትነት ይዞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪ የተሰጠውን የኑዛዜ ወራሽነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 360(2) መሰረት ሰርዞታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ሟች የውርስ ንብረታቸውን ለአሁኗ ተጠሪ በኑዛዜ መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ/ም ከሰጡ በኋላ መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. በተደረገ የስጦታ ውል ደግሞ ለተጠሪ መልሰው ማፅደቃቸው ንብረቱ የተላለፈለት ሰው አንድ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 900(1) መሰረት ተገቢ መሆኑን ገልጾ የኑዛዜ ሰነዱ በስጦታ አልተሻረም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 900(1) ሳይሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 898(2) መሆኑን ገልጾ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በስጦታ ውሉ በከፊል ተሽሯል በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ከአሻሻለ በኋላ የስር ፍ/ቤት ያልተሻረውን የኑዛዜ ክፍል በሚመለከት በኑዛዜው ላይ የቀረበውን ክርክር ተመልክቶ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሶ ልኮለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የከተማው ሰበር ለጉዳዩ አወሳሰን መሰረት አድርገውት የነበረው ኑዛዜ በ24/07/2001 ዓ.ም. በተደረገ የስጦታ ውል በከፊል ተሽሯል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የሟች እናታቸውን ንብረት ለመውረስ ሲፈልጉ ተጠሪ በሕጉ አግባብ ባልተደረገ የኑዛዜ ሰነድና የስጦታ ውል መሰረት የውርስ ንብረቱን ይዘው እንደሚገኙ ገልፀው ክስ ሊመሰርቱ የቻሉ መሆኑና የስር ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ያደረገው ደግሞ የኑዛዜ ሰነዱ በስጦታ ውሉ ተተክቷል፣ ሌሎች መከራከሪያ ነጥቦችን ደግሞ የስጦታ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ሲቀርብ የሚታዩ ናቸው በማለት የኑዛዜ ወራሽነትን ብቻ ሰርዞ ሲወስን የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የኑዛዜ ሰነዱ ሙሉ በሙሉ ሊሰረዝ አይገባም በማለት መወሰኑን ነው፡፡ ተጠሪ ስጦታ በሟች የሺ ይልማ ተደርጎልኛል የሚሉት መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ/ም ሲሆን ሟች ከዚህ አለም በሞት የተለዩት ህዳር 10 ቀን 2002 ዓ.ም. መሆኑን እንዲሁም መስከረም 21 ቀን 1999 ዓ.ም. ሟች ኑዛዜ ማድረጋቸውን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባሉት የስጦታ ውል ከሟቹ ህልፈተ ሕይወት በኋላ ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡ እንደዚህ አይነት የስጦታ ውል ላይ ስለኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 ድንጋጌ በሐይለ ቃል ያስቀምጣል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2443 ስር ደግሞ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ ስጦታ በግልፅ በሚደረግ ኑዛዜ አሰራር አይነት ካልተደረገ ፈራሽ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ አሰራር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 ስር ተመልክቷል፡፡ እንዲህ ከሆነ የሟች ሕጋዊ እና የኑዛዜ ወራሾች የስጦታው አሰራር በሕጉ የተቀመጠውን አሰራር የተከተለ መሆን ያለመሆኑን መሰረት አድርገው ስጦታው ኑዛዜውን ተክቷል የሚል ክርክር ቢያቀርቡ የሚከለከሉበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826(2)፣ 842 እስከ 856 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ ከሁሉም በላይ ሟች ሲሞት ተፈፃሚነት ያለው ስጦታ ከሆነ ስጦታው መሻር ያለመሻሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊረጋገጥ የሚችለው በውርስ ሕጉ ስለኑዛዜ መሻር በሚደነግጉት ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 898 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ለዚህ አይነት ስጦታም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ በግልጽ አኳኋን በተናዛዡ ሊሻር እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የኑዛዜ አንዱ አይነተኛ ባህሪይ ተናዛዡ በፈለገው ጊዜ የሚሽረው አይነት መሆኑ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ የመሻሩ ተግባር እስከተከናወነ ድረስ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ኑዛዜ ተናዛዡ በፈለገው ጊዜ የሚሽረው ስለመሆኑ ሕጉ የሚያስገነዝበን ከሆነ በዚህ ረገድ የሚሰጠው ትርጉምም የተናዛዡ ኑዛዜውን የመሻር ስልጣን በሚያጣብብ መልኩ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሆኑም የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ለጉዳዩ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 898 ድንጋጌን መሰረት አድርጎ ጉዳዩን በማየት ሚች መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ.ም. አደረጉ በተባሉት ኑዛዜ ስር የተዘረዘሩትን ንብረቶችን አይነት ብዛት ሚች መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. አደረጉ በተባለው የስጦታ ሰነድ ስር ከተጠቀሱት ንብረቶች አይነት እና ብዛት እንዲሁም ከሰነዶች ፎርማሊቲ አንፃር ተመልክቶ የኑዛዜ ሰነዱ በከፊል የተሻረ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 15894 ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የስጦታው አይነት ስጦታ ሰጪው ከሞቱ በኋላ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የተደረገ በመሆኑ ተጠሪ ስጦታው ኑዛዜውን የተካ ነው በማለትና የሥጦታ ውሉ በሕጉ የተቀመጠውን ስርዓት ያሟላ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት አግኝቶ የ23/01/1999 ዓ.ም. የኑዛዜ ሰነድ በ24/07/2001 ዓ.ም. የስጦታ ውል በከፊል ተሽሯል ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 75562

ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሶፊያ መሐመድ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መሐመድ ይመር - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸው ጸንቶ ባለበት ጊዜ በተጠሪ ስም እጣ የደረሰው ቢሆንም ቅድመ ክፍያ ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረስ በኋላ የተከፈለበት የኮንዶሚኒየም ቤት የጋራ ነው ተብሎ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 24 ቀን 2004 ዓ.ም. በጻፉት የሰበር ማመልከቻ አከራካሪው የኮንደሚኒየም ቤት በጋብቻ ጊዜ በስማቸው የደረሰ ቢሆንም እጣው ሊደርስ የቻለው መንግስት ለሴቶች የተለየ የእጣ እድል ስርዓት በመዘርጋቱ በመሆኑ እና እጣው ከደረሰ በኋላም ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈርሶ ለቤቱ የቅድመ ክፍያ ገንዘብ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ቤቱ በጋብቻ ጊዜ የተፈራ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚሉትን የቅሬታ ነጥቦችን ጠቅሰዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ተጠሪ የጋራ ንብረቶች ናቸው የሚሏቸውን አይነታቸውንና ብዛታቸውን በመግለፅ ዳኝነት መጠየቃቸውን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥም እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚከራከሩበት በሰሚት ሳይት የሚገኝ ሕንፃ ቁጥር 148/11 ባለ ሁለት መኝታ በተጠሪ ስም የተመዘገበ ኮንዶሚኒየም ቤት እጣው ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ የወጣ በመሆኑ በትዳር ጊዜ የተፈራ የጋራ ንብረት ስለሆነ ልንካፈል ይገባል የሚል የዳኝነት ጥያቄ ይገኝበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10/11 ውስጥ በ350 ካ.ሜትር ቦታ ላይ የሰፈረና በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት፣ የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች መኖራቸውን ገልፀው ክፍፍሉ እንዲደረግ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በሰጡት መልስም በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10/11 ውስጥ በ350 ካ.ሜትር ቦታ ላይ የሰፈረና በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት፣ የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች መኖራቸውን ሳይክዱ ክፍፍሉ ቢደረግ ተቃውሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሌላቸው መሆኑን የገለፀ ሲሆን የኮንዶሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ግን የጋራ ስላልሆነ ተጠሪ ሊጠይቁ አይችሉም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የንብረት ክርክሩ በዚሁ መልኩ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ተገቢውን ማጣራት ከአደረገ በሁዋላ የኮንዶሚኒየም ቤቱ የጋራ መሆኑ ማረጋገጡን ገልጾ አመልካች ለቅድመ ክፍያ ከፈልኩ የሚሉትን የብር 32,048.40 (ሰላሳ ሁለት ሺህ አርባ ስምንት ብር ከአርባ ሳንቲም) ግማሽ ብር 16,024.20(አስራ ስድስት ሺኅ ሃያ አራት ብር ከሃያ ሳንቲም) ተጠሪ እንዲተኩላቸው ቤቱ ከእነ ቀሪ እዳው ግን የጋራ ነው ፣ በማለትና የታመኑትን ንብረቶች በሕጉ አግባብ ሊከፋፈሉ የሚችሉበትን መንገድ በመዘርዘር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ኮንዶሚኒም ቤቱን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ አመልካች ቅሬታ አድሮባቸው ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የኮንዶሚኒየም ቤቱ የጋራ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ ሁኖ በመገኘቱ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መሰረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ሚያዚያ ወር 2002 ላይ አከራካሪው የኮንዶሚኒየም ቤት በተጠሪ ስም የደረሳቸው መሆኑን ፣ ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም. ደግሞ ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረሱን፣ ከዚህም በኋላ የጋብቻ ውጤት የሆነው የንብረት ክርክር ባልተካሄደበት ሁኔታ ነሐሴ 17 ቀን 2002 ዓ.ም. አመልካች ለኮንዲሚኒየም ቤቱ ቅድመ ክፍያ የከፈሉ መሆኑንና ጳጉሜ 04 ቀን 2002 ዓ.ም. ላይ ከሚመለከተው አስተዳደር አካል ጋር የኮንዶሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ውል የተዋዋሉ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ አመልካች አሁን በዚህ ሰበር ደረጃ አጥብቀው የሚከራከሩት ቤቱ ሴት በመሆናቸው ባገኙት ልዩ ድጋፍ የደረሳቸውና ቅድመ ክፍያውንም ከጋብቻ መፍረስ በኋላ የከፈሉት በመሆኑ የጋራ ሊሆን አይችልም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ አመልካች ለእጣው እንዲመዘገቡ የተደረገው ተጠሪ ካላቸው የስራ ባህርይ አንፃር አመልካች በቋሚነት አዲስ አበባ ስለሚኖሩ ጉዳዩን ለመከታተል እንዲቻል ስለመሆኑና እጣውም ሴት በመሆናቸው በተለየ መንገድ ያላገኙት መሆኑን ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የቤተሰብ ሕጉን ያገናዘበ በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር በበላይ ፍርድ ቤት ሊነሳ እንደማይችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የሚመራው በ1958ቱ የፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጋችን በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ ለዚህ ችሎትም ተፈጻሚነት ያለው ነው፡፡ በመሆኑም በበታች ፍርድ ቤቶች ያልተነሳ የፍሬ ነገር ክርክር በሰበር ችሎት የሚነሳበት አግባብ የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ በጋብቻ ውስጥ የደረሳቸው መሆኑን ሳይክዱ እጣው በሴትነታቸው የደረሳቸው መሆኑን ጠቅሰው ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የላቸውም በማለት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የቤቱ ዕጣ በጋብቻ ውስጥ ግራ ቀኙ እያሉ የደረሰ መሆኑ እንደተጠበቀ ሁኖ አመልካች እጣውን በሴትነት ያገኘሁት ነው በማለት እዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያቀርቡት የፍሬ ነገር ክርክር ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች እጣው የደረሰው በጋብቻ ውስጥ መሆኑን ሳይክዱ ለቤቱ ቅድመ ክፍያ ከጋብቻ መፍረስ በኋላ በስማቸው ወይም ከግል ገንዘባቸው መክፈላቸውና ውሉንም ከአስተዳደሩ ጋር ማድረጋቸው በጋብቻ ጊዜ የደረሰውን እጣ ውጤቱን የሚቀየርው ሊሆን የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ የኮንዶሚኒየም ቤት ለህብረተሰቡ የሚሰጥበትን አግባብ የሚገዙ ሕጎችም ከምዝገባ ጀምሮ የተለያዩ ሂደቶች ያሉ ስለመሆኑ የሚሳዩ ሲሆን በትዳር ውስጥ በሚገኙ ባልና ሚስት ለእጣው ሲመዘገቡ ሁለቱም ሊመዘገቡ እንደማይችሉ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም አንዱ ተጋቢ በጋብቻ ጊዜ ስሙ ከተመዘገበና እጣው ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ከደረሰ በቤቱ ላይ የሚገኘው መብትና ግዴታ የተጋቢዎች የጋራ ነው ከሚባል በስተቀር የቅድሚያ ክፍያ ጋብቻው ከፈረሰ በሁዋላ በአጭር ጊዜ ወይም ወዲያውኑ በመክፈሉና ውሉም ጋብቻው ፍርሶ የንብረት ክፍፍል ባልተደረገበት ሁኔታ ከሚመለከተው አካል ጋር እጣው በስሙ የወጣለት ተጋቢ በመፈራረሙ ብቻ ንብረቱ የዚሁ ቅድመ ክፍያውን የከፈለውና ውሉን የተዋዋለው ተጋቢ የግል ንብረት ነው የሚባልበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የኮንዶሚኒየም ቤቱ የግሌ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ስርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበና ሕጋዊ መሰረት የሌለው ሁኖ ስለአገኘነው በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ በመ/ቁ. 24526 ሐምሌ 19 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 115416 በ12/03/2004 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የኮንዶሚኒየም ቤቱ እጣ የደረሰው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ስለሆነና አመልካች ለቤቱ ቅድመ ክፍያ በመክፈል ውሉን ከአስተዳደር አካሉ አደረግሁ የሚሉት ጊዜ ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ ከፈረሰ በአጭር ጊዜ ውስጥና የንብረት ክፍፍሉ ባልተደረገበት ሁኔታ በመሆኑ ቤቱን የአመልካች የግል ንብረት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ብዙአየሁ ታደሰ - ጠበቃ ምህረትአብ ልዑልና ወ/ሮ አበባ መንግስቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሰሎሜ ሻወል - ጠበቃ አቶ ኃይሉ ንጋቱ ቀረቡ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ አመልካችና ተጠሪ የፍች ውጤትን በተመለከተ ያደረጉት ስምምነት ተፈፃሚነትን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ (ከሳሽ) አመልካች (ተከሳሽ) በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍች እንዲፈርስና የፍች ውጤት በሆነው የጋራ ንብረት ክፍፍልና የልጆች አስተዳደግ ጉዳይ ከአመልካች ጋር በመስማማት ስምምነቱን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ህምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም. ያስፀደቁ መሆኑን ገልፀው በስምምነቱ መሠረት አብዛኛው ሁኔታዎች የተፈፀሙ ቢሆንም በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 03/05 የሚገኘውና የካርታ ቁጥሩ 33799 ቁጥሩ 2310 የሆነ በተከሳሽ (አመልካች) ስም ያለና በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 20 የካርታ ቁጥሩ 33822 የሆነና ቁጥሩ 4057 የሆነ ፎቅ ቤት በስምመነታችን መሰረት ከዕዳና እገዳ ነፃ በማድረግ ለከሳሽ (ተጠሪ) አላዛወሩም፡፡ ተከሳሽ በስምምነቱ መሰረት እንዲፈፀም ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም በስምምነቱ መሠረት ያልፈፀመ በመሆኑ ንብረቱን ከዕዳና እገዳ ነፃ አድርገው እንዲያዛውሩ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ ይህ የማይቻል ከሆነ ግምታቸውን እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው በስምምነቱ መሰረት የቤቶቹን ስመ ንብረት ለከሳሽ (ተጠሪ) ለማዛወር አስፈላጊውን እንዳሟላ ከሳሽ ደግሞ የዴንቨሩን ጋብቻ ሰርተፊኬት አቅርበው የዴንቨሩን ጋብቻ እንድናፈርስ ስምምነት ተደርጓል፡፡ ጉዳዩ በሽማግሌ ታይቷል፡፡ ከሳሽ የዴንቨሩ ጋብቻ ሳይፈርስ ስም እንዲዛወር መጠየቋ ተገቢ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የስር ፍ/ቤት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለ ፍችና የፍች ውጤት አቅርበው ባፀደቁት ስምምነት ውስጥ፣ ተከሳሽ (አመልካች) ለከሳሽ (ተጠሪ) የቤቶቹን ስመሀብት የሚያዛውረው በኮሎራዶ ዴንቨር ያለው ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ነው የሚል ይዘት የለውም፡፡ ተከሳሽ በሁለት ዓመት ተኩል ጊዜው ውስጥ ቤቶቹን ከዕዳና እገዳ ነፃ አድርገው ለከሳሽ ለማዛወር የተስማሙ በመሆኑ አሁን ጊዜ ሲሰላ ሶስት ዓመት የሆነው በመሆኑ በስምምነቱ መሰረት ቤቶቹን ነፃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አድርገው ስመሀብቱን ለከሳሽ ያዛውሩ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል። አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል። ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል።

አመልካች ህዳር 11 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ በሁለት አገር የጋብቻ ሥርዓታቸውን ፈፅመዋል። የስር ፍ/ቤት ስምምነቱን ሲፈፅሙ የአመልካችና ተጠሪ ፍላጎት ምን እንደነበር ስለ ውሎች አተረጓጐም የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ስምምነቱን መተርጐም ሲገባው ይህንን ሳያደርግ ተጠሪ የኮሎራዶ ዴንቨር ያለውን ጋብቻ ሳታፈርስ የቤቱ ስመ ሀብት እንዲዛወር መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው። ተጠሪ የበኩሉን ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ አመልካች በስምምነቱ መሰረት እንዲፈጽም ትዕዛዝ ሊሰጥ አይገባም። የስር ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ዓለም አቀፍ የግለሰብ የህግ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። ስለዚህ በሰበር ታይቶ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል።

ተጠሪ በበኩላቸው አመልካችና ተጠሪ የነበራቸው ጋብቻ በፍች እንዲፈርስና ጋብቻው በፍች ከፈረሰ በኋላ ስለሚኖረው የጋራ ንብረት ክፍፍልና የልጆች አስተዳደግ ሥምምነት ፈፅመው ስምምነቱ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ፀድቋል። ክስ የቀረበባቸው ቤቶች የተጠሪ ድርሻ ስለመሆናቸው በስምምነቱ በግልፅ ተመልክቷል። ተጠሪ የጋራ ንብረት ለመካፈል ባደረገው ስምምነት መሰረት አመልካች እንድፈጽም ያቀረብኩትን ክስ ተቀብሎ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ የህግ ስህተት የለበትም። በሰበር የማጣሪያ ችሎት የተያዘው ጭብጥም እኔና አመልካች ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ካስመዘገብነው የፍችና የፍች ውጤት ከሚዘረዝረው ስምምነት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው ነው። አመልካች የኮሎራዶ ዴንቨር ያለው ጋብቻ ሣይፈርስ ስምምነቱን አልፈፅምም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም። ጉዳዩ የዓለም አቀፍ የግለሰብ ህግ ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም የሚል መከራከሪያ ያቀረቡ ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከስር የክርክሩ አመጣጥና አመልካች በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም በታች ፍ/ቤቶች አመልካችና ተጠሪ በመካከላቸው የነበረውን ጋብቻ ለማፍረስ ከፍች በኋላ የጋራ ንብረት ክፍያንና የልጆች አስተዳደግን በተመለከተ ባደረጉት ስምምነቶች ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት አቅርበው ባፀደቁት መሰረት አመልካች ክስ የቀረበባቸውን ሁለት ቤቶች ለተጠሪ ባለሀብትነቱን እንዲያስተላልፍ የሰጡት ትዕዛዝ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉትና የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ያፀደቀው ስምምነት የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ነው። አመልካችና ተጠሪ ሀምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የፍች የጋራ ሀብት ክፍፍልና የልጆች አስተዳደግ ስምምነት በማድረግ መጋቢት 21 ቀን 1985 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ግዛት ክልል በአዲስ አበባ የፈፀሙትን ብሔራዊ ጋብቻ በፍች እንዲፈርስ፣ ጋብቻው በፍች ሲፈርስ ያኗቸውን የጋራ ሀብቶች የሚከፋፈሉበት ሁኔታና የልጆች አስተዳደግ እንዴት እንደሆነ በዝርዝር ፅፈው፣ ፍችውና የፍች ውጤቱን በተመለከተ ያደረጉት ሥምምነት የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት እንዲያጸድቅላቸው በጋራ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ፍችንና የፍች ውጤትን በተመለከተ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ስምምነት የአመልካችና የተጠሪ ፈቃዳቸውን የገለጹበት፣ ለልጆች አስተዳደግና ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን በማረጋገጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም. የፀደቀው መሆኑን ከሥር ፍ/ቤት ውሳኔና ግራ ቀኙ በሰበር ካቀረቡት የፅሁፍ ክርክር ተረድተናል፡፡

የፍች ስምምነት እንዲያፀድቅ በባልና በሚስቱ ስምምነት ጥያቄ የቀረበለት ፍ/ቤት የፍች ስምምነቱን ከማጽደቁ በፊት የፍች ስምምነቱ የባልና የሚስቱ ትክክለኛ ፍላጎት መሆኑን ባልና ሚስቱ ፈቃዳቸውን በነፃ የሰጡ መሆኑን እንደዚሁም ስምምነቱ ለህግና ለሞራል የማይቃረን መሆኑን፣ ባልና ሚስቱ ስለፍች ውጤት ያደረጉት ስምምነት የልጆቻቸውን ደህንነትና ጥቅም በበቂ ሁኔታ የሚያስጠብቅ መሆኑና ስምምነቱ የሁለቱንም ተጋቢዎች ጥቅም ሚያስጠብቅ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለበት በተሸሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 80 ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም የፍችው ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ጊዜ ስምምነቱ ተፈፃሚነት የሚኖረው ፍ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ እንደሆነ የተሸሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 83 ንዑስ አንቀፅ 3 ይደነግጋል፡፡ የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ ሀምሌ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. ተፈራርመው በጋራ ማመልከቻ ፍ/ቤቱ እንዲያጸድቅላቸው የጠየቁትን የፍችና የፍች ውጤት ስምምነት ከማጽደቁ በፊት አስገዳጅነት ባለው በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 80 ሊጣሩና ሊረጋገጡ የሚገባቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች በማረጋገጥ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በህግ ስልጣን የተሰጠው ፍ/ቤት የስምምነቱን ይዘት፣ ስምምነቱ በልጆች አስተዳደግ ላይ የሚኖረውን ውጤት፣ የሁለቱንም ተጋቢዎች መብትና ጥቅም የሚያስከብር መሆኑን በማረጋገጥ ካፀደቀው ስምምነቱ ህጋዊ ውጤት ያለውና በባልና ሚስቱ ላይ አስገዳጅነት ያለው ሰነድ እንደሚሆን፣ ከቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 83 ንዑስ አንቀጥ 3 ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካችና ተጠሪ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን የጋራ ሀብታቸውን ለመከፋፈል ባደረጉት ስምምነት መሰረት አመልካች እንዲፈፅም ያቀረበችው ክስ የቤተሰብ ህጉን አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የፍትሃብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ያደረገ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት ስምምነት ተጠሪ ክስ ያቀረበችባቸው ሁለት ቤቶች የተጠሪ ድርሻ መሆናቸው በግልፅ እንደተቀመጠ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው በስር ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጋራ ንብረት ለመካፈል አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት ስምምነት የተጠሪ ድርሻ መሆናቸው የተገለጹትና ክስ የቀረበባቸውን ሁለት ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ለማስረከብ የሁለት ዓመት የስድስት ወር የጊዜ ገደብ የተሰጠው ከመሆኑ ውጭ ሌላ ቅድመ ሁኔታ ያልተቀመጠ መሆኑንና አመልካች ቤቶቹን የማስረክበው በአሜሪካን አገር የኮሎራዶ ዴንቨር ግዛት የተፈፀመው ጋብቻ መፍረስ ይገባዋል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ግልፅ የሆነውና ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ያፀደቀውን የፍችና የፍች ውጤት ስምምነት የሚጥስ ስለመሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ስምምነቱን የአመልካችና የተጠሪን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ትርጉም መስጠት ነበረባቸው በማለት በሰበር ያቀረቡት ክርክርም በመጀመሪያ ደረጃ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡትን የፍችና የፍች ውጤት ስምምነት ከማጽደቁ በፊት የአመልካችና የተጠሪ ፍላጎት በኢትዮጵያ ውስጥ መጋቢት 21 ቀን 1985 ዓ/ም ያደረጉት ጋብቻ በፍች ማፍረስ፣ እንደዚሁም የልጆቻቸውን አስተዳደግና የጋራ ንብረታቸውን ለመካፈል መሆኑን በማረጋገጥ ያፀደቀው በመሆኑ፣ እንደዚሁም ውሎች ግልፅ በሆኑ ጊዜ ግልፅ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ዳኞች ለመተርጎም እንደማይችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1733 በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ይህንን መሰረታዊ የውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አተረጓጐም መርህ በሚቃረን ሁኔታ ግልጽ የሆነውን የፍችና የፍች ውጤት ስምምነት ፍ/ቤቶች ሊተረጉሙት ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች ጉዳዩ የዓለም አቀፍ ግለሰብ ህግ ጥያቄ የሚያስነሳ መሆኑን በአሜሪካን አገር የሚኖር የህግ ባለሙያ የሰጣቸውን አስተያየት በሰበር አቤቱታቸው ውስጥ በመጥቀስ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት መጋቢት 21 ቀን 1985 ዓ.ም. የፈፀሙትን ጋብቻ በፍች ለማፍረስ ያደረጉትን ስምምነትና የፍችውን ውጤት በስምምነት ለመጨረስ ተስማምተው የቀረቡትን የልጆች አስተዳደግና የጋራ ንብረት ክፍያ ውል የተሸሻለውን የቤተሰብ ህግ መሰረት በማድረግ መርምሮ ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ/ም የስር ፍ/ቤት ቀደም ብሎ በማጽደቅ የሰጠውን ውሳኔ ለማስፈፅም የቀረበ ክርክር ነው፡፡ የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ሀምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም. ባፀደቀው ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትንና የተጠሪ ድርሻ የሆኑ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክብ ትዕዛዝ መስጠት የዓለም አቀፍ የግለሰብ ህግ ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ አመልካችና ተጠሪ ሀምሌ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ጋብቻቸው በፍች እንዲፈርስና የፍች ውጤትን በተመለከተ ተስማምተው የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት በተሸሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 80 እና አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት መርምሮ ባፀደቀው መሰረት ክስ የቀረበባቸውና የተጠሪ ድርሻ የሆኑት ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ስመ ሀብቱን እንዲያስተላልፍ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ትዕዛዝ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና የፍትሃብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ያደረገና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤትና የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ህዳር 13 ቀን 2004 እና ታህሳስ 05 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አሚናት አሊ ጠ/ሙሉጌታ ዘመነ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፋጡማ ውበት ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ ባቀረበችው ክስ ነው፡፡ የጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ከአቶ መሀመድ ሁሴን (የሥር ተከሳሽ) ጋር በ1987 ዓ.ም. በሰርግ ተጋብተው ሲኖሩ ቆይተው በኑሮ ስላልተሰማው ጋብቻው እንዲፈርስና ንብረት እንዲካፈሉ እንዲወሰን ሲሆን ተከሳሽ ቀርበው ጋብቻ የለንም አለ ከተባለም ሊፈርስ አይገባም የሚልና የሚፈርስ ከሆነም ከሥር ጣ/ገብ (የአሁን አመልካች) ጋር ሁለተኛ ጋብቻ ስላለ ንብረቱ ለሦስቱ ሊካፈል ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የአሁን አመልካች ሥር ፍ/ቤት ጣልቃ ገብ ሆና ባቀረበችው አቤቱታ የተከሳሽ ሚስት እሷ ብቻ ስለመሆኗ እና የንብረት ክርክሩ የጋራ ንብረት መብቷን የሚጐዳ ነው በሚል ወደ ክርክሩ እንድትገባ እንዲፈቀድላት አመልክታ ወደ ክርክሩ ገብታ መከራከሪያ አቅርባለች፡፡ የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ማስረጃ ከሰማ በኋላ ሁለቱም የአቶ መሀመድ ሁሴን ሚስቶች ስለመሆናቸው በበቂ ሁኔታ አስረድተዋል ካለ በኋላ ወ/ሮ ፋጡማ ውበት /ተጠሪ/ ጋብቻ የፈፀመችው በ1987 ዓ.ም መሆኑን በአንፃሩ ወ/ሮ አሚናት አሊ (አመልካች) ጋብቻ የፈፀመችው በ1990 ዓ.ም ስለሆነ የኋለኛው ጋብቻ በጋብቻ ላይ የተፈፀመ ነው በሚል እንዲፈርስ ወስኖ የንብረት ክርክደሩ በተጠሪ እና በተከሳሽ አቶ መሀመድ ሁሴን መካከል እንዲቀጥል ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባለች፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ሁለቱም ጋብቻ ያላቸው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የፊተኛው ጋብቻ በተጠሪ ጥያቄ እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ የኋለኛውም ጋብቻ ተጠሪ ባቀረቡት ጥያቄ መነሻ ሁለቱም በአንዱ እንዲፈርስ የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሯል፡፡ በዚሁም መሠረትም የአመልካች ጋብቻ እንዲፀና ሊቀጥል ይገባል ብሏናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንብረት ክርክርን አስመልክቶ የሁለቱንም ጋብቻ ውጤት ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ በቅድሚያ ሦስቱም ወገኖች የግል ሀብት የሚሉትን እንዲለዩ ከተደረገ በኋላ ሁለተኛው ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት የተፈራ ንብረት ለመጀመሪያ ተጋቢዎች እንዲሆን ተደርጐ የጋራ ሀብቱ ለሦስት እንዲካፈል ሲል በዚሁ አግባብ የንብረት ማጣራት ሂደት እንዲቀጥል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩላቸው በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለአማራ ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሁለቱም ጋብቻ መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ ሕጉ በጋብቻ ላይ ጋብቻን የማያበረታታ ነው ሲል ለቀደመው ጋብቻ ጥበቃ ሊያደርግ በሚያስችል መልኩ በንብረት ላይ ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚገባ አመልካች ከሁለተኛው ጋብቻ በኋላ የተፈራው ንብረት ለሦስት ይካፈሉ ሲል ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የመጀመሪያዋን ተጋቢ ጥቅም የሚጐዳ ነው በማለት በተጠሪ ተዘርዝረው ከቀረቡት ንብረቶች የግል የተባለ ከተለየ በኋላ የተቀረውን ተጠሪና አቶ መሀመድ ሁሴን እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

ንብረት የማጣራቱ ሂደትም በዚሁ አግባብ እንዲቀጥል ትእዛዝ ሰጥቷል አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበች ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ ሚያዝያ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት አቤቱታ የክርክሩን አመጣጥ በሰፊው በማተት የአመልካች ጋብቻ ፀንቶ ያለ ስለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ከፍተኛ ፍ/ቤት ካረጋገጡ በኋላ በንብረት ረገድ ግን አመልካች መብት የላትም መባሉ የክልሉን የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 74 እና 101 ድንጋጌ የሚጥስ ውሳኔ ነው በማለት እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ከሥር ተከሳሽ ጋር ከጥር ወር 1990 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ እንደነበራት ተረጋግጦ ሳለ በተጠሪ እና በአመልካች ባለቤት መካከል የነበረው ትዳር በፍቺ ሲፈርስ አመልካች በንብረት ክፍፍሉ ምንም ድርሻ የላትም መባሉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም አመልካች ጋብቻ አላት ሊባል እንደማይገባ በንብረት ረገድም ሁለተኛው ጋብቻ ህጋዊ ባልሆነበት ሁኔታ ንብረት ለመካፈል የሚያስችል አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪ ከአቶ መሀመድ ሁሴን ጋር ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ መሥርተው ይኖሩ እንደ ነበር አመልካችም ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ከእኝሁ ሰው ጋር ጋብቻ መሥርተው ይኖሩ እንደነበር በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በውሳኔያቸው እንዳሰፈሩት የተጠሪ ጋብቻ ከአመልካች የቀደመ ሲሆን የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ የነበረው አመልካች በጋብቻ ላይ ጋብቻ የፈፀመች ስለሆነ ይፍረስ የሚል ሳይሆን ተጠሪና ባለቤቷ በኑሮ ባለመስማማታቸው ጋብቻው እንዲፈርስ እንዲወሰን ነበር፡፡ በዚህ አግባብ የተጠሪ ጋብቻ የፈረሰ እና የአመልካች ጋብቻ ፀንቶ እንዲቀጥል ከተደረገ በዚህ የጋብቻ ሕይወት ውስጥ የተፈራ ንብረት ክፍፍል መርህ ምን ሊሆን ይገባል የሚል ጥያቄ ምላሽ የሚያሻው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ጥያቄ አወዛጋቢ ሆኖ ሊቀርብ የቻለው የአማራ ብ/ክልል መንግስት የቤተሰብ ሕግም ሆነ የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ በጋብቻ ላይ ጋብቻ የማይፈቅድ በመሆኑ በሁለት ተጋቢዎች መካከል የሚፈጥር የንብረት ክፍፍል ጥያቄን አስመልክቶ ሕጉ ግልጽ ምላሽ ስለማይሰጥ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ይህ ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ ወደ ፍርድ ቤት ሲቀርብ አጠቃላይ የሕጉን መንፈስና ማህበራዊ ሁኔታዎነችን በማገናዘብ ውሳኔ መስጠት ተገቢ ይሆናል።

ለተያዘው ክርክር መፍትሔ ለመስጠት የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ምክንያት ጋብቻው ሕጋዊ አይደለም ተብሎ ቢፈርስ እንኳን ጋብቻው ፀንቶ በቀረበት ጊዜ የተፈፀሙ ድርጊቶች ውጤት የሚያጡ አይደሉም በሚል ምክንያት ተጋቢዎቹ ያፈሩትን ንብረት እንዲካፈሉ ሲወሰን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ለመለወጥ የሰጠው ምክንያት ይህ ዓይነት አተረጓጐም ሕጉ ጥበቃ ያደረገለትን የመጀመሪያ ጋብቻ ጥቅም የሚጐዳ ነው የሚል ነው።

በእኛ በኩል እንደተገነዘብነው ሕጉ ጋብቻ ላይ ጋብቻ ባለመፍቀዱ ተፈጽሞ ሲገኝ ሕገወጥ ነው ይፍረስ በማለት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችሉት ወገኖች የቀደመ ጋብቻ ያለው ተጋቢ ወይም ዐቃቤ ሕግ ስለመሆኑ የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 18(ሐ) እና የአማራ ብ/ክ/መ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 29/ሐ/ በተመሳሳይ ሁኔታ ደንግገው እናገኛለን።

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪም ሆነች አመልካች ከአቶ መሀመድ ሁሴን ጋር ከአሥር ዓመታት ላላነሰ ጊዜ ጋብቻ መሥርተው ሲኖሩ የቀረበ መቃወሚያ ስለመኖሩ በዚህ ክርክር አልተጠቀሰም።

ስለሆነም ተጠሪ የቀደመ ጋብቻ የነበራት መሆኑ ቢረጋገጥም የአመልካች ጋብቻ እንዲፈርስ ያቀረበችው መቃወሚያ ሳይኖር ዛሬ በንብረት ክርክር ላይ ወደ ኋላ ተመልሶ ውጤት እንዳይኖር ማድረግ ፍትሀዊ ሆኖ አላገኘንም። ከዚህም ሌላ የቤተሰብ ሕጉ አጠቃላይ መንፈስ ሲታይ አንደኛዋ ተጋቢ በሌላኛዋ ተጋቢ ጥረት በተፈራ ንብረት ላይ ያለአግባብ እንድትበለጽግ ወይም ሌላኛዋ ተጋቢ ያለአግባብ መብቷንና የጥረቷን ውጤት እንድታጣ ለማድረግ ያሰበ አለመሆኑን መረዳት ተገቢ ይሆናል። ለዚህ ማሳያ ሊሆን የሚችለው ጋብቻ እንኳን ሳይኖር ከጋብቻ ወጪ እንደባልና ሚስት ከሦስት ዓመታት ላላነሰ ጊዜ አብረው የኖሩ ሰዎች በዚህ ጊዜ ውስጥ ያፈሩት ንብረት የጋራ ሀብታቸው ስለመሆኑ በፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 102(1) እና በአማራ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 113(1) ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑ ነው። ስለሆነም በተሻለ ምክንያታዊ ሁኔታ (for a stronger reason) በጋብቻ ውስጥ በተጋቢዎች መካከል የተፈራ ሀብትን በሚመለከት በግራ ቀኙ ማስረጃ የሚጣራ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከወዲሁ ግን ሁለተኛዋ ተጋቢ በንብረት ረገድ መብት የላትም የሚለው የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ድምዳሜ ተገቢነት የለውም።

ስለሆነም የተጠሪም ሆነ የአመልካች የንብረት ድርሻ ክፍፍል መርህ መሆን የሚገባው በሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው አስቀድሞ ሦስቱም የግል ንብረት የሚሉትን በማስረዳት የየግላቸውን መውሰድ ይገባቸዋል። የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 97(1) እንዲሁም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 86(1) ይህንኑ ያመለክታል።

ከዚህ ውጪ የሆነው ሀብት እና በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረት የባልና ሚስቱ ወይም የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ሆኖ የሚገመት ስለመሆኑ የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ። የጋራ ሀብት የሚሰኘው በተጋቢዎች የጋራ ጥረት ወይም በአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረትም የተፈራ ሊሆን እንደሚችልና በአንደኛው ተጋቢ ስም ተመዝግቦ ቢሆን እንኳ በጋብቻ ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈራ መሆኑ ከተረጋገጠ እና በተለያ ሁኔታ ሕጉ ባስቀመጠው አግባብ አንደኛው ተጋቢ የግል መሆኑን ካላስረደ ጭምር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62(1) ና 63(1) እንዲሁም የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 73(1) እና 74(1) ይህንኑ ያስረዳሉ፡፡

ከተያዘው ጉዳይ ጋር ስናያይዝ ሁለቱ ሚስቶች ናቸው እስከ ተባለ ድረስ በሕጉ መንፈስና ሃይል (by operation of the law) ከባለቤታቸው ጋር ያፈሩትን ንብረት ከባለቤታቸው ጋር እኩል የመካፈል መብት ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል አንደኛዋ ተጋቢ ከሌላኛዋ ተጋቢ በተለየ ሁኔታ ንብረት ለማፍራት በቀጥታ አስተዋጽኦ ያደረገች መሆኑን ማስረዳት ከቻለች ከሌላኛዋ ተጋቢ የተሻለ መብት ሊኖራት እንደሚገባ መረዳት ተገቢ ይሆናል፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአቶ መሐመድ ሁሴን ጋብቻ ከፈፀመችበት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በራሷ ጥረት ከባለቤቷ ጋር በባህር ዳር ከተማ ስትኖር ያፈራችው ሀብት ላይ ከባለቤቷ ጋር እኩሌታ የመካፈል መብት እንዳላት መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች በባህር ዳር ከተማ በባለቤቷ ስም የተፈራ ንብረት ላይ ሊኖራት የሚችለው መብት በሕጉ አግባብ መሠረት ከባለቤቷ ድርሻ ላይ ብቻ የእኩሌታ መብት እንዳላት በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ከአቶ መሐመድ ሁሴን ጋር ጋብቻ መሥርታ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ አ.አ ከተማ እየኖረች ያለች ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች በተረጋገጠው ፍሬ ነገር መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ በአመልካች ጥረት ከባለቤቷ ጋር በጋራ የተፈራ ንብረት አለ ከተባለ በዚህ ንብረት ላይ ግማሽ ድርሻ የአመልካች ይሆናል ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ በጋብቻ ውስጥ የተፈራውን ንብረት የማጣራት እና የማከፋፈል መርህን አስመልክቶ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ምንም መብት ሊኖራት አይገባም ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ የሕጉን መንፈስ ያላገናዘበ እና ፍትሀዊም ሆኖ ስላልተገኘ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ስለሆነም የአመራ ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በንብረት ክፍፍል ረገድ ምንም መብት አይኖራትም ሲል የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 17623 በ20/4/ 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 010126 በ01/08/2001 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/መ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪና በአቶ መሐመድ ሁሴን ስም በጋራ በባህርዳር ከተማ ከተፈራው ንብረት ተጠሪ እኩሌታ (50%) ድርሻ ያላት ሲሆን አመልካች ደግሞ ለባለቤቷ ከሚደርሰው ድርሻ ብቻ እኩሌታ ድርሻ ይኖራታል ብለናል፡፡
3. በአመልካችና በአቶ መሐመድ ሁሴን ስም በጋራ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈራ ንብረት ካለ አመልካች እኩሌታ (50%) ድርሻ ያላት ሲሆን ተጠሪ ደግሞ በባለቤቷ ድርሻ ላይ ብቻ የእኩሌታ ድርሻ ይኖራታል ብለናል፡፡
4. በዚሁ መሠረት የንብረት ማጣራትና ክፍፍል እንዲፈጸም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. በዚህ መዝገብ ግንቦት 5 ቀን 2001 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ አበበች ቡልቻ
ተጠሪ፡- የለም፡፡
መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የኑዛዜ አፃፃፍ ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ሟች አቶ በቀለ በዳኔ ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ/ም የተውት ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ለፍርድ ቤቱ አመልክተው ሚስትነታቸውና የህጻን ግርማ በቀለና አይናለም በቀለ የሟቹ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የኑዛዜውን ሰነድ በተመለከተ ግን በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት ያልተነበበ ነው በሚል ምክንያት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881(2)"ን" በመጥቀስ ውድቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ሆነ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ሟች ያደረጉት ግልፅ ኑዛዜ በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ሁኖ እያለ ኑዛዜው ስለመነበቡ አይገልጽም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው፣ ፎርማሊቲውን ፍርድ ቤቱ በራሱ ማንሳት አይችልም ነበር በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን በጉዳዩ ላይ ተጠሪም የሌለበት በመሆኑ የአመልካቾችን የቅሬታ ነጥብ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው አመልካቾች የሚከራከሩት ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ሁኖ እያለ በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት አልተነበበም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ ስለሆነም ሟች አቶ በቀለ በዳኔ ያደረጉት ኑዛዜ በሕጉ ላይ የተመለከተውን መስፈርት ያሟላል? ወይስ አያሟላም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ነው፡፡ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ግልፅ ኑዛዜ ነው፡፡ ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባቸው ስርዓቶች ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 እስከ 883 ድረስ በተመለከቱት ድንጋጌዎች ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ፣ ይህም ስርዓት መፈፀሙና በተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ፣ ተናዛዥና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም በውል አዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት የሚደረግ ከሆነ የምስክሮች ብዛት ሁለት በቂ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 882 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 883 ስር የተመለከቱት የምስክሮችን ችሎታ የሚመለከቱ ሕጋዊያን ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በሟች ተሰጠ የተባለው ኑዛዜም ውል የማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተደረገ፣ ሶስት ምስክሮች የፈረሙበት፣ ውል የማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ኑዛዜውን አረጋግጦ የፈረመበት፣ ኑዛዜው በምስክሮችና በተናዛዡ ፊት ስለመነበቡ በሰነዱ ላይ ስለመገለፁ የማያሳይ እና ተናዛዡ የፈረሙት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881(2) ሥር ከተመለከቱት ስርዓቶች ውስጥ ኑዛዜው በተናዛዡና በምስክሮች ፊት የመነበቡን ሥርዓት ያላሟላ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው የህጉን ሥርዓት አልተከተለም ያሉትም ኑዛዜው ስለመነበቡ አይገልጽም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ኑዛዜው በተናዛዡና በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ የሚያመላክት ነገር የለውም፡፡ አመልካች የሚከራከሩት ደግሞ ኑዛዜው የተደረገው ሶስቱ ምስክሮች ባሉበት ጊዜና ቦታ ከመሆኑም በተጨማሪ ውል የማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ፊት፣ ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ስለሆነ በኑዛዜው ላይ ስለመነበቡ ያለመገለፁ ኑዛዜውን ፈራሽ አያደርገውም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 882 ድንጋጌ ሲታይ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 ተከታይ ሁኖ ከኑዛዜ አይነቶች አንዱ ስለሆነው የግልፅ ኑዛዜን ፎርማሊቲነት የሚያወሳ ድንጋጌ መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ርዕስ፣ ይዘትና ቅርፅ የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 ስር ከተመለከቱት የኑዛዜ ፎርማሊቲዎች መካከል ለይቶ ያወጣው የምስክሮችን ቁጥር ብቻ ሁኖ ሁለት ምስክሮች በቂ የሚሆኑበትን አግባብ የሚያሳይ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881(2) ስር ኑዛዜው በምስክሮችና በተናዛዡ ፊት ስለመነበቡ የሚለው ስርዓት ስለመፈጸሙ በኑዛዜው ላይ ያለመገለፅ ውል አዋዋይ ወይም ዳኛ ፊት ለሚደረግ ግልጽ ኑዛዜ በፎርማሊቲ የማይፈለግ መሆኑን የሚገልፅ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ውል አዋዋዩ ሰው ምስክር ተብለው ባይገለፁም የምስክሩን ቁጥር በተመለከተ ኑዛዜው በሕጉ የተመለከተውን ፎርማሊቲ ያሟላ ነው ሊባል ከሚችል በስተቀር በሕጉ የሚፈለገውን የኑዛዜውን መነበብ ሥርዓት ግን ይኸው ይተካል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ውል አዋዋይ ሟች ኑዛዜውን በነፃ ፈቃዳቸው ሲሰጡና ኑዛዜውም የተናዛዡን መሆኑን አይተውና አረጋግጠው በኑዛዜው ላይ ፈርመዋል፣ የምስክሮች ዋና አስፈላጊነትም ኑዛዜ አድራጊው ኑዛዜውን በነፃ ፍላጎቱ እና በትክክለኛ አእምሮው የሰጠ መሆኑንና የኑዛዜው ቃልም የእርሱ መሆኑን ማረጋገጥ ነው የሚለው ምክንያት ሲታይም በሕጉ በግልጽ የተመለከተውን ፎርማሊቲ ወይም የኑዛዜው መነበብ ስርዓት ያለመፈፀምን አስፈላጊ አይደለም ለማለት የሚያስችል አይሆንም፡፡

በመሆኑም ኑዛዜው ለተናዛዡና ለምስክሮች ስለመነበቡ በሰነዱ ላይ ያለመገለፁ ብቻ የኑዛዜ ሰነዱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881(2) እና 882 ስር የተመለከተውን ፎርማሊቲ አያሟላም ተብሎ ፈራሽ እንዲሆን የግድ የሚል ነው፡፡ በአጠቃላይ ከውል አዋዋይ በተጨማሪ ሌሎች ሶስት ምስክሮች በኑዛዜ ሰነዱ ላይ ያሉ ከመሆኑም በላይ በውል አዋዋይ ፊት ቃለ መሐላ የተፈጸመበትና የሰነዱ ይዘት የተረጋገጠ ስለመሆኑ ሰነዱ የሚገልጽ ቢሆንም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 882 ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 ተከታይ በመሆኑና ስለኑዛዜው መነበብ ስርዓት መፈፀም በኑዛዜ ሰነዱ ላይ መገለጽ የግድ የሚል ሕጋዊ ፎርማሊቲ ሁኖ ስለአገኘነው ሟች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያላሟላ ነው፡፡ የኑዛዜ ፎርማሊቲ ጥያቄ ደግሞ ሰነዱ ለማስረጃነት እስከተጠየቀ ድረስና ከጉዳዩ የክርክር አመራር ሥርዓት አንፃር ሲታይ ፍርድ ቤቱ በራሱ ለማንሳት የሚችለው እንጂ የግድ ከተከራካሪ ወገን ሊነሳ የሚገባው ነው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካቾች ያነሱት ክርክርም ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የሟች አቶ በቀለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዳኔ ሕዳር 28 ቀን 2003 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ፈራሽ ነው ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881(2)፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 857 እና 882 ድንጋጌዎችን ያገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 3412/03 ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16084 ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም. በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 16126 ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ሟች አቶ በቀለ በዳኔ ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881(2) እና 882 መሰረት ፎርማሊቲውን ያላሟላ በመሆኑ ፈራሽ ነው ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌ-ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን-ነገረ ፈጅ በፍቃዱ መኮንን ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ሚ/ር ጀርመን ግናሆ - በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስልክ አገልግሎት ሂሳብ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ ጋር ጥር 10 ቀን 1998 ዓ.ም. በተፈረመ የጽሑፍ ውል ስምምነት ስልክ ቁጥር 200778 አመልካች አስገብቶላቸው ተጠሪ ሲገለገሉበት ከቆዩ በኋላ ያልከፈሉትን ገንዘብ ብር 5,873.20 እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአመልካችን ክስ መርምሮ የአመልካች ጥያቄ የአገልግሎት ሂሳብ በየወሩ የሚመጣ እዳን የሚመለከት ነው፣ እንደዚህ አይነት ጥያቄ እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት አመት ሳይከፈል ከቀረ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚል ምክንያት ይዞ የስልክ አገልግሎት ክፍያ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሰረት ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኖታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ጥቅምት 10 ቀን 2003 በጻፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ግንኙነቱ ውልን መሰረት ያደረገ ሁኖ እያለ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 ድንጋጌ መጠቀሱ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው እንዲሻር እና አመልካች የስልክ አገልግሎት ሂሳቡን እንዲከፍል ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ዋናውና የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጉዳይ፡- የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ ለስልክ አገልግሎት ሂሳብ (ገንዘብ) አግባብነት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 በጠቅላላው ሲታይ በሕግ የሕሊና ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ነጥብን (Legal Presumptions) የሚመለከት ሲሆን ዓይነቱም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2025 እና 2026 ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ውስን የሆነ የማስተባበያ ማስረጃ የሚቀርብበት (not freely rebuttable or rebuttable but in a limited way) የሕግ የህሊና ግምት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024 የተለያዩ የክፍያ አይነቶች የሚዘረዝር ሆኖ 2024 በጠቅላላው ሲታይ ግን በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች (እዳዎች) በዚሁ የሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ሳይጠየቁ የቀሩ እንደሆኑ ክፍያውን (እዳውን) የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን የተባለውን ክፍያ (እዳ) እንደከፈለ የሕግ ግምት እንደሚወሰድበት ያስገነዝባል፡፡ ድንጋጌው የስልክ አግልግሎት ሂሳብን ለይቶ አላስቀመጠም፡፡

ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ ተብሎ በተጠሪ የሚጠቀሰውን በስር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘው በፍ/ሕ/ቁጥር 2024 ድንጋጌ በፊደል (ረ) ስር የተመለከተው የክፍያ ግምት ሲሆን ሙሉ ይዘቱም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠ ነው፡፡
ቁ. 2024 በሁለት አመት የተወሰነ ጊዜ

እዳው እንዲከፈል መጠየቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠረው ፡-
(ረ)በብድር ለተሰጠ፤ የገንዘብ ወለድና በጠቅላላውም የዓመት ጊዜ ተወስኖለት በየዓመቱ ወይም ከዚህ ባነሰ የጊዜ ወሰን ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ዕዳ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛው ቅጂም፡-

Art. 2024 presumption of payment after two Years

The following debts shall be deemed to have been paid where two years have elapsed since they fell due:

(f) interest on loans and generally any sum payable annually or at shorter periodical intervals. በሚል ተቀምጧል፡፡
ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የድንጋጌው መጀመሪያ ፓራግራፍ የመክፈያ ጊዜያቸው ከደረሰ ጊዜ አንስቶ ሁለት አመት ያለፋቸው እዳዎች(ክፍያዎች) እንደተከፈሉ ይቆጠራሉ የሚል ሲሆን በተከታይ የተዘረዘሩት ንዑስ ድንጋጌዎች ደግሞ የሚወሰንባቸውን የክፍያ (እዳ) ዓይነቶችን የሚዘረዝር ነው፡፡ በድንጋጌው ፊደል (ረ) ስር የተመለከተው ሲታይ በብድር የተሠጠ ወይም ለማናቸውም የአከፋፈል ሁኔታ በየአመቱ ወይም ከአመት ባነሰ ጊዜ እየተከፈለ እንዲያልቅ ጊዜ ተቆርጦለት የተሰጠ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ ወለድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እዳው ከበሰለበት ወይም በየተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ተከፍሎ ማለቅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ በእነዚህ ክፍያዎች (እዳዎች) ላይ ሊጠየቅ የሚችለው የወለድ ክፍያ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወሰድ መሆኑን ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው <u>በብድር ለተሠጠ ገንዘብ ወለድ</u> ላይ ሲሆን ዋናውን የብድር ገንዘብ የ<u>ማይጨምር</u> መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና አቀራረፅ ያስገነዝባል፡፡ ምክንያቱም ድንጋጌው ዋናውን የብድር ገንዘብ የሚጨምር ቢሆን ኖሮ የብድር ገንዘብንና ወለድ በማለት ያስቀምጠው ነበር እንጂ ለብቻው ነጥሎ የብድር ገንዘብ ወለድን በማለት አይፅፈውም ነበር፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 29181 እና የሠ/መ/ቁጥር 35758 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገደድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ድንጋጌ አግባብነት የሚኖረው ለብድር ገንዘብ ወለድ እንጂ በዋናው የብድር ገንዘብ አይደለም፣ የስልክ ፍጆታ ሂሳብም ብድር ባለመሆኑ ከመነሻውም ድንጋጌው አግባብነት ሊኖረው አይችልም፡፡

ሌላው ስለክፍያ ግምት የሚያወሳው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 ሲሆን ይህ ድንጋጌ የስድስት ወር ጊዜ ማለፍ ክፍያው እንደተፈፀመ ያስቆጥራል በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የስድስት ወር ማለፍ ገንዘቡ እንደተከፈለ የሚያስቆጥርባቸው ሁኔታዎችን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የወርሃዊ የስልክ አገልግሎት ሂሳብ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2022 ድንጋጌ ሲታይም የተከፈለው እዳ ወለዶችን ወይም በተወሰነው ጊዜ የሚከፈሉትን ሌሎች የክፍያ ድርሻዎችን የሚመለከት እንደሆነ የተከፋዩን አይነት ለይቶ ሳይገልጽ ለአንዱ የክፍያ ደረሰኝ የሰጠ ባለገንዘብ ያለፈውንም ድርሻ እንደተቀበለ ይቆጠራል በማለት በንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ያስቀመጠ ሲሆን ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በዚህ ድንጋጌ መሰረትም ሊታይ የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የስልክ አገልግሎት ሂሳብ ከመሰረቱ ብድር አይደለም፤ የብድር ባህርይም የለውም፡፡ የስልክ አገልግሎት ሂሳብ አመልካች ለህብረተሰቡ በሚያቀርበው አገልግሎት መሰረት የሚከፈል ሲሆን መሰረቱም ውል ነው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረበው ተጠሪ በውሉ መሰረት ለተጠቀመበት ጊዜ የስልክ አገልግሎት ሂሳብ እንዲከፈለው ነው፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ቀርበው መልስ ስለመስጠታቸው የስር ብይን አያሳይም፡፡ በመሆኑም የስልክ አገልግሎቱ ተጠሪ በውል አግባብ ስለመጠቀሙ አመልካች ጠቅሶ የተከራከረ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከውሉና በውሉ መሰረት ደግሞ ተጠቃሹ የስልክ ቁጥር ሂሳብ መጠን በአመልካች ክስ የተጠቀሰውን መጠን ያህል የቆጠረ መሆን ያለመሆኑን በአመልካች የሚቀርበውን ክርክርና ማስረጃ አግባብነት እና ጥንካሬ በመመርመር ተገቢውን መወሰን ሲገባ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ ለብይኑ መሰረት ማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለስልክ አገልግሎት ሂሳብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) እና ድንጋጌን መሰረት ማድረጋቸው ያላግባብ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 163107 ሚያዚያ 07 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 95515 ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የስልክ አገልግሎት ሂሳብ ይከፈለኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2022 መሰረት የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበበት ከሆነ በይርጋ ደንብ የሚገዛ እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) ስር በተመለከተው የሕሊና ግምት የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ብር 5,873.20 (አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከሃያ ሳንቲም) ለአመልካች የሚከፍሉ መሆን ያለመሆኑን፣ የሂሳቡን መጠን የአመልካችን ክርክርና ለጉዳዩ የቀረቡትን ማስረጃዎችን አግባብነትና ጥንካሬ የስር ፍርድ ቤት መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
ሐጎስ ወልዱ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ

አመልካች ፡- ወ/ሮ እታለማሁ መስፍን - አልቀረበችም

ተጠሪ ፡- አጋ አንዴ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውል አፈፃፀምን መሠረት በማድረግ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ሲሆን፣ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው በውል የሸጠችልኝን ቤት ስም በስሜ ለማዛወር እንድችል በውሉ መሠረት እንድትፈፅምልኝ ብጠይቃት ፈቃደኛ አልሆነችም፡፡ፍርድ ቤት ያስገድድልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች በበኩልዋ ለክሱ በሰጠችው መልስ በአንድ በኩል ውል አልተደረገም የሚል ክርክር ስታቀርብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ውሉ በፍ/ብ/ሕግ 1723 የተመለከተውን መስፈርት ስለማያሟላ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክራለች፡፡ ክሱ የቀረበለት የሃላባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሁለቱ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፣ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ የቤቱን ሰነድ እና ማናቸውም ማስረጃ ሁሉ ለተጠሪ ትሰጥ በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃመም ይግባኝ በማቅረብዋ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሉ የሕጉን ፎርም አያሟላም የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ ሽሮአል፡፡ በመጨረሻም በተጠሪ አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ ችሎቱም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በመሻር የሃላባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ አቤቱታ ባቀረበችበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምላት ዘንድ ጠይቃለች፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው የአመልካች ክርክር ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ወይ? የሚለው ጭብጥ ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል በጽሑፍ ስለመደረጉ እና በዚህ ውል መሠረትም ተጠሪ ቤቱን ተረክቦ በይዞታው ሥር አድርጎት እንደሚገኝ ክሱን በሰማው ፍ/ቤት በማስረጃ ተረጋግጦአል፡፡ አመልካችም ብትሆን በአንድ በኩል የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የለም፤ ቢኖርም የሕጉን ፎርም አያሟላም በማለት ስትከራከር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቤቱ ተጠሪ ተረክቦት በይዞታው ሥር መገኘቱን አልካደችም፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ቤቱን ሊይዝ የቻለው በኪራይ ነው የሚል መከራከሪያ ወደ መጨረሻው አካባቢ አቅርባ እንደነበር፣ ነገር ግን በዚህ መሠረትም ማስረጃ ማቅረብ እንዳልቻለች በፍ/ቤቱ ውሣኔ ተመልክቶአል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ እንደውሉ እንድትፈፅም የወሰነውም እነዚህን በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ ነው፡፡

እንደምናየው አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገችው የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የበኩልዋን ክስ ወይም የተከሣሽ ከሳሽነት ክስ አላቀረበችም /የፍ/ብ/ሕግ. 1808/2/፡፡ ውሉን መሠረት በማድረግ ቤቱን ለተጠሪ እንዳስረከበችም ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማረጋገጥ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ተረጋግጦአል፡፡ ተጠሪ ክስ ሊመሰርት የቻለው ለውሉ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች እንዲሟሉለት ነው፡፡ እነዚህም ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶች ሲሆኑ፣ በፍ/ቤቶቹ የተወሰነውም አመልካች እነዚህን ሰነዶች እንድትሰጠው ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ የአንድ ነገርን ባለሃብትነት ማስተላለፍን ስለሚመለከቱ ውሎች በተደነገገው አንቀጽ 15 /የፍትሐብሔር ሕጉ/ በተመለከተው ደንብ መሠረት እንደሚመራ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2875 ተመልክቶአል፡፡ በአንቀጽ 15 ሥር ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ውስጥ ለያዝነው ጉዳይ ተገቢነት ካላቸው አንዱ በቁ. 2281 የተመለከተው ሲሆን፣ ይህም ሻጩ የሸጠውን ነገር ባለሃብትነት ለገዢው የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሻጩ የሸጠውን ነገር የማያስነካ መብት ለገዢው ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑትን ተግባሮች ለመፈጸም እንዳለበትም ደንጉአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች በሥር ፍ/ቤቶች የተወሰነበት በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ እንዲፈጽም ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሃላባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 02925 የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማፅናት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ. 39512 ነሐሴ 28 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቶአል፡፡
2. አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህዳር 7 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፀሐይ ፍቃዱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1- አቶ ብቻዬ ተስፋዬ - አልቀረቡም

2- አቶ መሰሉ አዳነ ወኪል ታደሰ አዳነ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ሃብትን አንደኛው ተጋቢ ለሌላ ሶስተኛ ወገን የፈፀመውን የሽያጭ ውል የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሣሽ ተጠሪዎች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ከአንደኛው ተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሣሥረው ሲኖሩ ጋብቻቸው ሀምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የፈረሰ መሆኑን ገልፀው በጋብቻ ወቅት ያፈራነውን በኦሮሚያ ክልል በባቱ ከተማ ያፈራነውን ቤት አንደኛ ተከሣሽ /አንደኛ ተጠሪ/ ለሁለተኛ ተከሣሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ ያለእኔ ፈቃድና ስምምነት ሸጧል፡፡ ቤቱ መሸጡን ያወቅሁት ነሐሴ 12 ቀን 2000 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ ያለፈቃድና ስምምነቴ አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ ያደረገው ውል ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ ቤቱን 1994 ዓ.ም ለአቶ መስፍን ዝንቱ አስተላልፌዋለሁ፡፡ ይህንንም ያደረግሁት በከሣሽ ፈቃድና ስምምነት ነው፡፡ ቤቱን እኔ ለሁለተኛው ተከሣሽ /ለሁለተኛው ተጠሪ/ አልሸጥኩም ቤቱ በሁለተኛ ተከሣሽ ስም ስለተዛወረ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ አይችልም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ መልስ ባለመስጠቱ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችና አንደኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አንደኛ ተከሣሽ ለሁለተኛው ተከሣሽ ቤቱን መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም. በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል በመሸጡ የቤቱ ስመሀብት ወደ ሁለተኛው ተከሣሽ የተዛወረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አንደኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሣሽ ቤቱን ለሁለተኛ ተከሣሽ አልሸጥኩም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል ቤቱ በገዥው በሁለተኛው ተከሣሽ ስም የተዛወረ በመሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1806 ውሉ ቀሪ ስለሆነ ከሣሽ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችንና የአንደኛ ተጠሪን ክርክር ከሰማ በኋላ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ጥቅምት 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የበታች ፍርድ ቤቶች ቤቱን ያለ እኔ ፈቃድና ስምምነት አንደኛው ተጠሪ ለሁለተኛው ተጠሪ የሸጠ በመሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ንብረቱ በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህንን ካጣሩና ካረጋገጡ በኋላ ውሉ ተፈፅሞ የቤቱ ስመሀብት በሁለተኛ ተጠሪ ስም የተዛወረ በመሆኑ ውሉ ቀሪ ስለሆነ እንዲፈርስ መጠየቅ አይችልም በማለት የሰጡት የህግ ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የተሸጠው 1994 ዓ.ም ለአቶ መስፍን ዝንቱ ነው፡፡ ከእኛችን ከወጣ ስምንት ዓመት ሆኖታል፡፡ ስለዚህ የአመልካች መቃወሚያ ተገቢነት የለውም፡፡ አመልካች ገንዘብ ይገባኛል በማለት አላቀረበችም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ ሀምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን መጥሪያ በአግባቡ አላደረሰችልንም፡፡ ቤቱን አንደኛ ተጠሪ 1994 ዓ.ም ለአቶ መስፍን ዝንቱ በሽያጭ አስተላልፈዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ለአቶ መስፍን ዝንቱ ባልቻ አንደኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችለው ውክልና መስከረም 9 ቀን 2000 ዓ.ም. ከአንደኛ ተጠሪ ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህ በኋላ እኔ ከአቶ ዝንቱ ባልቻ ቤቱን የገዛሁት በመሆኑ አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር ክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን አኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች በጋብቻ ወቅት የተፈራው የጋራ ንብረት አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ ለመሸጥ የተዋዋለው ውል ሙሉ በሙሉ ተፈፅሞ ቤቱ በሁለተኛው ተጠሪ ስም ተመዝግቦ ቀሪ ስለሆነ ውል ይፍረስልኝ ብሎ ለመጠየቅ አይችልም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን መሠረታዊ ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው የከፍተኛ ፍርድ ቤት በሌለበት ታይቶ የተወሰነበት ሁለተኛ ተጠሪ በሰበር ችሎት ያቀረባቸውን ክርክሮች ተገቢነት ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ጉዳዩ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሌለሁበት የታየው አመልካች በአግባቡ መጥሪያ ስላላደረሰችኝ ነው በማለት የሰበር መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሌለሁበት የታየው አላግባብ ነው የሚል ከሆነ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 78 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለሚመለከታቸው ፍርድ ቤቶች ከሚያቀርቡ በስተቀር ይህንን ነጥብ የሰበር መከራከሪያ አድርገው ማቅረባቸው ሥርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ክርክር ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በተጨማሪ አንደኛው ተጠሪ ቤቱ የተሸጠው 1994 ዓ.ም አመልካች አውቃና ፈቅዳ ነው። ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ የሸጥኩት እኔ ሳልሆን አቶ ዝንቱ ባልቻ ነው በማለት ያቀረበው የፍሬ ጉዳይ ክርክር ዕውነትነት የሌለው መሆኑንና አንደኛ ተጠሪ በወኪሉ አቶ ዝንቱ ባልቻ በኩል ለሁለተኛው ተጠሪ ቤቱን መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም የሸጠ መሆኑን ከባቱ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የተላከለትን ማረጋገጫና በሌሎች ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑን በመግለፅ ቤቱን ለሁለተኛው ተጠሪ የሸጠለት አንደኛ ተጠሪ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል።

ሁለተኛው ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ ያልተከራከረበትንና ሁለተኛው ተጠሪ በሌለበት ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የደረሰበትን መደምደሚያ ትክክል እንዳልሆነ በመዘርዘር ለሰበር ችሎት የሰጠው መልስ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329/1/ የሚጥስና ለዚህ ፍርድ ቤት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም።

ሁለተኛው ተጠሪ ሀምሌ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ በመጀመሪያው ገፅ ሁለተኛው ፖራግራፍ ቤቱን የገዛው አንደኛ ተጠሪ ቁጥሩ 4039/1/2000 በሆነና መስከረም 9 ቀን 2000 ቤቱን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችለው ልዩ የውክልና ሥልጣን ከሰጠው ከአቶ ዝንቱ ባልቻ መሆኑን ግልፅ አድርጎታል። አንድ ተወካይ ከወኪልነቱ ሥልጣን ወሰን ሣያልፍ በሌላ ሰው ስም የመዋዋል ተግባሮች የፈፀመ እንደሆነ በእሱ የተፈፀሙት ተግባሮች በቀጥታ በሚሚው እንደተፈፀመ እንደሚቆጠሩ በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2189 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ በመሆኑ አቶ ዝንቱ ባልቻ ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል በአንደኛው ተጠሪ እንደተፈፀመ የሚቆጠር ነው። ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች በጋብቻ ወቅት የተፈራውን የጋራ ንብረት ያለአመልካች ፈቃድ ለሁለተኛው ተጠሪ የሸጠው አንደኛው ተጠሪ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ስህተት የሌለውና ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል።

2. አመልካችና አንደኛ ተጠሪ በጋብቻ ተሣሥረው ሲኖሩ ያፈሩትንና በኦሮሚያ ክልል በባቱ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኘውን ቤት አንደኛ ተጠሪ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የውል ሰነድ ለሁለተኛው ተጠሪ የሸጠ መሆኑ ተረጋግጧል። አንደኛ ተጠሪ ቤቱን ለሁለተኛ ተጠሪ የሸጠው በወኪሉ አቶ ዝንቱ ባልቻ በኩል በመሆኑና አመልካች አቶ ዝንቱ ባልቻ የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት እንዲሸጥ እንዲለወጥ ውክልና ያልሰጡ በመሆኑና ቤቱ ሲሸጥ ፈቀዳቸውን ያልሰጡ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል።

የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው የቤቱ ስመሀብት በሁለተኛው ተጠሪ ስም የተዛወረ መሆኑን የባቱ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነሐሴ 12 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጧል። የአንድ ውል መፈፀም ውሉን ቀሪ የሚያደርገው በመሆኑ አመልካች ውሉ በሙሉ በመፈፀሙ ምክንያት ቀሪ የሆነ ውል ፈራሽ እንዲባል ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለትና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1806 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ መሆኑን ተገንዝበናል።

በመሠረቱ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1806 ተዋዋይ ወገኖች በውል የገቡት ግዴታ ቀሪ የሚሆንበትን መሠረታዊ ምክንያት የሚደነግግ ድንጋጌ ነው። ተዋዋይ ወገኖች በህግ አግባብ ያቋቋሙት ውል በመካከላቸው ሕግ እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1731/1/ ይደነግጋል። ስለሆነም ተዋዋይ ወገኖች አንዳቸው ለሌላው በዉል የገቡት ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከፈፀሙ ውሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደ ህግ ሆኖ ተዋዋዮቹን ማስገደዱ ቀሪ የሚሆን መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1806 ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው ተዋዋዮች በውሉ የገቡት ግዴታ ቀሪ የሚሆንበትን /Extinction of contract " ምክንያት ከሚሆኑት ነገሮች አንደኛውን የሚደነግግ ነው፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1806 ተዋዋይ ወገኖች የተዋዋሉትና ሙሉ በሙሉ ግዴታቸውን የፈፀሙበት ውል የእኔን መብትና ጥቅም የሚነካና ህጋዊ ዉጤት ሊሰጠው የሚገባ ውል አይደለም፡፡ ስለዚህ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ይወሰንልኝ የሚል ጥያቄ የሚያቀርቡ ሶስተኛ ወገኖች የውሉን ህጋዊነት በመቃወም ውሉ እንዲፈርስ ከመጠየቅ የሚገድብ የህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች አንደኛው ተጠሪ የጋራ ሀብቱ የሆነውን ቤት ያለእኔ ስምምነት ለሁለተኛው ተጠሪ ሸጧል፡፡ ስለዚህ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል ሙሉ በሙሉ ተፈፅሞ ቤቱ በገዥው በሁለተኛው ተጠሪ ስም መመዝገቡ የማያግዳት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍታብሔር ህጉ ስለውሉ ታውቆ መቅረት ለተደነገገው ክፍልና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1806 የተዛባ ትርጉም በመስጠት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. አንደኛ ተጠሪ ቤቱ የተሸጠው በአመልካች ስምምነት ነው፡፡ ቤቱ በ1994 ዓ.ም ከአቶ መስፍን ዝንቱ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ዕውነትነት የሌለው መሆኑንና ቤቱ አንደኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተጠሪ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የውል ሰነድ የተሸጠ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ የፈረሰው ሀምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሰጠ የፍች ውሣኔ መሆኑንና የቤቱን መሸጥ ያወቀችው ነሐሴ 12 ቀን 2000 ዓ.ም መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረበችው የክስ ማመልከቻ ገልፃለች፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገውን ቤቱ በአመልካች ስምምነት 1994 ዓ.ም ተሸጧል የሚለውን መከራከሪያ ከማቅረቡ ውጭ አመልካች አንደኛ ተጠሪ በወኪሉ ዝንቱ ባልቻ በኩል ለሁለተኛው ተጠሪ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የውል ሰነድ የሸጠ መሆኑን እንደምታውቅ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የሌለ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

ስለሆነም አመልካች አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የፈፀሙት የቤት ሽያጭ ውል በፍርድ ፈራሽ እንዲሆን ክስ ያቀረበችው ታህሣሥ 4 ቀን 2001 ዓ.ም. በመሆኑ ይኸም አመልካች ውሉ መፈፀሙን ካወቀችበት ከነሐሴ 12 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከአራት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ያሣያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉ ከተፈፀመበት መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በአንድ ዐመት ከሶስት ወራት ውሉ እንዲፈርስ ክስ ያቀረበች መሆኑን ያሣያል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አንደኛ ተጠሪ አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ያቀረበችው ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ሰበር ችሎት ያቀረበው ክርክር የተሻሻለውን የቤተሠብ ህግ አንቅፅ 69 ድንጋጌዎች መሠረት ያላደረገና ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን በባቱ ከተማ 01 ቀበሌ በአንደኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የነበረው ቤት አመልካችና አንደኛ ተጠሪ በጋብቻ ሲኖሩ ያፈሩት የጋራ ሀብት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ይህንን የጋራ ሃብት ያለአመልካች ስምምነት ለሁለተኛው ተጠሪ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ውል የሸጠው የተሻሻለው የቤተሠብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 69 ድንጋጌዎችን የሚጥስ ነው፡፡ ስለሆነም አንደኛ ተጠሪ የጋራ የሆነውን የንብረት ያለአመልካች ፈቃድ ለሁለተኛ ተጠሪ ለመሸጥ የፈፀመው ውል ፈራሽና አመልካች ላይ ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለው ነው ብለው መወሰን ሲገባቸው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1806 ድንጋጌ በመጥቀስ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አንደኛ ተጠሪ የአመልካች የጋራ ሃብት የሆነውን በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን ባቱ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኘውን መኖሪያ ቤት ለሁለተኛው ተጠሪ ለመሸጥ አመልካች ሣታወቅና ሳትስማማ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም በወኪሉ አማካኝነት የተዋዋለው ውል ፈራሽ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ በመሆኑ አመልካች በቤቱ ላይ ያላትን የጋራ ባለሀብትነት መብትና ድርሻ የመጠየቅ መብት አላት በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፣ መትከል ልምዓት ሁለገብ መ/ህ/ስ ማህበር

ተጠሪዎች፣ ቄስ ካላዩ ኪሮስ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በብድር የተሰጠን ገንዘብ ይመለስ በሚል የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው የስሃርቲሳምሬ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን የከሰሰው ታህሳስ 15 ቀን 1997 ዓ.ም. የውሃ ሞተር ዋጋው 4900.00(አራት ሺኅ ዘጠኝ መቶ ብር) በ9% ወለድ ስሌት ለአራት አመት ጊዜ ከፍለው እንዲጨርሱ ፣ጊዜው ካለፈ ግን በ18% ወለድ ስሌት እንዲከፍል በአይነት በብድር ውል የሰጣቸው መሆኑን፣ተጠሪ በጊዜው ሊከፍለው ያለመቻሉን ገልጾ ተጠሪ ዋናውን ገንዘብ ብር 4900.00 በ9% ብር 1764.00፣ጊዜው በማለፉ ደግሞ በ18% ወለድ ብር 1499 በጠቅላላው ብር 8163.00(ስምንት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ሶስት ብር) እንዲከፍለው ይወሰን ዘንድ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ውሉ ስለመኖሩና የመክፍያ ጊዜው ስለማለፉ አመነው ወለዱን በተመለከተ ግን አስተያየት እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤትም ተጠሪን ለገንዘቡ ያለመመለስ ኃላፊ አድርጎ የኃላፊነታቸውን መጠን ግን ዋናው ገንዘብ በ9% ወለድ ታስቦ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታውን ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የወለድ መጠኑ 18% መሆን ሲገባው የበታች ፍርድ ቤቶች 9% ብቻ በማለት የወሰኑት የፌዴራሉን አዋጅ ቁጥር 147/1991፣402/1996 እና በክልሉን አዋጅ ቁጥር 145/2000 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ዋናውን የብድር ገንዘብ ከ9% ወለድ ጋር ብቻ እንዲከፍሉ በበታች ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀፅ 34(2) እና አዋጅ ቁጥር 402/1996 አንቀጽ 5 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ ከአመልካች በውል የተበደሩት ገንዘቡ በአራት አመታት ውስጥ የሚመለስ ሁኖ በዚህ ጊዜ የሚታሰብ የወለድ መጠን 9%፣ጊዜው ካለፈ ደግሞ ወለዱ 18% እንደሚሆን መስማማታቸውን የብድር ውሉ የሚያረጋግጠው ጉዳይ ሲሆን ተጠሪም ይህንኑ ስምምነት የሚክዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የወለድ መጠኑ 9% እንዲሆን የወሰኑት አመልካች አግባብነት ያላቸውን የማህበራት ሕጎችን መሰረት አድርጎ ክርክሩን አቅርቦ እያለ በማለፍ ነው፡፡

በመሰረቱ በሕግ የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሕግን ያህል አስገዳጅነት ያላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡አንድ ውል ሕጋዊ ነው ለማለት ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678 ስር የተመለከቱትን የውል አቋሞችን ማሟላት ይገባዋል፡፡ በዚህም መሰረት የሚፀና ውል ነው ለማለት የሚቻለው ውል ለመዋዋል ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር፣በቂ የሆነ እግጠኛነት ያለው የሚቻልና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ እና በሕጉ የሚፈለገው የውሉ አፃፃፍ ፎርም መሟላት አለባቸው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው ነጥብ የወለድ መጠኑ 18% ሊሆን ይገባል ተብሎ በአመልካች የተጠየቀው ዳኝነት ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን ነው፡፡አመልካች ይህንኑ የዳኝነት ጥያቄ ሕጋዊ ነው በማለት በዋቢነት የሚጠቀሰው የማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 34(2) እና አዋጅ ቁጥር 402/1996 አንቀጽ 5 እንዲሁም የክልሉን የማህበራት አዋጅ ቁጥር 145/2000ን ነው፡፡

በበኩላችን እንደአየነው በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 34(2) ስር አንድ ማህበር ላበደረው ገንዘብ የሚያገኘው ወለድ ከባንክ የማበደሪያ ወለድ ሊበልጥ አይችልም በሚል በሃይለ ቃል የተቀመጠ የነበረ ሲሆን ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 402/1996 ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 34(2) ስር ተቀምጦ የነበረው ድንጋጌ ሙሉ በሙሉ መሻሩን በአንቀጽ 5 ስር አስፍሯል፡፡ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 147/1991ን ለማስፀፈም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 106/1996 በአንቀጽ 11 እና 14 ድንጋጌዎች ስር ከአስቀመጣቸው ሁኔታዎች የብድር አሰጣጥ ስርኣት በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ሊወሰን እንደሚችል መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክልሉ የማህበራት አዋጅ ቁጥር 145/2000ም ተመሳሳይ ይዘት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሕጉ ረገድ ያለው ማዕቀፍ ይህን የሚመስል ከሆነ አመልካች ከተጠሪ የ18% ወልድ ጥያቄ ያቀረበው በሕጉ አግባብ የተመሰረተው መተዳደሪያ ደንብ የሚፈቅድ መሆኑንና ይህንኑም ተጠሪ አውቀው ግዴታ የገቡ መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡እንዲህ ከሆነ አመልካች ከተጠሪ 18% ወለድ የማይጠይቅበት እና ተጠሪም በገቡት ግዴታ መሰረት የማይወጡበት ወይም 18% ወለድ የማይከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በዋናው ገንዘብ 9% ወለድ ብቻ ነው ሊከፍሉ የሚገባው በማለት የሰጡት ውሳኔ ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በሰሃርቲሳምራ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 004448 ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡባዊ ምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02682 ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም. እንዲሁም በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 40515 መስከረም 21 ቀን 2003 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

2. ከአመልካች ጋር በተደረገው የብድር ውል ተጠሪ የብድር ጊዜው ካለፈ በሁዋላ የሚታሰበው ወለድ 18% ነው ብለናል፡፡በዚህም መሰረት ተጠሪ በጠቅላላው ለአመልካች ብር 8163.00(ስምንት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ሶስት ብር) ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡-1. ሴንትራል ቬኑ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር — ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 ላሉት አመልካቾች ጠበቃ አቶ ዘላለም ክፍሌ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሸዋወንድም ተስፋዬ

3. አቶ ዳዊት ከበደ

4. የወ/ሪት ነጠረች ከበደ ወራሽ ወ/ሮ አስገደች አበበ ጠበቃ ቸርነት ወርዶፋ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡-1. አቶ ሰለሞን ከተማ — ጠበቃ አቶ ጥላሁን ደስታ ቀረቡ

2. አል-ሳልቫቶር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና የአራተኛ አመልካች ወራሽ ወ/ሮ አስገደች አበበ ከተጠሪዎች ጋር ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉትን የዕርቅ ስምምነትና በዕርቅ ስምምነቱ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 27497 መጋቢት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልካቾች በጋራ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሆቴል ንግድ ድርጅትና የሕንፃ ሽያጭ ውልን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ አመልካቾች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. የሴንትራል ቬንዩ ሆቴልን ከነመገልገያ ዕቃዎቹና ህንፃው ልንሸጥላቸው በፅሑፍ ውል ተዋውለናል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ቀብድ ከከፈለ በኋላ ቀሪውን ግዴታውን እንዲወጣ በሰጠነው ማስጠንቀቂያ መሠረት ግዴታውን ባለመወጣቱ ውሉን ሰርዘነዋል፡፡ ስለዚህ ሆቴሉን ከነመገልገያ ዕቃዎቹ እንዲያስረክበን፣ በውሉ መሠረት ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ መቀጫ እንዲከፍለን፣ የሆቴሉን ስም በመቀየር ላደረሰው ጉዳት ክስ የማቅረብ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ በክርክሩ አራተኛ አመልካችና ሁለተኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ተከራካሪዎች ሆነው ገብተዋል፡፡ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ እና ሁለተኛ ተጠሪ የሽያጭ ውሉ አለመፈፀም በኃላፊነት የሚጠየቁት ከሳሾች ናቸው፡፡ እኛ በውሉ በገባነው ግዴታ መሠረት ብር 6,450,000 /ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሀምሣ ሺህ ብር/ ዕዳ ከፍለናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ወስኖ ተጠሪዎች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተጠሪዎችና የአመልካቾችን ክርክር በሰበር መዝገብ ቁጥር 32299 ከሰማ በኋላ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 27497 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ይግባኝ ሰሚው ችሎት፣

1. የሥር ከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ ሸዋወንድም ተስፋዬ /ሁለተኛ አመልካች/ እና አቶ ዳዊት ከበደ /ሶስተኛው አመልካች/ ውሉን በተናጠል ሰርዘነዋል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም?

2. የውሉ መሠረዝ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

3. የሥር ጣልቃ ገብ የነበረችው ወ/ሮ ነጠረች ከበደ /አራተኛ አመልካች/ ውሉ እንዲፈረስ ለመጠየቅ ይችላሉ ወይስ አይችሉም? ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? መብት አላቸው ከተባሉ መብታቸው በምን ሁኔታ መከበር አለበት የሚሉትንና ሌሎች ከውል መሠረዝ ጥያቄ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተጨማሪ ነጥቦች በመመልከት ውሣኔ ይሰጥበት በማለት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መልሶታል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰበር ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 32299 ጥር 7 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ በመሠረታቸው ጭብጦችና ሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ነጥቦች ላይ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካቾች ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ የሚችሉበት ሁኔታ የለም በማለት ወስኗል፡፡ በሁለተኛው ጭብጥ አመልካቾች ውሉን በፍርድ ቤት ውሣኔ ለማሰረዝ የሚያስችል ምክንያት ያለ ስለመሆኑ በፍሬ ጉዳዩ ደረጃ አላስረዱም ውሉ ያልተፈፀመው በአመልካቾች ቀሪ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ባለመሆኑ ሻጮች /አመልካቾች/ ውሉን በፍርድ ለማስረከብ የሚያስችል የሕግም ሆነ የፍሬ ጉዳይ መሠረት የላቸውም የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ አራተኛ አመልካች የሚች ወራሽ መሆናቸው የተረጋገጠው ንብረቱ በውል ከተላለፈ በኋላ በመሆኑ ድርሻዋን ከሻጮች ከምትጠይቅ በቀር ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ አትችልም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት አላት ቢባል እንኳን ተዋዋዮቹን ወደ ነበሩበት መመለስ አይቻልም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43165 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡

አመልካቾች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ነው፡፡ አመልካቾች ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች አንደኛው ተጠሪ በውሉ መሠረት ግዴታውን እንዲወጣና ቀሪውን ክፍያ እንዲከፍሉ መስከረም 27 ቀን 1998 ማስጠንቀቂያ የሰጡት ቢሆንም ተጠሪ ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ውሉን በተናጠል ሰርዘውታል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ የሚያስችላቸው ሁኔታ የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሆቴል ድርጅቱን ህንፃውን በሆቴሉ ላይ ካለው ዕዳና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠራተኛ ዕዳ ጭምር ገዘቷል፡፡ ገዥ ለሻጮች ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን ብር/ ለመክፈል ከተስማማ በኋላ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ቀብድ ከፍሎ ቀሪውን ሰማኒያ ፐርሰንት ክፍያ ያልፈፀመና ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑና በእኛ በኩል ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሉን በፍርድ ቤት ውሣኔ ለመሰረዝ የሚያበቃ ሁኔታ የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1983/1/ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና በሰበር ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

አራተኛ አመልካችን በተመለከተ አከራካሪው ንብረት ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት ባለበት ሁኔታ ያለ አራተኛ አመልካች ፈቃድና ስምምነት ንብረቱን ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ እንደማይችል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1060 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1266 ተደንግጎ እያለና፣ አራተኛ አመልካች የሚች ወራሽ ናቸው ተብለው የሚያዙት ሚች ህይወት ካለፈበት ቀን ጀምሮ መሆን ሲገባው የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ አትችልም ተብሎ መወሰኑ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሉን አፍርሶ ተዋዋዮቹን ወደ ነበሩበት ለመመለስ አይቻልም በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ምክንያት ስህተት ያለበት ነው፡፡ በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ጎዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ የሚችሉ ስለመሆኑ በሽያጭ ውሉ በግልፅ አልተመለከተም፡፡ ገዥ ቀሪውን ብር 800,000 /ስምንት መቶ ሺህ ብር/ ለመክፈል የውል ግዴታ የገባው የንብረቱ ስመ ሀብት ወደ ገዥ ሲዛወር መሆኑ በውሉ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በጠየቅነው ጊዜ ቀሪውን ዋጋ ስላልከፈለን ውሉን ሰርዘናል በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካቾች ጎዳር 23 ቀን 1998 ዓ.ም ለሰጡት ማስጠንቀቂያ ተጠሪዎች ጎዳር 26 ቀን 1998 ዓ.ም በፅሑፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም ይባልልን፡፡ የሆቴል ድርጅቱ ሽያጭ ውል በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት አመልካቾች የሚከራከሩት ተጠሪዎች መሠረታዊ የሆነ የውል መጣስ ተግባር ፈፅመዋል በማለት ነው፡፡ አመልካቾች ገዥ የሸያጩን ሰማኒያ ፐርሰንት ዋጋ አልከፈለም በማለት የሚከራከሩት ገዥ በሁለት ባንኮች ይፈለግ የነበረውን ስምንት ሚሊዮን ብር /ብር 8,000,000/ ዕዳ የከፈለ መሆኑንና ሌሎች የውሀ፣ የመብራት፣ የስልክና የመሳሰሉት ውዝፍ ዕዳዎች በመክፈል በውሉ የገባውን ኃላፊነት የተወጣ መሆኑን ወደ ጎን በመተው ነው፡፡ ተጠሪዎች የውል ግዴታቸውን ከዘጠና ፐርሰንት በላይ የተወጡ ሲሆን አመልካቾች የሰጡትን ውክልና በመሻር የንብረቱ ስመ-ሀብት ወደ ገዥ እንዳይዘወር እንቅፋት በመፍጠር ኃላፊዎች ናቸው፡፡

ሚች አቶ ከበደ ጠቅላላ ንብረታቸውን ለሁለተኛ አመልካችና ለሶስተኛ አመልካች በኑዛዜ ሰጥተው የሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛው አመልካች የሚች የኑዛዜ ወራሾች መሆናቸው በመዝገብ ቁጥር 1262/90 ጎዳር 2 ቀን 1999 ዓ.ም በፍርድ ቤት ተወስኗል፡፡ አራተኛ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ በማቅረብ የሁለተኛና የሶስተኛ አመልካቾች የኑዛዜ ወራሽነት አላሰረዙም፡፡ ተጠሪዎች የግዥ ውል የፈፀሙት ሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛ አመልካች የሚች ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ በፍርድ ቤት የተሰጠውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አራተኛ አመልካች የሚች ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው ያቀረቡት ሚች ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ ከስምንት ዓመት በኋላ ሲሆን በክርክሩ ሂደት ንብረቱ ላይ የሰጡት የእግድ ትእዛዝ የለም፡፡ ስለዚህ አራተኛ አመልካች ቀደም ብሎ በፍርድ ቤት በተሰጣቸው ማስረጃ መሠረት ሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛ አመልካች የፈፀሙትን የሽያጭ ውል እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችሉበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የሥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማዕናት እንዲያሰናብተን በማለት ተከራክረዋል። አመልካቾች ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል። የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው፡-

1. ተጠሪዎች ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው ውል መሠረት ግዴታቸውን እንዲፈፅሙ ማስጠንቀቂያ ሰጥተናቸው ግዴታቸውን ያልፈፀሙ በመሆኑ ውሉን በተናጠል ሰርዘነዋል በማለት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የመጀመሪያው ጭብጥ የሚታላለፍ ቢሆን፣

2. ተጠሪዎች መሠረታዊ የውል መጣስ ተግባር የፈፀሙ በመሆኑ ውሉ በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?

3. አራተኛ አመልካች ሚች ወ/ሪት ነጠረች ከበደን በመተካት በሰበር ተከራካሪ የሆኑት ወ/ሮ አሰገደች አበበ ከተጠሪዎች ጋር ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት ተመዝግቦ ሕጋዊ ውጤት ሊሰጠው ይገባል ወይስ አይገባም?

4. አራተኛ አመልካች የነበሩት ወ/ሪት አበራች ከበደ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የእኔ የጋራ ሀብት የሆነውን የንግድ ድርጅትና ህንፃውን ለአንደኛ ተጠሪ ለመሸጥ የተዋዋሉት ውል እኔ ያልተስማማሁበት በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል በማለት ያቀረበችውን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሳይቀበለው መቅረቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚሉትን ጭብጦች ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተገቢውን ማጣራት አድርጎ ካረጋገጣቸው ፍሬ ጉዳዮችና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በመመርመር ውሣኔ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

1. የመጀመሪያው ጭብጥ ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 32299 ሲመልስ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አጣርቶ ውሣኔ እንዲሰጥባቸው ከመሠረታቸው ጭብጦች አንደኛውና የመጀመሪያው ነው። ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይህንን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ውሣኔ ሰጥቶበታል። አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ አመልካቾች ተጠሪዎች ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው የንግድ ድርጅትና የሕንፃ ሽያጭ ውል በገቡት ግዴታ መሠረት ቀሪውን ክፍያ ብር 800,000 /ስምንት መቶ ሺህ ብር/ በአእምሮ ግምት በቂ ነው ባልነው በአስር ቀን ውስጥ እንዲፈፅሙ መስከረም 27 ቀን 1998 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥተናቸዋል። ተጠሪዎች በውሉ መሠረት ክፍያ ያልፈፀሙ በመሆኑ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ውሉን በተናጠል የሰረዝነው መሆኑንና ይህንም በፍታብሔር ህግ የተደነገገ መሆኑን በማንሣት ያቀረበውን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው አላግባብ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል። ተጠሪዎች በበኩላቸው አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች በውል በገቡት ግዴታ መሠረት የሸጡትን የንግድ ድርጅትና ህንፃ ስመ ሃብት ወደ ገዥዎች እንዲዛወር ተገቢውን ተግባር አልፈፀሙም። ለውሉ አለመፈፀም በኃላፊነት የሚጠየቁት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች በመሆናቸው ውሉን በተናጠል የመሠረዝ መብት የላቸውም በማለት ተከራክረዋል።

በመርህ ደረጃ በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ሕግ በመሆናቸው ተዋዋይ ወገኖች በውል የገቡትን ግዴታ የመፈፀም ግዴታ አለባቸው። ተዋዋይ ወገኖች በሕግ አግባብ ያቋቋሟቸው ውሎች ተገዥ የመሆንና ግዴታቸውን በታማኝነት የመፈፀም ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለባቸው በመሆኑ ህጉ ተዋዋይ ወገኖች በህግ መሠረት ያደረጉትን ውል አንደኛው ወገን በፈለገው ጊዜ የፈለገውን ምክንያት እየሰጠ ውለታውን እንዲሰረዝ የሚፈቅድ አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ በህግ አግባብነት የተቋቋመን ውል አንደኛው ተዋዋይ ወገን በተናጠል ለመሰረዝ የሚችለው በሕግ በግልፅ ከተመለከቱ ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ አንድ ውልን ለመሰረዝ የሚያስችል ልዩ ሁኔታ መሟላቱን በማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በህግ የተደነገገው ውልን ለመሰረዝ በሚያስችል ልዩ ምክንያት ውሉን የሰረዘ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ውሉን በተናጠል ሰርዣዋለሁ የሚለው ተዋዋይ ወገን ነው፡፡

በአገራችን አንደኛው ተዋዋይ ወገን ውሉን በተናጠል ሊሰርዝ የሚችልባቸው ሁኔታዎች በፍታብሔር ሕግ ውልን ስላለመፈፀም በሚደነግገው ክፍል ተዘርዝረዋል፡፡ ስለሆነም በአገራችን አንደኛው ተዋዋይ ወገን በተናጠል ውል ሊሰርዝ የሚችለው ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1786 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንደኛው ተሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1786 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1789 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተከታታይነትና ተያያዥነት ያላቸውና አንደኛው ተዋዋይ በተናጠል ውልን ሊሰርዝ ስለሚችልባቸው ሁኔታዎች የሚደነግጉ መሆኑን የድንጋጌዎቹን አቀራረፅና ህግ አውጭው ለድንጋጌዎቹ የሰጠውን ተከታታይነት ያላቸው ተራ ቁጥሮች በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመጀመሪያ “በአንድ ወገን ብቻ የሚደረግ የውል ማፍረስ” የሚል ጠቅላላ ርዕስ የተሰጠው

- የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1786 ተራ ቁጥር 1 “የውል ማፍረሻ የሆኑ ቃሎች” በሚል

  ርእስ ሥር አንደኛውን የውል ማፍረሻ (መሠረዣዎች) ምክንያትን የሚደነግግ ሲሆን

- የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 በተራ ቁጥር 2 “ቁርጠኛ የሆነ የውል መፈፀሚያ”

- የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1788 በተራ ቁጥር 3 “መፈፀም አለመቻል”
- የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1789 በተራ ቁጥር 4 “መፈፀምን እንቢ ስለማለት”

በሚል ርዕስ አንደኛው ተዋዋይ ወገን በተናጠል ውል ሊሰርዝ የሚችልባቸውን ልዩ ሁኔታዎች ደንግገዋል፡፡ አመልካቾች ውሉን በተናጠል ሠርዘነዋል ብለው የሚከራከሩት ተጠሪዎች በውል የገቡትን ግዴታ በአስር ቀናት ውስጥ እንዲፈፀሙ ማስጠንቀቂያ ሰጥተናቸው፣ በተሰጣቸው አስር ቀናት ውስጥ ግዴታቸውን ያልፈፀሙ በመሆኑ ውሉን ሠርዘነዋል በማለት ነው፡፡ ይህ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሚያነሱት ክርክር አግባብነት ያለው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1787 ድንጋጌ በመሆኑ ሌሎቹን ማለትም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1786፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1788 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ድንጋጌዎችን ዝርዝር ይዘትና ትርጉም መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም፡፡

“ቁርጠኛ የሆነ የውል መፈፀሚያ ጊዜ” የሚል ርዕስ ያለው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1787 ዝርዝር ይዘት ስንመለከተው “በውሉ ላይ አንድ ግዴታ መፈፀሚያ ሆኖ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ፣ ወይም ማስጠንቀቂያ በተሰጠበት ጊዜ በአእምሮ ግምት ይበቃል ተበሎ በተሰጠው ቀን ወይም በዳኛ በተሰጠው የችሮታ ጊዜ ውስጥ ከተዋዋይ አንደኛው ወገን የገባው ግዴታ ሳይፈፀም የቀረ እንደሆነ ውሉ ይፍረስልኝ የሚለው ወገን ይህ ከዚህ በላይ የተነገረው የማፍረስ መብት አለው” የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ቅጅ “A party may cancel the contract where the other party has failed to perform his obligation with in the

https://t.me/ethiopianlegalbrief

period of time fixed in accordance with art 1770, 1774 or 1775 (b) “ በሚል መንገድ ይደነግጋል። ከዚህ ድንጋጌ የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቅጅ ለመረዳት እንደሚቻለው አንደኛው ተዋዋይ ወገን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ውልን በተናጠል ለመሠረዝ የሚቻለው ከሚከተሉት ሶስት ሁኔታዎች አንደኛው የተሟላ መሆኑን ለማስረዳት ሲችል ነው።

የመጀመሪያ ባለዕዳው በውሉ ላይ በተመለከተው መሠረት የውሉን ግዴታ የሚፈፀምበት ቁርጠኛ ጊዜ በውሉ ላይ በግልፅ ተመልክቶ እንደሆነና በውሉ ላይ የተገለፀው ቁርጥ የሆነ የውል መፈፀሚያ ጊዜ ያለፈ እንደሆነ ነው። በዚህ ሁኔታ አንደኛው ተዋዋይ ወገን በተናጠል ውሉን ለመሰረዝ የሚችል መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1775(ለ) ድንጋጌዎች በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል። ሁለተኛው ምክንያት ባለዕዳው ውሉን ያልፈፀመበትን ምክንያትና ሌሎች የአካባቢ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ዳኞች ባለዕዳው ውሉን የሚፈፅምበት የችሮታ ጊዜ ከሰጡት በኋላ ባለእዳው በዳኛ ወሣኔ በተሰጠው የችሮታ ጊዜ ውስጥ ግዴታውን ሣይፈጽም የቀረ እንደሆነ መሆኑን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 እና ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1770 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል።

ሶስተኛውና አመልካቾች መከራከሪያ ያደረጉት ባለገንዘቡ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1774 በተደነገገው መሠረት ሌላኛው ተዋዋይ (ባለዕዳው) በውል የገባውን ግዴታ የሚፈፅምበትን ጊዜ በመግለፅ ማስጠንቀቂያ የሰጠ ሲሆንና በማስጠንቀቂያው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይፈፅም ሲቀር መሆኑን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1774 እና ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አንደኛው ተዋዋይ ሌላው ወገን በውል የገባውን ግዴታ እንዲፈፅም በአእምሮ ግምት በቂ ነው የሚለውን የውል መፈፀሚያ ጊዜ ግልፅ ማስጠንቀቂያ ለመስጠትና በማስጠንቀቂያው የተገለፀው የውል መፈፀሚያ ሲያልፍ ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ የሚችለው እሱ በበኩሉ ምን ምን ተግባራትን ፈፅሞ ነው? የሚለው ነው።

አንደኛው ተዋዋይ ወገን ሌላኛው ተዋዋይ ወገን በውሉ መሠረት እንዲፈፅም ለመጠየቅና ማስጠንቀቂያ ለመስጠት የሚችለው በመጀመሪያ እሱ የበኩሉን ግዴታ የፈፀመ ወይም ለመፈፀም የተዘጋጀ ሲሆን እንደሆነ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1857 በግልፅ ይደነግጋል። ስለሆነም ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማና ግብ እንደዚሁም የድንጋጌው የተፈፃሚነት ወሰን ለመረዳት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1771 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1757 ድንጋጌዎች ጋር በማጣመር መመርመር ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር ስንመዝነው አንደኛው ተዋዋይ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1771 ንዑስ አንቀጽ 1 ሌላኛው ተዋዋይ ውሉን እንዲፈፅምለት ለመጠየቅ፤ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1774 ድንጋጌዎች መሠረት የውል መፈፀሚያ ጊዜ ግልፅ ማስጠንቀቂያ በመስጠትና በፍታብሔር ቁጥር 1787፣ በተደነገገው መሠረት ውሉን በተናጠል ለመሠረዝ በመጀመሪያ በእሱ በኩል በውል የተጣለበትን ግዴታ የፈፀመ ወይም ለመፈፀም ዝግጁ መሆኑ በማስረጃ ለማረጋገጥ የቻለ መሆን እንዳለበት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1771፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1774፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1757 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌዎችን ይዘትና መሠረታዊ ግብ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል። ሕግ አውጭው በውል ለገባው ግዴታ ተገዥ በመሆን በእሱ በኩል ያለውን ግዴታ ያልፈፀመ ወይም ለመፈፀም ዝግጁ መሆኑን በበቂ ሁኔታ ለማረጋገጥ ያልቻለ አንድ ተዋዋይ ወገን ሌላኛውን ተዋዋይ ወገን ቀድሞ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን በተናጠል እንዲሰርዝ በማሰብ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌን አውጇል ተብሎ አይገመትም። አንድ ተዋዋይ የውሉን መፈፀሚያ የጊዜ ገደብ በመግለጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሌላኛው ወገን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውል በተናጠል ለመሰረዝ የሚችለው በመጀመሪያ እሱ በውሉ የገባውን ግዴታ የፈፀመ ወይም ለመፈፀም ዝግጁ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። በያዝነው ጉዳይ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከተጠሪዎች ጋር ባደረጉት የንግድ ድርጅትና የህንፃ ሽያጭ ውል መሠረት የበኩላቸውን ግዴታ አሟልተው ያልፈፀሙ መሆኑንና በተቃራኒው ውሉ እንዳይፈፀም የተለያየ ችግሮችን የፈጠሩ መሆኑን ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያለው ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማረጋገጥ በውሣኔው አስፍሯል።

በመሆኑም አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች በውሉ የገቡትን ግዴታ አሟልተው ያልፈፀሙና ውሉ በአግባቡ እንዳይፈፀም የተለያዩ ችግሮችን የፈጠሩ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ፣ ተጠሪዎች በአስር ቀን ውስጥ በውሉ መሠረት ግዴታቸውን እንዲፈፀሙ ማስጠንቀቂያ ሰጥተን ግዴታቸውን ያልተወጡ በመሆኑ ውሉን በተናጠል ሠርዘነዋል በማለት ያቀረቡት ክርክር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1771፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1774፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1757 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1787 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያልተከተለና የህግ መሠረት የሌለው ነው። ስለዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ውሉን በተናጠል የሚሠርዝበት የሕግና የፍሬ ጉዳይ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

2. ሁለተኛው ጭብጥ አንደኛ፤ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ተጠሪዎች መሠረታዊ የሆነ የውል መጣስ ተግባር ስለፈፀሙ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሉ እንዲሰረዝ ውሣኔ አለመስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረቡትን ክርክር የሚመለከት ነው። በአንደኛ ተዋዋይ ወገን ጠያቂነት ዳኞች በሕግ አግባብ የተቋቋመ ውል እንዲሰረዝ ውሣኔ የሚሰጠባቸው ሁኔታዎች በፍታብሔር ህጉ ተደንግገዋል። ይኸውም ውልን በፍርድ ስለማሰረዝ የሚል ርዕስ ያለው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1784 አንደኛው ተዋዋይ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ግዴታዎቹን ያልፈፀመ እንደሆነና ወይም የፈፀማቸው ሙሉ ወይም ፍፁም ባልሆነ አኳኋን እንደሆነ ዳኞች በአንደኛው ወገን ጠያቂነት ውሉን ሊያስቀሩት እንደሚችሉ ለዳኞች የሕሊና ሚዛን ፈቃድ ሥልጣን በሚሰጥ አኳኋን የሚደነግግ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል። የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1784 በይዘቱ ፈቃጅ የሆነ የህግ ድንጋጌ በመሆኑ ዳኞች ውሉ እንዲፈርስ ሣይወስኑ ሊያልፉ የሚችሉ መሆኑንም የሚያመለክት ድንጋጌ ነው።

በአንፃሩ ዳኞች በአንደኛው ወገን ጠያቂነት ውል እንዲሰረዝ ውሣኔ ከመስጠታቸው በፊት የተዋዋዩቹን ጥቅምና ለቅን ልቦና የሚያስፈልገውን ነገር መሠረት ማድረግ እንደሚገባቸው በውሉ ላይ አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ካልተደረገ በስተቀር ዳኞች ውሉ እንዲሰረዝ ውሣኔ መስጠት እንደሌለባቸው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ይደነግጋሉ። አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካች ውሉ በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት የሚከራከሩት ተጠሪዎች መሠረታዊ የሆነ የውል መጣስ ተግባር ፈፅመዋል በማለት ምክንያት በመሆኑ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከአንደኛ ተጠሪ ጋር በተዋዋሉት ውል የተጠሪዎች ግዴታና ኃላፊነት ምንድን ነው? ተጠሪዎች በውሉ የገቡት ግዴታ ምን ያህል ፐርሰንቱን ፈፅመው ምን ያህል ፐርሰንት ይቀራቸዋል? ተጠሪዎች ቀሪውን ግዴታቸውን ያልፈፀሙበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚሉት ነጥቦች ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከደረሰበት መደምደሚያና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመርህ ደረጃ ተዋዋዮች ውል የመዋዋል ነፃነት አላቸው፡፡ ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በስተቀር ተዋዋዮች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት አላቸው በማለት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1711 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተዋዋዮች ለሚዋዋሉት ሰው በአንድ ነገር ላይ ያላቸውን መብት ለመስጠት ወይም አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ሊዋዋሉ እንደሚችሉና ውሎች አስገዳጅነታቸው በውሉ በተነገረው ጉዳይ ብቻ ሣይሆን ልማድ፤ ፍትሕ፣ ቅን ልቦና የውለታው ዓይነት የሚያስከትሏቸውን ነገሮች ጭምር እንደሆነ ከፍታብሔር ቁጥር 1712 እና ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1713 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾችና ተጠሪዎች ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም.በተደረገው ውል ያለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት ከላይ የተጠቀሱን የህግ ድንጌጋዎች መሠረት በማድረግ መመርመር ተገቢ ነው፡፡

በውሉ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሆቴል ንግድ ድርጅት ህንፃውንና በድርጅቱ ውስጥ ያሉትን የመገልገያ እቃዎች ላይ የነበራቸው የባለሀብትነት መብት ለአንደኛ ተጠሪ ለማስተላለፍ የተስማሙ መሆኑና አንደኛ ተጠሪ በበኩሉ በንግድ ድርጅቱና በህንፃው ላይ ያለውን ዕዳ ለባለመብቶች ለመክፈልና ለሻጮች ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን ብር/ ለመክፈል የተስማማ መሆኑን ግራ ቀኙ ያልተካካዱበትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሣኔው ያረጋገጠው ነጥብ ነው፡፡ ተጠሪዎች በውሉ ሁለት መሠረታዊ ግዴታዎች ተጥሎባቸዋል፡፡ የመጀመሪያው በንግድ ድርጅቱና በህንፃው ላይ ያለ የባንክ ዕዳ እና ሌሎች ያልተከፈሉ ውዝፍ ዕዳዎችን መክፈል ሲሆን ሁለተኛው ለሻጮች ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን ብር/ መክፈል ነው፡፡ ተጠሪዎች ለሁለተኛና ሶስተኛ አመልካች ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የከፈሉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪዎች የዕዳው መጠን በውሉ ላይ ያልተገለፀ ቢሆንም ከብር 6,450,000 /ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ በላይ የንግድ ድርጅቱንና የህንፃውን የባንክ ዕዳ፣ ሌሎች የውሃ፣ የመብራት የስልክና ሌሎች ውዝፍ ዕዳዎች የከፈሉ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣኑን መሠረት በማድረግ አረጋግጦ በውሣኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡

ይህም ተጠሪዎች በውል ከገቡት ግዴታ ከሰማኒያ አምስት ፐርሰንት በላይ የፈፀሙ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ተጠሪዎች በውሉ ከተጣለባቸው ግዴታቸው አብዛኛውን ክፍል የፈፀሙ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚው ችሎት አረጋግጧል፡፡ ተጠሪዎች አይነተኛ የሆነ የውል ግዴታቸውን ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም የሚለው ነጥብ የሚመዘነው ተጠሪዎች በውል መሠረት ለመፈፀም ከተስማሙባቸው ሁለት መሠረታዊ ግዴታዎች ምን ያህሉን ፈፅመው ምን ያህል ይቀራቸው የሚለውን በመመዘን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በማውጣት በውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት የገዙት የንግድ ድርጅት ከነበረበት ዕዳ የከፈሉት ተጠሪዎች ለእኛ ሊከፍሉ ከተስማሙት ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን ብር/ ውስጥ የከፈሉት ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ብቻ በመሆኑ መሠረታዊ የውል መጣስ ተግባር ፈፅመዋል በማለት አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎችን ይዘት መንፈስና ዓላማ መሠረት ያላደረገና ከቅን ልቦና ውጭ የቀረበ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪዎች በሽያጭ ውሉ የገቡትን አይነተኛ ግዴታቸውን የተወጡና ቀሪውን ግዴታቸውን እንዳይወጡ ችግር የፈጠሩት አንደኛ፣ ሁለተኛ ሶስተኛ አመልካቾች መሆናቸውን በማስረጃ በማረጋገጥ ውሉ በፍርድ ቤት ውሣኔ የሚሰረዝበት ምክንያት የለም በማለት የሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1784 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ድንጋጌዎች ላይ የጠቀስናቸውን ሌሎች የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

3. የሟች ወ/ሮ ነጠረች ከበደ ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው በክርክሩ አራተኛ አመልካች ወ/ሮ ነጠረች ከበደን በመተካት ተካፋይ የሆኑት ወ/ሮ አሰገደች አበበ ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ከተጠሪዎች ጋር የዕርቅ ስምምነት ፈፅመውና ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ከተጠሪዎች ጋር በጋራ ማመልከቻ ጽፈውና ፈርመው ከተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት እንዲመዘገብላቸው ሰኔ 15 ቀን, ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም.፣ እና ሰኔ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ለችሎቱ በአካል ቀርበው አመልክተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ አመልካቾች አስተያየት እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሶስተኛ አመልካች ዳዊት ከበደ እኔም የሟች ነጠረች ከበደ ወራሽ ስለሆንኩ የዕርቅ ስምምነቱ የእኔን መብት ይነካል በማለት ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም የዕሑፍ አስተያየት ሰጥቷል፡፡ ወ/ሮ አሰገደች አበበ ዕርቁን ትቸዋለሁ ፍርድ ቤቱ ክርክሩ እንዲቀጥል ያድርግልኝ በማለት ሀምሌ 19 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ አስተያየት ያቀረቡ ሲሆን ይህንኑ ታህሣሥ 20 ቀን 2004 ዓ.ም በአካል ለችሎቱ ቀርበው አረጋግጠዋል፡፡ ተጠሪዎች ዕርቁ የማይመዘገብበት ምክንያት የለም፡፡ ለህግም ሆነ ለሞራል ተቃራኒ አይደለም በማለት መስከረም 2 ቀን 2004 ዓ.ም የዕሑፍ አስተያየት አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወ/ሮ አሰገደች አበበ ዕርቁ እንዲመዘገብላቸው ከጠየቁ በኋላ ዕርቁን ትቸዋለሁ ማለት አይችሉም፡፡ የዕርቅ ውሉ ተመዝግቦ ህጋዊ ውጤት ሊሰጠው ይገባል በማለት የተጠሪዎች ጠበቃ ታህሣሥ 20 ቀን 2004 ዓ.ም ለችሎቱ በቃል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

እኛም ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገውን የዕርቅ ስምምነት ይዘት መርምረናል፡፡ በዕርቅ ስምምነቱ ወ/ሮ አሰገደች አበበ ከወ/ሪት ነጠረች ከበደ በውርስ የሚተላለፍላቸውን መብት ወይም በራሳቸው የሚደርሳቸውን መብትና ጥቅም ለተጠሪዎች ለማስተላለፍና ተጠሪዎችም ለወ/ሮ አሰገደች አበበ ብር 550,000 /አምስት መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ ለመክፈል ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት የሟች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ወራሽነትን አረጋግጠው የሚመጡ ሌሎች መብት የማይመለከትና ወ/ሮ አሰገደች አበበ የሟች ነጠረች ከበደ ወራሽ መሆናቸው በራሳቸው ያላቸውን መብትና ጥቅም ለተጠሪዎች ለማስተላለፍ የተደረገ በመሆኑ ሶስተኛ አመልካች የዕርቅ ስምምነቱ የእኔን ጥቅም ይነካል በማለት ያቀረበውን ተቃውሞ አልተቀበልነውም፡፡ ወ/ሮ አሰገደች አበበ ከተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት እንዲመዘግብላቸው ለችሎቱ ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓ.ም፣ ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም እና ሰኔ 23 ቀን 2003 ዓ.ም በአካል እየቀረቡ ካመለከቱ በኋላ የዕርቅ ስምምነቱን ትቸዋለሁ በማለት በዕሑፍና በቃል ያቀረቡት አስተያየት የዕርቅ ስምምነቱን ውድቅ ለማድረግ በቂ ምክንያት ባለመሆኑና የዕርቅ ስምምነቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ሆኖ ስላላገኘነው የአራተኛ አመልካች ወራሽ ወ/ሮ አሰገደች አበበ ከተጠሪዎች ጋር ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉትን የዕርቅ ስምምነት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 277/ሰ/ መሠረት በመመዝገብ የዕርቅ ስምምነቱ በወ/ሮ አሰገደች አበበና በተጠሪዎች መካከል አስገዳጅና ህጋዊ ውጤት ያለው ነው በማለት ወስነናል፡፡

4. አራተኛው ጭብጥ በሥር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የነበረችው አራተኛ አመልካች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረጉት የንግድ ድርጅትና የህንፃ ሽያጭ ውል እንዲፈርስ ያቀረቡትን ጥያቄ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ ይህንን ነጥብ ለመወሰን ወ/ሪት ነጠረች ከበደ የሟች አቶ ከበደ ዘለቀ ልጅና ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ የወራሽነት የምስክር ወረቀት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያገኘችው የንግድ ድርጅቱና የህንፃ ሽያጭ ውሉ ከመደረጉ በፊት ነው ወይስ በኋላ የሚለውን ነጥብ ማየቱ ተገቢ ነው።

ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ የሚች አቶ ከበደ ዘለቀ ልጅና ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ የወራሽነት የምስክርነት ወረቀት ከማግኘቷ በፊት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 996 መሠረት የሚች አቶ ከበደ ዘለቀ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን በፍርድ ቤት ውሣኔ ያረጋገጡት ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የንግድ ድርጅቱን እና ህንፃውን ለአንደኛ ተጠሪ የሰጡ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማረጋገጥ በውሣኔው አስፍሮታል። ይህም የሚያሣየው የፀና የወራሽነት ማስረጃ ያላቸው ሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛ አመልካች የሚች ከበደ ዘለቀ የውርስ ንብረት ክፍል የሆነውን የንግድ ድርጅትና ህንፃ ለአንደኛ ተጠሪ ከሸጡት በኋላ ወ/ሪት ነጠረች ከበደ የሚች ከበደ ዘለቀ ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ያገኙት መሆኑን ነው። ይግባኝ ሰሚው ችሎት ያረጋገጡትን ይህንን ፍሬ ጉዳይ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 997 ድንጋጌዎች አንፃር የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው የሚለውን ተመልክተናል። ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 996 ጋር ተያያዥነት ያለውና የዚሁ ድንጋጌ ተከታይ የሆነው የፍታበሔር ሕግ ቁጥር 997 "ውጤቶች" በሚል ርዕስ የወራሽነት ሰርተፊኬት መያዝ የሚያስከትላቸውን ህጋዊ ውጤቶች ይደነግጋል። የወራሽነት ወረቀቱ እስካልተሰረዘ ድረስ ወራሽ በተባለው የምስክር ወረቀት እንደተገለፀው ወራሽ እንደሆነ የሚገመት መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 997 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደግጋል። ከዚህ አንፃር ስናየው ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካች የሚች ከበደ ዘለቀ የኑዛዜ ወራሽ ናቸው የሚለውን የፍርድ ቤት የወራሽነት ማረጋገጫ እስከያዙና ይኸው የወራሽነት ማስረጃቸው እስካልተሰረዘ ድረስ የሚች ከበደ ዘለቀ ወራሾች ናቸው ብሎ ህጉ ግምት የሚወስድበት መሆኑን ነው።

ከዚህ በተጨማሪ " በወራሽነት ስም በወራሹ የተፈፀሙ ተግባሮች ያሉ እንደሆነ ተግባሮቹ በተፈፀሙበት ጊዜ የተባለው ወራሽ የወራሽነት መብት እንዳልነበረው በግልፅ ማወቁ ካልተረጋገጠ በቀር እነዚህን ተግባሮች ለመቃወም የማይቻል" መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 997 ንዑስ አንቀፅ 2 አስገዳጅነት ባለው መንገድ ይደነግጋል። ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው ሚች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሚች ከበደ ዘለቀ ወራሽ ስለመሆናቸው የፀና የወራሽነት የምስክር ወረቀት አግኝተዋል። ይህንን የፀና የወራሽነት ማስረጃ በመያዝ የንግድ ድርጅቱንና ህንፃውን አንደኛ ተጠሪ ለመሸጥ የተዋዋሉትን ውል እንዲፈርስ ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ለመጠየቅ የምትችለው ተጠሪዎች ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሚች አቶ ከበደ ዘለቀ ወራሾች አለመሆናቸውን እያወቁ ውል የተዋዋሉ መሆኑን በማስረጃ በማስረዳት ብቻ እንደሆነ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 997 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ይዘት ለመገንዘብ ይቻላል።

ወ/ሪት ነጠረች ከበደ እኔ የሚች ከበደ ዘለቀ ልጅና ወራሽ ነኝ የሚል ክርክር ከሚያቀርቡ በስተቀር ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሚች ከበደ ዘለቀ የኑዛዜ ወራሾች አይደሉም። አንደኛ ተጠሪ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የሚች ከበደ ዘለቀ ወራሽ አለመሆናቸውን እያወቀ የንግድና የህንፃ ሽያጭ ውል ተዋውሏል የሚል ክርክር አላቀረቡም። ይህንንም የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳላቀረቡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከሰጠው ውሣኔ ተገንዝበናል። ይህም በመሆኑ ሚች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ የሚች ከበደ ዘለቀ ልጅና ወራሽ መሆኑ በፍርድ ቤት ከመረጋገጡ በፊት የፀና የወራሽነት ማስረጃ በመያዝ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረጉት የንግድ ድርጅትና የህንፃ ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት የላትም። በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ችሎት አራተኛ አመልካች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ከአንደኛው ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት የላትም በማለት የሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 996 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 997ን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም አራተኛ አመልካች የነበረችው ወ/ሪት ነጠረች ከበደ በዚህ መዝገብ በክርክር በተያዘው ጉዳይ ያላት መብት የሚች ከበደ ዘለቀ የውርስ ንብረት ክፍል የሆነውን የንግድ ድርጅትና ህንፃ የሸጡት ሁለተኛ አመልካችና ሶስተኛ አመልካች ንብረቱን ሸጠው ካገኙትና ወደ ፊትም በውሉ መሠረት ከሚያገኙት የንብረቱ ዋጋ ከሆነው ገንዘብ ውስጥ በድርሻ መጠን እንዲያካፍሏት መጠየቅ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የሆቴል ንግድ ድርጅትና የህንፃ ሽያጭ ውል የሚሰርዝበትም ሆነ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 27497 መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. የአራተኛ አመልካች ወራሽ የሆኑት ወ/ሮ አሰገደች አበበና ተጠሪዎች ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የዕርቅ ስምምነት ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ባለመሆኑ ፀድቋል፡፡
3. ተጠሪዎች ለወ/ሮ አሰገደች አበበ በዕርቅ ውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት ብር 550,000 /አምስት መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ ይክፈሉ፡፡
4. የአራተኛ አመልካች ወ/ሪት ነጠረች ከበደ ወራሽ የሆኑት የወ/ሮ አሰገደች አበበ በዚህ መዝገብና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ያላቸው መብትና ጥቅም በዕርቅ ውሉ መሠረት ወደ ተጠሪዎች ተላልፏል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 64397

ጥር 01 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አንዳርጌ እምሩ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ዘሀራ መሀመድ - የቀረበ የለም
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ቴሌቭዥርን ከነሲዲው ተጠሪ እገዛልሃለሁ በማለት ተቀብላኝ ዕቃውም ተገዝቶ ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ ገንዘቡም አልተከፈለኝም በሚል የቀረበ ክስ ሲሆን የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 10/11/12 ማህበራዊ ፍርድ ቤት በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ ተከሳሽ መስከረም 17 ቀን 2001 ዓ.ም. በከሳሽ ቤት መጥተው አንድ ባለ 21 ኢንች ሶኒ ቴሌቪዥርን ከነሲዲው ቀረጡን ጨምሮ በብር 4750(አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ) ገዝቼ አመጣልሃለሁ ብለውኝ በምስክሮች ፊት ገንዘቡን ቆጥሬ ሰጥቼያቸው ቴሌቪዥኑን ያላስረከቡኝ ሲሆን ገንዘቡም እንዲሰጠኝ ብጠይቃቸው ወይም ዕቃውን እንዲያስረክቡኝ ብጠይቃቸው ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ዕቃውን እንዲያስረክቡኝ ወይም ገንዘቡን እንዲመልሱልኝ እንደዚሁም በክሱ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍሉኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ በቀረበው ክስ ላይ ተከሳሽ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዙት መሰረት መጥሪያ ተልኮላቸው ለመቀበል ፍቃደኛ ያለመሆናቸውን ከሳሽ በቃለ መሓላ ማረጋገጣቸውን በማመልከቱ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌሉበት እንዲታይ ትእዛዝ ተሰጥቶ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር ፍርድ ሰጥቷል፡፡ የሰጠውም የፍርድ ይዘት ተከሳሽ በቀረበው ክስ ላይ ቀርበው መልስ ያለመስጠታቸው የቀረበውን ክስ እንዳመኑ ስለሚቆጠር ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍሉ በማለት በአሁኑ ተጠሪ ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በቀጥታ ይግባኛቸውን ለከተማው አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የቀረበውን ቅሬታ ከመረመረ በኋላ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 337 መሰረት አጽንቷል፡፡ በዚህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በፍትሐ ብሔር ህግ ቁ. 2472(1)(2) መሰረት ከብር 500 (ብር አምስት መቶ) በላይ የሆነ ብድር በጽሑፍ፣ በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም ቃለ-መሓላ ካልሆነ በስተቀር በሰው ምስክር ማስረዳት እንደማይቻል፤ በተመሳሳይም ከብር 500 በላይ ከፍያለሁ በማለት የሚቀርበው ክርክር ይሄው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን በማመላከት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን ከቀረበባቸው ክስ በነጻ በማሰናበት በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩም ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች ቴሌቪዥን እና ሲዲ ገዝተው እንዲያመጡላቸው ለተጠሪ የሰጡትን ብር 4750 (አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) በሰነድ እንጂ በሰው ማስረጃ ማረጋገጥ አይቻልም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል የነበረ በመሆኑ ጉዳዩን ከዚሁ አኳያ ተመርምሮ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ስንመረምር የአሁን ተጠሪ በክሱ እንደተመለከተው ገንዘቡን የተቀበሉት ቴሌቪገርን እና ሲዲ ገዝቼ አመጣልሃለሁ በማለት እንጂ በብድር ምክንያት ያለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይም ተፈጻሚነት ያለው ከዚሁ ብድር ጋር በተያያዘ መልሼ ከፍያለው የሚል ተከራካሪን የሚመለከት እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ በግራ ቀኙ መካከል ብድርን መሰረት ያደረገ ክርክር በሌለበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ህግ ቁ.2472 ን በመጥቀስ ከብር 500 በላይ የሆነን የገንዘብ መጠን በሰው ምስክር ማስረዳት አይቻልም ወደ ሚለው መደምደሚያ መድረሱ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት አነስተኛ ድምጽ አስቀምጦት የነበረው ሃሳብ አግባብነት የነበረው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ተጠሪ መጥሪያ ለመቀበል ፍቃደኛ ያለመሆናቸው ተገልጾ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ በመስጠቱ የቀረበውን ክስ ከሳሽ በቆጠረው ምስክር ተከሳሽ ባይቀርቡም በመስማት እና ጉዳዩን በማጣራት ውሳኔ መሰጠት ሲገባው የተጠሪ ያለመቅረብ ጉዳዩን እንዳመኑ የሚያስቆጥር ባለመሆኑ ክሱን እንዳመኑት ይቆጠራል በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

ባጠቃላይ በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ቴሌቪገርን እና ሲዲ ለመግዛት ተጠሪ 500 ብር የተቀበሉ መሆኑን እንጂ የብድር ገንዘብ ስለመሆኑ ባልተነሳበት ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለውን የብድር ውል እና ክፍያ የተመለከተን ድንጋጌ በመጥቀስ ከብር 500 (ብር አምስት መቶ) በላይ በሰው ምስክር ማስረዳት አይቻልም በማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የደረሰበት መደምደሚያ እንደዚሁም ጉዳዩን በመጀመሪያ ተመልክተው የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቀርበው መልስ ያለመስጠታቸው ወይም ጉዳዩ በሌሉበት በመታየት ክሱን እንደማመን ይቆጠራል በማለት የሰጠውም ውሳኔ በተመሳሳይ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.14696 በቀን 07-04-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ በፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.04417 ህዳር 07 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 10/11/12 ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.016/03 መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የተከሳሽ በአንድ ክስ ላይ ቀርቦ ያለመከራከር ወይም የጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት መታየት የቀረበው ክስ ክሱን ሊያስረዱልኝ ይችላሉ በማለት ከሳሽ በክሳቸው በመዘርዘር ያቀረቡትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምስክሮች ብቻ በመስማት እና ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ ከሚሰጥ ውጪ የተከሳሽ ያለመቅረብ ጉዳዩን እንዳመኑት ይቆጠራል በማለት በክሱ መሰረት ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በክሱ ላይ የቆጠራቸው ምስክሮች ተሰምተው እና ለፍትህ አሰጣጡ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የማህበራዊ ፍርድ ቤቱ ያመነባቸውን ማስረጃዎች በመቀበል ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 71375

ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዳሽን የህትመትና የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ነ/ፈጅ አቶ ትዕዛዙ

ዓለማሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ፍስሐ ይሁን - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ የሰበር አመልካች በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ከተከሳሽ ጋር ባደረግነው ውል ከሳሽ ለተከሳሽ ፍስሐና ስራው የሚል መፅሐፍ 300 ቅጂ ለማዘጋጀትና ተከሳሽም ለከሳሽ ብር 50,000 (ሀምሳ ሺህ ብር) ለመክፈል የተስማማን ሲሆን በስምምነታችን መሰረት ተከሳሽ ቅድመ ክፍያ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) ከፍሎ መጽሐፎቹን ከሳሽ አዘጋጅቼ ባጠናቅቅም ቀሪውን ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) ሳይከፍለኝ ከአንድ ዓመት በላይ ስለቆየ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ሞቷል በመባሉ ወራሾች ካሉ ቀርበው ለክሱ መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ በተከሳሽ ቤት ተለጥፎ ወራሾች ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት ቀጥሎ የመ/ደ/ፍ/ቤቱ መዝገቡን በመመርመር በሰጠው ፍርድ ከሳሽ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ሁሉም በከሳሽ የተጻፉ ናቸው፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች ደግሞ እንደ ማስረጃ ሆነው የሚቀርቡት በራሱ በከሳሽ እንጂ በተከሳሽ ላይ አይደለም፡፡ ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ግዴታ ስለመኖሩ በማንኛውም ማስረጃ በበቂ ሁኔታ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ በመካከላቸው አስገዳጅ ውል መኖሩን ባላስረዳበት እንደውሉ እንዲፈጸምለት ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ መልስ ሰጪን መጥራት ሳያስፈልግ የይግባኝ ባይን የይግባኝ መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አመልካችም በመ/ደ/ፍ/ቤት ፍርድም ሆነ በከ/ፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅሬታ የህትመት ስራ ውል በቃል ጭምር ማድረግ የሚቻል ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሊያስገድዳቸው የሚችል የጽሁፍ ውል የለም ሲሉ ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

በሰበር ደረጃም የተጠሪው ወራሾች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ የፍ/ቤቱ መጥሪያ የደረሳቸው ቢሆንም ቀርበው መልስ ባለመስጠታቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

አመልካች ያቀረበው ክርክርና በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ፍርድ ከዚህ በላይ የተገለጸ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በስር ተከሳሽ መካከል አስገዳጅ ውል ስለመኖሩ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የለም ሲሉ ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ለስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሉ ስለመኖሩ በማስረጃነት ያቀረባቸው የጽሁፍ ሰነዶች ቅድመ ክፍያና ተጨማሪ ክፍያ ከተከሳሽ የተቀበላቸውን ደረሰኞችና አመልካች ለተከሳሽ የጻፈውን የዋጋ ማቅረቢያ ነው፡፡ ከእነዚህ ሰነዶች በስተቀር ውሉ በጽሁፍ የተደረገ ስለመሆኑ ያቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ የለም፡፡ በፅሁፍ የተደረገውን ውል አለማቅረብ ደግሞ በውል ሰጪና ውል ተቀባይ መካከል ውል የለም ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በፍ/ህ/ቁ/1681(1) እንደተደነገገው ውል በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ለውሉ መነሻ ከሆነው ምክንያት የተነሳ ግዴታ መግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ጭምር መግባት ስለሚቻል ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ሁሉም የውል ዓይነቶች በቃል ወይም በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ግዴታ ለመግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ይደረጋሉ ማለት አይደለም፡፡ ለዚህም የ/ፍ/ህ/ቁ/1725ን መመልከት ተገቢነት አለው፡፡ በዚህ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት ለብዙ ጊዜ የሚቆዩ ውሎች፤ እንዲሁም የዋስትና ውሎች፤ የኢንሹራንስ ውሎች እና ህጉ በግልጽ በጽሁፍ እንዲደረጉ የሚያስገድዳቸው የውል ዓይነቶች ሁሉ በጽሁፍ መደረግ አለባቸው፡፡

ይህንኑ የህግ አነጋገር ይዘን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ከስር ተከሳሽ ጋር ገብተናል በሚለው የህትመት ስራ ውል ውሉ በፅሁፍ እንዲሆን የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ አመልካች ከስር ተከሳሽ ጋር ገብተናል የሚለው ውልም በገቡት ውል መሰረት 300 ቅጂ መጽሀፎችን አባዝቶ ከመስጠት ያለፈና ለረጅም ጊዜ ይቆያል ተብሎ የማይገመት በመሆኑ የውሉ በጽሁፍ መሆን የግድ የሚያስፈልግ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረባቸውን አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመመርመር እንዲሁም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/264(2) እንደተደነገገው ውሉ ከዚህ በላይ በተጠቀሱ መንገዶች የተደረገ መሆን ስላለመሆኑ፣ በውል ሰጪና ውል ተቀባይ መካከል አለ ስለተባለው የውል ግንኙነት አመልካች ባቆይቆጠራቸውም እንኳን ምስክሮችን መስማት ጠቃሚ መስሎ ከታየ አስቀርቦ መስማት በጉዳዩ ላይ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮችን በአግባቡ አጣርተው ተገቢውን ፍርድ መስጠት ሲገባቸው ይሄንኑ በማለፍ አመልካች አስገዳጅ ውል መኖሩን አላስረዳም በሚል ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ባለመሆኑ የሰጡት ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 69348 በቀን 26/08/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 110517 በቀን 23/10/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካች ከስር ተከሳሽ ጋር አድርገናል በሚለው የህትመት ውል መሰረት ፍስሐና ስራው የሚል 300 ቅጂ መጽሐፎችን ማዘጋጀቱንና አለማዘጋጀቱን የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 272 መሰረት ምትክ ዳኛ እስከ ቦታው ድረስ በመላክ ምትክ ዳኛው ተገቢውን ምርመራ አድርገው በሚያቀርቡት የምርመራ ውጤት መሰረት የበኩሉን ፍርድ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጥ ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/343 (1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሱን ይቻል ብለናል፡፡
   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 69208

መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገብረስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካች፡- ወ/ሮ ንፁህ በላይ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ምንትዋብ አዳነ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደብረ ማርቆስ ወረዳ ፍርድ ቤት ፣ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የቤት ሽያጭ ውል የጠፋ መሆኑን በምስክር ለማስረዳት የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በደብረማርቆስ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ ፣ በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆነው አቶ እንዳወቅ አያሌው ተከሣሽ አመልካች ጣልቃ ገብ ተከራካሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ አቶ እንዳወቅ በማላውቀው ሁኔታ እቤቱ ውስጥ ገብቶ እየኖረ ስለሆነ ቤቱን እንዲለቅና የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡ አቶ እንዳወቅ ቤቱን ያከራዩት አመልካች መሆኑን ገልፆ በክርክሩ ጣልቃ እንድትገባ ጠይቋል፡፡ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብታ ቤቱን አሁን በህይወት ከሌለው ባለቤቷ አቶ አየነው ድርሻ በ2000 ዓ.ም ከተጠሪ ገዝተው ፣ ለሥር ተከሣሽ በውል ያከራዩት መሆኑን በመግለፅ የተከራከረች ሲሆን የሽያጭ ውሉ የጠፋ ቢሆንም ፣ ለቤቱ መብራትና ውሀ አስገብቻለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723/1/ መሠረት የሽያጭ ውል አላቀረቡም በማለት አመልካች ለተጠሪ ቤቱን ለቅቀው እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የተጠሪን ቃለመሃላ ከሰማ በኋላ እንደዚሁም የሰነድ ማስረጃው ይገኝባቸዋል ከተባሉ መስሪያ ቤቶች የተሰጠውን ምላሽ በማገናዘብ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ክስ ያቀረበችበትን ቤት በሚች ባለቤቱ አየነው ድረስ ስም ብር 38,000 /ሰላሣ ስምንት ሺህ ብር/ ተጠሪ ሸጣልን ፣ ገንዘቡን ከፍለን ቤቱን ተረክበን ኖረናል፡፡ ቤቱን ከተረከብን በኋላ በብር 30,000 ወጭ በማድረግ አድሰናል፡፡ መብራትና ውሀ በሚች ባለቤቱ አቶ አየነው ድረስ ስም አስገብተናል፡፡ የሽያጭ ውሉ ባለቤቱ አቶ አየነው ድረስ በመሞቱ ምክንያት የጠፋ በመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2003 እንዳስረዳ ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ መደረጉና የቤት ኪራይ ብር 2850 /ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሣ ብር/ እንዲከፍል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

ተጠሪ ነሐሴ 28 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቱን ለአመልካችም ሆነ ለሚች ባለቤቷ የቤቱ ባለሃብት የሆንኩት ተጠሪ አልሸጥኩላቸውም፡፡ አመልካች ቤቱ የተሸጠላቸው መሆኑን ያቀረቡት የፅሁፍ ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ቤት አድሻለሁ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተጠሪን የማይመለከትና በማስረጃ ያልተደገፈ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች መስከረም 15 ቀን 2004 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ ማለትም አመልካች ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ የተዋዋለችበት ሰነድ የጠፋ መሆኑን በምስክር ለማስረዳት ያቀረበችው ጥያቄ መታለፉ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሣሽነት ሣይሆን ቤቱን ከእሷ ተከራይቶ ይዞት ለነበረው አቶ እንዳወቅ አያሌው መድን በመሆን ጣልቃ ገብተው በክርክሩ የተሣተፉ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካች ተጠሪ ክስ ያቀረበችበትን ቤት በ2000 ዓ.ም ሚች ባለቤቷ አየነው ድረስ በውል የገዛ መሆኑና የሽያጭ ውሉ ሚች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የጠፋ መሆኑን በመጥቀስ ሰነዱ የጠፋ መሆኑንና ቤቱን በውል የገዛች መሆኑን ለማስረዳት ያቀረበችውን ጥያቄ የወረዳው ፍርድ ቤትም ሆነ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አልተቀበሉትም፡፡ ውል መኖሩን በማንሣት የሚከራከር ሰው የውል ግዴታው መኖሩን የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2001 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ በመሆኑ ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ቤቱን ከተጠሪ በውል የገዛችው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለባት በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው፡፡ የቤት ሽያጭ ውል በፅሑፍ ሊደረግ የሚገባው መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723/1/ እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2877 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

በመርህ ደረጃ በፅሑፍ መደረግ ያለባቸውን ውሎች ለማስረዳት የሚቻለው በፅሑፍ የተደረገውን ውል በማቅረብ መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2008 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ከተከታይ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ አጠቃላይ መርህ እንዳለ ሆኖ በልዩ ሁኔታ በፅሁፍ የተደረገን ውል በምስክሮች ወይም በህሊና ግምት ለማስረዳት የሚችልበት ሁኔታ ያለ መሆኑን “ውሉ በፅሑፍ እንዲሆን ሕግ ባዘዘ ጊዜ ይህ ፅሑፍ የተቀደደ ፣ የተሰረቀ ፣ የጠፋ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ውሉን በምስክሮች ወይም በህሊና ግምት ለማስረዳት አይችልም ” በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2003 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አቀራረፅና ይዘት አንድ ሰው በመጀመሪያ በፅሑፍ የተደረገው ውል የተቀደደበት የተሰረቀበት ወይም የጠፋበት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረብ ውሉ የተሠረቀ፣ የጠፋ ወይም የተቀደደ መሆኑን በበቂ ሁኔታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለፍርድ ቤቱ ካስረዳ በፅሑፍ የተደረገውን ውል በምስክሮች ቃል ወይም በህሊና ግምት እንዲያስረዳ የሚፈቀድለት መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ሟች ባለቤቷ አየነው ድረስ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ፣ ሟች ባለቤቷ አየነው ድረስ ከተጠሪ ቤቱን ለመግዛት ተዋውሎት የነበረው የቤት ሽያጭ ውል የጠፋበት ስለመሆኑ በምስክሮች ለማስረዳት ያቀረበችው ጥያቄ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2003 ድንጋጌን መሠረት ያደረገና የህግ መሠረት ያለው ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት በመጀመሪያ አመልካች ሟች ባለቤቷ አከራካሪውን ቤት ከተጠሪ ለመግዛት የተዋዋለው የፅሑፍ ውል የጠፋበት ስለመሆኑ የምታቀርባቸውን ምስክሮች በመስማት የፅሑፍ ውሉ የጠፋ መሆኑን አስረድታለች ወይስ አላስረዳችም? የሚለውን ጭብጥ መወሰንና ውሉ የጠፋ መሆኑን አመልካች በበቂ ሁኔታ አስረድታለች የሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ አመልካች በሟች ባለቤቷ አየነው ድረስና በተጠሪ መካከል የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል በምስክሮች ቃልና በህሊና ግምት እንድታስረዳ በመፍቀድ ማስረጃውን በመሰማትና በመመርመርና በመመዘን መወሰን ሲገባው ፣ አመልካች የሽያጭ ውል አላቀረበችም በማለት ቤቱን ለተጠሪ እንድታስረክብ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የዞኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች ያቀረበችውን ጥያቄ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2003 መሠረት በማድረግ መመርመርና መወሰን ሲገባው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2002 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ የተጠሪን ቃለመሃላ ሰምቶ ውሣኔ መስጠቱ የአመልካችን መብት ያጣበበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ከላይ የዘረዘርናቸው የህግ ስህተቶች ሣያርም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የወረዳው ፍርድ ቤት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2003 ድንጋጌ አመልካች ያላትን መብት የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደብረ ማርቆስ ወረዳ ፍርድ ቤትና ፣ የምስራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የደብረ ማርቆስ ወረዳ ፍርድ ቤት ፣ በመጀመሪያ አመልካች ሟች ባለቤቷ አቶ አየነው ድረስና ተጠሪ በፅሑፍ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የጠፋባት መሆኑን ለማስረዳት የምታቀርባቸውን ማስረጃዎች በመስማት፣ በመመርመርና በመመዘን አመልካች ውሉ የጠፋ መሆኑን በበቂ ሁኔታ አስረድታለች ብሎ ካመነ አመልካች የሽያጭ ውሉን በምስክሮች ቃልና በህሊና ግምት እንድታስረዳ በማድረግና የተጠሪን የመከላከያ ማስረጃ በመስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 72463
መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. አቶ ንጉሴ ሀይሌ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ማሚቱ ለታ

መልስ ሰጭዎች፡- 1. አቶ ሁሬሣ ደበል } ጠበቃ አቶ ታዬ ባንጃው ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሌሊሴ ራያ }

መዝገቡን መርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፊንፊኔ ዙሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሣሽ ተጠሪዎች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል ጉዳዩ ወለድ አገድ ውልን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካቾች ከተጠሪዎች ጋር መስከረም 28 ቀን 03 ዓ.ም ያደረጉት የወለድ አገድ ስምምነት ቁጥሩ 777 የሆነውን ቤትና ሌሎች ሁለት ክፍል ቤቶች ተጠሪዎች በወለድ አገድ በመያዝ እንዲጠቀሙበት አስረክበው ለአንድ አመት የሚቆይ 2500 /ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ መበደራቸውን ገልፀው፣ ተጠሪዎች ገንዘቡን ወስደው ቤቱን እንዲለቁ ቢጠይቋቸው ፈቃደኛ ስላልሆኑ ገንዘቡን ወስደው ቤቱን እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ አይታገድም ተከሣሾች /ተጠሪዎች/ ገንዘቡን ወስደው ቤቱን ለከሣሾች /አመልካቾች/ ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ብድሩን ለመመለስ የተስማሙት መስከረም 28 ቀን 1984 ዓ.ም በመሆኑ ውሉ በይርጋ ይታገዳል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበው አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡ አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ የውሉን ልዩ ባህሪ ያላገናዘበና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3128 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያመለከቱ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው አመልካቾች በአንድ ዓመት ውስጥ ለመመለስ የገቡትን የብድር ውል ሣይፈጽሙ ከአስራ ስድስት ዓመት በኃላ በመጠየቃቸው ክሱ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1845 በይርጋ ይታገዳል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ "ወለድ አገድ" ማለት አንድ ባለእዳ ግዴታውን ለመፈፀም ማረጋገጫ በማድረግ ለገንዘብ ጠያቂው የማይንቀሣቀስ ንብረት ለማስረከብ የሚገደድበት ውል መሆኑ በፍታብሔር ህገ ቁጥር 3117 ተደንግጓል፡፡ የወለድ አገድ፣ ውል የሚኖረውን ውጤት በተመለከተ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3124 የተደነገገ ሲሆን ማንም ሰው በወለድ አገድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ካስያዘ ወለድ አገድ የተቋቋመበትን ግዴታ በመፈፀም በማናቸውም ጊዜ ወለድ አገድ እንዲቀር ማድረግ እንደሚችል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3128 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3128 ንዑስ አንቀጽ 2 "እንዲሁም ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር የተባለው ወለድ አገድ የተቋቋመበትን ግዴታ በመፈፀም ባለእዳው በማናቸውም ጊዜ ወለድ አገዱ እንዲቀር ለማድረግ ይችላል" በሚል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ "ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር" የሚለውን ሀረግ ሲተረጉም የልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የድንጋጌውን መንፈስ አላማና ይዘት መሠረት ባደረገ ሁኔታ መተርጎም ሲገባው ይህንን አላደረገም፡፡ በዚህ ድንጋጌ "ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር" የሚለው አመልካቾች እስከ መስከረም 28 ቀን 1984 ቤቱ ተጠሪዎች በወለድ አገድ እንዲያዝ የተስማሙ ስለሆነ ከመስከረም 28 ቀን 1984 ዓ.ም በፊት ገንዘቡን በመክፈል ተጠሪዎች በወለድ አገድ የያዙትን ቤት ለማስለቀቅ የማይችሉ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በወለድ አገድ ውሉ የተገለፀው ጊዜ ካለፈ በኃላ አመልካቾች በማናቸውም ጊዜ እዳቸውን በመክፈል ቤታቸውን ማስመለስ የሚችሉ ስለመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3128 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት መጠየቅ አይችሉም ማለት አይደለም፡፡ ተጠሪዎች በወለድ አገድ የያዙት ቤት ባለሀብት ሆነው የሚቀሩበት የህግ መሠረት የለም፡፡ በቤቱ እየተጠቀሙና አላባ እየሰበሰቡ መኖር ካልተስማማቸው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3128 አንቀጽ 1 የወለድ አገድ መብቱን ለመተው የሚችልበት አጋጣሚ እንዳለ ተደንግጓል፡፡

በአጠቃላይ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3117 እስከ ፍታብሔር ህግ ቁጥር 1130 የወለድ አገድ የውል መሠረታዊ ባህሪ፣ ውጤትና የወለድ አገድ ውል እንዲቋረጥ ለመጠየቅ ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ ስለጠቅላላ ውል ህግ የተደነገገው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1845 ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ስለሆነም የልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾች ክስ በአስር ዓመት ይርጋ ይቋረጣል በማለት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ወስነናል፡፡
3. የውልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
4. አመልካቾች ብር 2500 /ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ለተጠሪዎች በመክፈል በወለድ አገድ ያስያዙትን ቤት የመረከብ መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፊሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሻምበል ይኩኖ ለገሠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መሐመድ በሸርና ቤተሰቦቹ ጨው አምራች ኃ/የተ/የግል ማህበር አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ እንደ ውሉ ያልተፈፀመለት ወገን በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ኪሣራ በመጠየቅ ረገድ የሚኖረው መብትና ተነፃፃሪ ግዴታን የሚመለከት ነው፡፡ ግራ ቀኙ ግንቦት 02 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ የፅሑፍ ውል የአሁን ተጠሪዎች በውል ሰጪነት/፤ አመልካች ደግሞ በውል ተቀባይነት ተሰይመው የውል ሰጭዎች የጨው ማምረቻ ቦታ ውል ተቀባይ ተረክቦ ለመጀመሪያ ሰባት አመታት በራሱ ወጪ እና ማቴሪያል ለሚያመርተው ምርት 70% ለእራሱ አስቀርቶ 30% ለውል ሰጭዎች ለማካፈል በቀሪው ሶስት አመታት ግን በግራ ቀኙ ውጭ ለሚመረተው ምርት እኩል በእኩል ለመካፈል ተስማምተዋል፡፡ እንደ ውሉ ያልፈፀመ ወገንም ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ውል ላልተፈፀመለት ወገን ከፍሎ ቀጣዩ በውሉ መሠረት እንዲፈጽም እንደሚደረግም አክለው ተስማምተዋል፡፡

ይህ ውል ከተደረገ ከአምስት ዓመት በኃላ የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በተዋዋይነው ጨው የማምረት ሥራ መሠረት ውል ተቀባይነት ሥራውን መሠረት ባለመቻሉ፣ እንደውል ባለመፈፀሙ የቀረብን የ30% ጥቅም ብር 3,548,666.00 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ስምነት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ብር) እና የገደብ መቀጮ ሊከፍለን ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች በተከሣሽነት እንደውሉ ያልተፈፀመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት እና ምክንያቱን በመጥቀስ የተቋረጠ ጥቅም ሊጠየቅ እንደማይገባ እንደውል አልተፈፀመም ከተባለም በውሉ መሠረት ሊጠይቁ የሚችሉት የ5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ የገደብ መቀጮ እና እንደውሉ በቀጣይ እንዲፈፀም ብቻ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ በግራ ቀኙ ከተነሣው ክርክር አንፃር የአሁን አመልካች እንደውሉ ሊፈጽም ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም፣ እንደውሉ ለመፈፀም አልቻለም፡፡ ስለሆነም ውሉ ፈርሶ ሁለቱም ወገኖች ወደ ነበሩበት ቦታ ይመለሱ፤ ውሉ በመፍረሱ ምክንያት ከሣሽ ይክፈለኝ የሚሉትን ገንዘብ በሌላ ክስ ይጠይቁ በማለት የአፋር ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲወስን፤ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የአሁን አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደውሉ ያልፈፀመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ባለመሆኑ ለውሉ አለመፈፀም ኃላፊ ነው፡፡ ውሉ ባለመፈፀሙ በአሁን ተጠሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ከሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ውሣኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ በዓመት በውል በተሰጠው መሬት ምን ያህል የጨው ምርት ማምረት እንደሚቻል የክልሉ ማእድንና ኢነርጂ ቢሮ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ እንደተመነና በተጠቀሰው ምርትም የጨው ዋጋ በስንት ሲሸጥ እንደነበር ለግብይት ማህበሩ በማጣራት አስተሳስቦ የደረሰባቸው ኪሣራ ይክፈል፤ እንዲሁም እንደውሉ ሊቀጥሉ የሚችሉ ወገኖች ባለመሆናቸው በውሉ መሠረት ገደቡን ብር 5,000 ይክፈል በማለት አሻሽሎ ወስኗል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭር የተጠቀሰው ሲሆን፤ የአመልካች የሰበር ቅሬታ ነጥብ ከሥር ፍ/ቤቶች ጀምሮ ባቀረበችው የመከራከሪያ ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ሲሆን ከተጠሪዎች የተሠጠ የተለየ ክርክር አልቀረበም፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተው ተመልክተናል፡፡ የአሁን አመልካች እንደውሉ ሊፈፀም ያልቻለው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ስላጋጠመው ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ረገድ የቀረበውን ምክንያት በማስረጃ አጣርተው እና ማስረጃውን መዝነው የአሁን አመልካች ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት አላጋጠመም የሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሱ በመሆኑ ጉዳዩ የህግ ትርጉምን የሚጋብዝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች አጠንክሮ የተከራከረበት ሌላው ነጥብ እንደ ውሉ አልተፈፀመም እንኳ ቢባል እደውሉ ሳይፈፀም በቀረ ጊዜ ምን ውጤት እንደሚከተል አስቀድመን በውላችን እንዲገዛ አድርገናል፡፡ በውሉም እንደተገለፀው ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ/ ለተጠሪዎች ከፍሎ እንደ ውሉ እንድፈጽም ነው ግዴታዬ የሚለው ነው፡፡

በእርግጥ የውሉ ይዘት አመልካቹ እንደሚለው መሆኑን በፍርዱ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው ቃል በቃል ሠፍሮ ተገኝቷል፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ውሉ ያልተፈፀመ ከሆነ እንደ ውሉ ያልፈፀመው ወገን ብር 5,000.00 ለሌላው ወገን ከፍሎ ቀጣይ የውል ግዴታውን ይወጣል የሚለውን የውሉ አገላለጽ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ተዋዋይ ወገኖች ባላቸው የመዋዋል ነፃነት ተጠቅመው ለአምስት ዓመት ያህል እንደውሉ ሥራ ቢጀምሩም ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ከፍሎ ቀጣይ ሥራውን ይጀምራል የሚለውንም ሁሉ ለማጠቃለል በማሰብ ያስገቡት የውል ቃል ነው ብሎ ለመተርጎም የሚቻል አይደለም፡፡ ይልቁንም የውሉ አገላለጽ መለስተኛ የጊዜ ብክነትን ለመቆጣጠር ታስቦ የተደረገ ለመሆኑ የገንዘቡ መጠን እና ያጋጠመው መስተጓጉል የግራ ቀኙን የውል መሠረታዊ ግንኙነት የሚያውከው መሆኑን በመገንዘብ ቀጣይ ሥራውን ያከናውናል የሚለው ውጤት አስረጂ ናቸው፡፡

ስለሆነም የአሁን አመልካች ለአምስት ዓመታት ያህል እንደውሉ አለማከናወኑ ቢታወቅም ብር 5,000.00 (አምስት ሺህ ብር) ከፍዬ ውሉን መቀጠል ብቻ ነው ግዴታዬ የሚለው ስለ ውል አተረጓጐም የተቀመጡትን ደንቦች መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪዎች ውሉ ከተደረገበት ከግንቦት 1996 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ዓመታት እንደ ውሉ አለመፈፀሙን እያወቁ ከውል የመነጨውን መብት ለማስጠበቅ ክስ ያቀረበችው በሰኔ 2001 ዓ.ም እንደሆነ ውሣኔው ያስረዳል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደውሉ ያልተፈፀመለት ወገን እንደ ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት በጥቅም መቋረጥ ስሌትም ሆነ በሌላ ኪሣራ የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1771 የተደነገገ ቢሆንም፤ ከውል አለመፈፀም የተነሣ ሊደርስ የሚችለውን የጉዳት መጠንን በመቀነስ ረገድ በእርሱም ላይ በተነሳባሪ ግዴታ የተጣለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1802 ተደንግጓል፡፡

ከዚህም አንፃር ተጠሪዎች ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አምስት ዓመት ዘግይተው በአምስተኛ ዓመቱ መገባደጃ ላይ የብር 3,548,666 /የሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ስላሳ ስድስት ብር/ ኪሣራ ዓመታትን መነሻ በማድረግ አስልተው ከማቅረብ ይልቅ እንደ ውሉ ያለመፈፀሙን፤ እንደውሉ ሊፈጽም የሚችልበትን ሁኔታ በመረዳት ሊደረስ የሚችለውን ኪሣራ ለመቀነስ ቀደም ብለው ክስ የማቅረብ ግዴታቸውን ያልተወጡ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

ስለሆነም ይህ በኪሣራ ጠያቂው በኩል በህግ የተጣለው ተነሳባሪ ግዴታ የኪሣራ መጠንን ለማስላት ግምት ውስጥ ሊገባ የማይገባ ሌላው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል የተቋረጠ የሚባለውን ጥቅም ለማስላት ፍ/ቤቶች የባለሙያን ድጋፍ የሚጠይቁ መሆኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ የሚቀርበውን ሙያዊው አስተየያት በማስረጃነቱ በመያዝ ስለኪሣራው መጠን እራሳቸው የሚወስኑትና የፍ/ቤቱን ዳኝነት የሚጠይቅ ተግባር ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደገለፀው የክልሉ ማእድንና ኢነርጂ መሬት በየዓመቱ ምን ያህል የጨው ምርት እንደሚያገኝ ዋጋውም ስንት እንደሆነ ከግብይት ማህበራት በኩል ተጣርቶ ድርሻቸውን ይከፈላቸው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት አማካኝነት ፍትህ የማግኘት መብታቸውን ያስከበረ ተግባር አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የአሁን አመልካች እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት በተጠሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት በሚል የተሰጠው ውሣኔ አግባብ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሊከፈል የሚገባውን የኪሣራ መጠን በመወሰን ረገድ የተጠሪዎች ተነሳባሪ ግዴታ ሳይያዝ፣ ይህ በተቻለ መጠን የጉዳት ኪሣራን በመቀነስ በኩል በተጠሪዎች በኩል መፈፀም የሚገባውን ግዴታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደውሉ ያልፈፀመው ወገን ሊከፍል የሚገባውን የጉዳት ኪሣራ ልክ ባባከነው ጊዜ አንፃር መሬቱ በሚያስገኘው የምርት መጠን እና በየጊዜው በነበረው የዋጋ ተመን መሠረት ይሆናል የሚለው ከተያዘ በዚህ መሠረት አስልቶ ለመወሰን የባለሙያ እገዛን ፍ/ቤቱ ከሚጠይቅ በቀር የኪሣራ አወሳሰኑን ዳኝነት ሰጭ አካል ላልሆነ አሳልፎ በመስጠት የተሰጠው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በዝርዝር ህጉን ባካተተው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት ይህንኑ ስህተት በማረም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 2108 መጋቢት 17 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት በማሻሻል፣ የአሁን አመልካች እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት በተጠሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኪሣራ የመክፈል ኃላፊነት አለበት የሚለው የውሣኔው ክፍል እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ግንቦት /1996/ ጀምሮ ተጠሪዎች ክስ እስካቀረቡበት ሰኔ 2001 ዓ.ም. ድረስ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1802 እንደተደነገገው ኪሣራ በመቀነስ ረገድ ተጠሪዎችም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚጠበቅባቸውን ተነፃፃሪ ግዴታ አለመወጣታቸው የኪሳራውን መጠን በማናር አስተዋጽኦ ያደረጉ መሆኑን ከግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባውን ጉዳይ መሆኑን መነሻ በማድረግ ለኪሣራው ስሌት መሠረት ሆኖ የሚያዘውን የጊዜ ርዝመት ፍ/ቤቱ ባለው የማመዛዘን ሥልጣን ተጠቅሞ እንዲቆረጥና የጊዜው ርዝመት ምን ያህል እንደሆነ ከተቆረጠ በኃላ በዚህ ጊዜ ውስጥ መሬቱ ምን ያህል የጨው ምርት ማስገኘት ይችል የነበረ መሆኑና በትይዩ ጊዜውም የጨው ዋጋ ስንት እንደነበር ፍ/ቤቱ በጠቀሳቸው አካላት ተተምኖ እና ተጣርቶ እንዲቀርብ ካደረገ በኃላ ይህንኑ ውጤት በማስረጃነት ይዞ የጉዳት ኪሣራውን ልክ መወሰን ይችል ዘንድ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት እንዲመለስ ወስነናል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ስላስከተለው ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 71927

ሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ቂስ አብርሃ በርሄ - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ብርነሽ ሕሉፍ - አልቀረቡም፡፡

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በመቀሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በቀዳማዊ ወያኔ ምድብ ችሎት ነው፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የብድር ገንዘብን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 7 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል ተጠሪ ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ እስከ የካቲት 1994 ዓ.ም ልትመልስ፣ በዚህ ጊዜ ባትከፍል መቀጫ 8,000 /ስምንት ሺህ ብር/ በድምሩ 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ ለመክፈል ተስማምታ በብድር ወስዳለች፡፡ ገንዘቡን ያልከፈለችኝ በመሆኑ በውሉ መሠረት ብር 20,000 ከነወለዱ እንድትከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በከሳሽነት ቀርበው ገንዘብ በብድር አልወሰድኩም ፊርማውም የእኔ አይደለም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪ ነው የተባለው ፊርማ እንዲመረመር ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ በምርመራው ፊርማው የማን እንደሆነ መለየት እንዳልተቻለ ተገልጿል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወስኖ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሉ ላይ የነበሩት ምስክሮች ሰምተህ ወስን በማለት በይግባኝ ሽሮ መልሶታል፡፡ በዚህ መሠረት የወረዳው ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል ከሰማ በኋላ ምስክሮች ተጠሪ ስትበድር አይተናል፣ በውሉ ላይ ፊርመናል ብለው መመስከራቸውን በመጥቀስ ተጠሪ በብድር የወሰደችውን ብር 12,000 እና መቀጫ ብር 8,000 በድምሩ 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ ዕዳው ተከፍሎ እስከሚያልቅ የባንክ ወለድ ታስቦ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ በባንክ ወለድ እንድትከፍል የሰጠውን ውሣኔ ብቻ በማሻሻል ሌላውን የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የወረዳው ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰው ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ድንጋጌን የሚጥስ ነው በማለት የወረዳውንና የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር ተጠሪ ለአመልካች ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቷል፡፡

አመልካች ነሐሴ 9 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በብድር ገንዘብ የወሰደች መሆኑን ለማስረዳት ያቀረብኩት የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡ ተጠሪ በሰነድ ላይ ያለውን ፊርማ ስለካዱና ፊርማውን በቴክኒክ ምርመራ ለማረጋገጥ ስላልተቻለ ውሉ ሲፈረም የነበሩ ምስክሮች ተጠሪ በሰነዱ ላይ የፈረሙ መሆኑን ለማረጋገጥ የሰጡትን ምስክርነት መሠረት በማድረግ የተሰጠውን ውሣኔ አላግባብ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ኅዳር 4 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ ግንቦት 7 ቀን 1993 ዓ.ም ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ ተበድራ የወሰደች መሆኑን ለማስረዳት የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ማለትም ግንቦት 7 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈና በተዋዋይ ወገኖች የተፈረመ የብድር ውል መሆኑን ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ ይህም አመልካች የብድር ውሉን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟላና ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆኑን ያሣያል፡፡

ተጠሪ በብድር ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የእኔ ፊርማ አይደለም በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2008 መሠረት ክዳ ተከራክራለች፡፡ በውሉ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ መሆኑን ለማረጋገጥ የቴክኒክ ምርመራ የተደረገ ቢሆንም ፊርማው የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ እንዳተልቻለ፣ የፖሊስ ፎረንሲክ ላብራቶሪ በመግለፁ፣ ፊርማው የተጠሪ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ /Authenticate/ ለማድረግ በውሉ ላይ ስማቸው የተገለፁት ሰዎች ተጠሪ በውሉ ላይ ስትፈርም ያዩ መሆኑን እንዲያረጋግጡ ተደርጓል፡፡ እዚህ ላይ ተበዳሪው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የብድር ውሉን ለማስረዳት በቀረበው የሰነድ ማስረጃ ላይ ያለው ፊርማ ተበዳሪው የእኔ አይደለም በማለት የካደ በሆነ ጊዜ ፊርማው የተበዳሪው መሆኑን ለማረጋገጥ ምን ዓይነት ማስረጃ ተቀባይነት አለው የሚለው በሰነድ ላይ ያሉ ፊርማዎችን ለማረጋገጥ /Authenticate/ ተቀባይነት ያላቸውን ማስረጃዎች መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

በሰነድ ላይ ያለ ፊርማ በተካደ ጊዜ ፊርማውን የማረጋገጫው የመጀመሪያው መንገድ የቴክኒክ ምርመራ እንዲደረግ ማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ፊርማውን በቴክኒክ ምርመራ የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ ባልተቻለ ጊዜ ፊርማው ሲፈረም የነበሩ ምስክሮችን ቃል በመስማትና በሌሎች ማስረጃዎች ፊርማው የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ /Authenticate/ ለማድረግ የሚቻል መሆኑ ከማስረጃ ሕግ ጠቅላላ መርሆች ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአገራችን ፊርማ በምስክሮች ቃልና በሌላ ማስረጃ እንዳይረጋገጥ /Authenticate/ እንዳይደረግ የሚከለክል ግልፅ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ በአንፃሩ ፊርማ በተካደ ጊዜና ፊርማውን በፎረንሲክ ምርመራ ለመለየት የማይቻል በሆነ ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በምስክሮች ቃልና በሌሎች ማስረጃዎች ማረጋገጥ እንደሚቻል በፍርድ ቤቶች ለረዥም ጊዜ የዳበረው የአሰራር ልምድ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የብድር ውልን በሰነድ ማስረዳት በአስገዳጅነት የሚደነግገውን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ በማስረጃነት በቀረበ ሰነድ ላይ ያለ ፊርማ ሲካድ ፊርማው ከሚረጋገጥበት ሁኔታ /Authentication/ ጋር ያላቸውን ልዩነት ሳያገናዝቡ አመልካች በውሉ ላይ ያለውን ፊርማ ከማረጋገጥ /Authentication/ ጋር አንድና ተመሣሣይ አድርጎ በመውሰድ የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ንዑስ አንቀጽ 1ን ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል በብድር ውል ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ ፊርማ መሆኑን በማስረጃ ያረጋገጡት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በብድር የወሰደችው ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ በተጨማሪ 8,000 /ስምንት ሺህ ብር/ ጨምራ እንድትከፍል የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2472 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚቃረንና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ እንደዚሁም የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የቀዳማዊ ወያኔ ወረዳ ፍርድ ቤትና የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
3. ተጠሪ ብር 12,000 /አስራ ሁለት ሺህ ብር/ በዚህ ጉዳይ ለወረዳ ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ታስቦ ለአመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለባት በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- አቶ ሽመልስ አበራ - ጠበቃ አቶ ማሩ ባዘዘው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጌታቸው አያልቁ - ቀረቡ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54218 በኀዳር 8 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63616 በመጋቢት 14 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ የፊልም ሥራ ውል አፈፃፀም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ ከተከሳሽ ጋር ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ ታሪክ ወደ ፊልም ለመቀየር ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም ውል ተዋውለናል፡፡ በውሉ ከሳሽ ለፊልም ሥራ ወጭ መሸፈን ግዴታ ያለብኝ ሲሆን ተከሳሽ ፊልሙን ለመሥራት የወጣው ወጭ ከተሸፈነ በኋላ ትርፍ እኩል ለመካፈል ተስማምተናል፡፡ ከሳሽ በውሉ መሰረት ፊልሙ ተጠናቆ ለእይታ እስከበቃ ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ አውጥቻለሁ፡፡ ተከሳሽ ፊልሙ ለእይታ ከበቃ በኋላ በውሉ መሰረት በፊልሙ የተገኘውን ገቢ አላሳወቀኝም፣ ለፊልሙ ሥራ ያወጣሁትን ወጭ አልከፈለኝም፡፡ ከስፖንሰር የተገኘውን ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር/ አልከፈለኝም፡፡ ከሣሽ ለፊልሙ ሥራ ከእንግሊዝ አገር ስመላለስ ብር 40,000 /አርባ ሺህ ብር/ አውጥቻለሁ፡፡ ስለሆነም ከሳሽ ከእንግሊዝ አገር ስመላለስ ያወጣሁትን ወጭ ተከሳሹ እንዲሸፍን፣ ፊልሙ ለእይታ እንዳይቀርብና የፊልሙ ማስተር እንዲቃጠልና ለገበያ የተሰራጨው እንዲሰበሰብ፣ በፊልሙ የተገኘው ገቢ ታስቦ ድርሻዬን እንዲያካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስና ከሳሽ በአማራጭ ሂሳቡ ተጣርቶ ለፊልም ሥራው ያወጣሁት ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ ተከሳሽ እንዲከፍል፣ ፊልም የሚያስተዳድር ባለሙያ ተሹሞ ፊልሙን ተረክቦ በማሳየትና በማስተዳደር ገቢውን እንዲያካፍለን፣ ከስፖንሰር ከተገኘው ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር/ ድርሻዬን ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ተከሳሽ እንዲከፍልና ተከሳሽ የፊልሙን ፕሮዲውሰር ሪሽ ማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት በሚል ስያሜ ከከሳሽ ስምምነት ውጭ ያሳተመ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34 ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት የኢኮኖሚና ሞራል ጉዳት ካሳ ከውሉ መቀጫ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው ከሳሽ በውሉ መሰረት ያወጡት ወጭ ብር 232,000 /ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ብር/ ብቻ ነው። ከከሳሽ ጋር ውል የፈጸመው ወጋየሁና አበራ የቴአትር ኢንተርፕራይዝ ስያሜው ሪሽ የማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት በሚል ስም በሕጋዊ መንገድ የተቀየረ በመሆኑ ክሱ የሕግ መሰረት የለውም። ሪሽ የማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት ለፊልሙ ሥራ የከሳሽ ወኪል እያጸደቀው ብር 307,338.73 /ሦስት መቶ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰባ ሦስት ሣንቲም/ ያወጣ በመሆኑ ከሳሽ ይህንን ገንዘብ ሊተካ ወይም ሊያቻቻል ይገባል። ከሳሽ ለፊልም ሥራ የሚሆነውን የድርሰት ሥራ በማቅረባቸው ብቻ የተከሳሽን የፕሮዲውሰርነት መብት ለመጋፋት አይችልም። ከስፖንሰር የተገኘው ገንዘብ ፊልሙን ለማስመረቅ ለወጣው ወጭ የዋለ ስለሆነ ከሳሽ ያቀረበው ጥያቄ ተገቢ አይደለም። ፊልሙን የማስተዳደር መብት ያለው ተከሣሽ በመሆኑ ክሱ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል።

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል የተደረገው ውል ሊፈረስ ይገባል ወይስ አይገባም? ከሳሽ ለፊልሙ ማሰሪያ ያወጣውና ለተከሳሽ የሚከፍለው ተጨማሪ ገንዘብ አለ ወይም የለም? ተከሳሽ ለከሳሽ ካሳ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች ከመሰረተ በኋላ ውሉ በተከሳሽ ጥፋት ሊፈረስ ይገባዋል ተከሳሽ ለፊልሙ ማሰሪያ አውጥቻለሁ በማለት ያቀረበው የተጨማሪ ገንዘብ ጥያቄ ሚዛን በሚደፋ ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። ከሳሽ ፊልሙን በካሳ ክፍያነት ይረከቡት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል። አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል። ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ከመረመረ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል።

አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም መጋቢት 21 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት። በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪ ውል የተዋዋለው በመጀመሪያ ወጋየሁና አበራ የቴአትር ኢንተርፕራይዝ ከሚባለውና በኋላ ስያሜው ሪሽ ማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት በሚል ስም በሕጋዊ መንገድ ከተቀየረው ድርጅት ጋር ነው። ስለዚህ ተጠሪ አመልካችን በስሙ መክሰሱ የሕግ መሰረት የለውም። የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የውል ግዴታውን በመተላለፍ የተጠሪን የስራ አመንጭነትና የኢኮኖሚ መብት አሳጥቷል በማለት ውሉ እንዲፈርስ የሰጡት ውሣኔ አዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2፣ አንቀጽ 30፣ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 5/ሐ/ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የሚተላለፍና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው። ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ መሰረት የሌለው ሲሆን አመልካች የተጠሪ ወኪል በመሆን ያጸደቀው ወጭ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል።

ተጠሪ ከሃያ አመት በፊት የደረስኩትና ተወዳጅ የሆነው የድርሰት ሥራዬን ወደ ፊልም ለመቀየር ከአመልካች ጋር ውል በመዋዋል በውሉ መሰረት ግዴታዬን ተወጥቻለሁ። አመልካች ውሉ ሲደረግ የነበረውን ድርጅት ስያሜ በመቀየር ከኃላፊነት ለማምለጥ የሞከሩ በመሆኑ ክሱ በስሙ መቅረቡ ተገቢ ነው። ለአዶቪዥርዋል ሥራው ሙሉ ግብአት የሆነው የእኔ ድርሰት በመሆኑና ለፊልም ስራው የወጣውን ወጭ ተጠሪ የሸፈንኩ በመሆኑ የፊልሙ ፕሮዲውሰር ተደርጌ መወሰድ ያለብኝ እኔ እንጂ አመልካች አይደለም። ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ውሉን ያላከበረ መሆኑን በማረጋገጥ ፊልሙን እኔ እንድረከብ የሰጡት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በሰኔ 24 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን ነጥቦች በማጠናከር ክርክር አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካችና ተጠሪ ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ ታሪክ ወደ ፊልም ለመቀየር ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም ያደረጉት ውል እንዲፈርስና ተጠሪ ፊልሙን እንዲረከብ የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካችና ተጠሪ ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው ውል ስላለባቸው ግዴታና ኃላፊነትና በውል የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት በሚፈጽሙበት ጊዜ ስለአከናወኗቸው ተግባራትና ሳይፈጸሙ ስለቀሩት ተግባራት፣ ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን የደረሱባቸው መደምደሚያዎችን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች የወጋየሁና አበራ የቴአትር ኢንተርፕራይዝ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በመቅረብ ከተጠሪ ጋር ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም ውል ተዋውለዋል፡፡

በውሉ ተጠሪ ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም ለመለወጥ የሚያስፈልገውን ወጭ ለመሸፈን፣ አመልካች ደግሞ የፊልም ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉትን ተግባራት ሁሉ በመፈጸም የፊልም ሥራውን በማጠናቀቅ ለዕይታ ለማብቃት ግዴታ የገቡ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም ለመለወጥ የወጣውን ወጭ ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ በውሉ መሰረት ሸፍኖለሁ በማለት የተከራከረ ሲሆን አመልካች ተጠሪ በውሉ መሰረት ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም ለመለወጥ ከወጣው ወጭ ብር 539,338 /አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር/ ውስጥ ብር 232,000 ብቻ የከፈለ በመሆኑ በውል የገባውን መሰረታዊ ግዴታ አልተወጣም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

ለፊልሙ ሥራ የወጣው ወጭና ተጠሪ ለአመልካች የከፈለው የገንዘብ መጠን ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት መሰረታዊ ጭብጥ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ነጥብ በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙን ማስረጃ የሰማውና የመረመረው የፊልሙን ሥራ ለማጠናቀቅ የወጣው ወጭ ብር 539,338 /አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር/ ነው በማለት አመልካች ተጠሪ ብር 307,338.73 /ሦስት መቶ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰባ ሦስት ሳንቲም/ ያወጣ በመሆኑ ለአመልካች ሊተካ ወይም ሊቻቻል ይገባል በማለት ታዓማኒነት ባለውና ሚዛን በሚደፋ ማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህንን የሥር ፍርድ ቤት መደምደሚያ የፊዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀብሎታል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ለፊልሙ ሥራ ማጠናቀቂያ ያወጣው አመልካች እንደሚለው ብር 232,000 /ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ/ ብር ሣይሆን ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ በውሉ መሰረት የፊልሙን ሥራ ለማጠናቀቅ የወጣውን ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ በመሸፈን በውሉ የገባውን ግዴታ ሙሉ በሙሉ የተወጣ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም በመለወጥ የፊልም ሥራው የተጠናቀቀና ፊልሙ ለዕይታ ከበቃ በኋላ በዚህ ክርክር ምክንያት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ፊልሙ ለዕይታ ከበቃ በኋላ በውሉ መሰረት ገቢውን ለተጠሪ አለማሳወቁ፣ ተጠሪ ያወጣው ወጭ በመጀመሪያ አለመተካቱና፣ ከተጠሪ ጋር በመጀመሪያ ውል የተዋዋለውን ወጋየሁና አበራ የቴአትር ኢንተርፕራይዝ የሚባለውን ድርጅት ሪሽ ማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት በሚል ስም እንዲመዘገብ በማድረግ የውል ግዴታውን በመፈጸም በኩል ጉድለት ያሳየ መሆኑን የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡

2. ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በስተቀር ተዋዋዮች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው መወሰን መብት ያላቸው መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1711 ተደንግጓል፡፡ የቅጅ መብት ባለቤቱ ኢኮኖሚያዊ መብቱን በሙሉ ወይም በከፊል በስምምነት ለማስተላለፍ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 23 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከአመልካች ጋር በውል ከተስማማ በኋላ የድርሰቱ ባለቤት እኔ ስለሆንኩ የኢኮኖሚ መብት ያለኝ እኔ ብቻ ነኝ በማለት የሚያቀርበው ክርክርና አመልካች የፊልሙ ፕሮዲውሰር በመሆኔ መብቱ የእኔ ብቻ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1711፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 23 ድንጋጌዎች ያላገናዘበና የሕግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአመልካችና ተጠሪ ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው ውል መሰረታዊ ይዘት የተጠሪ ድርሰት ሥራ የሆነውን ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም በመለወጥ ወጭው ከተተካ በኋላ የሚገኘውን ገቢ በመካፈል የፊልሙ የጋራ የሞራልና ኢኮኖሚ መብት ተጠቃሚ መሆን ነው፡፡ ተጠሪ በውሉ መሰረት የፊልሙን ሥራ ለማጠናቀቅ የወጣውን ወጭ ሙሉ በሙሉ በመሸፈን በውሉ የገባውን ግዴታ ሙሉ በሙሉ የተወጣ መሆኑን ፍሬ-ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም በመለወጥ የፊልም ሥራው የተጠናቀቀና ፊልሙ የተመረቀና ለዕይታ የበቃ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቀው አመልካች ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም ለመለወጥና የፊልም ስራውን ለማጠናቀቅ የገባውን መሠረታዊ ግዴታ አልተወጣም በሚል ምክንያት አይደለም፡፡ ተጠሪ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቀው ፊልሙ ከተመረቀና ለዕይታ ከበቃ በኋላ አመልካች ፊልሙን በውሉ መሰረት በማስተዳደር የተገኘውን ገቢ የማሳወቅና የተጠሪን የጋራ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ግዴታውን በአግባቡና በውሉ መሰረት አልተወጣም በማለት ነው፡፡

አንድ የጸና የውል ግዴታ የገባ ሰው ውሉ በፍርድ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችለው ሌላኛው ተዋዋይ ወገን በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ግዴታዎቹን ያልፈጸመ እንደሆነ ወይም የፈጸማቸው ሙሉ ወይም ፍጹም ባልሆነ አኳኋን እንደሆነ መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1784 ተደግንጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በውሉ አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ካልተደረገ በስተቀር ዳኞች ውሉ እንዲፈርስ እንደማይወስኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ሲሆን ዳኞች ውሣኔ ለመስጠት የተዋዋዮቹን ጥቅምና ለቅን ልቦና የሚያስፈልገውን ነገር መሰረት ማድረግ እንዳለባቸው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ አመልካችና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ የተጠሪ ድርሰት ሥራ የሆነውን ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም በመለወጥ ወጭው ከተተካ በኋላ የሚገኘውን ገቢ በመካፈል የፊልሙ የጋራ የሞራልና ኢኮኖሚ መብት ተጠቃሚ ለመሆን ያደረጉትን አይነተኛ የውል ግዴታ ፈጽመው አሁን ሚከራከሩት በፊልም አስተዳደር ሥራ አመራርና ገቢ ክፍፍል በተለይም ተጠሪ ለፊልም ሥራው ያወጣውን ወጭ ፊልሙ ለዕይታ ከቀረበ በኋላ በቀዳሚነት ሊሸፈን ይገባው ነበር፤ ይህንን ባለመፈጸሙ አመልካች የውል ግዴታውን ጥሷል በማለት ነው።

ውሉን ማፍረስ አመልካችና ተጠሪ፣ የተጠሪ ድርሰት ሥራ የሆነውን ቃልኪዳን የተባለውን ልብወለድ መጽሐፍ ወደ ፊልም በመለወጥ የሚገኘውን ገቢ በመካፈል የፊልሙ የጋራ የሞራልና ኢኮኖሚ መብት ተጠቃሚ መሆን ለማረጋገጥ የሚያስችል አይደለም። በያዝነው ጉዳይ ፊልሙ ከተመረቀና ለእይታ ከበቃ በኋላ የፊልሙን አስተዳደርና የገቢ ክፍፍል በማስመልከት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳውን አለመግባባት መነሻ በማድረግ ውሉ እንዲፈርስ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በውሉ ዓይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ካልተደረገ በስተቀር ዳኞች ውሉ እንዲፈርስ እንደማይወስኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም። እንደዚሁም ተጠሪ ከወጋየሁና አበራ የቴአትር ኢንተርፕራይዝ ከሚባለው አመልካች ሥራ አስኪያጅ ከሆነበት ድርጅት ጋር ውል ከተዋዋለ በኋላ የድርጅቱ ስያሜ ሪሽ ማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅት በሚል ስም በሕጋዊ መንገድ መቀየሩ ተጠሪ በፊልሙ ላይ ያለውን የሞራልና የኢኮኖሚ የጋራ ባለመብትነት የሚጋፋ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ አግባብነት ያላቸውንና ከላይ የጠቀስናቸውን ድንጋጌዎች ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም። ዳኞች ውሣኔ ለመስጠት የተዋዋዮቹን ጥቅምና ለቅን ልቦና የሚያስፈልገውን ነገር መሰረት በማድረግ እንዳለበትና የውሉ መሰረታዊ ነገሮች ባልተነካበት ሁኔታ ውሉ እንዲፈርስና ተጠሪ ፊልሙን እንዲረከብ የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1784 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 1፣ ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

3. ፊልሙ ከተመረቀና ለእይታ ከበቃ በኋላ የፊልሙን አስተዳደርና የገቢ ክፍፍል በማስመልከት አመልካች በውሉ መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል። የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፊልሙ ከተጠናቀቀ በኋላ አመልካች ቀጣይነት ያለውን ፊልሙን በውሉ መሰረት የማስተዳደር፣ ገቢውንና ወጭውን ለተጠሪ የማሳወቅና የማካፈል ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም በማለት የደረሱበት የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣናቸውን በመጠቀም የደረሱበት በመሆኑ በአግባቡ ነው። ሆኖም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ እንዲረከቡ የሰጡት ውሣኔ ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 4 በመጥቀስ ካቀረቡት የጉዳት ካሳ ጥያቄ የወጣና ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ግልጽ የዳኝነት ጥያቄ ያላቀረቡበትና የፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌን የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው።

የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ፊልሙን እንዲረከቡ የሰጡት ውሣኔ ተጠሪ በአማራጭ ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ፊልሙ ገለልተኛ በሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ እንዲተዳደር ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም መነሻ ፊልሙ ከተመረቀና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለእይታ ከበቃ በኋላ የፊልሙን አስተዳደርና የገቢ ክፍፍል በማስመልከት አመልካች በውሉ መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን መነሻ በማድረግ ውሉ እንዲፈርስ ከመወሰን ይልቅ ተጠሪ በአማራጭ ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ፊልሙ ገለልተኛ በሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ እንዲተዳደር በማድረግ ተጠሪ ለፊልሙ ሥራ ያወጣው ወጭ ከተተካ በኋላ አመልካች ሪሽ ማስታወቂያና የፊልም ሥራ ድርጅትና ተጠሪ ትርፉን እኩል እንዲካፈሉ ማድረግ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1785 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችን ይዘት መንፈስና ዓላማ የሚያሳካ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ በዝርዝር በጠቀስናቸው ምክንያቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሉ እንዲፈርስና ተጠሪ ፊልሙን እንዲረከብ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54218 በነዳር 8 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63616 በመጋቢት 14 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ ጥቅምት 16 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው ውል መሰረት አይነተኛ ግዴታቸውን ተወጥተው የፊልም ሥራው ተጠናቆ የተመረቀና ለዕይታ የበቃ በመሆኑ ውሉ አይፈርስም በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ለፊልም ሥራው ያወጣሁት ተጨማሪ ወጭ አለ በማለት የጠየቀውን ብር 307,338.73 /ሦስት መቶ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰባ ሦስት ሳንቲም/ የመቻቻል ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ ነው በማለት አጽንተነዋል፡፡
4. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለፊልም ሥራው የወጣውን ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ ሙሉ በሙሉ የሸፈነው ተጠሪ ነው በማለት የሰጡት የውሣኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
5. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፊልሙ ከተመረቀና ለእይታ ከበቃ በኋላ የፊልሙን አስተዳደርና የገቢ ክፍፍል በማስመልከት አመልካች በውሉ መሰረት ግዴታውን አልተወጣም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
6. ተጠሪ በአማራጭ ባቀረበው የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ፊልሙ ገለልተኛ በሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ እንዲተዳደር እንዲታይ በማድረግና ከዚህ በፊት ፊልሙ ከተመረቀና ለእይታ ከቀረበ በኋላ ፊልሙን በማሳየት የተገኘው ገቢ ፊልሙን ለማሳየት የወጣው ወጭ ሂሳብ ተሰርቶ በመጀመሪያ ተጠሪ ለፊልም ሥራው ያወጣውን ወጪ ብር 304,000 /ሶስት መቶ አራት ሺህ ብር/ እንዲተካ ከተደረገ በኋላ ትርፉን አመልካችና ተጠሪ በውሉ መሠረት እኩል እንዲካፈሉ በማድረግ በፊልሙ ላይ ያላቸው የጋራ የሞራልና የኢኮኖሚ መብት ተጠቃሚነት መብት ለማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ በዚሁ መንገድ የውሉ ተግባራዊነት ሊቀጥል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
7. በዚህ ችሎት ሚያዝያ 6 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
8. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኮንስትራክሽን እና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ ነጋ አበበ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ደበበ ተሊላ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ከማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ውል ጋር በተያያዘ ሁኔታ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በኦሮሚያ ብ/ክ/መ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአፈፃፀም ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን የአፈፃፀም ተከሳሾች ደግሞ እነ ስንዱ ሹሜ /ሶስት ሰዎች/ ነበሩ፡፡ ተጠሪው በአፈፃፀም ተከሳሾች ላይ ክስ የመሰረተው ብር 148,985.05 /አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ብር ከዜሮ አምስት ሳንቲም/ በፍርድ የተወሰነለት መሆኑን በመግለጽ ከወጪና ኪሣራ ጋር በድምሩ ብር 153,293.05 /አንድ መቶ ሃምሳ ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሦስት ብር ከዜሮ አምስት ሳንቲም/ በአንድነት እንዲከፍሉ፣ ይህንን ባይፈፅሙ የካርታ ቁጥሩ MR.497052 የሆነ ቤትና ለብድሩ 2ኛ የፍርድ ባለእዳ የሆኑት አቶ ሹሜ ሮቢ በመያዣ ቁጥሩ 355 የሆነ በሁሩታ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቤት ያስያዙ መሆኑን ገልፆ አፈፃፀሙ በዚህ አግባብ እንዲመራለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ በዚህ መሰረት ባለእዳዎች የተባለውን ገንዘብ መክፈል ባለመቻላቸው ተጠሪ የጠቀሰው ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ ትእዛዝ ሊሰጥ ንብረቱ ተገምቶ እንዲቀርብ የሚመለከተው አካል ሲታዘዝ ቁጥሩ 355 የሆነ ቤት ፈርሶ በቦታው ላይ አዲስ ሆቴል ቤት የተሰራ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ የገለጸ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም ይህንኑ የሆቴል ንብረት በብር 536,822.00 /አምስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ሁለት ብር/ ብድር በካርታ ቁጥር 8205/ሹ/71/88 ይዞ ለስር 2ኛ እና 3ኛ የአፈፃፀም ተከሳሾች ብድር ያበደረ መሆኑን ጠቅሶ በንብረቱ ላይ የቀደምትነት መብት ያለው መሆኑን ዘርዝሮ ሐራጁ በንብረቱ ላይ ሊቀጥል አይገባም ሲል ተቃውሞውን አቅርቦ የአሁኑ ተጠሪም ቤቱ ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ራሱ መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን አንስቶ ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣ አመልካች ንብረቱን የያዘው ከተጠሪ በተለየ ካርታና የቤት ቁጥር ስለመሆኑ መረጋገጡን ገልፆ የተጠሪ አፈፃፀም በሆቴል ቤቱ ሊቀጥል አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ በቦታው ላይ የነበረውን ቤት ቀድሞ በመያዣነት የያዘው የአሁኑ ተጠሪ መሆኑን፣ አመልካች ያገኙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚለው የሆቴል ቤት በቦታው ላይ እንደ አዲስ የተሰራ እንጂ የተለያየ ቤት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም የሚሉ ምክንያቶችን ይዞ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ያሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በመያዣነት የያዘው ንብረት በካርታ ቁጥሩም ሆነ በንብረቱ አይነት ተጠሪ በመያዣነት ያዝኩ ከሚለው ንብረት የካርታ ቁጥርና የንብረት አይነት የተለየ ሁኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመያዣ ቀዳሚ መብት ያለው ተጠሪ ነው በማለት መወሰናቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3066 ድንጋጌንና ሌሎች የመያዣ ሕግ ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ባግባቡ ያላገናዘበ ነው የሚል ሲሆን ጉዳዩ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ መታየት ያለበት መሆኑ ታምኖ እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርበው በዕሑፍ በሰጠው መልስ አመልካች ያዝኩ የሚለው የሆቴል ድርጅት ተጠሪ ቀድሞ በመያዣነት የያዘው ንብረት በነበረበት ቦታ ላይ የተሰራ በመሆኑ ይኸው ንብረት ተጠሪ ቀድሞ የያዘው ንብረት አካል ተደርጎ ከሚቆጠር በስተቀር የተጠሪን የመያዣ መብቱን ሊያሳጣ የሚችል አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ በመያዣ ይዞት የነበረው ንብረት መኖሪያ ቤት ሲሆን አመልካች ደግሞ የሆቴል ድርጅቱን መሆኑን፣ የሁለቱም ቤቶች ካርታ ቁጥር የተለያዩ መሆናቸው የሚታወቅ ከሆነ አመልካች በሌላ አዲስ ካርታ ቁጥር በመያዣ የያዘው የሆቴል ድርጅት ተጠሪ ቀደም ብሎ በመያዣነት ይዞት በነበረው መኖሪያ ቤት የፈረሰበት ቦታ ላይ የተሰራ በመሆኑ ብቻ ተጠሪ በመያዣ በተያዘው የሆቴል ድርጅት ላይ የቅድሚያ መብት አለው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመሰረቱ አከራካሪው ነጥብ የሚወሰነው ስለማይንቀሳቀሱ ንብረቶች መያዣ እና አፈፃፀሙን በሚመለከት በፍትሐብሔር ሕጉ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ ከሥር ጀምሮ በተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው ተጠሪ በመያዣ ይዞት የነበረው ንብረት መኖሪያ ቤት ሲሆን አመልካች ደግሞ የሆቴል ድርጅቱን መሆኑን፣ የሁለቱም ቤቶች ካርታ ቁጥር የተለያዩ መሆናቸውን፣ አመልካች በሌላ አዲስ ካርታ ቁጥር በመያዣ የያዘው የሆቴል ድርጅት ተጠሪ ቀደም ብሎ በመያዣነት ይዞት በነበረው መኖሪያ ቤት የፈረሰበት ቦታ ላይ የተሰራ መሆኑን፣ አመልካች ብድሩን የሰጠው ጥቅምት 18 ቀን 1989 ዓ/ም እና መስከረም 20 ቀን 1990 ዓ/ም በተፈረመ የብድር ውል ሁኖ የገንዘቡ መጠንም ብር 536,822.00 /አምስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ሁለት ብር/ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ብድሩን የሰጠው ሰኔ 05 ቀን 1985 ዓ/ም ሁኖ የገንዘቡ መጠንም ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ/ ነው፡፡ ይህም ማለት አመልካች ብድሩን ከተጠሪ በኋላ የሰጠ ሁኖ ለብድሩ በመያዣነት የተያዙት ንብረቶች የሚታወቁበት ካርታ ቁጥር፣ የንብረቶቹ አይነት የተለያየ ሁኖ አንድ የሚያድርጋቸው ቦታው ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በመሰረቱ የማይንቀሳቀው ንብረት በመያዣነት ከተሰጠ በኋላ አዲስ ሥራ ቢሰራ ወይም ማሻሻል ቢደረግ የመያዣ ውሉን አፈፃፀም በተመለከተ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? ለሚለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄ የፍ/ብ/ሕግ ቁ.3066 ግልጽ የሆነ መልስ ሰጥቶአል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ መብት የመያዣው መብት በሚመለከተው የማይንቀሣቀስ ንብረትና በዚሁ ንብረት ላይ የሚሰሩትን አዳዲስ ሥራዎች እንደሚያጠቃልል ያመለክታል፡፡ ይህን ድንጋጌ ከያዝነው ክርክር ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ተጠሪ ቤቱን በመያዣነት ከተበዳሪዎች ከያዘ በኋላ ተሰራ የሚባለው አዲስ ሆቴል ድርጅት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ንብረቱ የሚታወቅበት የካርታ ቁጥርና የንብረቱ መለያ ቁጥር ተጠሪ ከያዘው ንብረት በአይነትም ሆነ በመለያ ቁጥሩ ፈፅሞ የማይገናኝ ከሆነ ስራው አዲስ ቢሆንም ቀድሞ ከነበረው ንብረት ስር የሚጠቃለል ነው ሊባል የሚችል አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በተለይ የዚህን ድንጋጌ መንፈስ እና አላማ ስንመለከት መያዣ ሰጪው ንብረቱ በመያዣ የተሰጠ መሆኑን እያወቀ በንብረቱ ላይ አዳዲስ ስራዎችን ቢሰራ መያዣ ያገኑ አዳዲስ ስራዎችን ሁሉ በመያዣ እንደያዘ የሚያስቆጥረው እና መያዣ ሰጪው እያወቀ ለሰራቸው ሥራዎች መያዣ ያገኑን ለመጠበቅ ተብሎ የተቀረፀ ድንጋጌ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ይህንን ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ የንብረቱ መለያ የሆነው ካርታ ቁጥር ተለያይቶና ንብረቱ ሙሉ በሙሉ በአይነቱ ተለይቶ መሰራቱ ግንዛቤ ካልተወሰደና ይህንኑ መሰረት በማድረግ በንብረቱ ላይ እግድና እዳ የሌለ መሆኑን በመገንዘብ መያዣ የሚወስዱ ቅን ልቦና መያዣ ሰጪዎችን መብት ስንመለከት በሕግ ጥበቃ የማያገኙበት ምክንያት የለም፡፡ የፍ/ብ/ቁጥር 3052/1/ የአስተዳደር ክፍሉ የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት መሆኑን አውቆለት የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት ከሰጠው ሰው ጋራ የተደረገ የንብረት መያዣ ውል የሚፀና ነው በሚል የተቀመጠው ድንጋጌ በሕግ አግባብ የተሰጠውን ካርታ ይዞ የሚያበድረው አበዳሪ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በመያዣነት የያዘው ንብረት ካርታ ቁጥሩም ሆነ አይነቱ ከተጠሪ የተለየ ሁኖ እያለ ቦታው አንድ በመሆኑ ብቻ አመልካች የያዘው ንብረት ተጠሪ በያዘው ንብረት ስር የሚጠቃለል ነው ተብሎ ሊወሰን የማይገባውና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3066፣ 3052 እና ሌሎች ድንጋጌዎችን ዓላማና መንፈስ የሚጥስ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የኦሮሚያ ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 106039 ጥር 21 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 66122 ጥቅምት 06 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አንድ ቀድሞ በመያዣ የተሰጠ ንብረት ካርታ ቁጥሩና የቤት ቁጥሩ ተለውጦ እንዲሁም ንብረቱ ፈርሶ በቦታው ላይ አዲስ ንብረት ተሰርቶና አዲስ ካርታና የቤት ቁጥር ተሰጥቶ በተገኘ ጊዜ ይህንኑ አዲሱን ንብረት በመያዣ የያዘ አበዳሪ ቀድሞ የነበረውን ንብረት ከያዘው አበዳሪ የቅድሚያ መብት አለው ብለናል፡፡
3. በካርታ ቁጥር 8205/ሸ/71/88 በሚታወቀው የሆቴል ቤት የቀዳሚነት መብት ያለው አመልካች ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ጌታቸው በየነ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. የሕፃን ታቦት በቀለ
2. የሕጻን ሒሩት በቀለ
} ሞግዚት ሙሉቀን መንግስቱ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤትና የቦታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ሞግዚት ባሁኑ አመልካች ላይ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪዎች ክስ ይዘትም ከሴት አያታቸው ከወ/ሮ ጌጤ ለገሰ አባታቸውን አቶ በቀለ በየነን በመተካት የሚወርሱትን በባህርዳር ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና ቁጥሩ ኤ-49 በሚል የሚታወቀውን መኖሪያ ቤት የአሁኑ አመልካች ያላግባብ ይዘው እንደሚገኙና ሊለቁላቸውም ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ገልጸው ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቧቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡አመልካች ተጠሪዎች ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ቤቱና ቦታው የሟች ወ/ሮ ጌጤ ለገሰ ስለመሆኑ ሳይክዱ ቤቱና ቦታውን ሟች ለአመልካች በስጦታ ያስተላለፉላቸው መሆኑን፣ስጦታው ሊደረግላቸው የቻለውም ሟችን ሲጦራቸው ስለነበርና ለሟች በ1988 ዓ.ም ብር 10,000.00(አስር ሺህ ብር) አበድረው እስከ 1993 ዓ/ም ድረስ ሊከፍል ይችል የነበረው የጥሬ ገንዘብ ብድር ባለመመለሱ ምክንያት ቤቱን ሟች ብድሩን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተው የሰጧቸውና በስጦታ ውሉ መሰረትም ስመ ሀብቱ ለአመልካች እንዲዞር ሟች ወደ ሚመለከተው አካል ቀርበው በማመልከቻ ጠይቀው ጉዳዩ በሂደት ላይ እንዳለ የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ መሆኑን፣ቤቱን ይዘው ግብር እየገበሩበት እንደሚኖሩና በ1997 ዓ/ም በደረሰው የጎርፍ አዳጋ ምክንያትም ቤቱ በመፍረሱ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ወስደው ብር 56,347.00 ወጪ አድርገው ቤቱን የሰሩት መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአመልካችን ክርክሮች ሕጋዊ ያለመሆናቸውን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችንና ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን፣አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞችን ሁሉ በዋቢነት ከጠቀሰ በኋላ አመልካች ለተጠሪዎች ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኞቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኞቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ከዚህም በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436 እና 1723 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያላግባብ መተርጎማቸውንና በፍሬ ነገር ደረጃ ተዛማጅነት የሌላቸውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞችን በመጥቀስ ውሳኔ መስጠታቸውን በመግለጽ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቹ በስጦታ ውሉ ሳይፈርም መቅረቱ ውሉን ፈራሽ ያደርገዋል የመባሉን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436 ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተድርጎላቸውም ሞግዚታቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ ባቀረቡት ክርክር በይዘቱ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ክርክር በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎቸ በአመልካች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት ሴት አያታቸውን ሟች ወ/ሮ ጌጤ ለገሰን የእኚሁ ሴት ልጅ የሆነውንና ሴትዩዋን ቀድሞ የሞተውን አቶ በቀለ በየነን በመተካት በውርስ የሚያገኙትን ቤት የአሁኑ አመልካች ያላግባብ ይዞ ይገኛል በሚል ምክንያት መሆኑን፣አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ደግሞ በስጦታ ውሉ ላይ ስጦታ ተቀባይ የሆኑት አመልካች ባይፈርሙም ሟች ወ/ሮ ጌጤ ለገሰ በ24/03/1996 ዓ/ም ስጦታ አድርገውላቸው የቤቱ ስመ ሀብት እንዲዞር ለሚመለከተው አካል ማመልከቻ አስገብተው ጉዳዩ በመጣራት ላይ እንዳለ ወ/ሮ ጌጤ ለገሰ ከዚህ አለም በሞት የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ/ም የተለዩ መሆናቸውን ገልፀው ስጦታውን በተግባር የተቀበሉ መሆኑን ያሳያል በሚል መሆኑን ነው፡፡

አመልካች ስጦታ በሟች ወ/ሮ ጌጤ ለገሰ ተደረጎልኛል የሚሉት ሕዳር 24 ቀን 1996 ዓ/ም ሲሆን ሟች ከዚኅ አለም በሞት የተለዩት የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ/ም መሆኑንና እስከዚህ ጊዜ ድረስ የስመ ሀብት ዝውውር ማመልከቻ ቀርቦ ነበር ከማለት ውጪ አመልካች ቤቱን በይዞታቸው ስለማድረጋቸው ያለመረጋገጡንም ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባሉት የስጦታ ውል ከሟቹ ህልፈተ ሕይወት በኋላ ተፈፃሚ የሚሆነው ነው፡፡ በእንደዚህ አይነት የስጦታ ውል ስለኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 ድንጋጌ በኃይለ ቃል ያስቀምጣል፡፡በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2443 ስር ደግሞ በማይንቀሳቀስ ንብረት የሚደረግ ሥጦታ በግልፅ በሚደረግ ኑዛዜ አሰራር አይነት ካልተደረገ ፈራሽ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ አሰራር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 881 ስር ተመልክቷል፡፡እንዲህ ከሆነ የሟች ሕጋዊ እና የኑዛዜ ወራሾች የስጦታው አሰራር በሕጉ የተቀመጠውን አሰራር የተከተለ መሆን ያለመሆኑን መሰረት አድርገው ክርክር ሲያቀርቡ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን በመመልከት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስጦታ ውሉ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን በግራ ቀኙ ክርክር የቀረበበት ሲሆን የተጠሪዎች ሞግዚት አጥብቀው የሚከራከሩት የስጦታ ሰነዱ በሕጉ አግባብ ያልፀደቀና አመልካችም ያልፈረሙበት ነው በሚል ነው፡፡የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436(1) ድንጋጌ ሲታይም የስጦታ ውል ፍጹም የሚሆነው ስጦታ ተቀባዩ ለእርሱ የተደረገውን ልግስና እቀበላለሁ ብሎ አሳቡን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የገለጸ እንደሆነ ስለመሆኑ ያስቀመጠ ሲሆን በተጠቃሹ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ደግሞ ሰጪው ከሞተ ወይም ችሎታ ከአጣ በኋላ ስጦታውን እቀበላለሁ የማለት ቃል ዋጋ የለውም የሚል ሃይለ ቃል በያዘ መንገድ ተቀምጧል፡፡ሁለቱ ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩም የመቀበሉ አሳብ በፅሑፍ ይሁን በድርጊት ለይተው ያስቀመጡት ነገር የሌለ ሲሆን ከድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ በዚህ ረገድ መገንዘብ የሚቻለው የስጦታው መቀበሉ ሀሳብ በፅሑፍ(ፊርማ) ወይም በድርጊት መቀበል የሚቻል መሆኑን ነው፡፡ስለሆነም ስጦታ ተቀባዩ ስጦታውን ስለመቀበሉ የሚያስረዳ የጽሁፍ ማስረጃ ወይም ስለመቀበሉ ጠቋሚ የሆነ ድርጊት ስለመኖሩ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ስጦታ ውሉ ላይ ያልፈረሙ ስለመሆኑ የሚክዱት ፍሬ ነገር ሳይሆን ስጦታውን መቀበላቸውን ያሳያል በማለት የሚከራከሩት በቤቱ ላይ ግብር መገበራቸውን፣ቤቱ ላይ እድሳት ማድረጋቸውንና ሚች በወቅቱ የስጦታ ውሉን ይዘው ወደሚመለከተው አካል ቀርበው ስመ ሃብቱ ለአመልካች እንዲዞር አቤቱታ አቅርበው የነበረ ስለመሆኑ መረጋገጡን ነው፡፡ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለጸው የስጦታ መቀበል ተግባር መኖር ያለመኖሩ በጽሑፍ ማስረጃ ወይም በድርጊት ወይም በሌላ አግባብነት ባላቸው መንገዶች የሚረጋገጥ ሁኖ እነዚህ ፍሬ ነገሮች መኖር ያለመኖራቸውን ፍሬ ነገሩን ለማረጋገጥ እና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የሚያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን በዚህ አግባብም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የስጦታ ተቀባዩ እቀባለለሁ ስለማለቱ ሊያሳዩ የሚችሉ አይደሉም፣ሊታመኑም የሚችሉ አይደሉም በማለት ደምድሞ ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሙሉ በሙሉ ተቀብሎታል፡፡

በመሆኑም አመልካች ስጦታውን አልተቀበሉም ተብሎ ድምዳሜ የተደረሰው ፍሬ ነገሩ ተጣርቶና ማስረጃው ተመዝኖ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አንቀጽ 25/1988 አንቀጽ 10 ተለይቶ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር አመልካች ስጦታውን ስለመቀበላቸው ያሳያሉ በማለት የሚጠቅሷቸው ማስረጃዎች ታዓማኒነት እና ክብደት በዚህ የክርክር ደረጃ የሚታዩ ሁኖ አላገኘንም፡፡ አመልካች ሚች ከመሞታቸው በፊት ስጦታውን መቀበላቸው አልተረጋገጠም ከተባለ ደግሞ ከስጦታ ሰጪው መሞት በኋላ የስጦታ ውሉን እቀበላለሁ ቢሉ በሕጉ ዋጋ የሚሠጠው ተግባር ያለመሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436(2) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436(2) ድንጋጌን በመተርጎም ረገድ የፈጸሙት ስህተት የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት የስጦታ ውሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 ድንጋጌን ያላሟላ ነው በማለት የያዘው ምክንያት ሲታይ ግን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 ለስጦታ ውል ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 39803 ሐምሌ 02 ቀን 2001 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ምክንያቱ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት የብድር ጉዳዩን በተመለከተ ለውሳኔው አሰጣጥ በምክንያትነት መያዙም ሆነ ብድሩ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ረ) መሰረት እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው በማለት መደምደሙ ለክርክሩ አግባብነት የሌለው ሲሆን የክፍያ ግምት በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም በፍርድ ቤት ሊነሳ ይችላል ተብሎ በሰ/መ/ቁጥር 15493 ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁጥር 47988 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት የተለወጠ ስለመሆኑ ያላገናዘበ በመሆኑ ምክንያቱ ተቀባይነት የሌለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 እና ስለብድሩ የቀረበውን ክርክር በተጨማሪ ምክንያትነት በመያዝ የስጦታ ውሉ ፈራሽ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱበት አግባብ ተገቢ ባይሆንም የስጦታ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436(2) መሰረት ዋጋ የለውም በሚል የያዙት አብይ ምክንያትና ቤቱን አመልካች ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ ሲሉ የሰጡት የውሳኔ ክፍል ግን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በምእራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 27822 መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 289942 ሚያዚያ 14 ቀን 2002 ዓ.ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 09032 ሐምሌ 23 ቀን 2002 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች የሥጦታ ውሉን ስጦታ አድራጊዋ ከመሞታቸው በፊት የተቀበሉ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም ተብሎ በ24/03/1996 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የስጦታ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2436 መሰረት ዋጋ የለውም፣ቤቱን ለተጠሪ ሕፃናት እንዲያስረክቡ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች በቤቱ ላይ ያወጡትን ወጪ በሕጉ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት በ25/02/2003 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ለሚመከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቶች፡ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ - ነ/ፈጅ እንግዳወርቅ ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ- አቶ ተመስገን ማጉሌ } አልቀረቡም
2ኛ- ዶ/ር ብዙአየሁ ተስፋዬ }

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ከዋስትና ውል የመነጨ ግዴታ የሚጠየቅበትን አግባብ በሚመለከት በክልሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የህግ ትርጉም ግራ ቀኙ በሰበር ደረጃ ካደረጉት ክርክር ጋር በማገናዘብ ተገቢውን የህግ ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ 1ኛ ተጠሪ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር ለመማርና ተምሮ ሲጨርስ አገልግሎት ለመስጠት አመልካችም የሚጠበቅበትን ተነፃፃሪ የገንዘብ ክፍያ ለመፈፀም ጥቅምት 03 ቀን 2001 ዓ.ም ውል አድርገው በውሉም መሠረት 2ኛ ተጠሪ ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ 23 ወራት ያህል ከተማረ በኋላ ከስምምነቱ ውጭ ወደ ሌላ / ጣሊያን / ሀገር ስለሄደ ግዴታውን ጥሷል፡፡ ስለሆነም እንደውሉ ባለመፈፀሙ በጠቅላላው ብር 195,796 ብር ሊከፍል ይገባል 2ኛ ተጠሪም ከዋናው ባለዕዳ ጋር ከዋስትና ግዴታ የመነጨ የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ስላለባቸው ይክፈሉ ሲል የአሁን አመልካች በሥር በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ያቀረበው ክስ ሲሆን ተጠሪዎችም በየግላቸው መልስ ሰጥተዋል፡፡ ዋናው ባለዕዳ የተባለው 1ኛ ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት የውል መፈፀሚያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት እንደግዴታው እንዲፈፅሙ ሊጠየቁ እንደማይገባ ገልፀው ክሱ በነሳ እንዲሰናበቱ የጠየቁ ሲሆን፤ 2ኛ ተጠሪም በበኩላቸው የ1ኛ ተከሣሽ እምቢተኛ መሆኑ ሳይረጋገጥ መከሰሴ አግባብ አይደለም የግዴታውም ዓይነት ተራ ዋስትና በመሆኑ ከሣሽ ለግዴታው አፈፃፀም የዋናውን ባለዕዳ ንብረት ከመከተል ያለፈ ኃላፊነት ስለማይጥል የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤትም ይህንኑ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ተመልክቶ ሚያዚያ 12 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክሱ የቀረበው የግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ስለሆነ የግዴታው መፈፀሚያ ጊዜ ከደረሰ በኋላ ከሚጠይቅ በቀር በዚህ ደረጃ ላይ ተከሣሾችን ለመክሰስ አይችልም በማለት ዳኝነት የሰጠ ሲሆን ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይሄው የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ለይግባኝ ሙሉ ክርክር የሚያበቃ ሆኖ አልተገኘም በማለት የውሣኔውን አግባብነት ተቀብሎታል ::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ የሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያቀረቡትም ክርክር በይዘቱ በሥር ፍ/ቤት ከቀረቡት የተለየ ሆኖ ባለመገኘቱ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

ግራ ቀኙ በፍሬ ነገር ክርክር ደረጃ ካቀረቡት ክርክር አንፃር ሁለቱንም ወገኖች ያለያያቸውን ነጥብ ለይቶ በዚሁ ላይ ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ዳኝነት በመስጠት ረገድ በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው 1ኛ ተጠሪ የውሉ ግዴታ መፈፀሚያ ጊዜ ከመድረሱም በፊት ቢሆን በእራሱ ተግባር የተነሣ እንደ ውሉ ግዴታውን ለመፈፀም በማይችልበት ደረጃ ተገኝቷል ወይስ አልተገኘም? የሚለው እንጂ የግዴታ መፈፀሚያው ጊዜ ደርሷል ወይስ አልደረሰም የሚለው ጭብጥ አልነበረም፡፡

በዚህም ረገድ አመልካች እንደሚለው ተዋዋዩ ሃያ ሶስት ወራት በውሉ በተጠቀሰው አገር ከተማረ በኋላ ከተዋዋዩ ፈቃድ ውጪ በእራሱ አነሳሽነት ወደ ሌላ አገር መሣወሩ ከተረጋገጠ የተሣወረበት ምክንያትም በዋናው ውል ከተጠቀሰው ተግባር ጋር የተያያዘም አይደለም ከተባለ እና ይህ በማስረጃ የሚረጋገጥ ከሆነ 1ኛው ተከሣሽ እንደውሉ የመፈፀሚያው ጊዜ ከመድረሱ በፊት ውሉ ውጤት እንዳይኖረው በማድረግ እንደውሉ ግዴታውን ለመፈፀም የተሣነው በመሆኑ የውሉ መፈፀሚያ ጊዜ ከመድረሱም በፊት መረጋገጡን ስለሚያሳይ ከሣሹ የግድ የውሉ መፈፀሚያ ከደረሰ በኋላ እንጂ ከዚያ በፊት ከውል የመነጨ መብትህን ማረጋገጥ አትችልም ሊባል አይገባም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡትን ክርክር ተመልክቶ ተገቢውን ጭብጥ በመለየት ጉዳዩን ከመምራት አንፃር የተከተለው የጉዳይ አመራር ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ ተከሣሽ እንደ 1ኛ ተከሣሽ ሆኖ ለመፈፀም የገባው የዋስትና ዓይነት ተራ ዋስትና ነው ወይስ የአንድነትና የነጠላ? 1ኛው ተከሣሽ ግዴታውን ለመፈፀም እንዳልቻለ ተረጋግጧል ቢባል ሊከፈል የሚገባው ገንዘብ ምን ያህል ነው? የሚለውን አስመልክቶ ግራ ቀኙ በሥር ፍ/ቤትም ሆነ በዚህ ሰበር ደረጃ አንስተው የተከራከሩበት ቢሆንም በእነዚህ ነጥቦች ላይ የሥር ፍ/ቤት ዳኝነት ያላሳረፈበት በመሆኑ በዚህ ደረጃ የምንመለከተው አይደለም፡፡ ከዚህ በላይ በፍርዱ በተመለከተው ሐተታ ምክንያት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በፍ/ብ/ መ/ቁ 09829 ሚያዚያ 12 ቀን 2003 ዓ.ም ፤ የሰጠው ውሣኔ ፤ እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በቁጥር 53210 በ16/9/2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በፍርዱ ሐተታ በተመለከተው ጭብጥ መሠረትም ሆነ በክርክር ምክንያት ከባከነው ጊዜ አንፃር በመካከሉ የተከሰቱትን ሁኔታዎች ሁሉ አገናዝቦ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት ወደ ሥር ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡ ግልባጩ ይተላለፍ፡፡
3. የዚህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ማናቸውም ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 36887

ሕዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልጋነሽ አበበ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ገብሩ እሸቱ ገብሬ ቀርበዋል

2. ወ/ሮ ወርቂት እሸቱ ሁሴን ቀርበዋል

ጉዳዩ ከተመረመረ በኋላ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በጠ/ፍ/የፍ/ይ/መ/ቁ. 1051/99 የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካቾች መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ በመጠየቃቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት የአሁኗ አመልካች ከሳሽ፣የአሁኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች የነበሩ ሲሆን በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ደግሞ የአሁኑ ተጠሪዎች ይግባኝ ባይ እንዲሁም የአሁኑ አመልካች መልስ ሰጭ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የስር ከሳሽ ጥቅምት 28 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘቱ ተከሳሾች በኩታበር ከተማ፣ቀበሌ 01 የሚገኘውን በ500 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈውን ሁለት ክፍል የቆርቆሮ ቤት በመስከረም 13 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል በብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) ሸጠውልኝ ገንዘቡንም ሙሉ በሙሉ ተቀብለው እያለ ቤቱን እንዲያስረክቡና ስመ ንብረትነቱም ስላላዞሩልኝ ተገደው እንዲያስረክቡኝና ስመ ንብረቱም በስሜ እንዲያዞሩልኝ ውሳኔ ይስጠኝ የሚል ነው፤ውሉ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮም የቤቱን ኪራይ በወር ብር 60 (ስድሳ ብር) ሂሳብ የ26 ወራት ይክፈሉኝ ብለዋል፡፡

ተከሳሾችም በሰጡት መልስ ስልጣኑ የወረዳ ፍ/ቤት በመሆኑ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ የማከራከር ስልጣን እንደሌለው እንደተቃወሙና ውሉን ፈጽመን ገንዘቡን ከተቀበልን በኋላ ውሉ እንዳፈረስንና ገንዘቡን እንዲወሰዱ ለከሳሹ ቢያሳውቋቸውም ገንዘባቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆኑም፤ በመሆኑም የውሉ ይፈፀምልኝ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም ብለዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን እንደሚያይና በከሳሽና ተከሳሽ መካከል ከመጀመሪያውኑ ጀምሮ ውል መኖሩ የታመነ በመሆኑና እንደውሉ ላለመፈፀም ያቀረቡት ምክንያት ተቀባይነት ስለሌለው ተከሳሾች ውሉን ተገደው እንዲፈጽሙ፣ስመ ንብረቱንም በከሳሽ ስም እንዲያዞሩ እንዲሁም የቤቱን ኪራይ ብር 1500 ለከሳሽ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱ በሰጠው ፍርድ ቅሬታ በማሳደር የስር ተከሳሾቹ ወደ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታቸውን አቅርበው ከተከራከሩ በኋላ ፍ/ቤቱ በፍ/ይ/መ/ቁ.1051/99 የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በግራ ቀኙ ወገኖች ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ወደ ደቡብ ወሎ አስ/ፍ/መምሪያ የውልና ማስረጃ አካል ቀርቦ በመጣራት ላይ እያለ የቆመ በመሆኑና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ መሰረት ያልተፈፀመ በመሆኑ በመካከላቸው የሚጸና ውል እንደሌለና ተዋዋዮቹ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 መሰረት ወደ ነበሩበት ይመለሱ፣ ስለሆነም ይ/ባዮች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) ለመልስ ሰጪ የነበሩት የአሁኗ አመልካች እንዲመልሱ ወስኗል፡፡

ይህ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካች መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. የተፃፈ አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም ውሉ በጽሁፍና በምስክሮች ፊት የተፈፀመና ለምዝገባም ወደሚመለከተው አካል ቀርቦ እያለና ተጠሪዎች ውሉን ማድረጋቸውና ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) ወስደው እንደነበር አምነው እያለ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1723/1/ን መሰረት በማድረግ ውሉ በአዋዋይ ፊት አልተመዘገበም በሚል አተረጓጎም ውል የለም ማለቱ ተገቢ አይደለም፣ በመካከላቻው ውል መኖሩን አምነው ባለመመዝገቡ ብቻ ውል የለም ብለው ለመከራከር ለሚቃጡ ተከራካሪዎች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ አያገለግልም የሚል ሆኖ ተጠሪዎች በሰጡት መልስም ውሉ በሚመለከተው አካል ያልተመዘገበና በእንጥልጥል የቀረ በመሆኑ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሌለ እንዲጸድቅላቸው ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ በአጭሩ እንደተመለከተው ሲሆን ይህ የሰበር ችሎትም፣በመካከላቸው ውል አድርገው እንደነበር እያመኑ የቤት ሽያጩ በውልና ማስረጃ ባለመመዝገቡ ብቻ ምክንያት በማድረግ ውላቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ን መሰረት በማድረግ ተቀባይነት የለውም ሊሉ ይችላሉ ወይስ አይችሉም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በማስቀመጥ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል እንዳካሄዱና ተጠሪዎች የሸያጩ ጠቅላላ ገንዘብ ብር ለተጠሪዎቹ እንደሰጡ ሲገለጽ በስር ተከሳሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎችም ውል አድርገው የነበረ ቢሆንም በውልና ማስረጃ የተመዘገበ ባለመሆኑ የሰጧቸው ገንዘብ ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) እንዲወስዱ ቢጠይቋቸውም ለመውሰድ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቤቱን እንደሚያስረክባቸው ገልጸዋል፤ በዚህም የተጠሪዎች መልስ ከአመልካች ጋር የቤቱን ሽያጭ ውል አድርገው እንደነበር እንጅ ውሉ በመካከላቸው እንዳልነበረ ፈጽሞ የሚክዱ አይደለም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 21448 ሚያዝያ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ እና 2878 አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል እንደነበር አምነው በውልና ማስረጃ አካል ባለ መመዝገቡ ብቻ ውል የለም፤ ብለው የሚቃወሙ ተከራካሪዎችን የሚያጠቃልል አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ መሰረት የሚከናወነው የምዝገባ ዋና አላማ በተዋዋይ ወገኖች የቤት ሽያጭ ውል ለመኖሩ በማስረጃነት እንዲያገለግል ሆኖ ውል ማድረጉና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘብም ተቀብሎ እንደነበር አምኖ ውሉ አልተመዘገበም በሚል ምክንያት ብቻ መቃወሙ ከላይ ከተቀመጠው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ዓላማ ጋር የሚሄድ አይደለም፡፡ ስለሆነም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፤ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በሕግ የሚጸና የቤት ሽያጭ ውል አለ ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ. 013132 ሐምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፤የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በጠ/ፍ/የፍ/ይ/መ/ቁ. 1051/99 የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የስር ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች በስር ተከሳሽ የአሁኑ ተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት የቤት ሽያጭ ውል መፈጸም ጉዳይ በሚመለከት ተጠሪዎቹ የውሉ መኖርን አምነው የተከራከሩ በመሆናቸው በውልና ማስረጃ ያልተመዘገበ ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ መሰረት መቃወም አይችሉም፤የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ሁኔታ የሰጠው አተረጓጎም ተገቢነት የለውም፤ስለሆነም ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ለአመልካች ያስረክቡ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፤ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 64887

ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች ፡- አቶ አደም የሱፍ ቀረበ

ተጠሪ ፡- አቶ አብዱሰላም መሐመድ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤተታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የአሁን ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርቦ ያደራ መቻሬ መንገድ በንብረቱ ላይ በመውጣቱ ምክንያት መስከረም 9 ቀን 2001 ዓ.ም. ብር 86,440 /ሰማንያ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ብር/ ካሣ ተሰጥቶኝ ተከሣሽ /አመልካች/ የባለቤቴ ዘመድ ስለሆነ ይህንን ገንዘብ ገጠር ይዘህ አትሂድ ይገድሉሀል ገንዘቡን እኔ በአደራ ላስቀምጥልህ ብሎኝ መስከረም 13 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰው ማስረጃ ባለበት ብር 70,000 /ሰባ ሺህ ብር/ እንደታሰረ ሰጥቸዋለሁ፡፡ ተከሣሽ በአደራ የሰጠሁትን ገንዘብ እንዲሰጠኝ ብጠይቀው ሊሰጠኝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገንዘቤን እንዲከፍል ይወስንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከከሣሽ በአደራ የተቀበልኩት ገንዘብ የለም፡፡ ከብር 500 /አምስት መቶ ብር/ በላይ ብድር ወይም የአደራ ገንዘብ በሰው ማስረጃ ለማስረዳት አይቻልም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተከሣሽ /አመልካች/ ከከሳሽ /ተጠሪ/ በአደራ ገንዘብ የተቀበለ መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ሊመልስ ይገባዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቦ የነበረ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ምንም አይነት የሰነድ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ብር 70,000 እንዲከፍል በህግ ተቀባይነት የሌለውን የሰው ምስክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመስማት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እንደ እኔ ካሣ ተቀብለው ገንዘቡን ገጠር የወሰዱ አርሶ አደሮች በመዘረፋቸው ገንዘቡን ይኸው ገጠር ብሄድ የዘረፋ ወንጀል ሊፈፀምብኝ ይችላል በሚል ፍርሃት የሰው ምስክሮች ባሉበት የሰጡት አደራ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመተርጎም የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርቧል አመልካች መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ከተጠሪ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ እንዲከፍል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች በፍሬ ጉዳይ ደረጃ የደረሱበትን መደምደሚያ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ በመንገድ ሥራ ምክንያት በንብረቱ ላይ ለደረሰበት ጉዳት ከመንግስት ከተከፈለው የካሣ ገንዘብ ውስጥ ወደምኖርበት የገጠር ቀበሌ ይዤው ብሔድ ሰዎች ሊገድሉኝና ሊዘርፋኝ ይችላሉ በሚል ምክንያት ብር 70,000 /ሰባ ሺህ ብር/ እንደታሰረ ለተጠሪ በአደራ የሰጠ መሆኑን የግራ ቀኙን ምስክሮች በመስማት አረጋግጠዋል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2782 በአደራ ስለሚቀመጥ አላቂ ዕቃ ከሚደነግገው በተለየ ሁኔታ ተጠሪ ለአመልካች ገንዘቡን በአደራ መስጠቱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አንድ ሰው የራሱ ንብረት በሆኑት ዕቃዎች ላይ የማይታገድ እርግጠኛ አደጋ የሚደርስባቸው በሆነ ጊዜ እነዚህን ዕቃዎች ከቀረበው አደጋ ለማሸሽ ሲል ሌላ ሰው በአደራ ተቀብሎ እንዲያስቀምጥለት የሰጠ እንደሆነ ይህ አድርጎት አስፈላጊ አደራ የማስቀመጥ ድርጊት የሚል ልዩ የህግ ዕውቅናና ጥበቃ እንደሚሰጠው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2800 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አስፈላጊ የአደራ ማስቀመጥ ጉዳይ በማናቸውም የአሠራር ሥርዓት ነፃ እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2802 ንዑስ አንቀፅ 1 የሚደነግግ ሲሆን አንድ ሰው አስፈላጊ አደራ ለሌላ ሰው የሰጠ መሆኑን በማናቸውም አይነት መንገድ ማስረጃ ማቅረብ እንደሚችል የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2802 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡

ከላይ ይዞታቸው ከተገለፀው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠውን የፍሬ ጉዳይ ስናገናዝበው ተጠሪ በካሣ መልክ የተቀበለውን ገንዘብ ወደሚኖርበት ገጠራማ ቦታ ቢወስደው ደህንነቱን ጠብቆ ለማቆየትና ገንዘቡን ለማስቀመጥ የማይችል በአንፃሩ ገንዘቡን ለመዝረፍ ሲሉ ሰዎች ሊገድሉት የሚችሉ መሆኑን በግልፅ ለአሁን አመልካች በማስረዳት ብር 70,000 እንዲያስቀምጥለት የፈፀመው ተግባር በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2782 የተገለፀው አላቂ ዕቃ በአደራ የመስጠት ተግባር ሣይሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2800 ልዩ ትርጉም ህጋዊ ዕውቅናና ጥበቃ የተሰጠው አስፈላጊ የሆነ አደራ የመስጠት ተግባር ነው፡፡ ተጠሪ የፈፀመው አስፈላጊ የሆነ አደራ የመስጠት ተግባር ማናቸውንም አይነት ማስረጃ በማቅረብ ለማስረዳት እንደሚችል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2802 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች ብር 70,000 አስፈላጊ የሆነ አደራ ሲሰጥ ያዩትን ምስክሮች ቃል በመስማትና በመመዘን የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2782 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2472 ድንጋጌዎች በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን የህግ ግንኙነት ለመወሰን ተፈፃሚነት የሌላቸው ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ድንጋጌዎቹ ስለሚያልቅ ነገር አደራ አቀማመጥና የሚያልቅ ነገር በአደራ የተሰጠ ስለመሆኑ ማስረዳት ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚደነግጉ ጠቅላላ ድንጋጌዎች ሲሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2802 በልዩ ሁኔታ ስለአስፈላጊ አደራ አቀማመጥና አስፈላጊ አደራን ስለማስረዳት የሚደነግግ ልዩ ድንጋጌ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰው ምስክር በመስማት የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2782 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2472 ድንጋጌዎችን የሚጥስ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ ስላላገኘነው አልተቀበልነውም፡፡

2. አመልካች ተጠሪ በአስፈላጊ አደራ ብር 70,000 የሰጠኝ መሆኑን ባቀረበው ማስረጃ አላስረዳም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች ብር 70,000 እንደታሰረ በአስፈላጊ አደራ እንዲቀመጥለት የሰጠው መሆኑን ባቀረባቸው ምስክሮች ከአመልካች በተሻለና ሚዛን በሚደፋ ሁኔታ እንዳስረዳ በውሣኔቸው በግልፅ አስፍረዋል፡፡ አመልካች ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ በመካድ በሰበር ደረጃ ያቀረበው ክርክር ሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2800 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2802 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አመልካች ከተጠሪ የተቀበለውን የአስፈላጊ አደራ ብር 70,000 እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የካቲት 2 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሸ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 60217
ጥቅምት 15 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. ም/ኢ/ር ኃይላይ አስገለ ጠበቃ ም/ኮ ደጀኔ ወንድምነህ ቀረቡ

2. ም/ኮማንደር ይልማ ጥላሁን

ተጠሪ፡- የቤ/ን/ፍትሕ ቢሮ 0/ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የጉዳዩ መነሻ ተጠሪ 0/ሕግ አመልካቾች በ1949 ዓ/ም በወጣው የወ/መ/ሕግ ቁጥር 36(1)(ለ) ፣ 27(1) እና 523 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካቾች በአሶሳ ከተማ ክልል ውስጥ ልዩ ስፍራው ግሪን ሆቴል ተብሎ በሚጠራው ቦታ ሐምሌ 09 ቀን 1993 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 2፡15 በሚሆንበት ጊዜ በወንጀሉ ስራና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋዮች ሁነው ባልታወቀ ምክንያት ተነሳስተው የግል ተበዳይ አብዱል መሀሙድ ኢብራሂም የተባለውን ለመግደል አስበው፤ 1ኛ አመልካች ይዞት በነበረው ሽጉጥ ሁለት ጥይት ተኩሶ የግል ተበዳይን ቀኝ እጅ በመምታት እንዲሁም 2ኛ አመልካች ከወንጀሉ ድርጊት በፊትና በሂደቱ ወራ በማቀበል፣ ዘይ በመፍጠርና አንድ ጥይት በመተኮስ ሰውን የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ በማቅረቡ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአቃቤ ሕጉን ክስ ለአመልካቾች በግልጽ ችሎት አንብቦላቸው እንዲረዱ ከአደረገ በሁዋላ በክሱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በመጠየቅ ሁለተኛው አመልካች ክሱን እቃወማለሁ በማለት ምክንያታቸውን ገልፀው ተቃውሞ ያስመዘገቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎ ስለድርጊቱ አፈጻጸም አመልካቾችን የእምነት ክህደት ቃል ጠይቆ የድርጊቱን አፈፃፀም በመካዳቸው ምክንያት አቃቤ ሕጉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከል መብታቸው ተጠብቆላቸው መከላከያ ምስክሮቻቸውን ከአሰሙ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾችን መከላከያ ማስረጃ የአቃቤ ሕጉን ማስረጃ ለማስተባበል ብቃት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ ውድቅ ከአደረገ በሁዋላ አመልካቾችን በአቃቤ ሕጉ ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማድረግ እያንዳንዳቸውን በ 5 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይኸው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማፅናት ቅጣቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተመለከተ ግን 1ኛ አመልካችን በአራት ዓመት ፅኑ እስራት፣ 2ኛ አመልካችን ደግሞ በሶስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ በማለት በማሻሻል ወሰኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ሰበር ችሎቱ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አቃቤ ሕግ ከሰባት አመት በፊት ጉዳዩ አያስከስስም በማለት መዝገቡን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 42(1(ሀ)) ከዚጋው በሁዋላ እንደገና ክስ መመስረቱ ሕጋዊ ያለመሆኑንና የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችም የአመልካቾችን የወንጀል ተሳትፎ በበቂ ሁኔታ ባላስረዱበት እንዲሁም የአመልካቾች የመከላከል መብት ባግባቡ ባልተጠበቀበት አመልካቾች ለወንጀሉ ተጠያቂ መደረጋቸው ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በ1993 ዓ/ም በተፈጸመ ድርጊት ሆኖ ዐቃቤ ሕግ በ1994 ዓ/ም አያስከስስም በማለት ክሱን ከዚጋው ከሰባት አመት በሁዋላ በዚያው ድርጊት ጥፋተኛ ተብለው የመቀጣታቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪን ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምሮታል፡፡

አመልካቾች በጉዳዩ ላይ ድጋሚ ክስ ቀርቧል የሚሉበት ምክንያት የስር የዞኑ አቃቤ ሕግ በመጀመሪያ በጉዳዩ ላይ የተከናወነውን ምርመራ ተመልክቶ የተሰበሰበው ማስረጃ ክስ ለማቅረብ የማያስችል ነው በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 42(1(ሀ)) ዘግቶት ከቆየ በሁዋላ ከሰባት አመታት በሁዋላ ክሱን ማቅረቡ ተገቢነት የለውም በማለት ነው፡፡ ከዚህ የአመልካቾች ክርክር መገንዘብ የሚቻለው አመልካቾች በአንድ ጉዳይ ሁለት ጊዜ ልንከሰስ አይገባም በማለት በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የሚከለክለውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 23 ድንጋጌንና በዚህ ረገድ ተቀባይነት ያለውን የወንጀል ሕግ ፅንሰ ሀሳብ መሰረት በማድረግ የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ችሎቱም የዚህን የወንጀል ሕግ ጽንሰ ሀሳብ ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሰረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና የማይከሰስ ወይም የማይቀጣ መሆኑን ጽንሰ ሃሳቡ እንደሚያስገነዝብና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትም ይህንኑ በግልፅ የሚያስቀምጥ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በመሆኑንም በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የተከለከለው የመጨረሻ ውሳኔ በሆነ ጥፋተኝነቱ በተረጋጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል ሲሆን ነው፡፡ በዚህም መሰረት በወንጀል ሥነ ሥርዓቱ ለአቃቤ ሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ጉዳዩ ክስ ለመመስረት የሚያስችል አይደለም በማለት ተጠርጣሪውን በነፃ የመልቀቅ የውሳኔ ሃሳብ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የመከልከልን ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም፡፡ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የመከልከሉ ጥያቄ በፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ ተገቢ ነው የተባለ ውሳኔ መሰጠቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በዚህ ረገድ ያነሱት የሕግ ክርክር ስለድጋሚ ቅጣት ክልከላ መርህ (principle of double jeopardy) የተቀመጡትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን የሕግ ማስረጃዎች ክብደት እንዲሁም በክርክሩ አመራር የስር ፍርድ ቤት የተከተለውን ሥነ ሥርዓት የሕግ ግድፈት ያለበት መሆኑን አጥብቀው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካቾችን የክርክር ነጥብ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ጉዳዩን ከሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሰረት የስር ፍርድ ቤት አመልካቾችን ለድርጊቱ ኃላፊ ያደረጋቸው የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን በመስማትና ቃላቸው ለጉዳዩ አግባብነት፣ ክብደት ያለው መሆኑን በማመን አመልካቾች በመካላከያ ማስረጃዎቻቸው እንዲያስተባብሉ የመከላከል መብታቸውን በመጠበቅ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃዎችን ከሰማ በሁዋላ የመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ለማስተባበል የማይችሉ መሆኑን ዘርዝሮ ቃላቸውን ውድቅ በማድረግ መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አቀራረብ የስር ፍርድ ቤት ተገቢውን ሥነ ሥርዓት አልተከተለም ይበሉ እንጂ የአመልካቾች የመካላከል መብት ተጠብቆ ውሳኔ መሰጠቱን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተነሳው የአመልካቾች ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ክብደትን በተመለከተ ያቀረቡትን ቅሬታ ስንመለከተውም ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑና ይህ ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት ለዚህ ሰበር ችሎት ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ማረም ስልጣን ስር የማይወድቅ ወይም የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የማያሟላ በመሆኑ የምንቀበለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2717 ሚያዚያ 25 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02276 ሐምሌ 16 ቀን 2002 ዓ/ም ተሻሽሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02429 ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ/ም የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ውሳኔው የጸና መሆኑን እንዲያውቀው ለማረ/ቤቱ ይፃፍ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 67874

ጥቅምት 23 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡ ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- 1. አቶ ፅጌብርሃን ተሰራ
2. አቶ መስፍን አበበ } ጠበቃ መሠረት ተፈራ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን አቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉምሩክ ወንጀል ድርጊት ተፈጽሟል በሚል የቀረበውን ክስ ተከትሎ የተነሳውን የዋስትና ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ በጉዳዩ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሳሽ የሆነው የተጠሪው ባለስልጣን አቃቤ ሕግ በአመልካቾችና በሌሎች በርካታ ሰዎች ላይ ክስ መስርቷል፡፡ በአመልካቾች ላይ የቀረበው ክስ አንድ ሁኖ አመልካቾች የጉምሩክ ባለስልጣንን ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 60/1989 በአዋጅ ቁጥር 368/1995 እንደተሻሻለ በአንቀጽ 67 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ 1ኛ አመልካች በስር ፍርድ ቤት 5ኛ ተከሳሽ የሆነውንና በጉምሩክ አስተላላፊነት ስራ ላይ የተሰማራ ዩኒቨርሳል ሎጂስቲክ ሰርቪስ ኃ.የተ.የግል ማህበር የተባለውን ድርጅት በስራ አስኪያጅነት ሲያስተዳድሩ ፣ 2ኛ አመልካች ደግሞ የዚሁ ድርጅት በሰነድ ምርመራ (ኦፊሰር) ሰራተኛነት የስራ ኃላፊነት ሲያከናውኑ በመላው ሃሳባቸውና አድራጎታቸው ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት በመቀበል ለመንግስት በጠቅላላ ሊከፍል የሚገባ ብር 21,602,608.64(ሃያ አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሁለት ሺኅ ስድስት መቶ ስምንት ብር ከስልሳ አራት ሳንቲም) ሳይከፈል ወደ ሀገር ውስጥ የገባው ሲሚንቶ በሕገ ወጥ ጥቅም ላይ እንዲውል አድርገዋል በሚል አንድ ክስ መመስረቱን የአቃቤ ክስ ይገለፃል፡፡ አመልካቾች የዋስትና ጥያቄ ያቀረቡት በክሱ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የዋስትና መብት የሚያስነፍግ አይደለም በማለት ሲሆን አቃቤ ሕግ ደግሞ ይህንኑ የአመልካቾችን ጥያቄ የተቃወመው በአመልካቾች ላይ የተመሰረተው ክስ ከበድ ያለ ቅጣት የሚያስከትል በመሆኑ ምስክሮችን በማባበል ማስረጃ ሊያጠፉ ስለሚችሉና ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ይችላሉ የሚሉ ምክንያቶችን በማንሳት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67(ሀ)፣(ለ) እና (ሐ) ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ከዚህም በኋላ የስር ፍርድ ቤት ከሁለቱም ወገኖች የቀረበውን ክርክር መርምሮ እና በዚህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 59304 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በማድረግ በዚህ ውሳኔ መሰረት የስር ፍርድ ቤት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67 መሰረት ብይን ሲሰጥ በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ግምት ወስዶ የሚያስተናግዳቸው ስለመሆኑ መተርጎሙን ግንዛቤ ወስዶ አመልካቾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከሰሱት የወንጀል ክስ እስከ ሃያ አምስት አመት በሚደርስ እስራትና ከሃያ አንድ ሚሊዮን ብር በላይ መቀጮ ሊያስቀጣ የሚችል ነው ፣ የኢኮኖሚ አቅማቸውም ቀላል አይደለም ፣ ምስክሮችንም አያባብሉም ፣ የዋስትና ግዴታቸውንም አክብረው ችሎት ይቀርባሉ ብሎ ፍርድ ቤቱ ሊገምት አይችልም የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ የአመልካቾችን የዋስትና መብት በመንፈግ ማረሚያ ቤት ሁነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፊዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

እኛም የአመልካቾች ጠበቃ ሚያዚያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ጽፈው ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን በፁሑፍ እንዲያደርጉ አድርገናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የአመልካቾች አኮኖሚያዊ አቅም ቀላል የሚባል አይደለም ፣ በዋስ ቢለቀቁ ምስክሮችን አያባብሉም ፣ የዋስትና ግዴታቸውን አክብረው ችሎት ይቀርባሉ ተብሎ ፍርድ ቤቱ አይገምትም የሚሉ ምክንያቶች ተይዘውና የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67(ሀ) እና (ሐ)) ድንጋጌዎች ተጠቅሰው የዋስትና ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በሚል ውድቅ መደረጉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የአመልካቾች ጠበቃ እና አቃቤ ሕግ ያቀረቡትን የጹሑፍ ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ በራሱ ዋስትና የሚከለክል አለመሆኑን የተቀበሉት ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶቹ ለዋስትናው መንፈግ መሰረት ያደረጉት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 67 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ፍርድ ቤት ተግባራዊ ሲያደርግ ግምትን መነሻ ለማድረግ የሚችለው ሕጋዊ ስልጣን ያለው መሆኑንና የድንጋጌው አጠቃላይ ትርጉምም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) መሰረት አስገዳጅነት ባለው የሰበር መ/ቁጥር 59304 ላይ መሰጠቱን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

በመሰረቱ የዋስትና መብት በሕገ መንግስት ጥበቃ ከተደረጉት የተያዙ ሰዎች መሰረታዊ መብቶች አንዱ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ረፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 19(6) ስር የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በህገ መንግስቱ የተከበረው መብት ሊነፈግ ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ሊደረግ የሚችለውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሰረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ይኸው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የዋስትና መብት መሰረታዊ የሆነ ሕገ መንግስታዊ መብት ቢሆንም ፍፁም መብት ሳይሆን በሕጉ አግባብ ሊነፈግ ወይም ሊገደብ የሚችል ነው፡፡ ስለሆነም የዋስትናው ጥያቄ ተቀባይነት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ላይ ውሳኔ የሚሰጠው ፍርድ ቤት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረገድ አግባብነት ያለውን ልዩ ሕግ መሰረት አድርጎ ጉዳዩን ሊመዝነውና ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ጉዳይ መሆኑ እሙን ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ ያልተቀበለው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67(ሀ) እና((ሐ)) መሰረት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻ ለመቀበል የማይቻልባቸው ሁኔታዎችን አስቀምጧል፡፡ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67(ሀ)) ድንጋጌ ሲታይ በዋስትናው ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች አመልካቹ የሚፈጽም **<u>የማይመስል የሆነ እንደሆነ</u>** ፍርድ ቤቱ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻውን መቀበል እንደማይችል ሲደነግግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 67(ሐ)) ስር የተመለከተውና የዋስትና ወረቀቱን ላለመቀበል ምክንያት የሚሆነው ነገር ደግሞ አመልካቹ ምስክሮችን በመግዛት (በማባበል) ወይም አስረጂ የሚሆኑበትን **<u>ያጠፋ ይሆናል ተብሎ የሚገመትበት</u>** ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ይዘታቸው ሲታይ ፍርድ ቤቱ ግምት ለመውሰድ በሕጉ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ድንጋጌዎቹን በዚህ መንገድ መገንዘቡን በውሳኔው ላይ ጠቅሷል፡፡ በእርግጥም ድንጋጌዎቹ በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች አመልካቾች የሚፈፅሙ **የማይመስሉ እንደሆነና** ማስረጃዎችን የመግዛት(የማባበል) ወይም አስረጂ የሚሆኑበትን **ያጠፉ ይሆናል ተብሎ የሚገመትባቸው** ሁኔታዎች መኖራቸው ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ እንደሚቻል ያሳያሉ፡፡ እዚህ ላይ ሊስተዋል የሚገባው ዋናው ጉዳይ ግን ድንጋጌውን በመተግበር ረገድ ፍርድ ቤቱ ግንዛቤ/ግምት/ ውስጥ ሊያስገባው የሚገባው ምክንያት ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ለመከልከል ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች በተጠቀሰው ድንጋጌ በግልፅ አልተመለከቱም፡፡ እንዲህ ከሆነ አንድ ተከሳሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈፅም የማይመስል ነው ፣ ማስረጃም ሊያጠፋ ይችላል ተብሎ ግምት የሚወስደው በቂና እና ሕጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆኑ ይገባል ተብሎ የሚታመን ሲሆን ምክንያቶች በቂና ሕጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከተለያዩ ከባቢያዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አንፃር እየታየ በፍርድ ቤቱ ግንዛቤ ሊወሰድባቸው የሚችላቸው ነጥቦች ናቸው ተብሎ የሚታሰብ እንጂ ቁርጥ ያለ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች አሉ ለማለት የማይቻልበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 67 በጠቅላላው ሲታይ ፍርድ ቤት የዋስትና መብትን የሚነፍግባቸውን ሁኔታዎች የሚያሳይ ሲሆን ምክንያቶችን ፍርድ ቤቱ ከተለያዩ ሁኔታዎች በመመልከት ሊመዝናቸው የሚገባቸው ሲሆን የድንጋጌው ቅርጽ ፣ ይዘትና መንፈስ ሲታይ በሁኔታዎቹ ግምት የመወሰድ ያለመውሰድ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ስልጣን(Discretion) መሆኑን ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት በዋስትና ቢወጡ የዋስትናውን ግዴታ አክብረው ይገኛሉ ለማለት የሚቻል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ግምት መሰረቱ በአመልካቾች ላይ የተመሰረተባቸው ክስ ሊያስክትል ከሚችለው የእስራት ቅጣትና የገንዘብ መቀጮ የከበደ መሆኑ ፣ ምስክሮችን የማባበልና የማጥፋት እድልም አመልካቾች ሊሰሩ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች መኖራቸውን መገመቱንም ፍርድ ቤቱ በትዕዛዙ ላይ ገልጿል፡፡ ፍርድ ቤቱ በእነዚህ ምክንያቶች ላይ በመመስረት ዋስትናውን ነፍጎአል፡፡ እነዚህን ምክንያቶች ለግምቱ መነሻ እንዲያደርግ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው በሕጉ የተከለከለ ካለመሆኑም በላይ ግምት የመወሰድ ጉዳይ በሕጉ ለፍርድ ቤቱ የተሰጠው ስልጣን ነው፡፡ ግምቱ በቂ ነው ወይም አይደለም የሚለው ክርክር ደግሞ የጠቅላላ ሁኔታዎች ምዘና ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎት ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት የተሰጠው ሥልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ የማስረጃና የሌሎች ከባቢያዊ ነገሮችን ምዘና ጉዳይ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ማረም አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 19(6) እና የወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 67(ሀ)(ሐ) መሰረት የሠጡት ውሳኔ ሕጉ የሠጣቸውን ሥልጣን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር በሕጉ አተረጓጎምና አተገባበር ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

- በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 102532 የካቲት 14 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 65829 መጋቢት 08 ቀን 2003 ዓ/ም በውሳኔ የጸናው ትእዛዝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 75(2) መሰረት ፀንቷል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
ሐጎስ ወልዱ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ- ገ/እግዚአብሔር ሙናቸው ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. ገዳ ፎጫ ግለሰቦቹ አልቀረቡም
2. ነቢ ሲምሮ ኤጎ
3. ወሌና ወርቅና ታንታለም ማዕድናት አምራች እና ግብይት ኃ/የተ/የግል ማህበር — ጠበቃ ወ/ሮ ህትመት አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በመሠረተው የወንጀል ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የ3ኛ ተጠሪ ድርጅት እንደቅደም ተከተላቸው ዋና እና ምክትል ስራ አስኪያጆች ሲሆኑ፣ አራት ክሶች ቀርበውባቸዋል፡፡

የመጀመሪያው ክስ፡- በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1)፣ በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/85 አንቀጽ 53(1)፣(5) እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 52/85 አንቀጽ 26(4) በተመለከተው መሰረት ለስራ ተፈጻሚነት ባላቸው ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ማካሄድ ሲገባቸው በተጠቃሹ የማዕድን አዋጅ አንቀጽ 29(2) የተመለከተውን መረጃ የማኖር ወይም የመያዝ ግዴታን በመተላለፍ እንዲሁም በማእድን ስራዎች ደንብ ቁጥር 182/86 አንቀፅ 30(1ሀ(3))፣((ለ)) እና((4(ሐ)) ስር እንደተመለከተው የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ የተመረቱትን፣የተከማቹትን፣የተዘጋጁትን ወይም ለሽያጭ የቀረቡትን ማእድናትን አስመልክቶ መረጃ መያዝ እንዳለበት የተቀመጠውን ግዴታ በመጣስ እንዲሁም በተጠቃሹ ደንብ አንቀጽ 38 እና 39 ላይ እንደተመለከተው የተሟሉና ትክክለኛ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርቶችን፣ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረቡ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ካልሰጡ ጥፋት ነው ተብሎ የተደነገገውን በመተላለፍ ግንቦት 02 ቀን 2001 ዓ/ም መጠኑ 15863.18 ግራም ፣ዋጋው ብር 5,065,005.12(አምስት ሚሊዮን ስልሳ አምስት ሺህ አምስት ብር ከአስራ ሁለት ሳንቲም) የሆነውን የሐገር ውስጥ ጥፍጥፍ ወርቅ ትክክለኛና ሕጋዊ መረጃ ሳይኖራቸው ወይም ወቅታዊ ሁኔታዎችን የሚገልፅ ሰነድ ሳይዙ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-39968 አ.አ በሆነ ቪታራ መኪና በሮቹን በመፍታት መደበቂያ አዘጋጅተው ምንም አይነት ፈቃድ ሳይዙ በህገወጥ መንገድ ወርቅ ሲያዘዋውሩ የተያዙ በመሆኑ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁለተኛው ክስ ደግሞ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበ ሆኖ ይዘቱም የወ/ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 346 እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ለገበያ የሚቀርበውን ወርቅ ያገኙበትን መንገድ ወይም ቦታ ለማሳወቅ ወቅታዊ መረጃ ይዘው እንዲዘዋወሩ እና ያመረቱትን ወይም የገዙትን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ አቅርበው እንዲሸጡ የተጣለባቸውን ግዴታ በመተላለፍ መጠኑ በ1ኛው ክስ የተገለጸውን ወርቅ ወደ አዲስ አበባ በማንገዝ ሕጋዊ ወደአልሆነ ገበያ ለማቅረብ ሲሉ ተይዘዋል የሚል ነው፡፡

ሶስተኛው ክስም በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበ ሆኖ ይዘቱም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.591/2000 አንቀጽ 26(1)(ለ) እንዲሁም በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በስር 3ኛ ተከሳሽ በሀሰት የተዘጋጀውን ማስረጃ እያወቁ ተጠቅመዋል የሚል ነው፡፡

የመጨረሻው ክስ በ3ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበ ሆኖ ይዘቱም፡- በወርቅና ታንታለም ማእድናት ማምረት የግብይት ስራ መስክ የሕግ ሰውነት ተሰጥቶት ሲንቀሳቀስ የወርቅ ምርትን ከማንገዝና ለግብይት ከማቅረብ ጋር በተያያዘ አሰፈላጊውን ሕጋዊ ሰነድ መያዝ እና ማህበሩ ስላለው፣ ስላመረተው፣ ስላንገዘው እና ለግብይትም ስላቀረበው ወርቅ ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ማቅረብ እንዳለበት የማእድን ሃብትን ለማስፋፋት በወጣው አዋጅ ቁጥር 52/85 እና በማእድን ስራዎች ደንብ ቁጥር 182/86 ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች በመጣስ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣የማእድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቨይ በወርቅ ግዥና አቀራረብ ሂደት ስለሚከተሉት የጋራ አሰራር የወጣውን መመሪያ ቁጥር 01/2000 በመተላለፍ ያለምንም ሕጋዊ ፈቃድ መጠኑ 15863.18 ግራም የሆነ ወርቅ ሕጋዊ ላልሆነ ገበያ ለማቅረብ ሲንቀሳቀስ ተይዟል ተብሎ በ1997 ዓ/ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንደሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፏል በሚል ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የአቃቤ ሕግ ክስ ለተጠሪዎች እንዲደርስ አድርጎና በግልፅ ችሎትም ተነቦላቸው እንዲረዱት ካደረገ በኋላ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠይቅ ተጠሪዎች በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው፣ የድርጊቱን አፈጻጸም ግን ክደው ተከራክረዋል፡፡ አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰነድና የሠው ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ የዓቃቤ ህግን ማስረጃዎች ሰምቶ ተጠሪዎች የወንጀል ድርጊቶችን መፈጸማቸው በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ መረጋገጡን በማመን የተጠሪዎችን የመከላከያ ማስረጃዎችን የማሰማት መብት ጠብቆላቸው መከላከያ ማስረጃዎቻቸውን ሰምቷል፡፡ ቀጥሎም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃዎች ይዘት በአቃቤ ማስረጃዎች ይዘት ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ የፈጠረ ሆኖ ተገኝቷል የሚል ምክንያት በመስጠትና ተጠሪዎች የአቃቤ ሕጉን ማስረጃዎች ማስተባበላቸውን በመግለጽ ተጠሪዎችን ከክሱ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡በስር 3ኛ ተከሳሽ የሆነውን ግለሰብ ግን በወ/መ/ሕ/ቁጥር 375(1(ሀ))እና ((መ)) ስር ሐሰተኛ ሰነድ የመስጠት ወንጀል መፈፀማቸው ተረጋግጧል በማለት ጥፋተኛ አድርጎ ተገቢ ነው ያለውን ቅጣት አስተላልፎበታል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችን ከክሱ ነፃ ከማድረግ በተጨማሪም በኤግዚቢትነት የተያዘው የሀገር ውስጥ ወርቅም በጊዜው ባለው የወርቅ ተመን መሠረት የወርቁን ዋጋ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከሰሱት ሕጋዊ ፈቃድ የላቸውም በሚል ሳይሆን የወርቅ ግብይቱን ለሚመለከተው አካል ሳያቀርቡ በሕገ ወጥ መንገድ ለሌላ አካል ለመሸጥ ሲሉ ሲንቀሳቀሱ ተይዘዋል፣1ኛ ተጠሪም ማስረጃው በጥቅም አሰርቶ ያመጣው ከመሆኑም በላይ ለራሱና ለ2ኛ ተጠሪ ጥቅም ላይ ሊያውል ሲል መያዙ ተረጋግጧል የሚል ሆኖ እያለ ሕጋዊ ንግድ ፍቃድ ያላቸው ስለመሆኑ በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አረጋግጠዋል በማለት በነጻ የተሰናበቱት ያላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ ተጠሪዎች ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት እንዲጣል እና ኢግዚቢትነት የተያዘው ወርቅ ለመንግስት ውርስ እንዲሆን ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪዎች ከክሱ በነጻ የተነሰናበቱት ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው የተጠሪዎች ጠበቃ ባቀረቡት የዕሑፍ መልስ ተጠሪዎች በነፃ የተሰናበቱት ባግባቡ ተከላክለው በመገኘታቸው በመሆኑና አድራጎታቸውም የወንጀል ተጠያቂነትን የማያስከትል መሆኑ በመረጋገጡ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም ተጠሪዎች ከክሱ በነጻ እንዲሰናበቱ በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም በስር ፍርድ ቤት በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች እንዲሁም የተጠሪዎች መካላከያ ማስረጃዎች ያስረዱትን ፍሬ ነገር ይዘት ባጭሩ በሚከተለው መልኩ አይተነዋል፡፡

በአቃቤ ሕግ በኩል በ1ኛ ምስክርነት የተጠቀሱት ግለሰብ እውነት ለመመስከር ምለው በሰጡት የምስክርነት ቃል፡-ግንቦት 02 ቀን 2001 ዓ/ም ከጥዋቱ 2፡30 አከባቢ 1ኛ ተጠሪ ደውለውላቸው ወርቅ አምጣልኝ፣ከአዋሳ 2ኛ ተጠሪ ይጠብቅሃል ሲሏቸው ወደ 2ኛ ተጠሪ ደውለው 1ኛ ተጠሪ አገዘኛል ሲሏቸው 2ኛ ተጠሪ "ና!" ብሏቸው ከቀኑ 11፡30 አከባቢ አዋሳ ገብርኤል አካባቢ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተገናኝተው በጥቁር ሻንጣ ወርቁን እንዳመጣላቸው፣ከመንገድ ወጣ ብለው በመኪናው ሻግ ውስጥ በማድረግ ስድስቱን እሸግ ወርቅ በመደበቅ በእለቱ አዲስ አበባ መንቀሳቀስ እንደጀመሩ፣ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ሳሉም ከምሽቱ 4፡00 አከባቢ ወደ አቃቂ ቃሊቲ የጉምሩክ ፍተሻ አከባቢ ሲደርሱ በጉምሩክ ኦፊሰሮችና በጸጥታ ኃይሎች መያዛቸውንና ወዲያውኑ ወደ ጉምሩክ ጣቢያ እንዲገቡ መደረጋቸውን፣በጉዞ ወቅት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አፍሪካ ወርቅ ድርጅት ከተባለው ጋር በስልክ ይነጋገሩ እንደነበር፣በነጋው ወርቁን የት እንዳስቀመጡት ሲጠየቁም ሻጉን ከፍተው እንደሳዩ፣ወርቁን በተመለከተ ቀኑ 30/08/2001 ዓ/ም የሚል ተሰርቶ ማስረጃ እየመጣላቸው መሆኑን 2ኛ ተጠሪ ሲነግራቸው እንደነበር፣በወቅቱም ምስክር አትሁን ሲሏቸው እንደነበር፣ከዚያ በፊትም ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ወርቅ ሲያመጡ እንደነበር፣በሻግ ውስጥ የሚያስቀምጡትም የይለፍ ወረቀት ስለማይዙና በወቅቱም ያለመያዛቸውን፣ወርቁ ወደ ጅቡቱ እንደሚወጣም በስልክ 2ኛ ተጠሪ ሲናገር መስማታቸውን ዘርዝረው መስክረዋል፡፡

ሁለተኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ደግሞ የአቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክር የሆኑት ግለሰብ በእለቱ ከምሽቱ 5፡00 አካበቢ ሲሆን ጉምሩክ ታስራአለሁ ጠዋት "ና!" እንደአሏቸውና ጥዋት 1፡00 አከባቢ ጉምሩክ ሲደርሱም የታሰሩበት ምክንያት ወርቅ ጭነው እንደሆነ የተነገራቸው መሆኑን፣2ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ አብሮት እንደነበር፣ይኸው ተጠሪ ወዲያውኑ ለ1ኛ ተጠሪ ደውልለት ብሏቸው ለምስክሩ ሲነግሩትም ምስክሩ ለ1ኛ ተጠሪ ደውለውለት 2ኛ ተጠሪና ወርቁ መያዙን የነገሩት መሆኑን፣ከዚያም ቀን ላይ 1ኛ ተጠሪ መልሶ ደውለውለት እመጣለሁ ጠብቀኝ እንዳሉት፣ከቀኑ 8፡00 አከባቢም 1ኛ ተጠሪ ወረቀትም አስርቼ እያመጣሁ ነው ብለው ሲሏቸው ከኢትዮጵያ ሆቴል አከባቢ ሲገናኙ 1ኛ ተጠሪ ወርቁን ለማስለቀቅ ቀኑ በ30/08/2001 ዓ/ም ተብሎ ወደኋላ ተደርጎ የተጻፈ ወረቀት መያዛቸውን ለምስክሩ ገልፀው ወረቀቱን ለ2ኛ ተጠሪ ምስክሩ እንዲሰጥላቸው ነግሯዋቸው ምስክሩ "እኔ አልሰጥም፣ራስህ ስጥ ሲሉት" 1ኛ ተጠሪ ወረቀቱን ለመስጠት በሄዱበት መያዛቸውን እንደሚያውቁ መስክረዋል።

3ኛ እና 5ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በበኩላቸው 2ኛ ተከሳሽን በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ጊዜና ሰዓት ወርቅ ጭነው ሲመጡ በደረሳቸው መረጃ መሰረት ሃና ማሪያም ቀለበት መንገድ አከባቢ መያዛቸውን፣ወርቁም በመኪናዋ በሮች መደበቂያ ተሰርቶለት በአንድ በኩል ሶስት፣በሌላ በኩል ሶስት እሽግ ሆኖ ሲጓዝ እንደነበርና በወቅቱም ማስረጃ ተጠይቀው የለንም በማለት መልስ የሰጧቸው መሆናቸውን መስክረዋል። 4ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር ደግሞ 2ኛ ተጠሪን ወርቅ ከደቡብ ጭነው ሲመጡ ከሃና ማሪያም አከባቢ የያዟቸው መሆኑን፣ 1ኛ ተጠሪ ግንቦት 04 ቀን 2001 ዓ/ም ከቀኑ 4፡00 አከባቢ የይለፍ ወረቀት አጣጥፎ ለ2ኛ ተጠሪ በአጥር ሲያቀብሉ እንደያዙት መስክረዋል።ከዚህም በተጨማሪ አቃቤ ሕግ 3ኛ ተጠሪ የወርቅና የታንታለም ማእድናት አምራችና ግብይት ኃ.የተ.የግል ማህበር ስለመሆኑ ከክልሉ የማዕድን ቢሮ ፈቃድ አግኝቶ ማዕድን በማምረት ስራ ላይ የተሰማራ መሆኑን፣1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የዚሁ ማህበር አመራሮች መሆናቸውን፣በአዶ ሻኪሶ የሚገኘው የገቢዎች ጽ/ቤትም 3ኛ ተጠሪ የመረጃ አያያዙ ችግር ያለበት መሆኑን የገለፀበት መግለጫ፣2ኛ ተጠሪ ከአፍሪካ ወርቅ ቤት ጋር በስልክ ሲገናኙ የነበሩ መሆኑን የሚያሳዩ ከቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የተገኘና ሌሎች የወርቁን ዋጋና 2ኛ ተጠሪ ወርቁ ከተደበቀበት የመኪና ክፍል መርተው ሲያስወጡ የተነሱትን ፎቶ ግራፍ በሠነድ ማስረጃነት ማቅረቡን የሥር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ያሳያል።1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው የሰነድ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃነት ያቀረቡ ሲሆን የሰነድ ማስረጃዎቻቸው ይዘትም ከአንድ አመት በፊት ማዕድን ለማምረት ተደራጅተው ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የማእድንና ኢነርጂ ልማት ጽ/ቤት ፈቃድ ማግኘታቸውን፣ፈቃዱም የታደሰ መሆኑን፣ከብሔራዊ ባንክ ጋር ወርቅ የማቅረብ ግንኙነት እንዳላቸው፣ሮያሊቲ ታክስም እንደሚከፍሉ ከተደራጁበት ጊዜ ጀምሮ የከፈሉትን የሮያሊቲ መጠን፣ለብሔራዊ ባንክ ከአስራ ሁለት ጊዜ በላይ ወርቅ አቅርበው የሸጡ መሆኑን የሚያሳዩ መሆናቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል።

እንግዲህ በግራ ቀኙ ማስረጃዎች የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ከላይ የተገለጹት ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎችን ከክሱ ነፃ ያደረጋቸው ተጠሪዎች ሕጋዊ የወርቅ ማምረት ፍቃድ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፣በአዋጅ ቁጥር 52/865 አንቀጽ 2 መሰረት ማምረት ማለት መሸጥን እንደሚጨምር መደንገጉን፣ማዕድኑ ሲሸጥ ለማን እንደሚሸጥ ይህ ድንጋጌ በግልጽ ያላመለከተ መሆኑና በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 182/86 ደግሞ ማእድንን ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ማህበር ያመረተውን ማእድን በተመለከተ ያመረተውን፣ያጓጓዘውን፣ያከማቸውን እንዲሁም የሸጠውን መዝግቦ መያዝ እንዳለበት፣ሲጠይቅም ማሳየት እንዳለበት ከሚደነግግ ውጪ ማዕድኑን ለዚህ አካል መሸጥ ወይም ማስረከብ አለበት ብሎ የደነገገው ድንጋጌ ያለመኖሩን፣የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ማዕድን ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በጋራ ባወጡት መመሪያ ላይም ማንኛውም ሕጋዊ ወርቅ አምራች ያመረተውን ወርቅ ለባንኩ ማቅረብ ይችላል ከሚል በስተቀር የማቅረብ ግዴታ እንዳለበትና ከባንኩ ውጪ ለሌላ ሲያቀርብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቢገኝ በዚህ ሕግ መሰረት ይቀጣል ተብሎ ያለመደንገጉን፣በደንብ ቁጥር 182/86 አንቀጽ 38 እና 39 ስር ጥፋት ተብለው የተቀመጡት ድርጊቶች ሪኮርድ ያለመያዝ፣ስለአመረቱት ፣ስለአጓጓዙት፣ስለአከማቹት እና ስለሚሸጡት ማእድን ተገቢውንና ወቅታዊውን መረጃ ባለመያዛቸው የሚወሰድባቸው ቅጣት አስተዳደራዊ እንጂ የወንጀል ቅጣት ያለመሆኑን የደንቡ አንቀጽ 40 ድንጋጌ የሚያሳይ መሆኑን በምክንያትነት በመያዝ ነው።ተጠሪዎች እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚከራከሩትም ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው መሆኑና በተለያዩ ጊዜያት ለብሔራዊ ባንክ ወርቁን በማቅረብ ሲሸጡ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ ሲሆን አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ደግሞ ተጠሪዎች ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ሳይክድ የወርቅ ሽያጩን በሕገ ወጥ መንገድ ለመፈፀም ሲሯሯጡ ተይዘዋል፣ተገቢውን መረጃም በወቅቱ አልያዙም በማለት ነው።እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ ተመልክተነዋል።

በመሰረቱ የወርቅ ማዕድን ዝውውርን ለመቆጣጠር ስልጣን የተሰጠው ብሔራዊ ባንክ መሆኑን ብሔራዊ ባንክን ከአቋቋሙት ሕጎች መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው።የወንጀል ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 591/2000 ሲሆን ይህ አዋጅ በአንቀፅ 27(2) እና በአንቀጽ 5 ድንጋጌዎች ስር ብሔራዊ ባንክ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካትና አዋጁን በሚገባ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት የሚያስችል ስልጣን ሠጥቶታል።ይኸው አዋጅ በአንቀጽ 28 ስር ደግሞ አዋጁን የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ደንብ ወይም መመሪያ በአዋጁ ውስጥ የተመለከቱትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት እንደማይኖረው ይገልፃል።ከዚህ ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ይዘት መገንዘብ የሚቻለውም አዋጁን የማይቃረን ሕግ፣ደንብ እና መመሪያ በአዋጁ ውስጥ ለተመለከቱት ጉዳዮች ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ነው።በአዋጁ አንቀጽ 27/2/ እና አንቀፅ 5(9) ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች በተለይ ሲታዩም ስለወርቅና ስለውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ባንኩ መመሪያ የማውጣት ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ያስገነዝባሉ። ከዚህ ድንጋጌ እና ከአዋጁ አጠቃላይ መንፈስ መረዳት የሚቻለው የገንዘብ እና የወርቅ ሥራ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ያለውን አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት በመመልከት በተለየ ሁኔታ ሥርዓት እንዲበጅለት እና ቁጥጥር እንዲደረግበት ማድረጉ የሕግ አውጪው ፍላጎት መሆኑን ነው።ይህንንም በእውን ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ደግሞ በአዋጁ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ባንኩ በዝርዝር መመሪያ መሰረት ጉዳዮችን ለማስተዳደር እንዲችል ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን አዋጁ ያስረዳል።ስለሆነም ተጠሪዎች የተከሰሱበት ድርጊት ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረው መመሪያው ቁጥር ወን/001/1997 በአንቀጽ 1 እና 2 ስለወርቅ ንግድና ዝውውር፣መያዝ ወይም ማኖር የባንኩን ፈቃድ አስፈላጊነትና የመጠኑም ገደብ አስመልክቶ ድንጋጌ ይዟል።ይህ መመሪያ ከአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 27(2) እና 5(9) እንዲሁም አንቀጽ 28 ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት ሲታይ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሲሆን አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(1) ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ አዋጁን ወይም አዋጁን ተከትሎ የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የተላለፈ ሰው የሚቀጣበትን አግባብ አስቀምጧል።ስለሆነም የወንጀል ተጠያቂነትን አስመልክቶ የተደነገገው በአዋጁ መሠረት መሆኑን እንረዳለን። በአዋጅ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የሚወጣ መመሪያ ሕጋዊ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 43781 ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል።በመሆኑም ባንኩ በግልጽ በአዋጁ ስለወርቅ መመሪያ ማውጣት ስልጣን አለው ተብሎ ስልጣን በሕግ አግባብ ከተሰጠው መመሪያው ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል።ከዚህ አንፃር በመመሪያው የተመለከተውን ገደብ በመተላለፍ ለተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ተጠያቂነት በአዋጁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና በወንጀል ሕጉ በተመለከተው አግባብ የሚፈፀም በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ላይም መመሪያው ተፈጻሚነት አለው ብለናል።መመሪያ ቁጥር ወን/001/1997 ከግንቦት 10 ቀን 1997 ዓ/ም ጀምሮ በስራ ላይ ያለ ሲሆን በዚህ መመሪያ መሰረት የወርቅ አሻሻጥ ስርዓትን በብቸነት የመቆጣጥር ስልጣን ያለው አካል ብሔራዊ ባንኩ ነው።በዚህ መመሪያ መሰረት ወርቅ የሚሸጥ ግለሰብ ወይም ሰው በቅድሚያ መሸጥ ያለበት ለባንኩ በማቅረብ ነው።መመሪያው ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው ግለሰቦች ከባንክ ብቻ በሕጋዊ መንገድ ጥፍጥፍ ወርቅ መግዛት እንደሚችሉም ይደነግጋል።የመመሪያው አጠቃላይ ይዘት ሲታይም የወርቅ ግዥና ሽያጭ የሚከናወነው በብሔራዊ ባንክ ብቻ መሆኑን በግልፅ ያሳያል።በመመሪያው መሰረት ጥፍጥፍ ወርቅ የማምረት ፍቃድ ካላቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በቀጥታ የመግዛት ስልጣን ያለው ብቸኛ አካል ብሔራዊ ባንኩ ነዉ።ባንኩ ጥፍጥፍ ወርቁን ለመግዛት የሚችለው ደግሞ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ወርቁን ለባንኩ በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት ገቢ ሲያድርጉ ነው።በዚህ በመመሪያው መሰረት በተዘረጋው የወርቅ ግብይት ስርዓት መሰረት የማይከናወን ማንኛውም የወርቅ ግብይት ሕገ ወጥ ድርጊት ነው ተብሎ የሚፈረጅ መሆኑን የመመሪያው አጠቃላይ ይዘት፣መንፈስና ዓላማ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 346 ድንጋጌዎች ይዘት ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ያስረዳል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ተጠሪዎች የወርቅ ማምረት ፍቃድ አለን በማለት ያቀረቡትን ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች እንዳለ ሲቀበሉ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠውንና ሕገ ወጥ ነው የተባለውን ድርጊት ሳይለዩ አልፈዋል።ይኸውም አቃቤ ሕግ ለክሱ መሰረት ያደረገው የተጠሪዎችን ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው መሆን ያለመሆኑን ሳይሆን የወርቅ ግብይቱን በሕጉ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ ለመሸጥ ሲንቀሳቀሱ ተይዘዋል በሚል ነው።ለጉዳዩ ያቀረባቸው ማስረጃዎች ደግሞ ወርቁ ለብሔራዊ ባንክ ሳይሆን ለአፍሪካ ወርቅ ቤት ቀርቦ ወደ ጅቡቲ በመላክ ለመሸጥ በማሰብ ወርቁ ሲጓጓዝ የነበረ፣በወቅቱም መያዝ የሚገባቸው መረጃዎች ሁሉ በተገቢው ሁኔታ ያልተያዙ መሆኑን አረጋግጠዋል።ለጉዳዩ ቀጥተኛ ምስክር የነበረው የአቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክርና ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ይህንኑ የሚያስረዱ መሆናቸውን የሥር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ አግኝተናል።

ወደሕጉ ስንመጣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ በአቃቤ ሕግ የተጠቀሰው 1ኛው ክስ በዋናነት መሰረት ያደረገው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1)፣ በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/85 አንቀጽ 53(1)፣(5)፣26(4) ፣29 እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንደዚሁም በማእድን ስራዎች ደንብ ቁጥር 182/86 አንቀፅ 30(1ሀ(3))፣((ለ)) እና((4(ሐ)) ስር እንደተመለከተው የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ የተመረቱትን፣የተከማቹትን፣የተዘጋጁትን ወይም ለሽያጭ የቀረቡትን ማእድናትን አስመልክቶ መረጃ መያዝ እንዳለበት የተቀመጠውን ግዴታ በመጣስ እንዲሁም በተጠቃሹ ደንብ አንቀጽ 38 እና 39 ላይ እንደተመለከተው የተሟሉና ትክክለኛ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርቶችን፣ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረቡ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ያለማቅረባቸው የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል በማለት ነው።ይህ ችሎትም ጉዳዩን በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጡት ነጥቦች አንፃር ሲመለከት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 ስር የወንጀል ተጠያቂነት ሊከተል የሚችለው በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 346 በተመለከተው አኳኋን ማንም ሰው ሕገወጥ በሆነ መንገድ የከበሩ ማእድናት እንደወርቅ፣ፕላቲኒም፣ዩራኒየም እና ሌሎችንም እነዚህን የመሳሰሉ ማእድናት እንዲሁም የከበሩ ድንጋዮችን ለመጠበቅ ወይም ሕገ ወጥ ዝውውሩን ለመቆጣጠር የወጣውን ሕግ በመጣስ ወንጀል የተሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ሲሆን ቅጣቱም ወንጀሉን የፈፀመበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሀብት የመውረስ ደንብ የሚጸናበት መሆኑ ሳይቀር ከአስር አመት በማይበልጥ ዕኑ እስራትና ከሀምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ እንደሚሆን ሕጉ ያሳያል፡፡በደንብ ቁጥር 182/1986 አንቀጽ 38 እና 39 ላይ እንደተመለከተው የተሟሉና ትክክለኛ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርቶችን፣ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረቡ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ያለማቅረባቸው የአስተዳደራዊ ጥፋቶች ሊባሉ እንደሚችሉ በደንቡ የተመለከተ ሲሆን የጥፋቱን ደረጃና ተደጋጋሚነት መሰረት በማድረግም የሚመለከተው አካል አስተዳደራዊ ቅጣት ሊጥል የሚችልበት አግባብ የደንቡ አንቀፅ 39 እና 40 ድንጋጌዎች በግልፅ ያሳያሉ፡፡ደንቡ የወንጀል ተጠያቂነትን እንደሚያስከትሉ የሚገለፀው ከደንቡ አንቀጽ 38 እና 39 ውጪ ያሉትን ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈፀመውን ተግባር ስለመሆኑ በአንቀጽ 40(5) ስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡በመሆኑም በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ በአቃቤ ሕግ በኩል የተጠቀሰባቸው የደንብ ቁጥር 38 እና 39 ድንጋጌዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 347 መሰረት የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትሉ የማይችሉ መሆኑን ከደንቡ አንቀፅ 40(5) ስለተገነዘብን 1ኛ ክስን በተመለከተ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ኃላፊ የሚሆኑበትን አግባብ ስላላገኘን በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡

ሌላው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የተጠቀሰባቸው የወ/ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 346 እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ለገበያ የሚቀርበውን ወርቅ ያገኙበትን መንገድ ወይም ቦታ ለማሳወቅ ወቅታዊ መረጃ ይዘው እንዲዘዋወሩ እና ያመረቱትን ወይም የገዙትን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ አቅርበው እንዲሸጡ የተጣለባቸውን ግዴታ በመተላለፍ መጠኑ በ1ኛው ክስ የተገለጸውን ወርቅ ወደ አዲስ አበባ በማጓጓዝ ሕጋዊ ወደአልሆነ ገበያ ለማቅረብ ሲሉ ተይዘዋል የሚል ነው፡፡ከላይ በፍሬ ነገር ደረጃ እንደተገለጸው 1ኛ ተጠሪ የአቃቤ ሕጉን 1ኛ ምስክር ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተገናኝቶ ወርቁን ወደአዲስ አበባ እንዲያጓጉዝ ማድረጉ፣2ኛ ተጠሪ ወርቁን ሲያጓጉዙ ወደ ብሔራዊ ባንክ ሳይሆን አፍሪካ ወርቅ ቤት ለተባለው የንግድ ድርጅት በማቅረብ ወደ ጅቡቱ በመላክ ለመሸጥ በማቀድ ወርቁ ሲጓጓዝ በጉምሩክ አፊሰሮችና በጸጥታ ኃይሎች አማካኝነት በመንገድ ላይ የተያዘ መሆኑ በሚገባ በአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ስለሆነም ወርቁ በሕጉ አግባብ ከተዘረጋው ሥርዓት ውጪ ለገበያ ሊቀርብ ሲል የተያዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ይህም ተጠሪዎች ወርቁን በሕገ ወጥ መንገድ ለማዘዋወር በማሰብ ወንጀሉን በማድረግ፣የወንጀሉን ድርጊት እስከ መጨረሻው ያልተከታተሉት ወይም ለመከታተል ያልቻሉት ወይም የወንጀሉን ድርጊት እንዲፈፀም እስከ መጨረሻው ተከታትለው አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላገኙ ቢሆንም ተጠሪዎች ወንጀሉን ለመፈፀም ከማይመለሱበት ደረጃ /Point of no return/ ደርሰው የነበረ መሆኑ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ወርቅን በሕገ ወጥ መንገድ መሸጥ በወ/መ/ሕ/ቁጥር 27(1)፣32(1(ሀ))((ለ)) እና 346 መሰረት ወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ድርጊት መፈፀማቸውን የሚያስገነዝብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ተጠሪዎች ያቀረቡት የመከላከያ ሰነድም ተጠሪዎች ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ለክሱ መሰረት የሆነው ድርጊት ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ ወርቁን ለብሔራዊ ባንክ ሊያቀርቡ የነበረ መሆኑን የማያሳይ በመሆኑ ክብደት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም፡፡በመሆኑም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ2ኛው ክስ ነፃ ሊባሉ የሚችሉበት ማንኛውም አግባብ ስለሌለና ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው ደግሞ በአቃቤ ሕግ ክስ በተመለከተው መልኩ ሳይሆን ወርቁን በሕገ ወጥ መንገድ ለመሸጥ በመሞከር የወንጀል ድርጊት በመሆኑ በወ/መ/ሕ/ቁጥር 27(1)፣32(1(ሀ))((ለ)) እና 346 ስር በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት ሆኖ አግኝተናል፡፡ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የአቃቤ ሕግ ክስ ይዘትን ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ጋር በማዛመድ ጉዳዩን መመልከት ሲገባቸው ለክሱ መሰረት ያልሆነውን የተጠሪዎች ሕጋዊ ነጋዴ የመሆን ጉዳይ በምክንያትነት በመያዝ 1ኛ እና 2ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪን ከ2ኛው ክስ ሙሉ በሙሉ ነፃ በማድረግ መወሰናቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን የነፃ መልቀቅ ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2((ሀ)) መሰረት በመሻር 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በወ/ህግ አንቀጽ 27(1)፣32(1(ሀ))(ለ)) እና 346 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፉ ጥፋተኞች ናቸው ብለናል፡፡

ሌላው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ የተከሰሱበት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.591/2000 አንቀጽ 26(1)(ለ) እንዲሁም በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በስር 3ኛ ተከሳሽ በሀሰት የተዘጋጀውን ማስረጃ እያወቁ ተጠቅመዋል የሚል ነው፡፡ተጠሪዎች ማስረጃውን በጥቅም ላይ አውለው የተገኙ መሆኑ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ሐሰተኛ ማስረጃውን ያዘጋጀው የስር 3ኛ ተከሳሽም በበታች ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ ተብሎ ተገቢው ቅጣት የተወሰነበት መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችም ሕጋዊ የወርቅ አምራችና አቅራቢ ድርጅት የስራ ኃላፊ ከመሆናቸው ውጪ ግንቦት 02 ቀን 2001 ዓ/ም ሲያጓጉዙትና በሕገ ወጥ መንገድ ሊሸጡት ለነበረው ወርቅ ቀድመው ትክክለኛውን ማስረጃ የያዙ መሆኑን ሊያረጋግጥላቸው የሚችል የመከላከያ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ይልቁንም ተገቢውን ማስረጃ የያዙ ለማስመሰል ቀኑ ወደኋላ ሆኖ የተጻፈ ሐሰተኛ ሰነድ ለተገቢው አካል አቅርበው ጥቅም ላይ ለማዋል ሲሉ ተይዘዋል፡፡በመሆኑም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ3ኛ ክስም ነፃ የሚወጡበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2((ሀ)) መሰረት በመሻር 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና (ለ))) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የተላለፉ ጥፋተኞች ናቸው ተብለው ሊቀጡ የሚገባ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በመጨረሻም 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ ተገቢነት ተመልክተናል፡፡ይህ ተጠሪ ሕጋዊ ሰውነት የተሠጠው አካል ሲሆን የተከሰሰውም በ1997 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፏል በሚል ነው፡፡ከላይ እንደተለገፀው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የ3ኛ ተጠሪ ድርጅት የስራ ኃላፊዎች ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ በሕገ ወጥ መንገድ ወርቁን ለመሸጥ ሲሞክሩ በመገኘታቸው ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባ ሆነው ተገኝተዋል፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወ/ሕ/አንቀጽ 34 እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት በወንጀል ሊጠየቅ የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት 3ኛ ተጠሪ ነጻ የተባለበትን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ሀ))መሰረት በመሻር በ1997 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27(1)፣353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ሊባል የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎችን ሙሉ በሙሉ ነጻ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ሕጋዊ ባለመሆኑ ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ2ኛው ክስ የወ/ሕግ አንቀጽ 27(1)፣32(1)(ሀ)(ለ) እና አንቀጽ 346 እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ለገበያ የሚቀርበውን ወርቅ ያገኙበትን መንገድ ወይም ቦታ ለማሳወቅ ወቅታዊ መረጃ ይዘው እንዲዘዋወሩ እና ያመረቱትን ወይም የገዙቱትን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ አቅርበው እንዲሸጡ የተጣለባቸውን ግዴታ በመተላለፍ በሕገ ወጥ መንገድ ወርቅ ለመሸጥ ሲሞክሩ የተገኙ ጥፋተኞች ናቸው፣እንደሁም ሁለቱም ተጠሪዎች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 378 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመተላለፍ በስር 3ኛ ተከሳሽ በሀሰት የተዘጋጀውን ማስረጃ እያወቁ የተጠቀሙ ጥፋተኞች ናቸው፣ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ ያለምንም ሕጋዊ ፈቃድ መጠኑ 15863.18 ግራም የሆነ ወርቅ ሕጋዊ ላልሆነ ገበያ ለማቅረብ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አማካኝነት ሲንቀሳቀስ የተገኘ በመሆኑ በ1997 ዓ/ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34፣27(1)፣353(1(ለ))፣((ረ)) እንዲሁም አንቀጽ 354(1 እና 2)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 65325
ህዳር 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሣጅን ታዬ ተክለኂይማኖት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ ከሣሽ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን የተጀመረው በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ በተከሣሽ ላይ ቀርቦ የነበረው ክስ ሶስት ሲሆን ይዘቱ 1ኛው ክስ ተከሣሽ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 670 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ በሀዋሳ ከተማ ልዩ ስሙ ጨርቃ ጨርቅ አካባቢ በስራው አካባቢ በእጁ በሚገኙት የሀዋሳ ከተማ የፖሊስ ተሽከርካሪ የሆኑትን 1ኛ ከላይ ክፈት ላንድ ኪሩዘር የሰሌዳ ቁጥር ፖሊስ ደ.ህ 0007 2ኛ ሽፍን ሎንግ ቤዝ መኪና የሰሌዳ ቁጥሩ 4-11529 በማሽከርከር ዘወትር ማክሰኞና አርብ ከንግድ ስራቸው የሚመለሱትን የተለያዩ ስምንት ሰዎችን በተለያዩ ጊዜያት ያስጫናችሁት ዕቃ ይወረሳል ካልሆነ ገንዘብ አምጡ በማለት በማስፈራራት 10,700 ብር የተቀበለ በመሆኑ በፈጸመው የውንብድና ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፤ ሁለተኛ ክስ ደግሞ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 407/ሐ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከላይ በክስ አንድ ስር በተገለጹት ቀናት ወር ዓመተ ምህረት እና ቦታ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 ድረስ ስማቸው በተገለጹት የግል ተበዳዮች የፖሊስ አባል መሆኑንና የፖሊስ መኪና ማሽከርከሩን መከታ በማድረግ ይህ የያዛችሁት የንግድ ዕቃ "ቡና" ይወረሳል አልያም ገንዘብ አምጡ እያለ ገንዘቡን እየተቀበለ እንዲያልፉ በማድረግ በስልጣን አለ አግባብ መገልገል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው 3ኛው ክስ ደግሞ በክስ አንድ ስር የተጠቀሱትን የመንግስት ተሽከርካሪዎች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 677/1ሀ/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ያለአግባብ በመገልገል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተከሣሹን የእምነት ክህደት ቃል በመቀበል የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የውሣኔው ይዘት ተከሣሽ በአንደኛው ክስ ስር የውንብድና ወንጀል ሰርቷል በተባለበት ወቅት በእረፍት ላይ የነበረ ስለመሆኑ ከዐቃቤ ህግ ምስክር በተሻለ ያስመሰከረ በመሆኑ ከክሱ በነጻ ሊሰናበት ይገባል 3ኛ ክስ በተመለከተም በተመሳሳይ ተከሣሽ በእረፍት የነበረ ስለመሆኑ እና በወቅቱም የተጠቀሱትን ተሽከርካሪዎች ለሌላ ተረኛ ሹፌር ያስረከበ እና በእጁ የሌለ ስለመሆኑ ከመስሪያ ቤቱ የቀረቡት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተሸከርካሪ መረካከቢያ ቅጾች የሚያስገነዝቡ በመሆኑ የወንጀል ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሁለተኛ ክስ ስር ግን ፍ/ቤቱ በተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 407/ሐ/ ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በአምስት /5/ ዓመት ጽኑ እስራትና በ2000 ብር /ሁለት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመቀጠል ደግሞ ለክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታውን ያቀረበ ሲሆን የቀረበላቸውን ቅሬታ ባለመቀበል አያስቀርብም በማለት ቅሬታውን ሰርዘውለታል፡፡
አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሁፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በሁለተኛ ክስ ስር ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ በአግባቡ ስለመሆኑ ተመርምሮ እልባት ማግኘት ያለበት ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ሁለተኛውን የዐቃቤ ህግ ክስ እና አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበትን ድርጊት ስንመለከት ራሱን ችሎ የቆመ ሳይሆን በአንደኛው ክስ ውስጥ በተጠቀሰው ሰዓት ቀን ወር ዓመተ ምህረት ቦታ እና የግል ተበዳዮች ላይ ስለመሆኑ ከክሱ ይዞታ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ በአንደኛ ክስ ላይ በተመለከተው የውንብድና ወንጀል ክስ ስር ተከሣሽ በወቅቱ በእረፍት ላይ የነበረ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በማለት ከቀረበበት ክስ በነጻ እንዲሰናበት ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ይሄ ከሆነ በተመሣሣይ ጊዜ ቦታ እና የግል ተበዳዮች ላይ ተፈጸመ ለተባለው የስልጣን አለአግባብ የመገልገል ወንጀል ጥፋተኛ የሚባልበት አግባብ አይኖርም፡፡ በተመሣሣይ ሁለተኛውን ወንጀል ሲፈጽም የፖሊስ መምሪያ መኪና ተጠቅሟል ተብሎ በክሱ የተመለከተ ቢሆንም በአመልካች ላይ የቀረበው የመንግስትን ንብረት ያለአግባብ የመገልገል ወንጀል በተመሣሣይ ጊዜ ቦታ እና የግል ተበዳዮች ላይ ተፈጸመ ተብሎ በሶስተኛ ክስ ከቀረበበት ክስ በነጻ የተሰናበተ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ያለመፈጸሙን እና ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በእረፍት ላይ የነበረ ስለመሆኑ ወንጀሉንም ሲፈጽም የፖሊስ መምሪያውን ተሽከርካሪ ተጠቅሟል የተባለውም በወቅቱ የተባሉት ተሽከርካሪዎች በእጁ ያልነበሩና ለሌላ ተረኛ ሹፌር ያስረከበ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ስለመረጋገጡ በአንደኛውና በሶስተኛው ክስ ላይ መደምደሚያ ላይ ደርሶ እያለ በሁለተኛው ክስ ስር በተመሣሣይ ጊዜና ቦታ እንደዚሁም የግል ተበዳዮች ላይ ተፈጸመ ለተባለው ወንጀል ጥፋተኛ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ አንድ ተከሣሽ ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው ወንጀሉን ሊያቋቁሙ የሚችሉ ተግባራት ስለመፈጸማቸው በፍሬ ነገር ረገድ ለማጣራት ስልጣኑ ባላቸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በይግባኝ ያየው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ የወ/መቀጫ ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 141,142 እና 149/1/ ዓላማ ፣ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ እና ቦታ የሌለ መሆኑን ወይም በእረፍት ላይ የነበረ ስለመሆኑ እና ወንጀሉን ለመፈጸም ተጠቀመበት በማለት የተጠቀሱትንም ተሽከርካሪዎች በወቅቱ ያልያዘና ለሌላ ሰው አሳልፎ አስረክቦ በነበረበት ወቅት በመሆኑ አልተረጋገጠም ወደሚለው የፍሬ-ነገር መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ በመሆኑም ባልተረጋገጠ ፍሬ ነገር ፍርድ ቤቱ መልሶ በሁለተኛ ክስ ስር ጥፋተኛ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለውና ውሣኔውም እርስ በራሱ የሚጋጭ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከቱትን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 51055 በቀን 12-4-2003 ዓ.ም ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 50973 በቀን 23-3-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በመዝ.ቁ. 08979 በቀን 16-3-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 195/2/ /ለ/ /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ተሰርዞ በነጻ እንዲሰናበት ብለናል፡፡ የወንጀል ኃላፊነቱን ሊያቋቁሙ የሚችሉት ተግባራት በበታች ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. አመልካች በሌላ ወንጀል የሚፈለግ ካልሆነ ከማረሚያ ቤት እንዲለቀቅ መፍቻ ለሚመለከተው ይጻፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 46386

ታህሣሥ 03 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሃይሉ ተስፋኡ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ብርሃነ መብራቱ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ገንዘብን ለማስመለስ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪና በወ/ሪት መብርሂት ቅዱስ ላይ በትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመስረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም የአሁኑ ተጠሪ ዘበኛ፣ ወ/ሪት መብርሂት ቅዱስ ደግሞ የሽያጭና መዛኝ ሰራተኛ ሁነው በአመልካች የወፍጮ ድርጅት ውስጥ ሲሰሩ በወፍጮ ድርጅቱ ውስጥ ባለው መጋዝን ካዝና አመልካች ያስቀመጡትን ብር 17,000.00 (አስራ ሰባት ሺህ) መጋዝኑ ተከፍቶ ካዝናው ተሰብሮ ስለተሰረቀባቸው የተሰረቀው ይኸው ገንዘብ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የድርጅቱ ሰራተኛ መሆናቸውን ሳይክዱ ድርጅቱ ተሰረቀ በተባለበት ጊዜ በፈቃድ ለጠበል ሂደው ሌላ ቦታ ያደሩ መሆናቸውን ገልጸው ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር 2ኛ ተከሳሽ የነበሩትን ከክሱ ነጻ፣ ተጠሪን ደግሞ ኃላፊ በማድረግ ብር 17,000.00 (አስራ ሰባት ሺህ) ለዳኝነት የተከፈለበት ብር 662.00 ኪሳራና ሌላ ወጪ እንዲሁም የድካም ዋጋ በቁርጥ ብር 300.00 ለአመልካች እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኝቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረቡት የተጠሪ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የደርጅቱ ዘበኛ ሁነው ተቀጥረው እየሰሩ ቢኖሩም ካዝናው ተሰብሮ ገንዘቡ በጠፋበት በ30/05/2000 ዓ/ም በአመልካች ፍቃድ ወደ ጠበል ሂደው ስለነበር አልነበሩም፣ አመልካች ራሱ የፍርድ ቤት መጥሪያ ለተጠሪ በሚሰጡበት ጊዜ ገንዘቡ አልጠፋም ከእህቴ ጋር አግኝቼዋለሁ ብለው ሲናገሩ ሰምተናል ብለው ስለመሰከሩ እንዲሁም ብር 17,000.00 (አስራ ሰባት ሺህ) ያክል በመጋዘን ውስጥ በካዝና ያስቀምጣል ተብሎ አይገመትም የሚሉትን ምክንቶችን በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን ለገንዘቡ ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በወንጀሉ ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥፋተኛ ተብለው ተቀጥተው እያለ ለፍትሐብሔር ክስ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌን ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ በወንጀሉ ጉዳይ ጥፋተኛ ተብለው ተቀጥተው እያለ ለፍትሐብሔሩ ክስ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር፣ የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ ተጠሪ ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች ክሱን ሊመሰርቱ የቻሉት ተጠሪን በድርጅታቸው በጥበቃ ስራ ቀጥረው በማስራት እያሉ በድርጅቱ መጋዘን ውስጥ በሚገኘው ካዝና የተውት ገንዘብ ካዝናው ተሰብሮ እንዲሰረቅባቸው አድርገዋል በማለት ገንዘቡን እንዲተኩላቸው ሲሆን የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ የበታች ፍርድ ቤቶቹ ተገቢ ነው ያሉትን ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጥብቀው የሚከራከሩትና በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው ተብሎ የተያዘውም ተጠሪ በወንጀል ተከስሰው ጥፋተኛ ተብለው ተቀጥተው እያለ በፍትሐብሔሩ ክስ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤት ከቀረቡት የአመልካች ማስረጃዎች መካከል ተጠሪ በጉዳዩ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉበትና የተቀጡበትን የፍ/ቤት ውሣኔ ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ወይም ብቁነት ሳይገልጽ ስለማለፉ የውሣኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የተቆጠረው ወይም የቀረበው ማስረጃ ለክርክሩ መነሻ ከሆኑት ፍሬ ነገሮች ጋር ግንኙነት እያለው እና ፍሬ ነገሮችን ለማረጋገጥ በሕጉ ክልከላ ያልተደረገበት የማስረጃ ዓይነት እስከሆነ ድረስ በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ሁሉም ማስረጃዎች መመዘን አለባቸው፡፡ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ሁሉን ማስረጃዎች በአንድነት ሳይመዘኑ የተወሰኑትን ብቻ ነጥሎ በመወሰድ የሚሰራ ምዘናም ሆነ ውጤት ሕጋዊነት አይኖረውም፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ በወንጀል ተከሰው ፍ/ቤቱ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑንና በበላይ ፍ/ቤትም አለመለወጡ ተረጋግጦ እያለ ይህ የአመልካች ማስረጃ በሰበር ፍ/ቤት በዝምታ ታልፏል፡፡ ይህም የማስረጃ አቀባበል ሥርዓትን ያልተከተለ ነው፡፡ የዚህን ማስረጃ አግባብነት እና ብቁነት ስንመለከተውም ለጉዳዩ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር በማስረጃነት አግባብነት እና ብቃት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2149 ተቃራኒው ንባብ ያስገነዝባልና፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት በወንጀል የተሰጠ ውሣኔ በፍትሐብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት አግባብነት የሚኖረው በወንጀል ክሱ በወንጀል ፍ/ቤት ተከሣሹ ጥፋተኛ ተብሎ ከተወሰነ ስለመሆኑ እና ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት የወንጀል ክስ ማስረጃ አመዛዘን መርህ ከፍትሐብሔሩ የበለጠ ጠንካራና የማያሻማ ማስረጃ የሚጠይቅ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም የሚል ነው፡፡ ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስም በወንጀሉ ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎችም በፍትሐብሔሩ ጉዳይም የቀረቡና የተሰሙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በወንጀሉና በፍትሐብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች የተለያዩ ከሆነ እና በወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበበት ነጥብም ከፍትሐብሔሩ ክስ ጋር ግንኙነት የሌለው ከሆነ በወንጀል ክስ ተጠያቂ መሆን ሁል ጊዜ በፍትሐብሔሩ ክስ ኃላፊነትን የማያስከትል ስለመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና አላማ ያስገነዘበናል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን የፍትሐብሔር ጉዳይ የተመለከተው የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ክብደት በመመዘን ነው፡፤ በወንጀሉ ጉዳይ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉት በሰራተኝነት የጥበቃ ስራ ግዴታቸውን አልተወጡም በሚል ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ የፍትሐብሔር ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት ካገዘና ላይ የተቀመጠው ጥሬ ገንዘብ ስለተሰረቀብኝ ተጠሪ ይመልሱልኝ በሚል ነው፡፡ ይህም በግልጽ የሚያሳየው አመልካች ተጠሪ ሰርቀው የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ ክስ የቀረበባቸው መሆኑን እንጂ በንዝህላልነት የተሰጠውን የስራ አመራር ግዴታ ያለመወጣትንና በወንጀል ሕጉ 702(2) ስር የሚያስጠይቀውን የወንጀል ድርጊት ፈጸመው ገንዘቡ ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን የሚያሳይ አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ ተጠሪ በወንጀል ተከስሰው ጥፋተኛ ከተባሉት የወንጀል ድርጊት ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይነት የሌለው በመሆኑ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 መሰረት ኃላፊ የሚሆኑበት አግባብ የለም በማለት በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27225 መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 30033 ሚያዚያ 13 ቀን 2001 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 67411
ታህሳስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አደነ ንጉሴ

አመልካች፡- .1. አቶ ታረቀኝ ተክሉ ገመዳ

2. ወ/ሮ እማዋይሽ ገብረመስቀል

3. አቶ አብይ ታመነ

ተጠሪ፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሥነ ምግባር እና

የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ባለቤት ሆኖ የመገኘት የወንጀል ተግባርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ/ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ተጠሪ በአመልካቾች ላይ የመሰረተው ክስ ይዘት በ1997 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ለ))፣33 እና 419(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ አመልካቾች በግብረአብርነትና በልዩ ተካፋይነት ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ወይም ገንዘብ ለማፍራት የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ዝርዝር ይዘቱም፡-1ኛ አመልካች ከሰኔ 01 ቀን 1986 እስከ መጋቢት 30 ቀን 2000 ዓ/ም ድረስ በሀዋሳ ዙሪያ እና በወንዶገነት ወረዳዎች ታክስ አስተዳደር ጽ/ቤት በእለት ገቢ ሰብሳቢነት ሲሰሩ መነሻ ደመወዛቸው ብር 182.00(አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ብር) ሁኖ በየጊዜው በተደረገላቸው የእርከን ጭማሪ እና የደረጃ እድገት ስራቸውን እስከለቀቁበት መጋቢት 2000 ዓ/ም ድረስ ደመወዙ ብር 928.00(ዘጠኝ መቶ ሃያ ስምንት ብር) የደረሰ መሆኑንና የደመወዙ ከፍተኛ መጠን ሲሰላም ጠቅላላ ገቢያቸው ከብር 70,000.00(ሠባ ሺኅ ብር) እንደማይበልጥ፣2ኛ አመልካች ደግሞ የ1ኛ አመልካች ባለቤት ሁነው ከባለቤታቸው ደመወዝ ውጪ በግላቸው የሚያገኙት ሕጋዊ የሆነ የገቢ ምንጭ የሌላቸው የቤት እመቤት ሁነው እያለ በስማቸው የከተማ ቦታና እና የይስሙላ ንግድ ፈቃድ(የማይሰራበት ንግድ ፈቃድ) በመውሰድ በዚሁ ባልታደሰ ንግድ ፈቃድ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ በመውሰድ በሕገ ወጥ ንብረትና እና ገንዘብ ከ1ኛ አመልካች ጋር ግብረ አበር ወይም ልዩ ተካፋይ በመሆን ንብረቱን እንዳፈሩ፣3ኛ አመልካችም የ2ኛ አመልካች ወንድም ሁነው በስማቸው ቋሚ እና ሕጋዊ የገቢ ምንጭ የሌላቸው ተማሪ ሁነው እያለ ከ1ኛ እና ከ2ኛ አመልካቾች ጋር ያለውን ዝምድና ምክንያት በማድረግ 1ኛ አመልካች በስማቸው የሊዝ ቦታ ጠይቀው ከሊዝ ደንብና መመሪያ ውጪ G+1(Ground Plus

https://t.me/ethiopianlegalbrief

One) የመኖሪያ ቤት ሰርተው ከ2ኛ አመልካች ጋር የሚኖሩበትን ቤት ለ3ኛ አመልካች በሕግ የተረጋገጠ ወይም የተፈጸመ ወራሽነት ሳይኖረው ከወላጅ አባቱ ከውርስ ባገኘው ገንዘብ ቤቱን እንደሰራ በማስመሰል በስሙ ባወጣው የሐሰት ባለቤትነት ማረጋገጫ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ሕገ ወጥ ንብረት እንዲያፈሩ በማድረግ በግብረአብረት ወይም በልዩ ተካፋይነት ወንጀል መፈጸማቸውን የሚጠቅስና በጠቅላላው አመልካቾች ክስ እስከ ቀረበባቸው ድረስ ብር 3,602,000.84(ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሁለት ሺኅ ከሰማኒያ አራት ሳንቲም) የሚሆን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ማፍራታቸውንና ይህም ንብረት ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ የማፍራት የሙስና ወንጀል ነው በማለት አመልካቾች እንዲጠየቁ ክስ ማቅረቡን የሚያሳይ ነው።ክሱን ለማስረዳትም የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን ዘርዝሯል።አመልካቾች ክሱን ክደው በመከራከራቸውም ተጠሪ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል።ከዚህም በሁዋላ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል።ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ማስተባበላቸውን በመግለጽ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 149(2) መሰረት በነፃ አሰናብቷቸዋል።በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ አመልካቾች በተከሰሱት የሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብለው 1ኛ አመልካች በሌላ ጉዳይ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተቀጡ መሆናቸው በመረጋገጡ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት፣2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ደግሞ እያንዳንዳቸው በአንድ አመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ የተወሰነ ሲሆን በሕገ ወጥ መገንድ መገኘቱ የተረጋገጠውን ንብረት ደግሞ አይነቱና መጠኑን ይኸው ይግባኙን የተመለከተው ፍርድ ቤት ከለየው በሁዋላ ለመንግስት እንዲወረስ በማለት ወስኗል።በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም።የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

የአመልካቾች ጠበቃ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሚያዚያ 04 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል።ይዘቱም ባጭሩ፡-አመልካቾች በወንጀል ድርጊት እንዲጠየቁ የተደረገው የሀብት ምዝገባና ማሳወቂያ ሥርዓት ባልተዘረጋበት ሁኔታና የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው በተገቢው መንገድ ከሳሽ ሳያስረዳ መሆኑንና የአመልካቾች የመከላከያ ማስረጃዎች ቃልም ውድቅ የተደረገው ያላግባብ መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው እንዲሻር መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው።

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የምዝገባ ስርዓት ባልተዘረጋበት ሁኔታ አመልካቾች ምንጩ ያልታወቀ ሀብት አፍርተዋል ተብሎ የመቀጣታቸውንና ንብረታቸውም እንዲወረስ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው በመባሉ ማመልከቻው ለተጠሪው ተልኮ ተጠሪ ቀርቦ መልሱን በጽሑፍ እንዲሰጥበት ተደርጓል።ተጠሪ ሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የሀብት ምዝገባና ማሳወቂያ ስርኣት ያለመዘርጋት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 419 ስር በተመለከተው ድንጋጌ ከመጠየቅ የማይከለክል መሆኑን፣አመልካቾች ለሰበር ችሎቱ ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ በሥር ፍ/ቤት የህግ ስህተት ተፈጽሟል ብለው የገለጿቸው ምክንያቶች ስለማስረጃ ምዘና የሚመለከቱ እንጅ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያስረዱ አለመሆኑን፣የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲህ አይነት የማስረጃ እና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በሕጉ የማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በበቂና አሳማኝ ማስረጃ የወንጀል ድርጊቱን መፈፃማቸው ተነግሮባቸው በመከላከያ ማስረጃዎቻቸውም የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ባለማስተባበላቸው ምክንያት መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዘርዝሮ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሆኖ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቋል፡፡የአመልካቾች ጠበቃም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሱን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የምዝገባ ሥርዓት ባልተዘረጋበት ሁኔታ አመልካቾች ምንጩ ያልታወቀ ሀብት አፍርተዋል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የመቀጣታቸውንና ንብረታቸውም እንዲወረስ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ይሁን እንጂ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 መሰረት ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ የመገኘት የወንጀል ድርጊት ተጠያቂነት ለማስከተል የሚችለው የምዝገባ ሥርዓት ሲዘረጋ ስለመሆኑ የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ የሌለ በመሆኑ በአመልካቾች ጠበቃ በኩል የቀረበው ክርክርም ሆነ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ተቀባይነት የሚያገኝበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ሌላው አመልካቾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 419(1) ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በእጃቸው ገብቶ ተገኝቷል ተብለው በወንጀል የተከሰሱባቸውን ጉዳዮች በሚመለከት ይግባኙን በተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ሲታይም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለም፡፡ምክንያቱም ይኸው ፍርድ ቤት አመልካቾችን ለወንጀል ድርጊቱ ተጠያቂ ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ለጉዳዩ የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ ሲሆን የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ደግሞ በዚህ ሰበር ችሎት ሊታይ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነውና፡፡ይህ ችሎት ሊመለከተው የሚችለው የሕግ ጥያቄን ብቻ ሲሆን ከዚህ አንፃር በስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎቹ ተመዝነው የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ተይዞ በሕግ ረገድ ያለው ነጥብ ሲታይ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበትን የወንጀል ድርጊት ያቋቁማል? ወይስ አያቋቁምም? የሚለውን ጉዳይ ስንመለከተው የአሁኑ 1ኛ አመልካች በመንግሥት ሥራ ላይ ሆነው ከብር 182.00 የወር ደመወዝ ተነስተው በጭማሪና በዕድገት ብር 928.00 የወር ደመወዝ ላይ ደርሰው በዚህ መጠነኛ ደመወዝ ራሣቸውን ሲያስተዳድሩ እንደቆዩና ባለቤታቸውም ሌላ ህጋዊ ገቢ እንዳልነበራቸው፣3ኛ አመልካችም ሕጋዊ ገቢ ያልነበራቸው ሁኖ ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካች ጋር በመመሳጠር ሕጋዊ ያልሆነ ንብረት 1ኛ እና 2ኛ አመልካች እንዲይዙና በሕጋዊ መንገድ የተገኘ ለማስመሰል በመፈለግ በወንጀል ተግባሩ መካፈላቸው ተረጋግጦ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ምንጩ ያልታወቀ በሚሊዮን የሚቆጠር ንብረትና ገንዘብ በእጃቸው ገብቶ መገኘቱና ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረት ባለቤት ሆነው መገኘታቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ለ))፣33 እና 419(1) የወንጀል ተጠየቂነትን የሚያስከትል ተግባር ሁኖ አግኝተነዋል፡፡በመሆኑም አመልካቾች ጥፋተኛ መባላቸውም ሆነ የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ተጠይቆ ስለቅጣት በወንጀል ሕጉ የተመለከቱት የቅጣት አጣጣል መርሆች መሰረት ተደርገው እያንዳንዳቸው ላይ ተገቢ የእስራት ቅጣቱ መጣሉ እንዲሁም ንብረቱ እንዲወረስ መወሰኑ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት አላገኘንም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በመ/ቁጥር 33970 ተሰጥቶ በክልሉ የሰበር ችሎት በመ/ቁ 50929 ጥር 17 ቀን 2003 ዓ/ም የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195 ((2(ለ-2)) መሠረት ፀንቷል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/.ቁ 67777

ታህሳስ 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. ተወልደ ብስራት
2. ሃይላይ ገ/መድህን
3. ገላን ሰቦቃ

} ከጠበቃ ገብረ እግዚብሔር ተስፋዬ ጋር ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የለም፡፡

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በ1997 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 448(1 እና 3) መሰረት አንድን ሰው ለፍትህ እርዳታ ለመስጠት እንቢተኛ ሁኖአል በማለት ወዲያውኑ ለመቅጣት መሟላት ስላለባቸው ሕጋዊ መስፈርቶችን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ በከሳሽ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አቃቤ ሕግና በተከሳሾች እነ ተካበ ገ/ስላሴ ስድስት ሰዎች መካከል በነበረው የወንጀል ክስ ጉዳይ ነው፡፡ የወንጀል ክሱ በዐቃቤ ሕግ በኩል በተከሳሾች ላይ ከተመሰረተና በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ከቀረበ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ተከሳሾቹ ወደ አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲሄዱ ትዕዛዝ ሰጥቶ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን ምርመራ ክፍል ኃላፊዎች ተከሳሾችን ወደ ማረሚያ ቤት ሳይወስዱ ወይም ሳይልኩ በራሳቸው ማረፊያ ቤት ለረዥም ጊዜና ወራት አቆይተዋቸዋል፣ የፍርድ ቤቱንም ትእዛዝ ሳያከብሩ ቀርተዋል በማለት የስር ፍርድ ቤት አመልካቾችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 448(1) እና (3) መሰረት ጥፋተኛ በማድረግ እያንዳንዳቸውን በሁለት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ጉዳዩ ከተመረመረ በሁዋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት አመልካቾች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 448(1 እና 3) ስር ጥፋተኛ መባላቸውና ቅጣት መተላለፉን አግባብነት ተቀብሎ የቅጣቱን አፈጻጸም ብቻ በገደብ እንዲሆን በማድረግ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለጉዳዩ አመልካቾች ተጠያቂ መደረጋቸው የድንጋጌውን ይዘት እና በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ባላገናዘበ መልኩ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካቾችን ቅሬታ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው አመልካቾች የፍርድ ቤቱ ዋራንት በአግባቡ እንደደረሳቸው ሳይረጋገጥ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 448(1(ሀ)) እና (3) ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ መባላቸው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ሊባሉ የቻሉት የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን በአቶ ተካበ ገ/ስላሴ ላይ በመሰረተው የኮንትሮባንድ የወንጀል ክስ በመ/ቁጥር 162887 ፋይል ተከፍቶላቸው ፍርድ ቤት ቀርበው ፍርድ ቤቱም ጥር 03 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተከሳሹን የዋስትና መብት ጠብቆላቸው ተከሳሹ የተፈቀደላቸውን የዋስትና መብት ካላሟሉ በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ታስረው እንዲቆዩ ሲል የእስር ዋራንት እንዲፃፍ በማለት ትዕዛዝ የሠጠ ቢሆንም ተከሳሹ ወዲያውኑ ማረሚያ ቤት ሳይገቡ በባለስልጣን መስሪያ ቤት ደረቅ ፖሊስ ጣቢያ ከአስር ወራት በላይ ታስረው የተገኙ መሆኑን፣ ይኸው ግለሰብ በአጠቃላይ ከአንድ አመት ሁለት ወራት በላይ የታሰሩ መሆኑን፣ መስፍን ካሳሁን የተባሉት ተከሳሽም በተከሰሱበት ወንጀል በወንጀል መዝገብ ቁጥር 169690 ፋይል ተከፍቶባቸው በፍርድ ቤቱ ቀርበው ፍርድ ቤቱ ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት በተመሳሳይ መልኩ በመዝገቡ ላይ የዋስትና መብታቸውን ጠብቆላቸው ሲያበቃ የተፈቀደላቸው የዋስትና ግዴታ ተከሳሹ መፈፀም ካልቻሉ በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ታስረው እንዲቆዩ ሲል ትእዛዝ ሰጥቶ ተከሳሹ ወዲያውኑ ማረሚያ ቤት ሳይላኩ የእስር ዋራንቱ በመዝገቡ ላይ ከተሰጠ በሁዋላ በባለስልጣኑ ፖሊስ ጣቢያ ከስድስት ወራት በላይ መታሰራቸውን፣ ሃይሉ ወርቁ እና ሊዊዛ ፋርቤታ የተባሉት ሁለት ግለሰቦች ደግሞ በተከሰሱበት የጉምሩክ ማጭበርበር የወንጀል ድርጊት በመ/ቁጥር 167550 በሆነው ፋይል ተከፍቶላቸው ፍርድ ቤት ቀርበው በዋስትና መብት ላይ ትዕዛዝ ከተሰጠ በሁዋላ የዋስትና ግዴታቸውን በትዕዛዙ አግባብ መፈፀም ካልቻሉ በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ታስረው እንዲቆዩ ሲል ፍርድ ቤቱ የእስር ዋራንት እንዲፃፍ ሰኔ 18 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቶ በትእዛዙ መሰረት ወደ አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ሳይላኩ እያንዳንዳቸው እጃቸው በፖሊስ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ፍርድ ቤት እስከቀረቡበት ጊዜ ያለውን ሳይጨምር በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከስምንት ወራት በላይ ታስረው መቆየታቸው መረጋገጡን፣ መንግስቱ አብርሃምና አህመድ መሐመድ በተከሰሱበት የኮንትሮባንድ ወንጀል ደግሞ በመ/ቁጥር 172759 እና ባምላክ ይስማው የተባሉት ተከሳሽ ደግሞ በመ/ቁጥር 170203 ፋይል ተከፍቶላቸው ፍርድ ቤት ቀርበው በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ታስረው እንዲቆዩ የእስር ዋራንት እንዲጻፍ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቶ ወደ ማረሚያ ቤት ሳይላኩ እያንዳንዳቸው ቢያንስ ሶስት ወራትን ያህል በፖሊስ ጣቢያ መታሰራቸውን የስር ፍርድ ቤት መገንዘቡን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በቀጥታ ይመለከተቸዋል ያላቸውን የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት የወንጀል ምርመራ ቡድን አስተባባሪ ኃላፊዎችን ችሎት ቀርበው እንዲያስረዱና ሕጋዊ መግለጫ እንዲሰጡበት በማለት በሶስት የወንጀል መዛግብት ላይ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን የአሁኑ አመልካቾችም ወደ ፍርድ ቤቱ ቀርበው አለኝ ያሉትን ምክንያት ያቀረቡ ሲሆን የአሁኑ ሁለተኛው አመልካች የባለስልጣኑ መሰሪያ ቤት ፖሊስ ጣቢያ የእስረኞች ሰነዶች ክትትል ኃላፊ መሆናቸውን ገልፀው የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሳይከበር የቀረው ከፍርድ ቤቱ ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት የተላኩት የእስር ዋራንቶች የስም ስህተት ስለተከሰተባቸውና ማረሚያ ቤቱም አልቀበልም ስለአለ ነው፣ የሥም ስህተቱ በዋራንቱ እንዲስተካከልም በተደጋጋሚ ጊዜያት ወደ ፍርድ ቤቱ በመምጣት አቤት ብያለሁ፣ ከፍርድ ቤቱ ግን የተሰጠኝ አፋጣኝ ምላሽ የለም፣ ከዚህ ሌላም ከባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊዎች ጋር ደጋግሜ ተነጋግሬበታለሁ፣ ግን መፍትሔ ሊገኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለመቻሉ ተከሳሾች ለበርካታ ወራት ሲታሰሩ ችለዋል በማለት የዘረዘሩ ሲሆን የአሁኑ 1ኛ አመልካችም ከቦታው ላይ በኃላፊነት ከመመደባቸው ከመጋቢት 2002 በፊት ተከሳሾች በፖሊስ ጣቢያው ታስረው ነው ያገኟቸው መሆኑን፣ በፖሊስ ጣቢያ ለበርካታ ወራት መታሰራቸው ኃላፊነትን እንደሚያስከትል በመገንዘብም ወደ አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲገቡ የበኩላቸውን ጥረት እንደአደረጉ፣ በመዝገብ ላይ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ከሆነም ተገልብጦ እንዲመጣላቸው ዐቃቤ ሕጎችን ሳይቀር በተደጋጋሚ ጊዜያት መላካቸውን፣ ሆኖም ግን ከመስሪያ ቤቱ አቃቤ ሕጎች አንዱ የሆኑት አቶ ወንድወሰን ደሳለኝ ተከሳሾች ወደ አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲገቡ የተሠጠ ትዕዛዝ የለም ብለው ሊገልፁላቸው የቻሉ መሆኑንና ከዚያም ተከሳሾች ወደ ማረሚያ ቤት ሳይገቡ በእድገት ምክንያት ከወንጀል ምርመራ ቡድን አስተባባሪነታቸው መነሳታቸውን በምክንያትነት ያቀረቡ መሆኑን ነው፡፡ የአሁኑ ሶስተኛ አመልካች ደግሞ የወንጀል ምርመራ ቡድን አስተባባሪ ኃላፊ መሆናቸውን ጠቅሰው የወንጀል ምርምራ አጣርተው ከጨረሱ በኋላ ምርመራውን ያጣሩበትን ተከሳሽ በዋስ ሊወጣ/ሊለቀቅ የቻለ መሆኑን፣ ከዚያ በሁዋላ በተጠረጠረበት ወንጀል የወንጀል ክስ ተመስርቶበት ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ስለሆነው ነገር እንደማያውቁ፣ ተከሳሽ መስፍን ካሳሁን ወይም ሌሎች ተከሳሾች በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ፖሊስ ጣቢያ ለበርካታ ወራት መታሰራቸውን ያወቁት ቀርበህ አስረዳ ተብሎ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲደርሳቸው መሆኑን፣ የወንጀል ምርመራውን ያጣሩት እርሳቸው ስለሆኑ ጉዳዩን እስከመጨረሻው የመከታተል ኃላፊነት እንደነበረባቸውና ሌሎች ኃላፊዎችም ተከሳሾች ለበርካታ ወራት መታሰራቸውን እንደሚያውቁ ዘርዝረው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ እንግዲህ ከላይ የተመለከተው አመልካቾች እያንዳንዳቸው ያቀረቡት ምክንያት ሲሆን የሁሉም አመልካቾች የጋራ ምክንያታቸው በጥቅሉ ሲታይ ግን ተከሳሾች በፍርድ ቤቱ የእስር ዋራንት ትእዛዝ መሰረት በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ታስረው መቆየት ሲገባቸው በፖሊስ ጣቢያ ለበርካታ ወራት መታሰራቸው ስህተትም ጥፋትም መሆኑን አምነው ጥፋቱ ግን የእነርሱ ያለመሆኑን፣ የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ያልተከበረው በራሳቸው ምክንያት ያለመሆኑን ጠቅሰው መከራከራቸውን ነው፡፡

ከላይ ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች የሚያሳዩት ለአመልካቾች ለወንጀሉ ተጠያቂነት ምክንያት የሆነው በጉምሩክ ወንጀል ተከሰው ፍርድ ቤት የቀረቡት ተከሳሾች ማረሚያ ቤት እንዲታሰሩ የፍርድ ቤት ማሰሪያ ዋራንት ተሰጥቶ እያለ በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ፖሊስ ጣቢያ ለበርካታ ወራት እንዲታሰሩ መደረጉ ለፍትህ እርዳታ ለመስጠት እንቢተኛ መሆንን ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች መደምደሚያ ላይ መደረሱን ነው፡፡ ይህ ችሎትም ከላይ ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ ለመስጠት ይቻል ዘንድ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገውን ድንጋጌ ይዘት መመልከቱ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 448(1) ስር አንድ ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ስልጣን ያለው አካል በያዘው ጉዳይ ላይ በተከሳሽነት፣ በምስክርነት ወይም በልዩ አዋቂ ምስክርነት ወይም በአስተርጓሚነት፣ በነባሪነት ወይም በተቺነት እንዲረዳ በሕግ መሰረት የተጠራ ወይም ተከሳሽን ወይም ማስረጃን እንዲያቀርብ ወይም እንዲልክ የታዘዘ ማንም ሰው በቂ ምክንያት ሳይኖረው ሳይቀርብ የቀረ ወይም ለመቅረብ እንቢተኛ የሆነ እንደሆነ፣ ተከሳሽን ወይም ማስረጃን ያላቀረበ ወይም ያልላከ እንደሆነ፣ ወይም ቀርቦ ሕግን በሚቃረን አኳኋን ለተጠየቀው መልስ ለመስጠት ወይም እንደታዘዘው ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ሲሆን ይህ አድራጎት ወንጀል ሁኖ ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ ሳይሰጥ ወዲያውኑ ቅጣት የሚወስን ስለመሆኑም የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሶስት ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ ከድንጋጌው መንፈስ የምንገነዘበው አንድን ሰው ለፍትሕ እርዳታ ለመስጠት እንቢተኛ ሆኖአል በማለት በወንጀል ጥፋተኛ አድርጎ ለመቅጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ስልጣን ባለው አካል በተከሳሽነት፣ በምስክርነት፣ በልዩ አዋቂ ምስክርነት፣ በአስተርጓሚነት፣ በነባሪነት በተቺነት የተጠራ ወይም ተከሳሽን ወይም ማስረጃን እንዲያቀርብ ወይም እንዲልክ የታዘዘ መሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ የሚገባ የወንጀሉ መሰረታዊ የማቋቋሚያ ባህሪ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) እና 58 ጋር ተዳምሮ ሲነበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ስለመሆኑ ነው። ያለመቅረቡና የታዘዘውን ነገር ያለመፈፀሙን ምክንያት ማስረዳት ጉዳይ ደግሞ ከላይ የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ተሟልተው መገኘት ከተረጋገጠ በሁዋላ የሚፈፀም ተከታይ ተግባር መሆኑን የተጠቃሹ አንቀፅ አቀራረፅና ይዘት እንዲሁም ዓላማው የሚያስገነዝበን ነጥብ ነው።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ ባለማክበር በወንጀል የተከሰሱትን ሰዎች ማረሚያ ቤት መውስድ ሲገባቸው በባለስልጣኑ ፖሊስ ጣቢያ በማሰር ለበርካታ ወራት አቆይተዋል በሚል ነው። ይሁን እንጂ አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ተከሳሾች ለበርካታ ወራት በፖሊስ ጣቢያ ያላግባብ መታሰራቸውን አናውቅም በማለት ሳይሆን በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት ለማረሚያ ቤቱ ለማስረከብ ሲሞክር በስም ስህተት የተነሳ ማረሚያ ቤቱ ሊረከብ ያለመቻሉንና ፍርድ ቤቱም በማሰሪያ ዋራንቱ ላይ የተከሰተውን የስም ስህተት እንዲያስተካክል በተደጋጋሚ ጥያቄ ቀርቦለት ሊያስተካክል ያለመቻሉን፣ እንዲሁም በፍርድ ቤቱ የተሰጠ ማሰሪያ ዋራትን የሌለ መሆኑን የሚመለከታቸው የአቃቤ ሕግ ባለሙያዎች ሲገልፁላቸው የነበረ መሆኑን በመጥቀስ ነው። በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋጋጠው ደግሞ ተከሳሾቹ በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲታሰሩ በመዝገብ ላይ የማሰሪያ ዋራንት እንዲፃፍ ትእዛዝ መሰጠቱ እንጂ በትክክል የተፃፈ የማሰሪያ ዋራንቱ ለአመልካቾች ደርሷቸው አመልካቾች ይህንኑ እያወቁ የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ባለማክበር ተከሳሾቹን ያሰሩ ስለመሆኑ ካለመሆኑም በላይ የስም ስህተት ተከስቷል፣ ይህም ይስተካከልልን በማለት በባለስልጣኑ መሰሪያ ቤት በኩል የቀረበው ጥያቄ በፍርድ ቤቱ በተገቢው ጊዜ ምላሽ የተሰጠበት ስለመሆኑም በፍሬ ነገር ደረጃ አልተረጋገጠም። በመሆኑም ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተያይዞ ሲታይ አመልካቾች የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ባለማክበር ለፍትሕ እርዳታ መስጠትን እንቢ ማለት ወንጀል ፈፅመዋል ብሎ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ አመልካቾች ከላይ በምክንያትነት የገለጿቸው ፍሬ ነገሮች እውነት መሆን ያለመሆናቸው በተገቢው ማስረጃ ሊጣራ የሚገባው እንጂ ወንጀሉ የተፈጸመው በፍርድ ቤት ነው፣ ተከሳሾቹ ለበርካታ ወራት ተገቢ ባልሆነ ቦታ ታስረዋል በሚል ምክንያት ቀጠሮ ሳይደረግ ወዲያውኑ ቅጣት ለማስተላለፍ የሚያስችል አይደለም። ስለሆነም አመልካቾች ፈጸሙ የተባለውን አድራጎት በተመለከተ በማስረጃ ሳያጣራና ድርጊቱም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 448(1(ሀ)) ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ በተገቢው ሁኔታ ሳያረጋግጥ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾችን ወዲያውኑ ጥፋተኛ በማድረግ መቅጣቱም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቀበል የቅጣቱን አፈፃጸም በገደብ እንዲሆን መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተናል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 162887 ጥር 05 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በዚሁ ፍርድ ቤት በተጠቀሰው መዝገብ ጥር 05 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሠጠው የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 102668 ጥር 18 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሠጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-1)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካቾች የፍርድ ቤቱ ማሰሪያ ዋራንት በትክክል የደረሳቸው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 448(1(ሀ))እና (3) መሰረት ሊቀጡ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታህሣስ 06 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ታደሰ ናማጋ ሀያቱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ፖሊስ ወ/ምርመራ መምሪያ ዋና ሣጅን ደምሴ ሰጠኝ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ ሰበር አመልካች በስር የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረ ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱም እነዳዊት ጸጋዬ የተባሉት 23 ተከሣሾች ህዳር 27 ቀን 1992 ዓ.ም ከከሣሽ ብር 250,000 ዘርፈው ከተሰወሩ በኋላ በፖሊስ ታድነው በከፊል ተይዘው ክስ የቀረበባቸው ሲሆን በጊዜው ከከሣሽ ዘርፈው ከወሰዱት ገንዘብ ውስጥ ብር 94,000 በኢግዚቢትነት ተከሣሽ ሲይዝ በተረፈው ገንዘብ እነዚህ በወንጀል የተከሰሱ ግለሰቦች ዓይነታቸውን ባላውቅም የተለያዩ የገዙአቸውንም ቁሳቁሶች ጭምር ተከሣሽ በኢግዚቢትነት ይዟል፡፡ ሆኖም በኢግዚቢትነት የተያዙትን ቁሳቁሶች እና ገንዘብ ተከሣሽ እንዲያስረክበኝ ብጠይቅም ለማስረከብ ፍቃደኛ ስላልሆነ ተገዶ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሣሽም በሰጠው መልስ በጊዜው የውንብድና ወንጀል በፈጸሙ 23 ተከሣሾች ላይ 14 ክሶች የቀረቡባቸው ሲሆን በ2ኛ ክስ ከከሣሽ ብር 250,000 ስለመዝረፋቸው በክሱ ተጠቅሷል፡፡ ሆኖም በክሱ ኢግዚቢቶቹ ከ1-8 ተራ ቁጥር ከመዘርዘራቸው በቀር የከሣሽ በኢግዚቢትነት የተያዘው ገንዘብም ሆነ ንብረት ተለይቶ አልተቀመጠም፡፡ በሌላ በኩል በኢግዚቢትነት የተያዙ ንብረቶችን ፖሊስ የመጠበቅ እንጂ የመመለስ ስልጣን የፖሊስ ሳይሆን የፍ/ቤት በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በሚል ተከራክሯል፡፡

የስር የመ/ደ/ፍ/ቤትም በሰጠው ፍርድ ገንዘቡም ሆነ ሌሎች ቁሳቁሶች የከሣሽ ስለመሆናቸው ከሣሽ ያቀረበው ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ሌሎች ንብረትና ገንዘብ የተወሰደባቸው ሰዎችም ስላሉ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ወገኖች በማከራከር በሰጠው ፍርድ የስር የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቷል፡፡

አመልካችም በስር ፍ/ቤቶች ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲል አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት ያቀረበው የቅሬታ ነጥብም፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪው በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ቀርቦ ከአመልካች ወንበዴዎች የወሰዱትን ብር 94,000 እና በገንዘቡ የተገዙትን ቁሳቁሶች በኢ.ግ.ዚ.ት.ነት መያዙን አምኖ መልስ ሰጥቶ እያለ በማስረጃ አመልካች አላስረዳም መባሉና ክሱ ውድቅ መደረጉ ያለ አግባብ ነው የሚል ነው፡፡
ተጠሪው ለሰበር አቤቱታ መልሱን ያቀረበ ሲሆን በመልሱ ግን በስር ፍ/ቤት ከሰጠው መልስ የተለየ ነገር አላቀረበም፡፡

የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ ከዚህ በላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም የስር ፍ/ቤቶች በኢ.ግ.ዚ.ት.ነት የተያዘ ገንዘብና ንብረቶች የብዙ የግል ተበዳዮች ስለመሆኑና ከሣሽ የራሱ ገንዘብና ንብረት ነው የሚለውን ለይቶ በማስረጃ ስላላስረዳ ክሱ ውድቅ ነው ያሉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል ዐ/ሕግ በ12-7-1993 ዓ.ም በተጻፈ ክስ 14 የወንጀል ክሶችን የውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል በተባሉ ተጠሪዎች ላይ አቅርቦ የነበረ ሲሆን የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞባቸዋል ከተባሉት የግል ተበዳዮችም አንዱ በ2ኛ ክስ ስሙ የተጠቀሰው ያሁኑ አመልካች ነው፡፡ በክሱም ወንበዴዎቹ ከአሁኑ አመልካች ብር 250,000 ዘርፈው መውሰዳቸው ተገ.ል.ጿ.ል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከክሱ ጋር በተያያዘው የኢ.ግ.ዚ.ት ዝርዝር በተራ ቁጥር 3 በወንጀል ክሱ ሶስተኛ ተከሣሽ በ2ኛ እና በ5ኛ ክስ በፈጸመው ዘረፋና የማታለል ወንጀል የገዛው ጃኬት ጫማ ሽሚዝ እና ደብቆ የተገኘው ገንዘብ ብር 48,740 እንዲሁም ስድስተኛ ተከሣሽ በ2ኛ እና በ5ኛ ክስ ላይ በፈጸመው የማታለል እና የዘረፋ ወንጀል ካገኘው ገንዘብ ውስጥ ብር 40,610 እና ከዘረፋው ባገኘው ገንዘብ የተገዛ ሙሉ ሶፋ ፣ ፍሪጅ ፣ ፔርሙስ የመሳሰሉት ንብረት መያዛቸውን ተጠሪው ገልጿ.ል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠንና ንብረቶች የተያዙት በ2ኛ ክስ በግል ተበዳይነት ከተጠቀሰው ከአሁኑ አመልካች እና በ5ኛ ክስ ከተጠቀሰው የግል ተበዳይ አቶ ገብረማርያም አሰፋ ከተባለ ግለሰብ ነው፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስ ደግሞ በኢ.ግ.ዚ.ት በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተጠቀሰው ገንዘብና ንብረቶች ከሁለቱ የግል ተበዳዮች መካከል በሚደርሳቸውን የገንዘብ መጠንና የንብረት ዓይነት በማጣራት ከመወሰን በቀር በክሱ ውስጥ ያሉ የግል ተበዳዮች ሁሉ ንብረት እና ገንዘብ ነው በማለትና አመልካች ክሱን በማስረጃ አላስረዳም በሚል ውድቅ ማድረግ ስለማይገባ የስር ፍ/ቤቶች ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡
በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁጥር 75346 በቀን 06-7-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁጥር 92547 በቀን 26-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የስር የመ/ደ/ፍ/ቤት በ5ኛ ክስ የግል ተበዳይ የሆነውን አቶ ገብረማርያም አሰፋ የተባለውን ግለሰብ ወደ ክሱ እንዲገባ በማድረግ እንዲሁም በጊዜው በወንበዴዎቹ ላይ የተጣራውን የፖ.ሊ.ስ ምርመራ መዝገብ አስቀርቦ በመመልከት ማስረጃዎችን በመመዘን የበኩሉን ፍርድ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት እንደገና መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.60518
ጥር 15 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፈለቀ ሊቤ- ቀረበ

ተጠሪ፡- የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የስነ- ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ- አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት በቀረበው ክስ የአሁኑ አመልካች 3ኛ ተከሳሽ የነበረ ሲሆን ከቀረቡባቸው ሁለት ክሶች ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው በ3ኛው ክስ የተላለፈበት የጥፋተኝነት የቅጣት ውሳኔ ነው፡፡ የአሁኑን አመልካች ጨምሮ በስር 2ኛ፣9ኛና 14ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበባቸው 3ኛ ክስ ፍሬ ቃሉ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)፣33 እና 407(1) እና (2) የተደነገገውን በመተላለፍ 2ኛ ተከሳሽ የጠምባሮ ወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ምክትል ሀላፊ፣ 3ኛ ተከሳሽ የወረዳው ውኃ ሀብት ጽ/ቤት ሀላፊ፣9ኛ ተከሳሽ የወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ዋና ሀላፊ፣14ኛ ተከሳሽ የግል ኮንትራክተር ሆነው በሚሰሩበት ወቅት 2ኛ ተከሳሽ በቁጥር 1727/ፌ-126/99 በቀን 28/3/99 ዓ/ም እና በቁጥር 2030/ፌ-126/99 በቀን 23/3/99 ዓ/ም በተጻፉ ደብዳቤዎች ተሰርቶ ላልተጠናቀቀ ለባዳ ምንጭ ግንባታ ከተያዘው በጀት ብር 90,699.94 ላይ ብር 60,466.83 ያለ አግባብ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ለወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ህገ ወጥ ትዕዛዝ በመስጠቱ፤ 9ኛው ተከሳሽ በቁጥር 81/ፌ-126/99 በቀን 14/05/99 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ቀደም ሲል በ2ኛ ተከሳሽ ህገ ወጥ ድርጊት ሲከፈል የቀረውን ብር 30,000 ላልተሰራ ስራ እንዲከፈል ለወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ህገ ወጥ ክፍያ እንዲፈጽም ትዕዛዝ በመስጠቱ፤14ኛ ተከሳሽም ከ2ኛ፣ከ3ኛ እና ከ9ኛ ተከሳሾች ጋር በመመሳጠር በማመሳከሪያ ሰነዶች በሶስት የተለያዩ ቀናት በድምሩ ብር 90,466.83 ላልተሰራ ወይም ላላተጠናቀቀ ስራ ያለ አግባብ የመንግስትና የህዝብ ገንዘብ በመወሰዱ፣3ኛ ተከሳሽም የአሰሪው መ/ቤት ሀላፊ ሲሆን ከማንም እና ከምንም በላይ ከፍተኛ ሀላፊነት እያለው ላልተሰራ ስራ ወይም ላላተጠናቀቀ ስራ ክፍያ እንዲፈጸም በማመቻቸቱ ሁሉም ተከሳሾች ወንጀል ለመስራት በማቀድ እና በማሰብ ለራሳቸው ወይም ሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በዋና ወንጀል አደራጊነት እና በልዩ ተካፋይነት በፈጸሙት በስልጣን ያለ አግባብ የመገልገል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተካሳሹም የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ወንጀሉን አለመፈጸሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የሥር የከምባታና ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የከሳሽን ምስክሮች በመስማትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽ ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች በመመርመር በሰጠው ውሳኔ ተካሳሹ በመከላከያ ማስረጃነት አንዱ ያቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ በቁ/ጠወ/አስም/ 372/99 በቀን 3/04/99 የወረዳው ውኃ ጽ/ቤት ሀላፊ ሆኖ በውክልና እንዲሰራ የተጻፈለትን ደብዳቤ ሲሆን ለክሱ መነሻ የሆነው የባዳ ምንጭ ግንባታ ውል ደግሞ የተደረገው በ27/3/99 በመሆኑ ውሉ ሲደረግ ተከሳሽ ሀላፊነት ላይ አልነበረም፡፡

በውሉ መሰረት 1/3ኛ ክፍያ ተከሳሹ የጽ/ቤቱ ሀላፊ ሆኖ እንዲሰራ ከመወከሉ በፊት የተፈጸመ ቢሆንም ቀሪ ክፍያ ግን መፈጸም ያለበት ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ መሆን ሲገባው ተከሳሹ ከተወከለ በኋላ ላልተሰራ ስራ ከውሉ ስምምነት ውጪ በ25/4/99 ብር 30,233.30 እና በ26/4/99 ብር 30,000 በድምሩ 60,233.30 ክፍያ ተፈጽሟል፡፡ ስለሆነም የውክልና ማስረጃው አግባብነት የለውም፤ እንዲሁም ተከሳሽ ያቀረባቸው ሌሎች ድብዳቤዎች ማለትም በቁ/ጠወ/ውሃ/26/99 በቀን 17/12/99 እና በቁ/307/ጠጠ-35 በቀን 27/2/2000 የተጻፉት የኦዲት ውጤት ከታወቀ በኋላ ከሀላፊነት ለመሸሽ ሲል የጻፋቸው ስለሆኑ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የላቸውም በማለት በወ/ህ/ 32(1)ሀ፣33 እና 407(1)(ሀ)ስር ጥፋተኛ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ቅጣትን በሚመለከት የቅጣት ሪከርድ አልቀረበም በሚል በሁለት አመት ጽኑ እስራት እና በብር 500 መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ተከሳሽ ያቀረበውን ይግባኝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/195 (1) መሰረት የሰረዘ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔም ሆነ በጠ/ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረጉ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

አመልካች በዋናነት ያቀረበው የቅሬታ ነጥብም፡- ላልተሰራ ስራ ወይም ላልተጠናቀቀ ስራ ክፍያው እንዲፈጸም ያዘዘው የወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ሀላፊ ሲሆን ክፍያውን የፈጸመው ደግሞ የወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ነው፡፡ ነገር ግን የወረዳው ውኃ ሀብት ጽ/ቤት ፈጸመ ተብሎ አንድም የተጠቀሰ ድርጊት በሌለበት አመልካች ሁኔታዎችን አመቻችቷል በሚል ብቻ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተላለፈብኝ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/የወንጀል ህግ አንቀጽ 2፣23(2) እና 32 (1) ሀ-ሐ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚቃረን በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ አመልካች ላቀረበው ቅሬታ በሰጠው መልስ ያልተሰራውን ወይም ያልተጠናቀቀውን የባዳ ምንጭ ውኃ ፕሮጀክት በሀላፊነት የሚያስገነባውና የሚቆጣጠረው አመልካች በሀላፊነት የሚመራው የውኃ ሀብት ጽ/ቤት ሲሆን አመልካች ስራው ያለበትን ደረጃ የማወቅ ዕድል እንደነበረው ባቀረብናቸው የሰውና የጽሁፍ ማስረጃዎች አስረድተናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ላልተሰራ ወይም ላልተጠናቀቀ ስራ ክፍያ እንዲፈጸም ሁኔታዎችን ያመቻቸ በመሆኑ የተላለፈበት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

አጠቃላይ የክርክሩ ሂደት ከዚህ በላይ እንደተገለጸው አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም ላልተሰራ ወይም ላልተጠናቀቀ ስራ ክፍያ እንዲፈጸም አመልካች ሁኔታዎችን አመቻችቷል በሚል 32(1)ሀ፣33 እና 407(1)ሀ ስር ጥፋተኛ ነው ተብሎ የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በከፍተኛው ፍ/ቤት ቀርበው ከተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች አመሰካከር የተጣራው ፍሬ ነገር ስራው አልተሰራም ወይም አልተጠናቀቀም በሚል ለክሱ ምክንያት በሆነው የባዳ ምንጭ ግንባታ ለኮንትራክተሩ ያለ አግባብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን፣ ክፍያው እንዲፈጸም ደግሞ ትዕዛዝ የሰጠው የወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ምክትል ሀላፊ መሆኑንና ክፍያውን የፈጸመው ደግሞ የወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከኮንትራክተሩም ጋር ስለ ስራው ውል የገባው የወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት መሆኑ በስር ከ/ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በዚሁ ውል መሰረት ለኮንትራክተሩ ከጠቅላላው የውል ገንዘብ ውስጥ 1/3ኛው ውሉ በተገባበት ጊዜ ሲከፍል አመልካች በወረዳው ውኃ ሀብት ጽ/ቤት ሀላፊ እንዳልነበረም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች የውኃ ጽ/ቤት ሀላፊ ሆኖ በሰራባቸው ጊዜያትም ለምንጩ ግንባታ ቀሪ ክፍያዎች እንዲከፈሉ ለፋይናንስ ትዕዛዝ ስለመስጠቱ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር አይደለም፡፡ ሆኖም ተጠሪው አመልካች ለተፈጸመው ህገ ወጥ ክፍያ ሁኔታዎች አመቻችቷል የሚለው የስራው ባለቤት የአመልካች መ/ቤት በመሆኑ የስራውን መጠናቀቅና አለመጠናቀቅ ሁኔታን የመከታተልና የማወቅ ሀላፊነት አለበት በሚል ነው፡፡ ይህንኑ የተጠሪ ክርክር ደግሞ አመልካች ጥፋተኛ ነው ከተባለበት የወንጀል አንቀጽ 32 (1)(ሀ)፣33 እና 407 (1)(ሀ) አንጻር መመርመር ተገቢነት አለው፡፡

በዚሁ በተጠቀሰው ወንጀል ህግ አንቀጽ መሰረት ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ የተሰጠውን ሹመት ወይም ስልጣን በግልጽ ተግባር ወይም በግድፈት ያለ አግባብ የተገለገለበት እንደሆነ በሥልጣን ያለ አግባብ መገልገል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የሚቀጣ ሲሆን እነዚህ በአንቀጹ የተገለጹ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ደግሞ በፍሬ ነገር ደረጃ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

ተጠሪው ምንም እንኳን ገንዘቡ በህገ ወጥ መንገድ እንዲከፈል አመልካች ሁኔታዎችን አመቻችቷል ቢልም አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀጽ መሰረት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለመስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ለማደረስ የተሰጠውን ሹመት ያለ አግባብ ስለመገልገሉ በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ አንድም ነገር የለም፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ አመልካች የውኃ ሀብት ጽ/ቤት ሀላፊ በመሆኑ ብቻ በስልጣን ያለ አግባብ ስለመገልገሉ የሚያረጋግጡ ፍሬ ነገሮች በሌለበት ደግሞ ጥፋተኛ ነው ብሎ የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፍ ከወንጀል ህጉ ዓላማና ግብ ውጪ ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች በ3ኛ ክስ አመልካች ጥፋተኛ ነው ሲሉ የሰጡት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል ፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 03201 በቀን 15/03/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ በ3ኛ ክስ በአመልካች ላይ ያስተላለፈበት የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ክፍል እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35038 በቀን 25/6/2002 በዋለው ችሎት የሰጠውን የትዕዛዝ ክፍል እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38944 በቀን 24/10/2002 በዋለው ችሎት የሰጠውን የትዕዛዝ ክፍል በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195 (2) (ለ)(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካች ከቀረበበት 3ኛ ክስ በነጻ እንዲሰናበት ወስነናል፡፡ የመቀጮ ገንዘብም ከፍሎ እንደሆነ ሊመለስለት ይገባል ብለናል፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤት ቀርቦበት ከነበረው 2ኛ ክስም በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 141 መሰረት መከላከል ሳያስፈልግ በብይን መሰናበቱን መዝገቡ ስለሚያመለክት በሌላ ወንጀል የማይፈለግ ከሆነ ከሚገኝበት የማረሚያ ቤት ተቋም እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ይጻፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ወርቅነህ ዳቲ ጉዳይ ተከታታይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ተስፋዬ አባቡ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘቱም፡- አመልካች በ1996 ዓ/ም የወጣውን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዝዲንት ወንጀል አንቀፅ 32/1/ሀ/ እና 598/2/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን ወደ ውጪ ለመላክ የሚያስችል ምንም አይነት ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሣሽ ከነበረው ከአቶ ሙሉጌታ ገ/ማርያም ጋር ግብረ አብር በመሆን የግል ተበዳይ ነፃነት መንግስቱ የተባለችውን ታህሣሥ 27 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 12፡30 ሠዓት ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል በኢትዮጵያ አየር መንገድ አማካይነት ወደ ቤሩት በመላክ ሚች በአሰሪዎቿ ከባድ ድብደባ እየደረሰባት መሆኑን ለቤተሰቦቿ ውጪ አገር ባለችው ዘመዷ አማካይነት ስትናገር ይህ ጉዳይ እየደረሰባት መሆኑን በተመለከተ ለአመልካችና ለግብረ አብሩ ተገልፆ ሚች አገሯ እንድትመለስ እንዲያድርጉ ሲነገራቸው ተከሣሾች መምጣት አትችልም ፣ የሁለት አመት ከአርባ አምስት ቀናት የስራ ኮንትራት አላት በማለት መልስ ከመስጠታቸው ውጪ ወጪ በመክፈል ወደ አገር እንድትመለስ ሁኔታዎችን ጨርሳ ሚች በኢትዮጵያ አየር መንገድ መጋቢት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡10 ሲሆን ስትደርስ እግሯ በጣም ያበጠና መቆም የማትችል ፣ በአውሮኘላን ሰራተኛ ድጋፍ ወርዳ ወደ ቤቷ ሄዳ መጋቢት 27 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተወስዳ ምንም እርዳታ ሳይደረግላት በደረሰባት ጉዳት ከቀኑ 5፡00 ሠዓት ሲሆን ሕይወቷ ሊያልፍ መቻሉን ዘርዝሮ ተከሣሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊን ወደ ውጪ አገር መላክ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካች የአቃቤ ክስ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በሁዋላ አሉኝ ያላቸውን የክስ ተቃውሞ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ተገቢ ነው ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት ስለድርጊቱ አፈፃፀም የአመልካችን የእምነት ክህደት ቃል በመጠየቅ አመልካች ክዶ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች በዐቃቤ ህግ ማስረጃ ወንጀሉን መፈፀሙ መረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ገልፆ አመልካች እንዲከላከል መብቱን ጠብቆት አመልካችም አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን በማስቀረብ አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች ማስረጃዎች የአቃቤ ህግን ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ የሚችሉ አይደሉም በማለት ቃላቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውድቅ አድርጎ አመልካችን በተከሰሰበት የሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጓል። ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር በማገናዘብ በእያንዳንዱ ክስ ተገቢ ነው ያለውን የእስራት እና የገንዘብ መቀጮ ከአስቀመጠ በሁዋላ በድምሩ ደግሞ 9/ዘጠኝ አመት /ፅኑ እስራት እና በብር 3000.00/ሶስት ሺህ / የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል። በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/1/ መሠረት ተሰርዟል።

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለግል ተበዳይ መሞት ምክንያት አመልካች ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ አመልካች ለድርጊቱ ተጠያቂ መደረጉ ያለአግባብ መሆኑን ፣ ሟችን አመልካች ወደ ውጪ በመላክ ሂደት የተሳተፈ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ሳይረጋገጥና የመከላከያ ምስክሮች ቃልም ውድቅ የተደረገው ያለአግባብ መሆኑን ዘርዝሮ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔው እንዲታረም ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም የግል ተበዳይ የሞተችው በበረታ የሳምባ ምች በተሰራጨ የቲቢ በሽታ ታማ ሊሆን እንደሚችል የሕክምና ማስረጃ ቀርቦ እያለ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 598/2/ ስር ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም በሰጠው መልስ ሟች ወደ ውጪ አገር አመልካችና ግብረ አበሩ ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው ልከዋት በውጪ አገር እያለች እግሯ አብጦ መምጣቷና ወደ አገሯ እንደተመለሰች ህክምና ሳታገኝ ሕይወቷ ማለፉ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ የሳንባ ምች የሚባለው በሽታም ከድብደባ ጋር ተያይዞ ሊከሰት እንደሚችል ሳይንሱ የሚያረጋግጠው ሕቅ መሆኑን ዘርዝሮ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል። አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተከሰሰው የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 598/2/ ተጠቅሶበት ሁኖ ይዘቱም ባጭሩ ሲታይ አመልካች ምንም ሕጋዊ የሆነ ፈቃድ ሳይኖረው የግል ተበዳይ ነፃነት መንግስቴን ወደ ውጪ በመላክ የግል ተበዳይ ከተላከችበት አገር ድብደባ ደርሷባት እግሯ አብጦ ወደ አገሯ ከተመለሰች በሁዋላ በበነጋታው ሕይወቷ አልፏል የሚል ነው። አመልካች ክሱን የካደ ሲሆን አቃቤ ሕግ አሉኝ ባላቸው የሰውና የሠነድ ማስረጃዎች አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን ማስረዳቱን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል።

አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጠብቆ የሚከራከረውና ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በጭብጥነት የተያዘው ዋናው ነጥብ የግል ነፃነት መንግስቱ የሞተችው በአመልካች ድርጊት ምክንያት መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው። ይሁን እንጂ አመልካች የተጠቀሰበት ድንጋጌ ይዘትም ሆነ የክሱ ዝርዝር ይዘት አመልካች ለግል ተበዳይ ሞት ምክንያት የሆነ ድርጊት ራሱ በቀጥታ ፈፅሟል የሚል ሳይሆን ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ኢትዮጵያዊ ዜጋን ወደ ውጪ በመላክ የግል ተበዳይ ድብደባ የደረሰባት መሆኑንና ይህ ጉዳትም ከወጪ አገር ስትመለስ የነበረ ስለመሆኑና ከውጪ አገር ከተመለሰች በሁዋላ በሁለተኛው ቀን ሕይወቷ አገሯ ውስጥ አልፏል በሚል ነው። በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 598/2/ ድንጋጌ ስር አንድ ሰው ሊቀጣ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችለው ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለስራ ወደ ውጭ የላከ እንደሆነ እና በዚህ ድርጊት ምክንያት የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ፣ በህይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት የደረሰባት መሆኑ ከተረጋገጠ ሲሆን ቅጣቱም ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ እንደሚሆን ሕጉ ያሳያል፡፡ ይኸው ድንጋጌ በተጠቃሹ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ አንድ ስር የተመለከተው ድንጋጌ ቀጣይ ሲሆን ዝርዝር ይዘቱ ሲታይ ቅጣትን የሚያከብዱ ምክንያቶች መቀመጣቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው ማንም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ሕገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለስራ ወደ ውጭ አገር በመላኩ ድርጊት የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብት ፣ በሕይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት ከደረሰ የወንጀል ተጠያቂነት አለበት ፡፡ ድንጋጌው በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገር የተላከች ኢትዮጵያዊት ላይ በሰብአዊ መብቷ፣ በሕይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት መድረሱ መረጋገጡን እንጂ በሕገ ወጥ መንገድ የላከው ሰው ራሱ በቀጥታ በሚፈፀመው ድርጊት ወይም በሌላ ጣልቃ ገብ በሆነ ምክንያት ጉዳቱ መድረሱ መረጋገጡን በወንጀሉ ማቋቋሚነት አያስቀምጥም፡፡ በሌላ አገላለፅ በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጪ አገር የተላከች ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ ፣ በሕይወቷ ወይም በአካሏ ላይ ጉዳት ከደረሰና ይህም ጉዳት ውጭ አገር የደረሰ መሆኑ ከተረጋገጠ በሕገወጥ መንገድ የላከው ሰው ራሱ በቀጥታ ጉዳዩን ባያደርሰውም በሕገወጥ መንገድ በመላኩና ጉዳቱ በውጪ አገር በመድረሱ ምክንያት ብቻ የወንጀሉ ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ሚችን ወደ ውጪ አገር በመላክ የግል ተበዳይዋ ውጭ አገር እያለች ድብደባ ደርሶባት እግሯ አብጦ ወደ አገሯ ከተመለሰች በሁዋላ ሕይወቷ ማለፉና በአካሏ ላይ ጉዳት መድረሱ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 598/2/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አመልካች ለድርጊቱ ተጠያቂ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታም ሆነ የተያዘው ጭብጥ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሁኖ አላገኘንም፡፡ ቅጣቱን በተመለከተ የቀረበውን ቅሬታ ስንመለከተውም አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው የቅጣት መጠን ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት የሚደርስ ፅኑ እስራትና ከሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ሲሆን ቅጣቱ የተጣለው በግራ ቀኙ የቀረቡት የቅጣት አስተያየቶች ተመዛዝነው በወንጀል ሕጉ የተመለከቱትን የቅጣት አጣጣል መርሆችን እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሠረት ተደርጎ ነዉ፡፡ በመሆኑም በአመልካች ላይ የተጣለው የዘጠኝ አመት ጽኑ እስራትና የብር ሶስት ሺህ የገንዘብ መቀጮ የሚነቀፍ ሁኖ አላገኘውም፡፡ ሲጠቃለልም ጉዳዩ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ተከተዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

- በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 94074 ጥር 20 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው ጥፋተኝነት ውሣኔ እና በ26/05/2003 ዓ/ም የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 65555 ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/ለ-2/ መሠረት ጸንቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 15 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዲ - ኤም - ሲ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ ኢብራሂም ኢቲሶ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመደበኛ ጉዳይ ችሎትና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የውል አፈፃጸምና የጉዳት ካሳ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ክስ ያቀረበው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ በቱላ ክ/ከተማ ቶሎ ቀበሌ ክልል ባለኝ የይዞታ ቦታዬ ላይ የነበረኝን የድንጋይ ማውጫ ካባ ተከሳሽ ለአንድ ዓመት በኮንትራት ይዞ ለመጠቀም ተስማምቷል፡፡ ተከሳሽ ለካባው ዋጋ ብር 60,000 (ስድሳ ሺህ ብር) በመጀመሪያ የከፈለ ሲሆን ቀሪውን ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) ለመክፈል ከተስማማ በኋላ ቀሪውን ክፍያ ያልከፈለኝ ስለሆነ በውሉ መሠረት ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተከሳሽ ድንጋይ ሲያወጣ በአቅራቢያው የነበረውን የእርሻ መሬት ከጥቅም ውጭ በማድረግ ጉዳት አድርሶብኛል፡፡ በይዞታዬ በነበረው የእርሻ መሬት ላይ ላደረሰው ጉዳት ብር120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ለመክፈል የዕርቅ ስምምነት ውል የተዋዋለ በመሆኑ ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ይወስንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ በውሉ መሰረት የካባ ድንጋዩን እንድጠቀም ያላደረገና የውል ግዴታውን ያልፈፀመ በመሆኑ ቀሪውን ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ የለብኝም፡፡ የእርሻ መሬቱ ከሳሽ ድንጋይ እንዲወጣበት የፈቀደና የውል ግዴታ የገባበት ነው፡፡ ለደረሰበት ጉዳትም ብር 9000 (ዘጠኝ ሺህ ብር) ለሰጠሁት ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) የሚጠይቅበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ ጉዳዩን የያዘው ችሎትም አመልካችና ተጠሪ ከሚከራከሩበት መሬት ድረስ በመሄድ የእርሻ መሬቱ ላይ የደረሰውን ጉዳት ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በእርሻ መሬቱ ላይ በነበረው ንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት እንዲገመት በማድረግ ብር 62,000 (ስድሳ ሁለት ሺህ ብር) ግምት ያለው ንብረት የወደመ መሆኑን በግብርና ባለሞያ ግምት ተሰርቶ ቀርቦለታል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሳሽ በውሉ መሰረት የካባ ድንጋዩን በማውጣት የተጠቀመ ስለሆነ ብር 40,000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(አርባ ሺህ ብር) የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ እንደዚሁም ተከሳሽ የከሳሽን የእርሻ መሬት ከጥቅም ውጭ ያደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተከሳሽ በእርሻ መሬቱ ላይ ላደረሰው ጉዳት ለከሳሽ ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) በካሳ መልክ ለመክፈል የተስማማ መሆኑን የሚያረጋግጥ የፅሁፍና የሰው ማስረጃ ያቀረበ በመሆኑና የተከሳሽ ማስረጃ የከሳሽን ማስረጃ ለማስተባበል የማይችል በመሆኑ ተከሳሽ ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ብር 160,000 (አንድ መቶ ስድሳ ሺህ ብር) ለከሳሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሰኔ 8 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የታጠረ የእርሻ መሬቱ ጉዳት የደረሰበት የድንጋይ ካባውን ለአመልካች ከማከራየቱ በፊት ሆኖ እያለ አመልካች ጉዳት አድርሷል መባሉ ተገቢነት የለውም፡፡ በእርሻ መሬቱ ላይ አመልካች ጉዳት አላደረሰም እንጅ ጉዳት አድርሷል የሚባል ቢሆን የጉዳቱ መጠን ብር 62,000 (ስድሳ ሁለት ሺህ ብር) መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) አመልካች ለተጠሪ እንድከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የካባ ድንጋይ አመልካች እያወጣ እንዲጠቀም ያደረገው ውል የህገመንግስቱ አንቀፅ 43(3)ን የሚጥስ በመሆኑ ውሉ ይፈፀምልኝ በማለት ሊጠይቅ አይችልም፡፡ ተጠሪ ብር 8000 (ስምንት ሺህ ብር) መቀበሉን ባልካደበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ገንዘቡን አልተቀበለም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ሀምሌ 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በእርሻ መሬቱ ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በሰበር ጉዳት አላደረስኩም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም ብር 62,000 (ስድሳ ሁለት ሺህ ብር) በመሬቱ ላይ የነበሩ ዛፎችና ሌሎች ንብረቶች ግምት ነው፡፡ በጉዳቱ የደረሰብኝን ኪሣራ የሚያጠቃልል አይደለም፡፡ አመልካች ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ለጉዳቱ ካሳ ለመክፈል የተስማማ ስለመሆኑ ማስረጃ አቅርቤያለሁ፡፡ አመልካች ብር 8000 (ስምንት ሺህ ብር) ለተጠሪ አልከፈለም፡፡ የካባው ድንጋይ ጉዳይ የተጠሪና አመልካች መከራከሪያ ባለመሆኑ አመልካች ተጠሪ የድንጋይ ካባ ለማከራየት አይችልም በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢነት የለውም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ አመልካች ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) ለተጠሪ የከፈለው በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀም ተገድዶ በመሆኑ የሰበር መከራከሪያ አይደለም በማለት ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በተጠሪ ይዞታ መሬት ላይ የነበረውን የካባ ድንጋይ አውጥቶ ለመጠቀምና ለዚህም በበኩሉ ለመክፈል ከተስማሙበት ገንዘብ ውስጥ ቀሪውን ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደልም?አመልካች በተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ ያደረሰው ጉዳት ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ካሣ ይክፈል በማለት የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ የሚገኘውን የካባ ድንጋይ እያወጣ ለአንድ ዓመት ሲጠቀምና ለዚህም ዋጋ ይሆን ዘንድ ለተጠሪ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል ከተጠሪ ጋር ያደረገው ስምምነት ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት ያለው ውል ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ መሬት የመንግስትና የህዝብ ሀብት እንደሆነና በገፀምድርም ሆነ በከርሰ ምድር የሚገኝ ሀብት የመንግስትና የህዝብ ንብረት መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ወይም የሆነች አርሶ አደር የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀም መብት ያለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ የካባ ድንጋይ ያለበት መሬት ህጋዊ ባለይዞታ መሆኑና በይዞታው የመጠቀም መብት ያለው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ አከራካሪው ነጥብ ተጠሪ በህጋዊ የእርሻ መሬቱ ላይ ያለውን የካባ ድንጋይ የመጠቀም መብት ድንጋዩን እያወጣ ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት በውል እስከመሸጥ የሚደርስ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ የተጠሪና የአመልካች ውል መሠረታዊ ጉዳይ የሆነው ለግንባታ ስራ የሚያገለግል የካባ ድንጋይ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ውል የተዋዋሉበት ድንጋይ "የኮንስትራክሽን ማዕድን" እንደሆነ የኮንስትራክሽን ማዕድን ማለት፣ እብነበረድ ግራናይት፣ ባዛልት፣ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ድንጋይ፣ የሸክላ አፈር የመሣሰሉትና ሌሎች ሚኒስትሩ በመመሪያ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ብሎ የሚሰይማቸው ብረት ነክ ያልሆኑ መዕድናትን የሚያጠቃልል ነው በማለት በአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3 ከተሰጠው ትርጓሜ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ በህጋዊ የይዞታ መሬቱ ላይ ያለውን የኮንስትራክሽን ማዕድን በማምረትና ከሌላው ዋጋ እየተቀበለ ለመሸጥ በአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት ከክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ወይም ከቢሮው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የፀና ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡

ተጠሪ በህጋዊ መንገድ በያዘው መሬት ላይ የሚገኘውን ለግንባታ ሥራ የሚያገለግል ድንጋይ የመጠቀም መብት ድንጋዩን ለሌላ ሰው በውል ገንዘብ ተቀብሎ ለመሸጥ የሚያስችለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ በህጋዊ ይዞታው ላይ የሚገኘውን የኮንስትራክሽን ማዕድን የሆነውን ድንጋይ የመጠቀም መብት በህግ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጠው እስከምን ድረስ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 1 "ሕጋዊ የመሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው ሥፍራው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 6 መሠረት የተያዘ ወይም የተከለከለ ካልሆነ በስተቀር የኮንስትራክሽን ማዕድናት በይዞታው ሥር ከሚገኝ ሥፍራ ያለ ክፍያና ፈቃድ ሣያስፈልገው ለንግድ ላልሆነ ዓላማ አምርቶ ለመጠቀም ይችላል፡፡ ሆኖም የአዋሳኝ ባለይዞታዎች መሬት ወይም ንብረት አጠቃቀም ማወክ ወይም በእነዚሁ ላይ ጉዳት ማድረስ የለበትም" በማለት በግልፅ ደንግጎታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው ተጠሪ በይዞታው የሚገኘውን ድንጋይ ቤት ለመሥራት፣ አጥር ለመገንባትና ለሌሎች ግላዊ ለሆኑ አገልግሎቶች ያለማንኛውም አካል ፈቃድ አምርቶ ለመጠቀም የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም ተጠሪ ከሚመለከተው አካል ሣይፈቀድለት በይዞታው ሥር ያለውን የግንባታ ድንጋይ በውል ሌላ ሰው አውጥቶ እንዲጠቀምበት አሳልፎ መስጠትና የመሸጥ መብት የሌለው መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3፣ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 እና አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ የፌዴራል መንግስት ባወጣውና የክልል ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ መሠረት በይዞታው ሥር ያለውን የግንባታ ድንጋይ የማምረትና የመሸጥ ፈቃድ የተሰጠው ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በሰበር ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ ቀሪውን ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) አመልካች የከፈለኝ በመሆኑ እኔና አመልካች ድንጋዩን በተመለከተ ያደረግነው ውል በሰበር የቀረበው ክርክር አካል አይደለም በማለት ሀምሌ 5 ቀን 2003 ዓ.ም ዕፎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባቀረበው መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 እና አግባብነት ባለው የክልሉ የህግ መዕቀፍ መሠረት ሥልጣን ካለው አካል በይዞታ መሬቱ ላይ ያለውን ድንጋይ ለንግድ ተግባር ለማዋል የተፈቀደለት መሆኑን በመግለፅ ያልተከራከረ በመሆኑ የፀና ፈቃድ ሣይኖረው በይዞታ መሬቱ ላይ ይገኝ የነበረውን ድንጋይ አመልካች እያወጣ እንዲጠቀም በውል የሸጠ መሆኑን እንዳመነ የሚያስቆጥረው እንደሆነ ከፍትሐብሄር ሥነሥርአት ሕግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡
በመሆኑም ተጠሪ የፀና ፈቃድ ሣይኖረው በአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1986 አንቀፅ 36 ንዑስ አንቀፅ 1(ሀ) በመተላለፍ በይዞታው ሥር የነበረውን የኮንስትራክሽን መዕድን አመልካች ለአንድ አመት እያወጣ እንዲጠቀምበት የሸጠ መሆኑንና አመልካችም የፀና ፈቃድ ከሌለው ከተጠሪ ጋር የኮንስትራክሽን ማዕድኑን እያወጣ ለመጠቀም ውል በመዋዋል ድንጋዩን በመውሰድ የተጠቀመ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪና አመልካች የውሉ መሰረታዊ ነገር በማድረግ የተዋዋሉበት የግንባታ ማዕድን የፀና ፈቃድ ሣይኖር የመሸጥና የመግዛት ውለታ በአዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀፅ 53 ንዑስ አንቀፅ 5፣ በደንብ ቁጥር 182/1986 አንቀፅ 39 እና በወንጀል ህግ አንቀፅ 353(1)(ለ) በወንጀልነት የሚያስጠይቅ ህገወጥ ተግባር እንደሆነ የድንጋጌዎቹን ይዘት በማገናዘብ ለመለየት ይቻላል፡፡ የአንዲት አገር ህግ ህገወጥ ተግባር በተለይም ወንጀል መሆኑን በግልፅ በመደንገግ ማንኛውም ሰው ድርጊቱን እንዳይፈፅም የከለከለውን ተግባር ለመፈፀም ውል የተዋዋሉ የተስማሙ ሰዎች ውሉ በመሰረታዊ ባህሪውና ሞራላዊ ይዘቱ ህገወጥ የሆነውን ውላቸውን በፍርድ ቤት ውሣኔ በማስገደድ ለማስፈፀም አይችሉም፡፡ ዳኞችም በመሰረታዊ ይዘቱ ሞራላዊ ባህሪው ህገወጥ የሆነ ውል እንዲያስፈፅሙ ያቀረበላቸውን ጥያቄ አንቀበልም ማለት እንደሚችሉ ከፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1718 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በህገወጥ መንገድ በይዞታው ላይ ያለውን የኮንስትራክሽን ማዕድን ለመሸጥ ከአመልካች ጋር ያደረገው ውልና አመልካችም የፀና ፈቃድ ከሌለው ተጠሪ በመግዛት የኮንስትራክሽን ማዕድን ለመጠቀም የተዋዋለው ውል በመሰረታዊ ይዘቱ ሞራላዊ ባህሪው ህገወጥ ውል ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ተጠሪ አመልካች በውሉ መሠረት ያልከፈለኝ ገንዘብ በማለት የሚያቀርበውን ጥያቄም ሆነ አመልካች ህገወጥ በሆነው ውል መሠረት ክፍያ ፈፅሜ ተጠሪ የውል ግዴታውን አልፈፀመም በሚል ወይም በሌላ ምክንያት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት በህገወጥ ውል የከፈልኩት ክፍያ ይመለስልኝ በማለት የሚያቀርበውን ጥያቄ ፍ/ቤቶች በመቀበል የሚመለከቱበትና ውሳኔ ሊሰጡ የሚችሉበት የህግ መሠረት የሌለ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/1716 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ/1718 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም የፀና ፈቃድ ሣይኖረው የኮንስትራክሽን ማዕድን ለአመልካች ለመሸጥ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገውን ህገወጥ ውል በህግ ፊት ምንም አይነት ውጤትና ተፈፃሚነት የሌለው ሆኖ እያለ እንደ ህጋዊ ውል በመቁጠር አመልካች ለተጠሪ ቀሪውን የማዕድን ዋጋ ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) ከነወለዱ ለተጠሪ እንዲከፍል ውሳኔ መስጠቱና ውሳኔውንም አመልካችን በማስገደድ ማስፈፀሙ ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸውን የህግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የሀዋሳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገው ህገወጥ ውል እንዲፈፀምለት ያቀረበውን ጥያቄ በማስተናገድና በዳኝነት በማየት የሰጠውን ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ማረምና ማስተካከል ሲገባው የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡
2. ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ አመልካች የኮንስትራክሽን ማዕድን በሚያወጣበት ጊዜ የተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ በነበሩ ንብረቶች ማለትም የሙዝ ተክል፣ የእንሰትና የቡና ተክልና ዋንዛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዛፍ፣ የበቆሎ ሰብል ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው የሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል። አመልካች በእርሻ መሬቱ ላይ ባሉ ዛፎችና ተክሎች ላይ ብቻ ሣይሆን የእርሻ መሬቱ ላይ ለእርሻ ሥራ አገልግሎት ለመስጠት በማይችል ሁኔታ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ተረጋግጧል። አመልካች ጥፋት በሆነ አድራጎት በተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ ጉዳት በማድረስ በተጠሪ ላይ ላደረሰው ኪሣራ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት። ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች በተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ ጉዳት አላደረስኩም በማለት ያቀረበው ክርክር የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት በህግ በተሠጠው ሥልጣንና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 272 መሠረት ከቦታው ድረስ በመሄድ ያረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ ሰበር ችሎቱ እንዲለውጥ የቀረበና የሰበር ችሎት የህገመንግስቱን አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) እና የአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10ን ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም።

የካሳውን መጠን በተመለከተ አመልካች በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ብር 62,000 (ስድሳ ሁለት ሺህ ብር) ሆኖ እያለ ከደረሰበት ጉዳት በላይ ካሣ እንድከፍል ተወስኖብኛል በማለት ያቀረበውን ክርክር አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል። በመርህ ደረጃ ለተጎጂው የሚከፈለው የካሣ መጠን ከደረሰበት ኪሳራ ጋር የተመጣጠነ መሆን እንዳለበት ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2992 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይችላል። አመልካች በፈፀመው ጥፋት የሆነ ድርጊት ተጠሪ ላይ ያደረሰበት የጉዳት መጠን ምን ያህል ነው? የሚለውን ነጥብ ስንመለከተው የግብርና ባለሙያ ተጠሪ በእርሻ መሬቱ ላይ የተከላቸው የሙዝ፣ የቡና፣ የእንሰትና የዋንዛ ዘፍ እንደዚሁም የበቆሎ ሰብል በአመልካች አድራጎት የወደሙ መሆኑን ግምታቸውም ብር 62,000 (ስድሳ ሁለት ሺህ ብር) እንደሆነ በማረጋገጥ እንዳቀረበ የሥር ፍርድ ቤት በውሳኔው ገልፆታል።

ሆኖም አመልካች በተጠሪ ላይ ያደረሰው ጉዳት በመሬቱ ላይ የነበረውን ሀብት ግምት ብቻ አይደለም። የተጠሪ መሬት የእርሻ ተግባር ለመቀጠል በማያስችል ሁኔታ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ተረጋግጧል። አንድ አርሶ አደር ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው የእርሻ ሥራውን በይዞታው ላይ ለመሥራት በማይችልበት ሁኔታ በመሬቱ ላይ ባለው የንብረቱ ግምት ብቻ ሣይሆን የመፈናቀያ ካሣ ሊከፈለው የሚገባ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀፅ 8 እና አንቀፅ 9 ድንጋጌዎች በማመሳሰል ትርጉም በመስጠት ለማገንዘብ ይቻላል። ከዚህ አንፃር ስናየው አመልካች ተጠሪ በመሬቱ ላይ የነበረውን አትክልትና ሰብል ግምት ብቻ ሊከፈለው ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም። ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በተጠሪ መሬት፣ ሰብልና አትክልት ላይ ላደረሰው ጉዳት ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ካሣ ለመክፈል ከተጠሪ ጋር የግልግል ውል የተዋዋለ መሆኑን ውሉን የሚያረጋግጥ የጽሁፍና የሰው ማስረጃ እንደቀረበ የሥር ፍርድ ቤት በውሳኔው በግልፅ አስፍሮታል። በፍሬ ጉዳይ ረገድ የሥር ፍርድቤት ያረጋገጠውን ይህንን ፍሬ ጉዳይ በመያዝ አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር ስናገናዝበው አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው የግልግል ውል መሠረት ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3312 መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ አመልካች ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) እንዲከፍል መወሰኑ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) የጉዳት ካሳ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በተጠሪ መሬት ላይ ለደረሰው ጉዳት ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ካሳ ይክፈል በማለት የሰጡትን የቅጣት ውሳኔ አፅንተናል፡፡ በሌላ በኩል በተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገውን ህገወጥ ውል ምክንያት በማድረግ ተጠሪ አመልካች ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍለው ያቀረበውን ክስ ተቀብለው ማየታቸውና መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት አሻሽለን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1.የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የደ/ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

2.ተጠሪና አመልካች የኮንስትራክሽን ማዕድን ለመሸጥና ለመግዛት ፈቃድ ሣይኖራቸው ያደረጉት ውል ህገወጥ ውል ነው በማለት ወስነናል፡፡

3.በተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገው ውል ህገወጥ ውል በመሆኑ ተጠሪም ሆነ አመልካች የውሉን አፈፃፀም ሆነ ከውሉ ጋር ተያያዥነት ያለው ጉዳይ በፍ/ቤት ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥላቸው የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡

4.የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ህገወጥ ውል ይፈፀምልኝ በማለት ያቀረበውን ክስ ተቀብለው አመልካች ለተጠሪ ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍል የሰጡት የውሳኔ ክፍል ተሻሽሏል፡፡

5.የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ የነበረውን ንብረትና በእርሻ መሬቱ ላይ ላደረሰው ጉዳት ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ካሳ እንዲከፍል የሰጡት የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

6.በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዓሕመድልሃዲ ካህሳይ - ከጠበቃ ወ/ጊዮርጊስ ማሩ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ህግ - በሌሉበት፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች በሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ ቁ. 632/2002 በአንቀጽ 16(1) (መ)፣ 18(1) (ሀ)፣ 20(2) እና 40(3) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ተጠሪ በመሰረተው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የክሱም ዝርዝር ተከሳሽ (አመልካች) ኢትዮጵያውያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለመላክ የሚያስችል ፈቃድ አውጥቶ ገልፍ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሚል ከፍቶ በሚሰራበት ጊዜ የግል ተበዳይ ወ/ሪት ፋኢዛ ይመር ዘገየን በኤጀንሲው ፀሐፊ አማካኝነት ማሟላት የሚገባትን ቅድመ ሁኔታዎች እንድታሟላ ከተደረገች በኋላ በኤጀንሲው በኩል የአየር ቲኬት እና ቪዛ በኢሜል ተልኮላት በአዋጁ መሰረት ውሉን በሚመለከት በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ሳያዋውል ሚያዝያ 7 ቀን 2001 ዓ.ም ወደ ባህሬን አገር የላካት በመሆኑ ከተላከችም በኋላ መብቷንና ደህንነቷን መጠበቅ ሲገባው ባለመጠበቁ ተበዳይዋ ለብዙ ስቃይ እንድትጋለጥ በማድረጉ እንዲሁም ተበዳይዋን የስራ ዘመንዋ ሲያልቅ ወይም ሲቋረጥ ወደአገሯ መመለስ ሲገባው ባለመመለሱ ወይም ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ በፈጸመው የህግ መጣስ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በክሱ የተጠቀሰውን ድርጊት አልፈጸምኩም፤ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ በመከራከሩ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቅድሚያ የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ከሰማ በኋላ፣ አመልካች ሊከላከል ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎች የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም አመልካች እንደክሱ አቀራረብ የወንጀል ድርጊቱ ስለመፈጸሙ በማስረጃ ተረጋግጧል የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህም አመልካች በብር 8,000 (ስምንት ሺህ ብር) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ እኛም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የቀረበው የግል ተበዳይ በአመልካች ኤጀንሲ በኩል መሄድዋ ሳይረጋገጥ እንዲሁም በአካል ቀርባ እንግልት እንደደረሰባት ባላስረዳችበት አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት ሊመረመር ይገባል ተብሎ ነው፡፡ በመሆኑም ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር ከተሰጠው ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው ክስ በዝርዝር እና በግልጽ ፍሬ ነገሮችን ያመለከተ ከመሆኑም በላይ፤ በአመልካች ድርጊት ተጣሱ የተባሉትን የአዋጁ ድንጋጌዎችም እንደዚሁ በዝርዝር ተጠቅሰዋል፡፡ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም እንደክሱ ያስረዳሉ ተብለው በዓቃቤ ሕግ የተቆጠሩትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ሰምቷል፡፡ በሰማው ማስረጃ ተበዳይ ወደባህሬን የተላከችው በዓቃቤ ሕግ ክስ ዝርዝር በተገለጸው ሁኔታ አመልካች ባመቻቸው መንገድ መሆኑን፣ የግል ተበዳይ ወደ ባህሬን ከሄደች በኋላ ችግር እንዳጋጠማት ሲነገረው እና ወደሀገርዋ እንዲያስመጣት ሲጠየቅ ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን፣በመጨረሻም የግል ተበዳይ በራሷ ወጪ ተሳፍራ ወደ ሀገሯ ብትመጣም፤ ጤንነቷ ግን ደህና እንዳልሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ በዝርዝር እና በግልጽ ማመልከቱን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የግል ተበዳይ ወደውጪ ሀገር የተላከችው ከእሱ እውቀት (እውቅና) ውጪ በኤጀንሲው ፀሐፊ በኩል መሆኑን እንደሚያስረዳ በመግለፅ ባስያዘው ጭብጥ መሠረት የመከላከያ ማስረጃ ማሰማቱን እና ፍ/ቤቱ ግን የተሰማው መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻለም ለማለት ክብደት እንዳልሰጠው ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው አመልካች በዓቃቤ ሕግ በዝርዝር የተመለከተውን ፍሬ ነገር ክዶ በመከራከሩ ፍ/ቤቱ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመመስረት ማስረጃውን ሰምቷል፡፡ በዚህ ሂደት የሰማችውን ማስረጃዎችም መዝኖ መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ አመልካች ግን አሁንም የግል ተበዳይን ወደ ውጭ ሀገር ስለመላኩ በማስረጃ አልተረጋገጠብኝም በማለት ነው እየተከራከረ ያለው፡፡ ጭብጥ ለማስያዝ በሰበር ችሎቱ እንዲመረመርለት የጠየቀውም ይህን የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡ የግል ተበዳይ ቀርባ እስካልመሰከረችብኝ ድረስ እንግልት ደርሶባታል ተብሎ ጥፋተኛ መባል የለብኝም የሚል ክርክርም አንስቷል፡፡ እንደሚታወቀው ይህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የፍሬ ነገር ጭብጥን በማስረጃ የማጣራትም/የማንጠርም/ ሆነ ማስረጃውን በመመዘን ድምዳሜ ላይ የመድረስ ሥልጣን በሕጉ አልተሰጠውም፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(30(ሀ) እና በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 10 እንደተደነገገው ለሰበር ችሎቱ የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን የክርክር ሥርዓቱን ጨርሶ በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ የተፈጸመውን መሠረታዊ የህግ ስህተት በማረም የተወሰነ ነው፡፡ በመሆኑም ድርጊቱን ለመፈጸሜ በማስረጃ ሳይረጋገጥ ነው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተላለፈብኝ የሚለውን መነሻ በማድረግ አመልካች ያስያዘውን የፍሬ ነገር ጭብጥ የምንመረምርበት አግባብ የለም፡፡ የግል ተበዳይ የሆነ ሰው እስካልመሰከረ በሌሎች ማስረጃዎች የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ማረጋገጥ አይቻልም የሚል የህግ ፍልስፍናም ሆነ ሕግ ስለሌለም የግል ተበዳይ ቀርባ ስለደረሰባት እንግልት ሳታስረዳ ጥፋተኛ መባሌ ተገቢ አይደለም የሚለው የአመልካች መከራከሪያም ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነው የምንልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.95035 ሰኔ 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 59774 ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ/ሥ-ሥ-ሕ-ቁ. 195(2)(ለ) (2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 60542

የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ተክለድንግል ገ/ሚካኤል

ተጠሪ፡- የፌ/ሥ/ም/ፀ/ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሙስና ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካችና በሌሎች ስምንት ሰዎች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች የተከሰሱት በአንድ መዝገብ በተከፈተ ክስ ሲሆን የክሱ ይዘትም አመልካቹ በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1ሀ)፣33 እና 407(1(ሀ)(ሐ))፣(2) እና (3) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘትና በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በስር ፍርድ ቤት ቀደም ሲል አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተመድቦ ሲሰራ በነበረበት ወቅት በስራው አጋጣሚ በእጁ የገባውን የአዲስ አበባ ከተማ ማስተር ፕላን ከስራ ሲታገድ በሲዲ በመገልበጥና በኮምፒዩተር በመታገዝ በከተማው ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎችን በመለየትና ቀደም ሲል በነበረው ስርዓት ለማኅበራት ይፈቀድ የነበረውን የቤቶች ፕላን ቶፖሎጂ በወቅቱ በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የሚሰራባቸውን የቤቶች አይነት በፕላን በማዘጋጀት ሕጋዊ ያልሆኑ ማህበራትን ከሕግ ውጪ በማደራጀትና ቦታን በመስጠት የሙስና ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በአንደኛ ተራ ቁጥር ተከሳሽ ከነበረው ከአቶ በሃይሉ ለማ ድንቁ ጋር በጥቅም በመመሳጠር በሐሰትና በተቀነባበረ ዘዴ "ሻላ" የሚባል ሃሰተኛ የመኖሪያ ቤት የሕብረት ስራ ማህበር እንዲቋቋም አድርጎ በሀሰተኛ መንገድ የተዘጋጀው የማህበሩን ፋይል ከስር ሁለተኛ ተከሳሽ(ወ/ሮ ደሃብ ገ/ሕይወት) ጋር የጥቅም ግንኙነት በመፍጠር በ1998 ዓ/ም የካ ክፍለ ከተማ ማህበር ማደራጃ ፅ/ቤት ውስጥ እንዲገባ በማስደረግና የማህበሩ አባላትም የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና ማህበሩን ሕጋዊ አስመስሎ በማቅረብና በሁለተኛ ተከሳሽ በኩል ሃሰተኛውን ማህበር ሕጋዊ አስመስሎ እንዲነገር አድርጎ 248 የማህበሩ አባላት በሕገ ወጥ መንገድ መሬት እንዲያገኙ በማድረግና ቦጋለ የተባለውን ሐሰተኛ እና ሕገ ወጥ ማህበር ፋይልም ከ1ኛ ተከሳሽ በመቀበል ለሁለተኛ ተከሳሽ ሰጥቶ ወደ ክፍለ ከተማው ማህበራት ማደረጃ ፅ/ቤት እንዲገባ አድርጎ በሁለቱም ሐሰተኛ ማህበራት ሕገ ወጥ ጥቅም በማግኘት፣በማስገኘትና በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት በማድረስ የሙስና ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡ጉዳዩ አግባብነት ባለው ስነ ስነ ሥርኣት ተመርቶ አመልካች ክሱን በመካድ በመከራከራቸውም አቃቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተመርምረውም አመልካች "ሻላ" የሚባል የመኖሪያ ቤት ሕብረት ማህበር ሊቀመንበር ለመሆናቸው አቃቤ ሕግ ባቀረበው የሰነድ ማስረጃ ማስረዳቱ መረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ገልፆ ይህንኑ እንዲከላከሉ ተደርጎ አመልካች በበኩላቸው አሉኝ ያሏቸውን ማስረጃዎችን ለመከላከያ ማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ህግን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ ያልቻሉ መሆኑን በመግለፅ በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ ተጠቅሶ የቀረበባቸውን ድንጋጌ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 113(2) መሰረት ዝቅ አድርጎ አመልካችን በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ))፣33 እና 407(1(ሀ)) ስር ጥፋተኛ አድርጎአል፡፡ከዚህም በኋላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በሁዋላ አመልካችን በአምስት አመት ፅኑ እስራትና በብር 5,000.00(አምስት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 18 ቀን 2003 ዓ/ም በጻፉት አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ይዘቱም ባጭሩ፡-አመልካች የመንግስት ሰራተኛ ሳይሆኑ በሙስና መከሰሳቸው ያላግባብ መሆኑን፣በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ነጻ በተባሉበት ጉዳይም ተመልሶ ጥፋተኛ መባላቸው ስነ ሥርኣቱን ያልጠበቀ መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤት በአመልካች እንዲቀርብና ፊርማው እንዲመረመር የተጠየቀውን የሰነድ ማስረጃ በፎረንሲክ ሳያስመረምር አልፎ ውሳኔ መስጠቱም የማስረጃ አቀራረቡና አመዛዘኑ ሥርዓት ሕጉን ያልጠበቀ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ዘርዝረው በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በነጻ እንዲሰናበቱ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የቤት ስራ ማህበር ሊቀመንበር ናቸው ተብሎ ጥፋተኛ መደረጋቸው ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎል፡፡በዚህም መሰረት ተጠሪ የካቲት 15 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ መልሱን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩላቸው መጋቢት 09 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለአቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ ከጠቀሷቸው የቅሬታ ነጥቦች መካከል አንዱ ተጠሪ ክሱን በማስረጃ አለማስደገፉንና አመልካች እንዲመረመርላቸው የጠየቁት ሰነድ በፎረንሲክ ሳይመረመር እንዲሁም ለተሰሙት የመከላከያ ምስክሮች ቃል ክብደት ሳይሰጥ መታለፉን የሚመለከት ነው፡፡ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ በሰበር ችሎት እንዲታይ በጭብጥነት ያልተያዘ ከመሆኑም በላይ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ማስረጃ በማጣራትና በመመዘን የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎችን የአቃቤን ህግን ማስረጃዎችን የማስተባበል ብቃት የላቸውም በሚል ያለፉት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግሰት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ሥልጣን በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ ይህ ችሎት የሚመረምረው ሁኖ ስላላገኘው አልፈነዋል፡፡

ሌላው አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ ሳይሆኑ በሙስና ወንጀል መከሰሳቸው አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 7 ድንጋጌን በግልፅ የሚጻረር ነው በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 33 ድንጋጌን መንፈስና ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም አመልካች በስር ፍርድ ቤት የተከሰሱት የመንግስት ሰራተኞች ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ከመሆኑም በላይ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 33 መሰረት አንድ ሰው የመንግስት ሰራተኛ ባይሆንም በሙሉ ፈቃዱና እውቀቱ የሙስና ወንጀል ሙሉ ተካፋይ መሆኑ ከተረጋገጠ በሙስና የሚከሰስበት አግባብ መኖሩ የተደነገገ ነውና፡፡

በዚህ ችሎት እንዲታይ የተያዘውና አመልካች በመከራከሪያነት ያቀረቡት ሌላው ነጥብ አመልካች የቤት ማህበሩ ሊቀመንበር ናቸው በማለት ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች የተከሰሱት ሕጋዊ ያልሆኑ ማህበራትን የሊቀመንበርነት ስልጣን አለኝ በማለት አደራጅተው ለማህበሩ አባለት ያላግባብ ቦታ እንዲሰጥ አድርገዋል፣በዚህም በመንግስትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ሲሆን የማህበራቱ ሕጋዊ አለመሆንና ማህበራቱ ሲደራጁ እንዲሁም ቦታውን ሲወስዱ አመልካች የነበራቸው ሚና ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ነጥብ ነው፡፡በመሆኑም የቤቱ ማህበራት ሕጋዊ ያለመሆናቸውና የተደራጁትም አመልካች በሊቀመንበርነት በነበራቸው ሚና ጭምር መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች በወንጀል የማይጠየቁበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ሌላው አመልካች በዚህ ድርጊታቸው ነጻ ተብለው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 የተሰጠ ብይን የሌለ መሆኑን የስር ፍርድ ቤትን መዝገብ አስቀርበን የተመለከትን በመሆኑ በዚህ ረገድ የተነሳው ቅሬታም እውነትነት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡በአጠቃላይ በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 60587 ሚያዚያ 04 እና 14 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 56628 ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ/ም የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195((2(ለ-2)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረት ቅጣቱን ተከታትሎ ያስፈፅም ዘንድ ውሳኔው መፅናቱ ለማ/ቤቱ ይገለፅለት ብለናል፡፡ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት የዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1ኛ/ ሐሰን አማን መሐመድ ┐ ጠበቃ ሚሊዮን አበራ

2ኛ/ ብርሃን መኮንን ደሣለኝ ┘

ተጠሪ፡- የፌ/ሥ/ፀረ-ሙስና ኮሚሽን- ዐቃቤ ሕግ- ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በተጠሪ መስሪያ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቁና ክስ ሊመሰረትባቸው የሚገባቸውን የወንጀል ድርጊቶችን እንዲሁም በተጠሪ መስሪያ ቤት ስልጣን ስር የማይወድቅ ጉዳይ በኮሚሽኑ አቃቤ ሕግ ክስ ሊመሰረት የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤት የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ በአመልካቾች ላይ የመሰረተው ክስ በሁለት ምድብ የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክስ፡- የወ/ሕግ አንቀጽ 32/ሀ/ እና 379/1ሀ/ን ጠቅሶ አመልካቾች በሌሎች ሀሰተኛ ሰው ስም የተዘጋጀ የጅምላ ንግድ ፈቃድ አስመስለው አዘጋጅተው ለጨረታ አቀርበው ተወዳድረዋል የሚል ሲሆን ሁለተኛው ክስ ደግሞ የወ/ሕግ አንቀጽ 32/1ሀ/እና 696/ሐ/ የተመለከተውን ተላልፈው በ1ኛው ክስ ላይ የተጠቀሰውን ሰነድ ሐሰተኛነቱን ደብቀው ለጨረታ በማቅረብ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽኑን አታለው በመንግሥት ላይ የብር 707,805.00 ጉዳት በማድረሣቸው ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአቃቤ ሕጉን ክሶች ለአመልካቾች አንብቦላቸው እንዲረዱት ከአደረገ በሁዋላ አመልካቾች በክሱ ላይ ተቃውሞ በማቅረባቸው ጉዳዩን መርምሮ ተከሣሾች ሁሉም በግል የሚተዳደሩ እንደመሆናቸው የመንግሥት ሠራተኛ ተጣምሮ ባልተከሰሰበት ሁኔታ የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ በተከሣሾች ላይ ክስ ለመመስረት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 404/3/ አንፃር ስልጣን የለውም በማለት መዝገቡን በአብላጫ ድምጽ ዘግቶ ተከሣሾች ከእስር እንዲለቀቁ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ የሙስና ወንጀል ክስ ማቅረቡ ሕጋዊ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ ከመንግሥት ሠራተኞች ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሣያጣምር በግለሰቦች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚችልበት የሕግ አግባብ ሳይኖር የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ብይን መሻሩ ያላግባብ ነው በማለት ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በአመልካቾች ላይ የቀረበው ክስ የመንግስት ሰራተኞች ባይሆኑም የተጠሪ መስሪያ ቤት የማስተናገድ ስልጣን አለው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በፅሑፍ በሰጠው መልስ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክስ ያቀረበው ክሱን ለማቅረብ በተሰጠን ስልጣን ነው፣በተለይ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 379 የሙስና ወንጀል መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 404/4/ ላይ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን ይህም ድንጋጌ የመንግሥት ሠራተኞን ብቻ የሚመለከት አይደለም፣አንቀጽ 379 መሠረት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 375 እስከ 378 የተደነገገውን በአንቀጽ 375 ደግሞ "ማንም ሰው...." ብሎ ነው የሚጀምረው፣ ስለሆነም አንቀጽ 379 ጠቅሰን ክስ ለማቅረብ ሥልጣን ያለን ሲሆን አንቀጽ 696/ሐ/ አጣምረን የከሰስነው ድርጊቱ በ1ኛ ክስ ከጠቀስነው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 379 ጋር ተያይዞ የተፈፀመ በመሆኑ በማስረጃም ሆነ በውሣኔ አሰጣጥ የሚረዳ በመሆኑ እንጂ 696/ሐ/ በአመልካቾች ላይ የጠቀስነው ስልጣን አለን በሚል አይደለም፣ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ የወ/ሕግ አንቀጽ 379 በመጥቀስ በአመልካቾች ላይ ክስ መመሥረት ይችላል በማለት መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የስር ፍ/ቤት አመልካቾችን የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ ከአቀረበባቸው ክስ መዝገቡን ዘግቶ ያሰናበታቸው በወ/ሕግ አንቀጽ 404/3/ መሠረት ከመንግሥት ሠራተኛ ውጭ የሆነ ሰው ከመንግሥት ሠራተኛ ጋር ተጣምሮ ካልተከሰሰ ወይም ለመንግሥት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ከሰጠ ወይም ለመስጠት ከተስማማ ብቻ በመሆኑ እና ተከሣሾች የመንግሥት ሠራተኞች ስላልሆኑ ወይም ከመንግሥት ሠራተኛ ጋር ተጣምረው ባልተከሰሱበት ሁኔታ የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ ክስ ሊያቀርብባቸው አይችልም በሚል መሆኑንና ይህንን የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያልተቀበለው ደግሞ በመንግስት ሰራተኛ ባልሆነ ሰውም የኮሚሽኑ አቃቤ ሕግ የሙስና ክስ ለማቅረብ ሥልጣን አለው፣የሙስና ድርጊት ያልሆነውን የወንጀል ድርጊትም ከሙስና ወንጀል ጋር አጣምሮ ክስ ለማቅረብ የሚችልበት የሕግ አግባብ አለ በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 404/4/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው መንግሥታዊ ወይም ወታደራዊ ሠነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት እንደሙስና ወንጀል እንደሚቆጠር መደንገጉን ነው፡፡ይህን እንደሙስና ወንጀል የተደነገገውን ድርጊት ሊፈጽመው የሚችለው ማን እንደሆነ ለማወቅ ደግሞ በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል በአንቀጽ 375 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ማየትን የግድ ይላል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በወንጀል ሕጉ በሕዝብ ጥቅሞችና በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሚገዛው አራተኛ መፅሐፍ፣በሕዝብ አመኔታ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ርዕሥ ስር፣ሐሰተኛ ሰነዶችን መፍጠር፣ሰነዶችን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥና ማጥፋትን በሚመለከት ምዕራፍ ስር የተቀመጡ ሆነው የአንቀጽ 375 ድንጋጌ በግዙፍ የሚፈጸም ሐሰት በሚል ርዕስ የተቀረጸ ሁኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጀመሪያው ፓራግራፍ ማንም ሰው በሚል ሐረግ የሚጀመር ሁኖ በንዑስ ድንጋጌዎቹ ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች መኖራቸው ሲረጋገጥ የወንጀል ተጠያቂነት መኖሩን በግልጽ ያሳያል፡፡ በአንቀጽ 379 ድንጋጌ በንዑስ አንቀፅ አንድ ሥር ከተመለከተው ይዘትም የመንግሥት ሠራተኛ የሆነውን እና ያልሆነውን ማንኛውንም ሰው የሚመለከት መሆኑና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ስር ያሰፈረው ደግሞ የመንግሥት ሠራተኛን ብቻ የሚመለከት ስለመሆኑ መረዳት የሚቻለው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በአንቀጽ 379(2) ስር የሠፈረው ከመንግሥት ሠነዶች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው ሆኖ ሠነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት ወይም ወደ ሐሰት መለወጥን ተግባር ያከናወነውን የመንግሥት ሠራተኛ በግልጽ መለየቱ በአንቀፁ ንዑስ ቁጥር አንድ ስር የተመለከተው ደግሞ ሰነዱ የመንግሥት ሆኖ አስመስሎ ያዘጋጀው ወይም የለወጠው ማንኛውም ሰው ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ አመልካቾች አስመስለው አዘጋጁት የተባለው የንግድ ፈቃድ ማረጋገጫ መንግሥታዊ ሰነድን እንደመሆኑ ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩበት ወንጀልም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 379 "ን" የሚመለከት ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 379 "ን" የሚሸፍን ድርጊት ደግሞ የሙስና ወንጀል ነው ተብሎ በሕግ ተደንግጓል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በተሻሻለው የፌዴራል የስነምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/1997 መሰረት የሙስና ወንጀሎችን የመመርመርና የመክሰስ ሥልጣን የተሰጠው የፌዴራሉ ሥነ ምግባርና ፀረ- ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡በመሆኑም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሰረት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ የቀረበውን 1ኛ የወንጀል ክስ የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ የመክሰስ ስልጣን አለው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን መሻሩ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

2ኛውን ክስ በተመለከተ የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ ክስ የመሠረተው ስልጣን አለኝ ብሎ ሣይሆን ከ1ኛው ክስ ጋር ግንኙነት ያለውና ማስረጃውም የሁለቱ አንድ ነው በሚል እንደሆነ በስር ፍርድ ቤትና ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከተካሄደው ክርክር ተረድተናል፡፡ ኮሚሽኑ በዚህ መልኩ የሱ ስልጣን ያልሆኑ ነገር ግን ከመሠረተው የሙስና ወንጀሎች ጋር አጣምሮ ክስ ማቅረቡ ደግሞ ከወንጀል ሥነ ስርዓት ሕግ ዓላማጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነሥርአት እና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት የሙስና ክስ የሚመራበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ይሁን እንጂ አዋጁ የኮሚሽኑ አቃቤ ሕግ በእራሱ ስልጣን ስር የማይወድቅ ነገር ግን የሙስና ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተከሰሰ ሰው ከዚሁ ጋር አንድ ላይ መከሰስ ያለበትን የወንጀል ድርጊት አንድ ላይ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ በግልፅ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም፡፡ ሆኖም ተጠቃሹ አዋጅ በአንቀጽ 55 ስር የወንጀል ሥነሥርአት ህግ፣ የፍትህ ብሄር ሥነሥርአት ህግ፣ የወንጀል ህግና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል በሚል ደንግጎ በአዋጁ አንቀፅ 58 ስር **የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎችን ለይቶ ሲያስቀምጥ** የጸረሙስና የልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ 236/1993 እንደተሻሻለ መሻሩን፣ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ለማቅረብ ስልጣን ያለው አካል በሕጉ ከተሰጠው ስልጣን ጋር አንድ ላይ የሚታይና ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ስልጣኑ ከሆነው ጉዳይ ጋር ስልጣኑ ያልሆነውን ጉዳይ ክስ ለማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ የሚደነግጉ የወንጀል ስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት ከሙስና ወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ የቀረበውንም የወንጀል ክስ የማየት ስልጣን እስካለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድረስ ሁሉንም ክሶች አጣምሮ ቢያይ የፍ/ቤትን፣ የከሣሽን እና የምስክሮችንም ጊዜና ጉልበት የሚቆጥብ በመሆኑ የሚደገፍ ስለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 110 ድንጋጌ ሁለተኛው ፓራግራፍ ይዘትና መንፈስ ጋር አጣምረን ስናነበው የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ዋናውና ቁልፍ ነገር የጉዳዩ መታየት በትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጡ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው አሉታዊ ውጤት የሌለ መሆኑ መረጋገጡ ላይ ነው፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተዘረዘረጉት ሕጋዊ ምክንያቶች የፊዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ በአመልካቾች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማቅረብ ሥልጣን አለው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን በመሻር የተዘጋው መዝገብ ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ እንዲቀጥል ሲል የሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፊዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 60134 ታህሳስ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2ሀ/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡን ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- ውድማ አበጀ - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ዐ/ሕግ አልቀረበም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአንድ የወንጀል አፈፃፀም ተግባር በሙከራ ደረጃ ላይ ደርሷል የሚባለው መቼ፤ እንዴት ነው? የሚለውን ነጥብ በዚህ የወንጀል ጉዳይ በማስረጃ ከተረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳዮች ጋር በማናገዘብ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ በክልሉ የጉራጌ ዞን ዐ/ሕግ በአሁኑ አመልካችና በግብረ-አበሮቹ ላይ ሦስቱም ተከሳሾች በወ/ህ/ቁ 32/1/ /ሀ/፣ 27/1/ እና 671/1/ለ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በጅማ ወለኔ ቀበሌ የሚመላለሱትን ተሽከርካሪዎች ለመዝረፍ የጦር መሣሪያ፣ ጭንብል፣ የእጅ ባትሪ፣ ጩቤ በመያዝ ከመጋቢት 07 ቀን እስከ መጋቢት 08 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ተንቀሳቅሰው ጠብቀው ተሽከርካሪ በማጣታቸው ሲመለሱ በተደረገው ጥቆማ መነሻ በፀጥታ ኃይሎች ስለተያዙ በፈፀሙት ከባድ የውንብድና ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበው ክስ ሲሆን፤ የአሁን አመልካች በተከሳሽነቱ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡

በማስረጃነትም የሰው ማስረጃና ተከሳሾች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 27 እና 35 መሠረት በምርመራ ጊዜ ለመርማሪ ፖሊስ እና በፍ/ቤት የሰጡት ቃል ቀርቧል፡፡ በሰው ማስረጃው የተረጋገጠው መጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ከአንድ የመኪና አሽከርካሪ ሽፍቶች ለመዝረፍ ተሰማርተዋል የሚል ጥቆማ አግኝቼ ወዲያውኑ ስከታተል ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ተሽከርካሪ በማስቆም በተደረገው ጥብቅ ክትትል እነዚህ ሦስት ሰዎች መታወቂያ ሲጠየቁ የላቸውም፡፡ በግንባታ ሥራ ተሰማርተን የግንባታ ቁሳቁስ እጥረት ስለአጋጠመ ወደ መኖሪያችን እየሄድን ነው አሉ፡፡ ዕቃቸው ሲፈተሽ ግን አንድ የጦር መሣሪያ፣ ጩቤ፣ ጭንብል ተገኝቶባቸዋል የሚል ነው፡፡ እንዲሁም በምርመራ ጊዜ በሰጡት የእምነት ቃልም ለዘረፋ ተስማምተው አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት አድርገው ያመቸናል ብለው ወደ አሰቡበት ቦታ በመሄድ ጫካ ውስጥ ከአደሩ በኋላ ባገኙት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መኪና ተሳፍረው ሲመለሱ ከያዙት የዘረፋ ቁሳቁስ ጋር በፖሊስ ቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የሚገልፅ ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ይህንኑ የዐ/ሕግ ማስረጃ እና ተከሳሾች እንከላከላለን ሲሉ ያቀረቡትን ማስረጃ በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ እንደ ክሱ አቀራረብ ጥፋተኛ ናቸው ካለ በኋላ ከሦስተኛው ተከሳሽ በስተቀር በአሁን አመልካችና ሁለተኛ ተከሳሽ በነበረው ሌላ ግብረአበር ላይ የቀረበውን የወንጀል ጥፋተኝነት እና ቅጣት ሪከርድ መነሻ በማድረግ በአሁን አመልካች ላይ የ22 ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት ጥሏል፡፡

ከዚህም ቀደም ብለው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተባለበት ፅኑ እስራት የ10 ዓመቱን በእስር ሊጨርስ በሚል በአመክሮ መለቀቁን መነሻ በማድረግ የተጣለ ቅጣት እንደሆነ የውሳኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ በደረጃው ላሉ የበላይ ፍ/ቤቶች እንዲታረም ቅሬታ ቢያቀርብም ቅሬታው ውድቅ በመደረጉ ለመጨረሻ ጊዜ ጉዳዩን በዚህ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡

በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ክርክር ያደረጉበት ነጥብ ይህ አመልካች እና ሌሎች ግብረ-አበሮች የፈፀሙት ተግባር በሙከራ ወንጀል ሥር ሊወድቅ የሚችል ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ላይ ነው፡፡ እኛም በዚሁ ጭብጥ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ቅሬታ ከሥር ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በ1997 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27 እንደተደነገገው ማንም ሰው አስቦ ወንጀሉን ማድረግ ጀምሮ የወንጀሉን ድርጊት እስከመጨረሻው ባይከታተልም ወይም ለመከታተል ባይቻልም የወንጀል ድርጊቱ እንዲፈፀም እስከመጨረሻው ተከታትሎ አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላስገኘ ቢሆንም የሙከራ ወንጀሉን እንደፈፀመ እንደሚያስቀጥረው ተመልክቷል፡፡

በዚህም ጉዳይ በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው ከድርጊቱ በፊት ተከሳሾች ሁልጊዜ የዘረፋ ወንጀል በሚፈፀምበት ጫካ መግባታቸው፤ ይህን በተመለከተ በሰው ጥቆማ አማካኝነት በፀጥታ ኃይሎች በተደረገው ክትትል ተሳፍረውበት ከነበረው መኪና ከጦር መሣሪያ፣ ጩቤና ጭንብል ጋር መያዛቸው፤ እንዲሁም በእራሳቸው የእምነት ቃል እንደተረጋገጠው ለዘረፋ ወንጀል አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት አጠናቀው ከዚሁ ጫካ ውስጥ ሲጠባበቁ አድረው በማግስቱ በመኪና ተሳፍረው ሲሄዱ ለዘረፋ ተግባር ሲሉ ከያዙት ቁሳቁስ ጋር መያዛቸው ሁሉ ሲታይ አመልካችና ግብረ-አበሮቹ የዘረፋ ወንጀል ለመፈፀም እስከመጨረሻው ተከታትለው ነገር ግን የሚዘረፍ ነገር ባለማግኘታቸው ውጤቱን ያላገኙ መሆኑን አስረጂ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በአመልካችና በግብረ-አበሮቹ በኩል የተፈፀመው ተግባር በእራሱ የዘረፋ ወንጀሉን ለመፈፀም ወደ ኋላ ከማይመለሱበት ደረጃ ደርሰው የነበረ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቱ ይህንን ሁሉ በማገናዘብ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ አመልካች ተላልፎታል ተብሎ በተጠቀሰው ሕግ አነጋገር መሠረት ሆኖ የተገኘ እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 33619 በቀን 12/06/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
አመልካች ይህንኑ እንዲያውቀዉ ውጤቱ ባለበት ማ/ቤት ይገለፅለት፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 73953

መጋቢት 13 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

አመልካቾች፡- ከፋለ ሰፈነ - ጉዳይ ተከታታይ አስቀናው ከፋለ ቀረበ

ተጠሪ፡- የአማራ ክልል ዓ/ሕግ - የቀረበ የለም፡፡
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን ደምቢያ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የጉዳዩ መነሻ ተጠሪ በአመልካች ላይ የተመሰረተው ክስ ነው፡፡ አመልካች የተከሰሱት በ1996 ዓ/ም በወጣው የወ/መ/ሕግ አንቀጽ 438 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከመንግስት ስራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሕግ በተፈቀደው ውጭ አስቦ መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ/ም ደምቢያ ወረዳ ጫሂት ከተማ ላይ ምክትል ሳጅን ሙሉጉጃም ሙለአለም የተባለችው የትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ሆና በመስራት ላይ እንዳለች አመልካች የታርጋ ቁጥር ኮድ 3-28371 አ.አ የሆነች አይሱዚ የጭነት መኪና እያሽከረከረ ወደ ጎንደር አቅጣጫ ሲመጣ በተደረገ ቁጥጥር መንጃ ፈቃድ ሳይዝ በማሽከርከር በሕግ አግባብ ክስ አዘጋጅታ ስትሰጠው የክስ ቻርጅ አልቀበልም በማለት እምቢተኛ በመሆን በድጋሚ ሚያዚያ 11 ቀን 2003 ዓ/ም ደንቢያ ወረዳ ቆላድባ ከተማ 01 ቀበሌ በተደረገው የትራፊክ ደንብ መተላለፍ የክስ ቻርጅ የያዘ እንዲወስድ ቢጠየቅም እምቢተኛ በመሆኑ የመንግስት ስራን የማሰናከልና የመተባበር ግዴታ መጣስ የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በሚል ነው፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን በመካድ የተከራከረ ሲሆን አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች እንዲከላከል ተደርጎ የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ምስክሮችን ከአሰማ በሁዋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች መከላከያ ማስረጃ የአቃቤ ሕጉን ማስረጃ ለማስተባበል ብቃቱ የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ ውድቅ አድርጐ አመልካችን በአቃቤ ሕጉ ተጠቅሶ በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ በማድረግ በአንድ አመት ከስድስት ወር እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሲጸና የቅጣት ውሣኔው ግን ተሻሽሎ አመልካች በአንድ አመት እስራት እንዲቀጣ ተደርጓል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች ድርጊቱን ስለመፈፀሙ ሳይረጋገጥና ተረጋግጧል ቢባል እንኳ ድርጊቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 438 ስር የማይሸፈን ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሰጡት ያላግባብ ነው በማለት ውሣኔው እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 438 ስር ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መንዘብ የተቻለው አመልካች የተከሰሰው የትራፊክ ተቀጣጣሪ ፖሊስ ሆኖ በመስራት ላይ የነበረችው የትራፊክ ፖሊስ ጽ/ቤት ባልደረባ አመልካች የታርጋ ቁጥር ኮድ 3-28371 አ.አ የሆነች አይሱዚ የጭነት መኪና እያሽከረከረ ወደ ጎንደር አቅጣጫ ሲመጣ በተደረገ ቁጥጥር መንጃ ፈቃድ ሳይዝ በማሽከረከር በሕግ አግባብ ክስ አዘጋጅታ ስትሰጠው የክስ ቻርጅ አልቀበልም በማለት በተለያዩ ሁለት ቀናት እምቢተኛ በመሆን የመንግስት ስራን የማሰናከልና የመተባበር ግዴታ መጣስ የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በሚል ሲሆን አመልካች ክዶ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ምስክሮች ቀርበው በመሰማታቸውና አመልካችም የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት የመከላከያ ማስረጃዎችን ያሰማ ቢሆን የአቃቤ ህግ ማስረጃዎችን ለማስተባበል ያለመቻሉ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መገለጽን ነው፡፡ በዚህም መሠረት የሥር ፍ/ቤት አመልካቾችን ለድርጊቱ ኃላፊነት ያደረጉት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በመሰማትና ቃላቸው ለጉዳዩ አግባብነት፤ ክብደት ያለው መሆኑን በማመን አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎች እንዲያስተባብል የመከላከል መብቱን በመጠበቅ የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎችን ከሰማ በሁዋላ የመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ለማስተባበል የማይችሉ መሆኑን ዘርዝሮ ቃላቸውን ውድቅ በማድረግ መሆኑን ከውሣኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም አመልካች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ክብደትን በተመለከተ ያቀረበውን ቅሬታ ስንመለከተውም ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑና ይህ ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ለዚህ ችሎት በአንቀጽ 80 (3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰርት ለዚህ ሰበር ችሎት ከተሰጠው መሰረታዊ ሕግ ስህተት ማረም ስልጣን ስር የማይወድቅ ወይም የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የማያሟላ በመሆኑ የምንቀበለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ አመልካች የትራፊክ ፖሊስ ባልደረባ የትራፊክ ደንብ መተላለፋቸውን በመግለጽ የሰጠችውን ክስ አልቀበልም በማለት እምቢተኛ መሆኑ መረጋገጡን ይዘን ይህ አድራጐት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 438 ስር የሚወድቅ መሆን ያለመሆኑን ስንመለከተው የተጠቃሹ ድንጋጌ አርእስት “የመንግስት ስራን ማሰናከልና የመተባበር ግዴታን መጣስ” በሚል የተቀመጠ ሁኖ ድንጌው ለሌሎች ሰዎች በመንግስት ስራ ላይ የሚፈፅሟቸው ወንጀሎች በሚል “ምዕራፍ ሶስት” ስር የሚገኝ ሲሆን ይህ ምዕራፍ የሚያሳየውን ሌሎች ሰዎች ከመንግስት ስራ ጋር በተያያዘ መንገድ የሚፈፅሟቸው ወንጀሎች በሚደነግገው ክፍል ሁለት ስር ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም በላይ የድንጋጌው ይዘት ሲታይ ማንም ሰው ከመንግስት ስራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሕግ በተፈቀደው ወይም በፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዘዝ መሰረት በመንግስት ሰራተኛ ሲጠየቅ ቀርቦ ለማስረዳት፤ ተገቢውን መልስ ለመስጠት፤ ሰነዶችን ለማቅርብ ወይም ለማስመርመር ወይም ልዩ ልዩ ቤቶች፣ ቦታዎችን ወይም ነገሮችን ለማስፈተሽ እምቢተኛ ከሆነ በጠቅላላው ለምርመራ ያልተባበረ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የመንግስት ስራ ያደናቀፈ እንደሆነ ተጠያቂነት ያለበት መሆኑን ያሣያል፡፡ ከድንጋጌው ውስጥ “..... በሕግ በተፈቀደው.....” እና “..... በማናቸውም ሌላ መንገድ.....” የሚሉት ሐረጎች ሲታዩ የአመልካች አድራጐትም በዚሁ ድንጋጌ የሚሸፈን መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የትራፊክ ፖሊስ የትራፊክ ደንብን የመቆጣጠርና የማስፈፀም ስልጣን በህግ ተለይቶ የተሰጠው ሲሆን ከዚሁ ስራ ጋር በተያያዘ ኃላፊነቱንና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተግባሩን በመወጣት ሂደት ማንም ሰው ሊያስናክለው የማይገባ፣ ይልቁንም የመተባበር ግዴታ ያለበት መሆኑ የሚታወቅ ነውና፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(-2)) መሰርት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. ውሣኔው የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት የመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 73264

ሚያዝያ 09 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባልስልጣን-አቃቤ ሕግ ትዝታ ዘውዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ አልፈድል አሻፊ
2. አቶ ሰክርያ የሱፍ
3. አቶ ኢስማኤል ሐሰን

ጠበቃ መሐመድ ከድር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርመሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ በተሰጠ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ለማቅረብ በሕጉ ተለይቶ የተመለከተውን የጊዜ ገደብ የተመለከተ ነው፡፡ አመልካች ባሁኑ ተጠሪዎች በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32(1ሀ) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ሳይፈጸም አስራ አምስት የቀንድ ከብቶችን ወደ ሱዳን ለማስወጣት ሲሉ ሰባት ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው መያዛቸውን ገልፆ አንደኛ ተጠሪ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተጠሪዎች ደግሞ በግብረ አበርነት የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ የመሰረተባቸው ሲሆን ተጠሪዎች ክደው ተከራክረው አቃቤ ሕግ አሉን ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ ከአሰማ በኋላ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው አቃቤ ሕግ በማስረጃዎቹ አላስረዳም በማለት ተጠሪዎችን ምንም መከላከል ሳያስፈልጋቸው ወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 መሰረት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኙን ለቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት አቅርቦ ጉዳዩ ተጠሪዎችን በመልስ ሰጪነት ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የአመልካች የይግባኝ አቤቱታ አቀራረቡ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁጥር 187(2) ስር የተመለከተውን የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ጠብቆ ያልቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ጊዜውን ለመቁጠር መነሻ ያደረገበት ጊዜ ትክክለኛ ያለመሆኑንና ይግባኙን ግንቦት 25 ቀን 2003 ዓ.ም ግልባጩን በመቀበል ሰኔ 24 ቀን 2003 ዓ.ም ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበ ሆኖ እያለ የይግባኝ ግልባጩ ለአመልካች የደረሰው ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ አልፏል ተብሎ የይግባኝ መዝገቡ መዘጋቱ ሥነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥርዓቱን ያልተከተለ መሆኑን እንዲሁም በዋናው ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ያለመሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው ሊለወጥ ይገባል ሲል መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ የአመልካች የይግባኝ አቤቱታው በወቅቱ ያልቀረበ ነው ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውድቅ መደረጉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ በቅብጥነት የተያዘው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የይግባኝ ጊዜ ማቅረቢያ ሳይጠብቅ ይግባኙን አቅርቧል ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቶ አመልካች የይግባኝ መዝገቡ ተገልብጦ እንዲሰጠው ውሳኔ ከተሰጠ በ2ኛው ቀን ማለትም ግንቦት 11 ቀን 2003 ዓ/ም መጠየቁን፣ ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም ደግሞ የይግባኝ መዝገቡን ግልባጩን መቀበሉንና በዚህ ቀን ሸኚ የተሰጠው መሆኑና አመልካች ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰኔ 24 ቀን 2003 ዓ.ም ይግባኝ ማቅረቡ መረጋገጡን መርምሮ እነዚህ ፍሬ ነገሮችን መሰረት በማድረግም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 187(2) ስር የተመለከተው የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ሲሰላ አመልካች ይግባኙን ያቀረበው የሰባት ቀናት ጊዜ ከአለፈ በኋላ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡ አመልካች ይህንኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ድምዳሜ የተሳሳተ ነው በማለት በዚህ የሰበር ችሎት የሚከራከረው ይግባኙ ተገልብጦ የተሰጠው ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም ሳይሆን ግንቦት 25 ቀን 2003 ዓ/ም ስለመሆኑ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በነበረው የቃል ክርክር ጊዜ ተረጋግጧል፣ ማስረጃም ቀርቧል በሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ ይህ የአመልካች ክርክር እውነትነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍሬ ነገር የፈፀመው ስህተት የለም በማለት ለዚህ ችሎት በጽሁፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 187(2) ድንጋጌ የውሳኔው ግልባጭ የተሰጠው ሰው ይግባኙን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ይግባኙን ማቅረብ ያለበት ግልባጩ በተሰጠው በሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ስለመሆኑ አከራካሪ የሆነ የሕግ ጥያቄ አይደለም፡፡ አከራካሪውና በሰበር ችሎቱ ትርጉም ያስፈልገዋል ተብሎ በአመልካች ጥብቅ ክርክር እየቀረበ ያለው የይግባኝ መዝገቡ ግልባጭ ለአመልካች የደረሰው ግንቦት 25 ቀን 2003 ዓ/ም እንጂ ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የይግባኝ መዝገብ ግልባጩ የደረሰው ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም ሆኖ በዚሁ ቀን በተጻፈለት ሸኚ ደብዳቤ መሰረት ይግባኙ ሰኔ 24 ቀን 2003 ዓ/ም መድረሱን አረጋገጠ እንጂ አመልካች እንደሚለው በቃል ክርክር ወቅት ለአመልካች ይግባኙ የተሰጠው ግንቦት 25 ቀን 2003 ዓ/ም ስለመሆኑና ማስረጃም በስር ፍ/ቤት መዝገብ መቅረቡ አለመረጋገጡን በውሳኔው ላይ ገልፆ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲል ደምድሟል፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች መሰረት የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመዘን ሳይሆን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች በሕጉ አግባብ የደረሱበትን ድምዳሜ እንደ እውነት በመቀበል በሕጉ አተረጓጐም ወይም አተገባበር ረገድ መሰረታዊ የሆነ ስህተት ተፈፅሞ ከሆነ ይህንኑ ማረም ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም ለጉዳዩ ቀጥተኛ የሆነ ተፈጻሚነት ያለውን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 187(2) ድንጋጌን በመተርጐም ወይም በመተግበር ረገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፈፀመው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለ ሲሆን በአመልካች በኩል በቅሬታነት የቀረበው ነጥብም የፍሬ ነገር እንጂ የመሰረታዊ ሕግ ስህተትን መመዘኛ የሚያሟላ ባለመሆኑ ልንቀበለው የምንችለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም የአመልካች የይግባኝ ጊዜ አልፏል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በቤኒሻንጉል ጉምዝ ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 03080 መስከረም 10 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች ይግባኝ የቀረበው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 187(2) ድንጋጌ ስር የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከአለፈ በኋላ ነው ተብሎ የይግባኝ መዝገቡ መዘጋቱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት መስከረም 23 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፈትያ አወል - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቢ ህግ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ አመልካች እኔ ባልተገኘሁበትና የቅጣት አስተያየት ባልሰጠሁበት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሰረዝ ያቀረብኩት አቤቱታ ውድቅ ተደርጎብኛል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ከመዝገቡ እንደተረዳነው ተጠሪ አመልካች አዋጅ ቁጥር 104/90 አንቀጽ 20 እና አንቀጽ 18(2) በመተላለፍ የግል ተበዳይን ወደ ኩዬት እልክሻለሁ በማለት ብር 7800 በመቀበል ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ዱባይ የላከቻት በመሆኑ በክሱ የተጠቀሰውን አዋጅና የአዋጁን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ፈፅማለች በማለት ክስ አቅርቦ አመልካች ወንጀሉን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክራለች፡፡

ዐቃቤ ህግ ክሱን የሚያስረዱለትን ምስክሮች አመልካች ባለችበት አሰምቶ አመልካች የሰውና የፅሁፍ የመከላከያ ማስረጃዎችን አሰምታለች፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ሰኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም በነበረው ቀነ ቀጠሮ አመልካች ባለመቅረቧ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በሌለችበት ጉዳዩን የሚቀጥል ስለመሆኑ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሀምሌ 28 ቀን 2003 ዓ.ም አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ወንጀል የፈፀመች ጥፋተኛ ናት በማለት በአስር ወር እስራት እንድትቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በሌለሁበት የተሰጠው ፍርድ ይነሳልኝ (ይሰረዝልኝ) በማለት ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርባ የከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካች ጥያቄ የህግ መሰረት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርባ ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ስኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም በነበረው ቀጠሮና የሥር ፍርድ ቤት ፍርድ በሰጠበት ጊዜ ያልቀረበችው ውጭ አገር ሄዳ ልጇ በመታመሙ ምክንያት ወደኢትዮጵያ የምታደርገው ጉዞ የዘገየ መሆኑን ገልፃ የሥር ፍ/ቤት የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀፅ 4 በሚደነግገው መሰረት ጠበቃዬ እንዳይገኝ በማድረግ የቅጣት አስተያየት ሣይሰጥ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በሌለሁበት የተሰጠ ፍርድ በመሆኑ ሊሰረዝልኝ ሲገባ ጥያቄዬ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ ክርክር የተካሄደውና ማስረጃ የተሰማው አመልካች ባለችበት ነው፡፡ ስለዚህ ፍ/ቤቱ ፍርድ በሰጠበት ጊዜ አመልካች አለመገኘቷ ጉዳዩ በሌለችበት ታይቷል የሚያስብል አይደለም፡፡ ፍርዱ የሚሰረዝበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ያቀረበችውን የፍርድ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የወንጀል ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ወንጀሉን ያልፈፀመች መሆኑን በመግለጽ የተከራከረች መሆኑ፣ አመልካች ባለችበት ተጠሪ ማስረጃዎቹን ያሰማ መሆኑንና አመልካችም የመከላከያ ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃዎቿን ያቀረበች መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም አመልካች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት የተጠሪን ምስክሮች ቃል የመመርመርና የመጠየቅ መብቷ እና የእሷን የመከላከያ ማስረጃ አቅርባ የማሰማት መብቷ ሙሉ በሙሉ በተከበረበት ሁኔታ የአመልካችና የተጠሪ ክርክርና ማስረጃ የተሰማ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 በሚደነግገው መሰረት የከሳሽን ማስረጃ የመመርመርና የመጠየቅ መብቷ የተረጋገጠላትና የእሷንም የሰውና የፅሁፍ የመከላከያ ማስረጃ ያቀረበችው አመልካች የከሳሽንና የተከሳሽን ማስረጃ መርምሮ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ለመስጠት ቀጠሮ በያዘበት ቀን ሣትገኝ መቅረቷ ጉዳዩ በህገመንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው መሰረታዊ መብቷ ባልተሟላበት ሁኔታ ታይቷል ከሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በወንጀል የተከሰሰ ሰው የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ሲሰማ በመገኘት የዐቃቤ ህግን ምስክሮች የመጠየቅና የመመርመር መብቱን በአግባቡ ከተጠቀመና የመከላከያ ምስክሮችንና ማስረጃ ካሰማ በኋላ ቀጠሮውን አክብሮ ፍርድ ቤት ባይቀርብ ዳኞች የከሳሽንና የተከሳሽን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን ፍርድ ከመስጠት የሚገድባቸው አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች ቀጠሮውን አክብራ ባልቀረበችበት ሁኔታ የቅጣት አስተያየት የመስጠት መብቱ ታልፏል በማለት ያቀረበችው ክርክር የህገ መንግስቱን አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 እና የወንጀልኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 4 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ጉዳዩን የሥር ፍ/ቤት ተከሳሽ በሌለበት በሚታይበት ሥርዓት (default procedure) እንዳየው በመቁጠር ያቀረበችው አቤቱታ መጀመሪያውኑ አንድ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት በ(default procedure) ታየ የሚባለው መቼ ነው? ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክስ ስለሚታይበት ሁኔታ የሚደነግጉት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 161 እስከ 164 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት ትርጉምና ተፈፃሚነትና ውጤት እንደዚሁም ተከሳሽ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲሰረዝለት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 197 እስከ 202 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘት ትርጉም ተፈፃሚነትና ውጤት ያላገናዘበና ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት የተጠሪን ማስረጃ የመመርመርና የመጠየቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብቷ በተረጋገጠበትና የሰውና የሰነድ የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብቷን ሙሉ በሙሉ ከተጠቀመች በኋላ ፍ/ቤቱ ፍርድ በሰጠበት ቀን እኔ ስላልተገኘሁ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ ይሰረዝልኝ በማለት ያቀረበችው አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ይህ የአመልካች ጥያቄ የህግ መሰረት የሌለው ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የትግራይ ክልል አጽቢ ወረዳ ዐቃቤ ሕግ

ተጠሪ፡- ተማሪ ሐጎስ ወልደሚካኤል በሌለበት ታይቷል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 42048 በግንቦት 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአጽቢ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ በአንድ የወንጀል ድርጊት ሁለት ጊዜ የመከሰስና የመቀጣት ሕጋዊነትን አስመልክቶ በቀረበ ክርክር ላይ የተሰጠውን የሕግ ትርጉም የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ለአጽቢ ወረዳ ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪ በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 8.00 ሰዓት በማለት በም/እምባ ቀበሌ አረዋ ከተባለው መንደር ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት የገደለ በመሆኑ ሆነ ብሎ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ በወንጀል ክሱ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ሟችን ድንጋይ ወርውሬ መትቻለሁ፡፡ ነገር ግን ሟች ድኖ ሌላ ጊዜ የሞተ በመሆኑ ለሟች መሞት በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰው ምስክርና የፅሑፍ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ሟች በድንጋይ ከተመታ በኋላ ሕክምና ተደርጐለት ድኖ የመስኖ እርሻ ሥራ ሲሰራ የነበረ መሆኑን ያውቁልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ ተጠሪ በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት የገደለ በመሆኑ ጥፋተኛ ነው በማለት ተጠሪ በአሥር ዓመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውቅሮ ምድብ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ከመረመረ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ ነጥብ የለም በማለት የተጠሪን ይግባኝ በወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሰርዞታል፡፡

ተጠሪ አመልካች ከዚህ በፊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 8.00 ሰዓት በም/አምባ ቀበሌ አረዋ ከተባለው መንደር ድንጋይ ወርውሮ በመምታት በግል ተበዳይ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ለወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርቦብኝ ጥፋተኛ ተብዬ በብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም ተቀጥቻለሁ፡፡ አመልካች ተጠሪ በተቀጣሁበት ድርጊት በማንሣት በድጋሚ በወንጀል መከሰሱና የበታች ፍርድ ቤቶችም እኔን ጥፋተኛ ብለው ቅጣት መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች ተጠሪ በወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ይህንን ነጥብ መጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አድርጐ ያላቀረበ ስለሆነ የሰበር መከራከሪያ ሊያደርገው አይገባም፡፡ ተጠሪ ከዚህ በፊት የተከሰሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ነው አሁን የተከሰሰው በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሚች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት ገድሏል ተብሎ ስለሆነ የቀረበው ክስ በፊት ከተከሰሰበት ጋር በአንድ ጉዳይ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 23ና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 በመተርጐም የተከሰሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ በመሆኑ በድጋሚ በዚያው ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔን በመሻር ተጠሪን አሰናብቷታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ለዚህ የሰበር ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ላይ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበትና በድርድር ጥፋተኝነቱን አምኖ ጥፋተኛ ተብሎ ብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የተቀጣው የተሳሳተ ማስረጃ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አቶ ግደይ ገብረየሱስ የካቲት 21 ቀን 2002 በተጠሪ ድንጋይ ተመትተው መጋቢት 30 ቀን 2002 ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ የሟች አቶ ግደይ ገብረየሱስ ህይወት ለሕልፈት የበቃው ተጠሪ በድንጋይ ጭንቅላታቸው ላይ ባደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት መሆኑ በሚኒሊክ ሆስፒታል ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ትክክለኛውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ በወንጀል ሕግ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት ገድሏል በማለት ያቀረብነውን ክስ ተቀብለው የወረዳው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 የሚጥስ ነው በማለት በመሻር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በአድራሻው ተፈልጎ ያልተገኘ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ በወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 193 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካች ያቀረበው የሰበር ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ በወንጀል አንቀጽ 540 የተደነገገውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ድንጋይ ወርውሮ ሟች አቶ ግደይ ገብረየሱስ ጭንቅላታቸውንና አከርካሪያቸውን በመምታት ገድሏል በማለት በድጋሚ መክሰሱንና ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤትና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 5 የሚጥስ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ ስምንት ሰዓት በም/እምባ ቀበሌ አረዋ ከተባለው መንደር ድንጋይ ወርውሮ የግል ተበዳይ አቶ ግደይ ገብረየሱስን የመታቸው መሆኑን ያልካደ ሲሆን ይህ ፍሬ ጉዳይ በዓቃቤ ሕግ ማስረጃም ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ይህንን ድርጊት በፈጸመ በሁለተኛው ቀን ማለትም የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም አመልካች ለወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ በግል ተበዳይ አቶ ግደይ ገብረየሱስ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦበት ተጠሪ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የተቀጣ መሆኑን አመልካች ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክርና ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በግልጽ በማመን አቅርቦታል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በይዘቱ መጀመሪያ ለወንበርታ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቀላል የአካል ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ወንጀል ክስ፣ በዓቃቤ ሕግ የቀረበው የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ የሞት አደጋ ማድረሱ ከመታወቁ በፊት ነው፡፡ አሁን ግን የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ ሞት አደጋ ማድረሱ በመታወቁ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ሆነ ብሎ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ተጠሪን በድጋሚ መክሰሳችን ሕጋዊና ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት መሠረታዊ የወንጀል ሕግ መርህ አድርጎ ከደነገጋቸው ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች አንደኛው አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ በተቀጣበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና መከሰስና መቀጣት የለበትም የሚለው ነው፡፡ ይህ የወንጀል ሕግ መርህ በሕገ መንግስቱ ብቻ ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 ተደንግጓል፡፡ ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 23 "ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነሥርዓት መሰረት ተከስሶ የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም" በማለት ደንግጓል፡፡

የወንጀል ህግ መርሁ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መርህ ሲሆን አገራችን ባጸደቀችው በዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ሥምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 7 " No one shall be liable to be tried or punished again for an offence for which he has already been finally convicted or acquitted in accordance with the law and penal procedure of the country " በሚል መንገድ ደንግጎል፡፡

ሆኖም የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት አተረጓጎም በዕለት ከዕለት የወንጀል ክስ አቀራረብ በሚታዩ ስህተቶች የሚፈጠሩ ችግሮችን ዓቃቤ ሕግ በድጋሚ የወንጀል ክስ በማቅረብ ለማረም በሚፈቅድ ሁኔታ የተቀረጸ ነው ወይስ አይደለም፤ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ድንጋጌ እንዴት መተርጎምና ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል የሚለው ነጥብ አከራካሪ መሆኑን አመልካች ተጠሪ የግል ተበዳይን በድንጋይ ወርውሮ የመታው በግል ተበዳይ ላይ ቀላል የአካል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማጉደል ለማድረስ አስቦ በድርጊቱ ቀላል የአካል ማጉደል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈጽሟል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቦ ተጠሪ በአመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ተከራክሮ ከተቀጣ በኋላ፣ አመልካች ከዚህ በፊት በተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ ሳቀርብ የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ ያስከተለውን ወይም ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በማገናዘብም ሆነ አግባብነት ያለውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በመምረጥና በመጥቀስ የተሳሳትኩ ስለሆነ ተጠሪን ሆነ ብሎ ተራ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት በድጋሚ ክስ እንዳላቀርብ የሚከለክለኝ ሕግ የለም በማለት በዚህ መዝገብ ያቀረበውን ክርክር በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት የሚቻለው አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በድጋሚ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በአንድ ጉዳይ በድጋሚ ያለመከሰስና ያለመቀጣት መብቱን የሚጥስ ነው ብሎ ለመከራከርና የህገ መንግስቱም ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዲሆንለት ለመጠየቅ ሁለት መሠረታዊ መስፈርቶች ሊሟሉ ይገባል፡፡ የመጀመሪያው ተከሣሹ በተመሣሣይ የወንጀል ድርጊት በወንጀል ህግና ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት የተከሰሰ የነበረ መሆኑ ማረጋገጥ ነው፡፡ ሁለተኛው ተከሣሹ ከዚህ በፊት በተከሰሰበት ወንጀል ድርጊት የመጨረሻ በሆነ ፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ ወይም በነፃ የተለቀቀ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ በአንድ ተከሣሽ ላይ የወንጀል ክስ ለማቅረብ ወይም ላለመቅረብ የሚሰጠው ውሣኔና የወንጀል ክስ ለማቅረብ ከወሰነ በኋላ ተከሣሹ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችልበትን የወንጀል ድርጊትና የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በወንጀል የፍትህ ሥርዓቱና በወንጀል የፍርድ ሂደት ውስጥ እጅግ ወሣኝና የመጀመሪያውና መሠረታዊ ውሣኔና ክንውን ነው፡፡ ዐቃቤ ሕግ በአንድ ተከሣሽ ላይ የወንጀል ክስ ከማቅረቡ በፊት ተከሣሹ አንድ ወንጀል በመፈጸም ሃላፊ የሰራው አንድ የወንጀል ድርጊት ያስከተላቸውን ወይም ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ውጤቶች ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ በማገናዘብና አግባብነት ያላቸውን ህግ ድንጋጌዎች በመለየትና በመጠቀስ የወንጀል ክሱን በጥንቃቄ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት፣ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 1፣ ከወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 41፣ አንቀጽ 111 እና አንቀጽ 112 ና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ይህም ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ ሲያቀርብ በህግ የተጣለበትን ግዴታ ሣይወጣ ተከሣሹን በቀላል ወንጀል ኃላፊና ተጠያቂ የሚደርግ የወንጀል ድንጋጌ ጠቅሶ ክስ አቅርቦ ተከሣሹም፣ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የእምነት ክህደት ቃልን ከሰጠና ተከራክሮ በቀረበበት የወንጀል ክስ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ ከተቀጣ ወይም በነፃ ከተለቀቀ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ከዚህ በፊት በተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ ሳቀርብ የተጠሪ ድርጊት በግል ተበዳይ ላይ ያስከተለውን ወይም ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በማገናዘብም ሆነ አግባብነት ያለውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በመምረጥና በመጥቀስ ተሳሳቻለሁ በሚል በተከሣሹ ላይ በድጋሚ የወንጀል ክስ ቢያቀርብ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 በምን መንገድ መተርጉምና ተፈጻሚ መሆን አለባቸው የሚለውን ነጥብ እንድንመረምር ያስገድደናል፡፡

በዚህ መዝገብ አመልካች ያቀረበው የዚህ አይነት ክርክር ሲያጋጥም ከሁሉም በፊት ህገ መንግስታዊ ድንጋጌው ሊያሳካው የሚፈልገውን ግብና ዓላማ መሠረት በማድረግ ክርክሩን በመመርመር መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 23 ትርጉምና የተፈፃሚነት ወሰን አስመልክቶ የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች በህገ መንግስቱ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነቶች በተለይም ከዓለም ዓቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ሥምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 7 ይዘት፣ ትርጉምና የተፈፃሚነት ወሰን ጋር ማገናዘብና መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓለም ዓቀፍ የወንጀል ህግ መርህ መሠረታዊ ዓላማ የአንዲት አገር መንግስት ህግ አስከባሪ አንድ ጊዜ የወንጀል ክስ አቅርቦበትና ተከራክሮ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት የወንጀል ድርጊት በሌላ ጊዜ ተከሳሹን በድጋሚ ለመክሰስና ለማስቀጣት የማይችል መሆኑን በመደንገግ ሰዎችን በአንድ ወንጀል ድርጊት በተደጋጋሚ በሚቀርብ የወንጀል ክስ ስጋት ውስጥ እንዳይወድቁ በመከልከል ለሰዎች የተረጋጋና ሰላማዊ ኑሮ ዋስትና እና ጥበቃ መስጠት ነው፡፡

የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 በአቀራረጹና በይዘቱ በአንድ በኩል ዓቃቤ ህግ ለአንድ የወንጀል ድርጊት በተለያየ ጊዜ የተለያየ የወንጀል ርዕስና የህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ወይም ተመሳሳይ የወንጀል ህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ተከሳሽ ተከስሶ በፍ/ቤት በተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ነፃ ከወጣ ወይም ከተቀጣ በኋላ በድጋሚ በወንጀል እንዳይከሰስና እንዳይጠየቅ የሚከለክል በሌላ አነጋገር የመንግስት የወንጀል ክስ የማቅረብ ሥልጣንን የሚገድብ መሰረታዊ ድንጋጌ ነው፡፡ በሌላ በኩል ድንጋጌው አንድ ተከሳሽ የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል ተብሎ ከወንጀል ክሱ በነፃ በተለቀቀበት ወይም በተቀጣበት ጉዳይ ሌላ የወንጀል ክስና ተጠያቂነት ይመጣብኛል ከሚል ጭንቀት ሥጋት እንዳይሸማቀቅ ህገ መንግስታዊ ዋስትናና ጥበቃ በመስጠት ተከሳሹ በወንጀል ተከስሶ በመጨረሻ ፍርድ በነፃ በተለቀቀበት ወይም በተቀጣበት የወንጀል ድርጊት በድጋሚ የማይከሰስና የማይፈረድበት ስለመሆኑ ህገ መንግስታዊ ዋስትና ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የተረጋጋ ህይወት እንዲኖር የማድረግ ዓላማና ግብ ያለው ነው፡፡

አንድ ሰው በወንጀል ህግና በወንጀል ስነ ስርዓት ተከስሶ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ ተቀጥቷል ወይም በነፃ ተለቋል የሚለው መከራከሪያ በመጀመሪያ የወንጀል ክስ የክስ መቃወሚያ ሆኖ መቅረብ ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 የተደነገገ ሲሆን ፍ/ቤቱ ያቀረበው የክስ መቃወሚያና ማስረጃ በመመርመር ውሳኔ መስጠት ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 131 ተደንግጓል፡፡ ሆኖም አንድ ተከሳሽ በወንጀል ተከስሶ በመጨረሻ ፍርድ በነፃ በተለቀቀበት ወይም በተቀጣበት የወንጀል ድርጊት በድጋሚ ያለመከሰስ ያለመጠየቅ መብት መሰረታዊና ህገ መንግስታዊ መብት በመሆኑ ክርክሩ በሚካሄድበት በማናቸውም ደረጃ ሊነሳ የሚችልና በማስረጃ ተረጋግጦ በተገኘ ጊዜ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ብይን የሚሰጡበት የመከራከሪያ ነጥብ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ይህን ነጥብ በወረዳው ፍ/ቤት ሣይነሳ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰበር መከራከሪያ አድርጎ ማቅረቡና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተጠሪን ክርክር ተቀብሎ መወሰኑ የህግ መሰረት የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ስለሆነም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ አመልካች ያቀረበውን ሁለተኛ ክስ በመቀበልና በማከራከር የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሻሩ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረታዊ ይዘት፣ ዓላማና የተፈፃሚነት ወሰን ያገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 42048 በግንቦት 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 4 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-1. አንተነህ መኮንን

2. መንግስቱ ሞላ

3. ንግስት ከበደ

4. ታከለ መንገሻ

ጠበቃ ቀፀላ ሙላት ቀረበ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ህግ - ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

ጉዳዩ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሙስና ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች እና በሌሎች ሃያ ሰዎች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ አመልካቾችና የስር ሌሎች ሃያ ተከሳሾች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ)፣ (ለ)) እና በተሻሻለው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 214/1974 አንቀጽ 23(1(ሀ)(ለ)) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በስልጣን ያለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል ተብሎ ሲሆን የስር ፍ/ቤት የአቃቤ ህግ ማስረጃዎቹን ከሰማ በኋላ የአሁኑን አመልካቾች መከላከል ሳያስፈልጋቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 መሰረት በነጻ አሰናብቷል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ አመልካቾች ድርጊቱን መፈጸማቸውን አቃቤ ሕግ በማስረጃዎቹ አስረድቶ እያለ ምንም መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ እንዲሰናበቱ ተብሎ ብይን መሰጠቱ ያላግባብ ነው በሚል ምክንያት የስር ፍ/ቤትን ብይን ሽሮ አመልካቾች ሊከላከሉ ይገባል በማለት ጉዳዩን ለስር ፍ/ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው አቃቤ ህግ በማስረጃዎቹ አስረድቷል በሚል ምክንያት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአሁኑ አመልካቾች ከ15% በላይ የዋጋ መረጋጋት ለማድረግ ኤሪክሰን የተባለውን ኩባንያ እንዲያልፍ ጥረት አድርገው ሳይሳካ ቢቀርም የእነሱ ሕገ ወጥ ተግባር በውጭ ግዥ ኮሚቴ ግቡን እንዲመታ ተደርጓል በሚል ጥፋተኛ ናቸው የመባላቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ሲመረምር አስቀድሞ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው አቢይ ነጥብ ሆኖ ያገኘው ጉዳዩ በዚህ ሰበር ችሎት ለመታየት ብቁ ነው ወይ? የሚለው ነው።

ከላይ እንደተመለከተው የአሁኑ አመልካቾች በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ከመሰረተባቸው የሙስና ወንጀል ምንም መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ ተሰናብተው የነበሩ ሲሆን ይኸው የስር ፍ/ቤት የአመልካቾች በነፃ መለቀቅ ብይን ግን ይግባኙን በተመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሽሮ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት የመከላከያ ማስረጃ እንዲያሰሙ የተወሰነ ሲሆን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይኸው የይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው።

በመሰረቱ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዚዳንት ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ባገኙ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ይህንኑ ስህተት ማረም ነው። የአቤቱታው አቀራረብ ሥርዓትም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሰረት ተደንግጓል። በዚህም መሰረት ጉዳዩ ለሰበር እንዲታይለት የሚፈልግ አቤቱታ አቅራቢ ጉዳዩ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚልበትን ምክንያት በማመልከቻው ላይ ዘርዝሮና ጽፎ ማቅረብ ያለበት መሆኑን፣ ከማመልከቻው በተጨማሪ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ቅጅዎችን በማያያዝ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በዘጠና ቀናት ውስጥ ማቅረብ እንደአለበት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22 በዝርዝር ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰማው አስቀድሞ በሶስት የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች የሚሰየሙበት ችሎት ውሳኔው ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለው ብሎ ሲወሰን ነው። በድንጋጌው "የመጨረሻ ውሳኔ" የሚለው ሀረግ የሚያስገነዝበው ለሰበር ችሎቱ የሚቀርቡት ማናቸውም ጉዳዮች የይግባኝ አቀራረብ ስርዓቱን ያጠናቀቁና የመጨረሻ ፍርድ የተሰጣቸው መሆን ያለባቸው መሆኑን ነው። በመሆኑም የመጨረሻ ፍርድ ያላገኘ ጉዳይ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የሚችለበት አግባብ የለም።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች የተከሰሱት በሙስና ወንጀል ሆኖ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነሥርዓት እና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ነው። በዚህ አዋጅ መሰረት የሙስና ክስ የሚመራበት ሥርዓት ተዘርግቷል። አዋጁ ከደነገጋቸው ጉዳዮች አንዱ የይግባኝ መብት ነው። የአዋጁ አንቀጽ 40 የትዕዛዝ ይግባኝን የሚደነግግ ሲሆን ይግባኝ ሊባል የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 36(2) መሰረት በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ እንደሚቻል የሚደነግግ ሲሆን በአንቀጽ 36(2) መሰረት የሚሰጡ ውሳኔዎች ደግሞ በቅድመ ክስ ዝግጅት ሂደት ፍ/ቤቱ የማስረጃ ተቀባይነትን በተመለከተ በሚነሳ ጥያቄ፣ መደበኛው የክስ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ውሳኔ ሊያገኝ በሚገባው በማናቸውም የሕግ ጥያቄ ላይ ስለመሆኑ ድንጋጌው ያሳያል። ይሁን እንጂ አዋጁ አንድ ሰው በሙስና ወንጀል ተከሶ የኮሚሽኑ አቃቤ ሕግ ማስረጃ እንደክሱ ያስረዳ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱ አምኖ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ቢሰጥ በዚህ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ በግልጽ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም። ሆኖም ተጠቃሹ አዋጅ በአንቀጽ 55 ስር የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ፣ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ፣ የወንጀል ህግና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል በሚል ደንግጎ በአዋጁ አንቀጽ 58 ስር የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎችን ለይቶ ሲያስቀምጥ የፀረሙስና የልዩ ስነስርዓትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ. 236/1993 እንደተሻሻለ መሻሩን፣ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው ደንግጓል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ሥርዓት ሕጉ ላይ የተመለከቱት የይግባኝ አቀራረብ ስርዓትን የሚደነግጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑን ሲሆን በዚህ ሕግ አንቀጽ 184 እና 185 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች አንድ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 142(1) መሰረት ብይን ሲሰጥ ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል መሆኑን አያሳዩም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በጉዳዩ ላይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት መከላከያ ማስረጃ ሰምቶ በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካላቸው በስርዓቱ መሰረት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ በማቅረብ ጉዳያቸው ከታየና የመጨረሻ ፍርድ ካገኙ በኋላ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአቃቤ ሕግን ማስረጃ በተመለከተ በሰጠው ውሳኔ ላይ ጭምር በስርዓቱ መሰረት የሰበር አቤቱታ አጠቃልለው ከሚያቀርቡ በስተቀር ከወዲሁ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ ማቅረባቸው ስለሰበር አቤቱታ አቀራረብ የተደነገጉትን ሕጎች ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ አቤቱታቸው ለሰበር ብቁ አይደለም ተብሎ ሊዘጋ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካቾች በዋናው ጉዳይ ላይ ያቀረቡትን ቅሬታ መመርመር ሳያስፈልግ መዝገቡን ጉዳዩ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት ዘግተናል፡፡ አመልካቾች በአቃቤ ማስረጃ ላይ ያላቸውን ሕጋዊ ቅሬታ በስርዓቱ መሰረት በሚያቀርቡት የሰበር አቤቱታ ወደፊት ከማቅረብ ግን ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ጀማል መሐመድ - ጠበቃ አቶ ጥላሁን ምትኩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ህግ - አቶ ታምራት ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 87188 ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ፍርድና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 105387 በሰኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ የእምነት ማጉደል ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ ለራሱ ብልጽግና ለማግኘት አስቦ መስከረም 6 ቀን 2003 ዓ.ም ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል በአራዳ ክ/ከተማ ጥበበ ሆስፒታል ፊት ለፊት ከሚገኘው አይከል የኪራይና የኮንትራት የትራንስፖርት ድርጅት ወደ ጎንደር ለመላክ ከአቶ ገ/መስቀል በርሔ የተረከባቸውን ጠቅላላ ግምታቸው ብር 181,675 (አንድ መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰባ አምስት ብር) አመልካች ግንኙነቱ የሚስከትልበትን ግዴታና ኃላፊነት አጓድሎ ቢገኝ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የሚሉትን ጥያቄዎች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

አመልካች የተጠሪ ምስክር በሆኑት አቶ ተክለብርሃን በርሄ ንብረት የሆነ በአንድ ካርቶን የታሸገ እቃ ወደ ጎንደር እንዲልክለት የተጠሪ ሁለተኛ ምስክር ዳቆን ገብረመስቀል በርሔ መስከረም 6 ቀን 2003 ዓ.ም ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል እቃውን እንደታሸገ እሱ ባለቤት ሲያስረክበው እቃውን ወደ ጎንደር ለማጓጓዝ በመስማማት እቃውን እንደታሸገ ሰራተኞቹ አመልካች ባለበት መረከባቸውንና እቃውን ጎንደር ድረስ ለማጓጓዝ ከላኪው ብር 150 (አንድ መቶ ሃምሳ ብር) የተቀበለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንድ ሰው ዋጋ በመቀበል አንድን እቃ የታሰበበት ሥፍራ ለማድረስ የሚገባው ግዴታ የእቃ ማጓጓዝ ውል እንደሆነ አግባብነት ያላቸውን የህግ፣ ማእቀፎች በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትና ከላይ የተገለጹት ተግባራት የግል ተበዳይና አንደኛ የተጠሪ ምስክር በሆኑት አቶ ተክለብርሃን በርሄና በአመልካች (በአይከል የኪራይና የኮንትራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የትራንስፖርት ድርጅት) መካከል ህጋዊ ውጤት ባለው የእቃ ማንጓዝ ውል የተቋቋመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

አቶ ተክለ ብርሃን በርሄና በአመልካች (በአይከል የኪራይና የኮንትራት የትራስፖርት ድርጅት) መካከል የተቋቋመው ህጋዊ ውጤት ያለው የእቃ ማንጓዝ ውል የእቃው ላኪ ለአንጓዥው መክፈል ያለበትን የአገልግሎት ክፍያ የፈጸሙ ሲሆን አመልካች በውሉ መሰረት በልምድ መሰረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ እቃውን ማንጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ አመልካች በገባው የእቃ ማንጓዝ ውል መሠረት በካርቶን ታሽጎ የተሰጠውን እቃ በሙሉ ጥንቃቄ ማንጓዝ፣ በካርቶን የታሸገውን እቃ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች በገባው የእቃ ማንጓዝ ውል መሰረት በካርቶን ታሽጎ የተሰጠውን አቃ በሙሉ ጥንቃቄ ማንጓዝ፣ በካርቶን የታሸገውን እቃ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን አለመወጣቱ አመልካችን በፍታብሔር ተጠያቂ ከመሆን አልፎ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ በእምነት ማጉደል ወንጀል የሚያስጠይቃቸው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን መሠረታዊ ነጥብ ነው፡፡

ከላይ የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ አቀራረጽ ፣ ዝርዝር ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ የወንጀል ህጉ በንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝርበት ምእራፍ ሁለት በልዩ ሁኔታ በተንቀሳቀቃሽ ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝረው ክፍል አንድ ሥር የተደነገገው የዕምነት ማጉደል ወንጀል መሠረታዊ ባህሪ ይዘትና የሚስከትለው ኃላፊነትን የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ አማርኛ ቅጅ ቃል በቃል ሲነበብ ማንም ሰው ተገቢ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ ፣ የወሰደ ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል ፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 3 የተከሣሹ ወንጀል ሃሣብ ግምት የሚደነግግ ሲሆን ይዘቱም ተከሣሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ማስረዳት ካልቻለ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ማዋል ሃሣብ እንዳዋለው ይቆጠራል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

የእግለዝኛውን ቅጅ ስንመለከት Breach of Trust የሚል ርዕስ ያለው አንቀጽ 675 Whoever with intent to obtain for Himself or to Procure for a third person an unjustifiable enrichment appropriates , or Procures for another, takes or causes to be taken misappropriates uses to his own benefit or that of a third person or disposes of for any similar act in whole or in part a thing or a sum of money which is the Property of another and which has been delivered to him in trust or for a specific purpose, is punishable , according to the circumstances of the case with simple

https://t.me/ethiopianlegalbrief

imprisonment or with rigorous not exceeding five years በማለት በንዑስ አንቀጽ 1 የሚደነግግ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ 3 The intent to obtain for himself or to Procure for third person an unjustifiable enrichment shall be presumed where the criminal is unable upon call, to produce or repay the thing or sum entrusted or at the time when he should have returned it or accounted there for በማለት ይደነግጋል፡፡

አመልካች አይክል የኪራይና የኮንትራት የትራስፖርት ድርጅት ያለው በመሆኑ በገባው የእቃ ማጓጓዝ ውል መሠረት በካርቶን ታሽጎ የተሰጠውን እቃ በሙሉ ጥንቃቄ ማጓጓዝ በካርቶን የታሸገውን ዕቃ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሳ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን የሚወጣው እሱ ራሱ ብቻ በግሉ ዕቃውን በዕምነትና በአደራ ጎንደር ወስዶ በማስረከብ አይደለም፡፡ ዕቃውን በወኪሉ በሰራተኞቹ ወይም ከሌላ ሰው ጋር የዕቃ ማጓጓዝ ውል በመዋዋል ግዴታውን ሊፈጽም የሚችልበት ሁኔታ ሰፊ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ አመልካች በውሉ መሠረት በልምድ መሠረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ እቃውን ማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ባይወጣ በውሉ መሠረት ዕቃውን ባለማስረከቡ አግባብነት ባላቸው የህግ ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ከሚጠየቅ በስተቀር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 1 ተላልፏል ተብሎ በዕምነት ማጉደል ወንጀል ሊጠየቅ የማይችል መሆኑን ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 65 ድንጋጌ ዝርዝር ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 አመልካች በገባው የእቃ ማጓጓዝ ውል መሠረት በካርቶን ታሽጎ የተሰጠውን እቃ በመሉ ጥንቃቄ ማጓጓዝ በካርቶን የታሸገውን ዕቃ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ በዕምነት ማጉደል ወንጀል ተጠያቂ የሚሆን ስለመሆኑ አይደነግግም፡፡ ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ አንድ ለተወሰነ ግልጋሎት የሚለው አገላለጽ የእቃ ማጓጓዝ ውልን ይጨምራል በማለት የተከራከረ ቢሆንም የድንጋጌው ይዘት አንድ ሰው አንድን ንብረት ለአንድ አገልግሎት ለማዋል ኃላፊነት ተረክቦት ንብረቱን ለተባለው አገልግሎት ሳያውል ሲቀር በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቅ መሆኑን የሚመለከት እንጅ በማጓጓዝ ውሉ መሠረት በልምድ መሠረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ እቃውን በማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ያልተወጣ አጓዥ በዕምነት ማጉደል ወንጀል እንዲጠየቅ የድንጋጌው ይዘት መንፈስና ዓላማ የማያሟይ በመሆኑ በዚህ በኩል ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በካርቶን የታሸገውን ዕቃ የተረከበው በንግድ ድርጅቱ በኩል በማጓጓዝ ውሉ መሠረት በልምድ መሠረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ በመድረግ እቃውን ማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድረሶ ለተቀባዩ ለማስረከብ በማሰብ እንደሆነ በተጠሪ ማስረጃ ጭምር ተረጋግጧል፡፡

ማንም ሰው በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቀው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ባለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የተሰጠውን ዋጋ ያለው ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ የወሰደ ያስወሰደ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የአመልካች አድራጎት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገዉ የወንጀል ሃሣብ ግምት የማይሸፈን መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው የህግ የግዙፍ ተግባርና የሞራል ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 23 ተደንግጎል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ከላይ የዘረዘርነው የህግ የሃሣብ ሁኔታዎች አልተሟሉም ፡፡ ይህ ሁኔታ መሟላቱን ሳያረጋግጡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ የሰጡት ውሣኔ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ አቀራረጽ ዝርዝር ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 87188 ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ፍርድና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 105387 በሰኔ 7 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቀጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በገባው የእቃ ማጓጓዝ ውል መሠረት በካርቶን ታሽጐ የተሰጠውን እቃ በሙሉ ጥንቃቄ በማጓጓዝ በካርቶን የታሸገውን ዕቃ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን አለመወጣቱ አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚያስጠይቀው ባለመሆኑ በነጻ ይሰናበታል በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ከቀረበበት ወንጀል ክስ በነጻ ተሰናበተ በመሆኑ ከእስር እንዲለቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 78793

ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ብስራት ወልደመስቀል - ጠበቆች 1. አበበ አሣመረና

2. ሙሉጌታ ወንድመአገኘ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ሕግ - ደሴ መንበር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ጉቦ ማቀባበል ወንጀልን መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ የመሰረተው ክስ አመልካች የሕግ አማካሪና ጠበቃ ሆነው በወንጀል የሚፈለጉ ግለሰብ አቶ አትክልት ዘሪሁን ከወንጀል ተጠያቂነት እንዲያመልጡ ለማድረግ በማሰብ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አቃቤ ሕግ የሆኑትን አቶ ተስፋማርያም ገብረ ትንሳኤ በእጁ ያለውን መዝገብ እንዲዘጋና ለዚህም ብር 5000.00 እንዲቀበላቸው በተደጋጋሚ በመወትወት መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ/ም ከቀኑ በግምት 10፡30 ሰዓት ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ሓያ ሁለት ማዞሪያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኘው ጌታሁን በሻ ህንፃ 3ኛ ፎቅ ባለው ካፌ ውስጥ የህጉና የሙያው ምግባር ከሚፈቅደው ውጪ ለባለስልጣኑ መ/ቤት አቃቤ ህግ አቶ ተስፋማርያም ገ/ትንሳኤ ብር 5000.00 ሲሰጡ እጅ ከፍንጅ በመያዛቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 429 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል የሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም አመልካች ክሱ ደርሷቸውና በግልጽ ችሎት ተነቦላቸው ክሱን እንዲረዱት ካደረገ በኋላ የእምነት ክህደት ቃል ጠይቆ ስለድርጊቱ አፈፃፀም አመልካች የክህደት ቃል በመስጠታቸው አቃቤ ህግ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን በማቅረብ ካሰማ በኋላ አመልካች ድርጊቱን መፈጸማቸው መረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦ የመከላከል መብታቸውን ጠብቆላቸው አመልካች የመከላከያ ምስክሮቻቸውን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ያቀረቧቸው የመከላከያ ምስክሮች ቃል የማይታመን እና እርስ በራሱ የሚጣረስ መሆኑን በመግለጽ ውድቅ ከአደረገው በኋላ አመልካችን በተከሰሱበት የህግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ ቅጣቱን በተመለከተም መጠኑን በቅጣት መመሪያው መሰረት በመመርመር አንድ አመት ከአራት ወር ፅኑ እስራትና በብር ሶስት ሺህ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ስሚ ችሎት ይግባኙን አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ/ም በተፃፈ አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ምክንያቶችን ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አቃቤ ሕግ ክሱን በማስረጃ በበቂ ሁኔታ አላስደገፈም፣ የድርጊቱን አፈፃፀም የሚሸፍነው ድንጋጌ በዐቃቤ ህግ ተጠቅሶ የቀረበ አይደለም፣ የቅጣት አወሳሰኑም የቅጣት መመሪያውን መሰረት ያላደረገ ነው፣ ቅጣቱ እንዲገደብ የቀረበው ጥያቄም የታለፈው ያላግባብ ነው የሚሉትን የቅሬታ ነጥቦች በመዘርዘር ውሳኔው እንዲለወጥ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በፅሁፍ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በዋናነት የቅሬታ ነጥብ ያደረገው የአቃቤ ሕግ ክስ በበቂ ማስረጃ አልተደገፈም፣ የመከላከያ ማስረጃዎች ቃል ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው የሚለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሰበር ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ አተረጓጎም ስህተትን ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የአቃቤ ሕግ ክስን ለማስረዳት የቀረቡት ምስክሮች እንደክሱ አላስረዱም፣ የሚታመኑ አይደሉም፣ የድርጊቱ አፈጻጸም በአግባቡ አልታየም በማለት ያቀረባቸው የቅሬታ ነጥቦች የፍሬ ነገር ክርክሮች በመሆናቸው ይህ ችሎት ሊቀበላቸው የሚገባቸው የክርክር ነጥቦች ባለመሆናቸው አልተቀበልናቸውም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለድርጊቱ ኃላፊነት አለበት ተብሎ የተወሰነው ወንጀሉን መስራቱ ወይም መፈጸሙና ተሰራ ወይም ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በአመልካች መፈጸሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ድርጊቱ ተፈፅሟል ቢባል እንኳ ጉቦ ማቀባበል ወንጀልን የሚያቋቁም አይደለም በማለት በሰበር አቤቱታቸው ቅሬታቸውን ገልጸዋል፡፡ በመሰረቱ አንድ ሰው በወንጀል ሕግ ቁጥር 429 መሰረት ጉቦ ማቀባበል የወንጀል ድርጊት ሊጠየቅ የሚችለው ለራሱ ማናቸውንም አይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ስራን ለሚያከናውን ሰው ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ፣ ዋጋ ያለውን ነገር፣ አገልግሎት ወይም ሌላ አይነት ጥቅም ከሌላ ሰው የተቀበለ እንደሆነ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ አይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ መሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4) መሰረት ሲረጋገጥ ነው፡፡

ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች ወንጀል አድራጊው ገንዘቡን ከሌላ ሰው ተቀብሎ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ አይነት ጉቦ ለማቀባበል በማዋል ድርጊቱን የሚፈጽም መሆኑን የሚያሳዩ መሆናቸውን ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ለባለስልጣኑ መ/ቤት አቃቤ ህግ ጉቦ ለመስጠት ያሉበት ዋናው ምክንያት በወንጀል የተከሰሰውን ሌላውን ሰው ከሕግ ተጠያቂነት ለማዳን ሲሉ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመረጋገጡም በላይ ድርጊቱ የተፈፀመው ሌላውን ሰው ከሕግ ተጠያቂነት ለማዳን ካላቸው ፍላጎት ስለመሆኑ በአቃቤ ሕግ ምስክሮች መነገሩን መሰረት በማድረግ የስር ፍ/ቤት አመልካች ገንዘቡን ለማቀባበል የፈፀሙት ድርጊት መሆኑን በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ በእርግጥም ይኸው ፍሬ ነገር አመልካች ገንዘቡን በወንጀል ከሚፈለገው ሰው ተቀብለው ለባለስልጣኑ አቃቤ ሕግ ለመስጠት ያደረጉት ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ ለድርጊቱ መፈፀም መሰረት የሆነው ዋናው ነገር ሌላውን ሰው ከሕግ ተጠያቂነት ለማዳን ስለመሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች ከዚሁ ሰው ገንዘብ ስለመቀበላቸው ያለመረጋገጡ የጉቦ ማቀባበል ድርጊትን አያቋቁምም ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይሆንም፡፡ ይልቁንም ዋናውና መታየት ያለበት የድርጊት ፈፃሚው ፍላጎት (Motive) ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በወንጀል የሚፈለግ ሰው በሕግ እንዳይጠየቅ ከመነጨ ፍላጎት ሕገወጥና የሚያስቀጣ ድርጊት እያወቁ በራሳቸው ፍላጎት ያደረጉ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አድራጎታቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 429 ድንጋጌ ስር የሚወድቅ መሆኑን ከዚሁ ድንጋጌ እንዲሁም ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23((1) እና (4)) እና 58(1(ሀ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ሆኖ ስለአገኘን በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም በአመልካች የተፈፀመው ድርጊት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 429 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚያሟላ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው አመልካች የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት በቅሬታ ነጥብነት ያቀረቡት ክርክር የቅጣት አወሳሰኑን በተመለከተ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው የቅጣት መነሻው እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት፣ ወይም ከአስር አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና በመቀጮ ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የቅጣት መጠን አንድ አመት ከአራት ወር ፅኑ እስራት እና የብር 3000.00 መቀጮ ነው፡፡

በመሰረቱ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሳዩት ፍ/ቤቱ ቅጣቶቹን የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሉትና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉት የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የአሳቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈጻጸሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍ/ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን ያሳያል፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች በአመልካች ላይ ቅጣት ያስተላለፉት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብለው ከአመዛዘኑና በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ስለመሆኑ ውሳኔው ያሳያል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ለአመልካች ሶስት ምክንያቶችን በቅጣት ማቅለያነት ወስዶና ከቅጣት መመሪያውም ጋር አዛምዶ ቅጣቱን የጣለው መሆኑን ውሳኔው በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን የቅጣት መጠኑ ከድርጊቱ አፈጻጸም አንጻር ሲታይም በወንጀል ሕጉ ስለቅጣት የተቀመጡትን መሰረታዊ የሆኑ የቅጣት አጣጣል መርሆዎችን ያላገናዘበ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት አላገኘንም፡፡ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ቅሬታ (የቅጣት በዛ ክርክር ከሚሆን ውጪ) በቅጣት አወሳሰን ላይ የተጣሰ መርህ ስለመኖሩ የሚያረጋግጥ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ እንዲሁም አመልካች ቅጣቱ ሊገደብ ይገባ ነበር በማለት የሚያቀርቡት ክርክርም የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 190፣ 192፣ እና 194 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ፍ/ቤት በቅጣት አጣጣሉ ጊዜ ግንዘቤ ሊወስድባቸው ስለሚገባቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህጋዊ ምክንያቶች ያለገናዘበ በመሆኑ በዚህ ረገድም መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1.በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 98894 የካቲት 22 እና 28 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 77700 መጋቢት 21 ቀን 2004 ዓ.ም. የጸናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ ቁጥር 195(2(ለ(2)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡

2. ውሳኔው የጸና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለማ/ቤቱ ይገለጽለት ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኖች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፊሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. ታምራት ገለታ - ከጠበቃ በሻዳ ገመቹ ጋር ቀረቡ
2. ደጀኔ ስሜ
3. አዲሱ ሱልጣን } - ቀድሞ ጉዳያቸው አያስቀርብም ተብሏል
4. ኤልሣቤጥ አበራ

ተጠሪ፤ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - አቶ ዮሐንስ ግርማይ ቀረቡ
መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የሰው ግድያና የማታለል ወንጀል ስራ መፈጸሙ በተረጋገጠበት አጥፊ ላይ የወንጀሉ ውጤት ስለመሆናቸው የተረጋገጡት ንብረቶች ለመንግስት ውርስ መሆን የሚችሉ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተነሳው በአሁኑ አመልካቾችና በሌሎች ሁለት ግለሰቦች በጠቅላላው በስድስት ሰዎች ላይ የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተባቸው ክስ መነሻ ነው፡፡

በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ የሆነው ያሁኑ 1ኛ አመልካች ታምራት ገለታን በተመለከተ ተጠሪ ያቀረበባቸው ስድስት ክሶች ሲሆኑ ከእነዚህ ክሶች 1ኛው ክስ፡- አመልካች በ1949 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ)) 522(1ሀ እና ሐ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1999 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በተለያዩ ጊዜአትና ቦታዎች በጥንቆላ ተግባር ሰዎችን ከታመሙበት የበሽታ አይነት አድናለሁ በማለት ከተለያዩ ነገሮች የተቀመመ ውህድ በማጠጣት አቶ ተስፋ ተሾመ (አቶ ተስፋ ወረኢሉ)፣ ኢብራሂም ባርጌቾ፣ የአባቱ ስም ያልታወቀ ፈጠነ የተባለ ግለሰብ፣መሐመድ አረጋ፣ እና መካ አብዲላጊ የተባሉትን ግለሰቦች በግፍ ገድሏል የሚል ሲሆን 2ኛው ክስ ደግሞ በ1996 ዓ.ም. በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ)) እና 539(1ሀ(ሐ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ ላይ በተገለጸው አካኋን ሚች ወሰኔ ፈረደን በግፍ ገድሏል የሚል ነው፡፡3ኛ ክስ ደግሞ በ1949 ዓ.ም. በወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1ሀ)፣27(1) እና 522(1(ሐ)) የተመለከተውን በመተላለፍ ከኤች አይ ቪ ቫይረስ አድናለሁ በማለት ለወ/ሮ ቬነስ ዩሐንስ በጊዜው የምትወስደውን ዘመናዊ መድኃኒት እንድትተው በማድረግ ውህዱን በተደጋጋሚ በመስጠት በከፍተኛ ህመም ወስጥ እንድትወድቅ በማድረግ በውጪ አገር ህክምና የዳኑ በመሆኑ በግፍ ሰው ለመግደል ሞክረዋል የሚል ሲሆን ሌሎች ሶስት ክሶች ደግሞ የማታለል ተግባሮችን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ይኸውም 4ኛው ክስ በ1949 ዓ.ም. በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1ሀ) እና 656(ሀ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከ1991 ዓ.ም. የአባቱ ስም ካልተጠቀሰው መንግስቱ ከተባለው የግል ተበዳይ በጥንቆላው እምነት ስር እንዲወድቅ በማድረግ በማታለል ብር 50,000.00(ሃምሳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሺህ) ፣ከአቶ አረጋ ይማምና ከወ/ሮ ረሒማ ሰኢድን በጥንቆላው ስር እንዲወድቁና ልጃቸውን ወደ ውጪ ለመላክ ሲሉ ቤት እንዲሸጡ በማድረግ ብር 13,000.00 መውሰዳቸውን፣ ከአቶ አብድረልሒሚድ መሀመድና ከወ/ሮ ማረያም አብዱላሂ ደግሞ በጥንቆላው እምነት ስር እንዲወድቁ በማድረግ ብር 20,000.00 መውሰዳቸውን፣ከአቶ ተስፋዬ ታዬ እና ከአቶ ደረሰ ሰሙም በተመሳሳይ ዘዴ ሜሪኩሪ የተባለ ነገር ስለመሆኑ በጥንቆላው እንደአረጋገጡና እንዲገዙ በማድረግ የግል ተበዳዮች በብር 400,000.00 ከገዙት በኋላ ከራሱ ዘንድ እንዲያስቀምጥ በማድረግ መውሰዳቸውን፣ከአቶ አቶ ራሚ ያሲን ደግሞ በማታለል ብር 150,000.00 መውሰዳቸውን፣ ከአቶ እስማኤል ያሲንና ጀማል ከተባሉት ወንድማማቾች ደግሞ በተመሳሳይ የማታለል ዘዴ ብር 60,000.00(ስልሳ ሺኅ) መውሰዳቸውን የሚገልጽ ሲሆን 5ኛ ክስ በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና 696(1(ሐ)) ስር የተመከተውን በመተላለፍ በጥንቆላው ዘዴ በማታለል ወ/ሮ ወላንሳ አብርሃን መኖሪያ ቤታቸውን በስጦታ እንደሰጧቸው በማስመሰል አስፈርመው ቤቱንና ቦታውን መውሰዳቸውን የሚገልጽ ነው፡፡6ኛው ክስ ደግሞ በ1949 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 589(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በጥንቆላው ዘዴ በማስፈራራት የግል ተበዳይ ታየች ማሞ፣ ወ/ሮ ሜላት ሽፈራውን፣ ቬነሱ ዩሐንስን በተለያዩ ጊዜያት የግብረ ስጋ ግንኙነት ከ1ኛ አመልካች ጋር እንዲፈፅሙ አድርገዋል የሚል ነው፡፡አመልካች የተከሰሱባቸውን የወንጀል ድርጊቶችን ክደው በመከራከራቸው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያሏቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ቀርበው ከተሰሙና ከተመረመሩ በኋላ የአመልካች የመከላከል መብታቸው ተጠብቆላቸው ማስረጃዎቻቸው ከተሰሙ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው ሊያስተባብሉ አልቻሉም በሚል ምክንያት አመልካችን በስድስቱም ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ በጠቅላላው በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጡ፣ አመልካች ካፈሯቸው ንብረቶች መካከል በአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ መ/ቤት የምዕራብ ዞን ፅ/ቤት በቁጥር ምዕ/ዞን/12069/200 በቀን 21/11/2001 በጻፈው ደብዳቤ በገለፀው መሰረት የሰሌዳ ቁጥር 2-60978 አ.አ እና 2-49372 አ.አ የሆኑ ተሽከርካሪዎች፣ አቢሲኒያ ባንክ ሐምሌ 27 ቀን 2001 በጻፈው ደብዳቤ በኡራኤል ቅርንጫፍ በአመልካች ስም በቁጠባ ሂሳብ ቁጥር 2151 መኖሩ የተገለጸውን ብር 153,351.72፣በፍቹ ከተማ ቀበሌ 04 ሆቴልና በቀበሌ 03 የሚገኝ ከልማት ባንክ የተገዛ ቦታ በቁጥር 145/ፓ-58/02 በቀን 22/11/2001 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ በአመልካች ስም መኖሩ የተረጋገጠው ንብረት፣ በአዳማ ከተማ የሚገኘው ቤት የፍትሓብሔር ክርክርን ውጤት በጠበቀ መንገድ፣ ብዛቱ 131 ሆኖ 1445 ግራም ወርቅ፣ ብርና ሌሎች አርቲፊሻሎችን ለመንግስት ውርስ እንዲሆኑ በሚል የተወሰነ ሲሆን ለመንግስት ውርስ እንዲሆኑ በተባሉት ንብረቶች የሶስተኛ ወገኖች መብት መጠበቅ ያለበት ስለመሆኑም ተገልፆ ተወስኗል፡፡የአሁኖቹ 2ኛ አመልካች(ደረጀ ስሜ) እና 3ኛ አመልካች (አዲሱ ሱልጣን)ን በተመለከተ ደግሞ በ4ኛው ክስ ላይ የተገለፀውን የማታለል ወንጀል መፈፀማቸው ብቻ ነው የተረጋገጠው ብሎ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692(1) መሠረት እና በተጨማሪም በ1949 ዓ.ም፣ የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 606 ጠቅሶ ጥፋተኛ በማድረግ በ2ኛው አመልካች ላይ የ5 ዓመት ጽኑ እሥራት እና ብር 5000 መቀጮ፣ በ3ኛ አመልካች ላይ የ4 ዓመት ጽኑ እሥራት እና የብር 3000 መቀጮ ሲወሰን በአሁኗ 4ኛ አመልካች (ኤልሣቤጥ አበራ) በሚመለከት ደግሞ በ5ኛው ክስ ላይ የተገለፀውን የማታለል ወንጀል መፈፀሟ ሊረጋገጥባት ችሏል በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692(1) መሠረት ጥፋተኛ በማድረግ የአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት እና የብር 3000 መቀጮ ወሰኖበታል፡፡ሌሎች ተከሳሾች ላይም ተገቢ ነው ያለውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚኅም በኋላ ሁሉም አመልካቾች በተወሰነባቸው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪም በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለዚሁ ፍርድ ቤት ይግባኙን አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የአቃቤ ሕጉን ይግባኝ ውድቅ ሲያደርግ የ1ኛውን አመልካች ይግባኝ በተመለከተ በክሶቹ ላይ ተላልፏል ተብለው የተጠቀሱበት የሕግ አንቀጾች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 113/2/ መሠረት ተለውጠው 1ኛው አመልካች(ታምራት ገለታ) በ1ኛው ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 58/1/ እና 523 መሠረት፣ በ2ኛው ክስ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 58 እና 540 መሠረት እንዲሁም በ3ኛው ክስ በሰው ግድያ ሙከራ ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 58/1/ለ 27/1/ እና 523 መሠረት ጥፋተኛ ሊባል ይገባል በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ድንጋጌዎች ያሻሻለ ሲሆን በሌሎች ድንጋጌዎች ስር የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ግን እንዳለ በማፅናት ቅጣቱን በተመለከተ ተደራራቢ የሆኑ ወንጀሎች መገኘታቸው ሲረጋገጥ ቅጣት ሊወሰን የሚችለውን መርህ መሰረት አድርጎ ከአሰላ በኋላ በጠቅላላው አመልካች በ25(ሃያ አምስት) አመታት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ በመወሰን በንብረት አወራረስ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ደግሞ በውርስ የተገኘ ንብረት እንዳይወረስ ጠቅሶ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል። በ2ኛ አመልካችና (ደረጀ ስሜ) እና በ4ኛ አመልካች(ኤልሣቤጥ አበራ) ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የወሰነው የእሥራት ቅጣት በማሻሻል የእሥራቱ ቅጣት በአንድ ዓመት እንዲቀንስላቸው ተደርጎ ታሥረው የቆዩበት ጊዜ የሚታሰብላቸው ሆኖ እያንዳንዳቸው በአራት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ የወሰነ ሲሆን በ3ኛ አመልካች (አዲሱ ሱልጣን) የተሰጠው ቅጣት ግን እንዳለ እንዲፀና፣ በቀለ ገለታ የተባለው ደግሞ በነፃ እንዲሰናበት ሲል ወስኗል።የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ምክንያት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ አመልካቾች በጥፋተኝነት እና በእስራት ቅጣቱ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በሰበር ችሎቱ አጣሪ ችሎት ተቀባይነት ያጣ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው 1ኛ አመልካችን በተመለከተ ንብረቶቹ እንዲወረሱ የተሰጠው ትእዛዝ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 98 ድንጋጌ አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው። በዚህም መሰረት ለአቃቤ ሕግ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በሰጠው መልስ ንብረቶቹ እንዲወረሱ ትእዛዝ ሊሰጥ የቻለው ከወንጀል ፍሬ የተገኙ መሆናቸው ተረጋግጦ ስለመሆኑና ሕጉም የአስገዳጅነት ባህርይ ያለው በመሆኑ ነው በማለት በንብረቶቹ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲጸና ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው ልዩ ድንጋጌዎች ስለንብረት መወረስ የማይደነግጉ በመሆናቸው ንብረቶቹ ሊወረሱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።እንደመረመረውም የአመልካች ንብረቶቹ እንዲወረሱ በሚል የተሰጠው ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ አመልካች የተከሰሱትና ጥፋተኛ የተባሉት በስድስት ክሶች ሁኖ የአመልካች ጠበቃ እንደጠቀሱት ሁሉም የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸው ልዩ ድንጋጌዎች በቅጣት አወሳሰን ጊዜ የንብረት መወረስ ስለመኖሩ በግልፅ አያስቀምጡም።እንዲህ ከሆነ የአመልካች ንብረቶቹ የሚወረሱበት አግባብ ስለመኖሩ ሕጉ በሌላ መንገድ አስቀምጧል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይ? የሚለው ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው።ይህን ጥያቄ ለመመለስ የአመልካች ንብረቶች የተያዙበትን አግባብ እና የክሶችን ይዘት መመልከቱ ተገቢ ይሆናል።አመልካች የተከሰሱባቸው ድንጋጌዎች በጥንቆላ ዘዴ ሰዎችን በመግደልና በማታለል ንብረታቸውን ወስደዋል፣ያላግባብም በልጽገዋል በሚል ምክንያት ሲሆን ንብረቶቹ የወንጀሉ ፍሬዎች ስለመሆናቸው አቃቤ ሕግ በክሱ በማስረጃ ዝርዝር ገልጾ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በውርስ ከአገኙት እና ራሳቸው በግል ጉልበታቸው፣ ገንዘባቸው እና እውቀታቸው ሊያፈሩ ከሚችሉት በላይ ሀብት አካብተው መገኘታቸውን ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሯል። ይህ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ በይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎትም ተቀባይነት ማግኘቱን ውሳኔው ያስገነዝባል። እንዲህ ከሆነ ንብረቶቹ የወንጀል ፍሬ ናቸው የሚለው የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት ከተሰጠው የመሰረታዊ ህግ ስህተት ማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት የተለየ ድምዳሜ ሊያገበት ወይም ሊለወጥ የሚችል አይደለም። ምክንያቱም የዚህ ችሎት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ስላለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነውና። በመሆኑም ንብረቶቹ የወንጀል ፍሬዎች ስለመሆናቸው ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባለቸው ፍርድ ቤቶች መረጋገጡን እንዳለ የምንቀበለው ጉዳይ ሁኖ ወደ ሕጉ ስንመጣ ደግሞ በሕጉ ላይ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ከአንቀጽ 98 ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ንብረቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲወረስ ሊፈርድ እንደሚችል በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ ስር በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን በአንቀጹ ንኡስ አንቀጽ ሁለት ስር ደግሞ የጥፋተኛነት ውሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ስራ ወንጀለኛው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘው ንብረት እንደሚወረስ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ተደንግጓል። ከአንቀፅ 98(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የንብረት መውረስ ፍርድ ሊሰጥ የሚችለው ወንጀለኛው ንብረቱን ያገኘው የጥፋተኛነት ውሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ስራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ ስለመሆኑ ነው። በመሆኑም የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ድንጋጌ የንብረት መወረስ እንደሚኖር በቅጣት መልክ ባያስቀምጥም ንብረቱ የወንጀሉ ፍሬ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ የወንጀለኛው ንብረት ለመንግስት ውርስ እንዲሆን የግድ መፍረድ ያለበት መሆኑን ሕጉ በግልጽ ያሳያል።

ከዚህ አንጻር ስንመለከተውም የአመልካች ጠበቃ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 98(1) ድንጋጌን ብቻውን ነጥለው በመጥቀስ የሚያቀርቡት ክርክር የአንቀጹን ንኡስ አንቀፅ ሁለት ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ጋር ያገናዘበ ሁኖ አላገኘነውም።ስለሆነም የአመልካች ንብረቶቹ የተገኙት በወንጀል ስራ ስለመሆኑና ንብረቶቹ የወንጀሉ ፍሬ ስለመሆናቸው ተረጋግጦ ለመንግስት ውርስ እንዲሆኑ የተሰጠው ውሳኔ በ1949 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 97"ም" ሆነ በ1996 ዓ/ም ከወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 98(2) ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይ ሕጉን የተከተለ እንጂ የሚነቀፍ ሁኖ አላገኘነውም።

ሌላው ከዚሁ የንብረት መውረስ ውጤት ጋር ተያይዞ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንደተገለፀው ግልጽ ሁኖ መቀመጥ ያለበት ነገር ለመንግስት ውርስ እንዲሆኑ በታዘዙት የአመልካች ንብረቶች የሶስተኛ ወገኖች መብት ካለ የማይነካ መሆኑ ነው። ስለሆነም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው ግልጽ ውሳኔ እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውርስ የተገኙ ንብረቶች ሊወረሱ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ በንብረቶቹ ላይ ሶስተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገኖች ያላቸው መብት እንዳይነካ የሚገልጽ በመሆኑ በዚህ ረገድ መብት አለን የሚሉትን ሶስተኛ ወገኖች የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔም መብታቸውን የማይነካ መሆኑ ሊታወቅ የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ የንብረት ውርስ ውሳኔን ያጸናው የውሳኔ ክፍል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-2) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በወንጀሉ ተግባር ስለማግኘታቸው የተረጋገጡት ንብረቶች ለመንግስት ውርስ እንዲሆኑ መወሰኑ ሕጋዊ ነው ብለናል፡፡ ሆኖም የሶስተኛ ወገኖች መብት ግን የሚነካ ሊሆን አይገባም ብለናል፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/ይ/መ/ቁጥር 48915 ታህሳስ 28 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መጽናቱን እንዲያውቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይጻፍ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 75922
ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1ኛ/ አፈወርቅ ሌሊሳ
2ኛ/ ውብሸት ደምል
} ጉዳይ ተከታታይ በትናትናው ዕለት ቀርበው ውሳኔውን መዝገብ ቤት ይስሙ ተብሏል፡፡

ተጠሪ፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ዐ/ሕግ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካቾች በተከሰሱበት የግድያ ወንጀል ጥፋተኛ የመባላቸውን አግባብነት ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካቾች በ1997 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 539 የተመለከተውን በመተላለፍ አማረ ሙሉጌታ የተባለውን አስቀድሞ ለመግደል በነበራቸው ሀሳብ ሚያዝያ 05 ቀን 2003 ዓ.ም ከሌሊቱ 6፡00 እስከ 7፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በአዋሳ ከተማ በተለያዩ ሆቴሎች በመዘዋወር መጠጥ በማጠጣት በስካር እራሱን እንዲስት ካደረገ በኋላ በታቦር ክ/ከተማ በወጋኔ ዋጮ ቀበሌ ልዩ ስፍራው ማውንት አሌብ ት/ቤት ፊት ለፊት በመውሰድ 2ኛው ተከሳሽ የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ እራሱን እንዳይከላከል ሲያደርግ 1ኛ ተከሳሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በስለት የግራ ደረቱን ከወጋው በኋላ የፈፀሙት ወንጀል እንዳይገለፅ በሞትና ጣር ያለውን ሆስፒታል የወሰዱና ሆስፒታል ግቢ እንደገባ ህይወቱ በማለፉ በፈጸሙት ከባድ የግፍ አገዳደል ወንጀል ተከሰዋል የሚል የወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ ተከሳሽም ክደው በመከራከራቸው፤ የዐ/ህግ ማስረጃ ተሰምቷል፡፡ በዚህም ማስረጃ መሰረት እንዲከላከሉ፤ ተደርጎ እነርሱም በተራቸው፣ የመከላከያ ማስረጃ አቅርበው አሰምተዋል፡፡

ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ሲሰማ የቆየው ፍ/ቤትም በወ/መ/ቁ. 10239 ሐምሌ 28 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከድርጊቱ በፊት እና በኋላ፤ በድርጊቱ አፈፃፀም ጊዜ ተደርገዋል የተባሉትንና በዐ/ህግ ማስረጃ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች በቀጥታ የወንጀሉን ድርጊት ተከሳሾች የፈፀሙት ናቸው በማለት የሚያስረዱ ባይሆንም፤ ድርጊቱ በተከሳሾች የተፈፀመ ለመሆኑ በአካባቢ ማስረጃነታቸው በቂና ለድምዳሜ አጥጋቢ መነሻ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ስለሆነም ድርጊቱን መፈፀማቸውን አረጋግጫለሁ ካለ በኋላ ይሁን እንጂ በዚህ አኳኋን የተረጋገጠው ማስረጃ እንደ ክሱ ዝርዝር ሁኔታ ተከሳሾች አስቀድሞ በነበራቸው ሀሳብ ተነሳስተውና ተዘጋጅተው የፈፀሙት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚችል ሆኖ አልተገኘም ይልቁንም አድራጎታቸው በወ/ሕግ ቁጥር 540 ሥር የሚወድቅ ሆኖ ስለተገኘ በዚሁ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቅጣት አጣጣል ረገድም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት እና የድርጊቱን አፈፃፀም በማገናዘብ እያንዳንዳቸው በ10 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ይህም ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በክልሉ ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት ቀርቦ ውሳኔው የሚነቀፍበት ምክንያት የሌለ መሆኑ ተገልፆ የአሁን ተጠሪዎች በመሰናበታቸው ለዚሁ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የሰበር ቅሬታቸውም ይዘት የእያንዳንዳችንን አድራጎት ለይቶ ያስረዳ የዓይን ምስክር አልቀረበብንም፤ አልተመሰከረብንም ምስክሮች የአካባቢ ናቸው፡፡ ሆነ ተብሎ ለተፈፀመ ድርጊት ተጠያቂነት የለብንም፡፡ ዐ/ሕግ ክሱን አሻሽላለሁ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ እንደጥያቄው አሻሽሎ አለማቅረቡ ሲታወቅ ለጊዜውም ቢሆን ክሱ ተቋርጦ መሰናበት ይገባን ነበር፡፡ በክሱ ላይ ሌሎች ግብረአበሮች እንዳሉ በመገለፁ እነርሱ ህግ ፊት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው ብቻ እኛ ተሸክመን ሚችን ባደረስን መከሰሳችን አግባብነት የለውም ጥፋተኛ ናችሁ ከተባልንም ወጣትነታችንን፣ የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበብን፣ የሚችን ህይወት ከደረሰበት አደጋ ለማትረፍ ያደረግነው ጥረት ሁሉ ሳይመዛዘን የተጣለው ቅጣት የበዛ ነው ሊቀነስልን ይገባል የሚል ነው፡፡

የክልሉ ዐ/ህግ በዚህ ሰበር ጉዳይ በተጠሪነቱ ቀርቦ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤት የተደረገውን ክርክር መሰረት ያላደረገ መሆኑን በመዘርዘር ውሳኔው እንዲፀና ጠይቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል እንደመረመርነውም በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው ወንጀሉን ስለመፈፀሙ መቅረብ የሚገባው የማስረጃ ዓነይት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት የሚችል ድርጊቱን ሲፈፅሙ አያቻለሁ፣ ሰምቻለሁ ወዘተ የሚል ቀጥተኛ ማስረጃ ብቻ ነው የሚል የተደነገገ ህግ በህግ ሥርዓታችን አይገኝም ይልቁንም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 137 እንደተደነገገው በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችለው ስለተያዘው አከራካሪ ነጥብ /ጭብጥ/ ማስረጃው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለጉዳዩ የሚያውቀውን ዝርዝር የምስክርነት ቃል ሁሉ የሚጨምር ነው፡፡

ስለሆነም በዚህ ረገድ አመልካቾች በእኛ ላይ ቀርበው የተደመጡት ምስክሮች የዓይን ምስክሮች ሳይሆኑ የአካባቢ ናቸው፡፡ ስለሆነም ማስረጃው ተቀባይነት የለውም በሚል አንድምታ ያቀረቡት ክርክር ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

ለሟች ሞት መንስኤ የሆነው ተግባር በአመልካቾች የተፈፀመ ስለመሆኑ ማስረጃው አረጋግጧል እስከተባለ ድረስ የትኛውን ተግባር የትኛው ተከሳሽ እንደፈጸመ ለይቶ ያስረዳ ማስረጃ አልቀረበብንም የሚለውም ክርክር ቢሆን የየግላቸው የወንጀል ተሳትፎ ተለይቶ አለመታወቁ በሐሳብም ሆነ በተግባር በመተጋገዝ በግብረአበርነት ከፈፀሙት ድርጊት ነፃ ናቸው ከሚል መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችል አይደለም፡፡ እንዲሁም ዐቃቤ ሕግ ክሱን አሻሽላለሁ በማለት ሳያሻሽል ክርክሩ በቀረበው ክስ ቀጥሎ ከሆነ እንደትዕዛዙ አሻሻሎ ባለማቅረቡ ምክንያት የወንጀሉ ክሱ ለጊዜው ሊዘጋ እንደሚችል ስለዚሁ አግባብነት ባለው የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. አልተመለከተም ክሱ ተሻሽሎ አለመቅረቡ የማሻሻያ ጥያቄው በከሳሽ በዐ/ሕግ ተነስቶ የነበረ ከመሆኑ አንፃር በተከሳሾች ላይ ጉዳት አድርሷል ለማለት አያበቃም ክሱ እንደፍርዱ በትዕዛዝ ባለማሻሻሉ ምክንያት በክርክሩ አካሄድ የመከራከር መብታቸውን እንዴት እንዳጣበበ እና በምን አኳኋን የፍትህ መጓደል እንደደረሰም አላስረዱም፡፡

በሌላ በኩል ስለዋናው ጉዳይ ለሟች ሞት መንስኤ የሆነውን፣ ተግባር ማን ፈፀመው? ለሚለው ዐብይ አከራካሪ ነጥብ ተከሳሾች በዕለቱ ዕለት አብረው ማምሸታቸውን፣ ከሁለተኛው ተከሳሽ ጋር፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እደር አላድርም በሚል ትንቅንቅ ትግል በተከሳሾችና በሟች የነበረ መሆኑ፤ ሟች አላድርም ብሎ ወደ ቤቱ ሲሄድ ከአጭር በ2 እና ሦስት ደቂቃ በሚቆጠር ጊዜ መከተላቸው፤ በዚህ ጊዜ ሟች በሰው እጅ ተጎድቶ ተከሳሾች ሟችን ተሸክመው ወደ ሆስፒታል ባመጡት ጊዜ ሟች ከአንገቱ ሥር ከደረቱ ላይ በስለት ነገር መወጋቱ፤ ተከሳሽም ፊታቸው ሁሉ ሳይቀር ደም በደም የነበረ መሆኑን እና ከምስክሮች የመገረም ቃል አገላለፅ ተነስተው "የሞተው መቼ እሱ ብቻ እኛም ሞተናል አይ የኛ ነገር አበቃ የእኛ ነገር" ተከሳሽ በሚል መናገራቸውን ሁሉ ፍ/ቤቱ እንደ በቂ የግምት መነሻ በመውሰድ ሟችን ለህልፈተ ህይወት ያበቃው በተከሳሾች አድራጎት ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የሚያየው ፍ/ቤት ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማረጋገጥ፤ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በማስረጃነቱ አከራካሪ ነጥብ የሆነውን በማስረዳት ረገድ ያለውን ታማኝነትና ሚዛን የመለካት ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የተከናወኑ የዳኝነት ሥራ/ተግባራት በመሆኑ ጉዳዩ የህግ ጥያቄን የሚያስነሳ ሆኖ አይገኝም ምናልባትም የዚህ ማስረጃ አግባብነት ታማኝነትና ሚዛን ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 አንፃር ተገናዝቦ መታየቱንና አለመታየቱን በሚመለከት የህግ ጥያቄን ያስነሳል እንኳ ቢባል በዚህ ህግ በተቀመጠው የማስረጃ ሚዛን መለኪያ አኳያ ከላይ የተመለከተው የዐ/ህግ ማስረጃ ይታይ እንኳ ቢባል በህጉ መሰረት ከተቀመጠው ሚዛን የወረደ ስለሆነ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በብይን በነፃ መሰናበት ነበረባቸው የሚለውን የህግ ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም፡፡

ተከሳሾች በተራቸው እንከላከላለን በማለት ያቀረቡት የመከላከያ ማስረጃም ቢሆን በዕለቱ ዕለት በሟችና በ1ኛ ተከሳሽ ተፈጥሮ የነበረውን ቂም የሚያመለክትና በድርጊቱ አፈፃፀም ተጠያቂዎች ተከሳሾች እንጂ ሌላ ወገን አይደለም የሚለውን በማመላከት የዐ/ሕግ ማስረጃ የሚያጠናክር እንጂ በወ/መ/ሐ/ሥ/ሥ/ቁ/ 149 እንደተመለከተው ከወንጀሉ ተጠያቂነት ነፃ ሊያደርጋቸው የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በቅሬታቸው እንደገለፁት እና ከመደበኛ የሰበር ክርክር አቀራረብ ሥርዓት ውጭ በአቤቱታ እንደገለፁት ተከሳሾች በተከሰሱበት የወንጀል ጉዳይ ሌሎች ግብረአበሮች የነበሩ ስለመሆኑ ክርክሩ የሚያስረዳ ከመሆኑም በላይ እነዚህ አሁን አመልካቾች የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ለመፈፀማቸው የወንጀል ህግ ሥርዓት የሚጠየቀውን ሚዛን በጠበቀ ማስረጃ የተረጋገጠባቸው መሆኑ እስከታወቀ ድረስ በዚህ አኳኋን ያቀረቡት የመከራከሪያ ነጥብ ከኃላፊነት ነፃ ሊያደርጋቸው የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ቅጣትን በሚመለከት የቀረበውም ክርክር በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ እንደገና ሊታረም የሚችልበትን የህግ ጥያቄ የሚያስነሳ አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በሥር ፍ/ቤቶች በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

በዚህ ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃውን ጠብቆ በሰበር መ/ቁ 55532 በ28/2/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ አፅንተናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 75980

ሐምሌ 2 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረ ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ስማቸው ልንገርህ ዓለሙ በማ/ቤት ስለሆነ አልቀረበም

ተጠሪ፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የደቡብ ክልል ቅርንጫፍ

ዐቃቤ ሕግ አቶ ደስታ ንጉሴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርተው ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የኮንትሮባንድ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀፅ 3 እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91 ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ፣ ዋና ወንጀል አድራጊ በመሆን መስከረም 2 ቀን 2004 ዓ.ም በሀዋሳ ከተማ በታቦር ክፍለ ከተማ አላሙራ ከሚባለው ሥፍራ ከመካነ መቃብሩ ወደ ሪፈራል ሆስፒታል በሚያስሄደው መንገድ ላይ በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ያሸከረክረው በነበረው የመለያ ቁጥር 3-39349/አ.አ/ በሆነው አይሱዙ መኪና የታክስ መጠኑ ብር 220,939.98 /ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ከዘጠና ስምንት ሣንቲም / የሆነ 11,508 /አስራ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሥምንት ኪሎ ግራም/ የሆነ ህንድ አገር የተሠራ የጉምሩክ ቀረጥና ሥርዓት ያልተፈፀመበት ስኳር እንዲሁም በሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ ተከሣሽ የነበረው በሚያሽከረክረው የመለያ ቁጥሩ 3-32136 አ.አ በሆነ አይሱዙ መኪና የታክስ መጠኑ 10,297.80 /አንድ መቶ አስር ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከሰማኒያ ሣንቲም / የሆነ መጠኑ 5753 /አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሣ ሶስት ኪሎ ግራም/ የሆነ ህንድ አገር የተሠራ የጉምሩክ ቀረጥና ሥርዓት ያልተፈፀመበት ስኳር አስጭኖ ሲያጓጉዝ የፌዴራል ፖሊስ በደረሰው ጥቆማ መሠረት የተያዘ በመሆኑ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅሟል በማለት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች በክሱ በተገለፀው ጊዜና ሥፍራ አመልካች ሶስተኛው ተከሣሽ የነበረው የመለያ ቁጥሩ 3-32136 /አ.አ/ ከጋቤና ውስጥ ከሶስተኛው ተከሣሽ ጋር ቁጭ ብሎ ሁለተኛው ተከሣሽ በሚያሽከረክረው የመለያ ቁጥሩ 3-39349 በሆነው አይሱዙ መኪናና ሶስተኛው ተከሣሽ በሚያሽከረክረው አይዙሱ መኪና መጠኑ በዐቃቤ ሕግ ክስ የተገለፀው የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ህንድ አገር የተሠራ ስኳር እንደጫኑ በቁጥጥር ሥር ያዋሉ መሆኑንና አመልካች በመጀመሪያ ሲያዝ ተሳፋሪ ነኝ ያላቸው ቢሆንም በማግስቱ ህጋዊ ነጋዴ መሆኑንና ህጋዊና ቀረጥ የከፈለ መሆኑን የገለፀላቸው መሆኑን ስኳሩን ሻሸመኔ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እንዲራገፍ ማድረጋቸውን በዝርዝር መሥክረዋል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች ሹፌሮች መሆናቸውንና እያንዳንዳቸው በብር 1700 /አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር/ አመልካች የሚከፍላቸው መሆኑን ተስማምተው ዕቃውን እንደጫኑ ወዲያውኑ እንደተያዙ የተናገሩ መሆናቸውን መሥክረዋል፡፡ ተጠሪ ዕቃዎቹ ገቢ የሆኑበትን ሰነድ ፣ የተከሣሾች መቃወሚያና መንጃ ፈቃድ እንደዚሁም ተከሣሾች /አመልካች ጭምር/ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27 ንዑስ አንቀፅ 2 ለፖሊስ የሰጡትን የተከሣሽነት ቃል ለሥር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ያቀረበ መሆኑን ከውሣኔው ተረድተናል፡፡

አመልካች ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት መስከረም 2 ቀን 2004 ዓ.ም የመከላከያ ምስክሮችን ምሣ ጋብዟቸው ከበሉ በኋላ አመልካች ስልክ ተደውሎለት አናግሮ እንደተመለሰና ሀዋሳ ዱቄት የሚጭን ተመላሽ መኪና ስላገኘሁ ይቅርታ አድርጉልኝ ብሎ ወጥቶ እንደሄዱ የመሠከሩ ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሽ የነበሩት በምስክርነት ቀርበው የመከላከያ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመከላከያ ምስክሮችም አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም እያንዳንዳቸው ብር 1700/አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር/ ሂሣብ አመልካች ሊከፍላቸው ተስማምተው ዕቃውን አዲስ አበባ ቃሊቲ ማሰልጠኛ ፊት ለፊት የጫኑ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ በሁለቱ አይሱዙ መኪኖች የተጫነውን ስኳር ይዘው የተገኙ ሰዎች የስኳር ኮርፖሬሽን ደንበኞች እንዳልሆኑና ስኳርም እንዳልሸጠላቸው በፅሑፍ የተረጋገጠ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው በማስፈር አመልካች የጉምሩክ ሥርዓት ያልተፈፀመበት መጠኑ በወንጀል ክሱ የተገለፀውን በህንድ አገር የተሠራ ስኳር በባለሀብትነት ጭኖ ሲያጓጉዝ በመገኘቱ ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች የጉምሩክ ቀረጥ ያልተፈፀመበት ዕቃ በመጫን የትራንስፖርት አገልግሎት የሰጡ መሆናቸው ተረጋግጦባቸዋል፡፡ የመከላከያ ማስረጃቸው የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የሚያጠናክር እንጅ የሚያስተባብል አይደለም በማለት አመልካችና በሥር ሁለተኛ ና ሶስተኛ ተከሣሽ የሆኑት ሰዎች በወንጀል ህግ አንቀፅ 32/3/ እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91/2/ የተደነገገውን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው ብሎ አመልካች በሥምንት ዓመት ፅኑ እስራትና በብር 71,032/ሰባ አንድ ሺህ ሰላሣ ሁለት ብር /እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/1/ መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተያዘው ስኳር የእኔ ሣይሆን መሀመድ የተባለ በሀዋሳ ከተማ ውስጥ መጋዘን ያለው ነጋዴ መሆኑን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27/2/ መሠረት የተከሣሽነት ቃሌን ሰጥቻለሁ፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ወዲያውኑ እንደተያዝኩ እኔ ተጓዥ መሆኔን ዕቃው የእኔ አለመሆኑን እንደተናገርኩ ከመሰከሩ በኋላ በማግስቱ ዕቃው የእኔ ነው ብሏል በማለት የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመቀበል ጥፋተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መባሌ ተገቢ አይደለም፡፡ ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች የሰጡት ቃል በእኔ ላይ በማስረጃነት ሊያዝብኝ አይገባም ፡፡ የቅጣት ውሣኔውም ተገቢ አይደለም በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ አመልካች ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦበታል፡፡ አመልካች የክርክር ስልቱን በመለዋወጥ የሥር ፍርድ ቤት ያለበቂ ማስረጃ ፍርድ እንደተሰጠው ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም በማለት ሚያዚያ 3 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ግንቦት 7 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ በተጠሪ የተያዘው ስኳር የጉምሩክ ቀረጥ ያልተፈፀመበት መሆኑን አላስረዳም፡፡ በተቃራኒው ማስረጃው ስኳሩ የጉምሩክ ሥርዓት የተፈፀመበት መሆኑን ያሳያል፡፡ ፖሊሶች ቃሌ በማስረጃነት እንደሚቀርብብኝ ሣያስጠነቅቁኝ ዕቃው የእኔ ነው ብሏል በማለት የሰጡትን የምስክርነት ቃል መሠረት በማድረግ ጥፋተኛ መባሌ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መረምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በወንጀል ህግ አንቀፅ 32 እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91 ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ የተወሰነው የቅጣት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት የሥር ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ክሱ በገለፀው ጊዜ ማለትም መስከረም 2 ቀን 2004 ዓ.ም አመልካች በሀዋሳ ከተማ አላሙራ ከተባለው ሥፍራ በመካነ መቃብሩ ወደ ሪፈራል ሆስፒታል በሚያስሄደው መንገድ ሞተር አጥፍተው ተከታትለው ቆመው በነበሩት ሁለተኛው ተከሣሽ በሚያሽከረክረው የመለያ ቁጥር 3-39349 አ.አ በሆነ መኪናና ሶስተኛ ተከሣሽ ያሽከረክረው በነበረው የመለያ ቁጥሩ 3-32136 አ.አ በሆነ አይሱዙ መኪና ጋቤና ውስጥ ቁጭ ብሎ በቁጥጥር ሥር ያዋለ መሆኑን ፣ መኪኖቹ የጉምሩክ ቀረጥ ያልተፈፀመበት ህንድ ሀገር የተሠራ ስኳር ጭነው መገኘታቸውን አመልካችንና ሌሎቹን ተከሣሾች በቁጥጥር ሥር ለማዋል የሄዱት የፌዴራል ፖሊስ አባላት መኪናው ላይ ያለው ዕቃ ባለሀብት ማን እንደሆነ ሲጠይቋቸው ለእያንዳንዳቸው ብር 1700 ለመክፈል ተስማምቶ አመልካች ያስጫነው ዕቃ መሆኑን ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች የገለፁ መሆኑን አመልካች በወቅቱ ተሣፋሪ ነኝ ያለ መሆኑንና በማግስቱ ዕቃው ቀረጥ የተከፈለበት የእኔ ንብረት ነው ያለ መሆኑን ይህንን የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ አመልካች ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ ያላስተባበለና ማስረጃው በሰነድ ማስረጃዎችና ሌሎቹ ተከሣሾች ያቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች ቃል የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የሚያጠናክር ይዘት ያለው መሆኑን በውሣኔው በግልፅ አስፍሯል፡፡

ዕቃውን አመልካችንና ዕቃውን የጫኑትን ሹፌሮች በቁጥጥር ሥር ያዋሉት የተጠሪ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል በሁለት አይሱዙ መኪና ተጭኖ የነበረው የጉምሩክ ቀረጥ ያልተከፈለበት ህንድ አገር የተሠራ ስኳር በመኪናዎቹ እንደተጫነ በቁጥጥር ሥር ከማዋላቸው በፊት ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ አመልካችን ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች በመኪናዎቹ ላይ ከተጫነው ስኳር ጋር በቁጥጥር ሥር ሲያውሏቸው የነበረውን ሁኔታና አመልካችን ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሽ በቁጥጥር ሥር አውለው ወደ ካንኘ ሲወስዷቸው ስለነበረው ሁኔታ /circumstance/ እና ከዚህ ሂደት አመልካች ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች ያሳዩት የነበረውን የባህሪ ሁኔታ ይፈፅሙት የነበሩትን ድርጊትና በቃላት ሲገልፁ ስለነበረው ሀሣብ አስረድተው የተመለሱ ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር የተጠሪ ምስክሮች በወቅቱ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ /circumstantial evidence/ ሰጥተው የተመለሱ ናቸው፡፡ በአገራችን የህግ ሥርዓት ምስክሩ ስለአጠቃላይ ሁኔታዎች በአይኑ የታዘበውን በጆሮው የሰማውንና የሚያውቀውን ፍሬ ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊስመሰክር እንደሚችልና የምስክሩም ቃል ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 137 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካችና የተጠሪ ምስክሮች አመልካች የጉምሩክ ቀረጥ ያልተፈፀመበት ስኳር ጭነው በማከታተል ቆመው በቁጥጥር ሥር ከዋሉት መኪናዎች ውስጥ በአንደኛው ማለትም ከሶስተኛ ተከሣሽ ጋር ሶስተኛው ተከሣሽ ሲያሽከረክረው ከነበረው የመለያ ቁጥሩ 3-32136/አ.አ/ ከሆነው አይሱዙ መኪና ውስጥ ቁጭ ብሎ እንዳገኙት ፣ ወዲያውኑ ሲጠይቁት ተጓዥ ነኝ በማለት መናገሩንና በቁጥጥር ሥር ውሎ ከሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች ጋር ወደ ካንኝ እንደተወሰደ ካንኝ ታስሮ አድሮ በማግስቱ ዕቃው የእኔ ነው ህጋዊ የጉምሩክ ሥርዓት ተፈፅሞበታል በማለት መግለፁን ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሾች ለእያንዳንዳቸው ብር 1700 /አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር/ ለመክፈል ተስማምቶ ዕቃውን ያስጫናቸው አመልካች መሆኑን በቁጥጥር ሥር በሚውሉበት ጊዜ እንደገለፀላቸው በማረጋገጥ የሰጡት ምስክርነት ቃል የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ / circumstantial evidence / እንደሆነና ይህም አመልካች በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27/2/ ከሚሰጠው የተከሣሽነት ቃል የተለየ የማስረጃ አይነት መሆኑን ሣያገናዝብ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ምክንያቱም የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ በባህሪውና በይዘቱ አንድ ክስተት ከመፈጠሩ በፊት ፣ ክስተቱ ሲፈጠር ወይም ድርጊቱ ሲፈፀምና ክስተቱ ከተፈጠረ ወይም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ ያሉትን የአካባቢ ሁኔታዎች በማሣየትና በመግለፅ ዳኞች በጭብጥነት ስለተያዘው አከራካሪ ጉዳይ ሎጅካል ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ የሚያደርግ የማስረጃ አይነት መሆኑን “ circumstantial evidences is an evidence that tend to prove the matter by providing events or circumstances from which the occurrence of the matter at issue can be reasonably inferred circumstantial evidence not bearing directly the fact in dispute but make clear various attendant circumstances from which the judge might infer the occurrence of the fact in dispute ” በሚል መንገድ በህግ መዝገj ቃላትና በሌሎች አገሮች የማስረጃ ህግ ድንጋጌዎች የተገለፀውንና የእኛም አገር የህግ ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 137 ንዑስ አንቀፅ 1 ህጋዊ ተቀባይነት ያለው የማስረጃ አይነት መሆኑን በግልፅ የደነገገው መሆኑን ግንዛቤ ወስጥ በሚያስገባ ሁኔታ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪ ምስክሮች የሰጡትን የአካባቢ ሁኔታ የሚያስረዳ የምስክርነት ቃል መቀበሉ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ሆኖ ስላላገኘነው አልተቀበልነውም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪ ምስክሮች አመልካች አንደኛና ሁለተኛ ምስክር በቁጥጥር ሥር ከመዋላቸው በፊት ፣ በቁጥጥር ሥር ሲውሉና በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ ፣ አመልካችና ተከሣሾች ስለአሳዩት ባህሪ ፣ ስለፈፀሙት ድርጊትና በቃላት ስለገለፁት ሃሣብ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ተጠሪ ካቀረባቸው ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎችና በአመልካችና በሁለተኛና ሶስተኛ መከላከያ ምስክሮች ከሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር በማገናዘብና በመመርመርና በመመዘን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91 ንዑስ አንቀፅ 2 በመተላለፍ የኮንትሮባንድ ወንጀል የፈፀመ ነው በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማፅናቱ የበታች ፍርድ ቤቶች በህግ የተሰጣቸውን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን በመጠቀም ተገቢ ነው ከሚሉት መደምደሚያ ላይ የደረሱ መሆኑን የሚያሣይና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት የህግ ድንጋጌ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እስራትና ዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጮ የሚያስቀጣ መሆኑ በግልፅ ይደነግጋል፡፡ አመልካች በሁለት አይዙሁ መኪና ጭኖ ከተገኘው የስኳር መጠን ፣ ከአመልካች የወንጀል አፈፃፀም አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በስምንት ዓመት ፅኑ እስራትና በብር 71,032 /ሰባ አንድ ሺህ ሰላሣ ሁለት ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ የሰጡት ውሣኔ አመልካችን ቅር እንደሚለው መሠረታዊ የቅጣት አወሳሰን መርሆችን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 12/ለ-2 መሠረት ሊፀና ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1.የደቡብ ብሔር ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2 /ለ/ 2 መሠረት ፀንቷል፡፡

2. በአመልካች ላይ የተወሰነው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 77989

ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ለይኩን ብርሃኑ - ከጠበቃ አቶ ፍቅሬ ሞያ ጋር ቀረቡ

2. አቶ ምትኩ አብሹ - ጠበቃ ታደሰና መቶ

አለቃ ሽፈራው አመኑ ቀረቡ

3. አቶ ጌታሁን አስማረ - ጠበቃ አቶ ውብሸት ክብሩ ቀረቡ

4. አቶ ቸርነት ዋጋሪ - ጠበቃ አቶ ኃ/ማርያም ኃይሉ ቀረቡ

5. አቶ እንዳለ ቱኒ - ጠበቃ አቶ ውብሸት ክብሩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐ/ህግ - አቶ አድማሱ አለማየሁ ቀረቡ

አንደኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 77586 ፣ ሁለተኛ አመልካች በዚህ መዝገብ ማለትም በመዝገብ ቁጥር 77989 ፣ ሶስተኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 78427 ፣ አራተኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 77675 እና አምስተኛው አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 78428 ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በዚህ መዝገብ አጣምረን በማየትና በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች ከላይ ቁጥራቸው በተገለፁት የሰበር መዛግብት የፌዴራል የመጀመሪያው ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማፅናቱ መሰረታዊ ህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት በተናጠል ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቾች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በአመልካቾችና በዚህ ክርክር ተሳታፊ ባልሆኑ ሌሎች አምስት ተከሳሾች ላይ መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም ዕፎ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ፣ አመልካቾች በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና አንቀጽ 703

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከተውን በመተላለፍ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) የስራ አመራር በመሆን በተለያየ ደረጃ በሚሰሩበት ወቅት እንደ አውሮፖዊያን አቆጣጠር ከኦክቶበር 2009 ዓ.ም እና ዲሴንበር 2009 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የውጭ ምንዛሬ አጠቃቀምና አፈቃቀድ ጉድለት በመፈፀም በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) ላይ ጉዳት አድርሰዋል በማለት የቀረበው የወንጀል ክስ ሲሆን ዝርዝሩም ሲታይ የሚከተለው ይዘት ያለው ነው፡፡

1. በሥር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆኑት አንደኛው አመልካች አቶ ለይኩን ብርሃኑ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) ፕሬዚዳንት ሆኖ ሲሰራ በለገሀር ቅርንጫፍ ፣ በአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ፣ በሀብተ ጊዮርጊስ ቅርንጫፍና ፣ በመርካቶ ቅርንጫፍ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያ ከውጭ ምንዛሬ አፈቃቀድ ፣ አሰጣጥ ፣ አጠቃቀምና አጠያየቅ ጋር በተያያዘ የተፈፀመው ወንጀሎች እያወቀ በአዋጅ ቁጥር 592/2000 ዓ.ም በሚጥስ ሁኔታ የውጭ ምንዛሬ አፈቃቀድና አጠቃቀም እንዲካሄድ በማድረግና የግል ባንኮች መያዝ ፣ የሚገባቸውን የውጭ ምንዛሬ መጠን በተመለከተ ከብሔራዊ ባንክ የወጣውን መመሪያ በመተላለፍ የውጭ ምንዛሬ በመያዝ ፣ ማውጣት የሚገባውን የአሰራር ሥርዓትና መመሪያ ባለማውጣት የወጡ ፣ መመሪያዎች ሲጣሱ የእርምት እርምጃ ባለመወሰዱ ፣ የውጭ ምንዛሬ ደንበኞች ተራ ቅደም ተከተል ሊጣስና በቅድሚያ የውጭ ምንዛሬ ሊሰጣቸው የማይገቡ ግለሰቦች እያወቀ ባለመስተካከሉና የባንኩ ቋሚ ሰራተኞች የውጭ ምንዛሬ ሲወስዱ እያየ እርምጃ ባለመውሰድ የስራ አመራር ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

2. በስር ሁለተኛ ተከሳሽ የሆነው ሁለተኛ አመልካች አቶ ምትኩ አቦሽ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) ምክትል ፕሬዚዳንት የባንኩ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ ፣ በለገሀር ቅርንጫፍ ፣ በአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ፣ በሀብተጊዮርጊስ ቅርንጫፍ እና በመርካቶ ቅርንጫፎች በውጭ ምንዛሬ አፈቃቀድና አሰጣጥ የተፈፀሙ ጉድለቶችን ባለመስተካከሉና በባንኩ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ ያለ ኮሚቴው ፈቃድ በግል ትዕዛዝ የውጭ ምንዛሬ ግዥ ፈቃድ በመስጠት ፣ የውጭ ምንዛሬ ያለቅደም ተከተል ለሰዎች እንዲፈቀድላቸው ሲደረግ ባለመስተካከሉ ባንኩ በብሔራዊ ባንክ እንዲይዝ ከተፈቀደለት የውጭ ምንዛሬ መጠን በላይ 28,974,000 (ሃያ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ይዞ በመገኘቱና ከዚህ ውስጥ 14,473,000 ዶላር/ብር ለብሔራዊ ባንክ ሪፖርት ማይደረግና ማይመዘገብ እንዲያዝ ያደረገ በመሆኑ የውጭ ምንዛሬ ሊፈቀድላቸው የሚገባቸውን የባንኩን ደንበኞች በመከልከል የውጭ ምንዛሬ ሊፈቀድላቸው በማይገባቸው ሰዎች የውጭ ምንዛሬ በመስጠት በስራ አመራር ሂደት ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

3. በስር ፍ/ቤት አምስተኛ ተከሳሽ የሆነው ሶስተኛው አልካች አቶ ጌታሁን አላመረ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) የአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ ከባንኩ መመሪያ ውጭ የውጭ ምንዛሬ ለግሉ በመፍቀድ ለግል ጥቅሙ በማዋሉና ለባንኩ ደንበኞች በበላይ የስራ ኃላፊዎች የተፈቀደውን የውጭ ምንዛሬ ለሌሎች ላልተፈቀደላቸው ሰዎች በመስጠት በስራ አመራር ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

4.በስር ዘጠኛ ተከሳሽ የሆነው አራተኛው ተከሳሽ አቶ ቸርነት ዋጋሪ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ መርካቶ ቅርንጫፍ የውጭ ንግድ ክፍል ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ የውጭ ምንዛሬ ኮሚቴ ያልተፈቀደላቸውን ደንበኞች በማስተናገድ ፣ የደንበኞችን የምዝገባ ቅደም ተከተል ማይጠበቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለምዝገባ ተራቸው ሌሎች ግለሰቦች የውጭ ምንዛሬ እንዲያገኙ በማድረግ በስራ አመራር ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

5. በስር ፍ/ቤት ስድስተኛ ተከሳሽ የሆነው አምስተኛው አመልካች አቶ እንዳለ ቱዶ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ የአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ የውጭ ንግድ ክፍል ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ የውጭ ምንዛሬ የተፈቀደላቸውን የባንኩን ደንበኞች በመከልከል ላልተፈቀደላቸው ግለሰቦች የውጭ ምንዛሬ በመስጠት የስራ አመራር ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈፅሟል ፣ የሚል ክርክር ይዘት ያለው የወንጀል ክስ አቅርቦባቸዋል፡፡

ተጠሪ የቀረበው የወንጀል ክስ ኮፒ ለአመልካቾች ደርሷቸው የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት የአመልካቾችን የመጀመሪያ ደረጃ ክስ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎባቸዋል፡፡ አመልካቾች የወንጀሉን ድርጊት አልፈፀምንም ጥፋተኞች አይደለንም በማለት ክደው በመከራከራቸው ፣ ተጠሪ ዘጠኝ ምስክሮች በማቅረብ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ያደረገ ሲሆን የወንጀሉን ድርጊት ያስረዳሉ የሚላቸውን የፅሁፍ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ለምስክርነት አቅርቦ ካሰማቸው ምስክሮች ውስጥ ሁለቱ የአዋሽ ባንክ አክሲዮን ማህበር የአስተዳደር ቦርድ አባላት ፣ ሶስቱ ደግሞ በባንኩ ውስጥ ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ካላቸው አስር ባለሀብቶች የተወከሉ መሆናቸውን ገልጸው ባንኩ በውጭ ምንዛሬ አያያዝ ፣ አፈቃቀድና አጠቃቀም ችግር ያለበት ስለመሆኑ የደረሳቸውን መረጃ ለማጣራት ኮሚቴ የተቋቋመ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ምስክሮች ከቦርድ አባላትና ከባለመብቶች የተወጣጡ ኮሚቴዎች በአንድነት በባንኩ ሥራ አመራር በኩል የተፈፀሙ ተግባራት ሲያጣሩ ፣ ባንኩ በብሔራዊ ባንክ እንዲያገዘ የተፈቀደለት የውጭ ምንዛሬ የካፒታሉ 15% ብቻ መሆን ሲገባው ከዚያ በላይ ዶላር ይዞ መገኘቱንና በዚህ ምክንያት በብሔራዊ ባንክ ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) የተቀጣ መሆኑን፣ ሁለተኛ አመልካች ያለውጭ ምንዛሬ ኮሚቴ ፈቃድ በግሉ ለግለሰቦች ያለተራቸው የውጭ ምንዛሬ እንዲሰጣቸው ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ፣ በአዋሽ ባንክ ለገሀር ፣ አዲስ ከተማ ፣ ሀብተጊዮርጊስ ድልድይና በመርካቶ ቅርናጫፍ የውጭ ምንዛሬ የአፈቃቀድና አጠቃቀም ከፍተኛ ችግር የነበረበት ፣ ተመዝጋቢው ተራ የሚጠብቁ ሰዎች የውጭ ምንዛሬ ሳያገኙ ያልተመዘገቡና የባንኩ ደንበኛ ላልሆኑ ሰዎች የውጭ ምንዛሬ የተሰጠ መሆኑን ፣ አንደኛ አመልካች ይህንን ችግር በማስተካከል ማድረግ የሚገባውን ተግባር ያለመፈፀሙንና ለችግሩ መከሰት አመልካቾች የነበራቸውን ሚና በመዘርዘር መሥክረዋል፡፡ ምስክሮቹ አንደኛ አመልካች ተገቢውን የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱና ማውጣት የሚገባውን መመሪያ ባለመወጣቱ ሁለተኛው አመልካች በኃላፊነት የተሰጠውን ተግባር በአግባቡ ካለማውጣቱ በተጨማሪ ዳንኤል ለተባለ የባንኩ ሰራተኛ ለእሱ ፀሐፊ የውጭ ምንዛሬ እንዲወስዱ ፈቅዶ የተገኘ መሆኑን ባደረጉት ማጣራት እንደተገነዘቡ የመሰከሩ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ዘጠነኛ ምስክር የባንኩ ኢንስፔክሽን መምሪያ ኃላፊ ሲሆኑ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸውን ስድስተኛ ሰባተኛና ስምንተኛ ምስክሮች የባንኩ ኢንስፔክሽን ሰራተኞች መሆናቸውን ገልጸው፣ ተጠሪ በወንጀል ክሱ በገለጸው ጊዜ ውስጥ በባንኩ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መመሪያና በለገሀር ፣ አዲስ ከተማ ፣ ሀብተጊዮርጊስ ድልድይና መርካቶ ቅርንጫፍ የውጭ ምንዛሬ አፈቃቀድና አጠቃቀም በማጣራት የፅሑፍ ሪፖርት እንዳቀረቡ ገልፀው አንደኛው አመልካች በውጭ ምንዛሬ በመፍቀድ ያልተሳተፉ መሆኑንና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ሲያጋጥም ሁለተኛ አመልካች ሰብሳቢ በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛና ሶስተኛ ተከሣሽ የነበሩትና በዚህ ክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሳታፊ ያልሆኑት የኮሚቴው አባል ሆነው የውጪ ምንዛሬ ኮሚቴ መቋቋሙን ፣ ነገር ግን በመምሪያውና በአራቱ የባንኩ ቅርንጫፎች የውጭ ምንዛሬ አጠቃቀምና አፈቃቀድ ከፍተኛ ችግር የነበረበት መሆኑን እንዳረጋገጡ ምስክሮች ለሥር ፍርድ ቤት ከሰጡት የምስክርነት ቃል ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምስክሮቹ በመምሪያውና በአራቱ ቅርንጫፎች ያለውጭ ምንዛሬ ኮሚቴ ውሣኔ ለሁለተኛ አመልካች ለሶስተኛ አመልካች ለአራተኛ አመልካችና ለአምስተኛ አመልካች የውጭ ምንዛሬ ሰጥተው ያገኙ መሆኑን ፣ ሁለተኛው አመልካች ያለውጭ ምንዛሪ ኮሚቴ ውሣኔ በግሉ በርካታ የውጪ ምንዛሬ መፍቀጃ ቅፆች ላይ ፈርሞ ያገኙት መሆኑና መምሪያውና አራቱ ቅርንጫፎች የውጭ ምንዛሬ በማግኘት ተመዝግበው ተራ ለሚጠብቁ ደንበኞች የውጪ ምንዛሬ ሣይሰጡ ተመዝግበው ተራ ላልያዙና የባንኩ ደንበኛ ያልሆኑ ሰዎችን በማስቀደም የውጭ ምንዛሬ የሰጡ መሆኑን እንዳረጋገጡ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

ተጠሪ የወንጀል ክሱን ለማስረዳት ባቀረበው የሰነድ ማስረጃ ሁለተኛው አመልካች የውጪ ምንዛሬ ካሚቴ ውሣኔ ሳይሰጥበት በግሉ 9,280,755 /ዘጠኝ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ አምስት /የአሜሪካን ዶላር 2,938,535 ዩሮ /አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰላሣ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሰላሣ አምስት / ዮሮ እና 50,060/ ሃምሣ ሺህ ስልሣ / የእንግሊዝ ፖውንድ የፈቀደ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑንና የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ለገሀር ቅርንጫፍ ከፈቀደው 6,196,760.88 /ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ስልሣ/ የአሜሪካን ዶላር ውስጥ 2,125,725.04 /ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ አምስት ከዜሮ አራት/ የአሜሪካን ዶላር አለመከፈሉን ሶስተኛ አመልካች ሥራ አስኪያጅ አምስተኛው አመልካች የውጭ ንግድ ክፍል ኃላፊ ሆነው ሲሰሩበት የነበረው የአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ለሶስተኛ አመልካች የንግድ ድርጅት የፈቀደው 426,792/አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ሁለት/ የአሜሪካን ዶላር አለመከፈሉን አራተኛው አመልካች የውጪ ንግድ ክፍል ኃላፊ በመሆን ሲሰራበት የነበረው መርካቶ ቅርንጫፍ ከፈቀደው የውጪ ምንዛሬ 299,760 /ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሥልሣ የአሜሪካን ዶላር / አለመከፈሉን በአጠቃላይ በዚህ ሂደት ብር 3,154,328 /ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሣ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ስምንት የአሜሪካን ዶላር በህገ ወጥ መንገድ በውጭ ምንዛሬ ተሰጥቶ ለባንኩ ያልተመለሰ መሆኑን እንደሚያረጋግጥ በዚህ ወንጀል በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆኑትና ተከሣሾች ስማቸው ከተራ ቁጥር 2 እስከ ተራ ቁጥር 5 የተገለፀው አመልካቾች ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የሰነድ ማስረጃው እንደሚጠቁም ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አመልካቾች በተጠሪ የወንጀል ክስ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት የፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ተጠሪ ያቀረበ መሆኑን በመግለፅ አመልካቾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሥር ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 142 መሠረት ብይን ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን መሠረት አንደኛ አመልካች በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ያልፈፀሙና በኃላፊነትም ልጠየቅ የማይገባኝ መሆኑን ያስረዱልኛል ያሏቸውን አራት የመከላከያ ምስክሮች አቅርበው ያስመሰከሩ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ እንደዚሁም አንደኛ አመልካች የሰነድ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃነት እንዳቀረቡ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው ውስጥ አስፍሮታል፡፡ ሁለተኛው አመልካች በበኩሉ በነበረው ኃላፊነት የፈፀማቸው ተግባራት የሥራ አመራር ጉድለት አለመሆናቸውን የሚያስረዱ ሶስት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ ያሰማ መሆኑንና የሰነድ ማስረጃ የቀረበ መሆኑን ሶስተኛና አምስተኛው አመልካች በጋራ አምስት የመከላከያ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃ በመከላከያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃነት ያቀረቡ መሆኑን ፣ አራተኛው አመልካች አራት የመከላከያ ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃ በመከላከያ ማስረጃነት ያቀረቡ መሆኑን ከሥር ፍርድ ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካቾችን ማስረጃ ከመረመረና ከመዘነ በኋላ አንደኛ አመልካች በባንኩ ኃላፊና የሥራ መሪ ሆነው እያለ ሥራዎችን ለሁለተኛ አመልካች በውክልና ከሰጡ በኋላ የተለያዩ ችግሮች እየተፈጠረ ስለመሆኑ ጥቆማ የደረሳቸው መሆኑንና ሀሜትና አሉባልታ ናቸው እያለ በማለት በዝምታ በማለፍ በባንኩ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያና በአራቱ ቅርንጫፎች በተከሰተው ብልሹ አሠራር ምክንያት በባንኩ ላይ ለደረሰው ጉዳት በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት የመቆጣጠር የመከታተልና የባንኩን ሥራ የመምራት ኃላፊነት ባለመወጣቱ ተጠሪ /ዐቃቤ ሕግ / በወንጀል ክሱ የተገለፀውን የህግ ድንጋጌ በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 10,000/አስር ሺህ ብር / መቀጮ እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች ተጠሪ በወንጀል ክሱ የዘረዘራቸው የውጭ ምንዛሬ አጠቃቀምና አፈቃቀድ ችግሮችን የፈፀሙ መሆኑን በሰውና በፅሑፍ ማስረጃ ያረጋገጠበት በመሆኑና ሁለተኛው አመልካች ያቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ይህንን የማያስተባበል መሆኑን ገልፆ ሁለተኛ አመልካች ተጠሪ የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌ በመተላለፍ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኛ ናቸው በማለት በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 10,000/አስር ሺህ ብር መቀጮ/ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ሶስተኛ አመልካችና አምስተኛው አመልካቾች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው በማለት በሁለት ዓመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራትና በብር 15,000/አስራ አምስት ሺህ ብር/ እንዲቀጡ የወሰነ ሲሆን አምስተኛው አመልካች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ነው ብሎ በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 10,000/አስር ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተናጠል በተለያዩ መዝገቦች አቅርበዋል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካቾች የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግለፅ አንደኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 77586 የሰበር አቤቱታ አቅርበው ተጠሪ በሰበር አቤቱታው መልስ የሰጠበት ሲሆን ሁለተኛው አመልካች በዚህ መዝገብ ላቀረቡት የሰበር አቤቱታ ሶስተኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 78427 ላቀረበው የሰበር አቤቱታ ፣ አራተኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 77675 ላቀረበው የሰበር አቤቱታና አምስተኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 78428 ላቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በዚህ መዝገብ በማጠቃለል ግንቦት 28 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካቾች በየግላቸው የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች በተለያዩ መዝገቦች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ይዘት ተመልክተናል፡፡ አመልካቾች ሆነ ብለንና አስበን የአዋሽ ኢንተርናችናል ባንክ /አ.ማ/ ላይ ጉዳት ለማድረስ የፈፀመነው የወንጀል ድርጊት ስለመኖሩ ተጠሪ በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር ላይ የደረሰ ጉዳት መሆኑ በተጠሪ ማስረጃ አልተረጋገጠም አንድ ሰው በወንጀል የሚጠየቀው የግዙፍ ተግባር የሞራልና የህግ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ መሆኑን በወንጀል ህጉ አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ የተደነገገ ከመሆኑም በላይ ይህ ሰበር ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተመሣሣይ ጉዳይ ከዚህ በፊት አስገደጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል። አመልካቾች የፈፀምነው ግዙፍ የወንጀል ድርጊት ያለ መሆኑና የወንጀል ሃሣብ / ሞራላዊ ሁኔታ መኖር ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው። እንደዚሁም ተጠሪ እኛ ፈፅምነው በተባለው ድርጊትና በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ / አ.ማ/ ላይ ደርሷል በሚለው ጉዳት መካከል የድርጊትና የውጤት ግንኙነት መኖርን አላስረዳም። አመልካቾች በተጠሪ የቀረበውን ክስና ማስረጃ በመከላከያ ማስረጃችን አስተባብለን እያለን ጥፋተኛ መባላችን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው። የሥር ፍርድ ቤት ከአመልካቾች ጋር ተመሣሣይ ወንጀል ድርጊት ፈፅማችኋል ተብለው የጥፋተኝነት ውሣኔ የተሰጠባቸው ተከሣሾች ላይ ያስተላለፈውን የቅጣት ውሣኔ ሲገድብ በእኛ ላይ የወሰነው የቅጣት ውሣኔ አለመገደቡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን የሚል ይዘት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል። ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች ሆነ ብለው ጊዚያዊና ሠው ሠራሽ የውጪ ምንዛሬ እጥረት እንዲፈጠር ድርጊቱን መፈፀማቸው በሰውና በፅሑፍ ማስረጃ ተረጋግጧል። አንደኛ አመልካችም ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄ ባለማድረግና የባንኩ የበላይ አመራር በመሆናቸው መፈፀም የሚገባቸውን ተግባር ያልፈፀሙ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል። አመልካቾች በባንኩ ላይ የደረሱትን ጉዳት በገንዘብ በሚተመን መንገድ ብቻ ሣይሆን በባንኩ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጉዳት ያደረሱ መሆኑን አረጋግጠናል። ስለሆነም አመልካቾች በግዙፍ ተግባርና የሞራል ሁኔታ አልተሟላም በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ነው። አመልካቾች ያቀረቡት የሰውና የጽሑፍ መከላከያ ማስረጃ በተጠሪ በኩል የቀረበውን የወንጀል ክስና በተጠሪ ማስረጃ የተረጋገጠውን የወንጀል ድርጊት ለማስተባበል የማይችል መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል። አመልካቾች ክስ ከመቅረቡ በፊት ዐቃቤ ህግ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 42(1)ሀ መዝጋቱን እንደመከላከያ ያቀረቡት ቢሆንም ማስረጃ ሲገኝ ዐቃቤ ሕግ ክስ ለማቅረብ የሚከለክለው የህግ ድንጋጌ ባለመኖሩ ክስ ማቅረባችንና የሥር ፍርድ ቤትም ማስረጃችንን መዝኖ የጥፋተኝነት ውሣኔ መስጠቱ በአግባብ ነው። አመልካቾች ሌሎች ተከሣሾች በገደብ መለቀቃቸውን የሰበር መከራከሪያ ሃሣብ አድርገው ማቅረባቸው የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ያነሷቸውን የመከራከሪያ ሃሣቦች የሚያጠናክር የመልስ መልስ በተናጠል አቅርበዋል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካቾችና ተጠሪ በፅሑፍ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማጽናቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል። ይህንን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በማስረጃ እንዳረጋገጣቸውና አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃ እንዳላስተባበሏቸው በመግለፅ በውሣኔቸው ያስፈሯቸውን ፍሬ ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ነው።

1. ተጠሪ በወንጀል ክስ ማመልከቻው በገለፀው ጊዜ ውስጥ ማለትም እንደአውሮፖውያን አቆጣጠር ከኦክቶበር 2009 ዓ.ም እስከ ዲሴንበር 2009 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በአገር ደረጃ የውጭ ምንዛሬ እጥረት የነበረ መሆን ተረጋግጧል። ይህም በመሆኑ ባንኮች በቅደም ተከተል የውጭ ምንዛሬ ለደንበኞቻቸው የሚፈቅዱበትና የሚለቁበት ሥርዓት በመዘርጋት በቅደም ተከተል የማስተዳደር ኃላፊነት የነበረባቸው ቢሆንም የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) የዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያና የለገሀር ቅርንጫፍ ፣ የመርካቶ ቅርንጫፍ ፣ የአዲስ ከተማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅርንጫፍና የሀብተ ጊዮርጊስ ቅርንጫፍ በውጭ ምንዛሬ ለተመዘገቡ እና ተራ ለሚጠብቁ ሰዎች ሣይሰጡ ላልተመዘገቡትና የውጭ ምንዛሬ ሊፈቀድላቸው ለማይገቡ ሰዎች ጭምር የሰጡ መሆኑን ፣ በዚህም ባንኩ ለደንበኞቹ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ችግር የተፈጠረና መልካም ስምና ዝናው የተጐዳ የባንኩም ደንበኞች የሸሹት ስለመሆኑ ከባንኩ አስተዳደር ቦርድ እና በባንኩ ከፍተኛ አክሲዮን ድርሻ ካላቸው አስር ባለሃብቶች ተወክለው ሁኔታውን ያጣሩ የተጠሪ ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የባንኩ ኢንስፔክሽን ክፍል ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ በገለፀው ጊዜ ውስጥ በውጭ ምንዛሬ አጠቃቀም ፣ ፈቃድ ላይ በባንኩ ዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያና በአራቱ ቅርንጫፎች ከፍተኛ ችግር የፈፀሙና በህገ ወጥ መንገድ የውጭ ምንዛሪ ሊሰጣቸው የማይገባቸው ሰዎች የተሰጠ መሆኑን እንዳረጋገጡ፣

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲይዝ ከፈቀደለት በላይ ከብሔራዊ ባንክ እውቅና ውጭ የውጭ ምንዛሬ ይዞ መገኘቱና በዚህም ጥፋቱ በብሔራዊ ባንክ ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) የተቀጣ መሆኑ ፣ ሁለተኛው አመልካች ዳንኤል ለተባለ የባንኩ ሠራተኛና ለፀሐፊው ከህግ ውጭ የውጭ ምንዛሬ የሰጠ መሆኑ ፣ ሶስተኛ አመልካች ለግል የንግድ ድርጅት ለሌሎች ሰዎች የተፈቀደ የውጭ ምንዛሬ ወጭ አድርጐ የሰጠ መሆኑና በዚህ ድርጊት አምስተኛው አመልካች ሙሉ ተከፋይና ተባባሪ የነበረ መሆኑን ፣ አራተኛው አመልካች ለውጭ ምንዛሪ ላልተመዘገቡና ተራ ላልያዙ ሰዎች በቅድሚያ እንዲያገኙ ያደረገ መሆኑን እና የውጭ ምንዛሬ ሊፈቀድላቸው ለማይገባቸው ሰዎች የሰጠ መሆኑ ፣ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) በለገሀር ቅርንጫፍ በመርካቶ ቅርንጫፍ ፣ በሀብተጊዮርጊስ ድልድይ ቅርንጫፍና በአዲስ ከተማ መጠኑ በርካታ የሆነ የውጭ ምንዛሬ ወጭ አድርጎ ከሰጠ በኋላ የሒሳብ ምርመራ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ ያልተከፈለው መሆኑ ፣ ከላይ በዝርዝር በታዩት የሥር አመራር ጉድለት ለደረሱ ጉዳቶች አመልካቾች ኃላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ በተጠሪ በኩል በቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች መረጋገጡን በአመልካቾች በኩል የቀረበው የፅሑፍ የመከላከያ ማስረጃ ከላይ የተዘረዘሩት የሥራ አመራር ጉድለቶች በአመልካቾች ያልተፈፀሙ መሆናቸውን የማያሣዩ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡

2. በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ (አ.ማ) የዓለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያና በአራቱ ቅርንጫፎች የውጭ ምንዛሬ አያያዝ ፤ አጠቃቀምና አፈቃቀድ ላይ ተፈፅመዋል የተባለ ችግሮች ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ናቸው ካለን በማስከተል የሚነሣው ጥያቄ እነዚህ ችግሮች በወንጀል ህጉ በተዘረዘረው ግዙፍ ተግባር ውስጥ የሚካተቱና አመልካቾችን በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርጉ ናቸው ወይስ አይደለም ? የሚለው ነው፡፡ ይህንን ጭብጥ ለመመለስ በመጀመሪያ በሌላ ሰው ጥቅም የሥራ አመራር ላይ የተፈፀመ ጉዳት የማድረስ ወንጀል መሠረታዊ ይዘት የሚዘረዝረውን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

በሌላ ሰው ጥቅም የሥር አመራር ላይ የተፈፀመ ጉዳት የሚል ርእስ ያለው የወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 ሶስት የተለያዩ ይህንን ወንጀል የሚያቋቁሙ ሁኔታዎችን የሚደነግግ ሲሆን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 1 " ማንም ሰው በሕግ ወይም በውል ግዴታ የሌላን ሰው ንብረት ጥቅም እንዲጠብቅ ወይም ሥራውን እንዲመራ በሕግ ወይም በውል ግዴታ አደራ ተቀብሎ በተሰጠው ሃላፊነት አላግባብ በመገልገል ወይም የተጣለበትን ግዴታ ባለመፈፀም በሚጠብቀው ንብረት ጥቅም ላይ ወይም ለሚሠራበት ድርጅት በሚፈጽመው አገልግሎት ላይ አስቦ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ " በወንጀል ኃላፊ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

702 ንዑስ አንቀጽ 2 " ድርጊቱ በችልተኝነት የተፈፀመ እንደሆነ " በወንጀል ኃላፊ እንደሚሆን የሚደነግግ ሲሆን፣ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 3 " ተከሣሹ ወንጀሉን የፈፀመው የንብረት ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ እንደሆነ " ለወንጀል ኃላፊ እንደሚሆን ደንግጓል፡፡ በመሠረታዊነት አንድ ሰው በሌላው ሰው ጥቅም ሥራ አመራር ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በወንጀሉ ኃላፊና ተጠያቂ የሚሆነው ከላይ ከዘረዘርናቸው ሶስት ሁኔታዎች አንደኛውን ወይም ሁለቱን ወይም ሁሉንም ድርጊቶች ፈጽሞ ሲገኝ እንደሆነ የወንጀሉን መሠረታዊ ይዘትና ባህሪ ከሚዘረዝረው የወንጀል ህግ አንቀጽ 702 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ በአመልካቾች ላይ የወንጀል ክስ ሲያቀርብ የጠቀሰው እና አመልካቾች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 703 በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 702 ከተደነገጉት 3 ድንጋጌዎች አንደኛውን በመተላለፍ ወንጀል የተፈፀመ መሆኑ ሲረጋገጥ ወንጀሉ ከብዶ የሚታይበትንና በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችልበትን ሁኔታ የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የወንጀል ህግ አንቀጽ 702 የተዘረዘሩት ወንጀሎች የማክበጃ ሁኔታዎችን የሚዘረዝር ድንጋጌ ሲሆን አንደኛው የማክበጃ ምክንያት አመልካቾች በተከሰሱበትና ጥፋተኛ ሆነው በተገኙበት በወንጀል ህጉ 703 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተደነገገው ነው፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 703 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ ቃል በቃል ሲነበብ ፣ "ወንጀሉ የተፈፀመው በተሰጠው ሥልጣን ሥራውን በማከናወን ላይ በሚገኝ ፣ ወይም በተሰይ ታማኝነት በተሰጠው ሞግዚት ፣ ጠበቃ ፣ ውል አዋዋይ ፣ የባንክ ሠራተኛ ፣ የንብረት አስተዳዳሪ ወይም የሒሳብ አጣሪ ወይም ሹመት ሥልጣን ባገኘ ወይም የተሰየ እምነት በተጣለበት ማንኛውም ሌላ ሰው የሆነ እንደሆነ ወይም የዚህ ዓይነት ተመሣሣይ ኃላፊነት በተሰጠው በማንኛውም ሰው እንደሆነ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ሃምሣ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጫ ይቀጣል " የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

የወንጀል ህግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የሚከብደው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውንና ሆነ ተብሎ የተሠራውን ወንጀል ወይም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 702 ንኡስ አንቀጽ 3 ለራስ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ታስቦ የተሰራው ወይም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተዘረዘረውን ወንጀል ብቻ የሚያካብድ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ድንጋጌው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀውንና በችልተኝነት የተሰራን ወንጀል የሚያከብድ በአጠቃላይ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 702 የተዘረዘሩትን ሦስት የወንጀል ድርጊት አፈፃፀሞች የሚያከብድ ድንጋጌ መሆኑ " ከባድ ሁኔታ " ከሚለው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 703 ርዕስና ከድንጋጌው አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ካየነው አንደኛ አመልካች የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ/አ.ማ/ ፕሬዝዳንት ሆነው ሲሰሩ በኃላፊነታቸው ማድረግ የሚገባቸውንና ጥንቃቄ ባለማድረግ፣ መውሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች በወቅቱ ባለመውሰድ በባንኩ ሥራ አመራር ላይ ጉዳት ያደረሱ በመሆናቸው ፣ ይህንን ተግባር ሆነ ብለው አልፈፀሙትም ቢባል እንኳን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ በችልተኝነት የተፈፀመን ወንጀል አክብዶ የሚደነግገው በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች 1ኛ አመልካች በተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 የተዘረዘውን የግዙፍ ተግባር ፣ የሃሳብና የሕግ ሁኔታውን የሚያሟላና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛ አመልካች የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ የአለም አቀፍ ባንኪንግ መምሪያ ኃላፊና የባንኩ የውጭ ምንዛሬ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ ሲሰራ ያለኮሚቴው ፈቃድ በግሉ የውጭ ምንዛሬ በመፍቀድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኃላፊነቱን አላግባብ የተገለገለ መሆኑና ዳንኤል የተባለ የባንኩ ሠራተኛና በወቅቱ ፀሐፊው የነበረችውን ሴት ለመጥቀም በማሰብ አላግባብ የውጭ ምንዛሬ የፈቀደላቸው በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተዘረዘረውን ግዙፍ የወንጀል ተግባር የፈፀመና የወንጀል ሞራላዊ ሁኔታ የተሟላ በመሆኑ ይህንን ወንጀል በሚያከብደው በወንጀል ሕግ ቁጥር 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሶስተኛና አምስተኛ አመልካቾች የሶስተኛው አመልካች የግል ጥቅም ለማግኘት ሲል ለራሱ የንግድ ድርጅት ለሌሎች ሰዎች የተፈቀደ የውጭ ምንዛሬ ለሶስተኛው አመልካች የንግድ ድርጅት እንዲወስድ ማድረጋቸው ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑና ሌሎች ግድፈቶችን መፈፀማቸው ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚሸፈን በመሆኑና ይህንን ወንጀል በሚያከብደው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ጥፋተኛ መባላቸው በአግባቡ መሆኑ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡ አራተኛው አመልካች በመርካቶ ቅርንጫፍ የውጭ ንግድ ክፍል ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ በውጭ ምንዛሬ አጠቃቀምና አፈቃቀድ ላይ ከፍተኛ ችግር ከፈጠሩት የባንኩ የሥራ ኃላፊዎች አንደኛው እንደነበር የተረጋገጠበት በመሆኑና ወንጀሉን ሆነ ብዬ አልሰራሁትም ቢልም አድራጎቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 702 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚሸፈን በመሆኑ ይህንን ወንጀል በሚያከብደው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአጠቃላይ ስንመለከተው አመልካቾች በተለያየ የሀሳብ ሁኔታ ወንጀሉን የፈፀሙ መሆኑንና ከተለያየ የወንጀል ሃሳብ የተፈፀሙትን አድራጉቶች አጠቃልሎ በሚይዘውና በሚያከበደው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ጥፋተኛ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ የሕጉን ድንጋጌ ይዘትና መሠረታዊ ባህሪ ያገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው፡፡

3. የቅጣት ውሣኔውን በተመለከተ አመልካቾች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና እስከ 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ በሚደርስ መቀጮ የሚያስቀጣ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት በአመልካቾች በኩል ያቀረቡትን የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችና በተጠሪ በኩል የቀረበውን የቅጣት አስተያየት በመመርመርና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት በማድረግ የቅጣት ውሣኔውን የሰጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት የቅጣት ውሣኔ የቅጣት አወሳሰን መርሆችን መሠረት ያደረገ ፣ የአመልካቾችን የወንጀል አፈፃፀምና ግላዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካቾች የሥር ፍርድ ቤት በተመሣሣይ ሁኔታ በወንጀል ተከስሰው ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ ተከሳሾች ላይ የወሰነውን የቅጣት ውሣኔ የገደበው ሲሆን በእነሱ ላይ ቅጣቱ እንዲፈፀም የሰጠው ውሣኔ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 190 እና አንቀጽ 192 ድንጋጌ መሠረት ያላደረገ መሆኑን በመዘርዘር በሰበር አቤቱታቸው ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም የሥር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሣኔውን የገደበላቸው ተከሳሾች የቅጣት ውሣኔው ሊገደብላቸው የሚገባቸው ነበሩ ወይስ አልነበሩም በሚለው ነጥብ ተጠሪ የሰበር አመልካች ሆኖ ያልቀረበ በመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት የሚያየውና የሚመረምረው ነጥብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሆኖም አመልካቾች የቅጣት ውሣኔው ሊገደብልን ይገባል በማለት ያቀረቡትን ክርክር በሕጉ ሰፊ ፈቅድ ሥልጣን የተሰጠው የሥር ፍርድ ቤት ያልተቀበለው በመሆኑና ይህንን መከራከሪያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካቾችን ቅጣት ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ ያልሰጡበትና በአንዣሩ የአመልካቾችን ቅጣት ሊፈፀም ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ ያፀደቀው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በእኛም በኩል የቅጣቱ መፈፀም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 1 በሁለተኛው ፓራግራፍ የተቀመጠውን ግብ የሚያሳካ በመሆኑና ቅጣቱን ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተሟልተዋል የሚለው ክርክር የሕግ መሠረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ ስላላገኘነው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች የተወሰነባቸውን የቅጣት ውሣኔ እንዲፈፅሙ የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 703 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ የተደነገገውን በመተላለፍ በተለያየ የሥራ ኃላፊነት ተመድበው ሲመሩት በነበረው የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ/አ.ማ/ የሥራ አመራር ጥቅም ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው ብሎ የወሰነውን የቅጣት ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማፅናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/-2 መሠረት አፅንተነዋል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች አቶ ለይኩን ብርሃኑ ፣ ሁለተኛ አመልካች አቶ ምትኩ አበሹና አራተኛው አመልካች አቶ ቸርነት ዋጋሪ እያንዳንዳቸው በዚህ ጉዳይ እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሶስተኛው አመልካች አቶ ጌታሁን አስማረና አምስተኛው አመልካች አቶ እንዳለ ቴኒ በዚህ ጉዳይ ተጠርጥረው እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ እያንዳንዳቸው በሁለት ዓመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራትና በብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፊሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ተካልኝ ጌታቸው - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የፌ/ዐ/ሕግ - አቶ አበባው መንግስቱ ቀረቡ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ ተጠሪ የአሁኑን አመልካችን ጨምሮ በ6 ተከሳሾች ላይ ክስ ያቀረበ ሲሆን አመልካችም በ5ኛ ክስ 5ኛ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ተከሳሾቹ በኢ/ፌ/ዲሪ/ወ ህግ አንቀጽ 32(1)(ለ) እና 692(1) በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት በማሰብ ለወንጀሉ አፈፃፀም እንዲረዳ ሌላ ያልተያዘ አባሪያቸው ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጋር በ1ኛ ክስ የተጠቀሰውን ቼክ አመነዛዘር ላይ በመመካከር ለዚሁ ይጠቅማል ያለውን 3ኛ ተከሳሽን ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጋር በማገናኘት፣ 3ኛ ተከሳሽ 4ኛ ተከሳሽን ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጋር እንዲገናኝ በማድረግ፣ እንዲሁም 4ኛ ተከሳሽ 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾችን ከ1ኛና 2ኛ ተከሳሾች ጋር አገናኝቶ በ6ኛ ተከሳሽ አማካይነት በቼኩ ላይ የተጠቀሰው ገንዘብ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ ወደ ወጋገን ባንክ ጎፋ ቅርንጫፍ በ6ኛ ተከሳሽ በተከፈተው ተንቀሳቃሽ ሂሳብ እንዲተላለፍ ከተደረገ በኋላ 3ኛ ተከሳሽ ብር 100,000፣ 4ኛ ተከሳሽ ብር 100,000 እና 5ኛ ተከሳሽ ብር 50,000 ወስደው ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው በመላ ሀሳባቸው እና አድራጎታቸው በወንጀል ድርጊት እና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት የማታለል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካችም ወንጀሉን አለመፈፀሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ ክሱ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራቀኙን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ በሰጠው ፍርድ 5ኛ ተከሳሽ ከባንኩ ተጭበርብሮ ከወጣው ብር 750,000 ውስጥ ብር 50,000 መውሰዱን ለፖ/ሊስ የተከሳሽነት ቃሉን ሲሰጥ በቦታው የነበሩ የከሳሽ የደረጃ ምስክሮች መስማታቸውን ያረጋገጡ ሲሆን የተከሳሹ የመከላከያ ምስክሮች ደግሞ የተከሳሽ ቤት ሲበረበር ከማየታቸው በስተቀር ተከሳሹ ወንጀሉን አለመፈፀሙን አላስረዱም በሚል በወ/ሕ/ቁ/ 692 (1) ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በ3 ዓመት እስራትና በ5,000 ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(2)(ለ)(2) መሰረት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ፍርድ በማጽናቱ አመልካች በከፍተኛው ፍ/ቤት ፍርድ እና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በሚል የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- ክሱን ባቀረብኳቸው የመከላከያ ምስክሮች አስተባብዬ እያለሁ ፍርድ ቤቶቹ ማስረጃዎቼን በአግባቡ ሳይመዝኑ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ያስተላለፉብኝ ተገቢነት ያለው አይደለም
- በወንጀሉ አመልካች አግኝቷል በሚል በማስረጃ የተረጋገጠው ብር 50,000 ሆኖ ከተረጋገጠው ውጪ ብር 250,000 እንደወሰድኩ ተቆጥሮ ከቅጣትና መቀጫ እርከን መነሻው በማጋነን በተሳሳተ ስሌት የተወሰነብኝ ስለ ቅጣት አወሳሰን የወጣውን መመሪያ ያልተከተለ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪ መዝገቡ ለሰበር ያስቀርባል በተባለው ጭብጥ መነሻ በሰጠው መልስ፡- አመልካች የተከሰሰውና ጥፋተኛ ሆኖ የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት በአታላይነት ወንጀል በወ/ህ/አንቀጽ 692(1) ስር ሲሆን ከድንጋጌው መረዳት የሚቻለው ወንጀሉ ለራስ ተገቢ ያለሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማስገኘት ሊፈጸም የሚችል በመሆኑ አመልካችም በፈጸመው ወንጀል ለራሱ የደረሰው ጥቅም ብር 50,000 ቢሆንም ሌሎች በወንጀሉ የተሳተፉትም ቀሪውን ገንዘብ ተከፋፍለው ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ በመሆኑ ምክንያት ድርጅቱ ያጣው ብር 750,000 ስለሆነ አመልካችም ራሱ ጥቅሙን ከማግኘቱም ባሻገር ሌሎችም ጥቅም እንዲያገኙ ሀሳብ የነበረው በመሆኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት ቅጣትን በሚወስንበት ጊዜ ሌሎች ተከሳሾች ያገኙትን ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ጭምር የወሰነ ስለሆነ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም ከፍተኛው ፍ/ቤትም ሆነ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የቅጣት ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ወደ ተያዘው ጭብጥ ከመመለሳችን በፊት አመልካች ለዚህ ችሎት ካቀረባቸው ቅሬታዎች አንዱ ክስ የቀረበበትን ወንጀል አለመፈጸሜን በመከላከያ ምስክሮቼ አስተባብዬ እያለሁ ፍርድ ቤቶቹ የግራቀኙን ማስረጃዎች በአግባቡ አልመዘኑም የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሆነ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በማመዛዘን የተጠሪ ማስረጃዎች ያረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የአመልካች የመከላከያ መስረጃዎች ማስተባበል ባለመቻላቸው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፋቸውን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የፍሬ ነገር ጉዳዮችን የማጣራት ስልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች በተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መነሻ በተሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተፈፀመውን ስህተት ከሚያርም በስተቀር የፍሬ ጉዳዮች እንደገና ሊያጣራ የሚችልበት ወይም በስር ፍ/ቤቶች የተሰሙትን ማስረጃዎች የሚመዝንበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ወደ ጭብጡ ስንመለስ አመልካች የሚከራከረው ወስዷል ከተባለው የገንዘብ መጠን አንጻር ቅጣቱ የቅጣት አፈፃፀም መመሪያን የተከተለ አይደለም በሚል ሲሆን ይህንኑ የአመልካችን ክርክር አመልካች ጥፋተኛ ነው ተብሎ የቅጣት ውሳኔ ከተላለፈበት የወ/ህ/አንቀጽ 692(1) አንጻር መመርመሩ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 692(1) እንደተደነገገው ማንም ሰው የማይገባውን ብልጽግና ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታልሎ ራሱን ወይም የሶስተኛውን ወገን ንብረት ጥቅም የሚጎዳ አድራጎት እንዲፈጸም ማድረጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተረጋገጠ እንደሆነ የአታላይነት ወንጀል ፈፅሟል ለማለት የሚቻል ይሆናል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይም አመልካች የግል ተበዳይ የሆነውን የሙገር ሲሚንቶ ሰራተኞች የማህበራዊ ዋስትና ኢንተርፕራይዝ ማህበርን ገንዘብ ከሌሎች ወንጀል ፈጻሚዎች ጋር በመሆን በፈጸመው የማታለል ተግባር ገንዘቡ ከተቀመጠበት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጠመንጣ ያዥ ቅርንጫፍ ወደ ወጋገን ባንክ ጎፋ ቅርንጫፍ ብር 750,000 እንዲዛወር በማድረግ ከዚሁ ከተዛወረው ገንዘብ ውስጥም የተለያየ መጠን ያለውን ገንዘብ ተከፋፍለዋል፡፡

በክፍፍል ከደረሰው ገንዘብ ውስጥም አመልካች የወሰደው ብር 50,000 መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በድንጋጌው መሰረትም ይህን ገንዘብ ለግል ጥቅሙ አውሎታል ተብሎ ይወሰዳል፡፡ በዚሁ የወንጀል ድርጊትም ሌሎች ተከሳሾች ጭምር ጥቅም እንዲያገኙ አድርጓል፡፡ በመሆኑም አመልካች ወንጀሉን የፈፀመው ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር የነበሩት ሌሎች ተከሳሾችም ጥቅም እንዲያገኙ በሚል ስለሆነ ወንጀል የመስራት ሀሳቡ ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ብቻ በሚል የተሰራ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም የቅጣቱ መጠንም ራሱ በወሰደው የገንዘብ መጠን ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ተከሳሾች ጋር ወንጀል ለመስራትና ውጤቱን ለመቀበል በመስማማት ሆነ ብሎ ከፈጸመው የወንጀል ድርጊት ከባድነት አንጻር ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም ከፍተኛው ፍ/ቤት በጠቅላላው ከግል ተበዳይ ማህበር በተወሰደው የገንዘብ መጠን መሰረት የቅጣት ውሳኔ በአመልካች ላይ ያስተላለፈው እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ያፀናው ተገቢና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 95136 በቀን 28/07/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 67826 በቀን 03/04/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(2)(ለ)(2) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ላይ በጠቅላላው ከተበዳይ ማህበር በማታለል ወንጀል በተወሰደው የገንዘብ መጠን የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም ጥፋተኛ ነው በተባለበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 692(1) ስር በ3 ዓመት እስራትና በብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) እንዲቀጣ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 01 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፋሲል በላይነህ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - አደናይ ተ/ብርሃን ቀረቡ

መዝገቡ ተመረምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሕግ አግባብ የተወከለ ሰው በውክልና ስልጣኑ ከወካዩ የተረከባቸውን ንብረቶች ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱ ሲረጋገጥ በወንጀል የሚጠየቅበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ የተጀመረ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል መቅጫ ሕግ አንቀጽ 676(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት በማሰብ ሚያዚያ 23 ቀን 2002 ዓ.ም. ሰዓቱ በውል በማይታወቅበት በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ስጋ መደዳ አከባቢ የግል ተበዳይ ወ/ሪት አዲስ አያል የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ/ም ውክልና ሰጥታው በውክልና መሰረት የንግድ ድርጅት ለሁለት አመት ኮንትራት ይዞ ሲሰራ፡- 1ኛ/ የቤት ኪራይ አስራ ስምንት ሺህ ብር፣ 2ኛ/ ቪዲዮ ካሜራ አስራ ሁለት ሺህ ብር የሚያወጣ፣ 3ኛ/ አንድ ብርድ ልብስ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር የሚያወጣ፣ 4ኛ/ የተለያዩ ንብረቶች ግምታቸው አስራ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ሁለት ብር የሚያወጡ በአጠቃላይ ግምት ብር 48,000.00 (አርባ ስምንት ሺህ ብር) የሚያወጡ ንብረቶችን ተረክቦ መልስ ሲባል አልመልስም በማለት በፈጸመው ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ አመልካች ጉዳዩ የፍትሓብሔር እንደመሆኑ መጠን በወንጀል የሚጠየቁበት አግባብ የለም በማለት የክስ ተቃውሞ አቅርበው የነበሩ ሲሆን ይኸው ተቃውሞ ውድቅ ሆኖ ግን ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ የክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡ አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ ካሰማ በኋላ አመልካች የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት የመከላከያ ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በመከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ አልቻሉም በሚል ምክንያት ክስ በቀረበበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ በአምስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ አሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውን ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ የፍትሓብሔር ጉዳይ ከሚሆን በስተቀር በወንጀል የሚያስጠይቅበት አግባብ የለም፣ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እንደክሱ አላስረዱም፣ የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ የተደረገውም ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው የመቀጣታቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ቀርቦ በጽሑፍ በሰጠው መልስ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ተመዝነው በመሆኑ በሰበር ችሎት የሚታይ አይደለም፣ ቅጣቱም ለድርጊቱ ተመጣጣኝና የቅጣት መመሪያውን መሰረት አድርጎ የተሰጠ በመሆኑ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) በግልጽ ደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች የሚመለከት ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ አንቀጽ 24፣ 57 እና 58 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን የሚመለከቱ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት መውሰዳቸው የተረጋገጠውን ንብረት ግምቱ በአቃቤ ሕግ ክስ ማመልከቻ የተጠቀሰውን ያህል ባይሆንም በወኪልነት ስልጣናቸው ከግል ተበዳይ የተረከቡት ሆኖ እንዲመልሱ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ምክንያት ነው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ጉዳዩን በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ በሚያውቁት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን የአመልካች መከላከያ ማስረጃዎች ያላስተባበሉ መሆኑም በበታች ፍርድ ቤቶች በሚገባ መረጋገጡን ውሳኔው ያሳያል፡፡ አመልካች የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል የሚታመን አይደለም፣ የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክር ሲታይም የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑ ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌ መሰረት ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ማረም ስልጣን ስር የማይወድቅ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር ከሰበር ችሎቱ ስልጣን አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ያለው ባለመሆኑ አልፈነዋል፡፡ አመልካች የግል ተበዳይን ንብረት በውክልና ስልጣናቸው ወስደው ሊመልሱ ፈቃደኛ ያለመሆናቸው ተረጋግጧል ከተባለ ይህ አድራጎት የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆን ያለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

አንድ ወኪል ከወካዩ በውክልና ስልጣኑ የወሰደውን ንብረት ለመመለስ ፈቃደኛ ካለሆነ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 676(2) ድንጋጌ የሚጠየቅ ስለመሆኑ ተጠቃሹ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ ስለሆነም በውክልና ስልጣኑ መሰረት አደራ የተቀበለ ተዋዋይ ወገን እምነት አጉድሏል ተብሎ በወንጀል የሚጠየቅ ስለመሆኑ ስለእምነት ማጉደል የሚደነግጉት የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎችም ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 676(2) መሠረት ወንጀል ነው ተብሎ የተጠቀሰው የወኪሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድርጊት በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን ከወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2) እና ተጠቃሹ የወንጀል ህግ አንቀጽ 676(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በግልጽ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ለጉዳዩ በወንጀል ጥፋተኛ የተባለው የፍትሓብሔር ይዘት ብቻ ባለው ጉዳይ ነው ለማለት ስላልተቻለ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የወ/መ/ሕ/አንቀጽ 23(2) እና 676(2) ደንጋጌዎችን ያገናዘበ ሆኖ በመገኘቱ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ብለናል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም የቅጣት አጣጣል መርሆዎችን የጣሰ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87549 ጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 103799 መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም. የጸናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በወንጀል መጠየቃቸው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መፅናቱን በማወቅ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረሚያ ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ደረጀ ጎሳዬ - ጠበቃ ወገኔ ካሳሁን ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አቃቤ ሕግ የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዋስትና የተያዘ ገንዘብ ይመለስልኝ ጥየቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል በሶስት ምድብ የተከፈለ ክስ ቀርቦበት ፍርድ ቤቱ ለአመልካች የዋስትና መብቱን ጠብቆለት አመልካች ብር 500,000.00(አምስት መቶ ሺህ ብር) አስይዞ የተጠበቀለትን የዋስትና መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ ሲፈልግ በቼክ ጉዳይ በወንጀል ተከሶ የእስር ቅጣት በመፈረዱ ምክንያት ማረሚያ ቤት በመግባቱ የዋስትና መብቱን ሊጠቀምበት ያለመቻሉን ገልጾ በክርክር ሂደት ላይ ላለው ጉዳይ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስለትና ጉዳዩን ከማረሚያ ቤት እየተመላለሰ እንዲከታተል ይደረግ ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታው በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 75 መሠረት ይግባኙ የቀረበበት መሆኑን ገልፆና ይህ ድንጋጌ የሚያገለግለው የዋስትና መብት ሲነፈግ ይግባኝ ለማቅረብ ነው የሚል ምክንያት ይዞ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም አመልካች በሌላ ወንጀል በተፈረደው ፍርድ መሠረት ማረሚያ ቤት የሚቆይ በመሆኑ ለሌላ ጉዳይ የተጠበቀው የዋስትና መብት ተግባራዊ የማይሆን መሆኑ ግልጽ ስለሆነ ለጉዳዩ የተያዘው ገንዘብ እንዲመለስ መጠየቁ ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በሌላ መዝገብ ፍርደኛ በመሆኑ ከማረሚያ ቤት ተመላልሶ መከራከር የሚችል ቢሆንም ለዋስትና ያስያዘው ገንዘብ አይመለስለትም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ተጠሪ ቀርቦ በጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡
አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የዋስትና ገንዘብ ያስያዘው በተጠሪ መስሪያ ቤት አቃቤ ሕግ የተለያዩ የጉምሩክ ሕግ ድንጋጌዎች ተላልፏል ተብሎ በቀረቡት ሶስት ክሶች የዋስትና መብት በፍርድ ሲጠበቅለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቼክ ጉዳይ ተከሶ የአራት አመት ከስድስት ወር ፍርደኛ ሆኗል፡፡ ገንዘቡ እንዲመለስለት የሚጠይቀውም ፍርድ ቤት ያለውን የጉምሩክ ወንጀል ክርክርን ከማረሚያ ቤት በመመላለስ የሚከታተል መሆኑን በመገንዘብ ነው፡፡

በመሰረቱ ዋስትና ሕገ መንግሥታዊ መብት መሆኑንና ይህ መብት በልዩ ሁኔታ በሕጉ ክልከላ ካልተደረገ በስተቀር ለተከሰሱ ሰዎች ሊጠበቅ የሚችል መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 19(6) ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ በሕጉ አግባብ የዋስትና መብት ሲፈቀድ ደግሞ የተከሳሹ ፍርድ ቤት መቅረብ እውን እንዲሆን ተከሳሹ ገንዘብ እንዲያስይዝ ወይም ሌላ ዋስትና እንዲያቀርብ የሚደረግ መሆኑን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 69(1) ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ የዋስትና መብት የተፈቀደለት ተከሳሽ መብቱን ለመቀጠም የማያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለው መሆኑን በመግለፅ መብቱን ለመጠቀም ካልፈለገ ደግሞ መብቱ የራሱ ይሆናል፡፡ በፍርድ ቤት የተፈቀደለትን የዋስትና መብት ያለመጠቀም ፍላጎት ደግሞ የዋስትና መብት እንደተፈቀደ ወይም ከተፈቀደና ተከሳሹ መብቱን መጠቀም ከጀመረ በኋላም ሊመጣ ይችላል፡፡ ሕጋዊ ምክንያት እስካለው ድረስ በማንኛውም ደረጃ ተከሳሹ በሕጉ አግባብ የተፈቀደለትን የዋስትና መብት የመተው ፍላጎቱ ሊጠበቅለት የሚገባው ጉዳይ እንጂ ይህንኑ መብቱን ለመከላከል የሚያስችል ግልጽ ድንጋጌ የለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ትኩረት ሊያደርግና ሊቆጣጠረው የሚገባው ቁልፍና ዋናው ነገር በፍርድ ቤት ክስ የቀረበበት ሰው ቀጠሮውን ተከታትሎ የሚቀርብበት ትዕዛዝ መስጠቱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተከሳሽን የዋስትና መብት በማክበር ተገቢውን ዋስትና በማስጠራት ወይም ተከሳሹ ማረሚያ ቤት ሆኖ ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 68 እና 69 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ተከሳሽ የዋስትና መብቱ ከተከበረለት በኋላ በሕጋዊ ምክንያቶች መብቱን በመተው ጉዳዩን ማረሚያ ቤት ሆኖ ለመከታተል ፍላጎት ያለው መሆኑን ሲገለጽ ሊነፈግ አይገባም፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄ ያልተቀበለው አመልካች በዋስ የተለቀቀበት መዝገብ እልባት ያላገኘና ማረሚያ ቤት በሌላ ወንጀል ገብቷል የተባለውም በውሳኔ ይሁን በሌላ ምክንያት አልተረጋገጠም በሚል ሲሆን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ይግባኙ የሚቀርበው የዋስትና መብት ሲከለከል ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በሌላ ወንጀል ፍርደኛ መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 75”ን” ለአቤቱታው መሠረት ማድረጉም አቤቱታውን ለማስተናገድ ፍርድ ቤቱ አልችልም ብሎ ውድቅ ለማድረግ ሥነ ሥርዓታዊ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ፍርድ ቤቶቹ አመልካች እልባት ያላገኘውን ጉዳይ ከማረሚያ ቤት በመመላለስ የፍርድ ቤትን ቀነ ቀጠሮውን አክብሮ የሚከታተልበት አግባብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ትዕዛዝ በመስጠት ይህንኑም እንዲፈፅም ለማረሚያ ቤቱ ማስተላለፍ ሲገባቸው ሕጋዊ መሠረት የሌላቸውን ምክንያቶችን በመያዝ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ከአመልካች የንብረት መብትና መብቱ ሊያስገኝ የሚችለውን ፍሬ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 68 እና 69 ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 174010 የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 106592 ሐምሌ 08 ቀን 2003 ዓ/ም የጸናው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 174010 በቀረቡት ክሶች ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስለት ብለናል፡፡ አመልካች በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጉዳይ ማረሚያ ቤት ሆኖ እንዲከታተል የማሰሪያ ዋራንት ለማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ለአመልካች ገንዘቡን እንዲያስመልስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 65566

ታህሣስ 4 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የመከላከያ ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ- ሃምሣ አለቃ ተስፋዬ ቦያለው ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የመከላከያ ሠራዊት አባል በመደበኛ ፍርድ ቤት የቀረበበትን የወንጀል ክስ ለመከላከል የሚያስችለው የህግ ድጋፍ መስጠትን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የመከላከያ ሠራዊት አባል በሆኑት ሀምሣ አለቃ ቴውድሮስ ሃይለስላሴ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/11ሀ በመተላለፍ ባለ አንድ መቶ ሐሰተኛ የብር ኖት (100) ይዘው ተገኝተዋል የሚል የወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ ተከሣሳሹ የተከሰሱበት የወንጀል ክስ ተገቢውን የህግ ድጋፍ እንዲያደርግና በተከላካይ ጠበቃ እንዲታገዝ የመከላከያ ሠራዊት መከላከያ ጠበቃ መድቧል፡፡ የዞኑ አቃቤ ህግ የመከላከያ ሠራዊት አባላት መከላከያ ሚኒስቴር ተከላካይ ጠበቃ የሚያቆመው በመደበኛ ፍ/ቤት በሚያስከስሱ ወንጀሎች ሣይሆን በጦር ፍ/ቤት በሚያስከስሱ ወንጀሎች ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የመከላከያ ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ ተከሳሹን ወክሎ ለመከራከር አይችልም የሚል መቀወሚያ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የዞኑ አቃቤ ህግ ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል የመከላከያ ወታደራዊ ተካላካይ ጠበቃ ለተከሳሹ የህግ ድጋፍ የመስጠት በተከላካይ ጠበቃነት ቆሞ ለመከራከር አይችልም የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅረቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን አፅንቶታል፡፡ አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል የሆነውን ተከሳሽ እንድንከላከል የበታች ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 27/1988 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የመከላከያ ሠራዊት አባላት በወታደራዊ ተከላከይ ጠበቃ እንዲታገዙ አዋጅ ቁጥር 27/1988 የሚፈቅደው በወታደራዊ ፍርድ ቤት በሚከሰሱበት ጊዜ ብቻ ስለሆነ ለተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የህግ ትርጉም ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የመከላከያ ሠራዊት አባል ያሆኑት ሃምሣ አለቃ ቴድሮስ ሀይለስላሴ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 361 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል የሚል የወንጀል ክስ በተጠሪ በኩል ቀርቦበታል፡፡ የመከላከያ ሠራዊት አባሉ የተከሰሱበት ወንጀል ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 361 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አዋጅ ቁጥር 27/88 በአዋጅ ቁጥር 123/90 እንደተሻሻለ ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት ያለው የህግ ማእቀፍ ሲሆን በዚህ መዝገብ የተያዘው ጭብጥ የአዋጅ ድንጋጌ ብቻ ሣይሆን የህገ መንግስቱን አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5 ተፈፃሚነት መመርመር የሚጠይቅ ነው፡፡ ተከላካይ “ስለማቆም” የሚል ርእስ ያለው የአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ፤ “ራሱ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም ለማይችል ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሰው መንግስት ተከላካይ ጠበቃ ይመደብለታል የሚል ይዘት ያለው ሲሆን የእንግሊዘኛው ቅጅ “the state shall provide a defence counsel to a person charged with an offence punishable by imprisonment not less than five years and un able to retain a counsel” በሚል መንገድ የተደነገገ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ የአንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 2 በዚህ “አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በተከላካይ ጠበቃነት ለማቆም የሚችለው ከሠራዊቱ አባል መካከል ይሆናል፡፡ በማለት በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከላይ የተገለፀው የህግ ድንጋጌ ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል በወታደራዊ ፍርድ ቤትም ሆነ በመደበኛ ፍርድ ቤት ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ ክስ ሲቀረብበትና በራሱ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም የማይችል በሆነ ጊዜ መንግስት የህግ እውቀትና ልምድ ያለው የመከላከያ ሰራዊት አባል የሆነ ተከላካይ ጠበቃ በነፃ የማቆምና የመከላከል ግዴታ እንዳለበት የሚደነግግ ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 27/88 አንቀጽ 35 መንግስት ለሠራዊቱ አባላት በነፃ ተከላካይ ጠበቃ በማቆም የቀረበባቸውን የወንጀል ክስ እንዲከላከል በህግ የሚገዳድበትን ዝቅተኛ መስፈርት (minimum standard) የሚደነግግ ሲሆን የአገር መከላከያ ሚኒስትር የመከላከያ ሠራዊት አባላት በግዳጅ ላይ እያሉ ፈፀመውታል ተብሎ በተከሰሱበት ከ5 አመት እስራት በታች በሚያስቀጣ ወንጀል ተከላካይ ጠበቃ በነፃ ለማቆምና ለመከላከል ከፈለገ በወታደራዊ ፍ/ቤትም ሆነ በማናቸውም ደረጃ በሚገኝ መደበኛ ፍ/ቤት ተከላካይ ጠበቃ በመወከልና በነፃ የቀረበውን የወንጀል ክስ መከላከል የአዋጁ አንቀጽ 35 ድንጋጌዎችን የሚገድቡት እንዳልሆነ ከድንጋጌው አቀራረፅ ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ የአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀፅ 35 ድንጋጌዎች በወንጀል የተከሰሱ የመከለከያ ሠራዊት አባላት በግላቸው ጠበቃ ለማቆም የማይችሉ በሆነ ጊዜ ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም በመንግስት ወጪ የጠበቃ ድጋፍና እርዳታ የማግኘት መብት እንዳላቸው በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገውን በማጣብብና በተሻሻለ ሁኔታ የህገ መንግስቱን ድንጋጌ ተፈፃሚ በሚያደርግ መንገድ መተርጐምና ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ከ5 አመት በማያንስ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በወታደራዊ ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ በቀረበበት ጊዜና ተከሳሹ በግሉ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም የማይችል ሲሆን የመከላከያ ወታደራዊ ጠበቃ ድጋፍ በነፃ ማግኘት በአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀጽ 35 የተደነገገ የሠራዊቱ አባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብትና የአገር መከላከያ ሚኒስትር ህጋዊ ግዴታ ሲሆን የሠራዊቱ አባል በአምስት ዓመት በማያንስ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በመከላከያ ፍርድ ቤት ክስ በቀረበበት ጊዜ የአገር መካከላያ ሚኒስትር በነፃ የተከላከይ ጠበቃ ድጋፍ የሠራዊት አባል ማግኘት አለበት ብሎ ካመነ የመከለከያ ወታደራዊ ጠበቃ በነፃ የህግ ድጋፍና እገዛ እንዲያደርግለት በማድረግ መከላከል የሚችል መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀጽ 35 ድንጋጌዎች ይዘትና ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ ለመገንዘብ የሚቻል ሆኖ እያለ የመከላከያ ሠራዊት አባል በመከላከያ ወታደራዊ ጠበቃ ነፃ የህግ ድጋፍ የሚያገኘው በወታደራዊ ፍርድ ቤት በወንጀል ሲከሰስ ብቻ ነው በማለት ተጠሪ ያቀረበውን የህግ መሠረት የሌለው መቃወሚያ በመቀበል ተከሣሹ በመከላከያ ወታደራዊ ጠበቃ ነፃ የህግ ድጋፍ እንዳያገኝ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ብይን ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት በመደበኛ ፍርድ ቤት በወንጀል በተከሰሱበት ጉዳይ በነፃ የህግ ድጋፍና እገዛ የማድረግና የመከላከል መብት አለው በማለት ወስነናል፡፡

ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 63014
ሚያዝያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ወርቅነህ ከንባቶ

2. ወ/ሮ አመለወርቅ ዳሌ

ተጠሪ፡- የደቡብ ክልል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካቾች በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ ለ እና አንቀፅ 33 እና በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ በወንጀል ግብረ-አበርና ልዩ ተካፋይ በመሆን ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዘው የመገኘት ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ክርክር በሥር አንደኛ ተከሳሽ የሆነው አንደኛ አመልካች የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ ከተቀጠረበት ከመስከረም 1984 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ድረስ የታክስ አስተዳደርና ገቢ ሰብሳቢ ሆኖ የተለያየ የደረጃ እድገት እያገኘ እንደሠራ ገልፆ፣ አንደኛ አመልካች በሕጋዊ መንገድ በመንግስት ሥራው የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከብር 90,220 /ዘጠና ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ብር/ የሚበልጥ አይደለም፡፡ ነገር ግን ተከሶሾች፡-

- ሁለተኛ ተከሳሽ ዳሸን ባንክ በሒሳብ ቁጥር 50165201 ብር 332,363.63 /ሦስት መቶ ሠላሳ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስልሳ ሦስት ብር ከስልሣ ሶስት ሣንቲም/ ተቀምጦ ይገኛል፡፡
- አንደኛ ተከሳሽ በዳሸን ባንክ በሂሳብ ቁጥር 501651238200114004 ብር 1,646,371.24 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ አንድ ብር ከሃያ አራት ሣንቲም/ በስሙ የሚገኝ ሲሆን
- አንደኛ ተከሳሽ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሂሳብ ቁጥር 24499 ብር 46,802.11 /አርባ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ሁለት ብር ከአስራ አንድ ሣንቲም/ በስሙ የሚያንቀሳቅሰው ገንዘብ አለው
- ተከሳሾች በልጃቸው በደስታ ወርቅነህ ስም ብር 55,931.92 /ሃምሣ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሣ አንድ ብር ከዘጠና ሁለት ሣንቲም/ ግምት ያለው የመኖሪያ ቤት አላቸው፡፡ በጠቅላላው ተከሳሾች ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማንያ አንድ ሺ አራት መቶ ስልሣ ስምንት ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዘጠና ሣንቲም/ ምንጩ ያልተወቀ ሀብት ያላቸው በመሆኑ የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ክሱን ሊያስረዱ ይቻላሉ የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ አመልካቾች ክሱ ከደረሳቸውና እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የወንጀሉን ድርጊት አልፈፀምንም ጥፋተኞች አይደለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች በበኩላቸው በተጠሪ ክስ የተዘረዘረው ገንዘብ ሕጋዊ ምንጭ የሚሏቸውን በመዘርዘር አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች

- በወንዶገነት ወረዳ አባያ ቀበሌ ከ1984 ዓ.ም ከቤተሰብ የተሰጣቸው 2.5 ሄክታር መሬት ያላቸው መሆኑንና ጫት የተከሉ በመሆኑ በዓመት ከመቶ ስልሳ ሺህ ብር በላይ እንደሚያገኙ፣
- በሌላ በኩል 0.25 ሄክታር የሆነ መሬት እንዳላቸውና የሸንኮራ አገዳ በማልማት በዓመት ከሃያ አምስት ሺህ ብር በላይ እንደሚያገኙና በዚህ ገቢ ቤቱን እንደገዙት፣
- በሁለተኛ ተከሳሽ ስም በዳሸን ባንክ የነበረው ገንዘብ፣ ብር 5,000,000፣ የሚሰራ ፕሮጀክት አንደኛ ተከሳሽ ቀርፆ፣ ከባንክ ብድር ሲጠይቅ አንድ ሶስተኛ አሳይ በመባሉ በብድር የተገኘና ከሁለተኛ አመልካች አካውንት ወጥቶ በአንደኛው አመልካች አካውንት እንደገባና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደ መሆኑን፣
- በአንደኛው አመልካች ስም ከዳሸን ባንክ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ብር 1,120,500.00 /አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ ሺህ አምስት መቶ ብር/ የጋራራም ላንች እና የጋልማ ባህላዊ ሎዴ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ንብረት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ማስረጃዎች አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካቾችን ክስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች የተጠሪን ክስና ማስረጃ ያስተባበለ መሆኑን ገልፆ ከተሰሱበት ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ 149 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጨማሪ ማጣሪያ ካደረገና ተጨማሪ ምስክሮች ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን አፅንቷል፡፡ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ ታዓማኒነትና ክብደት የሌለው በመሆኑ የተጠሪን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል አይችልም በማለት አንደኛ አመልካች በሶስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ክስ የቀረበበት ንብረት እንዲወረስ፣ ሁለተኛ አመልካች በአንድ ዓመት ፅኑ እስራት እንድትቀጣ፣ ቅጣቱ እንዲገደብና በስሟ ያለና ክስ የቀረበበት ገንዘብ እንዲወረስ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ታህሣሥ 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የማረም እንጂ ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ ዐቃቤ ሕግ በክሱ የጠቀሰውን ገንዘብ ከየት እንዳገኘው አስረድተን እያለ ፍርድ ቤቱ የእኛን የመከላከያ ማስረጃ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ገንዘብም እንዲወረስ መደረጉ ተገቢነት የለውም፡፡ ስለዚህ በሰበር ታይቶ ይሻርልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መጋቢት 2 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አመልካቾች ያቀረቡትን የፍሬ ጉዳይ ክርክር የመመርመር ሥልጣን የለውም፡፡ ይህ የሚታለፍ ቢሆን አመልካቾች የወንጀል ክስ ከቀረበባቸው በኋላ በተለይም በይግባኝ በሚሰማበት ጊዜ ያመጡት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ነው፡፡ አመልካቾች ወንጀሉን የፈፀሙ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መጋቢት 30 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሰጠው አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለገቢ ምንጫቸው ያቀረቧቸው ምስክሮችና ማስረጃዎች ታዓማኒነት የሌላቸውና የተጠሪን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል የሚችሉ አይደሉም በማለት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው ውሣኔና የሰጠው በተጠሪ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ይዘት፣ ታዓማኒነትና ክብደት በዝርዝር በመመርመር በመመዘን እንደዚሁም በአመልካች በኩል የቀረበውን የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ በዝርዝር በመመርመርና የማስረጃውን ታዓማኒነትና ክብደት በመመዘን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠው የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፍሬጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት ፈፅመዋል የሚለውን ስህተት ለማረም የማስረጃ ምርመራና ምዘና በመፈፀም ነው፡፡

ይህም ፍሬጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት በክልሉ ፍርድ ቤቶች ወይም ሌላ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የፈፀሙት ስህተት ቢኖር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ፍሬጉዳይ አጣርቶና ማስረጃ መርምሮና መዝኖ የማረም ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ነጥብ እንድናይ የሚያስገድደን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ለ/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንደሚኖረውና ክርክሩ በሕግ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡ በ1994 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 75 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ሥልጣን ያለው መሆኑን በግልፅ ይደነግጋል፡፡ የክልሉ የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 43/1994 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 3 የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ በሰበር የማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከላይ የጠቀስናቸውን የፌዴራል ሕገ-መንግስት፣ የክልሉ ሕገ-መንግስት፣ የክልሉ አዋጅ ቁጥር 43/1994 ድንጋጌዎች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ፍሬጉዳይ የማጣራት፣ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የሚሰጡ ሆነው አላገኘናቸውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተጠሪንና የአመልካቾችን ማስረጃ በዝርዝር በመመርመርና በመመመዘን የተጠሪን ማስረጃ የወንጀል ክሱን የማስረዳት ብቃትና ታማኝነት አለው፡፡ የአመልካቾች ማስረጃ ታዓማኒነትና ክብደት የሌለው ነው በማለት የደረሰበትን መደምደሚያና፣ የግራ ቀኙን ማስረጃ መርምሮና መዝኖ የደረሰበትን መደምደሚያ መሠረት በማድረግ በአመልካቾች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ከላይ የገለፅናቸውን ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ፍሬጉዳይ የማጣራት፣ ማስረጃ የመመዘንና የመመርመር ሥልጣን የለውም ማለት፣ በክልሉ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ወይም የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት፣ መሠረታዊ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ሥርዓት ሳይከተሉ፣ መመስረት የሚገባቸውን ጭብጥ ሳይመሰርቱና ጭብጥን የማስረዳት ሁኔታ /Burden of proof/ ያለበት ተከራካሪ ወገን የማስረዳት ግዴታውን በአግባቡ እንዲወጣ ሳያደርጉና መጣራት የሚገባውን ፍሬጉዳይ ሳያጣሩ የሰጡትን ውሣኔ በሰበር ታይቶ የማረምና በክልሉ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ወይም ሌሎች የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት፣ ተገቢውን ጭብጥ በመመስረት፣ በሕግ የማስረዳት ግዴታ ያለበት አካል ግዴታውን የተወጣ መሆኑን በአግባቡ በመመርመርና በመመዘን እንደዚሁም መጣራት የሚገባውን ፍሬጉዳይ አጣርተው እንዲወስኑ ትዕዛዝ የመስጠትና ጉዳዩን የመመለስ የዳኝነት ሥልጣን የለውም ማለት እንዳልሆነ ትክክለኛ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በዝርዝር የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘንና በመመርመር ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ቢሆንም በውሣኔው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 በተከራካሪ ወገኖች ከሚጥለው የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ አንፃር አመልካቾችና ተጠሪ በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም? የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾችና በተጠሪዎች መካከል ያለውን አከራካሪ የፍሬጉዳይ ጭብጥ ለመወሰን መጣራት የሚገባቸውን ፍሬጉዳዮች በማጣራትና የግራ ቀኙን ማስረጃ የሕጉ ድንጋጌ የሚጥልባቸውን የማስረዳት ግዴታ መሠረት በማድረግ በመመርመርና በመመዘን ውሣኔ ሰጥተዋል ወይስ አልሰጡም? የሚሉትን ጭብጦች በውስጡ የያዘ መሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ከሰጠው ውሣኔ ተረድተናል፡፡

ከላይ የገለፅናቸውን ጭብጦች የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአግባቡ በማየት ውሣኔ የሰጡባቸው መሆን ያለመሆኑን ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካቾች የተከሰሱበት የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 33 እና አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ተጠሪና አመልካች ያለባቸውን የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካቾች የተከሰሱበትን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 33 እና አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ዝርዝር ይዘት ተመልክተናል፡፡ “ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ” የሚል ርዕስ ያለው የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 በንዑስ አንቀጽ 1 “የመንግስት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ማንም ሰው
/ሀ/ የኑሮ ደረጃው አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ ወይም፣
/ለ/ ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ፣

የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር እንደሁኔታው የንብረቱ መወረስ ወይም ለባለቤቱ መመለስ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል” የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ አንደኛ አመልካች ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ጉዳይ በወንጀል ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ በክልሉ በተለያየ ደረጃ የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ እየሰራ ያገኘው የተጣራና የታወቀ ገቢ ብር 90,220 /ዘጠና ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ብር/ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳለው በክሱ ከገለፀ በኋላ አመልካቾች በስማቸው በተለያዩ ባንኮች ባላቸው ሂሳብና በልጃቸው ስም የገዙት ቤት ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ያላቸው በመሆኑ ምንጩ ያልተወቀ ሀብት ይዘው ተገኝተዋል በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ አንደኛ አመልካች የመንግስት ሠራተኛ በነበረበት ጊዜ ያገኝ የነበረውን ገቢ፣ ሁለተኛ አመልካች የቤት እመቤት መሆናቸውንና ንብረቱ በጥሬ ገንዘብ ያለ በስማቸው ያለ መሆኑንና አመልካቾች በልጃቸው ስም ቤት ያላቸው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳቀረበ ፍሬጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። አመልካቾች በበኩላቸው በባንክ ሂሳባቸው ውስጥ የተገኘው ገንዘብና ቤቱን የሠሩበትን ሀብት ምንጭ ለማስረዳት የመከላከያ ማስረጃዎች እንዳቀረቡ ከሥር ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎቱ ከሰጡት ውሣኔ ተረድተናል።

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካቾች ተጠሪ ያቀረበውንና በማስረጃ ያረጋገጠውን ፍሬጉዳይ ማለትም በግልፅ ከሚታወቀውና አንደኛ አመልካች ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት ሠራተኝነት ያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ በላይ በባንክ ሂሳብ ቁጥራቸው የተገኘው ጥሬ ገንዘብና በልጃቸው ስም ቤት የሠሩበት ሀብት ማለት ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ትክክለኛ ምንጭ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለባቸው ወይስ የዐቃቤ ሕግን ክስና ማስረጃ ሊያስተባብሉ የሚችሉ አንድ አንድ ፍሬጉዳዮችን ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው በቂ ይሆናል ወይስ አይሆንም የሚለውን ነጥብ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ከተደነገገው የማስረዳት ግዴታ አንፃር መመርመር አስፈላጊ ነው።

ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ እና /ለ/ ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻለው ዐቃቤ ሕግ የመንግስት ሠራተኛ የሆነው ወይም የነበረው ሰው ያገኝ የነበረውና የሚያገኘው ገቢ ምን ያህል እንደሆነና የመንግስት ሠራተኛው በራሱ ስምም ሆነ በቤተሰቡ ስም ከሕጋዊ ገቢው ውጭ ይዞት የሚገኘውን የገንዘብና የንብረት ግምት የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑን በግልፅ ተደንግጓል። በሌላ በኩል የመንግስት ሠራተኛ የነበረው ሰውና ከእሱ ጋር በልዩ አባሪነት የተከሰሰ ሰው የመንግስት ሠራተኛው ሲያገኝ ከነበረውና ከሚያገኘው ገቢ በላይ ይዞት የተገኘው ገንዘብ ወይም ሀብት ትክክለኛው ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ሶስተኛው ፓራግራፍ፣ "....የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት እንደገባ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በስተቀር" ምንጩ ያልተወቀ ሀብት ይዞ በመገኘቱ /በመገኘታቸው/ ጥፋተኛ ተብለው በሕጉ የተደነገገው ቅጣት ሊጣልባቸው እንደሚችል በግልፅ ይደነግጋል። ከዚህም የምንረዳው ዐቃቤ ሕግ በግልፅ ከሚታወቀው ሕጋዊ ገቢ በላይ ነው በማለት በክሱ የገለፀውንና በማስረጃ ያረጋገጠውን ሀብት ትክክለኛ ምንጭ የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ በተከሳሾች ላይ የሚወድቅ መሆኑን ነው። የተከሳሾች የማስረዳት ግዴታም ዐቃቤ ሕግ በክሱ ከገለፀውና በማስረጃ ካረጋገጠው ውጭ ተከሳሾች ሌላ ገቢ የሚያገኙበት ሥራ ወይም የገቢ ምንጭ ያላቸው መሆኑን ብቻ ለፍርድ ቤቱ በማሳየት የሚወሰን ሳይሆን፣ በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ከተረጋገጠው ገቢ ውጭ በእጅ እንደተገኘ የተረጋገጠው ገንዘብና ሀብት ትክክለኛ ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 ሶስተኛው ፓራግራፍ ድንጋጌ አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት ይቻላል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አንደኛው አመልካች የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ ከሚያገኘው ደመወዝ /ሕጋዊ ገቢ/ በላይ በስማቸው በተከፈተ የባንክ ሂሳብና በልጃቸው ስም ቤት የተሰራበትና እንደያዙት የተረጋገጠው በአጠቃላይ መጠኑ ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከዘጠና ሳንቲም/ የሆነ ገንዘብና ሀብት ምንጩ በአንደኛ አመልካች ስም በወንዶገነት ወረዳ አባዮ ቀበሌ ካለው 2.5 ሄክታር የመሬት ይዞታ ላይ ካለሙት የጫትና የቡና ሰብል ሽያጭ፣ በሁለተኛ አመልካች ስም 0.25 ሄክታር መሬት ላይ ካለሙት የሽንኮራ አገዳ እንደሆነ፣ ከፊሉን በብድር ከግለሰብ ያገኙት መሆኑንና ከፊሉ የጋራራሙ ላንቶ የእንስሳት ማድለብና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና የጋልማ ባህላዊ ሎጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዳቀረቡ ከሥር ፍርድ ቤትና ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ችሎት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡

ሆኖም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች አንደኛ አመልካች ከሚሰራው የመንግስት ስራ በተጨማሪ ሌላ የገቢ ምንጭ የነበረው መሆኑን የሚያሣዩ ማስረጃዎች መሆናቸውን በመመልከት ብቻ መጣራት የሚገባቸው ፍሬጉዳዮችን ሳያጣሩና በተለይም አመልካቾች በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ከሕጋዊ ገቢያቸው በላይ የያዙ መሆናቸውን ብር 2,081,468.90 ያገኙበትን ትክክለኛ የገቢ ምንጭ የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት የማስረዳት ግዴታቸውን ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በሕጉ በአመልካቾች ላይ የተጣለውን የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ መሠረት በማድረግ ተገቢውን ማጣራት አድርገው መርምረውና መዝነው ውሣኔ የሰጡ አለመሆናቸውን ከውሣኔያቸው ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡ ምክንያቱም

/ሀ/ አመልካቾች በስማቸው እንዳለና ጫት፣ እንስት፣ ቡናና ሽንኮራ አገዳ እያለማን ገቢ እናገኝበታለን ያሉት 2.25 ሄክታር መሬት በተመለከተ አመልካቾች የእርሻ መሬቱ ባለይዞታ ናቸው ወይስ አይደሉም? የእርሻ መሬቱ ባለይዞታ ከሆኑ የእርሻ መሬቱን በይዞታነት የያዙት መቼ ነው? መሬቱን በማልማት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የተለያዩ ተክሎች በማልማት ምርት ገቢ ማግኘት የጀመሩት መቼ ነው? ከመሬቱ የሚገኘው ገቢና መሬቱን ለማልማትና ምርቱን ለገበያ ለማቅረብ የሚወጣው ወጭ ምን ያህል ነው? አመልካቾች ከመሬቱ ተጣርቶ የሚደርሳቸው ገቢ ምን ያህል ነው የሚለው ፍሬጉዳይ በአግባቡና በገለልተኛ ባለሙያ ተጣርቶ ባልታወቀበት ሁኔታ ከቀበሌና ከዞኑ ግብርና ጽ/ቤት የተፃፉ ደብዳቤዎችን ብቻ መሠረት በማድረግ አመልካቾች ከእርሻ የሚያገኙት ገቢ መጠን ከፍተኛ እንደሆነ መወሰኑ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 በአመልካቾች ላይ የሚደነግገውን የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ መሠረት በማድረግ ጉዳዩ ተጣርቶ የተወሰነ አለመሆኑን የሚያሣይ በመሆኑ፣

/ለ/ አመልካቾች በባንክ ሒሳባቸው ውስጥ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ብር 1,120,500 /አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ ሺህ አምስት መቶ ብር/ በአንደኛው አመልካች ስም የተቀመጠ ከፊሉ የጋራራሙ ላንቶ የእንስሳት ማድለብ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ገንዘብ ከፊሉ ደግሞ የጋልማ ባህላዊ ሎጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሆኑን ለማስረዳት የማህበራቱ ቃለ-ጉባኤና አባላት በማስረጃነት ያቀረቡ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤትና ከይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሣኔ ተገልጿል፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ ደረጃ ኃላፊነታቸው የተወሰኑ የግል ማህበራት የሚመሰርቱት የማህበሩ ዋና ገንዘብ ልክና የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ መግባቱን የሚያስረዳ መግለጫ ሲቀርብ መሆኑ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 519 ንዑስ አንቀጽ /መ/ እና /ሰ/ በአስገዳጅነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደነገገ በመሆኑ እነዚህ የንግድ ማህበራት ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው ተመዝግበው ከሆነ ሲመዝገቡ ያስመዘገቡትና ገቢ ያደረጉት የማህበሩ ዋና ገንዘብ ምን ያህል ነው? ማህበራቱ በካፒታልነት ካስመዘገቡት ካፒታል በላይ በአመልካቾች ስም ለማህበር መመስረቻ የተዋጣው ገንዘብ አለ በማለት የሚፅፉቸው የተለያዩ ማስረጃዎች ሕጋዊ ተቀባይነት፣ ያላቸው ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚሉት ነጥቦች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አመሰራረት፣ መዋጮ አከፋፈል፣ የማህበሩ ዋና ገንዘብና ገንዘቡ ገቢ ስለሚሆንበት ሁኔታ የተቀመጡ ሕጋዊ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ፣ መጣራት የሚገባቸው ፍሬጉዳዮች ተጣርተውና ማስረጃዎቹ አመልካቾች በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ያለባቸውን የማስረዳት ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ተጣርተው ውሣኔ የተሰጠበት ሆኖ አላገኘንም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ የዘረዘርናቸውን መጣራት የሚገባቸውን ፍሬጉዳዮች ሳያጣራና አመልካቾች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጣለባቸውን የማስረዳት ግዴታ /Burden of proof/ የተወጡ መሆኑን ያለመሆኑን የሚያሣዩና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሠረት ያደረጉና ተቀባይነት ያላቸው ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለውን ጭብጥ በመመስረት ውሣኔ ያልሰጡበት በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተጠሪንና የአመልካቾችን ማስረጃ በዝርዝር በመመርመርና በመመዘን የሰጠው ውሣኔም ሆነ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸውን ፍሬጉዳዮችን ሳያጣራና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የአመልካቾችን ማስረጃ ተቀባይነት ሳይመረምሩ የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችና ከላይ የዘረዘርናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥሱና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ናቸው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ከዚህ በፊት ጉዳዩን ያላዩት ዳኞች በመሰየም በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 2/ሀ/ እና /ለ/ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በማጣራትና የማስረጃዎቹን ተቀባይነት፣ ክብደትና ተዓማኒነት በመመዘን በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149/1/ መሠረት ፍርድ እንዲሰጥበት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ የውሣኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 54117

ጥቅምት 13 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ አ.ማ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመድን ውልን መሰረት ያደረገ የገንዘብ ክፍያ ይተካልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች የመድን ሽፋን የሰጣቸውን የደንበኛውን የኩርቱ ኢንተርናሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር ንብረት የሆኑትን 1,200 ጎማዎችን ተጠሪ ለማጓጓዝ የተረከበ ቢሆንም እነዚሁ ጎማዎች ተጠሪ በባህር ላይ በደረሰ ግጭት መጥፋታቸውን በመግለፁ አመልካች ከደንበኛው ጋር ባለው የመድን ውል መሰረት ለጠፉት ጎማዎች ግምት ብር 269,293.20 (ሁለት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ብር ከሃያ ሳንቲም) ወጪ አድርጎ ለደንበኛው መክፈሉን ገልፆ ተጠሪ ባለው የመጓጓዣ ውል መሰረት ለአመልካች ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ከተለያዩ ወጪዎችና ኪሳራዎች ጋር እንዲተካለት ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለአመልካች ክስ በሰጠው መከላከያ መልስም አመልካች ክስ ለመመስረት የሚያስችለው መብትና ጥቅም የሌለው መሆኑን ለክሱ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ጎማዎቹ በባህሩ ላይ ሊወድቁ የቻሉት በባህር ላይ በደረሰው የግጭት አደጋ ምክንያት ነው፣ ጉዳቱ የደረሰው በአጓጓዡ ጥፋት ወይም በአጓጓዡ ወኪሎች ወይም ሰራተኞች ጥፋት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎ ተጠሪን ከክሱ ነጻ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ጎማዎቹን በአግባቡና በጥንቃቄ ሳይጭናቸው በመቅረቱ ግጭቱ በደረሰበት ጊዜ ተወርውረው ባህር ውስጥ የገቡ መሆኑ እየታወቀና ይህንኑ ሁኔታ ከባህር ሕጉ አንቀፅ 196(2) ድንጋጌ ይዘት ጋር ፍርድ ቤቱ ማገናዘብ ሲገባው ተጠሪን ከክሱ መሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሉ ነጻ መልቀቁ ሕጋዊ አይደለም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የአመልካች ደንበኛ (ኩርት ኢንተርናሽናል ኃ.የተ.የግል ማህበር) ንብረት የሆነውን 1,200 ጎማዎችን አጓጉዞ ለማድረስ መረከቡንና ጎማዎቹ በባህር ላይ በነበረው ጉዞ በደረሰው ግጭት ምክንያት የጠፉ መሆኑ ግራ ቀኙ ያልተካካዱት ፍሬ ነገር መሆኑን ነው። አመልካች ተጠሪ ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው ባለበት የመድን ውል ለደንበኛው በንብረቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ ከከፈለ በኋላ ገንዘቡ እንዲተካለት ነው። ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው ኃላፊነት የለብኝም በማለት ሲሆን ለዚህ በቀዳሚነት የሚያቀርበው ክርክር ጎማዎቹ በባህር ላይ በደረሰው የመርከቦቹ ግጭት አደጋ የጠፉ እንጂ በተጠሪ ችግር ወይም ሰራተኞች ጥፋት አይደለም በማለት ነው።

በመሰረቱ በባህር ላይ እቃ አመላለሽ ያለበትን ኃለፊነት በተመለከተ የባህር ሕጉ በቁጥር 196 ስር ያስቀመጠ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት እቃ አመላላሽ ሁለት ሰፊና ዋና ዋና ግዴታዎች አሉት። የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ አንድን መርከብ በሙሉ በመከራየት (ቻርተር ፓርቲ) እቃን የሚያንጉዝ ባለመርከብ ስላለበት ግዴታ የባህር ሕጉን ቁጥር 138 በማጣቀስ የሚደነግግ ሲሆን የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ በመርከቡ ላይ የተጫኑትን እቃዎች በጥንቃቄና በሚገባ ለመጫን፣ ለአጠባበቃቸው በሚገባ አቀማመጥ እንዲደረደሩ፣ ስለጉዞዋቸው፣ ስለ ጥበቃቸው፣ ስለ መልካም አያያዛቸውና ስለ ማራገፉ መልካም አፈጻፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን በአስገዳጅ ሁኔታ ይደነግጋል። በመሆኑም አጓዡ በሕጉ የተጣሉበትን እነዚህን ግዴታዎች ካልተወጣ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያስረዳል። በጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ውስጥ አመላላሹ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የተደረገው ውል የማይፀና ስለመሆኑም የባህር ሕግ ቁጥር 205 በግልፅ ይደነግጋል። የአመላላሹ መከላከያ ሊሆኑ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች በባህር ሕጉ ቁጥር 197 ስር የተመለከቱት ምክንያቶች ናቸው። ከላይ የተመለከቱት የባህር ሕግ ድንጋጌዎች የአመላላሽን ኃላፊነት ሊያስከትሉና ቀሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያቶችን የሚደነግጉ ሲሆን ኃላፊነትን በተመለከተ ቀሪ ከሚያደረጉ ምክንያቶች ውስጥ አመላላሽ በእቃው ጉዳት የደረሰው በባህር ላይ በደረሰው የግጭት አደጋ (accident of the Sea) መሆኑ፣ ከአመላላሹ ጥፋት ወይም በእርሱ ወኪሎችና አሽከሮች ቸልተኝነትና ጥፋት ምክንያት ያለመሆኑና በአግባቡ ማስረከቡን መረጋገጡ ስለመሆኑም ያስገነዝባሉ። የእቃው እርክክብ ተፈጽሟል የሚባለው ደግሞ መቼና በምን ሁኔታ ሲፈጸም እንደሆነም ድንጋጌዎቹ በተለይ ከባህር ሕጉ ቁጥር 180(3) ጋር ተዳምረው ሲነበቡ ያሳያሉ። በዚህም መሰረት በጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ የተረጋገጠ የማመላለሻ ውልን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች የሚጸኑት በተለይ በመርከብ ላይ በተጫኑት የንግድ እቃዎች የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን በመሰለ ሌላ አይነት ሰነድ በተረጋገጡ የጭነት ማመላለሻ ውሎች ብቻ መሆኑ፣ የመርከብ መከራየት ውል ሰነድ ባለው ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን፣ ነገር ግን መርከቡ የተከራየው በኪራይ ሰነድ (በቻርተር ፓርቲ) የሆነ እንደሆነ የሚሰጠው የጭነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን የመሳሰለው ሌላ ሰነድ በአመላላሹና በሰነድ አምጪው መካከል ያለው ግንኙነት ከሚመራበት ጊዜ አንስቶ በዚሁ በሚሰጠው የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ላይ ድንጋጌዎቹ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ፣ የሚፀኑትም እቃዎቹ ከመርከብ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ እስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ የተጠቀሰው ድንጋጌ ያሳያል። የዚህ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሶስት በተለይ ሲታይም ".....ከመርከቡ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ እስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ ነው። "በሚል በኃይል ቃል ማስቀመጡ አመላላሹ በማራገፍ ሂደት ለሚከሰቱ ጉዳቶቹም ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በግልጽ የሚሳይ ነው።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ተጠሪን ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት በማለት የሚከራከረው ጎማዎቹ በባህር ላይ እንዲወድቁ የሆነው ተጠሪ ጎማዎቹን በመርከቡ ላይ በጥንቃቄና በሚገባ በመጫን፣ በሚገባ አቀመማጥ እንዲደረዱ ማድረግ (stow) ያለበት ስለመሆኑ በባህር ሕጉ አንቀፅ 196(2) ስር የተመለከተውን ግዴታ አልተወጣም የሚል ምክንያት በመጠቀስ ነው። የስር ፍርድ ቤት ይህንኑ የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው በማስረጃነት የቀረበው የባለሙያ ሰርቬይ ሪፖርት ጎማዎቹ ወደባህር የገቡት በመርከቦቹ ግጭት መሆኑን እንደሚያሳይ፣ አመልካች ጎማዎቹ በሌላ ምክንያት የጠፉ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የሌለ መሆኑንና በባህር ሕጉ አንቀጽ 197(1(ሐ)) ስር በባህር ላይ ለደረሰው ጉዳት ወይም ድንገተኛ መሰናክል ምክንያት ለደረሰ ጉዳት አመላላሹ ኃላፊነት እንደሌለበት መደንገጉንና ጉዳቱ በሌላ ምክንያት የተከሰተ ነው ከተባለም በባ/ሕ/ቁጥር 197(1(ከ))ስር አመላላሹ ኃላፊነት የሚኖርበት በአመላላሹ ጥፋት ወይም በእርሱ ወኪሎችና አሽከሮች ቸልተኝነትና ጥፋት ምክንያት መምጣቱ ሲረጋገጥ መሆኑንና በአመልካችና በተጠሪ መካከል ባለው ክርክር ግን የአመላላሹ ጥፋት ወይም የእርሱ ሰራተኞች ቸልተኝነት መኖሩ ያለመረጋገጡን በመተንተን ነው። ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች ተጠሪ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ አልተወጣም በማለት ክስ የመሰረተ እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ ሊያስረዳ የሚችል ለጉዳዩ አግባብነትና ጥንካሬ ያለውን ማስረጃ ማቅረብ ያለበት መሆኑን ነው። ተጠሪ በውሉ የተጣለበትን ግዴታ በመወጣት ሂደት ውስጥ በነበረበት ጊዜ በተለይም ጎማዎቹ በመርከቡ ሲጫኑ ጥንቃቄ ባለማድረግ በተገቢው አኳኋን ያልደረደራቸው ከሆነና በዚህ ምክንያት ጎማዎቹ በመርከቦቹ ግጭት ጊዜ ወደባህሩ ተወርውረው የገቡ ናቸው ተብሎ በአመልካች ክርክር እስከቀረበና በተጠሪ ደግሞ የአመልካች ክርክር እስከተካደ ድረስ የአመልካችን ክርክር የማስረዳት ግዴታ የራሱ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ክርክሮች የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ሥርዓት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። ከላይ እንደተገለጸው ለጉዳዩ ተገቢ ነው የተባለው የባለሙያ ሰርቬይ ሪፖርት ቀርቦ በማስረጃነቱ ሊሰጠው የሚችለው ክብደት በስር ፍርድ ቤት ታይቶ ማስረጃው የተጠሪን ጥፋት ሊያስረዳ የማይችል መሆኑ ተረጋግጧል።

ይህ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባለው የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል። ስለሆነም በጉዳዩ ላይ የቀረበው ማስረጃ ክብደቱ ተመዝኖ የተጠሪን ጥፋት ሊያስረዳ አይችልም ተብሎ ፍሬ ነገርን በሚያጣሩና ማስረጃን በሚመዝኑ ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ከተደረሰ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ ሊለውጠው የሚችልበት አግባብ የለም። ለማስረጃው የሚሰጠው ዋጋ የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ነው ከተባለ ደግሞ በባ/ሕ/ቁጥር 196(2) እና 197(1(ሐ)) እና (ከ)) ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ ተጠሪ ለጉዳዩ ኃላፊ የሚሆንበት ሕጋዊ አግባብ የለም። በአጠቃላይ ተጠሪ አንዳችኮነቱንና እቃው በመርከቦቹ ግጭት ምክንያት ከመርከብ ወደ ውሃ በመውደቅ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ሳይክድ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአመልካች ማስረጃ ተጠሪን ተጠያቂ ሊያስደርግ በሚችል በበቂ ማስረጃና ሕግ ያልተደገፈ መሆኑን በማረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰጡ መሆኑን የተገነዘበን በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87610 ሐምሌ 03 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71115 ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ውጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 24 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ውልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አለመልካች፡- ጎልደን ሮዝ አግሮ ፋርምስ ኃ/የተ/የግ ማህበር - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- አቶ ሐሊፎም ተስፋ ማሪያም - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍረድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፊደ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቀረቦ የነበረው ክስ የሠሌዳ ቁ. 3-24690 ኢት እና የልዩ ተጐታች/ተሳቢ/ ሠሌዳ ቁ. 3-09435 ኢት የሆነ የከሣሽ ተሽከርካሪዎች ናይትሪክ አሲድ የተባለ በኮንቴነር የታሸገ የተከሣሽ ንብረት/ጭነት/ ናይኮን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወይም ታሪንሶ አፍሪካን ትራንዚት በሚባል ተወካይ አማካይነት በከሣሹ ተሽከርካሪዎች ተጭኗል፡፡ ጭነቱን ወደ አዲስ አበባ ለማጓጓዝ እንደተጀመረ በኢትዮጵያ ጅቡቲ ድንበር አካባቢ ሲደርስ አሲድ የተጫነበት ኮንቴነር በየአቅጣጫው ማፍሰስና ማንጠባጠብ ጀምርዋል፡፡ በዚህም በዋናው የከሣሽ ጎታች (power unit) ተሽከርካሪ ላይ መጠነኛ ጉዳት የደረሰ ሲሆን ልዩ ተጎታቹ /ተሳቢ/ ግን በአሲዱ ሳቢያ በጉማው፣ በቸርኬው፣ ፖንሲውና በሌሎች አካላት ላይ እጅግ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ በአገልግሎት ላይ ማዋል እንደማይችል የባለሙያው ሪፖርት አረጋግጧል፡፡ በዚህ የተነሣ ተከሣሽ ከከሣሹ ጋር ባደረገው ድርድር መሠረት ዋናውን ተሽከርካሪ በጥገና የሚያስፈልገውን ወጪ እንደሚከፈል ወይም እንደሚያሠራ ልዩ ተጎታቹ ግን ከጥቅም ውጪ ስለሆነ ባለሙያው ባቀረበው ሪፖርት መሠረት ዋጋውን እንደሚከፍል በጊዜው በቃል ተስማምቷል፡፡ በመሆኑም ልዩ ጎታች ላይ ለደረሰው ጉዳት ለጥገና የሚያስፈልገውን ብር 26,154 (ሃያ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሃምሣ አራት ብር) ልዩ ተጎታች ወይም ተሳቢ ለመተካት የገበያ ዋጋ ብር 265,000 (ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ብር) እንዲሁም የተቋረጠ ገቢ 68,427.70 (ስልሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሃያ ሰባት ብር ከሰባ ሣንቲም) ይሆናል፡፡ ባጠቃላይ ተከሣሽ ብር 359,581.70 (ሦስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ አንድ ከ ሰባ ሣንቲም) ከእነ ህጋዊ ወለድ ጭምር እንዲከፍል እንዲወስንበት በማለት ነው፡፡

ተከሣሽ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተከሣሽ የዕቃው ተረካቢ እንጂ ላኪ አይደለም፣ ታሪንሶ አፍሪካ ትራንዚት ሰርቪስ ወይም ኒካን ኃለ/የተ/የግል ማህበር የተከሣሽ ወኪሎች አይደሉም፣ ተከሣሽ ለደረሰው ጉዳት ለከሣሽ ለመክፈል የገባው አንዳችም ስምምነት የለም፣ ተከሣሽ በከሣሽ ንብረቶች ወይም አሮጌ ተሽከርካሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት በአዲስ ለመተካት ኃላፊነት የለበትም፣ ከሣሽ በሰሌዳ ቁ. 3.09435 ኢት ተሳቢ ዋጋ ብር 265 000 ነው ያለውን በተመለከተ ሊከፍል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚገባው የካሣ መጠን በተሸከርካሪው ዋጋ ላይ ለአገልግሎት ዘመን ታስቦ የሚሆነውን የእርጅና እና የአሞርታይዘሽን ቅናሽ ታስቦ ለሚኖረው የተሸከርካሪ ዋጋ ነው እና ተቋረጠ ለተባለው ገቢ በአመታዊ ገቢው መሠረት ከግብር አስገቢ መሥሪያ ቤት የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ ተከሣሽ ለቀረበው ክስ ኃላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለውን ጭብጥ ከያዘ በኋላ ዕቃውን በከሣሽ መኪና /ተሸከርካሪዎች/ ላይ ያስጫነው የናይኮን ኃለ/የተ/የግል ማህበርም ሆነ ታሪንስ አፍሪካን ትራንዚት ሰርቪስ የተከሣሽ ወኪሎች መሆናቸውን ባለማስረዳቱና ተከሣሽ የደረሰውን ጉዳት ለመካስ የተዋዋለ ስለመሆኑ የሚያመለክት ማስረጃ ባለመኖሩ ተከሣሽ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በማስቀረብ ግራ ቀኙን ካከራከር በኋላ የአሁን አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት ከወሰነ በኋላ የካሣውን መጠን በተመለከተ ከሣሽ ቀረብኝ የሚለውን ገቢ በተመለከተ የቀረበውን ነጥብ ውድቅ በማድረግ በሁለቱም ተሸከርካሪዎች ደረሰ የተባለውን በአጠቃላይ ብር 291,154 (ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አራት ብር) ጉዳቱ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ 9% ወለድ ጋር የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ ተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሠኘት ይግባኙን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ሲሆን የአመልካች ጠበቃ በቀን 30-12-2002 ዓ.ም በሦስት ገጽ የፃፈው የቅሬታ ፍሬ ሃሣብ ተጠሪ ለባለቤቱ ለማድረስ የተረከበውን እቃ በአግባቡ ሳያደርስ በመቅረቱ ሊጠየቅ ሲገባው አሲዱ ተሸከርካሪዎቹ ላይ ፈሷል በማለት ያቀረበው ክስ ስለአጓጓዥ ግዴታዎች ተብለው በንግድ ሕጉ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች የሚፃረር በመሆኑ ኃላፊነት አለበት ቢባል እንኳ የተሸከርካሪዎቹ የአገልግሎት ዘመን እርጅና ተቀናሽ ሳይደረግ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በጠበቃው አማካኝነት ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የ3 ገጽ መልስ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ የአጓጓዥን ኃላፊነት በተመለከተ ተሸከርካሪው በመገልበጥ ወይም በመገጨት የደረሰ አደጋ ሳይሆን በዕቃው በራሱ አስተሻሸግ ጥፋት በመሆኑ እና የደረሰውን ጉዳት አግባብነት ባለው ባለሙያ አመልካችም ሆነ ተጠሪ ያስገመቱት በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም፡- አመልካች የራሱ ንብረት በሆነውና በተጠሪ ተሸከርካሪዎች ላይ በተጫነው ናይትሪክ አሲድ መፍሰስ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የአመልካች ንብረት የሆነው እና በመፍሰስ በተጠሪ ተሸከርካሪዎች ላይ ጉዳት አድርሷል የተባለው ናይትሪክ አሲድ በኮንቴነር እንደታሸገ ከጅቡቲ ወደብ በተጠሪ ተሸከርካሪዎች ላይ ያስጫነው አካል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ናይኮን ኃላፊነቱ የተ/የግል ማህበር ወይም ታሪንሶ አፍሪካን ትራንዚት ሰርቪስ የአመልካች ወኪል ስለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ያረጋገጠው ጉዳይ ከመሆኑም በላይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ አከራካሪ አልሆነም፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 561 እና ተከታዮቹን በምንመለከትበት ወቅት የማጓጓዝ ሂደቶችን በሚመለከት ተሣታፊ አካላት መካከል ላኪ፣ ተቀባይና አጓጓዥ ኃላፊነቶች በሰፊው ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በዚህ ጉዳይ ጉዳት አድርሷል የተባለው የአመልካች ንብረት የሆነው ናይትሪክ አሲድ አደገኝነት ያለው ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ከመሆኑ አኳያ በአግባቡ መታሸግ ያለበት ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም በአግባቡ መታሸጉን ማረጋገጥ ያለበት ወገን ደግሞ የላከው ስለመሆኑ በንግድ ሕግ ቁ. 578(2) ሥር የተደነገገ በመሆኑና በዚህ ጉዳይ ደግሞ ላኩ ሊባሉ የሚገባቸው ከጅቡቲ ወደብ እቃውን ያስጫኑት የአመልካች ወኪሎች በመሆናቸው እና አመልካች እንደ የእቃው ባለቤትነት ይዜ መርዘማነት ያለው ንብረት ከመጫኑ በፊት በአግባቡ ስለመጫኑ የማስረዳት ኃላፊነቱ የተጣለበት በመሆኑ ይሄንን ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ከላይ የተጣለበትን የህግ ኃላፊነት ስለመወጣቱ ካለማስረዳቱም በላይ የአሁን ተጠሪ የተጫነው ናይትሪክ አሲድ በአግባቡ ያለመታሸጉን እያወቀ የጫነ ስለመሆኑ እና በዚሁም የተነሣ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር የሌለ በመሆኑ ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚሁ መሠረት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍታሐብሔር ሕግ ቁ. 2069(1)ን በመጥቀስ አመልካች ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ማመልከቱ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው የህግ ድንጋጌ ያለመሆኑን ይዜ ችሎት የተረዳው ሲሆን ከውጤቱ አኳያ ግን ከላይ በዚህ ችሎት እንደተመለከተው አመልካች ኃላፊነት አለበት ወደ ሚለው መደምደሚያ የደረሰ በመሆኑ ምክንያቱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 342 መሰረት በመለወጥ የተሰጠውን የኃላፊነት ውሣኔ ተቀብለናል፡፡ በዚህ መሠረት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡትን የኃላፊነትና የካሣ መጠን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 54167 ሐምሌ 20 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 78535 ህዳር 3 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ተሸከርካሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት በቀን 11-2-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሠጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5. በትውስት የመጣው የመዝ.ቁ.05737 የሆነ መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊረማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 69603

ህዳር 08 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሀብተወልድ ዘርጋው የጂትሮ የስራ አመራር የማማከር

አገልግሎት ድርጅት ባለንብረት - ጠበቃ ተስፋ አዱኛ ቀረቡ

ተጠሪ፤- 1. አቶ ሳሙኤል አሰፋ የጂትሮ ሊደርሺፕ ኤንድ ማኔጅመንት

ወይም ዩቶር ሊደርሺፕ ኤንድ ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት- ራሣቸው ቀረቡ

2. የንግድ ሚኒስቴር - ነ/ፈጆ ተካልኝ ከድር ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንግድ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 686/2002 መሰረት የሚሰጣቸው የንግድ ስም ጉዳዮች ውድቅ የሚደረጉበትን አግባብና ቅሬታ ያለው ወገን ሊከተለው ስለሚገባው መፍትሔ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ ክሱ የተመሰረተውም ባሁኑ ተጠሪና በንግድ ሚኒስቴር ላይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በተጠሪና በንግድ ሚኒስቴር ላይ የመሰረተው የክስ ይዘት ባጭሩ፡- በንግድ ሚኒስቴር የተመዘገበውና ያሁኑ ተጠሪ የሚጠቀምበት ጂትሮ ሊደርሺፕ ኤንድ ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት (Jethro leadership and managemet institute) የሚለው የንግድ ስም አመልካች ከተጠሪ ቀደም ብለው ካስመዘገቡት ጂትሮ የስራ አመራር የማማከር አገልግሎት (Jethro management consultancy service) ከሚለው የንግድ ስም ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ የአመልካችን ተቃውሞ ሳይቀበል ይሄ ተመሳሳይ የንግድ ስም እንዲመዘገብ ማድረጉ በአመልካች ላይ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የሚያስከትል መሆኑን ዘርዝረው 1ኛ ተጠሪ "Jethro" በሚለው የንግድ ስም እንዳይጠቀም እንዲወሰንላቸው፣ 2ኛ ተጠሪም ለ1ኛ ተጠሪ የመዘገበውን የንግድ ስም እንዲሰርዝ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎችም በተከሳሽነታቸው ቀርበው በሰጡት መልስም የንግድ ስም ፈቃድ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 ሲሰጥ ተቃውሞ የሚያቀርበው ወገን ለንግድ ሚኒስቴር ተቃውሞውን በማቅረብ ጉዳዩ ከታየ በሁዋላ ቅሬታ ካለው በይግባኝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይታያል እንጂ ቀጥታ ክስ የሚመሰረትበት ጉዳይ ባለመሆኑ ጉዳዩ ከፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ውጪ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 61"ን" መሰረት በማድረግ ጉዳዩ በይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ እንጂ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀጥታ ክስ የሚስተናገድ አይደለም በማለት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 231(ሀ)(ለ) መሰረት ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ የማስተናገድ ስልጣን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሁኖ እያለ ጉዳዩ በይግባኝ ነው የሚታየው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የሥር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 61 መሰረት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የነበረው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ 2ኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 6፣ 7፣ 30 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ የመስጠት ስልጣን ያለው ሲሆን ይህንኑ ስልጣን ተግባራዊ ሲያደርግ የሚያስፈልጉትና ሊከተላቸው የሚገባቸው ስርዓቶች በአዋጁ ተዘርዝረው ተደንግገው እናገኛለን፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 2(9) እና (16) ድንጋጌዎች ከአዋጁ አንቀጽ 61 ድንጋጌ ጋር ተጣምረው ሲነበቡ ንግድ ሚኒስቴር የንግድ ስም በመመዝገብ ሂደት የሚቀርበውን አቤቱታ መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን አስተዳዳራዊ ውሳኔ መስጠት የሚችል መሆኑን ያሳያሉ፡፡ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን በሕግ ጉዳዮች ብቻ አቤቱታውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 61 ድንጋጌ የሚያስቀምጥ ሲሆን በድንጋጌው አቤቱታው ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት አግባብ የተመለከተ ቢሆንም አቤቱታው ቀጥታ ክስን ወይም ይግባኝን የሚመለከት ስለመሆኑ በግልጽ ሁኔታ በድንጋጌው ተቀምጧል ለማለት አይቻልም፡፡ ይሁን እንጂ በሕጉ ረገድ ያለው የውሳኔ አሰጣጥና የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ሕጉ 2ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን በሕግ ጉዳዮች ላይ ብቻ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት (The right to Appeal) እንዳለው ከማስቀመጡ ውጪ ይግባኙ በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች በየትኛው እርከን ለሚገኝ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ ግልጽ በሆነና አሻሚነት በሌለው አነጋገር አያስቀምጥም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ሕጉን መተርጎም ተገቢ ይሆናል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 61 ድንጋጌ ርእሱ ሲታይ አማርኛው "በአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ" በሚል የተቀመጠ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጂ ደግሞ "Submission of Complaints on Administrative Decisions)" በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ የድንጋጌው እንግሊዝኛ ትርጉም ዝርዝር ሲታይ Any person or a business person or a commercial representative against whom an administrative decision has been taken by the registering 0ffice or the appropriate authority may lodge appeal in connection with his complaints to regular courts only on matters of law. በሚል የተቀመጠ መሆኑን ያስረዳል፡፡ እንግዲህ ሕጉ በይዘቱና በቅርጹ ይህን የሚመስል ከሆነ ይግባኝ የሚለው የሕጉ አገላለፅ ለየትኛው ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩ መቅረብ ያለበት የሚለውን ጥያቄ ይፈታ ዘንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የይግባኝ ትርጉሙንና የአቀራረብ ሥርዓቱን በአጠቃላይ ማየቱን፣ የአመልካች መስሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣውን ሕግና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሕጎች የሚያስቀምጡትን የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት መመልከቱና ግንዛቤ መውሰዱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ታዋቂው የ “ Black’s Law Dictionary” ይግባኝ የሚለውን ቃል ሲተረጎም A proceeding undertaken to have a decision reconsidered by bringing it to a higher authority, especially, the submission of a lower court’s or agency’s decision to a higher court for review and possible reversal. በሚል ያስቀምጣል፡፡ ከዚሁ መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ በበታች አካል የተሰጠ አንድ ፍርድን ወይም ውሳኔን በመቃወም ለበላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረብ የስር ፍርዱ/ ውሳኔ እንደገና የሚታይበትን ወይም እንዲጣራ የሚደረግበትን ወይም ሊለወጥ የሚችልበትን ሥርዓት የሚያመላክት መሆኑን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 320/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ሲታይም በፍትሐብሔር ወይም በሌሎች ሕጎች ውስጥ በሌላ ሁኔታ እንዲፈጸም የሚያዝ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤት በተወሰነበት የመጨረሻ ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችሉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የይግባኝ ትርጉም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪ የነበረና በተሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን ይህንኑ ቅሬታውን ለበላይ ወይም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ የበታች ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ እንዲሻሻል፣ እንዲለውጥ ወይም በጠቅላላው ውድቅ እንዲሆንና ዳኝነቱ ለእሱ እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 ደግሞ የይግባኝ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 61 ድንጋጌ 2ኛ ተጠሪ በሰጠው የአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው በሕግ ጉዳዮች ላይ ብቻ አቤቱታውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ብሎ ሲያስቀምጥ “አቤቱታ” የሚለው የአማርኛ ሐረግ በእንግሊዝኛው "Appeal" በሚለው ቃል ተተርጎሞ መቀመጡ የሚያሳየው በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት መሆኑን እንጂ ቀጥታ ክስ የሚቀርብበት አለመሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም በሕጉ አነጋገር በፍሬ ነገር ላይ አቤቱታ ማቅረብ የማይቻል መሆኑ መቀመጡ ቴክኒካዊ በሆኑ ምክንያቶች አስተዳደራዊ አካሉ የሚሰጠው ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆኑ ታምኖበት በመሆኑ ፍሬ ነገር ላይ አቤቱታ እንደማይቀርብ ተከልክሎ በሕግ ነጥብ ላይ ብቻ ቀጥታ ክስ ይቀርብባቸዋል ብሎ መደምደም የአመልካች መስሪያ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ውጤት ያለው ማድረግ ያስችላል ተብሎ የማይታሰብ መሆኑን 2ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት የሚያስፈጽማቸው ሕጎች አውደ ንባብ (contextual interpretation) የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሠረት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን በሕግ የተሰጠው መብት ይግባኝ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ መመስረት አይደለም፡፡ በሕጉ የተዘረጋው ሥርዓት ይግባኝ ከሆነ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በጉዳዩ ላይ የይግባኝ ሥልጣን ያለው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በቀጥታ ክስ ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት የሰጡት ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 181815 ታህሳስ 22 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 103990 መጋቢት 05 ቀን 2003 ዓ.ም. የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. 2ኛ ተጠሪ የንግድ ስም ምዝገባን አስመልክቶ በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ያለበት ወገን ያለው መፍትሔ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መመስረት አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 63454

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-ዳት ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግል ማህበር ባለቤት ዶ/ር ጤናዬ አብተው
አልቀረቡም

ተጠሪ፡-1.የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ፅ/ቤት- ነ/ፈጅ ታምሬ ሀይሌ ቀረበ

2. ሲቫ ሳንቴ አሊማሊ ኤስአ/በፈንሳይ አገር የተመዘገበ- ጠበቃ ጥላሁን ደስታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአመልካች መስሪያ ቤት በአዋጅ ቁጥር 501/98 መሰረት በሚሰጡት ውሳኔዎች ቅሬታ ያለበት ወገን አቤቱታውን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ የሚገባበትን ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፊዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ናቸው፡፡የአሁኑ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ መሰሪያ ቤት ላይ የመሰረቱት የክስ ይዘት ባጭሩ፡-አመልካች በሕንድ ሀገር ከሚገኝ አሺሽ ላይፍ ሳይንስ ከተባለ ድርጅት "VEREVIN" የተባለ የእንስሳት መድኃኒት እያስመጣ በኢትዮጵያ ለማከፋፈል ሙሉ እውቅና ያለው መሆኑን፣ ይህን "VEREVIN" የሚለውን ስምና ተጨማሪ ALS የሚል በቀይ ሳጥን ያለመስቀል የሰራን ምስል በንግድ ምልክትነት እንደሚዘገብልን በማለት ለተከሳሽ አመልክተው ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን ገልጸ ይኸው የንግድ ምልክት እንዲመዘገብላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም አመልካች የንግድ ምልክት ምዝገባ እንዲደረግለት ከማመልከቱ በፊት "VEREVIN" ተመሳሳይነት ያለው የንግድ ምልክት ለእንስሳት መድሃኒትነት ምርት ተጠሪ በመመዝገቡ ምክንያት የአመልካችን ጥያቄ አሳካሪ የንግድ ምልክት በሚል መነሻነት አለመመዝገቡን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪም ወደ ክርክሩ በጣልቃ ገብነት ተካፋይ ሁኖ በሠጠው መከላከያ መልስ አመልካች እንዲመዘገብለት የጠየቀው የንግድ ምልክት ጣልቃ ገቡ ካስመዘገበና "VEREBIN" ተብሎ ከሚታወቀው ጋር ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ ሊመዘገብለት አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ እና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ከአጣራ በሁዋላ አመልካች እንዲመዘገብላቸው የጠየቁት ምልክት በአጻጻፉና በአጠራሩ ከጣልቃ ገቡ ምልክት ጋር ተቀራራቢ እንደሆነና ተጠቃሚውን ሊያሳክር እንደሚችል መረጋገጡን ገልፆ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ የአመልካች የንግድ ምልክት እንዲመዘገብላቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡ከዚህም በኋላ ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የአመልካች የንግድ ምልክት ሊመዘገብ አይገባም ተብሎ መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 2(4)፣3 እና 8(4) ድንጋጌዎችን የሚጥስ ነው በማለት ውሳኔው እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ወደ ኢትዬጵያ እያስመጣ የሚያከፋፍለው ምርት "VEREVIN" የሚባለው በሕንድ ሀገር ተመዝግቦና ተመርቶ የሚሠራጭ ሲሆን 2ኛ ተጠሪም ወደ ኢትዮጵያ እያስመጣ የሚያከፋፍለው ምርት "VEREBIN" የሚባለው በፈረንሳይ ሀገር ተመዝግቦና ተመርቶ የሚሰራጭ ከመሆኑ አኳያ የአመልካች ምርት በኢትዬጵያ ውስጥ አይመዘገብም ተብሎ በ1ኛ ተጠሪ መክልከሉን ከ2ኛ ተጠሪ ምርት ጋር ተቀራራቢ በመሆኑ ተጠቃሚውን ያሳክራል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የመወሰን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንጸር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ጉዳዩ በቀጥታ ክስ መቅረቡና በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየቱ ባግባቡ መሆን ያመሆኑ ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ቀጥታ ክስ መሆኑንና ጥያቄአቸውም 1ኛ ተጠሪ አለመዘግብም ያለው የንግድ ምልክት እንዲመዘገብ እንዲወሰንላቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 320/1995 አንቀጽ 6(1) መሰረት የንግድ ምልክት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማመልከቻዎችን በመቀበል አግባብ ባለው የአእምሯዊ ንብረት ሕግ መሰረት ምርመራ በማካሄድ ውሳኔ የመስጠትና በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 36 መሰረት በተመዘገበ የንግድ ምልክት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን በማየት ፈራሽ የማድረግ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በግልፅ ያስገነዝባሉ፡፡አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17(1) ድንጋጌ ሲታይም አመልካች መስሪያ ቤት ስለንግድ ምልክቱ ምዝገባ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡የአዋጁ አንቀጽ 49 ሲታይ ደግሞ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤትን ያሳያል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በአዋጁ አንቀጽ 47 መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ በተመለከቱት ጉዳዩችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችንና ተዛማጅ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የሚኖራቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በሚል የሚደነግግ ነው፡፡እንግዲህ በሕጉ ረገድ ያለው የውሳኔ አሰጣጥና የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ሕጉ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው የመጨረሻ ውሰኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት(The Right to Appeal) እንዳለው በግልፅ ከማስቀመጡ ውጪ ጉዳዩ በቀጥታ ክስ የሚቀርብበት ጉዳይ ስለመሆኑ የሚያመላክተው ሁኔታ የለም፡፡በሌላ በኩል አግባብነት ያላቸው የአእምሯዊ ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጎች ሲታዩ 1ኛ ተጠሪ መስሪያ ቤት በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን ቅሬታውን ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ የሚችለው በይግባኝ ስርዓት ስለመሆኑ እና ይህን ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ደግሞ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 25/1988 ከአእምሯዊ ንብረት ሕጎች ጋር ተጣምሮ ሲታይ የሚያስገነዝበን ጉዳይ መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 59025 ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝን ፍርድ ቤት የሚያስገደድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17(1) ድንጋጌ ርእሱ ሲታይ አማርኛው "ይግባኝ የማቅረብ መብት" በሚል የተቀመጠ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጂ ደግሞ "The Right to Appeal" በሚል የተቀመጠ ነው፡፡እንግዲህ ሕጉ በይዘቱና በቅርጹ ይህን የሚመስል ከሆነ ይግባኝ የሚለው የሕጉ አገላለፅ ለየትኛው ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩ መቅረብ ያለበት የሚለውን ጥያቄ ይፈታ ዘንድ የይግባኝ ትርጉሙንና የአቀራርብ ሥርዓቱን በአጠቃላይ ማየቱን፣የአመልካች መስሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣውን ሕግና ለመስሪያ ቤቱ ስልጣን የሚሰጡ ሌሎች ተዛምጅነት ያላቸው ሕጎች የሚያስቀምጡትን የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት መመልከቱና ግንዛቤ መውሰዱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ታዋቂው የ" Black's Law Dictionary" ይግባኝ የሚለውን ቃል ሲተርጎም "A proceeding undertaken to have a decision reconsidered by bringing it to a higher authority, especially; the submission of a lower court's or agency's decision to a higher court for **review** and **possible reversal**. በሚል ያስቀምጣል፡፡ከዚሁ መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ በበታች አካል የተሰጠ የአንድ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመቃወም ለበላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረብ የስር ፍርዱ/ውሳኔ እንደገና የሚታይበትን ወይም እንዲጣራ የሚደርግበትን ወይም ሊለወጥ የሚችልበትን ሥርአት የሚያመላክት መሆኑን ነው፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 320(1) የተመለከተው ድንጋጌ ሲታይም በፍትሓ ብሔር ወይም በሌሎች ሕጎች ውስጥ በሌላ ሁኔታ እንዲፈጸም የሚያዝ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በፍትሓ ብሔር ፍርድ ቤት በተወሰነበት የመጨረሻ ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችሉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት የይግባኝ ትርጉም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪ የነበረና በተሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን ይህንኑ ቅሬታውን ለበላይ ወይም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ የበታች ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ እንዲሻሻል፣እንዲለውጥ ወይም በጠቅላላው ውድቅ እንዲሆንና ዳኝነቱ ለእሱ እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 ደግሞ የይግባኝ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተመልክተዋል፡፡በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 17(1) ድንጋጌ ስለንግድ ምልክት ምዝገባ ፅ/ቤቱ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ብሎ ሲያስቀምጥ "የመጨረሻ ውሳኔ" የሚለው ሐረግ አቀራረፁና ይዘቱ የሚያሳየው በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት መሆኑን እንጂ ቀጥታ ክስ የሚቀርብበት አለመሆኑን መገንዘብ የሚቻል መሆኑን ነው፡፡እንዲሁም አመልካች የተቋቋመው አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈፅም ወይም ተፈጻሚነታቸውን የሚከታተል እንዲሁም አስፈላጊውን አቅም በመገንባት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጥ መንግስታዊ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 320/95 በመግቢያው ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሆን የዚሁ አዋጅ አንቀፅ 2 ደግሞ "አእምሯዊ ንብረት" እና "ፓተንት" የሚሉትን ቃላት ትርጉም አስቀምጧል፡፡በዚህም መሰረት አእምሯዊ ንብረት ማለት የሰው ልጅ አእምሮ ውጤት በሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ያለ ሕጋዊ መብት ሲሆን ፓተንትን፣የንግድ ምልክትን፣የምስክር ወረቀትንና ኮፒ ራይትን እንደሚጨምር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዋጁ አንቀፅ 2(1)ድንጋጌ የተቀመጠ ሲሆን ፓተንት ማለት ደግሞ የፈጠራ ስራን ለማስጠበቅ የሚሰጥ መብት ሲሆን በፈጠራ፣በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዲስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/187 መሰረት በፈጠራ፣በአነስተኛ ፈጠራና በኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የሚሰጠውን የአስገቢ ፓተንት፣የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የምዝገባ የምስክር ወረቀትን እንደሚጨምር በአንቀጽ 2(2) ስር በግልፅ ሰፍሮ እናገኛል።ይህ መስሪያ ቤት ከሚያስፈጽማቸው ሕጎች መካከል አዋጅ ቁጥር 410/1996 አንዱ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀፅ 2(9 እና 15) ድንጋጌዎች ሲታዩም በአዋጁ በሚገዙ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የመመልከት ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስለመሆኑ በግልፅ ያሳያሉ።በሌላ በኩል የፈጠራ፣የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 ስር የይግባኝ ሰልጣኑ የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስለመሆኑ አንቀፅ 2(1) እና 54 ድንጋጌዎች በአንድ ላይ ሲነበቡ የሚያሳዩት ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ሁኖ አግኝተናል።እነዚህ ሕጎች በአመልካች መስሪያ ቤት ይፈጸማሉ ተብለው ከተጠቀሱት ሕጎች መካከል ውስጥ ሲሆን አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ይግባኙ የሚቀርበው በግልፅ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን ያሳያሉ። ከላይ እንደተገለጸው አመልካች መስሪያ ቤትን ያቋቋመው አዋጅ ቁጥር 320/1995 መስሪያ ቤቱን ለማቋቋም ያስፈለገበትን አእምሯዊ ንብረትን የሚገዙ ብሔራዊ ሕጎችን የሚያስፈፅም ወይም ተፈጻሚነታቸውን የሚከታተል አካል ማቋቋም በማስፈለጉ መሆኑን በግልጽ ያስፈረ ሲሆን ይህ ምክንያት አመልካች መስሪያ ቤት ተመሳሳይ የአእምሯዊ ንብረት ጉዳዮችን ለማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው አካል ከመሆኑ ተዳምሮ ሲታይ ጽ/ቤቱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ይታያሉ፣ወይም በተወሰኑት ይግባኝ፣በተወሰኑት ደግሞ ቀጥታ ክስ ይቀርብባቸዋል ብሎ መደምደም የአመልካች መስሪያ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ውጤት ያለው ማድረግ ያስችላል ተብሎ የማይታሰብ መሆኑን አመልካች መስሪያ ቤት የሚያስፈጽማቸው ሕጎች አውደ ንባብ (Contextual interpretation) የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው።በመሆኑም አመልካች መስሪያ ቤት በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን በሕግ የተሰጠው መብት ይግባኝ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ መመስረት አይደለም።በሕጉ የተዘረጋው ሥርዓት ይግባኝ ከሆነ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና አግባብነት ባለቸው የፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት በጉዳዩ ላይ የይግባኝ ሥልጣን ያለው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው።ሲጠቃለልም የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀፅ 6፣17፣36 እና 49 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ከይግባኝ ትርጉምና አመልካች መስሪያ ቤት ከተቋቋመበት አላማና አመልካች መስሪያ ቤት የሚያስፈፅማቸው ከአዋጅ ቁጥር 501/98 ውጪ ያሉት ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሕጎች ከዘረጉት የይግባኝ አቀራረብ ሥርኣት አንጻር ሲታይ በንግድ ምልክት ምዝገባ ጉዳይ ላይ አመልካች መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት በይግባኝ ሥርዓት የሚከበር እንጂ በቀጥታ ክስ የሚስተናገድ አለመሆኑን፣ይግባኙ መቅረብ ያለበት ደግሞ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው።ከላይ የተመለከተው የሕግ ትንታኔ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 59025 በቀረበው ተመሳሳይ የሕግ ጥያቄ ላይ የተሰጠ ሲሆን ይህ የሕግ ትርጉም ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ ነው።በመሆኑም በሕጉ አግባብ እስካልተለወጠ ድረስ ለዚህ ጉዳይም ተፈፃሚነት ያለው ሁኖ አግኝናል።በዚህም መሰረት የፍርድ ቤት የስረ ነገር ሥልጣን በተከራካሪ ወገኖች ባይቀርብም በፍርድ ቤቱ አነሳሽነትም መነሳትና ቀድሞ እልባት ማግኘት ያለበት ነጥብ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(1ለ)) ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። ስለሆነም የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ በማየት ማስተናገዱም ሆነ ይህንኑ ስህተት ሳያርሙ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶችም በፍሬ ጉዳዩ ላይ የበኩላቸውን ውሳኔ መስጠታቸው ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 59025

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 113848 ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም.፣የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 50700 ጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ.ም. እንዲሁም በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 76501 ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የንግድ ምልክት ምዝገባ አቤቱታ ላይ አመልካች በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ማቅረብ እንጂ ቀጥታ ክስ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 36935

የካቲት 27 ቀን 2004ዓ.ም.

ዳኞች፡- መሥፍን ዕቁበዮናስ

አማረ አሞኘ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) - አቶ ብርሃኑ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ አቶ አዲሱ ዱሬሳ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 36819 መስከረም 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍ/ብሔር ይግባኝ ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 27357 መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለብድር ውል የተሰጠ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የሚያስከትለውን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ፣ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆነው አቶ መሐመድ አብደላ አንደኛ ተከሳሽ፣ አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ከሳሽ (ተጠሪ) ለሥር ፍ/ቤት ታህሳስ 7 ቀን 1997 ዓ/ም ባቀረበው የክስ ማመልከቻ፤ ሁለተኛ ተከሳሽ (አመልካች) ደንበኛ አንደኛ ተከሳሽ አቶ መሐመድ አብደላ፤ ከከሳሽ ድርጅት የወሰደውንና መጠኑ ብር 1,930,066.61 (አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሺህ ስድሳ ስድስት ብር ከስድሳ ሳንቲም) የብድር ገንዘብ አልከፈለም፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ አንደኛ ተከሳሽ በብድር የወሰደውን ገንዘብ የማይከፍል ከሆነ እሱ እስከ ብር 1,600,000 (አንድ ሚሊዮን ሥድስት መቶ ሺህ ብር) የሚከፍል መሆኑን በቁጥር YO/BOF/0478/00 በማረጋገጥ ያለቅድመ ሁኔታ የሚፈል የዋስትና የግዴታ ሰነድ ሰጥቶኛል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ እዳውን በብድር ውሉ መሰረት አልከፈለም፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ በሰጠው የዋስትና ግዴታ መሰረት አንደኛ ተከሳሽ ያልከፈለውን ብድር ዕዳ እንዲከፍለኝ ብጠይቀው ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ ተከሳሽ ለብድሩ አከፋፈል በሰጠው ያለቅድመ ሁኔታ የሚከፈል የዋስትና ግዴታ መሰረት አንደኛው ተከሳሽ ያልከፈለውን የብድር ገንዘብ ዕዳው ተከፍሎ እስከሚለቅ ድረስ ከሚታሰብ 13.5 ፐርሰንት ወለድና በዚህ ክስ ምክንያት ተከሳሽ ያወጣውን ወጪ ጨምሮ ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ከሳሽ ክሱን ያስረዱልኛል የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎችና የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ከክሱ ጋር በማያያዝ ያቀረበ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት በውሳኔው አስፍሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁለተኛ ተከሳሽ (አመልካች) መቃወሚያና መከላከያ መልስ ለሥር ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ የተቋቋመው ለንብረት፣ ለሰው አካልና ህይወት፣ ለኃላፊነት የመድን ዋስትና ለመስጠት ነው፡፡ የተከሳሽ ባለ አክሲዮኖችና የአስተዳደር ቦርዱ በማያውቁት ሁኔታ ከመድን ሥራ ውጭ ተበዳሪውን ዕዳ ለመክፈል የተሰጠው ዋስትና ግዴታ ሰነድ ከሁለተኛ ተከሳሽ መመስረቻ ጽሁፍ መተዳደሪያ ደንብ፣ ስለ መድን ሥራ ፈቃድ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 86/1986 እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተደነገገው ውጭና ሁለተኛ ተከሳሽ ከተቋቋመበት መሰረታዊ ዓላማ ውጭ የሆነ ተግባር ነው፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ተራ የመድን ሽፋን ሰጭ የኢንሹራንስ ድርጅት ነው፡፡ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ በተለይም ያለ ቅድመ ሁኔታ የሚከፈል የዋስትና ሰነድ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመ ልዩ የዋስትና ኩባንያ የሚሰጥ እንጂ በተራ መድን ድርጅት ሚሰጥ የዋስትና ሰነድ አይደለም፡፡ ከሳሽ ይህንን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የፈጸመው ተግባር ህገወጥ ነው፡፡ ስለሆነም ከሳሽ ላቀረበው ክስ ሁለተኛ ተከሳሽ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ከውል ወይም ከህግ የመነጨ ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ ከሳሽ ሁለተኛ ተከሳሽን የሚከስበት ምክንያት የለም፡፡

የሁለተኛ ተከሳሽ ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ እንድፈርም ልዩና ግልጽ የሆነ ሥልጣን አልተሰጠውም፡፡ ከሳሽ ሥልጣን የሌለው መሆኑን እያወቀ ዋና ስራ አስኪያጁ የፈረመውን የገንዘብ ዋስትና ሰነድ በመቀበል የፈጸመው ተግባር ከጅምሩ ሕጋዊ ውጤት የሌለውና ፍርስ በመሆኑ ከሳሽ ተከሳሽን የሚከስበት ምክንያት የለም፡፡ በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ ሊጠየቅ የሚችለው ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ብቻ መሆኑ በንግድ ህጉ አንቀጽ 674 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ ክሱን ያቀረበው ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ የሁለተኛ ተከሳሽ ዋና ሥራ አስኪያጅ ለከሳሽ ዋስትና ሰነድ ሰጥቷል የሚባል ቢሆን የዋስትና ሰነዱ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1725(ሀ) እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1727(ለ) በሚደነግጉት መሰረት በሁለት ምስክሮች ያልተፈረመ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና ፈራሽ ነው፡፡ ከሳሽ አንደኛ ተከሳሽ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ተበድሮ የወሰደ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ከሳሽ ተበዳሪው አንደኛ ተከሳሽ ምን ያህል እንደከፈለና ምን ያህል ዕዳ እንደሚፈለግበት የሒሳብ መግለጫ አላቀረበም፡፡ የከሳሽ ክስ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የከፍተኛ ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ ዕዳውን ያልካደ በመሆኑ የብድር ገንዘቡን የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ከወሰደው የብድር ገንዘብ እስከ ብር 1,600,000 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል የዋስትና ሰነድ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ዋስትና ሰነዱ ከመጀመሪያው ፈራሽና በህግ ፊት ውጤት የሌለው ነው በማለት ያነሳቸው ክርክሮች የህግ ድጋፍ የላቸውም፡፡ ከሳሽ ሁለተኛ ተከሳሽ በሰጠው የዋስትና ግዴታ ሰነድ መሰረት ገንዘቡን እንዲከፍለው መጋቢት 30 ቀን 1994 ዓ/ም እና ጥቅምት 8 ቀን 1995 ዓ.ም. ማስጠንቀቂያ የሰጠ መሆኑን ስላስረዳ ክሱ በይርጋ ቀሪ አይሆንም፡፡ የወለድ መጠኑም በብሄራዊ ባንክ የወጣውን የወለድ ተመን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሁለተኛው ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ተገቢ አይደለም፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ አንደኛ ተከሳሽ ከከሳሽ ወስዶ ካልከፈለውና ክስ ከቀረበበት የብድር ገንዘብ ውስጥ ብር 1,600000 (አንድ ሚሊዮን ሥድስት መቶ ሺህ ብር) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍታብሄር ይግባኝ ችሎት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍታብሄር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የከፍተኛው ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸውን መከራከሪያዎች በሰበር አቤቱታው በመዘርዘር አቅርቧል፡፡ መጋቢት 27 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር ማመልከቻ አመልካች የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠት በአመልካች መመስረቻ ጽሁፍ፣ በመተዳደሪያ ደንቡ፣ ስለ መድን ንግድ ሥራ ፈቃድ በወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 ድንጋጌዎች ከተፈቀደው ውጭ የሆነ ተግባር ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የዋስትና ሰነድ ህገ ወጥና ምንም አይነት ተጠያቂነት እንደማያስከትል በመዘርዘር ያቀረብኩትን ክርክር የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማለፍ መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የአመልካች ዋና ስራ አስኪያጅ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና በንግድ ህግ ቁጥር 363 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን የአስተዳደር ተግባራትን ከማከናወን ውጭ ሌሎች ልዩ ተግባራትን ማከናወን እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ የአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ እንዲፈርም በንግድ ህግ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 ልዩና ግልጽ የሆነ ሥልጣን አልተሰጠውም፡፡ የድርጅቱ ማኔጂንግ ዳይሬክተር የሰጠው የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የዋስትና ውል፣ መያዣ ውል የመዋዋል ሥልጣን የሌለው በመሆኑ ውሉ ከጅምሩ ህጋዊ ውጤት የሌለውና ፍርስ ነው፡፡

የስር ፍ/ቤት አመልካች የሰጠው የዋስትና ሰነድ ነው በማለት በተመሳሳይ ጉዳይ ሌሎች ችሎቶች የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው በማለት ከሰጡት የህግ ትርጉም የተለየ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ የዋስትና ሰነዱ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው የሚባል ከሆነ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የሁለት ዓመት የይርጋ መከራከሪያ ውድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በአመልካች የተሰጠው የዋስትና ሰነድ በህግ የተደነገገውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና ፈራሽ ነው በማለት ያቀረብኩትን ክርክር ሀጉን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም የታለፈ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል፡፡ አመልካች የዋስትና ሰነዱን የሰጠው በተጠሪና ብድሩን በወሰደው በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው መሐመድ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ተበድሮ ከመውሰዱ በፊት ነው፡፡ በአመልካችና በተበዳሪው መካከል የብድር ውል ከመፈረሙ በፊት የወጣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ህጋዊ ውጤት የሚኖረውና አመልካችን የሚያስገድድ አይደለም በማለት ያቀረብኩት ክርክር መታለፉ መሰረታዊ ህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ ከላይ የዘረዘርናቸው ተደራራቢ መሰረታዊ የህግ ስህተቶች የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አመልካች መጋቢት 27 ቀን 2000 ዓ/ም ጽፎ ላቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተጠሪ ጥር 15 ቀን 2001 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የአመልካች መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 4 አመልካች የተቋቋመው ከሌሎች ስራዎች በተጨማሪ አጠቃላይ መድን ሥራና የረዥም ጊዜ መድን ዋስትና ለመስጠት እንደሆነ ይገለጻል፡፡ አመልካች በህግ ያልተከለከሉ ሁሉንም የመድን ስራዎች ለመስራት ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ኢንሹራንስ ድርጅቶች ስለሚሰሩት አጠቃላይ የመድን ስራና የረዥም ጊዜ የመድን ዋስትና ሪፖርት የሚያደርጉበትን ለመወሰን ባወጣው መመሪያ የገንዘብ ዕዳ ለመክፈል የሚሰጥ ዋስትና በጠቅላላ የመድን ስራ ዘርፍ ውስጥ ከሚካተቱት ተግባራት አንደኛው እንደሆነ ይገለፃል፡፡ ለገንዘብ ዕዳ የሚሰጥ ዋስትና አንዱ የመድን አገልግሎት መሆኑ ለጽንሰ ሀሳቡ በህግ መዝገበ ቃላት የተሰጠው ትርጉም ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 23/2000 እና 24/2004

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለገንዘብ ዕዳ የሚሰጥ ዋስትና በመድን ድርጅቶች የሚሰራ ተግባር እንደነበር በመግለጽ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

የአመልካች ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 4(3) አመልካች የተቋቋመው በአጠቃላይ የመድን ሥራና የረኛርም ጊዜ መድን ዋስትና ከመስጠት በተጨማሪ ለኢንቨስትመንት አመች በሆኑ ሌሎች ሥራዎችን መስራትና እነዚህን የንግድ ዓላማ ለመተግበር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያግዝ ማንኛውንም የንግድ ሥራ እንደሚሰራ የሚያረጋግጥ በመሆኑ አመልካች የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠት ይችላል፡፡ አመልካች ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ የስር ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች የሰጠውን የብድር ክፍያ የዋስትና ግዴታ ሰነድ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ወይም የሚተላለፉ ገንዘብ ሰነድ ነው በማለት ክስ አላቀረበም፡፡ ስለዚህ የይርጋው ጊዜ የሚታሰበው በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1845 በተደነገገው መሰረት በመሆኑ ክሱ በይርጋ አይታደግም፡፡ አመልካች የዋስትና ሰነዱ በህግ የተደነገገውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለው ነው ያለው አግባብነት የለውም፡፡ የዋስትና ሰነዱ በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1922፣ በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1925 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1725 የተደነገገውን ፎርም ያሟላል አመልካች የዋስትና ሰነዱን የሰጠው በተጠሪና ብድሩን በወሰደው በስር አንደኛ ተከሳሽ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ተበድሮ ከመውሰዱ በፊት ስለሆነ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ የአመልካች ዋና ስራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የመፈረም ሥልጣን አለው፡፡ የአመልካች ዋና ስራ አስኪያጅ በንግድ ህጉ አንቀጽ 33 እና አንቀጽ 35 የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የመስጠት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ የሚደነግጉ በመሆኑ የአመልካች ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ የአመልካች ስራ አስኪያጅ የዋስትና ሰነድ የመፈረም ሥልጣን የለውም የሚባል ቢሆን፣ አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1808 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚደነግገው መሰረት በሁለት ዓመት የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ያላቀረበ በመሆኑ በሰበር ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ለውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በስር ፍ/ቤት መከራከሪያ አድርጎ ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም የሰበር ችሎት የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት እንዲያሰናብተኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን ነጥቦች በማጠናከርና ጥር 22 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ አምስት ገጽ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በዚህ መዝገብ ግራ ቀኙ የሚከራከሩባቸው ጉዳዮች ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ.40187 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ናቸው፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ ያቀረቧቸው ክርክሮች ውሳኔ ሊያገኙ የሚገባቸው የህግ ጭብጦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አመልካች የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠቱ አመልካቹ የኢንሹራንስ ኩባንያ ከተፈቀደለት፣ ከተቋቋመበትና ህጋዊ ህልውና አግኝቶ ከተመዘገበበት የንግድ ዓላማ ውጭ የተፈፀመ ተግባር በመሆኑ፣ በህግ ተጠያቂ ልሆን አይገባኝም በማለት ያቀረበው ክርክር፣ የህግ መሰረት አለው ወይስ የለውም?
2. አመልካች የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ የዋስትና ሰነድ ለማውጣት ሥልጣን ሳይኖረው ፈርሞ የሰጠውን የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ በመቀበል ተጠሪ ለፈጸመው ተግባር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህጋዊ ተጠያቂነት የለብንም፣ በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር መታለፉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?
3. አመልካች ለተጠሪ የተሰጠው የገንዘብ ግዴታ የዋስትና ሰነድ፣ ስለ ዋስትና ውል የተደነገጉትን ፎርማሊቲዎች የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና በኃለፊነት የማያስጠይቅ ነው፣ በማለት ያቀረበው ክርክር መታለፉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?
4. ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም?
5. አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ መሰረት በኃላፊነት ይጠየቃል ወይስ አይጠይቅም? አመልካች በኃላፊነት ይጠይቃል የሚባል ቢሆን የአመልካች የኃላፊነት መጠን ምን ያህል ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

1/ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 40187 የሰጠው ሰፊ ትንታኔ በዚህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ ላቀረቡት ክርክር ገዥነት ያለው ነው፡፡

ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አዋጅ ቁጥር 86/86 የመድን ንግድ ሥራ ዓይነቶች የሚላቸው ሕግ አውጭው በአዋጁ ትርጉም የሰጣቸውን ጠቅላላ የመድን ንግድ ሥራ፣ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ መድን ንግድ ሥራ፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲ(ፖሊሲ)፣ አብይ የመድን ንግድ ሥራ፣ ህይወት መድንና የጠለፋ መድን ሥራዎችን ብቻ እንዳልሆነ

« መድን ንግድ ሥራ ዓይነቶች ወይም የንግድ ሥራ ዓይነት ወይም ሌሎች ሥያሜዎች ባንኩ በዚህ አዋጅ በሚያወጣው መመሪያ የሚደነገግ ትርጉም ይኖራቸዋል» በማለት በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 በግልጽ ደንግጓል፡፡

ይህ ድንጋጌ አዋጁ ሲወጣ ትርጉም ያልተሰጣቸውና ያልተገለጹ አዋጁ ተግባራዊ በሚሆንበት ሂደት በተቆጣጣሪው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ትርጉም የሚሰጣቸውና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እንዲፈጽሟቸው የሚፈቀዱ መድን ንግድ ስራ ዓይነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉና የንግድ ሥራዎቹም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ትርጉም የሚሰጣቸው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው የመድን ንግድ ሥራ እንዲሰራ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው የኢንሹራንስ ኩባንያ፣ በአዋጁ የተተረጎሙና የተገለጹትን የመድን ንግድ ሥራዎች ብቻ ሳይሆን ሌሎች በብሔራዊ ባንክ ትርጉም የሚሰጣቸውን፣ የሚገለጹትና የሚፈቀዱለትን የመድን ንግድ ሥራ ዓይነቶች ለመስራት እንደሚችል የሚደነግግ ነው፡፡

አከራካሪው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) ምን ዓይነት የህግ ተግባር እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23 /2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትርጉም ሰጥቶታል፡፡ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ማለት በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 3 " Financial gurantee bond shall mean an obligation undertaken by an insurance company to pay for the lending bank or another creditors or supplier all outstanding claims arising from the non payment by debtor or debtors" የሚል ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2002 እና 2004 ዓ/ም ባወጣው መመሪያ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ ከልክሏል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ በግልፅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከለከሉ መሆኑን የደነገገው በመመሪያ ቁጥር 23 /2002 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/ 2004 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ነው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ብሔራዊ ባንክ መድን ንግድ ስራ የሚሰሩ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) እንዳይሰጡ በመመሪያ በግልጽ ከመከልከሉ በፊት በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የተሰጡ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች የሚኖራቸውን ህጋዊ ውጤት ባወጣው መመሪያ ግልጽ አድርጓል፡፡ በኢትጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 ከመከልከላቸው በፊት በኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ የተሰጡ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች የፀኑና ሕጋዊ ውጤት ያላቸው መሆኑን በመመሪያ ቁጥር 24/ 2004 አንቀጽ 3 በግልጽ ደንግጓል፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካችና ሌሎች የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 23 /2002 እና መመሪያ ቁጥር 24 /2004 በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) እንዳይሰጡ ከመከልከላቸው በፊት፣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የመስጠት ሥራን እንደ አንድ የመድን ንግድ ሥራ አይነት ሲያከናውኑት የኖሩት ተግባር እንደነበርና ይህም ተግባራቸው ህጋዊ ውጤት ያለውና ኃላፊነት የሚያስከትል መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 4/ 2004 አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የኢትጵያ ብሔራዊ ባንክ በመጀመሪያ መመሪያ ቁጥር 23 /2002/ በማውጣት፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) እንዳይሰጡ የከለከላቸው፣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠት የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ከተቋቋመበት መድን የንግድ ዓላማ ውጭ የሆነ ስራ ነው በማለት አይደለም፡፡ በኢትጵያ ብሔራዊ ባንክ የተደረገው ክልከላ መነሻ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሌላውን ሰው ዕዳ ለመክፈል የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ሲሰጡ ተበዳሪው ብድሩን ባለመክፈሉ ምክንያት በገቡት የዋስትና ግዴታ መሰረት ለባለመብቱ (አበዳሪው) የከፈሉትን ገንዘብ ከባለዕዳው ለማስመለስ የሚያስችላቸው በቂ መያዣ ሚሆን የተበዳሪው ንብረት ወይም ገንዘብ የማይዙ ወይም የማያገኙ በመሆኑና በአገሪቱ አስተማማኝ የሆነ የጠለፋ መድን ዋስትና የሌለ በመሆኑ ምክንያት፣ በኢንሹራንስ ኩባንያዎች ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመከላከል በማሰብ መሆኑን በመመሪያው መግቢያ ላይ በግልጽ አስፍሮታል፡፡

ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች አመልካች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ግልጽ መመሪያ በማውጣት፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) እንዳይሰጡ ከመከልከሉ በፊት ወጭ አድርጎ ለተጠሪ የሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች (Finanicial Gurantee Bonds) መስጠት ከተቋቋምኩበት የንግድ ዓለማ ውጭ የተፈጸሙ ተግባር በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የሌለውና አመልካችን በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የማይችል ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ግልጽ መመሪያ አውጥቶ ከመከልከሉ በፊት ለተጠሪ የሰጣቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች (Finanicial Gurantee Bonds) ፣አመልካች እንዲሰራ ከተፈቀደለት መድን ንግድ ሥራና ከተቋቋመበት የንግድ ዓላማ ውጭ የተሰጠ ሰነድ በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2/ ሁለተኛው ጭብጥ የገንዘብ ዋስትና የማዬታ ሰነዶቹ ወጭ በሆኑበት ወቅት የአመልካች ዋና ስራ አስኪያጅ የነበረውን ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡ የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተገደበ መሆኑን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የዋና ስራ አስኪያጁን ስልጣን መገደብና የስራ አስኪያጁ ስልጣን ላይ የተደረገውን ገደብ በንግድ መዝገብ ውስጥ በሚጻፈው ቃል እንድገባለትና እንድመዘግብለት በግልጽ ባቀረበው ማመልከቻ ውስጥ በመግለጽ፣ የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተገደበ መሆኑ በግልጽ በንግድ መዝገብ በተመዘገበው ቃል ውስጥ እንዲመዘገብ ካላደረገ በስተቀር የህንን መከራከሪያ በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊያደርገው አይችልም፡፡ ይህንንም ከንግድ ሁጉ አንቀጽ 36 አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) ድንጋጌዎች አቀራረጽና ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተቀነሰ ወይም የተገደበ መሆኑን በንግድ መዝገብ በሰፈረው ቃል ውስጥ አለማስመዝገቡ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡

አመልካች በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተቀነሰ መሆኑ እንደተገለጸ በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ ሆኖም ይህ የአመልካች ክርክር የንግድ ሕጉ በአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 ስራ አስኪሃጅነት ሥልጣን ያለው ሰው አንድ ቅርንጫፍ ሥራ ለማስኬድ ብቻ ሥልጣን በመስጠት ስልጣኑን የተወሰነ ለማድረግ ይቻላል፣ ስለሆነም እንደዚህ ያለው የስልጣን መቀነስ ማስታወቂያ በንግድ መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር በዚህ ህግ አንቀጽ 121 መሰረት መቃወሚያ ሊሆንባቸው አይችልም በማለት በግልፅ የደነገገውን ያላገናዘበ ነው፡፡ በተለይም የአመልካች ክርክር በግኝት ህጉ አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) እና የንግድ ህጉ በአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 2 ሌላው አይነት የስልጣን መቀነስ በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆንባቸው አይችልም በማለት ለሶስተኛ ወገኖች በግልጽ የሰጠውን ጥበቃ ያላገናዘበና የህግ ድጋፍና መሰረት የሌለው ነው፡፡ ሕግ አውጭው እነዚህን ድንጋጌዎች የደነገገው በግብይት ሂደት ውስጥ አክሲዮን ማህበሩ ጋር ውል የሚዋዋሉ ሰዎች የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መመርመርና ማንበብ እንደሚያስፈልጋቸውና ድርጅቱ በንግድ መዝገብ ያስገነዘባቸውን ፍሬ ጉዳዮች ብቻ በማየት ከአመልካች ጋር በቅን ልቦናው የሚዋዋሉ ሶስተኛ ወገኖች ውለታው በህግ ተፈጻሚነት የሚኖረው መሆኑን በማረጋገጥ ከፍተኛ ጥበቃ ለመስጠት ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች አመልካች ዋና ሥራ አስኪያጁ ስልጣን ሳይኖረው ለፈረማቸው የገንዘብ ዋስትና የማዬታ ሰነዶች በኃላፊነት አልጠየቅም በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ሥህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3/ ሶስተኛ ጭብጥ አመልካች ለተጠሪ የተሰጠውን የገንዘብ ግዬታ የዋስትና ሰነድ፣ ስለ ዋስትና ውል የተደነገጉትን ፎርማሊቲዎች የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና በኃላፊነት የማያስጠይቅ ነው፣ በማለት ያቀረበውን ክርክር የህግ መሰረት ያለው መሆኑን መመርመር የሚጠይቅ ነው፡፡ በመጀመሪያ የዋስትና ሰነዱ አመልካች ለሌላ ሰው ዕዳ ማለትም የአቶ መሐመድ አብደላ የብድር ዕዳ ለመክፈል የተሰጠ ሰነድ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ሰነዱ ስለዋስትና ግዬታ በፍታብሄር ህግ አንቀጽ 1922 የተደነገጉትን መሰረታዊ መስፈርት የሚያሟላ መሆኑ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች የሰጠው የዋስትና ሰነድ መሆኑንና በፍታብሄር ህግ አንቀጽ 1922 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገጉትን መሰረታዊ ሁኔታዎች የሚያሟሉ መሆኑን በስር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ አመልካች የዋስትና ሰነዱ የፍታብሔር ሕግ አንቀጽ 1725 ንዑስ አንቀጽ (ሀ) የፍታብሄር ሕግ አንቀጽ 1727 በተደነገገው መሰረት በተጠሪና በሁለት ምስክሮች አልተፈረመም በማለት ተከራክሯል፡፡ ሆኖም ይህ የአመልካች ክርክር (Finanicial Gurantee Bond) እንደማንኛውም የዋስትና ውል በተዋዋይ ወገኖች የሚዘጋጅ ሰነድ ሣይሆን የመድን ንግድ ሥራ እንዲሰራ የተፈቀደለት የኢንሹራንስ ኩባንያ በተሰጠው ልዩ ፈቃድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠቅሞ፣ የሚዘጋጀውና የሌላ ሰው ዕዳ ለመክፈል ራሱን ግዴታ ውስጥ የሚያስገባበት የማገቻ ሰነድ እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/ 2004 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 3 ለገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) የተሰጠውን ትርጓሜ ግንዘቤ ውስጥ የሚያስገባ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

እንደዚሁም አመልካች የሰጠው የማገቻ ሰነድ (Bond) የግድ በምስክሮች መረጋገጥ የሌለበት መሆኑን ሕግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 110/1990 በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 ለማገቻ ትርጉም ሲሰጥ "አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጭው የማይከፈልበት፣ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል" በማለት ከተጠቀመው አገላለጽና በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረው በአዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 18 ለዋስትና ሰነድ ከተሰጠው ትርጓሜ ለመረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአመልካች ክርክር በአዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ሥልጣን የተሰጠው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አመልካችና ሌሎች የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ሥያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Finanicial Gurantee Bond) እንዳያወጡ በመመሪያ ከመከልከላቸው በፊት ወጭ ያደረጓቸው የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነዶች (Finanicial Gurantee Bond) የጸኑና ህጋዊ ውጤት ያለቸው መሆኑን " Finanicial Gurantee Bond or other unconditional bonds issued by insurance conpanies and outstanding before the effective date of these directives shall remain enforce until the expiry date or shall be phased out in line with an action plan submitted by each insurance company and agree with the bank" በማለት የገለጸውን የመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ የሚቃረንና የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተበዳሪው አቶ መሐመድ አብደላ ከተጠሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ ባይከፍል እሱ የሚከፍል መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠውን የማገቻ ሰነድ ልዩ ባህሪ ያለውና በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሚዘጋጅና ወጭ የሚደረግ የማገቻ ሰነድ በመሆኑ፣ አመልካች ሰነዱ በሁለት ምስክሮች ስላልተረጋገጠ የዋስትና ሰነዱ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

4/ አራተኛው ጭብጥ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም? አመልካች የሰጠው ሰነድ የመድን ውል አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የሌላ ሰው ዕዳ ለመክፈል የአንድነት የዋስትና ግዴታ የገባ ሰው የዋናውን ባለ ዕዳ ግዴታ ነጻ የሚያደርጉ የይርጋና ሌሎች መከራከሪያዎች በማቅረብ ከኃላፊነት ነጻ እንደሚሆን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1926 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አቀራረጽ፣ ይዘትና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዋሱ ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው የይርጋ ጊዜ ገደብ በዋናው ባለዕዳ ላይ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ እንደሆነ፣ በዋናው ባለዕዳ ላይ የተጀመሩ ክሶች ለዋሱ መቆጠር የጀመረለት የይርጋ ዘመን ያቋርጡበታል በማለት ፍታብሔር ህግ ቁጥር 1929 የደነገጉትን ምክንያት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአበዳሪው በተጠሪና በተበዳሪው አቶ መሐመድ አብደላ መካከል የተደረገው የብድር ውል ላይ ተፈጻሚነት ያለው ስለ ውሎች በጠቅላላው የሚደነግገው የይርጋ ጊዜ ገደብ ነው፡፡ የአመልካች (የዋሱ) ግዴታ ቀሪ የሚሆነው የዋናው ባለዕዳ ግዴታ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የፍታብሄር ህግ ቁጥር 1845 እንደሆነና ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር መቀበላቸውና ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5/ አምስተኛው ጭብጥ አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ መሰረት በኃላፊነት ይጠየቃል ወይም አይጠየቅም? በኃላፊነት ይጠየቃል የሚባል ቢሆን የአመልካች የኃላፊነት መጠን ምን ያህል ነው? ሚለው ነው፡፡ አመልካች አቶ መሐመድ አብደላ ከተጠሪ በብድር የወሰደውን ገንዘብ በብድር ውሉ መሰረት ካልከፈለ እስከ ብር 1,600,000 (አንድ ሚሊዮን ሥድስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ ገንዘብ ለተጠሪ ለመክፈል የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ሰጥተዋል፡፡ ተበዳሪው ዕዳውን በብድር ውሉ መሰረት አለመክፈሉ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የዋስትና ግዴታ እስከሰጠበት ብር 1,600,000 (አንድ ሚሊዮን ስድስ መቶ ሺህ ብር) ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1930፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1924 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1922 ንዑስ አንቀጽ 2ን የመሰረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እንደዚሁም የስር ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ምክንያት ተጠሪ ለዳኝነት የከፈለውን ገንዘብና ሌሎች ወጪዎች አመልካች እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1931 ን መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ በዝርዝር ባየናቸው ጭብጦች ላይ የሰጡት የህግ ትርጉምና ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 36819 መስከረም 24 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 27357 መጋቢት 10 ቀን 2000 የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፣ ለሚመለከተው ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 47004

መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት- ነ/ፈጅ ናሆም ሸዋንግዛው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ባሌ ገጠር ልማት ድርጅት - ጠበቃ በሻዳ ገመቹ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች ሰጠ የተባለው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና (performance Bond) የሚገዛበት የሕግ ክፍልን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ የመድን ውልን መሠረት ያደረገ ነውና በንግድ ሕግ ቁጥር 674 በይርጋ ቀሪ ሆኗል ሲል የግልግል ጉባኤ በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሣኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የሚገዛው በፍትሐ ብሔር በተመለከተው የዋስትና ድንጋጌዎች እንጂ በንግድ ሕጉ በተመለከቱት ባለመሆኑና ይርጋውም የአስር አመት ጊዜ ሁኖ ያላለፈበት ነው ተብሎ በጉባኤው ውሣኔ መሻሩን በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ ለስራ ተቋራጩ የተሰጠው አረቦን /Premium/ ማስከፈል በመሆኑ፣ ይህንን ቦንድ የሰጠው የመድን ድርጅት መሆኑን እና እንደመቼውም የመድን ውሎች ኮንትራክተሩ ለሶስተኛ ወገን ጥቅም መድን የገባ መሆኑ ተረጋግጦ እየለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሕጋዊ ድጋፍ የሌላቸው ምክንያቶች /ትንታኔዎችን/ በመስጠት የግልግል ጉባኤው አብላጫ ድምጽ የሰጠውን ውሣኔ መሻሩ በንግድ ሕግ ቁጥር 654 እና በአለም አቀፍ ደረጃ የታወቁትን አሰራሮችን የሚፃረር ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች ሰጠ የተባለው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ የሚገዛው በንግዱ ሕጉ ስለመድን በተመለከቱት ድንጋጌዎች ነው ወይስ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ስለ ዋስትና በተመለከቱት ድንጋጌዎች ነው የሚለው ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲያቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ለሰበር ችሎት በሰጠው መልስም ተጠሪ ለሚያስራው መንገድ የጨረታ አሸናፊ የሆነው አክሱም ኮንስትራክሽን በኮንስትራክሽን ውሉ አንቀጽ 6 መሠረት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና /Performance bond/ ለማቅረብ በገባው ግዴታ መሠረት የአሁን አመልካች ስራ ተቋራጩ ለሚያደርሰው ማናቸውም የውል ቃለ አለመጠበቅ እስከ ብር 1,101,890 ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመውሰድ ጥቅምት 10 ቀን 1989 ዓ.ም የተፈረመ የመልካም ሥራ ዋስትና ለተጠሪ መስጠቱን፣ ኮንትራክተሩ በውሉ የገባውን ግዴታ ባለመውጣቱ በቀረበው ክስ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካች የተሰጠው ሰነድ በፍ/ብ/ሕጉ የተመለከተው ዋስትና ሆኖ በንግድ ሕጉ የሚገዛ የመድን ሽፍን አይደለም በማለት በ10 ዓመት በይርጋ አይታገደም ሲል የጉባኤውን ብይን መሻሩ ሕጋዊ ነው፤ ሰነዱ የተፃፈው “surety” ተብሎ እንጂ “insurer” አለመባሉን፣ ሕንፃ ተቋራጩ “contracter” እንጂ “insured” ተብሎ አለመገለጽን፤ ሌሎችም በውሉ ውስጥ የተጠቀሱት የተዋዋዮች ወገኖች ስያሜ በፍ/ብ/ሕግ የተጠቀሰውን እንጂ በንግድ ሕጉ የተጠቀሰውን “መድን ሰጪ” እና “መድን ተቀባይ” ያልተባለ መሆኑን፣ የግዴታ አቀባበል ባሕርያትም የመድን ውልን የሚመለከት መሆኑን አመልካች በግልጽ “ዋስ” ተብሎ መግለጽን፤ እንዲሁም ስለ “performace bond” እና “bond” በተለያዩ የሕግ መዝገብ ቃላት እና በመረጃ መረብ የተሰጡትን ትርጓሜዎች እና መሠረት ልማት በሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የተዘጋጀ “የሲቪል ስራ ፕሮጀክቶች የውል እስታንዳርድ” አካል በተደረገው ፌዲክ ሰነድ /FIDIC/ የተሰጠውን ትርጉም የሚያሳየው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ መሆኑን በመዘርዘር ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ለጭብጡ ምላሽ ለመስጠት ያመች ዘንድም የኮንስትራክሽን ስራ ልዩ ባህሪይን መመልከት የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ሰነድ ወይም (ቦንድ) ትርጉሙን ማየትና የዚህን ሰነድ ዓላማ ከኢንሹራንስ ውል ልዩ ባህርይ አንፃር ማየቱ አግባብነት ያለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

እንደሚታወቀው የኮንስትራክሽን ውል መንገድ፣ ሕንፃ፣ የሃይል ማመንጫ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ፣ የባቡር ሐዲድ፣ የውሃና ግድብና ቁፋሮ እና ሌሎች የሲቪል ምህንድስና ስራዎች ለማስገንባትና ለመገንባት የሚደረግ ውል ሲሆን የውሉ አመሰራረትና ውጤት በፍትሐ ብሔር ሕግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የሚገዛ ነው፡፡ የኮንስትራክሽን ውል ባሕርይው ሲታይ በተዋዋይ ወገኖች ብቻ የሚፈፀም ሳይሆን በበርካታ የውል ትስስሮች የተያያዘና ውሉን ለመዋዋልም ሆነ ለመፈፀም ብዙ ስራዎችን የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ አፈፃፀሙ ረዘም ያለና ተገቢውን ጊዜ የሚያስፈልገው መሆኑ ይታመናል፡፡
ወደ መልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ሰነድ /ቦንድ/ ትርጉሙንና ዓላማ ስንመጣ ደግሞ ታዋቂው የብላክስ ሎው የሕግ መዝገበ ቃላት፡-
“Peroformance bond is a bond given by a surety to ensure the timely performance of contract, a third parties agreement to guarantee the completion of construction contract upon the default of the general contractor. Also termed as completion bond, surety bond contract bond.” Suretyship bond a contractual arrangement between the surety, the principal and the oblige where by the surety agrees to protect the oblige if he default in perfoming the principals” contractual obligation.” The bond is the instrument which binds the surety” በማለት የሚተረጉመው ሲሆን ከዚህም በቀላሉ መረዳት የሚቻለው የመልካም ሥራ አፈፃፀም /ቦንድ/ ሰነድ በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውል ስለመፈፀሙ ለማረጋጥ የሚሰጥ ሰነድ፣ ሶስተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገን የሆነ አካል ስራ ተቋራጩ የኮንስትራክሽን ውሉን ካልፈፀመ ስራው በውል መሠረት እንዲፈፀም የሚሰጠው የዋስትና ሰነድ መሆኑን፣ ቃሉም የአፈፃፀም /ማስጠንቀቂያ/ ሰነድ፤ የዋስትና ሰነድ፣ የውል ሰነድ በሚሉ ቃላቶች ሊተካ የሚችል መሆኑን፣ የዋስትና ሰነድ ሰጪ ዋስ ተብሎ የሚጠራ ሶስተኛ ወገን መሆኑን፣ ይህም በባለገንዘብ እና በባለ እዳ መካከል የተደረገን ውል አፈፃፀም ለመጠበቅ የሚገባ ግዴታ መሆኑም፣ እና ዋሱ ግዴታ የገባበት ሰነድ መጠሪያም ቦንድ የሚባል ሰነድ መሆኑ ነው። ከላይ የተመለከተው የሕግ መዝገብ ቃላት የቃሉ ፍቺ ስለ መልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ጉዳይ ሁለት ውሎች የሚደረጉ መሆኑን እና ሶስት ወገኖች መኖራቸውን ያመልክታል። ይህንን ዓይነት የዋስትና ሰነድ /ቦንድ/ የማውጣት ወይም በመስጠት የሚታወቁት በዋናነት ባንኮች እና መድን ድርጅቶች እንደሆኑም ያመለክታል።

በአገራችን የሕግ ማእቀፍ ውስጥ ያሉትን አግባብነት ያላቸውን ሕጐች ስንመለከትም ስለ ቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 2/2/ የአማርኛ ቅጂ፡-
“ማገቻ” ማለት የተወሰነ ነገር በመፈፀሙ ወይም ባለመፈፀሙ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚያገባበት ማንኛውም ሰነድን ይጨምራል” በማለት ሲያስቀምጥ የእንግሊዝኛ ቅጂው ደግሞ፡-
“Bond includes any instrument…whereby a person obliges him self to pay money to another” በሚል አስቀምጦታል።
በዚህ አዋጅ “ቦንድ ወይም ማገቻ” ሰፋ ያለ ትርጉም የተሰጠው ሲሆን በተግባር የሚታወቁት በርካታ የቦንድ ዓይነቶች እንዳሉና እነዚህም በትርጉም ውስጥ ሊሸፈኑ እንደሚችሉ ተጠቃሹ አዋጅ ያሳያል። በዚህ መሠረት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና /performance bond/ bid bond ወይም /የጨረታ ሰነድ/ bail bond /የዋስትና ወረቀት/ /Treasury bond/ /የግምጃ ቤት ሰነድ/ የመሳሰሉት ትርጉሙ ሊያጠቃልል ይቻላል። እነዚህ ሰነዶች የተወሰነ የገንዘብ ነክ ግዴታ መፈጠሩን የሚያመለክቱ የገንዘብ ሰነዶች አሊያም እንደ አግባቡ የዋስትና ሰነዶች ሆነው ሊያገለግሉ የታሰቡ መሆናቸውን ከትርጉማቸው ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል። የዋስትና ሰነድ ማለት ለፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታን ለመፈፀም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ነገር ሲሆን፣ የግምጃ ቤት ሰነድን፣ የተስፋ ሰነድንና ቦንድን ይጨምራል በማለት በአዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀጽ 2(18) 18 ትርጉም ሰጥቶታል። ይህንኑ አዋጅ ቁጥር 57/1989 ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 2(20) ስር ደግሞ የዋስትና ሰነድ ማለት የፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታ ለመፈፀም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ማንኛውም ሰነድ ሲሆን፣የግምጃ ቤት ሰነድን፣ የተስፋ ሰነድንና ቦንድን ይጨምራል የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል።

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሱት አዋጆች ስለቦንድ ትርጉም የተሰጠ ሲሆን አከራካሪውን ጉዳይ ሊገዙ ይችላሉ ተብለው በተከራካሪ ወገኖች ለክርክር መሰረት በሆኑት የፍትሐ ብሔር ሕጉና የንግድ ህጉ ግን በዚህ ረገድ በግልጽ የተቀመጡ ወይም አመልካች የሆኑ ድንጋጌዎች የሉም። በአንድ ጉዳይ ቀጥተኛ ተፈጽሚነት ያለው ሕግ ስለአንድ ቃል ግልጽ የሆነ ትርጓሜ ያለማስቀመጡ ከታመነ በስራ ላይ ባሉት ሕጎች ውስጥ ያለውን ትርጉም መፈተሽና ለአከራካሪው ቃል ትርጓሜ መስጠት የሚፈቀድ ስለመሆኑ የሕግ አተረጓጉም ደንቦች የሚያሣዩት ነጥብ ነው። በመሆኑም የአመልካች ነገረ ፈጅ ስለአመልካች የስራ አፈፃፀም ትርጉም ለመስጠት የኢንሹራንስ ውሉን ከሚገዙ ሕጐች ውጪ ያሉትን ሌሎች ሕጎችን ለውሣኔው መሠረት ማድረግ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት የሚያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት የሌለው ሁኖ አግኝተናል። ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱት ሕጎችን መሰረት በማድረግም የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና መሠረታዊ ባሕርይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከኢንሹራንስ ውልና ከዋስትና ውል ማነፃፀሩ ጉዳዩን የሚገዛውን የሕግ ማእቀፍ ለመለየት የሚያስችል ሁኖ አግኝተናል፡፡

በዚህም መሰረት ስለ የመድን /ኢንሹራንስ/ ውል ምንነት እና አፈፃፀሙን ስንመለክት ደግሞ በ1952 ዓ/ም በወጣው የንግድ ሕግ በአንቀጽ 654 እስከ 712 ተደንግጐ እናገኛለን፡፡ የመድን ውሎች በጽሑፍ ከመደረጋቸውም በላይ "ፖሊሲ" በሚል ልዩ ሰነድ ላይ መደረግ ያለባቸው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1725(ለ)፣1720፣1727 እና 1719(2) እንዲሁም ከን/ሕ/ቁጥር 657(1) ድንጋጌዎች መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመድን ውሉ የሚፀናው ሊፈረም መሆኑን የተመለከትን ሲሆን በመድን ስራ ትልቁ ነገር ተብሎ ሊወሰድ የሚችለው የአረቦን ጉዳይ ሲሆን መድን ሰጪዎች በመድን ገቢዎች ላይ ለሚደርሰው አደጋ ካሣ የመክፈል ግዴታ የሚገቡት ከመድን ገቢዎች በአረቦን መልክ ገንዘብ ስለሚሰበሰቡ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በመድን ውል ከሚታወቁት ነጥቦች መካከል አንዱ የመድን ጥቅም /insurable interest/ የሚባለው ሲሆን ይህም ከመድን ሰጪው ካሣ የሚቀበለው ጉዳት በደረሰበት እለት ጉዳት በደረሰበት ንብረት ወይም እቃ ላይ የመድን ጥቅም ያለው ሰው መሆኑን የሚያስገነዝበን ሲሆን የመድን ጥቅም የሌለው ሰው ካሣ ለመጠየቅ የሚያስችለው የሕግ መሰረት የለውም፡፡ የመድን ጥቅም ያለው ሰው ሲባል እንግዲህ በደረሰው አደጋ ወይም ጉዳት በትክክል የተጎዳ ወይም ሊጎዳ የሚችል ሰው ስለመሆኑ ይታመናል፡፡ ጠቅለል ተደርጐ ሲታይ በን/ሕ/ቁጥር 654(1) ስር እንደተመለከተው የኢንሹራንስ ውል ኢንሹራንስ ሰጪ ተብሎ የሚጠራ ሰው ፕሪሚየም ተከፍሎት አንድ አይነት አደጋ ሲደርስ ተጠቃሚ ተብሎ ለሚጠራ ሰው የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል የሚገባው ግዴታ ሲሆን በንብረት ወይም በሰው ሕይወትና ጤንነት ወይም በሌላ መብት ላይ የአደጋው መድረስ የውሉን ውጤት ለማስገኘት መሠረታዊ ሁኔታ በመሆኑ የአደጋው አይነት ብዙ በመሆኑ በኢንሹራንስ የሚሸፈነው አደጋ በውሉ ላይ የተመለከተው ብቻ ይሆናል፡፡ በአንፃሩ የዋስትና ውል የፍ/ብ/ሕጋችን አንቀጽ 1920 እስከ 1951 ተደንግጓል፡፡ እነዚህን የሕግ ድንጋጌዎች በማነፃፀር የዋስትና ውል ልዩ ባህርያትን ስንመለከት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1921 ድንጋጌ የዋስትና ውል በችሮታ ላይ የተመሰረተ ግዴታ መሆኑን፤ እንዲህም ሲባል ዋሱ ዋስ በመሆኑ የሚያገኘው ጥቅም የሌለ በመሆኑ አንድ ሰው ባለእዳው ሳይጠይቅ ወይም ሳያውቅ ዋስ መሆን እንደሚችል መመልከቱ ግንኙነቱ የግድ ጥቅም ላይ ያልተመሰረተ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ የዋስትና ውል ሌላው ልዩ ባሕርይ ውሉ ደባል መሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1926(1) ስር እንደተመለከተው አቢይ ግዴታ ሲቀር የዋስትናው ግዴታ አብሮ የሚቀር መሆኑ የተደነገገ በመሆኑ የዋስትና ውል እንዲኖር በዋስትና ሊረጋገጥ የሚልች ግዴታ መኖር አለበት፡፡ እንዲሁም የዋስትና ውል ግልጽና የማያሻማ ግዴታ መሆን እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1922(1) እና (2) ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከዚህ ድንጋጌ በስተጀርባ ያለው ምክንያትም ዋስትና አንድ ሰው ራሱ በግል ተጠያቂ ለማይሆንበት ግዴታ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ብሎ የሚሰጠው ማረጋገጫ በመሆኑ ግዴታ ገቢው በግልጽ ተረድቶ ግዴታ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ኃላፊነቱን መሸከም ተገቢ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ የዋስትና ውል ግዴታ ከዋናው ግዴታ እኩል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1924(1) ስር የተመለከተ ሲሆን ውሉ ለባለ ገንዘቡ ብቻ የሚሰጥ ማረጋገጫ በመሆኑ ውጤት የሚኖረው በተዋዋዮቹ ማለትም በዋሱና በባለ ገንዘቡ መሃል ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1922 (3) ስር እንደተመለከተው ሌላው የዋስትና ውል ልዩ ባሕርይ የዋስትና ውሉ የዋሱን ግዴታ መጠን በግልጽ ማስቀመጥ ያለበት መሆኑ ሲሆን የዋስትና ገንዘብ መጠን ዋስትና ውል ላይ በግልጽ ካልተቀመጠ ዋስትናው ውጤት የለውም፡፡ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1920 እስከ 1951 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች የዋስትና ውል ማለት ሁለት ሰዎች ባደረጉት የባለገንዘብነትና የባለእዳነት ግዴታ ግንኙነት ውስጥ ከእነዚህ ተዋዋዮች ውጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሆነ ሌላ ሶስተኛው ባለእዳው እዳውን በመሉ ወይም በከፊል ያልከፈለ መሆኑ ከተረጋገጠ ወይም ግዴታውን በውሉ በተመለከተው አኳኋን በአግባቡ ያልተወጣ ከሆነ እኔ በባለእዳው ሥፍራና አቋም ሁኜ እዳውን እከፍላለሁ ወይም ግዴታውን እወጣለሁ ሲል ለባለገንዘቡ ማረጋገጫ የሚሰጥበት በሕግ አግባብ መቋቋሙ ከተረጋገጠ ከስተጀርባው ለአፈፃፀሙ የሕግ ጥበቃ የሚያገኝ ውል ነው፡፡

ሌላው ከላይ እንደተመለከትነው የዋስትና ግዴታ ሰነድ ብዙ ሰነዶችን ሊይዝ የሚችል መሆኑ ከላይ የተመለከተ ሲሆን የገንዘብ ዋስትና ግዴታ (financial Gureantee Bond) የሚጠቅስ ነው፡፡ ይህ ሰነድ ምን አይነት የህግ ተግባር እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትርጉም የሰጠበት መሆኑን፣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 ዓ.ም አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ3 “Financial guarantee bond shall mean an obligation undertaken by an insurance company to pay for the lending bank or another creditors or supplier all outstanding claims arising from the non payemt by debtor or debtors” የሚል ትርጓሜ ያለው መሆኑ፣ ይህ ሰነድ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1(1) እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 ዓ.ም አንቀጽ 1(3) ለገንዘብ ዋስትና ሰነድ የሰጠው ትርጉምና ከላይ በተጠቀሱት የሕግ ማእቀፎች ሕግ አውጭው የሰጠው ትርጓሜዎች ሲታዩ መሠረታዊ ባህሪውም ሆነ በይዘቱ የመድን ውል ወይም የኢንሹራንስ ፖሊሲ ጋር የማይመሳሰልና መሠረታዊ መስፈርት የሚያሟላ ስላለመሆኑና መገዛት ያለበትም በንግድ ህጉ በተመለከተው የይርጋ ድንጋጌዎች ሳይሆን በፍትሐ ብሔር ሕጉ ዋስትናን በተመለከተ በሚገዙ ሕጐች መሰረት ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 40187 በቀረበው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው ነጥብ ሰነዱ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ ሳይሆን የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ሰነድ ነው፡፡ በብሔራዊ ባንክ ወጥቶ ተግባራዊ የሆነው ከላይ የተጠቀሰው መመሪያ ስለዚህ ሰነድ የሚሰጠው ትርጉም የለም፡፡ መመሪያው ትርጉም የሠጠው ስለገንዘብ ዋስትና ሰነድ ሲሆን ለዚህም “Financial guarantee bond” shall mean a bond payable on demand issued by an insurance company obliging such insurance compamy to pay to a lending bank or another creditor or supplier all outstanding claims arising form non-payment by principal debtor or debtrs; በማለት ከገለፀ በሁዋላ “unconditional bond” shall mean a bond other than financial gurantee bond issued by an insrance company that is payable to the beneficaiary on demand, without any preconditions attached to such payemnt” ሲል ያስቀምጣል፡፡ እንዲህ ከሆነ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የሐረጉ ስያሜ እንዳለ ሲታይ አንድ ሰው አንድን የተለየና የተወሰነ ስራ ለሌላ ሰው ለመስራት ግዴታ ከገባ ይኸው ሰው በውሉ መሠረት የገባውን ግዴታ መፈፀም የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥ ሌላው ሰው የሚያቀርበው ውል ነው፡፡ በመሆኑም የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ሰነድ ብሔራዊ ባንክ በውሉ የተገባው ግዴታ በአግባቡ መከናወን የሚችል በመሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ሰነድ በመሆኑ “uncondtional bond” ተብሎ በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚወድቅ አይደለም፡፡

ከኮንስትራክሽን ሰዎች ጋር በተያያዘ ተፈጽሚነት አላቸው ከሚባሉት ሰነዶች መካከል አንዱ የ”ፊዲክ” የውል ፎርም ነው፡፡ አሰሪ የሆነው ተጠሪና የስራ ተቋራጭ ባደረጉት ውል የሥራና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተማ ልማት ሚኒስቴር የሲቪል ስራዎች ፕሮጀክት ስታንደርድ የውለታቸው አካል እንዲሆን መስማማታቸው በፍሬ ነገረ ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴ የሲቪል ስራዎች ፕሮጀክት ስታንዳርድ ደግሞ “The FIDIC form of contract” አካል ነው፡፡ ይህ የፌዲክ ውል ፎርሙ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ለኮንስራክሽን ስራው በውሉ መሠረት መከናወን ዋስትና የሚሰጥ ሰነድ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የኢንሹራንስ ፖሊሲ አይነተኛ ባህርይ መድን ገቢው የኢንሹራንስ ሽፋን በተሰጠው ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም (insurable interst) ያለው መሆኑን ይጠይቃል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ከስራ ተቆራጩ ጋራ ባደረገው ውል አከራካሪውን የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የግዴታ ሰነድ እንዲቀርብ የፈለገበት አይነተኛ ምክንያት ተጠሪ ለሚሰራው መንገድ የጨረታ አሸናፊ የሆነው አክሱም ኮንስትራክሽን በኮንስትራክሽን ውሉ አንቀጽ 6 መሠረት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና /performance bond/ ለማቅርብ በገባው ግዴታ መሠረት የአሁን አመልካች ስራ ተቋራጩ ለሚያደርሰው ማናቸውም የውል ቃል አለመጠበቅ እስከ ብር 1,101,890 ኃላፊነት በመውሰድ ኮንትራክተሩ በውሉ የገባውን ግዴታ ባይወጣ በውሉ መሰረት ስራው ባለመስራቱ ለሚደርሰው ጉዳት አመልካች የሚከፍለው መሆኑን በማመን ነው፡፡ ተጠሪ የመንገድ ስራውን የሰጠው ተቋራጭ መንገዱን በውሉ መሰረት ባለመስራት ለተጠሪ ባለእዳ ከመሆን አልፎ አመልካች ለመልካም ስራ አፈፃፀም ለመክፈል በተሰማማው ገንዘብ መክፈል ወይም አለመክፈል ላይ የመድን መብት ወይም ጥቅም (insurable interest) ያለው ወገን አይደለም፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በአክሱም ኮንስትራክሽን ድርጅት መካከል የተደረገው ውል መድን ውል ነው፣ ተጠሪ ደግሞ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ተጠቃሚ ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የሰጠው የመልካም ስራ አፈፃፀም ሰነድ ስራ ተቋራጩ በውሉ በተመለከተው ጊዜና ሁኔታ የመንገድ ግንባታው ስራውን ካላከናወነ ተጠሪ በመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ሰነድ የተገለፀውን ገንዘብ ለመክፈል በሰነዱ ውስጥ ለተገለፀው ስራ ብቻ ዋስትና የሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የሰጠው የመልካም ሰራ አፈፃፀም ዋስትና የግዴታ ሰነድ ስራ ተቋራጩ ስራውን ባይሰራ አመልካች መጠኑ በሰነዱ የተገለፀውን ገንዘብ ለመክፈል የአንድነትና የነጠላ የዋስትና ግዴታ የገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር አመልካች የሰጠው የመልካም ስራ አፈፃፀም ሰነድ በመሰረታዊ ባሕሪውና ይዘቱ የመድን ውል ሣይሆን ያልተነጣጠለ የዋስትና ግዴታ የገባ መሆኑን የሚያሣይ ሰነድ በመሆኑ ሊገዛ የሚገባው በንግድ ሕጉ በተመለከቱት ድንጋጌዎች ሣይሆን በፍታሐ ብሔር ሕጉ በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች የገባው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ግዴታ ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት የፍሬ ነገር እና የሕግ ምክንያቶች የመድን ውል ሳይሆን በፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1920 እና ተከታዮቹ የሚሸፈን የዋስትና ውል ነው፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 ስር የተመለከተው የአስር አመት ይርጋ ጊዜም አላለፈም ተብሎ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፊዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 410054 መጋቢት 30 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል
2. የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ግዴታ የኢንሹራንስ ውል ሳይሆን የዋስትና ውል በመሆኑ የሚገዛው በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 1921 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ የአስር ዓመት ጊዜ አላለፈበትም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ይግባኝ ባይ ዝርዝር የማቅረብ መብት ተጠብቋል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 71134
ሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ያሬድ ሲሳይ ከጠበቃ ግሩም አየለ ጋር ቀረቡ
ተጠሪ፡- አልግሪን አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር
ጠበቃ ውቤ ጓዳ ቀረቡ
መዝገቡ ያደረው ለውሣኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የማህበር ይፍረስልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበው ክስ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ማህበሩ የሚፈርስበት በቂና ትክክለኛ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የቀረበውን ክስ ወድቅ በማድረግ ውሣኔ መስጠቱ እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይሄንኑ ውሣኔ በማጽናቱ የተፈጸመው መሠረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ የቀረበ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በተጸፈ ባቀረበው አቤቱታ ተፈጸመ ያለውን መሠረታዊ የህግ ስህተት በማንሳት የተከራከረ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ፡- የበታች ፍርድ ቤቶች ማህበሩ አይፈርስም ወደ ሚለው ድምዳሜ የደረሱት ኃ/የተ/የግል ማህበር የተቀመጠውን የማፍረሻ ምክንያት ሳይሆን ስለማህበሮች በጠቅላላው የተመለከተውን በመሆኑ ፣ እንደዚህ ዓይነቱ ማህበር ፍጹም የሆነ መስማማት የሚጠይቅ ሁኖ እያለ እና አለመግባባቱ ፍርድ ቤት በደረሰበት ሁኔታ ብርቱ ጭቅጭቅ የለም በሚል መወሰኑ፣ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ማህበሩን በውክልና ማስተዳደራቸው እና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8.11 ስር 3ኛ ወገን ሊወክል የሚችለው በሁሉም ጉዳዮች ሳይሆን አስፈላጊ ሁኖ በታየ ጊዜ ብቻ በመሆኑ፣ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ጠርቶ የማያውቅ፣ አዲት ተደርጎ የማያውቅ፣ ስራ አስኪያጅ ማህበሩን ሀብት ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉት ሁኖ እያለ እና ጉዳዮችን በሽምግልና ታይቶ እልባት ማግኘት ባልቻለበት ሁኔታ ማህበሩ ሊፈርስ አይገባም በሚል ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ማህበሩ እንዲፈርስ፣ ስራ አስኪያጅ ደግሞ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባት እንዲባል እና ሂሣብ እንዲጣራ የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ መስከረም 15 ቀን 2004 ዓ.ም በሰጠው መልስ አንድ ማህበር ሲፈርስ በቂና ህጋዊ ምክንያቶች ሊሟሉ የሚገባቸው ስለመሆኑ በጠቅላላውም ሆነ በልዩ የማህበራት ማፍረሻ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች ስር ተመልክቶ እያለ ይሄንን ባላሟላ መልኩ የቀረበው ክስ ተቀባይነት ማጣቱ በአግባቡ በመሆኑ፣ ማህበራት ደግሞ ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ ያለበቂ ምክንያት የሚፈርሱበት አግባብ ባለመኖሩ፣ ድርጅቱም አመልካች እንደሚለው የከሰረ ሳይሆን ስራውን በአግባቡ እያከናወነ ያለ በመሆኑ፣ በድርጅቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውስጥም ብርቱ ጭቅጭቅ አለ ለማለት የማይቻል በመሆኑ እና ስራውንም በአግባቡ እያከናወነ ያለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ማህበሩ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው በሚል ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ፍርድ ቤቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አከራካሪው ማህበር አይፈርስም የተባለበትን አግባብ ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ቀደም ሲል ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ማህበሩ እንዲፈርስ የጠየቀበት ምክንያት ስራ አስኪያጁ ከባንክ ቤት ለማህበሩ ስራ መበደር ያለባትን ገንዘብ ያህል ያልተበደረች ስለመሆኑ፣ የማህበሩን ገንዘብ ለግል ጥቅሟ አውላለች፣ ማህበሩም ኪሣራ ላይ ስለመሆኑ ማህበሩን በውክልና ማስተዳደሯ እና አለመግባባት ስለመፈጠሩ በማመላከት እንደሆነ መመልከት ይቻላል፡፡ ጉዳዩን የተመለከቱት የበታች ፍርድ ቤቶች ለማህበር መፍረስ ምክንያት ሁነው የቀረቡት ነጥቦች በማስረጃ አልተረጋገጡም፣ ብርቱ ጭቅጭቅ አለ ለማለት የማያስችሉ፣ ከስራ አስኪያጅ ጋር አለመግባባት በራሱ ብርቱ ጭቅጭቅ ተብሎ ማህበርን ሊያፈርስ የሚችል አይደለም በሚል እና የማህበሩን ስራ አስኪያጅነት በውክልና ማስተዳደርን በተመለከተም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8/1/ ስር የተፈቀደ በመሆኑ አልተቀበልነውም በሚል ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው አመልካች ማህበሩ እንዲፈርስ ያቀረበውን ምክንያት በፍሬ ነገር ረገድ ያላስረዳ ስለመሆኑ ነው፡፡ የቀረቡት ምክንያቶች ደግሞ እስካልተረጋገጡ ድረስ ለማህበሩ ማፍረሻ ምክንያት ተደርገው የማይወሰዱ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድ ማህበር ሊፈርስ የሚችለው ደግሞ ከንግድ ህጉ አንቀጽ 217፣ 218 ፣ 511 እና 543 መመልከት እንደሚቻለው በድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት በርካታ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሁነው በቂ እና ህጋዊ ምክንያት እንደዚሁም በአባላት መካከል ብርቱ ጭቅጭቅ መኖር ያለበት ስለመሆኑ ያመለክታል፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን የቀረበው ብርቱ ጭቅጭቅ ስለመኖሩ መሠረት ያደረገ ክርክር ሲሆን ይሄ ስለመኖሩ ደግሞ ያልተረጋገጠ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ አመልካች ለማህበሩ ማፍረሻ ምክንያት ነው በማለት ያቀረበውን ነጥብ አስካላስረዳ ድረስ ደግሞ ማህበሩ የሚፈርስበት በቂ ምክንያት የለም ተብሎ መወሰዱ የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡

ሆኖም ግን አመልካች በማህበሩ የስራ አስኪያጅ አመራር ላይ የስራው በውክልና መተዳደርን ጨምሮ የተለያዩ ቅሬታዎች እንዳሉት ግልጽ ነው፡፡ አንድ የኃ/የተ/የግል ማህበር ስራው በአግባቡ አልተመራም በሚልበት ወቅት ባለው የማህበሩ መተዳዳሪያ ደንብ ወይም አግባብነት ባላቸው ህጎች እንዲስተካከል መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 37/1/ ስር ፍትሕ የማግኘት መብትን ከሚመለከተው ድንጋጌ መመልከት ይቻላል፡፡ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ማህበሩን በውክልና አስተዳድራለች ወይስ አላስተዳደረችም? ፣ አስተዳድራ ከሆነስ ከማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አኳያ እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር ተገናዝቦ መፍትሔ የሚያገኝ ጉዳይ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ከቀረበው የማህበር ይፍረስልኝ ጉዳይ ጋር በማያያዝ በመተዳደሪያ ደንቡ የተፈቀደ ነው በማለት ማለፍ ለተነሳው ክርክር አግባብነት ያለው ድምዳሜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለመሆኑ እና የማህበሩ የስራ አመራር እንዲስተካከል ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚችል ፤ አሁን ከተነሳው ክርክር ጋር የሚታይ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ሁኖ አልተገኘም በመሆኑም ይሄም ጉዳይ አመልካች የማህበሩ የስራ አመራር አካሄድን በተመለከተ ጥያቄ ሲያቀርብ አብሮ ታይቶ እልባት ሊያገኝ ሚችል ነው ብለናል፡፡ ሆኖም በዚህ የማህበር ይፍረስልኝ የክርክር ነጥብ ላይ ማህበሩ የሚፈርስበት በቂ ምክንያት የለም ተብሎ ውሣኔ መሰጠቱ ከውጤት አኳያ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት አግባብ አላገኘንም፡፡
ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች አከራካሪው ማህበር የሚፈርስበት በቂ ምክንያት አልቀረበም በሚል አመልካች ያቀረበውን ክስ ወድቅ ማድረጉ በአግባቡና የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 110861 ሐምሌ 08 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝ/ቁ 173919 በቀን 30/9/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው ኃ/የተ/የግል ማህበር ይፍረስልኝ ክስ ወድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ ይሄ ውሣኔ አመልካች የማህበሩን የስራ አመራር ጉድለት በተመለከተ እንዲስተካከል በሚል ከመጠየቅ የሚከለክለው አይደለም፡፡
3. በዚህ ችሎት ሐምሌ 27 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- መስፍን ዕቁበዮናስ

አማረ አሞኜ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) አቶ ብርሀኑ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ዳሸን ባንክ (አ.ማ) ነገረ ፈጅ አቶ ዮናታን አስፋው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታሐብሔር መዝገብ ቁጥር 41632 የካቲት 27 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታሐብሔር ይግባኝ ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 24055 ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለብድር ውል የተሰጠ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የሚያስከትለውን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ ግራስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አንደኛ ተከሳሽ፣ አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ከሳሽ (ተጠሪ) ለሥር ፍርድ ቤት ነሐሴ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ባቀረበው የክስ ማመልከቻ፤ ግራስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ ከከሳሽ በብድር ከወሰደው ገንዘብ ውስጥ የከፈለው ተቀናንሶ ብር 5,494,328.29 (አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም) ውስጥ ሁለተኛ ተከሳሽ (አመልካች) መጠኑ 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የብድር ገንዘብ ተበዳሪው የማይከፍል ከሆነ እሱ የሚከፍል መሆኑን በማረጋገጥ መጋቢት 17 ቀን 1993 ዓ.ም የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የሰጠ ሲሆን ይህንኑ የገንዘብ የዋስትና ሰነድ፣ የካቲት 5 ቀን 1994 ዓ.ም፣ መጋቢት 11 ቀን 1995 እና የካቲት 22 ቀን 1996 ዓ.ም አድሶታል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ብር 5,494,328.29 (አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሀያ ዘጠኝ ሳንቲም) ዕዳ አለበት፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ በሰጠው ያለቅድመ ሁኔታ የሚከፈል የዋስትና ግዴታ መሰረት እንዲከፍለኝ ብጠይቀው ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ ተከሳሽ ለብድሩ አከፋፈል በሰጠው የዋስትና ግዴታ መሰረት አንደኛ ተከሳሽ ከሚፈለግበት ዕዳ ውስጥ 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር) ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚታሰብ አሥራ አራት ፐርሰንት ወለድና በዚህ ክስ ምክንያት ከሳሽ ያወጣውን ወጭ ጨምሮ ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ከሳሽ ክሱን ያስረዱልኛል የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎችና ማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ከክሱ ጋር በማያያዝ ያቀረበ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሳኔው አስፍሯል፡፡

በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የሆነው (አመልካች) የመጀመሪያ ክስ መቃወሚያና የመከላከያ መልስ አቅርቧል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ድርጅቱ የተቋቋመው ለንብረት፣ ለሰው አካልና የሕይወት፣ ለኃላፊነት የመድን ዋስትና ለመስጠት ነው፡፡ የሁለተኛ ተከሳሽ ባለ አክሲዮኖችና የአስተዳደር ቦርዱ በማያውቁት ሁኔታ ከመድን ሥራ ውጭ የአንደኛ ተከሳሽን የብድር ዕዳ ለመክፈል የተሰጠው የገንዘብ ዋስትና የማዬታ ሰነድ ከሁለተኛ ተከሳሽ መመስረቻ ጽሁፍ፣ የመተዳደሪያ ደንብ፣ ስለ መድን ሥራ ፈቃድ የወጣውን ህግ የሚጥስ በመሆኑ ሁለተኛው ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም፡፡ የሁለተኛው ተከሳሽ ሥራ አስኪያጅ በፍታብሔር ህጉ፣ በአፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) መተዳደሪያ ደንብና በንግድ ሕጉ የተዘረዘሩትን የአስተዳደር ተግባራትን ከማከናወን ውጭ ሌሎች ልዩ ተግባራትን ማከናወን እንደማይችል በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የሁለተኛ ተከሳሽ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሰጠውን የገንዘብ ዋስትና ሰነድ በመቀበል ለከሳሽ የፈጸመው ተግባር ከጅምሩ ሕጋዊ ውጤት የሌለውና ፍርስ በመሆኑ ከሳሽ ሁለተኛ ተከሳሽን የሚከስበት ምክንያት የለም፡፡ በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ ሊጠየቅ የሚችለው ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ብቻ መሆኑ በንግድ ህጉ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ ክሱን ያቀረበው ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ፡፡

የሁለተኛ ተከሳሽ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ሰጥቷል የሚባል ቢሆን ሰነዱ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1725(ሀ) እና የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1727(ለ) በሚደነግጉት መሰረት በሁለት ምስክሮች ያልተፈረመ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና ፈራሽ ነው፡፡ ከሳሽ በሁለተኛ ተከሳሽ ተሰጥቶኛል የሚለው ሰነድ ገንዘብ መጠኑ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) መሆኑን ያሳያል፡፡ ከሳሽ ሁለተኛው ተከሳሽ በሰነድ ከሰጠው ዋስትና በላይ እንዲከፈለው ያቀረበው ክስ የህግ መሰረት የለውም፡፡ ከሳሽ ብድሩን ለወሰደው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ተበድሮ የወሰደ መሆኑን የሚሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ከሳሽ እዳው ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ የሚታሰብ አሥራ አራት ፐርሰንት ወለድ ሁለተኛ ተከሳሽ እንዲከፍለው ያቀረበው ክስ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2479 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች የሚጥስና የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ውድቅ በማድረግ ያሰናብተኝ፡፡ ከሳሽ ከሁለተኛ ተከሳሽ ተሰጥቶኛል የሚለው የዋስትና ሰነድ ከሳሽ ከተበዳሪው ጋር ያደረገው ብድር ውል የተደረገበት ጊዜና የብድሩ መጠን የሚገናኝ ባለመሆኑ ሁለተኛ ተከሳሽ በኃላፊነት አይጠየቅም፡፡ የከሳሽ አድራጎት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለ ገንዘብ ዋስትና ሰነዶች ያወጣውን መመሪያ በመጣስ የተፈጸመ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሆኖ እንዲሰናበት በማለት ተከራክሯል፡፡ ተከሳሽ ክሱን ለመከላከል ይጠቅሙኛል የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ከመልሱ ጋር በማያያዝ ያቀረበ መሆኑንና ማስረጃ ዝርዝር መግለጫ እንዳቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ተበዳሪውን ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የብድር ሂሳብ መግለጫ ከሳሽ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የብድር የሂሳብ መግለጫ ቀርቦለታል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሁለተኛ ተከሳሽ ሥራ አስኪያጅ ወጭ አድርጎ በሰጣቸው የገንዘብ ዋስትና ሰነዶች በኃላፊነት ይጠየቃል ወይስ አይጠየቅም? ሁለተኛ ተከሳሽ በኃላፊነት የሚጠየቅ ቢሆን የመክፈል ኃላፊነቱ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጭብጦች መሥርቷል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሳሽ የገንዘብ ዋስትና ሰነዶችን መስጠት ከተቋቋመበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓላማ ውጭ የሆነ ተግባር አይደለም፡፡ ተከሳሽ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ክልከላ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የሰጣቸው ገንዘብ ዋስትና ሰነዶች ሕጋዊ ውጤት ያላቸው ናቸው፡፡ የተከሳሽ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነዶችን የመፈረም ሥልጣን በንግድ ህጉ የተሰጠው በመሆኑና ሁለተኛ ተከሳሽ በህጉ መሰረት የሥራ አስኪያጁን ሥልጣን ያልገደበ በመሆኑ፣ ሥራ አስኪያጁ ለከሳሽ ፈርሞ በሰጣቸው የገንዘብ ዋስትና ሰነዶች በኃላፊነት ይጠየቃል፡፡ ከሳሽ ክሱን ያቀረበው በንግድ ህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ስለሆነ የከሳሽ ክስ በይርጋ አይታገድም፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ከሚፈለግበት ዕዳ ውስጥ ሁለተኛ ተከሳሽ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ከሣሽ ማስጠንቀቂያ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለከሳሽ በአንድነትና በነጠላ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታሐብሔር ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 15 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር ማመልከቻ በስር ፍርድ ቤት ያቀረባቸውን ክርክሮች በማጠናከር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የተቋቋመው አጠቃላይ የመድን ሥራና የረዥም ጊዜ የመድን ዋስትና ለመስጠት ነው፡፡ አመልካች ከመድን ሥራ ውጭ የብድር ዕዳ ለመክፈል የዋስትና ግዴታ ሰነድ ለመስጠት አይችልም፡፡ ገንዘብ ዋስትና መስጠት በአመልካች መመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ፣ ስለ መድን ሥራ ፈቃድ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 ድንጋጌዎች ውጭና አመልካች ከተቋቋመበት መሰረታዊ ዓላማ ውጭ የሆነ ለባንክ ብቻ የተፈቀደ ተግባር ነው፡፡ ተጠሪ ይህንን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የፈጸመው ተግባር ህገ-ወጥና ምንም አይነት ተጠያቂነት አያስከትልም፡፡ የአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና በንግድ ሕግ ቁጥር 363 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን የአስተዳደር ተግባራትን ከማከናወን ውጭ ሌሎች ልዩ ተግባራትን ማከናወን እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ የአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ እንዲፈርም በንግድ ህግ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 ልዩና ግልጽ የሆነ ሥልጣን አልተሰጠውም፡፡ ሥራ አስኪያጁ የሰጠው የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የኢንሹራንስ ፖሊሲ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የኢንሹራንስ ፖሊሲ አንድና ተመሳሳይ አድርጎ በመውሰድ ከጅምሩ ሕጋዊ ውጤት የሌለውና ፍርስ የሆነውን፣ ተግባር ህጋዊ ውጤት አለው በማለት የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የሰጠው የዋስትና ሰነድ ኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው በማለት የህግ ትርጉም ከሰጠ በኋላ አመልካች ያቀረበውን ሁለት ዓመት የይርጋ መከራከሪያ ውድቅ ማድረጉ እርስ በርሱ የሚቃረንና ወጥነት የሌለው ነው፡፡ በአመልካች ተሰጠ የተባለው የዋስትና ሰነድ በሕግ የተደነገገውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና ፈራሽ ነው፡፡ የዋስትና ሰነዱን የሰጠው በተጠሪና ብድሩን በወሰደው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ተበድሮ ከመውሰዱ በፊት ነው፡፡ በአመልካችና በተበዳሪው መካከል የብድር ውል ከመፈረሙ በፊት የወጣ ሰነድ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት ሊኖረውና አመልካችን የሚያስገድድ አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ ከላይ የዘረዘርናቸውን ተደራራቢ መሰረታዊ የህግ ሥህተቶች የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ለአመልካች የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ጥር 15 ቀን 2001 ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች በሕግ ያልተከለከሉ ሁሉንም የመድን ሥራዎች ለመሥራት ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 23/2000 እና 24/2004 ለገንዘብ ዕዳ የሚሰጥ ዋስትና በመድን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድርጅቶች የሚሰራ ተግባር መሆኑን በመግለጽ ትርጉም ሰጥቶበታል። አመልካች ክፍያ እየተቀበለ መድን አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ የድርጅቱ ማኔጅንግ ዳይሬክተር ተገቢውን አረቦን በማስከፈል የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የመስጠት ሥልጣን አለው፡ ከዚህ በተጨማሪ ንግድ ህጉ አንቀጽ 35 የድርጅቱ ማኔጅንግ ዳይሬክተር የገንዘብ ዋስትና ሰነድ የመስጠት ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ የሚደነግግ በመሆኑ የአመልካች ማኔጅንግ ዳይሬክተር የፈፀመው ተግባር ህጋዊ ውጤት አለው። አመልካች ክሱ ሁለት ዓመት የይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ያቀረብኩትን መከራከሪያ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት የለውም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጣው 23/2002 ለገንዘብ ዕዳ ስለተሰጠ የዋስትና ሰነድ መመሪያ አውጥቷል። አመልካች ሰነዱን የሰጠው 1993 ዓ.ም ሲሆን ሰነዱን በየዓመቱ ሲያድስ ቆይቶ ይህንኑ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ መስከረም 5 ቀን 1997 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 3 መሰረት እንዲራዘም ያደረገ በመሆኑ የይርጋ ጊዜ ገደቡ አላለፈም። አመልካች የዋስትና ሰነዱ በሕግ የተደነገገውን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና ፈራሽ ነው በማለት ያቀረበው ውሉ የመድን ፖሊሲ አወጣጥ ፎርም የሚያሟላ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ የህግ ስሕተት የሌለበት በመሆኑ ሰበር ችሎቱ በማጽናት እንዲያሰናብተኝ በማለት ተከራክሯል። አመልካች በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን ነጥቦች በማጠናከር ጥር 22 ቀን 2001 ዓ.ም. የተጻፈ ስድስት ገጽ የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው በመጀመሪያ አመልካች የሰጠው የገንዘብ ዋስትና ሰነድ ህጋዊነትና የሰነዱን ሕጋዊ ባሕሪና ሰነዱ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ነው ወይስ አይደለም? በሚሉት ነጥቦች ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቧቸውን ክርክሮች ቅድሚያ በማየት መወሰን አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም አመልካች የሰጠሁት የገንዘብ ዋስትና ሰነድ ምንም አይነት ኃላፊነትን የማያስከትልና ምንም አይነት ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት ያቀረባቸው መከራከሪያዎች የህግ መሰረት ያላቸው ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለውን መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ የሚከተሉትን ዝርዝር ጭብጦች በቅደም ተከተል አይተናል። በሰበር የታዩት ዝርዝር የህግ ጭብጦችም፡-

1/አመልካች የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠት አመልካቹ የኢንሹራንስ ኩባንያ ከተፈቀደለት፣ ከተቋቋመበትና ህጋዊ ህልውና አግኝቶ ከተመዘገበበት የንግድ ዓላማ ውጭ የተፈጸመ ተግባር በመሆኑ፣ በህግ ተጠያቂ ልሆን አይገባኝም በማለት ያቀረበው ክርክር፣ የሕግ መሰረት አለው ወይስ የለውም?

2/ አመልካች የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ ለማውጣት ሥልጣን ሣይኖረው ፈርሞ የሰጠውን የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ በመቀበል ተጠሪ ለፈጸመው ተግባር ህጋዊ ተጠያቂነት የለብኝም፣ በማለት ያቀረበውን ክርክር በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት የታለፈው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?

3/አመልካች የተሰጠው የገንዘብ ግዴታ የዋስትና ሰነድ፣ ስለ ዋስትና ውል የተደነገጉትን ፎርማሊቲዎች የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና በኃላፊነት የማያስጠይቅ ነው፣በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ያለፉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4/ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም?

5/አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ መሰረት በኃላፊነት ይጠየቃል ወይስ አይጠቅም? በኃላፊነት ይጠየቃል የሚባል ቢሆን የአመልካች የኃላፊነት መጠን ምን ያህል ነው?

1/የመጀመሪያው ጭብጥ አመልካች እንዲሰራው ከተፈቀደለት መድን ንግድ ሥራና ከተቋቋመበትና ህጋዊ ህልውና አግኝቶ ከተመዘገበበት የንግድ ዓላማ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አንድ የንግድ ድርጅት በንግድ መዝገብ ውስጥ ያስመዘገበውንና በጋዜጣ ታትሞ የወጣውን ጉዳይ መከራከሪያ ሊያደርገው እንደሚችልና ሶስተኛ ወገኖች በንግድ መዝገብ የገባውን ጉዳይ አላውቅም ነበር ብለው ማስረጃ ማቅረብ የማይፈቀድላቸው መሆኑን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 120 ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ አመልካች በህግ ከተፈቀደለትና ኩባንያው ከተቋቋመበት የንግድ ዓላማ ውጭ በተፈጸመ ተግባር በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባኝም በማለት የሚከራከረው፣ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 26ና የንግድ ሕጉ አንቀጽ 120 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያላቸው በመሆኑ በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባኝም በማለት ነው፡፡

ሆኖም ከላይ የተጠቀሱት የንግድ ሕጉ አንቀጽ 26ና አንቀጽ 120 ንኡስ አንቀጽ 2 ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በመጀመሪያ አመልካች ግራስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተጠሪ የተበደረውን ገንዘብ ካልከፈለ አመልካቹ እስከ 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚከፍል መሆኑን በማለጽ የሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ አመልካች እንዲሰራው ያልተፈቀደለት፣ አመልካች ከተቋቋመበት የንግድ ዓላማ ውጭ የሆነ፣ አመልካች ከሚሰራው የመድን ንግድ ሥራ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው ወይም አመልካች እንዳይሰራው በህግ በግልጽ የተከለከለ ተግባር መሆኑ ሲረጋገጥ በመሆኑ በመጀመሪያ ይህንን ነጥብ ቅድሚያ በመስጠት አይተነዋል፡

አከራካሪው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) ምን አይነት የህግ ተግባር እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትርጉም ሰጥቶታል፡፡ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ፣ በመመሪያ ቁጥር 23 /2002 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 3 " Financial guarantee bond shall mean an obligation undertaken by an insurance company to pay for the lending bank or another creditors or supplier all outstanding claims arising from the non Payment by debtor or debtors. " የሚል ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2002 ዓ.ም ና 2004 በወጣው መመሪያ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ በግልጽ ከልክሏል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ በግልጽ የተከለከሉ መሆኑን "Insurance companies are prohibited from issuing a Financial Guarantee Bond, by whatever name it may be referred to, in any form what so ever." በማለት በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 የደነገገ ሲሆን Insurance companies are prohibited from issuing a Financial Guarantee Bond, by whatever name it may be referred to, in any form wether conditional or otherwise. በማለት በመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ግልጽ ክልከላ አድርጎበታል፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመድን ንግድ ሥራ የሚሰሩ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) እንዳይሰጡ በመመሪያ በግልጽ ከመከልከሉ በፊት በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የተሰጡ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች የሚኖራቸውን ህጋዊ ውጤት ባወጣው መመሪያ ግልጽ አድርጓል። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 ከመከልከላቸው በፊት በኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ የተሰጡ የገንዘብ የዋስትና ግዴታ ሰነዶች የጸኑና ሕጋዊ ውጤት ያላቸው መሆኑን በመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 3 በግልጽ ተደንግጓል። በሌላ አነጋገር አመልካችና ሌሎች የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 23/2002 እና መመሪያ ቁጥር 24/2004 በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Gurantee Bond) እንዳይሰጡ ከመከልከላቸው በፊት፣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የመስጠት ሥራን እንደ አንድ የመድን ንግድ ሥራ አይነት ሲያከናውኑት የኖሩት ተግባር እንደነበርና ይህም ተግባራቸው ህጋዊ ውጤት ያለውና ኃላፊነትን የሚያስከትል መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመጀመሪያ መመሪያ ቁጥር 23/2002 በማውጣት፣የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) እንዳይሰጡ የከለከላቸው፣ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መስጠት የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ከተቋቋሙበት የመድን የንግድ ዓላማ ውጭ የሆነ ሥራ ነው በማለት አይደለም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የክልከላ መነሻ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሌላውን ሰው ዕዳ ለመክፈል የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ሲሰጡ ተበዳሪው ብድሩን ባለመክፈሉ ምክንያት በገቡት የዋስትና ግዴታ መሰረት ለባለመብቱ (አበዳሪው) የከፈሉትን ገንዘብ ከባለዕዳው ለማስመለስ የሚያስችላቸው በቂ መያዣ የሚሆን የተበዳሪው ንብረት ወይም ገንዘብ የማይዙ ወይም የማያገኙ በመሆኑና በአገሪቱ አስተማማኝ የሆነ የጠለፋ መድን ዋስትና የሌለ በመሆኑ ምክንያት፣ በኢንሹራንስ ኩባንያዎች ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመከላከል በማሰብ መሆኑን በመመሪያው መግቢያ ላይ በግልጽ አስፍሮታል።

ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች አመልካች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ግልጽ መመሪያ በማውጣት፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) እንዳይሰጡ ከመከልከሉ በፊት ወጭ አድርጎ ለተጠሪ የሰጣቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች (Financial Guarantee Bonds) ከተቋቋመበት የንግድ ዓላማ ውጭ የተፈጸሙ ተግባራት በመሆናቸው ሕጋዊ ውጤት የሌላቸውና አመልካችን በኃላፊነት ሊያስጠይቁ የማይችሉ ናቸው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል። የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ግልጽ መመሪያ አውጥቶ ከመከልከሉ በፊት ለተጠሪ የሠጣቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች (Financial Guarantee Bonds)፣አመልካች እንዲሰራ ከተፈቀደለት የመድን ንግድ ሥራና ከተቋቋመበት የንግድ ዓላማ ውጭ የተሰጡ ሰነዶች በመሆናቸው ሕጋዊ ውጤት የላቸውም በማለት ያቀረበውን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

2/ ሁለተኛው ጭብጥ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶቹ ወጭ በሆኑበት ወቅት የአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበረውን ሥልጣንና ሊፈጽማቸው የሚችላቸው የህግ ተግባሮች ምንድን ናቸው?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የዋና ስራ አስኪያጁን ሥልጣን በህግ የተቀመጡ ሁኔታዎች በማሟላት ገድቧል ወይስ አልገደበም የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ነጥቦች መመርመር የሚጠይቅ ነው፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 4 እና በአንቀጽ 6 የተደነገጉትን ልዩ መስፈርቶች በማሟላት ተመዝግቦና ፈቃድ አግኝቶ የመድን ንግድ ሥራ የሚያከናውን የአክሲዮን ማህበር (የኢንሹራንስ ኩባንያ) ነው፡፡ የመድን ንግድ ሥራ ለማከናወን የተቋቋመና ፈቃድ ያገኘ የአክሲዮን ማህበር

• የመድን ሥራውን በዋና ኃላፊነት የሚመራለት ሥራ አስኪያጅ የሚኖረው መሆኑ፣

• ሥራ አስኪያጁ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚወጣውን መስፈርት የሚያሟላ መሆን እንደሚገባውና ሥራውን የሚሰራው በብሔራዊ ባንኩ ስምምነትና ፅውቅና እንደሚሆን፣

• የስራ አስኪያጁ ማንነት የትምህርት ደረጃ ችሎታና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ የስራ አስኪያጆችንና ረዳቶችን ዝርዝር ሁኔታዎች ለመመዝገብ ባዘጋጀው መዝገብ የሚመዘገብ መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 32፣ አንቀጽ 33ና አንቀጽ 34 ድንጋጌዎችን ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሆኖም አዋጁ ከላይ የተቀመጡትንና በብሔራዊ ባንክ የሚወጡ መስፈርቶችን ማሟላቱ ተረጋግጦ የኢንሹራስ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ስለሚኖረው ሥልጣንና ኃላፊነት አዋጁ በዝርዝርና በግልጽ አይደነግግም፡፡ አዋጅ ቁጥር 86/1986 “ሥራ አስኪያጅ” ማለት በማናቸውም የማዕረግ ሥም ቢጠራም የድርጅቱን ሥራን ለመምራት በዋና ኃላፊነት የሚጠራ ሰውና ለእርሱ ወይም ለምክትሉ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ ሌሎች የኩባንያው ኃላፊዎች ናቸው፤ በማለት አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 20 ትርጉም ሰጥቶታል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ለኢንሹራስ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የተሰጠው ትርጓሜ የሥራ አስኪያጁን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመገንዘብ ጠቀሜታ ያለውና አመላካች (indicative) የሆነ ድንጋጌ ነው፡፡ ሆኖም ድንጋጌው የኢንሹራስ ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ያለውን ዝርዝር ሥልጣንና ሊፈጽማቸው የሚችላቸው የህግ ተግባሮች ለመወሰን በቂ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ አከራካሪዎቹን የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች በተሰጡበት ጊዜ የነበረውን ሥልጣንና ሊፈጽማቸው የሚችላቸው የህግ ተግባሮች ለመወሰን አግባብነት ካላቸውና ከላይ ከጠቀስናቸው የአዋጅ ቁጥር 86/1986 ድንጋጌዎች በተጨማሪ የአንድ አክሲዮን ማህበር ሥራ አስኪያጅ በንግድ ሕጉ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በንግድ ሕጉ መሰረት ስለተቋቋመ የአክሲዮን ማህበራት ፕሬዝደንት፣ ዋና ሥራ አስኪያጅና ጸሐፊ ሥልጣን የሚደነግገው የንግድ ሕግ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 ሥራ አስኪያጁ በአስተዳደሩ ምክር ቤት እንደሚሾምና የስራ አስኪያጁን ሥልጣን በተመለከተ የንግድ ህጉ አንደኛ መጽሐፍ፣ አንቀጽ 34፣ አንቀጽ 35፣ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) እና አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 ስለ ሥራ አስኪያጁ አመዳደብ (ሹመት) የሚደነግገው ክፍል ከላይ በዝርዝር የተገለጹት ማሻሻያዎች በአዋጅ ቁጥር 86/86 ድንጋጌዎች ተደርገውበታል፡፡ በሌላ በኩል በንግድ ህጉ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 ስለ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣን ተገቢነት እንዳላቸው የተደነገጉት ድንጋጌዎች የአመልካች ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ በወቅቱ የነበረውን ሥልጣን ለመወሰን ገዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ የድንጋጌዎቹን ይዘት ስንመለከት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

• የንግድ ሕግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ(ረ) የአክሲዮን ማህበሩ (አመልካች) በሥራ አስኪያጅነት የሾመውን ሰው በንግድ መዝገብ ማስመዝገብ እንደሚገባው የሚደነግጉ ናቸው።

• የንግድ ሕግ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 ከላይ በተገለጹት የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ንግድ ድርጅቱ ባይፈጽም የሚከተለውን ውጤት ይደነግጋል። ድንጋጌው የአክሲዮን ማህበሩ (አመልካች) የሥራ አስኪያጁን ሹመት በንግድ መዝገብ ሳያስገባ ቢቀር እንኳን ሥራ አስኪያጁ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ ሥራውን ለማከናወን የሚችል መሆኑን የሚደነግግ ይዘት ነው።

• "ስለ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣን" የሚል ርዕስ ያለው የንግድ ሕግ አንቀጽ 35" ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያገናኙት ጉዳዮች ሁሉ ሥራ አስኪያጁ ከነጋዴው ሥራ ጋር ነክነት ያላቸውን ማናቸውም ግዴታዎች ለመፈረምና የሚተላለፉ ሰነዶችን (ኔጎሽብል ኢንስትሩመንትስ) ጭምር መፈረም ሥልጣን እንዳለው ይቆጠራል" በማለት በንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ የሚደነግግ ሲሆን፣

• "የንግድ ሕጉ አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ(ሰ) ነጋዴው ወይም የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን የቅርንጫፉን ወይም የውክልናውን ሥራ ብቻ በማካሄድ የተወሰነ መሆኑ በንግድ መዝገብ በገባው ቃል ውስጥ የሌሉ ከሆነ ቅን ልቦና ያላቸው ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆኑ አይችሉም" በማለት ይደነግጋል።

• የአንቀጽ 35 ንኡስ አንቀጽ 2 በሥራ አስኪያጁ ሥልጣን ላይ ሕግ አውጭው የተጣለውን ገደብ ምን እንደሆነ የሚደነግግ ሲሆን "ሥልጣን ያለው ሥራ አስኪያጅ በግልጽ ሥልጣን ካልተሰጠው በስተቀር የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን መያዣ ማድረግ፣ ንግድ መደብሩን መሸጥ፣ ማከራየት ወይም በዕዳ ማስያዝ አይችልም" በማለት በግልጽ ይደነግጋል።

አመልካች ዋና ሥራ አስኪያጁ የፈጸመው ተግባር ከነበረው ሥልጣን ውጭ ነው በማለት በተጠሪ ላይ ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የሚኖረው ከሁለት ሁኔታዎች አንደኛው መሟላቱ ሲረጋገጥ ነው። የመጀመሪያው ሥራ አስኪያጁ ህግ አውጭው አስገዳጅ በሆነው በንግድ ህግ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 2 የደነገገውን ክልከላ ወይም የስልጣን ገደብ በመተላለፍ አመልካች በግልጽ ሥልጣን ሳይሰጠው በድንጋጌው ከተዘረዘሩት አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ተግባራት የፈጸመ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ነው። ሁለተኛው የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፈቃጅነት ባለው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 1 የተሰጠውን ሥልጣን አመልካች የንግድ ህግ አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ(ሰ) የተደነገገውን መስፈርት በሚሟላት የገደበው ሆኖ እያለ አመልካች ያስቀመጠውን የስልጣን ገደብ በመተላለፍ ሥራ አስኪያጁ ተግባሩን የፈጸመ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

ከላይ በሕግ የተቀመጡትን ሁለት መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የአመልካችን ክርክር መዝነናል። የአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ ተበዳሪው ግራስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተጠሪ ተበድሮ የወሰደውን ገንዘብ በብድር ውሉ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ካልከፈለ፣ አመልካች በዋስትና ሰነዱ እስከገለጸው ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚከፍል መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ፈርሞ የሰጠ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በሰበር አከራካሪ አይደለም። ይህ የአመልካች ሥራ አስኪያጅ የፈጸመው ተግባር፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 4 ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ወጭ አድርጎ የመስጠት የመድን ንግድ ሥራ አይነት እንደሆነ ትርጉም ሰጥቶበታል። እንደዚሁም የአመልካች ሥራ አስኪያጅ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዱን የፈረመው የኢትዮጵያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብሔራዊ ባንክ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ወጭ እንዳያደርጉ በመመሪያ ከመከልከሉ በፊት ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ተረጋግጧል፡፡

የአመልካች ሥራ አስኪያጁ የፈጸመውና በዚህ ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ተግባር የአመልካችን የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን መያዣ ማድረግ ወይም ንግድ መደብሩን መሸጥ ወይም ማከራየት ወይም ኩባንያውን በዕዳ የማስያዝ ተግባር አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የንግድ ሕግ ቁጥር 35 ንዑስ አንቀጽ 2 በመጥቀስ ሥራ አስኪያጁ የፈጸመው ተግባር ፈራሽና ሕጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የድንጋጌውን ይዘት ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ሁለተኛው አመልካች “የንግድ ሕጉ አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) የተደነገገውን መስፈርት በማሟላት የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ እንዳይፈርም ወይም ተመሳሳይ በሆነ ሌላ አገላለጽ የዋና ሥራ አስኪያጁን ሥልጣን ያልገደበ መሆኑንና በሥራ አስኪያጁ ሥልጣን ላይ አድርጌአለሁ የሚለውን ገደብ ወይም ቅነሳ በንግድ መዝገብ በገባው ቃል ውስጥ ያላስመዘገበ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የዋና ሥራ አስኪያጁ ሥልጣን የተገደበ መሆኑንና ሥልጣኑ መገደቡ በንግድ መዝገብ በገባው ቃል ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ ያላስረዳ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህም በመሆኑ ዋና ሥራ አስኪያጁ አመልካች እንዲሰራው በወቅቱ ተፈቀደውለት የነበሩ የመድን የንግድ ሥራዎች ጋር ግንኙነት የነበራቸውን ተግባራት የመፈጸም ሙሉ ስልጣን እንደነበረው ግምት የሚወሰድ መሆኑን ከንግድ ሕግ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 36 ድንጋጌዎችም ይዘታቸው ግልጽና ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡

አመልካች የዋና ሥራ አስኪያጁ ስልጣን የቀነሰ መሆኑን በንግድ መዝገብ ሳያስመዘግብ፣ ዋና ሥራ አስኪያጁ ሥልጣን በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ ተገድቧል፡፡ ሥራ አስኪያጁ በመተዳደሪያ ደንብ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የፈጸመው ተግባር ህጋዊ ተጠያቂነት የለብኝም በማለት ሶስተኛ ወገን የሆነውን ተጠሪን ለመቃወም ያቀረበው ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው መሆኑን መርምረናል፡፡ አንድ የአክሲዮን ማህበር በንግድ መዝገብ እንዲያስመዘግባቸው ህግ ግዴታ ያደረገበት ጉዳዮች በንግድ ሕጉ አንቀጽ 323 ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግገዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 86/86 አንቀጽ 6 እና በንግድ ህጉ አንቀጽ 323 ንዑስ አንቀጽ 2 የአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ፣ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ማሕበሩ ህጋዊ ህልውና እንዲገኝና እንዲመዘገብ ሥልጣን ላለው አካል ከሚቀርበው ማመልከቻ ጋር ተያይዘው መቅረብ እንዳለባቸው ይደነግጋሉ፡፡ የአመልካች ክርክር የድርጅቱ የመመስረቻ ጽሑፉና መተዳደሪያ ደንቡን የአክሲዮን ማህበሩ እንዲመዘገብ ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር አያይዘው መቅረባቸው ብቻውን የአክሲዮን ማህበሩ በመመስረቻ ጽሑፉና በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም ጉዳዮች በንግድ መዝገብ በገባው ቃል ውስጥ እንዳስመዘገበ የሚያስቆጥረው ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ እንድናይ የሚያስገድድ ነው፡፡

አክሲዮን ማህበሩ በንግድ መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብለት ሥልጣን በሕግ ለተሰጠው አካል በሚያቀርበው ማመልከቻ እንዲገልጻቸው በህግ የሚገደደው፤ የማህበርተኞች ስም፣ ዜግነት አድራሻና ለመግዛት የፈረሙት የአክሲዮኖች ብዛት፣ የማህበሩ መጠሪያ፣ የማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤትና ያሉት ከሆነ የቅርንጫፎች ሥፍራ፣ ማህበሩ የቆመበት ጉዳይ፣ የተፈረመና ገቢ የሆነውን ገንዘብ ልክ፣ የአክሲዮኑ ዋጋ ብዛቱ፣ አይነትና የአክሲዮኑ ልዩነት፣ በአይነት የተደረጉ መዋጮዎች ዋጋና የአገልግሎት አይነት፣ አስተዳዳሪዎቹን ብዛት ሥልጣን እንደዚሁም ለማህበሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደራሴ የመሆን አኳኋን፣ የተቆጣጣሪዎች ብዛትና ማህበሩ የሚቆይበትን ጊዜ መሆኑን የንግድ ሕጉ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 313 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 7፣ ከንዑስ አንቀጽ 10 እስከ ንዑስ አንቀጽ 12 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በማየት ለመገንዘብ ይቻላል። እንደዚሁም የአክሲዮን ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የሾመ መሆኑንና የሥራ አስኪያጁን ማንነት ካልሆነ በስተቀር የስራ አስኪያጁ ሥልጣን ወሰን በንግድ መዝገብ በሚገባው ቃል ውስጥ ማስመዝገብ ህጉ ግዴታ ያላደረገው ተግባር መሆኑን ከንግድ ህጉ አንቀጽ 348 ንዑስ አንቀጽ 3፣ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ(ረ) ድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘት ለመረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል የአክሲዮን ማህበሩ የሚጠቅመው ሆኖ ካገኘው የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን መገደብና የስራ አሰኪያጁ ሥልጣን ላይ የተደረገውን ገደብ በንግድ መዝገብ ውስጥ በሚጻፈው ቃል እንዲገባለትና እንዲመዘገብለት በግልጽ በሚያቀርበው ማመልከቻ ውስጥ በመግለጽ፣ የስራ አሰኪያጁ ሥልጣን የተገደበ መሆኑ በግልጽ በንግድ መዝገብ በተመዘገበው ቃል ውስጥ እንዲመዘገብ ካላደረገ በስተቀር በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊያደርገው እንደማይችል ከንግድ ህጉ አንቀጽ 36 እና አንቀጽ 121 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) ድንጋጌዎች አቀራረጽና ይዘት ለመረዳት ይቻላል።

በመሆኑም አመልካች የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተቀነሰ ወይም የተገደበ መሆኑን በንግድ መዝገብ በሰፈረው ቃል ወሰጥ ሳያስመዘግብ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የስራ አስኪያጁ ሥልጣን የተቀነሰ መሆኑን በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር፣

• የንግድ ሕጉ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን ያለው ሰው የአንድ ቅርንጫፍ ሥራ ለማስኬድ ብቻ ሥልጣን በመስጠት ሥልጣኑን የተወሰነ ለማድረግ ይቻላል፤ ስለሆነም እንደዚህ ያለው የስልጣን መቀነስ ማስታወቂያ በንግድ መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር በዚህ ህግ አንቀጽ 121 መሰረት መቃወሚያ ሊሆንባቸው አይችልም በማለት በግልጽ የደነገገውን የሚተላለፍና፣

• በተለይም በንግድ ህጉ አንቀጽ 121 ንኡስ አንቀጽ(ሰ) እና የንግድ ህጉ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 2 ሌላው አይነት የስልጣን መቀነስ በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆንባቸው አይችልም።

በማለት ለሶስተኛ ወገኖች በግልጽ የሰጠውን ጥበቃ ያላገናዘበና የሕግ ድጋፍና መሰረት የሌለው ነው። ሕግ አውጭው እነዚህን ድንጋጌዎች የደነገገው በግብይት ሂደት ውስጥ ከአመልካች ጋር ውል የሚዋዋሉ ሰዎች የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ መመርመርና ማንበብ እንደማያስፈልጋቸውና ድርጅቱ በንግድ መዝገብ ያስመዘገባቸውን ፍሬ ጉዳዮች ብቻ በማየት ከአመልካችጋር በቅን ልቦና የሚዋዋሉ ሶስተኛ ወገኖች ውለታው በህግ ተፈጻሚነት የሚኖረው መሆኑን በማረጋገጥ ከፍ ያለ ጥበቃ ለመስጠት ነው። በአጠቃላይ ከላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች አመልካች የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣን ሳይኖረው የፈረማቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነዶች እኔ በኃላፊነት አልጠየቅም በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢና የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

3/ ሶስተኛ ጭብጥ አመልካች የሰጠውን የገንዘብ ግዴታ የዋስትና ሰነድ፣ ስለ ዋስትና ውል የተደነገጉትን ፎርማሊቲዎች የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የሌለውና በኃላፊነት የማያስጠይቅ ነው፣ በማለት ያቀረበውን ክርክር የህግ መሰረት ያለው መሆኑን መመርመር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህንን ነጥብ ለመወሰን በመጀመሪያ የአመልካች ሥራ አስኪያጅ ፈርሞ የሰጠው ሰነድ በመሰረታዊ ባህሪውና ይዘቱ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው ወይስ የዋስትና ሰነድ የሚለውን ነጥብ ማየት ይጠይቃል፡፡ አመልካች ወጭ አድርጎ ለተጠሪ የሰጠው ሰነድ Financial Guarantee Bond በማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 በእንግሊዝኛ ቋንቋ ግልጽ ያደረገውን በኢንሹራንስ ኩባንያ የሚሰጥ የዋስትና ሰነድ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የሰጠው የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነዱን ሊያሟላው የሚገባውን ፎርም፣ የሰነዱን ባሕሪና የሚስከትለውን ውጤት ለመወሰን ሕግ አውጭው ለገንዘብ ዋስትና ሰነድ የሰጠውን የህግ ትርጓሜ መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የዋስትና ሰነድን በተመለከተ ሕግ አውጭው በተለያየ ጊዜ ባወጣቸው የህግ ማዕቀፎች ይዞታቸው ተመሳሳይ የሆኑ ትርጓሜዎችን የተጠቀመ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ዝርዝሩን እንመለከት፡-

- የዋስትና ሰነድ ማለት የፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታን ለመፈጸም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ነገር ሲሆን፣ የግምጃ ቤት ሰነድን፣ የተስፋ ሰነድንና ቦንድን ይጨምራል በማለት በአዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 18 ትርጉም ሰጥቶታል፡፡

- በአዋጅ ቁጥር 57/1989 ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 20 የዋስትና ሰነድ ማለት የፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታን ለመፈጸም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ማንኛውም ሰነድ ሲሆን፣ የግምጃ ቤት ሰነድን፣ የተስፋ ሰነድንና ቦንድን ይጨምራል፣ የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

- ቦንድ የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ማገቻ የሚል ፍች የሰጠው አዋጅ ቁጥር 110/1990 ማገቻ የተወሰነ ነገር በመፈጸሙ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ፣ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ፣ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጭው የማይከፈልበት አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል በማለት በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥረ 24/2004 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 3 የሰጠው ትርጉምና ከላይ በጠቀስናቸው የህግ ማዕቀፎች ሕግ አውጭው ተመሳሳይነት ባላቸው አገላለጾች የሰጣቸውን ትርጓሜ ስንመለከት አመልካች ወጭ አድርጎ የሰጠው ሰነድ በመሰረታዊ ባህሪውም ሆነ ይዘቱ የመድን ውል ወይም የኢንሹራንስ ፖሊሲ መሰረታዊ መስፈርት የሚያሟላ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የኢንሹራንስ ፖሊሲ በመሰረታዊ ባህሪው መድን ገቢው የኢንሹራንስ ሽፋን በተሰጠው ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም (Insurable Interest) ያለው መሆኑን ይጠይቃል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ከአመልካች አከራካሪውን የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ለማግኘት ከአመልካች ጋር ውል የተዋዋለው ግራስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዋናው ፍላጎቱ ተጠሪ በብድር የሚሰጠውን ገንዘብ ተበዳሪው ግራስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባይከፍለው አመልካች የሚከፍለው መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠውን የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ተጠሪ በማየትና ስለ ብድሩ አከፋፈል ከተበዳሪው ውጭ የሆነ አስተማማኝ ዋስትና ያለው መሆኑን በማመንና በማረጋገጥ የብድር ገንዘቡን እንዲለቅለት ማድረግና ገንዘቡን መበደር ነው፡፡ ግራስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማህበር አመልካች የሰጠውን የዋስትና ሰነድ አስይዞ የብድር ገንዘቡን ከወሰደ በኋላ ተጠሪ የሰጠውን ብድር ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ያለበት ባለዕዳ ነው፡፡ የተበዳሪው ባለዕዳነት አመልካች በሰጠው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ መሰረት ለተጠሪ የብድር ገንዘቡን ከከፈለ በኋላም የሚቀጥልና አመልካች ተጠሪን (አበዳሪውን) በመተካት ሊጠይቀውና ሊከታተለው የሚችለው ነው፡፡ የአመልካች ደንበኛ የሆነው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በጉዳዩ ዘላቂ ባለዕዳ ከመሆን አልፎ ተጠሪ በብድር የሰጠውን ገንዘብ የመክፈል ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም (Insurable Interest) ያለው ወገን ባልሆነበት ሁኔታ በአመልካችና በግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መካከል የተደረገው ውል የመድን ውል ነው ተጠሪ ደግሞ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ተጠቃሚ ነው ብሎ ለመደምደም አይቻልም ፡፡

በአንጻሩ አመልካች በሰጠው ሰነድ ከተጠሪ የአጭር ጊዜ የብድር ገንዘብ የወሰደው ግሬስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በብድር ውሉ በተገለጸው ጊዜ ዕዳውን ካልከፈለ አመልካች እስከ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ ገንዘብ ለመክፈል በሰነዱ ውስጥ ለተገለጸው ጊዜ ብቻ ዋስትና የሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የሰጣቸው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ግሬስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተጠሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ ተበዳሪው ባይከፍል አመልካች እስከ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል የአንድነትና ያልተነጣጠለ የዋስትና ግዴታ የገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ከላይ በዝርዝር የሰጠናቸውን ምክንያቶች ያላገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስሕተት ያለበት ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በማያያዝ አመልካች ሰነዱ ስለ ዋስትና ውል የተደነገጉትን ፎርማሊቲዎች የማያሟላ በመሆኑ በህግ ፊት ውጤት የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር መዝነናል፡፡ በመጀመሪያ የዋስትና ሰነዱ አመልካች የሌላ ሰው ዕዳ ማለትም የግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የብድር ዕዳ ለመክፈል የተሰጠ ሰነድ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ሰነዱ ስለዋስትና ግዴታ በፍታሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1922 የተደነገጉትን መሰረታዊ መስፈርት የሚያሟላ መሆኑ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ሕጉን ሲተረጉሙ ሰነዱ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው የሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ የደረሱ ቢሆንም አመልካች የሰጠው ሰነድ በፍታሐብሔር ህግ አንቀጽ 1922 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገጉትን መሰረታዊ ሁኔታዎች የሚያሟላ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ ይዘት ተረድተናል፡፡ አመልካች የዋስትና ሰነዱ የፍታሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1725 ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና የፍታሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1727 በተደነገገው መሰረት በተጠሪና በሁለት ምስክሮች አልተፈረመም በማለት ተከራክሯል፡፡

ሆኖም ይህ የአመልካች ክርክር (Financial Guarantee Bond) እንደ ማንኛውም የዋስትና ውል በተዋዋይ ወገኖች የሚዘጋጅ ሰነድ ሣይሆን የመድን ንግድ ሥራ እንዲሰራ የተፈቀደለት የኢንሹራንስ ኩባንያ በተሰጠው ልዩ ፈቃድ ተጠቅሞ፣ የሚያዘጋጀውና የሌላ ሰው ዕዳ ለመክፈል ራሱን ግዴታ ውስጥ የሚያስገባበት የማገቻ ሰነድ እንደሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 3 ለገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) የሰጠውን ትርጓሜ ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ ሆኖ አላገኘውም፡፡ እንደዚሁም አመልካች የሰጠው የማገቻ ሰነድ (Bond) የግድ በምስክሮች መረጋገጥ የሌለበት መሆኑን ሕግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 110/1990 በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 ለማገቻ ትርጉም ሲሰጥ “አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጭው የማይከፈልበት፣ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል" በማለት ከተጠቀመው አገላለጽ እና በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረው በአዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 18 ለዋስትና ሰነድ ከሰጠው ትርጓሜ ለመረዳት ችለናል።

ከዚህ በተጨማሪ የአመልካች ክርክር በአዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ሥልጣን የተሰጠው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አመልካችና ሌሎች የኢንሹራስ ኩባንያዎች በማናቸውም ሥያሜ የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) እንዳያወጡ በመመሪያ ከመከልከላቸው በፊት ወጭ ያደረጓቸው የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነዶች (Financial Guarantee Bond) የጸኑና ህጋዊ ውጤት ያላቸው መሆኑን " Financial Guarantee Bond or other unconditional bonds issued by insurance companies and outstanding before the effective date of these directives shall remain enforce until the expiry date or shall be phased out in line with an action plan submitted by each insurance company and agreed with the bank." በማለት የገለጸውን የመመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ የሚቃረንና የህግ መሰረት የሌለው ነው። ስለሆነም አመልካች ተበዳሪውን ግሬስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተጠሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ ባይከፍል እሱ የሚከፍል መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠውን የማገቻ ሰነድ ልዩ ባህሪ ያለውና በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሚዘጋጅና ወጭ የሚደረግ የማገቻ ሰነድ በመሆኑ አመልካች ሰነዱ በሁለት ምስክሮች ስላልተረጋገጠ ሰነዱ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም።

4/ አራተኛው ጭብጥ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የሚል ነው አመልካች የሰጠው ሰነድ የመድን ውል አለመሆኑ ተረጋግጧል። የሌላ ሰው ዕዳ ለመክፈል የአንድነት የዋስትና ግዴታ የገባ ሰው የዋናውን ባለዕዳ ግዴታ ነፃ የሚያደርጉ የይርጋና ሌሎች መከራከሪያዎች በማቅረብ ከኃላፊነት ነፃ እንደሚሆን ከፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1926 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አቀራረጽ፣ ይዘትና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ በዋሱ ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው የይርጋ የጊዜ ገደብ በዋናው ባለዕዳ ላይ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ እንደሆነ፤ በዋናው ባለዕዳ ላይ የተጀመሩ ክሶች ለዋሱ መቆጠር የጀመረለት የይርጋ ዘመን ያቋርጡበታል በማለት ሕግ አውጭው የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1929 የደነገገበትን ምክንያት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል። በአበዳሪው በተጠሪና በተበዳሪው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መካከል የተደረገው ብድር ውል ላይ ተፈጻሚነት ያለው ስለ ውሎች በጠቅላላው የሚደነግገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው። የአመልካች (የዋሱ) ግዴታ ቀሪ የሚሆነው የዋናው ባለዕዳ ግዴታ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው። ስለሆነም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የህግ ድንጋጌ በፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1845 የተደነገገው የይርጋ የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ ነው። ስለሆነም የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ንግድ ህግ 674 ንዑስ አንቀጽ 1 እንደሆነ አመልካች ያቀረበውን የይርጋ ክርክር መቀበላቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ቢሆንም በውጤት ደረጃ ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል። ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የህግ ድንጋጌ የፍታሐብሔር ህግ አንቀጽ 1845 በመሆኑ አመልካች የይርጋ ክርክር መታለፉ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5 አምስተኛው ጭብጥ አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ መሰረት በኃላፊነት ይጠየቃል ወይም አይጠየቅም? በኃላፊነት ይጠየቃል የሚባል ቢሆን የአመልካች የኃላፊነት መጠን ምን ያህል ነው? የሚለው ነው፡፡ አመልካች ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተጠሪ በብድር የወሰደውን ገንዘብ በብድር ውሉ መሰረት ካልከፈለ እስከ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ ገንዘብ ለተጠሪ ለመክፈል የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ ሰጥቷል፡፡ ተበዳሪው ዕዳውን በብድር ውሉ መሰረት አለመክፈሉ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ላበደረው ብድር የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የሰጠው ብድር ውሉ ከመደረጉ በፊት መሆኑን ገልጾ መጀመሪያውኑ ላልነበረ የብድር ውል የተሰጠ ዋስትና ግዴታ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የቀረበው ክርክር በፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1925 ንዑስ አንቀጽ 1 ወደፊት ለሚመጣ ወይም በአንድ አይነት ሁኔታ ለሚመጣ ግዴታ ዋስ መሆን ይቻላል በማለት የደነገገውን ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ አመልካች የሰጠው የዋስትና ግዴታ ሰነድ አመልካች እዳውን በአንድነት ለመክፈል የሚያረጋግጥ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተበዳሪው ግሬስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ተጠሪ ማጭበርበር ተግባር ፈጽመዋል በማለት ለሰበር በሰጠው የመልስ መልስ ያቀረበው ክርክር ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ መስማት ሥልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ያልተነሳና ያልተጣራ የፍታሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329 ንዑስ አንቀጽ 1 የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ክርክር ለሰበር ችሎት በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በሰጠው የገንዘብ የዋስትና ሰነድ መሰረት በኃላፊነት ይጠየቃል በማለት የሰጡት ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የአመልካችን የኃላፊነት መጠን በተመለከተ ዕዳን ለመክፈል ዋስ የሆነ ሰው ዕዳው ወለድ የሚያስከፍል እንደሆነ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር በዋስትናው ውል ውስጥ በተወሰነው ገንዘብ ልክ በወለዱም እንደተዋሰ እንደሚቆጠር የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1930 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ አመልካች የሰጠው የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ እስከ ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ድረስ ግዴታ የገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ሰነዱ ስለወለድ ተቃራኒ ቃል የሌለው መሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ለብድሩ ያለበት ዋስትና ግዴታ እስከሰጠበት ብር 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1930፣ የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1924 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1922 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ያደረገና የህግ ስሕተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በበታች በስር ፍርድ ቤት ከታህሳስ 26 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች በህግ የተደነገገውን ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ እንዲከፍል የወሰነው አመልካች በገባው ዋስትና ግዴታ መሰረት ባለመፈጸሙ ምክንያት ኃላፊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ምክንያት ተጠሪ ለዳኝነት የከፈለው ገንዘብና ሌሎች ወጭዎች አመልካች እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ የፍታሐብሔር ህግ ቁጥር 1931 መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ በዝርዝር ባየናቸው ጭብጦች ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ ስላገኘነውና የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች የሰጠው ገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለይርጋው ክርክር አግባብነት ያለው የንግድ ሕጉ አንቀጽ 674 ንኡስ አንቀጽ 1 ነው በማለት የሰጡት ህግ ትርጉምና ምክንያት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ቢሆንም በውጤት ደረጃ የደረሱበት መደምደምያ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው በእነዚህ ነጥቦች ላይ የሰጡትን የህግ ትርጉምና ምክንያት ብቻ በመለወጥ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታሐብሔር መዝገብ ቁጥር 41632 የካቲት 29 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታሐብሔር ይግባኝ ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 24055 ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ምክንያቱ ብቻ ተሻሽሎ ጸንቷል፡፡
2/ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
3/ በዚህ ችሎት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፣ ለሚመለከተው ይተላለፍ፡፡
መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. ጣና ኢንጂነሪንግ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ጠበቃ ሰለሞን ተሾመ ቀረቡ

2. ሚስስ ሴቬሪና ሴቲ
3. ሚስ አምብራ ዩልጋውዲዮ — ጠበቃ አበበ አሣመር ቀረቡ
4. ሚስ ጂያዳ ዩልጋውዲዮ

ተጠሪ ፡- ሚስተር አልቸዲ ዩልጋውዲዮ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያለአግባብ ከስራ አስኪያጅነት ተነስቻለው የሚል ክስን የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመጀ/ደ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች እንዲሁም 2ኛ ተከሳሽ የ4ኛ ተከሳሽ ተወካይ በመሆን ህዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም አድርገነዋል ባሉት ስብሰባ የማህበሩን ደንብ እና መመስረቻ ፅሑፍ በማሻሻል 1ኛ ከሳሽ ከምክትል ስራ አስኪያጅነት እንዲነሱ ተደርጎ የ2ኛ ተከሳሽ ልጅ 3ኛ ተከሳሽ ምክትል ስራ አስኪያጅ እንዲሆኑ ተደርጎ ቃለ-ጉባኤ የተያዘበት ቀኑ ሳይፃፍበት ከሳሾች ሳይጠሩ የተደረገው ውሳኔ ህሰተኛ እና ህገ-ወጥ በመሆኑ፣ 1ኛ ከሳሽ ም/ስራ አስኪያጅ የሆነው የግራቀኙን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል በመሆኑ፣ 1ኛ ከሳሽ ከምክትል ስራ አስኪያጅነታቸው መነሳታቸው ያለአግባብና መስተካከል ያለበት መሆኑን በስብሰባ ተማምነን ረቂቅ ማሻሻያ ተዘጋጅቶ በረቂቁ ላይ አስተያዬት ከሰጠን በኋላ በውልና ማስረጃ ለማስመዝገብ ፍቃደኛ ሳይሆኑ የቀሩ በመሆናቸው፣ በ1995 ዓ.ም በተደረገው የመመስረቻ ፅሑፍ ማሻሻያ የኩባንያው ጠቅላላ ጉባኤ ከፍተኛ አካል ሆኖ እያለ ከህግ ውጪ የጠቅላላ ጉባኤውን ስልጣን በሙሉ ለዋና ስራ አስኪያጅ በህዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም በመሰጠቱ፣ የሒሳብ ሰነዶችንም እንዳናይ የተደረግን በመሆኑ ተከሳሽ ከዋና ስራ አስኪያጅነታቸው እንዲነሱ አልያም በአግባቡ እንዲሰሩ፡፡ እንደዚሁም ህዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም የተደረገው የመመስረቻና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ፅሑፍ እንዲሻር፣ 1ኛ ከሳሽ ከምክትል ስራ አስኪጅነታቸው ሊነሱ አይገባም እንዲባልልኝ፣ የሒሳብ ሰነዶችን የመመልከት መብታችን እንዲከበርልን የሚል ነው፡፡ በቀረበው ክስ ላይ ተከሳሾች መልስ እንዲሰጡበት ታዘው በሰጡት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መልስ 1ኛ ተከሳሽን በተመለከተ መተዳደሪያ ደንቡና መመስረቻው በህጉ አግባብ የተደረገና በሚመለከተው አካል የፀደቀ ነው፣ ቀኑም በፀደቀበት ቀን ታትሟል፣ 1ኛ ከሳሽ ም/ስራ አስኪያጅ የሆኑት በተሻሻለው የመመስረቻ ጽሁፍ እና ኩባንያው ሲመሰረትም ስራአስኪያጅ አይደሉም፣ 1ኛ ከሳሽ ጥሪ ተደርጎላቸው በስብሰባው ላይ አልተገኙም፣ የመጨረውሻን የስብሰባ አጀንዳ አውቀው የተለያዩ ሃሳቦችን በማቅረብ በሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት ቀርቦ አልፈረሙም፣ ሰነዶቹም ተፈርሞባቸዋል፣ አለመግባባት ተፈጥሮ በስምምነት ለመጨረስ ተሞክሮ ሳይሳካ በመቅረቱ በአብላጫ ድምጽ የሚወሰኑ ውሳኔዎች በመሆናቸው በዚያው መልኩ የተወሰነ በመሆኑ፣ ሰነዱን አስፈቅደው ኮፒውን መውሰድ ስለሚችሉ ማስጠንቀቂያው ተቀባይነት አለው እና 2ኛው ተከሳሽ ስራቸውን በአግባቡ የተወጡት በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾችን በተመለከተ ያቀረቡት መልስ በቀጥታ የአንደኛ ተከሳሽ መልስ ጋር ተመሳሳይ ስለመሆኑ ተመልክቶ ሳይመዘገብ በበታች ፍርድ ቤቶች ታልፎአል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ግራቀኙን ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ አራት የተለያዩ ጭብጦችን በመያዝ ጉዳዩን መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በተደረገው ስብሰባ የመተዳደሪያ ደንቡ ሊሻሻል ስለመቻሉ በተመለከተ በንግድ ህጉ ቁ. 536(2) መሰረት የመተዳደሪያ ደንብ ለውጥ ¾ ባላቸው ባለአክሲዮን የድምጽ ብልጫ መወሰን እንዳለበት ስለሚያመላክት እና ተከሳሾች ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ 77.50% በመሆኑ የተደረገው የመተዳደሪያ ደንብ ለውጥ ህጋዊ አይደለም የሚባልበት አግባብ የለም፤ አንድ ስራ አስኪያጅ በስብሰባ የቀረቡትን እና የተወሰኑትን ውሳኔዎች የማሳወቅ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በንግድ ህግ ቁ. 533 ስር የተደነገገ በመሆኑ ይሄንኑ ኃላፊነታቸውን መወጣት ያለባቸው ስለመሆኑ ወስኗል፤ የድርጅቱ ባለአክሲዮኖች ያደረጉትን ስብሰባ በተመለከተ በሚመለከተው ባለስልጣን ፊርማ እና ማህተም የተረጋገጠ እና ቀንም ያለው በመሆኑ የባለስልጣኑ ፊርማ እና ማህተም ያረፈበት ቀን ማሻሻያው እንደተደረገ ይቆጠራል በማለት ከሳሾች ቀኑ የማይተወቅ ነው በማለት ያነሱትን ክርክር ውድቅ አድርጓል፡፡ በመቀጠልም 2ኛ ተከሳሽ ከስራ አስኪያጅነት እንዲነሱ በከሳሾች በኩል የተነሳውን ክስ ውድቅ ሲያደርግ በሌላ በኩል በባለአክሲዮኖች በተደረገው ስብሰባ የ1ኛ ከሳሽ ከምክትል ስራ አስኪያጅነት መነሳትም በተመሳሳይ በምክንያት ያልተደገፈ ባለመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ የተደረገው የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ ክፍል ተሽሯል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፌ/የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በመጀመሪያ ደረጃ ምክትል ስራ አስኪያጅ ስራ አስኪያጅን በሚመለከቱ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች ሊከራከር አይገባውም በማለት የተነሳውን ክርክር በተመለከተ ስለስራ አስኪያጅ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ከንግድ ህግ ቁ.525 እና ተከታዮቹን ስንመለከት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ስራ አስኪያጆች ሊሾሙ የሚችሉበትን አግባብ ስለሚያስቀምጥ እንደዚሁም ህጉ ለእነዚህ ኃላፊነቶች በእነዚሁ ድንጋጌዎች የሚስተናገዱ እንጂ ለእያንዳንዱ የተለያዩ ድንጋጌዎችን ያስቀምጣል ተብሎ ስለማይታሰብ ተቀባይነት ያለው ክርክር አይደለም ብለናል፡፡ በመቀጠል አመልካች በቅሬታቸው አጥብቀው የሚከራከሩት በመተዳደሪያ ደንባችን አንቀጽ 2(2.4) ውስጥ ስራ አስኪያጅ በማህበርተኞች ጠቅላላ ጉባዔ የሚሻር ስለመሆኑ ተመልክቶ እያለ ያለበቂ ምክንያት ሊሻር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይገባም መባሉ አግባብነት የለውም፣ የተባረረው ያለበቂ ምክንያት ነው ቢባል እንኳ በንግድ ህግ ቁ.527(3) መሰረት ኪሳራ ከሚቆረጥለት በስተቀር ወደ ስራ አስኪያጅነቱ ፍርድ ቤት የሚመልስበት አግባብ የለም፡፡ እንደዚሁም በባለ አክሲዮኖች የተደገረገው ስብሰባ ህጋዊ ነው ተብሎ ተወስኖ እያለ በሌላ በኩል ም/ስራአስኪያጅ የተነሳበትን የቃለ-ጉባኤ ክፍል መሰረዙ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን የሚል ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው ከምክትል ስራ አስኪያጅነት የተሻርኩት በጠቅላላ ጉባኤ ሳይሆን ተከሳሾች እናት እና ልጅ በመሆን ያደረጉት በመሆኑ የመመስረቻው ጽሑፍ አንቀፅ ተጠቅሶ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ በንግድ ህግ ቁ. 527(3) ስር የተጠቀሰው ፍርድ ቤት ሊቀበለው የሚችል በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ስራ አስኪያጅ ሊሻር የማይችል ስለመሆኑ በመመስረቻ ጽሑፍ ስለተቀመጠ ወይም ስላልተቀመጠ ሳይሆን ህግ በመሆኑ ሊተገበር ይገባል፡፡ እንደዚሁም በ1995 ዓ.ም በተሸሻለው የመመስረቻ ጽሑፍ ም/ስራአስኪያጅ የሆንኩት ከድርጅቱ ህልውና እና የአክሲዮን አባላቱ መብት ጋር ተያያዥነት ባለው ሁኔታ በመሆኑ ይሄውም 2ኛ አመልካች ስራ አስኪያጅ ሆነው የተጠሪን ድርሻ ጨምሮ የሌሎች ሁለት ባለአክሲዮኖች እንጀራ እናት በመሆናቸው አድሎ እንዳይፈጽሙ ታስቦ በመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረዉ ጭብጥ የመልስ ሰጪ ወደ ምክትል ስራ አስኪያጅነት ይመለስ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ የተያዘውን ጉዳይ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በንግድ ህጉ ቁ. 525 እስከ 537 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች የአንድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስራ አስኪያጅ የሚመረጥበት እንደዚሁም የሚሾምበት አግባብ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ስንመረምረው በመመስረቻ ጽሑፉ አንቀጽ 2(2.4) ስር በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ስራ አስኪያጅን ማንሳት የሚቻል ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር በተመለከተ በዚህ መልኩ ማንሳት እንደሚቻል ስምምነት ቢኖርም ያለበቂ ምክንያት እና በአባላት ፍቃድ ብቻ መሰረት በማድረግ ማንሳት የሚቻል ስለመሆኑ በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር ባለመኖሩ ከላይ የተመለከተውን የመመስረቻ ጽሑፍ ድንጋጌ በመጥቀስ የቀረበው ክርክር ከንግድ ህግ ቁ.527(4) ጋር አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእርግጥ የአሁን ተጠሪ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የተሾመው በመመስረቻ ጽሑፉ ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፤ በመመስረቻ ጽሑፍ የተመረጠ ስራ አስኪያጅ ለመሻር ደግሞ መመስረቻ ጽሑፍን ለማሻሻል የሚያስፈልገውን የ¾ኛ ካፒታል ድርሻ ባላቸው አባላት መደገፍ ያለበት ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ.527(1) እና 536(2) አጠቃላይ ንባብ የሚያስገነዝብ ከመሆኑም በላይ በዚህ ጉዳይ ስብሰባውን ያደረጉት የአመልካቾች ወገን 77.50% የካፒታል ድርሻ ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ በሌሎቹ የመመስረቻ ሰነዱን ማሻሻል በተመለከተ ህጋዊ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በማረጋገጥ ተቀብለዋል፡፡ ሆኖም ግን ስራ አስኪያጅን ስለመሻር በተመለከተ በንግድ ህግ ቁጥር 527 ስር የተደነገጉትን አንድ በአንድ ስንመለከት ከላይ የተመለከተው እና ስራ አስኪያጅን ለመሻር የሚያስፈልገው ድምጽ በንግድ ህግ ቁ.527(1) ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሦስት ስር ስራ አስኪያጅ ፍርድ ቤት ሊቀበለው በሚችል በቂ ምክንያት ካልሆነ ሊሻር እንደማይችል፣ የተሻረው ስራ አስኪያጅ ከተሻረበት ጊዜ አንስቶ ስራውን መስራት የማይችል ስለመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱም የተሻረበት በቂ ምክንያት ያለመሆኑን የተረዳው እንደሆነ የተሻረው ስራ አስኪያጅ ኪሳራ እንዲያገኝ ለመወሰን ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ ይሄ በንግድ ህግ ቁ.527(3) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ደግሞ ቀደም ሲል ከተመለከተው ከዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር አንድ ቀጥሎ የመጣ በመሆኑ ስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስኪያጅን ከስራ ለማንሳት መሟላት እንዳለበት በተለየ የሚደነግገውን ቅድመ ሁኔታዎቹ ስለመሟላት ወይም አለመሟላት መመልከቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የስራ አስኪያጅን መሻር በተመለከተ ፍርድ ቤት ሊያምንበት የሚችል በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ሊሻር እንደማይችል በግልጽ የደነገገ በመሆኑ ፍርድ ቤት ስራ አስኪያጁ የተሻረበትን አግባብ በመመርመር እንደጉዳዩ አግባብ እየተመለከተ ወደ ስራው ሊመልስ የሚችልበት ምንም ህጋዊ አካሄድ የለም በማለት በአመልካቾች በኩል የተነሳው ክርክር በህጉ በግልጽ የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በንግድ ህግ ቁ.527(3) ሁለተኛው እና ሶስተኛውን አረፍተ ነገር በተመለከተ ከኃላፊነት የተሻረ ስራ አስኪያጅ ወዲያውኑ እና ለዘለቄታው ስራውን ያቆማል መባሉ ስራ አስኪያጁ የተሻረበትን አግባብ ለመመርመር ለፍርድ ቤት የተሰጠውን ስልጣን የሚነካ እና የሚቃረን ካለመሆኑም በላይ ያለአግባብ የተሻረ ስራ አስኪያጅ ፍርድ ቤቱ ኪሳራ እንዲቆረጥለት መወሰን መቻሉ ፍርድ ቤቱ ማድረግ የሚችለው ኪሳራን መቁረጥ ብቻ ነው ከሚል ባለመሆኑ እና እንደየ ጉዳዩ አግባብ ለመወሰን እንዲችል ፈቃጅ (permissive) በሆነ መልኩ የተቀመጠ በመሆኑ ፍርድ ቤት ኪሳራ ቆርጦ ከማሰናበት ውጪ ስራአስኪያጁ የተሻረው ያለአግባብ መሆኑን ቢረዳም ወደ ስራው እንዲመለስ የሚወስንበት አግባብ የለም በማለት የተነሳውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ ምክንያቱም ያለበቂ ምክንያት ሊሻር የሚችል ስራ አስኪያጅ እንደሚኖር ሁሉ በበቂ ምክንያትም የሚሻር ስራ አስኪያጅ ሊኖር ስለሚችል ፍርድ ቤቶች እንደየጉዳዩ አግባብነት በመመልከት መወሰን እንዲችሉ ፈቃጅ በሆነ መልኩ የተቀረጸ ድንጋጌ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ያለበቂ ምክንያት የተሻረም ቢሆን እንደየጉዳዩ አግባብነት ኪሳራ ተከፍሎት እንዲሰናበት ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል ማለት ነው፡፡

በሌለ በኩል በንግድ ህግ ቁ. 527(3) ስር የተቀመጠውን ድንጋጌ ከአቀማመጡ አኳያ በተለየ ሁኔታ ስራአስኪያጅን ለመሻር የተመለከተውን ድንጋጌ ያስቀመጠው በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ አራት ስር የተቀመጠው ሲሆን ይሄውም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በማህበርተኞች ነጻ ፍቃድ (at the pleasure of the members) ሊሻር የሚችል ስለመሆኑ የተስማሙ እንደሆነ በማለት ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በእንደዚህ ዓይነት መልኩ የተስማሙ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር የሌለ እና አመልካች በቅሬታው ላይ ያነሳው በጠቅላላ ጉባኤ ማንሳት እንደሚቻል በመመስረቻ ጽሑፉ ተመልክቷል የሚል ሲሆን ይሄ ማለት ደግሞ በንግድ ህግ ቁ 527(4) ስር የተመለከተውን የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካቾች ተጠሪን ከም/ስራአስኪያጅነት ለማንሳት ያቀረቡት በቂ ምክንያት ያለመኖሩን በበታች ፍርድ ቤት በፍሬ-ነገር የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በክርክር ሂደት ግልጽ የሆነው ደግሞ ግራቀኙ የሚያስተዳድሩት ድርጅት እንደማንኛውም ተቀጣሪ ስራ አስኪያጅ ሳይሆን በውርስ የተላለፈላቸውና አመልካቾች በአንድ ወገን በመሆን ተጠሪ ደግሞ በሌላ ወገን በመሆን የተለያዩ ፍላጎቶች በመከሰታቸው የተጠሪ ከም/ስራአስኪያጅነት አለመነሳት በአግባቡ መሆኑን የሚያጠናክር ነጥብ ነው፡፡

ባጠቃላይ የአሁን ተጠሪ ከምክትል ስራአስኪያጅነት የተነሳው ያለአግባብ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ተመልክተው ወደ ስራው ይመለስ በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡና የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ ቁ.94715 ህዳር 28 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 140096 በቀን 05-9-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአሁን ተጠሪ ከምክትል ስራአስኪያጅነቱ የሚሻርበት ህጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ጥር 02 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 69291

ህዳር 8 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ጀማል አማን - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ተዋበች ፈረደ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የእርሻ መሬት ይዞታና የመጠቀም መብትን የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአርሲ ዞን የጉፋ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ብር 1020 /አንድ ሺህ ሃያ ብር/ ተበድሬ በወለድ አግድ ሶስት ቀርጥ የሚሆን መሬት ህዳር 10 ቀን 1990 ዓ.ም በተፃፈ ውል ሰጥቸዋለሁ፡፡ መሬቱን እንዲለቅልኝ ብጠይቀው እንቢተኛ ስለሆነ በፍርድ ተገድዶ ይልቀቅልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች መሬቱን ብር 1020 ተቀብላ ከሰጠችኝ በኋላ በገንዘቡ ችግሯን ከተወጣች በኋላ መሬቱን እንዲለቅላት መጠየቁ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ ከሰጠችው ሶስት ቀረጥ መሬት አንድ ቀርጥ መሬት ብቻ ለተጠሪ ይልቀቅላት በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳ ለህግ ተቃራኒ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡ አመልካች ተጠሪ መሬት ላይ የሰራውን ቤት አንስቶ መሬቱን ለተጠሪ ያስረክብ በማለት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

ተጠሪ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመግለፅ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች ። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል።

ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ መሬቱን ይዞ አስራ አንድ ዓመት እንደቆየና የተጠሪ ክስ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ መሬቱን እንድለቅ መወሰኑ ስህተት አለበት። ግምቱ ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ ብር/ የሚያወጣ ባህር ዛፍ ተክየበት እያለ እንድለቅ መወሰኑ ተገቢ አይደለም። ስለዚህ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ሰበር ችሎት ፍርድ ቤት ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል። ተጠሪ አመልካች መሬቱን የያዘው በውል ነው። ስለዚህ ይርጋን መከራከሪያ ማድረጉ ተገቢ አይደለም። አመልካች ብር 1020 /አንድ ሺህ ሃያ ብር/ ስለከፈለ መሬቱን ይዞ የሚቆይበትና የእኔን የመሬት ባለይዞታነትና ተጠቃሚነት መብት የሚያሳጣበት ምክንያት የለም። ስለዚህ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ የክልሉ አዋጅ ቁጥር 130/1999 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል። አመልካች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1810 እና 1845 በመጥቀስ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል ጉዳዩን እንደመረመርነው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ? ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች ከተጠሪ ጋር ህዳር 10 ቀን 1990 ዓ.ም አድርጌዋለሁ የሚለውን ውል ይዘትና መሠረታዊ ባህሪ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። አመልካች የተለያየ ንብረት አፍርቸበታለሁ የሚለው የእርሻ መሬት የተጠሪ ህጋዊ ይዞታ መሆኑን አልካደም። አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ችግር አጋጥሟት እኔ ብር 1020 /አንድ ሺህ ሃያ ብር/ ለችግር ማቅለያ እንዲሆናት ሰጥቻት ተጠሪ የእርሻ መሬቱን እኔ እንድጠቀምበት ሰጥታኛለች። የእርሻ መሬቱንም ከሰጠችኝ አስር ዓመት ያለፈው ስለሆነ ተጠሪ የእርሻ መሬቱን ይልቀቅልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት ነው። በእኛ በኩል አመልካች ከተጠሪ ጋር ህዳር 10 ቀን 1990 ዓ.ም የተዋዋለው ውል በመሠረታዊ ይዘቱ አመልካች ለተጠሪ በሰጣት ብር 1020 /አንድ ሺህ ሃያ ብር/ መክፈያ እንዲሆን ተጠሪ ሶስት ቀርጥ መሬት ላልተወሰነ ጊዜ እንዲጠቀምበት ግዴታ የገባች መሆኑን የሚያሣይ ነው። ውሉ በመሠረታዊ ይዘቱም ሆነ በባህሪው ተጠሪ በመሬቱ ላይ ያላትን የመጠቀምና የይዞታ መብት ለዘለቄታው ለአመልካች በብር 1020 /አንድ ሺህ ሃያ ብር/ ለመሸጥ የተስማማች መሆኑን የሚያሣይ ነው።

መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የመንግስትና የህዝብ ሀብት መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 ተደንግጓል። መሬት የመንግስትና የህዝብ ሀብት ሆኖ ማናቸውም ኢትዮጵያ አርሶ አደር የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀምና ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ያለው መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 በግልፅ ተደንግጓል። መንግስት የአርሶ አደሮችን የመሬት ባለይዞታ የመሆን መሬት የመጠቀምና ከይዞታቸው ያለመፈናቀል መብት ህጋዊና ተግባራዊ ለማድረግ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/93 እና በኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥር 130/99 በማውጣት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። በአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ አንድ አርሶ አደር የእርሻ መሬቱን ከሶስት ዓመት በላይ በኮንትራት መስጠት እንደማይችል የደነገገ ሲሆን ማንኛውም አርሶ አደር መሬቱን በኮንትራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሌላ ሰው ሲሰጥ ውሉ ሊያሟላቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ይዘረዝራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአንድ አርሶ አደርን የመሬት ይዞታና በመሬት የመጠቀም መብት በውል በመውሰድ በመሬቱ ላይ ቋሚና ተንቀሣቃሽ ሀብት ያፈራ ሰው ንብረቱን አፍርሶ በመውሰድ መሬቱን የመልቀቅ ግዴታ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀፅ 6 ተደንግጓል፡፡

አመልካች ከተጠሪ ጋር አድርጌዋለሁ የሚለው ውል በመሠረታዊ ይዘቱና ሞራላዊ ባህሪው በህገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 እና በህገመንግስት አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገውን የአርሶ አደሮች የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀምን ከይዞታቸው ያለመፈናቀል መብት የሚጥስ ከሆኑ በኋላ የፌደራል መንግስት ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 456/97 እና የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 130/99 ድንጋጌዎች የሚቃረን ህገወጥ የሆነ ውል ነው፡፡ ውሉ ህገወጥ ውል በመሆኑ ተጠሪ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ብር 1020 /አንድ ሺ ሃያ ብር/ በመክፍል የተጠሪን ሶስት ቀረጥ የእርሻ መሬት ለዘለቄታው ለመውሰድ የተዋዋለው ውል ህገወጥ ውል በመሆኑ ውሉ ፈራሽና ውጤት አልባ ነው በማለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ የህገ መንግስቱንና የፌደራሉ መንግስት ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 456/97 እና የኦሮሚያ ክልል ያወጣውን አዋጅ ቁጥር 130/99 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የተሰጠና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሀምሌ 6 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሸለማ ነገሰ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ፋይሣ መንግስቱ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኖኖ ቤንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ የእርሻ መሬትን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በኖኖ ቤንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በኖኖ ቤንጃ ቀበሌ ውስጥ በሰሰኮ ጎጥ ጋሴ ቀርጫ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ የተለያዩ አትክልቶች አርባ ግንድ ባህር ዛፍ አራት ግንድ ጌሾ አባቴ ተክሎ ሲጠቀምበት የኖረውን መሬት ተከሣሽ በሥልጣኑ ይዞታል፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች መሬቱን እኩል ያካፈሉን ሲሆን መሬቱ የአባቴ በመሆኑና ለእኔ ሊደርሰኝ ስለሚገባ የእርሻ መሬቱን እንዲለቅልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የአሁን አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ክስ የቀረበበትን መሬት ከአሥራ ሁለት ዓመት በፊት የከሣሽ አባት በህይወት እያለ የነበረውን ባህር ዛፍ ገዝቼ መሬቱን በ1981 ዓ.ም. ተመርቼ ይኸው እየተጠቀምኩበት እገኛለሁ፡፡ መሬቱ በአሉ ኤልፈታ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን አባቴ መሬቱን ለቆ ወደ ደጋ ሲባ ቀበሌ ሄዷል፡፡ መሬቱ የራሴ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የኖኖ ቤንጃ ወረዳ መሬትና የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት አመልካችም ሆነ ተጠሪ በመሬቱ ላይ ግብር እየከፈሉ አይደለም፡፡ በፊት መሬቱ የከሣሽ አባት ነበር በማለት ማስረጃ በመስጠቱ የወረዳው ፍርድ ቤት ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ የሰው ምስክሮችን ሰምቷል፡፡ የቀረቡት ምስክሮች የከሣሽ የተጠሪ አባት 1985 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን ከዚህ በኋላ ተከሣሽ አመልካች መሬቱን ይዞ የሚገኝ መሆኑን እና ግራ ቀኙ በክርክር ላይ ያሉ መሆኑን የተጠሪ ምስክሮች የመሠከሩ ሲሆን የአመልካች ምስክሮች አመልካች ተመርቸዋለሁ በማለት መሬቱን እንደያዘ ፣ ከቦታው ድረስ ሄደው እንደሚያውቁ መሥክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወረዳው ፍርድ ቤት የእርሻ መሬቱ የከሣሽ አባት የነበረ ስለሆነ ተከሣሽ መሬቱን ይልቀቅ በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል። አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ችሎት ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታውን አልተቀበሉትም።

አመልካች 1981 ዓ.ም መሬቱ ባዶ መሆኑን አመልካች ለእኔ ተሰጥቶኛል። አመልካች በህጋዊ መንገድ በይዞታዬ አድርጌ አሥራ ሁለት ዓመት ከተጠቀምኩበት በኋላ ተጠሪ የአባቴ መሬት ነበር በማለት ክስ አቅርቧል ። ከዚህ በፊት በዚሁ ጉዳይ የተጠሪ ወንድም ክስ አቅርቦብኝ የማህበራዊ ፍርድ ቤት መጋቢት 4 ቀን 1994 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቶበታል። ስለሆነም በፍርድ በተቋጨ ጉዳይ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በመቀበል የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል።

ተጠሪ በበኩሉ ሀምሌ 21 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ አመልካች ያነሣው የይርጋ ክርክር ተገቢነት የለውም። መሬቱንም አስራ ሁለት ዓመት አልያዘም። እኔም አካለመጠን ያልደረስኩ ነበርኩ አመልካች የማህበራዊ ፍርድ ቤት ወስኖልኛል ያለው በሥር ፍርድ ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው። ስለዚህ የሰበር አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካች ሀምሌ 22 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለረዥም ጊዜ መሬቱን በይዞታየ አድርጌ እየተጠቀምኩበት ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር በማለፍ መሬቱን ለተጠሪ እንዲለቅ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች የክርክሩ መነሻ የሆነውን የእርሻ መሬት የያዘው ከመቼ ጀምሮ ነው? ተጠሪስ አመልካች የእርሻ መሬቱን እንዲለቅለት ክስ ያቀረበው መሬቱን አመልካች ከያዘው ከስንት ጊዜ በኋላ ነው የሚሉትን ነጥቦች መመርመር አስፈላጊ ነው። አመልካች የክርክሩ መነሻ የሆነውን የእርሻ መሬት 1981 ዓ.ም. ጀምሮ ይዣቸዋለሁ በማለት የተከራከረ ቢሆንም ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳላቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል። በሌላ በኩል አመልካች አከራካሪውን የእርሻ መሬት የተጠሪ አባት 1985 ዓ.ም በሞት ከተለየበት ጊዜ ጀምሮ የያዘው መሆኑ ተጠሪ ለወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረባቸው ምስክሮች ተረጋግጧል።

የተጠሪ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል መነሻ በማድረግ ተጠሪ አመልካች የሚች የአባቱን ይዞታ መሬት እንዲለቅለት ክስ እስካቀረበበት 2003 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ አመልካች ለአሥራ ስምንት ዓመት የእርሻ መሬቱን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1140 በሚደነግገው መሠረት በእጁ አድርጎ በእውነት ሲያዝበት የኖረ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል። ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያቀረበው ሚች ወላጅ አባቴ በመሬቱ ላይ የነበረው የይዞታና በመሬቱ የመጠቀም መብት በውርስ ለእኔ ተላልፎልኛል በማለት ነው።

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የአርሶ አደር አባታቸውን ወይም እናታቸውን የእርሻ መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ያላቸው ወራሾች በውርስ ተላልፎልናል የሚሉትን መብት ለማስከበር ክስ ማቅረብ የሚችሉት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ነው? በሌላ አነጋገር የእርሻ መሬት የይዞታና የመጠቀም መብት ለማስከበር በሚቀርብ ክስ ላይ የይርጋ የጊዜ ገደቡ ምን ይሆናል? የሚለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነጥብ ነው፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አርሶ አደር የእርሻ መሬት ባለይዞታ የመሆንና ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ያለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 እና የኦሮሚያ ክልል ያወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቀቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 የመሬት ባለይዞታ የሆነና በመሬቱ የመጠቀም መብት ያለው ሰው ለሁለት ዓመት ያህል መሬቱን በመተው ከአካባቢው ከጠፋ የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀም መብቱ ቀሪ እንደሚሆን ይደግጋሉ፡፡ ሆኖም የህግ ማዕቀፎቹ የእርሻ መሬት ባለይዞታና የመጠቀም መብቱ በሌላ ሰው ተደፎሮብኛል የሚል አርሶ አደር የመሬት ባለይዞታነትና የመጠቀም መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ ያለበት በስንት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ የፌዴራሉ አዋጅ ቁጥር 456/97 እና የኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥር 130/1999 በግልፅ አይደነግጉም፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለውን የይርጋ ህግ ድንጋጌ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገውን የአርሶ አደሮች የመሬት ባለይዞታነትና የመጠቀም መብት በማያጣጣብብ ሁኔታ አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች በመተርጎም ውሣኔ መስጠት የሚገባው ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ድንጋጌዎች ስንመረምር በመጀመሪያው ድንጋጌ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው የሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ሆኖም ድንጋጌው በተለያየ መንገድ የይዞታና በመሬት የመጠቀም መብታቸውን በሌላ ሰው የተደፈረባቸው አርሶ አደሮች በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን የእርሻ መሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት የመጠቀም መብት በፍርድ ቤት ተከራክረው በማስከበር ሰፋ ያለ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ የማይሰጥ በመሆኑ በገጠር መሬት ላይ ያለን የባለይዞታነትና በመሬት በመጠቀም በሚቀርብ ክርክር ላይ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀፅ 2 ተመራጭ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ማንኛውም አርሶ አደር ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በእርሻ መሬት ላይ ያለውን የይዞታና የመጠቀም መብት ለማስከበር ተገቢውን ትጋት የማድረግ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም በሌሎች የይርጋ የጊዜ ገደብ በግልፅ ባልተደነገገላቸው ጉዳዮች ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት ለፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1677/1/ እና ለፍትብሔር ህግ ቁጥር 1845 የተደነገገው የአሥር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ አርሶ አደሮች በህገ መንግስቱ የተከበረላቸውን የመሬት ባለይዞታነትና በመሬት የመጠቀም መብት በፍርድ ከስሰው ለማስከበር ሰፋ ያለ እድል የሚሰጠው የፌዴራል አዋጅ ቁጥር 456/97 እና የኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥር 130/1999 መሠረታዊ ጋር የሚጣጣም ሆኖ አግኝተዋል፡፡ ስለሆነም ይዞታውን በሌላ ሰው የተነጠቀ አርሶ አደር ወይም ወራሾቹ ይዞታው በሌላ ሰው ከህግ ወይም ከውል ውጭ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ውስጥ የእርሻ መሬት የባለይዞታነትና የመጠቀም መብቱን ለማስከበር ክስ ካላቀረበ ክሱ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1677/3/ እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1845 በተደነገገው የአሥር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ይታገዳል ከሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሰናል፡፡

2. ተጠሪ አመልካች በ1985 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ወላጅ አባቱ የእርሻ መሬት ሊለቅልኝ ይገባል በማለት ያቀረበው በ2003 ዓ.ም ነው፡፡ ተጠሪ ክስ ያቀረበው አመልካች የእርሻ መሬቱን ለአሥራ ስምንት ዓመት ይዞ ከተጠቀመበት በኋላ መሆኑን ከክርክሩ ሂደትና ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ አመልካች መሬቱን ለአሥራ ስምንት ዓመት የያዘ መሆኑን በመግለፅ ተጠሪ ክስ ሊያቀርብብኝ አይገባም የሚለውን ክርክር ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት እንዳቀረበ ተገንዝበናል፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤት ወደ ፍሬ ጉዳይ ገብቶ የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ከመስማቱ በፊት በመጀመሪያ አመልካች ባነሣው የይርጋ የጊዜ ገደብ መቃወሚያ ላይ ብይን መስጠት እንዳለበት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ አመልካች የአባቱ ይዞታ የነበረውን መሬት እንዲለቅለት ክስ ያቀረበው አመልካች መሬቱን 1985 ዓ.ም ጀምሮ ይዞ አሥራ ስምንት ዐመት ከቆየ በኋላ መሆኑ በተጠሪ ምስክሮች ጭምር ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1677/1/ እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1845 የተደነገገው የአስር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ አመልካች መሬቱን እንዲለቅለት ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ በማለፍ መሬቱን ለተጠሪ እንዲለቅ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኖኖ ቤንጃ ፍርድ ቤት ፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ አመልካች መሬት እንዲለቅ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች መሬቱን ለተጠሪ የመልቀቅ ግዴታ የለበትም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 69821
ታህሳስ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- አቶ ጥላሁን ጎበዜ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ መከተ ኃይሉ - ቀረቡ

2. አቶ አወቀ መጫ - በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግሥት በፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ባቀረበው ክስ የተጀመረ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ ተከሣሾች በ1989 ዓ.ም በተደረገው የመሬት ሽግሽግ የተመራሁትን ስለያዙበኝ እንዲለቁልኝ በማለት አዋሣኙን በመጥቀስ እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡ ተከሣሾች በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንዲሠጡበት ታዘው በሰጡት መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት ከ1989 ዓ.ም. በፊትም የራሳቸው የነበረ ስለመሆኑ፣ በ1989 ዓ.ም. የመሬት ሽግሽግ ሲደረግ ለተከሣሾች የተቆጠረ ስለመሆኑ፣ በ1997 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው የሚጠቀሙበት የራሳቸው ይዞታ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ የወረዳ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተከሣሾች በዚህ አከራካሪ በሆነው የእርሻ መሬት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ስለተሰጣቸው ያለአግባብ የተሰጠ የይዞታ መረጋገጫ ከሆነ ይዞታውን ለሰጠው አካል ከማቅረብ ውጭ በቀረበው ክስ መሬቱ የከሣሽ ነው በማለት ማስለቀቅ አይቻልም በማለት በእንደዚህ ዓይነት መልኩ ክስ መቅረቡ ህጋዊ አይደለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ይግባኙን ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የበታች ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር ተከሣሾች ለክርክር ምክንያት የሆነውን የእርሻ መሬት ለከሣሽ (አመልካች) እንዲያስረክቡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በዚህ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎአል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች በቀረበው ክስ ላይ ውሣኔ የሰጡት ተገቢውን የማጣራት ሂደት በማድረግ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አዋጅ ቁ. 133/98 አንቀጽ 24(4) እና ይሄንን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው የደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 20(4) የይዞታ ማረጋገጫ የያዘ ሰው የመሬቱ ባለይዞታ እንደሆነ እንደሚገመት ይደነግጋል፡፡ ይሄ ማለት ግን በህጉ የተቀመጠው የባለይዞታነት ግምት ሊስተባበል የማይቻል በራሱ ብቻ አሳሪ ማስረጃ ስለመሆኑ የተመለከተ ነገር የለም፡፡

በአንድ የፍትሐብሔር ክርክር በህጉ በተለየ ሁኔታ የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቱ የተገደበ ካልሆነ በጽሑፍ፣ በምስክር፣ በህሊና ግምት፣ በተከራካሪዎች እምነት፣ ወይም በመሓላ ማስረጃ ማስረዳት እንደሚቻል በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 2002፣ 1195፣1196 እና በተለያዩ ህጎች ውስጥ የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቶችን የሚደነግጉ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ዓላማ፣ ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች ተከሣሾች ይዞታዬን ይዘውብኛል እና እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎችም የራሳቸውን መከራከሪያና በ1997 ዓ.ም የተሰጣቸውን የይዞታ ማረጋገጫ አቅርበዋል፡፡ ይሄ በሚሆንበት ጊዜ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያላቸውን ማስረጃ በመስማት እና ከሌላ የመንግሥት አካላትም መቅረብ ያለበትን ማስረጃ በመቀበልና የቀረቡትን ማስረጃዎች በማመዛዘን ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ሲገባው ተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ያቀረቡ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም፡፡ የይዞታ ማረጋገጫም ቢሆን እንደአንድ ማስረጃ ተቀባይነት ያለውና ሊመዘን የሚችል እንጂ ወሣኝ (conclusive evidence) ባለመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመቀበል እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ማስረጃዎች በመቀበል ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ሲገባ የይዞታ ማረጋገጫ ሊስተባበል እንደማይቻል ማስረጃ በመውሰድ እንደዚሁም መስተባበል ካለበት የይዞታ ማረጋገጫውን ለሰጠው አካል አቤቱታ በማቅረብ ብቻ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ በግራቀኙ ማስረጃ ጉዳዩን ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን እንደሌለው በመውሰድ የቀረበውን ክስ ህጋዊ አይደለም በማለት ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የደቡብ ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ያስቀርባል አያስቀርብም በማለት ተገቢውን ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ለተጠሪዎች የተሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠበትን አግባብ የወረዳው የመሬት አስተዳደር አካል መግለጫ እንዲሰጥበት ማድረጉ ተጠሪዎች የክርክሩ አካል ባልተደረጉበት ጊዜ በመሆኑ አግባብነት ያለው የማስረጃ አሰባሰብ ስርአት ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡ ምክንያቱም ማጣራቱ ተገቢ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካመነበት ግራቀኙ የክርክሩ አካል በሆኑበትና የእኩልነት መርህን በጠበቀ መልኩ መከታተልና በቀረበው ማስረጃ ላይ አስተያዬት መስጠት በሚችሉበት ሁኔታ መደረግ ነበረበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የእርሻ መሬት የማን ይዞታ ነው? የሚለውን ነጥብ በግራቀኙ ማስረጃ በማጣራት እንደዚሁም ከሌላ የመንግስት አካልም ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል አስፈላጊ ከሆነም ይሄው ስርአት ተፈፅሞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ሲገባው መሰረታዊ የማስረጃ አቀባበልና ምዘና ስርአት ባልተከተለ መልኩ የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የመዝ.ቁ. 07860 ሚያዝያ 24 ቀን 2003ዓ.ም በዋለው ችሎት፣የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.25228 በቀን 03-7-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣ የደቡብ ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 21099 በቀን 11-10-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት መዝ.ቁጥር ባልተጠቀሰ በቀን 15-4-2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው የእርሻ መሬት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ በመያዛቸው ብቻ ሊስተጓበል አይችልም በማለት የቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው አግባብነት ያለው አካሄድ አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት ግራቀኙ አከራካሪ በሆነው የእርሻ መሬት ላይ ያላቸውን ማስረጃ መስማትና ሌሎች ተገቢ ናቸው የሚለውን ተጨማሪ ማስረጃዎች ከሚመለከተው የመንግስት አካል በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 59504

የካቲት 27ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. አቶ እንዳለ ወርቅነህ - አልቀረቡም

2. ወ/ሮ ብዙነሽ ሰንበቶ - አልቀረቡም

3. አቶ ኪዳኑ ቦቦ - ቀረቡ

4. አቶ ተስፋዬ ፈይሳ - አልቀረቡም

5. ወ/ሮ በላይነሽ ታደሰ -አልቀረቡም

6. ወ/ሮ ዙፋን ታደሰ - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ተሸለ ቱቾ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቅድሚያ ግዥ መብት ጥያቄ የሚስተናገድበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ አመልካች ስድስት ክፍል ቤቶች የካርታ ቁጥሩ 968/አንቀፅ/ 96 የሆነውን በነቀምቴ ከተማ በዳርጌ አስተዳደር ክፍል ውስጥ የሚገኘውን በዚህ ሰበር ችሎት ከተራ ቁጥር ሶስት እስከ ተራ ቁጥር ስድስት ለተጠቀሱት በብር 360,000.00 (ሶስት መቶ ስልሳ ሺህ) ሽጠው ስም በማዛዋወር ላይ እንዳሉ ሰምተው ከነቀምት ከተማ አስተዳደር ላይ አጣርተው ይህን ቤት ለመግዛት ቀዳሚ መብት እንዳለቸው ማመልከታቸውን፣ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ተጠሪ የንግድ ድርጅታቸውን ከመግዛታቸው በፊት የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ንብረት የነበረ ሆኖ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በእዳ ይዞ ይኸው አካል በሕግ አግባብ የሸጠላቸው መሆኑን፣ በዚህ አግባብ በገዙት ንብረትም የባለቤትነት ማስረጃ የካርታ ቁጥር 352/አንቀጽ/2000 በሆነው ተሰጥቷቸው ከተራ ቁጥር ሶስት እስከ ተራ ቁጥር ስድስት የተጠቀሱት አመልካቾች ከገዙት ቤት ጋር በግድግዳ፣ በጣሪያውና በአንድ ምሰሶ ተያይዞ የተሰራ መሆኑን፣ ይህን ቤት አሳልፎ ለሶስተኛ ወገን መሸጥ ማለት አንድን ቤት ለሁለት ከፍሎው መሸጥ መሆኑንና ይህም የተጠሪን መብት የሚጎዳ መሆኑን ዘርዝረው ገዥዎች የገዙትን ዋጋ ተጠሪ ከፍለው በቀዳሚነት የመግዛት መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም በተጠሪና በሻጮች መካከል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቤቶቹ ላይ የጋራ መብት ስለመቋቋሙ የሚያሳይ ውል የሌለ መሆኑን፣ የቤቱ ጣሪያና ግድግዳ አንድ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ የግዥና የሽያጭ ውሉም ተመዝግቦ የባለቤትነት ማስረጃ ሊሰራ ቁጥር ስለመስጠታቸውና ተጠሪ የቅድሚ ግዥ ጥያቄ ለማቅረብ መብት የሌላቸው መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል። የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ጉዳዩን ተገቢ ነው ባለው መንገድ ከአጣራ በኋላ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1281 መሰረት በቤቱ ላይ የጋራ መብት ማቋቋማቸው መረጋገጡን፣ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1261፣ 1386 እና 1388 ድንጋጌዎች መሰረት ተጠሪ በግዥ የተላለፈውን ቤት በቀዳሚነት የመግዛት መብት እንዳላቸው የሚያሳይ መሆኑን ገልፆ ተጠሪ የቤቱን ዋጋ ከፍለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ይግዙ ሲል ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምስራቅ ወሊጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም የሽው ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል። ከዚህም በኋላ አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ፀንቷል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በቤቱ ላይ የቀዳሚነት መብት አላቸው ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች የተወሰነው በቤቱ ላይ ግራ ቀኙ ያቋቋሙትን መብት አይነት፣ መብቱ የተቋቋመበትን መንገድና ጊዜ እንዲሁም የጋራ መብት ያላቸው ሰዎች የቀዳሚነት መብት የሚኖራቸው ምን ምን ሕጋዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው የሚለውን ሕጋዊ ጥያቄዎች ተገቢውን ምልከታ ያላደረገና በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ውጪ የተሰጠ ስለመሆኑ ዘርዝረው ውሳኔው እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ቤቶች ለመግዛት የቅድሚያ መብት አለው የተባለው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በፅሁፍ በሰጡት መልስ የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ ስለጋራ ባለሀብቶች የተደነገጉትን የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ በመሆኑ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ውሳኔው እንዲፀናላቸው የተከራከሩ ሲሆን አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

በክርክሩ ሂደት ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ስድስት ክፍል ቤቶች የካርታ ቁጥሩ 968/አንቀጽ/ 96 የሆነውን በነቀምቴ ከተማ በዳርጌ አስተዳደር ክፍል ውስጥ የሚገኘውን በዚህ ሰበር ችሎት ከተራ ቁጥር ሶስት እስከ ተራ ቁጥር ስድስት ለተጠቀሱት በብር 360,000.00 (ሶስት መቶ ስልሳ ሺህ) ሽጠው ስም ለማዘዋወር ላይ እንዳሉ ሰምተው ከነቀምት ከተማ አስተዳደር ላይ አጣርተው ይህንን ቤት ለመግዛት ቀዳሚ መብት እንዳለቸው በማመናቸው መሆኑን፣ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ተጠሪ የንግድ ድርጅታቸውን ከመግዛታቸው በፊት የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ንብረት የነበረ ሆኖ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በእዳ ይዞ የሽው አካል በሕግ አግባብ ለተጠሪ የሸጠላቸው መሆኑን፣ በዚህ አግባብ በገዙት ንብረትም የባለቤትነት ማስረጃ የካርታ ቁጥር 352/አንቀጽ/2000 በሆነው የተሰጣቸው መሆኑን፣ ይኸው ቤት ከተራ ቁጥር ሶስት እስከ ተራ ቁጥር ስድስት የተጠቀሱት አመልካቾች ከገዙትና ለክርክሩ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሆኑት ቤቶች ጋር በአንድ በኩል በግድግዳ በአንድ በኩል ደግሞ ብሎኬት የተሰሩ ስለሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የምስራቅ ወለጋ ዞን ስራና ከተማ ልማትና ጽ/ቤት በባለሙያ አረጋግጦ ማስረጃ የሰጠ መሆኑን ነው፡፡

1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ለሌሎች አመልካቾች ሸጡ የተባሉት ቤትና ተጠሪ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ገዙ የተባለበት ቤት የተያያዙበት ግድግዳና ጣሪያ የጋራ ባለሀብትነት መብት በሕግ አግባብ የተቋቋመ ነው፡፡ በህጉ መሰረት የተፈጠረ የጋራ ባለሀብትነት ደግሞ የሚገዛው አግባብነት ባለው ህግ ነው፡፡ ከፍ/ህ/ቁ 1259-1277 ያሉት ድንጋጌዎች የሚያሳዩትም ይህንኑ ነው፡፡ የፍ/ህ/ቁ 1260/1/ ድንጋጌ የሚገልጸው ደግሞ እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት ድርሻውን ለመሸጥ ወይም በሌሎች መንገዶች የማስተላለፍ ወይም ለማስያዝ መብት ያለው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ስልጣኖች ሌሎች የጋራ ባለሀብቶች እየተቃወሙ ቢሆን እንኳን ባለድርሻው የጋራ ባለሀብት የሚተገብራቸው፣ በህግ የተጠበቁ ናቸው፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1281(1) ድንጋጌ ስር እንደተመለከተው ያንድ ቤት ልዩ ልዩ ፎቆች ወይም ለመኖሪያ የተመደቡ ክፍሎች (አፓርታማ) የልዩ ልዩ ባለሀብቶች ንብረት በሆኑ ጊዜ ተቃራኒ የሆነ ሰነድ ከሌለ ከእነዚህ ሀብቶች አንዱ ክፍል ለአንደኛው ባለንብረት የግል አገልግሎት የሚጠቅም እንዲሆን ከተደረገው በቀር የመሬቱና የሌላውም የቤቱ ክፍሎች የጋራ ንብረት እንደሆኑ የሚቆጠሩ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1289(1) ድንጋጌ ስር ደግሞ እያንዳንዱ የጋራ ባለንብረት የአንድነት ሀብት ባልሆነው ክፍል ንብረቱ ላይ ህግ ለባለሀብቱ የሚሰጣቸው መብቶች እንደሚኖሩት ተመልክቷል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1289(2) ድንጋጌ በተለይ ሲታይ ደግሞ የግሉ የሆነውን ለመኖሪያ የተመደቡትን ክፍሎች (አፓርታማ) ወይም ፎቅ ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ፣ ለማከራየት ወይም በዋስትና ለማስያዝ ባለሀብት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1290 ደግሞ የአንድነት ያልሆኑት ክፍሎች ላይ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1289 ስር የተመለከቱት መብቶች ያሉት ባለሀብት የተጣለበት ገደብ መኖሩ ተመልክቷል፡፡ ይህም ምንጊዜም የማይንቀሳቀሰውን ንብረት የተመደበበትን አግልግሎት አክብሮ መጠበቅ፣ እንዲሁም የተከፈለ ድርሻ የሆነው ንብረት እንዲያገለግል የተመደበበት ጉዳይም ሆነ የመጠቀሚያውን አይነተኛ ነገር ሌሎቹን ባለሀብቶች በሚጎዳ ሁኔታ ለመለወጥ ያለመቻል በሕጉ የተጣለበት ገደብ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያሳዩት አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት በጋራ ባለመብት የሚያደርጋቸው የንብረቱ ክፍል ካለ በዚሁ የጋራ ባለንብረት በሚያደርጋቸው የንብረቱ ክፍል ባለሀብቶቹ የሚኖራቸው መብት ለአንድ ባለሀብት ህጉ የሰጣቸው መብቶች ስለመሆናቸው ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተደነገጉትን የንብረት ህግ ድንጋጌዎችን ስንመለከት ባለቤትነት ከሁሉ የሰፋ መብት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በህግ የተቀመጡትን ገደቦችንና ወሰኖችን (Restriction and Limitation) ሳያልፍ የአንድ ንብረት ባለቤት በንብረት እንደፈለገው የመጠቀምና የመገልገል መብቱና ነፃነቱ በህግ የተከበረለት ስለመሆኑም ድንጋጌዎቹ ያሳያሉ፡፡ ለባለሀብቱ የባለቤትነት መብት ከሚሰጣቸው መብቶች መካከልም ንብረቱን በህጉ አግባብ ማስተላለፍ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1184 እና 1185 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በአጠቃላይ የባለቤትነት መብት ከሁሉ የሰፋ መብት ሲሆን በህጉ ከተጣሉት ገደቦች ውጪ የሚኾ ወይም ለሌላ ተላልፎ እንዲሰጥ የሚደረግ መብት አይደለም፡፡ ስለሆነም ሕጉ የጋራ ባለሀብት በህጉ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባቸው መብቶች ምን እንደሆኑ ለይቶ አስቀምጧል፡፡

በዚህም መሰረት የፍ/ህ/ቁ. 1261፣ 1388 እና 1406 ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይ የጋራ ባለሀብቶች ያልተከፈለውን የጋራ ንብረት ከማንኛውም 3ኛ ወገን በፊት፣ ሊሸጥ የታሰበውን ድርሻ አስገድዶ ለመግዛት የቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑን ያስረዳል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1281፣ 1289 እና 1290 ድንጋጌዎች ተግባራዊ የሚደረጉበትን አግባብ የሚገድቡ አይደሉም፡፡ ይልቁንም በበጉብረቱ ላይ ባለሀብቶች ያላቸው ድርሻ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1281፣ 1289 እና 1290 ድንጋጌዎች መሰረት የሚገዛ መሆኑ ከተረጋገጥው ውጪ የጋራ የሆነው ሀብት ሊሸጥ ሲታሰብ የጋራ ባለሀብቶች ከማንኛውም 3ኛ ወገን በፊት ሊሸጥ የታሰበውን ድርሻ አስገድዶ ለመግዛት የቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንድ ቤት በአንድ በኩል ግድግዳውና ጣሪያው የተያያዘ መሆኑ በሌሎች ክፍሎች ባለሀብቱ ያለውን መብት በፈለገው የገበያ ዋጋና ግዥ ወይም ለመለወጥ ሳይችል በአንድ በኩል የግድግዳው ባለሀብት ለሆነው ባለሀብት አጠቃሎ እንዲሸጥ በህግ ገደብ አልተጣለበትም፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት እንዲገዙት የወሰኑት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸው የፍ/ብሕ/ቁጥር 1281፣1289 እና 1290 ድንጋጌዎች ይዘት በፍሬ ነገር ደረጃ ቤቱ የተያያዘው በአንድ በኩል በግድግዳና ጣሪያ ስለመሆኑ ከተረጋገጠው ነጥብና ከተጠሪ ዳኝነት ይዘት ጋር በአግባቡ ሳያገናዝቡ እና በተጠሪ ላይ ሊደርስ ይችላል የተባለው ጉዳትም ሳይረጋገጥ ነው፡፡ ለአንድ ጉዳይ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ እያለ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት ደግሞ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀም ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል

ው ሳ ኔ

1. በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 12896 ጥር 24 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11851 20710 የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም. በትዕዛዝ ፀንቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 100754 ነሀሴ 12 ቀን 2002 ዓ.ም. በአብላጫ ድምጽ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በነቀምቴ ከተማ በዳርጌ አስተዳደር ክፍል በካርታ ቁጥር 968/አንቀጽ/ 96 በሆነው በ1ኛ አመልካች ስም ተመዝግቦ ያለው ስድስት ክፍል ቤቶች ለተጠሪ በቅድሚያ የሚሸጡበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡

3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዶ/ር ገነት ሥዩም - ጠበቃ ተስፋዬ ተገኘወርቅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17/18 አስተዳደር ፅ/ቤት - ነገረ ፈጅ አሸናፊ ሥዩም ቀረቡ

2. ወ/ሮ አመለወርቅ ሙላቴ
3. አቶ ባህረ ወ/ጊዮርጊስ

} ጠበቃ ላውጋለት ፀጋ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሕግ ውጪ የተያዘብኝ ቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡

የአመልካች የክስ ይዘትም አመልካች የደርግ መንግስት በስልጣን ላይ በነበረበት ወቅት በነበራቸው የፖለቲካ አመለካከት ሀገር ውስጥ ለመኖር ባለመቻላቸው ተሰደው ውጭ ሀገር መቆየታቸውን፣ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17/18 ክልል ውስጥ የሚገኘውና በካርታ ቁጥር 11442 የሚታወቀውን በ1985 ዓ/ም በቁጥር 15/31238 የሆነ የከተማ ቤት የባለቤትነት ደብተር ከከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የተሰጣቸው መሆኑን፣ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የቤት ቁጥሮች 268፣ 269 እና 270 በሚል መለያ ሰጥቶ ለ2ኛ፣ 3ኛ እና ለአቶ ዘሚካኤል ኃይሌ አከራይቶ ጥቅም እያገኘበት መሆኑን፣ ቤቱን 1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክባቸው ማስጠንቀቂያ ሰጥተውም ፈቃደኛ ሁኖ ያለመገኘቱን ገልፀው ቤቱን ለሕጋዊ ባለቤት እንዲያስረክብ፣ ተከራዮችም ቤቱን እንዲለቁ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም አከራካሪው ቤት በህግ በመንግስት መወረሱንና በፍርድ ቤት ስልጣን ስር የማይወድቅ መሆኑንና አመልካች ክስ ለማቅረብ የማይችሉ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ ቤቱ በሕግ የተወረሰ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ሌሎች ተጠሪዎችም ቤቱን ለረዥም አመታት ተከራይተው የሚጠቀሙበትና በ1ኛ ተጠሪ የሚተዳደር መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረቡትን መቃወሚዎችን ውድቅ አድርጎ ፍሬ ጉዳዩን መርምሮ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት አመልካች መሆናቸው ተረጋግጧል በማለት ቤቱን ተጠሪዎች ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩና 1ኛ ተጠሪ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ ከተደረገ በሁዋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች አለኝ የሚሉት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር መምከኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ ከዚህም በሁዋላ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተስርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 345(1ለ)) ድንጋጌን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በ1985 ዓ/ም ለአመልካች የተሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ በክርክር ላይ እያሉ ደብተሩ መክኗል ተብሎ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ መብት የላቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የነበረው የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ሕጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ውሳኔው ሊጸና ይገባል ሲሉ በፅሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፣ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሠረቱ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ንብረታቸው መሆኑን መጥቀሳቸውንና ይህንኑ መብታቸውን ያሳያል ያሉትንና በ1985 ዓ/ም በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ተሰጠኝ ያሉትን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ለማስረጃነት ማቅረባቸውን፣ የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት መከላከያ መልስ አመልካች በቤቱ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም፣ አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት ተወርሶ 1ኛው አመልካች ለረዥም አመታት የሚስተዳድረው መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከራቸውን፣ ይህንኑ የተጠሪዎችን ክርክር የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው በአመልካች በኩል የቀረበውን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርና ቤቱ ምትክ ያልተገኘበት ወይም ካሳ ያልተከፈለበት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቧል በሚል ምክንያት መሆኑን፣ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ የይግባኝ ክርክር ሲደረግ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ አመልካች አለኝ የሚሉትን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የተሰረዘ መሆኑንና ማስረጃው ሳይቀርብ የቀረበትን ምክንያት ገልፆ ማስረጃው እንዲቀርብ ጠይቆ ፍርድ ቤቱ የባለቤትነት ደብተሩ መምከኑን የሚያሳየውን የ1ኛ ተጠሪ ማስረጃ ተቀብሎ ጉዳዩን በመመርመር የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የሻረው መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ ከሣሽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222 መሠረት አዘጋጅቶ ከሚያቀርበው የክስ ማመልከቻ ጋር በክሱ መሰማት ወቅት ለጉዳዩ ማስረጃ ይሆኑኛል የሚሏቸውን የሠውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 234 ድንጋጌ ሲታይም በተከሳሹ ላይ ተመሳሳዩን ግዴታ ይጥላል፡፡ በተለይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137/3/ የሠነድ ማስረጃዎችን በተመለከተ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ወይም ከቀነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀጠሮ በፊት ወይም በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ ካልቀረበ በቀር ማስረጃው ሊቀርብ ወይም ይቅረብልኝ ተብሎ ሊጠየቅ እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ ይሄው ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኘው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 256 ስር በተመለከተው አኳኋን ማስረጃዎቹ ሣያቀርቡት የቀሩት ከባድና በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍ/ቤቱ ሲረዳ ብቻ ነው፡፡

የማስረጃ አቀራረብን በተመለከተ በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተው ሌላው ደንብ የይግባኝ ሠሚውን ፍ/ቤት ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345 ድንጋጌ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በራሱ አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውም ዓይነት ሠነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ ዓይነት ማስረጃ በተጨማሪነት እንዲቀርብለት የማዘዝ ህጋዊ ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145/1/ ድንጋጌም በሌላ ፍ/ቤት የሚገኝ ሠነድ የፀሁፍ ማስረጃ ወይም ፍርድ የተሠጠበት መዝገብ ለውሣኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍ/ቤቱ በራሡ አነሣሽነትም ሆነ በተከራካሪዎቹ ጠያቂነት እንዲቀርብለት ማዘዝ የሚችል ስለመሆኑ ያስረዳል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ውሣኔ የሠጠው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 345((1(ለ)) ድንጋጌ መሰረት የ1ኛ ተጠሪን የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄን ተቀብሎ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የማስረጃው መቅረብ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ተገቢ መሆኑን ማረጋገጡን የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካችን የባለቤትነትን መብት ሰርሢል የተባለው ማስረጃ ግን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በኋላ የተሰረዘበት አግባብ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን አመልካች ክርክር እንዲያቀርቡ እድል የተሰጠ ስለመሆኑ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልጽ አያሳይም፡፡ በአስተዳደር አካሉ የሚሰጥ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ይህንኑ የምስክር ወረቀት በስሙ የተፃፈለት ሰው የንብረቱ ባለቤት ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሕጉ የሚወሰደው ግምት ስለመኖሩ፣ ይኸው ግምት ግን አሳሪ ያለመሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ጋር ተዳምሮ ሲነበብ ያስረዳል፡፡ በሌላ አገላለፅ በአስተዳደር አካሉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ነው ተብሎ የምስክር ወረቀት መስጠት ማስረጃውን ድምዳሚ ወይም አሳሪ (Conclusive Evidence) የሚያደርገው አይደለም፡፡ ይልቁንም ይኸው ማስረጃ የተሰጠበት አግባብ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት ስለመሆኑ ማስረዳት ከተቻለ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ስር የተመለከተው ሕጋዊ ግምት ሊስተባበል የሚችል (rebuttable legal presumption) መሆኑን ከድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የአስተዳደር አካሉ የሰጠውን የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በሌላ ጊዜ መሰረዙ ከታወቀ ማስረጃው የተሰረዘበት አግባብ ከሕግ ውጪ መሆን ያለመሆኑ ተጣርቶ ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ ይኸው አካል ካርታውን አምክኗል ስለተባለ ብቻ ማስረጃው ክርክር ሳይደረግበት ተቀባይነት የሚያግኝበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የአስተዳደር አካሉ የሰጠውን የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በሌላ ጊዜ ሲሰርዝ ማስረጃው የተሰረዘበት ሰው የአስተዳደር አካሉን እርምጃ ክርክር ሊያቀርብበት አይገባም፣ በፍርድ ቤትም ሊጣራ የሚገባው አይደለም ከተባለ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 40(1 እና 2) የተረጋገጠውን የንብረት መብት ዋስትና ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባው ነው፡፡ አንድ ሰው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1206 መሰረት በንብረቱ ላይ የሚያቀርበው የመፋለም ክስ ተገቢው መጣራት ተደርጎና የመከራከር መብቱ በአግባቡ ሳይጠበቅለት ውድቅ የሚሆንበት አግባብም የለም፡፡ ፍርድ ቤት እውነትን ለማውጣት ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋቸውን ስለ ማስረጃ አቀራረብና አቀባበል የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ እነዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎች ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባው የክርክሩ አካሄድ በተሟላ አኳኋን ሲመራ መሆኑንም ያስገነዝባሉ፡፡ የክርክሩ አካሄድ ሳይሟላ የሚሰጥ ዳኝነት ሕጋዊ አይሆንም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች የተያዘው የባለቤትነት ማስረጃ ወረቀት በየካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም. የመከነን መሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርብ መደረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 345(1(ለ)) ድንጋጌን የጣሰ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ቢሆንም የአመልካችን የባለቤትነት ማስረጃ አመከነ የተባለው ማስረጃ የመከነበት አግባብ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ፣ የቤቱ ትክክለኛ ባለቤት ማን እንደሆነ ግን ተገቢው ማጣራት ሳይደረግ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ቤቱ የአመልካች አይደለም ተብሎ መወሰኑ ፍርድ ቤቶቹ የክርክሩን አመራር ከላይ በተመለከቱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች አለመምራታቸውንና ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1195፣ 1196 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጉዳዩን ያለመመልከታቸው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሠጡት የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ድንጋጌዎች በማይደግፉትና የፍርድ አካሄዱ ባልተሟላበት ሁኔታ በመሆኑ በየእርከኑ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሠጠው ውሣኔ እና ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ሊሻሩ የሚገባና የስር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ሁሉንም መከራከሪያ ነጥቦችንና የአመልካችን የባለቤትነት መብት አምክኗል የተባለው ማስረጃ የመከነበትን ሕጋዊ አግባብ እንዲሁም በአጠቃላይ የአከራካሪው ቤት ሕጋዊ ባለቤት ማን ነው? የሚለውን ጭብጥ በመያዝና ተገቢውን ማጣራት ሁሉ በማድረግ ጉዳዩን እንደገና በመመልከት ውሳኔ እንዲሰጡበት ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 58891 ጥቅምት 12 ቀን 2003 ዓ.ም የተሠጠው ትዕዛዝ፣ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በከ/መ/ቁ 78798 መጋቢት 22 ቀን 2002 ዓ.ም የተሠጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በከ/መ/ቁ 135792 ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም የተሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡

2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በከ/መ/ቁ 135792 ክርክሩን ቀጥሎ አመልካች አለኝ የሚሉትን የባለቤትነት ደብተር 1ኛ ተጠሪ የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም. ያመከነበት አግባብ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን፣ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት ማን እንደሆነ ግራ ቀኙ አሉን የሚሏቸውን ማስረጃዎችን በመስማትና ተገቢነት አላቸው የሚሏቸውን ማስረጃዎችን ሁሉ በማስቀረብ ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ ተገቢውን ውሣኔ ይሠጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካቲት 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማዉ ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዋት ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፎዚያ ቃዲ - የቀረበ የለም

መዝገቡ የተቀጠረው፤- ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የፍ/ቤት ውሳኔ በተከራካሪ ወገኖች ከቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ክልል ወሰን ሊያልፍ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት በመስጠት በሚል የቀረበ ነው፡፡ የጉዳዩም መነሻ የአሁን አመልካች በሥር የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በግዥ ባገኘሁት የንግድ ድርጅት ላይ የአሁን ተጠሪ ሁከት የፈጠሩብኝ ስለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ መሥርቷል፡፡

ተጠሪም ባመለከተው ክርክር የተነሳበት ንብረት ሊገመት ስለሚቻል ተገምቶ ተገቢው የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎበት ሊቀርብ ሲገባ ይህንኑ ሥርዓት አሟልቶ የቀረበ አይደለም፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረበው ውል የብድር እንጂ የሽያጭ አይደለም፡፡ መፃፍ ስለማልችል በተንኮል የተዘጋጀ ካልሆነ በቀር በእኔ የተደረገ አይደለም ስለሆነም ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ በህግ ፊት በማይፀና ውል ንብረቱ በእጅ ገብቷል ማለት ስለማይቻል እና በህግ ማሟላት የሚገባውን ሂደት ባላሟላ ውል ደግሞ በሁከት ክስ ማስፈጸም አይቻልም፡፡ ስለሆነም ክሱ በፍ/ብ/ሥ./ሥ/ሕ/ቁ 33(2) መሰረት ውድቅ ነው የሚል ዳኝነት ሰጥቶበታል፡፡

በዚህም የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ይግባኝ ተጠይቆበት በበላይ ፍ/ቤቶች የሰበር ሰሚ ችሎቱን ጨምሮ በየደረጃው ተቀባይነትን አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ዳኝነት ላይ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚልበትን ዝርዝር ነጥቦች አመልካች በመጥቀስ የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ የተነሳ ሲሆን፤ ተጠሪም ከላይ በመግቢያው ላይ በተጠቀሰው ነጥብ ላይ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክራቸውን አጠናቀዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በከሳሽነት የተሰየመ ወገን አንድ ንብረት በአንድ ህጋዊ ተግባር ሳቢያ ወደ እጁ ገብቷል በይዞታ ላይ እያለ ሁከት ተፈጠረብኝ የሚል ክስ ትክክለኛውን የሁከት የህግ ፅንሰ ሀሳብ ተከትሎ ማቅረቡ ከተረጋገጠ፤ ለዚሁ ክስ በተከሳሽነት የተሰየመው ወገን ከተሰማ በኋላ በፍ/ቤቱ ሊሰጥ የሚገባው ዳኝነት ሁከት ተፈጥሯል ይወገድ፤ ወይም የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት የሚወሰን እንጂ በከሳሹ እጅ ሊገባ የቻለበትን ህጋዊ ተግባር ለመመርመር የሚያበቃ ወይም የሚያስችል ምክንያት አይኖርም፡፡ ከሳሹ የክሱን ምክንያት ዘርዝሮ ሊያገኝ የሚገባውን ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 224 ሲጠይቅ፤ ውሳኔው ይህንኑ የጠየቀውን ዳኝነት ማግኘት የሚቻል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለይቶ ማዘዝ ስለሚገባ የወረዳው ፍ/ቤት ሁከት የተፈጠረ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም ካለ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት መወሰን ሲገባው ከዚህ አልፎ በሌላ የክርክር መስመር ታይቶና ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ሁሉ አካቶ ያለ ቦታው የሽያጭ ውሉ ዋጋ ያለው ነው? ወይስ አይደለም? በሚለው ላይ ዳኝነት መስጠቱ ከተጠየቀው ዳኝነት ክልል የወጣ በመሆኑ ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካችም በክስ ማመልከቻው ዘርዝሮ ያቀረበው እና የጠየቀው ዳኝነት ተዳምሮ ሲታይ በሽያጭ ውል ምክንያት በእጁ የገባው የንግድ ድርጅት በተጠሪ ተወስዶበት ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 226 (3) እንደተመለከተው የተወሰደን እና ተለይቶ የታወቀን ንብረት ለማስመለስ የተፈለገ እንደሆነ የዚህኑ ንብረት ዋጋ ተገምቶ የሥረ-ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ተገቢውን በመክፈል ክሱን አቅርቦ በዚሁ የክስ መስመር ተገቢውን ክርክርና ንጥጥር ተደርጎ ተገቢውን ዳኝነት ማግኘት ሲገባ በሥር የወረዳው ፍ/ቤት ክስ የቀረበበት መንገድ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149 እንደተመለከተው በሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚገባው ጉዳይ በንብረት ላይ የተፈጠረን ሁከት ለማስቆም (cessation of intereference) ወይም ከሁከት መፍጠር ተግባሩ እንዲታገድ (injuction) ለመጠየቅ እንጂ የተወሰደን ንብረት እንደገና ወደ እጁ ለማስገባት የሚያስችል አይደለም፡፡

ከእነዚህ ሁለት ሐተታዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች በየደረጃው በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45352 በ26/4/03፤ ይግባኝ ሰሚው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10876 በ16/5/2003 ዓ.ም. እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 129205 በ11/08/2003 ዓ.ም የሰጡት ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን ንብረት በሽያጭ ውል ካገኘ በኋላ በተከሳሽ ድርጊት ከእጁ ወጥቶ ከተገኘ ወይም በተከሳሽ ቁጥጥር ሥር ይገኛል ካለ የህንኑ የሽያጭ ውል ያለውን መነሻ አድርጎ ንብረቱን መልሶ ወደ እጁ ለማስገባት እንደ ሥርዓቱ ዳኝነት የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው ብለናል፡፡ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ የሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ሳቢያ ለወጣው ማናቸውም ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 57186

መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ሶስና ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ከፈሉ ታረቀኝ - ቀረቡ
መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን መሠረት ያደረገን የባለሃብትነት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ክልለ ወስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 031 የሆነ ቤት በውርስ ከአባታቸው ያገኙትና የተላለፈላቸው መሆኑንና የአሁኑ ተጠሪ ይገባኛል በማለት የያዘባቸው መሆኑን ገልፀው ቤቱ የግል ቤታቸው መሆኑ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ ቤቱ የተጠሪ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ጠቅሶ ሲያቀርብ በፍሬ ነገር ደረጃ ክርክር ደግሞ አከራካሪው ቤት በአዋጅ የተወረሰና ለተጠሪ የባለቤትነት ደብተር የተሰጣቸው ከአሰራርና ከደንብ ውጪ በመሆኑ ደብተሩ ስልጣን ባለው አካል መመዘኑንና በተሰረዘ ደብተር ደግሞ ተጠሪ ሊያገኙ የሚችሉት መብት የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች በፍርድ ኃይል መብቱን ከአጣ በኋላ የአከራካሪው ቤት የተጠሪን ባለሃብትነት የሚያሳይ ማስረጃ በአስተዳደር አካሉ መክኗል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ ቤቱን አመልካች ለተጠሪ ለቆ ሊያስረክብ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በሕግ አግባብ ተወርሶ በአመልካች የሚተዳደር ከመሆኑም በላይ ተጠሪ የቤቱ ባለመብት የሚያደርጋቸው ማስረጃ በሌለበትና የነበረውም በተሰረዘበት ሁኔታ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክብ ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ወረቀት የተሰረዘ መሆኑ እየታወቀ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክብ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባለ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ተጠሪ በፅሑፍ በሰጡት መልስ አከራካሪው ቤት በውርስ ተላልፎላቸው በሕግ አግባብ የባለቤትነት ደብተር የተሰጣቸው ከመሆኑም በላይ አመልካች በፍርድ ሃይል መብቱን ያጣ መሆኑ ተረጋግጦ በተሰጠው ውሣኔ ደብተሩ ተሰርዟል በሚል ምክንያት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት የሚችልበት አግባብ የለም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲፀናላቸው ገልፀው ተከራክረዋል። የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን በፅሑፍ ሰጥቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ክሱን የመሰረቱት አመልካች ቤታቸውን ያላግባብ የያዘባቸው መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን አመልካች ደግሞ ቤቱን በሕግ አግባብ የያዘው መሆኑን ጠቅሶ የተከራከረ መሆኑን ፣ የስር ፍርድ ቤትም አከራካሪው ቤት ባለቤትነት የማን ነው? የሚለውን ጭብጥ ከያዘ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አከራካሪውን ቤት ተጠሪ በውርስ ከአባታቸው ያገኙት መሆኑን ፣ ይህን የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃም ያቀረቡ መሆኑን ፣ ተጠሪ ከሌላ ግለሰብ ጋር ባደረጉት ክርክርም ቤቱ የተጠሪ መሆኑን ተረጋግጦ ከመወሰኑም በላይ አመልካች ውሣኔው መብቴን ይነካል በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት አቤቱታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ሳይቀበለው የቀረ በመሆኑን ፣ ይህ ከሆነ በኋላ አመልካች ተጠሪ በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉትንና ሚያዚያ 01 ቀን 1994 ዓ.ም. ተሰጠኝ በማለት ያቀረቡት የካርታ ቁጥር 9/05531 መሰረዝ በሕግ አግባብ የተጠሪን ባለሃብትነት ቀሪ የሚያደርግ አይደለም በማለት ውሣኔ መስጠቱን ነው። አመልካች ቤቱ በሕግ አግባብ የተወረሰ ስለመሆኑ ገልፆ በዚህ ረገድም ማስረጃ ያለው መሆኑን ጠቅሶ መከራከሩንም ከውሣኔው ይዘት ተገንዝበናል።

እንግዲህ ክርክሩ በይዘቱ አመልካች ቤቱን ያላግባብ ይዟል የሚለውን የተጠሪን ክስ መሠረት ያደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀድመው ከሌላ ግለሰብ ጋር በአደረጉት ክርክር አመልካችም ቀርቦ ክርክር ተደርጎበት ክርክሩ ተቀባይነት አጥቶ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ነኝ በማለት የአፈጻጸም ክስ ያላቀረቡ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቱም አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 99213 በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት አቤቱታውን አቅርቦ ተቀባይነት አጥቷል በማለት በፍርድ ሐተታው ላይ ያሰፈረው አገላለፅ የአመልካችና የተጠሪ ማስረጃዎች ተሰምተው ክርክሩ ተደርጎ ፍርዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 360 መሠረት የማይለወጥ ነው ተብሎ የፀና መሆኑን የሚያሳይ አለመሆኑን የማያስገነዝበን ሁኖ አግኝተናል። ተጠሪ ራሳቸው ክስ ሲመሰርቱ በአመልካች ላይ በአዲስ መልክ ቀጥታ ክስ ማቅረባቸውም በአመልካች ላይ ቀድሞ ያረፈ ፍርድ መኖር ያለመኖር ላይ ጥያቄን የሚያስነሳ መሆኑ ግልፅ ነው። እንዲህ ከሆነ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት አቤቱታ አቅርቦ ተቀባይነት ማጣቱን ሳይሆን ይኸው አቤቱታ ተቀባይነት ያጣበት ስርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት የሚቀርበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 359 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የተስተናገደ መሆን ያለመሆኑን፣ ተጠሪ ከሌላ ግለሰብ ጋር አደረጉ የተባለው ክርክርና የተሰጠው ውሣኔ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ሲያቀርብ የተለወጠ መሆን ያለመሆኑን የሚገልፅ መሆኑን ያለመሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባ ነበር ። ይኸው ግልጽ አለመሆኑ በእርግጥም አመልካችም በሕግ አግባብ በተካሄደው ክርክር ተሸናፊ ከሆነ በሁዋላ በስራው ባገኘው ሥልጣን በመጠቀም ካርታውን ማምከኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳይታይ የሚያደረግ ሁኖ ነው፡፡ ቀድሞ የተወሰነ ውሣኔ ካለም ተጠሪ በአዲስ መልክ ክስ የአቀረበቡት ምክንያትም ሊጣራ የሚገባው እና ሥነ ሥርዓታዊ መሆኑ ምላሽ የሚያስፈልገው ነበር፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያስፈረዱት ፍርድ የሌለ መሆኑን አምነው አዲስ ክስ ከአቀረቡ ደግሞ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው የቤቱ ባለቤት ማን ነው የሚለው ነጥብ ሁኖ የግራ ቀኙ ማስረጃዎች መሰማትና ተገቢ ሆኖ ከተገኘም ፍርድ ቤቱ በራሱ መነሻነት ፍሬ ነገሩን በማጣራት ትክክለኛውን ፍርድ መስጠት ነው፡፡ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የአስተዳደር አካሉ የሚሰጠው የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በስሙ ማረጋገጫው የተሠጠው ሰው የምስክር ወረቀቱ ለተጠቀሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195/1/ ድንጋጌ ከሰፈረው ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ሕጋዊ ግምቱ ሊስተባበል የሚችል መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ጋር ተዳምሮ ሲነበብ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ በአስተዳደር አካሉ የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ደምዳሚ ማስረጃ (conclusive evidence) ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ስር የተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች አለ የሚል ወገን በማናቸውም ማስረጃ ሊያስተባብለው የሚችለው ማስረጃ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የአስተዳደር አካሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 መሠረት የሰጠውን የባለሃብትነት ማረጋገጫ ደብተርን በሌላ ጊዜ ከሰረዘው ይኸው ተግባሩ በፍርድ ቤት ሊስተናገድ የሚችል አይደለም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/1/2/ እና 37 ድንጋጌዎች አንፃር ተዳምሮ ሲታይ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ አስተዳደር አካል ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖረው አንዴ የሰጠውን የባለቤትነት ደብተር ከሰረዘ ይኸው አካሄድ ሕጋዊ አይደለም የሚለው ሰው በፍርድ ቤት መብቱን ለማስከበር ክስ ሊያቀርብ የሚገባና ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ እና የንብረት ባለቤትነት መብትን ከሚጠብቁ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ውሣኔ የሚሰጥበት ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በአዲስ መልክ በቀረበው በተጠሪ ክስ ላይ ተጠሪ አለኝ የሚሉትን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር መሰረዙን ገልፆ የተከራከረ ሲሆን ክሱ በአዲስ መልክ የቀረበ እንደመሆኑ መጠን አመልካች ተጠሪ አለኝ የሚሉትን ካርታ የሰረዘው በሕጉ አግባብ በተዘረጋው ስርአትና አሰራር ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ በግራ ቀኙ ማስረጃ እና ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ተጣርቶ ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ፣ 1196 እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው የንብረት መብት ሕጎች ጋር ተዛምዶ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ሁኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ አዲስ ክስ ያቀረቡ መሆኑን ወደ ጎን በመተው ወይም ቀድሞ ተጠሪ ከሌላ ግለሰብ ጋር ሲያደርጉ በነበሩት ክርክር በአመልካች ላይ የተሰጠው ውሣኔ አመልካች የቤቱ ባለሃብት አይደለም የሚል መሆን ያለመሆኑን በግልጽ ሳያረጋግጥ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ያስረክብ ተብሎ መወሰኑ የክርክሩ አካሄድ በተሟላ ሁኔታ ተከናውኖና ተጣርቶ ያለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አንድ ክርክር በተሟላ የሥነ ሥርዓት አካሄድ ካልተመራ ደግሞ በውጤቱ የተከራካሪ ወገኖችን መሰረታዊ መብት የመጎዳት አጋጣሚ የሰፋ እንዲሆን የሚያደረግ መሆኑ የሚታመን ስለሆነ ተቀባይነት የሌለውና መሠረታዊ የሆነ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባውና በፍሬ ነገር ደረጃ በተገቢው መንገድ ያልተጣሩ ነጥቦች ተጣርተው ጉዳዩ እንደገና በስር ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን ማድረጉ ተገቢ ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77189 የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 91229 ሰኔ 01 ቀን 2002 ዓ.ም. በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 77189 እንዲቀጥል በማድረግ በቤቱ ላይ አመልካችን ባለመብት እንዳይሆን በሕጉ አግባብ ተመርቶ የተሰጠ ውሣኔ መኖር ያለመኖሩን ፣ የቤቱ ሕጋዊ ባለሃብት ማን እንደሆነ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን በመስማትና ተገቢውን ማጣራት ሁሉ በማድረግ ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ ቁ. 65140

መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- ወ/ሮ በላይነሽ ቢያድግልኝ ቀረበች፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስቱር ገበሬ አልቀረበችም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በኮንዶሚኒየም ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ በመጠየቅ በቀረበው ክስ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው አመልካች ስትሆን፣ ከተጠሪ ጋር ያደረገችው የቤት ሽያጭ ውል የኮንደሚኒየም ቤት ለተወሰኑ ዓመታት በሽያጭ እንዳይተላለፍ የሚከለክለውን ሕግ በመቃረን የተደረገ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት እንዲፈርስላት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡ ተጠሪ በበኩልዋ ለክሱ በሰጠችው መልስ ውሉ የሚፈርስበት የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ምክንያት እንደሌለ በመግለጽ ተከራክራለች፡፡ ከዚህ ሌላ ፍ/ቤቱ የሁለቱን ወገኖች ክርክር በመመርመር ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳይ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች በ22-11-2003 ዓ.ም. በዛፈችው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታ አቅርባለች፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው የቤቱ ሽያጭ ውሉ አይፈርስም የተባለው በሕጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጭብጥ ግራ ቀኝ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርመረናል፡፡

አመልካች ውሉ መፍረስ አለበት ለሚለው ክርክር መሠረት ያደረገችው ዋነኛው ነጥብ የሕግ ክልከላ ነው፡፡ በእርግጥ ውሉ የተደረገው በስህተት እና በድንገተኛ ተንኮል ነው የሚል መከራከሪያም እንዳለት ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ሕጉ በኮንዶሚኒየም (በጋራ ህንፃ) ላይ ቤት በእጣ የደረሰው ሰው እጣው ከደረሰው ቀን ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ባለው ጊዜ ቤቱን መሸጥ አይችልም የሚል እንደሆነ በመግለጽ ስለመከራከርዋም ተገንዝበናል፡፡ የፌዴራል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ያልተቀበለው መሸጥ የሚከለክል በሕግ ደረጃ የወጣ አዋጅ የለም፤ የሚከለክል ደንብ ወይም መመሪያ አለ ቢባል እንኳን ከሣሽ (አመልካች) ቤቱን ለተከሣሽ (ተጠሪ) በሽያጭ ለማስተላለፍ ስምምነትም በሰጠችበት ወቅት የዚህ ግንዛቤ እንደነበራት ግልጽ ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት እንደሆነ ውሣኔው ያመለክታል፡፡ አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የምትለው በዚህ መልክ የተሰጠውን ውሣኔ ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩልዋ ለሰበር አቤቱታው በሰጠችው መልስ አመልካች የጠቀሰቻቸው አዋጅም ሆነ ደንብ ቤቱን እንዳይሸጥ በግልጽ አይከለክሉም፡፡ አመልካች ቤቱን የሸጠችልኝ ወዳና ፈቅዳ በመሆኑ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክራለች፡፡

ከቀረበልን ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው በኮንዶሚኒየም (የጋራ ቤት ህንፃ) የተያዘ ቤት እንዳይሸጥ ለተወሰኑ ዓመታት ክልከላ ያደርጋል ተብሎ የተጠቀሰው “የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፖብሊክ የጋራ ህንፃ ቤት ባለቤትነት አዋጅ ቁጥር 370/1995” ነው፡፡ ይህ አዋጅ በእርግጥ በጋራ ህንፃ ቤት በእጣ የደረሰው ቤቱ ለሌላ ሰው ስለሚሸጥበት ሁኔታ በሚመለከት በግለጽ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም፡፡ በሌላ በኩል ግን የከተማው አስተዳደሮች አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ለማውጣት እንደሚችሉ በአንቀጽ 42 ግልጽ የሆነ ድንጋጌ ማስቀመጡን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በ1952 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1281 እስከ ቁጥር 1360 ያሉት ድንጋጌዎች በአዋጅ መሠረት በሚስተዳደር የጋራ ህንፃ ላይ ተፈፀሚ እንደማይሆኑ እንደዚሁም ማንኛውም ሕግ፣ ልማድ ወይም አሠራር በአዋጅ የተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው በአንቀጽ 43 ስለመደንገጉም ተመልክተናል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የሚገኝበት የጋራ ህንፃ (ኮንዶሚኒየም) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚተዳደሩት አንዱ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው አዋጅ ቁ. 370/95 ተፈጽሚ የሚሆነው በአዲስ አበባ እና በድሮው ከተማ አስተዳደሮች ላይ እንደሆነ በአዋጅ አንቀጽ 3 የተደነገገ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤትም በአዋጁ በተሰጠው አዋጁን ለማሰፈጽም የሚረዳ ደንብ የማውጣት ስልጣን መሠረት አዋጅ ቁ. 19/97 አውጥቷል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14(2) እንደተመለከተውም በኮንዶሚኒየም ቤት ያገኘ (በእጣ የተሰጠው) ሰው የቤቱን ጠቅላላ ዋጋ ከፍሎ ቢያጠናቅቅ እንኳ ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ የሚችለው ቤቱን ከገዛ (በእጣ ካገኘ) በኃላ አምስት ዓመት ሲሞላው ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን የተለመደ አሠራር ወይም ሕግ በአዋጁ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈፀሚነት እንደሌለውም በአንቀጽ 21 ተመልክቷል፡፡

እንደሚታየው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በወጣው አዋጅ የተቀመጠው የያዘነውን ክርክር የሚመለከተው ድንጋጌ ማለት ነው በኮንዶሚኒየም ቤት ያገኘ ሰው ቤቱን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ የሚችልበት አግባብ በሕግ ገደብ ተጥሎበታል፡፡ በእርግጥ ገደቡ በጊዜ (በዓመታት) የተወሰነ በመሆኑ ጊዜአዊ ቢሆንም፤ ጊዜው ከመድረሱ በፊት የሚደረገው ሽያጭ ግን ሕግን የጣሰ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለውሉ አመሠራረት በተመለከተ የተደነገገው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1678 አንድ ውል የሚፀና ውል ነው ሊባል የሚችለው በቂ ሲሆን እርግጠኛነት ባለው በሚቻልና ሕጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ መደረግ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው አከራካሪ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ሃይለ ቃል ውሉ ሕጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ መደረግ እንዳለበት የሚገልጽ ነው፡፡ ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከሕግ ውጪ የሆነ ነው በተባለ ጊዜም ውሉ ይፍርስ ዘንድ ለመጠየቅ እንደሚቻል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1808(2) ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሆነውም ይኸው ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የውል ይውረስልኝ ክርክር ውድቅ ለማድረግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠው ምክንያት ከዚህ አንፃር ሲታይ ሕጉን በአግባቡ ያለገናዘብ እንደሆነ ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል በሕጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከማብቃቱ በፊት የተደረገ ስለመሆኑ ባለከራከረበት ሁኔታ አይፈርስም ተብሎ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 31385 ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 110331 ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ (የኮንዶሚኒየም ቤት) ውል በሕግ ክልከላ የተደረገበት ስለሆነ ፈራሽ ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 67011

መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካች፡- የወ/ሮ ጣይቱ ከበደ ወራሾች

1. ወ/ሪት ሕሊና ፍቃዱ
2. መቅደስ ፍቃዱ

} ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ጥሩነሽ ኃየሌ

2. አቶ ቴዎድሮስ መኮንን

} በ2ኛ ተጠሪ ተወካይነት ቀረቡ

3. በአራዳ ክ/ከተማ የቀበሌ 03/09 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነገረፈጅ ናዝሬቱ ፈለቀ

ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባለሀብትነት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካቾች ከሳሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ የወላጅ እናታችን የወ/ሮ ጣይቱ ከበደ በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 03/09 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 615 የሆነ ከወላጅ አያቴ ከአቶ ወንድተገኝ በላይነህ በውርስ የተላለፈላትን የተፈቀደ ቤት ከሳሾች የእናታችን የወ/ሮ ጣይቱ ከበደ ወራሾች መሆናችንን በፍርድ ቤት አረጋግጠናል፤ ቀደም ሲል የከሳሾች ወላጅ እናት በፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ መስርተው ቤቱን እንዲለቁ የተወሰነባቸው ሲሆን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ቅሬታ አቅርበው በመዝ.ቁ.11399 በቀን 04-6-96 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የስር ከሳሽ ደብተር ወይም ካርታ አውጥተው ቤቱን ለማስለቀቅ ይችላሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ አውራሻችን ወ/ሮ ጣይቱ ከበደ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ በካርታ ቁ. አ03/09/0673 መስከረም 12 ቀን 1998 ዓ/ም የተሰጣቸው ሲሆን የቤትና ቦታ ግብር ከፍለዋል፡፡ ነገር ግን የከሳሾች አውራሽ በቤቱ ላይ ግብር እየከፈለች መሆኑን እያወቁ 3ኛ ተከሳሽ በህገ-ወጥ አሰራር ቤቱን በማከራየት የሚጠቀም ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የቤቱ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ከተሰጠበት መስከረም 12 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ ቤቱን እንዲለቁ ቢጠየቁም ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ቤቱን እንዲያስረክቡ እንደዚሁም የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉ የሚል ነው፡፡ ተከሳሾች በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንዲሰጡበት ታዞ መልስ የሰጡ ሲሆን 3ኛ ተከሳሽ የሰጠው መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤትን የመንግስት ባደረገው አዋጅ ቁ. 47/67 የተወረሰ ቤት በመሆኑ ከሳሾች በዚህ ቤት ላይ መብት የላቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ከሳሾች ለክሳቸው መሰረት ያደረጉት በዚህ ቤት ላይ በ1998 ዓ.ም. የተሰጣቸውን የባለሀብትነት ማረጋገጫ ሲሆን ቀድሞ በዚሁ መልክ ተሰጥቶ የነበረው ካርታ መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. የተሰረዘ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበውን ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩም ያስቀርባል በመባሉ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሁፍ ሰምቷል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል አከራካሪ በሆነው ቤት ላይ የቀረበው የአመልካች የባለሃብትነት ጥያቄ ተሰጥቶ የነበረው የባለሃብትነት ማረጋገጫ ተሰርዟል በማለት ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ ከዚሁ ቀደም ሲል ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካቾች ያቀረቡትን ክስ ውድቅ ያደረጉት በአንድ በኩል የባለሀብትነት ማረጋገጫ ካርታ በሚመለከተው የአስተዳደር ባለስልጣን የተሰጠው ሰው የንብረቱ ባለሀብት ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ እና በዚሁም መሰረት የአመልካቾች አውራሽ በ1998 ዓ/ም ካርታ በስማቸው በዚሁ አከራካሪ ቤት ላይ የተሰጣቸው በመሆኑ የዚሁ ቤት ባለሃብት ተደርገው የሚወሰዱ ስለመሆኑ በማመላከት በሌላ በኩል ደግሞ በ1998 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው ይሄው ካርታ የሚመለከተው መስተዳደር አካል ግራ ቀኙ በክርክር ላይ ባሉበት ወቅት መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰረዘ በመሆኑ ባለሃብትነታቸውን የሚያረጋግጠው ካርታ በመሰረዙ ምክንያት መብት የላቸውም በማለት ውሳኔ የሰጠ ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የተነሳውን ክርክር ስንመለከት በእርግጥ አንድ የሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠው የባለሃብትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይዜንን የምስክር ወረቀት ለያዘ ሰው ባለሃብት ስለመሆኑ ግምት የሚያሰጠው ስለመሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1195/1/ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው አግባብነት በሌለው መልኩ በሆነ ጊዜ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል የሚቻል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1196 ስር የተደነገገ በመሆኑ እና ስራውን በአግባቡ ያልተወጣ የሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ኃላፊነት ሊያስከትልበት የሚችል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1198 ስር ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ሁሉ አጠቃላይ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው አንድ ለማይንቀሳቀስ ንብረት የተሰጠ የባለሃብትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለሃብትነትን በተመለከተ የህግ ግምት የሚያሰጥ ቢሆንም በሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል፣ በተቃራኒው ከሚቀርቡት ማስረጃዎች ጋር ሊመዘን የሚችል እንጅ ማስተባበያ ሊቀርብበት የማይችል ወሳኝ /conclusive evidence/ ያለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ አንድ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ ተገቢውን ስርዓት እና ደንብ መከተል እንዳለበት ሁሉ የተሰጠን የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲሰረዝ አግባብነት ያላቸውን ስርዓቶችን መከተል ያለበት ስለመሆኑ እና የዚህ አፈፃፀም ሂደትም በአግባቡ ስለመፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል ስለመሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁ. 1195 እስከ 1198 ድረስ ካሉት ድንጋጌዎች ዓላማ፣ ይዘት እና መንፈስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ በክርክር ላይ ባሉበት ወቅት ለአመልካቾች አውራሽ ተሰጥቶ የነበረው የባለሃብትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ተሰርዟል በመባሉ ብቻ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች ማድረግ ያለባቸው የቀረበው ክስ የባለሃብትነት ክርክር እስከሆነ ድረስ በግራ ቀኙ የሚቀርቡትን ማስረጃዎች በመመዘን እና የካርታውን መምከን በተመለከተም የእርምጃው አግባብነት ባጠቃላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር ተመዝኖ የሚታይ ሆኖ እያለ በንብረቱ ላይ ተሰጥቶ የነበረው ካርታ በመምከኑ ብቻ ክሱን ውድቅ ማድረግ ከላይ የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች ዓላማ እና ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት አከራካሪው ቤት የአውራሻቸው አያት የአቶ ወንድተገኝ በላይነህ የምርጫ ቤት እንጂ በመንግስት የተወረሰ ቤት አይደለም በማለት ሲሆን 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የተወረሰ ቤት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይም የበታች ፍ/ቤቶች አከራካሪው ቤት የተወረሰ ስለመሆኑ ወይም የተወረሰ ስላለመሆኑ ጭብጥ በመያዝ ያጣሩት ነጥብ የሌለ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሚያከራክረው ቤት የተወረሰ ስለመሆን ወይም አለመሆን ክርክር በተነሳ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ የሚቀርቡትን ማስረጃ በመመልከት የተወረሰ ነው ወይም ያልተወረሰ ቤት ነው በማለት ውሳኔ ሊሰጡበት የሚችሉ ስለመሆኑ ከዚህ በፊት ይሄ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.24627 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ ፍ/ቤቶች በተመሳሳይ በዚህም ጉዳይ መወሰን የሚችሉ ስለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡

በአጠቃላይ የበታች ፍ/ቤቶች ከላይ እንደተመለከተው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ጭብጦች በመያዝ እና በግራ ቀኙ ማስረጃ ሳያጣሩ ውሳኔ መስጠታቸው በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.246 እስከ 248 ድረስ ያሉትን የጭብጥ አመሰራረት እና ክስ ማጣራትን በተመለከተ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው ብለናል፡፡

በአጠቃላይ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የደረሱት ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ እና በማጣራት ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.95545 በቀን 17-5-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.76167 በቀን 11-8-2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪውን ቤት በተመለከተ በፍርድ ሐተታው በተመለከተው መሰረት ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ እና በግራ ቀኙ ማስረጃ በማጣራት ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡

3.በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚያዝያ 24 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የአቶ አሰፋ አባዲዮ ባለቤት እና ወራሾች - አልቀረቡም

ወራሾች፡- 1. ወ/ሮ ፅጌ ሽኔ
2. አቶ ዋሚ አሰፋ
3. አቶ እስጢፋኖስ አሰፋ
4. ወ/ሮ ሚሚ አሰፋ
5. ወ/ሮ ፋሲካ አሰፋ
6. አቶ ሱራፌል አሰፋ
7. ወ/ሮ ጫልቱ አሰፋ

} አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ አቶ ጌታቸው ምንተስኖት

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ከአዋጅ ውጭ የተወሰደ ንብረት ነው በሚል ንብረት ያስመለሰ ወገን፤ የንብረቱ አመላለስ አግባብነት የሌለው ሆኖ መገኘቱ ከተረጋገጠና ንብረቱ ወደ ባለቤቱ ወደ መንግስት እንዲመለስ ከተደረገ ንብረቱ ያለአግባብ በዕጁ በቆየበት ጊዜ ንብረቱ ያስገኝ የነበረውን ገቢ ወይም የታጣ ገቢ ጭምር የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለውን ነጥብ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካቾች መጋዘን ከአዋጅ ውጭ ተወርሶብናል በማለት በ1992 ዓ.ም አቤቱታ በማቅረባቸው ይህንኑ ንብረት ሰኔ 29 ቀን 1997 ዓ.ም ተረክበዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ንብረት ያለአግባብ ወደ አሁን አመልካቾች እጅ ሊገባ የቻለ መሆኑ ተጣርቶ እንደገና ወደ መንግስት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ይህ መጋዘን ተገቢ ባልሆነ መንገድ በማስወሰናቸው የተነሳ ንብረቱ ሊያስገኝ ይችል የነበረውን ጥቅም በማስላት በጠቅላላው ብር 687,742.00 /ስድስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ሁለት/ ብር ይክፈሉ በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ክስ መስርቷል፡፡

የአሁን አመልካቾችም በተከሳሽነት ንብረቱን ስልጣን ባለው አካል አስወስነን የተረከብነው በመሆኑ የታጣ ጥቅም የመክፈል ኃላፊነት የለብንም፤ይመለስ በመባሉ ለታጣ ጉዳት ኃላፊ ልንሆን አይገባም፤ ለጉዳዩ አግባብነት ባለው አዋጅ አዋጅ ቁጥር 572/2000 መሰረት እንደ ከሳሽ አቀራረብ ከሆነ የታጣ ጥቅም ለመጠየቅ መብት አይሰጠውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር የተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የአሁን አመልካቾች አውራሽ ባቀረቡት ጥያቄ መነሻ ንብረቱ ተመልሶላቸዋል፣ በ1997 ዓ.ም ተረክበዋል፡፡ በተጭበረበረ ማስረጃ መሰረት የተወሰዱ ቤቶች በድጋሚ ወደ መንግስት እንዲመለሱ ለማድረግ በወጣው ህግ አዋጅ ቁጥር 572/2000 መሰረት ጉዳዩ ታይቶ ይኸው ንብረት እንደገና ወደ መንግስት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ በወንጀል ጉዳይ ተከሰን አልተቀጣንም ቢሉም ቦርዱ ለታጣ ጥቅም ሊጠየቁ የሚችሉ መሆኑን ገልፆ ወስኗል፡፡ በወንጀል ጉዳይም አለመጠየቅ የፍ/ብሔር ኃላፊነትን አያስቀርም የሚለውን ትንተና መሰረት አድርጎ ንብረቱን ያለአግባብ እንዲመለስ በማድረጋቸው ሳቢያ መንግስት ያጣውን ጥቅም የመተካት፤ የመካስ ኃላፊነት አለባቸው በማለት ከወሰነ በኋላ የታጣውን ጥቅም በሚመለከት ብር 92,786 መሆኑን ለይቶ ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታ በማቅረባቸው ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አፅድቆታል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበውም በዚህ አኳኋን የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለትና ምክንያቱን በመጥቀስ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ሲሆን፤ በወንጀሉ ጉዳይ ተከሰው ጥፋተኛ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ለታጣ ጥቅም ኃላፊ መባላቸው አግባብ ነው አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለመለየት ሲባል ተጠሪ ቀርቦ በዚህ ነጥብ ላይ ክርክሩን በፅሑፍ አቅርቧል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ሁለቱም ወገኖች ያቀረቡት የፅሁፍ ክርክር በይዘቱ በሥር ፍ/ቤት ካቀረቡት የተለየ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ጉዳይ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን፤ ይህንኑ ክርክር ከስር ፍ/ቤቶች ዳኝነትና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት ከአዋጅ ውጭ እንደተወረሰ በማስመሰል ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ጉዳዩ ታይቶ ንብረቱ ወደ አመልካቾች መመለሱንና በኋላ ግን በዚህ አኳኋን ያለአግባብ የተመለሱ የመንግስት ንብረቶችን እንደገና ለማስመለስ ሲባል በወጣው አዋጅ ቁጥር 572/2000 መሰረት የአመልካቾች ጉዳይ እንደገና ተመርምሮ ንብረቱን ወደ መንግስት እጅ እንዲመልሱ መደረጉን በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ረገድ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

አከራካሪ ሆኖ የተገኘውና በሰበር ችሎት ጉዳዩ ቀርቦ እንዲተረጎም የተደረገበት ዋናው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 572/2000 አንቀጽ 6 እንደተመለከተው ያለአግባብ ንብረት ያስመለሱ ሰዎች ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወንጀል ክስ ሊመሰረትባቸው እንደሚችል እና ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኙም ከወንጀሉ ቅጣት በተጨማሪ መንግስት ያገኝ የነበረውን ጥቅም በማጣቱ የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል በሚል መደንገጉ ለጉዳት ካሣ ጥያቄ በወንጀሉ ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና መቀጣት ቅድመ ሁኔታ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ይህንኑ አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ለመወሰን በቅድሚያ ለጉዳይ በተለይ አግባብነት ባለው አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እርስ በእርሳቸው በማቆራኘት፤ ዐውደ ንባቡን መሰረት በማድረግ ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አለአግባብ የተመለሱ የመንግስት ንብረቶችን ለማስመለስ የሚቻለው ቀደም ሲል ንብረቱ በቂ ባልሆኑ ወይም ሐሰተኛ በሆኑ ማስረጃዎች ለአመልካቾች እንዲመለሱ ተደርጎ የተገኘ እንደሆነ ስለመሆኑ በአዋጁ መግቢያ ሁለተኛ አንቀጽ እና ንብረቶችን ለማስመለስ ኃላፊነት የወሰደውን አካል አዳዲስ ሥልጣንና ተግባር በሚዘረዝረው አንቀጽ 4 ንዑስ ቁጥር 6 ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም የማስመለሻ ምክንያቶች አንድም በቂ ባልሆነ ምክንያት ወይም ደግሞ በሐሰተኛ ማስረጃ የተነሳ ተረክበውት የተገኙ እስከሆነ ድረስ ያለአግባብ ንብረት ያስመለሱ ሰዎች ሁሉ የወንጀል ክስ ይቀርብባቸዋል ማለት አይቻልም፡፡

ይሁን እንጂ የመንግስት ንብረት ወደ ግለሰቦች እጅ ሊገባ የቻለው በቂ ባልሆነ ምክንያትም ሆነ ወይም በሐሰተኛ ማስረጃ መሰረት ያለአግባብ እንዲመለስ የተደረገ የንግድ ድርጅት የተዘጋ ወይም ሊነጣጠል በማይችል ሁኔታ ከሌላ ንብረት ጋር የተቀላቀለ ከሆነ በርክክቡ ወቅት የነበረውን ንብረት ግምት ከእነ ወለዱ ለመንግስት እንዲከፈል ይደረጋል በሚል፤ የሚከፈለውም ወለድ የሚታሰበው ድርጅቱ ያለአግባብ ከተመለሰበት ቀን ጀምሮና በባንክ የማበደሪያ ወለድ ተመን መሰረት ይሆናል በማለት በአንቀጽ 5(2)(ለ) እና 5(3) ከተደነገገው መረዳት የሚቻለው በወንጀል ሊያስጠይቅ በማይችል በቂ ባልሆነ ምክንያት ንብረቱ የተመለሰ መሆኑ ቢታወቅም እንኳ ንብረቱን ከመመለስ ጋር ወለድ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ወለድ ደግሞ የታጣ ጥቅም ወይም የጉዳት ካሣ ለማስከፈል ሲባል እንደማካካሻ በህጉ የተቀመጠ አንዱ መንገድ ስለመሆኑ ስለ ውልና ከውል ውጪ ስለሚደርስ ኃላፊነት በህግ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንፃር በአዋጁ አንቀጽ 6 በወንጀሉ ጥፋተኛ ሆነው ከተጣለባቸው ቅጣት በተጨማሪ መንግስት ያገኝ የነበረውን ጥቅም በማጣቱ የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል በሚል የተደነገገው በፍ/ብሔሩ ጉዳይ የታጣ ጥቅምን ለመጠየቅ በወንጀሉ ጉዳይ አስቀድሞ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና መቀጣት ቋሚ ማሟያ መስፈርት ነው ከሚል መደምደሚያ ሊያደርስ አይችልም፡፡

ይልቁንም በዚሁ አንቀጽ 6 በወንጀሉ ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ ከመገኘትና ከመቀጣት ባሻገር የጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ የሚደረጉት ንብረቱን ተረክበው በእጃቸው አድርገው የተገለገሉበት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ በንብረቱ ሳይገለገሉ፤ ነገር ግን ንብረቱ ያለአግባብ እንዲመለስ በማስደረጉ ረገድ ተባባሪ ሆኖ የተገኘን ማናቸውም ሰው ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ በድንጋጌው ስር በወንጀሉ ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና የቅጣት መጣል ያለአግባብ በሐሰተኛ ማስረጃ ንብረት የማስመለስ ተግባር ሊያስከትል የሚችለውን የጎላ ኃላፊነት ለማመልከት እንጂ ምንጊዜም እና በማናቸውም ምክንያት የጉዳት ካሳ ክስ ለማቅረብ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና ቅጣት እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊወሰድ የሚገባ መሆኑን ሊያሳይ የሚችል ነው ከሚል መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ሁሉ ምክንያት በአዋጁ አንቀጽ 6 የወንጀል ኃላፊነትን በሚመለከት የተጠቀሰው አንድን ንብረት አንድ ሰው ያለአግባብ ወስዶ በተገኘ ጊዜ ንብረቱ በእጁ በነበረበት ጊዜ ያለአግባብ በበለፀገበት መጠን ከመካስ ጋር ንብረቱን የመመለስ ግዴታ አለበት በሚል በአጠቃላይ በፍ/ብሔር ህጉ የተመለከተውን ኃላፊነት የተካ ልዩ የሆነ አዋጅ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 572/2000 አንቀጽ 6 የተመለከተውን የወንጀል ኃላፊነት ለፍትሐብሔሩ ኃላፊነት ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ አድርገው በመተርጎም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፑብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/80 አንቀጽ 10 መሰረት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንድን የመጨረሻ ፍርድ ሊያርም የሚችለው በፍርዱ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ከተገኘ ብቻ መሆኑን መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 60439 የካቲት 15 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት አፅንተናል፡፡
2. አመልካች በሰበር ደረጃ ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡ በዚህ የሰበር ክርክር ሳቢያ ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ በየግላቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 69160

ሚያዚያ 24 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዶፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሶራሳ ጋሪ ከጠበቃ አቶ መልካም አለማየሁ ጋር ቀረቡ
ተጠሪ፡- አቶ አብርሃም ፍቃዱ - ቀረቡ
መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው አመልካች ለተጠሪ የሰጠሁትን ገንዘብ ብር 280,000.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር) ይመልስልኝ በማለት ያቀረበው የክስ አቤቱታ እና የጠየቀው ዳኝነት የገንዘብ አደራን መነሻ ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመለየትና ጉዳዩን ከማስረጃ አቀባበል ስርዓት አንፃር ተመልክቶ ተገቢውን የህግ ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡ የጉዳዩም አመጣጥ ባጭሩ የአሁኑን አመልካች መኪና ለመግዛት ወስኜ እያለ በመካከሉ ወደ ቻይና ሀገር ለመሄድ በማቀዴ የመኪናውን ዋጋ ተጠሪ እንዲከፍሉልኝ ብር 280,000.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር) በአደራ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ብሩን እንዲከፍሉኝ ብጠይቅ ዛሬ ነገ እያሉ ፍቃደኛ ስላልሆኑ ይመልሱልኝ በማለት በአሁን ተጠሪ ላይ ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪም በሰጡት መልስ የሥጋ ዝምድና፣ የሥራ ሽርክና ወይም የውክልና ግንኙነት ሳይኖረን ይህንን ብር ሰጠሁ የሚሉት ሐሰት ነው፡፡ አልሰጡኝም፡፡ በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ከዋናው የክርክር ደረጃ ከመድረሱ በፊት ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የግራ ቀኙ የፅሑፍ ክርክር ላይ በመመርኮዝ ከሳሽ የአሁን አመልካች ገንዘቡን በአደራ ሰጠሁ የሚለው ገንዘብ ተቀባዩ እንዲገለገልበት ፈቅዶ ከሆነ የግራ ቀኙ ክርክር በፍ/ብ/ህ/ቁ 2782(1) እንደተደነገገው የብድር ውልን በሚመለከቱት ደንቦች መሠረት ሊገዛ ወይም ሊወሰን የሚገባው ነው፡፡ ስለዚህ ከሳሽ የአሁኑ አመልካች ገንዘቡን ለተከሳሽ ለአሁን ተጠሪ የሰጠሁት የመኪና ግዥ ዋጋ እንዲከፍሉልኝ ነው በሚል ምክንያት ሰጠሁ ካሉ ገንዘቡ ሳይታሸግና ሳይዘጋበት መሰጠቱን ያሳያል ገንዘብ ሳይታሸግና ሳይዘጋበት ተሰጥቶ ከሆነ ደግሞ ገንዘብ ተቀባዩ እንዲገለገልበት ተፈልጎ እንደተሰጠ ስለሚቆጠር ይህ የግራ ቀኙ ጉዳይ ስለ ገንዘብ ብድር በሚመለከቱት ደንቦች መሠረት ሊጣራ የሚገባው ነው፡፡ ከእነዚህም ደንቦች መካከል በፍ/ብ/ህ/ቁ 2472 እንደተመለከተው ከብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) በላይ የተሰጠን የብድር ገንዘብ ለማስረዳት መቅረብ የሚገባው የማስረጃ አይነት የጽሑፍ እንጂ የሰው ምስክርነት ቃል አይደለም፡፡ ከሳሽ ክሱን ለማስረዳት የቆጠረው የሰው ማስረጃ ስለሆነ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም ስለዚህ ክሱ ወድቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሠረት ተቀባይነት የለውም በሚል በመዘጋቱ ምክንያት ይህ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ ችሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሰበር ቅሬታው ላይ የአሁን አመልካች ያቀረቡት እና በሰበር ፍ/ቤቶች ዳኝነት ያላረፈበት አንዱ የክርክር ነጥብ ለዚሁ የፍታብሔር ብይን መነሻ በሆነው ገንዘብ ምክንያት በተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ ቀርቦ ጉዳዩ ሲታይ ከቆየ በኋላ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ተጥሎበታል። ይህንን ማስረጃ በክሱ ሂደት ለስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በማስረጃነት ባቀርበውም ፍ/ቤት አልተመለከተልኝም የሚለው ነው። ተጠሪ በበኩሉ በሥር ፍ/ቤት ያልተሰማና ያልታየን ማስረጃ እንደ አዲስ በሰበር ደረጃ ባለ ክርክር ለማቅርብ ስነ ስርዓት ህጉ ሰለማይፈቅድ ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት ተከራክሯል። ከዚህ በቀር ሁለቱም ወገኖች በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡት ሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡትን ክርክር የሚያጠናክር በመሆኑ በድጋሜ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። እንዲሁም የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል።

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው የክስ አቤቱታ ከተገለፁት የፍሬ ነገር ዝርዝር ጉዳዮች ገንዘቡን በአደራ ሰጥቻቸዋለሁ የሚል ሀረግ እንደታከለበት ይመልከት እንጂ ዝርዝር የክስ ምክንያቱን ማየት እንደሚቻለው ገንዘቡን ለተጠሪ ሰጠሁ የሚሉበት ምክንያት እራሳቸው አመልካች ለፈፀሙት ውልና ግኘር ለክፍያ እንዲውል ክፍያውን እንደ አመልካች ሆነው እንዲፈፅሙላቸው እንጂ ገንዘቡ የተሰጠው ተጠሪ በእጃቸው አድርገው በአደራ እንዲያቆዩላቸው የሚገልጽ አይደለም። አደራ የሚለው ቃል መካተቱ የክሱን ጉዳይ በፍ/ብሔር ህጉ የተመለከተውን የአደራ የህግ ጽንስ ሀሳብ ሊያመለክት የሚችል አይደለም። ስለሆነም የአሁን አመልካች እንደ አባባላቸው ገንዘቡን ለተጠሪ ሰጥተዋል ወይስ አልሰጡም? የሚለውን ክርክር ለማስረዳት የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 መሰረት ዘርዝሮ ያቀረባቸው የሰው ማስረጃዎች ተቀባይነት ያላቸው በመሆኑ ክሱ ከጅምሩ በህግ በተፈቀደ ማስረጃ ተደግፎ እንዳልቀረበ ተቆጥሮ ወድቅ ነው መባሉ የክሱን አርእስተ ጉዳይ እና ጉዳዩን ለማስረዳት የቀረበውን ማስረጃና የማስረጃ አቀባበል ስርዓትን ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም።

በሌላ በኩል የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ እንደገለጸው ጉዳዩን የሚያስረዳልኝ በወንጀል ችሎት የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔና ቅጣት የስር ፍ/ቤት ሊመለከትልኝ አልቻለም በማለት የአሁኑ አመልካች ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 222 እና 223 በሚያዘው መሠረት የቀረበ አለመሆኑን ተረድተናል። ይልቁንም ክሱ ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀረበ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ሐምሌ 23 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በወንጀል ችሎት ጥፋተኛ መባሉ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው። ሆኖም ይህ ማስረጃ እንደ ሥርዓቱ የቀረበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ግራ ቀኙ በየፊናቸው ለሰበር ሰሚ ችሎት ለማስረዳት ካቀረቡት የጽሑፍ ክርክር መገንዘብ እንደተቻለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የፍ/ብሔር ክስ ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ ብይን ሰጥቶ የነበረ መሆኑንና ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ይህንኑ እርሱ በሌለበት እንዲታይ የሚያደርገውን ብይን ለማስነሳት ከእርሱ ቁጥጥር ውጪ በሆነ በወንጀል እስር ምክንያት ማረሚያ ቤት የነበረ መሆኑን በማስረዳት አቅርቦት በዚህም ሳቢያ ጉዳዩ እርሱ ባለበት ታይቶ ሊወሰን መቻሉን አስመልክቶ የአሁን አመልካች ያቀረበውን ክርክር የአሁን ተጠሪ አላስተባበለም። በዚህ አኳኋን በእራሱ ተከሳሽ በነበረው ወገን የቀረበን ማስረጃ እኔ ሳላውቀው እንደ አዲስ የቀረበ ማስረጃ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 239 የተመለከተውን ሥርዓት የሚያሟላ አይደለም በሚል የአሁን ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የማስረጃ ማቅረቢያ ጊዜንና ደረጃ አስመልክቶ የተመለከተውን ሥርዓት እና የህጉን መነሻ ዓላማ መሠረት ያደረገ አይደለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካችም ቢሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 መሠረት ለማረጋገጥ የቀረበን ማስረጃ በአንድ በኩል ከቁጥር 78 አንፃር የበኩሉን ክርክር ማቅረብ ወይም ማስረጃነቱን የሚቀበለው ከሆነም ሲያየው ጉዳዩ ያለውን አግባብነት በማሳየት እንደ ሥርዓቱ በማስረጃ እንዲታይለት መጠየቅ እንጂ በቁጥር 78 መሠረት ተከሳሹ ባለበት ክርክሩ ይታያል ወይስ አይታይም የሚለው ጭብጥ ለመለየት በተደረገው የክርክር ደረጃ ማስረጃው እኔንም አንደሚጠቅመኝ ገልፀው ተከራክሪያለሁ ሆኖም ፍ/ቤቱ አለተመለከተልኝም የሚለው መከራከሪያ ነጥብ የእራሱን የክርክር አቀራረብ ጉድለት ከሚያሳይ በቀር ፍ/ቤቱ የፈፀመውን የጉዳይ አካሄድ ጉድለት አይመለከትም፡፡

ይሁን እንጂ ማስረጃው ከፍ/ብሔር ክርክሩ ዘግይቶ መገኘቱን ክርክሩ ለደረሰበት ደረጃ እና ማስረጃው ለክርክሩ ካለው አግባብነት አንፃር በማየት ጉዳዩን ሲመለከተው የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ይህንኑ ማስረጃ በማቅረብ ረገድ የፈፀመውን የአቀራረቡ ሥርዓት እንዲታረምና እንዲስተካከል በማድረግ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲባል መቀበል ይችል የነበረ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 137፣256 እና 91 ደንጋጌዎች አመልካች ናቸው፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ይህ ጉዳይ በይዘቱ ገንዘብ አደራ ክርክር እንደሆነ በመቁጠር ይህንንም ክርክር ለማስረዳት የቀረቡት የሰው ማስረጃዎች ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም በማለት የተሰጠው ትርጉም መሰረታዊ የሥነ ሥርዓት ህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፤ እንዲሁም የአሁን ተጠሪ በዚሁ ጉዳይ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ የተባለበትና የቅጣት ውሣኔ የተሰጠበት የወንጀል ፍርድ ለፍትሐብሔሩ ክርክር በማስረጃነት ቀርቦ ሊታይ የሚችልበት ሥርዓትና አግባብ እያለ ሳይታይ በገዘምታ መታለፉም ከማስረጃ አቀባበል ሥርዓት አንፃር የታለፈ ጉድለት በመሆኑ እነዚህ በጉዳዩ አመራር ሂደት የተከሰቱት ሥነ ሥርዓታዊ ጉድለቶች የታረሙ ሆኖ በማግኘታችን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስ አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት የሚከለተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በክ/መ/ቁ. 34280 መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በመ/ቁ. 107513 ግንቦት 2 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በፍርድ ሐተታው እንደተገለፀው የግራ ቀኙ ገንዘብ ነክ ክርክር የአደራ ገንዘብ የሚመለከት ሳይሆን የአሁን ተጠሪ የመኪና ግዥ ዋጋ እንደ አመልካች እንደ ሥር ተከሳሽ ሆኖ ለመክፈል ብር 280,000.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር) ተቀብሏል ወይስ አልተቀበለም የሚለውን አከራካሪ ነጥብ የሚመለከት በመሆኑና ይህንንም በሰው ማስረጃ ለማስረዳት ህግ ስለማይከለክል እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ጉዳዩን ለማስረዳት የቀረበውን የወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔ በማስረጃነቱ ተይዞ በተሟላ የክርክር አካሄድ ግራ ቀኙን በማሰማት በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት መዝገቡን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡
3. ይህ የሰበር ክርክር ስለተገኘው ወጪና ኪሣራ ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 67691

ታህሳስ 16 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር

ነገረ ፈጅ አቶ አማረ ከፍያለው - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ አለምፀሐይ ወልዴ ጠበቃ አቶ ፀጋዬ ተስፋዬ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በሁከት ይወገድልኝ የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበችው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በቂርቆስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 ቁጥሩ 059 ከመንግስት ተከራይተው ብቻቸውን በመኖር ላይ እያሉ አመልካች ነሐሴ 27 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብደቤ በባለቤትሽ ስም የመኖሪያ ቤት ያለሽ በመሆኑ የያዝሽውን የቀበሌ ቤት እንድትለቂ የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኛል፡፡ ስለዚህ ባል ያለኝ ወይም የሌለኝ መሆኑን በአግባቡ ሣያረጋግጥ ቤቱን እንድለቅ ማስጠንቀቂያ በመፃፍ የፈጠረብኝ ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ ከከሳሽ ጋር ያለን ክቤት ኪራይ ውል የመነጨ ግንኙነት ነው፡፡ ከሣሽ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ሁለት ልጆች በትዳር ከወለዱላቸውና አብረዋቸው በሚኖሩት ባለቤታቸው አቶ ክፍሉ ኢሣያስ ስም ቤት እንዳላቸው ስለተረጋገጠ ከቀበሌ የተከራዩትን ቤት እንዲለቁ ማስጠንቀቂያ መስጠታችን ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ (ከሳሽ) በባለቤታቸው ስም መኖሪያ ቤት ያላቸው በመሆኑ አመልካች (ተከሣሽ) የቀበሌውን ቤት እንዲለቁ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ተገቢ ነው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ- ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰረዞታል፡፡ ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለከተማው የሰበር ችሎት አቅርበዋል የከተማው የሰበር ችሎት ተጠሪ ከአቶ ክፍሉ ኢሳያስ ጋር ጋብቻ ያላቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ሚያዚያ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በባለቤታቸው ስም የግል የመኖሪያ ቤት እንዳላቸው ተረጋግጦ እያለ ከአመልካች የተከራዩትን ቤት እንዳይለቁ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ከአቶ ክፍሉ ኢሣያስ ጋር ጋብቻ ወይም የጋብቻ ሁኔታ የሌለን መሆኑ ስለተረጋገጠ የከተማው ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሐምሌ 18 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካች በተጠሪ ላይ ሁከት ፈጥሯል በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ የሚኖሩበት የቤት ቁጥር 059 ባለሀብት መሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪ በዚህ ቤት ውስጥ የሚኖሩበት ከአመልካች ጋር ባደረጉት የኪራይ ውል መሠረት መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ እና በየደረጃው ባቀረቡት ክርክር አረጋገጠዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ በኪራይ ውል የያዙትን ቤት እንዲለቁ እና የኪራዩን ውል ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? አመልካች በኪራይ ውሉ ይገደዳል ወይስ አይገደድም? የሚሉት ጭብጦች በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የኪራይ ውልና አግባብነት ያላቸውን የህግ ማእቀፎች መሠረት በማድረግ የሚታይ ነው፡፡

አንድ ሰው በሌላው ሰው ላይ ሁከት ፈጠረ ተብሎ ውሣኔ የሚሰጠው የሌላ ሰውን ይዞታ የወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የፈጠረበት መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የቤቱ ባለሀብት የሆነው አመልካች ቤቱን በኪራይ የያዙት ተጠሪ እንዲለቁለት ማስጠንቀቂያ መፃፉና የኪራይ ውልን የማቋረጥ ሀሣብ ያለው መሆኑን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2966 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ማሳወቁ ከአከራይ ተከራይ ውልና ግንኙነት አንፃር የሚያታይ እንጂ እንደ ሁከት ተግባር የሚቆጠር አይደለም፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ለአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በግልፅ ያቀረበችው የዳኝነት ጥያቄ አከራዩ አመልካች ከህግ ውጭ የኪራይ ውልን ለማቋረጥ ማድረጉ ተገቢ ስላልሆነ በኪራይ ውሉ እንዲገደድ ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚል ሣይሆን አመልካች ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሁከት እየፈጠረብኝ ስለሆነ ሁከቱ ይወገድልኝ የሚል ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁከት አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ መወሰን ሲገባው አመልካች የኪራይ ውሉን ያቋረጠው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመመርመር ውሣኔ መስጠቱ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚጥስ ሲሆን የከተማው የሰበር ችሎትም አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጠረው ሁከት አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ ብቻ በመወሰን ውሣኔ መስጠት ሲገባው አመልካች የኪራይ ውልን ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ የሰጠው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካች ሁከት ፈጥሮብኛል ሁከቱ ይወገድልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ የህግ መሠረት የሌለው ሆኖ እያለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከጠየቀችው ዳኝነት በመውጣት አመልካች የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ላይ ውሣኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ የፈፀመው የሁከት ተግባር የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ይኸ ውሣኔ ተጠሪ የኪራይ ውሉን መሠረት በማድረግ ሥልጣን ላለው አካል መብቱን ከመጠየቅ የሚገድባት አይደለም፡፡ ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባንክ እና ኢንሹራንስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 68708

ታህሣስ 05 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የአቶ ናስር አባጃቢር አባጅፋር ሚስትና ወራሾች

1. ወ/ሮ ሊያ ታምራት
2. ፍራአል ናስር አባጃቢር
3. ፍሮሜ ናስር አባጃቢር

ጠበቃ ድጋፌ ለገሠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፊጅ ባይሣ ኤደሣ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች አውራሽ ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ሰኔ 01 ቀን 1992 ዓ.ም እና ህዳር 22 ቀን 1993 ዓ.ም በተደረገው የብድር ውል በዋስትና ያስያዙት ንብረት በሐራጅ በተሸጠበት ወቅት ተጠሪ ሆነ ብሎ በእዳ ከያዘው ንብረቶች ውስጥ በሐራጅ መካተት የሚገባቸውን ንብረቶችን ባለማካተቱና ንብረቱ በተገቢው መንገድ ባለመሸጡ ከሣሽ ብር 1,280 ,556.70 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ሺህ አምስት መቶ ሃምሣ ስድስት ብር ከሰባ ሣንቲም/ ያጡ መሆኑን ገልጸው ተጠሪ ይህንኑ ገንዘብ ከእነ ወለዱ እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸዉን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበው ክርክርም ሐራጁ ከተከናወነ ከሶስት ዓመት ከስድስት ወር በኋላ ክሱ መቅረቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 447/1/ ድንጋጌ መሠረት የማይፈቀድ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም የከሣሽ ጥያቄ ንብረቱ በሐራጅ በመሸጡ ላይ የቀረበ ተቃውሞ ሳይሆን በሐራጅ ጊዜ መካተት የሚገባቸው ንብረቶች ሣይካተቱ ቀርተው ጉዳት ደርሶብኛል የሚል ነው የሚል ምክንያት በመያዝ ይኸው ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 447/1/ መሠረት በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ሊቀርብ ይገባ ነበር በማለት ክሱን ውድቅ አድርጐታል፡፡ በዚህ ብይን የስር ከሣሽ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ ለክርክሩ ምክንያት በሆኑት ንብረቶች ላይ የተካሄደው የሐራጅ ሽያጭ ይፍረስልኝ ወይም ይሰረዝልኝ ሳይሆን ንብረቶችን ያለዋጋ ስለአስተላለፋቸው ግምታቸውን ተጠሪ ሊከፍል ይገባል የሚል ሁኖ እያለ የበታች ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 447/1/ በመጥቀስ ክሱ በሁለት ወር ይርጋ የታገደ ነው በማለት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢነት የሌለው ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለጉዳዩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 447/1/ ተጠቅሶ ክሱ በሁለት ወር ይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሣኔ ከህጉ ጋር አገናዝቦ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካቾች አውራሽና በተጠሪ መካከል የብድር ውል ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ብድሩ የተወሰደውም በተለያዩ ጊዜአት ሁኖ ተበዳሪው ገንዘቡን ሊመልሱ ባለመቻላቸው ተጠሪ በብድር ውሉ በመያዣነት የያዘውን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት በሐራጅ መሸጡን ተበዳሪው ግንቦት 05 ቀን 2002 ዓ.ም ለመሰረቱት ክስ መሠረት ያደረጉት ምክንያትም ተጠሪ በዋስትና የያዘውን ንብረት ታህሣስ 20 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሸጥ በሐራጁ መካተት የሚገባቸውን ንብረቶች ሳያካትት ቀርቶ ያለዋጋ ማስተላለፉን የሚገልጽ ሁኖ የጠየቁት ዳኝነት የእነዚህ ንብረቶች ግምት እንዲከፈላቸው መሆኑን ነው፡፡ የስር ከሣሽ ከሐራጅ መሰረዝ ወይም መፍረስ ጋር አያይዘው ያነሱት የዳኝነት ጥያቄ የሌለ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ የአንድ መብትና ግዴታ ምንጭ ህግ ወይም ውል ነው በህግ ወይም በውል ጥበቃ ያገኘ መብት ወይም ግዴታ ጉዳት ሲደርስበት ወይም ተገቢው ካሣ የሚያስከፍል ከሆነ በህጉ ተለይቶ በተመለከተው የጊዜ ገደብና አካል ተገቢው ዳኝነት እንዲሰጥ ክስ ሊቀርብበት የሚገባው ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የስር ከሣሽ ለክሳቸው መሠረት ያደረጉት ተጠሪ ባንክ ለብድሩ በዋስትና የተሰጡትን ንብረቶች በሐራጅ ሲሸጥ በሐራጅ መካተት የሚገባቸውን ንብረቶችን ሳያካትት በመቅረቱ ያለዋጋ ንብረቶችን በማስተላለፍ ጉዳት በማድረሱ የንብረቶችን ግምት ሊከፍል ይገባል በማለት ነው፡፡ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች በሐራጅ መሸጥ እንዲችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 አዋጅ ቁጥር 98/90 እና አዋጅ ቁጥር 216/92 መሠረት የህግ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ባንኩ መያዣውን ሲሸጥ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓትም በ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን ከቁጥር 394 እስከ 449 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ስለመሆኑም አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሲታይም የሐራጅ ሽያጩ ሂደት በህጉ አግባብ ካልተፈጸመ እና ይህ በተገቢው መንገድ ከተረጋገጠ ህጉ ባንኩን ለተፈጸመው ስህተትና ውጤቱ ተጠያቂ እንደሚያረገው ያስገነዝባል፡፡ አመልካች በተጠሪ ደርጊት ከላይ በተገለጸው አግባብ የተፈጸመባቸው እና የጉዳት ኪሣራ የጠየቁም አይደለም፡፡ ለክሳቸው መሠረት ያደረጉት በአዋጁ መሠረት አመልካች ሐራጁን ሊያወጣ መካተት የሚገባቸው ንብረቶች ሳይካተት ቀርቷል የሚል ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ የአመልካቾች አውራሽ የዳኝነት ጥያቄ መሠረት ያደረገው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027 እና 2028 መሠረት የጉዳት ካሣ የሚጠየቅበትን አግባብ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ንብረት በሐራጅ ሲሸጥ በሐራጁ መካተት የሚገባቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 423/2/ ስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተዘርዝረዋል፡፡ ይህ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 6 መሠረት ባንኩ የሐራጁን ስራ በሚያከናውንበት ጊዜ ሊከተላቸው ይገባቸዋል ተብለው ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ስር የሚገኝ ነው፡፡ ይህን ደንጋጌ ባለመከተል የሚደርሰው ጉዳት /DAMAGE/ ደግሞ የሚጠየቀው በአዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 7 መሠረት ነው፡፡ አንድ ሰዉ ህግን በመጣስ በሌላ ሰው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ከውል ውጪ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ደግሞ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027፣ 2028 ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2035 ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የውል ግንኙነትን መሠረት በማድረግ በሚካሄድ እንቅስቃሴና በአዋጅ ቁጥር 97/90 የተሰጠውን ስልጣን ለመጠቀም መነሻ ያደረገ እርምጃን ለመውሰድ በህጉ የተመለከተውን ስርዓት ያለመከተል እንደጥፋት በመቁጠር ባንኩ ካሣ እንዲከፍል አዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 7 ስለሚደነግግ እና ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2037 ድንጋጌ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ከላይ በተመለከተው መንገድ የሚጠየቀው የጉዳት ካሣ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143/1/ ድንጋጌ መሠረት እስከ ሁለት ዓመት ክስ ሲቀርብ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 447/1/ ስር የተመለከተው የሁለት ወር የጊዜ ገደብ የሐራጅ ይፍረስልኝ ወይም ይሰረዝልኝ ጥያቄን የሚገዛ እንጂ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ፣ 98/1990 እና 216/1992 በተዘረጋው ስርዓት መሠረት ሐራጁ በሚከናወንበት ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 394 እስከ 449 ድረስ ያሉትን ድንጋጌዎችን ባለመከተል የሚደርሰውን ጉዳት ካሣ ለመጠየቅ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በፎርክሎዠር ሕግ መሠረት የሚከናወን ሐራጅ በፍ/ቤት የሚሰርዝበትአግባብ የሌለ ሲሆን ሐራጁ በሕግ አግባብ ያለመከናወን በባንኩ ላይ የጉዳት ካሣ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ተቀምጧልና፡፡

በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች የአመልካች አውራሽ ጥያቄ የጉዳት ካሣ ጥያቄ ሆኖ እያለ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 447/1/ ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ውድቅ ማድረጋቸው በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143/1/ ድንጋጌ ስር የተመለከተው የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ማለፍ ያለማለፉ ሲታይ የአመልካቾች አውራሽ ክስ የመሰረቱት ግንቦት 05 ቀን 2002 ሲሆን ንብረቶቹ በሐራጁ ላይ ሳይካተቱ ተሸጡ የተባሉት ጊዜ ደግሞ ታህሣስ 20 ቀን 1999 ነው፡፡ ይህም ጊዜ ሲሰላ የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ከአለፈ በሁዋላ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ክሱን ውድቅ ማድርጋቸው በውጤት ደረጃ የምንቀበለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 92618 ጥቅምት 26 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/በት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 64130 የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ብይን ውጤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 342 መሠረት ምክንያቱ ተለውጦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143/1/ መሠረት በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ የታገደ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወጋገን ባንክ አ.ማ ነ/ፈጅ ገቢማ ተራማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ብሩክ ጫካ

2. ወ/ሮ አማረች ጫካ

3. ወ/ሮ ሂሩት ጫካ

4. አቶ ከበደ ጫካ

5. ወ/ሮ አለምጸሀይ ጫካ

6. ወ/ሮ አዳነች ጫካ

7. አቶ ጌታሁን ጫካ

ጠበቆች 1. አማን አሰፋ

2. ቴዎድሮስ ምህረት ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አበዳሪ ባንክ ለሰጠው ብድር ሁለትና ከዚያ በላይ መያዣ ይዞ ቆይቶ ብድሩ ባለመመለሱ ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት መያዣውን ለመሸጥ ሲንቀሳቀስ ከመያዣዎቹ መካከል ቀድሞ መሸጥ ያለበት ንብረት የትኛው እንደሆነ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሽ፣አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የመሠረቱት ክስ ባጭሩ፡- አመልካች ለሚለማ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለሠጠው ብር አምስት ሚሊዮን የአቨር ድራፍት ብድር በዋስትና መያዣነት ተበዳሪው በቡራዩ ከተማ ካለው መጋዘን ቤት በተጨማሪ በውርስ የተገኘውን የተጠሪዎችን መኖሪያ ቤት በተጨማሪ መያዣነት አስይዞ እንደነበር፣ተበዳሪው የተበደሩትን ብድር ያልመለሱ መሆኑን፣አመልካች ለሠጠው ብድር በመያዣነት የያዘውን የተበዳሪውን መጋዘን ሸጦ ለብድሩ ማስመለሻ ማድረግ ሲገባው የባለዳውን መጋዘን ትቶ የተጠሪዎችን የውርስ ቤት በሐራጅ ሊሸጥ እንደማይገባ ዘርዝረው በተጠሪዎች ቤት ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጀመረውን የሐራጅ ሽያጭ አቁሞ በመጀመሪያ የተበዳሪውን ንብረት የዕዳው ማስመለሻ አድርጐ እንዲቀጥል፣የተጠሪዎችን የቤት ካርታ እንዲመልስ ይወሠንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ በአዋጅ ቁ 97/90 እና 216/92 መሠረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ እዳው አለመከፈሉና ቤቱ መያዣ መሆኑ ባለመካዱ ተጠሪዎች ክስ ለማቅረብ መብት የሌላቸው መሆኑን፣ተበዳሪ ካልከፈለ በቅድሚያ በአንደኛ ደረጃ የተያዘው የተበዳሪው ንብረት ይሸጣል የሚል ስምምነት ባለመኖሩ በዚህ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣የፍ/ሕጉን ድንጋጌዎች በመጥቀስ የቀረቡ ክርክሮች ከአዋጅ ቁ 97/90 ድንጋጌ ውጪ መሆናቸውን፣አመልካች ከአዋጅ ቁ 97/99 አንፃር ያመነበትን ንብረት መሸጥ የሚችል መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከሣሽና ተከሣሽ በቅድሚያ የባለዕዳው ንብረት ሊሸጥ ይገባል በማለት በመያዣ በተሠጠ ንብረት ላይ የተጀመረ ሐራጅን ለማስቆም ይችላል? ወይንስ አይችልም? የሚል ጭብጥ መስርቶ መዝገቡን በመመርመር ባንክ የሠጠው ብድር ሣይመለስ ሲቀር መያዣውን በመሸጥ የባለቤትነት መብት እንዲዛወር ለማድረግ ካባለዕዳው ጋር መስማማትና በዚሁ ስምምነት ተፈጻሚ ማድረግ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት መደንገጉን፣ክስ በቀረበበት ጉዳይም ከሣሽ በመያዣ የሰጡት ቤት ዕዳ ካልተከፈለ ባንኩ እንዲሸጥ መስማማቱን የመያዣ ውሉ የሚያሳይ መሆኑን፣ይህ ሥርዓት በአዋጅ ለባንኩ የተፈቀደው ባንኩ የሰጠውን ብድር በፍጥነት መሠብሰብ የማስቻል ዓላማ የያዘ መሆኑ ግልጽ መሆኑን፣አመልካች በአዋጅ የተሠጠውን ሥልጣን ተፈፃሚ ለማድረግ ሲንቀሣቀስ ተጠሪዎች የፍትሓ ብሔር ሕጉ ስለተራ ዋስትና የደነገገውን መነሻ በማድረግ በቅድሚያ የባለዕዳው ንብረት ሣይሸጥ ባንኩ በተጠሪዎች ንብረት ላይ ሐራጅ መቀጠል አይችልም በማለት መከራከራቸው አግባብነት የሌለውና አዋጁን የሚቃረን መሆኑን በመዘርዘርና በምክንያትነት በመያዝ የተጠሪዎችን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል በመያዣነት የቀረበው የተጠሪዎችን ንብረት ማረጋገጫ ሰነድ በአመልካች ዘንድ እንደሆነ አመልካች በቅድሚያ ለዚሁ ብድር በመያዣ የያዘውንና በቡራዩ ከተማ የሚገኘውን የተበዳሪውን ንብረት በጨረታ ሸጦ የሰጠውን ብድር ያስመልስ፣አመልካች የሚሸጠው የተበዳሪው መጋዘን ብድሩን በሙሉ ካላስመለሰለት የተጠሪዎችን የመያዣ ንብረት ሸጦ ቀሪውን ብድር ያስመልስ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለውጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የአዋጅ ቁ 97/90 ዋና ዓላማ በፍ/ቤት የሚፈጀውን ጊዜ በማሣጠር ለልማት እንቅስቃሴው የሚሠጡ ብድሮችን ወቅቱን ጠብቆ እንዲሠበሰብ ማስቻል መሆኑን፣የደረሠ ጉዳትን ከሚመለከት ጉዳይ በስተቀር ጉዳዮች ወደ ፍ/ቤት ለመምጣት የማይችሉ መሆኑን፣ ወደ ፍ/ቤት መምጣት ይችላሉ ከተባለ ወደ ነበርንበት መመለስና ባንኮችም ብድራቸውን በጊዜው እንዳይሠበስቡ የሚያደርጋቸው መሆኑን፣በተጠሪዎች የተጠቀሱት የፍትሓ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌላቸው መሆኑን፣በሕጉ አግባብ በተደረገው ውል መሰረት አከራካሪው ንብረት መያዣ መሆኑ ያለመካዱን፣እንዲህ ከሆነ ደግሞ ግራ ቀኙ የሚገዙት በውሉ መሆኑን፣በውሉ ደግሞ መጀመሪያ የተበዳሪውን ንብረት ሸጠህ ነው ወደ እኔ የምትመጣው የሚል ስምምነት የሌለ መሆኑን፣ውሉ የሚለው ዕዳው ካልተከፈለ ንብረቱ ይሸጣል ስለመሆኑ፣ የተበዳሪው መጋዘን ብር 12 ሚሊዮን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያወጣል የተባለውም በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ ያልተረጋገጠ መሆኑን፣ ተበዳሪው በርካታ እዳ እንዳለባቸው እና ተጠሪዎችም የተበዳሪው ድርጅት እዳ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው መሆኑን፣ የመያዣውን ንብረት የመሸጥ መብት መያዣ ያገዙ ባንክ እንጂ ተበዳሪው ከመያዣዎቹ ውስጥ መያዣ ያገዙን ባንክ ይህን ሽጥ ይህን ደግሞ አትሸጥ የማለት መብት የሌላው መሆኑንና መብቱ የአመልካች ባንክ መሆኑን፣ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁ 97/90 አፈጻጸም ላይ ጣልቃ የሚገባቡት መንገድ የተለየ መሆኑን በመዘርዘር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሸሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርመሮም አመልካች በቅድሚያ የተበዳሪውን ንብረት ሽጦ ለእዳ መመለሻ ያውል የመባሉን እና ሌሎች ነጥቦችን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ የሰጡት መልስ ባጭሩ፡- የአዋጅ ቁጥር 97/90 ዓላማ ባንኮች በመያዣ የሚያዟቸውን ንብረቶች ለፍ/ቤት ማመልከት ሳያስፈልጋቸው በራሳቸው መሸጥ እንዲችሉ ሆኖ በመሆኑ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለውን በውል ላይ የተመሠረተ እኩልነትን ያረጋገጠ መሆኑን፣አመልካች የሰጠውን ብድር እጥፍ የሚሸፍን ንብረት በእጁ እያለ የተጠሪዎችን መኖሪያ ቤት ለመሸጥ መንቀሣቀሱ ቅን ልቦና የሌለው አካሄድ መሆኑን፣ተበዳሪው ከአመልካች ዘንድ በመያዣ የተያዘውን በቡራዩ ከተማ የሚገኘውን መጋዘን ሸጩ የብድሩ መመለሻ እንዳደርግ ይፈቀድልኝ ብሎ ጥያቄ አቅርቦ በአመልካች ትብብር መከልከሉ ያላግባብ መሆኑን፣ተጠሪዎች የተበዳሪው ንብረት በቅድሚያ እንዲሸጥ ጠቁመው በአመልካች ጥያቄአችን ውድቅ ተደርጎ የተጠሪዎች ንብረት ለመሸጥ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ትክክል አይደለም ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መወሰኑ የተጠሪዎችን በሕግ ፊት እኩልነትና ፍትሕ የማግኘት መብትን ያረጋገጠና በሕግ፣ በሞራልና ከአመክንዮ ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣የብድሩን መጠን በተመለከተ አመልካች በሰበር አቤቱታው ላይ የጠቀሰውም በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን በመዘርዘር የይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሣኔ ምንም የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የተጠሪዎች ጥያቄ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ አለ? ወይስ የለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት አመልካች በመያዣ ከያዛቸው ንብረቶች መካከል አንዱ የሆነውን የተጠሪዎችን ንብረት ከመሸጡ በፊት ሌላ መያዣ የሆነ የተበዳሪ ድርጅት መጋዘን ስለአለ ይህንኑ መጋዘን ቀድሞ ሊሸጥ ሲገባ የተጠሪዎችን መኖሪያ ቤት ለመሸጥ መንቀሳቀሱ ተገቢ አይደለም በሚል ምክንያት መሆኑን፣የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔውን ሊያሳልፍ የቻለው አከራካሪው ንብረት በመያዣ መሰጠቱን አረጋግጦ ከዚሁ ንብረት ጋር በመያዣነት የተሠጠ የተበዳሪ ንብረት ስላለ ይኸው ቀድሞ ሳይሸጥ የተጠሪዎች ንብረት መያዣ በመሆኑ ብቻ የሚሸጥበት አግባብ የለም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች በሐራጅ መሸጥ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 የሕግ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ባንኩ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ከቁጥር 394- 449 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስር በተመለከተው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 97/90 በአንቀጽ 6 በግልጽ አስፍሯል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀፅ 3 እና 4 መሰረት እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 216/19992 በተደረገው ማሻሻያ ባንኮች ለሰጡት ብድር አከፋፈል በመያዣነት በዋስትና የተቀበሉትን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት የብድር እዳው እንዲከፈለው በተወሰነው ጊዜ ሳይከፈል ከቀረ ከሰላሳ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የመያዣ ንብረቱን በሐራጅ ለመሸጥና ባለቤትነቱንም ለገዢው ለማዛወር ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከአዋጁ ድንጋጌዎችም መረዳት የሚቻለው አበዳሪው ባንክ በዋስትና የያዛቸውን ንብረቶች የብድር ገንዘቡን ካልተመለሰለት ያለማንም ጣልቃ ገብነት አግባብነት ያላቸውን የሕጉን ድንጋጌዎችን በመከተል በሐራጅ ሽጦ ለእዳው ክፍያ ማዋል እንደሚችልና በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ሕጉን ባለመከተል የፈጸመው ስህተት ቢኖርና በዚህም በባለእዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባለእዳው ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ የአዋጆቹ ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይም የሕጎቹ ዓይነተኛ አላማ ባንኮች የሚሰጧቸውን ብድሮች በተቀላጠፈ አኳኋን ለመሰብሰብ እንዲችሉ ስለመሆኑ የሚያስገነዝብ ሲሆን ይህ ስለመሆኑም አዋጅ ቁጥር 97/1990 መግቢያው ላይ በግልፅ አስቀምጧል፡፡

ባንክ ከላይ በተጠቀሱት አዋጆች መሠረት በመያዣ የያዘውን ንብረት አስገምቶ ሐራጅ ቢያወጣና ቢሸጥ ወይም በሕጉ መሠረት ቢረከብ ግምቱን ወይም በመያዣ የተሰጡትን ንብረቶች አሻሻጥ ቅደም ተከተል ምክንያት በማድረግ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና እንዲያይ፣እንዲያስገምት ወይም ከመያዣዎቹ አንዱ ቀድሞ መሸጥ አለበት ብሎ ለመወሰን የሚያስችል ከሕግ የመነጨ ሥልጣን የለውም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 7 ስር የተደነገገውን ድንጋጌ መግቢያ በማድረግ መያዣው በብድሩ ወቅት በተገመተበት ግምት እንዲያዝ መጠየቅም ሆነ በሐራጅ ወቅት የወጣው መነሻ ግምት አነስተኛ ነው ብሎ ለፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረብ ከፍ/ቤቱ ስልጣን ውጪ ከመሆኑም በላይ አዋጁ የወጣበትን ዓላማም ከግብ እንዳይደርስ የሚያደርግ ጭምር ስለመሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ይህ የሕጉ አጠቃላይ ቅርፅ የሚያስገነዝበን ሌላው ቁም ነገር በመያዣ ውሉ የተቀመጡት ንብረቶች ተለይተው የታወቁ እስከሆነ ድረስና የተያዙበት አግባብም አንዱ መያዣ ከሌላው በቅደም ተከተል የሚሸጥ አለመሆኑን የሚያሳይ ከሆነ ከመያዣዎች ውስጥ ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረት ሳይሸጥ አነስተኛ ግምት ያለው ቀድሞ ሊሸጥ አይገባም በሚል የሚቀርበው የዳኝነት ጥያቄ የመያዣ ውሉንና ከላይ ከተጠቀሱት አዋጆች አላማ ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ ፍርድ ቤት የሐራጁን ስርዓት በማስቆም የሚያስተናግድበት አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ባንክ የሐራጅ ሽያጩን የሚያከናውነው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 394-449 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ የሐራጁ ሽያጭ ሂደት በሕጉ አግባብ ካለተፈፀመ እና ይህ ከተረጋገጠ ሕጉ ባንኩን ለተፈፀመው ስህተትና ውጤቱ ተጠያቂ ያደርገዋል፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 7 ስር ከተመለከተው ድንጋጌ የምንገነዘበው ሐቅ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች ተላልፎ በመያዣው ላይ ሽያጭ ከተፈፀመ ሃላፊነቱ የባንኩ እንደሆነም በግልጽ ያሣያል፡፡ ከላይ የተመለከቱት የፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተጥሰዋል የሚለው ክርክር በባንኩ ላይ በፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችለው ባንኩ ሐራጁን እንዳያከናውን በማድረግ ሳይሆን የሐራጅ ስርአቱ ከተከናወነ በሁዋላ ስለመሆኑም የሚታመን ነው፡፡ ጥያቄው ከሐራጁ በፊት በፍርድ ቤት ሊታይና ሐራጁ እንዲቆም ሊደረግ ይችላል ከተባለ ከላይ እንደተገለጸው በፎርክሎዠር ሕጎች የታሰበው የብድሮች በተቀላጠፈ ሁኔታ የመሰብሰብ እድል የተገደበ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄ ይዘቱ ሲታይ አመልካች በመያዣ ከያዛቸው ንብረቶች መካከል የመኖሪያ ቤቱ ከመሸጡ በፊት ለእዳው ተመጣጣኝ የሆነ መጋዘን ስላለ ይህንኑ ንብረት መሸጥ አለበት የሚልና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

394(2) ስር የተመለከተውን የስነ ስርዓት ሕግ አጠቃላይ መንፈስ መሰረት ያደረገ ነው። በእርግጥ ይኸው ድንጋጌ ባንኩ እንዲከተለው በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ግዴታ የተጣለበት ነው። ይሁን እንጂ ይኸው ድንጋጌ ተጥሷል የሚለው ወገን በፍርድ ቤት ዳኝነት የሚያቀርበው የሐራጅ ስርዓቱ እንዲቆም በማድረግ ሳይሆን ይኸው ድንጋጌ በሐራጅ ጊዜ በባንኩ ባለመጠበቁ የደረሰ ጉዳት ካላ ይህንኑ በማረጋገጥ ነው። በአጠቃላይ ተጠሪዎች አመልካች በመያዣ ከያዛቸው ንብረቶች መካከል ከፍተኛ ግምት ያለውን የተበዳሪውን መያዣ ሊሸጥ ይገባል እንጂ በመያዣ የተሠጠውንና አነስተኛ ግምት ያለውን መኖሪያ ቤት አመልካች ሊሸጥ አይገባም በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በፍርድ ቤት የሚስተናገድ አይደለም። ስለሆነም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና 216/1992 ዓይነተኛ አላማን ከተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ እንዲሁም አከራካሪው ንብረት በሕግ አግባብ በተቋቋመ የመያዣ ውል መሰረት የተያዘ ከመሆኑ አንፃር በመመርመር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማስተናገድ ስልጣን ያለው መሆን ያለመሆኑን ማገናዘብ ሲገባው አመልካች ከያዛቸው ንብረቶች መካከል የተበዳሪ ድርጅት መጋዘን ከፍተኛ ግምት ስላለው የተጠሪዎች መኖሪያ ቤት ከመሸጡ በፊት ቀድሞ መሸጥ አለበት ሲል የሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/1992 ስር የተመለከቱትን ግልፅ ድንጋጌዎችን የሚቃረን ሁኖ አግኝተናል። ግልጽ ሕግ ደግሞ ውጤት እንዳይኖር የሚደረግበት የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትም ሆነ የሕግ አተረጓጎም ደንብ የለም። በመሆነም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች የስር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ስላገኘን የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል።

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 66087 ግንቦት 12 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል።
2. በሕግ አግባብ በተቋቋመ የመያዣ ውል ከተያዙት ንብረቶች መካከል የትኛው ንብረትና የማን ንብረት መሸጥ አለበት የሚለው ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንደተሻሻለው የዋስትና መያዣዎችን ባንኮች ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሽጠው ለዕዳ ክፍያ ማዋል የሚችሉ ስለመሆኑ ከተደነገገው ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም ብለናል። በመሆኑም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት በተሠጠው ስልጣን መሰረት በተጠሪዎች መኖሪያ ቤት ላይ የጀመረው የሀራጅ እንቅስቃሴ የተበዳሪው ንብረት የሆነውና የብድሩ መያዣ መጋዝን ከተሸጠ በሁዋላ ሊከናወን ይገባል ብሎ ፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችልበት ከሕግ የመነጨ ስልጣን የለውም ብለናል።
3. የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 99689 የካቲት 07 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል።
4. በዚህ የክርክር ደረጃ ያለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ በላቸው እሸቱ - ጠበቃ አቶ ወርቅዬ አባይነህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነገረ ፈጅ ማህሌት ዓለሙ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ለደረሰው አደጋ ተጠሪ ካሣ የመክፈል ከውል የመነጨ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም በሚለው ነጥብ ሲከራከሩ ቆይተው ተጠሪ አደጋውን ያደረሰው ጉዳት በመድን ውሉ መሠረት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

የዚህ ክርክር መሠረታዊ ጉዳይ አመልካች ማንነታቸው ባልታወቀ ግለሰቦች በእሳት የተቃጠለችው ቁጥር ኮድ 3-02549 ለሆነችው መኪና በመድን በውሉ የተሰጠው ሽፋን ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ በመሆኑ በዚህ መሰረት ሊከፈል ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ መኪናው አደጋ በደረሰበት ጊዜ የነበረው ዋጋ ብር 95,099.92 እንደሆነ በገለልተኛ ባለሙያ ተገምቷል፡፡ ልከፍል የሚገባው ይህንን ገንዘብ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት መኪናዋ አደጋ ሲደርስ የነበራትን ዋጋ አመልካች እንዳልተቃወመ በውሣኔው ገልፆ፣ ተጠሪ ብር 95,099.92 /ዘጠና አምስት ሺህ ዘጠና ዘጠኝ ብር ከዘጠና ሁለት ሣንቲም/ ለአመልካች እንዲከፍል የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሰኔ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በተባፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ ሒሳብ ፕሪሚየም ሲሰበሰብ ቆይቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ የንግድ ሕግ ቁጥር 654/1/ እና የንግድ ሕግ ቁጥር 665/1/ መሠረታዊ ድንጋጌዎች የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጎዳር 18 ቀን 2004 ዓ.ም በተባፈ የሰበር መልስ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የንግድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ ቁጥር 678 በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካች ሊከፈለው የሚገባው መድን የተገባለት መኪና በአደጋው ጊዜ የነበረትን ዋጋ ያህል ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በንግድ ሕጉ እውቅናና ጥበቃ ስለተሰጣቸው የኢንሹራንስ /የመድን ሽፋን/ አይነቶችንና ባህሪያት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በንግድ ሕጉ እውቅና የተሰጠው የመጀመሪያው የኢንሹራንስ ውል የደረሰን ጉዳት ለመካስ ወይም ለመተካት /Indemnity Insurance/ የሚደረግ ውል እንደሆነ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 654 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ ሲሆን፣ የደረሰን ጉዳት ለመካስ ወይም ለመተካት /Indemnity Insurance/ የሚደረግ የኢንሹራንስ ውሎች በንብረት ላይ ለሚደረስ ጉዳትና በፍታብሔር የሚመጣ ኃላፊነት /Indemnity Insurance/ የሚያካትት እንደሆነ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ሁለተኛው ዓይነት የኢንሹራንስ ውል የደረሰን ጉዳት ለመካስ ወይም ለመተካት ሳይሆን አደጋው ሲደርስ በውሉ የተገለፀውን ገንዘብ ለተጠቃሚው ወይም የመድን ውል ለገባው ሰው ለመስጠት የኢንሹራንስ ውል (non Indemnity Insurance or capital insurance) እንደሆነና ይህም ለህይወት ወይም በአካል ጉዳት ወይም በሕመም ለሚደርስ አደጋ የሚሰጥ የመድን ሽፋን እንደሆነ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 654 ንዑስ አንቀፅ 3 ተደንግጓል፡፡ የንግድ ሕጉ በተለያየ መንገድ ፈርጆ ያስቀመጣቸው እነዚህ ሁለት አይነት የመድን ውሎች በይዘታቸው፣ በባህሪያቸውና በሚኖራቸው ውጤት የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት ሁኔታ መኖሩን ሕግ አውጭው በምዕራፍ ሁለት ማለትም ከንግድ ሕጉ አንቀፅ 657 እስከ አንቀፅ 674 ጠቅላላ የመድን ሕግ ድንጋጌዎችን፣ በምዕራፍ ሶስት ማለትም በንግድ ሕጉ ከአንቀፅ 675 እስከ አንቀፅ 688 ስለጉዳት ኪሣራ ኢንሹራንስ ላይ ልዩ ተፈፃሚነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን፣ በምዕራፍ ሶስት ማለትም ከአንቀጽ 689 እስከ አንቀፅ 712 የሰዎች ኢንሹራንስ ላይ ተፈፃሚነት ያላቸውን ልዩ ድንጋጌዎች በመደንገግ በግልጽ አሳይቶናል፡፡

የንግድ ሕግ አንቀጽ 665 በአጠቃላይ ጉዳት ለመካስ ወይም ለመተካት እና ለሰዎች ኢንሹራንስ ላይ ተፈፃሚነት ያለው ጠቅላላ ድንጋጌ ሲሆን፣ በይዘቱ የመድን ሽፋን የሚሰጠው የኢንሹራንስ ኩባንያ ለመድን ገቢው ወይም ለተጠቃሚው ሊከፍለው የሚችለው ወይም ሊከፍለው የሚገባው የኢንሹራንስ ገንዘብ በመድን ውሉ ከተገለፀው ሊበልጥ የማይችል መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ንግድ ሕግ አንቀፅ 678 ስለንብረት የተደረገ ኢንሹራንስ ውል የሚኖረውን ውጤት በልዩ ሁኔታ የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ ነው፡፡ በመርሕ ደረጃ ለንብረት የሚሰጥ የኢንሹራንስ ሽፋን አደጋው በደረሰበት ጊዜ ንብረቱ የነበረውን ዋጋ የሚያካክስ መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ነው፡፡ በንብረት የሚደረግ ኢንሹራንስ መሠረታዊ ዓላማው ንብረቱ በመጎዳቱ ወይም ንብረቱ በመውደሙ በባለንብረቱ ላይ የደረሰውን ኪሣራ ለመተካት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የንብረቱ ዋጋ ከተሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን በልጦ ሲገኝ መድን ገቢው በመድን ውሉ ሽፋን ከተሰጠው ዋጋ በላይ ላለው ገንዘብ ራሱ የመድን ሽፋን እንደሰጠ ተቆጥሮ፣ መድን ሰጭው በውሉ የተገለፀውን ዋጋ ብቻ የሚከፍል ስለመሆኑ፣ የዕቃው ዋጋ ከተሰጠው የመድን ሽፋን አንሶ ሲገኝና መድን ገቢው የማታለል፣ የማጭበርበር ተግባር ያልፈፀመ በሆነ ጊዜ የዕቃው እውነተኛ ዋጋ የሚከፈለው መሆኑን በንግድ ሕጉ አንቀፅ 680 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም አንድ ሰው አንድን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት ለተመሣሣይ አደጋ ለተለያዩ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የመድን ሽፋን እንዲኖረው ቢያደርግ የመድን ሽፋን የሰጡት ኩባንያዎች በውላቸው ፕሮፖርሽናል በሆነ መንገድ አዋጥተው የዕቃውን ዋጋ ብቻ የሚክሱት ስለመሆኑና አንድ ሰው ከዕቃው ዋጋ በላይ የሆነ ገንዘብ አንድን ዕቃ በተለያየ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ሽፋን እንደሰጡት በማድረግ ሊያገኝ እንደማይችል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 681 በግልፅ ተደንግጓል፡፡

ከላይ ከገለፅነው መሠረታዊ ድንጋጌዎች አንፃር ስንመለከተው የአመልካች መኪና ጉዳት በደረሰበት ጊዜ የነበራት ዋጋ በመድን ውሉ ከተገለፀው ያነሰ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የሚከፍለው በውሉ የተገለፀውን የገንዘብ መጠን ሳይሆን ንብረቱ በአደጋው ውድመት ሲደርስበት የነበረውን ዋጋ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ የንግድ ሕግ አንቀፅ 678 እና የንግድ ሕግ አንቀፅ 680 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ስለንብረት ጉዳት የተደረገ የመድን ውል የሚኖረውን ውጤት የሚደነግጉ ሌሎች ልዩ ድንጋጌዎችን ይዘት፣ ባህሪያትና ውጤት ያገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 74898
ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቀረበ የለም
ተጠሪ፡- 1- አቶ ፍቃዱ ተስፋዬ ቀረቡ
2- አቶ በጡሬ ሲማ
3- ወ/ሮ ዘብደሩ ወኑ } አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ የፍርድ አፈፃፀም ጥያቄ በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ የባለእዳው ንብረት እዳውን ሊሸፍን ባለመቻሉ በከፊል ተፈፅሞ ከቆየ በኋላ የፍርድ ባለመብት የባለእዳውን ንብረት አፈላልጎ በማግኘት አፈፃፀሙን ለመቀጠል ሲፈልግ ይርጋው ሊቆጠር የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ የአፈፃፀም ክሱ /ክርክሩ/ የጀመረው በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በአፈፃፀም ክሱ እንደተመለከተው ለአቶ ፈቃዱ ተስፋዬ የሠጠው ብድር በወሉ መሠረት ባለመከፈሉ በፍርድ ቤት ክስ መስርቶ የአፈፃፀም ተከሣሾች /የአሁኑ ተጠሪዎች/ በአንድነት እና በነጠላ ያለባቸውን ቀሪ እዳ ብር 147,922.00 /አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሁለት ብር /እንዲከፍሉ ሕዳር 2 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት መወሰኑን ፣ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት በአገኘው መብት አፈፃፀሙን በራሱ ቀጥሎ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም. በዝዋይ ከተማ 02 ቀበሌ ውስጥ በአቶ ፍቃዱ ተስፋዬ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውንና ቁጥር 21/164/80 የሆነውን ቤት በብር 50,400.00 በመሸጥ ይህንኑ የሽያጭ ገንዘብ ከእዳው የቀነሰ ሲሆን በወቅቱ የባለእዳዎች ንብረት ባለመኖሩ አፈፃፀሙን መቀጠል ያለመቻሉን ፣ ከዚህ በኋላ የዋናው ተበዳሪ ዋስ በሆኑት በአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ ንብረት ማግኘቱን ገልጾ ቀድሞ በፍርድ ቤት በአገኘው ውሣኔ መሠረት አፈፃፀሙን በዚሁ በዋሉ ንብርት እንዲቀጥልለት ጥቅምት 23 ቀን 2004 ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአፈፃፀም መዝገቡ የቀረበው በፍርድ ቤቱ ውሣኔ ከተሰጠ ከአስራ አራት አመታት በኋላ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም አመልካች ቀሪ እዳ መኖሩን አውቋል ሊባል የሚችለው የአቶ ፈቃዱ ተስፋዬ ንብረት ሽጦ ቀሪ እዳው መኖሩን ከአወቀበት ጊዜ ጀምሮ ሁኖ እያለ ይርጋው ከሕዳር 02 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ ነው መቆጠር ያለበት ተብሎ የአፈፃፀም መዝገቡ መዘጋቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የአፈፃፀም መዝገብ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች የብድሩን ገንዘብ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለመክፈላቸው አመልካች በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦባቸው ፍርድ ቤቱ ሕዳር 02 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠቱን ይህንኑ ውሣኔ መሠረት በማድረግ አመልካች አፈፃፀሙን በፍርድ ሳይቀጥል ቆይቶ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት በአገኘው መብት አፈፃፀሙን በራሱ ቀጥሎ ግምቱ ብር 50,400.00 /ሃምሳ ሺህ አራት መቶ ብር/ የሆነውን የዋናውን ተበዳሪ ንብረት ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም በመሸጥ በፍርድ ቤቱ ከተወሰነበት ከብር 147,922.00 ገንዘብ ውስጥ ተቀናሽ ማድረጉንና ከዚህ በኋላ በመያዣነት ያልተያዘ የዋሱ ንብረት ተገኝቷል በሚል ምክንያት አፈፃፀሙን በፍርድ ቤት በኩል ለመቀጠል ጥቅምት 23 ቀን 2004 ዓ.ም መንቀሳቀሱን ነው፡፡ ከዚህ በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች የዋናውን ተበዳሪ ቤት ለእዳው መክፈያ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም ቢያውልም የቤቱ ግምት እዳውን ሙሉ በሙሉ ሳይሸፈን መቅረቱን ነው፡፡ የዋናውን ባለዕዳ ቤት ሽጦ ከእዳው ተቀናሽ ቢያደርግም በዚህ ረገድ ተከፈለ ሊባል የሚችለው ዕዳ በተጠሪዎች ላይ የሚፈለገውን አጠቃላይ ዕዳ የሚሸፍንለት ሆኖ ባለማግኘቱ ቀሪው ዕዳ እንዲከፈለው በመጠየቁ የአፈፃፀም ክስ መስርቶአል፡፡ አመልካች የዋሱን ቤት ሽጦ የሸያጩን ገንዘብ ከእዳ ተቀናሽ የአደረገበት ጊዜ ቀሪ እዳ የሚፈልግ መሆኑን ያረጋገጠበት ጊዜ ነው የሚባል ከመሆኑም በላይ ባለእዳዎች በዚህ ጊዜ እዳውን ለመሸፈን የሚያስችል ንብረት የነበራቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡

ለአፈፃፀም የሚውል የባለእዳ ንብረት ከሌለ አፈፃፀሙ መቀጠል የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329/2/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት የፍርድ ባለእዳውን እንደፍርዱ ለመፈፀም የማይቻል መሆኑን ከአረጋገጠ ፍርዱ እንዲፈፀም ትዕዛዝ እንደማይሰጥ ሆኖም ለመፈጸም ችሎታ በሚያገኝበት በማናቸውም ጊዜ እንዲፈፀም ትእዛዝ ከመስጠት እንደማይታገድ ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 384 ድንጋጌ ልዩ ሁኔታ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 384 ስር የተመለከተው የአስር አመት የጊዜ ገደብ የፍርድ ባለመብት ምንም እንቅስቃሴ ሳያደርግ ቆይቶ ፍርዱን ለማስፈፀም ሲንቀሳቀስ ተፈፃሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡ በሌላ በኩል በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ቡድኑን ለማስመለስ ስልጣን የተሰጠው ባንክ አፈፃፀሙን ራሱ የሚመራው ቢሆንም የባለእዳው መያዣ የሆነ ንብረት ያለመኖሩንና መያዣ በሆነ ንብረት እዳውን መሸፈን ካልቻለ አፈፃጸሙን መቀጠል ያለበት ይህንኑ ከአረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይገባል፡፡ አመልካች በባለእዳው ንብረት ላይ ሕዳር 23 ቀን 1990 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ ለአፈፀፀም ሊቀርብ የሚገባው በአስር አመት በመሆኑ አመልካች ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም በዋናው ባለእዳ ንብረት ላይ አፈፃፀም መቀጠሉ የይርጋ ጊዜውን የሚያቋርጥ ሕጋዊ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም አዲሱ ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው ከሕዳር 23 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ ሳይሆን ከግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ በመሆኑ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንደገና እንደአዲስ የይርጋ ዘመን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1852 መሠረት ሲቆጠር አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአፈጻጸሙን ክስ ያቀረበው ጥቅምት 23 ቀን 2004 ዓ.ም በመሆኑ በሕጉ የተመለከተው የአስር አመት የይርጋ ጊዜ አላለፈም፡፡ ስለሆነም ከግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 21 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ አስር ዓመት አልሞላም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች የይርጋውን ጊዜ ያሰሉት ከህዳር 23 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ የአስር ዓመትን የይርጋ ጊዜ መሠረት በማድረግ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው አልፎአል የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሳቸው በህጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የሆነ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 29879 ሕዳር 19 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 137198 ህዳር 22 ቀን 2004 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ብለናል፡፡ በመሆኑም የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን በተጀመረው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ በአፈፃፀም ክሱ ስረ ነገር ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች የሚያቀርቡለትን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጪ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡-ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አደነ ንጉሴ

አመልካች፡-አቶ ኤርሚያስ ሓይሉ የሆነስት የረር ማኔጂንግ ዳይሬክተር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ብርሃኑ ዳምጠው ወኪል አስፋው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሰረት ያደረገ የጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች እና በአቶ በላይ አያሌው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች የሆነና በስር ሁለተኛ ተከሳሽ በነበሩት በአቶ በላይ አያሌው ይሽከረከር የነበረ የሰሌዳ ቁጥር 3-28569 እና ተሳቢው 3-070339 የሆነ ተሽከርካሪ በኋላ ገጭቷአቸው በቀኝ እግራቸው ላይ ተሳቢው ቆሞባቸው እግራቸውን ከጥቅም ውጪ ያደረገባቸው መሆኑን፣በዚህም ምክንያት አሽከርካሪው በወንጀል ተከሶ የተቀጣ መሆኑን፣በወቅቱ ተጠሪ በግል ድርጅት ተቀጥረው በወር ብር 1500.00 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) እያገኙ ሲሰሩ እንደነበርና ይኸው ገቢ በጉዳቱ ምክንያት የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልጸው ወደፊት ለሰላሳ አመት አመታት ቢኖሩ ሊያገኙ የሚችሉትን የገቢ መጠን በማስላት አጠቃላዩን ደምረው ብር 920,000.00 (ዘጠኝ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስ ለክሱ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን እና የጉዳት ካሳ መጠኑም እጅጉን የተጋነነ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ ግን በሌሉበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን በመኪናው ባለንብረትነቱ ለተጠሪ አካል ጉዳት ኃላፊ በማድረግና የጉዳት ካሳ መጠኑን በተመለከተም የተጠሪ ወርሃዊ ገቢው እንዲጣራ ፍርድ ቤቱ ሲፈልግ አመልካች ትእዛዙን ሊያከብር ባለመቻሉ ታልፎ ተጠሪ በወር 1200.00 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) እንደሚያገኙ ግንዛቤ በመውሰድ ይህንኑ የገቢ መጠን አካላቸው ላይ ደረሰ ከተባለው የ70% (ሰባ ከመቶ) ጉዳት እና ተጠሪ ወደፊት ለሃያ አመታት ሊኖሩ እንደሚችሉ በመውሰድ አስልቶ ብር 201,600.00 (ሁለት መቶ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ብር) ሊሆን እንደሚገባ፣ከዚሁ የጉዳት ገንዘብ ውስጥም ተጠሪ ብር 92,300.00 (ዘጠና ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ብር) በአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከፈላቸው መሆኑን አረጋግጦ ቀሪውን ብር 109,000.00 (አንድ መቶ ዘጠኝ ሺህ ብር) አመልካችና የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የሆኑት አቶ በላይ አያሌው በአንድነትና በነጠላ እዲከፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ብሔረዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ ከዚኅም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2003 ዓ.ም. በዓፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑም ሆነ የጉዳት ካሳ ስሌቱ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ይህ ችሎት እንዲመለከተው የተያዘው ጭብጥ አመልካች ይካስ የተባለውን ገንዘብ አከፋፈል አስመልክቶ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095(2) አንጻር ሲታይ አመልካች በአንድ ጊዜ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ማየት እንዲቻል ሲባል ነው፡፡ ተጠሪ ቀርበውም የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ተገቢነት ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን በመዘርዘር ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊጸና ይገባል ሲሉ ሐምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሳቸውን የሰጡ ሲሆን አመልካችም ነሐሴ 10 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አከፋፈሉ በአንድ ጊዜ እንዲሆን መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095(2) ድንጋጌ አንፃር ለማየት ሲባል ነው፡፡

ተጠሪ በግል ድርጅት ተቀጥረው በስራ ላይ የነበሩ መሆኑና ሲያገኙት የነበረው የገቢ መጠንን ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳቱ ምክንያት ወደፊት ተጠሪ የሚቀርባቸውን ገቢና ከጉዳቱ ጋር ተያይዘው የወጡትን ወጪዎች በመለየትን የካሣ መጠኑን መወሰናቸውን የውሳኔአቸው ይዘት በግልጽ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን ፣መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣2091፣2092 ፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የካሳ መጠን ላይ ይግባኝ የሌለው መሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁር 2152 ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኙ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 ስር ተገልጸዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች በኩል የቀረበውን ቅሬታ መሰረት ስናደረግ በካሳ አተማመኑ ላይ በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ሳይገቡ በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ስለመሠጠቱ የሚያሳይ ነገር ያለ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ አካላቸው በሕገ መንግስቱም ጥበቃ የተደረገላቸው ሲሆን ካሳው ሲወሰንም ይህንኑና ጉዳቱ በአመልካች የወደፊት ኑሮ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው አጠቃላይ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ሊወሰን የሚችል እንጂ ተጠሪ 70% (ሰባ ከመቶ)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳት ቢደርስባቸውም ይሰሩ የነበሩትን ስራ ላለመስራት ወይም ሌላ ስራ ላለመስራት እንቅፋት አይሆንባቸውም በሚል ምክንያት ብቻ ካሳው ሊቀነስ ይገባል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ የሚገዙት የፍትሓብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች መንፈስ የጉዳትን ጠቅላላ ባህርይና የካሣ ልክ አተማመን ሁኔታዎችን ያስገነዝቡናል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ ችግር የሚያደርስ መሆኑን፣ይህም ጥቅም ማቴሪያሊዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራሊዊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጎዳ ሰው ደግሞ መካስ እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ የካሣውን አተማመን በተመለከተም መጠኑ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሁኖ መመዘን ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትን /future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች የጉዳት ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን ሕጉ በግልጽ ከማስቀመጡም በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብነት ሊለያይ የሚችል መሆኑን የሕጉ መንፈስ ያስገነዝባል፡፡

በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን የካሣ አከፋፈሉን ልክ በሚደነግገው የሕጉ ክፍል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በሌላ በኩል የካሣ አተማመን ሥርዓት ጠቅላላ የመሥራት አቅምን /General utility/ ሣይሆን ልዩ ጠቀሜታ/specific utility/ መርህን ቢከተል ፍትሓዊነት ያለው አሠራር መሆኑ ይታመናል፡፡ ይህም አሠራር በተጨባጭ የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የካሣውን ልክ ያላግባብ ላለማጋነንና ላለመቀነስ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ጉዳት መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠና ጉዳቱም በተጎጂው የወደፊት ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለመሆኑ ከተረጋገጠ ካሣ መወሰን ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ አኳያ አግባብነት ያለው ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተ በሕጉ ለዳኞች በተሰጠው ሥልጣን ወይም በጉዳዩ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት በመተመን ለተጎጂው መፍረድ የሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መኖሩን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎችና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2101 እና 2102 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ ውጪ ጉዳቱ መድረሱ እየታወቀ የአሁንና የወደፊት ቁሣዊ ጉዳት /material damage/ ስለመኖሩ ተጎጂው አላስረዳም ተብሎ የመካስ መብት ማሳጣት ከአጠቃላይ ከውል ውጪ ኃላፊነትን ከሚገዛው ሕግ አለማ ጋር አንድ ላይ የሚሄድ አይሆንም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ንብረትነቱ የአመልካች በሆነ መኪና በስር 2ኛ ተከሳሽ ሲሽከረከር ተግጭተው በአካላቸው ላይ 70% (ሰባ ከመቶ) ጉዳት መድረሱ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳቱ ወደፊት ሊጠፋ የሚችል ስለመሆኑም የተገለፀ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የመኪናው ባለንብረት በመሆናቸው፣የስር 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ በጥፋታቸው መሰረት ተጠሪ ካሳ የማይከፈሉበት ምክንያት የሌለ ሲሆን በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰላው የካሳ መጠንም ከላይ የተመለከቱትን የካሳ አተማመን መንገዶችን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው ከሚባል በስተቀር ጉልሕ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደዋናውና በዚህ ችሎት የሕግ ትርጉም ያስፈልገዋል ተብሎ ወደተያዘው ጭብጥ ስንመለስም የጭብጡ መነሻ የካሳው አከፋፈል መንገድ በጡረታ መልክ በየወሩ እንዲከፈል መወሰን ሲገባ በአንድ ጊዜ እንዲከፈል የተወሰነው ያላግባብ ነው የሚለው የአመልካች ቅሬታ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚህም መሰረት ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095(2) ድንጋጌ ሲታይ አርዕስቱ "ስለሞት አደጋና የሚች አንዳንድ የቅርብ ዘመዶች ስላላቸው መብቶች በሚል የተቀመጠ ሲሆን ይዘቱም ሲታይ ለእነዚህ ወገኖች የጉዳት ካሳ አከፋፈልን የሚደነግግ በመሆኑና በዚህ ጉዳይ ደግሞ ተጎጂው ራሳቸው ክስ አቅርበው የጉዳት ካሳ በመጠየቅ ላይ ያሉና በሕይወት ያሉ በመሆኑ የተጠቀሰው ድንጋጌ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2154 ድንጋጌ ሲታይም የጉዳት ካሳ አከፋፈል በአንድ ጊዜ ሊሆን የሚችል መሆን ያለመሆኑን በአቀራረፁና ይዘቱ ለፍርድ ቤቱ ፈቃድ የሠጠ ከመሆኑ አንፃር የካሣው አከፋፈል በጡረታ መልክ ሊሆን ይገባል የሚለው የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 08405 መጋቢት 27 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 106316 ታህሳስ 07 ቀን 2003 ዓ.ም. በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 117820 መጋቢት 09 ቀን 2003 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ተብለው ብር 109,300.00 (አንድ መቶ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ብር) ከአቶ በላይ አያሌው ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 63231

ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዩጵ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነ/ፊጅ ተስፋዩ ኬርጋ ቀረበ

ተጠሪ፡- አቶ ወልደ ሚካኤል ሻንቆ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የካሳ ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረዉ በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔ/ክልላዊ መንግስት በሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ከሳሽነት ነዉ፡፡ የካሳ ክፍያ ክሱን የተመለከተዉ ይሄዉ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በመስማት አመልካች በዘረጋዉ የኤሌክትሪክ መስመር ላይ እሳት በመፈጠሩ ምክንያት በተከሰተ አደጋ በተጠሪ የተለያዩ የሰዉነት ክፍሎች ላይ ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑ፣በዚህም ጉዳት ምክንያት የቀኝ እጁ ያለመንቀሳቀስ ችግር፣የቀኝ ቀለበት ጣት እና ትንሽ ጣት መቆረጥ፣የቀኝ መካከለኛ ጣት፣አመልካች ጣት እና የትልቁ ጣት መድረቅ እና ከአገልግሎት ዉጪ መሆን፣የቀኝ እግር 5ኛ ጣት መቆረጥ እና ስቃይ ደርሷል፤ በተጠሪ ላይ 63% ከፊል አቋም የአካል ጉዳት በመድረሱ እንደድሮዉ የማስተማር ስራዉን ማከናወን ባለመቻሉ፣ ስራዉን በአግባቡ በሚያከናዉንበት ወቅት የወር ጥቅል ደመወዙ ብር 1,692.00 /አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት/ ሁኖ ከዚህ ዉስጥ በእጅ የሚደርሰዉ 1,403.42 ብር /አንድ ሺህ አራት መቶ ሶስት ብር ከአርባ ሁለት ሳንቲም/ በመሆኑ እስከ ጡረታ መዉጫ ዕድሜ ታስቦ፣ የተለያዩ ወጪና ኪሳራ እንደዚሁም የሞራል ካሳን ጨምሮ ባጠቃላይ 139,228.26 /አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ ከሃያ ስድስት ሳንቲም/ አመልካች ድርጅት እንዲከፍለዉ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አሁን የቀረበዉ ቅሬታ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በቀን 07-4-2003 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያላቸዉን ነጥቦች ያነሳ ሲሆን ፍሬ-ሃሳቡ፡- አመልካች ኃላፊ ሊሆን በማይችልበት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ከ2124 እስከ 2136 ድረስ በተዘረዘሩት በሌላ ሰዉ ጥፋት የጉዳት ካሳ እንዲከፍል መደረግ የሌለበት በመሆኑ፣አደጋዉ ሊፈጠር የቻለዉ የከሳሽ ጎረቤት አቶ ማቴዎስ የቴሌቪዥን አንቴና የሰቀሉበት የባህር ዛፍ እንጨት ከሌሊቱ በግምት 9፡15 ላይ በነፋስ ኃይል ተገፍትሮ በአከባቢዉ ከሚገኘዉ የኤሌክትርክ መስመር ላይ ሲወድቅበት ቴሌቪዥኑ ከፍተኛ ድምጽ ሊያሰማ መቻሉ፣ይሄዉ ጎረቤታቸዉ ቤታቸዉ ውስጥ በከፍተኛ ብርሃን ሲሞላ አይተዉ የድረሱልኝ ድምጽ ማሰማቱ፣ተጠሪም በዚህን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወቅት ደርሰዉ መስመሩን ለማላቀቅ ሲሞክሩ የደረሰባቸዉ በመሆኑ ብቻ አመልካች በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2069 መሰረት ኃላፊነት አለበት ሊባል የማይገባ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ዉሳኔ አግባብነት የሌለዉና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ሌላዉ የክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ክስ ሲያቀርብ በየወሩ ያገኝ የነበረዉ ደመወዝ በቀለብ መልክ እንዳይቋረጥበት ዕድሜዉ 70 ዓመት እስኪሞላቸዉ እንዲከፈል ሆኖ እያለ በደረሰዉ ጉዳት መጠን ካሳ እንዲከፍል ውሳኔ መስጠቱ እና ይሰሩበት የነበረዉ መስሪያ ቤት የጡረታ መብታቸዉን እንዲጠብቅ ዉሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለዉ በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ነዉ፡፡

የቀረበዉ ቅሬታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2069 መሰረት በተጠሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት በበታች ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር በሚል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ቀርቦ መልሱን አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የሰጠዉ የመልስ ፍሬ-ሃሳብ፡- የቀረበዉ ቅሬታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያመላክት አይደለም፣ አመልካች ሌላ ሰዉ ባጠፋዉ ጥፋት ኃላፊ ሊሆን አይገባዉም ለሚለዉ ቅሬታ አመልካች በበታች ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባለዉ አመልካች በዘረጋዉ የኤሌክትሪክ መስመር ምክንያት ጉዳት በመድረሱ በዚህ ሁኔታ ዉስጥ ደግሞ ምንም ዓይነት ጥፋት ባይኖርም በሰራዉ አደገኛ ስራ ምክንያት በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2069 መሰረት ኃላፊነት ስላለበት በመሆኑ፣ የካሳ መጠኑን በተመለከተም የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ምክንያት የቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም የሚል ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረበዉ የመልስ መልስ ቅሬታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

በግራቀኙ መካከል የተደረገዉ የክርክር ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም በቅድሚያ እልባት ማግኘት ያለበት ነጥብ የበታች ፍ/ቤቶች በቀረበው ክስ ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የኃላፊነት እና የካሳ መጠን ውሳኔ የሰጡበት ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡

በእርግጥ በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 2027 ስር ከውል ውጭ ኃላፊነት የሚመጡበትን አግባቦች የሚያመለክት ሲሆን በተለይ የዚህ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር ሁለት ስር አንድ ሰው በህጉ ላይ እንደተመለከተው በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስራ ከሰራ ወይም በእጁ የያዘው ነገር በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ኃላፊ እንደሚሆን ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው ኃላፊነት ሊመጣበት የሚችለው ጥፋትን መሰረት አድርጐ ስለመሆኑ ከፍትሐብሔር ህግ ቁ. 2028 እና ተከታዮቹ እንደዚሁም ጥፋት ሳይኖርበት ኃላፊነት ሊመጣበት እንደሚችል ከፍትሐብሔር ህግ ቁ.2066 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ እንደየ ኃላፊነቱ ዓይነት መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የኤሌክትሪክ መስመሩ በራሱ ጉዳት አድርሶ ሳይሆን የጎረቤት የቴሌቪዥን አንቴና በተዘረጋው የኤሌክትሪክ መስመር ላይ በመውደቁ እና ከፍተኛ ድምጽ በዚህ ምክንያት በመፈጠሩ ጎረቤቶቹ የድረሱልኝ ድምጽ በማሰማታቸው አመልካች ለእነዚሁ ጎረቤቶች እርዳታ ለማድረግ ሲሄድ ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት የደረሰበት ስለመሆኑ ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ኃላፊነት አለበት ወደሚለው መደምደሚያ የደረሱት በደፈናው በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 2069 መሰረት አመልካች አውቆ የሰራው ጥፋት ባይኖርም አጥፊ ሳይሆን ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በመጥቀስ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖም አመልካች ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም?፣ ኃላፊነት አለበት ከተባለስ በየትኛው የህግ አግባብ እንደሆነ ድምዳሜ ከመደረሱ በፊት ሊጣሩ የሚገባቸው በርካታ ነጥቦች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ መጣራት ካለባቸው ነጥቦች መካከል በተጠሪ ላይ ጉዳት ሊደርስ የቻለው አመልካች እንደሚለው የተጠሪ ጎረቤት የቴሌቪዥን አንቴና በኤሌክትሪክ መስመሩ ላይ በመውደቁ ምክንያት ነው ወይስ በሌላ ምክንያት?፣ ጉዳቱ ሊደርስ የቻለው በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሆነ፣ አመልካችን ጥፋት ሳይኖር ኃላፊ ሊያደርጉ የሚችሉ አደገኛ ሁኔታዎችን ስለመፍጠሩ የሚያመላክት ነጥብ ስለመኖር ወይም አለመኖር፣ ወይም ጥፋትን መሰረት ያደረገ ኃላፊነት ሊያመጣ የሚችል እና አመልካች በስራው ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄ ሳያደርግ የቀረ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በግራቀኙ ማስረጃ በበታች ፍርድ ቤቶች መንጠር የነበረባቸው ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ሳይነጥሩ በዚህ ጉዳይ የበታች ፍ/ቤቶች ወደ ድምዳሜ መድረሳቸው በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 246፣247 እና ተከታዮቹ እንደዚሁም በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ፣ 259 እና ተከታዮቹ ስር የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ጭብጥ ስለመያዝ፣ ክስ ስለመስማት እና ማስረጃን ስለመመርመር በተመለከተ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ዓላማ፣ ይዘት እና መንፈስ ያላገናዘበ መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ውሳኔ የሰጡት ተገቢው ማጣራት ባልተደረገበት ሁኔታ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ባጠቃላይ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት የኃላፊነት እና የካሳ ክፍያ ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢው መጣራት ሳይደረግበት በመሆኑ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝ/ብሔ/ክል/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.50846 በቀን 24-03-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.06278 በቀን 19-2-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ወደሚለው መደምደሚያ የደረሱት ተገቢውን ማጣራት ሳያደርጉ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አካሄድ አይደለም ብለናል፡፡
3. የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍርድ ሀተታው በተመለከተው አግባብ የቀረበውን ክስ በግራቀኙ ማስረጃ በማጣራት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 69428

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ ነገረ ፈጅ አቶ ነጌሣ አሊ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1- መሐመድ አባ አሊ
2- ዘሀራ አባኑር
} አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ አመልካች እንዲከፍል የሰጡትን ውሣኔ ህጋዊነት አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች ለሞራል ካሣ በድምሩ ከአንድ ሺህ ብር በላይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ አመልካች የተጠሪዎች ልጅ በመሞቱ ምክንያት እንዲከፍል የተወሰነበትን የካሣ ገንዘብ በተመለከተ ለሰበር ችሎት ጭብጥ ሆኖ ያልቀረበ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ የፀናና ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡

የሞራል ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የሚከፈለው የካሣ መጠን በማናቸውም ሁኔታ ከብር አንድ ሺህ ብር /ብር 1000/ መብለጥ የሌለበት መሆኑን "የጉዳት ካሣውም በማናቸውም ምክንያት ከብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ የበለጠ ሊሆን አይችልም" በማለት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2116 ንዑስ አንቀፅ 3 ይደነግጋል፡፡ ይህም በአደጋው ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ብዙ ቢሆንም ለእነርሱ የሚከፈለው የሞራል ካሣ ተደምሮ ከብር 1000/አንድ ሺህ ብር/ ሊበልጥ የማይገባው መሆኑን ያሣያል፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ልጃቸው በአደጋው በመሞቱ ምክንያት ለደረሰባቸው የሞራል ጉዳት ለእያንዳንዳቸው ብር 1000/ አንድ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ አመልካች የሞራል ካሣ እንዲከፍል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2116 ንዑስ አንቀፅ 3 አስገዳጅ ድንጋጌን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ብር 52,200 /ሃምሣ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ብር/ ካሣ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ በድምሩ ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ ብቻ የሞራል ካሣ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሐጂ መሐመድ አመዴ ጠበቃቸው አቶ ብሥራት መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መኮንን መስፍን ጠበቃቸው አቶ ረዳኢ ባራኪ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው በፌ/ከ/ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመብት በሆኑት የአሁኑ ሰበር ተጠሪና 2ኛ የፍርድ ባለ ዕዳ በሆኑት የሰበር አመልካች መካከል በነበረው የአፈፃፀም ክስ የፍርድ ባለእዳው የሆነው ቤት ለእዳው እንዲሸጥ የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡ የፍርድ ባለዕዳው በዋናነት የሚከራከሩት በፍርድ ባለ መብት ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት በአራት ተከሣሾች ላይ ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን /እንዲንከፍል የተወሰነብን በመሆኑ ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ መክፈል የሚገባኝ ብር 250,000 እና የዚሁ ወለድ ነው በሚል ነው፡፡

የፍርድ ባለመብቱ በበኩላቸው ለፍርድ ባለዕዳው ክርክር በሰጡት መልስ እዳው የመጣው በወንጀል ሀላፊነት በመሆኑ ሀላፊነቱ የሚከፋፈል ባለመሆኑ የፍርድ ባለእዳው ድርሻቸውን ብቻ ለመክፈል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡

ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በዋናው ፍርድ የፍርድ ባለዕዳዎቹ ለካሣው ክፍያ ሀላፊነት አለባቸው ስለተባለ የፍርድ ባለእዳው ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የማይጠየቁበት ምክንያት የለም ብሏል፡፡ የፌ/ጠ/ፍርድ ቤትም የፍርድ ባለዕዳው ያቀረቡትን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡

የሰበር አመልካችም በሰበር ቅሬታቸው በዋናነት የጠቀሱት የፍርድ ባለዕዳዎቹ ሀላፊነት ያልተነጣጠለ ነው ከተባለ በዋናው ጉዳይ የተሰጠውን ፍርድ መሠረት ያላደረገ ነው የሚል ነው፡፡ ተጠሪው በበኩላቸው በሰጡት መልስ አመልካች ገንዘቡን ከፍለው ከሌሎች የፍርድ ባለዕዳዎች ከሚጠይቁ በስተቀር በድርሻቸው ብቻ ለመክፈል ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት የለውም ብለዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ያልተነጣጠለ ሀላፊነት ስላለባቸው በአፈጻጸም ክስ የቀረበውን ገንዘብ መክፈል አለባቸው በሚል የተወሰነው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለዚህ አፈፃፀም ክስ መነሻ የሆነውን ፍርድ በመ/ቁ 11789 የሰጠው የፌ/ከ/ፍርድ ቤት ሲሆን የቀበረውም ክስ የአሁኑን የሰበር አመልካች ጨምሮ በመዝገቡ ተከሣሾች የሆኑት በከሣሽ ንብረት ላይ ላደረሱት ጉዳት ብር 1,457,934.50 ባልተነጣጠለ ሀላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንባቸው የሚል ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአሁኑን የሰበር አመልካች ጨምሮ 4 ተከሣሾች ለደረሰው ጉዳት ሀላፊነት አለባቸው በሚል ብር 1,000,000/አንድ ሚሊዮን ብር/ ክሱ ከተመሰረተበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለከሣሽ ይክፈሉ ብሎ መወሰኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይ አመልካች እና በመዝገቡ ሀላፊነት አለባቸው የተባሉ ተከሣሾች ገንዘቡን እንዲከፍሉ ከመወሰኑ በስተቀር አከፋፈሉን በተመለከተ ሀላፊነት አለባቸው የተባለውን የገንዘብ መጠን እያንዳንዳቸው ድርሻቸውን እንዲከፍሉ በሚል በግልጽ ተለይቶ አልተወሰነም፡፡ የአመልካች የክስ አቀራረብም ቢሆን የጉዳቱን መጠን በገንዘብ ተምኖ በማቅረብ ተከሣሾቹ ባልተነጣጠለ ሀላፊነት እንዲከፍሉ የሚል እንጂ የሚፈለግባቸውን ገንዘብ በድርሻቸው ከፋፍለው አልጠየቁም፡፡ በፍ/ህ/ቁ 2155/1/ ብዙ ሰዎች አንድ በሆነ ጉዳይ ለደረሰው ጉዳት ካሣን እንዲከፍሉ የተገደዱ እንደሆነ በአንድነት እያንዳንዳቸው ሀላፊ እንደሚሆኑ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን የካሣው አከፋፈሉም ቢሆን ለበደሉ ተግባር አነሳሽ በሆነው ፣ በዋናው ወንጀል አድራጊና በበደሉ ተግባር ተባባሪ በሆኑ ሰዎች መካከል ልዩነት የማይደረግ መሆኑን በዚሁ በተጠቀሰው ደንጋጌ በንዑስ ቁጥር 2 ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም የሰር ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ባልተነጣጠለ ሀላፊነት በአፈጻጸም የማይገደዱበት ምክንያት የለም በሚል ዕዳውን በድርሻቸው መጠን ለመክፈል ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ማድረጉ ዋናውን ፍርድ መሠረት ያደረገ ከመሆኑም በላይ በፍ/ህ/ቁ 2155 ስለአንድነት ሀላፊነት የተደነገገውን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝም ሆነ የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንኑ በማጽናት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ 56822 በቀን 30/6/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 67086 በቀን 03/09/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ያልተነጣጠለ ሀላፊነት ያለባቸው ስለሆነ የአፈፃፀም ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ሊከፍሉ ይገደዳሉ በሚል የፌ/ከ/ፍርድ ቤትና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የወሰኑት በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ አመልካች ባልተነጣጠለ ሀላፊነት የተወሰነባቸውን ገንዘብ ከከፈሉ በኋላ ከድርሻቸው በላይ የከፈሉትን ገንዘብ ከመጠየቅ ይህ ውሣኔ የሚያግዳቸው አይደለም ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍርድ ቤትን ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ትዕዛዝ ኮሬ አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ነገረ ፈጅ አቶ ገብረ መድህን ባህታ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በንብረት ላይ ለደረሰ ጉዳት በኃላፊነት ስለመጠየቅና የካሣ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ተከራይቶ የንግድ ሥራ የሚያከናወንበት የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03/05 ቁጥር 382 በሆነ ቤት የሚያከናውነው "ዮድ አቢሲኒያ የባህል ምግብ አዳራሽ" የሚል የንግድ ስም የሚጠራ ድርጅት ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም. ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ተከሳሹ /ተጠሪ/ ሊቆጣጠረው በሚገባው የኤሌትሪክ መስመር ላይ የተፈጠረው ብልሽት ባስከተለው ቃጠሎ በንብረቱ ላይ ውድመት ደርሶብኛል፡፡ ስለዚህ ለጉዳቱ ተከሳሽ ኃላፊ በመሆኑ ብር 1,024,563.02 /አንድ ሚሊዮን ሃያ አራት ሺህ አምስት መቶ ስልሣ ሶስት ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ የእሳት አደጋው ደርሶ ንብረቱ ከመውደሙ በፊት የተበጠሰ ኤሌትሪክ የለም፡፡ የቃጠሎው ምክንያት ኤሌትሪክ ስለመሆኑ የቀረበው ማስረጃ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ መስመሩ ሲዘረጋ የንግድ ድርጅቱ አልነበረም ስለዚህ በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባኝም የሚል የፅሑፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ጭብጥ ለመመሥረት እንዲመቸው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አመልካች ተጠሪ ላደረሰው ጉዳት በጥፋት ላይ የተመሠረተ ኃላፊነት አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኤሌክትሪክ መስመሩ ተበጥሶ በከሳሽ ድርጅት ላይ በማረፉ ምክንያት የእሳት ቃጠሎ የተነሳ በመሆኑ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተከሳሽ /ተጠሪ/ በበኩሉ እሳቱ የተነሳው የኤሌትሪክ መስመሩ በመበጠሱ ምክንያት አይደለም፡፡ የኤሌትሪክ መስመሩ ያልተበጠሰ በመሆኑ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለብንም የሚለው የመከራከሪያ ነጥባቸው መሆኑን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም ባቀረቡት የቃል ክርክር አስመዝግበዋል፡፡

አመልካች /ተከሳሽ/ የእሳት ቃጠሎው የተነሳው ተጠሪ /ተከሳሽ/ ከዘረጋው የኤሌትሪክ መስመር መሆኑን ያስረዱልኛል የሚላቸውን የፅሑፍና የሰው ምስክሮች አቅርቧል፡፡ ተጠሪም የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ከዚህ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ /ተጠሪ/ ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? ኃላፊነት አለበት ከተባለ ተከሳሽ ለከሳሽ ምን ያህል ካሣ ሊከፍል ይገባል? የሚሉትን ጭብጦች በመመሥረት፣ ከሳሽ የተከሳሹ ኃላፊነት በጥፋት ላይ የተመሰረተ ነው ብሏል፡፡ የከሳሽ የሰነድ ማስረጃዎች ድርጅቱ የተቃጠለው ከሣሽ በዘረጋው የኤሌትሪክ መስመር መሆኑን ያሣያሉ፡፡ የከሳሽ የሰው ምስክሮችም ቃጠሎም የደረሰው የኤሌትሪክ መስመሩ ተበጥሶ በቤቱ ቆርቆሮ ላይ ከወደቀ በኋላ በተፈጠረው እሳት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ሆኖም ከሳሽ ቃጠሎው የደረሰው ተከሳሽ ሆን ብሎ ወይም በቸልኝነት በፈፀመው ተግባር መሆኑን "የማያስረዱ" በመሆኑ ተከሳሽ ለጉዳቱ በኃላፊነት አይጠየቅም፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ ጥፋት የፈፀመ መሆኑን ስላላስረዳ የተከሳሹን ማስረጃ ታዓማኒነትና ክብደት መመርመር አስፈላጊ አይደለም በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት የእሳት ቃጠሎው የተነሳው አመልካች በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የኤሌትሪክ መስመር ተበጥሶ በቤቱ ጣሪያ ላይ በማረፉ ምክንያት መሆኑን አመልካች በማስረጃ እንዳረጋገጠ በውሣኔው ውስጥ በግልፅ አስፍሯል፡፡ ተጠሪ በባለቤትነት የያዛቸው የሚያዝባቸውና የሚቆጣጠራቸው የኤሌትሪክ መስመሮች በተለያዩ ምክንያቶች ተበላሽተው ወይም ተበጥሰው በሌላው ሰው ህይወትና ንብረት ላይ አደጋ እንዳያደርሱ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የተጠሪ የኤሌትሪክ መስመር አደጋው ከመድረሱ በፊት ደርሶበት አመልካች ሪፖርት አድርጎ ከተጠገነ በኋላ ተጠሪ ያደረገው ጥገና አስተማማኝ ባለመሆኑ ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን አስረድቻለሁ፡፡ ይህም የተጠሪን ቸልተኝነት የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪን ማስረጃ ሣይመዝን ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከፖሊስ ያቀረቡትን ማስረጃ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪ የኤሌትሪክ መስመሩ ባለቤት ስለሆነ ብቻ ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ አይገባም፡፡ የእሳት ቃጠሎው የተነሳው ከተጠሪ የኤሌትሪክ መስመር ሳይሆን በአመልካች ወጥ ቤት በተነሣ የእሳት ቃጠሎ ምክንያት ስለመሆኑ ተጠሪ ሙያዊ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሕግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ግንቦት 19 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርመረናል፡፡ ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰንና የሥር ፍርድ ቤት አግባብነት ያላቸውን የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ተገቢውንና ትክክለኛውን ጭብጥ የመሠረተና የግራ ቀኙን ማስረጃ መዝኖ ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ለመረዳት እንድንችል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 74139 በትዕዛዝ በማስቀረብ ተመልክተናል፡፡

ከላይ የተገለፀውን መሠረታዊ ጭብጥ ተጠሪ የኤሌትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈልና የኤሌትሪክ ኃይል የመሸጥ ተግባር ሲያከናወን በምን ዓይነት የጥራት ደረጃ /quality standard/ ማከናወን አለበት የሚለውን ነጥብ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ ማንኛውም ኤሌትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ የማከፋፈልና የመሸጥ ሥራዎችን እንዲሠራ የተፈቀደለት ድርጅት አዋጅ ቁጥር 86/1989 እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ በሚመለከት የወጡ ሕጐችንና በኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ የተወሰኑትን የጥራት ደረጃዎች በማክበር ሥራውን ማከናወን እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 86/1989 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡ የኤሌትሪክ አቅርቦትን የመስመሮች እና የመሣሪያዎች ደህንነት በሚመለከት አቅርቦት፣ መስመሮችና መሣሪያዎች በተዘረጉበት የአካባቢ ሁኔታዎች የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በቂ ኃይል የመሸከምና የኢንሱሌሽን ብቃት እንደዚሁም በብልሽት ወቅት ሊከሰት የሚችለውን የኤሌትሪክ መጠን የመቋቋም ችሎታና በቂ የመካኒካል ጥንካሬ ደረጃ ሊኖራቸውና በሰው፣ በእንስሳት በንብረት ላይ አደጋ በማያስከትል ሁኔታ ሊገነቡ፣ ሊገጣጠሙ፣ ሊጠበቁና ሊጠገኑ እንደሚገባ አዋጅ ቁጥር 86/1989ን ለማስፈፀም የሚኒስሮች ምክር ቤት ያወጣው ደንብ ቁጥር 49/1991 አንቀፅ 35 የሚደነግግ ሲሆን ማንኛውም ኤሌትሪክ ለመሥራት ለማሰራጨትና ለመሸጥ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ሥራውን ሲያከናውን የሰውን ሕይወት፣ ንብረትና የአካባቢ ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስፈልጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ እንዳለበት በደንብ ቁጥር 49/91 አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች አደጋው ከመከሰቱ በፊት በመስመሩ ላይ ብልሽት ተከስቶ የነበረና ይህንንም ለተጠሪ አመልካችና ሌሎች በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች አሳውቀው ተጠሪ መስመሩን የጠገነ መሆኑን፣ ተጠሪ የጥገና ሥራውን ካከናወነ በኋላ የኤሌትሪክ መስመሩ ተበጥሶ ከአመልካች ድርጅት ቆርቆሮ ላይ በማረፉ የእሳት አደጋ በማስነሳቱ አመልካች መስመሩን በንብረት ላይ ጉዳት በሚያስከትል ሁኔታ የመጠገንና የመጠበቅ ግዴታውን ባለመወጣቱ ንብረቱ ወድሞብኛል፣ ተጠሪ ኃላፊነት አለበት በማለት በቃልና በዕሑፍ ያቀረበ ቢሆንም በቃል ክርክር ወቅት ዋናው የመከራከሪያ ጭብጡ በአመልካች ድርጅት ላይ ውድመት ያስከተለው የእሳት አደጋ በኤሌትሪክ መስመሩ ብልሽት ወይም መበጠስ ምክንያት የደረሰ አይደለም የሚለው ነጥብ እንደሆነ ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም በትራንስክራይበር ማሽን የተቀዳውና በዕሑፍ ተገልብጦ ከሥር ፍርድ ቤት ጋር ከተያያዘው የተጠሪን ክርክር ለመገንዘብ ችለናል፡፡

አንድ ፍርድ ቤት የክርክሩን ጭብጥ የሚመሰርተው ከሳሽ ያቀረበውን የክስ ማመልከቻና ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸውን የዕሑፍ ማስረጃዎች ተከሳሽ ያቀረበውን የመከላከያ መልስና የመከላከያ ማስረጃዎች እንደዚሁም ፍርድ ቤቱ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የቃል ምርመራ ሲያደርግ ተከራካሪዎች ያቀረቡትን ክርክር መሠረት በማድረግ መሆን እንደሚገባው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ድንጋጌዎች በግልፅ ይደነግጋሉ፡፡ አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ለተነሳው የእሳት አደጋ ዋናው መንስኤ አመልካች በአግባቡ ሊጠብቀውና ሊጠግነው ከሚገባው የኤሌትሪክ መስመር የኤሌትሪክ ሽቦ ተበጥሶ በአመልካች ድርጅት የጣሪያ ሽፋን /ቆርቆሮ/ ላይ በማረፉ ነው ወይስ አይደለም?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚለው ነጥብ ላይ ሰፊ ልዩነት ያላቸው መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት በቃልና በፅሑፍ ካደረጉት ክርክር ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ሊመሰርተው የሚገባው ጭብጥ የእሳት አደጋው የተከሰተው በኤሌትሪክ መስመሩ ብልሽትና የኤሌትሪክ ሽቦው ተበጥሶ በአመልካች ድርጅት የጣሪያ ክዳን /ቆርቆሮ/ ላይ በማረፉ ነው? ወይስ በአመልካች ኩሽና በተከሰተ ድንገተኛ የእሳት አደጋ የሚለው ጭብጥ መሆን ነበረበት፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችን ብቻ ሣይሆን ተጠሪ ይህንን ጭብጥ ለማስረዳት ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች መመርመርና ተጠሪ ታህሳስ 24 ቀን 2001 ዓ.ም ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር ማስረጃ ውስጥ ስማቸውን የጠቀሳቸውንና የሰማቸውን ሁለት ምስክሮች ቃል መመርመርና መወሰን ይገባዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ የእሳት አደጋው የተከሰተው ተጠሪ በሚያስተዳድረው የኤሌክትሪክ መስመር ላይ በተከሰተ ብልሽትና የኤሌትሪክ ማስተላለፊያ ሽቦው ተበጥሶ ከአመልካች ድርጅት የጣሪያ ክዳን /ቆርቆሮ/ ላይ በማረፉ ምክንያት ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ፣ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 86/1989፣ በደንብ ቁጥር 49/91 እና የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ ያወጣቸውን የጥራት ደረጃዎች ሙሉ በሙሉ አሟልቶ መስመሩን የመጠገንና የመጠበቅ ግዴታውን የተወጣ መሆኑን የማስረዳት ሸክሙን ተዓማኒነትና ክብደት ያለው ማስረጃ በማቅረብ አስረድቷል ወይስ አላስረዳም? የሚለውን ጭብጥ በመመዘን፣ አመልካች በተጠሪ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ምክንያት ለተከሰተው የእሳት አደጋና በንብረት ላይ ለደረሰው ውድመት ተጠሪ በኃላፊነት ሊጠየቅ ይገባል በማለት ያቀረበውን ክስ መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ ሲገባው፣ የሥር ፍርድ ቤት ትክክለኛውን ጭብጥ ሣይመሰረት፣ ተጠሪ በማስረጃ ዝርዝር መግለጫው ስማቸውን የገለፃቸው ምስክሮች ቃል ሣይሰማና የፍታብሔር የማስረጃ ምዘና መርህን መሠረት በማድረግ ከአመልካችና ከተጠሪ የተሻለና ሚዛን የሚደፋ ማስረጃ ያቀረበው የትኛው ነው? የሚለውን ነጥብ ይዞ የአመልካችና የተጠሪን ማስረጃ ተዓማኒነትና ክብደት ሣይመዝን የአመልካችን ማስረጃ ብቻ በመመርመርና በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ ስለ ጭብጥ አመሰራረት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 246፣ 247 እና 248 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሠረት ያላደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት በፍታብሔር ጉዳይ የተሻለና ሚዛን የሚደፋ ማስረጃ ያቀረበው ጉዳዩን እንዳስረዳ ይቆጠራል የሚለውን የፍታብሔር የማስረጃ አመዛዘን መርህ ያልተከተለና የተጠሪን የመከላከያ ምስክሮች ቃልና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ተዓማኒነትና ክብደት አልመረመረም፣ አልመዘነም፡፡ እንደዚሁም የሥር ፍርድ ቤት በወቅቱ በአካባቢው ተጠሪ የኤሌትሪክ ኃይል የማከፋፈል፣ የማሰራጨትና የመሸጥ ሥራ ሲያከናውን ሊያደርጋቸው የሚገቡ ቴክኒካል፣ ሜካኒካልና ሌሎች የጥንቃቄ መስፈርቶችን ያሟላ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁጥር 86/1989፣ ደንብ ቁጥር 49/1991 እና የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ ያወጣቸውን የጥራት ደረጃዎች መሠረት በማድረግ መመርመርና መመዘን ሲገባው ይህንን ያላደረገ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የፈፀማቸውንና ከላይ የዘረዘናቸውን ስህተቶች ሣያርም ውሣኔውን አፅንቶታል፡፡

በመሆኑም ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ በጉዳቱ በኃላፊነት አይጠየቅም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ድርጅት ላይ የደረሰው የእሳት አደጋ መንስኤ /ምክንያት/ ተጠሪ የሚያስተዳድረው የኤሌትሪክ መስመር ሽቦ ተበጥሶ ከአመልካች ድርጅት ጣሪያ /ቆርቆሮ/ ላይ በማረፉ ነው ወይስ አይደለም? አደጋው የደረሰው የኤሌትሪክ መስመሩ ተቆርጦ በተጠሪ ጣሪያ /ቆርቆሮ/ ላይ በማረፉ ምክንያት ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ፣ ተጠሪ በአካባቢው የኤሌትሪክ ኃይል ሲያሰራጭ፣ መስመሩን ሲዘረጋና እድሳት ሲያደርግ በአዋጅ ቁጥር 86/1989፣ በደንብ ቁጥር 49/1991 እና በኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ የወጡትን የጥራት ደረጃዎች በማሟላት አገልግሎቱን የሰጠ መሆኑንና ተጠሪ ማድረግ የሚገባውን ማናቸውንም ጥንቃቄ ያደረገ መሆኑን የቀረበው ማስረጃ ያስረዳል ወይስ አያስረዳም? ተጠሪ በሕግ የተጣለበትን ግዴታ በአግባቡ የተወጣ መሆኑን ካላስረዳ ለደረሰው ጉዳት ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት በኃላፊነት ይጠይቃል ወይስ አይጠየቅም? ተጠሪ በኃላፊነት ይጠየቃል ቢባል ሊከፍል የሚገባው የካሣ መጠን ስንት ነው? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝና የአመልካችንና የተጠሪን የፅሑፍ ማስረጃና የምስክሮች ቃል በመመርመርና በመመዘን አስፈላጊም ከሆነ የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ ሙያዊ ማብራሪያ እንዲያቀርብ በማድረግ በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
4. በትውስት የመጣው የከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ- 74111

ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የማህደር ኤጀንሲ ባለቤት ወ/ሮ አለምነሽ ኤርሞ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሪት አለም መስፍን ተወካይ ገበየ ደጉ ቀረቡ፡፡
መዝገቡ ያደረው ለውሣኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ክስ የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ከሣሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ ተከሣሽ ከሣሽን ወደ ቤይሩት ለስራ ብር 8000 በማስከፈል የተከች ሲሆን አሰሪዬ ከ3ኛ ፎቅ ወርውራኝ በግራ እግሬ ላይ 30% ዘላቂ ጉዳት ደርሶብኛል፣ በተጨማሪም አሰሪዬ የስድስት ወር ደመወዝ በወር 100 ዶላር ወይም ብር 1300 ያልከፈሉኝ ሲሆን ለህክምና እና ትራንስፖርት እንዲሁም ለምግብ ወጪ አውጥቼያለው፡፡ በመሆኑም ተከሣሽ ለደረሰብኝ ጉዳት ኃላፊ ስለሆነ ወደፊት በወር ብር 130 የቀረብኝ ሆኖ ለ33 ዓመት በጉዳት ምክንያት ያጣሁትን እና ሌሎች ወጪዎችን ጨምሮ ብር 200430 /ሁለት መቶ ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ብር/ ተከሣሽ እንዲከፍል እንዲወስንልኝ የሚል ነው፡፡ በቀረበው ክስ ላይ ተከሣሽ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ ተከሣሽ ብር 8000 /ስምንት ሺህ ብር/ አልተቀበለም፣ ተቀብሎ ቢሆንም ይመልስልኝ ማለት አይችሉም፣ በአሠሪያቸው ያልተከፈላቸው ደመወዝም የለም፣ የስድስት ወራት ደመወዝ በዌስተርን ዩኒየን ለአቶ አያልነህ ገና ተልኳል፡፡ የከሣሽ ደህንነት እንዲጠበቅ ተገቢውን አድርገናል፣ አሰሪዋ ከፎቅ የወረወረቻት ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፣ ተከሣሽም በሰብአዊነት አሣክሜያታለሁ እንደዚሁም ጉዳቱ የደረሰው ከካንሰር በሽታ ጋር በተያያዘ እንጂ በመውደቋ ባለመሆኑ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን በማለት ተከራክራለች፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በመቀበል ጉዳቱ የደረሰው በመውደቋ ምክንያት ስለመሆኑ የቀረቡት ማስረጃዎች አያስረዱም በማለት የተጠየቀውን የጉዳት ካሣ ክስ ውድቅ ሲያደርግ ተከሣሽን ወደ ውጭ አገር ለመላክ በሚል ብር 8000 /ስምንት ሺህ ብር/ በአዋጅ ቁ. 632/2001 መሰረት መቀበል የሌለባቸውን የተቀበሉ በመሆኑ ለከሣሽ እንዲመልሱ እና የከሣሽን ደመወዝ በተመለከተ የስድስት ወራት ደመወዝ ስለመላኩ ማስረጃ ስለቀረበ ሁኖም ግን ከሣሽ የሰራችው ለ11 ወራት በመሆኑ የቀሪዎቹን የ5/አምስት ወራት/ ደመወዝ ተከሣሽ እንዲከፍላት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ተጠሪ በተላከችበት አገር አሰሪዋ ከ3ኛ ፎቅ ላይ ተወርውራ በእግሯ ላይ ጉዳት የደሰረ ስለመሆኑ እና በዚህም ምክንያት በዊልቸር እየተንቀሳቀሰች እንደሆነ ከማረጋገጡ በላይ የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ደግሞ አመልካች ከቤይሩት አገር አስመጡ የተባለው እና ተጠሪ ከጥቁር አንበሣ ሆስፒታል ያቀረቡት የህክምና ማስረጃዎች ሲሆን 30% ቋሚ የአካል ጉዳት የደሰረባት ስለመሆኑ ስለሚያመላክቱ አመልካች ከሰጠችው የምስክርነት ቃል ጋር አንድ ላይ ስንመለከት በአሰሪዋ ከፎቅ ላይ በመወርወሯ ምክንያት ከላይ የተመለከተው ጉዳይ የደረሰባት ስለመሆኑ ያረጋግጣል በማለት 157440/ አንድ መቶ ሃምሣ ሰባት ሺህ አራት መቶ አርባ ብር/ አመልካች ለተጠሪ እንድትከፍል በማለት ክፍያው የሚፈጽምበትን አግባብ በማመላከት እና የሞራል ካሣ ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ በተጨማሪ እንዲከፈላት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙ ክርክር በጽሑፍ ተሰምቷል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊት አለባቸው በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር በሚል በመሆኑ የተያዘው ጉዳይ በዚህ መልኩ ቀደም ሲል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በአሰሪና ሰራተኛ አገናኝ አገልግሎት ሥራ የተሰማራ እንደመሆኑ መጠን የአዋጅ ቁ. 632/2001 አጠቃላይ ንባብ መገንዘብ እንሚቻለው በተለይ ወደ ውጭ አገር ለስራ የሚሄዱ ኢትዮጵያዊያን መብታቸው፣ ድህንነታቸውና ክብራቸው ተጠብቆላቸው ወደ ስራ የሚሰማሩበትን አግባብ ለማመቻቸት በመሆኑ እና ይሄንንም ኃላፊነት መወጣት ያለባቸው በዚሁ ስራ የተሰማሩት እንደአመልካች ዓይነት ድርጅቶች ስለመሆናቸው ያስገነዝባል፡፡ አመልካችም ቢሆን በበታች ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የተጠሪ ድህንነት እንዲጠበቅ ተገቢውን ሁሉ አድርጌአለሁ በሚል እንጂ ኃላፊነት የለብኝም በሚል የቀረበ ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ አሰሪዋ ላደረሰችው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በሚል የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው የደረሰው ቋሚ የአካል ጉዳት ከምን የተነሣ እንደሆነ አመልካች ተጠሪ ባለባት የካንሰር በሽታ እንጂ በመውደቅ የደረሰ አይደለም በሚል ተከራክራለች፡፡ ተጠሪ በበኩሏ ጉዳት የደረሰብኝ አሰሪዬ ከ3ኛ ፎቅ ላይ ስለጣለችኝ የደረሰብኝ ነው በማለት ተከራክራለች፡፡ ይሄን ክርክር በተመለከተ በተለይ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በመውደቋ ምክንያት ቋሚ 30% የአካል ጉዳት የደረሰባት ስለመሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል ወደ ሚለው ድምዳሜ ደርሷል፡፡ ይሄው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ፀንቷል፡፡ በተጠሪ አካል ላይ የደረሰው ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰው በመወድቅ ምክንያት ነው ወይስ በሌላ ምክንያት የሚለውን ክርክር ደግሞ የፍሬ ነገር እንጂ የመሠረታዊ የህግ ስህተት ክርክር ባለመሆኑ በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ሊነሣ የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ የክርክር ነጥብ ላይ ደግሞ የበታች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ጉዳቱ የደረሰው በደረሰባት የመውደቅ አደጋ ምክንያት እንደሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ማስረጃን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመዘን እና ፍሬ ጉዳይን ማጣራት ደግሞ የበታች ፍርድ ቤቶች ስልጣን በመሆኑ እና የዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠታዊ የህግ ስህተት ሲኖር ማቃናት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ. ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10 ስር የተመለከተ በመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች የተደረሰበትን ድምዳሜ እንዳለ የምንቀበለው ይሆናል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት በመውደቋ ሣይሆን በሌላ በሽታ ምክንያት ነው በማለት የምታነሣው ክርክር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ የሚስተናገድ ባለመሆኑ አልፈነዋል፡፡ አመልካችም ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባት ተብሎ ለተጠሪ ካሣ እንድትከፍል መወሰኑ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበትን ምክንያት አላገኘንም፡፡

ባጠቃላይ የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ለደረሰው ቋሚ የአካል ጉዳት አመልካች ኃላፊነት አለባት በማለት ካሣ እንድትከፍል መወሰኑ እና የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይሄንን ውሣኔ ማጽናቱ በአግባቡና የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ. ቁ. 72389 ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ.ም እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 103953 ሐምሌ 06 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ቋሚ የአካል ጉዳት ኃላፊነት አለባት በማለት በፌ/የከፍተኛ እና የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ታህሣስ 2 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉምሩክ

/ቀረጥ/

ግብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 54889

መስከረም 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐቃቤ ህግ አቶ ሽመልስ አበበ

ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ንጉሴ ገብረዋዲቅ - ጠበቃ አቶ አበበ ታዬ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተሻሽሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 64/4 እንደተሻሻለ በመተላለፍ የጋራ ንብረቱ በሆነውና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ የሆነውን መኪና በሹፌርነት እያሽከረከረ እያለ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ በህግ የተከለከለ ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ከቡታጅራ ወደ አዲስ አበባ ለማስገባት ሲሞክር ነሐሴ 1 ቀን 2000 ዓ.ም. ከሌሊቱ ዘጠኝ ሠዓት ሰበታ ከተማ ስለተያዘ የጉምሩክን ህግ የመጣስ ወንጀል ፈፅሟል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ የወንጀሉን ድርጊት አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ተጠሪ ሲያሽከረክረው በነበረው መኪና ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ተጭኖ የተገኘ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ እንዲሁም ወንጀሉ የተፈፀመበት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ የሆነው መኪና የተጠሪው የአቶ ንጉሴ ገ/ዋዲቅ እና የአቶ ጌታቸው ገዛኸኝ የጋራ ሀብት መሆኑን የሚያስረዳ የመኪናውን የባለሀብትነት ማረጋገጫ ደብተርና ከአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የተፃፈ የሰነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በወቅቱ እሱ ወባ ተነስቶበት ታሞ የነበረ መሆኑን ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ከእኔ እውቅና ውጭ የተጫነ መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረና ከመዘነ በኋላ ዐቃቤ ህግ ባቀረበው ክስ የጠቀሰውን አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀፅ 64/4/ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 113/2/ መሠረት ወደ አዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀፅ 74 በመለወጥ ተጠሪ ከላይ የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀፅ 74 እንደተሻሻለው በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቅጣት አስተያየት ከሰማ በኋላ ተጠሪ በሶስት ዓመት እስራት እንዲቀጣና የተያዘው ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ ያለበት የህግ ድንጋጌና የሰጠውን የቅጣት ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 7 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 60/89 እና የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ የተደነገገውን በመተላለፍ በሀላፊነት ይዞ በሚያሽከረክረውና የጋራ ንብረቱ በሆነው መኪና ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ይዞ መገኘቱ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የመጓጓዣያ ሀላፊ የሚለው ሀሳብ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 2/14/ ግልፅ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ድንጋጌ በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት ማንኛውም መጓጓዣያ በጉዞ ላይ እንዳለ እንዲይዝ፣ እንዲቆጣጠር ወይም ሥራውን እንዲመራ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ወኪሉን የሚያጠቃልል መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የተጠሪ አድራጎት በአዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 368/95 በአንቀፅ 64/4/ እንደተሻሻለው የሚሸፍን ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የህጉን ድንጋጌ ግልፅ ይዘት በመተላለፍ ተጠሪ የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 የተመለከተውን በተመላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት ተይዞ የነበረው መኪና ለተጠሪ እንዲመለስለት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀፅ 79፣ አንቀፅ 80/1/ አንቀፅ 81 የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲሻሽልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ታህሣሥ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ መልስ በመኪናው ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ጭኖ ተገኝቷል በተባለበት ዕለት በመኪናው ውስጥ የነበርኩ ቢሆንም እኔ ወባ ታምሜ ስለነበረ ህጋዊ መንጃ ፈቃድ ያለው የመኪና ረዳት ሹፌር አቶ ሀይሉ ቢሰጠኝ መኪናውን ያሽከረክር እንደነበርና ልባሽ ቦንዳ ጨርቁ በመኪናው ላይ መጫኑን የማላውቅ መሆኔን በመከላከያ ማስረጃ አስረድቻለሁ፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ባቀረበው የወንጀል ክስ የጠቀሰውን የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4 ድንጋጌ በመለወጥ በአዋጁ አንቀፅ 74 በተደነገገው መሠረት ጥፋተኛ ብለው የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔና ትዕዛዝ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ማስረጃ ተጠሪ የጋራ ንብረቱ በሆነውና በወቅቱም በሀላፊነት ይዞት በነበረው መኪና ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ጭኖ መገኘቱን የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ አረጋግጧል፡፡ ይህ የተጠሪ አድርጎት በየትኛው የህግ ድንጋጌ ያስጠይቃል የሚለውን ስንመለከት “በማንጓጓው የውጭም ሆነ የውስጥ አካል የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ክልከላ፣ ገደብ ወይም ቁጥጥር የተደረገበትን ወይም የኮንትሮባንድ ዕቃን ሲያንጉዝ ከተገኘ ይህንን የወንጀል አድራጎት ለመከላከል ተገቢነት ያላቸውን ጥንቃቄዎች ሁሉ መውሰዱን ካላሥረዳ ዕቃው ወይም ማንጓጓዣያው መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃው ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥ የማያንስ የገንዘብ መቀጮ እና ከአሥራ አምስት እስከ ሀያ ዓመት በሚደርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እስራት ይቀጣል በማለት በደነገገው በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4 ድንጋጌ የሚሸፈን ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የሥር ፍርድ ቤት የማንንቾርያ ሀላፊነትን የሚደነግገውን የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4 በመጥቀስ አመልካች ያቀረበውን ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2/ በመቀየር ተጠሪ ህገ ወጥ ዕቃዎችን ይዞ ስለመገኘት በሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀፅ 74 ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ የተጠሪን ግዙፍ ተግባር ሞራላዊ ሁኔታ አግባብነት ካለው የህጉ ድንጋጌ ጋር ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/2//ለ-2/ መሠረት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋኝነት ውሣኔ በማሻሻል ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀፅ 64/4 የተደነገገውን በመተላለፍ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ የጋራ ባለሀብት በሆነበት መኪና ሲያስገባ የተያዘ ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኛነት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

የቅጣቱን መጠን በተመለከተ፣ ተጠሪ በሶስት ዓመት እስራት እንዲቀጣና የተያዘው ዘጠኝ ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ እንዲወረስ የበታች ፍርድ ቤቶች ወስነዋል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ከዚህ የቅጣት ውሣኔ በተጨማሪ ተጠሪ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት የአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ ድንጋጌ መሠረት ተጠሪ አቶ ጌታቸው ገዛኸኝ ጋር የጋራ ባለንብረት የሆነበት የሰልዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ የሆነው መኪና ላይ ተጠሪ ያላቸው ድርሻ ሊወረስ እንደሚገባው ከህጉ ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሣኔ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ ላይ ያለው የባለሀብትነት ድርሻ ተወርሶ ለመንግስት ገቢ ሊሆን ይገባል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2/መ/ መሠረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ከአቶ ጌታቸው ገዛኸኝ ጋር የጋራ ባለሀብት የሆነበት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ በመሆነው መኪና ላይ ያለው ድርሻ ለመንግስት ገቢ ሊሆን ይገባል በማለት በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀፅ 64/4 መሠረት ወስነናል፡፡
3. ይኸ ውሣኔ አቶ ጌታቸው ገዛኸኝ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02587/አ.አ/ በሆነው መኪና ላይ ያላቸውን ግማሽ የጋራ ባለሀብትነት የሚነካ አይደለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡-1. አቶ አህመድ ሁሴን
2. አዞ ግሎባል ኃ.የተ.የግል ማህበር
ጠበቆች ወርቅነህ በረደድና ሙሉጌታ ወንድም አገኘሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - ዐ/ህግ ፍስሐ ዓለማየሁ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉምሩክ ወንጀልን ተከትሎ ሊጣል ስለሚገባው ቅጣትና ፍርድ ቤቱ በቅጣት አጣጣል ሊከተለው ስለሚገባው ስርዓት የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾችና በሌሎች አምስት ሰዎች የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93(1(መ) እና (2) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በአመልካቾች አማካኝነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ የተደረገ የባትሪ ድንጋይ ባልተሟላ ሰነድ ቀረጥና ታክስ ሳይከፍሉ ፣ ፍተሻ ሳይደረግ ፣ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይጠናቀቅ በማን እንደተዘጋጀ ባልታወቀ የእቃ መልቀቂያ እንዲለቀቅ በማድረግ የጉምሩክ ማጭበርበር ወንጀል ፈፅመዋል፣ እንዲሁም በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 97 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከላይ የተገለፀውን እቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት እንዲቆይ በማድረጋቸው የጉምሩክ ስነ ሥርዓትን የማሰናከል ወንጀል ፈጸመዋል በሚል በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ክሱን ክደው በመከራከራቸው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካቾች የወንጀል ድርጊቶቹን ስለመፈፀማቸው አቃቤ ሕግ በማስረጃዎቹ ማስረዳቱን ፍርድ ቤቱ በማመን አመልካቾች እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቶ አመልካቾች አሉን ያሏቸውን ማስረጃዎችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች የተከሰሱባቸውን ወንጀሎች ያለመፈጸማቸውን በመካላከያ ማስረጃዎቻቸው አስረድተዋል ፣ በዚህም ምክንያት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አስተባብለዋል በሚል ምክንያት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 149(2) መሰረት ክሱ በነሳ አሰናብቷቸዋል፡፡ ኢግዚብትን በተመለከተ ግን 1ኛ አመልካች በማጭበርበር ስራ ባይሳተፉም እንደባለንብረት ተከታትለው ጉዳዩን ከማስፈጸም አንፃር ያደረጉት ጥረት ስለመኖሩ አላስረዱም በማለት ንብረቱ ሊመለስላቸው የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም ሲል በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 106 መሰረት ለመንግስት እንዲወረስ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የሥር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስና ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3(ሀ)) ስር የተመለከተው መሆኑን በመለየት በስር ፍርድ ቤት ንብረቱ ለመንግስት ውርስ ይሁን ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሕጋዊ መሆኑን በመቀበል ውሳኔን በውጤት ደረጃ አንፅቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካቾች ከወንጀል ተግባሩ ነፃ ተብለው ከተወሰነ በሁዋላ በኢግዚቢትነት የተያዘው እቃ በመንግስት እንዲወረስ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3(ለ)) ድንጋጌ አኳያ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት እንዲታረምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች ከተከሰሱበት ወንጀል ነጻ የተሰናበቱ ቢሆንም በተጠሪ መስሪያ ቤት የነበረው ንብረት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3(ሀ)) መሰረት ሊወረስ ይገባል የመባሉን አግባብነት ከተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 104(3(ለ)) ድንጋጌ አኳያ ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ከሌሎች ሰዎች ጋር በስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበባቸው 1ኛ አመልካች ወደ ሀገር ውስጥ ባትሪ ድንጋይ ለማስገባት በዲክላራሲዮን ቁጥር C-22074 በስር ተከሳሽ በነበሩት የጉምሩክ አስተላላፊ ድርጅትና ሰራተኞች አማካኝት ዲክላራሲዮን ሲቀርብ ለጉምሩክ ባለስልጣን የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ለሚቀርበው ዲክላራሲዮን ጋር አባሪ ሆኖ የቀረበው የእቃ ማስጫኛ ሰነድ(packing list/ ብዛቱ 60,480 ደርዘን ኦሴል ባትሪ ድንጋይ ወደ አገር ውስጥ እንደሚገባ የሚገልፅ ሰነድ ለውጭ ምንዛሪ ማስፈቀጃ ለአቢሲኒያ ባንክ በሚቀርበው 100,800 ደርዘን ኦሴል ባትሪ ድንጋይ ወደ አገር ውስጥ እንደሚገባ አድርጎ በማቅረብ የጉምሩክ ሥነ ሥርአት ያልተፈፀመበትና የቀረጥና ታክስ መጠኑ ብር 278,247.09 (ሁለት መቶ ሰባ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሰባት ብር ከዜሮ ዘጠኝ ሳንቲም) ሳይከፈልበት በ2ኛ አመልካች መጋዘን በተደረገ ብርበራ ብዛቱ 4200 ካርቶን የሆነ ኦሴል ባትሪ ድንጋይ ተከማችቶ በመገኘቱ የጉምሩክ ማጭበርበር ወንጀልና የጉምሩክ ስነሥርዓትን የማሰናከል ወንጀል ተከሰው የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አስተባብለዋል በማለት በነፃ የተሰናበቱ መሆኑን ፣ ለወንጀል ድርጊቶች መሰረት የሆነውን የባትሪ ድንጋይ ግን ለመንግስት እንዲወረስ በማለት የቅጣት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በክፍል አራት በጉምሩክ ሥራ ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች የሚደነግጉ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ይኸው የአዋጁ ክፍል በምዕራፍ አንድ በባለስልጣኑ ሠራተኞች ስለሚፈፀሙ ወንጀሎችና ቅጣታቸው ሲደነግግ በምዕራፍ ሁለት ስር በተለይም ከአንቀፅ 92 እስከ 108 ድረስ በተደነገጉት ድንጋጌዎች በሌሎች ሰዎች ስለሚፈፀሙ የጉምሩክ ወንጀሎችና የቅጣት አይነትና መጠን እንዲሁም ስለፍርዱ ቤቱ ስልጣን የሚደነግግ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት የበታች ፍርድ ቤቶች የቅጣት ውሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 104(3(ሀ)) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት ማድረጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላግባብ ነው ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የአዋጁ አንቀጽ 104(3(ለ)) ስር የተመለከተው ነው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ሁለቱ ንዑስ ድንጋጌዎች ጥፋተኛ ወይም ነጻ የማድረግ ውሳኔ በውርስ ላይ ስለሚኖረው ውጤት በሚደነግገው አንቀጽ ስር ያሉ ሲሆን ተፈጻሚ የሚሆኑበት አግባብ የተለያየ መሆኑን የድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 104(3(ሀ)) ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው የአዋጁን ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የተከሰሰ ሰው በነፃ የተሰናበተ ከሆነ ፍርድ ቤቱ እቃው ወይም ማጓጓዣው የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈፀመበት ስለመሆኑ የቀረበለት ማስረጃ አጥጋቢ ሆኖ ካገኘው የውርስ ትዕዛዝ የሚሠጥበትን አግባብ የሚደነግግ ሲሆን በፊደል "ለ" ስር የተመለከተው ድንጋጌ ደግሞ እቃው ወይም ማጓጓዣው የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈፀመበት ስለመሆኑ የቀረበለት ማስረጃ አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት እቃው ወይም ማጓጓዣው ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰው እንዲመለስ የሚደረግበትን አግባብ የሚደነግግ ነው፡፡ ሁለቱ ድንጋጌዎች ይዘታቸው ሲታይ የሚፈጸሙበት አግባብ እጅጉን የተለያየ ነው፡፡ በጉምሩክ ወንጀል የተከሰሰ ሰው በነፃ የተለቀቀ ቢሆንም ወንጀሉ የተፈጸመበት እቃ ወይም ማጓጓዣ የሚወረሰው የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት ስለመፈፀሙ ፍርድ ቤቱን የሚያጠግብ ማስረጃ ሲቀርብ ሲሆን ማስረጃው አጥጋቢ ካልሆነ ብቻ ፍርድ ቤት እቃውን ወይም ማጓጓዣውን እንዳይወረስ በማድረግ ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ሊያዝ የሚገባው መሆኑን ድንጋጌዎቹ እንደየቅደምተከተላቸው ያሳያሉ፡፡ ለጉዳዩ የቀረበው ማስረጃ አጥጋቢ መሆን ያለመሆኑ ደግሞ ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ለወንጀሉ ክስ መሰረት የሆነው የባትሪ ድንጋይ በአዋጁ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2(1) ስር ስለእቃ የተሰጠውን ትርጉም የሚያሟላ ሲሆን ከአመልካቾች ጋር በስር ፍርድ ቤት ተከሰው በነበሩት የተወሰኑት ሰዎች የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈፀመበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቃቤ ሕግ በስር ፍርድ ቤት የተያዘው ንብረት የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ ባቀረበው ማስረጃ በአጥጋቢ ሁኔታ ማስረዳቱን በውሳኔው ላይ በግልፅ አስፍሯል፡፡ ይህ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ተቀባይነት የማያገኝበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም የማስረጃው አጥጋቢ መሆን ያለመሆኑ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ እንጂ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3(ለ)) ድንጋጌ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር ለወንጀል ድርጊቱ መሰረት የሆነው እቃ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት መሆኑን አቃቤ ሕግ በአጥጋቢ ማስረጃ አስረድቶ በመገኘቱ ፍርድ ቤቶቹ እንዲወረስ ያዘዙ መሆኑን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአዋጅን አንቀጽ 104(3)(ሀ)) ድንጋጌ ለምክንያቱ መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 90364 ታህሳስ 12 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3(ሀ)) ድንጋጌ በመሆኑ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ የሰባተኛው ቀን አደቬንቲስት ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን የአቃቂ አድቬንቲስት ሚሲዮን ት/ቤት - ጠበቃ ዶ/ር ዘውድነህ በየነ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአቃቂ ቃልቲ ክፍል ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት - ዐቃቤ ህግ ቶላኒ ታከለ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍ/ቤት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የቤትና የቦታ ኪራይና ግብር አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት አመልካች 1968 ዓ.ም እስከ 1992 ዓ.ም ያልከፈለው የቦታ ኪራይ የከተማው ቤት ግብርና መቀጮ ብር 734,110.20 /ሰባት መቶ ሰላሣ አራት ሺህ አንድ መቶ አስር ብር ከሃያ ሣንቲም/ እንዲከፈል የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ የሰጠው መሆኑን ገልጾ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግብር ውሣኔውን እንዲያስፈጽም ያቀረበው የአፈጻጸም ክስ ነው፡፡

አመልካች የበጐ አድራጐት ድርጅት በመሆኑ የቦታ ኪራይና ግብር ከመክፈል ነጻ መሆኑን በመጥቀስ ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍ/ቤት ባለመቀበል በመወሰኑና የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና ሰበር ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ በማጽናታቸው ጉዳዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ቀርቦ የስር ፍ/ቤት አመልካች ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ስለመሆኑ ወይም የበጐ አድራጐት ድርጅት መሆኑን አጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ በስር ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42319 ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ በሰጠው መመሪያ መሠረት አመልካች የበጐ አደራጐት ድርጅት ስለመሆኑ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ማህበር ኤጀንሲ ማብራሪያ እንዲሰጥበት በማድረግና አመልካች ከተማሪዎች ወርሀዊ ወይም ዓመታዊ ክፍያና የመመዝገቢያ ክፍያ የሚያስከፍል መሆኑን አመልካች በግቢው ውስጥ ገቢ የሚያስገኙ የተለያዩ የጓሮ አትክልት ልማት የዶሮ እርባታ የከብቶች ወተትና የወተት ተዋጽኦ ገቢ የሚያገኝ መሆኑን ከዚህ በተጨማሪ ከወፍጮ ቤት አገልግሎት ከሱቅና ለስላሣ ሽያጭ ገቢ የሚያገኝ መሆኑን ትምህርት ቤቱ ትፍፋማ ሊሆን የሚችል ቢሆንም ባለው ብልሹ አስተዳደር ምክንያት ትፍፋማ እንዳልሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመግለጽ የኪራይና የቤት ግብር ከመክፈል ነጻ የሚያደርጉ የበጐ አድራጐት ድርጅት መስፈርት አያሟላም፡፡ ብር 611,798.20 /ስድስት መቶ አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከሃያ ሣንቲም/ ለፍርድ ባለመብቱ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ አልተቀበለውም፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርቦ የከተማው የሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

መጋቢት 9 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የአቃቂ አድቬንቲስት ሚስዮን ትምህርት ቤት ህጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም አይደለም፡፡ ትምህርት ቤቱ በንግድ ህግ ቁጥር 5 መሠረት የንግድ ፈቃድ ከንግድ ቢሮ አውጥቶ የተቋቋመ አይደለም፡፡ ስለሆነም ትምህርት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 80/1968 አንቀጽ 14 መሠረት ከግብር ነጻ መሆን ሲገባው በተጠሪ የተወሰነውን ግብር እንዲከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በአፈጻጸሙ ክስ ላይ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ በማለፋ ከሀያ አራት ዓመት በኋላ የቀረበ ክስ በማስተናገድ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 384/1/ የሚጥስ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት ይህ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን ሲመልስለት እንዲጣራ ትዕዛዝ የሰጣቸውን ጉዳዮች በአግባቡ ሣያጣራ የሰጠው ውሣኔ በመሆኑ በትኩረት ሊታይልን ይገባል፡፡ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችን ማህበራት ኤጀንሲ በዚህ ጉዳይ ማስረጃ የመስጠት ስልጣን ያሌለው ሆኖ እያለ በህግ የተሰጠውን ስልጣን በመተላለፍ የሰጠውን አስተያየት መሠረት በማድረግ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህ ተቋሙ ሀይማኖታዊ ተቋም ሆኖ እያለ ተጠሪ የወሰነውን ግብር እንዲከፍል የሰጠውን ውሣኔ እንዲፈጽም የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል ግንቦት 26 ቀን 2003 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የአቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት ከኢትዮጵያ የሰባተኛው ቀን አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን የተለየ ህልውና ያለው የትምህርት ተቋም እንጂ ሀይማኖታዊ ተቋም አይደለም፡፡ የአቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት ከትምህርት ሚኒስቴር ፈቃድ ተሰጥቶት ቁጥራቸው ከሁለት ሺህ በላይ ከሆኑ ተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ ክፍያ በማስከፈል የትምህርት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ በስሙ ስፋቱ 129051 ካሬ ሜትር ቦታ በውል የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ከአራና ከተማ ልማት ቢሮ የተሰጠው ተቋም ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ ከተማሪዎች ከሚያስከፍለው ከፍተኛ ክፍያ በተጨማሪ በይዞታው ሥር ባለ ቦታ ላይ የተለያዩ ምርት እያመረታና የንግድ ስራ እያከናወነ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኝ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ የበጐ አድራጐት ድርጅት አለመሆኑ በአዲስ አበባ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የክትትልና ድጋፍ ክፍል ተረጋግጧል፡፡ ትምህርት ቤቱ ከሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በርቀት የሚገኝ ከመሆኑም በላይ ለአማኞች የተዘጋጀ የጸሎት ማከናወኛ ስፍራ ሣይሆን በሚመለከተው የመንግስት አካል ፈቃድ የተሰጠው የትምህርት ግልጋሎት የሚሰጥና ሌሎች ከፍተኛ የንግድ ስራዎችን የሚያከናውን ተቋም በመሆኑ አመልካች አዋጅ ቁጥር 80/68 አንቀጽ 14 በመጥቀስ የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 384 በመጥቀስ ያቀረበው ክርክርም የድንጋጌውን ይዘት ያልተከተለ ነው፡፡ አመልካች በ1997 በተደረገው ግብር ማሻሻያ መሠረት ተጠሪ ግብሩን አላሻሻልንም በማለት ያቀረበው ክርክር በወቅቱ መሟላት የሚገባቸውን ሁኔታዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች አሟልቶ ያልፈጸመ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቹ ግብር ላለመክፈል ለረዥም ጊዜ ጥረት የሚያደርግ በመሆኑና የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያሌለበት በመሆኑ እንዲያጸናልን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካች ትምህርት ቤቱ የሙያ ፈቃድ ያለው መሆኑ ራሱን የቻለ ህልውና ያለው ተቋም የሚያደርገው አይደለም፡፡ ትምህርት ቤቱ በቤተክርስቲያኑ ስር ያለ ነው፡፡ ቤተክርስቲያኗ ለትርፍ ያልተቋቋመች ናት፡፡ በትምህርት ቤቱ የቅጥር ግቢ የጸሎት ቤት አለ፡፡ አስር ዓመት ያለፈውን ግብር እንድንከፍል መጠየቁ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ ግብር እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በጽሀፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ በወሰነው ውሣኔ መሠረት እንዲፈጽም የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተገቢነው ወይስ አይደለም የሚለው መሠረታዊ ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች ለክርክሩ መሠረት ያደረገው የህግ ድንጋጌ ይዘትና ድንጋጌው አሁን ባለው የህግ ሥርዓት ሊሰጠው የሚገባውን ትርጓሜ መመልከት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች የቦታ ኪራይና የቤት ግብር የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከረው የከተማ ቦታውንና የቤት ግብር ለማስከፈል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 80/1968 አንቀጽ 14 በመጥቀስ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 14 ከኪራይና ከግብር ነጻ ስለመሆን የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን በይዘቱም አንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ 1 ከዚህ የሚከተሉት ከኪራይና ከግብር ነጻ ይሆናሉ፡፡

ሀ/ የህዝብ መንገዶች አደባባዮች መዝናኛዎችና የስፖርት ቦታዎች መካነመቃብር

/ለ/ ጸሎት ቤቶችና ቅጥር ግቢያቸው ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ትምህርት ቤቶችና ሆስፒታሎች የበጎ አድራጐት ድርጅቶች የመዝናኛና የስፖርት ቦታዎች

/ሐ/ ከጠቅላይ ግምጃ ቤት በሚሰጥ በጀት የሚተዳደሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በማለት የሚደነግግ ሲሆን የአንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ 2 የዓመት ኪራይ ግምታቸው እስከ ሶስት መቶ ብር የሆኑ ቤቶች ከግብር ነጻ ይሆናሉ በማለት ይደነግጋል፡፡

ይህ አዋጅ በመጋቢት ወር 1968 ዓ.ም የወጣ ሲሆን ለጸሎት አገልግሎት ለመስጠት ታስበው ከተገነቡ የሀይማኖት ተቋማትና ቅጥር ግቢያቸው ውጭ በሀይማኖት ተቋማት ባለሀብት የሆኑባቸው ሌሎች ህንጻዎችና የንግድ ድርጅቶች የቦታ ኪራይና የቤት ግብር ከመክፈል ነጻ የማያደርግ መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ /ለ/ "ጸሎት ቤቶችና ቅጥር ግቢያቸው" በሚል መንገድ ከገለጸው አገላለጽ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቱን ያቋቋመችው ትርፍ ለማግኘት አይደለም የሚል መከራከሪያ በአመልካች በኩል የቀረበ ቢሆንም አመልካች ትምህርት ቤቱ ያለትርፍ የትምህርት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም መሆኑን የማስረዳት ግዴታና ሀላፊነቱን አልተወጣም፡፡ በአንጻሩ ትምህርት ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠውን ዕውቅና እና ፈቃድ በመጠቀም ከሁለት ሺህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በላይ የሚሆኑ ተማሪዎችን በአገሪቱ ውስጥ በትርፍ የተቋቋሙ የግል ትምህርት ቤቶች ከሚያስከፍሉት ክፍያ የማይተናነስ ከፍያ እየሰበሰበ የሚያስተምርና ሌሎች ትርፍ የሚያስገኙ የንግድና የግብር ተግባራትን የሚያከናውን ስለመሆኑ ተጠሪ በቂ ማስረጃ እንዳቀረበ የስር ፍ/ቤት በውሣኔው በግልጽ አስፍሮታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አዋጅ ቁጥር 80/68 አሁን ያለውን ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ጋር ተጣጥመው ከወጡ ህጐች ጋር ተጣምሮ መተርጐምና ሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡ አዋጅ ቁጥር 80/68 በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 49 እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በየወቅቱ እያሻሻለ ባወጣው የአዲስ አበባ ቻርተር መሠረት የከተማው አስተዳደር ከተሰጠው ህግ የማውጣትና ህግ የማስፈጸም ስልጣን ባገናዘበ መልኩ መተርጐምና ስራ ላይ መዋል ያለበት የህግ ማዕቀፍ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ስናየው በአዲስ አበባ ከተማ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ከአዲስ አበባ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር ውል እየተዋዋሉ የበጐ አድራጐት ተግባራትን የሚያከናውኑ መሆኑንና የአቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት የበጐ አድራጐት ተግባር ለመስራት ከከተማው አስተዳደር ጋር የፕሮጀክት ውል በመዋዋል አገልግሎት እየሰጠ ያለ ተቋም እንዳልሆነ በጽሁፍ ማረጋገጫ የሰጠ መሆኑን ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አዋጅ ቁጥር 80/1968 አሁን በአገራችን ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ስለሚመዘገቡበትና ስራቸውን ሲያከናውኑ ሊደረግ ስለሚገባው ክትትልና ቁጥጥር በዝርዝር የሚደነግገውና የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲን የሚያቋቁመው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣም መንገድ መተርጐምና ስራ ላይ መዋል ያለበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ትምህርት ቤቱ በአሁኑ ወቅት በበጐ አድራጐት ድርጅትነት የተመዘገበ ወይም ያልተመዘገበ መሆኑን የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና የማህበራት ኤጀንሲን መግለጫ መጠየቁ ተገቢና መፈጸም የነበረበት ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ባጠቃላይ ተጠሪ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 80/68 አንቀጽ 14 /ለ/ ከቦታ ኪራይና ከቤት ግብር ነጻ አለመሆኑን አመልካች ተማሪዎችን ክፍያ በማስከፈል የትምህርት አገልግሎት የሚሰጥና ሌሎች ትርፍ የሚያስገኙ ስራዎችን የሚሰራ ተቋም መሆኑን ተጠሪ አስረድቷል፡፡ አመልካች የአቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት ንብረትነቱ የኢትዮጵያ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መሆኑን በመጥቀስ ትምህርት ቤቱ የራሱ የህግ ሰውነት የለውም ከሚል ውጭ ትምህርት ቤቱ ከሌሎች ለንግድ ከተቋቋሙ የግል ትምህርት ቤቶች በተለየ ሁኔታ ነጻ ወይም ትርፍ የማያስገኝ ተግባር ሲያከናውን የኖረ መሆኑን አላስረዳም፡፡

ትምህርት ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር ዕውቅና ፈቃድ አግኝቶ ትውልድ በትምህርት የማነጽ ሀላፊነት እየተወጣ ባለበት ሁኔታና በትምህርት ቤቱ ስም 129051 ካሬ ሜትር ቦታ በይዞታው ስር አድርጐ የሚያዝበትና ለዚህም የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ከከተማው አስተዳደር የተሰጠው መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ትምህርት ቤቱ የራሱ የሆነ ህልውና የሌለው ተቋም በመሆኑና ትምህርት ቤቱ የተቋቋመው በኢትዮጵያ ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በመሆኑ ከቦታ ኪራይና ከቤት ግብር ነጻ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር የአዋጅ ቁጥር 80/68 አንቀጽ 14 /ለ/ ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማና የአዋጁን ድንጋጌ አሁን ካለው ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ጋር ተጣጥሞ ስራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንጻር የቦታች ፍ/ቤቶች የአቃቂ አድቬንቲስት ትምህርት ቤት የቦታ ኪራይ እና የቤት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት የሰጡት የህግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካች የቦታ ኪራይና የቤት ግብር የመክፈል ሀላፊነት ያለበት መሆኑ ከላይ በዝርዝር ገልጸነዋል፡፡ በማስከተል የሚነሳው ጥያቄ አመልካች መክፈል የሚገባው የቦታ ኪራይና የቤት ግብር መጠን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ እንዲከፍል ከወሰነው ግብር ውስጥ የይርጋ ዘመን ያለፈበት አለ በማለት የተከራከረ ሲሆን የስር ፍ/ቤት ይህንን የአመልካችን መቃወሚያ በመቀበል ይርጋው አልፎበታል የሚለውን ገንዘብ ተጠሪ ካቀረበው ጥያቄ ላይ በመቀነስ ይርጋው አላለፈበትም ያለውን ገንዘብ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የይርጋን መቃወሚያ ለማቅረብ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁ. 384 በመጥቀስ የተከራከረ ቢሆንም ይህ ድንጋጌ ፍርድ ለማስፈጸም የተቀመጠ የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚመለከት በመሆኑና ተጠሪ ለአመልካች የግብር ውሣኔ ማስታወቂያውን ከሰጠው በኋላ አስር ዓመት ከመሙላቱ በፊት ተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ያቀረበ በመሆኑ ድንጋጌው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የቦታ ኪራይና የቤት ግብር በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 80/68 እና በህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 36/1968 በተቀመጠው ተመን መሠረት የመሬት ኪራይና የቤት ግብር የመክፈል ሀላፊነት ያለበት ተቋም ወይም ግለሰብ ግብሩን በየዓመቱ የካቲት ሰላሣ ቀን ድረስ እንደሚከፍል በአዋጅ አንቀጽ 8 ተደንግጓል፡፡ በአዋጁ መሠረት የሚከፈለውን ኪራይና ግብር በተወሰነው ጊዜ ያልከፈለ ግለሰብ ቤተሰብ ወይም ድርጅት ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር የኪራዩን ወይም የግብሩን አምስት በመቶ በመቀጫነት እንደሚከፍል ሆኖም መቀጫው ከዋናው ሂሣብ ከሀምሣ በመቶ መብለጥ እንደሌለበት የአዋጅ ቁጥር 80/1968 አንቀጽ 16 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ስንመለከተው አመልካች የቦታው ኪራይ ወይም የቤት ግብር ጥያቄው በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍና መሠረት የሌለው በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት እና ድጋፍ የሌለው በመሆኑና የአዲስ አበባ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ መጣራት የሚገባቸውን በማጣራትና አስፈላጊ ማስረጃዎችን በማስቀረብ የሰጠው ውሣኔ ተገቢ መሆኑን በማረጋገጥ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና የከተማው የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና የከተማው ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዳሽን ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ አዲስ ታደለ ቀረቡ
ተጠሪ፡- አቶ ኑረዲን መሐመድ - ጠበቃ አብራር አደም ቀረቡ
መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በቤት ኪራይ የሚከፈለውን የታክስ ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የፍርድ ባለመብት የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በመሰረቱት የአፈጻጸም ክስ በግልግል ዳኞች ታይቶ የተወሰነው የቤት ኪራይ ይከፈለኝ ጥያቄ እንዲፈጸምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የፍርድ ባለእዳ የሆነው የአሁኑ አመልካች እንደፍርዱ እንዲፈፅም የማይገደድበት ምክንያት ካለው ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም እንደፍርዱ ፈጽሞ እንዲቀርብ በማዘዙ አመልካች ቀርቦ የቤቱን ኪራይ በግልግል ዳኞች ውሳኔ መሰረት ለመፈጸም ፈቃደኛ መሆኑን፣ ነገር ግን ለፍርድ ባለመብቱ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ 2% የተቀናሽ ግብር በመቀነስ ለመክፈል ቢሞክርም ተጠሪ ግብሩ ሊቀነስብኝ አይገባም በማለት ሊቀበሉ ያልቻሉ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግልግል ዳኞች በሰጡት ውሳኔ ተጠሪ ተቀናሽ ግብር መክፈል እንዳለባቸው አልተመለከተም ፣ ማን መክፈል እንዳለበትም አልተጠቀሰም የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ አመልካች ሙሉውን ክፍያ ለተጠሪ እንዲፈፅሙ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 53 እና በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24(2) መሰረት የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት ተቀናሽ የኪራይ ግብር ለማስቀረት ሲንቀሳቀስ ይህንኑ ለማድረግ ውሳኔ አላረፈበትም ተብሎ መወሰኑ ሕጋዊ አይደለም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የበታች ፍርድ ቤቶች በግልግል ዳኞች ውሳኔ አልተሰጠበትም በሚል ምክንያት አመልካች ተቀናሽ የኪራይ ገንዘብ ማስቀረት አይችልም በማለት መወሰናቸው ከአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 53፣ 91 እና 101 ድንጋጌዎች አንጻር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው በሰጡት መልስም አመልካች በግልግል ዳኞች ዘንድ በነበረው ክርክር ተቀናሽ የኪራይ ገንዘብ መኖር ያለመኖሩን ገልፆ ባልተከራከረበትና በግልግል ዳኞች የተሰጠ ውሳኔ በሌለበት ሁኔታ የተጠሪ የኪራይ ግብር ከፋይ መሆኑን የሚያሳይ የግብር ሰብሳቢ ባለስልጣን ማስታወቂያ ሳይኖር ግብሩ ሊቀነስ ይገባል የሚለው የአመልካች ክርክር የፍርድ አፈጻጸም ስርዓቱን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስም የአመልካች ግዴታ ከሕግ የሚመነጭ በመሆኑ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አላረፈበትም ተብሎ በአፈጻጸም መዝገብ የሚታለፍ አይደለም በማለት የሰበር አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተጠሪው በኪራይ ይዞ እንደተገለገለበት እንዲሁም ቤቱም ለአመልካች ጥቅም በአገልግሎት ላይ በመዋሉ ምክንያት አመልካች ለተጠሪ የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍል በግልግል ዳኞች ተወስኖ ይኸው ውሳኔ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት እንዲፈጸምላቸው ተጠሪ የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍተው አመልካች በፍርድ ባለእዳነቱ ቀርቦ ስለፍርድ አፈፃፀም ሲያስረዳ ለተጠሪ ከሚከፍለው ገንዘብ ውስጥ ተቀናሽ ገንዘብ ሁለት ከመቶ (2%) የሚከፈል የኪራይ ገቢ ግብር ያለ ስለመሆኑ ለተጠሪ ገልፆ ቀሪውን ገንዘብ ለተጠሪ ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ቢያሳውቅም ተጠሪ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ጠቅሶ ተቀባይነት ማጣቱን ፣የስር ፍርድ ቤት ግብሩ መከፈል ያለበት መሆኑን አምኖና ተጠሪ ለታክሱ ኃላፊነት የለባቸውም ሳይል የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ያልተቀበለው ውሳኔ አላረፈበትም በሚል ምክንያት ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ፍርድ የሚፈጸመው በሕጉ አግባቡ ፍርድ ያረፈበት ስለመሆኑ ተረጋግጦ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ ውስጥ ተቀናሽ ማስቀረት አለብኝ በማለት የሚከራከረው ለአፈጻጸሙ መሰረት በሆነው የግልግል ዳኝነት ፍርድ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ውሳኔ አርፎበታል በሚል ምክንያት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 53 እና በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24(2) ድንጋጌዎች በሕግ የተጣለብኝ ግዴታ አለ በማለት ነው፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 53(1) በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24(2) ድንጋጌዎች መሰረት ግብር ተቀንሶ ቀሪ እንዲደረግበት ከተወሰነ ማናቸውም ክፍያ ላይ ግብሩን የማስቀረት ግዴታ (Duty of withholding of Income Tax on payments)ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ግዴታ ያለመወጣት ደግሞ በወንጀል ተጠያቂነትን ሊያስከትል እንደሚችል የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 91 እና 101 ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያል፡፡ ግብር ተቀንሶ ቀሪ እንዲደረግበት በሕግ ከተለዩት ክፍያዎች መካከል ደግሞ የህንጻ ኪራይ ገቢ ስለመሆኑ የደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24(2(ሸ)) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ እንዲያስቀር በሕግ ግዴታ የተጣለበት ሰው ግዴታውን ለመወጣት በአፈጻጸም መዝገብ በቀረበው ክርክር ቢያነሳ ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ደግሞ ይህንኑ የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 386(2) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሲታይም የፍርድ ባለእዳ የሆነ ሰው እንደፍርዱ የማይፈጽምበት ሕጋዊ ምክንያት ካለው ይህንኑ እንዲያስረዳ እድል እንዲሰጠው የሚያደርግ መሆኑ ሲታይ የፍርድ ባለእዳው በሕግ የተጣለበትን ግዴታንም ቢያስረዳ እንደፍርዱ ላለመፈጸም በቂና ህጋዊ ምክንያት ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚገባው መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው፡፡ ከሁሉም በላይ የግዴታ ምንጭ ሕግ ፣ በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎችና የፍርድ ቤት ውሳኔ መሆኑ የሚታመን በመሆኑ በሕግ የተጣለውን ግዴታ የፍርድ ቤት ወይም ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን ባለው አካል ታይቶ ፍርድ አላረፈበትም በሚል ምክንያት ውድቅ ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ በሕግ በተጣለበት ግዴታ መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ያስቀረን አካል ከግብሩ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ካለው ገቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጋር ተያይዞ በተነሳው ክርክር ከገቢው ግብሩን ለመቀነስ እንዲችል የተሰጠ ውሳኔ የለም በማለት በአፈጻጸም መዝገብ ግብሩን ሳይቀንስ ሙሉውን ገቢ እንዲከፍል ማስገደድ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታውን ለመወጣት በእጁ ያስገባውን ገንዘብ እንዲለቅ የሚያደርግና በውጤቱ ደግሞ ባለግዴታውን ለአላስፈላጊ ውዝግብ የሚዳርግ ነው፡፡ሲጠቃለልም አመልካች በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት ሲል ያቀረበው ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 53 እና ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 24(2) ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 386(2) ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲታይ ሕጋዊ በመሆኑ በአፈጻጸም መዝገብ ላይ ፍርድ ሳያርፍበት ሊያነሳ አይችልም በማለት የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 170985 ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 98673 ግንቦት 11 ቀን 2003 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 53 እና በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 24(2) የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት የተቀናሽ ሂሳብ ጥያቄን በአፈፃጸም መዝገብ ላይ ቢያነሳ የሚከለከልበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ ውስጥ 2% (ሁለት ከመቶ) ተቀናሽ ገቢ ማስቀረት ይችላል ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 74753

ታህሳስ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡ ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. ሐበሻ የባህል ማዕከልና
የስእል ጋለሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር
2. አቶ በድሩ መዘይን
3. ወ/ሪት መስከረም ጫላ
} - ጠበቃ መስፍን አደሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን ዓቃቤ ህግ - ሽመልስ አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር ተያይዞ የተነሳን የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- 1ኛ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለ በአንቀጽ 50//መ/2// ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከጥቅምት 01 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ በወጣው የህዝብ ማስታወቂያ መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ በመሆኑ ለሚያከናውናቸው ግብይቶች ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በሚወጣ ፊስካል ደረሰኝ መጠቀም ሲገባው በቀን 06/05/2002 ዓ/ም በግምት ከቀኑ 5፡00 ሰዓት አካባቢ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከሚወጣ ደረሰኝ ውጭ በሆነ ደረሰኝ ባለ 8.1 ግራም የሆነ የአገር ውስጥ የአንገት ሐብል በብር 93.15 የድርጅቱ ሰራተኞች በሆኑት ሶስተኛ አመልካች አማካኝነት ግብይት ፈጽሟል በሚል ሲሆን የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ደግሞ የ1ኛ አመልካች ድርጅት ስራ አስኪያጅ ሁነው ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው በአንቀፅ 50/መ(2)/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ 1ኛ አመልካች የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን የመጠቀም ግዴታ እያለበት ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ውጪ ግብይት እንዲከናወን አድርገዋል በሚል ነው፡፡ ሶስተኛ አመልካችም የተጠቀሰውን አዋጅ አንቀጽ 55 እና በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው በአንቀጽ 50/መ/2// ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛ አመልካች ድርጅት ውስጥ የሽያጭ ሰራተኛ በመሆን ሲሰሩ ከሽያጭ መመዝገቢያ ደረሰኝ ውጪ በሆነ ደረሰኝ ባለ 8.1 ግራም የሆነ የሐገር ውስጥ ሀብል በብር 93.15 በመሸጣቸው የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል በሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በሁዋላ በክሱ ላይ ተቃውሞ ያላቸው መሆኑን ገልፀው ፍርድ ቤቱም ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎ ስለድርጊቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃጸም ድርጊቱ መፈጸሙን አምነው ጥፋተኛ አይደለንም በማለት በመከራከራቸው አቃቤ ሕጉ አሉን ያላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ እንዲያሰማ ተደርጓል፡፡ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ቀርበው ሽያጩ ከሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ከሚወጣ ደረሰኝ ውጪ በሆነ ደረሰኝ መከናወኑን በማረጋገጣቸው አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎ አመልካቾች የሰውና የሰነድ ማስረጃዎቹን በመከላከያ ማስረጃነት አቅርበው አስምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካቾች የአቃቤ ሕጉን ማስረጃዎችን ለማስተባበል ያለመቻላቸውን ገልፆ የመከላከያ ማስረጃዎችን ቃል ውድቅ ከአደረገ በሁዋላ አመልካቾችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ክስ መሰረት ጥፋተኛ አድርጎ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችን እያንዳንቸውን በሶስት ወር ቀላል እስራት፣1ኛ አመልካችን ደግሞ በብር 7,000.00 (ሰባት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ/ም የወጣው የሕዝብ ማስታወቂያ የሚመለከተው የወርቅና የብር ጌጣጌጥ የንግድ ፈቃድ ስራ ላይ የተሰማሩትን ነጋዴዎች ሁኖ አመልካቾች የንግድ ፈቃድ ደግሞ የሚመለከተው የባህል እቃዎችንና ስእሎችን መሸጥ በመሆኑ ማስታወቂያው አይመለከተንም የሚል ነው፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ጥቅምት 1 ቀን 2002 ዓ/ም ለሕዝብ የተሰጠ ማስታወቂያ አመልካቾችንም የሚመለከት ነው ተብሎ አመልካቾች ጥፋተኛ ተብለው የመቀጣታቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ቀርቦ በጽሑፍ መልሱ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አመልካቾች ጥፋተኞች ተብለው መወሰኑ ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ሲሆን ቅጣት ጋር ተያይዞ የቀረበው ክርክር በዚሁ ጭብጥ እልባት የሚያገኝ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካቾች በተጠሪ ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌዎች መሰረት የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው ተጠሪ በሕጉ አግባብ አስረድቷል? ወይስ አላስረዳም? የሚለውን ጥያቄን በማንሳት በስር ፍርድ ቤት በአቃቤ ሕጉ ማስረጃዎች ከተረጋገጡት ፍሬ ጉዳዮች እና አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

አመልካቾች ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከሚወጣው ደረሰኝ ውጪ በሌላ ደረሰኝ ግብይት መፈጸማቸውን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ.ም. ለሕዝብ የተሰጠው ማስታወቂያ የንግድ ፈቃዳችንን የሚመለከት አይደለም በማለት ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የአመልካቾች ንግድ ፈቃድ የባህል እቃዎችና የስዕል ውጤቶችን የሚመለከት ቢሆንም ድርጅቱ የባህል ጌጣጌጥና ወርቅ የሚሸጥበት እንደነበረ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ.ም. የወጣው ማስታወቂያ አመልካቾችን ይመለከታቸዋል በሚል ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም አመልካቾች የሚከራከሩበት የንግድ ፈቃድ አመልካቾች የሚሉትን የንግድ ስራ የሚመለከት መሆኑን፣ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ.ም. ለሕዝብ የተሰጠው ማስታወቂያም የወርቅና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የብር ጌጣጌጥ ነጋዴዎችን የሚመለከት መሆኑን እንዲሁም አመልካቾች የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ባይገዙም በእለቱ ለተከናወነው ግብይት ግን ከሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ውጪ በሆነ ደረሰኝ ግብይቱን መፈፀማቸውን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጠው አመልካቾች የወንጀል ተጠያቂያነት አለባቸው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት ማስታወቂያው ይመለከታቸዋል፣ በሚመለከተው አካል ከተሰጠው የንግድ ፈቃድ ውጪ ስራውን ሲሰሩ የተገኙ መሆኑም ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ነው።

በመሰረቱ የአንድ ሰው በወንጀል ተጠያቂነት የሚኖረው ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ነገሮች በአንድነት ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ የወንጀል ሕግ በአንቀፅ 23(2) ስር በግልፅ አስፍሯል። በተያዘው ጉዳይ የአመልካቾች የሐሳብ ክፍል እና ሕጋዊ ተዋጽኦዎች በሚገባ የተሟሉ መሆን ያለመሆኑን መመልከት አስፈላጊ ነው። ከላይ እንደተገለጸው አመልካቾች የተከሰሱት ሽያጩን ከሽያጭ ማሽን በሚወጣው ደረሰኝ መሸጥ ሲገባቸው ከማሽኑ ባልወጣው ደረሰኝ ሸጠዋል በሚል ነው። ለዚህም ተጠሪ ተጥሷል የሚለው የሕግ ማዕቀፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 139/1999 ሲሆን ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌም በደንቡ በአንቀጽ 5(1(ለ)) ስር የተመለከተው ሁኖ ይዘቱም የሽያጭ መሳሪያውን ጥቅም ላይ ሊያውል የሚችለው በመሳሪያው ለመጠቀም የሚያስችለው ፈቃድ ላይ በተመለከተው የንግድ ስራ ብቻ ነው በሚል በግልጽ ተቀምጧል። በዚህ ደንብ ድንጋጌ መሰረትም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን ገዝተው የመጠቀም ግዴታ ያለባቸው ታክስ ከፋዮች በየምድባቸው መሳሪያውን ገዝተው መጠቀም የሚጀምሩበትን የሚያሳይ የጊዜ ሰሌዳ በሕዝብ ማስታወቂያ እንዲወጣ እንደሚደረግ በአስገዳጅነት ደንግጎ ይገኛል። የድንጋጌው ይዘት ሲታይም የሽያጭ መሳሪያውን የመጠቀም ግዴታ ያለባቸው ታክስ ከፋዮች ማስታወቂያው ሲነገራቸው የንግድ ፈቃድ የስራ ዘርፍ በግልፅ ተለይቶ የሚነገራቸው መሆኑን ነው። ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች በወንጀሉ ተጠያቂ የሆኑት የንግድ ፈቃዳቸው ወርቅና የብር ጌጣጌጥ በሚመለከት ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ/ም የወጣው የህዝብ ማስታወቂያ ይመለከታቸዋል ተብሎ ቢሆንም የንግድ ፈቃዱ የሚያሳየው ግን የባህልና የስእል ውጤቶቹን የመሸጥ የንግድ ስራ ፈቃድ መሆኑን ነው። ስለሆነም ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ/ም የወጣው የህዝብ ማስታወቂያ የአመልካቾችን የንግድ ዘርፍ ይመለከታል ለማለት የሚቻል ያለመሆኑን ከደንብ ቁጥር 139/1999 አንቀጽ 5(1(ለ)) እና ከወንጀል ሕጉ አንቀፅ 23(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል። የተጠሪ ማስታወቂያ የአመልካቾችን የንግድ ፈቃድ የሚመለከት ካለመሆኑም በላይ አመልካቾች ሽያጩን የፈፀሙት ከማሽን ባልወጣ ደረሰኝ መሆኑ ሲታይ ደግሞ አመልካቾች ድርጊቱን ለመፈፀም የነበራቸው የሓሳብ ክፍል ከድርጊቱ አፈጻጸም አንፃር ሲታይ የሚገባው እና ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ይዘትም አኳያ ሲታይም ሕጉ የሚጠይቀው መመዘኛ ያልተሟላ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በመሆኑም አመልካቾች ከሃሳባቸው በላይ ሊቀጡ የሚችሉበት አግባብ የለም። ሲጠቃለልም ሕጋዊና ሞራላዊ ነገሮች ባልተሟሉበት ሁኔታ አመልካቾች በወንጀሉ ተጠያቂ መደረጋቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ ይዘት ውጪ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመ ሁኖ አግኝተናል። በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 169689 ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ፣እንዲሁም ሰኔ 24 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ እና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 105743 ህዳር 20 ቀን 2004 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-1)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከቱት ነገሮች ተጣምረው ባልተገኙበት ሁኔታ በወንጀል የሚጠየቁበት ምክንያት አላገኘንም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት ዕ ዛ ዝ

1. አመልካቾች በሌላ ወንጀል የማይፈለጉ ከሆነ ዛሬውኑ ከስር እንዲፈቱ ብለናል፡፡ ለማረ/ቤቱ መፍቻ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ቴዎድሮስ ደበላ ጠበቆች ሽፈራው ጉሌና ተኮላ መሸሻ ቀረቡ
ተጠሪ፡- የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስሥልጣን የልደታ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ተወዳጅ ሲማ ቀረቡ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግብር ሰብሳቢ ባለስልጣን አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ በሚሰጠው የግብር ማስታወቂያ ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ለግብር ጉባኤ ለማቅረብ የተፈቀደውን ጊዜና የጊዜውን ስሌት የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ሚያዚያ 26 ቀን 2002 ዓ.ም አሻሽለው ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ አመልካች በአቤቱታቸው ከ1998 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ ባለው የግብር ዘመን እንዲከፈል የተወሰነብኝ የንግድ ስራ ገቢ ግብር ያላግባብ እና ከአቅሜ በላይ ነው ፣ ይህንኑ ቅሬታ ለተጠሪ መስሪያ ቤት አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ባቀርብም ኮሚቴው ተመሣሣይ ውሣኔ አስተላልፎብኛል በማለት ጉባኤው አመልካችን ያቀረቧቸውን ማስረጃዎችንና የግብር ማህደራቸውን በማስቀረብ ጉዳዩን በመመርመር ፍትሐዊ ዳኝነት እንዲሰጥ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስ የአመልካች ይግባኝ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የቀረበው በሕጉ የተመለከተው የሰላሣ ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከአለፈ በሁዋላ መሆኑን ጠቅሶ በዚህ መቃወሚያ መሠረት ይግባኙ ውድቅ እንዲሆንና ይህ የሚታለፍ ከሆነ ደግሞ ፍሬ ጉዳዩም ተቀባይነት የለውም የሚልባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ጉባኤም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ይግባኙ አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 107/2/1/ በሚደነግገው መሠረት በሰላሣ ቀናት ውስጥ ያልቀረበ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለማስማማት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ እና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሬጅስትራርን በመጥራት ጉዳዩን ከአጣራ በሁዋላ የሰላሣ ቀናት ጊዜ ሳያልፍ አመልካች ይግባኛቸውን ማቅረባቸው ተረጋግጧል በማለት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤን ውሣኔ ሽሮ በፍሬ ነገሩ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩን ለጉባኤው መልሶለታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ችሎቱ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 07 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፉት አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የይግባኝ አቤቱታውን ለግብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ጉባኤ አቅርበው አመልካች የተጠሪ መስሪያ ቤት ሃምሣ ፐርሰንት /50%/ የይግባኝ ማስያዣ እና የዳኝነት ሂሣብ እንዲከፍል የግብር ይግባኝ ጉባኤ ሬጅስትራር አመልካችን ሲያዝዙ አመልካች የተተመነውን ሂሣብ በባንክ ሲፒኦ አሰርተው ካስገቡ በሁዋላ የሲፒኦ ማስረጃ ስለማንቀበል ሲፒኦው ወደ ደረሰኝ መለወጥ አለበት በማለት አቤቱታቸውን ሬጅስትራሩ ባለመቀበላቸው ለተከሰተው የጊዜ ማለፍ አመልካች የሚቀጡበት አግባብ የለም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የይግባኝ ማስያዣና የዳኝነት ሂሣብ በሲፒኦ መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም. አሰርተው ለፋይናንስ ቢሮ መጋቢት 13 ቀን 2002 ዓ.ም. ብር 223,696.52 /ሁለት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከሃምሣ ሁለት ሣንቲም /ለዳኝነት ብር 8303.48/ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ሶስት ብር ከአርባ ስምንት ሣንቲም/ ከፍለው ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በወቅቱ አቅርበው እያለ የጉባኤው ሬጅስትራር ሲፒኦውን ወደ ደረሰኝ መለወጥ አለበት በማለት አቤቱታውን ባለመቀበላቸው የይግባኝ ማቅራቢያ ጊዜ አልፏል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ቀርቦ ግራ ቀኙ በዕሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር በሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ በCPO መጋቢት 10 ቀን 2002 ዓ.ም. በማሰራት ከተጠሪ ቢሮ ሰላሣ ቀን ከማለፉ በፊት ቀርበው የነበሩ መሆኑና ተጠሪ የገቢ ግብር ይግባኝ ለማቅረብ በCPO አመልካች ያቀረቡትን መያዣ ደረሰኝ ቆርጦ 13/07/2002 ዓ.ም የሰጠ ሲሆን የገቢ ግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ በመያዣነት ያቀረቡትን CPO ወደ ደረሰኝ ካልተለወጠ በማለት ሬጅስትራሩ ሳይቀበለው ቀርቶ በ13/7/2002 ዓ.ም ግን ደረሰኝ ቆርጦ የሰጠ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

በመሰረቱ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 107 ድንጋጌ መሠረት አንድ በማንኛውም ግብር /ታክስ አወሳሰን ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ በአንቀፅ ንኡስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር የተቀመጡትን ግዴታዎችን አሟልቶ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኙን ማቅረብ ያለበት መሆኑ በሕጉ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት በአዋጅ አንቀፅ 107/2/ ስር የተመለከቱት ግዴታዎች ግብር ከፋዩ አከራካሪ የሆነውን የግብር መጠን 50% /ሃምሣ ከመቶ/ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ማስያዝ እንደአለበትና ይግባኙንም የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ በደረሰው ወይም በአቤቱታው ኮሚቴ ውሣኔ በተሰጠ በሰላሣ ቀን ወስጥ መቅረብ እንደአለበት የሚያሳዩ ስለመሆናቸው ንኡስ ድንጋጌው በፊደል “ሀ” እና “ለ” ስር ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ የአዋጅ አንቀጽ 108 ድንጋጌ ሲታይም ይግባኙ የቀረበበት ቀን የሚባለው በቀጥታ ለይግባኝ ጉባኤው የቀረበ ሲሆን ይግባኙ ለመዝገብ ቤት የተመዘገበበት ቀን ወይም በሪኮማንዴ የተላከ ሲሆን በፖስታ ቤት የተመዘገበበት ቀን እንደሚሆን አስቀምጧል፡፡

አመልካችም ሆነ ተጠሪ በዚህ የህግ ይዘት ላይ ክርክር የላቸውም፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው አመልካች በጊዜ ገደቡ ይግባኛቸውን አቅርበዋል? ወይስ አላቀረቡም? የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ መያዣው በሚፈፀመበት ሥርአት በCPO አሰርተው ለተጠሪ ጊዜው ከማለፉ በፊት ማቅረባቸው ከተረጋገጠ በCPO ለክፍያ ያቀረበውን ገንዘብ አወራርዶ ደረሰኝ ለመስጠት ተጠሪ በአጋጠመው የአሰራር ወይም ሌላ ችግር ምክንያት ቀናት ወይም ወራት ቢወሰድበት ይግባኝ ባዩ ይግባኝ ለማለት መክፈል ያለበትን ገንዘብ በጊዜው አልከፈለም ሊባል ይገባዋል ወይ? የሚለው ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ከሕጉ አጠቃላይ መንፈስና ዓላማና ሕግ አውጭው ሊያሣካው ከሚፈልገው ግብ አንፃር መመርመርና ውሣኔ ማግኘት አለበት፡፡ ሕግ አውጭው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ የደረሳቸው ሰዎች የውሣኔ ማስታወቂያ በደረሳቸው በሰላሣ ቀን ውስጥ ማስያዝ የሚገባቸውን ገንዘብ 50% /ሃምሣ ከመቶ/ ለግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት በማስያዝ ይግባኝ ማቅረብ እንዳለባቸው በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 107/2ሀ/ ሲደነግግ ግብር ከፋዩ ለግብር አስገቢው መሥሪያ ቤት ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ለማስገደድ እንጅ ገንዘቡ ገቢ ግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ደረሰኝ ሣይሰጥ ቢቆይ በመሥሪያ ቤቱ የአሰራር ችግር ምክንያት የግብር ከፋዩ ይግባኝ የማቅረብ መብቱ እንዲጣበብ በማሰብ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች ተጠሪ ክፍያ የሚቀበልበትን ሥርአት በማሟላት ማለትም በCPO መክፈል አለብህ ተብሎ የተወሰነበትን የንግድ ገቢ ግብር 50% የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ በደረሰው በሰላሣኛው ቀን ማለትም 10/07/2002 ለተጠሪ ገቢ አድርጓል፡፡ ይህም አመልካች ከላይ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ የተወሰነው ጊዜ ከማለፉ በፊት ለተጠሪ ገቢ ማድረጋቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ሰላሣ ቀኑ ከማለፉ በፊት በCPO ገቢ ለሆነለት ገንዘበ ደረሰኝ ቆርጦ የሰጠው ከሶስት ቀን በኋላ ማለትም 13/7/2002 መሆኑ ይግባኝ ለማቅረብ ማስያዝ ያለበትን ገንዘብ አመልካች ከሰላሣ ቀን በኋላ ነው ገቢ ያደረገው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተከሰተውን ችግር አጣርቶ ችግሩ የአመልካች ያለመሆኑን በመደምደም ይግባኝ ጊዜው ያለፈው በአመልካች ችግር አይደለም በማለት የሰጠውን ውሣኔ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የተለየ ፍሬ ነገር ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት በኩል ያሉ የአሰራር ችግሮችና ክፍተቶች መሰረታዊ የሆነውን የአመልካችን ይግባኝ የማቅረብ መብት በማያጣብብ ሁኔታ በመተርጉም የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሣኔ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት መቀበሉ የሕጉን ድንጋጌ አተረጋጉምና ተፈፃሚነት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 14957 ጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14285 ሕዳር 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. የአዲስ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት በመያዣነት መክፈል የሚገባውን ገንዘብ ለተጠሪ ያስያዙ በመሆኑ የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመርና የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሶ መላኩ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አበበ ገ/እግዚአብሔር ጠበቃ ዮሐንስ ዘለቀ ቀረበ

ተጠሪ፡- አራዳ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ዐቃቤ ህግ ተወዳጅ ሲማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፤ የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የንግድ ሥራ ገቢ ግብርን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች የ2000 ዓ.ም የበጀት ዘመን ብር 472,594.89 /አራት መቶ ሰባ ሁለት ሺህ አምሥት መቶ ዘጠና አራት ብር ከሰማኒያ ዘጠኝ ሣንቲም/ ያልተጠራ ትርፍ ያገኘ መሆኑን የሚያሣይ የሒሣብ መዝገብ አቅርቦ ብር 83,507.02 /ሰማኒያ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ የንግድ ሥራ ከፍሏል፡፡ ተጠሪ አመልካች በአመቱ ውስጥ ያገኙት ጠቅላላ ገቢ ብር 5,647,298.90 /አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሥምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ መሆኑን አመልካች ያቀረበው የሂሣብ መዝገብ የሚያሣይ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ አመልካች የተሠማራበት የዕሕፈት መሣሪያ አስመጭነት ሥራ ዘርፍ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ አሟልተው ከገቡበት አሥራ አምስት ፐርሰንት ያልተጣራ ትርፍ የሚገኝ መሆኑ በአዲስ አበባ አስተዳደር ገቢዎች የተጠና ጥናትና የተዘጋጀ ቼክ ሊስት ያለ መሆኑን በመግለፅ በዚሁ ስሌት አመልካች ብር 303,610.71 / ሶስት መቶ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ አስር ብር ከሰባ አንድ ሣንቲም /ያልተጣራ ትርፍ ስላለ በዚሁ ስሌት ግብር እንዲከፍል የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ተጠሪ ለአመልካች ሰጥቷል፡፡

አመልካች ተጠሪ በሰጠው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርቧል፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሰጠውን የገቢ ግብር ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበው አቤቱታቸው ተቀባይነት አልተገኘም፡፡

አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ያቀረብኩት የሂሣብ መዝገብ የዋጋ ማሣነስ ወይም underinvocing የሌለው ነው፡፡ አመልካች የሒሣብ መዝገቡን ተቀብሎታል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ ተጨማሪ ግብር እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 286/94 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጥቅምት 14 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ለሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ ተጠሪ አመልካች ባቀረቡት የሒሣብ መዝገብ ላይ ያሉትን ጥቃቅን ስህተቶች በማረም ውሣኔ የሰጠው የአዋጅ ቁጥር 286/94 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ ቀደም ብሎ በተዘጋጀ መመሪያና ቼክ ሊስት መሠረት በማድረግ አመልካች ተጨማሪ ግብር እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ ያቀረብኩትን የሒሣብ መዝገብ ከተቀበለ በኋላ በተሰማራሁበት የዕሕፈት መሣሪያዎች አስመጭነት ንግድ ዘርፍ ሊገኝ ይችላል ተብሎ በግምት የተዘጋጁ የትርፍ ተመን መሠረት የግብር ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 69/1/ ግብር ከፋዩ ምንም አይነት የሂሣብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሣብ መዝገቡንና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ በዚህ ህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላሣወቀ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወስን ይችላል በማለት ይደግጋል፡፡ ተጠሪ አመልካች በዓመት ውስጥ አስገብቸዋለሁ በማለት በሒሣብ መዝገብ ያሣወቀውን ብር 5,647,298.90 እና ሌሎች የወጪ መግለጫዎች የተቀበለ መሆኑ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ባቀረበው ክርክር አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በበጀት ዓመቱ አግኝቻለሁ በማለት መግለጫ ያቀረበበት ያልተጣራ ትርፍ በዘርፉ ይገኛል ተብሎ በጥናት ከተረጋገጠው እና በመመሪያ ከተወሰነው አማካኝ ያልተጣራ ትርፍ በታች መሆኑን በማገናዘብ ይህንን የሒሣብ ስህተት በማስተካከል የግብር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ የአመልካችን የሒሣብ መዝገብ በከፊል በመቀበልና በከፊል በማስተካከል አመልካች ተጨማሪ የገቢ ግብር እንዲከፍል መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 71 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ጋር የሚቃረን ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም የህጉ ድንጋጌ ተጠሪ አመልካች ያቀረበው የሒሣብ መዝገብ ሙሉ በሙሉ የማይቀበልበት በቂ ምክንያት ካገኘ የአመልካችን የሒሣብ መዝገብ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ግብሩን በግምት የመወሰን ሥልጣን ለተጠሪ ይሰጠዋል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች ያቀረበው የሒሣብ መዝገብ በከፊል ተቀባይነት ያላቸው የሒሣብ መግለጫዎችን የያዘ በከፊል ደግሞ የሒሣብ አያያዝና የአሠራር ስህተት ያለበት ሆኖ ቢገኝ ተጠሪ በሂሣብ አያያዝ የተፈጠሩ ስህተቶችን በማስተካከል የግብር ውሣኔ ከመስጠት የአዋጅ አንቀፅ 69 ድንጋጌዎች የሚገድቡ /የሚከለክሉ/ አይደሉም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንፃር ስንመዘነው ተጠሪ አመልካች በ2000 ዓ.ም የበጀት ዓመት የፅህፈት መሣሪያዎችን በማስመጣት ስላገኘው ጠቅላላ ገቢና ስለሌሎች ወጭዎች ያቀረበውን የሂሣብ መግለጫ ተቀብሏል፡፡ ሆኖም አመልካች በበጀት ዓመቱ ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን የፅሕፈት መሳሪያ በመሸጥ አግኝቸዋለሁ ብሎ በሒሣብ መዝገቡ መዝግቦ የያዘው ያልተጣራ ትርፍ የፅሕፈት መሣሪያዎችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት እንደሚገኝ በጥናት ተለይቶ ከተያዘው አማካኝ ያልተጣራ የትርፍ መጠን ዝቅተኛ ሆኖ በመገኘቱ አመልካች በዓመት ውስጥ ስላገኘው ያልተጣራ ትርፍ ሠርቶ ያቀረበውን የሂሣብ መግለጫ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው ብሎ አልተቀበለውም፡፡ ስለሆነም ያልተጠራ የትርፍ መጠን ለመወሰን የወጣውን መመሪያና ቼክ ሊስት መሠረት በማድረግ የአመልካችን ያልተጣራ የትርፍ መጠን የሒሣብ መግለጫ በማስተካከል አመልካች ተጨማሪ የገቢ ግብር እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 69 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

- የአዲስ አበባ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፤ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
  መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.65041

የካቲት 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ሓጎስ ወልዱ

አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- አቶ አንዳርጌ እሸቱ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስን የሚመለከት ስሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሌሎች ግብረ አበሮች ጋር ፈጽሚል በሚል ከተከሰሰበት አጣቃላይ አራት ክሶች መካከል በሌሎች ሁለቱ ክሶች በነጻ ሲሰናበት በ4ኛ እና 5ኛ ክስ ስር በተመለከቱት የጉምሩክ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 100 ስር ለምርመራ ሳምፕል በማለት አንድ ፓኬት ባትሪ ወስዶ ባለመመለሱ እና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 95/ሀ/ ስር የተመለከተዉን በመተላለፍ ምንም ዓይነት የጉምሩክ አስተላላፊነት ፍቃድ ሳይኖረዉና ከጉምሩክ ባለሥልጣን ፍቃድ ሳያገኝ በክሱ የተመለከቱት ተሸከርካሪዎች የጫኑት የባትሪ ድንጋይ ጭነት የታሸገበትን ፕሎምፕ በመበጠሱ ተከሳሹ በፈጸመዉ እሸጎችን በመፍታት እና ምልክቶችን በማንሳት የወንጀል ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ነዉ በማለት ለሁለቱ የወንጀል ድርጊቶች በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ዉሳኔ በመስጠቱ እና የተሰጠዉም የጥፋተኝነት ዉሳኔ እና የቅጣት ዉሳኔ በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጽናቱ የተፈጸመዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ የቀረበ ነዉ፡፡

አመልካች ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ያላቸዉን ነጥቦች ያነሳ ሲሆን የካቲት 03 ቀን 2002ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ ፍሬ-ሃሳብ፡- ለናሙና የተወሰደን ዕቃ አልመለሰም በማለት በበታች ፍርድ ቤቶች የተላለፈበትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ በተመለከተ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ አሸከርካሪዉ ላደረገለት ትብብር በስጦታ መልክ ሰጥቶት ይዞ የሄደ እንጂ መጀመሪያ ላይ ለናሙና የተወሰዱትን የመለሰ ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ያለአግባብ በመሆኑ፣ በመተላለፍ ላይ ያሉ ወይም የጉምሩክ ወደብ በደረሱ የጭነት ማሸጊያ በመፍታት ወንጀልም ስር የዐቃቤ ህግ ምስክሮች በክሱ በተመለከተዉ መሰረት ያስረዱት ነጥብ ሳይኖር የተወሰነብኝ በመሆኑ እና ባጠቃላይ የቀረቡብኝ ክሶች በበቂ ማስረጃ ያልተረጋገጡ ከመሆኑም በላይ በመከላለከያ ምስክሮች የተከላከልኩ በመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የተላለፈብኝ የጥፋተኝነት ዉሳኔ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የቅጣት ዉሳኔን በተመለከተም ከብዶ የተወሰነ በመሆኑ አግባብነት የሌለዉ ነዉ በማለት የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ ተሽሮ በነጻ እንድሰናበት፤ ይሄ የማይቻል ከሆኑ ደግሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የእስራት ቅጣቱ ቀሎልኝ በገደብ እንድታለፍ በሚል ነዉ፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ግንቦት 6 ቀን 2003ዓ.ም በሶስት ገጽ በተጻፈ የሰጠዉ የመልስ ፍሬ-ሃሳብ፡- አመልካች ጥፋተኛ በተባለባቸዉ ሁለቱም የወንጀል ድንጋጌዎች ስር ባቀረብናቸዉ ምስክሮች የተረጋገጠ እና ያልተከላከለ በመሆኑ የተላለፈበት የጥፋተኝነት ዉሳኔ የሚነቀፍበት አግባብ የሌለ በመሆኑ እና የተላለፈበት የቅጣት ዉሳኔም ስንመለከት እጅግ ያነሰ በመሆኑ የቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘዉ ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች ከተከሰሰባቸዉ የጉምሩክ ወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መካከል በአዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 100 ስር ለናሙና የወሰደዉን ዕቃ ያልመለሰ ስለመሆኑ እና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 95/ሀ/ በተሸከርካሪዉ ላይ ያለዉ ጭነት የታሸገበትን መሸጊያ ስለመፍታቱ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ-ነገር ረገድ ተረጋግጧል፡፡ አሁን በአመልካች እየተነሳ ያለዉ ክርክር የቀረበዉ የዐቃቤ ህግ ምስክር በክሱ መሰረት አላስረዳም የሚል ሲሆን ይሄ ደግሞ የፍሬ-ጉዳይ ክርክር እንጂ የመሰረታዊ የህግ ስህተት ጥያቄ ባለመሆኑ እና ማስረጃን የመመዘን እና ፍሬ-ጉዳይን የማጣራት ስልጣን ደግሞ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ወይም በይግባኝ ያየዉ ፍርድ ቤት በመሆኑ እና የዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሲኖር ማቃናት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ህገ-መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 10 ስር የተደነገገ በመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ-ነገር ረገድ የተደረሰበትን መደምደሚ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ የተረጋገጡትን ፍሬ-ነገሮች ይዘን አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የወንጀል ህግ ድንጋጌ ስንመለከት በአዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 95/ሀ/ መሰረት ማንኛዉም ሰዉ አግባብ ካለዉ የባለስልጣኑ ሹም ፈቃድ ሳያገኝ በመተላለፍ ላይ ያሉ ወይም የጉምሩክ ወደብ በደረሱ ወቅት የዕቃዎች መያዣ ላይ የተደረገዉን ማሸጊያ የፈታ ወይም ያላቀቀ እንደሆነ በዚህ ድንጋጌ ስር የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠዉን ፍሬ-ነገር ስንመለከት የአመልካች ድርጊት የወንጀል ኃላፊነቱን ሊያቋቁም የሚችል ተግባር የፈጸመ ስለመሆኑ ከድንጋጌዉ ይዘት መገንዘብ ስለሚቻል በዚህ የወንጀል ህግ ስር አመልካች ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡ ሌላኛዉን የወንጀል ኃላፊነት በተመለከተ አዋጅ ቁ 622/2001 አንቀጽ 100 ን ስንመለከት ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ ለናሙና የወሰደዉን ዕቃ ያልመለሰ ወይም በዕቃዉ የተገለገለ ወይም ዕቃዉ እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ በማለት የሚደነግግ ሲሆን አመልካችም በዚሁ መልኩ ለናሙና የወሰደዉን ዕቃ ሳይመልስ የቀረ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ-ነገር ረገድ የተረጋገጠ ነጥብ በመሆኑ የወንጀል ኃላፊነቱን ሊያቋቁሙ የሚችሉ ተግባራትን የፈጸመ ስለመሆኑ ከተረጋገጡት ፍሬ-ነገሮች እና የወንጀል ድንጋጌዉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ መሰረት በዚህ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡ በአመልካች ላይ የተላለፈዉን የቅጣት ዉሳኔ በተመለከተም በቅጣት አጣጣሉ ሂደት የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያመላክት ነጥብ ባለመኖሩ በዚህ ዙሪያ የተነሳዉን ቅሬታም አልተቀበልነዉም፡፡

ባጠቃላይ በአመልካች ላይ የተላለፈዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ በአግባቡ እና የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተዉን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉ ሳ ኔ

1. የፊ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ ቁ.91025 ጥር 20 ቀን 2003ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እና የፊ/የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ. 155110 በቀን 8-6-2002ዓ.ም እና በቀን 22-6-2002 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.195(2(ለ(2))) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. በአመልካች ላይ የተላለፈዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡

3. የበታች ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ የጸና ስለመሆኑ ለሚመለከተዉ ማረሚያ ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. ጀሪኮ ሰርቪስ - ደሳለኝ መስፍን ቀረቡ

2. አቶ ሀሰን አብደላ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአንደኛው አመልካች ላይ የወሰነው የገንዘብ መቀጮ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአንደኛ አመልካች ላይ ያቀረባቸውን ሶስት የወንጀል ክሶችና የተጠሪን ማስረጃዎችና የአንደኛ አመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ አንደኛ አመልካች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከጥቅምት 1 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ከተመዘገበ በኋላ እስከ ሰኔ 2000 ዓ.ም. ለተከናወነው ግብይት መክፈል የሚገባውን ለብር 161,870.13 ተጨማሪ እሴት ታክስ ባለመክፈሉ የአዋጅ ቁጥር 255/94 አንቀጽ 49 በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ እንደዚሁም አንደኛ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀፅ 50/መ/1 እና የወንጀል ሕግ አንቀፅ 34 በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 በመተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት ወንጀል ለሚፈረድበት የአምስት ዓመት ፅኑ እስራት ወደ ገንዘብ በመለወጥ ብር 100,000 እንዲቀጣ፣ እንደዚሁም አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀፅ 50/መ/1 በመተላለፍ ጥፋተኛ በሆነበት ወንጀል ከሚወሰንበት ቅጣት ብር 50,000፣ ለሁለቱ ወንጀሎች ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ መቀጮ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ አንደኛ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተከሰሰበት ግብር ባለመክፈል ወንጀል በነፃ መሰናበት ተገቢ አይደለም፡፡ እንደዚሁም የበታች ፍርድ ቤት በጣምራ የገንዘብ መቀጮ መወሰን ሲገባው ሳይወሰን ማለፉ ተገቢ አይደለም በማለት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን አመልካቾች የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔውን በመቃወም ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችንና የተጠሪን ይግባኝ መዛግብት በማጣመር የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካቾች ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ አንደኛ አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 የእስራት ቅጣት ብቻ ሣይሆን የገንዘብ መቀጮ የሚደነግግ ነው በማለት የቀረበውን ይግባኝ በመቀበል የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 45 መሠረት በማድረግ የገንዘብ ቅጣቱን አስልቶ አንደኛ አመልካች ብር 604,546.74 /ስድስት መቶ አራት ሺህ አምስት መቶ አርባ ስድስት ብር ከሰባ አራት ሣንቲም/ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አንደኛ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ወደ ይግባኙ የሚያስገባ በቂ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመግለፅ የአመልካችን ይግባኝ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አንደኛ አመልካች የሰበር አቤቱታው በሰበር ማጣሪያ ችሎት ውድቅ ከተደረገው ከሁለተኛ አመልካች ጋር ሚያዝያ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. በጋራ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ሆኖ ባልተገኘበት የሕግ ድንጋጌ ቅጣት የወሰነበት መሆኑን የገለፀ ሲሆን በተለይ ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 በመተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው በእስራት ቅጣት ብቻ እንደሚቀጣ የሕጉ ድንጋጌ በግልፅ ደንግጎ እያለ ድንጋጌው በጣምራነት ገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጣ አድርጎ የተረጎመው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግልፅ የሆነውንና ትርጉም የማያስፈልገውን የሕግ ድንጋጌ በመተርጎም በአስተዳደራዊ ቅጣት ሊወሰን የሚገባውን የገንዘብ መቀጮ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ሊከፍለው የሚገባው የወንጀል መቀጮ ነው በማለት የገንዘብ ቅጣቱን የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 45 መሠረት በማስላት የሰጠው ውሣኔ የሕጋዊነት መርህን የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ድንጋጌ በአቀራረፅም ሆነ በይዘቱ ጥፋተኛው በእስራት ቅጣት ብቻ ሣይሆን በመቀጮ የሚቀጣ መሆኑን የሚደነግግ ነው በማለት ሰኔ 9 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ ማለትም አንደኛ አመልካች በእስራትና በመቀጮ እንዲቀጣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 285/1994 አስራ ሶስት ክፍሎችና 66 አንቀፆች ያሉት መሆኑን የአዋጁን ድንጋጌዎች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አቀራረፅና አደረጃጀት ስንመለከት አዋጁ በአስራ ሶስት ክፍሎች የተደራጀ ነው፡፡ የአዋጁ ክፍል አንድ ትርጓሜና ሌሎች ጠቅላላ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን የአዋጁ ክፍል ሁለት ታክስ ስለመጣልና ከታክስ ነፃ ስለሚሆኑ ግብይቶች ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ ክፍል ሶስት ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የሚከናወኑበት ቦታ ጊዜና ዋጋ ገኖርነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የያዘ ነው፡፡ ክፍል አራት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች እሴትና የገቡበትን ጊዜ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዙ ሲሆን ክፍል አምስት ስለምዝገባ የሚደነግጉ ድንጋጌዎችን የሚደነግግ ነው፡፡

የአዋጁ ክፍል ስድስት ስለታክስ ስሌት የሚደነግጉ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ክፍል ሰባት ስለተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደራዊ ሥርዓት ገኖርነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ያካተተ ሆኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እናገኘነዋን፡፡ የአዋጁ ክፍል ስምንት የታክስ አሰባሰብና አፈፃፀም የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን፣ በክፍል ዘጠኝ ስለ ሂሳብ ሰነዶች በክፍል አስር ይግባኝ ስለሚቀርብበት ሥርዓት ገዥነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ይዟል፡፡ የአዋጁ ክፍል አስራ አንድ ስለ አስተዳደራዊ ቅጣቶች በሚደነግጉ ድንጋጌዎች የተዋቀረ ሲሆን ክፍል አስራ ሁለት የወንጀል ጥፋቶችን የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡ የአዋጁ ክፍል አስራ ሶስት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የሚደነግግ ነው፡፡

አከራካሪው አንቀፅ 49 በአዋጁ በአስራ ሁለተኛው ክፍል ውስጥ የተደነገገ ድንጋጌ ሲሆን ይዘቱን ስንመለከተው “ሕጉን በመጣስ ታክስ ስላለመክፈል” የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል፡፡ ድንጋጌው “ሕግን በመጣስ የተሰበሰውን ታክስ ያላሳወቀ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ ወይም መንግስትን ለማጭበርበር በማሰብ የማይገባውን ተመላሽ ታክስ የጠየቀ ማንኛውም ሰው ወንጀል እንደፈፀመ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም በዚህ አዋጅ ክፍል አስራ አንድ መሠረት ከሚጣልበት በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት ይቀጣል” በማለት ይደነግጋል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ድንጋጌ የእንግዚኛ ቅጅ A person who evades the declaration of payment of tax, or a person who, with intention to defraud the government; applies for refund he is not entitled to, commits an offence and, in addition to any penalty under section 11, may be prosecuted and on conviction, be subject to a term of imprisonment of not less than five/5/ years” የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ከላይ የተገለፀው የአዋጅ አንቀፅ 49 ድንጋጌ ሕግን በመጣስ የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቀ፣ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ ወይም መንግስት ለማጭበርበር በማሰብ የማይገባውን ተመላሽ ታክስ የጠየቀ ሰው በክፍል አስራ አንድ የተዘረዘረውን አስተዳደራዊ ቅጣት የሚያስቀጣ ፍታብሔራዊ ጥፋት የፈፀመ መሆኑ በተጨማሪ ወንጀል እንደፈፀመ የሚቆጠርና በወንጀልም ተጠያቂ እንደሚሆን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ ሆኖም አንቀፅ 49 ድንጋጌን በመተላለፍ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ላይ የሚጣለው የወንጀል ቅጣት ከአምስት ዓመት የማያንስ የእስራት ቅጣት መሆኑን ድንጋጌው “በመሆኑም በዚህ አዋጅ ክፍል አስራ አንድ መሠረት ከሚጣልበት በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት ይቀጣል” በማለት የደነገገውንና በእንግሊዝኛ ቅጅ “in addition to any penalty under section 11, may be persecuted and on conviction to subject to the term of imprisonment not less than five years” ከሚለው የድንጋጌው አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት እንችላለን፡፡

የታክስ አሰባሰብ ሥርዓቱን በሚያስተዳድረው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በአዋጁ ክፍል አስራ አንድ ከአንቀፅ 45 እስከ አንቀፅ 47 የተደነገጉትን አስተዳደራዊ ቅጣቶች ለመወሰንና ለማስከፈል ግብር ከፋዩ በአዋጁ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልተወጣ መሆኑን በማረጋገጥ የሚወስነው ሲሆን አስተዳደራዊ ቅጣቱን ለመወሰንና ቅጣቱን ለማስፈፀም የግብር ከፋዩ በወንጀል መከሰሱና በፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግብር ከፋዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደር ሥርዓት የሚደነግጉ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሥልጣን ባለው የመንግስት መሥሪያ ቤት በአዋጁ በክፍል አስራ አንድ ከተደነገጉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች በአንደኛው ወይም በሁሉም የተቀጣ መሆኑ፣ በዚያው ጉዳይ የሚቀርብበትን የወንጀል ክስና ቅጣት የማያስቀርለት መሆኑን አንቀፅ 49 ግልፅ የሚያደርግ ድንጋጌ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ቁጥር 49 ግብር ከፋይ በአዋጅ ክፍል አስራ አንድ ከተደነገጉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች በአንደኛው ወይም በሁሉም መቀጣቱ በወንጀል ከመከሰስና ተጠያቂ ከመሆን የማያስቀር መሆኑን ከሚደነግግ ውጭ በአንቀፅ 49 ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ሰው ላይ የወንጀሉን ጉዳይ ያየው ፍርድ ቤት ጥፋተኛውን ከአምስት ዓመት በማያንስ የእስራት ቅጣትና በአዋጅ ክፍል አስራ አንድ የተደነገገውን የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ውሣኔ መስጠት የሚችል መሆኑን የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ አለመሆኑን ከላይ በዝርዝር ያየነው የአዋጁን አወቃቀር የድንጋጌውን አቀራረፅና ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡

ፍርድ ቤት በሕግ በግልፅ ከተደነገገው በቀር የወንጀል ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን መወሰን እንደማይችል በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 በሁለተኛው ፓራግራፍ ተደንግጓል፡፡ ችሎቱ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3 በሚደነግገው መሠረት ድንጋጌውን አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ሲያውጅ ሕግ አውጭው ሊደርስበት ያሰበውን ግብና የድንጋጌውን መንፈስና ዓላማ ለመረዳት የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዋጅ ቁጥር 285/94 ከማወጁ በፊት በረቂቅ አዋጁ ላይ ውይይት ያደረገበትን ቃለጉባኤ በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡ የሕግ አውጭ ምክር ቤት ውይይት ቃለ ጉባኤ የሚያስረዳው ሕግ አውጭው በፍርድ ቤት የሚወሰኑ ቅጣቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶችና ውሣኔዎችን የማጣመር ሀሳብና ፍላጎት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ሕግ አውጭው ሕጉን ሲያወጣ ባደረገው ውይይት አስተዳደራዊ ውሣኔዎችና ቅጣቶች በተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የራሱ የሆነ ድርሻና ዓላማ ያለው፣ በፍርድ ቤቶች ከሚወሰኑ ውሣኔዎችና ቅጣቶች ጋር ሳይያያዝ መታየት የሚገባው መሆኑን የሚያከራሩ ሀሳቦች እንዳሉበት ተረድተናል፡፡ ስለሆነም አንቀፅ 49 “በዚህ አዋጅ ክፍል አስራ አንድ መሰረት ከሚጣልበት በተጨማሪ” የሚለው ቃል ወይም በእንግሊዝኛው “in addition to any penalty under section 11” የሚለው አገላለጽ ግብር ከፋዩን በአዋጁ ክፍል አስራ አንድ ከተዘረዘሩት አስተዳደራዊ ቅጣቶች በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ቅጣቶች መቀጣቱ በወንጀል ከመከሰስና ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት መቀጣቱን የማያስቀርለት መሆኑን ለማሣየት የገባ እንጅ፣ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ከአምስት ዓመት በማያንስና በአዋጁ ክፍል አስራ አንድ መሠረት እየተሰላ በመቀጮ የሚቀጣ መሆኑን ለመደንገግ የገባ አለመሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ የገለፅነውን አተረጓጎም ሕግ አውጭው የገንዘብና የእስራት ቅጣትን በጣምራ ሲደነግግ፣ ድንጋጌዎቹን ለመቅረፅ የተጠቀመባቸውን የሕግ አቀራረፅ ጭብጦች የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ ሕግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 50 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/...ከአንድ ሺህ ብር በማያንስ ከብር ሃያ ሺህ በማይበልጥ መቀጫና ከአንድ ዓመት በማያንስ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡ በአንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ 2/ለ/...ከብር ሃያ ሺህ በማያንስና ከብር መቶ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከሶስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል” በማለት የገንዘብ መቀጮውንና የእስራት ቅጣቱን በጣምራ የሚወስኑ ቅጣቶች መሆናቸውን በግልፅ በማስቀመጥ ከተጠቀመባቸው የሕግ አቀራረፅ ጥበቦች ለመረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ከእስራት ቅጣት ጋር በጣምራ ጥፋተኛው በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ የሚደነግግ ድንጋጌ ነው በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉም የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 የድንጋጌውን አቀራረፅ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ እንደዚሁም ሕግ አውጭው ሊያሣካው የፈለገውን ግብ ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰራውን የሕግ ስህተት ሳያርም ማለፉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 የሰጡት የሕግ ትርጉምና ለሕጉ የሰጡትን ትርጉም መነሻ በማድረግ የወሰኑት የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአንደኛው አመልካች ላይ የሰጡት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በአንደኛው አመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አንደኛው አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘባቸው ወንጀሎች ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ መቀጮ ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡
4. አንደኛው አመልካች በቁጥር 3 ከተወሰነው መቀጮ ውጭ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጨምሮ የወሰነውን ብር 454,546.74 /አራት መቶ ሃምሳ አራት ሺህ አምስት መቶ አርባ ስድስት ብር ከሰባ አራት ሣንቲም/ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዘመነ ዮሐንስ ጀኔራል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ሙሉጌታ ፀጋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዳውድ ኢብራሂም ጠበቃ ክፍሌ ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የመጋዘን ኪራይ ውል አከፋፈል የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ለተከራየው መጋዘን የስድስት ወር ኪራይ ብር 78,000 (ሰባ ስምንት ሺህ ብር) እንዲከፍለው ተጠሪ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ይህንን ገንዘብ የምከፍለው፣ የመንግስት ግብር ቅናሽ ተቀንሶ መሆን ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ግብር ሣይቀንስ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ግብር ሣይቀንስ የቤቱን ኪራይ ብር 78,000 (ሰባ ስምንት ሺህ ብር) ለተጠሪ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡

አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ አዋጅ ቁጥር 286/1994 ድንጋጌዎችን የሚጥስና በእኔም ላይ የወንጀል ተጠያቂነት እና አስተዳደራዊ ቅጣት የሚያስከትል ስለሆነ በሰበር ይታረም በማለት የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የግብር እዳውን እኔ ከፍያለሁ፡፡ እሱ የኪራይ ውሉን አስመዝግቤያለሁ፡፡ ስለዚህ አመልካች የሚቀነስበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከጠቅላላ ግብር መክፈላቸው አመልካች ቀንሶ እንዲያስቀር በሕግ የተጣለበትን ግዴታ የሚያስቀር አይደለም በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተጠሪን መጋዘን በወር ብር 13,000 (አስራ ሶስት ሺህ ብር) የተከራየ መሆኑና አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው የስድስት ወር ኪራይ ብር 78,000 (ሰባ ስምንት ሺህ ብር) እዳ ያለበት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካችና ተጠሪን የሚያከራክራቸው አመልካች የኪራይ ገንዘቡን በጥቅሉ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 መሠረት መቀነስ የሚገባውን ግብር ቀንሶ ቀሪውን ሊከፍል ይገባዋል የሚለው ነጥብ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ማናቸውንም የአገልግሎት ግኘር ሲፈፀም ሻጩ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካለው የገዛውን አገልግሎት ወይም እቃ ዋጋ ሁለት ፐርሰንት፣ሻጭ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌለው ሰላሳ ፐርሰንት ቀንሶ በማስቀረት ለግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑ በአዋጅ 286/94 አንቀጽ 83 እና አንቀጽ 91 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ባደረግሁት የኪራይ ውል፣ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ተከራይ ሣይሆን አከራዩ መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

ተዋዋይ ወገኖች የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት (የመዋዋል) ነፃነት የሚኖራቸው ህግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች ውጭ ባሉ ጉዳዩች እንደሆነ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1711 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የተጠሪን መጋዘን የተከራየው አመልካች ለተጠሪ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ የመንግስት ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 286/1994 በአንቀጽ 56 እና አንቀጽ 91 በግልጽ ተወስኗል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ህግ በአስገዳጅነት የደነገገውን ግዴታ ለማስቀረት የሚችል ውል የመዋዋል መብት የላቸውም፡፡ አመልካችና ተጠሪ በህጉ በአስገዳጅነት የተደነገገውን በመተላለፍ ውል ተዋውለው ቢገኙ ውሉ ህግን የሚቃረን በመሆኑ ፈራሽና ሕጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 56 እና አንቀጽ 91 ድንጋጌዎችና ከፍታብሐር ህግ ቁጥር 1716 ድንጋጌዎች ጋር በማጣመርና በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 ዓ.ም የተጣለበትን ህጋዊ ግዴታ በመተላለፍ ለተጠሪ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ ግብር ሣይቀንስ እንዲከፍለው ተጠሪ ያቀረበውን ጥያቄ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1718 ድንጋጌ መሠረት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አስገዳጅ ድንጋጌዎች መሠረት የግብር ገንዘብ ሣይቀንስ የስድስት ወር የቤት ኪራይ ብር 78,000 (ሰባ ስምንት ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ተጠሪ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካቀረበ ሁለት ፐርሰንት ተጠሪ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረበ ሰላሣ ፐርሰንት በመቀነስ የስድስት ወር የመጋዘን ኪራይ ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 72824

ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፌሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ፅ/ቤት

ተጠሪ፡-አቶ ሚሊዮን አሰፋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ በሕጉ አግባብ ደረጃው ተለይቶ ግብሩን ሲከፍል የቆየ ግብር ከፋይ የገቢ መጠኑ ሲሻሻል የግብር ከፋይነቱ ደረጃ ለወጥ የሚወሰነው በግብር አስገቢው ባለስልጣን ነው ወይስ በግብር ከፋዩ ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሲሆን በዚህ አካል ይግባኝ ያቀረቡት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ተጠሪ ለዚህ አካል ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ በጥብቅና አገልግሎት የጥብቅና ፈቃድ በደረጃ "ሐ" ከፋይነት ያወጡ መሆኑ፣የአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤት ከደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይነት ወደ ደረጃ "ለ" ግብር ከፋይነት እንዲሻሻል የሰጠው ውሳኔ ሳይኖር ተርን ኦቨር ታክስ አሳውቀህ አልከፈልህም፣የ ደረጃ ለ ግብር ከፋይ ሁነህ መዝገብ ሳትይዝ ቀርተሃል በሚል መዝገብ ባለመያዝ ቅጣት የጣለባቸው መሆኑንና ይህ ተግባር ከአዋጁ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 48(1)፣89(1) እና ከደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 22(2) ድንጋጌዎች አንፃር ሕጋዊ ያለመሆኑን ገልፀው የአመልካች መስሪያ ቤት ውሳኔ እንዲሻርላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ጉባኤውም የአሁኑ አመልካች መልስ እንዲሰጥበት ያደረገ ሲሆን አመልካች ባቀረበው መልስም ተጠሪ አመታዊ ገቢያቸው ከብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በላይ በመሆኑ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ መሆናቸውን እንደሚያሳይ፣የደረጃ ለ ግብር ከፋይ ደግሞ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ እስካልሆነ ድረስ በደረጃው የሚጣለውን ማንኛውንም ታክስ መክፈል እንደሚኖርበት፣ በዚህም መሰረት በተቀመጠው የመክፈያ ወቅት ሊከፍሉ እንደሚገባ ስለሚታወቅ ሊከፍሉ እንደሚገባ፣ ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቱም በወቅቱ ባልከፈለውና ሊከፈል በሚገባው ግብር መነሻነት መዝገብ ካለመያዝ መቀጫ መጣሉ በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት መሆኑን፣ተርን ኦቨር ታክስ በአዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀፅ 3 መሰረት ከታክስ ነፃ ካልተደረገ በቀር በተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች ከአገር ውስጥ በሚሸጧቸው እቃዎችና አገልግሎት ላይ ተርን ኦቨር ታክስ እንደሚከፈል በግልፅ የተቀመጠና ተጠሪ ቅሬታ በቀረበባቸው ዘመናት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ባለመሆናቸው የተርን ኦቨር ታክስ የመክፈል ግዴታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደአለባቸው፣መዝገብ ባለመያዝ የተጣለው ቅጣትም ከደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በስተቀር በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ በሙሉ /በከፊል/ የሚከራዩ ሕንጻዎች ባለቤት የሆኑ የሒሳብ መዝገብና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ በህግ የተጣለባቸው መሆኑን፣ማናቸውም የግብር ከፋይ ለአንድ የተወሰነ የግብር ዘመን መያዝ የሚገባውን ተገቢ የሂሳብ መዝገብና መግለጫ ያልያዘ እንደሆነ የተወሰነበትን ግብር 20% መቀጫ እንደሚከፍል በሕጉ መመልከቱን፣ተጠሪውም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ በመሆናቸው የሂሳብ መግለጫ ለመያዝ ግዴታ ባለመወጣታቸው የተቀጡ መሆኑንና ይህንንም ለማድረግ የአሁኑ አመልካች በሕጉ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ ክርክሩ በዚኅ መልክ የቀረበለት ጉባኤም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የደረጃ "ለ" ከፍይነት ደረጃውን ራሱ መለወጥ ነበረበት የሚለው የአሁኑአመልካች ክርክር የሕግ ድጋፍ የሌለው መሆኑንና ከ1999 እስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ፍሬ ግብር አመልካች ከተጠሪ ሙሉ በሙሉ ከተቀበለ በኋላ መቀጫው መወሰኑ የህግ ድጋፍ እንደሌለው በምክንያትነት ይዞ የአመልካችን ውሳኔ ውድቅ አድርጎ ተጠሪ መቀጫውን ሊከፍሉ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ተጠሪ የግብር ከፋይነት የደረጃ ለውጡን ራሳቸው አውቀው የደረጃ ለ ግብር ከፋይ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ሲገባቸው የአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤት የደረጃ ለውጥ ውሳኔ አላሳወቀኝም በማለት የሚያቀርቡት ክርክርና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የጉባኤውን ውሳኔ በመሻር በመቀጫ ላይ የአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤት በተጠሪ ላይ የሰጠውን ውሳኔ አስመልክቶ ጉባኤው የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን መልሶ ልኮለታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ የሠበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የደረጃ ለውጥ ውሳኔ መሰጠት ያለበት በግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት እንጂ በግብር ከፋዩ ሊሆን አይገባም በሚል ምክንያት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሸሮ የጉባኤው ውሳኔ በድምጽ ብላጫ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ሁነው ቆይተው ገቢያቸው ማደጉን ራሳቸው አውቀው በደረጃ ለ ፍሬ ግብሩን ሲከፍሉ ከቆዩ በኋላ የደረጃ ለውጥ ስለመኖሩ አመልካች መስሪያ ወስኖ ስላላሳወቀኝ በደረጃ "ለ" ግብር ከፋይነት መዝገብ የመያዝ ግዴታ የለብኝም በማለት የሚያቀርቡትና በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አብላጫ ድምፅ ተቀባይነት ያገኘው ክርክር ሕጋዊ ድጋፍ የለውም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ስለመሆኑ ታምኖ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ በሰጡት መልስ የአመልካች መስሪያ ቤት ክርክር የሕግ ድጋፍ የሌለው መሆኑን ያሳያሉ ያሏቸውን ምክንያቶችን አንስተው ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች መስሪያ ቤት ነ/ፈጅም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙኝ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የግብር ከፋይ ደረጃ ለውጥ መኖሩን የመወሰን ስልጣን የግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ስልጣን ነው? ወይስ የግብር ከፋዩ ነው? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የተሰማሩበት የገቢ ማስገኛ ስራ 1ኛ ደረጃ የጥብቅና ስራ ሲሆን የተጠየቁትም የ1999፣2000 እና የ2001 ዓ.ም. የግብር ዘመን መዝገብ ባለመያዛቸው ቅጣት እንዲከፍሉ እንዲሁም በ1999 እና 2000 ዓ.ም. የግብር ዘመን የተርን ኦቨር ታክስ ፍሬ ግብር፣ገቢን ባለማስታወቅ ግብር በጊዜ ባለመክፍል ቅጣት እንደተወሰነባቸው የአመልካች መስሪያ ቤት የውሳኔ ማስታወቂያ የሚገልጽ መሆኑን ተጠሪ የአመልካች መስሪያ ቤትን ውሳኔ እየተቃወሙ ያሉት የደረጃ ሐ ግብር ከፋይ በመሆን ገቢዬን ሳልደብቅ ያስታወቅሁና የተወሰነውን ግብር የከፈልኩ ስለሆነ ግብር አስገቢው ባለስልጣን ደረጃዬን ሳይለውጥ በደረጃ ለ ግብር ከፋይ፣የተርን ኦቨር ታክስ ክፈል፣ገቢ ባለማስታወቅና በጊዜ ባለመክፈል እንዲሁም መዝገብ ባለመያዝ ልቀጣ አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን፣ተጠሪ አመታዊ ገቢአቸው ብር 100,000.00 ስለመሆኑ ገልፀው በዚህ አግባብ ጥሬ ግብሩን ሲከፍሉ የነበሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ነው።

በመሰረቱ ግብር አስፈላጊነቱ ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ሕጉ ይህንኑ የግብር አስፈላጊነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና የግብር አሰባሰብ ስርዓቱን ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ በማሰብ በግብር ከፋዩም በአጠቃላይ፣እንደታክስ ከፋይነቱ ደረጃና እንደ ታክሱ አይነት በታክስ ከፋዩ ላይ የጣለው ግዴታ ያለ ሲሆን በግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ላይም የጣለው ግዴታ መኖሩ የሚታወቅ ነው።ሁሉም የግብር ከፋይ ተገቢ በሆነው የሂሳብ አያያዝ ስርኣትና የታክስ ባለስልጣኑ በሚያስቀምጠውና በሚፈቀደው አኳኋን የሒሳብ መዛግብትንና ደጋፊ ሰነዶችን አሰናድቶ በስራ ሂደቱ መጠቀም ግዴታው ተብሎ ከሚጠቀሱ ነጥቦች አንዱ ስለመሆኑ ከገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 608/2001፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 609/2001፣ ከተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 611/2001፣ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 610/2001 እንዲሁም ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 እና በስራ ላይ ካሉት ሌሎች አዋጆች፣ደንቦች፣መመሪያዎች ጠቅላላ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት ሕጎችን ግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤትን ከአቋቋመው አዋጅ ቁጥር 587/2001 ጋር አንድ ላይ ስንመለከትም ግብር ሰብሰቢ መስሪያ ቤት ግብር የሚሰበሰብበትን ጊዜና ቦታ፣እያንዳንዱ ግብር ከፋይ የሚከፍለውን የግብር መጠን እንዲሁም ግብር የሚሰበሰብበትን ሁኔታ የግብር መሰብሰቢያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት በማያሻያማና ግልፅ በሆነ ሁኔታ ለግብር ከፋዩቹ ማሳወቅ ያለበት መሆኑን ያስገነዝባሉ።ይህ በታክስ ስርዓት ግልጽነት እንዲኖር የሚያደርግ ሲሆን በታክስ ሕግ ጽንሰ ሀሳብም ሙሉ ተቀባይነት ያለውና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 12 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይም በአግባቡ ሊተገበር የሚገባው ጉዳይ ነው።ከላይ የተጠቀሱት ሕጎች፣ደንቦችና በስራ ላይ ያሉ መመሪያዎች በአጠቃላይ ሲታዩ ለግብር ሰብሰቢው መስሪያ ቤት ስልጣን ሰጪ ሲሆኑ መስሪያ ቤቱ ግብርን በወቅቱ የማስከፈል፣ግብር ከፋዩቹ የገቢና ወጪ ሰነድ ካልያዙ የግብር ክፍያ መጠንም ተምኖ የማስከፈልን፣ግብር ከፋዩ በግብሩ አከፋፈል ስርኣት የግብር ህጎችን፣ደንቦችንና አግባብነት ያላቸውን መመሪያዎችን ጥሶ ከሆነ በሕግ እንዲጠየቅ ማድረግን፣የግብር ከፋዩን ንብረት መያዝንና የመሳሳሉት ስልጣንና ተግባራት ያሉት መሆኑን ያስገነዝባሉ።እነዚህን ስልጣንና ተግባራት ለመወጣት ደግሞ ግብር ከፋዮችን ደረጃውን የመለየት እና በተገቢው መንገድ ማሳወቅ ያለበት መሆኑ ይታመናል። ሕጉ በግብር ከፋዩ ላይ ከጣላቸው መሰረታዊ ግዴታዎች መካከል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገቢን ማሳወቅና በሕጉ አግባብ ግብሩን መክፈል ነው፡፡ገቢን የማሳወቅ ተግባር ለግብር ከፋዩ ደረጃ አወሳሰን ወሳኝ ሂደት ሲሆን ግብርን ለመክፈልም ቀድሞ መሟላት ያለበት ሁኔታ ነው፡፡ይህ የማሳወቅ ተግባር ደግሞ በሕጉ አግባብ ለእያንዳንዱ የግብር አይነት በሕግ በተቀመጠለት ጊዜና ባለስልጣኑ ተገቢ ነው ባለው መንገድ ተገቢውን ማስረጃ /ቅፅ /በመሙላት መካሄድ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡በአግባቡ ያልተያዘ መዝገብም ሆነ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ያልተከናወነ ገቢውን አሳውቆ ግብር መክፈል ድርጊት መቀጫን የሚያስከፍል ከመሆኑም በላይ በወንጀል ጭምር ሊያስቀጣ የሚችል ነው፡፡

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 11፣ 14 እና 17 ድንጋጌዎች ስር እንዲሁም በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 18 ስር የግብር ከፋዮች ደረጃ ተዘርዝሯል፡፡እነዚህ ድንጋጌዎች ለግብር ከፋዮች ደረጃ መሰረት ያአደረጉት አንዱ መነሻ የግብር ከፋዩን የአመታዊ ገቢ መጠን ነው፡፡የደንብ ቁጥር 78/1994 የእያንዳንዱ ደረጃ ግብር ከፋይ ስላለበት ግዴታ በግልጽ ያሳያል፡፡በዚህም መሰረት የደንቡ አንቀፅ 19 መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ግብር ከፋዮች ደረጃ "ሀ" እና ደረጃ "ለ" መሆናቸውን የሚያሳይ ሲሆን የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 48(1) ድንጋጌ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለባቸው መሆኑን ሲደነግግ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀፅ 10 ደግሞ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብና ታክሱን የመክፍል ግዴታ የተለያየ መሆኑን ያሳያል፡፡አንድ ግብር ከፋይ በወጣለት ደረጃ መሰረት ግብር የመከፍሉ ሁኔታ ሊቀጥል ወይም ሊለወጥ የሚችልበት አግባብ ስለመኖሩም ደንብ ቁጥር 286/1994 በአንቀፅ 22(2) ስር ተደግንጓል፡፡በዚህ ድንጋጌ አግባብ የግብር ከፋይ ደረጃ በነበረው ደረጃ እንዲቀጥል ወይም እንዲለወጥ የሚደረገው ግብር ከፋዩ የሚያቀርበውን መግለጫ፣መረጃዎችንና የአከባቢ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ሲሆን ይህ ተግባር በግብር አስገቢው ባለስልጣን መስሪያ ቤት ሊከናወን የሚችለው ለጉዳዩ ያገኛቸውን ማስረጃዎች በመመርመርና ክብደታቸውን በመመልከት ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ሕግ አውጪው በደንቡ አንቀፅ 18 ስር ለግብር ከፋዮቹ ደረጃ ከአወጣላቸው በኋላ በዚሁ አግባብ ደረጃው ቀጣይነት ሊኖር የማይችልበት አጋጣሚ እንደሚኖር በመገመት የደረጃ ለውጡን ባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ሊወስን የሚችበትን አግባብ በደንቡ አንቀፅ 22(2) ስር በግልፅ አስፍሯል፡፡ይህ ድንጋጌ ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የደረጃ ለውጡን ሊወስን ይችላል ብሎ ፈቃጅነት ባለው ሁኔታ መደንገጉ ግልፅ ሲሆን ይኸው የድንጋጌው ቅርፅና ይዘት ግን የደረጃ ለውጡ በግብር አስገቢው ባለስልጣን ሳይወሰን ቢቀር ግብር ከፋዩ በራሱ የደረጃ ለወጡን መወሰን ያለበት ስለመሆኑ አያስገነዝብም፡፡ግብር ከፋዩ በራሱ ጊዜ የደረጃ ለውጡን መወሰን አለበት ከተባለ በግብር አሰባሰብ ስርዓት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተእፅኖ ሊያስከትል እንደሚችል የሚታመን ነው፡፡የኾውም ግብር ከፋዩ ገቢውን አሳንሶ በማቅረብ ሊከፍል የሚገባውን ግብር ሳይከፍል እንዲቀር የማድረግና በታክሱ ስርዓቱ ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲስፋፋ ሰፊ በር የሚከፍት መሆኑ ይታመናል፡፡የግብር ሰብሳቢ ባለስልጣኑን ከአቋቋመው አዋጅ ቁጥር 587/2001ም ሆነ ከገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 38 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው የግብር አስገቢው ባለስልጣን በግብር ስርዓቱ ላይ ከፍተኛ የቁጥጥር ስራ በማድረግ የግብር ስርዓቱን ውጤታማና ቀልጣፋ የማድረግ ሃላፊነት ና ተግባር የተሰጠው መሆኑን ሲሆን ይህንኑ የባለስልጣኑን ሃላፊነትና ተግባር ውጤታማ እንዲሆን ከግብር ከፋዩ የሚጠበቀው ግዴታ በሕጉ የተጣሉበትን ግዴታ መወጣት ነው፡፡በግብር ከፋዩ ላይ በሕጉ የተጣሉበት ግዴታዎች በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት በወጣለት ደረጃ መሰረት ግብሩን በወቅቱ፣በተገቢው ቦታና ሁኔታ መክፈል እንጂ ደረጃውን ጭምር ግብር ከፋዩ አውጥቶ ግብርን እንዲከፍል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ሁነው ከ1999 እስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ ያገኙትን ገቢ ሳይደብቁ ገቢያቸውን ለአመልካች መስሪያ ቤት ማሳወቃቸው፣ግብር ባለመክፈል ወይም አሳንሰው በማሳወቃቸው የተወሰነባቸው ቅጣት የሌለ መሆኑ፣በአዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀፅ 10(2(ሐ)) መሰረት ተጠሪ ግዴታቸውን አልተወጡም የሚል ክርክር በአመልካች በኩል ያለመቅረቡን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው ጉባኤው ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች አሁን አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪው ገቢያቸው ከብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር) በላይ መሆኑን እያወቁ የግብር ከፋይነት ደረጃቸውን ከደረጃ "ሐ" ወደ ደረጃ "ለ" ራሳቸው ከፍ አድርገው በመወሰን የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ያለበትን መዝገብ የመያዝ ግዴታ መወጣት ነበረባቸው በማለት ነው፡፡ይሁን እንጂ ከላይ በዝርዝር ከተመለከትናቸው የሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና አላማ አንጻር ሲታይ አንድ ግብር ከፋይ ገቢውን በሕጉ አግባብ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ከማሳወቅ ውጪ ደረጃውን ራሱ ሊወስን እንደሚገባ በሕጉ ግልጽ ግዴታ የተጣለበት ባለመሆኑና የግብር ከፋዩን ደረጃ ለውጥ የመወሰን ስልጣን የግብር አስከፋዩ መስሪያ ቤት በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ላይ መቀጮ የሚጥልበት ሕጋዊ መሰረት የለም፡፡የአመልካቹ ክርክር የግብር ከፋዩን መብትና ግዴታ ከግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ሃላፊነትና ተግባር ጋር ያላገናዘበና ለታክስ ስርዓቱ ውጤታማነትና ቀልጣፋነትም አሉታዊ ውጤት ያለው በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በአንፃሩ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 38፣የደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 18 እና 22፣የአዋጅ ቁጥር 308/19995 አንቀፅ 10(2(ሐ)) እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 587/2001 እና ተቀባይነት ያላቸውን የታክስ ህግ መርሆችን ያገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 16215 ሐምሌ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. በአብላጫ ድምፅ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአንድ ግብር ከፋይ ደረጃ ለውጥ ሊወሰን የሚገባው በግብር ከፋዩ ሳይሆን በግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 69602

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1.አቶ አካሉ አለሙ - ጠበቃ ወልደሥላሴ ብርቱ ጋር ቀረቡ፡፡

2. አቶ ተስፋዬ ጸጋዬ - ጠበቃ መብራቱ መለሰ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 69392 ጋር እንዲጣመር የታዘዘ በመሆኑ ሁለቱም መዛግብት ተመርምረው ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከጉምሩክ አዋጅ ጋር የተያያዘ የወንጀል ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- 1ኛ አመልካች አቶ አካሉ ዓለሙ እ.ኤ.አ ከ1990 እስከ አፕሪል 2004 ድረስ ከአሜሪካ ቆይተው ወደ አገራቸው ሲመለሱ በተሰጣቸው የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት በመቀጠም የሰሌዳ ቁጥር 2-544552 አ.አ. የሞተር ቁጥር LM7-5892294፣ የሻንሲ ቁጥር 4T23 F 13 C64 UZ 79592 ቶዮታ፣ ከጃፓን መኪና አስገብተው ለአሁኑ ሁለተኛ አመልካች አቶ ተስፋዬ ጸጋዬ አሳልፈው በመስጠት እንዲጠቀሙበት ማድረጋቸውን፣ እንዲሁም ይህንኑ ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት ለግል መገልገያ የገባ በማንኛውም አገልግሎት ላይ የማይውል መሆኑን እያወቁ ለብር 259,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ብር) ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ መኪናውን በመያዣነት በመስጠት ብድር የወሰዱ መሆናቸውን፣ ሁለተኛ አመልካች ደግሞ ከላይ የተገለጸውን መኪና ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባ መሆኑን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ከአንደኛው አመልካች ተቀብለው እየተገለገሉበት እያለ ሕዳር 23 ቀን 2001 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 9፡00 ሰዓት ሜክሲኮ አደባባይ ከሚባለው አካባቢ ሲያሽከረክሩ የተያዙ መሆናቸውን በመዘርዘርና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1(ሀ(ለ)) እና የጉምሩክ ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1989 እንደተሻሻለ አዋጅ ቁጥር 368/1995 አንቀፅ 73(1(ሀ እና ለ)) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፈዋል በሚል አመልካቾች በወንጀል እንዲጠየቁ ክስ ማቅረቡን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች በዚህ መልኩ የቀረበባቸውን ክስ ክድው ተከራክረው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ማስጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎም የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን በመከላከያነት አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካቾች መከላከያ ማስረጃዎች እርስ በርሳቸው የሚጋጩ መሆናቸውን ጠቅሶ የዐቃቤ ሕጉን ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ የሚችሉ አይደሉም በሚል ምክንያት ክብደት ባለመስጠት ውድቅ አድርጎ አመልካቾችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ክስ መሰረት ጥፋተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አድርጎ አንደኛውን አመልካች በዘጠኝ ወር፣ ሁለተኛውን አመልካች ደግሞ በስድስት ወር እስራት፣ እንዲሁም ብር 170,603.21 (አንድ መቶ ሰባ ሺህ ስድስት መቶ ሶስት ብር ከሃያ አንድ ሳንቲም) እንዲቀጡ የወሰነ ሲሆን የእስራት ቅጣቱን እያንዳንዳቸው በሁለት አመት ገደብ ሁነው በውጪ እንዲጨርሱ፣ በኢግዚብትነት የተያዘው መኪና ደግሞ ለመንግስት እንዲወረስ ሲል ወስኗል። በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይት አላገኙም። የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን በተለያዩ መዛግብት ያስከፈቱ ቢሆንም ጉዳዮቹ አንድ ላይ ተጣምረው እንዲታዩ ተደርጓል። የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አንደኛው አመልካች በውጪ አገር ባፈሩት ገንዘብ በአገር ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ በሕጉ አግባብ ፈቃድ ወስደው አከራካሪውን መኪና በመያዣነት በባንኩ መመሪያና አሰራር መሰረት ያስያዙ መሆኑና ለጥገና ለሁለተኛው አመልካች አሳልፈው የሰጡ መሆኑ በሰውና በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጦ እያለ ጥፋተኛ መባላቸው ያላግባብ መሆኑን፣ 2ኛ አመልካችም ተሽከርካሪውን በወቅቱ ይዘው የተገኙት ባላቸው ሙያ የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት ለመስጠት ሁኖ እያለ ጥፋተኛ መባላቸው ያላግባብ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች የሠጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ክሱን ሊመሰርት የቻለው 1ኛ አመልካች ያለቀረጥ መብት ተጠቃሚ በመሆን ከውጪ ያስገቡትን የቤት መኪና በሕግ ላልተፈቀደለት ሰው አገልግሎት ላይ እንዲውል አድርገዋል፣ እንዲሁም ተሽከርካሪውን ለግል መገልገያ የገባና ለሌላ ማናቸውም አገልግሎት ላይ የማይውል መሆኑን እያውቁ ከባንክ ለወሰዱት ብድር መያዣ ሰጥተው ተገኝተዋል በሚል ሲሆን 2ኛው አመልካችም የ1ኛ አመልካች መኪና ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባ መሆኑን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ከ1ኛ አመልካች ተቀብለው እየተገለገሉበት እያለ ተይዘዋል በሚል መሆኑን ነው። 1ኛ አመልካችም ሆነ 2ኛ አመልካች መኪናው በሕጉ (አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 73(2) እንደተሻሻለ) ቤተሰብ ተብለው ከተቀመጡት ውጪ በሆነ ሰው ሲሸከረክር በተጠሪ መያዙን ሳይክዱ መኪናው በተያዘበት ወቅት መኪናውን ሲያሽከረክሩት የነበሩት የአሁኑ 2ኛ አመልካች መኪናውን በወቅቱ ይዘው የተገኙት ለጥገና ወደ ጋራዥ ለመውሰድ ነው የተያዘው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው። በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካቾችን ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን መርምረው የአመልካቾች መከላከያ ማስረጃዎች ቃል እርስ በርሱ የሚጋጭ በመሆኑ ሊታመን የሚችል አይደለም በሚል ነው። በሌላ አገላለፅ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት ፍሬ ነገርን አጣርተውና ማስረጃቸውን መዝነው ነው። የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልፅ የሚያሳየው አመልካቾች የመከላከያ ጭብጣቸውን ለማስረዳት የአቀረቧቸው ማስረጃዎች ታይተው ክብደት የሚሰጣቸው ባለመሆኑና የአቃቤ ሕጉን ማስረጃዎች ሊያስተባብሉ ያልቻሉ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በመገንዘብ ውሳኔ መስጠቱን ነው። እንግዲህ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን መሰረት በማድረግና ማስረጃን በመመዘን የተሰጠ ነው ከተባለ የአመልካች የሰበር ቅሬታ የሚያሳየው የስር ፍርድ ቤት ፍሬ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነገርን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን ረገድ ስህተት ሰርቷል የሚል ይዘት ያለው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ይህንኑ ስህተት ማረም ነው፡፡ በመሆኑም የማስረጃ ምዘና ጉዳይ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን ሊያሟላ የሚችል ባለመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ አመልካች መኪናው ለቤተሰብ አገልግሎት ሲውል የነበረ መሆኑን ባላስረዱበት ሁኔታ የሕግ ጥያቄ የሚነሳበትን ምክንያት አላገኘንም፡፡ እንዲሁም ለግል መገልገያ ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባ መኪናን ከባንክ ብድር ለመውሰድ የባንኩን መመሪያና ስርዓት መሰረት በማድረግ በመያዣ መስጠትም ከአዋጅ ቁጥር 280/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 60/1989 ማሻሻያ ከሆነው አዋጅ ቁጥር 345/1995 የተፈፃሚነት ጊዜ ቅደም ተከተል አኳያ ከሚኖረው የሕጎቹ አተረጓጎም መርህ አንፃር ሲታይ 1ኛ አመልካችን ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ ሊያደርጋቸው የሚችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ እንዲሁም 1ኛ አመልካች የተከሰሱት ለቤተሰብ አግልግሎት እንዲውል ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባ መኪና ለብድር መያዣነት ሰጥተዋል በሚል እንጂ ለኢንቨስትመንት የተፈቀደላቸውን መኪና ለብድር መያዣ ሰጥተዋል በሚል ባለመሆኑና አቃቤ ሕጉም እንደክሱ ያረጋገጠ በመሆኑ 1ኛ አመልካች አዋጅ ቁጥር 280/1994ን መሰረት በማድረግ የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካቾች ያቀረቡት ቅሬታ የገንዘብ መቀጮን በተመለከተ ሲሆን የአመልካቾች የቅሬታ ይዘት አመልካቾች እያንዳንዳቸው ብር 170,603.21 ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ይህንኑ ገንዘብ እያንዳንዳቸው እንዲከፍሉ የወሰነው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጥቅሉ አመልካቾች ብር 170,603.21 የገንዘብ መቀጮ ሊከፍሉ ይገባል በማለት በሰጠው የውሳኔ ክፍል የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን በማቅረቡ ነው፡፡ ከዚህ ከፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው የገንዘብ መቀጮው አመልካቾች እያንዳንዳቸው እንዲከፍሉ የተወሰነ መሆኑን ነው፡፡ እኛም የውሳኔውን ሕጋዊነት ተመልክተናል፡፡ አመልካቾች በወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 345/1995 እንደተሻሻለ አንቀጽ 73(1) በመተላለፍ ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች መሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ በእስራትና በገንዘብ መቀጮ በጣምራ የሚያስቀጣ የወንጀል ድርጊት ነው፡፡ ቅጣት የሚወሰነው የእያንዳንዱን ጥፋተኛ ግላዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነና ወንጀልና የወንጀል ቅጣት ግላዊ መሆናቸውንና ከአንዱ ወደ ሌላው የማይተላለፍ መሆኑ በ1996 በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 41 ስር ከተደነገገው መሠረታዊ መርህ ለመረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ የገንዘብ መቀጮ የወሰነው የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል አመልካቾች ያላቸውን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችና በህጉ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የገንዘብ መቀጮ መነሻ በማድረግና በማገናዘብ ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዳቸው ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የህግ ድንጋጌ በወቅቱ ለመንግሥት ይከፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ ገንዘብ መነሻ በማድረግ ፍርድ ቤቱ ሊወሰን የሚችል መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

በመሰረቱ ወንጀል በመፈፀሙ የሚወሰነው የገንዘብ ቅጣት በወንጀል ሕጉ የቅጣት አወሳሰን መርሆችን መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ በወንጀል ጥፋተኛ በተባሉ ሰዎች ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በፍታብሔር ለመንግሥት ሣይከፈለው የቀረውን ቀረጥና ታክስ በአንድነትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በነጠላ እንዲከፍል ለማድረግ ከሚቀርብ ክስና ከሚሰጥ ውሳኔ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አይነት ለሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች በአጥፊዎች ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በፍታብሔር ክርክር ጊዜ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ጋር ተመሳሳይነት የሌለውና በእያንዳንዱ አጥፊ ላይ ሊጣል የሚገባው መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 48956 በቀረበው ጉዳይ ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ድንጋጌ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሕጉ አግባብ አልተለወጠም፡፡ በመሆኑም በአመልካቾች ላይ የተጣለው የገንዘብ ቅጣት ከሰ/መ/ቁጥር 48956 የሕግ ትርጉም አንፃር ሲታይ የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ አመልካቾች ለድርጊቱ በወንጀል ጥፋተኛ መሆናቸውም ሆነ እያንዳንዳቸው ለመክፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ መክፈል ያለበት ገንዘብ ለፈፀሙት ወንጀል በመቀጫነት እንዲከፍሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ቀደም ሲል በተመሳሳይ ሁኔታ በሰ/መ/ቁጥር 48956፣ 47087 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ከተሰጡት ውሳኔዎች ጋር የተጣጣመ በመሆኑ ውሳኔው የወንጀል ህጉን መሠረታዊ የማስረጃ አመዛዘንና የቅጣት አወሳሰን መርሆች የተከተለና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

- በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 153922 ጥቅምት 09 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ፣ ይኸው ፍርድ ቤት በተጠቃሹ መዝገብ ህዳር 03 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፣ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 102670 በቀን 17/08/2003 ዓ.ም. በመ/ቁጥር 102888 ሚያዚያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሰረት ፀንተዋል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውክልና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 50985

ሕዳር 5 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1- አቶ ስሻህ ክፍሌ - አልቀረቡም

2- አቶ ሰጡኝ በቀለ ጠበቃ ጌትነት ያሻነህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1- ወ/ሮ አፀደ ዱቤ - አልቀረቡም

2- ወ/ሮ አዛለች ዱቤ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ከውክልና ሥልጣን ውጭ የተፈፀመ የቤት ሽያጭ ውልን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን ሁለተኛ አመልካች የተከሣሽ ከሣሽ ተጠሪዎች የከሣች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክራቸው ይዘትም የአንደኛ ተጠሪ ልጅና የሁለተኛ ተጠሪ ወንድም የሆነው አንደኛው አመልካች የማይንቀሣቀስ ንብረት እንዲሸጥ ፣ እንዲለወጥ ፣ ለሶስተኛ ወገን እንዲያስተላልፍ የተሰጠው ልዩ የውክልና ሥልጣን የለም፡፡ በአደራ እንዲያስተዳድር የሰጠነውን በመተሀራ ከተማ የሚገኝ ቤት ለሁለተኛው አመልካች በመሸጥ ስመሃብቱ የተዛወረ መሆኑን ገልፀው ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰንላቸው ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በተከሣሽነት ቀርበው ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት ሁለተኛው አመልካች ቤቱን ውክልና ካለው ሰው የገዛሁት ነው የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል የአሁን ሁለተኛ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ ቤቱን ከገዛሁ በኋላ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ ወጭ በማድረግና በማሻሻል ገንብቻለሁ፡፡ ስለዚህ የገነባሁት ቤት ባለሀብት ነህ ተብሎ እንዲወሰንልኝ ይህ የሚታለፍ ከሆነ ገንዘቡን በጋራና በተናጠል እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ እና ሌሎች የመከራከሪያ ነጥቦች በከሣሽ ተከሣሽነት ቀርበው አንስተዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አንደኛ ተከሣሽ ለሁለተኛ ተከሣሽ ቤቱን የሸጠው በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪዎች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን ይግባኝ አልተቀበለውም፡፡ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪዎች አንደኛ አመልካች የማይንቀሣቀሥ ሀብት እንዲሸጥ ልዩ የውክልና ሥልጣን ያልሰጡ በመሆኑ አንደኛው አመልካችና በሁለተኛው አመልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው፡፡ ሁለተኛ አመልካች ከፈለገ አንደኛ አመልካችን ከሚከስ በስተቀር በተጠሪዎች ላይ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ታህሣሥ 6 ቀን 2002 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000/1/ በመጥቀስ ያቀረብነውን ክርክር አላግባብ አልፎታል፡፡ ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች የሰጡት ውል አንደኛ አመልካች እንደነሡ ሆኖ እንዲከራከርላቸው ፣ ማናቸውም አቤቱታ አቅርቦ እንዲያስፈፅምላቸው ቃለመሃላ ፊርሞ እንዲያቀርብ እነሡን በሚመለከት ማስረጃ እንድቀበል በእነሡ ስም ውል እንዲዋዋል ዕርቅ እንዲደራደር ገንዘብ እንዲቀበል እና በተጠሪዎች ስም የሚዛውር ንብረት ፎርማሊቲ እንዲያሟላ እንዲያዛውር የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ውል እንዲዋዋል በተሰጠው የውክልና ሥልጣን ተጠቅሞ የተዋዋለውን የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ውሉ አይፈርስም እንጅ ይፈርሳል ቢባል ብር 250,000 በማውጣት አሻሽዬ የገነባሁት ሲሆን ስመሀብቱም ወደ ሁለተኛ ተጠሪ የዞረ በመሆኑ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ታይቶ ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባው በመሆኑ ይህ ነጥብ መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪዎች በቃል ባቀረቡት ክርክር አንደኛ አመልካች የማይንቀሣቀሥ ንብረት በተጠሪዎች ስም እንዲያዛውር እንጂ በተጠሪዎች ስም ያለን የማይንቀሣቀሥ ንብረት ለሌላ ሰው እንዲያስተላልፍ የተሰጠው ልዩ ውክልና የለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ ሁለተኛ አመልካች ብር 150,000 እንድንከፍለው ያቀረበው ክስ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በቃል ክርክር የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ሣያጣራና ማስረጃ ሣይመዝን ሁለተኛ አመልካች ያቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አልፎታል ስለዚህ የሁለተኛ አመልካች የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በአግባቡ ታይቶ ውሣኔ አልተሰጠበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር የቀረበው የሰበር አቤቱታና በግራ ቀኙ የተደረገው የቃል ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? ሁለተኛው አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ የሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ውሣኔ ተሰጥቶበታል ወይስ አልተሰጠበትም? የሁለተኛው አመልካች የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ አልተሰጠበትም የሚባል ቢሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ሁለተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች አንደኛ አመልካችን እንጂ ተጠሪዎችን መክሰስ አይችልም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም ? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመወሰን ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች መጋቢት 13 ቀን 1985 ዓ.ም በምዕራብ ሸዋ ዞን የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በማረጋገጥ የሰጡትን የውክልና ሥልጣን መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች የሰጡት የውክልና ሰነድ ይዘት ስንመለከተው " ወካዮች በምንከስበትም ሆነ በምንከሰስበት ሁሉ ተወካይ የአንደኛ ተወካይ ልጅ ፣ የሁለተኛ ተወካይ ወንድም እንደመሆኑ መጠን ስለእኛ ሆኖ እንዲከራከርልን ማናቸውም አቤቱታ አቅርቦ እንዲያስፈፅምልን ፣ ቃለመሃላና ማረጋገጫ ፈርሞ እንዲያቀርብ ፣ እኛን የሚመለከቱ ሁሉን ማስረጃዎች እንዲቀበልልን በእኛ ስም ውል እንዲዋዋል ፣ ዕርቅ እንዲደራደር ፣ ገንዘብ እንዲቀበልልን በእኛ ስም የሚዘዋወር ንብረት ማናቸውም ፎርማሊቲ እያሟላ እንዲያዛውርልን ከአቅሙ በላይ በሆነበት ጉዳይ ሌላ ወኪል ነገረ ፈጅ እንዲወክል በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 58 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2199 መሠረት የወከልነው መሆኑን እናረጋግጣለን " የሚል ነው፡፡ ይህ የውክልና ሥልጣን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 58 የተደነገገውን የነገረ ፈጅነት ሥልጣን እንዲኖረውና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2204 መሠረት አንደኛ አመልካች የአስተዳደር ሥራ እንዲሰራ ሥልጣን ከመስጠት ባሻገር አንደኛ አመልካች በተጠሪዎች አውራሽ በአቶ ገ/ኪዳን ቦንጋ ስም የነበረውን ቤት ወደ ተጠሪዎች ስም ካዛወረ በኋላ ቤቱን ለሌላ ሰው ለመሸጥ የሚያስችለው የውክልና ሥልጣን እንዳልሆነ ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች የሰጡትን ውክልና ሥልጣን ሰነድ ሙሉ ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተወካዩ ከአስተዳደር ሥራ በቀር ሌላ ሥራ ለመስራት የሚያስፈልግ ሲሆን ልዩ ውክልና እንዲኖረው አስፈላጊ መሆኑንና ተወካዩ ልዩ የውክልና ሥልጣን ከሌለው በቀር የማይንቀሣቀሡ ንብረቶችን ለመሸጥ ወይም አስይዞ ለመበደር የማይችል በመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2205 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪዎች አንደኛ አመልካች ወደ ተጠሪዎች ሊዛወር የሚችል ማናቸውም ንብረት አስፈላጊውን ፎርማሊቲ በማሟላት በተጠሪዎች ሥም ለማዛወር የሚችል የውክልና ሥልጣን የሰጡት ሲሆን አንደኛ አመልካች ወደ ተጠሪዎች ሥም ያዛወረውን የማይንቀሣቀሥ ንብረት እንዲሸጥ ፣ እንዲለውጥ ፣ በማያጠራጥር አስይዞ እንዲበደር ለሶስተኛ ወገን እንዲያስተላልፍ የሚል ልዩ የውክልና ሥልጣን በግልፅ ያልሰጡት መሆኑ ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች ከሰጡት የውክልና ሰነድ ይዘት ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡

አመልካቾች ተጠሪዎች ለአንደኛ አመልካች መጋቢት 13 ቀን 1985 ዓ.ም. በሰጡት የውክልና ሰነድ " በስማችን ውል እንዲዋዋል " በማለት የገለፀ በመሆኑ ይህ አገላለፅ ተጠሪዎች አንደኛው አመልካች የማይንቀሣቀሥ ሀብት ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችለው ልዩ ውክልና እንደሰጡ ሊተረጎም ይገባል የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2205 መሠረት የሚሰጥ ልዩ ውክልና በይዘቱ በልዩ ውክልና የሚፈፀሙ እያንዳንዳቸውን ተግባሮች በግልፅ የሚያመለክት መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪዎች አንደኛ አመልካች " በስማችን ውል እንዲዋዋል " በማለት የሰጡት ውክልና አንደኛ አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2204 የተዘረዘሩትን የአስተዳደር ተግባራት ለመፈፀም የሚያስችሉትን ውሎች በተጠሪዎች ስም ሊፈፅም እንደሚችል የሚያመላክት እንጂ የማይንቀሣቀሥ ንብረት ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችለው ልዩ የውክልና ሥልጣን እንደተሰጠው ተደርጎ የሚተረጎምበት አግባብ የለም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የውክልና ሥልጣን የሚተረጎመው ሣይስፋፋ በጠባቡ መሆን እንዳለበት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2181 ንዑስ አንቀፅ 3 የሚደነግግ ከመሆኑም በላይ ተጠሪዎች ለአንደኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሰጡት ውክልና ሙሉ ይዘት አንደኛ አመልካች በሌላ ሰው ስም ያለን ንብረት በተጠሪዎች ስም ለማዛወር የሚያስፈልጉ ፎርማሊቲዎች በማሟላት ወደ ተጠሪዎች ሥም እንዲያዛውር የተወከለ መሆኑን እንጂ አንደኛ አመልካች በተጠሪዎች በተሰጠው ውክልና ተጠቅሞ በተጠሪዎች ስም ያዛወረውን የማይንቀሣቀሥ ሀብት ለሌላ ሶስተኛ ወገን እንዲሸጥ እንዲለውጥ ያልተወከለ መሆኑን የሚያሣይ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም አንደኛ አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን ሣይኖረው የተጠሪዎችን ቤት ለሁለተኛ አመልካች ለመሸጥ ያደረገው ውል ተጠሪዎችን የማያስገድድ ፈራሽ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪዎች በአንደኛ አመልካችና በሁለተኛው አመልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ እንዲወሰንልንና ቤታችንን እንድንረከብ በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ የደረሰው ሁለተኛ አመልካች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀፅ 234/1/ሀ/ መሠረት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ ሁለተኛው አመልካች ቤቱንና ቦታውን በውል በመረከብ ተጠሪዎች ምንም አይነት ተቃውሞ ሣያቀርቡ በብር 150,000 ቤቱን የገነባሁ በመሆኑ የገነባሁት ቤት ባለቤት መሆኔ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1178 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1179 መሠረት ይወሰንልኝ፡፡ ይህ የሚታለፍ ቢሆን ተጠሪዎች በቤቱ ላይ ያወጣሁትን ብር 150,000 ለገኘሁው /ለሁለተኛ አመልካች/ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች ሁለተኛ አመልካች ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ላይ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያና ሌሎች የህግና የፍሬ ጉዳይ መከራከሪያዎችን እንዳቀረቡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሣኔ ተገንዝበናል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ላይ ሁለተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክረ በመመርመር ተገቢውን ጭብጥ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 246 ፣ አንቀፅ 247 እና አንቀፅ 248 መሠረት በመመሥረትና የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በመመርመር ውሣኔ አልሰጠበትም፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ የፍሬ ጉዳይ ወይም የህግ ስህተት የሌለበት መሆኑን በመግለፅ የተጠሪዎችን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት የሰረዘው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሁለተኛው አመልካች ባቀረበው የተከሣሽነት ክስ ላይ የሰጡት ውሣኔ የለም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው የተከሣሽነት ክስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ባየው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ያልተሰጠበት መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

3.ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የዳኝነት ሥልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ በሰበር አይቶ የማረም እንደሆነ በህገመንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ሁለተኛ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የተከሣሽነት ክስን መነሻ በማድረግ በሁለተኛ ተከሣሽና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ክርክር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተገቢው የፍሬ ጉዳይ ማጣሪያ ተደርጎለት ማስረጃ ተሰምቶና ተመዝኖ ውሣኔ አልተሰጠበትም፡፡ ስለሆነም የግራ ቀኙ ክርክር ከፍሬ ጉዳይና አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ያልተሰጠበትን የሁለተኛ አመልካች የተከሣሽነት ክስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጓዳኝ ጭብጥ አድርጎ በማየት ሁለተኛ አመልካች በአንደኛ አመልካች ካልሆነ በቀር ተጠሪዎች ላይ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት የሰጠው ውሣኔ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 80

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ እና ከላይ የዘረዘርናቸውን የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አንደኛ አመልካች የተጠሪዎች ወኪል ነኝ በማለት ከሁለተኛው አመልካች ጋር ሰኔ 11 ቀን 1994 ዓ.ም የፈፀመው የቤት ሽያጭ ውሉ ተጠሪዎችን የሚያስገድድና ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ በአንደኛ አመልካች የተጠሪዎች ወኪል ነኝ በማለት ከሁለተኛ አመልካች ጋር የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ተጠሪዎችን የሚያስገድድና ፈርሽ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ሁለተኛ አመልካች በተጠሪዎች ላይ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ለማቅረብ አይችልም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
4. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች በተጠዎች ላይ ያቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ፣ ተጠሪዎች ሁለተኛው አመልካች ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ላይ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያዎችና ሌሎች የፍሬ ጉዳይና የህግ ክርክር ፣ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት 341/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ንግስቲ እምነት - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ቴዎድሮስ ተክሌ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ልረከብ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ሲሆኑ ተከሳሽ ደግሞ አመልካች ነበሩ፡፡ ተጠሪ በወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች በአደራ እንዲጠብቁ ከተጠሪ አባት ሟች ተክሌ ኪዳኔ የተሰጣቸውንና በሎጊያ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት ህጋዊ ወራሽ ለሆኑት ተጠሪ እንዲያስረክቡ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን በመግለፅ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ቤቱን በሕጋዊ ውክልና መሰረት ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑን ገልፀው ቤቱን ለማስረከብ ልገደድ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች አቶ ተክሌ ኪዳኔ ኤርትራዊ በመሆናቸው ከአገር ሲወጡ ለአመልካች በሰጡት ውክልና መሰረት ቤቱን አመልካች ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ማስተላለፋቸው ተረጋግጧል በሚል ምክንያት በውክልና ስልጣን የተፈፀመ ተግባር አመልካችን ቤቱን እንዲያስረክቡ አያስጠይቃቸውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩና ተገቢው ማጣራትና ተጨማሪ ማስረጃዎች ከተሰሙ በኋላ ጉዳዩ የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎበት መታየት የነበረበት ነው በሚል ምክንያት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮ ጉዳዩ የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎበት እንዲታይ ወደ ስር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የይግባኝ አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን የዳኝነት ገንዘብ ሊከፈልበት የሚታይ ነው በማለት መመለሱ የስነ ስርዓት ሕጉን ያልተከተለ መሆኑን፣ እንዲሁም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጭብጡን ለውጦ ዋናውን ጉዳይ ሊመለከት የሚችልበት የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌ መኖሩን ጠቅሶና ድንጋጌውን ከለየ በኋላ ዋናውን ጉዳይ መርምሮ አመልካች አለ የሚሉትን የውክልና ስልጣንና የሽያጭ ውል ማስረጃዎች በሚመለከታቸው አካላት በተለያየ ጊዜያት የተለያዩ መግለጫዎች የቀረቡባቸው በመሆኑ የሰነድ ማስረጃዎችን አጠራጣሪ የሚያደርገው መሆኑን፣ አመልካች አለ የሚሉት የውክልና ሰነድ ማስረጃ ይዘቱ ሲታይም አከራካሪውን ቤት ለማስተዳደር እንጂ ለመሸጥና ለመለወጥ የማያስችላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ መሆኑን ጠቅሶና የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሻር የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በአቤቱታቸው የውክልና ስልጣን ማስረጃውን የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያለመቀበሉ ከሰነዱ ይዘት ውጪ ነው በማለት ዘርዝረው ውሳኔው ተሸሮ ለተጠሪ በውክልና ስልጣኑ መሰረት ቤቱን የሸጡበት ዋጋ ሕጋዊ ተቀናሽ ሂሳቦች ካሉ የሚቀነሱ መሆኑ ተገልፆ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ይህ ችሎት ለአመልካች የተሰጠው ውክልና ቤቱን ከማስተዳደር ባሻገር ለመሸጥ የሚያስችል አይደለም በማለት አመልካች ከውክልና ሥልጣናቸው አሳልፈው ተገልግለዋል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረት ያደረገው በፍሬ ነገር ክርክር ላይ በመሆኑ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት የመልሳቸውን ጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የተጠሪ አባት ሟች ተክሌ ኪዳኔ የሰጡት ፈቃድና ውክልና ሳይኖር አመልካች አከራካሪውን ቤት ለ3ኛ ወገን ማስተላለፋቸው ተረጋግጧል ተብሎ ነው በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው፡፡ የተጠሪ ክስ ሲታይም አመልካች ቤቱን በአደራ ለመጠበቅ ተረክበዋል የሚል ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከላይ ከተገለፀው ድምዳሜ ሊደርስ የቻለው አመልካች አለ የሚሉት የነሐሴ 19 ቀን 1990 ዓ.ም. የውክልና ስልጣን ማስረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ የውክልና ውሉን መዝግቧል የተባለው የክልሉ ፍትሕ ቢሮ መግለጫ እንዲሰጥበት በፍርድ ቤት ሲታዘዝ ሰነዱ በቢሮው ሊገኝ አልቻለም ብሎ ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ ከሰጠ በኋላ በድጋሚ በፃፈው የማስተካከያ ደብዳቤ የውክልና ሥልጣን ማስረጃው በቢሮው ተረጋግጦ የተመዘገበና በተገቢው ማህበር ውስጥ ተያይዞ የሚታወቅ መሆኑን መግለፁና በሽያጭ ውሉ ላይ ማጣራት አድርጎ መግለጫ እንዲሰጥበት የታዘዘው የአስተዳደር አካልም መጀመሪያ በሰጠው መግለጫ ውሉ የማይታወቅ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ከገለፀ በኋላ በድጋሚ ማስተካከያ ነው ብሎ በፃፈው ደብዳቤ የሽያጭ ውሉ በሕጉ አግባብ የሚታወቅ መሆኑን ማስታወቁ የሰነድ ማስረጃዎቹ አጠራጣሪ መሆናቸውን ያሳያል፣ የውክልና ስልጣን ሰነዱም ቤትን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችል አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች ዘርዝሮ ነው፡፡

በቅድሚያ ተጠሪ ጉዳዩ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር በመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚታይ አይደለም በማለት ያቀረቡትን መቃወሚያ ተገቢነት ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ያለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔን በመቃወም የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የውክልና ሰነዱ በመንግስት መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ሆኖ እያለና የሰነዱ ይዘትም ልዩ ውክልና ሊባል የሚችል ሆኖ እያለ ማስረጃው ተቀባይነት ማጣቱ ያለአግባብ ነው በሚል መሆኑን ከቅሬታቸው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ቅሬታቸው በውክልና ማስረጃው ተቀባይነት ማጣቱ ላይ በመሆኑና የሰነድ ማስረጃ ተቀባይነት ደግሞ የሕግ ጥያቄ በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን ስር የሚወድቅ እንጂ የፍሬ ነገር ወይም የማስረጃ ክርክር ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የተጠሪ ተቃውሞ የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል፡፡

ወደ ዋናው ስንመለስም፤ በመሰረቱ የአስተዳደር መ/ቤት አንድ ጊዜ የሰጠው የደብዳቤ መግለጫ ትክክለኛ ያለመሆኑን በሌላ ጊዜ ከደረሰበት በዚሁ ላይ ሌላ ማስተካከያ ደብዳቤ ቢጽፍ መ/ቤቱ ሁለት ጊዜ የተለያየ ይዘት ያላቸውን ደብዳቤዎች በመጻፉ ብቻ ደብዳቤዎቹ ለማስረጃነት ዋጋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሰጣቸው አይገባም ብሎ ሁልጊዜ መደምደም የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ዋናውና ቁልፉ ነገር ከተፃፉት ደብዳቤዎች መካከል የትኛው ነው ትክክለኛ የሚለውን በተገቢው መንገድ ማጣራት ሲሆን ትክክለኛነቱ የተረጋገጠው ደብዳቤ ካለ ለዚሁ ተገቢው የማስረጃነት ዋጋ ሊሰጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች አለ የሚሉትን የውክልና ስልጣንና የሽያጭ ውሉ በሚመለከታቸው አካላት ስለመኖራቸው በድጋሚ በተፃፉት የማስተካከያ ደብዳቤዎች ተረጋግጠዋል፡፡ እነዚህ ማስተካከያ ደብዳቤዎች ትክክለኛ ያለመሆናቸው ወይም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የተሰጡ ስለመሆኑ ተጠሪ ያነሱት ክርክር ካለመኖሩም በላይ ፍሬ ነገሩን ያጣሩት ፍ/ቤቶችም በዚህ ረገድ ያሉት ነጥብ የለም፡፡ በመሆኑም የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰነድ ማስረጃዎችን ዋጋ ያልሰጠበት ምክንያት ሕጋዊ ካለመሆኑም በላይ የውክልና ማስረጃውን በተመለከተም ማስረጃው ዋጋ የሌለው መሆኑን በውሳኔው ላይ ከአሰፈረ በኋላ ይዘቱን ተመልክቶ የደረሰበት ድምዳሜ ሕጋዊ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ነሐሴ 19 ቀን 1990 ዓ.ም. የተደረገ የተባለው የውክልና ስልጣን ማስረጃ የተጠሪ አባት ለአመልካች አከራካሪውን ቤት እንዲጠብቁላቸው፣ እንዲያስተዳድሩላቸውና ሽጠው ገንዘቡን በመቀበል እንዲልኩላቸው በሚል የተቀመጠ ስለመሆኑ ይዘቱ ያሳያል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ የውክልና ስልጣን ለአመልካች የተሰጣቸው ስልጣን ቤቱን የማስተዳደር ነው፣ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ማከናወን የሚችሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2203 እና 2204 ስር በተመለከተው መሰረት የማስተዳደር ተግባራት የሚባሉትን እንጂ ቤቱን የመሸጥ የመለወጥ ተግባርን ጭምር አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በውክልና ስልጣኑ አመልካች ቤቱን ከማስተዳደር በተጨማሪ መሸጥና መለወጥ የሚችሉ ስለመሆኑ የሚያሳየውን የዓረፍተ ነገር ክፍል በመተው የተያዘ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ በእርግጥ ለአመልካች በተሰጠው ውክልና ስልጣን ላይ አመልካች ምን ምን አይነት ተግባራትን ማከናወን እንደሚችሉ ከተዘረዘረ በኋላ የተጠቀሰው የፍትሓ ብሔር ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 2199 ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚያስችል ስልጣን ልዩ ውክልና እንደሚያስፈልገው የፍ/በ/ሕ/ቁጥር 2205 በግልፅ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ ቁጥር ንዑስ አንድ ድንጋጌ ተወካዩ ከአስተዳደር ስራ በቀር ሌላ ስራ ለመስራት የሚያስፈልግ ሲሆን ልዩ ውክልና እንዲኖረው አስፈላጊ መሆኑን ሲያስቀምጥ ንዑስ ሁለት ድንጋጌ ደግሞ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን መሸጥ ወይም አስይዞ መበደር የሚችለው ልዩ የውክልና ስልጣን ሲኖረው ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን ቤት ለመሸጥ የሚያስችላቸው ልዩ ውክልና የላቸውም የተባለው በውክልና ሰነዱ የተዘረዘሩት የተወካዩ ኃላፊነቶች ሙሉ በሙሉ ይዘታቸው ሳይታይ ከመሆኑም በላይ በሰነዱ ላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2199 መሆኑ ለአመልካች የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ጠቅላላ ውክልና ስለመሆኑ ያሳያል በሚል ምክንያትም ጭምር ነው፡፡ ይሁን እንጂ የውክልና ሰነዱ ይዘት በግልፅ ውክልና ተቀባዩ የተሰጠው ስልጣን የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለመሸጥ የሚያስችል ስለመሆኑ እየገለፀ ስለልዩ ውክልና አስፈላጊነት የተቀመጠው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2205 በውክልና ስልጣን ሰነዱ ያለመጠቀሱ ውክልናው ልዩ የውክልና ስልጣን አይደለም ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ስለመሆኑ የሚያሳይ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ ዋናውና ቁልፍ ነገር ለውክልና ተቀባዩ የተሰጡት ተግባሮች በዝርዝርና ግልጽ ሁኔታ ተጠቅሰው በውክልና ሰነዱ ላይ መገኘት እንጂ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ያለመጠቀሳቸው አይደለም፡፡ የሰነዱ ይዘት ግልጽ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በውክልና ስልጣን ሰጪውና በውክልና ስልጣን ተቀባዩ አልተጠቀሱም ተብሎ ሰነዱ ዋጋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲያጣ ማድረግ የተዋዋዮችን ሐሳብ ውጤት እንዳይኖረው የሚያደረግ በመሆኑ በውል አተረጓጎም ደንቦችም ተቀባይነት የሌለው አካሄድ ነው የሚሆነው፡፡ ስለሆነም የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የውክልና ሰነዱን ይዘት ሙሉ በሙሉ ሳይመለከትና በሰነዱ ላይ ስለልዩ ውክልና ሥልጣን የሚደነግገው የፍትሓ ብሔር ሕግ ድንጋጌ አልተጠቀሰም በሚል እምነት አመልካች ከተጠሪ አባት ቤቱን ለመሸጥ የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን የለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2179 ፣ 2205 እና 2005 /1/ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

የተጠሪ አባት ቤት በአመልካች የተሸጠው በሕጉ አግባብ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት ነው ከተባለ ቀጥሎ መታየት ያለበት ተጠሪ ያላቸው መፍትሔ ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የውክልና ስልጣን ሰጡ የተባሉት ግለሰብ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸው ከመረጋገጡም በላይ አመልካች ቤቱ የተሸጠበትን ገንዘብ ለተጠሪ ወይም ሌሎች ሕጋዊ የሚች አቶ ተክሌ ኪዳኔ ወራሾች ሰጥቼአለሁ የሚል ክርክር በበታች ፍርድ ቤቶችም ሆነ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የላቸውም፡፡ ይልቁንም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የጽሑፍ መልስ ቤቱ የተሸጠበትን ገንዘብ ለተጠሪ ከመክፈል ውጪ ቤቱን ለመመለስ የሚገደዱበት አግባብ የሌለ መሆኑን ግልጽ አድርገው ጠቅሰዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በሕጉ አግባብ በተሰጠ የውክልና ስልጣን የተሸጠውን ቤት አመልካች እንዲያስረክቡ መጠየቅ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት ባይኖርም ቤቱ ተሸጠ የተባለበትን ገንዘብ ግን በወራሽነት መብታቸው ልክ መሠረት ከአመልካች ከመጠየቅ አይታገዱም፡፡ በመሆኑም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2310 ነሀሴ 12 ቀን 2003 ዓ.ም አመልካች አከራካሪውን ቤት ከማስተዳደር ባሻገር ለመሸጥ የሚያስችላቸው የውክልና ስልጣን የለም ተብሎ የተሰጠው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ አባት ነሐሴ 19 ቀን 1990 ዓ.ም. የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ማስረጃ በማስረጃነት ተቀባይነት የማይሰጥበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሲሆን የሰነዱ ይዘት ሲታይ አመልካች አከራካሪውን ቤት ለመሸጥ የሚያስችላቸው በመሆኑ ሽያጩ የተከናወነው አመልካች በተጠሪ አባት በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ስለሆነ አመልካች ለተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክቡ ሊገደዱ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካች ቤቱን የሸጡበትን የሽያጭ ገንዘብ ተጠሪ ካላቸው የወራሽነት መብት መጠን አንጻር ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 68498

ሰኔ 07 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ገብረ ክርስቶስ ገብረ እግዛብሔር

ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ

ተጠሪ፡- ሳባ እምነበረድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ነገረ ፈጅ አቶ ቴድሮስ ገብረ ዮሐንስ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የእምነ በረድ ሽያጭ ውል አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በማዕከላዊ ዞን አድዋ ምድብ ችሎት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር 2781 ሜትር ኩብ እምነበረድ ከቫት ውጭ በብር 939,948 /ዘጠኝ መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስምንት ብር/ ለመግዛት ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም ውል የተዋዋለና በዚህ ውል መሠረት ሻጭ /ተጠሪ/ 616.4 ሜትር ኩብ የእምነበረድ በብር 205,017.47 /ሁለት መቶ አምስት ሺህ አስራ ሰባት ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ አስረክቦኛል፡፡ ገዥው /አመልካች/ ብር 661,217.37 /ስድስት መቶ ስልሣ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰላሣ ሰባት ሣንቲም/ ቅድሚያ ክፍያ ከፍያለሁ፡፡ ተከሣሽ/ ተጠሪ/ በሽያጭ ውሉ መሠረት ዋጋው ከተጨማሪ እሴት ታክስ ውጭ ብር 734,930.55 የሆነ 2164.60 ሜትር ኩብ እብነበረድ አላስረከበኝም ስለዚህ በሽያጭ ውሉ መሠረት እብነበረዱን እንዲያስረክብ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ እስጢፋኖስ አስፋው የተባለ የድርጅቱ ግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ በክርክር ጣልቃ እንዲገባ የጠየቀ ሲሆን ከከሣሽ /አመልካች/ ጋር የተዋዋልነው የእብነበረድ ሽያጭ የለም፡፡ ከሣሽ ብር 661,217.37 አልከፈለም፡፡ በህግ ፊት የፀናና ተጠሪን የሚያስገድድ የእብነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የድርጅቱ ግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባለት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የሥር ፍርድ ቤት በወቅቱ የድርጅቱ ግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ የሆኑትንና በሽያጭ ውሉ ላይ የፈረሙት የተጠሪ የሥራ ኃላፊ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ አድርጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካች ምስክሮች የሰጡትን ቃልና የተጠሪን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምስክሮች ቃልና በግራ ቀኙ በኩል የፅሑፍ ማስረጃ ከመረመረና ከመዘነ በኋላ የተጠሪ የግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ ከከሣሽ /አመልካች/ ጋር የእብነበረድ ሽያጭ ውል የተዋዋለው ሥራ አስኪያጅ በቃል ትዕዛዝ መሆኑን ገልፆ የተከራከረ ሲሆን ጣልቃ ገብ ይህንን በማስተባበል አልተከራከረም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች /ከሣሽ/ ለተከሣሽ /ተጠሪ/ ብር 500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በቼክ የከፈለ ሲሆን ተከሣሹም 616.4 ሜትር ኩብ እምነበረድ ለከሣሽ /ተጠሪ/ አስረክቧል፡፡ ስለሆነም በከሣሽ /አመልካችና/ በተከሣሽ /ተጠሪ/ መካከል የፀና የእምነበረድ ሽያጭ ውል ያለ በመሆኑ ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ውጭ ዋጋው ብር 734,930.35 የሆነ 2164.60 ሜትር ኩብ እምነበረድ የማስረከብ ግዴታ አለበት በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጡት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪን በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል የሽያጭ ውጭ የመዋዋልና የመፈረም ሥልጣን ያለው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ ከሥልጣኑ ውስን ውጭ ከአመልካች ጋር የተዋዋለው የእምነበረድ ሽያጭ ውል ድርጅቱን የማያስገድድ በመሆኑ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ የእምነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አቶ እስጢፋኖስ አስፋው ከሥራ አስኪያጁ በተሰጠው የቃል ትዕዛዝ መሠረት የሽያጭ ውሉን መዋዋሉን በግልፅ በማመን መልስ ሰጥቷል፡፡ የሰው ምስክሮችም የሽያጭ ውሉ ተፈፅሞ እብነበረድ እርክክብ የተጀመረ መሆኑን በማረጋገጥ አስረድተዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የማረም ሥልጣን ያለው ቢሆንም በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳና በማስረጃ ያልተጋገጠ ፍሬ ጉዳይ በማንሣት ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሰበር ችሎት የህሊና ግምት መሠረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሥራ አስኪያጅ ባይፈርምበትም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሽያጭ ውል የተዋዋሉ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪን የሚያስገድድ ውል የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 27 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው መልስ የተጠሪ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በውሉ ላይ ስላልፈረመበት ተጠሪ የሽያጭ ውሉን ለማቋቋም አስፈላጊ የሆነውን ፈቃዱን ሰጥቷል ለማለት አይችልም፡፡ በክርክሩ በተጠሪ ጠያቂነት ወደ ክርክር የገቡት ሰው በሥር ፍርድ ቤት የሰጡት መልስ ሽያጩ የእጅ በእጅ ስለሆነ የውል ሰነድ አያስፈልግም ነበር፡፡ የፅሑፍ ውክልና ሣይኖረኝ በቃል ተነግሮኝ በስህተት የፈረምኩት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ስለዚህ ተጠሪን የሚያስገድድ ውል አይደለም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ የፈረሙትና ተጠሪን የሚያስገድድ የፀና ውል አለመኖሩን በማረጋገጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች እኔ ስለተጠሪ ውስጣዊ አሰራር የማውቀው ነገር የለም፡፡ ከዚህ በፊት የገበያ ዋና ክፍል ኃላፊው የፈረሙበት የሽያጭ ውል ከተጠሪ ጋር ተዋውየ ውሉ ተፈፃሚ ሆኖልኛል፡፡ የፅሑፍ ውክልና አልተሰጠም በሚል ምክንያት ብቻ ውሉ አልተደረገም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን በቼክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲከፈለው ተቀብሏል፡፡ ስለዚህ ውል የለም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም በማለት ሀምሌ 7 ቀን 2003 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪና አመልካች የተዋዋሉት የእምነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ የህግ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተፃፈውን ጭብጥ ለመወሰን ፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የማዕከላዊ ዞን የአድዋ ምድብ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያረጋገጧቸውን ፍሬ ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ በማየት የአመልካችንና የተጠሪን ምስክሮች ቃል የሰማውና የግራ ቀኙን የሰነድ ማስረጃ የመዘነው የአድዋ ምድብ ችሎት የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊና አመልካች ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የእምነ በረድ ሽያጭ ውል የሚል ርዕስና ዝርዝር ይዘት ያለው የፅሑፍ ሰነድ የተፈራረሙ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ጠቅላላ ዋጋው ቫት ሣይጨምር ብር 939,948 /ዘጠኝ መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስምንት ብር/ የሆነ 2781 ሜትር ኩብ እምነበረድ ለመሸጥ መስማማቱን አመልካችና ተጠሪ ሰነዱን በተፈራረሙበት ዕለት አመልካች ብር 500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በቼክ የከፈለ መሆኑንና ሰነዱን ከተፈራረሙ በኋላ ተጠሪ ከቫት ውጭ ዋጋው ብር 205,017.47 /ሁለት መቶ አምስት ሺህ አስራ ሰባት ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ የሆነ መጠኑ 616.4 ሜትር ኩብ እብነበረድ ለአመልካች ማስረከቡ በማስረጃ እንደተረጋገጠ በውሣኔው ገልፆል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪን በመወከል ፊርማቸውን በሰነዱ ላይ ያሣረፉት /የፈረሙት/ የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ተደርጎ ሽያጩ የእጅ በእጅ ሽያጭ ስለሆነ ሰነድ አያስፈልገውም ነበር፡፡ በስህተት ነው የፈረምኩት ሰነዱ ላይ የፈረምኩት ሥራ አስኪያጁ በቃል ትዕዛዝ ስለሰጠኝ ነው በማለት መልስ የሰጠ መሆኑ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው የገለፃቸውና ከላይ የዘረዘርናቸው ፍሬ ጉዳዮች ትክክለኛና የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያረጋገጣቸው በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት በመሰረዝ አቋሙን በግልፅ አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያሣየን ከላይ የተገለፁት ፍሬ ጉዳዮችን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተመሣሣይ መደምደሚያ ላይ የደረሡ መሆኑን ነው፡፡

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ከላይ በዝርዝር የተገለፁትና ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮች በተጠሪና በአመልካች መካከል ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም. የእምነበረድ ሽያጭ ውል የተደረገ መሆኑን ወይም ውል ያልተደረገ መሆኑን ወይም ውሉ ጉድለት ያለበት መሆኑን ለመወሰን ያላቸውን ፋይዳ የተረዱበትና አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች የተረጎመበት ሁኔታ መመልከቱ ሁለተኛው መሠረታዊ ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪን በመወከል በህግ የፀና ውል የመዋዋል ሥልጣን ያለው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በውሉ ላይ ያልፈረመ በመሆኑ ተጠሪና አመልካች ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም. ያደረጉት የእምነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሁለት ሰዎች መካከል የሽያጭ ውል አለ ለማለት ሻጭ የሆነው ወገን ገዥ ለሆነው ሌላው ወገን ዋጋ በገንዘብ የተወሰነውን አንድ ነገር ገዥው ሊከፍለው ግዴታ በገባበት መሠረት ሊያስረክብና ባለቤትነቱን ሊያስተላልፍበት የሚገደድበት ውል ሲመሠርት እንደሆነ መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2266 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ ለሽያጭ ውሉ ድርጅቱን በመወከል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1178/ሀ/ መሠረት ፈቃድና ስምምነቱን መስጠት የሚችለው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ በውሉ ላይ ሥራ አስኪያጁ ያልፈረመበት በመሆኑ በህግ ፊት የፀና የሽያጭ ውል የለም በማለት ይከራከራል፡፡ በእርግጥ ሥልጣን ያለው ሥራ አስኪያጅ በንግድ ድርጅቱ ሥም በውክልና የመፈረምና ሥራውንም ለማካሄድ እንደሚችል በንግድ ህጉ አንቀፅ 33 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገ ሲሆን ፣ ሥራ አስኪያጁ የንግድ ድርጅቱ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማናቸውንም ግዴታ የመፈፀም ሙሉ ሥልጣን እንዳለው እንደሚገመት በአንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ ከላይ የጠቀስናቸው የህግ ድንጋጌዎች ተጠሪን በመወከል የእምነበረድ ሽያጭ ውልም ሆነ ሌሎች ውሎችን የመዋዋል ሙሉ ሥልጣን ያለው የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የተጠሪን ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ያህል ሙሉ ሥልጣን የሌላቸው የተጠሪ የሥራ ኃላፊዎች በሚያደርጉት የሽያጭ ውል ተጠሪ በልዩ ሁኔታ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ሁኔታ ይኖራል ወይስ አይኖርም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የተጠሪ ውክልና ባለሙሉ ሥልጣን የሆነው ሥራ አስኪያጅ አመልካችና ተጠሪ ታህሣሥ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በተዋዋሉት የእምነበረድ ሽያጭ ስምምነት ሰነድ ላይ ባይፈርምም፣ ተጠሪ ለአመልካች እምነበረድ በመሸጥ የገባውን የውል ግዴታ ሰነዱ ከመፈረሙ በፊት ያውቀው እንደነበርና በውሉ ላይ ስምምነቱን በፊርማው ያረጋገጠው የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ በውሉ ላይ የፈረመው ከተጠሪ ሥራ አስኪያጅ በተሰጠው የቃል ትዕዛዝ መሠረት መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት በሰጠው መልስ አረጋግጧል፡፡ ይህንን ፍሬ ጉዳይ ተጠሪ አላስተባበለም፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ “የእጅ በእጅ ሽያጭ ስለሆነ ውል አያስፈልግም? የፅሑፍ ውክልና ሳይኖረኝ በቃል ተነግሮኝ በስህተት የፈረምኩት ሰነድ” ነው በማለት የተከራከረ መሆኑን በግልፅ ያሰፈሩ ሲሆን የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በፅሑፍ ሣይሰጠው የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ የፈረመው ሰነድ ምንም አይነት ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ ድርጅቱ ከአመልካች ጋር የሚገባውን የእምነበረድ ሽያጭ ውል ግዴታ አስቀድመው አውቀውትና ተስማምተውበት ሰነዱን ሊፈርሙ የማይችሉ በመሆናቸው የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ ውሉን እንዲፈርሙ የቃል ትዕዛዝ የሰጡ መሆናቸውን ተጠሪ በግልፅ ክዶ ካልተከራከረና ካላስተባበለ የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ የሽያጭ ውሉን የፈረመው ከሥራ አስኪያጁ በተሰጠው የቃል ትዕዛዝ ነው የሚለውን ፍሬ ጉዳይ እንዳመነ የሚቆጠር መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀፅ 2/ሠ/ እና ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 235 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ ድርጅቱን በመወከል የእምነበረድ ሽያጭ ውሉን እንደዋዋል በሰጠው የቃል ትዕዛዝ መሠረት የግዥ ክፍል ኃላፊው የእምነበረድ ሽያጭ ውሉን ፈርሟል፡፡ የእምነ በረድ ሽያጭ ውል በልዩ ፎርም እንዲደረግ የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ ስለሆነም የተጠሪን ድርጅት የመወከል ሙሉ ሥልጣን ያለው ሥራ አስኪያጅ በልዩ ሁኔታ ከአመልካች ጋር የሚደረገውን የእምነበረድ ሽያጭ ውል ድርጅቱን በመወከል እንድፈራረም ለተጠሪ ግዥ ክፍል የሰጠው ውክልና የግድ በፅሑፍ መሆን እንደሌለበት “ስለውሉ አፈፃፀም ሕጉ አንድ አይነት ፎርም እንዲደረግ ያስገደደ እንደሆነ ውሉ የሚፈፀምበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥልጣን በዚሁ አይነት ፎርም ለወኪሉ መስጠት አለበት " በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2180 ድንጋጌ ይዘትና ይኸው ድንጋጌ በተቃራኒ ሁኔታ ሲታረሳም /acontrartio interpretation/ የሚኖረውን ውጤትና ተፈፃሚነት ወሰን በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም የተጠሪ ድርጅት ወኪልና ባለሙሉ ሥልጣን የሆነው የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2215 ንዑስ አንቀፅ 3 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2180 መሠረት በማድረግ የሰጠውን የቃል ውክልና በመቀበል የተጠሪ ድርጅት የግዥ ክፍል ኃላፊ ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም ከአመልካች ጋር ያደረገው የእምነበረድ ሽያጭ ውል በተጠሪ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ፅውቅና ስምምነትና ትዕዛዝ የተፈፀመ የሽያጭ ውል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ከላይ በዝርዝር ከተገለፀው በተጨማሪ ተጠሪ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በቃል የሰጠው ትዕዛዝና ውክልና የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊ ከአመልካች ጋር ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የተፈራረመውን ሰነድ ከተሰጠው ሥልጣንና ውክልና ውጭ ነው በማለት ውሉን በመቃወም ለአመልካች የፃፈው ደብዳቤ ስለመኖሩ አላስረዳም፡፡ ተጠሪ የግዥ ክፍል ኃላፊው የተፈራረመውን ውል ያፀደቀው መሆኑን በግልፅ ባያረጋግጥም ይህንን ሰነድ መሠረት በማድረግ የተቀበለውን የብር 500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ ቼክ ጥቅም ላይ ማዋሉና ሰነዱ ከተፈረመ በኋላ ከቫት ውጭ ዋጋው ብር 205,017.47 /ሁለት መቶ አምስት ሺህ አስራ ሰባት ብር ከአርባ ሳባት ሣንቲም/ የሆነ 616.4 ሜትር ኩብ እምነበረድ ለአመልካች ያስረከበ በመሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህም የተጠሪ የግዥ ክፍል ኃለፊ ከአመልካች ጋር ያደረገውን የእምነበረድ ሽያጭ ውል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2214 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች መሠረት ፈቅዶ እንደተቀበለው የሚያስቆጥረው ነው፡፡ ስለሆነም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ ከገለፅናቸው አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር ሣያገናዝብ በውሉ ላይ የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ አለመፈረማቸውን ብቻ መሠረት በማድረግ በተጠሪና አመልካች መካከል የተደረገ የእብነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

4. ተጠሪና አመልካች ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም የእምነበረድ ሽያጭ ውል ተዋውለዋል፡፡ በህግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋይ ወገኖች መካከል ህግ መሆናቸውና የህግ ያህል አስገዳጅነት ያላቸው መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ ውሉ ከተደረገበት ቀን አንስቶ በአንድ መቶ ሰማኒያ ቀን ውስጥ 2781 ሜትር ኩብ እብነበረድ በብር 939,948 ለአመልካች ለመሸጥ በገባው የውል ግዴታ መሠረት ዋጋው ብር 205,017.47 ሣንቲም ከቫት ውጭ የሆነ 616.40 ሜትር ኩብ የእምነበረድ ብቻ ያስረከበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው ተጠሪ 2164.60 ሜትር ኩብ እብነ በረድ የማስረከብ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከፍትብሔር ህግ ቁጥር 2274 ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ተጠሪ ለሚስረክበው እብነበረድ በውሉ መሠረት ዋጋውን የመክፈልና የገዛውን ዕምነበረድ የመረከብ ግዴታ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2303 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ውሉን በተዋዋለበት ቀን የብር 500,000 በቼክ ለተጠሪ ክፍያ የፈፀመ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች በውሉ መሠረት ሊከፍል የሚገባውን ብር 439,948 /አራት መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስምንት ብር / መክፈል ቀሪውን 2164.60 ሜትር ኩብ እብነበረድ ተረክቦ የመውሰድ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለበት ። ስለሆነም የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ በመሻር በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ የእምነበረድ ሽያጭ ውል የለም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
2. የትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን የአድዋ ምድብ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል።
3. ተጠሪና አመልካች ታህሣሥ 29 ቀን 2002 ዓ.ም ያፀናና ህጋዊ ውጤት ያለው የእምነበረድ ሽያጭ ውል ተዋውለዋል በማለት ወስነናል።
4. በውሉ መሠረት ተጠሪ 2164.60 ሜትር ኩብ እምነበረድ የማስረከብ ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል።
5. በውሉ መሠረት አመልካች ከዚህ በፊት በቼክ ለተጠሪ ከከፈለው ብር 500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በተጨማሪ ብር 439,948 /አራት መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ስምንት ብር/ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት ወስነናል።
6. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፈሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1/ አቶ አዕብሃ ወልዳይ
2/ አቶ ቅባቱ ግደይ
} አቶ ሀይማኖት ቢተው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዙሪያሽ አሰግድ የክልሉ ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ ፀሐይ አበራ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርባ ልጇ የሆነችው ወ/ሮ ድንቁ መኮንን በአሶሳ ዞን ኩርሙክ ወረዳ በኩሙሩክ ከተማ ውስጥ ከወ/ሮ ምስራቅ ኣንጋሉ ገዝታና አስፋፍታ ስትመራው የነበረውን የድርጅት ቤት በውክልና እንዲስተዳድርላት ለአንደኛ ተከሳሽ የውክልና ሥልጣን ሀምሌ 13 ቀን 1996 ዓ.ም ሰጥታው ሄዳለች፡፡ ወ/ሮ ድንቁ መኮንን ሀምሌ 29 ቀን 1998 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት የተለየች በመሆኑ የአንደኛው ተከሳሽ /አንደኛው አመልካች/ የውክልና ሥልጣን ቀሪ ሆኗል፡፡ ተከሳሾች /አመልካች/ ሟች ከሞተች በኋላ ለሁለት ዓመት የቤት ኪራይ ሲከፍሉ ቆይተው ከዚያ በኋላ ቤቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ሆነው ስላልተገኙ ክስ ያቀረበበትን ንብረት እንዲለቁና በየወሩ ብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ ሂሳብ ኪራይ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ አመልካቾች በተከሳሽነት ቀርበው የተጠሪ ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ አንደኛ አመልካች ከወ/ሮ ድንቁ መኮንን ሀምሌ 13 ቀን 1996 ዓ.ም. በተሰጠው የመሸጥና የመለወጥ የውክልና ሥልጣን መሠረት ቤቱን ሰኔ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. ለሁለተኛው ተከሳሽ /ሁለተኛ አመልካች/ የሸጡ መሆናቸውንና ገዥው ሁለተኛው አመልካችም ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን ተረክበው እያለሙና እያስፋፉ የሚገኙ መሆኑን በማንሣት ተከራክረዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አንደኛው አመልካች ቤቱን ለሁለተኛ አመልካች ሰኔ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. በተደረገ የሽያጭ ውል የሸጠ መሆኑንና ሽያጩም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትህ ቢሮ ቀርቦ የፀደቀ መሆኑን በመግለጽ የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ አመልካቾችን በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርባለች፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በፍታብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርባ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አንደኛ አመልካች የሽያጭ ውሉን ፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ በመቅረብ ያስመዘገበውና ስመሃብቱም ለገዥ ለሁለተኛው አመልካች እንዲዛወር ያደረገው ወካይም ወ/ሮ ድንቁ መኮንን ከሞቱ በኋላ በ2001 ዓ.ም እና በ2003 ዓ.ም. በመሆኑ አንደኛ አመልካች የውክልና ስልጣኑ ቀሪ ከሆነ በኋላ የፈፀመው ተግባር ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት አመልካቾች ክርክር የተነሳበትን ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት በአብላጫ ድምጽ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት መስከረም 23 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ሁለተኛ አመልካች የቤቱ ባለሀብት የሆነችው ወ/ሮ ድንቁ መኮንን የሰጠችው ውክልናን በሚመለከት ከአንደኛ አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት ብር 4000/ አራት ሺህ ብር/ በመግዛት እስከ ብር 400,000 /አራት መቶ ሺህ ብር/ በላይ በማውጣት ገንብቻለሁ፡፡ ስለዚህ ወደ ነበሩበት ይመለሱ ቢባል የማይቻል ሆኖ እያለ ውሉ ፈራሽ ነው መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች ታህሣስ 13 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ሁለተኛ አመልካች ቤቱን የቤቱ ባለሀብት ወኪል ከሆነው አንደኛ አመልካች ገዝቸአለሁ በማለት የሚከራከረው የህጉን ፎርም ሳያሟላና ሟች በሞት ከተለየችና የአንደኛ አመልካች የውክልና ስልጣን ቀሪ ከሆነ በኋላ ከቅን ልቦና ውጭ የፈፀሙት ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የቤት ሽያጭ ውሉ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ሟች ከሞተች በኋላ ቀርቦ የተመዘገበና አንደኛ አመልካች ይህንን ተግባር ያከናወነው ወካይዋ መሞቷንና የውክልና ሥልጣኑ ቀሪ መሆኑን እያወቀ በመሆኑ በአንደኛ አመልካችና በሁለተኛ አመልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውሉ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች ጥር 1 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ሰበር ችሎት አንደኛ አመልካች በክልሉ ፍትህ ቢሮ በመቅረብ የሸያጭ ውሉን ያስመዘገበው ወካይዋ ወ/ሮ ድንቁ መኮንን ከሞተችና የውክልና ስልጣኑ ቀሪ ከሆነ በኋላ በመሆኑ የቤት ሽያጭ ውሉ ፈራሽ ወይም ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አከራካሪው ቤት የሟች ወ/ሮ ድንቁ መኮንን ሀብት የነበረ መሆኑና ድንቁ መኮንን አንደኛ አመልካች ይህን ቤት እንዲያስተዳድር እንዲሸጥ እንዲለውጥ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2205 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ሀምሌ 16 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠችው መሆኗንና ወ/ሮ ድንቁ መኮንን ሀምሌ 29 ቀን 1998 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት የተለየች መሆኑ የሚያከራክሩ ፍሬ ጉዳዮች አይደሉም፡፡

ወካዩ የሞቱ እንደሆነ በሥፍራው አለመኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ለመስራት ችሎታ ያጣ እንደሆነ ወይም በንግድ መውደቅ ኪሣራ ደርሶበት እንደሆነ ለጉዳዩ ተቃራኒ የሚሆን ውል ካልተገኘ በቀር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውክልና ሥልጣኑ ወድያውኑ የሚቀር መሆኑን የፍታብሔር ሥ/ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ አንደኛ አመልካች በተሰጠኝ ውክልና መሠረት ለሁለተኛ አመልካች ቤቱን የሸጥኩት ሰኔ 20 ቀን 1997 ዓ.ም. ወካይዋ ከመሞቷ በፊት ነው በማለት የሚከራከርና ሁለተኛ አመልካችም ይህንን የመከራከሪያ ነጥብ የሚያቀርቡ ቢሆንም የቤት ሽያጭ ውሉ ፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ የተመዘገበው ሟች ወ/ሮ ድንቁ መኮንን በሞት ከዚህ ዓለም ከተለየች በኃላና የአንደኛ አመልካች የውክልና ሥልጣን በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት ቀሪ ከሆነ በኃላ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የአንድን ንብረት ባለሃብትነት በውል ለሌላ ሰው የሚተላለፈው ባለሃብት ወይም ባለሃብቱ የንብረቱን ባለቤትነት በውል ለሌላ እንዲያስተላልፍ የፀና ልዩ የውክልና ስልጣን ባለው ሰው እንደሆነ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1204 ንዑስ አንቀጽ 2፣ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2005 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አንደኛ አመልካች ሟች ድንቁ መኮንን በሰጠችኝ ልዩ የውክልና ሥልጣን መሠረት ቤቱን በብር 4000 (አራት ሺህ ብር) ለሁለተኛ አመልካች የሸጠ መሆኑን በማረጋገጥ በክልሉ ፍትህ ቢሮ የውክልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ያስመዘገበው በ2001 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ይህም የሚያሣየው ሁለተኛው አመልካች በፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በኩል በ2001 ዓ.ም የሟች ወ/ሮ ድንቁ መኮንን ቤት ለመግዛት ያደረጉት ውል የቤቱን ባለሃብትነት ለማስተላለፍ የፀና የውክልና ስልጣን ከሌለው ከአንደኛው አመልካች ጋር የተደረገ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አንደኛ አመልካች ለሁለተኛው አመልካች የድንቁ መኮንንን ቤት ለመሸጥ ያደረገው ውል ፈራሽና ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የዘረዘርናቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አነስተኛው ድምጽ የአንደኛው አመልካች ሟች ከሞተች በኃላ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በኩል ውሉን ማስመዝገቡ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚሸፈን ተግባር እንደሆነ ትንታኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የሸያጭ ውሉ የተደረገው ሰኔ 20 ቀን 1997 ዓ.ም ተደርገ ውሉ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ በ2002 ዓ.ም የተመዘገበ መሆኑን ጠቅሰው የአንደኛው አመልካች አድራጎት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚሸፈን ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ አመልካች ሁለተኛ አመልካች የቤት ሽያጭ ውል የፈፀመበት እርግጡን ቀን ተብሎ የሚያዘው እነርሱ ውሉ የተደረገበት ቀን ነው ብለው በውሉ ሰነድ ላይ የፃፉት ቀን ሣይሆን የሽያጭ ውሉን የክልሉ ፍትህ ቢሮ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ተቀብሎ የመዘገበበት ቀን እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2015(ሀ) በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ የአመልካቾች ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቅጽ 2 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ወካዩ ከሞተ በኃላ ተወካዩ የቤት ሽያጭ ውል እንዲያከናውን ወይም የቤት ሽያጭ ውሉን ለመፈፀም የውክልና ስራውን እንዲቀጥል ለማድረግ ታስቦ የተቀረፀ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካቾች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2232 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌን በመጥቀስ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛ አመልካች ገዝቸዋልሁ የሚሉትን ቤት ባለሃብትነት ለማስተላለፍ መብት ወይም የፀና የውክልና ስልጣን ከሌለው ሰው ጋር ያደረጉት ውል ከጅምሩ ፈራሽና ህጋዊ ውጤት የሌለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ ከቀረበው ፍሬ ጉዳይ በእጅጉ የተለየውንና ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 47800 ሰጥቶት የነበረውን የህግ ትርጉም በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ሁለተኛ አመልካች ተጠሪ የማይገባትን ብልጽግና አግኝታለች የሚል ከሆነ አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በተጠሪ ላይ ክስ የማቅረብ መብቷን ይህ ውሣኔ የሚገድበው አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 25 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል ይባፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሪት አሊያት ይማም መዝይን - ጠበቃ የሺጥላ አሰፋ ቀረበ

መልስ ሰጭ፡- አቶ እምነቱ እንደሻው - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የአሁን አመልካች ወኪል ናቸው በተባሉት እና በአሁን ተጠሪ መካከል ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል አመልካችን ሊያስገድድ የሚችልበት አግባብ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ነጥብ ለይቶ ለመወሰን ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ ሆነው በአሁን አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ሲሆን፤ ይዘቱም፣ የአሁን አመልካች በወኪላ አማካኝነት በ1994 ዓ.ም በተደረገ ውል በአዋሳ ከተማ በቀድሞ ከፍተኛ 02 ቀበሌ 04 ክልል በካርታ የምስክር ወረቀት ቁጥር 5045 የሚታወቀውን እና በ3000 ካ.ሜትር ያረፈውን ቤት በብር 300,000 (ሦስት መቶ ሺህ ብር) ሸጠውልኛል፡፡ በዚህም የሽያጭ ውል መሰረት ብር 95,000.00 (ዘጠና አምስት ሺህ ብር) ውሉ በተደረገበት ዕለት ወስደዋል፡፡ ብር 20,000.00(ሃያ ሺህ ብር) ደግሞ የካቲት 30 ቀን 1994 ወስደዋል፡፡ ስለዚህ ቀሪውን 185,000,00 ተቀብለው እንደውሉ እንዲፈጽሙ ይደረግልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁን አመልካችም በተከሳሽነት በሰጡት መልስ የቤት ሽያጭ ውል ፈጸመ ለተባለው አባቴ ውል ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ የሰጠሁት የውክልና ሥልጣን የለም ስለዚህ በ1994 ዓ.ም. የሰጠሁት ውክልና ስለሌለ የሸጥኩትም ሆነ የተቀበልኩት ገንዘብ የለም፡፡ አይመለከተኝም የሽያጭ ውል ነው የተባለው በቅንብር እንደተመዘገበ ለማስመሰል የተደረገ እንጂ በአዋዋይ ፊት የተደረገ አይደለም፡፡ ተሸጠ የተባለው ቤት አዋሳ ከተማ ስለሚገኝ ሊመዘገብ የሚችለው በዚሁ ከተማ አስተዳደር ሥር በሚገኘው መዝጋቢ አካል እንጂ በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ሊሆን አይችልም ይህ ተመዘገበ የተባለውም የሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ በቁጥር 1304/2003 በተፃፈ ደብዳቤ ይህ ውል በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ ውል ነው ለማለት የማይቻል መሆኑን ገልፆ ማረጋገጫ ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም እኔ ለአባቴ የውክልና ሥልጣን ከሰጠሁበት ከጥር 14 ቀን 1995 ዓ.ም በፊት የሸያጭ ውሉ ተደርጓል ስለተባለ እኔ ባልሰጠሁት የውክልና ሥልጣን ተደረገ በተባለው ረቂቅ ውል እና በሐሰት ተመዝግቧል የተባለው ውል እኔን የማይመለከተኝ ስለሆነ ከወጭና ኪሳራ ጋር እንድሰናበት ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ በፍ/መ/ቁ 10287 ሐምሌ 13 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተወካይና ከሳሽ በ1994 ዓ.ም የሽያጭ ውል በተዋዋሉበት ጊዜ ሻጩ ህጋዊ ውክልና ያልነበረው መሆኑ ቢታወቅም፤ ተወካዩ በ1994 ዓ.ም የገቡት ውል መስከረም 25 ቀን 1998 ዓ/ም መመዝገቡ ተረጋግጧል፡፡ ውሉ በተመዘገበበት ጊዜ ምስክሮች ውል አዋዋይ ፊት ቀርበው የመሰከሩ ባለመሆኑ በውሉ አመዘጋገብ ጊዜ የተፈጠረው ጉድለት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ይህ ውል ከተመዘገበበት ከ1998 ዓ.ም በፊት ጥር 04 ቀን 1995 ዓ.ም ተከሳሽ ለወኪላቸው ውክልና የሰጡ ስለሆነና ተወካዩ ያለህጋዊ ውክልና በ1994 ዓ.ም የገቡት ውል የውክልና ሥልጣን ከተገኘ በኋላ በ1998 ዓ.ም በመመዝገቡ የሽያጭ ውሉን ረቂቅነት ያስቀረዋል፡፡ ስለዚህ በ1994 ዓ.ም. የተከሳሽ ወኪል እና ከሳሽ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ተወካዩ ህጋዊ ውክልና እስካገኘበት ጊዜ ድረስ ረቂቅ ነው የሚባል ቢሆንም ረቂቅ መሆኑ በሲዳማ ዞን መምሪያ በ1998 ዓ.ም ቀርቦ ከተመዘገበ በኋላ ህጋዊነቱን ስላገኘ ተከሳሽን ያስገድዳታል፡፡ ስለሆነም እንደውሉ ልትፈጽም ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ አቅራቢነት ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በ1998 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የምዝገባ ስራ የአመዘጋገቡን ሥርዓት ካላሟላ ቅሬታ ያለው ወገን በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 7 መሰረት ሥርዓቱን ጠብቆ መፍትሄ ማግኘት ከሚቻል በቀር የማስረጃውን ተቀባይነት ከወዲሁ ውድቅ ለማድረግ አይቻልም፡፡ በዚህም አንቀጽ መሰረት አመልካች አቤቱታ የማቅረብ መብቷ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ከዚህ በፊት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር መ/ቁ 20890 በሆነው በአመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በወ/ሮ ዓለምነሽ ኃይሌ መካከል በነበረው ጉዳይ ትርጉም የሰጠበት መሆኑን ጠቅሶ ግራ ቀኙን የሚያከራክረው እና በ1994 ተደረገ የተባለው ውል በአዋዋይ ፊት የተደረገ ሆኖ ተገኝቷል የሚለውን መሰረት አድርጎ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናቱ የተነሣ የአሁን አመልካች በዚህ የፌዴራል ጉዳይ በሆነው የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚሉበትን የመከራከሪያ ነጥቦች በመዘርዘር ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪም ቀርቦ ለሰበር አቤቱታው ዝርዝር መልስ ሰጥቶበታል ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስለጉዳዩ ያቀረቡትን የፅሁፍ ክርክር እንዳየነው ሁለቱም ወገኖች በየፊናቸው በሥር ፍ/ቤቶች ያቀረቡትን ክርክር በማጠናከርና በማብራራት የቀረበ ከመሆኑ በቀር የይዘት ለውጥ ያለው አይደለም፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አነሳስና አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ለነገሩ መነሻ የሆነው የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው የአመልካች ወኪል የተባሉት ሻጭ ከንብረቱ ባለቤት ከአሁን አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን ሳይኖራቸው በ1994 ዓ.ም ከአሁን ተጠሪ ጋር ያደረጉት ስለመሆኑና ይህም ውል በአዋዋይ ፊት ያልተደረገ ለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም የተነሣ በዚህ አኳኋን የተደረገው ውል እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ የረቂቅነት ደረጃ እንደነበረውም የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ዳኝነት ተረጋግጧል፡፡

ሆኖም የአሁን አመልካች ጥር 04 ቀን 1995 ዓ.ም. ሻጭ ለነበረው ወገን የውክልና ሥልጣን የሰጡ የመሆኑን እና በ1994 ዓ.ም የተደረገው ውል በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ቀርቦ በ1998

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓ.ም. ተመዝግቦ ተገኝቷል የሚሉትን አውነታዎች (facts) በመያዝና ከዚሁም በመንደርደር በ1994 ዓ.ም የተደረገው ውል ረቂቅ መሆኑ ቢታወቅም በ1998 ዓ.ም በውል አዋዋይ ፊት የተመዘገበ ሆኖ ስለተገኘ ረቂቅነቱ ቀርቷል ህጋዊ ደረጃውን አግኝቷል። እንዲሁም ሻጭ ቤቱን በሸጠበት ጊዜ ከንብረቱ ባለቤት ከአሁን አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል ሥልጣን የነበረው ባይሆንም ውሉ በአዋዋይ ፊት ቀርቦ ከመመዝገቡ በፊት ሻጭ በጥር 04 ቀን 1995 ዓ.ም. የውክልና ሥልጣን አግኝቷል። ስለሆነም በ1994 ዓ.ም የተደረገው ውል በወኪሏ በአሁን አመልካች እንደተደረገ ይቆጠራል የሚለውን አተረጓጎም በመከተል ውሉ የአሁን አመልካችን የማስገደድ ኃይል አለው የሚል ዳኝነት ሰጥተዋል።

ይሁን እንጂ በአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠው ፍርድ እንደተገለፀው ይህ ክርክር ያስነሳው የቤት ሽያጭ ውል በ1998 ዓ.ም በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ቀርቦ እንደተመዘገበ ገልፆ የአሁን ተጠሪ ቢከራከርም በሰነዱ ላይ በእማኝነት/በምስክርነት የተጠቀሱት ምስክሮች በአዋዋይ ፊት ቀርበው ያስመሰከሩ መሆኑን በፍሬ ነገር ረገድ አረጋግጧል። ከዚህም በቀር እራሱ ውሉን በእራሱ ፊት መደረጉን አረጋገጠ የተባለው የሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ በቁጥር ሲ/ዞ/ፍ/መ/1304/2003 በ14/10/2003 እና በቁጥር ሲ/ዞ/ፍ/መ/1403-03 በ06/11/03 ዓ.ም በተፃፉ ማረጋገጫ ውሉ የተደረገው አዲስ አበባ ወሎ ሰፈር፤ የምስክሮችም አድራሻ አዲስ አበባ መሆኑንና ምስክሮችም በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ፊት ቀርበው የውሉን መደረግ አለማረጋገጣቸውን አረጋግጧል። በተለይም ውል አዋዋይ ፊት መሰከሩ ከተባሉት ምስክሮች መካከል ቅድስት በቀለ የተባለችውን አስቀርቦ እንዳረጋገጠው ውሉ አዲስ አበባ ወሎ ሰፈር ተደርጎ ምስክሮች በአዋዋይ ፊት ሳይቀርቡ እንዴት ተመዘገበ ሊባል እንደቻለ የአሁን ተጠሪ ቀርቦ እንዲያስረዳ ፍትህ መምሪያው ሲጠይቀው በተጠሪ ድርጅት ደብዳቤ በተረጋገጠ ተጠሪው በአዋሳ ከተማ ሊገኝ አይችልም በሚል ምክንያት ቀርቦ ሊያስረዳ ያልቻለ መሆኑንና ውሉ ተመዘገበ የተባሉትን ሂደት ሁሉ ካጣራ በኋላ ይህ 1994 ዓ.ም. ተደረገ ተብሎ በ1998 ዓ.ም በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ተመዘገበ የተባለው ውል በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ አለመሆኑን አረጋግጧል።

በመሆኑም ከዚህ በላይ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው የውል አደራረግ ሂደትን የማረጋገጥ የመመዝገብ ሥልጣን ባለው አካል እና ክርክር ያስነሳውን ውል እንደ ሥርዓቱ በእራሱ ያልተመዘገበ መሆኑን እያረጋገጠ፣ ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ፍሬ ነገር በማስረጃ መረጋገጡን እየተረዱ የሥር የአዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህ የውል አመዘጋገብ ጉድለት እንደተጠበቀ ሆኖ.... በሚል አገላለጽ በገዘታ ማለፉ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 20890 በሆነው በአመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በወ/ሮ ዓለምነሽ ኃይሌ መካከል ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ከዚህ ከተያዘው ጉዳይ ጋር የማይመሳሰል እና ተመሳሳይ ትርጉም ሊከተል የማይችል መሆኑ እየታወቀ የአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) የተመለከተውን ድንጋጌ ያለቦታው በመጥቀስ ክርክር ያስነሳውና በ1994 ዓ.ም አ/አበባ ከተማ ወሎ ሰፈር ተደረገ የተባለው ውል በ1998 ዓ.ም በሲዳማ ዞን ፍትህ መምሪያ ቀርቦ ተመዝግቧል ከሚል ውሳኔ መድረሳቸው ፍ/ቤቶች የሚሰጧቸው ትዕዛዞች፣ ብይኖች፣ ፍርዶች እና ማናቸውም ዳኝነት በተከራካሪ ወገኖች የተነሱትን ክርክሮች ከተከራካሪ ወገኖች ክርክር አንፃር በጭብጥነት በተያዙት ጉዳዮች በግራ ቀኙ የተሰማውን ማስረጃ መሰረት በማድረግና በዚህም በማስረጃ የተረጋገጠውን ጉዳይ ለመቀበልም ሆነ ውድቅ ለማድረግ የቻለበትን ምክንያትና አግባብነት ያለውን ህግ መሰረት በማድረግ ሊሆን ይገባል በሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182 እና 183 ስለፍርድ አፃፃፍ የተመለከተውን ሥርዓት የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም በ1994 ዓ.ም የተደረገው ውል ረቂቅ ሆኖ እስከ 1998 ዓ.ም የቆየ ቢሆንም በ1998 ዓ.ም ውል አዋዋይ ፊት ቀርቦ የተመዘገበ ሆኖ ስለተገኘ ህጋዊነቱን አግኝቷል የሚለው የፍርድ መነሻ ሀሳብ ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ሻጭ የተባለው ወገን ንብረቱን በ1994 ዓ.ም ሸጧል ከተባለ በኋላ የአሁን አመልካች ጥር 04 ቀን 1995 ዓ.ም ንብረቱን ሸጠ ለተባለው ወገን የውክልና ሥልጣን የመስጠታቸው ተግባር በእራሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678(ሐ)፣ 1719(2) እና 1723 በተደነገገው መሰረት ህጉ የሚጠይቀውን ማሟያ አሟልቶ ባለመገኘቱ ምክንያት በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል የለም፤ ውሉ ረቂቅ ነው የተባለበትን ማናቸውም ክንውን ለመቀበል ህግ አያስገድዳቸውም፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን አመልካች በ1995 ዓ.ም. የሰጡት የውክልና ሥልጣን አገልግሎት የውክልና ሥልጣን ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ለሚከናወኑ ህጋዊ ተግባራት ተብሎ የተሰጠ መሆኑን ከሚያመለክት በቀር የውክልና ሥልጣን ከመስጠቱ በፊት ወኪሉ የፈፀመውንም ማናቸውም ተግባር ለመቀበል እንደፈቀዱ፣ እንደፈለጉ ያስቆጥራቸዋል ለማለት የሚያበቃ የህግ መሰረት የለውም፡፡

ምናልባትም ይህ ዘግይቶ የውክልና ሥልጣን የመስጠት የአመልካች ተግባር ቀደም ሲል ወኪል የተባለው ሰው ፈፀመ የተባለውን የሽያጭ ተግባር ለማፅደቅ መፈለጋቸውን ያሳያል በማለት መተርጎም እንዳይቻል ለዚሁ አግባብነት ባለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2190 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉት የውክልና ሥልጣን ኖሮ ተወካዩ ከውክልና ሥልጣኑ በላይ አሳልፎ ለፈፀመው ተግባር እና የውክልና ሥልጣን ዘመኑ ካበቃ በኋላ ወኪል የነበረው ሰው ለፈፀማቸው ተግባሮች እንጂ አሁን እንደተያዘው ላለው ፈፅሞ የውክልና ሥልጣን ባልተሰጠበት ጉዳይ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ክርክር ያስነሳውና የቤት ሽያጭ የተባለው ውል የአሁን አመልካችን ሊያስገድድ የሚችል የህግ መሰረት በሌለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች ውሉ አመልካችን ይመለከታል፤ እንደውሉ እንዲፈፅሙ ይገደዳሉ በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፤

ው ሳ ኔ

1. የሰበር አቤቱታ የቀረበበት እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መ/ቁ 54799 በ19/12/2003 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ሀጂ ይማም ሙዘይን በውክልና ሥልጣን ከተጠሪ ከአቶ እምነቱ እንደሻው ጋር በ1994 ዓ.ም ተፈፀመ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ወካይ ናቸው በሚል ምክንያት የአሁን አመልካችን ወ/ሪት አሊያት ይማምን ሊያስገድድ የሚችል አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ በየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 67376
ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፍሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካቶች፡- 1- ወ/ሮ ንግስት ኪዳኔ አልቀረቡም
2- አቶ ዑቁባይ ሚካኤል ገብረየሱስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1- አቶ በለጠ ወልደሰማያት ቀረቡ
2- አቶ ገብረ እግዚአብሔር ሐዲስ ከጠበቃቸዉ ከአቶ ሐጎስ አብርሃ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር አመልካቾች ከሣሽነት የተጀመረው በፌ/ከ/ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ ከሣሾች ሰኔ 09 ቀን 2002 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ በቀድሞ ወረዳ 20 ቀበሌ 29 በአሁኑ አጠራር በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 08/09 የሚገኘውን ቁጥሩ 486 የሆነውን የግል ቤታችንን ከሣሾች በ1992 ዓ.ም. ከሀገር ስንወጣ ለ1ኛ ተከሣሽ ውክልና በመስጠት የሄድን ቢሆንም 1ኛ ተከሣሽ ቤቱን የማስተዳደር እንጂ የመሸጥና የመለወጥ ስልጣን ሳይሰጣቸው ለ2ኛ ተከሣሽ የሸጡ ስለሆነ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ቤቱን እንዲያስረክቡን ፣ ያለአግባብ የበለጸጉበትን በወር ብር 3000 ስሌት ብር 72,000 ከነወለዱ እንዲከፍሉ ፣ ወደፊትም የሚኖረውን ውዝፍ ገንዘብ ተከሣሾች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ፣ ቤቱን መመለስ የማይቻል ከሆነ ደግሞ 1ኛ ተከሣሽ ብር 1,250,000 እንዲከፍሉ ይወሰንልን ብለዋል፡፡

ተከሣሾችም ክሱ በፍ/ህ/ቁ 1810 መሠረት በይርጋ የሚታገድ ነው በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭ በፍሬ ነገሩ ላይ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከሣሾችም ለይርጋ መቃወሚያው በሰጡት መልስ በፍ/ህ/ቁ 1810 የተጠቀሰው ይርጋ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው በፍ/ህ/ቁ 1710/2/ መሠረት በተንኮል፣ በማሳሳት፣ በሀይል ወይም በእድሜ መግፋት እና ከመጃጀት ጋር ተያይዞ የተፈጸሙ ውሎች እንዲፈርሱ በሚል ለሚቀርብ ክርክር ሲሆን የከሣሾች ክስ ግን ከዚህ የተለየ በመሆኑ ለዚህ ክርክር አግባብነት የለውም፡፡ በእኛ እምነት ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው የፍ/ህ/ቁ 1845 ይርጋ ሲሆን ሽያጩን ካወቅነው ደግሞ ሁለት ዓመት ያልሞላው ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በሚል ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የመረመረው የፌ/ከ/ፍርድ ቤትም በሰጠው ብይን 1ኛ ከሣሽ ለ1ኛ ተከሣሽ ከሰጡት ውክልና ስልጣን ተከሣሹ አልፎ የከሣሽ ንብረት የሆነውን መኖሪያ ቤት የሸጠ በመሆኑ ለጉዳዩ ስለውሎች በጠቅላላው ክፍል የተደነገጉት የይርጋ ድንጋጌዎች አግባብነት የላቸውም፡፡ በወካይና በተወካይ መካከል ለሚፈጠር አለመግባባት ወይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ክስ ለማቅረብ ቢፈለግ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ በፍ/ህ/ቁ 2187 የተደነገገው ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ መሠረትም ክሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም በተያዘው ጉዳይ ቤቱ ከተሸጠ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ በውክልና ምክንያት በተሰራ ሥራ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሚል የቀረበ ክስ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው ነው ብሏል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረው የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይንና በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካቾች የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብም፡- ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ ከአገር ውጪ ስንኖር የነበርን ሲሆን ቤቱ መሸጡን ያወቅነው 2ኛ አመልካች ከወጪ ሀገር ከተመለስኩ ከሰኔ 07/2002 ዓ.ም. ጀምሮ ሆኖ እያለና ይህን ጊዜ ተጠሪዎች ሳያስተባብሉ አግባብነት የሌለውን በፍ/ህ/ቁ 1810 የተደነገገውን የሁለት ዓመት ይርጋ በመጥቀስ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በሚል የክስ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛው ፍርድ ቤትም ተጠሪዎች ያላነሱትን በፍ/ህ/ቁ 2187 የተደነገገውን የሁለት ዓመት ይርጋ በመጥቀስ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ሲል መዝገቡን በብይን የዘጋውና የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ያጸናው ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

1ኛው ተጠሪ በሰጡት መልስ በጊዜው በነበረው አጠራር የክልል 14 መስተዳድር በ18/08/1992 ዓ.ም ከአገር የወጡ ኤርትራዊያን ንብረት በሰጡት ውክልና መሠረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተወካዮቹ መሸጥ እንደሚችሉ ለውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ባስተላለፈው የመንግስት መመሪያ መሠረት ከራሴ ፈቃድ ውጪ ሽያጩን የፈጸምኩ ስለሆነና ሽያጩም ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ 11 ዓመታት ስላለፉት ፍርድ ቤቶች ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ የወሰኑት ተገቢ ነው በከፍተኛው ፍርድ ቤት የይርጋ መቃወሚያ ሳቀርብ ጠቅሼ ያቀረብኩት በፍ/ህ/ቁ 1810 የተደነገገውን የሁለት ዓመት ይርጋ ቢሆንም በ1ኛ አመልካችና በእኔ መካከል የነበረውን የወካይና ተወካይ ግንኙነት መነሻ በማድረግ አመልካቾች ቤቱን የሸጠው ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችለው ውክልና ሳይሰጠው ነው በሚል ላቀረቡት ክርክር ፍርድ ቤቶቹ አግባብነት ያለው ይርጋ በፍ/ህ/ቁ 2187 የተጠቀሰው የሁለት ዓመት ይርጋ ነው በሚል ክሱ በዚሁ በሁለት ዓመት ጊዜ ወስጥ ያልቀረበ ነው ሲሉ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው፣ አመልካቾች ሽያጩን ያወቅነው ሰኔ 07 ቀን 2002 ነው ቢሉም ይህን አባባላቸውን በማስረጃ አስደግፈው ለፍርድ ቤቶች ስላላቀረቡ ተቀባይነት የለውም ሲሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን/ ውሣኔ እንዲጸና ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው የኤርትራዊያን ቤት ለኢትየጵያዊያን እንዲሸጥ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት በመወሰኑ የኤርትራ መንግስት ሚዲያዎች ፣ የሰብአዊ መብት ተቋማት ፣ የኢትዮ ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን እና ሌሎች ወገኖች በግልጽ ሲሟገቱበት የቆየ የአደባባይ ሚስጥር ስለሆነና አመልካቾችም ይህን የአካባቢ ሁኔታ በግልጽ የሚያውቁት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የሚያከራክረውን ቤት ሚያዚያ 1992 ዓ.ም ገዝቼ ስመ ሀብቱም ተዛውሮልኝ ይገፎ የምገኝ ሲሆን ይህንኑ ቤት ለመረከብ አመልካቾች ያቀረቡት ክስም በሁለት ዓመት ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ ክሱ በፍ/ህ/ቁ 2187 መሠረት በይርጋ ይታገዳል ሲሉ ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ብይን/ውሣኔ ተገቢነት ያለው ነው፣ ይህ ቢታለፍ ቤቱ ከተሸጠበት ጊዜ አንስቶ ክስ እስከቀረበበት ያለው ጊዜ ሊቆጠር 10 ዓመት ያለፈው በመሆኑ ክሱ በፍ/ህ/ቁ 1845 መሠረት በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ችሎት ደረጃም የግራ ቀኙ ወገኖች በቃል ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ ፍርድ ቤቶቹ ክሱን ወድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው የሚያከራክረው ቤት የተመዘገበው በ1ኛ የሰበር አመልካች ስም መሆኑንና 1ኛ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስተዳድሩ ውክልና ሰጥተው ከ2ኛ አመልካቾች ጋር ወደ ኤርትራ ሀገር በ1990 ዓ.ም. ሄደው እያሉ 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ ሚያዚያ 05 ቀን 1992 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ቤቱን መሸጣቸውን ነው፡፡ አመልካቾችም በክሳቸው ሽያጩን በመቃወም እንዲፈርስ ሰኔ 09 ቀን 2002 ዓ.ም ክስ ያቀረቡት 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የማስተዳደር እንጂ የመሸጥና የመለወጥ ስልጣን ሳይሰጣቸው ለ2ኛ ተከሣሽ ሸጠዋል በሚል ነው፡፡ አመልካቾች ቤቱ የተሸጠ መሆኑን ያወቁት 2ኛ አመልካች ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ በሰኔ 07/2002 ዓ.ም መሆኑን በክሳቸው ከመጥቀሳቸውም በላይ በቃል ክርክር ጊዜም በዚሁ በተጠቀሰው ቀን ሽያጩን እንዳወቁ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎችም ክሱን ለመቃወም በዋናነት የጠቀሱት የይርጋ ህግ የፍ/ህ/ቁ 1810 ሲሆን ፍርድ ቤቶቹ ግን በወካይና በተወካይ መካከል ለሚፈጠር አለመግባባት ወይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜው በፍ/ህ/ቁ 2187 የተደነገገው ነው በሚል ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳል ማለታቸውን ከክርክሩ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የግራ ቀኙን ወገኖችን ለሚያከራክረው ጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ህግ ድንጋጌ የትኛው እንደሆነ መለየት ተገቢነት ያለው ነው፡፡ እንደራሴው በፈጸመው ውል ምክንያት የሻሚውና የእንደራሴው ጥቅሞች የሚቃወሙ የሆኑ እንደሆነ ይህን ውል የፈረመው 3ኛ ወገን ይህን ሁኔታ ያወቀና ሊያውቀው የሚገባ የሆነ እንደሆነ በሻሚው ጥያቄ መሠረት ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል በፍ/ህ/ቁ 2187/1/ የተመለከተ ሲሆን በሻሚውም ውሉን ለማፍረስ ክስ ሊያቀርብ የሚችለው የዚሁ አካባቢ ሁኔታ ስለመኖሩ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ መሆን እንዳለበት የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር 2 ይደነግጋል፡፡ ውክልና ተወካዩ ለወካዩ እንደራሴ ሆኖ አንድ ወይም ብዙ ህጋዊ ስራዎችን በወካዩ ስም ለማድረግ የሚደረግ ስምምነት ስለመሆኑ የፍ/ህ/ቁ 2198 የሚስገነዘብ ሲሆን ይህም ስምምነት ወካዩ የውክልና ስራ በሚፈጽምበት ጊዜ የወካዩን ህጋዊ ሁኔታዎች የመለወጥ ስልጣን የሚሰጠው በመሆኑ ተወካዩ የውክልናውን ስልጣን ተጠቅሞ ሲሰራ ለወካዩ ጥቅም ፍፁም ታማኝና በስራው ሁሉ የወካዩን ጥቅም ብቻ የማስጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜም ይህንን ለወካዩ ፍፁም የሆነ ታማኝነትና ሙሉ ለሙሉ ለወካዩ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚከለክለው ፍላጎት ወይም ታማኝነቱን የሚከፋፍል ሁኔታ የሚያስከትል የጥቅም ግጭት ሲፈጠር ተወካዩ ለስራው አፈጻጸም ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በመሆኑም እንደራሴው የውክልና ሥልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞችን የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን በወካይና በተወካይ መካከል የጥቅም ግጭት ያለ ስለመሆኑ አመልካቾች በክሳቸው ከላመግለጻቸውም ሌላ በቃል ክርክር ወቅትም በ1ኛ ተጠሪና በሻሚዋ መካከል የጥቅም ግጭት ስለመኖሩ ያሉት ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶቹ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በፈጸመው ውል ምክንያት የሻሚውና የ1ኛ ተጠሪ የጥቅም ግጭት ስለመኖሩ አመላካች ነገር ባልተገኘበት ሁኔታ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የሌለውን የፍ/ህ/ቁ 2187/2/ የተመለከተውን ይርጋ ለብይኑ / ለውሣኔ መሠረት ያደረጉት ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡

ተጠሪዎች በዋናነት ወዳነሱት የፍ/ህ/ቁ 1810 ይርጋ ስንመለስ አንድ ውል በሚመሰረትበት ጊዜ የችሎታ ወይም የፈቃድ ጉድለት ያለበት ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ችሎታ አልነበረኝም ወይም ፈቃዴን በአግባቡ አልሰጠሁም በሚለው ተዋዋይ ወገን ጠያቂነት ብቻ ውሉ ሊፈርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚችል፣ እንደዚሁም ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ለህግ ወይም ለሞራል ተቃራኒ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜና የውሉ አጻጻፍ ሥርዓትም ባልተጠበቀበት ወቅት ከተዋዋይ ወገኖች መካከል ወይም በሙሉ ጥቅም አለኝ በሚል 3ኛ ወገን አማካይነት የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ቀርቦ ሊፈርስ እንደሚችል በፍ/ሕ/ቁ 1808/1/ ተደንግጓል፡፡ የውል ይፍረስልኝ ክስ ማቅረቢያ ጊዜን በተመለከተ ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ አንስቶ በሁለት ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በፍ/ህ/ቁ 1810 ተጠቅሷል፡፡ ይህን የይርጋ ድንጋጌ በተመለከተ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ 59139 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተፈጻሚነቱ ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ቀሪ በሚሆንበት ጊዜ ሲሆን ይህም የሚመለከተው ከአንደኛው ተዋዋይ ወገን ችሎታ ወይንም ፈቃድ ጉድለት ጋር ተያያዘ መሆኑን በፍርዱ ላይ አስፍሯል፡፡ በዚሁ መሠረትም ውሉ በችሎታ ማጣት ወይንም በፈቃድ ጉድለት እንዲፈርስ የሚጠይቅ ወገንም በሁለት ዓመት ውስጥ ክሱን ካላቀረበ በዚሁ በተጠቀሰው የፍ/ህ/ቁ 1810 ይርጋ መሠረት የሚታገድ ይሆናል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካቾች ውሉ እንዲፈርስ የጠየቁት 1ኛ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በሙሉ እንዲጠብቁ ፣ እንዲቆጣጠሩ ፣ ክፍያዎችን ተሳስበው እንዲከፍሉ በአጠቃላይ ንብረቶቹን በተመለከተ በመንግስታዊ መ/ቤቶችና በህዝባዊ ድርጅቶች እየቀረቡ ጉዳዮችን እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ እንጂ ንብረቹን እንዲሸጡ ሥልጣን ሳይሰጣቸው በህገወጥ መንገድ ለ2ኛ ተጠሪ ሸጠዋል በሚል ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት የጠየቁት የችሎታ ወይም የፈቃድ ጉድለትን መሠረት አድርገው ሳይሆን የውሉን ሕገ ወጥነት በመጥቀስ ስለሆነ ተጠሪዎች ለክርክራቸው መሠረት ያደረጉት በፍ/ህ/ቁ 1810 የተደነገገው የሁለት ዓመት ይርጋ አግባብነት የለውም፡፡

ለዚህ ጉዳይ የፍ/ሕ/ቁ 1810 እና 2187/2/ ይርጋ አግባብነት የላቸውም ከተባለ ጉዳዩን ስለውሎች በጠቅላላው በተደነገገው ክፍል በሚገኘው በፍ/ህ/ቁ 1845 መሠረት መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

በፍ/ህ/ቁ 1845 ድንጋጌ መሠረት ህግ በሌላ አኳን ካልወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈጸም ወይም ከላመፈጸሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ መብት ያለው ወገን መብቱን በ10 ዓመት ውስጥ ካልጠየቀ መብቱ ቀሪ እንደሚሆን በግልጽ የተጠቀሰ ሲሆን አመልካቾችም የሽያጭ ውሉ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለማስተላለፍ በፍ/ህ/ቁ 2205 መሠረት ልዩ ውክልና ሳይሰጣቸው የፈጸሙት ውል በመሆኑ ውሉ ህገ ወጥ ነወ እስከሚሉ ድረስ ይህንኑ ህገወጥ ነው የሚሉትን ውል እንዲፈርስ ክስ ማቅረብ የሚችሉት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለሚሆን የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች የይርጋ ክርክር ለመወሰን አግባብነት ያለው ይሄው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡ ይርጋው የሚቆጥርበትን መነሻ ጊዜን በተመለከተም አመልካቾች የቤቱን ሽያጭ ያወቅነው ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ.ም ነው በሚል የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ቤቱ የተሸጠው በሚያዚያ ወር 1992 ዓ.ም በመሆኑ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ምንም እኳን አመልካቾች ከሀገር በ1990 ዓ.ም የወጡ ቢሆንም ከነበሩበት ከኤርትራ መንግስት ሚዲያዎች ፣ የሰብአዊ መብት ተቋማት ፣ የኢትዮ ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን እና ሌሎች ወገኖች በግልጽ ስለንብረታቸው የሚያውቁት ጉዳይ ነው ብለዋል፡፡ ሆኖም እነዚህ የተጠቀሱት ምንጮች 1ኛ ተጠሪ ቤታቸውን የሸጡባቸው ስለመሆኑ ያሣውቃሉ ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርሱ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ የሰበር አመልካች እስካሁን ድረስ በውጪ ሀገር የሚኖሩ ስለመሆናቸው ክርክሩ የሚያመለክት ሲሆን 2ኛ ተጠሪም ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት ሰኔ 07 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ካደረጉት ክርክር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ በመሆኑም ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠርም አመልካቾች ውሉ እንዲፈርስ ክስ ያቀረቡት በፍ/ህ/ቁ 1845 የተደነገገው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቶቹ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን በፍ/ህ/ቁ 2187/2/ የተደነገገውን የይርጋ ጊዜ በመጥቀስ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በሁለት ዓመት ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ የሰጡት ብይን /ውሣኔ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ 59139 በፍ/ህ/ቁ 1810 እና 1845 የተደነገጉትን የይርጋ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት በተመለከተ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ብይኑ/ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ 95609 በቀን 26/02/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይንና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 62492 በቀን 16/07/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ሽረናል፡፡
2. ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ በፍ/ህ/ቁ 1845 የተደነገገ ሲሆን በዚሁ የይርጋ ድንጋጌ መሠረት አመልካቾች ያቀረቡት ክስ የክስ ማቅረቢያ 10 ዓመት ከማለፍ በፊት የቀረበ ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳይ ላይ የግራ ቀኙን ወገን በማከራከርና ማስረጃዎችን ሰምቶ በመመዘን የበኩሉን ፍርድ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዕምሯዊ ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 70500

ታህሳስ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- ኢንጅነር አድማሱ ገብሬ (ገብሬ አድማሱ) ጠበቃ ገንዘቡ ገ/አምላክ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ህግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ከሣሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ ተከሣሽ የብሩክ ፊልምስ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ባለቤት ከሆኑት የግል ተበዳይ አቶ ብሩክ መክብብ ጋር መንተዮቹ የሚል ርዕስ ያለው የአማርኛ ፊልም ለመሥራት ተዋውለው ሳለ የግል ተበዳይ ሳያውቁ በግል ተበዳዩ (ፕሮዲዩሰሩ) የተሠራውን ፊልም ከተጠናቀቀ በኋላ ከግል ተበዳይ ሠራተኞች ጋር በመመሳጠር ከተቀበለ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በማምጣቱ እና ርዕሱን በመቀየር ‹‹ለአባቷ›› የሚል ርዕስ በመስጠት የፊልሙ ባለቤት ሳይሆን የፊልሙ ባለቤት በመምሰል ለህዝብ እይታ በማቅረብ የቅጅና ተዘማጅ መብቶችን ለመጠበቅ የወጣውን አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀጽ 7(1)(ሀ) እና 36(1) ሥር የግል ተበዳይን የኢኮኖሚ መብት በመጣስ ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሣሹ የቀረበበትን ክስ በመካድ የተከራከረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት በዚሁ በተከሰሰበት ወንጀል ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኋላ አመልካች በ2 ዓመት ከ6 ወራት እሥራት እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘቱ ይግባኙን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ካከራከረ በኋላ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በአሁኑ አመልካች እና የግል ተበዳይ መካከል የውል ግንኙነት ያለ ስለመሆኑ፣ በዚሁ የውል ግንኙነት መሠረት የግል ተበዳይ በአመልካች የሚቀርብለትን ድርሰት ወደ ፊልም ለመቀየር የተስማሙ ስለመሆኑ፣ በዚህ ስምምነት መሠረት ለመልካች ለሥራው ብር 800,000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊከፍልና የግል ተበዳይ ደግሞ ፊልሙን በማጠናቀቅ ለአመልካች የሚያስረክብና አመልካችም የፊልሙ ባለቤት እንደሚሆን የተሰማሙ ስለመሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር የተረጋገጡ ነጥቦች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በግራ ቀኙ መካከል በዚሁ የውል ግንኙነት መሠረት ያደረገ የፍትሐብሔር ክርክር እስከዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በመዝ.ቁ. 69247 ላይ እልባት ያገኘ ሲሆን አመልካች የፊልሙ ባለቤት ነው በማለት የግልግል ዳኞች የሰጡት ውሣኔ እና በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የፀደቀው የውሣኔ ክፍል በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎትም ያልተነካ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚሁ የፍትሐብሔር ጉዳይ አከራካሪ ከሆነው ፊልም ግራ ቀኙ ያላቸው መብትና ግዴታ ምን እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን ከሥራውም የሚገኘውን ትርፍ የሚከፋፈሉበትን አግባብ በተመለከተ ውሣኔ የተሰጠበት ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡

ከላይ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ይዘን የወንጀል ኃላፊነት ለያቋቁሙ የሚችሉ ተግባራት ስለመፈፀማቸው መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2) መሠረት አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች የተከሰሰበት የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁ.410/1996 አንቀጽ 7(1)(ሀ) መሠረት ለሥራው ባለቤት የተሰጠን ተግባር ባለቤት ሣይሆን ባለቤት በመምሰል ፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካች የፊልሙ ባለቤት ስለመሆኑ የግራ ቀኙ የተሰማሙበትን ውል መሠረት በማድረግ የግልግል ዳኞች የሰጡት ውሣኔ አልተሻረም፡፡ አመልካች የፊልሙ ባለቤት በተባለበት ሁኔታ ደግሞ የዚህ የወንጀል ህግ ድንጋጌ ተጥሷል ማለት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩልም ባለቤት የሆነ ሰው ፊልሙን በእጁ አድርጎ መገኘቱ ከዚሁ ባለቤት ነኝ ከሚል ሃሣብ የተነሣ ከመሆኑ ባሻገር የወንጀል ተግባር ወይም የግል ተበዳይን የኢኮኖሚያዊ መብት በመጣስ ሃሣብ የፈጸመ ስለመሆኑ የወንጀል ሞራላዊ ፍሬ ነገር ስለመረጋገጡ የተደነገጉት የወንጀል ህግ ከአንቀጽ 57 እስከ 59 ደረስ ያሉት ድንጋጌዎች አያመለክቱም፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ድንጋጌ ሥር የሞራላዊም ሆነ የህግ ፍሬ ነገሮች ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በመሆኑ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ አግባብነት የሌለውና ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች ባልተሟላበት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ባጠቃላይ በአመልካችና በግል ተበዳይ መካከል ያለው ግንኙነት የውል አፈፃፀምን የሚመለከት የፍትሐብሔራዊ ባህሪይ ያለው በመሆኑ አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ሥር ሕጋዊ ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ አግባብነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1/ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 59998 ሰኔ 23 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.74529 በቀን 19-12-2002 ዓ.ም እና በቀን 21-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 195(2(ለ(1)) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ሥር ሕጋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ባልተሟሉበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ አግባብነት የለሌውና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ከክሱ በነፃ እንዲሠናበት ብለናል፡፡

3. አመልካች በሌላ የወንጀል ጉዳይ የማይፈለግ ከሆነ ከማረሚያ ቤት እንዲለቀቅ ለሚመለከተው ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 68369
ጥር 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1- ሳሙኤል ሃይሉ - ቀረቡ

2- ሆራይዘን ማተሚያ ቤት ኃ/የተ/የግል ማህበር -

ጠበቃ እንዳልካቸው ይላቅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ስምረት አያሌው /ዘጠኝ ሰዎች/

1ኛ. ወ/ሮ ስምረት አያሌው 6ኛ. ቤተልሄም አያሌው

2ኛ. ወ/ሮ ፅዮን አያሌው 7ኛ. አዲስ አያሌው

3ኛ. ጳውሎስ አያሌው 8ኛ. ማህሌት አያሌው

4ኛ. የማነ አያሌው 9ኛ. ሙሉጌታ አያሌው

5ኛ. ፍሬሕይወት አያሌው - የሁሉም ጠበቃ ተስፋዬ ቀለመወርቅ -ቀረቡ

መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 70380 ከሆነው ጋር አጣምረን በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በቅጅ መብት ሕግ ጥበቃ የሚደረገውን መብት ፣ የመብቱን ተጠቃሚዎችንና መብቱ ተጥሶ ሲገኝ በሕጉ ስላለው መፍትሔ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆኑ ተከሣሾች የአሁኑ አመልካቾች ነበሩ፡፡ የተጠሪዎች የክስ ይዘት ወላጅ አባታቸው አለቃ አያሌው ታምሩ በሕይወት ዘመናቸው ብዛት ያላቸው ሐይማኖት ነክ የሆኑ የፈጠራ ስራዎችን መስራታቸውን፣ የተለያዩ ፅሑፎችን ማዘጋጀታቸውን፣ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይም በመጣጥፍና በቃለመጠይቅ ዙሪያ ስብከቶችን ማዘጋጀታቸውንና በሕይወት ዘመናቸው የእነኚህ ስራዎች የፈጠራ ባለቤት የነበሩና ከሕልፈተ ሕይወታቸው በኋላም መብቶቹ ለወራሾች መተላለፋቸውን ፣ የአሁኑ 1ኛ አመልካች የባለመብቶችን ፈቃድ ሳያገኝ የሚቹን የፈጠራ ስራ የሆኑትን ፅሑፎች በጋዜጣ እና በመፅሄት ላይ የወጡ ቃለመጠይቆችን ፣ መጣጥፎችን ፣ የሚች የመንፈቅ መታሰቢያ ፖስተር ላይ የወሰዱትን የመፅሐፉን የሽፋን ሥእልና የሀዘን መግለጫ ግጥሞችን ጭምር በማሰባሰብ በ2ኛ ተጠሪ ማተሚያ ቤት አማካኝነት “ትምህርተ ሃይማኖት” በሚል ርዕስ ከሕግ ውጪ ማሳተሙን ገልፀው በአዋጅ ቁጥር 410/1996 መሠረት ህትመቱ እንዲቆም ፣ የታተሙት መፍሐፎችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲወገዱ የሞራል ካሣ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ ብር/፣ ሶስት ሺህ መጽሐፎች በገበያ በመሸጣቸው ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ/፣ ተጠሪዎች ራሳቸው መጽሐፉን አሳትመው ቢሸጡ ኑሮ ይገኝ የነበረውን ገቢ ብር 250,000.00/ሁለት መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ 1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቧቸው መከራከሪያ ነጥቦችም ሚች አለቃ አያሌው ታምሩ የስራው አመንጪ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያለመቅረቡን፣ የፅሑፍ ስራው የአለቃ አያሌው የግል ስራ ሳይሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ወቅታዊ ሐይማኖት ጥያቄዎችን አስመልክቶ ያላቸውን የእምነት አቋም በተመለከተ የጻፏቸው መሆናቸውን ስራውን ሲያቀርቡ ስራውን ለማሰራጨት መብቱ የእሳቸው ብቻ መሆኑን የሚያሳይ ነገር ያለመኖሩን ፣ ጉዳዩ በሽምግልና እየታየ ባለበት ሁኔታ ክሱ ሊቀርብ እንደማይገባ የሚገልፁ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ሚች አለቃ አያሌው ታምሩ ስራውን የማሰራጨት መብታቸውን ባለመጠበቃቸው ስራው የራሳቸው የፈጠራ ስራ ነው ቢባል እንኳ ሌሎችን ከማሰራጨት ማገድ እንደማይችሉ የሚች አያሌው ታምሩ ስራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እውቀት መሠረት በማድረጉ የስራ አመንጪ ሊባሉ እንደማይችሉ ፣ ስራው ወጥ ስራ ያለመሆኑንና በሕግ ጥበቃ ሊያገኝ እንደማይገባ ሚች የጀመሩትን ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትምህርት ለሕዝብ ለማሰራጨታቸው አመልካቹ ሊከሰሱ እንደማይገባ ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች በበኩሉ በሰጠው መከላከያ መልስ አንደኛ አመልካች ለህትመት ባቀረቡት ፅሑፍ ምንጩ አለቃ አያሌው ታምሩ መሆናቸውን በመገለፁ የሚያስጠይቀው መሆኑን የወራሾችን ፈቃድ መጠየቅ ያለበት አሳታሚ እንጂ አታሚ ያለመሆኑን ፣ የሚች የፈጠራ ስራ ለመሆኑ ማስረጃ አለመቅረቡን ፣ አታሚው በራሱ አነሳሽነት ያለማተሙንና የሚች አለቃ አያሌው ታምሩ ስራ ስለመሆኑ የማያውቅ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በሁዋላ ሁለተኛ አመልካችን /አታሚ ድርጅቱን/ ከክሱ ነፃ ሲያደርገው አንደኛውን አመልካች በተመለከተ ግን ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ፍሬ ነገር ክርክሮችን ውድቅ በማድረግ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ/ ለቁሳዊ ጉዳት ካሣ፣ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ/ ለሞራል ካሣ ፣ በድምሩ ብር 160,000.00 /አንድ መቶ ስልሳ ሺህ/ እንዲከፍሉ ፣ የሚች አለቃ አያሌው ታምሩን ስራ እንዳያሳትሙና መብቱን ከመጣስ ተግባር እንዲቆጠቡ ፣ የታተሙትና ወደፊት የሚታተሙት መፅሐፍት እንዲወገዱ በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ አንደኛ አመልካች ለክሱ ኃላፊ በመባላቸው ፣ ተጠሪዎች ደግሞ ሁለተኛ አመልካች ከክሱ ነፃ ተብሎ በመወሰኑ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአሁኑ አንደኛ አመልካች ያቀረቡትን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ሲሰርዘው የተጠሪዎችን ይግባኝ ግን ተቀብሎ ከአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ጋር ከአከራከረ በሁዋላ አመልካችን ያለባለቤቱ ፈቃድ የተጠሪዎችን አውራሽ ፎቶ ግራፍ ከእነፈጠራ ስራቸው በመጽሐፍ አትሞ ማውጣቱ ተረጋግጧል በሚል ምክንያትና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27 ፣ 29 እና 2027 ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ለክሱ ኃላፊ አድርጎ ከአንደኛ አመልካች ጋር በአንድነት እና በነጠላ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነውን ካሣ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች በተናጥል ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አንደኛ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የአመልካች የመከላከያ ማስረጃዎች ሳይሰሙ ውሣኔ መሰጠቱና ስራው የሚቹ ወጥ ስራ ያለመሆኑን ፣ ሚቹ ስራው ለሕዝብ እንዳይሰራጭ ባለደረጉበት ሁኔታ በቅጅ ሕግ ጥበቃ የሚሰጠው መብት ነው ተብሎ መወሰኑ ያለግባብ መሆኑን ዘርዝረው ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛው አመልካች ደግሞ አታሚ እንደመሆኑ መጠን ሶስተኛ ወገን እንዲታተም ባቀረበው ጽሑፍ የሚጠይቅበት አግባብ የሌለ መሆኑንና ለክሱ መሠረት የሆነው ስራም የሚቹ ወጥ ስራ ሳይሆን ሚቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አገልጋይ በነበሩበት ጊዜ ቤተክርስቲያንን ወክለው መጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሱ ሲያስተምሩ የነበሩት የቤተክርስቲያኗ ስራ መሆኑና ሚቹም ያስተማሩትና መግለጫ የሰጡበት ስራቸው ከሣጣቡ አመንጪ ፈቃድ ውጪ ማባዛት ፣ ማሰራጨት ማተም ... ወዘተ የሚል ክልከላም ያስቀመጡት ሁኔታ የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ አመልካቹ ለክሱ ኃላፊ መደረጉ ከሕግ ውጪ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካቾች ለክሱ ኃላፊ ተብለው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደረጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሣኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሕግ ረገድ እንደሚከተለው ተመልክቶታል፡፡

በመሰረቱ አንድን የፈጠራ ስራ በትክክል ስራ ሊሰብለው የሚችለውና ለቅጅ መብት ጥበቃ ብቁ የሚያደርገው ስራው የመጀመሪያ ስራ ወይም በባሕርይው ለየት ያለ ስራ ሲሆን መሆኑ የአዋጅ ቁጥር 410/1996 ይዘትና መንፈስን የሚያስገነዝበን ነጥብ ነው፡፡ ስራው የመጀመሪያ ስራ /original/ ወይም ባሕርይው ለየት ያለ ስራ ነው ሊያስብለው የሚችለው ደግሞ ውጤቱ የግለሰብ የፈጠራ ጥረት መሆን ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡ ሕጉም ጥበቃ የሚያደርገው የግለሰቡን የፈጠራ ውጤት ነው፡፡ የፈጠራ ውጤት መኖሩ መረጋገጥ ደግሞ የፈጠራ ስራ ለቅጅ መብት ብቁ ከሚያደርጉት መመዘኛዎች /መለኪያዎች/ አንዱ ሲሆን ጥበቃ የሚደረገው ግለሰቡ ሐሳቡን የገለፀበት ቅርፅ እንጂ ሐሳብ ወይም በፈጠራ ስራው ውስጥ ያለው መረጃ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሣጣብ አገላለፅ ቅርጽ በቅጅ መብት ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን ሣጣቡ በራሱ ብቻ ግን አይሆንም፡፡ የሣጣቡን ይዘት ለሌሎች መግለፅ የፈጠራ ስራ መብት ጥሰትን የሚያስከትል ሲሆን ሌሎች ሰዎች ሣጣቡንና መረጃውን የራሳቸው ለየት ያለና ነፃ ስራ ተጠቅመው መገኘት የፈጠራ ስራ ውጤትን እንደመጣስ የማይቆጠር መሆኑን ሕጉ ለጥበቃው ካስቀመጠው መለኪያ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ የቅጅ መብት አይነተኛ አላማ ለስነ ፅሁፍ ፣ ኪነ ጥበብ እና ስነ ጥበብ ፈጠራዎች ሕጋዊ ጥበቃ ማድረግ ነው፡፡ የሕጉ አጠቃላይ ይዘት ሲታይ በቅድሚያ የቅጅ መብት የሚጐናፀፉት የፈጠራ አመንጪዎች መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ በቅጅ መብት ውስጥ መብት ተብሎ የሚታወቁት ደግሞ የኢኮኖሚ መብቶችና የሞራል መብቶች ሲሆኑ በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 7 እንደተደነገገው ከኢኮኖሚያዊ መብቶች አንዱ ተጥሶ በተገኘ ጊዜ የሞራል ጉዳት ጥሰት የሚኖር መሆኑ ተመልክቷል፡፡ አዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 7 የተመለከቱት ኢኮኖሚያዊ መብቶች ደግሞ ከአዋጅ አንቀፅ 9 እስከ 19 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥራ አመንጪ ወይም የአንድ ሥራ ባለቤት፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሀ/ ሥራን የማባዛት ፣

ለ/ ሥራን የመተርጐም ፣

ሐ/ ሥራን የማመሳሰል ፣ የማቀናበር ወይም ወደ ሌላ አይነት የመቀየር

መ/ በሽያጭ ወይም በኪራይ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን የማከፋፈል

ሠ/ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ከውጭ ሀገር የማስገባት

ረ/ ኦርጅናል ሥራን ወይም ቅጂውን ለሕዝብ የማሣየት

ሰ/ ሥራን በይፋ የመከወን

ሸ/ ሥራን ብሮድካስት የማድረግ

ቀ/ ሥራን በሌላ መንገድ የማሰራጨት መብቶችን ራሱ ሊፈጽም ወይም ሌላ ሰው እንዲፈፅማቸው ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል ተብሎ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ተቀምጧል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የ1ኛ አመልካች የተጠሪዎች አባት የፈጠራ ስራ የሆኑትን ፅሑፎች በጋዜጣ እና በመፅሄት ላይ የውጡ ቃለመጠይቆችን ፣ መጣጥፎችን ፣ የሚች የመንፈቅ መታሰቢያ ፖስተር ላይ የወሰዱትን የመፅሐፉን የሽፋን ሥእልና የህዘን መግለጫ ግጥሞችን ጭምር በማሰባሰብ በ2ኛ ተጠሪ ማተሚያ ቤት አማካኝነት “ ትምህርተ ሃይማኖት ” በሚል ርዕስ 1ኛ አመልካች ማሳተሙን ሳይክዱ የታተሙት ስራዎች የሚቹ ወጥ ስራዎች ሳይሆኑ ሚቹ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ሁነው ሲሰሩ በቤተክስቲያን ሐይማኖት የነበራቸውን አቋም የገለፁበት እንጂ የራሳቸው ወጥ ስራ አይደለም ፣ 1ኛ አመልካችም ለሕዝብ ከማሰራጨት በሚቹ አልተከለከሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክርክርም ሆነ በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት ክርክር የመጽሐፍ ገቢ ለሚች ቤተሰቦች እንዲሆን በማለት በመፅሐፉ መሳፋቸው የተረጋገጠ መሆኑ ሲታይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 83 እና 235 ድንጋጌዎች መሠረት የስራው ፈጠራ ባለቤት የተጠሪዎች አባት መሆናቸውን ማመናቸውን የሚያስረዳ ነው፡፡ ስለሆነም 1ኛ አመልካችም ሆነ 2ኛ አመልካች የስራው የፈጠራ ባለቤት የተጠሪዎች አባት መሆናቸውን በግልፅ ሳይክዱ መቅረታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ መከላከያ ማስረጃ ያለመሰማቱ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብት ያጣበበ ነው ለማለት ስላልተቻል በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

የተጠሪዎች አባት የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አገልጋይ በነበሩበት ጊዜ ስለሐይማኖቱ የሰጡትን አስተያየት ማንም ሰው ለማሳተም የሚችልበት አግባብ አለ? ወይስ የለም? የሚለውን ጥያቄ ስንመለከት ደግሞ ሐሳቡ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሐይማኖታዊ ትምህርት ነው ቢባል እንኳ ሚቹ ሐሳቡን የገለፁበት ቅርፅ ግን የራሳቸው የፈጠራ ስራ በመሆኑ በሕጉ ጥበቃ ለማግኘት የሚያስችለውን መመዘኛን ማሟላቱን የክርክሩ ፍሬ ነገሮች የሚያስረዱ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ሕጉ በዋነኛነት ጥበቃ የሚያደርገው የሐሳቡ አገላለፅ ቅርፅ እንጂ ሃሣቡን ራሱን አይደለም፡፡ 1ኛ አመልካች የተጠሪዎች አባት ስለሃይማኖቱ የገለፁበትን የሐሳብ አገለላጽ ቅርጽ ሳይለውጡ ሐሳቡ የተገለፀበትን መንገድ እንዳለ መውሰድና “ ትምህርተ ሐይማኖት ” የሚል ርዕስ በመስጠት ማሳተማቸውና ማሰራጨታቸው አልተካደም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 7 የተመለከተውን መብት መጣስ ነው፡፡ አመልካቾች የአዋጁን አንቀጽ 13 በመጥቀስ የሚያቀርቡት ክርክርም ሲታይ ሕጉ ለሕዝብ ስለማሰራጨት እና ማባዛት እንደቅደም ተከተላቸው በአንቀፅ 2/6/ እና 2/25/ ስር የተመለከቱትን ትርጓሜዎችን የሚያሟላ አይደለም፡፡ በሌላ አገላለጽ የፈጠራ ባለቤት የፈጠራ ስራዎቹን እንዳይሰራጩ አልከለከለም ተብሎ አንድን የፈጠራ ስራ በመፅሐፍ መልክ ባልታተመበት ሁኔታ በሕግ አግባብ መብት ያላገኘ ሰው ለሕዝብ ትምህርት ነው ብሎ ማሰራጨት ወይም ማባዛት በአዋጅ አንቀጽ 13/1/ መሠረት የቅጅ መብት ጥሰት አይደለም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 2/6/ እንደተመለከተው ለሕዝብ ማሰራጨት ማለት የአንድ ስራ ክወና ፣ የድምፅ ሪከርድ ወይም ብሮድካስት ምስል ፣ ድምጽ ወይም ሁለቱን በሽቦ ወይም ያለሽቦ ማሰራጨትን የሚመለከት ሲሆን ማባዛት ማለት ደግሞ አንድን ስራ ወይም የድምጽ ሪከርዲንግ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት የኤሌክትሮኒክ ማከማቻን ጨምሮ በማንኛውም አኳኋን ወይም መልክ ስራውን ወይም የድምጽ ሪከርዱን በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቅጅዎች መገልበጥ መሆኑን ደግሞ የአዋጅ አንቀፅ 2/25/ ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡

ከእነዚህ ድንጋጌዎች ጋር ተያይዞ የሚነሳው ድንጋጌ በአዋጅ አንቀፅ 13/1/ የሰፈረ ሲሆን ይዘቱም በዚህ አዋጅ ቁጥር 7/1/ሀ/ ፣ /ሸ/ እና /ቀ/ የተደነገገው ቢኖርም እስከተቻለ ድረስ የስራውን ምንጭና የስራ አመንጪውን ስም መጥቀስ እንደተጠበቀ ሆኖ የቅጅ መብት ባለቤቱ፣ የማባዛት ፣ ብሮድካስት የማድረግ ወይም ለህዝብ የማሰራጨት መብቱ የስራው አመንጪ ወይም የቅጅ ባለመብቱ መሆኑን በቅጅው ላይ በግልጽ የተጠቀሰ ነገር ከሌለ በወቅታዊ የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት ጉዳዮች ላይ በጋዜጣ ፣ በመፅሔት የወጡ ወይም ተመሳሳይ ባህሪ ኖሯቸው ብድሮድካስት የተደረጉ መጣጥፎችን በሌላ ጋዜጣ መጽሄት ማባዛት ፣ በብሮድካስቲንግ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ማድረሱን ሊከለክል አይችልም ተብሎ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የተጠሪዎች አባት በሕይወት ዘመናቸው ብዛት ያላቸውን ሐይማኖትን ነክ የሆኑ የፈጠራ ስራዎችን መስራታቸው ፤ የተለያዩ ፅሑፎችን ማዘጋጀታቸውን ፣ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይም በመጣጥፍና በቃለመጠይቅ ዙሪያ ስብከቶችን ማዘጋጀታቸውንና የሚቹን የፈጠራ ስራ የሆኑትን ፅሑፎችን በጋዜጣ እና በመፅሄት ላይ ወጡ ቃለመጠይቆችን ፣ መጣጥፎችን ፣ ከሚች የመንፈቅ ዓመት መታሰቢያ ፖስተር ላይ የወሰዱትን የመፅሐፍን የሽፋን ሥእልና የሀዘን መግለጫ ግጥሞችን ጭምር በማሰባሰብ በ2ኛ ተጠሪ ማተሚያ ቤት አማካኝነት “ ትምህርት ሃይማኖት ” በሚል ርዕስ ታትሞ መውጣቱ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም በግልፅ መረዳት የሚቻለው እነዚህ ስራዎች ለህዝብ መረጃ አገልግሎት አላማ የሚባዙና የሚሰራጩ ከሆነ በስራው ባለቤት በወጡበት መንገድ ከሚሆን በቀር በመጽሐፍ መልክ ታትመው የሚባዙበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 13/1/ ድንጋጌ ከህዝብ ስለማሰራጨትና ስለማዛባት ሕጉ ከሠጠው ትርጓሜ ጋር ተዳምሮ ሲነበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በአዋጁ አንቀፅ 13/1/ ስር “..... መፅሔት....” የሚለው ቃል “ Periodical ” የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚተካው መሆኑን ሕጉ የሚያሳይ በመሆኑ ይኸው ቃል በማንኛውም መለኪያ መፅሐፍ የሚለውን ቃል አይተካም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 13/1/ ድንጋጌን በመጥቀስ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች አባት በድንጋጌው በፊደል “ ሀ ” “ ረ ” እና “ ቀ ” የተመለከተው ወጥ(“ኦርጅናል”) ሥራን የማባዛት ፣ የማሳተም ወይም በሌላ መንገድ የማሰራጨት መብት ተጥሷል፡፡ ይኸውም የፈጠራ ስራቸው ከአውራሾች ፈቃድ ውጪ በመጽሐፍ መልክ ታትሞ በገበያ ላይ ውሎ በሕዝብ መነበቡ ነው፡፡ የሚቹ የፈጠራ ስራ ከወራሾቹ ፈቃድ ውጪ በ1ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች አሳታሚነት በመጽሐፍ መልክ ገበያ ላይ ውሎ መነበቡ ኦርጅናል ሥራውን ወይም ቅጅውን ለሕዝብ ማሳየት/public display of original or copies of the work/ የሚለው በሕጉ የተመለከተው የሚች ወራሾች መብት ተጥሷል ማለት ነው፡፡ ይህ መብት ተጥሶ የሞራል ጉዳት በደረሰ ጊዜ የካሣው መጠን በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34/4/ መሠረት ከ100,000/አንድ መቶ ሺህ ብር / የማያንስ የገንዘብ ካሣ ሊከፍል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት በተጠሪዎች ላይ የደረሰውን የህሊና ጉዳት ሞራል ካሣ 1ኛ አመልካች በተጠቀሰው አዋጅ መሠረት 100,000/አንድ መቶ ሺህ ብር / የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

ሁለተኛው አመልካች ከላይ የጠቅስናቸውንና ተቀባይነት የሌላቸው የሕግ ክርክሮችን ከማንሳቱም በተጨማሪ በአታሚነቱ የሚጠየቅበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27 ፣ 29 ፣ 2027 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ነው፡፡ ይኸው ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች በአከራካሪው መፅሐፍ የሚች አለቃ አያሌው ታምሩን ፎቶ ግራፍ ለጥፎ ማውጣቱን ፣ አሳታሚው አንደኛው አመልካች የሚቹን ፎቶ ግራፍ አትሞ ለማውጣት በቅድሚያ ስለመወከሉ ወይም ይህንን ለማድረግ ስልጣን ያለው መሆኑን ሁለተኛ አመልካች ያለማጣራቱን ፎቶውን የያዘው መፅሐፍ በገበያ ላይ መሰራጨቱን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧል፡፡ ሁለተኛ አመልካችም እነዚህን ፍሬ ነገሮችን አልካደም፡፡ እንዲህ ከሆነ ሁለተኛ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27/ ፣ 29 እና 2027 ድንጋጌዎች የማይጠየቅበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ለጉዳዩ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአሁኑን አንደኛ አመልካችን በተመለከተ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 88615 ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 62371 የካቲት 04 ቀን 2003 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ሁለተኛ አመልካችን በተመለከተ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 63119 ሚያዚያ 12 ቀን 2003 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
3. አመልካቾች ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ/ ለቁሳዊ ጉዳት ካሣ ፣ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ / ለሞራል ካሣ ፣ በድምሩ ብር 160,000.00/አንድ መቶ ስልሳ ሺህ/ እንዲከፍሉ፣ የሚች አለቃ አያሌው ታምሩን ስራ እንዳያሳትሙና መብቱን ከመጣስ ተግባር እንዲቆጠቡ፣ የታተሙትና ወደፊት የሚታተሙት መፅሐፍት እንዲወገዱ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት በመ/ቁጥር 70380 ሐምሌ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 64129

ህዳር 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ኢስላሚክ ሪሊፍ ኢትዮጵያ - ጠበቃ ቃሲም መሐመድ - ቀረቡ
ተጠሪ፡- አቶ መሐመድ ሠይድ - የቀረበ የለም
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክር በፍርድ ባለቀና የአፈጻጸም መዝገቡ ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መሠረት የቀረበ ነው፡፡ በአሁኑ ተጠሪ ቀርቦ የነበረው የአሰራና ሰራተኛ ጉዳይ ክስ በአፋር ብሔ/ክልላዊ መንግስት በዞን 4 እዋ ወረዳ ፍ/ቤት ውሣኔ ያገኘ ሲሆን ይዘቱ በተጠሪ ላይ የተፈጸመው የስንብት እርምጃ ህገ ወጥ ነው በማለት ሊከፍሉ የሚገባቸውንም ተያያዥ ክፍያዎች በማመላከት የተሰጠ ነው፡፡ በዚህ ውሣኔ ተከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ለክልሉ የዞን 4 ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በተጠሪ ላይ የተወሰደው እርምጃ ህገ ወጥ ስንብት መሆኑን በማጽናት ተያያዥ ክፍያዎችን በተመለከተ የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል የወሰነ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ አሁን አከራካሪ የሆነውና ለዚህ ቅሬታ መሠረት የሆነው የአሁን ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው የአፈጻጸም ማመልከቻ እና ፍ/ቤቱም የቀረበለትን ማመልከቻ በመቀበል ግራ ቀኙን በማከራከር ታህሣስ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የክልሉ የዞን 4 ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ የተመለከተውን ጉዳይ ማስፈጸም ያለበት ቀድሞውኑ በወረዳው ፍ/ቤት ላይ ተከፍቶ በነበረው የአፈጻጸም መዝገብ የወረዳው ፍ/ቤት እንጂ የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አይደለም፡፡ ስልጣኑ ካለመሆኑም በላይ የይግባኝ መብታችንን የሚያጣብብ በመሆኑ አግባብነት የለውም የሚል ሲሆን በሌላ በኩል የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአፈጻጸም መዝገቡ ላይ ትዕዛዝ ሲሰጥ ቀድሞ ፍርድ ያላረፈበትን ክፍያዎች ሁሉ በመጨመር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ ውሣኔ የሰጠበት በመሆኑ የአፈጻጸም ጉዳዩን ተመልክቶ ማስፈጸም ይችላል ከፍርድ ውጪ ተጨምረዋል የተባሉትን ክፍያዎች በተመለከተ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የወሰናቸው በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም በሚል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ የተጠሪ የሥራ ውል ከህግ ውጪ ተቋርጧል ተብሎ የካሣ ክፍያ የ85 ቀናት ደመወዝ ይከፈለው ተብሎ የተሰጠው ፍርድ እያለ በአፈጻጸም ውሣኔው ላይ የ180 ቀናት ደመወዝ ይከፈለው የመባሉን አግባብነት የነበረ ቢሆንም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሁን ችሎቱ ጉዳዩን ሲመለከተው ከተያዘው ጭብጥ በፊት የዞኑ ፍ/ቤት ያለውን ስልጣን መመልከት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የክልሉ የዞን 4 ከፍተኛ ፍ/ቤት የአፈጻጸም መዝገቡን ተመልክቶ ትዕዛዝ መስጠቱ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሠረት በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክር በክልሉ የዞን አራት የእዋ ወረዳ ፍ/ቤት ውሣኔ ያገኘ ስለመሆኑ ይዜ የወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ የተወሰደው የስንብት እርምጃ ህገ ወጥ ስለመሆኑ የዞኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በተመሳሳይ የተቀበለውና ያጸናው ሲሆን የአሁን አመልካች ባቀረበው ቅሬታ መሠረት የክፍያውን መጠን በተመለከተ ብቻ የወረዳውን ውሣኔ ያሻሻለው ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድን ፍርድ ማስፈጸም ያለበት ጉዳዩን በመጀመሪያ ተመልክቶት ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ የአፈጻጸም ሥርዓት የሚመራበትን አግባብ የሚያመለክተው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በተለይም በህጉ ከቁጥር 371- እስከ 385 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ዓላማ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡ ይዜ አሰራር ደግሞ በየደረጃው ያሉት ፍ/ቤቶች በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች ሊያሻሽሉ የሚችሉበት በርካታ አጋጣሚዎች ሊኖሩ ቢችሉም አፈጻጸሙ ግን አንድ ላይ ተጠቃሎ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው ፍ/ቤት እልባት ማግኘቱ ለተከራካሪዎች ወጪ ቆጣቢ ከመሆኑም በላይ በአፈጻጸም ሂደት በሚሰጡት ትዕዛዞች ላይ ቅሬታ ቢኖር እንኳ የይግባኝ መብት የማያጣብብ በመሆኑ ጠቀሜታው የጐላ ነው፡፡ በተጨማሪም ቀድሞ በወረዳው ፍ/ቤት ፍርድ መሠረት የአፈጻጸም መዝገብ በወረዳው ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ያስከፈቱ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውም ውሣኔ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሻሻለ ቢሆንም አፈጻጸሙ መቀጠል ያለበት በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን አይቶ ፍርድ በሰጠው የወረዳ ፍ/ቤት መሆን ሲገባው የክልሉ የዞን 4 ከፍተኛ ፍ/ቤት የእዋ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻሉ ብቻ የአፈጻጸም መዝገቡን አስከፍቶ ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም ብለናል፡፡ ባጠቃላይ የአፈጻጸም ክስ መስተናገድ ያለበት በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ የሰጠው ፍ/ቤት ሆኖ እያለ የክልሉ የዞን ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓቶችን የጣሰና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡
በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአፋር ብሔ/ክልላዊ መንግስት የዞን አራት ከፍተኛ ፍ/ቤት ታህሣስ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. በመዝ.ቁ. 00039 ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በዚህ ጉዳይ የአፈጻጸም ክሱን በመጀመሪያ ተመልክቶ ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለበት በጉዳዩ ላይ በመጀመሪያ ፍርድ የሰጠው የወረዳ ፍ/ቤት እንጂ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለመሆኑ በዚህ የአፈጻጸም መዝገብ ላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሰርዟል፡፡
   የፍርድ ባለመብት በፍርዱ መሠረት ሊፈጸምለት የሚገባቸውን ነጥቦች በተመለከተ በወረዳው ፍ/ቤት ከመጠየቅ የሚከለክለው ነገር የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 04 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቶች፡- 1- አቶ ልኡልሰገድ አጥላባቸው
2- አቶ ሱፊያን አራርሶ
3- አቶ ረመዳን ኢድሪስ
4- አቶ አብዱላዚዝ ኢብራሂም
ጠበቃ አስፋው ገ/አሊፍ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1- ፍሎራ ኢኮ ፖወር ኃ/የተ/የግል ድርጅት- ነገረ ፈጅ ሽመልስ ሣተናው ቀረቡ

2- የፍሎራ ኢኮ ፖወር ሠራተኞች ማህበር-ተወካይ ደሣለኝ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአፈፃፀም ክርክር የሚመለከት ሲሆን አመልካቾች በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የ1ኛ ተጠሪ የሆኑ ተሸከርካሪዎች በሀራጅ በሚሸጡበት ወቅት ግገር የፈጸሙ እና ፍርድ ቤቱም የሀራጅ ሽያጩን በተመለከተ በአግባቡ አልተከናወነም በማለት ሰርዞ አመልካቾቹም የተረከቡትን ማሽኖች እና ተሸከርካሪዎች እንዲመልሱ በመወሰኑ ፣ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውም ውሣኔ በክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት በመጽናቱ የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልን በማለት አመልካቾችን በማመልከታቸው የቀረበ ነው፡፡

አመልካቾች ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት ቅሬታ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያሉትን ነጥቦች ያቀረቡ ሲሆን ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ስድስት ገጽ የአቤቱታ ፍሬ ሃሣብ ፡- የገዛናቸው ተሸከርካሪዎች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በህጉ አግባብ ባወጣው ሀራጅ መሠረት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ራሱ ያዘዘውን በራሱ መልሶ መሻሩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ፣ በወጣው ማስታወቂያ መሠረት ጨረታውን ተሳትፈን የገዛነውን ተሸከርካሪዎች እንድንመልስ መወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ ፣ በጉዳዩ ላይ ሃሣባችንን እንድናቀርብ ሳይደረግ የተደረገው ሀራጅ መሻሩ አግባብነት ሌለው በመሆኑ ፣ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ተንቀሳቃሽ ንብረት በተመለከተ የሚደረገውን ሀራጅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 435 መሠረት መታየት ሲገባው የበታች ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 445 ን በመጥቀስ ሀራጁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲፈርስ መደረጉ አግባብ ባለመሆኑ ፣ ለተሸከርካሪዎቹ የከፍልነውን ገንዘብ በተመለከተ ምንም ሳይባል መታለፉ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዞ 1ኛ ተጠሪ በቀን 4/2/2004 ዓ.ም በሶስት ገጽ እና 2ኛ ተጠሪም በቀን 30/1/2004 ዓ.ም በሶስት ገጽ በተጻፈ የጽሑፍ መልስ የሰጡ ሲሆን ፍሬ ሃሣቡ ፡- የፍርድ ባለዕዳ ግዙፍ እና የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ማሽኖችን እና ተሽከርካሪዎችን በቂ ዕውቀት ባለው ባለሙያ ሳይገመት የጨረታው ማስታወቂያ ህጉ በሚያዘው መሠረት ሳይወጣ ፣ የፍርድ ባለመብት በእጅ አዙር የገዛው ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ ጨረታው እንዲሰረዝ የተደረገ በመሆኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካቾች የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ሽያጭ የሚመለከተው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 435 ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን የሚመለከተውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 445 መሠረት በማድረግ ጨረታውን የመሰረዛቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ ከዚሁ ከነበረው ጭብጥ አኳያ ጉዳዩ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አከራካሪ የሆነው የሀራጅ ሽያጭ የተካሄደው በጋዜጣ ማስታወቂያ ሳይወጣ እና በወስጥ ማስታወቂያ ብቻ ሀራጅ መደረጉ ፣ በሀራጅ ሽያጩ ላይ የማጭበርበር ተግባር የተፈጸመ ስለመሆኑ እንደዚሁም ንብረቶቹ ከዋጋቸው በታች የተገመቱ እና የተሸጡ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጡ ነጥቦች ናቸው፡፡ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ይዘን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት በእርግጥ በበታች ፍርድ ቤቶች የተከናወነው ሀራጅ እንዲፈርስ ሲደረግ የተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 445 መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 432 እስከ 438 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች እና በተለይም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 435 በመሆኑ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አኳያ የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት መመልከት ተገቢነት አለው፡፡

በዚሁ መሠረት በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ይዘን በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ ወይም የተከናወነውን ጨረታ መሰረዛቸው አግባብ ስለመሆን ወይም አለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 435 አኳያ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚህ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ድንጋጌ ርዕስ እንደሚያሳየው የሽያጩ ስርዓት በትክክል ያለመፈጸም ሽያጩን የሚያፈርስበት ሁኔታ በሚል የተቀመጠ በመሆኑ ፣ ወደ ድንጋጌው ይዘት ስንገባም በእርግጥ ለሽያጩ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ጉድለት በመገኘቱ ወይም የሽያጩ ስነስርዓት በትክክል አልተፈጸመም በማለት ብቻ የተከናወነው ጨረታ በሰበብ አስባብ ሊፈርስ እንደማይችል የሚደነግግ ቢሆንም በሂደቱ ላይ ጉዳት አድርሶ ከሆነ ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነን ሰው ካሣ እንዲከፍል መወሰን የሚቻል ስለመሆኑ ፈቃጅ በሆነ ሁኔታ የሚደነግግ ከመሆኑም በላይ እንደ ጉዳዩ አግባብ እየታየ የተከናወነው ጨረታ ፈርሶ የተሸጠውም ንብረት እንዲመለስ የሚወሰንበት አግባብ እንዳለ ከድንጋጌው አቀራረጽ ፣ ዓላማ ፣ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሚንቀሳቀስ ንብረት በሀራጅ በሚሸጥበት ጊዜ ማንኛውም ዓይነት ስህተት ቢፈጸም ጨረታው የሚሰረዝበት አግባብ የለም በሚል መልኩ በአመልካቾች የቀረበው ክርክር የዚህን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ዓለማ ያላገናዘበ እና በሂደቱ ፍትሐዊነት ላይ ፍርድ ቤቶች ያላቸውን ሚና ያላገናዘበ ነው ብለናል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም የተረጋገጡትን ፍራ ነገሮች በመመልከት የተከናወነው ጨረታ እንዲፈርስ ውሣኔ መስጠታቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 435 አኳያ ሲታይ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለ የሚያሰኝ አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔውን ሲያስተላል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 435ን መጥቀስ ሲገባቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 445. መጥቀሳቸው አግባብነት ያለው ድንጋጌ ባይሆንም ከውጤት አኳያ ግን ተቀባይነት ያለው መደምደሚያ በመሆኑ የተከናወነው ሀራጅ ይፍረስ መባሉ የሚነቀፍበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በሌላ በኩል በዚሁ የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ 64628 ላይ የፍርድ ባለመብት የነበሩት ግለሰብ የተከናወነው ጨረታ ሊፈርስ አይገባም በማለት በዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ በተመሣሣይ ቅሬታቸውን አቅርበው ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ከአሁኖቹ ተጠሪዎች ጋር ተከራክረው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የጸና እና በዚሁ ጭብጥ ላይ ንብረቶቹን ገዛን የሚሉት የአሁኖቹን አመልካቾች ክርክር ተመልክተን ከላይ በተመለከቱት ነጥቦች ምክንያት ተመሣሣይ መደምደሚያ ላይ ደርሰናል፡፡

ባጠቃላይ የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተካሄደው የሀራጅ ሂደት ጉልህ ግድፈቶች ስለመከሰታቸው በፍሬ ነገር በተረጋገጠበት ሁኔታ ሀራጁ ተሰርዞ አመልካቾች የገዙትን ንብረት እንዲመልሱ በመባሉ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ 124624 በቀን 26/7/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካቾች በመዝ.ቁ 107688 ላይ ያቀረቡትን ይግባኝ በመዝ.ቁ 107486 ላይ በማጠቃለል በቀን 03/5/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ 18376 በቀን 7/1/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በሀራጅ ሽያጭ ሂደት ግዙፍ ግድፈቶች በሚኖሩበት ጊዜ የተከናወነው ሀራጅ እንዲሰረዝ መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 65814

የካቲት 29 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ሚ/ር ቺዛኖ ቤነኛ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ዘውዱ ወልደሥላሤ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲሚ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች የአሁን ተጠሪ ከፍርድ ባለእዳ ከአቶ ወንድወሰን ካሣ ቤት ገዝተው ያልከፈሉት የቤቱ ዋጋ 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ አለ፡፡ ይህንንም ለማንም ሣያስተላልፉ ይዘው እንዲቆዩ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ ይህንን ገንዘብ ለፍርድ ባለእዳው እዳ መፈፀሚያ እንዲሆን በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በእኔ እጅ የነበረውን ገንዘብ ለመንግስት መከፈል ላለበት የካፒታል ጌይን ታክስና ሌሎች እዳዎች ከፍያዋለሁ በማለት መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የፅሑፍ መቃወሚያ አቀርበዋል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በእጃቸው የነበረውን የፍርድ ባለእዳ የቤት ዋጋ ለካፒታል ጌይን ታክስና ለሌሎች እዳዎች የከፈሉ በመሆኑ ገንዘቡ የፍርድ ማስፈፀሚያ ሊሆን አይችልም፡፡ የፍርድ ባለመብቱ የፍርድ ባለእዳውን ሌላ ንብረት አጣርተው ያቅርቡ በማለት መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚው ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ አፅንቶአል፡፡ አመልካች የካቲት 18 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የያዙት ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ለፍርድ ባለእዳው የሚከፈል ገንዘብ በመሆኑ ተጠሪና የፍርድ ባለእዳው ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህን ገንዘብ ተጠሪ ይዞ እንዲቆይና ለሌላ ወገን እንዳያስተላልፍ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ የፈፀመው ተግባር የሥር ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው የሚገባው አይደለም፡፡ የካፒታል ጌይን ታክስ የመክፈል ግዴታ የገዥ ሣይሆን የሻጭ ግዴታ ነው፡፡ አመልካች በገንዘቡ ላይ ከፍርድ የመነጨ የቀዳሚነት መብት ያለው ሆኖ እያለ ተጠሪ ገንዘቡን ለግል ጉዳዩ ተጠቅመውበታል ስለዚህ የተጠሪ አድራጎት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 156ን የሚጥስ በመሆኑ ገንዘቡን ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በበኩላቸው መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የፍርድ ባለእዳው ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ በእኔ እጅ እንዲቆይ ትእዛዝ መሰጠቱ የሚታመን ነው፡፡ ገንዘቡ በእኔ እጅ የቆየው የፍርድ ባለእዳ የሸጠለትን ቤት ወደ እኔ ስም ለማዘዋወር ሊከፍሉት የሚገባውን የመንግስት ግብር ለመክፈል ነው፡፡ ብር 84,580.47 /ሰማንያ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ ብር ከአርባ ሰባት ሣንቲም/ ከፍዬ ቀሪው ብር 4,085.80 ለቦታ ቅጣት የከፈልኩ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ገንዘቡ የተከፈለው በፍርድ ባለእዳው በአቶ ወንድወሰን ካሣ መሆኑ የቀረበው ደረሰኝ ያሣያል ተጠሪ ከፍሏል ቢባል እንኳን ገንዘቡ ከፍርድ ባለእዳ ጋር ያደረገውን ውል ማስፈፀሚያ ያደረገው የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ በመጣስ በመሆኑ ህጋዊ እውቅና ሊሰጠው አይገባም በማለት ሰኔ 26 ቀን 2003 ዓ.ም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ተጠሪ ለፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን ይዘው እንዲቆዩ የታዘዘውን ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ተጠሪ የፍርድ ባለ እዳው የሸጠልኝን ቤት ስም ለማዛወር ለካፒታል ጌይን ታክስና ለሌሎች እዳዎች ከፍያለሁ በማለት ያቀረቡትን ክርክር የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት መቀበላቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን የሥር አመልካች ተጠሪ ለፍርድ ባለእዳው ያልከፈሉትን ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ ለፍርድ ማስፈፀሚያ ለማድረግ ያቀረቡትን አቤቱታ፤ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና የአፈፃፀሙን ክርክር ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 29879 በትእዛዝ በማስቀረብ አይቶታል፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት የአፈፃፀም መዝገብ እንደተረዳነው የፍርድ ባለመብት የሆኑት አመልካች የፍርድ ባለእዳው አቶ ወንድወሰን ካሣ ለተጠሪ /አቶ ዘውዱ ወ/ሥላሤ የሸጡት ቤት ንብረትነት ሲዛወር የሚከፈል ብር በገዥው በተጠሪ እጅ ስላለ ገዥው ገንዘቡን ለባለእዳው ሣይከፍሉ በእጃቸው ይዘው እንዲቆዩ እና ይህንንም ለመፈፀማቸው ቀርበው እንዲያስረዱ ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ሐምሌ 2 ቀን 1996 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ተጠሪ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ለባለ እዳው ሣይከፍሉ ይዘው እንዲቆዩ አዟል፡፡ እንደዚሁም ፍ/ቤቱ የአሁን ተጠሪ በ ትእዛዙ መሠረት የፈፀሙ መሆኑን ወይም የማይፈጽሙበ ምክንያት ካለ በሚቀጥለው ቀጠሮ ቀርበው እንዲያስረዱ በማለት ሐምሌ 2 ቀን 1996 ዓ.ም. ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ለተጠሪም የእግድ ትእዛዙን ከመጥሪያ ጋር ልኳል፡፡

የአሁን ተጠሪ መጥሪያው እና የእግድ ትእዛዙ ከደረሳቸው በኋላ ሐምሌ 26 ቀን 1996 ዓ.ም ከጠበቃ ጋር ቀርበው ከተባለው ገንዘብ ውስጥ ብር 90,000 /ዘጠና ሺህ ብር/ ለመንግስት ግብር ተከፍሏል በማለት አስረድተዋል፡፡ አመልካች የተጠሪ ክርክር ትክክለኛ አይደለም ተጠሪ ገንዘቡን በሞዴል 85 ገቢ እንዲያደርጉ ትእዛዝ ይሰጠልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ መርምሮ ብይን ለመስጠት ለህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ ህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ብር 90,000 /ዘጠና ሺህ ብር/ ለመንግስት ግብር የከፈሉ መሆኑን የሚያሣየው ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑን ገልጾ ይህ ፍ/ቤት ገንዘቡ ታግዶ እንዲቆይ የሰጠው ትእዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ ለመንግስት ግብር የከፈለ መሆኑን የሚያሣየውን ህጋዊ ደረሰኝ ያቅርቡ በማለት ትእዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ ደረሰኝ የሚያቅርቡ ቢሆን ለመጠባበቅ ለህዳር 17 ቀን 1997 ዓ.ም. ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ ህዳር 17 ቀን 1997 ዓ.ም. የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው ባለፈው ቀጠሮ ደንበኛቸው ብር 90,000 /ዘጠና ሺህ ብር/ ለመንግስት ግብር ከፍያለሁ ያሉት በስህተት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው ገንዘቡ ገና አልተከፈለም ወደ ፊት የቤቱ ንብረትነት ከሻጭ ወደ ገዥ ሲዛወር የሚከፈል በመሆኑ ልንጠየቅ የሚገባው ክፍያ አይደለም በማለት አመልክቷል። ፍርድ ቤቱ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳውን ገንዘብ ለማንም ሣይከፍሉ በእጃቸው ይዘው እንዲቆዩ በማለት ህዳር 17 ቀን 1997 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል። ተጠሪ በእኔ እጅ የነበረውን ገንዘብ የፍርድ ባለእዳው መክፈል የሚገባቸውን የካፒታል ጌይን ታክስና ለትርፍ ቦታ ቅጣት ከፍያለው የሚሉት መጋቢት 26 ቀን 1997 ዓ.ም. መሆኑን ለሥር ፍ/ቤት ያቀረቧቸው ቁጥራቸው 981809 እና 931808 የሆኑ ደረሰኞች ያሳያሉ። ከላይ ይዘታቸውን የገለጽናቸው የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጣቸው ትዕዛዞች ተጠሪ አከራካሪውን ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ የፍርድ ባለ ዕዳው ሊከፍለው ለሚገባው የግብር ዕዳም ሆነ በሌላ ምክንያት ወጭ ሳያደርግ ባለበት ሁኔታ ይዞ እንዲቆይ ግልጽና የማያሻማ ትዕዛዝ ሰጥቶ እያለና ተጠሪም ይህንን የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ እያወቀ ገንዘቡን ለካፒታል ጌይን ታክስና በትርፍ ቦታ ቅጣት የከፈለ መሆኑን ነው።

የፍርድ ባለእዳ የሆነ ሰው በእጁ ያልገባ ከሌላ ሰው የሚጠይቀው በሚተላለፍ ሰነድ ያልተደገፈ ገንዘብ ያለው መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ገንዘቡን የመያዝ ወይም የማስከበሩ ሥርዓት የሚፈፀመው ፍርድ ቤት ግልጽ የሆነ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ለፍርድ ባለእዳው ገንዘብ መክፈል የሚገባው ሰው ይህንን የሚከፈለውን ገንዘብ ለማንም ሰው ሣይሰጥ በእጅ እንዲቆይ በማድረግ እንደሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 409 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል። የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሀምሌ 2 ቀን 1996 ዓ.ም፣ ህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም. እና ህዳር 17 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተጠሪ ገንዘቡ አንድ ጊዜ ለግብር እዳ ተከፍሏል። ሌላጊዜ ደግሞ ወደፊት ለግብር እዳ የሚከፈልና ጊዜ የማይሰጥ ነው በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ገንዘቡን ለማንም ሣይሰጥ በእጃቸው ይዘው እንዲቆዩ ግልፅና የማያሻማ ተደጋጋሚ ትእዛዝ የሰጠ መሆኑንና ትእዛዙም በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 409 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ያደረገ መሆኑን ነው።

የከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ እጅ ተይዞ እንዲቆይ ትእዛዝ የሰጠበት ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ ለአመልካች የእዳ መክፈያነት መዋል አለበት ወይስ ተጠሪ ከፍርድ ባለእዳው የገዙትን ቤት ስም ለማዛወር መክፈሉ አስፈላጊ ለሆነው የካፒታል ጌይን ታክስ ክፍያ መዋል አለበት? የሚለውን ጭብጥ ያልወሰነውና ወደፊት መርምሮ ትእዛዝ የሚሰጥበት መሆኑን ህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም በሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ በግልጽ አስፍሮታል። ተጠሪ ገንዘቡን ይዞ እንዲቆይ ትእዛዝ የተሰጠበት ገንዘብ ለአመልካች እዳ መክፈያነት ይውላል ወይም ተጠሪ ከፍርድ ባለእዳ የገዛውን ቤት ስመሀብት ለመዛወር ሻጭ (የፍርድ ባለእዳው) ለሚከፍሉት የካፒታል ጌይን ታክስ መክፈያነት ይዋል የሚለውን የሥር ፍርድ ቤት ሣይወሰንና ግልጽ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት አመልካች ከፍርድ ባለእዳው ጋር አድርጌዋለሁ የሚሉትን የቤት ሽያጭ በውሉ መሠረት የቤቱን ስመሀብት ሻጭ (የፍርድ ባለእዳው) ወደ ገዥ (ተጠሪ) ለማዛወር በህግ እንደ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠው የካፒታል ጌይን ታክስ ለመክፈል የሥር ፍርድ ቤት በተደጋጋሚ የሰጠውን የእግድ ትእዛዝ በመጣስ ገንዘቡን ወጭ ያደረግሁ መሆኑን ያሳዩልኛል የሚሏቸውን ደረሰኞች በማያያዝ ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነውን ትእዛዝ ለሰጠው ችሎት ክርክር አቅርበዋል። ይኸው ተጠሪ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ሐምሌ 2 ቀን 1996 ዓ.ም፣ ህዳር 9 ቀን 1997 ዓ.ም ተጠሪ ገንዘቡን ለማንም ሣይሰጡ በእጃቸው ይዘው እንዲቆዩ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ እዲነሣላቸው የሥነ ሥርዓት ህጉን መሠረት በማድረግ አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 409 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሰጠው የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሣያደርግ፣ ገንዘቡን በራሳቸው ፍላጎትና ግላዊ ውሣኔ የእሳቸውን መብትና ጥቅም ለሚያስከብር ተግባር /ክፍያ/ ወጭ ያደረጉት መሆኑን የሚያሣይ መሆኑን ተረድተናል፡፡

ፍርድ የሚያስፈፀመው ፍርድ ቤት አንድ ሰው የተወሰነ ነገር ከመፈፀሙ እንዲታገድ ትእዛዝ ሰጥቶ እያለ ትእዛዝ የተሰጠው ሰው በትእዛዙ መሠረት ሊፈፀም ሲችል ሆነ ብሎ ሳይፈፀም የቀረ እንደሆነ ወይም እንዳይፈፀም የተከለከለውን ነገር የፈፀም እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የእንቢተኛውን ንብረት እንዲያዝና እንዲሸጥ አድርጎ የተወሰነበትን ግዴታ እንዲፈፀም ለማዘዝና ተገቢ መስሎ ከታየውም ከንብረቱ ሽያጭ ለፍርድ ባለገንዘብ ካሣ ወይም ኪሣራ እንዲከፈል እንደሚወስን በፍታብሔር ህግ 400 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 156 ንዑስ አንቀጽ 2 የፍርድ ቤትን የእግድ ትእዛዝ ያላከበረው ሰው ንብረት ለፍርድ ባለገንዘቡ ገንዘብ መክፈያ በመሸጥ ለማስከፈል ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ እንደሚሰጥ የሚደነግግ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ እግድን ያላከበረውን ሰው የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ በመጋፋቱ በችሎት መድፈር ወንጀል የወንጀል ቅጣት ሊወሰንበት እንደሚችል የፍታብሔር የሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 156 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አመልካች ለፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን ይከበርልኝ በማለት የፍርድ ባለእዳው ሀብት የሆነ ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ ለማንም ሰው ሣይሰጥ በእጁ ይዞ እንዲቆይ የፌዴራል ከፍትኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ተደጋጋሚና ግልጽ ትእዛዝ እያወቀና ገንዘቡ የእግድ ትእዛዝ ሊሰጥበት አይገባም የሚል መቃወሚያ ሲያቀርብና በችሎት ሲከራከር ቆይቶ ፍርድ ቤቱ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሣይነሣና ተጠሪ ገንዘቡን የፍርድ ባለእዳ የሸጠውን ቤት ስመሀብቱ ለማዛወር ቅድመ ሁኔታ የሆነውን የካፒታል ጌይን ታክስና የትርፍ ቦታ ቅጣት መክፈያነት አውየዋለሁ በማለት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት መቀበላቸው ተገቢነት የሌለውና ከላይ የጠቀስናቸው የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት ያላደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ማንም ሰው ህጉን በእጁ አድርጉ እንዲጠቀምና በራሱ ጉዳይ ዳኛ ሆኖ እንዲወሰን አይፈቀድለትም፡፡ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳው ብር 100,000 /መቶ ሺህ ብር/ በእሱ እጅ የነበረ መሆኑን በመጠቀም ገንዘቡን ለማንም ሰው አሳልፎ እንዳይሰጥ ወይም እንዳይከፈል ፍርድን የሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት የሰጠውን ግልጽ የእግድ ትእዛዝ እያወቀ ሆነ ብሎ ገንዘቡን የፍርድ ባለእዳው ከእኔ ጋር ላደረገው የቤት ሽያጭ ውል ለሚፈለግበት የካፒታል ጌይን ታክስ እና የትርፍ ቦታ ቅጣት እጠየቃለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር የፍታብሔር ህግ ቁጥር 409 ንዑስ አንቀጽ 1፣ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 400 እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 156 ድንጋጌዎችን የሚጥስና የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ተግባር ሆኖ እያለ ተጠሪ አመልካች ላቀረበው የፍርድ አፈፃፀም ጥያቄ ተጠያቂነት የለበትም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ስለሆነም አመልካች ለማንም ሰው ሳይሰጥ ወይም ክፍያ ሣይፈጽም ፍርዱን በሚያስፈፀመው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ተደጋጋሚ ግልጽ ትእዛዝ በመጣስ የፍርድ ባለእዳው ከእኔ ጋር ባደረገው ውል ምክንያት ለነበረበት የካፒታል ጌይን ታክስና ለትርፍ ቦታ መቀጫ ክፍየዋለሁ የሚለውን ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ለፍርድ ባለመብት (አመልካች) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 409(1) የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 400 የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 156(2) መሠረት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍትኛ ፍርድ ቤት መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ህዳር 22 ቀን 2003 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ለአመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ውጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 69385

የካቲት 28 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዶፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዳሽን ባንክ (አ/ማ) ነገረ ፈጅ አቶ ካሌብ ተስፋዬ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ - ቀረቡ

2. አቶ ሐሴን አህመድ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረም በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በአፈፃፀም ክርክር ጣልቃ መግባትን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የነበራቸው ጋብቻ በፍች ከፈረሰ በኋላ የጋራ ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሁለተኛ ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳ ወይም በአፈፃፀም የሚከራከሩባቸው ንብረቶች ተጠሪዎች በጋብቻ በነበሩበት ወቅት ለወሰዱት ብር 12,835,838.26 (አሥራ ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር ከሀያ ስድስት ሣንቲም) በመያዣነት የተያዙ በመሆናቸው በአፈፃፀሙ ክርክር ጣልቃ እንድገባ ይፈቀድልኝ በማለት ያቀረበውን ማመልከቻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንብረቶቹ ፍርድ ያረፈባቸው በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 170105 ታህሣሥ 5 ቀን 2003 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡

አመልካች ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች ለወሰዱት ብድር በመያዣነት የያዛቸውን ቁጥራቸው አስራ ሁለት የሚሆኑ የማይንቀሣቀሱ እና የሚንቀሣቀሱ ንብረቶች በመዘርዘር አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ባላቸው ክርክር መነሻ ንብረቶቹ በሀራጅ እንዲሸጡ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ሰጥቶ ውክልና ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰጥቷል፡፡ አመልካች ዕዳው የተጠሪዎች የጋራ ዕዳ ንብረቶቹም የተመዘገቡ የብድር መያዣዎች መሆናቸውን በማስረዳት የቀዳሚነት መብት ለማስከበር በአፈፃፀም ክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት አመልክቷል፡፡ አንደኛ ተጠሪ አመልካች በአፈፃፀሙ ክርክር ጣልቃ እንድገባ ቢደረግ ተቃውሞ የለኝም በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ ንብረቶቹ የጋራ ንብረት መሆናቸው ፍርድ ያረፈባቸው ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ በጋብቻ ተሣሥረው የኖሩና ጋብቻቸው በፍች እንዲፈርስ የተደረገ መሆኑንና ሁለተኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳ በመሆን በአፈፃፀም የሚከራከሩት በጋብቻ ወቅት የገኙትን የጋራ ሀብት እንዲከፋፈሉ የተሰጠን ውሣኔ ለማስፈፀም በተከፈተው መዘገብ ነው፡፡

አመልካች አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ የጋራ ሀብት ለመከፋፈል በሚያደርጉት የአፈፃፀም ክርክር ጣልቃ ለመግባት የሚጠይቀው አመልካችና ተጠሪ የፀና ጋብቻ ላይ በነበሩበት ወቅት ቁጥራቸው አስራ ሁለት የሚሆኑ የማይንቀሣቀሱና የሚንቀሣቀሱ ንብረቶች በመያዝ ብር 12,835,838.26 ብድር የሰጠሁ በመሆኑ በንብረቶቹ ላይ የቀዳሚነት መብት አለኝ በማለት ነው፡፡ ከባል ወይም ከሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በፍርድ የተረጋገጠባቸው ወይም ሁለቱም ያመኑት ዕዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ ይኸው ዕዳ የባልና የሚስት ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ የሚከፈል ስለመሆኑ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 89 ይደነግጋል፡፡ አመልካች ላበደረው ብድር በመያዣነት የያዛቸውን ንብረቶች ሸጦ የብድሩ መክፈያ ለማድረግ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ የማያስፈልገው መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እንደተሻሻለ ህግ አውጭው አውጥቷል፡፡ እንደዚሁም በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት ንብረት እንዳይያዝ፣ ወይም እንዳይከበር የመቃወም አቤቱታ ሲቀርብ ወይም በቡዙ ንብረት ላይ ቀዳሚ መብት አለኝ የሚል ተቃዋሚ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መቀወሚያ ያቀረቡት ወይም እንዲያዝ በታዘዘው ንብረት ላይ ተቀዳሚ መብት አለን የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ክርክር ላይ ተካፋይ ባይሆኑም በሚያዘው ንብረት ላይ መብት እንዳላቸው በመቁጠር የሚያቀርቡትን አቤቱታ ተቀብሎ መመርመር እንዳለበት፣ አቤቱታውንና ማስረጃውን መርምሮ ውሣኔ መሰጠት እንደሚገባው በፍታብሔር የሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 418 እና ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 419 ድንጋጌዎች በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግና የፍታብሔር ህጉን ድንጋጌዎችና ሌሎች የህግ ማዕቀፎች መሠረት በማድረግ አመልካችና ተጠሪ በአፈፃፀም እንዲከፋፈሉአቸው ትዕዛዝ በተሰጠባቸው ንብረቶች ላይ ያለውን የቀዳሚነት መብት ለማሣየት ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል ወደ ክርክሩ እንዲገባ መፍቀድ ሲገባቸው ንብረቶቹ ውሣኔ ስለተሰጠባቸው በአፈፃፀም ጣልቃ መግባት አይፈቀድም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በአፈፃፀሙ ጣልቃ ለመግባት ያቀረበውን አቤቱታና ማስረጃ በመቀበልና የተጠሪዎችን ክርክርና ማስረጃ በመቀበልና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቀጥር 341 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፌሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- ወ/ሮ ሰይዳ ደበሌ - ጠበቃ ዕዮብ ገ/ህይወት ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሸሪፍ ሸኩር - በሌሉበት ታይቷል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችንና ተጠሪን በፍርዱ መሰረት በስምንት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያለውን ቤት ተከራካሪዎች የተለያየ ድንበር በማሣያታቸውና ቦታውም ሰነድ አልባ በመሆኑ ለማካፈልም ሆነ ለመሸጥ አስቸጋሪ እንደሆነ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን ጽ/ቤትና ቀበሌው የገለፁት መሆኑን ምክንያት በማድረግ አፈፃፀሙን መቀጠል አይቻልም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች መስከረም 12 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በጋብቻ ዘመን በጋራ ያፈራነውን ቤት እኩል እንድንካፈል የተሰጠውን ፍርድ ማስፈፀም አስቸጋሪ ነው በሚል ምክንያት አፈፃፀሙ መዘጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ መጥሪያ አልቀበልም ስለማለቱ በቃለ መሀላ አረጋግጣ ማመልከቻ አመልካች ስላቀረበች መልስ የመስጠት መብቱን በማለፍ ጉዳዩን በሌለበት መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አፈፃፀም ለመቀጠል አስቸጋሪ ነው የተባለው ቤት አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ሲኖሩ ያፈሩት የጋራ ሀብት መሆኑ ቀደም ሲል ፍርድ ተሰጥቶበታል፡፡ ቦታውና ቤቱ ግብር ሲከፈልበት የኖረ መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ ቦታውን ለረዥም ጊዜ ይዘውት እንደነበሩ አመልካች በሥርና በሰበር ካቀረበችው ክርክር ለመረዳት የሚቻል ሲሆን በፍርዱ መሰረት ቦታውና ቤቱን ለማካፈል ወይም በሐራጅ ለመሸጥ አይቻልም በማለት የሥር ፍ/ቤት የአፈፃፀም መዝገቡን የዘጋው ቦታው ሰነድ አልባ መሆኑን የመሬት አስተዳደር ባለስልጣንና የክፍሉ ቀበሌ አስተዳደር ዕርጋኛል በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 378 መሰረት ሲቀርብለት፣ የፍርድ ባለዕዳው የሚያቀርበውን መልስ በመቀበል፣ ፍ/ቤቱ ተገቢ የሆነውን ትዕዛዝ መስጠት እንዳለበት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 386 ተደንግጓል፡፡ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት በመሆኑ እኩል እንዲከፈል፤ እኩል ማካፈል የማይቻል ከሆነ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ ውሳኔ የተሰጠበት ንብረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው፡፡ ይህ ንብረት ካርታ ፕላን ባይኖረውም የማይንቀሳቀሰውን ንብረትና ይዞታ ለመለየት የሚያስችሉ ልዩ ምልክቶችንና የንብረቱን አዋሳኞች በመለየትና ግልፅ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረትና ቦታ ለፍርድ ባለመብትና ለፍርድ ባለዕዳ እኩል እንዲከፍሉ ትዕዛዝ ለመስጠት ወይም እኩል ለማካፈል የማይቻል ከሆነ ቤቱና ቦታው ካርታና ፕላን የሌለው መሆኑንና የንብረቱን አዋሳኞች በጨረታ ማስታወቂያው ላይ በመግለፅ ንብረቱን በመሸጥ ለማካፈል የሚቻልበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 423 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የፍርድ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በፍርድ አፈፃፀም ሂደት እንደዚህ አይነት ችግሮች ሲያጋጥሙት ለፍርዱ አፈፃፀም ተስማሚ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣንና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት መሆኑ በፍርድ ቀደም ብሎ የተረጋገጠው ቤት ሰነድ አልባ በመሆኑ ንብረቱን ለማካፈልም ሆነ ለመሸጥ አስቸጋሪ መሆኑን የአስተዳደር አካል ፅፎልኛል በማለት የአፈፃፀም መዝገቡን መዝጋቱ፤ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 371 ንዑስ አንቀጽ 1 የተሰጠውን ፍርድ የማስፈፀም ሥልጣንና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 392 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች የሚቃረን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ሣያርም ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና በማየት ፍርዱን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆነውን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/392 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በመስጠት ፍርዱን እንዲያስፈፅም ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 77175

ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-አሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ኢትዮጵያ- ጠበቆች 1. ማርሻል ፍቅረ ማርቆስ ቀረቡ

2. ሰለሞን እምሩ ቀረቡ

ተጠሪ፡-1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ

2.. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ ጎሳዬ

3. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የመሬት አስተዳደርና አየለ ቀረቡ

የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሊዝ ውል አፈጻጸም ጋር የተያያዘ ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁኖ በአመልካች ከሳሽነት ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም፡- በየካቲት 11 ቀን 1997 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሊዝ ቦርድ ባሳለፈው ውሳኔ በቀድሞው ዞን 3፣ ወረዳ 28 መር ቀበሌ ገበሬ ማህበር ክልል ውስጥ (ባሁኑ አጠራር በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20/21 ክልል ውስጥ የሚገኝ 303,000 ካ.ሜትር ቦታ በሊዝ እንዲሰጠው ተወስኖለት በከተማ ቦታ የምስክር ወረቀት ሴሪ ቁጥር 0710 እና በካርታ ቁጥር ሊዝ 0236 ተረክቦ ቦታው በአመልካች ይዞታ ስር እንደሚገኝ፣ ሆኖም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን ቁጥር መአግፈባ/502/03 በ8/02/2003 ዓ.ም. በጻፈው ደብዳቤ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ በ22/11/2002 በቃለ ጉባኤ ቁጥር 16/2002 አሳለፈ ያለውን ውሳኔ በመጥቀስ አመልካች ከክፍያ ነጻ በተሰጠው ቦታ ላይ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታ ሳያከናውን ቆይቶ የቦታ አገልግሎት ለውጥ ጥያቄ በማቅረቡ የሊዝ ውሉ ተሰርዞ ካርታው መክኖ ቦታው እንዲመለስ መወሰኑን፣ ይህም ከሕግና ከሊዝ ውል ስምምነቱ ውጪ መሆኑን፣ ግንባታው በጊዜ ገደቡ ውስጥ ካልጀመረ ውሉ እንደሚሰረዝ ግልፅ ስምምነት የሌለ መሆኑንና ግንባታው ሊዘገይ የቻለውም የካቲት 2002 ዓ.ም. ድረስ የቆየው አስተዳደሩ በውሉ አንቀፅ 3.1 በገባው ግዴታ መሰረት ቦታው ላይ የሰፈሩትን ሰዎች ካሳ ከፍሎ ባለማስናበቱና ለውጥን በተመለከተም አመልካች የፕሮጀክት ለውጥ እንዲደረግለት በውሉ እና በሕግ መሰረት ጥያቄ ማቅረብ ስለሚችል ለውሉ መሰረዝ ምክንያት ሊሆን እንደማይችል ዘርዝሮ ውሉ መሰረዙ ያላግባብ ነው ተብሎ የሊዝ ውሉ ጸንቶ በይዞታው የመጠቀም መብቱ እንዲጠበቅለት ይወሰን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የሚያነሱት ክርክር ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች እንጂ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አይደለም የሚል ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የሊዝ ውሉ የተሰረዘውና ካርታው የመከነው በውሉ እና በሕጉ መሰረት መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ነው፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ክሱ የቀረበው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት ላይ መሆኑና የክሱ መሰረትም የሊዝ ውል መሆኑን ጠቅሶና የአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41(1(ሀ) ድንጋጌን ዋቢ በማድረጉ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ ከሊዝ ውል አፈጻጸም ጋር የተያያዘ ሁኖ ከከተማው መሪ ፕላን ጋር የተያያዘ ባልሆነበት ሁኔታ ግንኙነት የሌለው ድንጋጌ ተጠቅሶ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ፍርድ ቤቶች ናቸው ተብሎ የተወሰነው አግባብነት ካለው ህግ ይዘትና በሰ/መ/ቁጥር 57435 ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ውጪ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ናቸው ተብሎ መወሰኑ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41(1(መ)) ድንጋጌና በሰ/መ/ቁጥር 45091 ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ሕጋዊ ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደረመረውም ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ናቸው? ወይስ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሐምሌ 14 ቀን 1990 ዓ.ም በተፈረመ የከተማ ቦታ ሊዝ ውል ጠቅላላ ስፋቱ 303,000 (ሶስት መቶ ሶስት ሺህ) ካሬ ሜትር ቦታ በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20/21 ክልል ውስጥ ለዘጠና አመታት መውሰዱንና ተጠሪዎች አመልካች ቦታውን በጊዜ ገደቡ ሳያለማ ለአስራ ሶስት አመታት ይዞ በመቆየቱና የፕሮጀክት ለውጥ ለማድረግ ጥያቄ አቅርቧል በሚል ምክንያት የሊዝ ውሉን በመሰረዝ ካርታውን ያመከኑ መሆኑንና አመልካች የሚጠይቀው ዳኝነትም የሊዝ ውሉ እንዲጸናና በይዞታው የመጠቀም መብቱ እንዲጠበቅለት መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ ከኢ.ፌ.ድ.ሪ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37/1/፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4፣ 9፣ 231 እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 እንዲሁም ተሻሽሎ በወጣው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ፍርድ ቤቶች አንድን ጉዳይ ማየት እና ውሳኔ መስጠት የሚችሉት በሕግ በግልጽ ተለይተው በተሰጧቸው ጉዳዮች መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ለእያንዳንዱ ፍርድ ቤት በሕግ የተሰጠው ስልጣንም መጠበቅ ያለበት ከመሆኑም በላይ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ በሕግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው መሆኑ ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ /ክርክር/ መሠረት ያደረገው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረገው የሊዝ ውል የተሰጠውን ቦታ በጊዜ ገደቡ አልለማም፣ የፕሮጀክት ለውጥ ተደርጎአል ተብሎ የሊዝ ውሉ መሰረዙና ካርታው መምከኑ ከሕግ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ ከሊዝ ውል አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ሲሆን የሊዝ ውል መሰረዝን ሕጋዊነት በተመለከተ ስራ ላይ ባለው የሊዝ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት የሚቀርበውን የዳኝነት ጥያቄ የከተማው አስተዳደር በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሣኔ የመጨረሻ እልባት የሚሰጥበት መሆኑን ወይም ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባው መሆኑን የሚደነግግ ሕግ የለም፡፡ የከተማው አስተዳደር ካርታ የመስጠት የመሠረዝ፣ የማሻሻል፣ የማምከን፣ የማገድ እና አሻሽሎ የመስጠት ሙሉ ስልጣን ያለው ቢሆንም የሊዝ ውልን መሠረት አድርጎ የተሰጠውን ካርታ መልሶ ከሕግ ውጪ ሰርዞ ሲገኝ በእርምጃው ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ጉዳዩን ለፍርድ ቤት እንዳያቀርብ የሚከለክልበት ስርዓት የሌለ ስለመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ስልጣንና ኃላፊነትን ለመደንገግ የወጣውና፣ ክርክሩ ሲጀመርም ሆነ ከተጀመረ በኋላ በስራ ላይ ያለው ሕግ ያሣያል፡፡ ይልቁንም የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሀ/ እና /መ/ ድንጋጌዎች አንድ ላይ ተጣምረው ሲታዩ የተያዘውን ጉዳይ አይነት የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ተቀብለውና አከራክረው ለመወሰን የስረ ነገር ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 41(1(መ)) በተለይ ሲታይም የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ስር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸውን አስተዳደራዊ ውሎች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮችን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ለከተማው ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ተፈፃሚነት ካላቸው ሕጎች አንነሳም የሊዝ ውሉም ከደንብ ቁጥር 29/2002 አንቀፅ 15 እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3132 ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በአስተዳደራዊ ውሎች ስር የሚሸፈን ሁኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች ይህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጠ በማለት የሚጠቅሱት መ/ቁጥር 57435 ሲሆን በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ግን በሊዝ ውል በተገኘው ቦታ ሁከት ተፈጠረብኝ በሚል ምክንያት ሁከቱ እንዲወገድ ዳኝነት የተጠየቀበት በመሆኑና እንዲህ አይነት ክርክር ከከተማው መሪ ፕላን አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ካልሆነ በስተቀር በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስረ ነገር ስልጣን ስር አይወድቅም በሚል ምክንያትና የአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41(1(ሀ)) ድንጋጌ በዋቢነት ተጠቅሶ ሲሆን በመዝገቡ ያሉት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮችና ለውሳኔው መሰረት የሆነው አብይ ምክንያት አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር በፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ሙሉ በሙሉ ግንኙነት አለው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ይልቁንም በሰ/መ/ቁጥር 45091 በቀረበው ጉዳይ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ከሊዝ ውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የከተማው አስተዳደር አካላት ተከራካሪ ወገኖች ሲሆኑ ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች እንጂ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አይደለም በማለት የአዋጁ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41(1(መ)) ድንጋጌን ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይህ የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብም በሰ/መ/ቁጥር 57435 በቀረበው ጉዳይ ላይ በግልጽ ተለውጧል ለማለትም የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው በማለት የሰጡት ብይን ከአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሀ/ እና /መ/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ሕጋዊ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ ምክንያት በውሣኔው ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 111380 ታህሳስ 10 ቀን 2004 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75753 ጥር 08 ቀን 2004 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ስር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸውን የሊዝ ውልን መሰረት አድርጎ የሚቀርበውን የውል አፈፃጸምና ተያያዥ ጉዳዮችን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች የስረ ስልጣን ነው ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ. 66957

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡ የኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ነ/ፊጅ አቶ አብርሃም አሻ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- በኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የሐዋሳ ቁጥር 2 ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የቦርድ አባላት፡-

1. አቶ ፊልጶስ ኪንዶ
2. ‹‹ ካሳሁን ይግዛው
3. ‹‹ ታመነ ተሰማ
4. ‹‹ ወንድሙ ጆፌ
5. ‹‹ ሀሳቡ ሀንቃሞ
6. ‹‹ ሲሳይ ዮሐንስ
7. ‹‹ አብሩ ዲቃሞ
8. ‹‹ አበበ ዱባሞ
9. ‹‹ ኤብሶ አታሮ
10. ‹‹ ተሾመ ሌዳሞ
11. ወ/ሮ አስቱር ሀናቃሞ
12. ‹‹ መስታወት አያሌው
13. አቶ ታደገ ቶማስ
14. ዶ/ር ኤልያስ አራጌ
14. አቶ ብርሃኑ ሉምቤሶ
16. ፓስተር ተፈራ ወልደማርያም
17. ወንጌላዊ መስከረም ኃይሌ
18. አቶ አብርሃም ጫፋሞ
19. ‹‹ ደነቀ አሻግሬ
20. ወ/ት ብርቱኳን ተስፋዬ
21. አቶ ኢያሱ ረጋሳ
22. ‹‹ ቡልቻ ላንጋኖ
23. ‹‹ ደስታ አኔቦ አቀረቡ
24. ‹‹ማርቆስ መለሰ
25. ‹‹ ማርቆስ ጋሉ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ክስ በአሁን ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በሐዋሳ ከተማ ከፍ/ፍ/ቤት ሲሆን ተከሳሽ ደግሞ የደቡብ ኢትዮጵያ ስራ መስክ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የሰበካ ጉባኤ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ቃልም የሐዋሳ ቁጥር 2 የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ህገ ደንብና መመሪያ መሰረት የተቋቋመች የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ስትሆን ቤተክርስትያኗ ከ300 እስከ 400 የሚደርሱ መዕመናንን አቅፋ በአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መሰረተ እምነትና የአምልኮ ስርዓት እየሰራች እያለ በ1967 ዓ.ም. ከወጣውና እስካሁን በስራ ላይ ካለው የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ 14 የተጠቀሰውን አብያተ ክርስቲያናት የሚቋቋመበት፣ የሚዋሀዱበትና የሚፈርሱበት ሁኔታን ባልተከተለ መልኩ እንዲሁም አጥቢያ ቤተክርስቲያኗ እንድትዘጋ፣እንድትፍርስ የሚያደርግ አንድም ምክንያት ሳይኖር በታህሳስ 8-9/2001 ዓ/ም የሰበካው ጉባኤ ባደረገው ስብሰባ በሀሰትና በፈጠራ ብቻ የአጥቢያ ቤተክርስቲያኗ እንድትፈርስ ጉባኤው የወሰነ ስለሆነ ውሳኔው ይሻርልን የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በበኩሏ በሰጠችው መልስ ቤተክርስቲያኗ እንድትዘጋ የተወሰነው በአመጽና በክህደት ተግባር ሲሆን ከሳሾችም ከተጠቀሱት ድርጊቶች እንዲታቀቡ የተሀድሶ ሰበካ ተደርጎ እንዲሁም ከስህተታቸው ተመልሰው ለመተዳደሪያ ደንቡ ተገዢ ሆነው እንዲቀጥሉ በመንፈሳዊ ርህራሔ ቢለመኑም በእምቢተኝነት ስለጸኑ እርምጃው ተወስዷል ብላለች፡፡

የስር ከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማና የጽሁፍ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ፍርድ እንድትዘጋ ውሳኔ የተሰጠባት ቤተክርስቲያን የአመጽም ሆነ የክህደት ተግባር ስለመፈጸሟ አልተረጋገጠም፣ ቤተክርስቲያኗ የፈጸመቻቸው ድርጊቶችም ቢሆኑ ከኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብና በተዘጋጀው ማኑዋል መሰረት በመሆኑና የሰበካው ጉባኤ ውሳኔም ይሔንኑ የመተዳደሪያ ደንብና ማኑዋል የጣሰ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ሲል ሰርዟል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባይዋን አሰናብቷል፡፡
በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች አቤቱታዋን ለዚህ ችሎት ያቀረበች ስትሆን በዋናነት የጠቀሰቻቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- ተጠሪዎች ከእናት ቤተክርስቲያን የተሰጣቸው ውክልና ሳይኖር በስማቸው የመክሰስም ሆነ የመከሰስ መብት የላቸውም ፣ ቤተክርስቲያኗ የተመዘገበችው በአዲስ አበባ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አከራክረው የመወሰን ስልጣን የላቸውም በሚል የቀረቡትን የመቃወሚያ ነጥቦችን አለመቀበላቸው ህግ ስህተት ነው፣
- አመልካች ሀይማኖታዊ ተልዕኮዋን ለማሳካት ቅርንጫፍ ቤተክርስቲያናትን የማስፋፋትና እንደአስፈላጊነቱ የአሰራር ስርዓቷን ተከትላ የመዝጋት ሙሉ መብት ያላት በመሆኑ የሐዋሳ ቁጥር 2 ቤተክርስቲያንን በመበተኗ ምክንያት ተጠሪዎች አንድም ያጡትን መብት ወይም ጥቅም ባላስረዱበት የተወሰነው ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33 ዓላማ ውጪ ነው፣
- የስር ፍ/ቤቶች በማስረጃነት ከቀረበው የመተዳደሪያ ደንብ ገጽ 156 ቁጥር(3) መንፈስ ውጪ ደንቡን በመተረጎም ጥፋቶቹ እንደክህደት ወይም አመጽ የሚፈረጁ አይደሉም ሲሉ ቤተክርስቲያኗ እንድትበተን የተሰጠውን ውሳኔ መሻራቸው ያለ አግባብ ነው፣የሚሉ ናቸው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡-

• በፍ/ህ/ቁ/448(1) መሰረት ተጠሪዎች በቤተክርስቲያኒቱ አባልነታችን ያልተቀበልናቸውንና የቤተክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ደንብ የሚጥሱትን የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎችን ለማሻር ክስ የማቅረብ መብት አለን፣
• የስር ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን ተቀብለው አከራክረው የመወሰን ስልጣን የላቸውም በሚል አመልካች ያቀረበችው መቃወሚያም ቢሆን የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህጉን ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣
• አመልካች ሀይማኖታዊ ተልዕኮን ለማሳካት ቅርንጫፍ ቤተክርስቲያን የማስፋፋትና እንደአስፈላጊነቱም የአሰራር ስርዓቷን ተከትላ የመዝጋት ሙሉ መብት እንደአላት ብትገልጽም ይህ መብትና ነጻነት ገደብ የለሽ ባለመሆኑ በሀይማኖት ነጻነት መብቷ ሽፋን የራሷን ደንብ በመጣስ ለጥቂት ግለሰቦች ፍላጎት በሚል በብዙሀኑ ፍላጎት ላይ መጫን አይገባትም በሚል በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት ጠቅለል ባለ መልኩ ከዚህ በላይ የቀረበ ሲሆን እኛም ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በፍርድ ቤት የሚወሰን ጉዳይ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሰበካው ጉባኤ ቤተክርስቲያኗ እንድትፈርስ ውሳኔ ያስተላለፈው ቤተክርስቲያኗ በራሷ ስልጣን እንድያገለግሏት የተመደቡላትን ፓስተር እና ወንጌላዊ አባርራለች፣ ለፓስተር የቅስና ማዕረግ ሰጥታለች፣ አስራትና መባ ለዋናው መስሪያ ቤት አትልክም፣ የተሰጣት ፈቃድ ሳይኖር ለሌሎች የአጥቢያ አድቬንቲስት ቤተክርስቲናት አገልግሎት በመስጠት የክህደትና የአመጽ ተግባር በመፈጸሟ ምክንያት ከድርጊቷ እንድትታቀብ የተሀድሶ ትምህርት ቢሰጣትም ልትመለስ አልቻለችም በሚል ነው፡፡ የተጠሪዋ ቤተክርስቲያን የቦርድ አባላት በበኩላቸው የክህደት እና የአመጽ ተግባር አለመፈጸማቸውንና በአድቬንቲስት መሰረተ እምነትና የአምልኮ ስርዓት የሚሰሩ ስለመሆናቸው ተከራክረዋል፡፡ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመመርመርና በ1967 ዓ/ም የወጣውን የኢትጵያ አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መመሪያ በምዕራፍ 14 አብያተ ክርስቲያናትን ስለማቋቋም፣ማዋሃድ እና ስለማፍረስ በተደነገገው ስር በገጽ 156 በቁጥር 3 ክህደት የሚለው ቃል በመመሪያው ያልተብራራ መሆኑን ጠቅሶ የክህደት እና አመጽ ድርጊቶች ናቸው ተብለው በአመልካች በኩል የተነገሩትን ከምስክሮች ቃል አንጻር ሲታይ ተቀባይነት የለውም፣ በከሳሾች በኩል የተፈጸሙ ድርጊቶችም ቢሆኑ በመመሪያው መሰረት በቤተክርስቲያኗ ማኑዋል መሰረት የተፈጸሙ ናቸው ብሏል፡፡

እንድትፈርስ የተወሰነባት ቤተክርስቲያን ማለትም የሐዋሳ ቁጥር 2 አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለው የአመልካች ቤተክርስቲያን አንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ስትሆን በአጥቢያው ቤተክርስቲያኑዋና በሰበካው ጉባኤ እንዲሁም በኢትዮጵያ 7ኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መካከል ሊኖሩ የሚችሉትን ከአምልኮና ከቤተክርስቲያኗ የውስጥ አስታዳደራዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በፍ/ቤት በመወሰን እልባት መስጠት የሚቻል መሆን አለመሆኑን መመርመር ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም የኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 (1)ን መመልከት ተገቢነት አለው፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ማንኛውም ሰው (የተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ያለው ድርጅት) በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ (justiciable

https://t.me/ethiopianlegalbrief

matter) ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡ በዚሁ አነጋገር በፍርድ ቤት ወይም በሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል ተቀብሎ አከራክሮ ውሳኔ ወይም ፍርድ ሊሰጥ የሚችለው ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ መንግስትና ሀይማኖት የተለያዩ መሆናቸውንና መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ፣ሀይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 11(1) እና (3) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ መንግስትና ሀይማኖት በህገ መንግስቱ የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስ የመንግስት አንዱ ክፍል የሆነው ፍርድ ቤት አመልካች እና ተጠሪዎች ባላቸው ሀይማኖታዊ በሆነ አለመግባባት ወይም በአምልኮ ስርዓት ጣልቃ ገብቶ ህገ ደንቡን በመተርጎም የሚወስንበት የህግ መሰረት የለውም፡፡

በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን በፍርድ ሊወሰን የማይችለውን ጉዳይ ተቀብሎ አከራክሮ መወሰኑም ሆነ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ ተቀብሎ ማጽናቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

- የሐዋሳ ከተማ ከፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 06162 በቀን 09/02/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 50948 በቀን 19/5/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
- ተጠሪዎች ያቀረቡት ጉዳይ በሚከተሉት ሀይማኖታዊ ስርዓት እና በሚመሩበት ደንብ መሰረት እልባት ከሚያገኝ በቀር በፍርድ ቤት የሚወሰን ጉዳይ አይደለም ብለናል፡፡
- የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ይሁን፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥር 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ አክሊለ ገብሬ - ጠበቃ ኪሩቤል ኃ/ማርያም ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- አቶ መለኮት ክንፈሚካኤል - ጠበቃ ፍስሐ ሐጐስ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአደራ የተሰጠ የንግድ ድርጅት ልረከብ ጥያቄን መሰረት ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም. የተጻፈ ሆኖ ይዘቱ በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02 የሚገኝ የቤት ቁጥር 164 የሆነ ንግድ ቤት በባለቤታቸው በአቶ ወልደማሪያም ወልደሚካኤል ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን፣ ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላም ሚስትነታቸውን አረጋግጠው የቤቱ ኪራይ በስማቸው መዛወሩን፣ ከተጠሪ ጋር በነበራቸው ቤተሰባዊ ቅርርብም ድርጅቱን እንዲሰሩበት በአደራ ሰጥተዋቸው ሲሰሩበት ከቆዩ በሁዋላ ድርጅቱን እንዲያስረክቧቸው ቢጠይቋቸው ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ገልጸው ተጠሪ የንግድ ድርጅቱን ለቀው ቤቱን እንዲያስረክቡ፣ እስከሚያስረክቡ ድረስ ደግሞ በወር ብር 3,000.00 እየታሰበ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ከአመልካች በአደራ የወሰዱት የንግድ ድርጅት ቤት የሌለ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ክርክሩ መሰረት ያደረገው የአደራ ውሉን መሆኑን በመገንዘብ የንግድ ድርጅቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገ በመሆኑ በዚህ ድርጅት ላይ የአደራ ውል ስለመኖሩ መረጋገጥ ያለበት በፍ/ሕ/ቁጥር 1723(1) በተመለከተው ሕጋዊ መስፈርት ነው በማለት እና አመልካች ደግሞ በፍ/ሕ/ቁጥር 1723(1) መሰረት የተደረገ የአደራ ውል ስለመኖሩ ያቀረቡት ማስረጃ የለም በማለት ክሳቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህም አመልካች ይግባኛቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ፣ የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በንግድ ድርጅት ቤት ላይ የሚደረገው የአደራ ውል በፍ/ሕ/ቁጥር 1723(1) ድንጋጌ መሰረት መደረግ ያለበት ነው ተብሎ የተወሰነው ያላግባብ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ለተጠሪም ጥሪ ተድርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደረመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በክሱ የጠየቁት ዳኝነት ቀበሌው በባለቤትነት የሚያስተዳድረውን ቤት የተከራይነት መብት ያላቸው መሆኑንና ይኸው መብት እያላቸው ድርጅቱን ተጠሪ እንዲሰሩበት በአደራ ሰጥተው ተጠሪ ሲሰሩበት ከቆዩ በኋላ እንዲያስረክቧቸው ሲጠየቁ ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል መሆኑን፣ ተጠሪ ደግሞ ከአመልካች ጋር ያደረጉት የአደራ ውል የለም ሲሉ በመከራከራቸው የስር ፍርድ ቤት የአደራ ውል አለ? ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ ይዞ ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም አግባብነት አላቸው ያላቸውን የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌዎችን በመመመርመር ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ስልጣንና ኃላፊነት ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣንና ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና በአዋጅ ቁጥር 408/1996 ተቀርሶ የተሰጠ ሲሆን በአዋጁ 361/1995 በአንቀጽ 41 ስር ደግሞ የስረ ነገር ስልጣናቸው በዝርዝር ተለይቶ ተሰጥቷል፡፡ በሕጉ ተለይተው ከተሰጡት የስረ ነገር ስልጣኖች መካከል ንብረትነቱ የከተማው አስተዳደር የሆነ ቤት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን አንዱ ስለመሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 41(1)(ረ) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘትም የከተማው ፍርድ ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማው አስተዳደር ስለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ፣ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ክርክሩ መሰረት ያደረገው የከተማው አስተዳደር የሚያስተዳድረውን ቤት የሚመለከት መሆኑ ብቻውን ሁሉንም ቤቱን መሰረት አድርገው የሚቀርቡትን ክርክሮች የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ለማስተናገድ ስልጣን የሚሰጣቸው አይደለም፡፡

በመሆኑም ክርክር የተነሳበት ቤት የከተማው አስተዳደር ነው? ወይስ የሌላ ግለሰብ? ወይም ድርጅት? የሚል መሰረታዊ ክርክር ያለበት ከሆነ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ይህንን የቤት ወይም የድርጅት ባለቤትነት ጥያቄ አስመልክቶ በከተማው አስተዳደርና በሌሎች ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በዳኝነት አይተው ለመወሰን የሚያስችል የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 (1) (ረ) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የቤቱን ሕጋዊ ባለቤትነትን አስመልክቶ በአመልካች በኩል ክርክር የቀረበበት ሳይሆን የንግድ ድርጅቱ የሚገኝበት ቤት ባለቤት የሆነው ቀበሌም የክርክሩ ተካፋይ አልሆነም፡፡ የክርክሩ መሰረት የአደራ ውል ሆኖ ተካራካሪ ወገኖች ደግሞ ግለሰቦች ሲሆኑ የጉዳዩ መሰረታዊ ጭብጥም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የአደራ ውል አለ? ወይስ የለም? የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ የቤት ይዞታ ወይም ከባለቤትነት በመለስ ያሉ ሌሎች መብቶች ክርክር ባለመሆኑ የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የቤት የይዞታ ክርክርንና ከባለቤትነት መብት በመለስ ያሉትንና ሌሎች ክርክሮችን በተመለከተ የዳኝነት ስልጣን በሕጉ የተሰጣቸው አደራ ውልንም የሚጨምር ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም የአደራ ውልን መሰረት አድርጎ የሚቀርብ ክርክር በከተማው ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑም አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 408/1996 ድንጋጌዎች የሚያሳዩት ጉዳይ አይደለም፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከማየቱ በፊት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም በማናቸውም የክርክር ደረጃ ፍርድ ቤቱ በራሱ ሊያነሳው የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 (1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ሣይኖራቸው ጉዳዩን ሰምተውና አከራክረው የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 05273 ጥር 05 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15309 የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 15663 መጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በሁለት ግለሰቦች መካከል የአደራ ውልን መሰረት በማድረግ የሚነሳውን ክርክር አይቶ የመወሰን ውሳኔ የመስጠት የሥረ ነገር ስልጣን የላቸውም ብለናል፡፡
3. አመልካች ያቀረቡት በአደራ የተሰጠ የድርጅት ቤት ልረከብ ጥያቄን ሥልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ወይም አካል አቅርበው ተገቢውን ዳኝነት የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሣኔ አይገድባቸውም ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 54990

ሕዳር 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን -

ተጠሪ፡- አቶ ማርቆስ አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች አመልካች የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ተከራካሪ የሆነበትን ጉዳይ ተመልክተው ለመወሰን የሚያስችል ሥልጣን ያላቸው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ የመሰረተው የጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ጥያቄ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው የሰ/ቁ/ 2-61006 አ.አ ተሽከርካሪ በስር 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት ግለሰብ ሲሸከረከር ግንቦት 07 ቀን 1999 ዓ.ም. የአመልካች ንብረት የሆነውን የሠ/ቁጥር 4-06809 ኢ.ት. መኪና በመግጨት ጉዳት በማድረሱ መኪናውን ወደ ነበረበት ለመመለስ የወጣውን ወጪ ብር 4,537.50 (አራት ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ተከሳሾች በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በአመልካች መኪና ላይ ጉዳት አደረሰ የተባለው የሰ/ቁጥር 2-61006 የሆነውን መኪና ከሕዳር 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ ለአቶ ሄኖክ ታደሰ በሽያጭ ውል ያስተላለፍኩ ስለሆነ ግጭቱ በደረሰበት ጊዜ የመኪናው ባለንብረት ስላልሆንኩ ልከሰስ አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ግጭቱን አደረሰ የተባለውን መኪና በግጭቱ ወቅት በይዞታቸው ስር አድርገው ሲጠቀሙ ያልነበሩ በመሆኑ ተጠያቂነት የሌለባቸው መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ሁለቱንም ወገኖች ካከራከረ በኋላ ተጠያቂ የሚሆነው መኪናውን የገዛው ሰው እንጂ ተጠሪ አይደሉም በማለት የወሰነ ሲሆን በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለከተማው መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይኸው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የመኪና ባለቤት የሚታወቀው በሊብሬ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 256/60 አንቀፅ 6(1) እና የደንብ ቁጥር 360/69 አንቀፅ 4 ድንጋጌዎች ያሳያሉ በማለት ተጠሪን ለጉዳቱ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይኸው ሰበር ሰሚው ችሎትም ወደ ጉዳዩ ዘልቆ ከመግባቱ በፊት ክሱ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ቀርቦ ሊታይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚገባው ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው የሥልጣን ጉዳይ በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው ነጥብ መሆኑን በጭብጥነት ይዞ የአሁን አመልካች በፌዴራል መንግሥቱ የተመዘገበ አካል ነው፣ይህን መሰል ወገን ተከራካሪ የሆነበትን ጉዳይ ተመልክተው የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል የሆነውን ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ተመልክተው ለመወሰን ከሕግ የመነጨ ሥልጣን የላቸውም በማለት በየደረጃው የተሰጠውን ውሣኔ ሽሮ ግራ ቀኙን አሰናብቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ ከላይ የተጠቀሰው ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 50(1) ስለማኅበራዊ ፍ/ቤቶች የተሰጣቸውን ሥልጣን ያገናዘበ አይደለም፣በሁለቱም አዋጆች ላይ ሥልጣንን በሚመለከት ግጭት አለ እንኳ ቢባል አግባብነት ያለውን አተረጓጎም ልንከተል ይገባል፣ ከዚህ ቅደም ተከተል አንፃር ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 361/1995 እንጂ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አይደለም፣ ስለሆነም የሕግ ስህተቱ ይታረምልን በማለት አመልካች በማመልከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወል የፍትሐብሔር ሥልጣንን በሚደነግገው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 (1) እና (6) መሠረት በጉዳዩ የተካተተው የገንዘብ መጠን ምንም ይሁን ምን የፌዴራል መንግሥቱ አካል ወይም በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ድርጅት ወይም ማህበር ተከራካሪ የሆነበትን ማናቸውም ጉዳይ ተቀብለው ለማስተናገድ ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ ይህ አዋጅ በፌዴራሉ መንግስት የወጣ ሲሆን በሌላ በኩል ተመሳሳይ በሆነ አካል (በፌዴራሉ የሕግ አውጪ) የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችን ለማደራጀት በወጣው አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50 ላይ ደግሞ ተከራካሪ ወገን ማንም ይሁን ማን እስከ ብር 5000.00 ሊደርስ የሚችለውን የገንዘብ ክርክር ጉዳይ በአዲስ አበባ ሥር እስከተነሣ ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ለመወሰን ሥልጣን የተሰጣቸው ስለመሆኑ የተጠቃሹ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(1) እና (6) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50 ይዘትና መንፈስ ጋር ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ይህን ለማድረግም ተገቢውን የሕግ አተረጓጎም ዘዴ መከተል የግድ ይላል፡፡ ከእነዚህም የአተረጓጎም ዘዴዎች ልንከተለው የሚገባው አንዱ፣አንድን ክርክር ያስነሳውን ጉዳይ ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው የትኞቹ ፍ/ቤቶች ናቸው? የሚለውን አስመልክቶ በእኩል ደረጃ የሚገኙ ሕጎች /አዋጆች/ በተለያየ ሁኔታ ደንግገው ከተገኙ ከጊዜ ቅደም ተከተል አንፃር በኋላ የወጣው ሕግ ከፍተኛና በልጦ ተፈፃሚነት ይኖረዋል የሚለው የትርጉም መርህ ነው፡፡ በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 361/1995 ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 ጋር እኩል ደረጃ ላይ የሚገኝ ሕግ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 361/1995 በኋላ የወጣ በመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 ቅድሚያ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/1እና 6/ ድንጋጌ መሠረት ይህ መሰል ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥር እንደሚወድቅ እየታወቀ ሕግ አውጪው ዘግይቶ ሥልጣንን በገንዘብ መጠን ወሰን አበጅቶ በሌላ አነስተኛ የፍርድ መድረክ ሥር ቀርቦ እንዲታይ ማድረጉ በክርክር ምክንያት የሚሰጠው ወጪና የሚባክነው ጊዜ ክርክሮች ከያዙት የገንዘብ መጠን ጋር የተመጣጠነ ሊሆን እንደሚገባው ታሳቢ በማድረግ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ሥልጣን ቀንሶ ለመስጠት ሲባል የወጣ ሕግ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተለይም ይህንኑ የትርጉም መስመር ይበልጥ የሚያጠናክረው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ተፈፃሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚሆንበት ከድሬዳዋ ከተማ ጋር በተያያዘ የድሬዳዋ ከተማ ቻርተር ለማቋቋም በወጣው በአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 41 ሥር ስለ ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሲደነግግ ከተላላፊ የገንዘብ ሰነዶች እና ከኢንሹራንስ ጉዳይ በቀር ሌሎች ግምታቸው እስከ ብር 2500.00 ድረስ ያሉትን ገንዘብ ነክ ክርክሮች ለማየት ሥልጣን ያላቸው የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት ከዚህ ቀድሞ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 ሥር የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን ለመለየት መነሻ ከሆኑት 10 ንዑስ ጉዳዮች መካከል ተላላፊ የገንዘብ ሰነድና የኢንሹራንስ ጉዳዮች ሊያስነሱ ከሚችሉት የተወሳሰበ የሕግ ጥያቄ አንፃር ሁሉቱን ብቻ በመለየት የፌዴራል ሆነው እንዲቀሩ፣ ከሌሎች ጉዳዮች የሚነሳው ክርክር ግን ግምቱ እስከ 2500.00 እስካልበጠ ድረስ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ወጥተው በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች እንዲታዩ መደረግ በገንዘቡ መጠን ትይዩ የሚታይበትን ፍርድ ቤት እና የክርክር ደረጃ ለመለየት ሆን ተብሎ የወጣ ሕግ መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው። ይህም የሕግ አውጪው ሐሳብ ምን ነበር? የሚለውን የአተረጓጎም መርህ በመከተል ልንደርስበት የምንችለው ድምዳሜ ነው። ስለሆነም በተመሳሳይ አካል የወጡት ሕጎች ስለፍርድ ቤቶቹ ስልጣን ያስቀመጧቸውን ድንጋጌዎች ከሕጎች አወጣጥ ቅደም ተከተልና ሕጎችን እርስ በራሳቸው አጣጥሞ ከሕግ አውጪው ሐሳብ ጋር በማዛመድ ከመተርጎም የሕግ አተረጓጎም ደንቦች አንፃር ስንመለከተው የአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50 ይዘት ከዚሁ ተለይቶ የሚታይ ሆኖ አላገኘነውም። ስለሆነም ከሥልጣን አደላደል አንፃር የሕግ ጥበቃ የተደረገለት የአሁን አመልካች የፌዴራል መንግስት አካል ወይም በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ መሆኑ ብቻ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የማያደርገው ሲሆን ተለይቶ መታወቅ ያለበት ክስ የቀረበበት ጉዳይ በባሕርይው ሲታይ ውስብስብ የሕግ ጥያቄ የሚያስነሳ መሆን ያለመሆኑ ነው። በመሰረቱ ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስልጣን የተሰጠው ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ተቆርሶ መሆኑ ግልፅ ነው። ስለሆነም ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ የገንዘብ መጠንን መያዙ ብቻ ስልጣኑን ለቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች እንዲሆን የማያደርገው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ከአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀፅ 41 ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር በማስተሳሰር ልንገነዘበው የምንችለው ነው። ስለሆነም ጉዳዩ የሚያስነሳው የሕግ ጥያቄና የጉዳዩ ልዩ ባህርይ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ለክሱ መሰረት ያደረገው የገንዘብ መጠን በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50 መሰረት የሚወድቀው በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ሥልጣን ስር ነው። ይሁን እንጂ አመልካች ክስ ያቀረበው ንብረቱ የሆነው ተሽከርካሪ በተጠሪ መኪና በመገጨት ጉዳት ስለደረሰበት የጉዳቱን ግምት ተጠሪ እንዲተኩለት ነው። ተጠሪ ደግሞ ግጭቱን ያደረሰው መኪና የራሳቸው ንብረት የነበረ ሁኖ ግጭቱን አደረሰ በተባለት ጊዜ ደግሞ በሽያጭ ወደሌላ ሰው የተላለፈና ገዥው ሲጠቀሙበት በነበረበት ጊዜ በአመልካች መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክረዋል። ስለዚህ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነቱ የማን ነው?፣የሻጩ ወይስ የገዥው?፣አንድ ሰው ከአዋጅ ቁጥር 256/60 እና ከደንብ ቁጥር 360/1969 እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች አንፃር ሲታይ የመኪና ባለንብረት ነው የሚባለው መቼ ነው?፣የመኪና ባለንብረት መኪናው ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆንበት የሕግ አግባብ ምንድነው? የሚሉትና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከላሳ መጠኑ ጋር ተዛምደው የሚነሱት ክርክሮች በባሕርያቸው ሲታዩ ውስብስብ የሕግ ጥያቄ የሚያስነሱ መሆኑ ግልጽ ነው። ስለሆነም በእጃችን ያለው ጉዳይ ከራሱ ልዩ ባህርይ አንፃር ሲታይ ውስብስብ የሕግ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ በመሆኑ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ሥር የሚወድቅ ሁኖ አልተገኘም። በአዲስ አበባ ከተማ ስር የሚገኙ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የገንዘብ መጠኑ ከብር 5000.00 (አምስት ሺህ ብር)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በታች የሆነውን ማንኛውንም የፍትሐብሔር ክርክር ለመመልከት ስልጣን አላቸው ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 50(1) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተግባራዊ መሆን ያለበት ተከራካሪው ወገን የፌዴራል መንግስት አካል ወይም በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ድርጅት ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ሳይሆን የተከራካሪ ወገኖች በፌዴራል መንግስት አካልነት ወይም የተመዘገቡ መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ የጉዳዩ ልዩ ባሕርይ እየታየ በጉዳዩ ላይ የሚነሳው የሕግ ጥያቄ ውስብስብነት በመመዘኛነት(መለኪያነት) ተይዞ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ላይ ያሉት ተከራካሪ ወገኖች ማንነት እና በክርክሩ የሚነሳው የሕግ ጥያቄን መሠረት በማድረግ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 እና ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 50(1) አንፃር ተመልክቶ ባለው አግባብ ሊስተናገድ የሚገባው ሆኖ ሳለ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የአመልካችን የፌዴራል መንግስት አካል መሆኑን ብቻ በመመልከት ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር አይውድቅም ያለው የምክንያት ክፍል ተገቢነት የሌለው ቢሆንም የተያዘው ጉዳይ በተለይ ሲታይ ግን ባሕርይው ውስብስብ የሕግ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የማህበራዊ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ተገንዝቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 9 እና 231/1/ለ/ መሠረት መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የቀረበው ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ሥር የሚወድቅ እንጂ በአዲስ አበባ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በሚል የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ትርጓሜ ሕጎቹ ከወጡበት ዘመን አንፃርም ሆነ የሕግ አውጪውን ሃሣብ ከመፈለግ አንፃር ሊሰጥ የሚገባውን የሕግ አተረጓጎም ዘይቤ ያልተከተለ ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት የምክንያት ክፍል ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ተገቢ ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 12394 በ21/05/2002 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 342 ምክንያቱን ለውጠን ውጤቱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት አፅንተነዋል፡፡
2. ክርክር ያስነሳው ጉዳይ ከአመልካች ማንነትና ከገንዘቡ መጠን አንፃር ሲታይ በመጀመሪያ ደረጃ ከአዲስ አበባ የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን የሚጀምር ቢሆንም የጉዳዩ ልዩ ባሕርይ ሲታይ ግን በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም ብለናል፡፡ የተያዘውን ጉዳይ አይነት የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 55273

ህዳር 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አመልካች፡- አቶ ዘውዱ ግዛው

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አየለች ደስታ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በወንዶገነት ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በልጁ ስም የገዛው ቤት በገዢ ስም እንዲዛወርለት ክስ አቅርቦ የወረዳው ፍ/ቤት ቤቱ በገዢ ስም እንዲዛወር ሀምሌ 6 ቀን 2001 ዓ.ም. ውሣኔ ሲሰጥ ውሉ ህጋዊ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ የተጠሪ ልጅ ወ/ሮ አይናለም እርቅነው ፍርዱን በመቃወም አቤቱታ አቅርባለች፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት በፊት የሰጠውን ውሣኔ በማጽደቅ ሀምሌ 6 ቀን 2002 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በውሣኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሲዳማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች በወረዳውና በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪን በችሎት አስቀርቦ በማየትና ተጠሪ በዕድሜያቸው በጣም የገፉ ማየትም ሆነ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ አሮጊት መሆናቸውን በማረጋገጥ እንደዚሁም በውሉ ላይ ያለው የጣት አሻራ ፊርማ የተጠሪ መሆኑን ለማጣራት በውሉ ላይ የተገለጸው ምስክሮች በማጣሪያ ምስክርነት አስቀርቦ በመስማት የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ቀርበው ሣይከራከሩ ቀርበው እንደተከራከሩ በማስመሰል የቤት ሽያጭ ውሉ ተፈጻሚነት አለው በማለት የሰጠው ውሣኔ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1728 ንኡስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የካቲት 24 ቀን 2002 ዓ.ም ባቀረበው አቤቱታ ውሉ በመጀመሪያ ለወረዳው ፍ/ቤት ባቀረብኩት ክስ ክርክር ተደርጐበት ቤቱን የገዛሁት አካለ መጠን ባልደረሰ ልጅ ስም ስለነበር በእኔ በአባቷ ስም እንዲዛወር ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡ የተጠሪ ልጅ ውክልና ሣይኖራት የክስ መቃወሚያ በህግ ከተፈቀደው ሥርዓት ውጭ አቅርባ ተሰርዞባታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በተከራካሪዋ ያልተነሳ ነገር ራሱ በዝርዝር በማስፈር የቤት ሽያጭ ውል ስለመኖሩ የተካደበት ነጥብ በሌለበት ሁኔታ ከህግ ውጭ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ጥር 6 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የወረዳው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ጉዳዩን አይቶ ሲወስን በፍ/ቤት ቀርቤ በቃል ክርክር እንዳመንኩ ተቆጥሮ በመዝገቡ በሌለሁበት ውሣኔ የሰጠ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሉ ሀሰተኛ መሆኑን በውሉ ላይ ስማቸው የተገለጸውን ምስክሮች በማጣሪያ ምስክርነት በመስማት አረጋግጦ የወሰነው ውሣኔ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያቀረቡት አቤቱታ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ የተገለጸውን ጭብጥ ለመወሰን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተጠሪን ማንበብና መጻፍ አለመቻል ተጠሪ ማየት የማይችሉ በእድሜ የገፉ መሆኑንና በውሉ ላይ ስማቸው የተገለጹ ምስክሮችን በመስማት ፍሬ ጉዳይ በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን የሰጠው ውሣኔን ተገቢነት ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንዳለውና ዝርዝሩ በህግ እንደሚወሰን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3/ለ/ ተደንግጓል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በክልል ጉዳዮች በተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ በሰበር አይቶ የማረም ስልጣን እንዳለው በክልሉ ህገ መንግስትና በክልሉ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ድንጋጌዎች መኖሩን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በዝርዝር ከገለጽናቸው የህግ ማዕቀፎች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ተጨማሪ ምስክር መስማትና ተጨማሪ ማስረጃ በመቀበል ማስረጃን በመመዘንና በመመርመር ውሣኔ መስጠቱ በክልሉ ጉዳይ በተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ከማረም ስልጣኑ ውጭ በመውጣት ውሣኔ የሰጠ መሆኑን የሚያሣዩ ናቸው፡፡ የሰበር ሥርዓት በመሠረታዊ ባህሪው ከይግባኝ ሥርዓት የተለየ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በዚህ መዝገብ ተጨማሪ ምስክሮችን በመስማትና ሌሎች ፍሬ ጉዳዮችን በማጣራት ማስረጃ በመመዘን የሰጠው ውሣኔ የአመልካቹን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብና የመስማት መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ አመልካች በፍሬ ጉዳይና በማስረጃ ምዘና ሂደት ተፈጽሟል የሚለውን ስህተት በይግባኝ የማሣየት መብቱን የሚያሳጣ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን ባየበትና ተጠሪን አስቀርቦ በአካል በአየበት ወቅት ሣይሆን ወሉን በተዋዋሉበት ጊዜ ማየት የተሣናቸው ነበሩ ወይስ አልነበሩም? ተጠሪዋ በወቅቱ ማህይም ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ነበሩ ወይስ አይደሉም? የሚሉት ነጥቦች ግራ ቀኙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በስር ፍ/ቤት ያልተከራከሩበትንና ማስረጃቸውን አቅርበው ያላሰሙበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ውሉ ላይ ተጠሪ ስለመፈረማቸው ወይም አለመፈረማቸውና ስለውል አፈራረም የግራ ቀኙ ማስረጃ አቅርበው ማሰማትና መከራከር ካለባቸው በስር ፍ/ቤት እንጂ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ሊሆን እንደማይገባ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ 3 /ለ/ ና ከሌሎች የክልሉ የህግ ማዕቀፎች እንደዚሁም ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ በአሁኑ ወቅት ማየት የተሳናትና ማህይም ናት በማለት በፍሬ ጉዳይ ደረጃ መደምደሚያ ላይ የደረሰው ተጠሪ ውሉ ከአመልካች ጋር ተዋዋለች በተባለበት ወቅት ስለነበረው ሁኔታ አመልካች የበኩሉን ማስረጃ እንዲያቀርብ እድል ያልሰጠና ከላይ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች የጣሰ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የወንዶገነት ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ውሉን ከአመልካች ጋር በተዋዋሉበት ጊዜ ማየት የተሣናቸው ነበሩ ወይስ አልነበሩም? ተጠሪ ውሉን በሚዋዋሉበት ጊዜ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ነበሩ ወይስ አልነበሩም? ተጠሪ ውሉን ከአመልካች ጋር ተዋውለዋል ወይስ አልተዋዋሉም? በሚሉት ነጥቦች ላይ የአመልካችንና የተጠሪን ምስክሮቻቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግና በውሉ ላይ በምስክርነት ተገኝተው ፈርመዋል የተባሉትን ምስክሮች ቃል በመስማት አመልካች ከተጠሪ ጋር አድርጌዋለሁ የሚለው ውል ፈራሽ ነው ወይስ አይደለም? ውሉ ፈራሽ ነው የሚባል ቢሆን ውጤቱ ምን ይሆናል በሚሉት ጭብጦች ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 64845

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሀብቱ ሀጋዚ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1- የኮምቦልቻ ግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ - አበበ ዘውዱ ቀረቡ

2- አቶ ዑመር የሱፍ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአንደኛ ተጠሪ ንብረት የሆነችውን ኮድ 4-00242 የሆነች መኪና በሁለተኛው ተጠሪ በመሸከርከር ላይ እያለ የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ገልፆ ያቀረበውን የካሣ ጥያቄ በመቀበል ፣ ለደረሰው ጉዳት ሙሉ በሙሉ ኃላፊዎች ተጠሪዎች ናቸው፡፡ ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 63,000 /ስልሣ ሶስት ሺህ ብር/ ካሣና ለህክምና የወጣውን ብር 11,277.90/አሥራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ይክፈሉ በማለት የሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05073 ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አንደኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪና አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ ለደረሰው ጉዳት አመልካች በከፊል ኃላፊነት አለበት በማለት አንደኛ ተጠሪ አመልካች ለህክምና ወጭ ያደረገውን ብር 11,277.90 /አሥራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ብቻ ይክፈል በማለት በመዝገብ ቁጥር 01663 ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረም ነው፡፡

አመልካች ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በከፊል በመሻር የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመዘርዘር አመልክተዋል፡፡ ጉዳዩ በሰበር የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ጭብጥ ተመርቶ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት መጥሪያ በመላኩ ተጠሪ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በፅሑፍ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

እኛም በመጀመሪያ በሰበር የተያዘውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት ጉዳዩ የይግባኝ ደረጃውን የጨረሰና በሰበር ለመታየት የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው በሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከራከሩት ተከራካሪ ወገኖች የሁለት ክልል ኗሪዎች ናቸው፡፡ አመልካች የሐረሪ ክልል ነዋሪ ሲሆን ተጠሪ የኦሮሚያ ክልል የተቋቋመ የግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመቀበል አከራክሮ የወሰነው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 4 በተሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የውክልና ሥልጣኑ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በማየት የወሰነው በህገመንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውክልና ሥልጣን ነው፡፡

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የፌደራል ጉዳይ ከሆነና የሐረሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውክልና ሥልጣኑ አይቶ የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና በተሰጠው ሥልጣን አይቶ ከለወጠው አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በመጀመሪያ ውሣኔው በይግባኝ እንዲታይለት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ሣያቀርብና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ ሣይሰጥበት ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በዳኝነት አይቶ ውሣኔ የሚሰጠው በይግባኝ ታይተው የመጨረሻ ውሣኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ እንደሆነ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም አመልካች የይግባኝ ደረጃውን ሣይጨርስ ጉዳዩ በሰበር ታይቶ እንዲወሰንለት ያቀረበው አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረብ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ እንዲያገኝ ሣያመለክት በሰበር ችሎት ያቀረበውን አቤቱታ ለማስተናገድ የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የዲላ ዩንቨርስቲ - ነገረፈጅ ተዘራ ገዳሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. አቶ የትናየት ጣፋ - የቀረበ የለም

2ኛ. አቶ ዳግም ጫላ - ቀረቡ

3ኛ. አቶ ነጌሳ ጥላሁን - የቀረበ የለም

መዝገቡ ያደረው ለውሳኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተጠሪዎች በዲላ ዩንቨርስቲ በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ክፍል ከTA II ወደ GA II የደረጃ እድገት እንዲሰጠን በተለያዩ የስራ ክፍሎች የተወሰነ ሆኖ ያልተፈጸመ ስለመሆኑ በማመላከት የደረጃ እድገቱ እንዲሰጣቸው እና ክፍያውም ከተወሰነላቸው ቀን ጀምሮ እንዲከፈለን በማለት የቀረበውን ክስ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የደቡብ ክልል የጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር በመስማት የደረጃ እድገቱም እንዲሰጣቸው እና ክፍያውም እንዲፈጸምላቸው ውሳኔ ሰጥቷል፣ ይሄው ውሳኔ በክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤትም በመጽናቱ አመልካች የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ የቀረበ ነው፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያላቸውን ነጥቦች ያነሳ ሲሆን ፍሬ ሃሳቡ፡- ተጠሪዎች በክሳቸው የተመለከተውን የደረጃ እድገት እንዲያገኙ በትምህርት ክፍላቸው አማካኝነት ለፋኩልቲው ቀርቦ እና ፋኩልቲውም ለተቋሙ ኘሬዚዳንት አስተላልፎታል፣ ሆኖም ይሄ የደረጃ ዕድገት ሊተገበር የሚችለው የፌ/ሲቪል ሰርቪስ ውክልና ያለው የፌ/ትምህርት ሚንስቴር የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ሲያጸድቀው በመሆኑ እና ይሄንን በማጽደቅ ያልመለሰ በመሆኑ የምፈጽመው የእድገት ጥያቄ የሌለ በመሆኑ በኋላ ላይ በትምህርት ሚንስቴር በተላለፈው ሰርኩላር መሰረት ዩንቨርስቲው የሚያያቸው የእድገት ጥያቄዎች ሊታዩ የሚችሉ ሁነው አሁን በፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ግን ከመመሪያ ውጭ እንድንሰራ የሚያደርግ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ቀደም ሲል በዩንቨርስቲው የተጻፈው ደብዳቤም ቢሆን ተጠሪዎች ወደ ደረጃ GA-I እንዲያድጉ እንጂ ወደ ደረጃ GA-II ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብነት የሌለው በመሆኑ እንድታረምልን የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል የስር ፍርድ ቤቶች ይሄንን ጉዳይ አይተው ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው መሆን አለመሆንን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.9 አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በመታዘዙ መልሳቸውን ሰጥተውበታል፡፡ የተሰጠውም የመልስ ፍሬ ሃሳብ፡- ለፍርድ ቤቱ ያቀረብነው ክስ በመካከላችን ያለውን ውል ይፈጸም እንጂ ያቀረብነው የደረጃ እድገት ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ይሄንን የፍታብሔር ክስ መመልከት ይችላል፡ አስፈላጊውን ሰነዶች ፍርድ ቤቱ ከስራ ክፍላችን በማስመጣት መመልከት የሚችል በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶችም የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ባቀረበው የመልስ መልስ አመልካች የመንግስት መስሪያ ቤት እንደመሆኑ መጠን የሚተዳደረው በፌ/የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 መሰረት በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ይሄንን ክስ የማስተናገድ ስልጣን የላቸውም በሚል ቅሬታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

በግራቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ይሄንን ጉዳይ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ክሱን ተመልክተው ውሳኔ ሊሰጡበት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ አልባት መስጠት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች የደረጃ እድገት እንዲያገኙ በዩንቨርሲቲው የተለያዩ የስራ ክፍሎች የውሳኔ ሃሳብ የተጻጻፉ ስለመሆኑ፣ ሁኖም ግን በስተመጨረሻ ለትምህርት ሚንስቴር የተጻፈ የውሳኔ ሃሳብ ስለመኖሩ እና የትምህርት ሚንስተር የቀረበለትን የደረጃ እድገት በማጽደቅ ያልመለሰ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፣ ሆኖም ግን የክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠየቀውን የደረጃ እድገት ጥያቄ የትምህርት ሚንስተር በማጽደቅ አልመለሰልኝም በማለት እጁን አጣጥፎ መቀመጥ የለበትም በማለት የደረጃ እድገቱም ሆነ ክፍያው እንዲፈጸምላቸው ውሳኔ የሰጠ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡

ከዚህ ሁሉ ክርክር እና በታች ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መገንዘብ የሚቻለው አከራካሪው ጉዳይ የደረጃ እድገት የሚሰጥበትን አግባብ የሚመለከት እንጂ ተጠሪዎች እንደሚሉት የውል ግንኙነትን መሰረት ያደረገ የፍትሐብሔር ክርክር አለመሆኑን ነው፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ይሄንን የደረጃ እድገት ጥያቄ ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ተቀብለው ማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ አልባት መስጠት ተገቢነት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ስንመለከት ተጠሪዎች የዲላ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ስለመሆኑ እና መስሪያ ቤቱም የመንግስት መስሪያ ቤት ስለመሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው የህግ ማዕቀፍ እንዳግባብነቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን መመልከት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ የህግ ማዕቀፎች አጠቃላይ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ የፌዴራል የመንግስት ተቋም ባጠቃላይ እና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን በተለይ የራሱ የሆነ የእድገት አሰጣጥ፣ የቅሬታ አፈታት እና አጠቃላይ አስተዳደራዊ ስራዎችን የሚያከናውኑበትን አግባብ ያስቀመጡ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይሄ ከሆነ ደግሞ የተጠሪዎች የደረጃ እድገት ክርክር በእነዚሁ አዋጆች በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ታይቶ እልባት ከሚያገኝ በስተቀር በቀጥታ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት እና ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በቀጥታ አይተው ውሳኔ የሚሰጡበት አግባብ አይኖርም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩ ሲቀርብላቸው ስልጣን እንደሌላቸው በመገንዘብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 9፣231/1/ለ/ ፣244/2/ሀ/ መሰረት መመለስ ሲገባቸው ክሱን በመቀበልና በማከራከር ውሳኔ መስጠታቸው አግባብነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ባቀረቡት የደረጃ እድገት ጥያቄ ላይ ስልጣን ሳይኖራቸው የሰጡት ውሳኔ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ክልል የጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 53540 በቀን 06-12-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 05259 በቀን 08-09-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የመደበኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን የደረጃ እድገት ጥያቄ በመመልከት ውሳኔ ለመስጠት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ብለናል፡፡ ይህ ማለት ግን ተጠሪዎች መብታቸውን በህጉ በተቀመጠው ስርዓት መሰረት መብታቸውን ከመጠየቅ ይሄ ውሳኔ አያግዳቸውም፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኖች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 68573

መጋቢት 12 ቀን 2004 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ. መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- 1. አቶ ጌታቸው ደያስ } ወ/ሮ ፈንቱ ተስፋዬ ቀርበዋል

2. ወ/ሮ ፋንቱ ተስፋዬ }

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሩቅያ ከድር

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 የተመለከተውን ድንጋጌ አፈፃፀምና ትርጉም የሚመለከት ሲሆን፤ ዝርዝር ጉዳዩም፣ የአሁን አመልካቾች በሻጭነት ተጠሪ በገዥነት ተሰይመው ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም አድርገውት በነበረው የቤት ሽያጭ ውል የተነሣ ግራ ቀኙ በመ/ቁ. 05508 በሆነው መዝገብ ላይ ውሉ ይፈርሣል ወይስ አይፈርስም? በሚለው ጉዳይ ላይ ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ክሱን ሲመለከት የነበረው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት በማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ የሽያጭ ውል ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ካልተደረገ በቀር የፀና ውል ሊሆን አይችልም፡፡ ፈራሽ ነው በማለት የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.21448 ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ትርጉም የሰጠበት ስለሆነና ይህም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ፈራሽ ነው በማለት በመ/ቁ. 05508 ላይ ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡

ይህ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ሻጭ የነበሩት የአሁን አመልካቾች ከዚህ በፊት በግራ ቀኞችን መካከል ተደርጎ የነበረው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ የተወሰነ ስለሆነ የሽያጭ ውል ከመደረጉ በፊት ወደነበርንበት ቦታ እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን ክስ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ክስ መሥርተዋል፡፡

ገዥ የነበሩትም የአሁን መልስ ሰጭ ውሉ ሥልጣን ባለው አካል ፊት እንዲመዘገብ አለመደረጉ የውሉን መፍረስ የማያስከትል ስለመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 36887 በታህሣሥ 10 ቀን 2001 ዓ.ም የተወሰነ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ አይገባም፤ የፀና ነው ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቱም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ በመ/ቁ. 06799 በ19/9/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከዚህ በፊት በመ/ቁ. 05508 በሆነው የግራ ቀኙ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ፈራሽ ነው በማለት ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በተመሣሣይ ጉዳይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 21448 በግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው የሕግ ትርጉም መሠረት ነው፡፡ ይህ ውሣኔ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤት በይግባኝም የተሻረ አይደለም አሁን ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበው ክርክር ደግሞ የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ የተወሰነውን መሠረት በማድረግ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ማድረግ ይቻል ዘንድ ታይቶ እንዲወሰን ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.36887 በ10/4/2001 ዓ.ም የተሰየ ውሣኔ ወይም ትርጉም መስጠቱ ለዚህ ለተያዘው ወደነበርንበት እንመለስ ጥያቄ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ሆኖም ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ክርክሩ በይግባኝ ቀርቦለት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ከዚህ በፊት የሥር ፍ/ቤት በመ/ቁ.05508 በ23/10/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በጊዜው ትክክል የነበረ ቢሆንም በተመሣሣይ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 36887 በታህሣሥ 18 ቀን 2001 ዓ.ም ውል መኖሩ እስካልተካደ ድረስ ውሉ የፀና ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ በዚህ አኳኋን በሰበር ሰሚ ችሎት ተስተካክሎ ከተወሰነ ወይም ከተተረጎመ ይህንኑ ከትርጉም በኋላ የተሰጠን ሁለተኛ ትርጉም መከተል የግድ ስለሆነ ከዚህ በፊት ፈርሷል የተባለው የቤት ሽያጭ ውል የፀና ነው በሚል ተስተካክሎ ሊወሰን ይገባል፡፡ ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ ይህም ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታረም ቀርቦ የሕግ ስህተት የተገኘበት ውሣኔ አይደለም የሚል ዳኝነት በማግኘቱ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

ሁለቱም ወገኖች በዚህ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያደረጉት የጽሑፍ ክርክር ከዚህ በፊት በሥር ፍ/ቤቶች ያቀረቡትን ክርክር የደገመ እና ያብራራ ከመሆኑ በቀር በይዘቱ የተለየ ባለመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የሠፈረው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80/3/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም ያለባቸው ውሣኔዎች የሰበር ሥርዓት መዘርጋት እንዳስፈለገበት ዓላማ በሀገሪቱ ሕጐች ወጥ የሆነ አተረጓጎምና የሕግ አፈፃፀም ይኖራቸው ዘንድ ተከታይ በሆነው አዋጅ ቁጥር 454/97 እንደተደነገገው ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች በየትኛውም ደረጃ በሚገኙ የሀገሪቱ ፍ/ቤቶችና የዳኝነት አካላት በተመሣሣይ ተፈፃሚነት እንዳላቸው ከዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ በሀገሪቱ በየደረጃው የሚገኙት ፍ/ቤቶችና ሌሎች አካላት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰጠው ትርጓሜ መሠረት ተመሣሣይ ጉዳዬችን በማየት መወሰን የሚችሉት ተመሣሣይ የሆነው ጉዳይ ክርክር ተደርጎበት ለውሣኔ በደረሰበት ጊዜ ሰበር ሰሚው ችሎት ትርጉም የሰጠበት ሆኖ ከተገኘ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በእጅ የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት በመ/ቁ. 05508 በሆነው መዝገብ ላይ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው ጉዳይ ክርክር ተደርጎበት ለውሣኔ በደረሰበት ጊዜ በተመሣሣይ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ መሆኑን የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተገንዝቦ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 መሠረት ይህንኑ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን የሕግ ትርጉም በመከተል ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 እንደተመለከተው የሰበር ሰሚ ችሎቱ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ቢሆንም በሌላ ጊዜ የተለየ ትርጉም ለመስጠት ሥልጣን ያለው በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ተመሣሣይ በሆነው ጉዳይ በሌላ ጊዜ የተለየ ትርጉም መስጠቱ ቢታወቅ እንኳ የዚሁ በሌላ ጊዜ የሰጠው ትርጉም ተፈፃሚነት ወሰን የሕጉ ትርጉም ከተሰጠ በኋላ በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ ሳይወሰን ለሚነሱ ክርክሮችና ክርክሮች ተደርገው ለውሣኔ በደረሱ ጉዳዮች ላይ የሚገደብ እንጂ በየደረጃው ያሉት ፍ/ቤቶችም ሆኑ ሌሎች የዳኝነት አካላት በጎንዮሽም ሆነ በላይኛው የክርክር እርከን ክርክር ተደርጎ በውሣኔ የተቋጨን ጉዳይ ሁሉ እየቀሰቀሱ እንደገና ለማየት በሚያስችል አኳኋን የተቀመጠ ሥልጣን ሰጭ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አልተደነገገም የሕጉ ዓላማም ውሣኔ የሚያሻቸው ጉዳዮች ዓይነት ከዚህ በፊት በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርበው ትርጉም ተሰጥቶባቸው ከሆነ በሀገሪቱ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጐምና አፈፃፀም ማስፈን እንዲቻል በተመሣሣይ ታይተው እንዲወሰኑ ለማድረግ እንጂ ሥርዓቱን አሟጦ በውሣኔ የተቋጨን ጉዳይ ሁሉ እንደገና እየቀሰቀሱ የተረጋጋውን ሁኔታ ለማናጋት ወይም ተከራካሪ ወገኖችን ተገማች ላልሆነ የዳኝነት ሥርዓት ለመጋበዝ ተፈልጐ አይደለም፡፡ ስለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ዳኝነት ከላይ በዝርዝር እንደሰፈረው በአዋጅ ቁጥር 454/97 የተፈፃሚነት አግባብ ላይ የሰጡት ትርጓሜ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው በሕገ - መንግሥቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት በማረም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 106340 ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ፤ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 124793 በ14/7/2003 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06799 በ19/9/2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

3/ በመ/ቁ. 05508 በሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ታየቶ የመጨረሻ ዳኝነት ያገኘ ጉዳይ ስለሆነ እንደገና ውሣኔውን ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 አንፃር አይቶ ለማረም የሚያስችል ሥርዓት የለም ብለናል፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ሁለቱም ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅጽ 12

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ውል				1
1.	አግባብነት ካለው የመንግስት አካል ፈቃድ ሳይኖር የከርሰ ምድር ቁፋሮ ሥራን ለመስራት የሚደረግ ውል ህጋዊና አስገዳጅ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ	54249	ጌታሁን አበበ ቦጋለ እና ሐሰን ገአስ ሁመድ	ጥቅምት 16/2003	2
2.	በህግ አግባብ ተመዝግቦ የሚገኝ የመያዣ ውል ተጠቃሚ የሆነ ወገን በህግ የተቀመጠው ጊዜ ከማለፉ በፊት ውሉ እንዲታደስለት ከጠየቀ የንብረቱ አስያዥ ፈቃድ መኖሩ ሳይረጋገጥ ውሉ ሊታደስና ሊመዘገብ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058/1/ እና /2,/ 1632/2/	40109	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ ተክሌ ዋከኔ	ጥቅምት 01/2003	4
3.	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ በፍርድ ሃይል የኪራይ ውል እንዲዋዋል የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ	42150	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና እነ አቶ ዳንኤል ካሣ /ሀያ ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 29/2003	7
4.	ውልን በተመለከተ በህግ የተቀመጠውን ፎርም አልጠበቀም በሚል አቤቱታ ለማቅረብ ስለሚችለው ሰው /ወገን/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808/2/	47617	ቁስ ገ/ሚካኤል አለምነው እና ወ/ሮ መልኬ ደምሴ	ህዳር 30/2003	14
5.	የዋስትና ግዴታን ቀሪ ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1925/2/	49041	የአ/አ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት እና አቶ ኤሣው መዓዛ /ሦስት ሰዎች/	ህዳር 02/2003	17
6.	ከመኪና ሽያጭ ጋር በተገናኘ ሽያጩ ከመከናወኑ በፊት በነበረ የፍ/ቤት እገዳ መነሻነት ገዢው በባለቤትነት መብቱ መገልገል ሳይችል ቢቀር በሻጩ ላይ የሚኖር ኃላፊነትና የጉዳት ካሣውን በመወሰን በኩል የገዢው ተነሣሪ ግዴታ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2341/2/ 2281, 2336, 2329, 2360, 1802, 1790	52106	እነ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ታደሰ አደራ	ህዳር 13/2003	20
7.	እቃን ለመግዛት በጨረታ ማስታወቂያ ያወጣ ድርጅት ተወዳዳሪዎች በጨረታ ላይ ከተነገረው የተለየን ዕቃ በማቅረብ ከተወዳደሩ በኋላ ድርጅቱ ተወዳዳሪ የሆነው አካል በጨረታ ሰነዱ ላይ ሞልቶ ያቀረበውን እቃ መሰረት በማድረግ ውል የተዋዋለ እንደሆነ ይህንኑ ውል ለመፈፀም የሚገደድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1695/2/	53968	እነ የምስራቅ ወለጋ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ፀጋዬ ነጋ	ህዳር 13/2003	24
8.	በማህበር አባላት ስምምነት የሚወጣ ደንብን አስመልክቶ በማህበሩ አባላት መካከል ብሎም በማህበሩ እና በአባላት መካከል የሚነሱ	54312	አቶ ሃይላይ ተክላይ እና	ህዳር 28/2003	27

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አለመግባባቶችን እልባት ለመስጠት በፍትሐብሔር ህጉ ውስጥ ስለ ውሎች በጠቅላላው የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1676/1/		ውቁር የጨው አምራቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር		
9.	ውል ጋር በተያያዘ ተዋዋይ የሆነ ወገን ውሉን የፈፀምኩት ተገድጄና ከፍላጐቴ ውጭ ነው በሚል የሚያደርገውን ክርክር ዳኞች (ፍ/ቤቶች) የዚህን ተዋዋይ ወገን እድሜ፣ ጾታ፣ የተዋዋይ ወገኖችን ልዩ ግንኙነት እና አጠቃላይ ተያያዥነት ያላቸው አካኋኖች ጭምር መሰረት በማድረግ መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1706/1/,1678/ሀ/,1809	55311	ወ/ሮ ብርሃኔ አጥናፉ እና ኢንስፔክተር ዮሃንስ ተሲላ	ህዳር 11/2003	31
10.	ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው ሊፈጠር የሚችለውን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት ለመፍታት ከተስማሙ በኋላ አንደኛው ወገን ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ሌላኛው ተዋዋይ ስምምነቱ እንዲፈፀም ለፍ/ቤት የሚያቀርበው አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/, 231	56368	ዶ/ር ሰለሞን ነጋሽ እና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ	ህዳር 01/2003	37
11.	የመያዣ ውል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተደርጐ ለማስረጃነት ዋናውን ሰነድ ማቅረብ ባልተቻለ ጊዜ የዋናው ሰነድ ግልባጭ ስለመሆኑ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተረጋግጦ የቀረበ የዋናው ሰነድ ኮፒ እንደ በቂ ማስረጃ ሊወሰድ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2011, 2008, 2009	56682	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አንዋር አብዱራህማን /ስምንት ሰዎች/	ህዳር 14/2003	39
12.	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/ረ/ እና 2023 ለውሃ ፍጆታ ክፍያ ተፈፃሚነት የሌላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2023, 2024/ረ/	48857	የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 አስተዳደር ጽ/ቤት	ታህሳስ 12/2003	42
13.	• የተሸጠለትን ነገር የተረከበ ገዢ የሸያጩን ዋጋ ወዲያውኑ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • ገዥ ለሻጭ /በሽያጭ/ ለማስረከብ በውል ከተስማማው መካከል የተወሰነውን ክፍል ያስረከበ መሆኑና ሻጭም በተረከበው መጠን ክፍያ ያልፈፀመ መሆኑ ለውሉ መፍረስ በቂ ምክንያት ሊሆን ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2278	49635	ሂጦስ የገበሬዎች የህብርት ስራ ማህበር እና የምስራቅ ዱቄት ፋብሪካ	ጥር 23/2003	46
14.	አንድን ዕቃ በውል የተረከበ ሰው የተረከበው ዕቃ ጉድለት አለው በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በአንድ ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2291, 2292, 2298/1/	55229	ወ/ሮ መሃዳ ይመር እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የአርሲ ቅርንጫፍ	ጥር 09/2003	50

https://t.me/ethiopianlegalbrief

15.	• የግንባታ ሥራን ለመንግስት ለመስራት ጨረታውን ያሸነፈ ሥራ ተቋራጭ ሥራውን ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሥራ ተቋራጭ /ሰው/ በህጋዊ መንገድ ሊሰቀቅ ወይም ሊያስተላልፍ የሚችልበት አግባብ • ከአሰሪ ጋር ያልተደረገና ከሥራ ተቋራጭ ጋር የተደረገ የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውልና የሚኖረው ውጤት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3202/1/ እና /2/ 3205, 3206, 3244/1/, 2107	56252	ተስፋዬ አበበ ሥራ ተቋራጭ እና ማዕረጉ ወርቁ ሥራ ተቋራጭ	ጥር 24/2003	53
16.	• ውሎችን ህገ ወጥ ናቸው ወይም በህግ የተቀመጠውን መስፈርት አላሟሉም (Unlawful contracts or illegal contracts) በሚል ለመለየት የሚቻልበት አግባብ እና የሚያስከትሉት ውጤት • በመያዣ ተይዟል በሚል ባለገንዘብ በሆነ ባንክ በሐራጅ ንብረቱ የተሸጠበት ሰው ባንኩ ንብረቱን ለመሸጥ መብት የለውም በሚል /ውሉ እንዲፈርስ/ የሚያቀርበው የመቃወም አቤቱታ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 446,447 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 6 አዋጅ ቁ. 216/92	43226	ጌታ ትራዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	የካቲት 7/2003	58
17.	የከተማ ቦታ ውልን መሰረት በማድረግ በሊዝ የሚሰጥበትና ውሉ ሊቋረጥ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 272/94 አንቀጽ 15/1/ /ለ/, 16	54596	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ እና ወ/ሮ ላቀች መንግስቱ	የካቲት 09/2003	65
18.	ውልን መሰረት በማድረግ ቀብድ የተቀበለ ወገን የቀብዱን አጠፊታ በመክፈል ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1885/2/	56794	አቶ ሳህሉ መሉጌታ እና እነ አቶ ሰለሞን ኤፍሬም /ሦስት ሰዎች/	የካቲት 07/2003	71
19.	• ተዋዋይ ወገኖች ውል ባለመፈፀሙ አንዳቸው ለሌላቸው መቀጮ /ገደብ/ እንዲከፈል በማለት የሚደርሱበት ስምምነት ተፈፃሚ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ • በውል በተወሰነ የገንዘብ ቅጣት ላይ የሚታሰብ የወለድ ክፍያ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1891, 1892/1/, 1889	58258	ወ/ሮ ዮርዳኖስ ሃጐስ እና ወ/ሮ ሀይማኖት ተፈራ	የካቲት 21/2003	75
20.	የእውቀት ሥራ /ግልጋሎት/ ውልን አሰሪ የሆነ ወገን በተናጠል ለማቋረጥ የሚችለው ባለሙያው ሥራውን ሙሉ በሙሉ አጠናቅቆ ለአሰሪው ከማስረከቡ በፊት ስለመሆኑና ባለሙያው ሥራውን አስመልክቶ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው የሙያውን ደንቦች በመጣስ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2637/2/, 2636/2/ና/1/	60469	ኮከብ ዱቄትና ፓስታ ፋብሪካ እና ሙሉ አለም የስራ አመራር አማካሪዎች	የካቲት 21/2003	79
21.	ከመንግስት አስተዳደር መ/ቤት ጋር የሥራ ውል	60951	የኢትዮጵያ	ግንቦት 19/2003	83

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ያደረገ ወገን እንደውሉ ለመፈፀም ባልቻለ ጊዜ የአስተዳደር መ/ቤቱ ተዋዋዩ ለውል ማስከበሪያ (contract security) በሚል ካስያዘው ገንዘብ ላይ ውሉ ባለመፈፀሙ የደረሰበትን የጉዳት ኪሣራ መቀነስ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 430/97 አንቀጽ 43 የመንግስት የግዢ መመሪያ ቁ. 117/5/ /ሀ-ሐ/		መንገዶች ባለስልጣን እና ካንትሪ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር		
22.	• በሃዋላ የተላከን ገንዘብ ባንክ ለዕዳ ማስመለሻ በሚል ያለፍርድ መያዝ የማይችል ስለመሆኑ • በፍትሐብሔር ግንኙነት እዳን ለማቻቻል ስለሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1838/1/, 1840, 1841	64203	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ መሐመድ ሙሳ /አራት ሰዎች/	ግንቦት 15/2003	87
23.	አንድን ስልጠና በአሰሪው ትብብር በውጪ አገር ተከታትሎ በምትኩ አገልግሎት ለመስጠት የተስማማ ሠራተኛ አስቀድሞ በውል የገባውን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ ሌላ /ተጨማሪ/ ስልጠና መጀመሩ በውሉ መሰረት ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን የሚያሳይና በኃላፊነት የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731	46574	ሐዋሳ ዩኒቨርስቲ እና እነ ዮናስ ካሣ /ሁለት ሰዎች/	መጋቢት 09/2003	90
24.	• ከመኪና ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ ከመኪናው ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶችን ለገዢ አሟልቶ ያስረከበ መሆኑ ከተረጋገጠ ገዢ ስመ ሃብቱ በስሜ አልተዛወረም በሚል ምክንያት ብቻ ውሉ እንዲፈርስ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ • ከመኪና ጋር በተገናኘ ስመ ሃብቱን ለማዞር አስፈላጊ ሁኔታዎችን አሟልቶ ስም እንዲዛወርለት ጥያቄ አቅርቦ መብቱ ሊረጋገጥለት ያልቻለ ሰው በሚመለከተው አካል ላይ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ መብቱን ለማስከበር የሚችል ስለመሆኑ	56569	አቶ ዳዊት አሰፋ እና አቶ ተሻለ ደስታ	መጋቢት 23/2003	9.3
25.	• በጽሁፍ እንዲደረጉ በህግ የተደነገጉ የውል አይነቶች ህጋዊና የተሟሉ ናቸው ለማለት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች /መስፈርቶች/ • የቤት ሽያጭ ውል ምስክር ሳይኖርበት በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በመደረጉ ብቻ ህጋዊና የሚፀና ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723/1/, 1727/2/, 2877	57356	ወ/ሮ መሠረት በቀለ እና ወ/ሮ ኤልሳ ሶሞኔላ	መጋቢት 22/2003	98
26.	ከግንባታ ሥራ ውል ጋር በተያያዘ የግንባታ ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ለባለቤት ወይም ለወኪሉ ስለመሆኑ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ክትትልና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 17, መመሪያ ቁ. 1/97	55359	አቶ ተድላ ማሞ ጌታቸው እና እነ አቶ ፍስሐ ሱመር /ሁለት ሰዎች/	ሚያዝያ 21/2003	101
27.	• ተዋዋይ ወገኖች ውል ለማድረግ ነፃ ቢሆኑም ህግ የወሰናቸውና የከለከላቸውን ነገሮች ባለመገንዘብ /ባለማክበር/ የሚደረጉ ውሎች የማይፀኑ እና የማይፈፀሙ ስለመሆናቸው • በመንግስትና በህዝብ መሬት ላይ ግለሰቦች አንዱ ሰፈር ሌላው ደግሞ ተቀባይ በመሆን የባለቤትነት መብት ሊመሰርቱ የማይችሉ ስለመሆኑ	58157	አቶ ዮሐንስ ታደሰ እና ወ/ሮ አማረች መንገሻ	ሚያዝያ 06/2003	107

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716				
28.	ህጋዊ ባልሆነ የቤት ሽያጭ ውል አማካኝነት የተሰጠን ገንዘብ ለማስረዳት ህጉ የደነገገው ልዩ የማስረጃ አይነት የሌለና በማናቸውም ማስረጃ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472, 2001, 2019, 1808/2/, 1815, 2162, 2164	58636	እነ አቶ ተሾመ ካሣ እና አቶ ቤዛ ኩሉ አዳም	ሚያዝያ 19/2003	111
29.	• የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች በመያዣ (pledge) ለሌላ ሰው ተሰጥተዋል ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ እና ውጤቱ • መኪና በመያዣነት ተሰጥቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2825, 2832, 2830, 1186/2/, 2828, 1727, 2930, 2027, 2028, 2054	43582	ራፒድ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ ድርጅት እና ኦርቢስ ንግድና ቴክኒክ ክፍል ሊሚትድ	ሰኔ 28/2003	114
30.	ጥሬ ገንዘብን በአደራ ከመስጠት ጋር በተያያዘ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ገንዘቡ በአደራ መልክ መሰጠቱን ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚችል ማስረጃ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2742 2782 2779	60204	አቶ ታደሰ ደምሬ እና አቶ ጌታሁን ለቻሞ	ሰኔ 14/2003	120
31.	አንድን ሥራ ለሥራ ተቋራጭ የሰጠ የመንግስት መ/ቤት በራሱ ጥፋት ጉዳት አድርሶ ከሆነ ወይም የሥራ ተቋራጩን ሥራ መደበኛ አፈፃፀም ከባድ ያደረገበት እንደሆነ ለሥራ ተቋራጩ ኪሣራ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3259	61110	አል ናይል ቢዝነስ ግሩፕ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን	ሰኔ 28/2003	124
32.	የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ ወደ ነበርንበት እንድንመላለስና የከፈልኩት ገንዘብ ይመለስልኝ በሚል ክስ መስርቶ ፍ/ቤት ጥያቄውን በህግ ፊት የሚፀና ውል የለም በማለት ውድቅ ያደረገበት ወገን ያለአግባብ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስልኝ በማለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለውና ህጋዊ ስለመሆኑና በመጀመሪያው ክስ ተጠቃሎ መቅረብ የነበረበት ነው ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1815, 1880/2/, 2001-2019, 2162, 2164 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 216/2/3/	62134	እነ ጣና ወ/ሰማያት እና ወ/ሮ አልማዝ አሰጋኸኝ	ሰኔ 28/2003	132
33.	• የጠፋ ዕቃን ላገኘ ወይም ሌላ ነገር ለፈፀመ ሰው ሽልማት ይሰጠዋል ተብሎ በተለጠፈ /በተነገረ/ ማስታወቂያ ወይም በአደባባይ ሊታወቅ በሚችል ሌላ አይነት ማስታወቂያ መሰረት ዕቃውን አግኝቶ የመጣ ወይም የተባለውን ሥራ የፈፀመ እንደሆነ የተስፋ ቃሉን የሰጠው ሰው የተገለፀውን ሽልማት /የገባውን ቃል/ የመፈፀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ • በውል የተገባ ግዴታ ፍፁም የማይቻልና የማይሞከር ነው ለማለት ተዋዋይ ወገን ብቻ ሳይሆን ማንም ሰው ሊፈጽመው የማይችለው ግዴታ መሆን ያለበት ስለመሆኑ • በአንድ ከተማ የሚገኝና መጠኑ ተለይቶ የታወቀ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በሽልማት መልክ	62146	ወ/ሪት ፍሬወይኒ ቴዎድሮስ እና ተርካንሬ ፕሮሞሽንና የማስታወቂያ ስራ ድርጅት	ሐምሌ 12/2003	135

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ለመስጠት በውል የተገባ ግዴታ ሊፈፀም የማይችል ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1715, 1741-1762, 1714, 1711, 1736, 1734, 1689				
34.	የደንበኛን ጉዳይ /ክርክር/ በፍ/ቤት ክስ መስርቶ መ.ያዊ አገልግሎት ለመስጠት የጥብቅና የውክልና ስልጣን የተሰጠው ጠበቃ በውል የገባውን ግዴታ በተገቢው ጊዜና ትጋት ለመወጣት አለመቻል በኃላፊነት የሚያስጠይቅና ለቅጣት የሚዳርግ ስለመሆኑ ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 8/2//ለ/ 3 አዋጅ ቁ. 199/92 አንቀጽ 24/3/ /ለ-3/	66210	አቶ ተስፋዬ ገ.ላ እና የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚ/ር	ሐምሌ 29/2003	140
35.	• ከቤት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ የስም መዛወር የሚፈፀመው በመንግስት አስተዳደር ፊት እንጂ ሻጭ ነው የተባለው ወገን ሊፈጽመው የማይችልና ከህግ ወይም ከውል ይመነጫል ሊባል የማይችል ግዴታ ስለመሆኑ • የስም ይዛወርልኝ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ	33945	አቶ ሳልህ ሁሴን እና ደግፌ ደርቤ	ጥቅምት 20/2001	143
36.	ስለ አስፈላጊ አደራ እና የማስረጃ አይነት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2782,2800,2802,2472	64887	አቶ አደም የሱፍ እና አቶ አብዱሠላም መ.ሐመድ	ሐምሌ 29/2003	
37.	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1810/2/ ላይ የተመለከተው የይርጋ ገደብ ተፈፃሚ የሚሆነው ውል በፈቃድ ጉድለት ወይም በችሎታ ማጣት የተነሳ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1810	48012	አቶ ኡመር ከድር እና አቶ በዳዳ ሰቦቃ /ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 03/2003	147
38.	ተዋዋይ የሆነ ወገን ወይም ጥቅም ያለው ማናቸውም ሰው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከህግ ውጪ ነው ወይም ለህሊና ተቃራኒ ነው ወይም ለውሉ አፃፃፍ የተደነገገው ፎርም አልጠበቀም የሚል መከራከሪያ ምክንያት በማቅረብ ወሉ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808/2/	43379	አበበ አበጋዝ እና ጥሩነሽ ተክሌ	ታህሳስ 25/2003	150
39.	የንግድ መደብር ሽያጭ ውል በግዴታ እንዲፈፀም ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2330, 2329, 1778/	44873	አቶ ሰሚር ሱሩር እና እነ ወ/ሮ ስንዱ ዱባለ	ጥር 13/2003	153
40.	• በብድር ከተወሰደ ገንዘብ አከፋፈል ጋር በተያያዘ ብድር መክፈያ ጊዜው የዘገየ እንደሆነ ለአበዳሪው በኪሣራ መልክ የሚከፈለው ህጋዊ ወለድ ብቻ ስለመሆኑና ከዚህ ህጋዊ ወለድ በተጨማሪ በመቀጫ መልክ ለመክፈል የሚደረግ ስምምነት ፈራሽ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2006/2/, 2005/1/, 2489, 1889	59882	ወ/ሮ አስገደች ዘርጋው እና አቶ አየለ ንዳኔ	የካቲት 21/2003	157
ወንጀል					**161**
41.	• ከ13 ዓመት እስከ 18 ዓመት ድረስ ባለው የዕድሜ	46412	የሐረሪ ክልል	ጥቅምት 30/2003	162

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ክልል ውስጥ ከሚገኝ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ • ድርጊቱን የፈፀመው ሠው ዕድሜ በዚሁ የአድሜ ክልል መገኘት የወንጀል ተጠያቂነቱን የማያስቀር ስለመሆኑ የወ/ህ/ቁ. 626/1/, 211/1/, 48-56		ዓቃቤ ሕግ እና ቦና አህመድ አሚን		
42.	ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖር ሰዎችን ወደ ውጪ አገር በመላክ ወንጀል የተከሰሰን ሰው ጥፋተኛ ነው ለማለት እና ቅጣት ለመጣል የሚቻልበት አግባብ የወንጀል ህግ ቁ. 598/1/ /2/	54839	አቶ ኢምራን ጉደሣ አብዲ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	ጥቅምት 30/2003	165
43.	በህጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የገባ የውጭ ምንዛሪን በህግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ከአገር ይዞ ለመውጣት መሞከር የሚያስከትለው ኃላፊነት /ውጤት	47935	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ወ/ሮ እየሩሳሌም ወንዴ	ህዳር 30/2003	169
44.	ከዋስትና መብት ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤቶች የተከሳሽን የዋስትና መብት ለመንፈግ የተከሰሰባቸውን የወንጀል ክሶች ብዛትና ከባድነት መነሻ ሊያደርጉ ስለመቻላቸው የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.67/ህ/	59304	እነ አቶ አያሌው ተሰማ /ሦስት ሰዎች/ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ህዳር 15/2003	171
45.	በወንጀል የተከሰሰ ሰው የዋስትና መብት እንዲከበርለት ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ትዕዛዙ ተነስቶ ዋስትናውን ሊከለከል ስለመቻሉ የወ/መ/ሥ/ህ/ቁ. 74	59855	ወ/ሮ ሊዊዛ ሮርቤታ እና አቃቤ ሕግ	ህዳር 28/2003	174
46.	በሚያሽከረክረው መኪና ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ የነበረ ሰው ወድቆ ለህልፈተ ህይወት የተዳረገበት ሾፌር በወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/ ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/	52075	አቶ ጌቱ ብርሃኑ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	ታህሳስ 26/2003	177
47.	• በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ ፍርድ የተሰጠበት ተከሳሽ የሚያቀርበው የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ • በይግባኝ ደረጃ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተሰጠ የጥፋተኝነት ፍርድ እንደመጨረሻ ውሣኔ ተቆጥሮ በሰበር እንዲታረም ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 193/2/, 197-202, 160, 164, 163, 195/2/ /ህ/ የወንጀል ህግ ቁ. 522, 526 አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 9, 10 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/	57632	ሰማሽኝ በለው እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	ታህሳስ 25/2003	179
48.	ዓቃቤ ሕግ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተጠረጠረና ምርመራ የተደረገበትን ሰው ተከሳሽ ከሚሆን ይልቅ ምስክር ቢሆን የተሻለ ነው ብሎ ካመነ ይህንኑ	57988	ዮርዳኖስ አባይ አሰፋ እና	ጥር 10/2003	196

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ለማድረግ የሚከለክለው ህግ የሌለ ስለመሆኑ		የፌዴራል አቃቤ ሕግ		
49.	• ከወንጀል ጉዳዮች የክስ ሂደት ጋር በተገናኘ ዓቃቤ ሕግ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ተግባራትና ኃላፊነቶች • የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ በሆነ ወገን ላይ ቅጣት ሊጥሉ ስለሚችሉበት ሥርዓት /አግባብ/ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 136/1/, 148/1/ ,149	47755	የፌዴራል አቃቤ ህግ እና አቶ ሚፍታህ ኑረዲን	ግንቦት 05/2003	198
50.	• በግድያ ወንጀል የተከሰሰ ሰው የወንጀል ቁጥር 540 ወይም 541ን መሰረት በማድረግ ጥፋተኛ አድርጎ ለመወሰን የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀምን እንዲሁም መነሻ ሁኔታዎች በአግባቡ መመልከት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ • የወንጀል ህግ ቁጥር 78 "ን" ተፈፃሚ ለማድረግ ሊሟሉ ስለሚገባቸው መስፈርቶች • ህጋዊ መከላከልን በማለፍ የተፈፀመ የነፍስ ግድያ በወንጀል ህግ ቁጥር 541 የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 78, 540, 541	57446	ሃለቃ ገ/እግዚያብሔር ኃይሉ እና የኦሮሚያ ክልል ዓ/ሕግ	ግንቦት 19/2003	202
51.	የወንጀል እና የፍ/ብሔር ክሶች ተጣምረው ሊታዩ የሚችሉት በወንጀል ህግ ቁጥር 101 አግባብ ብቻ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 101	59045	የስልጤ ዞን ምርመራና ክስ ዓ/ሕግ እና እነ አቶ ጌታቸው አስራት /አምስት ሰዎች/	ግንቦት 16/2003	106
52.	በወንጀል ድርጊት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ ሰው ከጉዳቱ በኋላ ተጐጂውን ወደ ህክምና ቦታ የወሰደው መሆኑ ብቻ በድርጊቱ የተፀፀተ መሆኑን ያሳያል በሚል ቅጣትን ከመነሻው በታች በመወረድ ቀልሎ እንዲወሰን ለማድረግ የሚያስችል ስላለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 543/3/, 59/1/, 575/2/, 82/1/ የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁ. 279/56 አንቀጽ 35	62332	አቶ ዘለቀ ካሣዬ እና የፌዴራል ዓ/ሕግ	ግንቦት 29/2003	211
53.	በወንጀል ተከሰሶ የቀረበ ተጠርጣሪ በፍ/ቤት በሰጠው የእምነት ቃል መሰረት ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ከተጣለበት በኋላ በተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የማይችል ስለመሆኑ	63741	አቶ መሐመድ ሰኢድ አሊ እና የፌዴራል ዓ/ሕግ	ግንቦት 15/2003	213
54.	ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ እውነታ የተጠቀሰውን ወንጀል የሚያቋቁም መሆን አለመሆኑ ጉዳይ የህግ ጭብጥ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊመረመር የሚችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 675/1/	64813	ያሲን አሕመድ መሐመድ እና የፌዴራል ዓ/ሕግ	ግንቦት 17/2003	215
55.	• የመወሰን ስልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ብቻ ያላቸው ሰዎች /ሰራተኞች/ በወንጀል ጉዳይ በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት አግባብ • የተቀጠረበትን የሙያ ሥራ በጥንቃቄና በአግባቡ አለመፈፀም በአዋጅ ቁ. 214/74 በስልጣን ያለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ያስጠይቃል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ	43049	አረጋሽኝ መርዕድ እና የፌ/ስ/ፀ/መ/ኮ/ዓ/ህግ	ግንቦት 26/2002	217

https://t.me/ethiopianlegalbrief

56.	አንድ ተከሳሽ በወንጀል ህግ ቁጥር 427/3/ መሰረት የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በሚል ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ የወንጀል ህግ ቁጥር 427/1/, /3/	55047	አቶ ነብይ በድሩ ሽፋ እና የፌደራል ሥ/ፀ/መ/ኮሚሽን ዓ/ህግ	መጋቢት 05/2003	221
57.	ፍ/ቤት በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው በተመለከተ አስቀድሞ የፈቀደውን የዋስትና መብት በራሱ አነሳሽነት ወይም በማናቸውም ባለጉዳይ አመልካችነት አዲስ ነገር ተከስቷል ብሎ ካመነ ዋስትናው እንዲነሳ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 74	61275	አቶ ኤልያስ ገረመው እና የኢ/ን/ን/ባ/ዓ/ህግ	ሚያዝያ 18/2003	226
58.	• በክብድ የሰው መግደል ወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ ተከሳሽ ስለሚጠየቅበት አግባብ • የተመሰረተበት ክስ በዓቃቤ ሕግ በኩል እንደክሱ አመሰራረት ያልተረጋገጠበት ቢሆንም ተከሳሹ የቀረበው ማስረጃ ከቀረበበት ክስ ባነሰ የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ተከሳሹ በነፃ እንዲሰናበት ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የማይኖር /የሌለ/ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 32/1/ /ሀ-ለ/, 539/1/ /ሀ/, 84, 86, 40, 445, 88 የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 113/2/ የወንጀል ህግ ቁጥር 40, 445	45595	የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ህግ እና እነ ኢዮስያስ አበራ ገ/ሚካኤል /አምስት ሰዎች/	ሰኔ 17/2003	229
59.	• በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበት ተከሳሽ ላይ የሚጣለውን የቅጣት አይነትና መጠን ለመወሰን ፍ/ቤቶች በህጉ ውስጥ ተካትተው የሚገኙትን የቅጣት ማቅለያ እና ማክበጃ ምክንያቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚችሉበት አግባብ • የሞት ቅጣት ሊተላለፉ የሚችልበት አግባብ የወንጀል ህግ ቁጥር 117, 32/1//ሀ-ለ/, 539/1//ሀ/, 84/1//ሀ-ሠ/, 183, 179, 180, 182, 88/2/, 87/1/	47831	እነ መስታወት ጌታነህ /አራት ሰዎች/ እና የፌደራል ዓቃቤ ህግ	ሰኔ 03/2003	240
60.	“የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት” በሚል በወንጀል ህጉ ውስጥ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ለማቋቋም ቼኩ ለክፍያ ባንክ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን /ያለመኖሩ/ ማረጋገጥ ብቻ በቂ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 693/1/	67947	አቶ አዱኛ አንበሎ እና የፌደራል አቃቤ ህግ	ሰኔ 15/2003	246
61.	• በህጉ በጠቅላላ የቅጣት ማቅለያነት የተመለከተን ምክንያት ወንጀሉን ለማቋቋም የቀረበ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች ይህንን ምክንያት እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያነት ሊጠቀሙበት የማይችሉ ስለመሆኑ • ፍርድ ቤቶች በህጉ ለዳኞች የሚሰጠውን አመዛዝኖ ቅጣትን የመወሰን ስልጣን ሲጠቀሙ በቅጣት አወሳሰን ረገድ ህጉ ያስቀመጣቸውን መሰረታዊ መርሆዎች ሊጥሱ የማይገባ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 82/2/, 189,86, 180, 179, 182, 184, 82/1/, 88/2/	59356	የፌደራል ዓ/ህግ እና በሪሁን ፍቃዱ	ሰኔ 03/2003	251
62.	በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ክስ ከቀረበበት ሰው ጋር በተገናኘ በሚካሄድ የቅድመ ክስ ሂደት ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት እንደቀረበው የወንጀል አይነት በመመርመር ወደ ዋናው ክስ የመስማት ሂደት	57938	እነ አቶ አደም አብዱ /ሁለት ሰዎች/ እና	ሐምሌ 14/2003	256

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	እንዲገባ በሚል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 419 አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 36/1//2/		የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ህግ		
63.	• በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የሚያቀርበውን ጥያቄ ፍ/ቤቶች ተከሳሹ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊጣልበት የሚችለውን የቅጣት ጣሪያ መነሻ በማድረግ ውሣኔ ሊሰጡበት የሚገባ ስለመሆኑ • ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ በእስራት ሊያስቀጣ የሚችል በሆነ ጊዜ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ሊፈቀድ የማይችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀጽ 4/1/ አዋጅ ቁ. 239/93 አንቀጽ 2 አዋጅ ቁ. 236/93 የወንጀል ህግ ቁጥር 676/1/	63344	የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/የ ሥ/ፀ/ሙ/ኮሚሽን እና እነ ላሉ ሰይድ አክልታ	ሐምሌ 28/2003	258
64.	ውልን /ስምምነትን/ መሰረት ባደረገ ግንኙነት አንድን ንብረት ወስዶ በውሉ መሰረት ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው የአምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል የወንጀል ክስ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 23/2/, 24, 57, 58	65054	ብሩክ ሚካኤል እና የፌዴራል ዓ/ህግ	ሐምሌ 14/2003	261
65.	• ዓቃቤ ህግ በወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የሚያቀርበው የወንጀል ክስ የወንጀሉን ዝርዝር ሁኔታ መያዝ እንዳለበት በተለይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል ክሱ ወንጀሉንና ሁኔታውን መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ • አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር የወንጀል ተካፋይ ሆኗል የሚባለው በወንጀሉ አፈፃፀም የግዙፍ ተግባር የሃሳብና የህግ ሁኔታዎችን መተላለፍ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 112 የወንጀል ህግ ቁ. 32/1/ 23/2/	57644	መ/ር አወት ተካ እና የትግራይ ዓ/ህግ	ሐምሌ 25/2003	264
66.	ተጨማሪ ማስረጃን ከመቀበል ጋር በተያያዘ በወንጀል ህግ ቁጥር 143/2/ ሥር የተመለከተው ድንጋጌ ፍ/ቤቱ ለፍትህ አሰጣጥ ተገቢ ነው ብሎ ሲያመን ትዕዛዝ ሊሰጥበት የሚችል ስለመሆኑ በፈቃጅነት (permissive) የተቀመጠ እንጂ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ ስላለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 143/2/	66767	አቶ ተስፋዬ ተሾመ እና የፌዴራል ዓ/ህግ	ሐምሌ 28/2003	269
67.	በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው የሚያነሳው የጤና ችግር ከዋስትና መብት አኳያ ሲታይ ስላለው ህጋዊ ጥበቃ	68407	ወ/ሮ ውልታ ደሳለኝ እና የኦሮሚያ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ህግ	ሐምሌ 14/2003	273
68.	• ወንጀልና የወንጀል ቅጣት የእያንዳንዱን ጥፋተኛ ግላዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ውሣኔ ሊሰጥባቸው የሚገባ ስለመሆኑ • የጉምሩክ ህግን በመተላለፈ ጥፋተኛ የተባሉ ሰዎች	48956	እነ ወ/ሮ ፍኖተ ፃድቅ አበራ እና የጉምሩክ ዓ/ህግ	መጋቢት 10/2002	276

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	/ተከሳሾች/ ላይ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በእያንዳንዱ ጥፋተኛ ላይ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 41, 32/1/ሀ/ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 73/1/ አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 73/1/				
69.	አንድ ሰው በወር ደመወዝ ከሚያገኘው ገቢ ውጪ ሌላ ህጋዊ የገንዘብ ምንጭ እንዳለው ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታ በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብትና ንብረት ባለቤት መሆኑ ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ ይዞ በመገኘት የሙስና ወንጀል የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 419	58514	አቶ ሃንካራ ሃርቃ ሃያሞ እና የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ /ሥ/ፀ/ሙ/ኩ/ዓ/ ህግ	ጥር 09/2003	278
70.	የንግድ ፈቃድ መብትን መጣስ በአዋጅ ቁ. 501/98 መሰረት የወንጀል ተጠያቂነትን ስለሚያስከትልበት አግባብ	69899	እነ ዮሴፍ ሀይሉ ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ	ሐምሌ 29/2003	280
71.	በአሸከርካሪነት ሥራው ማድረግ የነበረበትን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በሌላ ሰው ላይ የሞት አደጋ ያደረሰ ሰው በወንጀል ህግ ቁጥር 543/2/ የሚጠየቅ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 543/1/, /2/, /3/, 59/1/ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 113	55649	ኤልያስ ዲጋ እና የፌዴራል ዓ/ሕግ	መጋቢት 06/2003	286
72.	የወንጀል ክስ ቀርቦ ተከሳሹ እንዲከላከል በሚል በፍ/ቤት ብይን የተሰጠ መሆኑ ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ እንደተሰጠበት በመቁጠር የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ	59537	አነዚር ኢብራሂም እና የቤ/ን/ክ/ስ/ፀ/ ሙስና ኮሚሽን	ሚያዝያ 19/2003	291
73.	አንድ የወንጀል ድርጊት በእርግጥም ተጀምሯል /ተፈጽሟል/ ለማለት የሚቻለው የተደረገው ተግባር በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ ወንጀሉን ለመፈፀም ወደታሰበለት ግብ ለማድረስ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲቻል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ቁ. 27/1/ 540 555/ሀ//ለ/	63727	ፋሲል ታምራት እና የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ ከሳሽ	ሰኔ 13/2003	293
ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት					296
74.	በፍ/ቤቶች ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ትዕዛዝ የተሰጠው ተከራካሪ ወገን ጥሪ ተልኮለት ቀርቦ መልሱን አልሰጠም በሚል ምክንያት ክርክሩ ውጪ እንዲሆን የሚሰጥ ትዕዛዝ በክርክሩ ውስጥ ያሉ ሌሎች ወገኖችን መብት የሚያጣብብና የሥነ-ሥርዓት ህግን የሚጥስ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70, 41/3/, 199	53844	የወ/ሮ ቅድነሽ አካለታል ወራሾች /ሦስት ሰዎች/ እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ስራና ከተማ ልማት ቢሮ	ጥቅምት 18/2003	297
75.	በፍርድ ለሌላ ሰው የተላለፈ ንብረት የእኔ ነው በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418, 421, 455	50835	እነ አቶ ምናሴ ኢትሶ /ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 16/2003	300

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			እና ወ/ሮ ፋንታዬ ተረፈ		
76.	• የግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንደ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድ ሁልጊዜ ጥብቅ የሆነ የሙግት ሥርዓትን ተከትሎ ጉዳዩን ማየት የሌለበት ስለመሆኑ • የግልግል ጉባኤ ጉዳዩን ለማየት ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ያህል ሊወሰን ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 318/5/, 317/1/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3345	52942	አቶ ገብሩ ኮራ እና አቶ አመዲዮ ፌዴሬቼ	ጥቅምት 18/2003	303
77.	ተከራካሪ ወገኖች የሚሟገቱበት ጉዳይ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ይህ እንዲፈፀም ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/	48608	ወጋገን ባንክ አ.ማ እና አቶ ሃብቶም ረዘነ	ህዳር 02/2003	306
78.	• ተከራካሪ ወገኖች እንዲሰሙላቸው የሚቆጥሯቸው የሰው ማስረጃዎች የማስረዳት ብቃት ሊታወቅ የሚችለው ቃላቸው ከተሰማ በኋላ ስለመሆኑ • የተቆጠሩ ማስረጃዎች የማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት መርህ (relevancy and admissibility) ካልከለከለ በስተቀር በዝርዝር ሊሰሙ የሚገባ ስለመሆኑ • በሰው ማስረጃነት የተቆጠረ ኦዲተር በኦዲት ሪፖርት ላይ ከተመለከተው ውጪ /የተለየ/ ሊያስረዳ አይችልም በሚል ምክንያት ሊሰማ አይገባም ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ	49502	የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት እና እነ መርዕድ ተፈራ /ስድስት ሰዎች/	ህዳር 01/2003	309
79.	• መጥሪያ በጋዜጣ ጥሪ ሊደረግ የሚገባው ሌሎች አግባብነት ያላቸው የመጥሪያ አላላክ መንገዶች ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ ከተከናወኑ በኋላ ስለመሆኑ • መጥሪያ በአግባቡ ደርሷል ለማለት የሚላክለት ሰው ስም በተሟላ ሁኔታ ተገልጾ መላክ ያለበት ስለመሆኑ • መጥሪያ በህጉ አግባብ እንዲደርሰው ሳይደረግ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠበት ወገን ትዕዛዙ እንዲነሳለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 94-110, 7870/ሀ/	53113	እነ ወ/ሮ አበበች በጅጋ /ሁለት ሰዎች/ እና ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ	ህዳር 03/2003	311
80.	በዋናው ክርክር ላይ በተሰጠ ፍርድ መብቱ የተነካበት ሰው በፍርድ አፈፃፀም ወቅት መብቱ ከተነካበት ሰው በተለየ ሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ማቅረብ የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418, 419	53607	የምጥን መንደር መኖሪያ ቤቶች የህብረት ስራ ማህበር እና እነ ወ/ሮ ባየች አይገምት /ሦስት ሰዎች/	ህዳር 14/2003	315
81.	አስቀድሞ የተሰጠን ውሣኔ ለማስነሳት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችል ወገን በክርክሩ መግባት የሚገባው ሆኖ ነገር ግን ተካፋይ ያልነበረ እንደሆነ ባልተካፈለበት ክርክር የተሰጠውን ፍርድ መቃወም የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 41	42714	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፍትህና ህግ ጉዳዮች ቢሮ እና እነ	ህዳር 08/2003	318

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			የሽቀጣ ሽቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት /ሦስት ሰዎች/		
82.	ከሳሽ የሆነ ወገን ያቀረበው ክስ ውድቅ በተደረገበት ሁኔታ ተከሳሽ የዳኝነት ክፍያውን ለከሳሽ እንዲከፍል የሚደረግበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 215, 462	46281	ወ/ሮ አበባዬ አቢ ደራወርቅ እና ይገረም ፈዬ	ታህሳስ 28/2003	320
83.	• ልዩ ዕውቀትና ክህሎትን መሰረት በማድረግ አንድ ጉዳይ ተመርምሮ የተሰጠ የሙያ አስተያየት ሊስተባበል የሚችለው በጉዳዩ ላይ የተሻለ የሙያ እውቀትና ክህሎት ባለው ባለሙያ ጉዳዩን መርምሮ በሚሰጠው አስተያየት ስለመሆኑ • አንድን ሰው ለማንገዝ ውል የተዋዋለ ሰው በጉዞ ወቅት በተጓዡ ላይ ለደረሰ ጉዳት ሊከፍል የሚገባው የካሣ መጠን ከብር 40,000 መብለጥ የሌለበት ስለመሆኑ • የጉዳት ካሣ መጠኑ ከብር 40,000 ሊበልጥ የሚችለው በንግድ ህግ ቁ. 599 የተመለከተው መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/ የንግድ ህግ ቁ. 597/1/	47960	አቶ ታከለ ባልቻ እና ወ/ሮ አዜብ ፀጋዬ	ታህሳስ 12/2003	322
84.	• የበላይ ፍርድ ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሊሽር የሚችለው ህጋዊና በቂ ምክንያት ሲኖረው ብቻ ስለመሆኑ • በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች የበላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ለማድረግ የሚችለው የማይቀበልበትን ምክንያት በውሣኔው ላይ በግልጽ በማስፈር እንጂ በደፈናው "በተገቢው አልተረጋገጡም" የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ስላለመሆኑና በዚህ መልክ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 341 እና ተከታዮቹ	58540	ኪድስ ሊንክ ኢንተርናሽናል እና ሲስተር ገነት ወንድሙ	ጥር 27/2003	326
85.	ሁለት ተከራካሪ ወገኖች አንደኛው በሌላኛው ላይ የፍርድ ባለመብት ሆነው የአፈፃፀም አቤቱታው በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በቀረበ ጊዜ በፍርድ የበለጠው ገንዘብ በመቻቻል እንዲፈፀም በሚል በአንድ ፍርድ ቤት ተጠቃሎ እንዲታይ ለማድረግ የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት ያለውና ህጋዊ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 397	57378	ወ/ሮ አስቱር አርአያ እና ወ/ሮ አምሳለ ፀሐይ	ጥር 23/2003	329
86.	በባንክ በኩል ከተላከ ገንዘብ ጋር በተገናኘ በአግባቡ ለተላከለት ሰው አልደረሰውም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በላኪው ወይም በተላከለት ሰው ስም ክስ ቀርቦ ከተወሰነ በኋላ በሌላኛው /በላኪው/በተላከለት/ሰው/ ስም የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	51223	ዳሸን ባንክ አ.ማ እና ወ/ሮ ሀመልማል መኮንን	የካቲት 24/2003	332
87.	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 አቤቱታ እንዲያቀርብ ተፈቅዶለት ክርክር ተካሂዶ ውሣኔ የተሰጠበት ወገን በድጋሚ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447 "ን" መሰረት	53421	ወ/ሮ ወርቅነሽ ዋሴ እና	የካቲት 22/2003	335

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በማድረግ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 447, 354		አቶ ባንተይርጋ ወርቁ		
88.	በመጀመሪያ በቀረበ የክስ መከላከያ መልስ ያልተካተተን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መልስ እንዲሻሻል በሚል ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት ተካትቶ ሲቀርብ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91, 244 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1856	55973	ወ/ሮ አፀደ ኤዶ እና አቶ ትኩ ዋቅሹም	የካቲት 21/2003	339
89.	• ሌሎች ሰዎች ተከራካሪ በሆኑበት ጉዳይ ንብረትን አስመልክቶ በፍርድ ቤቱ የተሰጠ የማገጃ ትዕዛዝ ይነሳልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ሰው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሰረት ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ • አንድ ክርክር መጀመሩን ያወቀ ወገን የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከውሣኔው በኋላ የሚያቀርበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሰረት ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 153/3/, 418-421	56795	አቶ መባረክ ከድር እና እነ ሚስተር ኑዋምባ ሲርር /አምስት ሰዎች/	የካቲት 21/2003	342
90.	ፍርድ ቤቶች ከውሣኔ ሊደርሱ የሚገባው የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት፣ የመከላከል ብሎም በእኩልነት መርህ የመዳኘት መብት በጠበቀ መልኩ ስለመሆኑ	52546	እነ አቶ በቀለ አማረ /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ብዙነሽ ግርማ	ታህሳስ 13/2003	347
91.	ክስ ለመስማት ቀጠሮ ከተሰጠ በኋላ ያልቀረቡ ከሳሾችን ከክርክሩ ውጪ እንዲሆኑ በማለት ትዕዛዝ የሰጠ ፍ/ቤት /ችሎት/ በራሱ ተነሳሽነት አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ በማንሳት ክሱ ውጪ የሆኑትን ከሳሾች የክሱ አካል በማድረግ የሚሰጠው ውሣኔ ከሥነ ሥርዓት ህግ ውጪ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73, 74, 78	55078	ማበርፋይድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና እነ አሸናፊ አለሙ /ዘጠኝ ሰዎች/	ታህሳስ 25/2003	350
92.	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 377 ተፈፃሚ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ	52193	የኮንስትራክሽን እና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ እና እነ ወ/ሮ መድሀኒት ሃይሉ /ሁለት ሰዎች/	ታህሳስ 27/2003	352
93.	ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል የተደረገበት ተከሳሽ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያለመቅረቡን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ የመከራከር መብት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 72, 78/1/	61846	ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል እና ወሮ ፋጡማ አስማን	ግንቦት 29/2003	355
94.	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 እና 418 መሰረት በተሰጠ ፍርድ ላይ ተቃውሞ የሚቀርብበት ሥርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 359, 418, 222, 223, 137/3/	55842	የኦሮሚያ ክተሞች ፕላን ኢንስቲትዮት እና	መጋቢት 23/2003	358

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			እነ አቶ ካሣ ጭርሳ /አራት ሰዎች/		
95.	በፍ/ብሔር ክርክር ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ /ጭብጥ/ ለማስረዳት የሚቀርብን የሙያ ምስክርነት (expert witness) ውድቅ በማድረግ ባለሙያ ባልሆኑ ምስክሮች የተሰጠ የምስክርነት ቃልን ሊቀበል የሚችለው ይህን ለማድረግ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1/	65930	የሱ ኃ/የተ/የግ/ማህበ ር እና እነ አቶ ደጀኔ በቀለ /ሁለት ሰዎች/	ሰኔ 14/2003	362
96.	ከኢትዮጵያ ውጪ በሚገኝ ፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች እውቅና ሊሰጠው ወይም ተቀባይነት ሊኖረው የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 456-461	59953	ወ/ሮ አለምነሽ አበበ እና አቶ ተስፋዬ ገሰሰ	ሰኔ 02/2003	365
97.	• በህግ የተቀመጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንዲፈቀድ የሚቀርብ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ • ይግባኙ በጊዜው ሊቀርብ ያልቻለው የባለጉዳዩ ጠበቃ፣ ነገረፈጅ ወይም ወኪል የሆነው ሰው ባለመቅረቡ ወይም ከነዚህ ሰዎች ጋር በተያያዘ በተከሰተ ጉድለት መሆኑ ከታወቀ የማስፈቀጃ አቤቱታው በበቂ ምክንያት የተደረገ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 326/2/ /1/ 323/2/ 325	57360	አፍሪካ ኢንሹራንስ አ.ማ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ሐምሌ 15/2003	369
98.	በአንድ በመካሄድ ላይ ባለ የፍርድ ቤት ክርክር ተሳታፊ ለመሆን ጥያቄ አቅርቦ በብይን ውድቅ የተደረገበት እና በሌላ መዝገብ ክስ መስርቶ መብቱን እንዲያስከብር በሚል ትዕዛዝ የተሰጠበት ወገን በዚህ ትዕዛዝ መሰረት አዲስ መዝገብ በማስከፈት ወይም በሌላ መዝገብ በመግባት የክርክር ተሳታፊ ከመሆን የሚያግደው ነገር የሌለ ስለመሆኑ ወይም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5	62173	ወ/ሪት ቤተልሄም ታደሰ እና እነ ወ/ሮ ሃና ታደሰ /ሦስት ሰዎች/	ሐምሌ 11/2003	371
99.	ግልጽነት የጐደለው ክስ /አቤቱታ/ በቀረበ ጊዜ ክሱ በተከራካሪዎች አነሳሽነት ወይም ፍ/ቤቱ በራሱ ክሱ እንዲሻሻል ሳይደረግ በደፈናው የቀረበን የይገባኛል ጥያቄ ላይ የሚሰጥ ፍርድ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91/1/	63699	አፔኖ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅት እና አቶ ጥሩነህ ይመር	ሐምሌ 15/2003	375
100.	ፍ/ቤቶች በባንክ ለተሰጠ ብድር መያዣነት የተሰጠ ንብረትን በአዋጅ ቁ. 97/90 ባንኩ ሲረከበው በብድሩ ገንዘብ እና በንብረቱ ወቅታዊ የዋጋ ግምት መካከል ያለውን ልዩነት ማስላት አስፈላጊ መሆኑን ባመኑ ጊዜ ይህንን ለማድረግ ልዩ የሂሳብ አዋቂ (expert witness) በመመደብ ለጉዳዩ አልባት ሊሰጡ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136/1//2/	61227	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ኃይሉ አምቦ /ሁለት ሰዎች/	ሐምሌ 14/2003	377
101.	• በፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ የእግዱ ትዕዛዝ	61637	ዶ/ር አልሑሴን በድልገዋድ	ሐምሌ 11/2003	380

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ተጥሶ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት በተደረገ የሽያጭ ውል ለሦስተኛ ወገን በተላለፈ ጊዜ ሊኖር ስለሚችል ውጤት • እግዱ ተጥሶ በተከናወነው ተግባር መብቱ የተጐዳበት ሰው የእግዱን ትዕዛዝ በጣሰው ወይም እንዲጣስ ምክንያት በሆነው አካል ላይ ተገቢውን አቤቱታ በማቅረብ መብቱን ለማስከበር የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 156 አዋጅ ቁ. 334/95 አንቀጽ 15/2/ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1204, 1206, 1184, 1185, 1195		እና እነ ወ/ሮ ገነት ሐድጐ /ሁለት ሰዎች/		
102.	በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት እውቅና ካልተሰጠው በስተቀር በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የቀረበ አቤቱታ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ	54632	ወ/ሮ ራውዳ መሐመድ እና አምባሳደር አብደላ አብድራህማን	ግንቦት 29/2003	385
103.	የኤክስፐርት ማስረጃ ሙሉ እምነት ሊጣለበት የሚችል ማስረጃ ስላለመሆኑ	43453	አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት እና እነ ወ/ሮ ዘነበወርቅ ከበደ /ሁለት ሰዎች/	ህዳር 15/2002	388
104.	የባለመዓያ ማስረጃ ፍፁም ስላለመሆኑና ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ተገናዝቦ ብቃቱና ተአማኒነቱ ሊመዘን የሚገባ ስለመሆኑ	14981	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ ሀዋ መሐመድ	ግንቦት 04/1998	391
105.	በህግ /ፍርድ/ ኃይል የተወሰደ ንብረት ሊመለስ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349/1/	44238	አቶ ማሞ ደምሴ /ሦስት ሰዎች/ እና እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሄር /ሦስት ሰዎች/	ጥር 09/2003	393
106.	ከሀራጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447 እና 453 ትርጉምና ሊፈፀሙ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 447, 453	56130	ሊሲ ታነሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና እነ መአዛ አስፋው /ሦስት ሰዎች/	ጥር 26/2003	397
107.	• ክስ ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት ለመቅረብ ያልቻለው በቂ ሊባል በሚችል እክል /ችግር/ ምክንያት መሆኑን ያስረዳ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲነሳለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ • "በቂ ምክንያት" በሚል የሰፈረው ሃረግ ሊተረጐም የሚገባው ተከሳሹ ቀና ልቦና ያለው መሆኑንና የተለያዩ አግባብነት ያላቸው ነባራዊ ሁኔታዎችን	54080	እነ አቶ ላል ሮላንድ ቻፕማን እና አቶ ዜና ወ/ማሪያም	ጥቅምት 19/2003	401

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70/ሀ/, 72, 78/1/				
108.	የልዩ አዋቂ ምስክሮች በፍ/ቤት የሚሾመውበት፣ የሙያ ግዴታቸውን የሚያከናውኑበት እና ፍ/ቤቶችም የሚቀርበውን ሙያዊ ምስክርነት ሊቀበሉ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136	44522	ጭላሎ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አፍሪካ ኢንጂነርስ ኮንስትራክሽን	ታህሳስ 15/2003	404
109.	ክስ የቀረበበት ጉዳይ ለቃል ክርክር /ለመስማት/ በተቀጠረበት ዕለት ከሳሽ የሆነ ወገን በመቅረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 መሰረት የተዘጋ መዝገብን መነሻ በማድረግ በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 74/2/	58487	ወ/ሮ አባይነሽ ገ/ህይወት እና ወ/ሮ እታገኝ ደሳለኝ	መጋቢት 22/2003	407
110.	በፍ/ቤት በተሰጠ ፍርድ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የተቀመጠው የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትና የቀን አቆጣጠር ስሌት ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 323/2/	59085	ወ/ሮ ብርሃኔ አዱላ እና ግርማ አብዲሳ	መጋቢት 05/2003	410
111.	ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ሳይሰጥ በማለፍ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ ሠ, 234	59294	አቶ በቀለ ጃፋር እና እነ ወ/ሮ መሉነሽ ማሞ	መጋቢት 19/2003	413
112.	አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ጋር በተያያዘ “ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ” በሚል የተቀመጠው ሃረግ ትርጉም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 244/2/	62330	አቶ አዱኛ አጃው እና ቀስቅስ አየነው	ሚያዝያ 03/2003	416
	ባንክና ኢንሹራንስ				**419**
113.	በባንክ ከተቀመጠ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ትክክለኛው ገንዘብ አስቀማጭ ከሆነ ሰው ውጭ ለሆነ ሰው ገንዘብ ወጪ ተደርጐ የተከፈለ እንደሆነ ባንኩ በሃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረገ ወይም የባንኩን የተለመደ አሰራር ሳይከተል የሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ	41535	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ ግሎሪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር /አራት ሰዎች/	ጥቅምት 03/2003	420
114.	በንግድ ህጉ የመድን ሰጪን ግዴታና ኃላፊነት በተመለከተ የቀረቡ ድንጋጌዎች መድን ሰጪው ከመድን ገቢው ጋር አንዳንድ ኃላፊነቶችን ለማስቀረት በሚል ከተስማሙባቸው ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝበው ሥራ ላይ መዋል ያለባቸው ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 664/1/	50199	ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አቶ አያሌው ወርቁ	ታህሳስ 27/2003	423
115.	• ባንኮች ላበደሩት ገንዘብ በመያዣነት የያዙትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በዕዳ መክፈያነት በሐራጅ ለመሸጥ የተሰጣቸውን ስልጣን በተግባር ሲያውሉ ህግን በመተላለፍ በባለዕዳው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂነት ያለባቸው ስለመሆኑ • በመያዣነት የተያዘውን ንብረት በሐራጅ ለመሸጠም የፍርድ ቤት ውሣኔ ወይም ፈቃድ የማያስፈልጋቸው ስለመሆኑ	65632	ህብረት ባንክ አ.ማ እና አቶ አሊ አብዱ	ሐምሌ 13/2003	427

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• አበዳሪ የሆነ ባንክ በአዋጅ ቁ. 97/90 የተሰጠውን ስልጣን /መብት/ ትቷል (waive) ሊባል ስለሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394-449 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3, 6				
116.	መድን ገቢ የሆነ ወገን ጉዳት የደረሰበትን መድን የተገባለት ንብረቱ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ሊጠገንለት /ሊካስ/ ያልቻለ መሆኑን በተረዳ ወቅት በዚህ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የጉዳት ኪሣራ ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1802	47076	አፍሪካ ኢንሹራንስ /አ.ማ/ እና ወ/ሮ ጣይቱ አመዴ	መስከረም 25/2003	430
117.	ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለን ተበዳሪ ንብረት አበዳሪ ባንክ በአዋጅ ቁ. 97/90 በንብረቱ ግምት ከተረከበ በኋላ ቀሪውን ዕዳ በተመለከተ የሚያቀርበው ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1846	56010	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ ቃድሮ ኑሬ	ሐምሌ 29/2003	435
	የዳኝነት ስልጣን				**408**
118.	• የሊዝ ውል እንዲቋረጥ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ እና ሊከተል የሚችለው ውጤት • የሊዝ ውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ በአ.አ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የሚታይ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀጽ3/2/ አዋጅ ቁ. 272/94 አንቀጽ 2/7/, 15/1/ /ለ/	54697	አዲስ ኢንተርናሽናል አካዳሚ እና እነ አቶ ሃይማኖት አበበ /ዘጠኝ ሰዎች	መስከረም 24/2003	439
119.	• ከአዋጅ ውጪ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተወስዶብኛል በሚል በቀረበ አቤቱታ መነሻነት የፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በህጉ አግባብ የሚሰጠው ውሣኔ እንደ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሊቆጠር የሚችልና ለአፈፃፀም የሚቀርብ ስለመሆኑ • አንድን ጉዳይ የማየት ስልጣን ከፍርድ ቤት ውጪ ለሆነ አካል የተሰጠ በመሆኑ በዚህ አካል እየታየ ባለበት ተመሳሳይ ወቅት በፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 110/87 አዋጅ ቁ. 193/92 አዋጅ ቁ. 572/2000 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 8	48316	ወ/ሮ ዘነበች ተመስገን እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ጥቅምት 04/2003	444
120.	• የፌዴራል ጉዳይን በውክልና ስልጣን ተመልክቶ በክልል ፍርድ ቤት ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ መሰረት በማድረግ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ ስለሚቻልበት ሁኔታ /አግባብ/ • የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ በሚነሳ ክርክር ላይ እንደ ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ብሎም በይግባኝ ደረጃ ባለ ክርክር ደግሞ እንደ ፌዴራል ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ የፌዴራል ጉዳዮችን ለማስተናገድ የሚያስችል የውክልና ስልጣን ያለው ስለመሆኑ • አዋጅ ቁ. 322/95 የተወሰኑ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በህገ መንግስቱ ተሰጥቷቸው የነበረውን የፌዴራል ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸው	54577	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ሰለሞን ያቆብ	ህዳር 01/2003	447

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የማስተናገድ የውክልና ስልጣንን ብቻ የሚያስቀር እንጂ በይግባኝ ያላቸውን ስልጣን ጭምር የሚያስቀር ስላለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/2/, /5/ አዋጅ ቁ. 322/95				
121.	የአ.አ. ከተማ አስተዳደር ማንበራዊ ፍ/ቤቶች የፌዴራል ተቋማት ተከራካሪ የሆኑበትንና የገንዘብ መጠናቸው ከ5000 ብር ያልበለጠ የፍ/ብሔር ጉዳዮችን ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አዋጅ ቁ. 25/88	56118	የኢትዮጵያ ቴሌ ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ሮ ወርቅነሽ ወ/ማርያም	ህዳር 16/2003	451
122.	በውጭ አገር መንግስት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የማየት የዳኝነት ስልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 12/1/ የወንጀል ህግ ቁ. 263, 71	55299	ዓለም ገብሩ እና የትግራይ ዓቃቤ ህግ	መጋቢት 19/2003	454
123.	• የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁ. 67/89 ሥር የተደነገጉ የወንጀል ድርጊቶችን የተመለከቱ ክርክሮችን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ • ያለ ንግድ ፈቃድ በመነገድ ወንጀል የተከሰሱ ሰዎችን በተመለከተ የቀረበ ክርክርን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ • ሺሻ ጋር በተገናኘ የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ወንጀሎችን አይቶ ለመወሰን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 46 አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41/2/, 52	56893	የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አቤቱታና ምርመራ ክስ አቀራረብ ንዑስ የስራ ሂደት እና እነ ወ/ሪት ፍሬህይወት ፍቃዱ /አስራ ሁለት ሰዎች/	መጋቢት 22/2003	457
124.	• የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ንብረትነታቸው የከተማው አስተዳደር ለመሆናቸው ክርክር በማይቀርብባቸው ቤቶች ላይ የሚነሱ የይዞታ፣ የኪራይ እና ሌሎች ክርክሮችን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ • የሁከት ይወገድልኝ ክስ ከከተማው መሪ ፕላን ጋር እስካልተያያዘ ድረስ በከተማው ፍ/ቤቶች የሥረ ነገር ስልጣን ሥር የሚወድቅ ስላለመሆኑ • የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖር የሚሰጥ ፍርድ እንዳልተሰጠ የሚቆጠርና ህጋዊ አስገዳጅነት የሌለው ስለመሆኑ • ከቤት ይዞታ ጋር በተገናኘ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የተሰጣቸው ስልጣን ሁከት ይወገድልኝ በሚል የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄን መሰረት ባደረገ መልኩ ሊቀርብ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41/1//4//ረ/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9 231 /1/ /ለ/	64703	ሻምበል ለታይ ገ/መስቀል እና በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ጽ/ቤት	ሐምሌ 29/2003	641
125.	• የፖሊሳካ ተሿሚ የሆነ ሰው ከሥራ ኃላፊነቱ መነሳቱን ተከትሎ ያለውን ቅሬታ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅን መሰረት በማድረግ ለአስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩን አቅርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	63417	አቶ ትዕዛዙ አርጋው እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ	ሐምሌ 15/2003	464

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• ፍ/ቤቶች በዚህ መልኩ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 12/2/ የቤንሻንጉል ብ/ክ/መ/የሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ቁ. 29/95 አንቀጽ 71		ም/ቤት		
126.	• የኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ከአዋጅ ውጪ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ የቀረበን ጉዳይ አከራክሮና አጣርቶ የመወሰን ስልጣን በህግ የተሰጠውና ከፍ/ቤት ውጪ ያለ የዳኝነት አካል ስለመሆኑ • ውሣኔውን ለማስፈፀምም አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚችልና የሚሰጠውን ትዕዛዝ ለማስፈፀምም ማንኛውም የመንግስት አካል ተገቢውን ትብብር ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 110/87 አንቀጽ 74/ሐ/ 7 4 /ሐ/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371/1/ አዋጅ ቁ. 146/91 አንቀጽ 26/2/ 28/2/	63627	ሼህ አሸራቅ ሰይድ እና የቡታጅራ ከተማ ቀበሌ 02 አስተዳደር	ሐምሌ 14/2003	467
127.	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) አዋጅን በመተላለፍ የሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮችን ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 52/4/ /5/ 41/2/ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 96 አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 49 የወንጀል ህግ ቁ. 349/1/	59723	አብዱልፈታህ መሐመድ እና ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት	ሰኔ 16/2003	471
128.	• የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በሚመለከት የሚነሳውን ክርክር የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ • ከንግድ ምልክት ጋር በተያያዘ አንድ ድርጊት ያልተገባ የንግድ ውድድር ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/2/ /ሀ/, 11, 15 አዋጅ ቁ. 501/98 የንግድ ህግ ቁ. 133	55162	ዩኒሊቭር ፒ.ኤል.ሲ./ፖርት ሰንላይት ሚራል ማርሲ ሳይድ እና ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻ እና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	የካቲት 22/2003	473
129.	• አንድን ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ለሌላ የዳኝነት አካል ከሆነ ፍ/ቤቶች ጉዳዮን የማየት ስልጣን የማይኖራቸው ስለመሆኑ • የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በሚል በኤጀንሲው የተረጋገጠ ጉዳይን ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለሌላ የዳኝነት አካል የተሰጠ ነው በሚል ክርክር እስካልቀረበ ድረስ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆናቸው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1//ለ/, 9/2/, 244/3/ እና 328/3/ አዋጅ ቁ. 110/87	37964	እነ አቶ መሐመድ ሁሴን የእነ አቶ መሐመድ ሁሴን ወራሾች /ሦስት ሰዎች/ እና እነ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ /ሁለት ሰዎች/	ጥር 27/2003	476

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 47/67				
130.	• በአስተዳደራዊ ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ እንዲያገኙ በህግ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን በተመለከተ ፍ/ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ • የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ከሥራ የተሰናበተ ሰራተኛ በየትኛውም የፍርድ አካል ውሣኔ ወደ ሥራ የመመለስ መብት የማይኖረው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 578/2000 አንቀጽ 19/1/ /ለ/ ደንብ ቁ. 155/2000 አንቀጽ 37/1/ /2/	51790	እነ ወልዳይ ዘሩ /ስልሳ አንድ ሰዎች/ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ህግ	ግንቦት 16/2003	482
131.	• የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ያልተገባ የንግድ ውድድርን በተመለከተ የሚነሳ ክርክርን የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ • የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/2/ /ሀ/, 3, 15 አዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 49	47682	አም.ኤ ሸሪፍ ኃ.የተ.የግ.ማህበር እና ታደሰ ኃ.የተ.የግ.ማህበር	መጋቢት 06/2003	486
	የንግድ ህግ				**409**
132.	በቼክ ላይ የተፃፈለትን ገንዘብ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ክፍያ ያልጠየቀበት ሰው ወይም በይዞታው እያለ የታገደበት እንደሆነ ይህንኑ ቼክ እንደ ተራ ሰነድ በማስረጃነት በማቅረብ ያላግባብ የመበልፀግ ክስ ሊመሰርት የሚችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 799	40173	አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ አብዱልቃድር ጁሃር	ጥቅምት 05/2003	491
133.	የሐዋላ ወረቀት በይርጋ ስለሚታገድበት አግባብ የንግድ ህግ ቁ. 817/1/ /2/, 825	48242	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ቦጋለ መስቀሌ /ሁለት ሰዎች/	ጥቅምት 04/2003	496
134.	የአክስዮን ማህበር መሥራቾችና የአክሲዮን ድርሻ መብት ጋር በተያያዘ በሚቀርብ አቤቱታ ላይ የንግድ ህግ ቁ. 416/2/ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 416/2/	52269	እነ አቶ ከድር ሀድ ሁሴን /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ጁሀር አልይ	ጥቅምት 17/2003	499
135.	• ቼክ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የፍትሐብሔር ክስ ለቼኩ መፃፍ /መውጣት/ ምክንያት ከሆነው ውል ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባ ስለመሆኑ • ውልን መሠረት በማድረግ የተፃፈ ቼክ ሌላው ወገን የውል ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም በሚል ምክንያት ብቻ ቼኩን የፃፈው ወገን በቼኩ ከመጠየቅ ነፃ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ሕግ ቁጥር 717	55077	ወ/ሮ ጥሩወርቅ ዘገኑ እና አቶ ግደይ አብርሃ	ህዳር 28/2003	501
136.	በባህር ላይ በሚደረግ የዕቃ ማጓጓዝ ለደረሰ ጉዳት የሚከፈል የጉዳት ካሣ አወሳሰን የባህር ህግ ቁ. 198/1/ /3/	52667	ኒያላ ኢንሹራንስ አክስዮን	ታህሳስ 12/2003	503

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ማህበር እና የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ		
137.	• የአክስዮን ማህበር አባል በመሆን የሚገኝ መብትና ጥቅም ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችልበት አግባብ • ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለአክሲዮን የሆነ ሰው ላለበት የግል ዕዳ አክሲዮኖቹ /በወቅቱ የገበያ ዋጋ/ ተሸጠው እንዲከፈል ለማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 522-524	57288	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አሸብር ታደሰ /አምስት ሠዎች/	መጋቢት 19/2003	506
138.	በባህር ላይ በሚደረግ የዕቃ ማጓጓዝ ለሚደርስ ጉዳት የአጓጓዥ የኃላፊነት አድማስ የባህር ህግ ቁ. 196, 138, 205, 197, 180/3/	56480	የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሰኔ 14/2003	512
139.	• የአክስዮን ማህበር ወይም የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ድርጅቱ የሚያገበት ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ በድርጅቱ ስም በሚያወጣው/ በሚሰጠው/ ቼክ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ • የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ በንግድ ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ወይም የኩባንያውን መተዳደሪያ ደንብ በመጣስ መስራቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ከድርጅቱ ጋር በአንድነት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በተናጠል ሊጠየቅ ስለመቻሉ የንግድ ህግ ቁ. 530	57932	ተክሉ ካሣ ገብረየስ እና ማርኮ ባርዚ	ሰኔ 30/2003	516
140.	የንግድና ኢንዲስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ሥራ ፈቃድ ለመስጠት የቀረበው የንግድ ስም ቀደም ሲል ከተመዘገቡ የንግድ ስሞች ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች አለመሆኑን እንዲሁም ለመልካም ጠባይ ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 16/2/ 14 20 አዋጅ ቁ. 376/96 የንግድ ህግ ቁ. 137,138	58931	የንግድና ኢንዲስትሪ ሚኒስቴር እና ታይገር ሎጀስቲክ እና የንብረት ጥበቃ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሐምሌ 15/2003	518
141.	• ከቼክ ጋር በተያያዘ "የግል ግንኙነት" በሚል የተቀመጠው ሀረግ ሊተረጎም የሚችልበት አግባብ • በቼክ የሚገደዱ ሰዎች ላይ አውጭው ክስ ለማቅረብ የሚችለው ቼኩ ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ • በቼክ በተከሰሰና ለነዱን ይዞ በመጣው ሰው መካከል ያለን "የግል ግንኙነት" በመቃወሚያነት ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ • ቼክ የሚሰጥበት ምክንያት በሰጪውና በተቀባዩ የሚወሰን እንጂ በህጉ የተዘረዘረ ባለመሆኑ ቼኩን የፃፈው ሰው ቼኩን የሰጠሁት ለዋስትናነት ነው በሚል ቼኩን ይዞ በመጣው ሰው ላይ "የግል ግንኙነትን" መሠረት በማድረግ የሚያቀርበው መቃወሚያ ቼክ በዋስትና ሊሰጥ የማይችል ነው በሚል ውድቅ ሊደረግበት የማይገባ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 717/1/-/3/, 855, 881/1/, /ሀ/, 854, 640,868,752,850,827 - 840	24435	ሀጂ መሃመድ አደም እና አቶ ፍፁም ግርማ	የካቲት 04/2000	521

https://t.me/ethiopianlegalbrief

142.	• ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባል የሆነ ሰው ከአባልነቱ ለመውጣት የሚችልበት ብሎም ማህበሩ ሊመሰረትና ሊፈርስ የሚችልበት አግባብ • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ /ረ/ ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በሽምግልና ስምምነት ከመፋታት ጋር ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብ የንግድ ህግ ቁጥር 510/2/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ /ረ/	50537	ሲ/ር መአዛ ዮሴፍ እና ዶ/ር ዮሴፍ ደነቀው	ግንቦት 02/2003	529
143.	• በንግድ ህጉ ቁጥር 683 "ወኪሎች" በሚል የተመለከተው የእቃ አስተላላፊነት ሥራን ለጥቅም የሚሰሩ ወገኖችን የማያካትት ስለመሆኑ • መድን ሰጪው ክስ ሊያቀርብባቸው የማይችላቸው ወገኖች ከመድን ገቢው ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸውና ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለመድን ገቢው ጥቅም የሚሰሩ ወገኖችን ስለመሆኑ የንግድ ሕግ ቁ. 683/3/	49295	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ የቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን /ሁለት ሰዎች/	መጋቢት 22/2003	535
	አእምሯዊ ንብረት				**543**
144.	የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክት እና የንግድ ስምን አስመልክቶ ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማያዛባና ያልተገባ የንግድ ውድድር እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መሆን ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 329/95 አንቀጽ 10/1/, /2//ሀ/, እና /ሐ/ አዋጅ ቁ. 501/98 አዋጅ ቁ. 320/95 አንቀጽ 6/1/	57179	ኢትዮ ሴራሚክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና እነ የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት /ሁለት ሰዎች/	የካቲት 22/2003	544
145.	• የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በሚሰጣቸው ውሣኔዎች ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ያለው መብት ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ማቅረብ ነው እንጂ የቀጥታ ክስ ማቅረብ ስላለመሆኑ • የፌ/ጠፍ/ቤት ሦስት ዳኞች በሚሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው ትዕዛዝ /ውሣኔ/ አስገዳጅ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/1/ አዋጅ ቁ. 25/88 አዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 6, 17, 36, 49 አዋጅ ቁ. 320/95 አዋጅ ቁ. 410/96	59025	የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረቶች ጽ/ቤት እና አቶ ጥበበ አየለ	ግንቦት 19/2003	549
	ውክልና				554
146.	• አንድ ሰው ለሌላ ሰው በሰጠው ፍፁም የውክልና ስልጣን መሰረት የተከናወነውን ተግባር ለማፍረስና መከራከሪያው ሊያደርገው የሚችለው ወሳዩ ራሱ ስለመሆኑ • የወካይ ወራሾች ወኪሉ የውክልና ስልጣን ወሰኑን ሳያልፍ የሰራውን ተግባር የሚቃወሙበት ህጋዊ መሰረት ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2189/1/ እና /2/	38721	ካፕቴን ዮናስ ሕሉፍ እና እነ አቶ እስጢፋኖስ ኪዳኔ /አራት ሰዎች/	ህዳር 27/2003	555
147.	የውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ቀርቦ ካልተረጋገጠና ካልተመዘገበ በስተቀር ህጋዊ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 334/95 አንቀጽ 5/1//ለ/	59568	አቶ ቴዎድሮ ስተስፋዬእና አቶ ሙሉ አርጌ /ሁለት ሰዎች/	ሚያዝያ 05/2003	561

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ - 14

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

መስከረም 2006 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

ለተመሳሳይ ጉዳዮች በጣም የተራራቁ ውሣኔዎችን በመስጠት ይታይ የነበረውን ችግር በመቅረፍና የውሣኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ የሰበር ውሣኔዎች አስገዳጅ መሆን ከፍተኛ ውጤት አስገኝቷል ማለት ይቻላል። አልፎ አልፎ በውሣኔዎች ጥራትና ስርጭት ሊታዩ የሚችሉ ችግሮች ሥርዓቱ እየተጠናከረ ሲሄድ የሚፈቱ ሲሆን እነዚህን ችግሮች ለማቃለል እኛም ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን፣ ጥረታችን ሊሣካ የሚችለው በውሣኔዎቹ ላይ በሕግ ምሁራንና ባለሙያዎች ገንቢ የሆኑ ትችቶችና አስተያየቶች ሲቀርቡ ነው።

ለሰበር ውሣኔዎች ጥራትም ሆነ ለፍርድ ቤቶች መጠናከር እና በአጠቃላይ ለሥራችን መሻሻል ሊረዱ የሚችሉ አስተያየቶች ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን በድጋሚ መግለጽ እፈልጋለሁ።

የሰበር ውሣኔዎችን ቶሎ ቶሎ ለማሣተም ባደረግነው ጥረት ቅጽ 14ን በአጭር ጊዜ ማሣተም የቻልን ሲሆን ይህን የ2005 ዓ.ም. ውሣኔዎች የያዘውን ቅጽ 14ን ጨምሮ ከዚህ በፊት የታተሙትን ቅዶች በሙሉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረ ገጽ www.fsc.gov.et ላይ ማግኘት እንደሚቻል ማስታወስ እወዳለሁ።

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ2005 ዓ.ም. የሰበር ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አሠሪና ሠራተኛ				1
1.	በአሰሪ ከተደረገ የሥራ ቦታ ዝውውር ጋር በተያያዘ ሠራተኛው ወደነበረበት ሥራ ቦታና መደብ እንዲመለስ በፍ/ቤት ሲወሰን አሰሪው ሠራተኛው የሥራ ዝውውሩ ከመከናወኑ በፊት ይሰራበት ወደነበረበት ቦታና የሥራ መደብ በትክክል መመለስ ያለበት ስለመሆኑ፣	78536	በደሌ ቢራ አክሲዮን ማህበር እና አቶ አልማው ቤዛ	ታህሳስ 5/2005	2
2.	ሠራተኛ ተቀጥሮ የሚሰራበትን አሰሪ ተቋም መልካም ስምና ዝና እንዲሁም ጥቅምና ህልውና አደጋ ላይ በሚጥሉ ተግባራት የሚፈጽመው ጥፋት መጠንና ደረጃ እና የሚወሰድበትን እርምጃ ለመወሰን ሠራተኛው ከሚሰራው የሥራ አይነትና ባህሪ እንዲሁም ከአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መንፈስና ዓላማ አንፃር መታየት ያለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1)(ሸ)(ረ)	77134	ወሰኔ የህክምና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ዶ/ር ክብረወሰን አለማየሁ	ጥቅምት 8/2005	5
3.	የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ ሰው በሌላ የመንግስት ሥራ	72341	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	ህዳር 21/2005	8

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ተቀጥሮ ያለአግባብ የወሰደው የጡረታ አበል እንዲመለስ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር አመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑና የይርጋ ጊዜውም ግለሰቡ በሌላ የመንግስት ሥራ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣ • አንድ የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ መልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግስት ስራ ከተቀጠረ የቅጥሩ ሁኔታ በቋሚነትም ይሁን በጊዜያዊነት እንዲሁም ደመወዙ ከጡረታ አበሉ ያነሰ ሆነም አልሆነ ከደመወዙና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ ያለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 46(1) (2) አዋጅ ቁ.209/55 አንቀጽ 30(2) የፍ/ብ/ህ/ቁ.1677(1)		እና አቶ ታዬ አበራ		
4.	የሥራ ክርክር ችሎት አንድን ሠራተኛ ያለአግባብ የተሰናበተ ነው በሚል ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ወደኋላ ቀደም ብሎ ካለ ጊዜ ጀምሮ አሰሪው ወደ ሥራ እንዲመልስ በሚል ውሣኔ የሰጠ እንደሆነ ሠራተኛው ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ ውዝፍ ደመወዝ ለማግኘት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ፣	83012	ዝዋይ ሮዝ ድርጅት እና ወ/ሮ ፋንቱ ያሲን	ጥር 14/2005	13
5.	የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ያለው የህግ ባለሙያ በሙያው አገልግሎት ለመስጠት ከ3ኛ ወገን ጋር በሚያደርገው ውል የሚፈጠረው ግንኙነት በእውቀት ሥራ ውል ላይ የተመሠረተ እንጂ ሠራተኛውን እንደ የስራ መሪ ወይም ተቀጣሪ የማያስቆጥረው ስለመሆኑ፡ በአዋጅ ቁ.377/96 የማይገዛ ስለመሆኑ፣	81405	አቶ አህመድ ሲራጅ እና የአወሊያ ዋና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት	ጥር 29/2005	19

https://t.me/ethiopianlegalbrief

6.	አንድ ሠራተኛ መብቱን ለማስከበር በአሰሪው ላይ በፍ/ቤት ክስ መመስረቱ ብቻ ከአሠሪው ጋር ለወደፊት የሻከረ ግንኙነት ይፈጥራል የማያስብልና የስራ ውሉ እንዳይቀጥል ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43(3)	82336	የአብጃታ ሶዳ አሸ አክሲዮን ማህበር እና ማርታ አበበ	ጥር 02/2005	21
7.	ቀደም ሲል ስናገኘው የነበረው የደመወዝ መጠን የተቀነሠ ስለሆነ እንዲስተካከልልን በማለት በሠራተኞች የሚቀርብ ክስ የወል የሥራ ክርክር ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣	78865	የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት እና እነ አቶ ገ/ስላሴ ኃ/ማርያም (ስምንት ሰዎች)	ጥር 28/2005	24
8.	ከሥራ ቅጥር ግንኙነት ጋር በተገናኘ አንድ ሥራ "ቀጣይነት ያለው" ነው ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ • አንድ ሥራ በባህሪው "ቀጣይነት ያለው" ነው ለማለት ስራው ረዘም ላለ ጊዜ መስራቱን ብቻ ሣይሆን የሥራው ባህሪ ከአሠሪው ድርጅት (ተቋም) አይነተኛ ሥራ ጋር የሚሄድና በመደበኛነት የሚከናወን መሆኑን ጭምር ማረጋገጥ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፣	80350	ሸራተን አዲስ እና እነ አቶ ገናናው ከበደ (ሃምሳ አንድ ሰዎች)	ጥቅምት 20/2005	27
9.	የጡረታ መውጫ እድሜ ወሰንን በተመለከተ አሰሪው ከሠራተኛ ማህበር ጋር የሚያደርገው ስምምነት ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው በተመሣሣይ ጉዳይ ለሠራተኛ በህግ ከተደነገገው ይልቅ የህብረት ስምምነቱ የተሻለ (የበለጠ) ጥቅም የሚያስገኝ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 134(2),24(3)	80079	የመቶ አለቃ ጥላሁን ታችበሌ እና ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር	ህዳር 19/2005	33

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 715/2003 አንቀጽ 17(1)				
10.	አንድ ሠራተኛ በባህሪው ቀጣይነት ባለው ሥራ ላይ መቀጠሩ መረጋገጡ ብቻ ሠራተኛው ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ የሚያስቆጥረው ስላለመሆኑ፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24(1)	79853	የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን እና እነ አቶ ጌታቸው ደበበ (14 ሰዎች)	ህዳር 04/2005	36
11.	ሥራና ሰራተኛን ከመምራት እና ከመቆጣጠር ባለፈ በሠራተኛ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድም ሆነ ከሥራ ለማሠናበት ስልጣን በሌለው የቅርብ አለቃ ሠራተኛው ሥራ እንዲለቅ የተነገረ መሆኑ የሥራ ውል ተቋርጧል ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 3(2)(ሐ)	79212	ሮያል ከረሜላ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ወ/ሪት ፀሐይ ብርሀኑ	ጥቅምት 19/2005	40
12.	የሥራ ውል ወይም በሌላ ሠነድ ሠራተኛው ስምምነቱን ባልሰጠበት ሁኔታ አሰሪ የሆነው አካል እህት ድርጅት ወደ ሆነ ተቋም (ድርጅት) ሰራተኛውን አዛውሮ ለማሰራት አሠሪ መብት የሌለው ስለመሆኑ፣	83068	ዲ.ኤች.ገዳ ብርድልብስ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ወ/ሪት ቅድስት ጌታቸው	ታህሳስ 30/2005	43
13.	አንድ ሠራተኛ በሥራው አፈፃፀም ምዘና ደካማ ነው በማለት የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚቻለው ምዘናውን ሠራተኛው በተቀጠረበትና በተመደበበት የሥራ አይነት (መስክ) ላይ በማድረግ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 42, 43(1)	82335	ሆሊ ኤንጀልስ ት/ቤት ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና መ/ር መልካም አለማየሁ	ጥር 01/2005	46

https://t.me/ethiopianlegalbrief

		ውል			50
14.	• በተዋዋይ ወገኖች በተደረገ የጽሁፍ ሰነድ ላይ የሚገኝ የስምምነት ቃል እንዲሁም በሰነድ ላይ ስለተመለከተው (ስለተፃፈው) ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ውሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው በሚል ለመደምደም የሚቻለው እንደ ውለታው አይነት የጽሁፉ ውል አደራረግን በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በተሟላ ሁኔታ የተዘጋጀና የያዘ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ •የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ውሉ በውል አዋዋይ ፊት በህጉ አግባብ ባልተደረገበት ሁኔታ በውሉ ላይ የሠፈሩት ማናቸውም የውል ቃሎች ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዳሉ የሚታመኑና በማናቸውም የሰው ምስክርነት ቃል ማስተካከል አይቻልም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ •አንድ ውል በህግ ፊት የፀና ነው እንዲባል በህግ ውሉ የሚደረግበትን አግባብ በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በተመለከተ የተደረገ ካልሆነ በቀር ውሉን መሠረት በማድረግ እንደውሉ ይፈፀምልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ2005(1),1678(ሐ),1719(2,1723)	78398	እነ አቶ ሽፈራው ደጀኔ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሲሳይ አበቡ	ጥቅምት 19/2005	51
15.	•የአላቂ ነገር ብድር ውል ጋር በተገናኘ፣ የመመለሻ ጊዜው በግልጽ ተለይቶ የተሰጠን የገንዘብ ብድር በተመለከተ አበዳሪው በውሉ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላ ተበዳሪው የብድሩን	74950	ወ/ሮ ዙብዳ ኑረ ኬርሰማ እና ወ/ሮ ሚሊዮን ዳግም ሙሴ	ህዳር 5/2005	55

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ገንዘብ እንዲመለስ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ፣ •የብድሩ ገንዘብ መክፈያ ጊዜው በተወሰነ የብድር ውል ስምምነት ገንዘብ የተበደረ ወገን የመክፈያ ጊዜው ካለፈበት (ካበቃበት) ጊዜ ጀምሮ ወለድ ለመክፈል ስምምነት ያልተደረገ ቢሆንም፣ በድሩን ከነ ህጋዊ ወለዱ ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2482(2)(3),2483, 2489(1),1676, 2478		(አራት ሰዎች)		
16.	• ከውል አመሰራረትና መቋቋም ጋር በተገናኘ ዝምታ በመርህ ደረጃ ውልን እንደመቀበል ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑና አንድ ውል፣ ተሻሽሏል ለማለት የሚቻለው ማሻሻያው አስቀድሞ በተደረገው የአፃፃፍ ስርዓት አይነት የተከናወነ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ • የግልግል ጉባኤ አንድን ጉዳይ በማየት የዳኝነት መፍትሔ ሊሰጥ የሚችለው ተከራካሪ ወገኖች ከተስማሙበትና የሚፀና ወይም ዋጋ ያለው ግዴታ መኖሩን መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1682,1683,1684,1722,2001 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 356(ሀ)	63063	ኢትዮ ቴሌኮም እና ፒቲኢ ኢንተርናሽናል ኢንኮፖሬትድ	ህዳር 03/2005	58
17.	ከውርስ ሽያጭና ከስጦታ ውል የመነጨን የባለቤትነት መብት አስመልክቶ በሚነሣ የንብረት ክርክር የይርጋ ጉዳይ በተነሣ ጊዜ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ለጉዳዩቹ አግባብነትና ተፈፃሚነት ባለው የህግ ክፍል እና የህግ ይዘት	71537	እነ ወ/ሮ የሻረግ ከበደ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን	ታህሳስ 02/2005	68

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ				
18.	የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ አመዘጋገብ ጋር በተያየዘ በተፈፀመ ስህተት ንብረቱን በመያዣ የያዘው ወገን የሚደርስበትን ጉዳትና ኪሣራ ኃላፊነቱን በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመወጣት ስህተቱን የፈፀመው የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ጉዳትና ኪሣራውን በመያዣ በተያዘው ንብረት ዋጋ መጠን ለመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1640(2), 3052, 3053(1),3081	75743	የዳንግላ ማዘጋጃ ቤት ፍትህ ቢሮ፣ ዐ/ህግ እና እነ የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 17/2005	72
19.	ከዋስትና ውል ጋር በተገናኘ ዋስ የሆነ ወገን በውሉ ላይ የተመለከተውን ፊርማ የእርሱ አለመሆኑን ወይም የውሉን ቃል በተመለከተ በመካድ በግልጽ ባልተከራከረበት ሁኔታ ውሉ በሁለት ምስክር ፊት የተደረገ አይደለም በሚል የሚቀርብ ክርክር የዋሱን ግዴታ ተፈፀሚነት የሚያስቀር ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1727(2) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.83,235	79907	ልዩ የገንዘብ እገዛ ተቋም እና እነ ወ/ሮ የወይንሐረግ ትዕዛዙ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 02/2005	76
20.	ገቢ ለማስገኘት በተዘጋጀ ልዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን በተደረገ ጨረታ ተሣታፊ በመሆን የጨረታውን ገንዘብ በመክፈል መሬት ተረክቦ ለልማት ለማዋል በሚል ጨረታው ተወዳድሮ የጨረታው አሸናፊ የሆነ ወገን ጨረታውን ካዘጋጀው አካል ጋር የውል ስምምነት እንዳደረገ የሚቆጠር በመሆኑ በጨረታ ያሸነፈበትን የገንዘብ መጠን ለአዘጋጁ ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ፤ህ/ቁ.1771(1),1688(2),1757	76825	ጭላሎ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የአዳማ ከተማ የባኩ ሸነን ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት	ጥር 14/2005	79

https://t.me/ethiopianlegalbrief

21.	በብድር የሚሰጥ ገንዘብ ላይ ተዋዋይ ወገኖች ሊያቋቁሙት ስለሚችሉት የወለድ ምጣኔ (መጠን)፣ የውል ግዴታውን ያልፈፀመ ወይም ያዘገየ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ስለሚከፍለው የኪሣራ መጠን፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1803(2),1790(2),1800,2479(3),2488,2489	81857	አቶ አብዱልቃድር ጁሐር እና አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ጥር 13/2005	82
22.	ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች በመካከላቸው የሚነሣን አለመግባባት (ክርክር) በግልግል ዳኝነት እንዲያይ በሚል በውሉ የተሰየመ አካል በከሰመ ጊዜ ተዋዋዮች በጋራ ስምምነት ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት የሚያይ አዲስ አካል ለመሰየም ከሚችሉ በቀር አስቀድሞ የተሰየመው አካል በመክሰሙ ምክንያት ፍ/ቤት ጉዳዩን በግልግል ለማየት የሚችል አካል ለመሰየም ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.3336(1),3328(2),3337,3331,3325-3344,3329	80722	የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፓርትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት እና ዲ ኤም ሲ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር	ጥር 01/2005	86
23.	• ከግንባታ ሥራ ውል ጋር በተገናኘ የሚከፈል ክፍያ የሥራው ባለቤት የሆነው አካል በግንባታው ሂደት የሥራ ትዕዛዞችን እየሰጠ የሥራውን አካሄድ የመወሰንና ሥራውን በሚፈቅደው አይነት እንዲፈፀም የሥራ ተቋራጩን የማዘዝ ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ የሥራ ተቋራጩ ከሥራው ባለቤት ጋር የተደረገውን የግንባታ ሥራ ውል፣ በሥራው ባለቤት በተሰጡት ፕላኖች፣ ግንባታ ዲዛይን አይነቶችና የዋጋና የሥራ ማስታወቂያ መሠረት ግንባታውን የማካሄድ ግዴታ ያለበት በመሆኑ የሥራው ባለቤት በግንባታው ሥራ ውል ሰነዱ ላይ ከተመለከተው ክፍያ ውጪ	71972	አቶ ካሣሁን አያሌው እና የምስራቅ ጎጃም ጎዛምን ወረዳ ጤና ጽ/ቤት	ጥር 1/2005	90

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በተጨማሪነት በባለቤቱ ፈቃድና ትዕዛዞች መሠረት ለተሠሩ ሥራዎች ክፍያ ለመክፈል አልገደድም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በህጉ አግባብ በባለቤቱ የተሰጡ ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዞች የሥራ ውሉ አካል ተደረገው የሚወሰዱ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.3244,3225,(1)(2),3152(1),3266(1),3263,3265(3)				
24.	በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት ከወጣው መመሪያ ቁ.3/2004 አፈፃፀምጋር በተገናኘ የንግድ ቤቱን በማከራየት ከሚያገኙት ገቢ ውጪ ሌላ ገቢ የሌለውና በእድሜ አዛውንት የሆነ ተከራይ የኪራይ ውል ሊቋረጥ የማይገባ ስለመሆኑ፣ መመሪያ ቁ.3/2004 አንቀጽ 6(1)	83448	እነ ወ/ሮ ሙሉወርቅ ኃ/ገብርኤል (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሪት ጽጌ መብራቱ	ጥር 30/2005	96
25.	በአንድ ውል የተመለከተን እዳ ለማረጋገጥ ሲባል አዲስ ሰነድ በተዋዋይ ወገኖች የማደራጀት ተግባር የውል መተካት አድራጐት ነው ለማለት የሚቻለው በሁለተኛው ውል በግልጽ የተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ በባህር ላይ የሚደረግ የማጓጓዣ ውልን አስመልክቶ አጓዡ ለውሉ ምክንያት የሆነው እቃ (ንብረት) ጋር በተያያዘ የሚያቀርበው አቤቱታ ዕቃውን ከተረከበበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በስተቀር በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ፣ የባህር ህግ ቁ.146,203 የፍ/ብ/ህ/ቁ.1826,1828,1829(ሀ)	80642	የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት እና ባርጉባ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ታህሳስ 02/2005	102

https://t.me/ethiopianlegalbrief

26.	አንድ ውል የአስተዳደር ውል ነው ለማለት በህግ ወይም በተዋዋይ ወገኖች ግልጽ በሆነ ቃል የአስተዳደር መ/ቤት ውል ነው የተባለ እንደሆነ ወይም ደግሞ ተዋዋዮቹ ውል ያደረጉበት ጉዳይ ከህዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር ተያያዥና ለሥራ ውሉ አፈፃፀም የአስተዳደር አካልን (ፍ/ቤትን) ተካፋይነት ያለማቋረጥ የሚጠይቅ መሆኑን እንዲሁም በአጠቃላይ የውሉን አይነትና ባህሪ፣ የውለታውን አይነተኛ ጉዳይ ብሎም የተዋዋዮችን ማንነት መመልከት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.3132 አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(መ)	80464	ወይራ እንጨትና ብረት ሥራ ኃ/የተ/የሕብረት ሥራ ማህበር እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የንግድና ኢንዲስትሪ ልማት ቢሮ	ታህሳስ 16/2005	106
27.	• የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አስር ዓመት ድረስ ነው በሚል የተደነገገው ድንጋጌ የይርጋ የጊዜ ገደብን የሚደነግግ ሣይሆን የመያዣ ውሉ ቀሪ የሚሆንበት ወይም በህግ ውድቅ የሚደረግበት (Lapse of Mortgage Right) ስለመሆኑ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘ ባንክ በመያዣው ላይ ያለው መብቱ በይርጋ ቀሪ የሚሆነው የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ አስር ዓመት ከማለፉ በፊት በመያዣ መብቱ መገልገል ያልጀመረ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 (1)(3)	78444	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ ጥጋቡ ተፈራ	ጥቅምት 22/2005	109
28.	•በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውል ባለመፈፀሙ ምክንያት የጉዳት ኪሣራ እንዲከፈል በሚል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በውሉ	69797	ወ/ሮ ሂላላ ሱሌማን እና	ታህሳስ 04/2005	113

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ለዚሁ ዓላማ ተዋዋዮቹ ካመለከቱት የገንዘብ መጠን በላይ እንዲከፍል ለማስገደድ የማይቻል ስለመሆኑ፣ •የመልካም ሥራ አፈፃፀም ቦንድ መሰረታዊ ዓላማ በውል የተመለከተው ጉዳይ እንደውሉ ስለመፈፀሙ (የሚፈፀም ስለመሆኑ) ለማረጋገጥ ስለመሆኑ፣ •አንድን ዕቃ ማቅረብ ጋር በተያያዘ የተደረገ ውልን አስመልክቶ በአቅራቢው በኩል ከእቃው ዋጋ ጋር በተገናኘ በመንግስት የታወቀ የዋጋ ማሸበት መከሰቱ አቅራቢው ውሉን ሙሉ ለሙሉ ለማቋረጥ የሚያስችለው በቂ ምክንያት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3183(2),3188(1),1731,1734,1732,1889		ጎንደር ዩኒቨርስቲ		
የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት					**120**
29.	አንድ ለእዳ መክፈያነት በአፈፃፀም በጨረታ እንዲሸጥ በተደረገ ንብረት ጨረታ ላይ በመካፈል የጨረታው አሸናፊ ከሆነ በኋላ የጨረታ ሽያጩን ለመፈፀም ያልቻለ ወገን ንብረቱ በቀጣይ በወጣ ጨረታ ቀርቦ ሲሸጥ የተገኘው የሽያጭ ዋጋ ዝቅተኛ የሆነ እንደሆነ የመጀመሪያው ጨረታ አሸናፊ ለተከሰተው የዋጋ ልዩነት ለፍርድ ባለዕዳው በካሣ መልክ እንዲከፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 429	72017	አቶ ጉታ ኤጀታ እና አቶ መሀመድ ረዲ	ጥቅምት 20/2005	121
30.	• በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ተቋማት (ወገኖች) በድህ ደንብ ዳኝነት ሳይከፍል በፍ/ቤት ለመስተናገድ የሚያቀርቡት	79555	ቤተልሄም ፋርማሲ ቲዩካል ኃ/የተ/የግል ማህበር	ታህሳስ 02/2005	124

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ጥያቄ ተቋሙ ከሚገኝበት የገንዘብ አቋም አኳያ ተገናዝቦ መታየት ያለበት ስለመሆኑና ተቋሙ የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም (Financial status) ለመለየት ተቀባይነት ስለሚኖረው የማስረጃ አይነት፣ • ለዳኝነት የሚከፈለውን ገንዘብ ለመክፈል አልችልም በሚል በድሀ ደንብ ለመስተናገድ የህግ ሰውነት የተሰጠው ተቋም የሚያቀርበው አቤቱታ ሊስተናገድ ስለሚችልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 467 የንግድ ህግ		እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ		
31.	• በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43 መሠረት ወደ ክርክር እንዲገባ የተደረገ 3ኛ ወገን በክርክሩ ሂደት ሊያነሣ ስለሚችለው የክርክር አይነትና አድማስ፣ • 3ኛው ወገን ሊያነሣ የሚችላቸው የክርክር ፈርጆች በአንድ በኩል ከተከሣሽ ጋር ሆኖ ድርሻ ክፍያ ወይም ስለተከሣሽ ሆኖ የካሣ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተቀብሎ በተከሣሽ እግር ተተክቶ ተከሣሽ ለከሣሽ ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን፣ ኃላፊነት አለበት የሚባል ቢሆን እንኳን ሊከፈል የሚገባው የካሣ ክፍያ መጠን ላይ ከከሣሽ ጋር ንጽጽር በማድረግ መሟገት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድርሻ ወይም ካሣ ለመክፈል ለተከሣሽ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መከራከር ስለመሆናቸው፡፡ • 3ኛ ወገን ጣልቃ ገብ በክርክር ሂደቱ መሟገት የሚችለው ከተከሣሽ ጋር ብቻ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣	79465	ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ እና እነ አቶ አገኘው ገረመው (ሁለት ሰዎች)	ጥር 14/2005	126

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 አስፈላጊነት ተከታታይ ክስ ሳይኖር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በአንድነት እንዲታዩ በማድረግ የጎላፊነት መጠኑን እንዲሁም ከፋዩን ወገን በመለየት የመጨረሻ እልባት ለመስጠት ስለመሆኑ፣ •በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 መሠረት ጣልቃ የሚገባ ወገን ከመነሻውም ከተከሳሹ ጋር የህግ ወይም የውል ግንኙነት የለኝም በማለት ክርክር ያቀረበ እንደሆነ በመካሄድ ላይ ባለው ክርክር ተሣታፊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የማይኖር ስለመሆኑና ይህን መሰል ክርክር ራሱን በቻለ ሌላ መዝገብ ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43(1),76 የፍ/ብ/ህ/ቁ.1896,1897,1908,1909 የንግድ ህግ ቁ.687,688,683				
32.	የወጪና ኪሣራ ክፍያ ጉዳይ ሊስተናገድ ሊወሰን የሚገባው በዋናው ጉዳይ ፍርድ (ውሣኔ) በተሰጠበት መዝገብ ስለመሆኑ፣ • ወጪና ኪሣራ ክፍያን በተመለከተ ማን መክፈል እንዳለበት በዋናው ጉዳይ ላይ ተለይቶ ከተወሰነ በኋላ ምን ያህል መክፈል እንዳለበት በተመለከተ ደግሞ ዋናው ፍርድ ባረፈበት መዝገብ የወጪና ኪሣራ ዝርዝር ቀርቦ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ስለቀረበው የወጪና ኪሣራ አስፈላጊነት ስለመጠኑ እና በእርግጥም ወጪና ኪሣራ ስለመውጣቱ በተመለከተ የበኩሉን ክርክር ካቀረበ በኋላ የወጪና ኪሣራ ልኩ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣	83701	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ህንደያ እንድሪስ ወኪል አብዲ ዓሊ	ጥር 27/2005	129

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 183, 378, 462-464				
33.	አንድን ክርክር ለማስረዳት የቀረበን ማስረጃ ህጋዊነት አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክር ሊቀርብና ታይቶ ሊወሰን የሚገባው በዚያው ዋናው ጉዳይ በቀረበበት ፍ/ቤት ስለመሆኑ፣	74890	ወ/ሮ ሚስጢር ሰለሞን እና እነ አቶ ፍቃዱ ካሣሁን (አምስት ሰዎች)	ጥር 30/2005	131
34.	አንድ መዝገብ ላይ የተከሰሱ ሰዎች የኃላፊነት ምንጩ ከተለያየ የህግ ማዕቀፍ (ክፍል) በሆነ ጊዜ አንደኛው ወገን የተነሣው የይርጋ ክርክር በሌላኛው ወገን እንደተነሣ የማይቆጠር ስለመሆኑ፣ በአንድ ክስ (መዝገብ) ተጣምረው በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊነት አለባችሁ ተብለው ከተከሰሱ ወገኖች መካከል አንደኛው ወገን የሚያነሣው የይርጋ መቃወሚያ ያለቅድመ ሁኔታ በሌላኛው ተጣምሮ የተከሰሰው ወገን ላይ ተፈፃሚነት አለው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ • በፍ/ብሔር ጉዳይ የአንድነትና የነጣላ ኃላፊነት ከተለያዩ የህግ ክፍሎች እና ከተለያዩ ምክንያቶች ሊመነጭ የሚችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1852 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.244(3),36	80723	አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር እና እነ ዋቅቶሉ አብደሳ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 29/2005	134
35.	• ለተሰጠ የብድር ገንዘብ አመላለስ በመያዣ የተያዘ በኪሣራ የፈረሰ ማህበር (ድርጅት) ንብረት በሀራጁ ጨረታ የተሸጠ በመሆኑ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ እና ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን ለማየት	84353	ጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን አ/ማህበር ሒሣብ አጣሪ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና	ጥር 02/2005	138

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣ በመያዣ የተያዘውን ንብረት በባንኩ በሀራጅ የተሸጠ በመሆኑ በባለዕዳው በኩል ቢሸጥ የተሻለ ዋጋ ያስገኝ ስለነበረ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ •በህግ የተቋቋመ ባንክ በብድር የሰጠው ገንዘብ በአዋጅ ቁ.97/90 እና 216/92 መሠረት አስቀድሞ ለብድሩ አመላለስ ዋስትና ይሆን ዘንድ ከያዛቸው መያዣዎች መካከል አንዱን በመምረጥ በሐራጅ ሊሸጥ ይገባል፣ ለመሸጥ የተንቀሳቀሰበትን የመያዣ ንብረት ከመሸጥ ድርጊት ይታቀብ ይህም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ይሰጥልን በሚል የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ህግን ባለመከተል የፈፀመው ስህተት ቢኖርና በባለዕዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ግን ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባለዕዳው ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ እና ፍ/ቤቶችም ሀራጁን ለማስቆም ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣ የሰበር ችሎት የሚሰጠው አስገዳጅነት ያለው የህግ ትርጉም አንድ ክርክር የቀረበበት ጉዳይ (ድርጊት) ከተፈፀመ በኋላ ስለሆነ የተሰጠው የህግ ትርጉም በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394-449,224 አዋጅ ቁ.97/90 አንቀጽ 3,4		ወጋገን ባንክ አ/ማህበር		

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ.216/92 አዋጅ ቁ.98/90 አዋጅ ቁ.2584				
36.	• አንድ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ብይን መስጠቱ ፍርዱ ለከሣሽ በሚጠቅም መልኩ (መንገድ) የመወሰኑን ሁኔታ በአስገዳጅነት የሚያስከትል ነው ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣ • የማህበር ሊቀመንበርን ክስልጣን ለማንሳት ስለሚቻልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 70(ሀ)	82427	ዩኒስ ቡራሌ ሲጋል የራይስ ጫት ላኪዎች ማህበር እና አቶ አብዲ አልሚ መሐመድ	ጥር 27/2005	144
የንግድ ሕግ					**147**
37.	• የእሽሙር ማህበር ህጋዊ ሰውነት የሌለው እንዲሁም በጽሁፍ መረጋገጥና ሌሎች የንግድ ማህበሮችን በተመለከተ የተደነገጉት የማስታወቅና የማስመዝገብ ሥርዓቶች የማይፈፀምበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ የእሽሙር ማህበርን አስመልክቶ ማህበሩ እንዲፈረስ በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዬችን አስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • የእሽሙር ማህበር የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያደርገው በሽሪኮቹ ስም ስለመሆኑና ሽሪኮቹም እንደተራ ተዋዋይ ወገኖች የሚታዩ ስለመሆናቸው የንግድ ህግ ቁ. 212(1),272	76394	አቶ ወርቁ ወ/ዓዲቅ እና እነ የአቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ወራሾች (ሰባት ሰዎች)	ህዳር 18/2005	148
38.	•አንድ የንግድ ማህበር (ድርጅት) የሚጨበጥና የማይጨበጥ	80599	ጀሽዋ ኢነድ ካሌቤ ኃ/የተ/የግል	ጥር 15/2005	151

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	እንዲሁም የሚንቀሣቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት መብቶች ምን ምን እንደሆኑ በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ስለመሆኑ • አንድ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ሥራውን የሚያከናውንበት የንግድ ቦታ ኪራይ መብት የማህበሩ ህልውና ጋር የሚያያዝ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ •የንግድ ድርጅቱ የፈረሰ ቢሆንም የንግድ ሥራውን ሲያከናውንበት የነበረውን ቦታ በሌላ ጉዳይ በፍርድ እንዲለቅ በተወሰነ ጊዜ የማህበሩ ሒሳብ ተጣርቶ አለመጠናቀቅ ቦታውን ላለማስለቀቅ ምክንያት ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ፣		ማህበር እና ወ/ሮ እንቁጣጣሽ አሰፋ		
ቤተሠብ					**155**
39.	በአንድ ቦታ ከተደረገ በኋላ በሌላ ጊዜ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ እንዲረጋገጥና ማህተም እንዲደረግበት የተደረገ የኑዛዜ ሰነድ በህጉ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት እንደተደረገ ኑዛዜ የማይቆጠር ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.881,882	74734	ወ/ሮ ትዕግስት ሽባባው እና እነ እህት አለማው ወርቁ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 20/20085	156
40.	የኮንዶሚኒየም ቤትን በጋብቻ ወቅት እያሉ የደረሳቸው ባልና ሚስት የቤቱ ቅድመ ክፍያ በጋብቻ ወቅት ከተፈራ የጋራ ሀብት የተከፈለ እንደሆነና ቤቱን ለማሳመርና ለሌሎች ተያያዥ ወጪዎች ከጋራ ሀብቱ ወጪ በማድረግ ጥቅም ላይ በዋለበት ሁኔታ ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ እንደሆነ ቤቱ ለተጋቢዎቹ፣	74451	አቶ ደረጀ ማዘንጊያ እና ወ/ሮ ፍሬህይወት ጴጥሮስ	ጥቅምት 20/2005	160

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሊከፋፈል ስለሚችልበት አግባብ፣ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን ቤተሰብ የመመስረት መብት በመጠቀም ጋብቻ የፈፀሙ ወንዶች እና ሴቶች በጋብቻው አፈፃፀም፣ በጋብቻው ዘመን እንዲሁም በፍቺ ጊዜ እኩል መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ፣ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 35(1)				
41.	• የኑዛዜን ፎርማሊቲና የይዘቱን ህጋዊነት አስመልክቶ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ተቃውሞውን አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ወገን በሌላ ጊዜ በድጋሚ የኑዛዜው ይዘት ጋር በተገናኘ ተናዛዡ ከውርስ ነቅሎናል፣ እንዲሁም ሊደርሰን ከሚገባው ድርሻ ከ1/4ኛ በላይ ጉዳት ደርሶብናል በሚል ኑዛዜው እንዲሻር የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • ኑዛዜ የህጉን ፎርማሊቲ የጠበቀ ነው በሚል በፍ/ቤት መጽደቅ ኑዛዜው መብታችንን ይነካል በማለት ክርክር የሚያቀርቡ ወገኖች ክርክራቸውን ለዳኝነት አካል ከማቅረብ የማይከለክል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.51, 216, 217 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1123	77169	እነ አቶ ተሾመ ገበየሁ እና ወ/ሮ ሊሻንወርቅ ገበየሁ	ጥር 17/2005	163
42.	• የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው ቀደም ሲል ጋብቻ የነበረው እንደሆነ የጠፋው ሰው መመለስ በመጥፋት ውሣኔው የፈረሰውን ጋብቻ እንደገና ተመልሶ ህይወት እንዲዘራ (እንዲፀና) የማድረግ ውጤት አለው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣	74791	ወ/ሮ ውቢት ሕሩይ እና የሀዋሣ ከተማ ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት	ጥር 17/2005	167

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	•በፍ/ቤት የተሰጠ የመጥፋት ውሣኔ መሻር በመጥፋት ውሣኔው መሠረት የፈረሰን ጋብቻ ከፈረሰበት ቀን ጀምሮ (ግለሰቡ ከተመለሰበት ቀን ጀምሮ) መልሶ እንዲቋቋም (እንዲፀና) ለማድረግ የሚያስችል ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.170,171				
43.	አንድ ወራሽ የወራሽነት መብት በሌለው ንብረት ላይ ከህግ ውጪ የወራሽነት ሠርተፍኬት መያዙ በተረጋገጠ ጊዜ ይኸው ማስረጃ እንዲሰረዝ አቤቱታ ሊቀርብ ስለመቻሉ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.998(1)	73247	አቶ ልዑል ኪዳነማርያም እና እነ ሰብለ ኪዳነማርያም (ሶስት ሰዎች)	ጥር 14/2005	171
ጉምሩክ/ግብር/ ታክስ					**174**
44.	• በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቅቆ ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ወይም ወደ ውጪ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ የቀረበ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ • "የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተጠናቀቀ" ማለት ስለሚቻልበት አግባብ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 66(1), 2(17),66(29),66(2)	71070	ተሸአብ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን	መስከረም 21/2005	175
45.	የተሸከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው በተሸከርካሪው የተፈፀመ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ህግን የመጣስ ወንጀል ከራሱ እውቀት ወይም ፈቃድ ወጪ መሆኑን ማስረዳት የቻለ እንደሆነ የተፈፀመው ወንጀል ክብደት እየታየ የገንዘብ መቀጮ ከፍሎ	76976	የጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና አቶ ሊሻን ከተማ ገብሬ	መስከረም 22/2005	178

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ተሸከርካሪው ሊለቀቅለት (ላይወረስ) የሚችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 109(1) የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መመሪያ ቁ.50/2003 አንቀጽ 6(2)				
46.	የውጭ ምንዛሬ ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር ያለህጋዊ እውቅናና ፈቃድ ማስወጣት የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣ የወንጀል ድርጊትን የፈፀምኩት ባለማወቅ ነው በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለውና ህግን አለማወቅ ይቅርታ የማያሰጥ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 99 አዋጅ ቁ. 591/2000 አንቀጽ 20(3) የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22(1) የወንጀል ህግ አንቀጽ 2(2),25,23(2),81(1)(3)	80296	አቶ ሳምሶን መንግስቱ እና የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ጥር 30/2005	180
ንብረት					**184**
47.	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ህጋዊነትና ተቀባይነት ጋር በተናኘ የምስክር ወረቀቱ ሊሰጥ የቻለው የንብረት ባለሀብትነት መብትን ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው እንዴት መተላለፍ እንዳለበት በህጉ የተመለከተውን ደንብና ሥርዓት ሳይከተል ስለሆነ የንብረቱ ባለሀብት ስለመሆን የህግ ግምት መውሰጃ የሆነው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ቀሪ ነው፣ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት	75414	ወ/ሮ ዋሪቱ ቡቡሳ እና እነ የጎልጆታ ከተማ አስተዳደር (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 22/2005	185

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሊረጋገጥ የሚችል የዳኝነት ጥያቄ እንጂ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1195,1196				
48.	• በአንድ ወቅት የነበረን የተገነባ የመንገድ ደረጃ መነሻ (መሠረት) በማድረግ በመንገዱ ግራ ቀኝ አዋሣኝ በሆነ ይዞታ ላይ ተገቢውን ርቀት በመጠበቅ ንብረትን ያፈራ ሰው በሌላ ጊዜ የመንገዱ ደረጃ ከፍ እንዲል በመደረጉ የተነሣ በአዋሣኝ ይዞታው ላይ ግለሰቡ ያፈራቸው ንብረቶች ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ፣ ጉዳት ያደረሰው ወገን ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት (የሚኖርበት) ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 65/1936 አንቀጽ 2(ሀ) አዋጅ ቁ. 66/1936 አንቀጽ 1(ለ) አዋጅ ቁ. 455/1997,የኤ.ፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(8)	75343	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ በላይ ሀሰን	ህዳር 17/2005	188
49.	• አንድ ሰው የሌላ ሰው ንብረት ይዞ ሲጠቀም ከቆየና ንብረቱን በሚጠቀምበት ጊዜ ንብረቱን ከጥፋት ወይም ከብልሽት ለማዳን ሲል ተገቢውን ወጪ ያወጣ እንደሆነ ይኸው ወጪ በህጋዊ ባለሀብቱ እንዲተካለት ለመጠየቅ የሚችለው ወጪው የግድ አስፈላጊ ከሆነና በቅን ልቦና የተደረገ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ • ወጪው በክፉ ልቦና የተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ግን እቃውን (ንብረቱን) እንዲመልስ የተደረገው ሰው እንዲተካለት የጠየቀውን ወጪ መጠን ዳኞች ሊቀንሱት ወይም ጭራሹንም ሊያስቀሩት የሚችሉ ስለመሆኑ፣	81081	ወ/ሮ ፍሬህይወት መብራህቱ ገ/መድህን እና እነ አቶ መብራህቱ ገ/መድህን /ሁለት ሰዎች/	ጥር 13/2005	191

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	•በንብረቱ (እቃው) ላይ የተደረገው ወጪ «በክፉ ልቦና የተደረገ ነው» የሚባለው ወጪው በተደረገበት ጊዜ (ወቅት) ወጪው እንዲተካለት የሚጠይቀው ሰው ንብረቱን (እቃውን) ለባለቤቱ ለመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያወቅ እንደነበር ወይም ማወቅ ይገባው የነበረና ርትዕም ሲያስገድድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2172(1),2171(1),2168,2169				
50.	• የመኪና ሽያጭ ውል መደረጉን (መኖሩን) ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት፣ • የመኪና /ተሸከርካሪ/ ባለሀብትነት (ስመ ሀብት) እንዲተላለፍለት የሚጠይቅ ሰው ሊያቀርባቸው ስለሚገቡና ተቀባይነት ስላላቸው ማስረጃዎች አንድ ግዴታ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ፣ • አከራካሪ ሆኖ የቀረበን አንድ ፍሬ ነገር ማስረዳት ስለሚቻልበት የማስረጃ አይነት አግባብነት ባለው ህግ በተለይ የተቀመጠ ግለጽ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ አቅርቦ ጉዳዩን ለማስረዳት ስለመቻሉ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1186(1),(2),2001(1) ስለ ተሸከርካሪ መለያ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁ.681/2002 አንቀጽ 6(3)(4)	81406	እነ አቶ አህመድ ኢብራሀም (ሁለት ሰዎች) እና አቶ አመሀ ተ/ወይኒ	ጥር 13/2005	195
51.	• የመሬት ባለ ይዞታ የሆነ አርሶ አደር ይዞታውን ላለበት እዳ ለ3ኛ ወገን በመያዣነት ለመስጠት ወይም በስጦታ የቤተሰብ	79394	አቶ አብደላ ኢብራሒም እና	ጥቅምት 06/2005	199

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አባል ላልሆነ ሰው ለማስተላለፍ መብት የሌለው ስለመሆኑ፣ •በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ እና/ወይም የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ ከመነሻው ውጤት የሌለውና ፈራሽ ስለመሆኑ፣ የውሉ መሠረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 130/99 አዋጅ ቁ.89/89 አንቀጽ 2(3) አዋጅ ቁ. 456./97 አንቀጽ 8(2),1)		አቶ ኡሶ አብዲ		
	ከውል ውጭ ኃላፊነት				202
52.	የፌዴራልና የክልል ከተማ አስተዳዳር አካላት የግንባታ ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት የቴሌኮሚኒኬሽን ወይም የኤሌክትሪክ ሀይል አውታር ስለመኖሩ እንዲሁም ፈቃድ ጠያቂው አካልም ግንባታን ከማካሄዱ በፊት በቴሌኮሚኒኬሽንና በኤሌክትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑና በዚህም የተነሳ በቸልተኝነት ግንባታ በማከናወን ጉዳት ያደረሰ ወገን በኃላፊነት የሚጠየቅ ስለመሆኑ፣	77238	ኢትዮ ቴሌኮም እና አቶ ንጉሴ ተፈራ	ህዳር 03/2005	203

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ.464/97 አንቀጽ 3(3) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2027(1),2035(1),2028(1),2091 አዋጅ ቁ.49/89 አንቀጽ 23(1)				
	የዳኝነት ሥልጣን				207
53.	• አንድ ሰው በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለማስወሰን የሚችለው ከህግ የመነጨ መብት ያለው መሆኑን በክሱ ውስጥ በዝርዝር በፍሬ ነገር ደረጃ ማመልከት የቻለ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ • ሀይማኖታዊ (መንፈሣዊ) ትምህርት ለመስጠትና ለማሰልጠን በሚል ከሚቋቋሙ ተቋማት ጋር በተገናኘ በተማሪነት ማን እንደሚመለመል፣ ምን ምን መስፈርቶች ሊሟሉ እንደሚገባ፣ የመሰፈርቶቹ መሟላትና አለመሟላት እንዲሁም በተቋሙ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች ከትምህርት አቀባበል ሂደት ወቅት ሊገልጿቸው ስለሚገቡ የዲሲፕሊን ጉዳዬች ወዘተ በሀይማኖት ተቋማቱ የሚወሰን ስለመሆኑና ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮችን መደበኛ ፍ/ቤቶች አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣ • የግለሰብ ፍትህ የማግኘት መብት በፍ/ቤቶች ተግባራዊ ሊደረግ የሚችለው በፍርድ ሊያልቁ የሚባቸው ጉዳዬችን በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37	77479	የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቅድስት ሥላሴ መንፈሣዊ ኮሌጅ እና አቶ አሰግድ ሣህሉ	ጥቅምት 06/2005	208
54.	•የፌዴሬሽን ምክር ቤት የኢፌዴሪ ህገ መንግስትን ለመተርጉም ባለው ስልጣን ተጠቅሞ የሚሰጠው ውሣኔ	43511	እነ የአቶ ዋሲሁን መኮንን ሚስትና ወራሾች /8 ሰዎች/	ጥቅምት 23/2005	211

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የመጨረሻና ጉዳዩ በሚመለከተታቸው አካላት መከበርና መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ፣ • የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ የሚቀርብለትን አቤቱታ ህጋዊነት መርምሮ በመወሰን ሂደት ከፊል የዳኝነት ስልጣን ያለው አካል (quasi judicial body) እንደመሆኑ መጠን በህገ መንግስቱ የተጠበቁትን ፍትህ የማግኘት፣ የመሰማትና በእኩል ሚዛን የመታየት (የመዳኘት) መብት በሚያስከበር መልኩ ክርክሮችን ሊያስተናግድና ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ፣ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 62(1),37 አዋጅ ቁ. 251/93 አንቀጽ 3(1),56(1) አዋጅ ቁ. 87/86 አንቀጽ 8,9 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337, 336, 339		እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ		
55.	የአቃቤ ህግ ሙያን በሹመት የሚያከናውኑ ሰዎች ጋር በተገናኘ ቅጥር፣ ዝውውርና የደረጃ እድገትን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የተሰጠው አካል የአቃቤያነ ህግ አስተዳደር ጉባኤ ስለመሆኑና መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣ ደንብ ቁ.24/99 አንቀጽ 46(3), 41, 44, 2 (4) አዋጅ 568/2000 አንቀጽ 2(7),3,10(1),4,5 የአ/አ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁ.6/2000 አንቀጽ 2(5)(ሐ)	75034	አዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮ እና አቶ መኮንን ተክሉ	ህዳር 03/2005	216
56.	የፍ/ቤቶች የግዛት ስልጣን በዋነኛነት መሠረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረበት ቦታ ለተከራካሪ	75788	እነ አቶ በረከት ኃ/ኪሮስ (ሶስት ሰዎች)	ህዳር 05/2005	220

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ወገኖች የሚኖረውን አመቺነት ሲሆን የሥረ ነገር ስልጣን መሠረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ይዘት፣ የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ጥቅም ክብደትና መጠን እንዲሁም የጉዳዩን የውስብስብነት ደረጃ ስለመሆኑ፣ ፍርድን የማስፈፀም ጉዳይ በስረ ነገር ክርክር ተረጋግጠው የፍርድ ሀይል ያገኙትን የተከራካሪ ወገኖች መብቶችና ግዴታዎች በሥነ ሥርዓት ህጉ የተደነገገውን የአፈፃፀም ስርዓት ተከትለው እንዲፈፀሙ ከማድረግ ውጪ አዲስ መብትና ግዴታ የሚቋቋምበት ሂደት ስላለመሆኑና የማስፈፀም ስልጣን በመርህ ደረጃ የፍ/ቤቶች የሥረ ነገር ስልጣንን የሚከተል ስለመሆኑ፣ አስፈላጊ እና ተገቢ በሆኑ ሁኔታዎች ሥረ ነገሩን የወሰነ ፍ/ቤት በአፈፃፀም ጉዳዮችን በውክልና የሥረ ነገር ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ሊያስተላልፍ ስለመቻሉ፣ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(2) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371, 372, 9, 10		እና አቶ ጎይቶም ኃ/ኪሮስ		
57.	የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ (የኮንትራት) ሠራተኞች ቅጥር ጋር በተገናኘ በሠራተኛ እና በቀጣሪው መካከል የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ የመደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በቀጥታ ክስም ሆነ በይግባኝ ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 22(3) ,2(1) የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ	81963	አቶ አስፋው ጉደታ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ታህሳስ 03/2005	224

https://t.me/ethiopianlegalbrief

58.	በአዋጅ ቁ. 515/1999 መሠረት የተቋቋመና የሚተዳደር የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች የሚያቀርቡትን ክርክር በተመለከተ ተቋሙ በራሱ ገቢ የሚተዳደር በመሆኑ ምክንያት አዋጅ ቁ. 377/96 ን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን የመደበኛ ፍ/ቤቶች ለማየት ስልጣን አላቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አዋጅ ቁ. 515/99 አዋጅ ቁ. 553/99 አንቀጽ 6(1), 14(2)(ለ) አዋጅ ቁ. 545/99	80005	የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ እና አቶ ቦጋለ ዱንፋ	ጥቅምት 09/2005	226
59.	• የግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ መብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ክርክርን ለማየት ስልጣን ያለው አካል የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ስለመሆኑ፣ • የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የቀረበላቸውን ጉዳይ በህጉ አግባብ ያስተናገዱና ውሣኔ የሰጡ መሆኑን የማረጋገጥና የመቆጣጣር ኃላፊነትና ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.9,231 አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10(22) አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2(1) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 142, 147	83425	አብጀታ ሻላ ሶዳ አክሲዮን ማህበር እና አብጃታ ሶዳ አሸ መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር	ጥር 02/2005	228

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 345/95 አዋጅ ቁ. 209/55 አዋጅ ቁ. 715/2003 ደንብ ቁጥር 202/2003				
	ወንጀል				**233**
60.	በወንጀል ጉዳይ የወንጀል ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር ጋር በተገናኘ ፖሊስ የወንጀል ድርጊቱን ፈጽሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ላይ የሚያደርገው ምርመራ የይርጋ ጊዜውን የሚያቋርጠው ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ.221 106(1), 420(2), 271 (1) (ሠ) 219 (2)	77097	እነ አቶ ሀይላይ ተክሉ (ሁለት ሰዎች) እና የመቀሌ ከተማ ሰሜን ምድብ ዐ/ህግ	ጥቅምት 20/2005	234
61.	• አንድ ተከሳሽ የተከሰሰበትን የወንጀል ክስ ይዘት በሚገባ ተረድቶና አድራጎቱን በተመለከተም እንደቀረበበት የወንጀል ክስ በዝርዝር መፈፀሙን ገልፆ በማመን የእምነት ቃሉን ሰጥቷል በሚል መነሻ በተከሣሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ በአግባቡ ተሰጥቷል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ • ፍ/ቤቶች ተከሣሹ የቀረበበትን ክስ በተመለከተ በድርጊቱ አፈፃፀም ረገድ የገለፀውን ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታ በመዝገብ ላይ ባለማስፈር በደፈናው ክሱን አምኗል በማለት የሚሰጡት የጥፋተኛነት ውሣኔ ተገቢ ስላለመሆኑ፣ የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ.134(1) የወ/ህ/አ.23	77842	አቶ ሳሚ ሁሴን እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ	ታህሳስ 03/2005	237
62.	ተከሳሽ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ	73514	ተስፋዬ ጡምሮ	ህዳር 06/2005	240

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርባቸው ስለሚችላቸው መከራከሪያዎች ተከሳሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት የሚያቀርባቸው መቃወሚያዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130 ላይ የተመለከተቱት ጉዳዬች ጋር ብቻ በተገናኘ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ የማይችልና ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ተፈፃሚ በነበረው ህግ ከተመለከተው የቅጣት ጣሪያ በላይ ሊቀጣ የማይችል ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑና ዳኞች ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ክስ የቀረበበት ድርጊት ወንጀል ስለመሆኑ የሚደነግገው ህግ ፀንቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑን ከተረዱ በማናቸውም ጊዜ አንስተው ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉ ስለመሆኑ፣ ፍ/ቤቶች በዐ/ህግ የቀረበ የወንጀል ክስ በህገ-መንግስቱና በወንጀል ህጉ የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር የተቀመጡ መርሆዎችና ድንጋጌዎችን የሚያሟሉ መሆን አለመሆኑን በመመርመር የመወሰን ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ፣ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 5(2) ,13(1), 22(1) የወ/ህ/አ. (414/96)3,402,419,5(2) የወ/ህ/ቁ.(214/74)		እና የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ		

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት (ICCPR) አንቀጽ 15(1) የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130(2)(1)				
63.	• አንድ የንግድ ድርጅት (ማህበር) የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግንና ማሻሻያውን ተላልፏል በሚል በወንጀል ጥፋተኛ ሊሰኝና ሊቀጣ ስለሚችልበት አግባብ፣ •የህግ ሰውነት የተሰጠው (legal personality) ድርጅት የወንጀል ተካፋይ ሊሆን የሚችልበት አግባብ፣ • የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው ኃላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም ህጋዊ ግዴታን በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ ስለመሆኑና የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተከስሶ የጥፋተኛነትና የቅጣት ወሣኔ እስከተሰጠበት ድርስ ድርጅቱ የወንጀሉ ተካፋይ እንደሆነ የሚቆጠር ስለሆነ ጥፋተኛ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ. 34(1),(2) አዋጅ ቁ. 285/95 አንቀጽ 56(1)	74237	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና አብክለ እንደሻው ጠቅላላ የንግድ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር	ጥቅምት 19/2005	245
64.	ፍ/ቤቶች በወንጀል ረገድ የሚሰጧቸው ማናቸውም ውሣኔ በወ/ህ/አ. 2 የተደነገገውን የህጋዊነት መርህ መሠረት በማድረግ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣	75387	እነ አቶ ወርቁ ፍቃዱ (ሁለት ሰዎች) እና	ጥር 17/2005	249

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ፍ/ቤቶች በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በሚል ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉት በወንጀል ህግ በግልጽ የተደነገገ ድንጋጌ የተመለከተ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ በወንጀል ጉዳይ አንድ ንብረት (ሀብት) እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ሊወሠን የሚችለው ንብረቱ (ሀብቱ) አንድን ሰው ለወንጀል ሥራ እንዲያነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳው ወይም ደግሞ ወንጀሉን ለፈፀመበት ዋጋ እንዲሆነው የተሰጠው ወይም ሊሠጠው የታቀደን ማንኛውም ጥቅም የተመለከተ ንብረት (ሀብት) ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ ወይም ንብረቱ (ሀብቱ) የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም ያገለገለ ወይም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች ጋር የተያያዘ ወይም የተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ. 98,100,140, 2(1) (2)		የቤ/ን/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ህግ		
65.	• በወንጀል ጉዳይ ተከሰሶ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በቅጣት አወሣሠን መመሪያው የተሸፈነ እንደሆነ ቅጣቱ በመመሪያው አግባብ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ • በወ/ህ/አ 539(1)(ሀ) ድንጋጌ ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን ሊቀነስለት የሚገባ ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ. 539(1)(ሀ) የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ቁ.1/2002 አንቀጽ 16(7)	82572	መሪጌታ ፍቅረማርያም ካሴ እና የቤንች ማጂ ዞን		252

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባንክና ኢንሹራንስ					**255**
66.	መድን ሰጪ የሆነ አካል በመድን ውሉ ለተመለከተው አደጋ ብቻ ለመድን ገቢው የመድን ሽፋን ለመስጠት የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁ. 663(1),665(1)	76977	ኒያላ ኢንሹራንስ (አ.ማ) እና እነ አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 07/2005	256
አፈፃፀም					**260**
67.	በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰው ሰው ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ንብረቱ በቅጣት ለመንግስት እንዲወረስ በተወሰነ ጊዜ በአፈፃፀም ደረጃ ከአጥፊው (ወንጀለኛው) ንብረት ውስጥ ለቤተሰቡ ህይወትና መተዳደሪያ ሊውል የሚገባውን ድርሻ ለመወሰን ስለሚቻልበት አግባብ፣ በውርስ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ከተወሰነው የአጥፊው (የወንጀለኛው) ሀብትና ንብረት ውስጥ ለቤተሰቡ ህይወት መተዳደሪያ ሊውል የሚገባው ድርሻ ሊሸፍናቸው የሚገባው የወጪ አይነቶችና መጠናቸው፣ • የአጥፊው (ወንጀለኛው) ጋር ጋብቻ የመሠረተ ሰው እንዲወረስ ከተወሰነው ንብረት ግማሽ ድርሻ የነበረው መሆኑን መሠረት በማድረግ በአፈፃፀም የሚያነሣው የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ጥያቄው እንደ መብት አቤቱታ ሊቀርብበት የማይችል ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 98(ለ)(መ), 98(3) (ለ)	79860	ወ/ሮ ራሔብ መለሰ እና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	ህዳር 06/2005	261
68.	• ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተገናኘ በአንድ በቀረበ የዋና ጉዳይ	81616	ወጋገን ባንክ አ.ማ.	ጥር 15/2005	265

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ክርክር ሒደት የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ንብረት በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ በአፈፃፀም ደረጃ በተጠቃሸ ንብረት ላይ አፈፃፀም እንዲቀጥል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • ቀደም ሲል በዋና ጉዳይ ክርክር በፍ/ቤት ትእዛዝ እንዲታገድ የተደረገ መሆኑ የታወቀ ንብረት ላይ በድጋሚ በተመሳሳይ ንብረት ላይ መብትን ለማስከበር በሚል በሌላ ጊዜ በአፈፃፀም ደረጃ የሚቀርብ ጥያቄ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣		እና እነ ወ/ሮ ሠላማዊት ጥላሁን /ሁለት ሰዎች/		
አእምሯዊ ንብረት					**268**
69.	ባለ ሶስት አውታር (three dimention) ቅርጽ ሥራ ከባለቤቱ ፈቃድና ፍላጐት ውጪ በወረቀት ላይ እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ማድረግ የቅጂ መብት ጥሰት የሚያስከትል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀጽ 34(4)	78856	የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወዳጆችና ቤተሰቦች ማህበር እና አቶ ኤሊያስ አሰጋኸኝ	ታህሳስ 15/2005	269
ልዩ ልዩ					**274**
70.	ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተገናኘ በወንጀል ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ የተጣለበትን ቅጣት ፈጽሞ ያጠናቀቀ ሰው በፍርድ ቤት መሰየም በግለሠቡ የጡረታ መብት ላይ ስለሚኖረው ውጤት በመሰየም ሊገኝ የሚችለው መብት ግለሰቡ ከመሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረውን መብት ሳይሆን ግለሰቡ ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ፊት ሊጠበቅለት የሚገባውን መብት በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣	61221	አቶ አክለ ምህረቱ እና የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	መስከረም 22/2005	275

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የመንግስት ሰራተኛ የነበረና የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሠው በወንጀል ጉዳይ ተከስሶና ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ በፍ/ቤት ቢያንስ የ3 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት የተወሰነበት በመሆኑ የጡረታ መብቱን እንዲያጣ የተደረገ ሠው ከቅጣቱ በኋላ በፍ/ቤት መሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረውን የጡረታ መብቱን መልሶ ለማግኘት የማያስችል ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ. 231,235(1),232 አዋጅ ቁ. 209/55 አዋጅ ቁ. 5/67 አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 52/1/				
71.	ከጡረታ መብት ጋር በተገናኘ በሠራተኞች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ለማየት ስልጣን ያለው አካል የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተቋም ስለመሆኑና በኤጀንሲው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ሠራተኛ ቅሬታውን ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ በፍሬ ነገር ረገድ የመጨረሻ ስለመሆኑና በውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ቅሬታ ያለው ሠራተኛ አቤቱታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቀ. 714/2003 አንቀጽ 56(1) (4), 57	72928	አቶ አበራ ኪዳኔ እና የጋሞ ጎፋ ዞን አርባ ምንጭ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት	ጥቅምት 09/2005	279

https://t.me/ethiopianlegalbrief

72.	ከጡረታ መብት አበል ተጠቃሚነት ጋር በተገናኘ የእድሜ አቆጣጠርና ውጤቱን በተመለከተ የሚቀርብ አቤቱታን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያለው የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተቋም ስለመሆኑና በውሣኔው ቅሬታ ያለው ወገን ለኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ በኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጥ ውሣኔ በፍሬ ነገር ደረጃ የመጨረሻ ስለመሆኑና በውሣኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለው በማለት አቤቱታ ያለው ሠራተኛ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 714/2003 አንቀጽ 4(1),54(3),56(4) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343, 9, 231	80964	የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና እነ አቶ አበረ ቦከን (ሶስት ሠዎች)	ጥቅምት 23/2005	281
73.	የመንግስት ዩኒቨርስቲ መምህራንን በተመለከተ ከዲሲፕሊን ግድፈት ጋር በተገናኘ የሚሰጥ ውሣኔ በአስተዳደር ፍ/ቤት በይግባኝ ሊስተናገድ ስለሚችልበት አግባብ፣ አዋጅ ቁ. 515 /99 አንቀጽ 2(8),22(3),32(3) አዋጅ ቁ. 650/2001 አፀከት 44(ጎ)	78945	ደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ እና መምህር ባዬ ዋናያ የዳ	መስከረም 22/2005	286
74.	በባንክ በመያዣነት የተያዘ ተሽከርካሪ በሌላ በኩል የጉምሩክ ደንብ በመተላለፍ ወንጀል ባለቤቱ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦበት ተሽከርካሪውም በመንግስት እንዲወረስ ውሣኔ የተሰጠበት እንደሆነ በህግ ፊት ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊፈፀም ስለሚገባው ጉዳይ	81215	ወጋገን ባንክ (አ.ማ.) እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን	ጥር 03/2005	290

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በባንክ በመያዣነት የተያዘ ተሸከርካሪ ከመያዣው በኋላ በኮንትሮባንድ ወንጀል ምክንያት ለመንግስት ውርስ እንዲሆን በፍ/ቤት የመጨረሻ ፍርድ ባረፈበት ጊዜ ባለመያዣው በተሸከርካሪው ላይ ያለው የቀዳሚነት መብት እንዲሁም የውርስ ትዕዛዙ (ውሣኔው) ተፈፃሚ ሊደረጉ ስለሚችልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2828, 2857(1), 3059 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 የወንጀል ህግ አንቀጽ 98(1) አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 91(2)				
75.	የሥራ ግዴታን ካለመወጣት ጋር በተገናኘ ሠራተኛ የሆነ ሰው ከአሰሪው የተረከበው ንብረት ላይ ጉዳት እንዲከሰት በማድረጉ ወይም ንብረቱ እንዲጐድል (እንዲጠፋ) በማድረጉ ምክንያት በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠ እንደሆነ በተመሣሣይ ጉዳይ ሠራተኛው በአሰሪው ንብረት ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠን በፍትሐብሔር ሊጠየቅ ስለመቻሉ፣ ከአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሠራተኛው በአሰሪው ንብረት ላይ የደረሰ ጉዳትን በተመለከተ በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ ጉዳት የደረሰበትን ንብረት በተመለከተ በፍትሐብሔር ተጠያቂ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 515 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149	78414	የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እና እነ አቶ ቶላ መገርሣ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 07/2005	295

https://t.me/ethiopianlegalbrief

76.	**አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በህጉ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበስብ ሊፈቀድ የማይችል ስለመሆኑ፡** **አዋጅ ቁ.** 621/2001 **አንቀጽ** 2(2),(3)(4),14(5), 14(2), 6, 90, 111(2), 112,108,110, **ደንብ ቁጥር** 168/2001 **አንቀጽ** 18(3),10(2),36	74036	**የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ እና የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ**	**መስከረም** 23/2005	299

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሥሪና ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 78536

ታህሳስ 05 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መኮንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- በደሌ ቢራ አክሲዮን ማህበር ነገረ ፈጅ አቶ ታዬ ይገዙ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ አልማው ቤዛ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በፍርድ ባለመብት በሆነው በአሁኑ ተጠሪና በፍርድ ባለ እዳ በሆነው በአሁኑ አመልካች መካከል በነበረው የአፈጻጸም ክስ ክርክር የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በመ/ቁ/37192 ያቀረቡትን ክርክር በ29/06/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በመመርመር የሰጠውን ትዕዛዝ የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በማጽናቱ ነው፡፡

የአፈጻጸም ትዕዛዙም የፍርድ ባለመብቱ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ቀደም ሲል የተወሰነ ከመሆኑም በላይ በመ/ቁ. 37299 የፍርድ ባለመብቱ በበደሌ በዕቅድና ምርታማነት አሰራር ማሻሻያ ቡድን አስተባባሪነት መመደቡ አግባብነት ያለው መሆኑን ፍርድ ቤቱ የወሰነ ስለሆነና ውሳኔውም በይግባኝ እስካልተለወጠ ድረስ የስራ መደቡን፣ ደመወዝ፣ የሥራ ቦታ እና የስራ መጀመሪያ ቀን በመጥቀስ የስራ ምደባ ደብዳቤ የፍርድ ባለዕዳው ሊሰጥ ይገባል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት ለዚህ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 36405 በቀን 17/08/2003 ዓ.ም. ተጠሪው የ6 ወር ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ የወሰነውን የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁ. 69498 ጥር 02/2004 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ ያጸናው ሲሆን ከዚሁ ውሳኔ ውጪ እንዲሁም ተጠሪው በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ በሁለት የሥራ መደቦች ተወዳድረው የተቀመጡትን መስፈርቶች ማለፍ አለመቻላቸው ተረጋግጦ እያለ በእቅድ ምርታማነትና አሰራር ማሻሻያ ቡድን አስተባባሪነት መደብ እንዲሰጣቸው የታዘዘው ህግን የሚጻረር ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- አመልካች በፍርዱ መሰረት ምደባ ማድረጉን ገልጾ የሚከራከር ቢሆንም ምደባውን ያደረገው ከደረጃና ከደመወዜ ዝቅ በማድረግ ነው፡፡ ምደባው በመሰረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ የተሰጠ

ነው በማለት ያቀረበው ክርክርም ቢሆን መጀመሪያውኑ ከሥራና ደመወዝ እንድገለል ወስኖ የነበረው አስቀድሞ አመልካች ያስጠናው የሰው ሀይል ምደባ እና ደመወዝ እስኪል በመዋቅር ተጠንቶ ሥራ ላይ ከዋለ ከ5 ወር በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተደረገ ምደባ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በመልስ መልሱ ክርክሩን በማጠናከር አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ቀደም ሲል የፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/36405 በሰጠው ፍርድ እና ይህንኑ ፍርድ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 69498 ባጸናው መሰረት ፈጽሟል? ወይስ አልፈጸመም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የመ/ደ/ፍርድ ቤት ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መዝገብ በሰጠው ፍርድ ላይ በአሁኑ የሰበር አመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በመ/ቁ. 69498 ጥር 02 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ፍርድ በማጽናት የስራ ውሉ የተቋረጠው በአመልካች ህገ ወጥ ድርጊት ነው በማለት የ6 ወራት ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ መወሰኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ለዋናው ክስ መነሻ የነበረውም ተጠሪው ከሚሰሩበት ከአዲስ አበባ የሽያጭ ማስተባበሪያ ቢሮ በገበያ ጥናትና ማስታወቂያ ክፍል ሀላፊነት እንዲነሱ ተደርጎ በደሌ ሄደው በ29/02/2003 ዓ.ም. ሪፖርት እንዲያደርጉ ታዘው በተባለው ጊዜ ሪፖርት ሳያደርጉ ዘግይተዋል በሚል በአመልካች በመሰናበታቸው ሲሆን ይህ በ23/02/2003 ዓ.ም. የተጻፈው ደብዳቤ ይዘትም ደረጃቸውና ደመወዛቸው ሳይቀነስ በደሌ በሚገኘው የአመልካች ዋና መ/ቤት በእቅድና አሰራር ማሻሻያ ቡድን አስተባባሪነት መመደባቸውን የሚያሳይ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት የተቻለ ሲሆን ይህ ችሎትም ተጠሪውን አመልካች ያሰናበታቸው በህገ ወጥ መንገድ ነው በማለት የመ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ የህግ ስህተት የለበትም በሚል ካጸናው በኋላ አመልካች እንደ ፍርዱ መፈጸሙን ለመግለጽ ሁለት ደብዳቤዎችን ለተጠሪው ስለመጻፉ ተረጋግጧል፡፡ ደብዳቤዎቹ የተጻፉት ጥር 12 ቀን 2004 ዓ.ም. እና መጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ.ም. ሲሆን ጥር 12/2004 ዓ.ም. ከተጻፈው በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ተጠሪው በሚመደቡበት የሥራ መደብ ሥራ እንዲጀምሩና የ6 ወራት የተጣራ ደመወዝም እንዲከፈላቸው የሚል መሆኑን ነው፡፡ መጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ/ም ከተጻፈው ደብዳቤ የተረጋገጠው ደግሞ ቀደም ሲል ያገኙት በነበረው ያልተጣራ ደመወዝ ብር 3745 ላይ ብር 35 ተጨምሮ የደመወዝ ማስተካከያ ተደርጎላቸው ያልተጣራ ደመወዝ ብር 3780 እያገኙ በንብረት ክትትልና ቁጥጥር ባለሙያ የሥራ መደብ እንዲሰሩ ተመድበዋል የሚል መሆኑን ነው፡፡ ከእነዚህ አመልካች ከዋናው ፍርድ በኋላ እንደፍርዱ መፈጸሙን ለመግለጽ ከጻፋቸው ደብዳቤዎች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ደግሞ ከዋናው ፍርድ በፊት አመልካች ወደ በደሌ ተመድበው ሲሳኩ እንዲሰሩ ከተደረገው የሥራ መደብ የሚለያዩ መሆናቸውን ነው፡፡ የፍርድ ባለ እዳው ፍርዱን ለመፈጸም የማያስችለው በቂ ምክንያት አለመኖሩን ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ያረጋገጠ እንደሆነ ፍርዱ እንዲፈጸም ማዘዝ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 386(3) እና 392(1) ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ያለ በቂ ምክንያት እንደፍርዱ አለመፈጸሙን ከጻፋቸው ደብዳቤዎችና በአፈጻጸም ወቅት ካቀረባቸው የቃል ክርክሮች የሥር ፍርድ ቤቶች በማረጋገጥ ተጠሪው ቀደም ሲል ከአዲስ አበባ ወደ በደሌ ሲላኩ በተሰጣቸው የስራ መደብና ደረጃ አመልካች እንዲመድባቸው በሰጡት ትእዛዝ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/37192 በቀን 29/06/2004 ዓ.ም. የሰጠውን ትዕዛዝና የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በ/ቁ/116259 በቀን 01/08/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ተጠሪውን ቀድሞ በተመደቡበት በበደሌ ዋና መ/ቤት በዕቅድና ምርታማነት አሰራር ማሻሻያ የቡድን አስተባባሪነት የሥራ መደብ እንዲመልሳቸው ሲሉ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. ከዚህ በፊት በፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በአፈጻጸም መ/ቁ.37192 ተጀምሮ የነበረው የአፈጻጸም ክስ ታግዶ እንዲቆይ ተሰጥቶ የነበረው ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወሰኔ የህክምና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ዶ/ር ክብረወሰን አለማየሁ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የቀረበውን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች ከህግ ውጭ የሥራ ውሌን ያቋረጠ ስለሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ በተደጋጋሚ ሠዓት የማያከበር፣ ከታካሚዎች ጋር ጠብ የሚፈጥር በመሆኑ ከሥራ ተሰናብቷል ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ ተጠሪ የተካሚዎችን የግል ሚስጥር ለሶስኛ ወገኖች አላግባብ የሚገልጽና የሙያ ሚስጥር የማይጠበቅ መሆኑ፣ የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ከሚመጡ ታካሚዎች ጋር ጠብ መፍጠሩና ሠዓት ስለማያከብር ታካሚዎች ለካርድ የከፈሉትን ገንዘብ አስመልሰው የሄዱ መሆናቸው ተመስክሮበታል፡፡ ተጠሪ ይህንን በመከላከያ ማስረጃ አላስተባበለም፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተጠሪ በተደጋጋሚ የሥራ ሠዓት ባለማክበሩ በሥራው ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሷል የሚለውን አተረጓጎም የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1) ሀ እና (ለ) አቀራረጽና ይዘት የተከተለ አይደለም፡፡ የህክምና ዲስፕሊንን አለማክበር በሥር ውላቸው በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር የሥራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል ምክንያት አይደለም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች የካቲት 9 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የድርጅቱን መልካም ስምና ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረሱ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የሙያ ስነ ምግባር በማክበር ሥራውን የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ከሙያ ሥነ ምግባር ውጭ የሆኑ ተግባራትን እንደፈፀመ ተረጋግጦ እያለ የሥራ ውልን ለማቋረጥ ህጋዊ ምክንያት አይሆንም በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ አመልካች ያቀረበቸው ምክንያቶች የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በቂ አይደሉም የሚል ይዘት ያለው መልስ ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቀርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው የህግ ትርጉምና ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የህክምና ሙያ ሥነ ምግባር ደንብን በመተላለፍ በአመልካች የህክምና ተቋም የህክምና አገልግሎት ያገኙ ታካሚዎችን ሚስጥር የሚገልጽ ስለመሆኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው የሰው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ለምርመራ የቀረቡለትን ተካሚዎች የተሳደበ መሆኑንና ከታካሚዎች ጋር ጠብ የፈጠረ መሆኑ በወቅቱ በታካሚነት ቀርበው የነበሩ ሰዎች የምስክርነት ቃላቸውን በሥር ፍርድ ቤት ሰጥተዋል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ የህክምና ሙያ ሥነ ምግባር ደንብ በመተላለፍ በአመልካች መልካም ስምና ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረበውን ማስረጃ ሲመዘን የሥር ፍርድ ቤት ስህተት ሰርቷል የሚል የፍሬ ጉዳይ የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ የሌለው መሆኑን ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ በተለይም ተጠሪ የአመልካቹ ሠራተኛ ሆኖ ሲሰራ ያገኘውን የአመልችን ደንበኞች ምስጥር ለማይመለከታቸው ሶስተኛ ወገኖች የሚገልጽ መሆኑና የሥራ ውሉ ሊቋረጥ አካባቢ የአመልካችን አንዲት ደንበኛ ስም በመግለጽ ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ አለባት ብሎ ለሶስተኛ ወገን ሲገልጽ የሰማች መሆኑን የአመልካች ምስክርና የተጠሪ የሥራ ባልደረባ አስረድታለች፡፡ የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ወደ አመልካች ሄደው ተጠሪ እንዲመረምራቸው ቀርበው የነበሩ ታካሚዎች ተጠሪ የሰደባቸውና በማበሳጨት ለጠብ ጋብዟቸው የነበረ መሆኑን በማረጋገጥ የመስከሩ ሲሆን፣ በዚህ ምክንያት ወደ አመልካች የህክምና አገልግሎት ለማግኘት መሄዳቸውን እንዳቆሙ መስክረዋል፡፡ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለውን የአመልካች ምስክሮች ቃል ታዓማኒነትና ክብደት ያለው መሆኑን ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባለው የሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛው ፍርድ ቤትም የአመልካች ምስክሮች ቃል ታዓማኒነት እና ክብደት የሌለው ነው የሚል ውሣኔ አልሰጠም፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በአመልካች ምስክሮች የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ እውነትነት ያላቸው ቢሆኑም የሥራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም በሚል ምክንያት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ለውጦታል፡፡

ተጠሪ የአመልካች ደንበኞች ታካሚዎችን የግል ሚስጥር መግለፁና የህክምና አገልግሎት ለማግኘት የመጡ ታካሚዎችን መሣደቡ የአመልካች ምስክሮች የሰጡት ቃል ታዓማኒነትና ክብደት ያለው ማስረጃ መሆኑ አከራካሪ ባልሆነ፣ እነዚህ ተጠሪ በሥራ ሂደት ፈፀማቸው የተባሉ ጥፋቶች የሥራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችሉ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለው ነጥብ አመልካች ከሚሰጠው የህክምና ግልጋሎት ባህሪና ካለበት ኃላፊነት፣ ተጠሪ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግና በሙያ ሥነ ምግባር ደንቡ ከተጣለት ግዴታና ኃላፊነት እንደዚሁም የተጠሪ አድራጐት በአመልካች ላይ ከሚያስከትለውን ጉዳት አንፃር መመዘን ያለበት ነው፡፡

ማንኛውም ሠራተኛ በስራ ውሉ ላይ የተመለከተውን ሥራ ራሱ የመሥራትና በሥራ ውሉና በሥራ ደንቡ መሠረት በአሠሪው የሚሰጠውን ትእዛዝ የመፈፀም ግዴታ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህም ተጠሪ የተመደበበትን የህክምና ሥራ ሲሰራ ለሙያ ሥነ ምግባር ደንቦች ተገዥ በመሆን፣ ህሙማኑን በአክብሮት ማነጋገርና የማስተናገድ እንደዚሁም የህሙማኑን የግል ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ እንዳለበት ተጠሪ ይህንን የሙያ ሥነ ምግባርና ደንብ የማስከበርና በአመልካች ድርጅት ውስጥ በሠራተኝነት ከቀጠለ አመልካች የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ የተሰጠውን ፈቃድ ለማሣገድ ወይም ለማሰረዝ የሚችል ምክንያት ስለመሆኑ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 174/1986 ዓ.ም አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የአመልካችን ደንበኞች የግል ሚስጥር አለመጠበቁና ለማይገባቸው ሶስተኛ ወገኖች መግለፁ እንደቀላል ጥፋት የማይታይና በወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትል የሚችል የወንጀል ድርጊት መሆኑን ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 399 እና አንቀጽ 400 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ የአመልካች ሠራተኛ ሆኖ ሲሰራ እንደፈፀማቸው የተረጋገጡት ድርጊቶች በውጤት ደረጃ የአመልካችን መልካም ስምና ዝና በማጉደል ፈቃድ ባገኘበት የህክምና አገልግሎት የመስጠት የኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፍ ተወዳዳሪ እንዳይሆን የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ አመልካች ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ ለአመልካች ከመንግስት የተሰጠውን ፈቃድ ሊያሣግድ ወይም ሊያሠርዝ የሚችል ጥፋት መሆኑን ከላይ ከገለጽነው የደንብ ቁጥር 174/4986 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የፈፀማቸው ጥፋቶች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) መሠረት በሚያከማቸው ህሙማንን የመሣደብና የጠብ ጫሪነት ተግባር የፈፀመ መሆኑ የሚያሣዩና፣ የህክምና ሙያ ሥነ ምግባር ደንብን በመጣስ፣ የአመልካችን መልካም ሥምና ዝና እንደዚሁም ጥቅምና ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ ተግባራት ናቸው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ሸ) ድንጋጌም አመልካች ከሚሰጠው የህክምና ግልጋሎት ልዩ ባህሪና ተጠሪ ከሚጠበቅበት ከፍተኛ የሆነ የሥነ ምግባር ብቃት አንፃር ባለማክበሩ፣ በአመልካች ላይ የደረሰውን ወይም ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት በማያሻማ ሁኔታ መተርጎም ያለበት መሆኑን ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ዓላማ ከድንጋጌው ይዘትና ስለህክምና አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ የወጡ የህግ ማእቀፎችን ይዘት በመመርመር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የፈፀማቸው ጥፋቶች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) እና (ሸ) የሚሸፈኑና አመልካች የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ሆኖ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪ ጥፋቶች የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችሉ አይደለም በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 1(ረ) እና (ሸ) ድንጋጌዎች በተመሣሣይ መንገድ በመተርጎም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው በህግ አግባብ ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 72341

ሕዳር 21 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የማንበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ታዬ አበራ - ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሰው በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ደመወዝ መቀበሉ ሲረጋገጥ የጡረታ መብት ተጠቃሚ መሆኑ የሚቀጥል መሆን ያለመሆኑን ጥያቄውን የሚያቀርበው ወገን ክሱን ቀሪ የሚያደርገው የይርጋ ዘመን መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ በጡረታ መለያ ቁጥር ወ/515371 በሆነው ከግንቦት 01 ቀን 1984 ዓ.ም. ጀምሮ በየወሩ የጡረታ አበል እየወሰዱ ባለበት ሁኔታ ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ/ም ጀምሮ በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀጥረው የመንግስት ደመወዝና የጡረታ አበል በመቀበል ላይ መሆናቸውን ገልፆ ይህ የተጠሪ ተግባር በመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 209/1955 አንቀጽ 30(2) እና በመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 46(1) መሰረት ሕጋዊ ያለመሆኑን ጠቅሶ ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1995 ዓ.ም. ድረስ በየወሩ ብር 105.00 የወሰዱት ለሰባ አምስት ወራት ያህል ተባዝቶ የሚመጣውን ውጤት ብር በድምሩ ብር 7,575.00 (ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰባ አምስት ብር) እንዲሁም ከሐምሌ 01 ቀን 1996 ዓ.ም. እስከ ሀምሌ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ድረስ በየወሩ ብር 115.50 የወሰዱት ታስቦ የሚመጣውን ድምር ብር 4,045.50 (አራት ሺህ አርባ አምስት ብር ከሀምሳ ሳንቲም) ከወጪና ኪሳራ እንዲሁም ከሕጋዊ ወለዱ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሠጡት መልስም ከጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጋር የፈፀሙት የቅጥር ውል መኖሩን ሳይክዱ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ፣ መብቱ ቀሪ የሚሆነውም በአዲስ መልክ ሲቀጠሩ የሚያገኙት ደመወዝ ከብር 200.00 በላይ ከሆነ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአመልካች ክስ ተጠሪ ከተቀጠሩበትና የጡረታ አበል መቋረጥ ከሚገባበት ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ከአስራ ሁለት አመታት በላይ ቆይቶ የቀረበና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677 እና 1845 ድንጋጌዎች አኳያ ሲታይ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ጠቅሶ ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ አመልካች ዳኝነት እየጠየቀ ያለው ያለአግባብ የተከፈለውና ተጠሪ የበለፀጉበትን ገንዘብ ነው የሚል ምክንያት ይዞ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ዘመን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(1) ስር የተመለከተው

መሆኑን ገልጾ የአመልካችን ክስ በሁለት አመት ይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለጉዳዩ ይርጋ የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ተጠሪ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥረው ደመወዝ እየተቀበሉ ባሉበት ጊዜ የተቀበሉትን የጡረታ አበል ሊመልሱ አይገባም ተብሎ መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 209/1955 አንቀጽ 30(2) እና አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 46(1) ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርመሮም ተጠሪ ያላግባብ የተከፈለውን ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት አመልካች ያቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(1) ድንጋጌ መሰረት በሁለት አመት ይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡
የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ መሠረት ያደረጉት የአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 46/1/2/ የጡረታ አበል አመላለስን በተመለከተ የይርጋ ጊዜ የለውም በሚል መነሻ በሌሎች ሕጐች ያሉትን የይርጋ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ የአዋጅ ቁጥር 209/1955 እና አዋጅ ቁጥር 345/1995 ስር ያሉት ድንጋጌዎች ከሕግ ውጪ የተከፈለ የጡረታ ገንዘብ ይመለስ ጥያቄ መቅረብ ያለበትን የጊዜ ገደብ አላስቀመጡም፡፡ ይህ ማለት ግን ጥያቄው የሚቀርብበት ጊዜ ገደብ የለውም ወደሚለው ድምዳሜ የማያደርስ ስለመሆኑ ከይርጋ ፅንሰ ሀሳብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ ስለ ይርጋ የጊዜ ገደብ በግልፅ ያስቀመጠው ድንጋጌ ከሌለ በአገራችን የሕግ ስርአት የተዘረጋው መፍትሔ በውል ሕጉ የተመለከቱት ደንቦች የሚፈፀሙ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ያላግባብ መበልፀግን በተመለከተ የሚደነግጉ ድንጋጌዎች የይርጋ ደንብ የይርጋ ጊዜን በተመለከተ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ ከሌለ ተፈፃሚ የሚሆንበትን አግባብ የሚያሳይ ድንጋጌ የለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ክፍያው ያላግባብ ተወስዷል የሚል ነው በሚል ምክንያት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(1) ድንጋጌን ለጉዳዩ ተፈጻሚነት አለው በማለት የስር ፍርድ ቤት ያስቀመጠውን ድንጋጌ መለወጡ የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677 እና 1845 ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ በአስር አመት የይርጋ ጊዜ ጉዳዩ መታየት እንደአለበት የሰጠው ምክንያት ተገቢ ሁኖ የተገኘ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ይርጋው መቆጠር የሚጀመርበትን ጊዜ በተመለከተ ግን ተጠሪ ከተቀጠሩበት ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ/ም ጀምሮ ነው በማለት የወሰደው ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ የጡረታ አበሉንና በቅጥር የሚያገኙትን ደመወዝ በአንድ ላይ መቀበሉን በተከታታይ ሲፈጸሙበት ቆይተው ገንዘቡን ከሕግ ውጪ ሲቀበሉ የቆዩ መሆኑን አመልካች በማረጋገጥ የጡረታ አበሉን ለተጠሪ መክፈል ያቆመው ከነሐሴ 30 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ ሲሆን ተጠሪ ከሕግ ውጪ የወሰዱትን የጡረታ አበል እንዲመልሱ ክስ ያቀረበው ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ/ም ነው፡፡ ስለሆነም የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ክሱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን አቆጣጠሩም መሆን ያለበት ወደኋላ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ክሱ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ኋላ ሲቆጠር አስር አመት ያላለፈበት የጡረታ ገንዘብ ክፍያ ለአመልካች ሊመለስ

የሚገባው ይሆናል፡፡ አመልካች የይርጋው መቆጠር ያለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1847 መሰረት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር በየጊዜው የሚከፈለውን ገንዘብ የሚቀበል ሰው ክፍያው ሲቋረጥ መብቱን ለማስከበር የሚችልበትን የይርጋ ጊዜ ለመቁጠር የሚያስችለውን አግባብ የሚያሳይ በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ላይ አመልካች ክፍያ ተቀባይ ሳይሆን ከሕግ ውጪ የከፈለውን ገንዘብ እንዲመለስለት የሚጠይቅ በመሆኑ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ክሱ ከተመሰረበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ኋላ አስር አመት ያላለፈውን የጡረታ ገንዘብ መኖር ያለመኖሩን ስንመለከት አመልካች ገንዘቡ እንዲመለስ የጠየቀው ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1995 ዓ/ም በብር 105 ሂሳብ ለሰባ ወራት ይህል፣ እንዲሁም ከሐምሌ 01 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1998 ዓ/ም ድረስ ደግሞ ለሰላሳ አምስት ወራት ያህል በየወሩ ብር 115.50 የተከፈለውን የጡረታ አበል ክፍያ ነው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ከጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ኋላ አስር አመት ሲቆጠር አስር አመት የማይልፍበት የጡረታ አበል ክፍያ ከጥቅምት 19 ቀን 1993 ዓ.ም. ወዲህ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም ከጥቅምት 18 ቀን 1993 ዓ/ም ጀምሮ ወደ ኋላ ያለው ማለትም ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 18 ቀን 1993 ዓ/ም ድረስ ያለው የጡረታ አበል አስር አመት ያለፈበት በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ሊሆን የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ የይርጋው ጊዜ ያላለፈ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ፍሬ ነገሩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለማድረግ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) በሚያዘው መሰረት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መመለስ የሚቻል መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይህንኑ ለመፈፀም ግን ተከሳሽ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የሚነጥር የፍሬ ነገር ክርክር ማቅረባቸውን ያለማቅረባቸውን ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ አይነተኛ አላማ ጋር አገናዝቦ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንፃር የተጠሪን ክርክር ስንመለከተው የፍሬ ነገር ክርክር ሳይሆን የሕግ ክርክር በመሆኑ ለዚህ ነጥብ ሲባል ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መመለሱ ከውጪ፣ ጊዜና ጉልበት አንፃር ተገቢ ሁኖ ስላልተገኘ የሕግ ጥያቄውን በዚህ ችሎት እልባት መስጠቱ ስነ ስርዓታዊ ሁኖ አግኝተናል፡፡

ቀጥሎ መታየት ያለበት ጥያቄ ተጠሪ ለአመልካች ሊመልሱት የሚገባው የጡረታ አበል ክፍያ መጠን ምን ያህል ነው? የሚል ነው፡፡

በቅድሚያ ተጠሪ በቅጥር የሚያገኙት ደመወዝ ከ200.00 በታች በመሆኑ የጡረታ አበሉን ለመመለስ በሕግ እንደማይገደዱ ገልፀው ያቀረቡትን ክርክር ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

በመሠረቱ በዚህ ጉዳይ ክስ የተመሠረተው ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም. በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አዋጅ ቁጥር 345/1995 ከመሆኑም በላይ በአዋጅ ቁጥር 209/1955 እና 345/1995 የተፈጠሩ ህጋዊ ሁኔታዎች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት ጥበቃ ሊደርግላቸው እንዲሚገባ በአዋጁ አንቀጽ 59(1) ስር ተመልክቷል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 209/1995 አንቀጽ 30/2/ እና የአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀፅ 52(1) ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲነበቡ ደግሞ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ መልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ከተቀጠረ ከደሞዙ እና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ እንደሚኖርበት በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሥራው ደሞዝ የሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ መሆኑን እንጂ የቅጥሩ ሁኔታ በጊዜያዊነት ይሁን በቋሚነት እንዲሁም ደመወዙ ከጡረታ አበል ያነሰ ይሁን የበለጠ የሚል መስፈርት ከግምት ውስጥ አያስገባም፡፡ የአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 46(1) ሲታይም የአገልግሎት የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት እንደገና በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ደመወዝ ማግኘት ከጀመረ የጡረታ አበሉ ይቋረጣል በማለት በአስገዳጅነት

ያስቀመጠ ሲሆን ሕጉ ቅጥሩ ቋሚ ይሁን ጊዜያዊ ወይም በኮንትራት ስራ እንዲሁም በቅጥር የተገኘው ደመወዝ መጠንን አነስተኛ መነሻ በግልጽ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ የሕጉ ግልጽ አነጋገር የጡረታ ባለመብቱ እንደገና በሌላ መንግስታዊ ስራ ተቀጥሮ ከጡረታ ገንዘብ በተጨማሪ ሌላ ደመወዝ ካገኘ የጡረታ መብቱ የሚቆም መሆኑን ነው የሚያሳየው፡፡ በመሆኑም ደመወዝ የሚያስገኝ መንግስታዊ ቅጥር እስከተፈጸመ ድረስና ሕጉ ያስቀመጠው የቅጥር አይነትና የደመወዝ መጠን ልዩነት እስከሌለ ድረስ ሕጉ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባው ለማንኛውም የቅጥር ዓይነትና የደመወዝ መጠን እንጂ ለአነስተኛ ደመወዝ ሊሆን አይገባም ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ የሕጉ መንፈስ ይህ ስለመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በመ/ቁጥር 25899፣ በሰ/መ/ቁጥር 37111 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ይህ ጉዳይም በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት መታየት ያለበት በመሆኑ ተጠሪ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥረው ደመወዝ ማግኘታቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ደመወዙ ከብር 200.00 በታች ነው በማለት በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ይህ ውጤት የሚኖረው የጡረታ አበል ወይም ደመወዝ ከሁለት አንዱን በመመረጥ ለመመለስ ነው እንጂ በጠቅላላው አመልካች ጥያቄውን ለማቅረብ ለመከልከል አይደለም፡፡ ተጠሪ ከሰኔ 01 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ ተቀጥረው ሲያገኙት የነበረው ደመወዝ ከጡረታ አበል ያነሰ ስለነበር ይህንኑ ለመመለስ የሚፈልጉ መሆኑን ገልጸው አልተከራከሩም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ሊመልሱ የሚገባው የጡረታ አበሉን መሆኑን ክክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

እንግዲህ ተጠሪ የጡረታ አበሉን መመለስ አለባቸው ከተባለ መጠኑ ሊለይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከሐምሌ 01 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ድረስ ያለው የጡረታ አበል ገንዘብ መጠኑ ብር 4,042.50 ሲሆን ይህ ጊዜ ከላይ በተመለከተው የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር የአስር አመት የማይልፈበትን ጊዜ በግልጽ ያካተተ በመሆኑ እንዳለ ሊያዝ የሚገባው ሲሆን ከ1/10/1989 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 30/12/1995 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ተጠሪ የተቀበሉት ብር 7,575.00 ግን የአስር አመት ጊዜ የሚልፈበትን ጊዜ አካትቶ የተሰራ በመሆኑ ይሔው ጊዜ ሊለይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህም አግባብ ከ01/10/1989 እስከ ጥቅምት 1993 ዓ.ም. ድረስ ያለው የአርባ ወራት የጡረታ አበል መጠኑ በወርሃዊ የጡረታ አበል ብር 105.00 ሲታሰብ ብር 4,200.00 (አራት ሺህ ሁለት መቶ ብር) የሚመጣ በመሆኑ ይኼው ገንዘብ በአስር አመት ይርጋ ሊታገድ የሚገባው ሁኖ ቀሪው ከሕዳር 01 ቀን 1993 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1995 ዓ.ም. ድረስ ለሰላሳ ሶስት ወራት ለተጠሪ የተከፈለው ገንዘብ ብር በወር ብር 105 ሲታሰብ ብር 3,465.00 (ሶስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ አምስት ብር) በይርጋ የሚታገድ ባለመሆኑ ለአመልካች ተጠሪ ሊመለሱት የሚገባ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ይርጋ የአስር አመት ጊዜ በመሆኑና ይህ ጊዜ መሰረት ተደርጎ ሲሰላም አመልካች ከተጠሪ ሊመለስለት የሚገባው የገንዘብ መጠን በድምሩ ብር 7,665.00 (ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ አምስት ብር) ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሠጠው ውሳኔ ሙሉ በሙሉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ደግሞ የድምዳሜ ክፍሉ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03844 ህዳር 15 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 118234 ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም. ምክንያቱ ተለውጦ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ዘመን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ድንጋጌዎች መሰረት አስር አመት ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ከክሱ ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥ የአስር አመት ይርጋ ያላለፈውን ብር 7,665.00 (ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ አምስት ብር) ከሕግ ውጪ የወሰዱት በመሆኑ ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 83012
ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- ዝዋይ ሮዝ ድርጅት

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ፋንቱ ያሲን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በአዳሚ ቱሉ በወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን የሰበር ተጠሪ የአፈጻጸም ከሳሽ አመልካች ደርጅት ደግሞ የአፈጻጸም ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/28572 በቀን 24/01/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሰረት የአፈጻጸም ተከሳሽ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ ይታዘዝልኝ የሚል ነው፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም፡- በ17/04/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ መረዳት የተቻለው የፍርድ ባለመብቷን የፍርድ ባለዕዳው ወደ ሥራ እንዲመልሳቸው መወሰኑን እንጂ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው ባለመሆኑ የፍርድ ባለዕዳው የፍርድ ባለመብቷን ወደ ሥራ መመለሱን በ17/04/2004 ዓ.ም. ለፍርድ ቤቱ ከጻፈው ደብዳቤ የተረጋገጠ በመሆኑ እንደፍርዱ ፈጽሟል በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአፈጻጸም ከሳሽም በወረዳው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ቅሬታ፡- ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/28527 በ24/01/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የፍርድ ባለዕዳው ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ የወሰነ ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤትም ወደ ሥራ እንድመለስ ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ በሞዴል 85 መልስ ሰጪው እንዲያይዝ ካደረገ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ መልስ ሰጪው ይመልሳት ይላል እንጂ ስለ ክፍያው በግልጽ የሚለው ነገር የለም በማለት ገንዘቡ እንዲለቀቅ ማዘዙ ተገቢ ባለመሆኑ ወደ ሥራ እንዲመለስ ከተወሰነበት ቀን አንስቶ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ መልስ ሰጪው እንዲከፍል ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

መልስ ሰጪ ድርጅትም ቀርቦ ባለመከራከሩ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቀደም ሲል በመ/ቁ. 28527 በቀን 17/09/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ ከመረመረ በኋላ በውሳኔው ይግባኝ ባይዋ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ከመባሉ በስተቀር ከሥራ ከታገዱበት ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ያለው

ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያልተወሰነ በመሆኑ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡

የፍርድ ባለመብትም በስር ፍርድ ቤቶች ትእዛዝ/ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር እንዲሁም የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ቁጥሩ 28527 የሆነውን መዝገብ አስቀርቦ በመመርመር በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ውሳኔ በመ/ቁ/28527 ተደርጎ በነበረው ክርክር አመልካች ተጠሪዋን ከሥራ በህገ ወጥ መንገድ ስለማሰናበቱ ካለማስረዳታቸውም ሌላ ተጠሪውም አመልካችን አለማሰናበታቸውን ጠቅሶ በመከራከሩ ፍርድ ቤቱ በ24/01/2004 ዓ.ም. በሰጠው ውሳኔ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ወደ ሥራ እንዲመለሱ ሲወስን ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው በግልጽ የወሰነው ነገር ባይኖርም ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ሲል ውሳኔ መስጠቱ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንጽ 43(5) ጋር ተገናዝቦ ሲታይ አንድ በህገ ወጥ መንገድ ከሥራ ተሰናብቷል በሚል ወደ ሥራ እንዲመለስ የሚወሰን ሠራተኛ በመጀመሪያ የሥራ ክርክር ችሎት እስከ 6 ወር ደመወዝ፣በይግባኝ የታዬ እንደሆነ ደግሞ እስከ አንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ሊወሰን እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን በዚህ በተያዘውም ጉዳይ የፍርድ ባለመብት ወደ ሥራ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ይመለሱ ተብሎ መወሰኑ ከዚሁ ቀን ጀምሮ ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ማለትም እስከ 24/01/2004 ያለው ደመወዝ ተከፍሎአቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ የተወሰነ መሆኑን ስለሚያስገነዝብ ከ17/09/2003-24/01/2004 ያለው ውዝፍ ደመወዝ ታስቦ ሊከፈላቸው ይገባል በሚል የወረዳው ፍርድ ቤትና ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሠጡትን የትዕዛዝ /የውሳኔ ክፍል ሽሯል፡፡

አመልካችም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- ተጠሪ የሥራ ውሌ በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል ክስ ቢያቀርቡም ይህንኑ በማስረጃ ያላረጋገጡ በመሆናቸው በአመልካች ህገ ወጥ ድርጊት ውሉ አልተቋረጠም በማለት ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/28527 የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የህግ ስህተት የለበትም በሚል ካጸናው በኋላ በአፈጻጸም ወቅት ግን በውሳኔ ያልተገለጸውን ውዝፍ ደመወዝ አመልካች ሊከፍል ይገባል ሲል መወሰኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዋ በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/28527 በሰጠው ውሳኔ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን በፊት ያለውን ጊዜ በመጥቀስ ከዚሁ ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ አመልካች ወደ ሥራ እንዲመለስ የወሰነው ያልተከፈለውን ውዝፍ ደመወዝ አመልካቹ እንዲከፍል በሚል ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ላለመክፈል ሲል ያቀረበው ክርክር ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡ ተጠሪዋ ላቀረቡት መልስ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ለተጠሪዋ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፍል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካችና ተጠሪን በዋናነት እያከራከራቸው ያለው ለአፈጻጸም ክሱ መነሻ የሆነው ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/28527 በቀን 24/01/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ነው፡፡ በዚህ ፍርድም ተጠሪዋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ከመወሰኑ በስተቀር ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው በግልጽ አለመጠቀሱን የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ አንድ የአፈጻጸም ክስ የቀረበበት ሰው ደግሞ ሊገደድ የሚችለው እንዲፈጸም በቀረበው ፍርድ መሰረት መሆኑን ከፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 378 እና ከተከታይ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ እንዲሁም ፍርዱን የሚያስፈጽም ፍርድ ቤት በፍርዱ ወይም በውሳኔው መሰረት ከሚያስፈጽም ውጪ በአፈጻጸም ጊዜ ዋናውን ፍርድ ሊለውጥ የሚችልበት የህግ መሰረት አለመኖሩን ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/29344 እና በሌሎችም በርካታ መዝገቦች አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይም በዋናው ፍርድ አመልካች ወደ ሥራ ተጠሪዋን እንዲመልሳቸው ከመወሰኑ በተጨማሪ ውዝፍ ደመወዛቸውን እንዲከፍል የተወሰነ መሆን ስላለመሆኑ መመርመር የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመ/ቁ 28527 በቀን 24/01/2004 ዓ.ም. በተሰጠው ፍርድ ተጠሪዋ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የተወሰነው ከ17/09/2003 ጀምሮ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ፍርዱ ከተሠጠበት ከ24/01/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ተጠሪዋ ወደ ሥራ እንዲመለሱ መወሰን የሚችል ቢሆንም ወደ ኋላ ያለውን ጊዜ ወስዶ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የወሰነው በዚህ ችሎት እምነት ለተጠሪዋ ከዚሁ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ያለው ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው በሚል ነው፡፡ ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ ውዝፍ ደመወዝ ለተጠሪዋ እንዲከፈላቸው ለመወሰን የማይገባ መሆኑን ቢያምን ኖሮ በ24/01/2004 በተሰጠ ፍርድ ከ17/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የሚልበት ምክንያት ስለማይኖር ነው፡፡ በዚህ መልኩ የተሰጠውን ፍርድ ደግሞ አመልካች ውዝፍ ደመወዙን ለመከፈል በቂ ምክንያት የለም የሚል ከሆነ በይግባኝ አቅርቦ ሳያስለውጥ ከቀረ በኋላ በአፈጻጸም ወቅት ውዝፍ ደመወዝ በዋና ፍርድ ላይ አልተወሰነም ሲል መከራከሩ የፍርዱን ይዘት መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም ከዚህ በላይ በተገለጹት ምክንያቶች የተነሳ አመልካች ለተጠሪዋ ከ17/09/2003 ዓ.ም.ጀምሮ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፍል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምጽ የወሰነው ተገቢ ሆኖ በማግኘታችን በአብላጫ ድምጽ በውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በሚል ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.147105 በቀን 28/12/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት በአብላጫ ድምጽ አጽንተናል፡፡
2. ለተጠሪዋ አመልካች ከ17/09/2003 ዓ.ም. እስከ 24/01/2004 ዓ.ም. ያለውን ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፍላቸው የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት የወሰነው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የልዩነት ሐሣብ

የፍርድ አፈፃፀም ሥርዓትን አመራር አስመልክቶ ከላይ ከፍ ሲል የተገለፀውን ፍርድ ለመስጠት የአብላጫው ድምፅ በሰጠው የሕግ ትርጉም ባለመስማማት በፍርዱ ላይ ስማችን በተራ ቁጥር 1 እና 5 ላይ የተመለከተው ዳኞች የፍርዱ አፈፃፀም ሊመራ የሚገባበትን የተለየ የትርጉም መስመር እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን የመጨረሻ ፍርድ የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ውሣኔ እንደምርኩዝ አድርጎ የጠቀሰው በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ ድንጋጌ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ በእራሱ ፍርድ የአማርኛ ትርጉም ገጽ 2 የመጀመሪያው ፖራግራፍ ላይ እንደገለፀው ለአፈፃፀሙ መነሻ የሆነውን ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በመ/ቁ. 28527 መስከረም 24 ቀን 2004 ዓ.ም ፍርድ ሲሰጥ የአሁን አመልካች ተጠሪን ሕገ- ወጥ በሆነ መንገድ ከሥራ አሰናብቷታል የሚለውን መሠረት በማድረግ አይደለም ይልቁንም የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ሕገ- ወጥ ድርጊት የተሰናበተች ስለመሆኑ በማስረጃ አላረጋገጠችም፤ አሠሪውም እኔ ከሥራ አላናበትኳትም በማለት መከራከሩን ሁሉ መሠረት አድርጎ ወደ ሥራዋ ትመለስ በማለት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የተነሣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ ወደ ሥራ ትመለስ የተባለችበትን ምክንያት ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፍርድ የተገለፀውን እና በማስረጃ የተረጋገጠውን የፍሬ ነገር ጉዳይ በውል ካለመገንዘብ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት አለው የሚለውን የአዋጁን አንቀጽ 43/5/ በመመርኮዝ ምክንያት ከተሳሳተ መነሻ ተነስቶ ወደ ተሳሳተ የፍርድ መደምደሚያ ሊደርስ እንደቻለ የጉዳዩ አመጣጥ አስረጂ ነው፡፡

ምናልባት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መስከረም 24 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት እየወሰነ የአሁን ተጠሪ ከግንቦት 17/2003 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሥራዋ ትመለስ ማለት ምን ማለት ነው? ለሚለው አከራካሪ ነጥብ ከላይ የተመለከተውን የአዋጁን አንቀጽ 43/5/ ድንጋጌ ከጉዳዩ ጋር በማመሳሰል ለጉዳዩ ተፈፃሚነት እንዲኖረው አድርጎ ነው ከተባለም ይኸው የሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃውን ጠብቆ በቀረበለት የአፈፃፀም ጉዳይ ላይ በአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውን የፍርድ ይዘት አድማስ በማስፋት እና ለጥጦ ለመትርጎምና ይህንኑ የተለጠጠ ትርጉም ሁሉ ጨምሮ ፍርድን ለማስፈፀም የሚያስችል ሥልጣን በአገራችን የህግም ሆነ የዳኝነት አመጣጥ ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡

ይልቁንም የአንድ ፍርድ ይዘት አሻሚ ሆኖ እንደ አሁኑ ያለውን ክርክር እንዳያስነሳ ሙግት ተከናውኖ ካበቃ በኋላ ፍርድ እንዴት ሊሰጥ እንደሚገባው እና ምን ምን ሁኔታዎችን ማካተት እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182 እና 183 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይህም ፍርድ ሊሰጡ የሚችሉት ፍ/ቤቶች ዋናውን ጉዳይ ተመልክተውና አከራክረው በጉዳዩ ላይ ዳኝነት በመስጠት በጎንዮሽም ሆነ ከታች ወደ ላይ በተዘረጋው የፍርድ ቤቶች አወቃቀር በቀጥታም ሆነ በይግባኝ ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገረ ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡

በዚህ አኳኋን የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 372 መሠረት ሥልጣን ያላቸው የአፈፃፀም ችሎቶች ስለ ፍርድ አፈፃፀም የተዘረጉትን ሥርዓቶች በመከተል እንደ ፍርዱ ከመፈፀም በቀር የአንድ ፍርድ ይዘትን በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆነ በማስፋት ረገድ ፍርድን የመተርጎም ሥልጣን አልተሰጣቸውም፡፡

በዚህ ረገድ በኦሮሚያ ክልል የአዳሜ ቱሉ ወረዳ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በቀረበላቸው ጉዳይ "ፍርዱ" የአሁን ተጠሪ ከግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ አሠሪው ወደ ሥራዋ ይመልሣት በሚል በግልፅ ከመቀመጡ በቀር ከውዝፍ ደሞወዝ ጋር በሚል ስላልተወሰነ ከፍርዱ ይዘት አድማስ በመሻገር ለማስፈፀም የሚያስችል ሥልጣን የለንም በማለት የሰጡት ትርጉም የፍርድ አፃፃፍ ሥርዓት በየትኛው ፍ/ቤት እንደሚከናወንና የአፈፃፀም ችሎት ሥልጣን ውሱን እስከምን እንደሆነ ስለአፈፃፀም ሥርዓት አመራር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል።

በአኳያው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀረበለት የአፈፃፀም መዝገብ ላይ ፍርዱ ከተሰጠበት ዕለት ወደ ኋላ በመመለስ ሠራተኛው ወደ ሥራ ትመለስ በማለት መወሰኑ /መፈረዱ ትመለስ ከተባለቺበት ዕለት ጀምሮ ውሣኔ እስከተሰጠበት ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ይከፈላት ለማለት ካልሆነ በቀር የተለየ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም በማለት ለአፈፃፀሙ መነሻ የሆነውን የፍርድ ይዘት በማስፋት የሰጠው ትርጉም ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው በሕግ ባልተሰጠው ሥልጣን ከመሆኑም በላይ ይህ ዓይነት የአተረጓጎም መስመር ስለዋናው ጉዳይ ፍርድ አሰጣጥ እና ፍርዱን ስለማስፈፀም ሥርዓት አስመልክቶ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ጉዳዮች በሥርዓት እንዲመሩ በማድርግ በአፋጣኝ እና በአነስተኛ ጊዜና ወጭ እንዲቋጩ ማድረግን ታሳቢ አድርጐ የያዘውን ዋነኛ ዓላማ የሚንድ፤ ይህን ዓይነት የአተረጓጎም መስመር ከተከተልን ዳር ድንበር ለሌለው ሙግት ተከራካሪ ወገኖችን የሚዳርግ የሙግት አመራር ሥርዓትን የሚያፋልስ የአገሪቱ የፍርድ አሰጣጥ እና የአፈፃፀም ሥርዓት ተገማች እንዳይሆን ሊያደርግ የሚችል በመሆኑ ከህጉም ሆነ ከየትኛውም መመዘኛ አንፃር ከቶውንም ተቀባይነት ያለው አይደለም።

በተለይም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(3)(ሀ) እና ይህንኑ ሕገ መንግስትዊ ድንጋጌ ለመስፈፀም በወጣው ዝርዝር ሕግ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ስለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን መደንገግ ያስፈለገበት ዋነኛ የሕጎች መነሻ የአገሪቱን ሕጐች በማስፈፀምም ሆነ በመተረጐም ረገድ ወጥ የሆነ አሠራር እንዲሰፍን ለማድረግ በመሆኑ ይህም ስለመሆኑ እነዚህ ሕጐች ከወጡ በኋላ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጠው ትርጉም በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የዳኝነት አካል ላይ የአስገዳጅነት ባህሪ ይኖረዋል በሚል በአዋጅ ቁጥር 454/97 የተደነገገው አስረጅ ነው።

ከእነዚህ ሕጐች አንፃር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደ አሁኑ ያለ አጠቃላይ የፍርድን አመጣጥና የአፈፅፀም ሥርዓት የሚመለከት ጉዳይ በሁለት ተከራካሪ ወገኖች ክርክር መነሻ ሲቀርብለት በዚህ ዓይነት ጉዳይ በተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ላይ የተፈፀመን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በማረም ለእነዚህ ተከራካሪ ወገኖች ሕጉን መሠረት ያደረገ ዳኝነት ከመስጠቱ ባሻገር ዐበይት ተግባሩ ወደ ፊት ይህን መሰል ክርክር ቢነሳ ሕጉን መሠረት ያደረገ ትርጉም በመስጠት ወደ ፊት ለሚነሱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ትርጉሙ ተፈፃሚ እንዲሆን በማድረግ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ለማስፈን እንጂ የአፈፅፀም ጉዳይን እየተመለከተ ያለ ፍርድ የአፈፃፀም ፍ/ቤት እንደ አግባብነቱ ለፍርዱ ትክክለኛ ትርጉም በመስጠት ፍርዱን በተሟላ መንገድ የማስፈፀም ሥልጣን አለው የሚለው ትርጉም ሕጋዊ መሠረት የሌለው ከመሆኑም በላይ ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት አይተውና ሰምተው ፍርድ ለመስጠት የሚችሉትንና እንደፍርዱ የሚያስፈፅሙትን ችሎቶች ሥልጣን

የሚቀላቅል፣ የሚተረጉም ፍርድ አለ የለም? የሚተረጉምስ ከሆነ እንዴት ይተርጉም የሚሉትንና ለመሳሰሉት ወሰን ለሌላቸው ክርክር የሚጋብዝ፤ የአፈፃፀምን ጉዳይ በዘፈቀደ እንዲመራ የሚያደርግ እንጅ የፍርድ አሰጣጥና የፍርድ አፈፃፀም በሥርዓት እንዲመራ በማድረግ ወጥ ለሆነ የሕግ አፈፃፀም እና አተረጓጎም እንቅፋት የሚፈጥር በመሆኑ ትርጉም ሕጉንና ሕጐችን ለማውጣት ያስፈለገበትን ግብና መነሻ ሐሳብ መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡

ስለሆነም በዚህ በተያዘው ጉዳይ ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውን ፍርድ የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መስከረም 24 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን ተጠሪን አሠሪው ከግንቦት 17/2003 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሥራዋ ይመለሳት ሲል ፍርድ በመስጠቱ የተነሣ በአፈፃፀም ጊዜ ከግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ፍርድ እስከተሰጠበት እስከ መስከረም 24 ቀን 2004 ዓ.ም ያለውን ውዝፍ ደመወዝ ይጨምራል ወይስ አይጨምርም? ለሚለው ቀጥተኛ መልስ አይሰጥም፤ ፍርዱን ለማስፈፀም ያስቸግራል ውዝፍ ደመወዝ እንደተነፈገ ሊቆጠርብኝ ይችላል? የሚለው በፍርድ ግልጽ አለመሆን የሚጐዳው ወገን ፍርዱንና ጠይቆት ከነበረው ዳኝነት ጋር በማነፃፀር በበላይ ፍ/ቤት እንዲታረም ከማድረግ በቀር፡፡

እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከላይ በተገለፀው አኳኋን ፍርዱን ሊሰጥ የቻለበትን ምክንያት በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንፃር እና ለጉዳዩ ተፈፅሚነት እና አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ስለፍርዱ ይዘት አድማስ ተመልክቶ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት ሥልጣን ያላቸው ዋናውን ጉዳይ ሰሚው ከታች እስከ ላይ የተዋቀሩት ፍ/ቤቶች እንጂ ፍርዱን እንዲያስፈጽም የአፈፃፀም ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት የፍርዱን ይዘት በማጥበብም ሆነ በማስፋት ረገድ ትርጉም ለመስጠት የሚያስችለው ሥልጣን ሰጭ ድንጋጌ እና ሥርዓት የለውም ከዚህ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል በሚል ሊተርጉም ይገባል የሚለውን የፍርድ ሐሳብ ሰጥተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 81405

ጥር 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አቶ መሐመድ ሲራጅ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የአወሊያ ዋና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ነ/ፈጅ አቶ አሕመድ መዲ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2(1) መሠረት የስራ መሪ በመሆናቸው ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚዳኝ አይደለም የሥራ ክርክር ችሎቱም ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ እና በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ በማሰናበት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ስራ ክርክር ችሎት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊታረሙ ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርመሮ አመልካች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 እና በማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/1/ መሠረት በሰራተኛ ውስጥ የሚካተት ሳይሆን የስራ መሪ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ሊስተናገድ አይገባም የመባሉን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ክርክር ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተሰዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚስተናገድ አይደለም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሐግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በ07/03/04 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረቡት ክስ ይዘት ተጠሪው ድርጅት በሕግ አማካሪነት ቀጠሮ ሲያስራኝ ከቆየ በኋላ አላግባብ ከስራ ያሰናበተኝ በመሆኑ የስራ ውሉ መቋረጥ ሕገወጥ ነው ተብሎ ተጠሪው የካሣ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ፣የስራ ስንብት ክፍያ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት ያደረጉት ክፍያ ለጠቅላላ ሰራተኛ የተሰጠውን የ40% የደመወዝ ጭማሪ እና መሰል ክፍያዎችን እንዲከፍለኝ ውሳኔ ይሰጠኝ የሚል እና የአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሰጡት አመልካች የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአሰሪና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 የሚዳኝ አይደለም በማለት ቢሆንም በበኩላችን ግን በመዝገቡ ከቀረበው ክርክር አንፃር ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ግንኙነት የቅጥር ውል ነው ወይስ የእውቀት ሥራ ውል ነው? የሚል መሆኑን በመገንዘብ ከዚሁ ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ከተጠሪ ጋር የስራ ውል ከመሰረቱበት ጊዜ በፊት ጀምሮ የሰራ ግንኙነቱ እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ ፈቃድ አውጥተው የጥብቅና አገልግሎት በመስጠት ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ መሆኑንን ተጠሪው በሰበር መልሱ ላይ የገለፀ ሲሆን አመልካችም የተጠሪው ስራ ብዙ በመሆኑ በጥብቅና ፈቃዴ ሌላ ስራ ልሰራ አልቻልኩም ከማለት በስተቀር በጥብቅና ስራ አገልግሎት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ መሆኑን አላስተባበሉም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ የስራ ግንኙነት ደግሞ በፍ/ሕ/ቁ.2632-2638 በተመለከተው መሠረት በእውቀት ስራ ውል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንጂ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3(1) እና (2) መሠረት በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ባለመሆኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 እና 494/98 መሠረት ሰራተኛም ሆነ የሰራ መሪ ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ የግራ ቀኙ መብትና ግዴታም የሚወሰነው ከላይ በተጠቀሱትና አግባብነት የሚኖራቸው ሌሎች የፍ/ብሔር ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 በግራ ቀኙ መካከል ላለው ግንኙነት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይችልም፡፡ በዚህም ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች ለውሣኔያቸው የሰጡት ምክንያት የተሳሳተ ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ውሳኔው ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23650 በ19/08/04 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 119028 በ13/10/04 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በውጤት ደረጃ ፀንተዋል፡፡
2. በሰበር ደረጃ የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራቸውን ይቻሉ፡፡
3. ክርክሩ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 82336

ጥር 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአብጃታ ሶዳ አሸ አክሲዩን ማህበር

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ማርታ አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-በአመልካች ድርጅት ከግንቦት 16 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ በወር ደመወዝ ብር 1560.00 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ብር) እየተከፈላቸው ሲያገለግሎ እንደቆዩና ነሐሴ 27 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ ደብደቤ ከነሐሴ 28 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የስራ ውሉ ያተቋረጠ መሆኑን አመልካች ያሳወቃቸው መሆኑን ዘርዝረውና የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ መሆኑን ጠቅሰው የሞራል ካሳ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ የስራ ውልን መቋረጥን ተከትሎ የሚከፈሉ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ተጠሪ በሐኪም ውሳኔ መሰረት በእርሷ ጤናና ሙያ የሚመጥን የስራ መደብ ባለመኖሩ ድርጅቱ ባገኘው አማራጭ፤ክፍት የስራ መደብ ላይ መብታቸውን ሳይነካ እንዲሰሩ ቢደረጉም ቦታው ደረጃዬን አይመጥንም በማለት ስራቸውን ትተው ፍርድ ቤትና ህክምና በመመላለስ የስራ ጊዜአቸውን የሚያባክኑ ስለሆነ በአማራጭ የተመደቡበትን፣ሌላ የስራ መደብም ላይ እየሰራች ለመቀጠል ፍቃደኛ እንዳልሆኑ በመዘርዘር እርምጃው የሕብረት ስምምነቱንና ህጉን መሰረት ያደረገ መሆኑን ገልጸ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የአመልካች እርምጃ ሕጋዊ ነው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪን የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ በመክፈል ወደ ስራቸው ሊመልሳቸው ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በሐኪም አስተያየት ለጤናቸው የሚመጥናቸው የስራ መደብ ሲሰጣቸው ሊሰሩ ፍቃደኛ ያለመሆናቸው በመረጋገጡ ስንብቱ የተከናወነ መሆኑን የሚያረጋግጥ የአመልካች ማስረጃ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውድቅ የተደረገው የማስረጃውን ይዘት ካለማገናዘብ የተነሳ መሆኑንና ተጠሪ ወደ ስራ ይመለሱ ቢባል እንኳን ከአመልካች ጋር ሰላማዊ የሆነ የስራ

ግንኙነት የሚኖራቸው ባለመሆኑ ተገቢ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ያለመወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ተምኖበት እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 28(1(ለ)) አኳያ የተፈፀመው የስራ ውል ማቋረጥ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪን የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ በመክፈል ወደ ስራ ይመልስ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ክሱን የመሰረቱት የስራ ስንብቱ የተከናወነው ከሕግ ውጪ ነው በሚል ምክንያት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ስንብቱ በሕጉ አግባብ የተደረገ መሆኑን ገልፆ በመከራከሩ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን በመመርመር ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የደመደመውን ድምዳሜ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ስራ አልፈልግም በማለት ያስታወቁ መሆኑን አመልካች በማስረጃዎቹ ያለማረጋገጡን፣ይልቁንም ተጠሪ ለአመልካች በሰጡት መልስ በቀድሞው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸምላቸው የገለጹ መሆኑ መረጋገጡንና በጤናቸው ላይ የደረሰው የስራ ጉዳትም የስራ ግዴታቸውን ለዘለቄታው ለመፈጸም የማይችሉ መሆኑ ያለመረጋገጡ በክርክሩ ሂደት መታወቁን በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ ከዚህ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልፅ መረዳት የሚቻለው ውሳኔው የግራ ቀኙን ማስረጃና ክርክር በመመዘን በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ስንብቱ በአመልካች ከሕግ ውጪ መከናወኑን ወይም አመልካች ስንብቱን በሕጉ አግባብ ያከናወነ መሆኑን በማስረጃዎቹ ያላስረዳ መሆኑን ሲሆን ይህ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ድምዳሜ የተያዘው ማስረጃን በመመዘን መሆኑን ነው፡፡ይኸው ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነጥብ የመጨረሻ ነው፡፡እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው ስልጣን በበታች ፍርድ ቤቶች ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሲፈጸም ማረም እንጂ በማስረጃ ምዘና ላይ የሚያተኩር ክርክር የመመርመርና ስህተቱን የማረም ስልጣን የለውም፡፡በመሆኑም በተያዘው ጉዳይም የአመልካች ክርክር ማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ በመሆኑና አመልካች በስራ ላይ በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት ስራውን ለዘለቄታው መፈጸም የማይችሉ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 28(1(ለ)) ድንጋጌ አግባብ ያላረጋገጠ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አይቻልም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ከተጠሪ ጋር የመሰረተው የስራ ግንኙነት ከሕግ አግባብ ውጪ ተቋርጧል ቢባል እንኳን ከተጠሪ ጋር ለወደፊቱ መልካም ግንኙነት ሊኖር ስለማይችል ተያያዥ ክፍያዎች ተከፍሏቸው ተጠሪ ሊሰናበቱ ይገባ ነበር በማለት ነው፡፡በእርግጥ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል መልካም ግንኙነት መኖር ለኢንዱስትሪው ሰላምና ምርትና ምርታማነትን ከፍ በማድረግ ለአገር ኢኮኖሚ ተገቢውን አስተዋጽኦ ለማበርከት አስፈላጊ በመሆኑ ሰላማዊ ግኙነት እንደማይኖር የሚያሳዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ጉዳዩን ለመመልከት ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው አካል የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ቢደርስ እንኳን ሰራተኛው ወደ ስራ እንዲመለስ ከማድረግ በምትኩ ሕጋዊ ክፍያዎች ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ እንደሚገባ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43(3) ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ይህ ድንጋጌ ተግባራዊ ሲደርግ ግን የስራ ዋስትና ዋጋ በማያጣበት አግባብ ሊከናወን የሚገባ መሆኑ የድንጋጌው መንፈስ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሕግ አጠቃላይ ዓላማና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕግ መንግስት አንቀጽ 42 ስር ከተቀመጠው ድንጋጌ አንጻር ጋር ተዳምሮ ሲታይ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ከአመልካች ጋር በሕጉ አግባብ የቅጥር ውል መስርተው በስራ ላይ በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት ከጤናቸው ጋር በሚመጥን ቦታ አመልካች ተጠሪን መድቦ እንዲያስራ በፍርድ ቤት ተወስኖ የነበረ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሲሆን በዚህ ውሳኔ መሰረት ሳይፈጸም ግን አመልካች ሊሰሩ ፍቃደኛ አልሆኑም፣ስራውንም ለመፈጸም አይችሉም በሚሉ ምክንያቶች የስራ ውሉን ከነሐሴ 28 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ አቋርጧል፡፡ይህ የሚያሳየው አመልካች በተጠሪ ላይ የደረሰውን የስራ ጉዳት ምክንያት በማድረግ ለጤናቸው ተስማሚ በሆነው የስራ መደብ ላይ ለማሰራት ፍቃደኛ ባለመሆን የፀና መሆኑን ነው፡፡ይህ ደግሞ ሕገ ወጥነት ያለው ተግባር ከሚባል በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 377/196 አንቀፅ 43(3) ድንጋጌ መንፈስ መሰረት አመልካችና ተጠሪ መልካም የሆነ ግንኙነት አይኖራቸውም ብሎ ለመደምደም እና የስራ ውሉ እንዲቋረጥ ለማድረግ የሚበቃ ሕጋዊ ምክንያት አይሆንም፡፡ አንድ ሰራተኛ መብቱን ለማስከበር ፍርድ ቤት መሄዱ ብቻውን ከአሰሪው ጋር ለወደፊትም የሻከረ ግንኙነት ይፈጥራል ተብሎ የሚገመትበት ህጋዊ አግባብ የለም፡፡ይልቁንም በፍርድ ቤት ውሳኔ መብቱን በማረጋገጥ የሚሰራ ሰራተኛ ለኢንዲስትሪው ሰላም ችግር የማይፈጥር ሰላማዊና በሕግ ልዕልና ከፍተኛ እምነት ያለው ነው ተብሎ የሚገመት መሆኑ ይታመናል፡፡በመሆኑም አመልካች ተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው ሊሰናበቱ ይገባል በማለት የሚያቀርበው አማራጭ ዳኝነት በተጠሪ ላይ ደረሰ ከተባለው የስራ ጉዳትና ከሕጉ አጠቃላይ መንፈስ አንጻር ሲታይ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ሲጠቃለልም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 116264 ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ጥቅምት 14 ቀን 2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.78865

ጥር 28 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት

ተጠሪዎች ፡- 1. አቶ ገ/ስላሴ ኃ/ማርያም
2. ወ/ት እቴቱ ለማ
3. ወ/ት አማረች መንግስቱ
4. ወ/ሮ ለምለም እንዳለ
5. አቶ አካለወርቅ ሳልልህ
6. አቶ አርአያ ውብነህ
7. ወ/ሮ በቀለች ከበደ
8. አቶ እስማኤል ዓሊ

ጠበቃ ዘነበ ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ሆኖ በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ድርጅት ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- ተከሳሽ ድርጅት ባካሄደው የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ መሰረት በተጠናው የደመወዝ እስኬል ለእያንዳንዱ የሥራ መደብ መነሻ ደመወዝ ሲወሰን ከሳሾች በተመደብንበት የሥራ መደብ ማግኘት የሚገባንን ሲወስን ቀደም ሲል ስናገኝ የነበረውን ደመወዛችንን የቀነሰብን ስለሆነ ያለአግባብ የቀነሰብንን ደመወዝ መልሶ እንዲያስተካክልልን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ለክሱ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ፤-በተከሳሽ ድርጅት መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተደርጎ በመንግስት ከጸደቀ በኋላ በአማካሪ ድርጅት የተጠናውን አዲስ የደመወዝ እስኬል መነሻ በማድረግ ከሳሾች ክሱን ያቀረቡ ስለሆነና የደመወዝ ጭማሪን የሚመለከት ክስ የወል የሥራ ክርክር ስለሚሆን መቅረብ ያለበት ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በቀጥታ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ብሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ደ/መቃወሚያ ላይ በሠጠው ብይን፡- ከሳሾች ባቀረቡት ክስ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ጠቅላላ የደመወዝ እስኬል አሰራርን የሚነካ በመሆኑና ውጤቱም በሌሎች ሠራተኞች ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ

ተጽዕኖ ሊያስከትል ስለሚችል በወል የሥራ ክርክር የሚሸፈን በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ክሱን ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በሚል የክሱን መዝገብ ዘግቷል፡፡

የስር ከሳሾችም የመ/ደ/ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ቅር በመሠኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሠጠው ፍርድ ይግባኝ ባዮች ባቀረቡት ክስ ላይ የሚወሰነው ጭብጥ ተቋረጠብን የሚሉት የደመወዝ ጭማሪ ነው? ወይስ ድጎማ ነው? የሚለው ሲሆን በዚሁ ጭብጥ ላይ የሚሰጠው ውሳኔም ከይግባኝ ባዮች አልፎ የሁሉንም ሠራተኞች መብትና ጥቅም የሚነካ ባለመሆኑ ጉዳዩ በግል የሥራ ክርክር የሚታይ ነው በማለት የመ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በመሻር በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን ክርክሩን መልሶለታል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 147(2) መሰረት በወል ሥራ ክርክር የሚሸፈን ሆኖ እያለ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በግል የሥራ ክርክር የሚሸፈን ነው በማለት ጉዳዩን የሥራ ክርክር ችሎት እንዲወስነው የመለሰው ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሠጡት መልስ፡- ክሱ የቀረበው አመልካች ድርጅት ሲከፈልን በነበረው ደመወዝ ላይ መዋቅሩን መሥራት ሲገባው ደመወዛችንን በመቀነስ መዋቅሩን የሰራ በመሆኑ የቀነሰብንን ደመወዝ መልሶ እንዲያስተካክል ዳኝነት የጠየቅንበት እንጂ ክርክራችን በተሰራው መዋቅር ላይ ባለመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ክሱ በግል ሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ነው ሲል የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለው ሊጸና ይገባል በሚል ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ድርጅትም ለተጠሪዎች መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በወል የሥራ ክርክር የሚሸፈን ነው? ወይስ በግል ሥራ ክርክር የሚሸፈን ነው? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የግል የስራ ክርክሮች በመደበኛ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የሚታዩ ስለመሆናቸው ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 138 መገንዘብ የሚቻል ሲሆን የወል ሥራ ክርክር ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የሚታይ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 142(1)፣147(1)(ሀ) ተመልክቷል፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ምላሽ የሚሻው ጉዳይ ግን አንድ ጉዳይ የግል ወይም የወል የሥራ ክርክር ሊባል የሚችልበት አግባብ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/18180 በቀን 29/11/1997 ዓ/ም በዋለው ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በዚሁ የህግ ትርጉም መሠረትም አንድ ጉዳይ የወል የሚያሰኘው የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ሲሆን ክርክሩ የግል ነው የሚባለው ደግሞ ውጤቱ በተከራካሪ ሠራተኛ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሲሆን ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ቀደም ሲል ሲናገኝ የነበረውን ደመወዝ አመልካች ያለአግባብ በመቀነስ በተሰራው መዋቅር ላይ ያስቀመጠው ስለሆነ የቀነሰብንን ደመወዝ መልሶ እንዲያስተካክል ይወሰንልን በሚል ክስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም ቀደም ሲል በድጎማ መልክ ከደመወዛቸው ጋር ሲከፈላቸው የነበረው ገንዘብ ከደመወዛቸው ተቀንሶ በተሰራው መዋቅር ላይ ከመቀመጡ በስተቀር በደመወዛቸው እስኪል መሰረት ማግኘት የሚገባቸው ገንዘብ አልተቀነሰም በሚል ተከራክሯል፡፡ ይህ ከሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደግሞ ቀደም ሲል መዋቅሩ ከመሰራቱ በፊት ሲከፈላቸው የነበረው የደመወዝ መጠን የድጎማ ክፍያ ተጨምሮ ነው? ወይስ ሳይጨመር ነው? ድጎማው ተቀናሽ ተደርጎ በተሠራው መዋቅር መሰረት የደመወዝ እስኬል ሲቀመጥ ተጠሪዎቹ ማግኘት ከሚገባቸው የደመወዝ መጠን ቀንሷል? ወይስ አልቀነሰም? የሚሉ ነጥቦች ከተጣሩ በኋላ የሚሰጠው ውሳኔ ደግሞ ከተጠሪዎች አልፎ የሌሎች የድርጅቱን ሠራተኞች መብትና ጥቅም በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ ሊነካ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች መዋቅሩ ሲሠራ ቀደም ሲል ስናገኝ የነበረው የደመወዛችን እስኬል ተቀንሶብናል በማለታቸው ብቻ ጉዳዩ የወል ሥራ ክርክር ነው ሊባል የሚችልበት ምክንያት ባለመኖሩ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪዎቹ ያቀረቡት ክስ በግል የሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ነው ሲል በሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/115821 በቀን 10/7/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በግል የስራ ክርክር የሚሸፈን በመሆኑ ሊቀርብ የሚገባው ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ነው በሚል ከፍተኛው ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80350

ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- ሽራተን አዲስ - ጠበቃ ተካ አስፋው ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ገናናው ከበደ

2. አቶ ገ/ሥላሴ በላይ
3. አቶ ቢንያም እያሱ ወ/ኪዳን
4. አቶ አቢይ አድነው
5. አቶ ጮመረው ለማ
6. አቶ ተሻገር ትእግስቱ
7. አቶ ሳሙኤል ሹመት
8. ወ/ሪት መዓዛ ቁምላቸው
9. አቶ ኢዩቤል አሰፋ
10. ወ/ሪት እመቤት ፀሐይ
11. ወ/ሪት መሰረት ፍስሃ
12. አቶ ቦንያስ ስይፉ
13. አቶ ኤልያስ እንዳለ
14. አቶ ቴዎድሮስ አሸብር
15. አቶ ብርሃስላሴ ሐይሉ
16. ወ/ሪት ናርዶስ በላይ
17. አቶ ደጉ ተስፋዬ
18. አቶ ታዲዮስ ደርቤ
19. ወ/ት ሂሩት መልካ
20. ወ/ሪት ነጻነት በፈቃዱ
21. አቶ ብርሃነ ለገሰ
22. ወ/ሮ አነኒ ታደሰ
23. ወ/ት ባዩሽ ገብሬ
24. ወ/ት ስንዱ ሹምዬ
25. ወ/ት አስቴር ፍቅሩ
26. ወ/ሮ ሃና ዘሪሁን
27. አቶ ጌታቸው ተሾመ
28. ወ/ሮ አቦነሽ ክፍያው
29. ወ/ሪት እየሩሳሌም ታንኪ
30. አቶ ነጻነት ሽዋልዑል
31. ወ/ት ፍቅርተ ተፈሪ
32. ወ/ት አበባ እሸቱ
33. ወ/ሮ ጸጋነሽ ሄሊሶ
34. ወ/ት ጽጌሬዳ እሸቱ
35. ወ/ሮ አየለች ባነጫ
36. አቶ መላኩ ታደሰ
37. አቶ ፍቅረማሪያም ወርቅ
38. ወ/ት ሰርካለም አሰፋ
39. ወ/ት ሀይማኖት ጉተማ
40. አቶ ገረመው ወርቁ
41. ወ/ት አዜብ በየነ
42. ወ/ት አስናቀች ቢተው
43. አቶ ክብሮም ግደይ
44. አቶ ፈቃደ ታደሰ
45. ወ/ት ቃልኪዳን ሲሳይ
46. ወ/ት ሉባባ በያን
47. አቶ እዩብ ፅጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

48. አቶ ሱራፌል ፍቃደ
49. ወ/ት ረድኤት ታደሠ
50. ወ/ት ስርካለም ኤርምያስ
51. ወ/ት ሀረገወይን ባንቲ

- ለሁሉም ጠበቃ ግርማ ኃይሌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የቀረበውን የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች በፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪዎች ክስ ይዘት ሲታይም በአመልካች ድርጅት በተያለያዩ ጊዜአት ተቀጥረው የተለያዩ የአገልግሎት ዘመን እንዳላቸውና በባንኪቶት እና እስቲዋርዲንግ የስራ ዘርፎች እያገለገሉ እንደሚገኙ፣አመልካች ድርጅት በቅጥር ስርአት ላይ በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ ከተደነገገው ውጪ በሰራተኞች መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት በመፍጠር በተመሳሳይ የስራ ሰዓት ርዝመትና ስፋት የክፍያ ልዩነት በመፍጠር ለተጠሪዎች በሕግ የተሰጠውን መብት በመጣስ ከሕግ ጋር የሚጻረር ውል በማዘጋጀት እያስፈረመ በሕግ የተሰጣቸው ተገቢውን ክፍያና ጥቅማ ጥቅም መንፈጉን፣የስራ ሰዓት በወር 208 እንዲሆን በመገደብ በሰዓት ብር 5.50(አምስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) እያሰበ እንደሚከፍላቸውና በቀን ስምንት ሰዓት ለማሰራት በሕጉ የተጣለበትን የአሰሪነት ግዴታን ያለመወጣቱን፣ተመሳሳይ የሥራ መደብ ላላቸው ሰራተኞች የክፍያ ልዩነት መፍጠሩንና ለልዩነቱ የቅጥር ሁኔታ አልፎ አልፎ ለሚሰራ ስራ የተቀጠሩ ሰራተኛ እንደቋሚ ሰራተኛ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ሊጠበቁለት አይገባም በማለት በሕግ እውቅና የሌለውን ምክንያት መሰረት ማድረጉን ዘርዝረው ተጠሪዎች ለሰሩት ዘመን የተከለከሉትን ሰርቪስ ቻርጅ፣ቲፕ፣ቦነስ በሕግ አግባብ የስድስት ወር እንዲታሰብላቸው፣የአመት ፈቃድ፣የሕክምና አገልግሎት ፣የ24 ሰዓት የሰራተኞች የሕይወት ኢንሹራንስ ሽፋን፣የደመወዝ ጭማሪ፣ፕሮቪደንት ፈንድ የማጠራቀም መብት እንዲጠብቅላቸው እንዲሁም የትርፍ ስራ ሠዓት ሥራ ክፍያ፣የበዓላት እና የእሁድ ቀናት ስራ በመስራት ጥቅም የማግኘት መብት ዘርዝረውና በገንዘብ የሚተመነውን መብት መጠን በገንዘብ ለይተው ጥቅማ ጥቅሞችን የማግኘት መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪዎች የተቀጠሩት አልፎ አልፎ የሚሰራን ሥራ ለመስራት ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ሰርቪስ ቻርጅ፣ቦነስና ቲፕ የመክፍል፣የፕሮቪደንት ፈንድ መዋጮ የማድረግ፣ኢንሹራንስ የመግባት ግዴታ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ወይም በህብረት ስምምነት ወይም ሁለቱም ወገኖች በየግላቸው በተፈራረሟቸው የስራ ቅጥር ውሎች ግዴታ ያልተጣለበት መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ተቀባይት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ውል የጊዜ ገደብ ያለው ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ቢያስረዳም ተጠሪዎች ሲሰሩ የነበሩት ስራ ተከታታይነት ያለው ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን ገልጾ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜና ስራ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው፣እንዲህ ከሆነ በጥቅማ ጥቅም ማግኘት ደረጃ ከቋሚ ሰራተኞች የሚለዩበት ምክንያት የለም በማለት ለእየንዳንዳቸው በወር 4,956.70(አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከሰባ ሳንቲም) ታስቦ ክሱ ከመቅረቡ በፊት ላለው ስድስት ወራት በድምሩ ብር 1,576,230.60 (አንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ብር ከስልሳ ሳንቲም) ሰርቪስ ቻርጅ እንዲከፈላቸው፣አመልካች ድርጅት መደበኛ ሰራተኞች ለሚላቸው የሚሰጣቸው

ቲፕ (ጉርሻ) ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ እንዲያዝላቸው፣የአመት ፈቃድ ማግኘት መብታቸው እንደየአገልግሎታቸው እንዲያዝላቸው፣ፕሮቪደነት ፈንድ የማጠራቀም መብት እንዲጠበቅላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የበታች ፍርድ ቤት ሰርቪስ ቻርጁንና ጉርሻን በተመለከተ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ብቻ ሽሮ በሌሎች ነጥቦች ላይ የሰጠውን ውሳኔ ግን ሙሉ በሙሉ በማፅናት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ስራ አመልካች ድርጅት በመደበኛነት የሚሰራው ስራ ሳይሆን አልፎ አልፎ የሚሰራ በመሆኑ ግራ ቀኙ ይህንኑ ተገንዝበው ውል ያደረጉ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የውል ስምምነቱ ታልፎ ተጠሪዎች የሚሰሩት ስራ ተከታታይነት ያለው ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ለመደበኛ ስራተኞች የተጠበቁ መብትና ጥቅማ ጥቅሞች ለተጠሪዎችም ሊጠበቁ ይገባል ተብሎ የተወሰነው የአመልካች ድርጅትን የስራ ባህርይ፣የመዋዋል ነፃነትንና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 9፣10፣14(ረ)፣53(2) እና 134 ድንጋጌዎችንና ይዘትና መንፈስ ውጪ እንዲሁም ከአዋጁ ዓላማ ጋር እና አስገዳጅነት ያላቸውን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎችን ይዘት ባላገናዘበ መልኩ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖ እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ተጠሪዎች በሰጡት የፅሑፍ መልስ የተጠሪዎች የቅጥር ውል ሕጋዊ ያለመሆኑና ተጠሪዎች ለረዥም አመታት ይሰሩበት የነበረውና አመልካች አልፎ አልፎ የሚሰሩ ስራዎች ናቸው የሚላቸው በተከታታይነት የሚሰሩ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ከአመልካች ማስረጃዎች ጭምር ስለማረጋገጡ በመገንዘብ የሰጡት ውሳኔ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 11924 እና 25526 ከሰጣቸው አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች፣ከአለም አቀፍ የሰራተኞች ድርጅት ደንብና አግባብነት ባላቸው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕግ መንግስት ድንጋጌዎች መሰረት የተሰጠ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ አስገዳጅነት ያላቸው የሰበር ችሎት ውሳኔዎች ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጡት ተገቢውን ማጣራት አድርገው ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች አመልካችን ሊከሱት የቻሉት ቅጥሩ አልፎ አልፎ ለሚሰራ ስራ የተደረገ ነው በሚል ምክንያት በሕጉ ሊጠበቁ የሚገባቸውን ጥቅማ ጥቅሞችን አልጠበቀልንም፣ከልክሎናል በሚል ምክንያት ሲሆን አመልካች ተጠሪዎች ይገባናል የሚሏቸውን መብቶች የከለከላቸው መሆኑን ሳይክድ እርምጃውን ሕጋዊ በማለት ነው የሚከራከረው የተጠሪዎች ቅጥር አመልካች በመደበኛነት የሚሰራቸውን ስራዎች ለማሰራት የተደረገ ሳይሆን አልፎ አልፎ የሚያጋጥሙት ስራዎች እንደ ስብሰባ ዝግጅት፣የሰርግ ፣የፌስቱቫል እና የምርቃት ፓርቲ፣ክብረ በዓላት እና ኢየቤልዩ ሲከበር የሚሰሩትን ስራዎች ለመስራት አውቀውና ወደው በውል በመተሳሰር ተጠሪዎች ስራዎቹን ሲሰሩ የቆዩ በመሆኑ ለመደበኛ ስራ ሰራተኞች የተጠበቁት ጥቅማ ጥቅሞች ሊጠበቅላቸው አይገባም፣ከውል ወይም ከህግ የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መሆኑን ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበውን የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት ተጠሪዎች አመልካች አልፎ አልፎ የሚሰሩ ስራዎች ናቸው የሚላቸውን በተከታታይ ፕሮግራም እየወጣላቸው ሲሰሩ የነበሩ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡ ስራዎቹ ቀጣይነት ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው በሚል ምክንያት መሆኑንም ከውሳኔዎቹ ግልባጮች ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ሕግ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 9 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ ይህ የሕግ ግምት ሊስተባበል የሚችለው በተጠቀሰው አዋጅ አንቀፅ 10 በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት ነው፡፡ አሰሪው በዚህ አንቀጽ ስር በተመለከቱት ሁኔታዎች ቅጥሩ መፈፀሙን ካስረዳ በአዋጁ አንቀጽ 9 ስር የተመለከተውን የሕግ ግምት እንዳስተባበለ የሚቆጠር ሲሆን እርምጃውም ከዚሁ አንጻር ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ የሥራው ባህርይ ቀጣይነት ያለው መሆኑ እየታወቀ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል ጊዜን በመቁረጥ የሚደረግ የቅጥር ውል ስምምነት ሕጋዊ ጥበቃ የማይደረግለት ስለመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁጥር 11924፣25526 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 10(ሐ) መሰረት ተደርጎ የተመሰረተ መሆኑ ያልተካደ ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክርና በክርክሩ ሂደት የተረጋጠውን ፍሬ ነገር ተጠሪዎች የሚሰሩት ስራ ቀጣይነት ያለውና አመልካች ድርጅት መደበኛ ስራ ላይም ተጠሪዎችን ማሰራቱ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ሳይቀበሉት ቀርተዋል፡፡ በእርግጥ ከላይ የተጠቀሱት አስገዳጅነት ያላቸው የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች የስራው ባሕርይ ቀጣይነት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ አሰሪ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 10 መሰረት የስራ ውሉ ተደርጓል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው እንደማይገባ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የሰበር ሰሚ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መንፈሱ በጥንቃቄ ታይቶ ግንዛቤ ካልተወሰደበት ከሕጉ ዓላማና መንፈስ ጋር የማይሄድ ውጤትን ማስከተሉ የማይቀር መሆኑ እሙን ነው፡፡ ስለሆነም የስራው ባሕርይ ቀጣይነት ያለው ነው ለማለት መታያት ያለበት ነጥብ ስራው ለተከታታይ ሳምንታት፣ወራት ወይም አመታት በገበያው አመቺነት ምክንያት መቀጠሉን ነው ወይስ ከገበያው ምቹነት ሳይሆን ስራው ራሱ ብቻውን ሲታይ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው? ከሚለው ጥያቄ ጋር ሊለይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህም አግባብ ጉዳዩ ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 10 መሰረት ተደረገ ተብሎ የሚቀርበውን የቅጥር ውል ውድቅ ለማድረግ የስራው ቀጣይነት የሚለው መለኪያ መሰረት ማድረግ ያለበት ስራው በገበያው አመቺነት ረዘም ላሉ ጊዜያት መሰራቱን ብቻ ሳይሆን ስራውን በባህርው እና ከድርጅቱ መሰረታዊ አላማ ጋር ተዛምዶ ሲታይ ቀጣይነት ያለው መሆኑ መረጋገጥን ጭምር የሚጠይቅ ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ ድምዳሜ ውጪ የሚያዘው ድምዳሜ በአንድ ድርጅት ላይ ተገቢ ያልሆነ የሰው ኃይል እንዲኖር የሚያደርግ እና የድርጅቱን ተወዳዳሪነት በመፈታተን ለአገር ኢኮኖሚ ሊጫወተው የሚገባውን ሚና ሁሉ የሚገድብ ነው፡፡ የአንድን ድርጅት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለአገር ኢኮኖሚ የሚያበርክተውን አስተዋጽኦ የሚገድብ እርምጃ ደግሞ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ዓላማን የሚጻረረ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን አከራክሮ ለመወሰን ስልጣን የተሰጠው አካል አንድን ስራ በባሕርይው ቀጣይነት ያለው ነው ብሎ ለመደምደም ስራው ረዘም ላለ ጊዜ መሰራቱን ብቻ ሳይሆን የስራው ባህርይ ከድርጅቱ አይነተኛ ስራ ጋር የሚሄድና ቀጣይነት ያለው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ይህ ድምዳሜ ሲያዝም የድርጅቱ አጠቃላይ ተቋማዊ ሁኔታው በውል ሊታወቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይገባል፡፡ ይኼውም ድርጅቱ የተቋቋመበት ዓላማ፣ሊሸከመው የሚገባው የሰራተኛ ቁጥርና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በተገቢው መንገድ ተጣርተው ሊታወቁ ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች የተቋቋመበት መደበኛ የመኝታ፣የምግብና የመጠጥ አገልግሎቶችን መስጠት መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪዎች ይሰሩበት የነበረውን ስራ አልፎ አልፎ የሚሰራና የአመልካች ድርጅት መደበኛ ስራ ያለመሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሚሰራቸው መደበኛ ስራዎች አይነት እና ብዛት፣በእነዚህ መደበኛ ስራዎች የሚይዛቸው የሰራተኞች ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ፣አመልካች አልፎ አልፎ የሚሰራቸው ስራዎች አመልካች በቀጣይነት የሚሰራቸው መሆን ያለመሆኑ፣ስራዎቹ በቀጣይነት የሚሰሩበት ሁኔታ እንዴት ሊከሰት እንደሚችልና የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና ስራውን ለመስራት በቀን ወይም በወር ለአንድ ሰራተኛ ሊመደብ የሚችለው የስራ ሰዓት ምን ያህል እንደሆነ በአመልካች ማስረጃም ሆነ በተጠሪዎች ማስረጃ ነጥረው የወጡ ነጥቦች አይደሉም፡፡ ፍርድ ቤቱም የሚመለከታቸውን አካላት እንዲያጣሩለት ያደረገበት የክርክር አመራር ደረጃ ያለመኖሩን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በክርክሩ ሂደት የተነሱትና ለጉዳዩ አወሳሰን ወሳኝ የሆኑት ፍሬ ነገሮች በማስረጃ ሳይነጥሩ ትክክለኛና ፍትሃዊ ዳኝነት መስጠት የማይቻል መሆኑን የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓታችን ያስገነዝበናል፡፡ ዳኝነት ሰጪ አካል የሆነው ፍርድ ቤት በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የተከራካሪ ወገኖችን ማስረጃ አስቀርቦ ሣይመለከት፤ሳይሰማና ከተያዘው ጭብጥ ጋር አገናዝቦ ሣይመረምር በሕግ ባልተመለከተ ምክንያት የማስረጃ መሰማት መብትን በማለፍ ወይም ፍርድ ቤቱ ራሱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲባል ሊነጥር የሚገባውን ፍሬ ነገር ራሱ በሚያስቀርበው ማስረጃ ሳያነጥር ፍርድ የሚሰጥበት አካሄድ የዳኝነት አሰጣጥ ስርኣታችን የሚቀበለው ጉዳይ አይደለም፡፡ በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረው ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ሣያጣሩ መወሰን ደግሞ መሰረታዊ የሆነ የፍርድ አካሄድ ጉድለት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136፣137፣145፣264፣272፣345 እና ሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡን ሐቅም ይኼው ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተመለከቱት ፍሬ ነገሮች በተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች ወይም በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በሚቀርቡ የሚመለከታቸው አካላት ወይም የባለሙያ ማስረጃዎች ባልነጠሩበት ሁኔታ የተጠሪዎች ስራ አልፎ አልፎ የሚሰራ አይደለም ተብሎ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ባልተሟላ የፍርድ አካሄድ የተሰጠና በአመልካች ድርጅት ላይም ተገቢ ያልሆነ የሰራተኛ ኃይል የመጫን ውጤት ያለው በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ስለአገኘን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 61589 ጥር 14 ቀን 2004 ዓ/ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 116137 ግንቦት 27 ቀን 2004 ዓ/ም ተሻሽሎ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የሚሰራቸው መደበኛ ስራዎች አይነት እና ብዛት፣በእነዚህ መደበኛ ስራዎች የሚይዛቸው የሰራተኞች ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ፣አመልካች አልፎ አልፎ የሚሰራቸው ስራዎች በቀጣይነት የሚሰራቸው መሆን ያለመሆኑ፣ስራዎቹ በቀጣይነት የሚሰሩበት ሁኔታ ከነበረና ካለም እንዴት ሊከሰት እንደቻለና ወደፊትም ሊከሰት የሚችልበት ሁኔታ መኖር ያለመኖሩን፣ለስራዎቹ የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና ስራውን ለመስራት በቀን ወይም በወር ለአንድ ሰራተኛ ሊመደብ የሚችለው የስራ ሰዓት ምን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያህል ነው? የሚሉትን ፍሬ ነገሮችን፤ የአመልካችን ድርጅታዊ አቋም ባጠቃላይ ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ በማጣራት ክርክሩን በመዝገብ ቁጥር 61589 እንዲቀጥል በማድረግ ጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80079

ህዳር 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- የመቶ አለቃ ጥላሁን ታችበሌ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች ከሥራ በጡረታ ምክንያት በአሰሪ መሰናበታቸው እና ተፈፃሚነት ያለው ሕግ የሕብረት ስምምነት ነው ወይስ የጡረታ አዋጅ ነው የሚለው የሕግን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለመመርመር ነው፡፡ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት ያቀረቡት ክስ በተጠሪ ድርጅት በጥበቃ ሰራተኝነት ተቀጥረው እስከ ታህሣሥ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ማገልገላቸውና ተጠሪ ድርጅት ጡረታን ምክንያት አድርጎ መብታቸውን ሳይጠብቅ ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውላቸውን ያቋረጠ በመሆኑና ስንብቱ ሕገወጥ በመሆኑ ሕጉ በሚፈቅደው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጠይቋል፡፡ ተጠሪ ድርጅት በሰጠው መልስ በድርጅቱ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 32.5 መሠረት ተጠሪ የሠራተኞችን የጡረታ መውጫ ጊዜ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጠው መሆኑ አመልካችም ዕድሜያቸው 55 ዓመት የሞላቸው በመሆኑ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የፕሮቪደንት ፈንዳቸው ተከፍሏቸው በልዩ ሁኔታም የሁለት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ተሰናብቷል፡፡ ስንብቱም በአግባቡ የተከናወነ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር ያደመጠው የሥር ፍርድ ቤት ስንብቱ በሥራ ላይ ባለው የሕብረት ስምምነት የተፈፀመ በመሆኑ ሕጋዊ ነው፡፡ ምንም ክፍያ መጠየቅ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡ በይግባኝ ሥልጣኑ የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት የይግባኝ ባይ ቅሬታን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን አፅንቷል፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤቱ ፈጽሞታል ያሉትን የሕግ ስህተት በመዘርዘር ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ በአመልካች አቤቱታ ከተዘረዘሩት የቅሬታ ነጥቦች የጡረታ ዕድሜ በሕግ እንጂ በሕብረት ስምምነት ሊወሰን እንደማይገባ፤ አሰሪው /ተጠሪ/ ተቋም ሕገወጥ ስንብት የፈፀመ በመሆኑ የ6 ወር ደመወዝ በካሣ መልክ እንዲከፍላቸው እንዲወሰንላቸው አመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ምድብ 1ኛ የሥራ ክርክር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በመ/ቁ 62433 ህዳር 11 ቀን 2004 ችሎት የጡረታ ዕድሜ አግባብ ባለው ሕግ እንጂ

በሕብረት ስምምነት የሚወሰን አይደለም በማለት የሰጠው ውሣኔ እንዲታይላቸው አያይዘው አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት በተጠሪና በሠራተኞች ማህበር መካከል በተፈረመው የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 32.5 መሠረት ነው፤ ተዋዋይ ወገኖችም የጡረታ ዕድሜን ሊወሰኑ እንደሚችሉ የሕብረት ስምምነቱን የፈረሙት ተዋዋይ ወገኖች የተስማሙ በመሆኑና አመልካች በዚህ አግባብ በሕጋዊ መንገድ የተሰናበተ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው እንዲባልለት አመልክቷል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቅሬታቸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚገዙ ሠራተኞች የጡረታ ዕድሜ የሚወሰነው አግባብ ባለው ሕግ ነው ወይስ በሕብረት ስምምነት? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች በግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር በጥበቃ ሠራተኛነት ሲሰሩ እንደነበረ፤ በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 32.5 መሠረት 55 ዓመት የሞላቸው በመሆኑ በጡረታ ከሥራ እንዲሰናበቱ ተጠሪ መወሰኑ ከሥር ፍርድ ቤቶች መዝገብ መገንዘብ ተችሏል፡፡ አመልካች የጡረታ ጉዳይ መታየት ያለበት በሕግ እንጂ በሕብረት ስምምነት አለመሆኑን አጥብቀው ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩሉ የሕብረት ስምምነቱ በተጠሪ ድርጅት እና በሠራተኛ ማኅበር የተፈረመና ተግባራዊ መሆኑ ከሕግ እንደማይቃረን አመልክቷል፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የነበረው የሥራ ውል ግንኙነት ከሚቋረጥባቸው መንገዶች አንዱ ሠራተኛው በጡረታ ሲገለል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ጭብጥ የጡረታ መውጫ ጣሪያ ዕድሜ ስንት ነው? በሕግ ነው የሚወሰን ወይስ በሕብረት ስምምነት የሚለው ነው፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የጡረታ ዕድሜ ጣሪያ በግልጽ አልደነገገም፡፡ ይሁንና አዋጁ በአንቀጽ 24/3/ “ሠራተኛው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በጡረታ ሲገለል” የሥራ ግንኙነቱ በሕግ አግባብ የተቋረጠ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በአሰሪና ሰራተኛ ማህበር የሚፈረመው የሕብረት ስምምነት በተመሣሣይ ጉዳይ ለሠራተኛው በሕግ ከተደነገገው ይልቅ የሕብረት ስምምነቱ የበለጠ ጥቅም የሚሰጠው ከሆነ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው በአንቀጽ 134/2/ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ያለፈቃዳቸው በጡረታ ከሥራ እንዲሰናበቱ የተደረገ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪም የስንብት ድርጊቱ የተፈፀመው ለሠራተኛው የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በስንብት ስርዓቱ የሕብረት ስምምነት የተፈፀመ ነው ይበል እንጂ የሕብረት ስምምነቱ አግባብነት ካለው ሕግ በተሻለ መንገድ ለሠራተኛው የጠቀመ ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ክርክር አልተረጋገጠም፡፡ ስለሆነም የሕብረት ስምምነቱ የጡረታ ዕድሜን ከመወሰን አኳያ የተፈፃሚነት ወሰን ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም በቀር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሁለት የተለያዩ ምድብ ችሎቶች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24/3/ አተረጓጎም ላይ የተለያየ አቋም ወስደዋል፡፡ ይህ ደግሞ አዋጁን ወጥ በሆነ አግባብ ከመተርጎም አንፃር የራሱ የሆነ ውስንነት እንዳለው እንዲሁም የተከራካሪ ወገኖችን በሕግ ፊት እኩል የመዳኘት መብት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ አንደኛው ምድብ ችሎት በሕብረት ስምምነት የተወሰነውን የጡረታ ዕድሜ ጣሪያ ሲቀበል ሌላኛው ምድብ ችሎት አግባብነት ያለው ሕግ ማለት የሕብረት ስምምነት አለመሆኑን በመጥቀስ ውድቅ አድርጐታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አከራካሪው ጉዳይ አግባብነት ያለው ሕግ የምንለው የትኛው ነው የሚለው ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው የሕብረት ስምምነቱ በአንቀጽ 24/3/ የተመለከተውን ትርጓሜ የማይካተት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሕግ የምንለው ሥልጣን ባለው አካል የወጣ ሕግ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ የሕግ አወጣጥ ሥርዓት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በአስፈፃሚው አካል የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የሚያካትት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የጡረታ ዕድሜ መውጫን በተመለከተ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የተለያየ የዕድሜ ጣሪያ የተቀመጠ ቢሆንም በሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አዋጅ እንዲሁም የግል ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 17/1/ የሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜ 60 ዓመት መሆኑን ደንግጓል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሕግ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አዋጅ እንደ አግባብነቱ ወይም የግል ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ሆኖ ሳለ የሕብረት ስምምነቱን መውሰዳቸው መሠረታዊ የሕግ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት በኮ.መ.ቁ 63787 በ27/02/2004 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 115690 በ02/8/2004 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. ግሎባል ሆቴል ኃላ.የተ.የግል ማህበር እና የተቋሙ ሠራተኞች ማህበር የፈረሙት የሕብረት ስምምነት የጡረታ መውጫ ዕድሜን በተመለከተ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፡፡
3. ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር በተነሱት የክፍያና ተያያዥነት ያላቸው የመብት ጥያቄዎችን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79853

ህዳር 04 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን ነገረ ፈጅ አቶ ጌታቸው ለማ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ጌታቸው ደበበ ቀረቡ

2. አቶ ሽመልስ ኃይሉ ቀረቡ

3. ወ/ሮ ካሦች በርሄ ቀረቡ

4. ወ/ሮ እመቤት መ·ሉጌታ ቀረቡ

5. ወ/ሮ ፋናዬ ኢያኮ ቀረቡ

6. ወ/ሮ ምላነሽ ተሰማ ቀረቡ

7. አቶ ወዳጄ ስጦታው ቀረቡ

8. ወ/ሮ መኪያ ከድር ቀረቡ

9. አቶ ወጋየሁ አበራ ቀረቡ

10. አቶ አማረ ወርቁ ቀረቡ

11. አቶ ጀማል ሞሳ ቀረቡ

12. ወ/ሮ በቀለች ፀጋዬ ቀረቡ

13. ወ/ሮ ሸሸግ ኃይሌ ቀረቡ

14. አቶ ብርሃኑ ጐንፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 116131 ሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት አለበት በማለት ፍርዱ እንዲሻር እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 19101 ጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ይፀና ዘንድ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ተከሣሽ ሲሆን ተጠሪዎች ከሣሾች ነበሩ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩን አመጣጥ ስንመለከት ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ተከሣሽ /በአሁኑ አመልካች/ በተለያዩ ጊዜያት በጉልበት፣ በፌራዮነትና ረዳት ፌራዮነት በተለያየ የደመወዝ መጠን ቀጥሮ ሲያሰራን ቆይቶ አለአግባብ ከሥራ ያሰናበተን ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ሥራችን ይመልሰን ዘንድ ይወሰንልን ካልሆነም ያለአግባብ የሥራ ውሉ መቋረጥ ጋር በተያያዘ ሊከፍለን የሚገባውን ክፍያዎች ይከፍለን ዘንድ ይወስንልን የሚል ነው፡፡

ተከሣሽ /የአሁኑ አመልካች/ በሰጠው መልስ ከሣሾች /የአሁኑ ተጠሪዎች/ የደመወዝ መጠን የተለያየ መሆኑ የሥራ ውሉም የተቋረጠው ተጀምሮ የነበረው የፕሮጀክት ሥራ በመጠናቀቁ ስለሆነ የጠየቁት ክፍያ የሚገባቸው አይደለም ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተከሣሽ /የአሁኑ አመልካች/ ከሣሾችን /የአሁኑ ተጠሪዎች/ ሥም ዝርዝር ያለበትና በተለያየ ሙያ ሲሰሩ መቆየታቸው እና የበጋ ወራት ከጥቅምት 01 ቀን ጀምሮ ፕሮጀክቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የተቀጠሩ ለመሆናቸው የሚያሣይ ሰነድ ከሐምሌ 02 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የሥራ ውሉ የተቋረጠ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ያቀረበ ሲሆን ይህም ከሣሾች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑ ያመለክታል፡፡ 2ኛ እና 4ኛ ከሣሾችም ያቀረቡት የምስክር ወረቀት ላልተወሰነ ጊዜ ለመቀጠራቸው አያመለክትም በማለት ተከሣሽ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 77 መሠረት የዓመት ዕረፍት የ14 ቀን ክፍያ ለከሣሾች ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

ከሣሾችው በውሣኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሥራ ክርክር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ መልስ ሰጪ ቅጥሩ ለተወሰነ ጊዜ ነው ቢልም የሥራ ቅጥር አላቀረበም፣ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎችም ውስጥ ለውስጥ ራሱ የተፃፃፈባቸው ናቸው፣ ይግባኝ ባዮች ከ6 እስከ 14 ዓመት ያገለገሉ ለመሆናቸው ተረጋግጧል፣ ቋሚ ሰራተኞች ናቸው ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ፣ መልስ ሰጪ ለይግባኝ ባዮች የስንብት ካሣ፣ የማስጠንቀቂያ እና የዓመት ዕረፍት ክፍያዎችን ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በተወካዩ አማካኝነት ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ አጠር ባለመልኩ፡- ተጠሪዎቹ ለ2002 ዓ.ም የበጀት ዓመት ለበጋ ወራት መቀጠራቸው እየታወቀ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪዎቹ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ናቸው ሲል መወሰኑ የሕግ ሥህተት ነው ማስረጃችንንም አልመረመረም፡- ተጠሪዎቹ የቅጥር ጊዜ በማለት በክስ ማመልከቻቸው ላይ ከመግለፃቸው ባለፈ በማስረጃ ሣያረጋግጡ ተጠሪዎች ከ6 እስከ 14 ዓመት ድረስ አገልግለዋል ሲል ፍ/ቤቱ መወሰኑ፤ ተጠሪዎቹ የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑ የሥር ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24/1 መሠረት የሰጠውን ውሣኔ ቅጥሩ በአዋጁ አንቀጽ 39 እንደሆነ በማስመሰል የስንብት ካሣ ክፍያ ይከፈል ሲል መወሰኑ የሕግ ሥህተት ፈጽሟል፡፡ ተጠሪዎቹ የቀን ሰራተኞች እንደመሆናቸው መጠን በወር 22 ቀናት እንደሚከፈላቸው እየታወቀ ክፍያው በ30 ቀናት እንዲታሰብ ማድረጉ አግባብ ስላልሆነ፤ ችሎቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ያፅናልኝ የሚል ነው፡፡

ችሎቱ የሰበር አቤቱታውን መርምሮ ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት :“ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለፕሮጀክት ሥራ መሆኑንና ሥራው መጠናቀቁን አመልካች ቢያስረዳም፣ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪዎች በክሳቸው ላይ

የገለፁትን የአገልግሎት ዘመን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎች ለረዥም ጊዜ ሲሰሩ የቆዩ በመሆናቸው ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል በማለት የተለያዩ ክፍያዎችን ይከፈላቸው በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት ይቅረብ " ሲል አዟል።

የሰበር ችሎቱ ተጠሪዎቹ የሰበር አቤቱታው እንዲደርሣቸው በማድረግ፣ መልስ እንዲሰጡበት ያደረገ ሲሆን ተጠሪዎቹ ሐምሌ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት 4 ገጽ መልስ፡-ተጠሪዎች ከ2002 ዓመት በፊት ለመሥራታችን የ1999 ዓ.ም እና የ2000 ዓ.ም የመልካም ሥራ አፈፃፀም የምስክር ወረቀት አቅርበናል። መልስ ሰጪ ከ6 እስከ 14 ዓመት ላለመስራታችን አላስተባበለም " እኛ ግን ምስክሮቻችን አስረድተውልናል" ተጠሪዎች የተቀጠርነው በዋና ቱቦ ማምረቻ ምርት ክፍል ሲሆን ሥራው በጋ እና ክረምት ሣይል ሁሌ የሚሰራበት ነው። አመልካች ተጠሪዎች የቀጠርኳቸው ለበጋ ጊዜ መንገድ ሥራ ነው ያለ ቢሆንም በየትኛው የአስፋልት ሥራ ለመሆኑ አልጠቀሰም።
ደሞዝን በተመለከተ አመልካች ይከፍለን የነበረው በወርሃዊ የሂሣብ ክፍያ ሲሆን ቅዳሜ እና እሁድ እናርፍ የነበረው በዓላት በመሆናቸው ነው።

ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለሆነ የተፈፀመ የሕግ ሥህተት የለም በማለት ውሣኔውን በማጽናት ያሰናብተን የሚል ነው።
አመልካች ነሐሴ 17 ቀን 2004 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የመልስ መልስ የአመልካች መሥሪያ ቤት ከተቋቋመበት እስከ ተጠሪዎች ስንብት ድረስ 12 ዓመት ከ3 ወር የሚሆነው ሲሆን፤ ተጠሪዎቹ እስከ 14 ዓመት ድረስ የአገልግሎት ጊዜ ነበረን ማለታቸው እውነታ የሌለው ነው።
የምስክር ወረቀትን በተመለከተ ከ2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በስተቀር ምስክር ወረቀት ያቀረበ የለም። ምስክር ወረቀቱም ቢሆን በየዓመቱ ለሠራተኛ የሚሰጥ እንጂ ቋሚ ሥራን የሚመለከት አይደለም።
ተጠሪዎች በጊዜያዊነት የተቀጠሩት በቱቦ ሥራ ፕሮጀክት ቢሆንም ቅጥራቸው ለበጋ ወራት አስፋልት ሥራ ፕሮጀክት ነው የሚል ነው።
ችሎቱም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎቹ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ቋሚ ሠራተኞች ናቸው ሲል በመወሰኑ፣ የፈፀመው መሠረታዊ የሕግ ሥህተት አለ ወይስ የለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሯል።
ፍ/ቤቱ አመልካች ተጠሪዎችን ለተወሰነ ጊዜ ቀጥሯቸዋል ያለበት ምክንያት አመልካች የሥራ ቅጥር ውል አላቀረበም በሚል ነው። ግራ ቀኙ የሥራ ቅጥር ውል ያላቸው ለመሆኑ አልተካካዱም። አመልካች የሥራ ቅጥር ውል ካላቀረበ ቅጥሩ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው ሊባል የሚችልበት ሁኔታ የለም።
የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪዎች ናቸው ያለበት ሌላው ምክንያት አመልካች ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ለውስጥ የተፃፃፉባቸው ናቸው በሚል ነው። አመልካች ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ለቀረበው ክስ እና ለተያዘው ጭብጥ አግባብነት አላቸውን? በሚለውን ጥያቄ ዙሪያ መታየት ያለበት የሥራ ቅጥሩ ለተወሰነ ጊዜ ነው ወይስ ላልተወሰነ ጊዜ የሚለውን ጭብጥ ከማስረዳት አንፃር ታይቶ መወሰን ሲገባው ሰነዶቹ አመልካች ራሱ የተፃፃፉባቸው ናቸው በሚል ምክንያት ብቻ ውድቅ የሚደረጉበት አግባብ የለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሥር ፍ/ቤትም ቢሆን አመልካች ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በማስረጃነት የተቀበላቸው ማስረጃዎቹ የሥራ ቅጥሩ ለፕሮጀክት ሥራ ሆኖ የበጋ ወራት የአስፋልት ሥራ መሆኑን እና ሥራውን ማብቃቱ የሚያመላክቱ በመሆናቸው ሲሆን እነዚህ ማስረጃዎች ለተያዘው ጭብጥ አግባብነት የሌላቸው ስለመሆኑ ያስተባበሉት ነገር የለም፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎቹ ከስድስት እስከ አስራ አራት ዓመት የሥራ አገልግሎት አላቸው ሲል የደመደመው ተጠሪዎቹ በክስ ማመልከቻዎቻቸው ጠቅሰውታል በሚል እንጂ ተጠሪዎቹ ይህን ያህል የአገልግሎት ዘመን ያላቸው ባለመሆኑ ያመለከቱበት ደጋፊ ማስረጃ የለም፡፡

2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በ1999 ዓ.ም እና 2000 ዓ.ም ተሰጠን የሚሉት የመልካም ሥራ አፈፃፀም የምስክር ወረቀትም ቢሆን አመልካች ይህ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ምስክር ወረቀት ለሁሉም በየዓመቱ የሚሰጥ ነው በማለት የተከራከረ ሲሆን ማስረጃው ሁለቱ ተጠሪዎች በተጠቀሱት ሁለት ዓመት የምስክር ወረቀቶቹ የተሰጣቸው ለመሆኑ ከሚያሣይ በስተቀር ተጠሪዎቹ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ለመሆኑ የሚያሣይ አይደለም፡፡ አመልካች ተጠሪዎች የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ነው በማለት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪዎቹ አላስተባበሉም፡፡

ተጠሪዎቹ የተቀጠርንበት የቱቦ ሥራ ቀጣይነት ያለው ነው ያሉ ቢሆንም ተጠሪዎቹ ቀጣይነት ባለው የቱቦ ሥራ ለተወሰነ የሥራ ጊዜ የተቀጠሩ ከሆነ ሥራው ቀጣይነት ስላለው ብቻ ቅጥሩ ላልተወሰነ ጊዜ ነው በማለት ፍ/ቤቱ መወሰኑ የሕግ ሥህተት ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 116131 ሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 191001 ጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሠረት ፀንቷል፡፡

3. ተጠሪዎቹ ለተወሰነ የሥራ ጊዜ የተቀጠሩ ናቸው፡፡

4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን የየራሣቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79212

ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ.ም .

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- ሮያል ከረሜላ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ አቶ መድህን መሐሪ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ፀሐይ ብርሀኑ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጠሪ የሥራ ስንብት በአሠሪው (በአመልካች) አነሣሽነት የተፈፀመ ነው ወይስ በተጠሪ (በሠራተኛዋ) ጠያቂነት የተፈፀመ ነው የሚለውን ጭብጥ የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከህግ ውጭ ከሥራ ያሰናበተችኝ በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የተለየዩ ክፍያዎች እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ሥራቸውን በፈቃዳቸው የለቀቁት ከቅርብ አለቃቸው ጋር ባለመግባባታቸው ነው፡፡ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ (ከሣሽ) ወደ ሥራቸው እንድትመለስ በቃልና በጽሑፍ የጠየቋት ቢሆንም ከሣሽ (ተጠሪ) ወደሥራዋ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነችም፣፣ ከሣሽ (ተጠሪ)ን ከሥራ ለማሰናበት ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ የሥራ ውላቸው አልተቋረጠም፡፡ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ ፈቃድ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአሠሪው ነው ወይስ በሠራተኛው ተነሣሽነትና ፈቃድ የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ ተጠሪ ሥራውን የለቀቅሁት የቅርብ አለቃዬ ሥራውን እንድለቅና እንድሄድ ስላዘዙኝ ነው በማለት ጭብጥ አስይዘው ምስክሮች አስምተዋል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የተጠሪ የቅርብ አለቃ ተጠሪን ከሥራ ውጪ ካላት በኃላ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የቀረበችበት ደመወዝ ተከፍሏት ከቅርብ አለቃዋ ጋር የተፈጠረው ችግር ተስተካክሎ ሥራውን ለመቀጠል የምትችል መሆኑን ተጠይቃ ተጠሪ እንቢተኛ መሆኗን አመልካች አስረድቷል፡፡

ስለዚህ ተጠሪን ከሥራ የማስናበት ሥልጣን የሌለው ሰው ከሥራ ውጪ በማለት ተናግሮኛል በማለት ወደ ሥራ እንድትመለስ ብትጠየቅ እንቢተኛ በመሆኗ የሥራ ውሉ የተቋረጠ በመሆኑ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፈቃድ (አነሣሽነት) ነው በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ ብር 520 (አምስት መቶ ሃያ ብር) የዓመት እረፍት ፈቃድ በገንዘብ ተቀይሮ ብር 190.67 (አንድ መቶ ዘጠና ብር ከስልሣ ሰባት ሣንቲም) እና የዘጠኝ ቀን ደመወዝ ብር 48 (አርባ ስምነት ብር) እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ይግባኝ ባይ በቅርብ አለቃቸው ከሥራ እንዲወጡ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡ የይግባኝ ባይ የቅርብ አለቃ ሠራተኛ የማሰናበት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑና ይግባኝ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ተጠይቀው ወደ ሥራ ለመመለስ አለመስማማታቸው ስንብቱን ህጋዊ አያደርገውም፡፡ ስለዚህ አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ በመሆኑ፣ የመጀመሪያ ደረጃው ፍርድ ቤት ከወሰናቸው ክፍያዎች በተጨማሪ የካሣ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ መልስ ሰጭ ለይግባኝ ባይ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የቅርብ አለቃዋ ሥራዋን እንድታቋርጥ ከተናገራት በኃላ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ ስራዋን እንድትቀጥል የነገራትና እንቢተኛ ሆና ከሥራ ገበታዋ የቀረች መሆኑ እንደተረጋገጠ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሯል፡፡ ይህ ፍሬ ጉዳይ ህግ ወጥ ስንብትን ያሣያል በማለት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረታዊ ዓላማ ያልተከተለና የህግ መሠረት የሌለው ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በቅርብ አለቃዬ ተዘልፌና ሞራሌ ተነክቶ ነው፡፡ ሥራ አስኪያጁም ይህንን የቅርብ አለቃዬን ተግባር ደግፈዋል፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው መባሉ ተገቢ ነው በማለት ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም መልስ ሰጥታለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ካላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበታት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ የማስጠንቀቂያና የካሣ ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርመረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የተጠሪ የቅርብ አለቃ ተጠሪን ከስራ እንድትወጣ የተናገራት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተጠሪ የቅርብ አለቃ ተጠሪን ሥራ ለቅቃ እንድትወጣ ከተናገራት በኃላ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪን ቢሮ ድረስ በማስጠራት በቅርብ አለቃዋ የተሰጠው ትእዛዝ ተገቢ እንዳልሆነ፣ የቀረችበት ቀን ደመወዝ እንደሚከፈላትና ወደ ሥራዋ እንድትመለስ ጠይቋት ተጠሪ ወደ ሥራ ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነች መሆኑን የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪን ሥራ ለቅቃ እንድትሄድ የተናገራት የተጠሪ የቅርብ አለቃ በድርጅቱ ያለው ኃላፊነት በሥራ መሪነት የሚያስመድበውና፤ በሥራ መሪነቱ የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነትም ሠራተኛ ለማሰናበት የሚያስችለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) በአዋጅ ቁጥር 494/98 እንደተሻሻለው ተጠሪ አላስረዳችም፡፡ በሌላ በኩል የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የቅርብ አለቃ ስራዋን እንድትለቅ መወሰኑ ተገቢነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሌለው በመሆኑ ተጠሪ ወደ ሥራዋ እንድትመለስ ተጠሪን ጠይቀዋት ተጠሪ እንቢተኛ በመሆኗ የሥራ ውሉ የተቋረጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

አንድ ሠራተኛ ከሥራ ለማሰናበት ስልጣንና ኃላፊነት የሌለው የቅርብ አለቃው ከሥራ ለቅቆ እንዲሄድ ስለተናገረው ብቻ፣ አሠሪው የሥራ ውሉን አቋርጦታል ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ሠራተኛው የሥራ ውሌ ተቋርጧል ከማለቱ በፊት የቅርብ አለቃው በሥራ ያለውን ሠራተኛ፣ ከመምራትና ከመቆጣጠር ባለፈ በሠራተኛው ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድና ያለውን ሥልጣን በተለይም ከሥራ የማሰናበት ሥልጣን ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን የማወቅና የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ የቅርብ ኃላፊዋ ሥራ ለቅቃ እንድትወጣ ቢናገራትም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የቅርብ አለቃዋ እሷን ከሥራ የማሰናበት ስልጣን እንደሌለው ገልፀው ወደ ሥራ እንድትመለስ ጠይቀዋል፡፡

ይህ ከሆነ አመልካች የሥራ ውል ለማቋረጥና ተጠሪን ከሥራ ለማሰናበት ሥልጣንና ኃላፊነት ባለው የሥራ መሪ በኩል የሥራ ውልን አቋርጧል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል የህግ መሠረት የለም፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በቅርብ አለቃዋ ሥራ እንድትለቅ የተናገራት መሆኑ ብቻ የሥራ ስንብቱን ህገ ወጥ ያደርገዋል፡፡ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ ወደ ሥራ እንድትመለስ መጠየቁ ህገ ወጥ ስንብቱን ህጋዊ አያደርገውም በማለት የሰጠውን የህግ ትርጉም የአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.83068

ታህሣሥ 30 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አለ. መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች ፡- ዲ.ኤች ገዳ ብርድ ልብስ ፋብሪካ ኃ.የተ.የግ. ማሕበር ነ/ፈጅ አቶ ስንታየሁ

ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ቅድስት ጌታቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክር ስሆን የአሁኗ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ከሣሽ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክሱም ይዘት ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ተቀጥራ በማገልገል ላይ እያለች ተከሣሽ ድርጅት ሕጋዊነት የሌለውን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በማድረግ ከሣሽ የስራ ውል ወዳልፈፀመችበት ዲ.ኤች ገዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ነቀምቴ ቅርንጫፍ እንዳዛወራት እርሷም ዝውውሩን በመቃወም ክስ አቅርባ እያለ በተዛወርሽበት ቦታ ለአምስት ተከታታይ ቀናት በስራ ላይ አልተገኘሽም በሚል ምክንያት ተከሳሽ የስራ ውሏን አላግባብ እንዳቋረጠባት የሚገልጽ ሆኖ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ ከስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ እንዲወሰንላት ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ ተከሣሽ በበኩሉ የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 10.2 በሚፈቅደው መሠረት ከሳሽ ወደ ነቀምቴ ቅርንጫፍ እንድትዛወር የተደረገ ቢሆንም ዝውውሩን ተቀብላ በስራ ገበታዋ ላይ ባለመገኘቷ እንድትሰናበት የተደረገው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) መሠረት በአግባቡ መሆኑን እና የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የስራ ውሉን ለማቋረጥ በቅ ምክንያት ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ የፊ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በመ.ቁ.37778 በ04/03/01 በትርጉም አስገዳጅነት ያለው ውሳኔ የሰጠበት መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት የፊ/የመ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አሰሪ አንድን ሰራተኛ ጥቅሙን ሳያጓድል ከአንድ የስራ መደብ ወደ ሌላ የስራ መደብ አዛውሮ ማሰራት እንድሚችል በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 13(2) እና (7) የተመለከተ መሆኑን ሰራተኛውን ከአንድ እህት ኩባንያ ወደ ሌላ እህት ኩባንያ አዛውሮ ማሰራት እንደሚቻል በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 10.2 የተመለከተ መሆኑን በዝርዝር ገልጾ ክሱን ውድቅ በማድረግ ተከሣሽ የ14 ቀን የዓመት ፈቃድ በገንዘብ ለውጦ እንዲከፍልና የስራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጥ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአሁኗ ተጠሪ የቀረበለትን ይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሳሽ ድርጅት በሰበር ውሳኔውም መሠረት ቢሆን አንድን ሰራተኛ ማዛወር የሚችለው የራሱ ቅርንጫፍ ወደሆነ ሌላ የስራ ቦታ እንጂ በእህት ኩባንያ ስም ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ወዳለው ሌላ ማሕበር ባለመሆኑ ዝውውሩም ሆነ ዝውውሩን ተከተሎ የተወሰደው የስንብት እርምጃ አግባብነት የለውም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውስኔ ሽሮ ከስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ ውስኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ሲሆን በከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት አመልካች ከሰራተኞች ጋር ካቋቋመው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 10.2 አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የአሁኑ አመልካች የወሰደው የዝውውርም ሆነ የስንብት እርምጃ አግባብነት የሌለው በመሆኑ የስንብትና ተያያዥ ክፍያዎችን ለተጠሪ ሊፈጽም ይገባል በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች በሰበር ደረጃ አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዋ ተዛውራበት የነበረው የነቀምቴ የሽያጭ ማዕከል ለስራው አመራር አመቺነት ሲባል ብቻ የአመልካች እህት ኩባንያ በሆነው ደ.ኤች ገዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ኃ.የተ.የግ፤ ማህበር ስር እንዲተዳደር የተደረገ ቢሆንም በተለይ ከብርድልብስ ሽያጭ ጋር ተያይዞ የአመልካች ቅርንጫፍ ወይም የስራ ቦታ እንጂ የእህት ኩባንያው ቅርንጫፍ ወይም የስራ ቦታ ባለመሆኑ አመልካች ተጠሪዋን ያዛወረው ወደ እህት ኩባንያ እንደሆነ አድርጐ ፌ/ከ/ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢነት የለውም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሠረቱ ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የክርክሩን ፍሬ ነገር በማጣራትና የቀረበላቸውን የጽሑፍ ማስረጃ በመመዘን አመልካች ተጠሪዋን ያዛወረበት የነቀምቴ የሽያጭ ማዕከል የራሱ ቅርንጫፍ ወይም የስራ ቦታ ሳይሆን የእህት ኩባንያው ቅርንጫፍ ወይም የስራ ቦታ እንደሆነ በተመሳሳይ ሁኔታ ማረጋገጣቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት በሕግ የተሰጠው ስልጣን በስር ፍ/ቤቶች የተጣራውን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምሮ ውሳኔ ከመስጠት ውጪ ፍሬ ነገር በማጣራትና በማስረጃ ምዘና ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበትን ድምዳሜ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር የሚያስችለው አለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች ተጠሪዋን ያዛወረው ወደ እህት ኩባንያው መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ቀጥሎ የሚነሣው ጥያቄ አመልካች የዚህ ዓይነቱን ዝውውር ለማድረግ የሚያስችል መብት አለው ወይስ የለውም? የሚል ነው፡፡ በመሠረቱ ተጠሪ የቅጥር ውል ያቋቋመችው ከአመልካች ጋር ብቻ መሆኑ በአመልካች ያልተካደ ሲሆን የአመልካች እህት ኩባንያ ወደሆነ ሌላ ማሕበር ጭምር ተዛውራ ለመስራት በስራ ውሉ ወይም በሌላ ሰነድ በግሏ ወይም በጋራ የሰጠችው ስምምነት ወይም የገባችው ግዴታ ስለመኖሩ አመልካች በስር ፍ/ቤቶችም ሆነ በሰበር ደረጃ የቀረበው ክርክር አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ ረገድ ይደግፈኛል በማለት ጠቅሶ የሚከራከርበት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀደም ሲል በመ.ቁ. 37778 የሰጠው ውሳኔ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደገለፀው ወደ አሰሪው ድርጅት ቅርንጫፍ ወይም የስራ ቦታ የሚደረግ ዝውውርን እንጂ ወደ እህት ኩባንያ የሚደረግ የሰራተኛ ዝዉውርን የሚመለከት ባለመሆኑ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሁኔታ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፊ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 116426 በ14/12/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል
2. በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው የአፈፃፀም እግድ ተነስቷል፡፡
3. የውሳኔው ቅጂ ይላክ፡፡ ክርክሩ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ .82335

ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሆሊ ኤንጀልስ ት/ቤት ኃ/የተ/የግል ማህበር

ተጠሪ ፡- መ/ር መልካም አለማየሁ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ሲሆን በአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክሱም፡- በተከሳሽ (በአሁን የሰበር አመልካች) ት/ቤት በ2003 ዓ.ም በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ተቀጥሬ እየሰራሁ ተከሳሽ ከጊዜ በኋላ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዳስተምር ጠይቆኝ እኔም ችግሩን በመገንዘብ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ስላለኝ በተጨማሪነት እያስተማርኩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር እንደተቀጠርኩ በመቁጠር በህገ ወጥ መንገድ ከሥራ ስላሰናበተኝ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅትም ለክሱ በሰጠው መልስ፡- ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት የተቀጠሩት በመንግስት መስሪያ ቤት ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ጡረታ ከወጡ በኋላ ሲሆን የተቀጠሩትም የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲያስተምሩ ቢሆንም በማስተማር ሥራ ድክመት በማሳየታቸው በተለያዩ ጊዜያት ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ማሻሻል ባለመቻላቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 36 እና 38 መሰረት በተከሳሽ የታመነ ክፍያ በመፈጸም በህጋዊ መንገድ የስራ ውሉ እንዲቋረጥ ተደርጓል፤ ከሳሽ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የተለያዩ ክፍያዎች በተመለከተም፡- የስንብት ክፍያ ሊከፈል የሚገባው ከ 5 ዓመት በላይ ላገለገለ ሠራተኛ በመሆኑ ከሳሽም ከዚሁ ከተጠቀሰው ጊዜ በታች ያገለገሉ በመሆናቸው ሊከፈላቸው አይገባም ፣ የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው ያሉትም ቢሆን የመምህራን ዕረፍት በክረምት ወራት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያም ድርጅቱ ከሳሽን ያሰናበታቸው ማስጠንቀቂያ አስቀድሞ በመስጠት ስለሆነ የሚከፈል አይሆንም ፣ የካሳ ክፍያም የሥራ ውሉ በህጋዊ መንገድ የተቋረጠ በመሆኑ ሊከፈላቸው አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም፡- ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽ ከመንግስት መ/ቤት የሥራ ችሎታውን በመጨረስ በጡረታ የወጡ መሆናቸውን የሚያምነው ጉዳይ ሲሆን ከሳሽ ትምህርት እንዲማሩ ወይም ድክመታቸውን እንዲያሻሽሉ አድርጎ ማሻሻል አለመቻላቸውን የሚገልጽ ማስረጃ አላቀረበም፣ ከሳሽ ግን በአማርኛ ቋንቋ ተመርቀው ለ28 ዓመታት በአማርኛ ቋንቋ ስለማገልገላቸው ማስረጃ አቅርበዋል፣ በመሆኑም በተመረቁበት የአማርኛ ቋንቋ መ.ያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመዝነው ዝቅተኛ ዉጤት ስለማምጣታቸው ወይም በዚሁ የሥራ መደብ ድክመታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ተከሳሽ ሳያቀርብ ከሳሽ ባልተመረቁበትና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ተከሳሽን ለመርዳት ባስተማሩበት ከሚጠበቀው ደረጃ በታች ዉጤት አግኝተዋል በሚል የሥራ ውሉን ማቋረጡ ህጋዊ አይደለም ብሏል፡፡ ከሳሽ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን ክፍያዎች በተመለከተም፡- ከሳሽ ከሥራ ሲሰናበቱ ሲያገኙ የነበረው የደመወዝ መጠን ብር 1206 መሆኑን በክሳቸው የገለጹ ሲሆን ተከሳሽም በዚሁ የደመወዝ መጠን ላይ ያቀረበው ክርክር ባለመኖሩ እንደተቀበለ ይቆጠራል በሚል ለከሳሽ የሚገባቸውን ክፍያ በ7 ቀናት ውስጥ ባለመክፈሉ ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ ፣ ለስራ ስንብት ክፍያ የ1 ወር ደመወዝ ፣ ለማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የ2 ወር ደመወዝ፣ በአዋጁ አንቀጽ 42 እና 43(1) መሰረት የሥራ ውሉ በህገ ወጥ መንገድ በመቋረጡ የ2 ወር ደመወዝ ፣ በአንቀጽ 43(4)(ሀ) መሰረት ካሳ እንዲከፈቸው ሲል ሲወስን የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን በተመለከተ ግን የመምህራን የዕረፍት ጊዜ በክረምት በመሆኑ ሊከፈላቸው አይገባም በሚል ውድቅ አድርጓል፡፡

በሥር ተከሳሽ ድርጅት ይግባኝ ጠያቂነት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሠጠው ውሳኔ መልስ ሰጪው የተቀጠሩበት የሥራ መደብ በመምህርነት መሆኑን የቅጥር ማስረጃ የሚያመለክት ሲሆን በሌላ ማስረጃ ደግሞ የተቀጠሩት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተብሎ ስለመሆኑ የተሟላ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ይሁን እንጂ መልስ ሰጪው ተቀጥረው ይሰራሉ ተብሎ የሚታሰበው የሥራ መደብ የትምህርት ማስረጃ የወሰዱበት ነው ተብሎ ይገመታል ፣ ይግባኝ ባይም መልስ ሰጪውን በእንግሊዘኛ ቋንቋ ቀጠርኩ ይበል እንጂ ማስረጃው መልስ ሰጪው በእንግሊዘኛ ቋንቋ መሰልጠናቸውን የሚያሳይ ባለመሆኑ መልስ ሰጪው የእንግሊዝኛ ቋንቋን በተጨማሪነት እንዳስተምር ይግባኝ ባይ ሰጥቶኛል የሚሉት እውነት ነው ተብሎ የሚወሰድ ነው፡፡ በመሆኑም የግራ ቀኙ ወገኖች ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃዎች ሲመዘኑም ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪውን ያሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የወረዳው ፍርድ ቤት መድረሱ የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ብሏል፡፡

ለመልስ ሰጪው እንዲከፈላቸው የወረዳው ፍርድ ቤት የወሰነላቸውን ክፍያዎች በተመለከተም፡- ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪው ማግኘት የሚገባቸውን ክፍያዎች በህጉ በተቀመጠው ጊዜ የከፈላቸው ስለመሆኑ መዝገቡ ስለሚያሳይ ክፍያ ለዘገየበት የጠየቁትን ክፍያ የወረዳው ፍርድ ቤት እንዲከፈላቸው የወሰነው ተገቢ አይደለም ፣ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 42 እና 43(1) መሰረት የሚፈጸም የቅጣት ክፍያ በሌለበት በእነዚህ ድንጋጌዎች ሥር ክፍያ የወሰነው አግባብነት የለውም በማለት ከተወሰነላቸው ክፍያ ውስጥ በድምሩ ብር 6030.00 ተገቢነት የለውም ሲል በመሻር ሌሎች የተጠየቁትን ክፍያዎች በተመለከተ ግን የወረዳው ፍርድ ቤት የወሰነው ተገቢ ነው በሚል በማጽናት በድምሩ ብር 7236.00 ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጪው እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካችም በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በሚል የሰበር አቤቱታውን ውድቅ በማድረጉ አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

አመልካች በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም ሲጠቃለል ተጠሪው ለተማሪዎች ተገቢውን ትምህርት የማይሰጡ ከመሆናቸውም ሌላ የተማሪዎችን ደብተር ሲያርሙ ትክክል የሆነውን ትክክል እንዳልሆነ ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ትክክል እንደሆነ በማደናገር ስለሚያርሙ የተማሪዎች ቤተሰቦች በየጊዜው አቤቱታ በማቅረባቸውና

ተጠሪውም በዕድሜ መግፋት የተነሳ ድክመታቸውን ማሻሻል ባለመቻላቸው እንዲሰናበቱ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪው ማስጠንቀቂያ አልሰጠም ቢባል እንኳን ማስጠንቀቂያ ያለመስጠት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል ሊያደርግ ከሚችል በስተቀር ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ሊያሰኝ የሚያስችል ባልሆነበት አመልካች ያቀረብኳቸውን ማስረጃዎች ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ በማድረግ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የአመልካችን ክርክር ዋጋ ያሳጡት ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩላቸው በሠጡት መልስ፡- የሰለጠንኩትና ለ28 ዓመታት በመንግስት መስሪያ ቤት ያገለገልኩት በአማርኛ ቋንቋ ነው ፣ እንዲሁም በአመልካች ድርጅት የተቀጠርኩት በሰለጠንኩበት የአማርኛ ቋንቋ ስለመሆኑ የውል ሰነዱ ያመለክታል፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋም ቢሆን በማስተማር ሂደት ላይ ጉልህ የሆነ ስህተት ወይም ድክመት ያሳየሁት ስለመኖሩ አመልካች በማስረጃ አስደግፎ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክርክር የለም ፤ በመሆኑም አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግበት የሚገባ ነው ሲሉ ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ለተጠሪው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ተጠሪውን ያሰናበታቸው በህገ ወጥ መንገድ ነው በሚል የተለያዩ ክፍያዎችን ለተጠሪው እንዲከፍል የስር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካችና ተጠሪን በዋናነት የሚያከራክራቸው ነጥብ ተጠሪው በአመልካች ድርጅት የተቀጠሩበት የሥራ መደብና ተጠሪው አሳይተዋል የተባለው የሥራ ድክመት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪው የተቀጠሩት በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሥራ መደብ ነው ሲል ተጠሪው ግን ቅጥሩ የተፈጸመው በአማርኛ ቋንቋ የሥራ መደብ ነው ይላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪው በአማርኛ ቋንቋ የሰለጠኑ መሆናቸውን የፍሬ ነገር ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተጠሪውን የቅጥር ማስረጃ በመመርመርና በመመዘን ማረጋገጣቸውን ከውሳኔው መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪው የተቀጠሩት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ የሥራ መደብ ነው በሚል ለዚህ ችሎት ያቀረበው ቅሬታ የስር ፍርድ ቤቶች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር ወጪ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪው የተቀጠሩበት በሰለጠኑበት የአማርኛ ቋንቋ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋጠ ደግሞ ድክመት ያለባቸው መሆን አለመሆኑ ደግሞ ሊመዘን የሚገባው በተቀጠሩበት የሥራ መደብ እንጂ ባልተቀጠሩበት የሥራ መደብ ሊሆን አይገባም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ አመልካች ተጠሪው ከተቀጠሩበት የሥራ መደብ ወይም ሙያ ውጪ በመመዘን ድክመት አሳይተዋል በሚል ከሥራ ያሰናበታቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው በሚል የወሰኑት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም፡፡ ተጠሪው እንዲከፈላቸው የጠየቁትን ክፍያዎች በተመለከተም የወረዳው ፍርድ ቤት ለተጠሪው እንዲከፈል ከወሰነላቸው የክፍያ ዓይነቶች ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን ድንጋጌዎች በመመርመር ሊከፈላቸው የማይገቡትን ክፍያዎች በመለየት ከሰረዘ በኋላ ተገቢነት ያላቸውን ክፍያዎች ብቻ አመልካች እንዲከፍል የወሰነው በአግባቡ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሆኑም የወረዳው ፍርድ ቤት ሆነ ጉዳዩን በየደረጃው ያዩት የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የሥራ ውሉ በአመልካች አነሳሽነት በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል ሲሉ በሠጡት ውሳኔም ሆነ ክፍያን አስመልክቶ ከፍተኛው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት በማሻሻል በሠጠው ውሳኔና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ በማጽናት በሰጠው ትዕዝዝ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 13235 በቀን 03/08/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.147956 በቀን 03/11/2004 ዓ.ም. የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. የሥራ ውሉ በአመልካች ህገ ወጥ ድርጊት ተቋርጧል በሚል የተወሰነው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ አመልካች ለተጠሪው የስንብት ክፍያ ፣ ካሳ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፍል ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የወሰኑት ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ ተጀምሮ የነበረው የአፈጻጸም ክስ ክርክር ታግዶ እንዲቆይ በአ/ፈ/መ/ቁ/58289 ላይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ በመሆኑም ለአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲያውቀው ትዕዛዝ ይጻፍ፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው·ል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 78398

ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1ኛ አቶ ሽፈራው ደጀኔ ቀረቡ

2ኛ ወ/ሮ ፀሐይ ተስፋዬ በወኪልና 1ኛ አመልካች ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሲሳይ አበቡ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ ቤትን በሚመለከት ግራ ቀኙ ያደረጉት የቤት ሽያጭ የሰነድ ውል ቤቱ በምን ያህል ዋጋ ተሸጧል? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በማስረዳት ረገድ ይኸው የጽሑፍ ውል ያለውን የማስረጃ ተቀባይነት ከግራ ቀኙ ክርክር ጋር አገናዝቦ ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ ሲሆን የክሱም ይዘት ተከሳሾች እና እኔ ሐምሌ 17 ቀን 2003 ዓ.ም ባደረግነው የቤት ሽያጭ ውል በኡኪ ከተማ በአሁን 1ኛ አመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት በብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ ሸጠውልኛል፡፡ ነገር ግን በውሉ መሠረት የሽያጭ ዋጋውን ተቀብለው ከወሰዱ በኋላ የተሸጠውን ቤት እና የቤቱን ሰነድ ለማስረከብ እምቢተኛ ሆነዋል፡፡ ስለሆነም እንደ ግዴታቸው እንዲፈፅሙ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካችም በተከሳሽነታቸው የሰጡት መልስ ሐምሌ 17 ቀን 2003 ዓ.ም ባደረግነው የቤት ሽያጭ ውል አድራሻው የተገለፀውን ቤት በብር 40,000.00 /አርባ ሺህ ብር/ ሸጠናል፡፡ በዚህ የሽያጭ ሰነድ ላይም ገዥው የቤቱን ዋጋ በ10 ቀን ውስጥ ለመክፈል ግዴታ ገብቷል፡፡ ይሁን እንጂ የግዥው ዋጋ በቀብድም ሆነ በሙሉ የከፈለው ክፍያ የለም፡፡ ስለሆነም ገዥው እንደ ግዴታቸው የቤቱን ዋጋ በጊዜው ባለመክፈሉ የተነሳ ቤቱን ለመረከብና ስመሀብቱ እንዲዛወር ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑ ታውቆ ከወጪና ኪሣራ ጋር እንድንሰናበት ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክሱ የቀረበለት በምስራቅ ወለጋ መስ/ዞን የጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤትም አከራካሪው ቤት የተሸጠው በስንት ዋጋ ነው የሚለውን ነጥብ ለመለየት የግራ ቀኙን የሰው ማስረጃዎች ከሰማ በኃላ በመ/ቁ 19594 ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቀን 17/11/2003 ዓ.ም ግራ ቀኙ የቤት ሽያጭ ውል ማድረጋቸውን አምነው የቤቱን ዋጋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመክፈልና አለመክፈል እንዲሁም በተሸጠው የቤት ዋጋ ላይ ተካክደዋል፡፡ ሆኖም በቤቱ የሽያጭ ውል የቤቱ ዋጋ ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ መሆኑንና ይህም ዋጋ መከፈሉን በውሉ ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2005 (1) እንደተደነገገው በፅሑፍ ማስረጃ ላይ ተመዝግቦ የሚገኝ ቃልና ቀን በፈረሙት ሰዎች መካከል እምነት የሚሰጠው ማስረጃ ነው፡፡ በዚሁ የፅሑፍ ማስረጃ ላይ የሚገኘውን ቃል መቃወም የሚቻለው በመሃላ ቃል ብቻ እንጂ በሰው የምስክርነት ቃል ማስተባበል አይቻልም፡፡ ስለሆነም ሻጮች ግዴታቸውን ስላልተወጡ ቤቱን ለከሳሽ እንዲለቁ እና አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በማቅረብ ድጋፍ ያድርጉ፤ እንደ ግዴታቸው ባለመፈፀማቸውም ገደብ ብር 10,00.00 /አስር ሺህ ብር/ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመቀጫ ገንዘቡን ከማንሳቱ በቀር በተመሳሳይ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በዚህ ከላይ በተገለፀው መሠረት በየደረጃው የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኝነት በመሰጠቱ ይህ የሰበር ጉዳይ ለዚህ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

ግራ ቀኙ በሰበር ደረጃ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር በሥር ፍ/ቤት አንስተው የተከራከሩበትን የሚያብራራ እና የሚያከራክር እንጂ በይዘቱ የተለየ አየደለም፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2005 እንደተደነገገው በፅሑፍ ሰነዱ ላይ ስለሚገኘው የስምምነት ቃል እንዲሁም ስለ ተባፊው ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ብሎ ሊደመደም የሚችለው እንደውለታው ዓይነት የጽሑፍ ውል አደራረግን ሥርዓት አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 (ሐ)፣ 1719(2) የተመለከተውን በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል ለመያዝ አስፈላጊ የሆነውን የውል አደራረግ ሥርዓት አሟልቶ የያዘ ስለመሆኑ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678(ሐ) እና 1719 (2) መሠረት የውሉ አደራረግ ሥርዓት በተለየ አካኋን እንዲደረግ በህግ ተለይቶ ከተመለከተው ድንጋጌ አንዱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 (1) የተመለከተው ይገኝበታል፡፡ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለን የባለቤትነት መብት በሽያጭ ለማስተላለፍ ሲባል የሚደረገው የውል ስምምነት በፅሑፍ ሆኖ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ በዚህ አካኋን ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት መደረግ አለበት የሚለውም የህግ ማሟያ ክፍል አስፈላጊነት የሽያጭ ውል ተደርጓል ወይስ አልተደረገም? ተደርጎ ከሆነስ መቼ በምን ያህል ዋጋ፣ የትኛው ንብረት ወዘተ የሚለውን አስመልክቶ አላስፈላጊ የሆኑ ሙግቶችን ለማስቀረት ታስቦ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚፈፀሙ የባለቤትነትን መብት የሚያስተላልፉ ውሎች ውሉ ስለመኖሩ እስካልታመነ ድረስ በአዋዋይ ፊት መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህ በተያዘዉም ጉዳይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2005 (1) እንደተመለከተው በፅሑፍ ሰነድ ላይ ስለሚገኘው የስምምነት ቃል እንዲሁም በላዩ ላይ ስለተፃፈው ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚለው ድንጋጌ ከላይ በተገለፀው አኳኋን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678(ሐ)፣ 1719(2) እና 1723 (1) ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ለማናቸውም የፅሑፍ ውል ስምምነት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡

ይህ አከራካሪ የሆነው ሽያጭ ውል የተደረገው የማይንቀሳቀስ በሆነው ንብረት በቤቱ ላይ ነው፡፡ ውሉ የተደረገውም በፍ/ሕ/ቁ 1723 የተመለከተውን ድንጋጌ አሟልቶ አይደለም፡፡ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ተደርጎ ቢሆን ኖሮ የቤቱን ዋጋ እና ይህንኑ ዋጋ ተቀብለዋል አልተቀበሉም የሚለውን አስመልክቶ በፅሑፍ ከሠፈረው ቃል ውጭ የመቅረብ ማናቸውም ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2005(1) እንደተደነገገው ተቀባይነት ያለው ክርክር አይደለም፣ ከፅሑፍ ሰነዱ በቀር የሚቀርብ ማናቸውም ማስረጃ የሰውም ምስክሮች ቃል ተቀባይነት የለውም በማለት መደምደም ባልተቻለ ነበር፡፡

ስለሆነም በህግ ፊት ሊፀና በሚችል ውል ለመመደብ ቋሚ ማሟያ ሆኖ የተያዘውን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 (ሐ)፣ 1719(2) እና 1723 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተከትሎ የተደረገ ስምምነት ባለመሆኑ ይህ ዓይነት ስምምነት በህግ ፊት ዋጋ ያለው ሆኖ፤ ሊፀና የሚችል ስምምነት ነው ብሎ ውጤት ለመስጠት የሚቻል ባለመሆኑ የአሁን ተጠሪ ይህን በህግ ፊት ሊፀና የማይችለውን ውል መነሻ በማድረግ እንደ ውሉ ይፈፀምልኝ በማለት በአመልካቾች ላይ ክስ ለማቅረብ የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

ሆኖም የአሁን አመልካቾች ይህንኑ ቤት በብር 40,000.00 /አርባ ሺህ ብር/ ሸጠናል በማለት በፍሬ ነገር ረገድ ገልፀው የተከራከሩ ከመሆኑ እና የሽያጭ ዋጋም አልተቀበልንም በማለት የተከራከሩ በመሆኑ የአሁን ተጠሪ በዚሁ አመልካቾች በጠቀሱት የሽያጭ ዋጋውን ከፍለው ቤቱን ለመረከብ እና አስፈላጊ ሰነዶችን ለመጠየቅ ከፈለጉ ግን ይህ ውሳኔ ይህንኑ መብቱን ቀሪ ሊያደርግ የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም በዚህ ሁሉ ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ሽያጭ ውል የማይንቀሳቀስ የሆነውን ቤትን አስመልክቶ የተደረገ እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2005 (1) የተመለከተው ድንጋጌ አፈፃፀም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ሳይመለከት በዚህ በውል አዋዋይ ፊት ባልተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ላይ የሠፈሩት ማናቸውም የውል ቃሎች ሁሉ ያለቅድመ ሁኔታ እንዳሉ የሚታመኑ ናቸው፤ በማናቸውም ዓይነት የሰው ምስክርነት ቃል ማስተካከል አይቻልም በሚል የሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በምስራቅ ወለጋ ዞን መስተዳደር የጎቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 19594 በቀን 17/5/04 የሰጠው ውሳኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 27455 በቀን 28/06/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፋ.ቁጥር 139094 በቀን 11/07/2004 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፋ.ቁጥር 147416 በቀን 18/7/2004 የሰጠው ትዕዛዝ ሁሉ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ክርክር ያስነሳው ቤት ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገን የቤት ሽያጭ ውል መሠረት አድርጎ ያቀረበው የቤት ክርክር ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፤
3. ሆኖም ሻጮች ባመኑት ዋጋ መሠረት የሽያጭ ዋጋውን የመክፈል ግዴታ በእራሱ በኩል ከተወጣ ክርክር ያስነሳውን ቤት እና በዚህ ቤት ላይ ያለን የባለቤትነት መብት ለማስተላለፍ አስፈላጊ ከሆኑት ሰነዶች ጋር ያለውን የመረከብ መብት ይህ ውሳኔ አያግደውም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. በሥር ፍ/ቤቶችም ሆነ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከትለው ማናቸውም ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

<u>የመስማሚያ ሀሳብ</u>

እኔ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምፅ በደረሰበት መደምደሚያ የምስማማ ሲሆን አብላጫው ድምፅ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 (1) እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2005ን በማጣመር በሰጠው ትርጉም አልተስማማሁም፡፡ በእኔ እምነት የአመልካቾችን የትምህርት ሁኔታ በማጣራት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1728 ንዑስ አንቀፅ 3ን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መወሰን የተሻለ ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 74950

ህዳር 05 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይምሰል

አመልካች ፡- ወ/ሮ ዙቤዳ ኑር ኬርሰማ ጠበቃ አቶ ባህሩ መኮንን ቀረበ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ሚሊዮን ዳግም መሴ
2. አቶ ምንተስኖት ሀብታሙ
3. አቶ ደርባቸው ሀብታሙ
4. ወ/ት የትናየት ሀብታሙ

ጠበቃ አቶ መኮንን በዛብህ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የወለድ የገንዘብ ብድር የወሰደ ተበዳሪ የብድር ገንዘቡን መመላሻ ጊዜ ካሣለፈ የብድሩን ገንዘብ ብቻ ሣይሆን ከህጋዊ ወለድ ጋር የመክፈል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለውን ነጥብ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማጣቀስ ለመለየት ነው፡፡

የአሁን አመልካች ከአሁን 1ኛ ተጠሪ ባለቤት እና ከሌሎች ተጠሪዎች አባት ከሚች ከአቶ ሐብታሙ ብርሃኑ ታህሣስ 26 ቀን 1995 ዓ.ም በተደረገ የብድር ገንዘብ ብር 237,000.00 /ሁለት መቶ ሰላሣ ሰባት ሺህ ብር/ መበደራቸውና ይህንኑ የብድር ገንዘብ ጥር 30 ቀን 1995 ዓ.ም ለመመለስ ግዴታ የገቡ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

ተጠሪዎች ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ ተበዳሪው ዋናውን የብድር ገንዘብና ይህንኑ የብድር ገንዘብ መክፈል ከነበረበት ጊዜ ከየካቲት 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ሲጠይቁ የአሁን አመልካች ወለድ ለመክፈል በብድር ስምምነቱ ላይ ግዴታ ያልገባሁ በመሆኑና የመክፈያው ጊዜ እንዳለፈም ገንዘቡን እንድመልስ በማስጠንቀቂያ ያላሣወቁኝ ስለሆነ ወለድ የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር በከ/መ/ቁ. 97284 ተመልክቶ ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የብድር ውሉ አልተካደም ጥር 30 ቀን 1995 ዓ.ም ለመመለስም ተበዳሪው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግዴታ ገብቷል፡፡ የብድር መመለሻ ጊዜው በዚህ አኳኋን ቁርጥ ያለ ጊዜ ስለተቀመጠ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1775(ለ) መሠረት ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ ገንዘብ ጠያቂው ማስጠንቀቂያ መስጠት አያስፈልገውም፡፡ ስለሆነም ማስጠንቀቂያ ስላልተሰጠኝ ወለድ ልከፍል አይገባም የሚለው ክርክር ተቀባይነት ስለሌለው ተበዳሪ ከየካቲት 01 ቀን ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ዋናውን የብድር ገንዘብ ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህ ከላይ የተመለከተው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በፍሬ ነገርም ሆነ በህግ ረገድ ቅሬታን የሚያስከትል አይደለም፡፡ በማለት መልስ ሰጭዎችን ሣይጣራ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ዘግቶታል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበውም የአሁን አመልካች ይህ በጉዳዩ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡትን ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉበትን የመከራከሪያ ነጥብ በመጥቀስ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎችም በበኩላቸው ውሣኔው በህግ መሠረት የተሰጠ ነው የሚሉበትን ምክንያቶች በመዘርዘር መልሳቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም እንደ ሥርዓቱ ለዚሁ መልስ የመልስ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተው ተመልክተናል፡፡ የአሁኗ አመልካች ወለድ እንዲከፍል በገንዘብ ብድር ውሉ ላይ ግዴታ ስለመግባቱ ሣይገለጽ፤ እና ማስጠንቀቂያም ሣይደርሰኝ በወለድ ገንዘቡን ትከፍላለህ የሚለው ዳኝነት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1775 (ለ) የተመለከተው ድንጋጌ በአግባቡ ሣይታይ በመተርጎሙ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ይልቁንም በብድር ስምምነቱ ላይ ወለድ የመክፈል ግዴታ ባልተጠቀሰ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1478 እንደተደነገገው ወለድ የመክፈል ግዴታ እንደሌለብኝ ግልጽ ነው፡፡ የሚሉትን ነጥቦች በመጥቀስ በሥር በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሆኖም ግራ ቀኙን የሚያከራክረው ጉዳይ የገንዘብ ብድር ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሣን ክርክር ስለዚሁ ጉዳይ የሚገዛው ልዩ የህጉ ክፍል ተፈፃሚ በማድረግ ምላሽ የሚሰጠው ሆኖ ከተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1676 እንደተመለከተው ጉዳዩ በዚህ ለጉዳዩ በቀጥታ ተፈፃሚነት ባለው የህጉ ክፍል መሠረት የሚታይ እንጂ ስለውሎች በጠቅላለው በሚለው የህግ ክፍል የተቀመጡት ድንጋጌዎች አግባብነት አይኖራቸውም፡፡ ከዚህ አንፃር ይህንኑ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ለመወሰን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን በፍ/ብሔር ህጉ የሚያልቅ ነገር ብድርን አስመልክቶ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2478 ላይ ተበዳሪው ወለድ እንዲከፍል የውል ቃል ከሌላ በቀር ለአበዳሪው ወለድ መክፈል የለበትም በሚል የተቀመጠው ድንጋጌ ተዋዋይ ወገኖች ባላቸው የመዋዋል ነፃነት ተጠቅመው በገንዘብ ብድሩ ውል ስለወለዱ አከፋፈል የጠቀሱት ጉዳይ ባይኖር ይህ መሰል የገንዘብ ብድር ውል ስምምነት የወለድ ክፍያ ግዴታን ያስከትላል ወይስ አያስከትልም? የሚል ክርክር እንዳያስነሣ ህጉ ክፍተቱን ለመሙላት ማስቀመጡ እንጂ ተበዳሪው በገባው ግዴታ መሠረት የብድር ገንዘቡን በመመላሻው ጊዜ አለመክፈሉ ቢረጋገጥ ይህ የመክፈያ ጊዜው ላለፈበት ጊዜ ወለድ የማይከፈል መሆኑን ሁሉ የሚሸፍን አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህም በመሆኑ ነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2489(1) ተበዳሪው የተበደረውን ነገር ከመመለስ ወይም ከመክፈል የዘገየ እንደሆነ ስለውሎች በጠቅላላው በሚለውና አግባብነት ባለው ህግ መሠረት ጊዜ በማሣለፍ የሚከፈለውን ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት በሚል የተደነገገው፡፡ ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚነቱ የወለድ ግዴታን ላካተተም ላላካተተም ጭምር እንደሆነ ከይዘቱ መረዳት ይቻላል፡፡

ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2489(1) የተመለከተው ስለውሎች በጠቅላላው የህግ ክፍል አፈፃፀም እንደብደሩ ዓይነት እያታየ ተግባራዊ የሚሆኑ እንጂ ለማናቸውም የብድር ገንዘብ መቼም ቢሆን ተፈፃሚ ሊሆን እንደማይቻል የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2482 እና 2483 ድንጋጌ ንባብ አስረጂ ነው፡፡

በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2482 እንደተደነገገው ይህ ክርክር ያስነሣው የብድር ስምምነት የብድር ገንዘቡን መመለሻ ጊዜ አስቀድሞ ወስኖ ያስቀመጠ በመሆኑ እና ወለድ የመክፈል ግዴታም ያላስቀመጠ በመሆኑም እንደዚህ ያለ የብድር መመለሻ ጊዜ ተወስኖ ከሆነ የብድር ገንዘቡን ከዚህ መመለሻ ጊዜ በፊት የመክፈል ግዴታውን በተበዳሪው ላይ የሚጣል እንጂ ይህ የመክፈያ ጊዜ ካለፈ በኃላ አበዳሪው ለተበዳሪው ጊዜው እልፏልና ክፈለኝ በማለት ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የለበትም፡፡ አበዳሪ የማስታወቅ ግዴታ የሚኖርበት በብድር ውሉ ላይ የብድሩን ገንዘብ መመለሻ ጊዜው በውሉ ያልተወሰነ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ ተከታይ በሆነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2483 ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች የወሰዱትን የብድር ገንዘብ ብቻ እንጂ ወለዱንም ጨምረው ለመክፈል ግዴታ ያልገቡበት ስምምነት በመሆኑ እና የመክፈያ ጊዜው በወሉ ላይ ተወስኖ የተቀመጠ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2482(2) እና (3) መሠረት በመመላሽ ጊዜው የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተረድቶ ጊዜው ከማለፉ በፊት አለመክፈሉ እስከተረጋገጠ ድረስ የብድር ገንዘቡን ከህጋዊ ወለድ ጋር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት በውጤት ደረጃ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 71668 ነሐሴ 09 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪ የብድር ገንዘቡን ከየካቲት 01 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ከፍለው እስከሚያጠናቅቁ ድረስ ከህጋዊ ወለድ ጋር ሊከፍሉ ይገባል መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ በሰበር መ/ቁ. 74950 ታህሣስ 11 ቀን 2004 ዓ.ም በፍርዱ መሠረት በመ/ቁ. 111637 የተጀመረው የአፈፃፀም ጉዳይ ታግዶ ይቆይ በሚል ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.63063

ህዳር 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም - ነገረኛ ፈቃዱ ኃይሌ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ፒቲኢ ኢንተርናሽናል ኢንኮፖሬትድ - ተወካይ ዶ/ር ብርሃነ ገብራይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከስራ ውል ጋር ተያይዞ የመልካም ስራ አፈፀፃፀም ዋስትና ገንዘብ ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በግልግል ጉባኤ ነው፡፡ የግልግል ጉባኤው ግራ ቀኙ ሚያዚያ 09 ቀን 2000 ዓ/ም በፈረሙት ውል መሰረት የተቋቋመ ሲሆን ግልግሉ በውሉ መሰረት ከተቋቋመ በኋላ ክሱን ያቀረበው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአሁኑ ተጠሪና በአሁኑ አመልካች በታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ተደርጎ ሚያዚያ 09 ቀን 2000 በተፈረመና ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ/ም እስከ ነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ የሚቆይ ውል ተዋውለው እንደነበር፣ ውሉ የተደረገውም አመልካች አለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴሌኮም ኩባንያ ለመፍጠር እገዛ ለማድረግ ተግባር መሆኑና በውሉ መሰረት ተጠሪ የአመልካችን የሰው ኃይል ችሎታ ከፍ በማድረግ የአሰራር ሂደቶችን፣ ፖሊሲዎችንና የአሰራር ደንቦችን ለማጎልበት፣ አመልካች የአሰራር ሂደቱን ለመደገፍ በጥቅም ላይ ያዋለውን ቴክኖሎጂ እንዲረዳ ለማስቻል፣ የአሰራር ሂደቱ ከቴክኖሎጂው ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥና ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም በጥቅም ላይ የዋሉ ሲስተሞችና ሥርዓቶችን በተግባር ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣ ለአመልካች ፐርሶኔል /የሰው ኃይል/ ተገቢ የሆነ መዋቅርን በማቅረብ እነዚህን ቴክሎኖሎጂዎችና የአሰራር ሂደቶችን በተሳካ ሁኔታ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማስቻል፣ በትራንስፎርሜሽን /ለውጥ/ ሂደት ተሳትፎ የሚያደርጉ ፐርሶኔሎችን መሰረታዊ የስራ መስፈርቶችን ለማቅረብ፣ የስልጠና ፕሮግራሙ በተሳካ ሁኔታ መስጠት እንዲቻል ተገቢ የሆኑ ይዘቶችን እና አስፈላጊ የሆኑ ፋሲሊቲዎችን መለየትና የመፍትሔ ሃሳብን ለማቅረብ ግዴታ መግባቱን፣ አመልካች ለዚህ የተጠሪ ስራ $ 4,289,189.60 (አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ከስልሳ ሳንቲም የአሜሪካን ዶላር) ለመክፈል መስማማቱንና ተጠሪ ደግሞ አስራ አራት አማካሪዎችን ለማሰማራትና ከእነዚህ ውስጥ አምስቱ ለስምንት ወራት በቋሚነት እንዲሰሩ እና ስድስቱ ደግሞ ለሰባት ወራት እየተቀያየሩ የሚሰሩ አማካሪዎች እንዲሁም ቀሪዎቹ ደግሞ ለአራት ወራት እየተቀያየሩ የሚሰሩ አማካሪዎችን መድቦ የነበረ መሆኑን፣ በውሉ መሰረትም የአከፋፈሉ ሁኔታ ለመጀመሪያ ሶስት ወራት (ጥር፣ የካቲትና መጋቢት) ለተሰሩት ስራዎች

የውሉን ዋጋ 40%፣ ለሁለተኛው ሶስት ወራት (ሚያዚያ፣ ግንቦትና ሰኔ) ለሚሰሩት ስራዎች እንዲሁ የውሉን 40%፣ ቀሪውን የውሉን 20% ደግሞ በሁለት ወራት (ሐምሌና ነሐሴ) ለሚሰሩት ስራዎች እንደሚከፈል መገለጹን፣ 12% የሚሆነው የውሉ ዋጋ ደግሞ ከእያንዳንዱ ክፍያ ከመጀመሪያው ክፍያ ጀምሮ እየተቆረጠ ተይዞ እንደሚቆይ ስምምነት መደረጉና ተጠሪ ስራዎችን በትክክል አከናውኖ የስራ አፈጻጸምና በውሉ አስፈላጊ የሆኑት ተመጣጣኝ ደረሰኞችን ቢያቀርብም በውሉ አንቀፅ 11.4 መሰረት ሊከፈለው የሚገባው የተያዘ ገንዘብ መኖሩን ገልፆና የውሉ ዘመን ማብቃቱን ጠቅሶ አመልካች $293,050.12 (ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ ሃምሳ ከአስራ ሁለት ሳንቲም የአሜሪካን ዶላር) የተያዘ ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል፣ በዚህ ገንዘብ ላይ ከነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያበቃ ድረስ ወለድ እንዲታሰብለትና ለክሱ የወጡት ወጪና ኪሳራዎች እንዲተኩለት ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጠው መልስም በግራ ቀኙ ውሉ መኖሩን ሳይክድ ተጠሪ የሚጠበቁበትን ግዴታዎችን፣ መስራት ያለበትን ስራዎችን በሙሉ በመስራት ያላሟላ መሆኑን፣ የታቀደው በስራ ላይ ይውላል ተብሎ የነበረው አዲሱ ኩባንያ በተጨባጭ ሁኔታ ሊታይ እንዳልቻለና በውሉ መሰረት ስራው መጠናቀቅ በነበረባቸው የስምንት ወራት ጊዜ ውስጥ ያለመሰራቱን፣ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሩብ አመታት በውሉ መሰረት መጠናቀቅ የነበረበት ስራ 80% የነበረ ሁኖ በተጨባጭ የተጠናቀቀው ግን 41.5% ብቻ መሆኑን፣ በሁለተኛው ግምገማም የውሉ ዘመን ካለቀ በኋላ የተከናወነው ስራ 71.3% ብቻ መሆኑ መረጋገጡንና በአጠቃላይ የተጠሪ የስራ አፈጻጸም እንደውሉ ያልተናከናወነና አጥጋቢና ስኬታማ ያልነበረ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ያቀረበ ሲሆን እንደ ውሉ ባለመፈጸሙ የደረሰውን ኪሳራ ዘርዝሮ $428,918.96 (አራት መቶ ሀያ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስምንት ከዘጠና ስድስት ሣንቲም የአሜሪካን ዶላር) በተጠሪ እንዲከፈለው ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተገቢ ነው ያለውን መልስ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የግልግል ጉባኤውም ተጠሪ በውሉ መሰረት የገባውን ግዴታ ያለመወጣቱ መረጋገጡን ገልጾ አመልካች ለተጠሪ ሊከፈል ይገባ ከነበረው $4,289,189.60 ውስጥ በተሰራው ስራ መጠን $2,442,084.39 ወይም የውሉን 56.93% መክፈሉ ስራው በድጋሚ እንዲገመገም ከተደረገ በኋላ እና አመልካች ቴክኒካዊ ፐርሶኔል ክፍል የድጋፍ ደብዳቤ ከተፃፈ በኋላ $726,498.55 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፈል መደረጉንና በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ውል ለማቋረጥ መስማማቱ መረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ ለመልካም ስራ አፈጻጸም የተያዘው 12% ገንዘብ ከተሰራው ስራ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ሊለቀቅ የሚገባው እንጂ በአመልካች የሚያዝበት አግባብ የለም ሲል አመልካች ለተጠሪ $87,169.02 ከነሐሴ 09 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ (9%) ጋር እንዲከፍል፣ በዚሁ ገንዘብ መጠን የጠበቃ አበል 10% እንዲከፈል የወሰነ ሲሆን የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነትን ክስ ግን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በግራ ቀኙ ውል የግልግል ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑ በመገለፁ ምክንያት አቤቱታው ለዚህ ሰበር ችሎት በቀጥታ ቀርቧል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በግራ ቀኙ መካከል ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚነት እንዲኖረው የተደረገው ውል በሕጉ አግባብ ሳይሻሻልና ይህንኑ ተጠሪ ባላረጋገጠበት ሁኔታ የዳግም ግምገማ ውጤቱን መሰረት በማድረግ የመልካም ስራ አፈጻጸም መያዣ ገንዘብ በተሰራው ስራ መጠን ሊለቀቅ ይገባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተብሎ መወሰኑም ሆነ ተጠሪ እንደ ውሉ ግዴታውን ያልፈጸመ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በአመልካች መስሪያ ቤት ሰራተኞች እ.ኤ.አ መስከረም 15 ቀን 2008 በተደረገው የመልሶ ግምገማ (Re-evaluation) በግራ ቀኙ መካከል ውሉን ለመቋጨት የታለመ ስምምነት መደረጉን ያመላክታል በማለት እና በዚሁ መልሶ ግምገማ አመልካች ተፈጻሚነቱ ባበቃው ውል የነበረውን የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ የማቅረብ መብቱን ትቷል በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ከመደረጉም በላይ መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎትም የቃል ክርክር እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግራ ቀኙ ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ከነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ/ም ድረስ የሚቆይ የአለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴሌኮም ኩባንያ ለመፍጠር ሲባል የተለያዩ ተግባራት የሚከናወኑበትን ስምምነት ማድረጋቸውን ግራ ቀኙ የማይካካዱበት ጉዳይ መሆኑን፣ ግልግል ጉባኤውም በአመልካችና በተጠሪ መካከል በተደረገው ውል የጊዜ ገደብና በውሉ በተገለፀው መሰረት ስራው ውጤታማና ስኬታማ በሆነ መንገድ በተጠሪ ምክንያት ያልተፈጸመ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን፣ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው ዳግም ግምገማ ተካሄዶ ስራው 71.3% መሰራቱ በአመልካች ተወካዮች ተረጋግጦ የውሉ ገንዘብ በዚሁ በተሰራው ስራ መጠን ብር $726,489.55 እንዲሆን ተደርጎ ለተጠሪ እንዲከፈል ሲደረግ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ በተሰራው ስራ ልክ መለቀቅ ሲገባው ያላግባብ የተያዘበት መሆኑን ገልጾ ይኸው ገንዘብ እንዲለቀቅለት መሆኑን፣ አመልካች የሚከራከረው ደግሞ በዳግም ግምገማ ጊዜ የቀድሞው ውል ያልተሻሻለ መሆኑንና ክፍያ እንዲፈፀም የተደረገውም በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ለማቋረጥ በማሰብ የአከፋፈሉ ሁኔታ የቀድሞውን ውል መሰረት በማድረግ ሲሆን እንደሚገባ መስከረም 05 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈው ደብዳቤ ይዘት የሚገልፅ መሆኑና በጠቅላላው የቀድሞው ውል በሕጉ አግባብ ባልተሻሻለበትና ተጠሪ ግዴታውን እንደ ውሉ አልፈጸመም ተብሎ በተረጋገጠበት አግባብ አመልካች ለተጠሪ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ ሊለቅ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ስለ ውል መሻሻል የሚደነግጉትን የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎችንና የግራ ቀኙን ውል ይዘትና በጉዳዩ ላይ የተጠየቀውን ዳኝነት እንዲሁም የማስረጃ አቀራረብና የዳኝነት አሰጣጥ ስርአትን ያልተከተለ ነው በማለት መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በግልግል ዳኝነት ክሱን ሲያቀርብ የቀድሞው ውል በህጉ አግባብ ተሻሽሏል በሚል ዳኝነት ያለመጠየቁንና ውል ስለመሻሻሉ የሚያሳይ ማስረጃ አለ ብሎ የማይከራከር መሆኑን በዚህ ችሎት በተደረገው የቃል ክርክር ያረጋገጠው ጉዳይ ከመሆኑም በላይ በግልግል ጉባኤው የተደረገው የክርክር ሂደትም አመልካች ውሉ ተሻሽሏል በማለት ያቀረበው ክርክር የሌለ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲሁም ተጠሪ በውሉ መሰረት ስራውን ሙሉ በሙሉ ሰርቼአለሁ ብሎ የማይከራከርና 71.3% ብቻ መስራቱን መረጋገጡን የማይክደው ፍሬ ነገር ሲሆን በውሉ ላይ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ በተሰራው ስራ ልክ መለቀቅ ያለበት ስለመሆኑ ስምምነት ተደርጓል በማለት የማይከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ በተሰራው ስራ መጠን ሊለቀቅ ይገባል በማለት የሚከራከረው በግራ ቀኙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መካከል ያለውን ግንኙነት ለመቋጨት ዳግም ግምገማ እንዲደረግ ተደርጎ የተሰራው ስራ መጠን ተጣርቶ በዚህ አግባብ ክፍያ እንዲከፈል አመልካች በተወካዮቹ አማካኝነት ስምምነት ላይ ደርሷል በሚል ምክንያት መሆኑንም ተረድተናል፡፡ አመልካች የዳግም ግምገማው ሪፖርት ተቀባይነት ላይ ክርክር የሌለውና የዚህ ሪፖርት አላማ በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን ግንኙነት ወደፊት ቀሪ እንዲሆን ታስቦ የተከናወነ መሆኑንም የሚቀበለው ጉዳይ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ስለሆነም ምላሽ የሚያሻው የጉዳዩ ጭብጥም አመልካችና ተጠሪ ሚያዚያ 09 ቀን 2000 (እ.ኤ.አ አፕሪል 17 ቀን 2008) ያፀደቁት የሥራ ውል ተሻሽሏል ወይንስ አልተሻሻለም? የሚለው ነው፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ከማየታችን በፊት ግን የተጠሪ ወኪል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ባነሷቸው ነጥቦች ላይ ምላሽ መስጠቱ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

የተጠሪ ወኪል አመልካች የሰበር አቤቱታውን በጊዜ ገደቡ ያለማቅረቡንና በግልግል ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን ግራ ቀኙ የተስማሙት መሆኑን ገልጸው ጉዳዩ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ አይገባም በማለት ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሰበር አቤቱታውን እንዲያቀርብ በሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁጥር 62141 በሕጉ አግባብ የፈቀደለት በመሆኑ የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ማለፉን መሰረት በማድረግ የተጠሪ ወኪል ያቀረቡትን ተቃውሞ አልተቀበልነውም፡፡ እንዲሁም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ስምምነት ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው የሚል ቢሆንም እንኳ የሰበር ሰሚ ችሎቱን ስልጣን በስምምነት ለማስቀረት የሚቻልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 42239 በቀረበው ጉዳይ ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበው ተቃውሞም ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስም በመሰረቱ በውል አመሠራረት ሂደት ውል ተቀባይ ተብሎ የሚታወቅ ወገን ውሉን መቀበሉ በጽሁፍ፣ በልማዳዊ ምልክት ወይንም በተግባር ካላመለከተ በስተቀር መልስ ሣይሰጥ ቢቀር በግራ ቀኙ መካከል የውል ግዴታ ተቋቁሟል ለማለት እንደማይቻል ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1682 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ድንጋጌ የሚሳየው በመርህ ደረጃ ዝምታ ውልን እንደመቀበል ሊቆጠር እንደማይችል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ ሁኔታዎች ዝምታ ውልን እንደመቀበል እንደሚያስቆጥር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1683 እና 1684 ድንጋጌዎች ስር ከተመለከቱት ሁኔታዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም አግባብ አስቀድሞ በግራ ቀኙ መካከል የውል ስምምነት ባለ ጊዜ አንድ ወገን ይህንን ውል ለማደስ፣ የውሉን ዘመን ለማስረዘም፣ ለማሻሻል ወይም ከቀድሞው ውል ጋር በተዛመደ አኳኋን ተጨማሪ ውል ለማድረግ የሚያቀርበው ጥያቄ በበቂ ጊዜ ውስጥ በሌላው ተዋዋይ ወገን አሉታዊ ምላሽ ካልተሰጠበት ዝምታው መቀበልን እንደሚያስከትል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1684 ስር ተደንግጓል፡፡ የፍ/ሕ/ቁጥር 1722 ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ ቀድሞ የነበረ ውል በሚሻሻልበት ጊዜ አስቀድሞ በተደረገው የአፃፃፍ ሥርዓት መከናወን እንዳለበት በግልፅና አስገዳጅነት ባለው መልኩ ሰፍሯል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ግራ ቀኙ ሚያዚያ 09 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት የሥራ ውል ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ከነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ/ም ድረስ የሚቆይ አለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴሌኮም ኩባንያ ለመፍጠር ሲባል የተለያዩ ተግባራት የሚከናወኑበትን ስምምነት ማድረጋቸው በግራ ቀኙ የታመነ ቢሆንም በውሉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብና የአፈጻጸም ጥራት ስራው ያልተከናወነ መሆኑን ተጠሪ የማይክደው፣ እንዲሁም የግልግል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉባኤውም በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ነጥብ ነው፡፡ ተጠሪ የክፍያ ጥያቄውን ያቀረበውም የቀድሞው ውል በሕጉ አግባብ ተሻሽሏል በሚል ምክንያት ስላለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያረጋግጠው ነጥብ ሲሆን ተጠሪው ለጥያቄው መሰረት ያደረገው መስከረም 5 ቀን 2001 ዓ.ም. በተደረገው የመልሶ ግምገማ አመልካች ለተጠሪ ለተሰሩ ስራዎች ክፍያ እንዲፈፀም ስምምነት አድርጓል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ መስከረም 5 ቀን 2001 ዓ/ም በአመልካች መስሪያ ቤት ኃላፊዎች ተቀባይነት አግኝቷል የተባለው የመልሶ ግምገማ ሪፖርት ውጤት ተጠሪ ቀድሞ በተደረገው የውልና እና የጥራት ደረጃ 71.3% (ሰባ አንድ ነጥብ ሶስት ከመቶ) ብቻ የሰራ መሆኑ መረጋገጡን አመልካች በማመን አሁን አጥብቆ የሚከራከረው ይህ የመልሶ ግምገማ ሪፖርት በቀድሞው ውል ስለ ክፍያ አፈፃፀም የተመለከተውን ሌሎች የተዋዋይ ወገኖችን መብትና ግዴታ ቀሪ ያደረገ ባለመሆኑ ለመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና የተያዘው ገንዘብ ስለመሰራቱ ከተረጋገጠው የስራ መጠን ጋር ተዛምዶ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ አመልካች ለተጠሪ ሊለቅ የሚገባበት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለም በማለት ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን እንደተመለከተው ተጠሪ የቀድሞ ውል የተሻሻለ ስለመሆኑ መሰረት አድርጎ ክስና ክርክር ያላቀረበ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1722 መሰረትም የተሻሸለ ውል ስለመኖሩ የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2001 መሰረት መብቱን ያስረዳበት የክርክር ሂደት የለም፡፡ ተጠሪ የሚጠይቀውን ክፍያ ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2001 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ አኳኋን በተጠሪ በኩል የቀረበ የውል ማሻሻል ጉዳይ በሌለበት ሁኔታ አመልካች የመስከረም 5 ቀን 2001 ዓ/ም የመልሶ ግምገማ ውጤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1684 መሠረት በዝምታ ተቀብሏል ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብም ሊኖር አይችልም፡፡ ይልቁንም የአመልካች መስሪያ ቤት ኃላፊ የመልሶ ግምገማ ሪፖርቱን ከተመለከቱ በኋላ ተጠሪ አለኝ የሚለውን ክፍያ በቀድሞው ውል መሰረት እንዲከናወን በሚያስገነዘብ መልኩ ጠቅሰው በመልሶ ግምገማ ሪፖርቱ ላይ ማዘዛቸውን አመልካች በአቀረበው የሰነድ ማስረጃ ይዘት የተረጋገጠ ስለመሆኑ በጉባኤው ላይ የተደረገው የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የመስከረም 5 ቀን 2001 ዓ.ም. የመልሶ ግምገማ ሪፖርት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1722 መሠረት የቀድሞው ውል የተሻሸለበት መሆኑን ባልተረጋገጠበትና በሪፖርቱ ላይ የክፍያው አፈጻጸም በቀድሞው ውል ከተገለፀው ውጪ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ በቀድሞው ውል አንቀፅ 11.4 ድንጋጌ መሰረት ተጠሪ ከሚገባው ክፍያ በተሰራው ስራ መጠን መሰረት 12% እንደሚለቀቅለት በግልጽ ባልተቀመጠበት ሁኔታ ግልግል ጉባኤው የመልካም ስራ አፈጻጸም ቦንድ በመልሶ ግምገማ መሰረት በተረጋገጠው 71.3% ስሌት መሰረት እንዲለቀቅ መወሰኑ የውል ወይም የሕግ መሰረት በሌለበት ሁኔታ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ አንድ የግልግል ጉባኤ ጉዳዩን በማየት የዳኝነት መፍትሔ ሊሰጥ የሚችለው ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች በተስማሙበትና በሚጸና ወይም ዋጋ ያለውን ግዴታ በመከተል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 356(ሀ) ድንጋጌ አቀራረፅ፣ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ ይህ ድንጋጌ የግልግል ወይም የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ተከራካሪዎቹ ወገኖች የተስማሙበት ነው በማለት በማይጸና ወይም ዋጋ የሌለውን ግዴታ በመከተል ወይም ባለጉዳዮቹ ያላቀረቡትንና ያልተከራከሩበትን ጉዳይ መሰረት በማድረግ ብይን የሰጡ መሆኑ ከተረጋገጠ ጉዳዩ ይግባኝ የሌለው መሆኑን ቢስማሙም እንኳን ይግባኝ ለማቅረብ መሰረት ከሚሆኑ ነገሮች መካከል እንደሆኑ ጠቅሷል፡፡በመሆኑም የግልግል ጉባኤው የመልካም ስራ አፈጻጸምን በተመለከተ ተጠሪ ስለመስራቱ በመልሶ ግምገማ በተረጋገጠው መጠን ስሌት መሰረት ታስቦ ሊመለስለት ይገባል በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ከመልሶ ግምገማ በኋላ የቀድሞ ውል በሕጉ አግባብ የተሻሸለና ዋጋ ያለው ስምምነት ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከርበት ነጥብ የተከሳሽ ክሳሽነትን ክስ መሰረት ያደረገ የጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄ ነው፡፡ በክርክሩ ሂደት አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገው ውል በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያለመከናወኑና የተሰራው ስራም በውሉ የተገለፀውን ያህል መጠን ያለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች የጉዳት ካሳ ጥያቄን መሰረት ያደረገውም ስራው በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ያለመሰራቱና በውሉ አንቀፅ 17 የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ በውሉ አንቀፅ 17 ስር ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሙሉ ወይም በከፊል ግዴታውን ካልተወጣ ሌላው ወገን የጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑንና ሊጠየቅ የሚገባውን የጉዳት መጠን ምን ያህል እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ የመልካም ሥራ አፈጻጸም (ቦንድ) ሰነድ የውል አፈፃፀምን ለማረጋገጥ የሚሰጥ የዋስትና ሰነድ መሆኑን፣ ይህም በባለገንዘብ እና በባለ እዳ መካከል የተደረገን ውል አፈፃፀም ለመጠበቅ የሚገባ ግዴታ መሆኑ ከሰነዱ አይነተኛ ዓላማ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የመልካም ስራ አፈፃፀም ቦንድ መሰረታዊ አላማ ስራው በውሉ መሰረት ስለመሰራቱ ለማረጋገጥ የሚገባ ግዴታ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ የጸናው ውል በአንቀጽ 11.4 ስር ከመጀመሪያ ክፍያ ጀምሮ እየተቀነሰ 12% የሚሆነው የውሉ ዋጋ እንዲያዝ የሚደረግ መሆኑንና የውሉ ዘመን ካለቀ ከ15 ቀናት በኋላ ስራዎቹ በስኬታማ ሁኔታ መጠናቀቃቸውን በሃርድ ኮፒ እና በሶፍት ኮፒ ከተረጋገጠ በኋላ የሚለቀቅ መሆኑን በግልጽ ያሳያል፡፡ በዚሁ በውሉ ድጋንጌ ውስጥ ".....ስራዎቹ በስኬታማ ሁኔታ መጠናቀቃቸው----" የሚለው ሐረግ ሲታይ የመልካም ስራ አፈጻጸም ቦንድ ስራዎቹ በስኬታማ ሁኔታ ባይጠናቀቁ የሚደርሰውን ጉዳት ለማካካስ ጭምር ታስቦ የተገባ ግዴታ መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካች ተጠሪ በተከሳሽ ክሳሽነት በውሉ አንቀጽ 17 መሰረት የጠየቀው የጉዳት ካሳ መጠን በውሉ አግባብ ሳይሰራ በዘገየበት ጊዜና ስራውን ሰርቶ ለማጠናቀቅ በተጨማሪነት አስፈላጊ የሆነውን ጊዜ መሰረት በማድረግ ተሰልቶና በአመልካች እጅ ይገኛል ከተባለው የመልካም ስራ አፈጻጸም ገንዘብ መጠን የበለጠ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን ግንኙነት መሰረት በማድረግ የተሰራውን ስራ መልሶ በመገምገም በተሰራው ስራና ከታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ በጸናው ውል መሰረት ክፍያ እንዲፈጸም የተደረገ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ ስራውን በጊዜ ለማጠናቀቅ ባለመቻሉና ስራውን ወደፊት ሰርቶ ለመጨረስ የሚያስፈልገው ጊዜ ላይ ካሳ ለማስከፈል አመልካች ሃሳብ የነበረው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን ግንኙነት መሰረት አድርጎ በተሰራው የስራ መጠን ለተጠሪ ክፍያ በመፈጸም የውሉ ማጠናቀቂያ ጊዜ ከሆነው ከነሐሴ 2000 በኋላ ስራው ለዘገየበትና ስራውን ሰርቶ ለማጠናቀቅ ለሚያስፈልገው ተጨማሪ ጊዜ ያልተሰራውን ስራ 0.1% ያህል የክፍያ መጠን ለእያንዳንዱ ቀን ወይም የውሉን ጠቅላላ ዋጋ 10% በጠቅላላው የጉዳት ካሳ ከተጠሪ የሚጠይቅበት አግባብ ስለመኖሩ በማስረጃ ያላስደገፈው የክርክር ነጥብ ነው፡፡ ይልቁንም አመልካች ስራው በውሉ በተቀመጠው ጊዜና ጥራት ያለመጠናቀቁን እያወቀ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ቀሪ እንዲሆን መስከረም 05 ቀን 2001 ዓ.ም. በተደረገው የመልሶ ግምገማ ሪፖርት መነሻነት ስምምነት አድርጓል፡፡ ይህ ስምምነት የሚያሳየው ውሉ በጊዜው ባይጠናቀቅም በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት አቋርጧል፡፡ የተቋረጠ ውል ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች መካከል እስከተቋረጠ ድረስ እንጂ ውሉ ከተቋረጠ በኋላ ባለው ጊዜ ወይም ወደፊት ውጤት የሚያስከትልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1819(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ ውድቅ የሆነው የመስከረም 05 ቀን 2001 ዓ.ም. የመልሶ ግምገማን ሪፖርት አመልካች በመቀበል ስራውን ለወደፊት ለመስራት የሚያስፈልጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጊዜያትን ቀሪ በማድረጉ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የግልግል ጉባኤው በጉዳዩ ላይ ነሐሴ 06 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 353 መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል መስከረም 05 ቀን 2001 ዓ.ም. ተደረገ የተባለው የመልሶ ግምገማ ሪፖርት ስምምነት በመካከላቸው ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. የተደረውን ውል ያላሻሻለ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ በመልሶ ግምገማ መሰረት ስለመሰራቱ በተረጋገጠው 71.3% ስራ መጠን መሰረት የመልካም ስራ አፈጻጸም ቦንድ ለተጠሪ የሚለቅበት አግባብ የለም ብለናል፡፡ የአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ከተደረገው ውል አንቀፅ 11.4፣ 17 ይዘትና መንፈስ ከመስከረም 5 2001 ዓ.ም. የመልሶ ግምገማ ሪፖርትና ውጤቱ ጋር ባገናዘበ መልኩ ነው ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሐሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በሰጠው ውሣኔ በከፊል ያልተስማማሁ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ ከሙያ ባልደረቦቼ በከፊል የማልስማማባቸውና በከፊል የምስማማባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመጀመሪያው ልዩነቴ የግራ ቀኙን ክርክር ለመፍታት የሚያስችል ጭብጥ በመያዝ ለጉዳዩ እልባት መስጠት ያስፈልጋል የሚል ነው፡፡ አብላጫው ድምፅ “አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ያደረጉት የሥራ ውል ተሻሽሏል ወይስ አልተሻሻለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝና ይህንኑ ጭብጥ ለመወሰን አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1722፣ የፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1684 እና የውሉን ኃይለ ቃሎች በመተርጎምና መሠረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በእኔ በኩል የግልግል ጉባኤው አብዛኛውን የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በመሆኑ አሁን በሰበር የሚከራከሩበትን ጉዳይ ለመወሰን ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ውል በአመልካችና በተጠሪ ስምምነት ተቋርጧል ወይስ አልተቋርጠም? ውሉ በተዋዋዮቹ ፈቃድና ስምምነት ተቋርጧል የሚባል ቢሆን የውሉ መቋረጥ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? የሚሉትን ጭብጦች ካልተያዙና ስለ ውል መቋረጥ መሠረታዊ ባህሪይ፣ አፈፃፀምና ውጤት የሚደነግጉ የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ውሣኔ

ካልተሰጠ የግራ ቀኙን ክርክር በአግባቡ ለመፍታት አይቻልም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ ምክንያቱም አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት የሥራ ውል መሠረት ተጠሪ 71.3% ሥራ የሠራ መሆኑን ግራ ቀኙ ያልተካካዱበትና የግልግል ጉባኤው ያረጋገጠው፣ ይህ የሰበር ችሎትም ትክክል ነው ብሎ የተቀበለው ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አድርገውት የነበረውን ውል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት ለማቋረጥ (terminate) ለማድረግ መስማማታቸውና ውሉ በተዋዋዮቹ ስምምነት ቀሪ መሆኑ (terminate) መደረጉ በግልግል ጉባኤው ተረጋግጧል፡፡ አብላጫው ድምፅም አመልካች በአፀፋ ክስ ውሉ በአግባቡ ባለመፈፀሙ ተጠሪ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ የግልግል ጉባኤው ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የግልግል ጉባኤውን ውሣኔ በከፊል ያፀናው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ውል በተዋዋዮቹ ስምምነት ቀሪ መሆኑን (terminate) መደረጉን በመጥቀስ ነው፡፡

ተጠሪ በውሉ መሠረት 71.3% ሥራ ከሠራ በኋላ ውሉ በአመልካችና በተጠሪ ስምምነት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት መቋረጡ (ቀሪ) መሆኑ ካላከራከረ፣ አመልካችና ተጠሪ ውላቸውን በስምምነት ቀሪ ማድረጋቸው አመልካች የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የሚሆን ነው በማለት ውሉ ከተቋረጠ በኋላ 87,169.02 የአሜሪካን ዶላር አላግባብ የቀነሰብኝ ስለሆነ እንዲከፍል በማለት ተጠሪ ባቀረበው ጥያቄ ላይ የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? በተመሣሣይ ሁኔታ የውለታው በተዋዋዮቹ ስምምነት ቀሪ መሆን አመልካች ተጠሪ ውሉን አሟልቶ ባለመፈፀሙ ለደረሰብኝ ጉዳት ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ባቀረበው አፀፋ ክስ ላይ የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? የሚሉትን ነጥቦች መመርመር ይጠይቃል፡፡

ውለታን ለማስቀረት በተዋዋይ ወገኖች በፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚደረግ ስምምነት፣ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1675 በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገ ውል አቋቁመውት የነበረውን ግዴታቸውን ለማስቀረት ያደረጉት ውል ነው፡፡ ይህም ማለት አመልካችና ተጠሪ ውሉን ለማቋረጥ (ቀሪ) ለማድረግ በሚያደረጉት ስምምነት ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በስተቀር በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1711 መሠረት የመሰላቸውን የመወሰን መብት ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ ውሉ በተዋዋዮቹ ስምምነት ቀሪ መሆኑ (terminate) መደረጉ የሚያስከትለውን ውጤት በመረዳት አመልካችና ተጠሪ ውሉን ለማቋረጥ ሲስማሙ ፈቃዳቸውን የሰጡባቸውን መሠረታዊ ጉዳዮችና ስለውል መቋረጥ (termination of contract) የተደነገጉ የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ አከራካሪውን ጭብጥ መወሰን የሚጠይቅ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

2. አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አድርገውት የነበረውን የሥራ ውል ለማቋረጥ ሲስማሙ፣ አመልካች ተጠሪ ለሰራው ሥራ 657,408.51 የአሜሪካን ዶላር የተጣራ ክፍያ ለመክፈል መስማማቱን የግልግል ጉባኤው አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የተጠሪን የትራንስፖርት ወጭ፣ የአየር ትኬትና የቤት ኪራይ ወጭ መሸፈኛ የሚሆን 69,000 የአሜሪካን ዶላር ለመክፈል መስማማቱ በግልግል ጉባኤው ውሣኔ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች እነዚህን ክፍያዎች በመፈፀም ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሥራ ውል ለማቋረጥ (ለመዝጋት) የተስማማ መሆኑን አይክድም፡፡ የግልግል ጉባኤው ውሣኔ የሰጠበትና አመልካችንና ተጠሪን ያላግባባውና እስከ ሰበር ያከራከረው፡፡ አመልካች ተጠሪ ለሠራው ሥራ ከሚከፍለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

657,408.51 የአሜሪካን ዶላር፣ ከተጠሪ ጋር ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ያደረግሁት የሥራ ውል አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 መብት ይሰጠኛል በማለት 12% በመቀነስ ክፍያ መፈፀሙና በተመሣሣይ ሁኔታ አመልካች ለትራንስፖርት፣ ለአየር ትኬትና ለቤት ኪራይ የወጣ ወጭ መሸፈኛ ለመክፈል ከተስማማው 69,000 የአሜሪካን ዶላር 12% ቀንሶ ማስቀረቱ ነው፡፡

ተዋዋይ ወገኖች በውል አቋቁመውት የነበረውን ግዴታ በፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በስምምነት ቀሪ ሲያደርጉ የተለየ ፎርም መከተል እንዳለባቸው የሚደነግግ አስገዳጅ ድንጋጌ የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አድርገውት የነበረውን የሥራ ውል በስምምነት ማቋረጣቸው አከራካሪ ጭብጥ አይደለም፡፡ የውለታ በተዋዋዮች ስምምነት መቋረጥ (terminate) መደረግ ከውል መፍረስ ወይም ከውል መሠረዝ የተለየ ባህሪና ውጤት ያለው መሆኑን አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ድንጋጌዎች ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ እንደዚሁም ውል በስምምነት ቀሪ ማድረግ (termination of contract) ውልን ከማሻሻል (ውል ከመለወጥ) (variation of contract) እና ውል ከመተካት (Novation of contract) የተለየ ባህሪ፣ ይዘትና ውጤት ያለው መሆኑን፣ የፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1722 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1826 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ስመለከተው አመልካች ከተጠሪ ጋር በተደረገው ስምምነት ቀሪ የሆነውን ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ተደርጎ የነበረው የሥራ ውል አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 የፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1722 በሚደነግገው መሠረት ያልተሻሻለ በመሆኑ ለተጠሪ ከምከፍለው ክፍያ 12% ቀንሶ የማስቀረት መብት አለኝ በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ውልን በስምምነት ቀሪ በማድረግና ውለታን በማሻሻል መካከል ያለውን ልዩነት ያላገናዘበና የሕግ መሠረት የሌለው ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

የውሉ በተዋዋዮቹ ፈቃድና ስምምነት መቋረጥ (ቀሪ) መሆን የተዋዋይ ወገኖች የወደፊት የውል የመፈፀም ግዴታ የሚያስቀር መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም የውሉ መቋረጥ /ቀሪ/ መሆን ያለፈውን ሁኔታ የማይነካ መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የውል ቀሪ መሆን (termination of contract) ተዋዋዮቹ በውል አቋቁመውት የነበረውን መብትና ግዴታ ቀሪ የማድረግ ውጤት የሚኖረው መሆኑን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1807 /ለ/ ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አድርጎት የነበረውን የሥራ ውል ለማቋረጥ ሲስማማ ተጠሪ ለሰራው ሥራና ውሉን ለመፈፀም የወጣውን ወጭ ለመሸፈኛ እንዲሆን በድምሩ 726,408.51 የአሜሪካን ዶላር ለተጠሪ በመክፈል ውለታውን ለማቋረጥ የሰጠው ፈቃድና ስምምነት ውሉን ለማሻሻል የተሰጠ ፈቃድ ሳይሆን ውሉን ለማቋረጥ የተደረገው ስምምነት ልዩ ሁኔታና ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ውሉን ለማቋረጥ ከተጠሪ ጋር ባደረገው ስምምነት አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት ውል ያቋቋሟቸው መብቶችና ግዴታዎች ተቋርጠዋል (ቀሪ ሆነዋል)፡፡ አመልካች የውሉ ሕልውና በስምምነት ቀሪ የሆነውን ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ተደርጎ የነበረውን የሥራ ውል አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በማድረግ ለተጠሪ ውሉን ሲያቋርጥ ለመክፈል ከተስማማው ገንዘብ አሥራ ሁለት ፐርሰንት ቀንሶ ለማስቀረት የሚያስችለው ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ መብት የለውም፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን ውል ቀሪ ለማድረግ ያደረገው ስምምነት እንደ ማናቸውም ውል በተዋዋዮቹ ላይ የሕግ ያህል ገዥነትና አስገዳጅነት የሚኖረው መሆኑን የፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ከፍታሐብሔር ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ጋር በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሥራ ውል ቀሪ ለማድረግ ሲስማማ ለመክፈል ፈቃዱን የሰጠበትን ገንዘብ ሣይቀናነስ የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ አመልካች ውለታን ቀሪ ለማድረግ ከተጠሪ ጋር ባደረገው ስምምነት ገቸርነቱና ተፈፃሚነቱ ቀሪ የሆነውን የሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሥራ ውል አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 በመጥቀስ 87,169.2 የአሜሪካን ዶላር ለተጠሪ ከሚከፍለው ክፍያ ቀንሶ ማስቀረቱ ከላይ በዝርዝር የገለፅኳቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መሠረት የሌለው ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ ይህንን የአመልካች አድራጎት የግልግል ጉባኤው የሕግ መሠረት ስለሌለው ቀንሰህ ያስቀረኸውን ገንዘብ ለተጠሪ ክፈል በማለት መወሰኑ ተገቢና የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

3. አመልካች በስምምነት ሕልውናው፣ አስገዳጅነቱና ተፈፃሚነቱን ቀሪ ያደረገውን ከተጠሪ ጋር ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አድርጎት የነበረውን የሥራ ውል በመጥቀስ ተጠሪ በውሉ መሠረት ግዴታውን አጠቃልሎ ያልፈጸመ በመሆኑ፣ ውሉ ባለመፈፀሙ ተጠሪ ካሣ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበውን የአፀፋ ክስ የግልግል ጉባኤው ውድቅ አድርጎታል፡፡ የግልግል ጉባኤው የአመልካችን የአፀፋ ክስ ቀሪ ያደረገው ውሉን ለማቋረጥ (termination) ለማድረግ ስትስማሙ በውሉ አለመፈፀም ለደረሰ ጉዳት ካሣ የመጠየቅ መብት ያለህ ስለመሆኑ አልተገለፀም፡፡ በአንፃሩ ውሉን ቀሪ ለማድረግ የተስማማኸው በውሉ አለመፈፀም ካሣ የመጠየቅ መብትህን በመተው ነው በማለት ነው፡፡ አብላጫው ድምፅ ይህ የግልግል ጉባኤው ውሣኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1819 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያደረገ መሆኑን በመዘርዘር በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎ የግልግል ጉባኤው የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ እኔ በዚህ የውሣኔ ክፍል አብላጫው ድምፅ በሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ የምስማማበት ነጥብ ነው፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና ተራ ቁጥር 2 በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች አመልካች የሕግ ወይም የፀና የውል መሠረት ሣይኖረው ቀንሶ ያስቀረውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው ብዬ ስለማስብ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 71537

ታህሣስ 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች:- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ህይወት

አመልካቾች ፡- 1. ወ/ሮ የሻረግ ከበደ - ከጠበቃ አቶ ሐጎስ ደበሉ ጋር ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሃና አድማሱ - ከጠበቃ አቶ አለማየሁ ታደሰ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን ቀረቡ

ይህ በሰበር መ/ቁ. 71537 የተሰየመው መዝገብ በቀጥታ የአሁን 1ኛ አመልካችና የአሁን ተጠሪን የሚመለከት ቢሆንም፤ የአሁን 2ኛ አመልካች ወ/ሮ ሃና አድማሱና የአሁን ተጠሪ ወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን በሰበር መ/ቁ 72381 የሚከራከሩበት ጉዳይ ለሰበር መ/ቁ. 71537 መነሻ ከሆነው ከፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ. 75093 ጋር አብሮ የተነሣ ክርክርም ሆነ ውሣኔ ማስረጃው አብሮ የተሰማና በአንድ ቀን በአንድ ላይ ውሣኔ የተሰጠበት በመሆኑ እና ሁለቱም አመልካቾች በየፊናቸው ራሱን የቻለ የሰበር መዝገብ በማስከፈታቸው ምክንያት ተለያይቶ የቀረበ መሆኑን ሁሉ በማየት በሰበር መ/ቁ. 72381 የተነሣውን ጉዳይ ከዚህ ሰበር መ/ቁ. 71537 ጋር ተጣምሮ እንዲታይ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው በአሁኑ ተጠሪ ከሣሽነት እና በአሁን አመልካቾች ተከሣሽነት የተነሣውን ክርክር ተመልክቶ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 75093 የካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ በከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበው ክስ ላይ የአሁን አመልካቾችን 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች በማድረግ ያቀረቡት ክስ ፍሬ ቃል በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 19 የቤት ቁጥር 423 በተመዘገበው ቤት በ2905 ካ.ሜትር ውስጥ የሚገኘውን ቤት 1ኛ ተከሣሽ ወ/ሮ የሻረግ ከበደ ከሰኔ 14 ቀን 1986 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም ያላግባብ ይዘው እየተገለገሉበት ስለሚገኝ በዚህ በቤት ቁጥር 423 ውስጥ የሚገኘውን ሁለተኛውን ቤት ከእነ ማእድ ቤቱ ደግሞ ሁለተኛ ተከሣሽ ወ/ሮ ሃና አድማሱ ከግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በኃይል በመያዛቸው ቤቶችን ከኪራይ ክፍያ ጋር ያስረክቡኝ የሚል ነው፡፡

ለዚህም ክስ በማስረጃነት ያቀረቡት ወ/ሮ አለሙሽ አዲሱ ክስ የቀረበበትን ቤት ህዳር 12 ቀን 1966 ዓ.ም በተደረገ የስጦታ ውል ለከሣሽ ያስተላለፉ መሆኑን የሚገልጽውን የስጦታ ውል ቤቱ በወ/ሮ አበበች ወልደዮሐንስ ስም ግብር የተከፈለ መሆኑን የሚያሣይ የግብር ክፍያ ደረሰኝ እንዲሁም በመ/ቁ. 2525/89 እና 0691 በ24/2/98

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ፤ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 5865 በ11/3/94 ዓ.ም የተሰጠውን ውሣኔ በማያያዝ አቅርበዋል፡፡

1ኛ ተከሣሽ የነበሩት የአሁን 1ኛ አመልካች ወ/ሮ የሻረግ ከበደ በሰጡት መልስና ቤቱን ያላግባብ ይዛለች ከተባለበት ከሰኔ 14 ቀን 1986 ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲሰላ ክሱ በይርጋ ሊቋረጥ ይገባል፡፡ ስጦታው ክርክር የተነሣበትን ቤት የሚያመለክት አይደለም፡፡ ክስ የቀረበበትን ሁለት ክፍል ቤቶች ከወ/ሮ አበበች ወ/ዮሐንስ በስጦታ ያገኘሁትን ኩሽና ቤት አፍርሼ የሰራሁት የእራሴ ሀብት ነው ይኸው ክስ የቀረበበት ቤትም የስጦታ አድራጊ የተባሉት የወ/ሮ አለሙሽ ርስት ስለመሆኑም ማስረጃ የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሁለተኛ አመልካች በበኩላቸውም በኃይል ንብረቱን ወስዳለች ከተባለበት ከግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ሲታሰብ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ በህዳር 12 ቀን 1966 ዓ.ም. ተደረገ የተባለው የስጦታ ውል በይርጋ ቀሪ ከመሆኑም በላይ ያልተመዘገበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም እኔ እራሴ በእርሷ በከሣሽ ላይ ያቀረብኩት ክስ እየታየ ስለሆነ ይህ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበው ክስ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን በማስረጃነትም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 80684 የተሰጠ ውሣኔ አቅርበዋል፡፡

ክሱ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ 1ኛ ተከሣሽ የአሁን 1ኛ አመልካች ወ/ሮ የሻረግ ከበደ በቤት ቁጥር 423 በተመዘገቡ ሁለት ቤቶች መካከል በስጦታ ከወ/ሮ አበበች ወ/ዮሐንስ በመረከብ አፍርሰው ሁለት ቤቶችን መሥራታቸውን ጠቅሰው ቢከራከሩም የተሰጣቸው የስጦታ ውል በህግ ፊት ተቀባይነት የለውም ተብሎ በውሣኔ የፈረሰና ሰራሁ ስለሚሉትም ለቤቱ የቤት ባለቤትነት ማስረጃ ባለማቅረባቸው ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ በአካያው ክርክር የተነሣበትን ቤትና ይዞታ ከሣሽ ከእናታቸው ከወ/ሮ ዓለሙሽ አድማሱ በ12/3/66 በስጦታ ያገኙ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ቀርቧል፡፡ የአሁን ሁለተኛ አመልካች ክስ በቀረበበት ጉዳይ ከከሣሽ ጋር በመከራከር ላይ እገኛለሁ ቢሉም ቤቱን እንዲረከቡ አልተፈረደላቸውም፡፡ ቤቱም በወ/ሮ አበበች ወ/ዮሐንስ የተመዘገበና ለጊዜውም በባለቤትነት የምታወቀው እኔ ነኝ በማለት ከመከራከራቸው በቀር ሁለተኛውን ቤት አልያዝኩም በማለት በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ስለሆነም ሁለቱም ተከሣሾች ክስ የቀረበበትን ቤት ለከሣሽ እንዲያስረክቡ ይገደዳሉ፤ ያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡

ይህንን ውሣኔ በ1ኛ አመልካች አቤቱታ መሠረት በይግባኝ የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 68052 ሰኔ 06 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 እንደተደነገገው መዝገቡን ዘግቷል፡፡ እንዲሁም በሁለተኛው አመልካች ይግባኝ ባይነት በይ/መ/ቁ. 67759 ሰኔ 03 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተመሣሣይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥረ 337 መሠረት በመዝጋቱ የአሁን ሁለቱም አመልካቾች በየፊናቸው እንደቅደም ተከተሉ ለዚህ የሰበር ጉዳይ ማለትም በሰበር መ/ቁ. 71537 እና በሰበር መ/ቁ. 72381 ምክንያት የሆነውን የሰበር ቅሬታ በማቅረባቸው በእነዚሁም የሰበር መዛግብት ላይ ሁሉም ያላቸውን የጽሑፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አመልካቾችም ሆነ ተጠሪ በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር በይዘቱ በሥር ፍ/ቤት አንስተው የተከራከሩባቸውን ነጥቦች የሚያብራሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የዚህ የሰበር ጉዳይ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተውን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው እንደ ጉዳዩ አነሣስና ይዘት በዚህ ጉዳይ በቅድሚያ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው አከራካሪ ነጥብ የአሁን አመልካቾች የቀረበብን ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ካነሱት ነጥብ አንፃር ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህንን አከራካሪ ነጥብ አስመልክቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 75093 የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከሳሽ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ የባለቤትነት መብትን የሚመለከት በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ አይችልም የሚል ትርጉም ሰጥቶ ክሱ በይርጋ አይታገድም የሚል ዳኝነት እንደሰጠበት ከመዝገቡ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

በንብረት ላይ ያለን የመፋለም ክስ አስመልክቶ ይህ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 43600 ጥር 05 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደማይገባ ተንትኖ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በዚሁ ትርጉም በተሰጠበት ውሣኔ ላይ ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት ከውርስ ከሽያጭ እና ከስጦታ ውል የመነጨን የባለቤትነት መብት አስመልክቶ በሚነሳ የንብረት ክርክር የይርጋ ጉዳይ በተነሣ ጊዜ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ለጉዳዩቹ አግባብነትና ተፈፃሚነት ባለው የህግ ክፍል እና የህግ ይዘት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባ በተለይ አኳኋን ተመልክቶ ትንታኔ የሰጠበት እንጂ ማናቸውም በንብረት ላይ ያለን የባለቤትነት መብት ጥያቄ በይርጋ ሊታገድ የሚችል አይደለም በሚል አልወሰነም፡፡

ይህም አሁን በግራ ቀኙ የተነሣውን ክርክር እንዳየነው የአሁን ተጠሪ በስጦታ ውል ከወ/ሮ አለሙሽ አድማሴ የተላለፈልኝን ቤት ተከሣሾ /የአሁን አመልካቾች/ ያለአግባብ ይዘውብኛል በሚል መነሻ የቀረበ የንብረት መብት ማስከበር ጥያቄ እንደመሆኑ ከስጦታ ውል የመነጨውን የንብረት መብት ለማስከበር የሚቀርበው የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም? የይርጋ ክርክርን ሊጋብዝ የሚችል ከሆነስ የይርጋ ዘመኑ ምን ያህል ነው? የሚሉትና ተያያዥነት ያላቸው ክርክሮች ስለስጦታ ውል አመሰራረት ውጤት እና የመሳሰሉትን ዝርዝር ጉዳዮች በሚገዛው የህግ ክፍል እና የአፈፃፀም ወሰን መሰረት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር መ/ቁ 42691 መጋቢት 22 ቀን 2002ዓ.ም በዋለው ችሎት ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ ይህም ጉዳይ በዚሁ ትርጉም መሰረት ሊታይ የሚገባው እንጂ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደሰጠው ትርጉም በይርጋ የሚታገድ የክርክር ዓይነት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከዚህም አንፃር የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች ላይ ላቀረቡት ቤት ይመለስልን የዳኝነት ጥያቄ መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ የቤት ቁጥር 423 ባለንብረት የነበሩት እና ወ/ሮ አለሙሽ አድማሱ ህዳር 12 ቀን 1966 ዓ.ም በተደረገ የስጦታ ውል አስተላልፈውልኛል በሚል እንደሆነ በፍሬ ሐገድ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ለክርክሩ መሰረት ያደረጉት የስጦታ ውል ህዳር 12 ቀን 1966 ዓ.ም የተደረገ ሆኖ የተሻሻለ ክስ እስከ መሰረቱበት እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም ሆነ ንብረቱን ተከሳሾች ያለአግባብ ይዘዋል እስከተባለበት እስከ ሰኔ 14 ቀን 1986 እስከ ግንቦት 30 ቀን 1999 ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ እንኳ ከ20 ዓመት በላይ ነው፡፡ በዚህ ስጦታ ተደረገ በተባለበት በህዳር 1966 ዓ.ም እና ንብረቱ ያለአግባብ ተይዟል እስከተባለበት ጊዜ ድረስ የስጦታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሉ ውጤት ይኖረው ዘንድ መብትን ለማስከበር የቀረበ እንቅስቃሴም ሆነ ለአፈፃፀም የቀረበ አለመሆኑን ክርክሩ አስረጅ ነው፡፡ ይህም ከሆነ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 42691 እንደሰጠው ትርጉም የስጦታ ጉዳዩን የሚገዛው የህግ ክፍል ሰለይርጋ በተለየ መንገድ የደነገገው ጉዳይ ባይኖርም ስጦታ ውል እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1676/1/ እና 1845 ድንጋጌዎች መሰረት ከስጦታ ሊመነጨ የሚችል የግዴታ አይነት በ10 ዓመት የጊዜ ገደብ ሊገደብ የሚገባው ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ንብረቱን በስጦታ እግኝቻለሁ ካለበት ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ንብረቱን ተከሳሾች ያዙብኝ እስካሉበት ጊዜ ድረስ ከ20 ዓመት በላይ በሆነው ጊዜ ውስጥ በስጦታ ውሉ መሰረት ንብረቱን በእጅ ስለማድረጋቸው ወይም ክርክር ያስነሳውን ቤት በስጦታ ውሉ መሰረት በይዞታቸው ስር እንዲሆን በውሉ መሰረት እንዲፈፀሙላቸው ያቀረቡት ጥያቄ እንደሌለ በክርክርም ሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ የስጦታ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ስጦታ ውሉ ለማስፈፀም ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ደግሞ ከ10 ዓመት /ከአስር ዓመት/ በላይ የሆነ ጊዜ አልፎታል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ከስጦታ ውል የመነጨ የንብረት ጥያቄ በመሆኑና ጥያቄውም የቀረበው ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የህግ ክፍል የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአሁን አመልካቾች ያቀረቡትን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረጉበት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 75093 የካቲት 30 ቀን 2003ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና በዚህ ፍርድ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 68052 በ06/10/2003 እና በይ/መ/ቁ 67759 በ3/10/2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን ህዳር 12 ቀን 1966 ዓ.ም ተደርጓል ያሉትን የስጦታ ውል መሰረት አድርገው በአሁን አመልካቾች በወ/ሮ የሻረግ ክበደ እና በወ/ሮ ሀና አድማሱ ላይ ያቀረቡት የቤት ይለቀቅልን ጥይቄ በይርጋ የታገደ ነው፡፡ አመልካቾች ቤቶችን ለተጠሪ ለወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን ለማስረከብ አይገደዱም ብለናል፡፡
3. የዚህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ሁሉም ተከራካሪዎች የየራሳቸውን ይቻሉ
4. የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ የመ/ቁ 75093 በመጣበት አኳኋን ይመለስ፡፡
5. የዚህ ክርክር ውጤት እስኪታወቅ ድረስ በሚል በዚህ የሰበር መዝገብ በሰበር መ/ቁ 71537 ህዳር 06 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገበ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 75743

ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የዳንግላ ማዘጋጃ ቤት ፍትህ ቢሮ - ዐ/ህግ እዮብ ጌታቸው

ተጠሪዎች ፡- 1/ የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ - አልቀረቡም

2/ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ ተመስገን ዘውዴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ አመዘጋገብ ስህተት ላደረሰ ኪሳራ ካሳ የመክፈል ኃላፊነትን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ የአንደኛ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በስር ፍ/ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረችው ወ/ሮ ዘውዴ ሽፈራው ጥር 14 ቀን 1988 በተፈረመ የብድር ውል ለሆቴል ህንፃ ግንባታ የሚውል ብር 110,800 (አንድ መቶ አስር ሺህ ስምንት መቶ ብር) ከከሳሽ (አንደኛ ተጠሪ) ተበድራ ወስዳለች፡፡ ተበዳሪዋ ይህንን ገንዘብ የወሰዱት የካርታ ቁጥሩ 614/935/61 በሆነው ይዞታ ላይ የሰፈረውን የድርጅት ቤት በመያዣነት እንዲያዝ በመስማማት ሲሆን ይሕ የመያዣ ውል እንዲመዘገብልን ጠይቀን የዳንግላ ማዘጋጃ ቤት (አመልካች) በቁጥር 642/4188 ጥር 24 ቀን 1988 ዓ.ም የማይንቀሳቀስ ንብረቱን ለከሳሽ ብድር የመጀመሪያ መያዣ አድርጎ የመዘገበው መሆኑን አረጋግጠልኛል፡፡ ሆኖም ሁለተኛ ተከሳሽ (ተበዳሪዋ) በብድር የወሰደችውን ገንዘብ ባለመክፈሏ፣ ከሳሽ (ሁለተኛ ተጠሪ) መያዣውን በሀራጅ በመሸጥ የብድር ገንዘቡን ለመሰብሰብ ሲንቀሳቀስ፣ ይኸው የተበዳሪዋ የማይንቀሳቀስ ንብረት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሀምሌ 11 ቀን 1987 የብድር ውል ሲይዝ ቤቱን በመያዣነት የያዘው መሆኑን በማለፅ ደብዳቤ ፅፏል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ (አመልካች) ቤቱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ላበደረው ብድር መያዣ መሆኑን ቢገልፅልኝ ኖሮ የብድር ገንዘቡን ለሁለተኛ ተከሳሽ አልሰጥም ነበር፡፡ ስለዚህ ከተበዳሪዋ የምንፈልገውን ብር 265,661.40 እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ለንብረቱ ሁለት የይዞታ ማረጋገጫ ያልሰጠሁ በመሆኑ በኃላፊነት አልጠየቅም፡፡ ከሳሽ መጀመሪያ የተበዳሪዋን ንብረት በመከታተል ዕዳውን ለመሰብሰብ ሳይሞክር ክስ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ ሁለተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ጣልቃ ገብቶ ቤቱ መያዣው ስለነበር በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሰጠው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ለሁለተኛ ተከሳሽ ብድር ስናበድር ቤቱ የማይሸጥ የማይለወጥ ፣ የዕዳ መክፈያ መያዣ መሆኑን በቁጥር 30/2834 ሀምሌ 13 ቀን 1987 በዓፈው ደብዳቤ መያዣውን መዝግቦ አረጋግጦልናል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አመልካች የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሁለተኛው ተጠሪ በመያዣነት የተያዘ መሆኑን ለአንደኛ ተጠሪ ባለመግለፁ በአንደኛ ተጠሪዎች ላይ ለደረሰው ኪሳራ ኃላፊነት እንዳለበት ወስኗል፡፡ አመልካች ኃላፊ የሚሆነው አንደኛ ተጠሪ በመጀመሪያ የሁለተኛ ተከሳሽን ንብረት በማፈላለግ ዕዳውን ለማስከፈል ተገቢውን ትጋት አድርጎ ላልተከፈለው ገንዘብ እንደሆነና አመልካች የሚከፍለው ካሳ መጠን በመያዣነት ተሰጥቶ የነበረው የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሚያወጣው ዋጋ በላይ መሆን እንደሌለበት በመግለፅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 ሰርዞታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርቦ የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን በሰበር የማየት ሥልጣን የለኝም በማለት አሰናብቶታል፡፡

አመልካች መጋቢት 7 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ንብረቱ የሁለቱን ባንኮች ዕዳ የሚሸፍን ከሆነ መያዣው ሊመዘገብ የሚችልበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ አመልካች ጥፋት እንደፈፀመ መታየቱ ተገቢነት የለውም፡፡ መያዣው አስር ዓመት ያለፈው ስለሆነ ህጋዊ ውጤት ስለማይኖረው አመልካች መጠየቁ ተገቢ አይደለም፡፡ የመያዣው የገንዘብ መጠን ያለተገለፀ በመሆኑ ውሉ ውጤት የለውም፡፡ ስለዚህ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ አመልካች ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ በማድረግ ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ በአንደኛ ተጠሪ ላይ የደረሰውን ኪሳራ የመካስ ኃላፊነት አለበት፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ነሐሴ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በዕሁፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች እኔን በተጠሪነት መዝግቦ የሰበር አቤቱታ የሚያቀርብበት ምክንያት የለም በማለት ነሐሴ 30 ቀን 2004 ዓ.ም መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መስከረም 10 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ለሚደርሰው ኪሣራ በመያዣያ የተያዘው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚያወጣውን ዋጋ ያህል በኃላፊነት ይጠይቃል በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ ለነበረችው ወ/ሮ ዘውዴ ሽፈራው የሆቴል ህንፃ መስሪያ ብድር ገንዘብ ለመስጠት ተበዳሪዋ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት እንድታቀርብ መጠየቁና ተበዳሪዋም በካርታ ቁጥር 614/935/61 በሆነው ይዞታ ላይ ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ በመጀመሪያ ደረጃ መያዣነት ለመስጠት ለመስማማቷ አመልካች ይህንን ንብረት የመጀመሪያ ደረጃ መያዣ አድርጎ እንዲመዘገብለት አንደኛ ተጠሪን የጠየቀና አመልካችም ንብረቱን አንደኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደረጃ መያዣ አድርጎ በመመዘገብ ለአንደኛ ተጠሪ ያሳወቀው መሆኑንና አንደኛ ተጠሪ ዕዳውን ለማስከፈል የሚያስችል የመጀመሪያ ደረጃ መያዣ መብት አለኝ በማለት የብድሩን ገንዘብ ለተበዳሪዋ የለቀቀ(የሰጠ) መሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የማይንቀሳቀሰውን ንብረት የአንደኛ ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መያዣ አድርጎ የመዘገበው በመሆኑና በዕሁፍ ያረጋገጠው ጥር 14 ቀን 1988 ዓ.ም እንደሆነ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

ሆኖም የአመልካች የማይንቀሳቀስ ንብረት ለአንደኛ ተጠሪ ብድር የመጀመሪያ ደረጃ መያዣ መሆኑን በማረጋገጥ እንደመዘገበው ለአንደኛ ተጠሪ ጥር 14 ቀን 1988 ዓ.ም ከመግለፁ በፊት ይህንኑ ተመሣሣይ ንብረት ሁለተኛ ተጠሪ ለወ/ሮ ዘውዴ ሽፈራው ሀምሌ 11 ቀን 1987 በተደረገ የብድር ውል ለሰጠው የብድር ገንዘብ የመጀመሪያ ደረጃ መያዣ አድርጎ የመዘገበ መሆኑን ሀምሌ 11 ቀን 1987 ዓ.ም በባፈው ደብዳቤ ለሁለተኛው ተጠሪ እንዳረጋገጠና፣ ይህንን ዕውነታ ለአንደኛው ተጠሪ ያልገለፀ መሆኑን በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ምክንያት ባለዕዳዋ ወ/ሮ ዘውዴ ሽፈራው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት በመጀመሪያ ሁለተኛ ተጠሪ ለወሰደችው ብድር መያዣ እንደሆነ ተስማምታና መያዣውም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 3052 በአመልካች ተመዝግቦ በሁለተኛ ተጠሪ ገንዘብ ተበድራ ከወሰደች በኋላ ሰባት ወራት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ይህንኑ በዕዳ ያስያዘቸውንና ያስመዘገበችውን ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መያዣ አድርጋ ለአንደኛ ተጠሪ በማቅረብ የብድር ገንዘብ የወሰደች መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ በመያዣው ላይ ያለውን የቀዳሚነት መብት በመጠቀም ለዕዳው መክፈያ እንዲሆነው ንብረቱን የሸጠው በመሆኑ አንደኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የነበረውን የመያዣ መብት ሙሉ በሙሉ ያጣና በዚህም ምክንያት ዕዳውን ለማስከፈል ችግር ላይ የወደቀና ኪሳራ የደረሰበት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የማይንቀሳቀሰው ንብረት የተጠሪዎችን ዕዳ እንደሚሸፍንና ጥፋት እንዳልፈፀመ በመግለጽ የሚያቀርበው ክርክር በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠውን ነባራዊ እውነታ መሰረት ያላደረገና ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለባለዕዳዋ ላበደረው ብድር መያዣ አድርጎ የያዘ መሆኑን ሀምሌ 11 ቀን 1987 ዓ.ም በዕሁፍ አረጋግጧል፡፡ ይህም ሁለተኛው ተጠሪ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት /የመጀመሪያ ደረጃ የመያዣ መብት/ የሚኖረው ሁለተኛው ተጠሪ መሆኑን የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3081 ድንጋጌዎችን በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ንብረቱ የሁለተኛ ተጠሪ መያዣ መሆኑን አረጋግጦ አመልካች ሀምሌ 11 ቀን 1987 ዓ.ም ከመዘገበ፣ ይኸው ንብረት አንደኛ ተጠሪ በጥር ወር 1988 ዓ.ም ለሰጠው ብድር የመጀመሪያ መያዣ የሚሆንበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ስለዚህ አስቀድሞ በመያዣነት የተያዘውንና የተመዘገበውን የባለዕዳዋን ቤት በመጀመሪያ መያዣነት መዝግቤአለሁ በማለት አመልካች ጥር 14 ቀን 1988 ዓ.ም ለአንደኛ ተጠሪ የሰጠው ማረጋገጫ የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3081 አስገዳጅ ህግ ድንጋጌዎች የሚቃረንና ህጋዊ ውጤት የሌለው አንደኛ ተጠሪንም ያለመያዣ ያስቀረ ተግባር ነው፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ የሚመዘገበው ንብረቱ በሚገኝበት አገር ርዕተ መዝገብ መሆኑንና ንብረቱ እንዲመዘግብ ጥያቄ የቀረበለት የመንግስት አካል (ሰራተኛ) የመያዣ ውሉን የሚመዘግበው በህግ ስለማንቀሳቀሱ ንብረቶች አመዘጋገብ ሥርዓት የተደነገጉትን ደንቦች መሰረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3052 እና የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3053 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛ ተጠሪ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት በመጀመሪያ ደረጃ መያዣነት ይዣለሁ በሚል እምነት ያለምንም መያዣ ለባለዕዳዋ ገንዘብ ያበደረው አመልካች (የአመልካች) የሚመለከታቸው ሠራተኞች ንብረቱ ቀደም ብሎ በሁለተኛው ተጠሪ የተያዘና መያዣውም በማይንቀሳቀሰው ርዕተ መዘገብ የተመዘገበ መሆኑን በጥንቃቄ በመመርመር ስላልገለፀለት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህም በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 1640 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት፣ አመልካችን በአንደኛ ተጠሪ ላይ በደረሰው ጉዳት በኃላፊነት የሚያስጠይቅ እንደሆነ ከህጉ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በገለፅናቸው ምክንያቶች የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ንብረቱ ቀደም ብሎ በመያዣነት ሁለተኛው ተጠሪ የያዘውና መያዣውንም ያስመዘገበው መሆኑን ባለመግለፁ አንደኛው ተጠሪ በንብረቱ ላይ የአንደኛ ደረጃ መያዣ መብት አለኝ በሚል ዕምነት ለባለዕዳዋ በብድር ገንዘብ በመስጠት ለደረሰበት ኪሣራ በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑንና አመልካች በመያዣነት ተመዝግቦ የነበረው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚያወጣውን ዋጋ ያህል ብቻ በኃላፊነት እንደሚጠይቅ ይህም ባለዕዳዋ ለመክፈል ሣትችል ስትቀር መሆኑን በመግለፅ የሰጠው ውሳኔ ከላይ የተዘረዘሩትን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል የምዕራብ ጉጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 79907

ጥር 2 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ልዩ የገንዘብ እገዛ ተቋም ጠበቃ ሺፈታ በለጠ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. ወ/ሮ የወይንሐረግ ትዕዛዙ ጠበቃ አበበ ጥላዩ ቀረቡ

2. አቶ ፀጋየሁ ጋሹ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ከዋስትና ውል አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ጉዳዩ በተጀመረበት በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የአሁኖቹ ተጠሪዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የነበረ ሲሆን 1ኛ ተከሣሽ የነበረው ደግሞ የሰበር ክርክሩ አካል ያልሆነውና በአሁኑ አመልካች /በስር ከሳሽ/ መስሪያ ቤት በሰራተኛነት በተቀጠረበት ጊዜ የአሁኖቹ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ለብር 50,000.00 /ሀምሣ ሺህ ብር/ የዋስትና ግዴታ ገብተውለት ነበር የተባለ ግለሰብ ነው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረበው 1ኛ ተከሳሽ ይዞት የተሰወረውን ገብዘብ ብር 109,487.95 2ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች በዋስትናቸው መጠን ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ለማስወሰን ሲሆን የተጠሪዎቹን የዋስትና ውሎች አያይዞ አቅርቧል፡፡

የዋስትና ውሉን አስመልክቶ 1ኛ ተጠሪ በወቅቱ በዋስትና ውሉ ላይ ለመፈረም ወደ ከሳሽ ተቋም ሄጀ የከሳሽ ተወካይና ምስክሮች ስላልነበሩና ስላልፈረሙ ውሉ ረቂቅ ሆኖ ቀርቶአል፡፡ ከሳሽ የራሱን ተወካይ እና ምስክሮቹን ያስፈረመው በሌላ ጊዜ ነው በእጄ በሚገኘውና በማስረጃነት ባቀረብኩት የዋስትና ውሉ ቅጂ ላይ የከሳሽ ተወካይና የምስክሮች ፊርማ የለበትም በማለት የተከራከረች ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ የዋስትና ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ፈራሽ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ 1ኛ ተጠሪን አስመልክቶ ከሳሽ የቀረበው የዋስትና ውል የተሟላ ቢሆንም በ1ኛ ተጠሪ/በስር 2ኛ ተከሳሽ/ በኩል የቀረበው የዋስትና ውል ግን የከሳሽና የምስክሮች ፊርማ የማይታይበት መሆኑን ከሳሽ ያቀረበው የዋስትና ውል በኮምፒተር ጽሑፍ የተዘጋጀ ሆኖ የምስክሮች ስም ግን በእጅ ጽሑፍ የተፃፈ መሆኑን ይህም የዋስትና ውሉ የተደረገው በሁለት ምስክሮች ፊት እንዳልሆነ እና ከሳሽ ምስክሮቹን ያስፈረመው ውሉ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ መንዘብ የሚያስችል መሆኑን 2ኛ ተጠሪን /የስር 3ኛ ተከሳሽን/ አስመልክቶ በዋስትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሉ ግርጌ በእጅ ጽሑፍ ተሞልቶ የሚታየው የአንድ ምስክር ስም እና ፊርማ ብቻ እንደሆነ እና የዋስትና ውል በጽሑፍ ሆኖ በሁለት ምስክሮች ካልተረጋገጠ ውጤት እንደማይኖረው በፍ/ሕ/ቁ 1725/ሀ/ እና 1727/2/ ተደንግጐ የሚገኝ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ 1ኛ ተከሳሽ እንዲከፍል 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ግን እንዲሰናበቱ ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔው ግድፈት የለበትም በማለት የአሁኑ አመልካች ያቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ አሰናብቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ሲሆን የዋስትና ውሉ በጽሑፍ ሆኖ በሁለት ምስክሮች ስላልተረጋገጠ የፍ/ሕ/ቁ 1727/2/ መስፈርትን አያሟላም ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ በሰበር ደረጃ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡
የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን አኛም የዋስትና ውል በፍ/ሕ/ቁ 1727/2/ መሰረት በሁለት ምስክሮች ፊት ካልተረጋገጠ ውጤት አይኖረውም ሲሉ የአሁኖቹን ተጠሪዎች በማሰናበት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርመረናል፡፡
በዚህም መሰረት 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ አመልካች ለስር ፍ/ቤት በማስረጃነት ያቀረበው የዋስትና ውል የተጠሪዋ የአመልካች ተወካይ እና የሁለት ምስክሮች ፊርማ የሚታይበት መሆኑ ተረጋግጦአል፡፡ በውሉ ላይ መፈረሟንም 1ኛ ተጠሪ አልካደችም 1ኛ ተጠሪ በወቅቱ ውሉን ለመፈረም ወደ ከሳሽ ተቋም ሄጂ የተቋሙ ተወካይና ምስክሮች ስላልነበሩና ስላልፈረሙ ውሉ ረቂቅ ሆኖ ቀርቶአል ከማለት በስተቀር የሰበር ከሳሽ በማስረጃነት ያቀረበውና በተጠሪዋ ያልተካደው ፊርማ የሚገኝበት የዋስትና ውል የተሟላ ቅጅ በከሳሽ እጅ እንዴት ሊገባ ወይም ሊገኝ እንደቻለ ተጠሪዋ በግልጽ ያቀረበችው ክርክር አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ነገሩን በመሸሽ የቀረበ የዚህ ዓይነት ክርክር ደግሞ ውሉ በሁለት ምስክሮች የተረጋገጠው እርሷ በፈረመችበት ጊዜ እንደሆነ ተጠሪዋ አምና እንደተቀበለች የሚያስቆጥር መሆኑን ከፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 83 እና 235 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የተጠሪዋን ክርክር በዚህ አግባብ ተገንዝበው ውሣኔ መስጠት ሲገባቸው ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት መረጋገጡን እንደካደች አድርገው መውሰዳቸው በክርክሩ ስነስርአታዊ አመራር ረገድ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለቱም ተጠሪዎች በተናጠል የገቡት የዋስትና ውል በሁለት ምስክሮች ፊት ያልተረጋገጠ ነው ቢባል እንኳን ተጠሪዎቹ በፍ/ሕ/ቁ 1727 የተመለከተውን የፎርማሊቲ መስፈርት ጠቅሰው የሚከራከሩት ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት አልተረጋገጠም በማለት እንጂ አልፈረምንበትም በማለት አይደለም፡፡ በመሰረቱ ሕጉ የውሉን በሁለት ምስክሮች ፊት የመረጋገጥ አስፈላጊነት የደነገገው በውሉ መደረግ ወይም ይዘት ወይም መሰል ሁኔታዎች ላይ በተዋዋዮች መካከል ሊነሳ የሚችለውን አለመግባባት ወይም ክርክር ውሉ ሲደረግ በነበሩ ግለሰቦች እገዛ ጭምር ለመፍታት እንዲያስችልም በማሰብ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎቹ ውሉን ስላለመፈረማቸው ወይም ስለውሉ ቃል ያቀረቡት ማናቸውም ዓይነት ክርክር አለመኖሩን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ስለራሳቸው ፊርማ እና ስለ ውሉ ቃል በተጠሪዎቹ የተካደ ነገር ከሌለ ደግሞ እነዚህ ነጥቦች ቢካዱ ኖሮ በአስረጅነት ሊቀርቡ ይችሉ ነበር የሚባሉት ምስክሮች በውሉ ላይ ሳይፈርሙ መቅረታቸው የተጠሪዎቹን የውል ግዴታ ተፈፃሚነት ሊያስቀር የሚችል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች ክርክሩን በዚህ አግባብ መምራት ሲገባቸው የዋስትና ውሉ በሁለት ምስክሮች ፊት ስላልተረጋገጠ አይፀናም ሲሉ ተጠሪዎቹን በማሰናበት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ተጠሪዎቹን አስመልክቶ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 171276 በ25/03/04 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 119159 በ01/08/04 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል።
2. በስር 1ኛ ተከሣሽ በአቶ ተስፋዬ በላይ ላይ የተወሰነውን ገንዘብ ተጠሪዎቹ በገቡት የዋስትና ግዴታ መጠን ከተከሳሹ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ወስነናል።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
4. የውሣኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ።
5. ክርክር ውሣኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቶአል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 76825

ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ጭላሎ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር

ተጠሪ ፡- የአዳማ ከተማ የቦኩ ሸነን ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር ተጠሪ ክሳሽነት የተጀመረው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ የሰበር አመልካችም ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሳሽ አሻሽሎ በ01/08/2002 ዓ/ም ያቀረበው ክስ የከተማው አስተዳደር ለክሳሽ ቀበሌ ለልማት ሥራ ድጋፍ በሚል 400 ካሬ ሜትር ቦታ በመስጠቱ በተዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን ቦታውን በጨረታ ለመሸጥ ጨረታ ተድርጎ ተከሳሽም በጨረታው ተወዳዳሪ በመሆን በብር 370,000.00 ካሸነፈና የቦታውን ካርታ ከተቀበለ በኋላ ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ሲጠየቅ የአራት ወር ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቆ የተሰጠው ቢሆንም ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ወጪና ኪሳራ ተጨምሮ እንዲከፍል ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ለክሱ በሠጠው መልስ ክስ የቀረበበት መሬት በሊዝ ስምምነት የተሸጠ ሲሆን ሽያጩም ከህገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣ የሽያጭ ውሉ በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ ያልተረጋገጠ ከመሆኑም ሌላ በሊዝ ህግና ደንብ መሰረት የተፈረመ የውል ስምምነት የለም፣ገንዘቡን ለመክፈል የ4 ወር ጊዜ ጠይቄ እያለሁ በችኮላ የቀረበ ክስ ነው፣ጨረታው ውድቅ ከሆነ ያስያዝኩት ገንዘብ ቀሪ ከሚሆን በስተቀር ጠቅላላውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የለብኝም ሲሉ ተከራክሯል፡፡

ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስትም ሆነ በክልሉ ህገ መንግስት መሬት የማይሸጥ እና የማይለወጥ የመንግስትና የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት መሆኑ የተደነገገ ቢሆንም በስጦታ ወይም በኪራይ የባለይዞታነት መብት ማስተላለፍ የሚቻል ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 456/2005፣272/2002 እና በሊዝ ደንብ ቁጥር 1/1987 እንደተሻሻለው ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በሚያከራክረው ጉዳይም ተከሳሽ ጨረታውን ተወዳድሮ በብር 370,000.00 በማሸነፉ መሬቱ ወደ ተከሳሽ በሊዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተላልፎለት ወዲያዉኑ ሳይት ፕላን የተሰጠው ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ገንዘቡን ለከሳሽ የመክፈል ግዴታ አለበት ብሏል፡፡

የስር ተከሳሽም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ በዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት አጽንቷል፡፡

አመልካችም በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም፡- በአመልካች እና በተጠሪው መካከል የተፈረመ የሊዝ ውል ሳይኖር ጨረታው የተደረገበትን ዓላማ መሰረት በማድረግ ብቻ የጨረታውን ዋጋ እንድከፍል የሥር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/1994 አንቀጽ 9(1)(2) እና የፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 1723ን የሚቃረን ከመሆኑም ሌላ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ//ህገ መንግስት አንቀጽ 79(3) ዳኞች ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም በሚል የተደነገገውን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ የቀበሌው አስተዳደር ወደ አዳማ ከተማ ሲጠቃለል አዲስ በመሆኑ ምክንያት የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ለነዋሪው ህዝብ ለሚሚላት ሲባል በተዘጋጀው ቴሌቶን 400 ካሬ ሜትር ቦታ አመልካች በጨረታ ተወዳድሮ በማሸነፍ በብር 370,000.00 በመግዛቱ ወዲያውኑ ከከተማው ከንቲባ እጅ የቦታውን ሳይት ፕላን መረከቡ የተረጋጠ ሲሆን የይዞታ ማረጋጫ የምስክር ወረቀትም በከተማው የመሬትና የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ተዘጋጅቶለት እያለ ፎርማሊቲውን አሟልቶ መሬቱን እንዲረከብ እየተነገረው እያለ መሬቱ በሊዝ አዋጅ መሰረት እንደተላለፈለት በማስመሰል የሊዝ አዋጁ ፎርማሊቲ ስላልተሟላ በጨረታው አልገደድም ያለው ተገቢነት ስለሌለው ገንዘቡን እንዲከፍል የተወሰነበት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም በሚል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ተጠሪው ላቀረበው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች በጨረታው ተወዳዳሪ ሆኖ ጨረታውን ማሸነፉን የሚያምነው ጉዳይ ሲሆን በዋናነት ክርክሩን እያቀረበ ያለው ግን ጉዳዩን ከሊዝ ህግ ጋር በማገናኘት ነው፡፡ በወቅቱ ተፈጻሚ በነበረው የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/1994 የሊዝ ውሉ በተዋዋዮቹ መፈረም ያለበት ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 9(1) መገንዘብ የሚቻል ሲሆን የይዞታ ማረጋጫ የምስክር ወረቀትም የሚሰጠው ይሔው የሊዝ ውል ስምምነት ከተደረገ በኋላ ስለመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ የክፍያ አፈጻጸም ዝርዝር ሁኔታም በሊዝ ውሉ ወስጥ መካተት ያለበት ስለመሆኑ ድንጋጌው በንዑስ አንቀጽ 2 ተጠቅሷል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች ለተጠሪው ቀበሌ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ለመዘርጋት በተዘጋጀው ልዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን በተደረገው ጨረታ ተሳታፊ በመሆን ጨረታውን አሸንፎ የቦታውን ሳይት ፕላን ያገኘ በመሆኑ ለገንዘቡ አከፋፈል የሊዝ ውል ስምምነት አልተፈረመም የሚለውን ቅድመ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታ ሊያቀርብ የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በአመልካች እና አግባብ ባለው አካል መካከል የተፈረመ የሊዝ ውል አለመኖሩ ግልጽ ቢሆንም በመካከላቸው የውል ግንኙነት የተመሰረተ መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም፡፡

የውል ግዴታ መፈጸም የሚጠበቅበት ተዋዋይ ይህንኑ ግዴታ ባልፈጸመ ጊዜም በራሱ በኩል ያለውን ግዴታ የፈጸመው ተዋዋይ በፍ/ህ/ቁ/1771(1) እንደተደነገገው ሌላኛው ተዋዋይ የበኩሉን ግዴታ እንዲፈጽም የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም ውሉ ተዋዋዮቹ በአንድነት የሚፈጽሙትን ግዴታ (simultaneous performance) የሚጥል ሆኖ ከተገኘም ተዋዋዩ የተዋዋለበትን ግዴታ በውሉ እንደተመለከተው እንዲፈጸምለት የሚጠይቀው ወገን ከውሉ ስምምነት የተነሳ እሱም በበኩሉ ያለውን ግዴታ ወዲያውኑ መፈጸም ወይም ለመፈጸም የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባው መሆኑን የፍ/ህ/ቁ/1757 ያስገነዝባል፡፡ በዚሁ መሰረትም አመልካች የጨረታው አሸናፊ መሆኑ እንደተረጋገጠ በፍ/ህ/ቁ/1688(2) የተደነገገውን በመከተል ተጠሪው ሳይት ፕላኑን ለአመልካች በማስረከብ የበኩሉን ግዴታ በመፈጸም ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ሲያስታውቅ አመልካችም የክፍያው ጊዜ እንዲያራዘምለት በመጠየቁ በጥያቄው መሰረት የተራዘመለት ቢሆንም ለመክፈል አለመፈለጉን የፍሬ ነገር ጉዳዮችን የሚያጣሩ የሥር ፍርድ ቤቶት ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም በአመልካች እና በተጠሪው መካከል በተመሰረተው ውል መሰረት በጨረታ ተወዳድሮ ያሸነፈውን ገንዘብ በመክፈል ቀሪውን መሟላት የሚገባቸውን ነገሮች ተጠሪው ወይም አግባብ ያለው አካል እንዲያሟላ አመልካች መጠየቅ ሲገባው ህጋዊ መሰረት የሌላቸውን የመከራከሪያ ነጥቦችን በማንሳት ያቀረበውን ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ በማድረግ ያሸነፈበትን የጨረታውን ዋጋ ገንዘብ ገቢ እንዲያደርግ በሚል በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/09324 በቀን 1902/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሠጠውን ውሳኔ፣የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ10981 በቀን 30/03/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በ/ቁ/117557 በቀን 28/05/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 370,000 (ሶስት መቶ ሳባ ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ አለበት ብለናል፡፡
3. ከዚህ በፊት በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/10556 ተጀምሮ የነበረው የአፈጻጸም ክስ ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ በመሆኑም እንዲያውቀው ይጻፍ ብለናል፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 81857

ጥር 13 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አብዱልቃድር ጁሐር - ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማ - ጠበቃ አረጋ ፀጋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲሆን ክሱን የመሰረተው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ ግራ ቀኙ በ30/03/89 እና በ04/04/89 ባደረጓቸው የሰሊጥ ሽያጭ ውሎች መሰረት ተከሳሽ ሰሊጡን ተረክበው እያለ ዋጋውን ያልከፈሉ በመሆኑ በገቡት የውል ግዴታ መሰረት ገንዘቡን መክፈል ከነበረባቸውን ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 14% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልን የሚል ሲሆን ተከሳሹም የበኩላቸውን የመቃወሚያና የፍሬ ጉዳይ ነጥቦች በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከሳሽ አንዱን ኩንታል በብር 299.65 ሂሳብ በድምሩ 4,143.55 ኩንታል ሰሊጥ ለተከሳሽ ማስረከቡና ተከሳሹም ክፍያውን መፈፀም ይገባቸው የነበረው በ10/05/89 ዓ.ም መሆኑ መረጋገጡን፣ ተከሳሽ ወለዱ በ14% የታሰበው ከፍ.ሕ.ቁ. 2479(3) ውጪ ነው ቢሉም የወለድ ምጣኔው ተከሳሽ በውል ግዴታ የገቡበት ከመሆኑም በላይ ገንዘቡ የብድር ውልን የሚመለከት ባለመሆኑ ምክንያት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የፍ.ሕ.ቁ 2479(3) ሳይሆን 1803(2) መሆኑን እና ተከሳሽ ያቀረቧቸው የመቃወሚያና ሌሎች የፍሬ ነገር የክርክር ነጥቦች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን በዝርዝር በመግለፅ ተከሳሽ ብር 1,241,641.75 ከ10/05/89 ዓ/ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት 24/05/99 ዓ.ም ድረስ ከሚታሰብ 14% ወለድ ጋር እንዲሁም በዋናው ገንዘብ ላይ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ የሚታሰብ 9% ወለድ ከወጪና ኪሳራ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበለትን ይግባኝ ሰርዞ አሰናብቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረቡት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን በዋናው የገንዘብ ዕዳ ላይ የ14% ወለድ እንዲታሰብ የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ሕ/ቁጥር 2479(3) ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር አቤቱታው በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባዋል በመባሉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ከላይ ከተጠቀሰው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የፍ/ሕ/ቁ 2479 የሚናገረው በብድር በሚሰጥ ገንዘብ ላይ ተዋዋይ ወገኖች ሊያቋቋሙ ስለሚችሉት የወለድ ምጣኔ ጣሪያ እና ብድሩ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የሚከፈል ከሆነ በብድር ገንዘብ ላይ ሊታሰብ ስለሚገባው የወለድ ምጣኔ ጣሪያ ሲሆን የፍ/ሕ/ቁ 1803(2) ድንጋጌ ደግሞ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሳይከፈል በቀረ የገንዘብ ዕዳ ላይ የሚታሰበው የወለድ ምጣኔ ተዋዋዮቹ የተስማሙበት መጠን እንደሆነ የሚደነግግ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ሁለቱ ድንጋጌዎች ሁለት የተለያዩ የውል ግንኙነትና አፈፃፀም ሁኔታዎችን የሚመለከቱ መሆኑን ነው፡፡ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሳይከፈል የቀረን የገንዘብ ዕዳ የሚመለከተው የፍ/ሕ/ቁ 1803 ድንጋጌ በፍ/ሕ/ቁ 2479 መሰረት ተቋቁሞ ነገር ግን በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ያልተከፈለ የብድር ገንዘብን ጭምር የሚመለከት መሆኑን ከፍ/ሕ/ቁ 2488 እና 2489 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስር ተከሳሽ ኃላፊ የተደረጉበት ገንዘብ ከብድር ውል የመነጨ ካለመሆኑም በላይ የውል ግዴታ ገብተውለት የነበረው የገንዘብ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ካለፈ አስር ዓመታት ያህል ማስቆጠሩ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ለክርክሩ አወሳሰን አግባብነት የሚኖረው አመልካች እንደሚከራከሩት የፍ/ሕ/ቁ 2479(3) ሳይሆን የስር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የቁጥር 1803 (2) ድንጋጌ ነው፡፡

በሌላ በኩል የውል ግዴታውን ያልፈፀመ ወይም ያዘገየ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ የሚከፍለው የኪሳራ መጠን የግዴታው አለመፈፀም ወይም መዘግየት ካስከተለው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን እንደሚገባው በፍ/ሕ/ቁ 1790(2) እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የግራ ቀኙን ውል መሰረት በማድረግ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሰጡበት የ14% የወለድ መጠን በተጠሪ ላይ ከደረሰው የጉዳት መጠን የበለጠ ነው ለማለት የሚያስችል ሁኔታ ካለመገኘቱም በላይ በተጠሪ የተጠየቀው የወለድ መጠን ከደረሰበት ጉዳት በላይ ስለመሆኑ አመልካች በፍ/ሕ/ቁ 1800 መሰረት ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ የለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 11300 በ19/09/03 የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 77002 በ24/08/04 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ፀንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡
3. ክርክሩ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሃሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ የአብላጫውን ድምፅ የወለድ መጠኑን በተመለከተ በሰጠው የህግ ትርጉም በደረሰበት መደምደሚያ ያልተስማማሁ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ ከሙያ ባልደረቦች የተለየሁባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ተጠሪና አመልካች ህዳር 30 ቀን 1989 እና ታህሳስ 4 ቀን 1989 ዓ.ም ባደረጉት የሰሊጥ ሽያጭ ውል መሰረት፣ አመልካች ከተጠሪ የተረከቡት ሰሊጥ ዋጋ እንዲሆን፣ አመልካች ቼክ ቆርጦ የሰጠ ሲሆን፣ አመልካች በቂ ስንቅ የሌለው በመሆኑ ምክንያት አመልካችና ተጠሪ ውላቸውን በማሻሻል የአንድ ኩንታል ሰሊጥ ዋጋ በብር 299.65 (ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ብር ከስልሣ አምስት ሳንቲም ሒሳብ) እስከ ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም በጠቅላላው ብር 1,448,250 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ለመክፈል፣ ከጥር 10 ቀን 1998 ዓ.ም. በኋላ ክፍያ ከዘገየ ወለድ 14% (አስራ አራት በመቶ) ለመክፈል የተስማማ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካች የሰሊጡን ዋጋ በውሉ በተገለፀው ጊዜ (ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም) ያልከፈለ በመሆኑ በውላችን መሰረት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 14% ወለድ ጋር ታስቦ እንድከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን ክስ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመቀበል፣ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ አብላጫው ድምፅም አመልካች በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ የሰሊጡን ዋጋ ያልከፈለ በመሆኑ፣ 14% ወለድ በውሉ መሰረት እንዲከፍል መወሰኑ የፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 1803 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌን መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም የሚል የህግ ትርጉምና ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
2. እኔም በሀሳብ የተለየሁት፣ በዚህ የህግ ትርጉም ባለመስማማት ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2311(1) በሚደነግገው መሰረት ዋጋውን ጥር 10 ቀን 1989 ዓ.ም. ለመክፈል፣ በመስማማት በዱቤ ሰሊጥ የገዛ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ አመልካች የገዛውን የሰሊጥ ዋጋ በውሉ በተገለፀው ጊዜ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2310(3) ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ለተጠሪ የሰሊጡን ዋጋ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ካልከፈሉ በተጠሪ ላይ ኪሳራ የሚደርስበት ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ አከራካሪው ነጥብ አመልካች የውል ግዴታውን ባለመፈፀሙ ለተጠሪ የሚከፍለው የኪሳራ መጠን “አስራ አራት ፐርሰንት” ወለድ እንደሆነ በመግለጽ ያደረጉት ስምምነት ህጋዊ ተፈፃሚነትና ውጤት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

ይህንን ነጥብ አስመልክቶ የገንዘብ ዕዳ የሚከፈልበትን ጊዜ በማሳለፍ ስለሚከፈል ወለድ፣ የሚደነግገውና ጠቅላላ የውል ድንጋጌ የሆነው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1803 ንዑስ አንቀጽ (2) በውለታ ውስጥ የበለጠ ወለድ የታሰበ እንደሆነ በዚሁ በከፍተኛው ወለድ መታሰቡ ይቀጥላል” በሚል መንገድ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም የዚህ ድንጋጌ ትርጉም በዱቤ የሸጠ ሰው፣ ገዥው የዕቃውን ዋጋ ለመክፈል በተስማማበት ጊዜ ካልከፈለ፣ በውሉ ከፍተኛ መጠን ያለው ወለድ እንዲከፍል በውሉ ከተገለፀ፣ ከፍተኛ የሆነ የወለድ መጠን እንዲሰበሰብ የአገራችን የህግ ሥርዓት እንደሚፈቅድ ተደርጎ ሊተረጎም አይገባውም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1803 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ፣ ተዋዋዮች የመሰላቸውን ጉዳይ በውል የመወሰን ነፃነት ሕግ የከለከላቸውና የወሰናቸው ነገሮችን እንደማይጨምር በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1711 ከተደነገገው መሰረታዊ መርህና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

“ገዥው ዋጋውን ሳይከፍል በሚዘገይበት ጊዜ በሕግ በተወሰነው ወለድ መሰረት የመዘግየት ወለድ መክፈል አለበት” በማለት ከሚደነግገው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2361 ንኡስ አንቀጽ (2) ልዩ ድንጋጌና ተዋዋዮቹ በወለድ የሚከፈለውን ገንዘብ በዓመት በመቶ አስራ ሁለት በላይ እንደሆነ ለማዋዋል አይችሉም ከሚለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2479 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አንፃር መታየትና መተርጎም ይገባዋል የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

ስለሆነም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1803 ንኡስ አንቀጽ 2 በገንዘብ ዕዳ ምክንያት ከአስራ ሁለት በመቶ በላይ ወለድ እንዲከፍል የተደረገ ሥምምነት ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው በማሰብ ህግ አውጭው የደነገገው ድንጋጌ አይደለም፡፡ ለማናቸውም የገንዘብ ዕዳ በተለይም በዱቤ ለተፈፀመ ሽያጭ የሚከፈለው ገንዘብ በመዘግየቱ ምክንያት የሚከፈለው ወለድ በህጉ የተወሰነው የወለድ መጠን መሆን እንዳለበት ስለ ልዩ ውሎች በተለይም ስለሽያጭ ውል የተደነገገው የፍ/ብ/ህግ/ቁጥር 2361 ንኡስ አንቀጽ 2 የሚደነግግ በመሆኑ አመልካች የሰሊጡን ዋጋ ጥር 10 ቀን 1989 ካልከፈለ ወለድ አስራ አራት ፐርሰንት ለመክፈል የተስማማው ስምምነት በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2479 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ወደ ዘጠኝ በመቶ ዝቅ ተደርጎ ሊከፈል ይገባል በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ 80722

ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክ አገልግሎት ድርጅት ነገረ ፈጅ መላኩ መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዲ አም ሲ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ ውልን አስመልክቶ የሚነሳን ክርክር በግልግል ዳኝነት እንዲያይ በውሉ ላይ የተሰየመው አካል በከሰመ ጊዜ ክርክሩ በማን ሊታይ ይገባል? የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው የሽምግልና ዳኝነት አካል ይቋቋምልኝ ሲሆን የክሱም ፍሬ ቃል ከአመልካች ጋር መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ባደረግነው ውል ህንፃ ለመስራት ተስማምተናል፡፡ በውሉ መሠረት አለመግባባት ቢፈጠር ጉዳያችን በግልግል ዳኝነት ዕልባት እንዲያገኝ ተሰማምተናል፡፡ በዚህ መሠረት በመካከላችን የተፈጠረው አለመግባባት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት የግልግል ዳኝነት ተቋም እንዲታይ አቅርቤ እርሱም ቀርቦ ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት ማየት የሚችለው የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ባቋቋመው የዳኝነት ተቋም ሊሆነ ይገባል በማለት ለግልግሉ ፈቀደኛ ሳይሆን ስለቀረ ጉዳያችንን አይቶ ለሚወስንልን የግልግል ተቋም እንዲመራልን በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ይሰጥልን የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካችም ለዚሁ የክስ አቤቱታ በሰጠው መልስ ግራ ቀኞችን ባደረግነው ውል አንቀጽ 67 ላይ በመካከላችን የሚፈጠርን አለመግባባት በግልግል የሚዳኘው የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ወይም እርሱ የሚወከለው አካል እንደሆነ በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ ተመልክቷል፡፡ በአሁን ጊዜ ይህ የግልግል ተቋም የግልግል ተግባሩን መሥራት በማቆሙ፤ ሚኒስቴሩ የወከለው ሌላ አካል ባለመኖሩ ጉዳዩ ወደ ግልግል ተቋም ሊሄድ አልቻለም፡፡ ስለዚህ ይህ የግልግል የዳኝነት አካል በሌለበት ወይም ሁለታችንም ያለልዩነት የመረጥነው ሌላ የዳኝነት አካል በሌለበት ሁኔታ በሌላ የግልግል ዳኝነት ተቋም እንዲታይ አስገዳጅ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ክሳሽ ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተውም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 03283 ሚያዚያ 22 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት፡- በውሉ አንቀጽ 67 እንደተጠቀሰው አለመግባባት በሚከሰትበት ጊዜ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ወይም በተፈቀደለት ወኪሉ እንዲፈቱ ተስማምተዋል፡፡ ጉዳዩን እንዲያይላቸው የመረጡት አካል በአሁኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጊዜ እንደሌለ ተከሳሽ ገልጿል፡፡ ከሳሽም ይህንኑ አልተቃወመም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3336(1) ላይ አንድ የዘመድ ዳኛ ሆኖ የተመረጠ ወገን የሞተ ወይም ችሎታ ያጣ እንደሆነ በእርሱ ምትክ ሌላ ዳኛ የሚመረጥ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ጉዳይ በግራ ቀኙ የተሰየመው የግልግል ዳኛ ችሎታ ያጣ ወይም በአሁኑ ጊዜ የግልግል ሥራውን የማይሠራ በመሆኑ ጉዳዩ በሌላ የግልግል ዳኛ ሊታይ የሚገባ መሆኑን ፍ/ቤቱ አረጋግጧል፡፡

ከሳሽ ይህንኑ ተገንዝቦ ጉዳዩ በሌላ የዳኝነት አካል ቀርቦ እንዲታይ የሞከረ ቢሆንም ተከሳሽ በዚህ ከሳሽ በመረጠው አካል ለመዳኘት አልተስማማም፡፡ ስለሆነም በሁለቱም ወገኖች የተነሳውን አለመግባባት ሁለቱም በመረጡት ሌላ ተቋም እንዲታይ መስማማት ካልቻሉ ፍ/ቤቱ በሚመድበው አካል ሊታይ ስለሚገባ ክርክራቸው በጋራ በስምምነት በመረጡት የግልግል ዳኛ/ ተቋም/ ይታይ፡፡ በስምምነት የመረጡት አካል ከሌለ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዋና ፌጅስትራር በኩል ወደ ግልግል ዳኛ/ ተቋም/ ይመራ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ የአሁን አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 እንደተደነገገው ተቀባይነትን ባለማግኘቱ በዚህ አካኋን በሥር ባሉት ፍ/ቤቶች በየደረጃው የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እና በሰበር አቤቱታው በዝርዝር በማመልከት ጉዳዩ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ የአሁን አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ይህ የሰበር ጉዳይ ቀርቧል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ የሰበር ጉዳይ የበኩሉን ክርክር እንዲያቀርብ ጥሪ ቢደረግለትም ሊቀርብ ባለመቻሉ ክርክሩን በፅሁፍ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በዚህ ጉዳይ የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው የግራ ቀኙን አለመግባባት ተቀብሎ በግልግል ዳኝነት ለማየት የሚችል የግልግል ተቋም ፍ/ቤት በሚሰጠው ትዕዛዝ አማካኝነት ለመሰየም ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3328 ንዑስ ቁጥር (2) እንደተመለከተው አመልካችና ተጠሪ መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉትን የግንባታ ውል አስመልክቶ ወደ ፊት ክርክር በደረሰ ጊዜ ከዚሁ ውል ሊነሳ የሚችለውን ክርክር በግልግል ዳኛ ወይም ለግልግል ተቋም ለማቅረብና ዳኝነት ለማግኘት የሚችሉ ስለመሆኑ በውሉ አንቀጽ 67 ጠቅሰው የተስማሙ ለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህም በቀር ይህንኑ ከውሉ ሊመነጭ የሚችለውንም የግልግል ዳኛ/ተቋም/ ማንነት ሁሉ በስም ጠቅሰው የተስማሙ ለመሆኑም አላከራከረም፡፡

ከዚሁ መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ከተደረገው ውል የመነጨውን ክርክሩን የአሁን ተጠሪ በዳኝነት አካል አቅርቦ ለማስወሰን በፈለገበት ጊዜ ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት ተመልክቶ ዳኝነት እንዲሰጥበት በስም የተሰየመው የግልግል ተቋም የግልግል ዳኝነት ተግባሩን ማከናወን እንዳቆመም የተረጋገጠ የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡

ከላይ በፍሬ ነገር ረገድ ከተረጋገጡት ሶስት ጉዳዮች በመነሳት ግራ ቀኙን ያከራከረውን ጉዳይ ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት የሚቻለው የትኛው የዳኝነት አካል እንደሆነ ለይቶ ለመወሰን ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3337 የተመለከተው እንጂ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 3336 እንዳልሆነ የሁለቱ ድንጋጌዎች ጥምር ንባብ አሰረጂ ነው፡፡ ይኸውም የአሁን አመልካችና ተጠሪ ከላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተመለከተው ውል የመነጨ ክርክር ቢያጋጥማቸው ይህንኑ ክርክራቸውን በግልግል ዳኝነት ለመጨረስና በግልግል ዳኝነት ጉዳዩን የሚያየውን አካል ሳይቀር በስም ሰይመው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3328(2) እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3331 መሠረት በስምምነት ለይተው ያመለከቱ ወይም የመረጡ በመሆኑ በዚህ አኳኋን የተመረጠው የግልግል ዳኛ/ተቋም የግልግል ተግባሩን ማከናወን ማቆሙ ከተረጋገጠ ይህንኑ የግልግል ዳኛ/ተቋም/ ተክቶ የግልግል ዳኝነት ተግባሩን ሊያከናውን የሚችል ሌላ አካል ለመሰየም የሁለቱ የጋራ ስምምነት የግድ አስፈላጊ መሆኑን፣ ይህ ስምምነት ካልተገኘ ግን ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ ያደረጉት ስምምነት ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3337 በግልፅ በመደንገጉ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ይኸው ድንጋጌ በመሆኑ ነው፡፡

በዚህ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3336(1) "....እንደሆነ የዘመድ ዳኛው ስምምነቱ ቀሪ ይሆናል፡፡" ማለት ጉዳዩን እንደታሰበው በግልግል ለመጨረስ አድርገውት በነበረው ስምምነት ሊገደዱ እንደማይችሉ እንጂ በውሉ ላይ በተሰየመው የግልግል ዳኛ ባይሆንም በፍ/ቤት አማካኝነት በማሰየም ሌላ የግልግል ዳኝነት ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ ያደረጉት ስምምነት የፀና ነው የሚል ትርጉም ሊያሰጥ እንደማይችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3325 እና 3344 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን ግራ ቀኝ ወገኖች ካደረጉት የዋናው ጉዳይ ስምምነት ይዘት አንፃር ሲታይ ጉዳይቸውን በግልግል ዳኝነት አይቶ የሚወሰነው በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ወይም እርሱ በሚወክለው አካል በማለት አሰቀድመው በያዙት ውል ላይ በግልፅ ያመለከቱት ጉዳዩን በግልግል አይቶ ለመወሰን በጉዳዩ ላይ በቂ ዐቅምና ዕውቀት ያለውን ነው የሚል ሀሳብ ይዘው እንደሆነ ከተዋዋሉበት የውለታ ጉዳይ መገንዘብ ስለሚቻልና እንደዚያ ያለ አከራካሪ ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜም የዘመድ ዳኛ ሥልጣንን አስመልክቶ በውል ላይ የተመለከቱት የስምምነት ቃሎች በጠባቡ መተርጎም እንዳለባቸውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3329 ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም ግራ ቀኙ መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ካደረጉት የግንባታ ውል የመነጨውን ክርክር አይቶ ሊወስንላቸው የሚችለውን የግልግል ዳኛ/ተቋም/ በግልፅ በስም ጠርተው የሰየሙ በመሆኑ ክርክሩ በተነሳበት ጊዜም ይህ የግልግል ዳኛ የግልግል ዳኝነት ተግባሩን ማከናወኑን በማቆሙ ምክንያት ሁለቱም ወገኖች እንደነበራቸው ሀሳብ አሁንም ጉዳያቸውን በግልግል ተመልክቶ ሊያይላቸው የሚችለውን ወገን ሁለቱም ወገኖች በጋራ ስምምነት ከሚሰየሙ በቀር፤ ጉዳዩን ተመልክቶ ሊወስን የሚችልን የግልግል ተቋም ወይም አካል ፍ/ቤት የመወሰን ሥልጣን የለውም፡፡

የአሁን ተጠሪ ከውሉ የመነጨውን ክርክሩን በዳኝነት አካል አቅርቦ የማስወሰንና ፍትህ የማግኘት መብቱ ሊጣበብ ስለማይገባም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3337 የተመለከተው ድንጋጌ ከህገ መንግስቱ አነቀጽ 37 ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ይህንን ጉዳይ በጋራ ስምምነት በሚሰይሙት አካል አቅርበው የማስወሰን መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በጉዳዩ ከተካተተው የገንዘብ መጠን እና ከተከራካሪ ወገኖች ማንነት አንፃር በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5፣ 11(1) እንደተደነገገው ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያለው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊሆን ይገባል በማለት መተርጎም ሲገባ ያለ የጋራ ስምምነት የሽምግልና ዳኛ ሊያቋቁም የሚያስችል ትዕዛዝ በሥር ፍ/ቤቶች መሰጠቱ ከላይ በፍርድ ሐተታው እንደተገለፀው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 03283 በቀን 22/8/2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድም ሆነ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/ቁጥር 118971 ሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙ ከዚህ ቀደም መስከረም 04 ቀን 1999 ዓ.ም ባደረጉት ስምምነት መሠረት በመካከላቸው ከዚህ ውል የተነሳውን አለመግባባት በጋራ ስምምነት ሊያይላቸው የሚችለውን የግልግል አካል በእራሳቸው ከሚያቋቁሙ በቀር በፍ/ቤት የግልግል አካል ሊቋቋም አይቻልም ብለናል፡፡
3. ይህ የጋራ ስምምነት ካልተገኘ የአሁን ተጠሪ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ጉዳዩን አቅርቦ የማስወሰን እና ፍትህ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ የሰበር ችሎት ክርክር ምክንያት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ 71972

ጥር 1 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ካሣሁን አያሌው - ጠበቃ አቶ ፈንታ አያል ቀረቡ

ተጠሪ፡- የምስራቅ ጎጃም ዞዛምን ወረዳ ጤና ጽ/ቤት - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለግንባታ ሥራ የሚከፈል ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በዞዛምን ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ለወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት ተከሳሽ (ተጠሪ) የተመላላሽ ህክምና መስጫ አንድ ብሎክ ህንፃ ለማሰራት የጨረታ ማስታወቂያ አውጥቶ እኔ ተወዳድሬ አሸንፌአለሁ፡፡ ከተከሳሽ ጋር ሚያዝያ 2 ቀን 1999 ዓ.ም የግንባታ ስራ ውል ተዋውለን ግንባታው የሚከናወንበትን ቦታ አስረክቦኛል፡፡ ግንባታውን ሰርቼ የመጀመሪያ ክፍያ ጠይቄ፣ ከጠየቅሁት በመቀነስ ክፍያ እንዲፈጽም ለወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ደብዳቤ ፅፏል፡፡ እኔም ክፍያው የተሰራውን ሥራ የማይሸፍን መሆኑን በመግለጽ የግንባታውን ሥራ በመቀጠል ሁለተኛ ክፍያ በተቆጣጣሪ መሀንዲሱ ከፀደቀ በኋላ ተከሳሽ እንዲከፍለኝ ጥያቄ አቅርቤያለሁ፡፡ ተከሳሹ የክፍያ ሰርተፊኬቱ ለዞን ስራና ከተማ ልማት መምሪያ ያላከውና በውጤቱ ያልተስማማ መሆኑን በመግለፅ የግንባታ ሥራው ለጊዜው እንዲቋረጥ ሚያዝያ 3 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አሳውቆኛል፡፡ ከዚህ በኋላ የጀመርከውን የግንባታ ሥራ በውሉ መሰረት አጠናቅቀህ እንድታስረክብ በማለት ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ/ም ደብዳቤ የፃፈልኝ ሲሆን እኔ ያቀረብኩትን የክፍያ ጥያቄ መልስ አልሰጠኝም፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ለሰራሁት ሥራ መክፈል የሚገባውን ሁለተኛ ክፍያ ብር 88,913.39 (ሰማኒያ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሦስት ብር ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም) እዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ በግንባታ ስራ ውሉ ከተገለፀው አርባ ዘጠኝ ፐርሰንት ጭማሪ ያለው ነው፡፡ በግንባታ ሥራ ደንብና መመሪያ መሰረት ተጨማሪ ሥራና የሚከፈል ክፍያ ከሃያ አምስት ፐርሰንት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡ የዞኑ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ስለ ክፍያው የሰጠው አስተያየት በጉዳዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተፈፃሚነት ያላቸውን የህግ ማዕቀፎችና የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ የአመልካች ክስ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በበኩሉም ከሳሽ (አመልካች) በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ህንፃውን ሰርቶ አላስረከበም፡፡ የግንባታ ሥራው የሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ ያለፈ በመሆኑ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ለወረዳው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ አመልካች፣ የተከሳሽ ከሳሽ የዳኝነት ያልከፈለ በመሆኑ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን ሥርዓቱን አሟልቶ አላቀረበም፡፡ ግንባታው በወቅቱ ያልተጠናቀቀው የተከሳሽ ከሳሽ የግንባታ ሥራው ለጊዜው እንዲቋረጥ በፅሁፍ በማዘዙና በተከሳሽ ከሳሽ ጥፋት በመሆኑ ተጠያቂነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤት፡-

1ኛ የከሳሽ የክፍያ ጥያቄ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?

2ኛ/ ከሳሽ የጠየቀው ከግንባታ ሥራ ውሉ ውጭ ነው ወይስ አይደለም?

3ኛ/ የግንባታ ሥራው የተቋረጠው በተከሳሽ ጥያቄ ነው ወይስ አይደለም?

4ኛ/ ከሳሽ በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ግዴታውን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ከሳሽ በተሰጠው ዲዛይን መሰረት መስራት የሚገባውን ሥራ የሠራ ስለመሆኑ በተከሳሽ ተቆጣጣሪ መሀንዲስ በማረጋገጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት አጽድቋል፡፡ የዋጋው ልዩነት የተፈጠረው በመጀመሪያ በዲዛይኑ መሰረት ሥራውን ለመስራት የሚያስፈልገው የግንባታ ቁሳቁስና ሥራ መጠን (ቢል ኦፍ ኳንቲቲ) ተቆጣጣሪ መሀንዲስ ሲያወጣ ዝቅተኛ ግምት በማውጣቱ መሆኑ የዞኑ ስራና ከተማ ልማት መምሪያ ባደረገው ሙያዊ ምርመራ አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ከሳሽ የግንባታ ውሉን በተሰጠው ዲዛይን መሰረት ሥራውን የሰራ በመሆኑ ተከሳሽ ከሳሽ የጠየቀውን ብር 88,913.39 (ሰማንያ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሶስት ብር ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት አንደኛውንና ሁለተኛውን ጭብጥ ወስኗል፡፡ እንደዚሁም የግንባታ ሥራው የተቋረጠው በተከሳሽ ጥያቄ በመሆኑና ከሳሽ በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ኃላፊነቱን የተወጣ በመሆኑ፣ ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም በማለት የተከሳሽን የተከሳሽነት ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ተከሳሽ ክፍያውን ለከሳሽ እንዲከፍል፣ ከሳሽ በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ግንባታውን አጠናቅቆ ለተከሳሽ እንዲያስረክብ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

ተጠሪ በወረዳ ፍ/ቤት መከራከሪያ አድርጎ አቅርቧቸው የነበሩ ነጥቦችን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ በግንባታ ስራ ውሉ ከተገለፀው በላይ በመሆኑና የግንባታ ሥራ ውሉ በተዋዋዮች መካከል የህግ ያህል አስገዳጅነት ያለው የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 1731 የሚደነግግ በመሆኑ ይግባኝ ባይ (ተጠሪ) ለመልስ ሰጭው (አመልካች) የተጠየቀውን ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት የወረዳው ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች ሀምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የግንባታ ሥራውን ለመስራት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኜ ያሸነፍኩት ህንፃውን በዲዛይኑ መሰረት ሰርቶ ለማስረከብ ነው፡፡ የህንፃው ዲዛይን የግንባታ ሥራ ውሉ ክፍል እንደሆነ በግንባታ ሥራ ውሉ ተገልጿል፡፡ ዲዛይኑ ተሰርቶ የተሰጠኝ በተጠሪ ነው፡፡ የዋጋ ልዩነቱ የተከሰተው የስራውንና ስራውን ለመስራት ያስፈልጋል ተብሎ በተጠሪ በኩል የተገመተውና በውሉ የተገለፀው መጠን (ቢል ኦፍ ኳንቲቲ) የግንባታ ሥራው በዲዛይኑ መሰረት በሚሰራበት ወቅት የማነስ ወይም የመብለጥ ሁኔታ በመከሰቱ ነው፡፡ ይህም የቁፋሮና ገረጋንቲ ሥራ በውሉ ሰላሳ ሁለት ሜትር ኪውብ እንደሚሆን የተገለፀ ቢሆንም ሥራው ሲከናወን መጨረሻ ላይ ሲለካ አርባ ስምንት ሜትር ኪውብ መሆኑ፣ የቢም የፎርምወርክና የጣውላ ስራ አስራ ሰባት ሜትር ኪውብ እንደሚሆን በውሉ የተገለፀ ቢሆንም በዲዛይኑ መሰረት ተሰርቶ ሲለካ ዘጠና አራት ሜትር ኪውብ መሆኑ በተቆጣጣሪ መሃንዲሱና በስራና ከተማ ልማት መመሪያ መረጋገጡና በአንፃሩ 366 ካ.ሜትር እንደሚሆን በውሉ የተገለፀው የላይኛው አፈር ማንሳት ሥራ በዲዛይኑ መሰረት ስራው ሲሰራ ሁለት መቶ ሃምሳ ካሬ ሜትር እንደሆነ፣ በአጠቃላይ በዲዛይኑ መሰረት የግንባታ ሥራውን ለመስራት የሚያስፈልገውን የግንባታ ማቴርያልና የስራ መጠን ከሙያ አንፃር በአግባቡ ባለመሰራቱና ባለመገመቱ የተፈጠረ ልዩነት ነው፡፡ ስለዚህ እንደተጨማሪ ሥራ እንዲታይለት ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡ ተጨማሪ ስራ ነው የሚባል ቢሆን እንኳን ሥራው የተሰራው በተጠሪ አማካሪና ተቆጣጣሪ መሃንዲስ የስራ ትዕዛዝ መሰረት በመሆኑ ተጠሪ ክፍያ ከመክፈል ነፃ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 4 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የዋጋ ልዩነት የተፈጠረው አመልካች ሆነ ብለው ከመሃንዲስ ዋጋ በታች ዋጋ በማቅረብ ጨረታ በማሸነፉ ነው፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ ሥራ ሳይሰራ በጨረታ ካሸነፈበትና በግንባታ ሥራ ውሉ ከተገለፀው በላይ ዋጋ የምንከፍልበት ሁኔታ የለም፡፡ አመልካች በነጠላ ዋጋ በመግለፅ በዲዛይኑ መሰረት ለመስራት ውል እስከተዋዋለ ድረስ በውሉ መሰረት ግንባታውን ሰርቶ ለማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡ የአመልካች ጥያቄ ቅን ልቦናን መሰረት ያደረገ የውል አተረጓጎምና አፈፃፀም መርህን የተከተለ አይደለም፡፡ አመልካች ተጨማሪ ሥራ ሳይሰራ ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፈለው ያቀረበው ጥያቄ የግንባታ አሰራር ደንብንና ሌሎች የህግ ማዕቀፎችን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የክልሉ የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በበኩሉ ታህሳስ 12 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ በግንባታ ስራ ውሉ የተገለፀው የስራ መጠንና በተሰራው የስራ መጠን ላይ በመብለጥ ወይም በማነስ ተጠሪ በሞላው ዋጋ ምክንያት የመጣ አይደለም ልዩነቱ በስታንዳርድ ዲዛይኑ መሰረት ለጨረታ ቀርቦ የነበረው ቢል ኦፍ ኳንቲቲና የስራ መጠን ሥራው በዲዛይኑ መሰረት ከተሰራ በኋላ ከተገኘው ልኬት የመብለጥና (የማነስ) ልዩነት በማሳየቱ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ለተጠሪ ሥራ ክፍያ ለመክፈል ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ለሰራው የግንባታ ሥራ የጠየቀውን ክፍያ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 1999 ዓ.ም. ያደረጉት የግንባታ ውል መሰረታዊ ባህሪና ይዘት እንደዚሁም የውሉ አካል ተደርገው የሚያዙ አባሪዎችን በመመርመርና አመልካች የግንባታ ውሉ ሥራውን ያከናወነው በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ማየት ያስፈልጋል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገው የስራ ውል በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3244 በተሰጠው ትርጓሜ የሚሸፈን አንድ የመንግስት የሆነ ህንፃ ለመስራት ያደረገው የግንባታ ሥራ ውል ነው፡፡ ይህም መሆኑ ተጠሪ በግንባታ ሒደት ውስጥ የስራ ትዕዛዞችን እየሰጠ፣ የስራዎቹን አካሄድ የመወሰንና ስራው በሚፈቅደው አይነት እንዲፈፀም (አመልካችን) የስራ ተቋራጩን የማዘዝ፣ አመልካች በበኩሉ በተጠሪ በተሰጡት ፕላኖች አይነቶችና የዋጋና የስራ ማስታወቂያ መሰረት ጠንቅቆ የግንባታ ሥራውን የመስራት ግዴታ እንዳለበት በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3252 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡

ይህም የሚያሳየው የአመልካችና የተጠሪ የግንባታ የሥራ ውል አመልካችና ተጠሪ ሚያዝያ 9 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉት የግንባታ ሥራ ውል ሰነድን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን፣ ተጠሪ የግንባታ ሥራው እንዲሰራ ያወጣው ፕላንና የግንባታው ንድፍ (ዲዛይን)፣ በግንባታ ስራው ሂደት፣ ተጠሪ ለአመልካች በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 3152 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3266(1) ድንጋጌዎች መሰረት የሰጣቸው ተጨማሪ የስራ ትዕዛዞች የግንባታ ሥራ ውሉ አካል ተደርገው የሚያዙ ናቸው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በመደበው ተቆጣጣሪ መሀንዲስ መሰረት ግንቦት 1 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገው ውል ከተገለፀው የስራ መጠንና የግንባታ ጥቅል ዋጋ በላይ፣ የግንባታ ሥራውን በግንባታው ንድፍ (ዲዛይን) መሰረት ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ የስራ ትዕዛዞችን እየሰጠ አመልካቹ በመጀመሪያው ውል ከተገለፀው የስራ መጠንና ዋጋ በላይ አርባ ዘጠኝ ፐርሰንት የሚደርስ ተጨማሪ የስራ መጠን ያከናወነ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ በወረዳው ፍ/ቤት ያረጋገጡት እስከ ሰበር ባቀረቡት ክርክር የማይካካዱበት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች የግንባታ ሥራውን ሚያዝያ 9 ቀን 1999 ዓ/ም በተደረገው ልዩ የግንባታ ሥራ ውልና፣ የዚሁ ልዩ የግንባታ ሥራ ውል አካል በሆነው የግንባታው ንድፍ (ዲዛይን) እና አሰሪው(ተጠሪው) በግንባታ ሥራ ውሉ ሒደት በፅሁፍ በሰጠው የስራ ትዕዛዝ መሰረት በመሆኑ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገውን የግንባታ ሥራ ውል ልዩ ባህሪና ይዘት ሣያገናዝብ፣ የአመልካችና የተጠሪ የግንባታ ሥራ ውል ግንቦት 1 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገው የስራ ውል ላይ የተገለፁት ሀያለ ቃሎች ብቻ እንደሆኑ በመግለፅና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1731 ድንጋጌን በመጥቀስ አመልካች የሰራው ተጨማሪ የግንባታ ሥራና የጠየቀው ክፍያ ከግንባታ ሥራ ውሉ ውጭ የቀረበ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔና ትርጉም፣ ከላይ የገለፅናቸውን የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3252 እና የፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 3266(1) ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካች የተጠሪ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ በፅሁፍ እንዲሰራ በሰጠው የስራ ትዕዛዝ መሰረት ለተሰራው ሥራ ክፍያ የመፈፀም ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ነጥብ በተመለከተ፣ በመጀመሪያ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የግንባታ ስራ ውል፣ የሚፈፀመውን የስራ መጠንና ልኬታ መሰረት በማድረግ ክፍያ የሚፈፀምበት የስራ ውል መሆኑን ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህም የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3263 በሚደነግገው መሰረት አመልካች የህንፃውን ዲዛይን መሰረት ለመስራት የሰራው የስራ መጠን ተለክቶና ተረጋግጦ በጨረታ በአሸናፊነት ነጠላ ዋጋ መጠን እየተሰራ ለሰራው ሥራ ክፍያ የሚፈፀምለት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የሚያሠራውን ህንፃ በዲዛይኑ መሰረት ለመስራት የሚያስፈልገው የስራ መጠንን የገመቱት ባለሞያዎች የስራውን መጠን በማብዛት ወይም በመቀነስ፣ ትክክለኛ የሙያ ግምት አለማስቀመጣቸውና፣ አመልካች የግንባታ ሥራውን በዲዛይኑ መሰረት ሲያከናውን አንዳንድ የግንባታ ስራዎች በግንባታ ስራ ውሉ ከተገለፀው በላይ ከፍተኛ የስራ መጠን ጭማሪ ማሳየታቸው፣ አንዳንድ የግንባታ ስራዎች በግንባታ ስራ ውሉ ከተገለፀው በታች በዝቅተኛ የስራ መጠን የተከናወኑ መሆናቸው፣ በዚህ ምክንያት አመልካች የጠየቀው የግንባታ ስራ ክፍያ በግንባታ ሥራ ውሉ (ግንቦት 1 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገው ውል) ከተገለፀው በላይ እስከ አርባ ዘጠኝ ፐርሰንት የሚደርስ ጭማሪ ማሳየቱ በምስራቅ ጎጃም ዞን ስራና ከተማ ልማት መምሪያ ተጠሪ የሚያሰራውን ህንፃ ዲዛይን፣ ህንፃውን በዲዛይኑ መሰረት ለመስራት ያስፈልጋል ተብሎ ሥራው ከመጀመሩ በፊት በተቆጣጣሪ መሃንዲስ የወጣው የስራ መጠን ግምት፣ አመልካች የግንባታ ስራውን በዲዛይኑ መሰረት ሲሰራ የሰራው የስራ መጠንና ለዚህ ሥራ መጠን በግንባታ ሥራ ውሉ መሰረት ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ በመመርመርና በማጥናት ሙያዊ ማረጋገጫና ማስረጃ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የመደበው ተቆጣጣሪ መሃንዲስ እስከ አስር ፐርሰንት ድረስ ለሚሰጠው ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ ከመጠባበቂያ በጀት እስከ ሃያ አምስት ፐርሰንት ለሚሰጠው የስራ ትዕዛዝ ውሉ ተሻሽሎ ክፍያ እንደሚከፈልና ከሃያ አምስት ፐርሰንት በላይ ለተሰጠው የጭማሪ ሥራ ትዕዛዝ ሥራው የተሰራ መሆኑ ተመርምሮና ተጠንቶ ክፍያ እንደሚፈፀም የዞኑ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ለተጠሪ በሰጠው ሙያዊ ማብራሪያ እንደገለፀ፣ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡

የዞኑ ከተማ ልማት መምሪያ የሰጠው ሙያዊ ማብራሪያና ማረጋገጫ በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3265 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ አመልካች ህንፃውን በዲዛይኑ መሰረት ሰርቶ ለማጠናቀቅ በተቆጣጣሪ መሃዲስ ተገምቶ ከነበረው ዋጋ ከሃያ አምስት ፐርሰንት በላይ ጭማሪ ካሳየ፣ አመልካች ሥራውን በተቆጣጣሪ መሃንዲሱ ትዕዛዝ መሰረት በአግባቡ ካከናወነ በተጨማሪነት የሰራው ሥራ አሰሪው (ተጠሪ) ክፍያ እንዲከፍለው ጥያቄውን ለዳኞች በማቅረብ ማስወሰን እንደሚቻል የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 3265 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡

በመሆኑም አመልካች በተሰጠው የህንፃ ዲዛይን መሰረት ግንባታውን በሚያከናውንበት ወቅት ተጠሪ በመደበው ተቆጣጣሪ መሃንዲስ የስራ ትዕዛዝ ላከናወነው ግንባታ ክፍያ ጭማሪው ከሃያ አምስት ፐርሰንት በላይ ቢሆንም፣ የግንባታ ሥራው፣ ህንፃውን በዲዛይኑ መሰረት ለመስራት መከናወን ያለበት አስፈላጊ በመሆኑና፣ አመልካች ሥራውን የሰራ መሆኑ በተጠሪ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ እና በዞኑ ስራ ከተማ ልማት መምሪያ በኩል የተረጋገጠ በመሆኑ፣ አመልካች ለሰራው ሥራ ክፍያ አልፈፅምም በማለት ከኃላፊነት ነፃ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን የህግ ድንጋጌዎችን በመጥቀስና በመተርጎም አመልካች ላከናወነው የግንባታ ሥራ ክፍያ አይከፈለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ፣ የፍ/ብሔር ህግ አንቀጽ 3244፣ አንቀጽ 3152(1) አንቀጽ 3265 እና አንቀጽ 3266(1) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. በምስራቅ ጎጃም ዞን የጎዛምን ወረዳ ፍ/ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 83448

ጥር 30 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- 1.ወ/ሮ መሉወርቅ ኃ/ገብርኤል - የቀረበ የለም

2. በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ዲዛይንና አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፊጅ ሽመልስ ኃ/ጊዮርጊስ

ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ጽጌ መብራቱ - ቀረቡ

በሰ/መ/ቁጥር 84490 የቀረበው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች ሲካሄድ የነበረ መሆኑን ስለተገነዘብን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 11 መሰረት አጣምረን በመመርመር ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመንግስት ቤቶችን ላይ የተፈጠረውን ችግር ለመፈታት ታስቦ ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ/ም የወጣውን መመሪያ አፈጻጸም ጋር ተይይዞ የተነሳውን የተከራይነት ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ሲሆኑ ተከሳሾች የአሁኑ አመልካቾች ነበሩ፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 143 የሆነን የንግድ ቤት ከአሁኗ 1ኛ አመልካች በወር በብር 2500.00 (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) ሕዳር 07 ቀን 2003 ዓ.ም. በተደረገው ውል ተከራይተው በመስራት ላይ ባሉበት ሁኔታ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ቢሮ በመንግስት ቤቶች ላይ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ሲል መመሪያ ቁጥር 3/2004 ማውጣቱን፣ይህንን መመሪያ መነሻ በማድረግም ከአሁኗ 1ኛ አመልካች ጋር የነበረውን ውል በማቋረጥ ከአሁኗ ተጠሪ ጋር የኪራይ ውል አድርጎ በተጠሪ ስም የኪራይ ገንዘብ እየተከፈለ መቆየቱንና በኋላ ግን ውሉን አቋርጦ ለቀድሞ ተከራይ ለሆኑት 1ኛ አመልካች ቤቱ እንዲመለስ በማለት መወሰኑን ገልጸው ከ2ኛ አመልካች ጋር ያደረጉት የኪራይ ውል እንዳይቋረጥ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 2ኛ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም በመመሪያው መሰረት እርምጃ ሲወሰድ የ1ኛ አመልካች ጉዳይ ያላግባብ የተስተናገደ መሆኑን በማጣራትና 1ኛ አመልካችም አዛውንትና የራሳቸው የሆነ ገቢ የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጦ እና ይህ ደግሞ በመመሪያው መሰረት ውሉን ለማቋረጥ የማያስችል ምክንያት መሆኑ ታውቆ ከተጠሪ ጋር ያደረገውን ውል ማቋረጡን ገልፆ እርምጃው ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ የአሁኗ 1ኛ አመልካችም ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ክርክር በማቅረብ የተጠሪ ክስ ውድቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመርና 1ኛ አመልካች ገቢ ያላቸው መሆን ያለመሆኑን በማጣራት ጉዳዩን መርምሮ 1ኛ አመልካች አዛውንትና ገቢ የሌላቸው መሆኑ መረጋገጡንና ይህ ምክንያት ደግሞ አመልካች ከመንግስት የተከራዩትን ንግድ ቤት ለሶስተኛ ወገን አከራይተው ገቢ ቢያገኙበትም ከቀበሌው ጋር ያላቸውን የተከራይነት ግንኙነት ቀሪ የማያደርገው መሆኑ በመመሪያው መመልከቱን በምክንያትነት ይዞ የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ጉዳዩን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ተደርጎ 1ኛ አመልካች የግል ቤት ያላቸውና በግቢያቸው ካሉት ሱቆችም ለልጅ ልጃቸው ሰጥተው የልጅ ልጃቸው የንግድ ፈቃድ አውጥቶ የፎቶ ግራፍ ስራ የሚሰሩበት መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ ቀበሌው ከተጠሪ ጋር ያደረገው የኪራይ ግንኙነት ሊቀጥል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የ1ኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ገቢ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል በማለት የደመደመው የፍሬ ነገር ጉዳይ ከስልጣኑ ውጪ መሆኑንና በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው የማስረጃ ይዘት ውጪ መሆኑን በመጥቀስ ውሳኔው እንዲሻርላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ለአሁኗ አመልካች የኪራይ ግንኙነት እንዲቀጥል ያደረገው በአግባቡ በማጣራት በመመሪያው መሰረት መሆኑና የመዋዋል ነጻነቱን በመጠቀም መሆኑን ጠቅሶ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ሲል መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም 2ኛ አመልካች 1ኛ አመልካች አዛውንትና ገቢ የሌላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ኪራዩን ከ1ኛ አመልካች ጋር ለመቀጠል በመፈለግ ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል ማቋረጡ ያላግባብ ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ 1ኛ አመልካች ገቢ ያላቸው መሆኑ መረጋገጡንና በመመሪያው መሰረት የኪራይ ውሉ ሊቀጥልላቸው የማይገባ መሆኑን እንዲሁም በመመሪያው መሰረት ተጠቃሚ መሆን ያለባቸው ተጠሪ መሆናቸውን ዘርዝረው በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም 1ኛ አመልካች ገቢ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል ተብሎ በመመሪያው መሰረት ተጠቃሚ ሊሆኑ አይገባም ተብሎ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ክክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ጋር መስረተውት የነበረው የኪራይ ውል ተቋርጦ የነበረው በመመሪያ ቁጥር 3/2004 መሰረት ሲሆን አመልካች በመመሪያው መሰረት ጉዳዩ ያለመታየቱን በመግለፅ ለ2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻም ጉዳዩ እንደገና ታይቶ 1ኛ አመልካች አዛውንትና የራሳቸው ገቢ የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጦ እርምጃው እርምት ተወስዶ በተሳሳተ ውሳኔ ለተጠሪ ተሰጥቶ የነበረው የተከራይነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብት ቀሪ ሁኖ ከ1ኛ አመልካች ጋር የነበረው የኪራይ ውል እንዲቀጥል መደረጉን ነው።የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት 1ኛ አመልካች ገቢ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል ያለው በስር ፍርድ ቤት መጣራት ሲደረግ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የተፃፈውን ደብዳቤ ይዘት በመመልከት ነው። በዚህ ረገድ የወረዳው አስተዳደር በደብዳቤ ቁጥር የካ/ወ1/06-003/6862/04 ሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ.ም. ጽፎ የላከው ደብዳቤ ይዘት የአሁኗ አመልካች በግል ቤት ነዋሪ ሁነው የሚኖሩትም ከአራት የልጅ ልጆቻቸው ጋር መሆኑን ፣ በይዞታቸው በፊት በኩል ሱቅ ያለ ሁኖ በዚህ ሱቅ የልጅ ልጃቸው የሆነውን ቢኒያም ተስፋዬ በስሙ በተመዘገበ የንግድ ፈቃድ የፎቶ ቤት አገልግሎት የሚሰራበት መሆኑን የሚገልጽ ነው። ይህ የደብዳቤው ይዘት 1ኛ አመልካች የራሳቸው የሆነ የግል ይዞታ እንዳላቸውና በዚህ የግል ይዞታቸው ላይም የልጅ ልጃቸው የንግድ ፈቃድ አውጥቶ የሚሰራበት ሁኖ የንግድ ስራው የሚሰራበት ንብረት የ1ኛ አመልካች ስለመሆኑ ያረጋግጣል በሚል ምክንያት የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት 1ኛ አመልካች ገቢ አላቸው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ይሁን እንጂ 1ኛ አመልካች የግል መኖሪያ ያላቸውና በዚህ ይዞታቸው ስር ሱቅ የሚገኝ መሆኑ ከመረጋገጡ ውጪ ከመመሪያውም በፊትም ሆነ በኋላ በሱቁ ገቢ በትክክል እያገኙበት የነበረ ወይም እያገኙ ያሉበት መሆኑ አልተረጋገጠም። 1ኛ አመልካች ሱቁን በማከራየት ገቢ ማግኘት ይችሉ የነበረ መሆኑን ግን የደብዳቤው ይዘት የሚያስገነዝብ ቢሆንም ሱቁ ተይዞ የንግድ ስራው የሚከናወነው በልጅ ልጃቸው ከመሆኑም በላይ ስራው መመሪያ ቁጥር 3/2004 ከመውጣቱ በፊት የተጀመረና ሲሰራ የቆየ ከመሆኑ አንፃር ለቤተሰብ የሰጡትን ሱቅ ለግላቸው የኪራይ ገንዘብ በመቀበል ለራሳቸው ገቢ ማድረግ ነበረባቸው ማለት በነባራዊው ሁኔታ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ውጤት ያላገናዘበ ምክንያት መሆኑ እሙን ነው። በመመሪያው አንቀጽ 6.1 ስር አዛውንት የሆነ ከሆነና በማከራየት ከሚያገኙት ገቢ ሌላ ገቢ የሌለው መሆኑ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያለውን የኪራይ ውል እንዳይቋረጥ የሚያደርግ መሆኑ በግልጽ የተመለከተ ሲሆን ቀድሞ እነዚህ ሁኔታዎች ሳይጣሩ የተሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ በአግባቡ ከተጣራ በኋላ ቀሪ እንዲሆን መደረጉም ከአመልካች ሃላፊነትና ተግባር አንጻር ሲታይ የሚነቀፍ ካለመሆኑም በላይ **በመመሪያው ላይ ያሉትን ቅድመ ሁኔታዎችን** መሰረት አድርጎ ኪራዩን ከአመልካች ጋር ለመቀጠል በፈለገበት ሁኔታ ደግሞ 2ኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር የኪራይ ግንኙነት እንዲቀጥል በፍርድ ኃይል ማስገደድ የመዋዋል ነጻነትን ጽንሰ ሀሳብ የሚጻረርና 2ኛ አመልካች ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን አገልግሎትም በተገቢው መንገድ እንዳይወጣ የማድረግ ውጤት የሚያስከትል ነው። በመሆኑም 1ኛ አመልካች ከመመሪያው በፊት በይዞታቸው ስር ያለውን ሱቅ ለልጅ ልጃቸው ሰጥተው የልጅ ልጃቸው የንግድ ስራ የሚሰሩበት መሆኑ ገቢ ያገኙ ይችሉ የነበረ መሆኑን ከሚያስገነዝብ በቀር በትክክል አመልካች ገቢ ነበራቸው፣ ይህንኑ ገቢም ለእለት መተዳደሪያቸው በማድረግ የሚኖሩ መሆኑን በማናቸውም መመዘኛ የማያሳይ ሁኖ እያለ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት 1ኛ አመልካች ገቢ ሊያገኙ በሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ አሉ በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ የመመሪያውን ዓላማና መንፈስ ከመዋዋል ነጻነትና ከ2ኛ አመልካች ኃላፊነትና ተግባር ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 18284 ነሐሴ 16 ቀን 2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 06113ሰኔ 26 ቀን 2004 ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 18194 ሐምሌ 10 ቀን 2004 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. 2ኛ አመልካች ከ1ኛ አመልካች ጋር ያደረገውን ውል ሊያቋርጥ አይገባም፣ ከተጠሪ ጋር የኪራይ ውል እንዲያደርግ የሚገደድበት ምክንያት የለም በማለት በድምጽ ብልጫ ወስነናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ግልባጭ ከሰ/መ/ቁጥር 84490 ጋርም ይያያዝ ብለናል፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሀሳብ ልዩነት

ከሶስተኛው ተራ ቁጥርና በአራተኛው ተራ ቁጥር ሰማችን የተገለፀው ዳኞች አብላጫው ድምጽ በሰጠው ትርጉምና ውሣኔ የማንስማማ በመሆናችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡ ከስራ ባልደረቦቻችን የተለየንባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመጀመሪያው ልዩነታችን የመመሪያ ቁጥር 3/2004 አንቀጽ 6.1 ይዘት መንፈስና ዓላማ እንደዚሁም የተፈጻሚነት ወሰን አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም ትክክል አየደለም የሚል ነው፡፡ መመሪያ ቁጥር 3/2004 የወጣበት መሰረታዊ ዓላማና የንግድ ስራ እንሰራበታለን በሚል ከመነግስት ቤት ተከራይተው እያኖሩበት ወይም የንግድ ስራ እያሰሩ ሣይሆን የተከራዩትን ቤት መልሰው በማከራየት ገንዘብ የሚሰበሰቡ ሰዎችን የኪራይ ውል በማቋረጥ ቤቱን የንግድ ስራ እያሰሩ በሚተዳደሩበት ግለሰቦች በቀጥታ ከመንግስት እንዲከራዩ ማድረግ ነው ይህም የህገ መንግስቱ አንቀጽ 25 መሰረት የእኩልነትና እኩል የህግ ጥበቃና ዋስትና መበት ያላቸው ዜጎች አንደኛው የህዝብ ሀብት የሆነ የንግድ ማከናወኛ ቤት ከመንግስት በርካሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዋጋ ተከራይቶ ለሌላው ዜጋ በከፍተኛ ዋጋ እያከራየ ትርፍ የሚያጋብስበትን ሁኔታ በመከላከልና በመቆጣጠር ህንጻውን ከተከራይ አከራይ ተከራይተው የንግድ ስራ የሚሰሩ ዜጎች በቀጥታ ከመንግስት የሚከራዩበትን ሁኔታ የመፍጠር ታስቦ የወጣ መመሪያ ነው።

በዚህ መመሪያ አስገዳጅና ገዥነት ያለው መርህ ከመንግስት ቤት ተከራይቶ ለሌላ ሰው በማከራየት የሚኖር ሰው ከመንግስት ጋር ያለው የኪራይ ውል ተቋርጦ ህንጻውን ከተከራዩ ተከራይቶ ይኖር የነበረው ሰው በቀጥታ ከመንግስት የመከራየት መብቱን ማረጋገጥ ነው። መልሰ ሰጭም ይህ መመሪያ የወጣበት መሰረታዊ ዓላማና የመመሪያው ድንጋጌዎች መሰረት ከአመልካች ተከራይታ የነግድ ስራ ስትሰራበት የነበረውን ህንጻ የመከራየት መብታ ተረጋግጦላታል። የመመሪያ ቁጥር 3/2004 ቁጥር 6.1 ሀይለ ቃል ይዘትን ዓላማው አጠቃላይ መመሪያ ቁጥር 2/2004 ከወጣበት መሰረታዊ ዓላማና የመመሪያው ቁጥር 4 እና ቁጥር 5 ከተገለፀው በልዩ ሁኔታ የተቀመጠ ነው። የመመሪያ ቁጥር 3/2004 አነቀጽ 6.1 "በራሱ ሳይሰራበት ለሶስተኛ ወገን ቤቱን በማከራየት በሚያገኙት ገቢ ብቻ የሚተዳደሩ የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን ሰዎች እና በእድሜ የገፉ ሽማግሌዎችና አዛውንቶች፣ ቤቱን ለሌላ ሰው አከራይተው በመገኘታቸው የኪራይ ውል የማይቋረጥባቸው መሆኑን የሚገልፅ ነው። የዚህ ልዩ ሀይለ ቃል ዓላማ ከመንግስት ተከራይተው ለሌላ ሰው እያከራዩ ከሚያገኙት ገቢ ውጭ ሌላ መተዳደሪያ የሌላቸው በችግር ውስጥ ያሉ ዜጎች ችግራቸውን ለማቃለል በማሰብ ቤቱን ለሌላ ሰው አከራይተው ቢገኙም መንግስት ከእነሱ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል የሚያቋርጥ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። የመመሪያ ቁጥር 6.1 ሀይለ ቃል ልዩ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው በኢኮኖሚ አቅማቸው በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን መብት ለመጠበቅ ታስቦ የወጣ ነው።ሊተረጎም የሚገባው በጠባቡ ነው። ይህ የመመሪያው ሀይለ ቃል እንደ አመልካች ያሉ ለመኖሪያ ቤትና ለንግድ ሥራ ድርጅት የሚሆን የግል ቤት ኖሯቸው ኪራይ አከራይተው ገቢ ሊያገኙበት የሚችለውን ሰርቪስ የመኖሪያ ቤት ለልጃቸው በመኖሪያነት ሰጥተውት የንግድ ድርጅት መስሪያ የሚሆነውን የግል ህንፃቸውን የልጅ ልጃቸው የፎቶ ግራፍ ንግድ ስራ እንዲሰራበት ሰጥተው የሚኖሩ ሰዎችን የሚጨምር አይደለም። የመመሪያ ቁጥር 3/2004 ቁጥር 6.1 ከመንግስት የተከራዩትን ህንፃ ለሌላ ሰው የሚያከራዩ ሰዎች አማራጭ የሌላቸውና በከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና የጤና ችግር ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን የሚመለከት ነው። አመልካች ገቢ ለማስገኘት የሚችል ሰርቪስ የመኖሪያ ቤትና ለንግድ ስራ የሚሆን ክፍል ያላቸው መሆኑ አከራካሪ አይደለም። አመልካች ከሚኖሩበት መኖሪያ ቤት በተጨማሪ ያሉ ሰርቪስ ቤቶች እና ለንግድ ስራ የሚውል ህንፃ በማከራየት ገቢ እንዳያገኙ የሚያግዳቸው ነገር የለም። የንብረቱ ባለሀብትነት መብታቸውን በፈለጉት መንገድ መጠቀም ይችላሉ። ስለዚህ ይኸውን ንብረት ለሌሎች በነፃ እንዲገለገሉበት ለቅቀው ከመንግስት የተከራዩትን ህንፃ እያከራዩ እንዲኖሩ ሊፈቅድላቸው አይገባም። ከመንግስት በንብረት ላይ አመልካች ያላቸውን መብት ያህል ተጠሪም ተነፃፃሪ የሆነ መብትና ጥያቄ ይኖራታል።

2. ሁለተኛ ተጠሪም ቢሆን መመሪያ ቁጥር 3/2004 ለተጠሪ ያረጋገጠላትን መብት ተፈፃሚ ማድረግ ሲገባው የመመሪያ ቁጥር 3/2004 ቁጥር 6.1 ሀይለ ቃል በመመሪያው ከተካተተበት ዓላማና ከመመሪያው ይዘት ውጭ በመተርጎም የአመልካችን የተከራይነት መብት ለማስቀጠልና ተጠሪ በቀጥታ ከመንግስት የመከራየት መብት ለማረጋገጥ ከተጠሪ ጋር አድርጎት የነበረውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ የሰጠው ውሳኔ መመሪያውን መሰረት ያላደረገ ነው። ስለዚህ በመመሪያ መብትና ጥቅም የተረጋገጠላት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ሁለተኛ ተጠሪ የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመመሪያ ቁጥር 3/2004 የሚቃረንና መብቷን የሚጋፋ መሆኑ ታይቶ እንዲወሰንላት ክስ አቅርባለች፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ታይቶ ሊወሰንና ሊያልቅ የሚችል ነው፡፡ በፍርድ ሊታዩ የሚችሉ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ህገወጥ ናቸው ተብለው እንዲወሰንላቸው በውሳኔው መብታቸው የተነካባቸው ሰዎች ሊጠየቁ እንደሚችሉ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመመሪያ ቁጥር 3/2004 ተጠሪ ያገኘችውን መብት በመጋፋት ሁለተኛው ተጠሪ የሰጠውን ውሳኔ የሚያርም ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት የልዩነት ሀሳባችንን አስፍረናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 80642

ታህሣስ 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት - ጠበቃ

አቶ ማረን ወንደ ቀረበ

ተጠሪ ፡- ባርጉባ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል ለተነሳው የይርጋ ክርክር ጉዳይ ተፈፃሚነት ካለው ህግ አንፃር በማየት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለይቶ ለመወሰን ሲባል የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት የመንገዣ ውል መሠረት አመልካች ከጃካርታ ጅቡቲ ወደብ የጫነውን የተጠሪን ንብረት አንጡዞ እ..አ.ኤ በ02/06/09 ለተጠሪ ማስረከቡንና ተጠሪም እቃውን ከተረከበ ከ5 ወር ከ24 ቀናት በኃላ እ.ኤ.አ በ26/11/09 በተፈረመ የመተማመኛ ሰነድ መክፈል የሚገባውን የመንገዣ ዋጋ እ.ኤ.አ. በ10/01/2010 ለመክፈል ግዴታ የገባ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ በክርክር ሂደት የተረጋገጡ የፍሬ ነገር ጉዳዮች ናቸው፡፡

የአሁን አመልካች እቃዎችን ያንገዘበት ዋጋ በተጠሪ እንዲከፍለው መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የግራ ቀኞችንን ውል በሚገዛው የባህር ህግ አንቀጽ 146 እና 203 ድንጋጌዎች መሠረተ አንገቦ እቃውን ከተረከበበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንደለበት ተደንግጓል፡፡ ከሣሽ የሆነው የአሁን አመልካች ክሱን የመሠረተው ይህ በህጉ የተመለከተው የአንድ ዓመት የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኃላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የአሁን አመልካችም በዚህ በተጠሪ አመካኝነት ለቀረበበት የይረጋ ክርክር በቃል ክርክር ጊዜ ባቀረበው ክርክር ተከሣሹ በመካከሉ የዱቤ ክፍያ ሰነድ የፈረመ በመሆኑ የክፍያው ግዴታ በዓይነቱ ተቀይሯል፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብነት ያለው የፍ/ብሔር ህጉ እንጂ የባህር ህግ አይደለም፡፡ ስለሆነም የፍ/ብሔር የይርጋ ዘመኑ 10 ዓመት ስለሆነ በይርጋ ሊቋረጥ አይችልም የሚለውን አስመዝግቧል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ በከሣሽ እና በተከሣሽ መካከል የተደረገው የዱቤ አገለግሎት ክፍያና የተደረገው ግራ ቀኙ በመጀመሪያ የባህር ህጉን መሠረት አድርገው የተዋዋሉትን እና በባህር ህግ መሠረት የሚታየውን የመጓጓጥ ውል መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ በመሆኑ ተከሣሽ የአሁን ተጠሪ በዱቤ ውሉ እንደተገለፀው የመጓጓጥ ገንዘቡን እከፍላለሁ ካሉበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ የአንድ ዓመት ጊዜ ያለፈ በመሆኑ በባህር ህጉ አንቀጽ 203 መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

ይግባኙን የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራ ቀኙ የመጓጓጥ ዋጋውን የክፍያ ሁኔታ በሚመለከት ያደረጉት የዱቤ አገልግሎት ውል ቀደም ሲል ሁለቱም ወገኖች ያደረጉትና በባህር ህጉ መሠረት የሚገዛውን ውል ያሻሻለ እንጂ የተካ ሆኖ ስላልተገኘ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የባህር ህግ እንጂ የአሁን አመልካች እንደሚለው በፍ/ብ/ሕግ የሚሸፈን አይደለም፡፡ ስለሆነም ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ መባሉ አግባብ ነው በማለት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ብይን አጽንቶታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ይህንኑ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ዳኝነት ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ደረጃ ካደረጉት የጽሑፍ ክርክር ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች በገባው ግዴታ መሠረት እቃውን ጭኖና አጓጉዞ ለአሁን ተጠሪ ለሥር ከሣሽ እ.ኤ.አ. 20/06/09 ካስረከበ በኃላ እ.ኤ.አ. በ26/11/09 ከአሁን ተጠሪ ጋር ያደረገግነው የዱቤ አገልገሎት ውል በዓይነቱ እና በግቡ ሁለቱም ወገኖች ቀደም ሲል በባህር ህጉ መሠረት ያደረጉትን ውል የተካ ነው ወይስ ያሻሻለ? የሚለውን አከራካሪ ነጥበ በቅድሚያ ተመልክተናል፡፡

የአሁን አመልካች አጥብቆ እንዲሚያነሣው ክርክር የባህር ህጉን መሠረት በማድረግ ሁለቱም ወገኖች የደረጉት ውል በኃላ በዱቤ አግልግሎት ውል ተተክቷል፡፡ ስለሆነም ለተነሣው የይርጋ ጊዜ አግባብነት ያለው ይህንኑ የተነሳውን ጉዳይ በሚገዛው በፍ/ብ/ሕግ የተመለከተው የይርጋ ዘመን ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለይቶ ለመወሰን ከአንድ ውል የመነጨ ግዴታ በሌላ ውል የተተካ ስለሆነ ቀሪ ነው ለማለት ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1807(ሐ) እንደተደነገገው አመልካች ተጠሪ በመጀመሪያ በባህር ህግ እንዲገዛ አድርገው የተዋዋሉትን ውል በዱቤ አገልግሎት ውል እንዲተካ የመነጨና ማናቸውም መበትና ግዴታ እንዲተካ በማድረግ በባህር ህግ መሠረት ከሚታየው ውሉ የመነጨን ማናቸውም መብትና ግዴታ እንዲተካ በማድረግ በባህር ህጉ የሚገዛውን ውለታ ሙሉ በሙሉ ቀሪ ስለማድረጋቸውም ሆነ ስላለማድረጋቸው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1826 ጀምሮ በተቀመጡት መለኪያዎች አንፃር ሊታይ ይገባል፡፡

ከእነዚህም መከራከሪያዎች አንዱ ይተካል በተባለው እና ተተክቷል በሚባሉት ውሎች መካከል ያለው የውለታ ጉዳይም ሆነ የውለታው ምክንያት በይዘቱ አዲስ መሆኑ እንዳለበትና ይህንኑ በውለታውም አይነት ሆነ ከውለታው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት አንፃር ታይቶ አዲስ የሆነው ውል ከዚህ ቀደም ተደርጎ በነበረው ውል ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች በማያጣራጥር አኳኋን ሊያስቀር የሚችል ፈቃድ ከተዋዋይ ወገኖች እንዲኖር አስፈላጊ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1826 እና 1828 የተደነገገ ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1829(ሀ) እንደተመለከተው በመጀመሪያው ውል የተመለከተን እዳ ለማረጋገጥ ሲባል አዲስ ሰነድ የማደራጀት ተግባር የውል መተካት አድራጐት ሊሆን እንደማይችል፤ ይህ ተግበር የውል መተካት አድራጎት እንዲሆን ከተፈለገ በውሉ ላይ በግልጽ መመልከት እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም ሁለቱም ወገኖች የሚጓጓጉ ዋጋ ክፍያን አስመልክቶ በተከታይ የደረጉት ውል በዓይነቱም ሆነ ለውለታው ምክንያት ከሆነው መመዘኛ አንፃር ሲታይ አዲስ ግዴታ የተካተተበት ባለመሆኑ፤ ይህንኑ የኃላኛው ውል በዓይነቱም ሆነ በውለታው ምክንያት በመጀመሪያው ውል ከተመለከተው ግዴታ የተለዩ አይደለም እንጂ የመተካት ሃሣብ አላቸው ቢባል ይህንኑ የውል መተካት ጉዳይ በዚህ በኋላኛው የ ውል በግልጽና በማየሻማ አኳኃን የተደረገ ሆኖ ባለመገኘቱ እንዲሁም በዱቤ አገልግሎት ውሉ የተደረገው ከተጠሪ በተነፃፃሪነት የሚፈለግበትን የመጓጓጉ ዋጋ በውሉ በተመለከተው ጊዜ የነበረበት የመክፈል ግዴታ ለማራዘም ሲባል በእዳ ማረጋገጫ ሰነዱነቱ መደረጉን ይዘቱ አስረጂ ሆኖ በመገኘቱ ሁሉ ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል የውሉ መተካት ተግባር የተፈፀመ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይልቁንም የአሁን ተጠሪ በባህር ህጉ መሠረት በሚገዛው ውል ላይ ለመክፈል ግዴታ ገብቶ የነበረበትን የክፍያ ጊዜ እ.አ.አ በ26/11/09 በተደረገ የዱቤ አገልግሎት ክፍያ ሰነድ እ.አ.አ. በ10/01/2010 እከፍላለሁ በማለት የክፍያ ጊዜን የሚያሻሽል ግዴታ የገባ በመሆኑ በባህር ህጉ የተመለከተው የአንድ ዓመት የይርጋ ጊዜ በዚህ ከተሻሻለው የክፍያ ጊዜ እ.አ.አ. ከ10/01/2010 ጀምሮ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ስሌት ይርጋው ሊታሰብ ይገባል፡፡

በዚህ ረገድም ሲታሰብ ክሱ እስከቀረበበት እስከ መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ይህ የአንድ ዓመት የይርጋ ጊዜ አልፎታል፡፡ አመልካች ይህ የይርጋ ጊዜ ማለፉን ሣይክድ በመከራከሪያነት የሚቀርበው ከተሻሻለው የዱቤ ክፍያ ጊዜ ጀምሬ ሲታሰብ 10 ዓመት ያልሞላው ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም በማለት በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት ያለው የፍ/ብ/ብ/ሕገግ ነው ከሚለው የመነሻ ክርክር የመነጨ የክርክር መስመር ነው፡፡

ይህም ከላይ እንደተገለፀው ተቀበይነት ያለው የህግ ክርክር ባለመሆኑ የይርጋ ዘመኑ 1 ዓመት እንጂ 10 ዓመት አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበው ክስ በባህር ህጉ አንቀጽ 203 መሠረት የአንድ ዓመት የይርጋ ዘመን ያለፈው ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ነው ሲሉ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያተፈፀመበት ሆኖ ስላላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በከ/መ/ቁ. 117281 በሚያዝያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ምክንያት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80464

ታህሳስ 16 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወይራ እንጨትና ብረታ ብረት ሥራ ኃ/የተ/የሕብረት ሥራ ማህበር ጠበቃ

አቶ ወልደሥላሴ ብረቱ

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደርና የንግድ ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነገር ፈጅ-

አቶ ዮሐንስ ይረስህ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን ክርክር አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ናቸው ወይስ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ከውል የመነጨን ክስ በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርቦ፤ ተጠሪም በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የአሁን ተጠሪ በድምሩ ብር 395,026.55 (ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ሃያ ስድስት ብር ከ55% ሣንቲም) ለአሁን አመልካች ይከፈል በሚል ተወስኖል፡፡

የአሁን ተጠሪ በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩላቸው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ውል አስተዳደራዊ ውል ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41(1)(መ) እንደተደነገገው ተከሣሽ የሆነው መስሪያ ቤት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት አንዱ በመሆኑ ይህ የአስፈፃሚ አካል የገባውን አስተዳደራዊ ውል በሚመለከት የሚነሣው ክርክር የመዳኘት ሥልጣን የተሰጠቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሌለው ስልጣን የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለውም የአሁን አመልካች በዚህ በፌዴራል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ሥነ-ሥርዓታዊ ክርክርና መንስኤ የሆነው ውል አስተዳደራዊ ውል በሚለው ሥር የማይሸፈን መሆኑን መሠረት በማድረግ ጠቅሶ ክርክር በማቅረቡ ሲሆን፤ የአሁን ተጠሪ በበኩሉ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው መባሉ በህጉ መሠረት መወሰኑን እንጂ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን አያሣይም በማለት የጽሑፍ ክርክሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርቧል፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ሥነ-ሥርዓታዊ ክርክሩን በማስቀደም ያቀረበ ሲሆን፤ ይዘቱም የአሁን ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የተወሰነ እስከሆነ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት እርሱ በሌለበት ጉዳዩ ፍርዱን በፈረደው ፍ/ቤት እንደገና እንዲታይለት ከሚያቀርብ በቀር በቀጥታ የይግባኝ ክርክር የማቅረብ መብት የሌለው መሆኑ እየታወቀ በዚህ ከሥነ-ሥርዓቱ ውጭ በሆነ አቅራረብ ውሣኔው መሻሩ የህግ መሠረት የሌለው ስለሆነ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ይሁን እንጂ በተመሣሣይ የክርክር ነጥብ ከዚህ ቀደም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ 36412 በቀረበው ጉዳይ ላይ በ13/2/01 ዓ.ም. ቀን በዋለው ችሎት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 ድንጋጌ ይዘት የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንደ ቋሚ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠ አለመሆኑ ይልቁንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329 የተመለከተው ሥነ -ሠርዓታዊ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70(ሀ) መሠረት አንድ ጉዳይ ተከሣሹ በሌለበት የተሰጠ ከሆነ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ ለመከራከር መብት የሌለው ከመሆኑ በቀር የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ አግባብነቱ ከህግ አንፃር እንዲታይለት ይግባኝ የመጠየቅና በይግባኝ የማሰማት መብት ያለው መሆኑ በተብራራ አኳኋን ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በዚህም ጉዳይ ያሁን ተጠሪ ያደረገውና ያቀረበው ክርክር ቢኖር ተከሣሽ ቀረበም አልቀረበም አንድን ጉዳይ ተቀብሎ ለማየትና ለመዳኘት ሥልጣን ያለው በየትኛው ደረጃ የተደራጀ፤ (የተቋቋመ) ፍ/ቤት ነው? የሚለውን ነጥብ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 37፣ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 23(1)(ለ)፣ 244(3) አንፃር ተመልክቶ የጉዳዩ ባለቤት መሆኑንና አለመሆኑን ለይቶ መወሰን የዳኝነት ሥራ ተግባር የሚያስገድደው ሆኖ እያለ ይህንኑ በህግ የተመለከተ የዳኝነት ተግባር አልተወጣም፤ ይህ ከህጉ ጋር ተገናዝቦ ይታይ በማለት ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሐ/ቁ. 329 የተመለከተውን ሥነ- ሥርዓታዊ ድንጋጌ አፈፃፀም የጣሰ መሆኑን አያመለክትም፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ክርክር ያስነሣው ጉዳይ የአስተዳደር ውል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመለየት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3132 ላይ በህግ ተለይቶ በተደረገ ጊዜ ነው የሚለውን ድንጋጌ መነሻ በማድረግ አንድ ውል የአስተዳደር ውል ነው ብሎ ህግ ተነግሯል የሚባለው ደግሞ በንብረት ህግ አንቀጽ 1444(2)፣ 1446 እና 1447(1) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመከተል ነው ሲሉ ያቀረቡት ክርክር እጅግ የጠበበ ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3132(ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት እና ዓላማ የተከተለ የትርጉም መስመር አይደለም ይልቁም በፍ/ህ/ቁ. 3132 እንደተመለከተው አንድ ውል “የአስተዳደር ውል” ነው በሚለው ማእቀፍ ሥር ይወድቃል ወይስ አይወድቅም ብሎ ለመወሰን መመዘኛ ተደርገው የተያዙት በህግ ወይም በተዋዋዮቹ ግልጽ የሆነ ቃል የአስተዳደር መ/ቤት ውል ነው የተባለ እንደሆነና፤ ከህዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር ተያያዥና ለሥራ ውል አፈፃፀም የአስተዳደር ፍ/ቤቱን ተካፋይነት ያለማቋረጥ የሚጠይቅ መሆኑን ሁሉ የሚጨምር ነው፡፡ ከእነዚህም መስፈርቶች አንፃር አንድ ውል የአስተዳደር ውል ነው ለማለት የግድ በውሉ ላይ በግልጽ መነገር ብቻ ሣይሆን የውሉን ዓይነት የውለታውን ጉዳይ እንዲሁም የተዋዋዮችን ማንነት በማየት መለየት እንደሚገባ በዚሁ ህግ የተደነገገ በመሆኑ በዚሁ መሠረት የሚለይ እንጂ የአሁን አመልካች ከጠቀሷቸው የንብረት ህግ ድንጋጌዎች አንፃር ብቻ ታይቶ ሊወሰን ይገባል የሚለውን ትርጉም የሚሰጥ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህም አንፃር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተለይ ከአሁን አመልካች ጋር ውለታ የገባው ማን ነው የሚለውንና የውለታውን ጉዳይ በማየት ውሉ የአስተዳደራዊ ውል ነው፡፡ ይህንኑ አስተዳደራዊ ውልም የገባው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ከሚገኙት አስፈፃሚ አካላት መካከል አንዱ የሆነው ተጠሪ የመሆኑን ፍሬ ጉዳዮች መነሻ አድርጎ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3132(ለ) እና በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41(1)(መ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በአግባቡ ተመልክቶና ተርጉሞ መሆኑን እንጂ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራሉ ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 115093 በቀን 12/04/2004 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 76951 በቀን 25/08/2004 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ ሁሉ ፀንቷል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 176341 በቀን 10/10/2003 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
3. በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የክርክር ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ናቸው ብለናል፡፡
4. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 78444

ጥቅምት 22 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ አቶ አክሊሉ ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጥጋቡ ተፈራ ጠበቃ አቶ ታዬ ገብረመድህን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የማይንቀሣቀስ ንብረት ለማስያዝ የተደረገውን ውል በድጋሚ ማስመዝገብን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ለወሰደው የብድር ገንዘብ መያዣ እንዲሆን የማይንቀሣቀሥ ንብረት የመያዥያ ውል ከአመልካች ጋር በ18-07-1989 ዓ.ም የተዋዋለ መሆኑንና የመያዣ ውሉ በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል መጋቢት 23 ቀን 1989 ዓ.ም እንደተመዘገበ ገልጿል፡፡ ተጠሪ የመያዣ ውሉ ምዝገባ እንዲታደስ ተጠሪ መስከረም 17 ቀን 2003 ዓ.ም የሚመለከተውን የአስተዳደር አካል ጠይቋል፡፡ የአስተዳደር አካሉም ያለእኔ ፈቃድ መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም መያዣውን በድጋሚ በመመዝገብ /ለተከሳሽ/ አመልካች አሳውቋል፡፡ አመልካች የመያዣ ውል ምዝገባ እንዲታደስለት የጠየቀውና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/2/ የተደነገገው አስር ዓመት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ የታደሰው የመያዣ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡

አመልካች በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ፣ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠኝ ሥልጣን መሠረት በመያዣው ላይ ያለኝን መብት ለመጠቀም ለተጠሪ ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ/ም እና መስከረም 24 ቀን 1994 ዓ/ም ማስጠንቀቂያ የሰጠሁ በመሆኑ ተጠሪ /ከሳሽ/ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/2/ን በመጥቀስ ያቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ እንዳልደረሰው በመግለጽ በመከራከሩ፣ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ/ም የተፃፈ ማስጠንቀቂያ በአዋጅ ቁጥር 97/1996 አንቀጽ 3 በሚደነግገው መሠረት ለተጠሪ አድርሷል፡፡ አመልካች መስከረም 24 ቀን 1984 ዓ.ም የተፃፈውን ማስጠንቀቂያ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 መሠረት ለተጠሪ ሣይሆን ለሌላ ሰው እንዳደረሰ ማስረጃው ያሣያል፡፡ ስለዚህ አመልካች በሕግ በተደነገገው መሠረት መስከረም 24 ቀን 1994 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ አልሰጠም፡፡ አመልካች ማስጠንቀቂያ በአግባቡ ካደረሰበት ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ የመያዣ ውሉ በጊንቢ አስተዳደር ታድሶ እስከተመዘገበት መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያለው ጊዜ ሲሰላ ከአስራ ሁለት ዓመት በኋላ የመያዣ ውሉ የታደሰ መሆኑን ያሣያል፡፡ ስለሆነም የመያዥያ ውሉ የታደሰው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/2/ የተደነገገው የአሥር ዓመት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ በመሆኑ የመያዣ ውሉ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1632/1/ መሠረት ሊሰረዝ የሚገባው ነው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/2/ የተደነገገው የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ለተጠሪ የዕሑፍ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ፡፡ ይህም አመልካች በሕጉ የተደነገገው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት በመብቱ መገልገል መጀመሬን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች በመብቱ መገልገል ከጀመርኩ በኋላ ከመያዣው ላይ ያለኝ መብት ቀሪ የማይሆን ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 44800 ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ይኸ የሰበር ችሎት የሰጠውን የሕግ ትርጉም ሳያገናዝብ በመያዣው ላይ ያለኝ መብት እንዲሰረዝና ቀሪ እንዲሆን የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ የሰጠ መሆኑን በመግለፅ የሚያቀርበው ክርክር እውነትነት የለውም፡፡ አመልካች ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል ቢባል እንኳን፣ መያዣው የታደሰው መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም በመሆኑ ምዝገባው የታደሰው ከአስራ ሁለት ዓመት በኋላ ነው፡፡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 44800 ይህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠው፣ መያዣውን የሰጠው ሰው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው መሆኑን በማመን የተከራከረ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ መዝገብ ጋር የሚመሳሰል ባለመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ ስለዚህ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ በስር አቤቱታው ያነሳቸውን ነጥቦች በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የዕሑፍ ክርክር ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመያዣ ውሉ እድሳት ሊሰረዝና ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የመሠረትነውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ፍሬጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮች መለየትና ከሕግ አንፃር የሚያስከትሉትን ውጤት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሠረት ስንመለከተው ተጠሪ ከአመልካች ገንዘብ በብድር ሲወሰድ፡ ለብድሩ ዋስትና ይሆን ዘንድ የማይንቀሣቀሥ ንብረቱን መጋቢት 18 ቀን 1989 ዓ.ም በተደረገ የመያዣ ውል አስይዟል፡፡ አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 18 ቀን 1989 ዓ.ም የተዋዋሉት የመያዣ ውል መጋቢት 23 ቀን 1989 ዓ.ም በጊንቢ ከተማ አስተዳደር በኩል ተመዝግቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በኋላ አመልካች ለተጠሪ ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም መያዣውን በሰላሣ ቀን ውስጥ ሐራጅ አውጥቶ የሚሸጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 3 መሠረት ማስጠንቀቂያ ለተጠሪ የሰጠ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪ መስከረም 24 ቀን 1994 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ በማለት ያቀረበውን ክርክር ለማስረዳት በሕግ ተቀባይነትና ክብደት ያለው ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አረጋግጠዋል፡፡

አመልካች መጋቢት 23 ቀን 1989 ዓ.ም የተመዘገበው የመያዣ ውል እንዲታደስለት መስከረም 13 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የጊንቢ ከተማ አስተዳደር የጠያቀ መሆኑንና የጊንቢ ከተማ አስተዳደር የመያዣ ውሉን ምዝገባ መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም በማደስ የመዘገበ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

2. ከላይ የገለፅናቸውና ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ይዘን አመልካች በመያዣው ላይ የሚኖረውን መብት ለመወሰን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር ድንጋጌዎች ይዘትና መሠረታዊ ባህሪ፣ የአዋጅ ቁጥር 97/90 ድንጋጌዎች ይዘትና በመያዣው ላይ የሚያስከትሉትን ውጤት በማስመልከት ይህ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መመርመር ያስፈልጋል፡፡

የማይንቀሣቀሥ ንብረት የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አስር ዓመት ድረስ እንደሆነ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም የመያዣ ውሉ በሕጉ የተመለከተው የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የታደሰና በማይንቀሣቀሥ መዝገብ ውስጥ እንደተመዘገበ የተደረገ እንደሆነ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን እንደሚራዘም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/2/ የሚደነግግ ሲሆን፣ የመያዣ ውሉ አዲሱ ምዝገባ ከተከናወነበት ቀን ጀምሮ ወደፊት እስከ አስር ዓመት ውጤት የሚኖረው መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/3/ ደንግጓል፡፡

ከላይ ይዘታቸው በዝርዝር የተገለጹት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058 ድንጋጌዎች በጠቅላላውና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ በተለየ ሁኔታ፣ በባህሪው የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ አለመሆኑን፣ ድንጋጌው የመያዣ ውል ቀሪ የሚሆንበት ወይም በሕግ ውድቅ ስለሚሆንበት /Lapse of mortgage right/ የሚደነግግ እንደሆነ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44800 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይህም በመሆኑ ንብረቱን በመያዣነት የያዘው ባለገንዘብ በመያዣው ላይ ያለው መብት ቀሪ የሚሆነው፣ መያዣው ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ የተደነገገው የአስር ዓመት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በመያዣው ላይ ያለውን መብት መገልገል ካልጀመረ እንደሆነ በተጠቀሰው መዝገብ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

ይህም በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ በተደነገገው መሠረት ባንኮች በመያዣው ላይ ያለው መብታቸው ቀሪ የሚሆንባቸው በምን ሁኔታ ነው የሚለውን ነጥብ መመልከት የሚጠይቅ ነው፡፡ ባለገንዘቡ በማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ ያለው የመያዣ መብት በሕጉ የተደነገገው አስር ዓመት በማለፉ ምክንያት ውድቅ ሆኖበታል /ቀሪ ሁኗል/ ወይም /Lapse/ አድርጓል ተብሎ ሲወሰን የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ አስር ዓመት ከማለፉ በፊት በመያዣ መብቱ መገልገል ያልጀመረ እንደሆነ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 ባንክ ለሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብድር በመያዣ የያዘውን ንብረት፣ ብድሩ ያልተከፈለው መሆኑን የሰላሣ ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለመሸጥና የንብረቱን ባለሀብትነት ለገዥ ለማስተላለፍ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 3 ተደንግጓል። ስለዚህ ባንክ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በመብቱ መገልገል ጀምሯል ተብሎ ሊወሰድ እንደሚገባ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44800 በሰጠው ውሣኔ ግልፅ አድርጎታል።

ይህ የሰበር ችሎት ቁጥሩ ከላይ በተገለፀው መዝገብ ባንክ ማስጠንቀቂያ የሰጠው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ የተደነገገው አስር ዓመት ሣያልፍ ከሆነ፣ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ቤቱን ሳይሸጥ አስር ዓመት ያለፈ ቢሆንም እንኳን፣ የቤቱ ሽያጭ ሣይጠናቀቅ አስር ዓመቱ ማለፉ ብቻውን በመያዣው ላይ ያለውን መብት ቀሪ /Lapse/ እንደማያደርገው ትርጉም ሰጥቷል። ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ አስር ዓመት ከማለፉ በፊት ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 90/97 አንቀጽ 3 መሠረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት በመብቱ መገልገል መጀመሩ ተረጋግጧል። ይህ ከሆነ አመልካች በመብቱ በመገልገል ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ መያዣውን ሳይሸጥ አስራ ሁለት ዓመት ያለፈው ቢሆንም በመያዣው ላይ ያለው መብት ቀሪ እንደማይሆን /Lapse/ እንደማያደርግ ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 44800 ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም አስገዳጅ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/1/ የተደነገገውን የአስር ዓመት ጊዜ እንደ ይርጋ ድንጋጌ በመቁጠር አመልካች ማስጠንቀቂያ ከሰጠበት ግንቦት 18 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ አስር ዓመት ያለፈው ስለሆነ አመልካች በመያዣው ላይ ያለው መብት ይሰረዛል በማለት የሰጡት ውሣኔ ከላይ በተገለፀው መዝገብ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያልተከተለና በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 የተደነገገውን የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል።

ስለሆነም አመልካች በመያዣ መብቱ መገልገል በመጀመሩ፣ በመያዣው ያለው መብት ቀሪ /Lapse/ የማይሆን በመሆኑና አመልካች መያዣያውን ለማሳደስ ካስመዘገበበት መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አስር ዓመት የሚኖረው መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3058/3/ የተደነገገ በመሆኑ፣ የአመልካች በመያዣው ላይ ያለው መብት እንዲሰረዝ የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል።
2. አመልካች በመያዣ መብቱ መገልገል በመጀመሩ፣ በመያዣው ላይ ያለው መብት ቀሪ አይሆንም /Lapse/ አያደርግም በማለት ወስነናል።
3. አመልካች የመያዥያ ውሉ በጊንቢ ከተማ አስተዳደር መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም በድጋሚ ማስመዝገቡ ሕጋዊ ውጤት ያለው ነው በማለት ወስነናል።
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለራሣቸው ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል። መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 69797
ታህሣሥ 04 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
አዳነ ንጉሴ
መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሂላላ ሱሌማን - ከጠበቃ ወልደስላሴ ብርቱ ጋር ቀረቡ
ተጠሪ፡- ጎንደር ዩኒቨርሲቲ - ነ/ፈ አሸናፊ ልጃለም ቀረቡ
መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዳቦ አቅርቦት የተደረገውን የአስተዳደር ውል መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ሐምሌ 02 ቀን 2000 ዓ.ም. በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘት ሲታይም በመጋቢት ወር 2000 ዓ.ም. በወጣው የዳቦ ግዥ ውስን ጨረታ ለመሳተፍ የጨረታ ማስከበሪያ በC.P.O ብር 26,035.07 (ሃያ ስድስት ሺህ ሰላሳ አምስት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) በወጋገን ባንክ ጎንደር ቅርንጫፍ አስይዘው የዳቦ አቅርቦት ውል ማሸነፋቸውን፣ በውሉም ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ክብደቱ 125 ግራም ለሆነ አንድ ዳቦ በብር 0.80 ሂሳብ ለተጠሪ ሶስት ካምፓሶች ለቁርስ፣ ለምሳና ለእራት ለማቅረብ ስምምነት አድርገው በድምሩ 811,363 (ስምንት መቶ አስራ አንድ ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ሶስት) ዳቦ ማቅረባቸውን፣ በዚህ ሂደት ላይ እያሉም ተጠሪ ግንቦት 07 ቀን 2000 ዓ.ም. ላይ አዲስ የዳቦ ግዥ ውስን ጨረታ አውጥቶና አመልካች በጨረታው ላይ እንዳይሳተፉ በማድረግ ለሌላ ግለሰብ የዳቦ አቅርቦት ውሉን በመስጠት አዲሱ አቅራቢ ከግንቦት 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ አቅርቦቱን መጀመሩን፣ አመልካች እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ብር 122,534.40 (አንድ መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከአርባ ሳንቲም) ተጠሪ ከፍሏቸው የ658,195. ዳቦ ዋጋ የሆነውን ብር 526,556.00 (አምስት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር) ተጠሪ ያልከፈላቸውና እንዲከፍላቸው ቢጠይቃቸውም የመልካም ስራ አፈፃጸም ዋስትና መያዝ ከነበረበት መጠን በታች ነው በሚል ምክንያት ሊከፍላቸው ያልቻለ መሆኑን ዘርዝረው ዳቦ አቅርበው ያልተከፈላቸው ብር 526,556.00 እና ሕጋዊ ወለዱን፣ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 26,035.07 ከክርክሩ ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍላቸው በተፋጠነ ስርዓት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ለክሳቸውም የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካችም ለክሱ የመከላከያ ክርክር ለማቅረብ ይፈቅድለት ዘንድ በስርዓቱ መሰረት ጥያቄ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ተቀብሎ ተጠሪ የመካላከያ ክርክርና ማስረጃ እንዲያቀርብ የፈቀደለት ሲሆን ተጠሪ ባቀረበው ክርክር ከአመልካች ጋር ውሉ መደረጉን ሳይክድ የውሉ ጊዜ ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ሆኖ ተጠሪ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ዳቦውን ሊያቀርቡና የዳቦውን ዋጋ 10% የሆነው ብር 245,036.00 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ ከሰላሳ ስድስት ብር) ለመልካም ስራ አፈፃጸም ዋስትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስከበሪያ ሊያስይዙ የውል ግዴታ ገብተው የዳቦ ዱቄት ዋጋ ጨመረ በሚል ምክንያት አቅርቦቱን መቀጠል እንደማይችሉ ታውቆ የሰሩበት ገንዘብ ታስቦ እንዲሰጣቸው ለተጠሪ ፕሬዝዳንት በአድራሻ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. መጻፋቸውን፣ ለአመልካች ሥራ አፈፃጸም ዋስትና አመልካች ሊያስይዙ ይገባ የነበረው ብር 245,036.00 ሆኖ ያላስያዙና ቢያስይዙ ኑሮ በዩኒቨርሲቲው ላይ የደረሰውን ኪሳራ መተኪያ ሊሆን ይችል እንደነበርና ይህ ኪሳራውን ይተካል ባይባልም ውሉ ስለሚሸር የመልካም ስራ አፈፃጸም ተቀንሶ ሌላው የሰሩበት ገንዘብ ቢከፈላቸው ተቃውሞ የሌለው መሆኑ የተነገራቸው መሆኑን ዘርዝሮ ይኼው ተፈፅሞ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈል እንዲወሰንለት ገልፆ ተከራክሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ የተከሳሽ ክሳሽነት አቅርቧል፡፡ በዚህም ክሱ የአሁኗ አመልካች ለአርባ አንድ ቀናት ብቻ የዳቦ አቅርቦት ውሉን ፈፅመው አቅርቦቱ ለአፍታም ያህል ሊቋረጥ እንደማይገባው እየታወቀ በውሉ የገቡትን ቀሪውን 114 ቀናት ዳቦውን ላለማቅረብ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ/ም በጻፉት ደብዳቤ የአሁኗ አመልካች በማረጋገጣቸው ምክንያት ተጠሪ ሁለተኛ ጨረታ አውጥቶ ወ/ሮ ታደለች ጌታሁን የተባሉት ግለሰብ አንዱን ዳቦ በብር 1.31 ለማቅረብ ተጫርተው በማሸነፋቸው አመልካች አቀርባለሁ ካሉት ዋጋ በብር 0.51 ብልጫ እንዲያቀርቡ መደረጉን፣ በዚህም ምክንያት ተጠሪ ላይ ለአንድ መቶ አስራ አራት ቀሪ ቀናት የብር 0.51 ጉዳት በአንድ ዳቦ የደረሰበት ሁኖ በድምሩ ብር 1,148,846.40(አንድ ሚሊዩን አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ስድስት ብር ከአርባ ሳንቲም) ኪሳራ የደረሰበት መሆኑን ዝርዝሮ ይኼው ገንዘብ እንዲከፈለው ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ የተከሣሽ ክሣሽነት ክስ በሰጡት መልስም የውሉ ጊዜ ከ08/08/2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 19/09/2000 ዓ.ም. ድረስ እንጂ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ያለመሆኑንና ከ19/09/2000 ዓ.ም. በኋላ ዳቦ ያላቀረቡበት ምክንያት ዩኒቨርሲቲው በ07/09/2000 ጨረታ አውጥቶና አመልካች በጨረታው ላይ እንዳይሳተፉ በማድረግ ከ20/09/2000 ጀምሮ ለሌላ ሰው ዳቦ አቅርቦት ውሉን በመስጠቱ ሆኖ ኪሳራው የደረሰው ከአመልካች ጋር የነበረውን ውል እንዲቀጥል ተጠሪ ባለማስቻሉ ምክንያት በመሆኑ አመልካች የፈፀሙት ጥፋት ሳይኖር ለኪሳራው ኃላፊ የሚሆኑበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን፣ ተጠሪ በውሉ በገባው ግዴታ መሰረት አመልካች ለአቀረቡት ዳቦ ዋጋውን በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያትም በወቅቱ ከተከሰተው የዳቦ ዱቄት ዋጋ መናር ጋር ተዳምሮ አመልካች ግዴታቸውን እንዳይወጡ የራሱን አስተዋጽኦ ማድረጉን ዘርዝረው የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ጊዜው ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ መሆኑ መረጋገጡን፣ ለውሉ ያለመፈጸም ምክንያት የሆኑት የአሁኗ አመልካች መሆናቸውን፣ ለውሉ ያለመፈፀምም በቂና ሕጋዊ ምክንያት በአመልካች በኩል ያለመቅረቡንና ዩኒቨርሲቲው ከሌላ ሰው ጋር ውል ማድረጉን ያለበትን ኃላፊነትን ለመወጣት የፈፀመው ተግባር ነው ከሚባል በስተቀር ውል ማፍረሱን እንደማያሳይ ገልፆ አመልካችን ለውሉ መፍረስ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት መጠን በተመለከተም ብር 1,068,225.60 መሆኑና ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ አመልካች ዳቦ አቅርበው በተጠሪ ያልተከፈላቸው ገንዘብ ለጨረታው ማስከበሪያና ለመልካም ስራ አፈፃጸም የተያዘባቸው ገንዘብ ሲቀናነስ ብር 797,153.93 (ሰባት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከዘጠና ሶስት ሳንቲም) መሆኑን ለይቶ ይህንኑ ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ

ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሰኔ 08 ቀን 2003 ዓ.ም. በፃፉት አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም የስር ፍርድ ቤት የውሉን ጊዜ በተመለከተ ሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ/ም በቁጥር ጥበ/01/568/08/2000 የተጻፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ነው በማለት ድምዳሜ ላይ የደረሰው የደብዳቤውን አርዕስትና ይዘት ባግባቡ ሳይመለከትና የተዋዋይ ወገኖችን ሐሳብ ሳያገናዝብ መሆኑን፣ ለውሉ አለመፈፀም ምክንያቱ አመልካች ናቸው መባሉም የውሉን አንቀፅ 5.1 እና 6.2 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና ተጠሪ አመልካች ለአቀረቡት ዳቦ ክፍያውን በወቅቱ ያለመክፈሉን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑን፣በመንግስት ደረጃ እውቅና ያለው የዋጋ ግሽበት ስለመኖሩና የውሉን ሚዛን ስለማናወጡ ተረጋግጦ እያለ ይኼው ግምት ውስጥ ካለመግባቱም በላይ በውሉ አንቀጽ 8.2 እና 8.4 ድንጋጌዎች መሰረት ችግሩን ከተጠሪ ጋር በጋራ ለመፍታት አመልካች ጥያቄ አቅርበው እያለ ፈቃደኛ ያልሆነውና በውሉ ቃል መሰረት አመልካች ልፈፀም እያሉ ውሉ ሳይፈርስ በግንቦት 07 ቀን 2000 ዓ.ም. ጨረታ ያወጣው ተጠሪ መሆኑም ለውሉ መፍረስ ምክንያት የሆነውን ወገን በትክክል በመለየት ረገድ ስህተት መፈፀሙን እንደሚያመላክት፣ ውሉ ሲደረግ የዳቦ ዱቄት ዋጋ ለውጥ ይኖረዋል ተብሎ ያልተገመተ ሲሆን ውሉ የአስተዳደር ውል እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረገድ በተደነገጉት ድንጋጌዎች እና በጠቅላላ ውል ደንቦች የሚመራ በመሆኑ ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት የሆነውን ተግባር የፈፀመው ተጠሪ በመሆኑ ኪሳራ መክፈል የነበረባቸው አመልካች ሁነው እያለ መታለፉ ያላግባብ መሆኑንና የውሉ ማፍረሻ ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች በውሉ ተገልፀው እያለ በአግባቡ ሳይታዩ መታለፋቸውን፣ አመልካች በሕጉ መሰረት ተጠሪን ሳያስጠነቅቅ የውሉን መሻር መብት ሊሰራበት የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ ያለመኖሩንና የኪሳራው ልክ ሲሰላም በበታች ፍርድ ቤቶች ስህተት መፈፀሙን ገልፀው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበውን የክርክር ይዘት በአጭሩ ያስቀመጠ ሲሆን አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ከመስጠታቸውም በላይ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙን ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በቃል አከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልጉ አበይት ጭብጦች፡-

1. ውሉ ፈርሷል አልፈረሰም? ፈርሷል ከተባለስ ለውሉ መፍረስ ምክንያት የሆነው ማን ነው? እና
2. የኪሳራው ልክ ስንት መሆን አለበት? የሚሉት ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች ውሉ አልፈረሰም፣ ፈረሰ ከተባለም ምክንያቱ ተጠሪ ነው በማለት የሚከራከሩት የውሉ ጊዜ ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. እንጂ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ አይደለም፣ በትክክለኛው የውሉ ጊዜ የዳቦ አቅርቦት ግዴታዬን ተወጥቼአለሁ፣ የዳቦ ዱቄት ዋጋ በመጨመሩ ምክንያትም ተጠሪ ጋር ለመነጋገር ተደጋጋሚ ጥረት አድርጌ ተጠሪ ጥያቄዬን በውሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብ ሳያስተናግድና በሁለተኛው ጨረታም እንዳልሳተፍ ከልክሎኛል በሚሉት ምክንያቶች ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የውሉ ዘመን ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ሆኖ አመልካች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊያቀርቡ የተዋዋሉትን የዳቦ አቅርቦት የዳቦ ዱቄት ዋጋ ጨምሯል በሚል ምክንያት ከግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ/ም በኋላ ማቅረብ እንደማይፈልጉ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት በፃፉት ደብዳቤ በግልፅ ያሳወቁና ውሉንም ያፈረሱት አመልካች በመሆናቸው ለውሉ መፍረስ ምክንያት አመልካች ናቸው በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍሬ ነገርንና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ግን ውሉ ስለመኖሩ ሳይካድ በውሉ ጊዜ ላይ ግራ ቀኙ መካካዳቸውን ገልፆና ሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. በቁጥር ጥበ/01/586/2000 በተጻፈ ደብዳቤ አቅርቦቱ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ለአመልካች ተጠሪ ማሳወቁን፣ ሶስት እማኞች ባሉበት ይኼው ውል መገባቱን አረጋግጧል፡፡ ይህ የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተመሳሳይ ድምዳሜ የተያዘበት ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የደብዳቤውን ይዘት በተዛባ መንገድ መመዝገባቸውና ከውል አመሰራረት ደንቦች ጋር ያለማገናዘባቸውን መሰረት በማድረግ የሚያቀርቡት ክርክር የደብዳቤው ይዘት አመልካች በሚከራከሩት መልኩ ሆኖ ባለመገኘቱ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ይልቁንም ሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. የተደረገው ውል አንቀፅ 8.5 ውሉ የጨረታ ሰነዱ አካል ሆኖ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 እና 2005 መሰረት በሕግ ፊት የጸና ስለመሆኑ በግልፅ የሚያሳይ ሲሆን በጨረታ ሰነዱ ደግሞ የውሉ ጊዜ ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ስለመሆኑ የተጠቀሰ በመሆኑ አመልካች የውሉን ጊዜ እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በ08/08/2000 ዓ.ም. የተፈረመውን የውሉን ይዘት ባማባቡ ያገናዘበ አይደለም፡፡ አመልካች በግልጽ በተደረገው ጨረታ በሚሳተፉበት ጊዜ የውሉን ጊዜ በግልጽ አውቀው የነበረ ስለመሆኑ ከውሉ ይዘት የምንገነዘበው ከመሆኑም በላይ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ለዩኒቪርሲቲው በፃፉት ደብዳቤም ለሰባት ቀናት ብቻ ኣቅርቦቱን መቀጠል እንደሚችሉ፣ ከዚያ በኋላ መቀጠል እንደማይችሉ ያሳወቁ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ተዋዋይ ወገኖች በውሉ ጊዜም ሆነ በውሉ ወቅት ያደረጓቸውን ተግባራት መነሻ በማድረግ ስለውሉ ጊዜ የነበራቸውን ሐሳብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1734 ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይ የውሉ ጊዜ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የውሉን ጊዜ ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ ነው በማለት መወሰናቸው ከውሉ ሙሉ ይዘት፣ አመልካች ለተጠሪ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ከፃፉት ደብዳቤና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1732፣1734 እና ስለውል አቀራረብና አቀባበል የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘን አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ ለውሉ መፍረስ ምክንያት ማን ነው የሚለውን ጥያቄ ስንመለከት ደግሞ አመልካች እና ተጠሪ በመካካለቸው ከሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ የሚቆይ የዳቦ አቅርቦት ውል ማድረጋቸውና አመልካች አቅርቦቱን የቀጠሉት እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ከግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በኋላ አቅርቦቱን ያልቀጠሉት የዳቦ ዱቄት ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ይህንኑ ችግር ተጠሪ ከአመልካች ጋር ተወያይቶ ሊፈታ ባለመቻሉ ምክንያት መሆኑን ጠቅሰው ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩሉ የዳቦ ዱቄት ዋጋ መጨመር ለውሉ መፍረስ በምክንያትነት ሊጠቀስ እንደማይችልና አመልካችም አቅርቦቱን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለማቅረብ አውቀውና ወደው ግዴታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መግባታቸውን ገልፆ ለውሉ መፍረስ ምክንያት አመልካች ናቸው በማለት ተከራክሯል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም አመልካች ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. የጻፉት ደብዳቤ ውሉን መቀጠል እንደማይችሉ በግልጽ ለዩኒቨርሲቲው ያሳወቁበት ስለመሆኑ ያረጋገጡበት ሲሆን አመልካችም ቢሆኑ ይህንኑ ደብዳቤ ይዘቱ ሌላ ስለመሆኑ ሳይጠቅሱ ደብዳቤውን የጻፉበት ምክንያት ዩኒቨርሲቲው ችግሩን በጋራ ለመፍታት ዝግጁ ሁኖ ባለመገኘቱ ስለመሆኑ ገልጸው ተከራክረዋል፡፡ በእርግጥ በውሉ አንቀጽ 8 ስር ልዩ ልዩ የጋራ ሁኔታዎችን የሚገዙ ንዑስ ድንጋጌዎች የተካተቱ ሲሆን የውሉ መሻሻል በተዋዋይ ወገኖች የጋራ ስምምነት ሊሆን እንደሚችል በንኡስ ቁጥር 4 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የድንጋጌው ሙሉ ይዘት ሲታይ ይህ ውል ማሻሻያ ይደረግ ጥያቄ ቢቀርብ የሁለቱ ወገኖች ስምምነት ተጠይቆ ፈቃደኛነታቸው ከታወቀ ሊሻሻል ይችላል በሚል የተቀመጠ ሲሆን ድንጋጌው ፈቃደኝነት ባለው መልኩ የተቀመጠ በመሆኑ በተዋዋይ ወገኖች የሚቀርብ የውል ይሻሻል ጥያቄ ሁል ጊዜ ተቀባይነት እንደሚኖረው ወይም ይህ ጥያቄ ቀርቦ ባለበት ሁኔታ ሌላኛው ተዋዋይ ወገን በውሉ መሰረት እንዲፈፀም ቢፈልግ ይህንኑ ከማድረግ የማይከለክለው ወይም ውሉን ለማፍረስ በቅድመ ሁኔታነት መፈፀም ያለበት ጉዳይ ስለመሆኑ አስገዳጅነት ባለው መልኩ የሚያሳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ውሉን ያቋረጠው አመልካች የዳቦ አቅርቦቱን የሚቀጥሉበትን የጊዜ ገደብ በግልጽ አስቀምጠው ደብዳቤ በመጻፋቸው ምክንያት በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው አመልካች ያስቀመጡት የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት ውስን ጨረታ አውጥቶ ሌላ ግለሰብ ዳቦ አቅርቦቱን እንዲቀጥል ማድረጉ ከዩኒቨርሲቲው ኃላፊነትና ግዴታ አንፃር ሲታይ የሚነቀፍበት ምክንያት ካለመኖሩም በላይ በውሉ አንቀፅ 8.2 ስር ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ጉዳዩ በአገሪቱ የፍትሃብሔር ሕግ እንደሚፈታ ስለመሆኑ የተመለከተ በመሆኑ በዚሁ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ክርክር የዳቦ ዱቄት ዋጋ መናር የሚለውና በመንግስት የታወቀው የዋጋ ግሽበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሚያቀርቡት ለተማሪዎች ቁርስ፣ ምሳ እና እራት የሚሆን ዳቦ እንደመሆኑ መጠን የአቅርቦቱ ባህርይ ሲታይ ለአፍታ ጊዜ ያህል ሊቋረጥ የማይችል በመሆኑ በመንግስት የታወቀ የዋጋ ግሽበት ቢኖር እንኳ አቅርቦቱን ቀጥለው ኪሳራውን በፍ/ሕ/ቁጥር 3183(2) እና 3188(1) ድንጋጌዎች አግባብ ተጠሪ በከፊል እንዲችል የሚደረግበት ሕጋዊ መፍትሔ የነበረ በመሆኑ የዋጋ ግሽበቱ አመልካች አቅርቦቱን ወዲያውኑና ሙሉ በሙሉ እንዲያቋርጡ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ አመልካች ለአቀረቡት ዳቦ ተጠሪ ዋጋውን በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አልከፈለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክርም በአመልካች የዳቦ አቅርቦት ስራ ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ የሚኖረው መሆኑ ቢታመንም አመልካች ውሉን ለማቋረጥ ለተጠሪ ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት ደብዳቤ ይህንኑ ምክንያት በመጥቀስ ውሉን ለማቋረጥ ስለመገደዳቸው ያልፃፉ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ ምክንያት ውሉን ያፈረሰው ተጠሪ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡አመልካች በተለያዩ ጊዜያት ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ጋር ለመወያየት ጥረት ሲያደርጉ የነበሩ ስለመሆኑ ጠቅሰው የሚያቀርቡት ክርክር ሲታይም ግንቦት 05 ቀን 2000 ዓ.ም. በግልፅ ከፃፉት ደብዳቤ ይዘትና ከአቅርቦቱ ልዩ ባህርይ ሲታይ ለውሉ መፈረስ ምክንያቱ ተጠሪ ነው ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ውሉ የፈረሰና ለመፍረሱም ምክንያት አመልካች ናቸው ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ውል አንዱን ዳቦ በብር 0.80 ለማቅረብ ተዋውለው እስከ ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. 811,363 ዳቦ ያቀረቡ መሆኑና ከግንቦት 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጳጉሜ 05 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ አቅርቦቱ በሌላ ግለሰብ እንዲቀጥል በተደረገው ውል ግን የአንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳቦ ዋጋ ብር 1.31 ሁኖ ተጠሪ ለአንድ ዳቦ ብር 0.51 ብልጫ ለሁለተኛ ጨረታ አሸናፊ እንዲከፍል የተገደደ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ በክርክሩ ሂደት አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያለመከናወኑና ለሌላ ሰው ጨረታው ተላልፎ ሲሰጥም ተጠሪ ለዋጋ ጭማሪ መዳረጉ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ የጉዳት ካሳ ጥያቄን መሰረት ያደረገውም ስራው በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ሙሉ በሙሉ ያለመተግበሩንና ድጋሚ ጨረታ ያስከተለውን ተጨማሪ ወጪ ነው፡፡ ግራ ቀኙ ባደረጉት ውል ውስጥ የውል ማስከበሪያ ዋስትና የጠቅላላ ዋጋውን 10% ብር 245,036.00 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ ሰላሳ ስድስት ብር) አመልካች ለተጠሪ ማስያዝ እንደአለባቸው በአመልካች ግዴታነት በአንቀፅ 5.7 ስር በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን ከዚህ የገንዘብ መጠን ውጪ ለውሉ መዘግዬት ተብሎ የተጠቀሰው ለእንያንዳዱ ቀን የውሉን ዋጋ ብር 1/1000ኛ ታስቦ እንዲከፈል ውል ተቀባይ ግዴታ ያለው መሆኑን የሚሳይ የውሉ ድንጋጌ በውሉ አንቀፅ 5.10 ስር ተቀምጧል፡፡

የግራ ቀኙ ውል ከላይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎችን ከመያዙ ውጪ አንዱ ወገን በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሙሉ ወይም በከፊል ግዴታውን ካልተወጣ ሌላው ወገን የጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑንና ሊጠየቅ የሚገባውን የጉዳት መጠን ምን ያህል እንደሆነ አይገልጽም፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ የመልካም ሥራ አፈጻጸም /ቦንድ/ ሰነድ መሆኑንና ይህም ከተጠሪ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመካስ ተብሎ የተገባ ግዴታ መሆኑን ተጠሪ ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ የሚከራከርበት ነጥብ ነው፡፡ የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ ወይም የመልካም ስራ አፈጻጸም ቦንድ የውል አፈፃፀምን ለማረጋገጥ የሚሰጥ የዋስትና ሰነድ መሆኑን፣ ይህም በባለገንዘብ እና በባለ እዳ መካከል የተደረገን ውል አፈፃፀም ለመጠበቅ የሚገባ ግዴታ መሆኑን ከሰነዱ አይነተኛ ዓላማ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የመልካም ስራ አፈጻጸም ቦንድ መሰረታዊ አላማ ስራው በውሉ መሰረት ስለመሰራቱ ለማረጋገጥ የሚገባ ግዴታ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ሚያዚያ 08 ቀን 2000 ዓ.ም. የተደረገው ውል በአንቀፅ 5.7 ስር ይህንኑ የሚያስገነዝብ ሲሆን አመልካች በወቅቱ ብር 245,036.00 ሙሉ በሙሉ ባያስይዙም ብር 26,035.07 አስይዘው ጨረታውን ማሸነፋቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህ ሲታይ የመልካም ስራ አፈፃፀም ቦንድ ስራው በስኬታማ ሁኔታ ባይጠናቀቅ በተጠሪ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማካካስ ጭምር ታስቦ የተገባ ግዴታ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህም አመልካችና ተጠሪ ስለጉዳት ካሳ ቀደም ብለው በውላቸው የገለፁት መጠን መኖሩን የሚያስረዳ ነው፡፡ ግራ ቀኙ ባደረጉት ውል አመልካች እንደ ውሉ ሊፈጽሙ ባለመቻላቸው የተነሣ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት መጠኑን አስቀድመው ተምነው በውላቸው ላይ አስቀምጠዋል፡፡ ይህም ዓይነት ስምምነት በህግ የተፈቀደ እና ለተፈፃሚነቱ ለማናቸውም ጉድለት ነፃ ስለመሆኑ ያከራከረ ባለመሆኑ ይህም ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731 እና 1889 እንደተደነገገው እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማካካስ የጉዳት ኪሣራ ገንዘብ መጠኑ በብር 245,036.00 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ ሰላሳ ስድስት ብር) ብቻ እንዲወሰን በማድረግ ባደረጉት ስምምነት መሠረት በቃላቸው ሊታሰሩ እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ስለሆነም የአሁን አመልካች ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት በመሆናቸውና በዚህም የተነሣ በአሁን ተጠሪ ላይ ጉዳት መድረሱ ቢታወቅም ለውሉ አለመፈፀም ኃላፊ የሆኑት የአሁን አመልካች በውሉ ከተመለከተው የጉዳት ኪሣራ ገንዘብ ጣሪያ በላይ ተጠሪን እንዲክሱ ሊገደዱ የሚቻልበት የህግ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ለተጠሪ ሊከፍል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚገባው የኪሣራ መጠን ላይ የተሰጠው የውሣኔ ክፍል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው የጉዳት ኪሳራ መጠን ከብር 245,036.00 ሊበልጥ አይችልም ከተባለ አመልካች ለተጠሪ ዳቦ አቅርበው ያልተከፈላቸው ብር 526,556.00 (አምስት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር) መኖሩ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠና ተጠሪም ያልካደው ጉዳይ ነው፡፡አመልካች ይኼው ገንዘብ እንዲከፈላቸው በስር ፍርድ ቤትም ክስ የመሰረቱ በመሆኑ ተጠሪ ይህንኑ ገንዘብ የሚያስቀሩበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ በመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ማስያዝ ከሚገባቸው ገንዘብ ብር 245,036.00 ውስጥ ብር 26,035.07 ብር ያስያዙ በመሆኑ ማስያዝ ከሚገባቸው ገንዘብ ውስጥ ብር 219,000.00 ያላስያዙ በመሆኑ ይሔው ገንዘብ ከብር 526,556.00 ሊቀነስ የሚገባው ሆኖ ስለአገኘን ገንዘቡ ተቀንሶ የሚመጣው ውጤት ብር 307,555.07 (ሶስት መቶ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) ለአመልካች ተጠሪ ሊከፍል የሚገባው ገንዘብ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻሻል የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመ/ቁጥር 18461 ታህሳስ 25 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 64967 ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም. የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት በመሆናቸውና በዚህም የተነሣ በአሁን ተጠሪ ላይ ጉዳት መድረሱ ቢታወቅም ለውሉ አለመፈፀም ኃላፊ የሆኑት የአሁን አመልካች በውሉ ከተመለከተው የጉዳት ኪሣራ ገንዘብ ጣሪያ በላይ ተጠሪን እንዲክሱ ሊገደዱ የሚቻልበት የህግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡ አመልካች ብር 245,036.00 ሊያገኙ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ ዳቦ አቅርበው ካልተከፈላቸው ገንዘብ ውስጥ ብር 307,555.07 (ሶስት መቶ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) ተጠሪ ሊከፍላቸው ይገባል ብለናል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣውን ማናቸውንም ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 72017

ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ህይወት

አመልካች፡- አቶ ጐታ ኤጀታ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ መሠደሲር ረዲ - ጠበቃ አቶ መኮንን ኪዳን ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 ድንጋጌ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሌላ ጉዳይ የፍርድ ባለእዳ ስለነበሩ ንብረታቸው የሆነውና በአዲስ አበባ አዲስ አዲስ ክ/ከተማ ቀበሌ 13/15 ክልል የሚገኘው ዲዲስ መድኃኒት መደብር ተሸጦ ለእዳቸው ክፍያ እንዲውል በሐራጅ እንዲሸጥ ገዥዎች ተጋብዘዋል፡፡

በዚህም መሠረት የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ንብረት በብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) ለመግዛት በሐራጁ ሽያጭ ተወዳድረው አሸናፊ መሆናቸው ተለይቷል፡፡

ይሁን እንጂ ይህንኑ የግዥ ዋጋ ክፍያ ሊፈጽሙ ባለመቻላቸው ሁለተኛ የሐራጅ ሽያጭ ተከናውኖ አቶ አብዱ መሐመድ ይህንኑ ንብረት በብር1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) ለመግዛት የጨረታው አሸናፊ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ እኒህ ሁለተኛ ገዥም እንደ አሸናፊነታቸው ያሸነፉበትን የንብረቱን ዋጋ ከፍለው ሊረከቡ ባለመቻላቸው ለሶስተኛ ጊዜ የሐራጅ ሽያጭ ሲደረግ ንብረቱ በብር 265,000.00 (ሁለት መቶ ስልሣ አምስት ሺህ ብር) ተሸጧል፡፡ በዚህም የሐራጅ ሽያጭ ዋጋ የንብረቱ ሽያጭ ተከናውኗል፡፡

ከዚህ ከኃላ የአሁን አመልካች በአንደኛ እና ሁለተኛ የሐራጅ ሽያጭ ጊዜ በሐራጅ ሽያጩ ተወዳድረው ንብረቱን በብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) ለመግዛት እንደቅደም ተከተሉ አሸናፊነታቸው ከታወቀ በኃላ በማፈግፈጋቸው ንብረቱ በሶስተኛ ሐራጅ ሽያጭ ጊዜ ባሸቆለቆለ ዋጋ በብር 265,000.00 (ሁለት መቶ ስልሣ አምስት ሺህ ብር) እንዲሸጥ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 እንደተደነገገው በሐራጅ ሽያጩ ጊዜ የተከሰተውን የዋጋ ልዩነት 735,000 (ሰባት መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ብር) ሁለቱም በአንድነትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በነጠላ ሊከፍሉ ሲገባ በሥር በበየደረጃው ያሉት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች በሁለተኛው ሐራጅ ጊዜ አሸናፊነቱ የታወቀውን ብቻ ኃላፊ አድርገው በመጀመሪያው ሐራጅ ጊዜ ገዥነቱ የታወቀውን ከኃላፊነት ነፃ ማድረጋቸው ይህንኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ድንጋጌ አፈፃፀምን በአግባቡ የተከተለ አይደለም፡፡ ስለሆነም ሊታረም ይገባል በማለት ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ መነሻ ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ የጽሁፍ ክርክራቸውን አጠናቀው ጉዳዩ ለምርመራ የቀረበ ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነውም በአፈፃፀም እንዲሸጥ በሐራጅ ማስታወቂያ መሠረት በሁለት ተከታታይ የሐራጅ ሽያጭ ጊዜ ሁለት ተወዳዳሪዎች ተመሣሣይ የሐራጅ መግዣ ዋጋ ካቀረቡ በኃላ ሁለቱም ይህንኑ ያሸነፉበትን ዋጋ ሊከፍሉ ባለመቻላቸው ሶስተኛ ሐራጅ ተደርጎ ንብረቱ እነርሱ ካቀረቡት ባነሰ የመግዣ ዋጋ ከተሸጠ ይህንኑ የሽያጭ ዋጋ ልዩነቱን መክፈል ያለባቸው ሁለቱ ናቸው ወይስ በሁለተኛው ሐራጅ ጊዜ ተወዳድሮ ከመጀመሪያው የሐራጅ ጨረታ አሸናፊ ከሆነው ጋር ተመሣሣይ የመግዣ ዋጋ ያቀረበው ብቻ ነው? ለሚለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 ድንጋጌ ቀጥተኛ ምላሽ የሚሰጥ አይደለም፡፡

ያም ሆኖ የዚህ ድንጋጌ ግብ እና ዓላማ በሐራጅ ሽያጭ ጊዜ ተወዳድሮ አሸናፊ መሆኑ ከተረጋገጠ በኃላ እንደአሸናፊነቱ የሽያጭ ዋጋውን ባለመክፈሉ የተነሣ ለሌላ ለሁለተኛ ሐራጅ መንስኤ ከሆነና በዚህም ሌላ (ሁለተኛ) ሐራጅ ጊዜ ንብረቱ ከመጀመሪያው የሐራጅ ሽያጭ ዋጋ አንሶ ከተገኘ ይህን የዋጋ ልዩነት በካሣ መልክ የፍርድ ባለእዳው አዲያገኝ በማድረግ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ በመጀመሪያው የሐራጅ ሽያጭ ጊዜ ለንብረቱ ብር 1,000,000.00 /አንድ ሚሊዮን ብር/ የመግዣ ዋጋ አቅርቦ አሸናፊነቱ ከተለየ በኃላ ዋጋውን አለመክፈሉ እና ለሁለተኛ ሐራጅ ሽያጭ መንስኤ መሆኑ ቢረጋገጥም፤ ሁለተኛው የሐራጅ ሽያጭ ተደርጎ በዚህ ሁለተኛ የሐራጅ ሽያጭ አሸናፊ ሆኖ የተገኘው ገዥ ያቀረበው የመግዣ ዋጋ የአሁን ተጠሪ አቅርቦት ከነበረው የብር1,000,000.00 /አንድ ሚሊዮን ብር/ የግዥ ዋጋ ጋር ተመሣሣይ እንጂ ያነሰ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም የተነሣ የአሁን ተጠሪ ገዥነቱ ከታወቀ በኃላ የመግዣ ዋጋውን አለማቅረቡ በፍርድ ባለእዳው ላይ ያስከተለው ጉዳት የለም፡፡
ከዚህም አንፃር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 429 የተመለከተው ድንጋጌ ቀጥተኛ ምላሽ የሚሰጥ ባይሆንም ክፍተቱን ለመሙላት የአሁን ተጠሪ በመጀመሪያው ሐራጅ ጊዜ ገዥነቱን ካረጋገጠ በኋላ የግዥ ዋጋውን ባለመክፈሉ እና ለሁለተኛ ሐራጅ ሽያጭ ምክንያት መሆኑ ቢታወቅም ይህ መሆኑ በእራሱ በፍርድ ባለእዳው ላይ ያስከተለው ጉዳት እስከሌለ ድረስ በሁለተኛው ሐራጅ ሽያጭ ጊዜ አሸናፊነቱ ተለይቶ ካፈገፈገውና ለሶስተኛ ሐራጅ ሽያጭ ምክንያት ሆነው ንብረቱ ባነሠ ዋጋ እንዲሸጥ ቀጥተኛ ምክንያት ከሆነው እና ለልዩነቱ ብር 735,000.00 /ሰባት መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ብር/ ኃላፊ ከሆነው ከአቶ አብዱ መሐመድ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት የለበትም በሚል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 69945 ሐምሌ 08 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በተለያዩ የሐራጅ ሽያጮች ጊዜ ለተከሰተው የዋጋ ልዩነት የአሁን ተጠሪ ለአሁን አመልካች ለመክፈል የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት የለበትም መባሉ በአግባብ ነው፡፡ ብለናል፡፡
3. በዚህ የሰበር መዝገብ በሠበር መ/ቁ. 72017 ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተጠሪ ቤት ላይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ትእዛዙ ለተላፊላቸው ክፍሎች ይፃፍ፡፡
4. የዚህ ሰበር ጉዳይ ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79555

ታህሳስ 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ቤተልሄም ፋርማሲ ቲዩካል ኃ/የተ/የግል/ማህበር አልቀረበም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ነገረ ፈጅ ምህረት ኃ/የሱስ ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል በድሀ ደንብ መሠረት የሚቀርብበትን አግባብነት የሚመለከት ነው፡፡

የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ለማቅርበው የ47,705.069 ብር (የአርባ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ አምስት ሺህ ስድሳ ዘጠኝ ብር) ክስ ሊከፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ ብር 429,900.69 (አራት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር ከ69%) የሆነውን ገንዘብ ለመክፈል የገንዘብ አቅም ስለሌለኝ ክሱን በድሀ ደንብ እንዳቀርብ እንዲፈቀድ ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ የተደረገው ስለድህነቴ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ሳይሰሙ ስለሆነ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ዳኝነቱ በሕግ አግባብ የተሰጠ ስለሆነ በሰበር ሊታረም የሚችል የሕግ ስህተት የለም የሚለውን ክርክሩን አቅርቧል፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ክስ ለማቅረብ የፈለገ ወገን ከፍርዱ ለሚያገኘው የዳኝነት አገልግሎት መክፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል የገንዘብ አቅም የሌለው ከሆነ ክሱን ያለዳኝነት ገንዘብ በደሀ ደንብ መሠረት የማቅረብ መብት እንዳለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 215 ተደንግጓል፡፡

ክሱን የሚያቀርበው ወገን ድሀ በመሆኑ ምክንያት የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል ክሱን አቅርቦ እንዲያስማ ሊፈቅድለት ይገባል? የሚለው ጉዳይ ሊለይ የሚችልበት ዝርዝር አፈፃፀም ደንቡም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 467 እና ተከታዩ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እነዚህ ደንቦች ተፈፃሚነታቸው ክስ ለማቅረብ በፈለገ የተፈጥሮ ሰውም ሆነ በሕግ ሰውነት ያላቸው ወገኖችም ጭምር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ድሀ ነኝ፤ መብቴን ለማስከበር ያለኝ ፍላጐቴ በዳኝነት ገንዘብ እንቅፋት ምክንያት ሊሰናከል አይገባም፡፡ ስለሆነም በድሀ ደንብ መሠረት ክሱን በነፃ እንዳሰማ ይፈቀድልኝ የሚል ማናቸውም ከሳሽ ድሀ መሆኑን ሊያመለክት የሚችል የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ ይህም ከሳሹ የሚገኝበት የገንዘብ አቋም ከተረጋገጠ በኋላ ለክሱ ሊከፈል የሚገባው የዳኝነት ገንዘብ መጠን ከሳሹ ከሚገኝበት የገንዘብ አቋም አኳያ ተገናዝቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 467 መሠረት ድሀ የመሆኑና ያለመሆኑ ጉዳይ ሊለይ ይገባል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሕግ ሰውነት የተሰጠው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት ድሀ መሆኑንና አለመሆኑን በመለየት በመነሻነት ሊረዳ የሚችለውን ከሳሹ የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም በቅድሚያ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ይህ ዓይነት ከሳሽም የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም ለመረዳት በምን የገንዘብ አቋም ደረጃ ላይ ይገኛል የሚለውን ለመወሰን የሚገባው አግባብነት ባለው የንግድ ሕግ መሠረት ካልሆነ በስተቀር በሰው ማስረጃ መለየት የሚቻል አይደለም፡፡ ስለሆነም ከሳሹ የሚገኝበትን ደረጃ ለመለየት ለጉዳዩ ተቀባይነት ያለው የማስረጃ ዓይነት በንግድ ሕጉ ስለገንዘብ አቋሙ/ደረጃው ለማረጋገጥ ያስችላል ተብሎ የሚቀርበው የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡ የሰው ማስረጃዎች ስለጉዳዩ የሚሰጡት የምስክርነት ቃል በሕግ ዓይን ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካችም ስለምገኝበት የገንዘብ አቋም ሊያረጋግጥ ይችላል በሚል የአዲት ማረጋገጫ እንዳቀረበ ገልፆ ቢከራከርም ይህ ማረጋገጫ ክሱ ከመቅረቡ 8 እና 7 ዓመት በፊት የነበረውን ሁኔታ የሚጠቅሱ በመሆኑ አሁን ያለበትን ደረጃ ሊያመለክት የሚችል አይደለም፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 እንደተመለከተው የአንድ ሰው ፍትሕ የማግኘት መብቱ ሊከበር የሚችለው ይህንኑ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ለማስፈፀም ሲባል የተቀመጡትን ዝርዝር የክስ አቀራረብ ደንብም ጭምር ተሟልቶ ከተገኘ እንደሆነ ስለጉዳዩ የተዘረጋው የሕግ ማዕቀፍ አስረጂ ነው፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች ከከሳሹ ማንነት አንፃር በማየት አመልካች ድሀ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ከመለየት አንፃር የሰጡት ዳኝነት የማስረጃ አቀባበል ሥርዓትን የተከተለ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

በፌዴራል ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 77257 ሚያዝያ 26 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79465

ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ - ነ/ፊጅ ሠለሞን ረታ ቀረበ

ተጠሪ፡- 1. አቶ አገኘው ገረመው - የቀረበ የለም

2. ኪንግናም ቦንጋ ሚዛን የመንገድ ስራ ድርጅት - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 ድንጋጌን አፈጻጸም የሚመለከት ሲሆን ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው 1ኛ ተጠሪ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ በከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመሠረተው ክስ ነው፡፡ በክሱም በቁጥር 3-05118 ደሕ በሚል መለያ በራሳቸው ንብረትነት የምትታወቀውንና የህዝብ ማመላለሻ የሆነችን መኪናቸውን ንብረትነቱ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የሆነውና በቁጥር UR 666 የሚታወቀው ሩሮ ማሽን በውሽውሽ ከተማ ከሚገኘው የ1ኛ ተጠሪ መኖሪያ ቤት አከባቢ በቆመችበት ሁኔታ ገጭቶ ጉዳት ያደረባት መሆኑን ጠቅሰውና ለተለያዩ ውጪዎች መዳረጋቸውን ጠቅሰው የወጪውን አይነትና መጠን ዘርዝረው በድምሩ ብር 93733.00 (ዘጠና ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ 2ኛ ተጠሪም ጉዳት አደረሰ የተባለው መኪና የራሱ መሆኑን አምኖ ተሽከርካሪው በአሁኑ አመልካች የመድን ሽፋን የተገባለት መሆኑን ጠቅሶ በክሱ ውስጥ እንዲገባ ጠይቆ የአሁኑ አመልካችም ወደ ክሱ እንዲገባ ከተደረገ በኋላ በሰጠው መልስ ከአሁኑ አመልካች ጋር ያደረገው የመድን ውል ጉዳዩን የማይሸፍነው፣መድኑ የተገባው የ2ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ በሶስተኛ ወገን ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ሳይሆን ከመንገድ ኮንስትራክሽን ስራ ጋር በተያያዘ ለሚደርስ ጉዳት መሆኑን ጠቅሶ በጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ የሚከራከርበት አግባብ የሌለ መኑን ገልፆ ለጉዳዩ ተጠያቂነት የለብኝም በማለት የተከራከረ ሲሆን በአማራጭም የጉዳት ክሳ መጠኑ የተጋነነ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ 2ኛውን ተጠሪ በባለንብረትነቱ በ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ ጉዳት አድርሷል በሚል ምክንያት፣አመልካችን ደግሞ ለጉዳዩ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከመድን ውሉ ይዘት መረዳቱን ገልጾ ለጉዳቱ ሁለቱንም ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን የጉዳት ካሳ መጠኑንም በርትዕ ወስኖ በድምሩ ብር 41,100.00 (አርባ አንድ ሺህ አንድ መቶ) በማድረግ ይህንኑ የገንዘብ መጠን ለ1ኛ ተጠሪ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡የአሁኑ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎች አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ያለው የመድን ሽፋን ውል ጉዳዩን የማይሸፍን ሁኖ እያለ ጉዳዩን ይሸፍናል ተብሎ አመልካች ካሳውን እንዲከፍል መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ ጉዳዩን በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተገባው የመድን ሽፋን ውል የሚገዛው መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው አመልካች ወደ ክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 መሰረት እንዲገባ ሲደረግ በሰጠው መልስ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው ውል ጉዳዩን የማይሸፈን መሆኑን ገልጾ በተከራከረበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በ1ኛ ተጠሪ መዝገብ ላይ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

በ1ኛ ተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ጉዳት አደረሠ የተባለው መኪና የ2ኛ ተጠሪ የነበረ ሲሆን ይህ መኪና በአሁኑ አመልካች የመድን ሽፋን የነበረው መሆኑ አልተካደም፡፡አከራከሪው ነጥብ የመድን ሽፋን አድማሱ እስከምን ድረስና በምን ጉዳዮች ነው? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገው ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ሂደት ሊያነሳ የሚችለው ክርክር ምን ድረስ ነው የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ አስመልክቶ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 23692 እና 78314 የሰጠውና በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(1) መሰረት በየትኛም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በተጠቃሾቹ መዛግብት የክርክሩ ተካፋይ ሦስተኛ ወገን የሚያቀርበው ክርክር ሁለት ፈርጅ ሊይዝ የሚችል መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይኸውም “1ኛው ከተከሳሽ ጋር ሆኖ ድርሻ ክፍያ ወይም ስለተከሳሽ ሆኖ የካሣ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተቀብሎ በተከሳሽ እግር በመተካት ተከሳሽ ለከሳሽ ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን፤ ኃላፊነት አለበት እንኳ ቢባል ሊከፈል በሚገባው የካሣ መጠን ላይ ከከሳሽ ጋር ንጽጽር ማድረግ፤ መሟገት የሚችልበት ክርክር ሲሆን ሌላው እና ሁለተኛው ደግሞ ድርሻ ወይም ካሣ ለመክፈል ለተከሳሽ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መከራከር የሚችልበት መንገድ ነው፡፡” ስለሆነም የድንጋጌው ይዘት ጣልቃገብ ሦስተኛ ወገን ተከሳሽ በክርክሩ ከገባ በኋላ መሟገት የሚችለው ከተከሳሽ ጋር እንጂ ከከሳሽ ጋር ለመከራከር የሚያስችለው መብት የለውም የሚለው ድምዳሜ የሕግ መሠረት የለውም የሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡የሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ 23692 እና 78314 ላይ ይህንን ትርጉም ለመስጠት መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ እና የሙግት አመራር ውጤታማነት እንዲሁም የድንጋጌ ቁጥር 43(1) እና 76 እንዲሁም የመሠረታዊ ሕጉ ድንጋጌዎች ውስጥ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1896፣ 1897፣ 1908 እና 1909 አፈጻጸም እንዲሁም በንግድ ሕግ ቁጥር 687,688 እና 683 ድንጋጌዎች በክርክር አመራር ረገድ የሚፈፀሙበትን ሁኔታ እና ግብ መነሻ በማድረግ መሆኑ በፍርዱ ሀተታ ተገልጿል፡፡ ለማጠቃለል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 43 አስፈላጊነትም ተከታታይ ክስ ሳይኖር በአንድነት እንዲታይ በማድረግ የኃላፊነት እና መጠኑን እንዲሁም ከፋዩን ወገን በመለየት የመጨረሻ እልባት መስጠት ማስቻል እንደመሆኑ በተለይ ካሣ (indemnity) የመክፈል ግዴታ ያለበት አመልካችን መሰል የመድን ድርጅቶች ከከሳሹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና ተከሳሹ ጋር የሚኖራቸውን አጠቃላይ ክርክር ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ በውሳኔው ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 መሰረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ የሚጠራ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ወገን ከመነሻውም ከተከሳሹ ጋር የሕግ ወይም የውል ግንኙነት የለኝም በማለት ክርክር ከአቀረበ የክርክሩ ተሳታፊ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡እንዲህ አይነት ክርክር እልባት ማግኘት ያለበት በተለየ ክስ እና የክርክር መዝገብ እንጂ ከሳሽ ባቀረበው መዝገብ ሊሆን አይገባም፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 ድንጋጌ አላማም እንዲህ አይነት ክርክሮችን ሁሉ በአንድ አይነት መዝገብ አጠቃልሎ ለመወሰን ነው ተብሎ አይታሰብም፡፡ይልቁንም ጣልቃ ገብ ከመነሻውም ክዶ በተከራከረበት ጉዳይ የተከሳሽንና የጣልቃ ገብን ክርክርና ማሰረጃ ሰምቶ ውሳኔ መስጠት ከሳሽ ያቀረበው ክስ ያላግባብ ጊዜና ወጪን እንዲጨምር የማድረግ ውጤት የሚኖረው ይሆናል፡፡ስለሆነም አመልካች ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጋር ያለውን የውል ግኙነት የካደ ሁኖ እያለ ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጎ በውጤቱም አመልካች ለካሳው ኃላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ ጋር ባልተጣጠመ መልኩ ሁኖ ስለአገኘን በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሥነ ስርዓት ሕግ ግድፈት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በካፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 06440 ጥቅምት 27 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር09515 መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ/ም ባጸናው ውሳኔ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የመድን ውል ጉዳዩን ይሸፍናል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የመድን ውል መኖር ያለመኖሩ ከመነሻው አከራካሪ የሆነ በመሆኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 መሰረት የክርክሩ ተሳታፊ መደረግ አልነበረበትም ብለናል፡፡
3. 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ካሳውን ይክፈል የተባለው የውሳኔ ክፍል በዚህ ውሳኔ አልተነካም፣እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ ወደፊት የሚያቀርበው ሕጋዊ ጥያቄ ካለ ይህ ውሳኔ ቀሪ አያደርገውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመልስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>የሀሣብ ልዩነት</u>

እኔ በሶስተኛ ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ ቁጥር 43 ላይ በሰጠው ትርጉም የማልስማማ በመሆኑ በሀሣብ ተለይቻለሁ፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43 የተከሣሽና የሶስተኛ ወገን ተከራካሪውን ክርክሮች በማጣራትና በማስረጃ በማረጋገጥ ፍርድ ቤቶች ከሣሹ ከተከሣሽ የሚያገኘውን መብትና ጥቅም እንዲሁ ክዶ ቢከራከርም ከሶስተኛ ወገን ተከራካሪው የሚያገኘውን መብትና ጥቅም ያለመሆኑን ወይም አለመሆኑን ተከሣሽ ከሶስተኛ ወገን ተከራካሪው የሚያገኘው ጥቅም ካለ መጠኑን ለይተው ከመወሰን የሚገድባቸው አይደለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን የክርክሩ ተሣታፊ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ሃሣብ ያለኝ በመሆኑ በሀሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 83701

ጥር 27 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- ወ/ሮ ህንደያ እንድሪስ ወኪል አብዲ ዓሊ - ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርምራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የወጪና ኪሳራ አወሳሰን ሥርዓትን አስመልክቶ በተነሳ ክርክር ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በቀዳሚነት የወጭና ኪሳራ ዝርዝር ጉዳይ በየትኛው ዓይነት መዝገብ ቀርቦ ሊታይ ይገባል? የሚለውን አስመልክቶ ያቀረበውን ክርክር አግባብነት ተመልክተናል፡፡

አመልካች ይህ ብር 10,000.00 እንድንከፍል የተወሰነብን የወጭና ኪሳራ ጉዳይ ሊወሰን የሚገባው በአፈፃፀም መዝገብ ሆኖ ሳለ በተዘጋውና ዋናው ጉዳይ የታየበት መዝገብ ተንቀሳቅሶ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ የአፈፃፀም መዝገቡ ደግሞ በበላይ ፍ/ቤት ታግዷል፡፡ ስለሆነም ይህ የወጭና ኪሳራ ጉዳይ የሚታይበት ሥርዓት ሳይኖር የተወሰነብን አወሳሰን ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይሁን እንጂ በአፈፃፀም ጉዳይ ቀርቦ ሊታይ የሚገባው ማናቸውም ጉዳይ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 ተደንግጓል፡፡

ለአፈፃፀም ምክንያት የሆነው ፍርድ ከሚያካትታቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ፍርዱን ለማስወሰን ሲባል በክርክር ምክንያት የወጣው የወጭና ኪሳራ ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 183 በግልፅ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም ወጭና ኪሳራን ግን እንደሚከፍል በዋናው ጉዳይ ተለይቶ ከተወሰነ በኋላ ምን ያህል መክፈል እንዳለበት ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 463 መሰረት የወጭና ኪሳራ ዝርዝር ዋናው ፍርድ ባረፈበት መዝገብ ላይ ቀርቦ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ስለቀረበው የወጭና ኪሣራ አስፈላጊነት፤ ስለመጠኑ እና በእርግጥም ወጭና ኪሳራ ስለመውጣቱ የበኩሉን ክርክር ካቀረበ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 464 እንደተመለከተው የወጭና ኪሳራ ልኩ ይወሰናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንግዲህ የወጭና ኪሳራ አወሳሰን ሥርዓት ይህ ከላይ የተመለከተው በመሆኑ የአሁን አመልካች የወጭና ኪሳራ ጉዳይ ሊወሰን የሚገባው በአፈፃፀም መዝገብ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር ህጋዊ መሰረት የሌለው፣ የፍርድ አፈፃፀምን ጉዳይ መነሻ ሀሳብ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የስር ፍ/ቤቱ በወጭና ኪሳራ መልክ የቀረበውን እና ለጠበቃ ተከፈለ የተባለውን የጥብቅና አበል በሚመለከት በማስረጃነት የቀረበው የጥብቅና ውል ከጊዜ ቅደም ተከተል አንፃርም ሆነ ከጠበቃው ማንነት አንፃር በአስረጅነቱ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ከገለፀ በኋላ በሌላ በኩል ጠበቃ ተስፋሁን የተባለ ሌላ ጠበቃ በዋናው ጉዳይ ጊዜ የነበረ መሆኑን መታመኑን እና የጥብቅና አበል መጠን ክርክር በተደረገበት የገንዘብ መጠን አስራት መነሻ ተደርጎ የቀረበውን ባለመከተል ጉዳዩን ለመከታተል ወጣ ሊባል የሚችለው የጥብቅና አበል መጠን ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ነው ሲል ስለመጠኑም የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 በፍ/ቤቱ የተሰጠውን ፍቅድ ሥልጣን ከጉዳዩ ጋር በማዛመድ ተመልክቶ የወሰነው በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት የሚያስችል ሆኖ ባለመግኘታችን ምክንያት የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሐረሪ ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 02260 መስከረም 09 ቀን 2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የጥብቅና አበልን አስመልክቶ የሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት ፀንቷል፡፡
2. ቀደም ሲል በመ/ቁ 07208 የተጀመረው የአፈፃፀም ክስ ታግዶ እንዲቆይ በሚል በዚህ የሰበር መዝገብ ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም. የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ የሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ምክንያት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 74890

ጥር 30 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሚስጢር ሰለሞን በእራሱ ቀረበ

መልስ ሰጪ፡- 1ኛ. አቶ ፍቃዱ ካሣሁን ቀረቡ

2ኛ. አቶ አሊ ካሣሁን አልቀረቡም

3ኛ. አቶ መ·ላለም ካሣሁን አልቀረቡም

4ኛ. አቶ በላይ ካሳሁን ቀረቡ

5ኛ. አቶ አባተ ካሳሁን አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ክርክርን ለማስረዳት ሲባል የቀረበን ማስረጃ ህጋዊነት አስመልክቶ ክርክር በቀረበ ጊዜ ይኸው ክርክር ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ክርክሩ በቀረበበት ፍ/ቤት ወይስ በሌላ የተለየ ፍ/ቤት የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ከግራ ቀኙ ጉዳይ አንፃር ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ክስ ሲሆን የክሱም ይዘት ከአባቱ በውርስ ላገኘ የሚገባውን በአባቱ በአቶ ሰለሞን ካሳሁን ስም ተመዝግበው የሚታወቁትን በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 06/02 በቁጥር 020 የሚታወቀውን ቤት እና የሰሌዳ ቁጥሩ 01-4142 አ.አ የሆነውን መኪና ይዘው ስለሚገኙ እነዚህ ንብረቶች ላይ መብት የሌላቸው ስለሆነ እንዲያስረክቡን ቢጠየቁ አባቱ መጋቢት 10 ቀን 1986 ዓ.ም አድርጎታል ባሉት የቁም ስጦታ ለእናታቸው ያስተላለፉና እነሱም የእናታቸው ወራሽ ስለሆኑ በንብረቱ ላይ መብት እንደላቸው ገልፀው ለማስረከብ እምቢተኛ ሆነዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው የቁም ኑዛዜ ስጦታ በአባቱ ያልተፈረመ እና በአደራረግም ረገድ በህግ ተቀባይነት የለውም የሚሉበትን ምክንያት በመጥቀስ በንብረቱ ላይ መብት አያሰጥም፡፡ ስለሆነም የዚሁኑ ንብረቶች ካስገኙት የኪራይ ጥቅም ጋር እንዲያስረክቡ ይወስንልኝ የሚል ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም በዚህ ክስ መነሻ የአሁኑ ተጠሪዎች ያላቸውን ክርክር እንዲያቀርቡ ካደረገና የመልሳቸውንም ዝርዝር ይዘት ሳይመለከት መልሳቸውን በጥቅል ከጠቀሰ በኃላ በፍ/ብ/መ/ቁ 34398 በሆነው መዝገብ ሐምሌ 07 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ፡- ተደረገ የተባለውን የቁም ስጦታ ህጋዊ ነው? አይደለም? ሊፈርስ ይገባል አይገባም? የሚለውን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያለው ሌላ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሳሽ ሰነዱ በህግ ፊት ተቀባይነት የለውም ከሚሉት በቀር ስልጣን ባለው ፍ/ቤት አቅርበው ፈራሽ ነው በሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተወሰነበትን ውሳኔ አላቀረቡም በዚህም ግራ ቀኙ በሚከራከሩበት ፍ/ቤት ይኸው የቁም ስጦታ እንዲፈርስ ይደረግልን በማለት አልጠየቁም ስለሆነም በዚህ ሰነድ አማካኝነት ለሶስተኛ ወገን የተላለፈን ንብረት የአውራሽ አባቱ ስለሆነ ለእኔ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክስ ተገቢነትም ሆነ የህግ መሠረት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ይህም ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 በተመለከተው መሠረት በፍሬ ነገርም ሆነ በህግ ረገድ ግድፈት ያለበት ባለመሆኑ ሰርዘለሁ በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዳኝነት በመስጠቱ የተነሳ የአሁን አመልካች ለዚህ የሰበር ምክንያት የሆነውን፡

የሰበር አቤቱታ አቅረበዋል፡፡ በዚህ ሰበር ደረጃም ክርክር ባስነሳው “የቁም ስጦታ ላይ ክርክር ቀርቦበት እያለ ከሳሽ አላስፈረሰቺውም በሚል የአሁን አመልካች ክስ ውድቅ መድረጉ አግባብ ነው? አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ ግራ ቀኙ ያላቸውን ክርክር በዕሁፍ አቀርበዋል፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ይዘት እንደተረዳነው የአሁን አመልካች ክሱን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤትና መኪና ግምት መነሻው በማድረግ ክርክሩ በያዘው የገንዘብ መጠን ላይ የተወሰነን የስልጣን ዓይነት መሰረት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከሳሽ የክስ አቀራረብ ሥርዓት ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 14(1) አንፃር ሲታይ በእርግጥ ክሱ የቀረበው ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ባለው ፍ/ቤት በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 16 ፣ 9 ፣231(1)(ለ) አንፃር ሲታይ ከስልጣን አንፃር ሥርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ሲሆን፣ በዚህ ረገድም ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱን አልነቀፈውም፤ የአሁን ተጠሪዎችም ክርክር አላነሱበትም፡፡

ከላይ በተገለፀው አኳኋን አንድን ጉዳይ ተቀብሎ ለማየትና ለመወሰን የስረ-ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት የቀረበን ክርክር ለማስረዳት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 የቀረበን የሰነድ ማስረጃ ህጋዊነትን አስመልክቶ የሚቀርብን ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 246 ፣ 247 ፣ 248 እንደተደነገገው አከራካሪ ነጥብ ያስረዳ መሆኑ ታውቆ ክርክሩ በሚሰማበት የክርክር ደረጃ (at the trail stage) በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር እና ለክርክሩ አግባብነት ያለውን ህግ ተፈፃሚ በማድረግ በዚያው ክሱ በቀረበለት ፍ/ቤት የሚወሰን እንጂ ክርክርን በማስረዳት የቀረበን ማስረጃ ብቻ በመነጠል የዚህን ያለአግባብ የተነጠለውን የማስረጃ ህጋዊነት በሚመለከት በሌላ ፍ/ቤት ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ የሚያስችል ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡

ግራ ቀኙ በየፊናቸው ያቀረቡት ክርክር ተመልክቶ ለመወሰን ይኸው የቁም ስጦታ ህጋዊነት (validity) ከማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት አንፃር አይቶ እና ለይቶ በመወሰን ላይ የተመረኮዘ እንደመሆኑ መጠን የአሁን አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ በቀረቡት ክስ ውስጥ ይኸው የቁም ሥጦታ ሰነድ እንዲፈርስ ይወሰንልን በማለት የተለየ ዳኝነት እንደጠየቁ የሚያስገድድ የክርክር አቀራረብ ሥርዓትም የለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት አከራካሪ ሆኖ የተገኘውን የቁም ኑዛዜ ሰነድ ህጋዊነት አስመልክቶ የአሁን አመልካች ለዚህ የሰበር ጉዳይ ምክንያት በሆነው ክስ ላይ ማቅረብ አይችሉም፤ ሊያቀርቡ የሚችሉት እራሱን በቻለ የዳኝነት ጥያቄ በሌላ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ሊሆን ይገባል በሚል የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራልየመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 34398 በቀን 07/11/2003 ዓ.ም. የሰጠው ብይን፤ እና ይህ ብይን በአግባቡ የተሰጠ ነው በሚል ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/ቁ 115381 ህዳር 18 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ክርክር ያስነሳው የቁም ስጦታ ሰነድ ህጋዊ መሆንና አለመሆኑ ክሱ በቀረበለት ፍ/ቤት የሙግት ደረጃውን ጠብቆ ከግራ ቀኙ ክርክርና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር ተገናዝቦ ሊወሰን የሚገባ ስለሆነ በዚሁ መሰረት የዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት ጉዳዩን ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. በዚህ የሰበር ደረጃ የቀረበውን ክርክር ለመከታተል ግራ ቀኙ ያወጡት ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 80723

ጥር 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር ነገረ ፈጅ ብርሃኑ ሚልካሳ ቀረበ

ተጠሪዎች፡-1. ዋቅቶሉ አብደሳ ክርክሩ በዚህ ሰበር ችሎት ተቋርጧል

2. የጊምቢ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነገረ ፈጅ አቶ አዲሱ ደሳለኝ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ የተቋረጠ ነው በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት በሙግት ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መነሻ በማድረግ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር በማዛመድ በአግባቡ ታይቶ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለይቶ ለመወሰን ሲባል የቀረበ ነው፡፡

ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በዚህ የሰበር መዝገብ 1ኛ ተጠሪ በሚል የተሰየመው በአቶ ዋቅቶሌ አብደላ በብድር የወሰደውን ገንዘብ እንደውሉ መልሶ ለመክፈል የተሳነውና ያልቻለ በመሆኑ ቀሪ የብድር ገንዘብ እስከ መጋቢት 13/2003 የታሰበ ወለድና የወለድ ቅጣት ብር 100,240.74 /አንድ መቶ ሺህ ሁለት መቶ አርባ ብር ከ74/100/ በአጠቃላይ ብር 146,994.44 /አንድ መቶ አርባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ብር ከ74/100/ እንዲሁም ይኸው ዕዳ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ 14% ወለድ ጋር ይክፈለን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ተበዳሪው በብድር ለወለደው ገንዘብ አመላለስ ዋስትና ይሆን ዘንድ በዚሁ ተበዳሪ ስም በካርታ ቁጥር 033/00/88 የተመዘገበውንና በግምቢ ከተማ ቀበሌ 03 ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 667 የሆነውን መኖሪያ ቤት የግምቢ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከዕዳና እገዳ ነጻ መሆኑን በማረጋገጥ እና ለዚሁ ብድር የእኛ መያዣ መሆኑን መዝግቦ በማረጋገጡ ይህንኑ መያዣ ይዘን የብድር ገንዘቡን ለተበዳሪው ሰጥተናል፡፡ ሆኖም ይኸው ቤት በተበዳሪው ባለቤት በወ/ሮ ደሼ ተረፈ ስም በግምቢ ማዘጋጃ ቤት አማካኝነት ሌላ ካርታ ቁጥሩ 502/89 የሆነ ተዘጋጅቶ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለሰጠው ብድር መያዣ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት የልማት ባንኩ በሰጠው ብድር ምክንያት ይህንኑ ቤት የተረከበው መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ ስለሆነም ማዘጋጃ ቤቱ በፈፀመው ጥፋት ምክንያት ጉዳት እንዲደርስብን ያደረገ ስለሆነ ለዕዳው ተጠያቂ በመሆኑ ከዋናው ተበዳሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡

በዚህ ክስ መነሻ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው ዋናው ተበዳሪ አሁን በ1ኛ ተራ ቁጥር በተጠሪነት የተጠቀሰው ተከራካሪ ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ 10 ዓመት ካለፈው በኋላ ክሱ የቀረበ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1845 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ሲከራከር የአሁን 2ኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተከሳሽነቱ በሰጠው መልስ ላይ ባንኩ በእኛ ላይ ክስ ለማቀረብ አይችልም ንብረቱን መውሰድ ይቻላል በማለት በፍሬ ነገሩ ረገድ ከመከራከሩ በቀር እንደተከሰሰ የይርጋ ክርክርን ጠቅሶ ያቀረበው ክርክር እንዳልነበረ የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሣኔ ላይ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሁለቱም ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 እና 3058 መሰረት በይርጋ ውድቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡
በዚህ ውሣኔ መነሻ የአሁን አመልካች ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደማይገባ ገልፆ ከታች ወደ ላይ በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነትን ያላገኘ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረም ይገባል በማለትና ምክንያቱን በመዘርዘር ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ጉዳዩ ግራ ቀኙ ባሉበት በሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚገባ መሆኑ ተጠቅሶ መጥሪያ ለ1ኛው ተጠሪ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ የተሰጠው ቢሆንም ይህንኑ የሰበር ሰሚ ችሎቱን መጥሪያ በእራሱ ቸልተኝነት ወጭ አድርጎ ያለመውሰዱና ይህም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70/መ/ አንጻር ታይቶ ጥቅምት 28 ቀን 2005ዓ.ም በዋለው ችሎት በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው የሰበረ ክርክር ተሰርዞ ቀሪ ነው በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ዳኝነት አግባብነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡
በሌላ በኩል አመልካች የአሁኑን ሁለተኛ ተጠሪ አስመልክቶ ይኸው 2ኛ ተጠሪ ይርጋን በሚመለከት በስር የከፍተኛ ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ጊዜ በማንሳት ያልተከራከረበት ስለሆነ ክርክር ባልቀረበበት ጉዳይ በዚሁ ተከራካሪ ወገን ላይ ያቀረብነው ክስ በይርጋ ውድቅ ነው መባሉ አግባብ አይደለም በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ የመከራከሪያ ነጥብነቱ ሲያቀርብ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰጠው መልስ ስለይርጋ ጉዳይ 1ኛ ተከሣሽ የነበረው በማንሳት የተከራከረበት ስለሆነ እኛም እንድናነሳ አይጠበቅብንም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም በስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ከሳሽ የነበረው የአሁን አመልካች በሁለቱም ወገኖች ላይ በመሰረተው ክስ ሁለቱም ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት አለባቸው በሚል ሁለቱንም የከሰሳቸው ስለሆነ 1ኛው ተከሳሽ የነበረው ያነሳው የይርጋ ጊዜ ለሁለተኛ ተከሳሽም የሚጠቅም ይሆናል፡፡ ስለሆነም የብድር ውሉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ መብቱን ለማስጠበቅ እንቅስቃሴ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ 10 ዓመት ያለፈው ስለሆነ በብድር ምክንያት ንብረት በመያዥነት ከተመዘገበና ይኸው የመያዣ ጉዳይ ውጤት የሚኖረው ለ10 ዓመት ብቻ በመሆኑ ይህ የ10 ዓመት ጊዜ ከመሙላቱ በፊት የመያዣ ውሉ እንዲታደስ ካልተደረገ በቀር ውጤት የሚያስከትለው ለ10 ዓመት ብቻ ስለሆነ እንዲሁም ማስጠንቀቂያ ሰጠሁ የሚለው በዚሁ 10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሆኖ ስላለተገኘ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በሚል በስር ፍ/ቤት መወሰኑ አግባብ ነው በማለት ውሣኔውን አጽንቶ ወስኗል፡፡
ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውም ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሣኔ ላይ የአሁን አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም በየደረጃው ያሉት ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውስጥ ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጽሑፍ ካቀረቡት ክርክር ጋር በማገናዘብ ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡
እንደተመለከትነውም የአሁን 2ኛ ተጠሪ በአንደኛ ተጠሪነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከተሰየመው ጋር ተጣምሮ በተከሰሰ ጊዜ የይርጋ ክርክርን በማንሳት ያልተከራከረ ለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሣኔ የተረጋገጠ የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይኸው ተጠሪ ይርጋን ጠቅሶ ክርክር አለማቅረቡ ቢታወቅም የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት በሚል ከ1ኛው ተጠሪ ጋር ተጣምሮ የተከሰሰ በመሆኑ 1ኛው ተጠሪ ባነሳው የይርጋ ክርክር ተጠቃሚ መሆኑ አይቀርም የሚለውን ምክንያት በመጥቀስ ነው ይህንኑ ተከሳሽም አስመልክቶ የቀረበው ክስ በ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ቀሪ ነው የሚለውን ውሣኔ ሊሰጥ የቻለው፡፡

ይሁን እንጂ በተለያዩ የመሰረታዊ ህጐች ክፍል ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ወገኖች ለገንዘብ ጠያቂው ወይም ከሳሽ በመሆን ለሚሰየመው ወገን የአንድነትና የነጠላ ግዴታ አለባቸው በሚል የተቀመጡት የህግ ድንጋጌዎች መብትና ግዴታን በማቋቋም ረገድ ምክንያታቸውና መነሻ ሀሳባቸው ሁልጊዜም ተመሳሳይ መሆናቸው ታይቶ አይደለም የአንድነትና የነጠላው ኃላፊነት ከተለያዩ የህግ ክፍል እና ከተለያዩ ምክንያት ሊመነጭ ይችላልና፡፡
በዚህ በተያዘው ጉዳይ የአንደኛ ተጠሪ ኃላፊ ነው በሚል የቀረበው ክስ ከውል ህግ የመነጨ ሁለተኛው ተጠሪ ደግሞ ስለ ጉዳዩ ከአንደኛው ተጠሪ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት በሚል የቀረበበት ክስ ከሚጠበቅበት የስራ ግዴታ አንጻር የፈፀመው ድርጊት ጥፋት ነው በሚል ውል ሳይኖር በሚደረግ ኃላፊነት ህግ በሚገዛው ክፍል እንደሆነ ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

የሁለቱም ዓይነት የኃላፊነት ምንጭ ከተለያዩ የህግ ክፍል የሚነሳ እንደመሆኑ እንደቅደም ተከተሉ የይርጋ ክርክር በተነሣ ጊዜ የይርጋ ዘመናቸው ጉዳዩን እንደሚሸፍነው የህግ ክፍሉ በተቀመጠው የይርጋ ዘመን መሰረት እየታዩ የሚወሰን በመሆኑ አንዱ ያነሳው የይርጋ ክርክር ለሌላውም ይጠቅመዋል ብሎ ለመተርጎም የሚቻል አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 36 እንደተመለከተው የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ያለባቸውን ወገኖች አጣምሮ መክሰስ እንደሚቻል መደንገጉም ሁሉቱንም ወገኖች ለየብቻ ከመክሰስ ይልቅ በአንድ መዝገብ አጣምሮ መክሰሱ በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጭ ጉዳዮችን ለመቋጨት ያስችላል በሚል እንጂ አንዱ ተከሳሽ የሚያቀርበው ክርክር ያለቅድመ ሁኔታ ለሌላውም ተጣምሮ ለተከሰሰው ተከሳሽ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑ ታይቶ አይደለም፡፡
ስለሆነም በዚህ ጉዳይ 1ኛው ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያነሳው የይርጋ ክርክር በዚሁ አቅራቢ ላይ ብቻ የሚወሰን እንጂ የአሁን 2ኛ ተጠሪም እንዳቀረበው አድርጎ ለመቁጠርና ለመውሰድ የሚያስችል ህግ ባለመኖሩ 2ኛ ተጠሪ የይርጋ ክርክርን አስመልክቶ ክርክር አቅርቧል ማለት አይቻልም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244 እንደተመለከተው የይርጋ ክርክር መቅረብ በሚገባው ጊዜ ካልቀረበ እንዳተተው ክርክር ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚገባው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 244/3/ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1852 የተደነገገ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች የተሳሳተ የትርጉም መነሻ በመየዝ 1ኛው ተጠሪ ያቀረበው የይርጋ ጊዜ ለአሁን 2ኛ ተጠሪም የሚጠቅም ነው በማለት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 127608 በቀን 13/07/04ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 78660 በቀን 16/09/2003ዓ.ም የሰጠው ብይን ሁሉ ተሽሯል፡፡
2. በአሁን ሁለተኛ ተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በይርጋ ሊታገድ ይገባል በሚል እንደ ስርአቱ ክርክር ያልቀረበበት በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም ብለናል፡፡
3. በይርጋ ቀሪ ነው በሚል የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የአሁን አመልካች ከአሁን 2ኛ ተጠሪ ከግምቢ ማዘጋጃ ቤት ጋር ያቀረበው ክርክር እና ማስረጃ ታይቶ ተገቢው ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሰረት ጉዳዩን ወደ ምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
4. የዚህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡
   ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 84353

ጥር 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን አ/ማህበር ሂሣብ አጣሪ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነገረ ፈጆች አዲስ ቦጋለ እና ላዕከማሪያም ሊቁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወጋገን ባንክ አ/ማህበር ነገረ ፈጅ ገቢሳ ተሬሳ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አበዳሪ ወጋገን ባንክ ለጥቁር ዓብይ ኮንስትራክሽን ማህበር የሰጠው ብድር ባለመመለሱ ምክንያት ለብድር አመላለሱ ሲባል በመያዣር የያዘውን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት በሐራጅ ሲሸጥ ይህንም የሀራጅ ሽያጭ ሊፈርስ ይገባል በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበው ክርክር በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በዚህ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ የመሰረቱት ክስ ባጭሩ፡ የፈረሰውን ጥቁር ዓባይ አ/ማህበር አመልካች በሂሣብ አጣሪነቱ ተረክቦ በማጣራት ላይ እያለ አበዳሪ ወጋገን ባንክ አ/ማህበር በህግ በተሰጠኝ ስልጣን በሐራጅ የመሸጥ መብት አለኝ በማለት የባለዕዳውን ንብረት በሐራጅ እሸጣለሁ በማለቱና ይህም በማጣራቱ ስራ ላይ ችግር ስላስከተለ የተጀመረው በሐራጅ የመሸጥ እንቅስቃሴ እንዲቆም ይደረግልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጠው የመከላከያ መልስ በጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን አ/ማህበር እና በተጠሪ ወጋገን ባንክ መካከል በተፈረመው የብድር ውል መሰረት ተበዳሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ በውሉ መሰረት ስላልከፈለ ለብድሩ አከፋፈል በመያዣር የያዘውን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/92 በተሰጠን ስልጣን መሰረት በሐራጅ የመሸጥ ስልጣን ስላለው በህግ አግባብ በተቋቋመ የብድር ሰነድ ውል መነሻ ለብድር አመላለስ የተያዘን ንብረት የሐራጅ አሻሻጥን ምክንያት በማድረግ ፍ/ቤቱ ጣልቃ ገብቶ የማየት ስልጣን የለውም፡፡ ይህንንም በሚመለከት የፌደራል ሰበር ሰሚው ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር መ/ቁ 70824 በሆነው ጉዳዩን ፍ/ቤት ተቀብሎ የመወሰን ስልጣን የለውም በሚል ትርጉምም የተሰጠበት ስለሆነ መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል፡፡ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በቅድሚያ ከሳሽ ክስ ያቀረበበትን ጉዳይ ይህ ፍ/ቤት ተቀብሎ ለማየትና ለመወሰን የሚያስችል የዳኝነት ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጭብጥ ይዞ ይህንኑ ነጥብ ከሀጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቶ የተጠየቀው ዳኝነት በወጋገን ባንክ አ/ማህበር የተጀመረ የሐራጅ የመሸጥ እንቅስቃሴ እንዲቆም ትዕዛዝ እንዲሰጥ ነው፡፡ ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 90/97 አንቀጽ 3 እና 4 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 216/92 እንደተሻሻለው ባንኮች ለሰጡት ብድር አከፋፈል በመያዣነት በዋስትና የያዙትን ንብረት የብድር ዕዳው እንዲከፈለው በተወሰነው ጊዜ ሳይከፈል ከቀረ ከ30 ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይህንኑ በመያዣ የተያዘውን ንብረት ያለማንም ጣልቃ ገብነት በሐራጅ የመሸጥና የባለቤትነት መብት ለገዥው የማዛወር ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ባንኩ በእነዚህ ህጐች መሰረት ንብረቱን በሐራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በአሻሻጡ ሂደት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 394-449 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ባለመከተል ያደረሰው ጉዳት ካለ ለደረሰው ጉዳት ኪሣራ ከመጠየቅ በቀር የሐራጅ ሽያጭ በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲቆም ክስ የሚቀርብበት መብት እንደሌለና ፍ/ቤትም ተቀብሎ የማየት ስልጣን እንደሌለው በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 70824 የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ በዚህ አካኋን ተተርጉሟል፡፡ ስለሆነም በባንኩ የተጀመረ የሐራጅ ሽያጭ እንቅስቃሴ እንዲቆም የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ፍ/ቤቱ የማየትና የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ስለሌለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 244/2//ሀ/ እና 244/2/ መሰረት መዝገቡ ተዘግቷል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚህ ብይን ላይ የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ጉዳዩ በይግባኝ መልስ ሰጭን ያስቀርባል ወይስ አያስቀርብም? የሚለውን ነጥብ አስመልክቶ ዳኝነት ከመስጠቱ በፊት የአሁን አመልካች የዕግድ ትዕዛዝ አሰጥቶ ስለነበረ የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ተረድቶ በህግ በተሰጠን ስልጣን መሰረት የሐራጅ ሽያጭ ተከናውኖ የተሸጠው ንብረት ስመ ሀብትነቱ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር አማካኝነት ወደ ገዥው ተዛውሯል፡፡ ካርታና ኘላንም ገዥው ወስዷል፡፡ የቀረው በዚህ ፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ምክንያት የንብረቱ ርክክብ ብቻ ስለሆነ የሐራጅ ሽያጭ እንቅስቃሴያቸው ይቁም በሚል የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ይነሳልን የሚል አቤቱታ በማቅረቡ የተነሣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ የዕግድ ትዕዛዝ ይነሳ አይነሳ በሚለው ነጥብ ላይ ከክርክር በኋላ ዋናውን ጉዳይ ተመልክቶ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ብይን በአገባቡ ስለሆነ የአሁን ተጠሪ የሆነውን መልስ ሰጭን የሚያስቀርብ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሰረት ትዕዛዝ ሰጥቶ የዕግድ ትዕዛዙም እንዲነሳ አድርጓል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ዳኝነት በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በተመሳሳይ ጉዳይ በተባለው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 70824 ትርጉም የሰጠው የካቲት 27 ቀን 2004ዓ.ም ሲሆን ንብረቱ በሐራጅ የተሸጠው ደግሞ የካቲት 22 ቀን 2004ዓ.ም ስለሆነ የሰበር ሰሚው ችሎት ከሽያጩ በኋላ የሰጠው ትርጉም ወደ ኋላ ተመልሶ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም

በአዋጅ ቁጥር 25/84 መሰረት ከፈረሰው ድርጅት ገንዘብ የሚጠየቅ ባለመያዣ ገንዘብ ጠያቂ ወገን የሆነ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ ከሌላው በተለየ ሁኔታ ክፍያ እንደሚፈፀምለት ተገልፆ እያለ በመያዣ የተያዘው ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት የተሸጠ ነው የሚለውን በመያዝ ብቻ መወሰኑ አግባብነት የለውም ስለዚህ ማህበሩ በኪሣራ የፈረሰ በመሆኑ ማህበሩ ከፈረሰ ደግሞ ንብረት ገንዘብ አለን የሚሉ ወገኖች ከአዋጅ ቁጥር 25/84 አንፃር ፍ/ቤቶች አይተው የመወሰን ስልጣን እያላቸው ድርጅቱ ከመፍረሱ በፊት በወጋገን ባንክ በመያዣነት ንብረቱ ተይዟል በማለት በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ በሰጠው ትርጉም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚሉትን ምክንያቶች በመጥቀስ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ዳኝነት እንዲሻርለት መጠየቁን የሚያስረዳ ነው።

የአሁን ተጠሪም ለዚሁ የሰበር አቤቱታ በሰጡት መልስ ባጭሩ በግራ ቀኞችን መካከል ክርክሩ መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም ከመጀመሩ በፊት የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 70824 ላይ ትርጉም የሰጠ ስለሆነ ትርጉሙ በእኛ ጉዳይ ላይም ተፈፃሚነት አለው። የንብረት የሐራጅ ሽያጭ ሥርዓት በሚገባ ተከናውኖና ተጠናቆ ለገዥው አዋርዲንግ ሌተር እስከሰጠንበት ድረስ አ/ማህበሩ የፈረሰ ስለመሆኑ አላሳወቀም። በአዋጅ ቁጥር 25/84ም ቢሆን አመልካች የኪሣራ ጉዳይ ሥራ ሲያከናውን፤ የመክሰር ውሣኔን ለማሰጠት እና ለማሣወቅ አግባብነት ያላቸው የፍ/ብሔር እና የንግድ ሕጐች ተፈፃሚነት እንዳላቸው በአዋጁ አንቀጽ 4 ተመልክቷል። እንዲሁም የመክሰር ሥርዓት በድርጅቱ ላይም ተፈፃሚ እንደሚሆን በአንቀጽ 40/1/ ላይ ተመልክቷል። በዚህ ጉዳይ የአሁን አመልካች የአ/ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ በተገኘበት ንብረቱ ከተሸጠ በኋላ አክሲዮን ማህበሩ ፈርሷል በማለት ክስ ከማቅረቡ በቀር በህጉ መሰረት ስለመፍረሱ አላሳወቁም በመሆኑም የሐራጅ ሽያጭ ሥርዓትን አሟልቶ በአዋጅ 97/90 እና 216/92 መሠረት በሕግ በተሰጠው ሥልጣን የሐራጁ ሽያጭ ማስፈፀሙ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አያመለክትም በማለት የተከራከረበት ነው። የአሁን አመልካችም በሰጠው የመልስ መልስ ላይ የአ/ማህበሩ ሥራ አስኪያጁ ድርጅቱ መፍረሱን የሚገልፅ ደብዳቤ ጽፏል። የማጣራት ሥራው እንዳለቀ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ሁሉ ቅድሚያ በመስጠት እንደምንከፍለው የአረጋገጥን ስለሆነ የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል የሚለውንና በቅሬታው ላይ የገለፀውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት የሥር ፍ/ቤት ዳኝነቶች እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ በፍ/ቤት ሊታይ የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ አለ ወይስ የለም? የሚለው በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል።
ከክርክሩ መገንዘብ እንደተቻለው የጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ከአሁን ተጠሪ ላይ ገንዘብ በብድር መውሰዱን ይህን የብድር ገንዘብ በወሰደበት ጊዜ ለብድሩ ገንዘብ አመላለስ ዋስትና ይሆን ዘንድ በቀድሞ አጠራር በወረዳ 21 ቀበሌ 08 በአዲሱ አጠራር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የቤት ቁጥር 555 እና በባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ቁጥር ጂ አይ ኤስ 00001895 የተመዘገበውን የማይንቀሣቀሰውን ንብረቱን በመያዣ ያስያዘ መሆኑንና በአበዳሪና ተበዳሪ መካከል በተደረገው የብድር ውል መሠረት ተበዳሪው የጥቁር አባይ ኮንስትራክሽን አ/ማህበር የብድር ገንዘቡን ለመመለስ ያልቻለ የመሆኑ ጉዳይ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም።
እንደዚሁም የአሁን ተጠሪ ከላይ የተመለከቱትን ምክንያቶች መነሻ በማድረግ ለጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን ሰጥቶት የነበረውን የብድር ገንዘብ ሊመልስ ያልቻለ በመሆኑ ይህንኑ የብድር ገንዘብ ለማስመለስ ግራ ቀኙ ያደረጉትን የብድር ውል ስምምነት፣ ይህንኑ ስምምነት የሚገዛውን አዋጅ ቁጥር 97/90 አዋጅ ቁጥር 216/92 እንደተሻሻለ መሠረት በማድረግ በመያዣ የተያዘውን ንብረት አሸጦ ያበደረውን ገንዘብ ለመሰብሰብ በሥርዓቱ መሠረት የሐራጅ ሽያጭ ሥራ ባከናወነበት ጊዜ የአሁን አመልካች ይኸው የሐራጅ ሽያጭ ሊቆም ይገባል፤ ንብረቱ በአጣሪው እጅ ይገኛል በማለት የሐራጅ ሽያጩን ለማስቆም በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዳኝነት ጠይቋል። በዚህ በሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደረጃም ቢሆን የሐራጅ ሽያጩ የተጠናቀቀ ቢሆንም የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በማለት ክስ መመስረቱና አሁንም እየተከራከረ እንደሚገኝ ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡

ይሁን እንጂ በሕግ የተቋቋመ ባንክ በብድር የሰጠውን ገንዘብ ለማስመለስ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/92 መሠረት አስቀድሞ ለብድሩ አመላለስ ዋስትና ይሆኑ ዘንድ ከያዛቸው መያዣዎች መካከል አንዱን በመምረጥ በሐራጅ ሊሸጥ ይገባል፤ ለመሸጥ የተንቀሣቀሰበት የመያዣ ንብረት ከመሸጥ ድርጊቱ ይታቀብ፤ ይህም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ይሰጥልን በሚል በቀረበ ክስ መነሻ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 70824 በሆነው የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት “ በመሠረቱ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረት በሐራጅ መሸጥ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 የሕግ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ባንኩ ሊከተለው የሚገባው ሥርዓትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ.394- 449 ድረስ ያሉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በአንቀጽ 6 በግልፅ አስፍሯል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 216/92 በተደረገው ማሻሻያም ባንኮች ለሰጡት ብድር አከፋፈል በመያዣነት የተቀበሉትን ንብረት የብድር እዳው እንዲከፈለው በተወሰነው ጊዜ ሣይከፈል ከቀረ ከ30 ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የመያዣ ንብረቱን በሐራጅ ለመሸጥና ባለቤትነቱንም ለገዥው ለማዘዋወር ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከአዋጁ ድንጋጌዎችም መረዳት የሚቻለው በአበዳሪው ባንክ በዋስትና የተያዘውን ንብረት የብድር ገንዘቡ ካልተመለሰለት ያለማንም ጣልቃ ገብነት አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን በመከተል በሐራጅ ሸጦ ለእዳው ክፍያ ማዋል እንደሚችልና በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ሕጉን ባለመከተል የፈፀመው ስህተት ቢኖር በዚህም ባለዕዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባለእዳው ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ የአዋጆቹ ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዘትም ሲታይ የሕጐቹ ዓይነተኛ ዓላማ ባንኮች የሚሰጧቸውን ብድሮች በተቀላጠፈ አኳኋን ለመሰብሰብ እንዲችሉ ስለመሆኑ የሚያስገነዝብ ሲሆን ይህ ስለመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 97/1990 በመግቢያው ላይ በግልጽ አስቀምጧል፡፡” የሚለውን ትርጉም በመስጠት አበዳሪ ባንክ በብድር ውሉ መሠረት ያበደረው የብድር ገንዘብ ባልተመለሰለት ጊዜ ይህንኑ የብድር ገንዘብ ለማስመለስ አስቀድሞ የያዘውን የመያዣ ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 ፣ 98/90 እና 216/98 በሚያዙት መሠረት በፎርክሎዠር በእራሱ የሐራጅ ሽያጭ ሥራ የማከናወን ሙሉ ሥልጣን እንዳለው እና ማንም ወገን የበኩሉን ምክንያት በመስጠትና በፍ/ቤት ዳኝነት አማካኝነት የሐራጅ ሽያጩን የማስቆም መብት እንደሌለው ይህ መሰል መብትም በፍ/ቤት ዘንድ ከቀረበ የሚቀርበው የዳኝነት ጥያቄ የመያዣ ውሉንና ከላይ ከተጠቀሱት አዋጆች ዓላማ ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ ፍ/ቤት የሐራጅ ሽያጩን ለማስቆም የሚያስችል ስልጣን አይኖረውም በማለት ወስኗል፡፡
በዚህ በተያዘው ጉዳይ የሐራጅ ሽያጩ ሊቆም ይገባል የተባለበት ምክንያት ከሰበር መ/ቁ. 70824 የተለየ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.224 መሠረት የአሁን አመልካች ከጠየቀው ዳኝነት አንፃር ይህ ከላይ የተጠቀሰው የሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም ቀጥተኛ ተፈፃሚት እንዳለው ተገንዝበናል፡፡

ለጠየቀው ዳኝነት በምክንያትነት ከጠቀሰው ክርክርም አኳያ እንዳየው ቢሆን የአሁን አመልካች በቀረበው ክርክር ተጠሪ መያዣ በመያዝ የብድር ገንዘብ ጠያቂ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/84 ከፈረሰው ድርጅት ገንዘብ ከሚጠይቁ ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በተለዩ ሁኔታ ታይቶ ተገቢው ክፍያ እንዲፈጽምለት ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም ከዚህ ከፈረሰው ንብረት ገንዘብ አለን ከሚሉ ሌሎች ገንዘብ ከሚጠይቁ ወገኖች አንፃ አዋጅ ቁጥር 25/84 መሠረት ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው የመወሰን ስልጣን እያላቸው ድርጅቱ ከመፍረሱ በፊት በወጋገን ባንክ ንብረቱ በመያዣነት ተይዟል በማለት አዋጅ ቁጥር 97/90 እና ሰበር ሰሚው ችሎት አስቀድሞ በሰጠው ትርጉም መሠረት ብቻ ታይቶ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ በማለት የሚከራከር በመሆኑ ይህ የአመልካች ክርክር በአዋጅ ቁጥር 97/90 98/90 እና 216/92 የተመለከቱትን የህጐችን መሰረት ሃሣብ የሚደግፍ እንጂ በእነዚህ አዋጆች መሠረት በአበዳሪ ባንክ በተጠሪ አማካኝነት የተከናወነን የሐራጅ ሽያጭ ለማስቆምም ሆነ ለማስፈረስ የሚያስችል የህግ መሠረት ያለው ክርክር አይደለም፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/84 እና ከላይ በተመለከተቱ ከባንክ የብድር ማስፈፀሚያ አዋጆች መካከል ቅራኔ የለም እንጂ በህጐች መካከል ቀራኔ አለ እንኳ ቢባል በህጐች አተረጓጉም ደንቦች መሠረት ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የትኛው የህግ ክፍል ነው ለሚለወም ሕግ አዋጆች ከወጡበት ዘመን አንፃር ሲታይ ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለውና ጉዳዩን የሚገዛው የባንክ ብድር ማስፈፀሚያ የሆኑት አዋጆች በመሆናቸው ከላይ የተጠቀሰውን ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ የተሰጠውን ትርጉም አፈፃፀም የሚያስለውጥ የክርክር ነጥበ አይደለም፡፡
ምናልባትም የዚህ ክርክር እንደምታዊ ይዘቱና ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣው የመያዣ ንብረት በእኛ አማካኝነት ቢሸጥ ኖሮ ከፍተኛ ዋጋ ያወጣ ነበር የሚል ከሆነ ባንኩ ባደረገው የሐራጅ አሻሻጥ ሂደት በተፈፀመ ስህተት ምክንያት እንደ አባባሉ ሆኖ ከተገኘ የሥር ፍ/ቤቶች እንደሰጡትም ሆነ በሰበር ሰሚው ችሎት እንደተሰጠው ትርጉም በዚህ ረገድ የደረሰ ጉዳት ካለ በአዋጆች መሠረት ዳኝነት ከሚጠይቅ በቀር እንደቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የሐራጅ ሽያጩን ለማስቆምም ሆነ ማስፈረስ የሚያስችል መብት ሰጪ የክርክር ነጥብ ሆኖ አይገኝም፡፡

በመጨረሻም በአዋጅ ቁጥር 454/97 እንደተመለከተው ከአምስት ያላነሱ ዳኞች የተሰየሙበት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም ለተመሣሣይ ጉዳዮች ተፈፃሚነት እንዳለውና በየትኛውም ደረጃ ለሚገኝ የዳኝነት አካል የአስገዳጅነት ባህሪይ አለው በማለት የተቀመጠው የሕግ አነጋገር ተፈፃሚነቱ በተመሣሣይ ጉዳይ በሌሎች ወገኖች ክርክር በተፈጠረበት ጊዜ ይህንኑ አስመልክቶ በሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ትርጉም አለ ወይስ የለም ከሚለው ነጥብ አንፃር ታይቶ ተፈፃሚ የሚሆን እንጂ ትርጉም የተሰጠበትንና የክርክር ምክንያት የሆነው ነገር መቼ ተፈፀመ ተደረገ ከሚለው የጊዜ ቅደም ተከተል አንፃር እየታየ የሚፈፀም ባለመሆኑ የአሁን አመልካች ይፍረስ የተባለው ሐራጅ የተደረገው የሰበር ሰሚው ችሎት ትርጉም ከመስጠቱ ከአምስት ቀናት በፊት ስለሆነና የሰበር ሰሚው ትርጉም ወደ ኃላ ሂዶ ሊሰራ አይገባም በማለት ያቀረበው የአዋጅ ቁጥር 454/97 ትክክለኛ አፈፃፀም የተከተለ አይደለም፡፡
በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በፍ/ቤት አማካኝነት እንዲወሰንለት ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቶች ተቀብለው የማየትና የመወሰን ስልጣን የላቸውም፤ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም በማለት የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለመገኘታችን የሚከተለውን ወሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 192611 በቀን 30/11/2004 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ እና ይህንኑ ብይን በማጸናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 126468 ጥቅምት 14 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ሁሉ ፀንቷል፡፡
2. በህግ አግባብ በተደረገ የብድር ውል እና በህግ አግባብ በተቋቋመ የመያዣ ውል መነሻ አበዳሪ የአሁን ተጠሪ ወጋገን ባንክ በብድር የሰጠው የብድር ገንዘብ አለመመለሱን አረጋግጦ በአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 216/92 እንደተሻሻለው በመያዣ የያዘውን ንብረት በሐራጅ ሸጦ እዳውን የመሰብሰብ ተግባር ያለማንም ጣልቃ ገብነት እንዲያከናውን በሕግ የተሰጠው ስልጣን በመሆኑ በዚህ አካኋን የሐራጅ ሽያጩ በፍ/ቤት ይፍረስ ተብሎ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለማየትም ሆነ ለመወሰን ስልጣን የላቸውም ተብሎ መወሰኑ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ የክርክር ደረጃ ያለውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 82427

ጥር 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዩኒስ ቡራሌ ሲጋል የራይስ ጫት ላኪዎች ማህበር - ጠበቃ ነፃነት ጌታሁን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ አልሚ መሐመድ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ተጠሪ ከማህበሩ ሊቀመንበርነት በማህበሩ ደንብ መሰረት ተነስቷል ወይስ አልተነሳም የሚለውን ጭብጥ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሸንሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ማህበሩ አንድ መቶ ሃምሳ አምስት አባላት ያሉትና በ1999 ዓ.ም. የተቋቋመ ነው፡፡ ተከሳሽ የማህበሩ ሊቀመንበር እንዲሆን በማህበሩ አባላት ተመርጦ ለሶስት ዓመት ማህበሩን በሊቀመንበርነት መርቷል፡፡ ተከሳሽ የማህበሩን ንብረትና ሰነድ ለግል ጥቅም ያዋለ በመሆኑ ከማህበሩ ሊቀመንበርነት እንዲነሳ የማህበሩ አባላት ግንቦት 13 ቀን 2003 ዓ.ም. ባደረጉት ስብሰባ ወስነዋል፡፡ ስለዚህ የማህበሩን ዶክመንትና ንብረት እንዲያስረክብ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ አንድ የማህበሩ አባል ከአባልነት የሚወገድበት ሥርዓት በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ተደንግጓል፡፡ የማህበሩ አባላት በሙሉ ድምፅ የማህበሩ ሊቀመንበር ሆኜ እንድሰራ መርጠውኛል፡፡ ስለዚህ ከሊቀመንበርነት የምወገድበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤት የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11(2) የማህበሩ ሊቀመንበር ሥራውን በአግባቡ ለመፈፀም ካልቻለ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሊሰናበት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከሣሽ ከማህበሩ አባላት መካከል አንድመቶ ሃያ የሚሆኑ አባላት ተከሣሽ ከሊቀመንበርነቱ እንዲወገድ ውሣኔ የሰጡበት (የወሰኑ) መሆኑን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ አንዳንዶቹ አባላትም ፍርድ ቤት በመቅረብ ተከሣሽ ከማህበሩ ሊቀመንበርነት የተነሣ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህ ተከሣሽ በማህበሩ አባላት ውሣኔና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ከማህበሩ ሊቀመንበርነት የተነሣ በመሆኑ ሰነዶችንና ሥልጣኑን አዲስ ለተመረጠው ሊቀመንበር ያስረክብ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ መካሄዱንና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ከሊቀመንበርነት መነሣቱን የሚያሣይ የሰነድ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ከማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መካከል ሰባት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ፍርድ ቤት በመቅረብ ይህንን አረጋግጠዋል በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሸንሌ ዞን ዐቃቤ ሕግ ለሰበር ችሎቱ ደብዳቤ የፃፈ መሆኑን በመጥቀስ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ሽሮታል፡፡

አመልካች ተጠሪ በማህበሩ አባላት የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ አለመወጣቱ በማህበሩ አባላት ተረጋግጦ ከሊቀመንበርነቱ እንዲወገድ የማህበሩ አባላት የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በማድረግ ወስነዋል፡፡ ይህም ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ሥልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ጉዳዩን አመልካች በሌለበት እንዲታይ ሲያደርግ ህጉን ተከትሎ መወሰን ሲገባው፣ አመልካች ቀርቦ መልስ አለመስጠቱን እንደምክንያት በመግለጽ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ የሻረው፣ አመልካች መጥሪያ ከደረሰው በኋላ ቀርቦ ባለመከራከሩና ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተወሰነ በመሆኑ፣ የሸንሌ ዞን ዐቃቤ ሕግ የፃፈውን ደብዳቤ በማገናዘብና ተጠሪ ከሊቀመንበርነት ተወግዷል የተባለው በአንድ የማህበሩ አነሳሽነትና በጥቂት የማህበሩ አባላት የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰብስበን አዲስ ሊቀመንበር ሹመናል በማለት ማህበሩ ሣይጠራ እንደተጠራ አድርገው ባቀረቡት ማስረጃ መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ ስለሆነ ተገቢነት የለውም፡፡

አመልካች ታህሣሥ 16 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቀርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪ የማህበሩ ሊቀመንበር ከመሆን የተነሳ በመሆኑ ሰነዶችንና የማህበሩን ንብረቶች እንዲያስረክብ በማለት በሸንሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሣኔ የሻረው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ የሻረው አመልካች በሰበር ችሎቱ ክርክሩን እንዲያቀርብ መጥሪያ ከደረሰው በኋላ ባለመቅረቡና ጉዳዩ በሌለበት የታየ በመሆኑ ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ /ተጠሪ/ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ብይን መሰጠቱ ፍርዱ ለከሳሽ ወይም /በሰበር ደረጃ/ ለአመልካች በሚጠቅም መንገድ የመወሰኑን ሁኔታ በአስገዳጅነት የሚያስከትል እንዳልሆነ ከፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 70/ሀ/ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የሸንሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ አመልካች ያቀረበውን የሰነድ ማስረጃዎችና የማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ ኮሜቴ አባላት የምስክርነት ቃል በመስማትና ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን የሰጠውንና የደረሰበትን የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያ ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት የተፈፀሙ ስህተቶችን የማረም ስልጣን ባለው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በኩል ተመርምሮ የፀና መሆኑን ከውሣኔው ተረድተናል፡፡

የማህበሩ አባላት ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በማድረግ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11/2/ በሚደነግገው መሰረት ተጠሪ ከማህበሩ ሊቀመንበርነት እንዲነሳ የወሰኑ መሆናቸውንና ለማህበሩም ሌላ ሊቀመንበር የሾሙ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የሸነሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ መዝኖ ውሣኔ የመስጠት ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሣኔ የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ሀሰተኛ መሆኑን የሸንሌ ዞን ዐቃቤ ህግ ደብዳቤ ጽፎልኛል በማለት የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

በመሰረቱ ዐቃቤ ሕግ የጻፈው ደብዳቤ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመርመር በፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ በላይ ተአማኒነት እና ክብደት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ዐቃቤ ህግ የጻፈው ደብዳቤ አከራካሪው ጭብጥ ላይ ተጨማሪ ማጣራት የሚያስፈልገው መሆኑን የሚጠቁም ነው ከተባለ ጉዳዩ ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የሸንሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በኩል እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መመለስ ነበረበት፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በሸንሌ ዞን ዐቃቤ ሕግ በኩል የተጻፈውን ደብዳቤ ራሱ በመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች የተረጋገጠውን ዕውነታ ውድቅ በማድረግ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሸንሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
አዳነ ንጉሴ
ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ወርቁ ወ/ዓድቅ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የአቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ወራሾች
1.ወ/ሮ ወደ ምዕራቡሽ
2.ወ/ሪት ትርሲት ወ/ሥላሴ
3.ወ/ሪት እህቱ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ — አልቀረቡም
4.ወ/ሪት ገነት ተስፋዬ ወ/ሥላሴ
5.አቶ ብሩክ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ
6.አቶ ብርሃኑ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ
7.አቶ ናስፍ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ከሳሽ ሚያዚያ 28 ቀን 2002 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ከ1ኛ ተከሳሽ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተከሳሾች አውራሽ ጋር የሽርክና ውል የነበረን ሲሆን በውላችን መሰረትም ከመካከላችን አንደኛው ከሞተ መብቱ ለወራሽ እንደማይተላለፍ የተስማማን ሲሆን ተከሳሾች አቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ከሞቱ በኋላ በሽርክና ውል መነሻ የተቋቋመውን ድርጅት ተከራይተው የሚሰሩትን ሰዎች (ተከራዮች)

በማስለቀቅ ለራሳቸው ለመያዝ በሚያደርጉት ጥረት መግባባት ያልቻልን ስለሆነ በሽርክና ውሉ መሰረት ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ እንዲታዘዝ ሆኖ በሽምግልና እንዲታይ የማይስማሙ ከሆነ ደግሞ የሽርክና ውሉ ፈርሶ ድርሻችን ተለይቶ እንዲወሰን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ መልስ ያቀረቡ ሲሆን መቃወሚያውም ከዚህ በፊት ከሳሽ በዚሁ ጉዳይ ላይ ክስ አቅርበው የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 40977 ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም ሲል መዝገቡን የዘጋው ስለሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/5 መሰረት በዚያው ጉዳይ እንደገና ክስ ማቅረብ አይችሉም የሚል ሲሆን በአማራጭ ባቀረቡት መልስ ደግሞ በመካከላችን የሽርክና ውል የለም ብለው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የቀረበውን መቃወሚያ በተመለከተ በመዝገብ ቁጥር 40977 ተከራካሪ ወገኖች የተለያዩ ከመሆናቸውም ሌላ የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ አሁን ክስ ከቀረበበት ጉዳይ የተለየ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ ተከሳሾች የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/5ን ጠቅሰው ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው ፍርድ ከሳሽ የሽርክናው ማህበር ሰነዶች ናቸው በሚል ያቀረቡአቸው ውሎች ብቻ በመሆናቸውና የሽርክና ማህበር ነው የሚሉትም በንግድ ህጉ መሰረት የንግድ ስም የሌለው፣ በንግድ መዝገብ ያልተመዘገበ እና የመመስረቻ ጽሁፍ የሌለው በመሆኑ በከሳሽና በ1ኛ ተከሳሽ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ተከሳሾች አውራሽ መካከል የሽርክና ማህበር ውል የለም፡፡ የሽርክና ማህበር ባልተቋቋመበት ደግሞ እንዲፈርስ ጥያቄ ሊቀርብ ስለማይችል ከሳሽ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33(2) መሰረት ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም ብሏል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍርድ ቤትም የይግባኝ ባዩን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን በማሰናበቱ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ብይን/ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የቅሬታ ነጥቡም ሲጠቃለል፡- ከሚች አቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ጋር ለመኪና ጋራዥ ሥራ የሚሆን ቦታ የአፈር ኪራይ እየከፈልን በህብረት ለመስራት ህዳር 17 ቀን 1967 ዓ.ም. የህብረት ስምምነት ውል ፈጽመን እየሰራን እያለ ቦታው ለውኃ ማጠራቀሚያ መንግስት ስለወሰደው በምትኩ በቀድሞ ከፍተኛ 23 በአሁን አጠራር ቂርቆስ ክ/ከ/ቀበሌ 08/09 ቦታ ተሰጥቶን ቁጥሩ 826 የሆነ ቤት ሰርተን የመጀመሪያውን ውል የካቲት 27 ቀን 1979 በተጻፈ አዲስ ውል በመተካት ስንዋዋል የንግድ ፈቃዱ በሚች ስም እንዲሆንና ተሻራኪዎቹ የጋራገቡን ሥራ በአንድ መልክ እንድናስተዳድር፣ ፈቃዱ በስሙ የሆነው ተሻራኪ ቢሞት በህይወት

ባለው ተሻራኪ ስም እንዲሆንና በውርስ እንደማይተላለፍ በማድረግ ከ38 ዓመት በላይ የጋራ ባለሀብት በመሆን የቆየን ሆኖ ሳለና ክሱን ለማስረዳት በቂ ሰነዶችን አቅርቤ እያለሁ የስር ፍርድ ቤቶች ያቀረብኩትን ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 33(2) መሰረት ውድቅ ያደረጉት ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡
ተጠሪዎች በሰጡት መልስ፡- አመልካች እና ሚች ተስፋዬ ወ/ሥላሴ የጋራ የሆነ ቤትም ሆነ ቦታ ኖሮአቸው አያውቁም፣ አመልካች የሽርክና ማህበር አለ የሚሉት በንግድ ህጉ መሰረት ያልተመዘገበ፣ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ የሌለው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረጉት ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ክስ ባቀረቡት ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት የላቸውም ተብሎ ክሱ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33(2) መሰረት ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ክስ ሲያቀርቡ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 223 መሰረት በማስረጃነት የተለያዩ ውሎችንና ሌሎች ሰነዶችን ማቅረባቸውን የመ/ደ/ፍርድ ቤት ብይን ያመለክታል፡፡ የመጀመሪያው የውል ሰነድ ህዳር 17 ቀን በ1964 ዓ/ም የአሁኑ አመልካች፣ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተጠሪዎች አውራሽ እና መንግሥቱ ጋሼ የተባሉ ሰው ሆነው አቶ ነጋሽ ወሰኔ ከተባሉ ሰው ለመኪና ጋራዥ የሚሆን ቦታ ወስደው በ1960 ዓ/ም ለመኪና ማቆሚያ የሚሆን ቤት መሥራታቸውን በመግለጽ እነ ካሳሁን ቦሰና የተባሉ ሌሎች 4 ሰዎች በደባልነት ገብተው የጋቢናና የባሊስትራ ሥራ እንዲሰሩ ስምምነት ያደረጉበት ነው፡፡ እንዲሁም በውሉ የተካተቱት ሁሉም ሰዎች በ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተጠሪዎች አውራሽ ስም የንግድ ፈቃድ ወጥቶ የመንግስት ግብርም ሆነ ለባለይዞታው የሚከፈለውን የቦታ ኪራይ እየዋጡ ለመክፈል መስማማታቸውን ሰነዱ ይገልጻል፡፡ ከዚህ በኋላም የካቲት 27 ቀን 1979 ዓ/ም የአሁኑ አመልካች፣ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተጠሪዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አውራሽና ወ/ሮ አሥራት መንግስቱ ሆነው ቀደም ሲል ያደረጉትን ውል በማሻሻል ‹‹ የንግድ የጋራ ሽርክና ውል ›› በሚል ባደረጉት ስምምነት ቀድሞ ጋራዡ የተቋቋመበትን ቦታ ለውኃ ማጠራቀሚያ እንዲሆን በመፈለጉ በምትኩ በክፍተኛ 23 ቀበሌ 09 ክልል ውስጥ ቦታ ተሰጥቶ የጋራዡን ስራ መቀጠላቸውን በመጥቀስ ማንኛውም ስራ ተሻራኪዎቹ በአንድ መልክ ሆነው ለማስተዳደር፣ የንግድ ፈቃዱ በስሙ የወጣ ሰው በሞት ቢለይ በህይወት ባሉ ተሻራኪዎች እንዲዛወር፣ ከጋራዡ ሥራ የሚገኘውንም ገቢ እያንዳንዱ ተዋዋይ በሥራው ድርሻው ተጠቃሚ እንዲሆን ከመስማማታቸውም በላይ ሌሎች መብቶችና ግዴታዎችንም አካትተዋል፡፡ ከተጠቀሱት ውሎች በተጨማሪ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የተለያዩ የመንግስት አካላት የጻፉአቸው ደብዳቤዎችን አመልካች በማስረጃነት ለስር ፍርድ ቤት ስለማቅረባቸው በክርክራቸው ገልጸዋል፡፡ በዚህ መልኩ የቀረበውን ክስ ፍርድ ቤቱ ውድቅ ለማድረግ የጠቀሰውም በንግድ ህጉ መሰረት የተቋቋመ ማህበር የለም በሚል ነው፡፡ በንግድ ህጋችን ቁጥር 212(1) መሰረት የሚታወቁ የንግድ ማህበሮች 6 ሲሆኑ ከእነዚህም መካከል አንዱ በዚሁ ቁጥር በንዑስ ቁጥር 1 በፊደል (ለ) ስር የተጠቀሰው የእሽሙር ማህበር ተብሎ የሚጠራው ነው፡፡ የእሽሙር ማህበር ህጋዊ ሰውነት የሌለው እንዲሁም በጽሁፍ መረጋገጥና በሌሎች ንግድ ማህበሮች የተደነገጉት የማስታወቅና የማስመዝገብ ሥርዓቶች እንደማይፈጸሙበት በንግድ ህጉ አንቀጽ 272 ተጠቅሷል፡፡ ሽሪኮቹም እንደ ተራ ተዋዋይ ወገኖች የሚታዩ ናቸው፡፡ ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት የሌለው በመሆኑ ምክንያትም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያደርገውም በሽሪኮቹ ስም ነው፡፡ አመልካችና የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተጠሪዎች አውራሽ ያደረጉት የሽርክና ውል ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የእሽሙር ማህበር ባህርያት ጋር የሚመሳሰል ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ከእሽሙር ማህበር ውጪ ያሉ ሌሎች በንግድ ህጉ የሚታወቁ ማህበራት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ነጥቦች በመጥቀስ በንግድ ህጉ መሰረት የተቋቋመ ማህበር ባለመኖሩ እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ የለም ሲሉ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/33(2)ን ጠቅሰው የአመልካችን ክስ በብይን ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/53795 በቀን 08/03/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን እንዲሁም የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/116705 በቀን 9/05/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. በአመልካችና የ1ኛተጠሪ ባለቤትና ከተራ ቁጥር 2-7 ያሉ ተጠሪዎች አውራሽ መካከል የተቋቋመው የእሽሙር ማህበር በመሆኑ አመልካች ባላቸው የሽርክና ስምምነት መሰረት ክስ የማቅረብ መብት አላቸው ብለናል፡፡ ስለሆነም ፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ወደ ፍሬ ነገሩ በመግባት የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማትና በመመዘን አግባብ ባለው ህግ መሰረት የበኩሉን ፍርድ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 80599

ጥር 15 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ጀሽዋ ኤነድ ካሌብ ኃ/የተ/የግል/ማህበር ጠበቃ አቶ መሉጌታ ገብሩ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እንቁጣጣሽ አሰፋ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ አንድ ኃ/የተ/የግል ማህበር ስራውን የሚያከናውንበት የንግድ ቦታ መሆኑ በመታወቁ ምክንያት ብቻ በዚህ ቦታ ላይ የኪራይ መብትን እንዳቋቋመ ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም? በዚህ የንግድ ቦታ ላይ የኪራይ መብት የለውም፤ ከተባለ ማህበሩ ፈርሶ ሂሳብ ተጣርቶ እስኪታወቅ ድረስ በዚሁ የንግድ ቦታ ላይ የኪራይ መብት ያለው ወገን በመብቱ ሊገለገልበት አይችልም ለማለት ከህግ የመነጨ መብት አለው ወይስ የለውም? የሚሉትን አከራካሪ ነጥቦች ከግራ ቀኙ ክርክርና ስለዚሁ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች ከሰጡት ውሳኔ ጋር በማገናዘብ ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ሲባል የቀረበ ነው፡፡

ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ ከኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት በኪራይ ያገኘሁትን በቂ/ክ/ከ/ቁ/15/16 ከአከራይ ድርጅት ፊት ለፊት የሚገኘውን የመናፈሻ ቦታ የአሁን አመልካች የሆነው ኃ/የተ/የግል ማህበር ያለ አግባብ ይዞ ስለሚገኝ ለቆ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ሲሆን፤ የአሁን አመልካችም ለዚህ ለቀረበበት ክስ ማህበሩ ሳይፈርስ ድርጅቱ ያለበትን ቤትና ቦታ ይለቀቅልኝ ማለት አይቻልም፤ ከሳሽ የኪራይ ውሉን ከመፈረም በቀር በቦታው ላይ አንዳችም ነገር ኢንቨስት አላደረጉም፡፡ የድርጅቱን የቤት ግንባታና የውስጥ ቁሳቁሶች ያሟሉት ከሳሽ ሳይሆኑ የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ወ/ሮ ጃኪ አሰፋ ስለሆኑ ክሱን ያቀረቡት ያለአግባብ ነው በማለት መልስ ሰጥተውበታል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ የአሁን ተጠሪ ክርክር ያሰነሳውን የመናፈሻ ቦታ በኪራይ ያገኙት ስለመሆኑ አልተካደም ይህንኑም ከሳሽ አባል ለሆኑበት ማህበር በአይነት መዋጮ አላደረጉም ተከሳሽ በዚሁ ክርክር ባስነሳው የመናፈሻ ቦታ ወጭ አድርጎ የማልማት ሥራ ሠርቶ ከሆነ ይህንኑ ወጭ በህግ አግባብ ከሚጠይቁ በቀር የመናፈሻ ቦታው ባለመብት ሊያደርገው አይችልም በማለት ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች ይግባኝ ጠያቂነት ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ፣ ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ማህበር አቋቁመው ማህበሩ በዚህ ቦታ ላይ ሥራውን እንዲሰራ ፈቅደዋል፡፡

ይህንኑ መናፈሻ ቦታ የሚፈልጉት ከሆነ መልሰው የግል ለማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታ በመተዳደሪያ ደንብ ወይም በመመሥረቻ ፅሑፍ ላይ እንዲካተት አላደረጉም፡፡ እንደ ክሳቸው ማህበሩ ሥራውን የሚያከናውንበትን የመናፈሻ ቦታ ያስረክብ ቢባል የማህበሩን ህልውና የሚነካ፤ ጥያቄው ከማህበሩ ትርፍና ኪሣራ ጋር የተያያዘ በመሆኑና የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የሚጠይቅ በመሆኑ የእያንዳንዱ ማህበርተኛ ትርፍና ዕዳ ተለየቶ ከመታወቁ በፊት የከሳሽ የኪራይ መብት ይከበር፤ ማህበሩ ለከሳሽ ይልቀቅ በሚል ሊወሰን አይገባም፡፡ የሚለውን ምክንያት በመስጠት በሥር ፍ/ቤት ከሳሽ ማህበሩ ከቤትና ከቦታው እንዲለቅ ይደረግልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ውድቅ ነው በማለት የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ሰሚውን የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ወሣኔን ያፀና የመጨረሻ ፍርድ በመስጠቱ የተነሣ ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ እንደቻለ የጉዳዩ አመጣጥ አስረጅ ነው፡፡

በዚህ ሰበር ደረጃም በአመልካች የሰበር አቤቱታ መነሻ ክርክር ባስነሣው ቦታ ላይ ሥራውን ሲያከናውን የቆየው ማህበር ፈርሶ ሂሣቡ እንዲጣራ ተወስኖ በጉዳዩም ላይ የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥቶበታል፡፡ በዚህም መሠረት የማህበሩ ንብረት ተጣርቶ ሳይጠናቀቅ ማህበሩ አከራካሪውን የይዞታ ቦታ ለአሁን ተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚል በተያዘው ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

እንግዲህ ጉዳዩ ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን፤ እኛም ይህንኑ ጉዳይ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከላይ ባጭር ባጭሩ እንደተጠቀሰውና በየደረጃው ባሉት የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች ላይ እንደተመለከተው የዚሁ ክርክር ያስነሣው የመናፈሻ ቦታ ከኪራይ ውል በመነጨ የባለይዞታነት መብት ያላቸው የአሁን ተጠሪ ስለመሆናቸው የአሁን አመልካች ክዶ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ በመከላከያ መልሱ ላይ ካቀረባቸው ክርክሮች አንዱ ማህበሩ ሳይፈርስ ድርጅቱ ያለበትን ቤትና ቦታ ለቆ ለተከራይ እንዲያስረክብ ሊገደድ አይችልም የሚል ነው፡፡ ማህበሩ ከመፍረሱ በፊት እንዳባባሉ የመናፈሻ ቦታውን እንዲያስረክብ ላለመገደድ ከሕግ የመነጨ መብት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ድርጅት ወይም ማህበር በተከራይ ክስ አቅራቢነት በፍርድ ቤት እንዲፈርስ ተወስኖ በዚህ ውሣኔ ላይ ከታች ወደ ላይ ባለው የክርክር መስመር እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ጉዳዮች አጣሪ ችሎት ደረሶ ይፍረስ በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በሚል የመጨረሻ ዳኝነት ያገኘ ጉዳይ ስለመሆኑ የአሁን አመልካች እራሱ ባቀረበው ክርክር ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የመናፈሻ ቦታውን እንዳስረክብ ልገደድ አይገባም ለሚለው ክርክሩ መነሻ አድርጎ ከቀረባቸው ምክንያት አንዱ የሆነው በቅደመ ሁኔታነት ያቀረበው የማህበር መፍረስ ጉዳይ እንደ ክርክሩ በፍርድ ዕልባት ያገኘ ጉዳይ እንደመሆኑ ይህ የመከራከሪያ ነጥብ ማህበሩ ስራውን ሲያከናውን የነበረበትን የይዞታ ቦታ ለቆ ለማስረከብ እንዳይገደድ ለማድረግ የሚያስችል ሳይሆን ቀሪ መሆኑን ስለሚያመለክት ጭብጥ ለመመሰረት በፍሬ ነገር መሰረትነቱ ያከተመ የክርክር ነጥብ ነው፡፡ ስለሆነም የማህበሩ ቅድሚያ መፍረስና አለመፍረስ ከሳሽ ለጠየቁት ዳኝነት አግባብነት ያለው ጉዳይ አይደለም፡፡

ማህበሩም በፍርድ ከፈረሰ በኋላ የማህበሩ ሂሣብ በአሁኑ ሰአት አልተጠናቀቀም የሚባል ከሆነም የማህበሩ ሂሣብ ስራ የመጠናቀቁና ያለመጠናቀቁ ጉዳይ አሁን ግራ ቀኙን ካከራከረው ጉዳይ ጋር የሚያገናኘው ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም፡፡ የሂሣብ ስራው ተጠናቆ ውጤቱ ቢታወቅ ይህንኑ ከኪራይ ውል የመነጨውን የአሁን ተጠሪን መብት ቀሪ የሚያደርግበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የሂሣብ ማጣራት ስራ የሚያስከትለው ውጤት እና የዚህ ክርክር ጉዳይ ውጤት በየራሳቸው ችለው የቆሙ እንጂ የመጀመሪያው የክርክር አይነት ለኋለኛው እንደቅድመ ሁኔታ ወይም እንደ መያዣ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል አይደለም፡፡

ሁለተኛ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት አቅርቦ የነበረው በዚሁ የመናፈሻ ቦታ ላይ ለማስፋፋት ሥራ ከፍተኛ ወጭ አድርገው ያከናወኑት የማህበሩ ሥራ እስኪያጅ የሆኑት ሌላዋ የማህበሩ አባል ናቸው እንጂ የድርጅቱ ተከራይ አይደሉም የሚለው ሌላው የመከራከሪያ ነጥብ በመሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዳለው ይህ አይነት ወጭ ተደርጎ ከሆነ እራሱ በቻለ እኳኋን መብቱን የሚጠበቅበት በመሆኑና በሂሣብ ማጣራት ጉዳይም ተካቶ ሊወሰን የሚገባው እንጂ ለዚህ ግራ ቀኙን ካከራከረው ጉዳይ አግባብነት ያለው ሆኖ አይገኝም፡፡

ከዚህም በቀር ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያለው እንደመሆኑ መጠን የዚህ ማህበር የሚጨበጥና የማይጨበጥ የሚንቀሣቀስና የማይንቀሣቀስ ንብረቶችን መብቶች ምን ምን እንደሆነ በማህበሩ መመሥረቻ ጽሑፍና በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰኑ እንጂ ማህበሩ ሥራውን የሚያከናውንበት የመናፈሻ ቦታ ላይ ከኪራይ የመነጨ መብት የሌለው መሆኑ እየታወቀ ማህበሩ ሥራውን የሚያከናውንበት ሌላ ቦታ መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ ይህ የሥራ ቦታ ከሌለ ማህበሩ ህልውና አለው ማለት አይቻልም የሚለውን ምክንያት በመያዝ ብቻ የማህበሩን መብትና ጥቅም ማቋቋም አይቻልም፡፡

በማህበሩ መመሥረቻ ጽሑፍም ሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ ማህበሩ የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን የንግድ ሥራውን የሚያከናውንበትን የንግድ ቦታ የመከራየት መብትንም ሁሉ አካቶ ላለመያዙ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይልቁንም ከኪራይ መብት የመነጨ መብት ያላቸው የአሁን ተጠሪ ስለመሆናቸው የሥር ፍ/ቤቶች በማስረጃ ያረጋጡት የፍሬ ነገር ጉዳይም ከመሆኑ በላይ አመልካች እራሱ የካደው አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማህበሩ የማህበሩ የስራ ቦታ በነበረው የመናፈሻ ቦታ ላይ ማህበሩ እንደማህበር ወይም የማህበሩ አባል ያወጣው ወጭ ካለ የመጠየቅ መብቱን በመጠበቅ ክርክር ያስነሳው መናፈሻ ቦታ ከኪራይ ውል የተነሣ ህጋዊ ባለይዞታ የአሁን ተጠሪ እንጂ የአሁን አመልካች አለመሆኑን አረጋግጦ የአሁን አመልካች ለቆ ለአሁን ተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በማለት በሰጠው መጨረሻ ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 71325 መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ፀንቷል፡፡
2. በዚሁ ክርክር ባስነሳው የመናፈሻ ቦታ ላይ ማህበሩ ወይም በሌላ የማህበሩ አባል አማካኝነት በማስፋፋት ረገድ የወጣ ወጭ ካለ ይህንኑ የመጠየቅ መብቱን በመጠበቅ የመናፈሻ ቦታውን የአሁን አመልካች ለአሁን ተጠሪ ለቆ ያስረክብ መባሉ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ምክንያት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. በዚህ የሰበር ጉዳይ ክርክር እስከሚጠናቀቅ በሚል በዚህ የሰበር መዝገብ ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 170065 በቀን 22/06/2003 ዓ.ም. እንደዚሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 71325 መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም. በሰጠው ውሳኔ መሰረት አፈፃፀም እንዳይቀጥል በሚል ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ ለተላለፈላቸው ክፍሎች ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.74734

ህዳር 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ትዕግስት ሽባባው - ጠበቃቸው አቶ ኃ/ማርያም ኢትቻ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. እህት አለማው ወርቁ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ አበቡ ወርቁ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን የሰበር አመልካችም 3ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ክሱም ሟች አባታችን ያደረጉት ኑዛዜ እኛን ህጋዊ ወራሾች የነቀለን ከመሆኑም ሌላ ጉድለት ያለበት ስለሆነ ይሻርልን የሚል ነው፡፡

3ኛ ተከሳሽም በሰጡት መልስ ሟች አባታችን ባደረጉት ኑዛዜ ያላቸውን ንብረት ለከሳሾችም ሆነ ለተከሳሾች የተናዘዙ ስለሆነ ኑዛዜው ከሳሾችን የሚነቅል ካለመሆኑም በላይ ጉድለት የሌለበት በመሆኑ ሊሻር አይገባም ብለዋል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም ክርክሩ የውርስ ሀብት የሚመለከት በመሆኑ ክሱ ከመቅረቡ በፊት የውርስ ሀብቱ ተጣርቶ ድርሻ ሳይታወቅ ከሳሾች ባለመብት ሆነው ክስ ሊያቀርቡ ስለማይገባ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት የስር ከሳሾችም ይግባኝ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ መልስ ሰጪዋ በወረዳ ፍርድ ቤት ደረጃ በሰጡት መልስ ውርስ ማጣራትን በተመለከተ ያቀረቡት ክርክር ሳይኖር ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ከሳሾች በመጀመሪያ የሚደርሳቸውን የውርስ ንብረት ማጣራት ስለሚገባቸው ይሔው ሁኔታ በቅድሚያ ሳይፈጸም ክስ ሊያቀርቡ አይገባም ያለው ተቀባይነት የለውም፣ የግራ ቀኙን ወገን የሚያከራክረው በ23/07/1996 ዓ.ም. በጽሁፍ ተደርጓል የተባለው ኑዛዜም በህጉ መሰረት በሰው ማስረጃዎች ተሟልቶ ያልቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ሲል ውድቅ በማድረግ 1ኛ እና 2ኛ መልስ ሰጪዎች የአቶ ወርቁ ደስታ ወራሾች ስለመሆናቸው የቀረበውን የወራሽነት ማስረጃ ይግባኝ ባዮች ክደው ያልተከራከሩ በመሆኑ ይግባኝ ባዮችና 1ኛ እና 2ኛ መልስ ሰጪዎች በፍ/ህ/ቁ/842

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት የሚች አባታቸውን ሀብትና ንብረት እኩል የመውረስ መብት አላቸው በሚል የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

በሥር 3ኛ ተከሳሽ ይግባኝ ጠያቂነት የግራ ቀኙን ወገን ያከራከረው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ መልስ ሰጪዎች እንዲሻር የጠየቁት ኑዛዜ በፍ/ሀ/ቁ/882 መሰረት ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበ ከመሆኑም በላይ ሚች በፍላጎታቸው ያደረጉትና ወራሾችን ከውርስ የሚነቅል ባለመሆኑ ሊሻር አይገባም በሚል የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

የሥር ከሳሾችም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ኑዛዜው የህጉን መስፈርት የሚያሟላ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ኑዛዜው በኮምፒዩተር ተጻፈ እንጂ ማን እንደጻፈው አይገልጽም፣ በፍ/ሀ/ቁ/881 መሰረት በኑዛዜው አራት ምስክሮች መፈረም ያለባቸው ሲሆን በሚያከራክረው ኑዛዜ ያሉትና የፈረሙት ምስክሮች 3 ብቻ ሲሆን 4ኛው ምስክር ሆኖ የተመዘገበው የፈረመው 4ኛ ተጠሪ ነው፡፡ እንዲሁም ከፍ/ሀ/ቁ 882 አንጻር ሲታይም ኑዛዜው በሬጅስትራር ወይም አንድ ምስክር ባለበት ውል ለመመዝገብ ሥልጣን ባለው ሰው ፊት ያልተደረገ እና በ23/07/1996 ሌላ ቦታ ተደርጎ በ26/08/1996 ዓ.ም. የውል ምዝገባ ጽ/ቤት ማህተም የተመታበት በመሆኑ ከፍ/ብ/ሀ/ቁ. 881-882 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ ባለመሆኑ የሚሻር ነው ሲል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠውን ውሳኔ በመሻር የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አመልካችም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብም፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው በ23/07/1996 ዓ/ም የተደረገው ኑዛዜ በፍ/ሀ/ቁ/882 ስር በተደነገገው መሰረት ለምዕራብ ሸዋ ዞን ውል ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ በ26/08/1996 ዓ.ም. ተመዝግቦ በማህተም የተረጋገጠ ህጋዊ ኑዛዜ ሆኖ እያለና ተጠሪዎችም ከውርስ ሀብት ስለመነቀላቸው ባላስረዱበት ኑዛዜው ይፈርሳል ሲል የወሰነው ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- በፍ/ሀ/ቁ/881 መሰረት ኑዛዜ ሲደረግ ተናዛዡ እየተናገረ ሌላ ሰው ወይም ተናዛዡ ራሱ እየጻፈ በአራት ምስክሮች ፊት ተነቦ መፈረም ያለበት ሲሆን የሚያከራክረው ኑዛዜ ግን ተናዛዡ እየተናገረ ማን እንደጻፈው የሚገልጽ ካለመሆኑም ሌላ ምስክሮቹም ሶስት ብቻ ሲሆኑ ከእነርሱ ውስጥም አንዱ ኑዛዜ የተደረገለት ሰው ነው፣ ኑዛዜው በፍ/ሀ/ቁ/882 መሰረት የተፈጸመ ነው ለማለት ደግሞ አንድ ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሥራውን በሚያካሂድበት ክፍል ውስጥ ተደርጎ በዚያው ቀን በኑዛዜው ላይ ሁለት ምስክሮች መፈረም ያለባቸው ሲሆን የሚያከራክረው ኑዛዜ ግን በ23/07/1996 ዓ.ም. ተደርጎ በ26/08/1996 ዓ/ም በባለሥልጣኑ ሳይፈረም ማህተም ብቻ የተደረገበት በመሆኑ ጉድለት ያለበት ነው፣ እንዲሁም ኑዛዜው ተወላጆችን (ተጠሪዎችን) የሚነቅል በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን የሚገባ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በመልስ መልሳቸው ኑዛዜው የተደረገው በፍ/ሀ/ቁ/881 ሳይሆን በቁጥር 882 መሰረት በመሆኑና የተደረገውም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ሆኖ ሶስት ምስክሮች የፈሩመበት በመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች በኑዛዜው አራት ምስክሮች ሊፈርመበት ያስፈልጋል ያሉት ተቀባይነት የለውም፣ ኑዛዜው ተጠሪዎችን ከውርስ የሚነቅላቸው አይደለም ሲሉ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- የግራ ቀኙን ወገኖች የሚያከራክረው በ23/07/1996 ዓ.ም. ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ሊሻር የሚገባ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ኑዛዜ በህግ ፊት የጸና የሚሆነው ህጉ ያስቀመጣቸውን መለኪያዎች አሟልቶ ሲገኝ ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/17058 የሰጠው ፍርድ ያስገነዝባል፡፡ ኑዛዜ የሚሰጥበት ሥርዓት እንደ ኑዛዜው ዓይነት የሚለያይ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይም የግራ ቀኙን ወገኖች የሚያከራክረውን ኑዛዜ በፍ/ህ/ቁ 881 ግልጽ ኑዛዜን በተመለከተ ከተቀመጡት መስፈርቶች እና ተያያዥነት ካለው ከፍ/ህ/ቁ/882 ጋር በማገናዘብ ሊመረመር የሚገባ ነው፡፡

በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡ እየተናገረ ማናቸውም ሌላ ሰው ወይም ተናዛዡ የሚጽፈው ሲሆን ኑዛዜው ተናዛዡና አራት ምስክሮች ፊት መነበብ የሚገባው ነው፡፡ ይህም ስርዓት መፈፀሙና የተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መጠቀስ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ተናዛዡና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸውን ማረጋገጡ አስፈላጊ ነው፡፡ ኑዛዜው እነዚህን መስፈርቶች አሟልቶ ካልተገኘም ፈራሽ ነው፡፡ ሆኖም በግልጽ ኑዛዜ በፍ/ህ/ቁ 881 የምስክሮች ቁጥር አራት መሆን እንደሚገባ የተደነገገ ቢሆንም በፍ/ህ/ቁ 882 በተነገረው ዓይነት የተደረገ ኑዛዜ ከሆነ ደግሞ የምስክሮቹ ቁጥር ሁለት ከደረሰ በቂ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከምስክሮቹ መካከል አንዱ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሆኖ ኑዛዜው የተደረገው ዳኛው ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሥራቸውን በሚያካሂዱበት ክፍል ውስጥ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን ኑዛዜው በፍ/ህ/ቁ 881 በተነገረው መሰረት አራት ምስክሮች ተሟልተው በተገኙበት የተደረገ ካለመሆኑም ሌላ በፍ/ህ/ቁ 882 መሰረት ተደርጓል ለማለትም ውል ለመመዝገብ ሥልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኑዛዜው በ23/07/1996 ዓ.ም. ሌላ ቦታ ተደርጎ 26/08/1996 ዓ/ም ወደ ውል ለመመዝገብ ሥልጣን ወደአለው አካል ቀርቦ ማህተም የተመታበት በመሆኑ ነው፡፡ በህጉ ኑዛዜው ዳኛ ፊት ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሠጠው ሰው ሥራውን በሚያካሂድበት ክፍል ውስጥ መደረግ አለበት ሲል በግልጽ የተደነገገውን ባለመከተል ሌላ ቦታ የተደረገውን ኑዛዜ ከቆይታ በኋላ ውል ለሚመዘግበው አካል አቅርቦ ማስመዝገብ ኑዛዜው በህግ ፊት ዋጋ ያለው እንዲሆን የሚያደርግ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ኑዛዜው ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 - 882 ሥር የተመለከቱ ሁኔታዎችን የሚያሟላ አይደለም በሚል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመሻር አመልካችና ተጠሪዎች የውርስ ሀብቱን እኩል የመካፈል መብት አላቸው ሲሉ በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 25092 በቀን 18/03/2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔና የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/108978 በቀን 20/02/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. ሟች በ23/07/1997 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ የህጉን መስፈርት የሚያሟላ አይደለም በሚል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 74451

ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ደረጀ ማዘንጊያ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፍሬ ህይወት ጴጥሮስ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ክልል የሀዋሣ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመደበኛ ችሎትና የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍች ከፈረሰ በኋላ ያቀረበችው የጋራ ንብረት ክፍያ ጥያቄ ነው፡፡ ተጠሪ ስልሳ ሶስት ንብረቶችን ዘርዝራ ለመካፈል ጥያቄ ያቀረበች ሲሆን፣ በጋብቻ ውስጥ ያገኙትና ቅድመ ክፍያውን በጋራ የከፍሉት በስሜ የደረሰኝ ኮንደሚኒየም ቤት፣ ለመሸጥ ለመለወጥና ለመካፈል የማይቻል በመሆኑ ቀሪውን የቤቱን እዳ ክፍያ የእኔ ንብረት እንዲሆን ይወሰንልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ አመልካች በበኩሉ የኮንዶሚንየም ቤቱ በጋብቻ ወቅት የተገኘ የጋራ ንብረት ነው፡፡ ቤቱ የጋራ ንብረት እዳውም የጋራ እዳ ሆኖ እንዲወሰንና ቤቱ ተከራይቶ ለመንግስት መከፈል ያለበት እዳ እዲከፈል ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለኮንዶሚኒየም ቤቱ እስካሁን የተከፈለውን ክፍያ ግማሹን ቤቱን ለማስጌጥ የወጣው ወጭና ፓርቲሽን ለመሥራት የወጣው ወጭ ተሰልቶ ግማሹን ተጠሪ ለአመልካች ከፍላ ቤቱን እንድታስቀር በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ህዳር 12 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አከራካሪው ኮንዶሚኒየም ቤት በጋብቻ ወቅት ያገኘነው የጋራ ንብረት መሆኑ አልተካደም፡፡ በሥር ፍርድ ቤትም ተረጋግጧል፡፡ ንብረቱ የጋራ ንብረት ከሆነ የቤተሰብ ህጉን በመከተል እንዲካፈል መወሰን ሲገባው ተጠሪ እንድትወስድ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ የካቲት 28 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ለሰበር አቤቱታው በሰጠችው መልስ ኮንዶሚኒየም ቤቱ ለመሸጥ፣ ለመለወጥና ለመካፈል የማይመች ንብረት ነው፡፡ ውሳኔውም ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 85 እና ሴቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ መንግስት ከሚሠራው ስራ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካች መጋቢት 25 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ለቤቱ የወጣውን ወጪ ግማሹን ለአመልካች በመክፈል ተጠሪ የኮንዶሚኒየም ቤቱን እንድትወስድ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነውም አከራካሪው የኮንዶሚኒየም ቤት ተጠሪ በስሟ ያገኘችው ከአመልካች ጋር በትዳር ተሳስራ ስትኖር መሆኑን አላከራከረም፡፡ በተጠሪ ስም የተገኘው የኮንዶሚኒየም ቤት የቅድመ ክፍያ በጋብቻ ወቅት ካፈሩት የጋራ ንብረት የተከፈለ መሆኑን እና ቤቱን ለማሳመር እና የቤቱን ፓርቲሽን ለመስራት አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ወቅት ያፈሩትን ገንዘብ የተጠቀሙ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህም ቤቱ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/96 አንቀጽ 72 መሠረት የባልና የሚስት የጋራ ሀብት እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የኮንዶሚኒየም ቤቱ እና ለቤቱ ሊከፈል የሚገባው እዳ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት እና የጋራ እዳ ከሆነ የአመልካች እና የተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ ይሄ የጋራ ንብረት እና ዕዳ የሚካፈልበት ስርዓት በምን መልክ እንደሆነ መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡ በሕግ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን ቤተሰብ የመመስረት መብት በመጠቀም ጋብቻ የፈፀሙ ወንዶች እና ሴቶች በጋብቻው አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመን እና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት ያላቸው ስለመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ በፍቺ ወቅት የጋራ ንብረት ከአመልካች ጋር ስትካፈል ኮንዶሚኒየም ቤቱን የመውሰድ ልዩ መብት እንዳላት በማለፅ ያቀረበችው ክርክር የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የኮንዶሚኒየም ቤቱ እንደማንኛውም በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት ባልና ሚስቱ ስለቤቱና ስለቀረው ዕዳ አከፋፈል የሚስማሙ ከሆነ በስምምነታቸው መሰረት ሁለቱ የማይስማሙና በአይነት ለመካፈል የሚቻል ከሆነ በአይነት ማካፈል ከላይ የተገለፁት በሁለቱ መንገድ ቤቱን ለመካፈል የማይችል ከሆነ ቤቱ በሀራጅ ተሽጦ የቤቱ ቀሪ ዕዳ ለባንክ ተከፍሎ ቀሪውን ገንዘብ የጋራ ባለሀብት ለሆኑት አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ ማድረግ እንደሚገባ ይህ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 51893 ሀምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለኮንዶማኒየም ቤቱ እስካሁን የወጣውን ወጭ ግማሽ ገንዘበ ለአመልካች ከፍላ ቤቱን እንድታስቀር በማለት የሰጡት ውሣኔ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 75/96 አንቀጽ 72 አንቀጽ 102 እና አንቀጽ 103 ድንጋጌዎችን ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 1 ባልና ሚስት በፍች ወቅት እኩል መብት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ የተደነገገውንና ይህ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በሰበር መዝገበ ቁጥር 51893 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያልተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሀዋሣ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ሣያርሙ ማሳለፋቸውና ማፅናታቸው ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና ይህ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ (በሰበር መዝገብ ቁጥር 51893) የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ያልተከተለና የአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 ድንጋጌን የሚጥስ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሀዋሣ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ስለኮንዶማኒየም ቤቱ የሰጡት የውሣኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡
2. የኮንዶሚኒየም ቤቱ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ የኮንዶማኒየም ቤቱን እና ቀሪው የባንክ ዕዳ አከፋፈል ስርአት ላይ ከተስማሙ በስምምነታቸው መሰረት ይፈፀም፡፡ አመልካችና ተጠሪ ካልተስማሙና ቤቱን በአይነት ለማካፈል የሚቻል ከሆነ አመልካችና ተጠሪ ቤቱን በአይነት ይካፈሉ ዕዳውን ይክፈሉ፡፡ ቤቱን ከላይ በተገለፁት ሁለት መንገዶች ለማካፈል የማይቻል ከሆነ በሀራጅ ተሽጦ ቀሪው የባንክ ዕዳ ከተከፈለ በኋላ የሚተርፈውን ገንዘበ አመልካችና ተጠሪ እኩል መካፈል ይገባቸዋል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 77169

ጥር 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንገሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-እነ አቶ ተሾመ ገበየሁ ከጠበቃ አያው ካሣዬ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሊሻንወርቅ ገበየሁ - ጠበቃ ሚደቅሳ ባየሣ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወራሽነት ድርሻ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባሁኑ ተጠሪዎች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካቾች የስር አቤቱታ ይዘትም ወላጅ አባታቸው አቶ ገበየሁ ወልደአብ እና ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ ዘረፋ ኃይለኛ ወራሽ መሆናቸው መረጋገጡን ጠቅሰውና የአባታቸውና የእናታቸው የውርስ ንብረት መለየት ያለበት መሆኑን ገልጸው የውርስ ንብረቱ እንዲጣራ የውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚሳይ ነው፡፡ ተጠሪዎችም በአመልካች ጥያቄ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ውርሱ እንዲጣራና የውርስ አጣሪ እንዲሾም የፈለጉ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማሳወቃቸው ፍርድ ቤቱን አጣሪውን ሹሞ ውርሱ እንዲጣራ ያደረገ ሲሆን አጣሪውም የውርስ ሪፖርቱን ለፍርድ ቤቱ አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም በቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጎ የአሁኑ አመልካቾች የውርስ ሪፖርቱ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን የገለጹ ሲሆን ተጠሪዎች ግን ሟች ገበየሁ ወልደአብ የተዉት ኑዛዜ ቀድሞ በፍርድ ቤት ክርክር ተደርጎበት ፈራሽ ባልተባለበት ሁኔታ በውርስ አጣሪ መነቀፉ ያላግባብ ነው በማለት አስያየታቸውን የሰጡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የሟች አቶ ገበየሁ ወልደአብ የውርስ ንብረት ለወራሾች መለየት ያለበት በኑዛዜው መሰረት መሆኑን፣የሟች ወ/ሮ ዘረፋ ኃይለኛ የውርስ ንብረት ግን በሕጉ መሰረት ለወራሾች ሊከፋፈል እንደሚገባ ገልጾ የውርስ አጣሪውን ሪፖርት አሻሽሎ አፅድቆታል፡፡በዚህ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበውም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካቾች ሟች አቶ ገበየሁ ወልደአብ ባደረጉት ኑዛዜ ተቃውሞ ማቅረብ እንደሚችሉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበት እያለ ኑዛዜው አመልካቾችን በመንግስት ባዶ ይዞታ ላይ ብቻ መብት እንዳላቸው በመግለጽ አመልካቾችን ከውርሱ የነቀለ በመሆኑና የጎዳ መሆኑን ጠቅሰን ተከራክረን የበታች ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው ላይ ቀድሞ ክርክር ተደርጎ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የጸና ስለሆነ የሚቹ ንብረት በኑዛዜው መሰረት ክፍፍል ሊደረግበት ይገባል በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም የስር ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች ኑዛዜው ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ሳያስተናግዱ በኑዛዜው ዙሪያ አጣሪው ያቀረበውን ሪፖርት ውድቅ በማድረግ ብቻ ማለፋቸው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ በሰጡት መልስ የኑዛዜው ሕጋዊነት ቀድሞ ያለቀ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች ክፍፍሉ የሚፈፀምበት አግባብ በኑዛዜ ነው በማለት መወሰናቸው ተገቢነት ያለው ጭብጥ በመያዝና ህጋዊ ምክንያት በመስጠት ነው ሲሉ ውሳኔው እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጠተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ሰኔ 20 ቀን 1998 ዓ/ም ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያስጸደቁትንና ሟች አቶ ገበየሁ ወልደአብ በ24/1986 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ እንዲሻርላቸው በርካታ ምክንያቶችን በመጥቀስ የመቃወም አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቁኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካቾች ከአቀረቧቸው በርካታ ምክንያቶች ውስጥ ኑዛዜው የተደረገው ክፍፍል ባልተደረገበት የባልና ሚስት ንብረት በመሆኑ አፈጻጸሙን አስቸጋሪ የሚያደርገው ነው በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 865(2) ድንጋጌን ጠቅሶ ኑዛዜውን ፈራሽ ነው በማለት በመ/ቁጥር 72097 የወሰነ ሲሆን በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮና ጉዳዩን መርምሮ ኑዛዜው በጋራ ሀብት ላይ መደረጉ ኑዛዜውን እንዳይፈጸም የሚያደርገው ምክንያት ወይም ኑዛዜው በዚህ ምክንያት ውድቅ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ በመ/ቁጥር 03897 መወሰኑን እንዲሁም ይህ ውሳኔ በአመልካቾች አቤቱታ አቅራቢነት በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 05986 ከመጽናቱም በላይ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎትም በመ/ቁጥር 49226 በሆነው በጉዳዩ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት መዝገቡን መዝጋቱን ነው፡፡እንግዲህ አመልካቾች በኑዛዜው ሕጋዊነት ላይ ክርክር ከማቅረብ የሚከለክል ሁኔታ የለም በማለት በሚከራከሩት የተጠሪ የኑዛዜ ወራሽነት በዚህ መልኩ ከተጠናቀቀ በኋላ በውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጊዜ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡አመልካቾች አሁን ለዚህ ችሎት በሰጡት የመልስ መልስ ላይ ግልጽ በማድረግ የተከራከሩት አሁን ያቀረቡት ክርክር የኑዛዜውን ፎርማሊቲ በተመለከተ ሳይሆን ከሟች አባታቸው የውርስ ንብረት የተነቀሉና ከ1/4ኛ በታች ሊደርሰን አይገባም በማለት ነው በሚል ነው፡፡የአመልካቾች ክርክር ይህ ከሆነ ኑዛዜው አመልካቾችን ከውርስ ሀብቱ ነቅሏል? ወይስ አልነቀለም?፣ለአመልካቾች የተሰጠው ድርሻስ ከውርስ ንብረቱ ሊደርስ ይችል ከነበረው ንብረት ውስጥ ከ1/4ኛ በታች ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ ኑዛዜ የሕጉን ፎርማሊቲ የጠበቀ ነው ተብሎ በፍርድ ቤት መፅደቅ ኑዛዜው መብታቸውን ይነካል በማለት ክርክር የሚያቀርቡ ወገኖች ይህንኑ ክርክራቸውን በዳኝነት አካሉ ከማቅረብ የማይከለከሉ ስለመሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17058 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

አመልካቾች ባሁኑ የክርክር ደረጃ የሟች ኑዛዜ ከውርስ ነቅሎናል በማለት የሚቃወሙ ሲሆን ይህ የክርክር ነጥባቸው ግን በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለተጠሪ የተሰጠውን የኑዛዜ ወራሽነት ለማሰረዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቃውሞ ሲያቀርቡ ሚች አባታችን ኑዛዜ አላደረጉም፣ማድረጋቸውንም አልሰማንም፣ ኑዛዜው በሞቱ በአርባኛው ቀንም አልተነበበም፣ ሚቹ አባታችን ኑዛዜ ያደረጉበት ሀብት በሚች እናታችን የጋራ ሀብት ላይ በመሆኑ ተፈጻሚነት የለውም፣ ኑዛዜው የተደረገው የመንግስት ሀብት በሆነው ባዶ ቦታ ላይ በመሆኑ ሕጉን ይቃረናል በማለት ተከራክረው ፍርድ ቤቱ ሚቹ ባዶ ቦታው ላይ ያላቸውን የይዞታ መብት ለአመልካቾች መናዘዛቸው ሕጉን የሚቃረንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ውድቅ ያደረገባቸው መሆኑና ኑዛዜው ሕጋዊ ነው ተብሎ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት ከመወሰኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ ይህ የውሳኔ ክፍል ለአመልካቾች የተሰጠውን ባዶ ቦታ ተገቢነትን የሚያረጋገጥ ነው፡፡ አመልካቾች ይህ ባዶ ቦታ ይዞታ መብት ሊተላለፍላቸው ይገባል ተብሎ በፍርድ ከተቋጨ ደግሞ ኑዛዜው ከውርስ ንብረት ነቅሎናል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1123 መሰረት ከ1/4ኛ በታች ሊደርሰን አይገባም በማለት የሚያቀርቡት ክርክርም ቀድሞ ይሰጣቸው የተባለው የይዞታ መብት መጠንና የሚቹን ለተጠሪ ይተላለፍ የተባለውን የውርስ ንብረት ግምት በማነፃጸር በግልፅ ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ ቀድሞውንም ቢሆንም የክርክር ነጥብ ለማድረግ እየቻሉ ኑዛዜው ሕጋዊ ነው ተብሎ የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ማንሳታቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 216 እና 217 ድንጋጌዎች ይዘት፣ መንፈስና አላማ ውጪ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በፍርድ ቤት በጸደቀ ኑዛዜ ላይ ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል ተብሎ የተወሰነው ማስረጃውን በመቃወም አቤቱታ አቅርቦ ክርክር ተካሂዶ የመቃወም አቤቱታ በዝርዝር ታይቶ ውድቅ የሆነበትን ወገን ሳይሆን በፍርድ ቤት የፀደቀን ማስረጃ መሰረት አድርጎ የሚችን መብቶች ለመውሰድ ተገቢውን እንቅስቃሴ የሚያደርገው ወራሽ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ማስረጃው በተሰጠበት መዝገብ ላይ ተቃውሞ አቅርቦ የተቃውሞ ምክንያቶች በዝርዝር ታይተው ውድቅ ከሆኑና ኑዛዜው ተፈፃሚነት አለው ከተባለ በኋላ በንብረት ክፍፍሉ ጊዜም የቀድሞ የተቃውሞ መሰረት የሆኑትን ነጥቦችንና የተቃውሞ አቤቱታ በቀረበበት ወቅትም የክርክሩ አካል ሊሆኑ ይገባቸው የነበሩትን ነጥቦች ሁሉ እንደገና አንስቶ እንዲከራከር ማድረግ ክርክሩ መቋጫ እንዳይኖረው የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ከፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አይነተኛ ዓላማ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም ሚች አቶ ገበየሁ ወልደአብ በህጉ አግባብ ስለማድረጋቸው የተረጋገጠው ኑዛዜ ሊከበርላቸው ስለሚገባና ለአመልካቾችም በሕጉ በውርስ ለማስተላልፍ ክልከላ ያልተደረገበትን የይዞታ ቦታ እንዲሠጣቸው የተናዘዙ በመሆኑ አመልካቾች የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ አመልካቾች የኑዛዜውን ሕጋዊነት በተመለከተ የመቃወም ማመልከቻ በአቀረቡበት ጊዜ ተከራክረውበት ሚችም በኑዛዜው ላይ ለአመልካቾች ባዶ ቦታ መስጠት የሚችሉ መሆኑ ተጠቅሶ ኑዛዜው ተቀባይነት ከአገኘ በኋላ ከሚች ውርስ ተነቅለናል፣ ከ 1/4ኛ በታች ሊደርሰን አይገባም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ጉዳዩ ቀድሞ ያለቀ ነው በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች ማለፋቸው ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 79551 የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 107569 ጥር 04 ቀን 2004 ዓ.ም. የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የሚች አቶ ገበየሁ ወልደአብ የውርስ ንብረት ሚቹ በ24/12/1986 ዓ.ም. ባደረጉት ኑዛዜ መሰረት ሊከፋፈል ይገባል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 74791

ጥር 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ረታ ቶሎሣ
መስጠፋ አሕመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ውቢት ሕሩይ ተወካይ ሰብለ ገብሩ ቀረበ

ተጠሪ ፡- የሀዋሣ ከተማ ፋይናንስ እና ኢኮኖማ ልማት ጽ/ቤት ዐ/ሕግ አቶ ዮሐንስ አሉላ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በሌሎች ወገኖች መካከል ይደረግ በነበረው የአፈፃፀም ክርክር ሶስተኛ ወገን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት በቀረበው መቃወሚያ ላይ የተሰጠ ውሣኔን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሃዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የፍ/ባለመበት የነበረው የአሁን ተጠሪ ሲሆን የፍ/ባለእዳ ደግም የሰበር ክርክሩ አካል ያልሆነውና የአሁኗ አመልካች ባለቤት የነበረው አቶ ዝቋላ ሙሉጌታ የተባለ ግለሰብ ነው፡፡ አቶ ዝቋላ ሙሉጌታ ከሌሎች ተባባሪዎቿ ጋር ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀትና በመገልገል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሀዋሣ ቅርንጫፍ ከሚገኘው የአሁኑ ተጠሪ ሒሣብ ውስጥ ወጪ አድርገው ለወሰዱት ገንዘብ በወንጀል የተቀጡ ከመሆኑም በላይ ከተባባሪዎቹ ጋር በድምሩ ብር 3,005,002.03 (ሶስት ሚሊዮን አምስት ሺህ ሁለት ብር 03/100) እንዲከፍል በፍ.መ.ቁ.. 09336 በ11/06/03 ውሣኔ የተሰጠበት ሲሆን ገንዘቡን ወጪ አድርገው ወስደዋል የተባሉበት ከ2001 ዓ.ም. መጨረሻ እስከ 2002 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 ድንጋጌ መሠረት በ30/10/03 ዓ.ም. የተፃፈ መቃወሚያ ያቀረበችውም ተጠሪ ከላይ የተጠቀሰውን ፍርድ ለማስፈፀም ቁጥሩ 10106 የሆነ የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍቶ ፍ/ባለእዳው ሥም የሚታወቅ አንድ ቤት እና በፍ/ባለዕዳው ባለቤት ማለትም በአሁኗ አመልካች ስም የሚታወቅ ሌላ ቤት በሀራጅ ተሸጠው ለአፈፃፀም እንዲውሉ ጥያቄ አቅርቦ ትእዛዝ በመሰጠቱ ሲሆን የመቃወሚያው ይዘትም ባጭሩ እዳው የተጋቢዎች የጋራ እና ለትዳር ጥቅም የዋለ ሣይሆን የፍ/ባለእዳው በግሉ በወንጀል ድርጊት ምክንያት ያመጣው በመሆኑ ምክንያት በፍ/ባለእዳው ስም ከተመዘገበው ቤት ውስጥ ድርሻዬ በሆነው በግማሹ ላይ እና በስሜ በተመዘገበው የግል ንብረቴ በሆነው ቤት ላይ ሊፈፀም አይገባምውም የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ08/11/03 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 72(1)እና (2) መሰረት ንብረቱ በእንዳቸው የተመዘገበ ቢሆንም የጋራቸው እንደሆነ እንደሚቆጠር በስሚ የተመዘገበ ቢሆንም የጋራቸው እንደሆነ እንደሚቆጠር በስሚ የተዘመገበው ቤት የግል ንብረቷ ስለመሆኑ ያቀረበችው ማስረጃ እንደሌለ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 79(1) እና (2) መሠረት ከተጋቢዎቹ በአንዱ ብቻ የመጣ እዳ ከተጋቢዎቹ የጋራ ሃብትና ከዚያም አልፎ እዳው ባልተሸፈነበት ጊዜ ከተጋቢዎቹ የግል ሀብት ጭምር ሊከፈል እንደሚችል በዝርዝር በመግለጽ መቃወሚያው ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

የከተማው ከፍተኛ ፍ/ቤትም የመቃወሚያ ክርክሩን ከመረመረ በኃላ ተቃዋሚዋ በስሚ የተመዘገበው ቤት የግሏ መሆኑን ስላለስረዳች ሁለቱም ቤቶች የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ናቸው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 79(2) መሠረተ እዳው ለጋራ ጥቅም የዋለ መሆኑን የፍርድ ባለመብቱ ስላስረዱ ተቃዋሚዋ ከሁለቱም ቤቶች ያላት ድርሻ ለእዳው መክፈያነት ሊውል አይገባም በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በፍ/ባለመብቱ ጠያቂነት የቀረበለትን ይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኃላ ከተጋቢዎቹ ከአንዳቸው በግል የሚጠይቀው እዳ የሚከፈለው ከባለእዳው ተጋቢ የግል ሀብት መሆኑ የግል ሃብቱ እዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ በጋራ ሃብታቸው መሆኑ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 79(1) ተደንግጐ የሚገኝ መሆኑን ገልፆ ግማሽ ድርሻዋ ሊጠበቅላት ይገባል ሲል የሥር ፍ/ቤት ግማሽ ድርሻዋ ሊጠበቅላት ይገባል ሲል የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በማሻሻል የፍ/ባለዕዳውን ንብረት እዳውን የማይሸፍን ከሆነ የጋራ ሃብታቸው ተሸጦ ለአፈፃፀም ሊውል ይገባል በማለት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎትም ይህንኑ ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የአሁኗ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበችው የጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊሻሩ ይገባል በማለት ሲሆን በ25/03/04 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘትም ባጭሩ እዳው በአንዱ ተጋቢ የወንጀል ድርጊት የመጣ መሆኑ እንዳልተካደ፣ ከፍ/ባለእዳው ጋር ተጣልተው በ1999 ዓ.ም ጠፍታ ወደ ዱባይ እንደሄደች የፍ/ባለዕዳ በ2001 ዓ.ም. የመጥፋት ውሣኔ እንደተሠጠባት የመጥፋት ውሣኔ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 84(ሀ) መሠረት ጋብቻውን የሚያፈርስ ምክንያት እንደሆነ፣ ድጋሚ እንዳልተጋቡ፣ እዳው የመጣው ከመጥፋት ውሣኔው በኃላ ጋብቻው በፈረሰበት ጊዜ እንደሆነ እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 39837 የተሠጠው ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት እንዳለው የሚከራከር ነው፡፡ ተጠሪው በበኩሉ በ08/05/04 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ የመጥፋት ውሣኔ ከተሰጠ በኃላ አመልካቿ ቀርባ የመጥፋት ውሣኔውን ከነ ውጤት ያሻረች በመሆኑ ምክንያት ፍቺ እንዳልተፈፀመና እዳውም የመጣው በጋብቻ ጊዜ እንደሆነ የሚቆጠረ መሆኑን ጋብቻው መፍረሱን አመልካች ያላስረዳች መሆኑን በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 39837 የተሰጠው ውሣኔ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ በአንዱ ተጋቢ የመጣ እዳ አከፋፈልን የሚመለከት በመሆኑ ምክንያት የሚያግፈው የአመልካችን ሣይሆን የተጠራን የክርክር አቋም መሆኑን እና በነዚህም ምክንያቶች አቤቱታው የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አለመሆኑን ገልፆ የተከራከረ ሲሆን አመልካችም በ25/05/04 የተፃፈ የመልስ መልስ ሰጥታለች፡፡
የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው እዳ የሥር የፍ/ባለእዳ በወንጀል ድርጊት ጭምር ጥፋተኛ በተባለበት ሁኔታ የመጣ የግል እዳ መሆኑ በተጠሪ ያልተካደና በማስረጃም የተረጋገጠ ሲሆን በአንድ በኩል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት መቃወሚያው የቀረበለት የሃዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳዩን ቀጥለው የተመለከቱት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች በጉዳዩ ላይ የተለያየ ውሣኔ የሰጡት ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ እዳ ሊፈፀም ስለሚችልበት ሃብት በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 79 የተመለከተውን ድንጋጌ በተለየየ ሁኔታ በመተርጉም መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሠረቱ በድንጋጌው ውስጥ ".....ከባል ወይም ከሚስት....." በሚል የተቀመጠው ሐረግ መነሻ የሚያደርገው የጋብቻ መኖርን በመሆኑ ድንጋጌው ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው እዳው የመጣው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በሰበር አቤቱታ በሥር ከፍ/ባለእዳ ጋር ተጣልታ በ1999 ዓ.ም ጠፍታ ወደ ዱባይ ሃገር መሄዷን የፍ/ባለእዳው በ2001 ዓ.ም የመጥፋት ውሣኔ እንደሰጠበት፣ የመጥፋት ውሣኔው በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 84(ሀ) መሠረት ጋብቻን የማፍረስ ውጤት እንደሚያስከትል ከዚህ በኃላ ተመልሰው እንዳልተጋቡ እና እዳው የመጣው ከመጥፋት ወሣኔው በኋላ ጋብቻው በፈረሰበት ጊዜ እንደሆነ በዝርዝር በመግለጽ የተከራከረች ሲሆን ተጠሪውም በሰጠው መልስ እነዚህን ፍሬ ነገሮች ሣይክድ ነገር ግን አመልካች የመጥፋት ውሣኔውን ያሻረችው በመሆኑና የመጥፋት ወሣኔው መሻር ደግሞ የጋብቻ መፍረስን ጨምሮ የመጥፋት ውሣኔው ያስከተላቸውን ውጤቶች የሚሽር በመሆኑ ምክንያት ወንጀሉ የተደረገውም ሆነ እዳው የመጣው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ እንደሆነ ግምት ስለሚወሰድበት እና ጋብቻው በሕጉ አግባብ የፈረሰ ስለመሆኑ ያቀረባቸው ማስረጃ ስለሌለ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ይሁን እንጂ የመጥፋት ውሣኔ ውጤት ማስከተል የሚያቆምባቸው ሁኔታዎች እና ጠፋ የተባለው ሰው መመለስ የሚያስከትለው ውጤት በፍ/ሕ/ቁ. 170 እና 171 የተመለከተ ሲሆን በተለይ ለተያዘው ጉዳይ ቀጥኛ አግባብነት ያለው የፍ/ሕ/ቁ. 171 የመጥፋት ውሣኔ ከተሰጠበት በኃላ የሚመለስ ሰው በንብረቶቿ ላይ የነበረውን መብት መልሶ እንደሚጐናፀፍ የሚገልጽ ከመሆኑ በስተቀር ቀደም ሲል ጋብቻ የነበረው ከሆነ ጠፋ በመባሉ ምክንያት ፈርሶ የነበረው ጋብቻው ተመልሶ ሕይወት የሚዘራ ስለመሆኑ የሚጠቁመው ነገር የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የመጥፋት ውሣኔውን ማሻሯ የፈረሰውን ጋብቻ ከፈረሰበት ቀን ጀምሮም ሆነ ከተመለሰችበት ቀን ጀምሮ መልሶ የሚያቋቁመው ባለመሆኑ እዳው የመጣው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ እንደሆነ ይገመታል በማለት ተጠሪው ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ጋብቻው በሕጉ አግባብ የፈረሰ ስለመሆኑ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የለም በማለት ከተጠሪ የቀረበውን የክርክር ነጥብ በተመለከተ ከላይ እንደተገለፀው የመጥፋት ውሣኔ የሚያስከትለው የጋብቻ መፍረስ ውጤት ዘላቂነት ያለው እንጂ ጠፋ የተባለውን ሰው መመለስ ተከትሎ የሚሰረዝ ባለመሆኑ አመልካች ማቅረብ የሚጠበቅበት ማስረጃ አይኖርም፡፡ ይልቁንም አመልካች ከተመለሰች በኃላ የቀድሞ ባለቤታ ከሆነው የሥር የፍ/ባለእዳ ጋር አዲስ ጋብቻ ፈጽመዋል ወይም በቀድሞው ሁኔታ በትዳር መኖር ቀጥለዋል ጠግል ከሆነ ይህንን ማስረዳት የሚጠበቅበት ተጠሪው ሲሆን በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም ሁኔታ እዳው ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ በሥር የፍ/ባለእዳ በግል የመጣ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 79 ድንጋጌ ለጉዳዩ አገባብነት ሊኖረው የሚችልበትም ሆነ ካልተከፍለው የጋራ ሃብት ውስጥ አመልካች ያላት ግማሽ ድርሻ ለእዳው ማስፈፀሚያ ሊሆን የሚችልበትን የሕግ አግባብ ባለመኖሩ የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ጉዳዩን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 79 አፈፃፀም ጋር ያላግባብ በማያያዝ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል የሐዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ተቃዋሚ ከሁለቱም ቤቶች ያላት ድርሻ ለእዳው መክፈያ ሊውል አይገባም በማለት ለሰጠው ውሣኔ የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 79 ድንጋጌ በምክንያትነት መጥቀሱ ስህተት ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ውሣኔው ተገቢ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 55591 በ22/03/04 ዓ.ም. ያፀናው ውሣኔ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሀዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 10106 በ27/11/03 ዓ.ም. የሰጠው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 73247

ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
አዳነ ንጉሴ
ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ልዑል ኪዳነማሪያም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ሰብለ ኪዳነ ማሪያም ጠበቃ ሙሉጌታ ፀግዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ይገባኛል ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች አቶ ሚካኤል ኪዳነ ማሪያምና አቶ አለም ገ/መስቀል ኪዳነ ማሪያም ከተባሉ ግለሰቦች ጋር በመሆን የሟች በሻይ ኪዳነ ማሪያምን የውርስ ንብረት በማጣራት የውርስ ንብረቱ ስመ ሀብቱ በወራሾች ስም እንዲዞር አድርገው የወራሽነት ማስረጃ በያዛቸው የአሁኑ ተጠሪዎች ይህ የወራሽነት ማስረጃ ተጠሪዎች በማያውቁት ሁኔታ በ26/07/1964 ዓ.ም. በስጦታ ባገኙት በአዲግራት ከተማ በ43 ካ.ሜትር ላይ በሰፈረው የንግድ ቤት ጭምር ተደርጎ ይኼው ንብረት ወደ ወራሾች ስም እንዲዞር መደረጉ ያላግባብ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አግባብ ባቀረቡት የተቃውሞ አቤቱታ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችና ሌሎች የወራሽነት ማስረጃውን የወሰዱት ወራሾች ለተጠሪዎች የተቀውሞ አቤቱታ በሰጡት መልስም የተጠሪዎች እናት ከሟች በሻይ ኪዳነ ማሪያም ጋር ትዳር ያልነበራቸው መሆኑን ቀድሞ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑን፣ በወራሽነት ማስረጃውም የሟቹ አስራ ሶስቱ ወራሾች ተጠቅሰው መገኘታቸውን፣አከራካሪው ቤት በስጦታ ተሰጥቶናል የሚሉትም ከእውነት የራቀ መሆኑንና ስጦታ ከሆነም በውልና ማስረጃ ቀርቦ በርስተ መዝገብ ካልተመዘገበ ዋጋ የሌለው መሆኑን ፣በቤቱና በቦታው ላይ ከተጠሪዎች እናት ጋር ተከራክረው የተጠሪዎች እናት መብት የሌላቸው መሆኑ መረጋገጡንና ውሳኔው ያልተለወጠ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ቤት መጋቢት 26 ቀን 1964 ዓ.ም. ለተጠሪዎች ስጦታ ተደርጎ በጥር 08 ቀን 1972 ዓ;ም በቤተዘመድ ሽምግልና ጸድቆ ያለ መሆኑ እንዲሁም በፍርድ ቤት ፀድቆ እስከ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ደርሶ መዕደቁ መረጋገጡን በምክንያት ይዞ አከራካሪው የንግድ ቤት ለተጠሪዎች ሊሆን ይገባል ሲል በዚህ ረገድ የተሰጠውን የወራሽነት ማስረጃ ክፍል እንዲሰረዝ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካችና ሌሎች ወራሾች ይግባኛቸውን ለአዲግራት ማእ/ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ክርክሩን ያስነሳው የንግድ ድርጅት ቤት በሚች በሻይ ኪዳነ ማሪያም ስም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እስከሆነ ድረስ አመልካችና ሌሎች ወራሾች የያዙት የወራሽነት ሰርተፊኬት ተጠሪዎች መብታቸውን ከማስከበር የሚከለክል ምክንያት በሌለበት ሁኔታ እንዲሰረዝ መወሰኑ ያላግባብ ነው፣ተጠሪዎች ንብረቱ ላይ ክስ በማቅረብ መብታቸውን ሊያስጠብቁ ይችላሉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ ከተጠሪዎች እናት ጋር ቀድሞ ተከራክረው በፍርድ ጉዳዩ አልቆ እያለ ይኼው ታልፎ ንብረቱ የተጠሪዎች ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪዎች እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት ያነሱት ተቃውሞ በበታች ፍርድ ቤቶች መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች አመልካችና ሌሎች የስር የተቃውሞ አቤቱታ ተጠሪዎች የነበሩት ወራሾች በአከራካሪው ቤት ላይ ያገኙት የወራሽነት ሰርተፊኬት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው የሚጠይቁት በአዲግራት ከተማ በ43 ካ/ሜትር ስፋት ባለው ቦታ በሰፈረው የንግድ ቤትን በ1964 ዓ.ም. አባታቸው ሟች ባሻይ ኪዳነ ማሪያም በስጦታ የሰጧቸውና ስጦታውም በሕጉ አግባብ ፀድቆ ያለ መሆኑን ገልፀው መሆኑን፣አመልካች በንብረቱ ላይ ከተጠሪዎች ወላጅ እናት ጋር ተከራክረን ያለቀ ነው ቢሉም ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ከአመልካች እናት ጋር ሲከራከሩ የነበሩበት በሌላ ንብረት ከመሆኑም በላይ ክርክሩ ተደርጓል ቢባልም ተጠሪዎችን የማይመለከት መሆኑን ጠቅሰው የአመልካችን ክርክር ያለፉት መሆኑን፣አመልካች የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ክስ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር163/1993 ግንቦት 02 ቀን 1993 ዓ.ም. በ26/07/1964 ዓ.ም. የተደረገው ስጦታ ሊፈርስ አይገባም በማለት መወሰኑን፣ከዚህ ጊዜ በፊትም በ1972 ዓ.ም. ስጦታው በሕጉ አግባብ የፀደቀ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ወራሽ ከሕግ ውጪ፣ ወራሽነት በሌለው መብት ላይ የወራሽነት ሰርቲፊኬት ማስረጃ መያዙ ከተረጋገጠ ይኼው ማስረጃ ሊሰረዝ እንደሚገባ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 998 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ክርክር ዳግም ክስ ሊቀርብበት የማይገባው በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች በተመሳሳይ ፍሬ ነገሮችና የህግ ነጥቦች ላይ ክርክር ተደርጎ እልባት ማግኘቱ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 5(1) ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ከተጠሪዎች እናት ጋር ክርክር አድርገው የመጨረሻ እልባት የተሰጠበት ካለመሆኑ በላይ በቤቱ ላይ ሟቹ ስጦታ ያደረጉት ልጆቻቸው ስለመሆናቸው የተረጋገጠው ለተጠሪዎች በመሆኑ የተጠሪዎች እናት በንብረቱ ላይ መብት የላቸውም ተብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መወሰኑ ተጠሪዎች የሚያነሱትን የሕግ ክርክር ዋጋ የሚያሳጣበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪዎች አለን የሚሉት የስጦታ ውል በተለያዩ ጊዜያትና ፍርድ ቤቶች ጸድቆ ተጠሪዎች በአከራካሪው ንብረት ላይ መብት ያላቸው መሆኑ መረጋገጡ አመልካች እና ሌሎች ወራሾች በንብረቱ ላይ የወሰዱትን የወራሽነት ማስረጃ ለመሻር ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 998(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በንብረቱ ላይ በ1984 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ ተረክቤአለሁ የሚሉት የመከራከሪያ ነጥብ የክርክሩን ሂደትና ይዘት ያላገናዘበና በበታች ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ ግልፅ የሆነ መከራከሪያ ሳያቀርቡ በዚህ የሰበር ደረጃ ያነሱት አዲስ ክርክር በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) ድንጋጌ አንጻር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ክርክር ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻልበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 42006 ሚያዚያ 10 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 46439 ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በአከራካሪው የንግድ ድርጅት ቤት ላይ የወሰዱት የወራሽነት ሰርቲፊኬት ማስረጃ እንዲሰረዝ ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉምሩክ/ግብር ታክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 71070

መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አመልካች፡- ተሾአብ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ አወቀ ውቤ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐ/ሕግ ኃ/መለኮት አበበ ቀረቡ

መዝገቡን ምርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ የይርጋ የጊዜ ገደብ አቆጣጠርን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ከቱርክ አገር ዘጠና ሶስት ጥቅል (በንድል) የአርማታ ብረት ለማስገባት ታክስና ቀረጥ ከፍያለሁ፡፡ በመጀመሪያ ዙር ሰላሣ ስድስት ጥቅል ብረት ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም ተረክቤ ወስጃለሁ፡፡ በሁለተኛው ዙር አምሳ አራት ጥቅል ብረት የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ወስጃለሁ፡፡ በሁለት ዙር ይገባል ተብሎ ከሚጠበቀው ዘጠና ሶስት ጥቅል ሶስት ጥቅል ብረት መጥፋቱ ተረጋግጦ ነሐሴ 21 ቀን 2001 ዓ.ም ደብዳቤ ተፅፎ ዋጋው ከኢንሹራንስ ኩባንያው ተከፍሎኛል፡፡ተጠሪ ዴክራላሲዮን እንድበተን መስከረም 30 ቀን 2002 ዓ.ም ጠይቋል፡፡ ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም ተጠሪ ማስረጃ ሰጥቶናል፡፡ ስለዚህ በስህተት የከፈልኩት ብር 273,503.92 (ሁለት መቶ ሰባ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሶስት ብር ከዘጠና ሁለት ሣንቲም) እንዲመልስ ውሣኔ ይሰጠልኝ በማለት የቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ የተለያዩ መከራከሪያዎችን ያቀረበ ሲሆን በዋናነት ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ከገባና የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈፅሞበት ዕቃውን ከተረከበ ከስድስት ወር በኋላ ከሣሽ ያቀረበው ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ተከራክሯል፡፡የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በሁለት ዙር የሚገባውን ጥቅል ብረት ከተረከበ የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ያላቀረበ ስለሆነ በይርጋ ይታገዳል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሀምሌ 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አለቀ የሚባለው ዲክላራሲዮን ከተበተነበት ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ የስድስት ወር ጊዜ ያላለፈ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈፀመ የሚባለው አመልካች ዕቃዎችን ተረክቦ የወሰደበት ጊዜ ነው፡፡ ዕቃዎቹ የተለቀቁት የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ነው፡፡ ክስ ያቀረበው የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መስከረም 30 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ግራ ቀኙ በዕሑፍ ካቀረቡት ክርክር በተጨማሪ ችሎቱ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሚያዚያ 22 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሰምቷል፡፡ የቃል ክርክሩ ግልባጭ ተያይዟል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በዕሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው በዕቃዎች አሰያየም፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሒሣብ አሰራር ሥህተት ምክንያት በአብላጫ የተከፈለ የቀረጥና የታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ ተጣርቶ በብልጫ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ለከፋዩ ተመላሽ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 66 ንዑስ አንቀፅ 1 ገኖርነት ያለው መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም በዚህ መሠረታዊ መርህ መሠረት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሊታይ የሚችለው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አጠናቅቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ወጭ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ከቀረበ ብቻ እንደሆነ የአዋጁ አንቀፅ 66 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት የሕግ ጭብጥ ለይርጋ የጊዜ ገደብ ለመቁጠር “ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተጠናቀቀ” የሚባለው ምን አይነት ተግባራት ተፈፅመው ሲጠናቀቁ ነው” የሚለው ነው፡፡ ይህንን ነጥሎ መወሰን “ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ” ለሚለው ቃል አዋጅ ቁጥር 622/2001 የሰጠውን ትርጓሜ ፣ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በአዋጅ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 17 “ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ማለት ወደ አገር የሚገባ ፣ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላክ ወይም ተላለፊ ዕቃ የጉምሩክ ወደብ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ከጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እስከሚወጣ ድረስ የሚከናወን ማናቸውም የጉምሩክ አፈፃፀም ሒደት እንደሆነ ትርጓሜ ተሰጥቶታል፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 66 ንዑስ አንቀፅ 29 እና በአዋጅ ቁጥር አንቀፅ 2/17/ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ጉዳይ አድርገው የሚደነግጉት ዕቃዉ የጉምሩክ ሥርዓት አሟልቶ ወደ አገር የገባበት ወይም ከአገር የወጣበትን ጊዜ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተመላሽ ታክስና ቀረጥ ከፍየበታለሁ የሚለው ዘጠና ሶስት ጥቅል /በንድል/ የቶንድኖ ብረት ወደ አገር ውስጥ የሚገባው በሁለት ዙር መሆኑና አመልካች በመጀመሪያው ዙር የተጫነውን ሰላሣ ስድስት ጥቅል /በንድል/ የቶንዲኖ ብረት ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም የጉምሩክ ሥርዓት በማሟላት ተረክቦ የወሰደና ወደ አገር ውስጥ ያስገባ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በሁለተኛው ዙር የመጣለትን ሀምሣ አራት ጥቅል ብረት ፣ መሟላት የሚገባውን ፎርማሊቲ በማሟላት የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ወደ አገር ውስጥ ማስገባቱ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የሚጠብቀው ህጋዊ ሥርዓት አሟልቶ የያዘው በሶስተኛ ዙር የሚገባ ጭነት /ዕቃ /የለም፡፡ አመልካች በሁለተኛው ዙር ውጭ አገር እንዲላክለት ካዘዘው ዕቃ ውስጥ ሶስት ጥቅል ብረት የጠፋ መሆኑ ነሐሴ 12 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 66/2/ እና አንቀፅ 2/17/ መሠረት አመልካች በሁለተኛው ዙር ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን ብረት ከጉምሩክ መጋዘን በማውጣት አስፈላጊ የሆኑ ፎርማሊቲዎች አሟልቶ ተረክቦ ወደ አገር ውስጥ ካስገባበት የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ትርፍ ቀረጥና ታክስ ከፍየበታለሁ በማለት ተመላሽ ገንዘብ የጠየቀበትን ዕቃ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚፈፀመው የጉምሩክ ሥርዓት ተጠናቅቋል፡፡ አመልካች ተመላሽ ሒሣብ ካለው ከዚህ ቀን ጀምሮ ባለው ስድስት ወራት ውስጥ መጠየቅ ሲገባው ፣ ይህ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ጥያቄውን እንዳቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ አመልካች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተጠናቅቋል መባል የሚገባው ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ቀን ሣይሆን ዴክላራሲዮን ከተበተነበት ቀን ጀምሮ መሆን ይገባዋል በማለት ያቀረበው ክርክር የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 66/2/ እና አንቀፅ 2/17/ ድንጋጌ ይዘት ፣ መንፈስና ዓላማ እንዲሁም ህግ አውጭው አዋጁን ሲያውጅ ያሰባቸውን መሠረታዊ ዓላማዎች ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ጥያቄ በይርጋ የጊዜ ገደብ ያለፈበት ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 76976

መስከረም 22 ቀን 2005ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ነ/ፈጅ አጥሉ ሀብታሙ

ተጠሪ፡- አቶ ሊሻን ከተማ ገብሬ - ተወካይ መሀመድ ሸህ ዑመር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ለጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ የእኔ ንብረት የሆነችውን የሰሌዳ ቁጥር 2-0086 የሆነች ፔጆ መኪና በሌባ ተሰርቃ ስናፈላልግ ተከሳሽ/አመልካች/ መኪናዋ ኮንትሮባንድ ዕቃ ጭና ይዣታለሁ በማለት በቁጥጥር ስር አድርጎ ይዟታል፡፡ መኪናዋ ተሰርቃ የጠፋች መሆኑን ብገልፅለትም ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ ካልከፈልክ በማለት የያዛት ስለሆነ መኪናየን እንዲለቅ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች መኪናዋ የተያዘችው ህዳር 29 ቀን 2002 ዓ.ም. ቀረጥና ግብር ያልተከፈለባቸው የልጆች ነጠላ ጫማ አምስት ካርቶን የልብስ ሣመና እና 68 ካርቶን ፌስታል ጭና ከቀብሪቢያ ወደ ጅጅጋ ስታጓጉዝ አየር ማረፊያ አካባቢ ተይዛለች፡፡ ክሳሽ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 109 መሰረት እድሉ ተሰጥቶታል፡፡ ስለዚህ ክሱ ህጋዊ መሰረትና ምክንያት የሌለው በመሆኑ ይዘጋልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ ከፍሎ መኪናው ይለቀቅለት በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ፍርድ ቤቱ ከስልጣኑ ውጭ ቅጣት ወስኗል በማለት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች የካቲት 12 ቀን 2004ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ጉዳዩ በአስተዳደራዊ ውሣኔ የሚያልቅ በመሆኑ የቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት መመሪያ አውጥቷል፡፡ መኪናዋ ስታጓጉዝ የተገኘችው ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ ክልከላ የተደረገበት ዕቃ/ፌስታል/ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ተጠሪ መክፈል የሚገባው ብር 10,000 ሣይሆን ብር 50,000 ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በህግ በተሰጠው ፈቅደ ስልጣን መሰረት ያወጣውን መመሪያ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ መጋቢት 28 ቀን 2009ዓ.ም በተሰጠ መልስ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የሰጡት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 109 ንዑስ አንቀፅ 1 ለፍርድ ቤቱ ቅጣት ለማክበድና ለመቅለል ስልጣን የሚሰጥ ፈቃጅነት ያለው ድንጋጌ መሆኑን በማገናዘብና ድንጋጌው እስከ ብር 50,000 በሚደርስ መቀጮ ስለሚል ቅጣቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዝቅ አድርጎ መወሰንን ስለማይከለክል ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሚያዚያ 29 ቀን 2004ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 109 ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸውን መመሪያዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካች ቁጥጥር ስር የዋለችው ፔጆ መኪና በሌባ ተሰርቃ እንደጠፋችበት ክርክርና ማስረጃ አቅርቧል፡፡ በሌላ በኩል ንብረትነቷ የተጠሪ የሆነችው መኪና የተያዘችው የጉምሩክ ቀርጥና ታክስ ያልተከፈለበትና ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ በህግ ክልከላ የተደረገበትን ዕቃ ስታንገዝ መሆኑን አመልካች በማስረጃ ያረጋገጠ መሆኑን በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገልጿል፡፡ የማንጓጓዣው ባለቤት በተፈፀመው ወንጀል ከራሱ ዕውቀት ወይም ፈቃድ ውጭ መሆኑን ማስረዳት ከቻለ የተፈፀመው ወንጀል ክብደት እየታየ ከብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ እስከ ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ ተቀጥቶ ማንጓጓዣው እንደሚመለስለት የአዋጅ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 1 በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም የማንጓጓዣው ባለቤት ከአስር ሺህ እስከ ሀምሣ ሺህ ብር ባለው ሬንጅ ውስጥ ሊከፍለው ስለሚገባ መቀጮ ዝርዝር አፈፃፀም የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ስለመሆኑ ድንጋጌው በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጁ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት መመሪያ ቁጥር 50/2003 በማውጣት ተግባራዊ አድርጓል፡፡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ማንጓጓዣው የተያዘው ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ ዕቃ ከሆነ የማንጓጓዣው ኃላፊ ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ መቀጮ ከፍሎ መንጓጓዣው የሚለቀቅለት መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የተጠሪ መኪና ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ ክልከላ የተደረገበት ስልሣ ስምንት ካርቶን ፌስታል ይዞ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 622 አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ባወጣው መመሪያ ቁጥር 50/2003 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በብር 50,000/ ሀምሣ ሺህ ብር/ መቀጮ መቀጣት እንዳለበት በግልፅ ተደንግጎ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ ብቻ መቀጮ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ በአዋጁ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 2 ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተሰጠውን አስገዳጅነት ያለው መመሪያ የማውጣት ስልጣን የሚጋፋና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ብር 50,000 /ሀምሣ ሺህ ብር/ መቀጮ ከፍሎ መኪናውን ይረከብ በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80296

ጥር 30 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሴ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ሳምሶን መንግሰቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያቃቤ ህግ ወኪል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ የውጭ ምንዛሬ ያለፈቃድ ከአገር የማስወጣት ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን በመጀመሪያ የታያው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ክሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጸ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እንዲሁም መንገደኞች የውጭ ምንዛሬ ወደ ኢትዮጵያ ይዘው ስለሚገቡበትና ስለሚወጡበት በብሔራዊ ባንክ ማንቦት 21 ቀን 2001 ዓ.ም የወጣውን መመሪያ አንቀጽ 3 በመተላለፍ ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 3፡30 በቦሌ አየር መንገድ ከአገር ሊወጣ ሲል 5000 ዩሮ /አምስት ሺህ ዩሮ/ ይዞ ሊወጣ ሲል በኤክስሬይ ፍተሻ የተገኘ በመሆኑ በህገወጥ መንገድ የውጭ ምንዛሬ (ዕቃ) ማውጣትና የመያዝ ወንጀል ፈጽመዋል፡፡

አመልካች ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የወንጀል ክሱን ያስረዱልኛል በማለት ሁለት የሰው ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ተጠሪ ሰነድ ማስረጃውንና ከአመልካች እጅ የተገኘውን (5000 ዩሮ) በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ አመልካች የውጭ ምንዛሬውን ለጉምሩክ አሳውቀው ዴክራላሲዮን ተሰጥቷቸው ያስገቡ መሆኑንና የውጭ ምንዛሬው ከቦርሣቸው ውስጥ ሲገኝባቸው ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ የተሰጠውን ዴክላራሲዮን ያልያዙ መሆኑንና ወንጀል የመፈፀም ሀሳብ ያልነበረው መሆኑን ያስረዳልኛል የሚላቸውን የመከላከያ ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረና ከወሰነ በኋላ አመልካች የውጭ ምንዛሬውን ይዞ ለመውጣት የተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የውጭ ምንዛሬውን ይዞ በመውጣት ላይ እያለ ተይዟል፡፡ ተከሳሽ ውጭ ምንዛሬውን ይዞ የገባው አሳውቆና አስመዝግቦ በመሆኑ የውጭ ምንዛሬውን ይዞ ለመውጣት የተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የውጭ ምንዛሬ ለማውጣት ይዞ ቢገኝ የውጭ ምንዛሬውን የማውጣት መብቱን ከሚያሳጣው በስተቀር በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዲሰጠው የመጠየቅ መብቱን እንደማያሳጣው ጉዳዩ የወንጀል ኃላፊነት እንደማያስከትል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 47935 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ እንደዚሁም ተከሳሽ በበኩል የተፈፀመው ተግባር ተከሳሽ አሳውቆና አስመዝግቦ ወደ አገር ይዞት የገባውን የውጭ ምንዛሬ ይዞ መውጣት መብት እንዳለው በመቁጠር የፈፀመውና ወንጀል የመፈፀም ሀሳብ የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ ከቀረበበት ወንጀል ክስ በነፃ ይሰናበታል፡፡ ከሳሽ ከተሰሳሽ እጅ የያዘውን ዩሮ /የውጭ ምንዛሬ/ በተያዘበት ቀን ባለው ምንዛሬ በማሰብ በብር ለተከሳሽ ክፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ መልስ ሰጭ የውጭ ምንዛሬ ይዞ ሲወጣ ሲል ተይዟል፡፡ የውጭ ምንዛሬውን ይዞ ሊወጣ ሲሞክር ዲክላራሲዮኑ ከተፃፈ የስድስት ወራት ጊዜ አልፎታል፡፡ አመልካች መልስ ሰጭ የውጭ ምንዛሬ ይዞ ሲገባ የነበረው መመሪያ መልስ ሰጭ ይዞ ለመውጣት በሚሞክርበት ጊዜ የተቀየረ ሲሆን በጉዳዩ ተፈፃሚ የሚሆነው ነው መልስ ሰጭ ለማውጣት ሲሞክር ፀንቶ ስራ ላይ የነበረው መመሪያ ነው፡፡ መልስ ሰጭ የውጭ ምንዛሬው ገደብና ቁጥጥር የሚደረግበት እቃ መሆኑን ያውቃል፡፡ ህጉን በመተላለፍ የውጭ ምንዛሬ ለማውጣት ሲሞክር በኤክስሬይ ማሽን የተያዘ በመሆኑና የተከሰሰበትን ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት በአንድ ዓመት ከስድስት ውር ጽኑ እስራት እንዲቀጣና በተያዘው 5000 ዩሮ እንዲወረስ ወስኗል፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የእስራት ቅጣቱ አፈፃፀም ለሁለት አመት ተገድቦ እንዲቆይ ወስኗል፡፡

አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 195/1/ መሰረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች ግንቦት 24 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ሰበር አቤቱታ በጉዳዩ የስር ፍርድ ቤት የከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ ይዘት ከዘረዘረ በኋላ እኔ የውጭ ምንዛሬውን ይገፍ ለመወጣት ስሞክር ስራ ላይ የነበረው መመሪያ መጀመሪያ ዩሮውን አስመስግቤ ወደ አገር ውስጥ ሳስገባ ያልነበረ ነው፡፡ የውጭ ምንዛሬ ይገፍ በምወጣበት ጊዜ አልፏል የሚባል ከሆነም በወቅቱ በነበረው የኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ ከሚሰጠኝ በስተቀር ወንጀል ሰርተሀል ተብሎ ሊወረሰብኝ አይገባም፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሣኔ በተመሳሳይ ጉዳይ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 47935 የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ያልተከተለና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ነሐሴ 25 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች 5000 ዩሮ ከአገር ለማውጣት የተያዙት በኤክስሬ ምርመራ ነው፡፡ ገንዘቡን ወደ አገር ውስጥ ሳስገባ አስመዝግቤአለሁ በማለት ዲክላራሲዮን ያቀረቡት ገንዘቡ በፍተሻ ከተያዘ በኋላ ነው፡፡ ያቀረቡት ዲክራላሲዮን ከስድስት ወራት በላይ ያለፈው ከመሆኑም በላይ አመልካች ይዞት ወደ አገር ውስጥ ያስገባቸውን ዩሮ ቁጥር የሚገልጽ አይደለም፡፡ አመልካች ወንጀል የፈፀመው ያውም ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ ሲያስገባ ሳይሆን ይዞ ለመውጣት በሞከረበት ቀን /ጊዜ/ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚ የሚሆነው ወንጀሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲፈፀም ፀንቶ ሲሰራበት የነበረው ህግና መመሪያ ነው፡፡ አመልካች ሰበር ችሎት በፍ/ብሔር ጉዳይ የሰጠውን ውሣኔ ለወንጀል ጉዳይ መከራከሪያ አድርጎ ማቅረቡ የህግ መሰረት ያለውም፡፡ ስለዚህ አመልካች ጥፋተኛ መባሉና ገንዘቡም እንዲወረስ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሰበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና ለሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የውጭ ምንዛሬ በህገወጥ መንገድ ይዞ ሲወጣ የተያዘ ጥፋተኛ በመሆኑ ገንዘቡ በወርስ ለመንግስት ገቢ ይሁን በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር የውጭ ምንዛሬ ይዞ መውጣት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 የሚያስጠይቅ መሆኑ የውጭ ምንዛሬ ከአገር ውስጥ ስለሚገባበትና ስለሚወጣበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 መመሪያ የማውጣት ስልጣን ያለው መሆኑን ከህግ ማእቀፎቹ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተጠሪ 5000 ዩሮ ከአገር ለማስወጣት ሲሞክር ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በፍተሻ የተያዘው ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ አመልካች ያለ ህጋዊ እውቅናና ፈቃድ የውጭ ምንዛሬ ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር ሲያወጣ ተይዟል በማለት የተከሰሰው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 25 በሚደነግገው መሰረት ወንጀሉ ተፈፀመበት ቦታና ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜ ማለትም ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም በመጥቀስ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ስራ ላይ የነበረው የብሔራዊ ባንኩ መመሪያ ተፈፃሚነት ይኖረዋል በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የህግ ትርጉም የህገ መንግስቱን አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የወንጀል ህጉ አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጸ 2 መሰረት ያደረገና የህግ አተረጓጎም ስህተት የሌለበት በመሆኑ አመልካች የውጭ ምንዛሬውን ወደ አገር ውስጥ ይዞ ሲገባ የነበረው መመሪያ ሌላ ስለነበረ የውጭ ምንዛሬውን ይገፎ ስውጣ ጸንቶ ስራ ላይ ያለው መመሪያ በእኔ ጉዳይ ተፈፃሚነትና ተጠቃሽነት ሊኖረው አይገባም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም ፡፡

2. አመልካች የውጭ ምንዛሬውን ከአገር ሲያወጣ የተያዘው በፍተሻ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለው በይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የውጭ ምንዛሬውን በፈቃድ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ መሆኑን ከአገር ይዞ ለመውጣት የተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ያለፈበት በመሆኑ የውጭ ምንዛሬውን ይዞ ለመውጣት እንዲፈቀድለት አሳውቆና ጥያቄ አቅርቦ ሳይሆን በቦርሳው ውስጥ በማድረግ ይዞ ሲወጣ በኤክስሬይ ፍተሻ ስለተደረገበት የተያዘ መሆኑ አላከራከረም፡፡ ይህም የአመልካች አድራጎት ያለፈቃድ የውጭ ምንዛሬ ይዞ የመወጣት ወንጀል የሚያቋቁም ስለመሆኑ ከላይ የተገለፁት የህግ ማዕቀፎችና ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 23/2/ ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች የሚያቀርበው ክርክር በወንጀል ህጉ አንቀጽ 81 ስር የሚወድቅና የውጭ ምንዛሬውን ሳያስፈቅድ ይዞ መወጣት ወንጀል መሆኑን አላውቅም የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ሆኖም ህግ አለማወቅ ይቅርታን የማያሰጥ መሆኑን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 81 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገ በመሆኑና የአመልካች አድራጎት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 81 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የማይሸፍን መሆኑን በስር ፍርድ ቤትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በይግባኝና በሰበር ከቀረበው ክርክር ለመገንዘብ የሚቻል በመሆኑ አመልካች በተከሰሰከበት ወንጀል ጥፋተኛ መባሌ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

3. አመልካች ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 45435 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንና ወ/ሮ እየሩሳሌም ወንዴን በማከራከር ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የህግ ትርጉም ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት እንዳለው በመዘርዘርና በስር ፍርድ ቤትና በሰበር የተከራከረ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ይህንን መዝገብ በመጥቀስ አመልካችን ከወንጀል ነፃ ያደረገው መሆኑን ተረድተናል፡፡ ሆኖም በሰበር መዝገብ ቁጥር 45935 በመሰረተ ባህሪው ጭብጥ የፍትሐብሔር ክርክር የተስተናገደበት መዝገብ ሲሆን የያዝነው ጉዳይ ወንጀል ተፈፀሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚል ጭብጥ ያያዘ የወንጀል መዝገብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመዝገብ ቁጥር 45935 የውጭ ምንዛሬው በተከራካሪው እጅ የነበረ ሳይሆን ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ተቀብሎ በእጁ ይዞት ያቆየው ሲሆን በያዝነው ጉዳይ አመልካች ይዞት የወጣውን 5000 ዩሮ በእጅ ይዞ ወደ አገር ውስጥ የገባ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ስለዚህ አመልካች ከጉዳዩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት በሌለው ሰበር መዝገብ ቁጥር 45435 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በመሆኑም አመልካች ከህግ ውጭ የውጭ ምንዛሬ ይዞ የመውጣት ወንጀል ሲፈጽም የተያዘነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 195 ንዑስ አንቀጽ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በህገወጥ መንገድ ከአገር ሲያወጣ የተገኘው 5000 ዩሮ /አምስት ሺህ ዩሮ/ በውርስ ለመንግስት ገቢ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 75414

ጥቅምት 22 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ ዋሪቴ ሱቡሳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. የጎልጆታ ከተማ አስተዳደር ተወካይ አቶ ቡርቃ ፈጂሶ - ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ አየለች ሞሲሳ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን ፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ለዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነውን የመጨረሻ ፍርድ የሰጠው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው ክርክር በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም በሚል የሰጠውን ዳኝነት ካከራከረው የጉዳይ ይዘት አንፃር ተመልክቶ አግባብነቱን ለማየት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች በአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ሲሆን ፤ ይዘቱም የግል ንብረቴ በሆነው ቤቴ ላይ 1ኛ ተጠሪ የጎልጆታ ከተማ አስተዳደር የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታና ኘላን አዘጋጅቶ ለ2ኛዋ ተጠሪ የሰጣት ስለሆነ ይኸው ካርታና ኘላን ሊሰረዝ ይገባል የሚል ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ በ2ኛ ተጠሪ ስም ካርታና ኘላን አዘጋጅቶ ለመስጠት የሚያስችል ማስረጃ በ2ኛ ተጠሪ መቅረቡንና ይህንኑ መሠረት አድርገን የሰጠን ስለሆነ የከሣሽ ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው ገልፆ ተከራክሯል፡፡

የአሁን 2ኛ ተጠሪም በበኩላቸው ይህ ክስ የቀረበበትን ቤት ባለቤታቸው አቶ አንኮ ሐዊያ በ1981 ዓ.ም ገዝቶታል፡፡ ከዚህ በኋላም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ ሚስትነቴንና የወራሽነት መብት በፍ/ቤት በማረጋገጤ ምክንያት የከተማው አስተዳደር ቤቱን ወደ ስሜ ያዞረው ስለሆነ የንብረቱ ባለመብት እኔ ነኝ የሚል ክርክር አቅርባለች፡፡

ፍ/ቤቱም ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የማን ነው? የሚለውን ነጥብ ለመለየት በሁለቱም ወገኖች የቀረበውን የቤት ግዥ የፅሑፍ ውል ሰነድ ፤ ግብር የተከፈለበትን ደረሰኝ እና የሰው ማስረጃዎችን ቃል ከተመለከተና ከሰማ በኋላ ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች በየፊናቸው ያቀረቧቸው ማስረጃዎችን

የማስረዳት ጥንካሬውን መርምሮና የተሻለ ማስረጃ ማን አቅርቧል የሚለውን ለመለየት ማስረጃውን መዝኖ ይኸው ቤት የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ የሆኑት የወ/ሮ ዋሪቱ ሱቡሳ መሆኑን አረጋግጧል። ይህ ቤት የወ/ሮ ዋሪቶ መሆኑ እየታወቀ የከተማው አስተዳደር ያለአንዳች ማስረጃ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታና ኘላን አዘጋጅቶ ለ2ኛ ተጠሪ በመስጠቱ ምክንያት 2ኛ ተጠሪ ያለአግባብ የንብረቱ ባለቤት እንድትሆን ያደረጋት በመሆኑ የሰጠው ካርታና ኘላን ሊሰረዝ ይገባል በማለት ወስኗል።

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘን ረገድ ተመሳሳይ ትንታኔ ተከትሎ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አፅንቷል።

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በከተማው ውስጥ የሚገኙ መሬቶችን ቤቶችን ማስተዳደርና መቆጣጠር የባለይዞታነትና የባለቤትነት ማስረጃ መስጠት የከተማው አስተዳዳር ሥልጣን ነው። የከተማው አስተዳደርም ይህንኑ ክርክር የተነሣበትን ካርታና ኘላን አዘጋጅቶ የሰጠው በዚሁ ሥልጣኑ መሠረት በመሆኑ ይህ ካርታና ኘላን የተሰጠው በስህተት ፣ አግባብ ባልሆነ መንገድ ነው የሚባል ከሆነ እራሱ ይሰርዘው ዘንድ ጥያቄው ለከተማው አስተዳደር ከሚቀርብ በቀር በፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር ሊወድቅ የሚችል ጉዳይ አይደለም ስለሆነም በገልጆታ ከተማ አስተዳደር የተሰጠው ካርታና ኘላን በመደበኛ ፍ/ቤት ሊሰረዝ አይገባም በማለት የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ሽሮታል።

ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስለጉዳዩ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡትን የክርክር ይዘት ተከትለው የሚያብራራ በመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም።

እንግዲህ የጉዳዩ አነሳስ እና አመጣጥ ከላይ በአጭር በአጭሩ የተመለከተው ሲሆን ፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል።

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሣኔው እንደገለፀው በአንድ ከተማ ውስጥ የሚገኝን መሬት የማስተዳደር የመሬትን ስሪትን እና በስሪቱ መሠረት የተገኙ መሆኑን በማረጋገጥ የተገኘባው ንብረት /ቤት/ የባለቤት ማረጋገጫ ካርታና ኘላን የመስጠት የከተማው አስተዳደር በአስተዳደር ረገድ ለከተማው አስተዳደር የተሰጠ ተግባርና ሥልጣን ስለመሆኑ ይህ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሚስማማበት ጉዳይ ነው።

ይሁን እንጂ ይህ በዚህ ጉዳይ የጎልጆታ ከተማ አስተዳደር አከናወነ የተባለው ተግባር ከዚህ በላይ የከተማው አስተዳደር የአስተዳደር ሥልጣን ነው በተባለው ሥር ሊወድቅ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለው ነጥብ ግን ሊታይ የሚገባው ነው። በከተማ አስተዳደር ከሚከናወኑ ተግባራት አንዱ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሆነ የቤት የባለቤትነት መብት ከአንዱ ወደ ሌላው በሚተላለፍበት ጊዜ ንብረቱን ለማስተላለፍ የሚያስችል ህጋዊ ተግባር የተከናወነ መሆኑን በማረጋገጥ የዚሁ ንብረት የባለቤትነት መብት ከአንድ ወደ ሌላው የተላለፈ መሆኑን የሚያረጋግጠውን የንብረት ምዝገባ ተግባር ማከናወን ነው። በዚህ አኳኋን አረጋግጦ የምዝገባ ሥርዓቱን አከናውኖ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታና ኘላኑን ንብረቱ በተላለፈለት ሰው ስም አዘጋጅቶ በሰጠ ጊዜ በስሙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካርታና ኘላን ተዘጋጅቶ የተሰጠው ሰው የዚሁ ንብረት ባለቤት እንደሆነ በህጉ ግምት እንደተወሰደ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 1195 ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በዚሁ መሠረት በህጉ የሚወሰደውን የግምት አይነት ተከታይ በሆነው ድንጋጌ በተቃራኒ ማስረጃ ማስተባበል እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡

ከዚህ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 ጋር በተያያዘ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ አስቀድሞ በከተማው አስተዳደር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 የተሰጠውን የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ የማስተባበል ሥራ የሚከናወነውና ፤ በህጉ ተሰጥቶ የነበረው የባለቤትነት ግምት ቀሪ የመሆኑና ያለመሆኑ ጉዳይ የሚረጋገጠው በፍ/ቤት የዳኝነት ተግባር ጭምር ነው፡፡

ከዚህ አንፃር አሁን በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ የተነሣውን ጉዳይ ለአመልካች ክርክር ያስነሳው ቤት ባለቤት የአሁን አመልካች እንደሆኑ የሥር የወረዳ እና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሣኔ እንደተረጋገጠ ገልፆዋል፡፡ እንዲሁም የከተማው አስተዳደር በዚሁ የአመልካች መሆኑ በተረጋገጠው ቤት ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታና ኘላን በ2ኛ ተጠሪ ስም አዘጋጅቶ ሊሰጥ የቻለው 2ኛ ተጠሪ ስለጠየቀችው እንጂ የዚህን ቤት ባለቤትነት መብት ከንብረቱ ባለቤት ወደ 2ኛ ተጠሪ የተላለፈ መሆኑን የሚያሳይ ህጋዊ ተግባር /juridical act/ መቅረቡን አረጋግጦ እንዳልሆነ በግራ ቀኙ ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡

ይህም ከሆነ ምንም እንኳ ማዘጋጃ ቤቱ በእራሱ እምነት የዚሁ ንብረት ባለበት 2ኛ ተጠሪ መሆኗን አረጋግጫለሁ በማለት የባለቤትነት የምስክር ወረቀት የሰጠ መሆኑ ቢታወቅም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 እንደተደነገገው የአሁን አመልካች ይህ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ሊሰጥ የቻለው የንብረት ባለሀብትነት መብት ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው እንዲተ መተላለፍ እንዳለበት በህጉ የተመለከተውን ደንብና ሥርዓት ሳይከተል ስለሆነ የንብረቱ ባለሀብት ስለመሆኑ የህግ ግምት መውሰጃ የሆነው የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ቀሪ ነው ፤ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ያቀረቡት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 ፣ 1196 እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና 231/1/ሀ/ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት በፍ/ቤት ሊረጋገጥ የሚችል የዳኝነት ጥያቄ እንጂ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ አይደለም ለማለት የሚያበቃ አይደለም ከዚህ አንፃር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በማግኘታችን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 129383 በቀን 16/04/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙን ያከራከረው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ በመሆኑ ይኸው የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር ሥልጣኑ ጉዳዩን ተመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ እንደተመለከለተው አስፈላጊውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን መልሰናል፡፡
3. የዚህ የፌደራል ሰበር ሰሚ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 75343

ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ በላይ ሀሰን አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመንገድ ሥራ ምክንያት ለጠፋ ንብረት /የባህርዛፍ አትክልት/ የሚከፈልን የካሣ የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች መንገድ ሲሰራ፣ ቁጥሩ 4500 የሆነ የባህርዛፍ አትክልት ላይ ውድመት ያደረሰበት መሆኑን ገልፆ ብር 165,000 /አንድ መቶ ስልሣ አምስት ሺህ ብር/ ካሣ ተከሣሹ (አመልካች) እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ተጠሪ ባህርዛፍ የተከለው ከመንገዱ መጠበቅ የሚገባውን ርቀት ሣይጠብቅ በመሆኑ በደንብ ቁ. 6/1936 መሠረት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም፡፡ የተጠየቀው የካሣ መጠን የተጋነነ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የባህርዛፍ አትክልቱ የተተከለበትን ሁኔታ፣ በመንገድ ሥራው ምክንያት የወደመው ባህርዛፍ ዋጋ በባለሙያ ተገምቦ እንዲቀርብለት በማድረግ አመልካች ለተጠሪ ብር 17,942.00 /አስራ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ ሁለት ብር/ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ተጠሪ ባህርዛፍ ወደመብኝ የሚለው ከዋና መንገድ መሐል መስመር ወደግራና ወደ ቀኝ አስራ አምስት ሜትር ስፋት ያለው መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ አስራ አምስት ሜትር ወደ ግራና ቀኝ አትክልት እንዳይተከል አዋጅ ቁጥር 65/36 የሚከለክል በመሆኑና ተጠሪ ይህንን የህግ ክልከላ በመተላለፍ፣ መጠበቅ የሚገባውን እርቀት ሣይጠበቅ ስለተከለው ባህርዛፍ ግምት የመክፍል ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመግለጽ ያቀረበው ክርክር አላግባብ ውድቅ ተደርጓል፡፡ አመልካች እንዲከፍል የተወሰነው የካሣ መጠን የተጋነነ ነው በማለት የሰበር አቤቱታ አቀርበዋል፡፡ አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ፣ እኔ ባህርዛፍ ስተክል ከመንገዱ መጠበቅ የሚገባኝን ርቀት በመጠበቅ ነው የተከልኩት፡፡ አመልካች በመንገድ ሥራ ለወደመው ባህርዛፍ በተሟላ ሁኔታ ካሣ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲከፍል አልተወሰነበትም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም አመልካች በሰበር አቤቱታው ያቀረበውን ክርክር በማጠናከር ሚያዚያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የህግ ማእቀፎች ጋር በማገናዘብ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ያለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለሙያዎቹን በመመደብ ያረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን ጭብጥ ከቦታው ድረስ በመሄድ እንዲያጣራለት የመደበው ባለሙያ፣ ተጠሪ በመንገድ ሥራ ምክንያት በመንቀል ጉዳት የደረሰበት ባህርዛፍ አትክልት የተከለበት መሬት በህጋዊ መንገድ የተሰጠው የይዞታ መሬት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በተጠሪ የእርሻ ቦታ አዋስኖኝ የሚያልፈው መንገድ፣ ተጠሪ የባህርዛፍ አትክልቱን በሚተክልበት ጊዜና አመልካች መንገዱን ለማስፋት የሚቆፍርበት ጊዜ የነበረው ደረጃ ተመሣሣይ አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ተጠሪ ባህርዛፉን በሚተክልበት ወቅት በተጠሪ የይዞታ መሬት አዋሣኝ የነበረው መንገድ የተንታ ወረዳን ከዞኑ ከተማ ደሴ ጋር ለማገናኘት ታስቦ የተገነባ መንገድ እንደነበርና መንገዱ የተንታ ወረዳን ከአዲስ አበባ ጋር የሚያገናኝ መንገድ እንዳልነበር ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የዚህን መንገድ ደረጃ ከፍ በማድረግ ተንታን ከአዲስ አበባ ጋር ለማገናኘት የሚችል መንገድ ለመገንባት ባደረገው እንቅስቃሴ ተጠሪ የመንገዱ አዋሣኝ በሆነው የይዞታ መሬት ላይ የተከለውን የባህርዛፍ አትክልት የወደመበት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

2. ተጠሪ ካሣ የጠየቀበትን ባህርዛፍ ሲተክል በእርሻ መሬት ይዞታው አዋሣኝ ላይ ተገንብቶ አገልግሎት ሲሰጥ የኖረው መንገድ ወረዳውን ከዞኑ ዋና ከተማ የሚያገናኝ መንገድ እንደነበር የተረጋገጠ ነው፡፡ የዚህ አይነት መንገድ ደረጃው የአውራ ጎዳና መንገድ እንዳልሆነና መካከለኛ መንገድ በሚለው ደረጃ ውስጥ የሚሸፈን መሆኑ የጎዳናዎችና መንገዶች አከፋፈል አዋጅ ቁጥር 66/1936 የአንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎችን በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ተጠሪ ባህርዛፍ ሲተክል፣ የመንገዱ ደረጃ መካከለኛ የነበረ በመሆኑ ተጠሪ ከግራና ከቀኝ እስከ አስራ ሶስት ሜትር ርቀት የመጠበቅ ግዴታ የለበትም፡፡ ተጠሪ ለተከለው ባህርዛፍ ካሣ እንዲያገኝ የተወሰነው ደረጃው መካከለኛ ከነበረው መንገድ ከአራት እስከ አምስት ሜትር ያለውን ርቀት በመጠበቅ የተከላቸው የባህርዛፍ ተክሎችና ቅጥያ ብቻ እንደሆነ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

አመልካች ተጠሪ ቢያንስ አስራ ሁለት ሜትር ርቀት ሣይጠብቅ ባርህዛፍ የተከለ በመሆኑ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው የሰበር ክርክር አከራካሪው መንገድ በመጀመሪያ አውራ ጎዳና ያልነበረና መካከለኛ መንገድ የነበረ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍሬ ጉዳይ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ መንገዱ መጀመሪያ ወረዳን ከዞኑ ዋና ከተማ የሚያገናኝ የነበረ መሆኑንና አመልካች መንገዱን በማስፋትና ደረጃውን ከፍ በማድረግ ወረዳውን ከአዲስ አበባ ጋር ለማገናኘት የሚችል መንገድ ሲገነባ ለተጠሪ በይዞታው በተከለው ባህርዛፍ ላይ ጉዳት ማድረሱ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር ስለመገንዶችና ድልድዮች አጠባበቅ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 65/1936 አንቀጽ 2(ሀ) እና የጎዳናዎችና መንገዶች አከፋፈል አዋጅ ቁጥር 66/1936 አንቀጽ 1(ለ) ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

3. የካሣውን መጠን በተመለከተ አመልካች በሚሠራው መንገድ ተጠሪ የወደመበት ባህርዛፍ ዋጋ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ ፣ የባህርዛፉ ዋጋ በባለሙያ ተገምቶ ቀርቦለት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ በመንገድ ሥራው ምክንያት ከወደመበት ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ የማግኘት መብት የለው መሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 8 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የህግ ማእቀፎች በተለይም ከአዋጅ ቁጥር 455/1997/ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የወሰኑት የካሣ መጠን ከላይ የጠቀስነውን የህገ መንግስት ድንጋጌ መሠረት ያደረገና አመልካች ለሰበር ችሎት የካሣውን መጠን በተመለከተ የሚያቀርበው ክርክር የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ክርክር በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ከላይ በገለጽናቸው ምክንያቶች የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልለ የደቡብ ወሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሰኔ 19 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ ቁ. 81081

ጥር 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ወ/ሮ ፍሬ ሕይወት መብራህቱ ገ/መድህን ጠበቃ ኃይሉ ደቤሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ መብራህቱ ገ/መድህን ጠበቆች አቶ ሐጐስ አብርሃና ደባባ አመንሲሣ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ደስታ ወልደጋብር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ የሌላ ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረትን ይዞ ሲጠቀም የነበረ ሰው ቤቱን ለማደስ ወጪ ማውጣቱ ቢረጋገጥ ውጪውን የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት የሆነው ሰው የሚተካበት ሕጋዊ አግባብ መኖር ያለመኖሩንና በሕጉ ሊሟሉ ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎችን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ሲሆኑ ተከሳሾች ደግሞ የአሁኑ ተጠሪዎች ናቸው፡፡የአመልካች ክስ ተጠሪዎች ወደ አሜሪካን አገር ሲሄዱ ንብረትነቱ የተጠሪዎች የሆነውንና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02 ክልል ውስጥ የሚገኘውን በቁጥሩ 593 የሚታወቀውን ቤት ይዘው ሲኖሩ የእድሳትና የማሻሻያ ፈቃድ በማውጣት የቤቱን ይዞታ በማሻሻል ከፍተኛ ወጪ ማውጣታቸውን ገልፀውና ወጪ የወጣባቸውን ምክንያቶችን አይነትና የወጪውን መጠን በመዘርዘር በድምሩ ብር 265,812.92(ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሁለት ብር ከዘጠና ሁለት ሳንቲም) ማውጣታቸውን ጠቅሰው ከቤቱ ግምት ጋር ተቻችሎ የቤቱ ስመ ሃብቱ እንዲዞርላቸውና ከቤቱ ግምት የሚተርፈውን ወጪ ደግሞ ተጠሪዎች እንዲተኩላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአሁኑ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የአመልካች የወጪ ይተካልኝ ጥያቄ የህግ መሰረት የሌለው መሆኑንና ወጪውም የተጋነነ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማትና ተገቢ ነው ያለውን ማጣራትም አድርጎ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ቤቱን ይዘው እድሳት አደረግሁ በሚሉበት ጊዜ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ ህጋዊ መብት እንደነበራቸውና ቤቱን የመመለስ ህጋዊ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን እያወቁ እድሳት ማድረጋቸውና እድሳቱም አስፈላጊነቱ ታምኖበት የተደረገ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያለመቅረቡን በምክንያትነት ይዞ ሁሉንም የወጪ ድምር ለአመልካች እንዲከፈል መወሰን ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልጾና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2169፣2170 እና 2174

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎችን በዋቢነት ጠቅሶ በርትዕ ብር 15,000.00 (አስራ አምስት ሺህ ብር) ለአመልካች እንዲተካላቸው ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪዎችን ቤት ለማደሳቸው ተረጋግጦ የወጪው መጠንም በሁለት አካላት ተጣርቶ በአንደኛው አካል ብር 42,338.80፣በሌላኛው የመንግስት አካል ደግሞ ብር 63,942.43 መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት አነስተኛውን የወጪ ግምት እንኳን ሳይዝ በመቅረት በርትዕ ብር 15,000.00(አስራ አምስት ሺህ ብር) ብቻ ለወጪ እንዲታሰብ ማድረጉ ያላግባብ ስለሆነ ውሳኔው ተሽሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በጠየቁት መሰረት እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካች አወጣሁ የሚሉት ወጪ በሁለት አካላት ተገምቶ በቀረበበት ሁኔታ አነስተኛው ግምት ሳይያዝ ታልፎ በርትዕ ብር 15,000.00 ብቻ እንዲከፈላቸው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ በሰጡት መልስ የአመልካች ቅሬታ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ያለበት ያለመሆኑና የሕግ መሰረትም የሌለው መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፃናላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባበነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪዎቹ ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው ተጠሪዎች አሜሪካን አገር ሲሄዱ የተጠሪዎች ንብረት የሆነውን ቤት ይዘው ሲጠቀሙ በቆዩበት ጊዜ ቤቱን ለማደስና ለማሻሻል ወጪ በማውጣታቸው ወጪው እንዲተካላቸው፣ ከቤቱ ግምትና አመልካች ከአወጡት ወጪ አንጻርም ሲታይ ወጪው ከፍተኛ በመሆኑ ስም ሃብቱ ለአመልካች ሊዛወር ይገባል በሚል ምክንያት ነው፡፡ተጠሪዎች የአመልካችን ወጪ የሕግ መሰረት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረውም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን የግራ ቀኙን ክርክሮችንና ማስረጃዎችን እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት የወጪው መጠን በሚመለከታቸው አካላት ተገምቶ እንዲቀርብለት በማድረግና ከሕግ ጋር በማገናዘብ የአመልካችን አብዛኛውን ጥያቄ ውድቅ አድርጎ በተጠሪዎች ሊተካላቸው የሚገባውን የወጪ መጠን በርትዕ የወሰነ መሆኑን ከውሳኔው ይዘት ተመልክተናል፡፡የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የወጪ ይተካልኝ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አመልካች ወጪ ያወጡት ቤቱ ለተጠሪዎች የሚመለስ መሆኑን በሚያውቁበት ወቅት መሆኑንና ወጪውም አስፈላጊ የነበረ ስለመሆኑ ያለመረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ቤቱ ባይታደስ ኑሮ በጠቅላላ በቤቱ ይዘት ላይ ጉዳት ይደርስበት የነበረ ስለመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ ያለመኖሩንና ቤቱ ስለተጎዳ የቤቱን ህልውና ለማቆየት በቅን ልቦና አድሼአለሁ የሚል ክርክርም አመልካች ያላቀረቡ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመስረቱ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ያሉት ያላግባብ ስለመበልጸግ ጉዳይን በሚገዙት ደንቦች ስር ሲሆን ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2168 ድንጋጌ ይዘት ሲታይም አንድ ሰው ለተወሰነ ጊዜ በእጁ ያቆየውን እቃ እንዲመለስ የተገደደ እንደሆነ ለሕግ ወይም ለውል ተቃራኒ የሚሆን ድንጋጌ ከሌለ በቀር የተባለውን እቃ ከመለዋወጥ የተነሳ ያሉት መብቶችና ግዴታዎች ከድንጋጌው ቀጥለው ባሉት ደንቦች መሰረት የሚወሰን መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ ስር ከሰፈሩት ደንቦች መካከል አንዱ የሆነው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2169 ስር የተቀመጠው ደግሞ የያዘውን እቃ እንዲመልስ የተገደደ ሰው በእቃው ላይ ያደረገው ወጪ ሊመለስለት የሚገባው ወጪው የግድ አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ስለመሆኑና ወጪው አስፈላጊ ሳይሆን ከቀረ ወይም ወጪው እቃውን እንዲመለስ በተገደደው ሰው ወይም ተገዳጁ ኃላፊ በሚሆንበት ሰው ጥፋት ምክንያት ከሆነ ወጪው ሊመለስ የማይችል መሆኑን ያሳያል፡፡ሕጉ በአንቀጽ 2171(1) ስርም ለእቃው የተደረገው ወጪ የእቃውን ዋጋ ግምት ከፍ አድርጎት እንደሆነም እቃውን ለመመለስ የተገደደው ሰው ስለዚሁ ጉዳይ ያወጣው ገንዘብ ሊመልስለት እንደሚገባ የደነገገ ሲሆን ይህ ወጪ በክፉ ልቦና ስለመደረጉ የተረጋገጠ ወይም ርትዕም የሚያስገድድ ከሆነ ደግሞ ዳኞች ወጪውን ለመቀነስ ወይም ጭራሹን ለማስቀረት የሚችሉበት አግባብ መኖሩንን የተጠቃሹ ድንጋጌ ቀጣይ የሆነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2172((1) ይዘት ያሳያል፡፡ይህ ድንጋጌ አንድን ወጪ በክፉ ልቦና የተደረገ ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብም ወጪው በተደረገበት ጊዜ ወጪውን የሚጠይቅ ሰው እቃውን ለመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያውቅ እንደነበረ ወይም ማወቅ ይገባው የነበረና ርትዕም ሲያስገድድ መሆኑን በመለኪያነት አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ድንጋጌዎች ሲታዩ አንድ ሰው የሌላ ሰው ንብረት ይዞ ሲጠቀም ከቆየና ንብረቱን በሚጠቀምበት ጊዜ ንብረቱን ከጥፋት ወይም ከብልሽት ለማዳን ሲል ተገቢውን ወጪ ቢያወጣ ይኼው ወጪ በሕጋዊ ባለሃብቱ እንዲተካለት መጠየቅ የሚችልበት አግባብ የሚኖረው ወጪው የግድ አስፈላጊ ከሆነና በቅን ልቦና የተደረገ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የሚያስገነዝቡ ሲሆን በክፉ ልቦና የተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠውን ወጪ ግን እቃውን እንዲመለስ የተደረገ ሰው ሊቀነስበት ወይም ጭራሹንም ዳኞች ሊያስቀሩት የሚችሉ ስለመሆኑ ሕግ ስልጣን የሰጣቸው መሆኑን ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የተጠሪዎችን ቤት ይዘው ሲኖሩ ወጪውን ያወጡት ቤቱን ለተጠሪዎች የመመለስ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በሚያውቁበት ወይም ማወቅ ይገባቸው በነበረ ጊዜ መሆኑና ወጪውንም በክፉ ልቦና ያደረጉት መሆኑን ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን ይህ ችሎትም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 አግባብ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን እንዳሉ የሚቀበላቸው ሁኖ አግኝቷል፡፡ከዚህ አንጻር በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡን ፍሬ ነገሮችን ይዘን ጉዳዩን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2169፣2171 እና 2172 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው አመልካች አወጣሁ የሚሉት ወጪ ሙሉ በሙሉ ሊተካላቸው ይገባ የነበረ ወይም ፍርድ ቤት በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት መቀነስ የማይችልበት ሁኖ አላገኘነውም፡፡የስር ፍርድ ቤት በሁለት አካላት ተረጋግጦ የቀረበለት የወጪ ግምት እያለ አነስተኛ የተባለውን ብር 42,338.92 እንኳን መሰረት አድርጎ ውሳኔ ሳይሰጥ የወጪ መጠኑ ብር 15,000.00(አስራ አምስት ሺህ ብር) ብቻ እንዲሆን መወሰኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2171 እና 2172(1) ድንጋጌ መሰረት የተሰጠውን ስልጣን በመጠቀም ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻልበት ሕጋዊ ምክንያት ያለ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 32917 መጋቢት 07 ቀን 2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 107559 ግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች የተጠሪዎች ሕጋዊ ሃብት የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይዘው ሲጠቀሙ አወጣሁ የሚሉት ወጪ የግድ አስፈላጊ የነበረ በመሆኑ ወይም በቅን ልቦና ያደረጉት ስለመሆኑ ያለማስረዳታቸውን መሰረት አድርገውና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2169፣2171 እና 2172(1) ድንጋጌዎች አንጻር በመመልከት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የሌለበት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት ህዳር 12 ቀን 2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 81406

ጥር 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1. አቶ አህመድ ኢብራሂም } ጠበቃ ሙሉጌታ ታደሰ ቀረቡ

2. አቶ ሰኢድ ሃገረላዊ }

ተጠሪ፡- አቶ አመሀ ተ/ወይኒ ጠበቃ ሐጎስ አበረሃ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለመኪና ግዥ የተከፈለ ነው የተባለን ገንዘብ ከማስመለስ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት ፌ/ከ/ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ሲሆኑ አመልካቾቹ ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ ተከሳሾቹ አብረው በንግድ ስራ የተሰማሩ መሆናቸውን 2ኛ ተከሳሽ አ/አበባ በነበሩበት በ26/07/03 ለከሳሽ መኪና እንደሚሸጡላቸው ከከሳሽ ጋር ተነጋግረው የመኪናው ዋጋ በ1ኛ ተከሳሽ በኩል እንዲልክላቸው በገለጹት መሰረት ከሳሽ በ28/07/03 ብር 750,000.00 በወጋገን ባንክ ተ/ሀይማኖት ቅርንጫፍ በኩል የላኩላቸው መሆኑን ተከሳሾቹ መኪናውን ሳይልኩ እንደቀሩና ገንዘቡንም እንዲመልሱ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ እንደቀሩ የሚገልጽ ሆኖ ለክሱ ኃላፊ የሚሆነው ተከሳሽ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 36/5/ መሰረት ተለይቶ ብር 750,000.00 ከወለድና ክሱ ካስከተለው ወጪ ጋር እንዲከፍል ውሳኔ እንዲሰጥ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ ተከሳሾቹ በበኩላቸው መኪና ለመሸጥ 2ኛ ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር እንዳልተነጋገሩ ከከሳሽ ጋር የቆየ የንግድ ግንኙነት የነበራቸው በመሆኑ 2ኛ ተከሳሽ አ/አበባ ውስጥ የተነጋገሩት ከከሳሽ ስለሚፈለግ የእዳ መጠንና እዳው ስለሚከፈልበት ሁኔታ እንደሆነ ከሳሽ የሞባይል ቀፎዎችን ከተከሳሾች በካሽ እና በዱቤ ይገዙ ስለነበረ የብር 850,000.00 ዕዳ ይፈለግባቸው እንደነበር ከዚህ ውስጥ በ05/05/03 ብር100,000.00 በ2ኛ ተከሳሽ ስም በንብ ባንክ ወደ ጅጅጋ እንደላኩ በክሱ የተጠቀሰው ገንዘብም ከከሳሽ የሚፈለግ ቀሪ ዕዳ እንደሆነ ከሳሽ ክስ ሊያቀርቡ የቻሉት የሞባይል ቀፎ ዋጋ በመውረዱ ገንዘብ እንዲመለስላቸው ጠይቀው ተከሳሾች ባለመስማማታቸው እንደሆነ እና በከሳሽ በምስክርነት የተቆጠሩት ግለሰቦች ከከሳሽ ጋር አብረው የሞባይል ቀፎዎችን ከተከሳሾች ሲገዙ የነበሩ እንደሆነ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና የጽሑፍ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከሳሹ ብር 750,000.00 የላኩት ለመኪና ግዥ ነው ወይስ ከተከሳሾቹ ጋር በነበራቸው የሞባይል ቀፎ ሽያጭ ንግድ ግንኙነት ነው? የሚል ጭብጥ

መስርቶ ከሳሽ እና 2ኛ ተከሳሽ ስለመኪና ሽያጭ ጉዳይ መስማማታቸውን ያስረዳሉ ተብለው የተሰየሙት የከሳሽ ምስክሮች ከሳሽ እና 2ኛ ተከሳሽ ተገናኝተው ተነጋግረዋል ስለተባለበት ሰዓት እና የተለየበት እንዲሁም ስለተሸከርካሪው ዓይነት እና ዋጋ የሰጡት ምስክርነት ልዩነቶች የሚታይበት መሆኑን እነዚህ ልዩነቶችም ከሳሽ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ተነጋግረናል ባሉበት ጊዜና ቦታ ምስክሮቹ ያልነበሩና በጥናት እንደቀረቡ የሚያመለክት መሆኑን ከሳሽ መኪና ለመግዛት ተሰማሙበት ውል እንኳ የሌላቸው መሆኑን እና ምንም ውል ሳይኖር መኪና ለመግዛት ብር 750,000.00 እንዲሁ ይሰጣሉ ብሎ ለማመን የሚከብድ መሆኑን በዝርዝር ገልጾ ከሳሽ ገንዘቡን የላኩት የነበረባቸውን ዕዳ ለመክፈል እንጂ ለመኪና ግዥ ነው ማለት አልተቻለም ሲል ክሱ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከሳሽ የመኪና ግዥ ውል በጽሑፍ ባያቀርቡም የሀዋላ ሰነዱን በማስረጃነት እንዳቀረቡ ተከሳሾቹ ገንዘቡን መቀበላቸውን አምነው ምክንያቱን የካዱ በመሆኑ ከከሳሽ የሚፈልጉት እዳ ስለመኖሩ በጽሑፍ እስካላስረዱ ድረስ ገንዘቡን የማይመልሱበት ምክንያት እንደማይኖር እና ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ቀረበበትን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ ምስክሮችን በመስማት እልባት ለመስጠት መሞከሩ ተገቢነት ያለው የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት እንዳልሆነ በዝርዝር ገልጾ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ተከሳሾቹ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች ሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ወይም ሊሻር ይገባል በማለት ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ክርክር ያስቀርባል በመባል ግራ ቀኙ የስር ክርክራቸውን መሰረት በማድረግና በማጠናከር በሰበር ደረጃ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

ጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ ተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ ቀረበበት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በስር ፍ/ቤቶች በግራ ቀኙ ማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘት ከ2ኛ አመልካች ጋር የመኪና ሽጭ ውል ማድረጋቸውንና የሸያጩን ዋጋ 2ኛ አመልካች በጠየቁት መሰረት በ1ኛ አመልካች ስም በባንክ መላካቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ በመሰረቱ አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር የማስረዳት ሸክም እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁ 2001/1/ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተከሳሾ በከሳሽ የተላከውን ገንዘብ መቀበላቸውን አምነው ለገንዘቡ መላክ ምክንያት የሆነው ግን ከሳሽ እንደገለጹት የመኪና ሽያጭ ውል አለመሆኑን ክደው ተከራክረዋል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት የመኪና ሽያጭ ውል ተደርጎ የነበረ መሆኑን እና ገንዘቡም የተላከው በዚሁ ውል ምክንያት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቀው ከከሳሽ ወገን ነው፡፡ የውሉን መኖር ለማስረዳት ከሰሽ የሰሟቸው ምስክሮች በጥናት የቀረቡ ናቸው በሚል ከፍተኛ ፍ/ቤት ምስክርነታቸውን ውድቅ ያደረገ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ ይህንን የከፍተኛ ፍርድ ቤት አቋም ወይም ትችት በዝምታ በማለፍ ከሳሽ የሚና ግዥ ውል በጽሑፍ ባያቀርቡም የሀዋላ ሰነድ አቅርበዋል ሲል በውሳኔው ላይ አስፍሮአል፡፡ በመሰረቱ የሀዋላ ሰነዱ በተከሳሾቹ ያልተካደውን የገንዘቡን መላክ እና በተከሳሾች እጅ መግባት የሚገልጽ ከመሆኑ ወጪ ስለተላከበት ምክንያት የሚጠቁመው ነገር አለመኖሩ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ የሀዋላ ሰነዱን በማዘጋጀት በማቅረብ ማስረዳት ሸከማቸውን የተወጡት የገንዘቡን መላክ ምክንያት መሆኑን በተመለከተ ጭምር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሆነ አድርጎ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የያዘውና ለውሳኔው መሰረት ያደረገው አቋም ከላይ የተጠቀሰው ፍ/ሕ/ቁ 2001/1/ ድንጋጌ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል የመኪና ሽያጭ ውል መኖሩን ለማስረዳት መቅረብ የሚገባውን የማስረጃ አይነት በተመለከተ ግዙፍነት ያላቸው የተንቀሳቃሽ ንብረቶች ባለሀብትነት ንብረቱን በመግዛት ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘው ወይም በኑዛዜ የተሰጠው ሰው ንብረቱን በእጅ ባደረገ ጊዜ የተላለፈለት እንደሚሆን በፍ/ሕ/ቁ 1186/1/ የተደነገገ ሲሆን ልዩ የሆኑ አንዳንድ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን የሚመለከቱት የህጎች ድንጋጌዎች የተጠበቀ መሆናቸውም በፍ/ህ/ቁ 1186/2/ ተመልክቷል፡፡ መኪና ደግሞ ከልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች የሚመደል በመሆኑ ባለሀብትነት የማስተላለፉ ጉዳይ በተለይ ሕጎች የሚመራ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አንድ ተሸከርካሪ ባለሀብትነት እንዲተላለፍለት የሚጠይቅ ሰው አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሰነዶች በተጨማሪ ተሸከርካሪው ከውጪ ሀገር የገባ ከሆነ የጉምሩክ ዴክላራሲዮን በሀገር ውስጥ የተሰራ ከሆነ ተገዛበትን ኢንቮይስ እንዲሁም ከቀድሞ ባለንብረት በግዥ የተላለፈለት ከሆነ ደግሞ የገዘውውሩን ህጋዊነት ለማስረዳት በሚመለከተው አካል የተሰጠ ወይም ተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ እንደሚጠበቅበት ስለተሸከርካሪ መለያ መመርመሪያና መመዝገቢያ በወጣው አዋጅ ቁጥሩ 681/2002 በአንቀጽ 6 ስር በሚገኙ አራት ንዑሳን ቁጥሮች በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በተለይም አዋጁ አንቀጽ 6/3/ እና 6/4/ ድንጋጌዎች ጥምሩ ንባብ እንድ ተሸከርካሪ በቀድሞ ባለንብረት በሽያጭ ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑ ተረጋግጦ የባለሀብትነት ዝውውሩ ሊፈፀም የሚችለው ውሉ በጽሑፍ በተደርገ ጊዜ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችልነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም ከሳሽ የመኪና ሽያጭ መደረጉን ለማስረዳት ማቅረብ የሚጠበቅባቸው የሽያጭ ውሉ የተደረገበትን ሰነድ ሆኖ እያለ እና የዚህ ዓይነቱን ሰነድ ደግሞ ያላቀረቡ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከሳሽ የሀዋላ ሰነዱን ማቅረባቸው በቂ ነው ሲል ሰጠው ውሳኔ የክሱን እና የፍ/ሕ/ቁ 2001/1/ ድንጋጌን ይዘት ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለውሳኔው በምክንያትነት የጠቀሰው ሌላኛው ነጥብ ተከሳሾቹ ገንዘቡን መቀበላቸውን አምነው ምክንያቱን ከመካድ በስተቀር ከከሳሽ የሚፈልጉት ዕዳ ስለመኖሩ ያቀረቡት የጽሑፍ ማስረጃ ሳይኖር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበትን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ ምስክሮቹን በመስማት እልባት ለመስጠት መሞከሩ ተገቢነት ያለው የማስረጃ ሳይኖር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የቀረበበትን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ ምስክሮችን በመስማት እልባት ለመስጠት መሞከሩ ተገቢነት ያለው የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት አይደለም የሚል ነው፡፡ በመሰረቱ ተከሳሾቹ በማስረጃነት ያቀረቡት ምስክሮችን ብቻ ሳይሆን የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ንግድ ፈቃድ እና ከሳሽ ቀደም ሲል ብር 100,000 በባንክ የላኩበትን ሰነድ ጭምር ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አከራካሪ ሆኖ ቀረበን አንድ ፍሬ ነገር ማስረዳት ስለሚቻልበት የማስረጃ ዓይነት አግባብነት ባለው ሕግ በተለይ የተቀመጠ ግልጽ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ እንደዚህ ዓይነቱን ፍሬ ነገር በምስክር ጭምር ማስረዳት እንደሚቻል ከፍ/ሕ/ቁ 2002 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በግራ ቀኙ መካከል ስለነበረው የንግድ ግንኙነት ሁኔታ እና ከግንኙነቱ ስለመነጨው የገንዘብ ዕዳ በምስክሮች ማስረዳትን የሚከለክል ድንጋጌ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ምስክሮችን በመስማት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት መሞከሩ ተገቢነት ያለው የማስረጃ አቅራረብ ስርዓት አይደለም ከማለት በስተቀር የዚህ ዓይነቱን የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ተገቢነት የሚያሰጠው የትኛው ሕግ ወይም ድንጋጌ እንደሆነ በውሳኔው አልገለጸም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ ረገድ ለውሳኔ በምክንያትነት የጠቀሰው ነጥብ የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጨረሻም በዚህ መዝገብ ለክርክር የቀረበው ጉዳይ በግለሰቦች መካከል የሚደረግ የብር 750,000 ግምት ያለው ክርክር በመሆኑ እና የዚህ ዓይነቱ ክርክር ደግሞ ተመርምሮ አልባት ማግኘት የሚገባው የጉዳዩን ዋነኛ ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ በግራ ቀኙ ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ለክርክሩ መሰረታዊ ጭብጥ አግባብነት ካላቸው ህጎች አንፃር በመሆኑ ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና ከንግድ ፈቃድና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 686/2002 ጋር ተያይዞ በሰበር ደረጃ በተጠሪ መልስ ላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በዚህ ውሳኔ ላይ ማስፈሩን እና መመርመሩን አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃላል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የስር ተከሳሾች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ ለስር ከሳሽ ሊከፍሉ ይገባል ሲል የሰጠው ውሳኔ ከላይ በዝርዝር በሰፈሩት ምክንያቶች ሁሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 75752 በ22/09/04 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 107977 በ08/03/04 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ የስር መዝገብ ይመለስ፡፡
4. ውሣኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይምለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.79394

ጥቅምት 06 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አብደላ ኢብራሂም
ተጠሪ፡- አቶ ኡሶ አብዲ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በኮምቦልቻ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ከሳሽ ያቀረቡት ክስ ፍሬ ቃሉ፡- ከተከሳሽ ከአምስት ዓመት በፊት ብር 500 ተበድሬ ገንዘቡን እስከምመልስ ድረስ ተከሳሽ መሬቴን ይዞ እንዲቆይ በመያዣ ሰጥቼው ከሁለት ዓመት በኋላ ገንዘቡን በሽማግሌዎች ፊት ሰጥቼው ከለቀቀልኝ በኋላ የተቀበለውን ገንዘብ ለሽማግሌዎች መልሶ እንደገና መሬቴን በመያዝ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ለቆ እንዲወጣ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- ከሳሽን በወንድምነት ድሬው መሬቱን በስጦታ የሰጠኝ ሲሆን ለመሬቱም ከተከሳሽ የተቀበልኩት ገንዘብ የለም፡፡ በዚሁ መሬት በ1992 ዓ.ም. ጫት ተክየበት ከሁለተኛ ሚስቴ ጋር ስንጋባ የሰጠኋት በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በሚል ተከራክረዋል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም በሰጠው ውሳኔ፡- ከሳሽ መሬቱን በመያዣ ስለመስጠታቸው በፍ/ሀ/ቁ/2005 መሰረት በጽሁፍ ማስረጃ ያላረጋገጡ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ የስር ከሳሽም በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የይግባኝ ባዩን ይግባኝ በፍብ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ 337 መሰረት በመዝጋቱ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም የግራ ቀኙን ወገን ካራከረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ለጊዜው በመቸገሩ ምክንያት ብር 500 ተበድረው ይዞታቸውን ለዕዳ ማስያዛቸውን በግራቀኙ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/1999 መሰረት የገጠር መሬት ይዞታን አርሶ አደር በዕዳ ለማያስገዛ አይችልም፣ በስጦታም ቢሆን በአዋጁ መሰረት የገጠር መሬትን ከቤተሰብ አባል ውጪ አሳልፎ መስጠት የሚቻል አይሆንም በሚል ተጠሪ ከአመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ እንዲመልሱና አመልካችም መሬቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ ህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካች በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡- የሚያከራክረውን ይዞታ አመልካች ለ11 ዓመት ይገፉ የቆየሁ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በሚል ያቀረብኩት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገው ተገቢ አይደለም፣ተጠሪው መሬቱን በ1992 ዓ/ም በስጦታ ያስተላለፈልኝ ስለመሆኑ ከማመኑም ሌላ የቀበሌ ኮሚቴዎችና የአካባቢ ሽማግሌዎች አረጋግጠው እያሉ እንድለቅለት የተወሰነው አግባብ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪውም በሰጡት መልስ፡- አመልካች ይዞታውን በስጦታ አግኝቻለሁ ይበል እንጂ የተደረገለት ስጦታ የለም፣ ብር 500 ያበደረኝ ገንዘቡን እስከምመልስ ድረስ መሬቱን በመያዣነት ይዞ ነው፡፡ የገጠር መሬትን በዕዳ ማስያዝም ሆነ ከቤተሰብ አባል ውጪ በስጦታ ማስተላለፍ እንደማይቻል በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 የተደነገገ በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ክስ የቀረበበትን መሬት ለቅቀው እንዲወጡ የተወሰነው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በወረዳ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክርና ከቀረቡት የግራ ቀኙ ምስክሮች አመሰካከር የተረጋገጠው ፍሬ ነገር አመልካች ለተጠሪው ብር 500 በማበደር ለዚሁም የብድር ዕዳ የተጠሪውን መሬት መያዛቸውን ነው፡፡ አንድ ውል የሚጸና ውል ነው ለማለት ሶስት መሰረታዊ የሆኑ ሁኔታዎች እንደሚያስፈልጉ የፍ/ህ/ቁ.1678 የሚደነግግ ሲሆን እነዚህም ሁኔታዎች በድንጋጌው- (ሀ-ሐ) የተመለከቱት፡- ውል ለመዋዋል ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር ፣ በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ መሆንና፣ የውሉ አጻጻፍ ፎርም በህግ በታዘዘ ጊዜ ይህኑ ልዩ ፎርም አሟልቶ መገኘት ናቸው፡፡ ውሉ በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ ላይ መደረግ እንደሚገባው የሚያስገነዝበው በፊደል (ለ) ስር ሲሆን በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ደግሞ ህገ ወጥ ውል (unlawful contract) ይሆናል፡፡ አንድ ውል የተደረገበት መሰረታዊ ጉዳይ (object of contract) በህግ ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜ ውሉ በህግ ፊት ምንም ዓይነት ህጋዊ ውጤት የማያስከትል (void contract) ይሆናል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት ውል ተጠሪው የገጠር መሬት ይዞታውን በመያዣ በመስጠት ገንዘብ የተበደሩ ሲሆን መያዣ በተሰጠበት በ1992 ዓ.ም. የክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ባለመውጣቱ ተፈጻሚ የነበረው የአዋጅ ቁጥር 89/1989 ነው፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(3) በተሠጠው ትርጉም መሰረት ‹‹ የይዞታ ባለመብት ›› ማለት ማንኛውም አርሶ አደር የገጠር መሬትን ለግብርና ሥራ ለማዋል ፣ለማከራየት እና ይዞታው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ለቤተሰብ አባሉ ለማውረስ የሚኖረው መብት ሲሆን ይህም አርሶ አደሩ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ ንብረት ማፍራትና ይህንኑ ንብረት መሸጥ፣መለወጥና ማውረስ እንደማይጨምር የተጠቀሰ ሲሆን አርሶ አደሩ የይዞታ መሬቱን በዕዳ እንዲያስይዝ በህግ መብት አልተሰጠውም፡፡ አዋጅ ቁጥር 89/1989 ከተሻረ በኋላ በሥራ ላይ ባለው አዋጅ ቁጥር 456/97 በአንቀጽ 8(2) የገጠር መሬት መብትን አርሶ አደሮች በከፊል አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች እነርሱን በማያፈናቅል መልኩ ሌላ አርሶ አደር ወይም ባለሀብት በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር በሚወጣው አዋጅ የጊዜ ገደብ ከይዞታቸው ላይ ለተፈላጊው ልማት በቂ የሆነ መሬት የማከራየት መብት የሰጣቸው ሲሆን በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 5 ደግሞ ማንኛውም ባለይዞታ የገጠር መሬት የመጠቀም መብቱን ለቤተሰብ አባል የማውረስ መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በዚህ በተጠቀሰው አዋጅም ቢሆን ባለይዞታ የሆነ አርሶ አደር ይዞታውን ላለበት ዕዳ በመያዣነት እንዲያስይዝ ወይም በስጦታ ለቤተሰብ አባል ላልሆነ ሰው ለማስተላለፍ መብት አልተሰጠውም፡፡ አሁን በስራ ላይ ባለው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999ም ቢሆን የገጠር መሬትን በመያዣነት መስጠትም ሆነ ከቤተሰብ አባል ወጪ በስጦታ ማስተላለፍ የማይቻል መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪው ገንዘብ ሰጥተው መሬቱን በመያዣ ከያዙ በኋላ በስጦታ አግኝቻለሁ በሚል ያቀረቡት ክርክር የቤተሰብ አባል መሆናቸውን ባላረጋገጡበት ከመሆኑም ሌላ በህግ ባልተሰጠ መብት የገጠር መሬትን መያዣ በማድረግ ገንዘቡን ያበደሩ ስለሆነ ውሉ ህገ ወጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(unlawful contract) ነው፡፡ ህገ ወጥ ውል ደግሞ በፍ/ህ/ቁ/1716 መሰረት በህግ ፊት ውጤት የማይኖረው ፈራሽ ውል ነው፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ምላሽ ማግኘት ያለበት አመልካች ያቀረቡት የይርጋ ክርክር ነው፡፡ አመልካች ይርጋውን መቃወሚያ ያደረጉት ይዞታውን በ1992 ዓ.ም. ይገፎ ለ11 ዓመት የጫት ተክል በመትከል የምገለገልበት ነው በሚል ነው፡፡ በእርግጥ የመሬት ይዞታውን ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ድረስ መያዛቸውን ክርክሩ ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/ 43226 የካቲት 07 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የፍ/ህ/ቁ/1678፣1716 እና 1718ን በመተርጎም የውሉ መሰረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነውን ወል (unlawful contract) በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈጻሚነት የለውም በማለት ለመወሰን እንደሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑና የግራ ቀኙን ወገኖች የሚያከራክራቸውም ህገ ወጥ(unlawful contract) ውል በመሆኑ የይርጋው ክርክርም ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ ክርክር ውድቅ በማድረግ የመያዣ ውሉ ህገ ወጥ ነው በሚል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/132904 በቀን 29/08/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪው የገጠር መሬት ለዕዳ መያዣ በማድረግ የገቡት ውል ህገ ወጥ ውል (unlawful contract) በመሆኑ በህግ ፊት ወጤት ስለማይኖረው ተፈጻሚነት የለውም ሲል የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ወድቅ በማድረግ አመልካች ያበደሩትን ብር 500 ከተጠሪ ተቀብለው በዕዳ የያዙትን የተጠሪውን መሬት እንዲለቁ የወሰነው ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. ከዚህ በፊት በስር ወረዳ ፍርድ ቤት በአፈጻጸም መ/ቁ. 15265 ሲካሄድ የነበረው ክርክር ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

4.የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመልስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጭ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.77238

ህዳር 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም - ነ/ፈጅ በፍቃዱ መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ንጉሤ ረፈራ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር አመልካች ድርጅት ከሳሽነት የተጀመረው በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪም ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- ተከሳሽ የከሳሽ ድርጅት ንብረት የሆነውንና ከአዲስ አበባ ወደ ጅማ የተዘረጋውን ኦፕቲካል ፋይበር የሚባል ኬብል በ1/2 ሜትር ጥልቀት መሬት ውስጥ መቀበሩን እያወቀና እያየ በ10/06/2001 ዓ.ም. ከረፋዱ 4፡30 ሲሆን ይዞታውን በዶማ በመቆፈር መስመሩ እንዲቋረጥ በማድረግ በብር 48,998.72 የሚገመት ጉዳት ያደረሰ ሲሆን ተከሳሽም ጉዳት ማድረሱን በማመን መስመሩን ለመጠገን ሲባል ለጥገና፣ ለባለሙያዎችና ለጉልበት ሠራተኞች እንዲሁም ለትራንስፖርት የወጣውን ወጪ ለመክፈል በ08/07/2001 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ከሳሽ ድርጅትን በመጠየቁ ከሳሽም ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ጨምሮ ብር 48,998.72 እንደሚፈለግበት ቢያሳውቅም ገንዘቡን ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲከፍል ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- የወሊሶ ከተማ አስተዳደር በ1997 ዓ.ም. 1,888 ካሬ ሜትር የሆነ የከተማ ቦታ ከነፕላኑ ሲሰጠኝ በአዋጅ ቁጥር 464/1994 አንቀጽ 3(3) መሰረት በሰጠኝ መሬት ውስጥ የከሳሽ ንብረት የሆነው ኦፕቲካል ፋይበር ኬብል መኖሩን ሳላልነገረኝ ማወቅ የምችልበት ሁኔታ የለም፣ መስመሩ ከዋናው መንገድ ከ15 ሜትር በላይ መራቅ እንደሌለበት እየታወቀ 150 ሜትር ርቀት ላይ የተቀበረ ሲሆን በቦታው የተቀበረ ስለመሆኑ ከሳሽ ድርጅት ያደረገው ምልክት የለም፣ጉዳቱን በማመን ደብዳቤ ጽፏል የተባለውም ቢሆን በአገር ንብረት ላይ ደርሷል የተባለውን ጉዳት በተመለከተ በቅንነት የተጻፈ እንጂ እያወቅኩና እያየሁኝ ጉዳቱን አድርሻለሁ በሚል የተጻፈ አይደለም፡፡ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም እንጂ አለብህ የሚያሠኝ በቂ ምክንያት ቢኖር ከሳሽ ያቀረበው የጉዳት ግምት የተጋነነ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት ከፍተኛው ፍርድ ቤትም የከተማ አስተዳደር መሬቱን ለተከሳሽ ሲሠጥ የኬብል መስመር ስለመኖሩ የነገረው መሆን አለመሆኑን ማረጋገጫ እንዲልክ ጠይቆ አስተዳደሩም የከሳሽ ድርጅት ካርታ ለከተማው አስተዳደር ያልተሠጠው በመሆኑ ለተከሳሽ መስመሩ ስለመኖሩ ያልተነገረው መሆኑን በመግለጹ ፍርድ ቤቱም ለተከሳሽ በተሰጠውም ፕላን የኬብል መስመር ስለመኖሩ ስላልተገለጸ ተከሳሽ የኬብል መስመሩ በቦታው ስለመኖሩ ያውቅ ነበር ወይም አይቷል ለማለት አይቻልም፣ ተከሳሽ ለከሳሽ በጻፈው ደብዳቤም ጉዳቱን አምኗል በሚል ከሳሽ ያቀረበው ክርክርም ቢሆን ከደብዳቤው ይዘት መገንዘብ የተቻለው መስመሩ ከመንገድ 150 ሜትር ርቆ ያለ በመሆኑ ማወቅ አለመቻሉንና ጉዳቱ የደረሰውም የልማት ሥራ እየተሰራ በመሆኑ ኬብሉ የተጠገነበትን ወጪ እንዲሁም ለባለሙያና ለጉልበት ሰራተኞች ትራንስፖርትን ጨምሮ የወጣውን ልክፈል የሚልና ከሳሽ ያቀረበው የወጪ ግምት የተጋነነ ነው የሚል በመሆኑ ጉዳቱን አምኗል ለማለት የሚቻል አይሆንም ሲል ክሱን ውድቅ በማድረግ በነጻ አሰናብቶታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከራቸው በኋላ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- በአዋጅ ቁጥር 464/1997 አንቀጽ 3(3) የግንባታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በመሬት ውስጥ ኬብል መዘርጋቱንና አለመዘርጋቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት የወሊሶ ከተማ አስተዳደርና የግንባታ ፈቃድ ጠያቂው አካል (የተጠሪው ግዴታ) መሆኑ በግልጽ የተቀመጠውን ድንጋጌ በማለፍ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 49/1989 አንቀጽ 23(1) መሰረት ኬብል ስለመዘርጋቱ የከተማው አስተዳደርም ሆነ ተጠሪው አመልካች ድርጅትን ጠይቀው ማረጋገጥ እንዳለባቸው የተጣለባቸው የህግ ግዴታ ሆኖ እያለ መታለፉ ያለአግባብ ነው፣
- ተጠሪው የልማት ሥራ ሲሠራ በቸልተኝነት ጉዳት ማድረሱን አምኖ ግምቱ ተቀንሶ ለመክፈል መከራከሩ ግልጽ ሆኖ ባለበት በቀረበው ክስ መሰረት አምኗል የሚያሰኝ አይደለም በሚል አመልካች ያቀረብኩትን ክስ ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ ፡-

- ከከተማው አስተዳደር በተሰጠኝ ቦታ ኬብል የተዘረጋ ስለመሆኑ የተገለጸልኝ ነገር ባለመኖሩ ተጠሪው በመሬት ውስጥ ኬብሉ የተዘረጋ ስለመሆኑ የማወቅ ግዴታ አለበት በሚል አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፣
- በሥር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር ያመንኩት ጉዳት መድረሱን እንጂ ጉዳቱ የደረሰው በተጠሪው ጥፋት ነው በሚል አይደለም፣ሲል ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡-

- ተጠሪው በአመልካች ድርጅት ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- ተጠሪው ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት ቢባል የሚከፍለው የኪሳራው መጠን ምን ያህል መሆን አለበት? የሚሉትን ጭብጦች ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አንደኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪው የከተማው አስተዳደር በሠጠው የከተማ ቦታ ቁፋሮ ሲያካሂድ የአመልካች ንብረት የሆነው ኦፕቲካል ፋይበር ኬብል መቁረጡን ነው፡፡ ሆኖም የሥር ፍርድ ቤቶች በንብረቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪው ኃላፊነት የለበትም በሚል የወሰኑት ለተጠሪው በተሠጠው ፕላን ላይ ኬብል ስለመኖሩ የተደረገ ምልክት የለም፣ የከተማው አስተዳደርም መስመሩ ስለመኖሩ ለተጠሪው የገለጸው ነገር ባለመኖሩ እያወቀ ወይም እያየ ጉዳት አድርሷል ለማለት አይቻልም በሚል ነው፡፡ እነዚህን ፍርድ ቤቶቹ የጠቀሱአቸውን ምክንያቶች የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌትሪክ ሀይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 464/1997 እና አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ድንጋጌዎች አንጻር መመርመር የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ አዋጅ ቁጥር 464/1997 በአንቀጽ 3(3) ሥር የፌዴራልና የክልል ከተማ አስተዳደር አካላት የግንባታ ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት የቴሌኮሙኒኬሽን ወይም የኤሌትሪክ ሀይል አውታር ስለመኖሩ እና ፈቃድ ጠያቂው አካልም ግንባታ ከማካሄዱ በፊት በቴሌኮሙኒኬሽን ወይም በኤሌትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ድንጋጌው በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌትሪክ ሀይል አውታሮች ላይ በግንባታ ወቅት ጉዳት እንዳይደርስ አስቀድሞ እንዲያረጋግጡ ግዴታ የጣለው በፌዴራልና በክልል አስተዳደር አካላት ብቻ ሳይሆን የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ላይ ጭምር ነው፡፡ ተጠሪውም በዚህ የህግ ድንጋጌ መሰረት በቴሌኮሙኒኬሽን አውታር ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የተጣለበትን አስቀድሞ የማረጋገጥ ግዴታ ሳይወጣ ቦታውን በቸልተኝነት በመቆፈሩ ምክንያት ጉዳቱ ሊደርስ ችሏል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌትሪክ ሀይል አውታሮች ላይ እያወቀም ሆነ በቸልተኝነት ጉዳት ያደረሰ ሰው የሚቀጣ ስለመሆኑም ተደንግጓል ፡፡

ወደ ፍትሐብሄር ህጉ ስንመለስ አንድ ሰው በራሱ በኩል ምንም የጣው ግዴታ ሳይኖር በራሱ ጥፋት(አስቦ ወይም በቸልተኝነት) በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ኃላፊ እንደሆነ በቁጥር 2027(1) ከተደነገገው መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲሁም በህግ በትክክል ተገልጾ የተመለከተውን ልዩ ድንጋጌ፣ ልዩ ደንብና ሥርዓት የጣሰ ሰው ደግሞ ጥፋተኛ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ህ/ቁ 2035(1) ተመልክቷል፡፡ በአዋጁም ሆነ በፍትሐብሔር ህጉ በዚህ መልኩ ተደንግጎ እያለ ተጠሪው ጉዳት ማድረሱን ባልካደበት ጉዳት የደረሰበት ኬብል በቦታው ስለመኖሩ ለተጠሪው የከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት አላስታወቀም፣ እንዲሁም አመልካች ድርጅት በቦታው ላይ ያደረገው ምልክት የለም የሚሉትን ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤቶች በመጥቀስ በተጠሪው የተጣለበትን የህግ ግዴታ ባለማገናዘብ ድርጊቱን የፈጸመው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ስለመሆኑ ስላልተረጋጠ ለጉዳቱ ኃላፊነት የለበትም ሲሉ የወሰኑት በአዋጅ ቁጥር 464/1997 አንቀጽ 3(3) የተደነገገውን እና ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የፍትሐብሄር ህግ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ማንም ሰው ከራሱ ጥፋት የተነሳ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ላደረገው ጉዳት ኪሳራ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት በፍ/ህ/ቁ/2028 በአስገዳጅ ሁኔታ የተደነገገ ሲሆን ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ መሆኑ በህግ የታወቀ ሰው ደግሞ የሚከፍለው የጉዳት ካሳ መጠን ኃላፊነቱ ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ በማመዛዘን ስለመሆኑ ከፍ/ህ/ቁ 2090(1) እና 2091 ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪው በአመልካች የኬብል መስመር ላይ ጉዳት ማድረሱን በማመን ልዩ ልዩ የጥገና ወጪዎችን ለመክፈል በጻፈው ደብዳቤ ከአመልካች በኩል የቀረበው የኪሳራ መጠን የተጋነነ መሆኑን ስለመግለጹ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የደብዳቤውን ይዘት በፍርድ ላይ ካሰፈረው መገንዘብ የተቻለ ከመሆኑም ሌላ ተጠሪው ከሥር ጀምሮ ባደረገው ክርክርም የጉዳቱ መጠን ግምት የተጋነነ መሆኑን በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪው በአመልካች በኩል የቀረበውን የኪሳራ መጠን ግምት እስከተቃወመ ድረስም ግምቱ የተጋነነ ነው የሚልበትን ምክንያት እና አመልካችም ለግምቱ ምክንያት ያደረጋቸውን ሁኔታዎች የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማትና በመመዘን መወሰን የሚገባ ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው በአመልካች ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱን ባልካደበት ተጠሪውን ለጉዳቱ ኃላፊነት የለበትም በሚል በነጻ ያሰናበቱት በአዋጅ ቁጥር 464/1997 አንቀጽ 3(3) የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ግንባታ ከማከናወኑ በፊት የቴሌኮሙኒኬሽን እና የኤሌትሪክ አውታሮች ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የተደነገገውን እንዲሁም ከውል ወጪ ኃላፊነት ሊከተል ስለሚችልበት ሁኔታ በፍ/ህ/ቁ/2027(1)፣ 2028፣ እና 2035 የተደነገጉትን ሁኔታዎች ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/21371 በቀን 07/04/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/112894 በቀን 28/03/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. ተጠሪው በአመልካች ንብረት ላይ ላደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡ ስለሆነም በደረሰው የጉዳት መጠን ላይ የግራ ቀኙን ወገኖች በማከራከርና የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማት፣ እንዲሁም ተገቢ ሆኖ ከተገኘም በገለልተኛ ባለሙያ በማጣራት በጉዳዩ ላይ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ሥልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 77479

ጥቅምት 06 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢት/ያ ኦርቶዶክስ ቅድስት ሥላሴ መንፈሣዊ ኮሌጅ ነገረ ፈጅ ፀዳለ ዳና

ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አሰገድ ሣህሉ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ግራ ቀኙን ያከራከረው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ጉዳይ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለይቶ ለመወሰን ሲባል በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ሲሆን ፍሬ ቃሉም፡- ለ2003 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የዲግሪ ፕሮግራም መሥፈርት አሟልቼ ትምህርቱን እየተከታተልኩ እያለ፣ ማስታወቂያ በወጣበት ጊዜ ያልነበረነ መሥፈርት መሠረት በማድረግ ወደ ማታው የትምህርት ፕሮግራም ያዛወረኝ ከመሆኑም በላይ የአባልነት ማስረጃ በአጥቢያ ቤተክርሲቲያን ማቅረቤ እየታወቀ ትክክለኛ ማስረጃ አላቀረብክም በማለት እንዲሁም ለብዙ ቀናት በትምህርት ገበታ ላይ አልተገኘህም በሚሉ ምክንያቶች ትምህርቴን እንዳቋርጥ ስለወሰነ ትምህርቴን እንድቀጥል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ ኮሌጁ የኢት/ያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክስቲያን እምነቷን ለማስፋፋት እና አማኞቿን ለማስተማር ሲባል የተቋቋመ ኃይማኖታዊ ኮሌጅ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ፍ/ቤት ውሣኔ ለመስጠት አይችልም፡፡ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን አለው ከተባለ በሃይማኖታዊ ጉዳዩ ጣልቃ እንደመግባት ይቆጠራል ስለዚህ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ስለሌለው መዝገቡ ይዘጋልኝ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ካስቀደመ በኃላ በአማራጭም ከሣሽ ላቀረበው የፍሬ ጉዳይ ክርክር የበኩሉን ክርክር አቅርቧል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ስልጣንን በሚመለከት የቀረበው ክርክር ተመልክቶ የኮሌጁ ዋና ዓላማ መንፈሣዊ ትምህርት መስጠት የመሆኑ እውነታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብቻውን ይህ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ከመወሰን ሊያግደው የሚችል አይደለም፡፡ ከሣሽ ከትምህርት ገበታው የተሰናበተው በአግባቡ ነው ወይስ አይደደለም? የሚለውን ጉዳይ የግለሰብ መብትን ከህገ መንግስቱና ከሌሎች ህጐች አንፃር ማስከበር መሆኑን ስለሚያመለክት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለኝ የሚል ብይን ከሰጠ በኃላ በመቀጠልም ከሣሽ ቤተክርስትያኗ አስተምሮት ወጥና አራማጅ ነው ወይስ አይለም? ለምልመላ የሚያበቃውን ማስረጃ ከትክክለኛው የሰበካ ጉባኤ አቅርቧል ወይስ አልቀረበም? ከትምህርት ገበታው ስለመቆየቱ ተረጋግጧል ወይስ አልተረጋጠም? በሚሉት አከራካሪ ነጥቦች ላይ ማስረጃ ከሰማ በኃላ ሐምሌ 07 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የኢት/ያ ኦርቶዶክስ ቤተክስርስቲያን የማትቀበለውን ትምህርት ከሣሹ ስለሚያራምዱ በተከሣሽ ምስክሮች በሚገባ አልተረጋገጠም፡፡ ለምለመላ አስፈላጊ የሆነው የደብር ማስረጃ ከሣሹ ካቀረበ በኃላ በማታለል መሆኑ ተገልፆ የተሰረዘው ከሣሹ ከትምህርት ከታገደ በኃላ ስለሆነ ለማገዱ ተግባር መሠረት ነው ለማለት የማይችል በመሆኑ በላይ በሥራ ኃላፊ በሚፃፍ የዘፈቀደ ደብዳቤ የተማሪ የመማር መብት ሊገደብ አይገባም እንዲሁም ከትምህርት ቀርቷል ተባለ እንጂ ለመቅረቱ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም ከሣሹ የማታ ትምህርቱን እዲቀጥል ይደረግ በማለት ዳኝነት ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን የይግባኝ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 እንደተደነገገው ከላይ የተመለከተው ፍርድ ጉድለት ያለበት ባለመሆኑ ተጠሪን መጠራት አያስፈለግም በማለት መዝገቡን ዘግቶ አመልካችን አሰናብቶታል፡፡ ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውም አመልካች በዚህ የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚላቸውን ነጥቦች በመዘርዘር የሰበር አቤቱታውን በማቅረቡ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው ለመወሰን ስልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለውን ነጥብ በመመለከት ተጠሪው ቀርቦ ክርክሩን እንዲያሰማ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት የአሁን ተጠሪ ተከሣሹ ኮሌጅ በእራሱ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለሆነ ሊከሰም ሊከሰስም ስለሚችል በስልጣን ረገድ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ፍርድ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልሱን በፅሑፍ ያቀረበ ቢሆንም ይዘቱ በሰበር ቅሬታው ከገለፀው የተለየ አይደለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ በቀደም ተከተል የተጠቀሰው ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡ መደበኛ ፍ/ቤቶች በክሱ ደረጃ የቀረበላቸውን ጉዳይ ተቀብለው ወደ ዋናው የክርክር ይዘት ዘልቀውበት ከመግባታቸው በፊት ክስ የቀረበበት ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ጉዳይ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን በቅድሚያ የመመርመርና የማየት ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ ኢት/ያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ሥር ተደንግጓል፡፡ ዝርዝር ህግ በሆነው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4 ላይም ቢሆን መደበኛ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ማናቸውም ጉዳይ ያለገደብ ተቀብለው ለማስተናገድ የሚያስችል ስልጣን እንደሌላቸው ተመልክቷል፡፡

ከዚህ በቀር አንድ ሰው በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለማስወሰን የሚችለው ከህግ የመነጨ መብት ያለው መሆኑን በክሱ ዝርዝር በፍሬ ነገር ደረጃ ማመልከት የቻለ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33(2) ተደንግጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንፃር አሁን የቀረበውን ጉዳይ ስንመለከት ከሣሹ የአሁን ተጠሪ ለትምህርት ከገባበት ኮሌጅ ያለአግባብ የተሰናበት ስለመሆኑ ገልፆ ከቀረበው የፍሬ ጉዳይ ክርክር አንፃር ማጣቀሻ ሊሆን የሚችል የአገሪቱ የህግ ማእቀፍ አካል የሆነን ህግ መሠረት አድርጎ ክርክሩን አላቀረበም፡፡

በፍ/ቤት ሊከበር የሚችል መብት በሌላ የዳኝነት አካል እንዲታይ ካልተደረገ በቀር ከህግ የመነጨ መብት ሊሆን እንደሚገባ ከላይ እንደተመለከተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33(2) በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ይልቁንም ክስ የቀረበበት ኮሌጅ ከተቋቋመበት ዓላማ፣ በኮሌጁ ከሚሰጠው የትምህርት ይዘት ይህንንም መነሻ በማድረግ ለተማሪነት ማንን እንደሚመለምል፣ለምልመላው ማሟያ የሆኑ መስፈርቶች፤ እነዚህ መስፈርቶች መሟላትና አለመሟላታቸውን በኮሌጁ ትምህርት ተካፋይ የሆኑ ተማሪዎች በትምህርት አቀባበል ሂደት ሊገልጿቸው ስለሚገቡ የዲሲፒሊን ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ ኮሌጆችን ለአቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን የተተው ከመሆኑ በቀር ይህንን ጉዳይ ሁሉ ሊሸፍን የሚችል ዝርዝር ህግ በህግ አውጭው በኩል የተቀረፀ አይደለም፡፡

የተለያዩ ሙያዎችንና ክህሎቶችን ለማስረጽ እንዲቻል በሚል የተቋቋሙት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንኳ ለትምህርት ነፃነት ሲባል በተመሣሣይ ከላይ የተመለከቱትን ጉዳዮች አስመልክቶ ክርክር ቢነሣ እንኳ እንደማናቸውም ጉዳይ ያለገደብ በፍርድ ቤት ቀርበው ሊታዩ የማይችሉ ጉዳዮች እንደሆኑ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 ለአብነት ማሣያ ነው፡፡

ስለሆነም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከትምህርት ገበታው የተሰናበተው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ የግለሰብ መብቱን ስለሚመለከት ከህገ መንግስቱ አንፃር ማስከበር ስለሆነ የሚለውን ትርጉም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 የግለሰብ ፍትህ የማግኘት መብት በፍርድ ሊያልቁ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ መሆኑ ተገልፆ የተደነገገ መሆኑን ያላገናዘበና ከሌሎች ህጐች አንፃር በሚል በደፈናው ከመግለጽ ውጭ በየትኛው የህግ ዘርፍ ሥር እንደተመለከተም ያልተገለፀና ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተውም የግራ ቀኙን ጉዳይ የሚገዛ በህጋችን ማእቀፍ የተካተተ ዝርዝር ህግ የሌለ ከመሆኑ እንፃር ሁሉ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 36114 በ24/7/2003 እና በሐምሌ 07/2003 ዓ.ም የተሰጡት ብይን እና ፍርድ ተሽረዋል፡፡
2. የከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ በኮ/መ/ቁ. 115269 በ28/03/2004 የሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት የሆነውም ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
3. ከሣሽ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 እንደተደነገገው በፌዴራል ፍ/ቤቶች አማካኝነት በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ጉዳይ አይደለም ብለናል፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 43511

ጥቅምት 23 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- የሚች የአቶ ዋሲሁን መኮንን ሚስትና ወራሾች

1. ወ/ሮ ወ/ጻዲቅ ደሜ
2. ወ/ሮ መሰረት ዋሲሁን
3. አቶ ተስፋዬ ዋሲሁን
4. አቶ አበበ ዋሲሁን
5. ወ/ሪት ፋሲካ ዋሲሁን
6. ወ/ሪት የሺመቤት ዋሲሁን
7. አቶ ተሾመ ዋሲሁን
8. ወ/ሪት ሃና ዋሲሁን

ወኪል ጌትነት ዋሲሁን ቀረቡ

ተጠሪ፡- የመንግስት ቤቶች ኤጂንሲ - ነ/ፈጅ ጌታቸው ምንተስቶት ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንግድ ቤት ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጂንሲ ሲሆን በዚህ አካል አቤቱታ ያቀረቡት የአሁኑ አመልካቾች አባት ሲሆኑ ጊዜውም ጥቅምት 13 ቀን 1988 ዓ/ም ነው፡፡ የአመልካቾች አባት አቤቱታ ይዘት ሲታይም በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 7፣ ቀበሌ 34፣ የቤት ቁጥር 703 የሆነውን ንግድ ቤት በደርግ መንግስት ከአዋጅ ውጪ የተወሰደባቸው መሆኑን ገልጸው ንግድ ቤቱ እንዲመለስላቸው ይወሰን ዘንድ መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ከአቤቱታቸው ጋርም የቤቱን ባለሃብትነትና ቤቱ ከአዋጁ ውጪ ስለመወረሱ ያሳያሉ ያሏቸውን በርካታ የሰነድ ማስረጃዎች አያይዘው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት ኤጀንሲም የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት አቤቱታ ስለቀረበበት ንግድ ቤት በዝርዝር መግለጫ በማዘጋጀትና ከመስሪያ ቤቱ ሕጋዊ ውክልና በተሰጠው ሰው አማካኝነት ምላሽ እንዲሰጥበት ያደረገ ሲሆን ተጠሪ በወቅቱ በሰጠው ምላሽ ንግድ ቤቱ በመንግስት እጅ ያለ መሆኑን በመግለፅ ነገር ግን በምን ሁኔታ ሊወረስ እንደቻለ ማረጋገጫ ማስረጃ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ መልስ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኋላ አቤቱታ የቀረበለት ኤጀንሲ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና ምላሽ በመመልከትና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ጉዳዩን ከአጣራ በኋላ ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምሮ አቤቱታ የቀረበበት ንግድ ቤት ለአመልካቾች አባት እንዲመለስላቸው ሲል በመ/ቁጥር 20/ነ2/497/9987/93 በቀን 15/05/1993 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኋላ በወቅቱ ስያሜ ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ተብሎ የሚታወቀው አካል በመሰል ጉዳዮች የይግባኝ ስልጣን ለአለው የፕራይቬራይዜሽን ቦርድ ይግባኙን አቅርቦ ቦርዱም ጉዳዩን አመልካቾች በሌሉበት አይቶ ንግድ ቤቱ ለአመልካቾች አውራሽ እንዲመለስ በማለት የተሰጠውን የኤጀንሲውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም የሰበር ችሎቱ አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የኤጀንሲው ቦርድ ውሳኔ አስተዳደራዊ ከመሆኑ ባሻገር ይህንን አስተዳደራዊ ውሳኔ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል ወይም አልተፈጸመበትም ለማለት ችሎቱ ስልጣን የለውም በሚል ምክንያት ወደ ፍሬ ጉዳዩ ሳይገባ መዝገቡን ሚያዚያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ዘግቶታል፡፡

ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስነሳ ነው በማለት ለሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ ጥያቄ ቢያቀርቡም ተቀባይነት ያጡ ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አቅርበው ምክር ቤቱም ጉዳዩን ተመልክቶ የኤጂንሲው ቦርድ ዳኝነት መሰል አካል (Quasi judicial body) በመሆኑና ይህ አካል የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ ጉዳዩን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዳኝነት ስልጣኑ ማየት እንደሚችል በመግለጽ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣ 803(ሀ))፣ አዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 2(3)፣ 5(3) እና አዋጅ ቁጥር 87/86 አንቀፅ 8(5) ድንጋጌዎች በዋቢነት በመጥቀስ ጉዳዩን ሰበር ችሎት እንዲመለከተው በሙሉ ድምጽ በመወሰን ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በኋላ የሰበር ችሎቱ አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 87/1986 አንቀጽ 8(5) መሰረት የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ውሳኔው ላይ ለመድረስ የተከተለው አካሄድ የሕግን አግባብ የተከተለ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ያደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለትም ተጠሪ ቀርቦ በሰጠው መልስ ሰበር ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንደሌለውና የኤጀንሲው ቦርድ ጉዳዩን በይግባኝ ሲመለከት የተከተለው አካሄድም አግባብነት ያለው መሆኑን ጠቅሶ እንዲሁም አከራካሪው የንግድ ቤት ለአመልካቾች የሚመለስበት ሕጋዊ አግባብም እንደሌለ ዘርዝሮ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ጉዳዩን የሰበር ችሎት ለመዳኘት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት የመነጨ ስልጣን ያለው መሆኑን ጠቅሰውና የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ጭብጦች፡-

1. ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? እና፣
2. ከተባለስ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ስርዓቱን የተከተለ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ሁነው አግኝቷቸዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች የፕራይቬታይዜሽን ኤጂንሲ ቦርድ ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም. በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘትና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ምክንያት የካቲት 09 ቀን 2001 ዓ.ም. በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ለሰበር ችሎቱ አቅርበው አጣሪው የሰበር ችሎት የኤጀንሲው ቦርድ የሚሰጠው ውሳኔ አስተዳደራዊ በመሆኑ ጉዳዩ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ወይም አልተፈፀመም ለማለት ችሎቱ ስልጣን የለውም በሚል ምክንያት መዝገቡን ዘግቶት ጉዳዩ እስከ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ደርሶ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጉዳዩን መርምሮ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው መሆኑን በመዘርዘር የወሰነና ጉዳዩ በችሎቱ እንዲታይ የመለሰ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 62(1) መሰረት ሕገ መንግስትን የመተርጎም ስልጣን ያለው አካል ሲሆን የዚህን አካል ስልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀፅ 3(1) ስርም ህገ መንግስትን የመተርጎም ስልጣን የምክር ቤቱ መሆኑ በግልጽ ሰፍሯል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 56(1) ስር ደግሞ ምክር ቤቱ በቀረበለት ጉዳይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስርም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ውሳኔውን የማክበርና የመፈፀም ግዴታ ያለባቸው መሆኑ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ተቀምጧል፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከላይ በተገለፁት የሕግ ማዕቀፎች በተሰጠው ስልጣን መሰረት አመልካቾች ያቀረቡትን ጥያቄ መርምሮ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ ለመስጠት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን ዘርዝሮ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ ለጉዳዩ የመጨረሻ ሲሆን በዚህ ችሎትም ሆነ በሌሎች በሚመለከታቸው አካላት መከበርና መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 56 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያስነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የተጠሪ ነገረ ፈጅ ይህ ችሎት ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት የሚያቀርቡት ተቃውሞ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የሠጠውን ውሳኔ ይዘትና የአዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀፅ 56 ድንጋጌን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጂንሲ ቦርድ የኤጂንሲውን ውሳኔ የሻረው የአሁኑን አመልካቾችን ጠርቶና ተገቢውን ክርክርና ማስረጃ እንዲያስሙ በማድረግ ያለመሆኑን ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ይህ የኤጀንሲው ቦርድ አካሄድ በአዋጅ ቁጥር 87/1986 እና ይህንኑ አዋጅ ተከትሎ በወጡትና ስራ ላይ በነበሩት የቦርዱ መመሪያዎች ተገቢ ነው በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 87/1986 በአንቀጽ 8 ስር የኤጀንሲውን ቦርድ ስልጣንና ተግባር የዘረዘረ ሲሆን በተጠቃሹ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አምስት ስር የኤጀንሲውን ውሳኔ በሚመለከት ከማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚቀርብለትን ይግባኝ ሕጋዊነቱን መርምሮ መወሰን ከስልጣንና ተግባራቱ አንዱ ስለመሆኑ ያሳያል፡፡ ይህ ድንጋጌ የኤጀንሲው ቦርድ ይግባኙን ሲመረምር ሊከተለው ስለሚገባው ስነ ስርዓት በግልጽ አያስቀምጥም፡፡ ይሁን እንጂ የአዋጁ አንቀጽ 9 የቦርዱ ስብሰባ የሚመራበትን ስርዓት የሚደነግግ ሲሆን ስብሰባው የሚመራበትን ደንብ ቦርዱ ሊያወጣ እንደሚችል ደግሞ በአንቀፁ ንዑስ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አራት ድንጋጌ ስር ያስቀምጣል፡፡ ይህ አካል ከፊል የዳኝነት ስልጣን ያለው አካል እንደመሆኑ መጠን የሚሰጠው ውሳኔ የተፈጻሚነት ኃይል ያለው ስለመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በመ/ቁጥር 63627 በቀረበው ጉዳይ ላይ ሰጥቶታል፡፡ ቦርዱ ከፊል ውሳኔ ሰጪ አካል እንደመሆኑ መጠን የሚሰጠው ውሳኔ የሕጉን ስርዓት ተከትሎ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠለት የክርክር አመራርና አሰጣጥ ስርዓት እስከሌለ ድረስ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት የተጠበቁትን ፍትህ የማግኘት፣ የመሰማትና በእኩል ሚዛን የመታየት መብት ሊያከብር ይገባል፡፡ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሊጠበቁ ከሚገባቸው ሕገ መንግስታዊ መብቶች አንዱ ደግሞ ክርክር የማቅረብና ማሰረጃ የማሰማት መብት ነው፡፡ ይህ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የግድ ከሚላቸው የስነ ስርዓት አካሄዶች አንዱ ነው፡፡ ክርክሩን በአግባቡ እንዲያቀርብ እድል ያላገኘ ሰው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37 የተከበረለት ፍትህ የማግኘት መብቱ ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የመሰማት መብት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሊከበር የሚገባው መብት ነው፡፡ የመሰማት መብት ከመጀመሪያው ክርክር ጀምሮ እስከመጨረሻው የዳኝነት ሰጪ አካል መከበር ያለበት ስለመሆኑ በሕገ መንግስቱና ስለ ክርክር አመራር በተደነገጉት እንደፍትሐብሔር ስነ ስርአት አይነት ሕጎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚ የሆነ መደበኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ከፊል የዳኝነት ስልጣን ያላቸው አካላት በይግባኙ የክርክር ሂደት የተከራከሪ ወገኖችን የመሰማት መብት ሳያከብሩ ውሳኔ የሚሰጡበት ሂደት መኖር እንደሌለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337፣ 338፣ 339 እና ከሌሎች ስለ ማስረጃ አቀራረብ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ ጉዳዩን በይግባኝ ሲመለከት አመልካቾች በአካል አስቀርቦ የመሰማት መብታቸውን በመጠበቅ ጉዳዩን የመረመረ ስላለመሆኑ ተጠሪም የሚክደው ፍሬ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው የኤጀንሲው ቦርድ የአፈጻጸም መመሪያ 001/88 አንቀፅ 8.1 እስከ 8.6 እና ከአንቀጽ 9.1 -9.4.3 እንዲሁም 11.4 ስር ባሉት ድንጋጌዎች የአቤቱታ አመዘጋገብ፣ ማጣራትና ውሳኔ አሰጣጥ እንዴት መሆን እንዳለበት በዝርዝር የተቀመጠ በመሆኑ የኤጀንሲው ቦርድ የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን የፍርድ አሰጣጥ ስነ ስርዓት ባለመከተሉ ብቻ የሕግ ስህተት ፈጽሟል ለማለት አይቻልም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠቃሹ መመሪያ ምንጭ ማድረግ ያለበት አዋጅ ቁጥር 87/87 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ሲሆን በዚህ ረገድ የክርክር አመራርን በተመለከተ ስነ ስርዓት ሕጉን ቦርዱ እንደሚያወጣ የሚያሳይ ድንጋጌ የሌለ ሲሆን የአዋጁ አንቀጽ 9 የአማርኛ ቅጂው ርእሱ “የቦርዱ ስብሰባ" በሚል የተቀረፀ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቅጂ ደግሞ “Meetings of the board” በሚል የተቀመጠ እና በአንቀፁ ንዑስ ቁጥር አራት ድንጋጌ ስር ደግሞ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል ተብሎ መደንገጉን የድንጋጌው የአማርኛ ትርጉም ሲያሳይ፣ የእንግሊዝኛው ትርጉምም “The Board may determine its own rules of procedure.” በሚል ሰፍሯል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አዋጁ የይግባኝ ክርክር አመራር ስርዓትን በተመለከተ ግልፅ የሆነ ድንጋጌ ያላስቀመጠና ለቦርዱ ደንቡን እንዲያወጣ ስልጣኑን የሰጠውም የራሱን ስብሰባ በተመለከተ እንጂ የክርክር አመራሩን፣ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት ሂደትንና አተገባበሩን በተመለከተ ያለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አለ የሚለው መመሪያ በይግባኝ ክርክር ሂደት ሊሰሙ የሚገባቸውን ሰዎችን መብታቸው ሳይጠበቅ እንዲያልፍ ለማድረግ ሥልጣን ባለው አካል የወጣ ነው ለማለት የማያስችልና መመሪያው ስልጣን ባለው አካል የወጣ ነው ቢባል እንኳ ይዘቱና መንፈሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲታይ የክርክር አመራሩ ሂደት የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን የሚገድብ ሳይሆን ቦርዱ ጉዳዩን ሕጋዊ ስርዓቱን በመጠበቅ ለራሱ አሰራር አመቺ ነው ባለው መንገድ እንዲመራ ለማስቻል ነው ተብሎ የሚታመን ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የሚከናወን የክርክር አመራር በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 37 እና ኢትዮጵያ ተቀብላ ባጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የተከበረውን ፍትህ የማግኘት እና የመሰማት መብቶችን የመሸርሸር ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አካሄድ አይደለም፡፡ የኤጀንሲው ቦርድ ይግባኙን የተመለከተውና ውሳኔ የሰጠው የአመልካቾችን የመሰማት መብት ሳያከብር መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ስለ ክርክር አመራር በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተደነገገውን ስርዓት የጣሰ ሲሆን በክርክር አመራር ሂደት የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን ያለመጠበቅ ደግሞ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ነው፡፡ በመሆኑም የኤጀንሲው ቦርድ ይግባኙን የተመለከተው ሕጋዊ ስርዓትን ተከትሎ ባለመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የፕራይቬታይዜሽን ኤጂንሲ በጉዳዩ ላይ ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ/ም በቀድሞው ወረዳ 7 ቀበሌ 34፣ ቁጥር 703 የሆነ ንግድ ቤት ለአመልካቾች አውራሽ አቶ ዋሲሁን መኮንን እንዳይመለስ በማለት የሰጠው ውሳኔ የአመልካቾች የመሰማት መብት ሳይጠበቅ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፕራይቬይታዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ በመ/ቁጥር 20/ነ2/497/9987/93 በቀን 15/05/1993 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ 9ተገቢ መሆን ያለመሆኑን አመልካቾች ባሉበት አጣርቶና የአመልካቾችን የመሰማት መብት በሕጉ አግባብ በመጠበቅ እንዲመለከተውና ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 75034

ህዳር 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮ - ነ/ፈጅ መስፍን አበበ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መኮንን ተክሉ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከአቃቤ ሕግ ሙያ ጋር ተያይዞ የተነሳውን የስራ መደብና ቦታ ዝውውርን መቃወምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረቱት ክስ ይዘት ሲታይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት በአቤቱታ ምርመራና ክስ አቀራረብ ንዑስ የስራ ሂደት በምርመራና ክስ ኤክስፐርትነት የስራ መደብ ታክስን ጨምሮ ብር 4,210.00 ደመወዝ እየተከፈላቸው ለሁለት አመታት ያገለገሉ መሆኑን፣ የአካል ጉዳተኛ መሆናቸውንና በ2002 ዓ.ም እና 2003 ዓ/ም በተደረገ የስራ አፈጻጸም ግምገማ የላቀ የስራ አፈጻጸም ውጤት ያላቸው መሆኑን ገልጸው አመልካች ያላግባብ ወደ ልደታ ክፍለ ከተማ ንቃተ ሕግ መፍጠር ንኡስ የስራ ሂደት ተጠሪ ተዛውረው በሕግ ኤክስፐርትነት እንዲሰሩ በማድረግ ከቀድሞው ደመወዝና ጥቅማጥቅም ብር 425.00 እንዲቀነስ በማድረጉ ከሕግ ውጪ የተደረገና የተከናወነ ተግባር ነው፣ መድሎም ተፈጽሟል ተብሎ እና አንባቢ ተመድቦላቸው ወደ ቀድሞው ስራ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም አመልካች ዝውውሩን ለመፈጸም ስልጣን እንደአለውና ጉዳዩም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሊታይ የማይገባው እና በከተማው ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር እንደሚወድቅ ገልጾ ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲዘጋ ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪ የተሻለ ውጤት ሊያስመዝገቡ ይችላሉ ተብሎ በታመነው የስራ መደብ ላይ እንዲመደቡ መደረጉንና በደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ረገድም የስራ ቦታው የትራንስፖርት አበል የማያስፈልገው በመሆኑ ምክንያት ይሽው አበል ከመቀነሱ ውጪ የተቀነሰ ደመወዝ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በቃል ክርክር ወቅት ከአዋጅ ቁጥር 568/2000 አንጻር የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንደአለው ገልጸው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ያደረገው አዋጅ ቁጥር 568/2000 መሆኑና በዚህ አዋጅ አንቀፅ 2(7) ስር ደግሞ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት የሚችል መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ መደንገጉን ጠቅሶ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን ተቃውሞ ያለፈው ሲሆን ፍሬ ነገሩን መርምሮም የተጠሪ ዝውውር በአድሎአዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተግባር የተፈጸመ ሳላለመሆኑ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 7(2) ድንጋጌ መሰረት የማስረዳት ሸክሙን አልተወጣም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ዝውውሩን ሽሮ ተጠሪ ቀድሞ ይሰሩበት ወደ ነበረው ቦታና የምርመራና ክስ ኤክስፐርትነት የስራ መደብ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በፍርድ ቤቱ የታየው ከስልጣኑ ውጪና ባልተፈጋጠ ፍሬ ነገር ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዋጅ ቁጥር 568/2000 መሰረት በሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው በማለት ያቀረበው ተቃውሞ ታልፎ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዓቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 24/1999 መሰረት አስተናግደው ዝውውሩ ሕገ ወጥ ነው በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በፍርድ የሚያልቅ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት የሚሰሩት በአቃቤ ሕግነት ሙያ መሆኑን፣ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት ተጠሪ ከሚሰሩበት፤ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የፍትህ ጽ/ቤት የአቤቱታ ምርመራና ክስ አቀራረብ ንዑስ የስራ ሂደት በምርመራና ክስ ኤክስፐርት የስራ መደብ ወደ ልደታ ክፍለ ከተማ ፍትህ ጽ/ቤት ንቃተ ሕግ መፍጠር ንዑስ የስራ ሂደት አመልካች ያላግባብ አዛውሯል፣ ከቀድሞው ደመወዝና ጥቅማጥቅም ብር 425.00 እንዲቀንስ በማድረጉ ዝውውሩ ከሕግ ውጪ ነው፣ አካል ጉዳተኛ በመሆኔም መድሎ ተፈጽሟል በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ በአቃቤ ሕግነት ተሹመው የሚሰሩ መሆኑን ሳይክድ ዝውውሩ ስራና ሰራተኛን ለማገናኘት የተደረገ መሆኑን ጠቅሶ ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሊታይ እንደማይገባና በሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ወይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የሚታይ መሆኑን ገልጾ መከራከሩን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በአቃቤ ሕግነት ተሹመው የሚሰሩ የአመልካች ሰራተኛ መሆናቸውን ነው፡፡

በመሰረቱ የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪን ክስ ለመዳኘት የቻሉት የአዋጅ ቁጥር 568/2000 አንቀጽ 2(7) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ፍርድ ቤት ማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌዴራል ወይም የክልል ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ አዋጁ በአንቀጽ 10(1) ስርም በአዋጁ ድንጋጌዎች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ባለመከበራቸው ምክንያት መብቱ የተነካበት ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ ወይም አካል ጉዳተኛ አባል የሆነበት የአካል ጉዳተኞች ማህበር ወይም አካል ጉዳተኛው አባል የሆነበት የሰራተኛ ማህበር ወይም አዋጁን የሚያስፈጽም አግባብ ያለው አካል ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ እንደሚችል የተቀመጠ ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 3 ደግሞ አዋጁ በማንኛውም ስራ ፈላጊ አካል ጉዳተኛ ወይም አካል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳተኛ ሰራተኛና በአሰሪ መካከል በሚኖር የስራ ስምሪት ግንኙነት ላይ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው ተደግንጓል፡፡ እንዲሁም አዋጁ የአካል ጉዳተኞችን የስራ መብት መጠበቁና አድሎም መከልከሉን እንደ ቅደም ተከተላቸው በአንቀፅ 4 እና 5 ስር በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያሳዩት በሹመት የሚያዙ የስራ መደቦችን ሁሉ በተመለከተ በአዋጁ ለመግዛት የታሰበ ያለመሆኑን ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በአዋጁ የተቀመጡት የአካል ጉዳተኛ መብቶችን ተሿሚ የሆነውን አካል ጉዳተኛ የሚያስተዳድረው አካል ሊያከብራቸው አይገባም ማለት አይደለም፡፡ በመሆኑም ተሿሚ የሆነውን የአካል ጉዳተኛ ጉዳይ በአዋጁ አንቀጽ 2(7) መሰረት ፍርድ ቤት ሊመለከተው ይገባል ከተባለ በተለይም በዳኝነት ስራ ወይም በአቃቤ ሕግነት ስራ የተሰማሩትን አካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በዚህ ረገድ በሕግ አግባብ የተቋቋሙት አካላት እንዳይመለከቱ የማድረግ ውጤትን የሚያስከትል ነው፡፡ ስለሆነም አዋጅ ቁጥር 568/2000 ስለ አካል ጉዳተኞች የስራ ስምሪት የወጣ አዋጅ ሁኖ በአዋጁ፣ አግባብ ባለው ደንብና መመሪያ የተከበሩ መብቶችን የሚነካ ተግባር ሲፈጸም በፍርድ የሚያልቅበት አግባብ ያለ መሆኑን የሚደነግግ ቢሆንም ተሿሚ የሆኑ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ግን ጉዳዩ በፍርድ ቤት ክስ የሚቀርብበት ሳይሆን በዚህ ረገድ በሕግ ተለይተው ለተቋቋሙት አካላት የሚቀርብና እነዚህ አካላትም አዋጁንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሰረት አድርገው ጉዳዩን የሚያስተዳደሩበት ስለመሆኑ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ በማገናዘብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ባለው የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዐቃቢያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 24/1999 አንቀፅ 2(4) ዐቃቤ ሕግ ማለት በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር የፍትህ አስተዳደር እንዲያገለግል በደንቡ አንቀጽ 4 በተመለከቱት ደረጃዎች በአንዱ የተሾመ ሰራተኛ መሆኑን ትርጉም የተሠጠበት ጉዳይ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 አንቀጽ 2(5(ሐ)) ድንጋጌ ሲታይም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ዳኞችና አቃቢያነ ሕግን እንደማያካትት የተደነገገ ሲሆን የእነዚህ ባለሙያዎችን ጉዳይ በተመለከተ የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት የሚያስተናግድበት አግባብ አይኖርም፡፡ ከእነዚህ የሕግ ማዕቀፎች በግልጽ መረዳት የሚቻለው የአቃቢያነ ሕግ ስራ የሚገኘው በሹመት መሆኑን ሲሆን ጉዳዩን የሚገዛው የተለየ ሕግም በደንብ ቁጥር 24/1999 ወጥቶ ስራ ላይ ያለ መሆኑንና ይህ ደንብ በሕግ አግባብ ያልተለወጠ መሆኑን ነው፡፡ ደንቡ የዐቃቤነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ መቋቋሙን በአንቀፅ 44 በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን በአንቀጽ 46 ስር ደግሞ ስለጉባኤው ስልጣንና ተግባር ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ ከጉባኤው ስልጣንና ተግባራት መካከል አንዱ ደግሞ ደረጃቸው ከምክትል ረዳት ጠቅላይ አቃቤ ሕግ በታች የሆኑ አቃቤያነ ሕግን ቅጥር፣ ዝውውርና የደረጃ እድገት በሚመለከት ውሳኔ መስጠት ስለመሆኑ ደንቡ በአንቀጽ 46(3) ድንጋጌ ስር አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል፡፡ ደንቡ የይግባኝ መብትን በተመለከተም በአንቀፅ 41 ስር አስቀምጧል፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው ደንብ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ የከተማውን አቃቤያነ ሕግን በተመለከተ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ምክንያት የተለየ ሕግ ባልወጣበት ሁኔታና አዋጅ ቁጥር 568/2000 በሕግ ተዋረድ ከደንቡ በላይ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም አዋጁ ደንቡን ሙሉ በሙሉ የተካበት መንገድ ያለ ስለመሆኑ በግልጽ የሚያሳይ ድንጋጌ ሳይኖር በአዋጅ ቁጥር 568/2000 መሰረት የአካል ጉዳተኞች አቃቤያነ ሕግ የዝውውር ጉዳይ የአድሎ ተግባር የተፈፀመ ነው ተብሎ ስለተገለጸ ብቻ በፍርድ እንዲያልቅ የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በአቃቤያነ ሕግነት ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኛ እና ስራው ሹመት ሁኖ የተለየ የሕግ ማዕቀፍ በሆነው በደንብ ቁጥር 24/1999 የሚገዛ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 568/2000 ይዘትና መንፈስ አዛምደው ሳይመለከቱ ጉዳዩ በፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ቀጥታ ክስ የሚቀርብበትና እልባት የሚሰጥበት ነው በሚል ምክንያት ጉዳዩን መዳኘታቸው በሕጉ ባልተሰጣቸው ስልጣን ሁኖ ስለአገኘን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 4፣ 9 እና 231(1(ለ)) ድንጋጌዎች አኳያ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00746 ሐምሌ 08 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 111843 ህዳር 22 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪ አካል ጉዳተኛ ቢሆኑም በደንብ ቁጥር 24/1999 መሰረት ተሸመው የሚሰሩ በመሆኑ አከራካሪው ጉዳያቸው በደንቡ መሰረት ስልጣን ባለው አካል ከሚታይ በስተቀር በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም ብለናል፡፡

3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 75788
ህዳር 05 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሙስጠፋ አህመድ
ተኽሊት ይመስል

አመልካቾች፡- ፡- 1ኛ/ አቶ በረከት ኃ/ኪሮስ
2ኛ/ አቶ ዮሐንስ ኃ/ኪሮስ
3ኛ/ አቶ አስቻለው ስሜ - } ጠበቃ አቶ ለገሰ ማሞ ቀረቡ

ተጠሪች፡- አቶ ጎይቶም ኃ/ኪሮስ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር መነሻ የሆነው የአሁኖቹ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች እንዲሁም በክርክሩ ሂደት በሞት የተለየችው የምስራች ኃ/ኪሮስ የሚች አባታችን የአቶ ኃ/ኪሮስ አባይ ውርስ ይጣራልን ሲሉ በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አንዳቸው በሌላኛው ላይ ያቀረቡት ክስ መሆኑን የአሁኑ 2ኛ አመልካች ክሱን ያቀረበው በአሁኑ 1ኛ አመልካች እና በምስራች ኃ/ኪሮስ ላይ መሆኑን የምስራች ኃ/ኪሮስ ክስ ያቀረበችው ደግሞ በአሁኑ 1ኛ አመልካች ላይ መሆኑን ፍ/ቤቱም ለሁለቱ ክሶች የተከፈቱትን ሁለት መዝገቦች በማጣመር ውርሱ እንዲጣራ ያደረገ ቢሆንም የምስራች ኃ/ኪሮስ ባቀረበችው ይግባኝ መነሻ የአሁኑ 2ኛ አመልካች የውርስ ይጣራልኝ ክስ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመወሰኑ የአሁኑ 2ኛ አመልካች ከክርክሩ ውጪ መሆኑን በምስራች ኃ/ኪሮስ ከሳሽነት እና በአሁኑ 1ኛ አመልካች ተከሳሽነት በመ.ቁ. 17994 የተጣራው ውርስ በአፈፃፀም ደረጃ ደርሶ የምስራች ኃ/ኪሮስ በሚች ባለቤት በወ/ሮ ዘላለም ስሜ ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ ድርጅት (የውርስ ሀብት) በሀራጅ ለማሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ ጉዳዩ በቀጠሮ እያለ የምስራች ኃ/ኪሮስ በ12/11/02 በሞት በመለየቷ ምክንያት የጨረታው ሂደት ተቋርጦ መዝገቡ መዘጋቱን ከዚህ በኋላ በተከሳሽነቱ ሲከራከር የነበረው የአሁኑ 1ኛ አመልካች እና ቀደም ሲል ከክርክሩ ውጪ ተደርጎ የነበረው የአሁኑ 2ኛ አመልካች የሚች የምስራች ኃ/ኪሮስ ተተኪ ወራሾች መሆናቸውን በ05/12/02 በፍ/ቤት ያረጋገጡበትን ማስረጃ በመያዝ በ10/12/02 ቀርበውና ጉዳዩን አንቀሳቅሰው የውርስ ሀብቱ በሀራጅ እንዲሸጥ ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ቀሪ ተደርጐ ድርጅቱን በስምምነት ሸጠው ለመቅረብ እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ፍ/ቤቱ በመቀበሉ ድርጅቱን በስምምነት አጐታቸው ነው ለተባለው ለአሁኑ 3ኛ አመልካች መሸጣቸውን ገልፀው የሽያጭ ውሉን ይዘው በ12/12/02 በመቅረባቸው ፍ/ቤቱ የሽያጩን ውሉን አጽደቆ በውሉ መሰረት እንዲፈጸም በዚሁ ዕለት ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡን ዘግቶ ያሰናበታቸው መሆኑን ከዚህ በኋላ የስር በመቃወም አመልካች (የአሁኑ ተጠሪ) የአቶ ኃ/ኪሮስ አባይ ወራሽ

ስለመሆኑ ማስረጃ በማያያዝ የስር በመ/ተጠሪዎች (የአሁኖቹ አመልካቾች) ወራሽ መሆኔን እያወቁ እና የሚች የምስራች ኃ/ኪሮስ ውርስም በሕጉ አግባብ ሳይጣራ በ10/12/02 እና በ12/12/02 የሰጡት ትዕዛዝ መብቴን የሚነካ በመሆኑ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 358-360 መሰረት እንዲነሳ ይወሰንልኝ ሲል መቃወሚያ ማቅረቡን ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ የመ/ተጠሪዎች ተተኪ ወራሽ ነን ብለው መዝገብ ከማንቀሳቀስ ውጪ የየምስራች ኃ/ኪሮስ ውርስ በሕጉ መሰረት እንዲጣራ እንዳደረጉ በ10/12/02 እና በ12/12/02 የተሰጡት ትዕዛዞች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 3 መሰረት እንደፍርድ እንደሚቆጠሩ እና ወደ 3ኛ የመ/ተጠሪ የስም ዝውውሩ አለመፈፀሙን ከከተማው አስተዳደር እንዳረጋገጠ በዝርዝር በመግለፅ በመ.ቁ 17994 በ21/03/04 በሰጠው ውሳኔ በ10/12/02 እና በ12/12/02 ሰጥቷቸው የነበሩትን ትዕዛዞች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360 መሰረት መሰረዙን ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ 11312 በ04/04/04 በሰጠው ትዕዛዝ የቀረበለትን ይግባኝ ሳይቀበለው መቅረቱን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም አመልካቾች የሚኖሩት በደቡብ ክልል ተጠሪ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል በመሆኑ ምክንያት በተለያዩ ክልሎች በሚኖሩ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የተነሳ ክርክርን የማየት ስልጣን የፌ/ፍ/ቤቶች መሆኑን በመግለፅ በመ.ቁ. 56046 27/04/04 ጉዳዩን ማሰናበቱን የክርክሩ ሂደት ያስረዳል፡፡

አመልካቾች በ1/05/04 አዘጋጅተው ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ተከራካሪ ወገን የሚባሉት ከሳሽ እና ተከሳሽ እንጂ በመቃወም አመልካች ጭምር ስላልሆነ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የአሁኑ ተጠሪን በተከራካሪ ወገንነት መፈረጁ ስህተት ነው በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 358 መሰረት መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው በስረነገር ውሳኔ ላይ እንጂ በ10/12/02 እና በ12/12/02 በተሰጡት ዓይነት የአፈፃፀም ትዕዛዞች ላይ አይደለም 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የሸያጩን ገንዘብ የተቀበሉ የሰነድ እና የንብረት ርክክብ የተደረገ እና ውሉ እና ትዕዛዙ ከማህደሩ ጋር የተያያዘ በመሆኑ በ12/12/02 የተሰጠው ትዕዛዝ ተፈፅሟል እነዚህ ሁኔታዎችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንዳለባቸው የሚያረጋግጡ በመሆኑ እንዲሻሩ ይወሰንልን የሚል ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ በ7/9/04 በተፃፈ ማመልከቻ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 358 መሰረት መቃወሚያ ለማቅረብ የቻልኩት የአባቴ ኃ/ኪሮስ አባይ እና የእህቴ የምስራች ኃ/ኪሮስ ውርስ እንዲጣራልኝ በከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ መስርቼ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የፍ.ሥ.ሥሕ.ቁ 7 ድንጋጌን ጠቅሰው መቃወሚያ በማቅረባቸው እና ክስ ያቀረብኩበት መ.ቁ 10067 በመቃወሚያው መሰረት በመዘጋቱ ነው፣ ትዕዛዞቹ እንደፍርድ የሚቆጠሩ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ትርጉም ስህተት የለውም የስም ዝውውር አልተፈፀመም በመ.ቁ 23149 በ20/12/02 ዕግድ አሰጥቻለሁ ወራሽ መሆኔን እያወቁ እና ውርስ ሳይጣራ አመልካቾቹ ውሉን አቅርበው ያስፀደቁት ከቅን ልቦና ውጪ ነው 3ኛ አመልካች የ1ኛ እና የ2ኛ አመልካቾች የእናት ወገን አጐት ነው በ10/12/02 በተደረገው ውል በአንቀጽ 2.2. መሰረት ስም እስኪዛወር ድረስ ብር 50,000 በገዥው እጅ እንደሚቆይ ስለተገለፀ ክፍያ ተፈጽሟል የተባለው ሀሰት ነው በዚህም ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ውሳኔዎች ስህተት የሌለባቸው በመሆኑ እንዲፀኑ ይወሰንልኝ በማለት መልስ ሰጥቶ እና አመልካቾችም በ29/09/04 የተፃፈ የመ/መልስ አቅርበው የጽሁፍ ክርክሩ በዚሁ ተጠናቋል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በክርክሩ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ የደቡብ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት አቤቱታውን ያሰናበተው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት በሀገራችን ፍ/ቤቶች በተለያየ ደረጃ እና እርከን ተዋቅረው የሚገኙ ሲሆን ይህ አወቃቀር የክልል እና የፌዴራል ፍ/ቤቶችንም የሚያጠቃልል ነው፡፡ በተለያየ ደረጃ እና እርከን ተዋቅረው ከሚገኙት መካከል እያንዳንዱ ፍ/ቤት የሚያስተናግዳቸው የጉዳይ ዓይነቶች የሚወሰነው ለየፍ/ቤቱ በሕግ ተለይቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተሰጠ የስረ ነገር እና የግዛት ስልጣን ነው፡፡ የግዛት ስልጣን በዋነኛነት መሰረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረበትን ቦታ ለተከራካሪ ወገኖች የሚኖረውን አመቺነት እና መሰል ሁኔታዎችን ሲሆን የስረ ነገር ስልጣን መሰረት የሚያደርገው ግን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ይዘት፣ የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ጥቅም ክብደት እና መጠን የጉዳዩን የውስብስበነት ደረጃ እና መሰል ነጥቦችን በመሆኑ በጉዳዮች አመራር ስርዓት ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው እና በጥንቃቄ መጤን የሚገባው ነው፡፡ የፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 9 እና 10 ድንጋጌዎች ተገናዝበው ሲታዩም ሕጉ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ከግዛት ስልጣን ይልቅ ለስረ ነገር ስልጣን መሆኑን መገንዘብ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ የፍ/ቤቶች ስልጣን ሌላው ገጽታ ፍርድን የማስፈፀም ስልጣን ነው፡፡ ፍርድን የማስፈጸም ጉዳይ በስረ ነገር ክርክሩ ተረጋግጠው የፍርድ ኃይል ያገኙት የተከራካሪ ወገኖች መብት እና ግዴታ በስነ ስርዓት ሕጉ የተደነገገውን የአፈፃፀም ስርዓት ተከትለው እንዲፈፀሙ ከማድረግ ውጪ አዲስ መብት እና ግዴታ የሚቋቋምበት ባለመሆኑ ብዙ ሲያከራክር አይታይም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 371 ላይ እንደተመለከተው የማስፈፀም ስልጣን የስረ ነገር ስልጣንን የሚከተል ነው፡፡ ተገቢ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙም ስረ ነገሩን የወሰነው ፍ/ቤት አፈፃፀሙን በውክልና ወደ ሌላ ፍ/ቤት ሊመራው እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 372 የተመለከተ ሲሆን በላይኛው እርከን የሚገኙ ፍ/ቤቶች የአፈፃፀም ጉዳዮችን በውክልና በታችኛው እርከን ለሚገኙ ፍ/ቤቶች ጭምር የሚያስተላልፉባቸው አጋጣሚዎች ይኖራሉ፡፡ ይህ ሁኔታም ፍርድን የማስፈፀም ስልጣን ከስረ ነገር ስልጣን በእጅጉ የተለየ እና የስረ ነገር ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ጭምር በውክልና ሊሰጥ የሚችል መሆኑን መገንዘብ በሚያስችል ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የደቡብ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም ያለው ጉዳዩ በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ግለሰቦች የሚከራከሩበት መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ እንደተባለው ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች በሆኑ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚነሳ ክርክርን የማየት ስልጣን የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑ በአዋጁ 25/1988 አንቀጽ 5(2) ስር ተመልክቷል፡፡ አዋጁ በዚህ ሁኔታ የደነገገው የስረ ነገር ስልጣንን ነው፡፡ ለሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ግን የተነሳው ከስረ ነገር ፍርድ ሳይሆን ከፍርድ አፈፃፀም ትዕዛዞች መሆኑን መዘገቡ ያስረዳል፡፡ ሰበር ችሎቱ የጠቀሰው የአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2) ድንጋጌ ፍርድ የማስፈፀም ስልጣንን የሚገዛ አይደለም፡፡ ለአፈፃፀም የቀረበውን የስረ ነገር ፍርድ የሰጠው የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፍርዱን የማስፈፀም ስልጣን የሚኖረውም ይኸው ፍ/ቤት ነው፡፡ በአፈፃፀም ደረጃ ወደ ጉዳይ የገባው ተከራካሪ ወገን የሌላ ክልል ነዋሪ መሆኑ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 371 የተደነገገውን ፍርድን የማስፈፀም ስልጣን የሚነካ አይደለም፡፡ በዚህም ሁኔታ ሰበር ችሎቱ አቤቱታውን ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው ስልጣን የለኝም በማለት ያሰናበተው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የሌላ ክልል ነዋሪ የሆነ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ደረጃ ወደ ክርክሩ መግባቱ ጉዳዩን ወደ ፌዴራል ጉዳይነት ይለውጠዋል የሚባል ቢሆን ኖሮ ሰበር ችሎቱ አቤቱታውን አስተናግዶ የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች በሆኑ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የተነሳ ክርክርን የማየት ስልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም ? በሚለው ጭብጥ ዙሪያ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት የሚገባው ሆኖ እያለ ጉዳዩ በፌ/ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ በመሆኑ የሰበር አቤቱታውን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት አቤቱታውን ማሰናበቱ አቋሙ እና ትዕዛዙ የማይጣጣሙ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ ከላይ በዝርዝር በተገለፀው ሁኔታ የደቡብ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሁለት የተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ግለሰቦች ተከራካሪ የሆኑባቸውን ጉዳዮች የማየት ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት የፌ/ፍ/ቤት በመሆኑ የሰበር አቤቱታውን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 56046 በ27/04/04 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ በዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑን ተገንዝቦ ጉዳዩን በማንቀሳቀስ የአሁኖቹ አመልካቾች አቅርበውለት የነበረውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 341(1) መሰረት ወደ ክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲመለስ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. እልባት ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይምለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 81963

ታህሳስ 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ህይወት

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አስፋው ጉደታ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርምራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገው ጊዜያዊ/ኮንትራት/ የሰራተኛ ቅጥር ግንኙነት የመነጨን ክርክር እንደጊዜው ቅደም ተከተል በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የአሰሪና ሰራተኛ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የአሁን አመልካችን ካሰናበተው፤ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 515/99 የተቋቋመው የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤትም ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ ካደረገው፤ የአመልካች ጉዳይ በየትኛው የዳኝነት አካል ሊታይ ይገባል? የሚለውን ነጥብ ለይቶ ለመወሰን ሲባል ነው፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ በሆኑት በየደረጃው በተሰጡት ዳኝነቶች እና በግራ ቀኙ ክርክር እንደተረጋገጠው አመልካች የአሁን ተጠሪ ቋሚ ሰራተኛ አይደለም፡፡ ግንኙነቱ በጊዜያዊ የቅጥር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ተጠሪም በአዋጅ ቁጥር 515/99 የሚገዛ መንግስታዊ መ/ቤት ስለመሆኑም አላከራከረም፡፡

አመልካች ለዚህ የሰበር ጉዳይ ምክንያት የሆነውን ክስ በሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤት ከማቅረቡ በፊት በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የአሰሪና ሰራተኛን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ለማየት ስልጣን ባለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማቅረቡና ችሎቱም ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ዳኝነት ከዚህ የሰበር ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት ያለው ባይሆንም ከላይ በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው አሰሪው የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 መሰረት የሚተዳደር በመሆኑ የግራ ቀኙ ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ሊዳኝ የሚችል አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ የአሰሪና ሰራተኛ ችሎቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ዳኝነት በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የአሁን አመልካችን ፍትህ ለማግኘት መብት በሚያጣብብ አኳኋን በስልጣን ረገድ የተሳሳተ ዳኝነት ሰጥቷል በመሆኑም አመልካች ፍትህ የማግኘት መብቱን የት ያረጋግጥ? ፍትህ የመግኘት መብቱ ተነፍጓል፤ ለሚለው መደምደሚያ መነሻ ሊሆን የሚችል ዳኝነት አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሰረት የሚገዛ፤ የሚተዳደር መ/ቤት ይሁን እንጂ በእርሱ እና በሰራተኞች መካከል ከስራ ግንኙነት የመነጨ ክርክር በተነሳ ጊዜ በማን እና በምን አኳኋን መሰረት ሊስተናገድ እንደሚችል በሚደነግገው በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 2(1) ስር የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤቱ ሥልጣን በፌዴራል የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ በሚሰራ ሰራተኛ ላይ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ በሆነው በይ/መ/ቁ 01371/2004 ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት የአመልካችን ጊዜያዊ ወይም የኮንትራት ሠራተኛ መሆን መነሻ አድርጎ ጉዳዩን ለማየት በህግ ተለይቶ የተሰጠን ሥልጣን የለም በሚል የሰጠው ብይንም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ይልቁንም የአዋጅ ቁጥር 515/99 የተፈፀሚነት ወሰን በቋሚ ሰራተኞች ላይ የተወሰነ በመሆኑ የተነሳ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኞች ጉዳይን ጭምር ሊሸፈን ያልቻለ መሆኑ ታይቶ ይህንኑ ክፍተት ለመሙላት በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 22(3) መሰረት የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ በመስከረም ወር 2000 ወጥቷል፡፡ ይህ መመሪያ ቀጣሪ በሆነውና በጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኛ መካከል ሊነሱ ሚችሉትን ክርክሮች ሁሉ አይቶ መብትና ግዴታን በመወሰን ረገድ በተሟላ አኳኋን የወጣ መመሪያ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጉዳይ እንዳለ ሆኖ የዚህኑ መመሪያ አፈፃፀም በሚመለከት ቀጣሪው በሚሰጠው ውሳኔ ተቀጣሪው ካልተስማማ አቤቱታውን ወይም ይግባኙን ለመደበኛው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል በሚል የተደነገገው ለዚህ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንዳለው ተረድተናል፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካች የአዋጅ ቁጥር 515/99 የአፈፃፀም ወሰን፤ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 22(3) መሰረት የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ ለማውጣት ከተፈለገበት ዓላማ እና የተፈፃሚነት ወሰን አንፃር አገናዝቦ ሲታይ መ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ጉዳዩን ለፌዴራል ከፍ/ፍ/ቤት መቅረብ የሚገባው እንጂ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ሆነ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንፃር እንደቅደም ተከተሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም በሚል የተሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሳ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 01371/2004 ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ተመልክቶ ይኸው ብይን በህግም ሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 80357 ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ሁሉ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ጉዳዩን ሥልጣን ላለው አካል አቅርቦ የማስማት መብቱን ይህ ፍርድ አያግደውም ብለናል፡፡
3. በዚህ የሰበር ጉዳይ ክርክር የተነሳ ግራ ቀኙ ላወጡት ወጭና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80005

ጥቅምት 09 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ አላኒ በክረ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ቦጋለ ዱንፋ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የጅማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የስራ ግንኙነትንና ተፈፃሚነት ያለውን ህግ የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ድርጅት የጥበቃ ስራ መደብ ላይ ተመድቦ ሲሰራ ከየካቲት 22 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ ከስራና ከደመወዝ ያገደኝ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደስራዬ ይመልሰኝ በማለት ለወረዳው ፍ/ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ሰራተኞቹ በሲቪል ሰርቪስ ህግ (አዋጅ ቁጥር 515/99) መሰረት የሚተዳደሩ በመሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት ሥልጣን የለውም፡፡ ተጠሪ የኤጀንሲውን ሰራተኛ በመደብደቡ ከስራ የተሰናበተ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለኝ፣ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 377/96 ነው በማለት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ተጠሪን ያለአግባብ ከስራ ያሰናበተው በመሆኑ ወደ ስራው ይመለስ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች አዋጅ ቁጥር 553/1999 በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ነሐሴ 29 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ሰራተኞቹን የሚያስተዳድረው በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረታዊ መርሆዎች መሰረት እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህም በመሆኑ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት መብቱን ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት ማቅረብ ሲገባው ለጅማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ማቅረቡና የበታች ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን ተቀብለው መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች አቤቱታ የህግ መሰረት የለውም፡፡ ተጠሪ በዲሲፕሊን ኮሚቴ የተሰጠብኝ ውሳኔ የለም የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ሰኔ 28 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ሀምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን አመልካች ያነሳውን መቃወሚያ በማለፍ ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 553/1999 ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ የተቋቋመ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የአመልካች ዋና ዳይሬክተርም የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህግን መሰረታዊ መርሆዎች በመከተል ቦርዱ በሚያፀድቀው መመሪያ መሰረት የኤጀንሲውን ሰራተኞች የሚቀጥርና የሚያስተዳድር መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 553/1999 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህም የአመልካች ሰራተኞችን መሰረታዊ መብትና ግዴታ የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድና የስራ ስንብት ህጋዊነት በተመለከተ ተፈፃሚ የሚሆነው የህግ ማዕቀፍ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ሳይሆን አዋጅ ቁጥር 515/1999 መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡

የጅማ ዞን ወረዳ ፍ/ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 515/1999 የሚተዳደሩ የፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች የሚያቀርቡትን አቤቱታ የመቀበልና ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አልተሰጣቸውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በመቀበል ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችለን የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣን የለንም በማለት መዝጋት ሲገባቸው፣ አመልካች በራሱ ገቢ የሚተዳደር መስሪያ ቤት ስለሆነ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 377/1996 ነው በማለት ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል የጅማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት የሚታይ በመሆኑ የጅማ ወረዳ ፍ/ቤትና የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ስልጣን የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 83425

ጥር 02 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
አዳነ ንጉሴ
መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአብጃታ ሻላ ሶዳ አሸ አክሲዮን ማህበር - ጠበቃ ተሾመ ቢራ ቀረቡ
ተጠሪ፡- የአብጃታ ሻላ ሶዳ አሸ መሰረታዊ ሰራተኛ ማህበር ስለ ተወካይ ጃራ ኡሻ ቀረቡ

1. ነጋዎ ጤፎ
2. አሚኖ ኡሻ
3. አሉታ ዋዶ
4. አቡ መለቶ
5. ገበኦ ኤዱ
6. ሁሰን ማሉ
7. ቦኔ ሳክሎ
8. በዳሶ ቡዱ
9. ሁሴን ናኔሶ
10. አሊዬ ደቀቦ
11. ኢቲሶ በሩሻ
12. ቡሊ ሂርጳ
13. ከድር ሀጂ
14. ጢቤሶ ሮባ
15. ዳቤ ገልገሎ
16. ተሸቱ ቡዱ
17. አበሻ ሳፋኦ
18. ሁሴን ዳባ
19. ቱና ጢንቤ
20. መንግስቱ ሂንሴኔ
21. አማን ሀ/ሃሰን
22. ፈረዳ ቡታ
23. ግርማ ጎሌ
24. ጎዳና ቡላ
25. ጎዳና ሹቤ
26. ጎሌ ሻሌ
27.ወልዳዩ ሄርጳ
28. ኮርማ በዳሶ
29. ገመዳ ለገቶ
30. ሀሰን ዳለቻ
31. ሮባ ቱኔ
32. ታደለ ውብሸት
33. ቡዬ ቦረማ
34. ጠና ወቲቻ
35. ተሾመ ነገሥ
36. ተሸቱ ቢልቢላ
37. ገመዳ ሮባ
38. ገነሞ ቡልቃ
39. ቦንሶ ያሴ
40. ለሜቻ ተካልኝ
41. ገመዳ ዋታ
42. በቀለ ወልደማሪያ
43. ጃርጌ ሂንሴኔ
44. ጢሊሳ ማንዳዩ
45. ቱኪ ጎበና
46. የኔነሽ መንግስቱ
47. ይልማ ሞላ
48. ዋሪ ጅሩ
49. ወልዴ ጉተማ
50. ታደሰ በለጠ
51. ሊቃስ ለቤና
52. ቄሩ ገመዳ
53. ቄሩ ጀንጃሳ
54. ቃበቶ ጉዬ
55. ሂርጳ ሁልፌ
56. ሀይለኛው ወርቁ
57. ደጃ ጃንጁሳ
58. ደበበ ተክሌ
59. ግርማ ቡኪ
60. ገመቹ ጨራ
61. ገመዲ ገነሞ
62. አህመድ አደም
63. በለጠ አለማየሁ
64. ብርሃኑ ወዬሶ
65. በዳኔ ሚንጆሶ
66. አቤ ቡኑሼ
96. አንበሳ ጉዬ
97. ይርጋ ገበየሁ
98. ኩርኩሩ መቺሳ
128. ዋሪ በሪሳ
129. ዋዩ ሽቶ
130. ሂርጳ ጃርሶ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

67. አማን ስቱሳ
68. አበበ ደጆኔ
69. አቡሽ ማካንጎ
70. አበባ ቅጣው
71. አዱኛ ጉደታ
72. አበባ ቱራ
73. ዮሐንስ አየለ
74. ዋዶ ሀሰን
75. ተስፋዬ ሰይፉ
76. ወርቁ ገብሬ
77. እሸቱ ላታሞ
78. ጌታቸው ሐይሉ
79. ጃራ ኡሻ
80. ወለሳ ሙክታር
81. ጸሐይ ከበደ
82. ቶላ ወቲቻ
83. ሽታዬ ደምሴ
84. ሽመልስ ዳያሮ
85. ማስረሻ ወልዴ
86. መንገሻ ዋሌ
87. መሀመድ ዳውድ
88. ዮሴፍ ክሌቻ
89. አንለይ ገላው
90. አስረስ ቸኮል
91. አየለች በላቸው
92. በዳሶ ፉሪ
93. ቦንሶ ቶላ
94. በለጠ ባዩቦ
95. አሊ አብዱልቃድር
99. አደም ነገሞ
100. ግርማ ማሞ
101. አደም ከድር
102. መልከቶ ጢንቢሴ
103. ኩባ ሺግዳ
104. ካሪም ደቀቦ
105. ጃልዳ ገመዳ
106. ዱሌ ዳዲ
107. አበቡ ገመዳ
108. ቁፋ ገመዳ ጌሳሞ
109. አማን ሃጂ ጠደቻ
110. ሀቡ ገዳ
111. ባቲ ጡና
112. ነቢ ገባባ
113. ፊዬ ቢልቢላ
114. ሀጂ ጣደቻ
115. አማኖ ገመቹ
116. አቡ ቡታ
117. ሞገስ ዶያሮ
118. ገመዲ ጌላ
119. ሂርጳ ሌንጂሶ
120. ሀቢቦ ገልገሉ
121. ለማ ሀይሉ
122. ዋሪዩ ኡሼጦ
123. አቡ ቲያ
124. አብድልቃድር ጎበና
125. ቁፋ ደቀቢ
126. ለሜቻ ጋጉሮ
127. ጎዳና ገባባ
131. አቢቲ ዋሪ
132. ጃውሮ ዳሉ
133. ቃዎ ሜጢ
134. ገመዳ ዩቢሳ
135. አኑሎ ፈይሳ
136. ደስታ ደለቻ
137. ሌንጮ ገመዳ
138. ይርዳው አለሙ
139. ንጉሱ ጆሮ
140. ጌትነት መታፈሪያ
141. ቢልቢላ ቂጦ
142. ቁፋ ገረጂ
143. ብደላ እንድሪስ
144. ቀበቶ ገመዳ
145. ሚኤሶ ዳለቻ
146. አቤል ዳለቻ
147. ዋሪ ኤገቶ
148. ሜሻ ገዳ
149. ዲማ ኤንቶ
150. አብጃቶ ደገላ
151. ደቀቦ ኤገቶ
152. ዶኒ ዶሪ
153. ዋሾ ጎሴ
154. ጃልዶ ዋሪ
155. ደስታ ቡሎ
156. ወይንሸት ታደለ
157. ዱሬቲ ኤቢሳ
158. ዘቢደሩ አለማየሁ
159. ፈይሳ ጅሩ
160. ተሾመ ዋቁሼ
161. ሚኢሶ ደለቻ
162. አልማዝ በዳሶ
163. መሰማ ሀምሳ
164. ኮርማ ባቲ
165. ቲኬ ባሩሽ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጡረታ መብት ይጠበቅልን ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በቦርድ ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው ከ158 በላይ የሆኑትን ሰራተኞች በመወከል ሲሆን ሰራተኞቹ ከ1979 ዓ.ም ወይም በጊዜያዊነት የስራ መደብ ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ በማህበሩ በአባልነት ተመዝግበው እንደሚገኙ፣ ማህበሩ በጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀፅ 11(4/ሠ) ስር የሰራተኛው የአገልግሎት ዘመን እና የሰራተኛው የጡረታ መዋጮ 4% እና ከማህበሩ በተጠቀሰው መሰረት ሲፈፅሙ ከሰራተኞቹ አብዛኛዎቹ ለረዥም ጊዜያት በጊዜያዊነት ቅጥር የስራ መደብ ላይ ላገለገሉበት ጊዜ ለጡረታ ሳይመዘገብ በቋሚነት ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ብቻ በመመዝገብ ላይ ስለሆነ ይህ አፈፃፀም ትክክል ያልሆነ መሆኑ ተገልፆላቸው በማህበሩ ሰራተኞች መካከል ልዩነት ሳይፈጥር አካሄዱን በማስተካከል የጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀፅ 11(4/ሠ) ድንጋጌ በሚያዘው መሰረት የጡረታ ጊዜያአቸውን በጊዜያዊነት ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ በመመዝገብ የጡረታ መዋጮ ከሰራተኛው ደመወዝ የሚቆረጥ 4% ፣ ከማህበሩ ተቆራጭ የሚደረገው መዋጮ 6% በመሰብሰብ ከባንክ ወለድ ጋር ለጡረታና ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በመላክ ገቢ እንዲሆንላቸው ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን የሌለው መሆኑንና ማህበሩ ክስ የመሰረተላቸው ሰራተኞች ጊዜአዊ ሰራተኞች በመሆናቸው ለቋሚ ሰራተኞች የተጠበቀውን የጡረታ መብት ለመጠየቅ ክስ ለመመስረት መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ማህበሩ ክስ ያቀረበላቸው ሰራተኞች በኮንትራትና በቀን ስራ እንዲሁም በጊዜአዊነት የተቀጠሩ በመሆናቸው የአገልግሎት ዘመናቸው እና የስራ ልምዳቸው የተቆራረጠ በመሆኑ የስራ ልምድ ማስረጃ ለመስጠትም አስቸጋሪ መሆኑንና ሰራተኞቹ በኮንትራት ያገለገሉት ጊዜ ለጡረታ እንዲያገለላቸው የማድረግ ስልጣን የተከሳሽ ድርጅት ያለመሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ቦርዱም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩ በቦርዱ ስልጣን የሚወድቅ አይደለም በማለት መዝገቡን ዘግቶት የነበረው ሲሆን ማህበሩ በዚህ የቦርዱ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ቦርዱ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን እንዳለው በመግለፅ ውሳኔ በመስጠቱ ጉዳዩ ለቦርዱ የተመለሰለት ሲሆን ቦርዱም ጉዳዩን ማየት በመቀጠል ጉዳዩን መርምሮና አጣርቶ ክሱ የሚመለከታቸው ሰራተኞች ሁሉ የጡረታ ጊዜያቸው ሊቆጠር የሚገባው ስራቸውን ሳያቋርጡ መስራት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ስለሆነ አመልካች ድርጅት በእጁ ያለውን ማስረጃ መርምሮ እንዲያስብላቸውና ከሰራተኞቹ የሚሰበሰበውን መዋጮ 4% እና የአመልካች መዋጮ 6% አንድ ላይ በማጣመር ለሚመለከተው አካል ማሳወቅና ገቢ ማድረግ እንዲችል፣ ጡረታው ሊቆጠር ከሚገባው ጊዜና ቀን ጀምሮ እንዲቆጥርላቸውና እንዲፈጸምላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ የጡረታ መብት ይጠበቅልኝ ሁኖ እያለ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የተከበሩት መብቶችን ለማየት ስልጣን ለተሰጠው ቦርድ ቀርቦ መወሰኑ ያላግባብ መሆኑና ተጠሪ ክስ የመሰረተላቸው ሰራተኞች የኮንትራት ሰራተኞች በመሆናቸው ለቋሚ ሰራተኞች የተጠበቀላቸው መብት እንዲጠበቅላቸው የተወሰነው ከሕግ ውጪ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም

www.chilot.me

ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል የተባለው ቦርዱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የነበረው መሆን ያለመሆኑን፣ የተጠሪዎች ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም የመባሉን በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀፅ 11(1(ሀ)(ሠ)) መሰረት ተጠሪዎች ስራቸውን መስራት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ይቆጠርላቸው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡
የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሰፈልገው ጉዳይ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች ዳኝነት የተጠየቁት የጡረታ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ነው፡፡ ቦርዱ ይህንኑ የተጠሪዎች ጥያቄ አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልነበረው መሆኑን ገልፆ ክሱን ዘግቶ የነበረ ሲሆን ጉዳዩን እንደገና አይቶ ሊወስን የቻለው በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሠረት መሆኑን በውሳኔው ላይ ጠቅሷል፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ አሁን እንደገና ማየት ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የተመለከተው ጉዳዩ የስልጣን ጥያቄ በመሆኑና የስልጣን ጥያቄ ደግሞ በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም ክርክሩ ባለበት በማናቸውም ደረጃ በፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት መነሳት የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9 እና 231 /1/ለ/ ድንጋጌዎች ስር ከተመለከቱት ድንጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ/ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10፣ 22 እና አዋጅ ቁጥር 454/1997 2/1/ ከተሰጠው ስልጣን አኳያ ነው በመሆኑም ችሎቱ ተመሳሳይ ለሆኑ ጉዳዮች በአገሪቱ ወጥ የሆነ የፍርድ አሰጣጥ ስርዓት እንዲኖር አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንዲሰጥ በሕግ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑና የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ደግሞ በሕጉ አግባብ ጉዳዩን የመዳኘት ያለመዳኘታቸውን በዳኝነት ሥልጣኑ መቆጣጠር ያለበት በመሆኑ የስልጣን ጥያቄውን አሁን ክርክሩ ባለበት ደረጃም ቢሆንም ማየቱን ስነ ሥርዓታዊ የማያደርገው ሕጋዊ ምክንያት አላገኘም፡፡

ከዚህ አንጻር ቦርዱ ጉዳዩን ለመወሰን ስልጣን ያለው መሆን ያለመሆኑን ስንመለከት ለቋሚ ቦርድ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ተለይተው የተሰጡት የዳኝነት ስልጣን ጉዳዮች በአዋጁ አንቀጽ 142 እና 147 ድንጋጌዎች ስር የተዘረዘሩት ናቸው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ከተዘረዘሩት ጉዳዮች መካከል ደግሞ የሠራተኛ የጡረታ መብት ይከበር ጥያቄ በቦርዱ ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ የለም፡፡ ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ስለጡረታ መብትን የሚገዛው አዋጅ ቁጥር 345/1995 ሲታይም ከአሰሪያቸው ጋር ያለው ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የሰራተኞች የጡረታ መብታቸውም የሚገዛበት አግባብ መኖሩን አያሳይም፡፡ ተጠሪዎች ሥራ ሲጀምሩ አመልካች ድርጅት የመንግስት ሙሉ ይዞታ ነበር ቢባል እንኳን የተጠሪዎችን የጡረታ መብት ይከበርልን ጥያቄ በቦርድ የሚዳኝበት አግባብ ስለመኖሩ ለመንግስት ሰራተኞች የጡረታ መብት ይደነግጉ የነበሩት አዋጅ ቁጥር 209/1955 እና ማሻሻያዎቹ አያሳዩም አመልካች በመንግስትና በሌላ አካል በአክሲዮንነት ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮም ቢሆንም እንደማንኛውም የግል ድርጅት የሚታይ በመሆኑ ለግል ድርጅት ሰራተኞች የጡረታ መብት አግባብነት ያለው አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንጻር ጉዳዩ የሚታይ በመሆኑ በዚህ አዋጅ በተዘረጋው ስርዓት መሠረት የሚታይ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አግባብ የግል ድርጅት ሰራተኞች የጡረታ መብት ጥያቄ ላይ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጣን ያለው አካል የግል ድርጅት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጂንሲ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 53/1/ ስር በግልጽ የተመለከተ ሲሆን ይህ አካል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 202/2003 ተቋቋሞ ስራውን የሚሰራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ከሰኔ 07 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ በአንድ የግል ድርጅት የሚሰራ ሰራተኛ በአዋጅ ቁጥር 715/2003 አግባብ ለጡረታ መብት ብቁ መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው የግል ድርጅቶች ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እንጂ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተቋቋመው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች አዋጅ ቁጥር 715/2003 ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለት የሚከራከሩት ክሱ አዋጁ ከመጽናቱ በፊት ሲሆን አዋጁ ከመጽናቱ በፊት ስለግል ድርጅቶች ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ግልጽ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ አልነበረም፡፡ ቀድሞውኑ በመንግስት ይዞታ ስር የነበሩ ድርጅቶች ወደ ግል ሲዞሩም የሰራተኞችን መብትና ጥቅም በተመለከተ የሚነሳበት አግባብ ሊኖር አይገባም ከሚባል በስተቀር የጡረታ መብቱን በተመለከተ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተቋቋመው ቦርድ ለመዳኘት ስልጣን የሚያሰጥ አይሆንም ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 147/2/ እና አንቀጽ 142/ሀ/ ድንጋጌ መሠረት ቦርዱ ስለደመወዝና ስለሌሎች ጥቅሞች አወሳሰን በሚል በአማርኛው ቅጅ የተቀመጠው የሰራተኞችን የጡረታ መብት ሁሉ ሊያጠቃልል የሚችል ነው በማለት ተጠሪዎች የሚያቀርቡት ክርክር በድንጋጌው “wages and other benefits” በሚል ከተጠቀሰው የእንግሊዘኛ ቅጂ እና ለጡረታ መብት ብቁ መሆን ያለመሆኑ ለመወሰን የሰራተኛውን የተለያዩ ማስረጃዎችን መያዝና ማጠናቀርን የጡረታ አበል መጠንና የአከፋፈሉን ሁኔታ እንዲሁም ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን የሚገዛ ዝርዝር ሕግ እንዲኖር የሚጠይቅ ጉዳይ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ሲታይ “ሌሎች ጥቅሞች” የሚለው የድንጋጌው ሐረግ የጡረታ መብትን ሁሉ ይጨምራል ብሎ መተርጎም ከጡረታ መብት አጠቃላይ ዓላማና ለመብቱ ብቁ ለመሆን መማላት ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ጋር አብሮ የማይሄድ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 147/2/ እና አንቀጽ 142/1/ሀ/ ድንጋጌዎች ከአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 53 እና ከደንብ ቁጥር 202 አንቀጽ 5/7/ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የተቋቋመው ቦርድ የግል ድርጅቶች ሰራተኞች ለጡረታ መብት ብቁ መሆን ያለመሆናቸውን አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው ስልጣን ያለው መሆኑን የማያሳይ ሆኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ ተጠሪዎች የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪዎች ሊከበርልን ይገባል የሚሉት የጡረታ መብት ሊወሰን የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በተቋቋመው ቦርድ ባለመሆኑ ጉዳዩ ቦርድ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በምስራቅ ኦሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ 730/01/2004 በቀን 18/12/2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 151939 መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም. የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪዎች የጡረታ መብት ይከበርልኝ ጥያቄ በቋሚ ቦርድ ታይቶ የሚወሰን አይደለም ብለናል፡፡
3. በክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ይለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 77097

ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1.አቶ ሀይላይ ተክሉ
2. አቶ ተክላይ ገ/ሊባኖስ } ጠበቃቸው አበበ መስፍን ቀረቡ

ተጠሪ፡- የመቀሌ ከተማ ሰሜን ምድብ ዐ/ህግ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ የሰበር ተጠሪ የአሁን የሰበር አመልካቾችን ጨምሮ በ 8 ተከሳሾች ላይ ነሐሴ 11 ቀን 2002 ዓ/ም ያቀረበው ክስ፡- ተከሳሾች በትግራይ መንገዶች ባለሥልጣን የመኪና ግዥ የጨረታ የቴክኒክ ኮሚቴ ሆነው ሲሰሩ መሥሪያ ቤቱ ያወጣውን ባለ 11 ቴክኒካል መስፈርቶችን ወደ ጎን በመተው ከተጠየቀው መለኪያ በታች ያቀረበውን ሐግቤስ የተባለው ተወዳዳሪ ድርጅት ቅናሽ ዋጋ አቅርቧል በሚል ጨረታውን እንዲያሸንፍ አድርገው መስፈርት ያላሟላ መኪና እንዲገዛ በማድረጋቸው መኪናው የሚፈለገውን አገልግሎት ሳይሰጥ የተበላሸ በመሆኑ መንግሥት አስፈላጊ ያልሆነ ወጪ እንዲያወጣ በማድረግ በወ/ህ/አ/ 420/2/ የተደነገገውን በመተላለፋቸው ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾችም ባቀረቡት የክስ መቃወሚያ፡- ከሳሽ ጠቅሶ ያቀረበብን የወንጀል ህግ አንቀጽ 420 /2/ በእስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የእስራት ጊዜውም በወንጀል ህግ አንቀጽ 106(1) ሥር እንደተደነገገው ከአስር ቀን እስከ ሶስት ዓመት በመሆኑና የቀላል እስራት ይርጋ ዘመንም በወ/ህ/አንቀጽ 217(1)(ሠ) መሰረት አምስት ዓመት በመሆኑ ከሳሽ የወንጀሉ ድርጊት ተፈጽሟል በማለት በክሱ ከጠቀሰበት 29/04/1997 ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት እስከ 11/12/2002 ዓ/ም ድረስ አምስት ዓመት ከስምንት ወር ያለፈ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ ተከራከረዋል፡፡

ከሳሽም የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ በተመለከተ በሰጠው መልስ፡- ተከሳሾች የተከሰሱበት ወንጀል እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጣ ቢሆንም ወንጀሉን ስለመፈጸማቸው የታወቀው በ29/04/1997 ዓ.ም. ሳይሆን በ14/04/2001 ዓ.ም. ነው፡፡ በክሱ የተጠቀሰው ቀን 29/4/1997 ዓ.ም. ተከሳሾች የሚሰሩበት መ/ቤት ጨረታ ያወጣበት ሲሆን

www.chilot.me

ጉዳዩ የታወቀበት 14/04/2001 ዓ.ም. በመሆኑ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠርም የይርጋ ጊዜው ያላለፈ ስለሆነ ያቀረቡት የክስ መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም፡- ከሳሽ ተከሳሾች ወንጀሉን የፈጸሙት በ29/04/1997 ዓ/ም ሲሆን የወንጀሉ ድርጊት የታወቀው ደግሞ በ14/4/2001 ዓ/ም ነው ቢልም የክልሉ ኦዲተር ለክልሉ ፍትህ ቢሮ በ24/9/2001 ዓ.ም. የጻፈው ደብዳቤ በ14/4/2001 ዓ/ም መሆኑን አይገልጽም፣ በክሱ ወንጀሉ ተፈጽሟል የተባለው በ29/04/1997 ዓ/ም በመሆኑ ከሳሽ ክሱን መመስረት የሚገባው በ29/04/1997 ዓ/ም ነው፣ ተከሳሾች የተከሰሱበት ወንጀልም እስከ ሶስት ዓመት ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን ከአንድ ዓመት በላይ የሚያስቀጣው ቀላል እስራትም የይርጋው ዘመን አምስት ዓመት በመሆኑ ወንጀሉ ከተፈጸመበት ከ29/04/1997 ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ድረስም ያለው ጊዜ ሲቆጠር ከአምስት ዓመት በላይ ስለሆነ ክሱ በወ/ህ/አ/ 216 (ሠ) መሰረት በይርጋ የሚታገድ ነው ብሏል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የመቀሌ ከተማ ማዕከላዊ ፍርድ ቤትም፡- ይግባኝ ባይ ያቀረበውን ይግባኝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(1) መሰረት በመሰረዙ ይግባኝ ባይም በሥር ፍርድ ቤቶች ብይን ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በሰጠው ፍርድ፡- በዚህ ጉዳይ ወንጀሉ ተፈጽሟል የተባለው በ29/04/1997 ዓ.ም. በመሆኑ ክሱ እስከቀረበበት እስከ 11/12/2002 ዓ/ም ያለው ጊዜ የሚቆጠር ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው ፖሊስና ዐቃቤ ህግ ምርመራ ማጣራት የጀመሩት በ14/04 2001 ዓ.ም. መሆኑን የምርመራ መዝገቡ የሚሳይ ሲሆን የምርመራው መጀመር የይርጋውን መቆጠር የሚያቋርጥ

ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 221 ስለሚደነግግ አመልካች ያቀረበው ክስ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ያላለፈበት በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በሚል የስር ፍርድ ቤቶችን ብይን ሽሯል፡፡

አመልካቾችም በክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲሉ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡- ፖሊስ በተጠርጣሪዎች ላይ ምርምራ ለማድረግ ከፍርድ ቤት የመያዣ ወይም የብርበራ ትዕዛዝ ሳያገኝ የምርምራ መቅደም በ14/04/2001 ዓ.ም. መክፈቱን በመግለጹ ብቻ የይርጋ መቆጠርን ያቋርጠዋል በሚል ሰበር ሰሚው ችሎት መወሰኑ በወ/ህ/አ/219 እና 221 የተደነገገውን የሚቃረን ነው፣ ፖሊስ በአመልካቾች ላይ ምርመራ ጀምሯል ሊባል የሚችለውም በጉዳዩ ላይ የተከሳሽነት ቃላችንን እንድንሰጥ ደብዳቤ ከተጻፈልን ከ27/05/2002 ዓ.ም. ጀምሮ ስለሚሆን ወንጀሉ ተፈጸመ ከተባለበት ከ29/04/1997 ዓ/ም ጀምሮ ደብዳቤው እስከተጻፈበት ድረስም ያለው ጊዜ ሲቆጠር አምስት ዓመት ያለፈው ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው የሚሉ ናቸው ፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በጉዳዩ ላይ መልሱን እንዲያቀርብ ታዞ መጥሪያ የደረሰው ቢሆንም ቀርቦ መልስ ያልሰጠ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- በአመልካቾች ላይ የቀረበው ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪው አመልካቾች የተጣለባቸውን የስራ ኃላፊነት ባለመወጣት በመንግሥት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰዋል በሚል በወንጀል ህግ አንቀጽ 420(2) ሥር ክስ ያቀረበባቸው ሲሆን በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኞች ሆነው ቢገኙ ሊወሰንባቸው የሚችለው ቀላል እስራቱና መቀጮው በህጉ እስከተወሰነው ከፍተኛው ቅጣት ሊደርስ እንደሚችል ከድንጋጌው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ቀላል እስራትም ከአስር ቀን እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጣ መሆኑን የወንጀል ህግ አንቀጽ 106(1) የሚደነግግ ሲሆን በወንጀሉ ከባድነት የተነሳ በህጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ ወይም በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ ወይም ወንጀለኛው በተደጋጋሚ ሲቀጣ ቀላል እስራቱ አስከ አምስት ዓመት ሊደርስ እንደሚችል የድንጋጌው 2ኛው ፓራግራፍ ያመለክታል፡፡

ከአንድ ዓመት በላይ ቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን አምስት ዓመት መሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 217(1)(ሠ) ስር የተደነገገ ሲሆን የይርጋ ዘመኑም መቆጠር የሚጀምረው ጥፋተኛው የወንጀሉን ድርጊት ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 219(2) ይደነግጋል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ወንጀሉን ፈጽመዋል በሚል በክሱ የተጠቀሰው 29/04/1997 ዓ/ም ሲሆን ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበባቸው እስከ 11/12/2002 ዓ/ም ያለው ጊዜ ሲቆጠርም የክስ ማቅረቢያው አምስት ዓመት ማለፉ ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ወንጀሉ ተፈጽሟል የተባለው በ29/04/1997 ዓ/ም ቢሆንም ወንጀሉ መፈጸሙ የታወቀውና ፖሊስ ምርመራ እንዲያጣራባቸው የተደረገው በ14/4/2001 ዓ/ም ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ፖሊስ በአመልካቾች ላይ ከ14/04/2001 ዓ/ም ጀምሮ ምርመራ ማድረጉ እስከተረጋገጠ ድረስም በወንጀል ህግ አንቀጽ 221 እንደተደነገገው የይርጋ ዘመኑን መቆጠር የሚያቋርጠው ሆኖ ይርጋው እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምር ይሆናል፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ ፖሊስ ምርመራ ማጣራት የጀመረው በ14/4/2001 ዓ/ም በመሆኑ ክሱ በወ/ህ/አንቀጽ 221 መሰረት በይርጋ የሚታገድ አይደለም በሚል የሰጠው ፍርድ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 44044 በቀን 19/03/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(2)(ለ)(2) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ያላለፈበት በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 77842

ታህሣስ 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች ፡- አቶ ሳሚ ሁሴን አልቀረበም

ተጠሪ ፡- የፌደራል ዐቃቤ ህግ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካች በ1996 ዓ.ም በወጣው በወንጀል ህግ አንቀጽ 693(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በተለያዩ ጊዜ ለአንድ ሰው በቂ ስንቅ ሣይኖረው የተለያዩ ቼክ ቆርጦ ሰባት ዓይነት እራሱን የቻለ ጥፋት/offence/ ፈጽሟል በሚል የተሰጠውን የጥፋተኝነትና ውሣኔ አግባብነት ለማየት በሚል ነው፡፡

በአሁን አመልካች ላይ የፌዴራል ዐ/ሕግ ባቀረበው የወንጀል ክስ ዝርዝር እንደተመለከተው አመልካች በቂ ስንቅ ሣይኖረው ሶስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በተየያዩ ቦታ የተለያዩ ቼክ አቶ ማስረሻ ምንጃር ለተባለ አንድ ግለሰብ ብቻ ቆርጦ በመስጠቱ በ1996 የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የሚያዝበት ገንዘብ ሣይኖረው ቼክ ማውጣት ሰባት እራሱን የቻለ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ክስ አቅርቦበታል፡፡

የአሁን አመልካች የቀረበበትን የወንጀል ክሶች ይዘት እንደተረዳና እንደ ክሱ አቀራረብ ሰባቱንም ጥፋቶች ለመፈጽሙ አመኖ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.134(1) መሠረት የእምነት ቃሉን ሰጥቷል የሚለውን በመያዝ በወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ነው በሚል የጥፋተኝነት ውሣኔ እንደተሰጠ እና ለእነዚህም ጥፋቶች በህጉ የተመለከተው የቅጣት ወለል እና ጣሪያ፣ የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እና ተደራራቢ ወንጀል ተፈጽሞ በተገኘ ጊዜ ቅጣት የሚወሰንበትን ሥርዐት ሁሉ በማገናዘብ የአሁን አመልካች ቀደም ሲል በተመሣሣይ አካኋን ፈጽሟል የተባለውን 8ኛ ጥፋት ከግምት ወስጥ በማስገባት በአጠቃላይ በ25 ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ዓይነትና ዘመን እንደተጣለበት ከውሣኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

የአሁን አመልካችም ከቀረበበት ተደራራቢ የወንጀል ክስ ከባድነት አንፃር በህግ ባለሙያ ታግዞ ባለመከራከሩ ምክንያት እግ እንደ ህጉ አነጋገር የወንጀል አድራጐቱን ስለመፈፀሙ የእምነት ቃል መስጠቱ ሣይረጋገጥ አምኗል

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚል የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አግባብ አይደለም የሚልበትን ዝርዝር ምክንያት በኪር አቤቱታ ላይ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

የአሁን ተጠሪም በክሱ አሠማም ሂደት የአመልካችን የመከራከር መብት ሊያጣብብ የሚችል የክርክር ጉድለት ያለመፈጽሙንና የፋጥተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔው በህግ መሠረት ታይቶ የተሰጠ ነው የሚልበትን ምክንያት ጠቅሶ በበኩሉ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው በወንጀል ጉዳይ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 134(1) እንደተደነገገው ተከሣሹ የተከሰበበትን የወንጀል ክስ ይዘት በሚገባ ተረድቶ አድራጐቱን እንደቀረበበት የወንጀል ክስ ዝርዝር መፈፀሙን አምኖ የእምነት ቃል በሰጠ ጊዜ ይህ የእምነት ቃል ለቀረበበት የወንጀል ክስ ማስረጃ ሆኖ በዚሁ ማስረጃ መሠረት የጥፋተኝነት ውሣኔ መስጠት የሚቻልበት ሥርዓት ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አኳኋን ተከሣሹ የሚሰጠው የእምነት ቃል በማስረጃነቱ ተይዞ የሚሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ ውሣኔውን በሰጠው ፍ/ቤቱ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ የተሰማው ወገን በህገ-መንግስቱም አንቀጽ 20(6) ሆነ በዝርዝር በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሠረት ከታች ወደ ላይ በይግባኝ የመከራከር መብቱን ለማስጠበቅ የይግባኝ አቤቱታ የሚያቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

በዚህ መሠረት በይግባኝ በሚቀርበው መከራከሪያ ነጥብነቱ እንደ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 134(1) ድንጋጌ አነጋገር የወንጀሉን አድራጐት ለመፈፀሙ የእምነት ቃል አልሰጠሁም፤ ነገር ግን እንዳመንኩ ተደርጎ ጥፋተኛ ነህ ተብያለሁ በማለት ቅሬታ የቀረበ እንደሆነ ተከሳሹ ተላልፎታል በሚል የተጠቀሠበት ድንጋጌ ሥር የተቋቋመውን የወንጀል ዝርዝር ተከሣሹ በአፈፃፀሙ ረገድ የሰጠውን ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታ በማገናዘብ በእርግጥም እንደ ክሱ የወንጀሉን አድራጐት ፈጽሞታል ወይስ አልፈፀመውም የሚለውን ለመለየት ተከሣሹ ሰጠ የተባለው ዝርዝር የእምነት ቃል በመዝገቡ ላይ ሠፍሮ ካልተገኘ በቀር የበላይ ፍ/ቤቶች ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት አያስችላቸውም፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይም ተከሣሹ የአሁን አመልካች ሰባቱንም ጥፋቶች ለመፈፀሙ በደፈናው አምኗል በሚል በመዝገቡ ላይ ከመመዝገቡ በቀር ስለማመኑ የሰጠው ዝርዝር ቃል አልሰፈረም፡፡

ይህ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 134(1) ከተመለከተው ድንጋጌ ትክክለኛ አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የተነሣው ክርክር እንደ ተጠበቀ ሆኖ ተከሣሹ ስለወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም አምኗል በሚል ቃል መስጠቱን ቢታወቅም እንኳን ፍ/ቤቱ እንደነገሩ አግባብነት በዚህ በተከሣሹ የእምነት ቃል ማስረጃ ላይ ሣይወሰን ስለ ጉዳዩ ዐ/ሕግ ያቀረበውን ማስረጃ በመስማቱ ሙሉ የክርክር አካሂዱን ተከቶሉ ውሣኔ መስጠት የሚችልበትም ሥርዓት ተከታይ በሆነው ንዑስ ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡

ከዚህም አንፃር የአሁን አመልካች በአጭር ጊዜ ለአንድ ግለሰብ በተለያዩ ጊዜና ቦታ ሰባት ዓይነት ቼክ ቆርጦ ሊሰጥ ከቻለበት ሁኔታ አንፃር ለቼኩ መሰጠት ምክንያት የሆነው መስተጋብር ወይም ግንኙነት፣ እንዲሁም በዚህ ሁሉ ሂደት ቼኩን ቆርጦ በሰጠው ሰው እና ተበዳይ በተባለው ተቀባይ መካከል የነበራቸው የሃላፊ ሁኔታን ሊያመላክት የሚችል በዐ/ሕግ ማስረጃ የሚረጋገጥ የፍሬ ነገር ጉዳይ ካልተገኘ በቀር በወ/መ/ሕ/ቁ. 23 መነሻ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቀመጡትን ዝርዝር የወንጀል አፈፃፀም ደንቦች ተከትሎ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ውሣኔ መስጠት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ የከሣሽን የመደመጥ እና ፍተሃዊ ዳኝነት የማግኘት መብቱን በማስጠበቅ ረገድ ከተዘረጋው ትክክለኛ የሙግት አካሄድ አንፃር ሲታይ መሠታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወንጀል መዘገብ ቁጥር 101259 ጥር 2003 ዓ.ም እና ጥር 16 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ፤ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 66805 ታህሣስ 09 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2)(ለ)(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን ተጠሪ የፌዴራል ዐ/ሕግ በአሁን አመልካች ላይ ያቀረበውን ሰባት ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ተከሣሹ ስለመፈፀሙና አለመፈፀሙን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.134 መሠረት የሚሰጠውን ዝርዝር ቃል፤ እንዲሁም ዐ/ሕግ ክሱን ለማስረዳት ዘርዝሮ ያቀረበውን ማስረጃ በመስማትና ሙሉ የክርክር አካሄድን በመከተል በጉዳዩ ላይ ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን ወደ ሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ ይህንኑ እንዲያውቁት የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ከመሸኛ ጋር ለበታች ፍ/ቤቶች ይተላለፍላቸው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 73514

ህዳር 6 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- ተስፋዬ ጡምሮ

ተጠሪ፡- የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን - ዐቃቤ ህግ ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡

ተጠሪ አመልካች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ ቁጥር 419 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ፣ ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ ሰርቷል፡፡ ተከሳሽ የመንግስት ሰራተኛ በነበረበት ጊዜ በወር ብር 420 (አራት መቶ ሃያ ብር) እና ብር 530 (አምስት መቶ ሰላሳ ብር) እየተከፈለው የቆየ ቢሆንም፣ በመንግስት ስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሲያገኝ ከነበረው ገቢ ጋር የማይመጣጠን ብር 1,167,637.60 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር ከስልሳ ሳንቲም) በዳሽን ባንክ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በወጋገን ባንክና በንብ ባንክ ሲያንቀሳቅስ በመቆየቱና የሰሌዳ ቁጥሩ አ.አ. 2-78716 የቤት አውቶሞቢል መኪና በስሙ በመገኘቱ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ የመገኘት ወንጀል ፈፅሟል በማለት ጥር 14 ቀን 2002 ዓ.ም ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ አመልካች የክሱ ግልባጭ ከደረሰውና ከተነበበለት በኋላ የወንጀሉን ድርጊት አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ለማስረዳት አመልካች ሲያንቀሳቅስ ስለነበረው ሒሳብ የሚያሳዩ ከተለያዩ ባንኮች የተሰጠውን የሂሳብ ማመዛዘኛ የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ አመልካች በተጠሪ የቀረበበትን የሰነድ ማስረጃ መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብል የስር ፍ/ቤት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሾጌ የሲሚንቶ ውጤቶች የሁለገብ የህብረት ስራ ማህበር የሚባል በህግ የተመዘገበና ዕውቅና ያለው ድርጅት

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚሰጣቸው የሲሚንቶ ውጤቶች ዋጋ በመቀበል በስሙ ሒሳብ የሚያንቀሳቅስ መሆኑን የሚያሳዩ የሰነድ ማስረጃዎች ናቸው በማለት የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች በስሙ በተለያዩ ባንኮች ሲያንቀሳቅስ የነበረው በወንጀል ክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብና መኪና ምንጩ ህጋዊ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች አጠራጣሪ ናቸው በማለት አመልካች በ1997 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ ይዞ የተገኘ ጥፋተኛ ነው ብሎ፣ አመልካች በሁለት ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 66,660 መቀጮ እንዲቀጣ፡፡ መኪናውና በባንክ የተገኘው ብር 27,330 (ሃያ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ብር) እንዲወረሱ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት አቅርቦ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ጥቅምት 2 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ እኔ የመንግስት ሰራተኛ የነበርኩት ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ/ም መሆኑ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ በግልፅ ተጠቅሷል፡፡ አዲሱ የወንጀል ህግ በስራ ላይ እንዲውል ህግ አውጭው የደነገገው ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ይህም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 419 ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ በማድረግ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 5 የተደነገገውን መርህ የሚጥስ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ፍርድ የተሰጠብኝ መሆኑን ያሳያል፡፡ የታርጋ ቁጥር ኮድ 2-78716 የሆነችው መኪና የተገዛቸው በ2002 ዓ.ም መሆኑና ምንጩም የታወቀ መሆኑን አስረድቼ እያለ ለመንግስት ውርስ እንድትሆን መወሰኑ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ስለዚህ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ በነፃ እንድሰናበት በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የወንጀል ህጉ ወደኋላ ተመልሶ ሊሰራ አይገባም በማለት ያቀረበውን መከራከሪያ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 130 መሰረት በመጀመሪያ ክስ መቃወሚያ አድርጎ አላቀረበም፡፡ ስለዚህ በሰበር ደረጃ ይህንን መከራከሪያ አድርጎ እንዲያቀርብ የሚፈቅድለት ህግ የሌለ በመሆኑ ክርክሩ ውድቅ እንዲደረግልን፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን 1992 እስከ 1996 ዓ/ም ባለው ጊዜ ብቻ እንደተፈፀመ አድርጎ ያቀረበው ክርክር የወንጀሉን ባህሪ ያላገናዘበ ነው፡፡ አመልካች የወንጀል ምርመራ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስና እስከተከሰሰበት ድረስ የወንጀል ድርጊቱ ተፈፅሞ ተጠናቅቋል ለማለት ስለማይችል የአመልካቹ የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ጥር 5 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ጥር 23 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው እስከ 1996 ዓ.ም መሆኑን ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ በግልጽ አስፍሯል፡፡ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ መሆናቸው ከ1996 ዓ.ም በኋላ ከቆመ፣ በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የወንጀል ምርመራ እስከተጣራበትና ክስ እስከቀረበበት ድረስ ወንጀሉ የሚቀጥልበት ሁኔታ የለም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም (1) ተጠሪ አመልካች በ1997 ዓ.ም ሥራ ላይ የዋለው የወንጀል ህግ በእኔ ላይ ተፈፃሚነት የሌለው በመሆኑ፣ በዚህ ህግ መሰረት ልከሰስና ልቀጣ አይገባኝም በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 130 መሰረት በመጀመሪያ ክስ መቃወሚያነት

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላቀረበው በመሆኑ አሁን ይህንን ነጥብ የሰበር መከራከሪያ ሊያደርገው አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? (2) የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በ1997 ዓ.ም የወጣውንና ግንቦት 1 ቀን 1997 የፀናውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ ተገኝቷል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- የወንጀል ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ፎርምና ይዘት በመቃወም፣ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ሊያቀርብ የሚችል መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 130 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ክስ የቀረበበት ተከሳሽ፡-

- ጉዳዩ በሌላ ፍርድ ቤት እየታየ ያለመሆኑን፣
- ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን ወይም በይቅርታ ወይም በምህረት የተሰቀቀ መሆኑን፣
- ጉዳዩ ከሌሎቹ ተከሳሾች ጋር መጣመሩ መብቱን የሚያጣብብ መሆኑን፣
- ዐ/ህግ የወንጀል ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆነውን ፈቃድ ሳያሟላ የወንጀል ክስ ማቅረቡን፣
- በሌላ ፍ/ቤት የተያዘው ጉዳይ ካላለቀ የወንጀል ክስ ለማቅረብ የማይችል መሆኑንና ለድርጊቱ በኃላፊነት የማይጠየቅ መሆኑን በመጀመሪያ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርብ እንደሚችል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንኡስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት መቃወሚያዎች ተከሳሽ ወዲያውኑ ማቅረብ እንዳለበት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት የወንጀል ክስ መቃወሚያዎች አመላካች (indicative provision) እንጅ ሁሉንም በመቃወሚያነት ሊቀርቡ የሚችሉ ጉዳዮችን በሙሉ የሚዘረዝር (exhaustive provision) ድንጋጌ አይደለም፡፡ አመልካች የሰበር መከራከሪያ ያደረገው ነጥብ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130(2) የተመለከተ አይደለም ሆኖም ተጠሪ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ከመጽናቱ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ/ም በፊት 1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም እንደሆነ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ በግልፅ አስፍሮታል፡፡

የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረታዊ መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ዳኞች ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ፀንቶ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑን ከተረዱ በማናቸውም ጊዜ አንስተው ውሳኔ ለመስጠት የማይከለክሉና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) የተጣለባቸውን ሰብአዊ መብት የማስከበር ግዴታቸውን የሚወጡበት አንደኛው መንገድ በመሆኑና የወንጀል ክስ የቀረበበት ድርጊት በወንጀለኝነት የሚደነግግ ግልጽ የወንጀል ህግ ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ዳኞች በመመርመር የህገ መንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ የማስከበር ግዴታ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 22 እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 5 የተደነገገውን መሰረታዊ መርህ የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን በመመርመር የመወሰን ስልጣን በማናቸውም

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደረጃ በሚገኝ ፍ/ቤት የተሰየሙ ዳኞች ያላቸው በመሆኑ በዚህ በኩል አመልካች ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፣ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የፀደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ የሚፀናው በልዩ መዕሐፍ በነጋሪት ታትሞ ከወጣ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 3 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የመንግስት ሰራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች በሙስና ወንጀል ተጠያቂ ስለሚሆኑበት ወንጀል ዝርዝርና መሰረታዊ መርሆችን የሚደነግግ ከአንቀጽ 402 እስከ አንቀጽ 419 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም እና ከዚያ በኋላ የመንግስት ሰራተኛ በሆኑ ሰዎች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህንንም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2" የወንጀል ህጉ ድርጊቱ በዚህ ህግ መሰረት ወንጀል ሆኖ በተሻረው የወንጀል ህግ ግን እንደወንጀል ካልተቆጠረና የተፈፀመው ይህ ህግ ከመጽናቱ በፊት ከሆነ ሊያስቀጣ አይችልም" በማለት ደንግጎታል፡፡

ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም መሆኑን በግልጽ አስፍሯል፡፡ የወንጀል ህጉ በፀናበትና ስራ ላይ በዋለበት ግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም አመልካች የመንግስት ሰራተኛ እንዳልነበረ የተጠሪ የክስ ማመልከቻ ያረጋግጣል፡፡ ተጠሪ ክስ ያቀረበው አመልካች የወንጀል ህጉ ከመጽናቱ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም በፊት የመንግስት ሰራተኛ የነበረ መሆኑንና አመልካች ምርመራ በተጣራበት 2001 ዓ.ም በስሙ የተለያዩ ባንኮች ሒሳብ ከፍቶ ሲያንቀሳቅስ የነበረውን ገንዘብና በስሙ የገዛትን መኪና ከ1992 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ሲያገኝ ከነበረው ደመወዝ ጋር በማመዛዘን ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ይዟል በማለት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ እንደማይችልና ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ተፈፃሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ ሊቀጣ እንደማይችል በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም አገራችን ባፀደቀችው ዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 "No one shalll be held guilty of any criminal offence on account of any act or omission which did not constitute a criminal offence under national or international law, at the time which the criminal offence was committed" በሚል መንገድ ተደንግጓል፡፡

አመልካች የመንግስት ሰራተኛ የነበረው የኢፌዲሪ ወንጀል ህግ ከመጽናቱ በፊት ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ በነበረበት ጊዜ ተፈፃሚነት የነበራቸው የወንጀል የህግ ማዕቀፎች በ1949 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግና በ1974 ዓ.ም የወጣው የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት የተሻሻለው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ አዋጅ ቁጥር 214/1974 ናቸው፡፡ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ የወንጀል ድርጊት ሆኖ የተደነገገውና ይዘቱ የተዘረዘረው የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ በነበረበት ጊዜ ተፈፃሚነት ባላቸው የወንጀል ህግ ማዕቀፎች የወንጀል ድርጊት ሆኖ የተደነገገ ድርጊት አይደለም፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ከመፅናቱ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም በፊት የመንግስት ሰራተኛ በነበረውና የወንጀል ህጉ ከመፅናቱ በፊት የመንግስት ስራውን ለቅቆ በንግድ ስራ መሰማራቱ በክርክር ሂደት

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተገለፀው አመልካች ላይ የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 419 በመጥቀስ ያቀረበው ክስ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 የዓለም አቀፉን የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን መሰረታዊ የወንጀል ህግ መርህ የሚጥስና የአመልካችን መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ የተገለፀውን የህገ መንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ በማስፈፀም የተጠሪን የወንጀል ክስ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ በመገኘት የሙስና ወንጀል፣ የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) 1 መሰረት በመሻር አመልካች በነፃ እንዲሰናበት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) 1 መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በነፃ እንዲሰናበት የተወሰነ በመሆኑ በሌላ ጉዳይ ካልታሰረ በስተቀር በዚህ ጉዳይ ከእስር እንዲለቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት የመፈቻ ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡
3. አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ የተሰናበተ በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የወሰኑት የገንዘብ መቀጮና በአመልካች ስም በባንክ የሚገኝ ገንዘብና ቁጥር 2-78716 አ.አ የሆነችው መኪና እንዲወረስ የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 74237

ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ህይወት

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ተጠሪ፡- አብካስ እንደሻው ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪም 1ኛ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም ፤-ተከሳሽ በተጨማሪ እሴት ታክስ ቀ.1079.39005 እና በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር(TIN) 00512280 ለከሳሽ መሥሪያ ቤት ግብር ከፋይ ሲሆን፤ ግብይት ሲያካሂድ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማከናውን የህግ ግዴታው ሆኖ እያለ በ07/08/2003 ዓ/ም ከረፋዱ 4፡00 ሰዓት በተደረገው ድንገተኛ ክትትል ድርጅቱ ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ሲያከናውን በመገኘቱ በወ/ህ/ቁ/ 34(1) ፣አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56(1) እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣውን አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 22(1) እና 50(ለ)(1) የተደነገገውን በመተላለፉ ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅትም ክስ የቀረበበትን ወንጀል አለመፈጸሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የግራ ቀኙ ማስረጃዎችን ፍርድ ቤቱ በመስማትና በመመዘን በሰጠው ፍርድ የከሳሽ ማስረጃዎች ያስረዱትን ፍሬ ነገሮች ተከሳሽ ድርጅት ባቀረባቸው የመከላከያ ማስረጃዎች በቂ በሆነ ሁኔታ አስተባብሏል በሚል በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.149(2) መሰረት በነጻ አሰናብቶታል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ የሥር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2)ለ)(2) መሰረት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በሥር ፍርድ ቤቶች ወሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካች በዋናነት የጠቀሰው የቅሬታ ነጥብም ሲጠቃልል፡- ተጠሪው ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ያከናወነ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጦበት እያለ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ፍርድ ቤቶቹ ማስተላለፍ ሲገባቸው በወ/ህ/አንቀጽ 34(1) አንድ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል የሚጠየቀው ከድርጅቱ ሀላፊዎች ወይም ሰራተኞች አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ማራመድ ሲሆን ይህንኑ በአንቀፁ የተቀመጠውን ሁኔታ ባለማገናዘብ ክክሱ በነጻ እንዲሰናበት የወሰኑት ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

www.chilot.me

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- አንድ የንግድ ማህበር ወይም ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ/285/1994 እና ማሻሻያውን አዋጅ ቁ.609/2001 ተላልፏል በሚል በወንጀል ጥፋኛ ሊሰኝና ሊቀጣ የሚችለው የተጣሉበትን መሰረታዊ የግብር ከፋይነት ግዴታዎችን በመጣስ ሥርዓቱን በሚጻረር ህገ ወጥ የግብይት አሰራር ዘርግቶ ሲገኝ ወይም አሰራሩ ህገ ወጥ ግብይትን የሚያበረታታ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፣በዚህ ጉዳይም አንድ ዕለት ተፈጸመ በተባለና በተጨባጭም ባላተፈጸመ ስህተት ብቻ አዋጁን በሚጻረር መልኩ ህገ ወጥ የግብይት ሥርዓት ዘርግቷል ሊያሰኝና በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56(1) እንደተሻሻለው አንቀጽ 22(1) ሊያስቀጣ የሚችል አንድም ሁኔታ ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ በመገንዘብ በነጻ ያሰናበቱ ስለሆነ ውሳኔው የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ነው በሚል ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- ተጠሪው ከቀረበበት ክስ በነጻ እንዲሰናበት የተወሰነው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ማሰማቱን የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሚያመለክት ሲሆን እነዚህ ሁለቱም ምስክሮች ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለው ወቅት በተጠሪ ድርጅት ጭማቂ (ጅውስ) የጠጡና ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይቱ የተፈጸመ ስለመሆኑ ያስረዳሉ በሚል የቀረቡ ናቸው፡፡ ምስክሮቹም ለሥር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያስረዱት ፍሬ ነገር- ድንገተኛ ፍተሻ ለማድረግ ሶስት ሆነው ወደ ተጠሪው ድርጅት ሄደው ሶስት ጭማቂ (ጅውስ) አዘው ጭማቂው ከመጣላቸው በኋላ ጠጥተው ብር 30 ለአስተናጋጁ ሰጥተው መልሱን ሲጠባበቁ ከቆዩ በኋላ አስተናጋጁም ዝም በማለቱ መልስ እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ የሚመለስ ገንዘብ አለመኖሩን በመግለጹ ከ3-5 ደቂቃ ያህል ቆይተው ወደ ገንዘብ ያዥ (ካሸር) አስተናጋጁን ይዘው ሄደው የተቆረጠ ደረሰኝ መኖሩንና አለመኖሩን በመጠየቅና የተቆረጠ ደረሰኝ አለመኖሩን ማረጋገጣቸውንና በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ጥራዝ (ፓድ) የጭማቂው ሽያጭ አለመመዝገቡን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ምስክሮቹ የድርጅቱ ሥራ አስያኪያጅ በቦታው የነበሩ ስለመሆናቸው ለሥር ፍርድ ቤት ማስረዳታቸውን ፍርድ ቤቱ በፍርዱ ላይ አስፍሯል፡፡

የተጠሪ ምስክሮች ደግሞ ለስር ፍርድ ቤት ያስረዱት ፍሬ ነገሮች ፡-ተጠሪው ደርጅት ግብይት የሚያካሂደው በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መሆኑን፣ የድርጅቱ ሰራተኞችም በየዕለቱ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን ተከትለው እንዲሰሩ ተጠሪው ቅስቀሳ የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከቀረቡት 2 የመከላከያ ማስረጃዎች 1ኛው የመከላከያ ማስረጃ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለው ዕለት በቦታው ባለመኖሩ ምክንያት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መቆረጡንና አለመቆረጡን እንደማያውቅ ማስረዳቱን፣ እንዲሁም 2ኛ የመከላከያ ምስክር ደግሞ በጊዜው የተሸጡ ጭማቂዎች ሶስት ብቻ እንደሆኑና በደረሰኝ ቁጥር 20925 ሁለት ጫማቂዎች፣ በደረሰኝ ቁጥር 20929 ደግሞ አንድ ጭማቂ የተሸጠ ስለመሆኑ ማስረዳቱን የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርዱ አመልክቷል፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤትም እነዚህን የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መነሻ በማድረግ 3ኛ ተከሳሽ የነበረውን የተከሳሽ ድርጅት(ሐሮኒ ኢንተርናሽናል ሆቴል)ሥራ አስኪያጅ ቁጥጥር ባለማድረጋቸው ምክንያት ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሠኝ ግብይት ወይም ሽያጭ ተፈጽሟል በሚል የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አስተላልፎባቸዋል፡፡

የወንጀል ህግ አንቀጽ 34 የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይ ሊሆን የሚችልበትን አግባብ የሚደነግግ ሲሆን በዚሁ ደንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (1) በሁለተኛው ፓራግራፍ አንድ ደርጅት ወንጀል እንዳደረገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቆጥሮ የሚቀጣው ከሀላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ፣ወይም ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ፣ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት ፣በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ የተጠሪ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተከሰው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እስከተሰጠባቸው ድረስም በወንጀል ህግ አንቀጽ 34(1) በሁለተኛ ፓራግራፍ መሰረትም ተጠሪው ድርጅት የወንጀሉ ተካፋይ እንደሆነ የሚቆጠር በመሆኑም ተጠሪው ድርጅት በተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 34(1) አዋጅ ቁጥር 285/1995 አንቀጽ 56(1) ስር ጥፋተኛ መሆን ያለበት ነው፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ድርጅት ለግብሩ አከፋፈል የሚያገልግሉ ደረሰኞች የህትመት ፈቃድ ከአመልካች መ/ቤት በማግኘትና በሥራ ላይ በማዋል የሚጠበቅበትን አሟልቶ በመገኘት ለመንግሥት ገቢ መሆን ያለበትን ገንዘብ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ያመች ዘንድም ለድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በመቅጠር ስለ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሽያጭ ደረሰኝም ለሰራተኞቹ ትምህርትና ጥንቃቄ እንዲያደረጉ ተገቢውን ጥረት ስለማድረጉ የአመልካች ምስክሮች ከሳረዱት በተሻለ ሁኔታ የተጠሪው ምስክሮች ክሱን አስተባብለዋል በሚል ከክሱ ተጠሪው ድርጅት በነጻ እንዲሰናበት የወሰኑት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 34(1) እና አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56(1) የተደነገገውን እና ይህ ችሎት የወንጀል ጥፋት በአንድ ድርጅት ተፈጽሟል ሊባል ስለሚችልበት ሁኔታ በተመሳሳይ ጉዳይ በሰ/መ/ቁ/48850 የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ ያልተከተለ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2)(ሀ) መሰረት በመሻር ተጠሪው ድርጅት በተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀጽና እና በአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 56(1) ሥር ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 74237

ህዳር 06 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መኮንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐ/ሕግ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- እብካለ እንዳሻው ጠ/ንግድ ኃ.የተ.የግል ማህበር - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው የቅጣት ውሣኔ ለመስጠት ተብሎ ሲሆን የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረን ተከታዩን የቅጣት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅ ጣ ት

ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56/1/ን የተላለፈ ጥፋተኛ የተባለ ሲሆን አጥፊ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት አለበት፡፡ ቅጣት የሚወሰነው ደግሞ በወ/ሕ/አንቀጽ 88/2/ ስር ያሉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህን ሁኔታዎች ተመልክቷል፣ አመዛዝኗልም፡፡

ተጠሪ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሲሆን ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ድርጊት የሚያስቀጣው ከብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) በማያንስ እና ከብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከሁለት እስከ አምስት አመት በሚደርስ እስራት መሆኑን አዋጅ ቁጥር 285/1994 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለ ያሳያል፡፡ በተጠሪ አይነት ሰው ላይ ቅጣት የሚወሰንበትን አግባብ ደግሞ የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 90 መሠረት መሆኑን የወንጀል ህጉ የሚገልፅ ሲሆን የሕግ ሰውነት ባለው አካል ላይ የገንዘብ ቅጣት እና እስራት በሚጣልበት ጊዜ የእስራት ቅጣቱ ሁኔታ ወደ ገንዘብ በመቀየር መሆኑን የአንቀጹ ንዑስ ቁጥር ሶስት ድንጋጌ ይገልፃል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት እስከ አምስት አመት ቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል እስከ ብር አስር ሺህ፣ እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ለሚያስቀጣ እስከ ብር ሃያ ሺህ፣ እስከ አስር ዓመት ለሚያስቀጣ እስከ ብር ሃምሳ ሺህ፣ ከአስር ዓመት በላይ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ እስከተመለከተው ከፍተኛ ወሰን ማለትም እስከ ብር አምስት መቶ ሺህ ድረስ የገንዘብ መቀጮው ሊደርስ እንደሚችል ሕጉ ያሣያል፡፡ እንዲሁም የገንዘብ ቅጣትም በንዑስ ቁጥር አራት ድንጋጌ እንደተደነገገው እስከ አምስት እጥፍ እንደሚደርስ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90/3/ ድንጋጌ መሠረት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት እስከ ብር 20,000.00 ድረስ የገንዘብ ቅጣት እንደሚቀየር ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም የተጠሪን የድርጊት አፈፃፀም ስንመለከተው ቀላል ተብሎ ሊመደብ የሚገባ በመሆኑ በአመልካች ላይ ሊጣል የሚገባው የገንዘብ መቀጮ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ ሁኖ የእስራት ቅጣቱን ደግሞ የሁለት አመት ጽኑ እስራት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ይህ የሁለት አመት ጽኑ የእስራት ቅጣት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90/3/ በተደነገገው ስሌት መሠረት ወደ ገንዘብ ሲቀየር የሚመጣው ብር 8,000.00 በመሆኑ እና ይህ ከገንዘብ መቀጮ ከብር 10,000.00 ጋር ሲደመር የሚመጣው ውጤት ብር 18,000.00 /አስራ ስምንት ሺህ ብር/ ተጠሪን የሚያርም፣ ሌሎችን የሚያስተምርና የሚያስጠንቀቅ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ይህንኑ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲያደርግ፣ አመልካችም ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ብለናል፡፡

መዝገቡ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.75387

ጥር 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካቾች ፡- 1. አቶ ወርቁ ፍቃዱ ቀረቡ

2. አቶ ሹሜ አራርሶ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የቤ/ን/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ክርክር ሲሆን የተጀመረውም በቤ/ን/ክልል በመተከል ዞን በቡላን ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ የወረዳው ዐ/ሕግ በቁጥር 1569/2/89 በ28/11/03 በተሻ. ማመልከቻ በአሁኖቹ አመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/እና 433 ስር የተደነገገውን ተላልፈው በ28/11/03 ከቀኑ 5. ሰዓት ላይ ከሚመለከተው ባለስልጣን ሳያስፈቅዱና ፈቃድ ሳይኖራቸው ከቡላን ወረዳ ደቢና ባሩዳ ቀበሌ 15 የቀንድ ከብቶችን ገዝተውና በመኪና ጭነው ወደ ታግኒ ከተማ ሲጓዙ ኬላ ላይ በመያዛቸው ያለፈቃድ ከብት የማዘዋወር ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን ፍ/ቤቱም የዐ/ሕግን የሰው ማስረጃ እና የተከሳሾቹን የጽሑፍ መከላከያ ከመረመረ በኋላ በተከሳሾቹ ላይ በተከሰሱበት ድንጋጌ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በነፍስ ወከፍ የብር 1,200 መቀጮ ከወሰነ በኋላ በኤግዚቢትነት የተያዙት 15 ከብቶች ተሸጠው የጠባቂዎች አበል ከተቀነሰ በኋላ የሽያጩ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾቹ በቀጣይ እርከን ለሚገኙ የክልሉ ፍ/ቤቶች ያቀረቡት ይግባኝ እና አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ ሲሆን በ18/04/04 ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘትም በኤግዝቢትነት የተያዙት የቀንድ ከብቶች በወንጀል የተገኙ ናቸው ባልተባለበት እና አመልካቾቹ ጥፋተኛ የተባሉበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 433 ድንጋጌ የንብረት መውረስን ባልደነገገበት ሁኔታ ከብቶቹ ተወርሰው ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውና በበላይ ፍ/ቤቶች የፀናው ትእዛዝ ከወንጀል ድርጊቶች ጋር ተያይዞ ንብረት ስለሚወረስበት ሁኔታ በወንጀል ሕጉ የተመለከተውን መርህ የሚጥስ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በ26/06/04 በተሻ. ማመልከቻ በሰጠው መልስ የውርስ ትእዛዙ ዋና ቅጣት ሳይሆን ተጨማሪ ቅጣት መሆኑ የዚህ ዓይነቱ የውርስ ትእዛዝ በወ/ሕ. አ. 761/ሀ/ 791 እንዲሁም በፌዴራል የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/200 በአንቀጽ 60 ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት ያለውና የወንጀል ሕጉን መርህ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት ያደረገ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጐ የውርስ ትእዛዙ የተሰጠው በአግባቡ ነው ተብሎ እንዲፀና ተከራክሮአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡

በዚህም መሠረት አመልካቾቹ በተከሰሱበት ድንጋጌ የተሰጠባቸውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ተቀብለው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት አቤቱታ ያቀረቡት በውርስ ትእዛዙ ላይ ብቻ ሲሆን ለሰበር ክርክሩ በጭብጥነት የተያዘውም ይኸው ነጥብ ነው፡፡ በመሠረቱ በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ ሊደረግ የሚችልባቸው ሁኔዎች በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ተደንግገው የሚገኙ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች መካከልም በሕግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ ፍ/ቤቱ የወንጀለኛው ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲወረስ ሊወስን የሚችል ስለመሆኑ /አንቀጽ 98/ ፣አንድ ሰው ለወንጀል ስራ እንዲነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳው ወይም ወንጀሉን ለፈፀመበት ዋጋ እንዲሆነው የተሰጠው ወይም ሊሰጠው የታቀደው ማናቸውም ጥቅም ሁሉ ለመንግስት ገቢ ስለሚሆንበት አግባብ /አንቀጽ 100/ እና ወንጀልን ለመፈፀም ያገለገሉ ወይም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች ስለሚወረሱበት አግባብ /አንቀጽ 140/ በመሠረታዊነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ና የቅጣት ውሳኔን ተከትሎ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን መወሰን የሚችሉትና የሚገባቸው እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ጥፋተኞች የተባሉበት የወ.ሕ.አ. 433 ድንጋጌ የንብረት ውርስን አልደነገገም፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የሚሰጥ የጥፋተኝነት ውሳኔ የንብረት መወረስን ወይም ለመንግስት ገቢ መደረግን የሚያስከትል መሆኑን የሚገልጽ ሌላ ድንጋጌ የለም፡፡ በአመልካቾቹ ላይ ክሱን ያቀረበው የቡሌን ወረዳ ዐ/ሕግ የጥፋተኝነት ውሳኔን ተከትሎ ባቀረበው የቅጣት አስተያየት ከብቶቹ በውርስ ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ ያቀረበው ጥያቄ አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም ሆነ ቀጥሎ ያሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች ለንብረት ውርሱ ውሳኔ መሠረት ያደረጉትን ድንጋጌ በውሳኔአቸው አልገለጹም፡፡ ከብቶቹ ተሸጠው ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የተሰጠው ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ከላይ ከተጠቀሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 98፣ 100 እና 140 ድንጋጌዎች በአንዳቸውም ቢሆን የሚሸፈን ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ በመልሱ የጠቀሳቸው በደንብ መተላለፍ ክፍል የሚገኙት የወ.ሕ. አ. 761(ሀ) እና 791 ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት እንደሌላቸው ከይዘታቸው መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ የፌዴራል የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2000 አንቀጽ 60 ድንጋጌ አመልካቾቹ ያልተከሰሱበትና ጥፋተኛ ያልተባሉበት በመሆኑ ለንብረት ውርስ ውሳኔው መሠረት ሊሆን የሚችሉበት አግባብ አልተገኘም ፡፡ በመሠረቱ የወንጀል ሕግ ስለልዩ ልዩ ወንጀሎችና በወንጀል አድራጊዎች ላይ ስለሚፈፀሙት ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች በዝርዝር እንደሚደነግግ እና ፍ/ቤቶች በሕግ ከተደነገጉት በቀር ሌሎች ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን መወሰን እንደማይችሉ በወ.ሕ.አ. 2 (1) እና (2) ተመልክተዋል፡፡ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግን ጨምሮ ፍ/ቤቶች በወንጀል ረገድ የሚሰጡት ማናቸውም ውሳኔ በወ/ሕ/አ. 2 የተደነገገውን የሕጋዊነት መርህ መሰረት ያደረገ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም ሁኔታ በኤግዚቢትነት የተያዙት ከብቶች ተሸጠው የጠባቂዎች አበል ከተቀነሰ በኋላ የሽያጩ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲሆነ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ትእዛዝ /ውሳኔ/ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በኤግዚቢትነት የተያዙት ከብቶች ተሸጠው ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ ይሁን በማለት የቡላን ወረዳ ፍ/ቤት በወ.መ.ቁ. 01035 በ04/12/03 የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 05832 በ11/12/03 የቤ/ጉ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 03253 በ04/03/04 እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03391 በ04/04/04 ከሰጡት ትእዛዝ ውስጥ የንብረት ውርሱን የሚመለከተው ክፍል በወ.መ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በኤግዚቢትነት የተመዘገቡት 15 የቀንድ ከብቶች ከተሸጡበት ገንዘብ ውስጥ የጠባቂዎች አበል ተቀንሶ ለመንግስት ገቢ የተደረገው መጠን ለአመልካቾቹ ተመላሽ እንዲደረግ ወስነናል፡፡ የውሳኔው ቅጂ ይላክ፡፡
3. በበዓል ምክንያት ውሳኔው በአዳሪ በ17/05/05 ተነገረ
4. ክርክሩ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ብ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 82572

ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- መሪጌታ ፍቅረ ማርያም ካሴ ጠበቃ ማርታ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የቤንች ማጂ ዞን ዐ/ሕግ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካች በቀረበበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 539/1/ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ መባሉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? እንዲሁም የተጣለበት የቅጣት መጠን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት በአግባቡ ተሰልቷል ወይስ አልተሰላም የሚሉትን ነጥቦች ለማየት በሚል ነው፡፡

በዚህ አከራካሪ ነጥብም ላይ ግራ ቀኙ በዚህ የሰበር ደረጃ በበኩላቸው ያላቸውን ክርክር በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

እኛም በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ የአሁን አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ እና ተጠሪ ዐ/ሕግ ለሰበር አቤቱታው ከሰጠው መልስ ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የአሁን አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 539/1/ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የሰው ህይወት ለማጥፋት አስቦና አቅዶ የፀቡ መነሻ ምን እንደሆነ ባልታወቀ ምክንያት ተነሳስቶ ሚዛን ከተማ ዕድገት ቀበሌ ውስጥ ልዩ ስሙ ሸኮ በር አካባቢ ወ/ሮ ጥንቅሽ መታፈሪያን ሰርቪስ ቤት ከዲማ የመጣ መሆኑንና የመጣውም በገብርኤል ቤተክርስቲያን በቅስና ሊያገለግል ተቀጥሮ እንደሆነ ትክክለኛ ስሙን በመቀየር ቂስ ዘካርያስ ነኝ በማለት ህዳር 07 ቀን 2004 ዓ.ም ከተከራየ በኋላ ህዳር 08 ቀን 2004 ዓ.ም በግምት ከሌሊቱ 7፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ቀን አብሮት ሲዘዋወር የነበረውን ሟች ሽፈራው ደሳለኝን ከተከራየው ቤት ውስጥ በመጫኛ ገመድ አንቆ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ አንገላቶ በጭካኔና ነውረኛ በሆነ መንገድ አንቆ ገድሏል በሚል በግፍ ሰው አገዳደል ወንጀል ክስ ተከሷል፡፡

ተከሣሹ የአሁን አመልካች ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ክዶ በመከራከሩ የዐ/ሕግ የሰው ማስረጃዎች ቀርበው ተሰምተዋል፡፡ ሟች ታንቆ የተገደለበትም መጫኛ በኢግዚቢትነት ቀርቧል፡፡ የአስከሬን

www.chilot.me

ምርመራ ውጤቱንም የሚገልፅ ከሚዛን አማን ሆስፒታል የሰነድ ማስረጃ እና ሟች ሞቶ የተገኘበትን ሁኔታ የሚገልፅ ፎቶ ግራፍ በገላጭ ማስረጃነት ቀርቧል፡፡

በዐ/ሕግ በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች እንደ ክሱ አቀራረብ ተከሣሹ ሌሊት በግምት 7፡00 ሰዓት አካባቢ ሲሆን ለሟች ሞት ምክንያት የሆነውን ድርጊት የፈፀመው የአሁን አመልካች ነው ከሚል መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችለውን ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ከሟች የተሰማውን ጩኸት ይህንን ጩኸት ሰምተው ሟች ሞቶ ወደ ተገኘበት ቤት ሄደው በሩን ቢደበድቡ ፤ ቢያንኳኩ ተከሣሹ መብራት አጥፍቶ ድምፅ እንዳልሰጠ ፤ በኋላ በሩን በቁልፍ ከኋላ በኩል እንደሚቆልፉበት ሲገልፁለት ሟች ታሞብኝ ነው ማለቱንና መብራት ያጠፋው ይጋጭብኛል በማለት እንደሆነ ሁሉ አስረድተዋል፡፡ አመልካች ይህንን ድርጊት ከመፈፀሙ በፊት ለአቀደው ተግባር ዝግጅት ይሆን ዘንድ ስሙን በመቀየር ፤ የመጣበትም ተግባር ለቅስና አገልግሎት መሆኑን የመጣበትም አድራሻ ከትክክለኛው አድራሻ የተለየ መሆኑን ሁሉ ገልፆ ሟች ሞቶ የተገኘበትን ቤት መከራየቱንና ሟች ሞቶ ከቤት ውስጥ ከመገኘቱ በፊት ይኸው አመልካች በቤት አለመገኘቱን በጊዜው ከሁለቱ በቀር ሌላ ሰው አለመኖሩን ይልቁንም መጥፋቱን በኋላም በክትትል ከትክክለኛው አድራሻ መያዙን ሁሉ ገልፀው የመሰከሩ ሲሆን፤ የሟችን አሟሟት ሁኔታ ይገልፃል በተባለው የሟች አስከሬን ምርመራ ውጤት ላይ ደግሞ በሟች አንገት ላይ የመታነቅ ምልክት የነበረ እና ከቀኝ አይኑ የመመታትና የመበለዝ ምልክት የነበረ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሟች በሞተበት ጊዜ የተገኘው መጫኛም በችሎት የቀረበው መሆኑ በሰው ማስረጃዎችም ተነግሯል፡፡

የሥር ፍ/ቤትም ከዚህ በላይ በዐ/ሕግ በኩል ክሱን ለማስረዳት የቀረበውን ማስረጃ ከክሱ ጋር በማገናዘብ መርምሮ ተከሣሹ የአሁን አመልካች የወንጀሉን ድርጊት የፈፀመ ለመሆኑ ሊያረጋግጥ የሚችል አጥጋቢ ማስረጃ መሆኑን ጠቅሶ ይከላከል ሲል በይኗል፡፡ ይህም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ቀርቦ የተሰማ የታየ እና የተመረመረ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበን ክስ ለማስረዳት ባለው የማስረጃነት ክብደት በመመርመር ረገድ ባለው ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማረጋገጥና የተረጋገጠውን ጉዳይ በማስረጃነት በመመዘኑ ሥልጣን በመገልገል የሰጠው ዳኝነት በመሆኑ የአሁን አመልካች በማስረጃ አልተረጋገጠብኝም የሚለው ክርክሩ የማስረጃ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 እንደተደነገገው ከላይ የሠፈረው የዐ/ሕግ ማስረጃ የቀረበውን የወንጀል ጉዳይ ለማስረዳት በወንጀል ጉዳይ መቅረብ ከሚገባው የማስረጃ የማስረዳት ሁኔታ /standard of proof/ አንፃር ይታይ ቢባልም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 የተመለከተውን ድንጋጌ በመፈፀም ረገድ የሥር ፍ/ቤት የህግ ስህተት መፈፀሙን የሚያመለክት ሆኖ አልተገኘም፡፡

የአሁን አመልካችም እከላከላለሁ በማለት የሰው ማስረጃዎችን አቅርቦ ቢያሰማም እነዚህ የሰው ማስረጃዎች ከፊሎቹ ስለጉዳዩ ምንም የሚያውቁት ጉዳይ አለመኖሩን ቀሪዎቹ ደግሞ በዐ/ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ጉዳይ ለማስተባበል የማይችል መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ማስረጃውን መዝኖ ውድቅ ያደረገው በመሆኑ ከላይ እንደተመለከተው ይህ ማስረጃውን የመመዘን የዳኝነት ሥራ እንጂ የህግ ጥያቄን የሚያስነሳ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል በወ/መ/ሕ/ቁ 539/1/ ሥር የተመለከቱ ንዑሳን የህግ ክፍሎች እያሉ በየትኛው ንዑስ ክፍል የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈ ድርጊቱን የፈፀምኩ ለመሆኑ በግልፅ ተጠቅሶ ባለመከላከሌ የተነሣ ክሱን በመከላከል ረገድ መብቱን አጣቧል በማለት ይከራከር እንጂ በቀረበበት የወንጀል ክስ ዝርዝር ላይ የተገለፁት ፍሬ ጉዳዮች በሙሉ የአመልካች አድራጎት ሰውን ለመግደል አስቦ አመቺ ጊዜና ቦታ መርጦ ሟችን የገደለው

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑና አገዳደሉም ቢሆን ጭካኔንና ነውረኛነትን የተላበሰ መሆኑ ሁሉ የተገለፀ በመሆኑ አድራጐቱ በወ/ሕ/ቁ 539/1/ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ በሚል እንደሆነ እጅግ ግልፅ የሆነ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111 እና 112 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች አፈፃፀም ያልጣሰ በመሆኑ በዚህ በኩል ያቀረበውም የክርክር ነጥብ የህግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የአሁን አመልካች በወ/ሕ/ቁ 539/1/ሀ/ የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፎ ሟችን በመግደሉ በግፍ ሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ነው በሚል የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ በአግባቡ ከመሆኑ በቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል በዚህ አጥፊ ላይ ተገቢውን ቅጣት ለመጣል የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ተቀብሎ በመረመረበት ጊዜ በአሁን አመልካች በኩል አንድ የቅጣት ማቅለያ መቅረቡን አረጋግጦ ተቀብሏል፡፡ ሆኖም የዚህ አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን ሊያስቀንስ የሚችል ስለመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 16/7/ ስር በግልፅ ተመልክቶ እያለ ሁለት እርከን ብቻ መቀነሱ ይህንኑ የቅጣት መመሪያ ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ዐ/ሕግም ይህንኑ ተገንዝቦ በዚህ ረገድ ቅጣቱ ተስተካክሎ ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌለው ገልፆ መልሱን በፅሑፍ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም በቅጣት አጣጣል ረገድ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ የተገለፁትን ሁሉ በማየት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በቤንች ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10698 ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 50062 መጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 50278 ሰኔ 12 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ሁሉ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች ላይ በሥር በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. የአሁን አመልካች ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 539/1/ሀ/ ሥር የተቀመጠውን የቅጣት ዓይነት መነሻ በማድረግ ፣ እና ዝቅተኛውን የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት በመያዝ በቅጣቱ መመሪያ አንቀጽ 13/8/ ላይ የተመለከተውን እርከን 38 የወደቀ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት መወሰኑን ተቀብለን ከዚሁ እርከን ላይ በፍርድ ሐተታው ላይ እንደተገለፀው ሶስት እርከን በአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሲቀነስ 35 እርከን ላይ የሚወድቅ በመሆኑ በዚሁ እርከን ላይ የተቀመጠውን የቅጣት አንጓ በማየት አመልካች ከህዳር 19 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በሚታሰብ በአስራ ዘጠኝ ዓመት (በ19 ዓመት) ፅኑ እስራት ይቀጣ በማለት አሻሽለን ወስነናል፡፡
4. በዚህ ተሻሽሎ በተወሰነው የቅጣት ውሣኔ መሠረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለሚዛን ማረምና ማነፅ ተቋም ትዕዛዝ ይድረሰው ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ዲ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባንክና ኢንሹራንስ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 76977

ህዳር 7 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ኒያላ ኢንሹራንስ (አ.ማ) ነገረ ፈጅ አቶ ዮሴፍ ገብሬ ቀረቡ

ተጠሪዎች- 1. አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) ነገረ ፈጅ አቶ አወል ማስረሻ

2. አቶ እንድሪስ አደም በሌሉበት ተወስኗል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ ጉዳዩ በንብረት ላይ በደረሰ ጉዳት የኢንሹራንስ ሰጭው ያለበትን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አንደኛ ተጠሪ በሁለተኛው ተጠሪ ላይ ያቀረበው የዳረጐት ክስ ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ቁጥሩ 3-16776 ኢት የሆነው የሁለተኛ ተጠሪ መኪና የመድን ሽፋን የሰጠሁትን የሰሌዳ ቁጥር 3-35774 /ኢት/ የሆነ መኪና ግንቦት 9 ቀን 2000 ዓ.ም በመግጨት ጉዳት አድርሶበታል፡፡ መኪናውን ለማስጠገን ብር 30,556.52 /ሰላሳ ሺህ አምስት መቶ ሀምሣ ስድስት ብር ከሀምሳ ሁለት ሳንቲም/ አውጥቻለሁ፡፡ ስለዚህ ይህንን ገንዘብ ይተኩልኝ በማለት በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርቧል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች ጉዳት ያደረሰው መኪና በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት የመድን ሽፋን ሰጥቷል፡፡ በክርክሩም የሶስተኛ ወገን ተከራካሪ ሆኖ ይጠራልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በክርክሩ ሶስተኛ ወገን ተከራካሪ እንዲሆን ተጠርቶ ገብቶ ለጉዳቱ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑንና ኃላፊነት አለብህ ከተባልኩም የምከፍለው ካሳ መጠን ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ያነሰ ነው የሚል መከራከሪያ አቅርቧል ፡፡

የስር ፍርድ ቤት ጉዳት ያደረሰውን የሰሌዳ ቁጥር 3-16776 (ኢት) የሆነው ተሽከርካሪ ይሽከረክር በነበረው በሁለተኛው ተጠሪ ሹፌር ጥፋት ነው በማለት አመልካች ክስ ያቀረበቡትን ገንዘብ ለአንደኛ ተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የካቲት 13 ቀን 2004 ዓ.ም በተጻፈው የሰበር አቤቱታ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው የሰሌዳ ቁጥር ኢት 3-16776 ለሆነው መኪናና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-07520 ኢት ለሆነው ተሳቢ ነው፡፡ የአንደኛ ተጠሪ መኪና የተገኘው ተሸካርካሪውን የሚያንቀሳቅሰው ሞተር በተገጠመለት የሰሌዳ ቁጥር 3-16776/ኢት/ ሳይሆን ከዚህ መኪና ጋር ተገጥሞ ሲጎተት በነበረውና አመልካች የመድን ሽፋን ባልሰጠው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-06469 (ኢት) በሆነው ተሳቢ ተገጭቶ ነው፡፡ ስለዚህ የቀረበውን ክርክርና የፅሑፍ ማስረጃ በአግባቡ ሳይመረምር አመልካችን በኃላፊነት ይጠይቃል በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ሰኔ 10 ቀን 2004 ዓ.ም አመልካች የሰሌዳ ቁጥሩ 3-16776 ኢት ለሆነው መኪና ከነተሳቢው የመድን ሽፋን እንደሰጠ አምኗል፡፡ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-06469 የሆነው ተሳቢ መኪና ነው፡፡ ይህ ተሳቢ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው መኪና እየተጎተተ ሲሄድ ጉዳት ማድረሱ ካልተለየ የመኪና ላይ የተጫነ እቃ ወይም የሚጎተት አካል የደረሰው ጉዳት ባለመኪናውና ለመኪናው የመድን ሽፋን የሰጠው ሰው በኃላፊነት መጠየቃቸው ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመድን ሽፋን በሰጠሁት የሰሌዳ ቁጥር 3-16776 (ኢት) እና ጉዳት በደረሰበት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-35774 (ኢት) መካከል ምንም አይነት አካላዊ ንኪኪ የለም፡፡ ስለዚህ የመድን ሽፋን ባልሰጠሁት አካል ጋር ተገምቶ ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት የምንጠየቅበት ምክንያት የለም በማለት ሐምሌ 5 ቀን 2004 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተሳቢ የሰሌዳ ቁጥር 3-06469(ኢት) በአንደኛ ተጠሪ ደንበኛ ላይ ያደረሰውን ጉዳት የመሸፈን ኃላፊነት አለበት በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክርና ባቀረቡት ማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ጉዳዮች መመልከት ተገቢ ነው፡፡ አመልካች የተጠሪ ንብረት ለሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-16776 (ኢት) ለሆነ የጭነት መኪናና በዚሁ መኪና ለሚጎተተው የተሳቢ ቁጥሩ 3-07520 (ኢት) ለሆነው ተጎታች ሀምሌ 2 ቀን 2000 ዓ.ም በተፈረመ የመድን ውል በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአንደኛ ተጠሪ ደንበኛ መኪና በሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-35774 (ኢት) የሆነው መኪና የተጎዳው የሰሌዳ ቁጥር 3-16776 (ኢት) ከሆነው መኪና ጋር ተገጥሞ ሲጎተት በነበረው የተሳቢ ቁጥሩ 3-06469 /ኢት/ በሆነው ተጎታች የኋላ ክፍል ተገጭቶ መሆኑን በትራፊክ ፕላን መግለጫና በትራፊክ ፖሊስ በተሰጠው የምስክርነት ቃል የተረጋገጠ መሆኑን የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን መዝገብ ቁጥር 169698 በማስቀረብ ተረድተናል፡፡ ይህም አመልካች የመድን ሽፋን የተሰጠውን የተሳቢ ቁጥር 3-07520 /ኢት/ የሆነው ተጎታች ሣይሆን የመድን ሽፋን ያልተሰጠውን የተሳቢ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-06469 /ኢት/ የሆነው ተጎታች በማንቀሣቀስ ላይ እያለ፣ የተሳቢው የኋላ ክፍል የአንደኛ ተጠሪ መኪናን በመግጨት ጉዳት ያደረሰበት መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ከላይ የገለፅናቸው ፍሬ ጉዳዮች የሰሌዳ ቁጥር 3-16776 /ኢት/ በሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲጎተት በነበረው የተሳቢ ቁጥሩ 3-66469 ኢት የሆነው ተጎታች ለደረሰው ጉዳት፣ የባለሞተሩ መኪና ባለሀብት የሆነው ሁለተኛ ተጠሪ በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን ከፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 2081/1/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አደጋው የደረሰው በሁለተኛው ሠራተኛ /ሹፌር/ ጥፋት መሆኑ ስለተረጋገጠ ሁለተኛ ተጠሪ በፍታሐብሔር ሕግ ቁጥር 2130 ድንጋጌ መሠረት ጉዳቱን የመሸፈን ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 3-16776/ኢት/ የሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ሲንቀሣቀስ ለሚያደርሰው ጉዳትና፣ ይህ መኪና ተጎታች በሚጎትትበት ጊዜ የተሳቢ ቁጥሩ 3-07520 /ኢት/ የሆነውን ተጎታች ብቻ ሲያንቀሣቅስ በተጎታቹ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊ ለመሆን የመድን ውል ተዋውሏል፡፡ አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 3-16776 /ኢት/ የሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ማናቸውንም አይነት ተጎታች ሲያንቀሣቅስ፣ በተጎታቹ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ለመውሰድ አልተስማማም፡፡ ኢንሹራንስ ሰጭው በውሉ ለተመለከተው አደጋ ብቻ መድን ለገባው ሰው መድን እንደሚሆን በንግድ ሕግ ቁጥር 663 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም ኢንሹራንስ ሰጭው በውሉ ውስጥ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ ወይም በውሉ የተስማሙበት ቀን በደረሰ ጊዜ የተስማሙበትን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ እንዳለበትና ይህ ግዴታው በውለታው ከተጠቀሰው ሊበልጥ እንደማይችል "የኢንሹራንስ ሰጭው ግዴታ" በሚል ርዕስ ባለው በንግድ ሕግ ቁጥር 665 ተደንግጓል፡፡ አመልካች የሰሌዳ ቁጥሩ 3-16776 /ኢ.ት/ የሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ መኪና የተሳቢ ቁጥሩ 3-07520/ኢት/ የሆነውን ተጎታች ሲጎትት፣ በተጎታቹ ለሚደርሰው ጉዳት የመድን ሽፋን የሰጠ ሲሆን፣ ከዚህ የመድን ሽፋን ከሰጠው ተጎታች ውጭ ሌላ ተሳቢ ሲጎትት፣ በተጎታች የሚደርስ ማናቸውንም ጉዳት ለመሸፈን የመድን ውል አልተዋዋለም፡፡ ይህ ከሆነ የአንደኛ ተጠሪ ደንበኛ መኪና ጉዳት የደረሰበት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-16776/ኢት/ በሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ ተገጭቶ ሣይሆን፣ በዚህ ባለሞተር መኪና ሲጎተት የነበረውና አመልካች የመድን ሽፋን ያልሰጠው የሰሌዳ ቁጥር 3-06469 /ኢት/ በሆነው ተሳቢ የጎላ ክፍል ተገጭቶ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም አመልካች ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር ሐምሌ 2 ቀን 2000 ዓ.ም ከገባው የመድን ውል ውጭ፣ የሁለተኛው ተጠሪ መኪና የመድን ሽፋን የሌለውን ቁጥሩ 3-06469/ኢት/ የሆነውን ተሳቢ እየጎተተ ሲያንቀሳቅስ በተሳቢው ግጭት ላደረሰው ጉዳት አመልካች በኃላፊነት ይጠይቃል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የንግድ ህጉን አንቀጽ 663 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 665 ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

2. በአንደኛው ተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች በኃላፊነት አይጠየቅም በማለት በንግድ ሕግ አንቀጽ 633/1/ እና አንቀጽ 665/1/ መሠረት ወስነናል፡፡

3. በአንደኛው ተጠሪ መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት ያለበት ሁለተኛው ተጠሪ ነው በማለት ወስነናል፡፡

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. ሁለተኛው ተጠሪ አንደኛ ተጠሪ የደንበኛውን መኪና ለማስጠገን ያወጣውን ብር 30,556.62 /ሰላሣ ሺህ አምስት መቶ ሀምሳ ስድስት ብር ከስልሳ ሁለት ሣንቲም/ ከኅዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለዳኝነት፣ ለጠበቃ አበልና ኪሣራ የወሰነውን ብር 3,102 /ሦስት ሺህ አንድ መቶ ሁለት ብር/ ከጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለአንደኛው ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈ፻ፀም

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79860

ህዳር 06 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

አዳነ ንጉሴ

መኮንን ገ/ሕይወት

ተክሊት ይምሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ ራሔብ መለሰ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ ለመንግስት እንዲወረስ ከተወሰነው ከአንድ አጥፊ ንብረት ውስጥ ለቤተሰብ ህይወትና መተዳደደሪያ ሊውል የሚገባው ድርሻ ሊሸፍናቸው የሚገባቸውን የወጪ አይነቶችንና መጠናቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ቁጥር 81406 በሆነውና ታህሳስ 13 ቀን 2002 ዓ.ም. በተሰጠው የወንጀል ጉዳይ የፍርድ ባለመብት በመሆኑ በወንጀል ጉዳዩ 3ኛ ተከሳሽ የነበሩትና አጥፊነታቸው ተረጋግጦ ንብረታቸው ለመንግስት ውርስ እንዲሆን የተወሰነባቸው የፍርድ ባለእዳ የሆኑት አቶ ጌቱ ወርቁ ንብረቶችን አይነታቸውን ዘርዝሮ ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ የአስከፈተው የአፈጻጸም ማመልከቻ ነው፡፡የአፈፃፀም መዝገብ የተቀበረለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለእዳው ጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጡበት ያደረገ ሲሆን የአሁኗ አመልካች በአፈጻጸም መዝገቡ ላይ ሰኔ 09 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ የመቃወሚያ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በዋናው የወንጀል ጉዳይ ላይ አቶ ጌቱ ወርቁ በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ መሆናቸው በመረጋገጡ ምክንያት ሀብታቸው /ንብረታቸው/ በመንግስት እንዲወረስ ፍርድ ማረፉን፣በፍርዱ ላይ የልጆቹና የሶስተኛ ወገኖች መብት የተጠበቀ መሆኑንና እነዚህ መብቶች ከታዩና ከተመረመሩ በኋላ የአቶ ጌቱ ወርቁ ግማሽ ድርሻ ላይ የሚቀነሰው ከተቀነሰ በኋላ ተራፊ የሆነው ድርሻው ለመንግስት ውርስ እንዲሆን ፍርድ ቤቱ መወሰኑን ዘርዝሮ የአሁኗ አመልካች ሚስት በመሆናቸው ግማሽ ድርሻቸው እንዲጠበቅላቸው የፍርድ አፈጻጸሙን የያዘው ችሎት የወሰነ ሲሆን የልጆቹን መብት በተመለከተም በዋናው የወንጀል ጉዳይ ለተቀረው የቤተሰብ ሕይወትና መተዳደሪያ ወይም አስፈላጊ ለሆኑት የእለት ምግብና ለኑሮአቸው መደገፊያ የሆኑ ልዩ ልዩ ገቢዎች ሊወረሱ እንደማይችሉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 98(1(ለ)) መደንገጉንና ይህም በፍርድ አፈጻጸም ሂደትም የፍርድ ባለእዳ ልጆች መብት የተጠበቀ መሆኑንና የፍርድ ባለእዳው የእድሜ ልክ ፍርደኛ ቢሆንም በልጆች አስተዳደግ ላይ በሕጉ የተጣለባቸውን ግዴታ ሊወጡ እንደሚገባ እንደሚያስገነዝብ ፍርድ ቤቱ መረዳቱን ጠቅሶ ለህምክና፣ ለትምህርት፣ ለትራንስፖርት የስድስት ወር ወጪአቸው

www.chilot.me

ሊወረስ እንደማይገባ እንዲሁም ለመጠለያ፣ ለልብስና ለምግብ የሚያስፈልጋቸው ወጪ ለልጆቹ ሕይወትና መተዳደሪያቸው ወይም አስፈላጊ የሆኑ የእለት ምግብ ፣ለኑሮአቸው መደገፊያ አስፈላጊ በመሆናቸው ልጆቹ ራሳቸውን እስከሚችሉ ማለትም አስራ ስምንት አመት እስከሚሞላቸው ድረስ ወጪዎቹ ሊወረሱ እንደማይገባ፣ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ ተብሎ የቀረበው ግን በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይት እንደሌለው ገልጾና ለህክምና የስድስት ወር ወጪያቸው በወር ብር 1500.00 ሲታሰብ ለእያንዳንዳቸው ብር 900.00፣ የትምህርት ክፍያ የስድስት ወር ወጪ ለእያንዳንዱ ልጅ ብር 6243.00፣የትራንስፖርት ወጪ ብር 1000.00 ሊሆን እንደሚገባና በአንድ ልጅ ለ6 ወር ብር 3000.00 ሊሆን እንደሚገባ፣ለልብስና ለቀለብ የቀረበው ወጪም በወር ለአንድ ልጅ ብር 1500.00 ሊሆን እንደሚገባና ስሌቱም ልጆቹ አስራ ስምንት አመት እስከሚሞላቸው ሊታሰብ እንደሚገባ ገልጾ ለምስጋና ጌቱ ለልብስና ለቀለብ ብር 190,500.00፣ለአማንድ ጌቱ ደግሞ ብር 217,500.00 በጠቅላላ የሁለቱ ልጆቹ ወጪ ብር 428,286.00 እንደሚሆን እና የፍርድ ባለእዳ የሆኑት አቶ ጌቱ ወርቁ ከወጪው ግማሹን የመሸፈን ግዴታ እንደአለባቸው ደምድሞ ብር 214,143.00(ሁለት መቶ አስራ አራት ሺህ አንድ መቶ አርባ ሶስት ብር) ለመንግስት ውርስ ከሚሆነው ከፍርድ ባለእዳው ንብረት ላይ እንዲቀነስ ሲል ወስኗል። በዚህ የውሳኔ ክፍል የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያርቡም ተቀባይነት አላገኙም። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱቱ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች ያቀረቡት የቅድሚያ ግዥ መብት መታለፉ ያላግባብ ነው፣የልጆች የትምህርት፣ የሕክምናና የትንስፖርት ወጪ የስድስት ወር ብቻ ታስቦ ሌላው ተቀባይነት ማጣቱ ከልጆቹ መብትና ጥቅም አንፃር ያልታየ ነው በማለት ዘርዝረው ውሳኔው እንዲታረም ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች የቅድሚያ መብት የመታለፉና የልጆቹ የህክምና፣ የትምህርትና የትራንስፖርት ወጪ ለስድስት ወር ብቻ እንዲታሰብ የመደረጉን አግባብነት ከወ/መ/ሕ/አንቀፅ 98(1(ለ)) ድንጋጌ አኳያ ለመመርመር ተብሎ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፍርድ ባለእዳው ንብረት እንዲወርስ በወንጀል ችሎት ውሳኔ ያረፈበት መሆኑና የሶስተኛ ወገኖችና የልጆች መብት ግን የተጠበቀ መሆኑ በዋናው ፍርድ ጭምር የሰፈረ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን፣አመልካች የፍርድ ባለእዳ ባለቤት ሲሆኑ እንዲወረስ በተወሰነው ንብረት ላይ ግማሽ ድርሻ ያላቸው መሆኑና በፍርድ አፈፃፀም ጊዜ አቤቱታ ሊያቀርቡ የቻሉት መብታቸው እንዲጠበቅላቸውና የልጆቹ የቀለብ፣የልብስ፣ የትምህርት ፣የህክምና እና ትራንስፖርት ወጪ ለመንግስት ውርስ ከሚሆነው የፍርድ ባለእዳው ግማሽ ድርሻ ላይ እንዲቀነስላቸው መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ግማሽ ድርሻ የጠበቀላቸው ቢሆንም ስለቅድሚያ ግዥ ጥያቄ ግን በትዕዛዙ ላይ ያሰፈረው ነገረ የሌለ ሁኖ የልጆችን የትምህርት፣ የህክምና እና የትራንስፖርት ወጪ ግን ለስድስት ወር ብቻ እንዲታሰብላቸው፣ ቀለብና ልብስ ግን እድሜአቸው አካለ መጠን እስከሚደርሱ ድረስ በወር ብር 1500.00 እንዲታሰብላቸው ስሌት ይዞ የወሰነ መሆኑን ነው። እኛም ጉዳዩን በሚመለከተው መልኩ ተመልክተናል።

<u>አመልካች ያቀረቡን የቅድሚያ መብት ጥያቄ በተመለከተ፡-</u> አመልካች ለጥያቄአቸው መሰረት ያደረጉት ከፍርድ ባለእዳ ጋር ያላቸውን የጋራ ባለሃብትነት መብት ነው፡፡ ይህ መብት መሰረቱ ጋብቻ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የክርክሩ ምንጭ የወንጀል ጉዳይ በመሆኑ ይህንኑ የሚገዛው ቀጥተኛ ሕግ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 98(ለ(መ)) ሁኖ የሶስተኛ ወገኖች መብት የሚጠበቅበትን አግባብ ከሚደነግግ በስተቀር እነዚህ ወገኖች በንብረቱ ላይ የቅድሚያ ግዥ መብት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በግልጽ አይደነገግም፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ የአመልካች የቅድሚያ መብት ጥያቄ ቢጠበቅላቸው ተቃውሞ የሌለው መሆኑን በስር ፍርድ ቤት አስተያየት የሰጠ ከመሆኑም በላይ በዚህ የሰበር ደረጃም በጉዳዩ ላይ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን የመልሱ ይዘት ያሳያል፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች የቅድሚያ ግዥ መብት የማይጠበቅበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ጥያቄ በዝምታ ማለፋቸው ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡

<u>የልጆችን የትምህርት፣የህክምና እና የትራንስፖርት ወጪን በተመለከተ</u> ፡-በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካች የቀረበውን መጠን የተጋነነ መሆኑን አስልተው ተገቢ ነው ያሉትን መጠን ለይተው ወስነዋል፡፡ የወንጀለኛውን ንብረት መወረስን በተመለከተ የሚደነግገው የወንጀል ህግ አንቀፅ 98(3(ለ)) ስር ቢያንስ ለስድስት ወር ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ልዩ ሁኔታዎችን አይቶ ይገባል ብሎ በሚገምተው ምክንያት ለተገለጸና በቂ አስተያየት ሊሰጠው ተገቢ በሆነ ውሳኔ ከዚህ ለሚበልጥ ጊዜ ለተቀጪው ቤተሰብ ሕይወትና ለመተዳደሪያቸው ወይም አስፈላጊ የሆኑት የእለት ምግብና ለኑሮአቸው መደጐሚያ የሆኑ ልዩ ልዩ ገቢዎች ሊሆኑ እንዳይወረሱ ለማድረግ እንደሚገባ ሕጉ ያሳያል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አቀራረፅ፣ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የተቀጪው ቤተሰብ ሕይወትና መተዳደሪያ ወይም አስፈላጊ የሆኑት የእለት ምግብና ለኑሮአቸው መደገፊያ የሆኑ ለልዩ ልዩ ገቢዎች የሚሆኑትን የወንጀለኛውን ንብረቶች ለመንግስት ውርስ እንዳይሆኑ ለማድረግ የሚቻለው ቢያንስ የስድስት ወራት ጊዜአትን መነሻ አድርጎ መሆኑን፣ከዚህ ወራት በላይ ደግሞ እንደነገሩ ሁኔታ መወሰን የሚችልበት አግባብ መኖሩን ነው፡፡ በመሆኑን ፍርድ ቤቱ ከስድስት ወራት ላላነሰ ጊዜ እንዲወስን ሕጉ ግዴታ ከሚጥልበት በስተቀር ከዚህ በላይ ለሆነው ጊዜ ወይም ለማንኛውም ጉዳይ የተቀጪው ንብረት ከውርስ ቀሪ እንዲሆን ለማድረግ የማይቻል መሆኑን ሕጉ ያሳያል፡፡ የሕጉ መሰረታዊ ዓላማም ጥፋት ያልሰሩ የተቀጪው ቤተሰቦች ያላግባብ እንዳይጎዱ መጠበቅና ወንጀለኛው በተገቢው መንገድ እንዲታረም እና ቅጣቱ ሌላውን እንዲያስተምር በማድረግ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 87 እና 1 ስር የተመለከተውን ለማሳካት ነው ተብሎ ይታሳባል፡፡ በመሆኑም የወ/ሕ/አንቀጽ 98(3((ለ)) ድንጋጌ በፍርድ ቤቱ ላይ የሚጥለው ግዴታ አነስተኛ የጊዜ ገደብ ስድስት ወር ከመሆኑ ውጪ ለተቀጪው ቤተሰብ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ለረዥም ጊዜአት እንዲሆኑ እንዲታሰቡ አይደለም፡፡

ለስድስት ወር የተያዘው ወጪ መጠን ያነሰ ነው የሚለው የአመልካች የቅሬታ ነጥብ ሲታይ በማስረጃ የሚነጥርና ይህንኑ ለማድረግ በሕግ ስልጣን የተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች የሚያከናውኑትና በፍቅድ ስልጣናቸው (Discretionary power) ስር የሚወድቅ እንጂ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት በተሰጠው የመሰረታዊ ህግ ስህተት የማረም ስልጣን ስር የሚወድቅና የመሰረታዊ ህግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ሁኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች ቅሬታቸቸውን ከሕጻናቱ የትህምርት እና የህክምና ሕገ መንግስታዊ መብት ጋር አያያዝው ያቀረቡት ቅሬታ ሲታይም ህጻናቱ ከአባታቸው ድርሻ የስድስት ወር ወጪ እንዲያገኙ በመደረጉ ምክንያት ብቻ ይኼው የትምህርትና የህክምና መብታቸው አደጋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ የሚድቅበት አጋጣሚ ወደፊት የሚከሰት መሆኑን የሚጠቁሙ መነሻ የክርክር ነጥቦችን በማስረጃ ያመላከቱበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የክርክሩ ሂደት በግልፅ የሚያሳየው ጉዳይ ሁኖ ስለአገኘን የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም ብለናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የትምርት፣የህክምና እና የትራንስፖርት ወጪ ለህጻናቱ ለስድስት ወር ብቻ እንዲታሰብ ማለፋቸውን ገልፀው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 98(3(ለ)) ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠውን ስልጣን አድማስ ያላገናዘበ ሁኖ ስለአገኘን ቅሬታውን የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 175740 ሐምሌ 20 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 115859 መጋቢት 21 ቀን 2004 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የግማሽ ድርሻ በሆኑባቸው ንብረቶች የቅድሚያ ግዥ መብት ቢያገኙ ተጠሪ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን የገለጸ በመሆኑ ይኼው መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ብለናል፡፡
3. የልጆችን የትምህርት፣የሕክምና እና የትራንስፖርት ወጪን በተመለከተ የበታች ፍርድ ቤቶች ለስድስት ወር ብቻ እንዲሆን ማሰባቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀፅ 98(3(ለ)) ድንጋጌ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.81616

ጥር 15 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች፡- ወጋገን ባንክ አ.ማ ነ/ፈጅ ሰላማዊት አዳነ ቀርቧል

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ሰላማዊት ጥላሁን } ቀርበዋል፡፡

2. አቶ ነጋሲ በርሔ }

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀም ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በት/ብ/ክ/መንግስት የአክሱም ዞን ማእከላዊ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ በዚያ ፍ/ቤት አመልካች የፍርድ አፈፃፀም ክሣሽ በመሆን ተጠሪዎች ላይ በፍ/ቤት ላስፈረደው ውሣኔ አፈፃፀም እንዲውልለት በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ በተሽከርካሪ ሰ.ቁ. 3-27506 አ.አ የሆነ ተሽከርካሪ ተይዞ በሀራጅ ተሸጦ እዳው እንዲከፈለው ፍ/ቤቱን ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ተጠቃሹ ተሽከርካሪ በሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት በኩል እንዲታገድ ትእዛዝ ሲያስተላለፍ ተሽከርካሪዋ ቀደም ብላ በፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት በሌላ ምክንያት የታገደች መሆኑ በጽሑፍ ተገልፆለታል፡፡ ከዚህ በኃላ ተሽከርካሪዋ ቀደም ብላ በሌላ ፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ የተሰጠባት የአፈፃፀም ክሣሽ (የአሁኑ አመልካች) ጭምር በጉዳዩ ተከራካሪ ወገን በሆነበት መዝገብ ላይ መሆኑን ፍ/ቤቱ ተገንዝቤያለሁ በማለት ይህ ቀደም ብሎ የተሰጠው እግድ ሣይነሣ ተሽከርካሪዋን ሽጦ ለፍርድ አፈፃፀሙ ማዋል ስለማይችል የአፈፃፀሙ ክሣሽ ሌላ የንብረት ዝርዝር እስከሚያቀርብ ድረስ ለጊዜው መዝገቡን በመዝጋት ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በዚህ ትእዛዝ ባለመስማማት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢቀያርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንን ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘትም ባጭሩ ተሽከርካሪዋ ላይ የቅድሚያ መብት አለኝ የሚል ወገን ሣይኖር ፍ/ቤቱ በራሱ በሌላ ፍ/ቤት የተሰጠው እግድ ሣይነሣ እንዲሸጥ ማዘዝ አይቻልም በማለት የሰጠው ትእዛዝ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ በተሽከርካሪዋ ላይ ከአመልካች የቀደመ መብት ያለው 3ኛ ወገን ስለመኖሩ አልተረጋገጠም እንጂ ቢኖርም ይህ መኪናዋ እንዳትሸጥ የሚከለክል አለመሆኑን መኪናዋንም በዋስትና ይዘን በዚህ ምክንያት ከማንም በፊት ያሣገደው አመልካች ሆኖ እያለ በሌላ

www.chilot.me

ፍ/ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሣይነሣ በመኪናዋ ላይ ውሣኔውን ማስፈፀም አይቻልም መባሉ ከሕግና ሥነ ሥርዓት ውጪ በመሆኑ ትእዛዙ ተሽሮ አፈፃፀሙ በመኪናው ላይ እንዲቀጥል እንዲታዘዝላቸውና ወጭና ኪሣራ እንዲከፈላቸው ጭምር ጠይቋል፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይዘቱም አመልካች መኪናዋን በዋስትና በመያዝ ለተጠሪ አበድሮ የነበረው ገንዘብ መኪናዋን የገዛት አቶ ደረጀ ወንድሙ የሚባል ከፍሎ ካጠናቀቀ በኃላ አመልካች የመኪናዋን ሊብሬ ሊያስረክበው ፊቃደኛ ባለመሆኑ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት መ.ቁ. 179925 በሆነው ላይ አመልካች መኪናዋን በዋስትና ይዞ ያበደረው ገንዘብ የተከፈለው በመሆኑ የመኪውን ሊብሬ እዳውን ለከፈለውና መኪናውን ለገዛው ሰው እንዲያስረክብ ተወስኖበታል፡፡ ሊብሬውንም በፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት አፈፃፀም መ.ቁ. 195425 በሆነው ላይ አመልካች መኪናውን ለገዛው ሠው በፍርድ ቤት ትእዛዝ አስረክቧል፡፡ ይህ ውሣኔና ትእዛዝ በሕግ አግባብ ባልተሻረበት ሁኔታ አመልካች ከቅን -ልቦና ውጪ እያቀረበ ያለው ክርክር ውድቅ ተደርጎ በቂ ኪሣራ ተቆርጦላቸው እንዲሰናበቱ የሚል ነው፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከለይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለክርክሩ መነሻ የሆነችው መኪና ላይ ቀደም ብሎ በሌላ ፍ/ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሣይነሣ መኪናዋን እንድትሸጥ ማድረግ አይቻልም መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነችው መኪና ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ከሰጠው የእግድ ትእዛዝ ቀደም ብሎ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ራሱ የክርክሩ ተካፋይ በሆነበት መዝገብ ላይ የታገደች መሆኑ በአመልካች አልተካደም፡፡ ይህ ደግሞ በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ተከራክሮ ያጣውን ወይም የተከለከለውን መብት ከሕግ ስነ-ሥርዓትና ቅን -ልቦና ውጭ በሆነ አካኋን ፍርዱን በሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ለመጐናፀፍ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ መኪናዋ ለፍርዱ አፈፃፀም ተከብራና ተይዛ የምትሸጥበት የሕግ አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡ ይህ ከወዲሁ የሚታወቅ ከሆነም ፍ/ቤቱ በመኪዋ ላይ መብት አለን የሚሉ ወገኖችን ክርክር የግድ የሚጠብቅበት ሁኔታም አይኖርም፡፡

በተጨማሪም መኪናዋን ቀደም ብዬ ከማንም በፊት በዋስትና ይዣለሁ የሚለው ክርክርም ቢሆን በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣ ክርክር ከመሆኑ ባሻገር ይህም ቢሆን በዚህ መዝገብ ላይ ሊነሣ የሚገባው ክርክር ሣይሆን አመልካች ራሱ የክርክሩ ተካፋይ በነበረበት የፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገቦች ላይ ሊነሣ የሚገባው ክርክር ነው ሲጠቃለል በሥር ፍ/ቤቶች ትእዛዝ ላይ የተፈጠረ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላላገኘን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ የአክሱም ዞን ማእከላዊ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 17188 ሚያዚያ 26 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 52873 ሰኔ 19 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አእምሯዊ ንብረት

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
አዳነ ንጉሤ
መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወዳጆችና ቤተሰቦች ማህበር ጠበቃ አቶ ታዬ ወጂ ቀረቡ
ተጠሪ ፡- አቶ ኤሊያስ አሰጋኸኝ ጠበቃቸው አቶ ያለልኝ ተሾመ ቀረቡ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በፌ/ከ/ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካችም 1ኛ ተከሳሽ፣የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ ነበር፡፡ ከሳሽ የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ/ም ያቀረበው ክስ 1ኛ ተከሳሽ በቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑትን ሰዎች ለማሰብ ሐውልት ለማሰራት የሐውልት ኪነ ቅርጽ አወዳድሮ ለመምረጥ ባወጣው ጨረታ ተወዳዳሪ በመሆን ያዘጋጀሁትን ቅርጽ በ1990 ዓ/ም ያስረከብኩ ቢሆንም ተከሳሹ ቅርጹን ከተረከበ በኋላ ማሸነፍ አለማሸነፌን ሳይገልጽልኝ እያመላለሰኝ ከቆየ በኋላ የራሱ ቅርጽ እንደሆነ በማስመሰል ለመገናኛ ብዙኃን ያሰራጨ በመሆኑ፣ 2ኛ ተከሳሽም የቅርጹን ምስል የያዙትን 60,000 ቴምበሮች በማሳተም አንዱን በብር 3.00 በመሸጥ ብር 180,000 የሰበሰበ ስለሆነ ተከሳሾቹ የከሳሽን የፈጠራ መብት በመጣስ ከቅርጹ ማግኘት የሚገባኝን ብር 100,000 በማሳጣት የብር 280,000 ጉዳት ያደረሱብኝ ስለሆነ የሂሊና ጉዳት ብር 150,000 ጨምረው በድምሩ ብር 580,000 እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተከሳሾችም ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በ12/04/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በብይን ውደቅ ማድረጉን ከፍርዱ መገንዘብ የተቻለ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ 1ኛ ተከሳሽ በሰጠው መልስ፡-1ኛተከሳሽ የተቋቋመው በ1995 ዓ/ም ሲሆን ከሳሽ ቅርጹን ሰጥቻለሁ የሚለው በ1990 ዓ/ም በመሆኑ ከከሳሽ የተቀበልኩት ቅርጽ የለም፣በቴምብር የወጣው ቅርጽና ከሳሽ የኔ ነው የሚለው ቅርጽም ይለያያል፣ከከሳሽ ጋር ከውል ወይም ከውል ወጪ የመነጨ ግንኙነት ስለሌለን ክሱ ተቀባይነት የለውም፣ ከክሱ ጋር ያቀረባቸው ማስረጃዎችም አግባብነት ያላቸው አይደሉም በሚል ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተከሳሽ በበኩሉ በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው መልስ፡- ወጣ ስለተባለው ጨረታ የማውቀው ነገር የለም፣1ኛ ተከሳሽ ቴምብሮች እንዲታተሙለት በሚል ሶስት ምስሎችን በመላኩና ትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴርም እንዲታተሙ ትዕዛዝ በመስጠቱ ታትመዋል፣በታተሙት ቴምብሮች ላይ ያለው ምስልና የከሳሽ ሥራ የሚለያዩ ናቸው፣የካሳው መጠንም የተጋነነ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሰጠው ፍርድ፡- የአዲስ አበባ የደርግ አፈናና ጭፍጨፋ ተፋራጆች ሰብአዊ መብት ማህበር የተባለው በቀይ ሽብር ለሞቱት ሰዎች የመታሰቢያ ሐውልት ለማሰራት የወድድር ማስታወቂያ ማውጣቱን፣ከሳሽም

www.chilot.me

በዚሁ ማስታወቂያ መሰረት የሐውልት ቅርጽ ሰርቶ ለማህበሩ ማስረከቡን ፣በማስታወቂያው ከ1ኛ-3ኛ የወጡት አሸናፊዎች የገንዘብ ሽልማት እንደሚሰጣቸውና ከሽልማቱ በኋላ ማህበሩ የቅርጹ ባለቤት እንደሚሆን መገለጹን ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎች በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ፤እንዲሁም ቅርጹን ከከሳሽ የተረከበው የአዲስ አበባ የደርግ አፈናና ጭፍጨፋ ተፋራጆች ሰብአዊ መብት የተባለው ማህበር ቢሆንም በኋላ ግን ቅርጹ የሰማዕታት ሐውልት ግንባታ ማህበር እጅ መቆየቱንና ከሳሽም ቅርጹን በተመለከተ ሲደራደር የነበረው ከዚሁ ማህበር ጋር መሆኑን በ07/11/2000 ዓ.ም. ከተጻፈ ማስረጃ መረጋገጡን፣ተከሳሾችም የከሳሽ ሥራ አዲስ (0riginal) አለመሆኑን በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር አለመኖሩንና የተከሳሾች ምስክሮች የከሳሽ ሥራ ባለ ሶስት አውታር መጠን (dimension) መሆኑንና በቴምብሮቹ የታተመው ባለሁለት አውታር ነው ቢሉም 1ኛ ተከሳሽም የከሳሽን ቅርጽ ጨምሮ ሶስት ዲዛይኖችን ለ2ኛ ተከሳሽ እንዲታተሙ በሚል ስለመላኩ መረጋገጡን በፍርዱ ላይ በማስፈር 1ኛተከሳሽም ቅርጹ የከሳሽ መሆኑን እያወቀ የከሳሽ ሥራ የሆነውን ባለ ሶስት አውታር ወደ ባለ ሁለት አውታር በመቀየር ለ2ኛ ተከሳሽ አሳልፎ በመስጠቱና 2ኛ ተከሳሽም ቅርጹን በቴምብሮቹ ላይ በማተሙ 1ኛ ተከሳሽ ለተፈጸመው የቅጂ መብት ጥሰት ሀላፊነት አለበት፡፡ 2ኛ ተከሳሽ ግን በራሱ መርጦ የከሳሽ ሥራ የሆነውን ቅርጽ ያላተመና የቅርጽ ምስሉ ሲላክለትም 1ኛ ተከሳሽ የቅርጹ ባለቤት ስለመሆን ስላለመሆኑና የማጣራት ግዴታ ያለበት ባለመሆኑ ለክሱ ሀላፊነት የለበትም በማለት አሰናብቶታል፡፡

የካሳ መጠንን በተመለከተም ከሳሽ ከቅርጹ 100,000 ማግኘት የሚችል ስለመሆኑ በማስረጃ ያላረጋገጠ ከመሆኑም ሌላ ቅርጹ ለቀይ ሽብር ሰማዕታት በሚል የተሰራ በመሆኑ ለሌላ አካል ተሸጦ ገቢ ያስገኛል ተብሎ የሚጠበቅ አይደለም፣ እንዲሁም በጨረታዉ ላሸነፈው ተወዳዳሪ የሚከፈለው የሽልማት ገንዘብ መጠንም ብር 12,900.00 ብቻ በመሆኑ ብር 100,000.00 ማግኘት እችል ነበር ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 34(4) መሰረት የሞራል ጉዳት ካሳ መነሻ ብር 100,000.00 እንዲከፍል ወስኖበታል፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዩን አሰናብቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ እና በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካች በዋናነት ያቀረባቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- ተጠሪው ቅርጹን ለአመልካች አስረክቤአለሁ የሚለው በ1990 ዓ/ም ሆኖ ክሱን ያቀረበው ደግሞ በ16/06/2002 ዓ/ም በመሆኑ ክሱ በፍ/ህ/ቁ/1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በሚል ያቀረብኩትን የመ/ደ/መቃወሚያ ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ ያደረጉት ተገቢነት የለውም፣
- በቴምብሮቹ ላይ እንዲታተም የተደረገው ተጠሪው የፈጠራ መብት ባለቤትነት አግኝቼበታለሁ ከሚለው የቅርጽ ሥራ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለው በባለሙያ ምስክሮች ተረጋግጦ እያለ የተጠሪ ሥራ ነው በሚል ለደረሰው ጉዳት ሀላፊነት አለብህ በሚል የሞራል ካሳ እንድከፍል የተወሰነው ተቀባይነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- ክስ ያቀረብኩት የቅጂ መብት ተጥሶብኛል በሚል ከህግ የመነጨውን መብት መሰረት በማድረግ ነው እንጂ ከውል በመነጨ መብት መነሻ ባለመሆኑ አግባብነት ያለው በፍትሐብሔር ህጉ ከውል ወጪ ሀላፊነት በተመለከተው ክፍል የተደነገገው የክስ ማቅረቢያ የ2 ዓመት ይርጋ እንጂ ስለውሎች ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው በፍ/ህ/ቁ/1845 ሥር የተመለከተው የይርጋ ጊዜ አይደለም ፡፡ ክሱም የቅጂ መብቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነሐሴ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ተጥሶብኛል በሚል የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. የቀረበ በመሆኑ የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት የቀረበ ነው፡፡ በቴምብር ታትሞ የወጣው ባለ ሁለት አዉታር (dimension) ሲሆን የተጠሪ ደግሞ ባለሶስት አውታር ሥራ ነው በሚል አመልካች ያቀረበው ክርክርም ቢሆን ማንኛውም በምድር ላይ ያለ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ነገር በወረቀት ላይ ወይም በፎቶ ግራፍ ምስል ሲወጣ ከባለሶስት አውታር ወደ ባለሁለት አውታር መቀየሩ ተፈጥሮአዊ በመሆኑ ክርክሩ ተገቢነት የለውም በሚል በከፍተኛውና በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

- ተጠሪው ያቀረበው ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው? ወይስ አይደለም?
- ክሱ በይርጋ አይታገድም ቢባል አመልካች ለክሱ ሀላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦች ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አንደኛውን ጭብጥ በተመለከተ ፡- የአመልካች ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ስለውሎች በጠቅላላው ክፍል በፍ/ህ/ቁ/1845 ስር የተደነገገው የ10 ዓመት ይርጋ ሲሆን ተጠሪው ቅርጹን ካቀረበበት ከ1990 ዓ/ም ጀምሮ ሲቆጠርም መብቱን ሊጠይቅ የሚችልበት የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ አልፏል በሚል ሲሆን ተጠሪው የሚከራከረው ግን የተጣሰው ከህግ የመነጨ መብት እንጂ ከውል የመነጨ መብት ባለመሆኑ ተፈጻሚነት የሚኖረው በፍ/ህ/ቁ/2143(1) ስር ከውል ወጪ ሀላፊነትን በሚመለከት ካሳ ለመጠየቅ የተደነገገው የሁለት ዓመት ጊዜ ሲሆን ይኸው መብት ከተጣሰ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠርም የሁለት ዓመት የክስ ማቅረቢያ ጊዜው አላለፈም በሚል ነው፡፡

ሆኖም ከግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ የተቻለው ቀደም ሲል የነበረው ማህበር ባወጣው ጨረታ መነሻ ተጠሪውም በጨረታው ተወዳዳሪ በመሆን የፈጠራ ሥራውን ማስታወቂያውን ላወጣው ለቀድሞ ማህበር ስለማስረከቡና ማህበሩም ስለመቀበሉ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ነው፡፡ የውል አቀራረብና አቀባበል በፍ/ህ/ቁ/1681(1) በተደነገገው መሰረት ፈቃድን በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ለውሉ መነሻ ከሆነው ምክንያት የተነሳ ግዴታን ለመግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ጭምር የሚደረግ በመሆኑ በተጠሪውና በቀድሞው ማህበር መካከል ግልጽ በሆነ ሁኔታ የተደረገ የጽሁፍ ውል ባይኖርም ፈቃድን በቃል በመግለጽ የውል ስምምነት ተደርጓል ለማለት የሚቻል ከመሆኑም በላይ ማህበሩ የተጠሪውን ሥራ መቀበሉ በመካከላቸው የውል ግንኙነት መመሰረቱን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከተጠሪው ጋር የተደረገ የውል ስምምነት የለም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ተጠሪውም ቢሆን ከአመልካች ጋር ያለው ግኝኙነት በውል ላይ የተመሰረተ ሆኖ እያለ ከህግ በመነጨው መብት ላይ አመልካች ጥሰት የፈጸመ በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ይርጋ ጊዜ ከውል ውጪ ሀላፊነት ሊኖር ስለሚችልበት አግባብ በፍትሐብሔር ህግ ክፍል የተደነገገው የካሳ ክስ ለማቅረብ የተቀመጠው የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው በማለት ያቀረበው ክርክርም ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንቶያች የተነሳ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የውል ግንኙነት መኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ ጉዳዩን ስለውሎች በጠቅላላው በተደነገገው ክፍል በሚገኘው በፍ/ህ/ቁ/1845 ይርጋ መሰረት መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡ በፍ/ህ/ቁ/1845 ድንጋጌ መሰረት ህግ በሌላ አካ ካልወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈጸም ወይም ከላመፈጸሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ መብት ያለው ወገን መብቱን በ10 ዓመት ወስጥ ካልጠየቀ መብቱ ቀሪ እንደሚሆን በግልጽ ተጠቅሷል፡፡ በዚህ

www.chilot.me

ጉዳይ የአመልካች የቀድሞ ማህበር የተጠሪውን ቅርጽ የተቀበለው በ1990 ዓ.ም. መሆኑን ከክርክሩ መረዳት የተቻለ ሲሆን ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት እስከ የካቲት 16 ቀን 2002 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ከ10 ዓመት በላይ ነው፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ምላሽ ማግኘት ያለበት ግን የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ከመቼ ጀምሮ ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አመልካች ጊዜው መቆጠር ያለበት ተጠሪው ቅርጹን ገቢ ካደረገበት ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ ነው ሲል ተጠሪው ግን መብቱ መጣሱን ያወቅኩት ከነሐሴ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ስለሆነ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠርም ክስ እስከቀረበበት እስከ የካቲት 16/2002 ዓ.ም. ሁለት ዓመት አላለፈውም በሚል ይከራከራል፡፡ ሆኖም የሰማዕታት ሐውልት ግንባታ ማህበር ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ለሆነው የመታሰቢያ ቀን ቴምብሮቹ እንዲታተሙ የትራንስፖርትና መገኛኛ ሚኒስቴር ለፖስታ አገልግሎት ድርጅት ደብዳቤ የጻፈው ታህሳስ 02/2000 ዓ.ም. መሆኑን ከቀረቡት ማስረጃዎች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪው ቴምብሮቹ የራሱ የፈጠራ ቅርጽ ምስል ተደርጎባቸው መታተማቸውን ሊያውቅ ይችላል ተብሎ የሚወሰደውም ከመታሰቢያው ቀን ማለትም ከግንቦት 19/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን ተጠሪውም ከውል የመነጨውን መብቱን ሊጠይቅ የሚችለው አመልካች በውሉ ግዴታ መሰረት ባለመፈጸም መሥራቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በተመሳሳይ ጭብጥ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ.67376 በቀን 30/11/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም ተጠሪው ቅርጹ ለ3ኛ ወገን ተላልፎ ምስሉ በቴምብሮች ወጥቶና ተባዝቶ ለገበያ መዋሉን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲቆጠር 10 ዓመት ያላለፈው በመሆኑ አመልካች ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- በከፍተኛው ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች የተጠሪው የፈጠራ ሥራ ባለሶስት አውታር መሆኑንና በቴምብሮቹ ምስሉ ወጥቶ የተባዛው ባለሁለት አውታር ነው በሚል ቢከራከርም ከፍተኛው ፍርድ ቤት በቴምብሮቹ ታትሞ የወጣው ምስል የተጠሪው ኦርጅናል ሥራ መሆኑንና ተጠሪውም ለዚሁ ስራ ባለቤት ስለመሆኑ የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማትና በመመዘን በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጡን በፍርዱ ላይ የገለጸ ሲሆን በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በመመልከት አጽንቶታል፡፡ የፍሬ ነገር ጉዳዮችን የማጣራትና የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶችም ያረጋገጡአቸውን ፍሬ ነገሮችን ይህ ችሎትም የሚቀበላቸው ናቸው፡፡ አንድ የመጨረሻ ፍርድ/ውሳኔ ያገኘን ጉዳይ ይህ ችሎት ማረም የሚችለው በፍርዱ/በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተመለከተ ሲሆን በዚህ በህግ በተሰጠ ሥልጣን መሰረት ማስረጃን የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባለቸው ፍርድ ቤቶች በተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች መሰረት ክርክሩን እንደመረመርነው በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/90008 በቀን 27/07/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሠጠውን ፍርድ እና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/72497 በቀን 16/04/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሠጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ተጠሪው ባለቤት የሆነበትን የቅርጽ ስራ በውሉ መሰረት ለመክፈል የተስማማውን ክፍያ ለተጠሪው ሳይከፍል በቴምብሮች ተባዝቶ ለገበያ እንዲቀርብ በማድረጉ የቅጂ መብት ጥሷል ተብሎ የሞራል ካሳ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ለተጠሪው እንዲከፍል የተወሰነበት የቅጅና ተዛማጅ መብቶችን በተመለከተ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 34(4) ስር የተደነገገውን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ህጋዊ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ጥ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 61221

መስከረም 22 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- . አቶ አከለ ምህረቱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ምንዳገኝ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከጡረታ መብት አከባበር ጋር ተያይዞ የተነሳውን የመሰየም ውጤት የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ላይ ተጠሪ በሰጠው ውሳኔ የይግባኝ አቤቱታ በማቅረባቸው ምክንያት ነው፡፡ አመልካች ለዚህ አካል ባቀረቡት አቤቱታ ከሰላሳ አመታት በላይ በመንግስት መስሪያ ቤት ያገለገሉ ቢሆንም ተጠሪ መስሪያ ቤት ግንቦት 6 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የሶስት አመት ፅኑ እስራት የተፈረደባቸው በመሆኑ በጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 5/1967 አንቀጽ 34 መሰረት ከ1995 ዓ/ም በፊት የሰጡት አገልግሎት የማይያዝ ስለሆነ ለዘለቄታ ጡረታ መብት ብቁ እንዳልሆኑ ገልፆ የወሰነባቸው መሆኑን፣ ከእስር ከተፈቱ በኋላ ወደ መደበኛ ስራቸው ተመልሰው እስከ ጥር ወር 2002 ዓ/ም ድረስ ሲያገለግሉ ቆይተው ከየካቲት 01 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ መገለላቸውን አሰሪው መስሪያ ቤታቸው መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም. እና ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፈው ደብዳቤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው ደንብ መሰረት እድሜአቸው ከሃምሳ በላይ እና አገልግሎታቸው ከሃያ አምስት አመታት በላይ አገልግሎት የሰጡ የመንግስት ሰራተኞች የእድሜ ልክ የጡረታ አበል እንደሚከፈላቸው ተወስኖ የአመልካች መስሪያ ቤትም የጡረታ መብቱ እንዲከበርላቸው የጠየቀላቸው መሆኑን፣ አዋጅ ቁጥር 345/1995 በስራ ላይ ከዋለ በኋላ የጡረታ መብት ጥያቄ የቀረበ በመሆኑ መብታቸውን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት እንደሌለ በመግለጽ አሰሪው መስሪያ ቤት የጠበቀላቸው ቢሆንም ተጠሪ መስሪያ ቤት ተገቢውን ያልፈፀመ መሆኑን፣ በወንጀል ተከሰው በነበሩበት ጉዳይ የመሰየም ውሳኔ ከሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ/ም ጀምሮ የተሰጠላቸው መሆኑንና በአዋጅ ቁጥር 345/1995 በተሻረው አዋጅ ቁጥር 5/1967 መሰረት መብታቸው የሚገደብበት ምክንያት የሌለ መሆኑን ዘርዝረው የዘላቂ የጡረታ መብት እንዲከበርላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪም አመልካች ከመታሰራቸው በፊትም ሆነ በኋላ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥረው መስራታቸውን ሳይክድ የአመልካች የዘላቂ ጡረታ መብት ሊከበርላቸው አይገባም በማለት የሚከራከረው ከመታሰራቸው በፊት ያገለገሉበት ጊዜ ሊቆጠር አይገባም፣ መሰየም ውጤቱ ወደፊት ነው እንጂ ወደኋላ አይደለም በሚል ምክንያት

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የመሰየም ውጤት ወደፊት እንጂ ወደኋላ ሊሄድ እንደማይችል ገልፆ አመልካች ያላቸው መብት ከእስር ከተፈቱ በኋላ ያገለገሉበት የሰባት አመት ከዘጠኝ ወራት አገልግሎት የሚያስገኝላቸው መብት ዘላቂ የጡረታ መብት ሳይሆን እንደገና ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ከስራ እስከተሰናበቱ ጊዜ ድረስ ከደመወዛቸው እየተቆረጠ ሲጠራቀም የነበረው 4% የጡረታ መዋጮ ነው ተብሎ በተጠሪ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የመሰየም ውጤት ወደፊት እንጂ ወደኋላ አይሰራም ተብሎ መወሰኑ ስለመሰየም የተደነገጉትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች እስራቱን ከጨረሱ በኋላ ወደቀድሞ መስሪያ ቤታቸው ተመልሰው ስራ ከመጀመራቸውና ከመሰየማቸው አንፃር ከእስራት በፊት ያበረከቱት አገልግሎት ሊታሰብ አይገባም ተብሎ በኤጀንሲው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት የቀረበ ሲሆን በነገረ ፈጁ አማካይነት ባቀረበው የፅሁፍ ክርክር ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ የመሰየም ውጤት ወደፊት እንጂ ወደኋላ ሊሆን እንደማይችል፤ መሰየም ለጡረታ መብትም ሊሰራ የማይችል መሆኑን ዘርዝሮ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በጡረታ መለያ ቁጥር ሰ/130745 የተመዘገቡና ከየካቲት 08 ቀን 1967 እስከ ህዳር 21 ቀን 1989 ዓ/ም ድረስ ለ22 አመታት ያህል በፍትህ ሚኒስቴር አገልግለው በወንጀል ተከሰው ከህዳር 22 ቀን 1989 እስከ የካቲት 08 ቀን 1994 ዓ/ም ድረስ በ5 አመታት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተወስኖባቸው የእስር ጊዜአቸውን በመጨረስ የተፈቱ መሆኑን፣ ከእስር ከተፈቱ በኋላም ከግንቦት 01 ቀን 1994 ዓ.ም. እስከ ጥር 30 ቀን 2002 ዓ.ም. ድረስ ለሰባት አመታት ከዘጠኝ ወራት ያህል በመንግስት መስሪያ ቤት ሲያገለሉ ቆይተው ከየካቲት 01 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ መስሪያ ቤቱ ባካሄደው የአሰራር ለውጥ ማሻሻያ ጥናት መሰረት የተገለሉ መሆኑን፣ ከሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ የተሰየሙ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች የዘላቂ ጡረታ መብት ተጠቃሚነት ሊከበርልኝ ይገባል በማለት የሚከራከሩት መሰየሙ ውጤቱ ከእስር በፊት የነበረውን የአገልግሎት ዘመን እንዲቆጠር ያደርገዋል፣ ይህ ጊዜ ከተያዘ የሃያ አምስት አመታት የአገልግሎት ዘመንና የሃምሳ አመት እድሜ ቅድመ ሁኔታ ይሟላልኛል በሚል ምክንያት ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጡት ነጥቦች በመነሳት በሕጉ ረገድ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ጉዳይ የመሰየም ውጤት ወደፊት ነው? ወይስ ወደኋላ? የሚለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ይህንኑ ጭብጥ ከመመለሳችን በፊት የተጠሪ ነገረ ፈጅ ጉዳዩን ለዚህ ሰበር ችሎት አመልካች ሊያቀርቡ አይችሉም ወይም ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት በሰ/መ/ቁጥር 18342 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመጥቀስ ያቀረቡትን ተቃውሞ ተመልክተናል፡፡

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ስር እንደተመለከተው ከአምስት ያላነሱ የዚህ ችሎት ዳኞች ተሰይመው የሚሰጡት የሕግ ትርጉም ተመሳሳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማናቸውም እርከን የሚገኝን ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ ነው፡፡ አንድ የሕግ ትርጉም ለተመሳሳይ ጉዳይ ገዥነት እንዲኖረው ለማድረግ ደግሞ በመሰረታዊ ነጥቦች ላይ ጉዳዮቹ መመሳሰል ያለባቸው ስለመሆኑ ከአስገዳጅ የሕግ ትርጉም ፅንሰ ሀሳብ የምንገነዘበው ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በሰ.መ.ቁጥር 18342 የተሰጠው የህግ ትርጉም የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የቀረበለት የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ስለሰጠና ውሳኔውም ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስላስተናገደው የቀረበ አቤቱታ ሲሆን የሰበር ሰሚ ችሎትም በህግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍርድ ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን የለውም፣ የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የላቸውም በማለት ወስኗል፡፡ ውሳኔው ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱም ቢሆንም ሊቀርብ የሚገባ አይደለም የሚል ይዘት የለውም፡፡ ለዚህ ውሳኔ መነሻ የሆነው በግለሰቦች የቀረበው ክርክር ደግሞ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ማህበራዊ ዋስትና ያላግባብ ከእኛ ሂሳብ አውጥቶ የወሰደውን ገንዘብ በሚመለከት የጡረታ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት ለማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣንም ሆነ ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ክስ አቅርበን በስማችን ውሳኔ ስለመስጠቱ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም፣ የአገልግሎት ዘመናችን ተቀንሶብናል ወይም ያለአግባብ እድሜአችን ጡረታ ሳይደርስ በጡረታ እንድንገለል ተደርጓል በሚል ያቀረብነው ክስ ስለሌለ በጡረታ ሕጉ መሰረት የሚታይ ጉዳይ የለም፣ አመልካች ያላግባብ ከሂሳባችን አውጥቶ የሰጠውን ገንዘብ ተቀብሎ ወደ ነበረበት ሂሳብ እንዲያስገባ በሚል የቀረበውን ክስ አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ ግን ቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የቀረበበት ወይም የይግባኝ አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረምልኝ ይገባል በሚል በቀጥታ ለዚህ ችሎት የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ በተነሳበት ጊዜ ስራ ላይ በነበረው ሕግ አግባብ ማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው ከተባለ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 በተመለከተው አግባብ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ከማቀረብ የሚከለክል ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 18342 የተሰጠው ትርጉም የሰበርን ስልጣንም የሚጨምር አይደለም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ነገረ ፈጅ የሰ/መ/ቁጥር 18342"ን" መሰረት በማድረግ ያቀረቡት ተቃውሞ በመዝገቡ ላይ ያሉትን መሰረታዊ የክርክር ነጥቦችንና ጉዳዩ መታየት የጀመረበትን አካሄድ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር በመሰረታዊነት የሚለይ መሆኑና ሰበር ችሎቱ በሕገ መንግስቱ በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተትን የማረም ስልጣን ያለው መሆኑን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ስለአገኘን ተቃውሞውን አልተቀበልነውም፡፡

ወደዋናው ጭብጥ ስንመለስም በመሰረቱ የጡረታ አዋጅ ቁጥር 209/1955 በአዋጅ ቁጥር 5/1967 እንደተሻሻለው አንቀጽ 34 አንድ የመንግስት ሰራተኛ ወይም ጡረተኛ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆኑ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ሲረጋገጥና ቢያንስ የሶስት አመት የፅኑ እስራት ቅጣት ሲወሰንበት የጡረታ መብቱን እንደሚያጣ ወይም በመከፈል ላይ ያለው የጡረታ አበል እንደሚቋረጥ ደንግጓል፡፡ አመልካች ይህ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 345/1995 የተሻረ በመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 345/1995 በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ለቀረበ ጥያቄ ተፈፃሚነት የለውም በማለት

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚከራከሩ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በአዋጅ ቁጥር 209/1955፣ በአዋጅ ቁጥር 5/1967 እንደተሻሻለ የተገኙት መብቶችና ግዴታዎች ቀሪ ያልሆኑ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 52/1/ ስር የተደነገገ በመሆኑ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ በመ/ቁጥር 50590 እና 50591 በቀረቡት ጉዳዮች ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ በዚህ በኩል የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የመሰየም ውጤትን በተመለከተ የቀረበውን ክርክርና በይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የተሰጠውን ውሳኔ ሕጋዊነት ስንመለከትም መሰየም አንድ ተቀጪ በዋናው ቅጣት ወይም በዋናው ቅጣትና ተጨማሪው ቅጣት ምክንያት አጥቶት የነበረውን ንፁህ ሰው ሆኖ የመገመት መብቱን እንደገና መልሶ የሚያገኝበትንና ተወስኖበት የነበረው ዋናው ቅጣትም ሆነ ተጨማሪ ቅጣት ተመዝግቦበት ከነበረው ከግል የፍርድ ሰሌዳው ላይ ተሰርዞ ለሶስተኛ ወገኖች ይኸው ሁኔታ የሚገለፅበትንና የሚታወቅበትን አግባብ የሚመለከት የሕግ አካሄድ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 232 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ከአስቀመጡት መንፈስና ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 235(1) ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ተቀጥቶ የነበረው ሰው ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ተወስኖበት የነበረው የመብት፣ የማዕረግ፣ ወይም የችሎታ ማጣት ለወደፊቱ ቀሪ ሆኖለት ሕዝባዊ መብቱንና ቤተሰብ የማስተዳደርና የሙያ ስራ መስራት መብቱን እንደገና ለመያዝ ችሎታ ይኖረዋል በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ማንም ተቀጪ በመሰየሙ ሊያገኝ የሚችለው መብት ከመሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረውን መብት ሳይሆን ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ወደፊት ሊጠበቅበት የሚገባውን መብት ብቻ ስለመሆኑ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች ከመሰየማቸው በፊት በመንግስት መስሪያ ቤት ያገለገሉበት አገልግሎት ጊዜ በመሰየማቸው ምክንያት ዋጋ እንዲኖረው ሊደረግ ይገባል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ከላይ ስለመሰየምና ውጤቱ በሕጉ በግልፅ የተመለከተውን መስፈርት መሰረት ያላደረገ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ሰሚው ጉባኤ መሰየም ውጤቱ ወደፊት እንጂ ከመሰየም አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖ የነበረውን መብት መልሶ ማግኘት አይደለም በማለት አመልካች ከየካቲት 08 ቀን 1967 እስከ ህዳር 21 ቀን 1989 ዓ/ም ድረስ ያገለገሉት የአገልግሎት ዘመን ሊያዝላቸው አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በጉዳዩ ላይ በይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. መሰየም ውጤት የሚኖረው ተቀጪው ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ወደፊት እንጂ ከመሰየሙ አስቀድሞ በቅጣቱ አጥቶት የነበረውን መብት አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 72928

ጥቅምት 09 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ
ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አበራ ኪዳኔ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የጋሞ ጎፋ ዞን አርባ ምንጭ ማህበራዊ ዋስትና ቅ/ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች ለመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ባቀረቡት አቤቱታ የትውልድ ዘመናቸው 1943 መሆኑን በመጥቀስ በ30/07/2003 ዓ.ም. ዕድሜያቸው 60 ዓመት ስለሚሞላ ከ01/08/2003 ጀምሮ የዘለቄታ የጡረታ ባለመብት መሆናቸው ታውቆ የጡረታ አበል እንዲወሰንላቸው የጠየቁ ሲሆን ኤጀንሲውም አመልካች በጋሞ ጎፋ ዞን ሥራና ከተማ ልማት በ1986 ዓ/ም ሲቀጠሩ የትውልድ ዘመናቸው 1943 ዓ.ም. ነው በሚል በሕይወት ታሪክ ፎርም የሞሉ ቢሆንም በገንዘብ ሚኒስቴር ተቀጥረው ሲሰሩ የትውልድ ዘመናቸው በ27/7/1933 በሚል የሞሉ ስለሆነ በጡረታ መገለል የነበረባቸውም በ01/08/1988 ዓ.ም. ነው፡፡ በገንዘብ ሚኒስቴር ተቀጥረው ከ01/03/1958-30/01/1969 በሚሰሩበት ወቅትም ገንዘብ በማጉደላቸው በወንጀል ተከሰው በ3 ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 500 የተቀጡ ስለሆነ በተሻሻለው የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 5/1967 አንቀጽ 34 የመጀመሪያው አገልግሎታቸው ውድቅ የሚደረግ በመሆኑ የሚቆጠረውም ከ20/10/1986-30/07/1988 ዓ.ም. ያለው ነው፡፡ ይህም ጊዜ 1 ዓመት ከ9 ወር ከ11 ቀን ስለሚሆን ሊከፈላቸው የሚገባው የዘለቄታ የጡረታ አበል ሳይሆን የዳረጎት ክፍያ ነው በሚል የወሰነ ሲሆን፣ ከ01/9/1988-30/07/2003 ዓ.ም. ድረስ ከዕድሜ ጣሪያ በላይ ለፈጸሙት አገልግሎትም የከፈሉት የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ሊደረግላቸው ይገባል ብሏል፡፡

አመልካችም በኤጀንሲው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ያቀረቡ ቢሆንም ጉባዔው ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የኤጀንሲውን ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም ፡- በወንጀል የተሰጠብኝ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በመሰየም ተሰርዞ እያለ የአገልግሎት ዘመኔ ውድቅ መደረጉ፣ እንዲሁም የትውልድ ዘመኔ 1933 ዓ/ም ሳይሆን 1943 ዓ/ም ስለመሆኑ በፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ ተረጋግጦ እያለ ተቀባይነት የሚኖረው የትውልድ ዘመን 1933 ዓ/ም ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪው መሥሪያ ቤት በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- አንድ የመንግስት ሰራተኛ በጡረታ ከመንግስት ሥራ የሚሰናበተው ሰራተኛው በሚያቀርበው የልደት ዘመን ማስረጃ ሳይሆን በመጀመሪያ ጊዜ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲቀጠር በሞላው የህይወት ታሪክና የልደት ዘመን መሰረት ነው፣ መሰየም የታጣውን መብት እንደገና የሚያስገኝ አይደለም በማለት የኤጀንሲውና የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሳኔ የህግ ስህተት የለበትም በሚል ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በህጉ መሰረት ደረጃውን ጠብቆ የቀረበ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በዚህ ጉዳይ የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ጉባኤ ውሳኔ የሰጠው ሐምሌ 18 ቀን 2003 ዓ.ም. ሲሆን ውሳኔው በተሰጠበትም ወቅት ተፈጻሚ የነበረው ስለመንግስት ሰራተኞች ጡረታ ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 714/2003 ነው፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 56 (1) መሰረት በኤጀንሲው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለመብት ቅሬታውን በአዋጁ አንቀጽ 57 ለተቋቋመው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ በንዑስ አንቀጽ 4 ደግሞ ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን የተደነገገ ሲሆን ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን የሚያምን ተከራካሪ ደግሞ ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌ/ጠ/ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ተጠቅሷል፡፡ ከድንጋጌው የመጨረሻ ክፍል መገንዘብ የተቻለውም የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ውሳኔ በፍሬ ነገር ደረጃ የመጨረሻ መሆኑንና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑ ሲታመን ግን በይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መቅረብ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ አመልካች ቅሬታቸውን ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ማቅረብ ሲገባቸው በሰበር ለዚህ ችሎት ማቅረባቸው ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በህጉ የተቀመጠውን የአቀራረብ ደረጃ ጠብቆ የቀረበ ባለመሆኑ ውድቅ አድርገናል፡፡
2. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80964

ጥቅምት 23 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ነ/ፊ.ጅ ተስፋዬ ምንዳገኝ ቀረበ

ተጠሪ፡- 1. አቶ አበራ ቦሳን - ጠበቃ ሀቢቢ ረጋሣ ቀረቡ

2. አቶ አየለ ታደሰ - ቀረቡ

3. አቶ ተስፋዬ ቅጣው - ቀረቡ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 80965 እና 80966 ከዚህ መዝገብ ጋር እንዲጣመሩ የተደረገ በመሆኑ ሶስቱንም መዛግብት በመመርመር ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከጡረታ መብት ጋር የተያያዘ የእድሜ አቆጣጠርንና ውጤቱን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በአመልካች ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ለየብቻቸው ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ አመልካች ኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መስከረም 29 ቀን 2004 ዓ.ም. በቁጥር ጡ/ይ/1/1/870/2004 የሰጠውን ውሳኔ የተቃወሙ ሲሆን የይግባኝ ቅሬታው ይዘትም ከኢትዮጵያ ፖልፕና ወረቀት አክሲዮን ማህበር የሰው ኃይል አስተዳደር መምሪያ ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ የጡረታ መውጪያ ጊዜን ለማሳወቅ ተብሎ በተፃፈልኝ ደብዳቤ የልደት ዘመንህ እ.ኤ.አ 1944 ተብሎ የተላከና እድሜዬ ለጡረታ የሚደርሰው እ.ኤ.አ ጃኑዋሪ 1/2004 እንደሆነና ያለኝን የአመት እረፍት ከሰኔ 27 ቀን 2003 ዓ.ም. በፊት እንድወስድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኛል፣ ይሁን እንጂ እኔ በዚህ ድርጅት የተቀጠርኩት እ.ኤ.አ በ05/04/71 በመሆኑ ስቀጠር እድሜዬ 17 እንደነበርና የልደት ዘመኔም ሐምሌ 19 ቀን 1946 ዓ.ም. በመሆኑ በተሰጠኝ ደብዳቤ እንደተመለከተው ከሰባት አመት በፊት ወደ ጎላ ጡረታ መውጣት እንደአለብኝ የሚገልጽ በመሆኑ የጡረታ አበሉና የአገልግሎት ዘመን የሚቀንስ ነው፣ በተቀጠርኩበት ጊዜ የቅጥር ፎርሙ የተሞላው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሁኖ በወቅቱ የነበሩት አሰሪዎች የውጪ አገር ዜጎች በመሆናቸው የዘመን አቆጣጠሩ በምን እንደሞሉት የማላውቅ ነበር፣ ጡረታም የምወጣው ወደፊት ሐምሌ 20 ቀን 2006 ዓ.ም. በመሆኑ የልደት ዘመኑ 1946 ዓ.ም መሆኑ ታውቆልኝ የጡረታ መውጪያ ጊዜ ይስተካከልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪ ለኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ይዘት ደግሞ በኢትዮጵያ ፖልፕና ወረቀት አ.ማ እ.ኤ.አ ጥር 14 ቀን 1972 ዓ.ም. የተቀጠርኩ ሲሆን በወቅቱ እድሜዬ 20 ዓመት፣ የተወለድኩት ሰኔ 12 ቀን 1944 ዓ.ም. ሁኖ እያለ ከአሰሪ ድርጅቱ የተሰጠኝ ደብዳቤ ከሰባት አመት በላይ ወደ ጎላ ጡረታ መውጣት እንዳለብኝ የሚገለጽ በመሆኑ በጡረታ አበልና በአገልግሎት ዘመኑ ላይ ቅነሳ የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ የትውልድ ዘመኔ እ.ኤ.አ 1944

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሰኔ 12 ቀን 1944 ስለሆነ ለጡረታ መውጫ እድሜ ላይ ያልደረስኩ በመሆኑ በተቀጠርኩበት ጊዜ የቅጥር ፎርሙ የተሞላው በእንግሊዝኛ ቋንቋና በነበሩት የውጪ አገር አሰሪዎች ሁኖ የዘመኑ አቆጣጠሩ በምን እንደተሞላ የማላውቅ በመሆኑ ታውቆ ትክክለኛው የልደት ዘመኔ ሰኔ 12 ቀን 1944 ዓ.ም. ሊያዝልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ሶስተኛ ተጠሪ ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ይዘቱ ሲታይም የጡረታ መውጪያ ጊዜ አያያዝ ላይ እንደ አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ችግሩ የተከሰተበት መንገድ ተመሳሳይ መሆኑን ገልጸው ትክክለኛው የትውልድ ዘመናቸው ነሐሴ 25 ቀን 1943 ዓ.ም. ሁኖ እንዲያዝላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪዎች ይግባኝ በተናጠል በሰጠው መልስም የልደት ዘመን የሚያዘው ሰራተኛው ለስራው ሲቀጠር በሞላው ፎርም ላይ የተመዘገበ የልደት ዘመን መሆኑን ገልጾ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በጡረታ መለያ ቁጥር ድ/543275 መመዝገባቸውንና የተጠሪ የልደት ዘመን በፎረንሲክ የምርመራ ውጤት መሰረት እ.ኤ.አ 1944 ተወለድኩ ብለው የሞሉና ይህንን የሚቀይር የተሞላ የልደት ዘመን የሌለ በመሆኑ ይኼው የልደት ዘመን እንዲያዝላቸው መደረጉን፣ የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪም በጡረታ መለያ ቁጥር ድ/529780 የተመዘገቡና እ.ኤ.አ በ14/1/1972 በሞሉት የህይወት ታሪክ ፎርም ላይ እ.አ.አ 1944 የተወለዱ መሆኑን ገልፀው የሞሉ መሆኑን እና ሶስተኛ ተጠሪ በጡረታ መለያ ቁጥር ድ/407412 የተመዘገቡና በእ.ኤ.አ በ4/07/1973 የሞሉት የህይወት ታሪክ ፎርም ላይ እ.ኤ.አ 1941 ተወለድኩ ብለው የሞሉና ይህን የሚቀየር የተሞላ የልደት ዘመን የሌለ በመሆኑ ይኼው የትውልድ ዘመን እንዲያዝላቸው የተደረገ መሆኑን ዘርዝሮ በሕጉ አግባብ የተከናወነ ተግባር ስለሆነ የኤጀንሲው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የኤጀንሲው ጉባኤም ጉዳዩን መርምሮ በማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የአፈፃጸም መመሪያ ለጡረታ ተግባር የሚያዘው እድሜ በቅድሚያ በተሞላ የስራ መጠየቂያ ወይም የሕይወት ታሪክ መግለጫ ቅጽ ወይም የተያዥ መስጫ ወይም የምዝገባ ቅፅ ላይ የተመዘገበ የልደት ዘመን መሆኑን፣ 1ኛ ተጠሪ በኢትዮጵያ ፖልፕና ወረቀት አክሲዮን ማህበር እ.ኤ.አ. በ05/04/1971 ለስራ ሲቀጠሩ በሞሉት የሕይወት ታሪክ ፎርም ላይ የተመዘገበው የልደት ዘመን ስርዝ ድልዝ ያለው በመሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት በ26/8/2002 በቁጥ ፌሮ/1-1/31/7452/2002 በተጻፈ ደብዳቤ አባሪ ሆኖ በተላከው የሰነድ የምርመራ ውጤት መግለጫ ላይ በአቶ አበራ ቦከን ስም በተዘጋጀው ሰነድ ላይ በእንግሊዝኛ የልደት ዘመን በሚለው ፊት 1954 በሚል የተጻፉ ቁጥሮች ቀደም ሲል 1944 በሚል ከተጻፈ በኋላ ተደልዘውና ተለውጠው አሁን እንደሚታየው 1954 የተደረገ መሆኑ መረጋገጡን፣ 2ኛ ተጠሪም እ.ኤ.አ. በ14/1/1972 ለስራ ሲቀጠሩ በሞሉት ፎርም ላይ የልደት ዘመን ስርዝ ድልዝ በመሆኑ በፎረንሲክ ምርምራ ተብሎ በእንግሊዝኛ የትውልድ ዘመን በሚለው ቃል ፊት ያለው 1952 በሚል የተፃፉ ቁጥሮች ቀደም ሲል 1944 ከተፃፈ በኋላ ተደልዘውና ተለውጠው አሁን እንደሚታየው 1952 የተደረገ መሆኑን የፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት በ26/08/2002 ዓ.ም. በቁጥር ፌሮ/1-1/31/7452/2002 በተፃፈ ደብዳቤ ያረጋገጠ መሆኑን፣ ሶስተኛ ተጠሪን በተመለከተም በእ.ኤ.አ በ4/7/1973 ሲቀጠሩ በሞሉት የህይወት ታሪክ ፎርም ላይ የልደት ዘመን ስርዝ ድልዝ ያለው በመሆኑ በፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርምራ በእንግሊዝኛ የልደት ዘመን በሚል ከተቀመጠው ቃል ፊት ለፊት 1951 በሚል የተፃፉ ቁጥሮች ቀደም ሲል 1941 በሚል ከተፃፈ በኋላ ተደልዘውና ተለውጠው አሁን እንደሚታየው 1951 የተደረገ መሆኑን በ26/08/2002 ዓ.ም. በቁጥር ፌሮ/1-1/31/7452/2002 በተፃፈ ደብዳቤ መግለፁን በመጥቀስና 1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 12 ቀን በሞሉት የመንግስት የሆኑ ድርጅቶች ሰራተኞች የግል አገልግሎትና የቤተሰብ ሁኔታ መግለጫ ቅጽም ላይ የትውልድ ዘመናቸውን 1946 ዓ.ም. በሚል የመዘገቡት፣ ሁለተኛ ተጠሪም እ.ኤ.አ 1952 በሚል

www.chilot.me

የመዘገቡት፣ ሶስተኛ ተጠሪ ደግሞ 1943 በሚል የመዘገቡት ቅድሚያ እንደሌለው ገልፆ የአመልካችን የትውልድ ዘመን አያያዝን በተመለከተ ኤጀንሲው የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪዎች በተናጠል የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የአመልካቾች እድሜ ስርዝ ድልዝ ያለው መሆኑ ቢረጋገጠም ማን እና እንዴት ሊሰረዝ እንደቻለ ሳይረጋገጥ ውሳኔ መስጠት ተገቢ ያለመሆኑና የሕግ ግምቱንም ያልተከተለ መሆኑን ጠቅሶ በጉዳዩ ላይ በይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የልደት ዘመኑ በማን እና እንዴት እንደተሰረዘ አጣርቶ እንዲወስን በማለት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ በእያንዳንዱ መዝገብ ላይ የቀረበው የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም ሆኖ እያለ ፍሬ ነገሩን ማጣራቱና ማስረጃን መመዘኑ ከስልጣኑ ውጪ መሆኑን እንዲሁም ተጠሪዎች የተወለዱበት ዘመን መጀመሪያ ሲቀጠሩ በትክክል የተሞላና በኋላ ደግሞ የተሰረዘና የተለወጠ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በኋላ የተሞላውን የትውልድ ዘመን እንዴት እንደተሞላና የቀድሞውን ማን እንደሰረዘው እንዲጣራ ማድረግ ለጉዳዩ አወሳሰን አስፈላጊ ያልሆነ ነጥብ መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 4(1)፣ 54(1)፣ 56(4) ድንጋጌዎችን ይዘት ያላገናዘበ መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በአዋጅ ቁጥር 714/2003 በአንቀጽ 4(1) መሰረት ለመንግስት ሰራተኛ ለጡረታ የሚያገዝ የልደት ዘመን የመንግስት ሰራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር ያስመዘገበው የልደት ዘመን መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ የፍትሐብሔር ችሎት በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 56(4) መሰረት ፍርድ ቤቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተቶችን ብቻ በይግባኝ እንዲያይ ተደንግጎ እያለ በፍሬ ነገር ላይ ጉባኤው ሌሎች ማስረጃዎችን እንደገና መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች ሲቀጠሩ በሞሉት የሕይወት ታሪክ ፎርም ላይ ያለው የትውልድ ዘመን ተሰርዞና ተደልዞ የተለወጠና ቅድሚያ የሞሉት የትውልድ ዘመን ስንት እንደነበር በፎረንሲክ ምርምራ መረጋገጡን፣ ተጠሪዎች የትውልድ ዘመኑ ላይ እ.ኤ.አ አቆጣጠር የተሞላ ስለነበር የተከሰተ ችግር እንጂ ቀድሞ ሲሞሉት የነበረውን በመለወጥ የተከሰተ ችግር ያለመሆኑና በቅጥር ጊዜ በነበረው የቋንቋ ችግር መከሰቱን ገልጸው የአመልካች ኤጀንሲ ውሳኔ በጡረታ አበል መጠኑና በአገልግሎት ዘመናቸው ላይ ችግር የሚያስከትልባቸው መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን፣ አመልካች በአንዳንድ የተጠሪዎች የትውልድ ዘመን በተገቢው መንገድ ተረጋግጦ እያለ እንዴት እንደተሰረዘና ማን እንደሰረዘው ይረጋገጥ ተብሎ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መወሰኑ ያላግባብ መሆኑንና የራሱ እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት የተከናወነ መሆኑን ገልጾ የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ ለመንግስት ሰራተኛ ለጡረታ የሚያዝ የልደት ዘመን የመንግስት ሰራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በቅድሚያ የመዘገበው የልደት ዘመን መሆኑን አዋጅ ቁጥር 714/2003 በአንቀጽ 4(1) ስር በግልጽ ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ የሚያሳየው አመልካች መስሪያ ቤት ለመንግስት ሰራተኞች የጡረታ አበል ውሳኔ የሚሰጠው በአዋጁ መሰረት ሰራተኛው በመጀመሪያ ጊዜ በመንግሰት መስሪያ ቤት ሲቀጠር የሞላውን የልደት ዘመን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ነው፡፡ በተጠቃሹ አዋጅ አዋጁን ለማስፈፀም በተመለከተ መመሪያ የማውጣት ስልጣን ለአመልካች ኤጀንሲ መሰጠቱን በአንቀፅ 60(2) ስር ሰፈሯል፡፡ አመልካች በዚህ አግባብም የልደት ዘመንን አያያዝና ሌሎች አፈፃፀሞችን በተመለከተ መመሪያ ስራ ላይ ማዋሉም በክርክሩ ሂደት ክርክር ያልቀረበበት ጉዳይ ነው፡፡ ኤጀንሲው በአዋጁ ለሚሰጡ ለማናቸውም አበል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መሟላታቸውን የማረጋገጥና የአበሉን መጠንና አይነት የመወሰን ስልጣን ያለው መሆኑ በአዋጅ አንቀፅ 54(1) ስር በግልጽ የሰፈረ ሲሆን በዚህ ረገድ ውሳኔ ሲሰጥም የራሱን የመረጃ ማህደር፣ በአዋጁ አንቀጽ 53 መሰረት የሚተላለፉን መረጃዎችንና እንደ አግባብነቱ ባለመብቱ የሚያቀርባቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ መሆኑን አንቀጽ 54(2) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ በኤጀንሲው ማህደርና በሚቀርበው ሌላ ማስረጃ ልዩነት ቢፈጠር ደግሞ ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ የሚወስነው ኤጀንሲው ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 54(3) ድንጋጌ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ አዋጁ የኤጀንሲው ውሳኔ በኤጀንሲው ዳግም የሚታይበትን ስርዓት የዘረጋ ሲሆን ዝርዝር ሁኔታዎችንም በአንቀጽ 55 ስር አስፍሯል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ሁሉ ይግባኙን የሚያቀርበው ለኤጀንሲው ጉባኤ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 56(1) ይገልፃል፡፡፡ የኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 56(4) ስር በግልጽ የተደነገገ ሲሆን የይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችልም ይኸው ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙ የሚቀርበው በፍሬ ነገር ክርክር ወይም በማስረጃ ምዘና ሳይሆን በመሰረታዊ የህግ ስህተት ላይ ብቻ ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች መስሪያ ቤት የተጠሪዎችን የልደት ዘመን የያዘው ማህደሩን በመመልከትና በማህደሩ የተከሰቱን ችግሮች በማጣራት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤትም በተጠሪዎች የህይወት ታሪክ ላይ ቀድሞ የተሞላው ትክክለኛ ዘመን የለየው ሲሆን በኋላ ተሞልቶ የተገኘው ግን የቀድሞው ተሰርዞ የተቀመጠ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ለጉባኤው እንዲመለስ ያደረገው የትውልድ ዘመኑ በተለያዩ ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል፣ ማህደሩ በአሰሪ እጅ ባለበት ሁኔታ የሰረዘው ማን ነው የሚለው ጥያቄም የሕግ ግምት ነው፣ ተጠሪዎች በኋላ ሞላን የሚሉት ወይም ስርዝ ነው የተባለው የትውልድ ዘመን ቀድሞ እ.ኤ.አ ተሞልቶ ስለነበር ይህንኑ ለማስተካከል ተብሎ ሊሆን ይችላል የሚሉትን ነጥቦችን በመያዝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለውሳኔ መሰረት ያደረጋቸው ምክንያቶች በይዘታቸው ሲታዩ የፍሬነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳዩን የሚመለከቱ ሲሆን ያላግባብ የገባውና በትክክል ሰራተኞቹ ሲቀጠሩ የተሞላው የልደት ዘመን በፎረንሲክ ምርምራ እስከተለየ ድረስ በኋላ የገባውን የልደት ዘመን ማን ሰረዘው፣ እንዴት ተሰረዘ የሚለውን ማጣራቱ በተጠሪዎች የጡረታ መብት ውሳኔ ላይ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት አይኖርም፡፡ ምክንያቱም ኤጀንሲው የሰራተኛውን ማህደር በመመርመርና የመብቱ ተጠቃሚ የሚያቀርበውን ማስረጃ መመርምሮ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ የትኛው እንደሆነ ለይቶ መወሰን እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 54(3) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በፎረንሲክ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምርመራ መሰረት ተጠሪዎች ሊያዝልን ይገባል በማለት የሚጠቅሱት የልደት ዘመን በቅጥር ጊዜ የተሞላ ያለመሆኑ ተረጋግጦ እያለና ኤጀንሲውም የተጠሪዎችን አለን የሚሉትን ማስረጃ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሳይቀበለው መቅረቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ የትውልድ ዘመኑን የሰረዘው ማን ነው?፣ እንዴት ተሰረዘ? የሚለው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ማድረግ ኤጀንሲው በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያልተቀበለውን ማስረጃ እንዲቀበል የማስገደድ ኃይል ያለው ውሳኔ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 56(4) ድንጋጌ መሰረት በሕጉ ተሰይቶ የተሰጠው ሥልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም ሁኖ እያለ አመልካች መስሪያ ቤት ፍሬ ነገሩን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን ድምዳሜ ላይ የደረሰበትን የተጠሪዎችን የትውልድ ዘመን እንደገና እንዲጣራ ማድረጉ ያለሥልጣኑ የተሠጠ ውሳኔ ሁኖ አግኝተናል፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መዳኘት ያለበት ደግሞ በሕጉ ተሰይቶ በተሰጠው ስልጣን አድማስ ውስጥ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያሳየን ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 ድንጋጌ መሰረት አንድ ጉዳይ ውሳኔውን ለሰጠው አካል እንዲመለስ የሚደረገውም ለውሳኔ አሰጣጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በሕጉ በተመለከተው የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ስርዓት መሰረት ሳይጣሩና የክርክሩ አካሄድ ሳይሟላ ውሳኔ ተሰጥቶ ሲገኝ ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ በዚህ ረገድ የበላይ ፍርድ ቤት መሪ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለውም በሕጉ ስልጣን ያለው መሆኑ ሲረጋግጥ ነው፡፡ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት የማረም ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በስር ፍርድ ቤት ወይም ዳኝነት መሰል አካል እንዲጣራ ሊያደርግ እንደሚችል የመሰረታዊ ሕግ መመዘኛዎች የሚያሳዩን ጉዳይ ሲሆን ይህንን መሪ ትእዛዝ ሲሰጥ ግን ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያለው አካል በፍሬ ነገር ደረጃ በሕጉ አግባብ የደመደመውን ፍሬ ነገር ውድቅ የሚያደርግበት ስልጣን ሊኖረው አይችልም፡፡ ሲጠቃለልም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 4(1)፣ 54፣ እና 56(4) ድንጋጌዎችን እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343 ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 75355፣ በመ/ቁጥር 74770 እና በመ/ቁጥር 74769 ሚያዚያ 10 ቀን 2004 ዓ.ም. የሰጣቸው ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. በጉዳዮቹ ላይ የመንግስት ሰራተኞች የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መስከረም 13 ቀን 2004 ዓ/ም፣ ጥቅምት 25 ቀን 2004 ዓ.ም. የሰጣቸው ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከሰ/መ/ቁጥር 80965 እና 80966 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 78945

መስከረም 22 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡- መምህር ባዬ ዋናያ የዳ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግስት ዩኒቨርሲቲ መምህራን በዲስፕሊን ግድፈት ከስራ እንዲባረሩ የሚሰጥ ውሣኔ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚቀርብበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍ/ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት ይግባኙን ያቀረቡት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ የተጠሪ የይግባኝ አቤቱታ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ ከዩኒቨርሲቲው ያላግባብ ከስራ እንደተባረሩ ገልፀው ወደ ስራ እንዲመለሱና ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፍላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ከሰጠው መልስም በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ በየኒቨርሲቲው ቦርድ ሳይሰጥ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት መቅረቡ ያላግባብ መሆኑና ይግባኙ መቅረብ የሚገባው ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ እንጂ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት መሆኑን ገልፆ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የአስተዳደር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 2(8) ስር መደንገጉን ገልፆ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች ተቃውሞ ሳይቀበለው ያለፈ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ መምህር ከስራ የተሰናበቱት ያለግባብ ነው በሚል ምክንያት ተሰጠ የተባለውን ውሣኔ መሻሩን ገልፆ ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመለሱና ያልተከፈላቸው ውዝፍ ደመወዝ በሕጉ አግባብ እንዲከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የዩኒቨርሲቲውን መምህራን የዲሲፕሊን ግድፈትን በተመለከተ ጉዳዩ የሚገዛው በደንብ ቁጥር 1/2002 ሁኖ በስንብት ውሣኔ ቅሬታ ያለው የአካዳሚክ ሰራተኛ ቅሬታውን ማቅረብ ያለበት ለየኒቨርሲቲው ቦርድ ሁኖ እያለና በቦርዱ የሚሰጠው ውሣኔም የመጨረሻ ሁኖ እያለ የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር አስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማየቱ ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ያቀረበው ተቃውሞ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 በተዘረጋው ስርዓት መሠረት የመጨረሻ ፍርድ አግኝተዋል ወይስ አላገኙም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 መሠረት ወደ አስተዳደር ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ማቅረብ ያለብኝ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ከሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ለማቅረብ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 በተዘረጋው ስርዓት ተፈቅዶልኛል በማለት ሲሆን የአስተዳደር ፍርድ ቤትም ተጠሪ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 2(8) ስር የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የመንግስት መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ተብሎ የሚመደብ በመሆኑና በዚህ ባለስልጣን በሚሰጠው ውሣኔ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ይገባኝ ማቅረብ ይቻላል በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው የዩኒቨርሲቲው አካዳሚ ሰራተኞች የዲስፕሊን አፈፃፀም ደንብ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 33(4) ይግባኙ የሚቀርበው ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ መሆኑንና ይህ አካል የሚሰጠው ውሣኔም የመጨረሻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44(ጎ) ድንጋጌ ያሣያል በማለት መሆኑን ተረድተናል፡፡

እኛም ይህንኑ የአመልካች መከራከሪያ ነጥብ በአዋጅ ቁጥር 65/2001 አንቀጽ 22(3)፣ 44(ጎ) መሠረት ለዩኒቨርሲቲ ቦርድ ከተሰጡት ኃላፊነቶችና ተግባራት አንፃር ተመልክተናል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 32 ሥር የአካዳሚክ ስራተኞች ግዴታዎች የተዘረዘሩ ሲሆን የተጠቃሹ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር ሶስት ድንጋጌ ደግሞ ተቋማቱ በዚህ አንቀጽና አግባብነት ባላቸው የአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች ላይ የተመሠረተና የአካዳሚክ ሰራተኞችን ያሣተፈ የአካዳሚክ ሠራተኞች የዲስፕሊን ደንብ አውጥተው ተግባራዊ ማድረግ የሚኖርባቸው መሆኑን በአስገዳጅ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ በዚህ የአዋጁ አግባብም አመልካች ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ሰራተኞች የዲሲፕሊን ደንብ ቁጥር 1/2002 አውጥቶ ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ አከራካሪ የሆነ ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ ደንብ የአካዳሚክ ሰራተኞች የዲሲፕሊን ጥፋቶችና ቅጣቶች፣ የዲሲፕሊን ክስ አመሰራረት፣ የምርመራ አፈፃፀምና ውሣኔ አሰጣጥ፣ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት፣ የይግባኝ ምክንያቶችና የጊዜ ገደብን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ ደንቡ የአካዳሚክ ሰራተኛ የዲሲፕሊን ግድፈት ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ውሣኔ የሚሰጡበትን አግባብ በአንቀጽ 32 ያስቀመጠ ሲሆን ይህ አካል ከስራ የመባረርን ውሣኔ አስመልክቶ በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ አስመልክቶ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ሰራተኛ ጉዳዩ እንዲታይለት ይግባኙን በአስር ቀናት ውስጥ ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ ሊያቀርብ እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44(ጎ) መሠረትም የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ እንግዲህ ከላይ የተመለከተው ስርዓት አመልካች ዩኒቨርቲው በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 32(3) መሠረት የአካዳሚክ ሰራተኞችን የዲስፕሊን ግድፈት ለመግዛት የዘረጋው ስርዓት ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 650/2001 ከአዋጅ ቁጥር 515/1999 በኋላ የወጣ በመሆኑና የሚገዛው ጉዳይም ተለይቶ የተሰጠው በመሆኑ በአዋጅ በተካተቱት ጉዳዮች ከማንኛውም አቻ ሕግ የበላይ ገዥነት የሚኖረው ስለመሆኑ ተቀባይነት ያለቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያሣዩን ሐቅ ነው፡፡ ስለሆነም በአመልካች ዩኒቨርሲቲ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አካዳሚክ ሰራተኞች የዲሲፕሊን ጉዳይ ከአዋጅ ቁጥር 515/1999 ቀዳሚ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 650/2001 በመሆኑ በዚህ አዋጅ የተዘረጋው ስርዓት ሊከበር ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ይግባኙን ለቦርዱ ሣያቀርቡ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ያቀረቡት መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ የሚያሣይ ከመሆኑም በላይ በሰበር የክርክር ደረጃ መልሣቸውን ለማሻሻል ጥያቄ ባቀረቡበት ወቅትም ይህንኑ ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ምክንያት የሰበር መልሣቸውን ለማሻሻል ያቀረቡት ጥያቄም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 91 አንፃር ሲታይ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ አልፈነዋል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ ቀርቦ ያልታየ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው ውሣኔውን በሰ/መ/ቁጥር 26480 ከተሰጠው የሕግ ትርጉም ጋር አዛምዶ ለመወሰን ሲባል ሲሆን በዚህ የሰበር መዝገብ የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ክርክር የተነሣበት ጊዜ፣ የተከራካሪ ወገኖች የሚገዙበት ሕግ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር የማይገናኝና በመሠረታዊ ነጥቦች ጉዳዮቹ የተለያዩ መሆናቸው ግልጽ ከመሆኑም በላይ አሁን በተያዘው ጉዳይ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ግንኙነት የሌለውን የሰበር መዝገብ ቁጥር 46402 ከመጥቀሱ ውጪ ጉዳዩ የመጨረሻ የአስተዳደር ውሣኔ ያገኘ መሆን ያለመሆኑን፣ ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ስልጣን ያላቸው መሆን ያለመሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44(ጎ) ድንጋጌ አኳያ ታይቶ መፍትሔ ያልተሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባሁኑ የክርክር ደረጃ በዚህ ረገድ ምላሽ የሚሰጠበት ጉዳይ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ባሁኑ የክርክር ደረጃ መታየት ያለበት አቢይ ነጥብ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 መሠረት በተዘረጋው ስርዓት ይግባኛቸውን አሟጠው ጨርሰዋል ወይስ አልጨረሱም? የሚል በመሆኑ ይህን ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ የይግባኝ ስርዓታቸውን ለሚመለከተው አካል አቀርበው ያልጨረሱ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች በአስተዳደራዊ አካላት መታየት ያለበትን የይግባኝ ስርዓት ያልጨረሰ የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ሰራተኞች የዲሲፕሊን ጉዳይ ደግሞ በፍርድ ቤት የሚታይበት አግባብ አይኖርም፡፡

በአጠቃላይ የተጠሪ ይግባኝ ወደ አስተዳደር ፍርድ ቤት የሄደው ስርዓቱን ጠብቆ ይግባኙን ሣይጨርስ በመሆኑ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔና ይህንኑ ውሣኔ ያፀናው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትእዛዝ አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 32(3) እና አመልካች ዩኒቨርሲቲው ያወጣውን ደንብ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 34(4) ድንጋጌዎችን የጣሰና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ. 01247/2004 ታህሣስ 05 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ብይን እንዲሁም ይኸው አካል ታህሣስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 75990 መጋቢት 12 ቀን 2004 ዓ/ም የፀናው ብይንና ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 32(3) መሠረት ዩኒቨርሲቲው ባወጣው የአካዳሚክ ሰራተኞች የዲሲፕሊን ደንብ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 33(4) መሠረት ይግባኙን ማቅረብ ያለባቸው ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ሣይሆን ለዩኒቨርሲቲው ቦርድ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 81215

ጥር 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወጋገን ባንክ ኃ/ፈጅ ጌጡ ፀጋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐ/ህግ ሜሮን አንማው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጉምሩክ ወንጀል ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠበት የአሸከርካሪ ባለቤት ወይም አሽከርካሪ በቅጣት ረገድ ተሸከርካሪው በመንግሥት እንዲወረስ ውሳኔ ከተሰጠበትና የወንጀል ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት ተሸከርካሪው በባንክ መያዣነት መያዙ ከተረጋገጠ በሕግ ፊት ቅድሚያ ሊጠበቅ የሚገባው በወንጀሉ ጉዳይ ተሸከርካሪው ውርስ እንዲሆን የተሰጠው ውሳኔ ነው ወይስ ወይም የመያዣ መብቱ ነው? የሚለውን የሕግ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በመቀሌ ከተማ ማዕከላዊ ፍ/ቤት ሚያዚያ 01 ቀን 2002 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ በክሱ ላይም ንብረትነቷ የአቶ በርሔ ሓጎስ አድሃና የሆነች የኮድ ቁጥር 3-29644 አ.አ አይሱዚ የጭነት መኪና አቶ ብርሔ ሓጎስ ከከሳሽ ባንኩ ሲበደሩ መኪናዋን አስይዘው ብር 90,000.00 /ዘጠና ሺህ/ መበደራቸውንና በየወሩ ብር 2,905.00 እየከፈሉ ክፍያውን በማቋረጣቸው መኪናዋ በፎርክሎጅር ሕግ መሠረት ተሸጣ ለእዳው የሽያጭ ገንዘቡ ገቢ እንዲሆን በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ትዕዛዝ የተሰጠባት መኪና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የመቀሌ ቅርንጫፍ ጠይቆ መኪናዋ ቦንዳ ጭና በመገኘቷ የተወረሰች መሆኑን ለባንኩ የገለፀላቸው መሆኑን ገልጾ በመኪናው ላይ ከማንኛውም ወገን ቅድሚያ ያለው በመሆኑ መኪናውን ተጠሪ እንዲያስረክብ ይወሰንልት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለአመልካች ክስ በሰጠው መልስም ንብረትነቷ የአቶ በርሔ ሓጎስ አድሃና የሆነች ኮድ 3-29644 አ.አ አይሱዚ መኪና ባለንብረቱ በገንዘብ ተከሶ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት እንደሚገኝ፣ የመኪናዋ ባለቤት አቶ በርሔ ሓጎስ አድሃና መስከረም 28 ቀን 2002 ዓ.ም ጣልቃ ገብተው ወጋገን ባንክ በቁጥር 126/ተሰአ/2002 በ3/2/02 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ በማይጨው ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 13144 ሲከራከር ቆይቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ5/02/2002 ዓ.ም በመ/ቁጥር 48628 ተጠቃሹ መኪና በተጠሪ እጅ ሊቆይ እንደሚገባ መወሰኑን ገልጾ በመከራከሩ ፍርድ ቤቱ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተያዘው ጉዳይ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 197/2/ መሠረት አቆይቶ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ግንቦት 05 ቀን 2003 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠቱን የስር ፍ/ቤት ከተገለፀለት በኋላ የተዘጋውን መዝገብ ሲያንቀሳቅስ

www.chilot.me

የአሁኑ ተጠሪ መልሱን ለማሻሻል ጥያቄ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ፈቅዶለት ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው መልሱ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አከራካሪዋ መኪና በወንጀሉ ጉዳይ ለመንግሥት ውርስ እንድትሆን የወሰነ መሆኑንና ይህ ደግሞ አመልካች በመኪናዋ ላይ መብት የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሶ በመጨረሻ ፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ ክሱ መቀጠል የለበትም ሲል ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ጉዳዩ የተለያየ ስለሆነ የመጨረሻ ፍርድ አግኝቷል ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ የመያዣ መብቱ ቅድሚያ እንዲጠበቅለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነችው መኪና በጉምሩክ ወንጀል ምክንያት ለመንግሥት ውርስ እንድትሆን በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠባት መሆኑን በምክንያትነት ይዞ በመኪናዋ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244/2/መ/ መሠረት ሌላ ክርክር የሚቀርብባት አግባብ የለም ሲል ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 32/2/፣ 244/2/ለ/መ/ ድንጋጌዎች ጠቅሶ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም መኪናዋ ለባንክ ብድር ለመያዣነት የተሰጠች ሆኖ እያለ ከመያዣው በኋላ ለተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ለመንግሥት ውርስ እንድትሆን መወሰኑ ለቅድሚያ መብት ጥያቄው ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት የማያስችል መሆኑን ዘርዝሮ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ አንድ ጉዳይ ቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ነው ለማለት መሟላት የሚገባቸውን መመዘኛዎችንና የመያዣ መብትን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች በብድር መያዣነት የያዘው ተሽከርካሪ የኮንትሮባንድ ወንጀል የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲወረስ ቀደም ሲል በመወሰኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 32/2/፣ 244/2/ለ/መ/ መሠረት አመልካች ሌላ ክስ ማቅረብ አይችልም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3059/2/ እና ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 98/3/መ/ እና አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 95/2/ ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በሰጠው መልስም አመልካች የመያዣ መብት ሊጠቀም የሚችለው በፍትሐብሔር ጉዳዮች እንጂ በወንጀል ጉዳዮች ያለመሆኑንና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሠረት በማይጨው ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከፈተው መዝገብም ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ሲያጣ ቆይቶ የመጨረሻ ፍርድ ሲሰጥ የቅድሚያ መብትን መሠረት አድርጎ ክስ መመስረቱ ሕጋዊ አካሄድ ያለመሆኑን ዘርዝሮ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች ለአቶ በርሔ ሓጎስ መስከረም 02 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገና በተወሰነ ጊዜ በሚከፈል የብድር ውል ብር 90,000.00 /ዘጠና ሺህ ብር/ ሲሰጥ ንብረትነቱ የተበዳሪው የሆነውንና አሁን ክርክር ያስነሳውን ቁጥሩ 3-29644 የሆነውን አይሱዙ ተሽከርካሪ በአዲስ አበባ መንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በመያዣነት ማስመዝገቡን፣ ይህ ሆኖ እያለ ግን መኪናው የኮንትሮባንድ እቃ

www.chilot.me

በ24/06/2001 ዓ.ም ጭኖ በመገኘቱ የንብረቱ ባለቤት የሆነው አቶ በርሔ ሓጎስ በተጠሪ መስሪያ ቤት ዓቃቤ ህግ በትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ክስ ቀርቦባቸው ክርክሩ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ከተካሄደ በኋላ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁጥር 48628 በሆነው መዝገብ ግንቦት 05 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቶ በርሔ ሓጎስ ላይ የተጣለውን የሶስት አመት ቀላል እስራትና የብር 5,000.00 የገንዘብ መቀጮ በማጽናት መኪናውን በተመለከተ ደግሞ ለመንግሥት ውርስ እንድትሆን የታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፣ አመልካች በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የወንጀሉ ክርክር ሲካሄድም አመልካች በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ይፈቀድለት ዘንድ ጥቅምት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ጠይቆ የነበረ መሆኑን ሰ/መ/ቁጥር 48628 ከተያያዘው አቤቱታ የተረጋገጠ መሆኑንና አመልካች በስር ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 08782 ያቀረበውና ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ የፍትሐብሔር ክርክርን መሠረት ያደረገ መሆኑን ነው፡፡ እንግዲህ ከዚህ የክርክር ሒደት በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው አከራከሪዋ መኪና ለብድር መያዣነት አመልካች የያዛት የወንጀል ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት መሆኑንና ተጠሪም የአመልካች ክርክርና የዳኝነት ጥያቄ ሥነ ሥርታዊ አይደለም የሚለውን ጥብቅ ክርክር ከማቅረቡ ውጪ በመኪናዋ ላይ አመልካች በሕጉ አግባብ ያቋቋመው የመያዣ ውል የለም በማለት የማይከራከር መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ምላሽ የሚያስፈልገው የሕግ ጥያቄ በመያዣ የተያዘ ተሽከርካሪ ከመያዣው በኋላ በኮንትሮባንድ ወንጀል ምክንያት ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን በፍ/ቤት የመጨረሻ ፍርድ ከአረፈበት ባለመያዣው በተሽከርካሪው ላይ ያለው መብት በምን አግባብ ሊከበር ይገባል? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመያዣ መብት በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር የፍ/ሕ/ቁጥር 2828፣2857/1/ እና 3059 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሕግ አግባብ የተቋቋመው የመያዣ ውል መኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ ይኼው መብት ያለው ሰው ከሌላው ሰው የቀደመ መብት ያለው መሆኑን የተጠቃሾቹ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ያስረዳል፡፡ የፎርክሎዝር ሕጎቻችን ሲታዩ ደግሞ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች እዳው ሳይከፈለው በቀረ ጊዜ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ለተበዳሪው በመስጠት ያለማንም ጣልቃ ገብነት በመያዣ የያዘውን ንብረት በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም ሌላ መያዣ የተቀበለ ባለገንዘብ ከመያዣው ሽያጭ ዋጋ ከሌሎች ባለገንዘቦች ቀድሞ የመቀበል መብት እንዳለውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2857/1/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንጻር አመልካች ለብድር አከፋፈል በመያዣነት በያዛቸው ንብረቶች ላይ የቀደምትነት መብት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም የወንጀል ሕጉን በመተላለፍ ለሚፈፀም ድርጊት ወንጀሉ የተፈፀመበት ንብረት ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን ቢወሰንና ይኼው ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን የተወሰነበት ንብረት በመያዣ የተያዘ መሆኑ ቢረጋገጥ የመያዣ መብት ያለው ሰው መብት በምን አግባብ ሊከበር እንደሚችል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 98 ድንጋጌ በግልጽ የሚያስቀምጠው ድንጋጌ የለም፡፡ የኮንትሮባንድ ወንጀሎችን በተመለከተ በልዩ ሁኔታ የሚገዛው አዋጅ ቁጥር 622/2001 ወይም ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጎችም ቢሆኑ በዚህ ረገድ ግልጽ ድንጋጌ ይዘው አናገኛቸውም፡፡ በሕጉ ማዕቀፍ ያለው ሁኔታ በዚህ መልክ ግልጽ ያልሆነ ከሆነ ደግሞ በሌሎች የሕግ ማዕቀፎች ስር ያለውን አግባብ በመመልከት ጉዳዩን እልባት መስጠት ተገቢ ስለመሆኑ ተቀባይነት ካላቸው የህግ አተረጓጎም ደንቦች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሰሪና ሠራተኛን ጉዳዩ በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት በቅጥር ላይ ከተመሠረተ የሥራ ግንኙነት የሚመነጭ የሠራተኛ የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የእዳ ክፍያ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚኖረው በአንቀጽ 167 ላይ ተመልክቷል፡፡ የዚህ የሕግ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያሳየው በቅጥር ላይ ከተመሰረተ የሥራ ግንኙነት የሚመነጭ ማንኛውንም የሠራተኛ የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የእዳ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚሰጠው የተደነገገ እንደመሆኑ መጠን የሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች አቋም ተራ ገንዘብ ጠያቂዎች /ordinary creditors/ ወይንም እንደ አመልካች በመያዣ ብድር የሰጠ ባለገንዘብ /secured creditors/ ሆኑም አልሆኑ የሠራተኛው የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚሰጠው ስለተደነገገ ከባንክ ጭምር ቅድሚያ መብት ያላቸው ሠራተኞች መሆናቸውን የሚያሳይ ሲሆን በዚህ የሕግ ማዕቀፍ የሕግ አውጪው ለማሣካት ያሰበው የሠራተኞች ክፍያ ጥያቄዎች ከሠራተኛው የዕለት መተዳደሪያ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ሠራተኛው ለሕይወቱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንዲያገኝ ማድረግ ስለመሆኑ ይታመናል፡፡ ሌላው የሕግ ማዕቀፍ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 80 ስር እንደተመለከተው ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የግብር ሰብሳቢው መብት ግብር የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሐብት ላይ ከማናቸውም ሌሎች እዳዎች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል በማለት ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ይህም የሚያሳየው ከግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ሁሉ የመያዣ መብት ያላቸው ሰዎች ቅድሚያ መብት እንዳላቸው የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በሌሎች የሕግ ማዕቀፎች ያለው አጠቃላይ ሁኔታ ከላይ የተገለፀው ሲሆን በወንጀል ሕጉ ላይ ለመንግሥት እንዲወረስ ውሳኔ በሚሰጥበት ንብረት ላይ የመያዣ መብት ስላላቸው ሰዎች መብት ግን በግልጽ የተመለከተ ድንጋጌ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለፀው የወንጀል ሕጉን አይነተኛ ዓላማ ከመያዣ ሕጎች መሠረታዊ ዓላማ እና አዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀጽ 91/2/ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ለጉዳዩ እልባት መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ የመያዣ ውል መሠረታዊ ዓላማ የንግድ እንቅስቃሴ ዋስትና እንዲኖረው ማስቻል መሆኑ የሚታመን ሲሆን የወንጀል ሕጉ ደግሞ ለጠቅላላው ሕዝብ ሠላምና ደህንነት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ባንኮች የሕዝብ መብትና ጥቅም ያላቸው ተቋማት መሆናቸው ክርክር የሚቀርብበት ጉዳይ አለመሆኑ የሚታመን ነው፡፡ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የአገሪቱ የገቢ ማሰባሰብ ስርዓት ሕጋዊ እንዲሆን ማስቻል መሆኑ አዋጅ ቁጥር 578/200 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የግብር እና ታክስ ህጐች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዘበን ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 80 ድንጋጌ ስር መያዣ ያላቸው ሰዎች ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑ በግልጽ ከተደነገገ ግብር አስገቢ መስሪያ ቤት ሕጉን ለማስከበር በሚያደርገው እንቅስቃሴ አጥፊዎችን በፍ/ቤት ሲያስቀጣና አጥፊዎች ወንጀሉን የፈፀሙባቸውን ንብረቶች በሕጉ አግባብ ለመንግሥት እንዲወረሱ በሕጉ አግባብ ከተወሰነ በዚህ ንብረት ላይ መብት ያላቸው ሰዎች መብት ንብረቱ በወንጀል ምክንያት ለመንግሥት ገቢ እንዲሆኑ መወሰኑ ብቻ መያዣ ያላቸው ሰዎች መብት ዋጋ የሚያጣበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑ የሕግ አውጪው ሐሳብ መሆኑን የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች አንድ ላይ ሲታዩ የሚያስረዱን ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች በአከራካሪው ንብረት ላይ ከወንጀል ድርጊቱ በፊት ሕጋዊ የሆነ የመያዣ መብት ያቋቋመ ስለመሆኑ ክርክር ያልቀረበበት ጉዳይ በመሆኑና ይኼው መብት ከመያዣው በኋላ ተበዳሪው በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ውጤት አልባ የሚሆንበት ሕጋዊ አግባብ ሊኖር ስለማይገባ የአመልካች መብት ከተጠሪ ክስና ሕጋዊ ውጤት ቅድሚያ ጥበቃ ሊሰጠው ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አቅጣጫ በማየት እልባት መስጠት ሲገባቸው ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን ድንጋጌዎች በመጥቀስ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌላው እልባት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የተጠሪ መብት በምን አግባብ ሊከበር ይገባል የሚል ነው፡፡ የወንጀል ድርጊቱን የፈፀሙት ግለሰብ በተሸከርካሪው የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈፀማቸው ከተረጋገጠ የውርስ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚገባው በተሸከርካሪው ላይ ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የመያዣ መብት ያለው ወገን መብቱን ቀድሞ እንዲያስከበር ከተደረገ ከመያዣ ባለመብቱ የሚተርፈው የንብረቱ ግምት ወይም በወንጀሉ ምክንያት እንዲወረስ የተባለው ንብረት በመያዣው ውል መነሻ ሙሉ በሙሉ በመያዣ ሰጪው የሚያወድ ከሆነ ተራፊው የመያዣ ንብረቱ ግምት ለመንግሥት የማይመለስበት ወይም ተራፊ ከሌለ ደግሞ ውርስ እንዲሆን በወንጀል ጉዳይ ተወስኖበት የነበረው የንብረቱ ግምት ይህል ድረስ በአጥፊው ሌላ ንብረት ላይ መንግሥት አፈጻጸሙን እንዲቀጥል የማይደረግበት አግባብ ሊኖር አይገባም፡፡ ምክንያቱም አጥፊው በወንጀል ተግባሩ አትራፊ ሊሆን አይገባውምና፡፡ በመሆኑም አመልካች የሚፈልገውን የብድር እዳ የአከራካሪው መኪና ዋጋ ሸፍኖ የሚተርፍ ገንዘብ ካለ ተራፊውን ገንዘብ ለመንግሥት እንዲወረስ ማድረጉ ወይም የሚተርፍ ነገር ከሌለው ንብረቱ ይወረስ ተብሎ በተወሰነበት ጊዜ በነበረው ግምት ያህል በሌላ የወንጀል ድርጊቱ አጥፊ የግል ንብረት ላይ አፈፃፀሙን እንዲቀጥል ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የመያዣ መብት የተቋቋመበት ተሽከርካሪ በኮንትሮባንድ ተግባር ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን ውሳኔ ከተሰጠ መያዣ ሰጪው ቅድሚያ መብት ያለው በመሆኑና ይሄው መብቱ ሊከበርለት የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ስለሚቻል አመልካች በአከራካሪው ንብረት ላይ የቅድሚያ መብት ስላለኝ በዚህ ንብረት ላይ የወንጀል ውርስ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት ያቀረበውን አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉት መቅረታቸው በአግባቡ ስላልሆነ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአቶ በርሔ ሓጎስ አድሃና የሆነች የኮድ ቁጥር 3-29644 አ.አ አይሱዚ የጭነት መኪና የኮንትሮባንድ ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት በአመልካች በሕግ አግባብ የመያዣ መብት የተቋቋመባት መሆኑ ስለተረጋገጠ ለብድር ገንዘቡ መመለሻ ቅድሚያ ልትውል ይገባል ብለናል፡፡ በተበዳሪው ላይ አመልካች የሚፈልገው የብድር መጠን ከመኪናው ዋጋ በታች ከሆነ ተራፊው ገንዘብ ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን፣ መኪናው ላይ የሚመለስ ወይም ተራፊ ገንዘብ ከሌለ ደግሞ መንግሥት መኪናው ይወረስ ተብሎ በወንጀል ጉዳይ ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ የነበረውን ዋጋ ያህል ከአቶ በርሔ ሓጎስ አድሃና የግል ንብረት ላይ አፈፃፀሙን ቀጥሎ ተጠሪ ለመንግሥት ገንዘቡን ገቢ ማስደረግ ይችላል በማለት ወስነናል፡፡
3. የክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 78414

ጥቅምት 07 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነ/ፈጅ ፍሬው ሃይሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1.አቶ ቶላ መገርሣ ቀረቡ

2.አቶ ታምራት ኃይሌ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ግዴታን ባለመወጣት በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ የሲቪል ሰራተኛ በጥፋቱ ምክንያት የመንግስት ንብረት መጥፋቱ ሲረጋገጥ በሕግ ፊት ስላላው የፍትሐብሔር ሓላፊነትን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቸው ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-ተጠሪዎች በአመልካች መስሪያ ቤት በጥበቃ ሰራተኛነት በማገልገል ላይ ሳሉ በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02 አካባቢ ከሚገኘው የአመልካች መጋዘን በሚያዚያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም. ሌሊት የጥበቃ ተረኛ በነበሩበት ወቅት የአመልካች የሆኑ መለያቸው 70×168 PR የሆኑ እያንዳንዳቸው ብር 1977.39 የሚያወጡ አስራ ሶስት ብሪጅስቶን ጎማዎችን ያጠፉ መሆኑንና ተጠሪዎችም የስራ ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት ሳቢያ ለፈፀሙት ወንጀል በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑን ገልፆ ተጠሪዎች የጎማዎቹን ዋጋ ብር 25,706.07 (ሃያ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ስድስት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም በአመልካች መስሪያ ቤት በጥበቃ ስራ ተቀጥረው በሚሰሩበት ጊዜ ንብረቶቹን ለስራ የተረከበው ግለሰብ ሌላ መሆኑን ፣በወንጀል ጉዳይ የመሰከሩት ምስክርም እቃው ጠፋ በተባለበት ወቅት ያልነበሩና ያላዩ መሆናቸው መታወቁን፣መጋዘኑ ዝግ ሁኖ ማደሩ መረጋገጡን፣የገንዘብ መጠኑ ከፍ ያለ በመሆኑ በሰው ማስረጃ ሊረጋገጥ እንደማይችል፣በርክክብ ሰነዱም ለተተኪ የጥበቃ ሰራተኞች በሰላም ማስረከባቸውንና ክሱም በማስረጃ ያለመደገፉን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪዎች በወንጀል የተቀጡ ስለመሆኑ

www.chilot.me

ቢረጋገጠም ጠፉ የተባሉትን ንብረቶች የወሰዱ ስለመሆኑ የወንጀል ውሳኔው እንደማያሳይ፣ንብረት ቢጠፋ ተጠሪዎች የጠፋውን ንብረት ለአመልካች ለመክፈል የተደረገ ስምምነት ወይም ውል የሌለ መሆኑና በጠፉት ንብረቶች ተጠሪዎች የበለፀጉበት ሁኔታ ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡን በምክንያትነት ይዞ ተጠሪዎችን ከክሱ በነጻ አሰናብቷቸዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች የስራ ግዴታቸውን ባለመወጣት በወንጀል ጥፋተኛ ሁነው ተገኝተው እያለና የወንጀል ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ደግሞ ጎማዎቹ መጥፋታቸው ተረጋግጦ እያለ ተጠሪዎች ለፍትሐ ብሔር ክሱ ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ ክሱ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በዕሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙኝ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ምላሽ የሚያስፈልገው የጉዳዩ ጭብጥ ተጠሪዎች በአመልካች መስሪያ ቤት በጥበቃ ሰራተኛነት በማገለገል ላይ ሳሉ ጠፉ ለተባሉ ጎማዎች የስራ ኃላፊነታቸውን አልተወጡም በማለት በወንጀል ከተቀጡ በኋላ ተጠሪዎች የጠፉትን ጎማዎች ግምት እንዲከፍሉ በቀረበባቸው ክስ ጎማዎቹን ወስደው ባለመበልጸጋቸው ወይም ጎማዎቹ ቢጠፉ ለመክፈል ከአመልካች ጋር ያደረጉት ውል ባለመኖሩ የሚከፈሉት ግዴታ የለም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ጎማዎች መጥፋታቸውና የስራ ግዴታቸውን ባለመወጣት በወንጀል የተቀጡ ስለመሆኑ ሳይክዱ ለጎማዎቹ ግምት ኃላፊነት የለብንም በማለት የሚከራከሩት ንብረቶቹን ስለመረከባችን የሚያሳይ ማስረጃ የለም፣መጋዘኑም አልተሰበረም፣ለወንጀሉ ጉዳይ ምስክርነት የሰጠው ግለሰብም ጉዳዩን ሳይመለከት ነው የመሰከረው የሚሉትን ምክንያቶችን በመጥቀስ ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም ወደሚል ድምዳሜ መድረስ የቻለውም የወንጀሉ ውሳኔ ተጠሪዎችን ጎማዎቹን ስለመውሰዳቸው አይሳይም፣ ንብረቶቹ ሲጠፉም ለመክፈል ስምምነት ውል የለም፣ እንዲሁም ተጠሪዎች ስለመበልፀጋቸው የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም በሚሉ ምክንያቶች ነው፡፡

ይሁን እንጂ ተጠሪዎች አከራካሪ እቃዎቹን ለአመልካች መስሪያ ቤት እስከሚያስረክቡ ጊዜ ድረስ በጥበቃ ላይ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ በንብረቶቹ ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት፣ብልሽት ወይንም መጥፋት በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህ ችግር እንዳይከሰት ተገቢውን የጥበቃ ስራ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ይታመናል፡፡ አንድ ሰራተኛ ከአሰሪው መስሪያ ቤት ለስራ እቃዎቹን ሲረከብ የሚፈርመበት ዋናው ምክንያትም ይህንኑ ግዴታውን ካልተወጣ ኃላፊነት ሊከተልበት ስለሚገባውና የእቃዎቹን ግምት በማወቅ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲወጣ ለማስቻል እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 እና በሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች የተካተቱት ድንጋጌዎች ይዘት፣መንፈስና ዓላማ ያስገነዝባል፡፡ በሌላ በኩልም ተጠሪዎች የአመልካችን ንብረቶች ያስቡትን መጋዘን ሲጠብቁ በመጋዘኑ ውስጥ ያሉት እቃዎች እንዳይጠፉ፣እንዳይሰረቁም ሆነ ሌላ ጉዳት እንዳይደርስባቸው

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚጠበቅባቸው በሥራ ሰዓት ሲሆን ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት ከተጠሪዎች ጥንቃቄ ጉድለት ውጪ በሆነ ምክንያት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጭና በተጠሪዎች እጅ ባልነበሩበት ጊዜ የጠፉ ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ ይህንኑ ግዴታቸውን የተወጡ ስለመሆኑ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ማስረጃን መዝነው ያረጋገጡት ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም አመልካች ተጠሪዎች የስራ ግዴታቸውን ሳይወጡ ቀርተው በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ስለመሆኑ የሚሳይ የውሳኔ ግልባጭ ያቀረበና ተጠሪዎቹም ቢሆኑ በወንጀል ጉዳይ ላይ የምስክርነት ቃል የሰጠውን ምስክር ጉዳዩን አይውቅም ብለው ከመከራከራቸው ውጪ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ በስርአቱ መሰረት መለወጡን ገልጸው አልተከራከሩም፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች የስራ ግዴታቸውን ባለመወጣት ጎማዎቹ እንዲጠፉ ስለማድረጋቸው በወንጀል ችሎት ውሳኔ መረጋገጡን በቀላሉ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ቀጥሎ መታየት ያለበት አቢይ ነጥብ በወንጀል ችሎት የተሠጠ ውሳኔ በፍትሐ ብሔር ክርክር ጊዜ ስላላው የማስረጃነት ዋጋ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በወንጀል ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ እና በፍትሃብሔር ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ የሚመዘኑበት መርህ የተለያየ ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ የሚመዘነው ጥብቅ በሆነ መንገድ ሲሆን በፍትሐብሄር ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ ደግሞ ከተከራካሪ ወገኖች መካከል የተሻለ ያስረዳ የትኛው ወገን ነው? የሚለው መለኪያ ተይዞ የማስረጃው ክብደት የሚለይበት ስርአት በመሆኑ የማስረጃ አመዛዘኑ መርህ ከወንጀል ጉዳይ የማስረጃ አመዛዘን መርህ የላላ ነው፡፡ እነዚህ ተቀባይነት ባለቸው የማስረጃ ሕግ ደንቦች የሚታወቁ የማስረጃ አመዛዘን መርሆች አንዱ በሌላው ላይ ስላለው ውጤት ሲታይም በፍትሃብሔር ሕጋችን ቁጥር 2149 ስር የተመለከው ድንጋጌ ምላሽ ይሰጠናል፡፡ ይኸውም በፍትሃብሔር በኩል ጥፋት ተደርጎአል ብሎ ለመወሰን በወንጀል ፍርድ ተከሳሹ ነፃ መለቀቁ ወይም በወንጀል አያስከስሰውም ተብሎ መበየኑ ዳኞቹን አያግዳቸውም በሚል ሓይለ ቃል በያዘ መንገድ ተቀምጧል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበው ከወንጀል ክስ ነጻ መሰናበት የፍትሐብሔር ተጠያቂነትን ቀሪ የማያደርገው መሆኑን ነው፡፡ የድንጋጌው ተቃራኒ ንባብ ሲታይም በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው በፍትሐብሔር ተጠያቂ መደረግ ያለበት መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይህም በወንጀል ጉዳይ የሚቀርበው ማስረጃ በጥብቅ መንገድ የሚመዘን እስከሆነ ድረስ የላላ የማስረጃ ምዝና ስርዓትን ለሚጠይቀው የፍትሃብሔር ጉዳይ በቂ ዋጋ እንደአለው ተደርጎ መወሰድ አለበት የሚለው የማስረጃ ሕግ ደንብ መሆኑን የሚያሳየን ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የተሰጠውን ውሳኔ ይዘት ከላይ ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር ሳያገናዝቡ መወሰናቸው ያላግበብ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪዎች ስለመበልጸጋቸውና ንብረቶቹ ሲጎድሉ ለመክፈል ስምምነት ያለማድረጋቸው ከሃላፊነት ነፃ ለማድረግ በምክንያትነት መጠቀሱም በአመልካች ላይ በሕጉ ያልተጣሉ ግዴታዎች በመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 93529 ህዳር 22 ቀን 2004 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117394 የካቲት 14 ቀን 2004 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች የስራ ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት በአመልካች ጎማዎች ላይ ላደረሱት ጉድለት በአንድነትና በነጠላ ብር 25,706.07 (ሃያ አምስት ሺኅ ሰባት መቶ ስድስት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 74036

መስከረም 23 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ጠበቃ ይልማ አቻሜ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ ነ/ፈጅ መዓዛ ገ/ልዑል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በተጠሪ የታገደ ገንዘብ ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በይግባኝ ደረጃ የታየው በተጠሪ ቦርድ ነው፡፡ በዚህ ቦርድ ይግባኝ ባይ የነበረው የአሁኑ አመልካች ሲሆን የይግባኝ አቤቱታው ዋና ሐሳብም አመልካች የአዋጅ ቁጥር 621/2001 ተግባራዊ መሆን ከመጀመሩ በፊትና ደንብ ቁጥር 168/2001 በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ድርጅቱ በልዩ ልዩ ሁኔታ በህጋዊ መንገዶች ከውጭ ምንጭ ያገኘውን ገንዘብ ኤጂንሲው በቁጥር01/chsa-2980/N1146 ታህሳስ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. በዛፊው ደብደቤ በድርጅቱ የባንክ ሂሳቦች ላይ የጣለውን እገዳ በቦርዱ እንዲነሳ እና በደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 10(2) ድንጋጌን በተጻረረ መንገድ የተከናወነ እገዳ ከምዝገባችን ቀድሞ የተጣለብን መሆኑና ድርጅታችን ያልሰራበት ገንዘብ እንኳን ቢኖር ከለጋሾች ጋር በገባነው ስምምነት መሰረት ሊመለስላቸው ሲገባ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ድርጅቱ ለረዥም ጊዜ በወለድ ያጠራቀመው ገንዘብ በጅምላ በመታገዱ ቦርዱ ይህንኑ አውቆ እገዳውን እንዲያነሳልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በአዋጁ መሰረት የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ መመዝገቡንና የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ደግሞ ከ10 ከመቶ በላይ ከውጭ ገቢ ምንጭ መጠቀም እንደማይችል አዋጁ የሚከለክል መሆኑንና በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከውጭ የሰበሰበው በርካታ ገንዘብ የነበረው ከመሆኑም በላይ አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 በኋላ በርካታ ገንዘብ ከውጭ የገቢ ምንጮች የሰበሰበ መሆኑን፣አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ.ም. በኋላ በቀድሞ ሕጎች የተገኙ መብትና ግዴታዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት አዋጁን የማይቃረኑ ብቻ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 111(1) መደንገጉንና ድርጅቱ ኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ በመሆኑ ገንዘቡን ለተሰማራበት ዓላማ መጠቀም የማይችል መሆኑን፣በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከአገር ውስጥ ምንጭ 90% የሚያመነጭ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ መመዝገቡንና ከመመዝገቡ በፊት ከውጭ ምንጭ የሰበሰበው **ስምንት ሚሊዮን** ብር የነበረው ቢሆንም በአዋጁ መሰረት ገንዘቡን መጠቀም ስለማይችል በኤጂንሲው መታገዱን፣በአዋጁ መሰረት ገንዘቡን ለሌላ ድርጅት ማስተላለፍ ቢቻልም ኤጂንሲው የወሰደው አቋም ግን በየአመቱ **90%** ከአገር ውስጥ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመንጭቶ ለኤጂንሲው ሲያቀርብ ቀሪው 10% ደግሞ ከታገደው ገንዘብ ውስጥ እየተለቀቀለት መንቀሳቀስ እንዲችል የሚያደርግ መሆኑን ዘርዝሮ ይግባኙ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ቦርዱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ የተጠሪ እርምጃ ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 104 በተዘረጋው የይግባኝ ስርዓት መሰረት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የቦርዱ ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ አከራካሪውን ገንዘብ ለማገድ ሕጉ ስልጣን የማይሰጠው መሆኑና እግዳውም የተደረገው አመልካች ድርጅት ሕጉ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በልዩ ልዩ ሁኔታና ሕጋዊ መንገዶች ከውጭ ምንጭ የተገኘ ገንዘብ የሚታገድበት ሕጋዊ አግባብ የለም ብሎ መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 111(1)፣አዋጁን ለማስፈፀም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከወጣው ደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀፅ 10(2) እና የፍትህ ሚኒስትር መጋቢት 16 ቀን 2001 ለተለያዩ የፌዴራልና የክልል አካላት በአዋጁ መሰረት የምዝገባና የድጋሚ ምዝገባ ሥርዓት እስከሚጀምር ድረስ ነባር የበጎ አድጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቀድም ሲል ሲሰሩ በነበረበት ሁኔታ ስራቸውን መቀጠል እንደሚችሉ በመግለጽ ከፃፈው ደብዳቤ አንፃር ለመመርመር ሲባል ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለቦርዱ አቤቱታውን ሊያቀርብ የቻለው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመፅናቱ በፊትም ሆነ የምስክር ወረቀት እስከተሰጠበት እስከ ታህሳስ 06 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ ከውጭ የተሰበሰበውን ገንዘብ ያላግባብ ኤጂንሲው አግዶብኛል፣ይህንን ለማድረግ አዋጁም ሆነ ደንቡ አይፈቅዱለትም፤ስልጣን አይሰጡትም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው የሠበር ቅሬታም ተጠሪ በሕጉ ስልጣን ያልተሰጠው ከመሆኑም በላይ የአዋጁንና የደንቡን ዝርዝር ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍትህ ሚኒስቴር መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈውን ደብዳቤ ይዘት ባላገናዘበ መልኩ እገዳውን ማከናወኑን ዝርዝሮ መከራከሩን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከውጪ የሚሰበሰበው ገንዘብን መሰረት በማድረግ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራት ትርጉም፣ አይነታቸውንና ዓላማቸውን ለይቶ ገደብ ያደረገ ስለመሆኑ የሚያመላክቱ ድንጋጌዎችን ይዞ ይገኛል፡፡ ይህንኑ መለኪያ መሰረት አድርጎም አዋጁ ሶስት አይነት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በአገሪቱ የህግ ማዕቀፍ የሚታወቁ መሆኑን የሚያሳዩ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 2 ንዑስ ቁጥር (2)፣ ንዑስ ቁጥር (3) እና ንዑስ ቁጥር (4) ድንጋጌዎች እንደየ ቅደም ተከተላቸው ሲታዩም የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት፣የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት እና የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት በሕጉ የሚታወቁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማህበራት አይነቶች መሆናቸውን በመጥቀስ ትርጓሜአቸውን አስቀምጠው እናገኛለን፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማህበራት አይነት የሚወሰነው

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረታዊነት የገቢ ምንጭን በመመርኮዝ ስለመሆኑ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ኢትዮጵያዊ ነው ተብሎ ሊመደብ የሚገባው በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት መመስረቱ ብቻ ሳይሆን ከውጪ ምንጮች የሚገኘው የገቢ መጠን ከጠቅላላ ገቢው አስር ከመቶ (10%) የማይበልጥ ሲሆን ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከጠቅላላ ገቢው ከአስር ከመቶ በላይ የሆነውን ገቢ ከውጭ ምንጮች ስለማግኘቱ ከተረጋገጠ የኢትዮጵያ ነዋሪ ተብሎ እንደማይመደብ በአዋጁ አንቀፅ 2(2) እና 2(3) የተቀመጡት የትርጓሜ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ሕጉ በዚህ ረገድ ያስቀመጠው የትርጉም መሰረት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚሰማራበትን ዓላማ ለመለየትም መለኪያ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 14 ድንጋጌ ከላይ ከተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር ተጣምሮ ሲነበብ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡

የአዋጁ አንቀፅ 14(2) የበጎ አድራጎት ማህበራትና ድርጅቶችን ዓላማዎች የዘረዘረ ሲሆን በአንቀፁ ንኡስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ ስር ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ተለይተው የተሰጡትን ዓላማዎችን አስቀምጧል፡፡ በዚህ ንኡስ ድንጋጌ መሰረት ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ብቻ ተለይተው የተሰጡት አላማዎች የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊነትን ማበረታታት፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጾታ እና የሐይማኖት እኩልነት መረጋገጥን ማበረታታት፣ የሕጻናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን ማበረታታት፣ የግጭት አፈታትን ወይም እርቅን ማስፋፋት እና የፍትህና የሕግ ማስፈጸም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት ማጠናከር ስለመሆናቸው በግልጽ ተለይቶ ተደንግጓል፡፡ አዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አይነትና ዓላማቸውን ለይቶ ከማስቀመጡም በላይ አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ እንደሚችል፣ ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች፣ የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች እንዲሁም አዋጁ የሚፀናበትን ጊዜ እንደየቅደም ተከተላቸው በአንቀፅ 109፣110፣111 እና በአንቀፅ 112 ስር አስቀምጧል፡፡ በዚኅ አግባብም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 168/2001 አውጥቶ ከጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን ያደረገ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 621/2001 ደግሞ ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 112 በግልጽ ያሳያል፡፡ የአዋጁ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111 ንዑስ ቁጥር (1) ድንጋጌ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና ግዴታ አዋጁን እስካልተቃረነ ድረስ ብቻ እንደሚቀጥል ሲደነግግ የንዑስ ቁጥር(2) ድንጋጌ ደግሞ ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አለባቸው በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ ደንግጓል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ድርጅት የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሁኖ ታህሳስ 06 ቀን 2002 ዓ.ም. መመዝገቡንና አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከፀናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 በኋላ በርካታ ገንዘብ ከውጭ የገቢ ምንጮች የሰበሰበ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው፤አቤቱታውን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የተጠሪ መስሪያ ቤት ቦርድና ጉዳዩን በይግባኝ እንዲመለከት በአዋጁ አንቀፅ 104(3) መሰረት ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጧቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ አመልካችም በርካታ ገንዘብ ከውጭ ምንጮች አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከጸና በሁዋላ መሰብሰቡን ሳይክድ አንዱ የክርክር ነጥብ አድርጎ የሚያቀርበው ጉዳይ አመልካች ድርጅት አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ በፊትም ሆነ ከወጣ በኋላ በውጭ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ተመዝግቦ አያውቅም፣ዜግነቱም ኢትዮጵያዊ ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ በፊት በማህበርነት ተመዝግቦ ሲሰራ የነበረ ሲሆን አዋጅ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 621/2001 ከወጣ በኋላ በአዋጁ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ዳግም የተመዘገበ በመሆኑ አዋጁ ከጸና በኋላ በአዋጁ ለኢትዮጵያ ማህበር በተፈቀዱት ዓላማዎች መስራት ያለበት በአዋጁ መሰረት በመሆኑ ቀድሞ የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሁኖ ያለማወቁ የአዋጁ ቁጥር 621/2001 አፈጻጸም ላይ የሚያመጣው ለውጥ ስለሌለ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

እንዲሁም አዋጁ በአንቀጽ 108 ስር አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወደ ሌላ በጎ አድራጎት ድርጅት አይነት ሊቀይር ከፈለገ የሚችል ስለመሆኑ የሚሳይ ሲሆን አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 18(3) ድንጋጌ ስር ደግሞ አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ከውጪ ምንጭ ያገኘውን ገንዘብ ይዞ በሕጉ አግባብ ኢትዮጵያዊ ለመባል የማይችል ስለመሆኑ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች በአዋጁ መሰረት እንደገና መመዝገቡ ከውጭ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወደ ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንደተቀየረ አያስቆጥረውም በማለት የሚያቀርበው ክርክር በአዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅት ኢትዮጵያዊ ለመባል መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችና ለኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በሕጉ የተፈቀዱለትን ዓላማዎች አይነት ሳይለይ የቀረበ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደደለም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ነጥብ ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18 ተፈጻሚነት የሚኖረው በአዋጁ መሰረት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ፈቃድ አግኝቶ ከተመዘገበ በኋላ ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጅ አመልካች አዋጁ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ በፊት በሕጉ አግባብ ተመዝግቦ ሲሰራ የነበረ ሲሆን አዋጁ ከወጣ በኋላ ዳግም ተመዝግቦ በአዋጁ ለኢትዮጵያዊ ድርጅት ወይም ማህበር የተፈቀዱትን ዓላማዎችን ይዞ እንደሚንቀሳቀስ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አዋጁ ከፀናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ከውጭ ምንጭ ከ10% በጀት በላይ መሰብሰብ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን የአዋጁን አንቀጽ 2(2)(3)፣14(5) እና የደንብ ቁጥር 18(3) ድንጋጌዎችን አንድ ላይ በምናነብበት ጊዜ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክርም የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ ስላላገኘን የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ገንዘቡ በችሮታ ጊዜ የተሰበሰበ በመሆኑ አዋጁንና ደንቡን ይቃረናል ሊባል አይችልም በማለትም ክርክር አቅርቧል፡፡ለዚሁ ክርክሩ መሰረት የሚያደርጋቸው የሕግ ድንጋጌዎቹም የአዋጁ አንቀፅ 111(1) እና የደንቡን አንቀጽ 10(2) ድንጋጌን ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 111 ርዕሱ "የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች" በሚል የተቀመጠ ሲሆን ከላይ እንደተጠቀሰው ንዑስ አንቀፅ አንድ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና ግዴታ አዋጁን እስካልተቃረነ ድረስ እንደሚቀጥል ሲያስቀምጥ፣ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ ያለባቸው ስለመሆኑ በአስገዳጅ መልኩ ደንግጓል፡፡ የደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 10(2) ደግሞ የድጋሚ ምዝገባ ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከጸናበት ጊዜ ከአንድ አመት በኋላ ይሆናል ሲል አስቀምጧል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩ ቅራኔ ያላቸው ናቸው ለማለት የሚቻል ሳይሆን እርስ በእርሳቸው የተጣጣሙ ናቸው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በመሸጋገሪያ ጊዜው ውስጥ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በሕጉ ከተመለተከው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበሰብ የሚፈቀድበት አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም የመሻጋገሪያ ድንጋጌ አይነተኛ አላማ ቀደም ሲል በነበሩ ሕጎች የተገኙ መብቶች እና ግዴታዎች አዲስ ሕግ ሲወጣ አከራካሪ

www.chilot.me

እንዳይሆኑ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ግልጽ ምላሽ ለመስጠት ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩም ቀደም ሲል ለተገኙት መብቶችና ግዴታዎች ተፈፃሚነት ያጣው ሕግ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ሳይሆን በአዲሱ ሕግ እንዲሸፈኑ መደረጉን የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡ እንዲሁም ቀደም ሲል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባ የሕግ ማዕቀፍ የሌለውና ከአዋጅ ቁጥር 621/2001 ዓላማ ጋር አንድ ላይ የማይሄድና የማይጣጣም በመሆኑና እንደአይነታቸውና ባሕርያቸው በተለያዩ ድንጋጌዎች ስለሚገዙ አዋጁ በወጣ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አስፈላጊ መሆኑ መደንገጉ አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ በአዋጁ የተከለከሉ ዓላማዎችን በቀድሞው ሕግ መሰረት ማከናወን መቀጠል የማይቻል ስለመሆኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም. የፍትሕ ሚኒስቴር ፃፈ የሚለውን ደብዳቤ ይዘት ጠቅሶ ያቀረበውን ክርክር ስንመለከተውም የደብዳቤው ይዘት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መፅደቁን አስታውሶ መንግስት በአዋጁ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የሚመዘግብና የሚከታተል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጂንሲ ለማቋቋም በሂደት ላይ ያለ ስለመሆኑ ጠቅሶ ኤጂንሲው ተቋቁሞ በአዋጁ መሰረት የምዝገባና የድጋሚ ምዝገባ ሥርዓት እስከሚጀምሩ ድረስ ነባር የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከዚህ በፊት ይሰሩ በነበሩበት ሁኔታ እየሰሩ መቀጠል እንደሚችሉ ለሚመለከታቸው የአስፈጻሚ አካላት ስርኩላሩ መተላለፉን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ሰርኩላር ይዘቱ የሚስገነዝበው የአዋጁን አፈጻጸም ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ኤጀንሲው እስከሚቋቋም ድረስ የሚመለከታቸው አካላት ሊያከናውኑ የሚገባቸውን ተግባራት የሚያሳይና አዋጁን ለማስፈፀም ይቋቋማል የተባለው ኤጀንሲ ከተቋቋመ በኋላ ግን ሁሉም ነገር በአዋጁ መሰረት መሰራት ያለበት መሆኑን የሚያስረዳ በመሆኑ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 2(2) እና 111(2)፣በደንቡ አንቀጽ 10(2) ድንጋጌዎች መሰረት በችሮታው ጊዜ የራሱን አደረጃጀት በማስተካከል ያልተጠናቀቁ ስራዎችን ለማጠናቀቅ እንዲችል ሕጉ በሰጠው ችሮታ ጊዜ መንቀሳቀስ የሚገባበት እንጂ ገቢውን ከአዋጁ ይዘትና መንፈስ ውጪ እንዲሰበስብ እድል የሚሰጠውና የአዋጁን አላማ ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ ተፈጻሚ የሚሆን አይሆንም፡፡

አመልካች የአንድ ድርጅት ወይም ማህበርን ገቢ በማየት ዓላማ ሊወሰን አይችልም፣ዓላማው የሚወሰነው በመተዳደሪያ ደንቡ ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር ስንመለከተውም የድርጅቱ ወይም የማህበሩ ዓላማ በመተዳደሪያ ደንቡ መጠቀስ ያለመጠቀሱ በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 2(2)(3)(4)) እና 14(5) ድንጋጌዎች መሰረት ዋነኛው ነጥብ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከውጪ የሚያሰባስበው የገንዘብ መጠን ከገቢው 10% በላይ ከሆነ በሕጉ ተለይተው ለኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበራት በተሰጡ ዓላማዎች ላይ መሰማራት አይችልም ተብሎ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

ተጠሪ በሕግ ተቋቁሞ አዋጅ ቁጥር 621/2001 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በሕጉ አግባብ ስልጣን የተሰጠው አካል ያወጣቸውን ደንቦች ለማስፈጸም የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 6 ስር ከተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባራት ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን መፈጸም እንደሚችል በተጠቃሹ አንቀፅ ፊደል "ቸ" ስር ከተቀመጠው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ማየት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 90 መሰረት ለኤጀንሲው የተሰጠውን ስልጣን ስንመለከተው በተጠቃሹ የአዋጁ ድንጋጌ የንብረት ጥበቃ ወይም እገዳ ተግባር የሚፈፀመው ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም በማህበር መፈጸሙ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት ያሳያል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን ገንዘብ ያገደው በአዋጁ አንቀፅ 90 መሰረት ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር በአመልካች ተፈጽሟል በሚል አይደለም፡፡ ይልቁንም

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ዓላማ አመልካች ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚያደርገው ሁኖ እያለ አዋጁ ከጸናበት ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ ከውጪ ምንጭ በርካታ ገንዘብ ሰብስቧል፣አመልካች ዓላማው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ሁኖ እስከተመዘገበ ድረስ ይህንኑ ከውጪ የተገኘውን ገንዘብ ለዓላማው ማስፈፀሚያነት ሊያውለው አይችልም በሚል ነው፡፡ እንዲህ አይነት ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ መፍትሔው ምን እንደሆነ አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18 ምላሽ ይሰጣል፡፡ ይህ የደንቡ ድንጋጌ በኢትዮጵያ ውስጥ በአዋጁ መሰረት ፈቃድ አግኝቶ የተመዘገበ የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በበላይ አካሉ ውሳኔ ወደ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ሊቀየርና የምስክር ወረቀት ሊያገኝ እንደሚችል በንዑስ ቁጥር አንድ በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን ማንኛውም የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ሲለወጥ በባለቤትነቱ ስር ያለን ከውጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት ለተለወጠው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሊያስተላልፍ እንደማይችል፣በንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ መሰረት ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ለመለወጥ ያመለከተ የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የነበረው ከውጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት በድርጅቱ የበላይ አካል ወይም **በኤጀንሲው ውሳኔ** ተመሳሳይ ዓላማ ላለው የውጪ የበጎ አድራጎ ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተላለፍ እንዳለበት የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለትና ሶስት እንደ የቅደም ተከተላቸው ሓይለ ቃልን በያዘ አቀራረፅ ያስቀመጡት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካችን አይነት የበጎ አድራጎት ድርጅት ህጉ ከመፅናቱ በፊትም ሆነ በኋላ ከሕግ ውጪ ከውጭ ምንጭ የሰበሰበውን ገንዘብ ተጠሪ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተመሳሳይ ዓላማ ላለው ድርጅት ወይም ማህበር ማስተላለፍ እንዳለበት የደንቡ አንቀጽ 18(3) በግልጽ ያሳያል፡፡ እንግዲህ በአመልካች የተፈፀመው ተግባር ላይ ተጠሪ በሕጉ ሊያደርገው ይገባ የነበረው ገንዘቡን ከማገድ የበለጠ ውጤት ያለውን፤ ገንዘቡን ለሌላ ተመሳሳይ ድርጅት ወይም ማህበር ማስተላለፉን የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በህጉ ከተቀመጠው ያነሰ እርምጃ ተጠሪ መውሰዱ አመልካችን የጠቀመ ነው ከሚባል በስተቀር ለተጠሪ በሕግ ከተሠጠው ስልጣን አድማስ ውጪ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ሊሆን የሚችለው በሕጉ ተለይቶ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር ውጪ ተፈጽሞ ሲገኝ እንጂ በውጤቱ በሕጉ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር ከሚያስከትለው ያነሰና ፍትሓዊ ነው የሚለውን አስተዳደራዊ እርምጃ በመፈፀሙ ተግባሩ ከስልጣኑና ከተግባሩ አድማስ ውጪ ነው ለማለት የሚያስደፍርበት ሕጋዊ ምክንያትና አግባብ የለም፡፡ በሕግ ያልተከለከለን ተግባር መፈፀም ተቀባይነት የማያገኝበት አግባብም የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ስልጣንና የተወሰደውን እርምጃ መሰረት አድርጎ ያቀረበው ክርክርም ከአዋጁ አንቀጽ 90 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም በደንቡ አንቀጽ 18(3) ስር ከተመለተከቱት እርምጃዎች ውጤት አኳያ ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለልም የአመልካች ተግባር ከአዋጅ ቁጥር ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 2(2፣3፣እና 4)፣6፣ 14(5)፣90፣111 እና 112፣እንዲሁም ከደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 10(2)፣18(3) እና 36 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይ ገንዘቡ በተጠሪ እንዳይታገድ የሚያደርግበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ ተጠሪ ገንዘቡን ማገዱም ሆነ አመልካች ከአገር ውስጥ የገቢ ምንጭ 90% ያህሉን መሰብሰቡ እየተረጋገጠ ከታገደው ገንዘብ ውስጥ 10%

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲለቀቅለት መደረጉ ሕጋዊ ከሚባልና በውጤቱም ፍትሃዊ ነው ተብሎ ከሚደመደም በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በተጠሪ ቦርድ ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 108144 ጥቅምት 13 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ውሣኔው በ9/02/05 ዓ.ም. ተነበበ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሃሣብ ልዩነት

እኔ በአራተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው የህግ ትርጉምና ውሣኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡ በዚህ መዝገብ የቀረበው የህግ አተረጓጉም ጥያቄና ክርክር በሰበር መዝገብ ቁጥር 75877 ከቀረበው የህግ አተረጓጎም ጥያቄና ክርክር ጋር ተመሣሣይነት ይዘት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም የሥራ ባለደረቦቼ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 እና ደንብ ቁጥር 168/2002 ድንጋጌዎችን በመተርጎም ሒደት የምለይባቸውን መሠረታዊ ምክንያቶች በሰበር መዝገብ ቁጥር 75877 በዝርዝር የፃፍኩ በመሆኑ በዚህ መዝገብ በድጋሚ መፃፍ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ አብላጫው ድምጽ ከሰጠው የህግ ትርጉም ውሣኔ የምለይባቸውን ዝርዝር ምክንያቶች ለመረዳት በሰ/መ/ቁ. 75877 የፃፍኩትን ልዩነት ሃሣብ ማንበብ እንደሚያስፈልግ እየገለጽኩ ተጠሪ አመልካች በድጋሚ ከመመዝገቡ በፊት ከውጭ ምንጭ ያሰባሰበውን ገንዘብ ለማገድ የሚያስችለው ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 621/2001 እና ደንብ ቁጥር 168/2002 አልተሰጠውም በማለት በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅጽ 13 (በ2004 ዓ.ም. የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ)

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍትሐብሔር ሥነ- ሥርዓት				1
1	በሥር ፍ/ቤት ቀርቦ የተሰጠ ውሣኔ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቀርቦ በተወሰነ መልኩ ተሻሽሎ መወሰኑ በጉዳዩ ቅር የተሰኘ ወገን ውሣኔውን አስመልክቶ ለሰበር ችሎት የሚያቀርበው አቤቱታ የመጨረሻ ፍርድ ያልተሰጠበት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የትግራይ ብ/ክ/መ/ አዋጅ ቁ.93/97 አንቀፅ 30(2)(ሀ), አዋጅ ቁ.49/94 አንቀፅ 16(ለ) እና 17	61480	አቶ ገ/እግዚአብሔር ከበደ እና ወ/ት ሠላማዊት ወ/ገብርኤል	ጥቅምት 22/2004	2
2	• የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በሰበር ችሎት የተሻረ ሲሆን በውሣኔው መብቱ የተነካ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት ለሰበር ችሎት መቃወሚያ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ፣ መብታቸው የተነካ ወገኖች ሊስተናገዱ ስለሚችሉበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10	31264	ወ/ሮ እመቤት መኮንን እና ወረዳ 20 ቀ. 29 አ/ጽ/ቤት ተቃዋሚ አቶ አይናዲስ ገዳሙ	ህዳር 06/2004	5
3	በተከሳሽ ወይም ከሳሽ ሞት ምክንያት በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ የነበረ ክርክር በተቋረጠ ጊዜ ክርክሩ በወራሾች አማካኝነት ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታና በህጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ፣	62452	እነ የሚች ወንድሙ ደምሴ ሚስትና ወራሾች	ጥር 03/2004	7

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.49(1), 55(2)		(ሶስት ሰዎች) እና አቶ በርሄ ንስራን		
4	በንብረት ላይ በፍ/ቤት የተሰጠን የእግድ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158 መሠረት መልሶ ለማንሳት ስለሚቻልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158	71316	የኢት/ያ ንግድ ባንክ እና ለገሠ ጌታሁን	ግንቦት 9/2004	13
5	በአንድ ጉዳይ በክሳሽነትና በተከሳሽነት በተሰየሙ ወገኖች መካከል በተካሄደ ክርክር የተሰጠ ፍርድ ጋር በተያያዘ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ወገን ወይም እርሱ ባልተካፈለበት ሁኔታ በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር መብቱ/ጥቅሙ የሚጐዳበት ሰው በክርክሩ በመግባት መብቱን በህግ አግባብ ሊያስከብር ስለሚችልበት ሁኔታ፣ • ከላይ በተመለከተውና ባልተካፈልኩበት ክርክር የተሰጠ ፍርድ ሥርዓትን ባለመከተል የተሰጠ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ፍርዱ ዋጋ እንዲያጣ ወይም አንዱ የተሰጠ ፍርድን ወደ ጐን በመተው በሌላ ጊዜ በሚሰጥ አዲስ ፍርድ እንዲቀየር ለማድረግ የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህቁ. 41, 358, 212	67127	አቶ አበራ ሁንዴ እና ፍንፍኔ የደን ደርጅት	ሰኔ 08/2004	16
6	በበላይ ፍ/ቤት ትዕዛዝ አንድን በነጥብ ወደ ሥር ፍ/ቤት የተመለሰ ጉዳይ አይቶ እልባት እንዲሰጥበት የተላለፈለት ፍ/ቤት የተመለሰውን ጉዳይ የበላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ መሠረት በማድረግ በአግባቡ ውሣኔ ለመስጠት ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍብ/ሥምሥ/ህ/ቁ. 343(1)	72189	አቶ ካሳዬ ያደቴ እና ሲኖር ፍራንችስኮ ቬንሲያ	ሰኔ 18/2004	20
7	• በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ ውስጥ የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች የሚታዩበት አግባብ በፍ/ብ/ህጉ በተመለከቱት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ድንጋጌዎች ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 መሠረት በሌለሁበት የተሰጠ ፍርድ ይነሳልኝ በሚል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በህጉ የተመለከተው የአንድ ወር ግዜ ገደብ በፍታብሔር ህጉ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስሌት መሠረት ሊሰላ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1848, 1856(2)	76601	አቶ ሽመልሽ አማረ እና አቶ አማረ መኮንን	ሰኔ 18/2004	23

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78, 195				
8	ግዜው ያለፈበት የይግባኝ አቤቱታን ማስፈቀጃ በመቀበል ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በበላይ ፍ/ቤት በተካሄደ ክርክር የማስፈቀጃ አቤቱታው ተቀባይነት ማግኘቱ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ ወሣኔ የተሰጠ እንደሆነ የስር ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ፍርድ ተፈፃሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 325,326,349	74785	አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ሐምሌ 03/2004	27
9	• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ በግልጽ ያልሸፈናቸውና ለፍ/ቤት የቀረቡ ጉዳዮችን አካሄድ (አሰራር) በተመለከተ ህጉ ከመውጣቱ በፊት ተጽፈው በሥራ ላይ የነበሩ አግባብነት ያላቸው ህጐች እንደ አግባብነቱ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ስለመሆኑ፣ • ክስ አቅርቦ ለከሳሽ የሚላከውን መጥሪያ ከፍ/ቤት ወጪ አድርጐ ነገር ግን ለተከሣሽ መጥሪያውን ከማድረሱ በፊት ክሱ እንዲቋርጥ ያደረገ ከሣሽ ለዳኝነቱ የከፈለው ገንዘብ በመሉ እንዲመለስለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • በፍ/ቤት ክስ የመሰረተ (ያቀረበ) ወገን የክስ መሰማቱ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ክሱን በማንሣት መዝገቡ እንዲዘጋ ያደረገ ከሆነ ለዳኝነት ከከፈለው ገንዘብ ለፍ/ቤቱ በኪሣራ ስም የሚቀነሰው ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ ሊመለስለት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 232(1) (ለ) ,245(4),3,278(1) የህግ ክፍል ማስታወቂያ 177/74 አንቀጽ 11	76786	አቶ አልዩ ተክሉ እና አቶ መስፍን ስለሺ	ሐምሌ 03/2004	31
10	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 የተመለከተው የጣልቃ ገብነት ሥርዓት አፈፃፀም	77322	የደብረ ዘይት መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያ እና እነ እሌኒ ዓለማየሁ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 17/2004	34
11	በተከራካሪዎች ፈቃድ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ በህግ ስልጣን ባላቸው የሽሪዓ ፍ/ቤቶች ክርክር ተካሂዶ በፍርድ ያለቀን ጉዳይ በተመለከተ እንደ አዲስ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ሊቀርብ የማይችል ስለመሆኑ	58119	ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል እና	ጥቅምት 21/2004	37

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ.188/92 አንቀፅ 4(2), 5(4) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 78(5), 34(5)		አቶ ዓሊ በከር		
12	በህጉ አግባብ ሊሟላ የሚገባው የዳኞች ቁጥር ባልተሟላበት ሁኔታ የሚሰጥ ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ እንደተሰጠ የማይቆጠርና ህጋዊ ውጤት ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73,337	73696	ወ/ሪት ሃና አበባው እና አቶ አብዱ ይመር	ሚያዝያ 9/2004	39
	አሠሪና ሠራተኛ				43
13	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሠራተኛን ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የቅጥር ሁኔታ ለመወሰን የተቋሙን ድርጅታዊ አቋም ብቻ መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 9,10	67533	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ በረከት በለጠ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 08/2004	44
14	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ አስቀድሞ በሥራ ላይ የነበረን የድርጅት መዋቅርን መሰረት በማድረግ ሆኖ ጉዳዩ ለአፈፃፀም በቀረበ ጊዜ የድርጅቱ መዋቅር የተለወጠ መሆኑ ከተረጋገጠ ፍርዱ ሊፈፀም የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.392(1),(2)	69471	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን እና አቶ ጥበቡ ተሰማ	ጥቅምት 20/2004	46
15	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ ለሠራተኛ የሚከፈል የሥራ ስንብትና ካሣ ክፍያ ላይ የገቢ ግብር ሊቀነስ የሚገባ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 13, 10(2), 2(10) ደንብ ቁ.78/94	61549	የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን እና ወ/ሮ ብርቁሣ አብራሂም	ህዳር 06/2004	48
16	አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ከአሰሪው ፈርሞ የተረከበው ንብረት በጠፋ ጊዜ ተጠያቂ የሚሆነው ንብረቱ በእጁ እያለ እንዳይጠፋ ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረገ ወይም ለንብረቱ መጥፋት የሠራተኛው ቸልተኝነት መኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ	69179	የኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ ባለስልጣን እና	ህዳር 04/2004	50

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ.515/99 አንቀፅ 65		አቶ ታሪኩ ጫኔ		
17	በህግ ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል በግልጽ በተላለፈ መመሪያ መሰረት የሠራተኛን የሥራ ውል ያቋረጠ አሠሪ የሥንብትና የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሚገደድበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 28, 12(1)(ሀ)	69125	ወ/ሪት ሠላም ተስፋዬ እና አልካን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	ታህሣሥ 02/2004	53
18	ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ አሰሪና የሥራ መሪ የሆነ ሰው መካከል የሚፈጠርን አለመግባባት ለመፍታት ተፈፃሚነት ያለው ደንብ (መመሪያ) በስምምነት የተዘጋጀ እንደሆነ ይሄው ደንብ ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ	60489	አቶ አምባዬ ወ/ማሪያም እና የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት	ጥር 14/2004	55
19	• ከአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ጋር በተያያዘ ሰራተኛው ከሥራ ሲሰናበት ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት አላስረከበም በሚል ሰራተኛው ሊከፈለው ከሚገባው ክፍያ ቀንሶ ለማስቀረት የሚቻለው በሰራተኛው በኩል ዕዳ ስለመኖሩ መተማመን ላይ ሲደረስ ስለመሆኑ • ሰራተኛው ከተረከበው ንብረት አለመመለስ ጋር በተገናኘ ዕዳ ስለመኖሩ በግራ ቀኙ መካከል ክርክር (አለመግባባት) ያለ እንደሆነ አሰሪው ጉዳዩን በፍ/ቤት አቅርቦ መብቱን ማስከበር ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 36-38, 59(1), 53(2)(1)	67382	እነ አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች) እና አቶ አርጋው አበበ	ጥር 04/2004	58
20	• ከአምስት አመት በላይ ያገለገለ ሰራተኛ የጡረታ መዋጮው ተመላሽ የተደረገለት መሆኑ የጡረታ አበል ተጠቃሚ እንደሆነ ተቆጥሮ የስራ ስንብት የሚያስከለክለው ስላለመሆኑ • በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ የጡረታ "አበል" በሚል የተመለከተው ሀረግ የጡረታ መዋጮ ተመላሽንም የሚጨመር ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ.345/95 አንቀፅ 2(13),(14) አዋጅ ቁ.494/98 አንቀፅ 2(1)(ሸ)	73258	እነ ወ/ሮ አበራሽ ፈይሳ (ሶስት ሰዎች) እና ጂ ሰቭን ንግድና ኢንዲስትሪ ኃ.የተ.የግል ማህበር	ጥር 16/2004	61
21	• ሠራተኛ በሥራ ቦታና በሥራ ወቅት ሆን ብሎ በራሱ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት	67201	አቶ ምትኩ ኃይሉ	የካቲት	64

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አሰሪው ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ • የአደጋ መከላከያ ደንቦችን በመጣስ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በአደንዛዥ ዕፅ አስክሮ በሥራ ላይ በመገኘቱ በሠራተኛ ላይ የደረሰ ጉዳት ሆን ተብሎ እንዳደረሰ የሚቆጠርና አሠሪው ጉዳቱን ለመካስ የማይገደድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 96(ሀ)(ለ), 96(1)		እና አቶ መስፍን ጥላሁን	26/2004	
22	ከስራ ክርክር ጋር በተገናኘ በዲሲፕሊን ተከስሶ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ሠራተኛው በፈፀመው የማታለል ድርጊት ጥፋተኛ የተባለ መሆኑን መነሻ በማድረግ የተሰናበተ ሰራተኛ የዲስፕሊን ኮሚቴው አባላት በሥራ ክርክር ሰሚው አካል ፊት ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ስላልሰጡ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ሐ) እና (መ)	73881	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ደቡብ ሪጅን እና አቶ ተፈራ ሹና	የካቲት 27/2004	67
23	የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ የመንግስት ሠራተኛ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰና ጥፋተኛ ተብሎ በጽኑ እስራት ቅጣት በተቀጣ ጊዜ የጡረታ መብቱ የሚቋረጥ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 95/1967 አንቀጽ 34 አዋጅ ቁ. 345/1995 አንቀጽ 52(2) እና (3) አዋጅ ቁጥር 209/1955	50590	ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ በርገኔ ኢንኮ	መጋቢት 28/2004	70
24	ከሚሠራበት ድርጅት ብድር ወስዶ ከፍሎ ያላጠናቀቀ ሠራተኛ በገዛ ፈቃዱ ሥራ ሲለቅ ተከፍሎ ያላለቀው ብድር ከሚያገኘው ፕሮቪደንት ፈንድ ሊቀንስ የሚችለው ሠራተኛው ዕዳ እንዳለበት ያመነ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 59(1)	71507	ሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃ.የተ.የግል ማህበር እና አቶ ሰይፉ ተፈሪ	መጋቢት 10/2004	73
25	አንድ ሠራተኛ በአሠሪው በንብረት ላይ ጉዳት አደረሰ የሚባለው ንብረቱ የአሰሪውን ወይም ከአሠሪው ድርጅት ሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(ሸ)	74400	ግዮን ኢንዱስትሪያልና ኮሜርሺያል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ኃይሉ	ግንቦት 07/2004	76

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ናርዬ		
26	ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች (መያዶች) በስራቸው የሚቀጥሯቸውን ሠራተኞች በተመለከተ አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ሕጎች የሚዳኙ መሆኑን በመግለጽ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ያደረጉ እንደሆነ በድርጅቶቹ እና በሰራተኞቻቸው መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በስምምነቱ መሠረት እልባት ሊያገኝ የሚገባ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 3(3)	67996	ሳሳካዋ ግሎባል 2000 ፕሮጀክት እና አቶሸዋድንበር ደቻሳ	ሰኔ 19/2004	79
27	በሥራ ላይ በደረሰ ጉዳት በሞት ምክንያት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሠራተኛው የጉዳት ካሣ በመድን ፖሊሲ ተሸፍኖ ሲገኝ የካሣ ክፈያውን ሊጠይቁ ስለሚችሉ ወገኖች፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 110(1)(2),134(2),128,129,133 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 842, 1732, 1735, 1736, 1734	72645	የኢትዩጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ክፍለዩሐንስ ተሰማ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 03/2004	82
28	አሰሪ ሲሰራው የነበረው ሥራ በመቀነሱ ወይም በመቀዝቀዙ ምክንያት ካሉት ሠራተኞች መካከል ከአሥር ፐርሰንት በታች የሆኑትን የሥራ ውል ሚቋረጡ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሥራ ውላቸው የሚቋረጥና ሥራ የሚቀጥሉትን ሠራተኞች ለመለየት ሊከተለው ስለሚገባ አካሄድ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 28(8), 29(3)	74230	አቶ አስቻለው ጌታሁን (አስር ሰዎች) እና አልፋ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ	ሐምሌ 17/2004	90
29	የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ ውስጥ "እንደ ጥፋቱ ክብደት በሥራ ቦታው አምቧንሮ ወይም ጠብ አጫሪነት ተጠያቂ መሆን..." በሚል የተመለከተው ሀረግ ሊተረጐምና ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ፣ "የሥራ ቦታ" የሚለው ሀረግ አሰሪው (ተቋሙ) ለሥራና ለመኖሪያ በሚል ለሰራተኞች የሚሰጠውን ቦታ እንዲሁም ተፈፀመ የተባለውን የአምባንሮ ድርጊት ከሥራ ሰዓት ሙጪ መሆኑንም ጭምር የሚያካትት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ረ),97,4	79105	ወርልድ ቪሽርን ኢትዮጵያ እና አቶ መዘምር መክብብ	ሐምሌ 03/2004	94

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

30	አሰሪ ደንብን ባልጠበቀ መንገድ ሠራተኛው ወደ ሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሰራ ተመድቦ ፈቃደኛ አልሆነም በሚል ሠራተኛውን ማሰናበቱ ተገቢ ስላለመሆኑ	77113	አኪኮ ቦዲዋይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ገረመው አበበ	ሐምሌ 27/2004	97
31	በሥራ ላይ ንብረትንም ሆነ ህይወትን ለአደጋ የሚያጋልጥ ድርጊት መፈፀም ህገ ወጥ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1)(ቀ) 14(2)(ሀ)	79096	ሪመምበር ዘ ፕረሰት ኮሚዩኒቲ እና ዘውድነሽ ማሞ	ሐምሌ 20/2004	100
32	በሥራ ላይ ከሚደረስ አደጋ ጋር በተያያዘ አደጋው የደረሰው ከሥራ ሰዓትና ከሥራ ቦታ ውጪ ከሥራው ጋር ግንኙነት በሌለው አጋጣሚ እና ከአሰሪው ትዕዛዝ ሳይኖር እንደሆነ አሰሪው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 95, 96, 97	68138	ወ/ሮ ጥሩሰው ጥላሁን (ሶስት ሰዎች) እና ሲቪል ወርክስ አማካሪ መሃንዲሶች ኃ/የተ/የግል ማህበር	ጥር 17/2004	103
33	በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች ህግ መሠረት አንድን ጉዳት በሥራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብ (ሁኔታ) እና በጉዳቱ ሞት በተከሰተ ጊዜ የጉዳት ካሣ ለሟች ቤተሰብ የሚሰጥበት አግባብ፣ አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀጽ 47(2)(ሐ) አዋጅ ቁ. 262/94 አንቀጽ 46(2)(5)(ለ)	61717	ወ/ሮ አበበች አዱኛ በራሳቸውና በህጻን ረቂቅ ተክሉ ስም እና በስራና ክተማ ልማት ሚኒስቴር የተንዳሆ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት	ጥር 15/2004	111
34	የሠራተኞች ስንብት ተከትሎ አሰሪ የሆነ አካል የከራካሪ የሆኑ ክፍያዎችን በተመለከተ ሊያዘገይ እንደሚችልና ክፍያ በማዘግየት በሚል ሊቀጣ የሚችለው ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ሳይኖር ወይም የሚያከራክር ክፍያ ሳይኖር ያለአግባብ ያዘገየ እንደሆነ	74636	ኢትዮ ቴሌኮም እና ትዕግስት	ሰኔ 21/ 2004	116

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 37, 38, 36		ሙሉዓለም (15 ሰዎች)		
	ቤተሰብ				120
35	በፍርድ ቤት የተቋቋመ የውርስ አጣሪ አበል መጠን ሊወሰን የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ 959, 946-1125	69153	ብርሃኑ ከፍያለው እና እነ ወ/ሮ ሮማን ይርጋ (11 ሰዎች)	ጥቅምት 06/2004	121
36	የጋብቻ ፍቺን በተመለከተ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ከሌለ በስተቀር የባልና ሚስት የጋራ ንብረትን አስመልክቶ የፍቺ ውጤት የሆነውን የክፍፍል ጥያቄ በፍ/ቤት ማቅረብ አይቻልም ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 76	61357	አቶ ፍቅሬስላሴ እሸቱ እና ወ/ሮ ዋጋዬጋይም	ህዳር 22/2004	124
37	በባል ወይም በሚስት ለጋራ መተዳደሪያቸው በሚል ከሚካሄድ የንግድ ሥራ ማስኬጃ ጋር በተያያዘ የተገባ ዕዳ የተጋቢዎች የጋራ እዳ እንደሆነ የሚቆጠር ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ.19 የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92, አንቀፅ 70	68190	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ እመቤት ቱርፌ	ታህሣሥ 05/2004	127
38	ከባልና ሚስት የጋራ ንብረት ጋር በተገናኘ በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ አማካኝነት ከባንክ ወጪ ተደርጐ ለ3ኛ ወገን የተላለፈ (የተሰጠ) ገንዘብ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚገመትበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 85-93	70442	አቶ በቀለ ቱፋ እና ወ/ሮ ባዩሽ እሸቱ	ታህሳስ 30/2004	130
39	የወራሾች የጋራ ሀብት የሆነን ንብረት ለመሸጥና ለማስተላለፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ የጋራ ባለንብረቶቹ ሁሉ ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1262, 1060(1)	64371	ፍቅረዲን ሰይፈዲን እና እነ አበራ ለማ (አምስት ሰዎች)	ጥር 02/2004	134
40	ከባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጋር በተገናኘ በአንደኛው ተጋቢ በውርስ የተገኙ ንብረቶች (ሀብቶች) ለልማት በሚል በመፍረሳቸው የተገኘ የካሳ ክፍያ በግብይት እንደተገኘ ተቆጥሮ የግል ስለመሆኑ በፍ/ቤት አልተረጋገጠም በሚል እንደ የጋራ ሀብት	65708	አቶ አራጋው አበበ እና ወ/ሮ ራሔል	ጥር 02/2004	137

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 58, 57		ውብሸት		
41	• የጋብቻ ፍቺ ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማግሌዎች ወይም በባለሞያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሣኔው ተፈፃሚነት የሚኖረው ስፍ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነትን ሲያገኝ ብቻ ስለመሆኑ • ፍቺን እና የፍቺን ውጤት በተመለከተ ውሣኔ የመስጠትና የማፅደቅ ስልጣን የፍ/ቤት ብቻ ስለመሆኑ፣ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 83(3), 117 የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.69/95 እና አዋጅ ቁ.83/96 አንቀፅ 110(5)	69657	ወ/ሮ ሐምዚያ ሼክ ኢብራህም እና አቶ አብዲ ኡስማኤል	የካቲት 28/2004	141
42	በጋብቻ ተሳስረው የነበሩ ሰዎች ግንኙነታቸው እስካልተቋረጠ ድረስ ለረጅም ጊዜ ተለያይተው በመኖራቸው ብቻ በመካከላቸው ያለው የትዳር ግንኙነት ፈርሷል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣	67924	ወ/ሮ ምንያ ገ/ሥላሴ እና ወ/ሪት መሠረት ዓለማሁ	መጋቢት 26/2004	144
43	ከባልና ሚስት ጋብቻና ፍቺ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የቀረበን ጉዳይ ስልጣን ያለውና ተከራካሪዎቹ ለመዳኘት ፈቃዳቸውን የገለፁለት የሽሪአ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆኑን በመግለጽ መዝገቡን የዘጋው እንደሆነ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ማስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. አንቀጽ 37(1), 34(5), 78(5),	72420	ወ/ሮ ኬሪያት ያህያ እና ሐጂ ጅሀድ ኡመር	ሚያዝያ 22/2004	148
44	የውርስ ሀብት ማጣራት ጋር በተገናኘ የንብረት አጣሪው የሚች ያለኑዛዜ ወራሾች በሚል የተጠቀሱ ወራሾች በአካባቢው በሚገኘው የመረዳጃ እድር ሰፍሯል በማለት የውርስ ድርሻ አላቸው በሚል የሚያቀርበው የውሣኔ ሀሳብ ህጋዊ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 842, 856, 962, 944(ሀ),1097,1113	71895	አቶ ሞላ ንጉሴ እና አቶ ንጉሴ ገለታ	ግንቦት 10/2004	151
45	የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጋር በተገናኘ አንድን የጋራ ንብረት በዓይነት ለመካፈል ተጋቢዎቹ ከስምምነት ላይ ለመድረስ ያልቻሉ እንደሆነና ሁለቱም የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ ያቀረቡ እንደሆነ ንብረቱ ለጨረታ ቀርቦ እንዲሸጥ በማድረግ ገንዘቡን መካፈል ያለባቸው ስለመሆኑ፣	71126	ወ/ሮ ወርቅነሽ ሰብስቤ እና እነ ሻለቃ ባሻ	ሰኔ 05/2004	154

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/መ/ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/96 አንቀጽ 103(1)		እንደሻው (ሁለት ሰዎች)		
46	ሚች አድርጉት የነበረ ኑዛዜ በተመሣሣይ ንብረት ላይ በኋላ በተደረገና ከሞተ በኋላ ተፈፃሚነት ባለው ስጦታ የተተካ እንደሆነ ኑዛዜው በስጦታው እንደተሻረ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2428, 2443, 881, 826(2), 856, 898	72286	አቶ ኃ/ስላሴ ወርቁ እና ወ/ሮ ምስራቅ ወርቁ	ሰኔ 19/2004	157
47	በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ ስም የተመዘገበና በጋብቻ ወቅት ዕጣው የወጣ የኮንዶሚንየም ቤት ላይ ያለ መብት የቤቱ ውል ከጋብቻ መፍረስ በኋላ የተፈፀመና ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ መሆኑ (የንብረት ክፍፍል እስካልተፈፀመ ድረስ) ንብረቱን የግል የሚያስብል ስላለመሆኑ	75562	ወ/ሮ ሶፊያ መሐመድ እና አቶ መሐመድ ይመር	ሰኔ 18/2004	160
48	ፍቺን በስምምነት ለመፈፀም ለፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡ ባል እና ሚስት የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ያደረጉትን ስምምነት ፍ/ቤት ለህግና ለሞራል የማይቃረን መሆኑን በማረጋገጥ ያፀደቀው እንደሆነ ስምምነቱ ተፈፃሚ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ፣ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 80,83(3) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277(2)	74376	አቶ ብዙአየሁ ታደሰ እና ወ/ሮ ሰሎሜ ሻወል	የካቲት 27/2004	163
49	አንድ ወንድ ሁለት ሚስቶች ጋር ተጋብቶ በሚገኝ ጊዜ የንብረት ክፍፍል ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የፌዴራል የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 102(1),86(1),62(1),63(1) የአማራ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 113(1),97(1),73(1),74(1)	45548	ወ/ሮ አሚናት አሊ እና ወ/ሮ ፋጡማ ውበት	መስከረም 24/2003	167
50	ውል አዋዋይ ወይም ዳኛ ፊት የተደረገ ኑዛዜ በህጉ የተመለከተውን የኑዛዜው መነበብ ሥርዓትን ያላሟላ ከሆነ ህጋዊ ፎርማሊቲን የሚያሟላ እንደሆነ ለመቁጠር የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 881(2), 882, 857	70057	እነ ወ/ሮ አበበች ቡልቻ (ሶስት ሰዎች) ተጠሪ፡- የለም	ህዳር 06/2004	171
ውል					174

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

51	የፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(ረ) ድንጋጌ ከስልክ አገልግሎት ክፍያ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2024(ረ), 2023, 2022	61331	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ሚ/ር ጀርመን ግናሆ	ጥቅምት 10/2004	175
52	ከማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ጋር በተገናኘ ሻጭ የሆነ ወገን የሸጠውን ነገር ባለሃብትነት ለገዢው የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2875, 2281,1808(2)	61913	ወ/ሮ እታለማሁ መስፍን እና አጋ አንዴ	ጥቅምት 20/2004	179
53	ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉት ውል ምንም እንኳን የተፈፀመ ቢሆንም ውሉ የ3ኛ ወገኖችን መብትና ጥቅም የሚነካ ከሆነ ይህንኑ በመግለፅ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ይወሰን ዘንድ ለፍ/ቤት አቤቱታ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1806	61808	ወ/ሮ ፀሐይ ፍቃዱ እና እነ አቶ ብቻዬ ተስፋዬ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 07/2004	181
54	አንድ ማህበር ለለጠው ብድር የሚያገኘውን የወለድ መጠን ከመደበኛው የባንክ ማበደሪያ ወለድ መጠን ከፍ አድርጐ ለማበደር ስለመቻሉና ይኸውም ተፈፃሚ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.147/91 አንቀፅ 34(2) አዋጅ ቁ.402/96 አንቀፅ 5 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731,1678 የትግራይ ብ/ክ/መንግስት አዋጅ ቁ. 145/2000	62162	መትከል ልምዓት ሁለገብ መ/ህ/ስ ማህበር እና ቂስ ካላዩ ኪሮስ	ህዳር 21/2004	186
55	ከውል መፈፀም ጋር በተገናኘ ተዋዋይ ወገኖች ውልን በተናጠል ለመሰረዝ (unilateral cancellation of contract) ስለሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1771, 1774, 1757, 1787, 1785, 1786, 1789, 1788	57280	እነ ሴንትራል ቬኑ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (አራት ሰዎች) እና እነ አቶ ሰለሞን	ጥር 03/2004	189

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ከተማ (ሁለት ሰዎች)		
56	የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472 ከብድር ውጪ በሆነ ግንኙነት ከተከፈለ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ የሚሆንበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472	64397	አቶ አንዳርጌ እምሩ እና ወ/ሮ ዘሀራ መሀመድ	ጥር 01/2004	200
57	ውሎች በቃል፣ በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ግዴታ ለመግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ሊደረጉ ስለመቻላቸው የፍ/ብ/ህ/ቁ.1681(1)	71375	ዳሽን የህትመትና የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ፍስሐ ይሁን	ጥር 16/2004	203
58	የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል የጠፋበት ሰው የሽያጭ ውሉ የጠፋ ስለመሆኑ ለማስረዳት በሚል የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለውና የሚቀርቡት ማስረጃዎች በተገቢው ሁኔታ ተመርምረው አሳማኝ መሆናቸው ከታወቀ (ሲረጋገጥም) ተከራካሪው የሽያጭ ውሉን በምስክሮች ለማስረዳት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው የማገባ ስለመሆኑ የፍ/ህ/ብ/ህ/ቁ 2003,2002	69208	ወ/ሮ ንፁህ በላይ እና ወ/ሮ ምንትዋብ አዳነ	መጋቢት 10/2004	206
59	በወለድ አገድ ውል መሰረት የማይንቀሣቀስ ንብረቱን ያስያዘ ተዋዋይ ወገን በውል የተገለፀው ጊዜ ካለፈ በኋላም በማናቸውም ጊዜ ዕዳውን ከፍሎ ንብረቱን ለማስለቀቅ የሚችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 3128/2/ 3117-3130	72463	እነ አቶ ንጉሴ ሀይሌ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሁሬሣ ደበል (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 26/2004	209
60	እንደ ውል አልተፈፀመልኝም በሚል የጉዳት ኪሣራ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቶች የጥያቄ አቅራቢውን ተነፃፃሪ የውል ግዴታ ግምት ውስጥ በማስገባት የጉዳት ኪሣራ ሊወሰኑ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1771, 1802	69915	ሻምበል ይኩኖ ለገሠ እና አቶ መሐመድ በሽርና ቤተሰቦቹ	ሚያዝያ 25/2004	211

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ጨው አምራች ኃ/የተ/የግል ማህበር		
61	በሰነድ ላይ የተመለከተ ፊርማ በተካደ ጊዜ ሰነዱ ሲፈረም የነበሩ የምስክሮችን ቃል በመስማትና በሌሎች ማስረጃዎች ፊርማው የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ /Authenticate ለማድረግ/ የሚቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472(1) እና (3)	71927	ቂስ አብርሃ በርሄ እና ወ/ሮ ብርነሽ ሐሉፍ	ሚያዝያ 10/2004	215
62	የፀና የውል ግዴታ የገባ ሰው ውሉ በፍርድ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ የሚችለው ሌላኛው ተዋዋይ ወገን ግዴታውን በአግባቡ ያልፈፀመ (ያልተወጣ) እንደሆነ ወይም የፈፀመው ፍፁም ባልሆነ አኳኋን ከሆነ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1784 1785(2),(1)	66935	አቶ ሽመልስ አበራ እና አቶ ጌታቸው አያልቁ	ሰኔ 05/2004	218
63	አንድ ቀድሞ በመያዣ የተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ካርታ ቁጥሩና የቤት ቁጥሩ ተለውጦ እንዲሁም ቀደም ሲል የነበረው ቤት ፈርሶ በቦታው ላይ አዲስ ቤት ተሠርቶና አዲስ ካርታና የቤት ቁጥር ተሰጥቶ በተገኘ ጊዜ አዲሱን ቤት በመያዣ የያዘ አበዳሪ ቀድሞ የነበረውን ቤት በመያዣ ከያዘው አበዳሪ የቅድሚያ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 3052, 3066	75902	የኮንስትራክሽን እና ቢዝነስ ባንክ አ.ማ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ሰኔ 22/2004	224
64	ከስጦታ አድራጊው ሞት በኋላ ተፈፃሚ የሚሆን የስጦታ ውልን በተመለከተ ስለ ኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው ስለመሆኑ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግ ስጦታ በህጉ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ አስራርን በተከተለ መልኩ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.881, 2428, 2443, 2436	61421	አቶ ጌታቸው በየነ እና እነ የሕፃን ታቦት በቀለ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 17/2004	227
65	በአሰሪው በኩል የተመቻቸን የውጪ የትምህርት እድል ተጠቃሚ በመሆን በምትኩ ለተወሰነ ጊዜ ለማገልገል ከተደረገ ውል ጋር በተገናኘ ሠራተኛው በውሉ ያለበትን ግዴታ እንዲወጣ ከሚጠበቅበት ጊዜ በፊት ከአሰሪው ፈቃድና እውቅና ውጪ ለሌላ ትምህርት ወደ ሌላ አገር በመሄዱ የመጀመሪያው ውል ውጤት እንዳይኖረው ያደረገ እንደሆነ ሠራተኛው በውሉ የተመለከተውን ግዴታ ለመፈፀም እንዳልቻለ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ	70963	ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ እና እነ አቶ ተመስገን ማኑሌ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 30/2004	231
66	የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ውል መኖሩን በማመን ነገር ግን ውሉ	36887	ወ/ሮ አልጋነሽ አበበ	ህዳር	233

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሠረት የተከናወነ አይደለም በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • በፍ/ብ/ህ/ቁ.1723(1) መሠረት የሚከናወን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ምዝገባ ዓላማ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውል መኖሩን ለማስረዳት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723(1),2878		እና እነ አቶ ገብሩ እሸቱ (ሁለት ሰዎች)	18/2001	
67	ስለ አስፈላጊ አደራ እና የማስረጃ አይነት የፍ/ብ/ህ/ቁ.2782,2800,2802,2472	64887	አቶ አደም የሱፍ እና አቶ አብዱሠላሣ መ/ሐመድ	ሐምሌ 29/2003	236
	ወንጀል				**239**
68	በአንድ ጉዳይ ድጋሚ ክስ ወይም ድጋሚ ቅጣት (principle of double jeopardy) ክልክል ስለመሆኑ የተደነገገው መርህ ሊተረጐም ስለሚችልበት አግባብ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 23 የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.42(1)(ሀ)	60217	እነ ም/ኢ/ር ኃይላይ አስገለ (ሁለት ሰዎች) እና የቤ/ን/ፍ/ት/ሕ ቢሮ	ጥቅምት 15/2004	240
69	• ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የዋስትና ጥያቄን ላለመቀበል ሥልጣን (discretion) ያላቸው ስለመሆኑ፣ • ዋስትናን ለመከልከል ፍ/ቤቶች የሚሰጡት ምክንያት በቂና ህጋዊ ናቸው ሊባሉ የሚችሉበት አግባብ፣ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.67	67874	እነ አቶ ፅጌብርሃን ተሰራ (ሁለት ሰዎች) እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን	ጥቅምት 23/2004	243
70	ማዕድናትና የከበሩ ድንጋዮችን ከማዘዋወርና ለሽያጭ ከማቅረብ ጋር በተገናኘ ስለሚኖር የወንጀል ኃላፊነት፣ የወ/ህ/ቁ 346፣347፣378	60345	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ሕዳር 07/2004	247

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 52/85 አንቀጽ 53(1), (5), 26(4) ደንብ ቁ. 182/80/ አንቀጽ 30(1)(ሀ), 3(ለ) እና 4(ሐ), 38-40 አዋጅ ቁ. 591/2000 አንቀጽ 26(1)(ለ)		እና . ገዳ ፎጫ በሊ-ግለሰቦቹ (ሶስት ሰዎች)		
71	በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ ከአንድ አይነት የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ በሁለት የተለያዩ የወንጀል ክሶች የተከሰሰ ተጠርጣሪ በአንዱ የወንጀል ክስ የተመለከቱ ፍሬ ነገሮች መከሰት ጋር በተገናኘ ጥፋተኛ ለማለት ያልተቻለ እንደሆነ በሌላኛው ክስ ጥፋተኛ ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ የወ/ህ/ቁ 407(ሐ), 670, 677 የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 141, 142, 149(1)	65325	ሣጅን ታዬ ተክለኃይማኖት እና የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ መርማሪ	ህዳር 22/2004	256
72	• በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር ክርክሩ አግባብነትና ብቃት የሚኖረው በወንጀል ክሱ ተከሳሹ በወንጀል ፍ/ቤቱ ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነ ከሆነና ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስም በወንጀሉ ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች በፍ/ብሔሩ ጉዳይም ቀርበው የተሰሙ መሆን ያለባቸው ስለመሆኑ፣ • በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ማስረጃ ለፍትሐብሔር ጉዳይ አግባብነትና ብቃት የሚኖረው በሁለቱም ጉዳዩች የተሰሙት ማስረጃዎች አንድ አይነት ሲሆኑ ስለመሆኑ፣ • በወንጀልና በፍ/ብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች የተለያዩ ከሆነ እና በወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበበት ነጥብም ከፍ/ብሔሩ ክስ ጋር ግንኙነት የሌለው ከሆነ በወንጀል ክስ ተጠያቂ መሆን ሁልጊዜ በፍ/ብሔር ክስ ኃላፊነትን የሚያስከትል ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2149 የወንጀል ህግ ቁጥር 702(2)	46386	አቶ ሃይሉ ተስፋሉ እና አቶ ብርሃነ መብራቱ	ታህሣሥ 06/2004	259
73	ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ በመገኘት ወንጀል አንድ ሰው ተጠያቂ የሚሆነው የምዝገባ ሥርዓት የተዘረጋ እንደሆነ ብቻ ነው ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ ስላለመኖሩ የወ/ህ/ቁ.419	67411	እነ አቶ ታረቀኝ ተክሉ ገመዳ (ሶስት ሰዎች) እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የሥነ ምግባርና	ታህሣሥ 30/2004	262

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			የፀረ ሙስና ኮሚሽን		
74	በወንጀል ህግ ቁጥር 448 ስር አንድ ሰው ለፍትህ እርዳታ ለመስጠት እንቢተኛ ሆኗል በሚል ወዲያውኑ ጉዳዩን በያዘው ፍ/ቤት ለመቅጣት ስለሚቻልበት አግባብ የወ/ህ/ቁ 448(1), (3), 23(2), 58	67777	እነ ተወልደ ብስራት (ሶስት ሰዎች) ተጠሪ የለም	ታህሣሥ 04/2004	266
75	በኤግዚቢትነት በፖሊስ ከተያዙ ንብረቶች ጋር በተገናኘ የንብረቶቹ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ንብረቱ ይመለስለት ዘንድ በፖሊስ ጽ/ቤቱ ላይ የሚያቀርበው ክስ በተገቢው ማስረጃ ተጣርቶ እልባት ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ	62504	አቶ ታደሰ ናማጋ ሀያቱ እና የፌዴራል ፖሊስ ወ/ምርመራ መምሪያ ዋና ሣጅን ደምሴ ሰጠኝ	ታህሣሥ 06/2004	271
76	አንድ ሰው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 407 መሰረት በስልጣን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል ጥፋተኛ ተደርጐ ቅጣት ሊጣልበት የሚችልበት አግባብ፣ የመ/ህ/ቁ 407(1)(ሀ)	60518	አቶ ፈለቀ ሊቤ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/የስነ- ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ጥር 15/2004	273
77	አንድ ሰው በወንጀል ህግ አንቀጽ 598(2) መሰረት በህገ-ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ወደ ውጪ አገር ልኳል በሚል ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ ስለሚችልበት አግባብ የወ/ህ/ቁ 598(2)	71753	አቶ ወርቅነህ ዳቲ እና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	ጥር 03/2004	277
78	• የግንባታና የኮንስትራክሽን ማዕድን ማውጣት ሥራ ጋር በተያያዘ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የፀና ፈቃድ ሣይኖር ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የመግዛትና የመሸጥ ውል መፈፀም በወንጀል ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለመቻሉ • ህገ ወጥ ወይም ወንጀል ስለመሆኑ የተደነገገ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተደረጉ ውለታዎችን (ውሎችን) በህግ ኃይል እንዲፈፀሙ በሚል ለፍ/ቤት ጥያቄውን በቀረበ ጊዜ ዳኞች ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ የሚገባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1718, 1716	69822	ዲ - ኤም - ሲ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና አቶ ኢብራሂም ኢቲሶ	ጥር 15/2004	280

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወ/ህ/ቁ.353(1)(ለ) አዋጅ ቁ.52/85 አንቀፅ 53(5) ደንብ ቁ.182/86 አንቀፅ 39				
79	• የሥራና ሠራተኛን ማገናኘት አዋጅ ቁ.632/2002 በመተላለፍ ሊኖር ስለሚችለው የወንጀል ተጠያቂነት • ከቀረበ የወንጀል ክስ ጋር በተያያዘ የግል ተበዳይ የሆነ ሰው ቀርቦ ካልመሰከረ በስተቀር ክሱን ለማስረዳት የሚቀርቡ ሌሎች ማስረጃዎች ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማለት ብቁ አይደሉም ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.632/2002 አንቀፅ 16(1)(መ), 18(1)(ሀ), 20(2), 40(3)	71184	ዓሕመድልሃዲ ካህሳይ እና የፌዴራል ዓቃቤ ህግ	ጥር 18/2004	286
80	የመንግስት ሰራተኛ ሳይሆኑ ነገር ግን ከመንግስት ሰራተኞች ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር በህዝብና በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረስ በሙስና ወንጀል ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.434/97 አንቀፅ 7 የወ/ህ/ቁ.407(1)(ሀ),33	60542	አቶ ተክለድንግል ገ/ሚካኤል እና የፌ/ሥ/ም/ፀ/ሙስና ኮሚሽን	የካቲት 27/2004	289
81	• ከመንግስት ሰራተኞች ውጪ በሆኑ ሰዎች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችን በተመለከተ የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ክስ ሊያቀርብ ስለመቻሉ • ኮሚሽኑ የወንጀል ክስ ለመመስረት ስልጣን ከተሰጠው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ወይም ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተከሰሰ ሰው ከሙስና ወንጀሉ ጋር አንድ ላይ መከሰስ ያለበትን የወንጀል ድርጊት አንድ ላይ (አጣምሮ) ሊያቀርብ ስለመቻሉ የወ/ህ/ቁ 379(2), 375, 404(4)(3) አዋጅ ቁ. 434/97 አንቀፅ 58 አዋጅ ቁ.236/93 አንቀፅ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.110	64612	እነ ሐሰን አማን መሐመድ (ሁለት ሰዎች) እና የፌ/ሥ/ፀረ-ሙስና ኮሚሽን-	የካቲት 27/2004	292
82	አንድ የወንጀል አፈፃፀም ተግባር ሙከራ ደረጃ ላይ ደርሷል (Attempt) ሊባል የሚችልበት አግባብ የወ/ህ/አ 32(1)(ሀ),27(1),671(1)	66856	ውድማ አበጀ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል	መጋቢት 26/2004	296

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

83	የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጋር በተያያዘ የክስ ቻርጅን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን በወ/ህ/አ.438 በየመንግስት ሥራን ማሰናከልና የመተባበር ግዴታን መጣስ ወንጀል ሊያስጠይቅ ስለመቻሉ፣ የወ/ህ/አ.348	73953	ከፋለ ሰፈነ እና የአማራ ክልል ዓ/ህግ	መጋቢት 13/2004	299
84	በወንጀል ጉዳይ በተሰጠ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ለማቅረብ በህጉ ተለይቶ ስለተመለከተ የጊዜ ገደብ፣ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 187(2)	73264	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ አቶ አልፈድል አሻፊ (ሶስት ሰዎች)	ሚያዝያ 9/2004	302
85	• በወንጀል ፍርድ ሂደት አንድ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ወይም በክርክሩ ሂደት ተሳታፊ ሳይደረግ (ሳይሆን)(default procedure) ነው የታየው ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ • የቅጣት አስተያየት በሚሰጥበት ጊዜ ያለመቅረብ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ውሣኔ ነው ሊያስብል የማይችል ስለመሆኑ፣ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.161, 164, 197, 202, 149 (4) (1) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20(4))	76909	ወ/ሮ ፈትያ አወል እና የፌዴራል ዐቃቢ ህግ	ግንቦት 10/2004	205
86	ማንኛውም ሰው በወንጀል ህግና ሥርዓት መሠረት ተከስሶ የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም (Principle of Double Jeopardy) በሚል የሚታወቀው የወንጀል ህግ መርህ ሊተረጐምና ሥራ ላይ ሊውል የሚችልበት አግባብ፣ • አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በድጋሚ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በአንድ ጉዳይ በድጋሚ ያለመከሰስና ያለመቀጣት መብቱ ተጥሷል በሚል ክርክር ለማቅረብ ሊሟሉ ስለሚገቡ ህጋዊ መስፈርቶች፣ ዐቃቤ ህግ በአንድ ተከሳሽ ላይ የወንጀል ክስ ከማቀርቡ በፊት ተከሳሹ አንድ ወንጀል በመፈፀም ሀላፊ የሠራው አንድ የወንጀል ድርጊት ያስከተላቸውን ወይም ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ውጤቶች ሁለተናዊ በሆነ መንገድ በማገናዘብ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመለየትና በመጥቀስ የወንጀል ክሱን በጥንቃቄ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣	72304	የትግራይ ክልል አጽቢ ወረዳ ዐቃቤ ሕግ እና ተማሪ ሐጎስ ወልደሚካኤል	ሰኔ 18/2004	308

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወ/ህ/አ 2(5), 24(1) የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130,131, 41, 111, 112 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህግ መንግስት አንቀጽ 23,13(2)				
87	• አንድ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ በሚል ፍ/ቤት በሚሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የሚያስችል የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የሙስና ክስ ከሚመራበት ሥርዓት ጋር በተገናኘ ተከሳሽ የሆነ ተከራካሪ ወገን ይግባኝ ለማቅረብ ስለሚችልባቸው ህጋዊ ጉዳዮች፣ • ለሰበር ችሎት የሚቀርቡ ማናቸውም ጉዳዮች የይግባኝ አቅራረብ ሥርዓትን ያጠናቀቁና የመጨረሻ ፍርድ የተሠጠባቸው መሆን የሚገባቸው ስለመሆኑ፣ አዋጀ ቁ. 25/88 አንቀጽ 22 አዋጀ ቁ. 434/97 አንቀጽ 36(2) 40, 55 አዋጀ ቁ. 236/93	74041	እነ አንተነህ መኮንን (አራት ሰዎች) እና የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ	ሰኔ 04/2004	313
88	አንድ ሰው በወ/ህ/አ. 675(1) የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል ሊከሰስና ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ ስለሚችልበት አግባብ፣ የወ/ህ/አ.675(1),23	74530	ጀማል መሐመድ እና የፌዴራል ዐ/ህግ	ሰኔ 22/2004	316
89	አንድ ሰው በወ/ህ/አ. 429 ጉዐ ማቀባበል የወንጀል ድርጊት ክስ ሊቀርብበትና ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችልበት አግባብ፣ የወ/ህ/አ. 429,23(4,(1),58)	78793	አቶ ብስራት ወልደመስቀል እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ሰኔ 21/2004	320
90	በፍ/ቤት የወንጀል ክስ ቀርቦ የጥፋተኝት ውሣኔ በተሰጠበት የወንጀል ድርጊት ወንጀለኛው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘው ንብረት ለመንግስት እንዲወረስ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ 98(1)(2),	66943	እነ ታምራት ገለታ (አራት ሰዎች) እና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	ሐምሌ 18/2004	324
91	በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀሙ ለማስረዳት መቅረብ	75922	እነ አፈወርቅ ሌሊሳ	ሐምሌ	329

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የሚገባው የማስረጃ አይነት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸው ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት የሚችልና ድርጊቱ ሲፈፀም አይቻለሁ ወይም/እና ሰምቻለሁ የሚል ቀጥተኛ ማስረጃ ብቻ ነው ለማለት የሚያስችል የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 137, 141, 149		(ሁለት ሰዎች) እና የደቡብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት	04/2004	
92	አንድ የወንጀል ድርጊትን ማስረዳት ጋር በተያያዘ የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ (circumstantial evidence) በይዘቱ አንድ ክስተት ከመፈጠሩ በፊት፣ ክስተቱ ሲፈጠር ወይም ድርጊቱ ሲፈፀምና ክስተቱ ከተፈጠረ ወይም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ፣ ያሉትን አካባቢያዊ ሁኔታዎች የሚያሣይና የሚገልጽ በመሆኑ ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 137(1)	75980	ስማቸው ልንገርህ ዓለሙ እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የደቡብ ክልል ቅርንጫፍ	ሐምሌ 02/2004	322
93	የባንክ ሥራ ጋር በተገናኘ የሥራ አመራር ላይ ጉድለት በመፈፀም ስለሚደረግ ወንጀል፣ የወ/ህ/አ. 703	77989	እነ አቶ ለይኩን ብርሃኑ (አምስት ሠዎች) እና የፌዴራል ዐ/ህግ	ሐምሌ 04/2004	337
94	የወንጀል ህግ አንቀጽ 692(1)ን በመተላለፍ አንድ ሰው በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችልበት ሁኔታ፣ የወ/ህ/አ. 692,32(1)(ለ)	77592	ተካልኝ ጌታቸው እና የፌ/ዐ/ሕግ	ሐምሌ 27/2004	347
95	አንድ ወኪል ከወካዩ በውክልና ስልጣኑ የወሰደውን ንብረት ለመመለስ ፈቃደኛ ያለመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 676(2) ድንጋጌ መሰረት ሊያስጠይቀው ስለመቻሉ የወ/ህ/ቁ 676(2)	67408	አቶ ፋሲል በላይነህ እና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	ጥር 01/2004	350
96	በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው የዋስትና መብቱ በፍ/ቤት ከተከበረለት በኋላ ህጋዊ ምክንያቶችን በማቅረብ የዋስትና መብቱን በመተው ያስያዘው ገንዘብ ተመልሶለት ጉዳዩን ማረሚያ ቤት ሆኖ ለመከታተል የሚያቀርበውን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣	73569	አቶ ደረጀ ጎሳዬ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አቃቤ	ጥር 17/2004	353

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ሕግ		
97	በወንጀል የተከሰሱ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በግላቸው ጠበቃ ለማቆም የማይችሉ በሆነ ጊዜ በመንግስት ወጪ የጠበቃ ድጋፍና እርዳታ ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 20(5) አዋጅ ቁ.27/88 አንቀፅ 35 አዋጅ ቁ.123/90 አዋጅ ቁ.27/885	65566	የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ እና የኦሮሚያ ክልል ዐ/ህግ	ታህሣሥ 04/2004	357
98	የሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ማስረጃ የመመዘንና የመመርመር ስልጣን የሌለው ቢሆንም በሥር ፍ/ቤቶች ወይም የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት መሰረታዊ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ስርዓትን ሳይከተሉ፣ መመስረት የሚገባቸውን ጭብጥ ሳይመሰርቱና ጭብጡን የማስረዳት ግዴታ (Buden of proof) ያለበት ተከራካሪ ወገን የማስረዳት ግዴታውን በአግባቡ እንዲወጣ ሳያደርጉና መጣራት ያለበትን (የሚገባውን) ፍሬ ጉዳይ ሳያጣሩ የሰጡትን ውሣኔ በሰበር አይቶ ለማረም ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ በወ/ህ/አ. 419	63014	እነ አቶ ወርቅነህ ከንባቶ (ሁለት ሰዎች) እና የደቡብ ክልል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ሚያዝያ 09/2004	359
	የንግድ ህግ				366
99	• በባህር ላይ እቃ አመላላሽ በእቃዎች ላይ ለደረሰ ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብ፣ • በባህር ላይ እቃን ለማመላለስ የውል ግዴታ የገባ ወገን ከእቃዎቹ መጐዳት ጋር በተያያዘ ስላለበት የኃላፊነት አድማስና ከኃላፊነት ነፃ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የባህር ህግ ቁ.196,138,205,197,180(3)	54117	ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ አ.ማ	ጥቅምት 13/2004	367
100	እቃን ከማንገዝ ጋር በተገናኘ ከእቃው አደገኛ (ጉዳት አድራሽ) ባህሪ የተነሣ ዕቃውን በሚያንገዝው ተሸከርካሪ ላይ ለደረሰ ጉዳት የእቃው ባለቤት (ባለንብረት) የዕቃውን በአግባቡና በጥንቃቄ አለመታሸግ (አለመያዝ) ጋር በተገናኘ በኃላፊነት ሊጠየቅ ስለመቻሉ የንግድ ህግ ቁ.578(2)	60385	ጎልደን ሮዝ አግሮ ፋርምስ ኃ/የተ/የግ ማህበር እና አቶ ሐሊፎም ተስፋ ማሪያም	ጥቅምት 24/2004	371

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

101	ከንግድ ስም አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የንግድ ሚኒስቴር በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታ በይግባኝ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ አዋጅ ቁ.686/2002 አንቀፅ 6, 7, 30, 2(9), 16, 61	69603	አቶ ሀብተወልድ ዘርጋው የጂትሮ የስራ አመራር የማማከር አገልግሎት ድርጅት እና እነ አቶ ሳሙኤል አሰፋ የጂትሮ ሊደርሺፕ ኤንድ ማኔጅመንት(ሁለት ሰዎች)	ሀዳር 08/2004	374
102	ከንግድ ስም ወይም ምልክት ምዝገባ ጉዳይ ጋር በተገናኘ በሚመለከተው ተቋም በተሠጠ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት በይግባኝ ሥርዓት የማሳረም ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 501/98/ አንቀጽ 6,17,36,49	63454	ዳት ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ/ባለቤት ዶ/ር ጤና አብተው እና እነ የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ፅ/ቤት (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 26/2004	378
103	• ለገንዘብ እዳ የሚሰጥ ዋስትና አንድ የመድን ተቋም ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል አንዱ ስለመሆኑ፣ • በመድን ሰጪ ድርጅቶች ተዘጋጅቶ የሚሰጥ የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) ስለሚኖረው ውጤት • የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ ሊያሟላቸው የሚገቡ ፎርማሊቲዎች እና አቤቱታ ከማቅረብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት ስለሚኖረው የይርጋ ደንብ አዋጅ ቁ.86/86 አንቀፅ 2	36935	አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	የካቲት 27/2004	383

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ህ/ቁ 1845, 1922(2)(3), 1725(ሀ), 1727, 1926, 1929, 1930, 1931 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀፅ 1(1), 2(1) መመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀፅ 1(3), 2(1), 3 የንግድ ህግ ቁ.36(1)(2), 121(ሰ) አዋጅ ቁ.110/90 አንቀፅ 2(2) አዋጅ ቁ.57/89 አንቀፅ 2(18)				
104	• ስለ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantee Bond) • የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ውል በባህሪው ከመድን ውል የሚለይና በፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1921, 1719, 1720, 1727, 1719(2), 1920, 1845, 1924(1), 1922(3), 1926 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁ23/2002 አንቀጽ 1(1), የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ 24/2002 አንቀጽ 1(3) የንግድ ህግ ቁ. 654(1), 657(1), 712 አዋጅ ቁ. 57/1989 አዋጅ ቁ 648/2001 አንቀጽ 2/20 አንቀጸ 2(18) አዋጅ ቁ. 110/90 አንቀጽ 2(2)	47004	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ባሌ ገጠር ልማት ድርጅት	መጋቢት 11/2004	392
105	• አንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንዲፈርስ ለመጠየቅ በቂና ህጋዊ መስፈርቶች መሟላታቸው መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፣ • የማህበር ሥራው በአግባቡ አልተመራም ከሚል ጥያቄ ጋር በተያያዘ አግባብነት ያለው አካል የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጐች መሠረት በማድረግ እንዲስተካከል ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁጥር 217, 218, 511, 543	71134	አቶ ያሬድ ሲሳይ እና አልግሪን አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሰኔ 04/2004	399
106	ስለ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarangee Bond) እና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ የተከለከሉ ስለመሆኑ የአክሲዮን ማህበራት ፕሬዚዳንት ወይም ዋና ሥራ አስኪያጅ ስላለው ስልጣን እና በህግ	40186	አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) እና ዳሸን ባንክ (አ.ማ)	የካቲት 27/2004	402

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አግባብ ስልጣኑ ተገድቧል ለማለት ስለሚቻልበት ሁኔታ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ እንደ የኢንሹራንስ ፖሊሲ የማይቆጠር ስለመሆኑና በፍ/ብሔር ህጉ ስለ ዋስትና ግዴታ በተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ፡ ቁ. 24/2004 አንቀጽ 3,1(3) ቁ. 23/2004 አንቀጽ 1(1) አዋጅ ቁ. 86/86 አንቀጽ 2(4) ,6,4 32-34 አዋጅ ቁ. 87/89 አንቀጽ 2(18) አዋጅ ቁ. 110/90 አንቀጽ 2(2) የፍ/ብ/ህ/ቁ.1725(ሀ),1727,1922(2),(3) አዋጅ ቁ. 648/2001 አንቀጽ 2(20) የንግድ ህግ ቁ.36(1)(2), 121(ሰ), 348(3), 313(1)-(7), 313(10-12), 34(1),1 09(ረ), 323(2-3), 35(1), 26, 120				
107	የአክሲዮን ማህበር ሥራ አስኪያጅ ያለአግባብ ከስልጣኔ (ከስራ አስኪያጅነቱ) ተሽሬያለሁ በሚል በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍ/ቤት ግለሰቡን ወደ ስራ አስኪያጅነቱ እንዲመለስ ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁ. 525-537	63200	እነ ጣና ኢንጂነሪንግ ኃላ/የተ/የግል ማህበር(አራት ሰዎች) እና ሚስተር አልቸዲ ዩልጋውዲዮ	ታህሳስ 30/2004	417
	ንብረት				422
108	• የመሬት ይዞታና በመሬት የመጠቀም መብት ያለው ወገን በውል ለ3ኛ ወገን ሊያስተላልፍ ስለሚችለው የመብት አድማስ • በመሬት የመጠቀም መብት የተላለፈለት ሰው በመሬቱ ላይ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ያፈራ እንደሆነ ንብረቱን አፍርሶ (ነቅሎ) የመውሰድ መብትን ብቻ ሊያገኝ የሚችል ስለመሆኑ	69291	አቶ ጀማል አማን እና ወ/ሮ ተዋበች ፈረደ	ህዳር 08/2004	423

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(3), (4) አዋጅ ቁ.456/97 የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ.130/99 አንቀፅ 6				
109	•የመሬት ባለ ይዞታ የሆነና በመሬቱ የመጠቀም መብት ያለው ሰው ለሁለት ዓመት ያህል መሬቱን በመተው ከአካባቢው ከጠፋ የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬቱ የመጠቀም መብቱ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ •በገጠር የእርሻ መሬት ላይ አርሶአደሮች ያላቸውን የይዞታና የመጠቀም መብት መደፈር ጋር በተያያዘ የሚነሣ ጥያቄ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.456/97 የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ.130/99 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(4) የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677(1)(3), 1845	69302	አቶ ሸለማ ነገሰ እና አቶ ፋይሣ መንግስቱ	ታህሣሥ 20/2004	426
110	የገጠር መሬት ባለይዞታነትን በማረጋገጥ የተሰጠ የምስክር ወረቀት የመጨረሻና የማይስተባበል ማስረጃ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ የአማራ ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁ.133/99 አንቀፅ 24(4) ደንብ ቁ.51/99 አንቀፅ 20(4)	69821	አቶ ጥላሁን ንበዜ እና እነ አቶ መኮተ ኃይሉ (ሁለት ሰዎች)	ታህሣሥ 17/2004	430
111	በአንድ ንብረት ላይ የጋራ መብት ካላቸው ሰዎች ጋር በተገናኘ የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ፣ • የጋራ ባለሃብቶች ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዱ ካለበት ያልተከፈለ ዕዳ የተነሣ ንብረቱ የሚሸጥ ቢሆን ሌሎቹ የጋራ ባለሃብቶች ሊሸጥ ያለውን ድርሻ አስገድዶ ለመግዛት የቅድሚያ መብት ያላቸው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1289(1)(2), 1290, 1261, 1388, 1406, 1281	59504	እነ አቶ እንዳለ ወርቅነህ (ስድስት ሰዎች) እና አቶ ተሸለ ቱቾ	የካቲት 27/2004	433
112	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን በማረጋገጥ ከሚሰጥ የምስክር ወረቀት (ካርታ ወይም ደብተር) ጋር በተያያዘ በአንድ ወቅት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል የተሰጠን የምስክር ወረቀት መሰረት በማድረግ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በሌላ ጊዜ ሰነዱ በአስተዳደር አካሉ መምከን የተሰጠውን ፍርድ በአንድ ጊዜና ሙሉ ለሙሉ ዋጋ የሚያሳጣ ሳይሆን ካርታው	64014	ዶ/ር ገነት ሥዩም እና እነ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17/18	የካቲት 28/2004	437

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በመምከኑ የተጐዳው ወገን የአስተዳደሩን አካል እርምጃ (ውሳኔ) ክርክር ሊያቀርብበት የሚችልና ፍ/ቤቶችም የእርምጃውን አግባብነትና ህጋዊነት ሊያጣሩት የሚችሉት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1195, 1196, 1206 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(1)(2)		አስተዳደር ፅ/ቤት (ሶስት ሰዎች)		
113	በከሳሽነት የተሰየመ ወገን አንድ ንብረት በአንድ ህጋዊ ተግባር ሳቢያ ወደ እጁ ገብቷል በይዞታዬ ላይ እያለ ሁከት ተፈጠረብኝ በሚል የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ በእርግጥም ሁከት ተፈጥሯል አልተፈጠረም የሚል ጭብጥ በመያዝ ሊስተናገድ የሚገባ እንጂ ክርክር የተነሣበት ንብረት በከሳሹ እጅ እንዴት እንደገባ ወይም ወደ ከሳሹ እጅ ሊገባ የቻለበትን ህጋዊ ተግባር ለመመርመር የሚያበቃ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1149	70801	ዋት ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ወ/ሮ ፎዚያ ቃዲ	የካቲት 30/2004	441
114	• የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ጋር በተያያዘ የሚመለከተው የአስተዳዳር አካል አንዴ የሰጠውን የባለሀብትነት ማረጋገጫ ደብተር (የምስክር ወረቀት) በሌላ ጊዜ የሰረዘው እንደሆነ ይኼው ተግባር በፍ/ቤት ክስ ሊቀርብበት የማይችል ወይም የማይስተናገድ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ • የአስተዳደር አካል ህጋዊ ምክንያት ሣይኖረው በአንድ ወቅት የሰጠውን የባለቤትነት ደብተር ከሰረዘ ይኸው አካሄድ ህጋዊ አይደለም የሚለው ወገን በፍ/ቤት መብቱን ለማስከበር ክስ ሊያቀርብና ፍ/ቤቱም ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1195,1196	57186	ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ከፈሉ ታረቀኝ	መጋቢት 10/2004	443
115	የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ የደረሰው ሰው እዳውን ከፍሎ ያጠናቀቀ ቢሆን እንኳን እጣው ከደረሰው ቀን አንስቶ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ የማይችል ስለመሆኑና ከዚህ ጊዜ በፊት ቤቱን አስመልክቶ የሚደረግ ውል ፈራሽ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 370/95 አንቀጽ 14(2) የአ.አ አስተዳዳር አዋጅ ቁ 19/97 አንቀጽ 21 የፍ/ብ/ህ/ቁ 1678,1808(2)	65140	ወ/ሮ በላይነሽ ቢያድግልኝ እና ወ/ሮ አስቱር ገበሬ	መጋቢት 10/2004	447

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

116	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን አስመልክቶ የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተገቢውን ስርዓት እና ደንብ በመከተል የተሰጠ መሆን ያለበት ስለመሆኑና በተመሳሳይም በአንድ ወቅት የተሰጠን የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመሰረዝ አግባብነት ያላቸውን ስርዓቶች በመከተል መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1195-1198	67011	እነ የወ/ሮ ጣይቱ ከበደ ወራሾች (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ጥሩነሽ ኃየሌ (ሶስት ሰዎች)	መጋቢት 11/2004	450
117	ከአዋጅ ውጪ የተወሰደ ንብረት ነው በሚል ንብረትን ከመንግስት አካል ያስመለሰ ወገን የንብረቱ አመላለስ አግባብነት የሌለው ሆኖ በመገኘቱ ንብረቱ ወደ መንግስት እንዲመለስ ሲወሰን ንብረቱን ያለአግባብ በእጁ ያቆየው ወገን ንብረቱ ያስገኝ የነበረውን ገቢ ወይም የታጣ ገቢ ጭምር የመክፈል ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ 572/2000 አንቀጽ 6	67631	የአቶ አሰፋ አባዲዮ ባለቤትና ወራሾች እነ ወ/ሮ ፅጌ ሽኔ (ሰባት ሰዎች) እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ሚያዝያ 24/2004	453
118	አንድ ጉዳይ ለመፈፀም (ለማስፈፀም) በሚል ምክንያት መነሻነት የሰጠሁትን ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለተሰጠበት ዓላማ አላዋለም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የአደራ ህግ ጽንስ ሀሳብን መሠረት በማድረግ ሊስተናገድ የማይገባ ስለመሆኑና ጉዳዩን ለማስረዳት የሰው ማስረጃ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣	69160	አቶ ሶሬሳ ጋሪ እና አቶ አብርሃም ፍቃዱ	ሚያዝያ 24/2004	457
119	አከራይ የሆነ ወገን ተከራይ ለሆነው ወገን ቤት እንዲለቀቅ በሚል የሚፅፈው ማስጠንቀቂያ ከአከራይና ተከራይ ውልና ግንኙነት አንፃር የሚታይ እንጂ እንደ ሁከት ተግባር የማይቆጠር ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1149(1), 2966(1)	67691	የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር እና ወ/ሮ አለምፀሐይ ወልዴ	ታህሣሥ 16/2004	460
ባንክና ኢንሹራንስ					**463**
120	በፎርክሎዠር ህግ መሰረት የሚከናወን ሐራጅ በፍ/ቤት የሚሰረዝበት አግባብ ስላለመኖሩና	68708	እነ የአቶ ናስር	ታህሣሥ	464

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሐራጁ በህግ አግባብ ያለመከናወኑ በባንኩ ላይ የጉዳት ካሣ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.97/90 አንቀፅ 7, አዋጅ ቁ.216/92 የፍ/ብ/ሥ/ሣ/ህ/ቁ 447(1), 423(2) የፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(1), 2027, 2028, 2035		አባቻቢር አባጅፋር ሚስትና ወራሾች(ሶስት ሰዎች) እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	05/2004	
121	ባንክ ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘውን ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ንብረቶች አሻሻጥ ቅደም ተከተል ጋር በተገናኘ አቤቱታ ሊቀርብበትና ፍ/ቤቶችም ውሣኔ ሊሰጡበት የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ97/90 አንቀፅ 7, 6 አዋጅ ቁ.216/92	70824	ወጋገን ባንክ አ.ማ እና እነ አቶ ብሩክ ጫካ (ሠባት ሠዎች)	የካቲት 27/2004	467
122	የደረሰን ጉዳት ከመካስ ጋር በተገናኘ በንግድ ህጉ እውቅና ስለተሰጣቸው የመድን ሽፋን (የኢንሹራንስ ውል) አይነቶችና ባህሪያት • ለንብረት የሚሰጥ የኢንሹራንስ ሽፋን አደጋው በደረሰበት ጊዜ ንብረቱ የነበረውን ዋጋ ለመካስ የሚያስችል መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁ. 654(2)(3),657, 674, 675, 688, 665, 678, 681, 680	69966	አቶ በላቸው እሸቱ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሚያዝያ 10/2004	472
123	• የፍርድ አፈፃፀም ጥያቄ በህጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ የባለዕዳው ንብረት እዳውን ለመሸፈን ባለመቻሉ በከፊል ተፈጽሞ ከቆየ በኋላ የፍርድ ባለመብት የባለዕዳውን ንብረት አፈላልጐ በማግኘት አፈፃፀሙን ለመቀጠል ሲፈልግ ይርጋ ሊቆጠር ስለሚችልበት አግባብ፣ አበዳሪ የሆነ ባንክ ከዕዳው አከፋፈል ጋር በተያያዘ በባለዕዳው ላይ የአፈፃፀም ክስ መስርቶ እንደ ፍርዱ ለመፈፀም የማይችል መሆኑ የተረጋገጠ ከሆነ በሌላ ጊዜ በባለዕዳው ንብረት ላይ በፍርድ ባለመብቱ የሚቀርበው የአፈፃፀም አቤቱታ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ መቆጠር ስለሚጀምርበት ጊዜ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384, 329(2) አዋጅ ቁ. 97/90	74898	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ፍቃዱ ተስፋዬ (ሶስት ሰዎች)	ሚያዝያ 25/2004	475

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

124	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ከደረሰ ጉዳት ጋር በተያያዘ ለተጐጂው የሚከፈል የጉዳት ካሣ አከፋፈል በአንድ ጊዜ እንዲከፈል ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2154, 2095(2)	67225	አቶ ኤርሚያስ ሓይሉ የሆነስት የረር ማኔጂንግ ዳይሬክተር እና አቶ ብርሃኑ ዳምጠው	የካቲት 26/2004	479
125	በኤሌክትሪክ መስመር ምክንያት ከደረሰ የቃጠሎ አደጋ ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የጉዳት ኃላፊነትንና ካሣን ለመወሰን፣ ጉዳቱ በምን ምክንያትና ሁኔታ እንደደረሰ፣ መብራት ሀይል ጥፋት ሳይኖር ኃላፊ ሊያደርጉ የሚችሉ አደገኛ ሁኔታዎችን ስለመፍጠሩ ወይም በሥራው ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄ አለማድረጉ ወዘተ ተገቢነት ባላቸው ማስረጃዎች ማንጠር ያለባቸው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2028,2066,2069,2027 በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.246,247,259	63231	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ወልደ ሚካኤል ሻንቆ	ግንቦት 06/2004	483
126	ለጉዳት ከሚከፈል የሞራል ካሣ ጋር በተያያዘ ልጃቸውን በሞት ያጡ ወላጆች ሁለት በመሆናቸው ለእያንዳንዳቸው 1000 ብር ሊከፈል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2116(3)	69428	አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ እና እነ መሐመድ አባ አለ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 26/2004	486
127	ብዙ ሰዎች በአንድ ጉዳይ ለደረሰ ጉዳት ካሣን እንዲከፍሉ የተገደዱ እንደሆነ እያንዳንዳቸው ለደረሰው አጠቃላይ ጉዳት ኃላፊ የሚሆኑ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2155(1)	68613	ሐጂ መሐመድ አመዴ እና አቶ መኮንን መስፍን	ሰኔ 18/2004	488

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

128	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ማንኛውንም ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍና የማከፋፈል ብሎም የመሸጥ ስራዎች በሚያከናውንበት ወቅት ሁሉ የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት የወጡ ህግጋትን በማክበር መሆን ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.86/89 አንቀፅ 13(1) ደንብ ቁ.49/91 አንቀፅ 23(2), 35	65395	አቶ ትዕዛዝ ኮሬ እና የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	የካቲት 26/2004	490
129	ከአሰሪና ሠራተኛ አገናኝ አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሰዎችን ወደ ውጪ አገር የላከ ሰው በተላኩት ሰዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ካሣ የመክፈል ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 632/2001	74111	የማህደር ኤጀንሲ ባለቤት ወ/ሮ አለምነሽ ኤርሞ እና ወ/ሪት አለም መስፍን ተወካይ ገበየ ደጉ	ሐምሌ 04/2004	495
	ጉምሩክ /ቀረጥ/ ግብር			**498**	
130	በኃላፊነት ይዞት በሚገኝ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትን በመተላለፍ ዕቃን ሲያጓጉዝ የተያዘ ሰው ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብና ተፈፃሚ ስለሚሆነው የህግ ድንጋጌ አዋጅ ቁ.60/89 አንቀፅ አዋጅ ቁ.368/95 አንቀፅ 79,80(1), 81,64(4)74 ወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.113(2)	54889	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና አቶ ንጉሴ ገብረፃዲቅ	መስከረም 26/2004	499
131	በጉምሩክ ወንጀል የተከሰሰ ሰው በነፃ የተለቀቀ ቢሆንም ወንጀሉ የተፈፀመበት እቃ ወይም ማጓጓዣ የሚወረሰው የጉምሩክ ህግን የመተላለፍ ድርጊት ስለመፈፀሙ ፍርድ ቤቱን የሚያጠግብ ማስረጃ ሲቀርብ ስለመሆኑና ማስረጃው አጥጋቢ ካልሆነ ብቻ ፍ/ቤት እቃውን (ማጓጓዣውን) እንዳይወረስ በማድረግ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ሊያዝ የሚገባው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀፅ 104(3)(ሀ), 104(3)(ለ)	64115	እነ አቶ አህመድ ሁሴን (ሁለት ሰዎች) እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ጥቅምት 08/2004	502

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

132	የበጐ አድራጐት ሥራን የሚሰሩ ድርጅቶች ከቦታ ኪራይ እና የቤት ግብር ነፃ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ አዋጅ ቁ.80/68 አንቀፅ 14(ለ) የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ.36/68 አንቀጽ 8	66474	የኢትዮጵያ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን የአቃቂ አድቬንቲስት ሚሲዮን ት/ቤት እና የአቃቂ ቃልቲ ክፍል ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት	ጥቅምት 17/2004	506
133	•ህንፃን (ቤትን) በኪራይ ይዞ የሚገለገል ወገን ለአከራዩ ከሚከፍለው የኪራይ ዋጋ ላይ በህግ የተመለከተውንና ለመንግስት ገቢ ሊሆን የሚገባውን ግብር ተቀናሽ ለማድረግ ስለመቻሉና ይህንን ለማድረግም የግዴታ የፍ/ቤት ውሣኔ የማያስፈልገው ስለመሆኑ •በፍርድ የኪራይ ዋጋን ለአከራይ እንዲከፍል የተወሰነበት ተከራይ ለመንግስት የሚከፈልና ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ እንዲያስቀር የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ያለበት በመሆኑ ሙሉውን የኪራይ ዋጋ ለአከራዩ እንዲያስረክብ በአፈፃፀም ሊገደድ ስላለመቻሉ አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 91, 101, 53(1) ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀፅ 24, 2(ሸ)	69677	ዳሽን ባንክ አ.ማ እና አቶ ኑረዲን መሐመድ	ታህሣሥ 20/2004	511
134	የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ መወጣት ጋር በተያያዘ ታክስ ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን የመጠቀም ግዴታ የሚኖርባቸው የንግድ ፈቃድ የሥራ ዘርፍ በግልፅ ተለይቶ በተመለከተባቸው ሽያጮች ጋር በተገናኘ ብቻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.285/94 አንቀፅ 55 አዋጅ ቁ.609/201 አንቀፅ 50(መ)(2) ደንብ ቁ.139/99 አንቀፅ 5(1)(ለ) የወ/ህ/ቁ.23(2)	74753	እነ ሐበሻ የባህል ማዕከልና የስእል ጋለሪ ኃ.የተ.የግል ማህበር (ሶስት ሰዎች) እና የፌዴራል ገቢዎችና	ታህሣሥ 17/2004	514

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ጉምሩክ ባለሥልጣን ዓቃቤ ህግ		
135	ከታክስ/ግብር አከፋፈል ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ያለውን ቅሬታ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በይግባኝ ለማቅረብ የተፈቀደው ጊዜና ስሌቱን ተግባራዊ ስለማድረግ አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 107(2), 108	66350	አቶ ቴዎድሮስ ደበላ እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን የልደታ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት	ጥር 02/2004	518
136	ግብር ከፋይ የሆነ ወገን ምንም አይነት የሂሣብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደ ሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሣብ መዝገቡንና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለስልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ሊከፈል የሚገባው የግብር መጠን በግምት ሊወሰን ስለመቻሉ አዋጅ ቁ.286/94 አንቀፅ 69(1), 71	69921	አቶ አበበ ገ/እግዚአብሔር እና አራዳ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ዐቃቤ ህግ	ጥር 02/2004	521
137	• ከጉምሩክ ባለስልጣን ሹም ፈቃድ ሳያገኝ በመተላለፍ ላይ ያሉ ወይም የጉምሩክ ወደብ በደረሱ ወቅት የእቃ መያዣ ላይ የተደረገን ማሸጊያ መፍታት በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ • በጉምሩክ ወደብ በምርመራ ላይ ካሉ ዕቃዎች ለሳምፕልነት በሚል ወስዶ አለመመለስ በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀፅ 100, 95(ሀ)	65041	አቶ አንዳርጌ እሸቱ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ህግ	የካቲት 30/2004	524
138	የተጨማሪ እሴት ታክስን ተግባራዊ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 49 መሰረት በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ላይ ቅጣት ሊጣል ስለሚችልበት ሁኔታ፣ አዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 49,47,50(2) የወ/ህ/አ 2(2)	68422	እነ ጀሪኮ ሰርቪስ (ሁለት ሰዎች) እና የኢትዮጵያ	መጋቢት 14/2004	527

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን		
139	ተከራይ የሆነ ወገን ለአከራይ ከሚከፍለው የኪራይ ገንዘብ ለመንግስት የሚከፈለውን ግብር ሳይቀንስ ለአከራዩ እንዲከፈል ለማስገደድ የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1716, 1718, 1711 አዋጅ 286/94 አንቀጽ 56, 91, 83	65361	ዘመነ ዮሐንስ ጀኔራል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና አቶ ዳውድ ኢብራሂም	ሚያዝያ 09/2004	532
140	•የግብር ከፋይ የሆነ ሰው ገቢውን በህጉ አግባብ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ከማሣወቅ ውጪ ደረጃውን በራሱ ሊወሰን /ሊለወጥ/ የማይችል ወይም የማይገባ ስለመሆኑ፣ •የግብር አከፋፈል ስርዓት ለግብር ከፋዩ ግልጽ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 38 ደንብ ቁ. 78/94 አንቀጽ 18,22 አዋጅ ቁ. 308/95 አንቀጽ 10(2)(ሐ) አዋጅ ቁ. 587/2001	72824	የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ፅ/ቤት እና አቶ ሚሊዮን አሰፋ	ሐምሌ 18/2004	534
141	• ለግል አገልግሎት ከቀረጥና ከታክስ ነፃ የገባን መኪና ለብድር መያዣነት መስጠት በወንጀል ኃላፊነትን (ተጠያቂነትን) የሚያስከትል ስለመሆኑ • በወንጀል ጉዳይ በቅጣት መልክ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ በፍ/ብሔር ጉዳይ ከሚኖረው የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት የተለየ ስለመሆኑና ቅጣቱ በእያንዳንዱ አጥፊ ላይ ለየብቻ ሊጣል የሚገባው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 73(1) አዋጅ ቁ. 60/89 አዋጅ ቁ.280/94 የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ), 41	69602	እነ አቶ አካሉ አለሙ (ሁለት ሰዎች) እና የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ	የካቲት 06/2004	539
ውክልና					543

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

142	• የውክልና ውሎች በጠባቡ ሊተረጐሙ የሚገባ ስለመሆኑ • “በስማችን ውል እንዲዋዋል” በሚል በደፈናው የተሰጠ ውክልና ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2181(3), 2205, 2204	50985	እነ አቶ ስሻህ ክፍሌ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ አፀደ ዱቤ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 05/2004	544
143	• ልዩ የውክልና ስልጣን ለመስጠት በተዘጋጀ ሰነድ ላይ ልዩ ውክልና ስለመስጠት በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች ያለመጠቀስ ልዩ የውክልና ስልጣን እንዳልተሰጠ የሚያስቆጥር ስላለመሆኑ • የአስተዳደር አካል የሆነ ተቋም በአንድ ወቅት የሰጠውን የፅሁፍ ማስረጃ በሌላ ጊዜ ማስተካከሉ በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት የተለያዩ ሰነድ ቀርቧል በሚል እንደማስረጃ ሰነድ ዋጋ የሚያጣበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ • በውክልና ሰነድ ላይ ለተወካይ የተሰጠው ስልጣን በይዘቱ ልዩ ውክልና የሚያመለክት ሆኖ ሰነዱ ስለ ልዩ ውልክና አስፈላጊነት የተቀመጠውን የፍ/ብ/ህ/ቁ 2208 ያለመጥቀሱ ብቻ ለተወካዩ ልዩ የውክልና ስልጣን እንዳልተሰጠ የሚያስቆጥር ስላለመሆኑ፣ •ከሰነድ ማስረጃ ተቀባይነት ጋር በተያያዘ የሚነሣ ጥያቄ የህግ ጥያቄ በመሆኑ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2205, 2005(1), 2179, 2199, 2203, 2204	72337	ወ/ሮ ንግስቲ እምነት እና ቴዎድሮስ ተክሌ	የካቲት 26/2004	549
144	አንድን ተቋም ወክሎ ውል ለመዋዋል በህግ ስልጣን የተሰጠው ሥራ አስኪያጅ ስልጣኑን ለሌላ ሰው በህግ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ አስተላልፎ ውል የተደረገ እንደሆነ ተቋሙ በሥራ አስኪያጁ በራሱ በመፈረም ውል አላደረገም በሚል ምክንያት ብቻ በውሉ አንገደድም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731 2274 2214(1 2215(3),2180)	68498	አቶ ገብረ ክርስቶስ ገብረ እግዛብሔር እና ሳባ እምነበረድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	ሰኔ 07/2004	553
145	የፀና የውክልና ስልጣን ከሌለው ሰው ጋር የተደረገ ውል ከጅምሩ ፈራሽና ህጋዊ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2232(2),2015(ሀ),2005(2),1204	73291	እነ አቶ አፅብሃ ወልዳይ (ሁለት ሰዎች) እና	ሐምሌ 04/2004	559

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ወ/ሮ ዙሪያሽ አሰግድ የክልሉ ፍትህ ቢሮ		
146	የውክልና ውል ሳይኖር ወኪል ነኝ በሚል የሚደረግ ውል ህጋዊ ውጤት አግኝቶ የሚፀናበት አግባብ ስላለመኖሩ፣ የውክልና ሥልጣኑ ከመሰጠቱ በፊት የተደረገ ውል ውክልና ከተሰጠ በኋላ ሊፀና ይችላል ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑና ወካይ የሆነ ሰው የወካዩን ድርጊት እንደተቀበለ ሊቆጠር የሚችለው በህግ የሚፀና የውክልና ውል ኖሮ ነገር ግን ወኪሉ ከተሰጠው ስልጣን በላይ ሰርቶ የተገኘ እንደሆነ ወይም የውክልና ስልጣኑ ካበቃ (ከተቋረጠ) በኋላ ወካዩን በመወከል የሰራቸውን ሥራዎች በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2190, 1678 (ሐ),1719(2),1723	74538	ወ/ሪት አሊያት ይማም ሙዘይን እና አቶ እምነቱ እንደሻው	ሐምሌ 20/2004	563
147	ወካይ የሆነ ወገን በተወካይ አማካኝነት የተደረገን ህገ ወጥ ውል እንዲፈርስ በሚል የሚያቀርበው አቤቱታ በአሥር አመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1)(2),2198,1810,1808(1),1845	67376	እነ ወ/ሮ ንግስት ኪዳኔ (ሁለትሰዎች) እና እነ አቶ በለጠ ወልደሰማያት(ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 30/2004	567
	አዕምሯዊ ንብረት				**572**
148	ከቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጋር በተያያዘ የፊልም ባለቤት ለመሆን በማሰብ በባለሃብትና ፊልሙን ለመስራት በሚል በተደረገ ስምምነት መነሻነት ፊልሙን ለህዝብ ከማቅረብ ጋር ተያይዞ ጉዳዩ በፍ/ብሔር ክርክር ተደርጉበት በተሰጠ ውሣኔ መሰረት ፊልሙን በእጅ አድርጉ መገኘት በወንጀል ተጠያቂነት የማያስከትል ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.410/96 አንቀፅ 7(1)(ሀ), 36(1) የወ/ህ/ቁ.23(2), 57-59	70500	ኢንጅነር አድማሱ ገብሬ እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ	ታህሣሥ 17/2004	573
149	• ከቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጋር በተያያዘ የመብቱ ተጠቃሚዎችና የመብቱ አድማስ • የቅጅ መብት እንዲከበር ለመጠየቅ መሟላት ስለሚገባቸው ነገሮችና መብቱ እንደተጣሰ የሚቆጠርበት አግባብ	68369	እነ ሳሙኤል ሃይሉ (ሁለት ሰዎች) እና	ጥር 04/2004	576

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀፅ 7, 9-19, 2(6)		እነ ወ/ሮ ስምረት አያሌው /ዘጠኝ ሰዎች/		
	አፈፃፀም				582
150	ፍርድን ከማስፈፀም ጋር በተያያዘ በተጀመረ የአፈፃፀም መዝገብ የተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ቀርቦበት በበላይ ፍ/ቤት ትዕዛዙ ከተለወጠ የአፈፃፀም ሂደቱ መቀጠል ያለበት አፈፃፀሙን በጀመረው የበታች ፍ/ቤት ደረጃ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 371-385	64129	ኢስላሚክ ሪሊፍ ኢትዮጵያ እና አቶ መሐመድ ሠይድ	ህዳር 21/2004	583
151	• ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተገናኘ የሚንቀሳቀስ ንብረት የሀራጅ ሽያጭን አስመልክቶ ተፈፃሚነት ያላቸው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች • የሚንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የተካሄደ ጨረታ ሊፈርስ የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.432-438, 445	70378	እነ አቶ ልኡልሰገድ አጥላባቸው (አራት ሰዎች) እና እነ ፍሎራ ኢኮ ፖ'ወር ኃ/የተ/የግል ድርጅት (ሁለት ሰዎች)	ጥር 04/2004	585
152	ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በፍ/ቤት የተሰጠን ትዕዛዝ አለማክበር ስለሚያስከትለው ውጤት፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 156, 409(1) የፍ/ብ/ህ/ቁ.400	65814	ሚ/ር ቺዛኖ ቤነኛ እና አቶ ዘውዱ ወልደሥላሜ	የካቲት 29/2004	588
153	ለባልና ሚስት በብድር ገንዘብ የሰጠ ባንክ የባልና ሚስቱ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ተወስኖ ንብረት ለመከፋፈል በአፈፃፀም ደረጃ ለሚገኝ ፍ/ቤት መብቱን ለማስከበር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 418 የሚያቀርበው የተቃውሞ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.418, 419 አዋጅ ቁ. 97/90	69385	ዳሽን ባንክ (አ/ማ) እና እነ ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 28/2004	593

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ.97/90 የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 89				
154	አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው በሚል ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ክፍፍሉን በተመለከተ ጥያቄ የቀረበለት የአፈፃፀም ችሎት ንብረቱ ሰነድ አልባ ነው የሚል ምክንያትን ብቻ በመያዝ ለአፈፃፀም የቀረበውን መዝገብ በመዝጋት የሚሠጠው ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 225(2),423,392(1),371(1)	73041	ወ/ሮ ሰይዳ ደበሌ እና አቶ ሸሪፍ ሸኩር	ሰኔ 22/2004	596
	የዳኝነት ስልጣን				**598**
155	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር አስፈፃሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳዳር ባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸው የሊዝ ውሎችን መሠረት አድርገው የሚነሱ የውል አፈፃፀምና ተያያዥ ጉዳዮችን አይቶ ለመወሰን የከተማው ፍ/ቤቶች የሥረ-ነገር ስልጣን ያላቸው (የተሰጣቸው) ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ሀ) እና (መ)	77175	አሜሪካ ዩኒቨርሲቲ አፍ ኢትዮጵያ እና እነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር (ሶስት ሰዎች)	ሐምሌ 19/2004	599
156	ሃይማኖታዊ ከሆኑ አለመግባባቶች ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቶች የአምልኮት ሥርዓትን ሆነ ሃይማኖታዊ ህገ-ደንቦችን በመተርጎም ውሣኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 11(1)(3), 37(1)	66957	የኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን እና በኢትዮጵያ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትቤተክርስቲያን የሐዋሳ ቁጥር 2 ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የቦርድ አባላት፡-	የካቲት 26/2004	603

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

157	የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የከተማው አስተዳዳር የሚያስተዳድራቸውን የንግድ ቤቶች ባለቤትነትን በተመለከተ በግለሰቦች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን ለማየት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(ረ) አዋጅ ቁ. 408/96 አንቀጽ	69064	ወ/ሮ አክሊለ ገብሬ እና አቶ መለኮት ክንፈሚካኤል	ጥር 18/2004	607
	ልዩ ልዩ				**610**
158	የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች የገንዘብ መጠኑ ከብር 5000 በታች የሆኑ ማናቸውም የፍትሐብሔር ክርክር ለመመልከት ስልጣን አላቸው ተብሎ በአዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 50(1) የተመለከተው ድንጋጌ ተግባራዊ መሆን ያለበት የቀረበው ጉዳይ ልዩ ባህሪ እየታየ በጉዳዩ ላይ የሚነሣው የህግ ጥያቄ ውስብስብነት በመመዘኛነት (በመለኪያነት) ተይዞ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 50(1) አዋጅ ቁ.25/88 አንቀፅ 5(1), 6 አዋጅ ቁ.416/96 አንቀፅ 41	54990	የኢት/ቴሌኮ ሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ማርቆስ አበበ	ህዳር 18/2004	611
159	• የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት በክልል ጉዳዮች ላይ የሰጡትንና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ ለማረም ስልጣን ያለው ስለመሆኑ • የሰበር ስርዓት በባህሪው ከይግባኝ ሥርዓት የተለየ ስለመሆኑና በሰበር ደረጃ ተጨማሪ ምስክሮችንና ማስረጃዎችን አስቀርቦ መስማትና የፍሬ ነገር ጉዳዮችን ተቀብሎ ማስተናገድ አግባብነት የሌለውና ህገ-ወጥ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገመንግስት አንቀፅ 80(3)ለ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.343(1)	55273	አቶ ዘውዱ ግዛው እና ወ/ሮ አየለች ደስታ	ህዳር 18/2004	615
160	የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባለው የውክልና ስልጣኑ በዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠን ውሣኔ የለወጠው ከሆነ ጉዳዩ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ከመቅረቡ በፊት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ), (2)(4)	64845	አቶ ሀብቱ ሀጋዚ እና እነ የኮምቦልቻ	የካቲት 26/2004	618

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ.322/95 አዋጅ ቁ.25/88 አንቀፅ 9(2), 5(2)		ግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ (ሁለት ሰዎች)		
161	የፌዴራል መንግስት ተቋማት በአጠቃላይና የከፍተኛ ት/ት ተቋማት በተለይ የራሳቸው የሆነ የእድገት አሰጣጥ፣ የቅሬታ አፈታትና አጠቃላይ አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚከናወንበት አግባብ ያለ በመሆኑ በቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩ ቀርቦ ውሣኔ የሚሰጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 515/99	73549	የዲላ ዩንቨርስቲ እና እነ አቶ የትናየት ጣፋ (ሶስት ሰዎች)	ሰኔ 22/2004	620
162	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአንድ ወቅት የሰጠውን የህግ ትርጉም በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ የተለየ የህግ ትርጉምና የተለየ አቋም መያዙ በቀደመው የህግ ትርጉም መሠረት ዳኝነት የተሰጠበት ጉዳይን እንደገና እንደ አዲስ እንዲስተናገድ ለማድረግ የማያስችል ስለመሆኑ፣	68573	እነ አቶ ጌታቸው ዳየስ /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ሩስያ ከድር	መጋቢት 12/2004	623

www.chilot.me

https://t.me/ethiopianlegalbrief



https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ - 15

የኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ሐምሌ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

ለተመሳሳይ ጉዳዮች በጣም የተራራቁ ውሳኔዎችን በመስጠት ይታይ የነበረውን ችግር በመቅረፍና የውሳኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ የሰበር ውሳኔዎች አስገዳጅ መሆን ከፍተኛ ውጤት አስገኝቷል ማለት ይቻላል። አልፎ አልፎ በውሳኔዎች ጥራትና ስርጭት ሊታዩ የሚችሉ ችግሮች ሥርዓቱ እየተጠናከረ ሲሄድ የሚፈቱ ሲሆን እነዚህን ችግሮች ለማቃለል እኛም ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን። ጥረታችን ሊሳካ የሚችለው በውሳኔዎች ላይ በህግ ምሁራንና ባለሙያዎች ገንቢ የሆኑ ትችቶችና አስተያየቶች ሲቀርቡ ነው።

ለሰበር ውሳኔዎች ጥራትም ሆነ ለፍርድ ቤቶች መጠናከር እና በአጠቃላይ ለስራችን መሻሻል ሊረዱ የሚችሉ አስተያየቶች ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን በድጋሚ መግለጽ እፈልጋለሁ።

የሰበር ውሳኔዎችን ቶሎቶሎ ለማሳተም ባደረግነው ጥረት ቅፅ 15ን በአጭር ጊዜ ማሳተም የቻልን ሲሆን ይህን የ2005 እና 2006 ዓ.ም ውሳኔዎች የያዘውን ቅጽ 15ን ጨምሮ ከዚህ በፊት የታተሙትን ቅጾች በሙሉ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረ ገጽ www.fsc.gov. et ላይ ማግኘት እንደሚቻል ማስታወስ እወዳለሁ።

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ2005 እና 2006 ዓ.ም የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች

ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
አሠሪና ሠራተኛ					
1.	• አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የደረሰበትን የአካል ጉዳት በተመለከተ የጉዳት ካሣ ክፍያ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችለው በአማራጭ አንድም በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ መሠረት አሰሪውን ያለጥፋት በሥራ ክርክር ችሎት ከሶ በመጠየቅ ወይም የአሰሪውን ጥፋት መነሻ በማድረግ የጉዳት ካሣ ክፍያ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በፍ/ሔር ችሎት በአሠሪው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ፣ • በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ የጉዳት ካሣን ለመጠየቅ በህጉ የተመለከቱትን መብቶች በአግባቡና በትክክል ተገንዝቦ እንደ ጉዳቱ ሁኔታ፣ አይነትና አግባብነት በተሻለ ሁኔታ የሚጠቅመውን የመብት አድማስ አውቆ በመለየት ተገቢው መብቱ ከመነጨበት የህግ አግባብ አንፃር ክሱን ሊያቀርብ የሚገባ ስለመሆኑ፣ • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5 ድንጋጌ ይዘት አድማሱ በግልጽ በተወሰኑ ጭብጦች ላይ ብቻ ሣይሆን በተከራካሪ ወገኖች ቢነሱ ኖሮ ሊወሰኑ ይችሉ የነበሩ ጭብጦችን ጭምር የሚያካትት ስለመሆኑ፣	80343	ዋሊያ የቆዳ ማለስለሻ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ደረጀ ውለታው	ግንቦት 06/2005	2

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1)፣97 109፣ 138(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 80(2)				
2.	አሠሪ ሠራተኛውን እንደ ሠራተኛ በመቀበል የሚሰራውን ሥራ ባልሰጠበት ሁኔታ ሠራተኛውን ከሥራ ገበታው ቀርቷል በሚል ያለ ማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1) ለ	82091	ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እና አቶ ለገሠ ደሣለኝ	መጋቢት 25/2005	9
3.	የሥራ መሪ የሆነ ሠራተኛ ያለ አግባብ ከሥራ መሰናበቱ ተረጋግጦ ሲወሰንና የአሰሪው የመተዳደሪያ ደንብ የሚፈቅድለት ከሆነ በአዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት ኪሣራ ታስቦ ሊከፈለው የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2574(2) አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 43(4) (ሀ)	84661	አቶ ዳዊት ሽዋቀና እና ስኳር ኮርፖሬሽን	መጋቢት 27/2005	12
4.	ከሥራ ጋር በተገናኘ እንዲከፈል በሚል የሚቀርቡ የደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓት እና ሌሎች ክፍያዎች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው ሠራተኛው ክፍያዎቹን መጠየቅ ይችላል (ይገባዋል) ከሚባልበት ግዜ ጀምሮ እንጂ የሠራተኛው የሥራ ውል ከተቋረጠበት ግዜ ጀምሮ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(1-4)	79476	ኢትዩ ቴሌኮም እና እነ አቶ ዘሪሁን ታዬ (ዘጠና ስድስት ሰዎች)	የካቲት 12/2005	17
5.	የስራ ውል የሚመሠረተው ማንኛወም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሠነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሰሪው ለመስራት የተስማማ እንደሆነ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 2(3),4	81814	እነ ወ/ት ፌቨን የሺጌታ (12 ሰዎች) እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ	ሐምሌ 18/2005	24
6.	በአሠሪው ንብረት ላይ ጉዳት በማድረሱ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የተሰናበተ ሠራተኛ ጉዳቱን ያደረሰኩት በሥራ መደራረብ እና ከልምድ ማነስ ነው የሚል ምክንያት አቅርቦ የተከራከረ መሆኑ ስንብቱን ህገ ወጥ ነው ለማለት የሚያበቃ (የሚያስችል) ስላለመሆኑ፣	86284	ሆራይዞን አዲስ ጎማ (አ.ማ) እና	መጋቢት 13/2005	27

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሸ), 13(3)		አቶ መኮንን ዓለሙ		
7.	አንድ ሠራተኛ የቅጥሩ ውል አይነት ቋሚም ይሁን ግዜያዊ ለሠራተኛ በህጉ በተፈቀዱ ጥቅሞች የመጠቀምና ህጉ የሰጣቸውን ከለላዎች የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 42(2)	87338	ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር እና እነ አቶ ገብሬ በላይነህ (አምስት ሰዎች)	ግንቦት 21/2005	30
8.	አንድ ሠራተኛ ከሥራ መቅረቱ በህመም ምክንያት መሆኑ እንደበቂ ምክንያት ሊወሰድ የሚችለው በህጉ አግባብ፣ በህመሙ ምክንያት ስለመቅረቱ ለአሰሪው ያሳወቀና ፈቃድ ያገኘ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 85(4)	87285	ወ/ሮ የውብዳር ንጋቱ እና ገነት ሆቴል	መስከረም 23/2006	34
9.	የሥራ ኃላፊነቱን ባለመወጣት ተገቢነት የሌላቸው ሰዎችን ወደ አሰሪው ድርጅት ውስጥ ዘልቀው እንዲገቡ በማድረግ ጥፋት የፈፀመ የጥበቃ ሰራተኛ ወደ ድርጅቱ በገቡት ሰዎች ምክንያት የተፈጠረ የፀጥታና የደህንነት ችግር አልተከሰተም በሚል ምክንያት ብቻ አሰሪው በሰራተኛው ላይ የፈፀመውን የስራ ውል ማቋረጥ ተግባር ህገ ወጥ ነው ሊያስብል የሚችል ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሸ), 17(1)(ሸ)(ቀ), 14(2)(ሀ)	90389	የኢትዮጵያ ኤርፖርት ድርጅት እና አቶ በሪሁን በላይ	ጥቅምት 18/2006	38
10.	አንድን ሠራተኛ የሥራ መሪ ነው ለማለት የሚቻለው በህግ ወይም እንደ ድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሰሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈፀም እንዲሁም በተጨማሪነት ወይም ይህንን ሣይጨምር ሠራተኞን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ የማገድ፣ የመመደብ ወይም ሌሎች የሥነ-ሥርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውን እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3(2)(ሐ) አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(1)(ሐ)	92466	ሳይግን ቴክስታይል ቢዩልዲንግ ኮንስትራክሽን ትሬድ ኢንዳሪኢንክ ኢትዮያ ብራንች እና አቶ ተስፋዬ ጥላሁን	ጥር 02/2006	41

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል					
11.	የንግድ ቤትን ከመንግስት የተከራየ ተከራይ ከአከራዩ እውቅና ውጭ ለ3ኛ ወገን የንግድ ቤቱን ማስተላለፉ አከራዩ የመጀመሪያውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ የሚያስችለው ስለመሆኑ፣ በዚሁ መሠረትም አከራዩ ቤቱን ለማስለቀቅ የሚያያደርግው እንቅስቃሴ ሁከት ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6 የፍ/ብ/ህ/ቁ.1140, 1149	82670	እነ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 አስተዳደር ፅ/ቤት (ሁለት ሰዎች) እና ዋጋዬ አሰፋ	መጋቢት 09/2005	46
12.	•አንድን በጽሁፍ የተደረገ ውል ዋና ሰነድ ጠፍቷል በማለት ክርክር በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤት በማስረጃነት በቀረበው የውሉ ሰነድ ኮፒን ተቀብሎ በውሉ የተመለከቱትን ምስክሮች ሊሰማ የሚገባው ጠፍቷል የሚለው ወገን ዋናው ሰነድ ስለመጥፋቱ በተመለከተ በአግባቡ ያስረዳ እንደሆነና የውሉንም ኮፒ አግባብነት ያለው አካል ዋናው የውል ሰነድ ጋር ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው እንደሆነ ስለመሆኑ፣ • የምስክሮቹ ቃል ሊሰማ የሚገባውም የውሉ ቃል ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2011(1),2003 ,1730(1)	84330	አቶ መንግስቱ አሾ እና እነ ወ/ሮ እመቤት ጥላሁን (አምስት ሰዎች)	ሚያዝያ 10/2005	50
13.	አስቀድሞ በተደረገ የኪራይ ውል መነሻነት አንድን የአከራይ ንብረት ይዞ ሲጠቀም የቆየ ተከራይ የኪራይ ውል ግዜው ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ አከራዩ የኪራዩን ዋጋ በመጨመር አዲስ የኪራይ ዋጋ እንዲከፈል ገልፆ እያለ ተከራዩ በቀረበው አዲስ የኪራይ ዋጋ ሳይስማማ ወይም እየተቃወመ በንብረቱ መገልገሉን በቀጠለ ጊዜ ተከራይ ለአከራዩ ሊከፍለው የሚገባውን የኪራይ ዋጋ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2950(1) (2), 1687	81163	አቶ ሲሳይ ረታ እና የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት	የካቲት 11/2005	55
14.	• ከውል አፈፃፀም ሂደት ጋር በተገናኘ በተዋዋይ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኪሣራ ሊሰላ ስለሚችልበት አግባብ፣ • የኪሣራው ልክ ከውል ውጪ የሚደርስ ኃላፊነትን መሠረት በማድረግ በርትዕ ሊወሰን	79794	የማይክሮሊንክ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኮሌጅ	ሚያዝያ 22/2005	59

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለሚችልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790, 1800, 2102(1)(2)		ኃ.የተ.የግል ማህበር እና የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር		
15.	አንድ ውል (ስምምነት) ህግ በጽሑፍ እንዲሆን ሲያስገድድ ውሉ በጽሁፍ መደረግ ያለበት እና በተዋዋይ ወገኖችና በሁለት ምስክሮች ፊርማ ሊረጋገጥ የሚገባ ስለመሆኑና መሀይማንና ማየት የተሳናቸው ሰዎች የሚያደርጉት ውል በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት የተደረገ ካልሆነ በቀር በውሉ የማይገደዱ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1727, 1728(3), 2005	83674	ወ/ሮ እቴነሽ ካሳ እና ሀጂ ጀማል ይማም	ግንቦት 19/2005	65
16.	በመያዣ ውል መነሻነት አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት ከነይዞታው የያዘ ሰው በይዞታው ላይ የንብረቱ ባለቤት ሳይቃወመው ግንባታ የፈፀመ ከሆነ ተጠቃሹ የመያዣ ውል አይፀናም በሚል ተዋዋዬቹ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ሲደረግ የንብረቱ ባለቤት በመያዣው ይዞታ ላይ የወጣውን የግንባታ ወጪ ግንባታውን ላካሄደው ወገን ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1818, 2162	90862	ወ/ሮ ተዋበች ኃይሌ እና ወ/ሮ አያንቱ በዬቻ	ታህሳስ 14/2006	69
17.	የማይንቀሣቀስ ንብረት ተከራይ የሆነ ሰው ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል ለ3ኛ ወገን በኪራይ ሊሰጥ የሚችለው ተከራዩ አስቀድሞ ለአከራዩ አሳውቆ አከራዩ የማይቃወም መሆኑ ሲታወቅ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2957(1)(2), 1731 በአ.አ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ቢሮ ደንብ ቁጥር 3/2004, 4/2004	86847	አቶ ፀጋዬ አማን እና እነ አቶ መሐመድ ነጋሽ (ሶስት ሰዎች)	ጥቅምት 18/2006	73
18.	ከሠራተኛ ቅጥር ውል ጋር በተገናኘ የዋስትና ግዴታ የገባ ሰው የሠራተኛው የቅጥር ውል እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ ከተደረገ በኋላ ሠራተኛው ከተሻሻለው ወይም ከተለወጠው የቅጥር ውል ጋር በተያያዘ ያለበትን ተጠያቂነት አስመልክቶ አስቀድሞ	86813	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት እና	መስከረም 22/2006	77

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በገባበት የዋስትና ግዴታ መሰረት ተጠያቂ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1827(1)		እነ ሰሚር መላኩ (ሶስት ሰዎች)		
19.	• ተከራካሪ ወገኖች በአንድ የሰነድ ማስረጃ ላይ የተመለከተን ፊርማ የማን ስለመሆኑ በሚመለከተው የመንግስት አካል ተጣርቶ ውጤቱ ከቀረበና ከታወቀ በኋላ ሰነዱ በውጭ አገር ተመርምሮ ውጤቱ እንዲታወቅ በማለት የሚያቀርቡት ጥያቄ በህግ አግባብ አጥጋቢና አሣማኝ ምክንያትን በመጥቀስና በማስረጃ አስደግፈው ያላቀረቡ እንደሆነ ጥያቄው ተቀባይነት ሊኖረው የማይቻል ስለመሆኑ፣ • የፍ/ቤት የተሰጠ ትእዛዘ /ውሣኔ/ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚቻለው በተከራካሪ ወገኖች ፍትህ የማግኘት መብት ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2008, 2007, 2001, 2005	86187	አቶ ዳንኤል ዘሚካኤል እና አቶ ቢሃሪ ባቡላል ሞዲ	ሰኔ 21/2005	80
የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት					
20.	• በፍ/ብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገሩ እንዲነጠር የሚደረገውም በማስረጃ የሚነጥረው ፍሬ ነገር ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ፣ • ማስረጃ እንዲሠማ የሚፈልግ ወገን ማስረጃው የሚሰማበትን ነጥብ ለይቶ የማስረጃውን አይነትና የሚገኝበትን ቦታ ሁሉ በመጥቀስና በእጁ ላይ ያለውንም አያይዞ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.223,234,137(3),145,256,136-138,246,248	77983	እነ አቶ እንድሪስ አደም (አምስት ሰዎች) እና ወ/ሮ አስናቀች ጥላሁን	መጋቢት 24/2005	87
21.	አንድን ጉዳይ በተመለከተ ተከራካሪ ወገኖች በየበኩላቸው በተለያዩ ፍ/ቤቶች (ችሎቶች) አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ክሶች ባቀረቡ ግዜ (የክርክሮቹ ደረጃ ምንም ይሁን ምን) ክሶቹ ተጣምረው ታይተው ሊወሠኑ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 8(1),11,244, 245	81275	ወ/ሮ ዘምዘም ወንድሙ እና አቶ አብዲሰቡር አብዱሰመድ	ሰኔ 05/2005	92
22.	• ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ ጋር በተገናኘ መብቱን ለማስፈፀም ጠይቆ በአፈፃፀም	83007	እነ ወ/ሮ አልማዝ	ሰኔ 03/2005	98

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ ውሣኔ ተሰጥቶ እያለ ባለመብት ነኝ የሚለው ወገን የሚያነሣው የመብት ጥያቄና ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • በአንድ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በህግ አግባብ እስካልተሻረ ድረስ የውሣኔው አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት በባለጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ ሣይሆን በማናቸውም አስፈፃሚ አካላትና በማናቸውም ፍርድ ቤት ላይ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 79(2)		ገመቹ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ፋዩ ገመቹ		
23.	በአንድ ጉዳይ ተከሣሽ የሆነ ወገን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ካቀረበ ፍ/ቤቱ ከቀረቡት ክሶች መካከል በሥረ-ነገር ስልጣኑ ሥር ያሉትን መርጦ ለማየትና ከሥረ-ነገር ስልጣኑ በላይ የሆነውን ጉዳይ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይቅረብ በማለት የከሣሽን ክስና የተከሣሽን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ተነጣጥለው እንዲታዩ በማድረግ የሚሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 30(1)¸324(1) (ሀ),215(2)¸17(3)	83169	ፕሮፌሰር አደም ዓሊ አህመድ እና አዳማ ጠቅላላ ሆስፒታልና ሜዲካል ኮሌጅ ኃ/የተ/የግል ማህበር	መጋቢት 28/2005	103
24.	• አንድ ስምምነት በፍ/ቤት ሊፀድቅ የሚችለው ጉዳዩ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት በመታየት ሂደት ላይ እያለ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩን በስምምነት የጨረሱ መሆኑን ገልፀው ይኼው ስምምነት ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣ • ከፍርድ ቤት ውጪ በሚደረግ እርቅ ወይም ግልግል መሰረት ያለመግባባትን ያስቀሩ ወይም ለጉዳያቸው እልባት ያገኙ ሰዎች የእርቁን ወይም የግልግሉን ስምምነት በፍርድ ቤት ማስመዝገብ ወይም ማስፀደቅ የማያስፈልጋቸው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3312 እና 3324	85873	እነ ወ/ሮ ኒኢማ አባድጋ አባዋጂ እና አቶ ጣሐ ጀማል አደም	መጋቢት 13/2005	108
25.	አንድን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የሚመለከት ፍ/ቤት በህጉ አግባብ ክስ ተሻሽሎ ከፍ ያለ ዳኝነት ባልተጠየቀበት ሁኔታ በግምት ላይ ተቃውሞ ቀርቦ ግምቱ እንዲጣራ ሲደረግ የንብረቱ ግምት ከፍ ማለቱ በመረጋገጡ ብቻ ቀድሞ ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ	86551	ወ/ሮ ብዙነሽ ወ/ሚካኤል እና	መጋቢት 25/2005	112

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1) ,92, 225, 226, 250,136		እነ አቶ ሽመልስ ቦጋለ		
26.	ወራሽነትን በማረጋገጥ በተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ ላይ መብቱን ወይም ጥቅሜን ይነካል በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ የመቃወሚያ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ሥለመሆኑ እና ተረጋግጦ የተሰጠውን ማስረጃ በሌላ ክርክር መቃወም የሚችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358	79871	እነ ወ/ሮ የውብዳር ባንቱ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሎሚ ተሊላ (አምስት ሰዎች)	የካቲት 11/2005	116
27.	አንድን ጉዳይ አስመልክቶ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው እስከሆነና ጉዳዩን ለማየት በህግ በግልጽ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ሌላ አካል እስከሌለ ድረስ ጉዳዩ በቀጥታ በፍ/ቤት ቀርቦ ሊስተናገድና ውሣኔ ሊሰጥበት የሚችልና የሚገባ ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1), 79(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4	80202	እነ አቶ ሐጎስ ሸጎዕ (ሁለት ሰዎች) እና የመሸነ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	የካቲት12/20 05	120
28.	የክስ አቀራረብ ሥርዓቱን አሟልቶ ያልቀረበ ክስን ፍ/ቤቶች ሌላኛውን ወገን ሳይጠሩ ለመዝጋት ስለመቻላቸው፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 33, 80, 222, 225, 226 እና 231	83915	አቶ ዩሐንስ በቀለ እና የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	የካቲት 29/2005	123
29.	የማይንቀሳቀስ ንብረት የመፋለም ክስ ጋር በተያያዘ ክርክር ቀርቦ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በክርክሩ ተሣታፊ የነበረ ወገን ንብረቱን አስመልክቶ ተሰጥቶ የነበረው የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መክኗል በሚል የሚያቀርበው አዲስ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በፍርዱ መሠረት የተጀመረው አፈፃፀም ሂደትን ለማስቆም የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195,1196 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6,358,378 የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78(1), 79(1)(4) , 37	42501	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የአስር አለቃ ደምሴ ዳምጤ ወራሾች (ሶስት ሰዎች)	የካቲት 28 /2005	126

https://t.me/ethiopianlegalbrief

30.	የማይንቀሣቀስ ንብረት (ቤት) ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ በውሉ መሠረት የቤቱን ስመ-ንብረት የሚመለከተው አካል ወደ ገዢው ለማዞር እንዲችል በሚመለከተው ክፍል ቀርቦ ተገቢውን እንዲፈፀም በማለት ገዥ የሚያቀርበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(1)(ሀ), 33(2-3), 222, 224	82234	አቶ አየለ መኮንን እና እነ ወ/ሮ ጦቢያው ወንድም ገዛው (ስድስት ሰዎች)	የካቲት 26/2005	130
31.	ፍርድ ቤቶች ለቀረበላቸው ጉዳይ አወሣሠን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን የተገነዘቡ ከሆነ ይዜው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያሉትን ማጣራት ሁሉ ለማድረግ ስለመቻላቸው፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136, 137, 272, 327(3), 345	72980	ወ/ሮ ይርገዱ አዲሱ እና እነ ህጻን ምስጋናው ዘሪሁን (ሶስት ሰዎች)	ሐምሌ 06/2004	134
32.	ሚስትነትን በተመለከተ የአመልካችን ማስረጃ ብቻ በመቀበል ሚስትነትን በማረጋገጥ በፍ/ቤት የሚሰጥ ማስረጃ (Declaratory Judgment) በማናቸውም ጊዜ ተዓማኒነትና ክብደት የሌለው ማስረጃ መሆኑን ለማሳየት ክርክር ሊቀርብበትና ተቃራኒ ማስረጃ ተሰምቶ ውድቅ ሊደረግ የሚችል እንጂ ማስረጃውን በተሰጠው ፍ/ቤት ተቃውም በማቅረብ ያልተሻረ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣	82679	ወ/ሮ ከበቡሽ ሸዋረገድ እና ወ/ሮ እንዳገር ጌቱ	መጋቢት 27/2005	138
33.	በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ከነበረ ክርክር ጋር በተገናኘ በተከራካሪዎቹ ወገኖች አመልካችነት ጉዳይ በእርቅ በማለቁ የተከራካሪዎቹን የእርቅ ስምምነት ተቀብሎ በማጽደቅ እንዲመዘገብ በማለት በፍ/ቤት የተሰጠ ትእዛዝ ላይ መብቴ ወይም ጥቅሜ ተነክቷል የሚል ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚያቀርበው የመቃወሚያ አቤቱታ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ትእዛዙን የሠጠው ፍ/ቤት አቤቱታውን ተቀብሎ ሊያስተናግደው የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358,360,277(1)(2)	83582	ወ/ሮ ወርቅነሽ ውብነህ እና እነ ወ/ሮ አልማዝ ዓለሙ (ሶስት ሰዎች)	መጋቢት 27/2005	144
34.	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 ተፈፃሚነት በተከራካሪ ወገኖች መካከል በዋናው ጉዳይ ላይ ከላይ ወደ ታች በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች ከተደረገ ክርክርና ከተሰጠ ውሣኔ ጋር በተገናኘ እንጂ በአፈፃፀም ከተሰጠ ትእዛዝ (ውሣኔ) ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ ነው ሊባል የማይችል	84446	ጠበቃ አንበርብር ዓባይነህ እና	ሚያዝያ 24/2005	149

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 32		ፍትህ ሚኒስቴር		
35.	አንድን ጉዳይ ለማየት በህግ ስልጣን በሌለው ፍ/ቤት ታይቶ የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ካልደተረገ በቀር በጉዳዩ ላይ አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 212	85718	አቶ ቴምድሮስ አማረ እና አቶ አዲሱ ፍሰሃ	ሰኔ 03/2005	153
36.	በአንድ የቀረበ ክስ በተከሣሽነት የተሰየመ ወገን በከሳሽ ከቀረበበት ክስ ጋር በተገናኘ ክስ በቀረበበት ንብረት (ጉዳይ) ጋር በተያያዘ የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ በህጉ አግባብ የተከሣሽ ከሣሽነት ክሱን ተገቢውን ዳኝነት በመክፈል ያቀረበ ካልሆነ በስተቀር ዳኝነት ሊሰጥ የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1) (ረ)(ሠ), 215(2), 235(2)	86454	እሪ ወ/ት ፍሬወይኒ አለም (ሶስት ሰዎች) እና አቶ አለም መሐሪ	ግንቦት 23/2005	156
37.	•ከሣሽ የሆነ ወገን የሚያቀርበውን የዳኝነት ጥያቄ አይነትና መጠኑን በክሱ ማመልከቻ በግልጽ በማስፈር ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣ •ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በህግ የተፈቀደን መፍትሔ ለማግኘት በግልጽ ዳኝነት መጠየቅ የሚገባቸው ስለመሆኑ፣ •የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241 ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማ ተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ያቀረቡት ክርክር ለማብራራት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 246-248 መሠረት ጭብጥ ለመመስረት እንዲያግዝ እንጂ በጽሁፍ ማመልከቻ ላይ ያልሰፈረን የዳኝነት ጥያቄ ተከራካሪዎች እንዲጠይቁ የሚያስችል ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 222, 234, 235, 236, 83, 224, 182, 241, 246-248, 251, 255	86510	ሙሉ ኤሌክሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል /አ.አ/	ሰኔ 18/2005	160
38.	በፍ/ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተመለከተው 60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ግዜ ታሳቢ የሚያደርገው እና ተፈፃሚ የሚሆነው ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት ውሣኔ መሰጠቱን ወይም ለውሣኔ የሚያበቃ ክርክር የተደረገ መሆኑን ተረድተው ቀርበው ለመከታተልና የዳኝነቱን ውጤት ለመስማትና ለማወቅ ያልፈለጉትን ወይም ደግሞ የተከራካሪዎችን የመደመጥ መብት ማክበር ይቻል ዘንድ በህጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በአግባቡ ጥሪ	87190	ቄስ ዳንኤል አርኬ እና የኮልፌ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ	መስከረም 21/2006	164

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ተደርጉላቸው በጥሪው መሠረት ክርክራቸውን በአግባቡ ለመምራት ባልቻሉ ወገኖች ላይ ስለመሆኑ፣				
39.	• የኑዛዜ ህጋዊነት ጋር በተያያዘ በተካሄደ ክርክር ተሣታፊ ሆኖ ተቀባይነት ያጣና ኑዛዜው በፍርድ ቤት የፀደቀበት ሰው በሌላ ጊዜ የኑዛዜውን ህጋዊነት አስመልክቶ በመቃወሚያነት የሚያቀርበው ክርክር ወይም አዲስ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ዳኝነት መስጠት የሚገባው በስርዓቱ መሠረት የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ መሠረት በማድረግ እንጂ ቀድሞ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ተገቢ አልነበረም በሚል ምክንያት ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5,212 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881	85102	አቶ ሰንደቁ አበበ እና አቶ ሐብታሙ ቃበቶ	መስከረም 21/2006	168
40.	•በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ መደበኛውን የሙግት ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ መከናወን ያለበት ስለመሆኑ፣ •በፍርድ አፈፃፀም ደረጃ ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር በሚል የመቃወሚያ አቤቱታ በቀረበ ግዜ ጉዳዩን የያዘው የአፈፃፀም ችሎት በንብረቱ ላይ ተቀዳሚ መብት አለኝ በሚል የቀረበውን የመቃወም አቤቱታ በመደበኛው የሙግት ሥነ-ሥርዓት ሂደት ክርክሩን በማስተናገድ ንብረቱ እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የሚያደርግ ህጋዊና በቂ ምክንያት መኖር ያለመኖሩን በማስረጃ በማጣራት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 419, 421	86133	እነ አቶ ፍቅሩ ከበደ (አስራ አንድ ሰዎች) እና ወ/ሮ አስቴር አርአያ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 20/2006	172
41.	የፍርድ ቤትን እገዛ በመጠየቅ ማስረጃ ማስቀረብ የሚቻለው ጠያቂው ተከራካሪ ወገን እንዲቀርብ የተጠየቀውን ማስረጃ ትክክለኛ ግልባጭ በቅርብ ግዜ ለማምጣት የማይችልበትን ወይም ለማስገልበጫ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመክፈል የማይቻል መሆኑን እንዲሁም ማስረጃው ለክርክሩ ምን ያህል ጠቃሚነት እንዳለውና ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያስችል ስለመሆኑ በጽሁፉ ገልፆ ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ስለመሆኑ፣	89494	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የሚች ዘካሪያ ኢብራሂም ባለቤት ሳዲያ ኢብሮሽ	ጥቅምት 19/2006	177

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 145(1)(2),				
42.	• ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጋር በተገናኘ አንድ ሰው ሚች በተውት ኑዛዜ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ክፍያ እንዲከፈለው ክስ አቅርቦ ገንዘቡ እንዲከፈል ዳኝነት ከተሰጠ በኋላ በሌላ ግዜ የሚቹ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በማለት የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • ኑዛዜን መሠረት አድርጐ የሚቀርብ የኑዛዜ ተጠቃሚት መብት ይረጋገጥልን ጥያቄና የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄዎች ተመሳሳይ የሆነ የፍሬ ነገርና የህግ ጥያቄ የሚያስነሱ ጉዳዬች ስለመሆናቸው፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(2)	90543	እነ አቶ ተሾመ አሰፋ (ሶስት ሰዎች) እና ወ/ሪት መስታወት አሰፋ	ጥቅምት 21/2006	183
43.	በችሎት በመገኘት ስልክን ማስጮህ ብሎም ፍርድ በሚነበብበት ጊዜ በችሎት ዳኛው ሥነ-ሥርዓት እንዲይዝ ሲነገረው ችሎቱ በሥነ-ሥርዓት ያናግረኝ በማለት ያልተገባ ባህሪ ማሣየት በችሎት መድፈር ወንጀል ሊያስቀጣ የሚችል ተግባር ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 481 የወንጀል ህግ ቁጥር 449(1)(ሀ)	92459	አቶ ፍጽም ብርሃን ገ/ክርስቶስ እና ተጠሪ፡ የለም	ጥቅምት 19/2006	186
44.	• ከወጪና ኪሣራ አወሣሠን ጋር በተገናኘ ከቅን ልቦና ውጪ ለክርክር የተዳረገ ወገን የክርክሩ ረቺ መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ቅን ልቦና ከሌላው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት በሚል ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ፣ • የወጪና ኪሣራ ጥያቄን አስመልክቶ ፍ/ቤቶች በመጠኑ ላይ ለመወሰን በህግ ስልጣን የተሰጣቸው ስለመሆኑና ረቺ የሆነ ወገን ሁል ግዜ ወጪና ኪሣራ እንዲተካለት ሊወሰን ይገባል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 462-464	91103	ዩቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር እና እነ የአቶ ፉአድ መሃመድ እናት ወራሽ ወ/ሮ ማሪያም አብዱላሂ (ሁለት)	ታህሳስ 16/2006	188
45.	በሌለበት የተሰጠ ውሣኔ እንዲነሣ በቀረበ አቤቱታ መነሻነት ፍ/ቤቱ አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ያነሳውና አቤቱታ አቅራቢው ክርክሩን እንዲያቀርብ በድጋሚ እድል ከተሰሠጠው	90452	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ጥር 14/2006	191

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በኋላ የጽሁፍ ክርክሩን ያላቀረበና ክሱ በሚሰማበት ቀጠሮ ያልቀረበ እንደሆነ ክርክሩን እንደገና ለመስማት በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት የከሣሽ ክስና ማስረጃ እንደገና ተመርምሮ ተገቢው ውሣኔ ከሚሰጥበት በቀር እንዲነሣ ትእዛዝ የተሰጠበት የቀድሞው ውሣኔ በቀጥታ ተመልሶ እንደገና እንዲፀና ሊደረግ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78(2), 70(ሀ)		እና አቶ ገ/ሥላሴ በርሄ		
46.	ሀሰተኛ ማስረጃ ለፍ/ቤት በመቅረቡ የተነሣ የተወሰነበት ተከራካሪ ወገን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)ን መሠረት በማድረግ ፍርዱ በድጋሚ እንዲታይለት አቤቱታ ባቀረበ ጊዜ ሀሰተኛ ማስረጃውን የሰጠው አካል በምን ምክንያት በህገ ወጥ ተግባር ሀሰተኛውን ማስረጃ ሊሰጥ እንደቻለ የማስረዳት ግዴታ ጭምር አለበት ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) የወንጀል ህግ አንቀጽ 403፣405	91968	አቶ ግርማ ሰንበት እና ወ/ሮ አልማዝ ገብረየስ	ታህሳስ 15/2006	194
47.	• ተከራካሪ ወገኖች በቅድሚያ ሊያቀርቧቸው ሲችሉ ሆነ ብለው ወይም በቸልተኝነት ያላቀረቧቸውን ማስረጃዎች በክርክር ሂደት ሁሉ እያንጠባጠቡ ሊያቀረቡ ወይም የማስረጃ ማሰባሰብ ሥራውን ፍርድ ቤት እንዲያከናውን ሊጠይቁ የሚችሉበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ • በፍ/ቤት እገዛ ማስረጃ የሚቀርበው ተከራካሪ ወገን አጠቃቅሎ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ስለመሆኑና ፍ/ቤቱ የተጠየቀው ማስረጃ ለተያዘው ጉዳይ ያለውን አግባብነት በተመለከተ የተቀበለው እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1)	85468	ማባ ኢንጂንሪግ ኃ.የተ.የግል ማህበር እና የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጂንሲ	መስከረም 24/2006	197
48.	• ተከራካሪ ወገኖች ለክርክራቸው ምክንያት ሊሆን የሚችለውን ጉዳይ ወይም ያከራከራቸውን ጉዳይ በእርቅ ስምምነት የጨረሱ እንደሆነ የእርቅ ስምምነቱ ግብ ተከራካሪዎቹ (ታራቂዎቹ) በግላቸው ያላቸውን መብትና ግዴታ እንደሁኔታው በማስተካከል ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን ጉዳይ በስምምነት ማስቀረት ስለመሆኑና የእርቅ ስምምነቱ ውጤትና ተፈፃሚነቱ እርቁን ባደረጉት ተከራካሪ ወገኖች መካከል ብቻ ተገድቦ	87834	በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት እና	መስከረም 21/2006	204

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የሚቀር እንጂ የሌሎች 3ኛ ወገኖች መብትና ግዴታ ሁሉ በማካተት የ3ኛ ወገኖች መብትና ግዴታን አብሮ በእርቅ እንዳለቀ የሚያስቆጥር ስላለመሆኑ፣ • የተከራካሪ ወገኖች የእርቅ ስምምነት በፍ/ቤት ትእዛዝ (ውሣኔ) መጽደቅና መመዝገብ መብቴን ወይም ጥቅሜን ይነካል በሚል 3ኛ ወገኖች የሚያቀርቡት የመቃወም አቤቱታ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3311 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358		ፀዳለ ካሣቀ (ሶስት ሰዎች)		
49.	አንድ ፍርድ ቤት ክርክርን በሚሰማበት ወቅት የሚሰጠው ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ (Interlocutory order) ላይ በመነጠል ክርክር የሚካሄድበት ዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችለው የተሰጠው ትእዛዝ በባህሪው የሰውን መታሰር ወይም የንብረት ማስተላለፍን ወይም ስም ማዞርን ጉዳይ በተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320(3)(4)	89893	ኮንቴክ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ወልዱ ሀሉፍ	መስከረም 24/2005	207
50.	• የዳግም ዳኝነት (Review of Judgement) ዓይነተኛ ዓላማ ተገቢ ሁኔታዎችና ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸው ሲረጋገጥ በሀሰተኛ ማስረጃ፣ በመደለያና በመሰል ወንጀል ጠቀስ ድርጊቶች ምክንያት የተዛነፈን ፍትህ ወደ ነበረበት መመለስ ስለመሆኑ፣ • የዳግም ዳኝነት ጥያቄ (አቤቱታ) ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ተግባራት የሚከናወንበት በመሆኑ ጥያቄው ለሰበር ችሎት በቀረበ ጊዜ ችሎት አቤቱታውን ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ላላቸው የስር ፍ/ቤቶች ሊመራውና ሊያስተላልፈው በሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)(ሀ)(ለ) አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ)	93137	ወ/ሮ ብጥር ታገለ እና ወ/ሮ አገር ተሰማ	የካቲት 11/2006	210
51.	በተከራካሪ ወገኖች ክርክር በሚካሄድበት ወቅት በፍ/ቤት ትእዛዝ በተከራካሪ ወገን ስም በባንክ የሚገኝ ገንዘብ ታግዶ እንዲቆይ ተደርጐ ትእዛዙ ፀንቶ በነበረበት ግዜ በገንዘቡ ላይ	83771	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	መጋቢት 10/2005	214

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ወለድ ሊታሰብ ይገባል ወይስ አይገባም በሚል ክርክር የተነሣ እንደሆነ ከጉዳዩ ልዩ ባህሪ ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የልዩ አዋቂ ምስክርነትና የባለሙያ ማብራሪያን አስቀርበው በማጣራት ሊወሰኑ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136		እና እነ ወ/ሮ ዘነበች አለማየሁ (ሁለት ሰዎች)		
52.	ባለ አምስት ዳኞች የሚሰየሙባቸው የክልል ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች በአጣሪው ችሎት ጉዳዩ ያስቀርባል በሚል በተመለከተው ነጥብ (ጭብጥ) ሳይገደብ ሌላ (ሌሎች) ጭብጦችን በመመስረት ክርክሩ እንዲሰማ በማድረግ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣	90298	አቶ ኃይሉ ዴሬሳ እና ወ/ሮ ሱፌ አለሙ	የካቲት 10/2006	217
የንግድ ህግ					
53.	• የንግድ መደብር ኪራይ ከንግድ ቤት ኪራይ የተለየ ስለመሆኑ፣ • የንግድ መደብር የተከራየ ሰው ያለአከራዩ እውቅና እና ፈቃድ መደብሩን ለ3ኛ ወገን በኪራይ አሳልፎ ለመስጠት ስለመቻሉ፣ የንግድ ህግ ቁ. 127 (ሐ),145(ለ),	79561	አቶ ፀጋዬ አማን ለጃ እና በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት	የካቲት 11/2005	221
54.	የንግድ ማህበር ሒሣብ ከተጣራና ትርፍና ኪሣራው ተለይቶ ከቀረበ በኋላ የማህበር አባል (ባለአክሲዮን) የሆነ ሰው ከትርፍ ሊደርሰው የሚገባውን የድርሻ ክፍያ በመለየት ክፍያ እንዲፈፀምልኝ በማለት የሚያቀርብው ጥያቄ ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁጥር 211, 517, 518, 532(1)	82503	እነ ወ/ሪት ቤዛ ዱጉማ (ሁለት ሰዎች) እና ዘሚሊ ቀለም ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሚያዝያ 21/2005	224
55.	• የህብረት ሥራ ማህበራት ንብረት እንደ የአባለቱ የጋራ ሀብት (ንብረት) ተቆጥሮ ንብረቱን ለመሸጥ የሁሉም አባላት ስምምነት ያስፈልጋል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ • የህብረት ሥራ ማህበራት አሰራር ጋር በተያያዘ ውሣኔ ለማሳለፍ የሚችለው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስለመሆኑ፣	85009	ሃጅ ፈዬ ገመቹ ሄዳኡ እና እነ አቶ ዓለሙ በቀለ (አስራ አምስት ሰዎች)	መስከረም 21/2006	229

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 147/91 አንቀጽ 21, 18, 32, 19 ደንብ ቁጥር 106/96 አንቀጽ 20(2) 123				
56.	አበዳሪ የሆነ ባንክ ለተበዳሪው ላበደረው ገንዘብ በመያዣነት ለያዘው ንብረት የመድን ሽፋን የገባለት እና የአርቦን ክፍያን ለመክፈል የተስማማ እንደሆነ ለመድን አስገቢው ተቋም የአረቦን ክፍያውን ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ • የንግድ ህግ ቁጥር 657, 675	83489	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ግንቦት 19/2005	233
ቤተሠብ					
57.	ከሚች በስጦታ ወይም በኑዛዜ የተሰጠን ንብረት ወደ ውርስ መልሶ ማግባት (Collation) ስለሚከናወንበት ሥርዓት፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1065-1078	80920	ወ/ሮ ውድነሽ እሸቱ እና አቶ ፍቅረማሪያም ወርቁ	የካቲት 25/2005	237
58.	ኑዛዜ ፈራሽ ነው በሚል ስለሚቀርብ ክስ እና ክሱ ሊቀርብ ስለሚገባበት የጊዜ ገደብ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973, 974	82585	እነ ወ/ሮ ሱዛን ሞንታልባን (ሶስት ሰዎች) እና እነ አቶ ሙራድ አሊ (ስድስት ሰዎች)	የካቲት 13/2005	240
59.	ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጋር በተገናኘ የውርስ ሀብት ተጣርቶና ሪፖርት ቀርቦ በመጽደቁ መነሻነት ሀብቱ ተከፋፍሎ ከተፈፀመ በኋላ ወራሾቹ ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሣይኖራቸው ውርሱን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ አድርጓል በሚል እውነተኛ ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት የውርስ ንብረቶች እንዲመለሱለት በሚል ለመጠየቅ የሚችለው ተገቢውን የዳኝነት ክፍያ በመክፈል አዲስ ክስ በመመስረት እንጂ ክፍፍሉ ተፈጽሞና ውሣኔ አግኝቶ የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996(1), 998(1), 999	89641	እነ ወ/ሮ ሐረገወይን ብርሃኑ(ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ አዜብ ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 21/2006	243

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91, 6				
60.	ተጋቢዎች የጋብቻቸውን ፍቺ አስመልክቶ ጉዳዩ በመደበኛው ፍ/ቤት ቀርቦና ክርክር ተካሄዶ ውሣኔ ከተሰጠበት በኋላ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጉዳይ ሀይማኖታዊ ስርዓትን በመጠቀም በሸሪአ ፍ/ቤት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1)(2), 244(2)(ለ), 245(2) አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 5(4), 6(2) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 34(5)	93779	ወ/ሮ ጂአቶ ያሲን ሺበሺ እና አቶ ሐሰን መሐመድ	ታህሳስ 30/2005	247
61.	• የአባት ስም እንዲስተካከልልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ • አንድ ሰው አንድ የቤተዘመድ ስምና አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞችና የአባት ስም ሊኖረው ስለመቻሉና የአንድ ልጅ የአባት ስም የሚሆነው የአባቱ የግል ስም ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231 (1)(ሀ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 32(1)፣ 36(1)	95995	ወ/ት ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ እና ተጠሪ፡- የለም	የካቲት 10/2006	251
62.	የቤተ ዘመድ ስም እንዲለወጥ በፍ/ቤት ጥያቄ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 42 , 33(1) , (2)	87420	ወ/ሪት ማህሌት ልዑለቃል እና ተጠሪ የለም	ሚያዝያ 24/2005	254
ጉምሩክ/ግብር/ታክስ					
63.	ግብር የተጣለበትን የካፒታል ንብረት ዝውውር የመቀበል ወይም የመመዝገብ ወይም በማናቸውም መንገድ የማጽደቅ ስልጣን ያለው (የተሰጠው) የመንግስት አካል ግብሩ መከፈሉን ሣያረጋግጥ ዝውውሩን እንዲቀበል፣ እንዲመዘግብ ወይም እንዲያፀድቅ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 37(7)	79189	የኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ባለስልጣን እና ጂ.ኤም.ቲ ኢንዱስትሪያል	መጋቢት 9/2005	258

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			ኃ/የተ/የግል ማህበር		
64.	• አንድ ሰው ለመንግስት ሊከፍል የሚገባውን ግብር ባለመክፈሉ በወንጀል ተግባር ሊጠየቅና ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚችለው ግብሩን ላለመክፈል በማሰብና ግብር አስገቢው መ/ቤትም ንብረቶቹን በመያዝና በመሸጥ የግብር ገንዘቡን ገቢ እንዳያደርግ ለማድረግና ግብር የመክፈል ኃላፊነቱን ለማምለጥ ንብረቶቹን ለማሸሽ፣ የመሰወር ወይም ሌሎች ተገቢነት የሌላቸው ህገ ወጥ ተግባራትን በመፈፀም ግብርን ያልከፈለ መሆኑ ሲረጋገጥ እንጂ በሌሎች በህግ ተቀባይነት ባላቸው ምክንያቶች ግብሩን ለመክፈል ሳይችል የቀረ እንደሆነ ስላለመሆኑ፣ • ማንኛውም ሰው በፍ/ብሔር ጉዳይ ያለበትን እዳ ለመክፈል ባለመቻሉ ምክንያት ብቻ በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የማይገባ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 49 አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 96, 162 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 13(2) ደንብ ቁጥር 78/94 ICCPR- አንቀጽ 11	84623	እነ ጅ. አግሪ ፖክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች) እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት	ሰኔ 04/2005	261
65.	የንግድ ሥራ ፈቃድ ኖሮት ነገረ ግን በህግ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፈቃዱ ሳይታደስ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የተገኘ ሰው የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ እንደሌለው ተቆጥሮ በወንጀል ኃላፊነት ጥፋተኛ ተደርጐ ሊያስቀጣው የሚችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 2(10), 36, 60(1)	86388	አቶ ባዘዘው ይሁን እና የአ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ	ሰኔ 17/2005	268
66.	ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተገናኘ ከሚመለከተው የገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ፈቃድ ሳያገኝ ተገቢ ያልሆኑ ፓዶችን (የVAT ደረሰኞችን) ማሳተምና መገልገል በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑና የድርጅቱ ባለሀብት (ሥራ አስኪያጅ) ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው ያልነበረ መሆኑን በመግለጽ የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው ማንኛውም በጐ አሳቢ ሰው ሊያደርገው የሚችለውን ጥንቃቄ ያደረገና ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ድርጅቱን በመምራት ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን ማስረዳት	86597	ግሎሪ ኢትዮጵያ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር እና አቶ በርሀ ረዳ ኪዳኑ	መስከረም 21/2006	271

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የቻለ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56(3),(ለ), 3(1)(ለ), 2(11), 3(1)(ሀ) አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 2, 19(50) (ሐ)				
67.	አንድ በንግድ ሥራ የተሰማራ ሰው (ድርጅት) በተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ለሰበት ለማለት የሚቻልበት እንዲሁም መመዝገብ ሲኖርበት ሳይመዘገብ ቀርቶ ግብር ሊጣልበት ስለሚችልበት አግባብ፣ አዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 3(1)(3), 16(1)(ለ)	82061	አቶ አብዶልቀድር ሁሴን እና የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት	መስከረም 20/2006	274
68.	የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነ ነጋዴ (ሠው) ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሽያጭን አከናውኗል በሚል በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችልበት አግባብ፣ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 11(1)(2)፣ 22(1)(3) አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 11(1) የወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2)፣ 58(3) ደንብ ቁጥር 139/1999	86672	የኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ እና አቶ በቀለ ተሰማ (ሁለት ሰዎች)	መስከረም 22/2006	277
69.	• ከጉምሩክ ህግና አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በኮንትሮባንድ ወንጀል ተጠርጥሮ በጉምሩክ ተቋም በቁጥጥር ሥር እንዲውል የተደረገ የንግድ ተሽከርካሪን አስመልክቶ ለንብረቱ ባለቤት የተቋረጠ ጥቅም (ገቢ) እንዲከፈል ሲወሰን የካሣውን መጠን ለመወሰን የተሽከርካሪውን ዓመታዊ የተጣራ ገቢ በተመለከተ ባለንብረቱ ለሚመለከተው የመንግስት አካል በህጉ አግባብ ያሳወቀውን የገቢ መጠን ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብና መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ • በአንድ የመንግስት ባለስልጣን ተረጋግጦ የተሰጠ የሰነድ ማስረጃ በህጉ መሠረት ተቃውሞ ቀርቦበት ዋጋ የሌለው ስለመሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ማስረጃው በማስረጃነት ዋጋ ሣይሰጠው ሊታለፍ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣	89640	የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን እና ሰይፈዲን አብዱልቃድር	መስከረም 23/2006	281

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2010, 2011, 2090, 2091, 2141, 2152, 2153 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136, 138, 180 (1)				
	ንብረት				
70.	የአንድ እምነት ወይም ሐይማኖት ተከታይ ወይም አማኝ በመሆን በሐይማኖታዊ ተቋሙ ውስጥ የመቃብር ቤት ገንብቻለሁና የቤቱን ግምት ይከፈለኝ በሚል ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር በተገናኘ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179 ድንጋጌ ተፈፃሚ ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1179 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 11,27 (1-3) UDHR-Art. 18 ICCPR.Art. 18(1)	85979	የሐረር (ደ/ሳ) ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን እና ወ/ሮ ማንያህልሻል አበራ	መጋቢት 13/2005	286
71.	ከመንግስት የተከራየውን ቤት ከአከራዩ ፈቃድ ውጪ ለ3ኛ ወገኖች አከራይቶ ሲገለገል የነበረ ሰው በመንግስት መመሪያ መሠረት ቤቱ ተከራይቶ ሲሰራበት ለነበረው ሰው በመተላለፉ ምክንያት የመጀመሪያው ተከራይ በመመሪያው መሠረት ቤቱ የተላለፈለት ሰው ላይ የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣	88798	አቶ ሙሉ አብርሃ ገ/ሕይወት እና እነ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት (ሶስት ሰዎች)	ሐምሌ 18/2005	291
72.	•የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ነገር በቀጥታ ወይም በጥበቃ ሥር የሆነ ይዞታ ሲኖረው ስለመሆኑ፣ •የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም አይነት መብት በሌለው ሰው ላይ ስለመሆኑ፣ •የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርብ ሰው ንብረቱ በይዞታው ሥር የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚዉ የኃይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጥር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ፣	80241	ጽናት የሆቴል ቱሪዝም ስራዎች ኃ.የተ.የግል ማህበር እና እነ አቶ ዳመነ ነጋ (አምስት ሰዎች)	የካቲት 12/2005	295

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	•የሁከት ተግባር ተፈጥሯል ለማለት ባለይዞታ የሆነው ሰው በይዞታው ሥር በሚገኘው ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ወይም ረብሻ የፈጠረበት ስለመሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፣ •በህግ አግባብ በተደረገ የኪራይ ውል መነሻነት ይዞታን በእጁ ያደረገ ሰው (ተከራይ) ላይ አከራይ የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣				
73.	የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ጋር በተገናኘ ንብረትነቱ ከአገር የወጡ ኤርትራዊያን የሆነ ቤትን ለማስተዳደር ውክልና የተሰጠው ሰው የመሸጥ ውክልና በባለቤቱ ያልተሰጠ ቢሆንም እንኳን በሚመለከተው የመንግስት አካል በተሰጠ (በተላለፈ) መመሪያ መሠረት ከተወካዩ ቤቱን የገዛ ገዥ ተወካዩ ቤቱን የሸጠለት በሌለው የውክልና ስልጣን ነው በሚል ገዝቶ ስመ ንብረቱ ከተላለፈለት በኋላ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ቤቱ ለባለቤቱ ሊመልስ ይገባል ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀጽ 2(1), 4(1), 5(1)(ሀ)	83060	ገ/ማሪም ገ/መድህን እና ጣዕመ ወ/ስላሴ	ሰኔ 21/2005	300
74.	የውርስ ሀብትን እንዲያጣራ የተመደበ የውርስ ሀብት አጣሪ የንብረትነቱ የሚች የግል ሀብት መሆን በተመለከተ በሪፖርቱ ገልጿል በሚል ምክንያት ከንብረቱ ጋር በተገናኘ የባለሀብትነት ክርክር ያቀረበውን ወገን ጥያቄ በአግባቡ ባለማስተናገድ ውሣኔ ላይ መድረስ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መግስት አንቀጽ 40(1), 37 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 1206	83665	ወ/ሮ እታፈራሁ ፀጋዬ እና እነ ወ/ሮ መሰረት ግርማ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 22/2005	305
75.	• አንድ ሰው ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ የሚችለው በህግ ጥበቃ የሚደረግለትንና ያለውን መብት እንጂ የሌላውን መብት ስላለመሆኑ፣ • በህግ ጥበቃ የሚደረግለት መብት ሣይኖር በስሙ የተመዘገበ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀተ ከያዘ ሰው ንብረቱን በመንደር ውል የገዛ ገዢ ተገቢውን ማጣራት በማድረግና፣ በጥንቃቄ፣ የገዛና የቅን ልቦና ያለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ • የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት	88084	ወ/ሮ ወጋየሁ ታምሩ እና እነ የወ/ሮ አስካለ ወሰኔ ወራሽ ፍሬዘውድ ጌታቸው (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 19/2006	309

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ደንብና አሰራርን መሠረት ያላደረገ እንዲሁም ከስልጣን ውጪ የተሰጠና በህግ ፊት የማይፀና ስለመሆኑ በማናቸውም ማስረጃ ለማረጋገጥ የተቻለ እንደሆነ በተሰጠው የምስክር ወረቀት የተፈጠረውን የህጉን የህሊና ግምት ማፍረስ የሚቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196, 2884, 2882-2884 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(1)(2)				
76.	ፍርድ ቤቶች ከሣሽ በክሱ ገልፆ በትክክል ዳኝነት የጠየቀበት ጉዳይ በቤት ላይ ያለውን የባለሀብትነት መብት ለማስከበርና የመፋለም ክስ ሆኖ እያለ ክሱ የቀረበው በአዋጅ የተወረሰ ቤት ወይም ከአዋጅ ውጪ በባለስልጣን ቃል ትእዛዝ ወይም በቀላጤ የተወሰደን ቤት ለማስመለስ ነው በሚል ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሚሰጡት ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 47/67 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2257	86049	አቶ ሻፊ አብዱራህማን አብዱ እና ወ/ሮ አንሻ እንድሪስ (ሶስት ሰዎች)	መስከረም 20/2006	313
ከውል ውጭ ኃላፊነት					
77.	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት አንድ ሰው በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ባደረሰ ጊዜ ጉዳት የደረሰበት ንብረት ባለቤት ለንብረቱ የመድን ዋስትና የገባ ሆኖ የመድን ተቋሙ በመድን ውሉ መሠረት ጉዳት ለደረሰበት ወገን የጉዳት ካሣ በመክፈል በጉዳት አድራሹ ንብረት ባለቤት ላይ ብቻ ክስ በመመስረትና ጉዳቱን በቀጥታ ያደረሰውን ሰው በመተው ጉዳቱ ለደረሰበት ሰው የከፈለውን የጉዳት ካሣ ክፍያውን እንዲከፍለው ለመጠየቅ ስለመቻሉ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677, 1896, 2081, 18, 2156 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 36(2)	89504	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና እነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን (ሁለት ሰዎች)	መስከረም 22/2006	317
78.	• ባለፎቶግራፍ ወይም ባለስዕሉ ካልፈቀደ በቀር የማንም ሰው ፎቶግራፍ ወይም ስዕል በህዝብ አደባባይ ሊለጠፍም ሆነ ሊባዛ ወይም ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑና ፎቶው ወይም ስዕሉ ጥቅም ላይ ለዋለበት የማስታወቂያ ሥራ ባለፎቶው ወይም ባለስዕሉ ካሣ ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ፣	91710	ሕጻን ሪያን ሚፍታህ እና ኤልሲውዲ ኬብልስ	ህዳር 16/2006	319

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• ለባለ ፎቶው ወይም ለባለስዕሉ የሚከፈለውን የካሣ መጠን ድርጊቱን የፈፀመው ሰው በዚሁ ድርጊት ያገኘው ሀብት (ጥቅም) ተመዛዛኝ በሚሆንበት መጠን በዳኞች ሊወሰን ስለመቻሉ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 28 29(2), 2142		ኃላፊነቱ የተ.የግል ማህበር		
79.	• ጥቅምን መሠረት ባላደረገ ሁኔታ ህፃናትን (እድሜው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰውን) አሳፍሮ በመንዝ ወቅት በደረሰ አደጋ ምክንያት በህፃናቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ የተሸከርካሪው ባለቤትና በወቅቱ በተሸከርካሪው ሲገለገል የነበረ ወይም ሹፌሩ የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርባቸው ስለመሆኑ፣ • የተሸከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው ጥቅም በሌላው ግንኙነት መነሻ በተሸከርካሪው ተሳፍሮ ሲጓዝ በነበረ ሰው ላይ ለሚደርስ የአደጋ ጉዳት ካሣ ለመክፈል የማይገደድ ቢሆንም ጉዳቱ የደረሰው ከፍተኛ ጥንቃቄና እንክብካቤ ሊደረግላቸው በሚገባ ህፃናት ላይ በሆነ ጊዜና ህፃናቱም ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ በተሸከርካሪው ላይ የተጫኑ (የተሣፈሩ) እንደሆነ የተሸከርካሪው ባለቤት የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 36(2), 15, 25 የህፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3, 6(1) የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 4(1), 5(1) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2126(2), 2127, 2130 2131, 2089(2), 2081(1)	92020	እነ የኢ.ፌ.ዲ.ፌ ፌዴሬሽን ምክር ቤት (ሁለት ሰዎች) እና ቁስ ማሞ ይታፈሩ	ታህሳስ 15/2005	323
80.	አንድ ሠው በሰራው ሥራ ወይም በፈፀመው ድርጊትና ድርጊቱ በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ምክንያት በ3ኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በፍ/ብሔር ኃላፊነት ተጠያቂ የሚሆን ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2069	88432	ወጣት ደሣለኝ ወንታ እና አቶ ኡስማን መሐመድ	መስከረም 22/2006	327
81.	•አንድ የመንግስት መ/ቤት በሠራተኛው ተግባር በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው በሠራተኛው የተፈፀመው ጥፋት የሥራ ጥፋት ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ፣ •አንድ ጥፋት የሥራ ጥፋት ነው ተብሎ የሚወሰደው ጥፋት አድራጊው በጥፋቱ ላይ	82154	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እና	መጋቢት 24/2005	330

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወደቀው በቅን ልቦና በስልጣኑ ለሥራው ክፍል መልካም ያደረገ መስሎት የፈፀመው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑና ከዚህ ውጪ በሆነ ጉዳይ ግን ጥፋቱ እንደ ግል ጥፋት የሚቆጠር ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2126, 2127 (1)(2)(3)		ተጠሪ፡ አቶ ፍቅሩ ኃይሌ		
የዳኝነት ስልጣን					
82.	ከንግድ ምዝገባ ፈቃድ ጋር በተገናኘ የሚነሱ የፍሬ ነገር ክርክሮችን የመደበኛ ፍ/ቤቶች አይተው ለመወሰን ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 686/2002 አንቀጽ 61	81934	የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት እና 50 አለቃ ታምራት ከበደ	የካቲት 28/2005	336
83.	ከአስገብኚና የጉዞ ወኪል የንግድ ሥራ ፈቃድ ጋር በተያያዘ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ መኪኖችን በተመለከተ የሚቀርብ ክርክርን መደበኛ ፍ/ቤቶች በቀጥታ ክስ ለማስተናገድ የሥረ ነገር ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 87(1), (5), (9), (10), ደንብ ቁጥር 146/2000	86817	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ግሎሪ ኢትዮጵያ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር	መስከረም 22/2006	338
84.	የክርክሩ ገንዘብ መጠን ከአምስት ሺህ ብር በታች በመሆኑ ምክንያት ብቻ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የሚቀርብን ክርክር የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች አይተው ለመወሰን ስልጣን አላቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 138, 142 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9(1), 231(1)(ለ), አዋጅ ቁ. 416/96 አንቀጽ 41(1),	89530	ቲኤንቲ ኮንስትራክሽንና የንግድ ስራዎች ድርጅት እና አቶ እያዩ ደጀኔ	ጥቅምት 21/2006	341

https://t.me/ethiopianlegalbrief

85.	ከህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በተገናኘ የማህበር የሥራ ኃላፊዎችን በተመለከተ ገንዘብ አጉድለዋል በማለት ገንዘቡ እንዲከፈል ማህበሩ በኃላፊዎቹ ላይ የሚያቀርበው ክስ አስቀድሞ በእርቅ ካልተቻለ ደግሞ በሽምግልና ሊታይ የሚገባው እንጂ በቀጥታ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ሊቀርብበት አይችልም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑና መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49(1-4), 47(1), 26(2), 39(1)(ለ)(ሐ), 152 አዋጅ ቁጥር 402/96 አንቀጽ 46 ደንብ ቁጥር 106/96 አንቀጽ 14(ሀ)(ሐ)(መ)	90737	የንጋት ኮከብ ሸማቾች ኃ/የተ የግል ማህበር እና እነ አቶ የሴፍ እንድሪስ (አስር ሰዎች)	ህዳር 16/2006	344
86.	አንድን ክርክር በማስተናገድ ላይ ያለ የክልል ፍ/ቤት በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ተቋም (ድርጅት) አግባብነት ያለው የጣልቃ ገብ አቤቱታ በቀረበለት ጊዜ ጉዳዩን ጣልቃ ገቡን ወደ ክርክሩ በማስገባት አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሌለው በመሆኑ ክርክሩ ጣልቃ ገብን ባካተተ መልኩ ለማየት ወደሚችለውና ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ጉዳዩ ቀርቦ ሊታይ የሚገባ መሆኑን ገልፆ መዝገቡን መዝጋትና ተከራካሪዎችን ማሰናበት የሚገባ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(6),14 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(4) የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 64(4) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9, 231(1)(ለ)	90920	ዓባይ ኢንሹራንስ አ.ማ እና አቶ አለማየሁ አሰፋ	ህዳር 06/2006	347
		ወንጀል			
87.	አንድ ሠው በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከስሶ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በተመሳሳይ ማስረጃ በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ተጠያቂ ነው (ኃላፊነት አለበት) ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149 የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 141	78470	አቶ ታሪኩ ጫኔ እና የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	ሚያዝያ 07/2005	351
88.	አንድ ሠው በአንድ ወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ የሆነ ውሣኔ ተሰጥቷል	85237	ዘካሪያስ ገ/ጻዲቅ	መጋቢት 27/2005	355

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በማለት በድጋሚ ልከሰስ አይገባም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ከዚህ ቀደም ተጣርቶ ክስ የቀረበበትና የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት የወንጀል ድርጊትን በድጋሚ (ለሁለተኛ ጊዜ) ክስ ቀርቦበታል ከተባለው የወንጀል ድርጊት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 2(5), 678, 696(ሐ) እና 378 ህገ መንግስት አንቀጽ 23		እና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ		
89.	በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሣሽ ላይ የሚወሰነው የእስራት ቅጣት አፈፃፀም እንዲገደብ ለማድረግ ስለማይችልባቸው ሁኔታዎች፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 194(1) እና (2)¸190¸192	85596	እነ ሰይፉ ደስታ እና የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ	መጋቢት 25/2005	359
90.	ህጋዊ መከላከል (Legitimate self-defense) በወንጀል የማያስቀጣው የራስን ወይም የሌላን ሰው መብት ህገ ወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ህገ ወጥ ጥቃት ለማዳንና ጥቃቱ እንዳይደርስ ከማድረግ ሌላ አማራጭ (መንገድ) ሣይኖር ከሁኔታው መጠን ባለማለፍ የተፈፀመ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 78 ,79	86570	ጌታቸው ገላዬ ፈረደ እና የደቡብ ክልል ዐቃቤ ሕግ	ሚያዝያ 07/2005	363
91.	• አንድ ሠው የአራጣ ወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችልበት አግባብ፣ • በወር 10% ወለድ ታስቦ እንዲከፈል በመስማማት ገንዘብ ማበደር በአራጣ የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ 667(1)	80119	አቶ ተድላ ተገኝ እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ	የካቲት 11/2005	367
92.	• በሌላ ሰው ጥቅም የሥራ አመራር ላይ ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ •በተከታታይ ለተፈፀመ ወንጀል ይርጋ ስለሚቆጠርበት አገባብ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/፣702/3/፣219/2/	79389	እነ ዶ/ር ታጀዲን ያህያ (ሁለት ሰዎች) እና የአማራ ክልል ዐ/ሕግ	መጋቢት 12/2005	371

https://t.me/ethiopianlegalbrief

93.	አንድ ሰው በስራው ስልጣን መሠረት በአደራ የተሰጠውን ወይም ሊጠብቀውና ሊከላከለው የሚገባውን የህዝብ ወይም የመንግስት ጥቅም የሚጐዳ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ በወንጀል ህግ አንቀጽ 411 መሠረት በወንጀል ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 411(ሐ), 407	86845	የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ እና አቶ ሰለሞን ዩሐንስ	መስከረም 22/2006	374
94.	•የአንድ ደርጊት ወይም ግድፈት ወንጀልነት በህግ በግልጽ ተደንግጐ በማይገኝበት ሁኔታ የድርጊቱን ወይም የግድፈቱን ፈፃሚ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ፣ •በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክስ ስለ ድርጊቱና አፈፃፀሙ የሚሰጠው መግለጫ ድርጊቱን ወንጀል ከሚያደርገው ህግ አነጋገር በጣም የተቀራረበ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ፣ •በንግድ ሥራ ለተሰማሩ ወይም ሌሎች ሰዎች በግለሰብ ደረጃ መጠኑ በርካታ የሆነ ገንዘብን በተደጋጋሚ በብድር የመስጠት ተግባር በህግ የተከለከለ ወይም በወንጀል የሚያስቀጣ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 2, 23(2), 3, 61 የወ/መ/ህ/ሥሥ/ቁ. 112 አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1), (ሸ), 2(ሀ),	81178	የኢዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ እና እነ አቶ ከበደ ተሰራ (ሁለት ሰዎች)	መስከረም 21/2006	380
95.	ነፍሰጡር (እርጉዝ) የሆነች ሴትን ሆዷ ላይ በመምታት ጽንሱ እንዲሞት ማድረግ ድርጊቱን በፈፀመው ሰው ላይ በግድያ ሙከራ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 27(1), 581(ለ), 540	90089	ዘኒት አባቡ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ዐ/ህግ	ጥቅምት 20/2006	384
96.	• አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈጽሟል ሊባል የሚችለው የድርጊቱን ውጤት እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ድርጊቱ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ማወቅ ይችል ነበረ ለማለት የሚቻል እንደሆነ ስለመሆኑ፣ • አንድ ሰው የፈፀመው ድርጊት በቸልተኛነት ነው ለማለት በመስፈርትነት ሊወሰድ የሚገባው የድርጊቱ ፈፃሚ በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ	93741	አቶ አብነት ዋቆ ብሩ እና የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ	ታህሳስ 14/2005	387

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ስለመሆኑና ይህም የድርጊቱ ፈፃሚ የነበረው እውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባውን እውቀትና ግንዛቤ መመዘን ያለበት ከግለሰቡ እድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ የትምህርት ደረጃ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 59(1), 543(2), 57				
97.	ፈቃድ የሌላቸው የጦር መሳሪያዎችና ጥይቶችን በቤቱ ውስጥ አከማችቶ የተገኘ ሰው መሣሪያዎቹን ለመነገድ በሚል ሀሳብ የያዘ መሆኑ የተረጋገጠ ካልሆነ በስተቀር ግለሰቡ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው በወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) ሣይሆን በአንቀጽ 809(ሀ) ሥር በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ), 809(ሀ)	93173	እነ አቶ ተዋበ እስጢፋኖስ (ሁለት ሰዎች) እና የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ	ታህሳስ 17/2006	391
98.	አንድ ሠው የአንድን ጉዳይ መከሰት በምክንያትነት በመግለጽ ከሌላ ሰው ገንዘብን ተበድሮ መውሰድ ተከስቷል የተባለው ጉዳይ ካለመከሰት ጋር በተገናኘ ተበዳሪው በእምነት ማጉደል ወንጀል ሊያስጠይቀው የሚችል ስላለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 675	89276	ተፈሪ ሚናሞ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ዐቃቤ ሕግ	መስከረም 23/2006	395
99.	• አንድ ሠው ወንጀል አደረገ የሚባለው ህገ ወጥነቱ እና አስቀጪነቱ በህግ የተደነገገ ድርጊት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ስለመሆኑና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ስለመሆኑ፣ • ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በሙላ አሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆኑ ድርጊቱን የራሱ ያደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 2፣23(1)፣ 32(1)	91535	አቶ አህመድ አደም በሽር እና የአማራ ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ	የካቲት 12/2006	400

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 111፣112፣141፣142				
ባንክ እና ኢንሹራንስ					
100.	የመድን ዋስትና ሽፋን ውል ተደርጓል እንዲሁም ውሉ ተሻሽሏል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ የንግድ ህግ፡ 657	78180	አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና ወ/ሮ አስቱር ንጉሴ	መጋቢት 09/2005	405
101.	• አንድ ውል በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ ለማከናወን ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ፣ • የመድን ዋስትና ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ ከትራንስፖርት ጋር በተገናኘ በወጡ ህጐች ከተፈቀደው የመጫን አቅም በላይ ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ መድን ሰጪው የዋስትናውን ሽፋን ገንዘብ ለመድን ገቢው የመክፈል ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678(ለ)	90793	ግሎባል ኢንሹራንስ እና እነ አቶ ፍጹም ላቀው (ሁለት ሰዎች)	ታህሳስ 04/2006	410
አፈፃፀም					
102.	• በውጭ አገር የተሰጠን ፍርድ በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ለማስፈፀም ስለሚቻልበት አግባብ፣ • በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድን በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ከማስፈፀም ጋር በተያያዘ በአፈፃፀም ሂደቱ ክርክር በተነሣ ግዜ የፍርድ አፈፃፀሙን በያዘው ፍ/ቤት ክርክሩ ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 458-460	78206	እነ ወ/ሮ ዩስራ አብዱልመኢን (ሶስት ሰዎች) እና አቶ አብዱልቀኒ አብዱልመኢን	ሰኔ 20/2005	415
103.	• በአንድ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ላይ ፍርድ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁ የፍርድ ባለገንዘቦች ያሉ እንደሆነ አፈፃፀሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 መሠረት ሊስተናገድ የሚገባ እንጂ በሌላ የፍ/ባለመብት ምክንያት በሌላ የአፈፃፀም መዝገብ ላይ የተሰጠው	88867	ሪዩስ ኢንጂነሪንግ አክሲዮን ማህበር እና	ታህሳስ 28/2006	423

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የእግድ ትእዛዝ ተነስቶ የአፈፃፀም ጥያቄው ካልቀረበ በስተቀር ሊቀጥል አይችልም ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣ • አፈፃፀሙ በሚካሄድበት ወቅት በንብረቱ ላይ የመያዣ ውልን መነሻ በማድረግ የቀዳሚነት መብት አለን የሚሉ ወገኖች ያሉ እንደሆነም ጥያቄው በቀረበ ጊዜ እንደየአግባብነቱ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ስለመሆኑ፣ • አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በንብረቱ ባለቤት ላይ የገንዘብ ክፍያ ፍርድ አሰጥተው እና ገንዘቡም እንዲከፈላቸው ጥያቄ ያቀረቡ የፍርድ ባለገንዘቦችን አስቀርቦ ጥያቄያቸውን በመመርመር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አኳያ አገናዝቦ በመመልከት አፈፃፀሙ ሊመራ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403, 378		የአክሱም ኮንስትራክሽን ባለቤት አቶ ጌታሁን ሁሴን		
104.	ለፍርድ አፈፃፀም ከተያዘ የሀራጅ ጨረታ ሽያጭ ጋር በተገናኘ ለሁለተኛ ጊዜ በወጣው ጨረታ የተያዘው ንብረት ሊሸጥ የሚገባው ባለሙያ ካቀረበው የንብረቱ ግምት ዋጋ በላይ በተገኘ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች ብቻ ሣይሆን የባለሙያው ግምት ሳይጠበቅ በሁለተኛው ጨረታ ከተወዳዳሪዎች መካከል ከፍተኛ የሆነውን ዋጋ ላቀረበው ተጫራች ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 428(1)	89088	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ሞላ እርቂ	ታህሳስ 17/2006	426
105.	አንድን የተሰጠ ፍርድ ከማስፈፀም ጋር በተገናኘ የአፈፃፀም ስልጣን መሰረቱ ፍርዱን መስጠት ወይም ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም የሚያስችል ውክልና ማግኘት እንጂ የፍርድ ባለዕዳውን ወይም ባለመብቱ የሚኖርበት ክልል (ከተማ) ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378	85764	እነ አቶ ኃ/ሚካኤል ታደሰ (አራት ሰዎች) እና አቶ ተስፉ ታደሰ	መስከረም 21/2006	429
ልዩ ልዩ					
106.	የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ቀድሞ የተሰጠን የቤትና ቦታ ካርታና ፕላን ጠፍቷል በሚል ሲጠየቅ በምትኩ ሌላ ሊሠጥ የሚገባው በ3ኛ ወገኖች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት	81023	አቶ ገላና አልጅራ እና	ግንቦት 5/2005	433

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ለማስወገድ በቅድሚያ ጠያቂው በቂ ዋስትና እንዲሰጥ በማድረግ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1197(2)		እነ አቶ ገዛኸኝ ፋይስ (ሶስት ሰዎች)		
107.	•አንድ የመንግስት ሠራተኛ መ/ቤቱን በመወከል ተቋሙ ከ3ኛ ወገን ጋር ካለው አለመግባባት ጋር በተገናኘ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት በዳኝነት ተሰይሞ ለጉባኤው የሚከፈለውን አበል ክፍያ መወሰኑ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሟል ሊያስብለው የሚችል ስላለመሆኑ፣ •በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ዳኝነት የተሰየመ ዳኛ በህግ ስላለበት ኃላፊነት፣ •የግልግል ዳኛ ሆኖ የተሰየመ ሰው በግልግል ዳኝነቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ በወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 351(2)(መ), 317, 318(መ) የወንጀል ህግ አንቀጽ 399 የአ.አ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አዋጅ ቁ. 6/2000 አንቀጽ 31	80301	አቶ አንተነህ ሲሳይ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ	ሚያዝያ 24/2005	440
108.	የመንግስት የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታነት፣ ወይም ወደ አክስዮን ማህበር፣ በሚለወጥበት ወይም ወደ ቀድሞ ባለሀብቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት የማይተላለፉ ሒሣቦችን ለመሰብሰብ ዕዳዎችን ለመረከብና የፍርድ ቤት ጉዳዮችን ለመከታተል ስልጣን የተሰጠው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 208/92 አንቀጽ 5፣6	88060	የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ አ/ማህበር እና አቶ ምስጋናው ጥሩነህ	መስከረም 23/2006	444
109.	• የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የማስተዳደር ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ • የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በህግ የተሰጠውን የማስተዳደር ስልጣን መሠረት በማድረግ በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬት በተመለከተ የከተማዋን መሪ ፕላን እንዲሁም የከተማውን ማህበረሰብ ፀጥታና ደህንነት ታሣቢ በማድረግ በከተማው የሚገኝ ቦታ (መሬት) ለምን ለምን አገልግሎት መዋል እንዳለበት የመወሰን ስልጣንና ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑና ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደ የሁከት	88959	የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ደብረ አማን ተክለኃማኖት ቤተክርስቲያን	ህዳር 17/2006	447

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ተግባር ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑ፣ • አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 11(2)(ለ)(ሰ), 38				
110.	በአቃብያነ ህግ ሙያ የተሰማሩ ሠዎች ላይ ከዲሲፒሊን ጉዳዬች ጋር በተያያዘ ክስ በቀረበ ጊዜ ጉዳዩ በተዋረድ በተቋቋሙትና ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ታይቶ ሊወሰን ስለሚችልበት አግባብ፣ የአቃቤ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁ. 44/1991 አንቀጽ 78, 79, 82(1)(2), 83(1)(3), 84(ሀ), 85, 86(ሀ) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 25, 37	92546	አቶ አብዱራዛቅ ኢብራሒም እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ህግ	ታህሳስ 18/2006	450
111.	አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በህጉ ከተመለከው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበሰብ ሊፈቅድ የማይችል ስለመሆኑ፡- አዋጅ ቁ. 621/2001 አንቀጽ2/2/፣3/4/፣14/5/፣14/2/፣6፣90፣111/2/፣112፣108፣110 ደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 18/3/፣10/2/፣36	75877	የኢትዮጲያ የህግ ባለሙያ ሴቶችማህበር እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	መስከረም 23/2005	454

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሥሪና ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80343

ግንቦት 6 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- ዋሊያ የቆዳ ማለስለሻ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ አቶ አይሸሹም መድፉ በመዝገብ ቤት እሰማለሁ በማለታቸው ዛሬ አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- አቶ ደረጀ ውለታው - ተጠሪም በተመሳሳይ ምክንያት አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ ሠራተኛ በስራ ላይ እያለ ለደረሰ የአካል ጉዳት ካሳ ክፍያ እንዲከፈለው በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1) አግባብ አሰሪውን ያለጥፋት በስራ ክርክር ችሎት ከሶና አስፈርዶ ክፍያውን ከተቀበለ በኋላ በዚያው ጉዳት የአሰሪውን ጥፋት መነሻ በማድረግ የጉዳት ካሳ ክፍያ ከውል ውጪ ባለው ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በተጨማሪ እንዲከፈለው በፍ/ብሔር ችሎት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል የህግ አግባብ መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ነበር፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአመልካች ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ በመስራት ላይ እያለ አራት የቀኝ እጅ ጣቶች እና ሦስት የግራ እጅ ጣቶች በማሽን የመቆረጥ የአካል ጉዳት እንደደረሰበትና ጉዳቱም የደረሰው በአሰሪው ጥፋት መሆኑን በመግለፅ እና በዚህ ምክንያት ሊከፈለው የሚገባው የጉዳትና ሞራል ካሣ ክፍያ በድምሩ ብር 335,680 አመልካች እንዲከፍለው እንዲወሰንለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካችም ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ አሁን ክስ ባቀረቡበት የአካል ጉዳት ካሣ ክፍያ ከዚህ ቀደም በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1)፣ 97 እና 109 ድንጋጌዎች መሰረት በስራ ክርክር ችሎት ክስ አቅርቦና በዚሁ መሰረት ብር 24,000 አስፈርዶ ገንዘቡን በአፈፃፀም ከተቀበለ በኋላ በዚያው ጉዳት ተጨማሪ የጉዳት ካሣ ክፍያ ጥያቄ ለማቅረብ የማይችል መሆኑን በመጀመሪያ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ-ነገር ደረጃም ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ጥፋት ባለመሆኑ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት መሆኑንና በድጋሚ የቀረበው የክስ አቤቱታም የህግ መሰረት እንደሌለው በመግለፅ ክሱ ውድቅ ተደርጎ ሊወሰን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አሁን የቀረበው ክስ ከክዚህ ቀደሙ ክስ ጋር ጭብጣቸው የሚለያይ ነው በሚል ምክንያት የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉን ከገለፀ በኋላ ፍሬ-ነገር ክርክሩን አስመልክቶ አሠሪው ተጠሪ በሚሰራበት ማሽን ላይ ተገቢ የጉዳት መከላከያ መሣሪያ ባለመግጠሙ እና በአሰሪው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥፋት ጉዳቱ የደረሰ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው ሲል ከወሰነ በኋላ የጉዳት ካሣ መጠኑን በተመለከተም ተገቢ ነው ባለው አኳኋን አስልቶ ባጠቃላይ ብር 139,219.9 አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ቀርበው እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ የበታች ፍ/ቤት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡ አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም ለሁለቱም ክሶች ብቸኛ ምክንያት የሆነውና በተጠሪ ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት ካሣ ክፍያ በስራ ክርክር ችሎት ተወስኖለት በአፈፃፀም ካሳውን የተቀበለ ሲሆን ሆኖም ግን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 96(3) ድንጋጌ አግባብ የጉዳት ካሣ ጥያቄ የማቅረብ መብት የተሰጠው ሰራተኛው ከፍ/ብሔር ህጉና ከአሠሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህጉ አንዱን በመምረጥ በአሰሪው ላይ ያለጥፋት ኃላፊነት ወይም በጥፋት ላይ በተመሰረተ በአንዱ ክስ የማቅረብና እንዲካስ እንጂ ያለጥፋት ክስ አቅርቦ ካሣውን ከተቀበለ በኋላ በዚያው የአካል ጉዳት በጥፋት ላይ በተመሰረተ ኃላፊነት ድጋሚ የጉዳት ካሣ ለመጠየቅ አይደለም፡፡ የአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 በአዋጁ ውስጥ እንዲካተት የተደረገው በሰራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት በአሰሪው ጥፋት ከሆነ ለሰራተኛው ሊከፈለው የሚገባ የካሣ መጠን በአዋጁ አንቀጽ 109 ስር በተወሰነው እንዳይገደብ ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባው ከፍ ሲል በተገለፀው መልኩ ሆኖ ሳለ የበታች ፍ/ቤቶች ለድንጋጌው የሰጡት ትርጉም ከድንጋጌው አነጋገር ጋር የማይሄድ ከመሆኑም በላይ አንድ ተጎጂ ለአንድ ጉዳት ሁለት ጊዜ ካሣ የመጠየቅና ሁለት ጊዜ ካሣ የማግኘት መብት አለው በማለት የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ከበቂ ኪሣራና ወጪ ክፍያ ጋር ተሸሮ እንዲወሰንለት በመጠየቅ አመልክቷል፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ተጠሪ አንድ ጊዜ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ያለጥፋት ኃላፊነት በአመልካች ላይ በስራ ክርክር ችሎት ክስ አቅርቦ እና አስፈርዶ የጉዳት ካሳ ክፍያውን ከተቀበለ በኋላ በዚያው ጉዳት እንደገና አሰሪውን በጥፋት ላይ በተመሰረተ ኃላፊነት በፍ/ብሔር ክርክር ችሎት ሌላ ክስ አቅርቦ የጉዳት ካሳ እንዲከፈል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ ጉዳት ከደረሰበት አሰሪው ጥፋት ባይኖርበትም ለደረሰው ጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ ስር የተመለከተ ሲሆን የካሣ መጠኑም በህጉ በተቀመጠው ስሌት መሰረት የሚከፈል ስለመሆኑ ከተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 109 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን የጉዳት ካሣ ዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ እና አይቶ ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው አካልም የሥራ ክርክር ችሎት እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 138(1)(ሠ) ድንጋጌ ስር ተለይቶ የተቀመጠ ጉዳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል ጉዳቱ በሰራተኛው ላይ ሊደርስ የቻለው በአሰሪው ጥፋት ምክንያት የተነሳ እንደሆነ ሰራተኛው የጉዳት ካሣ ክፍያ ጥያቄውን አግባብ ባለው ህግ መሰረት መጠየቅ እንደሚችል ከተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 96(3) ድንጋጌ

ይዘት መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በዚህ ንዑስ አንቀጽ አግባብ መሰረት የሚቀርብ የጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄም በፍትሐብሔር ክርክር ችሎት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተጠቃሹ አዋጅ እና አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው ሰራተኛው በህጉ የተመለከቱትን መብቶች በአግባቡ እና በቅጡ በትክክል ተገንዝቦ እንደየጉዳዩ ሁኔታ ዓይነት እና አግባብነት በተሻለ ሁኔታ የሚጠቅመውን የመብት አድማስ አውቆ በመለየት ተገቢው መብቱ ከመነጨበት ህግ አግባብ አንፃር ለማቅረብ ሲችል ነው፡፡ ሰራተኛው ከደረሰበት ጉዳትና ከጉዳቱ አፈፃፀም በመነሳት ከሁለቱ የአሰሪ ኃላፊነት መንገዶች ውስጥ አንዱን ብቻ በመምረጥ አሰሪውን ያለጥፋት ወይም የአሰሪውን ጥፋት መሰረት ባደረገ ኃላፊነት ክሱን ከወዲሁ ለይቶ የተሻለ መብቱ ከመነጨበት ህግ አኳያ ከሚያቀርብ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ 96(1) እና 96(3) ስር የተመለከቱትን መብቶች ሁለቱንም በማፈራረቅ እንደፈለገ እንዲጠቀም ለማስቻል ታስቦ እና ተፈልጎ አይደለም፡፡ በተጨማሪም አንድ ሰው ክሱን መስርቶ ዳኝነት በሚጠይቅበት ጊዜ በክስ አቤቱታው ላይ የሚጠይቀውን መብት የሚያቋቁሙለትን ትክክል የሆኑትንና የሚታዩትን ተጨባጭ ፍሬ-ነገሮችን ብቻ ገልፆ በማስፈር ክስ ማቅረብ እንዳለበት ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 80(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ይህ በክስ አቤቱታው ላይ ተገልፀው የሚቀርቡት ፍሬ-ነገሮችም እውነት ስለመሆናቸው በአቤት ባዩ መረጋገጥ እንዳለበት እንዲሁ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 92 ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡

የክስ አመሰራረት እና አቀራረብን አስመልክቶ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህጉ ከተደነገጉት አግባብነት ካላቸው ከፍ ሲል ከተገለፀው መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ከዚህ አኳያ ደግሞ አንድ ሰራተኛ አንድ ጊዜ በስራ ላይ የደረሰበት ጉዳትን መነሻ በማድረግ አንዱ የአሰሪውን ያለጥፋት ኃላፊነት ሊያስከትሉ የሚችሉ ፍሬ-ነገሮችን በመግለፅ በሌላ ጊዜ ደግሞ ያንኑ ጉዳት በሚመለከት የአሰሪውን በጥፋት ላይ በተመሰረተ ኃላፊነት የሚያስከትሉ ፍሬ-ነገሮችን እንደፈለገ እና በዘፈቀደ በመግለጽ የተለያየ ዓይነት ክሶችን ለማቅረብ፣ በክርክር አመራር ስርዓት የሚደገፍ እና ተቀባይነት ያለው ድርጊት አይደለም፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ለዚህ ክርክር መነሻ በሆነው ጉዳት መነሻነት አመልካችን ያለጥፋት ለጉዳቱ ኃላፊ በሚያደርገው አኳኋን በስራ ክርክር ችሎት ክስ አቅርቦ እና የአካል ጉዳት ካሳ ክፍያውን ብር 24,000 አስፈርዶ በአፈፃፀም መቀበሉ ይታወቃል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከፍ ሲል በተገለፀው መልኩ በሌላ ጊዜ በድጋሚ ያንኑ ጉዳት በሚመለከት በጥፋት ላይ በተመሰረተ ኃላፊነት የጉዳት ካሳ ክፍያ ከውል ውጪ ባለው ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በፍትሐብሔር ችሎት ታይቶ እንዲወሰንለት ያቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም ምክንያቱም ጉዳዩ በሌላ አኳኋንና መልክ ይዞ ቢሆንም አስቀድሞ ቀርቦ ውሳኔ እንዳገኘ የሚቆጠር ነው፡፡ የመጨረሻ ውሳኔ ስላገኙ ጉዳዮች የሚያወሳው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 ድንጋጌ ይዘት አድማሱ በግልጽ በተወሰኑ ጭብጦች ላይ ብቻ ሳይሆን በተከራካሪ ወገኖች ቢነሱ ኖሮ ሊወሰኑ ይችሉ በነበሩ ጭብጦች ሁሉ ላይም ጭምር በመሆኑና ከዚህ አኳያ ተጠሪ በኋላ ላይ ያቀረበው የክስ ጭብጥም አስቀድሞ እንደቀረበ እና ውሳኔ እንዳገኘ ጉዳይ የሚቆጠር በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5(2) አንፃር በድጋሚ ሊቀርብ አይችልም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች በድጋሚ የቀረበውን የጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄ ተቀብለው እና አይተው አመልካች ለተጠሪ ብር 139,219.9 እንዲከፍል በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ መሰጠቱም ሆነ ይሄው በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም መታረም ሲገባ መፅናቱ ከፍ ሲል በተገለፁት ምክንያቶች ሁሉ በአግባቡ እና ስነ-ስርዓታዊ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ፤ መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 23356 መስከረም 20 ቀን 2004 ዓ/ም ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍ/ፍ/ቤት መ/ቁ 117346 ሚያዝያ 18 ቀን 2004 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በህጉ ከተቀመጡት አማራጮች የላቀውን ጥቅም ወይም መብት የሚያስገኝለትን በመለየት የጉዳት ካሳ ጥያቄውን ማቅረብ ሲገባው በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ መሰረት ጥያቄውን በስራ ክርክር ችሎት አቅርቦና አስፈርዶ የካሳ ክፍያውን ከተቀበለ በኋላ እንደገና ያንኑ ጉዳይ በሚመለከት ከውል ውጪ ኃላፊነት በሚያስከትሉ ድንጋጌዎች አግባብ ያቀረበው ሁለተኛ ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በአዋጁ አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ አኳኋን የጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄ በስራ ክርክር ችሎት አቅርቦና አስፈርዶ የተቀበለ በመሆኑ ሌላ ተጨማሪ የሚከፈለው የጉዳት ካሳ ክፍያ የለም ብለናል፡፡
4. የሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሃሳብ ልዩነት

እኔ በሶስተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የማልስማማ በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ በሀሳብ የተለየሁባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ከላይ በአብላጫው ድምፅ ውሳኔ እንደተገለፀው ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ የነበረ መሆኑና በስራ ላይ እያለ አራት የቀኝ እጁን ጣቶች እና ሶስት የግራ እጁን ጣቶች በማሽን በመቆረጣቸው የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ጣቶቹ ከተቆረጡ በኋላ አመልካች ያለጥፋት አሰሪ በመሆኑ በስራ ላይ ለደረሰብኝ የአካል ጉዳት መክፈል የሚገባውን ካሳ ይክፈለኝ በማለት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96(1) መሰረት በማድረግ ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት እስከ እዚህ ሰበር ችሎት ተከራክሮ አመልካች ለተጠሪ ብር 24,900 (ሃያ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር) እንዲከፍል ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እያለ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍትሐብሄር ችሎት ማሽኑ በሰባት ጣቶቹ ላይ ጉዳት ያደረሰብኝ የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ሳይገጠምለት በመቅረቱ ነው ፤ ጉዳቱ በአሰሪው ጥፋት የደረሰ በመሆኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በፍትሐብሔር ሕጉ ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት በሚወስኑት ድንጋጌዎች መሰረት ካሳ እንዲከፍለኝ ይወሰነልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ተጠሪ በስራ ክርክር ችሎት ክስ አቅርቦ ጉዳዩ ውሳኔ አግኝቷል ፤ ሁለተኛ የካሳ ጥያቄ ማቅረብ አይችልም በማለት መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያው ክስና በሁለተኛው ክስ የሚነሳው ጭብጥ አንድ አይደለም በማለት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪ ብር 139,219.90 (አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ አስራዘጠኝ ብር ከዘጠና ሳንቲም) እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

2. አብላጫው ድምጽ በሥራ ላይ እያለ ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ አሰሪውን ጥፋት ሳይኖረው በአሰሪነቱ የጉዳት ካሳ በአዋጁ አንቀጽ 96(1) መሰረት እንዲከፍለው ከጠየቀ በኋላ ጉዳቱ የደረሰው በአሰሪው ጥፋት በመሆኑ ካሳ ይክፈለኝ በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96(3) መሰረት ለመጠየቅ አይችልም፤ ተጠሪውን በሁለቱም ድንጋጌዎች መክሰስ አይችልም፤ መጀመሪያውኑ ከሁለቱ አንደኛውን የመምረጥ ኃላፊነት አለበት በማለት ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በእኔ በኩል የአዋጅ ቁጥር 377/96 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች በአማራጭ የሚጠቀሱና የሚፈፀሙ ሳይሆኑ ጎን ለጎን በአንድ አሰሪ ላይ ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ድንጋጌዎች ናቸው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ድንጋጌዎች አቀራረጽና መሰረታዊ ዓላማዎች የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ስለካሳ አከፋፈል የሚያራምዳቸው መርሆዎች ናቸው፡፡

3. አዋጅ ቁጥር 377/96 በስራ ምክንያት ስለሚመጡ ጉዳቶች በምዕራፍ ሁለት ከአንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102 ይደነግጋል፡፡ አዋጁ እነዚህን ድንጋጌዎች በሁለት ዘርፍ የከፈላቸው ሲሆን በዘርፍ አንድ ኃላፊነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ከአንቀጽ 96 እስከ አንቀጽ 99 ደንግጓል፡፡ በዘርፍ ሁለት የካሳ አከፋፈል ሥርዓቱን በአንቀጽ 101 እና አንቀጽ 102 ደንግጓል፡፡ አዋጁ በአንቀጽ 95 ገቸርነት ያለውን መርህ የሚደነግግ ሲሆን መርሁ አንድ ሰራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ ወይም ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ጉዳት ከደረሰበት በምዕራፍ ሁለት የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑና በአዋጁ በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡

4. ትርጉሙና ተፈፃሚነቱ አከራካሪ የሆነው የአዋጁ አንቀጽ 96 “በጥፋት ላይ ያልተመሰረተ ኃላፊነት” የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን ንኡስ አንቀጽ 1 “አሰሪው ጥፋት ባይኖረውም ሰራተኛው በስራ ላይ ሳለ በሚደርስበት ጉዳት ኃላፊ ነው፡፡ ይህም ኃላፊነት የሚወሰነው በዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል” የአንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 2 ከጠቅላላው መርህ ከተደነገገው በልዩ ሁኔታ ሰራተኛው ሆነ ብሎ በራሱ ላይ ላደረሰው ማንኛውም ጉዳት፣ አሰሪው ኃላፊነት የሌለበት መሆኑንና ሰራተኛው በአሰሪው አስቀድሞ በግል የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች በመጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን በመተላለፍ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሰክሮ በመገኘቱ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት ሰራተኛው ሆነ ብሎ በራሱ ላይ እንዳደረሰው ጉዳት እንደሚቆጠር የሚደነግግ ነው፡፡ የአንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 3 አሰሪው ሰራተኛው በሥራ ላይ ለደረሰበት ጉዳት በአዋጅ ቁጥር 377/96 ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሕጎች መሰረት ኃላፊ የሚሆንበት ልዩ ሁኔታ የሚያስቀምጥ ድንጋጌ ነው፡፡ የአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ “የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ማንኛውም ሰራተኛ በአሰሪው ጥፋት የተነሳ በስራ ላይ ጉዳት ሲደርስበት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ካሳ የመጠየቅ መብቱን አይነኩበትም” የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የአንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 3 የእንግሊዘኛው ቅጅ “The provision of sub Art 1 of this article shall not affecte the right of the workers to claim damage in accordance with the relevant law where an ocupational injury is a resulet of

https://t.me/ethiopianlegalbrief

fault on the part of the employer" የሚል ነው፡፡ የአንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 3 የቃላት አሰካክ አቀራረፅና ሙሉ ንባብና መልዕክት፣ በአሰሪው ጥፋት በሰራተኛው ላይ ጉዳት መድረሱ ከተረጋገጠ ሰራተኛው አሰሪው ከአንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102 ባሉት ድንጋጌዎች ካሳ እንዲከፍልው የሚያቀርበው ጥያቄና የሚወሰነው ውሳኔ ሰራተኛው አሰሪውን በሌላ ሕግ መሰረት ለጉዳቱ ኃላፊ እንዲባልና ካሳ እንዲከፍለው የመጠየቅ መብቱን የማይነካበት መሆኑን የሚገልፅ ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

5. በእኔ እምነት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አሰሪው ለሰራተኛው በአንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ኃላፊ ከሚሆንበትና ከአንቀጽ 101 እና አንቀጽ 102 መሰረት ከሚከፍለው ካሳ በተጨማሪ አሰሪው ጥፋት በፈፀመ ጊዜ ኃላፊ የሚሆንበት ድንጋጌ ነው፡፡ የአንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ከስራው ጋር በተያያዘ የሰራተኛው ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅና ከአደጋ ለመከላከል የሚያስፈልጉት እርምጃዎችን ሁሉ የመወሰድና እነዚህንም እርምጃዎች በሚመለከት ረገድ አግባብ ባላቸው ባለስልጣኖች የሚሰጡትን ደረጃዎችና መመሪያዎች ባለመከተል፣ ወይም በመጣስ ሰራተኛው በስራ ላይ ለአደጋ ካጋለጠና አደጋ እንዲደረስበት ካደረገ፣ ማናቸውም አሰሪ ከሚከፍለው የካሳ ክፍያ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 4 የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣቱ ምክንያት ሰራተኛው ለደረሰበት ጉዳት ከአሰሪና ሰራተኛ ከተደነገገው ውጭ በሌሎች ሕጎች ኃላፊ የሚሆንበትን የሚደነግግ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 አሰሪው በአዋጅ አንቀጽ 12(4) እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት በመተላለፍና ሌሎች ኃላፊነት የሚያስከትሉ ጥፋቶችን በመፈፀሙ በሰራተኛው ላይ ጉዳት ከደረሰ አሰሪው ከአሰሪነቱ ከሚከፍለው የጉዳት ካሳ በተጨማሪ በጥፋቱ ካሳ የመክፈል ኃላፊነቱ የማይቀርለት መሆኑን የሚደነግግ ነው የሚል ሃሳብ አለኝ ስለዚህ የአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ አሰሪዎች እንዲያከብሩና አሰሪው ጥፋት ሰራተኞች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የተደነገገው ሕግ ለማስከበሪያነት የሚያገለግል የፍትሐብሔር ቅጣት (ኃላፊነት) (civil sanction) ነው፡፡ አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 1 ጉዳቱ የደረሰው በስራ ላይ እና ከስራው ጋር በተያያዘ እስከሆነ ድረስ ሁሉም አሰሪዎች ለሰራተኛው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረት ኃላፊ የሚሆኑበትን መንገድ የሚደነግግ ነው፡፡ የአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 ጥፋት የፈፀመ አሰሪ ጥፋት ካልፈፀመ አሰሪ የበለጠ ኃላፊነት የሚኖርበት መሆኑን የሚደነግግ ድንጋጌ እንጅ፣ ከንዑስ አንቀጽ 1 በአማራጭ የተደነገገ ድንጋጌ አይደለም፡፡

6. በአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ በሌላ ሰው ጥፋት ጉዳት ቢደርስበት፣ ከአዋጅ አንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102 ከአሰሪው ካሳ ከተቀበለ በኋላ በፍትሐብሔር ሕጉ ጉዳቱን ካደረሰው ሰው ካሳ የሚጠይቅበትን ሁኔታ በሚያስከብር መልኩ መተርጎም አለበት የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ በአንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 ጥፋቱን የፈፀመው አሰሪው በመሆኑ ሰራተኛው አሰሪውን ያለጥፋትና በጥፋት ለደረሰበት ጉዳት ካሳ እንዲከፍለው ከመጠየቅ የሚከለክል ድንጋጌ አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህንን መብት ለሰራተኛው የሚጠብቅ ድንጋጌ ነው፡፡

7. በኢትጵያ የሕግ ሥርዓት ካሉት የካሳ አከፋፈሎች አንደኛው ሰራተኛው ጉዳት ሲደርስበት ከአሰሪው የጡረታ አበል ወይም ካሳ ከተቀበለ በኋላ ጉዳቱን ካደረሰበት እና ለጉዳቱ ኃላፊ ከሆነው ሰው ካሳ እንዲከፍለው የሚጠይቅ መሆኑ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2094 ተደንግጓል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች በአንድ በኩል የተጠሪ አሰሪ በመሆኑ በአዋጁ ከአንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተደነገገው መሰረት ካሳ ከፍሎታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተጠሪ ላይ ጉዳቱ የደረሰው አመልካች በአዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት ለሰራተኛው የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን በማሸኑ ላይ ባለመግጠሙ ምክንያት የደረሰ ከሆነ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2094 እና ሌሎች ድንጋጌዎች መሰረት ለተጠሪ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ኃላፊነቱ በአዋጅ አንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102 በተደነገገው መሰረት ካሳ መክፈል ወይም በፍትሐብሔር ሕግ መሰረት ካሳ መክፈል ነው የሚለው አተረጓጎም የሕግ ሥርዓታችን ከዘረጋው የካሳ አከፋፈል ሥርዓት ጋር የሚጣጣም አይደለም ብዬ ስለማስብ፣ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች አመልካች በአዋጅ ከአንቀጽ 95 እስከ አንቀጽ 102 በተደነገገው መሰረት ለሰራተኛው (ለተጠሪ) ካሳ መክፈሉ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 96 ንኡስ አንቀጽ 2 እና በአዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገጉትን በመተላለፍ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2035 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2094 በተደነገገው መሰረት ለተጠሪ ካሳ እንዲከፍል መጠየቁን የሚያስቀርለት አይደለም፡፡ ስለሆነም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 82091

መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ጠበቃ ንጋቱ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ለገሠ ደሣለኝ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የሥራ ግንኙነት የተቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በሥር ፍ/ቤቶች በነበረው ክርክር ከተረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳዮች በመነሣት አግባብነት ያለውን የሕግ ትርጉም ለመስጠት ሲባል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ ሕጉ ከደነገገው ውጭ አመልካች የሥራ ውሌን አቋርጧል፤ስለሆነም ለሕገ ወጥ ስንብት በሕጉ የተፈቀደውን ልዩ ልዩ ክፍያዎች ይፈጽምልኝ በማለት የክፍያ ዓይነቶችን ዘርዝሮ ዳኝነት ሲጠይቅ፤ የአሁን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ከየካቲት 20 እስከ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉት ተከታታይ ቀናት በሥራ ገበታው ባለመገኘቱ ምክንያት የሥራ ውሉ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ለ/ በሚያዘው መሠረት እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ለሕጋዊ ስንብት ክፍያ እንድንፈጽም አንገደድም በማለት ተከራክሯል፡፡

ሆኖም የአሁን አመልካች በሁለተኛው ወሰን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለመምህራን የሚያስተምሩትን የትምህርት ዓይነቶች /ኮርሶችን/ ሲደለድል፤ ለአሁን ተጠሪ እንደ መምህርነቱ የሚያስተምረውን የትምህርት ዓይነት ለመመደብ የሚቻልበትን ምክንያት ሣይገልፅ የሚያስተምረውን ኮርስ እንዲያገኝ ስለማድረጉና የኮርስ ድልደላ ከመደረጉ በፊት የነበረውን የጥር ወር ደመወዝ እንዳይከፈለው ማገዱን፤ ለምን እንዳይከፈል እንደተደረገ ተጠሪ በጽሑፍ ከመግለጽ ጋር ይኸው ደመወዝ እንዲከፈለው የካቲት 13 ቀን 2004 ዓ.ም ሲጠይቅ በጥያቄው መሠረት ያልተከፈለው ከመሆኑም በላይ ላለመክፈል የሚያስችል በቂ ምክንያት ስለመኖሩ አመልካች በአሠሪነቱ መልስ እንዳልሰጠው የተረጋገጡ እውነታዎች ናቸው፡፡

አመልካችም እነዚህን ሁኔታዎች ይቀበልና ተጠሪው የሚያስተምረውን ኮርስ አለመደልደል መብቱ እስካልተጓደለበት ድረስ ከሥራ እንዳሰናበትነው ሊያስቆጥር አይችልም በማለት ይከራከር እንጂ አመልካች ያደረገው ተግባር ተጠሪው የሚያስተምረውን የትምህርት ዓይነት አለመስጠቱ ብቻ ሣይሆን የትምህርት ዓይነቶች ለመምህራን ከመደልደላቸው በፊት ያለውን የጥር ወር ደመወዝ ለመክፈል እምቢተኛ የሆነበትን በቂ ምክንያት አቅርቦ አላስረዳም ስለሆነም የአሁን አመልካች እንደውላቸው ሠራተኛው የሚሠራውን ሥራ የማቅረብ በሕግ ግዴታ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አመልካች ተጠሪው የሚያስተምረውን ትምህርት ደልድሎ አለመስጠቱ ብቻ ሳይሆን በተቀጣሪነቱ ሊያገኝ የሚገባውንም የጥር ወር ደመወዝ እንዳይከፈለው አድርጓል(ነፍጐታል)፡፡ ስለሆነም የተጠሪው መብት እስካልተጓደለ ድረስ የሚያስተምረውን የትምህርት ዓይነት አለመደልደል ሠራተኛውን ለማሰናበት ተፈልጐ እንደተደረገ ተግባር ሊቆጠር አይገባም የሚለው ክርክሩ በሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ያለበቂ ምክንያት ደመወዝ የማግኘት መብቱን ክልከላ ያላገናዘበ፤ በመሆኑ ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካች የተጠሪን የጥር ወር ደመወዝ እንዳይከፈል ለማድረግ የሚያበቃው ሕጋዊ ወይም በቂ ምክንያት ሳይኖረው የዚህኑ የጥር ወር ደመወዝ እንዳይከፈል የከለከለው መሆኑና በተከታዩም በየካቲት ወር ተጠሪው ሠራተኛ መሆኑን ተቀብሎ የሚሠራው ሥራ እንዳይሰጠው የከለከለበት ወር መሆኑ እየታወቀ እና እነዚህም ሁለት ተግባራት ድርብ ውጤት ተጠሪው የአመልካች ሠራተኛ መሆኑን ተገንዝቦ እንደማንኛውም ሠራተኛ የሥራ ቀንና የሥራ ሥዓት አክብሮ እንዲገኝ ከማድረግ ይልቅ ሠራተኛነቱን ያልተቀበለው መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ እያለ እንደገና ተጠሪው በዚህ በየካቲት ወር በነበረው የሥራ ጊዜ ከየካቲት 20 እስከ የካቲት 26 ቀን ባሉት ከአምስት ተከታታይ ቀናት በላይ ከሥራ ገበታው ስለቀረ ተሰናብቷል፡፡ ይህም ሕጋዊ ስንብት መሆኑን ያመለክታል የሚለው ክርክሩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ መሠረት ያላደረገ፤ ድንጋጌውን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያበቁ ሁኔታዎችን ያላሟላ ክርክር በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት በሕጉ ከተደነገገው ውጭ እንዲሰናበት ተደርጓል፤ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት ለዚህ ዓይነት ሕገ-ወጥ ስንብት ሊከፈል የሚገባውን የክፍያ ዓይነትና መጠን ገልፀው የሰጡት ትርጉም ሕጋዊ እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 125715 በቀን 18/11/2004 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ፀንቷል፡፡
2. የአሁን አመልካች በሰበር ደረጃ ያቀረበው ክርክር ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም ብለናል፡፡
3. የአሁን አመልካች ተጠሪን በሕጉ ከተደነገገው ውጭ ከሥራ አሰናብቶታል፤ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለትና ለዚህ ሕገ-ወጥ ስንብት የሁለት ወር ደመወዝ በማስጠንቀቂያ ምክንያት፤ የሥራ ስንብት 2,125.00 /ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ አምስት ብር/ የካሣ ክፍያ ብር 9000.00 /ዘጠኝ ሺህ ብር/ ያልተከፈለው የጥር ወር ደመወዝ ብር 1500.00 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ከብር 400.00 /አራት መቶ ብር/ የወጭና ኪሣራ ገንዘብ ጋር ይከፈለው መባሉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ የሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ሲከራከሩ በክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት.ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 84661

መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ዳዊት ሽዋቀና - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ስኳር ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ አቶ ጌታቸው አክሊሉ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ የአዲት ክፍል ሀላፊ ሆኜ እየሠራሁ የሥራ አፈጻጸምህ ዝቅተኛ ነው፣እንዲሁም በሥራ ላይ ቸልተኝነት አሳይተሃል በሚል ያለማስጠንቀቂያ ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ/ም የሥራ ውሌን ያቋረጠብኝ በመሆኑ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ ካልሆነም ካሳ፣የስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ክፍያ በዘገየበት እና የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ ሰጥቷል፡፡ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠው መልስም፡- ከሳሽ ከሥራ የተሰናበቱበት ምክንያት በተሰጣቸው የስንብት ደብዳቤ ላይ የተገለጸ ሲሆን ወደ ሥራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄም ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፣እንዲሁም እንዲከፈላቸው ከጠየቁአቸው ክፍያዎችም ውስጥ የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ የተከፈላቸው ሲሆን ሌሎች ክፍያዎች ግን ሊከፈሉአቸው አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡

የመ/ደረጃ ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ያቀረበውን መቃወሚያ ቀደም ሲል በብይን ውድቅ ማድረጉን በመግለጽ በሰጠው ፍርድ፡- ተከሳሽ ለከሳሽ በጻፈው የስንብት ደብዳቤ የሥራ አፈጻጸማቸው ሲገመገም ዝቅተኛ ስለመሆኑ የተመዘኑበትን ማስረጃ ካለማቅረቡም ሌላ በሥራቸው ቸልተኝነት አሳይተዋል ቢልም በምን ምክንያት ቸልተኝነት እንዳሳዩ አልዘረዘረም በማለት የሥራ ውሉ በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ በአማራጭ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተም የስራ መሪ ያለበቂ ምክንያት ከሥራ አሰሪው ቢያሰናብት ወደ ሥራ

የመመለስ መብት እንዳለው በፍትሃብሔር ህጉ፣በህብረት ስምምነቱም ሆነ በሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ ስላልተገለጸ ተቀባይነት የለውም ሲል ወድቅ ያደረገ ሲሆን፤እንዲከፈላቸው የጠየቁትን ክፍያዎች በተመለከተም፡- የስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ሲወስን፤ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በሚመለከት ከሳሽ የሚሠሩበት ሥራ የእምነት ሥራ እና ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑ ማስጠንቀቂያ አለመሥጠት በፍ/ህ/ቁ/2577(2) መሰረት ኪሳራ የሚያስከትል አይሆንም ሲል ያልተቀበለው ሲሆን ካሳ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የህግ መሰረት ያለው አይደለም በሚል ውድቅ ሲያደርግ የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ የተከፈላቸው መሆኑንም በቃል ክርክር ወቅት ከሳሽ ስላመኑ በድጋሚ ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡ እንዲሁም ክፍያ በዘገየበት የጠየቁትን ክፍያ በተመለከተም የሚከፈላቸው ክፍያ አይኖርም ሲል ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽም በመ/ደ/ፍርድ ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የይግባኙን መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 በመዝጋት በማሰናበቱ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸውም በዋናነት ያቀረቡት የቅሬታ ነጥብ፡-

- የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና ካሳን ፍርድ ቤቶቹ በአዋጅ ቁጥር 377/1996፣በህብረት ስምምነቱና በሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሰረት መወሰን ሲገባቸው ሳይወስኑ ያለፉት አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፡-

- ኮርፖሬሽኑ በደንብ ቁጥር 192/2003 የተቋቋመ ሆኖ እያለ አመልካች የተሻሩትን የሥራ መሪዎች ደንብና የህብረት ስምምነት መሰረት በማድረግ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉአቸው ያቀረቡትን ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

አመልካችም ተጠሪው ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

- አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ነው በሚል የሥር ፍርድ ቤቶች ከወሰኑ በኋላ ካሳና የማስጠንቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም ያሉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? በሚል መዝገቡ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል በተያዘው ጭብጥ መሰረት ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ወደተያዘው ጭብጥ ከመመለሳችን በፊት ተጠሪው ድርጅት በአዲስ መልክ በደንብ ቁጥር 192/2003 የተቋቋመ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሥር ፍርድ ቤቶች ፍርድ ለመስጠት መሰረት ያደረጉት የሥራ መሪዎች ደንብና የህብረት ስምምነት ስለተሻሩ አግባብነት የላቸውም ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑ ሊመረመር የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ደንብ ቁጥር 192/2003 ተፈጻሚ የሆነው ከጥቅምት 19 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ስለመሆኑ በደንቡ አንቀጽ 12 የተደነገገ ሲሆን አመልካችም ክሱን ያቀረቡት ጥር 27 ቀን 2004 ዓ/ም በመሆኑ ክሱ የቀረበው ደንቡ ጸንቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ነው፡፡ በዚህ ደንብ ቀደም ሲል በየራሳቸው የማቋቋሚያ ደንብ ተቋቁመው የነበሩት አራት የስኳር ፋብሪካዎች የስኳር ኮርፖሬሽን በሚል መቋቋማቸውን ከደንቡ መገንዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚቻል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪው ቀደም ሲል በደንብ ቁጥር 122/1998 እንደተሻሻለው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ በሚል ሲጠራ የነበረ ሲሆን የራሱ የሆነ የህብረት ስምምነት እና የሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ ያለው ነው፡፡ተጠሪው የህብረት ስምምነቱና የሥራ መሪዎች የመተዳሪያ ደንቡ ተሽረዋል በሚል ክርክር ስለማቅረቡ የመ/ደ/ፍርድ ቤት ፍርድ የማያመላክት ሲሆን ክርክር አቅርበዋል ቢባል እንኳን ፍርድ ቤቱ ባለመቀበል በተሻሩ የሥራ መሪዎች ደንብና የህብረት ስምምነቱ መሰረት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሰጥቶ ከሆነ ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በማቅረብ ፍርዱን ማስለወጥ ሲገባው ይግባኝ አቅርቦ አላስለወጠም፡፡ በዚህ በሰበር ደረጃ ባደረገውም ክርክር የህብረት ስምምነቱ እና የሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ መሻራቸውን ከመግለጹ በስተቀር በየትኛው የህብረት ስምምነትና የሥራ መሪዎች ደንብ እንደተተኩ አልጠቀሰም፡፡ ስለሆነም የህብረት ስምምነቱና የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ የተሻሩ ናቸው ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ወደ ጭብጡ ስንመለስ፡- ተጠሪው የሥራ ውሉን ለመቋረጥ የጠቀሳቸው ምክንያቶች የአመልካች የሥራ አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ ነው፣ እንዲሁም በሥራ ላይ ችልተኝነት አሳይተዋል በሚል እንደሆነ ለሥር ፍርድ ቤቶች በማስረጃነት ከቀረበው የሥንብት ደብዳቤ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪውም አመልካች በሥራ አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ ስለመሆኑ የተመዘኑበትን ማስረጃ ባለማቀረቡ እንዲሁም በሥራ ላይ ችልተኝነት አሳይተዋል ላለውም ምክንያቱን በመዘርዘር ማስረዳት ባለመቻሉ ሥንብቱ ህገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የሥር ፍርድ ቤቶች ደርሰዋል፡፡ በመሆኑም የሥራ ውሉ በህገ ወጥ መንገድ መቋረጡ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር እስከሆነ ድረስ ተጠሪ ከሳሳና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል የሚገባ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር አገናዝቦ መመልከት ይገባል፡፡ ከክርክሩ መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች ሥራ መሪ ናቸው፡፡ አሰሪው የሥራ ውሉን ቀሪ በማድረግ ወይም አላድስም በማለት ይህን ውሳኔ በግልጽ የሚያረጋግጥ በቂ ምክንያት የሌለው እንደሆነ ሠራተኛው ተገቢ የሆነ ኪሳራ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ህ/ቁ/2573 ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በዚህ መልኩ በህጉ የሥራ ውሉ በቂ ባልሆነ ምክንያት የተቋረጠ ከሆነ አሠሪው ኪሳራ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የተሰናበቱት ያለበቂ ምክንያት መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ካረጋገጡ በኋላ ኪሳራውን ሳይወስኑ ማለፋቸው ህጉን የተከተለ አይደለም፡፡ ኪሳራ መክፈል ተገቢ መሆኑ ከታመነ ደግሞ ስለሚከፈልበት ሁኔታም አግባብነት ያላቸውን ህጎች መመልከት የሚገባ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው የ6 ወር ደመወዝ ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁት አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አንድ የሥራ መሪ የሥራ ውሉ ያለ በቂ ምክንያት ሲቋረጥ ሊከፈል የሚገባው የኪሳራ ልክ ሠራተኛው ባለፈው ሶስት ወር ከተቀበለው ደመወዝ ሊበልጥ እንደማይችል በፍ/ህ/ቁ. 2574 (2) የተደነገገ ሲሆን ይህንኑ የህግ አነጋገር ይዘን በታህሳስ ወር 2002 ዓ/ም ወደወጣው የተጠሪ የሥራ መሪዎች የመተዳደሪያ ደንብ ስንመለስ ፡-

በአንቀጽ 51(1) በዚህ ደንብ ውስጥ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በሌሎች ህጎች ፣ደንቦች ወይም በሌላ አኳኋን ተለይቶ የተወሰነው የተሻለና የበለጠ ጥቅም የሚያስገኝ ሆኖ በዚህ ደንብ ውስጥ ባልተጠቀሱም ሆነ በተጠቀሱ ጉዳዮች፣በህብረት ስምምነት የተደነገጉት፣በአሰራር ደንብ የተወሰኑትና የሚታወቁት ስለሥራ ሁኔታ፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት፣ የሥራ አካባቢ፣ጥቅሞች፣ግልጋሎቶች፣ሥልጠና፣የሥራ ዉጤት መለኪያ ዘዴ እንዲሁም ይህን ደንብ የማይቃረኑ አግባብ ያላቸው ሌሎች የሥራ ውል ግንኙነቶች የሚመለከቱ ዝርዝር ደንጋጌዎች የሥራ መሪው የሥራ ውል አካል ሆነው ይቆጠራሉ በሚል ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚሁ ደንጋጌ መሰረትም በፍ/ህ/ቁ ከተመለከተው የኪሳራ መጠን ይልቅ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43(4)(ሀ) የተመለከተው የካሳ መጠን

የተሻለ ጥቅም የሚያስገኝ በመሆኑ ለአመልካችም ተጠሪው ካሳ ሊከፍላቸው የሚገባው በዚሁ የአዋጁ አንቀጽ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

ሌላው አመልካች የጠየቁት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ነው፡፡ ተጠሪው የአመልካችን የሥራ ውል ሲያቋርጥ ቅድመ ማስጠንቀቂያ አለመስጠቱ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶችም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለአመልካች አይገባቸውም በሚል የወሰኑት አመልካች የሚሰሩት የሥራ ባህሪ በመግለጽ ሲሆን ለዚህም መሰረት ያደረጉት የፍ/ህ/ቁ. 2577(2) ድንጋጌን ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር (1) የሥራው ውሉ ልዩ የሆኑ ችሎታዎችን የሚጠይቁ፣የእምነት ሥራዎች እንደሆኑ አሠሪው ውሉን ቀሪ የሚያደርግበትን ወይም የማያድስበትን ምክንያት ለማስታወቅ የማይገደድ መሆኑ የተደነገገ ሲሆን ኪሳራ ለመክፈል የሚገደደው ግን ውሉ እንዲቀር የተደረገው በማይገባ ጊዜና አንደኛውን ወገን ለመጉዳት ወይም ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ባለማሰብ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን የውሉ ያለ ማስጠንቀቂያ ቀሪ መሆን አሠሪው ለሠራተኛው ኪሳራ እንዲከፍል የሚያስገድድ አይሆንም፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን ውሉ ቀሪ የተደረገው በማይገባ ጊዜ ወስጥ ስለመሆኑ፣ወይም ተጠሪው አመልካችን ለመጉዳት ወይም ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ባለማሰብ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ውሉን ቀሪ ስለማድረጉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም፡፡ አመልካች በተጠሪው ደርጅት የአዲት ክፍል ሀላፊ የነበሩ እንደመሆናቸው መጠን የሥራ ውሉ ልዩ ችሎታን የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ ሥራውም በእምነት የሚሰራ በመሆኑ አስቀድሞ የሥራ ውል የሚቋረጥ ስለመሆኑ ማስታወቅ የአሰሪውን ጥቅም ሊጎዳ የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጥር ስለሚችል ማስጠንቀቂያ አለመሥጠቱ በፍ/ህ/ቁ.2577(2) እንደተመለከተው ኪሳራ እንዲከፍል የሚያስገድደው አይሆንም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ለአመልካች ከሚሠሩት የሥራ ባህሪ የተነሳ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ የሥራ ውሉን በማቋረጡ ምክንያት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለመክፈል አይገደድም ያሉት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም፡፡

ሲጠቃልል፡- የሥር ፍርድ ቤቶች ለአመልካች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም ያሉት ከዚህ በላይ በተገለጹት ምክንያቶች የተነሳ ተገቢ በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በሚል ፍርድ ቤቶቹ የወሰኑት ተገቢ ቢሆንም የሥራ ውሉ በህገ ወጥ መንገድ የተቋረጠ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ ግን ካሳ እንዲከፈላቸው ሳይወስኑ ያለፉት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/03537 በቀን 15/10/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ፍርድ እና የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/126268 በቀን 17/12/2004ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. የስር ፍርድ ቤቶች የሥራ ውሉ በተጠሪው ህገ ወጥ ድርጊት ተቋርጦ እያለ ለአመልካች የካሳ ክፍያ እንዲከፈላቸው ሳይወስኑ ያለፉት ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43(4)(ሀ) መሰረት የአመልካች የቀን አማካይ ደመወዝ በ180 ተባዝቶ በሚመጣው ስሌት መሰረት እንዲከፈላቸው ወስነናል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤቶች ከካሳ ክፍያ በስተቀር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያም ሆነ ሌሎች ክፍያዎችን በተመለከተ የሠጡትን የውሳኔ ክፍል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
4. የካሳ ክፍያን በተመለከተ በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የአፈጻጸም ክሱን ለያዘው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይጻፍ ብለናል፡፡
5. የግራ ቀኙ ወገኖች የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የየራሳውን ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79476

የካቲት 12 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡-ኢትዩ ቴሌኮም VC በትክክል ሊሥራ ሰላልቻለ መቅረብ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተጠሪ፡-

1. አቶ ዘሪሁን ታዬ
2. አቶ ተስፋዬ አለማየሁ
3. ታየች ታደሰ
4. አቶ ያሬድ ዘውገ
5. አቶ ምስራቅ ታምራት
6. ማርሸት እንግዳወርቅ
7. አቶ ደረጀ ይልማ
8. አቶ ሚሊዮን አባይነህ
9. ለምለም አስፋው
10. ካሳሁን አንዱአለም
11. መልካሙ ሀይሉ
12. ድርሳነ ተስፋዬ
13. ማን ታጋፍቶት አበበ
14. ሄለን ተስፋዬ
15. ስለእናት አደመ
16. መስፍን ገሰሰ
17. ብዙአየሁ ደበበ
18. እታገኘሁ ዳኜ
19. ማለፊያ በቀለ
20. ወለንሳ አስታጥቄ
21. ቴዎድርስ ክበበው
22. መሰሉ ሲራጅ
23. ፍጹም ታዬ
24. ዳንኤል ግርማ
25. እንዳልካቸው መንግስቱ
26. ወይንሸት ተፈራ
27. ተሰማ ዘውዴ
28. መዐዛ መርሻ
29. አመለወርቅ ጎሹ
30. አሕመድ ሀሰን
31. ብዙአየሁ ወንድአጥር
32. ወይንሸት ምህረተአብ
33. ምስራቅ መኮንን
34. መቅደስ ታምራት
35. ወርቅነሽ እሸቱ
36. ሳምራዊት ስዩም
37. ዘነቡ ከበደ
38. ፍስሀ አሰፋ
39. መድሀኒት አግዛ
40. ጸሐይ ቸርነት
41. ተገል ማሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

42.እኑሽ ቤተ
43.መቅደስ ደስታ
44.ቦጋለች ተድላ
45.ተገኔ ከበረ
46.ቅድስት አየለ
47.ሄኖክ አበራ
48.ታደሱ ለማ
49.ትዝታ ሀይሌ
50.ትዕግስት ነጋሽ
51.ስመኝ ዘገየ
52.ሽብሬ ሰይፉ
53.ዳምጠው ወ/ተንሳይ
54.ከተማ ኩዩ
55.ምንዳ ጠና
56.ታምራት ደነቀ
57.ደጅይጥኑ ይልማ
58.ሮማን ነጋሽ
59.የሺጥላ እስጢፋኖስ
60.ደስታ ገሰሰው
61.ተሾመ መልከጸዲቅ
62.መቅደስ ይልማ
63.ይታየው ጠጁ
64. ምትኩ አባይነህ
65.ሁሴን አህመድ
66.ባንተየሁ ገብሬ
67.ሐያት አብዱሰላም
68.ዝናሽ ሐይሉ
69.ዘብደር ሉልሰገድ
70.እንዳለ ሙሉጌታ
71.ሱፊያ ኢድሪስ
72.ናሆም ዮሐንስ
73.ብርሃኔ ታደሰ
74.አያለሌው ክብረት
75. ሐይሉ በቀለ
76.የሺወርቅ ቤቶኒ
77. እዮብ ደጀኔ
78.መስፍን ታደሰ
79.መሰረት ባርባ
80.ንግስቱ ደግፍ
81.ማሞ ሽፈራው
82.ወንዱ መኩሪያ
83.አብዱላህ መሳ
84. ላቀች ገበየሁ
85.ፀደቀ ዳዊት
86.ውብሸት ጀማነህ
87.ዘነበች አባተ
88.አስናቀች ሽፈራው
89.አይናለም ደነቀ
90.ስንዱ ፊይሳ
91.ዘቢደር ኃ/ጊዮርጊስ
92.አባይነሽ ኃ/ሚካኤል
93.መሠረት ፋሲል
94.ዮውብዳር ምንነህ
95.ትእግስት አሰፋ
96.ኃድራ ሸኩር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርደ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የቀረበውን የደመወዝ ጭማሪና የቦነስ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪዎች በአሁን አመልካች ላይ በድሬዳዋ ከተማ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ላይ ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው የተጠሪዎች ክስ ይዘትም ከቀድሞ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙንኬሽን ኮርፖሬሽን እና በሠራተኛ ማሕበር መካከል በ1999 ዓ/ም በተፈረመ የሕብረት ስምምነት መሠረት ከሐምሌ 01 ቀን 2001 ዓ/ም አስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ለሰሩበት ከሐምሌ 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ የደመወዝ ጭማሪ እንዲሁም በጸጉሜ 2002 ዓ/ም ለሰራተኛ የተደረላቸውን የቦነስ ክፍያ አመልካች እንዳልከፈላቸው ገልፀው እንዚህን ክፍያዎች እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮች አቅርቧል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሣቸው ነጥቦች ጉዳዩ በአዲስ አበባ አሠሪና ሰራተኛ ጉዛይ ወሣኝ ቦርድ እየታየ ባለበት ሁኔታ በድጋሚ ሌላ ቦታ ክስ መቅረቡ ያለአግባብ መሆኑን፣ ተጠሪዎች የመክሰስ መብት የሌላቸው መሆኑን እና ክሱ በስድስት ወር ይርጋ የሚታገድ መሆኑን ገለፃ የተከራከረባቸው ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ተጠሪዎች ለክሱ መሠረት ያደረጉት የሕብረት ስምምነት የተፈጻሚነት ጊዜው ያላበቃለት በመሆኑ ለደመወዝና ለሌሎች ጥቅማጥቅሞች ተፈፃሚ የሚሆንበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ተጠሪዎች የደመወዝ መጠናቸውና ይገባናል የሚሉትን ጭማሪና ቦነስ መጠኑን ለይተው ያለማቅረባቸው የአመልካችን የመከላከል መብት የሚያጣብብ ከመሆኑም በላይ ከዳኝነት አሰጣጡም አመቺ ያለመሆኑን አመልካች በበጅት አመቱ የአግልግሎት ጥራትና ምርታማነቱን ከፍ ያደረገ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ክፍያዎቹ የሚጠየቁበት አግባብ የሌለ መሆኑንና በህብረት ስምምነቱም የክፍያዎቹ ጥያቄዎች የሚፈፀሙት ከማህበሩ ጋር አመልካች በሚያደርገው ድርድር እንጂ በሰራተኞች ቀጥታ ጥያቄ ያለመሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ቦርድም የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለተጠሪዎች ከሐምሌ 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ የደመወዝ ጭማሪ እንዲያደርግ ክፍያውም በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 18 መሰረት እንዲፈፀም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የቦርዱ ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ ሁኖ እያለ መታለፉም ሆነ የህብረት ስምምነቱ ተፈጻሚነቱ ያበቃ ሁኖ እያለ ለክፍያዎቹ ጥያቄ ተፈፃሚ እንዲሆን መደረጉ ያላግባብ መሆኑን የደመወዝ ጭማሪ የሚደረገው አመልካች የአገልግሎት ጥራት እድገትና አመታዊ የትርፍ ገቢ ከተገኘ ስለመሆኑ በህብረት ስምምነቱ በግልጽ ተቀምጦ እያለና ይህ ስለመሆኑ ተጠሪዎች አግባብነት ባለው የስነድ ማስረጃ ሳያረጋገጡ መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የተጠቀሰውን የደመወዝ ጭማሪ ለተጠሪዎች ይክፈል ተብሎ በአስሪና ሰራተኛ ጉዳይ ውሳኝ ቦርድ የመወሰኑንና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የመጽናቱን አግባብነት

ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸውም 1ኛ፣2ኛ፣84ኛ እና ከ86ኛ እስከ 93ኛ፣ 6ኛ፣7ኛ 8ኛ፣27ኛ፣ 53ኛ.55ኛ፣61ኛ 69ኛ፣74ኛ 81ኛ፣ 85ኛ 94ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ቀርበው መልሳቸውን በጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን 5ኛ፣ 9ኛ፣ 19ኛ፣29ኛ፣ 31ኛ፣ 38ኛ፣46ኛ፣ 48ኛ፣ 53ኛ፣ 56ኛ፣ 69ኛ፣ 73ኛ፣ 74ኛ79ኛ 81ኛ፣ 82ኛ፣ 84ኛ፣8 5ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች መጥሪያ በህጉ አግባብ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ ሌሎች ተጠሪዎችም በህጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ያልቀረቡ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመውም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/1/ ስር የተመለከተው ነው? ወይስ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሶስት ስር የተመለከተው ነው? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ክስ ሊመሰረቱ የቻሉት አመልካች በ1999 ዓ/ም በወጣው የድርጅቱ የሕብረት ስምምነት መሰረት በ2001 ዓ/ም የበጀት አመት ከሐምሌ 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ሊከፈል የሚገባቸውን የደመወዝ ጭማሪ በጳጉሜ 2002 ዓ/ም ለሰራተኞች ያደረገውን ቦነስ አልከፈለንም በሚል ምክንያት ሲሆን አመልካች የተለያዩ የመቃወሚያ የክርክር ነጥቦችን ከማቅረቡም በተጨማሪ የደመወዝ ጭማሪ የሚከፍልበትን ስርዓትና የህብረት ስምምነቱን የተፈፀሚነት ጊዜ ጠቅሶ ኃላፊነት የለብኝም ሲል ተከራክሯል፡፡ ቦርዱም ሆነ ይግባኙን የተመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች ክርክር ውድቅ ያደረጉት የሕብረት ስምምነቱ በሌላ እስከሚተካ ድረስ ተፈፃሚ እንዲሆን የድርጅቱና የማህበሩ ተወካዮች ሚያዚያ 30 ቀን 2001 ዓ/ም ተስማምተው የፈረሙበትና በማህተም ያረጋገጡት ማስረጃ እንዲሁም ስምምነቱ ለሰራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለምዝገባ ቀርቦ ጸድቆ የተመዘገበ ስለመሆኑ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ግንቦት 02 ቀን 2001 ለሁለቱም ወገኖች በአድራሻ የፃፈላቸው ደብዳቤ ፎቶ ያስረዳል በሚል ምክንያት መሆኑንና ህብረት ስምምነቱ ተፈፃሚ እንዲሆን ግራ ቀኙ ከተሰማሙ ደግሞ ሕጋዊ አይደለም በማለት የቀረበው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ እኛም ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

አመልካች የተጠሪዎች የደመወዝ ጭማሪና የቦነስ ክፍያ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የሚከራከረው የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162/3/ ስር የተጠቀሰውን ስድስት ወር ጊዜ በመጥቀስ ነው፡፡ ቦርዱም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በአዋጁ አንቀጽ 162/1/ ስር የተጠቀሰው የአንድ አመት ጊዜ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን ሲመለከት የተጠሪዎች ክስ ለቦርዱ የቀረበው ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ/ም ሁኖ የዳኝነት ጥያቄው መሰረት የሆነው ደግሞ የደመወዝ ጭማሪ ነው፡፡ ይህ የደመወዝ ጭማሪ የሚደረገውም አመልካች ደርጅት በ2001 ዓ/ም የበጀት አመት የአግለግሎት ጥራት እድገትና አመታዊ ትርፍ ግብ ሲመታ ስለመሆኑ አመልካች ራሱ ጠቅሶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚከራከርበት የድርጅቱ የሕብረት ስምምነት በግልጽ የሚያሳየው ጉዳዩ ነው፡፡ እንግዲህ ከዚህ የህብረት ስምምነት ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የደመወዝ ጭማሪ የድርጅቱን የበጀት አመት የጥራት እድገትና የትርፍ ግብ መምታትን መሰረት ያደረገ መሆኑን ሲሆን የድርጅት የበጀት አመት በግልጽ አንድ አመት መሆኑ ከመጠቀሱም በላይ የድርጅቱ የጥራት እድገትና ትርፍ መኖሩ የሚረጋገጠው ደግሞ ከበጀት አመቱ መጠናቀቅ በኋላ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ስለሆነም የድርጅቱ የጥራት እድገትና ትርፍ ግብ መምታቱ የሚረጋገጠውና የደመወዝ ጭማሪውም በዚሁ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ከሆነ ተጠሪዎች ጥያቄውን ማቅረብ የሚችሉት የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ እና የደመወዝ ጭማሪውን ለማስገኘት የሚያስችለው ሁኔታ መሟላቱ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑ እሙን ነው፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሚቆጠረው የይርጋ ጊዜ ርዝማኔ ነው፡፡ ይኼውም ጊዜው ስድስት ወር ነው ወይስ አንድ አመት ነው የሚለው የህግ ጥያቄ በአግባቡ ሊለይ ይገባል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በግራ ቀኙ የቀረበው ሙግት የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ አግባብነት ያለው ሕግም የአዋጅ ቁጥር 377/96 ነው፡፡ ይህ የአዋጅ ቁ.377/96 በክፍል አስር ምእራፍ አንድ አንቀጽ 162-166 በሚገኙት ድንጋጌዎች ስር ስለ ይርጋ ደንብ ደንግጓል፡፡ የአዋጅ ቁ.377/96 የመብት ጥያቄዎች ለሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ በአንቀጽ 162 ስር ደንግጓል፡፡ ከመነሻው የተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በዚህ ሕግ ወይም በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ እስካልተወሰነ በስተቀር ጉዳዩን ማቅረብ ከሚቻልበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ካልቀረበ የመብቱ ጥያቄ በይርጋ እንደሚታገድ አመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ የጉዳዩ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ጉዳዩን ለማቅረብ ከሚቻልበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡ እንዲሁም በሕግ የተለየ የጊዜ ገደብ ያልተደረሰት ጉዳይ ሁሉ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊቀርብ እንደሚገባው በመደንገግ አጠቃላይ የሆነ የጊዜ ገደብ አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም ይኸው የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162 በንዑስ አንቀጽ /2/ ፣/3/ እና /4/ ላይ ሕጉ የተለየ የይርጋ ጊዜ የወሰነላቸው የአቤቱታ አይነቶች ለይቶ አመላክቷል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 162 የተለየ ይርጋ ጊዜ ከወሰነላቸው የመብት ጥያቄዎች ውስጥ የመጀመሪያ የሆነው አንቀጽ 162/2/ “ሰራተኛው የስራ ውሉ ከሕግ ውጭ ተቋርጦብኛል በማለት ወደ ሥራው ለመመለስ የሚያቀርበው ክስ ውሉ በተቋረጠ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል” በማለት ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩልም የስራ ውልን መቋረጥ ምክንያት አድርጎ ሰራተኛው በአሰሪው ላይ አሊያም አሰሪው በሰራተኛው ላይ የሚያነሳው የክፍያ ጥያቄ የስራ ውሉ ተቋረጠ በስድስት ወር ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ በዚሁ አንቀጽ 162/4/ ላይ ተደንግጓል፡፡ በግልፅ እንደሚታየው የመጀመሪያው ድንጋጌ የስራ ውሉን መቋረጥ ሕጋዊነት በመቃወም ወደ ስራዬ ልመለስ ይገባል የሚል ሰራተኛ ይህን ጥያቄውን ለማቅረብ የሶስት ወር ጊዜ ብቻ እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ ሁለተኛው ድንጋጌ ደግሞ የስራ ውልን መቋረጥ መነሻ አድርገው የሚቀርቡ ማናቸውም አይነት የክፍያ ጥያቄዎች በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተገደቡ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ከእነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች አቤቱታ አቅራቢው ስራ ውሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በመብቱ መጠቀም የሚችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ሌላው የአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 162 የተለየ የይርጋ ጊዜ የወሰነለት የአቤቱታ በንዑስ አንቀጽ /3/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይኸውም “ሰራተኛው የሚያቀርበው ደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓትና የሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ መጠየቅ ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ….” መቅረብ እንደሚገባውና ይሄ ካልሆነ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጓል፡፡ ከድንጋጌው መረዳት እንደሚቻለው ይህን አንቀጽ ተመስርቶ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል የተፈፀመው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስራ ውል ፀንቶ በአለበት ሁኔታ ሰራተኛው ከአሰሪው የሚጠይቀው ክፍያ የሚመለከት እንጂ የግድ የስራ ውሉን መቋረጥ ተከትሎ የሚነሳ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የስድስት ወሩ የይርጋ ጊዜ አንደመብቱ መብሰል እየታየ ሊወሰን የሚገባው ወይም መብቱን መጠየቅ/ሊጠይቅ/ ይገባ ነበር የሚሰኝበት እለት ተመስርቶ መቆጠር የሚጀምር እንጂ ውስን መነሻ ጊዜ የተቀመጠለት አይደለም፡፡ ይኽ አንቀጽ 162/3/ ሰራተኛው አሰሪውን ደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓትና ሌሎችም ክፍያዎችን ሊጠይቅ የሚችልበትን ውስን ጊዜ ያስቀመጠ ቢሆንም የስራ ውልን መቋረጥ ለይርጋው ጊዜ አቆጣጠር እንደመነሻ ባለመወሰዱ ከአንቀጽ /2/ እና /4/ ይለያል፡፡ እንዲሁም የድንጋጌው ይዘት ሲታይ ክፍያዎቹ ስራ በመስራት የሚገኙ መሆናቸውን ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ሌሎች ክፍያዎች የሚለው የድንጋጌው ሐረግ የሚያሣየው ሰራተኛው ስራውን በመስራት ሊያገኝ የሚችላቸውን ክፍያዎች ስለመሆኑ የድንጋጌው አቀራረጽ ያሣያል፡፡ ከድንጋጌው ውስጥ "...የሌሎችም ክፍያዎች.." ወይም ".. 0thher payments ~ የሚለው ሐረግ ጠቅላላ ቃል መሆኑ ግልጽ ሲሆን እንዲህ በሆነ ጊዜ ቃሉን ሕግ አውጪው የተጠቀመው ምንን ለማመላከት ነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሣቱ ተገቢ ሲሆን የሕግ አተረጓጎም መርሆዎችን መሠረት በማድረግም ምላሹን ማግኘት ይቻላል፡፡ በዚህም መሠረት ከጠቅላላው ቃል በፊት የተዘረዘሩት የቃላት ዝርያ የሚያሣዩትን ሁኔታ በመመልከት ጠቅላላ ቃል ሌሎች ያልተዘረዘሩትን ተመሣሣይ ዝርያ ያላቸውን ቃላት ለመጠቀም ታስቦ የተቀመጠ ነው በሚል እንደሚተረጎም ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም መርሆዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም ደመወዝ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎች በመርህ ደረጃ ስራ ሲሰራ የሚከፍሉ የክፍያ ዓይነቶች ሲሆኑ በድንጋጌው የገባው የሌሎች ክፍያዎች ሐረግም ይዘቱና መንፈሱ ሲታይ በዚህ መልክ ለሰራተኛው የሚገቡትን የክፍያ አይነቶችን የሚገልጽ ነው፡፡ ይርጋውም ሠራተኛው የተጠቀሱትን ክፍያዎች ይጠይቅ ይገባው ነበር ከሚሰኝበት ጊዜ ይነሣና ምናልባትም የሥራ ውሉ ተቋርጦ እንኳ ቢሆን ይኸን ከግምት ውስጥ ያስገባና እስከ ስድስት ወር ድረስ መቆጠሩ ይቀጥላል፡፡ እንግዲህ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162 መሠረት አንድ የሥራ ክርክር ጉዳይ የተለየ የይርጋ ጊዜ የተቀመጠላቸውን የመብት ጥያቄዎች የሚመለከት ከሆነ ከንዑስ አንቀጽ /2/ እስከ /4/ የተጠቀሱትን የሦስት ወይም ስድስት ወራት የጊዜ ገደብ አክብሮ የቀረበ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ሥር የማይሸፈን ከሆነ ደግሞ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተውና በአንባሩም ሰፊ በሆነው የአንድ ዓመት የጊዜ ወሰን ውስጥ አንዲቀርብ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የይርጋ ጊዜ የተወሰነበት የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162 ሠራተኛውና አሰሪው አንዱ ከሌላቸው የመብት ጥያቄዎችን የሚያቀርቡበትን ሁኔታ ብቻ በመጥቀስ የተደነገገ መሆኑን ከአንቀጾቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁት ክፍያ ስራ በመስራት የአመልካችን ድርጅት እቅድና ግብ ሲያሳኩ የሚገኙት ክፍያ የሚመለከት እንጂ አመልካች ስራ ባይሰራ ቢቀርም በህብረት ስምምነቱ መሠረት ሊፈከላቸው የሚገባውን ጥቅማ ጥቅም የሚመለከት አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/3/ ስር በተመለከተው ድንጋጌ ሌሎች ክፍያዎች በማለት የተቀመጠው ሐረግ እንደተገለፀው ሰራ በመስራት ሰራተኛው የሚያገኛቸውን የክፍያ አይነቶች የሚሸፍን እንጂ በሕብረት ስምምነቱ ስራ ከመስራት ውጪ የሚገኙትና የተጠበቁትን ክፍያዎችን የሚሸፈን አይደለም፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ 162/1/ ሥር የተመለከተው የአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ሣይሆን በአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሶስት ድንጋጌ ስር የተቀመጠው የስድት ወር ጊዜ በመሆኑና ይህ የስድስት ወር ጊዜ ገደብም የአመልካች የበጀት ዓመት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠናቀቀበት ወይም ድርጅቱ የአገልግሎት ጥራት እድገትና ምርታማነቱን ግቡን ማሣካቱን ከአረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊቆጥር የሚገባው በመሆኑ ተጠሪዎች በዚህ ረገድ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የአንድ አመት ይርጋ ነው በማለት ከመከራከራቸውም ውጪ ስድስት ወር ያላለፈው መሆኑን ገልጸው ያልተከራከሩ በመሆኑ ወይም የአመልካች የበጀት አመት ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ተጠናቅቆ ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡት ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ስለሚያሳይ አመልካቾች ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በስድስት ወር የይርጋ ጊዜ የታገደ ነው።

ሲጠቃለልም ቦርዱም ሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከላይ በተዘረዘረው ምክንያት አግባብ መመልከት ሲገባቸው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የአንድ አመት ይርጋ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ በተጠሪዎች የተጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ ስራ ከመስራትና የድርጅቱን እቅድና ግብ ከማሳካት ጋር የተያያዘ የክፍያ አይነት መሆኑን ሳያገናዝቡ የተሰጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የፈጸሙ ሁኖ ስላአገኘን ተከታዩን ወስነናል።

<u>ውሣኔ</u>

1. በድሬዳዋ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ጥቅምት 07 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 07453 ሚያዝያ 04 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡትና እንዲከፈላቸው የተወሰነው የደመወዝ ጭማሪ ክፍያ ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 162 (3) መሰረት በስድስት ወር የጊዜ ገደብ የታገደ ነው ብለናል። አመልካች ክፍያውን ሊከፍል አይገደድም ብለናል።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 81814

ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሰሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካቾች፡- እነ ወ/ት ፌቨን የሺጌታ (12 ሰዎች) የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ጠበቃ ሽዋዬ ታከለ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የስራ ውላችንን በማቋረጥ ከስራ ያሰናበተን አላግባብ በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተቋረጠ ማናቸውም ክፍያ ተከፍሎ ወደ ስራችን እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቅርበው በነበረው ክስ ሳቢያ ፍ/ቤቱ ክርክሩን ከሰማ በኃላ ከሳሾቹ ከተከሳሹ ጋር የነበራቸው ግንኙነት የሰልጣኝ እና የአሰልጣኝ ከመሆኑ ውጪ አግባብነት ባላቸው የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች መሰረት የተቋቋመ የስራ ውል የነበራቸው መሆኑን ስላላስረዱ ተከሳሹ የስራ ውላችንን አላግባብ አቋርጦብናል በሚል ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ያቀረቡት ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም በማለት የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በትዕዛዝ የጸናው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ከሳሾቹ በ07/11/2003 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ ተከሳሽ በተለያየ ቀን እና ዓ.ም. ከከሳሾቹ ጋር በተናጠል ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር የሚቆይ የስልጠና እና የብድር ስምምነት እንደፈረመ፣ስልጠናው በአራት ክፍሎች የተከፈለ ሆኖ ከሳሾቹ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች "ሰልጣኝ"፣በቀሪዎቹ ሁለት ክፍሎች ደግሞ "ሰራተኛ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶአቸው እንደነበረ፣የመጨረሻዎቹን ሁለት ክፍሎች ስልጠና ሲወስዱ መካከለኛ የበረራ አስተናጋጅ ተብለው በወር ብር 1,242 ደመወዝ እየተከፈላቸው ይሰሩ እንደነበረ፣ከሳሾቹ መብትና ግዴታ የተጠበቀላቸው ሰራተኞች ስለመሆናቸው በ23/04/2002 ዓ.ም.በተዘጋጀው ማንዋል ላይ በግልጽ እንደተቀመጠ፣በዚህ ሁኔታ ተከሳሽ እና ከሳሾች የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ያላቸው ሆኖ እያለ ተከሳሽ የቀጣሪነት የበላይነቱን ተጠቅሞ ሕገወጥ ውል በማስፈረም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3ኛ፣ከ5ኛ እስከ 8ኛ፣10ኛ፣11ኛ እና 12ኛ ከሳሾችን የሁለት ዓመት ከስድስት ወር የስልጠና ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት እንዳሰናበታቸው፣ቀሪዎቹን 1ኛ፣2ኛ፣4ኛ እና 9ኛ ከሳሾችን ደግሞ የስልጠናው ጊዜ ከተጠናቀቀ ከስድስት ወር በኃላ እንዳሰናበታቸው የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሽ ያልተከፈሉ ክፍያዎችን ፈጽሞ ከሳሾችን ወደ ስራቸው እንዲመልስ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው።ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ28/11/2003 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ በመካከላቸው የነበረው ውል የስልጠናና የብድር ብቻ እንደሆነ፣ከሳሾቹ ሰራተኞች እንዳልሆኑ፣መካከለኛ የበረራ ሰራተኛ በሚል ስያሜ መጠራትና መስራትም በስምምነቱ መሰረት የስልጠናው አካል እንደሆነ፣ በወር ይከፈላቸው የነበረው ብር 1,242 ደመወዝ ሳይሆን የኪስ ገንዘብ እንደሆነ፣ደመወዝ ባለመሆኑም ግብር እንደማይከፈልበት እና የሰራተኛ ማህበር መዋጮ እንደማይቆረጥበት፣የስልጠናና የብድር ስምምነቱን ወደ ጎን በመተው ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን ሌሎች ሰነዶች በመጥቀስ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው በመግለጽ ተከራክሮአል።ፍ/ቤቱም ክሱን ከሰማ እና የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ከሳሾቹ ከተከሳሽ ጋር በሕጉ አግባብ የተቋቋመ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ውል ያላቸው መሆኑን አላስረዱም በማለት ክሱን በብይን ውድቅ ያደረገው ሰራተኛ ማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 4 በተመለከተው መሰረት ከአሰሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ማለት እንደሆነ፣በግራ ቀኙ መካከል የቅጥር ግንኙነት የሚኖረው የስልጠናው ጊዜ ተጠናቆና ተከሳሽ ሰልጣኞቹን ለመቅጠር የሚፈልግ ሆኖ የቅጥር ውል ሲደረግ ብቻ ስለመሆኑ በስልጠናና በብድር ውሉ በአንቀጽ 8 እና 9 ላይ እንደተመለከተ፣መካከለኛ የበረራ አስተናጋጅ የሚል ስያሜ የተሰጣቸውም ከሳሾቹ ከተከሳሽ ጋር ባደረጉት ተጨማሪ ስምምነት እንደሆነ፣ክፍያውም ደመወዝ ሳይሆን የኪስ ገንዘብ ስለመሆኑ በስምምነቱ በአንቀጽ 3 እና 4 እንደተመለከተ፣ የሁለት ዓመት ከስድስት ወር የስልጠና ጊዜ ከማብቃቱ በፊትም ሆነ ካበቃ በኃላ የተሰናበቱት ከሳሾች ከተከሳሽ ጋር ከስልጠናና ብድር ስምምነት ውጪ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ውል የነበራቸው ስለመሆኑ እንዳላስረዱ፣ከሳሾቹ በተዋዋዮቹ መካከል ሕግ የሆነውን የስልጠናና የብድር ስምምነት ይዘት ወደጎን በመተው ለክርክሩ አግባብነት የሌላቸውን የተከሳሽ ድርጅት ሰነዶች በማጣቀስ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው በዝርዝር በመግለጽ ሲሆን ከሳሾቹ በብይኑ ቅር በመሰኘት ያቀረቡለትን ይግባኝ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ዘግቶ አሰናብቶአል።ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካቾቹ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተጠቀሰው የሁለቱ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታ የቀረበበትን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለመመርመር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ አጠቃላይ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የስር ከሳሾች ከስር ተከሳሽ ጋር በሕጉ አግባብ ያቋቋሙት የስራ ውል መኖሩን አላስረዱም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚል ነጥብ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል።

በዚህም መሰረት አመልካቾች በተናጠል ከተጠሪ ጋር ያቋቋሙት ውል እና ተጨማሪ ውል ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር የሚቆይ የስልጠና እና የብድር ስምምነት መሆኑ፣በስምምነቱ መሰረት አመልካቾች በአራት ክፍሎች የተከፈለውን የስልጠና መርሐ ግብር በስኬት ካጠናቀቁ በኃላ አመልካቾችን ሰራተኛ አድርጎ በመቅጠር ረገድ የመወሰን መብት የተሰጠው ለተጠሪ መሆኑ፣ተጠሪ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከአመልካቾች መካከል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፊሎቹን ያሰናበተው የስልጠና መርሐ ግብሩን ከማጠናቀቃቸው በፊት መሆኑ፣ከፊሎቹ ደግሞ የስልጠና መርሐ ግብሩን በስኬት ያጠናቀቁ ቢሆንም ተጠሪው በስምምነቱ በተሰጠው መብት መሰረት ሰራተኛ አድርጎ ለመቅጠር ያልወሰነ መሆኑ በክርክሩ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ሲሆኑ የስር ፍ/ቤቶችም አግባብነት ባላቸው የአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች መሰረት አመልካቾች ከተጠሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ውል ያቋቋሙ መሆኑን አላስረዱም በማለት ክሱን ውድቅ ያደረጉትም ከላይ የተጠቀሱ በክርክሩ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን መሰረት በማድረግ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ሠራተኛ ማለት በአዋጁ በአንቀጽ 4 በተመለከተው መሰረት ከአሠሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 2(3) የተመለከተ ሲሆን የስራ ውል የሚመሰረተውም ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአሰሪው ለመስራት ሲስማማ መሆኑ በአዋጁ በአንቀጽ 4(1) ተደንግጎአል፡፡አመልካቾች ከተጠሪ ጋር በተናጠል ያቋቋሟቸው ውሎች እና ተጨማሪ ውሎች ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የስልጠና እና የብድር ውል እንጂ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ውል አይደለም፡፡ህግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር ተዋዋዮች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት እንዳላቸው በፍ.ሕ.ቁ. 1711 የተመለከተ በመሆኑ እና በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ደግሞ ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ ሕግ መሆናቸው በፍ.ሕ.ቁ.1731(1) የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪው የቀጣሪነት የበላይነቱን በመጠቀም ሕገ ወጥ ውል አስፈርሞናል በማለት አመልካቾች ያቀረቡት የክርክር ነጥብ ሕጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡አመልካቾቹ ውሉ ሕገ ወጥ ነው የሚሉበት ምክንያት ቢኖር እንኳ ይህን የውሉን ሁኔታ መሰረት አድርገው ክስ እና ክርክር ማቅረብ ይችሉ የነበረው ውሉ ፍጻሜ ከማግኘቱ በፊት እንጂ ውሉ ፍጻሜ አግኝቶ ተጠሪ የማይቀጥራቸው መሆኑን ካረጋገጡ በኃላ አይደለም፡፡በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካቾቹ ከተጠሪ ጋር በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የስራ ውል ያላቸው መሆኑን አላስረዱም ሲሉ ክሱን ውድቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 73969 በ02/08/2004 ዓ.ም. የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 119009 በ24/09/2004 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 86284

መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ረታ ቶሎሣ
ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካች ፡- ሆራይዘን አዲስ ጎማ (አ.ማ) ጠበቃ ሒሩት መለሰ ቀረቡ
ተጠሪ ፡- አቶ መኮንን ዓለሙ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ ሥንብት ህጋዊነት የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች በተለያዩ የሥራ መደቦች ሲያሰራኝ ቆይቶ ከሕግ ውጭ ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ሰራ እንዲመልሰኝ ወይም በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ /ተጠሪ/ በድርጅቱ ላይ ጉዳት አድርሷል፤ጆንያ ተቆጣጥሮና ተከትሎ እንዲያስረክብ ትእዛዝ ተሰጥቶት ለሌሎች የቀን ሠራተኞች ኃላፊነቱን በመተው 390 /ሶስት መቶ ዘጠና/ ጆንያ ነው ተብሎ የተጫነው፣ መውጫ በር ላይ ሲቆጠር 580 /አምስት መቶ ሰማኒያ/ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ተከሣሽ 190 /አንድ መቶ ዘጠና ጆንያ/ ከድርጅቱ ሊያሰወስድ የነበረ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በወቅቱ 190 ጆንያ በትርፍ ተጭኖ በር ላይ በጥበቃ ሠራተኞች የተያዘ መሆኑን ሣይክድ ጥፋቱ የተፈፀመው አሠሪው /አመልካች/ ልምድና ክህሎት በሌለኝ የሥራ መደብ ላይ ስለመደበኝና በአንድ ጊዜ ተደራራቢ ሥራ እንድሰራ ትእዛዝ ስለሰጠኝ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተጠሪ በተመደበበት የሥራ መደብ በቂ የሆነ ልምድና ክህሎት ስለሌለውና አመልካች ተደራራቢ ሥራ እንዲሰራ ትእዛዝ ስለሰጠው 190 ጆንያ በትርፍነት ተጭኖ ሊወጣ ሲል በግቢው ጥበቃ ሠራተኞች ተይዟል፡፡ ይህንን ጥፋት የፈፀመው በልምድ ማነስና በሥራ ጉጉት ስለሆነ ጥፋቱ ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም፤ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው፤ አመልካች የስድስት ወር ደመወዙን ከፍሎ ተጠሪን ወደ ሥራው ይመልሰው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስንብቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕገ ወጥ ነው ካለ በኃላ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን በመክፈል ተጠሪን ያሰናብተው በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ ተጠሪ በኃላፊነት የተረከበውን ጀንያ በትእዛዙ መሠረት ቀንሶ እንዲጭን የማድረግና የድርጅቱ ትርፍ ጀንያ ያልተጫነ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ ተጠሪ ይህንን ኃላፊነቱን በአግባቡ ስላለመወጣቱ 390 /ሶስት መቶ ዘጠና/ ጀንያ እንደተጫነ በመፈረም የሰጠው ማረጋገጫ እውነተኛ መሆኑና 580 /አምስት መቶ ሰማኒያ/ ጀንያ ተጭኖ የተገኘ መሆኑ ስለተረጋገጠ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ መሰናበቱ ሕጋዊ ሆኖ እያለ ሕገ ወጥ ነው መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ጥር 9 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 6 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በወቅቱ ስህተት የተከሰተው አመልካች በሁለትና ከዚያ በላይ ሰው መስራት ያለበትን ሥራ በእኔ በማሰራቱ ከፍተኛ የሥራ መደራረብ ስለነበረብኝ ነው፡፡ እኔ ንብረቱን ለግል ጥቅሜ አላዋልኩም፡፡ ስለዚህ ከሃያ አመት በላይ ስሰራ በመልካም ባህሪ የሠራሁ በመሆኑ ጥፋቱ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ተጠሪ በሕጋዊ መንገድ መጫን ከሚገባው ጀንያ ውጭ አንድ መቶ ዘጠና ጀንያ በትርፍነት ተጭኖ እንዲወጣ ሲያደርግ በጥበቃ ሠራተኞች የተያዘ ቢሆንም ጥፋቱ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ 390 /ሶስት መቶ ዘጠና ጀንያ/ ብቻ እንዲያስጭንና ወጭ እንዲያደርግ ትእዛዝ ተሰጥቶት የነበረ መሆኑንና ተጠሪ 390 ጀንያ ነው በማለት ያስጫነው ማረጋገጫ የሰጠበት ጭነት በጥበቃ ሠራተኞች ሲፈተሽና ሲቆጠር 580 ጀንያ ሆኖ መገኘቱ በዚህ ምክንያትም አመልካች 190 /አንድ መቶ ዘጠና ጀንያ/ ወጭ ሊደረግበት የነበረ መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱም ተጠሪ 190 ጀንያ በትርፍ ተጭኖ መገኘቱን ሣይክድ የልምድ ማነስ ስለነበረብኝ የሥራ መብዛትና መደራረብ ስላለብኝ ነው ስህተቱ የተሠራው የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ ተደራራቢ የሥራ ትእዛዝ ከደረሱት ሥራዎችን በቅደም ተከተልና በአግባቡ የመፈፀምና በጊዜ አጥረትም ምክንያት ሣይሰራው የቀረውን ሥራ ኃላፊነት ሪፖርት ከሚያደርግ በስተቀር የድርጅቱ ንብረት በማስመዝበር ለሠራው ጥፋት የሥራ ብዛትና መደራረብ የይቅርታ ምክንያትና መከራከሪያ አድርጐ ለማቅረብ አይችልም፡፡ እንደዚሁም ሠራተኞች 390 ጀንያ ቆጥረው ለገዥው እንዲያስረክብ እና እንዳይጭኑ ማድረግና ይህንን ሥራ በኃላፊነት መቆጣጠር መከታተል፣ የተለየ የሥራ ልምድ ክህሎትና ችሎታ የሚጠይቅ ሥራ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ጥፋት የፈፀምኩት በሥራ ብዛት፣መደራረብና በልምድ ማነስ ነው በማለት ያቀረበው መከራከሪያ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት በአሠሪው ንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰን ሠራተኛ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ /1/ ሸ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኃላፊነት የተረከበውን የአሠሪውን ንብረት /እቃ/ በጥንቃቄ የመጠበቅ ግዴታውን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/3/ መሠረት ያልተወጣ መሆኑን የግራ ቀኙ ክርክርና ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የተጠሪ አድራጎት በአዋጅ አንቀጽ 27/1/ሸ የሚሸፈንና አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችለው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ መሠረት ከሥራ ያሠናበተው በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ የካሣ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 87338

ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ተሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር - ነ/ፈጅ ፋሲል አስራት ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1/ አቶ ገብሬ በላይነህ
2/ አቶ ግርማ ስንታየሁ
3/ አቶ አበጀ ካሴ — አልተጠሩም
4/ አቶ መጣለም ገነት
5/ ወ/ሮ ገበያነሽ መኮንን

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የቀን ሰራተኛ ሆነው የተቀጠሩ ሰራተኞች የሳምንት እረፍት ቀናት የዓመት እረፍት ቀናት እና የህዝብ በዓላት ቀናት ክፍያ ሊያገኙ የሚችሉበት ሕጋዊ አግባብ መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ የተጠሪዎች የክስ ይዘትም፡- በአመልካች ድርጅት በተለያየ ጊዜ በግንበኝነትና በአናጺነት ስራ ተቀጥረው በመስራት ላይ መሆናቸውንና ያገለገሉበትን ጊዜ ጠቅሰው በስራ ላይ በቆዩባቸው ጊዜያት ያልተጠቀሙበት የዓመት ፈቃድ የነበራቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የሳምንት እረፍት የህዝብ በዓላት የሰሩበት ታስቦ ያልተከፈላቸው መሆኑን፣ ካሌንደሩ የማይዘጋቸው ቀናትም ያላአግባብ ተዘግተው ስራ ሳይሰሩ የቀሩ መሆኑን ጠቅሰው ለእያንዳንዳቸው ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ገልፆ የተከራከረው ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚገባው አይደለም፣ ይህ ከታለፈም ክሱ በይርጋ የታገደ ነው የሚሉትን ነጥቦችን በማንሳት ነው፡፡ በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪዎች በቀን የሚከፈላቸው ክፍያ በክሳቸው ላይ ያቀረቧቸው የክፍያ ጥያቄዎችን ክፍያ ከግምት ውስጥ አስገብቶና አጠቃልሎ የያዘ በመሆኑ የተለየ ክፍያ ሊኖር የሚችል ስለመሆኑ የሚሰራበት መሆኑንና በቅጥር ውሉ ላይ የተለየ እንደማይደረግ እና ክፍያ የሚፈፀምላቸው በካርዳቸው ላይ ስራ የተሰራባቸው ቀናት ተቆጥረው ስራ ለተሰራበት ቀን ብቻ እንደሚከፈል የተስማሙ ስለሆነ ጥያቄው አግባብነት የለውም በማለት

ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በአመልካች በኩል የቀረቡትን መከራከሪያ ነጥቦችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ አመልካች ለተጠሪዎች የሳምንት እረፍት፣ የሕዝብ በዓላት እና የዓመት እረፍት ክፍያ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች በቀን በሰሩት ስራ መጠን ታስቦ ክፍያ የሚፈጸምላቸው በመሆኑ የጠየቁትን የክፍያ አይነቶች ሊያገኙ አይችሉም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ክርክሩ የግል የስራ ክርክር በመሆኑ በመደበኛ ፍርድ ቤት መታየቱ ተገቢ መሆኑን፣ ተጠሪዎች በቀን በሰሩት ታስቦ በወር የደመወዝ ክፍያ የሚከፈላቸው መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን በምክንያትነት ይዞና የሕጉ ጥያቄ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስትም ሆነ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንፃር ሲታይ ለክሱ መሰረት የሆኑትን የመብት ጥያቄዎች ተጠሪዎች ለመጠየቅ የማይችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪዎች የሳምንት እረፍት ጊዜ፣ የሕዝብ በዓላትና በካሌንደሩ ላልተዘጉት ቀናት ክፍያ እንደሚገባቸው፣ የዓመት የረፍት ጊዜአት ግን የስራ ውሉ ባልተቋረጠበት ሁኔታ በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈልን በማለት ተጠሪዎች መጠየቅ የማይችሉ መሆናቸውን ዘርዝሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሠጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪዎች ጥያቄ ከራሳቸው አልፎ ሌሎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተቀጥረው የሚሰሩትን በርካታ ሰራተኞችን ተመሳሳይ ጥያቄ እንዲያነሱ የሚያደርግ ሆኖ እያለ ክርክሩ የግል የስራ ክርክር መባሉ ያላግባብ ነው፣ ተጠሪዎች በስራ ላይ በቆዩባቸው ከሶስት አመታት የሚበልጥ ጊዜ ለሰሩባቸው ቀናት ብቻ እየታሰበ ሲከፈላቸው የነበረ መሆኑን፣ በቀን ታስቦ የሚከፈለው ገንዘብ የእሁድና የበዓላት ቀናትን የሚያጠቃልል መሆኑን ስራ ሲጀምሩ በተደረገው የስራ ውል ተስማምተው ክፍያው በዚሁ መልክ ሲፈፀም እና እየተሰራበት ያለ ሆኖ እያለ ለተጠሪዎች የተጠየቁት ክፍያዎች እንዲከፈሉ መወሰኑ ያለግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ የተጠቀሰው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ፡- በተጠሪዎች የተጠየቁት የበአላት፣ የሳምንት እረፍትና የዓመት እረፍት ክፍያዎች አመልካች በስራ ላይ ተጠሪዎች ላሳለፉት ቀናት ብቻ እንጂ እነዚህን ክፍያ ሊፈጸም አይገባም፣ ተጠሪዎች ከሶስት አመት በላይ በሰሩበት ጊዜም እነዚህን ጥቅማጥቅሞች ጠይቀው አያውቁም በማለት ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከዚህ ጭብጥ አንፃር ብቻ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት በኮንስትራክሽን ስራ የተሰማራና ተጠሪዎችን ቀጥሮ ሲያሰራ የነበረው በግንበኝነትና በአናጢነት ስራ መሆኑን፣ አመልካች ለተጠሪዎች ለቀን ስራ የሚያስበው የደመወዝ መጠን የተለያየ ሆኖ አከፋፈሉ ግን በወር ተጠቃልሎ በፔሮል የሚከፈል መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ ሲታይ በአጠቃላይ የቅጥር ውል አይነቶች ለተወሰነ ሥራ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊደረግ የሚችሉ ናቸው፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ሕጉ የቅጥር ውል አይነቱ ቋሚም ይሁን ጊዜያዊ ለሰራተኛው በሕጉ የተፈቀዱ ጥቅሞችና ከለላዎች የቅጥሩ አይነት መሰረት ተደርጎ ልዩነት ማድረግ የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ጊዜያዊ ሰራተኞችም ሆነ ቋሚ ሰራተኞች በሕጉ የተጠበቁላቸውን ጥቅማጥቅሞችንና ከለላዎችን እንደሚያገኙ የህጉ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከሁሉም በላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 42(2) ድንጋጌ ሲታይ ሰራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የስራ ሰዓት እረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የስራ አካባቢ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን ይኼው የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ሕገ መንግስት ድንጋጌ እነዚህን ጥቅሞችና ከለላዎችን የሚያገኙትን ሰራተኞች ብሎ በጥቅሉ ከማስቀመጥ ባለፈ የቅጥር አይነቱን ለይቶ አላሰፈረም፡፡ በመሆኑም ጊዜያዊ ሰራተኞችም ቢሆኑ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጡትን ጥቅሞችና ከለላዎች ተጠቃሚ የማይሆኑበት አግባብ የለም፡፡

አመልካች ተጠሪዎችን የቀጠረው በኮንስትራክሽን ስራ መሆኑ ከተረጋገጠ የቅጥሩ አይነት ለተወሰነ ስራና ጊዜ የተቀጠሩ መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ከላይ እንደተጠቀሰው ተጠሪዎች በሕጉ የተጠበቁላቸውን ጥቅሞች ከለላዎች ተጠቃሚ የማይሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች የመብቶቹ ተጠቃሚ የማይሆኑበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ሕጋዊ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ሌላው አመልካች ከጊዜ ጋር በማያያዝ የሚያሳየው ክርክር ሲታይ ተጠሪዎች በአመልካች ድርጅት ከሶስት አመታት በላይ ሲሰሩ የጥቅማ ጥቅሞችን ጥያቄ አንስተው ያለማወቃቸው የሚገልፅ ሲሆን እንዲህ መሆኑ ተጠሪዎች ጥያቄውን ከእነጭራሹ እንዳይጠይቁ የማድረግ ሕጋዊ ውጤት የለውም፡፡ ምክንያቱም በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ጥቅማ ጥቅሞችን ከማግኘት የሚያግዳቸው ከሚሆን በስተቀር የአመልካችን እርምጃ ሙሉ በሙሉ ሕጋዊ ሊያደርግ የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 162 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪዎች ለሶስት አመታት ያህል ጥያቄውን አላቀረቡም የሚለው ክርክር ተጠሪዎች ጥያቄውን ለማንሳት አይችሉም ለማለት የማያስችል ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች በይርጋ የማይታገዱትን ክፍያዎች ለይተው የወሰኑ በመሆኑ በዚህ ረገድም የሕግ ስህተት አለ ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

የዓመት እረፍትን በተመለከተም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለተጠሪዎች እንደሚገባቸው፣ ግን የዓመት እረፍቱን መጠቀም ሲገባቸው በስራ ላይ እያሉ በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸው ጥያቄ ማቅረባቸው ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 77(5) ድንጋጌ አንፃር ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልፆ መወሰኑ ሕጋዊ እንጂ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ስራ ለመስራት ዝግጁ ሆነው አመልካች ለተጠሪዎች ስራ የመስጠት ግዴታውን ያለመወጣቱ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካቹ ለተጠሪዎች ለእነዚህ ቀናት ደመወዝ የመክፈል ሕጋዊ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያስከትልበት ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 12(1(ሀ))፣ 12(2)፣ 53 እና 54 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔም የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪዎች ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩና ደመወዝ በቀን ሂሳብ ታስቦ በወር የሚከፈላቸው ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ለማንኛውም ሰራተኛ የተጠበቁትን ጥቅማጥቅሞችንና ከለላዎች የማግኘት መብታቸውን የሚነፈጉበት ሕጋዊ መሰረት የሌለ በመሆኑ በይርጋ ያልታገዱትን ጥቅማ ጥቅሞችን ብቻ በመለየት ተጠሪዎች እንዲያገኙ ተብሎ በተሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 24912 ጥር 06 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ተጠሪዎች በቀን ሂሳብ ታስቦ በወር ደመወዝ የሚከፈላቸው ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩ ሰራተኞች ቢሆንም የሳምንት እረፍት፣ የሕዝብ በዓላት እረፍት ደመወዝ ክፍያ የማግኘት፣ የዓመት እረፍት የማግኘትና ያለካሌንደር የተዘጉ ቀናት ክፍያ ደመወዝ የማግኘት መብት አላቸው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 87285

መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አመልካች፡- ወ/ሮ የውብዳር ንጋቱ

ተጠሪ፡- ገነት ሆቴል ነ/ፈጅ ፀጋዬ ጌታነህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የቀረበውን የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች የክስ ይዘትም በተከሳሽ ድርጅት ከ1975 ዓ/ም እስከ ጥር 21 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ ተቀጥረው እየሰሩ መቆየታቸው፣በደረሰባቸው የእግር በሽታ ምክንያት ከጥር 21 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ጥር 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሕክምና ተከታትለው እያለና ስለሁኔታው ለስራ ባልደረቦቻቸው አቶ በላይ ተገኝ ነግረው እሳቸውም ለአቶ ታደሰ ሶልቤ ለተባሉት ኃላፊ ነግረው እያለ ድርጅቱ ይህንኑ ወደ ጎን በመተው የአመልካችን የስራ ውል ያቋረጠ መሆኑን ዘርዝረው የተጠሪ እርምጃ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ወይም ሕጋዊ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካች በተደጋጋሚ የስራ ሰዓት ባለማክበራቸው በማስጠንቀቂያ ታልፈው በመጨረሻም ከጥር 21 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ከስራ ስለቀሩ የተሰናበቱ መሆኑን፣ስለመታመማቸው ተጠሪ የማያውቅ መሆኑን በመግለጽ ስንብቱ ሕጋዊ ነው፣ከተጠየቁት የክፍያ አይነቶች መካከልም ያልተከፈላቸው ደመወዝ፣የአመት ፍቃድ ክፍያና የሰርቪስ ቻርጅ ተገቢነት ያላቸው መሆኑና ሌሎች የክፍያ አይነቶች ግን የማይገባቸው መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ስለመታመማቸው ለተጠሪ ያላማሳወቃቸው መረጋገጡን፣አሳውቀዋል ቢባል እንኳን ሕመማቸው ተጠሪ ዘንድ ቀርበው በማስቱ ለአሰሪያቸው ማሳወቅ/ፍቃድ ማግኘት የማይከለክላቸው ስለነበረና ይህንንም በአግባቡ ስላላሳወቁ አመልካች ከጥር 21 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ለአምስት ተከታታይ ቀናትና ከዚያ በላይ የቀሩት ያለበቂ ምክንያት ነው የሚል ምክንያት በመያዝና የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ለ)) ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ የስራ ስንብት እርምጃው ሕጋዊ ነው በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በሕመም ምክንያት የቀሩ መሆኑን የሚያሳይ የህክምና ማስረጃ ከመቅረቡም በላይ ስለሁኔታው ለተጠሪ አሳውቀው እያለ ይኼው ታልፎ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም አመልካች በሕመም ምክንያት ህክምና ላይ የቆዩና ይህንንም በስራ ባልደረባቸው በኩል ለተጠሪ አሳውቀው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ስለሁኔታው በአካል ቀርበው ለተጠሪ ለማሳወቅ ህመሙ ክልከላ የማያደርግ ነው ተብሎ ከአምስት ተከታታይና ከዚያ በላይ የስራ ቀናት ከስራ ስለቀሩ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከጥር 21 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ጥር 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ በህመም ላይ ሁነው ህክምና ሲከታተሉ የነበሩ መሆኑን በሐኪም ማስረጃ የተረጋጠ ፍሬ ነገር ሲሆን አከራካሪው ፍሬ ነገር ስለህመሙ ለተጠሪ ማሳወቅ ያለማሳወቃቸው ሁኖ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የተሰጠው የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ከአሰፈራቸው በርካታ ምክንያቶች ውስጥ ለውሳኔው አብይ ምክንያት ያደረገው የህመሙ አይነት አመልካችን በአካል ቀርበው ለተጠሪ ስለህመሙ ከማሳወቅና ፈቃድ በሕጉ አግባብ ከመጠየቅ አይከለክላቸውም የሚል መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰራተኛ በሕመም ምክንያት ከስራ ከቀረ ስለሁኔታው ለአሰሪው ማሳወቅና ፈቃድም ማግኘት ያለበት መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 85(4) ድንጋጌ ስር ከተመለከተው ድንጋጌ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ድንጋጌው የህመም ፈቃድ ማግኘት በሕጉ የተጠበቀ መብት መሆኑና መብቱን ለማግኘት በቅድሚያ መሟላት ስለአለባቸው ሁኔታዎች በግልጽ የሚያስቀምጥ ቢሆንም ስለሁኔታው ለአሰሪው ያለማሳወቅ የሚያስከትለውን ውጤት ግን በግልጽ አያስቀምጥም፡፡ይሁን እንጂ ሕመም ከስራ ለመቅረት እንደበቂ ምክንያት ሊወሰድ የሚገባው መሆኑን ሕግ አውጪው ታሳቢ አድርጎ የሕመም ፈቃድ ማግኘትን መብት የደነገገ መሆኑ ግንዛቤ ከተወሰደ በሕጉ አግባብ የሕመም ፈቃድ ያልወሰደ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ሰራተኛ ከስራ የቀረው በበቂ ምክንያት ነው ተብሎ የሚገመትበት አግባብ ስለማይኖር ያለበቂ ምክንያት ከስራ ስለመቅረትና ውጤቱን የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ ለጉዳዩ ተፈፃሚ የማይሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡አዋጁ በአሰሪና በሰራተኛ መካከል ያለውን ግንኙነት በተለይ ለመግዛት ተብሎ ታስቦ የወጣ በመሆኑ በአዋጁ ውስጥ ያሉትን ድንጋጌዎችን አስተሳስሮ ተገቢውንና የአዋጁን ዓላማና መንፈስ የሚያሳካ ትርጉም ለአንድ ድንጋጌ መስጠት በሕግ አተረጓጎም ደንቦችም የተፈቀደ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች ስለመታመማቸው የሚያረጋግጥ የህክምና ማስረጃ ከሚመለከተው የህክምና ተቋም የወሰዱ መሆኑና ይህንኑም በስራ ባልደረባቸው በኩል ለተጠሪ ማሳወቃቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተቀባይነት ከአገኘ አመልካችን ያመማቸው ሕመም በአካል ቀርበው ለተጠሪ ለማሳወቅ ወይም ፍቃድ ለማግኘት

የሚከለክላቸው አይደለም ተብሎ ከስራ ስለመቅረታቸው ያቀረቡት ምክንያት በቂ አይደለም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡አንድ አሰሪ የህመም ፈቃድ ለሰራተኛው መስጠት እንዲችል ስለሁኔታው እንዲያውቅ የሚደረገው መሰረታዊ አላማም ሰራተኛው ከስራ በመቅረቱ ምክንያት የሚፈጠረውን ክፍተት በተገቢው መንገድ እንዲሞላ ለማድረግ ምርትና ምርታማነቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳይፈጠርበት ነው ተብሎ የሚታመን መሆኑን አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 85 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ በመግቢያው ከተመለከተው የአዋጁ መሰረታዊ አላማ ጋር አንድ ላይ በማንበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም ተጠሪ አመልካቿ በሕመም ላይ የነበሩ መሆኑን ከአወቀ በስራው ላይ ክፍተት እንዳይፈጠር ተገቢውን ለማድረግ በሚያስችለው ሁኔታ ውስጥ የነበረ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ይህ ሁኖ እያለ አመልካችን ያለበቂ ምክንያት ከስራ ቀርተዋል በማለት የስራ ስንብት እርምጃ መውሰዱ የሕጉን መንፈስና ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ሕገ ወጥ ነው፡፡ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አንጻር መመልከት ሲገባቸው አመልካች በአካል ቀርበው ለተጠሪ ማሳወቅ ነበረባቸው በሚል ምክንያት ላይ ትኩረት በማድረግ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ቀጥሎ የተመለከትነው ውጤቱን ነው፡፡አንድ ሰራተኛ በአሰሪው ከስራው የተሰናበተው ህገ ወጥ በሆነ እርምጃ መሆኑ ከተረጋገጠ ውጤቱ ሰራተኛው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው እንዲመለስ ማድረግ ወይም በዚህ ምትክ ሕጋዊ ክፍያዎች ተከፍለውት እንዲሰናበት ማድረግ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 39 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡እነዚህ በሕጉ የተመለከቱት ውጤቶች የሚወሰኑበት ምክንያትም የአዋጁን መሰረታዊ ዓላማ ያገናዘበ መሆን ያለበት ስለመሆኑ ከድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በሌላ አገላለፅ የእርምጃው ውጤት የሰራተኛውን የስራ ዋስትና እና የኢንዲስትሪውን ሰላም ለመጠበቅ በሚያስችል መንገድ ሊወሰን እንደሚገባው የድንጋጌዎቹ መንፈስና ይዘት ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካችን ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራ እንዲመለሱ ማድረግ ተገቢነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ምክንያቱም ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ምክንያት ከመከሰቱ በፊትም አመልካች ከስራ በተደጋጋሚ ይቀራሉ በሚል ተጠሪ በማስጠንቀቂያ ያለፋቸው መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ አመልካች ከተጠሪ 1ኛ ምስክር ከነበሩትና የቅርብ አለቃቸው ከሆኑት ሰው ጋርም በጥሩ ግንኙነት ውስጥ ያለመሆናቸውን፣ይልቁንም በመካከላቸው በተፈጠረው ፀብ የወንጀል ክስ አቤቱታ አቅርበው በሚመለከተው አካል ዘንድ በመታየት ላይ እንደሚገኝ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር የገለፁ በመሆኑ አመልካች ወደ ስራው ቢመለሱ ከተጠሪ ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት ይኖራቸዋል፣በስራ ቦታው ላይ የኢንዲስትሪ ሰላም ይሰፍናል ብሎ ለመገመት የሚያስችግር መሆኑን የሚያሳዩ ምክንያቶች መሆኑን ክርክሩ የሚያሳይ ነውና፡፡ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43(3) መሰረት አመልካች ወደ ስራ ከሚመለሱ ይልቅ በምትኩ ሕጋዊ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ማድረግ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ሲሆን ውጤቱን በተመለከተ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 43(3) መሰረት መወሰን ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ስንብቱን አስመልክቶ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04639 ነሐሴ 22 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12679 ጥር 28 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረተ ተሻሽሏል፡፡
2. የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ወደ ስራ ከሚመለሱ ይልቅ በምትኩ ሕጋዊ ክፍያዎች፤በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 39 መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ፣የሚገባው በአንቀጽ 42/4/ ካሳ፤በአንቀጽ 35/1/ሀ/ መሰረት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ተከፍሏቸው ይሰናበቱ ብለናል፡፡በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰኑት የጥር ወር 2004 ዓ/ም የ21 ቀን ደመወዝ፣የታህሳስ ወር እና የጥር ወር 21 ቀናት 2004 ዓ/ም የሰርቪስ ቻርጅ ክፍያና የ43 ቀናት የአመት ፍቃድ በገንዘብ ተለውጦ የሚከፈለው ክፍያ እንደፀኑ ናቸው፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ. 90389

ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤርፖርት ድርጅት ነ/ፈጅ እፀገነት ከድር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ በሪሁን በላይ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ ውል መቋረጥን የሚመለከት ነው በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ከሣሽ /ተጠሪ/ 23-10-2002 ዓ.ም ጀምሮ በጥበቃ የሥራ መደብ ተቀጥሬ ስሰራ ተከሣሽ /አመልካች/ 27-04-2004 ዓ.ም በተፃፈ የሥራ ስንብት ደብዳቤ ከ30-05-2004 ዓ.ም ጀምሮ ከሥራ ያሰናበታቸው በመሆኑ ወደ ምድብ ሥራዬ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ ወይም የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ፍርድ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ የተመደበበት የሥራ መደብ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሆኖ እያለ ተከሣሽ /ተጠሪ/ 10-02-2004 ተረኛ ሆኖ ተመድቦ ሲሰራ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ወደውስጥ ዘልቆ እንዲገባ በማድረግ ሰውየው አውሮፕላን የሚቆምበትና የተከለከለ ቦታ ላይ ቆሞ በፖሊሶች ተይዟል፡፡ እንዲሁም ከሣሽ በተመሣሣይ ሁኔታ 27-03-2004 ዓ.ም አራት ማንነታቸው ያልታወቁ ሰዎች ወደ ውስጥ ዘልቀው እንዲገቡ በማድረጉ እና በድርጅቱ ላይ የከፋ ችግር በመፍጠሩ ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ ተሰጥቶት የሥራ ውል በሕጋዊ መንገድ የተቋረጠ በመሆኑ የከሣሽ ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተከሣሽ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠ መሆኑንና ተጠሪ በጥበቃ ሥራ ላይ እያለ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ወደ ድርጅቱ እንዲገቡ በማድረግ ጥፋት የፈፀሙ መሆኑን ገልጿል፡፡ ነገር ግን በተጠሪ ጥፋት ምክንያት በድርጅቱ ላይ የተፈጠረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችግር የሌለ በመሆኑ የሥራ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት አመልካች የተለያዩ ክፍያዎችና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ከፍሎ ተጠሪን ከሥራ ያሰናብተው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሸኘት አመልካች ይግባኝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ የሰጠ በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ክፍያ መክፈል የለበትም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ በማሻሻል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች በ22-09-2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ማንነታቸው የማይታወቅና ያልተፈቀደላቸውን ሰዎች ወደ ድርጅቱ ውስጥ በማስገባት ድርጅቱን ለከፍተኛ የፀጥታ ሥጋት የዳረገ መሆኑና አመልካች የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ከሥራ ያሰናበተው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ 3-11-2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚለውን ነጥብ በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡ አመልካች 11-11-2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
4. ከሥር የክርክር አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በተሠማራበት የጥበቃ ሥራ ላይ እያለ ጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ሣይፈተሽ ወደ ኦውሮፕላኖች ማረፊያ ድርጅቱ እንዲገባ ያደረገና ሠውየውም አውሮፕላኖች መቆሚያ ቦታ ላይ በፖሊሶች መያዙ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም ይህንን ጥፋት የፈፀመ መሆኑን በማመን በጽሑፍ ይቅርታ የጠየቀ መሆኑና በጋራዥና ትራንስፖርት በር ላይ ተመድቦ እንዲሠራ አመልካች 16-02-2004 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ግራ ቀኙ በሥርና በሰበር ደረጃ ካደረጉት ክርክር ተረድተናል፡፡
6. አመልካች ተጠሪን 10-2-2002 ዓ.ም በማስጠንቀቂያ ያለፈው ቢሆንም ተጠሪ ሕዳር 27 ቀን 2004 ዓ.ም በጥበቃ ሥራ ላይ እያለ የጥበቃ ቀጠናውን ክፍት ትቶ በመሄዱ አራት ሰዎች ወደ ውስጥ ገብተው ክሊኒኩ አከባቢ ሲደርሱ በፖሊስ የተያዙ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ 27/03/2004 ዓ.ም. ይህንን ጥፋት ከፈፀመ በኃላ የጥበቃ አስተባባሪው በትራንስፖርትና ጠቅላላ አገልግሎት ቡድን ሪፖርት ያቀረበ መሆኑና የትራንስፖርት አገልግሎት ቡድን ሁኔታውን ከመረመረ በኃላ የተጠሪ የሥራ ውል ታህሣስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም የሚያበቃ መሆኑን ገልፆ የተጠሪ የስራ ውል ለአንድ ወር ብቻ እንዲራዘምና ይህም የቅድመ ማስጠንቀቂያ መስጫ ጊዜ ሆኖ ተቆጥሮ የሥራ ውላቸው እንዲቋረጥ ታህሣስ 23 ቀን 2004 ዓ.ም ውሣኔ የሰጠ መሆኑን ተረድተናል፡፡
7. ተጠሪ የሚሠራበት ድርጅት የጥበቃ ሥራ በከፍተኛ ጥንቃቄ መከናወን የሚገባውና ለድርጅቱም ሆነ ለተገልጋዮና ደንበኞች ደህንነት አጠባበቅ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ይህንን የሥራ ተግባሩን በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመፈፀሙ የድርጅቱን ደህንነት ለከፍተኛ ችግር ያጋለጠና ማንነታቸው ያልታወቀና ያልተፈተሹ ሠዎች ወደ ድርጅቱ ዘልቀው ገብተው በፖሊስ የተያዙ ስለመሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የፈፀመው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥፋት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1/ሸ/ የሚሸፈንና የተጠሪን የሥራ ውል ያለ ማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የጥበቃ ተግባሩን በአግባቡ ባለማከናወኑና ሰዎቹ ሣይፈተሹ ወደ ድርጅቱ ዘልቀው በመግባታቸው በአመልካች ላይ የደረሰበት የፀጥታና ደህንነት ችግር /ጉዳት/ የለም በማለት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲሉ በማለት የሰጡት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 17/1/ሸ እና /ቀ/ እንዲሁም አንቀጽ 14/2/ሀ/ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት መንፈስ አላማ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

8. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል በአንድ ወር በማራዘምና ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የሥራ ውል ማቋረጡ አመልካች የተጠሪን መብት ለመጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ማድረጉን የሚያሣይ እንጂ ሕገ ወጥ ተግባር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕግ አግባብ በመሆኑ አመልካች የካሣ ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወሰነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92466

ጥር 2 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ አዳነ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አሕመድ

አመልካች፡- ሳይግን ቴክስታይል ቢዩልዲንግ ኮንስትራክሽን ትሬድ ኢንዳትሪ ኢንክ ኢትዮጲያ
ብራንች ነ/ፈጅ መቅደስ ሽፈራው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ጋር ተያይዞ የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ ከሣሽ በተከሣሽ ደርጅት ውስጥ ከ22/06/02 ዓ.ም ጀምሮ በመሐንዲስነት እና በፕሮጀክት ስራ አስኪያጅነት የስራ መደብ ተቀጥረው በማገልገል ላይ እያሉ ተከሣሹ ያለአግባብ የሥራ ውላቸውን ያቋረጠባቸው መሆኑን ጠቅሰው ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ መሠረት ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲፈፀምላቸው እንዲሁም የሥራ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በሚል ዳኝነት የጠየቁ መሆናቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሥር ተከሣሽም ቀርበው ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ፡- ከሣሽ ተከሣሽን በመወከል ስራዎችን የሚያቅዱ ለሠራተኞች ስራ የሚሰጡ እና የሥራ ጥራታቸውን የሚቆጣጠሩ መሆኑን፣ ስራዎችን የሚያስተባብሩ እና የስራ አፈፃፀማቸው አጥጋቢ ባልሆኑ ሠራተኞች ላይ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን ጠቅሶ ከሳሽ የሥራ መሪ እንጂ ሠራተኛ ባለመሆናቸው የሥራ ክርክር ችሎቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬ ነገሩ ረገድም የበኩሉን መከራከሪያ በማቅረብ መልስ መስጠቱን የሥር ፍ/ቤቱ ውሣኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙ የጽሑፍ እና የቃል ክርክር ከሰማ እና ለከሣሽ የተሰጠው የሥራ መዘርዘር በትእዛዝ አስቀርቦ መመልከቱን ከገለጸ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የከሣሽን የሥራ ተግባር የፕሮጀክቱን ስራ በኃላፊነት መምራት፣ማደራጀት፣ መቆጣጠር እና ማስተባበር መሆኑን በማስረጃ መረጋገጡን ከገለፀ በኃላ የዚህ አይነቱን ተግባራት የሚፈጽም ግለሰብ ደግሞ በአዋጁ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3 እና በማሻሻያ አዋጁ ቁ.494/98 አንቀጽ 2/ሐ/ ድንጋጌዎች እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ.42901 በሰጠው የሕግ ትርጉም መሠረት የሥራ መሪ እንጂ ሠራተኛ ሊባል ስለማይችል ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ መሠረት ስለማይስተናገድ የሥራ ክርክር ችሎቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244/2/ /ሀ/ መሠረት በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡

በአሁኑ ተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ክሰማ በኃላ ጉዳዩን በመመርመር ተጠሪ የተመደበበት የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የስራ መደብ ሥራ መዘርዘር ሁኔታ ከአዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/ሐ/ ድንጋጌ ይዘት አኳያ ተገናዝቦ ሲታይ ተጠሪ የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈጸም ጭምር ኃላፊነት አልተሰጠውም፣ ከነዚህ በተጨማሪም ወይም እነዚሁኑ ሣይጨምር ሠራተኞችን የመቅጠር የማዛወር የማገድ የማሰናበት የመመደብ ወይም የስነ ስርዓት እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ሣይሰጠው የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የፕሮጀክቱን ስራ በኃላፊነት ይመራሉ፣ ያደራጃሉ፣ ይቆጣጠራሉ በማለት ጉዳዩን ከሰበር መ.ቁ. 42901 ገ/ር ውሣኔ ጋር በማያያዝ ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው የሚል ድምዳሜ ይዞ የሰጠው ብይን የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ብይኑን ሽሮ የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገሩ ክርክር ላይ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥ ክርክሩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት መልሶለታል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይሄንኑ በፈደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የሥራ መሪ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ በተሰጠው ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታልና ስህተቱ በዚህ ሰበር ችሎት ታይቶ ይታረመልን የሚል ነው፡፡ አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ የሥራ መሪ ነው በሚል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመሻሩ አግባብነት ለተጠሪ ከተሰጠው ስራ ኃላፊነት እና ተግባር አኳያ ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም የተደረገለትን ጥሪ መነሻ በማድረግ ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን የግራ ቀኙ የሰበር ጽሑፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተጠሪ የሥራ መሪ ነው? ወይስ ሠራተኛ? የሚለው ነጥብ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እልባት ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረቱ የሥራ መሪ ማለት በሕግ ወይም እንደየድርጅቱ የስራ ፀባይ በአሠሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊስዎችን የማውጣት የማስፈፀም ከነዚሁ በተጨማሪ ወይም እነዚሁኑ ሣይጨምር ሠራተኞን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ የማገድ፣ የማሰናበት የመመደብ ወይም የስነ-ስርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውንና የሚወሰን ግለሰብ ስለመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ ቁ. 377/96 3/2/ /ሐ/ አና በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2(1) (ሐ) ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘትም መገንዘብ የሚቻለው አንድ ተቀጣሪ ግለሰብ የስራ መሪ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለይቶ ለመወሰን በቅድሚያ ተቀጣሪው ግለሰብ በቀጣሪው ተቋም እንዲያከናውን የተሰጠው ተግባራት እና የሥራ ኃላፊነቶች እያንዳንዳቸው ምን ምን እንደሆኑ በጥንቃቄ ተመልክቶ በቂ ግንዛቤ መያዝ የግድ መሆኑን ነው፡፡ ከዚያ በኃላ በግለሰቡ የሚከናወኑትን የስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተግባራት ወይም የሥራ ኃላፊነትቶቹን ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የሕጉ ድንጋጌ ይዘት አኳያ አንድ በአንድ በጥንቃቄ አገናዝቦ መመልከቱ እና በመመርመር ተገቢ ወደ ሆነው ድምዳሜ ላይ መድረስን ይጠይቃል፡፡

ከዚህ አኳያ ወደ ተያዘው ጉዳይ ተመልስን ስንመለከተው ተጠሪ በድርጅቱ የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅነት የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ የዚህን ስራ መደብ ተግባራትን ሲያከናውን የነበረ ስለመሆኑ እና በዚሁ መነሻነትም የድርጅቱ ማኔጅመንት አባልም በመሆኑ ጭምር አጠቃላይ የሆነውን የድርጅቱ ስራ አመራር ውስጥም በመሣተፍ የበኩሉን ድርሻሲያከናውን የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪ ራሱ ባቀረበው ክስ አቤቱታ ማመልከቻ፣ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አቤቱታ ማመልከቻ እና በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ቃል ክርክር የታመነ ጉዳይ ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ግልባጭ ይዘት ያስረዳል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በፕሮጀክት ስራ አስኪያጅነቱ ከሚያከናውናቸው ዋና ዋና የሥራ ተግባራት እና ኃላፊነቶች በተጨማሪ በድርጅቱ የማኔጅመንት አባልነቱም በድርጅቱ የሥራ አመራር ኃለፊነት ውስጥ ተሣትፎ የነበረው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅነቱ የስራ መደብ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ብዛት የመወሰን፣ በሥሩ ያሉትን ሠራተኞች የመምራት የመቆጣጠር የሥራ አፈፃፀማቸወን የመገምገም፣ ብቃታቸውን የማሣደግ፣ የፕሮጀክቱን ስራ አመራር የማቀድ፣ የመፈፀም፣ የማስተባበር እና የመሣሰሉትን ዋና ዋና የስራ ተግባራት እና ኃላፊነቶችን ሲያከናውን የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪ ተመድቦ ይስራበት የነበረውን የሥራ መደብ ስራ መዘርዝር መረጋገጡን እንዲሁ ከሥር ፍ/ቤቱ ውሣኔ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ የአመልካች ድርጅት የሥራ መሪነት የሥራ ድርሻ ወይም ሚና ነበረው ከሚያሰኝ በቀር ሠራተኛ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘንም በመሆኑም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የሥራ መሪ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ የሰጠው ፍርድ ተጠሪ በድርጅቱ ማኔጅመንት አባልነቱም ሆነ በፕሮጀክት ስራ አስኪያጅነቱ ሲያከናውናቸው የነበረው የሥራ ተግባራት ኃላፊነቶች እና የሥራ አመራር የሥራ ድርሻነቱን በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/2/ሐ/ እና የማሻሻያ አዋጁ ቁ.494/98 አንቀጽ 2/1/ሐ/ አኳያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በከ/መ/ቁ. 135628 በ2/11/2005 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሥራ ክርክር ችሎት በከ/መ/ቁ. 81696 በ15/8/2005 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው እንጂ ሠራተኛ አይደሉም ብለናል ስለዚህ ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት የሚስተናገድ አይደለም፡፡
4. የሰበር ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ቤ/ዮ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 82670

መጋቢት 09 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1ኛ/ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 አስተዳደር ፅ/ቤት - የቀረበ የለም

2ኛ/ አቶ ኑስባ መሀመድ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዋጋዬ አሰፋ - ጠበቃ እሌኒ አስራት - ቀረቡ

መዝገቡ ከሰ/መ/ቁጥር 83247 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በንግድ ቤት በኪራይ ውል የተገኘ መብት ሊቋረጥ አይገባም የሚል ጥያቄ መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኗ ተጠሪ ከአቶ ግርማ እሸቱ ጋር በመሆን በአሁኑ አመልካቾች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ቁጥሩ 528/ለ/ የሆነ መኖሪያ ቤት ከቀበሌ በመከራየት እንደሚኖሩበት በቤቱ ግቢ ውስጥ ሱቅ ሰርተው መነገድ እንዲችሉ ፈቃድ ጠይቀውም የአሁኑ 1ኛ አመልካች ፈቅዶላቸው የኪራይ ውል ተዋውለው በስር 2ኛ ከሳሽ በነበሩት በአቶ ግርማ እሸቱ ስም የንግድ ፈቃድ በማውጣት ሲሰሩ የቆዩ መሆኑን፣ በዚሁ ቤት ቁጥር ተጠሪ ከአሁኑ አንደኛ አመልካች ጋር ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ/ም ለአንድ አመት የሚቆይ የኪራይ ውል ተፈራርመው የአሁኑ 2ኛ አመልካችም የንግድ ፈቃድ አውጥተው ሲሰሩበት የቆዩ መሆኑን፣ የቁርስ ቤት ስራ ልምድ ካለው ሰው ጋር በጋራ ለመስራት በማሰብ ከ2ኛ አመልካች ጋር መስከረም 01 ቀን 2000 ዓ/ም በተፈረመ ውል ትርፍ እኩል ለመስራት በመስማማት በቤቱ ውስጥ ባሉ የስር ሁለተኛ ከሳሽ እቃዎች እና ንብረቶች እንዲሰሩና ውሉም እስከ መስከረም 2006 ዓ/ም ድረስ እንደሚቆይ በመስማማት በመስራት ላይ እያለ የአሁኑ 1ኛ አመልካች ለአሁኑ 2ኛ አመልካች ቤቱን ተጠሪ እንዳከራዩ በማስመሰል በተጠሪ ስም የነበረውን የኪራይ ውል ሰርዞ በአሁኑ 2ኛ አመልካች ስም አዋውሎ ኪራይ እየተቀበለ እንደሚገኝ፣ ከሳሾች ከአሁኑ 2ኛ አመልካች ጋር የኪራይ ግንኙነት የሌለ መሆኑን በመዘርዘር 1ኛ አመልካች ውሉን እንዲቀጥል 2ኛ አመልካችም የያዘውን ቤት ከነሙሉ ንብረቱ ለከሳሾች እንዲያስረክቡና የገቡትን ውል ያፈረሱ በመሆኑ በውሉ መሰረት ብር 3000.00 ኪሳራ ለከሳሽ እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የስር 2ኛ ከሳሽ የሆኑት አቶ ግርማ እሸቱ ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ተጠሪ በውሉ የተከራዩትን የንግድ ቤት ለአከራይ ሳያሳውቁና ፈቃድ ሳያገኙ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው የተገኙ መሆኑ ተረጋግጦ በመመሪያው መሰረት ለአሁኑ 2ኛ አመልካች እንዲከራይ መደረጉ የሁከት ተግባር ያለመሆኑን በመካከላቸው ያለው የኪራይ ውልም ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ከመሆኑም በላይ በፍ/ብሔር ሕጉ መሰረት የንግድ ቤቱን ለሶስተኛ ወገን ማከራየት ከመፍቀዳቸው በፊት ለአከራዩ ሊያሳውቁ ይገባ እንደነበር፣ ተጠሪ ከውሉ በተቃራኒ ንግድ ቤቱን ለአቶ አምደግባ መሐመድ ያከራዩ መሆኑ እና አቶ አምደግባ መሀመድ ደግሞ ለአሁኑ 2ኛ አመልካች ያከራዩ መሆኑ ተረጋግጦ ውሉ መቋረጡን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ 2ኛ አመልካች በሰጡት መከላከያ መልስም የንግድ ቤቱን በጋራ ለመስራት ስምምነት እንደተደረገ አድርገው ያቀረቡት ሰነድ ሐሰተኛ መሆኑንና ቤቱን አከራይተዋቸው የሚጠቀሙበት መሆኑን ዘርዝረው አንደኛ አመልካች በመመሪያው መሰረት ኪራዩ ከእርሳቸው ጋር እንዲሆን ማድረጉ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም 2ኛ ከሳሽ የነበሩትን አቶ ግርማ እሸቱን ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ ገልፆ በብይን ያሰናበታቸው ሲሆን በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል ያለውን ጉዳይ በተመለከተ ግን የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ቤቱን በኪራይ ከስር 2ኛ ከሳሽ ለነበሩት ግለሰብ ይሁን ለሌላ ለሶስተኛ ወገን በኪራይ ያስተላለፉ ስለመሆኑ የሚያስረዳ የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ ያለመቅረቡን ሰኔ 06 ቀን 1996 ዓ/ም የተደረገው የኪራይ ውልም ወረዳው በተከራይነት የሚያውቋቸው እና ፍርድ ቤቱ የመሆን ጥቅም አላሳዩም ሲል ባሰናበታቸው በስር ሁለተኛ ከሳሽ በነበሩት አቶ ግርማ እሸቱ የተደረገ ውል እንጂ በተጠሪ የተደረገ ውል ያለመሆኑንና አቶ ግርማ እሸቱ ደግሞ የንግድ ቤቱን ለሌላ ሰው በኪራይ የማስተላለፍ መብት በውልም ሆነ በሕግ ያላገኙና የውሉ ጊዜም ታህሳስ 6 ቀን 1997 ዓ/ም የሚቆይ ሆኖ ውሉን ያደረጉት በራሳቸው እንጂ በውክልና ስለመሆኑ ያለመግለፁን በምክንያትነት ይዞ ተጠሪ ከአሁኑ 2ኛ አመልካች ጋር እንደአደረጉት ተቆጥሮ በ1997 ዓ/ም የውሉ ዘመን መጠናቀቁ በግልፅ ተቀምጦ እያለ በ2004 ዓ/ም በወጣው መመሪያ መሰረት ተጠሪ ለአሁኑ 2ኛ አመልካች ቤቱን ባላከራዩበት እንዲሁም ሁለተኛ አመልካች በጋራ ለመስራት ውል የተፈራረሙ መሆኑን አምነው ይዘቱን ሳላነብ ነው የፈረምኩት የሚሉትን ውል ስልጣን ባለው አካል እንዲፈርስ ባላደረጉበት ሁኔታ በመመሪያው መሰረት ከ1ኛ አመልካች ጋር ያደረጉት ውል ቤቱን ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈዋል ተብሎ ኪራዩ የሚቋረጥበት አግባብ የለም በማለት ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ጋር ያላቸው የኪራይ ውል እንዲቀጥል ሁለተኛ አመልካችም ቤቱን እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ለየብቻቸው ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች በተናጠል ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ቤቱን ለሶስተኛ ወገን ከአከራይ ፈቃድ ውጪ አከራይተው የቆዩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ መመሪያው ቁጥር 4/2004 ለጉዳዩ አግባብነት የለውም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ምክንያት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ የንግድ ቤቱን ለሶስተኛ ወገን አሳልፈው አልተገኙም በሚል ምክንያት በመመሪያው አይሸፈኑም ተበሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ንግድ ቤቱ የአንደኛ አመልካች ሆኖ ተጠሪ ተከራይተው ይገለገሉበት የነበረ መሆኑን፣ ተጠሪ የንግድ ቤቱን በስር ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ለመክሰስ የሚያስችል መብት የለህም ተብለው በብይን ከክርክሩ ውጪ ከሆኑት ግለሰብ ጋር የኪራይ ውል አላደረጉም፣ እኚህ ግለሰብ በ1996 ዓ/ም ከአሁኑ 2ኛ አመልካች ጋር ያደረጉትና እስከ ታህሳስ 06 ቀን 1997 ዓ/ም ድረስ ቆይቷል የተባለው የኪራይ ውል መብት በሌላቸው ጉዳይ የተደረገ ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤት ተቀባይነት ማጣቱን እና የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያላቸው ግንኙነት በንግድ ቤቱ አንድ ላይ በመስራት ትርፉን ለመጋራት ተስማምተዋል በሚል ምክንያት የስር ፍ/ቤት ሁለተኛ አመልካችን ተከራይ አይደሉም ወደሚለው ድምዳሜ መድረሱን፣ ከዚህም በተጨማሪ በቤቱ ውስጥ አሉ የተባሉት እቃዎች ንብረትነታቸው በስር ፍ/ቤት 2ኛ ከሳሽ የነበሩት የአቶ ግርማ እሸቱ ስለመሆናቸውም ተጠሪ ክሳቸውን ሲመሰርቱ በክስ ማመልከቻው ላይ ያሰፈሩና ይህንኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 92 መሰረት ጭምር የአረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በቀላሉ ለመገንዘብ የሚቻለው የቤት ቁጥር 528/ለ በሚል በሚታወቀው የንግድ ቤት ውስጥ የአሁኑ 2ኛ አመልካች የሚኖሩ መሆኑና ይዞታውን የያዙትም ተጠሪ እያወቁ መሆኑ መረጋገጡን፣ ተጠሪ ያለ 1ኛ አመልካች እውቅና ንግድ ቤቱ በአቶ ግርማ እሸቱ አማካኝነት ለአሁኑ 2ኛ አመልካች ተሰጥቶ አመልካቹ ይዞ ባለበት ሁኔታ በመንግስት ቤቶች አጠቃቀም ላይ የተከሰተውን ችግር ለመቅረፍ ሲባል መመሪያው መውጣቱን ነው፡፡ 2ኛ አመልካች በንግድ ቤት የሚገኘውን ትርፍ በጋራ ለመጠቀም ከስር ሁለተኛ ከሳሽ ከነበሩትና የመክሰስ መብት የላቸውም ተብሎ ከክሱ ከወጡት ከአቶ ግርማ እሸቱ ጋር በተዋዋሉት መሰረት ቤቱን ይዘው መገኘታቸውም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ከክርክር ሂደት ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መመሪያ አንድ ሰው ከመንግስት የተከራየውን የንግድ ቤት ከአከራዩ እውቅና ውጪ ለሌላ ሶስተኛ ወገን አስተላልፎ መገኘቱ ከተረጋገጠ ውሉ የሚቋረጥና ቤቱን የሚያስተዳድረው አካልም በመመሪያው የተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች ተሟልተው እስከተገኙ ድረስ ውሉን ቤቱን ከቀድሞው ተከራይ ከተከራየው ሰው ጋር ሊገባ እንደሚገባ ያሳያል፡፡ ይህንኑ ይዘን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የበታች ፍ/ቤቶች የ1ኛ አመልካችን እርምጃ ሁከት ነው፣ ኪራዩን ከተጠሪ ጋር ሊቀጥል ይገባል ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት ተጠሪዋ ከአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ጋር ያደረጉት የኪራይ ውል የለም፣ አቶ ግርማ እሸቱ ከአሁኑ 2ኛ አመልካች ጋር ያደረጉት ሕጋዊ ውል የለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች እና አቶ ግርማ እሸቱ አደረጉ የተባለው ውል ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ በውሉ መብትና ግዴታ ባገኙት ተዋዋይ ወገኖች ላይ ተገቢውን ውጤት የሚያስከትል ከሚሆን በስተቀር ንግድ ቤቱ ለሶስተኛ ወገን ከአሁኑ አንደኛ አመልካች እውቅና ውጪ አልተላለፈም ወደሚለው ድምዳሜ የማያደርስ ነው፡፡ ይልቁንም ተጠሪ አቶ ግርማ እሸቱ ተገቢውን ውል ያደረጉ መሆኑን አምነው በአንድ የከሳሽነት ዘንግ አሰልፈው ክስ መመስረታቸው ሲታይ አቶ ግርማ እሸቱ ቤቱን ለአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ማስተላለፋቸውን የሚያሳይ እና ተጠሪዋ በቤቱ ራሳቸው ሳይሰሩበት በሌላ አግባብ ለማሰራት የፈቀዱ መሆኑን አረጋጋጭ ነው፡፡ ሲጠቃለልም የአሁኗ ተጠሪ ቤቱን ከሚመለከተው አስተዳደር አካል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጋር ውል ገብተው ከተከራዩ በኋላ ከአከራዩ እውቅና ውጪ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው ያሉ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍ/ቤቶች አስተዳደር አካሉን የማይመለከተው የጋራ ስራ ጥቅም ስምምነት ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን መሰረት በማድረግ የ1ኛ አመልካችን እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት መወሰናቸው በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እና 1149 ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች አንድ ተግባር ሕገ ወጥ ነው ለማለት የሚቻልባቸው ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ያሰፈሩትን መመዘኛ ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 04938 መጋቢት 24 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 17796 ሐምሌ 17 ቀን 2004 እና በመ/ቁጥር 17696 ሚያዝያ 15 ቀን 2004 በተሰጡ ትእዛዝ፣ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 18358 ነሐሴ 4 ቀን 2004 ዓ/ም እና በመ/ቁጥር 18247 ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ/ም በተሰጡት ትዕዛዛት የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ አከራካሪውን የንግድ ቤት ከአከራዩ እውቅና ውጪ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው የተገኙ በመሆኑ 1ኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የኪራይ ግንኙነት አቋርጦ ከአሁን ሁለተኛ አመልካች ጋር ማድረጉ በመመሪያው መሰረት ህጋዊ ነው፣ ከተጠሪ ጋር ኪራይ እንዲቀጥል አይገደድም፣ ሁለተኛ አመልካችም ለተጠሪ ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመ/ቁጥር 83247 ጋር ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 84330

ሚያዚያ 10 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አቶ መንግስቱ ኦሾ /ቀረቡ/

ተጠሪዎች ፡-1. ወ/ሮ እመቤት ጥላሁን
2. ወ/ሮ አልማዝ ጥላሁን
3. አቶ ስዩም ጥላሁን
4. አቶ ፍቃዱ ጥላሁን
5. ወ/ሮ ትዕግስት ጥላሁን

ተወካይ ቀረቡ

መዝቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን የሚመለከት ሆኖ በአሁን የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ከሳሽ ባቀረቡት ክስ፡- ከተከሳሾች ጋር በ22/10/2002 ዓ/ም ባደረግነው የጥብቅና አገልግሎት ውል በውርስ ንብረት ላይ ክርክር እንዳካሂድና ከሚያገኙት ድርሻም ብር 30,000 በቁርጥ ለመክፈል የተስማሙ ሲሆን እኔም በውሉ መሰረት በተለያዩ መዛግብት ክርክር በማድረግ ያስወሰንኩ ቢሆንም በተለያየ ጊዜ ብር 9,000 ከፍለው ቀሪውን የሚፈለግባቸውን ብር 20,000 ያልከፈሉኝ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ በውሉ ከተቀመጠው የገደብ መቀጫ ብር 6,000 ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

ተከሳሾችም ለክሱ በሰጡት መልስ፡- ከሳሽ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጡ መስማማታችን የማይካድ ቢሆንም በ22/10/2002 ዓ/ም በጽሁፍ ያደረግነው ስምምነት የለም፣በማስረጃነት ባቀረቡት የውል ኮፒም ላይ የተፈረመው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፊርማ የእኛ አይደለም፣ከከሳሽ ጋር በቃል ስምምነት ያደረግን ሲሆን ስምምነቱም በፍርድ ቤት ቀጠሮ ባለበት ቀን ብቻ ቆመው እንዲከራከሩልን ሲሆን በስምምነታችን መሰረት የሚፈለግብንን ብር 4,000 የከፈልን በመሆኑ በሀሰት ያቀረበብን ክስ ውድቅ ሊሆን የሚገባ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ኮፒው የቀረበው የጽሁፍ ውሉ የተካደ በመሆኑ ዋናውን ውል ከሳሽ እንዲያቀርቡ አዞ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው ከጠየቁ በኋላ ዋናው ውል ከመዝገቡ ውስጥ የጠፋብኝ በመሆኑ ማግኘት አልቻልኩም በማለታቸው በቀረበው የውል ኮፒ ላይ ስማቸው የተጠቀሰውን የከሳሽ ምስክሮች እና ተከሳሾች ያቀረቡአቸውን ምስክሮች በመስማት በሰጠው ውሳኔ የከሳሽ ምስክሮች በ22/10/2002 ዓ/ም ከሳሽና ተከሳሾች ባደረጉት ውል ተከሳሾቹ ለጥብቅና አገልግሎት ብር 30,000 ለመክፈል በከሳሽ ጽ/ቤት ውስጥ መስማማታቸውን ሲያስረዱ በተከሳሾች በኩል ከቀረቡት ምስክሮች ውስጥ 1ኛው ምስክር ከሳሽ እና ተከሳሾች እንደ ቤተሰብ የሚታዩ እና ከሳሽም ተከሳሾች በፍርድ ቤት ቀጠሮ ባላቸው ጊዜ ብቻ ፍርድ ቤት እየቀረቡ ሲከራከሩ መቆየታቸውንና ተከሳሾችም በተለያዩ ጊዜያት ገንዘቡን ሲከፍሉ ማየታቸውን ከዚያም በፐርሰንት ክፈሉ ውልም ፈርመው በማለታቸው የተነሳ ተከሳሾቹ ስላልተስማሙ ግንኙነታቸው መቋረጡን ማስረዳታቸውን 2ኛ ምስክር ደግሞ በፍርድ ቤት በቀጠሮ ቀን ለዋሉበት ተከሳሾቹ ለከሳሽ ገንዘብ ሲከፍሉ መቆየታቸውን እንጂ ስምምነቱ በጽሁፍ ወይም በቃል ስለመሆኑ እንደማያውቁ ማስረዳታቸውን በመግለጽ፤ ተከሳሾች ብር 30,000 ለመክፈል የተስማሙ መሆናቸውን በውሉ ኮፒ ላይ ስማቸው የተጠቀሰው ምስክሮች ያስረዱ ስለሆነና ተከሳሾችም ስምምነቱ ውሸት መሆኑን ገልጸው ከመከራከራቸው በስተቀር ገንዘቡን ስለመክፈላቸው በግልጽ ክደው ባለማከራከራቸውና ባቀረቡአቸው ምስክሮችም ባለማስተባበላቸው ቀሪውን ገንዘብ ብር 20,000 ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ የመቀጫ ገንዘብን በተመለከተ ግን ከሳሽ በአንድ በኩል ውሉ እንዲፈጸምላቸው እየጠየቁ በሌላ በኩል የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፈላቸው የጠየቁት ተገቢ ባለመሆኑ በፍ/ህ/ቁ/1890(2) መሰረት ሊከፈላቸው አይገባም ብሏል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት ይግባኝ ባዮችን አሰናብቷቸዋል፡፡

የስር ተከሳሾችም በፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በማቅረባቸው ችሎቱ የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ፡-

በጽሁፍ የተደረገ የውል ስምምነት የለም በሚል በአንደኛው ተከራካሪ ወገን በተካደ ጊዜ ውል አለ የሚለው ወገን ዋናውን ውል ወይም የግልባጩ ትክክለኛነት የተረጋገጠውን በማስረጃነት ማቅረብ የሚገባው ሲሆን በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪው ዋናውን ውል ማቅረብ የማይችሉ መሆኑን የገለጹ ሲሆን ያቀረቡት የውሉ ግልባጭም (ኮፒ) ይህንኑ ለማረጋገጥ ሥልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ ቀርቦ ያልተረጋገጠ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የውል ስምምነት መኖር አለመኖሩን በውሉ ላይ ያሉትን ምስክሮች ሊሰሙ የማይገባ ሆኖ ሳለ ሰምተው የወሰኑት የፍ/ህ/ቁ/1719፣1726 እና 1727 ፣2001፣2003፣2005 እና 2012 ድንጋጌዎችን የሚቃረን ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች(የሥር ተከሳሾች) ገንዘቡን እንዲከፍሉ የሰጡትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታም ለዚህ ችሎት የቀረበው በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በዋናነት የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብ ሲጠቃለል፡- ተጠሪዎች የአባታቸውን እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የእናታቸውን የውርስ ሀብት በተመለከተ እንድከራከርላቸው በቁጥር 022956 በቀን 01/10/2002 ዓ/ም የተጻፈ ውክልና ሰጥተው በዚሁ ውክልና መሰረት በ6 መዛግብት ላይ በወረዳ ፍርድ ቤት ተከራክሬ አስወስኜ እያለሁና ተጠሪዎቹም ስከራከርላቸው ስለመቆየቴ አምነው በጽሁፍ ውል አልተዋዋልንም ሲሉ በመከራከራቸው የወረዳው ፍርድ ቤት በውሉ ላይ ያሉትን የአመልካች ምስክሮችና የተጠሪዎችን ምስክሮች በመስማትና በመመዘን የአመልካች ምስክሮች ያስረዱትን የተጠሪዎቹ ምስክሮች ማስተባበል አለመቻላቸውን በማረጋገጥ የሰጠውን ውሳኔና ከፍተኛው ፍርድ ቤትም ያጸናውን ሰበር ሰሚው ችሎት ዋናው ሰነድ ከጠፋ ኮፒው በፍጹም ዋጋ እንደሌለው አድርጎ የፍርድ ቤቶቹን ውሳኔ የሻረው የህግ መሰረት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- አመልካች ተጠሪዎች ያልፈረምንበትን የሐሰት ውል አዘጋጅተው ዋናው ስለጠፋ በውሉ ላይ ባሉት ምስክሮች ይረጋገጥልኝ ሲሉ ያቀረቡትን ክርክር የወረዳው እና ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተቀበለው ቢወስኑም የጠፋ ሰነድ የሚመሳከርበት ሌላ ሰነድ እስካልቀረበ ድረስ በሰው ማስረጃ ማረጋገጥ የማይቻል በመሆኑ ምክንያት ሰበር ሰሚው ችሎት ክሱን ውድቅ ያደረገው ተገቢ በመሆኑ አቤቱታቸው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ለተጠሪዎች መልስም፡- አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤቶች የሠጡትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪዎች ክስ የቀረበባቸውን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም ሲል የወሰነው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በመካከላቸው የጥብቅና አገልግሎት ውል ስለመኖሩ የሚያምኑት ጉዳይ ሲሆን የሚያለያያቸው ነጥብ ግን ውሉ የተደረገበት ሁኔታና የገንዘቡ መጠን ነው፡፡ ይሔውም አመልካች ውሉ በጽሁፍ መደረጉንና የተዋዋሉበት የገንዘብ መጠንም ብር 30,000 መሆኑን ገልጸው የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች ግን ውሉ የተደረገው በጽሁፍ ሳይሆን በቃል መሆኑን እና በስምምነቱ መሰረትም የሚፈለግባቸውን ብር 4,000 ስለመክፈላቸው በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡ በጽሁፍ እንዲደረጉ በግልጽ በህግ ካልተደነገጉ የውል ዓይነቶች በስተቀር ማንኛውም ውል በቃል፣በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ግዴታ ለመግባት መፍቀድን በማያጠራጥር አሰራር በማስታወቅ ሊደረግ ይችላል፡፡ እንዲሁም ውሉ በጽሁፍ እንዲደረግ ህጉ ባያስገድድም ተዋዋይ ወገኖች ውላቸውን በጽሁፍ እንዲሆን የማድረግ መብት አላቸው፡፡ በዚህ ጉዳዩ ግን ውሉ በጽሁፍ ተደርጓል የሚሉት አመልካች ሲሆኑ ለዚህም በማስረጃነት የውሉን ኮፒ ማቅረባቸውን ከክርክሩ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ አመልካች የውሉን ኮፒ ያቀረቡት ዋናው ውል ጠፍቷል በሚል ሲሆን ይህ በማስረጃነት የቀረበው የውሉ ኮፒም አግባብ ባለው አካል ከዋናው ውል ጋር ስለትክክለኛነቱ በፍ/ህ/ቁ/2011(1) መሰረት የተረጋገጠ አይደለም፡፡ አመልካች ውሉ በጽሁፍ ተደርጎ ተፈራርመናል እስካሉ ድረስም ዋናውን ውል በተመለከተ ማስረዳት የሚጠበቅባቸው ውሉ የጠፋ ስለመሆኑ እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ/2003 ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በአንድ ውል የተጠቀሱ ምስክሮችም መሰማት ያለባቸው ተዋዋዮች ውሉን ተስማምተው የፈጸሙ መሆናቸውንና የውሉ ቃል ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ/1730(1) ተመልክቷል፡፡በዚህ ጉዳይ ግን ዋናው ውል ስለመጥፋቱ አመልካች

በማስረጃ ሳያስረዱ በውሉ ኮፒ ላይ ስማቸው የተጠቀሰውን ምስክሮች እንዲሰሙላቸው ያቀረቡትን ክርክር የወረዳው ፍርድ ቤት ተቀብሎ የምስክሮችን ቃል መስማቱ ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

አመልካች ዋናውን የጽሁፍ ውል በማስረጃነት ማቅረብ የማይችሉ ከሆነና ኮፒውም አግባብ ባለው አካል ስለትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ ከሆነ በሌሎች ማስረጃዎች ተጠሪዎች በውሉ ለጥብቅና አገልግሎት ብር 30000 ለመክፈል የተስማሙ ስለመሆናቸው ክሱን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ መልኩ የማስረዳት ሸክማቸውን ማስረጃን የመስማትና የመመዘን ሥልጣን ላላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ማስረጃዎቻቸውን አቅርበው አለማስረዳታቸው ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች ባቀረቡአቸው ማስረጃዎች አመልካች በቀጠሮ ቀን ብቻ ፍርድ ቤት የሚገኙ ስለመሆናቸው እና ለተገኙባቸው የቀጠሮ ቀናትም ገንዘብ የከፈሉአቸው ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር በማስረጃ ካስረዱት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች ክሱን አስረድተዋል ቢባል እንኳን ተጠሪዎቹ እንዲከፍሉአቸው የጠየቁት የአገልግሎት ክፍያ ተገቢና ሚዛናዊ መሆን ስላለመሆኑ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት በመመርመር ከመጠን በላይ ተዋውለው ከተገኙም ለመቀነስ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ህ/ቁ 2635 ከተደነገገው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ችሎት እምነት አመልካች በክሳቸው ተጠሪዎቹ እንዲከፍሉዋቸው ከገለጹት ገንዘብ መጠን እና ተጠሪዎች በቃል ውሉ አመልካች በቀጠሮ ቀን ብቻ ፍርድ ቤት እየተገኙ እንዲከራከሩላቸው ተስማምተናል በሚል በማስረጃ ካረጋገጡት ፍሬ ነገር አንጻርም የተቀበሉት ገንዘብ በቂ ነው ተብሎ የሚወሰድ ነው፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ምንም እንኳን የጽሁፍ ማስረጃ በመኖሩ የሰው ምስክሮችን መስማት አይገባም ሲል በውሳኔ ላይ ያሰፈረው ትችት ከውል ጋር ተያይዞ የጽሁፍ ማስረጃ ቢኖር እንኳን ምስክሮች ሊሰሙ ስለሚችሉበት አግባብ በፍ/ህ/ቁ/1730(1) የተመለከተውን መሰረት ያደረገ ባይሆንም፤ እንዲሁም በተከራካሪዎቹ መካከል የጸሁፍ ውል ባይኖርም የቃል ውል ስለመኖሩ ተጠሪዎቹ አምነው በተከራከሩበት ሁኔታ ሰበር ሰሚው ችሎት ውል የለም ሲል በውሳኔው ያሰፈረው የፍሬ ነገር ክርክሮችን የሚመረምሩ ፍርድ ቤቶች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት ባይኖረውም በዉጤት ደረጃ በውሉ ኮፒ ስማቸው የተጠቀሰውን ምስክሮች በመስማት ከተጠሪዎች ምስክሮች ቃል ጋር በማመዛዘን በክሱ የተመለከተውን ገንዘብ ተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል ሲሉ የሥር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት ውሳኔ በመሻር ገንዘቡን ሊከፍሉ አይገባም በሚል በሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የኦ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/147419 በቀን 05/02/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ በመቀበል በፍ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ዋናው ውል የጠፋ መሆኑን ባላስረዱበትና በማስረጃነት ያቀረቡት የውሉ ኮፒም ከዋናው ውል ጋር ተገናዝቦ ትክክለኛነቱ አግባብ ባለው አካል ባለመረጋገጡ በተከራካሪዎቹ መካከል በጽሁፍ የተደረገ የጥብቅና አገልግሎት ውል የለም ብለናል፡፡ ሆኖም በቃል በተደረገው ውል መሰረት ተጠሪዎች ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ለአመልካች የከፈሉ ስለመሆናቸው የተረጋገጠ በመሆኑ ቀደም ሲል ከከፈሉት ገንዘብ በተጨማሪ ሊከፍሉ አይገደዱም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 81163

የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ሲሳይ ረታ ጠበቃ አቶ መዝገቡ ወልዴ ቀርቧል

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ነ/ፈጅ አቶ ሙሉጌታ ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመጋዘን ኪራይ ውል ጋር ተያይዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ያሁኑ ተጠሪ በአ/ብ/ክ/መንግስት ሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከ/ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ የተጠሪ ንብረት የሆነውና በጎንደር ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኘው መጋዘን አመልካች ከመጋቢት 1 ቀን 1997ዓ.ም እስከ የካቲት 30 ቀን 2001ዓ.ም ድረስ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ በወር ብር 5109.45 ኪራይ እየከፈለ ሲጠቀም የቆየ መሆኑን ጠቅሶ የኪራይ ውሉ ከሚያበቃበት መጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ አመልካች የመጋዘኑን ወራሃዊ ኪራይ ክፍያ ብር 13,800 እየከፈለ ውሉ በዚህ መልኩ ተሻሽሎ እንዲቀጥል ወይም በዚህ መልኩ ተስማምቶ ለመቀጠል ካልፈለጉ ደግሞ መጋዘኑን እንዲያስረክብ በተለያዩ ደብዳቤዎች ማስጠንቀቂያ ቢጻፍለትም እምቢተኛ በመሆንና ከእኛ ፈቃድ ውጪ የቀድሞውን የመጋዘኑን የኪራይ መጠን በባንክ ሂሣባችን እያስገባ በመጋዘኑ መጠቀም የቀጠለ በመሆኑ የመጋዘኑን ኪራይ ከቀን 1/7/2001ዓ.ም እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ18 ወራት ኪራይ ክፍያ በ13,800 ታስቦና ካለእኛ ፈቃድ የከፈለው ተቀንሶለት ባጠቃላይ ብር 156,429 እንዲከፍልና እንዲሁም ከመስከረም1 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ መጋዘኑን እስኪያስረክብ ድረስ ያለውን ብር 13,800 ወርሃዊ ኪራይ ክፍያ ታስቦ ከወለድ ጋር እንዲከፈላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አመልካችም ቀርቦ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬ ጉዳዩ ላይም ወርሃዊ የመጋዘኑን ኪራይ ክፍያ በተመለከተ በብር 13,800 እንዲከፍል የሚያስገድደው የውልም ሆነ የህግ ግዴታ አለመኖሩን በመከራከር መልስ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ከመረመረ በኋላ የቀድሞው የኪራይ ውል ጊዜ ከማለቁ በፊት ተጠሪ ከመጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የመጋዘኑ ወርሃዊ ኪራይ መጠን ብር 13,800 መሆኑን ጠቅሶ በተለያዩ ጽሑፎች ለአመልካች በመግለጽና በዚሁ መልኩ ውሉ ተሻሽሎ እንዲቀጥል አልያም በዚህ የማይስማማ ከሆነ ደግሞ መጋዘኑን እንዲያስረክብ በተገለፀለት መሰረት አመልካች ቀርቦ ካለመዋዋሉም ባሻገር የቀድሞ ኪራይ ውል ጊዜ ከተጠናቀቀም በኋላ መጋዘኑን ሣያስረክብ ይዞ መጠቀሙን መቀጠሉ በተጠሪ የቀረበለትን ድርድር ወይም አዲሱን ወርሃዊ የኪራይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጠን በዝምታ የተቀበለ መሆኑን ስለሚያሳይ ከመጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ የካቲት 15 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ያለው ወርሃዊ ክፍያ በብር 13,800 ታስቦና የተከፈለው ተቀንሶለት ብር 387,990.45 ለተጠሪ ከፍሎ መጋዝኖቹንም እንዲያስረክብ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ቅሬታውን ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ቅሬታውን ሰርዞታል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ በመቃወም ሲሆን አመልካች ሰኔ 25 ቀን 2004ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ማመልከቻ ይዘትም ባጭሩ አመልካች የመጋዘኑን ኪራይ በተመለከተ በወር ብር 13,800 ለመክፈል በየትኛውም መልኩ የተስማማሁት ውል ሣይኖር እና እንዲሁም አዲሱን የኪራይ መጠን እንደማልቀበል በግልጽ ለተጠሪ ምላሽ በመስጠትና ይልቁንም በመጀመሪያ የኪራይ መጠን መቀጠል እንደምፈልግ ሐሳቤን በመግለጽ አሳውቄ እያለሁ አዲሱን ዋጋ በዝምታ ተቀብሎታል በማለት የተሰጠው ውሣኔ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1684 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ውሣኔው ታርሞ በተዋዋልኩት ውል መሰረትና በቀድሞው የኪራይ መጠን እንዲከፍል ውሣኔ እንዲሰጥለት ዘንድ ጠይቋል፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ አመልካች አዲሱን የመጋዘን ኪራይ ዋጋ በዝምታ በመቀበል ተስማምቶበታል ተብሎ በአዲሱ የኪራይ ዋጋ ስሌት መሰረት የኪራይ ገንዘቡን እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2950 አኳያ ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪም ቀርቦ የሰር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈጠረ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለመኖሩን ጠቅሶ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ፀድቆ ከበቂ ወጪና ኪሣራ ጋር እንዲወሰንለት ዘንድ በመጠየቅ መልሱን የሰጠ ሲሆን አመልካችም የበኩሉን የመልስ መልሰ ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድጋጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች የቀረበለትን አዲሱን የኪራይ ዋጋ በዝምታ በመቀበልና መጋዘኑንም የቀድሞ የኪራይ ውል ጊዜ ከተጠናቀቀም በኋላ ሣያስረክብ መጠቀሙን የቀጠለ በመሆኑ በአዲሱ ዋጋ እንደተስማማ ተቆጥሮ የኪራዩን ገንዘብ በዚህ ስሌት ዋጋ አመልካች ሊከፍል ይገዳደዳል በሚል ተጠሪ የሚከራከር ሲሆን አመልካች ደግሞ በተጠሪ የቀረበውን የኪራይ ዋጋ እንደማልቀበልና እንደማልስማማበት ሐሳቤን ገልጨ ስቃወም ስለነበረ በዝምታ እንደተቀበልኩ ተቆጥሮ የሚወሰድበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ይከራከራል ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ አመልካች በተጠሪ የቀረበለትን አዲሱን የመጋዝን ኪራይ ዋጋ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1684 ድንጋጌ ስር በተመለከተው መልኩ በዝምታ ተቀብሎ እንደተስማማበት ሊቆጠር ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው መፍትሔ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጠሪ የቀረበለትን የኪራይ ዋጋ ማሻሻያ መጠን አስመልክቶ አመልካች በመቃወም ምላሽ የሰጠ ስለመሆኑና ይህንኑ ምላሽ የሰጠበትን የጽሑፍ ሰነድም በማስረጃነት ቆጥሮ ለስር ፍ/ቤት በማቅረብ የተከራከረ ስለመሆኑ ከቀረቡት ውሳኔ ግልባጮች መገንዘብ ተችሏል፡፡ ተጠሪም የኪራይ ማሻሻያውን አመልካች በዝምታ ተቀብሎታል በሚል በደፈናው መከራከሩን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1684 (2) ስር እንደተመለከተው ለምላሹ በቂ ጊዜ ተቆርጦለት በዚያው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ አመልካች መልስ ሣይሰጥ በመቅረቱ የማሻሻያ ዋጋውን እንደተቀበለ ይቆጠራል በሚል የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ምላሹ የተቆረጠ የጊዜ ገደብ ስለመኖሩ የተገለፀ ነገር ካለመኖሩም ባሻገር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ረገድ የቀረበ ክርክርም ባለመኖሩ በተጠሪ የቀረበውን የኪራይ መጠን ማሻሻያ ዋጋ ድርድር ወይም ሐሳብ አመልካች በደረሰ በወሩ ወይም ከዚህም በበለጠ ጊዜ ውስጠ አመልካች የተቃውሞ ሓሳቡን በመግለጽ ምላሹን ከሰጠ ድርድሩን በዝምታ ተቀብሎታል ተብሎ ሊወሰድ የሚቻልበት የሕግ አግባብ አይኖርም በተጠሪ የቀረበለትን የኪራይ መጠን ዋጋ ማሻሻያ ሐሳብ ከላይ በተገለፀው መልኩ አመልካች በዝምታ እንደተቀበለ የሚቆጠርበት አግባብ የለም የሚል መደምደሚያ ላይ ከተደረሰ ደግሞ የኪራይ መጠኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2950(1) ስር እንደተገለፀው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ተወስኗል ለማለት አይቻልም፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ምንም እንኳ የቀድሞው የኪራይ ውል ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ አዲሱ የኪራይ ልክ በሕጉ አግባብ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ተወስኖ ያልታወቀ ቢሆንም አመልካቹ መጋዘኑን መጠቀም የቀጠለ በመሆኑ ላገኘው አገልግሎት ኪራይ ሊከፍል ይገደዳል ፡፡ ምን ያህል የኪራይ ልክ ሊወሰን ይገባል የሚለውን በተመለከተ አመልካች የቀድሞውን የኪራይ ውል መነሻ በማድረግ በወር ብር 5,109.45 መሆን አለበት ብሎ የሚከራከረውም ሆነ ተጠሪ በወር ብር 13,800 መሆን አለበት የሚለው ክርክር ከላይ በተገለፀው መልኩ የሁለቱንም ወገኖች ስምምነት መነሻ ያደረገ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2950(2) ስር በተመለከተው መልኩ የኪራይ ልኩ በተዋዋይ ወገኖቹ ስምምነት ሣይወሰን የቀረ እንደሆነ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት በወሰኑት በታሪፍ መሠረት ወይም ይህ በሌለ ጊዜም የአካባቢውን የወቅቱን ነፃ ገበያ ዋጋ መነሻ በማድረግ ሊወሰን እንደሚገባ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሲጠቃለል የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከ/ፍ/ቤት ከመጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን የመጋዘኑን ወርሃዊ የኪራይ መጠን እላይ በተገለፀው መልኩ በማዘጋጃ ቤቱ የተወሰነ ታሪፍ ካለ በዚያ መሰረት ይህ ከሌለ ደግሞ የአካባቢውን ልማድ ወይም ወቅታዊ ነፃ ገበያ ዋጋ መነሻ በማድረግ መወሰን ሲገባ የአመልካች ፍቃድና ስምምነት የሌለበትን ወርሃዊ ኪራይ ክፍያ ብር 13,800 በመቀበልና በዚህ አስልቶ መወሰኑና እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም ይህን ስህተት ማረም ሲገባ ማፅናቱ በውሳኔዎቹ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከ/ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የመጋዘኑን ወርሃዊ ኪራይ መጠን ብር 13,800 እንደሆነ በመወሰድና ከመጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን የኪራይ ገንዘብ በዚህ በማስላት ያልተከፈለውን ብር 387,990.45 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነው የውሳኔ ክፍል ብቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከ/ፍ/ቤት የራሱ መ/ቁ 05667 የሆነውን በማንቀሳቀስ ከመጋቢት 1 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ያለውን ወርሃዊ የኪራይ መጠን እላይ በፍርዱ ክፍል ውስጥ በተገለፀው መልኩ ግራ ቀኙን በድጋሚ አከራክሮ በመስማት አጣርቶ ከወሰነ በኋላ ያልተከፈለውን የኪራይ ገንዘብ በዚያ በማስላት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ ህ/ቁ 343(1) መሰረት በመመለስ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር ምክንያት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79794

ሚያዝያ 22 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የማይክሮሊንክ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ኃ.የተ.የግል ማህበር

ስራ አስኪያጅ ዳዲ ሁንዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጌ/ፈጅ ትቤሶ በዛብህ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከኪራይ ውል ጋር ተያይዞ የተነሳውን የንብረት ጉድለትና የተቋረጠ ጥቅም ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም፡- ከአሁኑ አመልካች ጋር ሐምሌ 01 ቀን 1990 ዓ/ም በተፈረመ ውል በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10/11/12 የሚገኘውንና ቁጥሩ 672 የሆነውን የተጠሪን ህንጻ ለአሁኑ አመልካች ማከራየቱን፣የኪራዩ ዘመንም ተራዝሞ ከአስር አመት በላይ አመልካች ሕንጻውን ሲገለገልበት መቆየቱን፣የኪራይ ዘመኑ ሲያልቅ ሕንጻውን አድሶና ተረክቢቸው የጠፉ፣የተሰበሩና ያረጁ እቃዎችን በአዲስ ተክቶ ሊያስረክብ ተከራይ የሆነው አመልካች ግዴታ መግባቱን፣የኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኋላ የርክክብ ሁኔታውን በተመለከተ ሰኔ 16 ቀን 2001 ዓ/ም በተፈረመ ሰነድ ሕንጻውን አድሶ የጠፉ፣የተሰበሩና የአረጁ እቃዎችን በአዲስ ተክቶ ሊያስረክብ መተማመኛ መስጠቱን፣ሕንጻውን ለማሳደስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ እድሳቱ በብር 151,725.25 እንዲከናወን አሸናፊ መመረጡን፣ለጠፉ፣ለተሰበሩና ላረጁ እቃዎች መተኪያ የብር 150,848.00 ፕሮፎርማ መሰብሰቡን፣በዚህ መሰረት ሕንጻውን አሳድሶና እቃዎቹን ተክቶ እንዲያስረክብ የአሁኑ አመልካች ቢጠየቅም ፈቃደኛ ያለመሆኑን፣ተጠሪ ህንጻውን በወር በብር 20,000.00፣የህንጻውን አዳራሽ ደግሞ በወር ብር 4000.00 አከራይቶ ገቢ ሊያገኝ ይችል እንደነበር፣አመልካች የውል ግዴታውን ባለመፈጸሙ ተጠሪ ከመስከረም 01 ቀን 2001 ዓ/ም አንስቶ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ ባሉት ሃያ ሁለት ወራት ብር 528,000.00 የኪራይ ገንዘብ ማጣቱን፣ለህንጻው ማሳደሻ ብር 302,573.25 እንደሚያስፈልግ እንዲሁም እንደውሉ ባለመፈፀሙ ደግሞ በውሉ አንቀፅ 6(12) መሰረት ብር 30,000.00 ለመክፈል ስምምነት ማድረጉን ዘርዝሮ በድምሩ ብር 860,573.25 እና ለክሱ የወጣውን ወጪና ኪሳራ እንዲከፍል ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካች ህንጻውን አሳድሶ መስከረም 01 ቀን 2001 ዓ/ም ሙሉ በሙሉ መልቀቁን፣ተጠሪ ህንጻውን አመልካች እንዲረከብ በተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያቀርብ ቆይቶና ተደጋጋሚ መሻሻፍ አድርጎ ሰኔ 16 ቀን 2001 ዓ/ም ህንጻውን ተጠሪ መረከቡን፣ርክክቡ የዘገዬው በተጠሪ ጥፋት በመሆኑ ለዘገዬበት ጊዜ ተጠሪ የጠየቀው የኪራይ ገንዘብ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ፣በህንጻው ያለመታደስ ምክንያት እንዴት አድርጎ የብር 528,000.00 ጉዳት እንደደረሰበት ተጠሪ ያለማስረዳቱን፣የቀረበው ስሌትም የውል መሰረት እንደሌለውና ርክክቡን ተጠሪ ለማከናውን ያልቻለው በመጠነኛ ጉድለት ምክንያት እንጂ ህንጻውን ለመጠቀም የማያስችሉ ጉድለቶች በመኖራቸው ምክንያት ያለመሆኑን፣ሕንጻውን ተጠሪ የተረከበው መልሶ ለማከራየት ሳይሆን ለራሱ ሊጠቀምበት በመሆኑ የኪሳራው ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው፣ሕንፃው ለረኽርም ዘመን ያገለገለ በመሆኑ በተፈጥሮ ማርጀቱንና የተጠሪ ጥያቄ ህንጻውን ማሳደስ ሳይሆን መቀየር በመሆኑ የራሱን የጨረታ ኮሚቴ አቋቁሞ ያቀረበው የእድሳት ገንዘብ ጥያቄ አግባብ ያለው እንዳልሆነ፣ህንጻውን ሲረከብ የነበረው የተፈጥሮ እርጅና ግምት ውስጥ ገብቶ ተጠሪ እዳሳት የማያስፈልገውን የሕንፃ ክፍል ለይቶ አመልካችም ለዚያ እድሳት ለምን ኃላፊ እንደሚሆን አስረድቶ ሕንፃውን ሲሰራ ወይም ህንጻ ሲሰራ ወደ ነበረበት ሁኔታ ሳይሆን በአመልካች ጥፋት እድሳት ላስፈለገው የህንጻ አካል ብቻ በገለልተኛ ወገን በሚገመተው መሰረት እንዲያሳድስ እንዲወሰንለት፣የሚተኩ እቃዎችን በተመለከተ የቀረበው ጥያቄ ግልፅ ባለመሆኑ ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ፣ሕንጻው በሰጠው አገልግሎት ምክንያት ያረጁትን እቃዎች ሁሉ እንዲተካ መጠየቁ አግባብነት የሌለው መሆኑንና የቀረቡት ፕሪፎርማዎችን የተነጋገነ ዋጋ የያዙ መሆኑን እንዲሁም ዋጋውም ስምምነቱን መሰረት ያላደረገ መሆኑና የኃላፊነት መጠኑ ከብር 50,000.00 እንደማይበልጥ በውሉ መመልከቱን፣አመልካች የውል ግዴታውን ባይፈፅም የሚኖርበት የኃላፊነት መጠን የብር 30,000.00 ብቻ ስለመሆኑ ውሉ እንደሚያስረዳ ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለህንፃው ማሳደሻ የተጠቀየውን ገንዘብ ብር 302,573.25፣ተጠሪ ያጣውን የኪራይ ገቢ ብር 488,000.00 ክስ ከተመሰረተበት ከሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል፣ወጪና ኪሳራ በቁርጥ ብር 2000.00(ሁለት ሺህ) እንዲከፍል ወስኖበታል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ህንጻው ቢከራይ ኑሮ ሊያስገኝ ይችል በነበረው የኪራይ ገቢ መጠኑ ላይ ብቻ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ችሎቱ በዚህ ረገድ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር በመመርመር አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ መባሉን በመቀበል የኃላፊነት መጠኑን በተመለከተ ግን ከብር 488,000.00 ወደ ብር 244,000.00(ሁለት መቶ አርባ አራት ሺህ ብር) ዝቅ አድርጎ አመልካች ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል መጠኑን ለይቶና ለእድሳት ያስፈልጋል የተባለውን ገንዘብ ብር 302,573.25 ለተጠሪ እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማፅናት ዳኝነት ሰጥቷል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን የመከራከርያ ነጥቦችን በማጠናከር የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በተገቢው መንገድ ያልተመለከቱት መሆኑንና የሕግ መሰረት በሌለው አኳኋን መወሰኑን የሚጠቅስና ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ሕንጻ ተጠሪ ለጳውሎስ ሚዲካል ኮሌጅ እያከራየው የነበረ ስለመሆኑ በከፊልም ቢሆን አምኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በርትዕ አይቶ ለመወሰን የሕግ መሰረት የነበረው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩን ከዚሁ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከተጠሪ ህንጻውን ተከራይቶ ሲጠቀምበት የቆየ መሆኑንና የኪራይ ዘመኑ ሲያልቅ ሕንጻውን አድሶና ተረክቧቸው የጠፉ፣የተሰበሩና ያረጁ እቃዎችን በአዲስ ተክቶ ሊያስረክብ ተከራይ ግዴታ መግባቱን፣የኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኋላ የርክክብ ሁኔታውን በተመለከተ ሰኔ 16 ቀን 2001 ዓ/ም በተፈረመ ሰነድ ሕንጻውን አድሶ የጠፉ፣የተሰበሩና የአረጁ እቃዎችን በአዲስ ተክቶ ሊያስረክብ መተማመኛ መስጠቱን፣ሕንጻውን ለማሳደስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ እድሳቱ በብር 151,725.25 እንዲከናወን አሸናፊ መመረጡን፣ለጠፉ፣ለተሰበሩና ላረጁ እቃዎች መተኪያ የብር 150,848.00 ፕሪፎርማ መሰብሰቡን፣በዚህ መሰረት ሕንጻውን አሳድሶና እቃዎቹን ተክቶ እንዲያስረክብ የአሁኑ አመልካች ቢጠየቅም ፈቃደኛ ያለመሆኑን፣ ተጠሪ ሕንፃውን በወር ብር 20,000.00፣የህንጻውን አዳራሽ በወር ብር 4000.00 ተከራይቶ ገቢ ሊያስገኝ ይችል እንደነበር ቢገልፅም የአደራሹ የኪራይ ገቢ ያለመቋረጡን፣አመልካች የውል ግዴታውን ባለመፈጸሙ ተጠሪ ከመስከረም 01 ቀን 2001 ዓ/ም አንስቶ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ ባሉት ሃያ ሁለት ወራት ብር 528,000.00 የኪራይ ገንዘብ ማጣቱን ቢገልፅም የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ያለመቀበላቸውን፣ለህንጻው ማሳደሻ ብር 302,573.25 እንደሚያስፈልግ በጨረታ ኮሚቴ መረጋገጡንና አመልካችም በሂደቱ ሲሳተፍ የነበረ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ነው፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በኪራይ ሲጠቀምበት የነበረው ሕንጻ በተገቢው ጊዜ ለተጠሪ ያላስረከበው በአመልካቹ ጥፋት ነው? ወይስ በተጠሪው ጥፋት ነው? የሚለው ጭብጥ በስር ፍርድ ቤቶች ታይቶና የግራ ቀኙ ክርክሮችና ማስረጃዎች ተመርምረው ርክክቡ ያልተፈጸመው በአመልካች ጥፋት መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ይህ ችሎት ርክክቡ የዘገዬው በአመልካች ጥፋት ነው? ወይስ በተጠሪ ጥፋት ነው? የሚለውን በማስረጃ የሚነጥረውን የፍሬ ነገር ክርክር በመመርመር የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የደረሱበትን ድምዳሜ ለመለወጥ የሚያስችለው ስልጣን የሌለው መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ አመልካች የርክክቡ ጊዜ በተጠሪ ጥፋት የዘገዬ ነው በማለት የሚያቀርበውን ክርክር የሚቀበልበት አግባብ አልተገኘም፡፡ሌላው አመልካች ህንጻውን አድሼአለሁ፣የእቃ ርክክብም ፈፅሜአለሁ እንዲሁም ጠፉ፣ተሰበሩ የተባሉት እቃዎች በህንጻው እርጅና የተከሰቱ ናቸው በማለት የሚያቀርበው ክርክር ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ የተደረገ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ እንጂ የመሰረታዊ ሕግ ስህተትን መመዘኛ የሚያሟላ የክርክር ነጥብ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም፡፡እንግዲህ አመልካች በኪራይ የተረከበውን ህንፃ ከኪራይ ዘመኑ ማለቅ በኃላ በተገቢው ጊዜ በማደስ፣የጠፉ፣የተሰበሩና የአረጁ እቃዎችን በመተካት ለባለንብረቱ ተጠሪ ለማስረከብ በውል ስምምነት ማድረጉ ከመረጋገጡም በላይ በውሉ በገባው ግዴታ መሰረት ግዴታውን ያለመወጣቱ ከተረጋገጠ ተጠሪ በሕግ አግባብ

በተቋቋመ ውል መሰረት አመልካች ግዴታውን እንዲወጣ መጠየቁና ፍርድ ቤቶቹም በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎችን በመመርመር አመልካችን ግዴታውን አልተወጣም በማለት መወሰናቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ)፣1731፣1790 እና 1757 ድንጋጌዎች አንፃር ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

በሕግ አግባብ የተቋቋመ ውል እንደውሉ ያልተፈጸመለት ወገን እንደውሉ እንዲፈፅምለት ለመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ)፣1718፣1771(1)፣1790 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በዚህ አግባብ ጥያቄ የሚያቀርበው ተዋዋይ ወገን ሌላኛው ተዋዋይ ግዴታውን ባለመፈጸሙ ውሉን በግዴታ እንዲፈጽም ወይም እንዲፈረስ ከማስደረግም በቀር ከነዚሁ ማሻሻያዎች ጋራ አጣምሮ አንዱ ወገን ለደረሰበት ጉዳት ኪሳራ መጠየቅ እንደሚችል የፍ/ሕ/ቁጥር 1790(1) ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ጥያቄም አመልካች በውሉ በገባው ግዴታ ተገቢውን እንዲፈፅምና ባለመፈፀሙ ደግሞ የደረሰውን ኪሳራ እንዲተካ ይወሰን ዘንድ የሚያሳይ ነው፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩ ሲታይ የእድሳት ወጪም ሆነ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት እቃዎች ዋጋ በጨረታ ተወዳዳሪ ተጋብዞ የዋጋ መጠናቸው የተለዩ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ከላይ እንደተገለጸው በዚህ ረገድ በሰበር አቤቱታ ላይ የቀረበው ክርክር የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጭብጥ ያልተያዘበትና የፍሬ ነገረ ክርክር በመሆኑ የመጠኑ ተገቢነት በዚህ ችሎት የሚታይ አይደለም፡፡የህግ ትርጉም ያስፈልገዋል ተብሎ ከጉዳት ጋር ተያይዞ የቀረበው ነጥብ አመልካች ህንጻውን በተገቢው ጊዜ አድሶ ባለማስረከቡ ለባከነው ጊዜ ሕንፃው ቢያከራይ ኑሮ ሊገኝ ይችል የነበረ የኪራይ ገቢ መጠን ምን ይህል ሊሆን ይገባል?፣በርትዕስ መወሰኑ ተገቢነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

በመሰረቱ በውል አፈፃጸም ሂደት የሚደርሰው የጉዳት ኪሳራ የሚሰላበት አግባብ በፍ/ሕ/ቁጥር 1790 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት የሚቻለውም የጉዳት ኪሳራ መጠን በጉዳዩ በሚቀርበው ማስረጃና አእምሮ ያለው ሰው ውሉ ባለመፈጸሙ ይደርሳል ብሎ በሚገምተው አስተያየት ልክ ሊወሰን እንደሚችል፣የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1800 በተለይ ሲታይም ባለገንዘቡ ከጠየቀው ዝቅ ያለ ጉዳት ያገኘው መሆኑን ባለእዳው ያስረዳ እንደሆነ ኃላፊነቱ በዚሁ ልክ እንደሚሆንና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1790(2) ድንጋጌም ኪሳራው ልኩ ከውል ውጪ ስለሚደርስ አላፊነት በሚለው ምዕራፍ በተጻፉት ድንጋጌዎች መሰረት እንደሚወሰን ደንግጓል፡፡ከውል ውጪ የኪሳራ ልክ ከሚወሰንባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ ርትዕ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 2102(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ይህ ድንጋጌ ኪሳራ የሚወሰነው ያለምንም መነሻ ሳይሆን የኪሳራውን ልክ በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ የሆነ እንደሆነ ዳኞቹ የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎችንና ተጎጂውም ያደረገውን ጥንቃቄ አመዛዝነው በመገመት የኪሳራውን ልክ በርትዕ እንደሚወስኑ ያሳያል፡፡ የሚከፈለው ካሳ መጠንና የጉዳቱ መፈፀም የሚያጠራጥር በሆነ ጊዜ ግን ማናቸውንም የጉዳት ካሳ እንዲከፈል ለማድረግ የማይቻል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102(2) ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሕንጻውን በውሉ በገባው ግዴታ መሰረት በተገቢው ጊዜው አድሶ ባለማስረከቡ ተጠሪ በኪራይ ያገኝ የነበረው ገቢ መቋረጡ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡መጠኑም በተመለከተም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ስሌት መሰረት ሕንፃው በወር በብር 20,000.00 አደራሹ በብር 4000.00 ሊከራይ ይችል እንደነበር ጠቅሶ ለሃያ ሁለት ወራት ብር 528,000.00 ገቢ ማጣቱን ገልጾ የተከራከረ ሲሆን የበታች ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች አመልካች አዳራሹን ለአስር ወራት በብር 4000.00 ሺህ አከራይቶ ገቢ ማግኘቱ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ ብር 40,000.00 የኪራይ ገቢን ተጠሪ ከጠየቀው የኪራይ ገቢ መጠን ብር 528,000.00 ተቀናሽ አድርጓዋል፡፡በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነው የብር 488,000.00 የሕንፃው የወር ኪራይ ገቢ መጠን የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማሻሻ ዝቅ ያደረገው ህንጻውን ተጠሪ ለጳውሎስ ሚዲካል ኮሌጅ እያከራዩ ነው በማለት አመልካች ያቀረበውን ክርክር ተጠሪ በከፊል አምኖታል በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ አመልካች ህንጻውን እንደለቀቀ ወዲያውኑ ተጠሪ ሕንፃውን ሳይታደስ ለኮሌጁ አከራይቶ ጥቅም ሲያገኝበት የነበረ መሆኑን ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር ኮሌጁ ዘግይቶም ቢሆንም ህንፃው ባልታደሰበት ሁኔታ መከራየቱ ሕንጻው ሊከራይ ይችል የነበረ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው የሚል በመሆኑና ሕንፃው ኮሌጁ ከተከራየው በኋላ ስለመታደሱ ማስተባበያ ክርክር በአመልካች በኩል ያልቀረበበት በመሆኑ በተጠሪ ላይ ጉዳት አልደረሰበትም ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ይልቁንም ተጠሪ ሕንጻው ለኮሌጁ አከራይቶ ብር 60,000.00 በወር ገቢ ማግኘቱን አመልካች የሚያምነው ሐቅ መሆኑ ሲታይ ተጠሪ ሕንጻው ሳይታደስ ቆይቷል ለተባለበት ጊዜ በወር ብር 24,000.00 ገቢ ያስገኝ ነበር በማለት ክስ ማቅረቡ ጉዳዩን በርትዕ ለመወሰን መሰረት ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡በሌላ አገላለጽ ተጠሪ ህንጻው ባለመታደሱ ምክንያት ያጣውን የገቢ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1799(1) ድንጋጌ አስረድቶ እያለና አመልካች በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1800 ድንጋጌ መሰረት በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ዝቅ ያለ ነው በማለት ማስረጃ አቅርቦ ባላስረዳበት ሁኔታ ተጠሪ ህንፃው ሳይታደስም ማከራየት ይችል ነበር በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ የለም፡፡በተጠሪ ላይ የደረሰ ጉዳት በማስረጃ ተረጋግጦ እያለና አመልካች ህንጻውን ለማሳደስ በውሉ ግዴታ ከመግባቱም በላይ ግዴታውን ለመወጣት በጨረታ አወጣጡ ሂደት ሁሉ ሲሳተፍ ቆይቶ የጨረታውን ውጤት ከአወቀ በኋላ ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ ስላለመሆኑ በማስረጃ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሕንፃው ሳይታደስም ቢሆን መከራየት ይችል ነበር የሚል እንድምታ ባለው ምክንያት ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የካሳውን መጠን በርትዕ መወሰኑ ግራ ቀኙ በጉዳት መጠኑ ላይ በሕጉ የተጣለባቸውን ግዴታ ከመወጣት አንጻር ታይቶ የተወሰነ ነው ሊባል ከሚችልና በውጤቱም አመልካችን የጠቀመ ነው ከሚባል በስተቀር ውሳኔው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1790(2)፣1799፣1800፣1802 እና 2102 ድንጋጌዎችን የጣሰ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 97396 ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 65129 መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ/ም ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ለህንፃው ማሳደሻ የተጠቀየውን ገንዘብ ብር 302,573.25(ሶስት መቶ ሁለት ሺ አምስት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም)፣ተጠሪ ያጣውን የኪራይ ገቢ ብር 244,000.00(ሁለት መቶ አርባ አራት ሺህ ብር) እንዲከፍል፣ወጪና ኪሳራ በቁርጥ ብር 2000.00(ሁለት ሺህ) እንዲከፍል በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ዛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 83674

ግንቦት 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ እቴነሽ ካሳ - ጠበቃ አስቴር ዓለማሁ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሀጂ ጀማል ይማም - ጠበቃ ተሰማ ዘርፋ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ውልን መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኗ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪ ክስ ይዘትም፡- ከአመልካች ጋር ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም በተጻፈ የሽያጭ ውል በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና ቁጥሩ 3798 የሆነው ቤት በብር 200,000.00(ሁለት መቶ ሺህ) ከአመልካች በመግዛት በእለቱ ብር 55,000.00 አመልካች ከተጠሪ ተቀብለው ቤቱን ማስረከባቸውን፣ ቀሪውን ብር 145,000.00 (አንድ መቶ አርባ አምስት ሺ ብር) በገዥ ስም ካርታ አስርተው ለአመልካች ካስረከቡ ከአንድ ዓመት በኋላ ሊከፍሉ መስማማታቸውና በስምምነቱ መሰረት አመልካች ካርታውን አሰርተው ለማስረከብ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ዘርዝረው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ካርታውን እንዲያስረክቡና ውሉን ለማፍረስ በመሞከራቸውም ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኗ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል በባዶ ቦታ እንጂ በመኖሪያ ቤት ያልተደረገ ሕገወጥ መሆኑና በእለቱም ብር 5000.00 (አምስት ሺ) እንጂ ብር 55,000.00 (ሃምሳ አምስት ሺ) ያለመቀበላቸውን ጠቅሰው ብር 5000.00 ከፍለው ሌላው የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ስምምነት በመኖሪያ ቤት ላይሆን በባዶ ቦታ የተደረገ ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡንና ስምምነቱም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40(3) ድንጋጌን የሚጻረር መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የተጠሪን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰው ምስክሮችን መስማቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005 ድንጋጌን የሚጥስ መሆኑን በመጥቀስ በሰነዱ ላይ የተሸጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መኖሪያ ቤት እንጂ ባዶ ቦታ ያለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔን በመሻር የአሁኗ አመልካች በውሉ በገቡት ግዴታ መሰረት ሊፈጽሙ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላና እስከቦታው ድረስ በመሄድ ጉዳዩን በማጣራት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የሸጡት መኖሪያ ቤት እንጂ ባዶ ቦታ መሆኑን ሊያረጋግጡ አልቻሉም የሚል ምክንያት ይዞ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል በባዶ ቦታ ስለመሆኑ የሰነዱ ይዘት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ቁጥሩ 3798 የሆነውን ቤትና ቦታውን እንዲረከቡ የተሠጠው ውሳኔ አመልካች በሕጉ አግባብ ያገኙቱን 647 ካ.ሜትር ሁሉ አጠቃልሎ እንዲወሰድ የሚያደርግ እንዲሁም ሽያጩ በመኖሪያ ቤት አልተደረገም እንጂ ተደርጓል እንኳ ቢባል አመልካች መሐይም በመሆናቸውም በሕግ ፊት የማያስገድዳቸው ሁኖ እያለ በበታች ፍርድ ቤቶች መታለፉ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርመሮም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጽሑፍ በሰጡት መልስ አመልካች መሐይም ነኝ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳና ስርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ መሆኑን እንዲሁም ጉዳዩ ይግባኙን በሰማው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚገባ ተጣርቶ የተወሰነ መሆኑን ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል ፡፡እንደመረመረውም ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም ተደረገ የተባለው ስምምነት አመልካችን በሕግ ፊት የማስገደድ ሃይል አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ በቅብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም ተፃፈ በተባለውና በ200 ካ.ሜትር ስፋት ቦታ ላይ የሰፈረው የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል አፈፃጸም መሰረት አድርገው መሆኑን፣ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል በውልና ማስረጃ ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ አመልካች መሐይም ሁነው ያደረጉት መሆኑና በሰነዱ ላይ ለአመልካች ተሰጠ የተባለው የቤት ስፋትና የገንዘብ መጠን በውሉ ላይ በተገለፀው አኳኋን ያለመሆኑን በምስክሮች ቃል የተረጋገጠው የተለያየ መሆኑን፤አመልካች በቦታው ላይ ቁጥር 3798 ተብሎ የተጠቀሰው ቤት የሰፈረው በ200 ካ.ሜትር ብቻ ሳይሆን በ647 ካ/ሜትር መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ ተጠሪ ግን በዚህ ረገድ ግልጽ መከራከሪያ ያላቀረቡ መሆኑን፣የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዳኞች እስከ አከራካሪው ቦታ ድረስ ሂደው ተሸጠ የተባለው ባዶ ቦታ መሆኑን አመልካች ሊያሳዩ ያልቻሉ መሆኑንና ይልቁንም መኖሪያ ቤት የሸጡ መሆኑን ማስተባበያ ሊያቀርቡ አልቻሉም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱ መሆኑን ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪ ክስ ያቀረቡት እንደውሉ እንዲፈጸምላቸው ሲሆን አመልካች ደግሞ ውሉ የቤት ሽያጭ ውል ያለመሆኑንና ሕጋዊ ያለመሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ አመልካች መሐይም ነኝ በማለት ስለ ውሉ ሕጋዊነት የሚያቀርቡት ክርክር በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ነው ከማለት ውጪ ሌላ ማስተባበያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር ያላቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በዚህ ረገድ መከራከሪያ ነጥብ አንስተው የተከራከሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ የሽያጭ ሰነዱም በማስረጃነት የቀረበበትና የመኖሪየ ቤት ሽያጭ የለም በማለት የተከራከሩበት ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ይቻል ዘንድ የሰነዱን ምንነት መለየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም የተፈረመው ሰነድ ርእሱ የ **"መኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት** " የሚል ሲሆን የገዢና ሻጭ እንዲሁም የምስክሮች ፊርማ የያዘ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ወደ ይዘቱም ሲገባ ሻጭ ተብለው የተጠቀሱት የአሁኗ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 ክልል ወስጥ ቁጥሩ 3798 የሆነውን፣የቦታው ስፋት 200 ካ/ሜትር ሁኖ በካርታ ቁጥር ቦሌ/10/02/93-4208/22572/01 የሆነውን በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኘወን የመኖሪያ ቤታቸውን ለአሁኑ ተጠሪ በብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) ሸጠው ብር 55,000.00 ሌላ ደረሰኝ ሳያስፈልጋቸው በስምምነቱ እለት የተቀበሉና ቤቱን ያስረክቡ መሆኑን፣የመጨረሻውን ክፍያ ደግሞ ገዥ በሚፈልጉበት ቦታ ላይ በገዥ ስም ካርታ ሻጭ ከሚመለከተው ክፍል በስማቸው አሰርተው ካስረከቧቸው ከአንድ አመት በኋላ ብር 145,000.00(አንድ መቶ አርባ አምስት ሺ)አጠቃልለው ሊከፍሏቸው መስማማታቸውን፣ የሸጡትን ቤት በቆርቆሮ አጥር አጥረው፣በር ገጥመው፣ውሃ፣መብራት፣ስልክ አስገብተው እንዲሁም ጊዜያዊ ሽንት ቤት ሰርተው ሊያስረክቧቸው መስማማታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪም በውሉ በሰነዱ በተገለጸው አኳኃን ክፍያውን የፈፀሙና ለመፈጸም የተስማሙ ሁነው ቤቱን የተረከቡ መሆኑን በመግለፅ መስማማታቸው በሰነዱ ላይ ተጠቅሷል፡፡ በሰነዱም ላይ ሁሉም ተዋዋዮችና ምስክሮች ፈርመውበታል፡፡

ከላይ እንደተገለፀውም አመልካች ለክርክራቸው መሰረት ከአደረጓቸው ነጥቦች አንዱ መሓይምነት ሲሆን ክርክሩ ስለመነሳቱ ግንዛቤ ከተወሰደ ጉዳዩ በፍ/ሕ/ቁ.1728/3/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚመለከት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1728(3) ድንጋጌ አንድ ስምምነት በጽሁፍ እንዲሆን ሕግ ሲያስገድድ ውሉ በጽሁፍ መሆንና ግዴታ ባለባቸው ሰዎች ሁሉና በሁለት ምስክሮች ተፈርሞ ሊረጋገጥ እንደሚገባ፤ማየት የተሳናቸው ወይም የመሐይማን ፊርማ የነሱ ለመሆኑ ውል አዋዋይ ወይም የፍርድ ፀሐፊ ወይም አንድ ዳኛ በስራው ላይ ሆነው ካላረጋገጧቸው እንደማያስገድዷቸው ከፍ/ሕ/ቁ. 1727 እና 1728/3/ መረዳት ይቻላል፡፡እንግዲህ ተዋዋዮች ንብረታቸውን አስመልክቶ ባላቸው ተወዳዳሪ ግንኙነት መብት ለማቋቋም፤ለመለወጥ፤ወይም ለማስቀረት በሚደረግ ስምምነት ሁሉቱም ግዴታ የሚገቡበትን ነገር አውቀውትና ተገንዝበውት ነፃ ፈቃዳቸውን ሊሰጡ ስለሚገባ ማንበብና መፃፍ ለማይችሉ ወይም ማየት ለተሳናቸው ተዋዋዮች ህጉ ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ በመሆኑም በጽሁፍ የሰፈረውን ውል ገለልተኛ በሆኑ 3ኛ ወገኖች ፊት ካልፈረሙ በውሉ ሊገደዱ አይችሉም፡፡አመልካችና ተጠሪ በ30/05/2000 ዓ/ም አደረጉ የተባለው ስምምነት ደግሞ በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት እንዲደረግ ህጉ የሚያስገድደው ነው፡፡በመሆኑም አመልካች መሃይምነታቸውን ምክንያት በማድረግ የሽያጭ ውል ስምምነቱ በዳኛ ወይም በአዋዋይ ፊት አልተደረገም በሚል ምክንያት እንደማያስገድዳቸው ያቀርቡት ክርክር በበታች ፍርድ ቤቶች መታለፉ የግራቀኙን የክርክር አቀራረብና የሰነዱን ይዘት ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰነዱ የመንደር ውል ሁኖ እያለ በሰነዱ የሠፈሩት ነጥቦች ሁሉ ደምዳሚ ናቸው በማለት ውሉ እንዲፈፀም መወሰኑም ሆነ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም አመልካች ውሉን አላስተባበሉም በማለት ውሉ እንዲፈጸም የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005፣ 1723 እና 1728(3) ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ ውጤቱ ሲታይ ግን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ከላይ በተጠቀሱት ህጋዊ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 103872 ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71988 ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 166591 ህዳር 20 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎቱ አመልካችና ተጠሪ ጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም ያደረጉት ስምምነት ሕጋዊ አይደለም ብሎ የሰጠው የውሳኔ ክፍል በተለወጠ ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 342 እና 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ጥር 30 ቀን 2000 ዓ.ም የፈረሙት ስምምነት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1728(3) መሰረት ያልተደረገ በመሆኑ አመልካችን በሕግ ፊት የማስገደድ ሓይል የለውም ብለናል፡፡ይሁን እንጂ አመልካች ከተጠሪ ብር 5000.00(አምስት ሺ ብር) መቀበላቸውን ያልካዱ በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ ከጥር 30 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ(9%) ለተጠሪ ሊመልሱ ይገባል ብለናል፡፡እንዲሁም ተጠሪ ለአመልካች የከፈሉት ሌላ ገንዘብ ካለ በሕጉ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ል/ተ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90862

ታህሳስ 14 ቀን 2006ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች- ወ/ሮ ተዋበች ኃይሌ ቀረቡ

ተጠሪ- ወ/ሮ አያንቱ በዬቻ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሽያጭ ምክንያት ተይዞ በቆየው ይዞታ ላይ ለተሰራ ቤት የወጣው ወጪ /ገንዘብ/ ይተካልኝ የሚል ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ባሁኗ ተጠሪ እና በአቶ በዬቻ ሆርዶፋ ላይ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አቶ በዬቻ ሆርዶፋ ሕዳር 10 ቀን 1992 ዓ/ም በተጻፈ የብድር ውል ነሐሴ 30 ቀን 1992 ዓ/ም የሚመለሰውን ብር 10,000.00 (አስር ሺ ብር) ተበድረው መውሰዳቸውን፣ይህንኑ ገንዘብ በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ካልመለሱ ደግሞ በአለምገና ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና በ147 ካ/ሜትር የቦታ ስፋት ላይ የሠፈረውን ባለአስራ ስድስት ሉክ/ዚንጎ/ ቆርቆሮ ፣በመያዣነት መስጠታቸውንና ስምም ለማዞር ግዴታ ገብተው የነበሩ መሆኑን፣በዚህ የውል ስምምነት መሰረት ግዴታቸውን እንዲወጡም በመ/ቁጥር 07334 በሆነው ክስ አቅርበው አቶ በዬቻ ወርዶፋ የውል ግዴታቸውን አምነው መልስ በሰጡበት ሁኔታ የአሁኗ ተጠሪ በብድር ገንዘቡ ምክንያት ለመያዣነት የተሠጠው ቤት የአቶ በዬቻ ወርዶፋ የግል ቤት ሳይሆን ከሚች እናታቸው ከወ/ሮ ጌጤ በዳኔ ጋር በጋብቻ የተፈራ የጋረ ንብረት በመሆኑ ስምምነቱ ሕጋዊ አይደለም በሚል ምክንያት ወደ ክርክሩ ገብተው ክርክሩ ከተካሄደ በኋላ በቤቱ ላይ የተደረገው ስምምነት ሕጋዊ አይደለም ተብሎ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት ቢሆንም ይህንኑ ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት አመልካች በብድር ስምምነቱ መነሻ ያወጡትን ወጪ የመጠየቅ መብታቸውን የጠበቀላቸው መሆኑን፣አመልካች ለአቶ በዬቻ ሆርዶፋ ከብድር ገንዘቡ በተጨማሪ ብር 20,800.00(ሃያ ሺ ስምንት መቶ ብር) በቦታው ላይ የሰሩትን ቤት ሊለቁላቸው በአገር ሽማግሌ ፊት ተስማምተው የሰጡ ቢሆንም ይህ ስምምነትም በአሁኗ ተጠሪ ተቀዋሚነት በወራሽነታቸው ድርሻ ላይ ስምምነታቸውን ያልሰጡበት ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ውድቅ የተደረገ መሆኑን፣በቦታው ላይ የሰሩት ባለሰባ ስምንት ሉክ/ዚንጎ/ቆርቆሮ መኖሪያ ቤትም ግምቱ ብር 88,330.00(ሰማንያ ስምንት ሺ ሶስት መቶ ሰላሳ ብር)መሆኑን ጠቅሰው በድምሩ ብር109,130.00(አንድ መቶ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ብር) ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም አመልካች ውል የፈፀመችው ከአቶ በዬቻ ጋር መሆኑን፣ውሉም ፈርሶ ወደ ነበሩበት ይመለሱ ተብሎ የተወሰነ በመሆኑ ውጤቱን በተመለከተ ክስ ማቅረብ የሚችሉት ውሉን ከተዋዋሉት ሰው ጋር መሆኑን፣በቦታው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ የተሰራ ቤት ካለመኖሩም በላይ ቤት እንዲሰሩበት ስምምነት የሌለ መሆኑን፣ከባለይዞታው ፈቃድ ውጪ ለተሰራ ቤት የሚጠየቁበት ሕጋዊ ምክንያት ያለመኖሩንና የግንባታ ወጪ መጠኑም በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡አቶ በዬቻ ወርዶፋ በበኩላቸው ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ማለቁንና በአፈጻጸም ሂደት ላይ እንደሚገኝ እንዲሁም በቦታው ላይ የተሰራ ቤት ያለመኖሩን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡የሥር ፍርድ ቤትም የቤቱን ግምትም በተገቢው ባለሙያ እንዲገመት ከአደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርምር ተጠሪንና አቶ በዬቻን ለክሱ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን የኃላፊነት መጠኑን በተመለከተ ግን አቶ በዬቻ ከብድሩ በኋላ በሽማግሌዎች ፊት የወሰዱትን ብር 20,800.00 እና የቤቱን ግምት ግማሽ ብር 41,507.87(አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም) በድምሩ ብር 62,307.87(ስልሳ ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ሰባት ብር ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም) የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ የቤቱን ግምት ግማሽ ብር 41,507.87(አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም) እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ወጪና ኪሳራን በተመለተከም ብር 600.00 በቁርጥ፣የዳኝነት ብር 3,487.95 ተጠሪና አቶ በዬቻ ወርዶፋ ለአመልካች እንዲተኩላቸው በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው አመልካች ጋር እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ አመልካች ከባዬቻ ሆርዶፋ ጋር ባደረጉት ውል የወጣውን ወጪ የሚተኩበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ሲል ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠውን የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ የክሱ ምክንያት የሆነውን ጠቅላላ ገንዘብ ብር 103,815.75(አንድ መቶ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ አስራ አምስት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም) አቶ በዬቻ ሆርዶፋ ለአመልካች ሊተኩላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተተ የለበትም ተብሎ ፀንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በቦታው ላይ በተሰራው አዲስ ቤት የግማሽ ባለመብት ሁነው እያለ የቤቱን ግምት ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ከአላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ፡- ተጠሪ የአከራካሪውን ቤት ግምት ግማሽ ለአመልካች ለመክፈል ይገደዳሉ ወይስ አይገደዱም የሚለው ነጥብ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪና በአቶ በዬቻ ሆርዶፋ ላይ ክስ የመሠረቱት አቶ በዬቻ ሆርዶፋ ለገንዘብ ብድር በዋስትና ውል አሳልፈው በሰጧቸው ቦታ ላይ አዲስ ቤት ሰርተው ቤትና ይዞታውን በመያዝ በመጠቀም ላይ እያሉ ይሄው የመያዣ ውል ሕጋዊ አይደለም፣ሊፀና አይገባም የሚል ክርክር በተጠሪ በኩል ቀርቦ ውሉ ሊፈርስ እንደሚገባና ይፈርሣል ከተባለም ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ተብሎ በመ/ቁጥር 07334 በስር ፍርድ ቤት ከተወሰነ በኋላ ለአሁኑ የሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ መቅረቡን፣በዚህ ክስም አመልካች ዳኝነት የጠየቁት ለአዲስ ግንባታ ያወጡት ወጪ አቶ በዬቻ ሆርዶፋና ተጠሪ እንዲከፍሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይወሰንላቸው ዘንድ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪም የመያዣ ውሉ የተደረገው ከአቶ በዬቻ ሆርዶፋ ጋር በመሆኑ ተጠሪን የሚያስጠይቅበት ህጋዊ ምክንያት ያለመኖሩንና ክባለይዞታው እውቅናና ፈቃድ ውጪ ለተሰራ ግንባታ ተጠያቂ የሚሆኑበት የህግ አግባብ ያለመኖሩን ጠቅሰው ውሉ በተጠሪ ላይ ተጠያቂነት የሚያስከትል አይደለም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በአመልካችና በአቶ በዬቻ ሆርዶፋ መካከል የተደረገው የመያዣ ስምምነት በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የተደረገ ነው ተብሎ ሕጋዊ የሆነ የቤት መያዣ ውል እንደሌለ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተረጋገጠ ሲሆን ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ሲወሰንም አመልካች አለኝ የሚሉትን መብት በክስ ማስጠበቅ የሚችሉ መሆኑ ተገልጾ መወሰኑን ክክርክሩ ሂደት መገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ጉዳይ ያቀረቡትም የቤት መያዣ ውል ሕጋዊ አይደለም፤ ፈራሽ ነው፣ ቤቱን ለተጠሪና ለአቶ በዬቻ ሆርዶፋ ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ ውሣኔ ከተሰጠ በሁዋላ ሲሆን ተጠሪ በይዞታው ላይ በአመልካች ገንዘብ የተሰራ አዲስ ግንባታ መኖሩን በተመለከተ ያቀረቡት የማስተባበያ ክርክር በማስረጃ ያልተደገፈ ሁኖ በመገኘቱ በስር ፍርደ ቤት ውድቅ የሆነ ሲሆን የበላይ ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ የተለዬ ድምዳሜ ላይ አልደረሱም፡፡አመልካች አዲስ ግንባታ መኖሩን ጠቅሰው ይህንኑ ለማስረዳት የቆጠሩት ማስረጃ በስር ፍ/ቤት ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን የቤቱ ግምትም በሚመለከተው አካል ተገምቶ ብር 83,015.75 ነው ተብሎ መረጋገጡን የስር ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ ያሣያል፡፡ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተጠሪን የተሰራውን ቤት የግንባታ ወጪ ግማሹን ተጠሪ ሊጠየቁ አይችሉም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት ለመያዣ ውሉ ስምምነት ምክንያት የሆኑት ተጠሪ ሳይሆኑ አቶ በዬቻ ሆርዶፋ ናቸው በሚል ምክንያት ነው፡፡

እንግዲህ ከላይ የተመለከቱት ነጥቦች በስር ፍ/ቤት የተረጋገጡ ሲሆን ከላይ እንደተገለጸው ምንም እንኳን የመያዣ ውሉ የጋራ ባለንብረቶችን ስምምነት ሳያገኝ የተደረገ ነው ተብሎ ፈራሽ ቢሆንም ውሉ በመፍርሱ ወይም በመሰረዙ ምክንያት ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰው ንብረቱን ለውጦ ወይም በዚሁ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ባወጣው ወጪ መጠን ሊጠይቅ እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ 1818 ያመለክታል፡፡ ስለሆነም አመልካች ይዞታውንና ቤቱን እንዲለቁ ሲደረግ ቤቱንና ቦታውን እንዲረከቡ ዳኝነት ያገኙት ሰዎች በቦታው ላይ የሰፈረውን ቤት ግምት ሊከፍሉ የማይገባበት ምክንያት የለም፡፡ምክንያቱም አመልካች በቦታው ላይ አዲስ ቤት ሲገነቡ ተቃውሞ የቀረበባቸው መሆኑ በፍሬ ነገር ያልተረጋገጠ ሲሆን ይዞታውን ለመያዝም የቻሉት ሕጋዊ ውል አለኝ በሚል እምነት መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ ይህ ድንጋጌ የወጪውን መመለስ በተመለከተ ያላግባብ ስለመበልፀግ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንደሚኖራቸውም ያስገነዝባል፡፡ ከውል መፍረስ ጋር ተያይዞ ለሚነሳ የወጪ ክርክር ወጪውን አውጣሁ የሚለው ወገን በሕጉ ያለው መፍትሔ ምን እንደሆነ ሕጉ ያስቀመጠው ሁኔታ ይህ ከሆነ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት አለኝ የሚሉት በሚች እናታቸው በወ/ሮ ጌጤ በዳኔ ድርሻ በመሆኑ እና አዲስ የተሰራውንም ቤት እንዲረከቡ መብት የተጠበቀላቸው ስለሆነ በአመልካች ጥሬ ገንዘብ የተሰራውን ቤት ሲወስዱ ገንዘቡን የማይመልሱበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1818 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚታይ ነው እንጂ ተጠሪን በውሉ ስምምነት ያልሰጡ መሆኑን ብቻ መሰረት አድርጎ የሚታይ አይደለም፡፡ ያላግባብ የመበልጸግ ጥያቄ የውል ግንኙነትን መሰረት በማድረግ የዳኝነት መፍትሔ የሚሰጥበት አለመሆኑ ግልጽ ሁኖ እያለ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተጠሪ የውሉ ተካፋይ ያለመሆን ጋር በማያያዝ የሰጡት ዳኝነት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1818 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 እና ተከታይ ቁጥሮች ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ባለገናዘበ መልኩ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ሲጠቃለልም አመልካች በቤት መያዣ ውል ምክንያት በያዙት ይዞታ ላይ በራሳቸው ገንዘብ ለሰሩት ግንባታ ተጠሪ የቤቱን ግማሽ ድርሻ እንዲረከቡ ከተደረገ ቤቱ የተሰራበትን ወጪ ለአመልካች የማይተኩበት ህጋዊ ምክንያት ያለመኖሩን ከፍ/ሕ/ቁጥር 1818፣2162 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው በመሆኑ ተጠሪን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 113645 የካቲት 06 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 147924 መጋቢት 09 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01302 ሐምሌ 22 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ አመልካች የሰሩትን ቤት ዋጋ ግምት ግማሽ ብር 41,507.87 (አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም) በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠቀሰው አግባብ ለክርክሩ ከወጡ ወጪዎች ጋር የመክፈል ግዴታ አለባቸው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86847

ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፀጋዬ አማን ተወካይ ዘነበች አበራ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. አቶ መሐመድ ነጋሽ } ጠበቃ ሸምስ ከድር ቀረበ

2. ወ/ሮ ከድጃ ሚፍታህ }

3. በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 8 አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ ልማት ፅ/ቤት

ነ/ፈጅ አንዋር መ·ስጠፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከመንግስት የንግድ ቤት ኪራይ ውል ጋር ተያይዞ የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡በአመልካች የቀረበው የክስ አቤቱታ ይዘትም በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ክልል ውስጥ የሚገኘውንና ቁጥሩ 4-078/879/ የሆነውን ንግድ ቤት ከወረዳው በሕጉ አግባብ ተከራይተው እና የንግድ ፈቃድ በማውጣትና የዳግም የንግድ ምዝገባ አካሂደው በመነገድ ላይ እያሉ ያለባቸውን የስራ ጫና ለማቃለል ሲሉ ከአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር መጋቢት 05 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ የስራ ውል በማድረግ ለተጠሪዎቹ ደመወዝ እየከፈሉ በቤቱ እየሰሩበት እያለ ተጠሪዎች ወደ ወረዳው አስተዳደር በመሄድ ተቀጣሪዎች አይደለንም፣ተከራይተን ነው በማለት አስመዝገበው በመገኘታቸው አመልካች ከእነዚህ ተጠሪዎች ጋር የነበራቸውን የሥራ ቅጥር ከጥቅምት 25 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ያቋረጡ መሆኑን፣ከዚህ በኋላም ቤቱን እነዚህ ተጠሪዎች እንዲለቁ አመልካች ቢጠይቋቸውም ሊለቁ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን፣ቤቱንና ግምቱ ብር 15,000.00 የሆነውን አታክልት ይዘው እንደሚገኙ፣3ኛ ተጠሪም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ከንግድ ቤቱ እንዲያስለቀቅላቸው ቢጠየቅም በመመሪያ ቁጥር 3/2004 እና 4/2004 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሊፈጽም ያልቻለ መሆኑን በመዘርዘር ቤቱና አታክልቱ እንዲለቀቅላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ቀርበው በሰጡት መልስም ከአመልካች ቤቱን በብር 18,000.00 ወርሃዊ ኪራይ መክራየታቸውን፣የስራ ቅጥር ውል የሌላቸውና የተከራይ አከራይ መመሪያ ሲወጣ አመልካች ፈርተው ተጠሪዎችን ፍጹም በሆነ የሞራል መገደድ ያስፈረሙ መሆኑንና ቅጥሩም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ስለ ስራ ቅጥር ውል ፎርም የሚደነግገውን ፎርማሊቲ የማያሟላ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ደግሞ ክሱ እንደማይመለከተውና አመልካች ቤቱን ያለአከራይ ፈቃድ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው መገኘታቸው በሚመለከተው ኮሚቴ ተጣርቶና ተረጋግጦ በመመሪያው መሰረት ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ኪራዩ መደረጉን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ወ/ሮ ዘነበች አበራ የንግድ ድርጅቱን በሕጉ አግባብ የገዙትና ስመ ሃብቱ እንዲዞርላቸው ሊወሰን እንደሚገባ ጠቅሰው ማመልከቻ በማቅረባቸው ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን በመስማት ጉዳዩን በመመርመር በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል በመመሪያ ቁጥር 3/2004 እና ቁጥር 4/2004 መሰረት የተደረገ ነው፣የቅጥር ውሉ አሳማኝነት የለውም የሚል ምክንያት ይዞ 3ኛ ተጠሪ ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረገው ውል ተቋርጦ የአመልካች ተከራይነት መብት ሊረጋገጥ አይገባም፤1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ቤቱንና አታክልቱን ለቀው ለአሁኑ አመልካች ሊያስረክቡ አይገባም፣ እንዲሁም የጣልቃ ገቧ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካችና ወ/ሮ ዘነበች አበራ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለየብቻቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ መዛግብቱን አንድ ላይ አጣምሮ በመመርመር 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ተቀጣሪ ሰራተኛ መሆናቸው ተረጋግጧል የሚል ምክንያት ይዞ በእነዚህ ተጠሪዎችና በአሁኑ አመልካች መካከል የኪራይ ውል የለም፣ወ/ሮ ዘነበች አበራ የንግድ መደብሩን የገዙት ስለመሆኑ ያላስመዘገቡ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም የሚሉትን ምክንያቶችን ይዞ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል በወ/ሮ ዘነበች አበራ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ያደረገው ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ግን ከአመልካች ጋር ያላቸው ግንኙነት የቅጥር ውል ነው በማለት 3ኛ ተጠሪ ከአሁኑ አመልካች ጋር ያለውን ውል ማቋረጡ ያላግባብ ነው ብሎ ደምድሟል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም ይህን ውሣኔ በከፊል በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማ አስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ በድምፅ ብልጫ በመሻር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት የወሰነ ሲሆን ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤትም አመልካችንና ተጠሪዎችን በድጋሚ አከራክሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቷል፡፡ከዚህ በኋላ ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት የአሁኑ አመልካች ሲሆኑ ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘቱም በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እና በአመልካች መካከል የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ስለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት በሚገባ ተረጋግጦ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቀድሞ የሻረውን ውሳኔ ጉዳዩ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ሲመለስለት ያለምንም ምክንያትና ትችት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ማፅናቱ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰሚ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የሰበር ፅሑፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባው ነጥብ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የከተማው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአሁኑ አመልካች እና ወ/ሮ ዘነበች አበራ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት በመ/ቁጥር 18210 እና 18209 በሆኑት ላይ ይግባኙን አቅርበውለት እነዚህን መዛግብት አጣምሮ በመመርመር ነሐሴ 03 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04905 በሆነው በ7/10/2004 ዓ/ም የሠጠውን ውሳኔ የሻረ ቢሆንም የአሁኑ ተጠሪዎች ጉዳዩን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ሰበር ሰሚ ችሎቱ በጉዳዩ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያለመታየቱን ደምድሞ የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሮ ጭብጡን ለይቶ ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከመለሰለት በኋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመ/ቁጥር 18210 በድጋሚ ተመልክቶ በመመርመር የስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04905 ሰኔ 07 ቀን 2004 የሠጠውን ውሳኔ ጥቅምት 30 ቀን 2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት ያጸናው መሆኑን፣በዚህም ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የአመልካች ተቀጣሪ ሰራተኞች ሳይሆኑ ተከራይ መሆናቸውን የስር ፍርድ ቤት የያዘውን መደምደሚያ ሙሉ በሙሉ የተቀበለ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች ከ3ኛ ተጠሪ የተከራዩትን የንግድ ቤት ያለአከራዩ ፈቃድ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያከራዩ ስለመሆናቸው ማስረጃዎችን የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር በመሆኑ አመልካች ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት የአሰሪና ሰራተኛ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር ውጪ በመሆኑ ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ስልጣን ስር የማይወድቅ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

በፍ/ሕ/ቁ/2957(1) ተከራይ የተከራየውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሙሉ ወይም በከፊል ለ3ኛ ወገን ሊያከራይ የሚችል ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን ይህንኑ የማከራየት መብቱን ሊጠቀም የሚችለው ደግሞ በዚሁ ቁጥር በንዑስ ቁጥር ሁለት በተገለረው መሰረት አስቀድሞ ተከራዩ አሳቡን ለአከራዩ አስታውቆ አከራዩ በዚሁ ጉዳይ ላይ ሊኖረው የሚችለውን አቋም ካወቀ በኋላ መሆን እንዳለበት ህጉ በአስገዳጅ ሁኔታ አስቀምጧል፡፡በመሆኑም አመልካች አከራይ ከሆነው ከአሁን 3ኛ ተጠሪ ፈቃድ ሳያገኙ የንግድ ቤቱን ለ3ኛ ወገን ያከራዩት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2957 በንዑስ ቁጥር 2 የተቀመጠውን አስገዳጅ ሁኔታ የሚቃረን ነው፡፡

በመሆኑም አመልካች የተከራዩትን ቤት ከ3ኛ ተጠሪ የተሰጣቸው ፈቃድ ሳይኖር ለ3ኛ ወገን አከራይተው የተገኙት የፍ/ህ/ቁ 1731(1)፣2957(2) ድንጋጌዎችንና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቢሮ በንግድ ቤቶችና ወደ ንግድ ቤት በተቀየሩ የመኖሪያ ቤቶች ላይ የተፈጠሩ ችግሮችን ለማስወገድ ተሻሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 3/2004 እና 4/2004 የሚጥስ ሆኖ በመገኘቱ የሥር ፍርድ ቤቶች 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል ሊቋረጥ አይገባም፤ ቤቱንና አታክልቱን ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 04905 በቀን 07/10/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/18210 በቀን 30/02/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ውሳኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 19016 በቀን 12/04/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የንግድ ቤትና አታክልክት ይለቀቅልኝ ጥያቄ በበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86813

መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድረጅት ነ/ፈጅ ታደሰ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡ 1. ሰሚር መላኩ አልቀረበም

2. አቶ መላኩ በቀለ ቀረቡ

3. አቶ ንብረቱ ምትኩ ወኪል 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የጎደለ ገንዘብን ከማስከፈል ክርክር ጋር ተያይዞ የቀረበ ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መንግስት ቁለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ በአመልካች የቀረበው የክሱ ይዘትም በአመልካች ድርጅት ውስጥ 1ኛ ተጠሪ ፖስተኛ ሆኖ በሚሰራበት ጊዜ ግምቱ ብር 54,150 የሆነ ቨውቼር ካርድና ብር 6,338 የሆነ ቴምብር ቀረጥ በድምሩ ብር 61,088 የጎደለ ስለመሆኑ በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠበት መሆኑን ጠቅሶ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ 1ኛ ተጠሪ ሲቀጠሩ እያንዳንዳቸው ብር 30,000 ዋስ ስለሆኑ ሶስቱም ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነ ወለዱ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን 1ኛ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ የስራ ድርሻው ፖስተኛ ስለሆነ ጎደለ የተባለው ገንዘብ እሱን እንደማይመለከትና ተደርጓል የተባለው የኦዲት ስራም እሱ በሌለበት መሆኑን ጠቅሶ ለክሱ ኃላፊ ሊሆን እንደማይገባ በመከራከር መልሱን ሰጥቷል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ዋስትና የገቡት 1ኛ ተጠሪ ለ6 ወራት ብቻ በጊዜያዊ ቅጥር በፖስተኛነት ለተቀጠረበት ስራ ነው እንጂ ከዚያ በኋላ በ1ኛ ተጠሪና አመልካች መካከል በአዲስ መልክ የቅጥር ውሉ ለታደሰው ስራ አለመሆኑን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ መነሻ የሆነውን ገንዘብ ማጉደሉ ተረጋግጦበታል በማለት ገንዘቡን ለዳኝነት ከተከፈለው ገንዘብና ወጪና ኪሳራ ብር 1500 ጋር ለአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲከፍል ሊወሰንበት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ ግን እነዚህ ተጠሪዎች ዋስትና የገቡበት የ1ኛ ተጠሪ ጊዜያዊ ቅጥር ውል ጊዜው አልቆ ውሉ በአዲስ መልክ በሌላ ስራ መደብ ላይ በ1ኛ ተጠሪና አመልካች መካከል ሲደረግ የዋስትና ውሉ አብሮ ያልተደሰ በመሆኑ ኃላፊነት የለባቸውም በማለት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡

በአመልካች ጠያቂነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት በመሰረዝ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ያፀና ሲሆን አሁን የቀረበው ሰበር አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሆኖ መሰረታዊ ይዘቱም የዋስትና ውሉ በጊዜ ያልተገደበና እንዲሁም የ1ኛ ተጠሪ ጊዚያዊ የስራ ቅጥር ውል መታደስ በራሱ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በመጀመሪያ ቅጥር ጊዜ የገቡትን የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሊያደርገው እንደማይችል እየታወቀ የበታች ፍ/ቤቶች 2ኛና 3ኛ ተጠሪዎችን ከኃላፊነት ውጭ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ በገቡት ዋስትና መጠን ከነወለዱ እንዲከፍሉ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የገቡት የዋስትና ውል በጊዜ አለመገደቡ እየታወቀ የስር ፍ/ቤት ዋሶቹ ለታደሰው 2ኛ ቅጥር ውል ዋስትና ግዴታ ስላልሰጡ ለእዳው ተጠያቂነት የለባቸውም በማለት ከኃላፊነት በነጻ የማሰናበቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ በአመልካችና 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል የጽሑፍ ክርክር የተደረገ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ግን ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው 2ኛና 3ኛ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ የገቡበት የ1ኛ ተጠሪ የመጀመሪያ ጊዜያዊው የስራ ቅጥር ውል ጊዜው አልቆ በሌላ ሰራ ቅጥር ውል እንዲተካ ወይም በአዲስ መልክ ተሻሽሎና የስራ መደቡም ከፖስተኛነት ወደ ክለርክነት እንዲቀየር በተደረገበት ጊዜ የዋስትና ውሉም አብሮ አለመታደሱ ወይም ዋሶቹ ፈቃዳቸውን አለመስጠታቸው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ለዋስትና ውል መሰረት የሆነው የመጀመሪያ ውል ተለውጦ በሌላ ውል በሚተካበት ጊዜ ዋስትና ግዴታው ለተለወጠው ቅጥር ውልም ቀጣይነት ኖሮት እንዲቆይ በግልጽ ካልተሰማሙ በስተቀር ወደ ተለወጠው ውል ሊተላለፍ እንደማይችል ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1827/1/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይም ተፈርሞ የነበረው የዋስትና ግዴታ ወደ ተለወጠውና 2ኛ ቅጥር ውል እንዲተላለፍ በግልጽ የተሰማሙ መሆናቸውን አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎቹ ተጠያቂነት የለባቸውም ተብለው በስር ፍ/ቤት ከኃላፊነት በነፃ መሰናበታቸው የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. የሰበር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 86187

ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች:- አቶ ዳንኤል ዘሚካኤል - ጠበቆች ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ እና አቶ ፊሊጶስ አይናለም ቀረቡ፡፡

ተጠሪ:- አቶ ቢሃሪ ባቡላል ሞዲ - ጠበቃ አቶ አምሃ በድሉ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የግራ ቀኙን የገንዘብ ጉዳይ ክርክር ሰምቶ በመወሰን ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች ከተከተሉት የጉዳዩ አካሄድ አንፃር ተመልክቶ የሠጡት ዳኝነት አግባብነትን ለማየት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ሲሆን ይዘቱም ተከሳሽ ለንግድ እንቅስቃሴው ባጋጠማቸው የገንዘብ እጥረት ምክንያት ለንግድ ሥራቸው የሚውል ገንዘብ እንዲያበድሯቸው ከሳሽን በጠየቋቸው መሰረት ከሳሽ የተከሳሽን ችግር በመመልከት ከ1998 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ/ም ድረስ በተለያዩ ጊዜያት ከሳሽ ለተከሳሽ ላበደራቸው ገንዘብ ተከሳሽ ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ/ም የተፈረመ የገንዘብ ብድር መተማመኛ ውል መሰረት ብር 7,079,604.86 (ሰባት ሚሊዮን ሰባ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ አራት ብር ከሰማንያ ስድስት ሳንቲም) ይፈለግባቸዋል፡፡ ከታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ/ም በኋላም በተከሳሽ ፈቃድ መሰረት በተለያዩ ጊዜያት ለተከሳሽ የንግድ ሥራ ያወጡላቸውን ወጭዎች ብር 946,270.06 (ዘጠኝ መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ብር ከስድስት ሳንቲም) በብድር የወሰዱ ለመሆኑም ተከሳሽ በኢሜይል ደብዳቤዎች በዕሁፍ አረጋግጠዋል፡፡ በአጠቃላይ ብር 8,025,874.92 (ስምንት ሚሊዮን ሃያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ አራት ብር ከ$^{92}/_{100}$ ሳንቲም) በዕዳ እንደሚፈለግባቸውና ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉ ሲጠየቁ የ6 ወራት የመክፈያ ጊዜ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ከዚህ ጊዜ በኋላ ገንዘቡን እንዲከፍሉ በተደጋጋሚ ቢጠየቁም እከፍላለሁ በማለት የተስፋ ቃል ከመስጠት በቀር ሊከፍሉ አልቻሉም፡፡ ስለሆነም የ6 ወሩ የዕዳ መክፈያ ከተጠናቀቀበት ከግንቦት 03 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ የወለድ ተመን ጋር በአንድ ጊዜ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽም በሰጠው የመከላከያ መልስ ከከሳሽ ጋር የቆየ መልካም የጓደኝነትና የንግድ ግንኙነት አልነበረኝም ተከሳሽ የገንዘብ እጥረት ያጋጠማቸው መሆኑን ለከሳሽ ገልፀው አያውቁም፣ ከከሳሽ ጋር ያለኝ የአሰሪና ሰራተኛ እንዲሁም የወካይና ተወካይ ግንኙነት ያለን በመሆኑ ገንዘብ ሊያበድሩኝ የሚችሉበት ምክንያታዊ መነሻ የላቸውም፤ ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ/ም በእኔ ተፈረመ የተባለውን ሰነድ አላውቀውም፡፡ ይህ ሰነድ ተፈረመ ከተባለበት ከ1999 ዓ/ም በፊትም ሆነ በኋላ ተከሳሽ በኢትዮጵያ ውስጥ አልኖሩም፤ ለአድዋ ዱቄት ፋብሪካ ሲባል ገባ የተባለውን ዕዳ ተከሳሽ በግለሰብ ደረጃ መተማመኛ ወይንም ማንኛውም ውል ሊያደርጉ ስለማይችሉ በሰነዱ ልገደድ አልችልም፡፡ ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ/ም ተፃፈ በተባለው ሰነድ እንደተመለከተው ከሳሽ ለወደፊት ወጭ ያወጡ ከሆነ ተከሳሽ መተማመኛ ይሰጡ ዘንድ ብር 946,270.06 ወጭ ያደረጉ ስለመሆኑ የሚያመለክት ማስረጃም ያልቀረበ ስለሆነ የተጨማሪውም የገንዘብ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም፡፡ ከብር 500.00 በላይ የሆነን የብድር ዕዳ ለማረጋገጥ በሚያስችል አኳኋን የቀረበ የሰነድ ማስረጃም አልቀረበም፡፡ የኢሜይል ሰነዶችንም በተመለከተ በተከሳሽ ያልተፃፈ ተከሳሽ የማያውቃቸው በሐሰት ተቀናብረው የተዘገጁ ናቸው ታህሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ተከሣሽ በከፍተኛ የአእምሮ ጭንቀት በሽታ ምክንያት በሆስፒታል ተኝተው የነበረ በመሆኑ ሰነዱን ሊፈርሙት አይችሉም፡፡ በአጠቃላይ በከሣሽ በኩል የቀረበው ክስና ማስረጃ የህግ መሠረት የለውም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

ይህ የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ከተጠናቀቀ በኋላ ፍ/ቤቱ የቃል ክርክር ካደረገና በተከሣሽ የተካደውን ታህሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ተፈረመ የተባለው ሰነድ ላይ የተቀመጠው ፊርማ በተከሣሽ የተፈረመ መሆኑን እና አለመሆኑን ለማረጋገጥ በፎረንሲክ ሳይንሳዊ ምርመራ ሁለት ጊዜ እንዲመረመር ካደረገና ውጤቱን ከተቀበለ በኋላ ግራ ቀኙን ያከራከራቸውን ነጥቦች ለይቶና ከግራ ቀኙ ማስረጃዎች ጋር አገናዝቦ መርምሮ በመ/ቁ. 87441 ጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት፡-

ከሣሽ ለቀረበው ክስ በማስረጃነት ያቀረበው ታህሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈው ሰነድ በተከሣሽ ያልተፈረመ ለመሆኑ ሁለት ጊዜ በተደረገው የፎረንስክ ምርመራ ውጤት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ሰነድ ተከሣሽ ለከሣሽ ብር 7,079,604.86 የተበደረ ለመሆኑ አያረጋግጥም ::

በማስረጃነት የቀረበውም በኢሜል እና በፋክስ የመልእክት ልውውጥ የተደረገ በመሆኑ የብድሩ ስምምነት መኖሩን ያስረዳል በማለት የቀረቡት ሰነዶች ሲሆኑ በተከሣሽ የተደረጉ ሳይሆን ሰለሞን ቢሀሪ ሞዲ በተባለ ግለሰብ የተደረገ ስለመሆኑ ሰነዱ ያስረዳል ሰለሞን ቢሀሪ የተከሣሽ ልጅ ነው የሚባል ቢሆን እንኳ ስለተከሣሽ ሆኖ ገንዘብ ለመበደር የሚያስችል የውክልና ሥልጣን ተከሣሽ እስካልሠጠ ድረስ ማስረጃው ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፡፡ እንዲሁም የኢሜል የመልእክት ልውውጥ ሁልጊዜም በባለአድራሻው የሚደረግ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል አይደለም በዚህ ሁሉ ምክንያት ማስረጃው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

በተጨማሪነት ስለቀረበው የብር 946,270.06 የንግድ ሥራ ወጭ በሚመለከት ከሣሽ ይህንኑ ወጭ አወጣው የሚለው በውክልና ሠራው በሚለው ሥራ እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ የገንዘብ ወጭ እያደረገ የተከሣሽን ሥራ ለመሥራት የማያስችለው ግልጽ የሆነ የውክልና ሥልጣን አልተሰጠውም ከብር 500.00 በላይ ተሰጠ ለሚል የገንዘብ ብድርም በሰው ማስረጃ ማስረዳት የሚቻል አይደለም በመሆኑም ከሣሹ ለተከሣሹ የንግድ ሥራ ውል በብድር መልክ ለተከሣሽ ይህንኑ የንግድ ሥራ ወጭ ያደረገ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚሉት ምክንያት ራሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሣሽ ለብር 8,025,874.92 /ስምንት ሚሊዮን ሃያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ አራት ብር ከ ዘጠና ሁለት ሣንቲም/ የብድር ገንዘበ ክስ በማስረጃ አስደግፎ አላረገገጠም ተከሣሹ ክሱ ነፃ ነው በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ የቀረበውን የይግባኝ ጉዳይ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የመጨረሻ ዳኝነት ሰጥቶበታል፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውም የአሁን አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ክርክር የመከራከሪያ ነጥቦች በመጥቀስ በቀረበው የሰበር አቤቱታ ምክንያት ሲሆን ተጠሪውም ይኸው በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት በሕግ አግባብ መሠረት ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት አመልካች በቀረበው የክርክር ነጥቦች አንፃር የጽሑፍ ክርክሩን አቅርቧል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሱን በጽሑፍ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠይቋል፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭር ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው አይደሉም? የሚለውን ጉዳይ ለማስረዳት ግራ ቀኙ በሰበር ደረጃ ያቀረቡትን የመከራከሪያ ነጥቦች ለእነዚሁ በበታች ፍ/ቤቶች ከተሰጡት ውሣኔዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአሁን አመልካች ላቀረበው ክስ በማስረጃነት ያቀረበውን ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተደረገውን የገንዘብ መተማመኛ ሰነድ ተከሣሹ በሰጠው መልስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 234/1/ሠ/ እንደተመለከተው በግልጽና በዝርዝር ክዶ የተከራከረ ለመሆኑ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከተሰጠው የፍርድ ሐተታ በግልጽ ተመልክቶ እያለ በዚሁ ሰነድ ላይ የተቀመጠውን ፊርማ ተከሣሹ በግልጽ አልካደውም በሚል የአመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ያቀረበው ክርክር የተከሣሽን የመልስ ይዘት ያገናዘበ አይደለም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2001 እና 2005 በተደነገገው መሰረት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረበውን ክስ ለማሰረዳት ካቀረባቸው ማስረጃዎች መካከል ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በተከሣሽ ፊርማ ተረጋግጦ ተሰጥቷል የተባለው የሰነድ ማስረጃ አንዱ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2007 መሰረት ይህንኑ የሰነድ ማስረጃ እንደማያውቀው ፊርማውም የእርሱ አለመሆኑን ክዶ ተከራክሯል፡፡ ይህ ሰነድም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ አይደለም፡፡ ይህንኑ ዓይነት ሰነድ አስመልክቶ በማስረጃነት የቀረበበት ወገን ጽሐፈቱን ክዶ የተከራከረ ከሆነ ሰነዱ ወይም ፊርማው በካደው ወገን የተደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመለየት የጽሕፈት ምርመራ እንዲደረግ ፍ/ቤቱ ማዘዝ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2008 ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሰረት የጽሕፈት ምርመራው ስራ እንዲከናወን ፍ/ቤቱ በክርክር ሂደት ለፌደራል ፖሊስ ፎረንሲክ ምርመራ ክፍል ትዕዛዝ ሰጥቶ በመጀመሪያው የምርመራ ውጤት በሰነድ የተቀመጠው ፊርማ በተከሣሽ የተደረገ አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይህ የምርመራ ውጤት ከታወቀ በኋላ የአሁን አመልካች የሰነድ ምርመራ ስራው በውጭ ሀገር እንዲደረግለት አመልክቶ ፍ/ቤቱ እንደ አመልካች ጥያቄ የሰነድ ምርመራው በውጭ ሀገር እንዲደረግ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ እንደገና በሌላ ጊዜ ይህ በውጭ ሀገር በኩል ሰነድ ተመርምሮ እንዲቀርብ በሚል ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ አግባብ አለመሆኑን ጠቅሶ ለማመሳከሪያነት የሚያገለግሉ ሰነዶች የሚመጡበትን ስፍራ እና እንዴት መምጣት እንዳለባቸው አመልካች ባመለከተው መሰረት በተጨማሪነት ከሚመጡት የፊርማ ምርመራ ማመሳከሪያ ሰነዶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጋር ተገናዝቦ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ በፎረንሲክ የምርመራ ክፍል ተመርምሮ ውጤቱ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በትዕዛዙም መሰረት የምርመራ ስራው ተጠናቆ ለሁለተኛ ጊዜ ፊርማው በተከሣሽ የተፈረመ አለመሆኑን የሚገልጽ ውጤት ቀርቧል፡፡

ከዚህ ከሰነድ ምርመራ ስራ ሂደት ጋር በተያያዘ አመልካች ያቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ አንዱ ፍ/ቤቱ ሰነዱ በውጭ ሀገር እንዲመረመር ካዘዘ በኋላ ዳኛ ለለተለያየ ብቻ እንደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያው ችሎት አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ መሻሩ ከፍ ያለ የስነ ስርአት ጉድለት የፈፀመበት ነው በዚህ ጉልህ ስህተት ምክንያት ፍትህ ተጓድሎብኛል የሚለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ይህ ክርክር ያስነሳውን ሰነድ በኢት/ያ የሚገኘው የፎረንሲክ ክፍል መርምሮ ትክክለኛ ውጤቱን ለመግለጽ ብቃት፣ ችሎታ እንደሌለው አልገለፀም፡፡ ይልቁንም ይህንኑ ዓይነት ሰነድ አስመልክቶ የምርመራ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የፌዴራል ፖሊስ ፎረንሲክ ክፍል ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን እንደ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰነድ ምርምራ ሥራ በሳይንሳዊ መንገድ እያከናወነ በሚሰጠው ማረጋገጫ መሰረት በአገሪቱ በሚከናወነው የወንጀልም ሆነ የፍ/ብሔር የፍትህ አስተዳደር የፍርድ ስራ ሂደት ሙያዊ ግዴታውን የሚወጣ ክፍል ነው፡፡

በዚህም ማረጋገጫ መሰረት ፍ/ቤቶች በቀረበላቸው ጉዳይ እንደ ህጉ ፍትህ ያገናዘበ ዳኝነት ሲሰጡ ቆይተዋል ይህ ሆኖ እያለ አመልካች የመጀመሪያ የሰነድ ምርመራ ውጤት በፎረንሲክ ምርመራ ክፍል ተደርጎ ለአመልካች ተቃራኒ የሆነ ውጤት መቅረቡን ካረጋገጡ በኋላ ይኸው መርማሪ ክፍል የዚህኑ ሰነድ ምርመራ ስራ በአጥጋቢ ሁኔታ ለማከናወን ለምን እንደማይቻል ከብቃት ከችሎታ ወይም ከገለልተኛነት የመነጨ አሳማኝ ምክንያትና ክርክር ባልተጠቀሰበት ሁኔታ በደፈናው አመልካች እንዳቀረበው ጥያቄ ፍ/ቤቱ ሰነድ በውጭ ሀገር ተመርምሮ ይቅረብ ማለቱን ችሎቱ በሌላ ጊዜ ተገንዝቦ ቀደም ሲል በክርክር ሂደት የሰጠው ትዕዛዝ ሥነ-ሥርዓታዊ ጉድለት የፈፀመበት መሆኑን በተገነዘበ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 207 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ለማረም ስልጣኑ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው አከራካሪ ነጥብ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ አመልካች የክርክር ነጥብ ፍ/ቤቱ ስነ-ሥርዓታዊ ጉድለት ፈፅመዋል፤ ስህተት አድርጓል እንኳ ቢባል ይህንኑ ስህተት በሰበር ማረም የሚቻለው ስህተቱ መሠረታዊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ስለመሆኑ በህገ- መንግስቱ አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 እና 22 ተደንግጓል፡፡

"መሠረታዊ" የሚለውም ህጋዊ ትርጉሙ ይኸው ስህተት ሳይታረም በመቅረቱ ምክንያት ውጤቱ ሊለወጥ ያልቻለ ወይም በተከራካሪው ወገን ፍትህ የማግኘት መብት ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ይህንኑ ጉዳይ እንደተመለከትነው ከላይ እንደተገለፀው አመልካቹ ድሮውንም ቢሆን በውጭ ሀገር ሰነዱ ይመርምርልኝ በማለት ያቀረቡት የጥያቄ አግባብነት በምክንያት በማስረጃ ሳይደገፍ የቀረበ በመሆኑ ይህም ጥያቄ የቀረበው የመጀመሪያው የምርምራ ውጤት ከታወቀ በኋላ ከመሆኑ ይህም ሆኖ እራሱ አመልካች ባመለከተው መሰረት የማመሳከሪያ ሰነዶች እንደገና ይምጡ ከተባለበት ስፍራ እና ሲመጡም በተከሳሹ እጅ ሳይሆን ሰነዱን ለማረጋገጥ ሥልጣን ባለው ገለልተኛ መንግስታዊ አካል አማካኝነት እንዲመጡ እና በድጋሚ የሰነድ ምርምራ እንዲደረግ ከታዘዙ በኋላ በቀረበ የማረጋገጫ ውጤት እንዲቀርብ የተደረገበት የጉዳይ አካሄድ እንደመሆኑ መጠን ይህ በስር ፍ/ቤት ተፈጸመ የተባለው ስነ ስርዓታዊ ጉድለት መሠረታዊ ስህተት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የሥር ፍ/ቤትም በዚሁ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት ብቻ ተመስርቶ ለጉዳዩ ፍርድ እንዲሰጥ ተቆጥሮ ሰበር ሰሚው ችሎት የፎረንሲክ የሰነድ ምርምራ ውጤት ስለማስረጃነቱ ያለውን የማስረዳት ብቃት ሙሉ በሙሉ እምነት የሚጣልበት አባሪ ማስረጃ ነው ወይስ አይደለም? በሚል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት የሰጠውን ትርጉም በማጣቀስ የቀረበው ክርክር ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው አይደለም የሥር ፍ/ቤቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለጉዳዩ በሙግት የክርክር ደረጃ ጊዜ የአሁን አመልካች ላቀረበው ክስ በማስረጃነት ዘርዝሮ ያቀረባቸውን የሰነድ የሰው ማስረጃዎች ሁሉ አንድ በአንድ በማየት ማስረጃዎቹ ለጉዳዩ ያላቸውን አግባብነት እና የማሳመን የማስረዳት ብቃት እየመረመረ እና እየለካ ማስረጃዎችን መዝኖ ፍርድ የሰጠበት ጉዳይ ስለመሆኑ የፍርድ ይዘት አስረጂ ነው፡፡

በከሳሽ የተቆጠሩት ምስክሮች እንደ ክሱ ጭብጥ ያስረዳሉ የተባለበትን ነጥብ አስመልክቶ ተከሳሹ ሰነዱን በኢት/ያ ሀገር ሊፈርም የማይቻልበትን ምክንያት በመጥቀስ ላቀረበው ክርክር አመልካች ሰነዱ የተደረገው ኢት/ያ ውስጥ ሳይሆን ጅቡቲ ሀገር ነው የሚል ክርክር አላቀረበም ይልቁንም ፍ/ቤቱ እንደ ክሱ ጭብጥ ምስክሮች በማስረዳት ረገድ የሚሰጡትን ቃል ታማኝነት ከተከሳሹ ክርክር ጋር አጣቅሶ ለመለካት እንዲያስችለው ተከሳሹ ወደ ኢትዮጵያ ሀገር መቼ መቼ እንደገባ ሁሉ ለሚመለከተው በኢምግሬሽን ጽ/ቤት ማረጋገጫ አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ ጅቡቲ ሀገር ነው የተደረገው እንዳይባልም ምስክሮች ወደ ጅቡቲ ሀገር ወጥተው አያወቁም ለሚለው የክርክር ነጥብም ማስተባበያ እንዳላቀርበ በስር ፍ/ቤቶች ፍርድ የተረጋገጠ የፍሬ ጉዳይ ነጥብ ነው፡፡ እንግዲህ የአሁን አመልካች በእያንዳንዱ የክርክር ደረጃ የተደረሰበትን ዳኝነታዊ ውጤት እየተከተለ በማፈራረቅ ከሚያቀርበው ክርክር አንፃር የሰው ማስረጃዎች ስለጉዳዩ ቃላቸውን ሳይሰጡ በመታለፋቸው የመደመጥ መብታችን ታልፎብናል የሚለው ክርክሩ ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

ስለጉዳዩ ያስረዳል በሚል የአሁን አመልካች ያቀረበውን የኢሜል እና ፋክስ መልዕክት ልውውጥ በማን የተደረገ ነው ይዘቱስ ለጉዳዩ ያለው አግባብነት ምንድን ነው፡፡ ክርክር ከቀረበበት የገንዘብ መጠን አንፃር በማስረጃነቱ ያለውን ተቀባይነት ሁሉ በመዳሰስ የማስረጃውን አግባብነት ተቀባይ እና የማስረጃነቱን ዋጋ አይቶና መዝኖ የሰጠውም ዳኝነት የማስረጃ አቀባበል ስርዓትን መሰረት ያደረገ ከመሆኑ በቀር ጉድለት ያለበት አይደለም፡፡

ከዚህም በቀር በተጨማሪ ማስረጃነት ቀርቦ እንዲታይልን ጠይቀን ጉዳዩን በተጨማሪ ማስረጃነት የማስረዳት ዕድሉን ተነፍገናል በማለት ያቀረቡትን ክርክር ይቅረብ ከተባለው የማስረጃ ስርአት አንፃር ሲታይም ሁለቱን ወገኖች ያለያያቸውን ነጥብ ለይቶ ለመወሰን የማስረጃነት አግባብነትና ብቃት የሌለው መሆኑን ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍርዱ ምክንያት ሰጥቶ ያለፈው በመሆኑም በይግባኝ ሰሚነቱ ስልጣን ስር የወደቀውን በተከራካሪ ወገን የሚቀርብ ማስረጃ ለጭብጡ አመሰራረት ሆነው የተያዙትን ፍሬነገሮች በማስረዳት በኩል ማስረጃው በትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ያለውን ዋጋ ሁሉ በማየት የሰጠው ዳኝነት በመሆኑ የተጨማሪን ማስረጃን አቀባበል ስርዓት የጣሰ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከሁሉም በላይ ክርክር እንዳስነሳው ታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በተከሣሽ ተደረገ እንደተባለው የፅሑፍ ማስረጃ ላይ ተከሣሹ ይህንኑ መተማመኛ ሰነድ የፈረመው ከሳሹ በተለያዩ ጊዜ ተከሣሹ ላጋጠመው የገንዘብ እጥረት ማቃለያ ሲባል “7,079,604.86 ያበደሩኝ መሆኑን ከሰነዶች ያረጋገጥኩ በመሆኑ ወደፊትም ለንግድ ስራዬ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሚያመጡልኝ ገንዘብ አባሪ ሰነዶች ኮፒ ተደግፎ ሲመጡልኝ የሚል ይዘት እንዳለው በግልፅ የተመለከተ በመሆኑ ከሳሹ የዚያን ማስረጃ መኖርና አለመኖር በስር ፍ/ቤት ሆነ በይግባኝ ሰሚው በትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ መስፈርት እነዚህን ደጋፊ ሰነዶች በሙሉ ወይም በከፊል በማቅረብ እንዲታይለት በማድረግ ከማስረጃው አግባትነትም ሆኖ የማስረጃ ብቃት አንፃር ጉዳዩ ታይቶ እንዲወሰን ማድረግ እየቻለ ይህ ዓይነት ሰነድ በየትኛውም ደረጃ ባለው ፍ/ቤት አለማቅረብና ለማቅረብ የአለመጠቀሱ ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ዳኝነት አግባብነት የሚያመለክት እንጂ ከጉዳዩ አካሄድ አኳያ የመከራከር መብቱ የተገደበ መሆኑን አያሳይም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 78275 ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ክሱ ለቀረበበት ገንዘብ የአሁን ተጠሪ ለአመልካች ለመመለስ ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ ግዴታ የለበትም መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 77983

መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1. አቶ እንድሪስ አደም - የቀረበ የለም

2. ወ/ሪት ዚነት እንዲሪስ
3. አቶ አንዋር እንድሪስ
4. አቶ ካሚል እንድሪስ
5. ወ/ሮ ብርቱካን በላይ

ጠበቃ ወርቁ አበበ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስናቀች ጥላሁን ጠበቃ ይልማ አቻሜ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጋብቻ ውጤት በሆኑ ንብረቶች ላይ በአንደኛው ተጋቢ የተደረጉ የሽያጭ ውሎች የሚፈርሱበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት ከሣሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ናቸው፡፡ ተከሣሽ ደግሞ የአሁኑ አመልካቾች ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካቾች በመሰረቱት ክስ ከአሁኑ አንደኛ አመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው ቆይተው በመካከላቸው በተፈጠረው ያለመግባባት ጋብቻው እንዲፈርስ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው የጋብቻ ውጤት የሆኑት ንብረቶችን ለማስከበር የፍርድ ቤት ትእዛዝ ይዘው ወደሚመለከታቸው አካላት ሲሄዱ ንብረቶቹ በሶስተኛ ወገኖች ስም የሚታወቁና በሽያጭ የተላለፉ መሆኑን የእግድ ትእዛዙን ይዘውላቸው የሄዱባቸው አካላት እንደገለፁላቸው ንብረቶቹን ባል የሆኑት አንደኛ አመልካች ከሕግ ውጪ ለብቻ ልጆቻቸው ከተጠሪ እውቅና ውጪ ያስተላለፉ መሆኑንና የተላለፉትን ንብረቶችንም፡-

- በአዲስ አበባ ከተማ በአ/ክ/ከተማ በቀበሌ 19/20 የቤት ቁጥር 816 በሆነው ቤት በ1ኛ አመልካችና ከወ/ሮ ብርቱካን በላይ ጋር፣
- በአዲስ አበባ ከተማ በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 01/02 በሚገኘውና ቁጥሩ KH-B2 B104 በሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት ከወ/ሪት ዜኒት ኢድሪስ ጋር፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 2 የሚገኘውና ቁጥር GEB1 Co/04 ከሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት ከአቶ አንዋር ኢድሪስ ጋር፣
- የሰሌዳ ቁጥር 2-52682 በሆነችው የቤት መኪና ላይ ከወ/ሪት ዜኒት ኢድሪስ ጋር፣
- የሰሌዳ ቁጥር 3-46778 ኢት በሆነው የጭነት መኪና ከወ/ሮ ዜኒት እንድሪስ ጋር
- የሠሌዳ ቁጥር 2-42462 አ.አ በሆነችው የቤት መኪና ከካሜል ኤድሪስ ጋር እና

የሰሌዳ ቁጥር 3-06469 የሆነ ከባድ መኪና ከአቶ አንዋር ኢድሪስ ጋር በተደረጉት የማስመሰያ የሽያጭ ውል እንደተላለፉ በገዥነት የተመዘገቡት የትኞቹ የባል ልጆች እንደሆኑ ለይተው ስማቸውን ገልፀው በንብረቶቹ የተደረጉ ውሎች እንዲፈርሱና ንብረቶቹ በቀድሞው ሁኔታ እንዲመዘገቡ እና ውጪ ኪሣራ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ 1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ከተጠሪ ጋር ጋብቻ መኖሩን አምነው ተፈጠረ የተባለውን ያለመግባባት ወይም ጠብ ግን እንደማያውቁትና ተጠሪ ጋብቻው እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ክስ መሥርተው ያሉ መሆኑን ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ንብረቶች በሽያጭ ውሉ ለሌሎች አመልካቾች ያስተላለፉት ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ወደ መጥፎ ሁኔታ ከመቀየሩ በፊት ከተጠሪ በቁጥር 5904/13/2000 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት መሆኑንና የሽያጭ ውሎቹ መደረጋቸውንም ተጠሪ ያውቁ እንደነበር ገልፀው የሽያጭ ውሎችም ሊፈርሱ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ 2ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ አመልካቾች በጋራ በሰጡት መልስም ለክርክሩ ምክንያት የሆኑነት ንብረቶችን ተጠሪ በወኪላቸው አንደኛ አመልካች አማካኝነት በሽያጭ ውሉ ላይ ፈቃዳቸውን የሰጡ በመሆኑ የተሻሻለውን የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 68 እና 69 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ክርክር ሊያደርጉባቸው እንደማይችሉ ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ 4ኛ አመልካች በበኩላቸው በግል የመከላከያ መልሣቸውን ያቀረቡ ሲሆን በአቀረቡት መልስም አመልካቹ ገዙ የተባለውን መኪና ከተጠሪ ሕጋዊ ወኪላቸው የአሁኑ አንደኛ አመልካች የገዙትና የሽያጭ ውሉ ገንርው የወኪሉ ልጅ በመሆናቸው ብቻ ሊፈርስ እንደማይገባ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ንብረቶቹ የጋብቻ ውጤት መሆናቸውና የአሁኑ አንደኛ አመልካች ከተጠሪ በተሰጣቸው ውክልና መነሻ ገቢና መተዳደሪያ ለሌላቸው ለአሁኑ አንደኛ አመልካች የብቻ ልጆች ለሆኑት ከተራ ቁጥር ሁለት እስከ ተራ ቁጥር አምስት ድረስ ለተጠቀሱት አመልካቾች መሸጡ መረጋገጡንና አንደኛ አመልካች አንድ ወኪል በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ አክብረው ሽያጩን አከናውነዋል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከክርክሩ መገንዘቡና እንዲህ አይነት የወኪል ተግባር ደግሞ ሕጋዊ ያለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 2208፣ 2209 እና 2188 ድንጋጌዎች እንደሚያስረዱ በመጥቀስ በንብረቶቹ ላይ የተደረጉት ሽያጮች እንዲፈርሱና ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመላክቾች ቅር በመሰኘት የአሁኑ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱት በይ/መ/ቁጥር 70423 የአሁኗ 5ኛ አመልካች ደግሞ በይ/መ/ቁጥር 70623 ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ መዝገቦችን አጣምሮ ከተመለከተና ከመመርመረ በኋላ አከራካሪ ንብረቶችን አንደኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር ወደ አለመግባባት ከገቡ በኋላ መተዳደሪያ ለሌላቸው ተማሪ ለሆኑት አንዳንዶቹ ለአቅመ አዳም እንኳን ላልደረሱ ልጆቻቸው በአፋጣኝ የሸጡ መሆናቸውን መገንዘቡን በውሳኔ ላይ ከአሰፈረና ይህም አንደኛ አመልካች ንብረቶቹን ከቅን ልቦና ውጪ ለብቻቸው ለመጠቀም በማሰብ ያደረጉት ዘዴ መሆኑን ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ መሆኑን ጠቅሶ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ተገቢ ነው ብሎ ሙሉ በሙሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንፅንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አንደኛ አመልካችና ተጠሪ ወደ አሜሪካ ሀገር ለመሄድ ለመኖር በማሰብ በአደረጉት ስምምነት መሰረት ተጠሪ ከአመልካቹ ውክልና ሰጥተው ንብረቶቹን አመልካች በውክልና ስልጣናቸው መሸጣቸው የማይካድ ሀቅ ሆኖ እያለ ሐቁ ተገቢው ጭብጥ ተይዞ በተገቢው የክርክር አመራርና ማስረጃ ሳይጣራ ንብረቶቹ ለአንደኛ አመልካች ልጆች በመሸጣቸው ምክንያት ብቻ የሽያጭ ውሎቹ እንዲፈርሱ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው የተጠሪ ጠበቃ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎች እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳይ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አንደኛ አመልካችን ተጠሪ ለረዥም አመታት በባልና ሚስት ሲኖሩ በሽያጭ ውሉ ተላለፉ የተባሉትን ንብረቶችን በጋራ ያፈሩ መሆኑን፣ በመካከላቸው በተፈጠረው ያለመግባባትም ተጠሪ የፍቺ ጥያቄ ለፍርድ ቤት አቅርበው ጉዳዩ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ እንዳለ ንብረቶችን ለማስከበር እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ንብረቶቹ ከፍቃዳቸው ውጪ መሸጣቸውን አውቀው ሽያጭ ውሎቹ እንዲፈርሱላቸው ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነውን ውሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸውን፣ ንብረቶቹን ከአንደኛ አመልካች ገዙ የተባሉት የአሁኑ ከተራ ቁጥር ሁለት እስከ አምስት ያሉት አመልካቾች ደግሞ የአሁኑ የብቻ ልጆች ሆነው የራሳቸው መተዳደሪያ የሌላቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ለአቅመ አዳም እንኳን ያልደረሱ መሆኑን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በውሳኔ ላይ መግለፁን፣ ንብረቶቹን የተጠሪ ባል የሆኑት የአሁኑ አመልካች ለልጆቻቸው ለመሸጥ ስልጣን ያገኙት ከተጠሪ ግንቦት 25 ቀን 2005 ዓ/ም በተሰጠው ስልጣን ቢሆንም ንብረቶቹ የተሸጡት ከተጠሪ ጋር ያለመግባባት ከተፈጠረ በኋላ በአፋጣኝ ስለመሆኑ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ማረጋገጡን ነው፡፡ አንደኛ አመልካች በዚህ የክርክር ደረጃ አጥብቀው የሚከራከሩት ከተጠሪ ጋር አሜሪካን አገር ለመኖር በማሰብ ንብረቶቹ መሸጣቸውንም ተጠሪ ያውቁ እንደነበር ገልፀው ተከራክረው ከአመልካች ልጆች ውስጥ የራሳቸው ገቢና መተዳደሪያ ያላቸው ሁሉ እያሉ ይሔው ሳይጣራ ተገቢ ያልሆነ የክርክር አመራር በስር ፍ/ቤት ተከናውኖ ውሳኔ መሰጠቱ ሐቁ እንዳይወጣ ሆኗል፣ ተጠሪ ባሁኑ ጊዜ የሚኖሩት አሜሪካን አገር መሆኑም ከአመልካቹ ጋር የነበራቸውን የቀደመ ሐሳብ የሚያረጋግጥ ነው በሚል ሲሆን ሌሎች አመልካቾች ደግሞ ሽያጩ በተጠሪ እውቅና የተደረገ ሆኖ እያለ ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ ያለግባብ ነው በሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው ችሎት ሲሆን ንብረቶቹ አንደኛ አመልካችና የአሁኗ ተጠሪ በመካከላቸው ያለመግባባት ከተፈጠረ በኋላ በአፋጣኝ ለአሁኑ አንደኛ አመልካች ልጆች ለሆኑትና የራሳቸው መተዳደሪያ ገቢ ለሌላቸው ጭምር መሸጣቸው ከክርክሩ ሂደት መገንዘቡን በውሳኔ ላይ አስፍሯል፡፡ ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍሬ ነገር ድምዳሜ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከደረሰበት ድምዳሜ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ከተሰጠው የመሰረታዊ ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስህተት የማረም ስልጣን አንፃር ሲታይ የበታች ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ድምዳሜ የያዙት ጉዳይ የሚለወጥበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አንደኛ አመልካች ንብረቶቹን ከተጠሪ ጋር ያለመግባባት ከተፈጠረ በኋላ በአፋጣኝ መሸጣቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠ ንብረቶቹን ሸጥኩ የሚሉበት ምክንያት አሜሪካን አገር ለመኖር ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ስምምነት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በማስረጃ እንዲነጥር ያለመደረጉ ለጉዳዩ አወሳሰን መሰረታዊ ጠቀሜታ የሌለው ነው፡፡ በአንድ የፍትሃ ብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገሩ እንዲነጥር የሚደረገውም በማስረጃ የሚነጥረው ፍሬ ነገር ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136፣ 137፣ 138፣ 246፣ 247፣ 248፣ 256፣ እና ሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን ከሚደነግጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ማንኛውም የክርክር ነጥብ ሁልጊዜ በማስረጃ እንዲነጥር የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡ ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሆኖ ተከራከሪ ወገኖች በተለያዩባቸውና ዳኝነት በሚሹ ነጥቦች ላይ ከሚሰማ በስተቀር በማንኛውም ፍሬ ነገር ላይ እንዲሰማ የግድ የሚል የማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን ደንብ የለም፡፡ ከሁሉም በላይ ማስረጃ እንዲሰማ የሚፈልግ ተከራካሪ ወገን ማስረጃው የሚሰማበት ነጥብ ለይቶ የማስረጃውን አይነትና የሚገኝበትን ቦታ ሁሉ በመጥቀስና በእጁ ላይ ያለውን ማስረጃውም አያይዞ ማቅረብ እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 223፣ 234፣ 137(3)፣ 145፣ 256 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም 1ኛ አመልካች በስር ፍ/ቤት የመከላከያ ማስረጃ ጥር 25 ቀን 2003 ዓ/ም ዘርዝረው ሲያቀርቡ በመልስ ማመልከቻው ውስጥ የዘረዘራቸው ፍሬ ነገሮችን የሚያውቁና የሚያስረዱ ሶስት የሰው ምስክሮችን ዘርዝረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ምስክሮቻቸው የተሰሙ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ የማያሳይ ቢሆንም ከላይ እንደተገለጸው ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ንብረቶቹ የተሸጡበት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ወደ ያለመግባባቱ ከገቡ በኋላ በተፋጠነ ሁኔታ መሆኑ ከረጋገጡ አንፃር ሲታይ የአመልካች ምስክሮች ያለመሰማት መሠረታዊ የመሰማት መብትን አጣብቂል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ የውክልና ውሉን መሠረት አድርገው ክስ ያለመመስረታቸውም በክርክሩ ሂደት አመልካቾች በመከላከያነት ክርክር እስካቀረቡ ድረስ ፍ/ቤቱ ውክልናውን ተከትሎ የተፈፀመውን ተግባር ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን ከመመርመርና ተገቢውን ዳኝነት ከመስጠት የሚያገደው አይደለም፡፡ ይልቁንም ውክልናው መኖሩን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን በመለየት ዳኝነት መስጠታቸውን የክርክሩ ሒደት የሚያሳይ በመሆኑ ተጠሪ ክስ ሲመሰርቱ ውክልናን ጠቅሰው ያለማቅረባቸው በክርክር አመራሩና ዳኝነት አሰጣጥ ውጤት ላይ መሠረታዊ የሕግ ግድፈት አስከትሏል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ሌላው አንደኛ አመልካች ንብረቶቹን ለብቻ ልጆቻቸው የሸጡ መሆኑን ሳይክዱ አንድ ተወካይ ሊወጣ የሚገባውን ሕጋዊ ግዴታ ተወጥተው ንብረቶቹን የሸጡ ስለመሆኑ ጠቋሚ ሊሆኑ የሚችሉትን የንብረቶቹን የገበያ ዋጋ ለንጽጽር እንኳን ጠቅሰው እስከዚህ ሰበር ደረጃ በአቀረቡት ክርክር ያለመጥቀሳቸው ሲታይም የአመልካቾች የማስረጃ ያለመሰማት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል አስፈላጊ ፍሬ ነገር አልተሟላም ለማለት የማያስደፍር መሆኑን የሚያስገነዝብ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

አንደኛ አመልካች ንብረቶቹ ተሸጡ በተባለባቸው ጊዜያት የተጠሪ ባልና ተወካይ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ተወካዩ ከወካዩ ጋር የሚያስተሳስረው ግንኙነት ውስጥ ጥብቅ የሆነ ቅን ልቦና ሊኖረው እንደሚገባ በፍትሐብሄር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ ቁጥር 2208(1) ስር ተደንግጓል ። ከዚህ በተጨማሪ ተወካዩ የተወካይነት ሥራውን የሚፈጽመው በተለይ የወካዩን ጥቅም ሊሰጥ በሚችልበት መንገድ ብቻ መሆን እንዳለበት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2209 (1) ድንጋጌ ያሳያል። ከዚህም በተጨማሪ ተወካዩ በውክልና ሥራው ላይ በሚገኝባቸው ጊዜዎች ሁሉ በውክልና በተሰጠው አደራ አንድ መልካም የቤተሰብ አባት ቤተሰቡን ለመጠበቅ እንደሚያደርገው ሁሉ በትጋትና በጥንቃቄ መጠበቅ ያለበት መሆኑን በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2211(1) ስር በግልጽ ተደንግጓል። አንደኛ አመልካች ከላይ በጠቀስናቸው አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት ያልተወጡ መሆናቸውን ከዚህ በሚቃረን አኳኋንና የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2187(1) ባላገናዘበ መልኩ ለብቻ ልጆቻቸውና የራሳቸው የሆነ መተዳደሪያ ለሌላቸው ከተራ ቁጥር ሁለት እስከ አምስት ለተጠቀሱት አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለመግባባት ከተፈጠረ በኋላ በአፋጣኝ አከራካሪ ንብረቶችን መሸጣቸው ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመወሰን ሥልጣን ባላቸው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ በሆነው ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል። ለአንደኛ አመልካች በውክልና ከተጠሪ የተሰጣቸውን አደራ በመጣስና ንብረቶቹን ከጋብቻ የጋራ ውጤት ከመሆን ለማሸሽ ክፉ ልቦና የፈፀሙት የንብረት ሽያጭ ስለመሆኑ ንብረቶቹ በአፋጣኝ መሸጣቸው የሚያስገነዝብ መሆኑን ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከአረጋገጠ ደግሞ የአንደኛ አመልካች ተግባር በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2188(1) ድንጋጌ መሠረት የጥቅም ግጭት መኖሩን የሚያሳይ ነው። ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር በተጠቀሱት ሕጋዊ ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99766 ግንቦት 01 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 70423፣70632 ታህሳስ 24 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ጸንቷል።
2. በአከራካሪ ንብረቶች የተደረጉ ውሎች እንዲፈርሱ፣ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 21 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ ብልናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 81275

ሰኔ 5 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘምዘም ወንድሙ - ከጠበቃ አትሙት አሰፋ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዲሰቡር አብዱሰመድ - አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ተመሳሳይ የሆኑ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ክሶችን በአንድ ፍ/ቤት በመቅረባቸው የተነሳ አንደኛው ወገን ይህን ተገንዝቦ ጉዳዮች ተጣምረው እንዲታዩለት ለፍ/ቤቱ ባመለከተ ጊዜ ፍ/ቤቱ ሊፈፅመው የሚገባውን ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፤ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ የሆኑበትን የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺ) የብድር ገንዘብ ክርክር ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቁራ ምድብ ችሎት ተመልክቶ በኮ/ቁ 37363 በሆነው መዝገብ ላይ በቀን 25/06/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ላቀረቡት የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ) የገንዘብ ብድር ክስ መሰረት አድርገው የጠቀሱት በሁለቱም መካከል ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደርጓል የተባለውን የገንዘብ ብድር ውል ሲሆን በዚህ ውል ተበዳሪ ገንዘቡን እስከ መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ/ም ድረስ በመመለሱ በን/ስ/ላፍቶ ክ/ከተማ ቀበሌ 02 የሚገኘውንና በቤት ቁጥር B6/14 የተመዘገበውን የኮንዶሚኒየም ቤት በመያዣነት አስይዘዋል፡፡ ይሁን እንጂ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ገንዘቡን አልከፈለም፡፡ ስለሆነም የብድር ገንዘቡን ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ህዳር 05 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ የክስ ምክንያታቸውን ገልፀው ዳኝነት የጠየቁበት ሲሆን፤

የአሁን አመልካችም በተከሳሽነታቸው በዚህ የብድር ውል በተባለው ሰነድ ሊገደዱ የማይችሉበትን የፍሬ ነገርና የህግ ክርክር በመጥቀስ ዝርዝር መልሳቸውን ሰጥተውበታል፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች መስከረም 02 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ለዚሁ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቁራ ምድብ ችሎት በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻ የኮ/ቁ 45441 የሆነውን መዝገብ አስከፍተው በኋላም መጋቢት 06 ቀን 2002 ዓ/ም የተሻሻለ ክስ እንዲቀርብ ተደርጎ የክርክሩ መሰማት በዚሁ ፍ/ቤት ቀጥሏል፡፡ የአሁን አመልካች በኮ/ቁ 45441 በሆነው መዝገብ ላይ ባቀረቡት ክስ የጠቀሱት ዝርዝር

ምክንያት የአሁን ተጠሪ ከላይ በአድራሻና በቁጥር የተጠቀሰውንና በዕዳ የደረሰኝን የኮንዶሚኒየም ቤት አስመልክቶ በማስላት ሐምሌ 12 ቀን 1998 ዓ/ም እና ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለውን የሽያጭ ውል፤ ሐምሌ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለውን የሥጦታ ውል እና ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለውን የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) የብድር ውል ያስፈረመኝ ስለሆነና እነዚህም ውሎች በህግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል ለመያዝ የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች አሟልቶ የተደረገ ባለመሆኑ ሊፈርሱ ይገባል የሚል ነው፡፡

ለዚህም ክስ የአሁን ተጠሪ የዕሁፍ መልስ የማቅረብ መብቱ የታለፈ ቢሆንም፤ ክርክር በሚሰማበት ዕለት ቀርቦ ከአሁን አመልካች ጋር ያደረጉት የብድር ስምምነት በህግ ፊት የፀና ነው የሚሉበትን ምክንያት በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡

እነዚህ ሁለት ክሶች በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ፍ/ቤት ቀርበው እየተሰሙ ባሉበት ጊዜ በአሁን አመልካች እነዚህ ተመሳሳይ ጭብጥ የሚያስነሱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ተጣምረው ሊታዩ ይገባል በሚል በማመልከታቸው ፍ/ቤቱ በኮ/መ/ቁ 45441 በሆነው መዝገብ ላይ ተከሳሽ የነበሩትን የአሁን ተጠሪን ምስክሮች ዝርዝር ቃል ከተቀበለ በኋላ በቁራ ምድብ 1ኛ ፍ/ብ/ችሎት እየታዩ የሚገኘው የኮ/ቁ 37363 የሆነው መዝገብ ቀርቦ ከመ/ቁ 45441 ጋር ተጣምሮ እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቶበታል፡፡ ሆኖም የኮ/መ/ቁ “37363” ተብሎ መፃፍ ሲገባው የመጨረሻዋ “3” የምትለው ቁጥር ተሰርዞና ተደልዞ “6” በሚል በመፃፉ ምክንያት እንደ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ይኸው መዝገብ እንዲጣመር አልተደረገም፡፡ በዚህም የተነሳ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ሁለቱንም ጉዳዮች ጐን ለጐን ሲያይ ከቆየ በኋላ በኮ/መ/ቁ 37363 በሆነው መዝገብ የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአሁን ተጠሪ ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገው የብድር ውል መሰረት ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ለአበዳሪ ለአሁን ተጠሪ የመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት ሲወስን፤ በኮ/መ/ቁ 45441 በሆነው ጉዳይ ደግሞ ይኸው ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለው የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) የብድር ውል እና የመያዣ ውል በህግ ፊት የፀና ውል ሆኖ ባለማግኘቱ ፈራሽ ነው የሚለውንም ጭምር ያካተተ አስቀድሞ ከሰጠው ፍርድ ጋር በተቃራኒ አኳኋን ሰኔ 10 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡

በዚህ አኳኋን የተቃረነ ፍርድ መስጠቱን እንደተረዳ በኮ/መ/ቁ 45441 የሆነውን መዝገብ ከተዘጋ በኋላ እንደገና በማንቀሳቀስ ቀደም ሲል በክርክር ሂደት ተከስቶ የነበረውን የመዝገብ ቁጥር አፃፃፍ ስህተት ታርሞ ቁጥር “6” በሚል የተፃፈው የመዝገብ ቁጥር የመጨረሻ አኃዝ ቁጥር “3” በሚል ሊስተካከል ይገባል በማለት በሰጠው እርስ በእርሱ የተቃረነ ፍርድ ላይ አንዳችም ውጤት ሊያስከትል የማይችል ትዕዛዝ ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ/ም እንደሰጠበትም ከሰጠው የትዕዛዝ ዳኝነት ግልባጭ ተረድተናል፡፡

የአሁን አመልካችም ተከሳሽ በነበሩበት በኮ/መ/ቁ 37363 በሆነው መዝገብ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረባቸው ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ተመልክቶ በመ/ቁ 119226 በቀን 04/08/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ይኸው በኮ/መ/ቁ 37363 የተሰጠው ፍርድ በፍሬ ነገርም ሆነ በህግ ረገድ ጉድለት የተገኘበት አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ ምክንያት የሆነውም በዚህ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉበትን የክርክር ነጥቦች በመጥቀስ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ሲሆን የአሁን ተጠሪም ይኸው ፍርድ ህጋዊ መሰረት ያለው ነው ሊፀና ይገባል በማለት ከእነምክንያቱ ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

እንግዲህ የዚህ ጉዳይ መነሻና አመጣጡ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻና ምክንያት የሆነው ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ግራ ቀኙ አድርገውታል የተባለው የብድር ውል ስምምነት ህጋዊ ውጤትን ያስከትላል ወይስ አያስከትልም? የሚለውን አከራከሪ ነጥብ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የመሰረተ ህጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን ከማየታችን በፊት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 347(4) እና 182(3) እንደተደነገገው በቅድሚያ ከዚሁ ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ ከተባለው የብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ) የብድር ውል እና የመያዣ ውል በመነሳት እነዚሁ ሁለት ተከራከሪ ወገኖች በከሳሽነትና በተከሳሽነት በመፈራረቅ አንድ ዓይነት የፍሬ ነገርና የህግ ክርክሩ ጭብጥ በሚያስነሳ ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በአንድ ፍ/ቤት በተለያዩ ክሶች እየተከራከሩ የነበሩ መሆኑ ሲታወቅ በስር ፍ/ቤቶች ሊከተሉት የሚገባው ስርዓት ምን ሊሆን ይገባ ነበረ? የሚለው ጭብጥ ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንደዚህ ባለ ተመሳሳይ ጉዳይ ተመሳሳይ የሆኑ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ፍ/ቤት በተለያዩ ክሶች መከራከራቸው ሲታወቅ ጉዳዩን በመጀመሪያም ሆነ በይግባኝ ደረጃ የተመለከቱት ፍ/ቤቶች እንዚህ ሁለት ጉዳዮች ተጣምረው እንዲታዩ ካላደረጉ በቀር በአንድ ጉዳይ ላይ በተለያዩ አካኋን ፍርድ ሊሰጥ ስለሚችልና በተመሳሳይ ተከራከሪ ወገኖች በሚከራከሩበት ተመሳሳይ ጉዳይ አንድ ፍ/ቤት በተለያዩ ክስ ተቀብሎ በማስተናገዱ ምክንያት የተለያየ ፍርድ መስጠቱ በየትኛውም መለኪያ ቢሆን ፍትሐዊ እና ህጋዊ ካለመሆኑም በላይ በዚህ አካኋን የተሰጡትንም ፍርዶች ለማስፈፀም አዳጋች ሆኖ ይገኛል፡፡

ይህንንም በመገንዘብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ እንደዚህ ያለ ሁኔታ እንዳያጋጥም ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ ይኸውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8(1) ላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ነገር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ምላሽ የሚያስፈልገውም የሥረ - ነገር ጭብጥና ተከራከሪ ወገኖችም ተመሳሳይ ሆነው ጉዳዩ በቅድሚያ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ቀርቦ በመሰማት ላይ እያለ ሌላው ፍ/ቤት ይህንኑ አንድ የሆነውን ጉዳይ ተቀብሎ ለመከራከር አይችልም በማለት ተመሳሳይ የሆነው ጉዳይ በአንድ ፍ/ቤትም ሆነ በሌላ ፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ክርክሩ ሊቀጥል እንደማይገባ አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ደንግጓል፡፡ ምናልባትም ይኸው ሥርዓት ሳይፈፀም ተመሳሳይ የሆነውና በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች የተነሳው ጉዳይ በተለያየ ክስ አማካኝነት በተለያየ ፍ/ቤት ቀርቦ በመሰማት ላይ የሚገኝ መሆኑ ከታወቀም የክርክሩ ተነጣጥሎ መታየት ለዳኝነት ሥራ አመራር ወይም ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ የማይመች ወይም የማይገባ ሆኖ ስለሚገኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 11 መሰረት ተጣምሮ መታየት እንደሚኖርበት ወይም በቁጥር 244 እና 245 በተነገረው መሰረት አስፈላጊው ብይን ሊሰጥበት እንደሚገባም ተከታይ የሆነውን የማረሚያ ሥርዓት አበጅቷል፡፡

ከዚህም ድንጋጌ ሥር ከተመለከተው "... ለዳኝነት ሥራ አመራር..." የማይመች..." የሚለው ሐረግ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማው አንድ ክርክሮችን ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአፋጣኝ እንዲታዩ በማድረግ ጊዜን፣ ጉልበትን እና ገንዘብን ለመቆጠብ እንደመሆኑ መጠን ተመሳሳይ ጉዳይ በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአንድ ፍ/ቤትም ሆነ በተለያዩ ፍ/ቤቶች ማቅረብና ቀርቦ እንዲታይ ማድረጉ ከዚሁ መሰረታዊ ከሆነው የሥነ-ሥርዓት ህጉ ዓላማ ጋር የማይስማማ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን፤ "... ወይም ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ የማይመች ወይም የማይገባ...." የሚለው ሐረግ ደግሞ ተለያይተው ክሶች የመቅረባቸው ውጤት በክርክር አመራር አመቺነት ወይም ጊዜን ወጭንና ድካምን በማስቀረት ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በመጨረሻ በሁለቱም ክሶች ላይ የሚሰጠው ፍርድ ከቶውንም ቢሆን ተመሳሳይ ሊሆን ስለማይችል ውጤቱ ትክክለኛ ፍርድ ሊሆን የማይችል መሆኑን የሚያመለክት ነው።

የዚሁ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 8 ን ድንጋጌ ሙሉ ለማድረግ በተቀመጠውም በቁጥር 11 ላይ የተመለከተውም ድንጋጌ ይዘትና ሀሳብ ይህንኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉን ዓላማ የተንተራሰ ነው። በተለይም በቁጥር 11(1) ላይ ከአንድ ጉዳይ የመነጩት ክሶች በተመሳሳይ ተከራከሪ ወገኖች በአንድ ፍ/ቤት የቀረቡ መሆኑ ከተረጋገጠ የክርክሩ ደረጃ ምንም ይሁን ምን ክሶች ተጣምረው መታየት እንደሚገባቸው በግልፅ ያመለከተ ሲሆን፤ በቁጥር 11(2) ላይም ".... ማስረጃ መቀበልና ማከራከር ከመጀመሩ በፊት..." በሚል መቼ መጣመር እንደሚገባቸው ጊዜን አስመልክቶ የተቀመጠው ሐረግ በተቻለ መጠን ተከራከሪ ወገኑ ይህንኑ እንደተረዳ ወዲያውኑ ማቅረብ ያለበት መሆኑን ለማስገንዘብ ነው ከሚባል በቀር የአሁን ተጠሪ በዚህ የሰበር ደረጃ ባቀረቡት የፅሁፍ ክርክር እንደገለጹት ምንም እንኳ ክሶች ተለያይተው የቀረቡ መሆኑ ቢታወቅም በሁለቱም ክሶች ላይ የማስረጃ መሰማቱ ሥራ ካለቀ ሁለቱም ጉዳዮች ተነጣጥለው ለየብቻ ታይተው ፍርድ እንዲሰጣቸው ሥርዓቱ ይፈቅዳል ከሚለው ትርጉም የሚያደርስ አይደለም።

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8 እና 11 መሰረት የሚነሱት ክርክሮች በይዞታቸው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ሥር የሚታቀፉ በመሆናቸው መቼ መቅረብ እንዳለባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 234 እንደተደነገገው ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት የመከላከያ መልስ በሚቀርብበት ጊዜ ለመሆኑ መደንገጉና፤

ሆኖም በዚህ ጊዜ መቅረብ ሲገባቸው ያልቀረቡት የመቃወሚያ የክርክር ነጥቦች በይዞታቸው ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያሰናክሉ ሆነው ከተገኙ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሊቀርቡ እንደሚችሉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(3) ከተደነገገው አንፃር የቁጥር 11(2) ድንጋጌ ይዘት ሲታይ ከላይ የተመለከተውን ትርጉም የሚደግፍ ነው።

በዚህ ጉዳይ ሁለታችንም በሌላ ፍ/ቤት እየተከራከርን እንገኛለን ይህ ለሁለተኛ ጊዜ በዚያው ፍ/ቤትም ሆነ በሌላ ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ከዚህ በፊት ቀርቦ እየተከራከርን ከምንገኝበት ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ስለሆነም ክርክሩ ሊቀጥል አይገባም ወይም ተጣምሮ ሊታይ ይገባዋል የሚለው በቁጥር 8 ሆነ 11 መሰረት የሚቀርበው ክርክር ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ያልቀረበ ስለሆነ ክርክርን በአፋጣኝ እና በአነስተኛ ወጭ ለማየት አያስችልም ስለሆነም ጊዜው ካለፈበት በኋላ የቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም የሚያሰኝ የክርክር ዓይነት ሳይሆን ይህ ዓይነት ክርክር መኖሩ እየታወቀ ከታለፈ ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የማያስችል በመሆኑ ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ እንዲቀርቡ ከሚድረጉት የመቃወሚያ ክርክሮች ዘርፍ የሚመደብ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ቢሆን እነዚህን ሁለት ክሶች ይዘታቸውን ተመልክቶ ተጣምሮ እንዲታዩ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ የሰጡበት እንጂ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ያልቀረበ ስለሆነ ሊጣመሩ አይገባም በሚል ዳኝነት አልሰጡበትም፡፡

በመዝገብ አፃፃፍ ስህተት ሁለቱም ጉዳዮች በተናጠል ታይተው የተለያየ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ እራሱ የሰጠውን ፍርድ እንደይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቱ የመሻር ስልጣን የሌለው በመሆኑ በክርክር ሂደት በመዝገብ አፃፃፍ ጊዜ የተፈፀመውን የቁጥር አፃፃፍ ዝንፈት በማረም ተገድቧል፡፡

ሆኖም የሥር ፍ/ቤት በቁጥር አፃፃፍ ስህተት ምክንያት እንጂ ድሮውንም ተጣምረው ሊታዩ የሚገባቸው ተመሳሳይ ጉዳዮች መሆናቸውን ተገንዝቦ ቀደም ሲል ተጣምረው እንዲታዩ በሚል የሰጠውን ትዕዛዝ ተከትሎ ፍርድ ከሰጠም በኋላ ቢሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 208 መሰረት የእርማት ዳኝነት የሰጠበት ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ/ም ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዳኝነት አልሰጠበትም፡፡ የመጨረሻ ዳኝነት የሠጠበት ከ6 ወር በኋላ ነው፡፡

በመሆኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8 እና 11 ድንጋጌዎች አፈፃፀም በሚመለከት በአሁን አመልካች አማካኝነት የይግባኝ መዝገብ ከተከፈተም በኋላ ክርክሩ ሲቀርብለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345፣ 32(2) እና 244(3) ድንጋጌ አንፃር በማየት የቀረበለትን የይግባኝ መዝገብ ከመዝጋት ይልቅ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 11(3) መሰረት ተገቢውን መፈፀም ይቻል ዘንድ በመ/ቁ 45441 የተሰጠው ውሳኔ ደረጃውን ጠብቆ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መቅረብና አለመቅረቡን መጠባበቅ ይገባው አንደነበረም ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በኮ/መ/ቁ 45441 በሆነው ጉዳይ ላይ የአሁን አመልካች በሁለቱም ጉዳዮች ተመሳሳይ ሆነው እያለ በአንድ ፍ/ቤት የተለያየ ፍርድ ሊሰጥ የቻለበትን ምክንያት በመግለፅ የተፈፀመው የሥነ - ሥርዓታዊ ግድፈት በይግባኝ ደረጃ እንዲታረም በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 116629 ማስከፈታቸውን ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲረዳ አስቀርበን ከተመለከትነው መዝገብ የተረዳን ከመሆኑ በቀር የአሁን ተጠሪ በዚህ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተደረገ የተባለው የብድርና የመያዣ ውል ፈራሽ ነው በሚል በመ/ቁ 45441 በሆነው መዝገብ ላይ ከታች ወደ ላይ ያቀረቡት ክርክር የለም ክርክር ያቀረቡበትም ለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር አልተገኘም፡፡ ይህም በመሆኑ ምክንያት በመ/ቁ 45441 የተሰጠው ፍርድ ደረጃውን ጠብቆ በቀረበ ክርክር እንደገና ታይቶ ሥልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች እስካልተለወጠ ወይም እስካልተሻሻለ ድረስ የፀና እና ተፈፃሚነት ያለው ፍርድ ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በይግባኝ መ/ቁ 119226 በቀረበለት የይግባኝ ጉዳይ የስር ፍ/ቤት በአንድ ጉዳይና በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች የተነሳውን ሁለት የተለያዩ ክሶች ከጉዳዩ አመራር ሥርዓት ውጭ ነጣጥሎ በማየቱ ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8፣ 11፣ 244(3) የተመለከቱትን ሥነ - ሥርዓታዊ ድንጋጌዎች የጣሰ መሆኑንና በማየትና በመ/ቁ 45441 የተሰጠውን ፍርድ የአሁን አመልካች ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ በይግባኝ ደረጃ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዳኝነት ከመስጠቱ በፊት ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 345 የተመለከተውን ሥነ - ሥርዓታዊ ድንጋጌ ምርኩዝ ያደረገና አቤቱታው ከድንጋጌው ትክክለኛ አፈፃፀም ጋር የሚጣጣም መሆኑን ሁሉ ተገንዝቦ በይግባኝ መዝገቡ ላይ ተገቢውን ፍርድ መስጠት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እየቻለ በመ/ቁ 37363 በሆነው መዝገብ ላይ ብቻ ተወስኖ ሚያዝያ 04 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንዲሁም በመ/ቁ 37363 በሆነው መዝገብ ለተነሳው ክርክር መሰረት የሆነው ነሐሴ 21 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገው የብድር እና የመያዣ ውል በህግ ፊት ሊፀና የማይችል፤ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል መሆኑ ተገልፆ ፈራሽነቱ በመ/ቁ 45441 የተወሰነ በመሆኑና ይህም ውሳኔ ከታች ወደ ላይ ባለው የክርክር መስመር ታይቶ ያልተለወጠ ያልተሻሻለ ሆኖ በመገኘቱ የመጨረሻ ፍርድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም አንፃር ለብር 400,000.00 ብር (አራት መቶ ሺ) ክርክር መሰረት የሆነው የብድር ውል ፈራሽ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውና በመ/ቁ 37363 የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ/ም በዚሁ መዝገብ ላይ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ብር 400,000 (አራት መቶ ሺ) ይክፈሉ በሚል የተሰጠውም ፍርድ ዋጋ ያለው እና ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 119226 ሚያዝያ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በጉዳዩ ላይ የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች ለተጠሪ ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ለመክፈል ግዴታ የለባቸውም ብለናል፡፡
3. የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መዝገቡ የመ/ቁ 116629 በመጣበት አካኋን ይመለስ፡፡
4. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 83007

ሰኔ 3 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶልሣ

ሙስጠፋ አሕመድ

አመልካቾች፡-1. ወ/ሮ አልማዝ ገመቹ } ጠበቃ አቶ ገናናው ተሾመ ቀረቡ

2. አቶ ዮሐንስ ገመቹ }

ተጠሪ፡- አቶ ፋዩ ገመቹ ጠበቃ አቶ ተስፋዬ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳይ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 147083 ሰኔ 4 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ንብረት በአንደኛው ወራሽ ስም እንዲመዘገብ የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በስዮ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሣሽ የደንቢ ዶሎ ማዘጋጃ ቤት ተከሣሽ ተጠሪዎች ደግሞ ጣልቃ ገብ ተከራካሪዎች ሆነው ቀርበው ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ከአባቱ በውርስ ያገኘሁት ቤት ስመ ንብረቱን እንዲያዛውርልኝ ተከሣሹ /የደንቢ ዶሎ ማዘጋጃ ቤት/ ስጠይቀው ስም ለማዛወር እንቢተኛ ስለሆነ ስመሀብቱን እንዲያዛውር ውሣኔ ይሰጥኝ በማለት ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ በሥር ተከሣሽ የነበረው የደንቢ ዶሎ ማዘጋጃ ቤት ግብር የተከፈለው በሚች አቶ ገመቹ ገዳም ወራሾች ስም በመሆኑና አንደኛ አመልካች ወ/ሮ አልማዝ ገመቹ/ የቤቱ ስመ ሀብት ወደ ተከሣሽ እንዳይዛወር ያመለከቱ በመሆኑና ስም አላዛወርኩም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካቾች ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆነው ቀርበው ቤቱ በወራሾች ስም ግብር የሚከፍልበት እና በሽማግሌ ዳኞች ወራሾች እንድንካፈለው በ1992 ውሣኔ የተሰጠበት እና በ1998 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት የፈፀምንበት የሚች ወራሾች የጋራ ሀብት በመሆኑ ወደ ከሣሽ ስም ሊዛወር አይገባም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡
2. የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪና አመልካቾች በሚከራከሩበት ቤት ላይ የተጠሪዎች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን ከዚህ በፊት ውሣኔ ተሰጥቶበታል ስለዚህ የቤቱ ስመሃብት ወደ ከሣሽ /ተጠሪ/ እንዲዛወር ለተከሣሹ ደንቢዶሎ ማዘጋጃ ቤት ይፃፍ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ትእዛዝ ቅር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰኘት ለቁለም ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ቤቱ ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት እንደሆነ በመግለጽ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

3. ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የአሁን አመልካቾች ተጠሪ የያዘውን ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 99/90 የካቲት 10 ቀን 1992 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንዲያካፍለን የሚል የአፈፃፀም ክስ በመዝገብ ቁጥር 12882 አቅርበው ነበረ ተጠሪ በበኩሉ የአፈፃፀም ክስ ያቀረበው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 384 የተደረገው የአስር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኃላ በመሆኑ የአፈፃፀም ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም አመልካቾች /ይግባኝ ባይዎችና/ እና መልስ ሰጭ /ተጠሪ/ በመዝገብ ቁጥር 12882 ያቀረቡትን ክርክር በመመርመር አመልካቾች ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ የሚታገድ መሆኑን ገልፆ ታህሣስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ባዮች /አመልካች/ በዚህ መዝገብ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ አላቀረቡም፡፡ ይግባኝ ባዮች በመዝገብ ቁጥር 12882 የተሰጠውን ውሣኔ ለማሻር የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 323/2/ በሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት ይግባኝ ሣያቀርቡ ተጠሪ የደንቢ ዶሎ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14255 ሀምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ባቀረቡት ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 12882 የተሰጠውን ውሣኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሻሩ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስኗል፡፡

4. አመልካች ጳጉሜ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የቤቱ ባለቤትነትና ግብር ከ1951 ዓ.ም ጀምሮ በወራሾች ስም የሚከፈል መሆኑን ተጠሪ በማመን ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1060/1/ መሠረት የንብረቱ የጋራ ባለሃብት ናቸው፡፡ አመልካቾች በመዝገብ ቁጥር 12882 ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በአስር አመት ይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ተጠሪን ብቸኛ የቤቱ ባለሃብት እያደርገውም፡፡ አመልካቾች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1168 መሠረት ለተከታታይ አስራ አምስት ዓመት ግብር የገበሩ በመሆናቸው የቤቱ ባለሃብት ናቸው፡፡ በማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የሚቀርብ ክስ በይርጋ ቀሪ እንደማይሆን ይኸ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43600 ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

5. ተጠሪ ሕዳር 21 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ቤቱን እንዲያካፍላቸው የአፈፃፀም ክስ አቅርበው ጥያቄቸው በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ በመዝገብ ቁጥር 12882 ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡አመልካቾች በሕግ በተደነገገው መሠረት ይህንን ውሣኔ በይግባኝ አላሻሩም አመልካች ይህንን ውሣኔ በይግባኝ እንዲለወጥ ወይም እንዲሻር ሣያደርጉ ቤቱ የጋራ ሃብታችን ነው በተጠሪ ስም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሣወር አይገባም ብለው ለመከራከር የሚችሉበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች ታህሣስ 9 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የአመልካቾችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
7. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካችና ተጠሪ የሚች አባታቸው የአቶ ገመቹ ገዳም የውርስ ንብረት ክፍል የሆነው ቤት የጋራ ወራሾች መሆናቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ እንደዚሁም በሚች ወራሾች ስም በጋራ ለቤቱ ግብር ሲከፈል የቆየ መሆኑም ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም በዚህ መዝገብ እያከራከረ ያለው ጉዳይ አመልካቾች በወራሽነታቸው በቤቱ ላይ ያረጋገጡት የወራሽነት መብት ያለ መሆኑ ወይም አለመሆኑ አይደለም፡፡ አከራካሪ የሆነው አመልካቾች በንብረቱ ላይ ያላቸውን ያልተከፋፈል የጋራ ባለሃብትነት ለማስፈፀም አቅርበውት የነበረውን የአፈፃፀም ክስና በአፈፃፀም ክሱ ላይ የተሰጠውን ውሣኔ ይግባኝ ቀርቦበት ሣይሻር ፣ሣይለወጥ ወይም ሣይሻሻል መቅረቱ አመልካቾች በቤቱ ላይ የሚያነሱት የመብት ጥያቄና ክርክር ላይ ምን አይነት ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል የሚለው የሥነ ሥርዓት ጉዳይ ነው፡፡
8. አመልካቾች በተጠሪ ይዞታ ሥር የነበረው የማይንቀሣቀስ የውርስ ንብረት /ቤት/ የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 99/90 የካቲት 10 ቀን 1992 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት ለሶስት እኩል እንዲያካፍላቸው ፍርድ ቤቱ የአፈፃፀም ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው በመዝገብ ቁጥር 12882 የአፈፃፀም ክስ አቅርበው የነበረ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በዚህ መዝገብ አመልካቾች ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 384 የተደነገገው የአሥር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኃላ ነው ስለዚህ በይርጋ ቀሪ ነው የሚል ክርክር አቅርቦ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች በመዝገብ ቁጥር 12882 ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ታህሣስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ዘግቶታል፡፡ አመልካቾች በህጉ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን በማቅረብ ወደ ይኸ ውሳኔ እንዲሻር ፣እንዲለወጥ ወይም እንዲሻሻል አላደረጉም፡፡ ስለሆነም በመዝገብ ቁጥር 12882 ታህሳስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ አመልካቾች በቤቱ ላይ ያላቸውን የወራሽነት መብት በፍርድ ለማስፈፀም በሕግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለማቅረባቸው ተጠሪ ቤቱን እንዲያካፍላቸው የመጠየቅ መብታቸውን በይርጋ ቀሪ የሚሆን በመሆኑ ጉዳዩ ላይ የተሰጠ የመጨረሻ አስገዳጅነት ያለው ውሣኔ ነው፡፡
9. አመልካቾች በቤቱ ላይ ያላቸው መብት በፍርድ ሃይል እንዲፈፀም ለመጠየቅና ለመከራከር የማይችሉና ጥያቄያቸው በይርጋ ቀሪ እንደሆነ በመዝገብ ቁጥር 12882 ታህሣስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ አንቀጽ 320/1/፣ አንቀጽ 324፣ አንቀጽ 327 እና በሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርበው ሣያሸሩ ተጠሪ በውርስ በተገኘው ቤት ላይ በፍርድ ሊፈፀም የሚችል መብት ያለኝ እኔ ብቻ ነኝ ስለዚህ የደንቢ ዶሎ ማዘጋጃ ቤት ስመ ሃብቱን እንዲያዛውር ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበውን ክስ በመቃወም ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የሚሆኑበት በሕግ ፊት የፀናና ሊፈፀም የሚችል መብትና ጥቅም የላቸውም፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የአመልካቾች በቤቱ ላይ አለን የሚሉት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብት በፍ/ቤት ውሣኔ /ትእዛዝ/ እንዲፈፀም ጥያቄ ሊያቀርቡበት የማይችሉና የይርጋ የጊዜ ገደብ ያለፈበት መሆኑ ቀደም ሲል መወሰኑን ገልፆ የአመልካቾችን ክርክር በመዝገብ ቁጥር 14255 ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም ውድቅ አድርጓል፡፡

10. አመልካቾች በዚህ መዝገብ የተሰጠውን ብይን መነሻ በማድረግ በውጤት ደረጃ በመዝገብ ቁጥር 12882 ታህሣስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 07355 የይግባኝ ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች በመዝገብ ቁጥር 12882 የተሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ ለማሻር ወይም ለማስለወጥ የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ይግባኝ ያላቀረቡ መሆኑን ሳያገናዝብ በመዝገብ ቁጥር 14255 በተሰጠው ትእዛዝ ያቀረበውን ይግባኝ መነሻ በማድረግ በመዝገብ ቁጥር 12882 የተሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ የሚሽርና ውጤት አልባ የሚያደርግ ውሣኔ መስጠቱ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድ በይግባኝ እና በሰበር ለማሣረም ሊውሉ የሚገቡ አስገዳጅ ሥርዓቶችን ያልተከተለና አንድ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በሕግ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት በይግባኝ በሌላ ሥርዓት ወይም በሰበር ካልታረመ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅነት ያለው ውሣኔ ነው የውሣኔው አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት በባለጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ ሣይሆን በማናቸውም አስፈፃሚ አካልና ማናቸውም ፍርድ ቤት የሚመለከት እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ፣በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 2 የተካተተውን መሠረታዊ መርህ የሚጥስ ነው፡፡

11. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14255 በሰጠው ትእዛዝ መነሻ አመልካቾች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 320/1/ አንቀጽ 324፣ አንቀጽ 327 እና ሌሎች ድንጋጌዎች መሠረት የይግባኝ ቅሬታ ያላቀረቡበትንና በጉዳዩ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅነት ያለውን የወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12882 የሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 07355 መሻሩ የሕግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ አመልካቾች በዚህ መዝገብ የጠቀሷቸውን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1060፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1168፣ እና ሌሎች ድንጋጌዎች ይዘትና ትርጉም በመተንተን የይግባኝ ቅሬታ በማቅረብ ለማስለወጥ ወይም ለማሻር በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 324 በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የይግባኝ ቅሬታ ማቅረብ የነበራቸው የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12882 ታህሣስ 4 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ላይ ነበር፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ በማቅረብ ውሣኔውን አላስለወጡም ወይም አላሻሩም

12. በመዝገቡ ቁጥር 12882 የተሰጠው ውሣኔ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ ባልተሻረበት ወይም ባለተለወጠበት ሁኔታ የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14255 ሐምሌ 11 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝ መነሻ በማድረግ በቀረበው ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 12882 የተሰጠው ውሣኔ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የገለጽናቸውን የፍርድ ቤቶች ውሣኔ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት መርህንና አስገዳጅ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ የሚጥስ ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ከላይ የገለጽናቸውን ሥነ ሥርዓታዊ ምክንያቶችንና መሠረታዊ የዳኝነት ሥራ አካሄድ መርሆች መሠረት በማድረግ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻራቸውና የአመልካቾች ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ በየየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 83169

መጋቢት 28 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ፕሮፌሰር አደም ዓሊ አህመድ ጠበቃ አስፋ ንጉሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አዳማ ጠቅላላ ሆስፒታልና ሜዲካል ኮሌጅ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጠበቃ

አቶ በሻዳ ገመቹ ቀረቡ

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን ሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣንን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ እንዲሁም አመልካች የተከሳሽ ከሳሽ ተጠሪ የከሳሽ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በሰባት ሰዎች የተመሰረተ የንግድ ማህበር መሆኑን ገልጾ፣ የማህበሩ ጠቅላላ ካፒታል 140, 000,000/አንድ መቶ አርባ ሚሊዮን ብር/ ነው ተከሳሽ/አመልካች/ በማህበሩ ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋ ብር 35,000,000 /ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ብር/ ቁጥሩ ኤቢቲ 094872 በሆነ ቼክ አስይዘው አባል ሆነዋል፡፡ ሆኖም ይህንን ገንዘብ ባለመክፈላቸው ከሳሽ/ተጠሪ/ የገንዘብ ችግር ገጥሞት አቶ ከቢር ሁሴን ዋቆ በማህበሩ አባላት በቃለ ጉባኤ በሚወሰን ውሣኔ ሲሸፍኑ ቆይተዋል፡፡ ተከሳሽ የአክሲዮን ድርሻ ክፍያቸውን እንዲከፍሉ ቢጠየቁ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው የአባልነት ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡ ስለዚህ የማህበሩ አባልነታቸው ተሰርዞ ቼኩ እንዲመለስላቸው ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው እኔ ብር 35,000,000 /ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ብር/ ለመክፈሌ በቂ ማስረጃ አለኝ፡፡ ስለዚህ ከሳሽ ያቀረበው ክስ ከማህበር አባልነት ይሰረዝልኝ የሚል ቢሆንም የክርክሩ መሰረታዊ ጭብጥ ተከሳሽ ብር 35,000,000 /ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ብር/ ከፍሏል ወይስ አልከፈለም? የሚለው በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ የገንዘብ መጠን ላይ አከራክሮ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች በበኩላቸው የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበሩ እንዲፈርስ ለመጠየቅ የሚያስችሉኝ ምክንያቶች ናቸው የሚላቸውን በመዘርዘር ማለትም በአንደኛ ደረጃ ብር 35,000,000 የአክሲዮን ድርሻ ከፍያ እያለ አልከፈለም መባሉ፣ በሁለተኛ ደረጃ በእኔ ስም የነበረ መሆኑ ከእኔ እውቅና ውጭ ወደ ከሳሽ ስም መዛወሩ፣ በሶስተኛ ደረጃ አቶ ከበር ሁሴን ብር 78, 750,000 /ሰባ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ ብቻ ገቢ አድርገው እያለ ተጨማሪ ገንዘብ ገቢ ሳያደርጉ ገቢ እንዳደረጉ የተያዘ በመሆኑ ማህበሩ ፈርሶ በአክሲዮን ድርሻ ግምት ድርሻዬን እንዳገኝ ውሳኔ ይሰጥልኝ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ሆስፒታሉ ስራ ሲጀምር በሜድካል ዳሬክተርነት አገኝ የነበረው በወር 40,000 በ1993-2000 ዓ.ም ብር 3,360,000 እና በስራ አስኪያጅነት የሰራ ጊዜዬንና አእምሮዬን በማጥፋት ለሰጠሁት አገልግሎት አበል ብር 5,000,000 ከነወለዱ የተከሳሽ ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በሶስተኛ ደረጃ መሬቱን መካከለኛ ሆስፒታል ለመገንባት 40,600 ካሬ ሜትር በአዳማ ከተማ አስተዳደር በግሌ የተሰጠኝ ነው፡፡ ሆስፒታሉ እንዲገነበባት የተስማማሁት የመሬቱ ባለይዞታ በመሆኔ፣ ተገምቶ ወደ ፊት ጥቅም የማገኝ መሆኑን ተወያይተን ስለተሰማማንበት ነው፡፡ አሁን ግን እኔ ሳላውቅ የባለይዞታነት መብቴ ተገፎ ወደ ከሳሽ ተከሳሽ የተዛወረ በመሆኑ ይዞታዬ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1179 መሰረት እንዲለቀቅ ይወሰንልኝ በማለት የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ ማህበሩ የሚፈርሰበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የመሬት ካርታ ይሰርዝልኝ ጥያቄ በአስተዳደር የሚታይ እንጂ በፍርድ ቤት የሚታይ ጉዳይ አይደለም፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከሳሽ ክሳሽ የጠየቁት የገንዘብ ጥያቄ አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም የሚል መከራከሪያዎችን አቅርቧል፡፡

3. የአዳማ ልዩ ዞን በተጠሪ ክስና በአመልካች የተከሻስ ክሻስነት ክስ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያዎች ከመረመረ በኋላ ከሳሽ/ተጠሪ/ በተከሳሽ/አመልካች/ ላይ ያቀረበው ክስ የማህበርን አባልነት ግዴታውን ያልተወጣ ስለሆነ ከማህበር አባልነቱ ይሰረዝልኝ የሚል ነው፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ ብር 35,000,000 ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ብር እንዲከፍለው ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የለም፡፡ ጭብጡ ተከሳሽ ከማህበሩ አባልነቱ ይሰረዛል ወይስ አይሰረዝም የሚል በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡

• የተከሳሽ ክሳሽ የከሳሽ ተከሳሽ ብር 8,360,000 /ስምንት ሚሊዮን ሶስት መቶ ስልሳ ሺ ብር/ እንዲከፍለው ያቀረበው ጥያቄ ፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 14 ከተሰጠው ስልጣን በላይ በመሆኑ፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለኝም

• ማህበሩን መፍረስ በተመለከተ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን አለኝ፡፡

• የመሬቱ ይዞታ ከተከሳሽ ወደ ከሳሽ ተከሳሽ የተዛወረ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ለተከሳሽ ክሳሽ የተሰጠው የይዞታ የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝና በተከሳሽ ስም የይዞታ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን የለውም፡፡ በማለት ብይን ሰጥቶ በሌሎች ነጥቦች ላይ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ለመስማት ቀነ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

4. በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በተከሳሽ ክሳሽነት የጠየቀው ብር 8,360,000 በስር ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚታይ ባለመሆኑ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ትዕዛዝ መሰጠቱ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪ በክሳሽነት ያቀረበው ከማህበር አባልነት ይሰርዝልኝ በማለት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስር ነገር ስልጣን አለው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ማህበሩ የተመሰረተበትን መሬት ጉዳይ አይቶ የመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን ተገቢ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች መሬቱን በተመለከተ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ማህበሩ እንዲፈርስ ካቀረበው ጥያቄ ጋር ታይቶ ውሣኔ ይሰጥበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. አመልካች መስከረም 7 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብር 35,000,000 የተከፈለ መሆን አለመሆኑን የክርክሩ ጭብጥ የሆነበትን ጉዳይ የማየት ስልጣን አለው መባሉ ስህተት ነው፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በተከሣሽ ክሣሽነት ያቀረቡት የገንዘብ ጥያቄ ተነጥሎ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በማለት የሰጠው ውሣኔ የተሣሣተ ነው፡፡ ስለመሬቱ የሰጠውን ውሣኔም ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ታህሣስ 26 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በስልጣኔ ሥር ናቸው ባላቸው ጉዳዮች ውሣኔ ሣይሰጥ፣ የአመልካች ክርክር በይግባኝና በሰበር መስተናገዱ ስህተት ነው፡፡ አመልካች ያቀርቧቸው ክሶች ተለይተው ሊቀርቡ የሚገባቸው ናቸው ስለዚህ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ከማግኘቱ በፊት ያቀረበው ክርክር በሕግ የተደነገገውን ስርአት የተከተለ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥር 21 ቀን 2005 ዓ.ም የሥር ፍርድ ቤት የከሣሽን ክስና አራት ራሣቸውን የቻሉ የዳኝነት ጥያቄዎችን የያዙ የተከሣሽ ክሣሽነት ክሶች ቀርበውለታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤት ብይን በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን የመጨረሻ ውሣኔ ላይ ውጤት ያለው በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌውን የተከተለ ነው በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአዳማ ልዩ ዞን ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን አለው፣ የአመልካች የተከሣሽነት ክስ የጠየቁት ብር 8,360,000 ተነጥሎ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይቅረብ በማለት የተሰጠው ብይን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

6.1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን፣ በመጀመሪያ ለአዳማ ልዩ ዞን ተጠሪ ያቀረበው ክስና በአመልካች በኩል የቀረበው የተከሣሽነት ክስ ተጠሪ ከአመልካች የሚጠይቀውን የመብትና የዳኝነት ጥያቄ እና አመልካች ከተጠሪው የሚጠይቀውን የመብትና የዳኝነት ጥያቄ የያዙና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሕግ አውጭው በከሣሽ በኩል ክስ የቀረበበት ተከሣሽ፣ ክሱን ለመከላከል ከሚያቀርበው መልስ በተጨማሪ ጉዳዩን እያየ ላለው ፍርድ ቤት የተከሣሽ ክሣሽነት ክስ ማቅረብ እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 30/1/ አንቀጽ 324/1/ሀ እና በአንቀጽ 215/2/ የደነገገው፣ የከሣሽ ክስና የተከሣሽ ክስ የተከሣሽ ክሣሽነት ክስ በአንድ ላይ ተጠቃልለው ጉዳዮን የመወሰን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት መታየታቸው፣ የተከራከሪዎቹንና የፍርድ ቤቱን ጊዜና ወጭ የሚቆጥብና ትክክለኛ ፍትሕ ላይ ለመደረስ፣ ጠቀሜታ እንዳለው በመገንዘብ ነው፡፡

ተከሣሽ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ካቀረበ ፍርድ ቤት ከቀረቡለት ጉዳዮች በሥረ ነገር ስልጣኑ ሥር ያሉትን መርጦ የማየትና ክሱ ከስረ ነገር ስልጣን በላይ የሆኑትን ጉዳዮች ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይቅረብ በማለት የከሣሽ ክስና የተከሣሽ ተከሣሽነት ክስ ተነጣጥለው እንዲታዩ ትእዛዝ መስጠት አይችልም፡፡ ምክንያቱም የከሣሽን ክስ ተቀብሎ ለመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በማየት ላይ እያለ ተከሣሹ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ካቀረበ የፍርድ ቤቱ የሥረ ነገር ስልጣን የሚወሰነው አንደኛው ወገን ያቀረበውን ከፍተኛ የሃብት ግምት መሠረት በማድረግ እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውን ክስና አመልካች ያቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አጠቃልሎ ለማየት የሚያስችለው የሥረ ነገር ስልጣን የሌለው በመሆኑና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ውስጥ የብር 8,360,000 የዳኝነት ጥያቄ የያዘውን ጉዳይ አከራክሮ የመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም፡ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይቅረብ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ይህንን ጉዳዩ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነጥሎ እንዲያቀርብ የሚያስገድድ ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የይግባኝ ቅሬታና የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የሥር ፍርድ ቤት በከሣሽ ያቀረበውን ክስና በተከሣሽ የቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አጠቃልሎ ለመወሰን የሚያስችለው የሥር ነገር ስልጣን ከሌለው መዝገቡን ዘግቶ ማስናበት እንጂ የተጠሪ ክስ እና እኔ ያቀረብኩት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተነጣጥለው ግማሹ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግማሹ በሌላ ፍርድ ቤት እንዲታይ ትዕዛዝ መስጠት አይችልም በማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ካቀረባቸው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውስጥ የተወሰኑትን የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይንና ከሳሽ ያቀረበውን ክስና አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ከጠየቃቸው የተወሰኑትን ስልጣን አለኝ ብሎ ማከራከር መቀጠሉ ተጠሪ እንዲሚለው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320 ንዑስ አንቀጽ /3/ መሰረት ይግባኝ የማይባልበት ጊዚያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ብይን ክስና የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በቀረበበት ጉዳይ የፍርድ ቤቱ ስረ ነገር ስልጣን ስለሚወሰንበት ሁኔታ የተደነገገውን አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ የሚጥስና ጉዳዩ ተነጣጥሎ በፍርድ ከማለቁ በፊት በይግባኝና በሰበር መታረም የሚገባው የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣንን በተመለከተ ልዩ ባህሪና ውጤት ያለው የመጨረሻ ውሳኔ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 320 ንዑስ አንቀጽ 3ን በመጥቀስ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

ተጠሪ አመልካች ብር 35,000,000 የአባልነት መዋጮ የአክሲዮን ክፍያ ያልከፈለ ስለሆነ ከማህበር አባልነት ይሰረዝልኝ በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የከሳሽ ክስ ተከሳሽ ከአባልነት ይሰረዛል ወይስ አይሰረዝም የሚል ጭብጥ የሚያስነሳ መሆኑን በመግለጽ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን አለው በማለት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ብይን ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ተጠሪ ብር 8,360,000 /ስምንት ሚሊዮን ሶስት መቶ ስልሳ ሺ ብር/ ሊከፍለኝ ይገባል የሚልና ሌሎች የዳኝነት ጥያቄዎችን የያዘ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡

የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለው ጭብጥ የሚወሰነው ከተጠሪና አመልካች ካቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ከፍተኛ የኃብት ግምት ያለውን ማለትም አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ የጠየቀውን ብር 8,360,000 መሰረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንፃር ሲታይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪን ክስም ሆነ የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችለው የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ ተደንግጎ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪውን ክስና አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ካቀረባቸው የዳኝነት ጥያቄዎች የተወሰኑትን በዳኝነት አይቶ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን አለኝ ሌሎቹን ደግሞ የስረ ነገር ስልጣን የሌለኝ በመሆኑ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አመልካች ያቅርብ በማለት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የተጠሪን ክስና የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አጠቃልሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን እንዲቀርብ በመወሰን የስር ፍርድ ቤት የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 17 ንዑስ አንቀጽ 3ን በመጣስ የፈፀመውን ስህተት ሳያርም ማለፍ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 11396 ግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 150799 ሰኔ 14 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበውን ክስም ሆነ በአመልካች ያቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ለማየት የሚያስችለው የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ሕግ ቁጥር 17/3/ መሰረት ወስነናል፡፡
3. ጉዳዩ መታየት ያለበት የተጠሪን ክስና የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አጠቃልሎ ለማየትና ውሣኔ ለመስጠት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመሆኑ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያስተላልፍለት በማለት ወስነናል፡፡
4. አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን መሰረት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሲያቀርብ የከፈለው የዳኝነት ገንዘብ በደንቡ መሰረት ተቀንሶ ተመልሶለት ከሆነ፣ በሕጉ መሰረት የዳኝነት ገንዘቡን እንዲከፍል ሊደረግ ይገባል ብለናል፡፡ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ. 85873

መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ኒኢማ አባድጋ አባዋጂ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጣሐ ጀማል አደም ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በውጭ አገር የተደረገ የእርቅ እና የግልግል ስምምነት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊፀድቅ የሚችልበትን ሕጋዊ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ከአሁኗ አመልካች ጋር የነበራቸውን ጋብቻና ውጤቱን በተመለከተ በሸማግሌ ፊት ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በስምምነት በሰዑዲ አረቢያ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት ቆንጽላ ጽ/ቤት በተረጋገጠው አግባብ መደረጉን ገልፀው ይኼው ስምምነት እንዲፀድቅላቸው ለፌደራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው የካቲት 17 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ ለተጠሪ ያጸደቀላቸው ሲሆን የአሁኗ አመልካች ሰኔ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ማመልከቻ የአሁኑ ተጠሪ ያቀረቡት የስምምነት ፍቺ በሌሉበትና እና ሙሉ ፍላጎታቸው ሳይጠየቅ በተጠሪ ተፅፎ የቀረበ ስለመሆኑና በውጤቱም እጅጉን የጎዳቸው መሆኑን ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ ክርክር አድርገው የመኸር ገንዘብ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር)፣ የቤት ንብረት፣የልጅ ቀለብ ላይ ውሳኔ እንዲሰጣቸው የመቃወም ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት አድርጎ ጉዳዩን በመመርመር ተጠሪና አመልካች ሰኔ 01 ቀን 2002 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት አመልካች የተሳተፈበት መሆኑ የተረጋገጠ ነው በሚል ምክንያት ቀድሞ የእርቅ ስምምነቱን ያጸደቀበትን ውሳኔ ባለበት አጽንቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጋብቻው በስምምነት የፈረሰ ቢሆንም በንብረቱና በልጅ አስተዳደግ ላይ ግን ተገቢውና ሕጋዊ ስምምነት ባልተደረገበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች በስምምነት መሰረት ልትጸና ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ የሸሪዓ ሕጉንም ሆነ መደበኛውን ሕግ የሚጥስ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመረውም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም የተደረገ ነው ያሉትን የእርቅ ስምምነት ለፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው አመልካች በሌሉበት እንዲጸድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሕጉ ተለይቶ የተሰጣቸውን ስልጣን ምን እንደሆነ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ባልና ሚስት የነበሩ መሆኑን፣ ባሁኑ ደረጃ ተለያይተው እንደሚገኙና በባልና ሚስትነት ሲኖሩ በሳውዲ አረቢያ ውስጥ በሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንፅላ ጽ/ቤት ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በሽማግሌዎች ፍቺ ተደረገ በተባለ የእርቅና የግልግል ስምምነት የሚል ርዕስ ባለው ሰነድ ጋብቻውን በፈቃዳቸው አፍርሰው ንብረቱንም ሆነ በጋብቻ ወቅት ያፈሯትን ሕጻን አስተዳደግ በተመለከተ ስምምነት ተደርጓል በሚል ምክንያት ተጠሪ ሰነዱን ለፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም አመልካች በሌሉበት ሁኔታ የካቲት 16 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ስምምነቱ ፀድቋል ተበሎ የተወሰነ መሆኑንና አመልካች ይህንኑ ውሳኔ ለማስነሳት የተቃውሞ አቤቱታ ማቅረባቸውን፣ ለአቤቱታቸው መሰረት ያደረጉት ምክንያትም ተጠሪ አለ በማለት ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ስምምነት የማያውቁትና በተጠሪ ፍላጎት ብቻ ተፅፎ የቀረበ እንዲሁም የአመልካችን የንብረት መብትም ሆነ የህጻኗን አስተዳደግ የጎዳ መሆኑን መጥቀሳቸውን የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 34 (5) ስር የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሀይማኖት ወይም በባሕሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን በሕገ መንግስቱ ክልከላ እንዳልተደረገበት በግልጽ ከማስቀመጡም በላይ ዝርዝሩ በሕግ እንደሚወሰን ያሳያል፡፡ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የመዳኘት መብትም ምንጩ ይኸው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ ሲሆን የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 188/1992 መሰረት ተደራጅተዋል፡፡ በዚሁ አዋጅም ስልጣናቸው ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ በአዋጁ የክርክሩን የአመራር ሥርዓት ካልሆነ በስተቀር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በስረ ነገር ስልጣናቸው ሥር የሆኑ ጉዳዮች የሚቀርብላቸውን አቤቱታና ክርክር የሚወስኑት የሸሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 188/92 በአንቀጽ 6 (1) ስር በግልፅ የተደነገገ ሲሆን አንድ ሰው ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ሲያቀርብ ሥነ ሥርዓታዊ ከሆነው ጭብጥና ጥያቄ ውጭ የሆኑት ጉዳዮች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ፈቃድ የሰጠ መሆኑም ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ በመሆኑም የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ዳኝነት ከመሰጠቱ በፊት በአዋጅ ቁጥር 188/1992 ዓ.ም አግባብ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የተሰጠው መሆኑን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ የሚገባ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 6 ድንጋጌና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 (1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 80 (3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6 ጣምራ ንባብ መሰረት ስነ ስርዓታዊ የሆነ የህግ ጥያቄን ብቻ ለማየት ስልጣን እንዳለው ግንዛቤ በመውሰድ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ ሕጎችን መሰረት አድርጎ የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን ከጭብጡ አንጻር መርምሯል፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ በሸሪዓ ፍርድ ቤት የእርቅ ስምምነት እንዲፀድቅላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ያቀረቡት ሰነድ የእርቅ ግልግል ስምምነት መሆኑን በርዕሱ የሚገልፅና በይዘቱም ጋብቻንና ውጤቱን እንዲሁም የልጅ አስተዳደግን በተመለከተ ግራ ቀኙ ያደረጉትን ስምምነትን ምንነት የያዘ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስምምነቱ የተደረገው የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመጀመሪያው ለማየት በቀጥታ በተከፈተለት መዝገብ ሳይሆን በውጪ አገር ተደርጎ የመጣው የእርቅ ስምምነት እንዲፀድቅ ተጠሪ አመልካች በመሆን ባስከፈቱት መዝገብ ነው፡፡ በዚሁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገብ ላይ በአመልካችነት የአሁኑ ተጠሪ ስም የተመዘገበ ሲሆን በመዝገቡ ተጠሪ በሚል በተቀመጠው ቃል ትይዩ ግን የአሁኗ አመልካች ወይም ለጉዳዩ ተከራካሪ የሆነ ሰው ስም ያለመመዝገቡን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ አንድ እርቅ በፍርድ ቤት ሊፀድቅ የሚችለው ጉዳዩ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በመታየት ሂደት ላይ እያለ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩን በስምምነት የጨረሱ መሆኑን ገልፀው ይኼው ስምምነታቸው ለሕግ እና ለሞራል ተቃራኒ ያለመሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ እርቁ ወይም ስምምነቱ በፍርድ ቤት ተመዝግቦ ክርክሩ እንዲቆምላቸው ሲያመለክቱ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 277 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከዚህ ውጪ ከፍርድ ቤት ውጪ በሚደረግ እርቅ ወይም ግልግል መሰረት ያለመግባባትን ያስቀሩ ወይም ለጉዳያቸው እልባት ያገኙ ሰዎች እርቁ ወይም ግልግሉ እንደተፈረደ ፍርድ ሊቆጠርላቸው የሚገባ እና በውጤቱም በፍርድ ቤት ማስመዝገብ ወይም ማስፀደቅ ሳያስፈልገው ራሱን ችሎ ሊፈጸም የሚችል ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3312 እና 3324 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እርቁ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት እንዲጸድቅ ያቀረቡት ማመልከቻ በሕጉ ያልተቀመጠውን ስርዓት መሰረት በማድረግና በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አግባብም ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ባልተሰጠው ሁኔታ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከላይ እንደተገለጸው የአሁኗ አመልካች በአካል ያልቀረቡ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ በሕጉ አግባብ ተወክለው ጉዳዩ ያልታዩ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ ይልቁንም አመልካች ያቀረቡት የእርቅ ስምምነት ይዘት አመልካች የማያውቁት እና በተጠሪ ተፅፎ የቀረበ ነው በማለት ለመቃወም አቤቱታ ማቅረቢያ መነሻ ያደረጉ መሆኑ ሲታይ ተጠሪ ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም ተደረገ የተባለውን ስምምነት በሸሪዓ ህግ መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ቀድመው ፈቃዳቸውን በአዋጁ አንቀጽ 2 (4)፣4 (5) እና 5 (1) ድንጋጌዎች አነጋገር መሰረት ሰጥተዋል ለማለት ሁሉ የማያስደፍር መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ምክንያቱም አመልካች በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 5 (1) እና ከአዋጁ ጋር በተያያዘው አባሪ (ፎርም) በመሙላት ማረጋገጥ እንደአለባቸው ሕጉ ያሳያል፡፡ ይህም የመከራከር መብትን በህጉ አግባብ ለማስከበርና ለማረጋገጥ የተዘረጋ ስርዓት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ ተደረገ የተባለው የእርቅ ስምምነት በሌላ አግባብ ውጤት ከሚያገኝ በስተቀር በሸሪዓ ፍርድ ቤትም ሆነ በመደበኛ ፍርድ ቤት ክርክር በሌለበት ሁኔታ ቀርቦ የሚጸድቅበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ በመሆኑ እርቁ መፅደቁ ከአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6 (1) እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 277 ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 4595/04 የካቲት 17 ቀን 2003 ዓ.ም እና ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 007/05 ታህሳስ 22 ቀን 2005 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም በውጪ አገር ተደረገ የተባለው ስምምነት በሸሪዓ ፍርድ ቤት በቀጥታ ቀርቦ የሚጸድቅበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. አመልካች ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው የኖሩ ከሆነ ውጤቱንም ሆነ የልጅ አስተዳደግን በተመለከተ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ከመጠየቅና መብታቸውን ከማስከበር ተጠሪ ነሐሴ 01 ቀን 2002 ዓ.ም ተደረገ የሚሉት ስምምነት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ጸድቋል ተብሎ ሊከለከሉ አይገባም ብለናል፡፡ ተጠሪም ስምምነቱ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ጸድቋል ከሚለው ነጥብ በመለስ ይህንኑ ስምምነት መሰረት አድርገው የሚያቀርቡትን ክርክር ይህ ውሳኔ አይከለክላቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86551

መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ብዙነሽ ወ/ሚካኤል - ወኪል ታፈሱ አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ሽመልስ ቦጋለ - ጠበቃ ተስፋዬ ግዛው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በቅምብቢት ወረዳ ፍ/ቤት ባሁኗ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪዎች ክስም በውርስ የሚገባቸውን የሚች አባታቸውን ቆርቆሮ ቤት የአሁኗ አመልካች ይዘው እንደሚገኙ ገልፀው የቤቱን ግማሽ ግምት ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) አመልካች እንድትሰጣቸው ወይንም ቤቱን በአይነት እንድታካፍላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካችም የቤቱ ግምት ያላግባብ ከፍ መደረጉን ቤቱ ሶስት ክፍል ሰርቪስ ቤት ቢሆንም ብር 50,000.00 አያወጣም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም አመልካች የቆርቆሮ ቤቱን የተጠሪዎች አባት ድርሻ ሊያካፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቶ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ስንት ብር እንደሚያወጣ በባለሙያ ተገምቶ በአማራጭ በቀረበው ክስ ግምት ላይ ተመስርቶ ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት ጭብጥ ይዞ ለስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መለሰለት ሲሆን የወረዳ ፍ/ቤትም የሸኖ ከተማ አስተዳደር በባለሙያ እንዲያስገምት ትዕዛዝ ሰጥቶ ይሄው አካልም በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት በባለሙያ አስምምቶ የቤቱ ግምት ብር 93,750.00 (ዘጠና ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) መሆኑን በቁጥር 64/353/2005 በ30/01/2005 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ገልጾለት ፍ/ቤቱ ይህንኑ ግምት ከተቀበለ በኋላ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጎ አመልካች ግምቱ ትክክል አይደለም የሚል ተቃውሞ ያቀረቡ መሆኑን ከመዘገበ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ግምቱን የተቃመቡበት ምክንያት በቂ አይደለም የሚል ምክንያት ይዞ በቀረበው ግምት መሰረት ተጠሪዎች የአመልካችን ድርሻ ከፍለው ቤቱን እንዲወስዱ ወይም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት እኩል መካፈል የሚቻል ከሆነ እኩል እንዲካፈሉ ወይም ሸጠው ገንዘቡን እኩል እንዲከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪዎች የቤቱ ግምት ብር 50,000.00 ሆኖ ይህንኑ ግምት በመቃወም በይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅሬታ ያቀረብኩ እኔ ሆኜ እያለና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በእኔ ቅሬታ መነሻ ግምቱ እንደገና እንዲከናወን እንዲደረግና ጉዳዩ እንዲወሰን ትዕዛዝ ሰጥቶ በዚሁ መነሻ በተገኘው የተጋነነ ግምት መሰረት ተቃውሞ እየቀረበ እያለ የወረዳው ፍ/ቤት ግምቱን ከፍ አድርጎ ተጠሪዎች ግምቱን ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ በማለት በቅድሚያ የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም የአመልካች ቅሬታ ዋናውን ውሳኔ መሰረት ያላደረገና በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር መሆኑን ዘርዝረው የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ የተከራከሩ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች የተጠሪዎችን ግምት በመቃወም ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ ግምቱ እንደገና እንዲገመት ሲደረግ ከፍ በማለቱ በዚሁ ግምት መሰረት ተጠሪዎች ቅድሚያ ቤቱን የማስቀረት መብት እንዳላቸው ተገልፆ ሌሎች የክፍፍል ቅደም ተከተሎች ተጠቅሰው ውሳኔ መስጠቱ ከዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ተጠሪዎች የሚጠይቁት የአባታቸውን ድርሻ መሆኑን አመልካች ክርክር ያላቀረቡበት ጉዳይ ሲሆን ተጠሪዎች ንብረቱን በብር 50,000.00 ገምተው ድርሻቸውን ብር 25,000.00 አመልካች እንዲሰጧቸው፣ ይህን ማድረግ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ቤቱን በአይነት እንዲከፋፈሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን ክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የወረዳው ፍ/ቤት የቤቱን ግምት ሳያጣራ ክፍፍሉ እንዲደረግ ውሳኔ ሰጥቶ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ የተሰማቸው የአሁኑ አመልካች ሲሆን የቅሬታቸው መሰረታዊ ነጥብም ቤቱ ብር 50,000.00 ግምት ሊያወጣ አይችልም የሚል የነበረ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ መርምሮ ግምቱ እንደገና እንዲከናወን ማድረጉን፣ በዚህ ውሳኔ መሰረት ግምቱ ሲከናወን ግን ተጠሪዎች መጀመሪያ ገምተው ከአቀረቡት ግምት እጅጉን የላቀ ሆኖ መገኘቱን አመልካች በድጋሚ ግምት ትክክል አይደለም በማለት ቢቃወሙም የወረዳው ፍ/ቤት የአመልካች ምክንያት በቂ አይደለም ከማለት አልፎ ተጠሪዎች በአዲሱ ግምት መነሻ ቤቱን እንዲያሰሩ በማለት በመጀመሪያ አማራጭነት መወሰኑን ክርክሩ ሂደት መረዳት ተችሏል፡፡

በመሰረቱ ክርክር በሚደረግበት ንብረት ላይ የግምት ተቃውሞ ከተነሳ ግምቱ ተጣርቶ ክርክሩ መካሄድ ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 250፣ 136፣ እና ከሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብ ከሚደነግጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባው በተጠቀሰው መጠን ሆኖ አግባብነት ባለው ማስረጃ ነጥሮ በታወቀው ውጤት መሰረት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1) ድንጋጌ መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ አንድን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከት ፍ/ቤት በሕጉ አግባብ ክስ ተሻሽሎ ከፍ ያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኝነት ባልተጠየቀበት ሁኔታ በግምት ላይ ተቃውሞ ቀርቦ ግምቱ እንዲጣራ ሲደረግ የንብረቱ ግምት ከፍ ማለቱ በመረጋገጡ ብቻ ቀድሞ ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 92፣182(1) ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 225 እና 226 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) ገምተው ድርሻቸውን ብር 25,000.00 በአመልካች እንዲሰጣቸው በመጀመሪያ ደረጃ የጠየቁት ዳኝነት ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ቤቱን በአይነት ልንከፋፈል ይገባል በማለት በሁለተኛ አማራጭ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የቤተሰብ ሕጉንና የውርስ ሕጉን መሰረት አድርገው የሚቀርቡ የንብረት ክፍፍል ጥያቄቆች ላይ ክፍፍሉን በተመለከተ ውሳኔ ሲሰጥ በሕጉ የተቀመጡ ቅደም ተከተሎች ያሉ ሲሆን ተከራከሪ ወገን ይህንኑ በመተው ክፍፍሉን ሲጠይቅ ግን ሕጉን የማይፃረር መሆኑ ተረጋግጦ በተጠየቀው መሰረት ውሳኔ መስጠት የሚቻል መሆኑን አግባብነት ካላቸው ሕጎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የግምት ይከፈለኝ ጥያቄ በቅድሚያ አማራጭነት ከቀረበ ፍ/ቤቱ የግምቱን ትክክለኛነት አረጋግጦ በተጠየቀው ውሳኔ ቢሰጥ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን የጠበቀ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪዎች የቤቱን ግምት በግልፅ አስቀምጠው ግምቱን አመልካች ተቃውመው እንደገና እንዲገመት በተደረገበት ሁኔታ ግምቱ ከፍ ሲል ይህንኑ ከፍ ያለውን ግምት መሰረት አድርጎ ውሳኔ መስጠት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1) ድንጋጌን የጣሰ ሆኖ አግኝተናል፡፡ አመልካች ግምቱ እንዲቀነስ በማሰብ ይግባኝ አቅርበው ተቀባይነት አግኝተው በይግባኙ መነሻ ግምቱ ሲከናወን ከፍ በማለቱ ብቻ ይሄው መሰረት ተደርጎ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የይግባኝ ጽንሰ ሃሳብና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን የሚፃረር ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ተከራከሪ ወገን ይግባኝ የሚያቀርበው መብቱን ለማስፋት እንጂ መብቱን ለማጥበብ ያለመሆኑን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከት ፍ/ቤት ዳኝነት መስጠት ያለበት በተጠየቀውና ሕጋዊ በሆነው መጠን መሰረት ብቻ መሆኑን ከይግባኝ አቀራረብና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓቶች የምንገነዘበው ጉዳይ ነውና፡፡ ሥለሆነም የወረዳው ፍ/ቤት በይግባኙ መነሻ የቤቱ ግምቱ ከፍ ሲል ተጠሪዎች በጠየቁት ዳኝነት መጠን ተወስኖ የክፍፍል ውሳኔ መስጠት ሲገባው ይህንኑ በማለፍ ከፍ ብሎ በቀረበው ግምት መሰረት ተጠሪዎች ግምቱን ለአመልካች ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ በመጀመሪያ አማራጭነት መወሰኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1)፣ 250 እና ስለይግባኝ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን የጣሰ ሲሆን ይህንኑ ውሳኔ የክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች ሳያስተካክሉ ማለፋቸውም የህግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳይ ሆኖ ስለአገኘን በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በቅምብቢት ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 02775 ጥቅምት 22 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 35974 ጥቅምት 27 ቀን 2005 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 157217 ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በትዕዛዝ ያፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች በቅድሚያ ዳኝነት የጠየቁት ቤቱን በብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ብር) ገምተው ድርሻቸውን አመልካች እንዲከፍሏቸው በመሆኑ ግምቱ ላይ አመልካች ባቀረቡት መቃወሚያ መሰረት እንደገና በመገመቱና ከፍ በማለቱ ተጠሪዎች ከፍ ያለውን ግምት መሰረት አድርገው ለአመልካች ድርሻቸውን ሰጥተው ቤቱን ያስቀሩ በማለት መወሰኑ ያላግባብ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች የቤቱ ግምት 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) መሰረት አድርገው ግማሹን ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) ለተጠሪዎች እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስቀሩ፣ ይህንን ማደረግ የማይችሉ ከሆነ ቤቱን በአይነት እኩል እንዲከፋፈሉ፣ ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ቤቱን በስምምነት እንዲሸጡ፣ ካልተቻለም በሀራጅ ተሸጦ የሸያጩን ገንዘብ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስነናል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሰረት አፈፃፀሙን የወረዳው ፍ/ቤት እንዲያስፈፅም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ተጠሪዎች በብር 93,750.00 (ዘጠና ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) ላይ በታሪፉ መሰረት የከፈሉት የዳኝነት ገንዘብ እንዲመለስ እንዲያደርግ የስር ፍ/ቤት ታዝዟል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79871

የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ የውብዳር ባንቱ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ መአዛ ጥበቡ - ተወካይ አዜብ ጥበቡ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሎሚ ተሊላ
2. ወ/ሮ ብርቁ ተሊላ
3. ወ/ሮ ትርንጎ ተሊላ
4. ወ/ሮ ቀበኒ ተሊላ
5. አቶ ደሴ ተሊላ

} ጠበቃቸው አቶ ብርሃኑ ተሊላ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በአሁን የሰበር አመልካቾች የመቃወሚያ አቤቱታ አቅራቢነት በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አቤቱታውም፡- በ04/05/1994 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል አቶ ደሴ ተሊላ ለወ/ሮ የሺ ወ/መድህን የሸጡትን ቤት ወ/ሮ የሺም በ24/07/1994 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ለአመልካቾች ለእያንዳንዳችን አንድ አንድ ክፍል ሸጠውልን ይዘን እያለ በመቃወም ተጠሪዎች ፍርድ ቤቱን በማሳሳትና ባዶ ቦታ በማስመሰል በውርስ የተላለፈልን ነው በሚል የወራሽነት ውሳኔ ያሰጡ ስለሆነ ውሳኔው እንዲሰረዝ ይወሰንልን ብለዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሠጡት መልስ፡- የሚያከራክረውን ቤትና ቦታ ከሚች አባታችንና እናታችን በውርስ ያገኘነው ነው፣ ወ/ሮ የሺ ወ/መድህን ከወንድማችን ደሴ ተሊላ እንደገዙና አመልካቾችም ከግለሰቧ እንደገዙ በመጥቀስ ያቀረቡት ማስረጃ የሐሠት ነው፤ማስረጃው አለ ቢባል እንኳን በህግ ፊት የሚጸና አይደለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማትና በመመዘን በሰጠው፡- ውሳኔ የግራ ቀኙ ምስክሮች ቤቱ የተጠሪዎች አባት እና እናት መሆኑን ያስረዱ በመሆናቸው በመቃወም አመልካቾች ወ/ሮ የሺ ወ/መደህን ከተባሉት ግለሰብ ገዝተናል ቢሉም ግለሰቧ እነዚህን ሰዎች በመወከል ሊሸጡ አይችሉም፣ እንዲሁም የሽያጭ ውሉ የተመዘገበ ባለመሆኑ በህግ ፊት ተቀባይነት የለውም፣ ስለሆነም አመልካቾች ከፈለጉ ግለሰቧን በመክሰስ መብታቸውን ከሚያስጠብቁ በስተቀር ለተጠሪዎች የተሰጣቸው የወራሽ ማስረጃ ሊሰረዛባቸው አይገባም በሚል የመቃወም አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

በመቃወም አመልካቾችም በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በሰጠው ውሳኔ ክርክር ያስነሳው ቤት በ1990 ዓ/ም ከመልስ ሰጪዎች እጅ መውጣቱን ከአዳማ ከተማ አስተዳደር እና ከደቤ ሶለቂ ቀበሌ አስተዳደር ከተጻፉት ደብዳቤዎች ከመረጋገጡም ሌላ መልስ ሰጪዎች (በመቃወም ተጠሪዎች) በ26/09/2002 ዓ/ም ለወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ አባታቸው በ1976 ዓ/ም፣እናታቸው ደግሞ በ1990 ዓ/ም መሞታቸውን የገለጹ ሲሆን የወራሽነት ማስረጃውን የያዙት ደግሞ በመ/ቁ/38843 በቀን 28/05/2002 በመሆኑ ማስረጃውን የወሰዱት 10 ዓመት ካለፈ በኋላ ሆኖ እያለ የወረዳው ፍርድ ቤት በቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ላይ ብይን ሳይሰጥ ማለፉ ተገቢነት የለውም በሚል መልስ ሰጪዎች የወራሽነት ማስረጃ ያወጡት በፍ/ህ/ቁ 1845 የተደነገገው 10 ዓመት ይርጋ ካለፈው በኋላ ነው ሲል የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

በመቃወም ተጠሪዎች ይግባኝ ጠያቂነት ጉዳዩን የመረመረው የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ በሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ባዮች እናት እጅ የነበረው ቤት ፈርሶ 5ኛ ይግባኝ ባይ (አቶ ደሴ ተሊላ) በቦታው አራት ክፍል ቤት መስራታቸው የተረጋገጠ በመሆኑና ቤቱ ወደ መልስ ሰጪዎች የተላለፈው በ5ኛ ይግባኝ ባይ በመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የወራሽነት ማስረጃውን ይግባኝ ባዮች ያወጡት የ10 ዓመት ይርጋ ካለፈ በኋላ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው በሚል የጠቀሰው ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን የሚነቀፍ አይደለም ሲል አጽንቷል፡፡

በመቃወም ተጠሪዎችም በከፍተኛው እና በክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ በሠጠው ውሳኔ፡- ተጠሪዎች አቤቱታ ያቀረቡት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 358 ሲሆን ይዘቱም ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ ለአመልካቾች የተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሻር ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ መሰረት መቃወሚያ የሚያቀርብ ሰው ደግሞ መብቱን የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣ በከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ ቤት ደግሞ ባለንብረት ለመሆን የባለይዞታነት ማረጋጫ ማስረጃ (ካርታና ፕላን) መኖር ግዴታ ነው፣ይህ በመሆኑ ግዥ እና ሽያጭ መፈጸም ብቻ የቤቱ ባለቤት ማድረግ እንደማይችል የፍ/ህ/ቁ/1185 ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ ተጠሪዎቹ መብት በሌላቸው ንብረት ላይ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358ን ጠቅሰው ያቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ የሚሆን ነው ሲል የከፍተኛውን እና የክልሉን ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾችም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡-

- የተጠሪዎች አባት ከሞቱ ከ26 ዓመት በኋላ እንዲሁም እናታቸው ከሞቱ 12 ዓመት በኋላ ተጠሪዎች በቦታውና ቤቱ ላይ ወራሽነት ይገባናል በሚል የያዙት የወራሽነት ማስረጃ በፍ/ህ/ቁ/1000(1) እና 1845 የተደነገጉት ይርጋ ጊዜያት ካለፉ በኋላ የተሠጣቸው በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በሚል ያቀረብነው የመከራከሪያ ነጥብ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዝምታ ማለፉ ተገቢነት የለውም፤
- ክርክር ያስነሳውን ቤትና ቦታ የተጠሪዎች ወላጆች ከሞቱ በኋላ በ5ኛ ተጠሪ እጅ ገብቶ ተጠሪውም ቀደም ሲል የነበረውን ቤት አፍርሶ በአዲስ መልክ ሰርቶ ለወ/ሮ የሺ ወ/መድህን የሸጠ ሲሆን ግለሰቧም አስፋፍታ ግንባታዎችን በማካሄድ በጽሁፍ በተደረገ የሽያጭ ውል ለአመልካቾች ሽጣ እያለ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ወጪ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት የፍሬ ነገር ጉዳዮችን ለማጣራት ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ካርታ እና ፕላን በተመለከተ ክርክር ያልተነሳውን በራሱ ጊዜ በማንሳት የከፍተኛውንና የክልሉን ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሠጡት መልስ፡- የሚያከራክረው ቤትና ቦታ የወላጆቻችን የነበረ ሲሆን ወላጆቻችን በሞት ከተለዩ በኋላ በእጃችን የሚገኝ ሆኖ እያለ አመልካቾች በሽያጭ አግኝተው በእጃቸው መግባቱን በመጥቀስ በሐሰት በተቀነባበረ ማስረጃ የሚከራከሩ ቢሆንም የሽያጭ ውሉ አመልካቾች እንደሚሉት ተፈጽሟል ቢባል እንኳን የጋራ የውርስ ንብረት አንዱ ወራሽ ብቻ አደረገ በተባለው የሽያጭ ውል መነሻ ሌሎች ወራሾች የመውረስ መብታችንን የምናጣበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፤እንዲሁም ተጠሪዎች የውርስ ንብረት ይለቀቅልን በሚል ያቀረብነው ክስ በሌለበት የይርጋ ክርክር ሊነሳ የማይችል ከመሆኑም ሌላ ይርጋን መከራከሪያ ሊያደረግ የሚችለው ተከሳሽ የሆነ ወገን እንጂ ከሳሽ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾችም ተጠሪዎች ለሠጡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 መሰረት ሊቀርብ የሚገባ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካቾች ካቀረቡት ክርክር መረዳት የተቻለው ተጠሪዎች ወላጅ አባታቸውና እናታቸው በሞት የተለዩ መሆናቸውን በመግለጽ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ለፍርድ ቤቱ አመልክተው ወራሽ ናቸው በሚል በተሰጠ ውሳኔ መነሻ የውርስ ሀብት ነው በሚል በግዥ ያገኘነውን ቤት ስለያዙ የተሰጣቸው ማስረጃ እንዲሠረዝባቸው ሲሉ መጠየቃቸውን ነው፡፡

በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው በክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንዲሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ሰው ወይም ጠበቃው ወይም ነገረ ፈጅ መሆኑን ከድንጋጌው መረዳት የሚቻል ሲሆን መቃወሚያውም ሊቀርብ የሚገባው ለመቃወሚያው መሰረት የሆነው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የሚች እናታቸው እና አባታቸው ወራሾች መሆናቸው እንዲወሰንላቸው ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወራሾች ናቸው በሚል በመ/ቁ/38843 በቀን 28/05/2002 ዓ/ም ፍርድ/ውሳኔ የተሠጠ መሆኑን መዝገቡ ያመላክታል፡፡ በዚህ በተጠቀሰው መዝገብ ተጠሪዎች ወራሾች ስለመሆናቸው ባቀረቡት አቤቱታም ሆነ በሚደረገው ክርክር እንዲሁም በሚሠጠው ፍርድ ወይም ውሳኔ የሚያከራክረውን ቤት ስለገዛን ፍርዱ ወይም ውሳኔው መብታችንን ይነካል በሚል ምክንያት የተጠሪዎች የወራሽነት ማስረጃ እንዲሠረዝባቸው አመልካቾች መቃወሚያ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ህጋዊ ሁኔታ አይኖርም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪዎች የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ከጠየቁት ዳኝነትም ሆነ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር አመልካቾች የውርስ ሀብቱን በሽያጭ ውል አግኝተናል በሚል ያቀረቡት የንብረት መብት ጥያቄ የሚገናኝ ባለመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በሚያከራክረው ንብረት ላይ መብት አለን የሚሉ ከሆነ ተገቢውን ዳኝነት ክፍለው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው መብታቸውን ከሚጠይቁ በስተቀር በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 358 መሰረት የፍርድ/የውሳኔ መቃወሚያ ሊያቀርቡ አይገባም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 መሰረት ሊቀርብ የማይገባውን መቃወሚያ ተቀብለው በማከራከር ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢ ባይሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጡትን ውሳኔ በመሻር የመቃወሚያ አቤቱታቸውን ውድቅ ያደረገው በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/131390 በቀን 06/09/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ውሳኔ ምክንያቱን ለውጠን በውጤት ደረጃ በመቀበል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካቾች የውርስ ሀብት የሆነውን የሚያከራክረውን ቤትና ቦታ በግዥ ስላገኘን ለተጠሪዎች የተሠጣቸው የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልን ሲሉ ያቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 መሰረት ሊቀርብ የሚገባ አይደለም ብለናል፡፡ ይህ ውሳኔ አመልካቾች ለሚያከራክረው ንብረት ተገቢውን ዳኝነት ከፍለው መብታቸውን በሚጠይቁት ወገን ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክስ አቅርበው መብታቸውን ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይሆንም ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ
   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

ት/ዘ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80202

የካቲት 12 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1. አቶ ሐጎስ ሸጎፅ የቀረበ የለም } መቀሌም በፕላዝማ አልቀረበም

2. አቶ ተስፋዬ ጥጋቡ ሸጎፅ የቀረበ የለም }

ተጠሪ፡- የመሸነ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከቦታ ማስለቀቅ ጋር ተያይዞ የተነሳ የካሳ ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁኖቹ አመልካቾች በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ ተከሳሽ በሚተዳደርበት የከተማ ቦታ ኪራይ ደንበ መሰረት ለሆቴል አገልግሎት የሚውል 3250 ካ.ሜ ቦታ ለ1ኛ ከሳሽ እና የ2ኛ ከሳሽ አባት ለሆኑት ለአቶ ጥጋቡ ሸጎፅ በውል ሰጥቶ እንደነበረ በዚሁ ቦታ ላይ ግንባታውን በከፊል አከናውነው ከፊሉ ደግሞ በግንባታ አዲት ላይ እያለ ተከሳሽ አቅም ስለሌላቸሁ ቦታውን አስረክቡ በማለት በ18/05/01 በተፃፈ ደብዳቤ እንዳስታወቀቸው እነርሱም ጉዳዩ የተንተተው በአቶ ጥጋቡ ሸጎፅ ሞት ምክንያት ከውርስ ማጣራት ጋር ተያይዞ መሆኑን ለተከሳሽ እንደገለጹ እና በተጠየቁት መስረት የፋይናንስ አቅማቸውን የሚያመለክት ማስረጃ ለተከሳሽ እንዲያቀርቡ ለግንባታው ከብር አንድ ሚሊዮን በላይ ወጪ እንዳደረጉና ተከሳሽ ተገቢውን ምላሽ ሊሰጧቸው እንዳልቻሉ የሚገለፅ ሆኖ በሂደት እያለሙት የነበረውን ቦታ ተከሳሽ እንዲመልስላቸው የማይመልስ ከሆነ ደግሞ ያወጡትን ወጪ ብር እንድ ሚሊዮን ከተዛማጅ ወጪዎች ጋር እንዲመልስላቸው ውሳኔ እንዲሰጣቸው ዳኝነት የተጠየቀባቸው ነው፡፡ ተከሳሽ በበኩሉ የቦታ ማስለቀቅ እና የካሳ ጉዳይን ፍ/ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ማየት ስለማይችል መዝገቡን ዘግቶ ያስናብተን በማለት መቀወሚያ ከቀረበ በኋላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ክሳሾቹ ሆቴል እና የነዳጅ ማደያ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ገንብተው አገልግሎት ላይ ለማዋል ውል ገብተው ቦታውን በ1994 ከተረከቡ በኋላ አስከ 1999 ዓ.ም ደረስ የተወሰኑ ክፍሎችን ከመስራት በስተቀር በገቡት ግዴታ መሰረት ግንባታውን አጠናቀው ስራ ላይ ባለማዋላቸው በ1999 ስራውን እንዲያቆሙ እንደታዘዙ እና ቀጥሎም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲያስረክቡ እንደተደረገ ይህ እርምጃም የተወሰደው ለከተማ አስተዳደሩ በተሰጠው ስልጣን መሰረት እንደሆን እና ቦታው በጨረታ ለሌሎቹ ባለሀብቶቹ ሊተላለፍ እንደሆነ በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡

ፍ/ቤቱም መቃወሚውን ውድቅ አድርጎ የግንባታው ዋጋ በባለሙያ እንዲገመት ካደረገ በኋላ ተከሳሽ የግንባታውን ወጪ ብር 618,815.93 ለከሳሾች ይክፈል ከዚህ በኋላ ቦታውን ከነግንባታው ይረከብ በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ሁለቱም ወገኖች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የመረመርው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው የከተማ ቦታን በኪራይ ስለመያዝ እንደገና ለመደንገግ በክልሉ በወጣው ደንብ ቁጥር 19/1995 አንቀጽ 13/2/ መሰረት የቦታ ማስለቀቅ እና የካሳ ክፍያ ጉዳይን በመጀመሪያ ደረጃ ለማየት የሚያስችል ስልጣን ሳይኖው ነው በማለት ውሳኔውን በሁለቱም መዝገቦች የሻረው ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ ዘግቶ አስናብቶአል፡፡

አመልካቾች አቤቱታ ያቀረቡት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ ሊታረሙ ይገባል በማለት ሲሆን ይህንኑ ክርክራቸውን በ12/11/04 አዘጋጅተው ባቀረቡት የተሻሻለ አቤቱታ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠው በሌለው ስልጣን ነው ተብሎ በበላይ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት በክርክሩ ከተጠቀሰው ደንብ ቁጥር 19/1995 አንቀጽ 13/2/ አንፃር ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ለማየት ስልጣን ሳይኖረው ነው በሚል የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የሰጠው ውሳኔ እና ከዚህ ውሳኔ የቀረበለትን አቤቱታ ዘግቶ በማስናበት የጠ/ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ከላይ እንደተጠቀሰው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ጉዳይ በይግባኝ ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ በፍ/ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት ለሰጡት ውሳኔ መሰረት ያደረጉት የከተማ ቦታን በኪራይ ስለመያዝ እንደገና ለመደንገግ በክልሉ የወጣውን ደንብ ቁጥር 19/1995 ሆኖ በተለየም የደንቡን አንቀጽ 13/2/ ደንጋጌ ነው፡፡ ተጠሪው ይዞታውን ለአመልካቾቹ በኪራይ የሰጠው ሆቴል እና ነዳጅ ማደያ ገንብተው በሁለት ዓመት ውስጥ አገልግሎት ላይ እንዲያውሉ ግዴታ በማስገባት መሆኑ እና የተጀመረውን ግንባታ አቁመው ይዞታውን እንዲያስረክቡ ያደረገው ደግሞ ግንባታውን በተባለው ጊዜ አጠናቀው አገልግሎት ላይ አለማዋላቸውን እና የአቅም ውስንነት የታየባቸው መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ መሆኑ በክርክሩ ተረጋግጦአል፡፡ የተጠሪ እርምጃን በመቃወም በመሆኑ የደንቡ አንቀጽ 13 ድንጋጌ በተያዘው ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት ያለው መሆን አለመሆኑ ሊጤን የሚገባው ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ በመሰረቱ ደንቡ የሚደነግገው ሁለቱ ጉዳዮችን ነው፡፡ የመጀመሪያው አስተዳደሩ የከተማ ቦታ በኪራይ ስለሚሰጥበት ሁኔታ እና ከኪራይ ይዞታ ጋር ተያይዞ በአስተዳደሩ እና በኪራይ በለይዞታዎች መካከል ስለሚኖረው አጠቃላይ ግንኙነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የከተማ ቦታን ስለማስለቀቅ ሆነ ቦታ እንዲለቁ በሚደረጉ ባለይዞታዎች እና በአስተዳደሩ መካከል ስለሚኖረው አጠቃላይ ግንኙነት ነው፡፡ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የከተማ ቦታውን እንዲለቅ የማስቀለቀቂያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትዕዛዝ የተሰጠው ባለይዞታ በማስለቀቅ ትዕዛዙ ላይም ሆነ በክሳ ጉዳይ ላይ ቅሬታ የሚኖረው ከሆነ የዚህ ዓይነቱ ቅሬታ የሚስተናገድበትን ስርዓት ጨምሮ ከቦታ ማስለቀቅ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በደንቡ ተደንግገው የሚገኙት ከአንቀጽ 13 ጀምሮ ነው፡፡ የደንቡ አንቀጽ 13/2/ የሚደነግገውም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የከተማ ቦታን ከማስለቀቅ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቅሬታዎን በቀጥታ ለፍ/ቤት ክስ ሊቀርብባቸው የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾቹ ቦታውን እንዲያስረክቡ ተጠሪ የወሰነው ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ተፈልጉአል በማለት ሳይሆን አመልካቾቹ በገቡት ግዴታ መሰረት ግንባታውን በተገቢው ጊዜ አጠናቀው ለአገልግሎት አላበቁም የፋይናንስ አቅም ችግርም ታይቶባቸዋል በማለት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በደንቡ ከአንቀጽ 13 እስከ 16 ያሉት ድንጋጌዎች በጉዳዮ ላይ ተፈፃሚ ሊደረጉ የሚችሉበት አግባብ አይኖርም፡፡ የተያዘው ጉዳይ የኪራይ ይዞታ ማቋረጥን የሚመለከት በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ደንቡ አንቀጽ 10 እና 11 ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ደግሞ የኪራይ ይዞታ ማቋረጥን አስመልክቶ አስተዳደሩ በሚወስዳቸው እርምጃዎች ላይ ባለይዞታው ቅሬታ ሲያድርበት ጉዳይ ሊታይ ስለሚችልበት የደኝነት መድረክ የሚገልጹት ነገር የለም፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው እስከሆነ እና ጉዳዩን ለማየት በሕግ በግልጽ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ሌላ አካል እስከሌለ ደረስ ደግሞ አመልካቾቹ ጉዳያቸውን በቀጥታ ለፍ/ቤት አቅርበው ፍትሕ ከማግኘት የሚታገዱበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 37/1/ እና 79/1/ እንዲሁም የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 4 ድንጋጌዎችም ይህንኑ የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩ በቀጥታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ አይችልም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የት/ብ/ክ/ከመንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 47481 በ04/04/04 እና በመ/ቁ 47436 በ04/04/04 የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 49966 በ03/08/04 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ጉዳዩ በቀጥታ ለፍ/ቤት ክስ ሊቀርብበት የሚችል መሆኑን እና የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን አስተናግዶ ውሳኔ የሰጠው በዚሁ አግባብ መሆኑን በመገንዘብ ሁለቱን የይግባኝ መዝገቦች አንቀሰቅሶ በዋና ጉዳይ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341/1/ መሰረት ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት እንዲመለስ ወስነናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 83915

የካቲት 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ዩሐንስ በቀለ ጠበቃ መረሣ ፍስሃ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት 1. ዐ/ህግ ታመነ ታደሰ ቀረቡ

2. ዐ/ህግ ኬሮ ወ/ሚካኤል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የከተማ ክልል ይዞታ ለማስለቀቅ የተወሰደውን እርምጃ በመቃወም ለፍርድ ቤት የቀረበ ክስ ተጠሪ ሳይጠራ ውድቅ በመደረጉ ምክንያት የቀረበ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በከፋ ዞን ቦንጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች ክስ በቦንጋ ከተማ ካላቸው ይዞታ ውስጥ ተጠሪ ትርፍ ይዘሃል በሚል ምክንያት እንዲለቁ እያደረጋቸው መሆኑን ጠቅሰው ይህንኑ እንቅስቃሴ ተጠሪ በፍርድ ኃይል እንዲያቆሙ እንዲደረግላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የአሁኑ ተጠሪ ሳይጠራ የአመልካች ክስ በትርፍነት የያዙትን ቦታ እንዲለቁ ሲጠየቁ ይህንኑ ለማድረግ አልችልም በሚል የቀረበና ከማዘጋጃ ቤቱ ስልጣን ውጪ ነው በሚል ምክንያት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸው ለከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ሳይጠራ አመልካችን ብቻ በመስማት ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ንብረታቸው ከሕግ ውጪ መውደሙን ቤት፣ ቡና፣ አታክልት፣ ባህር ዛፍ፣ ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል ይህንን ያጠፋው ማዘጋጃ ቤቱ ነው ከስር ክሱን ንብረቱን ገምቼ አላቀረብኩም ከስር የከሰስኩት በሁከት ይወገድ ነው የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አላይም በማለት የዘጋው ያላግባብ ነው እየተጠየቀ ያለው በህጋዊ መንገድ ሰርቼ ላገኘሁት ግምት ሊከፈለኝ ይገባል ብዬ ነው በማለት ጉዳዩን አመልካች እንዳብራሩት በመመዝገብ ይግባኛቸውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ዘግቶባቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪን ጠርተው ጉዳዩን በማስረጃ ሳያጣሩ መዝጋታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታመኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጸሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪን ሳይጠሩ የአመልካችን ክስ መዝጋታቸው ስነ ስርዓታዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለው በጭብጥነት የሚታይ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርቱ በሁከት ይወገድልኝ ስለመሆኑ በይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያስመዘገቡ ሲሆን በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ደግሞ በንብረት ግምት መሰረት የካሳ ይከፈለኝ ክስ ሳያቀርቡ ጥያቄአቸው ለንብረታቸው ካሳ ይከፈለኝ በማለት አቤቱታ እያሰሙ ያሉ መሆኑን ያረጋገጡ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ክስ ለፍርድ ቤት የሚያቀርብ ሰው ክሱን የሚያቀርበበት ስርዓት በሕጉ የተዘረጋ ሲሆን ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ሌላኛውን ወገን ከመጥራቱ በፊት ክሱ ህጋዊ ፎርማሊቲ ያሟላ መሆን ያለመሆኑ መመርመር ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33፣80፣222፣225፣226፣ እና 231 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በህጉ መሰረት ያልቀረበ ክስ ተከሳሽ የሆነውን ተከራከሪ ወገን መጥራት ሳያስፈልግ ሊዘጋ የሚችልበት አግባብ መኖሩን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በህጉ አግባብ መቅረቡ ከተረጋገጠ ደግሞ የግራ ቀኙ የመስማት መብት በሕጉ አግባብ መጠበቅ ያለበት መሆኑን 223፣234፣241 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ክስ ሲመሰርቱ ትርፍ ቦታ መያዛቸውን ተረድተው ለመልቀቅ ፈርመው ለማዘጋጃ ቤቱ ማሳወቃቸውን የከተማው መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን ይህም በትርፉ ቦታ ጥቅም ወይም መብት የሌላቸው መሆኑን በመነሻነት የሚያሳይ ሲሆን አመልካች ቦታውን ልለቅ አይገባም ሲሉ ቆይተው ጥያቄአቸው የካሳ ይከፈለኝ ጥያቄ መሆኑን በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አረጋግጠዋል፡፡ የካሳ ይከፈለኝ ጥያቄ ደግሞ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 225 መሰረት የዳኝነት ተከፍሎበት ያልቀረበ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በመሆኑም አመልካች የክስ አቀራረባቸውን በሕጉ በተዘረጋ ስርዓት መሰረት አስተካክለው ሳያቀርቡ ወጥነት በሌለው አካኋን የጠየቁትን ዳኝነት እየቀሩ የመሰማት መብቱ ሳይከበር ክሴ ተዘግቷል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ የዘጉት አግባብ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/፣222፣225፣226 እና 231/1/ሀ// አንፃር ሲታይ የሚነቀፍ ባለመሆኑ በጉዳዩ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ትዕዛዝ በማጽናት በመ/ቁጥር 50332 ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች ክስ ውድቅ የተደረገው የክስ አቀራረብ ሰርዓቱን አሟልቶ ባለመቅረቡ በመሆኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ሕጋዊ መብታቸውን መሰረት በማድረግ የሚያቀርቡት የካሳ ክፍያ ጥያቄ ካለ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 42501

የካቲት 28 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ታደሠ ታፈሠ ቀረበ

ተጠሪ ፡- የአስር አለቃ ደምሴ ዳምጤ ወራሾች (ሶስት ሰዎች) - ለራሣቸውና ለሌሎች ወኪል - ደጀኔ ደምሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአንድ የማይንሰሣቀስ ንብረት ላይ የባለቤትነት መፋለም ክስ በመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ከታየና የመጨረሻ ፍርድ ካረፈበት በኃላ ጉዳዩ ለአፈፃፀም ተይዞ ባለበት ሁኔታ ለፍርዱ መሠረት የሆነውና በአስተዳደር አካሉ የተሰጠ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በአስተዳደር አካሉ ሲመክን በፍርድ አፈፃፀም ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን ሕጋዊ ውጤት የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት የተያዘውና ለአሁኑ ክርክር መነሻ በሆነው የአፈፃፀም ጉዳይ የፍርድ ባለመብቶች የሆኑት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆኑ አመልካችና አቶ ክፍሉ ዮሴፍ የፍርድ ባለእዳ ነበሩ፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ባሁኑ አጠራር በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08 ክልል ውስጥ የቤት ቁጥር 305 የሆነውን ቤት ፍርድ ያረፈበት መሆኑን ጠቅሰው ቤቱን በፍርድ ሃይል እንዲረከቡ ትእዛዝ እንዲሰጣቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም በፍርድ ባለእዳነት ቀርቦ በሰጠው መልስ የቤቱ ደብተር መሰረዙን ገልፆ የሚፈፀም ውሣኔ የለም ሲል ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካችን ምክንያት ባለመቀበል ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ የፍርድ አፈፃፀም ትእዛዝ የአሁን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀረብም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የተጠሪዎች የባለቤትነት ደብተርና ካርታው ተሰርዟል፣ ፍርዱ ሊፈፀም የሚችል አይደለም የባለቤትነት ማረጋገጫው የተሰረዘበትን ደብዳቤ እስካላሻሩ ድረስ ቤቱን ልናስረክብ አይገባም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 280 ድንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ የባለቤትነት ማረጋገጫው ደብተር ተሰርዟል እየተባለ አመልካች ቤቱን ሊያስረክብ ይገባል ተብሎ የመታዘዙን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀረበው መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪዎች በጽሑፍ በሰጡት መልስም የባለቤትነት ማስረጃውን አምክኗል የተባለው ደብዳቤ ከዚህ ቀደም በነበረው ክርክር ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቀርቦ ክርክር ተደርጎበት ውድቅ መደረጉን የመሬት ልማት አስተዳደር መምሪያው ማስረጃውን ያመከነው አምኖበት ሣይሆን ፍትሕ ሚኒስቴር በሕግ ከተሰጠው ስልጣን ውጪ ባስተላለፈው ትእዛዝ መሰረት መሆኑን ጉዳዩ እስከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ውሣኔ ካረፈበት በኃላ ሊሻር፣ ሊሻሽል የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች በአፈፃፀም ጉዳይ የሰጡት ትእዛዝ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም አመልካች የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩ ተሰርሿል በማለት የሚያቀርበው ምክንያት እንደ ፍርዱ ላለመፈፀም የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ ምላሽ የሚያስፈልገው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክር መሠረት የሆነው ቤት ተጠሪዎች ሕጋዊ ባለቤትነታቸው በፍርድ ቤት ውሣኔ ተረጋግጦላቸው እንዲረከቡ እስከ የአገራቱ የመጨረሻ የዳኝነት አካል ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደርሶ የሰበር ችሎቱ የመጨረሻ ዳኝነት ያሰረፈበት መሆኑን ተጠሪዎች ክርክሩ በዚህ አግባብ የመጨረሻ መፍትሔ ከአገኘ በኃላ የፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ እንዲፈጸምላቸው የአፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው ተገቢውን መዝገብ በሕጉ አግባብ ከፍተው አመልካች እንደ ፍርዱ እንዲፈጽም የማይፈጽምበት ሕጋዊ ምክንያት ካለም ቀርቦ እንዲያስረዳ ሲደረግ አመልካች ፍ/ቤት ቀርቦ እንደ ፍርዱ ላለመፈፀም ያቀረበው ምክንያት ለፍርዱ መሠረት የሆነውና የተጠሪዎችን የባለቤትነት መብት የማያረጋግጠው ደብተር በአስተዳደር አካሉ ከፍርድ ቤቱ ውሣኔ በኃላ መክኗል የሚል መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደ ፍርዱ መፈፀም ያለበትም ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች በተዘረጋው ስርዓት አግባብ በመመራት ካልሆነ በስተቀር በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በሌላ አካል ዋጋ የሚያጣበት አግባብ አይኖርም፡፡ ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያስገንዝቡት አቢይ ነጥብ የፍርድ አፈፃፀም ስርዓት ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በእራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር ወይም ውጤት የሚለወጥበት ሥርዓት መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘትና መንፈስ በጥንቃቄ ሲታይም የፍርድ አፈፃፀም ስለፍርድ አፈፃፀም የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመከተል ፍርዱን በተግባር መተርጐም እንደመሆኑ መጠን የአፈፃፀም ስርዓቱ ሕጉን መሠረት ማድረግ ያለበት እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉን መሠረታዊ አላማ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአንስተኛ ወጪ ጊዜና ጉልበት በተፋጠነና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም በሚያስችል አግባብ ሕግ አውጪው ያስቀመጣቸው መሆኑን የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

እንዲሁም በሕግ አግባብ የተሰጠ ፍርድ ዋጋ እንዳይኖው የሚደረግው የዳግም ዳኝነት ወይም የፍርድ መቃወሚያ ጥያቄ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት ቀርቦ ከታየና ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ስለመሆኑ ከፍ/ብሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 እና 358 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ አንድ የአስተዳደር አካል በፍርድ ቤት ክርክር መረታቱን ከተረዳ በኃላ በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን መነሻ በማድረግ ለፍርዱ መሰጠት መሠረት የሆነውን ማስረጃ ዋጋ በማሣጣቱ ምክንያት የፍርድ አፈፃፀም ዋጋ እንዲያጣ የማድረግ ውጤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78/1/ እና 79/1/ እና /4/ ስር የተረጋገጠውንና የተከበረውን የነፃ ፍርድ ቤት መኖርንና የዳኝነት ስልጣን ትርጉም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልባ የሚያደርገው ነው፡፡ ይህ ብቻ ሣይሆን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ሥር የተረጋገጠው የዜጎች ፍትህ የማግኘት መብትም ውጤት ባለው መልኩ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ ጠባብ እንዲሆን የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ክርክሮች መቋጫ እንዳይኖራቸው የሚጋብዝ የፍርድ ቤትን ጊዜ ጉልበትና በጀት ለብክነት የሚዳርግ እንዲሁም ሕዝቡ በፍርድ ቤት አመኔታ እንዳይኖረው የሚያደርግ ነው፡፡ የነፃ ፍርድ ቤት መገለጫው ደግሞ የሕግ የበላይነት መኖሩና መረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ውጤታማ የሚሆነው አንዱ የመንግሥት አካል ሌላኛውን ሲቆጣጠረው ከመሆኑ በተጨማሪ ፍርድ ቤት የራሱን ውሣኔ ዋጋ የማያሣጣና የሕግ መሠረት የሌለውን የአስተዳደር አካል እርምጃ ውድቅ ሲያደርገው መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ፍርድ ቤት በሕገ መንግስቱ አንዱ የመንግስት አካል እንደመሆኑ መጠን የመንግስት የስልጣን አጠቃቀም የተወሰነና የተገደበ መሆኑ ሊያረጋግጥ እንደሚገባ ይህ ሊከወን ከሚያስችሉት መንገዶች አንዱ ደግሞ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ትርጉም እንዲኖረው በማድረግ ስለመሆኑ በሕገ መንግስቱ ስለፍርድ ቤቶች ስልጣን ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እና በአገራቱ የሕግ አካል ከሆኑ አለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ ከሰፈሩት መርሆዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ከላይ እንደተጠቀሰው ሕገ መንግስቱ ከተመሠረተባቸው መርሆች አንዱ የሕግ የበላይነት ስለመሆኑ በሕገ መንግስቱ መግቢያው ላይ የሰፈረ ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድ ቤት ለሁሉም ወገኖች እኩል ተፈፃሚነት ባለው ሕግ መመራት ያለበት ስለመሆኑም የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 25 እና 13/1/ ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ በማየት መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በሕግ አግባብ የተቋቋመ ፍርድ ቤት አከራክሮ መወሰን ብቻ ሣይሆን የወሰነው ውሣኔ ውጤት ባለው መልኩ ወደ ተግባር መለወጡን ጭምር ማረጋገጥ አብይ ሀላፊነትና ተግባር በመሆኑ ይህንኑ በሕግ የተሰጠውን ስልጣን አንድ የመንግስት አካል የሚዘረጋው አሠራር ወይም የሚወስደው እርምጃ በፍርድ ቤቶች የፍርድ ስርዓት ላይ /በዳኝነት አካሉ ላይ/ የሚያመጣው ውጤት በሕግ የተመሠረተና የሚገዛ ስለመሆኑ ማየት የግድ ይላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድ የአስተዳደር አካል የቤት ባለቤትንት ማስረጃ በፈለገው ጊዜ ከሕግ ውጪ እንዲሰረዝ ማስቻል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/1ና2/ ድንጋጌ ሥር የተከበረውን የንብረት ባለቤትነት መብት ዋጋ የሚያሣጣው ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲነበቡም የአስተዳደር አካል በባለቤትን ማረጋገጫ ማስረጃ አሰጣጥ ላይ ፍጽም የሆነ አስተዳደራዊ ስልጣን ያለው ስለመሆኑ አያሣዩም፡፡ ይልቁንም ድንጋጌዎች እርስ በእርሣቸውም ሆነ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1198 ድንጋጌ ጋር ተዛምደው ሲታዩ የባለቤትን ማረጋገጫ ደብትር የሚሰርዘው በሕጉ በተመለከቱት ምክንያቶች ብቻ መሆኑን ከሕጉ ውጪ ተግባሩ ተከናውኖ ከተገኘም መብቱ የተነካው ሠው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣78 እና 79 ድንጋጌዎች መሠረት ጉይዩን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቅርቦ አቤቱታው እንዲታይለት የሚያርግበት ጉዳይ እንጂ አስተዳደር አካሉ የሰጠው ውሣኔ በፍርድ ቤት እንዳይታይ የሚገደብበት ስርዓት የሌለ መሆኑን የምንገነዘበው ነው፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ቀድሞ በፍርድ ቤት በነበረው ክርክሩ ተሣታፊ ሁኖ በፍርድ ኃይል ከተረታ በኃላ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በሕጉ አግባብ እንዳይፈጽም በሚል እሣቤ በዋናው ክርክር ጊዜ የተጠሪ ባለቤትነት የተረጋገጠበትን ማስረጃ በመሠረዝ ፍርዱን አስራካሪውን ቤት አላስረክብም ማለቱ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑና የበታች ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ የአመልካች ክርክር ውድቅ በማድረግ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል የሰጡት ውሣኔ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 64032 ህዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75215 ታህሣስ 24 ቀን 2001 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ቀድሞ የክርክሩ ተሣትፊ ሁኖ እስከ በላይ ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር ተረቺ መሆኑ ከተረጋገጠ በኃላ ለቀድሞው ውሣኔ መሠረት የሆነውን የባለቤትነት ምስክር ወረቀት በማምከን አዲስ ክስ የሚመሰርትበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 82234

የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አየለ መኮንን /ከጠበቃ አቶ ምናሴ ዘሪሁን ጋር ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ ወ/ሮ ጦቢያው ወንድም ገዛው

2ኛ ወ/ሮ ውቢት በየነ

3ኛ አቶ ብሩክ በየነ

4ኛ ወ/ት ሰናይት በየነ

5ኛ ወ/ት እጥፍወርቅ በየነ

6ኛ ወ/ት መሰረት በየነ

5ኛ ተጠሪ እና የሁሉም ጠበቃ አቶ አበበ ማስረሻ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ግራ ቀኙን ካከራከረው ጉዳይ አንፃር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 231/1/ሀ/ የተመለከተው ስነ ሥርዓታዊ ድንጋጌ ለጉዳዩ ያለውን አግባብነት ለማየት ሲባል ነው፡፡

የአሁን አመልካች በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ የጉዳዩ መነሻ ሲሆን የዚህም ክስ ይዘት በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 696 የሆነው ቤት አካል የሆነውን ሰርቪስ ቤት ከ2ኛ እስከ 6ኛ ተራ ቁጥር ከተጠቀሱት ተጠሪዎች አባት ከአቶ በየነ ወልደሚካኤል እና ከባለቤታቸው ከአሁን 1ኛ ተጠሪ ጋር ህዳር 27 ቀን 1990 ዓ.ም ባደረግነው የሽያጭ ውል ገዝቼ ተረክቢያለሁ ሻጮችም ቀደም ሲል ቤቱን የገዙበትን ውል እና የግብር ደረሰኝ አስረክበውኛል፡፡ በቤቱም ላይ ያለውን ካርታ ተከታትዬ እንዲሰጣቸው አድርጌያለሁ አስረክቢያቸዋለሁ፡፡ ሆኖም ከዚህ በፊት በሽያጭ ውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት በገዛሁት ሰርቪስ ቤት ላይ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጠኝ ለማድረግ ፈቃደኛ አልሆኑም ስለሆነም የገዛሁት ሰርቪስ ቤት ስመ ሀብትነት በስሜ እንዲዞር ተከሳሾች ስመ ሀብትነትን በሚያዛውር አካል በመቅረብ የመለያ ውል በመፈረምና አስፈላጊ ሰነዶችን ይዘው በመቅረብ ስመ ሀብቱ እንዲዛወር ያደርጉ ዘንድ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎችም በመካከላችን የተደረገ የሽያጭ ውል የለም፡፡ ቢኖርም እንኳ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2879 መሰረት ቤቱንና ሰነዶችን ለገዥ ማስረከብ እንጂ ውል እንድንዋዋል አንገደድም፡ ፍ/ቤቱም ውል ተዋዋሉ ብሎ ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመስጠት አይችልም፡፡ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም የሚለውን ክርክር ካስቀደመ በኋላ ስለዋናው ጉዳዩም ዝርዝር መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ወደ ዋናው ጉዳይ ከመግባቱ በፊት በአሁን አመልካች አማካኝነት የቀረበው ክስ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ መስርቶ እና ጉዳዩን ተመልክቶ በኮ/መ/ቁ 37513 በሆነው በቀን 25/7/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከሳሽ የጠየቁት ዳኝነት ተከሳሾች የሸጡልኝን ቤት ካርታ እና የሽያጭ ውሉን በክ/ከተማው መሬት አስተዳደር በማቅረብ የመለያያ ውል እንዲፈርሙ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ሆኖም ውል በሁለት ተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ የሚቋቋም እንጂ ሁለቱም ቀርበው ውል ሊያደርጉ ይገባል በሚል ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የሚደረግ አይደለም፡፡ ከሳሽ በጠየቀው ዳኝነት መሰረት የሚሰጠው ውሣኔ ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሣኔ መሠረት የሚደረግ አይደለም ከሳሽ በጠየቀው ዳኝነት መሰረት የሚሰጠው ውሣኔ ፍ/ቤት ለሁለት ወገኖች ውል የመፍጠር ያህል ውጤት የሚያስከትል ስለሆነ ጥያቄው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1679 ከተመለከተው ደንጋጌ ዓላማ ውጭ ሆኖ ስለተገኘ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም በማለት በይኗል፡፡

ይግባኙን የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ የአሁን ተጠሪዎቹን መጥራት ሳያስፈልገው ይግባኙን ሰርዞ የአሁን አመልካችን ያሰናበተ የመጨረሻ ዳኝነት በመስጠቱ በዚህ የመጨረሻ ዳኝነት የቀረበ የሰበር ጉዳይ ነው፡፡

ግራ ቀኙ በዚህ የሰበር ደረጃ በየፊናቸው ያላቸውን የጽሁፍ ክርክር ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ብይኑን በሚመለከት በየግላቸው ያቀረቡትን ክርክር የያዘ ከመሆኑም በላይ የዋናውን ጉዳይ ዝርዝር ክርክርንም ሁሉ አካቶ መያዙን የሚያሳይ ነው፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የአሁን አመልካች በጉዳዩ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው መብት የለውም በሚል የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ዳኝነት አግባብነት ለግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ይዘት እና ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

አመልካቹ ባቀረበው ክስ ላይ ግራ ቀኙ ካደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የመነጨ በተሸጠው ንብረት ላይ መብት አግኝቻለሁ በዚሁ ባገኘሁት መብት መገልገል እችል ዘንድ ሻጭ በሸጠው ነገር ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት ለገዥው ለማስተላለፍ በህግ ይገደዳል ስለሆነም የእኔ እና የሻጩ መብትና ግዴታ ታይቶ ሻጭ የሚጠበቅበትን ግዴታ እንዲወጣ ይወሰንልኝ የሚል፤የአሁን ተጠሪዎችም ለአሁን አመልካች መብት ከእኛ ላይ ደግሞ ግዴታ ሊፈጥር የሚችል ህጋዊ ተግባር አልፈፀምንም የቤት ሽያጭ ውል አላደረግንም አድርገናል እንኳ ቢባል የእኛ የግዴታ ውሉን ከሳሹ የሚለውን ሁሉ አይጨምርም በከሳሹ የተጠየቀው ዳኝነት በእኛ አማካኝነት የሚፈፀም አይደለም ከሚለው ጀምሮ በህግ ረገድ ግዴታ ሊፈጥር የሚችል ከከሳሹ ጋር የፈጠሩት ግንኙነት ሁሉ እንደሌለ ገልፀው የተከራከሩበት ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች በየቅላቸው ያቀረቡት ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ እንደተደነገገው ከውል ወይም ከህግ የመነጨ መብትና ግዴታ ያለ መሆኑን ለማመልከት የሚያበቃ ክርክር እንዳቀርቡ አስረጂ ነው፡፡ ይህ መብትና ግዴታ በእርግጥም አለ ወይስ የለም በክርክር ሂደት የሚረጋገጥ ነው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማው በዋናው ህግ የተቀመጡትን መብትና ግዴታዎች ወደ ተግባር ለመለወጥ እንዲያስችል ታስቦ የተዘረጋ ስርዓት እንደመሆኑ መጠን በከሳሽነትም ሆነ በተከሳሽነት

ተሰይመው ለመከራከር በቅድሚያ ክርክሩ ቀጥሎ አንደ ክርክራቸው ሁለቱም ወገኖች በማስረጃ አስደግፈው ቢያስረዱ ለህግ ወይም ከውል የመነጨ መብትና ግደታ ያላቸው መሆኑን ለማመልከት በሚያስችል ደረጃ ክሱ ተብራርቶ እና ተዘጋጅቶ መቅረብ እንዳለበት በሚያስገነዝብ አካኋን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ መደንገጉ እና የእነዚህ ድንጋጌዎችን መስፈርት ባላሟላ ክስ ተከሳሹን መጥራት እንደማያስፈልግ እና ክርክሩም በጅምር ደረጃ ሊቋረጥ እንደሚገባ ተገልፆ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 231/1/ሀ/ መደንገጉም ክርክር ውጤት ኖሮት በመሰረተ ህጉ የተቀመጡትን መብትና ግዴታ ሊያስከብር መቻሉን ለማረጋገጥ ነው፡፡

ከዚህም አንፃር አሁን በግራ ቀኙ መካከል የተነሳውን ክርክር እንዳየነው የአሁን አመልካች ካቀረበው ክስ መረዳት እንደሚቻለው ግራ ቀኖችን ካደረግነው የሽያጭ ውል የመነጨ የንብረት መብት አለኝ፤ ተከሳሾችም ከዚህ ውል የተነሣ ግዴታ አለባቸው ግዴታቸውም የተሸጠውን ነገር ስመ ሀብትነት በሚመለከተው ክፍል ቀርበው ለማዛወር ግዴታ ገብተዋል፡፡ እንደገቡት ግዴታ ይፈጽሙልኝ የሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን የክስ ዝርዝር ጥቅል በማየት የክስ ምክንያቱ እና የሚጠይቀው ዳኝነት ምንድን ነው የሚለውን ከእነ ሙሉ ይዘቱ መውሰድ ሲገባው የመለያያ ውል እንዲያደርጉ የሚለውን ሐረግ ብቻ መውሰዱ በፍ/ብ/ሥ//ሥ/ህ/ቁ 222 እና 224 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ግብና ዓላማ መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡

ተከሳሾችም ቀርበው በሰጡት የመከላከያ መልስ ከከሳሽ ጋር የፈፀምነው የሽያጭ ውል የለም የሚለውንና የመሳሰለውን ክርክር ያቀረቡ በመሆኑ በቅድሚያ ተለይቶ ሊረጋገጥ የሚገባው ጉዳይ ለከሳሽ መብት ለተከሳሾች ደግሞ ግዴታ ሊፈጥር የሚችል ህጋዊ ተግባር ተከናውኗል ወይስ አልተከናወነም? የሚለው እንደመሆኑ መጠን የግራ ቀኙን ክርክር ተመልከቶ እንደ ስነ ስርዓት ህጉ ዓለማ ትርጉም እና ውጤት ያለው ዳኝነት በመስጠት ረገድ በጭብጥ አያያዝ ረገድም ስነ ስርዓታዊ ጉድለት የታየበት ዳኝነት ነው፡፡

ስለሆነም ከሳሽ የአሁን አመልካች ያቀረበው የክስ አቤቱታ ከእነ ሙሉ ይዘቱ ሲታይ ሻጮች ስመ ሀብትነቱን በሚመለከተው ክፍል ቀርበው ሽጠውታል በተባለው ቤቱ ላይ ስመ ሀብትነት ለማዞር የሚያስችል ውል እንዲያደርጉ ሳይሆን የተሸጠውን ንብረት ስመ ሀብትነት ስልጣን ያለው አካል ወደ ገዥው ማዞር እንዲችል አስቀድመው በውሉ ላይ የገቡትን ግዴታና ህጉ በሻጭ ላይ የሚጥለውን ግዴታ እንዲፈፀሙ የሚል በመሆኑ ይኸው የክስ አቀራረብ እና የዳኝነት ጥያቄ ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ አንፃር ሲታይ ክርክሩ ቀጥሎ በግራ ቀኙ ማስረጃ ከመለየቱ በፊት ከወዲሁ ከሳሹ ድሮውንም ቢሆን የክስ ምክንያት የለውም ብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 231/1/ሀ/ መሰረት ዳኝነት ለመሰጠት የሚያስቻል አይደለም፡፡

በመሆኑም ከግራ ቀኙ ክርክር እና ክርክራቸውን ለማስረዳት ካቀረቡት ማስረጃ አንፃር በቅድሚያ ሊታዩ የሚገባቸው የክርክር ነጥቦች እያሉ የአሁኑ አመልካች ያቀረበው የክስ ምክንያትና የጠየቀውን ዳኝነት ሙሉ ይዘቱ እና ሀሳቡ ሳይታይ በስር ፍ/ቤቶች ክሱ የክስ ምክንያት ያለው አይደለም በሚል የሰጡት ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/፣33/3/ እና 231/1/ሀ/ ደንጋጌዎች ትክክለኛ አፈፃፀም የተከተለ ሁኖ ስላላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 37513 በቀን 25/7/2004 ዓ.ም የሰጠው ብይን ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 118522 ግንቦት 06 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የክርክሩን ቅደም ተከተል ጠብቆ በግራ ቀኙ መካከል የተነሱት ሌሎች አከራካሪ ነጥቦች በማስረጃ እንዲለዩ በማድረግ የአሁን አመልካች በህግ ፊት ከፀና ውል ወይም ከህግ የመነጨ መብት የለውም ካልተባለ በስተቀር የግራ ቀኙ ክርክር ከደረሰበት የክርክር ደረጃ አንፃር የአሁን አመልካች የክስ ምክንያት የለውም ሊባል አይችልም ብለናል ስለሆነም የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ክርክሩን ቀጥሎ አስፈላጊውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሰረት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልስናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 72980

ሐምሌ 06 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ይርገዱ አዲሱ - ጠበቃ ይርጉ ሰንበቶ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ሕጻን ምስጋናው ዘሪሁን ሞግዚት - ወ/ሮ ጠጋ ሙለይ
2. ሕጻን መስከረም ዘሪሁን ሞግዚት ወ/ሮ የሺ ባልቻ } ጠበቃ የምስራች ደሣለኝ ቀረቡ
3. ቤቱልሔም ዘሪሁን ሞግዚት ወ/ሮ ሰናይት ሰንደቁ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሚስትነት ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኗ አመልካች የሚች አቶ ዘሪሁን ብርሃኑ ሚስት ናቸው ተብሎ ማስረጃ እንዲሰጥላቸው አመልክተው ፍርድ ቤቱን የአመልካችን በቃለ መሃላ ተደግፎ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ከሚቹ ጋር በአገር ባህል የተጋቡ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ሚስትነታቸውን የሚያረጋገጥ ማስረጃ የሰጠ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎች ሚቹ ከተለያዩ ሴቶች ልጆችን የወለዱና አመልካች በ1996 ዓ/ም ከሚቹ ጋር አብረው ከመኖር ውጪ በሀገር ባህል ተጋብተው የኖሩ ያለመሆኑን ገልፀው ለአመልካች የተሰጣቸው የሚስትነት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱንም ግራ ቀኙን በመቃወሚያ አቤቱታው ላይ ከአከራከረ እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በቀበሌ የቤተሰብ ቅፅ ላይ ሚስት ተብለው የተመዘገቡ ቢሆንም በቤተዘመድና በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ ባልና ሚስት የተቀበሏቸው መሆናቸውን በበቂ ሁኔታ አስረድተዋል ለማለት ስለማይቻል አመልካች ጋብቻ ለመፈጸማቸው የትዳር ሁኔታ እንዳላቸው በማረጋገጥ አላስረዱም የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ ቀድሞ የሰጠውን የሚስትነት ማስረጃ ሰርዞታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የይግባኝ አቤቱታቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ባል ወይም ሚስት በቀበሌ ፎርም ላይ ሞልተው ማረጋገጣቸው ራሳቸውን እንደ ባልና ሚስት እየቆጠሩ የሚኖሩ መሆኑ እና ማህበረሰቡም በዚህ መልኩ የተቀበላቸው መሆኑን እንደሚያመላክት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 20036 ግንቦት 16 ቀን 1998 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 መሰረት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል የሚል ምክንያት በመያዝ ከመቃወሚያው በኋላ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ አመልካች የሚች አቶ ዘሪሁን ብርሃኑ ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህም በኋላ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ከሚች ጋር በባህላዊ የጋብቻ አፈፃፀም ስርዓት ጋብቻ የፈጸሙ እና ይህንኑ የሚያረጋገጥ የሰነድ ማስረጃ በመጥፋቱ ምክንያት ማቅረብ ያልቻሉ ቢሆንም በ1996 ዓ/ም ከሚች ጋር ባደረጉት ስምምነት በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 ጽ/ቤት ሁለታቸውም ቀበሌ ቀርበው በቀበሌው ጽ/ቤት ውስጥ በሚገኘው በሚች የግል ማህደር ላይ ባልና ሚስት ፎርም ቅፅ ላይ በባልና ሚስትነት ስማቸው መመዝገቡንና እስከ እለተሞቱ ድረስ አንድ ላይ በመሆን ንብረት ሁሉ ያፈሩ ስለመሆኑ እየታወቀ አመልካች ከሚች ጋር የመሰረቱት ሕጋዊ ግንኙነት የለም ተብሎ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የሚች ሚስት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከሰ/መ/ቁጥር 20036 አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የተሰጠው ጉዳዩ በአግባቡ ተጣርቶ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ከሰ/መ/ቁጥር 20036 አንፃር መታየት ያለበት ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከሚች ጋር ሕጋዊ ጋብቻ መስርተናል የሚሉት በባህላዊ የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓት ሲሆን ይህንኑ ያሳያል የሚሉት ሰነድም የጠፋባቸው ስለመሆኑ ገልፀው ከመከራከራቸውም በላይ በ1996 ዓ/ም ግን ከሚች ጋር በክፍሉ ቀበሌ ጽ/ቤት ቀርበው በባልና ሚስት ፎርም ላይ ቅጹን የሞሉ መሆኑንና ከሚች ጋር በባልና ሚስትነት ይኖሩ እንደነበር በመዘርዘር መሆኑን፣ ተጠሪዎች የአመልካችን ከሚች ጋር ጋብቻ አልፈፀሙም በማለት የሚከራከሩት ለአንድ ወር ከሚች ጋር ከመኖራቸው ውጪ ጋብቻ አልመሰረቱም፣ በባልና ሚስትነትም የሚታወቁ አይደሉም፣ ሚች ሌሎች ሴቶች ጋር ህጋዊ ግንኙነት የነበራቸው በመሆኑ ከአመልካቻቸው ጋር በጋብቻ ውስጥ አልነበሩም በማለት መሆኑንና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው አመልካች ቀድመው ማስረጃ ሲወስዱ ከሚች ጋር በአገር ባህል እንደተጋቡ አድርገው ገልፀው ቆይተው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ደግሞ በ1996 ዓ/ም ቀበሌ ፅ/ቤት ቀርበን ቅፁን ሞልተናል ማለታቸው ቀድሞውንም ጋብቻ ያልፈጸሙ መሆኑን እንደሚያጠራጥር፣ ይልቁንም እንደ ባልና ሚስት ሁነው ይኖሩ እንደነበረ መግለፃቸውን እንደሚያሳይ ጠቅሶ ጋብቻ መኖሩ ተገልጾ ክርክር ባልቀረበበት ሁኔታ ደግሞ ጋብቻ መኖር ያለመኖሩን ማስረዳት አለማስረዳትን መመርመሩ አስፈላጊ አይደለም የሚሉ ምክንያቶችን በመያዝ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተመለክተናል፡፡

ከዚህ አንፃርም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን ተጠሪዎች በተቃዋሚነት በጉዳዩ ቀርበው የተከራከሩት የአሁን አመልካች የሚች ሚስት አይደሉም የሚሉበትን ክርክር በማቅረብ ነው፡፡ ተጠሪዎች ይህንኑ ክርክር ለማቅረብ የሚያስችላቸውን የእራሳቸው የሚስትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አላቀረቡም፣ ወይም ህጋዊ ሚስቶች የተባሉትም ቀርበው አልተከራከሩም፡፡ ስለሆነም በዚህ በግራ ቀኙ መካከል በተነሳው ክርክር ለጉዳዩ እልባት መስጠት በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ነጥብ የአሁን አመልካች የሚች አቶ ዘሪሁን ብርሃኑ ሚስት ሊሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይችልበትን ፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ባሁኑ ተጠሪዎች በኩል በሕጉ አግባብ ቀርቧል ወይስ አልቀረበም?፣ ፍርድ ቤቱስ ጉዳዩን በሕጉ አግባብ ማጣራት ነበረበት ወይስ አልነበረበትም? የሚለው ነው፡፡ ከዚህ ነጥብ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከት ተጠሪዎች ሚች ከሌሎች ሴቶች ጋር ጋብቻ መስርቶ ነበር በሚለው ነጥብ ላይ አትኩረው የተከራከሩ ከመሆኑ በቀር የአሁን አመልካች ሚስት ሊሆኑ ያልቻሉበትን ክርክርና ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ምንም እንኳ የእርሷ ሚስትነት ከክርክሩ አካሄድ አኳያ ጥያቄ ውስጥ የገባ ቢሆንም ይህ ግን ፍርድ ቤቱ ራሱ በሚያጣራው ማስረጃ ነጥሮ ሊወጣ ይችል የነበረ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች የሚች ዘሪሁን ብርሃኑ ሚስት መሆን ያለመሆናቸው ጉዳይ መታየት የነበረበት በቀበሌው ውስጥ ተሞልቷል የተባለው ቅጽ አሞላሉ እንዴት እንደነበር (ሚችና አመልካች በግንባር ቀርበው መሆን ያለመሆኑ፣ የባልና ሚስት ሁኔታን ሊያረጋገጥ የሚችል ማስረጃ በቀበሌው ጽ/ቤት ቀርቦ ታይቶ መሆን ያለመሆኑና ሌሎች የቀበሌ ጽ/ቤቱ የሚከተላቸው አሰራሮች ምን ምን እንደሆኑ) ከተጣራ በኋላ መሆን እንደነበረበት ተረድተናል፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን ከተገነዘበ ይኸው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ሁሉ ማድረግ እንደሚችል ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136፣137፣ 272፣ 327(3)፣ 345 እና ከሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ደንብ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች ክርክር ወጥ ያለመሆኑን በመግለጽ ውሳኔ መስጠቱም አጠቃላይ የክርክሩን ይዘትና ፍርድ ቤት እውነትን ለማውጣት በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት ተግባር ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ሊወሰን የቻለው በክርክሩ ሂደት ሊጣራ የሚገባቸው ነጥቦች ባልተሟሉበት ሲሆን የክርክር ሂደት ሳያሟላ ዳኝነት መስጠት ደግሞ የፍርድ አካሄድ ስርዓት የሚቀበለው ጉዳይ ባለመሆኑ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው አመልካች ከሚች አቶ ዘሪሁን ብርሃኑ ጋር በሕግ አግባብ ጥበቃ ሊደረግ የሚችል ግንኙነት መኖር ያለመኖሩን በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 94 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንዲሁም በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 20036 በተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ለመወሰን በቅድሚያ አመልካች የአገር ባህል የጋብቻ ስርዓት የፈፀሙ ስለመሆኑ ያሳያል ያሉት ሰነድ የጠፋ መሆኑን የገለፁ ስለሆነ ይኸው ፍሬ ነገር ተገቢ ነው በተባለው መንገድ ሁሉ እንዲጣራ፣ በ1996 ዓ/ም አመልካች ሚች አቶ ዘሪሁን በቀበሌው ጽ/ቤት ፎርም ሲሞሉ ባልና ሚስት ናቸው ተብሎ እንዴት ሊሞላ እንደቻለና በቅጽ ባልና ሚስት ተብሎ መሞላቱ ስላለው ውጤት የክፍሉ ቀበሌ መግለጫ እንዲያቀርብ ማድረጉ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓቱ የግድ የሚለው ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1879/02 መጋቢት 08 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 16359 ጳጉሜ 01 ቀን 2003 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15639 ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔም ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1879/02 ክርክሩን ቀጥሎ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተመለከተው አግባብ ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(2) መሰረት መልሰንለታል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 82679

መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ከበቡሽ ሸዋረገድ / አክሊሉ አበባው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- ወ/ሮ እንዳገር ጌቱ - ጠበቃ ጌታሁን ተስፋዬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በጋብቻ የተፈራ የጋራ ሀብት ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት ተጠሪና ወ/ሮ እብስቴ በልስቲ አመልካች የአሁን አመልካችና እነ ጤናዬ በልስቲ ተጠሪዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ የተነሳው የሟች በልስቲ አወቀ ውርስ በሚጣራበት ወቅት ነው፡፡ አመልካች 1960 ዓ.ም ጀምሮ ሟች ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለየበት ድረስ በህጋዊ ጋብቻ ተሳስረን ኖረናል፡፡ በጋብቻ ስንኖር በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 09/15 የቤት ቁጥር 487 የሆነውን ቤት አፍርተናል፡፡ ስለዚህ ይህ ቤት ግማሹ የሟች በልስቲ አወቀ ግማሹ ደግሞ የአመልካች ማለትም የከበቡሽ ሸዋረገድ መሆኑ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 09/15 የሚገኘው የቤት ቁጥር 457 ሟች አቶ በልስቲ አወቀ ከእኔ ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበረበት ጊዜ ያፈሩት ንብረት ነው፡፡ ስለዚህ የቤቱ የጋራ ባለሀብት እኔ ነኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሟች አቶ በልስቲ አወቀን ውርስ እንዲያጣራ የተመደበው ውርስ አጣሪ በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 08/15 የቤት ቁጥር 487 ሟች አቶ በልስቲ አወቀ ከማንኛቸው ጋር እንዳፈራው አከራካሪ በመሆኑ ፍ/ቤቱ መርምሮ ውሳኔ ይስጥበት በማለት አስተያየት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፣ አከራከሪውን ቤት ሟች በልስቲ አወቀ ከወ/ሮ ከበቡሽ ሸዋረገድ ጋር ያፈራው ንብረት ነው፡፡ ስለዚህ የቤቱ ግማሽ ባለሀብት ወ/ሮ ከበቡሽ ሸዋረገድ (አመልካች) ናት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሸኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርባለች፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የቤቱ ግማሽ ባለሀብት ወ/ሮ አንዳገር ጌቱ (ተጠሪ) ናት በማለት የሥር ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች ይህንን በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርባለች፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች (ይግባኝ ባይ) ተጠሪ (መልስ ሰጭዋ) ከሚች ጋር ከተለያየች አስር ዓመት ካለፈው በኋላ ያቀረበችው የጋራ ንብረት ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረብኩትን መከራከሪያ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አላግባብ ውድቅ አድርጎብኛል፡፡ ቤቱም የጋራ ንብረቴ ሆኖ እያለ የጋራ ሀብትሽ አይደለም መባሉ ስህተት ነው በማለት ያቀረበችውን የይግባኝ ቅሬታ ለማጣራት ጭብጥ ይዞ፣ መልስ ሰጭ (ተጠሪን) በማስቀረብ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይርጋውን ክርክር አመልካች አንስተው ቢሆን እንኳን፣ ይህንን የይርጋ መከራከሪያ ሁለቱ ፍ/ቤቶች ያልተቀበሉት በመሆኑ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለሶስተኛ ጊዜ ይህንን መከራከሪያ ሊመረምር እንደማይችል በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 የተደነገገ በመሆኑ ይህንን መከራከሪያ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ መርምሮ የመወሰን ሥልጣን ስለሌው አልፈነዋል፡፡

ቤቱ የይግባኝ ባይ (የአመልካች) የጋራ ሀብት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ መልስ ሰጭ (ተጠሪ) የሚች ሚስት መሆኗን በማረጋገጥ የደብረ ኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ ቤቱም ይግባኝ ባይ (አመልካች) ከሚች በልስቲ አወቀ ጋር በጋብቻ ስትኖር ያፈራችው ስለመሆኑ ያስረዳል ተብሎ የቀረበው ማስረጃ ቤቱን ይግባኝ ባይ ከሚች ጋር ያፈሩት መሆኑን የማስረዳት ብቃት የለውም፡፡ ስለዚህ አከራከሪው ቤት ሚች አቶ በልስቲ አወቀ ከመልስ ሰጭ(ተጠሪ) ጋር ያፈሩት ሀብት ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሠጡትን ውሳኔ ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 07 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የሚች በልስቲ አወቀ ሚስት መሆኗን አረጋግጣ ያቀረበችው የሚች መደበኛ የመኖሪያ ቦታ ባልሆነው ምስራቅ ጎጃም ዞን በሚገኘው ደብረኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ይህንን ማስረጃ በመቃወም ማስረጃው ትክክለኛውን ፍሬ ጉዳይ የማያሳይ መሆኑን ያቀረብኩትን ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመጀመሪያ የደብረኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ አላሻረም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው የሕግ ስህተት አለበት፡፡

ተጠሪ ከሚች ጋር ከተለያየች አስር ዓመት ያለፋት መሆኑን በመግለፅ የተጠሪ ክርክር በይርጋ ይታገዳል የሚለውን ክርክር ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት አቅርቤያለሁ፡፡ ይህ የይርጋ መከራከሪያ መታለፉ ተገቢ አለመሆኑን በመግለፅ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተከራክሬያለሁ፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማጣራት እንዲወስንልኝ ያቀረብኩትን ክርክር በይግባኝ ደረጃ እንደተነሳ አዲስ ክርክር አድርጎ በመውሰድ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ተጠሪ ሚች በልስቲ አወቀ 1954 ቦታውን የተመራ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከማቅረቧ ውጭ ቤቱ 1954 የተሰራ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበችም፡፡ ስለዚህ ቦታው የተመራበትን ጊዜ ቤቱ እንደተሰራበት ጊዜ በመውሰድ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክታለች፡፡

ተጠሪ በበኩሏ ታህሳስ 5 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ቤቱ እኔና ሚች ከተጋባን ከአራት አመት በኋላ የተፈራ ነው፡፡ አመልካች ቤቱ ሲሰራ አልነበሩም፡፡ የይርጋ ክርክር ለስር ፍ/ቤት አላቀረቡም፡፡ የሚስትነት ማስረጃ ከሚች መደበኛ መኖሪያ ውጭ በሚገኝ ፍ/ቤት አስወስኖ በመቅረብ የጋራ ሀብት መጠየቅ የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ ስለዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ተጠሪ ከሚች ጋር የነበራት ጋብቻ ከሃምሳ ዓመት በኋላ ያቀረበችውን ጥያቄ በመቀበል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አከራከሪው ቤት የሚች በልስቲ አወቀና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ባህሪና ሕጋዊ ውጤት እንዲሁም አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችና ይኽ ሰበር ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ግራ ቀኙ በስር ፍ/ቤት በይግባኝና በሰበር ያቀረቧቸውን ክርክሮችና በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካችና ሚች በልስቲ አወቀ 1960 ዓ.ም ጋብቻ ፈፅመው በትዳር ፀንተው የኖሩና ጋብቻቸው በሚች መሞት ምክንያት የተቋረጠ መሆኑን በስር ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ ከአመልካች ጋር 1950 ዓ.ም ጋብቻ ፈፅመው የነበረ መሆኑና ተጠሪ የሚች ሚስት መሆኗን በማረጋገጥ የደብረኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት የሚስትነት ማስረጃ እንደሰጣት ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክርና የበታች ፍ/ቤቶች ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተረድተናል፡፡

ተጠሪ የሚች ሚስት መሆኗን ለማስረዳት የደብረ ኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጣትን የሚስትነት ማስረጃ ብታቀርብም ተጠሪ ከሚች በልስቲ አወቀ ጋር ተለያይታ የኖረች መሆኑን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም ፅፋ ባቀረበችው አቤቱታዋ ያመነች መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍ/ቤት በውሳኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ተጠሪ ከሚች ጋር የነበራት ጋብቻ የፈረሰ መሆኑን ጋብቻው ከፈረሰ ከሃምሳ ዓመት በኋላ የጋራ ንብረት አለኝ በማለት የክፍያ ጥያቄ ማቅርቧ ተገቢ አለመሆኑን ለዚህ ሰበር ችሎት ነሐሴ 7 ቀን 2004 ዓ.ም ፅፋ ባቀረበችው የሰበር አቤቱታ በግልፅ በማስፈር ተከራክራለች፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ የሚች ሚስት መሆኔ በውሳኔ ተረጋግጧል ከማለት ውጭ ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ ሚች ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩ ጊዜ ድረስ ከሚች ጋር የነበረን ጋብቻ አልፈረሰም በማለት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 234(1) በሚደነግገው መሰረት በግልፅ ክዳ ያቀረበችው ክርክር የሌለ መሆኑን ተጠሪ ለዚህ ሰበር ችሎት ታህሳስ 4 ቀን 2005 ዓ/ም ፅፋ ያቀረበችውን መልስ የዘት በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ተጠሪ ከሚች ጋር ከተለያየች ሃምሳ ዓመት ሆኖታል በማለት አመልካች በሰበር አቤቱታዋ ያቀረበችውን ክርክር በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 235(2) መሰረት እንዳመነች የሚያስቆጥራት ነው፡፡

ተጠሪ የሚች ሚስት ስለመሆኗ የደብረ ኤልያስ ወረዳ የሰጣትን የሚስትነት ማስረጃ ብታቀርብም በፍሬ ጉዳይ ደረጃ አመልካችና ተጠሪ ተለያይተው የኖሩ መሆኑንና አመልካች ከሚች ጋር ከ1960 ዓ.ም ጀምሮ በፀና ጋብቻ የኖረች መሆኑን ተጠሪ በክርክር ሂደት ለስር ፍ/ቤት ካቀረበችው የፅሁፍ አቤቱታና ለዚህ በሰበር ችሎት ከሰጠችው መልስ በመሸሽ መልክ ካቀረበችው ክርክር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ አከራከሪው ቤት በሚች አቶ በልስቲ አወቀና በአመልካች ስም የተመዘገበና አመልካች የቤቱ የጋራ ባለሀብት መሆኗን የሚያሳይ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ያላት መሆኑን ተጠሪም የምትክደው አይደለም፡፡ ተጠሪ የምትከራከረው ቤቱ የተሰራው ሚች አመልካችን ከማግባቱ በፊት ነው በማለት ነው፡፡

2. ከላይ የገለጽናቸው ፍሬ ጉዳዮች የአመልካችና የተጠሪን የማስረዳት ኃላፊነት በማቅለል ወይም በማክበድ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ናቸው፡፡ አመልካች ከሚች በልስቲ አወቀ ጋር ከ1960 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚች ህልፈተ ህይወት በፀና ጋብቻ መኖራቸው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 62(1) በአንደኛው ተጋቢ ስም ቢመዘገብም ማንኛውም ንብረት የባልና የሚስቱ የጋራ ሀብት ናቸው ተብለው ይገመታሉ በማለት በግልፅ የደነገገው የህግ ድንጋጌ ተጠቃሚ የምትሆነው አመልካች መሆኗን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ከሚች ጋር ተለያይታ የኖረች መሆኑ ለስር ፍ/ቤትና ለሰበር ያቀረበችው ክርክር ስለሚያሳይ የአዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62(1) የተደነገገው የሕግ ግምት ተጠቃሚ አትሆንም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ከሚች በልስቲ አወቀ ጋር የቤቱ የጋራ ባለሀበት ሆና የማይንቀሳቀሰው ንብረት መዝገብ ውስጥ መመዝገቧና አመልካች ከሚች ጋር ባለሀብት መሆኗን በአስተዳደሩ ክፍል የተመዘገበ መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የቤቱ ባለሃብት እንደሆነች የሚያስገምት እንደሆነ ከህጉ ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ አመልካች የቤቱ የጋራ ባለሀብት መሆኗ ከላይ የገለፅናቸው የሕግ ድንጋጌዎች የህሊና ግምት የሚወስድበት በመሆኑ በሕጉ የተደነገገውን ግምት ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ የማፍረስ ወይም የማስተባበል ግዴታው ያለባት ተጠሪ ናት፡፡ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62(1) የተደነገገውንና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195(1) የተደነገገውን የአመልካችን የቤቱን የጋራ ባለሀብትነት ግምት ለማፍረስና ለማስተባበል የሚያስችል ማስረጃ የማቅረብ ኃላፊነት አለባት፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው ተጠሪ ሚች ቦታውን 1954 ዓ.ም መመራቱን የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረብ ከላይ በተገለፁት የሕግ ድንጋጌዎች የተደነገገውን የአመልካችን የቤቱ የጋራ ባለሀብትነት ግምት የማፍረስ ወይም የማስተባበል ግዴታና ኃላፊነት ለመወጣት አትችልም፡፡ በተለይም ተጠሪ አመልካች ከሚች ጋር የቤቱ ባለሀብት መሆኗ የቤቱ ዕርስተ መዝገብ የተመዘገበች መሆኗንና በቤቱ ባለቤትነት የአስተዳደሩ ክፍል መዝገብ ላይ ስሟ በባለሀብትነት መገለፀን፣ ለማስተባበል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ከተደነገጉት ሁኔታዎች አንደኛውን በማስረጃ በማረጋገጥ የማስተባበል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195(1) የተደነገገውን የአመልካችን የቤቱ የጋራ ባለሀበትነት ግምት የማስተባበልና የማፍረስ ኃላፊነቷን ባልተወጣችበት ሁኔታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ቤቱ የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የሚች ሚስት ስለመሆኗ በደብረኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጣት ማስረጃ (ውሳኔ) እውነታውን የሚያንፀባርቅ አይደለም በማለት አመልካች ተቃውሞ ብታቀርብም የወረዳው ፍ/ቤት ሚስትነቷን በመግለፅ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 360(2) መሰረት ካላሰረዘ ተጠሪ የሚች ሚስት ናት ወይስ አይደለችም የሚለውን ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ስልጣን የለኝም በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንዳለፈው ከውሳኔው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተረድተናል፡፡ የደብረኤልያስ ወረዳ ፍ/ቤት የተጠሪን አቤቱታና ማስረጃ ብቻ በመቀበል የሰጠው የሚስትነት ማስረጃ በማስረጃነት በቀረበበት በማናቸውም ጊዜ ተዓማኒነትና ክብደት የሌለው ማስረጃ መሆኑን ለማሳየት ክርክር ሊቀርብበትና ተቃራኒ ማስረጃ ተሰምቶ ውድቅ ሊደረግ የሚችል (Declaratory Judgment) ነው፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪን ሚስትነት በመግለፅ የሰጠውን የሚስትነት ውሳኔ አመልካች ካላሻረች ውሳኔውን መቃወምም ሆነ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እውነትነት የሌለው መሆኑን መከራከር አትችልም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠው የሚስትነት ማስረጃ ትክክል መሆን አለመሆኑን የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የለውም በማለት የተሰጠው ትርጉም ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 14290 እና የሰ.መ.ቁ 17058 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

4. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበችውን የይርጋ ክርክር መነሻ በማድረግ ለአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 የሰጠው ትርጓሜ ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ስልጣን የሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር 25/1988 ይግባኝ ሰሚው ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው የተለየ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ስልጣን እንዳለው በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ደንግጓል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካች የጋራ ሀብት ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ስልጣኑ አይቶ በመሻር ቤቱ የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምራ የይርጋ መከራከሪያ እንዳነሳች ገልፃ የከፍተኛው ፍ/ቤት ጥያቄው በይግባኝ ደረጃ እንደተነሳ በውሳኔው የገለፀውና መከራከሪያውን ውድቅ ያደረገው ስህተት ስለሆነ በይግባኝ ታይቶ ይሻርልኝ በማለት ጠይቃለች፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9(2) አንድ ተከራካሪ ያነሳው የህግ መከራከሪያና ምክንያት በስር ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከታለፉ የክርክሩ ውጤት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ቢለውጠውም በሁለቱም ፍ/ቤቶች የታለፈውን የሕግ መከራከሪያ በይግባኝ የማየት ስልጣን እንደሌለው በመግለፅ የሰጠው ትርጓሜ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ይዘት ዓላማና ተግባራዊ ተፈፀሚነት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራካሪው ቤት የአመልካች ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመለወጥ አከራካሪው ቤት የተጠሪ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9(2) በተጠበቀላት የይግባኝ መብት ተጠቅማ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ለማሳረም ያቀረበቻቸውን የፍሬ ጉዳይና የሕግ ክርክሮች የመመርመርና ውሳኔ የመስጠት የስረ ነገር ሥልጣን ብቻ ሣይሆን ኃላፊነትና ግዴታ በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ተጥሎበታል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መከራከሪያ በሁለቱ ፍ/ቤቶች የታለፉ በመሆኑ በይግባኝ የማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው የህግ ትርጉም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው የሕግ ምክንያቶች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌዴራል ክፍተኛ ፍ/ቤት አከራካሪው ቤት የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ክፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በጉለሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 09/15 የሚገኘው ቁጥሩ 487 የሆነው ቤት የአመልካችና የሟች በልስቲ አወቀ የጋራ ሀብት ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 83582

መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ረታ ቶሎሣ
መስጠፉ አሕመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ ውብነህ አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡- 1. ወ/ሮ አልማዝ ዓለሙ
2. አቶ አለባቸው አሰፋ } ጠበቃ ብርሃኑ ቀረቡ
3. አቶ ታደሰ ገብሬ በሌሉበት ታይቷል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ያፀደቀው የእርቅ ስምምነት ያስረዝልኝ በሚል መንገድ የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቅራቢ /አመልካች ተጠሪዎች የፍርድ መቃወሚያ ተጠሪዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ በኮልፌ ቀራንዩ ክፍል ከተማ ወረዳ 7 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥር ያልተሰጠውን አዲስ ቤት ከሶስተኛ ተጠሪ እኔ በሕጋዊ ውል ገዝቼና ተጨማሪ ግንባታ በማካሄድ እየተገለገልኩበት እገኛለሁ፡፡ ሆኖም አንደኛ የመቃወም ተጠሪና ሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ በመካከላቸው በፍርድ ቤት ሲያደርጉት የነበረው ክርክር ለማቋረጥና ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ለእዳ መክፈያ እንዲሆን በመግለጽ በመስማማት ይህንን ስምምነታቸውን ፍርድ ቤቱ እንዲያውቅና እንዲመዘግበው በማድረግ እኔ ተካፋይ ባልሆንኩበት ክርክር ንብረቴን ለማሸጥ በማንቀሣቀስ ላይ ናቸው፡፡ ስለዚህ እኔ በክርክሩ ገብቼ ውሣኔው እንዲሰረዝልኝ በማለት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቀርባለች፡፡ ተጠሪዎች የእዳ መክፈያ እንዲሆን የእርቅ ስምምነት ያደረጉበትን ቤት፣ እኔ ከእዳና እገዳ ነፃ መሆኑን አረጋግጪ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በተደረገ ውል ከሶስተኛው ተጠሪ ገዝቼ ቤቱንና ይዞታውን ተረክቤያለሁ፡፡ ቤቱን በማሻሻ ከተረከብኩ በኃላ በከፍተኛ ወጭ ተጨማሪ ግንባታ ሥራ ሠርቻለሁ፡፡ የሥር ፍርድ ቤት 06-04-2002 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ቤቱ በፍርድ አፈፃም መምሪያ ሊሸጥ የሀራጅ ማስታወቂያ በግድግዳው ላይ ሲለጠፍበት ሁኔታውን በማወቁ በመጀመሪያ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 418 መሠረት በአፈፃፀም ጣልቃ ገብቼ መቃወሚያየን አቅረብኩ፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ችሎት በመጀመሪያ የእርቅ ስምምነቱን የመዘገበው ችሎት በእርቁ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንዲፈፀም የሰጠውን ትእዛዝ ሣይሰረዝ ጥያቄሽ ተቀባይነት የለውም በማለት መቃሚያን ውድቅ አደረገብኝ የሥር ፍርድ ቤት መዝግቦና በፍርድ ቤቱ ማህተም አረጋግጦ ያስተላለፈው በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል እየተፈፀመ ያለውን ከፍርድ ቤቱ የፀደቀው የአፈፃፀም ስምምነት እኔ ባለሁበት ታይቶ እንዲሰረዝ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርቤለት ውድቅ አድርጎብኛል፡፡ ስለዚህ ውሣኔው የእኔን መብትና ጥቅም የሚነካና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምለኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ በበኩላቸው አንደኛ ተጠሪና 3ኛ ተጠሪ በጋብቻ ተሣስረን የኖርን ባልና ሚስት ነበረን በ1996 ዓ.ም ጋብቻችንን በስምምነት ስናፈርስ የጋራ ሃብት የሆነውን ክርክር የተነሣበትን ቤት እኩል እንድካፈል የትግራይ ክልል ማህበራዊ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ በኃላ ሁለተኛው ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት አለኝ በማለት በመያዙ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርቤ ተጠሪዎች በስምምነትና በእርቅ ጉዳዩን በመጨረሣችን፣ የሥር ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182 መሠረት የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡ አመልካች ፍርድ ቤት ያልሰጠውን ውሣኔ አንዲሰረዝላት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ ከሚያዘው ውጭ ያቀረበችው የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ የአንደኛ አንደኛ ተጠሪ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ ባቀረቡበት ቤት ላይ ክርክር ተካሂዶ በዚህ ፍርድ ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ የለም፡፡ መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው ሶስተኛው ተጠሪ እንጂ አመልካች አይደለም፡፡ ማመልከቻቸው ውድቅ ይደረግ በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን፣ ሁለተኛ ተጠሪ ከአንደኛ ተጠሪ የተለየ ምላሽ የለኝም ብሏል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ መልስ አላቀረበም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ቤቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የሰጠው ውሣኔ የለም፡፡ መዝገቡ የተዘጋው ተከራካሪ በነበሩት ተጠሪዎች ጥያቄ ነው፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ የሰጠው ውሣኔ ባለመኖሩ የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ የሕግ መሠረት የሌለው ነው በማለት የአመልካችን የመቃሚያ ማመልከቻ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ባልና ሚስት የሆኑት አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የጥቅም ተካፋያቸው ከሆነው ሁለተኛ ተጠሪ ጋር በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 18281 የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርበው ክርክር ካደረጉ በኃላ፣ በመጀመሪያ ሕዳር 3 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ የእርቅ ስምምነት በማጽደቅ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን እንዲዘጋላቸው ጠየቁ በማስከተል ሕዳር 23 ቀን 2002 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት በማድረግ ፍርድ ቤቱ እንዲያፀድቅላቸው ሲያቀርቡ በመዝገቡ የተያዘው ጭብጥ የሁከት ይወገድልኝ ሆኖ እያለ ቤቱ ተሸጦ የእዳ እንዲሆን በማለት ተስማምተው መቅረባቸውን በመዘርዘር የእርቅ ስምምነቱን ሣያፀድቅ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪዎች ለሶስተኛ ጊዜ የእርቅ ስምምነት አቅርበው ፍርድ ቤቱ 06-04-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 377 መሠረት መዝግቦና በፍርድ ቤቱ ማህተም አረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎችም በሀራጅ ተሸጦ የእዳ መክፈያ እንዲሆን የእርቅ ስምምነት ያደረጉበትን ቤት ቤቱ ከእዳና እገዳ ነፃ መሆኑ ተረጋግጦና በሶስተኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑንና ሶስተኛ ተጠሪም ሚስት የሌለው መሆኑን ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርቦ በሰነዶች ምዝገባ ጽ/ቤት በተደተገ የቤት ሽያጭ ውል አመልካች ገዝቼዋልሁ፡፡ ቤቱን ከሶስተኛ ተጠሪ በውል ከገዛው በኃላ ቤቱንና ይዞታውን ተረክቤ በከፍተኛ ወጭ ተጨማሪ ግንባታ አከናውኛለሁ፡፡ ተጠሪዎች ባደረጉት የእርቅ ስምምነትና የሥር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18281 ታህሣስ 6 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መነሻ ቤቱን በአፈፃፀም በሐራጅ ለማሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ተሰጥቷል፡፡ እኔም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 ጣልቃ ገብቶ ያቀረቡትን መቃወሚያ የእርቅ ስምምነት የፀደቀበት ትእዛዝ ሣታሸሪ በአፈፃፀም ጣልቃ ልትገቢ አትችይም በማለት አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ውድቅ አድርጎብኛል ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ የተጠሪዎች የእርቅ ስምምነት ላይ ተቃውሞ እንዳላቀርብ የሚገድብና የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

አንደኛ ተጠሪ ታህሣስ 1 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቱ ከሶስተኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ሲኖሩ ያፈራው የጋራ ሃብት ነው ጋብቻችን ሲፈርስ ቤቱን እንድንካፈል በማሕራዊ ፍርድ ቤት ተወስኗል፡፡ ሶስተኛ ተጠሪ መደበኛ መኖሪያው መቀሌ ሆኖ እያለ ከባህር ዳር ሚስት የሌለው መሆኑን የሚገልጽ የሐሰት ማስረጃ በማቅርብ ከአመልካች ጋር ያደረገው የሽያጭ ውል እኔ በቤቱ ላይ ያለኝን መብት የሚጎዳ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ በመቀበል ፍሬ ጉዳዩን በማጣራ መወሰን ነበረበት፡፡ ይህንን በማድረጉ እኔን በተጨማሪ ክርክር ማለት ባለሃብትነት የመፋለም ክስ በመዝገበ ቁጥር 24007 እንዳቀርብ አስገድዶኛል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ ተመልሶ ሁለቱ መዛግብት ተጣምረው ተጣርቶ እንዲወሰንልኝ በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ ታህሣስ 22 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ እኔና ሶስተኛ ተጠሪ በሶስተኛ ተጠሪ ስም ቤት በጋራ ገዝተን ለመሸጥ በነበረን ስምምነት ቤቱ በሶስተኛ ተጠሪ ስም ሲገዛ ገንዘብ አዋጥቻለሁ፡፡ ሶስተኛ ተጠሪ ከእኛ በመደበቅ ቤቱን ለመሸጥ ሲንቀሣሰቅ ስለደርስንበት አንደኛ ተጠሪና እኔ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርበንበታል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪም በእርቅ ለመጨረስ ስለተስማማ፣ ጉዳዩ በእርቅ አልቋል ስለዚህ የአመልካች አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የሶስተኛ ተጠሪ መልስ የመስጠት መብት በብይን ተልፏል፡፡
ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክና ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበችውን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ውድቅ ማድረጋቸው ሕጋዊ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18281 አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ከሣሾች ሶስተኛው ተጠሪ ተከሣሽ በመሆን ይከራከሩ ነበር፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን መዝገብ ከዘጋው በኃላ ተጠሪዎች ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በመካከላቸው ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በመመዝገብ ለሚመለከተው ክፍል እንዲያስተላልፍላቸው በመጠየቃቸው የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 18281 በማንቀሣቀስ ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት የፍርድ ቤቱ ማህተም ተደርጎበት ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ በማለት ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር ፍርድ ቤት በፍርድ ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል እዲተላለፍ ትእዛዝ የተሰጠበትና ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደጉት የእርቅ ስምምነት በይዘቱ አመልካች በሕጋዊ ውል ገዝቻዋለሁ የምትለውን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት በሶስተኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቁጥር ያልተሰጠው አዲስ ቤት ተጠሪዎች ባለበት ሁኔታ ሸጠው፣ ዋጋውን ለሶስት እኩል ለመካፈል ያደጉት የእርቅ ስምምነት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በፍርድ ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝና ከዚሁ ትእዛዝ ጋር የተያያዘውን በሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት መሠረት በማድረግ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪዎች የፍርድ ባለመብቶች ሶስተኛው ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ ሆኖ የሚከራከሩት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 184598 ተከፍቶ ቤቱ በባለሙያ ተገምቶ የሀራጅ ማስታወቂያ ወጥቶበታል፡፡

2. አመልካች ፍርድ ቤቱ ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በፍርድ ቤቱ ማሕተም ተረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላፍ ያደረው ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነትና በሶስተኛው ተጠሪ ቤት ላይ የተደረገ የእርቅ ስምምነት አይደለም፡፡ ሶሰተኛው ተጠሪ ቤቱን ለእኔ የሸጠልኝ በመሆኑ የእርቅ ስምምነቱ መጽደቁና በፍርድ ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ መተላለፉ የእኔን መብን የሚነካ ነው፡፡ ስለዚህ ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ተጠሪዎች ያደጉት የእርቅ ስምምነት በመመዝገብ የተሰጠውን ትእዛዝ ይሰረዝልኝ የሚል የመቃወሚያ ማመልከቻ አቅርባለች፡፡

የሥር ፍ/ቤት ታህሣስ 06 ቀን 2003 ዓ.ም ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በፍርድ ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ በማለት የሰጠው ትእዝዛ በይዘቱም ሆነ በሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት የእርቅ ስምምነቱ ሕግና ሞራልን የማይቃረን መሆኑን በመቀበልና በማረጋገጥ የመዘገበው መሆኑ የሚያሣይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 377 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተቀብሎ አጽድቄዋለሁ ብሎ በዝርዝር ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ውስጥ አለመፃፉ ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉትን የእርቅ ውል ተቀብሎ አላፀደቀውም፣አልመዘገበውም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት ህጋዊ ውጤትና አስገዳጅነት በሚያገኝበት መንገድ ትእዛዝ ከሰጠ፣ ተጠሪዎች በፍርድ ቤቱ በማህተም ተረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል እንዲተላለፍ ትእዛዝ የሰጠበትን የእርቅ ስምምነት እንዲፈፀምላቸው መጠየቅ የሚችሉ መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካች በክርክሩ ተካፋይ ሣልሆን የሥር ፍርድ ቤት ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ እውቅና በሰጠውና ባፀደቀው ተጠሪዎች ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በእኔ ንብረት ላይ የተደረገ ነው፡፡ ክርክሬንና ማስረጃዬን አቅርቤ ፍርድ ቤቱ ለተጠሪዎች ስምምነት እውቅና ለመስጠትና ለመመዝገብ የሰጠው ትእዛዝ ሊሰረዝልኝ ይገባል በማለት ያቀረበችው የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትእዛዝ ማለት ውሣኔ የተለያና በፍርድ ቤት የሚሰጥ ማናቸውም አይነት እንደ ብይን የሚቆጠር ተፈፃሚ ትእዛዝ ማለት እንደሆነ የተሰጠው ትረጓሜ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የእርቅ ስምምነት መጽደቁ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር. 227 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤትና የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ያገናዘበና መሠረት ያደረገ ጥያቄ ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ለተጠሪዎች የእርቅ ስምምነት እውቅና የሰጠበትንና የመዘገበበትን ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትእዛዝና ከዚሁ ትእዛዝ ጋር ሕጋዊ ተፈፃሚነት ያገኘው የሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት በመቃወም ተከራካራ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 360 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ካላስረከበች መብቷን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 ሆነ በሌላ መንገድ ለማስረከብ የማትችል መሆኑን አልተረዱትም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 የሰጡት ትርጉም የጠበበ ነው፡፡ እንደዚሁም የእርቅ ስምምነት በፍርድ ቤት ትእዛዝ ተረጋግጦና ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ መባሉ የፍርድ ያህል አስገዳጅነት ያለው መሆኑና አስገዳጅነቱን ለማስቀረት እርቁን ያፀደቀው ፍርድ ቤት እርቁ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም እርቁን የፀደቀው ፍርድ ቤት እርቁ ለሕግና ለሞራል ተቀራኒ አይደም በእርቁ መሠረት ይፈፀም በማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሰጠውን ትእዛዝ መሰረዝ አስፈላጊ መሆኑን ሣያገናዝቡ አመልካች ያቀረበችውን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጋቸው ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18281 የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 118786 ነሐሴ 24 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ሕዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ያደጉት የእርቅ ስምምነት በፍርድ ቤቱ እውቅና ሊሰጠውና ሊመዘገብ አይገባም በማለትና ፍርድ ቤቱ ታህሣስ 6 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት ያቀረበችውን ማመልከቻና ማስረጃ እንደዚሁም ተጠሪዎች የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በመቀበልና በመመርመር በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360 መሠረት የመሰለውን ውሣኔ አንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ጉዳይ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
4. መዘገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 84446

ሚያዝያ 24 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አደነ ንጉሴ

አመልካች፡- ጠበቃ አንበርብር ዓባይነህ አልቀረቡም

ተጠሪ፡ የፍትሕ ሚኒስቴር አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካች የጠበቆችን ስነ ምግባር ደንብ ተላልፎ ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቷል በሚል በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24/3 መሰረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የጠበቆች የዲስፕሊን ጉባኤ ውሳኔ ተሰጥቶ በፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር የጸደቀው ውሳኔ አግባብነት በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ክርክር ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች በመነሳት ለጉዳይ አግባብነት ካለው ከዚህ ህግ አንፃር ለማየት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በጥብቅና ተወክሎ የሚከራከርበት ጉዳይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተወስኖ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በይግባኝ ታይቶ የፀናውን እና በፍርድ ያለቀ ጉዳይ መሆኑን እያወቀ እንደገና በዚያው በፍርድ ያለቀው ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንደገና አቤቱታ ከማቅረብ በፊት በፍርድ ባለቀው ጉዳይ የተለየ ዳኝነት እንዲሰጥ በማድረጉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5 ከተወሰነው ድንጋጌ አንፃር ይኸው ተግባሩ የሙያ ጥፋት ሆኖ ስለተገኘ በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24/3/ መሰረት ጥፋተኛ ለዚህም ጥፋቱ ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቃጮ እንዲቀጣ በአዋጅ መሰረት በፌዴራል ጠበቆች የዲስፕሊን ጉባኤ ተወሰኖ ሚኒስቴር ሚኒስትር በመጽደቁ እና ጉዳዩንም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በማጽናቱ ምክንያት የአሁን አመልካች ይህንኑ የመጨረሻ ውሣኔ ለማስለወጥ ሲል ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በማቅረብ ነው::

የፍትሕ ሚኒስቴርም በተጠሪነቱ በጉባኤው የተሰጠው ውሳኔ በህጉ አግባብ ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለትም በጽሁፍ መልሱን አቅርቧል፡፡

ከላይ በጭሩ እንደተመለከተው አሁን አመልካች ጉዳዩን በጥብቅና ይዞ ክርክር ያደረገበት የአፈፃፀም ጉዳይ ነው ለአፈፃፀም መሰረት የሆነው ዋናው ፍርድ በመ/ቁ 05802 በቀን 09/10/2002 የተሰጠው ሲሆን የፍርዱም የተፈፃሚ ክፍል ‹‹... የሚቻል ከሆነ በዓይነት .... ይህ ሁሉ ካልተቻለ ንብረቱ በሐራጅ ተሸጦ በፍርዱ በተመለከተው የድርሻ መጠን መሰረት ይከፋፈሉ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህንንም ፍርድ ለማስፈፀም ሲባል ለተከፈተው በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 173354 የሆነው የአፈፃፀም መዝገብ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲመለከት ቆይቶ እንደ ፍርዱ ንብረቱን በዓይነት ለማካፈል የሚቻል መሆኑን በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል በባለሙያ ተረጋግጦ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

በዚህ መሰረት ከባለሙያ በቀረበው ማረጋገጫ መሰረት ንብረቱን በዓይነቱ ለማከፋፈል አይቻልም ከሚል መነሻ ተነስቶ ንብረቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሰጠበት መሆኑና በዚህም ትዕዛዝ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞ ስለማሰናበቱ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

እንዲሁም የፍርድ አፈፃፀም መመሪያው ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ንብረቱን በማየት ቦታውን በዓይነት ማካፈል የሚቻል ሲሆን ቤቱን በተመለከተ ግን ከቤቱ አተማመን አኳያ እኩል በእኩል ለማካፈል እንደማይቻል ሆኖም ትንሹንም ድርሻ ቢሆን አሁን አመልካች የወከሏቸው በአፈፃፀም መዝገቡ ላይ 1ኛ የፍርድ ባለዕዳ የነበሩት ጠይቀዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ማስፈፀም ይቻል እንደሆነ ማብራሪያ ይሰጥበት በሚል ገልፆ እያለ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ግን ከዚሁ ከፍርድ አፈፃፀም መመሪያ የተሰጠን ሙያዊ መግለጫ ከደረሰው በኋላ እንደ ፍርዱ ንብረቱን በዓይነት ለማካፈል የልቻል አይደለም ከሚል መደምደሚ ደርሶ በመጨረሻው የፍርድ አማራጭ መሰረት ንብረቱ በሐራጅ እንዲሸጥ በሚል ትዕዛዝ የሰጠበት ስለመሆኑም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ በሐራጅ ይሸጥ በተባለው ትዕዛዝ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦ ተቀባይነት ካጣ በኋላ አሁን አመልካች አፈፃፀሙን በመጀመሪያ ደረጃ ለያዘው ፍ/ቤት ደንበኛቸው ንብረቱ በሐራጅ ከሚሸጥ ይልቅ በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል እንደተረጋገጠው ቢጎዳም አነስተኛው ድርሻ ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል ስለሆነም በዚሁ መሰረት እንዲፈፀም ይታዘዝልኝ በማለት በመጠየቃቸው ፍ/ቤቱ እንደጥያቄው ተቀብሎ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በዚህ አኳኋን ቀድሞ ሰጥቶት የነበረውን የሐራጅ ሽያጭ አማራጭ ትቶ አመልካች እንዳቀረበው አቤቱታው በዓይነት ይካፈሉ ብሎ ካዘዘ በኋላ እንደገና መዝገቡን አንቀሳቅሶ ከዚህ በፊት በሐራጅ ተሸጦ ይከፋፈሉ በሚል የሰጠው ዳኝነት በይግባኝ ታይቶ የጸና መሆኑን የ1ኛ ፍርድ ባለዕዳ እያወቀ እንደገና በፍርዱ ባለቀ ጉዳይ ላይ አዲስ ጥያቄ በማቅረብ የተለየ ዳኝነት እንዲሰጥ አስደርጓል፡፡ ይህም አግባብ አይደለም በማለት በዓይነት ክፍያውን አማራጭ አንስቶ የአሁን አመልካች ፍ/ቤቱን በማሳሳት ለፈፀመው ተግባር ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ሁሉ በኋላ ነው አመልካች የጥብቅና ሙያ ስነ ምግባር ከሚያዘው ውጭ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ አቤቱታ በማቅረብ በሚል ጉዳይ ላይ መጉላላቱንአስከትሏል፡፡ ይህም አድርጊቱ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5 አንፃር ሲታይ ሙያዊ ጥፋት መፈፀሙን ያረጋግጣል በማለት ጥፋተኛ ብሎ የገንዘብ መቀጮ የቀጣው ስለመሆኑ ሁሉ የተረጋገጡ ጉዳዮች ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭር ባጭሩ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም የጉባኤውን ውሳኔ አግባብነት እንደሚከተለው መረምረናል፡፡

በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5 ተፈፃሚነቱ ከታች ወደ ላይ የተዋቀሩት ፍ/ቤቱ ዋናውን ጉዳይ አከራካሪው ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ብቻ የተወሳነ ስለመሆኑ ከአፈፃፀም ቢመለስ በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ የቀረቡት ጉዳዮች አካሄድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚመሩበት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌዎች ያላቸውን የተፈፃሚነት ውሰን በሚደነግገው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 32 ተመልክቷል፡፡

ይህ ለዚህ ሰበር ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ የአፈፃፀም እንደመሆኑ መጠን ይኸው በቁጥር 5 የተመለከተው ስነ ሰርዓታዊ ድንጋጌ በዚህ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው አይደለም፡፡

ይልቁንም የተፈረደ ፍርድን በማስፈፀም ሂደት የጉዳዩ አካሄድ የሚጣራው ስለፍርድ አፈፃፀም በተመለከቱት እራሳቸውን ችለው በተዘረጉት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌዎች መሰረት ነው በዚህም የአፈፃፀም ጉዳይ የሚመለከትን ስርዓት አስመልክቶ በተደረገው ስነ ስርዓታዊ ዝርዝር የህግ ክፍል ማየት እንደሚቻለው የአፈፃፀም ጉዳዩን የያዘ ፍርድ ቤት እንደ ፍርዱ በማስፈፀም ረገድ ከፍርዱ ይዘት ሳይወጣ እንደፍርዱ ተቋጭቶ መዝገቡ እስኪዘጋ ድረስ በተለያዩ ጊዜ የተለያዩ ፍርድ የማስፈጸሚያ ስልትና ዘዴ በመከተል የተለያዩ ትዕዛዞችን ለመስጠት ስልጣን ተሰጥቶታል

በዚህ ጉዳይ በአፈፃፀም መዝገቡ ላይ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ንብረቱ በሀራጅ ተሸጦ እንዲከፋፈሉ ይደረግ ብሎ ካዘዘበት ጊዜ ጀምሮ ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚ ችሎት ደርሶ ከፀናና እንደገና አሁን አመልካች እንደገና የአፈፃፀም ችሎት ቀደም ሲል ንብረቱ ተሸጦ ይከፋፈሉ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ አግባብነቱ እንደገና ይታይልኝ በማለት እስከጠየቀበት ድረስ ፍርዱ ፍፃሜ ያገኘ ጉዳይ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

ከዚህ በላይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡትን ጉዳዮች በተጠቀሰበት በዚህ ፍርድ ላይ እንደተገለፀው ፍርድ አፈፃፀም መምሪያ የሰጠው ሙያዊ ማረጋገጫ ይዘት ንብረቱን በዓይነት ለማካፈል የሚቻል አይደለም በሚል ሳይሆን አንደኛውን ወገን ጠቅሞ ሌላኛውን ወገን ካልጎዳ በቀር ማካፈል ይቻላል በዚህም መሰረት 1ኛ የፍርድ ባልዕዳ ቢጎዳም ልጎዳ በማለት እነስተኛው ድርሻ ተሰጥቷቸው ክፍፍሉ በዓይነት እንዲደረግ ጠይቀዋል ይኸው ታይቶ አስፈላጊው ዳኝነት ይሰጥበት የሚል ሆኖ እያለ ፍ/ቤቱ በዘፈቀደ ንብረቱ በሐራጅ ይሸጥ በማለት ማዘዙ ስህተት የፈፀመ መሆኑን ያስገነዘበው ጉዳዩም ፍፃሜ አግኝቶ ባለጉዳዮች የተሰናበቱ እስካልሆነ ድረስ ፍርድን ተገቢ በሆነ መንገድ በማስፈፀም ረገድ ለአፈፃፀም ፍ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተስተካከለ ዳኝነት እንዲሰጥ የአሁን አመልካች ለደንበኛው ተገቢን ሙያዊ ድጋፍ ማሰጠት ካለበት ግዴታ አንፃር ለፍ/ቤቱ አመልክቷል ከሚባል በቀር የፈፀመው መያዊ ጥሰት አልተሰተዋለበትም፡፡

በፍርዱ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ድርሻ ግማሽ ቀሪው የሌሎች ተከራካሪዎች እንደመሆኑ መጠን ንብረቱን በዓይነት ለማካፈል ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለውን ለመለየት ይኸው የፍርድ ባለዕዳ ግማሽ ድርሻ መነሻ ከሚሆን በቀር የቀሪውን ግማሽ ድርሻ ቀሪ ተከራካሪዎች በዓይነት ሊከፈሉ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ነጥብ ሊሆን አይገባም በዚህም ምክንያት ግማሹ ድርሻ ለቀሪ ሶስት ወገኖች የሚከፈፈል የመሆኑ ጉዳይ የአፈፃፀሙን አካሄድ ሊያስቀይረው የሚችል ሆኖም አላገኘነውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የዲስፕሊን ጉባኤ ለጉዳዩ አግባብነት ከሌለው ድንጋጌ አንፃር እንጂ ፍርድን እንደ ፍርዱ በተገቢው መንገድ በሚስፈጽም ረገድ ፍ/ቤቱ ሊከተለው ከሚገባው ስርዓት አንፃር ባለማየቱ ምክንያት የአሁን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአመልካች ሙያዊ ጥፋት ፈጽሟል ሲል የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ቀጠይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የዲስፕሊን ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ መነሻ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/ቁ ነው 125177 ጳጉሜ 01 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች በወሰነበት መሰረት የገንዘብ መቀጮውን ክፍያ ፈፅሞ ከሆነ ለገንዘብ መቀጮው ምክንያት የሆነው ውሳኔ የተሻረ ስለሆነ ገንዘቡ እንዲመለስለት ታዟል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ
3. በዚህ ሰበር ክርክር ምክንያት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ሁለቱም ወገኖች ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 85718

ሰኔ 03 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ቴዎድሮስ አማረ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አዲሱ ፍሰሃ ጠበቃ አቶ አባቡ ሞላ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአላማጣ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02693 ህዳር 19 ቀን 2005ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲሻርልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አላማጣ ምድብ ችሎት ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ሟች ወ/ሮ አስካለ አርአያ መስከረም 10 ቀን 1993ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይታለች፡፡ ሟች ተወላጅና እናትና አባታቸው የሌሉ በመሆኑ በእናት መስመር የተከሣሽ/ አመልካች/ እናት የሆነችው ወ/ሮ አረጋነሽ አርአያ በእናት መስመር የእናቷ ልጅ የሆነችው ወ/ሮ ብርታንን ፋንታዬ ወራሾች መሆናቸው በወፍላ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 0793 02-06-1993ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ተረጋግጧል፡፡ ወ/ሮ ብርታንን ፋንታዬ የሟች አስካለ አርአያ ወራሽ መሆኑን ካረጋገጠች በኋላ ከዘጠኝ ዓመት በኋላ ህዳር 28 ቀን 2001ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፡፡ እኔ የሟች ብርታንን ፈንታዬ ተተኪ ወራሽ መሆኔ የሰቆጣ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 4609 ታህሣስ 16 ቀን 2001ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አውራሽ ወ/ሮ ብርታንን ፈንታዬ ከሟች አስካሉ አርአያ በኮረም ከተማ 01 ቀበሌ ከሰራችው ሁለት ክፍል ቤት የሚደርሳት አንድ ክፍል ቤት ተከሣሽ እንዲያስረክበኝና ስመ ንብረቱ እንዲዛወርልኝ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡
2. አመልካች በተከሣሽነት ቀርቦ ከሣሽ ተጠሪ ከዚህ በፊት በኮረም ወረዳ ፍ/ቤት ክስ አቅርቦብኝ የወረዳው ፍ/ቤት ጥር 2 ቀን 2004ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡

   ስለዚህ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ስለሆነ በድጋሚ ሊቀርብብኝ አይገባም የሚል ሌሎች መከራከሪያዎችን አቅርቧል፡፡ የአላማጣ ምድብ ችሎት የኮረም ከተማ ፍርድ ቤት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የተጠሪንና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካችን ክርክር ከሰማ በኃላ የተከሣሽን /የተጠሪን/ ክስ ውድቅ በማድረግ ውሣኔ የሰጠ መሆኑ ገልፆ የከሣሽ /ተጠሪ/ መኖሪያ አማራ ክልል ሰቆጣ ከተማ የተከሣሽ መኖሪያ ትግራይ አፍላ ወረዳ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/1985 አንቀጽ 5/2/ መሠረት ስልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሆኑ የኮረም ወረዳ ፍርድ ቤት በሌለው የዳኝነት ስልጣን የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ጉዳዩ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ እንዳይወሰን የሚገድብ አይደለም በማለት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአመልካቾችና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ አመልካች አንድ ክፍል ቤት ለተጠሪ እንዲያካፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ፀንቷል፡፡

3. አመልካች ታህሣስ 19 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የኮረም ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ሣይሻር የአላማጣ ምድብ ችሎት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5/1/ ድንጋጌ በተዛባ መንገድ በመተርጉም ያቀረቡኩትን የመጀመሪያ የፍርድ መቃወሚያ በማለፉ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ተጠሪ በሚች አስካለ አርአያ ጋር ምንም አይነት ዝምድና የሌለው በመሆኑ የውርስ ንብረት አንዲካፈል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 27 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አውራሽ ቀደም ብላ ሚች አስካለ አርአያን ወራሽ መሆኗን አረጋግጣለች የኮረም ወረዳ ፍርድ ቤት ጥር 5 ቀን 2004 ዓ.ም ከሥር ነገር የዳኝነት ስልጣኑ ውጭ በማየት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አለመሆኑን በማየት ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአላማጣ ምድር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. የሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አላማጣ ምድብ ችሎት ቀደም ሲል በኮረም ወረዳ ፍርድ ቤት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠ አይደለም በማለት ተጠሪ ያቀረበለትን ክስ በማየት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ማፅናታቸው የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች የሚች አስካለ አርአያ የውርስ ንብረት የሆነውንና በኮረም ከተማ የሚገኘውን ቤት እንዲያካፍለው በኮረም ከተማ ምድብ ችሎት ክስ አቅርቦ፣ የኮረም ከተማ ምድብ ችሎት የተጠሪን /የከሣሽንና/ የአመልካችን /የተከሣሽን/ ክርክር ህዳር 10 ቀን 2004 ዓ.ም ከሰማ በኋላ የከሣሽን ክስ ውድቅ በማድረግ ጥር 2 ቀን ዓ.ም ብይን የሰጠ መሆኑን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአላማጣ ምድብ ችሎት ያረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የዳኝነት ስልጣን ያለው የኮረም ከተማ ምድብ ችሎት ተጠሪ አመልካች ቤቱን እንዳካፍለው ያቀረበውን ክስ በማየት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320/1/፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 314፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 327 እና ሌሎች አስገዳጅ የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ቀርቦበት አልተሻረም ወይም አልተለወጠም፡፡ ተጠሪ የኮረም ወረዳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምድብ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2/ የተደነገገውን በመተላለፍ፣ በሁለት ክልል ኗዋሪዎች መካከል የተነሣውን ክርክር በማየት ውሣኔ መሰጠቱ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 4 የሚቃረን ስለሆነ በይግባኝ ታይቶ እንዲሻርለት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ፣ የኮረም ምድብ ችሎት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ያላሻረ በመሆኑ ውሣኔው በጉዳዩ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅነት ያለው መሆኑ የሚቀርበት ምክንያት የለም፡፡

6. የኮረም ምድብ ችሎት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በሕግ ከተሰጠው የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ውጭ የሆነ ጉዳይ በማየት የሰጠው ቢሆንም፣ ይህ ውሣኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ካልተደረገ በስተቀር በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 212 በጉዳዩ ላይ አስገዳጅነት ያለውና የመጨረሻ ውሣኔ ነው፡፡ በመሆኑም የኮረም ምድብ ችሎት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በይግባኝ ወይም በሰበር ታይቶ ባልተሻረበት ሁኔታ በዚያው ጉዳይ ተጠሪ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አላማጣ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02693 ያቀረበው ክስ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ የአላማጣ ምድብ ችሎት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ የተዛባ ትርጉም መስጠት የኮረም ምድብ ችሎት ቀርቦ ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም በፍርድ ባለቀና ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ያልተሻረ ሆኖ እያለ ተጠሪ ያቀረበውን ክስና ክርክር በማየት ሚያዝያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ከላይ የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የአላማጣ ምድብ ችሎት የፈፀመውን የሕግ ስህተት ሣያርሙ ማለፋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአላማጣ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02693 የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26210 የሰጠው ትዕዛዝ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 56287 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በኮረም ከተማ ምድብ ችሎት ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም በፍርድ ያለቀ በመሆኑ ተጠሪ ይህንን ውሣኔ ለይግባኝ ወይም በሌላ የፍርድ ማረሚያ ሥርዓት ሣያሸር ሌላ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 511 መሠረት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86454

ግንቦት 23 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ት ፍሬወይኒ አለም በ VC ቀርባለች፡፡

2. ወ/ት ሣምራዊት አለም
3. አቶ በረከት አለም፡ } አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ አለም መሐሪ ጠበቃ አቶ ምናስቦ ገብሩ ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከንብረት ግምት ክፍያ ጋር ተያይዞ የቀረበ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ያሁኑ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በት/ቤ/ክ መንግስት አዲግራት ወረዳ ፍ/ቤት በመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ ከወ/ሮ አለምነሽ ተ/ብርሃን ጋር በትዳር ተሳስሮ በመኖር ላይ ሳሉ በመካከል ለስራ ወደ ምዕራብ ትግራይ ሄዶ በቆዩበት ወቅት አመልካቾች የተጠሪን የመጥፋት ውሣኔ በማሳወጅና ከዚያ በኋላም ውርስ እንዲጣራ በማድረግ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የነበረው ግምቱ ብር 80,000 የሆኑ 4 ክፍል ቤቶች ግማሹ ድርሻ ወደ ባለቤታቸው ስም ቀሪውን የተጠሪ ግማሽ ድርሻ ደግሞ ወራሾች ለሆኑት ወደ አመልካቾች ስም በማዘጋጃ ቤት በኩል ተላልፎ እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ አሁን ለስራ ከሄድኩበት ተመልሼ አመልካቾች የሰጡትን የመጥፋት ውሣኔም ስላስነሳው በዚህ ምክንያት ተወርሶና ወደ አመልካቾች ስም ተላልፎ የነበረው የቤቱ ግማሽ ድርሻዬ ወይም ንብረቴን እንዲመልሱልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ ያሁኑ አመልካቾች /የስር ተከሣሾች/ በበኩላቸው ቀርበው ለክሱ በሰጡት መልስ የቤቱ ግምት ብር 80,000 ሳይሆን ከ200,000 በላይ መሆኑንና ከመጥፋቱ በፊት በተጠሪ ስም የነበረው ባዶ መሬት ብቻ መሆኑንና የባዶ መሬት ባለቤት ደግሞ መንግስት እንጂ ተጠሪ ባለመሆኑና ተጠሪ ከጠፋ በኋላ በባዶ መሬቱ ላይ ሀብታችን አፍስሰን የሰራነውን ቤት ከ 18 ዓመት በኋላ መጥቶ ሊጠይቅ እንደማይገባ በመጀመሪያ መቃወሚያነት የተከራከሩ ሲሆን ፍሬ-ጉዳዩን በተመለከተም ቤቱ በባዶ መሬት ላይ በእኛ በአመልካቾች መሰራቱ ታውቆ በህጋዊ መንገድ ወደ ስማችን የተዛወረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ የተጠሪ አይደለም፡፡ ሆኖም ግን ባዶ መሬቱ ለተጠሪ ሊሆን ይገባል ከተባለም ቤቱ በባለሙያ ተገምቶና በግምቱ መሰረት ክፍያ እንዲፈፀምላቸው ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ወረዳ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር 5 የአመልካቾች ምስክሮች ሰምቶ በተጠሪ በኩል ከቀረቡት ሰነድ ማስረጃዎች ጋርም በማገናዘብ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ምንም እንኳ ቤቱን የሰሩት አመልካቾች ስለመሆናቸው በእነሱ በኩል ቀርበው በተሾሙት ምስክሮች ቢነገርም ከዚህ ቀደም ውርሱ በአመልካቾች እንዲጣራ ሲደረግ ቤቱ የተጠሪ እንደሆነ በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ላይ የተገለፀ በመሆኑና አሁን ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ቤቱ የአመልካቾች ነው በማለት የቀረበው ክርክር እርስ በራሱ የሚጣረስ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ለክርክሩ መነሻ የሆነውና ወደ አመልካቾች ስም የተላለፈው ሁለቱ ክፍል ቤቶች ለተጠሪ ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካቾችም በተሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለምስራቃዊ ዞን ማዕከላይ ፍ/ቤት አቅርበውና ግራ ቀኙም ቀርበው እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ክርክር የተነሳበት ቤት በአመልካቾች መሰራቱ ተረጋግጦ ሳለ አመልካቾች ያለ ምንም ግምት ክፍያ ቤቱን ለቀው ለተጠሪ ሊመልሱ ይገባል በማለት የተሰጠው ውሣኔ አለአግባብ መሆኑን ከገለፀ በኋላ ተጠሪ በባለሙያ ተገምቶ በቀረበው ግምት መሰረት የቤቱን ግምት ብር 160,482.765 ለአመልካቾች ከከፈሉ በኋላ ቤቱ ተመልሶለት በስሙ እንዲመዘገብ በማለት የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ይህንን ውሣኔ በመቃወም የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ቀርበው እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ አመልካቾች የቤቱ ግምት እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ክስ ወይም የተከሣሽ ከሳሽነት ክስ በሌለበትና እንዲሁም በአመልካቾች የተከፈለ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ሳይኖር ተጠሪ ራሱ ዳኝነት ከፍሎ ባስከፈተው መዝገብ ላይ ብር 160,482.765 እንዲከፈላቸው በዞኑ ፍ/ቤት መወሰኑ ስነ-ስርዓታዊ አይደለም በማለት ይህንን በሚመለከት የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል ሽሮ ሆኖም ግን ንብረቱ ለተጠሪ ሊመለስ ይገባል በማለት በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ /የውሣኔ ክፍል/ በማፅናትና አመልካቾችም በቦታው ላይ ሀብታቸውን አፍስሰናል የሚሉ ከሆነ ይህንን በህጉ አግባብ የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን በመግለፅ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ደግሞ በተራቸው በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታው በድምፅ ብልጫ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተወስኖና በክልሉ ሰበር ችሎት ድምፅ ብልጫ የፀናውን በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም በአንድ በኩል ንብረቱ ለተጠሪ ይመለስ እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ እኛ አመልካቾች የንብረታችንን ግምት ከሳችሁ ጠይቁ በማለት የተሰጠው ውሣኔ ጊዜና ጉልበት ከማባከን ውጪ ሌላ ለውጥ ስለሌለው ውሣኔው ተሽሮ በፍ/ብ/ህ/ቁ 171/1/ ድንጋጌ መሰረት ያፈሰስነው ሀብት ግምታችን እንዲከፈለን ይወሰንልን በማለት አመልክተዋል፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በመባሉ ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠበት ሲሆን አመልካቾችም የመ/መልሳቸውን ሰጥተውበታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የሰበር አቤቱታ በቀረበበት ውሣኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ ሊመረምር የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክር ሂደቱ መገንዘብ እንደሚቻለው ከሳሽ የነበረው የአሁን ተጠሪ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ዳኝነት ጠይቆ እየተከራከረ ያለው ወደ አመልካቾች ዞሮ የነበረው ንብረቱ ይመለስልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካቾችም በበኩላቸው ንብረቱ ለተጠሪ የሚመለስ ከሆነ በቦታው ላይ ያፈሰስነው ሀብት በባለሙያ ተገምቶ ግምቱ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል መከራከሪያ ነጥብ በማቅረብ እየተከራከሩ ያሉ መሆናቸውን መገንዘብ ችለናል፡፡ ሆኖም ግን አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ተከሳሾች እንደመሆናቸውና እነሱም በበኩላቸው ከተጠሪ የሚጠይቁት መብት ካላቸው በህጉ አግባብና በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 234/1/ /ረ/ መሰረት ከመከላከያ መልሳቸው ጋር የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 215/2/ ስር እንደተመለከተው በመፈፀም በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የተጠቀሰው የቤቱ ግምት እንዲከፈላቸው በሚል የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ የለም፡፡ በዚህ አግባብ ተሟልቶ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ በለሌበት ደግሞ ዳኝነቱ ሊሰጥ አይችልም፡፡

በሌላ በኩል ከፍ ሲል እንደተገለፀው የአመልካቾች ክርክር የቤቱ ግምት እንዲከፈላቸው ይወሰንልን በማለት ከመከራከር ውጭ ጨርሶ ቤቱንም ልናስረክብ አይገባም የሚል አይደለም፡፡ ጥያቄያቸው ይህ ከሆነ ደግሞ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ ሰበር ችሎቱ ግምቱ ሊከፈላቸው አይገባም በሚል ውሣኔ የሰጡ ሣይሆን ይህ የዳኝነት ጥያቄቸው በዳኝነት አካሉ ተቀባይነት አግኝቶ ሊስተናገድ የሚገባው መጀመሪያውኑ በህጉ አግባብ ስርዓቱን ጠብቆ ሲቀርብ መሆኑን በማለት ነው፡፡ አመልካቾችም እራሳቸው ይህንኑ መሆኑን ተረድተው ይህ አከራካሪው የቤቱ ግምት እንዲከፈላቸው በተጠሪ ላይ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት አዲስ ክስ ማቅረባቸውን ተጠሪ ለሰበር አቤቱታ መልሱን ሲሰጥ ጠቅሶ ባቀረበው ክርክር ላይ ምንም ያሉት ነገር የለም ይህ ደግሞ እርግጥም እንደተባለው በዚህ ጉዳይ አዲስ ክስ ያቀረቡ መሆናቸውን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 234/1/ /ሠ/ እና 235 /2/ ስር እንደተመለከተው እንደመሆኑ ተቆጥሮ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

ሲጠቃለል ከፍ ሲል በተገለፁት ምክንያቶች የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች የዳኝነት አገልግሎት ፈፅመው ዳኝነቱንም በስርዓቱ ባላቀረቡበት ሁኔታ ይህ የተጠቀሰው የቤቱ ግምት ብር 160,482.765 ተጠሪ ራሱ ዳኝነት ከፍሎ ባስከፈተው መዝገብ ላይ ሊወሰንላቸው አይገባም በማለት ተወስኖ በሰበር ችሎቱም በድምፅ ብልጫ እንዲፀና በማለት በተሰጠው ትእዛዝ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መ/ቁ 54034 ጥቅምት 26 ቀን 2005 በዋለው ችሎት ተወስኖ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ 55375 ህዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ የፀናው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡
3. በዚህ መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የአፈፃፀም እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የሰበር ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 86510

ሰኔ 18 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሙሉ ኤሌክሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጠበቃ ታደሠ ጉርሙ ቀረቡ

መልስ ሰጪ፡- ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል /አ.አ/ ነ/ፈጅ ዳንኤል ጥላሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ከውል አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የተነሳውን የክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመስረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም የአሁኑ አመልካች ለልብ ሕመማን አገልግሎት የሚውል ECLO car diagram ultra sound GE modele VIVID of system የተባለ የልብ ህክምና መመርመሪያ መሳሪያ ለተጠሪ ለማስረከብ ውል ተዋውሎ ቅድሚያ ክፍያ 30% ብር 702,000.00 /ሰባት መቶ ሁለት ሺ ብር/ ተቀብሎ መሳሪያውን ሊያቀርብ ያለመቻሉን ገልፆ መሳሪያውን በአስቸኳይ እንዲያቀርብ ካልሆነም በቅድሚያ የወሰደውን ገንዘብ እጥፍ አድርጎ ብር 1,404,000.00 ከነወለዱ እንዲከፍለን ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከተጠሪ ጋር ውል መዋዋሉንና የቅድሚያ ክፍያ መቀበሉን ሳይከድ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሳሪያ ለተጠሪ ያላስረከበው መሆኑን ገልፆ መሳሪያውን ለማምጣት ኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና እንክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን የግዥ ውል ከጠቅላላ ሰነድ ጋር ቀርቦለት እንዲፀድቅ መጠየቅ እንዲሁም መሳሪያው ከውጪ እንደሚመጣ በመሆኑ ባንክ ምንዛሬ እንዲፈቅድ መጠየቅ ስለነበረበት ተጠሪም ትብበር እያደረገ ስምምነቱ ከተደረገበት ባንክ እስከ ተፈቀደበት ሚያዚያ 12 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ አስራ አንድ ወራቶች መቆጠራቸውን መሳሪያው ወደ አገር እንዲገባ የሚፈቅደው አካል ደግሞ ያልፈቀደለት በመሆኑ እየተጠባበቀ የሚገኝ መሆኑንና በዚህ ችግር ምክንያት ውሉን ያልፈጸመ ስለመሆኑ ገልጾ መሳሪያውን እንዲያስረክብ እንዳደረግ ይህ የማይፈቀድ ከሆነ ተጠሪ የቅድሚያ ክፍያ እጥፍ እንዲከፈለው ያቀረበው ጥያቄ በውሉ ከተቀመጠው ግዴታ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከተሰማ በኋላ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ በውሉ በተመለከተው ግዴታ መሰረት መሳሪያውን ማስረከብ ከሚገባበት ከሐምሌ 12ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ሲታሰብ 437 ቀናት ማለፋቸውንና ለእያንዳንዱ ቀን 0.1% መቀጮ የግዥ ዋጋ ከሆነው ብር 2,340,000 .00 ሲታሰብ ብር 999, 180. 00 /ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሰማንያ ብር/ የሚመጣው ገንዘብ በመቀጮነት አመልካች ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው መሆኑን ገልፆ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል እንዲሁም የቅድሚያ ክፍያ ብር 702,000.00 /ሰባት መቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁለት ሺህ ብር/ ክሱ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፈዬራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በተጠሪ የተጠየቀውን ዳኝነት ይዘት ያላገናዘበና በጉዳዩ ላይ ሊመሰረት ይገባው የነበረውን ጭብጥ በአግባቡ ያልለየ መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው እንዲለወጥ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም አመልካች ብር 999,180.00 በመቀጮነት እንዲከፈል የተወሰነው በተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ቀርቦ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአመልካች ጋር ተደርጓል በሚለው ስምምነት አከራካሪውን እቃ በወቅቱ አመልካች ያላስረከበ መሆኑን ገልጾ እንዲወሰንለት ዳኝነት የጠየቀው የህክምና መሳሪያውን በአስቸኳይ እንዲያስገባ መስሪያውን በውሉ መሰረት ማስገባት ካልቻለ በቅድሚ የወሰደውን ገንዘብ በእጥፍ አድርጎ በድምሩ 1,404,000.00 /አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አራት ሺ ብር/ መሳሪያውን ማስገባት ከነበረበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ገንዘቡን እንዲከፍልና ወጪና ኪሳራም ዝርዝር የማቅረብ መብቱ እንዲጠበቅለት መሆኑን ጥቅምት 02 ቀን 2004 ዓ.ም ተጠሪ ያቀረበው የክስ ማመልከቻ የሚያሳይ መሆኑን አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጠው መልስም ውሉ መኖሩንና ከተጠሪ ቅድመ ክፍያ መቀበሉን ሳይክድ ለውሉ አለመፈጸም ሕጋዊ ምክንያት ናቸው ያላቸውን ምክንያቶችን አንስቶ መከራከሩን ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች ውሉን ለመፈፀም አላስቻለኝም በማለት አጥብቆ የሚከራከርበት ነጥብ የልብ መመርመሪያ መሳሪያውን ለማስመጣት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ያለማግኘቱን ጠቅሶ ነው ይሁን እንጂ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ማስረጃ ያለመኖሩንና እቃውን ሳያስገባ ያለፉት ቀናት ብዛት ሲታዩ ፈቃድ ያለማግኘቱን ያሳያል ወይም ውሉን ለመፈፀም ተገቢውን ጥረት አድርጓል ለማለት የሚቻል አለመሆኑን ደምድመዋል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የበታች ፍርድ ቤቶች የልብ መመርመሪያ መሳሪያው ወደ አገር ውስጥ ያልገባው ፈቃድ ከሚሰጠው አካል ፈቃድ ሳይገኝ መቅረቱን አረጋግጠዋል በማለት የተያዘው ፍሬ ነገር ድምዳሜ በበታች ፍርድ ቤቶች የተደረገውን የግራ ቀኙን ክርክርና የማስረጃ ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች መሳሪያውን ለማስገባት የሚመለከተው አካል የከለከለው ስለመሆኑ በማስረጃ ያለማስደገፉ ከተረጋገጠ ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1792 ድንጋጌን ጠቅሶ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሚገኝበት አግባብ የለም፡፡

ወደ ዋናው ጭብጥ ስንመለስም ከላይ እንደተገለፀው በተጠሪ ከተጠየቁት ዳኝነቶች መካከል አንዱ የቅድመ ክፍያ ገንዘብ እጥፍ ሁኖ እንዲመለስ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ዳኝነት የሰጠው ግን አመልካች እቃውን ማስገባት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከነበረበት ከሐምሌ 12 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ በሚታሰብ 427 ቀናት ማለፋቸውንና ለእነዚህ ቀናትም የውሉን ጠቅላላ ዋጋ ብር 2, 340,000. 00 0.1% ሲታሰብ የሚመጣውንና ከውሉ ዋጋ 10% ያልበለጠውን መቀጮ አመልካች በውሉ አንቀጽ 2.3/ለ/ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1731 ለመከፈል ይገደዳል የሚል ምክንያት ይዞ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም አመልካች የቅደም ክፍያ የከፈለ ሁኖ እያለ ቀብድ አድርጎ እጥፍ መጠየቁ ስህተት መሆኑን አምኖ ክሱ ሊመሰረት የጠየቀው ዳኝነት የቅድመ ክፍያ እጥፍ ቢሆንም ክሱ በተሰማበት ወቅት የመቀጫ ገንዘብ መጠየቁ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ማጽናቱን ተገንዝበናል፡፡

በመስረቱ ክርክር የሚመራውና ዳኝነት የሚሰጠው በህጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ነው፡፡ በህጉ ከተዘረጋው የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣት ስርዓት ውጪ ክርክር የመምራትና ዳኝነት የመስጠት አካሄድ የዳኝነት ሰጪ አካሉን ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ዳኝነት የሚሰጠው በተከራካሪ ወገን የተጠየቀ ሁኖ በሕጉና በውሉ የተፈቀደ መሆኑን በጥንቃቄ አረጋግጦ ሲሆን ተከራካሪ ወገን በሕጉ ወይም በውሉ የተፈቀደለትን መፍትሔ ለማግኘት በግልጽ ዳኝነት መጠየቅ የሚገባው መሆኑን ስለክስ አመሰራረትና የመከላከያ መልስ አቀራረብን የሚደነግጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 222፣234፣235፣236 እና 83 ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 224 እና 182 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር ተዳምረው ሲታዩ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የዳኝነት ጥያቄ አይነትና መጠኑን በክሱ ማመልከቻ በግልጽ መስፈር ያለበት መሆኑን ያሳያል ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 224 ድንጋጌ ጠቅላላ ይዘቱ ሲታይም ከሳሹ በጉዳዩ ላይ የሚጠይቀው ዳኝነት ጠቅላላ ፍርድ ቤቱ የክሱን ጭብጥና የማስረጃውን አከባቢ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ትክክለኛ መስሎ የታየውን ፍርድ ሊሰጥ እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 241 ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ ተከራካሪ ወገኖች/ በጽሑፍ ያቀረቡትን ክርክር ለማብራራትና በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 246-248 ድንጋጌች አግባብ ጭብጥ ለመመስረት እንዲያገዝ ሲሆን በጽሑፍ ማመልከቻው ላይ ያልሰፈረን ዳኝነት ለመጠየቅ የሚስችል ያለመሆኑን የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያስረዳል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ከመጀመሪያው ክረክር ላይ ካቀረቡት በቀር ሌላ ተጨማሪ ሙግት ወይም ሌላ ማስረጃ ማስቀረብና መመርመር የሚያስፈልግ ከሆነ ወይም ቀድሞ የተያዘው ጭብጥ የሚሻሻል ወይም ተጨማሪ ጭብጥ የሚያገዝ መሆኑ ከታመነም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 255 እና 251 አግባብ የሚፈፀም እንጂ ያለህጋዊ ምክንያት በማናቸውም የክርክር ደረጃ የቀረበ ክርክር ሁሉ ተቀባይነት የሚያግኝበት የክርክር አመራር የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የጠየቀው ዳኝነት ቅድመ ክፍያ አጥፍ ሁኖ እንዲከፈል ሲሆን በውሉ በተመለከተው አግባብ መቀጫ እንዲከፈለው በግልጽ አልጠየቀም የቅድመ ክፍያው እጥፍ ሁኖ እንዲከፈለው ጥያቄ ያቀረበው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1883 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተቀመጠውን የቃብድ መሰረተ ሐሳብ ይዞ ስላለመሆኑ የክስ ማመልከቻው ያሳያል እንዲህ ከሆነ አመልካች ለተጠሪ የቅድመ ክፍያውን እጥፍ አድርጎ ለተጠሪ የሚከፍልበት አግባብ መኖር ያለመኖሩ በጭብጥነት ተይዞና የክሱን ጭብጥና የማስረጃውን አከባቢ ሁኔታ መሰረት አድርጎ ዳኝነት ከሚሰጥበት በስተቀር የመቀጫ ገንዘብ በጭብጥነት የሚያዝበት አግባብ የለም፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለቀብድ የያዘው ጭብጥ ተገቢነት ያልነበረው ሲሆን ውጤቱ ሲታይ ተጠሪ በውሉ አለመፈፀም ከአመልካች የሚጠይቀውን ኪሳራ ከመጠየቅ ሊከላከለው የማይገባ መሆኑን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ አመልካችን የጠየቀው የቅድመ ክፍያ እጥፍ ክፍያ ለጉዳቱ ተገቢ ነው ብሎ ያሰበውና ጠቅላላ አገላለጽ ነው ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 224 መሰረት ግንዛቤ የሚወሰድበት ነውና፡፡ ይህ የተጠሪው የክስ ዳኝነት ጥያቄ ዝርዝር ይዘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደግሞ ግራ ቀኙ በውሉ ከአቋቋመበትና በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር በመነሳት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በውሉ የተጠቀሰው ስሌት መሰረት ተደርጎ የሚመጣው መጠን በማናቸው ምክንያት ተጠሪ በግልጽ መጠኑን ለይቶ ከአቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ሊበልጥ የሚችልበት የዳኝነት አሰጣጥ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የቅድመ ክፍያውን እጥፍ ሲጠይቅ በውሉ የተቀመጠው መሆኑን ገልፆ ባለመሆኑና አመልካችም የቅድመ ክፍያውን መወሰዱን ያልካደው በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ሊገደድ የሚገባው የክፍያ መጠን ቅድመ ክፍያውንና ተጠሪ በመቀጫነት ሊታሰብ ይገባል ያለው የዚሁ ገንዘብ መጠን ነው፡፡ ተጠሪ ውሉን መሰረት አድርጎ ስሌቱን ቢሰራ ኖሮ የመቀጫው ገንዘብ የሚመጣው ብር 999, 180.00 ሲሆን ይህን ባለማድረጉና ቅደመ ክፍያው እጥፍ ነው ሊከፈል የሚገባው ብሎ ዳኝነት በመጠየቁ የመቀጫ ገንዘቡ ከብር 702,000.00 /ሰባት መቶ ሁለት ሺ ብር/ ሊበልጥ የሚችልበት አግባብ የለም በመሆኑም የተጠሪ ክስ ማመልከቻ ጠቅላላ ይዘት ሲታይ ለውሉ ያለመፈፀም የጠየቀው የመቀጫ ገንዘብ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያደረሰን በመሆኑ መጠኑን በተመለከተ ግን ተጠሪ በግልጽ ያስቀመጠ በመሆኑ የመቀጫ ገንዘቡ 999,180. 00 ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከቅድመ ክፍያ ገንዘብ ጋር ተዳምሮ ሲታይ አመልካች በግልጽ ከጠየቀው ከብር 1, 404,000.00 / አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አራት ሺ ብር/ የብር 297,180. 00 /ሁለት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ አንድ መቶ ሰማንያ ብር/ ብልጫ ያለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182/2/ ድንጋጌን በግልጽ የሚጻረር በመሆኑ ከዚህ አንጻር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች የውሳኔ አሰጣጥ ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱትን የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተችቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 111482 የካቲት 20 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 78582 ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ አመልካች በውሉ ላይ በተመለከተው መሰረት የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፈለው ዳኝነት ያልጠየቀ በመሆኑ በውሉ በተመለከተው ስሌት መሰረት መቀጫውን አመልካች ለተጠሪ ሊከፈል አይገደድም ብለናል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የቅድመ ክፍያውን አጥፍ መሰረት አድርጎ የመቀጫ ገንዘቡ እንዲከፈል የተጠየቀ በመሆኑ ለመቀጫ ብር 702,000.00 /ሰባት መቶ ሁለት ሺ/ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. አመልካች የቅደመ ክፍያው ብር 702,000. 00 /ሰባት መቶ ሁለት ሺ/ በተመለከተ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ ከፍል በሙሉ ጸንቷል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ይህንኑ ገንዘብ ለተጠሪ ክፍሉ ከሆነ በአፈፃፀም ጊዜ እንዲታይለት ከማድረግ ይህ ውሳኔ አያግደውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

ሐ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 87190

ግንቦት 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ቄስ ዳንኤል አርኪ ከጠበቃ ሙሉጌታ ዱላ ጋር ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኮልፌ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ - አልቀረበችም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የይግባኝ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜ አልፏል ወይስ አላለፈም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው ክርክር ከተረጋገጠውና ይህንኑ የተረጋገጠውን ጉዳይ መነሻ አድርጎ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለዚሁ ጭብጥ ከሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት ጋር አገናዝበን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በዋናው ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16273 ፍርድ ሰጥቶ ግራ ቀኙን ካሰናበተ በኋላ የአሁኗ ተጠሪ ግንቦት 21 2004 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 208 መሠረት በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ፍርድ ቤቱ የአሁን አመልካችን ሳይጠራ ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ ግንቦት 22 ቀን 2004 በጥያቄው መሠረት ዳኝነት የሰጠበት ስለመሆኑ፤

እንዲሁም ይህ መዝገብ ከተዘጋ በኋላ ትዕዛዝ የተሰጠ በመሆኑ የአሁን አመልካች በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም የደረሰው ስለመሆኑ የአሁን ተጠሪ ማስተባበያ ያቀረበበት በመሆኑና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም እነዚህኑ ፍሬ ነገሮች መነሻ አድርጎ ዳኝነት የሰጠበት እንደመሆኑ መጠን እነዚህ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ፍሬነገሮች የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የቀረበለትን የይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄ በይግባኝ ከተመለከተ በኋላ ለአሁን አመልካች የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ዳኝነት ከደረሳቸው ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ከማለፉ በፊት 9 ቀን የነበራቸው ከመሆኑ አንፃር በዚህ በዘጠኝ ቀን ጊዜ ውስጥ የይግባኝ አቤቱታ አዘጋጅቶ የይግባኝ አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለማቅረብ በቂ ጊዜ የነበራቸው ሆኖ እያለ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሳያቀርቡ ምክንያት አለኝ ይፈቀዳልኝ በሚል ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው የይግባኝ አቤቱታ ሊቀርብልኝ ይገባል በማለት የአሁን አመልካች ጥያቄ ያቀረቡበት ዳኝነት የተሰጠው መዝገብ ከተዘጋ በኋላ እንደገና ከተንቀሳቀሰ በኋላ ስለሆነ፤

በዚህ አኳኋን ተንቀሳቅሶ በታየው ጉዳይ ላይ የአሁን አመልካች የበኩላቸውን ክርክር ማቅረብ ይችሉ ዘንድ የመደመጥ መብታቸው እንዲከበር ጥሪ ያልተደረገላቸው ከመሆኑም በላይ መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ ተንቀሳቅሶ ዳኝነት የተሰጠበት ስለመሆኑ እርሷ በጊዜው እንዲያውቁት አልተደረገም፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የተቀመጠው የ60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ታሳቢ የሚያደርገው ተከራካሪው ባሉበት ውሳኔ መስጠቱን ወይም ለውሳኔ የሚያበቃ ክርክር የተደረገ መሆኑን ተረድቶ ቀርቦ ለመከታተል እና የዳኝነቱን ውጤት ለመስማትም ሆነ ለማወቅ ያልፈለገውን ወይም ደግሞ የተከራካሪው የመደመጥ መብት ይከበር ይቻል ዘንድ በሕጉ በተዘረጋው መረዳት መሠረት በአግባቡ ጥሪ ተደርጎለት በጥሪው መሠረት ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት ያልቻለ እንደሆነ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ይህ የ60 ቀን ጊዜ መታሰብ ያለበት ስለመሆኑ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁን አመልካች ሳይጠራ ዳኝነት የተሰጠ በመሆኑ አመልካች ሳይጠራ ግንቦት 22 ቀን 2004 ዓ.ም የተዘጋው መዝገቡ ተንቀሳቅሶ ዳኝነት የተሰጠ መሆኑን እንዲያውቀው በጊዜው ያልተደረገ መሆኑ እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ ይህ በሕጉ በተቀመጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ተጠቃሚ ሊሆን እንዳልቻለ ተገንዝበናል፡፡ በዚህ ሕጉ ታሳቢ አድርጎ ባስቀመጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚቻል ከተረጋገጠ ደግሞ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው በቂ ነበረ ወይስ አልነበረም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ዳኝነቱ መሰጠቱን ከተረዳበት ጊዜ ጀምሮ ከቀረው ዘጠኝ ቀን አንፃር በማየት ዘጠኝ ቀን የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ ያስችል ነበር አልነበረም ከሚለው አንፃር ሊታይ የሚገባው አይደለም፡፡

አመልካች በሕጉ ከተሰጠው የ60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ 51 ቀን በፍርድ ቤቱ በተፈፀመው ሥነ ሥርዓት ጉድለት ሳቢያ የባከነበት መሆኑ እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ አመልካች የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ የቀረው የዘጠኝ ቀን ጊዜ በቂ መሆኑና አለመሆኑ መለኪያ ሊሆን የሚገባ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ የአሁን አመልካች ስለመንቀሳቀሱም ሆነ የመደመጥ መበቱ እንዲከበር ሳይጠራ ዳኝነቱ መስጠቱ እየታወቀ በዚህም ምክንያት በሕጉ በተሰጠው የ60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ ሊጠበቅ እንዳልልቻለ እየታወቀ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንኑ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በቀረው የዘጠኝ ቀን ጊዜ ብቻ ተወስኖ ይህ ዘጠኝ ቀን በጉዳዩ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ በቂ ነበር ወይስ አልነበረም? ከሚለው ማነፃፀሪያ አኳያ ብቻ ተመልክቶ ማስፈቀጃው ተቀባይነት የለውም በሚል የሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ማስፈቀጃውን ጉዳይ ተመልክቶ በኮ/መ/ቁ 126464 በቀን 7/5/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች በሕጉ በተሰጠው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ለመጠቀም በሚያስችላቸው ደረጃ የተሰጠ ዳኝነት በመሆኑ ይህ ዳኝነት መሰጠቱን ከተረዳበት ጊዜ ከሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የይግባኝ አቤቱታ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ ሲሰላ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው እንዳለፈባቸው ስለማይቆጠር በጉዳዩ ላይ የይግባኝ አቤቱታቸውን አቅርበው እንዲያሰሙ ሊፈቀድ ይገባል ብለናል፡ ተፈቅዷል፡፡
3. በዚህ በሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 85102

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ሰንደቁ አበበ - ጠበቃ ወንድአወክ አየለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሐብታሙ ቃበቶ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ኑዛዜን መሰረት አድርጎ የቀረበውን የውርስ ንብረት ይለቀቅልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ/ም በአቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ በመሰረቱት ክስም ተጠሪውና የአሁኑ አመልካች በሞግዚትነት የሚያስተዳድሯት እህታቸው ስመኝ ቃበቶ የአንድ እናትና አባት ልጆች መሆናቸውን፣ከእናታቸው ከሟች ወ/ሮ ነጠር አስፋው የተላለፈላቸው መኖሪያ ቤት በባህርዳር ከተማ ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ እንደሚገኝና አመልካች፣ ተጠሪውና እህቱ ህፃን መሆናቸውን ተገን በማድረግ እንደ አንድ ወራሽ በመሆን በመኖሪያ ቤቱ ላይ የውርስ ማስረጃ በማውጣት ከ1989 ዓ/ም ጀምሮ ባለድርሻ ሁነው የቤቱን ኪራይ ተካፋይ ሲሆኑ መቆየታቸውን፣ተጠሪም ይህንኑ የአሁኑ አመልካች ድርጊት በመቃወም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ያገኘውን የውርስ ማስረጃ እንዲሰረዝ፣የእህታቸው ሞግዚትነትና አስተዳዳሪነት እንዲነሳ ለፍርድ ቤት አመልክተው ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች የያዘውን የውርስ ማስረጃ ሕግ በሚደግፈው መንገድ ያልተገኘ ስለሆነ ተሸሯል፣ነገር ግን የሞግዚትነት ስልጣንን በተመለከተ ግን የሟች ኑዛዜ ቃል ሊከበር የሚገባው በመሆኑ ህፃኗ አካለ መጠን አድርሳ የበኩሏን መብት እስከምታስጠብቅ ድረስ የጸና ነው በማለት መወሰኑንና በይግባኝም ውሳኔው ያለመለወጡን ዘርዝረው አመልካች በተሳሳተ የውርስ ማስረጃ ለአስራ ሶስት አመታት የተጠቀሙበትን የገንዘብ መጠን ብር 139,900.00 መሆኑን በመዘርዘርና የተጠሪውን የድርሻ መጠን በመለየት በጠቅላላው ብር 23,316.20 እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም የመጀመሪያ ወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው ጉዳዩ በይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እየታየ መሆኑን፣ስመኝ ቃበቶን በተመለከተ የውክልና ስልጣን ስለሌላቸው ክስ ለማቅረብ የማይችሉ፣ጉዳዩ ከዚህ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ በመሆኑ በድጋሚ ሊቀርብ እንደማይገባ፣ክሱ በይርጋ የታገደ በመሆኑ ክሱ ሊቀጥል እንደማይገባ፣የአመልካች የወራሽነት ማስረጃ የተሰረዘው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሊሆኑ አይችሉም በሚል እንጂ የኑዛዜ ወራሽነትን በሚመለከት ያለመሆኑን የሚመለከቱ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡ ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍሬ ነገር ክርክር ረገድ ደግሞ ተጠሪ በክሱ ላይ የጠቀሱት ገንዘብ ብር 139,900.00(አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር)፣የተጠሪ ድርሻ ተብሎ የተገለፀውን ብር 23,316.60 ለብቻቸው ያልተጠቀሙበት በመሆኑ ሊከፍሉ የማይገባ መሆኑን፣ከ1989 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ ወር1998 ዓ/ም ድረስ ቤቱ ተከራይቶ ይገኝ የነበረውን የተለየ መጠን ያለውን የኪራይ ገቢ ተጠሪ በየወሩ ድርሻቸውን እየተረከቡ ምግባቸውን ከአመልካችና ከስመኝ ቃበቶ ጋር ሁነው ሲጠቀሙ የነበረ መሆኑን፣ተጠሪ በ1996 ዓ/ም የውርስ አጣሪ ይሾምልኝ አቤቱታ አቅርበው ስለነበር አመልካች ቀርበው መልስ ከሰጡ በኋላ ሽማግሌዎችን መርጠው ድርድር ጀምረው ተቋርጦ ከቆየ በኋላ እንደገና ድርድሩ ጀምሮ ስምምነት ላይ ተደርሶ ድርሻቸውን ተከፋፍለው እየተጠቀሙ እንደሚገኙ ዘርዝረው በክሱ ላይ የተገለፀውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም አመልካች የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸው ስለተረጋገጠ ከተጠሪ ጋር እንደ ያለ ኑዛዜ ወራሽ ሁነው ንብረቱን እኩል የሚካፈሉ ናቸው የሚል ምክንያት ይዞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 915(1) ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ አመልካችና ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰውን የኪራይ ገንዘብ በጋራ የተጠቀሙ ስለሆነ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም፣የስመኝ ቃበቶ ሞግዚትነት ስልጣንን በተመለከተ ግን አካለ መጠን ያደረሰች በመሆኑ ራሷ ከምትጠይቅ በስተቀር ተጠሪ ሊጠይቅ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምእራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የአመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ጥያቄ ኑዛዜው ስለግልጽ ኑዛዜ አደራረግ ሕጉ ያስቀመጠውን መስፈርት የማያሟላ ሁኖ ተገኝቷል በሚል ምክንያት ማስረጃውን ውድቅ ያደረገውና የሟች ወ/ሮ ነጠር አስፋው ሕጋዊ ወራሾች ተጠሪና እህታቸው ስምኝ ቃበቶ ናቸው ሲል የደመደመ ሲሆን ውጤቱንም በተመለከተ የቤቱን ኪራይ ገቢ አመልካች ሕጋዊ ወራሽ ነኝ በሚል እምነት ከተጠሪ ጋር በጋራ የተጠቀሙበት በመሆኑ ሊከፍሉ አይገባም፣ቤቱን በተመለከተ ግን ለሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ለተጠሪና ለወ/ሮ ስመኝ ቃበቶ አመልካች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት በድምጽ ብልጫ ተሰርዞባቸዋል፡፡

ከዚህም በኋላ የሰበር አቤቱታቸው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩን ከይርጋ መቃወሚያ አንፃር ብቻ በመመልከት ጉዳዩ የጋራ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ስለሆነ በማናቸውም ጊዜ ሊጠየቅ የሚችል ነው የሚል ምክንያት ይዞ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ሁኖ እያለ ስለኑዛዜው ሕጋዊነት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በማንሳት በዚህ ረገድ የተሰጠውን የወረዳውን ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻራቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ወ/ሮ ነጠር አስፋው ሰኔ 03 ቀን 1988 ዓ/ም ባደረጉላቸው ኑዛዜ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውና ኑዛዜውም በወቅቱ በፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99/89 ፀድቆ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዕናቱ እየታወቀ ባሁኑ ተጠሪ ከሳሽነት በመ/ቁጥር 19749 የተጀመረውን ክርክር በመቀበል ኑዛዜው በፍርድ ቤት መጽደቅ አይገባውም ነበር፤ኑዛዜው በሕግ የተቀመጠውን መስፈርት አያሟላም በማለት ጉዳዩን ዳግም በማየት ኑዛዜውን የመሻራቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪና ስመኝ ቃበቶ የሚች ወ/ሮ ነጠር አስፋው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸው መረጋገጡን፣አመልካች የሚጂ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በመ/ቁጥር 99/89 መጋቢት 15 ቀን 1994 ዓ/ም ከወረዳው ፍርድ ቤት አግኝተው የነበረ መሆኑን፣ተጠሪ ይህ ማስረጃ በአመልካች የተገኘው ያላግባብ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ለወረዳው ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው የወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16107 ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካች ከሚች የተወለዱ ባለመሆኑ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሊያደርጋቸው የሚችል ሌላ ሕጋዊ ግንኙነት የሌለ በመሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉበት የሕግ መሰረት የለም በማለት ማስረጃውን ሰኔ 03 ቀን 2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰረዘው መሆኑን፣ይህ ውሳኔ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ቀርቦም በመ/ቁጥር 33024 በሆነው ግራ ቀኙ ተከራክረውበት ህዳር 21 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተቀባይነት አግኝቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካች የሚጂ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉበት የህግ መሰረት የለም፣የአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ በሚል በተጠሪ ቀርቦ በታየውና በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝ ዳኝነት ላይ አመልካች ስለኑዛዜ ክርክር የሚያቀርቡበት አግባብ የለም በማለት የመ/ቁጥር 05200 በሆነው ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአጸናው መሆኑንና ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የተጠሪ ክስ በወረዳው ፍርድ ቤት የተመሰረተውም መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ/ም መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተጠሪና አመልካች በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በጋራ የመ/ቁጥር 99/89 በሆነው በአስከፈቱት መዝገብ በኑዛዜው ላይ የነበሩ ምስክሮች ቀርበው መስክረው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ኑዛዜው የሕግን ፎርማሊቲ ያሟላ ነው በማለት ኑዛዜውን መጋቢት 14 ቀን 1994 ዓ/ም ያፀደቀው መሆኑን፣የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ አመልካች ኑዛዜው ቀድሞ ፀድቋል፣በፍርድ ያለቀ ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ያደረጉት ኑዛዜው በፍርድ ቤት መፅደቁንና ተጠሪ የክርክሩ ተካፋይ የነበሩ መሆኑን በማመን ኑዛዜው ቀድሞውንም የሕጉን መስፈርት የማያሟላ ሁኖ እያለ በፍርድ ቤት መጽደቁ ያላግባብ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ሚች ያደረጉት ኑዛዜ ግልፅ ኑዛዜ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባቸው ስርዓቶች በፍ/ሕ/ቁ.881 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ፣ይህም ስርዓት መፈፀሙና የተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ፣ተናዛዥና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡በሚች ተሰጠ የተባለው ኑዛዜም ሰነዱ ሲታይ አራት ምስክሮች ያልፈረሙበት፣ኑዛዜው በምስክሮች እና በተናዛዡ ፊት ስለመነበቡ የማይገልጽ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42623 በቀረበው ክርክር ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም ሚች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ሕ/ቁ. 881 ሥር የተመለከቱትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስርዓቶችን ያላሟላ ነው ተብሎ ውሳኔ የተሠጠው አመልካችና ተጠሪ ቀድሞ በመ/ቁጥር 99/89 በቀረበው ክርክር ከተከራከሩና ኑዛዜው ሕጋዊ ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ከፀደቀ በኋላ ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት የወሰነው ቀድሞውኑም ስርዓቱን ሳያሟላ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 99/89 ማፅደቁ ተገቢ አልነበረም በሚል ምክንያት ነው፡፡ይሁን እንጂ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17058 የሠጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በፍርድ ቤት ኑዛዜው የፀደቀ ነው ተብሎ ሲወሰን ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ይህንኑ ከማቅረብ የማይከለከሉ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የኑዛዜውን ሕጋዊነት መሰረት አድርጎ ተከራክሮ ተቀባይነት ያጣና ኑዛዜው በፍርድ ቤት የፀደቀበት ሰው በሌላ ጊዜ ስለኑዛዜው ሕጋዊነት ክስ መመስረት ወይም መቃወሚያነት ማቅረብ የሚችል መሆኑን የሚያሳይ አንድምታ የሌለው ነው፡፡በመሆኑም በሕግ አግባብ የተደረገን ኑዛዜ በፍርድ ቤት ማስጸደቅ ያስፈልጋል? ወይስ አያስፈልግም? የሚል ጭብጥ ተይዞ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበትን የሰ/መ/ቁጥር 17058 ጉዳይ መሰረት አድርገን ጉዳዩን ስንመለከተው አንዱ በፍርድ ቤት ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ የፀደቀ ኑዛዜ ቀድሞውንም መፅደቅ አልነበረበትም ተብሎ ፈራሽ እንዲሆን የሚደረግ የሕግ ምክንያት የለውም፡፡አግባብነት ያላቸው ተከራካሪ ወገኖች ስለኑዛዜው ሕጋዊነት ክርክር አቅርበው ኑዛዜው ሕጋዊ መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በጉዳዩ ላይ በድጋሚ ክስ ማቅረብና ፍርድ ቤቱም መቀበል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚጥስ ነው፡፡በዚህ ድንጋጌ አግባብ ጉዳዩ በፍርድ ቀደሞ ያለቀ ነው ተብሎ ተቀባይነት እንዲያገኝ ካልተደረገ በስተቀር ክርክሮች መቋጫ እንዳይኖራቸው የሚያደርግና ተከራካሪ ወገኖችን ለአላስፈላጊ የገንዘብ፣ጊዜና ጉልበት ብክነት የሚዳርግ፣ከስነ ስርዓት ሕጉ መሰረታዊ አላማም ውጪ ነው፡፡አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ዳኝነት መስጠት የሚገባውም በስርዓቱ መሰረት የቀረበለትን ይግባኝ መሰረት አድርጎ ነው እንጂ ቀድሞ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ተገቢ አልነበረም በሚል ምክንያት እንዳልሆነ ስለይግባኝ ስርዓት ከተደነገጉት ድንጋጌዎችና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 ድንጋጌ ጣምራ ንባብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ተጠሪ የኑዛዜን ወራሽነት አስመልክቶ አመልካች የሚያቀርቡትን ክርክር በመ/ቁጥር 99/89 ያልተካሄደ ነው ወይም በወቅቱ በጉዳዩ ላይ ክርክር ለማቅረብ የማያስችሉ ሕጋዊ ምክንያት የነበራቸው ስለመሆኑ ገልፀው ያልተከራከሩ ከመሆናቸውም በላይ አመልካች የሚች ነጠር አስፋው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ አይደሉም ተብሎ ማስረጃው እንዲሰረዝ በቀረበው ክርክር አመልካቹ ስለኑዛዜው ሕጋዊነት እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር አቅርበው ችሎቱ በመ/ቁጥር 05200 ሐምሌ 27 ቀነ 2002 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በመዝገቡ የተያዘው ክርክር ስለመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነት እንጂ ስለኑዛዜ ተጠቃሚነት ያለመሆኑን ጠቅሶ በዚህ ነጥብ ላይ ዳኝነት ሳይሰጥበት ማለፉ በዚህ ረገድ አመልካች ወደፊት የሚያቀርቡትን ክርክር ያልገደበው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡በአንድ ጉዳይ በጭብጥነት ተይዞ እልባት ያላገኘ ነጥብ ደግሞ ቀድሞ በፍርድ አልቋል ለማለት የማይቻል መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዘባል፡፡ስለሆነም አመልካች ኑዛዜውን አስመልክቶ የሚያቀርቡት ክርክር የመጨረሻ ፍርድ ያላገኘ ሲሆን የተጠሪ ግን በመ/ቁጥር 99/89 በተሰጠው ፍርድ መሰረት የመጨረሻ ዳኝነት ያገኘ ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለለም አመልካች በፍርድ ቤት የፀደቀው ኑዛዜ ተጠቃሚነትን መሰረት አድርገው ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ቤት ያለቀ ነው በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የታለፈው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ውጪ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በምእራብ ጎጃም ዞን መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42623 ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01-32078 ሰኔ 29 ቀን 2003 ዓ/ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 18331 ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ሟች ወ/ሮ ነጠር አስፋው አደረጉት የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያላሟላ በመሆኑ ፈራሽ ነው ተብሎ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ የተሰጠ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌንና በፍርድ ቤት በጸደቀ ኑዛዜ ተቃውሞ የሚቀርብበትን አግባብ ያላገናዘበ ነው ብለናል፡፡
3. በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር በ19749 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፤አመልካች ሟች ወ/ሮ ነጠር አሰፋው ሰኔ 03 ቀን 1988 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ ተጠቃሚነታቸው በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99/89 በተሰጠ ውሳኔ የተረጋገጠ ነው ብለናል፡፡
4. ተጠሪ እና ስመኝ ቃበቶ በአከራካሪው ቤት ላይ ከአመልካች ጋር እኩል መብት አላቸው ብለናል፡፡አመልካች ለተጠሪ የሚከፍሉት የኪራይ ገንዘብ የለም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 86133

ጥቅምት 20 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-

1. አቶ ፍቅሩ ከበደ
2. አቶ ገብረወልድ በርጋ
3. አቶ ከበደ አርጋው
4. አቶ ኃይሉ ግዛው
5. አቶ መህዲ መሐመድ
6. አቶ ግንባሩ አረጋው
7. አቶ ሳዲቅ አውል
8. አቶ ከድር ረሺድ
9. አቶ ፈድሉ ኑረዲን
10. አቶ ወልዴ ብዛ
11. አቶ መንግስቱ ኃ/ማሪያም

ጠበቃ ታፈሰ ይርጋ ቀረቡ

ተጠሪ፡ 1. ወ/ሮ አስቱር አርአያ - አልቀረቡም

2. ወ/ሮ ፋንታዬ መኮንን - ጠበቃ ዮሴፍ ደስታ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥቷል፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍርድ አፈፃፀም ጊዜ በአንድ ንብረት ላይ አፈጻጸሙ ሲመራ በንብረቱ ላይ ሕጋዊ መብት አለን የሚሉ ሰዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት አቤቱታ ሲያቀርቡ አቤቱታቸው ሙሉ የክርክር አመራር ስርዓትን መሰረት አድርጎ ሊከናወን የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡የአፈፃፀሙ ክርክር የተጀመረው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ባሁኗ 2ኛ ተጠሪ ላይ የጥብቅና አበል አልተከፈለኝም በሚል ያቀረቡት የዋና ክርክር ጉዳይ ታይቶ የፍርድ ባለመብት መሆናቸው በመረጋገጡ ይኼው ፍርድ ቤት እንዲፈፅምላቸው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባስከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ ነው፡፡1ኛ ተጠሪ ለፍርዱ ማስፈፀሚያ ይሆንላቸው ዘንድም 2ኛ ተጠሪ በውርስ መብት አግኝተውባቸዋል ባሏቸው፤በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ አጠራር በወረዳ 3፣ቀበሌ 32 ክልል ውስጥ በሚገኙትና ቁጥራቸው ከ803 እስከ 805 በሆኑ ቤቶች እንዲሁም በወረዳ 5፣ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ በሚገኙትና ቁጥራቸው ከ936 እስከ 953 በሚል ተመዝግቦ በሚገኙ ጋራዥ ቤቶች ላይ ለፍርድ ቤቱ የገለፀ ሲሆን የአሁኑ አመልካቾች በወረዳ 5 ቀበሌ 06 ክልል በሚገኙትና ቁጥራቸው ከ936 እስከ 953 ተብሎ የተመዘገቡ የመኮነን ነጋሽ የሕዝብ ማመላለሻ ድርጅትና ጋራዥ በድርጅትነት እንደሚታወቅና ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ/ም በተደረገ የንግድ ቤት ድርጅት ሽያጭ ውል የሚች አቶ መኮንን ነጋሽ ሚስት ወ/ሮ የሺወርቅ ግዛው ከልጆቻቸው እነ ፋሲል መኮነን ነጋሽ (ሰባት ራሳቸው) እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን ሽጠውላቸው ነሐሴ 08 ቀን 1999 ዓ/ም የተረከቧቸው መሆኑን ገልፀው 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የፍርድ ይፈፀምልኝ ጥያቄ በንብረቶቹ ላይ ሊቀጥል እንደማይገባ፣በወረዳ 3 ቀበሌ 32 በቤት ቁጥር 803 እስከ 805 በሚታወቁት ቤቶች ላይ አፈፃፀሙ ቀጥሎ በእነዚህ ንብረቶች ላይ የፍርድ ባለእዳዋ ድርሻ እዳውን የሚሸፈን ካልሆነ የአሁኑ አመልካቾች ሻጮች ባደረጉት ውል መሰረት ተፈጽሞ 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ ቀሪ ድርሻ እንዳላቸው ቀሪውን በፍርድ ባለእዳዋ ድርሻ ልክ ይዘው ለመክፈል የሚችሉ መሆኑን ገልጸው አፈፃፀሙ በዚህ መልክ እንዲመራ አመልክተዋል፡፡የአሁኗ ተጠሪ ለአመልካች አቤቱታ በሰጡት መልስም አመልካች አለን የሚሉት ውል ሕጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ ያልተደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው ጥያቄአቸው ሙሉ በሙሉ ውድቅ እንዲሆን ያመለከቱ ሲሆን 2ኛዋ ተጠሪም አመልካቾች በወረዳ 5 ቀበሌ 06 ክልል ውስጥ የሚገኙትንና ቁጥራቸው 936/2/፣947 እስከ 952፣953/2/ ፣954 እና 954/2/ የሆኑትን በውል ገዝተው የተረከቧቸው መሆኑን ጠቅሰው እንደውሉ ተጠብቆ እንዲፈፀምላቸው ቢደረግ የማይቃወሙ መሆኑን፣የቤት ቁጥር 803 የተባለውን ግን እንደማያውቁት፣የቤት ቁጥር 936/3/፣938/1/፣946 እና 947/2/ ለአመልካቾች ያልተሸጡላቸው፣ገንዘብ ያልተቀበሉባቸው እና ያላስረከቧቸው በመሆናቸው የፍርድ ባለመብት ፍርዱን ሊያስፈጽሙባቸው የሚችሉ በመሆኑ የአመልካቾች ጥያቄ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣የቤት ቁጥር 937/1/፣938፣940፣941፣943፣944፣945 የሆኑት ደግሞ የመንግስት ቤቶች በመሆናቸው ፍርዱ ሊፈጸምባቸውም ሆነ መቃወሚያ ሊቀርብባቸው የማይችልባቸው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

አፈጻጸሙን የያዘው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካቾች ያቀረቡት ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723(1) ስር እና በንግድ ሕጉ ቁጥር 127 እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1432(1) ድንጋጌዎችን ይዘት የሚያሟላ አይደለም በማለት የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የአሁኑ አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 አግባብ ያቀረቡት በመደበኛ የሙግት ስርዓት ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንፃር ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ባለመሆኑና ይህንኑ እድል ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስ አቅርቦ መጠቀም እንደሚቻል፣ይህ ስለመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37214 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት መሆኑን ዘርዝሮ የሥር ፍርድ ቤትን የአፈጻጸም ትእዛዝ ምክንያቱን ለውጦ በማፅናት የአመልካቾችን አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸውን ጠብቋል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 እና 421 ድንጋጌዎች አተገባበር የሰጠው ትርጉም የሕጉን መንፈስና አላማ ያላገናዘበና ትርጉሙ ውጤት የሌለው መሆኑን እንዲሁም የሥር ፍርድ ቤት ሽያጩ በሕጉ የተዘረጋውን የሽያጭ አደራረግ ስርዓት ያልተከተለ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ለድርጅት ሽያጭ የተመለከቱትን የሕግ ድንጋጌዎችን ባግባቡ ያላገናዘበ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ አመልካቾች በንብረቶቹ ላይ ያላቸው መብት እንዲጠብቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡እንደመረመርነውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት የሚቀርብ አቤቱታ መደበኛ የሙግት ስርዓት ተከትሎ የሚከናወን አይደለም፣አቤቱታው ውድቅ የሆነበት አካል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421 አግባብ ሌላ ክስ አቅርቦ መብቱን ማስጠበቅ ይችላል በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉም ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክር ሂደቱ መገንዘብ እንደተቻለው የአሁኑ አመልካቾች በወረዳ 5 ቀበሌ 06 ክልል በሚገኙትና ቁጥራቸው ከ936 እስከ 953 ተብሎ የተመዘገቡ የመኮነን ነጋሽ የሕገዘብ ማመላለሻ ድርጅትና ጋራዥ በድርጅትነት እንደሚታወቅና ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ/ም በተደረገ የንግድ ቤት ድርጅት ሽያጭ ውል የሚች አቶ መኮነን ነጋሽ ሚስት ወ/ሮ የሻሸወርቅ ግዛው ከልጆቻቸው እነ ፋሲል መኮነን ነጋሽ (ሰባት ራሳቸው) እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን ሽጠውላቸው ነሐሴ 08 ቀን 1999 ዓ/ም የተረከቧቸው መሆኑን ገልፀው 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የፍርድ አፈጻጸም ጥያቄ በእነዚህ ንብረቶች ሊቀጥል እንደማይገባ ገልፀው በሽያጭ ያገኙት መብት እንዲጠብቅላቸው ዳኝነት ጠይቀው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሽያጭ ውሉ ሕጉን የማያሟላ ነው በማለት የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉና የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግን የአመልካቾች አቤቱታ በመደበኛ ሙግት አመራር ስርዓት መሰረት ሊከናወን የማይችልና መብታቸውን በአዲስ ክስ ማስከበር የሚችሉ መሆኑን ዘርዝሮ የስር ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ ምክንያቱን ለውጦ በውጤት ደረጃ የተቀበለው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 እና 419 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር የመቃወሚያ አቤቱታ ሲቀርብ ወይም በዚሁ ንብረት ላይ ተቀዳሚ መብት አለኝ የሚል ተቃዋሚ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በሚያዘው ንብረት ላይ መብት እንዳላቸው በመቁጠር የሚያቀርቡትን መቃወሚያና አቤቱታ ተቀብሎ መመርመር እንዳለበት እንዲሁም በመጨረሻ ላይም የቀረበለትን አቤቱታና ማስረጃውን ከመረመረ በኋላ ንብረቱ እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የሚያደርግ በቂ ምክንያት ያለመኖሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተረዳ እንደሆነ ንብረቱ እንደሁኔታው በሙሉ ወይም በከፊል እንዲለቀቅ ወይም ንብረቱ በፍርዱ አፈጻጸም መያዙ ተገቢ ሆኖ ካገኘው ደግሞ አቤቱታውን እንደሚሰረዝ ያስገነዝባሉ፡፡ሆኖም ግን እነዚህ ድንጋጌዎች በተለይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 419 መሰረት ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ሲሰጥ የሌላውን ተከራካሪ ወገን ህገ መንግስታዊ የመስማት መብቱ ሣይከበርለት እና እንዲሁም አግባብነት ባለው መሰረት የተከበሩለትን መብቶች አንስቶ መከራከሪያ ሣያደርግባቸው ሊፈጸም የሚችል አይደለም፡፡በሌላ አነጋገር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 419 ድንጋጌ ይዘት የሌላውን ተከራካሪ ወገን የመስማት፤የመደመጥ እና በህጉ አግባብ ክርክሩን የማቅረብ መብቱን የሚከለክል ያለመሆኑን ከላይ በተገለጸው አግባብ በመተንተን ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 87833 በቀረበው ጉዳይ ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡በሰ/መ/ቁጥር 37214 በቀረበው ጉዳይ ይህ የመሰማትና የመደመጥ መብት የማይከበር ስለመሆኑ በግልጽ አቋም ያልተያዘበት የሕግ ትርጉም ሲሆን በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የሚያሳያው የቀዳሚነት መብት አለኝ በሚል መቃወሚያ አቅርቦ ጥያቄው ውድቅ የተደረገበት ሰው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421 መሰረት በድጋሚ ክስ ለማቅረብ የተፈቀደለት በአፈፃፀም ችሎቱ የንብረቱ ባለመብትነት በጭብጥነት ተይዞ በመደበኛው የሙግት ስርአት አይነት የአመልካቹ ጥያቄ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንፃር ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ባለመሆኑ ይህንን እድል ለመስጠት ነው በሚል ነው፡፡ሆኖም ችሎቱ ድንጋጌው የመደበኛ ሙግት ስርዓትን በመከተል መቃወሚያ አቤቱታውን ለማስተናገድ ሕጉ በግልጽ ክልከላ አድርጓል ወደሚለው ድምዳሜ ያልደረሰ ሲሆን በሰ/መ/ቁጥር 87833 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡በመሆኑም በሕጉ አግባብ የቀረበን መቃወሚያ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ተገቢውን ዳኝነት መስጠት የፍትሓብሄር ስነ ስርዓት ሕጉን መሰረታዊ አላማ ያሳካል ከሚባል በስተቀር ሌላ አሉታዊ ውጤት በክርክር አመራር ስርዓት ላይ የሚያስከትል አይደለም፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት አቤቱታ ያቀረበ ወገን በሕጉ አግባብ ማስረጃ ቆጥሮ ተቃውሞውን ከአቀረበ ጉዳዩ በአፈጻጸም መዝገብ እንዲከናወን ማድረግ ጊዜን፣ጉልበትንና ወጪ የሚቆጥብ መሆኑ የሚታመን ሲሆን ክርክሩ የመደበኛ መግት ስርዓትን ተከትሎ እንዲከወን ለማድረግ የሚያስችል አቤቱታ መቅረቡ እስከተረጋገጠ ድረስ የግራ ቀኙን የመከራከር መብት ጠብቆ በጉዳዩ ላይ ዳኝነት መስጠት ተገቢ አይደለም፣የሕጉን አላማ አያሳካም ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያትም የለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 አግባብ የተሟላ ክርክርና ማስረጃ ያቀረበ ወገን አቤቱታው በመደበኛ ሙግት እንዲከናወን እንዳይጠይቅ ሕጉ ግልጽ ክልከላ ያላደረገበት ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421 ስር የተጠበቀው መብትም በሕጉ አግባብ የሚቀርቡ መቃወሚያዎች እንደተጠበቁ ሁነው አመልካቹ በምርጫው እንዲጠቀምበት የተቀመጠ እንጂ ይህንኑ ስርዓት እንዲከተል የግድ የሚደረግበት ያለመሆኑ ድንጋጌው በፈቃደኝነት የአቀራረፅ ስርዓት መቀመጡ አስረጂ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች በአፈጻጸም ሊያዙ የማይችሉበትን ሕጋዊና በቂ ምክንያት ካላቸው ይህንኑ አንስተው ሙሉ በመደበኛው የሙግት ክርክር አቅርበው መብታቸው ሊከበርላቸው የማይገባበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በእርግጥም ሽያጭ ውሉ በህጉ አግባብ የተደረገ መሆን አለመሆኑንና ወይም በንብረቶቹ ላይ አመልካቾች ያቋቋሙት መብት መኖር ያለመኖሩና አመልካቾች በሽያጭ ንብረቶቹን አስተላልፈዋል የሚሏቸው ወገኖች ተግባሩን ለመፈፀም ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት ያላቸው መሆኑና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የሕግና የፍሬ ነገር ክርክሮችን በጭብጥነት ይዞና በግራ ቀኙ ማስረጃዎችም ሆነ ፍርድ ቤቱ በሚያስቀርባቸው ሌሎች አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች በማንጠር የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች አለ የሚሉት የሽያጭ ውል ሕጋዊ አይደለም በማለት የሰጠው ትእዛዝ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የፈዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሊወስንበት የሚገባው ሁኖ ሳለ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418፣419 እና 421 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ በመውጣት ጉዳዩ በመደበኛ የሙግት ስርዓት ሊከናወን የሚችል አይደለም፣አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚቻልበት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ፣ የፍታብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አይነተኛ አላማ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 87833 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በዚህ ጉዳይ ላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 81670 ታህሳስ 23 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁ 81670 ቀጥሎ የግራ ቀኙን አስቀርቦ የአመልካቾች አቤቱታ በህጉ አግባብ በተቀመጠው ሙሉ የመስማት መብት ጠብቆ እና ጉዳዩ በግራ ቀኙ ክርክር እና አግባብነት ባለው ማስረጃ እንዲጣራ ከተደረገ በኋላ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341 መሰረት ክርክሩን መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 89494

ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የኢትዩጵያ መድን ድርጅት ነ/ፈጅ ሠናይት በዳሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የሚች ዘካሪያ ኢብራሂም ባለቤት ሳዲያ ኢብሮሽ /ጠበቃ ወረደ ፀሐይ ወ/ዮሐንስ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በመድን ውሉ መሰረት የተከፈለ ገንዘብ ይተካልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ እና በአቶ ቶፊቅ ኡስማን ላይ በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች ክስ ይዘት፡-ንብረትነቱ የአቶ ዘነበ ተካን፤የአመልካች ደንበኛ የሆነውንና በሰሌዳ ቁጥር 3-52129 የሚታወቀው ሚኒባስ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወደ ጅጅጋ አስር ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ ንብረትነቱ የአሁኑ ተጠሪ የሆነውና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-00947 ሐረር በሚል የሚታወቅ መኪና በስር ሁለተኛ ተከሳሽ በነበሩት አቶ ቶውፊቅ ኡስማን ሲሽከርከር ከመንገድ በመውጣት በ23/11/2003 ዓ/ም በመግጨት ጉዳት ያደረሰበት መሆኑንና በጉዳቱም በተሳፋሪዎች የመቁሰል አደጋ ከመድረሱም በተጨማሪ መኪናው ከስራ ውጪ የሆነ መሆኑን፤ለተሳፋሪዎች የተከፈለውንና መኪናው ከስራ ውጪ በመሆኑ በድምሩ የብር 287,003.40 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ ሶስት ብር ከአርባ ሳንቲም) ጉዳት የደረሰበት መሆኑን፤ከዚህ ገንዘብ ውስጥ የመኪናውን ሳልቬጅ በብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ ብር) የሸጠ እና ገቢ ያደረገ መሆኑን ጠቅሶ ቀሪውን ብር 187,003.40 ግን ተጠሪና የተጠሪን መኪና ሲያሽከርክር የነበሩት ግለሰብ አቶ ቶፊቅ ኡስማን እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ለማስረጃነትም የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዞ አቅርቧል፡፡የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ቶውፊቅ ኡስማን በሌሉበት ጉዳዩ የታየ ሲሆን የአሁኗ ተጠሪ ግን ቀርበው በሰጡት የመከላከያ መልስ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፤ለአደጋው መድረስ የተጠሪ መኪና ጥፋት ያለበት መሆኑ አለመረጋገጡን፤የጉዳቱን መጠን ለማስረዳት የቀረቡት ደረሰኞችም ስርዝ ድልዝ ያለባቸው በመሆኑ በሕጉ ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን፤ስለመከፈሉ ያስረዳል ተብሎ በቀረበው የሰነድ ማስረጃም የጉዳቱ መጠን በአጎዝና በፊደል የተቀመጠው የተለያየ በመሆኑ ሊወሰድ የሚገባው የፊደል መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው አደጋ ያደረሰው የተጠሪ መኪና መሆኑ ያለመረጋገጡን ጠቅሶ ለጉዳቱ መድረስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁለቱም ተሸከርካሪዎች የራሳቸው አስተዋጽኦ እንደነበር በመደምደም ሁለቱም ተሸከርካሪዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2084(3) ድንጋጌ መሰረት የጋራ ኃላፊነት አለባቸው በማለት የወሰነ ሲሆን የጉዳቱን መጠን በተመለከተ ደግሞ በአመልካች በኩል ከቀረቡት የተወሰኑት ደረሰኞች እምነት የማይጣልባቸው መሆኑን ለይቶ ውድቅ አድርጎ በድምሩ ብር 245,588.25 (ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺ አምስት መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም) ጉዳት መደረሱን፣ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺ ብር) ሳልቬጅ ሲቀነስ ቀሪው ብር 145,588.25 መሆኑን በመግለፅ ይኼው የጉዳት መጠን ለሁለት ሲካፈል ተጠሪ ብር 72,794.12. (ሰባ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአስራ ሁለት ሳንቲም) ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲያቀርብ ተጠሪ ባሉበት ጉዳዩ እንዲጣራ በመደረጉ ተጠሪም በስርኣቱ መሰረት የመስቀልኛ ይግባኝ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪን መኪና ሲያሽከርክሩ የነበሩት አሽከርካሪ ለጉዳቱ ሙሉ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ በወንጀል ተቀጥተው እያለና ይኼው ውሳኔ በማስረጃነት በፍርድ ቤቱ እገዛ እንዲቀርብ አመልካች ጠይቆ እያለ ማስረጃው ሳይቀርብ ጉዳቱ የደረሰው በሁለት ተሸከርካሪዎች ግጭት ነው ተብሎ አግባብነት የሌለው ሕግ ተጠቅሶ ኃላፊነቱ የጋራ ተደርጎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ የተጠሪን መኪና ሲያሽከርክር የነበረው አሽከርካሪ በወንጀል ያለመቀጣቱን፣አመልካችም የወንጀል ችሎት የሰጠውን ውሳኔ አለ ከማለት ውጪ በየትኛው ፍርድ ቤትና በየትኛው መዝገብ ቁጥር ስለመሆኑ ለይቶ ባልጠቀሰበት ሁኔታ ማስረጃው ሳይቀርብ ቀርቷል በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 ድንጋጌ አተገባበርን ያላገናዘበ መሆኑን በመጥቀስና ተጠሪ ያላግባብ ለጉዳቱ የጋራ ሃላፊነት አለባቸው ተብሎ መወሰኑ ተጠሪን የጎዳና አመልካችን የጠቀመ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡የአሁኑ አመልካች በሰጠው የመልስ መልስም የወንጀል ውሳኔ የተባለውን ማስረጃ ውሳኔውን የሠጠውን ፍርድ ቤትና መዝገቡን ለይቶ ሳይጠቅስ የሰበር አቤቱታውን ይዘት በመድገም ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገውን የአደጋ ቦታ ፕላንና መግለጫ ይዘት ታልፎና በፍርድ ቤት እገዛ እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ ሳይቀርብ በበታች ፍርድ ቤቶች ኃላፊነቱ የጋራ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ ከእነዚህ ነጥቦች አንጻር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው መኪና ሐምሌ 23 ቀን 2003 ዓ/ም በተጠሪ መኪና ግጭት የደረሰበት መሆኑን አመልካች ገልጾ ጉዳት በደረሰበት መኪና ለነበሩት ተሳፋሪዎች የተከፈለውን ወጪ፣መኪናውን ከስራ ውጪ በመሆኑ ምክንያት የታጣውን ገቢ መጠን ዘርዝሮና የሳልቤጁን ዋጋ መጠን ለይቶ በድምሩ ብር 187,003.40 ለደንበኛው የከፈለው የጉዳቱ ወጪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ገልፆ ይሔው ገንዘብ እንዲተካ ጥያቄ አቅርቦ የአሁኗ ተጠሪም በኃላፊነቱም ሆነ በመጠኑ ላይ የቀረቡት ክርክሮች ያላግባብ የቀረቡ ናቸው የሚል ክርክር አቅርበው የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክሮችና ማስረጃዎችን መርምሮ በአመልካች የመድን ሽፋን የተሰጠው መኪና ከተጠሪ መኪና ጋር ሐምሌ 23 ቀን 2003 ዓ/ም መጋጨቱን፣ለግጭቱ ምክንያት የሆነውን ጥፋት የፈፀመው አሽከርካሪ ግን የትኛውን መኪና ሲያሽከርክር የነበረ አሽከርካሪ እንደሆነ በጉዳዩ የቀረቡት የአመልካች ማስረጃዎች እንደማያሳዩ ገልጾ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር በከፊል ያለፈው መሆኑን ነው፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ደንበኛ መኪና እና የተጠሪ ንብረት በሆነው መኪና ግጭት መድረሱንና ለጥፋቱ ሙሉ ኃላፊነቱን ሊወስድ የሚገባው አሽከርካሪ ግን ያለመለየቱን ፍሬ ነገሩን አጣርቶና ማስረጃን መርምሮ ድምዳሜ ላይ የደረሰበት ጉዳይ ሲሆን ይኸው የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

እንግዲህ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው መኪና ከተጠሪ መኪና ጋር ተጋጭቶ ጉዳት የደረሰበት ከመሆኑ ውጪ በተጠሪ አሽከርካሪ ሙሉ ጥፋት ግጭቱ ስለመድረሱ በጉዳዩ ላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች ይዘትና መንፈስ የስር ፍርድ ቤት መገንዘብ ያለመቻሉን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣኑን ተጠቅሞ ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡አሁን አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት በዚህ ረገድ ያቀረበው ቅሬታ የስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 መሰረት እንዲቀርብ የተጠየቀውን ማስረጃ ሳያስቀርብ አልፏል የሚል ነው፡፡በእርግጥ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 መሰረት የተጠየቀ ማስረጃ ሳይቀርብ ፍርድ መስጠት የፍርድ ሳካሄዱ በተሟላበት ሁኔታ የተሰጠ ነው ለማለት የማይቻል መሆኑ የሚታመን ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 መሰረት የፍርድ ቤቱን እገዛ በመጠየቅ ማስረጃ ማስቀረብ የሚቻለው ግን ጠያቂው ወገን እንዲቀርብ የተጠየቀውን ማስረጃ ትክክል ግልባጭ በቅርብ ጊዜ ለማምጣት የማይችልበትን ወይም ማስገልበጫ የሚያስፈልገውን ወጭ ለመክፍል የማይችል መሆኑን እንዲሁም እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ ለክርክሩ ምን ያህል ጠቃሚነት እንዳለው፣ትክክለኛን ፍርድ ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን በፅሁፍ ገልፆ ማስረዳት እንዲሚጠበቅበት የተጠቃሹ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡በመሆኑም ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤት እገዛ ማስረጃ እንዲቀርብለት ሲጠይቅ በሕጉ የተመለከቱትን መስፈርቶችን በግልጽ ገልፆ ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145(1) እና (2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች በፍርድ ቤት እገዛ እንዲቀርብለት የሚጠይቀው የፅሑፍ ማስረጃ የፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሆን ውሳኔው በየትኛው ፍርድ ቤትና በየትኛው የመዝገብ ቁጥር እንደተሰጠ ካለመግለፁም በላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 ስር የተመለከተውን የሕጉን አገላላፅ ለማስረዳት የጠቀሳቸው ምክንያቶችም የሉም፡፡እንዲሁም አመልካች የወንጀል ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በየትኛው ፍርድ ቤትና መዝገብ ቁጥር እንደተሰጠ ያለመግለጹን፣በስር ፍርድ ቤትም ፍርድ ቤቱንና የመዝገብ ቁጥር እንዲጠቅስና ማስረጃውንም እንዲያቀርብ እድል ተሰጥቶት በእድሉ ሊጠቀም ያለመቻሉን ተጠሪ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጡት መልስ በግልጽ ጠቅሰው ተከራክረውም አመልካች በዚህ ረገድ ባቀረበው የመልስ መልስ ለተጠሪ የክርክር ነጥብ ማስተባበያ ክርክር አላቀረበበትም፡፡በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት እድሉ ተሰጥቶ ተገቢውን ሊፈፅም ያለመቻሉን አመልካች እንዳመነ የሚያስቆጥረው መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 235 እና 83 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ሲሆን በዚህ የሰበር የክርክር ደረጃ እንኳን አመልካች አለኝ የሚለውን የወንጀል ውሳኔ የሠጠውን ፍርድ ቤትና የመዝገቡን ቁጥር በግልጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅሶ ያለመከራከሩ በማስረጃው አቀራረብ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቱ ተገቢውን እገዛ እንዲያደርግ አመልካች በራሱ በኩል ተገቢውን ያለመፈፀሙን የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡

አመልካች በትራፊክ መርማሪ ፖሊስ ጥፋቱ የተጠሪን መኪና ሲያሽከርክር የነበረ አሽከርካሪ መሆኑ ተገልጾ እያለ በበታች ፍርድ ቤቶች ይኼው ታልፏል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ደግሞ ማስረጃው በስር ፍርድ ቤት ተመዝኖ የታለፈ በመሆኑና ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን መዝኖ የራሱን ድምዳሜ ከመያዝ የሚከልክል ሕግ የሌለ ስለመሆኑ፣ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንደዚህ አይነት ማስረጃ እንደማንኛውም ማስረጃ ሊመዝን የሚችል እንጂ ደምዳሚ ማስረጃ ያለመሆኑን ገልጾ በሰ/መ/ቁጥር 14981፣43453 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት መሆኑን ያላገናዘበ በመሆኑ የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር ከመሆኑም በላይ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ይዘት ውጪ በመሆኑ አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ማጣራትና በማስረጃ ምዘና ሂደት ሰርተውታል የሚለውን ስህተት የማጣራትና የማረም ስልጣን ይኽ ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ያልተሰጠው ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ያለው ክርክር ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ግጭቱ በሁለት ተሽከርካሪዎች የደረሰ ከሆነና ጥፋቱ የየትኛው ተሽከርካሪ እንደሆነ በማስረጃ መለየት ካልተቻለ አንዱ ባንዱ ላይ አደጋ እንደአደረሰ እንደሚቆጠር፣ለየእንዳንዱ ተሽከርካሪ ባለሃብት ወይም ለአደጋው አላፊ የሆነው ሰው በአደጋው ምክንያት ከደረሰው ጠቅላላ ጉዳት ገሚሱን መክፈል ያለበት መሆኑን ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2084(1) እና (2) ድንጋጌዎች በግልጽ ያሳያሉ፡፡

በአጠቃላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145 ድንጋጌ መሰረት እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ በስር ፍርድ ቤት ሳይቀርብ የቀረው አመልካች በሕጉ በተመለከተው አኳኋን ማስረጃውን ለማቅረብ ያልቻለበትን ሕጋዊ ምክንያትና ማስረጃው የሚገኝበትን ፍርድ ቤትና የመዝገቡን ቁጥር ለይቶ ባለማቅረቡ ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት መረጋገጡን የተገነዘብን ስለሆነና በትራፊክ ፖሊስ ማስረጃ ላይም አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተፈጽሟል የሚለው ስህተት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት በመሆኑና ይህ ደግሞ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛ ባለመሆኑ በዚህ ችሎት ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ ስለሌለ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 940/03 ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 185/2004 የካቲት 08 ቀን 2005 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ለአደጋው የአመልካች ደንበኛ መኪና እና የተጠሪ መኪና የጋራ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የጉዳት መጠኑን እኩል እንዲጋሩ ተደርጎ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ቤ/ዮ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90543

ጥቅምት 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-1.አቶ ተሾመ አሰፋ
2.ማርሸት አሰፋ
3.ፍቅረዓለም አሰፋ
} የጠበቃ ወኪል ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት መስታወት አሰፋ/ቀረበች

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ከወ/ሪት ቦንቱ አሰፋ ጋር በመሆን በሀዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የስር ከሳሾች ያቀረቡት ክስ ይዘትም የከሳሾችና የተከሳሾች ወላጅ አባት የሆኑት አቶ አሰፋ በዳሳ የካቲት 15 ቀን 1994 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውንና ንብረቶቻቸውም በተከሳሾች እንደሚተዳደሩ ገልፀው የሟቹ የውርስ ንብረቶች እንዲጣሩ ይደረግላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም ጉዳዩ በይርጋ የታገደና ቀድሞ በፍርድ ያለቀ መሆኑን ጠቅሰው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ መቃወሚያ መነሻ አድርጎ ጉዳዩን የተመለከተ ሲሆን ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ መሆኑ መረጋገጡን ገልጾ ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ መሰረት ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ብይን ከሳሾች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ያጡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ከሳሾች በመ/ቁጥር 01110 አቅርበውት የነበረው ክስ ሟች አቶ አሰፋ በዳሳ በተውት የቁም ኑዛዜ ከሰጧቸው ብር 20,000.00 ውስጥ ቀሪውን ብር 10,000.00 የአሁኑ 1ኛ አመልካች እንዲከፍል ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የጠየቁበት ሁኖ በጉዳዩ ላይ በ7/7/2004 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔም ይህንኑ ጥያቄአቸውን በመቀበል በኑዛዜው መሰረት ቀሪው ገንዘብ እንዲከፈላቸው የሚገልፅ በመሆኑና በአዲሱ ክስ ከሳሾች ክስ የመሰረቱት የውርስ ንብረት ይጣራልኝ በሚል እንጂ በኑዛዜ የተሰጣቸውን ገንዘብ እንዲሰጣቸው የሚጠይቅ ባለመሆኑ፤በሁለቱ መዛግብት የተነሱት የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክሮች ተመሳሳይ ባለመሆናቸው ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ አልቋል ለማለት የሚቻል አይደለም በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶችን ብይን በመሻር ፍሬ ጉዳዩ በስር ፍርድ ቤት ታይቶ ተገቢው ዳኝነት እንዲሰጥበት ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ ቀድሞ በኑዛዜ ክርክር ጊዜ ያለቀ ሁኖ እያለ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄና በኑዛዜው መሰረት ይፈፀምልኝ ጥያቄ ተመሳሳይነት የላቸውም ተብሎ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰጠቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ አይደለም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪና ወ/ሪት ቦንቱ አሰፋ የካቲት 08 ቀን 2004 ዓ/ም ለሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ባቀረቡት ማመልከቻ ሟች አባታቸው አቶ አሰፋ በዳሳ መስከረም 16 ቀን 1994 ዓ/ም በተውት ኑዛዜ ላይ ለእያንዳንዳቸው ብር 10,000.00 በአቶ ተሾመ አሰፋ በኩል እንዲሰጣቸው የተናዛዡላቸው መሆኑንና ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 10,000.00 በአቶ ተሾመ አሰፋ ተሰጥቷቸው ቀሪው ብር 10,000.00 ያልተሰጣቸው መሆኑን ገልጸው ይኼው በኑዛዜ የተሰጣቸው ገንዘብ ሙሉ በሙሉ እንዲከፈል ዳኝነት እንዲሰጣቸው የጠየቁ መሆኑንና ክርክሩም ከአቶ ተሾመ አሰፋ ጋር ብቻ ቀጥሎ አቶ ተሾመ አሰፋ በክሱ ኃላፊ ተደርገው ገንዘቡን እንዲከፍሏቸው ዳኝነት የተሰጠበት ጉዳይ መሆኑን፣እነ ወ/ሪት መስታወት አሰፋ ግንቦት 28 ቀን 2004 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ደግሞ አቶ ተሾመንና ሌሎች ሁለት እህቶቻቸውን በአንድ ላይ አድርገው፣በተከሳሽነት ሰይመው ዳኝነት እንዲሰጣቸው የጠየቁት ጉዳይ የአቶ አሰፋ በዳሳ የውርስ ንብረት እንዲጣራላቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የፍትሐ ብሔር ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ እንዲኖረው በማሰብ ከተደነገጉ የስነ ስርዓቱ ድንጋጌዎች አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውጤት ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍኑ መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን፣በውሣኔ፣በትእዛዝ፣ወይም በጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ መንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ አቅፎ የያዘ፣ክርክር አንድ ቦታ ላይ እንዲቆም ታስቦ በሕግ የተዘረጋ ስርዓት ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካላባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡
ሕጉ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ስለመሆኑም ያስገነዝባል፡፡ ከሕጉ ይዘትና መንፈስ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው ፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5(1)እና (2) ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2(ለ)) እና 245(2) ድንጋጌ ጋር ተጣምረው ሲታዩ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/2/ ድንጋጌ በግልጽ ሲታይም በቀድሞው ክርክር ላይ የማስረጃ ወይም የመከላከያ ወይም የመቃወሚያ መሰረት መሆን ይገባቸው ነበር ወይም ለመሆን ይችሉ ነበር የሚባሉት ነገሮችና ምክንያቶች ሁሉ ለሥረ ነገሩ መሰረት በመሆን ከቀድሞው ውሳኔ ጋር ተቀላቅለው እንዳለቁ የሚቆጠሩ ናቸው በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 216 ድንጋጌ ጋር ተዛምዶ ሲታይም ክርክሮች ተጠቃልለው እንዲታዩ የግድ የሚል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡በመሆኑም በተከራካሪ ወገኖች በግልጽ የሚታወቁና በቀዳሚው ክርክር ሊነሱ ይችሉ የነበሩት ነገሮችና ምክንያቶች ሁሉ ለሌላ ክስ ምክንያት ሁነው ሊቀርቡ እንደማይገባና ፍርድ ቤቱም ተቃውሞው በስርዓቱ መሰረት ሲቀርብለት በመቀበል ክርክሩ እንዲቆም ማድረግ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ከላይ ከተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች በተጨማሪ በቀድሞው ክርክርና ሙግት ላይ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ጥያቄው ተቀባይነትን ሳያገኝ የታለፈ እንደሆነ የተጠየቀው ዳኝነት እንደተከለከለ እንደሚቆጠር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(3) ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጧል፡፡በአጠቃላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ሲታይ በቀዳሚው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑ የተከራካሪ ወገኖች አንድነት ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ ከላይ የተመለከቱት መመዘኛዎች በተሟሉበት ሁኔታ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት በመሆኑ ድጋሚ ክስ የሚቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን ያስረዳል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከእህታቸው ቦንቱ አሰፋ ጋር ሁነው ቀደም ሲል በአሁኑ 1ኛ አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ መስከረም 16 ቀን 1994 ዓ/ም በተደረገው ኑዛዜ መሰረት ጥሬ ገንዘብ እንዲሰጣቸው ሲሆን ይኸው የዳኝነት ጥያቄአቸው በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ገንዘቡ በ1ኛ አመልካች እንዲከፈል ተወስኗል፡፡ይህ የተጠሪና የእህታቸው የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ያደረገው ኑዛዜውን ሲሆን ኑዛዜው ለተጠሪና ለእህታቸው ምን ያህል ገንዘብ እንደሚሰጥ በግልጽ አስቀምጦ በኑዛዜው ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን ውጪ ሌላ ገንዘብም ሆነ ንብረት ሊጠይቁ እንደማይችሉ ተናዛዡ መግለጹ በኑዛዜ ላይ የተቀመጠ ጉዳይና ተጠሪና እህታቸው ስለኑዛዜው ሰነድ ይዘት እውቀት የነበራቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ከዚህ በኋላ ተጠሪና እህታቸው ለፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ 1ኛ አመልካችን ጨምሮ በሌሎች ሁለት እህቶቻቸው(2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች) ላይ የቀረበ ከመሆኑ ውጪ ጠቅላላ የዳኝነት ጥያቄው የውርስ ንብረት ይጣራልኝ የሚል ነው፡፡እንግዲህ የውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 944 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብ የሚፈፀም ሲሆን የኑዛዜ መኖርና ያለመኖር እንዲሁም ተጠቃሚዎች የሚለዩበት አግባብ እንደሆነ ከሕጉ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም ኑዛዜን መሰረት አድርጎ የሚቀርበው የኑዛዜ ተጠቃሚነት መብት ይረጋገጥልኝ ጥያቄና የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄዎች ተመሳሳይ የሆነ የፍሬ ነገርና የህግ ጥያቄ የሚያስነሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ተጠሪና እህታቸው ከኑዛዜው ጋር ተያይዞ የሚነሱትን ማናቸውንም የሕግ ጥያቄዎች በኑዛዜው መብት ተጠቃሚነት ይከበርልኝ በማለት ክስ በመሰረቱበት ጊዜ ሊያቀርቡ የሚችሉት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በኑዛዜው ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቀመጠውን የገንዘብ መጠን ብቻ ጠይቆ መውሰድ ደግሞ በኑዛዜው የተደረገውን ክልከላንም ጭምር እንደመቀበል የሚያስቆጥር ነው፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ ሟች በተውት ኑዛዜ መሰረት ጥሬ ገንዘብ እንዲከፈላቸው ክስ አቅርበው ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ከተሰጠ በኋላ የሟች ውርስ ንብረት ይጣራልኝ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ቀድሞ በቀረበው ክስ ጊዜ ሊያቀርቡ ይችሏቸው የነበሩትን ነገሮችና ምክንያቶችን ከተዉ በኋላ ያቀረቡት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት ተቀባይት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ አይደለም፡፡ተጠሪ የኑዛዜውን ሰነድ ይዘቱን እንደሚያውቁም የሚታመን ሲሆን በኑዛዜው ላይ ሌላ ማናቸውንም ገንዘብ ወይም ንብረት ከሟቹ እንዳይጠይቁ ክልከላ ተደርጎባቸው እያለ ይኼው የኑዛዜው ክፍል ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን በቀድሞው ክስ ክርክር አቅርበው እልባት ማግኘት ሲገባቸው ኑዛዜውን ተቀብለው በኑዛዜው መሰረት ተጠቃሚነታቸው ከተረጋገጠላቸው በኋላ ሌላ የውርስ ንብረት መብት እንዳላቸው በመቁጠር የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ማቅረባቸው በቀድሞው ክርክር ላይ የማስረጃ ወይም የመከላከያ ወይም የመቃወሚያ መሰረት መሆን ይገባቸው ነበር ወይም ለመሆን ይችሉ ነበር የሚባሉት ነገሮችና ምክንያቶች ሁሉ ለሥረ ነገሩ መሰረት በመሆን በቀድሞው ውሳኔ ጋር ተቀላቅለው እንዳለቁ የሚቆጠሩ ናቸው በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(2) የተደነገገውን የሚጥስ ነው፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪና እህታቸው በቀደመው ክስ መሰረት ያደረጉት ኑዛዜ ሁኖ እያለና በኑዛዜው ደግሞ ሌላ ገንዘብ ወይም ንብረት ለመጠየቅ የማይችሉ መሆኑ በግልፅ ተመልክቶ እያለ በዚህ ረገድ ተገቢው ክርክር ቀርቦ መፍትሔ ሊያገኝ ይችል የነበረውን ጉዳይ ተጠሪ በኋላ ያቀረቡት ክስ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ነው በማለትና ይህ ተግባር ኑዛዜን ማፈላለግና ተጠቃሚዎችን የመለየት ስራዎችን ጭምር የሚይዝ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገባ የኑዛዜ ተጠቃሚነትና የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ የተለያዩ ነገሮች ናቸው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5፣244(2(ለ)) እና 245(2) ድንጋጌዎችን እንዲሁም አጠቃላይ የስነ ሥርዓት ሕጉን ዓላማ ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በደ/ብ/ብ/ሕ/ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 57725 የካቲት 28 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01280 ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 12576 ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ የአባታቸውን የአቶ አሰፋ በዳሳ ኑዛዜን መሰረት አድርገው ክስ አቅርበው ተጠቃሚነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጥያቄ ክስ የሚመሰረትበት አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
4. *በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየረሰሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡*

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92459

ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ፍፁም ብርሃን ገ/ክርስቶስ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው አመልካች ፍርድ ቤትን የመድፈር የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል ተብሎ በፈዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 አግባብ የጥፋተኝነትና የአምስት ቀን ቀላል እስራት መወሰኑም ሆነ በፈዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይኼው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መፅናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልካች ስለአመለከቱ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2005 ዓ/ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ የነበረውን ሂደትና ጉዳዩ በችሎት መድፈር የማያስጠይቃቸው መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶቸ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተተ ያለበት በመሆኑ እንዲሻርላቸው ወይም የእስራት ቅጣቱ በገንዘብ መቀጮ እንዲቀየርላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡እኛም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተተ ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካችን በፍርድ ቤት መድፈር የወንጀል ድርጊት እንዲቀጡ ትዕዛዝ ሊሰጥ የቻለው ፍርድ እየተነበበ ባለበት ሰዓት ትዕዛዙ በተሰጠበት መዝገብ ቁጥር 72908 ተከሳሽ የሆነው ድርጅት ካሌብ ሆቴል ጠበቃ የሆኑት የአሁኑ አመልካች ስልክ በማስጮህ እንደሁም ከሳሽ ከሆኑት ግለሰብ ከአቶ ሀብታሙ በላይ ጋር ያልተገባ ክርክር በመፍጠር ፍርድ ቤቱ ስነ ስርዓት እንዲይዙ ቢያሳውቃቸውም ስነ ስርዓት ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው፣እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በስነ ስርዓት ያናግረን በሚል ያልተገባ ባህርይ ማሳያታቸውን፣ከዚህም በተጨማሪ በችሎት ውስጥ ስልክ ማስጮህ እንደማይቻል ተገቢው ማስታወቂያ ተለጥፎ እያለና አመልካችም የሕግ ባለሙያ ሁነው እያለ የችሎቱን ስርዓት ያወኩ መሆኑን በመግለፅ ሲሆን እነዚህ የፍሬ ነገር ነጥቦች መኖራቸውን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የፈዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሙሉ በሙሉ ተቀብሎአቸዋል፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በችሎት መድፈር ወንጀል ሊቀጡ የቻሉት ስልክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማስጮሃቸው ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ ስነ ስርዓት እንዲይዙ አሳውቆአቸው ስነ ስርዓት ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረትና ፍርድ ቤቱ በስነ ስርዓት ያናግረን በሚል ያልተገባ ባህርይ ሁሉ ለችሎቱ በማሳየታቸው መሆኑን ጭምር ነው።ትዕዛዙን የሰጡት ዳኛም በጊዜው በፍርድ ማንበብ ስራ ላይ እንደነበሩ በመዝገቡ ላይ የሰፈረ ጉዳይ ነው።

እንግዲህ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ጉዳይ ያለመሆኑ የሚታወቅ በመሆኑ ከላይ የተገለፁትን ፍሬ ነገሮችን እንዳሉ የምንቀባላቸው ይሆናል። ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ደግሞ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ አመልካች በችሎት ውስጥ ሞባይል ስልክ አስጨኽዋል ተብለው በዚህ ድርጊት መነሻነት ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን ጋር በተደረገ የቃላት ልውውጥ መነሻነት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 449(1(ሀ)) እንዲቀጡ መደረጉ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ የተያዘው ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከችሎቱ ዳኛ ስነ ስርዓት እንዲይዙ የተነገራቸውን ትዕዛዝ ሳያከብሩ መቅረታቸውን እንዲሁም ችሎቱንም በስነ ስርዓት ያናግረን በማለት ያልተገባ ባህርይ ማሳየታቸውን የስር ፍርድ ቤት የመዘገበውን ፍሬ ነገር ባግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ይህ ችሎት የሚቀበለው ሁኖ አልተገኘም።አመልካች ፍርድ ቤቱ ፍርድ በሚያነብበት ጊዜ ስነ ስርዓት እንዲይዙ የተነገራቸውን ትዕዛዝ ያለማክበራቸውንና "ፍርድ ቤቱን በስነ ስርዓት ያናግረን" በሚል ያልተገባ ባህርይ ማሳየታቸው የፍርድ ስራ በሚከናወንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱን ማወክቸውን የሚያሳይ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 481 አግባብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 449(1(ሀ)) ድንጋጌ ስር ተጠያቂነት የሚያስከትል ተግባር ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም።በመሆኑም የአመልካች የሠበር አቤቱታ ይዘትና የሰበር አጣሪ ችሎት ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አሰጣጥ መነሻ የሆኑትን ፍሬ ነገሮችን ሙሉ በሙሉ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተገቢነት የሌለው ሁኖ ተገኝቷል።ቅጣቱን በተመለከተም አመልካች በገንዘብ መቀጮ እንዲቀየርላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የመሰረታዊ ሕግ መመዘኛን የሚያሟላ ነው ለማለት አልተቻለም።ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ጸንቷል።
2. አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ፍርድ እየተነበበ ባለበት ጊዜ የችሎቱን ስነ ስርዓት ባለማክበርና ያልተገባ ባህርይ ማሳየታቸው ተረጋግጦ ፍርድ ቤቱን በመድፈር የተቀጡ በመሆኑ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል።

መዝገቡ ተዝግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበበ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 91103

ታህሳስ 16 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- ዩቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር - ጠበቃ ረዳኢ ባራኪ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. የአቶ ፉአድ መሃመድ እናት ወራሽ ወ/ሮ ማሪያም አብዱላሂ -

2. የአቶ አልፍሬዶ ፈሪርቶ ዶመኒኮ ወራሾች እነ አቶ ሚሊዩኝ አልፍሪዶ (5 ሰዎች) በሌሉበት የሚታይ ነው

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የወጭና ኪሣራ አወሣሰን ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡ ለወጭና ኪሣራው መነሻ የሆነ የውሳኔ ክፍል ከመስጠቱ በፊት የአሁን 1ኛ ተጠሪ አውራሽ በሆኑት አቶ ፉአድ መሃመድ እና በአቶ አልፍሬድ ፈሪሬቶ መካከል ሐምሌ 26 ቀን 1991 ዓ/ም በብር 350,000.00(ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) የተደረገን የቤት ሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ክርክር በፈዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተደርጎ ሻጭ አቶ አልፍሬድ ፈሪሬቶ ቤቱን ለገዥ አቶ ፉአድ መሃመድ እንዲያስረክቡ ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውሳኔ አግኝቶ የነበረ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ቤቱን ህዳር 30 ቀን 2001 ዓ/ም በሕጋዊ የሽያጭ ውል በብር 2,000,000.00(ሁለት ሚሊዩን ብር) ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪዎች አውራሽ የገዛው መሆኑን ጠቅሶ ውሳኔን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ተቃውሞ ቀርቧል፡፡ተቃውሞ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ሻጭ ከአሁኑ አመልካች ጋር ሕጋዊ ሽያጭ ውል አድርጎ እያለ ከቅን ልቦና ውጪ ከአቶ ፉአድ መሃመድ በድጋሚ መሸጣቸው ያላግባብ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የቀድሞውን ውሳኔ በመሻር ቤቱን የአሁኑ አመልካች ሊለቅ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤቶች ያልተለወጠ ሲሆን ወጪና ኪሳራን በተመለከተ ደግሞ የአቶ ፉአድ መሃመድ ወራሽ ዝርዝሩን የማቅረብ መብታቸውን ሲጠብቅ የአሁኑን አመልካች ጥያቄ ግን በዝምታ አልፎታል፡፡ አመልካች የወጪና ኪሳራ ይተካልኝ ጥያቄ በተመለከተ በዝምታ በመታለፉ ምክንያት ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፈዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ከቅን ልቦና ውጪ ለተደረገ የሽያጭ ውል ለክርክር የተዳረገ መሆኑ እየታወቀ የበታች ፍርድ ቤቶች የወጪና ኪሳራ ዝርዝሩን ማለፋቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አንደኛ ተጠሪን በተመለከተ ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚያስቀርብ የሕግ ነጥብ የለውም ተብሎ የተዘጋ ሲሆን 2ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ ግን ያስቀርባል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪዎች በሕጉ አግባብ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ጭብጥ አመልካች በ2ኛ ተጠሪዎች አውራሽ ቅን ልቦና ውጪ በሆነ ተግባር ለክርክር የተዳረገ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የወጪና ኪሳራ ጥያቄው በዝምታ መታለፉ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ ክርክር ተጠናቆ በፍርድ እንዲቋጭ ሲደረግ ለዚህ ፍርድ ምክንያት የሆነው ክርክር ስላስከተለው ወጭና ኪሣራ ጉዳይ በፍርድ ተካቶ ሊወሰን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 183 ሥር ተመልክቷል ፡፡ ዝርዝር አወሣሰኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462-464 ተደንግጓል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 እንደተመለከተው በክርክር ምክንያት የወጣን ወጭና ኪሣራ ማን እንደሚከፍልና ምን ያህል እንደሚከፍል ፍ/ቤቱ በመሰለው ሊወስን እንደሚችል ፈቃደ- ስልጣን እንዳለው በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የዚሁ ድንጋጌ ተከታይ የሆነው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 463 ደግሞ በዚሁ ሕግ የተሰጠው ፈቃደ ስልጣን ተጠቅሞ ፍ/ቤቱ ማን ይክፈል? የሚለውን በመለየት ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ጉዳዩች ሁሉ ተመልክቶና አረጋግጦ ተረቺ ለረቺ ይክፍል ብሎ ሊያዝ እንደሚችል ያሳያል፡፡የወጪና ኪሳራ ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማም ሰዎች ያላግባብ ለክርክር እንዳይዳረጉ መከላከል መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ክርክሩ ከሕግ ውጪ የቀረበ መሆኑ ከታወቀ ደግሞ ለክርክሩ ያላግባብ የተዳረገ ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪና ኪሳራ ለዚሁ የዳረገው ወገን ሊተካለት ይገባል ፡፡በእርግጥ የክርክሩ ረቺ የሆነ ወገን ሁሉ ወጪና ኪሳራ ይተካለት ማለት እንዳልሆነ ከድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ሆኖም አንድ ተከራካሪ ወገን በሌላኛው ተከራካሪ ወገን ቅን ልቦና ውጪ በሆነ ተግባር ለክርክር ተዳርጎ መገኘቱ ከተረጋገጠ የወጪና ኪሳራ ጥያቄ ውድቅ ማድረግ የስነ ስርዓት ሕጉ ሊያሳካ ከአሰበው ዓላማ ውጪ በመሆኑ የሕግ መሰረት የሌለው ነው፡፡በመሆኑም

የውጪና ኪሳራ ጥያቄን አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ በመጠኑ ላይ በሕጉ ስልጣን የተሰጠው መሆኑና ረቺ ሁልጊዜ ወጪና ኪሳራ እንዲተካለት መደረግ የሌለበት መሆኑ ግንዛቤ የሚወሰድበት ቢሆንም ከቅን ልቦና ውጪ ለክርክር የተጋበዘውን ወገን በተመለከተ ግን የክርክሩ ረቺ መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ቅን ልቦና ከሌለው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት ማድረግ ክርክሮች ያላግባብ እንዳይፈጠሩ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባው ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣም አመልካች በ2ኛ ተጠሪዎች አውራሽ ከቅን ልቦና ውጪ በሆነ ምክንያት ለክርክሩ መዳረጉን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው በሚገባ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ የተለየ ድምዳሜ የሌለው መሆኑን የትዕዛዙ ድምዳሜ አስረጅ ነው፡፡በመሆኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 463 እና 464 በተመለከተው መሠረት የግራ ቀኙ ክርክር ስላስከተለው ወጭና ኪሣራ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪዎች ለአመልካች የመተካት ግዴታ ሊኖርባቸው ይገባል፡፡ተጠሪዎች ሊተኩ የሚገባው የወጪና ኪሳራ መጠን ደግሞ አመልካች ዝርዝሩን አቅርቦ ግራ ቀኙ ክርክር አድርገውበትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 “..... ምን ያህል ይክፈል.....” የሚለውን በሚመለከት በሕጉ ለፍ/ቤቱ የተሰጠውን ፈቃደ ስልጣን ሁሉ በመጠቀም የሚወሰን ሁኖ አግኝተናል፡፡

ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት አመልከች በ2ኛ ተጠሪዎች አውራሽ ቅን ልቦና መሰረት ባላደረገ ሁኔታ ለክርክር የተዳረገ መሆኑ አረጋግጠው እያለ የወጪና ኪሳራውን ጥያቄ በዝምታ ማለፉም ሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ክፍል ሳያርም መቅረቱ ወጭና ኪሣራ አወሣሰን ትክክለኛ አፈፃፀም የተከተለ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81591 የካቲት 14 ቀን 2005 ዓ/ም በአመልካች የቀረበውን ወጪና ኪሳራን አስመልክቶ የሰጠው የውሳኔ ክፍልና በዚሁ የውሳኔ ክፍል አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ በመ/ቁጥር 89064 ሚያዚያ 29 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የወጪና ኪሳራ ዝርዝሩን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የማስወሰን መብት አለው ብለናል፡፡ይፃፍ፡፡
3. የዚህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90452

ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሌሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ትዕግስት አሸናፊ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ገ/ሥላሴ በርሄ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በውሉ በተመለከተው መሰረት አልተከፈለም የተባለን በብድር የተሰጠ ገንዘብ ከማስመለስ ጋር የተያያዘ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በብድር የወሰዱትን ገንዘብ ባለመክፈላቸው ከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ያቀረበውን ክስ ተከሳሽ ቀርበው ባለመከላከላቸው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ተከሳሽ በሌሉበት አይቶ ዋናውን ገንዘብ እና ወለዱን ጨምሮ በድምሩ ብር 300,109.15 ከ 29/05/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ በ26/02/2001 ዓ.ም. ውሳኔ በመስጠት እና በ19/11/2002 ዓ.ም. ደግሞ የብር 6,294.30 የወጪና ኪሳራ ውሳኔ በመስጠት መዝገቡን ከዘጋ በኃላ ተከሳሽ ክርክሩ በሌሉበት ተሰምቶ ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው በመደበኛ መኖሪያ አድራሻቸው በአግባቡ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ መሆኑን ገልጸው ውሳኔው ተነስቶ ክርክራቸውን ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት በማግኘቱ ውሳኔው ተነስቶ የጽሁፍ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶአቸው የነበረ መሆኑን፣ይሁን እንጂ ተከሳሽ በቀጠሮው ዕለት መልስ ባለማቅረባቸው መብታቸው ታልፎ ክሱን ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ የተያዘ መሆኑን፣ክሱን ለመስማት በተያዘው ቀጠሮም ሳይቀርቡ በመቅረታቸው ጉዳዩ በድጋሚ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠ መሆኑን ፣ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ በህግ ግምት የሚሸፈን የፍሬ ነገር ክርክርን ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ግምቱን ፍ/ቤቱ በራሱ ተፈጻሚ ማድረግ እንደሚገባው፣እስከ ሁለት ዓመት ያልተከፈለ የወለድ ገንዘብ እንደተከፈለ የሚቆጠር ስለመሆኑ በፍ.ሕ.ቁ. 2024(1) ስር የተመለከተው ግምት በባንክ በሚሰጥ ብድር ጉዳይም ተፈጻሚነት ያለው ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 29181 በ20/04/2002 ዓ.ም. አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንደሰጠ እና ይህንን የሕሊና ግምት ለማፍረስ ከሳሽ በፍ.ሕ.ቁ. 2473(2) መሰረት ያቀረበው ማናቸውም ዓይነት ማስረጃ እንደሌለ ገልጾ ተከሳሽ ከዋናው ዕዳ ያልተከፈለውን ብር 41,391.50 እና ለኢንሹራንስ የተከፈለውን ብር 19,586.87 ከወለድ እና ከቅጣት ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ እና የወጪና ኪሳራ መጠኑንም ከቀድሞው ዝቅ በማድረግ በ22/02/2004 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣በከሳሽ ጠያቂነት የይግባኝ ክርክሩን የሰማው ፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ የስር ተከሳሽ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ቢሆንም በጽሁፍም ሆነ በቃል ያቀረቡት ክርክር በሌለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የቀድሞ ውሳኔውን እራሱ በመለወጥ የሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ አይደለም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ውሳኔውን ሽሮ በቀድሞው ውሳኔ መሰረት አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ውሳኔ መስጠቱን እና በመጨረሻም በስር ተከሳሽ ጠያቂነት የይግባኝ ክርክሩን የሰማው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የቀድሞው ውሳኔ የተነሳ በመሆኑ ጉዳዩን እንደገና ከመመርመር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትን የሚያግደው ነገር እንደሌለ ገልጾ የከ/ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የፍሬ ነገር ክርክሩን መርምሮ ይወስን ዘንድ ጉዳዩን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 343(1) መሰረት ለፌከ/ፍ/ቤት በመመለስ ውሳኔ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪ ብር 300,109.15 ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ በማለታቸው ውሳኔው ቢነሳም ተጠሪ የጽሁፍም ሆነ የቃል ክርክር ሊሰማ በተቀጠረበት ቀጠሮ ባለመቅረባቸው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በድጋሚ በሌሉበት አይቶ ተጠሪ በፍ.ሕ.ቁ. 2024(1) በተመለከተው የሕሊና ግምት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል በማለት የወለድ ጥያቄውን ውድቅ አድርጎ ዋናውን ዕዳ ብቻ እንዲከፍሉ ሲወስን ቀደም ብሎ አመልካች የወለድ አሰላሉን በተመለከተ ያያዘውን ሰነድ ሳይመለከት የማለፉን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነጥብ ተከሳሽ በሌሉበት በመጀመሪያ ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 78(2) መሰረት ተነስቶ ተከሳሽ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ የጽሁፍ መልስ ሳያቀርቡና ክሱ ሊሰማ በተያዘው በቀጠሮም ሳይቀርቡ ከቀሩ በድጋሚ በሌሉበት ታይቶና ተመርምሮ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት ከሚሆን በስተቀር የተነሳው ውሳኔ ተመልሶ እንዲጸና የሚደረግበት አግባብ የለም ሲል የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት በመመለስ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚል ጭብጥ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አንድ ተከሳሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ውሳኔው ወይም ትእዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትዕዛዙ ወይም ውሳኔው እንዲነሳለት ሊያመለክት እንደሚችል እና ፍ/ቤቱም የሌላኛውን ወገን አስተያየት ከሰማ በኃላ የአመልካቹን አቤቱታ ተገቢ አድርጎ ከተቀበለው ውሳኔውን በማንሳት ክርክሩ እንደገና የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ እንደሚሰጥ በፍ.ስ.ስ.ሀ.ቁ. 78 ተመልክቶአል፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በሌሉበት ታይቶ የተሰጠባቸው ውሳኔ ተነስቶ ክርክራቸውን ለማቅረብ እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ውሳኔው ከተነሳ እና ክርክሩን እንደገና ለመቀጠል ቀጠሮ ከተያዘ በኃላ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ለሁለተኛ ጊዜ ተጠሪ በሌሉበት የአመልካችን ክስ እና ማስረጃ መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት የቻለው ተጠሪ በጽሁፍም ሆነ በቃል ክርክራቸውን ለመስማት በተሰጠው ቀጠሮ ባለመቅረባቸው ክርክሩን በድጋሚ በሌሉበት በማየት ነው፡፡በመሰረቱ አንድ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሳኔ ተነስቶ ክርክሩን ለማሰማት እነዲፈቀድለት ጠይቆና ተፈቅዶለት ለጽፍም ሆነ ለቃል ክርክር በተያዘው ቀጠሮ በድጋሚ ሳይቀርብ ከቀረ ፍ/ቤቱ ክርክሩን መምራት የሚገባው በምን ዓይነት ስርዓት እንደሆነ የስነ ስርዓት ሕጉ በግልጽ ያስቀምጠው ነገር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለም፡፡ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ ተጠሪ ክርክሩን እንደገና ለማየት የሚያስችል በቂ ምክንያት ያቀረቡ መሆኑን አረጋገጦ የቀድሞውን ውሳኔ ያነሳው እስከሆነ ድረስ ተጠሪ ክርክራቸውን እንዲያቀርቡ በድጋሚ በተሰጣቸው ዕድል ተጠቃሚ ሳይሆኑ ከቀሩ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 70(ሀ) በተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እና ክርክሩን እንደገና ለመስማት በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የአመልካች ክስ እና ማስረጃ እንደገና ተመርምሮ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚደረግ ከሚሆን በስተቀር እንዲነሳ አስቀድሞ ትዕዛዝ የተሰጠበት የቀድሞ ውሳኔ በቀጥታ ተመልሶ እንዲፀና ሊደረግ የሚችልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡የከሳሽ ወገን ክስ እና ማስረጃ እንደገና ተመርምሮ የሚሰጠው ውሳኔ ደግሞ እንደነገሩ ሁኔታ ከበፊቱ ውሳኔ ጋር ተመሳሳይ ወይም የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡በመሆኑም ተከሳሽ ወገን የቀድሞውን ውሳኔ ለማሰለወጥ የሚችል የጽሁፍም ሆነ የቃል ክርክር ያላቀረበ አስከሆነ ድረስ የከሳሽ ወገንን ክስ እና ማስረጃ እንደገና መመርመር ሳያስፈልግ የተነሳው የቀድሞ ውሳኔ ተመልሶ እንዲጸና መደረግ ነበረበት በማለት አመልካች ቀረበውን ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ በሌሉበት በመጀመሪያ ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 78(2) መሰረት ተነስቶ ተጠሪው ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ የጽሁፍ መልስ ሳያቀርቡና ክሱ ሊሰማ በተያዘው በቀጠሮም ሳይቀርቡ ከቀሩ በድጋሚ በሌሉበት ታይቶና ተመርምሮ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት ከሚሆን በስተቀር አስቀድሞ የተነሳው ውሳኔ ተመልሶ እንዲጸና የሚደረግበት አግባብ አለመኖሩን ገልጾ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር እና የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት በመመለስ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የስር ተከሳሽ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ በጽሁፍም ሆነ በቃል ያቀረቡት ክርክር በሌለበት ሁኔታ የስር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀድሞ ውሳኔውን እራሱ በመለወጥ በመቁ.114956 በ22/02/2004 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በማለት ውሳኔውን ሽሮ በቀድሞው ውሳኔ መሰረት አፈጻጸሙ እንዲቀጥል የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.118042 በ08/12/2004 ዓ.ም. የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪው ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ የጽሁፍ መልስ ሳያቀርቡና ክሱ ሊሰማ በተያዘው በቀጠሮም ሳይቀርቡ ከቀሩ በድጋሚ በሌሉበት ታይቶና ተመርምሮ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት ከሚሆን በስተቀር አስቀድሞ የተነሳው ውሳኔ ተመልሶ እንዲጸና የሚደረግበት የሕግ አግባብ አለመኖሩን ገልጾ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ረገድ የይግባኝ ክርክሩን መርምሮ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ.ስ.ስ.ሀ.ቁ. 343(1) መሰረት ወደ ፌ/ከ/ፍ/ቤት በመመለስ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 82803 በ21/06/2005 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 91968

ታህሳስ 15 ቀን 200ዓ.ም.

ዳኞች፡ አለማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ሰንበት አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ገብረየስ ጠበቃ ወንድወሰን ይልማው ቀረቡ

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 37983 ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 መሰረት በድጋሚ በማየት እንዲያርምልኝ ያቀረብኩትን ማመልከቻ በቂ ህጋዊ ምክንያት የለውም ብሎ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

1. ከዚህ በፊት የአሁን አመልካች/ከሳሽ/ በመሆን ተከራክረዋል አመልካች ተጠሪ የራሳቸው መጸዳጃ ቤት የላቸውም ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር የመፀዳጃ ቤት በጋራ በመጠቀም ላይ እያለን ከሳሽ መፀዳጃ ቤቱን በጋራ ለመጠቀም ባለመቻሉ የራሴን መፀዳጃ ቤት ለመገንባት የእድሳት ፈቃድ አውጥተን ከሰራተኞች ጋር ተዋውዬ ቤቱን ማፍረስ ላይ እያለሁ ስራውን እንዳቆም የተደረግሁ በመሆኑ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድና የመፀዳጃ ቤቱን በማደስ ስራውን እንዳጠናቅቅ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርባ መፀዳጃ ቤቱን የሰራሁት እኔ ነኝ መፀዳጃ ቤቱ የሚገኘው በእኔ ይዞታ ስር ነው በማለት ተከራክራለች ፍርድ ቤቱም የክፍሉን አስተዳደር መፀዳጃ ቤቱ በማን ይዞታ ስር እንደሆነ አረጋግጦ እንዲልክለት ጠይቆ መፀዳጃ ቤቱ በተጠሪ ይዞታ ስር መሆኑን በማረጋገጡ ይዞታው የተጠሪ ነው በማለት ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
2. አመልካች በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 09 አስተዳደር ከዚህ በፊት የሰጠው የባለሙያ ማስረጃ ተገቢነት የሌለው መሆኑን አላግባብ የቤት ቁጥር 417 /አመልካች ቤት የጋራ መገልገያ የሆነውን መፀዳጃ ወደ ቤት ቁጥር 418 ያጠቃለላ በመሆኑ ከዚህ በፊት የተፃፈው ደብዳቤ መሻር ያለበት ነው በማለት ጽፏል ስለዚህ ቀደም ተብሎ ተጠሪ የውሳኔ ባለመብት የሆነችው ሀሰተኛን መረጃ መሰረት በማድረግ በመሆኑ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 መሰረት ፍርድ በድጋሜ ተይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት በቁጥር7/ክ/ከ/ወ0 የሰኦ/363/105 ታህሳስ 23 ቀን 2005 ዓ/ም የተፃፈውን ደብዳቤ በመጥቀስ የሰጠውን ማስረጃ በማያያዝ ጥያቄ አቅርቧል የስር ፍርድ ቤት አመልካች ፍርድ እንደገና እንዲታረምለት ያቀረበውን ጥያቄ ለማስረዳት ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ቀደም ብሎ የተሰጠው ውሳኔ በሀሰተኛና ወንጀል ነክ ተግባሮች በተገኙ የሰነድ ማስረጃዎች መሆኑን የሚያሳይ አይደለም ፍርዱ በድጋሜ የሚታይበት ምክንያት የለም በማለት ሚያዚያ 18 ቀን 2005 ዓ/ም ብይን ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች ሀምሌ 12 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የመጀመሪያው ውሳኔ የተሰጠው በሀሰት ተዘጋጅቶ በተሰጠ ማስረጃ መሰረት መሆኑን የሚሳይ ሰነድ አቅርቤአለሁ ይህም የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 መሰፈርት አያሟላም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ተገቢነት የሌለው ነው በማለት አመልክቷል ተጠሪ መስከረም 13 ቀን 2005 ዓ/ም የመጀመሪያ ውሳኔ የተሰጠው ሀሰተኛና በተጭበረበረ የወንጀል ተግባር መሆኑን የአመልካች ማስረጃ አያሳይም የስር ፍድ ቤት ብይን ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥታለች አመልካች ጥቅምት 4 ቀን 2006 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡
4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የስር ፍድ ቤት አመልካች ከጉለሌ ከፍለ ከተማ ወረዳ 9 አስተዳደር ያቀረበው ማስረጃ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ አንቀጽ 6/1/ መስፈርት አያሟላም በማለት ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው የስር ፍድ ቤት ይዞታው የተጠሪ ነው ብሎ ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ.ም ለሰጠው ውሳኔ መሰረት የሆነው በጉለሌ ክፍለከተማ የወረዳ 9 የመሬትናፕሮሰስ ካውንስል የፃፈው ደብዳቤ ቀደም ሲል በሚመለከተው ክፍል በGIS ላይ 9997 ተብሎ የተገለፀው ቦታ የማን ይዞታ እንደሆነ ለማየት የሚያስችግርና የጋራ መገልገያ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠውን ውሳኔና የተፃፈውን ደብዳቤ ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ በመሬት ላይ ይዞታውን /መጸዳጃ ቤቱን/ አመልካችና ተጠሪ በጋራ የሚገለገሉበት መሆኑን የሚደብቅና በቀድሞው የወረዳ 8 ቀበሌ 11 የቤት ቁጥር 417 ነዋሪ የሆነውን አመልካችን የመፀዳጃና የማብሰያ ቤት ለቤት ቁጥር 418 በማጠቃለል በካርታ ቁጥር 20/11/26812/00 እንዲሰጥ ያደረገ መሆኑን የጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 አስተዳደር አረጋግጦ በደብዳቤ የገለፀ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡
6. ይህም ይዞታው የተጠሪ ነው ተብሎ ውሣኔ ለመስጠት መሰረት የሆነው መረጃ እውነታውን የማያሳይና ከዚህ በፊት የተሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችንና የተፃፉ ደብዳቤዎችን አላግባብ በማለፉ የተሰጠ ሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑን የሚያሳይ ነው አንድ የመንግስት አካል /ባስልጣን/ እወነተኛውን ሳያጣራ መሰጠት የማይገባውን ሀሰተኛ ማስረጃ ለፍርድ ቤት በመስጠቱ ውሳኔ የተሰጠበት ወገን ማስረጃው ሀሰተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እስካቀረበ ድረስ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6/1/ መስፈርትን ያላሟላህ ስለሆነ ፍርድ በድጋሜ አይተይልህም መባሉ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ አንቀጽ 6/1/ መሰረታዊ ዓላማ የሚያሳካ ሆኖ አላገኘውም ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ በደጋሚ እንዲታይ የጠየቀው ሰው ሀሰተኛ መረጃ የተሰጠው መንግስት በኃላፊነት ቦታ ላይ ባስቀመጠው ባለስልጣን እና በመንግስት አካል መሆኑን ከማስረዳት አልፎ የመንግስት ባለስልጣን ይህንን ህገወጥ ተግባር የፈፀመበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ሊጠይቅ የሚገባው እንዳልሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 403 እና አንቀጽ 405 ድንጋጌዎች ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6/1/ ድንጋጌ ጋር በማጣመር በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

7. ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም ለሰጠው ውሳኔ መሰረት ያደረገው ለክፍሉ አስተዳደር የተፃፈ ደብዳቤ እውነታውን የማያሳይና ሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑን የጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09 አስተዳደር በፃፈው ደብዳቤ የተገለፀ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት ፍርዱን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6/1 መሰረት እንደገና ለማየት በቂና ህጋዊ ምክንያት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ፍርዱን በድጋመ ለማየት በቂ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 37483 ሚያዚያ 15 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 መሰረት ጉዳዩን በድጋሜ በማየት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመቀበልና በመስማት እንደዚሁም አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 85468

መስከረም 24 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሣባ ኢንጂንሪግ ኃ.የተ.የግል ማህበር ጠበቃ ምስጋናው ካሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጂንሲ ነ/ፈጅ መስፍን በሻህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በሽያጭ ውል መሠረት ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባውን ቀሪ የሽያጭ ገንዘብና የተጣራ ትርፍ ክፍያ እንዲከፍል ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ክስ መሥርቶ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ በመስጠቱና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይሄው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በአመልካች ላይ በፌዴራል ከፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የቦሌ ቡልቡላ ጠጠር ማምረቻ አክሲዩን ማህበርን ለመሸጥ ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት ከተወዳዳሪዎች መካከል አመልካች የአክሲዩን ማህበሩን ሙሉ ድርሻ ለመግዛት ባቀረበው ዋጋና ቢዝነስ ፕላን መሰረት አሸናፊ በመሆኑ ሀምሌ 08 ቀን 1999 ዓ/ም በተፈረመ የሽያጭ ውል በብር 17,020,570.00 ለመግዛት ስምምነት ማድረጉን፣የሽያጭ ውሉ አንቀጽ 4(2) መሻሻል በማስፈለጉ ጥር 12 ቀን 2002 ዓ/ም ማሻሻያ የተደረገለት መሆኑን፣በዚሁ መሰረትም አመልካች የሽያጩን ጠቅላላ ዋጋ 35% ብር 5,957,060.00 ከፍሎ ቀሪውን 65% የሽያጭ ዋጋ ደግሞ በየዓመቱ በእኩል ክፍያ ወለድን ጨምሮ አመልካች ለተጠሪ እየከፈለ ሐምሌ 08 ቀን 2004 ዓም ድረስ ለማጠናቀቅ ስምምነት መደረጉን፣ክሱ እስከቀረበበት ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም እና እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ መክፈል የነበረበትና ያልተከፈለ የሽያጭ ቀሪ ገንዘብ ብር 5,129,494.00፣ወለድና ቅጣት ብር 735,637.00 በጠቅላላው ብር 5,865,131.00 እንደሚፈልግበት፣በሽያጭ ውሉ አንቀጽ 6(2) መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ ርክክቡ እስከተጠናቀቀበት እለት ድረስ ያለውን የተጣራ ትርፍ አመልካች ለተጠሪ መክፈል ያለበት መሆኑ በግራ ቀኙ ስምምነት የተደረገበት መሆኑና አመልካች ያልከፈለው ብር 2,821,490.00

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኖ ይህም አክሲዩን ማህበር ላይ የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ያረጋገጡት የሂሳብ መጠን መሆኑን፣ተጠሪ ገንዘቡ እንዲከፈለው በተለያዩ ጊዜአት ለአመልካች ማስጠንቀቂያና ማሳሳቢያ ቢልክለትም አመልካች የተለያየና አጥጋቢ ያልሆነ ምክንያት እያቀረበ ለመክፈል ፈቃደኛ ያለመሆኑን ዘርዝሮ ከዋናው የሽያጭ ገንዘብ ቀሪ እና የተጣራ ትርፍ ክፍያ በጠቅላላው ብር 8,686,621.00 (ስምንት ሚሊዩን ስድስት መቶ ሰማንያ ስድስት ሺ ስድስት መቶ ሃያ አንድ ብር) እና በውሉ ላይ የተመለከተውን ወለድ(7.5%) ገንዘቡን ከፍሎ እስከሚያጠናቅቅበት ጊዜ ድረስ ታስቦ አመልካች እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የተጠሪ ክስና ማስረጃ ለአመልካች ደርሶ በሰጠው መልስ የሽያጭ ውሉ መኖሩና 35% መክፈሉን፣ እንዲሁም ቀሪው 65% የሽያጭ ገንዘብ ተከፍሎ የሚጠናቀቅበት ጊዜ ሐምሌ 08 ቀን 2004 ዓ/ም መሆኑን ሳይክድ ክሱ በውሉ የተመለከተው የጊዜ ገድብ ሳያልቅ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣አመልካች ድርጅት የገባውን ውል ግዴታ የሚያፈርስ አንዳችም ጥፋት ያለመፈጸሙን፣ለመክፍል እምቢተኛ ያለመሆኑን፣ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት አለመክፈሉም እንደ እምቢተኛ ያስቆጥረዋል የሚባል ከሆነም በተለያየ ጊዜ የተከሰተውን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች አስመልክቶ የተሰጡት የጽሁፍ መልሶችና ማስረጃዎች መቅረባቸውን፣የማሻሻያ ውሉም የመክፍያ ጊዜ ገደቡን ያልነካው መሆኑን፣የመጀመሪያ ውል ከተደረገ በኋላ በየዓመቱ እኩል ክፍያ የሚል ሐረግ ተጠሪ በማስገባት ውሉ እንዲሻሻል ያደረገው አመልካች ያጋጠመውን የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥና በፈረቃ ሥራ እንዲሰራ የመደረጉን ሁኔታ ያላገናዘበና በወቅቱ በተፈጠረው ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ችግሮች ምክንያት ጥያቄዎችን ለተጠሪ ሲያቀርብ ውሉ ተሻሻለ እንጂ ቀደም ሲል የነበረውን ውል በየዓመቱ በእኩል ክፍያ ትከፍላለህ የሚል ስምምነት ያለመደረጉን፣አመልካች በኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ለሁለት አመታት ያህል ማምረቱን ማቆሙን፣ለ150 ሰራተኞች ደመወዝ ከብር 200,000.00 በላይ መከፍሉንና ይህንን ችግር ለተጠሪ ማሳወቁን፣በዚህም መሰረት ውይይት ተደርጎ የሽያጭ ዋጋና ወለዱ በረኸርም ጊዜ ክፍያ ተከፍሎ እንዲያልቅ በውሉ ላይ የተቀመጠው ቅጣት ደግሞ እንደማይከፈልና እንደሚነሳ የድርጅቶቹን ሕልውናና የሰራተኞችን ቀጣይ ሕይወት ለመታደግ ሲባል ስምምነት ላይ የተደረሰና በኤጂንሲው ቦርድም እንዲጸድቀና ተቀባይነት እንዲያገኝ መደረጉን፣አመልካች ድርጅት ከሚፈልግበት እዳ ላይ በቅድሚያ ብር 5,957,060.00 እና በተለያዩ ሰነዶች የተከፈለ ብር 3,732,622.00 በአጠቃላይ ብር 9,689,682.00 ከነትርፍ ድርሻው የመክፍያውን የጊዜ ገደብ ሳይጠብቅ መከፈሉን፣ተጠሪ ከሚያዚያ 30 ቀን 2003 ዓ/ም በኋላ ያለውን እንዳልፈለገው ተቆጥሮ እዳው ከመክፈል ቀሪ ይሆናል ስለሚል ሕጉ ተጠሪ መስሪያ ቤት የጠየቀው ወደፊት የመክሰስ መብት በሕግ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣አመልካች የጠጠር ማምረቻ ቦታ ሚያዚያ 03 ቀን እና ሚያዚያ 26 ቀን 2003 ከቦሌ ክፍል ከተማ አስተዳደር የወረዳ 12 ዋና ስራ አስኪያጅ ፅ/ቤት በተፃፈ ደብዳቤ ቦታውን እንዲለቅ በመደረጉ ድርጅቱ ስራውን ማቆሙንና ይህም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መሆኑን ዘርዝሮ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በውሉ መሰረት ለክሱ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን፣የኤሌክትሪክ መቋረጥም ሆነ የቦታው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መወሰድ የውል ግዴታውን ለመፈፀም የማያስችሉ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ናቸው ሊባሉ የማይችሉ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክርም ውድቅ ያደረገው ሲሆን አመልካች በሽያጭ

ውሉ መሰረት ሊከፈለው የሚገባውን ቀሪ ገንዘብ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ መክፈል የነበረበትን ብር 5,129,494.00፣በመጀመሪያው ውልና በተሻሻለው ውል መሰረት መክፈል የነበረበትን ገንዘብ ባለመክፈሉ በውሉ አንቀጽ 8(3) መሰረት ቅጣት ብር 735,637.00፣ በዋናው ውል አንቀጽ 6(2) መሰረት ከሐምሌ 1ቀን 1998 ዓ/ም ጀምሮ ርክክቡ እስከተጠናቀቀበት እለት ድረስ ያለውን የተጣራ ትርፍ ብር 2,821,490.00፣በውሉ አንቀጽ 4(4) መሰረት ደግሞ ላልተከፈለው ቀሪ የሽያጭ ገንዘብ ለተጣራ ትርፍ ክፍያ ወለድ ብር 7.5% ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ድረስ ያለውን አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በውሉ የተመለከተው የመክፈያ ጊዜ ሳይጠናቀቅና ውሉ የተሻሸለ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በፍርድ ቤቱ እገዛ እንዲቀርብ ተጠይቆ ማስረጃው ሳይቀርብ መቅረቱ እንዲሁም የውል ግዴታውን አመልካች ከኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥና ተጠሪ የሸጠው የጠጠር ማምረቻ ድርጅት ያለበትን ቦታ መንግስት ለኮንዶሚኒየም መስሪያ በመፈለጉ በአስቸኳይ ቦታው እንዲለቀቅ ተጠይቆ ቦታውን አመልካች በመልቀቅ ስራውን ያቆመ መሆኑ የውል ግዴታውን ለመወጣት የማያስችሉ ምክንያቶች ሁነው እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ሁኔታዎቹ ስለመፈጠራቸው እንኳ በአግባቡ ሳይመረምሩ ማለፋቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስ ይቻል ዘንድም በአመልካች የቀረቡትን መሰረታዊ የቅሬታ ነጥቦች አንድ ባንድ መመልከቱ ተገቢ በመሆኑ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች አጥብቆ ከሚከራከርባቸው መሰረታዊ ነጥቦች አንዱ ስለውሉ መሻሻል እንደሚያስረዳ ተገልፆ በፍርድ ቤት እገዛ እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ በስር ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ውሳኔ መሰጠቱ ያላግባብ ነው የሚል ይገኝበታል፡፡አመልካች ይህ ማስረጃ ቃለ ጉባኤ ስለመሆኑ ጠቅሶ ማስረጃው ቢቀርብ የሚያስረዳው አመልካቹ ከወለድና ከቅጣት ነጻ መሆኑን ስለመሆኑ የገለፀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በተጠሪ እጅ የሚገኘው ቃለ ጉባኤ ለማስረጃነት መቅረቡን፣ወለድና ቅጣትንም ነፃ ለማድረግ ስምምነት የሌለ መሆኑን ጠቅሶ መልሱን ሰጥቷል፡፡

በመሰረቱ ከላይ ክሱን ሲያቀርብ አስፈላጊ ማስረጃዎችን በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ ሊያቀርባቸው የማይችላቸውን ደግሞ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 መሰረት በፍ/ቤቱ እገዛ እንዲቀርቡለት መጠየቅ የሚችል መሆኑን በፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ ስር የተደነገጉት የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች ያሳያሉ፡፡ይህ የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ለተከሳሽም የሚሰራ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 234(1) ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም ከሳሹ ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሹ ሊያቀርባቸው ሲችል ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ያላቀረባቸውን ማስረጃዎች በክርክር ሂደት ሁሉ እያንጠባጠበ ሊያቀርብ ወይም የማስረጃ ማሰባሰብ ስራውን ፍርድ ቤት እንዲያከናውን ሊጠይቅ የሚችልበት የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት የሌለ ሲሆን ከሥነ ስርዓት ህጉ አላማ ጋርም አብሮ የማይሄድ ጉዳይ በመሆኑ ሕጉ የሚፈቅደው አካሄድ አይደለም፡፡በፍርድ ቤት እገዛ ማስረጃ የሚቀርበው ተከራካሪ ወገን አጠቃልሎ ማቅረብ የማይችላቸው መሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፍርድ ቤት ማስረጃ እንዲቀርብ ጥያቄ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ ማስረጃው ለጉዳዩ ያለውን አግባብነትም በመመልከት ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት የሚችል መሆኑን ከማስረጃ አቀራረብ ደንቦች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች አልቀረበልኝም የሚለው ማስረጃ ስለመቅረቡ ተጠሪ የገለፀ ከመሆኑም በላይ አለ የተባለው ማስረጃ ደግሞ ቃለ ጉባኤ ሁኖ በወለድና በቅጣት ኃላፊነት ላይ በይዘቱ ከዋናው ውልና ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ/ም ተደረገ ከተባለው የማሻሻያ ውል የተለየ መሆኑን አመልካች ጠቅሶ የሚከራከር በመሆኑ አመልካች የውሉ ቅጂ የራሱን ድርሻ ከተጠሪ ሳይወስድና ሳይኖረው የሚቀርበት ሕጋዊ ምክንያትና አግባብ ይኖራል ተብሎ ስለማይታሰብ ማስረጃውን ራሱ ማቅረብ ይገባው የነበረ ከመሆኑም በላይ ሰነዱ ቃለ ጉባኤ ብቻ ነው ከተባለ ደግሞ በፅሑፍ የተደረገውን ውል ማሻሻል የሚቻለው የመጀመሪያው ውል በተደረገበት የጽሑፍ አግባብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1722(1) ድንጋጌ የሚያስገነዝበን ጉዳይ በመሆኑ ማስረጃው ቢቀርብም በሕግ ፊት ዋጋ የሚሠጠው ነበር ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም አመልካች ማስረጃውን ለማቅረብ የማይችል የነበረ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበትና ማስረጃውም በሕጉ አግባብ ውሉ መሻሻሉን የሚያሳይ ሳይሆን ቃለ ጉባኤ መሆኑን ጠቅሶ በሚከራከርበት አግባብ የማስረጃ ማቅረብ መብቱ ሳይጠበቅ ውሳኔ እንደተሰጠ አድርጎ የሚያቀርበው ቅሬታ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከርበት ነጥብ በውሉ የተመለከተው የመክፈያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ክስ መቅረቡ ያላግባብ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡በእርግጥ አንድ ተዋዋይ በውሉ የተመለከተውን ግዴታ እንዲወጣ የሚጠየቀው በውሉ በተመለከተው የክፍያ የጊዜ ገደብ ግዴታውን ሳይወጣ መቅረቱ ሲረጋገጥ መሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731(1)፣1740፣1756፣1846 እና ከሌሎች ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይም የሽያጭ ገንዘቡን አመልካች ከፍሎ ለማጠናቀቅ በውሉ ተቆርጦ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሐምሌ 08 ቀን 2004 ዓ/ም መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጊዜ በሕጉ አግባብ ተሻሽሏል የሚል ክርክር አመልካች የሌለው መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡እንግዲህ በውሉ የተመለከተው የገንዘቡ መክፍያ ጊዜ ሐምሌ 08 ቀን 2004 ዓ/ም ሁኖ እያለ ተጠሪ አመልካች ግዴታውን አልተወጣም በሚል ክስ ያቀረበው ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም፤በውሉ ከተመለከተው ጊዜ ቀድሞ ነው፡፡ይህ ተገቢ ያልነበረ መሆኑን ይህ ችሎት የሚቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ይሁን እንጂ አሁን የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሰጠበት እስከ ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስም ሆነ ክርክሩ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ባለበት ሁኔታ በውሉ የተመለከተው የሽያጭ ገንዘቡን ከፍሎ የማጠናቀቂያ የጊዜ ገደብ አልፎ ከአንድ ዓመት በላይ ተጨማሪ ጊዜ ማለፉን የክርክሩ ሂደት የሚያስገነዝበን ፍሬ ነገር ነው፡፡በመሆኑም በውሉ የተመለከተው የጊዜ ገደብ አልደረሰም የሚለው የአመልካች የክርክር ነጥብ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰጥም ሆነ ባሁኑ ጊዜ ቀሪ የሆነ በመሆኑና በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደግሞ አመልካች ግዴታውን የተወጣ መሆኑን ወይም እየተወጣ የሚገኝ መሆኑ ገልፆ ያቀረበው ክርክር ስለሌለ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 280 አግባብ የገንዘቡ መክፍያ ጊዜ አልደረሰም የሚለው መከራከሪያ ነጥብ የክርክሩ ምክንያት ሊሆን የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች መከራከሪያ ነጥብም ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካች የሚከራከርበት ነጥብ የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥና ከተጠሪ የገዛው የጠጠር ማምረቻው ድርጅት የነበረበት ቦታ ለኮንዶሚኒየም መስሪያ በመንግስት መወሰዱ ግዴታውን ለመወጣት የማያስችሉ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ናቸው ተብሎ የቀረበው ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች የታለፈው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መፈጠር አለመፈጠሩ እንኳ በአግባቡ ሳይመረመርና ቦታውን አመልካች እንዲለቅ ያደረገው የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት ባንክና ከተማ ማደስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ሳይደረግ ነው የሚል ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት የነበረ መሆኑና ድርጅቱ የነበረበት ቦታ ለኮንዶሚኒየም መስሪያ ተፈልጎ በአስቸኳይ እንዲለቀቅ ሚያዚያ 03 እና 16 ቀን 2003 ዓ/ም በሚመለከተው የመንግስት አካል ለአመልካች ደብዳቤ መፃፉ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ሲሆን የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረቱ ግን አመልካችን ድርጅቱን ከተጠሪ ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከ ቀረበበት ጊዜ ድረስ ሙሉ በሙሉ እንዳይጠቀም ያደረገው ስለመሆኑ ተገልጾ በአመልካች ክርክር ያልቀረበበት ከመሆኑም በላይ የስር ፍርድ ቤት ችግሩ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ለማለት የማያስችል ነው በማለት ውድቅ ያደረገው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር በአግባቡ ሳይመረመር አልፏል የሚለው የአመልካች ቅሬታ የስር ፍርድ ቤትን የውሳኔ ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ እውነት የሌለው ነው፡፡ስለሆነም በሕግ ጭብጥነት መታየት ያለበት የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል? ወይስ አይችልም? የሚለው ነው፡፡

በዚህ መሠረትም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ለማለት የሚቻለው መቼ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1792 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህም ድንጋጌ ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ኃይል ደርሷል የሚባለው ባለአዳው ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍፁም መሰናክል በሆነ አይነት የሚደግፈው ነገር ባጋጠመ ጊዜ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለአዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈፃፀም ከባድ የሆነ ወጭ በባለአዳው የሚደርስበት ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው ባለእዳው በምንም መልኩ በቅድሚያ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይችል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለአዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገመት ወይም ሊያስብና ጥንቃቄ ሊያደረግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገተኛ ደራሽ ነገር ቢሆን እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሥር ፍ/ቤቶች አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረጉት የክሱ ምክንያት የሆነውን እዳ ለመክፈል የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡በመሆኑም አመልካች የገዛው ድርጅት የጠጠር ማምረቻ እና ይህንኑ ስራ የሚሰራውም በኤሌክትሪክ ኃይል መሆኑ ቀድሞ የሚታወቅ ሲሆን ለስራው ቀጣይነት የኤሌክትሪክ ኃይል አስተማማኝ መሆኑን ለሥራ በሚሰማራበት ጊዜም ሆነ በወቅቱ በአገሪቱ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አጣርቶ የክፍያ ምንጩ የድርጅቱ ስራና በስራው የሚገኘው ገቢ ከመሆኑ ጋር አገናዝቦ የክፍያ ጊዜውን በተመለከተ ከተጠሪ ጋር ስምምነት ሊያደርግበት ይችል የነበረ መሆኑ የሚታመን ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጎ ግዢውን ከፈፀመ በኋላም ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚችልበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ሣያደርግ ቀርቶ ጉዳት ቢደርስ እንደሕጉ አነጋገርና መንፈስ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም አመልካች ከላይ እንደተመለከተው በድርጅቱ ግዢ ወቅትም ሆነ ከግዢ በኋላ የኃይል ችግር እንዳይደርስበት አስቀድሞ ሊገምተውና ሊከላከለው ሲገባ ይህንን የመከላከልና የጥንቃቄ ዕርምጃ አስቀድሞ ሣይወስድ በመቅረቱ እዳውን ለመክፈል ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ሊባል የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡በተጨማሪም አመልካች ስራውን በፈረቃ ይሰራ የነበረ መሆኑን በክርክሩ ሂደት የገለፀ በመሆኑ ፍጹም በሆነ መሰናክል ውስጥ ነበር ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡

ሌላው ከአቅም በላይ ምክንያት ጋር አያይዞ አመልካች የሚያነሳው ነጥብ በግዥ ያገኘው ድርጅት ያለበት ቦታ ለኮንዶሚኒየም መስሪያ የመንግስት አካል ተረክቦታል የሚለው ነው፡፡በእርግጥ ቦታው እንዲለቀቅ ሚያዚያ 03 እና 16 ቀን 2003 ዓ/ም የተጻፉ ደብዳቤዎች የሚያሳዩና ተጠሪም ያልካደው ፍሬ ጉዳይ ሲሆን አመልካች የጠጠር ማምረቻ ስራውን የሚሰራበት ምትክ ቦታ የተሰጠውና ስራውንም እየሰራ የሚገኝ መሆኑንና ተገቢውን ካሳም አመልካች እንዲያገኝ ተጠሪ የበኩሉን ስለማድረጉ ገልጾ በሰጠው መልስ ግን አመልካች የማስተባበያ ክርክር አላቀረበበትም፡፡ይህም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 235 እና 83 ድንጋጌዎች መሰረት የሚያሳየው አመልካች የገዛው ድርጅት እስከ ሚያዚያ 16 ቀን 2003 ዓ/ም በቦታው የነበረ መሆኑንና በምትክም ሌላ ቦታ አመልካች ወስዶ ስራውን የቀጠለ መሆኑን አመልካች በግልጽ ያልካደው፣ይልቁንም እንዳመነ የሚቆጠር ፍሬ ነገር መሆኑን ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ይህ ምክንያት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1791,1792 እና 1793 (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች አግባብ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ብሎ ለመወሰድ የሚቻልበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሚያስገነዘበን ነው፡፡ቦታው እንዲወሰድ ትዕዛዝ ያስተላለፈው አካልም የክርክሩ ተካፋይ በመሆን የሚያስጠብቀው መብት ወይም ጥቅም እንዲሁም እንዲወጣ የሚገደድበት ግዴታ የሌለ በመሆኑ የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ውሳኔ ተሰጥቷል የሚለው የአመልካች ክርክር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39 እና 40 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች በሕጉ አግባብ ማቅረብ የሚችለውን ማስረጃ ማቅረቡ ስለተረጋገጠና ያለፍርድ ቤት እገዛ ደግሞ ማስረጃውን ማቅረብ የማይችል መሆኑ ያልተረጋጠ በመሆኑ፣የእዳው መክፍያ ጊዜም በክርክሩ ሂደት የደረሰና አመልካችም ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ እንዲሁም ግዴታውን ለመፈፀም ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ተከስተዋል ለማለት የሚቻል ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ውጤቱ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 108074 ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 82501 በ17/03/2005 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ ውጤቱ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 87834

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አቶ ግርማ አበራ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ ፀዳለ ካሣ
2ኛ/ ገነት ካሣ } ሁለቱም ቀርበዋል
3ኛ/ ጌጤ ካሣ - ከጠበቃ አቶ ከፈለኝ ካሣ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 የተመለከተው ድንጋጌ በግራ ቀኙ መካከል ለተነሳው ክርክር ያለውን አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪዎች በመካከላቸው የተነሳው የውርስ ክርክር ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እየታየ እያለ፣ ጉዳያቸውን በእርቅ/ በስምምነት የጨረሱ መሆኑን በመግለፅ በደረሱበት የእርቅ ስምምነት መሰረት ጉዳዩ እንዲቋጭ ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ሰኔ 29 ቀን 1993 ዓ/ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን በመ/ቁ 27/93 ተመልክቶ የእርቅ ስምምነቱን በማጽደቅ በስምምነቱ መሰረት ጉዳዩ የተቋጨ መሆኑን ሚገልጽ ዳኝነት ሰጥቷል፡፡

በዚህ አካኋን በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸምላቸው የአሁን ተጠሪዎች በአፈፃ/መ/ቁ 178781 እንደጠየቁ የአሁን አመልካች በእርቅ ስምምነቱ እንዲከፋፈሉ የተስማሙበት ንብረት የይዞታ ማረጋገጫ የሌለው መሆኑን ይህንኑ ዓይነት ንብረት በስምምነት እንድንከፋፈል ተስማምተናል በማለታቸው ምክንያት የእርሱን መብትና ጥቅም የነካ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለበትን ዝርዝር የፍሬ ነገር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማጣቀስ አቤቱታውን ዋናውን ውሳኔ ለሰጠው ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም ቀደም ሲል በውሳኔ የዘጋውን የመ/ቁ 27/93 የሆነውን መዝገብ ካንቀሳቀሰ እና የአሁን አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መነሻ የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ ቀደም ሲል ውሳኔ የሰጠው ግራ ቀኙ ያደረጉትን ስምምነት ተቀብሎ በማጽደቁ ምክንያት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በተከራከሪ ወገኖች የእርቅ ስምምነት መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተሰጠው ውሳኔ በሶስተኛ ወገን ላይ ውጤት እንደማያስከትል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3311 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ይህ በእርቅ ስምምነት መሰረት የተሰጠው ውሳኔ በአመልካች ላይ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ባለመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም የሚል ዳኝነት በመስጠቱና ይህም ዳኝነት በበላይ ፍ/ቤቱ በመዕደቁ የተነሳ ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ እንደቻለ ከጉዳዩ አመጣጥ ተገንዝበናል፡፡

እኛም በዚህ አኳኋን በተሰጠው ዳኝነት ላይ ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡትን የጽሁፍ ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3311 ድንጋጌ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ወገኖች በሙግት ምክንያት ሊሆን የሚችለውን ጉዳይ ወይም ደግሞ ያከራከራቸውን ጉዳይ በእርቅ በጨረሱ ጊዜ ይህ የእርቅ ስምምነት በሶስተኛ ወገን ላይ ውጤት አያስከትልም በሚል የተመለከተው የድንጋጌ ይዘት ግብና ዓላማ የእርቅ ስምምነቱ ግቡ ታራቂዎች በየግላቸው ያላቸውን መብትና ግዴታ እንደሁኔታው በማስተካከል ለክርክር መንስኤ ሊሆን የሚችለውን ወይም የሆነን ጉዳይ በስምምነት ማስቀረት እንደመሆኑ መጠን በዚህ የእርቅ ስምምነት ላይ ቀሪ የሆነን መብት እና ግዴታን ወይም የተፈጠረን መብትና ግዴታን ሊመለከት የሚችለውና ተፈጻሚነቱ በእነዚያው በታራቂ ወገኖች ላይ ብቻ ተገድቦ የሚቀር፤ የሌላ ሰውን መብትና ግዴታ ሁሉ በማካተት የእነዚህ ሶስተኛ ወገኖች መብትና ግዴታ አብሮ በእርቅ እንዳለቀ ሊቆጠር እንደማይችል የእርቅ ስምምነቱ አንፃራዊ ውጤቱ በተስማሚ ወገኖች ላይ ብቻ የተገደበ መሆኑን የሚያመለክት እንደመሆኑ መጠን ይህ ክርክር የተነሳበት የእርቅ ስምምነት ጉዳይ የማንም ሦስተኛ ወገን መብትና ግዴታን ሳይነካ በእራሱ ችሎ ሊፈፅም የሚችል የመሆኑ ጉዳይ ሊረጋገጥ ይገባል አሁን በተያዘው ጉዳይ ግን የእርቅ ስምምነት እንደ ታራቂዎች ሀሳብ በስምምነቱ ላይ የተገለፀው መብትና ግዴታ ተፈፃሚነቱ በተስማሚዎች መብትና ግዴታ ላይ ብቻ ተወስኖ ሊቀር ያልቻለ መሆኑን የማያመለክት የፍሬ ነገርና የህግ ክርክር የአሁን አመልካች አቅርቧል፡፡ የአሁን አመልካች ይህንኑ ከመጥቀሱም በላይ እንደፍርዱ እንዲፈፀምላቸው በፍርድ ኃይል ዕገዛ የአሁን አመልካች ግዴታውን እንዲፈጽም የአፈፃጸም ክስ ማቅረባቸውም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3311 ከተመለከተው አንፃር ይታይ እንኳ ቢባል ተጠሪዎች የደረሱበት ስምምነት ወይም እርቅ ከእራሳቸው መብትና ግዴታ አልፎ 3ኛ ወገን የአሁን አመልካችን መብትና ጥቅም የነካ ስለመሆኑ አመልካች ክርክር ያቀረበ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የእርቅ ስምምነቱ የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት በታራቂዎች ላይ ብቻ ተወስኖ እንዳልቀረ እየታወቀ የሥር ፍ/ቤቱ ለድንጋጌው የሰጠው ትርጉም መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የአሁን አመልካች ተጠሪዎች እርስ በእርሳቸው ያደረጉት የእርቅ ስምምነት እና በፍ/ቤት የፀደቀው ውሳኔ እና የስምምነቱ አካል ሳልሆን ክርክሬ ሳይሰማ መብትና ጥቅሜን ያስቀረ እኔን የጎዳ ውሳኔ ሊሰጥ በመቻሉ መብትና ጥቅሜን በክርክር ማስከበር እንድችል የክርክር ተካፋይ ልሁን በማለት ያቀረበው ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 አፈፃፀም ማሟያ የሚሆኑትን የፍሬ ነገር ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማጣቀስ የተደገፈ መሆኑ እስኪታወቅ እና ለዚህም ማስተባበያ እስካልቀረበበት ጊዜ ድረስ አመልካች በጉዳዩ ላይ የክርክር ተካፋይ ሊሆን ሲገባ እንዲሁም የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ ያቀረበው አቤቱታ በፍ/ሕ/ቁ 3311 ከተመለከተው ድንጋጌ አፈፃፀም ጋር ተደጋጋፊ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ከእነዚህ ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትክክለኛ አፈፃፀም እና ትርጉም በመራቅ የአሁን አመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተሉ በጉዳዩ ላይ በመ/ቁ 27/93 ነሐሴ 29 ቀን 2004 ዓ/ም እና በኮ/መ/ቁ 127958 ታህሳስ 02 ቀን 2005 ዓ/ም በትዕዛዝ አማካኝነት የሰጡት ዳኝነት ሁሉ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 27/93 ሰኔ 29 ቀን 2003 ዓ/ም በተጠሪዎች መካከል የቀረበውን የእርቅ ስምምነት ተቀብሎ ያፀደቀበት ውሳኔ የአመልካች መብትና ጥቅም የነካ ስለመሆኑ ሊያመለክት የሚችል የክርክር መነሻ በአሁን አመልካች በኩል የቀረበ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት ፍ/ቤቱ በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ጉዳዩን የአሁን አመልካች ባለበት እንደገና በማየት በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሰረት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡
3. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 89893

መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ኮንቴክ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ አለልኝ ምህረቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ወልዱ ህሉፍ - ጠበቃ ሰለሞን ገ/ሚካኤል ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮም ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከስነ-ስርዓት ክርክር ጋር ተያይዞ የቀረበ ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ድርጅትና የድርጅቱ ባለአክሲዮኖች በሆኑት ሌሎች 2 ሰዎች ከሳሽነት ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ጥር 24 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ አመልካችና የአመልካች ድርጅት ባለአክሲዮኖች በሆኑት አቶ ሳልህ ሁሴንና ወ/ሮ አለም ካሣ በጋራ በመሆን በተጠሪ ላይ ያቀረቡት የክሱ ይዘት ባጭሩ ተከሳሽ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ሆኖ በሰሩበት ወቅት ያለአግባብ ያባከኑት የድርጅቱን ገንዘብ ብር 3,641,052.04 እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸውና እንዲሁም ተከሳሹ በድርጅቱ ባለአክሲዮንነት ማዋጣት ከሚጠበቅበት የአክሲዮን ድርሻ ውስጥ ገቢ አድርጐ የተገኘው ብር 516,744.56 በመሆኑና በዚህ የተነሳም የማህበሩ ካፒታል ወደ ብር 4,442,616.36 ብቻ ቀንሶ በመገኘቱ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ድርሻ እያንዳንዳቸው ባደረጉት ካፒታል ልክ እና እንዲሁም የማህበሩ ጠቅላላ ካፒታልም በተከፈለው ልክ ብቻ ነው ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ የተለያዩ መከራከሪያ ነጥቦችን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ሰኔ 8 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የማህበሩን ካፒታል እና የባለአክሲዮኖቹን የአክሲዮን ድርሻ መጠን ጋር በተያያዘ የተጠየቀው ዳኝነት በፍ/ቤት የሚወሰን አይደለም በማለት በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበውን መቃወሚያ ወይም መከራከሪያ ነጥብ በመቀበል ያለፈ ሲሆን ተጠሪ በስራ አስኪያጅነት ኃላፊነታቸው አባክነዋል የተባለውን የድርጅቱን ገንዘብ በተመለከተ ግን ምክንያቶቹን በበለጠ በመተንተንና ግልፅ በማድረግ ክሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ሌሎች ከሳሾች ከክሱ በመቅረት የአሁኑ አመልካች ብቻ ሐምሌ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ ክሱን አሻሽያለሁ በማለት ለፍ/ቤቱ ያቀረበ ሲሆን ይህ ተሻሽሎ የቀረበ ነው የተባለው የክሱ ይዘትም ባጭሩ ተከሳሹ ያልከፈሉትን የአክሲዮን ድርሻ ወይም ዋጋ ብር 2,438,255.44 ና እንዲሁም በስራ አስኪያጅነታቸው ዘመን ያባከኑትን የድርጅቱን ገንዘብ ብር 5,488,693.84 ከህጋዊ ወለድ ጋር ታስቦ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪም በበኩሉ ክሱ በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት ተሻሽሎ አለመቅረቡንና ሌሎች ክርክሮችንም በማንሳት መልሱን ሰጥቷል፡፡ ቀጥሎም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በ15/8/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተሻሽሎ የቀረበው ክስ ፍ/ቤቱ በ8/10/2003 ዓ/ም ከፈቀደው ውጪ መሆኑን ፍ/ቤቱ ለመገንዘብ ችሏል በማለት የተከሳሽን መቃወሚያ በመቀበል ከሳሽ ፍ/ቤቱ በ8/10/2003 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ክሱን አሻሽሎ ያቅርብ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሁኑ አመልካች በ15/8/2004 ዓ/ም የተሰጠው ብይን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(2) መሰረት እንዲታረምለት ጉዳዩን እንዲያይ ለተመራለት ሌላ ችሎት አቤቱታ በማቅረቡና ችሎቱም በቀረበው አቤቱታ ላይ ተጠሪም የበኩሉን መልስ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ሐምሌ 21 ቀን 2003 ዓ/ም አሻሽሎ ባቀረበው ክስ የካፒታል መጠን ይወሰንልኝ የሚለውን ጥያቄ ያስቀረ ከመሆኑም በላይ በሌላ በኩል ከተከሳሽ የሚጠይቀውን ዳኝነትም በዝርዝር አብራርቶ ያቀረበ በመሆኑና የገንዘብ መጠኑም ቢሆን ጨምሮ መቅረቡ ፍ/ቤቱ ክሱ እንዲሻሻል ትዕዛዝ ሲሰጥ የገንዘብ መጠኑ ከፍ ብሎ እንዳይቀርብ የገደበው ባመሆኑና ይህም ወደፊት ተከሳሹ ይጠየቅበታል? ወይስ አይጠየቅበትም? ተብሎ የሚመረመር እንጂ ከወዲሁ ክሱ እንደገና ይሻሻል ተብሎ ትዕዛዝ የሚሰጥበት ሆኖ ባለመገኘቱ ቀድሞውንም ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ተሻሽሎ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ሚያዝያ 15 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠውን ብይን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(2) መሰረት ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ መሰል ስህተቶችም ለማረም እንደሚቻል የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 17352 የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ በአመልካች ተሻሽሎ የቀረበው ክስ ተቀባይነት ያለው ነው በማለት ሐምሌ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ተሻሽሎ በቀረበው ክስ ክርክሩ ይቀጥል ሲል ትዕዛዙው ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪም ይህንኑ ትዕዛዝ በመቃወም ይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረቡና ችሎቱም ግራ ቀኙ ቀርበው በጉዳዩ ላይ እንዲከራከሩ ካደረገ በኋላ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በ15/8/2004 ዓ/ም እራሱ የሰጠውን ብይን ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(2) ድንጋጌን መነሻ በማድረግና ያለስልጣኑ መሻሩ ተገቢ አይደለም በማለት ለይግባኝ አቤቱታ መቅረብ መነሻ የሆነውን ትዕዛዝ በመሻር ክርክሩ ሚያዝያ 15 ቀን 2004 ዓዓም በዋለው ችሎት በፍ/ቤቱ በተሰጠው ብይን መሠረት ይቀጥል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341 መሠረት ወደ ፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመመለስ ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟልና ስህተቱ ይታረምልን የሚል ሲሆን አቤቱታውም ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠበት ሲሆን አመልካችም የመልስ መልሱን ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት አጠር ባመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ አስቀድሞ ሚያዝያ 15 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት እራሱ ሰጥቶ የነበረውን ብይን መለወጡ ወይም መሻሩ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ መመልከቱ አስፈላጊ ሳይሆን መጀመሪያውኑ ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ/ም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሠረቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(4) ስር የተመለከቱትን የሰው መታሰርና የንብረት ማጣት ጉዳይ የሚመለከቱ ልዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር በማናቸውም ፍ/ቤት ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜና ከስረ-ነገሩ ፍርድ በፊት በጉዳዩ ላይ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ማናቸውም ትዕዛዝ በተሰጠ ጊዜ በትዕዛዙ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ እንደማይቻል ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(3) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳዩም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በባህሪው የሰውን መታሰርና የንብረት ማስተላለፍን ወይም ማዛወርን የሚመለከት ትዕዛዝ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(4) ስር የተደነገገው ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት እና ግንኙነት የሌለው በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ይህ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ድምዳሜ ላይ ደርሶ በውጤት ደረጃ የሰጠው ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካች (የስር ከሳሽ) ሐምሌ 21 ቀን 2003 ዓ/ም አሻሽሎ ባቀረበው ክስ መሠረት በፍሬ-ጉዳይ ላይ ክርክሩ በግራ ቀኙ መካከል ቀጥሎ ክሱ ይሰማ የሚል ሲሆን ይህ ትዕዛዝም ከስረ-ነገር ፍርድ በፊትና የጉዳዩ መሰማት በግራ ቀኙ መካከል ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ የተሰጠ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ (interlocutory order) ነው ከሚባል በስተቀር በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ወይም እልባት የሰጠ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የትዕዛዙ ይዘትና ባህሪይ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ በትዕዛዙ ላይ ቅሬታ ካለውም በስረ-ነገሩ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ይህንን ቅሬታም ጨምሮ በአንድ ላይ በማጠቃለል ይግባኙን ያቀርባል እንጂ ክርክሩ ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ በየጊዜው በሚሰጠው ጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ በፍ/ብ/ስ/ሰ/ህ/ቁ 320(3) መሠረት የተከለከለ ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዙ ላይ በተጠሪ የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ በዚህ ምክንያት ውድቅ ማድረግ ሲገባው ይህንን አልፎ ይግባኙን በመቀበል ማስተናገዱና ወደ ክርክር ጉዳዩ ገብቶ ውሳኔ መስጠቱ የስነ-ስርዓት ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 81511 በ21/8/2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 99819 ሰኔ 6 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው (interlocutory order) በመሆኑ በትዕዛዙ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል አይደለም ብለናል፡፡
3. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩ ከቆመበት ጀምሮ እንዲታይ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/ትዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93137

የካቲት 11 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ብጥር ታገለ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አገር ተሰማ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል።

<u>ፍርድ</u>

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ማስረጃ መመዘንን የሚያስከትል በመሆኑ እና ሰበር ችሎቶች የማስረጃ ምዘና ተግባር የሚያስከትሉ ጥያቄዎችን የማስተናገድ ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ ቀደም ሲል ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ አመልካች ለሰበር ችሎቱ ያቀረቡት የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ሲል የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው።

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ከሚች ወ/ሮ አብንደጅ አምባው የተላለፈልኝን የእርሻ ይዞታ አላግባብ ይዘውብኛል በማለት የአሁኗ አመልካች የሰበር ክርክሩ ተካፋይ ባልሆኑት በእነ አቶ የሻምበል ተሰማ ላይ በሜጫ ወረዳ ፍ/ቤት ክስ መመስረታቸውን፣ ተከሳሾቹም ቀርበው መራቱን ይዘው የሚገኙት ስለ አሁኗ ተጠሪ መሆኑን በመግለጻቸው ተጠሪ በጉዳዩ በጣ/ገብነት መከራከራቸውን፣ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል እና በሚች የቤተሰብ አባልነት የተመዘገቡት ከሳሽ ስለመሆናቸው ከሚመለከተው አካል ተጣርቶ የተላከለትን ማስረጃ መሰረት በማድረግ እና ጣ/ገብ በማስረጃነት ያቀረቡት በቀበሌው ማህበራዊ ፍ/ቤት በ15/09/1995 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በጉዳዩ ተከራካሪ ወገን ባልነበሩት የአሁኗ ከሳሽ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል ባለመሆኑ ምክንያት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ክርክር ያስነሳውን የእርሻ ይዞታ ጣ/ገብ ለከሳሽ ለቀው እንዲያስረክቡ በ19/08/2002 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣ይ/ሰሚው ፍ/ቤትም ጣ/ገቢ ያቀረቡለትን ይግባኝ በ26/08/2002 ዓ.ም. ዘግቶ ማሰናበቱን እና በጣ/ገብ ጠያቂነት ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ጣ/ገብ መራቱን የያዙት ከሳሽ ተከራካሪ ወገን በነበሩበት በማህበራዊ ፍ/ቤት በ15/09/1995 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ መሰረት መሆኑ ተረጋግጦ እያለ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ጣ/ገብ መራቱን ለከሳሽ እንዲለቁ የተሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ ጣ/ገብ መራቱን ለከሳሽ ለመልቀቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይገደዱም በማለት በ15/02/2004 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች አቅርበውት የነበረው የሰበር አቤቱታ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ.ቁ.75679 በ27/04/2004 ዓ.ም. መዘጋቱን፣ አመልካች ይህ በ15/02/2004 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ እንዲሰረዝላቸው በፍ.ስ.ስ.ሀ.ቁ. 6 ድንጋጌ መሰረት የዳግም ዳኝነት ይታይልኝ አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረቡትም ሰበር ችሎቱ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ለመሻር መሰረት አድርጎት የነበረው በ15/09/1995 ዓ.ም. በማህበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠ ነው የተባለው ውሳኔ ሀሰተኛ መሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ ተረጋጦአል መባሉን መሰረት በማድረግ መሆኑን እና ቀደም ሲል በመግቢያው እንደተገለጸው የክልሉ ሰበር ችሎት ይህንን የአመልካች ጥያቄ ባለመቀበል በ17/11/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አቤቱታ የቀረበበትን ብይን የሰጠው አቤቱታው ማስረጃ የመመዘን ተግባርን የሚያስከትል በመሆኑ በሰበር ሊታይ አይችልም በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ችሎት ክርክር የተነሳበት መሬት በ1995 ዓ.ም. ለተጠሪ የተወሰነ ነው በማለት ቀደም ሲል ለሰጠው ውሳኔ መሰረት አድርጎት ለነበረው የማህበራዊ ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረት የሆነው ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ ስለተረጋገጠ ዳኝነቱ በድጋሚ ይታይልኝ በማለት አመልካች በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6 ድንጋጌ መሰረት ያቀረቡት ጥያቄ ማስረጃን በሰበር ችሎት የመመዘን ዕድል ይፈጥራል በማለት ጥያቄውን ውድቅ የማድረጉን አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ቀደም ሲል በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የእርሻ መሬት የይዞታ ክርክር ሁለቱ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሰጡት ለአሁኗ አመልካች ጥቅም ሲሆን የሁለቱን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ በመሻር ጉዳዩን ለአሁኗ ተጠሪ ጥቅም የወሰነው የክልሉ ሰበር ችሎት ነው፡፡የክልሉ ሰበር ችሎት ለውሳኔው መሰረት ያደረገውም ከሳሽ ተካፋይ ባልሆኑበት ክርክር የተሰጠ ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶች ውድቅ ያደረጉትን 15/09/1995 ዓ.ም. በማህበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠ ነው የተባለውን ውሳኔ ነው፡፡በመሰረቱ ማንኛውም ውሳኔ የተሰጠበት ሰው በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6(1)(ሀ) እና (ለ) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ወይም ከእነዚህ አንዱን መሰረት በማድረግ የዳግም ዳኝነት አቤቱታውን ማቅረብ የሚችለው ፍርዱን ለፈረደው ወይም ትዕዛዙን ወይም ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6(1) ስር በግልጽ ተመልክቶአል፡፡አመልካቿን ተረቺ የሚያደርግ ውሳኔ የሰጠው የክልሉ ሰበር ችሎት እስከሆነ ድረስ የዳግም ዳኝነት ጥያቄው በቀጥታ ለሰበር ችሎቱ መቅረቡ ከድንጋጌው አነጋገር አንጻር ሲታይ ተገቢነት የለውም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡የዳግም ዳኝነት ጥያቄን የሚያስተናግድ ፍ/ቤት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች የማጣራት እና የግራ ቀኙን ማስረጃ የመመዘን ተግባራትን ማከናወን የሚጠበቅበት መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡በሌላ በኩል በክልሎችም ሆነ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ውስጥ የሰበር ስርዓት የተዘረጋበት ዓይነተኛ ዓላማ አንድ ወጥ የሕግ አተረጓጎም ስርዓትን ለማስፈን ይቻል ዘንድ በመጨረሻ ውሳኔዎች ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተትን ማረም ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(3)(ሀ) እና(ለ)፣በብ/ክ/መንግስታት ሕገ መንግስቶች እንዲሁም በፌዴራልና በክልሎች ዝርዝር ሕጎች በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ይህም አግባብነት ባላቸው የስረነገር እና የስነ ስርዓት ሕጎች መሰረት ፍሬ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የተሰጠው ለመጀመሪያ ደረጃ እና ለይ/ሰሚ ፍ/ቤቶች መሆኑን እና በዚህ ረገድ ለሰበር ችሎቶች የተሰጠ ስልጣን አለመኖሩን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ ለተያዘው የክርክር ጭብጥ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ይቻል ዘንድ የፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6 ድንጋጌን ዓላማ እና ይዘት የሰበር ችሎቶችን የስልጣን ወሰን ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የሰበር ክርክር የሚመራበት የተዘረጋ የተለየ ስነ ስርዓት ባለመኖሩ አጠቃላይ የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች በሰበር ክርክር ጉዳይም እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡በመሰረቱ የፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6 ዓይነተኛ ዓላማ ተገቢ ሁኔታዎችና ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸው ሲረጋገጥ በሀሰተኛ ማስረጃ፣ በመደለያና በመሰል ወንጀል ጠቀስ ድርጊቶች ምክንያት የተዛነፈውን ፍትሕ ወደነበረበት መመለስ ነው፡፡ይህ ሂደት ከሰበር ችሎቶች የስልጣን ወሰን ውጪ የሆነው ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ተግባራት የሚከናወንበት በመሆኑ ምክንያት በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ የተጠቀሰውን የስነ ስርዓት ድንጋጌ ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ የሚኖረው አማራጭ የዳግም ዳኝነት አቤቱታው ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ተግባራትን የማከናወን ስልጣን ባላቸው የስር ፍ/ቤቶች እንዲስተናገድ ማድረግ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ጉዳዩ የሚመራለት የስር ፍ/ቤትም የዳግም ዳኝነት ጥያቄው የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው በፍ/ቤቶች የስልጣን ተዋረድ መሰረት የበላይ የሆነው ሰበር ችሎት የመሆኑን ጉዳይ ከግምት ሳያስገባ ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ተግባራትን አከናውኖ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ በመስጠት ረገድ በስነ ስርዓት ድንጋጌው መሰረት ሙሉ ስልጣን ይኖረዋል፡፡ የተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብት እንዳይጣበብ ለማድረግ ያስችል ዘንድም ጉዳዩ ለወረዳው ፍ/ቤት እንዲመራ መደረጉ የተሻለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ሰበር ችሎት የዳግም ዳኝነት ጥያቄውን እራሱ ማስተናገድ እንደማይችል የያዘው አቋም ተገቢ ቢሆንም ጉዳዩ ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ተግባራትን የማከናወን ስልጣን ባላቸው የስር ፍ/ቤቶች እንዲታይ መምራት ሲገባው የአመልካች የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ተንጠልጥሎ እንዲቀር ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 09404 በ17/11/2005 ዓ.ም. የሰጠው ብይን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ከላይ በተ.ቁ.1 ከተጠቀሰው ብይን ውስጥ የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ተግባራት የሚከናወንበት በመሆኑ ምክንያት በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል አይደለም በሚል የተሰጠው የብይኑ ክፍል በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
3. ከላይ በተ.ቁ.1 ከተጠቀሰው ብይን ውስጥ አቤቱታው በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችል ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም በሚል የዳግም ዳኝነት አቤቱታው በእንጥልጥል እንዲቀር በማድረግ የተሰጠው የብይኑ ክፍል በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሮአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. በአመልካቿ የቀረበውን የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ተቀብሎ በማስተናገድ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6 ድንጋጌ መሰረት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 341(1) መሰረት ለሜጫ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲላክ ወስነናል፡፡
5. በዚህ ውሳኔ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሜጫ ወረዳ ፍ/ቤት ይላክ፡፡
6. እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለክልሉ ሰበር ችሎትም ይላክ፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 83771

መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

መስጠፉ አሕመድ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፊ/ጅ አቶ ሰለሞን ፍቅሬ

ተጠሪዎች ፡- 1. ወ/ሮ ዘነበች አለማየሁ - ጠበቃ አቶ መሉጌታ ቀርቧል

2. አቶ አዱኛ ደምሴ -ቀርቧል፡፡

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በባንክ የቁጠባ ሂሣብ ውስጥ ያለው ገንዘብ ለማንም ሣይከፈል ታግዶ እንዲቆይ ተብሎ በፍ/ቤቱ የተላለፈው የእግድ ትእዛዝ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ በገንዘቡ ላይ ወለድ ይታሰብበታል? ወይንስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በዚህ ሰበር ችሎት ተመርምሮ ተገቢው ምላሽ እንዲሰጥበት በማለት የቀረበ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 እና 359 መሠረት ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባቀረበው የመቀወሚያ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ የመቃወሚያ ማመልከቻ ይዘቱም የይግባኝ መ.ቁ. 58449 በሆነው ላይ በተጠሪዎች መካከል በነበረው የንብረት ክፍፍል ክርክር መነሻነት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በ2ኛ ተጠሪ ስም በተከፈተው የቁጠባ ሂሣብ 34951 ውስጥ ያለው ገንዘብ ለማንም ሣይከፈል እንዲቆይ በሚል አረጋግጠው የእግዱ ትእዛዝ መነሻነት ባንኩ ገንዘቡን በዝግ ሂሣብ ውስጥ እንዲቀመጥ አድርጓል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ችሎቱ በተጠሪዎች መካከል ሲካሄድ በነበረው ክርክር ላይ ታህሣስ 8 ቀን 2003 ዓ.ም ውሣኔ ሲሰጥ ከሐምሌ 26 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ፍ/ቤቱ የእግድ ትእዛዝ መሠረት ወደ ዝግ ሂሣብ ውስጥ የገባው ገንዘብ ላይ ጭምር ወለድ ታስቦበት ከነወለድ እንዲከፈላቸው በሚል የተሰጠው ውሣኔ መብቴን ስለነካው በዝግ ወይም ተካፋይ ሂሣብ ውስጥ በተቀመጠ ገንዘብ ላይ ወለድ ስለማይታሰብ ገንዘቡ ወደ ዝግ ሂሣብ ከገባበት ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ጀመሮ ባለው ጊዜያት ወለድ ሣይታሰብበት ዋናው ገንዘብ ብቻ ይከፈላቸው በሚል ውሣኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360 /2/ ስር በተመለከተው መልኩ ተሻሽሎ ወይም ታርሞ እንዲሰጥ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎ ሁለቱም ተመሣሣይነት ባለው መልኩ በገንዘቡ ላይ ወለድ የማይታሰብበት በቂና ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ የቀረበው መቃወሚያ ማመልከቻ ውድቅ እንዲደረግላቸው በመከራከር መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ፍ/ብ/ይ/ሰሚ ችሎቱም ግራ ቀኙን ሰምቶ ጉዳዩን ከመረመር በኃላ ቁጠባ ሂሣብ ውስጥ ያለው ወጪ ሆኖ ለጊዜ እንዳይከፈል የእግድ ትእዛዝ ከመስጠት በስተቀር አመልካች እንደሚለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘቡን ከቁጠባ ሂሣብ ወጥቶ በዝግ ወይም ተከፋይ ሂሣብ ውስጥ እንዲቀመጥ በሚል የሰጠሁት ትእዛዝ ስለሌለ በገንዘቡ ላይ ወለድ የማይታሰብበት ምክንያት የለም በማለት የቀረበውን የመቃወም ማመልከቻ ሣይቀበል ቀርቷል፡፡ አሁን በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ ሲቀመጥ በገንዘቡ ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ በውጤት ደረጃ ገንዘቡ በዝግ ሂሣብ እንዲቀመጥ እንደማለት መሆኑ ግልጽና የማያሻማ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካችም ይህንኑን በመረዳት ገንዘቡን በዝግ ሂሣብ እንዲቀመጥ በማድረጉና በዝግ ሂሣብ በተቀመጠ ገንዘብ ላይ ደግሞ አመልካች ወለድ አስቦ ለመክፈል የሕግም ሆነ የውል ግዴታ ሣይኖርበት በዝግ ሂሣብ የተቀመጠ ገንዘብ ከነወለዱ ታስቦ ይከፈል ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሣኔው ታርሞ በጥያቄያችን መሠረት ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በመባሉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ ቀርበው የበኩላቸውን መልስ የሰጡበት ሲሆን አመልካችም የመ/መልስ ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም በገንዘቡ ላይ የእግድ ትእዛዝ ከተሰጠበት ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ጊዜያት አመልካች ከነወለዱ አስቦ ገንዘቡን ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው አከራካሪ ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ ምላሽ ሊሰጥበት የሚባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

እንግዲህ ከክርክር ሂደቱ መገንዘብ እንደተቻለው በ2ኛ ተጠሪ ስም በአመልካች ባንክ በተከፈተ የቁጠባ ሂሣብ ቁጥሩ 34951 ውስጥ ያለው ገንዘብ ለማንም ሣይከፈል ታግዶ እንዲቆይ ተብሎ የእግዱ ትእዛዝ መተላለፍ የተረጋገጠ ፍሬ-ነገር ከመሆኑም በሻገር ይህ ስለመሆኑ በግራ ቀኙም አይካድም፡፡ አመልካችም ይህንኑ የተረጋገጠውን ፍሬ-ነገር መነሻ በማድረግ በአጽኖት እየተካራከረ ያለው በፍ/ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ አጠቃላይ ይዘቱ ከፍ ሲል እንደገለፀው ቢሆንም ወይም ቃል በቃል ሲነበብ ገንዘቡ ወደ ዝግ ሂሣብ ተዛውሮ እንዲቀመጥ በሚል የሰፈረ ባይሆንም ገንዘቡ ለማንም ሣይከፈል ታግዶ ይቆይ በሚል አገላለጽ መተላለፉ በራሱ ገንዘቡን ማንም እንዳያንቀሣቅሰው ወይም ማንም እንዳይጠቀምበት ወይም በተለመደው አባባል በዝግ ሂሣብ እንዲቀመጥ የሚያደርግ ወይም ውጤት ያለው ትእዛዝ በመሆኑና ይህንኑ መነሻ አድርገን በዝግ ሂሣብ እንዲቀመጥ በተደረገ ገንዘብ ላይ ወለድ ሊታሰብ አይገባም በሚል ይከራከራል፡፡

ተጠሪዎችም በበኩላቸው ገንዘቡ ወደ ዝግ ሂሣብ ተዛውሮ እንዲቀመጥ በፍ/ቤቱ የእግድ ትእዛዝ ያልተሰጠ በመሆኑና አመልካች በራሱ በተሣሣተ ትርጉም በተከፋይ ሂሣብ /payable account/ እንዲቀመጥ ያደረገውን በፍ/ቤቱ የእግድ ትእዛዝ መነሻነት ወለዱን ለመክፈል አስመሰሉ የሚያቀርበው ክርክር ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል ይከራከራሉ፡፡

እንዲህ ከግራ ቀኙ እየቀረበ ያለው ክርክር አንድ ቁጠባ ሂሣብ ውስጥ ያለው ገንዘብ እንዴትና በምን አይነት ሁኔታዎች ወደ ዝግ ወይም ተከፋይ ሂሣብ እንዲቀመጥ ሊደረግ ይችላል የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ላይ መፍትሔ ከመስጠቱ በፊት ሙያዊ አስተያየት ወይም ማብራሪያ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጥበት ማድረጉ የግድ ይላል ተከራካሪ ወገኖች የሚከራከሩበት ነጥብ ከክርክሩ ልዩ ባህሪይ የተነሣ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና የባለሙያን ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በዚህ አኳኃን እንዲጣራ ማድረግ እንደሚገባው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 136/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በያዝነው ጉዳይም ከፍ/ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ገንዘቡን በዝግ ሂሣብ እንዲቀመጥ ውጤት ያለው ነው ወይም አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ የባንክ ባለሙያዎች አስተያየት ሙያዊ ማብራሪያ የሚያስፈልግ በመሆኑ እንደሁኔታው ከብሔራዊ ባንክና እንዲሁም በዚህ ረገድ ያለው የሌሎች የግል ንግድ ባንኮች የታወቀና የተለመደ ልማድ ባካተተ መልኩ ተገቢው ሙያዊ አስተየየት እንዲሰጥበት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ታልፎ መወሰኑ ወይም በክርክሩ ሂደት አግባብነት ያላቸው ፍሬ-ነገሮች ሣይጣሩ ታልፎ በመወሰኑ በጉዳዩ ላይ የተሟላ ዳኝነት ተሰጥቷል ለማለት አልተቻለም በመሆኑም በክርክር አመራር ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 58449 ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መዝገቡን አንቀሣቅሶ ግራ ቀኙን በማስቀረብ ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ቁጠባ ሂሣብ ውስጥ የነበረው ገንዘብ ወደ ዝግ ወይም ተከፋይ ሂሣብ ተዛውሮ እንዲቀመጥ የማድረግ ውጤት ያለው መሆን አለመሆኑን እንደሁኔታው በብሔራዊ ባንክ ባለሙያና ተገቢ ሆኖ ከተገኘም ከሌሎች ንግድ ባንኮችም ሙያዊ አስተያየት ወይም ማብራሪያ እንዲሰጥበት በማድረግና ጉዳዩን በሥነ-ሥርዓት ሕጉ አግባብ በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት በመመለስ ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90298

የካቲት 10 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ኃይሉ ዴራሳ - ከጠበቃ ጅራኛ ለሜሳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሱፊ አለሙ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ ከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች የቀረበ የንብረት ክፍፍል ጥያቄን አስመልክቶ የተደረገ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተ ጉዳዩ ተጣርቶ በስር ፍ/ቤቶች በውሳኔ የተቋጨ ሲሆን አከራካሪ ሆኖ የቀጠለው እና በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክርም ምክንያት የሆነው በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ በቀበሌ 01 ውስጥ በአሁኑ አመልካች ስም በባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ቁጥር AM/691/89 ተመዝግቦ የሚታወቀው ቤት ነው፡፡ይህንኑ ቤት በተመለከተ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተፈራ የአሁኑ አመልካች የግል ንብረት ነው በማለት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በአሁኗ ተጠሪ ጠያቂነት ይግባኙን የተመለከተው የምዕራብ ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ሰርቪስ ቤቶቹ ከጋብቻ በፊት፣ዋናው ቤት ግን ከጋብቻ በኃላ የተሰሩ መሆኑ ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ መገንዘብ እንደተቻለ ገልጾ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማሻሻል ዋናው ቤት በጋብቻው ጊዜ የተፈራ በመሆኑ ግራ ቀኙ እኩል ሊካፈሉት ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ሰርቪስ ቤቶቹ የአመልካች የግል ንብረት ናቸው በመባሉ በዚህ የከ/ፍ/ቤት ውሳኔም ቅር ተሰኝተው ይግባኝ በማቅረባቸው እና የአሁኑ አመልካች ደግሞ ዋናው ቤት የጋራ ነው በመባሉ ቅር ተሰኝተው መስቀልኛ ይግባኝ በማቅረባቸው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት ጉዳዩ እንደገና በተጨማሪ ማስረጃ እንዲጣራ ካደረገ በኃላ በጋራ የተፈሩ መሆናቸው እንደተረጋገጠ ገልጾ የከ/ፍ/ቤት ውሳኔን በማሻሻል ዋናውንም ሆነ ሰርቪስ ቤቶቹን ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

ዋናውን እና ሰርቪስ ቤቶቹን አስመልክቶ በአሁኑ አመልካች ጠያቂነት ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታውን መርምሮ ሰርቪስ ቤቶቹን በጋራ ያፈሩት ነው በማለት ግራ ቀኙ እንዲካፈሉ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለክልሉ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ሶስት ዳኞች የተሰየሙበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጣሪ ችሎት በመ.ቁ. 158167 በ21/06/2005 ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡትም የክልሉ ሰበር ችሎት ሰርቪስ ቤቶቹን ብቻ ነጥሎ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱ ዋናውን ቤት በተመለከተ ለክልሉ ሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት እንዳጣ የሚያስቆጥር ነው በማለት ነው፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ከመገባቱ በፊት በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱታ ለሰበር ብቁ የመሆን አለመሆኑ ጉዳይ በቅድሚያ እልባት ማግኘት የሚገባው መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በቀጥታ ወደ ተያዘው ጭብጥ ከመገባቱ በፊት በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለክርክር እንዲቀርብ የተያዘው ጭብጥ ከአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት እና የዳኝነት ጥያቄ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑ በቅድሚያ መታየት የሚገባው ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሰርቪስ ቤቶቹን በተመለከተ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሂደት ላይ የሚገኝ በመሆኑ አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት ዋናውን ቤት በተመለከተ ስለመሆኑ በ19/09/2005 ዓ.ም. አዘጋጅተው ካቀረቡት የሰበር አቤቱታ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር መቅረብ የሚገባው መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ተገቢው ትዕዛዝ ሊሰጥበት ይገባው የነበረው ዋናውን ቤት በተመለከተ ብቻ ሆኖ እያለ ሰርቪስ ቤቶቹ የጋራ ናቸው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት በሚል በዚህ መዝገብ ለክርክር ተይዞ የቀረበው ጭብጥ የአመልካቹን የሰበር አቤቱታ ይዘት መሰረት ያደረገ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ዋነኛ ጭብጥ በተመለከተ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው በአምቦ ከተማ በቀበሌ 01 ውስጥ በአሁኑ አመልካች ስም በባለቤትነት ማረጋገጫ ቁጥር AM/691/89 ተመዝግቦ የሚታወቀው ቤት ነው፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት ዋናው ቤት የጋራ ነው መባሉን በመቃወም ሲሆን በሌላ በኩል የዚሁ ቤት ሰርቪስ ክፍሎች ጉዳይ በክልሉ ሰበር ችሎት በክርክር ላይ ይገኛል፡፡ጉዳዩ አምስት ዳኞች ለሚሰየሙበት የክልሉ ሰበር ችሎት የተላለፈው ሰርቪስ ቤቶቹን በተመለከተ ቢሆንም በሰበር ችሎቱ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ አልታወቀም፡፡አምስት ዳኞች የሚሰየሙበት የክልሉ ሰበር ችሎት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው በአጣሪው ችሎት በተያዘው ጭብጥ ላይገደብ በሌሎች ነጥቦች ላይም ጭምር ጭብጥ በመመስረት ክርክሩ እንዲሰማ አድርጎ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ መስጠት የሚችል በመሆኑ ሰርቪስ ቤቶቹን አስመልክቶ የቀረበውን የአቤቱታ ነጥብ ለማጣራት ጉዳዩ ለክልሉ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ሶስት ዳኞች የተሰየሙበት አጣሪ ችሎት በመ.ቁ. 158167 በ21/06/2005 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ነው ከሚባል በቀር የመጨረሻ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ትዕዛዙ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ነው ከተባለ ደግሞ አመልካች ዋናውን ቤት በተመለከተ አቤቱታቸውን ለዚህ ሰበር ችሎት ማቅረብ የሚገባቸው በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 320(3) ድንጋጌ መሰረት በክልሉ ሰበር ችሎት የተያዘው ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኃላ ነው፡፡በመሆኑም ሰርቪስ ቤቶቹን የሚመለከተው የክርክሩ ክፍል በሂደት ላይ ባለበት እና የመጨረሻ ውሳኔ ባላገኘበት ሁኔታ ዋናውን ቤት አስመልክቶ አመልካች በዚህ መዝገብ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአሁኑ የክርክር ደረጃ ሊስተናገድ የሚችል ሆኖ ባለመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. ሰርቪስ ቤቶቹን የሚመለከተው የክርክሩ ክፍል በክልሉ ሰበር ችሎት በሂደት ላይ ባለበት እና የመጨረሻ ውሳኔ ባላገኘበት ሁኔታ ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎት በመ.ቁ. 158167 በ21/06/2005 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ አመልካች በዚህ መዝገብ ያቀረቡት አቤቱታ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
2. አመልካች በክልሉ ሰበር ችሎት በመ.ቁ.158167 የተያዘው ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኃላ ለዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነውን ዋናውን ቤት አስመልክቶ ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታ ከማቅረብ ይህ ውሳኔ የሚያግዳቸው አይሆንም በማለት ወስነናል፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79561

የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ፀጋዬ አማን ለኛ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አንዋር መስጠፋ አህመድ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኪራይ ውል ግንኙነት እንዲቀጥል የቀረበውን ጥያቄ መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ እና በወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው። የአመልካች ክስ ይዘትም ንብረትነቱ የአሁኑ ተጠሪ የሆነ የንግድ ቤት በ18/12/1998 ዓ/ም በተፈረመ ውል ከቀድሞው የንግድ መደብሩ ባለቤት ከአቶ አቦቸር ሁንዴ በመግዛት የንግድ ቤቱ ኪራይ ውሉን በስማቸው እንዲዛወር በማስደረግ መደብሩን ከገዙበት ጊዜ አንስቶ የንግድ ስራውን ሲያከናውኑ ቆይተው የንግድ መደብሩን ለስር ሁለተኛ ተከሳሽ ለሆኑት ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ያከራዩ መሆናቸውን፣ ወ/ሮ አስካለም አመልካች በአወጡት የንግድ ፈቃድ መሰረት የንግድ ስራቸውን በማከናውን እንዳሉ የአሁኑ ተጠሪ የአመልካችን ተግባር እንደ ሕገወጥ ተግባር በመቁጠር ከአመልካች ጋር ያለውን የንግድ ቤት ኪራይ ውሉን በማቋረጥ ከወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ጋር የኪራይ ውል ማድረጉን ዘርዝራ ተጠሪ ከወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ጋር ያደረገው የኪራይ ውል ተሰርዞ አመልካች ጋር የነበረው የኪራይ ውል ግንኙነት እንዲቀጥል እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካች የንግድ ቤቱን ከተጠሪ እውቅና ውጪ ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ አከራይተው በመገኘታቸው ችግሩን ለማስተካከል በወጣው መመሪያ መሰረት ከአመልካች ጋር የነበረው ውል ተቋርጦ ከወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ጋር ኪራይ ውል መደረጉን ገልጾ እርምጃውን ሕጋዊ ነው በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ተከራክሯል። የስር ሁለተኛ ተከሳሽ የሆኑት ወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ በሌሉበት ጉዳዩ ታይቷል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ያከራዩት የንግድ መደብሩን መሆኑንና ይህም ተግባር በንግድም ሕጉም ሆነ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ተገቢ መሆኑን ዘርዝሮ እና አግባብነት አላቸው ያላቸውን ድንጋጌዎችንም በመጥቀስ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የኪራይ ውሉን ሊቀጥል ይገባል ሲል ወስኗል። በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ያከራዩት የንግድ ቤቱን መሆኑ ያልተካደ ፍሬ ነገር መሆኑን፣ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የንግድ ቤቱን ለሶስተኛ ወገን አሳልፈው ሲያከራዩ የአከራዩን ፈቃድ ማግኘት ያለባቸው መሆኑ በከራይ ውሉ መመልከቱንና ሕጉም ግዴታ የሚጥልባቸው መሆኑን በምክንያትነት ይዞና አግባብነት ያላቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎችን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል እንዲቀጥል ሊገደድ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት የሰበር አቤቱታቸው ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ የንግድ ሕጉ ስለንግድ መደብር ኪራይ ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪ ባሉበት እንዲታይ የታዘዘ በመሆኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በፅሑፍ በሰጠው መልስ አመልካች ለሶስተኛ ወገን ያከራዩት የንግድ መደብሩን ሳይሆን የንግድ ቤቱን ስለመሆኑ ማስተባበያ ክርክር ያልቀረበበት መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑና ይህም የአመልካች ተግባር በንግድ ሕጉ ስለንግድ መደብር ኪራይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ የሚታይበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙኝ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለውው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት ንብረትነቱ የአመልካች የሆነውን የንግድ ቤት ተከራይተው የንግድ ፈቃድ በስማቸው አውጥተው ሲሰሩበት ከቆዩ በኃላ ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ የንግድ መደብሩን አከራይተው የንግድ መደብሩን ተከራይ የሆኑት ግለሰብ ቤቱን ሲጠቀሙ መቆየታቸውና ይህ ተግባር በንግድ ሕጉ የተፈቀደ ሁኖ እያለ በተጠሪ በኩል ሕገ ወጥ ነው በሚል ምክንያት አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው የኪራይ ውል እንዲቋረጥ ተደርጎ አመልካች የንግድ መደብሩን ከአከራያቸው ግለሰብ ጋር ተጠሪ ሌላ የኪራይ ውል ተዋውሏል በሚል ምክንያት መሆኑን፣ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ያከራዩት የንግድ መደብሩን ሳይሆን የንግድ ቤቱን ሁኖ ይህንን ለማድረግም ደግሞ የአከራዩን ፈቃድ አመልካች ማግኘት ይገባቸው የነበረ መሆኑን ጠቅሶ በወቅቱ በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት ባለው መመሪያ መሰረት ሕጉን ተከትሎ ተግባሩን መፈፀሙን አምኖ የተከራከረ መሆኑን፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የንግድ ቤት ለወ/ሮ አስካለ ብርሃኑ ያከራዩ መሆኑን ያልካዱ መሆኑን በውሳኔው ላይ ያሰፈረ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዱ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ውሳኔ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ሳይሆን በማናቸውም የመጨረሻ ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ማረም ነው፡፡ በመሆኑም ችሎቱ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡን ፍሬ ነገር እንደ ተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመቀበል በሕጉ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ ስህተት መኖሩን በማረጋገጥ ይህንኑ ስህተት ማቃናት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ጉዳይ በመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነጥብ ባለመቀበል የሚቀርበውን ክርክር የሚመለከትበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያከራዩት የንግድ ቤቱን ስለመሆኑና ቤቱን ሲያከራዩ ለአከራዩ አስቀድሞ የማሳወቅ የውል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ማስተባበያ ክርክር አላቀረቡም፡፡ ይልቁንም አመልካች ይህንኑ ተግባር ሕጋዊ ነው በማለት የሚከራከሩት የን/ሕ/ቁጥር 127(ሐ) እና 145(1) ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ነው የንግድ ቤት ከንግድ መደብሩ የተለየ ሊሆን አይችልም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ ለአመልካች ያከራየው የንግድ መደብር ካለመሆኑም በላይ የንግድ ቤቱን በተመለከተ ግን አመልካች ለሶስተኛ ወገን ሲያስተላልፉ ለአከራዩ የማሳወቅ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በውሉ ስነድ ያረጋገጠ በመሆኑና የን/ሕ/ቁጥር የአከራይን ፈቃድ ተከራይ አስቀድሞ እንዲያገኝ በሕግ ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንዲሁም በዚህ ረገድ ውል ተገብቶ ከሆነ እንኳ ሕጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን የሚያስቀምጠው የንግድ መደብር ከራይን በሚመለከት እንጂ የንግድ ቤትን ኪራይ በሚመለከት አይደለም፡፡ አንድ ውል በሕጉ አግባብ ከተቋቋመ ደግሞ የሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ) እና 1731 ድንጋጌዎችን በአንድ ላይ በማጣመር ስናነብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የንግድ ቤትን ኪራይ የተከራየ ሰው ያለአከራዩ ፍቃድ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፎ መስጠት የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል ስለመሆኑ በውሉ ላይ ከተመለከተ ይህ ስምምነት በሕግ ጥበቃ የማይደረግለት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች ከተጠሪ ያተከራየው የንግድ መደብሩን ሳይሆን የንግድ ቤቱን ስለመሆኑና የንግድ ቤቱን ደግሞ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው ሲሰጡ የአከራዩን ፈቃድ ማግኘት ያለባቸው መሆኑን በውሉ ላይ ግዴታ ገብተው ይህንኑ ግዴታቸውን ሳይወጡ የንግድ ቤቱን ለሶስተኛ ወገን አስተላልፈው መስጠታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ ከአመልካች ጋር የነበረውን የኪራይ ግንኙነት ተጠሪ እንዲቋረጥ ማድረጉ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ)፣1731 እና 2959 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ከን/ሕ/ቁጥር 127 እና 145 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችልበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17579 በ12/08/2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 17782 በ25/08/2004 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ የተከራዩት የንግድ መደብሩን ሳይሆን የንግድ ቤቱን በመሆኑና በንግድ ቤቱ ያላቸውን ኪራይ መብት ለሶስተኛ ወገን ሲያስተላልፉ ለአከራይ ለማሳወቅ የውል ግዴታ የገቡ ሁነው ይህንኑ ግዴታቸውን ሳይወጡ የንግድ ቤቱን ማከራየታቸው ሕገ ወጥ ነው ተብሎ በተወሰነው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 82503

ሚያዚያ 21 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
አዳነ ንጉሴ
መስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡- 1.ወ/ሪት ቤዛ ዱጉማ
2.አቶ ብሩክ ዱጉማ } ጠበቃቸው አቶ ዮሴፍ አእምሮ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ዘሚሊ ቀለም ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ አለሙ ገበየሁ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌ/ከ/ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን የሰበር አመልካቾች እንደየቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ከሳሾች፤ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- በአጭር ሥነ ሥርዓት የቀረበ ሲሆን፡- ፍሬ ቃሉም ከአባታችን በውርስ ያገኘናቸው የ1ኛ ከሳሽ 840 አክሲኖች፣ የ2ኛ ከሳሽ ደግሞ 841 አክሲዮኖች በተከሳሽ ድርጅት ያለን ሲሆን ተከሳሽ በ2001ዓ/ም ከተገኘው ትርፍ ሊከፍለን የሚገባንን ድርሻ የከፈለ ቢሆንም በ2002 ዓ/ም ፋብሪካው ብር 24,340,165.11 ከግብር በኋላ ማትረፉ በውጪ ኦዲተር የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ከኦዲት ሪፖርት 11,036,538.97 ለባለ አክሲዮኖች ሳይከፈል የተቀመጠ መኖሩ ስለተረጋጠና በአጠቃላይ ማህበሩ ብር 35,376,704.08 የሚከፈል ትርፍ ስላለው ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ የመንግስት ግብርና ታክስ እንዲሁም በድርጅቱ ያለብን ብድር ተቀንሶ ለእያንዳንዳችን ብር 1,206,057.76 ስለሚደርሰን ለሁለታችን ሊደርሰን የሚገባውን ብር 2,412,115.52 ገንዘቡን መክፈል ከሚገባው ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም ክሱን እንዲከላከል ተፈቅዶለት ባቀረበው መልስ፡- ከሳሾች በኦዲት ሪፖርት ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ የመንግስት ግብርና ታክስ ተቀንሶ ድርሻቸው እንዲሠጣቸው የጠየቁ ቢሆንም የኦዲት ሪፖርት ከካሽ ፍለው ስቴትመንትና (cash flow statement) እና ከባላንስ ሽት (Balance sheet) ጋር አብሮ መናበብ ይገባዋል፡፡ ክስ የቀረበበት ገንዘብ በዋነኛነት በጥሬ ገንዘብ የተገኘ አይደለም፣ የኦዲት ሪፖርት ካሽ ፍለው ስቴትመንት እንደሚያመለክተው ከብር 35,376,704.08 ውስጥ በጥሬ ገንዘብ የተገኘው 107,181.78 ብቻ ሲሆን ቀሪው ከሳሾች

ትርፍ ነው ብለው የመዘገቡት ገንዘብ ከተከሳሽ ድርጅት እህት ኩባንያዎች የሚሰበሰብ ነው፣ከትርፍ ክፍፍል በፊት ከሳሾችን ጨምሮ ባለአክሲዮኖች ያላዋጡት መዋጮ ብር 25,311,616.61 ስላለ ትርፉ ሊከፈላቸው የሚገባው ገንዘቡን *ለዲ.ሌች. ገዳ ዴይንግ ሌንድ ብሊቺንግ ፋብሪካ* ባለአክሲዮኖች በቅድሚያ ከከፈሉና ከእህት ኩባንያዎች ላይ ገንዘቡ ከተሰበሰበ በኋላ ነው፡፡ እንዲሁም ትርፍ ገንዘብ በጥሬ ገንዘብ ቢኖር ትርፉ ለባለአክሲዮኖች ከመከፋፈሉ በፊት ከድርጅቱ የሚፈለጉ ሁሉም ወጪዎች እና በድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት መቀነስ ያለባቸው ሌሎች ወጪዎች ከተቀነሱና ክፍያዎችም ከተከፈሉ በኋላ የሚተርፍ ቀሪ ገንዘብ ካለ ብቻ ነው፣በኦዲት ሪፖርቱ የተገለጸው ትርፍ ዋና ዓላማ በአዋጅ ቁጥር 286/1996 መሰረት መከፈል ያለበትን ታክስ ለመወሰን ነው፣የኦዲት ሪፖርትም መጽደቅ ያለበት በጠቅላላ ጉባኤ ሲሆን ትርፍ የሚከፋለውም በጠቅላላው ጉባኤ ሲወሰን ነው፣ከሳሾች ለእህት ኩባንያዎች ሊከፍሉ የሚገባ የካፒታል መዋጮ ብር 6,958,221.21 መኖሩን የኦዲት ሪፖርት ስለሚያመላክት ይህ ገንዘብ ከሳሾች ከሚያገኙት ትርፍ ሊቀነስ የሚገባ ነው በሚል ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የጋራ ምስክር የሆኑት ኦዲተር የሰጡትን የምስክርነት ቃል ከሰማ በኋላ በሰጠው ፍርድ ከሳሾች አለ የሚሉት ትርፍ ገና ያልተሰበሰበ ከመሆኑም ሌላ የተለያዩ ወጪዎች፣ብድሮች፣ የካፒታል መዋጮዎች ያልተከፈሉበት እና ስለትርፍ አከፋፈልም ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ለከሳሾች የሚከፈላቸው የትርፍ ክፍያ የለም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

የሥር ከሳሾችም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዘጋት ስላሰናበታቸው የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡

በሰበር አቤታቸውም በዋናነት የጠቀሱአቸው የቅሬታ ነጥቦች፡-

- የሽርክና ማህበሩ ዋና አላማ የኢኮኖሚ ሥራ በመሥራት ትርፍ ማግኘት ሲሆን እያንዳንዱ ባለአክሲዮንም በየዓመቱ ከተጣራ ትርፍ ላይ ድርሻውን የማግኘት መብት እንዳለው በንግድ ህግ አንቀጽ 345(1) ከመደንገጉም በላይ በድርጅታችን የመመሥረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7 ሥር የድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ለባለ አክሲዮኖች እንደሚከፋፈል የተደነገገውን ተጠሪው በመጣስ የ2002 ዓ/ም ትርፍ ለመከፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ እንዲከፍል እንዲወሰንልን ያቀረብነውን ክስ ፍርድ ቤቶቹ የድርጅቱን ያልተሰበሰበ ገንዘብ ሰብስቦ የማስገባት እንዲሁም በድርጅቱ አለበት የተባለውንም የብድር ገንዘብ በወቅቱ በመክፈል በድርጅቱ ወጪዎች ማስያዝ የተጠሪ ሀላፊዎች ሥራ ሆኖ ሳለ ተጠሪው እነዚህን ነጥቦች በተመከለተ ያቀረበውን ክርክር እንደ በቂ ምክንያት የተቀበሉት ያለአግባብ ነው፡፡
- ተጠሪው የድርጅቱ ወጪዎች አልተከፈሉም ብሎ ቢከራከርም የኦዲት ሪፖርቱ ወጪዎች ሁሉ የተከፈሉ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ነው፣
- በተጠሪ የመተዳደሪያ ደንብ እና የመመሥረቻ ጽሁፍ የማህበሩ ካፒታል ሙሉ በሙሉ የተከፈለ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ሰነዶቹ አግባብ ባለው አካል ፊት ተመዘግበው እያሉ ፍርድ ቤቶቹ የካፒታል መዋጮ አልተከፈለም ያሉት ተገቢነት የለውም፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- በመመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7 የደርጅቱ የተጣራ ትርፍ ለባለቤቶቹ እንደሚከፍል እንጂ ለትርፍ ክፍፍል የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ እንደሚያስፈልግ የማይገልጽ ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቶቹ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ለትርፍ ክፍፍል ያስፈልጋል ያሉት ተቀባይነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፡-

- በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11(1) የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ መሰበሰብ የሚገባ ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን የጠቅላላ ጉባኤ ዋና አላማም የዉጪ ኦዲተር ሪፖርት ሰምቶ ማጽደቅና ስለትርፍ ክፍፍል መወሰን ሲሆን በዚህ ጉዳይ ጉባኤው ተሰብስቦ የትርፍ ክፍፍል እንዲደረግ የኦዲት ሪፖርቱን አላጸደቀም፤
- በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 7 የተጣራ ትርፍ ለአባላት የሚከፈል መሆኑን የሚደነግግ ቢሆንም አንቀጹ የትርፍ ክፍፍሉ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሳያስፈልግ ክፍፍሉ ይፈጸማል አይልም፤
- አመልካቾች ለትርፍ ክፍያ ጥያቄ መነሻ ያደረጉት በኦዲት ሪፖርቱ ላይ የተገለጸውን የተጣራ ትርፍ ቢሆንም በሪፖርቱ የተጣራ ትርፍ ነው የተባለው በዋናነት የተዘጋጀው ለግብር ዓላማ እንጂ ለትርፍ ክፍፍል በሚል የተዘጋጀ አይደለም፤
- በኦዲት ሪፖርቱ የተጣራ ትርፍ ነው የተባለውም አመልካቾችን ጨምሮ ከባለአክሲዮኖች ወደ ፊት የሚሰበሰበውን የካፒታል መዋጮን የሚያካት በመሆኑ አመልካቾችም በኦዲት ሪፖርቱ የተጣራ ትርፍ ነው የተባለውን ትክክል ነው ብለው የሚወስዱ ከሆነ ትርፉ ያልተከፈለ የካፒታል መዋጮን የሚጨምር መሆኑን ሊቀበሉት ይገባል፤
- በምስክርነት ቀርበው ቃላቸውን የሰጡት ኦዲተርም ብር 107,181.78 ትርፍ መሆኑን ቢገልጹም ከብር ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን በላይ አመልካቾች ባለአክሲዮኖች ከሆኑባቸው እህት ኩባንያዎች የሚሰበሰበው መሆኑን፣ ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ ብር ሃያ ሁለት ሚሊዮን የሚሰበሰበው ከባለአክሲዮኖች ሲሆን የተወሰኑት እናት ኩባንያዎችም የተዘጉና ሥራ ያቆሙ በመሆናቸው ሊሰበሰብ የማይችል መሆኑን አረጋጠዋል፤ በመሆኑም ለትርፍ ክፍፍሉ ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት አመልካቾች ያቀረቡትን የትርፍ ክፍፍል ጥያቄ የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

አመልካቾችም ለተጠሪው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካቾች ያቀረቡትን ክስ ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ማንኛውም በሽርክና ስምምነት መሰረት የሚቋቋም ማህበር የንግድ ማህበር እንደሚባል ከንግድ ህጉ ቁጥር 210(1) መገንዘብ የሚቻል ሲሆን የሽርክና ስምምነቱም ተሻራኪዎች በህብረት ሆነው የኢኮኖሚ ተግባር ያለውን ሥራ ለመሥራትና ከሚገኘው ትርፍም ሆነ ዕዳ ተካፋይ ለመሆን የሚደረግ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 211 ያስገነዝባል፡፡ ተጠሪ ማህበር ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን በንግድ ህጉ ቁጥር 517 እና 518 መሰረት የራሱ የሆነ የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ያለው ነው፡፡ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ በአንቀጽ 7 ለማህበሩ አባላት ዓመታዊ ትርፍ የሚከፈል መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን፣ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ሲባልም በመተዳደሪያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደንቡ የተመለከተውን ህጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ ከተከፈለና ሌሎችም ወጪዎችና ክፍያዎች ከተፈጸሙ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ ስለመሆኑ ያመላክታል፡፡ እንዲሁም በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 10(2) እያንዳንዱ አባል ማህበሩ ከሚያገኘው ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ የመካፈልና ማህበሩ ሲፈርስም ከሚገኘው ገንዘብ የመካፈል መብት ያለው መሆኑንና የትርፍ አከፋፈሉም በመመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7 መሰረት እንደሚሆን የደንቡ አንቀጽ 15 ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በመመስረቻ ጽሁፍም ሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ አባላት የተጣራ ዓመታዊ ትርፍ የመካፈል መብት ያላቸው ስለመሆኑ የተደነገገ ከሆነ ተጠሪው የትርፍ ክፍፍሉን ለማድረግ በጠቅላላ ጉባዔ የኦዲት ሪፖርት ቀርቦ አልተወሰነም፣የማህበሩ ገንዘብ ከባለአክሲዮኖችና እንዲሁም ከእህት ማህበሮች አልተሰበሰበም ፣የማህበሩ እዳና የተለያዩ የወጪዎችና ክፍያዎች አልተከናወኑም በሚል ያቀረባቸው እና በስር ፍርድ ቤትም ሆነ በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ደረጃ ተቀባይነት ያገኙትን እነዚህ ምክንያች አግባብነት ያላቸው መሆን አለመሆኑን መመርምር የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ እነዚህ ተጠሪ ያቀረባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች በሶስት ተከፍለው የሚታዩ ናቸው፡፡ አንደኛው ለማህበሩ አባላት የተጣራ ዓመታዊ ትርፍ ለመከፈል የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ የሚፈልግ ነው? ወይስ አይደለም? ሲሆን የንግድ ህጉ ቁጥር 532(1) ከ 20 በላይ የሆኑ ማህበረተኞች ባሉባቸው ማህበሮች ውስጥ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው ቀን አንድ ጠቅላላ ጉባኤ መደረግ አለበት ሲል በአስገዳጅ ሁኔታ ያስቀመጠ ሲሆን የማህበርተኞቹ ቁጥር ከ20 በታች በሆኑባቸው ማህበሮች ግን ጠቅላላ ጉባኤ በየዓመቱ የሚደረግ ስለመሆኑ በህጉ የተቀመጠ ግዴታ የለም፡፡ ሆኖም በዚህ ጉዳይ ተጠሪው ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ በየዓመቱ የሚደረግ መሆኑን በደንቡ አንቀጽ 11(1) የተመለከተ ሲሆን የማህበሩ ትርፍ በተመለከተ ግን በጠቅላላ ጉባኤ ሲወሰን ብቻ ለአባላት የሚከፋፈል ስለመሆኑ ደንቡ የሚያመላክት አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪው ትርፍ ለባለአክሲዮኖች ሊከፈል የሚችለው የኦዲት ሪፖርቱ ላይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሲሰጥበት ነው ሲል ያቀረበው የመከራከሪያ ሀሳብ ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡

ሁለተኛው የተጠሪው ክርክር ከማህበሩ ባለ አክሲዮኖችና ከእህት ማህበሮች የሚሰበሰብ ገንዘብ ገቢ ባልሆነበት የተጣራ ትርፍ ሊከፋፈል አይገባም የሚል ሲሆን ይህ ተጠሪው ያቀረበው በቅደመ ሁኔታነት በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍም ሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ የተቀመጠ ካለመሆኑም ሌላ የማህበሩ ሥራ አስኪያጆች በንግድ ህጉ አንቀጽ 528(1) እንደተመለከተው ከማህበሩ ዓላማና ወሰን ሳያልፉ በማንኛውም ሁኔታዎች ሁሉ በማህበሩ ስም ለመሥራት ሙሉ ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን በመተዳደሪያ ደንቡም በአንቀጽ 8 የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የማህበሩን አመራር በሚያካሂዱበት ወቅት ከአንድ ወኪል እንደሚጠበቀው ጥንቃቄ በማድረግ እንዲሁም በታታሪነትና በቅንነት መስራት እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን በመመሥረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 9 ፊደል (ሀ)ም ሥራ አስኪያጁ ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን መሥራት እና ማህበሩን መምራት እንዲሁም ከፊደል (ለ-ቀ) ያሉትን የማህበሩን ሥራዎች የማከናወን ግዴታ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ከድንጋጌዎቹ መንፈስ መረዳት እንደሚቻለውም ሥራ አስኪያጁ የተጣለበትን ሀላፊነት በታታሪነትና በቅንነት መወጣት የሚጠበቅበት መሆኑን ሲሆን ከባለአክሲዮኖች ያልተሰበሰበ የካፒታል መዋጮ ካለም በወቅቱ እንዲሰበሰብ የማድረግ እንዲሁም ከእህት ማህበሮችም የሚሰበሰብ ገንዘብ ካለ በተያዘለት ጊዜ መሰረት ገንዘቡ ለማህበሩ ገቢ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህን በንግድ ህጉም ሆነ በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንብ የተጣለበትን ግዴታ የተጠሪው ሥራ አስኪያጅ አልተወጣም ቢባል እንኳን የማህበሩ ባለአክስዮኖች ለሚጠይቁት የትርፍ ክፍፍል እንደቅድመ ሁኔታ ሊቀመጥ የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ ስለሆነም ተጠሪው የትርፍ ክፍፍል ለማድረግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የካፒታል መዋጮና ከእህት ማህበሮች የሚሰበሰብ ገንዘብ ለማህበሩ ገቢ አልተደረጉም ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሶስተኛው የተጠሪው ክርክር የማህበሩ እዳና የተለያዩ ወጪዎችና ክፍያዎች አልተከናወኑም የሚል ሲሆን በእርግጥ ከማህበሩ የመመሥረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 7 መገንዘብ እንደሚቻለው የተጣራ ትርፍ ሲባል በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 13 የተመለከተው የመጠባበቂያ ገንዘብ ከተቀመጠ በኋላ እንዲሁም ለሌሎች ወጪዎችና ክፍያዎች ከተፈጸሙ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የመጠባበቂያ ገንዘብ ፣የመንግስት ግብርና ታክስ ጨምሮ ሌሎች ወጪዎችን ክፍያዎችም እንዲሁም ማህበሩ ያለበት ዕዳም ካለ ዕዳው በመቅድሚያ ሊከፍል የሚገባ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን ክፍዎች በተገቢው ጊዜ ማህበሩ ሒሳቡን በማስመርመር ክፍያዎቹ መኖራቸው ሲረጋገጥ ከትርፍ ክፍፍል በፊት ከፍሎ ማጠናቀቅ የሚገባ ሆኖ ሳለ ይህንኑ ባለማድረግ ዕዳዎች እና የተለያዩ ወጪዎች እንዲሁም ክፍያዎች አልተከፈሉም በሚል አመልካቾች በንግድ ህጉም፣በመመስረቻ ጽሁፍ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ያገኙትን ትርፍ የመካፈል መብት ሊያዘገይ ወይም ሊያሳጣ አይገባም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በንግድ ህጉ፣እንዲሁም በማህበሩ በመመስረቻ ጽሁፉና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለአመልካቾች ከማህበሩ የተጣራ ትርፍ ድርሻቸውን እንዲከፍላቸው ላቀረቡት ክስ ተጠሪ የዘረዘራቸውን አግባብነት የሌላቸውን ምክንያቶች ፍርድ ቤቶቹ ተቀብለው ክሱን ውድቅ ያደረጉት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/108018 በቀን 19/06/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እና የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/78730 በቀን 18/11/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡትን የትርፍ ክፍፍል ክስ ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ ያደረጉት ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡
3. በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፉና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የማህበሩ የመጠባበቂያ ገንዘብ፣ እንዲሁም ዕዳዎች፣ወጪዎችና የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለው የተጣራ የ2002 ዓ/ም ትርፍ መኖሩ በአግባቡ ከታወቀ በኋላ አመልካቾች በማህበሩ ባላቸው አክሲዮኖች መጠን መሰረት የትርፍ ድርሻቸው ተሰልቶ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም በዚሁ ውሳኔ መሰረት የፌ/ከ/ፍርድ ቤት ሂሳቡ እንዲሰራ በማድረግ ተጣርቶ ሲቀርብ ውሳኔ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 85009

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሃጅ ፈዬ ገመቹ ሄዳኦ ከጠበቃ አቶ በሽር ወያ ጋር ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.አቶ ዓለሙ በቀለ
2. አቶ ክፍለ ማሪያም ከበደ
3. አቶ አሰፋ ጥላሁን
4. አቶ አሰፋ ይመር
5. አቶ ታደሰ ደምሴ
6. አቶ ገስጥ ይነሱ
7. አቶ ንጉሱ ነሲቡ
8. ፱ አለቃ ለማ በየነ
9. አቶ ደበሌ ማርም
10. አቶ ማስረሻ ገ/ሚካኤል
11 አቶ እንዳለ ጭልቆ
12. አቶ ብርሃኑ ዙርጋ
13. አቶ ወርቁ ባሆ
14. አቶ አባተ በቀለ
15 አቶ በየነ አማረ

ተወካይ አቶ አለሙ በቀለ እና አቶ ክ/ማሪያም ከበደ ቀረቡ

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፤

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በኦሮሚያ ክልል የአሪሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06633 የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63806 የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 134880 የሰጠው ውሳኔ፣ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው። ጉዳዩ የንግድ ድርጅት ቤት ሽያጭ የሚመለከት ነው። በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል።

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች በወኪሎቻቸው በኩል በአመልካች (አንደኛ ተከሳሽ) በሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ በሆነው አየለ ኃይለስላሴ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው። በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በከሳሽነት ቀርበው በአርሲ ዞን በአሰላ ከተማ በቀበሌ 07 ውስጥ በ4000 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሚገኝ ሰሚኒያ አራት አባላት ያሉት የልብስ ሰፊዎች የህብረት ሥራ ማህበር ንብረት አለ። ይህንን የልብስ ሰፊዎች የህብረት ሥራ ማህበር የማይንቀሳቀስ ንብረትና ግምቱ ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) በላይ የሆነውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁለተኛ ተከሳሽ ከማህበሩ አባላት ፈቃድ ውጭ በአነስተኛ ዋጋ ለአንደኛው ተከሳሽ በመሸጥ በከሳሾች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶብናል፡፡ ስለዚህ አንደኛ ተከሳሽ ከሁለተኛ ተከሳሽ ጋር 30/09/97 ያደረጉት የንግድ ቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ ውሳኔ ይሰጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

2. አመልካች በአንደኛ ተከሳሽ በመሆን ቀርቦ በክሱ የገለፀውን ንብረት፣ የንብረቱ ባለሀብት ከሆነው የልብስ ሰፊዎች የህብረት ሥራ ማህበር ሕጋዊ ወኪሎች 30/9/1987 ዓ/ም በተፃፈና በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ውል በብር 110,000 (አንድ መቶ አስር ሺህ ብር) ገዝቸዋለሁ አንደኛ ተከሳሽ የማይነቀሳቀሰውን ንብረት ዋጋ የንብረቱ ባለሃብት ለሆነው የልብስ ሰፊዎች የህብረት ሥራ ማህበር ሙሉ በሙሉ በመክፈል የማይነቀሳቀሰው ንብረት በስሜ አዛውሬአለሁ፡፡ የንብረቱም ባለንብት አንደኛ ተከሳሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ ካርታና ፕላን በአስተዳደሩ ክፍል ተዘጋጅቶ ተሰጥቶኛል፡፡ ስለዚህ ውሉ ሊፈርስ የሚችልበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

3. የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ ከሳሾች የማህበሩ አባላት ናቸው፡፡ የአከራካሪው ንብረት ባለሃብት የሆነው የልብስ ሰፊዎች የህብረት ስራ ማህበር ሰማኒያ አራት አባላት እንደነበሩት ተረጋግጧል፡፡ ከሰማኒያ አራቱ አባላት ንብረቱን እንዲሸጡ ለሁለተኛው ተከሳሽና ለሌሎች ሶስት ማህበሩ አመራር አባላት የውክልና ሥልጣን የሰጡት ሰላሳ አምስት አባላት ብቻ ናቸው፡፡ የማይነቀሳቀሰውን ንብረት የአባላቱ ያልተከፋፈለ የጋራ ሀብት የሚቆጠር በመሆኑ ንብረቱ ለመሸጥ የሁሉም አባላት ሥምምነት አስፈላጊ ነው፡፡ የንብረቱም ግምት ብር 200450 (ሁለት መቶ ሺ አራት መቶ ሃምሳ ብር) እንደሆነ በባለሙያዎች ተገምቶ ቀርቧል፡፡ ስለዚህ ውሉ ፈርሶ - ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ውሳኔ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ጸንቷል፡፡

4. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት 25/3/2005 ዓ/ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ጉዳዩ መታየት ያለበት ከአዋጅ ቁጥር 147/91 እና ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 106/1996 አንፃር መሆን ሲገባው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍ/ብሔር ሕጉ ስለ ጋራ ንብረት የተደነገጉትን መሰረት በማድረግ መወሰናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ እኔ የገዛሁት የማህበሩ ንብረት የሆነ ቤት በመሆኑ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ከሰማኒያ አራቱ አባላት በሞት የተለዩትን ተተኪ የሌላቸው ሰላሳ ዘጠኝ ሰዎች የማህበር አባልነታቸው ቀሪ ሆኗል፡፡ አመልካች ቤቱን በምገዛበት ወቅት ማህበሩ የነበሩት አርባ አምስት አባላቶች ብቻ ነበሩ፡፡ አርባ አምስቱ ማህበሩ አባላት ንብረቱ እንዲሸጥ አርባ አባላት ተገኝተው ተወያይተው ውሳኔ አሳልፈዋል፣ ውክልና ሥልጣን ሰጥተዋል፡፡ ይህም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አስገዳጅ ውሳኔ ለማሳለፍ የሚችሉ የማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተገኝተው ፎርም ተሟልቶ በተሰጠ ውሳኔና ውክልና መሰረት የገዛሁት ሆኖ እያለ ውሉ እንዲፈርስ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪዎች በ2/7/2005 ዓ/ም በተፃፈ መልስ የማህበሩ አባላት በማህበሩ ውስጥ ያላቸው መብት እኩል ነው፡፡ ማህበሩ 84 አባላት ያለው ሆኖ እያለ ከሰላሳ ዘጠኝ የማይበልጡ አባላት ብቻ ባስተላለፉት ውሳኔና በሰጡት ውክልና አመልካች ቤቱን መግዛታቸው ውሉን የጸና አያደርገውም፡፡ ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ከማህበሩ አባላት 50 ፐርሰንት በላይ ተገኝተውና ምልዕተ ጉባኤ ተሟልቶ በተሰጠው ውሣኔ ገዝቻለሁ በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍታብሔር ሕጉ ስለ ጋራ ንብረት የተደነገጉትን መሠረት በማድረግ መወሰናቸው ተገቢና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡ ስለዚህ የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንድስናበት በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በ7/08/2005 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም በታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ቤቱን ለመግዛት የተዋዋለው ውል ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሰረትና ድጋፍ ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

7. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች አሰላ ከተማ ሸማኔዎች አገልግሎት የህብረት ሥራ ማህበር፣ በአሰላ ከተማ ከፍተኛ ቀበሌ 07 የሚገኘውን ድርጅት ቤት የገዙት አቶ ተስፋዬ በሻህ (የማህበሩ ሊቀመንበር) አቶ ሲሳይ ጅራቱ የማህበሩ ፀኃፊ አቶ አየለ ኃይለ ስላሴ እና አቶ ኃይለማሪያም ደምሴ የተባሉት የማህበሩ ስራ አስፈፃሚ (ስራ አስኪያጅ) ኮሚቴ አባላት በተገኙበት ሌሎች የማህበሩ ሰላሳ አምስት አባላት ማህበሩ መንግስት ግብርና የዘበኛ ደመወዝ ለመክፈል ባለመቻሉ ንብረቱን ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው አራቱ የማህበሩ ስራ አስፈፃሚ (ስራ አስኪያጅ) ኮሚቴ አባላት ንብረቱን ለአመልካች በብር 110,000 / አንድ መቶ አስር ሺ ብር / በመሸጥ ገንዘቡን እንዲቀበሉ ግንቦት 29 ቀን 1987 ዓ.ም የሰጡትን ውሳኔ እና የውክልና ስልጣን በመመልከት ነው ፡፡

8. አቶ ተስፍዬ በሻ (የማህበሩ ሊቀመንበር) ፣ አቶ ሲሳይ ጅራቱ የማህበሩ ፀኃፊ አቶ አየለ ኃ/ለስላሴ እና አቶ ኃ/ማሪያም ደምሴ የተባሉት የማህበሩ ስራ አስፈፃሚ (ስራ አስኪያጅ) ኮሚቴ አባላት እነሱን ጨምሮ ሰላሳ ዘጠኝ የማህበሩ አባላት ግንቦት 29 ቀን 1987 ዓ.ም ባስተላለፉት ውሳኔ እና በሰጧቸው ውክልና ስልጣን መሰረት የአሰላ ከተማ ሸማኔዎች አገልግሎት የህብረት ስራ ማህበርን በመወከል ግንቦት 30 ቀን 1987 ዓ.ም አከራካሪውን የማህበሩን ንብረት አመልካች በሽያጭ አስተላልፈዋል፡፡ የሽያጭ ውሉን በወቅቱ የውልና ምዝገባ አገልግሎት የመስጠት ስልጣን በነበረው አርሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውልና ምዝገባ ክፍል ቀርቦ ተመዝግቧል፡፡ የማህበሩ ስራ አስፈፃሚ (ስራ አስኪያጅ) ኮሚቴ አባላት ቤቱን ለአመልካች የሸጡት ማህበሩን በመወከል ፣ በማህበሩ ስምና /የአሰላ ሸማኔዎች ሁለገብ የህብረት ስራ ማህበር ጽ/ቤት/ የሚል የማህበሩን ማህተም በመጠቀም ነው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የሽያጭ ውሉ የተደረገው የአሰላ ሸማኔዎች ሁለገብ የህብረት ስራ ማህበር እና በአመልካች መካከል ነው፡፡

9. የህብረት ስራ ማህበራት የራሳቸው የሆነ ልዩ አላማ ያላቸው ፣ የራሳቸው ባህሪያትና ሕጋዊ ሕልውና ያላቸው ናቸው ፡፡ እያንዳንዱ አባል በማህበሩ ውስጥ ያለው መብትና ግዴታ የሕብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ፣የሕብረት ስራ ማህበራት አዋጅን ለማስፈፀም በወጣው ደንብና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ነው፡፡ ተጠሪዎች የማህበሩ አባላት ሰማኒያ አራት ናቸው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ቤቱ ሲሸጥ ማህበሩ ሰማኒያ አራት አባላት የነበረው መሆኑን የማስረዳት ግዴታቸውን እንዳልተወጡ ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ይዘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማህበሩ ቤቱ እንዲሸጥ ውሳኔ ሲያስተላልፍ ያልነበሩ ሌሎች አባላት አሉ ቢባለ እንኳን ተጠሪዎች ሌሎቹም አባላት ወክለው ክስ ማቅረብ ስልጣን የላቸውም፡፡

10. የሕብረት ስራ ማህበራት ንብረት ላይ መወሰን የሚችለው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀፀ 21 የተደነገገ ሲሆን የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ እንደሚካሄድ በደንቡ ቁጥር 106/1996 አንቀጽ 20/2/ የተደነገገ ሲሆን ውሳኔ የሚተላለፈው በድምጽ ብልጫ መሆኑ በደንቡ አንቀጽ 23 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ያለሰላ ሸማኔዎች ሁለገብ የሕብረት ስራ ማህበር ሰላሳ ዘጠኝ አባላት ያስተላለፉትን ውሳኔና የሰጡትን ውክልና በማየት ቤቱን ገዝተዋል፡፡ ተጠሪዎች ይህንን የሚያስተባብል ማስረጃ ያላቀረቡ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ያሳያል፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት የማህበሩ ንብረት እንደ አባላቱ የጋራ ሀብት ሊቆጠርና ንብረቱን ለመሸጥ ሁሉም አባላት ስምምነት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1266 መሠረት አስፈላጊ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ የአመልካቾች ክርክር በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 32፣ አንቀጽ 18 ፣ አንቀጽ 19 እና ደንብ ቁጥር 106/1996 አንቀጽ 20 እና አንቀጽ 23 የሚጥስና የሕግ መሠረት የሌለው ነው ፡፡

11. የበታች ፍርድ ቤቶች የአለሳ ሸማኔዎች ሁለገብ የሕብረት ስራ ማህበርና በአመልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 1266 መሠረት በማድረግ የማህበሩ ንብረት የአባላቱ የጋራ ሀብት በመሆኑ ንብረቱን ለመሸጥ የሁሉም አባላት ስምምነት ያስፈልጋል በማለት ውሉ እንዲፈርስ መወሰናቸው ከላይ የጠቀስናቸውን የአዋጅ ቁጥር 147/1991 እና የደንብ ቁጠር 106/1996 ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06633 የሰጠው ውሳኔ ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጠር 63806 የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 134880 የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል ፡፡
2. በአለሳ ሸማኔዎች ሁለገብ የሕብረት ስራ ማህበርና በአመልካች መካከል ግንቦት 30 ቀን 1987 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የሚፈርስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ይህ ውሳኔ ተጠሪዎች ከቤቱ ሽያጭ የሚደርሳቸው ድርሻ ካለ የአለሳ ሸማኔዎች ሁለገብ የሕብረት ስራ ማህበርን ወይም ገንዘቡን ተካፍለው ወሰዱ የተባሉ አባላትን ከመጠየቅ የሚገድባቸው አይደለም በማለት ወስነናል ፡፡
4. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 83489

ግንቦት 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ አልሣቤጥ ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ሀሮን ካሣዬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ለመድን አረቦን ኃላፊ መሆን የሚገባው ወገንን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪ ክስ ይዘትም አመልካች ደንበኛ ለሆነው አቶ መኮንን ጸጋው የሰ.ቁጥር 3-40259 ኢት የሆነ የጭነት መኪና አጠቃላይ የመድን ዋስትና ሽፋን ተጠሪ እንዲሰጥላቸው በውል እድሳት ማሳወቂያ ሰነድ ማዘዙን፣የኢንሹራንስ ውሉም ለአንድ አመት የሚቆይ መሆኑና ተጠሪ ውሉን አድሶ አመታዊ አርቦን ብር 12,154.75(አስራ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አራት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም) እንዲከፍል ጠይቆ አመልካች ደንበኛው ወይም ባንኩ ይከፍላችኋል የሚል ምላሽ ሰጥቶ ከቆየና የመኪናው ባለንብረትም ውሉ እንዲታደስ ጥያቄ አላቀረብኩም በማለታቸው ለባለንብረቱም ሆነ ለባንኩ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን እንዲሰረዝ ማድረጉን በመጥቀስ አመልካች ውሉ እንዲታደስ ትዕዛዝ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ውሉ እስከተሰረዘበት ጊዜ ላለው ብር 6,079.88 እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከተጠሪ ጋር በሕጉ አግባብ የገባው ግዴታ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የመድን ውሉ እንዲታደስ አመልካች ጥያቄ ማቅረቡ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት አመልካችን ከውል የመነጨ ግዴታ አለብህ በማለት ለክሱ ኃላፊ ያደረገው ሲሆን የኃላፊነቱን መጠን በተመለከተም ውሉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ ነው በማለት ጊዜውን ሶስት ወር አድርጎ በመለየት ለዚሁ ጊዜ ብር 3,453.30(ሶስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከሰላሳ ሳንቲም)ነው በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች የመድን ውሉ ተጠቃሚ እንጂ ገቢ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበትና የእድሳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄውን አመልካች አቅርቧል ተብሎ ለአረቦን ክፍያው አመልካች ኃላፊ መደረጉ የን/ሕ/ቁጥር 657 እና 675 እንዲሁም አስገዳጅነት ያለውን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከለተው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አመልካች ለመድን አረቦን ክፍያው ኃላፊ ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ይዘት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ንብረትነቱ የአቶ መኮንን ፀጋው የሆነ የጭነት ተሽከርካሪ አመልካች በመያዣነት ይዞ የመድን ሽፋን የተገባለት መሆኑን በመግለፅ ለመኪናው የመድን ሽፋን እድሳት ጥያቄ በአመልካች በኩል ቀርቦ እድሳቱ ከተደረገ በኋላ ለአንድ አመት የመድን ሽፋን መከፈል የነበረበት የአረቦን ክፍያ በድምሩ ብር 12,154.75 የሚፈለግባቸው ስለሆነ አመልካች እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡አመልካች ግዴታ የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ግዴታው የሚመነጨው ከውል ወይም ከሕግ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር በንግድ ህግ ቁጥር 657 ወይም በንግድ ህግ ቁጥር 675 ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገው የመድን ውል ያለ መሆኑ አንደኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠው እና በሰበር ካደረገው ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች መያዣው አስተማማኝ ዋስትና እንዲኖረው በማሰብ አቶ መኮንን ፀጋው የተባለ ደንበኛው በመያዣነት በተያዘው መኪና ላይ ለሚደርስ ጉዳት የመድን ውል እንዲገቡ ሲያደርግ በመድን ውሉ ፖሊሲው ላይ በተበዳሪውና በአመልካች ስም መፃፉን፣በተለይም መጀመሪያ የተደረገው የመድን ሽፋን ጊዜ ሲያበቃ አመልካች በራሱ ጠያቂነት ለተጠሪ ባቀረበው የእድሳት ጥያቄ ተጠሪ ጥያቄውን ተቀብሎ ውሉን በማድስ ለአንድ አመት እንዲቆይ ከአደረገ በኋላ የመድን አረቦን ክፍያውን ጥያቄ አመልካች ራሱ ወይም ደንበኛውም ለመክፈል የሚችል መሆኑን ለተጠሪ ሲገልፅለት ከቆየ በኃላ የመኪናው ባለንብረትም ሆነ አመልካች ክፍያውን ሊፈጽሙ ያልቻሉ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን ይህንኑ የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜ ደግሞ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሙሉ በሙሉ ተቀብሎታል፡፡ይህ ችሎት እነዚህን ፍሬ ነገሮች ማጣራት ወይም ማስረጃውን መመዘን የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡አመልካች የእድሳት ጥያቄውን ራሱ ማቅረቡና የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለትም ባንኩ ወይም ደንበኛው የሆኑት አቶ መኮንን ፀጋው እንደሚከፍሉ ለተጠሪ ሲገልጽለት የቆየ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠ አመልካች ከውል የመነጨ አረቦን የመክፈል ኃላፊነት የለበትም የሚባልበት አግባብ የለም፡፡አመልካች የሰበር መዝገብ ቁጥር 43886 በመጥቀስ በጉዳዩ ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል በማለት የሚያቀርበው ክርክርም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ምክንያቱም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሰ/መ/ቁጥር 43886 መያዣ ያዥ የሆነው ባንክ ለመድን አረቦን ክፍያ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የተወሰነው የእድሳት ጥያቄው ባንኩ አቅርቦ ካለመሆኑም በላይ መድን ገቢውም ከስር ጀምሮ እስከ ሰበር በተደረገው ክርክር ኃላፊነቱ የራሱ መሆኑን ገልፆ ተከራክሮ ነው፡፡በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን የመኪናው ባለንብረት የሆነው ግለሰብም የክርክሩ ተሳታፊ ያልሆነ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ወደ ክሱ ያመራውም ግለሰቡን ማስንጠቀቂያ ሰጥቶ ግለሰቡ የእድሳት ጥያቄውን ባለቀረቡበት ሁኔታ የሚጠየቁበት አግባብ የለም በማለት ከገለፁለት በኋላ በመሆኑ በመዝገቡ ያሉት የክርክሩ መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች በሰ/መ/ቁጥር 43886 ካሉት የክርክሩ መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ጋር የሚገናኙ አይደሉም፡፡ የክርክሩ መሰረታዊ ነጥቦች የተለያዩ ከሆነ ደግሞ በአንድ ጉዳይ ላይ የተሰጠ የሕግ ትርጉም በሌላ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የሚደረግበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከአስገዳጅ የህግ ትርጉም ፅንሰ ሐሳብና ከአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም ጉዳዩ በሰ/መ/ቁጥር 43886 ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ታይቶ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ባለመሆኑ እና አመልካች ከውል የመነጨ ግዴታ ያለበት በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር በገባው የመድን ውል መሠረት ውሉ እስከተሰረዘበት ጊዜ ድረስ ያልከፈለውን የአረቦን ክፍያና ተያያዥ ወጪውን ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80920

የካቲት 25 ቀን2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ተሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ውድነሽ እሸቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ፍቅረማሪያም ወርቁ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ክርክር ሲሆን የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ በሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ ሁለቱም ወላጆች በሞት መለየታቸውን እና በውርስ ንብረቱን ሁለቱ ተከሳሾች ይዘው እንደሚገኙ የሚገልጽ ሆኖ ክርክሩ ከቀረበው ንብረት ውስጥ ድርሻው የሆነውን አንድ ስድስተኛ እንደያስከፍሉ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ 2ኛ ተከሳሽ የነበረው ሰው ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል በመባሉ ከክርክሩ ውጭ የተደረገ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው የአሁኗ አመልካች በበኩሏ ከሳሽ የውርስ ሀብት ናቸው ሲል ከዘረዘራቸው መካከል ወፍጮ እና ወፍጮው የሚገኝበትን ቤት ሚች እናታችን በህይወት እያሉ በስጦታ አስተላልፈውልኝ የቤቱ ባለቤትነቱም ሆነ የወፍጮው ንግድ ፍቃድ በስሜ ተዛውሮ የሚገኝ በመሆኑ የውርሱ አካል አይደለም ቀሪዎቹን ንብረቶች በተመለከተ ግን እኔም ወራሽ ስለሆንኩኝ እንዲከፋፈሉን ቢደረግ ተቃውሞ የለኝም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ ፍ/ቤቱም ከቤቱ ማህደር ጋር ተያይዘዎል የተባሉትን ሰነዶች ከኩየራ ከተማ አስተዳደር አስቀርቦ ከተመለከተ በኃላ ሰነዶች በፍ.ስ.ቁ.2443 እና 881 መሠረት ስጦታ መደረጉን ማስረዳት የማይችሉ በመሆኑ የተከሳሽ ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ከውርስ ንብረቶቹ ውስጥ አንድ ስድስተኛው ለከሳሽ ይሰጥ ሲል ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የምዕራብ አሩሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ የይግባኝ ክርክሩን ከሰማ በኃላ ሚች በሂወት እያሉ ለስር 1ኛ ተከሳሽ በስጦታ አስተላልፈው በስሟ የተዛወረው የወፍጮ ቋት እና ቤቱ የውርስ ንብረቱ አካል ነው የተባለው አላግባብ ነው ሲል በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡

የስር ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በተራው ባቀረበው ይግባኝ መነሻ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ክርክሩን ከሰማ በኃላ የወረዳው ፍ/ቤት ለውሳኔው የተሰጠውን ምክንያት በመደገፍና በማጠናከር የከፍተኛውን ሽሮ የወረዳ ፍ/ቤትን ውሳኔ ያፀና ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤት ስበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ውርሱን የሚቀበለው የሚቹ ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ የሆነ ሰው መመለስ የለብህም ተብሎ ከሚቹ ያገኘው ችሎታ ስለሆነ በስተቀር አስቀድሞ በስጦታ ወይም በኑዛዜ ተሰጥቶት የነበረውን ንብረት መልሶ ከውርሱ ንብረት ጋር መቀላቀል እንዳለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ.ሕ.ቁ.1065 እና 1067 (1) እና (2) ተደንግጐ የሚገኝ መሆኑን በተጨማሪ ምክንያትነት በመጥቀስ የይግባኝ ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ አፅድቋል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረበችው ከከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በስተቀር ቀሪው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን በ 20-10-04 አዘጋጅታ ያቀረበችው አቤቱታ ተመርምሮ ሟች በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ቀድሞውኑ በኑዛዜ ያስተላለፉት ስመ ሀብቱን ያዛወሩት እና በሞቱበት ጊዜ የራሳቸው ያልነበረው ንብረት የሟች የውርስ ንብረት አካል ነው ተብሎ ለወራሾች ይከፋፈል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጣዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ከስር ጀምሮ በአንድ በኩል የወፍጮውን ቋት እና ወፍጮው የተቋቋመበትን ቤት ሟች በሕይወት እያሉ በስጦታ ያስተላለፈልኝና በስሜ ተዛውሮ የሚገኝ በመሆኑ የውርስ አካል ተደርገው ሊወሰድ አይገባም በማለት ስትከራከር መቆየቷ እና በሌላ በኩል ደግሞ በስጦታ ተላልፎልኛል ከምትለው ንብረት ውጪ ያለውን ውርስ እንደ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ለመካፈል ዝግጅ ወይም ፍቃደኛ መሆኗ እንዲሁም በስጦታ ተላልፎልኛል የምትለውን ንብረት ወደ ውርሱ መልሶ ከማግባት በሟች ነፃ ተደርጌአለሁ በሚል ያቀረባቸው ክርክርና ማስረጃ አለመኖሩ በስር የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጠዋል፡፡ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እነዚህን የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና በክርክር ለተረጋገጠው ፍሬ ነገር አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በመለየት አመልካች በስጦታ የተላለፈላትን ንብረት መልሳ በውርሱ ውስጥ ማግባት እንዳለባት የሰጠው ውሳኔ በመሰረቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ይሁን እንጅ ሰበር ችሎቱ የዚህ አይነቱ ንብረት ወደ ውርሱ መልሶ እንዲገባ የሚደረግበትን ስርዓት ጭምር በውሳኔው ውስጥ በግልጽ ሳያሰፍር የቀረው በአግባቡ መሆኑ አለመሆኑ ሊጤን የሚገባው ሆኖ ተገኝቶአል በዚሁም መሠረት የጋራ ወራሾች ስለሚመለሱት ንብረት እና መመለሱ ስለሚፈፀምበት ስርዓት ተደንግጐ የሚገኘው በፍ/ሕጉ አንቀጽ 5 በምዕራፍ 3 በክፍል 2 ቁጥር 1065 እስከ 1078 ድረስ ሲሆን ከሟች በስጦታ ወይም በኑዛዜ የተሰጠውን ንብረት ወደ ውርስ መለሶ የማግባት ግዴታ ያለበት ወደታች የሚቆጠር የሟች ተወላጅ ከውርሱ መልሶ ማግባት ያለበት ንብረቱን ራሱን ሳይሆን የንብረቱን ዋጋ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁ.1065 እና 1074 (1) በግልጽ ተደንግጋል የንብረቱ የዋጋ ግምት የሚታወቅበት ስርዓትም በቁጥር 1077 ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ንብረቱን መልሶ ወደ ውርስ በማግባት ስርዓት መፈፀም የሚገባው ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተከትሎ መሆኑን በውሳኔው ላይ በግልጽ ማስፈር ሲገባው አላስፈለጊ የሆነ ተጨማሪ ሙግት በሚጋብዝ አኳኃን አመልካች በስጦታ የወሰደችውን ንብረት መልሳ ከውርስ ጋር መቀላቀል አለባት በማለት በደፈናው የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የሻሸመኔ ወረዳ ችሎት በመ.ቁ.29205 በ19/09/2003 ዓ.ም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.119303 በ24/04/2004ዓ.ም እና የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ.135371 በ04/10/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ.348 (1) *መሠረት* ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ወደ ውርሱ መልሳ ማስገባት ያለባት ንብረቱን እራሱን ሳይሆን የዋጋ ግምቱን ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የንብረቱ ግምት ጉዳዩ ከላይ በተጠቀሰው የፍ.ሕ.ቁ.1077 *መሠረት* በሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.36929 በተያዘው የአፈፃፀም ክርክር ታይቶ የሚወሰን ይሆናል በማለት ወስነናል፡፡
4. የሰበር ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ፡፡
5. የአፈፃፀም ዕግድ ተነስቷል፡፡
6. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
7. ውሳኔ ያገኙ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ ቁጥር 82585

የካቲት 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡-1. ወ/ሮ ሱዛን ሞንታልባን
2. ወ/ሮ ለይላ አሊ
3. ወ/ሪት ሜሪያም አሊ
} ስለ ሶስቱም ጠበቃ ያለለት ተሾመ ቀረቡ

ተጠሪዎቹ፡- 1. አቶ መራድ አሊ
2. ዶ/ር ሰሚር አሊ
} ስለ ሁለቱም ጠበቃ መሉጌታ ገበሩ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ኑዛዜን የማስፈረስ ክስ ወይም አቤቱታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ የሚገባበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኖቹ አመልካቾች ሟች አቶ አሊ አህመድ ታህሳስ 4 ቀን 2001ዓ.ም አደረጉት የተባለውን ኑዛዜ ለአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት አቅርበው ውሣኔ በማሰጠት የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ከወሰዱ በኋላ የአሁኖቹ ተጠሪዎች የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሆነን እያለ በኑዛዜው የተደረገው ድልድል መብታችንን የሚነካ በመሆኑ ኑዛዜው ሊሻር ይገባል በማለት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 358 መሰረት መቃወሚያ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመ/አመልካቾቹ ኑዛዜው ሲነበብ ያልነበሩ እና ወኪልም ያልነበራቸዉ ቢሆንም ኑዛዜ መኖሩን ስለኑዛዜው ስልጣን በተሰጣቸው 3ኛ በመ/ተጠሪ እንዲያውቁ የተደረገ እና በክፍፍሉ ረገድም ሀሳባቸውን ሲሰጡ የነበሩ ስለመሆኑ የመ/ተጠሪዎች ካቀረቧቸው የሰነድ ማስረጃ መገንዘብ ስለተቻለ እና ስለድልድሉ ከ3ኛ የመ/ተጠሪ ከሰሙበት ጊዜ ጀምሮ አቤቱታቸውን በ15 ቀን ውስጥ ስላላቀረቡ አቤቱታቸው በፍ/ሕ/ቁ 973 እና 974 መሰረት በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት በብይን አሰናብቶአቸዋል፡፡

ይ/ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር የመ/ተጠሪዎች ውርስ አጣሪው በአግባቡ ተሰይሞ ስለውርስ ክፍፍልም ሆነ ድልድል ለስር የመ/አመልካቾች የገለፀላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዳላቀረቡ ከስር የመ/አመልካቾቹ ጋር ሲጻጻፍበት ነበር የተባለውም ማስረጃ የመ/አመልካቾች ኑዛዜ ሰለመኖሩ ያውቁ ነበር የሚለውን ከሚያስረዳ በስተቀር አሁንም ስለውርስ ክፍፍልና ድልድል የሚገልፀው ነገር እንደሌለ በዚህም ምክንያት አቤቱታው በፍ/ሕ/ቁ 973/1/ መሰረት በይርጋ ይታገዳል የተባለው በአግባቡ እንዳልሆነ በዝርዝር ገልጾ ብይኑን በመሻር የውርስ ክፍፍልን አስመልክቶ በኑዛዜው ላይ የቀረበውን ክርክር መርምሮ ውሣኔ ይሰጥበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዘንድ ጉዳዩን ወደስር ፍ/ቤት የመለሰው ሲሆን የአሁኖቹ አመልካቾች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት ያቀረቡለትን አቤቱታ ዘግቶ በማሰናበቱ ነው፡፡

አመልካቾቹ በ17/12/04ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር የተለዋወጡ ሲሆን እኛም የይ/ሰሚው ችሎት ውሣኔ እና የሰበር ችሎቱ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አንድ ኑዛዜ ፈራሽ ነው በሚል ስለሚቀርብ መግለጫ እና ክስ እንዲሁም መግለጫው እና ክሱ ሊቀርብ ስለሚገባበት የጊዜ ገደብ በፍ/ሕ/ቁ 973 እና 974 ተደንግጐ ይገኛል፡፡ ቁጥር 973 ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው ኑዛዜው ሲነበብ በነበሩ ወይም በተወከሉ ሰዎች ጉዳይ ሲሆን ቁጥር 974 ድንጋጌ ደግሞ በኑዛዜው ስነስርዓት ባልነበሩ ወይም ባልተወከሉ ሰዎች ጉዳይ ነው፡፡ የፍ/ሕ/ቁ 973 እና 974 ድንጋጌዎች አቤቱታ አቅራቢው ኑዛዜው ሲነበብ የነበረ ወይም የተወከለ የመሆን አለመሆኑን መስፈርት መሰረት በማድረግ ይርጋው መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ እና ፍጹም የሆነ የይርጋ ጊዜ /974 ንዑስ ቁጥር 2/ በተለየ ሁኔታ ከመደንገጋቸው በስተቀር ሁለቱም ድንጋጌዎች ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል ክስ የሚቀርብበትን ስርዓት የሚደነግጉ በመሆናቸዉ በመሰረቱ ተያይዥነት አላቸው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ኑዛዜው ሲነበብ ያልነበሩ ወይም ያልተወከሉ መሆኑ አላከራከረም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ቢያንስ ሁለቱንም ድንጋጌዎች አጣምሮ መጥቀስ ሲገባው በውሣኔው ውስጥ ቁጥር 973 ድንጋጌን ብቻ ነጥሎ መጥቀሱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህ አንጻር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ቁጥር 973 ድንጋጌ በመጥቀስ የሰጠው ውሣኔ የተሳሳተ ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ከድንጋጌው አጠቃቀስ አንጻር ብቻ ተገቢነት ያለው ቢሆንም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ ተመርምሮ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ አቋም የሚወሰድበት ከድንጋጌው አጠቃቀስ አንጻር ብቻ ሳይሆን በሙሉ ይዘቱና መንፈስ ነው፡፡

ዋናውን ፍሬ ጉዳይ በተመለከተ ተጠሪዎቹ ኑዛዜውን ያውቁ የነበረ መሆኑን ይ/ሰሚው ፍ/ቤት አረጋግጦ እያለ እና አጣሪውም በኑዛዜው ከተመለከተው ውጪ የሚያቋቁመው የተለየ የንብረት ድልድል በማይኖርበት ሁኔታ ተጠሪዎቹ ስለንብረት ድልድሉ እንዲያውቁ መደረጉን አመልካቾች አላስረዱም ሲል ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የተሳሳተ ነው በማለት አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ተከራክረዋል፡፡ በመሰረቱ ኑዛዜ መኖሩን ማወቅ እና የኑዛዜውን ሙሉ ይዘት ማወቅ የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ተጠሪዎቹ የኑዛዜውን ቅጂ እንዲያገኙ ተደርጐአል የሚል ክርክር አመልካቾቹ በስር ፍ/ቤቶችም ሆነ በሰበር ደረጃ አላቀረቡም፡፡ አመልካቾቹ ያቀረቡት ማስረጃ የኑዛዜውን መኖር እንጂ በኑዛዜው የተደረገውን የንብረት ድልድል ተጠሪዎች እንዲያውቁት መደረጉን የሚያስረዳ አይደለም በማለት ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የተሰጠው ይ/ሰሚው ፍ/ቤት በማስረጃ ምዘና ረገድ የሰጠውን ውሣኔ አግባብነት መመርመር ደግሞ በዚህ ሰበር ችሎት የስልጣን ወሰን ውስጥ የሚካተት አይደለም፡፡

በመጨረሻም ተጠሪዎቹ በኑዛዜው የተደረገውን የሀብት ድልድል ያወቁት በ13/03/04 ዓ.ም መሆኑን በሰበር መልሳቸው ያመኑ በመሆኑ እና የመቃወም አቤቱታቸውን ያቀረቡት ግን 15 ቀናት ካለፉ በኋላ በ03/05/04 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ውድቅ መደረግ ነበረበት በማለት አመልካቾች በመ/መልሳቸው ተከራክረዋል፡፡ በመሰረቱ በፍ/ሕ/ቁ 973/1/ የተመለከተው የ15 ቀን የጊዜ ገደብ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ሳይሆን የመግለጫ ማቅረቢያ ጊዜ ነው፡፡ በኑዛዜው የተሰየሙ አጣሪ ናቸው የተባሉት የአሁኗ 3ኛ አመልካች ስለንብረት ድልድሉ ለአሁኖቹ ተጠሪዎች ያሳወቁት ነገር አለመኖሩን ይ/ሰሚው ፍ/ቤት አረጋግጦአል፡፡ ተጠሪዎቹ የንብረት ድልድሉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲያውቁ አልተደረገም ከተባለ ደግሞ መግለጫ የማቅረብ ግዴታ አይኖርባቸውም፡፡ የዚህ ዓይነቱ ግዴታ ከሌለባቸው ደግሞ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ተጠሪዎቹ በኑዛዜው የተደረገውን የንብረት ድልድል ማወቃቸውን ከገለጹበት ከ13/03/04ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ በ03/05/04 ዓ.ም ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ በፍ/ሕ/ቁ 973/3/ በተመለከተው አነስተኛው የሶስት ወር የይርጋ ዘመን እንኳ የይርጋ ጊዜው ያለፈበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ማለት ስላልተቻለ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአ/አበባ ከተማ ይ/ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 17753 በ17/09/04 ከሰጠው ውሣኔ ውስጥ ይርጋን የሚመለከተው የውሣኔው ክፍል እና የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት በመ/ቁ 18053 በ06/11/04 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. በአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 1944/03/ የተያዘው ክርክር ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡
4. የውሣኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
5. ውሣኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 89641

ጥቅምት 21 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ሐረገወይን ብርሃኑ

2. አቶ ፀጋዬ ከድር የህጻን ቤቤቶ ፀጋዬ እና የህጻን ናትናኤል ፀጋዬ ሞግዚት

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አዜብ ብርሃኑ

2.አቶ እስክንድር ኮከቤ

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር አመልካቾች የክስ አቤቱታ አቅራቢነት የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካቾች የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ/ም አሻሽለው በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት የክስ አቤቱታ አመልካቾችና 1ኛ ተጠሪ የሚች አቶ ብርሃኑ ገ/ማሪያም እና የወ/ሮ ፀዳለ በዳዳ ወራሾች መሆናችን በድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ የወራሽነት ማስረጃ ወስደን የውርስ ንብረቶች ተጣርተው ሪፖርቱም ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ የጸደቀ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ ቀደም ሲል እውነተኛ ወራሽና ተወላጅ ሳይሆኑ የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ ከህግ ውጪ አሳስተው የወሰዱ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰረዘ በመሆኑ በተሰረዘ ወራሽነት ማስረጃ ከሚቾች ወራሾች ጋር የውርስ ሀብት ሊከፋፈሉ ስለማይገባ የውርስ ሀብቶችን ከወራሾች ጋር እንዲከፋፈሉ የተሰጠው ትዕዛዝ ይሰረዝልን ብለዋል፡፡

ተጠሪዎችም በሰጡት መልስ፡- አመልካቾች 1ኛ ተጠሪ የሚቾች ልጅ መሆኗን አምነው የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸውም ሆነ የውርስ ሀብቶች እንዲከፋፈሉ ለፍርድ ቤት ሲያመለክቱ ቆይተው የሚቾች ልጅ እና ወራሽ አይደለችም በሚል ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6(1)(ሀ)የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ስለማያሟላ ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በሰጠው ብይን፡- አመልካቾችና 1ኛ ተጠሪ የሚች ብርሃኑ ገ/ማሪያም እና ወ/ሮ ጸዳለ በዳዳ ልጆች ስለመሆናቸው አንድ ላይ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ የውርስ ንብረቶች ተጣርተው የአጣሪው ሪፖርት ቀርቦ ስለትክክለኛነቱ ወራሾቹ በሰጡት አስተያየት በመስማማታቸው ከጸደቀና የፍርድ ቤቱ የውሳኔ አካል ሆኖ እንዲፈጸም ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 ስር ከተደነገጉት ሁኔታዎች ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሲል ውድቅ አድርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾችም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከራቸው በኋላ በሰጠው ፍርድ፡- ይግባኝ ባዮች ቀርቦ የነበረውን ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/91 መሰረት በማሻሻል በ12/08/2004 ዓ/ም የተጻፈ የክስ አቤቱታ ቢያቀርቡም የክስ አቤቱታቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ የተፈቀደላቸው ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያመላክትም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ አቤቱታቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ሳይፈቅድላቸው ያቀረቡት የክስ አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/91 ስለአቤቱታ አቀራረብ ከተደነገገው ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣በሌላ በኩል ይግባኝ ባዮች በ25/04/2004 ዓ/ም እና በ12/06/2004 ዓ/ም ያቀረቡኣቸው አቤቱታዎች ጥቅምት 09/2004 ዓ/ም የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲሻሻልላቸው የጠየቁባቸው ቢሆንም አቤቱታዎቹ በመዝገቡ ላይ የመጨረሻ ውሳኔና ትዕዛዝ ተሰጥቶ ከተዘጋ በኋላ የቀረቡ በመሆናቸው በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 አንጻር የሚታዩ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በዚሁ የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር መሰረት በማየት ውደቅ ማድረጉ ተገቢ ነው ሲል አጽንቷል፡፡

አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በሥር ፍርድ ቤቶች ብይን/ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የቅሬታ ነጥቡም ሲጠቃለል፡-አመልካቾች በህጉ አግባብ ተገቢውን የዳኝነት ክፍያ ከፍለን በ12/06/2004 ዓ/ም ባቀረብነው ቀጥታ የክስ አቤቱታ ተጠሪዎች በተሰረዘ የወራሽነት ማስረጃ መሰረት የያዙትን የውርስ ንብረቶች እንዲመልሱ እንዲወሰንልን ዳኝነት ጠይቀን ሳለ ፍርድ ቤቶቹም የክሱን አርዕስት፣ተከራካሪ ወገኖችንና የክሱን ማስረጃ ዝርዝር እንዲሁም በክሱ አቤቱታ የተጠየቀውን ዳኝነት በማየት በፍ/ህ/ቁ/ 999 መሰረት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው ጉዳዩ እንደገና ዳኝነት እንዲታይ በሚል እንደቀረበ በመቁጠር የክስ አቤቱታችንን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 መሰረት መርምረው ውድቅ ያደረጉት ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- ጉዳዩ እልባት አግኝቶ በተዘጋ መዝገብ ላይ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 91(1)ን በመጠቅስ አመልካቾች የውርስ ሀብቱ ይመለስልን ሲሉ ያቀረቡትን አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 6(1) መሰረት በመመርመር ውድቅ ያደረጉት ህግን መሰረት ያደረገ ነው፣አመልካቾች ያቀረብነው አቤቱታ ሊታይ የሚገባው በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6(1) ሳይሆን በፍ/ህ/ቁ/999 መሰረት ነው ቢሉም በፍ/ህ/ቁ/999 መሰረት የሚቀርብ ጉዳይ አዲስ ክስ ቀርቦ አዲስ ዳኝነት የሚሰጥበት እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት መዝገብ ተንቀሳቅሶና በፍ/ሥ/ሥ/ህ ቁ 91 መሰረት የክስ አቤቱታ ተሻሽሎ የሚወሰን ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ የሚገባ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾችም ለተጠሪዎች መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-አመልካቾች ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካቾችና 1ኛ ተጠሪ የሁለቱም ሟቾች ወራሾች ስለመሆናቸው እንዲወሰንላቸው በጋራ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ወራሽነታቸው በፍርድ ቤት ተረጋግጦ መወሰኑንና የሟቾች የውርስ ሀብቶች እንዲጣሩ ተደርጎ ተጣርተው ከቀረቡ በኋላ የአጣሪው ሪፖርት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ ስለመጽደቁና ክፍፍሉም እንዲፈጸም ታዞ መዝገቡ ጥቅምት 09 ቀን 2004 ዓ/ም መዘጋቱን የስር ፍርድ ቤቶች በውሳኔያቸው ካሰፈሩት መገንዘብ ተችሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾችም መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ በታህሳስ ወር 2004 ዓ/ም ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጻፉት አቤቱታ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጣቸው የወራሽነት ማስረጃ የተሰረዘ በመሆኑ ተጠሪዋ ከውርስ ሀብቱ ¼ኛ እንዲካፈሉ የተሰጠው ትዕዛዝ ተሽሮ ለአመልካቾች እንዲደርሳቸው በተወሰነው የውርስ ሀብት ድርሻ ላይ እንዲጨመርላቸው ጠይቀው የተጠሪዋን መልስ ፍርድ ቤቱ ከተቀበለ በኋላ መዝገቡ ለምርመራ ተቀጥሮ ባለበት አሁን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የክሱን አርዕስት በፍ/ህ/ቁ/999 መሰረት የአመልካቾችን የውርስ ድርሻ ለማስለቀቅ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/91 መሰረት ተሻሽሎ የቀረበ የክስ አቤቱታ የሚል አቅርበዋል፡፡ ይህን ተሻሽሎ ቀረበ የተባለውን የክስ አቤቱታ ፍርድ ቤቶቹ የመረመሩት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6(1) መሰረት መሆኑንም ከውሳኔያቸው መገንዘብ ችለናል፡፡

የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91 ተከራካሪ ወገኖች አቤቱታቸውን ወይም የመከላከያ መልሳቸውን ሊያሻሽሉ ወይም ሊለውጡ ስለሚችሉበት አግባብ የሚደነግግ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር 1 እንደተመለከተው አቤቱታ ወይም ክርክር ለመሻሻል ወይም ለመለወጥ የሚቻለው በተካራከሪ ወገኖች ጥያቄ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ሲያዝ ሲሆን ተከራካሪ ወገኖቹም አቤቱታቸውን ወይም ክርክራቸውን አሻሽለው ወይም ለውጠው ሊያቀርቡ የሚችሉት የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን በይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ይረዳል ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲገምት ብቻ ነው፡፡ አቤቱታውን ለማሻሻል ወይም ክርክሩን ለመለወጥ የሚቻለውም በጉዳዩ ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ስለመሆኑ በዚሁ በንዑስ ቁጥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካቾች አቤቱታቸውን አሻሽለው ለማቅረብ እንዳልተፈቀደላቸው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍርድ የሚያመላክት ከመሆኑም ሌላ አቤቱታቸውን ያቀረቡትም በጉዳዩ ላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥቅምት 09 ቀን 2004 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቶ መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ አቤቱታው በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91 መሰረት የሚስተናገድ አይሆንም፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ይህን አቤቱታ የመረመሩትም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 መሰረት ሲሆን ድንጋጌው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆን አለመሆኑን መመርመር ይገባል፡፡

በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 (1)(ሀ) መሰረት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሚኖረው የመጨረሻው ፍርድ ወይም ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠው በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበውን ሰነድ ወይም ሀሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሰረት በማድረግ ሲሆን አቤት ባዩም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጎ ለማወቅ አለመቻሉን ማስረዳት የሚጠበቅበት ከመሆኑም በላይ በፊደል (ለ) እንደተጠቀሰውም እነዚህ የተዘረዘሩት ተግባሮች መፈጸማቸው ቢገለጽ ኖሮ ለተሰጠው ፍርድ መለወጥ ወይም መሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችሉ እንደነበር አቤት ባዩ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች በክስ አቤቱታቸው የገለጹት 1ኛ ተጠሪ እውነተኛ ወራሽ ሳይሆኑ የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰረዘባቸው በመሆኑ የተቀበሉትን የውርስ ሀብት ድርሻ ለአመልካቾች እንዲለቁ በፍ/ህ/ቁ/999 መሰረት ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ ከዚህ የክስ አቤቱታው ይዘትም መረዳት የሚቻለው አቤቱታው በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6(1)(ሀ) እና (ለ) የተመለከቱትን ሁኔታዎች አለመያዙንና በውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት መቅረቡን ነው፡፡ በፍ/ህ/ቁ 996 (1) ወራሽ የሆነ ሰው ለሟቹ ወራሽ መሆኑንና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመላክት የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፍርድ ቤት ማመልከት የሚችል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሆን የተሰጠው የወራሽነት ምስክር ወረቀትም በፍ/ህ/ቁ/998(1) በተመለከተው ሁኔታ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በፍ/ህ/ቁ/999 በተደነገገው መሰረት አንድ ሰው ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው ውርሱን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ ያደረገ እንደሆነ እውነተኛው ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት የውርስ ንብረቶች እንዲመለሱለት የወራሽነት ጥያቄ ክስ ማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ የአመልካቾች አቤቱታም 1ኛ ተጠሪ እርግጠኛ ወራሽ ሳይሆኑ የወራሽነት ማስረጃ በመያዝ የውርስ ሀብት ድርሻ ስለያዙ እንዲመልሱ ይወሰንልን የሚል እስከሆነ ድረስ የዳኝነት ክፍያ በታሪፉ መሰረት ከፍለው በፍ/ህ/ቁ/999 እንደተጠቀሰው አዲስ ክስ ከሚያቀርቡ በስተቀር የውርስ ሀብት ተጣርቶ ክፍፍሉ እንዲፈጸም ተወስኖ የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ እንዲከራከሩ የሚፈቅድ የፍ/ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌ የለም፡፡

በመሆኑም አመልካቾች የውርስ አጣሪ ሪፖርት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ ከጸደቀና የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ ታዞ ድርሻቸውን ወሰደው መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91 መሰረት ቀደም ሲል የቀረበውን የክስ አቤቱታ አሻሽለን አቅርበናል በማለት የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ/ም ያቀረቡትን አቤቱታ ፍርድ ቤቶቹ ተቀብለው በማከራከር አቤቱታውን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 6 መሰረት መመርመራቸው የፍ/ሥነ ሥርዓት ህግን የተከተለ ባለመሆኑ ምክንያቱን ለውጠን በውጤት ደረጃ ግን የክስ አቤቱታውን ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 38608 በቀን 12/08/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ብይን/ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 07907 በቀን 03/08/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ ምክንያቱን ለውጠን በውጤት ደረጃ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. የአመልካቾች አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 6 መሰረትም ሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91 መሰረት ሊስተናገድ የሚገባ አይደለም፡፡ ይህ ውሳኔ አመልካቾች ተገቢውን የዳኝነት ክፍያ ከፍለው አግባብነት ባላቸው የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት መብታቸውን በሚጠይቁት ወገን ላይ የሚያቀርቡትን ቀጥታ ክስ የሚያግድ አይሆንም፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ/ቁ. 93779

ታህሳስ 30 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጂአቶ ያሲን ሺበሺ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ሐሰን መሐመድ - በሌሉበት የሚታይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጋብቻ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፋንቲ ረሱ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ነው፤፤ ፍርድ ቤቱ ለአሁኗ ለአመልካች በቁጥር ፋ/ሸ/577/05 በቀን 21/06/2005 በአድራሻቸው በፃፈው ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የተፋቱ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረቡም፣ከአቶ አደም አንባዬ ጋር ተጋባሁ ስለሚሉት ጋብቻ ያቀረቡት ማስረጃ የማጭበርበሪያ ወረቀት መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት አመልካቿ የተጠሪው ሚስት እንጂ የአቶ አደም አንባዬ ሚስት አይደሉም ሲል መወሰኑን አረጋግጧል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታም መሰረታዊ ይዘትም በያሎ ወረዳ ፍርድ ቤት ከተጠሪ ጋር በነበራቸው የጋብቻ ይፍረስልኝ ክርክር የወረዳው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ/ቁጥር 14/2003 በቀን 04/06/2003 በሰጠው ውሳኔ ጋብቻው መፍረሱን አረጋግጦ ባለበት ሁኔታ ጉዳዩ በሸሪዓ ፍርድ ቤት እንዲታይ መደረጉ ስነ ስርዓቱን የተከተለ አይደለም፣በአገሪቱ ሕገ መንግስት የተረጋገጠውን ጋብቻን በፈቃደኝነት የመመስረት መብትም የጣሰና የእኩልነት መብትን ያላስከበረ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታቸው ተመርምሮም የግራ ቀኙ ጋብቻ በመደበኛ ፍርድ ቤት በክልሉ ከፈረሰ በኋላ የክልሉ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ዳግም የማስተናገዳቸውን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ጉዳዩን በያሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍቺ ጉዳይ ተከራክረው በመካከላቸው ያለው ጋብቻ የፈረሰ መሆኑ በመ/ቁጥር 14/2003 በቀን 04/06/2003 ከተወሰነ በኃላ የጋብቻው ጉዳይ ተመልሶ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የታዬና አመልካች ያለፍላጎታቸው ከተጠሪ ጋር በጋብቻ እንዲቀጥሉ ተብሎ የተወሰነ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 34(1) ስለ ተጋቢዎች በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት ያላቸው ስለመሆኑ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን በአንቀጽ 35(2) ድንጋጌም ሴቶች በሕገ መንግስቱ በተደነገገው መሰረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸው መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል ሕገ መንግስቱ በሕግ በተለይ በሚዘረዝረው መሰረት በሐይማኖት፣ በባህል የሕግ ስርአቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ እንደሚችል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 34(4) ከማስቀመጡም በላይ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር አምስት ድንጋጌ ስር ሕገ መንግስቱ የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሀይማኖታቸው ወይም በባህሎቻቸው ሕጎች መሰረት መዳኘትን እንደማይከለክል፣ዝርዝሩም በሕግ እንደሚወሰን አስቀምጧል፡፡ በዚህም አግባብ የሸሪዓ ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 188/1992 የተቋቋሙ ሲሆን በቤተሰብ ጉዳይ ላይ ያላቸው የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ተለይቶ ተቀምጦላቸዋል፡፡ አሁን የተያዘው ጉዳይም በሕገ መንግስቱና በአዋጅ ቁጥር 188/1992 መሰረት ለሸሪዓ ፍ/ቤቶች በተሰጠው ስልጣን መሰረት እንዲታይ በተጠሪ በኩል የቀረበ ሲሆን አመልካች ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 188/1992 መሰረት በተዘረጋው ስርዓት እንዲታይ ፈቃድ የሰጡ ስለመሆኑም የክርክሩ ሂደት የማያሳይ ቢሆንም አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በመደበኛ ፍርድ ቤት ከፈረሰ በኃላ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚታይበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት ጉዳዩ ሊታይ የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 5(4) እና 6(2) በተደነገገው መሰረት የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ሲመሩ የፈፀሙት የስነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት ካለ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ሐይማኖትን መሰረት በማድረግ የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሚሰጡት ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ይህ ችሎት የመመርመር ስልጣን የለውም፡፡ከዚህ አንጻር የሸሪዓ ፍርድ ቤት አመልካች ያለፍላጎታቸው ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ሊቀጥሉ ይገባል በማለት የደረሰው ድምዳሜ በዚህ ችሎት የሚታይበት አግባብ የሌለ በመሆኑ አመልካች በሕገ መንግስቱ የተከበረላቸውን በፍላጎት ጋብቻ የመመስረት መብት መሰረት አድርገው የሚያቀርቡትን ክርክር አልፈነዋል፡፡

አመልካች በተያዘው ጉዳይ ተፈፀመ የሚሉት የስነ ስርዓት ሕግ ግድፈት በመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ የፍቺ ውሳኔ እያለ ዳግም በሸሪዓ መታየቱ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ በክልሉ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ስልጣን በፌዴራል በአዋጅ ቁጥር 188/1992 ከተዘረጋው የተለየ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ክርክር ያልቀረበ ሲሆን በተጠቃሹ የፌዴራሉ አዋጅ አንቀጽ 4 ስር የተመለከተ ሲሆን አዋጁ ፍርድ ቤቶቹ ስለሚሰሩባቸው ሕጎችም በአንቀጽ 6 ስር ደንግጓል፡፡በዚህ አንቀፅ ስር ከተመለከቱት ሕጎች መካከል ስራ ላይ ያለውና በ1958 ዓ/ም የወጣው የፍትሐ ብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ አንዱ ስለመሆኑ የተጠቃሹ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ከዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም የፍትሐ ብሔር ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ እንዲኖረው በማሰብ ከተደነገጉ በ1958 ዓ/ም በወጣው የስነ ስርዓቱ ድንጋጌዎች አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ እልባት ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍኑ መሆናቸውንና እንዲህ አይነት እልባት አግኝተዋል የሚባሉት ጉዳዮች ደግሞ በፍርድ፣ በብይን፣ በውሣኔ፣ በትእዛዝ፣ ወይም በጊዜያዊ አገልግልት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ መንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ አጠቃልሎ የያዘ መሆኑንና መሰረታዊ አላማውም ክርክር አንድ ቦታ ላይ እንዲቆም ታስቦ በሕግ የተዘረጋ ስርዓት የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካላባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡

ሕጉ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ስለመሆኑም ያስገነዘበባል፡፡ከሕጉ ይዘትና መንፈስ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ለይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው ፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 (1) እና (2) ድንጋጌዎች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2(ለ)) እና 245(2) ድንጋጌ ጋር ተጣምረው ሲታዩ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ሲታይ በቀዳሚው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑ የተከራካሪ ወገኖች አንድነት ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ ከላይ የተመለከቱት መመዘኛዎች በተሟሉበት ሁኔታ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት በመሆኑ ድጋሚ ክስ የሚቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይህ ድንጋጌ ጉዳዮችን በአግባቡ ለመመራትና ተከራካሪ ወገኖች ለአላስፈላጊ ወጪና እንግልት እንዳይዳረጉ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑም ይታመናል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በያሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ከተጠሪ ጋር በነባራቸው የጋብቻ ይፍረስልኝ ጥያቄ ፍርድ ቤቱ በ1952ቱ የፍትሃ ብሔር ሕግ ስለቤተሰብ በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ ጉዳዩን በመመራት ጋብቻው መፍረሱን መወሰኑን በመ/ቁጥር 14/2003 በቀን 04/06/2003 የተሰጠው ውሳኔ ያሳያል፡፡ተጠሪ ይህንኑ ውሳኔ የሚያውቁት መሆኑን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ተጠሪ ጉዳዩን ወደ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመውሰድ አሁን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ይኸ የተጠሪ የክርክር ስልት በአገሪቱ ሰዎች በፈቃዳቸው በሀይማኖት ወይም በባህል ህግ መሠረት የመዳኘት መብት እንዳላቸው በህገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መንግስቱ አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 5 የተረጋገጠውን መብት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሞከሩ መሆናቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ተጠሪ በያሎ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ ታይቶ እልባት ያገኘውን የፍቺ ጉዳይ ከውሳኔ በኋላ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን ያቀረቡት ጥያቄ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 34(5)፣የአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6(2) እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(1) የሚጥስ ነው፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የፋንቲ ረሱ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤትና የአፋር ክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪ ሚስት ናቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የስነ ስርዓት ሕግ ግድፈት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፋንቲ ረሱ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በቁጥር ፋ/ሸ/577/05 በቀን 21/06/2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በአፋር ክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00012/05 ሰኔ 28 ቀን 2005 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ጋብቻ በያሎ ወረዳ መደበኛ ፍርድ ቤት የፈረሰና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5(1) አግባብ ፍርድ የተቋጨ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6(2) መሰረት በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ዳግም የሚዳኝበት ስነ ስርዓት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95995

የካቲት 10 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች:- ወ/ት ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ - ቀረቡ

ተጠሪ:- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአባት ስም ይስተካከልልኝ ጥያቄን የሚመለት ሲሆን የተጀመረውም አመልካች ከአሁን ቀደም በወላጅ አባታቸው ስም ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ተብለው እና በአሳዳጊ አባታቸው ስም ሞሚና ወርቁ ይብሬ ተብለው በሁለት የአባት ስም ይጠሩ እንደነበረ እና አሁን ግን በትክክለኛው አባታቸው ስም መጠራት እንደፈለጉ በመግለጽ ሞሚና ወርቁ ይብሬ ተብለው መጠራታቸው ቀርቶ ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ብቻ ተብለው እንዲጠሩ ይወሰንላቸው ዘንድ በመጠየቅ ለአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ነው፡፡ፍ/ቤቱም አቤቱታውን እና የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካች አሁንም ቢሆን ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ተብለው የሚጠሩ መሆኑን ከሰነድ ማስረጃዎቹ መገንዘብ መቻሉን ገልጾ አመልካች እየተጠሩበት ባለው የአባት ስም እንድጠራ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም በማለት መዝገቡን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 231(1)(ሀ) መሰረት በብይን ዘግቶአል፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡትም ለከተማው የበላይ ፍ/ቤቶች ያቀረቡት ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በሁለት የአባት ስሞች እንደሚጠሩ በሰነድ ማስረጃ በተረጋገጠበት ሁኔታ ያቀረቡት የአባት ስም ይስተካከልልኝ ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የአመልካች ክርክር ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን የክስ አቤቱታ ተቀብለው ክርክሩን መስማት ከመጀመራቸው በፊት በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለጸው ጉዳይ የሚያስከስስ መሆን አለመሆኑን ማርጋገጥ የሚገባቸው መሆኑ እና በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለጸው ጉዳይ የማያስከስስ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የክስ አቤቱታው ተቀባይነት እንደሌለው ገልጸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመለስ የሚገባቸው መሆኑ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 231(1)(ሀ) ስር ተደንግጎ እንደሚገኝ የሚታወቅ ነው፡፡ይሁን እንጂ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጉዳዩ የሚያስከስስ አይደለም ተብሎ ተቀባይነት ከማጣቱ በፊት በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለጸው ጉዳይ በርግጥም የማያስከስስ መሆኑ በአግባቡ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው የአመልካቿ የዳኝነት ጥያቄ ከአሁን ቀደም በወላጅ አባታቸው ስም ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ተብለው እና በአሳዳጊ አባታቸው ስም ሞሚና ወርቁ ይብሬ ተብለው በሁለት የአባት ስም ይጠሩ እንደነበረ እና አሁን ግን በትክክለኛው አባታቸው ስም መጠራት እንደፈለጉ በመግለጽ ሞሚና ወርቁ ይብሬ ተብለው መጠራታቸው ቀርቶ ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ብቻ ተብለው እንዲጠሩ እንዲወሰንላቸው ሲሆን ይጠሩበት በነበሩት ሁለቱም የአባት ስሞች የተዘጋጁ ወይም ከመንግስታዊ ተቋማት የተሰጡ ሰነዶችንም በማስረጃነት ማቅረባቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በመሰረቱ እያንዳንዱ ሰው አንድ የቤተዘመድ ስምና አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞች እና የአባት ስም እንደሚኖረው፣እንዲሁም ለልጁ የአባት ስም የሚሆነው የአባቱ የግል ስም እንደሆነ በፍ.ሕ.ቁ.32(1) እና 36(1) ድንጋጌዎች ተመልክቶአል፡፡አንድ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች በአባቱ ብቻ ሳይሆን በአሳዳጊው ስም ጭምር ሊጠራ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው የሚታወቅ ሲሆን እንዲህ ዓይነቱ ሰው ተገቢ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በአሳዳጊው ስም ጭምር መጠራቱ ቀሪ ሆኖ ከላይ በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ መሰረት በአባቱ ስም ብቻ እንዲጠራ የመወሰን መብት ያለው በመሆኑ ይህንኑ መብቱን በፍርድ ለማረጋገጥ የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡አመልካች ክሱን ያቀረቡት በሚጠሩበት የአሳዳጊያቸው ስም የተሰጡ ሰነዶችን ወደሚጠሩበት አባታቸው ስም በሕግ አግባብ ለማስቀየር እና እነዚሁ ሰነዶች በሚሰጡት መብት ለመገልገል ጭምር መሆኑን ከክርክራቸው ይዘት መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ ሞሚና ወርቁ ይብሬ ተብለው መጠራታቸው ቀርቶ ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ ብቻ ተብለው እንዲጠሩ ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ሊሰጥ የሚችለው ውሳኔ በአመልካቿ መብት ላይ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት አይኖርም ሊባል የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል ክሱ የቀረበለት የአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበለትን የክስ ማመልከቻ እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት የሚገባው ሆኖ እያለ በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለጸው ጉዳይ የሚያስከስስ አይደለም በማለት ሲል የሰጠው እና በከተማው የበላይ ፍ/ቤቶች በትዕዛዝ የፀናው ብይን የክስ ማመልከቻውን እና የፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 231(1)(ሀ) ድንጋጌን ይዘትና ዓላማ በአግባቡ ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. አመልካች ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ የክስ ምክንያት የለውም ሲል መዝገቡን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 231(1)(ሀ) መሰረት በመዘጋት የአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 2908 በ07/12/2005 ዓ.ም. የሰጠው እና በከተማው ፍ/ቤቶች ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ እና በመ.ቁ. 20742 በ27/12/2005 ዓ.ም.እና በመ.ቁ.21123 በ27/02/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1)መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ላይ የተገለጸው ጉዳይ የክስ ምክንያት ያለው መሆኑን ተገንዝቦ ጉዳዩን በማንቀሳቀስ የቀረበለትን የክስ ማመልከቻ እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 341(1)መሰረት ወደ አ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
3. በዚሁ መሰረት ይፈጸም ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 87420

ሚያዚያ 24 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አዳነ ንጉሤ

አመልካች ፡- ወ/ሪት ማህሌት ልዑለቃል ጠበቃ በፈቃዱ ተሊላ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍርድ ቤት ውድቅ በማድረጉና በየደረጃው ያሉ የከተማው አስተዳደር የበላይ ፍርድ ቤቶችም የመ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናታቸው ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 04 ቀን 2004 ዓ/ም ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ቃሉ ፡- ከአባቴ ከአቶ ፈለቀ ደንበልና ከእናቴ ከወ/ሮ ፋንቱ ገብረሕይወት ተወልጄ ማህሌት ፈለቀ በሚል ስም በላፎንቴን መዋዕለ ሕጻናት ትምህርት ቤት እየተጠራሁ ትምህርቴን የጀመርኩ ቢሆንም መደበኛ ትምህርቴ ሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ሲቀጥል በት/ቤቱ መምህር በሆኑት አሳዳጊዬ በአቶ ልዑለቃል ገብረየሱስ ስም በመመዝገብ ተምሬ እስከ ዩኒቬርሲቲ ያጠናቀቅኩ ቢሆንም አሁን ግን በሥጋ ወላጆቼ ስም መጣራት ስለምፈልግ ማህሌት ፈለቀ ደንበል ተብዬ እንዲጠራ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የመ/ደረጃ ፍርድ ቤትም፡- አመልካች አቤቱታቸውን ለማስረዳት ያቀረቡት የሰው ምስክሮች የሰጡትን ቃልና የጽሁፍ ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን በሰጠው ውሳኔ፡- አመልካች በፍ/ህ/ቁ/32(2) መሰረት ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የቤተዘመድ ስም የሚገልጽ ማስረጃ ካለማቅረባቸውም ሌላ የተሰሙት ምስክሮችም ‹‹ ልዑለቃል ገብረየሱስ ›› በሚል ስትጠራበት የነበረው የአሳዳጊ አጎቷ ስም መሆኑን እንጂ የቤተዘመድ ስም አለመሆኑን ስላስረዱና እንዲለወጥላቸው የፈለጉት ስም የቤተዘመድ ስም ስለመሆኑ ተገቢውን ማስረጃ በማቅረብ ስላላስረዱ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ሲል ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህ ውሳኔም ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ እንደተገለጸው በበላይ ፍርድ ቤቶች በመጽናቱ ምክንያት ለዚህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው በዋናነት የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብም ሲጠቃለል፡- አንድ ሰው አንድ የቤተዘመድ ስምና አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞችና የአባት ስም እንደሚኖረው በፍ/ህ/ቁ/32(1) የተደነገገ ሲሆን በቁጥር 33(1) ደግሞ የልጁ የቤተዘመድ ስም ማለት የአባቱ የቤተዘመድ ስም እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ስሙ እንዲለወጥለት በሚጠይቅ ሰው አቤቱታም የአቤቱታ አቅራቢውን የቤተዘመድ ስም ዳኞች ሊለውጡ እንደሚችሉ ቁጥር 42 ተመልክቷል፡፡ በአሁን በአገራችን ባለው ተጨባጭ የስም አሰጣጥ ባህል መሰረትም የቤተዘመድ ስም የሚባል የለም፡፡ የቤተዘመድ ስም ሳይኖርው ሲቀር ደግሞ የቤተዘመድ ስም ነው ተብሎ የሚወሰደው የአባት ስም እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ/ 33 (2) ተደንግጎ እያለና አመልካችም የቤተዘመድ ስሜ በወላጅ አባቴ ስም እንዲሆን እንዲወሰን በቂ የሰውና ጽሁፍ ማስረጃዎችን አቅርቤ ሳለሁ ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም ብለዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን አመልካች በወላጅ አባቴ ስም እንድጠራ ይወሰንልኝ ሲሉ ያቀረቡትን አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመርህ ደረጃ አንድ ሰው የቤተዘመድ ስም(family name)፣አንድ ወይም ከዚያ በላይ የግል ስሞች(first names) እና የአባት ስም(patronymic) እንደሚኖረው በፍ/ህ/ቁ/32(1) የተደነገገ ሲሆን ለልጁ የአባት ስም የሚሆነው ደግሞ የአባቱ የግል ስም እንደሆነ በቁጥር 36 ተመልክቷል፡፡
የልጁን መወለድ መግለጫ ሊሰጥ የሚገባው ሰው ደግሞ ልጁ ከተወለደበት ቀን አንስቶ ባለው ተከታዩ ዘጠና ቀናት ውስጥ ለልጁ የተሰጠውን የግል ስም ልጁ በተወለደበት ቀበሌ(አጥቢያ) ለሚገኘው የክብር መዝገብ ጽህፈት ቤት መግለጫ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በቁጥር 37 ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ የመወለድ ጽሑፍም ከሚያካትታቸው መስፈርቶች አንዱ በአንቀጽ 99(መ) ሥር የተመለከተው የቤተዘመድ ስም ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው የቤተ ዘመድ ስም እንዲለወጥ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑ በቁጥር 42 የተመለከተ ሲሆን በዚህ ረገድ የሚቀርበውን ጥያቄ ዳኞች ተቀብለው ስሙ እንዲለወጥ መወሰን የሚችሉት ስሙን ለመለወጥ በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያረጋግጡ ሲሆን የስሙ መለወጥም በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ላይ አንድም ጉዳት እንዳያስከትል ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባቸው ስለመሆኑም ህጉ ያመላክታል፡፡ እንግዲህ በክብር መዝገብ ሊሰፈር የሚገባው የመወለድ ጽሑፍ ቃል የቤተዘመድ ስምንም የሚያካትት እስከሆነ ድረስ በጊዜው ልደትን፣ጋብቻና ሞት የሚመዘግበው የክብር መዝገብ ሹም ባለመኖሩ በፍ/ህጉ በቁጥር 3361(1) ስር ስለ ክብር መዝገቦች የተዘረዘሩት የፍ/ህግ ቁጥሮች በሥራ ላይ የሚውሉበት ቀን ተወስኖ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ እስከሚወጣ ድረስ ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው የተደነገገ ሲሆን በንዑስ ቁጥር 2 ልደትን፣ጋብቻን እና ሞትን የሚገልጽ ማስረጃ በጊዜው በነበረው አጠራር የአገር ግዛት ሚኒስቴር የመረጣቸው ሰዎች ያዘጋጁትን የታወቁ ጽሁፎች በማቅረብ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ የተመለከተ ቢሆንም በይበልጥ ከዚህ ከሚያከራክረው ጉዳይ ጋር ተያይዞ የቤተዘመድ ስም የግል ስም እንዲሁም የአባት ስም(patronymic) በተደራጀ መልኩ የሚመዘግብ አካል የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በተወለዱበት በ1979 ልደትን በአግባቡ መዝግቦ ማስረጃ የሚሰጥ የክብር መዝገብ ሹም ወይም አካል በሌለበት ሁኔታ አመልካች እንዲለወጥላቸው የጠየቁት ስም የቤተዘመዳቸው ስም ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(ሰነድ) አለቀረቡም በሚል አቤቱታቸውን ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ ያደረጉት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ህጋዊ ምክንያች ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡

ወደ ፍሬ ጉዳዩ ስንመለስ አመልካች ላፎንቴን መዋዕለ ሕጻናት ትምህርት ቤት በ23/12/1991 ዓ/ም በተሰጣቸው የተማሪ ውጤት መግለጫ(ካርድ) ላይ ማህሌት ፈለቀ በሚል ስማቸው መመዝገቡን ፣ሲሴ ገብረማርያም 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ሲማሩ ደግሞ ማህሌት ልዑለቃል ገ/የሱስ በሚል ተመዝግበው መማራቸውን እንዲሁም በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የንግድ ትምህርት ቤት ሲማሩም ማህሌት ልዑለ ቃል ገብረየሱስ ተብለው እንደሚጠሩ በመ/ደ/ፍርድ ቤት ከቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋጠ ሲሆን፤ ቀርበው ከተሰሙት የአመልካች አባት እና እናት ከሆኑት ምስክሮች ቃልም፡- አቶ ልዑለ ቃል ገብረየሱስ የአመልካች እናት ወንድም መሆናቸውን እና በት/ቤቱም መምህር ስለነበሩ አመልካችን ት/ቤቱ እንዲቀበላቸው በሚል የወላጅ አባታቸው ስም ተለውጦ በመምህር ልዑለ ቃል ገብረየሱስ ስም እንዲመዘገብ መደረጉን ካስረዱት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡

እነዚህን ማስረጃዎችን የመመዘንና የመመርመር ሥልጣን ባለው የሥር የመ/ደ/ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ይዘን ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ቀደም ሲል ሲጠሩበት የነበረውን የአባታቸውን ስም በመለወጥ ማህሌት ልዑለቃል ገ/የሱስ ስም የተጠሩት መደበኛ ትምህርታቸውን ለመማር በሚፈልጉበት ትምህርት ቤት ገብተው ለመማር አንዲያስችላቸው በሚል ምክንያት ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቶቹ በተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች መሰረት ጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ሲገባቸው ልዑለ ቃል ገብረ የሱስ የቤተዘመዳቸው ስም ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም ሲሉ ውድቅ ያደረጉት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/2827/2004 በቀን 20/10/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/18469 በቀን 23/12/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የከተማው አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/19021 በቀን 24/03/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካች በወላጅ አባታቸው በአቶ ፈለቀ ደንበል ስም እንዲጠሩ በጠየቁት መሰረት ቀደም ሲል ሲጠሩበት የነበረው ስም ማህሌት ልዑለቃል ገብረየሱስ ተቀይሮ ማህሌት ፈለቀ ደንበል በሚል እንዲጠሩ ወስነናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉምሩክ/ግብር/ታክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79189

መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- የኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ወ/ሕይወት ደምሰው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- ጂ.ኤም.ቲ ኢንዱስትሪያል ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ ሙሉጌታ ገብሩ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር በተጀመረበት ፌ/ከ/ፍ/ቤት ተጠሪ እና አመልካች እንደቅደም ተከተላቸው ከሳሽ እና 2ኛ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የነበሩት ደግሞ የሰበር ክርክሩ አካል ያልሆኑት እንደቅደም ተከተላቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የማረሸ፣ የወገልና የቢላዋ ስ/አ/ህብረት ስራ ማህበር ናቸው፡፡ በ06/07/02 ተሻሽሎ የቀረበው ክስ ይዘትም ከሳሽ በ1ኛ ተከሳሽ ስር ከሚገኘው የፍ/አ/መምሪያ የ3ኛ ተከሳሽ ንብረት የነበረ ድርጅት በጨረታ ገዝቶ መረከቡን፣ ይሁን እንጂ ከ3ኛ ተከሳሽ የሚፈለግ የካፒታል ዕድገት ግብር ካለ እንዲገለፅ ከ1ኛ ተከሳሽ ለተዛወለት ደብዳቤ 2ኛ ተከሳሽ በወቅቱ ምላሽ ባለመስጠቱ፣ 1ኛ ተከሳሽም የ2ኛ ተከሳሽን መልስ ሳይጠብቅ እና ግብሩን ሳይቀንስ ተራፊውን ገንዘብ በሙሉ ለ3ኛ ተከሳሽ በመመለሱና የ3ኛ ተከሳሽ ካርታ ሳይቀርብ ከሳሽ በንብረቱ እንዲበደር ለባንክ ማረጋገጫ በመስጠቱ 3ኛ ተከሳሽ ከግብር ነፃ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃና ካርታ ሳያቀርብ ሙሉ ገንዘብ በመቀበሉ በአጠቃላይ ተከሳሾቹ በአንድነትና በመመሳጠር በፈጸሙት ተግባር ከሳሽ ስሙን አዛውሮ በንብረቱ ለመጠቀምና ብድሩን ለመክፈል አለመቻሉን የሚገልጽ ሆኖ በከሳሽ ላይ የታሰበውን የብድር ወለድ ብር 1,785,539.20 ተከሳሾቹ ለከሳሽ እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት የተጠየቀበት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ክስ የቀረበበትን የወለድ ገንዘብ ለመክፈል ተከሳሾቹ የሕግም ሆነ የውል ግዴታ የለባቸውም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በፍ/ባለመብት አሰፋ አርጋው እና የፍ/ባለዕዳ በነበረው 3ኛ መ/ሰጪ መካከል በነበረው አፈፃፀም ይ/ባይ የ3ኛ መ/ሰጪ ንብረት የነበረውን ድርጅት በ22/03/99 ዓ/ም በብር 6,700,000 በጨረታ ገዝቶ ገንዘቡን አጠቃሎ ገቢ በማድረግ ድርጅቱን እንደተረከበ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድርጅቱን ለመግዛት ይ/ባይ ከወጋገን ባንክ ጎፋ ቅርንጫፍ ብር 4,265,100 ሲበደር የስም ዝውውሩ ወደ ይ/ባይ ሲፈፀም ካርታውን በቀጥታ ለባንኩ እንዲልክ ለ2ኛ መ/ሰጪ በደብዳቤ የሚያሳውቅ መሆኑን በመግለፅ የፍ/አ/መምሪያ ለባንኩ ማረጋገጫ እንደሰጠ፣ ከ3ኛ ተከሳሽ የሚፈለግ የካፒታል ዕድገት ግብር እንዲገለጽለት 1ኛ መ/ሰጪ ለ2ኛ መ/ሰጪ ደብዳቤ የፃፈው በ09/09/99 ዓ/ም ሆኖ 2ኛ መ/ሰጪ ብር 803,997.33 የካፒታል ዕድገት ተቀንሶ እንዲሰጠው በመጠየቅ ምላሽ የሰጠው ከዘጠኝ ወራት በኋላ በ06/06/2000 ዓ/ም እንደሆነ፣ በዚህ ጊዜ መሀል 3ኛ መ/ሰጪ ተራፊውን ገንዘብ በሙሉ እንደወሰደ፣ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 37 መሰረት የካፒታል ዕድገት ግብር የመክፈል ግዴታ የሻጭ በመሆኑ ግብሩ እንደሚፈለግብኝ አላውቅም ነበር በማለት 3ኛ መ/ሰጪ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው 1ኛ መ/ሰጪ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ አይገባውም ወይም ግብሩ ሊኖር እንደሚችል መገመት የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም ባይባልም ግድፈቱ ሚዛን የሚደፋ እንዳልሆነ በፍ/ቤቶች የሚፈፀም ስህተት በይግባኝ ከሚታረም በስተቀር ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው የሚባል ከሆነ በሀገሪቱ ምስቅልቅል የሚፈጠር እንደሆነ፣ 2ኛ ከዘጠኝ ወር በኋላ ግብሩ ገቢ እንዲደረግለት ጠይቆ ገንዘቡ ለ3ኛ መ/ሰጪ መለቀቁ ሊገለጽለት ለፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት እና ለፌዴራል ፀረ ሙስና ኮሚሽን ደብዳቤ መፃፉ የራሱን ስህተት ግምት ውስጥ እንዳያስገባ ስህተቱን ሌሎች መ/ሰጪዎች እንደፈፀሙት በማድረግ መሯሯጡ ተገቢነት እንዳልነበረው በዝርዝር ከገለፀ በኋላ ይ/ባይ ድርጅቱን የተረከበው በመሆኑ መ/ሰጪዎች የባንክ ብድር ወለድ ይክፈሉኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው ይሁን እንጂ ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው ይ/ባይ ግዴታውን ሙሉ በሙሉ ተወጥቶ እያለ ስሙ እስካሁን ያልተዛወረለት በመሆኑ 2ኛ መ/ሰጪ የድርጅቱን ባለቤት ስም ወደ ይ/ባይ ያዘውር የካፒታል ዕድገት ግብሩን ብር 803,997.33 ገንዘቡን ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር 3ኛ መ/ሰጪ ለ2ኛ መ/ሰጪ ገቢ ያድርግ 2ኛ መ/ሰጪም ተከታትሎ ገቢ ያስደርግ ይ/ባይ ለዳኝነት የከፈለውን ገንዘብ 2ኛ እና 3ኛ መ/ሰጪዎች በታሪፉ መሰረት ግማሽ ይክፈሉት፣ ቀሪውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የጠ/ፍ/ቤቱ ይ/ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን በ24/08/04 አዘጋጅቶ ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በጨረታ አሸንፎ የተረከበውን ድርጅት በአመልካችና በሌሎች የስር ተከሳሾች ጥፋት ወደስሙ ማዛወር ባለመቻሉ ከባንክ ለወሰደው ብድር ለብር 1,785,539.20 የወለድ ክፍያ የተዳረገ በመሆኑ ወለዱ ሊተካልኝ ይገባል የሚል ሆኖ አመልካች ስም እንዲያዘውር የካፒታል ዕድገት ግብር ከነወለዱ ከስር 3ኛ መ/ሰጪ ተከታትሎ ገቢ እንዲያደርግ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ከክሱ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የይ/ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በ06/07/02 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻ አሻሽሎ ባቀረበው ክስም ሆነ ለይ/ሰሚው ፍ/ቤት ባቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ የጠየቀው ዳኝነት የወለድ ክፍያ መሆኑን እና በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ዳኝነት ደግሞ የስም ዝውውር እንዲፈፀም መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ በከ/ፍ/ቤትም ሆነ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ዳኝነት ለጠየቀበት የወለድ ክፍያ ዋንኛ መንስኤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሆነው በስር ተከሳሾች (መ/ሰጪዎች) ድርጊት ሳቢያ የስም ዝውውሩ ሊፈፀም አለመቻል መሆኑን በግልጽ ሲከራከርበት የነበረ በመሆኑ የድርጅቱ የስም ዝውውር ጉዳይ የስር ፍ/ቤቶች ዳኝነት ከጠየቁበት ጉዳይ ውጪ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን የስም ዝውውሩን እና የካፒታል እድገት ግብሩን ክፍያ መፈፀም ቅደም ተከተል አስመልክቶ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ከገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንፃር ተገቢ መሆን አለመሆኑ መጤን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ማናቸውም በዚህ አንቀጽ ግብር የተጣለበትን የካፒታል ንብረት ዝውውር የመቀበል ወይም የመመዝገብ ወይም በማናቸውም መንገድ ማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው ሰው ግብሩ መከፈሉን ሳያረጋግጥ ዝውውሩን እንደማይቀበል እንደማይመዘግብ እና እንደማያፀድቅ በአዋጅ በአንቀጽ 37(7) ስር በግልጽና በአስገዳጅነት ተደንግጐ ይገኛል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ግልጽ የሕግ ክልከላ ባለበት ሁኔታ ደግሞ የስም ዝውውሩ ከግብር ክፍያው አስቀድሞ ሊፈጸም የሚችልበት አግባብ ስለማይኖር በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው የአፈፃፀም ቅደም ተከተል ከአዋጁ ድንጋጌ አንፃር መስተካከል የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ከስር 3ኛ መ/ሰጪ የካፒታል እድገት ግብሩን ተከትሎ ገቢ እስኪያስደርግ ድረስ የስም ዝውውሩ መዘግየት ጉዳት ያስከትልብኛል የሚል አቋም ኖሮት ተጠሪው ግብሩን ከፍሎ የስም ዝውውሩን የሚያስፈፅም ሆኖ ከተገኘም የከፈለውን የካፒታል ዕድገት ግብር ከስር 3ኛ መ/ሰጪ የማስተካት መብት እንዲኖረው መደረጉን ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 69181 በ30/06/04 የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ካፒታል እድገት ግብሩን ይ/ሰሚው ፍ/ቤት በውሳኔው መሰረት ከስር 3ኛ መ/ሰጪ ተከታትሎ ገቢ ካስደረገ በኋላ የስም ዝውውሩን ያስፈጽም በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ የጉዳዩ መዘግየት ሊያስከትልበት የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ያስችለው ዘንድ ግብሩን እራሱ ከፍሎ ከስር 3ኛ መ/ሰጪ ለማስተካት የሚፈልግ ከሆነ የካፒታል እድገት ግብሩን ብር 803,997.33 (ስምንት መቶ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት ከ33/100) ከፍሎ የስም ዝውውሩን እንዲያስፈፅም እና የስር 3ኛ መ/ሰጪም ይ/ሰሚው ችሎት በወሰነው መሰረት ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ ለተጠሪ እንዲተካ ወስነናል፡፡
4. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው የወጪና ኪሳራ ውሳኔ አልተነካም፡፡
6. የአፈፃፀም እግዱ ተነስቷል፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 84623

ሰኔ 04 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- 1. ጅ. አግሪ ፖክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

2. አቶ ጌታሁን አስፋው ጠበቃ ገ/እግዛብሔር ሙናቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታርምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ታክስ አለመክፈልን የሚመለከት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቾች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ነው፡፡ተጠሪ በስር አንደኛ ተከሳሽ የሆነው አንደኛው አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ እና በአዋጅ ቁጥር 255/94 አንቀጽ 26/1/ለ/2 አንቀጽ 56/1/2/ እና አንቀጽ 49 የተደነገገውን በመተላለፍ የታክስ ከፋይነት መለያ ቁጥርና የተጨማሪ እሴት ታክስ መለያ ቁጥር ተስጥቶት እያለ ከመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2001 ዓ.ም በሚያከናውነው የንግድ እንቅስቃሴና ሽያጭ በየወሩ ተጨማሪ እሴት ታክስ በመሰበሰብ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ማሳወቅና መክፈል ሲገባው የንግድ ማህበሩ የማስታወቅ ግዴታውን ብቻ በመወጣት የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ በሶስተኛ ወገን በተሰጠ ጥቆማ መነሻ በተደረገው ማጣራት መክፈል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስና አስተዳደራዊ መቀጫ ብር 9 ,065,777.59 /ዘጠኝ ሚሊየን ስልሳ አምስት ሺ ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከሃምሳ ዘጠኝ ሳንቲም/ ያልከፈለ በመሆኑ የወንጀል ክስ ቀርቦበታል የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የአንደኛ ተከሳሽ ዋና ስራ አስኪያጅ የሆነው ሁለተኛው ተከሳሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 26/1/ለ/2/ አንቀጽ 56/1/2 እና አንቀጽ 49 የተደነገገውን በመተላለፍ አንደኛው ተከሳሽ/አንደኛ አመልካች/ የአክስዮን ባለድርሻና ባለንብረት እንዲዚሁም በመመስራቻ ጽሁፍ የተሾመ ስራ አስኪያጅ ሆኖ እያለ ከላይ መጠኑ የተገለፀውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የመክፈል ግዴታውንና ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ የወንጀል ክስ ቀርቦበታል የሚል ይዘት የለው ነው፡፡
3. አንደኛ ተከሳሽ በወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 53 ንዐሱ አንቀጽ 1፣2 እና 3 አንቀጽ 102 እና አንቀጽ 96 የተደነገገውን በመተላለፍ ከዕቃ ገዥዎች በቅድሚ ክፍያ ተቀንሶና ተሰብስቦ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ማስገባት የነበረበትን ብር 374,818. 81 /ሶስት መቶ ሰባ አራት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከሰማኒያ አንድ ሳንቲም/ ያልከፈለ በመሆኑ የወንጀል ክስ ቀርቦበታል
4. ሁለተኛ ተከሳሽ ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የአንደኛው ተከሳሽ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ በቅድመ ክፍያ ቀንሶና ሰብስቦ መክፈል የሚገባውን መጠኑ በሶስተኛው ክስ የተገለጸውን ገንዘብ የልከፈለ በመሆኑ የወንጀል ክስ ቀርቦበታል የሚል ይዘት የላቸው አራት የወንጀል ክሶችን አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው የወንጀሉን ድርጊት አልፈጸምንም ጥፋተኛ አይደለመንም በማለት ተከራክረዋል፡፡
5. ተጠሪ ክሱን የሚያስረዱልን ምስክሮች አሉ በማለት ሶስት ምስክሮችን በማቅረብ አሰምቷል፡፡ የመጀመሪያው ምስክር አንደኛ ተከሳሽ ተጨማሪ እሴት ታክስና የደመወዝ ግብር ገቢ በሕግ አግባብ እያሰበሰበና እየከፈለ አይደለም የሚል ጥቆማ ድርሰን፡፡ የደመወዝ ግብር ገቢ ለክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን እንዲያውቀው አድርገን የተጨማሪ እሴት ታክሱን በኦዲት እንዲጣራ ተደርጎ በአንደኛው የክስ ማመልከቻ መጠኑ የተጠቀሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ አንደኛው ተከሳሽ እንዳልከፈለ ተረጋግጧል ከዚያ በኋላ አንደኛ ተከሳሽ ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አመልክተው ጥያቄው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ሁለት ፐርሰንት ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ እያደረገ ለግብር አስገቢ መስሪያ ቤት ያልከፈለ መሆኑንና በሶስተኛው ክስ መጠኑ የተገለጸውን ገንዘብ እንዳልከፈለ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የግብር ገንዘቡን ለማስከፈል እንቅስቃሴ ቢያደርግም አንደኛ ተከሳሽ ከዳሸን ባንክ ለወሰደው ብድር ባንኩ መደባውን በመሸጡና በባንኩ እዳ የተረፈ ገንዘብ የሌለ መሆኑ ስለተነገረን ሌሎች ንብረቶችን በማፈላለግ ላይ እንገኛለን በማለት እንደመሰከሩ የስር ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልጽ አስፍሮታል፡፡
6. ሁለተኛዋ የተጠሪ ምስክር አንደኛ ተከሣሽ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሣወቂያ ቅጽ መሠረት በየወቅቱ ለተጠሪ ያሣወቀ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ነገር ግን አመልካች ተጨማሪ እሴት ታክስ ከፍሎ አያውቅም፡፡ የድርጅቱን /አንደኛ/ ተከሣሽን ኦዲት ሠርቻለሁ፡፡ ኦዲት ስንሰራ እኛ ድርጅቱ በሣምንት አንድ ቀን ማለትም እሁድ ቀን ምርት እንደማያመርትና በወር አራት ቀናት እንደማያመርት በመቀነስ በወር ሃያ ስድስት ቀናት እንደሚያመርት በመያዝ ሂሣቡን ሠርተናል፡፡ አንደኛ ተከሣሽ በወር ሃያ ስድስት ቀናት የማምረት አቅሙን ተጠቅሞ የሚያመርተውን በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሣወቂያ ቅጽ አላሣወቀም የዊዝ ሆልድግ ታክሱም አለበት በማለት እንደመሰከረች ከስር ፍ/በት ውሣኔ ተረድተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

7. ሶስተኛው የተጠሪ ምስክር የአንደኛ ተከሣሽ ሒሣብ ኦዲት ሲደረግ አንደኛው ተከሣሽ የተሟላ መረጃ ይዞ አለመገኘቱንና የቀን ግምቱን መነሻ በማድረግ የግብሩን መጠን የሰሩ መሆኑን@ የድርጅቱን ትክክለኛ የሽያጭ መጠን ለማወቅ የተሟላ ሪከርድ የሌለ መሆኑንና አስቸጋሪ እንደሆነ፣ የቀን ግምት በመውሰድ በወንጀል ክሱ የተገለፁት የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድመ ተከፋይ ተቀናሽ /ዊዝሆልድግ/ ታክስ የሚፈለግበት መሆኑን በመግለጽ ሪፖርት አቅርበናል የሚል ይዘት ያለው የምስክርነት ቃል እንደሰጠ ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ ይዘት ተረድተናል፡፡
8. አመልካቾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሰር ፍ/ቤት ብይን ሰጥቶ ሁለተኛው ተጠሪ የመከላከያ የምስክርነት ቃሉን የሰጠ ሲሆን፣ በቂ እውቀትና ክህሎት ያለው የሰለጠነ የሰው ኃይል ባለማግኘታችን የምርት ብልሽትና ብክነት ተከስቷል፡፡ ከመጋቢት 1999 እስከ 2001 መብራት ይቆራረጥ የነበረ በመሆኑ ድርጅቱ በአንድ ፈረቃ ብቻ ለማምረት ከመገደዱም በላይ ለቀናትና ለወራት ጭምር የምርት ስራ የቆመበት ሁኔታ ነበር፡፡ ለዙሁም ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የተፃፈልን የጽሑፍ ማስረጃ አለ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከወር ሃያ ስድስት ቀናት በሶስት ፈረቃ እንደሚያመርት በመገመት የተሰራው የኦዲት ስራ እውነታውን የሚያሣይ አይደለም በማለት የምስክርነት ቃሉን የሰጠ ሲሆን ሌሎች የአመልካቾች ሁለት ምስክሮችም ከመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ.ም የመብራት መቋረጥ ምክንያት የምርት ስራ ተቋርጧል የሚሉበትን ሁኔታ በዝርዝር የመሰከሩ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡
9. ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የሃዋሣ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩልና በአመልካቾች በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ አንደኛ ተከሣሽ /አንደኛ አመልካች/ ተጠሪ ባቀረበው በአንደኛውና በሶስተኛው የወንጀል ክሶች ውስጥ የጠቀሣቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ፣ በተጠሪ ክስ የተገለፁትን የወንጀል ድርጊቶች የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ተከሣሽ/ሁለተኛ አመልካች/ ተጠሪ በሁለተኛውና በአራተኛው የወንጀል ክስ የጠቀሣቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በክሱ የተገለፁትን የወንጀል ድርጊቶች የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተ አንደኛው አመልካች በብር አርባ ሺ ብር/ብር 40,000/ መቀጮ እንዲከፍል ሁለተኛው አመልካች ከሐምሌ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በሚታሰብ አምስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ይግባኝ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/1/ መሠረት ሰርዞታል፡፡
10. አመልካቾች ጥቅምት 9 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በወንጀል ክሱ የጠቀሣቸው የአዋጅ ቁጥር 285/94 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 ድንጋጌዎች የታክስ ስወራ ወንጀል የሚፈጸሙ ሰዎችን በወንጀል ኃላፊ እንዲሆንና እንዲቀጣ ለማድረግ ታስበው የታወጁ ናቸው፡፡ አመልካቾች በወቅቱ ለግብር ሰብሣቢው መስሪያ ቤት የማሣወቅ ግዴታችንን የምንወጣ መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስና አቅርቦ ባሰማቸው ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ኦዲተሮች በወቅቱ የነበረውን በኤሌክትሪክ ሀይል እጥረት ምክንያት ምርት የሚቋረጥባቸውን ጊዜዎች ሣያገናዝቡ ድርጅቱ በሶስት ፈረቃ ሃያ ስድስት ቀናት እንደሚያመርት የህሊና ግምት በመያዝ የሰሩት ሒሣብና ያቀረቡት ሪፖርት በግምት ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከተና የተመረተውን እርግጠኛ ምርትና የተደረገውን ግብይት መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ@ በዚህ ማስረጃ መነሻ የወንጀል ክስ መቅረቡም ሆነ ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትም ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በዊዝሆልዲንግ ታክስ ጥሰት ቢፈፀም እንኳን የወንጀል ተጠያቂነትና ቅጣት የሚያስከትል መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 286/94 ያልተደነገገ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ሶስተኛውና አራተኛው የወንጀል ክስ የሕጋዊነት መርህን የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር እንዲያሰናብተን በማለት አመልክተዋል፡፡

11. ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 285/94፣ በአዋጁ ቁጥር 286/94 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/94 የተጣለባቸው የተጨማሪ እሴት ታክስና የዊዝሆልዲንግ ታክስ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች የማሣወቅ ግዴታቸውን መወጣታቸው መክፈል የሚገባቸው ታክስ ባለመክፈላቸው የሚደርስባቸውን የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስቀርላቸው አይደለም፡፡ ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ግብር በግምት እንዲወሰን የሚፈቅድለት የሕግ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ ስለዚህ በግምት የተወሰነው የግብር ውሣኔ በወንጀል ጉዳይ እንደማስረጃ መቅረቡን በመቃወም አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ በአጠቃላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 16 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

12. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

13. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስና ክሱን የወንጀል መሠረታዊ ይዘት ያለው መሆኑን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 285/96 ድንጋጌዎች በመተላለፍ በሚፈፀው ወንጀሎች የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በመተላለፍ የሚፈፀው በመሆኑ ክሱ የሚመሠረተው የሚታየውና በይግባኝ የሚቀርበው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት እንደሆነ በአንቀጽ 48 የሚደነገግ ሲሆን የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 94 ተመሣሣይ ይዘት ያለው እንደሆነ እንረዳለን ይህም በመሆኑ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 111 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 112 መሠረት የተዘጋጀን አመልካቾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሕግ የሞራልና የግዙፍ ተግባር ሁኔታ በተሟላበት ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49፣ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በተለይ የሕግ ጥሰት በመፈፀም ታክስ ያለመክፈል ወንጀል የፈፀመ መሆኑን የሚያሣይ የወንጀል ክስ ይዘትና ባህሪ ያለው ሊሆን ይገባዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

14. የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 ድንጋጌዎች ሕግን በመጣስ ተክስን አለመክፈል ወይም በእንግሊዘኛው “Tax Evasion” የሚል ርእስ ያላቸው ሲሆን ይዘታቸው ተመሣሣይነት ያለው ነው፡፡ የድንጋጌዎቹ ይዘት ቃል በቃል ሲነበብ ሕግን በመጣስ የሰበሰበውን ግብር ያላሣወቀ ወይም የሚፈለግበትን ግብር ያልከፈለ ወይም መንግስትን ለማጭበርበር በማሠብ የማይገባውን ተመላሽ ታክስ የጠየቀ ማናቸውም ሰው ወንጀል አንደፈፀም ይቆጠራል በመሆኑም በዚህ አዋጅ ክፍል አሥራ አንድ መሠረት ከሚጣልበት መቀጮ በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ሲረጋገጥ ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት ይቀጣል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

15. አመልካቾች ግብር የማሣወቅ ግዴታቸውን የፈፀሙ መሆኑን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ባቀረባቸው የወንጀል ክሶች በግልጽ ያሰፈረው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአንደኛ አመልካችን ሂሣብ ለማጣራት የተመደቡት የተጠሪ ምስክሮች አመልካቾችን በየወቅቱ በሂሣብ በግብር ማሣወቂያ ቅጽችን በመሙላት ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ያሣውቁ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 በተደነገገው መሠረት ግብር የማሣወቅ ግዴታቸውን በመተላለፍ ታክስ ባለመክፈል የፈፀሙት ግዙፍ የወንጀል ተግባር የሌለ መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስና ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

16. አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 285/96 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 በተደነገገው መሰረት መንግስትን ለማጭበርበር በማሰብ የማይገባቸውን የታክስ ተመላሽ በመጠየቅ ግዙፍ የወንጀል ተግባር የፈፀሙ መሆናቸውን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረባቸው የወንጀል ክሶች አይገልጽም፡፡ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረቧቸው ምስክሮችም አመልካቾች የማይገባቸውን የታክስ ተመላሽ በመጠየቅ መንግስትን የማጭበርበር ስራ ስለመስራታቸው የሰጡት የምሰክርነት ቃል የለም፡፡

17. ተጠሪ አመልካቾች የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽመዋል በማለት ክስ ያቀረበው አመልካቾች ከመጋቢት ወር 1999ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2001ዓ.ም ድረስ በግምት የተወሰነባቸውን ብር 9,065,577.59 ተጨማሪ እሴት ታክስ ከነመቀጫውና ብር 374,818.81 ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ በወቅቱ አልከፈሉም በማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት አመልካቾች አንደኛ አመልካች ያመረተውን የምርት መጠንና ያከናወኑትን ግብይት ከግብይቱ የሰበሰቡትን ገቢ በየወቅቱ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ያቀርቡ የነበረ መሆኑ በተጠሪ ክስና ማስረጃ የተገለፀና የተረጋገጠ በሆነበት ሁኔታና አመልካቾች በየወቅቱ ባቀረቡት የግብር ማሳወቂያ ቅጽ በመጀመሪያ አንደኛ ተከሣሽ ዕቃዎችን ሲያስገባ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ እና አንደኛ ተከሣሽ የፋብሪካ የምርት ውጤቱን ሲሸጥ የሰበሰበው ተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናንሰው ባላንሱ ዜሮ መሆኑንና ለመንግስት የሚከፍሉት የግብር ገንዘብ የሌለ መሆኑን በየወሩ መጨረሻ ሲያሳውቁ መኖራቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ አዲተሮች ሂሣቡን አዲት ሲያደርጉ ፋብሪካው በሙሉ አቅሙ ማለትም በሶስት ፈረቃ በወር ሃያ ስድስት ቀናት ሊያመርት ይችላል የሚለውን የህሊና ግምት በመያዝ የወሰኑት ግብር ባለመክፈላቸው በወንጀል የቀረበባቸው ክስ እና የተሰጠባቸው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 162 መስፈርት የማያሟላ መሆኑን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

18. በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 ግብር አለመክፈል የወንጀል ተግባር ተደርጎ የተደነገገው ግብር ከፋዩ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ባሳወቀና ባልከፈለው ግብርና ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ግብር ከፋዩ የያዛቸውን የሂሣብ ሰነዶችና ማስረጃዎች በተለያየ ምክንያት በመጣል በግምት በወሰነው ግብር መካከል ልዩነት ሲፈጠር ግብር ከፋዩን በወንጀል ለመጠየቅና ለመቅጣት በማሰብ አይደለም፡፡ ይልቁንም መክፈል የሚገባውን የግብር ገንዘብ ላለመክፈል በማሰብና ግብር አስገቢው መስሪያ ቤትም ንብረቶቸን በመያዝና በመሸጥ የግብር ገንዘቡን ገቢ እንዳያደርግ ለማድረግና ግብር ከመክፈል ኃላፊነቱ ለማምለጥ ንብረቶቹን የማሸሸና የመሰወር እና ሌሎች ተመሣሣይነት ያላቸውን ህገወጥ ተግባራት በመፈፀም ግብር ያልከፈለ ግብር ከፋይን ተጠያቂ ለማድረግ እንደሆነ ይኸ ሰበር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 53544 በቀን 11/10/02 ዓ.ም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

19. ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካቾች በየወቅቱ ግብር የመስጠት ግዴታቸውን ሲወጡ ቆይተዋል፡ አመልካቾች በየወቅቱ ባቀረቡት የሂሣብ ሪፖርት ለመንግስት የሚከፈል ገንዘብ የሌለ መሆኑን ያሳወቁ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት በወንጀል ክሱ የተጠቀሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የዊዝ ሆልዲንግ ታክስ ገንዘብ ከአንደኛው አመልካች የሚፈለግ መሆኑን በመወሰን የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ከሰጣቸው በኋላ አመልካቾች በህጉ መሰረት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካቾች በግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የተወሰነውን ግብር ያልከፈሉት የአንደኛው አመልካች ንብረት በዳሽን ባንክ ዕዳ ምክንያት በመሸጡና የባንክ ዕዳ ተከፍሎ ቀሪ ገንዘብ ባለመኖሩ መሆኑን አንደኛው የተጠሪ ምስክር በስር ፍ/ቤት ባስመዘገበው የምሰክርነት ቃል እንደተገለፀ ተረድተናል፡፡

20. ማናቸውም ሰው የፍታብሄር ዕዳ ለመክፈል ባለመቻሉ ምክንያት በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ እንደማይቀጣ በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 11 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 49 እና የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 ድንጋጌዎችም ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 13(2) እና ከላይ ከጠቀስነው ዓለም አቀፍ ድንጋጌ ጋር በማጣጣም ሁኔታ መተርጎምና ተፈፃሚ መሆን ያለባቸው መሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 53544 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ፣ አመልካቾች ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት በግምት የወሰነውን የግብር ገንዘብ ለመክፈል ባለመቻላቸው ምክንያት በወንጀል ተጠያቂና ጥፋተኛ ሊባሉ የሚችሉበት የህግ መሰረት የለም፡፡ በመሆኑም በህጉ የተደነገጉት መስፈርቶች ሳይሟሉና በወንጀል ህግ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው የሃሳብና የግዙፍ ተግባር ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካችን ህግን በመተላለፍ ግብር ያለመክፈል ወንጀል ፈፅመዋል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 11768 የሰጠው ፍርድ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57769 የሠጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(1) ሀ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ አንደኛው አመልካች ብር 40,000 (አርባ ሺ ብር) መቀጮ ከመክፈል በነፃ ተሰናብቷል፡፡ አንደኛው አመልካች የመቀጮውን ከፍሎ ከሆነ ይመለስለት፡፡
3. የበታች ፍርድ ቤቶች የሠጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ ሁለተኛው አመልካች ከእስር እንዲለቀቅ በክፍሉ ማረሚያ ቤት መፍቻ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86388

ሰኔ 17 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አሕመድ

አመልካች፡- አቶ ባዘዘው ይሁን የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የአ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በሕግ የፀና ንግድ ፍቃድ ሣይኖረው መነገድ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መንግስት በአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ጃዊ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በተጠሪ የቀረበበት ክስም አመልካች የንግድ ምዝገባ ፈቃድ አዋጅ ቁ. 686/2002 አንቀጽ 60/1/ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ሚያዚያ 22 ቀን 2003 ዓ.ም ከለሊቱ በግምት 11፡30 ሲሆን ፈንደቀ ከተማ ልዩ ስሙ መናኸሪያ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ አመልካች ባልታደሰ የንግድ ፈቀድ ሁለት ማደበሪያ የፍየልና የበግ ቆዳ በሕገ-ወጥ ማመላለሻ መኪና በኪስ ውስጥ ይዞ ሊወጣ ሲል የትያዘ ስለሆነ በፈፀመው የፀና የንግድ ፈቃድ ሣይኖረው መስራት ወንጀል ተከሷል የሚል ሲሆን አመልካችም ቀርቦ ክሱ ከተነበበለት በኃላ ቆዳውን ይገዬ ተገኝቻለሁ ነገር ግን ሕጋዊ ፈቃድ ስላለኝ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ዐ/ሕግም እንደ ክሱ ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም የቀረበውን የሰው ምስክር ሰምቶ ጉዳዩን ከማስረጃ ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኃላ አመልካች እንደ ክሱ ባልታደሰና በማያገለግል ንግድ ፈቃድ ተጠቅሞ የበግ እና የፍየል ቆዳ ሲነግድ በመያዙ የተመሠከረበት በመሆኑ ክሱን ሊከላከል ይገባል በማለት ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ አመልካቹም በበኩሉ ክሱን ለመከላከል አቅርቦ ያሰማቸው የመከላከያ ምስክሮች አመልካች ንግድ ፈቃድ የነበረው መሆኑ እንጂ ንግድ ፈቀዱ የታደሰ ይሁን አይሁን ለይተው የማያቁ መሆናቸውን በመግለጽ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመጨረሻም ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመረመር በኃላ አመልካች ወንጀሉን አለመፈፀሙን በመከለከያ ማስረጃ ማስተባበል ባለመቻሉ በተከሰሰበት የሕገ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት ከወሰነ በኃላ ቅጣትን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት ሃሣብ ተቀብሎ ከመረመር በኃላ በ7 ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 150,000 የገንዘብ መቀጮ ይቀጣ ሲል ውሣኔ ሰጥቷል እንዲሁም ቆዳው የተሸጠበት ገንዘብም ብር 2,432 ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

አመልካችም በተሰጠው ውሣኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለአዊ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኙን ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/1/ መሠረት ተቀባይነት አላገኘም በመቀጠልም አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርቦ ችሎቱም ግራ ቀኙ ቀርበው እንዲሰሙ ካደረገ በኃላ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ በማጽናት ቅጣቱን በተመለከተ ግን በ3 ዓመት ተኩል ጽኑ እስራት እና 5000 ብር መቀጮ በማሻሻል ወስኗል፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ ላይ የሕግ ግድፈት መፈፀሙን በመግለጽ እስከ አሁን የታሰርኩት ራሱ ከበቂ በላይ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ከጥፋቱና ቅጣቱ በነፃ አንድሰናበት ይወሰንልኝ የሚል ነው አቤቱታውም ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ ያቀረበ ሲሆን አመልካችም የመ/መልሱን ሰጠቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክር ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች የፀና የንግድ ሥራ ፈቀድ ሣይኖረው በቆዳና ሌጦ ንግድ ሥራ ተሰማርቶ ተገኝቷል በሚል የተከሰሰበትን ድርጊት መፈፀሙን ሣይክድ ነገር ግን ድርጊቱን ሊፈጽም የቻለው የተጠቀሰውን የንግድ ሥራ ሊያሰራ የሚችል የንግድ ሥራ ፈቀድ ያለው በመሆኑ ጥፋተኝነት እንደሌለበት በመግለጽ የተከራከረ መሆኑን ተረድተናል ሆኖም ግን አመልካች አለኝ የሚለው የቆዳና ሌጦ ንግድ ሥራ ፈቃድ በአዋጅ ቁ. 686/2002 አንቀጽ 2/10/ እና 36 ድንጋጌዎች ይዘት አኳያ በሕግ በተቀመጠው የግዜ ገደብ ውስጥ ያለቅጣትም ሆነ በቅጣት የታደሰ ባለመሆኑ /የማያገልግል ፈቃድ በመሆኑ/ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ነው ለማለት የሚቻል አይሆንም በሕጉ አግባብ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሣይኖረው በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የተገኘ ሰው ደግሞ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ እንደሌለው ተቆጥሮ በወንጀል ኃላፊ ሆኖ እንደሚቀጣ በአዋጅ አንቀጽ 60/1/ ስር ተደንግጓል በመሆኑም በዚህ ረገድ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘንም፡፡

በሌላ በኩል ቅጣትን አስመልክቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የቀጣት ውሣኔም ቢሆን አመልካች ተላልፏል ተብሎ ጥፋተኛ የተባለበት የሕግ ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከ7 ዓመት እስከ 15 ዓመት ጽኑ እስራት እና እንዲሁም በብር 150,000 እስከ 300,000 የገንዘብ መቀጫ ቢሆንም ችሎቱ የአመልካቹን የግል ሁኔታ የቀድሞ ባህሪውን የወንጀሉን አፈፃፀም እና እንዲሁም የወንጀሉን ክብደት እና ቅለት በማገናዘብ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሣሰን መመሪያ አኳያ በማስላት በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ቅጣት በማሻሻል በ3 ዓመት ተኩል 3½/ ጽኑ እስራት እና በብር 5,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑ የሚነቀፍ እና መሠረታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው የሰበር አቤቱታም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ውሣኔ

1. በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔም ሆነ ቅጣት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/2//ለ//2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔ መጽናቱን አመልካች በሚገኝበት ማረሚያ ቤት በኩል ይገለጽለት፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86597

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- በትግራይ ገቢዎች ልማት ባለስልጣን ዐ/ህግ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ በርሀ ረዳ ኪዳኑ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ሕጎች ጋር ተያይዞ የተነሳውን የወንጀል ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በዞኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ ከአክሱም ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ሳይፈቀድላቸው የቅዱስ ገብርኤል ማተሚያ ቤት መሳሪያ መደብር ፈቃድ አውጥተው ሲሰሩ ሃያ አንድ ፓድ ደረሰኝ አትመዋል፣ በሁለት ኮፒ የሚታተም ደረሰኝ በአንድ ገፅ 100 ፓድ አትመው ደግሞ ተራፊ የሌለው አድርገው አትመዋል በዚህ አድራጎታቸው መንግስት ሊያገኘው ይገባ የነበረ ገቢ አሳጥተዋል፣ እንደዚሁም ማህተም ብቻ በማድረግ ብር 1,908.00 ያለ ቫት ክፍያ ተጠቅመዋል በማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅ 609/2001 አንቀጽ 19፣ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 22(1)(2)፣ 50(ሐ) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ተላልፈዋል በሚል የቀረበባቸው መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪ ክደው ተከራክረው አቃቤ ህግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ተጠሪ እንዲከላከሉ ተደርጎም የመከላከያ ማስረጃዎች የተሰሙላቸው ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪን መከላከያ ማስረጃዎች ቃል ውድቅ አድርጎ ተጠሪን በአቃቤ ህግ ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ በማድረግ በስድስት ወር እስራትና በብር 15,000.00 (አስራ አምስት ሺ ብር) እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሙሉ በሙሉ የፀና ሲሆን ጉዳዩ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ግን ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ህትመቱን ሰራ የተባለው አካል በሕጉ ድርጅት የሚለውን መስፈርት የማያሟላና ተጠሪም የግል ባለሃብት እንጂ በድርጅት መሪነት የሚሸፈኑ አይደሉም የሚሉ ምክንያቶችን ይዞ የስር ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነትና ቅጣት ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ የድርጅቱ ባለቤትና ስራ አስኪያጅ ሆነው እያለና ሕጉ ደግሞ ማንኛውንም ሰው ተጠያቂ እንደሚያደርግ ደንግጎ ባለበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባልቀረበለት የፍሬ ነገር ክርክርና ከሕጉ ይዘትና መንፈስ ውጪ ተጠሪ በወንጀል አይጠየቁም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መወሰኑ ያለግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ተጠሪ የወንጀል ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ክስ የቀረበበት አካል ድርጅት መሆኑን ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የሚያሳዩት ክስ የቀረበው በድርጅት ያለመሆኑን፣ አመልካች የግል ባለሃብት መሆናቸውን ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ለ)) እና በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 64(2(ሐ)) እንዲሁም በክልሉ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 49/1994 አንቀጽ 16 እና 17 ስለ ሰበር ችሎት ዳኝነት ስልጣን ከሚደነግጉት ስርዓት ውጪ ነው፡፡ ተጠሪ የማተሚያ ቤቱ ንግድ ፈቃድ በራሳቸው መሆኑና ግብርም በስማቸው የሚገብሩ መሆኑን ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን በሕጉ የተሰጣቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያረጋገጧቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

ይህንኑ ይዘን ወደ ሕጉ ስንመጣም ተጠሪ በስራ አስኪያጅነት የሚመሩትና የግል ሃብታቸው በሆነው የንግድ ድርጅት በአመልካች በክሱ የተመለከቱትን ድርጊቶች ድርጅቱ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳያገኝ ተገቢ ያልሆኑ ፓዶችን ማሳተሙን፣ ብር 1908 ያለ ቫት ደረሰኝ መጠቀሙ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ በመርህ ደረጃ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 2(11) እና 56(1) እንዲሁም በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 19(50(ሐ)) ድንጋጌዎች መሰረት ጥፋተኛ የሚባሉ መሆኑ በህጉ ተደንግጓል፡፡

ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከቱትን ልዩ ሁኔታዎች በማስረዳት ከተጠያቂነት ነፃ ለመሆን ይጠቅመኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር በሌላ ቦታ የነበሩ መሆኑን ያሳያሉ ያሉት የመከላከያ ማስረጃ ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ በሌላ ቦታ የነበሩ መሆኑ ከወንጀል ተጠያቂነት የሚያድናቸው አይደለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 3/ለ/ በተደነገገው መሰረት ማንኛውም በጎ አሳቢ ሰው ሊያደርገው የሚችለውን ጥንቃቄ ያደረጉና ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ድርጅቱን በመምራት ኃላፊነታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያለማቅረባቸውን ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች ከሰጡት የውሣኔ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3/1/ሀ/ መሰረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ተመዝግበውና የድርጅቱ ባለሃብትና ስራአስኪያጅ ሁነው ያልተፈቀደ ደረሰኝ በማተምና ብር 1908 ያለ ቫት የተጠቀሙ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ስራ አስኪያጅ ሳይሆኑ የግል ባለሃብት ስለሆኑ የወንጀል ተጠያቂነት የለባቸውም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሻሩ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 2/11/፣3/1/ሀ/፣56 እንዲሁም ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 2፣19/50/ሐ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ባላገናዘበ ሁኔታ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 52605 ታህሳስ 23 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/2/ለ-1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17403፣ በቀን 24/7/2004 ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 51850 ሚያዝያ 26 ቀን 2004 ዓ.ም የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/2/ለ-2/ መሰረት ጸንቷል፡፡

3. ተጠሪ በጉዳዩ ላይ የታሰሩበት ጊዜ የሚታሰብላቸው ሆኖ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነባቸውን የስድስት ወር ቀላል እስራትና የብር 15,000.00 የአክሱም ማረሚያ ቤት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ታዟል፡፡ የዞኑ ፖሊስም ተጠሪን ይዞ ለማረሚያ ቤቱ እንዲያስረክብ ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 82061

መስከረም 20 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አብዱልቀድር ሁሴን ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዐ/ሕግ ሜሮን ግርማ ቀረቡ

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰራዊ የሀግ ሥህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ይታይልኝ በማለት የቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በተጠሪ የተወሰነው የገቢ ግብርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብርን የሚመለከት ነው፡፡በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው አመልካች ይግባኝ ባይ፣ተጠሪ መልስ ሰጭ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ ያቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ ነው፡፡ ይግባኝ ባይ (አመልካች) የተዘጋጁ ልብሶችና ቦርሳዎችን በችርቻሮ የመሸጥ የንግድ ሥራ የተሰማራሁ ግብር ከፋይ ነኝ፡፡ የይግባኝ ባይ ድርጅት ካለፈው ዓመት ያሳየው እድገት የለም፡፤ መልስ ሰጭ ገቢዬንና የንግድ ሥራዬን በአግባቡ ሳያጠናና በቂ ማስረጃ ሳይኖረው ባለፈው ዓመት የከፈልኩትን ገቢ ግብር እጥፍ እንድከፍል ወስኖ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶኛል፡፡ እንደዚሁም ይግባኝ ባይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሳልሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶኛል፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ባይ ከሕግ ውጭ የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ ባለፈው ዓመት በከፈልኩት መሰረት በቁርጥ እንድከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ መልስ ሰጭ በበኩሉ የይግባኝ ባይ የቀን ገቢ በኮሚቴ ተጠንቷል፡፤ ገማች ኮሚቴ ባጠናው የጥናት ውጤት መሰረት ገቢ ግብሩ ተስተካክሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው፡፡ የይግባኝ ባይ የቀን ገቢ ከብር 1700 (አንድ ሺ ሰባት መቶ) በላይ መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሰረት ከሀምሌ ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት በመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚያዚያ ወር 2003 እስከ ሰኔ 2003 ዓ.ም መክፈል ያለበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር እንዲከፍል ውሳኔው ማስታወቂያ በነሀሴ ወር 2003ዓ.ም እንዲደርሰው የተደረገው በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ይግባኝ ባይ መልስ ሰጭ በይግባኝ ባይ ላይ ገቢ ግብር ጨምሮ የወሰነው በገማች ኮሚቴ የይግባኝ ባይን የቀን ገቢ በማስጠናት በመሆኑ ተገቢ ነው፡፡ ለይግባኝ ባይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የደረሰው የቀን ገቢው ብር 1700(አንድ ሺ ሰባት መቶ) በመሆኑ ነው፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ስህተት የለበትም፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኛ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል ፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ገቢ ግብር በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶ፣የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ ሽሯል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ሰበር አቤቱታ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የከተማው ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

3. አመልካች 2/11/2004 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች የቁርጥ ግብር ከፋይ ነኝ፡፡ ተጠሪ ገቢ ግብር አስተካክሎ መወሰን የሚችለው በየ አምስት ዓመቱ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሥከረም ወር 2002 ዓ.ም በሰጠው ግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ቅር ተሰኝቸ ይግባኝ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርቤ ተሻሽሎ ተወስኖልኛል፡፡ ተጠሪ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ግብሩን አሻሽሎ ውሳኔ ከሰጠ ከሥምንት ወራት በኋላ በእጥፍ አሳድጎ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አመልካች የምሰራው የችርቻሮ ንግድ ስራ ሆኖ እያለ ጅምላ አከፋፋይ ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ አመልካች ተጨማሪ አሴት ታክስ እንድመዘገብ የተወሰነ መሆኑን ሳያሳውቅ በህጉ መሰረት አሳውቀኝ የሶስት ወር ተጨማሪ አሴት ታክስ እድከፍል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በ04/06/2005 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ስለ ገቢ ግብር ውሳኔና ተጠሪ አመልካች የሶስት ወር ተጨማሪ አሴት ታክስ እንድከፍል የሰጠው ውሳኔ ማስታወቂያ ተገቢ ነው በማለት የሰጠው ትርጉምና ውሳኔ የሕጉን መንፈስ የተከተለ ነው የሚል ይዘት ያለው መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በ14/06/2005ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር ክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የገለፅነው ሲሆን እኛም የአዲስ አበባ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካች ላይ ገቢ ግብር ጨምሮ የወሰነው በመጋቢት ወር 2003 ዓ/ም በገማች ኮሚቴ የአመልካችን የቀን ገቢ በማስጠናት መሆኑ እና የቀን ገቢው ብር 1700(አንድ ሺ ሰባት መቶ ብር) መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባለው የግብር ይግባኝ ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉባኤ ተረጋግጧል፡፡ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ፍሬ ነገርና ማስረጃ ምዘና የሚመለከት በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

6. የአመልካች የንግድ እንቅስቃሴ በዓመት ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 መሰረት በፈቃዱ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ሲገባው እንዳልተመዘገበና አመልካች የቀን ገቢ ብር 1700 (አንድ ሺ ሰባት መቶ ብር) እንደሆነ ተጠሪ በገማች ኮሚቴዎች በኩል ባደረገው ጥናት ተረጋግጧል ። ይህም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3(1) ከነሀሴ 1 ቀን 2002 እስከ ነሃሴ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ማመልከቻ አቅርቦ መመዝገብ የነበረበት መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3(1) ከነሀሴ 1 ቀን 2002 እስከ ነሃሴ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ማመልከቻ አቅርቦ መመዝገብ የነበረበት ሰው ካልተመዘገበ ፣ ለመመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብ ከሚጀምርበት የሂሳብ ጊዜ አንስቶ ታክስ ከፋይ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3(3) ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ከሚቀጥለው የሂሳብ ጊዜ ማለትም መስከረም 2003 ዓ.ም ጀምሮ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ተጠሪ ከመጋቢት ወር 2003 ዓ/ም በገማች ኮሚቴ የአመልካችን የቀን ገቢ በማስጠናት መሆኑ እና የቀን ገቢው ብር 1700(አንድ ሺ ሰባት መቶ ብር) መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ከሚያዚያ 2003 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2003 ዓ.ም አመልካች ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ . በመሆኑም ተጠሪ የሰጠው ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 3(1) ፣ አንቀጽ 3(3) እና አንቀጽ 16(1) /ለ/ መሰረት ያደረገ በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ ፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት ማጽናታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86672

መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ መቅደስ ብሩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ በቀለ ተሰማ ቀረቡ

2. ዝናሽ ዘየደ በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ባለሁኑ ተጠሪዎች እና በሐናን በላይ ላይ በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡

ተጠሪዎች የተከሰሱት በሁለት ምድብ በተከፈለ ክስ ሲሆን አንደኛው ክስ ባለሁኑ 1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበ ሁኖ ይዘቱም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 50(ለ) እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 22(11) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የንግድ ፈቃድ ቁጥር 06/64213/01/00000040 መሰረት በራስቶራንት ንግድ ላይ ተሰማርቶ ከሕዳር 16 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ በመሆኑ በቁጥር 3313860032 በሆነ ተመዝግቦ እያለ የካቲት 11 ቀን 2004 ዓ/ም ከቀኑ በግምት 6፡05 ሰዓት በአዳማ ከተማ ቀበሌ 05 ክልል ውስጥ በሚገኘው የቤት ቁጥር 840 በሆነ የኬሮድ ባርና ሬስቶራንት ውስጥ ይታገስ አሸናፊ፣ግርማ ሚኮሬና ኮንስታብል ኢብራሂም አማን የተባሉ ሰዎች ሁለት ቅቅል ምግብና እና ሶስት ለስላሳ በአሁኗ ሁለተኛ ተጠሪና በስር ሶስተኛ ተከሳሽ በነበረ ሐናን በላይ በክል ብር 67.00 የሆነ ዋጋ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መሸጣቸውን ዘርዝሮ ተጠሪው የግል ባለንብረት በመሆናቸው የወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው በማለት ክስ ማቅረቡን የሚያሳይ ሲሆን 2ኛው ክስ ባሁኗ 2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበ ሁኖ ዝርዝር ይዘቱም ተከሳሾቹ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 55 እና በማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 609/01 አንቀጽ 50(ለ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ እንዲሁም ለአግልግሎቱ ተጠቃሚዎች የብር 67.00 ሽያጭ ደረሰኝ መቁረጥ ሲገባት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሽያጩ እንዲፈፅም በማድረጓ 1ኛውን ተጠሪ የመርዳት ወንጀል ፈፅማለች የሚል ነው፡፡ 3ኛው ክስ በስር ሶስተኛ ተከሳሽ በነበረችው ሐናን በላይ ላይ የቀረበ ሁኖ በ1ኛው ክስ በተመለከተው ጊዜና ቦታ እንዲሁም ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች ደረሰኝ ቆርጣ መስጠት ሲገባት ይህንኑ ባለመፈፀሟ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 55 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 50(ለ) ስር የተመለከተውን ተላልፋለች የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች የወንጀል አፈፃፀሙን ክደው ተከራክረው ዐ/ሕግ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን በማቅረብ አስምቷል፡፡ከዚህም በኋላ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎ መከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአቃቤ ህግ ምስክሮች ከፍለው የነበረው ገንዘብ ደረሰኝ አልተሰጠንም በሚል ምክንያት መልሰው መውሳዳቸው ሽያጭ ያለመፈፀሙን እንደሚያሳይ፣ሽያጭ ተፈጽሟል ከተባለም 1ኛ ተጠሪ የቫት ደረሽኝ አሳትሞ ለተገልጋዮች እየቆረጠ የሚሰጥ መሆኑ መረጋጡን፣ተጠሪው የሽያጭ ማሽኑን በ25/05/04 ዓ/ም ገዝተው በ01/06/2004 ዓ/ም የተረከቡ መሆኑንና ወንጀሉ የተፈጸመበት ጊዜ በ11/06/2004 ዓ/ም አንፃር ሲታይ ስልጠና እስከሚያገኙ ድረስ ጊዜው አጭር መሆኑን፣ክሱ ለአቃቤ ሕግ ምስክሮች ደረሰኝ አልተሰጠም የሚል ሁኖ በማስረጃ የተረጋገጠው ግን ምስክሮቹ በእጅ የተፃፈ ደረሰኝ ተሰጥቷቸው በማሽን የተፃፈ ደረሰኝ ካልሆነ አልንቀበልም ማለታው መሆኑን፣ደረሰኞቹ በተጨማሪ ታክስ ምጣኔው ላይ ልዩነት የሌላባቸው መሆኑንና በእጅ የሚፃፈው ደረሰኝም በተገቢው አካል ጥያቄ ቀርቦ 1ኛው ተጠሪ ያሳተሙትና ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ ተጠሪዎች በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው የአቃቤ ሕግን ማስረጃዎች ጥርጣሬ ውስጥ ከተዋል በማለት ተጠሪዎችን በነፃ አሰናብቷዋል፡፡

በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርደ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በስር ፍርድ ቤቶች የተሠጠው የተጠሪዎች ነፃ መለቀቅ ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ሲሆን የአመልካች መስሪያ ቤት አቃቤ ህግ ጥር 03 ቀን 2005 ዓ/ም የተፃፈ የሠበር ማመልከቻ ስላቀረቡ ነው፡፡ የሠበር አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪዎች ሽያጩ አልተከናወነም በሚል ነፃ ተብለው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክር በፅሑፍ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክክርክር ለሠበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ፈፅመዋል ተብለው የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ለማስረዳት ዐ/ሕግ ያቀረቧቸው ሁለት ምስክሮች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ኬሮድ ምግብ ቤት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ውጪ ሽያጭ መፈፀሙ የሚያሳይ ሪፖርት ደርሷቸው መስሪያ ቤቱ ወደ ቦታው በክስ በተገለጸው ጊዜ የላካቸው መሆኑን፣ወደ ቦታው ደርሰውም ሶስት ምግብና ሶስት ለስላሳ በማዘዝ ከተጠቀሙ በኋላ ብር 100.00 ሂሳብ ከስር 3ኛ ተከሳሽ ለነበረችው አስተናጋጅ ሰጥተው እሷም ለአሁኗ 2ኛ ተጠሪ ከሰጠች በኋላ መልስ ብር 33.00 ያለደረሰኝ የመለሰችላቸው መሆኑን፣1ኛ ተጠሪም በጊዜው በቦታው ላይ እንዳልነበርና በኋላ ከመጣ በኋላ ምስክሮቹ ሲጠይቁትም ለጠየቀን እንሰጣለን ብሎ እንደመለሰላቸውና ከዚህ በኋላ ተከሳሾችን በቁጥጥር ስር ያዋሏቸው መሆኑን ነው፡፡ተጠሪዎች ያቀረቧቸው መከላከያ ምስክሮች ደግሞ ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ምግብ ቤት በአስተናጋጅነት የሚሰጡ ሁነው በክሱ በተጠቀሰው ጊዜ ሶስት ሰዎች ወደ ምግብ ቤቱ መጥተው ምግብና ለስላሳ አዝዘው ከተጠቀሙ በኋላ የማሽን ደረሰኝ 3ኛ ተከሰሽ የሆነችውን አስተናጋጅ አምጪልኝ በማለት ሲጠይቋት ማሽኑ ስራ ስላልጀመረ በእጅ የሚሞላ ደረሰኝ አመጣላችኋለሁ ስትል በእጅ የሚፃፍ ደረሰኝ አንፈልግም፣የማሽን ነው እንጂ በማለት እምቢ ብለው ሄደው ከሶስት ደቂቃ በኋላ ተመልሰው በመምጣት ለአገልግሎቱ የከፈሉትን ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

100.00 መልስ መውሰዳቸውን፣ቤቱ በእጅ የተጻፈ ደረሰኝ እንደሚጠቀምና ይህንኑ ደረሰኝ ምስክሮቹ ወስደው ቤቱን ያሸጉና ስራው የተከለከለ መሆኑን ሲሆን የሰነድ ማስረጃዎች ደግሞ የተጨማሪ እሴት ታክስ አስመልክቶ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በህዳር 30 ቀን 2004 ዓ/ም ማስታወቂያ መውጣቱን፣1ኛው ተጠሪ በ08/05/2004 እና 09/06/2004 ዓ/ም ለተፈፀሙ ሽያጮችም ደረሰኝ መቆረጣቸውን፣ተጠሪው ማሽኑን በ25/05/2004 ዓ/ም ገዝተው በ01/06/2004 ዓ/ም መረከባቸውን እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ፍቃድ ከምስራቅ ሸዋ ዞን ገቢዎች ፅ/ቤት አግኝተው ደረሰኙን አሳትመው ወደ ስራው የገቡ መሆኑ በሰውና በሰነድ ማስረጃዎች መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሯል፡፡

እንግዲህ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን አጣርቶና ማስረጃን መዝኖ የደረሰባቸው ድምዳሜዎች ከላይ የተጠቀሱት ሲሆን ተመሳሳይ ስልጣን ያለው የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤትን የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ መቀበሉን የክርክሩ ሂደት ያስገነዝባል፡፡በመሆኑም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ስለሌለው ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ስለመረጋገጣቸው የተጠቀሱትን ነጥቦች እንዳሉ የሚቀበላቸው ይሆናል፡፡እዚህን ይዘን ወደ ሕጉ ስንመጣም ተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ የሚገዛው ራሱን በቻለ ሕግ ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 285/1994 እና ከማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 609/2001 ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡እነዚህ ሕጎች የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ተግባራትን ዘርዝረው ማስቀመጣቸውን ድንጋጌዎቹ ያሳያሉ፡፡አዋጆቹን የማስፈፀም ስልጣንና ተግባርም የፌዴራል መንግስት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 99 እና ይህንኑ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ 03 ቀን 1994 ዓ/ም ባደረጉት ሁለተኛ መደበኛ የጋራ ስብሰባ መወሰኑ የሚታወቅ ነው፡፡በመሆኑም የአዋጆችን የአፈጻጸም የመቆጣጠር ስልጣንን መሰረት አድርጎ የተጠሪዎች ጠበቃ ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡የተጨማሪ እሴት ሽያጭ ተከናወነ የሚባልበትን አግባብም በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 11(1)(2)፣ 22(1) እና (3) በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው በግልጽ ተመልክቷል፡፡የአዋጁ አንቀጽ 11(1) በመርህ ደረጃ ሽያጭ ተከናወነ የሚባለው ለግብይቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሲሰጥ ነው በሚል የሚያስቀምጥ ሲሆን በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ደግሞ እቃዎቹ ለተረካቢው ዝግጁ ሁነው መቀመጣቸው፣የእቃዎቹ ርክርብ ሽያጭ ወይም ማስተላለፍ መፈፀም ወይም የአገልግሎት መሰጠት፣እንዲሁም የእቃዎችን ርክክብ ማጓጓዝን የሚያካትት ሲሆን የእቃዎችን ማጓጓዝ ሲጀመር ሽያጭ ተከናወነ ብሎ ለመደምደም የሚቻል መሆኑን በልዩ ሁኔታነት ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች በግልጽ መረዳት የሚቻለው ሽያጭ ተከናወነ ለማለት ለተከናወነው ግብይት ሂሳብ መክፈሉ ወይም አለመክፈሉ በቅድመ ሁኔታ የተቀመጠ ሳይሆን ሕጉ ትኩረት የሚያደረገው እቃዎቹ ለተረካቢው ዝግጁ ሁነው በተቀመጡ ጊዜ አገልግሎቶች በሚሰጡበት እና የመሳሳሉት ተግባራት መፈጸማቸው ላይ ነው፡፡በመሆኑም እነዚህ ተግባራት በሚፈጽሙበት ጊዜ የተጨማሪ እሴት ደረሰኝ ባይቆረጥም እንኳን ሽያጩ እንደተከናወነ ሕጉ እንደሚቆጥር የድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ማእቀፍ ሽያጭ ተከናወነ የሚባልባቸውን ሁኔታዎችን ለይቶ አስቀምጦ እያለ በዚህ ረገድ ልዩ ሕግ የደነገገው ነገር እንደሌለ በመቁጠር በፍትሐ ብሔር ሕጉ ስለሽያጭ የሚገዙትን ድንጋጌዎች ለጉዳዩ ተፈጻሚ ማድረጉ አግባብነት ያልነበረው ሁኖ አግኝተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀጥሎ የተመለከትነው ተጠሪዎች ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ናቸው ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ውጤቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) በግልፅ ደንግጓል፡፡እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎችን ነፃ በማድረግ ሊወሰን የቻለው ሽያጩ አልተከናወነም በሚል ብቸኛ ምክንያት ሳይሆን የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በእጅ የተፃፈ የቫት ደረሰኝ አንቀበልም ማለታቸው በተጠሪዎች የመከላከያ ማስረጃዎች መረጋገጡን ተቀብሎ 1ኛው ተጠሪ ለቫት ከተመዘገቡበት፣ማሽኑን ከገዙበትና ከተረከቡት ጊዜ አንፃር ሲታይ ድርጊቱ ተፈጸመ የተባለበት ጊዜ አጭርና ለማሽኑ አጠቃቀም ስልጠና የሚያስፈልግ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ ጭምር ነው፡፡ከዚህም መረዳት የሚቻለው ማሽኑ እያለ ሕጋዊነቱ በተረጋገጠው ደረሰሠኝ በእጅ ተፅፎ ለአቃቤ ሕግ ምስክሮች የሸያጭ ደረሰኙ ሊሰጥ የነበረ መሆኑ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች መረጋገጡን ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች በወቅቱ ሽያጩን ያለቫት ደረሠኝ ለማከናወን ፍላጎትና ዝግጁነት የነበራቸውና የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም የሓሳብ ክፍላቸው ተሟልቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡በእርግጥ ለቫት የተመዘገበና ማሽኑን የተረከበ የቫት ተመዝጋቢ ሽያጩን ማከናወን ያለበት በማሽኑ ደረሰኝ መሆኑ በሚንስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 139/1999 የተደነገጉ ሲሆን ማሽኑ ጋር ተገቢውን ስልጠና መውሰድም ግዴታ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ማሽኑ ገብቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከማሽኑ አሰራር ጋር ባለመታዋወቅ በእጅ በተፃፈ ሕጋዊ ደረሰኝ ሽያጩን ያከናወነ ሰው በአቃቤ ሕግ በኩል በቀረበው ክስ አቀራረብ አይነት በወንጀል እንዲጠየቅ ማድረግ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (2)፣58 (3) ስር የተመለከቱትን መርሆዎች የሚጥስ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል አይደለም፡፡በመዝገቡ ከተያዘውና በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠው የጉዳዩ ልዩ ባህርይ ስንነሳ ተጠሪዎች የወንጀል መስራት ሓሳብ ነበራቸው ለማለት የሚያስችል የፍሬ ነገር ምክንያት አላገኘንም፡፡ሊጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ያረጋገጧቸው ነጥቦች በዚህ ችሎት የሚለወጡበትን አግባብ ስላላገኘንና በዚህ ረገድ የቀረቡት የአመልካች የቅሬታ ነጥቦች የማስረጃ ምዘና እንጂ የመሰረታዊ ሕግ ስህተትን መመዘኛ የማያሟሉ ሁነው ስለአገኘናቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎችን በነፃ በማሰናበት የሰጡት የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13453 መስከረም 10 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 152242 ህዳር 27 ቀን 2005 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ተጠሪዎች በነፃ እንዲሰናበቱ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 89640

መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን-የሐረር መቆጣጠሪያ ጣቢያ- ዐ/ሕግ ጌቱ ቀዎች ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሰይፈዲን አብዱልቃድር ጠበቃ ሻምበል ተሾመ ደምሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉምሩክ ሕግንና አፈጻጸሙን መሰረት ባላደረገ መንገድ መኪናው ተይዞ ለቆየበት ጊዜ ይገኝ የነበረውን ገቢ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ የመሰረቱት ክስ ይዘቱ ባጭሩ፡- ኮድ 3-00700 ሐረ ላንድ ክሩዘር የጭነት መኪና የሆነ ተሽከርካሪያቸውን በቆመበትና ምንም የኮንትሮባንድ ድርጊት ሳይፈፅም ጥቅምት 01 ቀን 2002 ዓ/ም አመልካች ከሕግ ውጪ መያዙንና ሊለቅ ባለመቻሉ በፍርድ ቤት ክስ መስርተው መኪናው የተያዘው ከሕግ ውጪ መሆኑ ተረጋግጦላቸው መኪናው እንዲለቀቅ እስከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተወሰነላቸውና መኪናውን መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ/ም በፍርድ ኃይል መረከባቸውን፣በዚህ ጊዜ ውስጥ ሊያገኙ ይችሉ የነበረው የቀን ገቢ ብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) ሁኖ በድምሩ የሁለት አመት ከስድስት ወራት ብር 450,000.00 (አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ገቢ የቀረባቸው መሆኑን ገልጸው ይህንኑ የተቋረጠባቸውን ገቢ አመልካች ከተለያዩ ወጪና ኪሳራ ጋር ጭምር እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርቧል፡፡በክርክሩም ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባው መሆኑና መኪናው የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት በመሆኑ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያከናወነው ተግባር መሆኑን፣የመኪናው ገቢም ቢሆን በተጠሪ የተገለጸው ሳይሆን ከክፍሉ ገቢዎች ባለስልጣን የተሰጠው ማስረጃ የሚያረጋግጠው ብር 3000.00 በአመት የሚያገኘው መሆኑንና በዚህ ሂሳብ ሲሰላም መኪናው ለቆመበት ጊዜ ከብር 10,500.00 (አስር ሺህ አምስት መቶ ብር) በላይ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪን ምስክሮች ከሰማ በኋላ አመልካች አለኝ የሚለውና ከክፍሉ የገቢዎች ባለስልጣን የመኪናው አመታዊ የተጣራ ገቢ ብር 3000.00 ስለመሆኑ የሚገልጸውን ማስረጃ ውድቅ ከአደረገ በኋላ የተጠሪ ምስክሮች የሰጡትን ቃል መሰረት በማድረግ ገቢው በቀን ብር 500.00 መሆኑን ተቀብሎና መኪናው ስራ ሊሰራባቸው የማይችላቸውን የእሁድ ቀናት ቀንሶ በጠቅላላው ብር 349,500.00 (ሶስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ብር) ተጠሪ የተቋረጠባቸው መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ይህንኑ ገንዘብ በታሪፉ መሰረት ከዳኝነት ገንዘብና ከ10% የጠበቃ አበል ጋር አመልካች እንዲከፍላቸው ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለሐረሪ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ሚያዚያ 10 ቀን 2005 ዓ/ም በጻፉት አስር ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ይዘቱም ባጭሩ፡- የተጠሪ ክሱ የተመሰረተው በሕጉ አግባብ የውክልና ስልጣን ለተጠሪ ጠበቃ ሳይሰጥ መሆኑን፣አመልካች በሕጉ አግባብ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የፈፀመው ድርጊት ስለመሆኑ ገልፆ ከመከራከሩም በተጨማሪ መኪናው የሚያስገኘው አመታዊ ገቢን የሚያሳየው ማስረጃ ከሚመለከተው የገቢዎች ባለስልጣን ቀርቦ እያለ ማስረጃው ውድቅ መደረጉና የተጠሪ የሠው ምስክሮች ቃል ተቀባይነት አግኝቶ በቀን ብር 500.00 መሰረት ተደርጎ ካሳው መሰላቱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090 እና 2011 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ መሆኑን ዝርዝረው ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተድርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ የአመልካች የሰነድ ማስረጃ ውድቅ ተደርጎ በተጠሪ የሰው ምስክሮች ብቻ ካሳው መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም ? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ተሽከርካሪ ያላግባብ በአመልካች ተይዟል በሚል ክስ አቅርበው አመልካች ከሕግ አግባብ ውጪ የያዘው መሆኑ በፍርድ ተረጋግጦ መኪናው እንዲለቀቅላቸውና መኪናው ተይዞ ለቆመበት ጊዜ ገቢ እንዲከፈላቸው ተጠሪ ወደፊት ክስ አቅርበው የመጠየቅ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው መኪናው እንዲለቀቅላቸው እና የጉዳት ኪሳራውን የመጠየቅ መብታቸው ተጠብቆ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሰጥቶ ውሳኔው እስከዚህ ሰበር ችሎት ደርሶ የጸና መሆኑን የሰ/መ/ቁጥር 75913 የሚያረጋግጠው ጉዳይ መሆኑን፣አመልካች አሁን አጥብቆ የሚከራከረው የጉዳት ካሳ መጠን የተሰላበት አግባብ ከሕግ ውጪ የተጠሪ የሠው ምስክሮች ቃል ብቻ መሰረት ተደርጎና ከሚመለከተው አካል የቀረበው የአመልካች የሰነድ ማስረጃ ግን ውድቅ ተደርጎ ስለመሆኑ ዘርዝሮ መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካችን ለጉዳቱ ሀላፊ ነው ያሉት ቀድሞ በፍርድ ያለቀውን ጉዳይ መሰረት በማድረግ በመሆኑና አመልካችም የተጠሪን ክስ ነጣጥሎ በማቅረብ ላይ ግልጽ ቅሬታ ያላቀረበበት ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብም በጭብጥነት ያልተያዘ በመሆኑ የኃላፊነት ጭብጥ በዚህ ችሎት አሁን የሚታይበትን አግባብ አላገኘንም፡፡በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ነጥብ የጉዳት ካሳ መጠኑ የተወሰነበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መንገድ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ስለሆነ ይህንኑ ጭብጥ ግንዛቤ ውስጥ አስገብተን ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመለክተናል፡፡በመሰረቱ ለደረሰው ጉዳት አላፊ መሆኑ በህግ የታወቀ ሰው የጉዳት ኪሳራ መክፈል ያለበት ሲሆን ጉዳት የደረሰበት ሰው የሚካሰውም ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ኪሳራ በመክፈል እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ/2090(1) ተመልክቷል፡፡ የኪሳራው ልክም ሀላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ በመመዛዘን መሆን እንደሚገባ የፍ/ህ/ቁጥር 2091 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በሚቀርቡለት ማስረጃዎች የጉዳቱን መጠንና ሊከፈል የሚገባውን ካሳ መጠን አመዛዝኖ በህጉ መሰረት መወሰን የሚገባው ስለሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141፣2152 እና 2153 ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው ሲሆን ጉዳቱ ያስከተለውን ኪሳራ በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነም በፍ/ህ/ቁ/2102 በተመለከተው አግባብ በርትዕ ለመወሰን እንደሚቻል ሕጉ ያስቀምጣል፡፡ እንዲህ ሲደረግ ግን ለጉዳዩ የቀረቡት ማስረጃዎች ለጉዳዩ አግባብነት፣ጥንካሬና ክብደት ያላቸው መሆኑን በቅድሚያ ማረጋግጥን የግድ ይላል፡፡በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ማስረጃዎቹ በሕጉ አግባብ ከቀረቡለት ደግሞ ማስረጃዎችን የማይቀበልበትን ሕጋዊ ምክንት በግልጽ ማስፈር ያለበት መሆኑን የሚሰጠው ምክንያትም ሕጋዊ መሰረት ያለው መሆን ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 138፣ 180 (1) እና ሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ከሚደነገጉት የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የጉዳት ካሳ ግምቱን የወሰነው በተጠሪ በኩል የቀረቡትን የሰው ምስክሮች ቃል ተቀብሎ በአንጻሩ ግን አመልካች በሕጉ አግባብ በመኪናው የአመታዊ ገቢ ግብር ተጠሪ እንደሚከፍሉበት ያሳያል የተባለውን የሰነድ ማስረጃ በማለፍ ነው፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበዉ ይህ ማስረጃ በበታች ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያጣበት ሕጋዊ ምክንያት ግን በግልጽ በውሳኔው ላይ አልሰፈረም፡፡በአንድ የመንግስት ባለስልጣን የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ ደግሞ የማስረጃነት ዋጋ ሳይሰጠው የሚታለፍበት አግባብ በሕጉ መሠረት ተቃውሞ ቀርቦበት ዋጋ የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2010 እና 2011 እንዲሁም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 140 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ጉዳዩ በመኪና ገቢ የግብር መጠን የሚጣልበትን አግባብ የሚያስረዳ ሙያዊ ምስክርነት ማስቀርብን የሚያስፈልግ መሆኑንም የክርክሩ ባህርይ ያስገነዝባል፡፡እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 ድንጋጌ አኳያ ከሚመለከተው አካል የሙያ ምስክር አስቀርቦ ከተጠሪ ምስክሮች ቃል፣አመልካች አለኝ ከሚለው የሰነድ ማስረጃ ይዘት ጋር ማመዛዘንና ዳኝነት መስጠትን የግድ የሚል ነው፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎችን ትክክለኛና ሕጋዊ ያለመሆናቸውን በተገቢው መንገድ ሳያረጋግጥ ለተጠሪ ምስክሮች ቃል ብቻ ክብደት ሰጥቶ የጉዳት ካሳ መጠኑን መወሰኑ የማስረጃ አቀባበል መርህንና የጉዳት ካሳ መጠን መወሰን ያለበት ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሁኖ ተመዛዝኖ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090 እና 2091 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን መርህ የሚጥስ ሁኖ አግኝተናል፡፡በሌላ በኩል የተጠሪ መኪና ለበርካታ ወራት ያለስራ በአመልካች ሕገ ወጥ ተግባር መቆሙ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ የተቋረጠባቸው ገቢ የለም ብሎ ለማለት የሚቻልበት አግባብም የለም፡፡ስለሆነም ለካሳው መጠን አወሳሰን ይረዳ ዘንድ በተጨማሪነት ሊጣሩ የሚገባቸው ፍሬ ነገሮች ያሉ ሁነው አግኝተናል፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. አመልካች የተጠሪን መኪና አመታዊ የተጣራና ግብር የሚከፈልበትን የገቢ መጠን ያሳያል በማለት ያቀረበው ሰነድ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2010 መሰረት ተቃውሞ የሚቀርብበትና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2011 አግባብ የማስረጃነት ዋጋ የማይሰጥበት ሕጋዊ ምክንያት አለ? ወይስ የለም?
2. የተጠሪ መኪና አመታዊ የተጣራ ገቢ ብር 3000.00 ተብሎ የተወሰነበት አግባብ ሕጋዊ መሰረት አለው? ወይስ የለውም? ፤የሚመለከተው የክፍሉ የገቢዎች ባለስልጣን የተጠሪን አይነት መኪና ላይ ግብር የሚያስከፍልበት አሰራር ምንድው?
3. አመልካች የተጠሪ የመኪና የተጣራ አመታዊ ገቢ በማለት የገለፀው ብር 3000.00 የሆነው ተጠሪ በሕጉ አግባብ ባሳወቁት የገቢ መጠን ነው? ወይስ ባለስልጣኑ መስሪያ ቤት በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተገቢውን ማጣራትና አሰራር ተከትሎ በሰጠው ውሳኔ ነው? የሚሉትና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የፍሬ ነገር ነጥቦች በተገቢው መንገድ በፍርድ ቤቱ ሊቀርቡ በሚገባቸው ማስረጃዎች ሊጣሩ የሚገባቸው ሁነው አግኝተናል፡፡

እነዚህ ፍሬ ነገሮች በሕጉ አግባብ ሳይጣሩና ሳይሟሉና የጉዳት ካሳ መጠኑ መወሰን የጉዳት ካሳ አወሳሰን መሰረታዊ ዓላማና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን የሚጥስ መሆኑን ተረድተናል፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ ስላላገኘነው ውሳኔው በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወሰንናልወ፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 09627 በቀን 22/04/2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 02400 መጋቢት 05 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች በተጠሪው መኪና ላይ በፈፀመው ሕገ ወጥ ተግባር ለደረሰው ጉዳት ሀላፊ ነው በሚል የሠጡት የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ብለናል፤ጸንቷል፡፡
3. የጉዳት ካሳ መጠኑን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ ግን በተገቢው መንገድ ለጉዳዩ አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ሳይጣራ የተሠጠ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡በመሆኑም የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 09627 ቀጥሎ በፍርደ ሐተታው ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 የተጠቀሱትን ነጥቦችንና ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ነጥቦችን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች ከሚመለከተው የክፍሉ የገቢዎች ባለስልጣን እንዲቀርቡ በማድረግና የባለሙያ አስተያየት ሁሉ በመስማት በጉዳዩ ላይ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገወ ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 85979

መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የሐረር (ደ/ሳ) ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- ወ/ሮ ማንያህልሻል አበራ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው በሐረር ክልል የከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የመቃብር ቤት ግምት ይከፈለኝ በማለት የቀረበን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሐረሪ ሕዝብ ክልል የከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በሐረር ከተማ በሚገኘው ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስትያን ግቢ ውስጥ የመቃብር ቤት ለመስራት እንዲፈቀድልኝ ጠይቄ የመቃብር ቤት እንድሰራ ስለተፈቀደልኝ ለእኔና ለዘመዶቼ የቀብር ስርዓት የሚፈፀምበት ቤት የመቃብር ቤት በብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ሰርቻለሁ፡፡ ሆኖም ቤተክርስቲያኗ ኃይማኖትሽን የለወጥሽ በመሆኑ በመቃብር ቤቱ ለመጠቀም አትችይም በማለት በግልፅ ደብዳቤ አሳውቆኛል፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኃይማኖት ተከታይ በነበርኩበት ጊዜ የሰራሁትን የመቃብር ቤት ያለምንም ካሳና ግምት ለመልቀቅ የውል ግዴታ ያለገባሁ በመሆኑ የመቃብር ቤቱን ለመስራት ያወጣሁትን ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) እንድከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል መቃወሚያው በብይን ታልፏል፡፡ አመልካች ተጠሪ የመቃብር ቤት ሰርታለች፡፡ ተጠሪ በሰራችው የመቃብር ቤት የዘመዶቿ ስርዓተ ቀብር ተፈፅሞ የዘመዶቿ አጽም አርፎበት ይገኛል፡፡ ተጠሪ (ከሳሽ) ኃይማኖቷን የለወጠች በመሆኑ በመቃብር ቤቱ የመጠቀም መብት የላትም፡፡ የመቃብር ቤት ግምት የመክፈል ያደረግነው ውል የሌለ በመሆኑ ክሱ የእምነቱን መሰረታዊ ቀኖናና አሰራር የሚፃረር በመሆኑ የመቃብር ቤት ግምት የመክፈል ኃላፊነት የለብንም፡፡ ተጠሪ የሰራችው ቤት ግምትም ከብር 13,000 (አስራ ሶስት ሺህ ብር) የሚበልጥ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራቀ ኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ተጠሪ የሰራችውን የቤት ግምት የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት በመቃብር ቤቱ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ መጋቢት 26 ቀን 2003 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ መቃብር ቤቱ በባለሙያ ብር 50,153.40 (ሃምሳ ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከአርባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳንቲም) የተገመተ በመሆኑ አመልካች ይህንን የመቃብር ቤቱን ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 ሰርዞታል፡፡

አመልካች ታህሳስ 25 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በነበረችበት ወቅት ስሞት ስርዓተ ቀብሬ መፈፀሚያ ይሆናል በማለት መቃብር ቤት እንድትሰራ ፈቃድ ጠይቃ ተፈቅዶላታል፡፡ ተጠሪ በመቃብር ቤቱ ስርዓተ ቀብሯ ሊፈፀም የሚችለው የእምነቱ ተከታይ ሆና ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ ነው፡፡ ተጠሪ ኃይማኖቷን ከቀየረች በቤተክርስቲያኑ የመቃብር ሥፍራ የሌላ እምነት ተከታይ የሆነ ሰው የማይቀበር በመሆኑ በመቃብር ቤቱ ስርዓት ቀብሯ ሊፈፀም አይችልም፡፡ አመልካች ይህንን ለተጠሪ ማሳወቁ ተገቢ ነው፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ ቦታው የመቃብር ቦታና የእምነቱ ጋር የተያያዘ መሆኑን ሳያገናዝብ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ሕ/ቁጥር 1179 በመጥቀስ የመቃብር ቤት ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ የካቲት 4 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ መልስ የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ከሰራችው የመቃብር ቤት ውስጥ የቀብር ስርዓት ያልተፈፀመበት ቦታና ክፍል ግምት አመልካች እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠው 26-1-2003 ዓ/ም ነው፡፡ ይህ ውሳኔ አመልካች ይግባኝ ብሎ አላሻረም፡፡ ስለዚህ ቤቱ ከተገመተ በኋላ ያቀረበው ይግባኝ በአፈፃፀም እንደቀረበ ይግባኝ መታየት ያለበት ስለሆነ መዝገቡ ይዘጋልኝ፡፡ ተጠሪ የገነባቸውን የመቃብር ቤት እንዳትጠቀም አመልካች የከለከለ በመሆኑ፣ የቤቱን ግምት እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ሰበሰር በጽሁፍና በቃል ባደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ተጠሪ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሰራችውን የመቃብር ቤት ግምት እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይም አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት ተጠሪ አመልካችን የሰበር አቤቱታ በመቃወም ያቀረበውን ክርክር ህጋዊነት ተመልክተናል፡፡ አመልካች የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ አመልካች ተጠሪ የሰራተኛውን የመቃብር ቤት ግምት የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብሎ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ የስር ፍ/ቤት በዚያው መዝገብ ንብረቱን አስገምቶ አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው የመቃብር ቤት ግምት ብር 50,153.40 (ሃምሳ ሺህ አንድ መቶ አምሳ ሶስት ብር ከሰርባ ሳንቲም ነው) በማለት መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በማጠቃለል ይግባኝ ማቅረቡና ይግባኙ ውድቅ ሲሆንበት የሰበር አቤቱታ ማቅረቡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 327 ንዑስ አንቀጽ 3 የመጀመሪያውን ፓራግራፍ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ተጠሪ ይግባኙ የአፈፃፀም ይግባኝ ነው በማለት ያቀረበ ቢሆንም የከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካች ለክሱ ኃላፊ መሆኑንና ለተጠሪ መክፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን የወሰነው የተጠሪንና የአመልካችን ክስ ባስተናገደበት የመዝገብ ቁጥር 06816 መሆኑን ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ፍርዱን ለማስፈፀም ያስከፈተችው የአፈፃፀም መዝገብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥሩ 20166 መሆኑን ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር ተረድተናል። ስለሆነም ተጠሪ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት ያቀረበውን መቃወሚያ አልተቀበልነውም።

2. ዋናውን ጭብጥ በተመለከተ፣ ተጠሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሃይማኖት ተከታይ በነበረችበት ወቅት የኃይማኖቱን መሰረታዊ ቀኖና ስርዓት መሰረት በማድረግ በምትሞትበት ጊዜ የእሷና የዘመዶቿ አስክሬን የሚያርፍበትና ሥርዓተ ቀብር የሚፈፀምበት የመቃብር ቤት በአመልካች ግቢ ውስጥ ለመስራት እንዲፈቀድላት ጠይቃ የመቃብር ቤት እንድትገነባ ልዩ ፈቃድ በመስጠት የተጠሪን “privilege” ጠብቆላታል። ተጠሪም በአመልካች በተሰጣት ልዩ ፈቃድ መሰረት መቃብር ቤቱን በአመልካች ግቢ ውስጥ በራሷ ወጭ የሰራች መሆኑ ግራ ቀኙ የሚተማመኑበት ፍሬ ጉዳይ ነው። እንደዚሁም ተጠሪ በሰራችው የመቃብር ቤት ውስጥ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኃይማኖት ተከታይ የሆኑ የተጠሪ ዘመዶች አስክሬን የተቀበረ መሆኑና አሁንም በመቃብር ቤቱ ውስጥ የተጠሪ ዘመዶች አፅም ያረፈበት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም።

አመልካችና ተጠሪን የሚያከራክረው ጭብጥ በአሁኑ ወቅት የተለየ ኃይመኖት ተከታይ የሆነችው ተጠሪ በአመልካች በተሰጣት ልዩ ፈቃድ መሰረት በሰራችው የመቃብር ቤት ስትሞት የመቀበር መብት ይኖራታል ወይስ አይኖራትም? ተጠሪ በመቃብር ቤቱ የመቀበር መብት የላትም ከተባለ አመልካች የመቃብር ቤቱን ግምት ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ነጥብ ነው።

ማንኛውም ሰው የማሰብ የሕሊናና የኃይማኖት ነፃነት ያለው መሆኑንና ይህም መብት የመረጠውን ኃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ የመቀበል ኃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎቹ ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን እንደሚያካትት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል። እንደዚሁም ማንኛውው ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል የማይቻል መሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 3 በግልፅ ተደንግጓል። ይህ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠው የእምነትና የኃይማኖት ነፃነት፣ ማናቸውም ሰው በሚያምንበት እምነትና በሚከተለው ኃይማኖት ቀኖና ስርዓት መሰረት በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በኋላ መንፈሳዊ ፀጋ አገኝባቸዋለሁ የሚላቸውን የበጎ አድራጎት ተግባራቶችንና ሌሎች ስራዎችን የማከናወን ነፃነትን ጭምር የሚመለከት ነው።

በዚህ መሰረት ተጠሪ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኃይማኖት ተከታይ በነበረችበት ወቅት በአመልካች ግቢ ውስጥ የመቃብር ቤት እንድትገነባ ልዩ ፈቃድ የተሰጣት እሷም የመቃብር ቤቱን በግል ወጭዋ የገነባችው አመልካች የሚያረምደውን ኃይማኖታዊ ቀኖና ሥርዓት በማመንና ተገዥ በመሆን እንደነበር ከግራ ቀኙ ክርክር ለመረዳት ይቻላል። አመልካች የመቃብር ቤቱን እንድሰራ ልዩ ፈቃድና ክብር የተሰጣት የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ተከታይ አማኝ ስለነበረች ነው። አመልካች ትከተለው የነበረው የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ኃይማኖታዊ ቀኖና ሥርዓት የመለወጥና የመረጠችውን ኃይማኖት የመያዝና የማምለክ የመተግበር ነፃነት ያላት መሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1ና ንዑስ አንቀጽ 3 እንደዚሁም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አለም አቀፉ የሰብዓዊ መብቶች ሁለተናዊ መግለጫ አንቀጽ 18 እና ዓለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 18(1) ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተረጋገጠላት በመሆኑ ኃይማኖቷን በመለወጥና የምታምንበትን ኃይማኖት የመያዝ መብቷን ማረጋገጧ የሚገድብ አይደለም፡፡ አመልካችም ይህንን የተጠሪን መብትና ነፃነት የሚገድብ ደብዳቤ ያልፃፈና ሌሎች የተጠሪን መብት የሚገድቡ ተግባሮችን ያልፈፀመ መሆኑን ተረድተናል፡፡

3. ተጠሪ የአመልካችን ኃይማኖታዊ ቀኖና ሥርዓት መከተሏን አማኝ መሆኗን በማቆም የሌላ ኃይማኖት ወይም እምነት ተከታይ መሆኗን በመካድ ያቀረበችው ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ የአመልካችን የሚያራምደውን ኃይማኖትና መንፈሳዊ አስተምሮት በመተው የሌላ ኃይማኖት ወይም እምነት ተከታይ መሆኗ ካልተካደ ተጠሪ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታይ አማኝ የነበረች በመሆኑ ምክንያት አመልካች ሰጥቷት የነበረው ክብር መብትና ጥቅም በነበረው ሁኔታ እንዲቀጥልላት ለመጠየቅ አትችልም፡፡ ተጠሪ የሌላ እምነትና ኃይማኖት ተከታይ መሆን ስትጀምር ከአመልካች ጋር የነበራት ኃይማኖታዊና መንፈሳዊ ትስስርና ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ይቋረጣል፡፡ አመልካች በቅጥር ግቢው ውስጥ በሚገኘው የመካነ መቃብር ቦታ ተጠሪ የመቃብር ቤት እንድትሰራ ልዩ ፈቃድ የሰጣት ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራትን የኃይማኖትና የእምነት ትስስር መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በአመልካች ቅጥር ግቢ ውስጥ ተጠሪ የመቃብር ቤት የገነባችው ከአመልካች ጋር በነበራት ጥብቅ የሆነ ኃይማኖታዊና መንፈሳዊ ግንኙነት ምክንያት እንጂ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በገንዘብ የሚተመን የኢኮኖሚያዊ ውልና ስምምነትን መሰረት በማድረግ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች በቅጥር ግቢው የሚገኘው የመካነ መቃብር ቦታ ላይ ተጠሪ ቤት እንድትሰራ የሰጠው ልዩ ፈቃድና ተጠሪም በዚህ ፍቃድ መሰረት የሰራችው የመቃብር ቤት ከኃይማኖቱና ከእምነቱ ተለይቶ የሚታይ የሚፈፀምና የሚተገበር ተራ የሆነ የውል ወይም የንብረት ግኑኝነት ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የኃይማኖቴና የእምነቴ ተከታይ ናት በሚል ምክንያት የሰጣትን ልዩ ፈቃድ መሰረት በማድረግ በአመልካች ቅጥር ግቢ ውስጥ በሰራችው የመቃብር ቤት ላይ ያላት መብትና ጥቅም፣ ተጠሪ ኃይማኖቷን ከለወጠችና የሌላ እምነት ተከታይ ከሆነችበት ጊዜ ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ይቋረጣል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲመዘን አመልካች ትከተለው የነበረውን ኃይማኖትና እምነት በመለወጥ ሌላ ኃይማኖት ተከታይ በመሆነሽ በአመልካች ግቢ ውስጥ በሰራሽው የመቃብር ቤት የመጠቀምና ስትሞችም በመቃብር ቤቱ የመቀብር መብት የለሽም በማለት ለተጠሪ የፃፈው ደብዳቤ የህገ-መንግስቱን አንቀፅ 11 አንቀፅ 27 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና ተገቢነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

4. ከላይ በተለዩት የህገ መንግስቱ ድንጋጌዎችና በሌሎች ዓለም አቀፍ የስብዓዊ መብቶች ህግጋት ድንጋጌዎች የተረጋገጠለትን ሃይማኖቱን የመለወጥና የሚያምንበትን ኃይማኖት የመያዝ የማመለክና የመተግበር መብቱን ዕውን ያደርገ ሰው በፊት ሲከተለው የነበረውን ኃይማኖትና እምነት መሰረት በማድረግ ለሰራቸው ተግባራት እንዲፈርሱለት እንዲመለሱለት ወይም ለሰራቸው ተግባሮች ግምት እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም? የሚለውን ነጥብ መታየት አለበት፡፡ የኃይማኖትና የእምነት ነፃነትና ኃይማኖትንና እምነትን የመለወጥ መብት አንድ ሰው በፊት ይከተለው የነበረውን ኃይማኖትና እምነት መሰረት በማድረግ ኃይማኖታዊና መንፈሳዊ ግዴታውን ለመወጣትና መንፈሳዊ ፀጋና ቡራኬ ለመጎናፀፍ በማሰብ የሰጣቸው ስጦታዎች ወይም ወጫቸውን በመሸፈን የሰራቸው የኃይማኖትና የእምነት ማምለኪያና ኃይመኖሮታዊ ትምህርት ማስተማሪያ ቤቶች ወይም በእምነቱ መሰረት የቀብር ስርዓት መፈፀሚያ እንዲሆን በማሰብ የሰራው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት እንዲመለስለት ወይም እንዲፈርስ ወይም ግምታቸው እንዲከፈለው የመጠየቅ መብትን የሚያስከትል አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የአመልካች ኃይማኖታዊ አስተምሮትና እምነት ተከታይ በነበረችበት ወቅት ለእሷና ለዘመዶቿ ስርዓተ ቀብር ማስፈጸሚያ ይሆናል በሚል ዕምነት የሰራችውን የመቃብር ቤት ግምት አመልካች እንዲከፍላት ለመጠየቅ የሚያስችላት ህጋዊ መሰረት የለም፡፡ አመልካችም ተጠሪ የኃይማኖቱ ተከታይ በነበረችበት ጊዜ የኃይማኖቱን መሰረታዊ ቀኖና ስርዓት መሰረት በማድረግ ለስርዓተ ቀብሯ ማስፈፀሚያ ይሆናል በሚል ኃይማኖታዊና መንፈሳዊ እምነት ወጭውን ችላ በቅጥር ግቢው ውስጥ የሰራችውን የመቃብር ቤት ዋጋና ግምት የመክፈል ኃላፊነት የለበትም፡፡

የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለውሳኔቸው መሰረት በማድረግ የጠቀሱት የፍታብሄር ህግ ቁጥር 1179 ድንጋጌዎች ኃይማኖታዊና መንፈሳዊ እምነት መሰረት በአንድ ኃይማኖታዊ ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ የተገነባ የመቃብር ቤት ላይ ተጠቃሽም ሆነ ተፈፃሚ የሚሆኑ አይደሉም፡፡

ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1179 ድንጋጌዎች ይዘት ፣ ዓላማና ተፈፃሚነት ወስጥ፣ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 11 እና አንቀፅ 27 ድንጋጌዎች ጋር በማጣመር ሳይተረጉሙ፣ አመልካች ተጠሪ ለእኔና ለዘመዶቼ ስርዓተ ቀብር ማስፈፀሚያ ይሆናል በማለት የሰራችውን የመቃብር ቤት ግምት ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሐረሪ ክልል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06816 መጋቢት 20 ቀን 1983 ዓ.ም የሠጠው ውሳኔና መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02332 የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪ በቅጥር ግቢው ውስጥ የገነባችውን የመቃብር ቤት ግምት የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 88798

ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡ አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ሙሉ አብርሃ ገ/ሕይወት ጠበቃ ብናልፈው ነጋ ቀረቡ

ተጠሪ፡-1. በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል

2.አቶ ወንድሙ አይፈዬ } ጠበቃ በላቸው ታደሠ ቀረቡ

3.አቶ ዳንኤል ገብሩ }

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ በአዲስ ከተማ ክፍል ከተማ፣ወረዳ 8 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 911 የሆነውን ንግድ ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ላይ ተከራይተው ሕጋዊ የሆነ የንግድ ፈቃድ በማውጣት ሰራተኞችን በመቅጠር የንግድ ስራ ሲሰሩበት የቆዩ መሆኑን፣1ኛ ተጠሪ የአመልካች ሰራተኞች የሆኑት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን ተከራይ ነን በማለታቸው የኪራይ ውሉን በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት ያቋረጠው መሆኑንና ተግባሩም ሁከት መሆኑን በመግለፅ የሁከት ተግባሩ እንዲወገድላቸው፣የኪራይ ውሉ ያላግባብ በመቋረጡ ምክንያት ያጡትን የቀን ገቢ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም ክርክሩ መሰረት ያደረገው የመንግስት ቤትን መሆኑን በምክንያት ጠቅሰው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ አመልካች በወኪላቸው አቶ ዳዊት አብርሃም አማካኝነት ሚያዚያ 17 ቀን 2001 ዓ/ም ከተጠሪዎቹ ጋር የንግድ ቤት ኪራይ ውል በመፈፀም በወር ብር 2350፣በኋላም ብር 3000.00 ሲሰበስቡ መቆየታቸውን፣መንግስት ያወጣውን መመሪያም ተከትሎ አመልካች የንግድ ቤቱ እንዳይወሰድ ሆነ ብለው ተጠሪዎችን በማባበል እና በማስገደድ የሰራተኝነት ውል ማስፈረማቸውን፣ሆኖም የሰራተኝነት ውሉም ተቀባይነት የሌለውና ተጠሪዎቹ ሰራተኛ ሳይሆኑ ተከራይ የነበሩ መሆኑን፣አመልካችም ቢሆኑ የስራ ገቢ ግብር በስማቸው ለመክፈላቸው ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው አመልካች የንግድ ቤቱን በከፍተኛ ዋጋ አከራይተው ሲገለገሉ በመመሪያው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት የንግድ ቤቱን ለተጠሪዎቹ መተላለፉ የሁከት ተግባር ሊባል አይችል በማለት ተከራክረዋል፡፡የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ግን በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎለት ክሱ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ጭምር ሳይቀርብ በመቅረቱ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችንና የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን ክርክር ሲሰማ አመልካች ለተጠሪዎቹ ድርጅቱን እንጂ ቤቱን ያላከራዩ መሆኑን መግለፃቸውን አረጋግጦ ተጠሪዎቹ ስልጣንን መሰረት አድርገው ያነሱትን ተቃውሞ ወድቅ አድርጎ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎቹ ማስተላለፍ ያለማስተላለፋቸውን በጭብጥነት ይዞ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ሰምቶ የአመልካች ሁለቱ ምስክሮች ተጠሪዎች ሰራተኛ መሆናቸው ላይ ተመሳሳይ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን የምስክርነት ቃላቸው እንደሚያሳይ፣የተጠሪዎች ሶስቱም ምስክሮች ደግሞ ተጠሪዎች ተከራይ እንጂ ሰራተኛ ያለመሆናቸውን መመስከራቸውን፣ተጠሪዎች በሰነድ ማስረጃነት ያቀረቡት ሰነድም ተጠሪዎች ቤቱን ተከራይተው ግምቱ ብር 6000.00 የሆነ ንብረት ያላቸው መሆኑን መግለፁ የተከራዩት ቤት እንጂ ድርጅቱን ያለመሆኑን እንደሚያሳይና ያለአከራይ እውቅና አመልካች ቤቱን ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አስተላልፈው እንደአከራዩ መረጋገጡን በምክንያት ይዞ የተፈጠረ ሁከት የለም፣አመልካች የቀረባቸው የቀን ገቢም የለም፣ወጪና ኪሳራ በቁጥር ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ብር 8000.00(ስምንት ሺህ ብር) ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የአመልካች ቅጥር ሰራተኞች መሆናቸው ተረጋግጦ እያለና ውሉን ተገደው የፈረሙ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ የአመልካች ምስክሮች ቃልና የቅጥር ውሉ ሰነድ ይዘት እንዲሁም አመልካች በቃል ክርክር ጊዜ ስለድርጅት ቤት ኪራይ የገለፁት አገላለፅ በተዛባ መልኩ ተመዝግቦና መንግስት ከአወጣው መመሪያ ይዘት ውጪ ቤቱን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲነጥቁ የተደረገ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ግን ቀርበው በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት ከመንግስት ተከራይተው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በሰራተኝነት ቀጥረው በማሰራት የሚጠቀሙበት ቤት 1ኛ ተጠሪ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 ውጪ ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በኪራይ አሳልፎ ሰጥቶብኛል፣ይህም የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊወገድልኝ ይገበል በማለት ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስም ቤቱን ከአመልካች ሊያገኙ የቻሉት በሰራተኝነት ሳይሆን በኪራይ መሆኑን፣የሰራተኝነት ቅጥር ውል የተባለው ሰነድም መመሪያውን ተከትሎ የተደረገ ሽፋን እንጂ ትክክለኛ ያለመሆኑን ገልፀው ተግባራቸው ሁከት የሚሆንበት አግባብ የለም ሲሉ መከራከራቸውን ነው፡፡የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ የሰማ ሲሆን አመልካች ለተጠሪዎች ያከራየሁት የድርጅት ቤት ነው በማለት በቃል ክርክር ከመግለጻቸው በተጨማሪ አሉኝ የሏቸውን ምስክሮችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበውም ተጠሪዎች ሰራተኛ መሆን ያለመሆናቸው ላይ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ያደረጉ መሆኑን ገልፆ ምስክሮች ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ተጠሪዎቹ የአመልካች ቅጥር ሰራተኞች መሆናቸውን ያለመመስከራቸውን፣የተጠሪዎች ምስክሮች ግን ተጠሪዎቹ የአመልካች ሰራተኞች ሳይሆኑ የንግድ ቤቱን ተከራይተው የሚሰሩ መሆኑን በተመሳሳይ ሁኔታ መመስከራቸውን እንዲሁም የኪራይ ሰንዱ ተጠሪዎች ግምቱ ብር 6000.00 የሆነ ንብረት በቤቱ አስገብተው ያሉ ስለመሆኑ የሚገልጽ መሆኑ ተጠሪዎች የተከራዩት የንግድ ቤቱን እንጂ የድርጅት ቤቱን ያለመሆኑን እንደሚያሳይ ዘርዝሮ ቤቱ ለተጠሪዎች ተላልፎ የተሰጠው በመመሪያ ቁጥር 4/2004 በመሆኑ ተግባሩ የሁከት ተግባር ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የለም በማለት ውሳኔ የሠጠ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡እንግዲህ አመልካች በዚህ የሰበር ደረጃ ባቀረቡት ቅሬታ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን በአግባቡ ያልመዘገበና ከአመልካች የክርክር ነጥብና ማስረጃዎቹ ከአረጋገጡት ውጪ መሆኑን ጠቅሰው እንደዚህ አይነት የዳኝነት አሰጣጥ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት አይደለም ሊባል የማይችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን አጥብቀው ገልጸዋል፡፡ይሁን እንጂ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ ስለመረጋገጣቸው የገለጻቸው ፍሬ ነገሮችን በውሳኔው ላይ በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን ይህንኑ የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ሙሉ በሙሉ የተቀበለው በመሆኑና ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ተያይዘው የሚቀርቡት የበታች ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 21 እና 22 ስለሚያስገነዝቡ ይህ ችሎት ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ይዘት አይቶ ተገቢውን ዳኝነት ከመስጠት በሰበር ደረጃ የቀረበው የአመልካች ቅሬታ የሚያግድው ሁኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች መሰረት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተትን ማረም እንጂ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የያዙትን ድምዳሜ ለመለወጥ የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች ከመንግስት የተከራዩትን ቤት ከአከራዩ ፈቃድ ውጪ ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አከራይተው ሲጠቀሙ የነበሩ መሆኑን፣ያከራዩትም የንግድ ድርጅቱን ሳይሆን የንግድ ቤቱን፣ተጠሪዎች የአመልካች ቅጥር ሰራተኞች ሳይሆኑ ተከራይ መሆናቸውን፣አመልካች አለ የሚሉት የኪራይ ውልም የመንግስት መመሪያን መውጣት ተከትሎ ለሽፋን የተደረገ መሆኑን ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን በሕጉ ስልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ከመንግስት ተከራይተው የነበሩት ቤት ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ1ኛ ተጠሪ ተላልፎ የተሰጠውና 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ይዘው ለአመልካች ሊለቁ ፈቃደኛ ያለመሆናቸው የሁከት ተግባርን የሚያቋቁምበት የሕግ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት የሚቻል ሁኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 191282 ጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128223 ጥር 02 ቀን 2005 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በአመልካች ላይ የተፈጠሩ ሁከት የለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80241

የካቲት 12 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ጽናት የሆቴል ቱሪዝም ስራዎች ኃ.የተ.የግል ማህበር -ጠበቃ ኃ/ማሪያም ተመስገን ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-1. አቶ ዳመነ ነጋ

2. አቶ አሰበ ፈቃዱ

3. አቶ ሱልጣን በደዊ - ጠበቃ በለጠ ጉራራ ቀረቡ፡፡

4. አቶ አበራ አመንሲሳ

5. ወ/ት አለምፀሐይ ሰለሞን

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክስን መሰረት አድርጎ የቀረበውን በተከራይነት የተገኘ የንብረት ይዞታ ይልቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሀኑ ተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርደ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች ክስ ይዘትም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በወረዳ 5 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ቁጥሩ 169 የሆነው ቤት ከሰላሳ ዘጠኝ ክፍሎች እና ከሁለት ሰርቪስ ቤቶች ጋር በ10/09/2003 ዓ/ም በተፈጸመ የኪራይ ውል ከመንግስት ቤቶች ተረክቦ ባለበት ሁኔታ ተጠሪዎች ምንም ሕጋዊ መብት ሳይኖራቸው እያንዳንዳቸው አንድ አንድ ክፍል በመያዝ ጨርቃ ጨርቅ በመያዝ እየነገዱ እንደሚገኙ ገልፆ በዚህ አድራጎታቸው ሁከት የተፈጠረበት ስለመሆኑ ጠቅሶ ሁከቱ እንዲወገድለትና ክፍሎቹ እንዲለቀቁለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ጉዳዩን የመንግስት ቤቶች ኤጂንሲ በመመሪያው መሰረት እየተመለከተው መሆኑን ጠቅሰው ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም፣አመልካችም በክፍሎቹ ላይ ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች ከመንስት ቤቶች ኤጀንሲ ንብረቱን በወርሃዊ የኪራይ ገንዘብ ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

40,000.00 ተከራይቶ ለተጠሪዎች ደግሞ ክርክር ያስነሱትን ክፍሎች እያንዳንዳቸውን በብር 15,000.00 ወርሃዊ የኪራይ ገንዘብ በማከራየት ጥቅም እያገኘበት መሆኑን የአመልካች ጠበቃ በክርክሩ ወቅት ማረጋገጣቸው፣ተጠሪዎች ወርሃዊ ኪራዩን ለመንግስት ቤቶች ኤጂንሲ እየከፈሉ እንደሚገኙ ገልጾና መመሪያው ሲወጣ ደግሞ አመልካች ተጠሪዎች ሁከት ፈጥረዋል ብሎ ክስ ማቅረቡ የመመሪያው አፈጻጸም እንዳይነካው በማሰብ ምክንያት ነው የሚሉትን ነጥቦችን በምክያትነት ይዞ ጉዳዩን ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብቶ የሚዳኘው አይደለም በማለት እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 231 ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞበታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች ክፍሎችን የያዙበትን አግባብ በተመለከተ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ባወጣው መመሪያ የማይሸፈን ስለመሆኑ በኤጂንሲው የተረጋገጠ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ማስረጃዎችን በአግባቡ ሳይሰሙና የጉዳዩን ክርክር በስርዓቱ መሰርት ሳይመሩ ውሳኔ መስጠታቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ክፍሎችን ከአመልካች የተከራይ አከራይ ሁኖ ተጠሪዎች ተከራይተው ይዘው ሲጠቀሙ እንደነበርና በመመሪያው መሰረትም የመንግስት ቤቶች ከተጠሪዎች ጋር የኪራይ ግንኙነት እንዲቀጥል በማድረግ ሲጠቀሙ መቆየታቸውን፣የመንግስት ቤቶች ኤጂንሲ ጉዳዩ በመመሪያው እንደማይሸፈን የገለፀበት ሁኔታ ተገቢነት የሌለው መሆኑንና ባሁኑ ጊዜ ከመንግስት ቤቶች ኤጂንሰ ጋር በክርክር እንደሚገኙ ገልጻው የበታች ፍርድ ቤቶች ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይንና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የአመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ ውድቅ ተደርጎ የተሰጠው ብይን ውጤቱ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ተጠሪዎች ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ የመሰረተው አመልካች ከመንግስት ቤቶች ኤጂንሲ የተከራየውን ቤት ተጠሪዎች ምንም መብት ሳይኖራቸው ይዘው ይገኛሉ በሚል ምክንያት መሆኑን፣ተጠሪዎች በበኩላች ክፍሎችን የያዙት ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል አድርገው መሆኑን፣የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ መመሪያ ሲያወጣ ደግሞ ከአመልካች ጋር ያላቸው ግንኙነት ተቋርጦ የኪራይ ገንዘቡን ለቤቱ ባለቤት እየከፈሉ እንዲቀጥሉ መደረጉን በመግለፅ የተፈጠረ ሁከት የለም ሲሉ መከራከራቸውን ነው፡፡የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን በሰማበት ወቅት የአመልካች ጠበቃ ለተጠሪዎች ክፍሎችን አመልካች አከራይቶ በወር ብር 15,000.00 ከእያንዳንዳቸው እንደሚሰብሰብና ከመንግስት ቤቶች ቤቱን ከተከራየበት ጠቅላላ ወርሃዊ ገንዘብ ብር 40,000.00(አርባ ሺኅ ብር) በላይ ብር 35,000.00(ሰላሳ አምስት ሺኅ) ማግኘቱንና ሌሎች ክፍሎችን ይዞ በመጠቀም ላይ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆነ ይህንኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍሬ ነገር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀብሎታል፡፡አመልካቾች ይህንኑ ፍሬ ነገር ፍርድ ቤቱ ገለልተኛ ሁኖ ጉዳዩን አልተመለከተም ከሚሉ በስተቀር በግል የሚክዱት ጉዳይ አለመሆኑን ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ተችሏል፡፡እንግዲህ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጧቸው ነጥቦች ከላይ የተመለከቱት ከሆነ ይህ ችሎት እነዚህን ፍሬ ነገሮች የሚለውጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕግ መነግስት አንቀፅ 80(3(ሀ))እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም እንዚህን ፍሬ ነገሮችን ይዘን በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ሊሰጡ ይገባ የነበረውን ዳኝነት አይነት እና የበታች ፍርድ ቤቶችን ብይን ውጤት ተገቢነት ተመልክተናል፡፡ይህንኑ ለይቶ ለመደምደምም በአመልካች የተጠየቀውን ዳኝነት አይነትና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች በስር ፍርድ ቤት እንዲሰጠው የጠየቀው ዳኝነት በተጠሪዎች የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድለት ነው፡፡ተጠሪዎች ደግሞ ይዞታውን በሕግ አግባብ የያዙት ስለመሆኑ ጠቅሰው የአመልካችን ክስ ክደዋል፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በጭብጥነት ሊመለከተው ይገባ የነበረው መሰረታዊ ነጥብ ሁከት? አለ ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡ ይህ የጭብጥ አመራረት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246 እስከ 248 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ያገናበዘ ሲሆን ዳኝነቱ መሰጠት ያለበት በከሳሽ በተጠየቀው መሰረት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1) ድንጋጌ ከተቀምጠው መርህ ጋርም የተጣጣመ ይሆናል፡፡ይህንኑ ጭብጥ ለመፍታት ደግሞ ስለሁከት የተደነገጉትን የፍትሐ ብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፍስ በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ጋር በማገናዘብ መመልከትን የግድ ይላል፡፡

በመሰረቱ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ይዞታውን ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈፀምን ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ወይም ንብረቱ እንዲመለስለት ህጉ ከጠበቀላቸው መንገዶች አንዱ አማራጭ የይዞታ ክስ ማቅረብ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 1149/1/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ መቅረብ የሚችለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ነገር በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረው ነው፡፡ እንዲሁም የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም ዓይነት መብት በሌለው ሰው ላይ ስለመሆኑም የድንጋጌው መንፈስ ያስረዳል፡፡ የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅራቢ በማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ንብረቱ በይዞታው ስር የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የኃይል ተግባር በመቀጠም ወይም በሚስጢር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ነው፡፡ ሁከት መፍጠር የሚኖረው ባለይዞታ የሆነው ሰው በይዞታው ስር በሚገኘው ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ሲፈጥርበት ወይም ረብሻ ሲፈጥርበት ነው፡፡

እንግዲህ የሁከት መፍጠር ድርጊት አጠቃላይ ትርጓሜና ይዘቱ ከላይ የተመለከተው ስለመሆኑ ከፍ/ህ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንግጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሁከት የወገድልኝ ክስ የሚያቀርበው ሰው ንብረቱ በእርሱ ግልጽ ቁጥጥር ስር መሆኑንና በዚህ ንብረት እንዳይገለገልበት ተከሣሹ ረብሻ የተነሣበት ወይም መሰናክል የተፈጠረበት ስለመሆኑ በማስረጃ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ በሌላ አገላለጽ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅራቢ የተሻለ የይዞታ መብት ያለው ስለመሆኑ ማሣየት ይጠበቅበታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ክፍሎች አመልካች ከመንግስት ቤቶች ኤጂንሲ ባገኙት የተከራይነት መብት በቁጥጥር ስር አድርጎ ሊጠቀምበት ከተከራየ በኋላ ለተጠሪዎች ያከራየ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡የመንግስት ቤቶች ኤጂንሲም ጉዳዩን አጣርቶም የኪራይ ውሉን ተጠሪዎች ከመንግስት ቤቶች ጋር እንዲቀጥሉ ወስኖ የነበረ መሆኑና በኃላ ግን ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘ ነው በሚል ምክንያት ጉዳዩ በመመሪያው እንደማይሸፈን እና ኪራዩም እንደገና ከአመልካች ጋር እንዲቀጥል በማለት ደብዳቤ መፀፉን፣ተጠሪዎች ደግሞ የመንግስት ቤቶችን እርምጃ ተቃውመው በፍርድ ቤት በሌላ መዝገብ ክርክር ላይ እንደሚገኙ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው የአከራካሪ ክፍሎች ሕጋዊ ተከራይ ማን ነው? ወደፊት ሕጋዊ ተከራይ ሁኖ መቀጠል ያለበት አመልካች ነው ወይስ ተጠሪዎች ናቸው? የሚሉት ነጥቦች ከሚታዩ በስተቀር አመልካች ተጠሪዎችን በራሱ ተነሳሽነት አከራይቶ ቆይቶ የሁከት ተግባር ፈጥረዋል ብሎ ክስ የሚያቀርብበት አግባብ የለም፡፡ተጠሪዎች በኃይል ተግባር የአመልካችን ይዞታ እስካልያዙ ድረስ ክርክሩ የሁከት ይወገድልኝ ክስን መሰረት አድርጎ የሚታይበት አግባብ የለም፡፡በሌላ አነጋገር የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለውና መብቱ የሚከበረው የተሻለ የይዞታ መብት በማሣየት ነው፡፡እንዲሁም የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርብ ወገን የሚጠይቀው ዳኝነት የሁከት አድራጉት እንዲቆም በይዞታው ስር የነበረው ንብረት ሊያስገኝለት የነበረውን ጥቅም በኪሣራ መልክ እንዲከፈለው ሲሆን በህጉ አግባብ የተፈፀመ የኪራይ ውል አለመኖሩን ተከትሎ የሚቀርበው ጥያቄ ግን ውጤቱ ከሁከት ይወገድልኝ ጥያቄ ጋር ተመሣሣይነት የለውም፡፡በመሆኑም በሁከት ይወገድልኝ ክስ ሕጋዊ ተከራይ ማን ነው የሚለው ጥያቄ ተነስቶ ዳኝነት የሚሰጥበት ሁኔታ ስለመኖሩ መሰረታዊውም ሆነ የስነ ስርአት ህግ ድንጋጌዎችን አያመላክቱም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ክፍሎች ለተጠሪዎች አከራይቶ ቆይቶ ለተጠሪዎች የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት የተከራይነት መብት ሲያስተላልፍ ሁከት ፈጥረዋል በማለት የሚያቀርበው ክርክር የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እና 1149 ድንጋጋዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ ማየትና ዳኝነት መስጠት እየተገባው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 555/2000 መሰረት በመንግስት ቤቶች ኤጂንሲ ታይቶ እልባት የሚሰጥበት እንጂ ፍርድ ቤት ጣልቃ የሚገባበት ነው በማለት የሰጠው የምክንያት ክፍል የተጠቃሹን አዋጅ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ከፍርድ ቤት ስልጣን አድማስ ጋር ያላገናዘበ ቢሆንም ክሱን ውድቅ ማድረጉ ግን በውጤት ደረጃ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 188655 መጋቢት 13 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 118491 ሚያዚያ 11 ቀን 2004 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናው ብይን በተለወጠ ምክንያት ውጤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች ክፍሎችን በኪራይ ከአከራየ ከአስተላለፈ በኋላ ተጠሪዎች ሁከት ፈጥረዋል ብሎ ክስ ማቅረቡ ስለ ሁከት ይወገድልኝ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ የፈጠሩት ሁከት የለም ብለናል፡፡
3. አመልካች በሌላ አግባብ መብቱን ለማስከበር ይህ ውሳኔ አያግደውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሣ/ክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 83060

ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ገ/ማሪም ገ/መድህን ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጣዕመ ወ/ስላሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ በአመልካች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ሻለቃ ኃይለማርያም ኃ/ስላሴ ላይ የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 20 ቀበሌ 19 ክልል ቁጥር 513 የሆነውና የካርታ ቁጥር 13079 በሚል የሚታወቅ ቤት ባለቤት መሆናቸውን ለ1ኛ ተከሳሽ ቤቱን እንዲያስተዳድሩ እንዲያከራዩ በሚል የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው ቢሆንም ቤቱን ወደ ሌላ ሰው የማስተላለፍና ስልጣን እንዳልተሰጣቸው 1ኛ ተከሳሽ የተሰጣቸውን ስልጣን ሽፋን በማድረግ ሐምሌ 10 ቀን 1992 ዓ/ም በተፃፈ ውል አማካኝነት ቤቱን ለአሁኑ አመልካች በብር 148,000.00/አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ ብር/ የሸጡ መሆናቸውን አሁኑ አመልካች በዚህ የመሸጥ የመለወጥና የማስተላለፍ ሥልጣን በማያካትተው የውክልና ሰነድ ወይም ህገ ወጥ ሰነድ አማካኝነት ቤቱን መግዛታቸውን ገልፀው የሽያጭ ውል ሕገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲፈርስ እንዲሁም ውሉን ተከትሎ የተከናወኑት ተግባራት ዋጋ አልባ ናቸው እንዲባሉ ቤቱን የአሁን አመልካች ለቀው እንዲያስረክቧቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት ፍርድ ቤቱ ጉዳን ለማየት ሚያስችለው ስልጣን የሌለው መሆኑን ተጠሪ የክስ ምክንያት የሌላቸውና ክሱን ለማቅረብም መብት ወይም ጥቅም የሌላቸው መሆኑን የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን ሚገልፅ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ካርታው የተሰረዘ መሆኑን በሕጉ አግባብ የተደረገ ቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያትዬሌለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑንና ተጠሪ የውጭ ሀገር ዜጋ በመሆናቸው የማይንቀሳቀስ ንብረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለመያዝ ህጋዊ መብት የሌላቸው መሆኑንና ሌሎች ነጥቦችን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤትም በመጀመሪ ደረጃ መቃወሚያነት ተጠሪ ያቀረቧቸውን ነጥቦች ሙሉ በመሉ ውድቅ አድርጎ አልፎ ፍሬ ጉዳዩን መርምሮ የቤት ሽያጩ ውሉ ሕጋዊ አይደለም በሚል ምክንያት ፈራሽ ነው በማለት ቤቱን ተጠሪ ሊረከቡ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1808 መሰረት ውል እንዲፈርስ ጥያቄ የሚቀርብባቸው ውሎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1810 መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገዱ ናቸው፡፡ ተጠሪ የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም ክሱን የመሰረቱት ሐምሌ 14 ቀን 1992 ዓ/ም የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው በመሆኑና ጊዜ ሲሰላም የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ያለፈበት በመሆኑ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ ከዚህም በኃላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ችሎቱ ጉዳዩ በይርጋ የታገደ አይደለም በማለት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ሲል ጉዳዩን ለፌዴራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን የፍሬ ጉዳይ ክርክርን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ውሉ ፈራሽ ነው ቤቱን አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም አመልካች በመንግስት መመሪያ መሠረት በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ በጊዜው የወጣው የመንግስት መመሪያ የውሉን ይዘትና ለጉዳዩ መቅረብ ያለባቸውን ማስረጃዎችን አይነትና የአቀራረባቸውን ስርዓት እንዲሁም ማስረጃዎቹን ይዘት ያላገናዘበና በጉዳዩ ላይ የክርክሩ የግድ ተሳታፊ ሊሆን ይገባው ነበረውን ወገን ወደ ክርክሩ እንዲገባ ሳይደረግ ክረክሩ የተመራበት ለተጠሪ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 07 ቀን 2001 ዓ.ም የወጣው መመሪያ ያስቀመጠው መፍትሔ መሰረት ያላደረገ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ የቤትሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስም የቤት ሽያጭ ውሉ በመንግስት መመሪያ መሰረት የተደረገ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠና በመንግስት መመሪያ ተደርጓል ቢባል አንኳን መመሪያው ሕጉን ለማውጣት ስልጣን ባለው አካል የወጣ ባለመሆኑ የህግ አቋም የሌለውና የውክልና ሕግ መርህዎችን የሚፃረር በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የማየይገባ መሆኑን ዘርዝረውና የአመልካች መከራከሪያ ነጥቦች ድግግሞሽ ያለባቸው ስለመሆኑ ገልፀውና የህግ መሰረት የሌላቸው መሆኑን ያሳያሉ የሚሏቸውን ምክንያቶች ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር መልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከለይ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም አቤቱታው ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ መርምረናል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አከራካሪው ቤት ሊሸጥ የቻለው የውክልና ሰነዱንም መሰረት አድርጎ ሳይሆን በምንግስት በወጣ መመሪያ ነው እየተባለና ይህንንም መመሪያ አመልካች ከመልሳቸው ጋር እንደማስረጃ ሳያቀርቡ በመቅረታቸው ብቻ ይሄ ታልፎ የሽያጭ ውሉ ተሰረዞ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ መልሰው ያስረክቡ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሀምሌ 10 ቀን 1992 ዓ/ም ከተጠሪ ወኪል ከተባሉት ከሻለቃ ሀብተማሪያም ሀብተስላሴ ጋር ያደረጉት መኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ መሆኑን መስከረም 25 ቀን 1993 የተደረገው ውልም በተመሳሳይ አካል ፊት የተደረገ መሆኑን የክልል መስተዳደር ጽ/ቤት በቁ/አመ/አ.አ 73 በ18/8/1992 ዓ/ም ለውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በዓፈው ደብዳቤ ኤርትራዊያን ከሀገር ሲወጡ ንብረታቸውን የመጠበቅ የማስተዳደር የመሸጥ የመሳሰሉት የውክልና ሰነዶች/ማስረጃዎች/ ያሏቸው ሰዎች መሸጥ መለወጥ ይችላሉ የሚል ይዘት ያለው መሆኑን ተጠሪ ኤርትራዊ መሆናቸውና ለወኪላቸው ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል ስልጣን ያልሰጡ መሆኑን የተረጋገጠ መሆኑን በቁጥር ቀ2/ጠ67/61/92 በቀን 10/10/92 በተፃፈ ደብዳቤ ተጠሪ በአከራካሩው ቤት ጥር 13 ቀን 1974 ዓ/ም የወሰዱት የካርታ ቁጥር 13079 ለተወካያቸው ሳይሰጡ ከሀገር የወቱ በመሆናቸው ከሚመለከተው አካል ተረጋግጦ በመቅረቡ ምክንያት ተጠሪ የወሰዱት ካርታ እጃቸው ላይ እንዳለ በማምከን ለአሁኑ አመልካች ቁጥሩ 39897 ሆነ አዲስ ካርታ ሰኔ 09 ቀን 1992 ዓ/ም የተሰጣቸው መሆኑን ከሚመለከተው አካል የተፃፈ የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ሐምሌ 10 ቀን 1992 ዓ/ም በውልና ማስረጃ በተደረገው የስምምነት ሰነድ ይዘቱ ሲታይ የውሉን አላማ የኤርትራዊያን ቤት ወኪሎች የሆኑት ወኪል የሆኑበትን ቤት ሽጠው ገንዘቡን በዝግ ሂሳብ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባንክ ገቢ እንዲያደርጉ በክልል 14 ቢሮ ቁጥር 20 የተጠሪ ወኪል ተጠርተው በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት ቤቱን ለመሸጥ መሆኑንና ወኪሉ የወኪል አድራጊያቸው ባለቤት መጥተው ቢከራከሩ ወይም ያገባኛል ቢሉ ሁሉንም ነገር በኃላፊነት የሚመልሱ መሆኑን በመግለፅ ፊርማቸውን ማስቀመጣቸውንና የቤቱን ዋጋ በወቅቱ የተከፈለውን የገንዘብ መጠንና ቀሪው ገንዘብ የሚከፈልበትን ሁኔታ እንዲሁም ሌሎች የገዥንና ሻጭን መብትና ግዴታዎችን በዝርዝር የያዘ መሆኑን የሚያስገነዝብ መሆኑን ነው፡፡

እንግዲህ ከላይ የተገለጹት ነጥቦች በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡ ሲሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ሊወስኑ የቻሉት አመልካች ቤቱ የተሸጠው በመንግስት ትዕዛዝና መመሪያ መሆኑን ገልፀው ቢከራከሩም ለጉዳዩ ለማስረጃነት የቀረቡት የውል ሰነዶች አያሳም እንዲያውም ወኪሉ ቤቱ የእኔ ነው ባይ ወይም ተከራካሪ ወገን ቢመጣ የመመለስ ኃላፊነቱ የውል ሰጪው ነው በሚል የስምምነት ግዴታ የተቀመጠ መሆኑ ቤቱ የተሸጠው በመንግስት ትዕዛዝ ሳይሆን የተጠሪ ወኪል በራሳቸው ፈቃድ ተነሳስተው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው የሚል ምክንያት በመያዝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሐምሌ 10 ቀን 1992 ዓ/ም የተደረገው ውል እንደከፍተኛው ፍርድ ቤት ድምዳሜ በመንደር የተደረገ ሳይሆን በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ ከመሆኑም በላይ እንደተጠቀሰው ይዘቱ ወኪሉ በክልል 14 ቢሮ ቁጥር 20 ተጠርተው በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት ሽያጩን ያከናወኑ መሆኑን በግፅ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የሰነዱ ይዘት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005 እና አዋጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 334/1995 አንቀፅ 2(1) ፤ 4(1) እና 5(1(ሀ) መሰረት ተቀባይነት የማያገኝበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሲሆን ውሉን ያረጋገጠው አካልም ኤርትራዊያን ከሀገር ሲወጡ ቤት ለመሸጥ የሚያስችል ስልጣን ለተወካቻቸው ባይሰጡም ተወካዩቹ የማስተዳደር መጠበቅና የመሳሰሉ የውክልና ሰነዶችን ቢይዙም ንብረቶቹን መሸጥ መለወጥ የሚችሉ መሆኑን ከአዲስ አበባ መስተዳደር ሚያዝያ 18 ቀን 1992 ዓ/ም የተላለፉትን መመሪያ መሰረት አድርጎ ስምምነቱን ማረጋገጡን ሁለቱም ሰነዶች አንድ ላይ ሲታ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሲታይም የተጠሪ ወኪል ተግባሩን የፈፀሙት ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችላቸው ሕጋዊ ውክልና አለኝ በሚል ሳይሆን በጊዜው በነበረው ነባራዊና አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ሁነው መሆኑንና አመልካች ደግሞ ይህንኑ በማየትና በመገንዘብ ስምምነቱ ውስጥ የገቡ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ የተጠሪ ነባር የባለቤትነት ካርታ በሚመለከተው አካል መሰረዙ ከላይ ከተጠቀሰው የክልል 14 መስተዳድር መመሪያና ውሉ በውልና ማስረጃ ፊት ቀርቦ ከመደረጉና ሕጋዊ ነው ተብሎ ከመረጋጡ ጋር ተዳምሮ ሲታይ አመልካች ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው ግዢውን የፈፀሙ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የመንግስት መመሪያ ስለመኖሩ አመልካች ማስረጃ አላቀረቡም በማለት የያዙት ድምዳሜ ከላይ የተጠቀሰውን ውል ይዘት ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ ከሆነም በራሳቸው አነሳሽነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145(1) እና 345(1)(ለ) ድንጋጌዎች አግባብ ማስቀረብ ይችሉ የነበረ ጉዳይ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን የውሉ ሰነድ ይዘት በግልፅ ሽያጩ በመንግስት አስተዳደር አካል ትዕዛዝ የተከናወነ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ይሄው የሰነዱ ይዘት ለጉዳዩ ተቀባይነት ያለውና ተግባሩ በአስተዳደር አካሉ ትዕዛዝና መመሪያ የተፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች ሽያጩ በመንግስት አስተዳደር አካል ትዕዛዝ ወይም መመሪያ መሰረት የተከናወነ መሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ሐምሌ 10ቀን 1992 ዓ.ም. እና መስከረም 25 ቀን 1993 ዓ.ም. የተደረጉትን ውሎችን ይዘትና መንፈሳቸውን ለውሎች መደረግ ከሚመለከተው አካል ለዚሁ ውል አረጋጋጭ አካል ሲተላለፉ የነበሩትን ደብዳቤዎችን ይዘት ያላገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ወኪል ውክልናውን መሰረት አድርገው ሸጠዋል በማለት በአመልካች ክርክር ባልቀረበበትና በወቅቱ በነበረው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምክንያት በመንግስት አስተዳደር አካል በተወሰደው እርምጃ መሰረት ወደ ግብይት የገቡት ዜጎች አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ የፈፀሙት ተግባር መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ጉዳዩ በወቅቱ ከነበረው ልዩ ሁኔታ ታይቶ በራሱ ዳኝነት ከሚያገኝ በስተቀር የውክልና ህግ መርህዎች መሰረት ተደርገው ተግባራቸው ህጋዊ ጥበቃ የሚነፈግበት አግባብ ሊኖር አይገባም፡፡ በወቅቱ የተወሰደውን እርምጃ በመገንዘብም በወቅቱ የተከናወኑትን ተግባራትና መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓ/ም ወጥቶ ስራ ላይ መዋሉም መንግስት በማመን የግዥ ተግባር ያከናወኑትን ዜጎች ዋስትና ለመስጠት ነው ተብሎም ይታሰባል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ከሀገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራዊያ በመንግስት አስተዳደር ንብረታቸው ተሸጦ በዝግ ባንክ አካውንት የተቀመጠ ገንዘብ ካላቸው ማስረጃ ሲያቀርቡ ካለወለድ ገንዘባቸውን በብር እንዲያገኙ እንደሚደረግ በአንቀፅ 4(2) ስር በግልፅ ሰፍሯል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከሀገር ወጥተው የነበሩ ኤርትራዊ መሆናቸውንና አመልካች ለቤቱ የከፈሉት ገንዘብ ብር 148,000.00(አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ) በኢትጵያ ንግድ ባንክ ፊሊፊኔ ቅርንጫፍ በዝግ ሂሳብ መቀመጡና የባንክ ደብተሩም በአዲስ አበባ መስተዳደር መቀመጡን አመልካች ጠቅሰው ላቀረቡት ክርክር በተጠሪ በኩል ማስተባበያ ክርክር ያልቀረበበትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሐ/ቁጥር 234(1(ሠ)፤235 እና 83 ድንጋጌዎች እንደታመነ የሚቆጠር በመሆኑ ተጠሪ ያላቸው መፍትሔ ይህንኑ ገንዘብ መቀበል እንጂ የቤት ሽያጩ እንዲፈርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስደረግና ቤቱን የመረከብ መብት አይደለም፡፡ ሲጠቃለልም አመልካች በመንግስት አስተዳደር አካል በተላለፈው መመሪያ መሰረት ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው የገዙትና ለበርካታ አመታት ሲጠቀሙበት የነበረውን ቤት ውሉ ፈርሶ ለተጠሪ ሊያስረክቡ የሚገደዱበት ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን የበታች ፍርድ ቤቶች የክርክሩን ልዩ ባህርይና በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን የውል ሰነዶችን ይዘታቸውን በአግባቡ ሳይመለከቱ ለጉዳ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት የሌለለውን ውክልና ሕገ መርህዎችንና በአመልካች ላይ መመሪያውን ለማስረጃነት ማቅረብ ግዴታን ሕጉ ባልጣለበት አግባብ የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 40449 ህዳር 04 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87379 ነሐሴ 18 ቀን 2004 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አከራካሪው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ሊገደዱ አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ያላቸው መፍትሄ የቤቱን ሽያጭ ገንዘብ ብር 148,000.00(አንድ መቶ አርባ ስምንት ሺህ ብር) በኢትጵያ ንግድ ባንክ ፊኒፊኔ ቅርንጫፍ ከሚገኘው የዝግ የሂሳብ አካውንት መውሰድ ነው ብለናል፡፡
4. ለክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአመስት ዳኞች ፊርማ አለበት፤

እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 83665

ግንቦት 22 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

መስጠሩ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ እታፈራሁ ፀጋዬ ቀረቡ

ተጠራዎች፡-1. ወ/ሮ መሰረት ግርማ ወኪል ሁለተኛ ተጠሪ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፍሬህይወት ግርማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32817 ታህሳስ 5 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 118115 መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ሀብትና የጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪዎች ወላጅ አባታችን አቶ ግርማ ብሩ መጋቢት 24 ቀን 1988 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ እኛም ወራሽነታችን በፍርድ በማረጋገጥ ውርስ እንዲጣራልን አድርገናል፡፡ የውርስ አጣሪው ሪፖርት በመዝገብ ቁጥር 30327 ህዳር 15 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፀድቋል፡፡ አባታችን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ቁጥሩ 076/ሀ/ የሆነ ቤት አላቸው፡፡ ተከሳሽ /አመልካች/ ቤቱን ይዛ ግማሹን እያከራየች ትገኛለች፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ ቤቱን እንዲለቁና የኪራይ ገንዘብ ብር 20400 /ሃያ ሺህ አራት መቶ ብር/ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡
2. አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው ከሳሾች ክስ ያቀረቡበት የውርስ ንብረት ጥያቄ በአስር ዓመት የይርግ ጊዜ ገደብ ቀሪ ይሆናል፡፡ የቤት ቁጥር 076 የሆነው ቤት ባለቤቱ /የከሳሾች አውራሽ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሞተ በኋላ በእርጅና ምክንያት በመፍረሱ በአዲስ መልክ ሃምሳ ሁለት ቆርቆሮ ጣራውን በአዲስ መልክ ሰርቼ የምጠቀምበት የግል ንብረቴ ነው በማለት ተከራክራለች

3. የስር ፍርድ ቤት በውርስ ማጣራቱ ቤቱ የአቶ ግርማ ብሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የቤቱ ስመ ሀብትም በከሳሾች አውራሽ በአቶ ግርማ ብሩ ስም ነው፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 ወረዳ 09 ቁጥሩ 076/ሀ/ የሆነውን ቤት ለከሳሾች ያስረክቡ የቤቱን ኪራይ 10200 /አስር ሺህ ሁለት መቶ ብር/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ተከሳሽ ለከሳሾች ይክፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ቤቱ የመልስ ሰጭዎች /ተጠሪዎች/ አውራሽ መሆኑ በውርስ ማጣራት ሂደት ተረጋግጧል፡፡ የውርስ አጣሪው ሪፖርት በፍርድ ቤት ፀድቋል፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው በማለት አፅንቶታል፡፡

5. አመልካች መስከረም 28 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ከተጠሪዎች አውራሽና ወላጅ አባት ጋር ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ተጋብተን ስንኖር ሁለተኛ ተጠሪን ወልጃለሁ አመልካች የሚች አቶ ግርማ ብሩ ሚስት መሆኔና ተጠሪዎች ደግሞ የሚች ልጆችና ወራሾች መሆናቸው በመዝገብ ቁጥር 376/88 ጥር 6 ቀን 1989 ዓ.ም በፍርድ ቤት ውሣኔ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪዎች ወራሽነታቸውን ካረጋገጡ ከአስራ ሶስት ዓመት በኋላ በ2002 ዓ.ም ውርስ እንዲጣራላቸው ጠይቀው እኔም ይህንን ጥያቄ በመቃወም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተከራክሬ የውርስ ማጣራቱ የአንቺን መብት የሚነካ አይደለም ተብሎ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ አመልካች የአከራካሪው ቤት ግማሽ ባለንብረት ስለመሆኔ ከሚች ባለቤቴ ጋር የተሰጠን የጋራ የቦታ ማረጋገጫ ሰነድ የሚያሳይ ሲሆን ንብረቱም በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ሀብት ነው፡፡ ስለዚህ ተጠሪዎች የንብረት ታስረክበኝ ጥያቄ እያቀረቡ የጋራ ባለሀብትነት መብቴን በማለፍ ንብረቱን ለተጠሪዎች እንዳስረክብ የተሰጠው ውሣኔ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎችና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1845 የሚጥስ በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

6. ተጠሪዎች በበኩላቸው ታህሳስ 2 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጡት መልስ አመልካች የውርስ አጣሪው ቤቱ የሚች ግርማ ብሩ የግል ንብረት ነው በማለት የቀረበውን ሪፖርት በማፅደቅ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ተከራክረው ክርክራቸው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ ቤቱ የጋራ ሀብት ነው በማለት የምታቀርበው የሕግ መሰረት የለውም፡፡ ቤቱም በጋብቻ የተፈራ ሣይሆን ሚች ከአባቱ በስጦታ ያገኘው ንብረት ነው፡፡ ጉዳዩ ክርክር ሲደረግበት የቆየ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ታህሳስ 22 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

7. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የክስ መቃወሚያና የፍሬ ጉዳይ ክርክር ውድቅ በማድረግ ቤቱን ለተጠሪዎች እንድታስረክብ የሰጡት ውሣኔ ተገቢነት ያለው መሆኑን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

8. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ተጠሪዎች የሚች አቶ ግርማ ብሩ ውርስ እንዲጣራላቸው ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 30327 አመልካች አቅርበው የነበረውን መቃወሚያና ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ብይን ይዘት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች የቤት ቁጥር 076 የግል ቤቱ ነው፡፡ ውርስ እንዲጣራ የቀረበው ጥያቄም በአስር ዓመት ይርጋ ቀሪ ነው የሚል የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች ያቀረቡት የውርስ ይጣራልን ጥያቄ ነው፡፡ ውርስ ሲጣራ የውርስ አጣሪው ወራሾች ኑዛዜ፣ የሚች ዕዳና ንብረት መለየት እንጂ በሶስተኛ ወገኖች የመፋለም መብትን የሚያሳጣ ውሣኔ መስጠት አይችልም የውርስ አጣሪው ስራ ውርስ ማጣራት እንጂ የአሁኑ የመቃወም አመልካች ንብረት ወይም ቤት አይደለም ብሎ በዚህ መዝገብ በቤት ቁጥር 076 ላይ የተሰጠ ውሣኔ የለም" ስለዚህ በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ የመቃወም አመልካች መብት ሊነካ የሚችል ውሣኔ ያልተሰጠ በመሆኑ የመቃወም አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ አልተቀበልነውም በማለት ጥር 20 ቀን 2002 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህንን ትዕዛዝ በመቃወም ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 11408 ሰኔ 9 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው፣ በሰበር ችሎት የሚታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በሰበር መዝገብ ቁጥር 72275 ታህሳስ 9 ቀን 2004 ዓ.ም ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ማጣሪያ ችሎት ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል፡፡

9. ተጠሪዎች የሚች ውርስ እንዲጣራ ጥያቄ ባቀረቡበትና የውርስ አጣሪው ሪፖርት በፀደቀበት በመዝገብ ቁጥር 30327 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥር 20 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የአመልካችን የመቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ ያደረገው የውርስ አጣሪው ሪፖርት ቤቱ የሚች የግል ንብረት ነው ወይስ የአመልካች የጋራ ሀብት የሚለው ጭብጥ የማይመለከትና በቤቱ ላይ መብት ያለው ማናቸውም ሶስተኛ ወገን በቤቱ ላይ ያለውን መብት የባለሀብትነት መብት ለማስከበር ክርክር ከማቅረብና ከመፋለም የማይገደብ ነው በቤት ቁጥር 076 ላይ የተሰጠው ውሣኔ የለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ተጠሪዎች ቤቱን እንድትለቅና እንድታስረክባቸው ያቀረቡት ክስ ለመቃወም አመልካች ያቀረበችው የይርጋ ክርክርና ሌሎች የመከራከሪያ ሀሳቦችና ማስረጃዎች በመቀበልና በመመርመር ውሣኔ መስጠት ሲገባቸው፣ ቤቱ በውርስ አጣሪ የሚች ንብረት ነው ተብሎ ውሣኔ ተሰጥቶበታል በማለት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን የመጀመሪያ የክሱ መቃወሚያና ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 30327 ጥር 20 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ ይዘትና ህጋዊ ውጤት ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. የሚች ውርስ እንዲያጣራ የተመደበ የውርስ አጣሪ፣ አንድ ንብረት የሚች የግል ንብረት አለመሆኑ አከራካሪ ሆኖ ሲያገኘው፣ ንብረቱ የሚች የግል ንበረት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመመስረት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ማስረጃ በመመርመር በመመዘን ውሣኔ የመስጠት ስልጣን የለውም፡፡ ከዚህ አንፃር ቤቱ የሚች የግል ንብረት መሆኑ ለውርስ አጣሪው ሪፖርት ተገልጿል በማለት አመልካች የባለሀብትነት ክርክር ሣይቀበሉና ማስረጃዎን ሳይመረምሩና ሳይመዝኑ ውሣኔ መስጠታቸው አመልካች ፍትህ የማግኘት መብት የሚያጣብብ ሆኖ አገኝተነዋል፡፡ አመልካች የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በመቃወም ያቀረቡት ክርክር የአንቺን መብት የሚነካ አይደለም በማለት ውድቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች ንብረት ያስረክቡኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ በመቃወም ቤቱ የጋራ ሀብቴና የግል ንብረቴ ነው በማለት ያቀረበችው ክርክር ሣይታይ የሚታለፍ መታለፉ አመልካች በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 የተረጋገጠለትን የንብረት ባለቤትነት መብት ለማስከበርና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1206 መሰረት የመፋለም መብቱን ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የማቅረብና የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 የተረጋገጠውን ፍትህ የማግኘት መብቷን በሚጥስ ሁኔታ በቤቱ ላይ አለኝ የምትለው መብትና ጥቅም በፍርድ ሳይጣራና ሣይረጋገጥ የሚቀርበትን ክፍተት የሚፈጥር ነው ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ንብረቱን ሙሉ በሙሉ ለተጠሪዎች እንድትለቅና እንድታስረክብ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32817 የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 118115 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ላይ አመልካች ያቀረበችውን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያና የመከላኪያ መልስ እንዲሁም የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በመመርመር በጉዳዩ ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 88084

ህዳር 19 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ወጋየሁ ታምሩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. የወ/ሮ አስካለ ወሰኔ ወራሽ ፍሬዘውድ ጌታቸው ቀረቡ

2.አቶ በኃይሉ ከፍያለው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ቤት ይገባኛል ጥያቄ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች ባሁኗ 1ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም፡- አመልካች የሟች ወ/ሮ አይከልክሉሽ ደስታ መንገሻ ወራሽ ስለመሆናቸውን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አረጋገጠው ማስረጃውን የያዙ ሁኖ ከሟች ሊያገኙ የሚገባውን የውርስ ሃብት 1ኛ ተጠሪ ከፊሉን እያከራዩ በመጠቀም ላይ እንደሚገኙ ገልፀው የውርስ አጣሪ ተሹሞ የውርስ ሃብቱ እንዲጣራላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ በሰጡት መከላከያ መልስም ጥያቄው በይርጋ የሚታገድ መሆኑንና የሚጣራ የውርስ ንብረት የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡የሥር ፍርድ ቤትም ይርጋን መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር አልፎ ውርሱ እንዲጣራ ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ አመልካችም ወደ ክርክሩ ገብተው በውርስ ማጣራት ሂደቱም እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡የውርስ ማጣራት ተግባሩን እንዲያከናወኑ በፍርድ ቤት የተሾሙት የውርስ አጣሪም የሟቿ ብቸኛ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የአሁኗ አመልካች መሆኗን፣ የውርስ ንብረቱን በተመለከተ ደግሞ የአሁኗ አመልካች ለይተው ያቀረቡት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ቀበሌ 14/21 ቁጥሩ 482 የሆነው ቤት ሁኖ ይህ መኖሪያ ቤት በ1ኛ ተጠሪና በሟች አይከልክሉሽ ደስታ በውርስ ተይዞ ቆይቶ በኃላ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝና በመንደር ውል ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ተጠሪ የሸጡ መሆኑ መረጋገጡን፣በቤቱ ብር 1900.00(አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር) መሰብሰቡን ማጣራቱን ገልጾ ጉዳዩን ለፍርድ ቤት የመለሰለት ሲሆን የውርስ ሪፖርቱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ አስተያየት ከተቀበለ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ በቤቱ ላይ አመልካች የሟች አይከልክሉሽ ደስታ ድርሻን የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ ቤቱ በብር

115,000.00 (አንድ መቶ አስራ አምስት ሺህ) ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በቅን ልቦና የተሸጠ መሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ አመልካች የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ግማሽ ድርሻ አላቸው ሲል የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በማሻሻል ማዕደቁን ገልጾ ይኼው ማስረጃው ለግራ ቀኙ እንዲሰጣቸው ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፤የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በውርስ የሚያገኙን የቤቱን ግማሽ ድርሻ 1ኛ ተጠሪ ሐሰተኛ የወራሽነት ማስረጃ ይዘው በመንደር ውል ለ2ኛ ተጠሪ መሸጣቸው ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርደ ቤቶች አመልካች ሊያገኙ የሚገባው የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ግማሽ ነው በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ስለቀረቡ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች በአከራካሪው ቤት ብቸኛ ወራሽና ባለቤት መሆናቸው በተረጋገጠበት 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል ሕጋዊ መብት ያልነበራቸው መሆኑ ባልተካደበት፣2ኛ ተጠሪ ሕጋዊ መብት ከሌላቸው 1ኛ ተጠሪ መግዛታቸው ባላከራከረበት የቅን ልቦና ገዥ ናቸው በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች የመወሰናቸው አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡በመሆኑም ከዚሁ ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የሟች ወ/ሮ አይከልክሉሽም ደስታ ብቸኛ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸው መረጋገጡን፣1ኛ ተጠሪ የሟች ወራሽ ነኝ በማለት ይዘው የነበሩት ማስረጃ በአመልካች ተቃዋሚነት መሰረዙን፣አመልካች በውርስ ይገባኛል የሚሉት ቤትን በሟች ወ/ሮ አይከልክሉሽም ደስታ እና በ1ኛ ተጠሪ ወላጅ እናት በእማኝይ ወ/ጊዩርጊስ ስም የተመዘገበ እንደሆነና ቤቱም እኚህ አሟች ከሞቱ በኋላ 1ኛ ተጠሪና የአመልካች እናት በጋራ በውርስ ሃብትነት ይጠቀሙት እንደበር፣የአመልካች እናት ከሞቱ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ብቸኛ ወራሽ ነኝ በማለት አሳውጀው የወራሽነት ማስረጃ ይዘው የቤቱን ስመ ሃብት አዙረው የተገኙ መሆኑን፣ይህን ቤት በመንደር ውል ለአሁኑ 2ኛ አመልካች በብር 115,000.00 1ኛ ተጠሪ መሸጣቸውን ከውርስ ማጣራት ሂደቱ ጀመረው አምነው የሚከራከሩ ቢሆንም ሰነዱ ግን በውርስ አጣሪውም ሆነ በፍርድ ቤት ያልቀረበ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው አንድ ንብረት ለሌላ ሰው በሕጋዊ መንገድ ሊያስተላልፍ የሚችለው በንብረቱ ላይ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት መብት ሲኖረው ብቻ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡በሌላ አገላለፅ በሕግ ጥብቃ የማይደረግለት ወይም የሌለ መብት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ አይችልም፡፡ይህ ተቀባይነት ያለው የሕግ መርሕ ነው፡፡የሌላ ሰው ንብረት ለመሸጥ፣ለማስተላላፍ ወይም በዋስትና ለማስያዝ ወይም የተመደበበትን አገልግሎት ለመለወጥ ሕጋዊ የሆነ ስልጣን ሊኖር ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣም 1ኛ ተጠሪ በአከራካሪው ቤት ግማሽ ድርሻ ላይ በሕጉ አግባብ ጥብቃ የሚደረግላቸው መብት ሳይኖር ቤቱን ለአሁኑ 2ኛ አመልካች በመንደር ውል አስተላልፌአለሁ በማለት መከራከራቸው በሌላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብት ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2884 አግባብ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ አይደለም፡፡አንድ ሰው ለሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚችለው በህግ ጥበቃ የሚደረግለትንና ያለውን መብት እንጂ የሌለውን መብት ሊሆን እንደማይችል ተቀባይነት ያለው የህግ ጽንሰ ሐሳብ በመሆኑ የአቶ እንዳልካቸው አካሉና የአቶ ግርማ ወ/የስ ተግባር የተጠሪን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀፅ 40(1)(2) ድንጋጌዎች ጥበቃ ያገኘውን የንብረት ባለቤትነት መብት ሊጎዳ አይገባም፡፡

1ኛ ተጠሪ የወ/ሮ አይከልክሉሽም ደስታ ወራሽ ነኝ በማለት ማስረጃ ከያዙ በኋላ የቤቱን ስመ ሃብቱን የሚያሳይ ማስረጃ መያዛቸውን ገልጸው የተከራከሩ ሲሆን አመልካችም ቢሆን ይህንኑ ሳይክዱ ስመ ሃብቱ የዞረው በሐሰተኛ የወራሽነት ማስረጃ በመሆኑ በሕግ ፊት ውጤት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሠጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀስውን ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊገመት እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ይህን ማስረጃ የያዘ ሰው ደግሞ ሃብቱን በሕጉ አግባብ ከሸጠ ተግባሩ ሕገ ወጥ የሚባልበት ምክንያት የለውም፡፡አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን መብት በሕጋዊ መንገዶች ለሌላ ለማስተላለፍ መብት አለውና፡፡ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ስር የተመለከተው የሕግ ግምት ፍፁም የሆነ ወይም ደምዳሚ ማስረጃ አይደለም፡፡ግምቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ስለመኖራቸው በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት ነው፡፡በመሆኑም አንድ ሰው በአስተዳደር አካል የተሰጠ ካርታ በመያዙ ብቻ በካርታው የተጠቀሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሕጋዊ ባለሃብት እንደሆነ ሕጉ ግምት ቢወስድለትም ይህ ግምት ግን ካርታው የተሰጠበትን አግባብ ከደንቡ፣ከአሰራሩና ከስልጣኑ ውጪ እንዲሁም በማይረጋ የምስክር ወረቀት መሰረት ማስረጃው ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ የሕጉን ሕሊናዊ ግምት ማፍረስ እንደሚቻል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ በግልፅ ያሳያል፡፡ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ በሐሰተኛ የወራሽነት ማስረጃ ስመ ሃብቱን መያዛቸው የአመልካችን መብት ቀሪ የማያድርገው መሆኑን ከተጠቃሽ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዙት ሙሉ ባለመብት ካልሆኑ 1ኛ ተጠሪ በመንደር ውል በመግዛት መሆኑ ከተረጋገጠ ሕጋዊ ባልሆነ ሽያጭ መነሻ ቤቱን አግኝቼአለሁ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የአመልካችን ክርክር ዋጋ የሚያሳጣበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡1ኛ ተጠሪ ውሉን በውልና ማስረጃ ያላደረጉ መሆኑ ግልፅ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች የ2ኛ ተጠሪን ተግባር ሕጋዊ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት የቅን ልቦና ገዥ ናቸው በሚል ምክንያት ነው፡፡ይሁን እንጂ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሕጋዊ መብት የሌለው ሰው በውሉ ለገዥው መድህን ለመሆን ግዴታ ገብቶ ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሃብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ የገዛውን ገዥ ሳይሆን ሻጩን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2882 እስከ 2884 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 997 ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት የምንገነዘበው ነጥብ ቢሆንም አመልካች ይህንኑ ግዴታ በተገቢው መንገድ ተወጥተዋል ለማለት የሚቻል ያለመሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያስገነዝብ ሁኖ ተገኝቷል፡፡2ኛ ተጠሪ በመንደር ውል ቤቱን የገዙ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ተገቢውን ማጣራት አድርገውና በጥንቃቄ የገዙና ቅን ልቦና ያላቸው ናቸው ተብሎ ሕጋዊ ገዥ ናቸው ሊባሉ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በአጠቃላይ 2ኛ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት የገዙት የፍርድ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካለመሆኑ በላይ የመንደር ውሉን ሰነድን እንኳን ያላቀረቡት ካርታው በ1ኛ ተጠሪ ስም ተሰርቶ ተሰጥቷል በሚል ምክንያት ብቻ የሽያጭ ውሉ ሕጋዊ ነው ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1)(2) የተከበረላቸው እና በፍትሓ ብሔር ሕጉ ስለውርስ በሚደነግጉት ድንጋጌዎች ጥበቃ የሚደርግለት የባለሃብትነት መብታቸው ከሕግ አግባብ ውጪ ስለመደረጉ በተረጋገጠው የሽያጭ ውል ቀሪ የሚሆንበት ምክንያት አለመኖሩን በመገንዘብ የበታች ፍርድ ቤቶች የአከራካሪው ቤት ሕጋዊ ባለሃብት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ናቸው በማለት በአይነት የውርስ ሃብት ነው በማለት መወሰን ሲገባቸው አመልካች የሸያጩን ገንዘብ እንዲወስዱ ሲሉ የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 32341 ሚያዚያ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 118918 ታህሳስ 09 ቀን 2005 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ቀበሌ 14/21 ቁጥሩ 482 የሆነው መኖሪያ ቤት በ1ኛ ተጠሪና በሟች አይከልክሉሽም ደስታ በውርስ ተይዞ የቆየ በመሆኑና ለ2ኛ ተጠሪም በሕጋዊ ሽያጭ ያልተላለፈ በመሆኑ የአመልካች ግማሽ ድርሻ በውርስ ሕጉ በተመለከቱት የክፍፍል ስርዓቶች መሰረት የሚገባቸው ነው ብለናል፡፡ የኪራይ ገንዘቡን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
3. የ2ኛ ተጠሪ የሽያጭ ውል ሕጋዊ አይደለም ብለናል፡፡2ኛ ተጠሪ የሽያጩን ገንዘብ ከ1ኛ ተጠሪ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፤

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86049

መስከረም 20 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች - ተሻገር ገብረሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ሻፊ አብዱራህማን አብዱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ አንሻ እንድሪስ - ቀረቡ

2. አቶ ኢተፋ በቀለ
3. ወ/ሮ ደምሌ (ፋጡማ) አሊቶ } አልቀረቡም

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በኢሉ ገላን ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመፋለም የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርበው በአጃጂ ከተማ ውስጥ ቁጥሩ 858 እና ቁጥሩ 859 የሆነ ቤት አለኝ፡፡ በእነዚህ ቤቶች ከዚህ በፊት የእህል ንግድ ሳከናውንባቸው ቆይቼ ኪሳራ ስለደረሰብኝ ቤቶቹን ዘግቼ ሥራ ፍለጋ ሌላ ቦታ ሄጄ ቆይቻለሁ፡፡ በዚህ ወቅት የተዘጉትን ቤቶች ቀበሌው በመክፈት ለሌሎች ሰዎች ሲያከራየው ቆይቷል፡፡ እኔም ከሄድኩበት ተመልሼ ቤቱ እንዲለቀቅልኝ ስጠይቅ ከተማው አስተዳደር በጽሁፍ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የቀበሌው አስተዳደርም ለተከራዮቹ(ተጠሪዎች) በጽሁፍ አሳውቋል፡፡ ተከሳሾችም ቤቱን ለእኔ ኪራይ እየከፈሉ ለመኖር ጠይቀውኝ በወር ብር 5 (አምስት ብር) አከራይቻቸዋለሁ፡፡ እኔም የቤቱን ግብር ያለማቋረጥ እየከፈልኩ እገኛለሁ፡፡ ሆኖም በማላውቀው ሁኔታ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ የቀበሌው አስተዳደር ቤት ኪራይ ከተከራዮች እየተቀበለ በመሆኑና ተከሳሾች ቤቱን እንዲለቁ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቀበሌው የቤት ኪራይ መቀበሉን እንዲያቆምና ተከሳሾች ቤቱን እንዲያስረክቡኝ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተጅ ቀበሌ 01 በአንደኛ ተከሳሽነት ቀርቦ ቤቱ በደርግ ጊዜ የተወረሰ ነው፡፡ የከሳሽ ንብረት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪዎችም(ተከሳሾች) ቤቱ መንግስት ወርሶን ያከራየንና ለረዥም ጊዜ በእጃችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቆየ ነው፡፡ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፣ ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

2. የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ የአምቦ ከተማ አስተዳደር ክስ የቀረበባቸውን ቁጥራቸው 858 እና 859 የሆኑ ቤቶች ቀበሌው አላግባብ የያዘባቸው መሆኑን በማረጋገጥ ቤቱ እንዲለቀቅ ደብዳቤ ጽፏል፡፡ የቀበሌው አስተዳደርም ተከራዮቹ ቤቱን ለከሳሽ እንዲለቁ በማለት በደብዳቤ አሳውቋል፡፡ ከዚህ በኋላ ተከሳሾች ቤቱን ከከሳሽ ፈቃድ ውጭ የሚይዙበት የህግ መሰረት የሌለ በመሆኑ ቤቱን ለቅቀው ለከሳሽ እንዲያስረክቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከሕግ ውጭ የተወረሱ ቤቶች መዳኘት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት አይደለም፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ሥልጣን የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ጸንቷል፡፡

3. አመልካች በ01/05/2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ቤቶቹ ከአዋጅ ውጭ የተወረሱ ቤቶች አይደሉም፡፡ ቤቶቹን ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የእህል ንግድ ሳከናውንባቸው የነበሩ የግል ንብረቶች መሆናቸውንና የንግድ ኪሳራ ሲደርስብኝ ዘግቼ ወደሌላ ቦታ በመሄድ ቀበሌው ከፍቶ ሲያከራያቸው የነበሩ መሆናቸውን በአስተዳደሩ ክፍል ተረጋግጧል፡፡ ይህም በመሆኑ እኔ ያቀረብኩት የመፋለም ክስ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ሆኖ እያለ፤ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትና የሰበር ችሎት ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የላቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በ11/06/2005ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቱ በመንግስት የተወረሰ ሥለሆነ አመልካች አላግባብ ተወርሶብኛል የሚል ከሆነ ለፕራይቬታይዜሽን ኤጅነሲ ያቅርቡ በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በ28/06/2005 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቶች ሥልጣን የላቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች ለሥር ፍ/ቤት ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ መሰረታዊ ባህሪና ይዘት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች እንዲለቀቁለት የሚጠይቃቸው ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት በትርፍነት ያልተወረሰና ከአዋጅ ቁጥር 47/1967 በኋላ በእሱ እጅ የነበሩና የእህል ንግድ ሲያከናውንባቸው የነበሩ መሆናቸውን በክሱ የገለጸ መሆኑን ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ቤቶቹ ከአዋጅ ቁጥር 47/1967 ውጭ በባለስልጣን ቃል ትዕዛዝ ወይም በቀላጤ ያልተወረሱ መሆኑና አመልካች በሚነግድበት ወቅት ስለከሰረና ቤቶቹን ዘግቶ አካባቢውን ለቆ ለረዥም ጊዜ በመጥፋቱ የቀበሌው አስተዳደር ቤቶቹን ከፍቶ ማስተዳደርና ለሌሎች ሰዎች ማከራየት የጀመረ መሆኑን በክሳቸው ገልፀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

6. ይህ አመልካች በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆነው ተጅ ቀበሌ 01 ቀበሌ ቤቶቹን የያዘውና ማስተዳደር የጀመረው በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ተወርሰው ወይም ከአዋጅ ውጭ በባለስልጣን ቃል ትዕዛዝ ወይም በቀላጤ ሳይሆን የቤቶቹ ባለቤት በመጥፋቱና ቤቶቹ ተዘግተው ረዥም ጊዜ በመቆየታቸው በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 2257 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት የስራ አመራር ተግባር ለመፈፀም በወሰደው እርምጃ ነው የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ አመልካች በማስረጃነት ያቀረባቸውና አንቦ ከተማ አስተዳደርና ቀበሌው አስተዳደር የጻፏቸው ደብዳቤዎች ይህንን የአመልካችን ክስ ባህሪና ይዘት የሚመለከቱ ናቸው፡፡
7. በጥቅሉ ሲታይ አመልካች ክስ ያቀረበው በአዋጅ የተወረሰ ቤት ለማስመለስ ወይም ከአዋጅ ውጭ በባለስልጣን ቃል ትዕዛዝ ወይም በቀላጤ የተወሰደባቸውን ቤት ለማስመለስ አይደለም፡፡ አመልካች ክስ ያቀረበው በቤቶቹ ላይ ያለውን የባለሃብትነት መብት ለማስከበርና ለመፋለም ነው፡፡ ይህንን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች እንጅ የፕራይቬታይዜሽን ኤጅንሲ ወይም ሌላ አካል አይደለም፡፡ የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቶች ሥልጣን የላቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቶች ሥልጣን የላቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ይግባኝና አመልካች የሰጠውን መልስ በመመርመር በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጪ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 89504

መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን

2ኛ. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት } የቀረበ የለም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ግራ ቀኙ በሥር ፍ/ቤቶች ባደረጉት ክርክር ከተረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳዮች በመነሳት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በመዳረግ ለቀረበው የጉዳት ካሣ ክስ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የአሁን አመልካች ለንብረት ጉዳት ካሣ መድን በመግባቱ ምክንያት የመድን ሽፋን የተሰጠው መኪና በሶስተኛ ወገን ተግባር ጉዳት ደርሶበታል በሚል በገባዉ የመድን ዋስትና ግዴታ መሰረት በተጎዳው መኪና ባለቤት እግር ተተክቶ በመዳረግ ክስ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው በተጎጂው መኪና ባለቤት እግር ተተክቶ በመዳረግ የሚጠይቀውን የጉዳት ካሣ ገንዘብ መጠየቅ የሚችለው ከማን ነው? የሚለውን ነው፡፡

በቀጥታም ሆነ በመዳረግ ሶስተኛ ወገን ተግባር ጥፋት ሳቢያ በደረሰ ጉዳት የጉዳት ገንዘብ ከማን ላይ መጠየቅ እንደሚቻል ጉዳዮን በቀጥታ በሚመለከተው አግባብነት ካለው የፍ/ብሔር ህግም ሆነ በአንድ ጉዳይ በተከሳሽነት መጨመር የሚገባቸው ወይም የሚችሉት ወገኖች እነማን እንደሆኑ በሚያመለክተው ስነ-ስርዓታዊ ህጐች በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ መሰረታዊ ሆነ ሥነ-ስርዓታዊ ድንጋጌዎች መሰረት ከሳሽ የሆነው ወገን በክስ የሚጠይቀውን ገንዘብ አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ማግኘት እንዲችል እነማንን አጣምሮ መክሰስ እንደሚችል ከመደንገጉ በቀር በጉዳት ካሣ ክስ ምክንያት ሊጠየቁ የሚችሉትን ወገኖች ሁሉ አጣምሮ መክሰስ እንዳለበት በህጉ ግዴታ አልተጣለበትም፡፡ አጣምሮ መክሰስ የሚገባውን ሁሉ በቶሎ እና ክርክሩ በተነሣበት የዳኝነት አካል አጣምሮ ያለመክሰሱ ተግባር በማግኘትም ሆነ በማጣት ረገድ በእራሱ ላይ ጉዳት ከሚያስከትል በቀር በጉዳዩ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚመለከታቸውን ሁሉ በአንድ ላይ በአንድ ፍ/ቤት አጣምሮ እንዲከስ በህግ የተጣለበት ግዴታ የለም፡፡ በዚህም መሰረት የአሁን አመልካች የጉዳት አድራሹ መኪና ባለቤት ነው ባለው በአሁን 1ኛ ተከሳሽ ላይ ክስ አቅርቧል፡፡ ይህ 1ኛ ተከሣሽም ጉዳት ያደረሰው መኪና ባለቤት ስለመሆኑ እንደ ህጉ አነጋገር የመኪናውን ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ በማረጋገጥ የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1677፣1896 እና 2081ና በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 36/2/ መሰረት የአንድነትና የነጠላ ግዴታ ካለባቸው ወገኖች መካከል የአሁን አመልካች በከሳሽነቱ የመኪናዉ ባለቤት ላይ ክስ የማቅረብ መብት ያለው በመሆኑና 1ኛ ተጠሪም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 18 እና 2156 መሰረት ኃላፊነቱን በመጨረሻ በሚሸከመው ወገን ላይ በተራው ተተክቶ ክስ ከሚያቀርብ በቀር ልከሰስ አይገባም በማለት ለመከራከር ህጉ መብት አይሰጠውም፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ ለዚህ ጉዳይ መነሻ በሆነው ክስ ላይ መጠቀስ ያለበት የመኪናው ባለቤት ማን ነው? የሚለው ሳይሆን ተሸከርካሪው ጉዳት በደረሰበት ጊዜ ለግል ጥቅሙ ሲገለገልበት የነበረው ማን ነው? የሚለው ነው፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የመኪናው ባለቤት መሆኑ ቢረጋገጥም ከሳሽ ይህንኑ 1ኛ ተጠሪን ለመክሰስ ከህግ የመነጨ መብት የለውም የሚለውን ትርጉም በመከተል የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ከዚህ በላይ በፍርድ ሐተታው ከተገለፀው ህጋዊ ምክንያት አንፃር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ይግባኝ ሰሚው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ እንደቅደም ተከተሉ በኮ/መ/ቁጥር 126387 ጥር 15 ቀን 2005 ዓ.ም እና በኮ/መ/ቁጥር 190104 ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጡት ፍርዶች ሁሉ ተሽረዋል፡፡
2. የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሰ/ቁ 5-01-00002 አ.አ የሆነው ተሸከርካሪ ባለቤት በመሆኑ ምክንያት ብቻ ለቀረበበት የጉዳት ካሣ ገንዘብ ክስ ከህጉ የመነጨ የመካስ ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡ ስለሆነም የመካስ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ታውቆ በሌላው የኃላፊነት ነክ ክርክሩ ረገድ ማለትም ጥፋት አለ የለም? ጉዳት ደርሷል አልደረሰም? የጉዳት ልክስ ምን ያህል ነው በሚል በፍሬ ነገር ክርክር ደረጃ የተነሣ ክርክር ካለ በስር ፍ/ቤት በአቤቱታ ፅሑፍ አቀራረብ የክርክር ደረጃ አንስቶ ከተከራከረበት ነጥብ አንፃር በማየት ጉዳዩ ታይቶ ይወሰን ዘንድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 341 መሰረት ጉዳዩን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ደረጃ የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 91710

ህዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሕጻን ሪያን ሚፍታህ ሞግዚት ወ/ሮ ፋጡማ በሽር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ኤልሲውዲ ኬብልስ ኃላፊነቱ የተ.የግል ማህበር የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጉዳት ካሳን የሚመለከት ነው፡፡የአመልካች ሞግዚት በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ የከሳሽን እውቅናና ፈቃድ ሳያገኝ የህፃኑን ፎቶ ከሰኔ ወር 2000 ዓ/ም ጀምሮ ለማስታወቂያ ስራ በመጠቀም ግዙፍ የሆነ የማስታወቂያ ሰሌዳ በማሰራት ድርጅቱንና የድርጅቱን ምርቶች በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ቦታዎች እና ግብጽን ጨምሮ በተለያዩ ሃያ አምስት ሀገራት በኢተርኔት ሲያስተዋውቅ መቆየቱን፣ይህ ሕገ ወጥ ተግባር በመሆኑ ተገቢውን የካሳ ክፍያ እንዲፈፅም ቢጠየቅም ፈቃደኛ ሳይሆን ቆይቶ በኋላ ላይ ብር 15,000.00 (አስራ አምስት ሺህ ብር) ለመክፈል ቢደራደሩም ክፍያው በማስታወቂያ ስራ ከተገኘው ጥቅም ጋር ሲነፃፀር ተመጣጣኝ ያልሆነና አነስተኛ በመሆኑ ከሳሽ ሊስማሙ ያለመቻላቸውን ዘርዝረው ከሰኔ ወር 2000 ዓ/ም ጀምሮ እስከ የካቲት ወር 2004 ዓ/ም ለማስታወቂያ ስራ ለተጠቀመው የህፃኑ ፎቶ ብር 400,000.00 (አራት መቶ ሺህ) እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ እና የፍሬ ነገር ክርክሮችን ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱንም የተጠሪ በኩል የቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገር ደረጃ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው ሲሆን የካሳውን መጠንም በተመለከተም በርትዕ ብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) ሊሆን እንደሚገባው ወስኖ ይህንኑ የገንዘብ መጠን ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የአሁኗ አመልካች ደግሞ የካሳ መጠኑ ላይ ቅር በመሰኘት መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱ የአመልካችን መስቀለኛ ይግባኝ ሰርዞ በተጠሪ ይግባኝ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ለክሱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ያፀናው ሲሆን በካሳ መጠኑ ላይ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ግን በማሻሻል ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) እንዲሆን ወስኗል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በጉዳዩ ላይ ካሳን በተመለከተ ሁለቱም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል ምክንያት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በዕሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ተጠሪ የህጻኑን ፎቶ ለማስታወቂያ ስራ የተጠቀመበት ስለመሆኑና ይህንንም ሲያደርግ ከሕፃኑ ሞግዚት ተገቢውን ፈቃድ ያላገኘ መሆኑ እንዲሁም በማስታወቂያው ተጠሪ የኤሌክትሪክ ኬብል ምርቶችን በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ቦታዎች በሰሌዳ ለጥፎ ማስታወቁን፣በግብጽና በሌሎች <u>ሃያ አምስት ሃገራት</u> በኢንተርኔት ሲያስተዋውቅም የሕፃኑን ፎቶ ጥቅም ላይ ያዋለ መሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ተጠሪም ቢሆን በዚህ ረገድ በበታች ፍርድ ቤቶች የተደረሰው ድምዳሜ ስርዓቱን ጠብቆ በበላይ ፍርድ ቤት ስለመቀየሩ ገልጾ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ስለሆነም ተጠሪ የህጻኑን ፎቶ ለኤሌክትሪክ ኬብል ምርቶቹ ለማስተዋወቅ ያለሕፃኑ ሞግዚት ፈቃድ መጠቀሙ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27 ድንጋጌ ስር ባለፎቶግራፉ ወይም ባለስዕሉ ካልፈቀደ በቀር የማንም ሰው ፎቶግራፍ ወይም ስዕል በሕዝብ አደባባይ ሊለጠፍም ሆነ ሊባዛ ወይም ሊሸጥ እንደማይቻል የተመለከተ በመሆኑና በፍ/ሕ/ቁጥር 28 ስር የተመለከተው ልዩ ሁኔታ ስለመኖሩም ተጠሪ ጠቅሶ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የሌለ በመሆኑ የሕፃኑ ፎቶ ጥቅም ላይ ለዋለበት የማስታወቂያ ስራ ተጠሪ ካሳ የማይከፍልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡በዚህ ሰበር አከራካሪ የሆነው የከሳ መጠኑ ሲሆን ካሳው የሚከፈልበትን አግባብ በተመለከተ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የሕጉ ክፍል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) ድንጋጌ ስር አስፍሯል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት በርትዕ አስፈላጊ ሁኖ ሲታይ ስዕሉን በአደባባይ በመለጠፍና በመሸጥ የተጠቀመው ሰው በዚሁ ምክንያት ያገኘው ሀብት ተመዛዛኝ በሚሆንበት መጠን ዳኞች ካሳ እንዲከፍል ሊወስኑበት እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የካሳውን መጠን ክዶ በመከራከሩና አመልካችም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 በተመለከተው አግባብ ትክክለኛውን የካሳ መጠን በማስረጃ ያለማስረዳታቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የካሳውን መጠን ብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) እንዲሆን የወሰነ ሲሆን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘትም በስርዓቱ መሰረት የመስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የካሳ መጠኑን የሕጻኑ ፎቶ በማስታወቂያው ከተገለፁት የምርት አይነቶች ጋር የሚኖረውና ሊያስገኝ ከሚችለው ጥቅም አንፃር፤ከነባራዊው ሁኔታ በመነሳት በመመርመር በስር ፍርድ ቤት የተወሰነው የካሳ መጠን የባዛ ሁኖ ማግኘቱን ጠቅሶ ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) የካሳ መጠን ሊሆን እንደሚገባ ወስኗል፡፡ይህ የበታች ፍርደ ቤቶች የካሳ ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡የአመልከች የመስቀለኛ ይግባኝም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ታይቶ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ይህም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 340 እና 337 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የተከተለ መሆኑን ከሚያስገነዝብ ውጪ የአመልካች የመስቀልኛ ይግባኝ ሳይታይ የታለፈ ነው ለማለት የማያስችል በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝም የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም ካሳን አስመልክቶ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳት ካሳ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት 182576 መጋቢት 18 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 135075 ሰኔ 24 ቀን 2005 ዓ/ም የተሻሻለው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ለአመልካች በርእት ብር 150,000.00(አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ተጠሪ እንዲከፍል በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈፀመም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የልዩነት ሐሣብ

በዚህ ጉዳይ የፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ የህፃን ሪያን ሚፍታህን ፎቶ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ላሉት 4 ዓመታት ያለፈቃዳ ምርቱን በሐገር ውስጥ ግብጽ እና በሌሎች 25 ሃገራት በተለያዩ መንገዶት ሲያስተዋውቅበት መቆየቱን ካረጋገጠ እና ለክሱም ተጠሪ ኃላፊ መሆኑን ከወሰነ በኃላ የካሣ መጠኑን በተመለከተም ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 2090፣ 2091፣2102 እና 29/2/ ድንጋጌዎች ይዘት አኳያ በመመርመር አመልካች እንዲከፍለው የጠየቀውን የካሣ ክፍያ ብር 400,000 እንዳለ ባለመቀበል እና በሌላ በኩልም ተጠሪ የህፃኑን ፎቶ በመጠቀም ያገኘው ጥቅም በትክክል ምን ያህል እንደሆነ ሂሣቡ ተሰልቶ በግልጽ የታወቀ ነገር ባይኖርም ሆኖም ንግ ፎቶውን ለምርቱ ማስታወቂያነት የተጠቀመበትን የጊዜ እርዝማኔ እና ማስታቂያ የተሰራጨበትን ሃገራት ብዛትና የስርጭት አድማሱን ግምት ውስጥ በማስገባት እና በሁለቱም በኩል ግንዛቤ ውስጥ ገብተው ሊታዩ የሚገቡትን አጠቃላይ ሁኔታዎች በመመዘን ተጠሪ በርትእ ብር 200,000 ለህፃን ሪያን እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

በተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ኃላፊነትን በተመለከተ በበታች ፍ/ቤት የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል ሙሉ በሙሉ ካፀና በኃላ የካሣ መጠኑን በተመለተ የሰጠውን የውሣኔ ክፍል ግን ብር 200,000 የተጋነነ ነው በማለት መጠኑን ወደ ብር 150,000 በመቀነስ ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ሆኖም ግን በመርህ ደረጃ የካሣ መጠንን አስመልክቶ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ደኞች በተወሰነ ፍርድ ላይ ለበላይ ፍ/ቤቶች ይግባኝ ለማለት አይቻልም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2152 ሥር ከተደነገገው አኳያ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም የካሣ መጠንን በተመለከተ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ የሚቀፈቀደው በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2153 ሥር እንደተመለከተው ልዩና የተበቁ ሁኔታዎች ሲኖሩ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎችም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካሣ አከፋፈሉን ሲወስን ግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ የማይገባቸውን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ እንዲገቡ አድርጐ ከሆነ ወይም ግንዛቤ ውስጥ መግባት የነበረባቸውን ሁኔታዎች ሣያስገባ ቀርቶ እንደሆነና፤
- የካሣ መጠኑም በግልጽ ከአእምሮ ግምት ውጭ በሆነና የተወሰነውም በማድላት ወይም በዝንባሌ መሆኑ እርግጥ ሆና የተገኘ እንደሆነ፤
- እንዲሁም በፍ/ቤቱ የተወሰነው የካሣ ገንዘብ በሒሣብ ረገድ ስህተት ያለበት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከፍ ሲል እንደተገለፀው ለአመልካች ሊከፍል የሚገባውን የካሣ ክፍያ ከማስታወቂያው ጊዜ ቆይታ እና የስርጭት እንድማሱን ግምት ውስጥ በማስገባት እና ጉዳዩንም ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 29/2/፣ 2102፣2090 እና 2091 ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስ አኳያ አገናዝቦ ተጠሪው ካገኘው ጥቅም ጋር ተመዛዛኝ ነው ያለውን ብር 200,000 ለአመልካች እንድከፍለው ወስኗል ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ እንደሚታወቀው ልጆች በተፈጥሮአቸው ከአዋቂ ሰው በተለየ ሁኔታ ተወዳጅ እና የሰውን ስሜት የሚስቡ በመሆናቸው ተጠሪም ከዚህ ውጭ ባልሆነ ምክንያት ያለምንም የልጅም ሆነ የልጁ ሞግዚት ፈቃድ ውጭ ፎቶውን ለምርቱ ማስተዋቂያነት ተጠቅሞ ጥቅም እስካገኘ ድረስ ለህፃኗ ካሣ የማይከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ በዚሁ አግባብ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በርትእ ተገቢ ነው ያለውን ተመዛዛኝ የሆነ ውሣኔ ሰጥቷል ሆኖም ግን ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2152 እና 2153 ድንጋጌዎች ይዘት አኳያ በበታች ፍ/ቤት የተሰጠውን የኪሣራ ገንዘብ በይግባኝ ክርክር ደረጃ ተመልክቶ ውሣኔውን ለመለወጥ የሚያስችለው በቂ የሕግ እና የፍሬ ነገር ምክንያት ሣይኖር የተጋነነ ነው በሚል ምክንያት ወደ ብር 150,000 መቀነሱ አግባብ አይደለም፡፡ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የሕጉን ድንጋጌወች ይዘትም ያገናዘበ አይደለም ይህ በሕጉ ረገድ የተፈፀመው ስህተትም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት መታረም ሲገባ በአብላጫ ድምጽ እንዲፀና መደረጉ ተገቢ አይደለም በማለት ስሜ በ3ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ የልዩነት ሐሳቤን አስቀምጫለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92020

ታህሣስ 15 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አሕመድ

አመልካች፡- 1. የኢ.ፌ.ዲ.ፌዴሬሽን ምክር ቤት
2. አቶ ተስፋዬ ጌታሁን
} ነ/ፈጅ ጥሩነሽ ገረመው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ቄስ ማሞ ይታፈሩ ቀረቡ

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ምንም የጥቅም ግንኙነት በሌለበት ሁኔታ አቅመ አዳም ያልደረሰን ሕፃን በተሸከርካሪ ጭኖ በመንዝ ሂደት ተሸከርካሪው ተገልብጦ ሕፃኑ ለሞት ሲዳረግ የመኪናውን ባለንብረትና አሽከርካሪው ስላለባቸው ፍትሐብሔር ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የተታየው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ተከሣሽ፣ ተጠሪ ደግሞ ከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ 2ኛ አመልካች አሽከርካሪ በመሆን የ1ኛ አመልካች ንብረት የሆነውን የሰሌዳ ቁጥር 4-14199 ኢት ፒካፕ የሆነ መኪና ሲያሽከረክር ግንቦት 08 ቀን 2002 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍል ከተማ ቀበሌ 03/04 ብረት ድልድይ ከተባለ ቦታ ወደ ፈረንሣይ ኢንባሲ አቅጣጫ እያሽከረከረ በውጪ እቃ መጫኛ ላይ እድሜው 13 አመት የሆነ ደረጃ ማሞ የተባለ ህፃን ጭኖ በመንዝ ላይ እያለ ሕፃኑ ወድቆ እንዲሞት ማድረጉ ሕፃኑን በሕይወት እያለ ጫማ በመጥረግ ለተጠሪ ገቢ ሲያገኙላቸው የነበረ መሆኑን በጉዳቱ ምክንያት ለህክምናም ሆነ ለቅብር ስነ ስርዓት ወጪ ያወጡ መሆኑን፣ ሕፃኑ በሕይወት ቢኖሩ ኑሮ እድሜው ሃምሳ ዓመት እስኪሞላው ለተጠሪ ያስገኝ የነበረው የቀን ገቢ ብር 8.00 እንደሚቀጥልና በመሞቱ ምክንያት ግን መቋረጡን ዘርዝረው ይህንኑ ገቢና በጉዳቱ ምክንያት ያወጡትን ወጪ በድምሩ ብር 119,870.00 (አንድ መቶ አስራ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ብር) እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ለክሱ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑንና የቀረበው የካሳ ክፍያም የሕግ መሰረት የሌለው መሆኑን

ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ መድን ድርጅትም በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ተደርጓል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና የተጠሪን ምስክሮች በመስማት ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾችን ለክሱ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን ጣልቃ ገቡን ግን ከክሱ ነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡ የካሳውን መጠን በተመለከተም በርትዕ በድምሩ ብር 31,300.00 (ሰላሳ አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር) እንዲሆን ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኙ በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን አመልካቾች ለጉዳቱ ኃላፊ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በክርክሩ ውስጥ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡት ነጥቦች የተጠሪ ልጅ የሕዝብ ማመላለሻ ባልሆነው የ1ኛ አመልካች መኪና በ2ኛ አመልካች በእቃ መጫኛው ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ ወድቆ ለሕልፈተ ሕይወት መዳረጉና 2ኛ አመልካች የ1ኛ አመልካች ተቀጣሪ ሰራተኛ መሆናቸው፣ ለጉዳቱ መድረስ ጥፋቱ የሹፌር መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣ በመሰረቱ የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2089/1/ የሚገኘው ከውል ውጪ ስለሚደርስ አላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ በሚለው በፍታብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13 ስር ነው፡፡ ተጠሪ አመልካቾች የከሰሱትም ከውል ውጪ ደረሰ የሚለውን ኃላፊነት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በስር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው ህፃኑ የተባለው ጉዳት የደረሰበት በ1ኛ አመልካች መኪና በመገጨቱ ሳይሆን፣ በመኪናው ላይ በ2ኛ አመልካች እውቅና ተሳፍሮ ሲሄድ ከመኪናው በመውደቁ ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ መኪናው የ1ኛ አመልካች ንብረት ነው፡፡ ሆኖም መኪናው ገንዘብ በማስከፈል ሰዎችን የሚያጓጉዝ የንግድ መኪና ሳይሆን ለመንግስት ስራ ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ህፃኑ በመኪናው ላይ ስለመሳፈሩ 1ኛ አመልካች ያውቃል ወይም ማወቅ ይጠበቅበታል ተብሎ አይገመትም፡፡ መኪናው የተሰማራው ሰዎችን ለማጓጓዝ ባለመሆኑ 1ኛ አመልካች ሟቹን ህፃን በማሳፈር ያገኘው ጥቅም አለ ብሎ ለመደመደም የሚቻልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ እነዚህን ሁኔታዎች ከተረጋገጡ ቀጥሎ መታየት ያለበት አመልካቾች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆኑበት የሕግ አግባብ አለ? ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2081/1/ እንደተደነገገው የመኪናው ባለቤት መኪናው በሶስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ የሚሆንበት አግባብ አለ፡፡ ይህ እንግዲህ በአጠቃላይ የተቀመጠ የኃላፊነት መርህ ሲሆን፣ በቁ 2089 ደግሞ ልዩ ሁኔታ ማለትም የመኪናው ባለቤት ኃላፊ የማይሆንበት ሁኔታ ተደንግጎአል፡፡ ከድንጋጌው ርእስ መገንዘብ እንደሚቻለው ጉዳቱ የደረሰው ጥቅም በሌለው ግንኙነት ጊዜ ሲሆን የመኪናው ወይም ጉደቱን ያደረሰው ንብረት ባለቤት ኃላፊነት አይኖርበትም፡፡ ከላይ እንዳመለከትነው ተጠሪ በአመልካች መኪና የተገለገለው ለአመልካች ጥቅም በማያስገኝ ሁኔታ ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ 1ኛ አመልካች በዚህ ረገድ ጥፋት ፈጽሞአል አልተባለም፡፡ ይልቁንም የ1ኛ አመልካች ሹፌር፣ 2ኛ አመልካች ጥፋት መፈፀሙ ተረጋግጧል ተብሎ 1ኛ አመልካች ኃላፊነቱን እንዲወስድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መደረጉን የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በግልጽ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2089/2/ ድንጋጌ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አንድ ስር የተቀመጠውን መርህ በልዩ ሁኔታ ያስቀመጠ ሲሆን ባለሃብቱ ወይም ጠባቂው ጥፋት ማድረጋቸው ከተረጋገጠ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ድንጋጌው ያሳያል፡፡ በዚህ ልዩ ሁኔታ አነጋገር መሰረት የመኪናውን ባለሃብት ወይም ጠባቂውን ጥቅም በሌለው ግንኙነት መኖሩ ቢረጋገጥም ተጠያቂ ማድረግ የሚቻለው ባለሃብቱ ወይም ጠባቂው ጥፋት ካለባቸው ብቻ ነው፡፡ በድንጋጌው ስር ባለሃብት የሚለው ቃል ግልጽ ሲሆን ጠባቂ የሚለው ቃል ግን ግልጽነት የጎደለው መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ በዚህ ረገድ በተጠሪ በኩል ለቃሉ እየቀረበ ያለው ክርክር ባይኖርም ተቀጣሪ ሹፌር ጠባቂ በሚለው ቃል የሚሸፈን ነው ወይስ አይደለም የሚለው የሕግ ጥያቄን ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአማርኛው አቻ የእግሊዘኛ ቃሉ "holder" በሚል የተቀመጠ ሲሆን ይህ ቃል በሕግ መዝገበ ቃላት ከተሰጠው ትርጉም አንዱ a person who possesses or uses property በሚል የተቀመጠ መሆኑን ታዋቂው የብላክስ ሎው መዝገበ ቃላት ያሳያል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ጠባቂ የሚለው ቃል ለራሱ ጥቅም መኪናውን ይዞ የሚገኘውን ሰው መሆኑን ነው፡፡ ሹፌር በሰራው ምክንያት ላጠፋው ጥፋት ካልሆነ በስተቀር አሰሪው የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ባለሃብት ተጠያቂ የሚሆንበት አግባብ የሌለ መሆኑን ተጠቃሹን ድንጋጌው ከፍ/ህ/ቁጥር 2126/2/፣2127፣2130 እና ከፍ/ሕ/ቁጥር 2131 ድንጋጌዎች ይዘት ጋር በማገናዘብ ስናነብ የምረዳው ጉዳይ ነው፡፡ የ1ኛ አመልካች ሹፌር የሆኑት 2ኛ አመልካች ስራውን ሲሰሩ የፈፀሙት ጥፋት የሌለ ስለመሆኑ ወይም ጥፋቱ የ2ኛ አመልካች የግላቸው ስለመሆኑ 1ኛ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2126/2/ እና 2127 ድንጋጌዎች አግባብ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ ይልቁንም ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግላቸው ከሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሆነውን የተጠሪ ልጅ ህፃን ደረጀ ማሞን በእቃ መጫኛው ላይ 2ኛ አመልካች በስራ ላይ እያሉ ጭነው ለህልፈት መዳረጋቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ አንድ ባለሃብት ጥቅም በሌለው ግንኙነት ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነት የሚወስድበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 38457 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/ በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍ/ቤትን የሚያስገድድ የህግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ቢሆንም ይህ ጉዳይ ግን ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ ሊታይ የሚገባው ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም በሰ/መ/ቁጥር 38457 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመሰረታዊ ፍሬ ነገሮች በዚህ መዝገብ ከተያዘው ጉዳይ ጋር የሚገኛኝ ሁኖ ስላልተገኘ ለውሳኔው መሰረት ለማድረግ የምንገደድበት ሁኖ አልተገኘም ምክያቱም ጉዳቱ የደረሰው ህፃን ላይ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግለት ለሚገባው ለዚህ ህፃን 2ኛ አመልካች በ1ኛ አመልካች ስራ ላይ እንዳሉ ባሉበትና ጥንቃቄ ሳያደርጉ በተሸከርካሪ እቃ መጫኛ ጭነው ሲጓዙ ለህልፈት የዳረጉት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 38457 የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ሲነፃፀር ከተበዳዩም ሆነ በተበዳዩና በባለንብረቱ ከነበረው ግንኙነት ጋር የሚገናኝ አይደለምና ህፃናት በኢ.ፌ.ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 36/2/፣15 እና 25 ድንጋጌዎች እንዲሁም ኢትዮጵያ ተቀብላ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶም በሕፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3፣ 6/1/ በአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 4/1/፣5/1/ ድንጋጌዎች በሕይወት የመኖርና የአካል ደህነት ጥበቃ የተደረገላቸው መሆኑ ግልጽ ስለሆነ የካሳ ክፍያ ጉዳይም እነዚህን ሕጎችን ሁሉ እግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት ነው በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካቾች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የማይሆኑበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብ የለም ሲጠቃለልም የሰር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በውጤት ደረጃ ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 37334 ሰኔ 17 ቀን 2005 ተሰጥቶ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 140091 ሐምሌ 11 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብሕ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ጸንቷል
2. አመልካቾች በተጠሪ ልጅ ላይ ደረሰ ለተባለው የሞት ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ በድምሩ ብር 31,300.00 /ሰላሳ አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር/ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ በሚመለከት ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ

ት ዕ ዛ ዝ

ሐምሌ 22 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የመስማሚያ ሀሳብ

እኔ ስሜ በሁለተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምፅ አመልካች ለተጠሪ ካሳ መክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ደረሰበት ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ፡፡ ሆኖም አብላቻው ድምፅ በሌሎች መዝገቦችና ተሳፋሪዎች ካሳ ሊያገኙ አይገባም በማለት በሰጣቸው የህግ ትርጉሞች የማልስማማ በመሆኑ የመኪናው ባለሀብት ሰራተኛው ላጠፋው ጥፋት ተጠያቂ በመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2089 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ መሰረት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የመስማሚያ ሀሳቤን አስፍሬአለሁ፡፡

ቤ/ዮ

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 88432

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ/ም

ዳኞች፡-1. ተሻገር ገ/ሥላሴ

2. አልማው ወሌ

3. ዓሊ መሐመድ

4. ረታ ቶሎሣ

5. መስጠፉ አሕመድ

አመልካች፡- ወጣት ደሣለኝ ወንታ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ኡስማን መሐመድ የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በደቡብ ብሔር ብሔረሰሶችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በጋሞ ጎፋ ዞን የሳውላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ አመልካች ተጠሪ መንገድ ላይ በቆለለው አፈር ምክንያት በደረሰብኝ አደጋ የአካል ጉዳይ የደረሰብኝ ስለሆነ ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ በሣውላ ከተማ ኩሪቲ 01 ቀበሌ በሚገኘው መኪና መንገድ ተከሣሽ /ተጠሪ/ ለቤት መምረጊያ የሚሆን አፈር ቆልሏል፡፡ ተከሣሽ የቆለለው አፈር በምሽት ለማየት የሚያስቸግር ሲሆን ተከሣሹ ምልክት አላስቀመጥም፡፡ ከሣሽ በመንገዱ መስከረም 13 ቀን 2004 ዓ.ም በምሽቱ በአንድ ሰአት የሞተር ሣይክል እያሽከረከኩ ስንዝ ከማይታየው ተከሣሽ በቆለለው አፈር ላይ በመውጣቱ ሞተር ሣይክሉ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ አደጋ ደርሶብኛል፡፡ በደሰረብኝ አደጋ 12 የፊት ጥርሶች ወልቀዋል፡፡ የመንጋጋ ጥርሴም ጉዳት ደርሶበታል ስለዚህ ተከሣሹ በአውራ ጉዳና ላይ በግልጽ በማይታይ ሁኔታ ያለምልክት በቆለለው አፈር ምክንያት ለደረሰብኝ ጉዳት ብር 108810 /አንድ መቶ ስምንት ሺ ስምንት መቶ አስር ብር/ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ ኃላፊነት የሚያስከትል ምንም ተግባር ያልፈፀምኩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝ ለአደጋው ተጠያቂ መንጃ ፈቃድ ለሌለው ለከሣሽ ሞተር ሣይክል ያዋሠው ሠውና ከሣሽ ነው፡፡ ከሣሽ መንጃ ፈቃድ አለኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

2 የሥር ፍርድ ቤት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሞተር ሳይክሉ ከቁጥጥር ውጭ የወጣው የቴክኒክ ብቃት ስለሌለውና አሽከርካሪው (ከሳሽ) ብቃት ስለሌለው ሊሆን ስለሚችል ተከሳሽ ለከሳሽ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችን ይግባኝ ከመረመረና የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተከሳሽ በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት ለሥር ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡የሥር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል ከሰማ በኃላ በከሳሽ(አመልካች) ላይ ለደረሰው ጉዳት ተከሳሽ(ተጠሪ) በከፊል ኃላፊ ነው በማለት ተከሳሽ ለከሻስ ብር 12235(አስራ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ብር) ካሳ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሥር ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ በአመልካች ላይ ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት የሚጠየቅበት ምክንያት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካቾች መጋቢት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ባልተፈቀደ የህዝብ ጎዳና አፈር መቆለሉና መንገዱ አፈር ተቆልሎበት ምልክት አለማስቀመጡ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ጉዳት የደረሰብን በተጠሪ ጥፋት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ አይደለም በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 19 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በመንገዱ ላይ አፈር የቆለለበት መሆኑን አስቀድሞ ያውቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ጉዳት የደረሰበት ከመሥመሩ ውጭ ሲያሽከረክር ነው፡፡ አመልካች በዚህ ሁኔታ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የሌለው ስለሆነ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራረዋል፡፡ አመልካች በ7/10/2005 ዓ.ም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረነል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ በፈጸመው ከፊል ጥፋት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታውን የተወጣ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሳኔአቸው አረጋግጠዋል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ዕውነትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማፈላለግ ሥልጣናቸውን በመጠቀም በአመልካች ላይ አደጋው የደረሰው ተጠሪ በህዝብ አውራ ጎዳና መንገድ ላይ አፈር በመቆለሉና መንገዱ አፈር የተቆለለበት መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ባለማስቀመጡ አመልካች በምሽት መስመሩን ይዞ ሞተር ሳይክል በማሽከርከር ላይ እያለ ከተቆለለው አፈር ላይ በመውጣቱ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ መመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋጧል፡፡

6. ይህም አመልካች በተጠሪ ድርጊት የደረሰበትን ጉዳት ልክና የአካባቢ ሁኔታዎችን መሰረት በማረግ ተከሳሹ/ተጠሪ/ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2141 በተደነገገው መሰረት የማስረዳት ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን ያሳያል ለጉዳቱ አመልካች በከፊል አስተዋጽኦ የበረከተ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ቢሆንም ተጠሪ የመንገዱን ቀርጽ አፈር ቆልሎ በመቀየሩና መንገዱ አፈር የተቆለለበት መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ባለማድረጉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069 መሰረት ለአደጋው እና በአደጋው ምክንያት በአመልካች ላይ ለደረሰው ጉዳት በከፊል በኋላፊነት ተጠያቂ መሆኑን የሚያስቀረው አይደለም ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ ለጉዳቱ ምንም አይነት ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የጋሞጎፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የሳውላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ጸንቷል
3. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ በማለት ወስነናል

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 82154

መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች ፡- አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቱል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንጽህና አቃዎችን ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም አቅርቦት ውልን መሠረት አድርጐ የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪ ክስ ይዘትም የአሁኑ አመልካች በ2001 ዓ.ም የበጀት አመት ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ መደበኛ ተማሪዎች አገልግሎት የሚውል የንጽህና እቃዎች ግዥ ጨረታ በአዲስ ዘመ 67ኛ አመት ቁጥር 337 ነሐሴ 17/2000 ዓ.ም. ታትሞ በወጣው ጨረታ ማስታወቂያ አውጥቶ የአሁኑ ተጠሪ ተወዳድረው የተሻለ ዋጋ አቅራቢ መሆናቸው ተረጋግጦ የአሁኑ አመልካችም የተጠሪን አሸናፊነትን በቁጥር አምዩ 92128/42 በቀን 13/02/2001 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የገለፀላቸው መሆኑን ተጠሪ በአስር ቀናት ውስጥ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የጠቅላላ ዋጋ 10% ብር 63,468.50 (ስልሳ ሶስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ ምስንት ብር ከሀምሳ ሳንቲም) የአሁኑ አመለካች በስሙ ባስከፈተው ባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲደረግ እና በሚሰጠው ኘርግራም መሠረት የአሁኑ ተጠሪ እቃዎችን እንዲያቀርቡ ውል እንዲፈጽሙ ያዘዛቸው መሆኑን በዚህም መሠረት ተጠሪ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትናዉን ገንዘበ ሕዳር 02 ቀን 2001 ዓ/ም በውል በመፈፀም አስይዘው በውሉ መሠረት ለአሁኑ አመልካች ብር 634,685.00 (ስድስት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ አምስት ብር) የሚያወጣ የንጽህና እቃዎችን አቅርበው አመልካችም ገቢ በማድረግ ዋጋውን የከፈላቸው መሆኑን ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ተጠሪን ጠቅላላ የጨረታውን ዋጋ 25% ማለትም የብር 333,155.00 (ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ብር) እቃ እንዲያስገቡ አዝዟቸው በዚሁ ትእዘዝ መሠረት የእቃ ግዥ መጠየቂያ ቀርቦ በአመልካች መስሪያ ቤት በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተፈርሞና ደብዳቤው ተሰጥቶ የብር 333,155.00 ዋጋ ያለው እቃ ተጠሪ ገዝተው ለአመልካች በማቅረብ ንብርቱን ለአመልካች በሞዴል 19 ጣምራ ቁጥር 098954 በሆነው ገቢ አድርገው ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑን የአመልካች ማስሪያ ቤት የእቃ ግዥ ንብረት አስተዳደር ክፍልም እቃውን ቆጥሮ ከተረከበ በኋላ ለአመልካች መስሪያ ቤት ፋይናንስ መመሪያ እቃውን ስለመረከቡ ማረጋገጫ የሰጠ መሆኑንና በውሉ መሠረት ክፍያ እንዲፈፀምላቸው ጥያቄ ቢያቀርቡም አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፈቃደኛ ያልሆነ መሆኑን ዘርዝረው አመልካች ብር 333,155.00 ከተለያዩ ወጪና ኪሣራ እንዲከፍል ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ሕዳር 02 ቀን 2001 ዓ.ም የተደገው ውል የራሱን ፍጻሜ ያገኘ በመሆኑ ለክሱ መሠረት ሊሆን እንደማይገባ ተጠሪ የማይመጥን እቃ እንዲያስገባ የአመልካች ተቋም የበላይ ኃለፊ በየጽሑፍ ደብዳቤ ያላዘዙ መሆኑንና ተጠሪ ከበታች ሰራተኞች ጋር በመመሳጠር የልታዘዘ ግዢ በሕገ ወጥ መንገድ በመነገድ ወደ ተቋሙ እንዲገባ መደረጉን ያለጨረታ ግዥ እንዲፈፀም የሚደረገውም በፋይናንስ ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 68(2(ሀ)) ላይ እንደሰፈረው የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በጣም አስቸኳይ በሆነና ቢዘገይ በመስሪያ ቤቱ ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥርና የመስሪያ ቤቱ የስራ አፈፃፀም ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን በማመን በጽሑፍ ስረጋገጥ ብቻ እንጂ በሌላ ሰው ትእዛዝ ያጨረታ ግዥ መፈፀም እንደሌለበት መደንገጉን ተቋሙ ለጨረታ ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በግዥ ፈፃሚ አካላት የበላይ ኃላፊ ውሳኔ መግባት የሚችለው ለአንድ ጊዜ እስከ ብር 30,000.00 ብቻ መሆኑን የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ እንደሚያዝና የንብረት አስተዳደር የእቃ ግዥ ጥያቄ አቅርቦም በዚሁ ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ ግዥው የመንግስትን ግዥ መመሪያ በመጠበቅ እንዲፈፀም መታዘዙን ሆኖም አግባብነት የሌለውን ጥቅም ለተጠሪ ለማስገኘት አስበውና አቅደው ከመንግስት ግዥ መመሪያ ውጪ አቶ ቶማስ ወልዱ ተጨማሪ ጽሑፍ ያስገባ በመሆኑ ስለእቃው አገባብ በግላቸው ከሚጠየቁ በስተቀር አመልካችን የሚያስጠይቅ ሕጋዊ ውል የሌለ መሆኑን እቃው ያላገባብ የገባ መሆኑን አቶ ቶማስ ወልዱ ተረድተው ለስራ ወጪ እንደሆነ መግለፁንና ይህ ግለሰብ ከአቶ ብዙነህ ደሞዝ ጋር ሁነው ባጠፉት ጥፋት ለተጠሪ ከሚጠየቁ በስተቀር አመልካችን እንደማያስጠይቀው ግለሰቦቹ ወደ ክሱ እንዲገቡ ተደርጐ ክርክሩ እንዲመራና ከሕግ ውጪ ወደ ዩኒቨርሲቲው የገቡት እቃዎችም ብልሽት ቢደርስባቸዉ አመልካች ተጠያቂ ሊሆን ስለማይችል ተጠሪ የመጋዝን ኪራይ ከፍለው እቃዎችን እንዲረከቡ እንዲደረግና እንዲሁም በቀድሞው ውል መሠረት ፈሳሽ ሳሙና ባለአራት ሊትር በጀርካን ሆኖ ዋጋው ብር 60,000.00 ሆኖ እያለ ያለአግባብ ወደ ሊትር በመለወጥ የአንድ ሊትር ዋጋ ብር 60,000.00 በማስላት ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ወጪ መሆኑን ተደርሶበት ያለ ሆኖ በድጋሚ በማጭበርበር ጥቅም ለማግኘት ክስ መመስረቱ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ከዳኝነት ወጪ ከ7% የጠበቃ አበል ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዝህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለደቡብ ብሄር በሄረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ጉዳዩ ተመርምሮ በድምጽ ብልጫ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመጽናት ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፣፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም ከተጠሪ ጋራ በህዳር 02 ቀን 2001 ዓ.ም ተደርጐ ከተፈፀመው ውል ውጪ የካቲት 03 ቀን 2001 ዓ.ም በተጨማሪነት ተደረገ የተባለው ውል ከመንግስት ግዥ መመሪያ ውጪ ተጠሪ ከአመልካች ተቋም የበታች ሰራተኞች ጋር በመመሳጠር ያደረጉትና በሕጉ አግባብ ያልፀደቀ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በተጠሪ መካከል ውል አለ በማለት ለክሱ መሠረት የሆነውን ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰናቸው የላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐላቸው ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጽሁፍ እንዲከራከሩ የተደረገ ሲሆን የከርክራቸው መሰረታዊ ይዘትም በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ተመልክተናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ስሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በስር ፍርድ ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገቡ የጠየቃቸው ሰራተኞች ወደ ክርክሩ ሳይገቡ ውሳኔ መስጠቱ ስነ ስርዓታዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በሕጉ አግበብ ስለመደረጉ ክርክር ያልቀረበበትና ህዳር 02 ቀን 2001 ዓ.ም ያደረጉትን የንጽህና እቃዎች ግዥ ውል ፈፃሚ እንዲያገኝ አድርጉው አሁን እያከራከራቸው ያለው የካቲት 03 ቀን 2001 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የንጽህና እቃዎች ውል መሆኑን ይህ ውል በቀድሞው ውል ጠቅላላ ብር 634,685.00 (ስድስት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ አምስት ብር) ዋጋ 25% ማለትም የብር 333,155.00 (ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ብር) እቃ እንዲያስገቡ ተጠሪ በአመልካች ታዝዘው በዚሁ ትእዛዝ መሠረት የእቃ መጠየቂያ ቀርቦ በአመልካች መስሪያ ቤት በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተፈርሞና ደብዳቤው ተሰጥቶ የብር 333,155.00 ዋጋ ያለው እቃ ተጠሪ ገዝተው ለአመልካች በማቅረብ ንብረቱን ለአመልካች በሞዴል 19 ጣምራ ቁጥር 098954 በሆነው ገቢ አድርገው ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑንና የአመልካች መስሪያ ቤት የእቃ ግዥ ንብረት አስተዳደር ክፍልም እቃውን ቆጥሮ ከተረከበ በኋላ ለአመልካች መስሪያ ቤት ፋንናንስ መመሪያ እቃውን ስለመረከቡ ማረጋገጫ የሰጠ መሆኑን ተጠሪ ጠቅሰው የሚከራከሩ ቢሆነም ይህ ሁሉ የሆነው ግን የአመልካች መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ተገቢውን ትእዛዝ አድራጉቱን ፈፀሙ ለተባሉት የበታች ሰራተኞች አስተላልፈው ስለመሆኑ ያለመረጋገጡን ነው፡፡ የበታች ፍርድ በቶች አመልካችን ለክሱ ተጠያቂ ያደረጉት እነዚህ ፍሬ ነገሮች መኖራቸውን አረጋጋጠው የአመልካች ሠራተኞች ከአመልካች ጋር ባላቸው የሥራ ግንኙነት መሠረት የደረሱበትን ኪሣራ ወይም ጉዳት አመልካች ሊጠይቅ የሚችለው ሠራተኞቹን እንጂ ከተጠሪ ጋር መከራከሪያ ሊያደርገው አይችልም በሚል ምክንያት መሆኑንም ውሳኔው የሚሳይ መሆኑን ተረድተናል፡፡

በመሠረቱ አንድ ውል የሕግ ጥበቃ የሚያገኘው በሕጉ አግባብ የተቋቋመ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ) ድንጋጌ ጋር በጣምራ ስናነብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ውሉ ሕጉን በሚቃረን መልኩ የተቋቋመ መሆኑ እየተረጋገጠና ውሉን ተዋውሏል የተባለ ተዋዋይ ወገንም ውሉ ሕጋዊ አይደለም በማለት ክርክር እያቀረበ በውሉ እንዲገደድ ማድረግ የመዋዋል ነፃነትን መሰረታዊ መርህ የሚጥስና ፍላጐቱንና ፈቃዱን ያልሰጠ ሰው ግዴታውን እንዲወጣ በማድረግ ሌላኛው ተዋዋይ ነኝ የሚል ወገንም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም እንዲያገኝ የማድረግ ውጤት የሚስከትል ከመሆኑም በላይ በተለይ እንዲህ አይነቱን ግዴታ እንዲወጣ ጥያቄ የቀረበው በመንግስ መስሪያ ቤት ከሆነ የመንግስት ግዥን ስርአት ለመስያዝ የወጣውን ሕግ ውጤት አልባ የሚያደርግ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ አንድ የመንግስት ሠራተኛ በሕጉ የተሰጠው ኃላፊነትና ተግባር እያለ ከዚሁ ኃላፊነትና ተግባር አድማስ ውጪ ባደረገው ግንኙነት በተቋመ ግዴታ የሚያስከትል ተግባር ፈጽሞ ከተገኘም ኃላፊነቱን ሊወስድ የሚገባው እንዲ አይነቱን ተግባር ያከነወነው ሰራተኛ በግሉ ከሚሆን በስተቀር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቋመ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ አንድ የመንግስት መስሪያ ቤተ ለሰራተኛው ተግባር ኃላፊነት ሊህረው የሚችለው በሰራተኛው የተፈፀመው ጥፋት የሥራ ጥፋት ሆኖ ሲገኝ ሲሆን አንድ ጥፋት የስራ ጥፋት ነው ተብሎ የሚወሰደውም ጥፋት አድራጊው በዚህ ጥፋት ላይ የወደቀው በቅን ልቡና በስልጣኑና ለስራው ክፍል መልካም ያደረገ መስሎት የፈፀመው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑና ከዚህ ውጪ በሆነ በማናቸውም ሌላ ጉዳይ ግን ጥፋቱ እንደግል ጥፋት ሁኖ እንማሚቆጠር የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2126 እና 2127(1) እና (2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስረዳሉ፡፡ ጥፋቱ በቅን ልቦና ያልተፈፀመ መሆኑም በተቃራኒ ማስረጃ ሊረጋገጥ እንደሚችልና ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ ግን የራተኛው አሰራር በቅን ልቦና እንደተሰራ በሕጉ ግምት እንደሚወሰድበት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2127/3/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከላይ የተመለከቱት የሕግ ጉዳዮች በፍርድ ተገቢውን አልባት የሚሰጥባቸው ደግሞ በክርክሩ የግድ ተካፋይ የሆነው ወገኖች በከርክሩ እንዲሳተፉ ተደርጐ ጉዳዩ በተገቢው ማስረጃ በጥንያቄ ሲጣራ ነው፡፡

በመሠረቱ በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ሲቀርብና የክሱም ምክንያት የብዙ ሰዎችን መብትና ጥቅም የሚነካ ወይም ኃላፊነት ያለበትና ግዴታውን ሊወጣ የሚገባው የትኛው ወገን መለየት የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከእነሱ አንዱ ወይም ከፊሉ ክስ በቀረበ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ መብትና ጥቅም የሚነካ ወይም ግዴታው በሕጉ አግባብ እንዲወጣ ሊደረግ የሚችል ሲሆን በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በሕጉ አግባብ ተጠያቂ የሚሆን ወገንም የክርክሩ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ የሚመነጨው ከዚህ አግባብ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎችን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 36/5/ ጋር ተጣምረው ሲነበቡ የሚያገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ተካፋይ ሳይሆነ የሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑም የተጠቃሽ ድንጋጌዎች መንፈስ ያሰረዳል፡፡ በመሆኑም በክሱ መግባት ያለበት ተከሳሽ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆንና በቀረበው ክስና መልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ ሊያዘው የግድ የሚል ስለመሆኑ ሥነ ሥርዓቱ የሳያል፡፡ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ማለት ደግሞ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው መብታቸው ወይም ግዴታቸው የሚነካ፡ በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች ስለመኖቸውም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 40 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ድንጋጌው ክርክሮች ወደፊት እንዳይነሱ በማድረግ የወጪ ጊዜና ጉልበትን ብክነት በመቆጠብ አፋጣኝ ዳኝነት የመስጠትን የስነ ስርዓት ሕጉን መሰረታዊ አላማ ያገናዘበ ነው ተብሎ ይታሳባል፡፡

ወደተያዙው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ውሉ የተገባው በመንግስት ግዥ መመሪያ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 68(2)(ሀ)) ድንጋጌ መሠረት በአመልካች መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የጽሑፍ ትእዛዝ የተላለፈ ትእዛዝ መኖር ያለመኖሩን በተመለከተ ከአመልካች ሰራተኞች ጋር ተደረገ የሚሉት የቀድሞ ውልን መነሻ በማድረግ ሕጋዊ ስርዓትን የተከተለ ስምምነት አለ የሚሉ ሲሆን በዚህ ረገድ በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ደግሞ ውሉ ላይ መጻፃፎች እንዲኖሩ ያደረጉት ሰራተኞች ከተጠሪ ጋር ተመሳጥረው ያደረጉት ተግባር እንጂ ሕጋዊ አይደለም በማለት በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ አመልካች የተቋመ ሰራተኞች ተግባሩን የፈፀሙት ከተጠሪ ጋር ተመሳጥረው ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክር ሰራተኞቹ ወደ ክርክሩ እንዳገቡ ተደርጐ የግራ ቀኙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ ተሰምቶ ጉዳዩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2126 እና 2127 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ተፈፅሚነት የነበረውን የመንግስት የግዥ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር ተዛመዶ ዳኝነት የማስጥበት እንጂ አመልካች ከወዱሁ በሰራተኞቹ የግል ጥፋትም ቢሆንም እንኳን ሃላፊነቱ የአመልካች ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ ሕጋዊ አካሄዱን በተከተለ የተደረሰ መደምደሚያ አይደለም፡፡ የአመልካች ሰራተኞች ተግባሩን የፈፀሙት ከቅን ልቦና በመነጨ ሁኔታ ነው? ወይስ ከዚህ ውጪ ነው? ተጠሪስ የእቃዎቹን አቅርቦት ለአመልካች የፈፀሙት ከሰራተኞቹን የመመሳጠር ተግባር ፈጽመው ነው ወይስ ሕጋዊ አንድ ጠንቃቃ ነጋዴ ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ አድርገው የንገድ ስራው የግድ የሚለውን አካሄድ ተከትለው ነው? የእቃቹ አቅርቦት ከተጠሪ ጋር የነበረውን የቀደመ ግንኙነት መሠረት አድርጐ እንዲከናወን የተጠሪ ተቋም የበላይ ኃላፊ ለሰራተኞቹ በሕጉ አግባባ ያሰተላለፉት እትዛዝ አለ ወይስ የለም? የተላለፈ ትእዛዝ አለ ከተባለም ሰራተኞቹስ ስራውን ያከናወኑት በበላይ ኃላፊ ትእዛዝ መሠረት መሆን ያለመሆኑ ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ ተገቢውን ማጣራት ማድረግን የሚጠይቁ ሲሆን ይህ ሁሉ መከናወን ያለበት ግን ሰራተኞቹን የክርክሩ ተሳታፊ በማድረግ የመደመጥ መብታቸውን በማስከበር እና የፍታ ብሄር ስነ ሥርዓት ሕጉን አይነተኛ አላማ በማገናዘብ ሌላ ክርክር ወደፊት እንዳይነሳ የሚያደርግ የክርክር አመራርት ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡ ሲጠቃለልም የስር ፍርድ ቤቶች ተገቢ ባልሆነ የክርክር ደረጃ አመልካች ለሠራተኞቹ ተግባር ጭምር ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባል በሚል ምክንያት የአመልካች ሰራተኞች የሆነት አቶ ቶማስ ወልዴ አቶ ብዙነህ ደመወዝ የተባሉት ግለሰቦች ወደ ክርክሩ ይግበልኝ የሚለውን የአመልች ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ለማለት አልተቻለም ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ግለሰች ወደ ክርክር ሳይገቡ የተሠጠው ውሳኔ ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አለነም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

ው ሳ ኔ

1. በጋሞ አከባቢ ከተፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10689 ነሐሴ 14 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 56013 ግንቦት 03 ቀን 2004 ዓ.ም በድምጽ ብልጫ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ተቋም ሰራተኞች የሆነትና ከእቃው አቅርቦት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ነበራቸው የተባሉ አቶ ቶማስ ወልዴና አቶ ብዚነህ ደመወዝ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን ያለባቸው መገኖች በመሆኑ ለቀረበው ክስና መልስ መከላከያቸውን እንዲያቀርቡ የጋሞ አከባቢ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሠጥቶ ጉዳዩን እንደገና በመመልከት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ሥልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 81934

የካቲት 28 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- የአቀቂ ቃሊት ክ/ከተማ ወረዳ 5 ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡- ሃምሳ አለቃ ታምራት ከበደ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከንግድ ስራ ፈቃድ ማገድ ጋር ተያይዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በአ/አበባ ከተማ መስተዳድር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ በአቃቂ ቃሊት ክ/ከተማ ወረዳ 5 ክልል ውስጥ ባለኝ የመኖሪያ ቤት ይዞታዬ ላይ የመኪና ማቆሚያ ንግድ ስራ ህጋዊ ፍቃድ ተሰጥቶን እየሰራሁ እያለሁ ተጠሪ በቁጥር 415/2004 ታህሳስ 23 ቀን 2004 ዓ/ም በተፃፈ ማስጠንቀቂያ እየሰራህ ያለው የንግድ ስራ ከፀጥታ ከጤና እና ከአካባቢ ብክለት አንፃር በአካባቢ ጥበቃ ላይ ከፍተኛ ችግር እያደረሰ ነው በሚል ምክንያት የንግድ ፍቃድን ለማገድ ሁከት ስለፈጠረብን የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ በአዋጅ ቁ 686/2002 ዓ.ም አንቀጽ 37/ሀ/ መሰረት እግድ መስጠቱ ህጋዊ እርምጃ በመሆኑ የቀረበው የሁከት ይወገደልኝ አቤቱታ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ክሱ ወድቅ ተደርጎ እንዲሰናበት በመጠየቅ መልስ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የከተማ መ/ደ/ፍ/ቤትም የተጠሪ መኪና ማቆሚያ ንግድ ስራ በአካባቢው የጤናም ሆነ ብክለት ላይ ችግር ማስከተሉ በማስረጃ ሳይደገፍ የንግድ ስራ ፈቃዱ በአመልካች መታገዱ የሁከት ተግባር በመሆኑ የተፈጠረው ሁከት ይወገድ ሲል ወስኖል አመልካችም ይህን ውሣኔ በመቃወም ቅሬታውን ለከተማ መስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡ እንዲሁም አቤተታውን ለከተማው መስተዳድር ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም አሁንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ሐምሌ 24 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ አመልካች በአዋጅ ቁ 686/2002 አንቀጽ 37/1/ሀ/ መሰረት ተጠሪ የፈጠረው ችግር አስኪታረም ድረስ የንግድ ስራ ፈቃዱን ማገዱ በህግ የተሰጠን ስልጣን ሲሆን ይህም በተሰጠን ስልጣን መሰረት ሀላፊነትና ግዴታችን መወጣት እንጂ የሁከት ተግባር ሊባል የማይችል በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈጠረ ሁኩት የለም ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዘንድ ጠይቋል፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የገባል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠ ሲሆን አመልካችም የመ/መልሱን ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ጋር በተያያዘ ጉዳይ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል አስተዳደራዊ እርምጃን በሚወስደበት ጊዜ በተወሰደው እርምጃ መብቱ ተነክቷል፡፡ የሚል ሰው ካለ መብቱን በምን አይነት ሰርዓት እና መንገድ ሊያስከብር ይችላል? የሚለው ነጥብ በቅድሚያ ታይቶ የምላሽ የሚሻ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህን ጉዳይ በተመለከተ አግባብነት ያለው ህግ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 ሲሆን አዋጅ አንቀጽ 61ም በአስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ በሚለው የድንጋጌው ርዕስ ስር በዚህ አዋጅ መሰረት በመዝገቢው መስሪያ ቤት ወይም አግባብ ባለው ባለስልጣን አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት ሰው ሊኖረው ከሚችለው ቅሬታ ጋር በተያያዘ በህግ ጉዳዮች ላይ ብቻ ለመደበኛ ፍ/ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል በሚል በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መንፈስ ደግሞ መረዳት የሚቻለው በህግ ጥያቄዎች ላይ ብቻ ካልሆነ በስተቀር የፍሬ ነገር ክርክርን በሚመለከት መደበኛ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ለማየት ስልጣን ያለተሰጣቸው መሆኑን ነው፡፡ ከህግ አተገባበር ጋር በተያዘ የተፈጠረ ስህተት ካለ እሱን በተመለከተ ብቻ ተቀብለው ከማረም ውጭ የፍሬ ነገር ክርክርችን በማስረጃ አጣርተው ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን የለችውም በተያዘው ጉዳይም ሁከት ይወገደልኝ በሚል የቀረበውን የክሱን ፍሬ ነገር በተመለከተ የስር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙን በማከራከርና በማስረጃ በመጣራት የሰጡት ውሳኔ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ምክንያት የህግ መሰረት ያለው አይደለም በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የፍሬ ነገር ጉዳይን በሚመለከት አከራክረው የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለገኘን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በዚህ ጉዳይ የአ/አበባ አስተዳደር መ/ደ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. መደበኛ ፍ/ቤቶች ከንግድ ምዝባና ፈቃድ ጋር በተያዘ የሚነሱ የፍሬ ነገር ክርክሮችን አይተው ለመወሰን ስልጣን የላቸውም፡፡
3. ተጠሪ የህግ ጉዳይን ወይም ጥያቄን በተመለከተ ብቻ በአዋጅ ቁ 686/2002 61 መሰረት ስልጣን ላለው መደበኛ ፍ/ቤት አቅርቦ መብቱን ለማስከበር ይህ ውሳኔ አይከለክለውም፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86817

መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - ዐ/ህግ ቢኒያም አብርሃም ቀረቡ

ተጠሪ፡- ግሎሪ ኢትዮጵያ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ ጫንያለው ከበደ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከአስጎብኚና የጉዞ ወኪል የንግድ ፈቃድ ስራ ጋር በተያያዘ ለአንድ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ይዘት በአጭሩ ድርጅታቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የኢንቨስትመንት ባለስልጣን የማስጎብኘት አገልግሎት ፈቃድ የተሠጠው መሆኑን፣በዚሁ መሰረት መንግስት በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሰጠውን ከቀረጥ ነጻ መብት ተጠቅሞ በደንብ ቁጥር 146/2000 አግባብ በተሠጠው መብት መሰረት ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች አስፈላጊውን ሁኔታ ሁሉ አሟልቶ፣ተሽከርካሪዎችን ገዝቶ ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ የአሁኑን አመልካች በመጠየቅ ሐምሌ 15 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ መኪኖቹ ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነጻ ሁነው እንዲገቡ በፈቀደው መሰረት ተሽከርካሪዎቹ አስፈላጊ የሆኑ ፎርማሊቲዎችን አሟልተው ቀረጥ ሳይከፈልባቸው መግባታቸውን፣ ተጠሪ መኪኖቹን ወደ ስራ ከአሰማራ በኋላ ከሶስቱ መኪኖቹ አንዱ ከ10 ሰው በታች የሚጭን ስለሆነ ቀረጥና ታክስ መክፈል አለብህ በ ማለት አመልካች መጠየቁን፣ ተሽከርካሪዎቹን አስመልክቶ መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች የመግለፅና የማሳወቅ ስልጣን የተሠጠው ለትራንስፖርት ባለስልጣን መሆኑ እየታወቀና ይኼው ባለስልጣን ማብራሪያ ተጠይቆ ሚኒባስ ማለት አሽከርካሪውን ሳይጨምር ከ7-14 ሰው የሚጭን መሆኑን ገልጾ ማብራሪያ መስጠቱንና በዚህ አግባብ አመልካችም ሲያስተናግድ ቆይቶ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ባልታወቀ ሁኔታ ቀረጥና ታክስ ካልከፈልክ ማለቱ ያላግባብ መሆኑን ዘርዝሮ ሁከቱ ተወግዶ የአመልካች የቀረጥ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ ሁኖ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች ቀርቦም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በቀጥታ ለማየት የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ እርምጃው በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን መሰረት አድርጎ የተከናወነ መሆኑን በመጥቅስና ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን የህግ ማዕቀፎችን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም አመልካች ስልጣንን መሰረት አድርጎ ያነሳውን ክርክር በተመለከተ የተጠሪ ጥያቄ ከቀረጥ ነጻ መብት የተያያዘ እንጂ ከቀረጥና ከታክስ አከፋፈል ጋር የተያያዘ አይደለም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎታል፡፡ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር የአመልካች ጥያቄ ሕጋዊ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ማየቱ በሕጉ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ መሆኑንና በአከራካሪው መኪና ላይ የአመልካች የቀረጥና የታክስ ይከፈል ጥያቄ በሕጉ በተፈቀደው አግባብና ስልጣኑን መሰረት አድርጎ የተከናወነ ሁኖ እያለ ተጠሪ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ጭብጥ ሳይመሰርትና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች በአግባቡ ሳይመለከት የአመልካች ጥያቄ አግባብ አይደለም ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በመደረጉ የግራ ቀኙ ክርክር በፅሑፍ እንዲደረግ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ ማስናገዱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ ባለው የኢንቨስትመንት ፈቃድ በኢንቨስትመንት ስራ ላይ በመሰማራት ለስራው የሚገለገልባቸውን ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ከታክስ ነጻ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ፈልጎ ይህንኑ በማመልከት ስለተፈቀደለት አስፈላጊ ዶክመንቶችን በማሟላት መኪኖችን ገዝቶ ከአስገባና ስራ ላይ ከአሰማራ በኋላ ከገቡት ተሽከርካሪዎች ውስጥ አንዱ ከአስር ሰው በታች የሚጭን በመሆኑ ቀረጥ ሊከፍልበት ይገባል በማለት አመልካች መሰሪያ ቤት መጠየቁን ገልጾ ጥያቄው ሁከት በመሆኑ ሊቆም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን፣የአመልካች ዋና የመከራከሪያ ነጥብ ደግሞ ለተጠሪ የቀረበው አይነት ጥያቄ በአመልካች መቅረቡ በሕጉ የተፈቀደና በጥያቄው ቅሬታ ያለው ወገንም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አግባብ በአመልካች መስሪያ ቤት በተዘረጋው ስርዓት ቅሬታውን ማቅረብ፣በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካደረበትም ጉዳዩ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ከሚቀርብና በስርዓቱ መሰረት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ለበላይ ፍርድ ቤቶቸ ቅሬታው ታይቶ ከሚስተናገድ በስተቀር በቀጥታ ክስ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት ጉዳይ አይደለም፣ከአስር በታች የሆነ ሰው የሚጭን መቀመጫ ያለው ተሽከርካሪ ደግሞ “ሚኒባስ” በሚለው ትርጉም አይካተትም በሚል መሆኑን ነው፡፡

ከላይ ከተገለፀው የግራ ቀኙ ክርክር መረዳት የሚቻለው ተጠሪ የቀረጥና የታክስ ነጻ መብት አለኝ በማለት ከመጥቀሱ ውጪ አከራካሪው ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ተብሎ በሕጉ አግባብ ሊመደብ የሚችል መሆን ያለመሆኑ የክርክሩ መሰረታዊ ጭብጥና ግራ ቀኙን የሚያከርከር ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ከእቃው አመዳደብ፣የጉምሩክ ስነስርዓት፤ ከቀረጥና ታክስ አከፋፈል ጋር ተያይዞ ቅሬታ መነሳቱን የሚያመላክት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀጽ 87 (1) ስር በግለጽ እንደተመለከተው በእቃዎች አሰያየም፣አመዳደብ ወይም በታሪፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልክ ላይ ተቃውሞ ካለ እንዲሁም በተጠቃሹ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 (ሐ) ስር እንደተመለከተው ማንኛውም ከጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ጋር በተያያዘ በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው አካል አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ቀጥታ ለፍርድ ቤት ሳይሆን በተጠቃሹ አዋጅ በተዘረጋው የይግባኝ ሰርዓት መሆኑ ተመልክቷል፡፡የይግባኝ አቀራረብ ስርዓቱም ጉዳዩ ከአመልካች መስሪያ ቤት የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቀርቦ ከታዬ በኋላ ቅሬታ ያለው ወገን በአንቀጽ ንዑስ ቁጥር 5 መሰረት ለግብር ይግባኝ ሰሚ መቅረብ እንደአለበት፣ ከዚያም በአንቀጹ ንኡስ ቁጥር 9 መሰረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረብ እንደአለበት፣በዚህ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገንም በአንቀጹ ንኡስ ቁጥር 10 ድንጋጌ አግባብ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 112 እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቀጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች አግባብ ለበላይ ፍርድ ቤት እንደየቅደምተከተሉ ይግባኙንና የሰበር አቤቱታውን ማቅረብ እንደሚችል የድንጋጌዎች አቀራራጽና ይዘት ያሳያል፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ የአመልካች የቀረጥና የታክስ ክፍያ ጥያቄ አግባብነት የለውም የሚለው የተጠሪ ክርክር በእነዚሁ አዋጆች በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ታይቶ እልባት ከሚያገኝ በስተቀር በቀጥታ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት እና ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በቀጥታ አይተው ውሳኔ የሚሰጡበት አግባብ አይኖርም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩ ሲቀርብላቸው ጉዳዩን በቀጥታ የማየት ስልጣን እንደሌላቸው በመገንዘብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9፣231(1(ለ)) እና 244(2(ሀ)) መሰረት መመለስ ሲገባቸው ክሱን በመቀበልና በማከራከር ውሳኔ መስጠታቸው የሕጉን አካሄድ የተከተለ ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ባቀረቡት የቀረጥና የታክስ ክፍያ ጥያቄ ላይ ስልጣን ሳይኖራቸው የሰጡት ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለው፣የክርክሩን አጠቃላይ ይዘት አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 176250 ነሐሴ 13 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በ07/02/2004 ዓ/ም የተገለጸውና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117291 ጥር 06 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የመደበኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውን ጥያቄ በቀጥታ ክስ በመቀበልና በመመልከት ውሳኔ ለመስጠት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 89530

ጥቅምት 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ቲኤንቲ ኮንስትራክሽንና የንግድ ስራዎች ድርጅት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ እያዩ ደጀኔ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተመሰረተ የስራ ግንኙነትን መሰረት አድርጎ የተነሳውን ለተሰራ ስራ የሚከፈል ክፍያ ይከፈለኝ ጥያቄን ለማየት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለውን አካል የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በድሬዳዋ አስተዳደር አስተዳደር ቀበሌ 02 ማህበራዊ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪ የክስ ይዘትም፡- ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ድርጅት ውስጥ በወር ብር 2000.00 ተቀጥረው ስራ መስራታቸውንና ለሰሩት ስራ ብር 2000.00 ያልተከፈላቸው መሆኑን ዘርዝረው ይህንኑ ገንዘብ አመልካች እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ጉዳዩ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ሊታይ የማይችል መሆኑንና ክፍያው ለተጠሪ ያልተፈጸመው ተጠሪው በፈጸሙት ጥፋት መሆኑንና ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ብር 3000.00 ብድር ወስደው አንድ ሺህ ብር ብቻ ከፍለው ቀሪውን ባለመክፈላቸው መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ጉዳዩ የቀረበለት የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በማየት አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ከተለያዩ ወጪዎች ጋር በድምሩ ብር 2134.00 ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይግባኙን ቢያቀርብም ግራ ቀኙ ከተራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታይ ሁኖ እያለ በአዋጅ ቁጥር 416/1996 ከተሰጠው ስልጣን ውጪ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማየቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ ተደርጎ ለተጠሪ ጥሪ ቢደረግላቸው ጥሪው በሕጉ አግባብ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የታቸው ተጠሪ ከአመልካች ጋር ቅጥር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መስርተው ስራ መስራታቸውንና ለሰሩት ስራ ደመወዝ ያልተከፈላቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ የገንዘቡን መጠን ለይተው ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የመጠቃቸውን፣አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የተጠሪ ክስ መሰረት ያደረገው ቅጥርን በመሆኑ በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የማይወድቅ መሆኑን ገልፆ የተከራከረ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙት ፍርድ ቤቶችና ሌሎች የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ስልጣናቸው በአዋጅ ቁጥር 416/1996 ከአንቀጽ 31 እስከ 42 ድረስ በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች መሰረት የተዘረጋ ሲሆን የአዋጁ አንቀጽ 41(1) ድንጋጌ በተለይ ሲታይም የአስተዳደሩ ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ግምታቸው ከብር 2000.00 ያልበለጠ የገንዘብና የንብረት ክርክሮችን የማየት ስልጣን ያላቸው መሆኑን በግልጽ ደንግጓል፡፡በሌላ በኩል የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን በተመለከተ ሕግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የተለየ ሕግ አውጥቶ አዋጁን መሰረት አድርገው የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን ያላቸውን አካላት ለይቶ ማስቀመጡን የአዋጁ አንቀጽ 138 እና 142 ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያል፡፡ይህ ህግ የገንዘብ መጠንን ግንዛቤ ውስጥ ሳያስግባ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የተቋቋመውን ግንኙነት መሰረት አድርጎ የሚነሳው የግል የስራ ክርክር በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደሚታይ፣የወል የስራ ክርክር ከሆነ ደግሞ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚዳኝበትን አግባብ የዘረጋ ነው፡፡በመሆኑም ሕጉ ለአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነቶች ልዩ ሕግ እንደመሆኑ መጠን ለጉዳዩ ከሌሎች ሕጎች ሁሉ የበላይ ተፈፃሚነት አለው፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት ግንኙነት የአሰሪና ሰራተኛ መሆኑን በግልጽ ጠቅሰው ክስ በመሰረቱበት ሁኔታ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የገንዘቡ መጠን ብር 2000.00 መሆኑን ብቻ በመመልከት፣ጉዳዩን ከአዋጅ ቁጥር 377/196 አንጻር በመመልከት ስልጣኑ መሆኑን ሳያረጋግጥ ጉዳዩን ተቀብሎ ማየቱ ከአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 41(1)፣ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9(1) እና 231(1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ፣በጉዳዩ የተሰጠው ውሳኔ በሕጉ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ ስልጣን በሌለው አካል የተሰጠ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 02 ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0113/05 ጥር 14 ቀን 2005 ዓ/ም ተሠጥቶ በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00336 መጋቢት 27 ቀን 2007 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የተመሰረተውን ግንኙነት መሰረት አድርጎ የሚቀርበውን ክርክር የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ጥያቄአቸውን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የማቅረብ መብታቸውን ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝግብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 90737

ህዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- የንጋት ኮከብ ሸማቾች ኃ/የተ የግል ማህበር ጠበቃ አቶ እሸቱ ጓንጉል ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ የሴፍ እንድሪስ
2. አቶ መክብብ አሰፋ
3. አቶ ፀጋ መሰለ
4. አቶ ወጋየሁ ላቀው ቀረቡ
5. አቶ ጎንጀባ ጎንባ
6. አቶ ጎሳዬ ጎቴ
7. አቶ መንግሰቱ ታደሰ አልቀረቡም
8. አቶ ይልማ ኪዳነ ወልድ
9. አቶ ዘካሪያስ ሀ/ማርያም ቀረቡ
10. አቶ አብጤ ካሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ መዝገብ እና በሰ/መ/ቁ 90738 ያሉት ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ዘንግ የሚመደቡ ከመሆናቸውም ሌላ የቀረበው የህግ ክርክርና የነገር ጭብጥም አንድ ዓይነት በመሆኑ ሁለቱን መዝገቦች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 11(1) መሰረት በማጣመር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ከተራ ቁጥረ 1-5 ያሉት ያሁን ተጠሪዎችም በመ/ቁ/40407 ተከሳሾች ነበሩ፡፡ መ/ቁ/40406 በሆነው ደግሞ የአሁን አመልካች ከሳሽ ፣ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 ያሉ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ቁጥሩ 40407 በሆነው መዝገብ ከሳሽ በቀን 27/09/2004 ዓ/ም ያቀረበው ክስ፡- ከሳሽ ማህበር በህብረት ሥራ ማህበር አዋጅ ቁጥር 147/1991 የተቋቋመ ሲሆን ተከሳሾችም የማህበሩን የእለት ተዕለት ሥራ እንዲሰሩ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጠው ከ20/07/2003- 27/11/2003 በማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባልነትና በዕቃ ግዥ ሲሰሩ ከከሳሽ የመተዳደሪያ ደንብ ውጪ ህገ ወጥ አሰራር በመከተል በሥልጣናቸው ያለአግባብ በመገልገል የማህበሩን ገንዘብ ብር 369,202.75 መውሰዳቸው በኦዲት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ ከ9% ወለድ ጋር በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ከሳሽ መ/ቁ/40406 በሆነው ደግሞ በመ/ቁ/ 40407 የተጠቀሱትን ተከሳሾች ጨምሮ በድምሩ በ10 ተከሳሾች ላይ ግንቦት 27/1004 ያቀረበው ክስ ተመሳሳይ ሆኖ ተከሳሾቹ ከ01/07/2001-19/07/2003 ዓ/ም የከሳሽ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ ፣ የዕቃ ግዥ እና ቁጥጥር ኮሚቴ ሆነው ሲሰሩ ሥልጣናቸውን ያለአግባብ በመገልገል የማህበሩን ብር 176,587.31 ማጉደላቸው በኦዲት ሪፖርት ስለተረጋገጠ ይህንኑ ገንዘብ ከ9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሳሾችም ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በህብረት ሥራ ማህበር አዋጅ ቁጥር 147/1991 በክፍል ዘጠኝ በአንቀጽ 46 መሰረት በቅድሚያ ጉዳዩ መታየት ያለበት በእርቅ መሆኑን፣ በእርቅ ማለቅ ካልቻለም ለሽምግልና ዳኝነት ጉባዔ ቀርቦ የሚወሰን ሆኖ ሳለ ከሳሽ በቀጥታ ለፍርድ ቤት ያቀረበውን ክስ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ አከራክሮ ለመወሰን ሥልጣን የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ክስና ተከሳሾች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንጽ 46 እና 49 ጋር አገናዝቦ በመመርመር፡- የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የማህበሩ አባል መሆናቸውን ያልተካካዱ ስለሆነና ጉዳዩም በቀጥታ በእርቅ ካልሆነም በሽምግልና ሊታይ የሚገባ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተቀብሎ አከራክሮ ለመወሰን የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የለውም ሲል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 244(2)(ሀ) መሰረት ሁለቱንም የክስ መዝገቦች ዘግቷል፡፡

ከሳሽም በሁለቱም መዝገቦች ይግባኝ የጠየቀ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት በማሰናበቱ የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ አመልካች በሁለቱም መዝገቦች በዋናነት ያቀረበው የቅሬታ ነጥብ ሲጠቃለል፡- ተጠሪዎች የአመልካች ማህበር የመተዳደሪያ እና የፋይናንስ ደንብ ተከትለው ባለመሥራታቸው ምክንያት በኦዲት ሪፖርት የተረጋጠውን የጉድለት ገንዘብ እንዲከፍሉ በአዋጅ ቁጥር 147/1991

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 39(1)(ሀ) መሰረት ጥረት ቢደረግም ፈቃደኞች ሆነው ባለመገኘታቸው በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ያጎደሉትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ በሚል የቀረቡትን ክሶች የሥር ፍርድ ቤቶች በአባላት መካከል እንደተነሳ አለመግባባት ቆጥረው በዕርቅ ወይም በሽምግልና ሊፈታ የማይችለውን ጉዳይ ከአዋጁ አንቀጽ 46 እና 49 ዓላማና መንፈስ ውጪ በዕርቅ እና በሽምግልና ሊታይ የሚገባ እንጂ ለፍርድ ቤት ቀጥታ የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም በሚል ክሶቹን በብይን ውድቅ ያደረጉት ከዚህ በላይ የተቀመጡትን የአዋጁን ድንጋጌዎች ያላገናዘበና በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 37(2)(ሀ) -የህብረት ስራ ማህበራት ክስ መስርተው ፍትህ የማግኘት መብት አላቸው በሚል የተደነገገውን የሚቃረን ስለሆነ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በተከሰሱበት የክስ መዝገብ በየበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- አመልካች የህብረት ሥራ ማህበር ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ የቀድሞ የማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ወይም በአዋጁ አገላለጽ ሹሞች በመሆናችን በመካከላችን የተፈጠረው አለመግባባት ሊታይ የሚገባው ከፍርድ ቤት ይልቅ በአዋጁ አንቀጽ 46፣47 እና 49(3) መሰረት በእርቅ ወይም በሽምግልና ዳኝነት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ብለዋል፡፡

አመልካችም ተጠሪዎች ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች በቀጥታ ያቀረቧቸውን ክሶች ለማየት የዳኝነት ሥልጣን የለንም ሲሉ የክስ መዝገቦቹን የዘጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ተቀብለው አከራክረው ለመወሰን የስረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን እንደሌላቸው በመግለጽ የክስ መዝገቦቹን የዘጉት የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የማህበሩ አባል መሆናቸውን ያልተካካዱ ስለሆነ ጉዳዩ በቀጥታ በእርቅ ካልሆነም በሽምግልና ሊታይ ይገባል በሚል ነው፡፡ የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 402/1996 አንቀጽ 46 በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 49(1-4) የተመለከቱት ክርክሮች ለሽምግልና ዳኝነት ከመቅረባቸው በፊት ተከራካሪ ወገኖች በሚመርጡት 3ኛ ወገን በእርቅ መታየት ይችላል በሚል የተደነገገ ሲሆን በዕርቅ ያላለቁ እንደሆነ ደግሞ ለሽምግልና ዳኝነት እንደሚቀርቡ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 47(1) ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ/70351 በቀን 17/11/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት፡- ማህበሩ የሚጠይቀው ጉድለትን መሰረት ያደረገ ገንዘብ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 47 እና 49 መሰረት በዕርቅ ወይም በሽምግልና መታየት አለበት ሊባል የሚችል አለመሆኑን ፤ይልቁንም በአዋጁ አንቀጽ 26(2)፣39 (1)(ለ)(ሐ) እና በደንብ ቁጥር 106/1996አንቀጽ 14(ሀ)(ሐ)(መ) መሰረት የማህበሩ የሥራ ሀላፊዎች ያጎደሉትን ገንዘብ እንዲተኩ በቀጥታ ክስ ለፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚቻል በተመሳሳይ ጉዳይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በመሆኑም በተጠሪዎች ላይ አመልካች በሁለቱም መዝገቦች ክስ ያቀረበው የከሳሽ ማህበር የሥራ አመራር አካላት፣የቁጥጥር ኮሚቴ እና ዕቃ ግዥ ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ በእጃቸው የገባውን የማህበሩን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው በማዋል በማጉደላቸው ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲከፍሉ እንዲወሰን በሚል እስከሆነ ድረስም ክስ የቀረበባቸውን ገንዘብ በተመለከተ ክርክር ተደርጎ በማስረጃዎች በሚረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሰረት ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚሰጥበት ጉዳይ እንጂ አስቀድሞ በእርቅ ካልሆነም በሽምግልና ዳኝነት ከታዬ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 52 መሰረት በይግባኝ ሥርዓት ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ሊመጣ የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑ ይህን ችሎት ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ የአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 47፣ 49፣26(2)፣39 (1)(ለ)(ሐ) እና ደንብ ቁጥር 106/1996 አንቀጽ 14(ሀ)(ሐ)(መ) መሰረት ተፈጻሚነትን በተመለከተ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ባላገናዘበ መልኩ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሁለቱም መዝገቦች በቀጥታ የቀረቡ ክሶችን አከራክሮ ለመወሰን ሥር ነገር የዳኝነት ሥልጣን የለኝም ሲል የክስ መዝገቦቹን በብይን የዘጋውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ብይን ተገቢ ነው ሲል ያጸናው መሰረታዊ ሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/40406 በቀን 25/07/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን ፣እንዲሁም በመ/ቁ/40407 በቀን 26/07/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል ከ/ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ከተመለከተ በኋላ በመ/ቁ/135108 በቀን 15/9/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና በመ/ቁ/135110 በቀን 22/09/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቧቸው ክሶች በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 49 ሥር የተደነገጉትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ አይደለም፡፡ ስለሆነም ክሶቹ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ በመሆናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አከራክሮ ለመወሰን ስረ ነገር ሥልጣን አለው በማለት የተዘጉትን የክስ መዝገቦች በማንቀሳቀስ የግራ ቀኙን ወኖች በማከራከር፣ ማስረጃዎችን በማስማትና በመመዝን በጉዳዩ ላይ የበኩሉን ውሳኔ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራቀኙ ወገኖች የየራቸውን ይቻሉ፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. የዚህ ፍርድ ግልባጭ ከሰ/መ/ቁ/ 90738 ጋር ተያይዞ ይቀመጥ፡፡
2. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሮ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90920

ህዳር 06 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ዓባይ ኢንሹራንስ አ.ማ

ተጠሪዎች፡- አቶ አለማየሁ አሰፋ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የልማት ድርጅት በክልል ወረዳ ፍርድ ቤት በተጀመረ ክስ የጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሲሆን ጉዳዩን የወረዳው ፍርድ ቤት ለማየት የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአቶ ኃይለጊዩርጊስ አበጀ ላይ በውጫሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ሁኖ ተከራክሯል፡፡የተጠሪ ክስ ይዘትም፡- ንብረትነቱ የስር ተከሳሽ የአቶ ኃይለጊዩርጊስ አበጀ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር 3-22157 ተሽከርካሪ መኪናቸውን ነሐሴ 11 ቀን 2003 ዓ/ም በመግጨት ጉዳት አድርሶባቸው ለጥገናው ብር 13,970.00 (አስራ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባት ብር) ማውጣታቸውንና በጉዳቱ ምክንያት ደግሞ ብር 15,000.00 ገቢ የተቋረጠባቸው መሆኑን በመጥቀስ በድምሩ ብር 28,970.00 (ሃያ ስምንት ሺኅ ዘጠኝ መቶ ሰባ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መነሻ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር የተደረገ ሲሆን ለክሱ በሰጠው መልስም ግጭቱን አደረሰ የተባለው የደንበኛው መኪና ለጉዳቱ ኃላፊ ስለመሆኑ በትራፊክ ማስረጃ ያለመረጋገጡን፣ለተቋረጠ ጥቅም ደግሞ ለደንበኛው የሰጠው ሽፋን የሌለና በመድን ውሉ የተገለለ ጉዳይ በመሆኑ ኃላፊነት እንደሌለው ገልጾ ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም በጉዳዩ ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመለክቶ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻሩና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ኃላፊነቱ ተጣርቶ እንዲወሰን ለወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መልሶለት ጉዳዩ የተመለሰለት የወረዳው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አጣርቶ ኃላፊነቱን የአመልካች ደንበኛ ነው በማለት የደመደመ ሲሆን የካሳ መጠኑን በተመለከተም ብር 26,230.43 (ሃያ ስድስት ሺኅ ሁለት መቶ ሰላሳ ብር ከአርባ ሶስት ሳንቲም) መሆኑን ገልጾ ይኼው ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፈል፣አመልካች የውል ግዴታው ከዚህ በታች ከሆነ ተከሳሽ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በወረዳው ፍርድ ቤት የታዬው ያልስልጣኑ መሆኑንና የተቋረጠ ገቢ አመልካች የሚከፍልበት የሕግ አግባብም የሌለ መሆኑን ጠቅሶ መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመራም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ውሳኔ የሰጠው የውጫሌ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ነበረው? ወይስ አልነበረውም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በዚህም መሰረት ከሳሽ ክሱን ያቀረበው በመኪናቸው ላይ ለደረሰበት ጉዳት ያወጡት ወጪ እንዲተካላቸውና የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፈላቸው ሲሆን የክርክሩ የገንዘብ መጠንም በድምሩ ብር 28,970 (ሃያ ስንምት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ብር) ነው፡፡በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/200 በአንቀጽ 28(1)(ለ)) እና በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 226(1) መሰረት የከሳሽ የዳኝነት ጥያቄ የሚወድቀው በወረዳው ፍ/ቤት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር መሆኑ ግልፅ ነው፡፡አመልካች ጣልቃ ገብ ሁኖ የተከራከረ ሲሆን ጣልቃ ገብነት በፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ አግባብ የተፈቀደ አንዱ የክርክሩ ተሳታፊነት የሚገለፅበትና የራሱን የቻለ መሰረታዊ አላማ ያለው፣በስነ ስርዓት ሕጉ የተዘረጋ ስርዓት ነው፡፡በ1958ቱ የፍትሃ ብሄር ስነ ስርዓት ሕግ ወደ ክርክሩ ሊገባ የሚችልበት ስርዓት የተለያየ ቢሆንም ይህ ስርዓት አገሪቱ ከምትከተለው የፌዴራል ስርዓትና በዚሁ ስርዓት ከተዘረጋው የፍርድ ቤቶች አደራጃጀት ጋር ተጣጥሞ በመታየት ስራ ላይ ሊወል የሚገባው መሆኑ ይታመናል፡፡በመሆኑም አንድን ጉዳይ የፌዴራል ወይም የክልል ብሎ ለመየት ይቻል ዘንድ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 የተቀመጠው መስፈርት ታይቶ የጉዳዩን የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣንም ከዚሁ አንጻር መለየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 ስር አንድን ጉዳይ የፌዴራል ጉዳይ ለማለት የሚያችሉ ምክንያቶች ተገልጸዋል፡፡የአሁኑ አመልካች በፌዴራል መንግስት የተቋቋመና የተመዘገበ የልማት ድርጅት ሲሆን በፌዴራል መንግስቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶችና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑ እና እስከ ብር 500,000 ግምት ያለው የገንዘብ ክርክር የማየት ስልጣን ደግሞ በፌዴል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/88 በአንቀጽ 5(6) እና በአንቀጽ 14 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80 (4) እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መንግስት በአንቀጽ 64(4) በተመለከተው የስልጣን ውክልና መሰረት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ በክልሉ የሚነሱ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የተሰጠው ለክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ስለሆነም የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን በሕገ መንግስቱ አልተሰጠውም፡፡የሥረ ነገረ የስልጣን ጥያቄ በማናቸውም የክርክር ደረጃ የሚነሳና ፍርድ ቤቱም በራሱ አነሳሽነት ጭምር ማየት የሚችለው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም የውጫሌ የወረዳው ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ወደ ክርክሩ መግባቱ ጉዳዩን ከስረ ነገር ስልጣኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውጪ የሚያደርገው መሆኑን ተገንዝቦ ክሱ ጣልቃ ገቡን ባካተተ ሁኔታ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይቀርብ ዘንድ ጉዳዩን ዘግቶ ማሰናበት ሲገባው ክርክሩን ቀጥሎ በማየት ውሳኔ መስጠቱና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በዚህ ረገድ የተፈጸመውን ስህተት ሳያርም መቅረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(1(ለ)) ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 90005 በቀረበው ተመሳሳይ የሕግ ጥያቄ ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር የማይጣጣም ሁኖ ስለአገኘነው የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በውጫሌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05563 በ23/04/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 36566 በ17/08/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁኑ አመልካች በጣልቃ ገብነት ተከራካሪ የሆነበትን ጉዳይ ተቀብሎ ማየት በአዋጅ ቁጥር 25/88 በአንቀጽ 5(6) መሰረት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የስር ከሳሽ ለውጫሌ ወረዳው ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረውን ክስ የአሁኑን አመልካች ጭምር በተከሳሽነት በማካተት ስልጣኑ ለሆነው ለሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት የማቅረብ መብቱ በዚህ ውሳኔ ቀሪ አልሆነም ብለናል፡፡

4.በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 78470

ሚያዝያ 7 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች:- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

አመልካቾች:- አቶ ታሪኩ ጫኔ - የቀረበ የለም

ተጠሪ :- የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ አንድ ሰው በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከስሶ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በጉዳዩ ላይ በወንጀል የሚጠይቅበት ሕጋዊ አግባብ መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ነው። አመልካች ላይ ተጠሪ ክስ ያቀረበው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1ሀ(ለ)) እና 413(ሀ) እና (ለ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ነሐሴ 20 ቀን 2001 ዓ/ም በኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ ባለስልጣን የአካባቢና ምግብ ጨረር መጠን ክትትል ባለሙያ ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት እና በመንግስት ሀብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ከመስሪያ ቤቱ ፈርመው የተረከቡትን የቀረጥና የማጋጋጥ ዋጋ ሳይጨምር ግምቱ ብር 76.867.34 የሆነን ዩኒቨርሳል ሰርቬየር ሜትር ሞዴል አር፣ጂ፣ኤስ የሆነ የጨረር መጠን መከላከያ መሳሪያ (Universal servey meter) RGS-200 እና የርቀት መቆጣጠሪያ ያለው በባትሪ የሚሰራ ባለ ብዙ ዘርፍ አገልግሎት ዲጂታል የራጂ ማሽነሪ፣ የጥራት መቆጣጠሪያ ኪት (digital diagnostic quality control)(RAD-Check plus model p6 526 multifunction meter with remot control model Rmt 240 A and collimation test too) የተሰኙ መሳሪያዎችን አመልካቹ በአዳማ ከተማ የአዳማ ሆስፒታል የራጅ መሳሪያዎችን ፍተሻ እንዲያከናውን ታዞ በተጠቀሰው ቀን በስር ሁለተኛ ተከሳሽ ከነበረውና ከመስሪያ ቤቱ ሹፌር በሆነው በአቶ አረጋዊ ታደገ በሚሽከረከር መኪና በመጫን ወደ ናዝሬት ከወሰዱ በኋላ በተጠቀሰው ሆስፒታል ተገኝተው የምርመራ ስራቸውን ማከናወናቸውን ተከትሎ እንዚህን መሳሪያዎች ለመስሪያ ቤቱ ማስረከብ ሲገባቸው ያለአግባብ ለመበልጸግ ንብረቶችን ባለመመለሳቸውና በመሰወራቸው የመውሰድና የመሰወር የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል በሚል ነው። አመልካች ክደው ተከራክረው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን ያሰማ ሲሆን አመልካችም የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸውን ያለመከላከላቸው ተረጋግጧል በሚል ምክንያት በክሱ ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ጥፋተኛ አድርጎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በስድስት ወር ጽኑ እስራትና በአንድ ሺህ ብር እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበውም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች በንብረቱ ላይ የፍ/ብሔር ክስ ቀርቦባቸው ሃላፊነት የለባቸውም ተብሎ መጨረሻና አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመስጠት ስልጣን ባለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰሚ ችሎት ውሳኔ በተሰጠበት ሁኔታ ጥብቅ የሆነ ማስረጃ ምዘና በሚጠይቀው የወንጀል ጉዳይ ላይ ጥፋተኛ መባላቸው በወንጀል ጉዳይ የማስረጃ ምዘና መርህን ያላገናዘበ መሆኑን ጠቅሰው መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፍ/ብሄር ጉዳይ ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ ተወስኖ እያለ በወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው ተብሎ በእስር እንዲቀጡ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

አመልካች በንብረቶቹ መሰወርና መውሰድ በፍትሐ ብሔር ተከሰው ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ በሰ/መ/ቁጥር 69179 የተወሰነ መሆኑን፣ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች በወንጀል ጉዳዩም የተሰሙ መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከሩ ነጥቦች ሲሆን አከራካሪው የሕግ ጥያቄ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ ነፃ የተባለ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚጠይቅበት ሕጋዊ አግባብ አለ? ወይም የለም? የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ የወንጀል ችሎት በፍትሓ ብሔር ችሎት ውሳኔ ሊገደድ የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የለም በማለት የሚከራከር ሲሆን አመልካች በበኩላቸው በወንጀል ጉዳይ የማስረጃ ምዘና መርሁ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ የማስረጃ ምዘና መርህ የጠበቀ በመሆኑ በፍትሓ ብሔር ጉዳይ ነፃ የተባለ ሰው በተመሳሳይ ጉዳይና ማስረጃ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆንበት ሕጋዊ አካሄድ የለም በሚል የሚከራከሩ መሆኑን ተረድተናል፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር በማስረጃነት አግባብነት እና ብቃት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2149 ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ያስገነዝበናል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል የተሰጠ ውሣኔ በፍትሐብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት አግባብነት የሚኖረው በወንጀል ክሱ በወንጀል ፍ/ቤት ተከሣሹ ጥፋተኛ ተብሎ ከተወሰነ ስለመሆኑ እና ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት የወንጀል ክስ ማስረጃ አመዛዘን መርህ ከፍትሐብሔር የበለጠ ጠንካራና የማያሻማ ማስረጃ የሚጠይቅ መሆኑ ነው፡፡ ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስም በወንጀሉ ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎችም በፍትሐብሔሩ ጉዳይም የቀረቡና የተሰሙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በወንጀሉና በፍትሐብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች የተለያዩ ከሆነ እና በወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበበት ነጥብም ከፍትሐብሔሩ ክስ ጋር ግንኙነት የሌለው ከሆነ በወንጀል ክስ ተጠያቂ መሆን ሁል ጊዜ በፍትሐብሔሩ ክስ ኃላፊነትን የማያስከትል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና አላማ ያስገነዝበናል፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 46386 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍ/ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን በወንጀል ጉዳይ የቀረበ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ ክብደት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ለፍትሐብሔሩ ክርክር ብቃት ያለው ማስረጃ መሆኑና በፍትሐብሔር ክብደት ሊሰጠው አይገባም የተባለ ማስረጃ ለወንጀሉ ክስ ሲቀርብ ክብደት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በጉዳዩ በፍትሐብሔር ክስ ቀርቦባቸው ኃላፊነትን የሚያስከትል ድርጊት አልፈጸሙም ንብረቶቹን በጥንቃቄ አስቀምጠው እያለ ከራሳቸው ቁጥጥር ውጭ በሆነና በሌላ ሰው በተፈፀመ የስርቆት ተግባር ንብረቶቹ መጥፋታቸው ተረጋግጧል በማለት በሰ/መ/ቁጥር 69179 በሆነው አስገዳጅና የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥቶ ባለበት ሁኔታ አመልካች በጉዳዩ በሙስና ወንጀል ተከሰው በፍትሐብሔር የቀረቡት ተመሳሳይ ማስረጃዎች በቀረበበትና በተሰሙበት እንዲሁም ተመሳሳይ ፍሬ ነገር በተረጋገጠበት ሁኔታ ጥብቅ የሆነ የማስረጃ ምዘና በሚጠይቀው የወንጀል ጉዳይ አመልካች የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል፣ አድራጎቱም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘትና በመንግስት ንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ የተፈፀመ ነው ተብሎ ድምዳሜ መያዙ መሰረታዊ የሆነ የወንጀል ማስረጃ ምዘና መርህን ባልተከተለ ሁኔታ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለልም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ድርጊት አመልካች በፍትሐብሔር ተከሰው ነጻ ከተባሉበት ድርጊት ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ጋር የሚጣረስና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 94166 ነሐሴ 20 እና 23 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 73873 ጥር 02 ቀን 2004 ዓ.ም የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ሐ) መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል ።
2. አመልካች የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸማቸው በወ/መ/ሕ/ሥሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አልተረጋገጠባቸውም ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የመስማሚያ ሀሣብ

እኔ ሰሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔ እስማማለሁ፡፡ ነገር ግን አብላጫው ድምጽ በወንጀል የተሰጠ የጥፋተኝነት ውሣኔ በፍትሐ ብሄር ጉዳይ በማስረጃነት ሲቀርብ ስለሚኖረው ውጤትና በፍትሐ ብሄር የተሰጠ ውሣኔ በወንጀል ጉዳይ ስለሚኖረው ውጤት የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 2149 ድንጋጌ በሰጠው ትርጉም የማልስማማ መሆኔ ይህንን የመስማሚያ ሀሣብ ጽፌለሁ፡፡

የፍትሐ ብሄር ሕገ ቁጥር 2149 በወንጀል ተከስሶ በነጻ መለቀቅ የፍትሐ ብሄር ኃላፊነትን የማያስቀር መሆኑን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡ ይኸ ድንጋጌ ቀድሞ በፍትሐ ብሄር ተከስሶ ኃላፊነት የለበትም የተባለ ሰው በወንጀል ጉዳይ ሲከሰስ ማስረጃዎቹ ተመሣሣይ ሲሆን ከወንጀሉ ክስ በነጻ የሚሰናበት መሆኑን የሚደነግግ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌው የራሱ የሆነ ልዩ ባህሪና ዓላማ ያለው በመሆኑ የታቃርኖ አተረጓጎም “Acontrario Interpretation” ተግባራዊ ሊሆንበት የሚችል አይደለም፡፡ በፍትሐብሄር ጉዳይ ተከራካሪዎቹ ግለሰቦች በመሆናቸው በራሳቸው ችሎትና ያለጠበቃ ተከራክረው በወንጀል የተጠረጠረው ወይም የተከሰሰው ሰው የፍትሐ ብሄር ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ሊወሰን የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ በወንጀል ጉዳይ በፍትሐ ብሄር የተሰሙትን ምስክሮችና ማስረጃ በተጠናከረ ሁኔታ በማቅረብ ዕውነቱን እንዲያወጡም ማድረግና የተከሣሹ ማስረጃ ዕምነት የማይጣልበት መሆኑን በማሳየት በወንጀል የተከሰሰው ሰው ወንጀል መፈፀሙን በሌላ ሁኔታ ለማስረዳት ከተቻለ ተከሣሹ በፍትሐ ብሄር ተከሰሶ ኃላፊነት የለበትም በመባሉ ብቻ ከወንጀል ክሱ በነጻ እንዲሰናበት የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 2149 ድንጋጌ ሊተረጎም አይገባውም፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ላይ በፍትሐ ብሄር ከተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ በተለየ ሁኔታ በወንጀል በቀረበው ማስረጃ ተጠሪ አላረጋገጠም፡፡ ይህም የተጠሪ መልስ አመልካች ወንጀል የፈፀመ መሆኑን በበቂ ሁኔታ የማስረዳት ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ አብላጫው ድምጽ አመልካች በነጻ እንዲለቀቅ መወሰኑ ተገቢ ነው ብየ በምክንያቱ ላይ ብቻ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 85237

መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ዘካሪያስ ገ/ጻዲቅ አለማየሁ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ጉዳይ በድጋሚ ክስ ሊቀርብበት አይገባም ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የሚመለከት ነው።ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁነ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ የመሰረተው ክስም በሁለት ምድብ የተከፈለ ነው።አንደኛው ክስ አመልካች ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት አስቦ በቦሌ ክፍለ ክተማ ቀበሌ 10 ውስጥ የሚገኘውን ንብረትነቱ የኦቶ ታደሰ ሙለታ መኖሪያ ቤት የሆነውን ከተከራየ በኋላ ካርታ ላሳድስላችሁ ብሎ በውክልና ከወሰደ በኋላ ቤቱን ለመሸጥ ሺል በመታወቁ የተሠጠው ውክልና ተነስቶ ክስ ቀርቦበት ይህ ቤት እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት, አግድ ተሰጥቶ እያለ ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ/ም ሐሰተኛ ሰነድ የእግድ ትእዛዝ አዘጋጅቶ እግድ እንዲነሳ ከአደረገ በኋላ የግል ተበዳይ ታደሰ ሙለታ ውክልና የተሰጠው በማስመሰል በሐሰተኛ ውክልና በመገልገል ቤቱን በብር 1,030,000.00(አንድ ሚሊዩን ሰላሳ ሺህ ብር) ለወ/ሮ ሰናይት ብርሃኑ ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ/ም ሸጦ ለግል ጥቅም በማዋል በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 696(ሐ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ ማታለል ፈፅሟል የሚል ሲሆን ሁለተኛ ክስ ደግሞ በሐሰተኛ ሰነዶች በመገልገል የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 378 ድንጋጌን ተላልፏል የሚል ነው።የአሁኑ አመልካችም ክሱን ክዶ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ስድስት የሰው ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ ክሱን ማስረዳቱን ፍርድ ቤቱ ከተገነዘበ በኋላ የአመልካችን የመከላከል መብት በመጠበቅ የመከላከያ ማስረጃዎችን ሰምቷል።ከዚኅም በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በክሱ መሰማት ጊዜ ቀድሞ በጉዳዩ ላይ ተከሰው በነፃ የወጡ መሆኑን የገለጹ መሆኑን የተረዳ መሆኑን ጠቅሶ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን የመከራከሪያ ነጥብ ቀድሞ አመልካች ተከሰው ነጻ የወጡበት ጉዳይ በኋላ ከቀረበባቸው ክስ ጋር ልዩነት ያለው ነው በማለት በሚል ምክንያት ውድቅ ያደረገው ሲሆን ዋናውን ጉዳይ በተመለከተም አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎች የአቀቤን ማስረጃዎችን ያላስተባበለ መሆኑን በመግለጽ የመከላከያ ማስረጃዎችን ውድቅ በማድረግ አመልካችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሰው በቀረቡት ሁለቱም ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ አድርጎታል።ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አሰተያየት በመቀበል ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ መመልከቱን በመግለፅ ለሁለቱም ክሶች በድምሩ በ17(አስራ ሰባት)አመት ፅኑ እና በብር 40,000.00(አርባ ሺህ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል።በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሰበር አቡቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በጉዳዩ ላይ ቀድሞ ክስ ቀርቦበት በነፃ ተለቀው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የነፃ መለቀቁ ውሳኔ ጸንቶ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ አልፈው አመልካችን በድጋሚ ክስ ቀርቦ በመቀበል ተጠያቂ በማድረግ መወሰናቸው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 23 ስር የተመለከተውን የሚጥስ ነው በማለት መከራከሩንና በዚህ ምክንያት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ቀድሞ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ;ጥር 64230 ክስ ቀርቦበት በነጻ ተሰናብቶ ይኼው ውሳኔ በመ/ቁጥር 109368 በይግባኝ ቀርቦ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጸንቶ ባለበት ሁኔታ ሁኔታ በድጋሚ ክሰ ቀርቦበት በወንጀል ተጠያቂ የመባሉትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለአሁኑ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በአመልካች ላይ የተሰጠው በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 696(ሐ) እና 378 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የወንጀል ድርጊቶቹን መፈፃማቸው ተረጋግጧል ተብሎ መሆኑን፣አመልካች በነፃ ተሰናብቼአለሁ በማለት የሚከራከሩበት ጉዳይ ደግሞ አንቀጽ 678 ስር የተመለከተውን ተላልፈዋል ተብሎ ክስ ቀርቦባቸው የነበረ መሆኑን፣በሁለቱም ክሶች የቤቱ ባለንብረት የተባሉትና ለክርክሩ ምክንያት የተባለው የቤት ሕጋዊ ባለንበብት የሆኑት ግለሰብ አቶ ታደሰ ሙለታ የተባሉት መሆናቸውን፣አመልካች በነጻ ወጡ የተባለበት የወንጀል ድርጊት ዝርዝር ይዘቱ ሲታይም አመልካቹ ያግባብ ለመበልፀግ ሳይሆን የንብረቱን ባለቤት በንብረቱ እንዳጠይቀምበት ለማድረግ በማሰብ ታህሳስ 30 ቀን 2002 ዓ/ም በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/09 ልዩ ቦታው የቦሌ ክፍለ ከተማ መስተዳደር ግቢ ውስጥ የግብለ ተበዳይ አቶ አጋ ሙሉታ በሰጡት ህጋዊ ውክልና ተጠቅሞ የቤት ቁጥቱ 52716 የሆነውን ኦርጂናል የቤት ካርታ ወስዶ ባለመመለሱ የግል ተበዳይ ንብረትነቱ የአቶ ታደሰ ሙሉታ የሆነውን በውክልና የሚያስተዳድሩበትን ኦርጅናል የቤት ካርታና ፕላን ህዳር 15 ቀን 2002 ዓ/ም ከወሰደ በኋላ የግል ተበዳይ መልስልኝ ሲሉት ባለመመለሱ በሌላ ሰው ሃብት ያላግባብ መገለገል ወንጀል ፈጽሟል የሚል መሆኑን፣የአሁኑ ክስ ግን በሐሰተኛ ሰነድ የአቶ ታደሰ ሙሉታን ንብረት በመሸጡ ከባድ የማታላል ወንጀል ፈጽሟል፣በሐሰተኛ ሰነድም ተገልግለዓል የሚል ሁኖ ድርጊቶቹ የተፀሙበት ጊዜና ሁኔታ ቀድሞ ቀርቦ ከነበረው ክስ ጋር የተለያዩ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪብሊክ ሕገ መንግስት የወንጀል መርህ ተደርገው ከተደነገጉት መብቶች አንዱ አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነት ተረጋጋግቶ በተቀጣበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና መከሰስና መቀጣት የሌለበት መሆኑን የሚደነግግው አንቀጽ 23 ይገኝበታል፡፡ይህ መርህ በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ውስጥም በአንቀጽ 2(5) ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(4) መሰረት የአገሪ የህግ አካል በተደረጉ አለምአቀፍ ስምምነቶች ውስም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሲቭልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት በአንቀጽ 14 ስር ያስቀመጠው ድንጋጌ ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡በመሆኑም ይህ መብት በሕግ ጥበቃ የተደረገለት መሆኑ ግልጽ ሲሆን መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ በሕጉ የተቀመጡት መመዘኛዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ የግድ ይላል፡፡አንድ ሰው በድጋሚ ልከሰስ አይገባም ብሎ ለመከራከር በሕጉ ይዘትና መንፈስ መሰረት መሟላት ያለባቸው ሕጋዊ መሰፈርቶች ተከሳሹ በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ መሰረት ተከሶ የነበረ መሆኑና ቀድሞ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት የመጨረሻ በሆነ ፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ ወይም በነፃ የተለቀቀ መሆን በሚገባ መረጋገጥ ስለመሆናቸው ከመርሁ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡የዚህ መርህ ዓይነተኛ አላማም ዜጎች በአንድ የወንጀል ድርጊት በተደጋጋሚ በሚቀርብ ክስ ስጋት ውስጥ ከመኖር ነጻ እንዲሆኑ ማድረግ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡በሌላ በኩል መርሁ ተግባራዊ ሲደረግ በሕጉ የተቀመጡት መመዘኛዎችን በጥንቃቄ በማየት የተከሳሹን መብት ተገቢ በሆነ ሁኔታ ለማስከበር ከማስቻሉም በላይ አጥፊዎች ከወንጀል ድርጊት ነጻ እንዳይወጡና ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግና የወንጀል ሕጉን ዓላም በሚያሳካ መልኩ ተግባራዊ መደረግ ያለበት መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ የተመለከቱትን ሕጋዊ መመዘኛዎችንና ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መመልከቱና ዳኝነት መስጠቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

የአመልካችን ጉዳይ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በቀድሞው ክስ የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥትቶ አመልካች በነፃ የተሰናበቱ መሆኑን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥ 64230ና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ቁጥር 109368 የሚያረጋግጡት ሀቅ ሲሆን በእነዚህ መዛግብት የታዩው ጉዳይ አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 678 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በሌላ ሰው ሃብት ያላግባብ መገልገል ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው የተከሰሱትና በኋላም ፍርድ ቤቶቹ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ተጠሪን ነፃ ያደረጉበት ምክንያት አመልካች የወሰዳቸው የቤት ካርታዎች በሽያጭና በብድር ውል መያዣነት መሆኑን ተረጋግጧል በሚል ነው፡፡ይህም የሆነው በክሱ ላይ የተጠቀሳን የባለቤትነት ደብተር ካርታና ፕላን እንዲያወጡ እንዲረከቡ ውክልና ሰጪው ለአመልካች ውክልና መስጠታች በመረጋገጡ፣የቤቱ ባለቤት ከባለቤታቸው ጋር በመሆኑን ቤቱን ለአመልካች በመሸጣቸውና በአሁኑ አመልካችና በአቶ ታደሰ ሙለታ የገንዘብ ብድር ውል ተደርጎና በፍርድ ቤት አመልካቸ አቶ ታደሰ ሙለታን በመክሰስ በመ/ቁጥር 88655 የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ/ም ለአሁኑ አመልካች የተፈረደላቸው መሆኑን በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል በማለት ፍርድ ቤቶቹ ድምዳሜ ላይ በመድረሳቸው ምክንያት ነው፡፡ባሁኑ ጉዳይ አመልካች የተከሰሱት የግል ተበዳይ ቤት እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍድ ቤት በመ/ቁጥር 165253 እግድ ተሰጥቶ እያለ ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ/ም በሐሰተኛ ሰነድ የእግድ ትዕዛዝ በማዘጋጀት እግዱ እንዲነሳ ከአደረገ በኋላ የግል ተበዳይ የአቶ ታደሰ ሙለታ ወክልና የተሰጠው በማስመሰል በሐሰተኛ ውክልና በመገልገል ቤቱን ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ/ም ሸጠዋል በሚል ነው፡፡ስለሆነም አመልካች ቀድመው በግል ተበዳይ ላይ የፍትሓ ብሔር ክስ አቅርበው የነበሩ መሆኑ ቢረጋገጥም በፍርድ ቤት የተሰጠውን እግድ ግን ለውጠዋል፣እግድ የተነሳ መሆኑን የሚሳይ ማስረጃም ሐሰተኛ ነው በማለት አቃቤ ክስ መመሰረቱን በግልጽ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡አመልካች ከግል ተበዳይ ወሰዱ የተባሉትና ስለመኖሩ በመ/ቁጥር 64230 በቀረበው የወንጀል ክስ ተረጋግጧል የተባለው የውክልና ሰነድም በጥር ወር 2002 ዓ/ም ውስጥ መሻሩ አሁን እያከራከረ ባለው የወንጀል ጉዳይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 678 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል ተብሎ በአቃቤ ሕግ በስር ፍርድ ቤት ክስ የቀረበባቸውም የካቲት 17 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2002 ዓ/ም ስለመሆኑ በፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 64230 ጋር ተያይዞ ካለው የክስ ማመልከቻ ተመልክተናል፡፡እግዲህ የግል ተበዳይ ቤት የተሸጠው በሐሰተኛ የፍርድ ቤት እግድ ማንሻ ትዕዛዝና የውክልና ስልጣን ስለመሆኑ በሰው ምስክርነትም ሆነ በፎረንሲክ ምርምራ ውጤት ማስረጃዎች በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ በቀደመው ክስ አመልካች የግል ተበዳይን በቤቱ እንዳይገለገል አድርጓል የተባለው የቤቱን ካርታ ሊመለስ አልቻለም ተብሎ ሲሆን በሁለተኛው ክስ ግን ሐሰተኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት የግል ተበዳይን ቤት ሸጧል በሚል ነው፡፡ በግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም ወይም በፊት አመልካች የግል ተበዳይን ቤት በሕጋዊ መንገድ የገዙት ስለመሆኑም አልተረጋገጠም፡፡በመሆኑም አመልካች አሁን የቀረበበት ክስ ዝርዝር ይዘቱ፣የድርጊቱ አፈጻጸም እና ጥሰት ተደርጎበታል የተባለው የግል ተበዳይ የመብት አድማስ ቀድሞ ክስ ከቀረበበት ጉዳይ ዝርዝር ይዘት ጋር የማይገናኝ ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት በአንደ ጉዳይ በድጋሚ በወንጀል የተከሰሱ መሆናቸውን ገልጸው ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አላገኘንም፡፡

የወንጀል ድርጊቶችን አፈጻጸም በተመለከተ አመልካች ግልጽ የሆነ የሰበር ቅሬታ ያላቀረበቡት ቢሆንም ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርደ ቤቶች በሚገባ ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑና ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ሲታይም የተለዩ ድምዳሜ የሚያዝበት ሁኖ አልተገኘም፡፡አመልካች ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ያልወጡትን ሰነዶችን ከመንግስት መስሪያ ቤቶች እንደወጡ በማስመሰል፣በሐሰተኛ መንገድ በማዘጋጀት የግል ተበዳይን ቤት የሸጡ መሆናቸው በአንቀፅ 696(ሐ) ስር የተመለከተውን መተላለፋቸውን የሚያሳይ ሲሆን ይህንኑ ቤቱን ለመሸጥ አድራጎት ጥቅም የዋሉት ሐሰተኛ ሰነድ መሆኑ ደግሞ ይኼው አድራጎት በተገቢው ድንጋጌ በተደራቢነት የሚያስጠይቃቸው መሆኑን ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 699 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም አመልካች በአንቀጽ 696(ሐ) እና 375 ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ መባላቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2)፣58 እና ከወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንጻር ሲታይ ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው ድንጋጌዎች ከሚያስቀጡት የቅጣት መጠንና ከቅጣት አጣጣል መርሆዎች እንዲሁም ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 101193 ሕዳር 21፣ታህሳስ 02 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 79603 መስከረም 30 ቀን 2005 ዓ/ም የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ሐ)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ለማረሚያ ቤቱ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች በአንድ የወንጀል ድርጊት ድጋሚ አልተከሰሱም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.85596

መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አለማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- እነ ሰይፉ ደስታ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሠጠው የቅጣትና የቅጣት አፈፃፀም ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በከባድ ቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፊንፊኔ ዙሪያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆኑ ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ፣ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-41869 በማሽከርከር ላይ እያለ ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ ጥር 27 ቀን 2003 ዓ.ም ከቀኑ ስምንት ሰዓት ተኩል ሲሆን ጫናጮ ከተማ ቀበሌ 01 ፊኔት ግዛው የተባለች ልጅ በመግጨት በከባድ ቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል፡፡ አመልካች አደጋው ተከስቷል፡፡ ከአቅሜ በላይ በሆነ ሁኔታ ህፃኗን ገጭቻለሁ በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የሰው ምስክሮችና የትራፊክ ፕላን መግለጫ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ ተጠሪ መከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(2) የተመለከተውን በመተላለፍ በከባድ ቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ነው በማለት ውሳ ሰጥቷል፡፡

የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ አመልካች በህፃኗ ወላጆች ብር 35,000 (ሰላሳ አምስት ሺ ብር) ካሳ የከፈለ መሆኑን፣ የዘወትር ፀባዩ መልካም የነበረ መሆኑንና በዐቃቤ ህግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመዘርዝር አመለካች በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ቀላል እስራትና በብር 1500 (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የቅጣት ውሳኔውን በማሻሻል አመልካች በስምንት ወር እስራትና በብር 700(ሰባት መቶ ብር) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት የቅጣት ውሳኔው ሳይፈፀም አመልካች ለሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ መስጠት ተገቢ ሆኖ ያገኘው መሆኑን በመግለፅ፣ የቅጣት ውሳኔው ለሁለት ዓመት ተገድቦ እንዲቆይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ይህ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የእስራትና የገንዘብ ቅጣቱን የወሰነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያወጣውን የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2000 ሳይከተል ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን የቅጣት ውኔሳ አፅንቶታል፡፡

የእስራት ቅጣት አፈፃፀሙንም በተመለከተ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የእስራት ቅጣቱ አፈፃፀም ለሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ ታግዶ እንዲቆይ የሰጠውን ትዕዛዝ በመሻር አመልካች የተወሰነበትን የአንድ ዓመት ከስድስት ወር የእስራት ቅጣት ይፈፅም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን የቅጣት ውሳኜ የሻረው ያለበቂ ምክንያትና ሕጋዊ መሰረት ነው፡፡ ተጠሪ የቅጣት ውሳኜው አፈፃፀም መገደብ የለበትም በማለት የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ቅጣቱ የእስራት ቅጣትና መቀጮ በጣምራ የያዘ መሆኑን ገልፆ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ቅጣቱ በሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ ያመይገደብበትን ምክንያት በውሳኔው ሳገልፅና ሳይዘረዝር ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቅጣት ውሳኔው እንዲገደብ የሠጠውን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ተጠሪ ጥር 2 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ የወንጀል ህጉንና የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ማፅናቱ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች ምንም አይነት ሙያዊ ጥንቃቄ ባለማድረጉና በፍጥነት በማሽከርከር ህፃኗን ገጭቶ የሞት አደጋ አድርሷል፡፡ ይህ የአመልካች አድርጎት የቅጣት ውሳኔውን ለመገደብ የሚያስችል ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቅጣት ውሳኔው እንዲገደብ የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር እሎት መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ጥር 24 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያደረጉት የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የእስራት ቅጣት አፈፃፀሙ በሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ ተገድቦ እንዲቆይ የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ህጉን መሰረታዊ ድንጋጌዎችና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 16 መሰረት በማድረግ የአንድ ዓመት ከስድስት ወር እስራትና ብር 1500(አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) መቀጮ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን የቅት ውሳኔ የሻረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን በተዛባ መንገድ በመተርጎም መሆኑን ከውሳኜ ይዘት ተረድተናል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በመሻር፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ማፅናቱ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲታይ በጭብጥነት የተያዘ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አመልካች በአንድ ዓመት ከስድስት ወር የእስራት ቅጣትና በብር 1500 (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) መቀጮ እንዲቀጣ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የሌለበት ነው፡፡

2. በዚህ ሰበር ችሎት አከራከሪ የሆነው ጭብጥ በአመልካች ላይ የተሰጠው የእስራት ቅጣት ውሳኔ አፈፃፀም ለሁለት አመት የሙከራ ጊዜ ሊገደብ ይገባዋል ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት አፈፃፀም ለሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ እንዲገደብ ውሳኔ የሰጠው የቅጣት ውሳኔው መገደቡ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 192 የተመለከተውን መሰረታዊ ዓላማ የሚያሳካ ነው በማለት እንደሆነ ከውሳኔው ተረድተናል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የእስራት ቅጣቱ አፈፃፀም እንዲገደብ የሰጠውን ውሳኔ የሻረው አመልካች ከባድ በሆነ ቸልተኝነት የግል ተበዳይን በመግጨት የሞት አደጋ አስከትሎባታል በማለት ነው፡፡ ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት አመልካች የወንጀል ህጉን አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 2 በመተላለፍ በከባድ ቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱን በመመልከት ብቻ የቅጣት ውሳኔው አፈፃፀም ለመገደብ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ሆኖም በተከሳሽ ላይ የተወሰነ የቅጣት ውሳኔ ከመገደቡ ወይም የገደብ ውሳኔው ከመሻሩ በፊት የቅጣት ገደብ ስለሚከለከልበትና ስለሚሻርበት ሁኔታ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘትና አላማ ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሳሽ የቅጣት አፈፃፀም እንዲገደብ ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ መስጠት የማይችሉባቸው ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 194 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች፣ አንደኛውን ሁኔታ አመልካች የሚያሟላ ስለመሆኑ በውሳኔው አልገለፀም፡፡ ይህም በአመልካች ላይ የተወሰነውን የቅጣት ውሳኔው አፈፃፀም እንዳይገደብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 የተዘረዘሩት የመከላከያ ምክንያቶች በሌሉበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 2 ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱን በመመልከት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቅጣት ውሳኔው እንዲገደብ የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ፣ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 194 ድንጋጌዎች ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ መሰረት ያላደረገ ነው፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ አመልካች የተወሰነበት የእስራት ቅጣት ከሚፈፀም ይልቅ የቅጣት ውሳኔው ታግዶለት አመሉ ቢፈተን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 190 በተደነገገው መሰረት የአመልካችን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻልና አመልካችን ወደመደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ የሚያስችል መሆኑ ስለ አመልካች ባህሪ ማህራዊና አቋም፣ የትምህርት ደረጃና የወንጀለኛነት ባህሪና ፀባይ ማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለው በይግባኝ ሰሚው ችሎት የታመነበትና ውሳኔ የተሰጠበት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ከተሰጠው የሰበር ሥልጣን በመውጣት ስለአመልካች ጠባይ አመልካች ከጥፋቱ ሊታረምና ሊሻሻል ስለሚችልበት ሁኔታ ያሉትን ፍሬ ጉዳዮች በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 190 እና 192 መሰረት ቅጣቱ እንዲገደብ የሰጠውን ወሳኔ መሻሩ የሕግ መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ ረገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔና የሕግ ትርጉም ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 32280 እና በሌሎች መዝገቦች የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያልተከተለና የአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት በሁለት ዓመት ሙከራ ጊዜ እንዲገደብ የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሰራታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በአመልካች ላይ የተወሰነው የቅጣት ውሳኔ ሊገደብ አይገባም፣ አመልካች የእስራት ውሳኔውን ይፈፀም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡
2. በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የወሰኑት የአንድ ዓመት ከስድስት ወር የእስራት ቅጣት በሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ ተገድቦ እንዲቆይ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 190 እና አንቀጽ 192 መሰረት ወስነናል፡፡ በዚህ በኩል የእስራት ቅጣት ውሳኔው አፈፃፀም እንዲገደብ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 190፣ አንቀጽ 192 እና አንቀጽ 194 መሰረት ያደረገ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት በማለት ወስነናል፡፡
3. በአመልካች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት አፈፃፀም ለሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ የተገደበ መሆኑን እንዲያውቁት ለኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ኮሚሽንና ፍትህ ቢሮ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86570

ሚያዝያ 07 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ጌታቸው ገላዬ ፈረደ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የደቡብ ክልል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሰው የመግደል ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ባሁኑ አመልካች እና አቶ ሰይፈ ገ/ሚካኤል በተባሉት ግለሰብ ላይ በሐዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተከሳሾቹ በዋና ወንጀል አድራጊነትና ተካፋይነት ሰኔ 02 ቀን 2004 ዓ/ም በሀዋሳ ከተማ ባህል አዳራሽ ክፍለ ከተማ በአደሬ ቀበሌ ፋሚሊ ሆቴል ተብሎ በሚጠራው ቤት ሚች ቡቹ ወይም ብስራት ተፈሪ የተባለውን የአሁኑ አመልካች በያዘው ሽጉጥ ተኩሶ ግራ ብብቱን መትቶ እንደገደለውና የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው ግለሰብ ደግሞ የውሲኪ ጠርሙስ ይዞ ሚች እንዳይቀሳቀስ ያደረገውና ሚች የተመታበት ሽጉጥ ቀላህ በመሰወር የአሁኑን አመልካች የረዳ መሆኑን ዘርዝሮ ተከሳሾቹ ሆነ ብለው በፈፀሙት ከባድ የግድያ ወንጀል በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕጉ አንቀፅ32(1(ሀ) እና 539(1ሀ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም እንደክሱ ድርጊቱን ያለመፈፀማቸውን ጠቅሰው ጥፋተኛ ያለመሆናቸውን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም ድርጊቱን ራሱ ለመከላከል ሲሉ የፈፀሙት መሆኑን የሚያሳይ ጭብጥ አስይዘው የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአመልካች ድርጊት በሕጋዊ መከላከል ስር የማይወድቅ መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን ጠቅሶ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክረክር ውድቅ በማድረግ የወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰ ሲሆን ድርጊቱ የሚሸፍነው ደግሞ በአቃቤ ክስ በተመለከተው ድንጋጌ ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 540 ስር ነው በማለት አመልካችን በተራ የሰው ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ያላቸው ሲሆን ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን ጋር አዛምዶ መመልከቱን ገልፆ አመልካችን በ15 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁን አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በተራ የሰው ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ መባላቸውን በተመለከተ ያፀናው ሲሆን ቅጣቱን በተመለከተ ግን አሻሽሎ ስምንት ዓመት ሊሆን ይገባል ሲል ምክንያቱን ጠቅሶ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበል የቀረ ሲሆን የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም ድርጊቱን በሕጋዊ መከላከል ስር የሚሸፍን ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ አመልካችን በወንጀል ተጠያቂ ማድረጋቸው ከህጉ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ተጠሪ ቀርቦ በሰጠው መልስ የአመልካች አድራጎት በሕጋዊ መከላከል ስር የማይሸፈን ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን ጠቅሶ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በወንጀል ድርጊት ተጠያቂ መደረጋቸው ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክስሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ሟችን መግደላቸውን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት ድርጊት ሕጋዊ መከላከል ነው፡፡ በወንጀል ተጠያቂነትን አያስከትልም በማለት መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን በወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው በማለት ውሳኔ ሊሰጡ የቻሉት አመልካች ከሟች ጋር ተጣልተው በሰዎች ከተገላገሉ በኃላ ሟች ወደ አመልካቹ በመሄድ ላይ እያለ አመልካቾ ሌሎች አማራጮችን ሳይጠቀሙ የጦር መሳሪያ ያልያዘውን ሟች ወደ አመልካቹ ሳይጠጋ ተኩሰው መምታታቸው በሕጋዊ መከላከል ስር የሚሸፈን አይደለም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ አመልካቹ ሟች በሕይወቱ ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል ሳንጃ ይዞ በመምጣት ጥቃት ሊሰነዝርብኝ ሲል ድርጊቱን መፈፀሜ ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን ውድቅ ማድረጋቸው ያላግባብ ነው በማለት አድራጎታቸው በሕጋዊ መከላከል ስር እንዲወድቅ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ ባግባቡ ያልታዩላቸው መሆኑን በመግለጽ የሚከራከሩ መሆኑንም ተረድተናል፡፡ ሆኖም አመልካቹና ሟቹ ተጣልተው ቆይተው ሰዎች ከገላገሏቸው በኃላ ሟቹ ወደ አመልካች የሥራ ቦታ ተመልሶ በመሄድ ላይ እያለ በሽጉጥ ጥይት ተመትቶ ስለመሞቱ ከመረጋገጡ ውጪ አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ ሟቹ በህይወት አትኖራትም ብሎ ዝቶ ከሄደ በኃላ ሳንጃ ይዞ በመመለስ ሌላ አማራጭ በሌለበት ሁኔታ ጥቃት ሊያደርስ ሲል ነው ድርጊቱጁ የተፈፀመው በማለት የሚያነሷቸው ፍሬ ነገሮች ፍሬነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያላረጋገጧቸው በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረት ከተሰጠው ስልጣን አንፃር በዚህ የሰበር ደረጃ ተቀባይነት የሚሰጣቸው ነጥቦች አይደለም፡፡ ይህ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተትን ከማረም ውጪ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን በሕግ አልተሰጠውምና፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጧቸው ነጥቦች አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ ከሚያነሷቸው ጋር የማይጣጣሙ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረቡትን የአመልካችን ቅሬታዎችን የምንቀበላቸው ሁነው አልተገኘም በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች እንዳለ ይዘን ጉዳዩ በህጋዊ መከላከል ስር የሚወድቅ መሆን ያለመሆኑን ተመልክተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ ህጋዊ መከላከል በወንጀል የሚያስቀጣው የራስን ወይም የሌላውን ሰው መብት ህገ ወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ህገወጥ ጥቃት ለማዳን ጥቃቱ እንዳይደርስ ለማድረግ ሌላ መንገድ ሳይኖር ከሁኔታው መጠን ባለማለፍ የተፈጸመ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪብሊክ የወንጅል ሕግ አንቀጽ 78 ይዘትና መንፈስ የምረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ሕጋዊ መከላከል የወንጀል ተጠያቂነትን የማያስከትለው ተመጣጣኝ የሆነ ዘዴ ወይም መሳሪያ በመጠቀም በቅርብ መድረሱ የማይቀረውን ህገ ወጥ የሆነ ጥቃት ለመከላከል አስፈላጊ የሆነ ድርጊት መፈፀም ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪብሊክ የወንጀል ህግ አንቀፅ 78 እነ 79 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ በግልጽ ያሳያል፡፡ አመልካች በሕይወታቸው ጥቃት እንዳይደርስ ሌላ አማረጭ ያልተጠቀሙ መሆኑን ሟቹ ከያዘው መሳሪያ ተመጣጣኝነት የሌለውን መሳሪያ መጠቀማቸው በሚገባ የተረጋጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ድርጊቱ የተፈፀመው በህጋዊ መከላከል ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 541 ስር በተመለከተው አኳኋን ሕጋዊ መከላከልን ከመጠን የማላለፈው አድራጎት ነው እንዳይባልም ድርጊቱ የተፈፀመው አመልካቹና ሟቹ ጠብ አስነስተው በሰዎች ተገላግለው ከተለያዩ በኃላ በመሆኑ ቅጣትን የሚያቀሉ ምክንያቶች ሰውን የመግደል ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጡት ነጥቦች ስንነሳ የአመልካች አድራጎት መበህጋዊ መከላከል ስር የሚሸፈን ሁኖ ስላላገኘነው በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ሌላው አመልካች በቅጣት አወሳሰን ጊዜ የበታች ፍርድ ቤቶች የወንጀሉን ደረጃ ከባድ ነው በማለት መመደባቸው ተገቢ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ውሳኔ ሲሰጥ የያዘው ድምዳሜ መሰረት ያደረገ እንጂ ይሕ የሥር ፍርድ ቤት ድምዳሜ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተለውጦ ወንጀሉ መካከለኛ ደረጃ ተብሎ የተመደበ መሆኑን መሰረት ያላደረገ የክርክሩን ሂደት የማያሳይ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም አመልካች በወንጀል ተጠያቂ ናቸው ተብሎ በተራ ቁጥር የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው በስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስላላገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12474 ጥቅምት 14 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58175 ታህሳስ 04 ቀን 2005 ዓ.ም ቅጣቱ ብቻ ተሻሽሎ የፀናው እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር58330 ታህሳስ 18 ቀን 2005 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች ድርጊት በሕጋዊ መከላከል የሚሸፈን አይደለም ብለናል፡፡
3. በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የፀና መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲየስፈጽም ለማ/ቤቱ ይገለፅለት ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80119

የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ረቶ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ተድላ ተገኝ ጉዳይ ተከታይ ቢያዝን አበራ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ሕግ የረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተው ክስ በአምስት ምድብ የተከፈለ ሲሆን አንደኛው ክስ በ1949 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 667(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ጥር 10 ቀን 1995 ዓ/ም ለአቶ አመሸ ጌታሁን በሰጡት የብር 40,000.00(አርባ ሺህ) ገንዘብ ብድር በወር 10% እንዲከፍል በመጠየቅና በመዋዋል ገንዘቡን በማበደር ተበዳይ ወለዱን ለወራት ሲከፍሉ ቆይተው በማቋረጡ በፍርድ ቤት ተከሰው በጠቅላላ ከእነወለዱ ብር 58,000.00(ሃምሳ ስምንት ሺኅ ብር) ቤቱን ሸጦ እንዲከፈል በማድረጋቸው የአራጣ የወንጀል ድርጊት ፈጸመል የሚል ሲሆን 2ኛው ክስም አመልካች ቀኑ በትክክል ባልታወቀበት በነሐሴ ውር በ1994 ዓ/ም ለግል ተበዳይ አቶ አሰፋ አበበ በወቅቱ የገጠመውን የገንዘብ ችግር ምክንያት በማድረግ ብር 20,000.00(ሃያ ሺኅ ብር) በማበደር በህግ ከተፈቀደው የወለድ መጠን በላይ በወር 10% ሊከፍል በመዋዋልና በመያዣነት የገንዘብ መጠን የተፃፈበትን ቼክ በተበዳይ የተፈረመና በአመልካች ልጅ ስም የተፃፈ በመቀበል ብድሩን በመስጠት ተበዳይ ዋናውን ገንዘብ ከፍለው ወለዱን ብር 18,000.00 ሳይከፈሉ በመቅረታቸው በፍርድ ቤት ክስ በመመሰረት የመኖሪያ ቤታቸውን ያሸጡ መሆኑን በመጥቀስ ነባሩን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 667(1) ተላልፈዋል የሚል ነው፡፡3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ ክሶችም በተለያዩ ግለሰቦች፣በተለያዩ ጊዜያአት ከተፈጸሙ የአራጣ ወንጀል ድርጊቶች ጋር የተያያዙ ሁነው በስር ፍርድ ቤት በተለያየ የክርክር ደረጃ አመልካች በነጻ እንዲሰናበቱ የተደረጉባቸው ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

አመልካችም ክሱን ከተረዱት በኋላ በሶስተኛው ክስ ላይ ተቃውሞ ከማቅረባቸው ውጪ በሌሎች ክሶች ላይ ተቃውም የሌላቸው መሆኑን በመግለጻቸው ምክንያት ስለየድርጊቱ አፈጻጸም የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ክደው ተከራክሯል፡፡አቃቤ ሕግ በበኩሉ የሰውና የሰነድ ማስጃዎች ያሉት መሆኑን ገልጾ ማስረጃዎችን አስምቷል፡፡የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ከተሰሙ በኋላም የአመልካች የመከላከል መብቱ ተጠብቆላቸው የመከላከያ ማስረጃዎች ተሰምተዋል፡፡ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች የመከላከያ ማስጃዎች የአቃቤ ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃዎችን ለማስተባበል የሚችሉ ሳይሆኑ የሚያጠናክሩ ሁነው መገኘታቸውን ገልጾ የመከላከያ ማስረጃዎችን ውድቅ በማድረግ አመልካችን በሁለት ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ ቅጣቱን በተመለከተ ደግሞ ለሁለቱ ክሶች ለእያንዳንዳቸው በአንድ አመት ከስድስት ወር፣በድምሩ በሶስት አመት ፅኑ እስራትና በብር 4000.00(አራት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የአቃቤ ሕግ ክስ ይዘት በወንጀል ሕጉ ስለአራጣ የተደነገገውን ድንጋጌ እንደማያቋቁም፣አቃቤ ሕግ በማስረጃዎቹ አቀራረብና የማስረዳት ግዴታ በሕጉ የተመለከተውን መመዘኛ ያላሟላ መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኛነት ውሳኔ እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ላይ ከተጠቀሱት ክሶች ውስጥ በተራ ቁጥር ሁለት በተጠቀሰው የወንጀል ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተው ክስ ብዛቱ አምስት ሲሆን ጥፋተኛ የተባሉት ግን በሁለት ክሶች ብቻ ሁኖ በእነዚህ ክሶችም አመልካች የግል ተበዳዮች የገንዘብ ችግር ያጋጠማቸው መሆኑን በማወቅና በተለያዩ ዘዴዎች የግል ተበዳዮችን በማግኘት በተለያዩ ጊዜያአት፣ለተለያዩ ግለሰቦች የተለያየ መጠን ያለውን የገንዘብ ብድር ሰጥተው ከህግ ከተደነገገው ውጪ የወለድ ተመን ሲያስከፍሉ ቆይተዋል፣በዚህ አድራጎታቸውም የአራጣ ወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል በሚል ነው፡፡አመልካች የወንጀል ድርጊቶችን ክዶ የተከራከረ ሲሆን አቃቤ ሕግ በኩሉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ ከአሰማ በኋላ የቀረቡት ማስረጃዎች የወንጀል ድርጊቱ ስለመፈጸሙ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት በበቂ ሁኔታ መመስከሩን ፍርድ ቤቱ በመገንዘብ አመልካች የአመልካችን የመከላከል መብት ያከበረላቸው ሲሆን አመልካች የመከላከያ ማስረጃዎቹን አቅርበዋል፡፡በዚህ ችሎቱ እንዲታይ በጭብጥነት ለተያዘው የሁለተኛ ክስ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ለመከላከል ያቀረቡት በፍርድ ቤት የተሰጠውን የፍትሀ ብሔር ክስ ውሳኔዎችን ሲሆን ፍርድ ቤቱም እነኚህን የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃዎች ይዘት በመመዘን የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን የማስተባበል ብቃት የሌላቸው መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን ዘርዝሮ ውድቅ አድርጓቸዋል፡፡በዚህ ረገድ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩትም በክሱ ለተጠቀሱት ግለሰብ መያዣ ይሆነው ዘንድ ቼክ ተፅፎ የተሰጠው ለአመልካች ልጅ እንጂ ለአመልካች አይደለም፣የፍትሃ ብሄር ክሱ የሚያሳየውም አመልካችን ሳይሆን የአመልካችን ልጅ ነው በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የአመልካች ልጅ የተሰጣቸው ቼክ መነሻው ለግል ተበዳዩ አመልካች የሰጡት ብድር መሆኑንና ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑን፣ አመልካች ብድሩን ለግል ተበዳይ ማበደራቸውን፣የብድሩ ወርሃዊ የወለድ መጠንም ሕጋዊ ያለመሆኑን ከማረጋገጡም በተጨማሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች ልጅ በወንጀሉ አፈጻጸም ተሳታፊ ነበሩ ከሚያስኝ በስተቀር አመልካችን ከወንጀል ተጠያቂነት የማያድናቸው መሆኑን በፍርዱ ሐተታ ላይ በገለፀው ምክንያት መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ይህ የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቷል፡ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ ከተቀመጡባቸው ድርጊቶች ሁለተኛው ክስ በልጃቸው ስም በመያዣነት በተሠጠው ቼክ እና የልጁ ተወካይ በመሆን የተበዳይን ቤት ማሸጡ ሆኖ ባለበት የስር ፍርድ ቤቶች በአራጣ ማበደር ወንጀል ጥፋተኛ ማለታቸው ተገቢ መሆን ያመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለጸው የቼኩ መነሻው የአመልካች ብድር መሆኑና ወለዱም ሕጋዊ ያልነበረ መሆኑ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ስለመረጋገጡ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ አመልካችን ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፡፡ይልቁንም አመልካች በድርጊቱ በነባራቸው ተሳትፎ መጠን በወንጀል የሚጠየቁ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡በመሆኑም አመልካች ድርጊቶችን ስለመፈፀማቸው አቃቤ ሕግ በማሰረጃቹ አላስረዳም፣በመከላከያ ማስረጃዎችም ተደግፈአለሁ በማለት አመልካች የሚያቀርቡት የሰበር ቅሬታ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ሁኖ ስለአገኘነው ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕግ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ስልጣን አንጻር የምንመለከታቸው ሁኖ ስላለአገኘን አልፈናል፡፡

በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡትን ነጥቦች ይዘን ወደ ሕጉ ጥያቄ ስንመጣ አመልካች ከሕግ ከተደነገገው ውጪ በወር 10% በማስከፈል ለግል ተበዳዮች ገንዘብ ማበደራቸው የተረጋገጠ በመሆኑ ከአበደሩት ገንዘብ እጥፍ የሆነ ገንዘብም ከግል ተበዳዮቹ የሰበሰቡና ንብረታቸውም እንዲሸጥ ያደረጉ በመሆኑ አድራጎታቸው የአራጣ ወንጀል የሚያቋቁም ሁኖ አግኝተናል፡፡ቅጣትን በተመለከተ የቀረበ ቅሬታ ባለመኖሩ የምንመረምረው ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 45515 መጋቢት 03 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02-04311 ሚያዚያ 02 ቀን 2004 ዓ/ም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 23702 ሚያዚያ 24 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ሐ) መሰረት ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በሁለት የአራጣ የወንጀል ድርጊቶች ጥፋተኛ ተብለው በሶስት አመት ፅኑ እስራትና በብር 4000.00(አራት ሺህ)የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ተብሎ በተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠ የቅጣት ውሳኔ የፀና መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረሚያ ቤቱ ይጻፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 79389

መጋቢት 12 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ረታ ቶሎሣ
አዳነ ንጉሴ
መስጠፉ አህመድ

አመልካቾች፡- 1. ዶ/ር ታጀዲን ያህያ
2. አቶ መሐመድ ጀማል } ቀርቧል

ተጠሪ፡- የአማራ ክልል ዐ/ሕግ አቶ አዱኛ ማራዊ - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሌላ ሰው ጥቅም የስራ አመራር ላይ የተፈፀመ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በአ/ብ/ክ/መንግስት ደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካቾች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ 702/3/ በመተላለፍ በደሴ ከተማ ቀበሌ 09 ማዕከል መርከዘል ብርሃን የሚባል ለሙስሊሙ ማህበረሰብ በበጐ አድራጐትነት ወይም በወቅፋ የተሰጠ ለትርፍ ያልተቋቋመ ህጋዊ ሰውነት ያለውን ድርጅት 1ኛ አመልካች ከሚኙ ወላጅ አባቱ በተሰጠው የኑዛዜ ውክልና መሰረት የድርጅቱን ስራ ሊመራ ሲገባ ድርጅቱ ከተቋቋመ ዓላማ ውጪ በስሙ የንግድ ፈቃድ በማውጣት ወደ አትራፊ ንግድ ድርጅት ቀይሯል፣2ኛ አመልካችም ድርጅቱን ወደ ግል ድርጅት እንዲዞር በማሰብ አዲስ የሚቋቋም ተቋም በማስመሰል በሚያዝያ ወር 1992ዓ.ም ንግድ ፈቃድ በማውጣት የድርጅቱን ገቢና ሃብት ለግል ጥቅማቸው በማዋል በሌላ ሰው የንብረት ጥቅም ስራ አመራር ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ክስ የቀረበባቸው ሲሆን አመልካቾችም እንዲቀርቡ ከተደረገ በኋላ ወንጀሉን አለመፈፀማቸው ክደው የእምነት ክህደት ቃላቸውን በመስጠታቸው ዐ/ህግ እንደ ክሱ የሚያስረዱለትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ ከተሰሙና ከተመረመሩ በኋላ አመልካቾች ወንጀሉን መፈፀማቸው ተረጋግጦባቸዋል በማለት እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ አመልካቾችም በትዕዛዙ መሰረት ወንጀሉን ለመከላከል የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረቡ ቢሆንም በዐ/ህግ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ማስተባበል አልቻሉም በሚል የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሰጠባቸው በኋላ 1ኛ አመልካች በ6 ወር እና 2ኛ አመልካች ደግሞ በ1 ወር እስራት እንዲቀጡ ከተወሰነ በኋላ በወ/ህጉ አንቀጽ 192 መሰረት ቅጣቱ በ2 ዓመት የፈተና ጊዜ በመስጠት እንዲገደብላቸው ተደርጓል፡፡ በ1ኛ አመልካች የተሰጠው የድርጅቱ ንገድ ፈቃድም ከንግድ መዝገብ ተሰርዞ ድርጅቱ በቀድሞ ሁኔታ እንዲተዳደር በማለት ተጨማሪ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

አመልካቾችም በተሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለዞኑ ከፍ/ፍ/ቤትና ክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ሁለቱም ፍ/ቤቶች ተመሣሣይነት ባለው መልኩ የስር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚያዝያ 30 ቀን 2004ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህንኑን ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ የቀረበብን ክስ በወ/ህጉ ቁ. 217/1/ሠ/ መሰረት በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ ጥፋተኛ ተብለን መቀጣታችን መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑን ጉዳዩ ቀደም ሲል በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ቀርቦ ውሣኔ ያገኘ መሆኑ እየታወቀ እንደገና በወንጀል ቀርቦና ታይቶ ጥፋተኛ መባላችን ስህተት መሆኑን ድርጅቱም በጉ አድራጉት ድርጅት ነው መባሉ ስህተት መሆኑን የድርጅቱ ንግድ ፈቃድ በእኔ 1ኛ አመልካች ቢወጣም የድርጅቱ ካርታና ኘላን በድርጅቱ ስም ያለ መሆኑንና የድርጅቱ ንግድ ፈቃድም በ1ኛ አመልካች እንዲወጣ የተደረገው አቅም ካላቸው ተማሪዎች መጠነኛ ክፍያዎችን በመቀበል ለተለያዩ ወጪዎችና ለአስተማሪዎች ደመወዝ እንዲውል መደረጉ ድርጅቱን ከተረጅነትና በዘላቂነት ከችግሩ ለማውጣት በማሰብ እንጂ የግል ጥቅምን ለማሟላት አይደለም፡፡ ይልቁንም 1ኛ አመልካች ከግል ወደ 500,000 ብር በላይ ለድርጅቱ እርዳታ ማድረጌ ጥፋተኛ የተባልኩበትን ወንጀል ለመፈፀም ሀሳብ የሌለኝ መሆኑ እየታወቀ ጥፋተኛ ሆነን መቀጣታችንና የድርጅቱ ንግድ ፈቃድም ተሰርዞ በቀድሞ ሁኔታ እንዲተዳደር በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተሽሮ እንዲወሰንላቸው በመከራከር ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርብ ተደርጎ የበኩሉን መልስ ሰጥቶበታል፡፡ አመልካቾችም የመ/መልሳቸውን ሰጥተውበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበባቸው ውሣኔዎችና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በውሣኔዎቹ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው መሆን አለመሆኑን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውና በደሴ ከተማ ቀበሌ 09 መርከዘል ብርሃን ተብሎ የሚጠራው ት/ቤት በመጀመሪያ በበጎ አድራጊዎች ሲቋቋም ለትርፍና የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት የተቋቋመ ሣይሆን በበጎ አድራጎት ማህበር ዓይነት ወላጅ አልባ የሆኑ ህጻናትን በነጻ ማስተማር አረብኛ ቋንቋንና ቅዱስ ቁራንን ማስተማርና እንዲሁም መስጊዶችን ለመስራት የተቋቋመ ስለመሆኑ በእነዚህ በጎ አድራጉ በሆኑ ሰዎች በተሰበሰበ ንብረት አማካኝነት ት/ቤቱ የመምስረቻ ጽሑፍ ተቀረፆለት በ1984ዓ.ም የተቋቋመ መሆኑና ከተቋቋመም በኋላ ለተወሰኑት ዓመታት ስራውን ያለምንም ክፍያ በነጻ ሲያከናውን የቆየ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ነገር ነው፡፡ ይሁን እንጂ በኋላ ላይ 1ኛ አመልካች ድርጅቱን እንዲመራ ከሚች አባቱ በኑዛዜ በተሰጠው ኃላፊነትና 2ኛ አመልካችም ከ1ኛ አመልካች ባገኘው ውክልና መነሻነት የት/ቤቱን ስራ በመምራት ላይ እያሉ በ1992ዓ.ም የድርጅቱን ንግድ ፈቃድ በ1ኛ አመልካች እንዲወጣ በማድረግ በፊት ከተቋቋመለት ዓላማ ወጪ ወደ ንግድ ድርጅትነት ቀይረው እስከ አሁን በዚሁ አኳኋን እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ት/ቤቱ በፊት ያለ ክፍያ በነጻ ሲያከናውን የነበረው ስራ ቀርቶ አሁን ከሚያስተምራቸው ተማሪዎች ገንዘብ እየሰበሰቡ መሆናቸውን አመልካቾችም አይክዱም፡፡ የተከሰሱበት ድርጊትም ይሄው ነው፡፡ ይህ ድርጊት ደግሞ እስከ አሁንም ሣይቋረጥ የቀጠለ በመሆኑ በወ/ህጉ አንቀጽ 219/2/ ስር እንደተመለከተው በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የይርጋ ክርክርን በሚመለከት የቀረበው የሰበር አቤቱታ በዚህ ምክንያት ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ጉዳዩ ከዚህ ቀደም በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ታይቶ የመጨረሻ ውሣኔ አግኝቶ እያለ በድጋሜ በወንጀል ተከሰን ጥፋተኛ መባላችን አግባብ አይደለም በሚል የቀረበው ክርክርም ቢሆን በፍታብሔር ኃላፊነት ተከሰው በጉዳዩ ላይ ስልጣን ባለው አካል ውሣኔ መስጠቱ በወንጀል ህጉ በኩል ያለውን ኃላፊነት ሊያስቀር የሚችል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበው አቤቱታ ከወ/ህጉ አንቀጽ 2/5/ እና እንዲሁም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 130/2/ለ/ አኳያ ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡ የተከሰሱበት ድርጊትም በህግ ወይም በውል አማካኝነት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ያለአግባብ በመገልገል በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ጉዳት በሚያደርስ አኳኋን በጎ አድራጎት የነበረን ድርጅት ወደ ንግድ ድርጅትነት ቀይሯል በሚል ሲሆን ይህ ድርጊትም ስለመፈፀሙ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ስልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች መፈፀሙ የተረጋገጠው ድርጊትም አመልካቾች የተከሰሱበትን የወንጀል ህጉን ድንጋጌ አንቀጽ 702/3/ ስር የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁም ነው፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበባቸው ውሣኔዎች ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው ሆኖ ስላላገኘን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በዚህ ጉዳይ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍ/ፍ/ቤትና እንዳሁም በክልሉ ሰበር ችሎት የተሰጡት ውሣኔዎች በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ.195/2/ለ/2/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 86845

መስከረም 22 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አመልካች፡- የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ ዋልታንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሰለሞን ዩሐንስ ከጠበቃ ተስፋዬ አባተ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የወንጀል ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውም የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ሕግ ተጠሪን ጨምሮ በአምስት ሰዎች ላይ በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1(ሀ) እና 407(1)(ሀ)(ለ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በስልጣን ያላግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል በማለት በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ተጠሪው ጥፋተኛ ተብለው በሶስት አመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እና በብር 2000.00 (ሁለት ሺህ) እንዲቀጡ በተሰጠው ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ተጠሪን በወንጀል ተጠያቂ መደረጉን ተቀብሎ አድራጎታቸው የሚወድቀው ግን የስራ ግዴታን መጣስ በሚያስጠይቀው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420(1) ድንጋጌ ነው በማለት ቅጣቱን በተመለከተ ደግሞ ከቅጣት አወሰሳን መመሪያው በመውጣት በአራት ወር ቀላል እስራት እና በብር 600.00 እንዲቀጡ አሻሽሎ በመወሰኑ ነው፡፡

አመልካች በተጠሪው ላይ ያቀረበው ክስ ዝርዝር ይዘት ተጠሪው የወ/ህ/ቁ 32(1(ሀ) እና 407(1(ሀ)(ለ)) በመተላለፍ በትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዩን ማህበር ምህንድስና መምሪያ ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ የተሰጣቸውን የስልጣን ችሎታ ከመጠን በላይ አሳልፈው በመገልገል ሕገ ወጥ ጥቅምን ለሳባ ኢንጂነሪንግ ለማስገኘትና በመንግስትና ሕዝብ ጥቅም ላይም ጉዳት ለማድረስ በማሰብ የትራንስፖርት እና ኮንስትራስክሽን ዲዛይን አክሲዩን ማህበር ለጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 002/97 በ29/10/2004 እ.ኤ.አ በአወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት አዲስ ሪግ ግዥ ተፈጽሞ እቃው በውለታውና በ"እስፔስፊኬሽኑ" መሰረት በትክክል ሳይቀርብ በኢንስፔክሽን ኮሚቴው በቀረበው ሪፖርት ላይ የሪጉ አካል ስለሆነው የውሃ ፓምፕ የተገለጸው በ"ስፔሲፊኬሽን"ና "ሰርቴፊኬት ኦፍ ኦርጂን" መሰረት እንዳልሆነ እና አሮጌ መሆኑ ተገልጾላቸው እያለ አዲስ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ርክክቡ እንዲፈፀም ሰኔ 02 ቀን 1998 ዓ/ም ለጂ.ኦ ቴክኒካል ምህንድስና ዋና ክፍል በጽሑፍ ትዕዛዝ በመስጠት እንዲሁም ከሳባ ኢንጂነሪግ ጋር ሚያዚያ 06 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1998 ዓ/ም በተደረገው ውይይት ተገዛ የተባለው ሪግ የውሃ ፓምፕ አሮጌ እና የማያገለግል መሆኑን በውይይት ጊዜ ተገልጾ እያለ የመስሪያ ቤቱን ጥቅም በሚጎዳ አኳኋን ስለውሃው ፓምፕ የተገለፀውን ጉዳይ ወደ ጎን በመተው በሌሎች አነስተኛ ጉዳዮች ላይ ብቻ ስምምነት በመፈሙና "አክሴፕታንስ ሰርተፊኬት" እንዲፃፍ በማድረጋቸውና ከሌሎች ተከሳሾች ጋር ሁነው በሙሉ ፍላጎታቸውና እውቃታቸው በብር ከፍተኛ ወጪ የተገዛው ንብረት ለመንግስት ያላግባብ ገቢ እንዲሆን በማድረግ ጉዳት አድርሰዋል የሚል ነው፡፡

ተጠሪ የቀረበባቸውን የወንጀል ክስ ክደው ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ዓቃቤ ሕግ ክሱን ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰውና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ዓቃቤ ሕግ እንደክስ አቀራረቡ አስረድቷል በማለት ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን በመሰጠቱ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃቸውን አቅርበዋል፡፡ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪን መከላከያ ማስረጃዎችን የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን የሚያስተባብሉ አይደሉም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎ ተጠሪን በቀረበባቸው የወንጀል ክስ ጥፋተኛ ናቸው በማለት በሶስት አመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እና በብር 2000.00 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ በተጠሪ ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ድንጋጌውን በመቀየር ያፀናው ሲሆን ቅጣትን በተመለከተ ግን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ መውጣት ተገቢ መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን ጠቅሶ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ በመውጣት በአራት ወር ቀላል እስራትና በብር 600.00 ተጠሪው እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎት በአመልካች የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መነሻ በማድረግ ግራ ቀኙን በጽሑፍ እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት ክሱን መጀመሪያ በቀረበበት ፍ/ቤትና ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው ፍ/ቤት የተሰጡ ውሣኔዎች አግባብነት ካላቸው ሕጐች ጋር በማገናዘብ በሚከለተው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዋና ቅሬታ የተጠሪ አድራጎት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ))እና በአንቀጽ 4107(1(ሀ)(ለ) ስር የሚሸፈን ነው፣ይህ ቢታለፍ እንኳን አድራጎቱ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 411 ስር የሚወድቅ እንጂ እንደይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ድምዳሜ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420 ስር የሚሸፈን አይደለም፣ከተጠሪ ጋር የተከሰሱት ግለሰቦችም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባሉትና የተቀጡት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 411 ስር ነው፣ተጠሪ በውሉ አግባብ ያልቀረበ መሆኑን በኢንሲፔክሽን ኮሚቴ ተረጋግጦና ይህንኑ እያወቁ በጻፉት የአክሴፕታንስ ሰርቲፊኬት በመንስግስት ላይ ጉዳት መደረሱ ተረጋግጦ እያለ አድራጎታቸው የሙያ ግዴታ በመጣስ የሚሸፈን ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው፣እንዲሁም ተጠሪው ለግዥው ስፔሲፊኬሽን ሲሰራ ያልነበሩ መሆኑ ተጠያቂ የሆኑት ከግዥው በኋላ ለነበረው ሂደት በመሆኑና ከሌሎች የማኔጅመንት አባለት ጋር ሁነው የግዥ ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ማድረጋቸውም የተጠሪ ጥረት ምን እንደሆነ በማስረጃ ባልተረጋገጠበት እና ወንጀሉ ውጤቱን ከአገኘ በኋላ በሌላ ሰው በተፈፀመ የፍትሃ ብሄር ክስና ክርክር መነሻ ሁኖ በመሆኑ አንቀፁን ለመለወጥ የማያስችሉ ምክንያቶች ናቸው፣ተጠሪው የአደገኛነት ባህርይ ያላቸው ናቸው የሚል ነው፡፡ተጠሪ በበኩላቸው የአመልካች የሰበር ቅሬታ ነጥቦች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑንና ጥፋተኛ የተባሉትም የወንጀል መስራት ሀሳብ ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ መሆኑን ዘርዝረው መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን የተመለከትነውም ከዚሁ ከቀረበው አቤቱታ አንፃር ነው፡፡ ይህ ችሎት በዋናነት መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ተፈፅሟል ሲባል ብቻ ውሣኔዎችን የሚመለከት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ለውሣኔዎቻቸው መሠረት ያደረጉዋቸውን ፍሬ ነገሮች ትክክለኛነት ወደማጣራት ወይም ግራ ቀኙ ያቀረቡዋቸውን ማስረጃዎች ወደ መመዘን አልሄደም፣ይልቁንም እነዚህን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዳሉ በመውሰድ የተረጋገጠው ፍሬነገር በተጠሪ የቀረበውን ክሱ የሚያቋቁም መሆን አለመሆን የሚመለከተውን የሕግ ነጥብ ተመልክቷል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት እንደቻልነው ተጠሪ የትራንስፖርትና የኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዩን ማህበር የምህንድስና ኃላፊ ሁነው ሲሰሩ አከራካሪውን ሪግ ከውሉ ውጪ የቀረበ ስለመሆኑ በሚመለከተው ኮሚቴ ተረጋግጦ እያለና ተገቢ ያልሆነ ቃል ጉባኤ ከሌሎች የማኔጅመንት ኮሚቴ አባለት ጋር ሁነው ይዘው የርክክብ ደብዳቤ በመጻፍ ለአቅራቢው ክፍያው እንዲፈፀም አድርገው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 407(1(ሀ)(ለ) በሚዛረር ሁኔታ በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰዋል የሚል ነው፡፡

በፍርዱ ሂደት ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ሪጉ በውሉ በተመለከተው ስፔሲፊኬሽን መሰረት ያልመቅረቡንና ተጠሪም ሆነ ሌሎች አብሯቸው የተከሰሱት የድርጅቱ ኃላፊዎች እውቀት የነበራቸው መሆኑ በማስረጃ ማረጋገጡን የገለፀ ሲሆን በዚህ ረገድ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የተለየ ድምዳሜ የሌለው መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡የርክክብ ደብዳቤ ሊፃፍ የቻለው መሰረታዊ ምክንያትም ይሄው በማሽኑ ላይ ያለው ችግር ታውቆ አቅራቢው ድርጅት ችግሩን እንዲያስተካክል የድርጅቱ ተወካይ ባለበት ውይይት ተደርጎ በአስራ አምስት ወራት ውስጥ ችግሩን እንደሚያስተካክል ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ ስለመሆኑም በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ይህ ችሎትም ይህ የተጠሪ አድራጎት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተጠቀሰው ድንጋጌ መስፈርት ጋር በማያያዝ ትክክል መሆን አለመሆኑን ተመልክቷል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ እቃው እንደውሉ የሚቆፍር መሆኑ ተፈትሾ እና ተረጋግጦ ርክክብ ይፈፀም የሚል ሀሳብ በማኔጅመንቱ ስብሰባ ሲያቀርቡ የሳባ ኢንጂነሪግ ተወካይ አቅራቢው ድርጅት የማስሞከር ግዴታ እንዴለለበት በመግለፃቸው በዋስትናው ጊዜ አስራ አምስት ወራት ውስጥ ጉድለት ካለ አስተካክላለሁ በማለታቸው የእቃው ርክክብ እንዲፈፀምና የአክሴፕታንስ ሰርቲፊኬት ለመስጠት ስምምነት ተደርሶ ተጠሪውም ስምምነቱ ላይ መድረሳቸው፣ተጠሪ ከሚመሩት የዲዛይን መመሪያ በ14/11/1998 ዓ/ም በተፃፈ የውስጥ ማስታወሻ ማሽኑ አዲስነቱ ተረጋግጧል፣ገቢ ይሁን ተብሎ በመፃፉ የመልካም አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ (Perfomance bond) ለአቅራቢው ድርጅት ከተለቀቀለት በኋላ ሪጉ ሲፈተሽ በውሉ የተገለጸውን የ158 ሜትር ጥልቀት እንደማይቆፍር በፍሬ ነገረ ደረጃ መረጋገጡን ነው፡፡

እነዚህ ፍሬ ነገሮች በግልጽ የሚያሳዩት ተጠሪ የሪጉን አዲስነት ከማረጋገጥ ጀምሮ የአስራ አምስት ወራት የዋስትና ጊዜ ውስጥ ጉድለቱ እንዲስተካከል የአቅራቢው ድርጅት ተወካይ ያቀረበው ሃሳብ ተጠሪው ጭምር ተሳታፊ በሆኑበት ኮሚቴ ተቀባይነት አግኝቶ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ ለአቅራቢው እንዲለቀቅ የሚያደርግ ተግባር እስከተፈፀመባቸው ሂደቶች ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡እነዚህ ፍሬ ነገሮች ተጠሪው የመወሰን ስልጠን የነበራቸው መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 420 ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው የመወሰን ሥልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ባለቸው ሰዎች ነው፡፡እነዚህ ሰዎች በአንቀጽ 407 አግባብ የሚጠየቁት ግልፅ በሆነ ሁኔታ አንድን ሰው ለመጥቀም ወይም ራሳቸውን ለመጥቀም በማሰብና ኃላፊዎቻቸውን ለማሣሣት የፈፀሙት ጉልህ ተግባር መኖሩ ሲረጋግጥ ነው፡፡ይህ እስካልተረጋገጠ ድረስ በሥልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አላግባብ የመገልገል ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው ሊጠየቁ አይገባም፡፡ ስለሆነም በአንቀጽ 420 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት ተጠሪው የሙያ ተግባሩንና ሥራው በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመፈፀሙ ምክንያት በመንግስት ላይ ጉዳት አድርሰዋል ሊባሉ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤተ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈንበት ድንጋጌ ስንመለከትም አመልካች በአንቀጽ 407 ስር ሊሆን በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኘው ሁኖ አልተገኘም፡፡ምክንያቱም ከተጠሪ ጋር የተከሰሱት ግለሰቦች በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 76525 እና 76941 በሆኑት ታይቶ አድራጎታቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ) እና 411(1(ሀ)(ለ) ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ የተባሉ በመሆኑና ውሳኔዎቹ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ለሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርብም መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በመ/ቁጥር 86844 እና 86846 በሆኑ መዛግብት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ በመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 4፣41 እንዲሁም ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25 ድንጋጌዎች አኳያ በሕግ ፊት እኩል ሁኖ የመታየት መብት አንፃርም ሆነ የወንጀል አድራጎቱን የበለጠ የሚሸፈነው ድንጋጌ አንቀጽ 407 ሳይሆን 411(1(ሀ)(ለ) ሁኖ ተገኝቷልና፡፡

በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 411 ሥር ወንጀል የሚያቋቁሙት ድንጋጌዎች የሚገኙት በንኡስ አንቀፅ (1) (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ነው፡፡ ማንኛውም በዚህ አንቀፅ ሥር የተከሰሰ ሰው በዚህ አንቀፅ ሥር ከተመለከቱት ውስጥ የትኛውን ወንጀል እንደፈፀመ በግልፅ በሚያመለክት ሁኔታ ክስ ሊቀርብበትና ሊከላከል ይገባል፡፡ተጠሪ የዲዛይን መምሪያ ኃላፊ ሁነው የሪጉን አዲስነት ተረጋግጧል በማለት ማስረጃ እንዲቀርብ ማድረጋቸውም ሆነ የዋስትናውን ጊዜ በተመለከተ በአቅራቢው ድርጅት ግዴታ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ተሳትፈው ከውሉ ውጪ በሆነ ሁኔታ ስምምነት ላይ መደረሳቸው ሲታይ የመንግስት ሥራን በማይመች አኳኋን መምራታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ከላይ ከተገለጹትና በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች አንፃር ለጉዳዩ አግባብነት ያለውና ሊጠቀስ ይገባ የነበረው አንቀፅ 411(ሐ) መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ አንቀፅ መሠረት የወንጀል ተጠያቂነት የሚከተለው ደግሞ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፣ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ተጠቅሞ በጠቅላላው በሥራው ሥልጣን መሠረት በአደራ የተሰጠውን ወይም ሊጠብቀውና ሊከላከለው የሚገባውን የሕዝብ ወይም የመንግስት ጥቅም የሚጉዳ ተግባር በማናቸው ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ" ነው፡፡

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 411 አንድን ሰው ጥፋተኛ የሚያደርገው በሕጉ የተቀመጡት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ክሱ ላይ እንደተገለፀው አንዱ መሟላት ያለበት መስፈርት በዚሁ አንቀፅ የተከሰሰው ሰው የማይገባ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ለሦስተኛ ወገን ለማስገኘት መንቀሳቀሱ ነው፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ሪጉ አዲስ ነው በማለት ርክክቡ እንዲፈፀም የአክሴፕታንስ ሰርቲፊኬት መፃፋቸው ጥፋት ነው የተባለ ሲሆን የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብም በዚህ ደብዳቤ መነሻ ለአቅራቢው ድርጅት መከፈሉ ተረጋግጧል፡፡ይህ ደግሞ በስራቸው ሥልጣን መሠረት በአደራ የተሰጣቸውን ወይም ሊጠብቁትና ሊከላከሉት የሚገባውን የሕዝብ ወይም የመንግስት ጥቅም የሚጉዳ ተግባር መፈፀማቸውን የሚያሳይ ነው፡፡በመሆኑም ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በአንቀጽ 411(1(ሐ)) ስር ሆኖ ስለአገኘነው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2)) እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2/ መሠረት በመለወጥ ተጠሪ በወንጀል ህግ አንቀፅ 411(1(ሐ)) ስር የተመከተውን ድንጋጌ የተላለፈ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

የቅጣቱን መጠን በተመለከተ በሌሎች የተጠሪ ግብረአበሮች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅጣት ሲወስን ወንጀሉ ከውል አፈፃጸም ጋር ተያይዞ የተፈጸመ መሆኑንና ውሉም እንዲፈርስ የተደረገ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በቅጣት አወሰሳን መመሪያው አንቀፅ 13(2) መሰረት ሊጣል የሚገባው ዝቅተኛ የወንጀል ደረጃውን ያገናዘበ ቀላል እስራት ቅጣት ሊሆን እንደሚገባ፣በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 13(3) መሰረት የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ያለውን ቅጣት ርዝመት ለአራት እኩል ተካፍሎ የሚመጣው ዝቅተኛ ወንጀል ደረጃ የቅጣት ፈቅድ ስልጣን ከአንድ አመት እስከ አንድ አመት ስድስት ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን፣ይህም ፍቅድ ስልጣን በቅጣት አወሰሳን መመሪያ አባሪ አንድ ከእርከን 7 ስር የሚሸፈን መሆኑን ግንዘቤ ውስጥ አስገብቶ እያንዳንዱ አጥፊ በግል ያቀረበውንና ሕጋዊ የቅጣት ማቅላያ ምክንያት በመቀበል ተገቢ ነው ያለውን እስከ ስድስት ወር ቀላል እስራት እና ብር 1000.00 የገንዘብ መቀጮ ቅጣት ያስተላለፈ በመሆኑ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረታዊ አላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በተጠሪ ላይ የሚጣለው የቅጣት መጠንም ከላይ በግብረ አበሮቹ ላይ ቅጣት ሲወሰን ተፈፃሚ የሆነውን አካሄድ ሊከ,ተል የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው በቀላል እስራት በመሆኑና ቀላል እስራት ደግሞ ከአስር ቀን እስከ ሶስት አመት ሚደርስ ስለሆነ በመመሪያው አንቀጽ 13(3) መሰረት መነሻና መድረሻው መካከል ያለውን ቅጣት ርዝመት ለአራት እኩል ተካፍሎ የሚመጣው ዝቅተኛ ወንጀል ደረጃ ቅጣት ፍቅድ ስልጣን ከአንድ አመት እስከ አንድ አመት ከስድስት ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ነው፡፡በዚህ ፍቅድ ስልጣን ያለው ቅጣት በመመሪያው አባሪ አንድ እርከን ሰባት ስር የሚሸፈን ነው፡፡በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን ተጠሪ ሪኮርድ የሌለባቸው፣የቤተሰብ አስተዳደሪ እና የዲስክ መንሸራተት በሽታ ያለባቸው መሆኑ በፌዴራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በቅጣት ማቅላያነት የተያዙ ምክንያቶች ስለሆኑ ይህ ችሎትም የሚቀበላቸው በመሆኑ ሶስቱ የቅጣት ማቅላያ ምክንያቶች ሲያዙ እርከኑ ወደ እርከን አራት ይወረዳል፡፡በዚህ እርከን የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ ከአራት ወር እስከ ሰባት ወር እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው በስድስት ወር ቀላል እስራት ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሠረት የበታች ፍርድ ቤቶችን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በማሻሻል ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ሲጠቃለልም የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈነው በአቃቤ የሕግ ማመልከቻ በተጠቀሰው ድንጋጌ ወይም በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርደ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተጠቀሰው ድንጋጌ ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 411(1(ሐ)) ድንጋጌ በመሆኑና ቅጣቱም ከዚህ ድንጋጌ አንጻር የሚጣል በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አሻሽለናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 57547 ታህሳስ 11 እና 26 ቀን 2004 ዓ/ም፣በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 77102 ህዳር 06 ቀን 2005 ዓ/ም የተሻሻለው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ)) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ)(ለ) እና 411(1(ሐ)) ድንጋጌ ስር ነው ብለናል፡፡ቅጣቱን በተመለተከተም ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ማናቸውም ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ በስድስት ወር ቀላል እስራትና በብር 1000.00 ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በዚህ ችሎት እንዲቀጡ ከተወሰነባቸው የእስራት ጊዜ በላይ በጉዳዩ ላይ የታሰሩ መሆኑ ስለተረጋገጠ የእስራት ዋራንት እንዲጻፍ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፣የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ ግን ተጠሪ ያልከፈሉትን ቀሪ ገንዘብ ካለ አመልካች ተከታተትሎ ገቢ እንዲያስደርግ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 81178

መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ - ዐ/ሕግ ሜቴ አቶምሳ እና አሰፋ ሐፎስ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ክበደ ተሰራ - ጠበቃ ተስፋዬ ኃ/ማርያም እና ወ/ሮ መሰረት ስዩም ቀረቡ

2. አቶ ሌንጫ ዘገየ - ሌንጫ ዘገየ

አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ቁጥሩ 81178 በሆነው በዚህ መዝገብ፣በ2ኛተጠሪ ላይ ደግሞ ቁጥሩ 81179 በሆነው መዝገብ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በዚህ መዝገብ ተጣምሮና ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ተጠሪዎቹ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በተናጠል በተለያየ መዝገብ ተከሰው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠባቸው የወንጀል ክሶች መካከል ሁለቱንም ተጠሪዎች በ1ኛ ክስ ከተመለከተው ወንጀል በነፃ በማሰናበት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አመልካች በተጠሪዎቹ ላይ በተለያዩ መዝገቦች ያቀረባቸውን የተለያዩ የወንጀል ክሶች የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኃላ፤

በ1ኛ ተጠሪ ላይ በአምስት ክሶች የጥፋተኝነት እና በድምሩ የሃያ ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ከብር 165,000 መቀጮ ጋር፤ በ2ኛ ተጠሪ ላይ በአምስት ክሶች የጥፋተኝነት እና በድምሩ የአስራ ሶስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ከብር 100,000 መቀጮ ጋር፤ ውሳኔ መስጠቱን፣በውሳኔው ቅር በመሰኘት ሁለቱ ወገኖች ያቀረቡለትን ይግባኝ የመረመረው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ተጠሪዎቹ ያቀረቡትን ይግባኝ በተመለከተ ከላይ እንደተጠቀሰው ሁለቱንም ተጠሪዎች ከ1ኛ የወንጀል ክስ በአብላጫ በነጻ በማሰናበት እና በሌሎች የወንጀል ክሶች ተጠሪዎቹ ያቀረቡትን ቅሬታ በሙሉ ድምጽ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ መስጠቱን፤አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ በተመለከተም የተጠሪዎቹ የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ በተደረገባቸው የወንጀል ክሶች በተጠሪዎቹ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት ተጥሎ የነበረውን የቅጣት መጠን ከፍ በማድረግ በ1ኛ ተጠሪ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት በአምስት የወንጀል ክሶች ተጥሎ በነበረው የሃያ አመት ጽኑ እስራት ምትክ በይግባኝ ደረጃ የጥፋተኝነት ውሳኔው በጸናባቸው አራት የወንጀል ክሶች የ25 ዓመት ጽኑ እስራት፤በ2ኛው ተጠሪ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት በአምስት የወንጀል ክሶች ተጥሎ በነበረው የ13 ዓመት ጽኑ እስራት ምትክ በይግባኝ ደረጃ የጥፋተኝነት ውሳኔው በጸናባቸው አራት የወንጀል ክሶች የ20 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት በመጣል ውሳኔ መስጠቱን፤በ2ኛ ተጠሪ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት የተጣለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመቀጮ መጠን በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያልተለወጠ ሲሆን በ1ኛ ተጠሪ ላይ ተጥሎ የነበረው የብር 165,000 መቀጮ ወደ ብር 300,000 ከፍ መደረጉንና እና በንብረት ውርስ ረገድም አንዳንድ ማሻሻያዎች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መካተታቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት ከላይ እንደተገለጸው በተጠሪዎቹ ላይ በ1ኛ ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመሰረዝ ተጠሪዎቹ በእነዚህ የወንጀል ክሶች ረገድ በነጻ እንዲሰናበቱ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አመልካች በሶስት መዝገቦች ያቀረበው አቤቱታ ቁጥሩ 81117 በሆነው መዝገብ ተጣምሮ ከታየ በኃላ ተጠሪዎቹ ብድርን እንደመደበኛ ስራቸው በማድረግ በተደጋጋሚ ጊዜ ቼኮችን፣የቦታ ካርታን፣የንግድ ፍቃድን እና የመኪና ሊብሬን መያዣ በማድረግ ለተለያዩ ሰዎች በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ በብድር ይሰጡ እንደነበር ከፍተኛ ፍ/ቤት በማስረጃ አረጋግጦ የጥፋተኝነት ውሳኔ በሰጠበት ሁኔታ ተጠሪዎቹ ብድር መስጠትን እንደመደበኛ ስራ በማድረግ ተደጋጋሚ ብድር መስጠታቸውም ሆነ ብድሩን የሰጡት በተደጋጋሚና በከፍተኛ መጠን መሆኑ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አነጋገር አንፃር የባንኮችንና የሌሎች የገንዘብ ተቋማትን ስራ ያለ ፍቃድ ሰርተዋል ለማለት የማይቻል በመሆኑ ድርጊቱ በወንጀል ህግ አንቀጽ 61 መሰረት በአራጣ ወንጀል ክስ ስር ተጠቃሎ የሚታይ ነው በማለት በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በ1ኛ ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የመሰረዙን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለመመርመር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪዎቹ በተያዘላቸው ቀጠሮ መልስ ባለማቅረባቸው መብታቸው ከታለፈ በኃላ 1ኛ ተጠሪ በተያዘላቸው ቀጠሮ መልስ ያላቀረቡበትን ምክንያት ገልጸው በተፈቀደላቸው መሰረት በጠበቆቻቸው የተዘጋጀና የተፈረመ መልስ በማያያዝ የክርክሩ ተካፋይ ሆነዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የተጠሪዎቹን ይግባኝ በከፊል በመቀበል በፌ/ከ/ፍ/ቤት ከተሰጠው ውሳኔ ውስጥ በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በ1ኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሰርዞ ተጠሪዎቹ ከእነዚህ ክሶች በነጻ እንዲሰናበቱ በድምጽ ብልጫ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በተጠሪዎቹ ላይ ቀርቦ የነበረው 1ኛ ክስ ተመሳሳይ ድንጋጌ የተጠቀሰበት ሆኖ ይዘቱ በጥቅል ሲታይ ተጠሪዎቹ በገንዘብና በባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሸ) እና 2 (ሀ)ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የብድር ስራ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ከብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ፍቃድ ሳይኖራቸው ለተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ በብድር በመስጠትና ለብድሮቹም ቼኮችንና የተለያዩ ሰነዶችን በመያዣነት በመቀበል ለባንኮችና ለመሰል ፋይናንስና አክሲዮን ማህበራት የተፈቀደውን የባንክ ስራ በህገወጥ መንገድ እንደንግድ ስራ በተደጋጋሚ የመስራት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ሲሆን ወንጀሉን ፈጽመዋል የተባሉትም 1ኛ ተጠሪ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ አምስት ጊዜ ለአንድ ድርጅት በድምሩ ብር 12,090,000 ፤2ኛ ተጠሪ በአስር ዓመታት ውስጥ በ25 የውል ሰነዶች ለ11 ተበዳሪዎች በድምሩ ብር 3,711,111 በብድር በመስጠት መሆኑን የክሶቹ ዝርዝር ያመለክታል፡፡ሁለቱ ተጠሪዎች በየቀረበባቸው 1ኛ ክስ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን፣በየክሶቹ በተመለከተው የጊዜ ወሰን፣የድግግሞሽ መጠን እና ሁኔታ በየክሶቹ ለተጠቀሱት ግለሰቦችና ድርጅቶች በብድር መስጠታቸውን ክሱ የቀረበለት ፌ/ከ/ፍ/ቤት በማስረጃ አጣርቶ ያረጋገጠ ሲሆን በክሶቹ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠባቸውም ተጠሪዎቹ ከሳሽ ወገን ያስረዳባቸውን ፍሬ ነገሮች በመከላከያቸው አላስተባበሉም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ነው፡፡በክሶቹ የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬ ነገር በተጠሪዎቹ መፈጸሙ በማስረጃ ተጣርቶ ተረጋግጦአል መባሉ በመሰረቱ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔውን በሰጠው አብላጫ ድምጽም ቢሆን አልተነቀፈም፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት ግዙፋዊ ፍሬነገሩ ተረጋግጦአል መባሉን ተቀብሎ ነገር ግን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔውን በአብላጫ ድምጽ ለመሰረዝ የሰጠው ዓይነተኛ ምክንያት በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በቀረበው 1ኛ ክስ ማንኛውም ሰው "...በማናቸውም ሌላ አካኋን የዚህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈጻጸማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ ወንጀል የተሰራበት እንደሆነ ወንጀል የተሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀለኛ ህግ መሰረት ይቀጣል፡፡" የሚል አነጋገር እና "ወንጀሉ የተፈጸመው ሥልጣንን መከታ በማድረግ ወይም በመንግስት ስራ አጋጣሚ ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትን ለማካበት ወይም በተደጋጋሚ ሲሆን ወንጀል የተሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣቱ ከአስራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 20,000 የማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡" የሚል አነጋገር ያዘሉት የአዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሸ) እና (2)(ሀ) ድንጋጌዎች በተደጋጋሚ፣ለንግድ መጠን እና ለበርካታ ተበዳሪዎችም ቢሆን በግለሰብ ደረጃ ብድር የመስጠት ስራ የተከለከለ ወይም የሚያስቀጣ የወንጀል ተግባር መሆኑንና እና ብድር የመስጠት ስራ ሊከናወን የሚችለው በባንክ ብቻ መሆኑን በግልጽ እንደማይደነግጉ፣ፍ/ቤቶች ሕግን ከመተርጎም የማይታገዱ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕገወጥነቱ በሕግ ያልተደነገገ ድርጊት ወይም ግድፈት እንደ ወንጀል ሊቆጥሩትና ቅጣት ሊወስኑበት እንደማይችሉ፣በሕግ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች ጋር ይመሳሳል በማለት ወንጀልነቱ በግልጽ ያልተደነገገ ድርጊት ወይም ግድፈት እንደ ወንጀል ሊቆጥሩት እንደማይችሉ በወንጀል ህግ በአንቀጽ 2 ስር የተደነገገ በመሆኑ ወንጀልነቱ በግልጽ ባልተደነገገ ድርጊት በተጠሪዎቹ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መተላለፉ መሰረታዊ የሆነውን የህጋዊነት መርህ የሚጻረር ነው የሚል መሆኑን የውሳኔው አጠቃላይ ይዘት ያስገነዝባል፡፡

እንደተባለው በከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለቱ ተጠሪዎች በ1ኛ ክስ ጥፋተኛ ተብለውበት የነበረው የገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1)(ሸ) እና (2)(ሀ) ድንጋጌዎች ይዘቱ ቀደም ሲል የተገለጸውንና በተጠሪዎቹ መፈጸሙ የተረጋገጠውን ግዙፋዊ ፍሬነገር በወንጀልነት የሚፈርጁ ወይም የሚደነግጉ አለመሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት አብላጫ ድምጽ የሰጠውን ሰፊ ትችት እና የደረሰበትን ድምዳሜ በበኩላችን ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የወንጀል ሕግ በተወሰኑ ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ ህጉ ደንግጎ ሲገኝ ግምት የሚወስድባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በመሰረታዊነት ግን የአንድ ድርጊት ወይም ግድፈት ወንጀልነት በሕጉ በግልጽ ተደንግጎ መገኘት የሚገባው መሆኑ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2 በተመሳሳይ ሁኔታ ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክስ ስለድርጊቱ እና ስላፈጻጸሙ የሚሰጠው መግለጫ ድርጊቱን ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 112 የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ የድርጊቱ ወይም የግድፈቱ ወንጀልነት በሕጉ በግልጽ ያልተደነገገ በሆነ ጊዜ ወንጀልን ለማቋቋም ከሚያስፈልጉት ፍሬ ነገሮች መካከል አንዱ የሆነው ሕጋዊ ፍሬ ነገር የተጓደለ ስለሚሆን ከወ.ሕ.አ. 23(2) መሰረታዊ ድንጋጌ አንጻር ወንጀል ተፈጽሞአል ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የወንጀል ሕግን መሰረታዊ መርሆዎች መሰረት በማድረግ በተጠሪዎቹ በቀረበለት ይግባኝ መነሻ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በሁለቱ ተጠሪዎች ላይ በ1ኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሰርዞ በዚህ ረገድ ተጠሪዎችን በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪን አስመልክቶ በመ.ቁ. 59831 በ03/08/2004 ዓ.ም.፤2ኛ ተጠሪን አስመልክቶ በመ.ቁ. 55859 በ01/08/2004 ዓ.ም. ከሰጠው ውሳኔ ውስጥ በተጠሪዎቹ ይግባኝ መነሻ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በ1ኛ ተጠሪ ላይ በመ.ቁ. 82321 በ09/09/2002 ዓ.ም.፤በ2ኛ ተጠሪ ላይ ደግሞ በመ.ቁ. 82644 በ16/06/2002 ዓ.ም. በአንደኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሰርዞ በዚህ ረገድ ተጠሪዎቹን በማሰናበት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቶአል፡፡
2. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ክርክሩ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ ከተወሰነው መ.ቁ. 81179 ጋር እንዲያያዝ ይደረግ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90089

ጥቅምት 20ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ዘኪት አባቡ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ዐ/ህግ በሌለበት ታየ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጧል፤

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረውም በቤ/ጉ/ክ/መንግስት አሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ ነበር፡፡ የቀረበው ክስም አመልካቿ የወ/ህ/ቁ27/1/ 540 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በባሞበሲ ወረዳ ባሞበስ ከተማ 02 ቀበሌ ጥቅምት 14 ቀን 2004 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 1፡00 ሰዓት አካባቢ የግል ተበዳይ ጠይባ መሐመድ መኖሪያ ቤት አካባቢ የግል ተበዳይ በሆድዋ ላይ በመምታት ሆድዋ ውስጥ የነበረው ፅንስ ቦታውን እንዲለቅና የመውለጃ ቀን ያልደረሰ ፅንስ በሆድዋ ውስጥ እንዲሞት በማድረግ የምጥ አመጣጥና ከ4 እስከ 5 ከወሊድ በኃላም የደም መርጋትና የደም መፍሰስ እንዲፈጠር በማድረግ በፈፀመችው የመግደል መከራ ወንጀል ተከሳለች የሚል ሲሆን አመልችም ፍርድ ቤት ቀርባ የፅምነት ክደት ቃሏን ስትጠየቅ የወንጀሉን ያልፈፀመች መሆኑን ክዳ ቃልዋን ሰጥታለች ቀጥሎም ፍ/ቤቱ በግራ ቀኙ በኩል የተቆጠሩትን ምስክሮች አስቀርቦ ከሰማ እና ጉዳዩንም ከመረመረ በኃላ ድርጊቱ ተፈፅሟል በተባለበት ጊዜ ማለትም ከጥቅምት 9 አስከ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ አመልካች ፅቃዋን ለመውሰድ ሱዳን ሀገር ልዩ ቦታው ኩርሙክ ተብሎ የሚጠራ ቦታ ሄዳ እዚያ የነበረች እና በቦታው አለመኖሯ በመከላከያ ማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ በሌላ በኩልም አመልካች እንደተባለው በእርግጥም በወቅቱ በቦታው ብትኖርና ጉዳቱን የፈፀመች ቢሆን ኖሮ ጉዳዩ ወዲያውኑ ለፖሊስ ሪፖርት በተደረገ እና አመልካችም ሳትቆይ ወዲያውኑ ቁጥጥር ስር በዋለች ነበር በማለት አመልካቿ ድርጊቱን አለመፈፀሟን በበቂና አሳማኝ ሁኔታ ተከላክላለች በማለት በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 149(2) መሠረት ክሱ በነጻ እንድትሰናት በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ ሰጧል፡፡

የአሁን ተጠሪም (የስር ከሳሽ) በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረቡና ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ በጉዳዩ ላይ እንዲከራከሩ ካደረገ በኃላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች በክሱ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ የ8ወር እርጉዝ የነበሩትን የግል ተበዳይ በክንዷ ሆዷን እንደመታቻት የግል ተበዳይም ወዲያውኑ በዚሁ ምክንያት ህመም እንደተሰማና ፅንሱም መላወሱን እንዳቆመ በኃላም የግል ተበዳይዋ ወደ ሀኪም ቤት ተወስደው ሲታዩ ሽሉ ሞቶ በመገኘቱ በህክምና መሳሪያ እንዲወጣ መደረጉንና ሆኖም

ግን የግል ተበዳይ በዚሁ ጉዳት ምክንያት የታመቀና የረጋ ደም መፍሰስ ያጋጠማት ስለመሆኑ የግል ተበዳይ ጨምሮ በዐ/ህግ በኩል ቀርበው በበታች ፍ/ቤት በተሰሙት ምስክሮች ቃል እና ህክምና ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ገልጾ በአንባር ግን በአመልካች በኩል የተሰሙት መከላከያ ምስክሮች ቃል በተለይም አመልካቿ በተጠቀሰው ጊዜ ኩርሙክ ቦታ ሄዳ እዚያ የነበረች ስለመሆኑ በምን አግባብ ሊያውቁ እንደተቻሉ በሚመለከት የአንዱ ምስክር ቃል ከሌላው የሚጣረስ በመሆኑና በዚህም ምክንያት ክብደት እንደማይሰጠውና ተዓማኒነት የሌለው መሆኑ እየታወቀ የበታች ፍ/ቤት ተከሳሽዋ ወንጀሉን ተከላክላለች በማለት በነፃ እንዲሰናበቱ በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢነት የሌለውና ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከሳሿ ክሱ በቀረበበት የህጉ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ሊባል ይገባል በማለት የጥፋተኝነትም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና ከህጉ ጋርም አገናዝቦ መመልከቱን ከገለፀ በኃላ በ3 ዓመት ከ 7 ወር ፅኑ እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስኗል የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎትም ጉዳዩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለውም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበል አልፏል።

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም በጥቅሉ ጥፋተኛ የተባልኩበትን ድርጊት አለመፈፀሜና በመከላከያ ማስረጃ በሚገባ በማረጋገጥ የተከላከልኩ ስለመሆኔ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመርምሮ የተሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ተሽሮ ጥፋተኛ ተብዬ መቀጣቴና እንዲሁም ይኼውም ክልሉ ሰበር ችሎትም መፅናቱ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳው ሊሻርልኝ ይህ የሚታፍ ከሆነም አባት የሌላቸው ልጆች የማሳድግ መሆኔንና የመሳሰሉት ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ቅጣቱ ሳይፈፀም በገደብ ታግዶ እንዲቆይ አሊያም እንዲቀነስልኝ የሚል ነው አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለሰበር ክርክር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በመባሉ ምክንያት ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ በጽሑፍ እንዲሰጥ መጥሪያ እንዲደርሰው የተደረገ ቢሆንም ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል።

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር አቤቱታ በቀረበት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ላለት ይቻላል ? ወይ ወይስ አይቻለም የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል።

እንደመረመርነውም የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ የግራ ቀኙን ምስክሮች ስምቶና ጉዳዩንም መርምሮ የሥር ተከሳሽ ወንጀሉን ተከላክላለች በሚል ምክንያት በነፃ እንዲሰናበት በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በአሁን ተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ካደረገ በኃላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች በመካከላቸው የነበረውን ጥል መነሻ በማድግ የ8 ወር እርጉዝ የሆነችውን የግል ተበዳይ ጠይባ መሐመድን በሆድዋ ላይ በክንዷ መትታ ጉዳት ያደረሰችባት መሆኑ የግል ተበዳይዋም በዚሁ ምክንያት ከተመታችበት ቦታ ሳትንቀሳቀስ ብርቱ ህመም እንደተሰማትና ፅንሱም መላወሱን ማቆሙን ከዚያም ሀኪም ቤት ተወስዳ በባለሙያ ምርም ሲደረግላት ፅንሱን ሞቶ በመገኘቱ ምክንያት በህክምና መሳሪያ እንዲወጣ መደረጉንና ከግል ተበዳይዋም ብዙ የረጋና የታመቀ ደም በመፍሰሱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባት ስለመሆኑ በምስክሮች ቃልና ህክምና ማስረጃ መረጋገጡን የገለፀ ሲሆን በአንባሩ ደግሞ በስር ተከሳሽ በኩል የተሰሙት የመከላከያ ምስክሮች ቃል አንዱ ከሌላው ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ተአማኒነት የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመለወጥ በአመልካች የጥፋተኝነት ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካስተላለፈ በኃላ በ3 ዓመት ከ7 ወር ፅኑ እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ቅጣት ጥሏል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት ክል ሰበር ችሎትም ውሳኔው ስህተት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

እንግዲህ እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ወንጀሉን ሊያስተባሉ አልቻም ሚል ድምዳሜ የጥፋተኝነት ውሳኔውን ሊሰጥ የቻለው በህግ የተሰጠውን የማስረጃ ምዘና ተግባሩን መነሻ በማድረግ መሆኑን ከውሳኔው ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ተጠቅሞ ያረጋጠውን ፍሬ ነገር ይህ ችሎትም እንዳለ የሚቀበለው ጉዳይ ይሆናል እንጂ በዚህ ረገድ የሚቀርበውን ክርክር ችሎቱ ለማት በህግ ስልጣን አልተሰጠውም፡፡

በሌላ በኩል እነዚህን በይገባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የተረጋገጡትን ፍሬ-ነገሮች መነሻ በማድግ በህግ አተገባበር ረገድ በበታች ፍ/ቤቱ ውሳኔ ላይ የተፈጠረ ስህተት መኖር አለመኖሩን በተመለከተ ስንመለከተው ደግሞ አመልካች የ8ወር እርጉዝ በቀጥታ በሆዷ ላይ የመታችሁ ከመሆኑ አኳያ ድርጊቱ በወ/ህ/ቁ581/ለ)፤ 27(1) 540 ስር የተመለከተውን የግድያ ሙከራ የሚያቋቁም በመሆኑ በዚህ ረገድ በጥፋተኝቱ ውሳኔ ላይ የተፈጠረ ስህተት አላገኘንም፡፡

ቅጣትን በሚመለከት የቀረበው የሰበር አቤቱታም ቢሆን ቅጣቱ በወ/ህ/ቁ192 መሠረት ሳይፈፀም ታግዶ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያስች ምክንያቶች ተሟልተው ባልተገኙበት ሁኔታ ቅጣቱን ማገድ የማይችል ሲሆን መጠኑን በተመለከተም ከደረሰው ጉዳትና ወንጀሉ ክብደት አኳያ በስር ፍ/ቤት የተጣለው ቅጣት ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የቤ/ጉሙዝ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ03748 በ24/7/2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁጥር 04446 በ17/8/2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቷል፡፡

2. የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ የፀና መሆኑን አመልካች በሚገኙበት ማረሚያ ቤት በኩል ይገለፅላቸው ፡፡ ይፃፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93741

ታህሳስ 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች:- አቶ አብነት ዋቆ ብሩ - ጠበቆች መሃመድ አሚን እና ጫንያለው እሸቱ ቀረቡ

ተጠሪ:- የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በጂማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው። የክሱ ይዘትም:- አመልካች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(2) ስር የተመለከተውን በተመላለፍ በሾፌርነቱ ሙያቸው የሌላውን ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለባቸው ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ/ም ከጠዋቱ 12:30 ሲሆን የሰሌዳ ቁጥሩ 3-28157 ኦሮ የሆነውን ሚኒባስ መኪና እያሽከረከረ ከጅማ ከተማ ወደ አጋሮ ከተማ ሕዝብ ጭኖ በማሽከርከር ላይ እያሉ መንገዱን ለቅቆ ከእንጨት ጋር አጋጭቶ በመገልበጥ የተሸከርካሪው ረዳት የሆነው አብዲ ዋቆ የገደላቸው በመሆኑ በፈፀሙት በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው። የአሁኑ አመልካችም የክስ ማመልከቻው ደርሷቸው ክሱን እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ዳኛ በመሆናቸው ያለመከሰስ መብት ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው በክሱ ላይ ተቃውሞ እንዳላቸው የገለፁ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አቃቤ ሕጉ አመልካቹ ድርጊቱን እንደፈፀሙ ወዲያውኑ የተያዙ መሆናቸውን ገልፀው ያለመከሰስ መብታቸው ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡትን አስተያየት በመቀበል የክስ ተቃውሞውን ያለፈው ሲሆን የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተ ግን የክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል። አቃቤ ህግ በበኩሉ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል። ከዚህም በኋላ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀማቸውና ሟች በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ሕይወታቸው ያለፈ መሆኑን አቃቤ ህግ በማስረጃዎቹ ያስረዳባቸው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ታምኖበት ይህንኑ እንዲያስተባብሉ እድል ተሰጥቶ አመልካች አደጋው የደረሰው በድንገተኛ አደጋ አጋጣሚ መሆኑን የሚያሳይ ጭብጥ አስይዘው የመከላከያ ማስረጃ ያሰሙ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በመከላከያ ማስረጃዎቹ የዐቃቤ ህግ ማስረጃዎቹን ያላስተባበሉ መሆኑን በመጥቀስ አመልካችን በአቃቤ ህግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጓቸዋል። ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት በመቀበልና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ በአንድ አመት ከስድስት ወር ቀላል እስራት እና በብር 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር) እንዲቀጡ ሲል ወስኗል። በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን የሰበር አቤቱታቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደየቅደም ተከተላቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርቡም ቅሬታቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ቁጥር 195(1) መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 16 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የአመልካች ያለመክሰስ መብት የታለፈው ያላግባብ መሆኑን፣ አመልካች ድርጊቱን የፈፀሙት በወንድማቸው ላይ ሆኖ ከአቅም በላይ በሆነ የአደጋ አጋጣሚ ሆኖ እያለ በስር ፍርድ ቤቶች መታለፉ ያላግባብ መሆኑን፣ የቅጣት ውሳኔም ተገቢነት የሌለው መሆኑና የእስራት ቅጣቱ መገደብ ሲገባው መታለፉም ያለግባብ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነውው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ጥፋተኛ መባላቸው ከሰ/መ/ቁጥር 42703 አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌወች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) በግልጽ ደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደምተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በምክንያትነትና በውጤት መካከል ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 24 በተመለከተው አግባብ ግንኙነት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ሲያሽከረክሩት የነበረው ተሽከርካሪ ተገልብጦ ሟችን ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ/ም መግደላቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች የሚከራከሩበት ነጥብ ሟች የሞቱት በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሥር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለውን የባለሙያ የምስክርነት አስተያየት፣ በአደጋው ቦታ የተነሳውን ፕላንና የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል መዝኖ አመልካች የተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ቀርተው አደጋው መድረሱን ማረጋገጡን ደምድሟል፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ ማስረጃ ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ከመሆኑም በላይ ታአማኒነቱ ሲታይ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 በተመለከተው የማስረጃ ምዘና አግባብ ጉዳዩን ለማስረዳት በቂና አሳማኝ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ይህን ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክብደት ሊሰጠው አይገባውም ነበር ለማለት የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች አደጋው በድንገተኛ አጋጣሚ የተከሰተ ነው በማለት የሚያቀርቡት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር በዚህ ችሎት ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57 በግልፅ እንደሰፈረው “ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆነም በአንፃሩ አንድ ሰው “የፈፀመው ድርጊት በሕግ የሚያሰቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈፀመ ወይም የደረሰ ሆኖ ሲገኝ በወንጀል ሕግ ሊፈረድበት አይገባውም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 57(2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የሕጉ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ህግ ድርጊቱ የተፈፀመው ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን ማስረደፋት የሚጠበቅበት መሆኑን ነው፡፡ ድርጊቱ ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑ ማስረጃ ካልቀረበ ወይም ድርጊቱ ከአቅም በላይ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በተከሳሽ በኩል ከቀረበ የተከሰሰውን ሰው በወንጀል ሕግ ጥፋተኛ ብሎ መፍረድ ከሕጉ መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ቸልተኛ ነበር? ወይስ አልነበረም? የሚለው ጥያቄ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 59 የሰፈረውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ አሁን ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው በመሆኑም የሕጉን ይዘት እንዳለ ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው፡፡ ይኸው፡- ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አደርጓል የሚባለው፡-

(ሀ) ድርጊቱ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን ፣ ወይም

(ለ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያሰቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ነው፡፡”

በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል የመባለው ውጤቱን እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ደግሞ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ውጤቱን ማወቅ ይችል ነበር ማለት ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም ቸልተኝነት አለ ለማለት ሕጉ የሚጠቀምበት ዋነኛ መስፈርት የተከሰሰው ሰው በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ነው፡፡ ድርጊቱን የፈፀመው ሰው ነበረው ዕውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባው ዕውቀትና ግንዛቤ የሚመዘነው የሰውዬው እድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃው ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነም የሕጉ አንቀጽ 59(1) ይደነግጋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በሙያቸው አሽከርካሪ ሆነው እያለና በአሽከርካሪነት ሙያው ደግሞ የሌላውን ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለባቸው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-28157 ኦሮ የሆነውን ሚኒባስ መኪና እያሽከረከረ ከጅማ ከተማ ወደ አጋሮ ከተማ እያሽከረከሩ ተገቢውን ጥንቃቄ ከማድረግ ጉድለት መኪናው ተገልብጦ ሟች የሞቱ በመሆኑ አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) ስር የማይጠበቁበትን ምክንያት አላገኘንም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም አመልካች የጥፋተኝነት ውሳኔውን አስመልክቶ የሚያቀርቡት ክርክር ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23፣24፣57፣57 እና 543(2) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2) መሰረት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሊቀጣ የሚገባው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እስራት እና ከሦስት ሺህ እስከ ስድስት ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ነው፣ ቅጣት ደግሞ ሊጣል የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ስር የተመለከቱትን ነጥቦች በማመዛዘን ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ ቅጣት ሲጥል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር እና በወንጀል ሕጉ ከተመለከቱት የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ጋር በማገናዘብ ቅጣቱን መወሰኑን የገለፀ ቢሆንም ሟቹ የአመልካች ወንድም በመሆናቸው ምክንያት ቅጣቱን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1) መሰረት ማክበዱ የሕግ መሰረት ያለውና የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ አላማ የሚያሳካ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ይሄው ምክንያት ሊያዝ የማይገባው ከሆነ አመልካችን ሊያርማቸው፣ ሌላውን ደግሞ ሊያስጠነቅቅ የሚችለው የቅጣት መጠን አንድ አመት ቀላል እስራት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ የተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢ ቢሆንም የቅጣት ውሳኔ ክፍል ግን በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 26643 ነሐሴ 03 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 167016 ነሐሴ 12 ቀን 2005 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 123422 ነሐሴ 30 ቀን 2005 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ)(2)) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፉ ጥፋተኛ ናቸው መባላቸው በአግባቡ ሲሆን ቅጣቱ ግን ተገቢ ያልሆነ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተይዞ እንዲከብድ የተደረገ በመሆኑ ምክንያቱን ውድቅ በማድረግ አመልካች ሊቀጡ የሚገባው የቅጣት መጠን በአንድ አመት ቀላል እስራት ነው ብለናል፣ የገንዘብ መቀጮው ብር 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር) እንዲቀጡ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤት የእስራት ቅጣት ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረሚያ ቤቱ ይገለጽለት ብለናል፡፡
4. ***መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡***

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93173

ታህሳስ 17 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካቾች ፡- 1.አቶ ተዋበ እስጢፋኖስ

2. ወ/ሮ አበራሽ አስራት

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ ለሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በምዕራብ አርሲ ዞን ቆሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች እንደቅደምተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ክሱም፡- ተከሳሾች በኢ/ፌ/ዲ/ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(3) እና 481(1) (ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ በክሱ የተዘረዘሩትን ህገ ወጥ የጦር መሳሪያዎችንና ጥይቶችን በቤታቸው አከማችተው በፍርድ ቤት የብርበራ ትዕዛዝ ቤታቸው በፖሊስ ሲፈተሽ የጦር መሳያዎቹና ጥይቶቹ ስለተገኙ ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

1ኛ ተከሳሽም በሰጡት የእምነት ክህደት ቃል በክሱ ከተጠቀሱት ጦር መሳሪያዎች መካከል በተወሰኑት ላይ ፍቃድ ያለኝ ሲሆን ከቤቴ የተገኘ ቦንብ ባለመኖሩ የፈጸምኩት ወንጀል የለም፣ጥፋተኛም አይደለሁም ሲሉ ክደው የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ የእምነት ክህደት ቃል ስለመስጠታቸው የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያመላክት አይደለም፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም 1ኛ ተከሳሽ ፈቃድ አለኝ ያሉአቸውን የጦር መሳሪያዎች በተመለከተ ፍቃድ የተሰጠበትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማዘዙ የሁለት ቺኮዝ ፣የክላሽንኮፕ ፣የኡዝ እና ካርቤን መሳሪያዎች ፍቃድ የተሠጠባቸውን ማስረጃዎች ማቅረባቸውን በፍርድ በማስፈር ኤፍ1-1 የሆነ ቦንብና በክሱ ተዘርዝረው ፍቃድ የሌላቸውን የጦር መሳሪያዎች በተመለከተም የከሳሽ ምስክሮችን ቃል ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የተሰጠው የብርብራ ትዕዛዝ የ1ኛ ተከሳሽ እና ሼህ አህመድ ሐጂ አህመድ የተባሉት ግለሰብ ቤቶች እንዲበረበሩ ሲሆን የሚበረበሩ የጦር መሳሪያዎች ዓይነት በዝርዝር በፍርድ ቤት ብርበራ ትዕዛዝ ካለመገለጹም ሌላ ብርበራው የተካሄደው 1ኛ ተከሳሽ በሌሉበት ቤታቸው ተሰብሮ በመሆኑ ብርበራው የተካሔደው ህጋዊ አካሄዱን ጠብቆ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንጂ ተከሳሾች ይህን ያህል የጦር መሳሪያ በቤት ውስጥ ማስቀመጣቸው ተገቢ ባለመሆኑ ሊማሩበትና የአካባቢውም ሌሎች ሰዎች ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ እንዲሁም ብርበራው የህጉን ሥርዓት ተከትሎ ያልተደረገ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ክስ የቀረበባቸውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) በመቀየር በወንጀል ህግ አንቀጽ 809 ጥፋተኞች ናቸው ሲል እንዳንዳቸው በብር 50 (አምሳ) እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

ከሳሽም በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሸኘት ይግባኙን ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማቅረባቸው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከራቸው በኋላ በሰጠው ውሳኔ፡- በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፖሊስ የመልስ ሰጪዎችን ቤት ሲፈተሽ የጦር መሳሪያዎቹ መገኘታቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፣የስር ፍርድ ቤትም ይግባኝ ባይ ምስክሮችን ከሰማ በኋላ የመልስ ሰጪዎችን ማስረጃዎች መስማት ሲገባው መልስ ሰጪዎቹ ያቀረቡትን መቃወሚያ መነሻ በማድረግ የጦር መሳሪያዎቹን ፍቃድ እንዲያቀርቡ በማድረግ በቀረበው ማስረጃ ላይ ይግባኝ ባይ አስተያየት ሳይሰጥበት ከመዘገቡ ጋር ማያያዙ ተገቢነት የለውም፣እንዲሁም መልስ ሰጪዎቹ እንዲከላከሉ ብይን ሳይሰጥ ያለአግባብ ክስ የቀረበባቸውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ በመቀየር ቀላል ቅጣት የወሰነው መልስ ሰጪዎችንና መሰሎቻቸውን የማያስተምር እንዲሁም የህዝቡን መረጋጋት የማያረጋግጥ ጉድለት ያለበት ውሳኔ ነው፡፡ በመሆኑ የይግባኝ ባይ ምስክሮች የመልስ ሰጪዎች ቤት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲፈተሽ ቦንብ እና ኡዝ መትርየስ የተባሉት በግል የማይያዙና ፈቃድ የማይሰጥባቸው የጦር መሳሪያዎች የተገኙ ስለመሆናቸው በማረጋገጣቸው ክስ በቀረበባቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኞች ሊሆኑ ይገባል ሲል በዚሁ ድንጋጌ እያንዳንዳቸው በሁለት ዓመት እስራትና በብር 3000 እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

ተከሰሾችም በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የይግባኝ ቅሬታቸውን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/195(1) መሰረት የሰረዘባቸው ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከራቸው በኋላ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔና በክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል የሰበር አቤቱታቸውን ውድቅ በማድረጉ ለዚህ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች በአቤቱታቸውም የጠቀሱት ቅሬታ ነጥብ ሲጠቃለል፡- የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት ያስተላለፉብን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባ ነው የሚል ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- አመልካቾች የጦር መሳሪያዎቹን በቤታቸው አከማችተው የተገኙት ለንግድ አላማ ስለሆነ ክስ በቀረበባቸው ወንጀል ህግ አንቀጽ ጥፋተኞች ናቸው በሚል የቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸው የሚነቀፍበት ምክንያት ባለመኖሩ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾችም ተጠሪው ላቀረበው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም፡- አመልካቾች የፈጸሙት ወንጀል በወንጀል ህግ 481(1)(ሀ) የሚሸፈን ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካቾች ቤት በፍርድ ቤት በተሰጠ የብርበራ ትዕዛዝ በፖሊስ ሲፈተሽ ቦንብ እና ኡዝ መትርየስ የተባሉት በግለሰብ ደረጃ የማይያዙና ፈቃድ የማይሰጥባቸው የጦር መሳሪያዎች የተገኙ ስለመሆናቸው የተጠሪ ምስክሮች ለሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርበው ካስረዱት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ ይህን የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ይህ ችሎትም የሚቀበለው ነው፡፡ ይህንኑ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ይዘን ክስ ወደቀረበበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) ስንመለስ፡- ማንም ሰው መንግስት አደጋ ላይ ስለመጣል በተወሰኑት ድንጋጌዎች ከተመለከተው ውጪ ፈቃድ ሳይኖረው ወይም ህግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማናቸውንም አይነት የጦር መሳሪያዎች፣ፈንጂዎች፣ወይም ጥይቶች በመነገድ ዓለማ የሰራ፣ከውጭ አገር ያስመጣ ፣ወደ ወጭ አገር የላከ፣ያጓጓዘ፣የገዛ፣የተቀበለ፣ያስቀመጠ፣ያከማቸ፣የደበቀ ፣ለሽያጭ ያቀረበ ወይም እንዲዘዋወሩ ያደረገ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ በዚሁ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ሆኖ እንደሚቀጣ ተመልክቷል፡፡ አመልካቾችም በብርበራ ከቤታቸው የተያዙትን የጦር መሳሪያዎች ውስጥ ፈቃድ የላቸውም የተባሉትን የጦር መሳሪያዎች በቤታቸው ውስጥ ያከማቹት ለንግድ በሚል እንደሆነ የተጠሪ ማስረጃዎች ስለማስረዳታቸው የሥር ወረዳ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚያመላክት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 481(1)(ሀ) በተነገረው መሰረት አንድን ሰው በዚህ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ነው ለማሰኘት ግለሰቡ መሳሪያዎቹን ያከማቸው ወይም በድንጋጌው ከተዘረዘሩት ድርጊቶች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ድርጊቶች የፈጸመው በመሳሪያዎቹ ለመነገድ በሚል እንደሆነ ክሳሽ ሊያስረዳ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) በጠቅላላው ለአንቀጽ 481 ከተሰጠው ርዕስ ወይም ስያሜ ጋር በማያያዝ ሊተረጎም የሚገባ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾቹ የፈጸሙት ወንጀል በወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) ስር የሚሸፈን ሆኖ አላገኘንም፡፡ ይልቁንም ይህ ችሎት እንደሚገነዘበው አመልካቾች ፈቃድ የሌላቸውን የጦር መሳሪያዎችንና ጥይቶችን በቤታቸው አከማችተው የመገኘታቸው ሁኔታ የኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ የወንጀል ህግ አንቀጽ 808(ሀ) የጦር መሳሪያዎችን ና ጥይቶችን ስለመቆጣጠር የተደነገገውን የሚጥስ ሆኖ ስለሚገኝ በዚሁ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር የጥፋኝነትና ቅጣት ውሳኔ ሊተላለፍባቸው የሚገባ ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት አመልካቾችን በወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) ጥፋኞች ናቸው ሲሉ በዚሁ ድንጋጌ የቅጣት ውሳኔ ያስተላለፉባቸው በዚሁ ድንጋጌ ስር ጥፋተኞች ሊሆኑ የሚያስችሉት ህጋዊ ፍሬ ነገሮች ስለመኖራቸው ተጠሪው ባላስረዳበት ሁኔታ ስለሆነ ውሳኔው በከፊል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/12859 በቀን 04/12/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/119417 በቀን 10/05/2005ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/146183 በቀን 13/12/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 195(2) (ለ)(2) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. አመልካቾች እንዳንዳቸው በ2 ዓመት እስራትና በ3000 ብር እንዲቀጡ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት የሰጡትን የውሳኔ ክፍል ሽረናል፡፡
3. አመልካቾች ጥፋተኞች ናቸው ሊባል የሚገባው በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(3) እና አንቀጽ 481(1)(ሀ) ስር ሳይሆን በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና 808(ሀ) ስር ነው በማለት በመወሰን በዚሁ ድንጋጌ እጃቸው ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በ3 (ሦስት)ወር እስራት ሊቀጡ ይገባል ብለናል፡፡ሆኖም አመልካቾቹ በዚሁ ወንጀል የታሰሩበት ጊዜ ከ3 ወር በላይ መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንጻር ስለተረዳን በሌላ ወንጀል የማይፈለጉ ከሆነ ዛሬውኑ ከሚገኙበት ማረሚያ ቤት እንዲለቀቁ አዘናል ፡፡ ለሚገኙበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ ብለናል፡፡
4. ፈቃድ የሌላቸውን የጦር መሳሪያዎችና ጥይቶች መንግስት እንዲወርሳቸው የሥር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሠጠው የውሳኔ ክፍልና ይህንኑ የውሳኔ ክፍል የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት በማጽናት የሰጡት የውሣኔ ክፍል አልተካም ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/89276

መሥከረም 23 ቀን 2006 ዓ ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሸገር ገ/ ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

መ.ሥጠፋ አህመድ

አመልካች ተፈሪ ሚናሞ አልቀረቡም

ተጠሪ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ዐቃቤ ሕግ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የሶዶ ከተማ መጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09361 ህዳር6ቀን 2005 ዓ.ም፣ የሰጠው ፍርድና የወላይታ ዞን ከፍተኛፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 23731በ ጥር 9ቀን 2005ዓ.ም የሰጠው ውሳኔናየደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎትመሰረታዊ የህግ ሥህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የእምነት ማጉደል ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡በሥር ፍርድ ቤት አመካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ተከሳሽ (አመልካች) በወኝጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ ለራሱ ብልጽግና ለማግኘት አስቦ ተካሳሹ የቅርብ ጓደኛው የሆነውን የግል ተበዳይ አቶ አሰፋ ደመቀ ሶዶ መርካቶ ክፍለከተማ ከሚገኘው የግል ድርጅቱ(ግሮሰሪ)በህዳር ወር 2003 ዓ.ም ዓ.ም በመሄድ ጨረታ አሸንፌአለሁ በማለትና በሚስቱ ሥም የተዘጋጀ ፐርፎርማ በማስያዝ ብር 21000 (ሃያ አንድ ሺ ብር) ከወሰደ በኋላ ግል ተበዳዩ በሽማግሌ ሲጠቀው ካመነ በኋላ ገንዘቡን ያልከፈለው ስለሆነ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ መጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አቅርቦ ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ አመልካች ወንጀል አልፈጸምኩም፣ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡
2. ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት ሥድስት የሰው ምስክሮች አቅርቧል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ የተጠሪ ምስክሮች የግል ተበዳይና አመልካች ጓደኛሞች መሆናቸውን፣ አመልካች የጋምጎፋ ዞን ደንባ ጎፋ ወረዳ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት አላቂ ዕቃ ለማቅረብ በጨረታ አሸንፌአለሁ፡፡ ለሥራ ማስኪያጃና ለቅድመ ክፍያብር 21000 (ሃያ አንድ ሺ ብር) ስጠኝ በማለት በዕምነት ወስዶ አልመለሰም፡፡ ሌሎቹ ምስክሮች የግል ተበዳይንና አመልካችን ሲያሸማግሉ አመልካች ገንዘቡን የወሰደ መሆኑን ለሽማግሌዎቹ ያመነ መሆኑን የመሰከሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ጉዳዩ ያሳያል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከግል ተበዳይ በአደራ ወሰድኩት ገንዘብ ላለመኖሩ ያስረዱልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን እንዳቀረበ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤትየግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኃላተከሳሽ ጨረታ አሸንፌአለሁ በማለት ከግል ተበዳይ ለሥራ ማስኪያጃና ለቅድመ ክፍያ ወሰደውንብር 21000 (ሃያ አንድ ሺ ብር) ያልመለሰ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በ አንድ ዓመት ከ አምስት ወር እሥራት እንድቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝለ ወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችንናየተጠሪን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠውን የጥፋኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር195 ንዑስ አንቀጽ2(ለ)2 መሰረት አጽንቶታል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡

4. አመልካች ሚያዚያ 11ቀን200ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታየሥር ፍርድ ቤት፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትየሰጡትውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የግል ተበዳይ የሰጠው ምስክርነት ለአመልካች ብር 21000 (ሃያ አንድ ሺ ብር) በብድር ሰጥቸው አልመለሰልኝም የሚል ነው፡፡ይህ ፍታብሔራዊ ግኑኝነትን ሚመለከት እንጂ ወንጀል አይደለም፡፡ በተጠሪ ክስም ሆነ ማስረጃ እኔ እንደፈጸምኩት የተገለጸው ተግባር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነነውን የእምነት ማጉደል ወንጀል የማቃቀምና በወንጀል ሕጉ በወንጀልነት ያልተደነገገነው፡፡ እንደዚሁም ተጠሪ ክስና ማስረጃ አመልካች በወንጀል ህጉ አንቀጽ23 መሰረት የህግ፣ የግዙፍ ተግባርና ሞራል ሁኔታ በተሟላበት ሁኔታ ወንጀል የፈጸምኩ አለመሆኑያላረጋገጠበት ሆኖ እያለ የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍርድ ቤት፣ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካችበወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድ ዓመት ከአምስት ወር እሥራት እንድቀጣ የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ህጉን አንቀጽ23 የሚተላለፍና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሥለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶትና መልስ የሚያቀርብበት ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶት መልስ ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገጸው ሲሆን እኛምየሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካችበወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድ ዓመት ከአምስትስት ወር እሥራት እንድቀጣ የሰጡት ውሳኔተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥበመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለ መወሰን በመጀመሪያ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ መሰረታዊ ፍሬ ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

6. ተጠሪ አመልካች የእምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ስለመሆኑ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማስረጃ በይዘቱ፣ የግል ተበዳይና አመልካች ጓደኛሞች እንደሆኑ፣ አመመልካች የጋምጎፋ ዞን ደንባ ጎፋ ወረዳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት አላቂ ዕቃ ለማቅረብ በጨረታ አሸንፌአለሁ፡፡ ለሥራ ማስኪያጃና ለቅድመ ክፍያብር 21000 (ሃያ አንድ ሺ ብር) ስጠኝ በማለት የጠየቀው መሆኑንና ገንዘቡን የግል ተበዳዩ አመልካችንሰነዶችን በሚስቱ በኩል በማስፈረም በመያዣነት ይዞ ገንዘቡን ለአመልካች የሰጠው መሆኑን፣ አመልካች ገንዘቡን ለግል ተበዳይ ያልመለሰ መሆኑን እንዳስረዱ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትና ከላይ የተገለጹት ተግባራት የግል ተበዳይና በአመልካች መካከል የመሰረቱት ግኙኝነት አደራ ሰጭና የአደራ ተቀባይ ነው ወይስ አበዳሪና የተበዳሪ ግኑኝነት አመልካችና የተጠሪ ግኑኝነት አበዳሪና የተበዳሪ ግኑኙነት አላቸው ቢባልህጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው የሚሉት ጥያቄዎች መታየት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

7. ከላይ የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ አቀራረጽ ፣ዝርዝር ይዘትናመሰረታዊ ዓላማ መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ በወንጀል ህጉ በንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝርበት ምእራፍ ሁለት በልዩ ሁኔታ በተንቀሳቃሽ ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝረው ክፍል አንድ ሥር የተደነገገ የዕምነት ማጉደል ወንጀል መሰረታዊ ባህሪ፣ ይዘትና የሚስከትለውን ኃላፊነት የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ1 ድንጋጌ የአማረኛ ቅጅ ቃል በቃል ሲነበብ ማንም ሰው ተገቢ ብልጽግና ለማግኘት ወይምለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው የደረገ፣የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን መሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ3 የተከሳሹ ወንጀል ሃሳብ ግምት ሚደነግግ ሲሆን ይዘቱም ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ማስረዳት ካልቻለ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ማዋል ሀሳብ እንዳለው ይቆጠራል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

8. የእንግሊዘኛውን ቅጅ ስንመለከት- Breach of Trust የሚል ርዕሥ ያለው አንቀጽ 675 Whoever, with intent to obtain for himself or to procure for a third person an unjustifiable enrichment, appropriates, or procures for another, takes or causes to be taken, misappropriates, uses to his own benefit or that of a third person, or disposes of for any similar act, in whole or in part, a thing or a sum of money which is the property of another and which has been delivered to him in trust or for a specific purpose, is punishable, according to the circumstances of the case, with simple imprisonment, or with rigorous imprisonment not exceeding five years. በማለት በንዑስ አንቀጽ1 የሚደነግግ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ3 The intent to obtain for himself or to procure for third person an unjustifiable enrichment shall be presumed where the criminal is unable upon call, to produce or repay the thing or sum entrusted, or at the time when he should have returned it or accounted there for. በማለት ይደነግጋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

9. አመልካች ከግል ተበዳይ ጨረታ ያሸነፍኩ ስለሆነ ለሥራ ማስኪጂያና ለቅድመ ክፍያ ብር 21000 (ሃያ አንድ ሺ ብር) የጠየቀና የግል ተበዳይም የአመልካችን ሰነዶች በመያዣነት ይዞ የሰጠው መሆኑን በተጠሪ ማስረጃ እንደተገለጸ ተረድተናል፡፡ አንድ ሰው ለሌላው የተበደረውን ነገር በአይነቱ ለመመለስ ተገዳጅ በማድረግ ገንዘብ ወይም በማገልገል የሚያልቅ ሌላ ነገር ለተበዳሪው ለመስጠትና ኃብትነቱን ለማስተላለፍ የሚፈጽሙት ተግባር የማያልቅ ነገር ብድር እንደሆነ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2471 ከተሰጠው ትርጓሜ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንድን ነገር በብድር መሥጠትና አንድን ነገር በአደራ መስጠት የተለያየ ባህሪና ይዘት ላቸው ናቸው፡፡ አደራ አደራራ ተቀባዩ አደራ አስቀማጩ ሰጠውን ዕቃ ተቀብሎ በአደራ እንዲያስቀምጥለት የሚገባው ግዴታና ተግባር መሆኑንከፍታብሔር ሕግ ቁጥር2779 ከተሰጠው ትርጓሜ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአደራ የተቀበሉትን ገንዘብ ለአደራ አስቀማጩ አለመመለስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ1 በመተላለፍ በዕምነት ማጉደል ወንጀል ሊያጠየቅ የማይችል የወንጀል ተግባር ነው፡፡
10. በአንጻሩ ተበዳሪ በብድር የወሰደውን ገንዘብ በወቅቱ አለመክፈሉ አግባብነት ባላቸው ህግ ድንጋጌዎች በፍታብሔር ከሚጠየቅ በስተቀርየወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ1 ተላልፏል ተብሎ በዕምነት ማጉደል ወንጀል ሊጠየቅ የማይችል መሆኑንከወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ ዝርዝር ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡.ማንም ሰው በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቀው ተገቢ ብልጽግና ለማግኘት ወይምለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው ፡፡ የአመልካች አድራጎትየወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ3 በሚደነግገው ወንጀል ሃሳብ ግምት የማይሸፈን መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡
11. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በህግ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ እንደማይችል በህገ መበንግስቱ አንቀጽ22 ንዑስ አንቀጥ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው የህግ ፣የግዙፍ ተግባርና የሞራል ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ23 ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ከላይ ዘረዘርነው የግዙፍ ድርጊት የህግ የሃሳብ ሁኔታዎች አልተሟሉም፡፡ ይህ ሁኔታ መሟላቱን ሳያረጋግጡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካችበወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድዓመት አምስት ወር እሥራት እንዲቀጣ የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ አቀራረጽ ፣ዝርዝር ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና መሰርታዊ የህግ ስህተት ያለበት በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የሶዶ ከተማ መጀመሪያ ፍርድ ቤት ፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛፍርድ ቤትናየደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ ቁጥር195 ንዑስ አንቀጽ2(ለ)1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ጨረታ አሸንፌለሁ በማለት ለሥራ ማስኬጃና ለቅድመ ክፍያ የሚሆን ብር21000(ሃያ አንድ ሺ ብር) ከግል ተበዳዩ በብድር የወሰደውን ገንዘብ ለግል ተበዳይ አለመክፈሉ (አለመመለሱ) አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚያስጠይቀው ባለመሆኑ በነጻ ይሰናበታል በማለት ወስነናል፡፡

3. አመልካች ከቀረበበት ወንጀል ክስ በነጻ ተሰናበተ በመሆኑ ከእስር እንዲለቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 91535

የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሰሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አህመድ አደም በሽር - ከጠበቃ ሌ/ኮ ስንታየሁ ደመቀ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአማራ ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን በህክምናና በጤና አጠባበቅ ሙያ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የመስራት የወንጀል ክስ አስመልክቶ በሶስቱም የክልሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በሁለቱ የስር ፍ/ቤቶች ተሰጥቶ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በ03/07/2004 ዓ.ም. በተዘጋጀ የክስ ማመልከቻ በኮምቦልቻ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት 3ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 535(3)(ሀ) እና (መ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የህክምና መመርመሪያ መሳሪያዎችን በአግባቡ የመያዝ ሙያዊ ግዴታ እያለባቸው በ21/11/2003 ዓ.ም. በኮምቦልቻ ከተማ በቀበሌ 03 ክልል የኮምቦልቻ ጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች የግል ክሊኒኮችን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ በተገኙበት ጊዜ ተከሳሹ ሀያት በተባለ መካከለኛ ክሊኒክ በህክምና ባለሙያነት እየሰሩ በነበረበት ጊዜ አንዱን የሽንት መመርመሪ መሳሪያ ለሶስት በመሰነጣጠቅ አብዝተው ሲሰሩ የተገኙ በመሆኑ በህክምና በጤና አጠባበቅ ሙያ ሕገወጥ በሆነ መንገድ የመስራት ወንጀል አድርጎአል የሚል ነው፡፡ አመልካች ተጠይቀው ወንጀሉን አላደረግሁም በማለታቸው ተጠሪ በክሱ መሰረት ያስረዱልኛል ያላቸውን ሶስት ምስክሮች አቅርቦ አሰምቶአል፡፡ የጽሁፍ ማስረጃም አቅርቦአል፡፡ፍ/ቤቱም ተጠሪ በክሱ መሰረት ያስረዳ መሆኑን ገልጾ አመልካቹ መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 142 በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት አመልካች መሳሪያዎቹ ለልምምድ የሚላኩ የህክምና ሙያ ተማሪዎች ሲጠቀሙባቸው የነበሩ እንጂ ለሕክምና ስራ የዋሉ አለመሆናቸውን ያስረዱልናል በማለት የሰው እና የጽሁፍ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ ከክሱ ጋር አገናዝቦ ከመረመረ በኃላ አመልካቹ በተጠሪ ማስረጃ የተመሰከረበትን ፍሬ ነገር በማስረጃው አላስተባበለም በማለት በክሱ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት እና ቀጥሎም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል በአመልካቹ ላይ የአራት ዓመት ጽኑ እስራት እና የብር 16,000 መቀጮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅጣት ወስኖአል፡፡አመልካች በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ይግባኝ በማቅረባቸው የደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔውን በትዕዛዝ ሲያጸናው የሰበር ክርክሩን የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የጥፋተኝነት እና የጽኑ እስራት ቅጣቱን በማጽናት እና መቀጮውን ብቻ ወደ ብር 10,000 በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ሶስት ቦታ ተሰነጣጥቆአል የተባለው የሽንት መመርመሪያ መሳሪያ ድርጊቱ በራሱ ጥፋት መሆን አለመሆኑን ከወ.ሕ.አ. 535(ሀ)እና (መ) አንፃር፣ይህ ቢታለፍ የዐ/ሕግ ምስክሮች ወደ ክሊኒኩ ሲሄዱ በተሰነጣጠቀ የሽንት መመርመሪያ መሳሪያ ባለሙያዎቹ ሲጠቀሙ አላየንም ባሉበት ሁኔታ አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመከለተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባው ነጥብ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ መሰረት የማስረዳት ግዴታውን ተወጥቶአል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቹ ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት ክደው የተከራከሩ ሲሆን በዐ/ሕግ በኩል የክስ ነጥቡን ለማስረዳት የቀረቡት የተጠሪ ምስክሮች ለቁጥጥር ተግባር በተሰማሩበት ጊዜ አመልካች በሚሰሩበት የመመርመሪያ ክፍል ውስጥ ከሚገኘው ጠረጴዛ ላይ 68 የተሰነጣጠቁ የሽንት መመርመሪያ መሳሪዎችን (ዲፕ ስቲክስ) ማግኘታቸውን ከመግለጽ ውጪ በእነዚህ መሳሪያዎች አመልካቹ ሲገለገሉበት ስለማየታቸው ወይም አመልካቹ ቀደም ብለው የተገለገሉባቸው ስለመሆኑ ወይም በክፍሉ ውስጥ ተቀምጠው የተገኙት በአመልካቹ በአገልግሎት ላይ ሊውሉ ታስበው ስለመሆኑ በማረጋገጥ የሰጡት ምስክርነት አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡የጽሁፍ ማስረጃውም የሽንት መመርመሪያ መሳሪያዎችን ሰነጣጥቆ መጠቀም ተገቢ ስላለመሆኑ የሙያ አስተያየት የተሰጠባቸው ናቸው፡፡የኮምቦልቻ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ የሰጠውና በኃላም አልተከላከሉም በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ያስተላለፈባቸው ይዘቱ ከላይ በተገለጸው ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ሲሆን በበኩላችን ይህ ማስረጃ ዐ/ሕግ በክሱ መሰረት አስረድቶአል ለማለት የሚያስችል መሆን አለመሆኑ በአግባቡ መጤን የሚገባው ሆኑ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገ ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገ ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወ.ሕ.አ. 23(1) እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑም በወ.ሕ.አ. 32(1) ስር ተደንግጎአል፡፡በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወ.ሕ.አ. 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል መማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡በሌላ አነጋገር ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቶአል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመለከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 142 መሰረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ስለመሆኑ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በዐ/ሕግ በኩል በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጡት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች አመልካች በሚሰሩበት የመመርመሪያ ክፍል ውስጥ ከሚገኘው ጠረጴዛ ላይ 68 የተሰነጣጠቁ የሽንት መመርመሪያ መሳሪዎችን(ዲፕ ስቲክስ) መገኘታቸው ብቻ ሲሆን አመልካቹ ተላልፈውታል ተብሎ የተጠቀሰባቸው ድንጋጌ የሚቀጣው ደግሞ ደህንነቱና ጥራቱ ባልተረጋገጠ፣በተከለከለ፣በተበላሸ፣በተጭበረበረ፣በተበከለ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት በሚያደርስ የሕክምና መገልገያ መሳሪያ መገልገልን ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለህክምና ተግባር በእነዚህ መሳሪዎች ሲገለገሉ አልተገኙም፤ተቀምጠው የተገኙት ለሕክምና አገልግሎት ከዋሉ በኃላ ወይም ለማዋል በማሰብ ስለመሆኑም አልተረጋገጠም፤የሽንት መመርመሪያ መሳሪያዎቹ የተሰነጣጠቁት በምን ምክንያት እንደሆነም አልተገለጸም፡፡በመሰረቱ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 ስር በግልጽ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ይዘቱ ከላይ የተገለጸው የዐ/ሕግ ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርግ ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ተጠሪ ለዚህ ችሎት ባቀረበው መልስም ይህንኑ በመገንዘብ በአመልካቹ ላይ ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ ቢሻር ተቃውሞ የሌለው መሆን ገልጾአል፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤት በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 መሰረት ተከሳሹን ማሰናበት ሲገባው የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱም ሆነ በመጨረሻም የዐ/ሕግን ማስረጃ አላስተባበለም በማለት በአመልካች ላይ የሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የጥፋተኝነት የቅጣት ውሳኔ ከላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ የሆኑ የወንጀል ሕግ እና የወንጀል ስነስርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. አመልካች አቶ አህመድ አደም በሸርን አስመልክቶ በኮምቦልቻ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 202797 በ21/09/2004 ዓ.ም.ተሰጥቶ በደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመ.ቁ. 0205343 በ27/09/2004 ዓ.ም. እና በመ.ቁ. 27041 በ19/10/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ እና በውሳኔ የፀናው የጥፋተኛነት ውሳኔ፤እንዲሁም በኮምቦልቻ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 202797 በ24/09/2004 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 0205343 በ27/09/2004 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 27041 በ19/10/2005 ዓ.ም. የተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሽረዋአል፡፡
2. ተጠሪ ባቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ አመልካች ወንጀሉን ማድረጋቸውን ያላስረዳ እና በሕግ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታ ያልተወጣ በመሆኑ አመልካች ከተከሰሱበት በህክምናና በጤና አጠባበቅ ሙያ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የመስራት የወንጀል ክስ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. በአመልካች ላይ ተጥሎ የነበረው የአራት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት የተሻረ ቢሆንም አመልካች ቀደም ሲል በዚህ ችሎት ትዕዛዝ በራሳቸው ዋስትና በዋስ የተለቀቁ በመሆኑ ለማረሚያ ቤት የሚተላለፍ ትዕዛዝ አይኖርም፡፡
4. አመልካች ተጥሎባቸው የነበረውን የመቀጮ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ አድርገው ከሆነ ተመላሽ እንዲደረግላቸው ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡
5. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባንክና ኢንሹራንስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 78180

መጋቢት 09 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳን ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጠበቃ አትናፍን]ጋሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስቱር ንጉሴ ወኪል የአሮ ኤፍሬም ንጉሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመድን ዋስትና ሽፋን ውል የሚሻሻልበትን ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 17 ቀን 2004 ዓ.ም በፃፈው አቤቱታ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 10522 የካቲት 09 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ለተጠሪ አመልካች በድምሩ ብር 73,523.00 ከዳኝነት፣ ከሕጋዊ ወለድ እና ከ10 የጠበቃ አበል እንዲሁም በቁጥር ከብር 500.00 ወጪ ጋር እንዲከፍል የሠጠውና በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 150259 መጋቢት 07 ቀን 2004 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ግድፈት የተፈጸመበት ነው በማለት እንዲሻርለት ስለጠየቀ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በስር ተከሳሽነት፣ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ በከሳሽነት ነው፡፡

የተጠሪ ክስ ይዘቱም አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 2-78918 አ.አ በሚል ለምትታወቀውና ንብረትነቷ የአሁኑ ተጠሪ ለሆነችው የኪራይ መኪና የኢንሹራንስ ሽፋን ሰጥቶ የነበረ መሆኑን፣ ይህ መኪና በተጠሪ ተወካይ አቶ ስንታየሁ ተካልኝ ለተባለ የመንጃ ፈቃድ ላለው ሰው ተከራይቶ የተከራየው ሰው በማሽከርከር ላይ እያለ የፊት ጎማው ፈንድቶ በመገልበጥ በመኪናው ላይ የአካልና የመካኒካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑን፣ ከአመልካች ላይ ባላቸው የመድን ውል በዚህ መኪና ላይ አደጋ እንደደረሰ የሚጠግኑ ጋራጆችን አወዳድረው የዋጋ ማቅረቢያ ከሰሰበሰቡ በኋላ አመልካች ኢንሹራንስ ከገባው ሰው ወይም እሱ ከቀጠረው ሹፌር ወጪ በሌላ ሶስተኛ ወገን ሲሽከረከር አደጋ የደረሰበት ሰለሆነ የደረሰውን ጉዳት ለመተካት ኃላፊነት የለብኝም በማለት ጥገናውን ወይንም ለጥገናው የሚያስፈልገውን ወጪ አልቀበልም ማለቱን፣ ከዚህ በኋላ ተጠሪ ይህን መኪና አካል ጨረታውን ባሸነፈው ጋራጅ አሰርቶ ለውስጥ እቃ ጉዳት የሚያስፈልገውን የመለዋወጫ እቃም አወዳድሮ ከአሸናፊው ጋራጅ ላይ ማግኘቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገልፆ አመልካች ከጉዳቱ ኃላፊነት አለበት ተብሎ መኪናውን ለማስነሳት፣ ለትራንስፖርት የወጣውን የማስጠገኛ ዋጋ በድምሩ ብር 76,523.00 ለተጠሪ እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ለደረሰው አደጋ በሕጉ አግባብ ከተጠሪ ጋር የገባው የመድን ዋስትና ውል እንደሌለ፣ ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ተጨማሪ ውል ላይ ቀደም ብለው ያደረጉትን የኢንሹራንስ ሽፋን መኪናው ላይ አደጋ የደረሰው ኢንሹራንስ ገቢው ወይም እሱ ከቀጠረው ሹፌር ውጪ በሶስተኛ ወገን ሲሽከረከር ከደረሰ ኢንሹራንስ ሰጪን የማይመለከተው መሆኑን በመግለጽ ስምምነት መደረጉን ገልፆ ኃላፊነት የለብኝም በማለት በኃላፊነት ረገድ የተከራከረ ሲሆን በኃላፊነት መጠኑ ላይም የአደጋ መነሻ ብር 3000.00 ሳይቀነስ መቅረቡ ተገቢ ያለመሆኑን፣ መኪናውን ለመጫን ብር 5000.00 ክፍያለሁ የሚሉትም ሐሰት መሆኑን፣ በመኪው ላይ የደረሰ የመካኒካል አደጋ ለመኖሩ በባለሞያ የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ በተደረገው ጨረታ አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ስራውን መውሰድ ሲገባው ከፍተኛውን ያቀረበ መውሰዱ ያላግባብ መሆኑን፣ ለመካኒካል ጉዳት ያስፈልጋል ተብሎ ከተጫራቾች ቀረበ የተባለው ፕሪፎርማ እርስ በራሱ የሚጋጭ መሆኑን ገልጾ ገንዘቡንም ልከፈል አይገባም በማለት የተከራከረ ሲሆን ገንዘቡን ክፍል የሚባል ከሆነም ተጠሪ የመለዋወጫ እቃዎችን ሊመልስ ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ተጨማሪ ውሉን የማያውቁት መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ተጠሪ በሕጉ አግባብ ያደረጉት የተጨማሪ የመድን ሽፋን ውል መኖሩ መረጋገጡን፣ በዚህ ውል ደግሞ የመድን ሽፋን የተሰጠው መድን ገቢው ወይም እሱ በቀጠረው ሹፌር እየተሽከረከረ ባለበት ጊዜ እንጂ በሌላ ሶስተኛ ወገን ሲሽከረከር አደጋ ከደረሰ አመልካች ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን መገለጹን በምክንያትነት ይዞ የተጠሪን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎልታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ አመልካቹ ውሉ ስለመሻሻሉና ይህን ውል ስለማሻሻሉ ለተጠሪ ያሳወቀ መሆኑን አላስረዳም በሚል ምክንያት ተጨማሪ የመድን ውል የለም ሲል በቀድመው የመድን ውል መሰረት አደጋው እንደሚሸፍን ጠቀሶ ለጉዳዩ አመልካችን ኃላፊ ያደረገ ሲሆን የካሳውን መጠን በተመለከተ ደግሞ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሶለት የስር ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች ለተጠሪ ብር 73,523.00 ከዳኝነት፣ከሕጋዊ ወለድ እና ከ10 የጠበቃ አበል እንዲሁም በቁጥር ከብር 500.00 ወጪ ጋር እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ የካሳ መጠን ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ውሳኔውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 377 መሰረት አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አሁን በተያዘው መዝገብ ላይ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተጨማሪ የመድን ሽፋን ውል ስለመኖሩ የተጠሪ ወኪል መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም የጻፉት ማመልከቻ ቀርቦ እያለ ይኼው ሳይታይ ታልፎ ተጨማሪ ውል የለም ተብሎ ለአደጋው ሽፋን እንዳለው ተደርጎ ካሳውን ለተጠሪ እንዲከፈል መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ጠበቃቸው በሰጡት መልስ አመልካች ኃላፊነቱን አስመልክቶ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ያልጠበቀ መሆኑን፣ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ የተባለውም ተጨማሪ ውሉን ተጠሪ ያልፈረሙበትና የሚያውቁት ስለመሆኑ ባለማስረዳቱ መሆኑን፣ መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም የተጠሪ ወኪል ጻፉ የተባለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማመልከቻም በክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ታይቶ የሚታመን አይደለም፣ ተጨማሪ ውል ሰለመኖሩ የሚያሳይ አይደለም ተብሎ ውድቅ የተደረገ እና በዚህ ችሎት ሊመዘን የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ከሰ/መ/ቁጥር 76942 አንፃር ሲታይ የሰበር ማቅረቢያ ጊዜው ያላለፈ መሆኑን በመጥቀስና ሌሎች የሰበር አቤቱታ ነጥቦችን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብቅ አንጻር በሚመለከተው መልኩ መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት ተጨማሪ የመድን ሽፋን ስምምነት አልተደረገም ተብሎ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ መባሉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለተጠሪ ጥያቄ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከረው አደጋው መድን የገባው ወይም እርሱ ከቀጠረው ሾፌር ውጪ በለ ሶስተኛ ወገን ሲሽከረከር ከደረሰ ሽፋን የሌለው መሆኑ ሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም የተጨማሪ ውል ስምምነት አድርገናል፣ ይኼው ውል ስለመኖሩ ደግሞ የተጠሪ ወኪል መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም የፃፉት ማመልከቻ ያሳያል በማልት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ተጨማሪ ውል የለም፣ አላውቀውም፣ በቀደመው መሰረት አደጋ ሽፋን አለው በሚል ነው፡፡ በቅድሚያ ተጠሪ ኃላፊነቱን አስመልክቶ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ጊዜውን ጠብቆ የቀረበ አይደለም በማለት ያቀረቡትን ተቃውሞ ተመለክተናል፡፡

አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ኃላፊነቱን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ የካቲት 13 ቀን 2004 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የሰበር አቤቱታውን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ በመ/ቁጥር 76942 ተከፍሎ ለባለሶስቱ የሰበር አጣሪ ችሎት ቀርቦ እስከ ሚያዝያ 03 ቀን 2004 ዓ.ም ተገቢው ትዕዛዝ ሳየሰጥበት ከቆየ በኋላ የኃላፊነቱን መጠን ተመልክቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት የታዘዘው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የካቲት 09 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቶ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት መጋቢት 07 ቀን 2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት በማፅናቱ አመልካች በዚሁ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን መጋቢት 17 ቀን 2004 ዓ.ም ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ጉዳዩ አሁን በተያዘው መዝገብ ተከፍቶ የሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ መጋቢት 24 ቀን 2004 ዓ.ም ሊመረመር የሚገባ የሕግ ነጥብ መኖሩን አምኖ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ ያደረገ ሲሆን ሚያዝያ 02 ቀን 2004 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ አመልካች በሰ/መ/ቁጥር 76942 ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ባሁኑ መዝገብ አጠቃልሎ ማቅረቡንና ጉዳዩም ያስቀርባል የተባለ መሆኑን በመዘርዘር በሰ/መ/ቁጥር 76942 የቀረበው መዝገብ እንዲዘጋለት አመልክቶ የሰበር አጣሪ ችሎትም ይህንኑ የአመልካችን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ዋናውን ጉዳይ ሳይመለከት የዳኝነት ገንዘቡ በደንቡ መሰረት ተቀንሶ እንዲመለስለት በማዘዝ መዝገቡን ዘግቶአል፡፡ በመሆኑም አመልካች በኃላፊነት ውሳኔው ላይ በወቅቱ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የካሳ መጠን ክርክሩ ደግሞ በሰበር አጣሪው ችሎት የቀረበው የኃላፊነት ቅሬታ መቋጫ ሳያገኝ አስቀድሞ እልባት አግኝቶ የካሳው መጠን ውሳኔ ቅሬታ ለአጣሪ ችሎቱ ቀርቦ በኃላፊነት ጉዳይ ላይም ቅሬታ ተጠቃልሎ ቀርቦ ታይቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገቢው ትዕዘዝ የተሰጠ መሆኑን ስለተገነዘብንና በአንድ ጉዳይም ሁለት መዝገቦች መከፈት የሌለባቸው በመሆኑ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡት መቃወሚያ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22(4) እና ከክርክር አመራር ስርዓት አንጻር ተገቢነት ያለው ሁኖ ስላለገኘን አልተቀበልነውም፡፡ ዋናውን ጉዳይ በተመለከተ ከላይ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 657 ስለኢንሹራንስ ውሉ ፎርማሊቲ የሚደነግገውም ሀሳብ የያዘ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት የኢንሹራንስ ውል የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ በሚባል ጽሁፍ እንደሚገለጽና የመድህን ገቢውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ በፖሊሲው ላይ መድህን ሰጭው ከፈረመ ህጋዊ የሆነ የኢንሹራንስ ውል ግንኙነት በመድህን ሰጭው እና በመድህን ገቢው መካከል እንደሚመሰረት ተቀምጧል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የንግድ ሕጉ ልዩ የሆነ የኢንሹራንስ ውል እንደመሆኑ መጠን ከጠቅላላው ሕግ የበላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የሚደረግ መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያሳዩን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የኢንሹራንስ ውል አደራረግ አፈጻጸሙ በጠቅላላ የውል ሕግ የሚመራ ግንኙነት አይደለም፣ ይህ ሰበር ችሎትም የኢንሹራንስ ውል አደራረግ አፈጻጸሙ በጠቅላላ የውል ሕግ የሚመራ ግንኙነት አይደለም፣ ይህ ሰበር ችሎትም የኢንሹራንስ ውል አለ ለማለት መድን ሰጪው በሚያዘጋጀው ፖሊሲ ላይ መፈረም እንዳለበት በን/ሕ/ቁጥር 657 ላይ ከመመልከቱ በስተቀር መድን ገቢው መፈረም እንደሚገባው ያልተመለከተ በመሆኑና በውል ማቅረቢያ ሰነዱ ላይ መድን ገቢው ከፈረመና በፖሊሲው ላይ ደግሞ መድን ሰጪው ከፈረመ በሁለቱ መካከል የመድን ውሉ ስለመደረጉ በቂ መሆኑን በሰ/መ/ቁ. 24703 ሚያዝያ 09 ቀን 2000 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ እንዲሁም የኢንሹራንስ ፖሊሲ ተጨማሪ በሆነ ጽሑፍ ካልሆነ በቀር ሊለወጥ እንደማይቻል የን/ህ/ቁጥር 657(2) አስገዳጅነት ባለው መልኩ ደንግጓል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሲታይም ፖሊሲው ወይም የፖሊሲው ተጨማሪ ጽሁፍ ከመፈረሙ በፊት ለጊዜው ኢንሹራንስ ሰጪው ኢንሹራንስ ለሚገባው ሰው ፖሊሲው ወይም ለፖሊሲው ተጨማሪ ጽሑፍ እስከ ተፈረመ ድረስ ማረጋገጫ መድን የሚሆነው ጽሑፍ የሠጠው እንደሆነ ኢንሹራንስ ሰጪውና ኢንሹራንስ ገቢው አንዱ ለአንዱ ግዴታ እንደገቡ ይቆጠራል በሚል ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አይነተኛ ዓላማም ውሉ ስለመኖሩ የሚረጋገጠው በጽሑፍ በሆነ ሰነድ መሆኑን ማሳየት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ከመድን ገቢው ወይም እራሱ ከቀጠረው ሾፌር ውጪ መኪናው ሲሸከረከር አደጋ ከደረሰ የመድን ሽፋን የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ተጨማሪ ውል አለ በማለት የተከራከረው ሰነዱን በማቅረብና ይህንኑ ሰነድ ተጠሪ ባይፈርሙበትም ሰነዱ ያለ ነው፣ ሰነዱ የለ መሆኑንም በተጠሪ ወኪል መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም ያቀረቡት ማመልከቻ ያሳያል በማልት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጨማሪ ውሉ ተጠሪ የሚየውቁት ስለመሆኑ አመልካች አላስረዳም፣ መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም ተጻፈ የተባለ ማመልከቻም የሚታመን አይደለም በማለት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው መሆኑን ውሳኔው ያሳያል፡፡ ይህም የሚያሳየው ተጠሪ በተጨማሪ ውል ላይ መፈረም አለመፈረማቸው የሚያስከትለው የሕግ ውጤት ምንድነው የሚለውን ከመታየቱ በፊት ሰነዱ በተጠሪ የማይታወቅ፣ ማመልከቻውም የማይታመን ነው ወደሚለው ድምዳሜ ፍሬ ነገርን የማጣራት፣ ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ በዚህ ችሎት የሚታይበት አግባብ የሌለ መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3) ሀ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪ ደረሰ የተባለውን አደጋ የሚሸፈነው የቀደመው ውል በተጨማሪ ውል ስለመለወጡ ፈቃዳቸውን የሰጡ ወይም ተጨማሪ ውሉን ያወቁት የነበረ መሆኑን ፍሬ ነገሩን በመመርመርና ማስረጃን በመመዘን የሚይዘው ድምዳሜ የለም፡፡ በመሆኑም በተጠሪ ወኪል መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም ተፃፈ የተባለው ማመልከቻ በማስረጃነት ቀርቦ ሰነዱ የማይታመን መሆኑና ተጠሪ ተጨማሪ ውሉን እንደሚያውቁት ሊያስረዳ እንደማይችል በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የቀደመውን ውል ከአስር ወር ቆይታ በኋላ አሻሽዬዋለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ ጥያቄ በመሆን ከላይ ከተጠቀሱት የንግድ ህጉ ድንጋጌዎችና ከን/ሕ/ቁጥር 659 ድንጋጌ አኳያ ሊታይ የሚገባው ሁኖ አላገኘንም፡፡ በካሳ መጠኑ ላይ የቀረቡት ክርክሮችም የፍሬ ነገርና የማስረጃ ክርክሮች በመሆናቸው በዚህ ችሎት የሚታዩበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም የአመልካች የሰበር አቤቱታ የመሰረታዊ ሕግ መመዘኛን የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ልዩን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 10522 የካቲት 09 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በክ/መ/ቁ 121982 ነሐሴ 26 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ፣ እንዲሁም በዚሁ ችሎት በመ/ቁጥር 150259 መጋቢት 07 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ለተጠሪ አመልካች በድምሩ ብር 73,523.00 /ሰባ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሶስት ብር/ ከዳኝነት፣ ከሕጋዊ ወለድ እና ከ10 የጠበቃ አበል እንዲሁም በቁጥር ከብር 500.00 ወጪ ጋር እንዲከፍል የተሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90793

ታህሳስ 04 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- ግሎባል ኢንሹራንስ አልቀረበም

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ፍጹም ላቀው
2. ወ/ሮ ብስኩት ዘለቀ

} ጠበቃቸው አትናቦን ነጋሳ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም የከሳሾች አውራሽ የጋራ ንብረት የሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3.19516 ኦ.ሮ ሚኒባስ መኪና በተከሳሽ ኩባንያ የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው ሲሆን በ20/10/2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 12፡10 ሲሆን ከአዳማ ወደ አዲስ አበባ እየተጓዘ ቢሾፍቱ ከተማ መግቢያ ላይ ትክክለኛ ምልክት ሳያሳይ መንገድ ዘግቶ የቆመውን መኪና በመግጨት ከፍተኛ የሆነ ጉዳት የደረሰበት ሲሆን ተከሳሽም መኪናውን አንስቶ የተጎዱ ተሽከርካርካሪዎች ወደሚጠገኑበት ቦታ ወስዶ መኪናውም ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የተሸርካሪውን ዋጋ ብር 350,000 ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ለከሳሾች ከገለጸ በኋላ መኪናው ላይ አደጋ የደረሰው ትርፍ ሰው በመጫኑ ምክንያት በመሆኑ ክፍያውን እንደማይፈጽም ስለገለጸልን የሚፈለግበትን ብር 350,000 ከ20/10/2004 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ 9% ጋር እንዲከፍል ይወሰንበት የሚል ነው፡፡

ተከሳሽም በሰጠው መልስ፡- ለመኪናው ኢንሹራንስ የተገባለትና ከአደጋ ቦታም እንዲነሳ የተደረገ ቢሆንም ስለአደጋው ፖሊስ ሪፖርት እንዲያቀርብ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ በመኪናው ላይ አደጋ በደረሰበት ጊዜ 18 ሰዎችን ጭኖ የነበረ መሆኑን ገልጿል፡፡ በከሳሾችና እና በከሳሽ መካከል የተደረገው የውል ስምምነትም በኢንሹራንስ ፖሊሲ ላይ የተመሰረተ ሲሆን አደጋው የደረሰበት መኪናም ሹፌሩን ሳይጨምር የመጫን አቅሙ 11 ሰው ሆኖ እያለ 7 ሰዎችን በትርፍ ጭኖ በጠቅላላው 18 ሰዎችን ጭኖ የደረሰ አደጋ መሆኑና አደጋውም የደረሰው ከአቅም በላይ በመጫኑ ምክንያት ፍሬን እንዳይታዘዝ በማድረጉና መሪውንም ወደሚፈለግበት መምራት ባለመቻሉ ነው፡፡ ኢንሹራንስ ዋስትና የተገባለት ተሸርካርካሪ መጫን ከሚችለው አቅም በላይ ትርፍ በመጫን አደጋ በደርሰበት ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኢንሹራንስ ፖ/ሊሲ አንቀጽ 6 በተመለከተው መሰረት አደጋ የደረሰበትን መኪና ዋጋ ተከሳሽ የመክፈል ግዴታ ስለማይኖረው ክሱ ተቀባይነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከተከሳሽ ድርጅት እና ከኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ድርጅት አንድ አንድ የሰርቬይ ባለሙያ በማስቀረብ ሙያዊ ምስክርነታቸውን በመስማት እንዲሁም ከትራፊክ ፖ/ሊስ ስለአደጋው የቀረበውን ሪፖርት ከባለሙያዎቹ የምስክርነት ቃል በማገናዘብ እና በመመርመር በሰጠው ውሳኔ፡- ከአቅም በላይ መጫን አደጋ አያስከትልም ማለት የማይቻል ቢሆንም ከትራፊክ ፖ/ሊስ የቀረበው የመኪና አደጋ ሪፖርት ለአደጋው መድረስ መንስኤ የሆነው በፍጥነት በማሽከርከርና በማንቀላፋት መሆኑን ከሚገልጽ ውጪ አደጋው መኪናው ከአቅም በላይ በመጫኑ ምክንያት መሆኑን የማያመለክት ስለሆነና ሪፖርቱም አደጋ በደረሰበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ መሰረት አድርጎ የቀረበ በመሆኑ የሚታመን ነው፤በሌላ በኩል ተከሳሽ አደጋ የደረሰው ከአቅም በላይ መኪናው በመጫኑ ነው ቢልም በከሳሾችና ተከሳሽ መካከል በ30/08/2012 የተፈረመው የኢንሹራንስ ውል ስምምነት ኢንሹራንስ የተገባለት መኪና ከአቅም በላይ ወይም ትርፍ ሰው ጭኖ ቢገኝ ካሳ አይከፈልም የሚል ባለመሆኑ የውል ስምምነቱ ለሚደርሰው የሞት አደጋ፣የአካል ጉዳት እንዲሁም በንብረት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ካሳ የሚከፈል መሆኑን ስለተስማሙና ይህም ስምምነት በፍ/ህ/ቁ/1731(1) መሰረት ህግ ሆኖ ስለሚያስገድድ ተከሳሽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ፣ለዳኝነት የተከፈለውን እንዲሁም ወጪና ኪሳራ ሊከፍል ይገደዳል ብሏል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት በማሰናበቱ የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታም የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦች ፡-ጉዳት የደረሰበት ሚኒባስ መኪና የኢንሹራንስ ሽፋን ዋስትና የተገባለት ቢሆንም በወቅቱ 18 ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ መንገድ ዳር ተበላሽቶ ከቆመ መኪና ጋር ተጋጭቶ 14 ሰዎች ሞተው 4 ሰዎች የተጎዱ መሆኑን የአድአ ወረዳ ፖ/ሊስ በደብዳቤ ከገለጸው የተረጋገጠ ሲሆን በኢንሹራንስ ውሉም ሆነ በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በተሰጠው የባለቤትነት ማረጋጫ ደብተር(ሊብሬ)የመኪናው የመጫን አቅም 11 ሰው ብቻ መሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ መኪናው 7 ሰዎችን በትርፍነት ጭኖ ጉዳቱ በመድረሱ በኢንሹራንስ ኩባንያ ፖ/ሊሲ ጠቅላላ ማግለያ በሚለው ክፍል ተራ ቁጥር 6 ‹‹ በኢንሹራንስ ውሉና ከሚመለከተው አካል በተሰጣቸው የባለቤትነት ማረጋጫ ደብተር ላይ ከተገለጸው ሰው ብዛትና መኪናው ካለው መቀመጫ ብዛት በላይ ጭኖ ለሚደርስ አደጋ ኢንሹራንስ ኩባንያው ማንኛውንም ክፍያ ለመክፈል ኃላፊነት አይኖርበትም ›› ስለሚል ይህንንም ግዴታ ኢንሹራንስ ሰጭም ሆነ ኢንሹራንስ ገቢው በንግድ ህግ አንቀጽ 657(2-3) መሰረት በተጨማሪ የማግለያ ውል የግዴታ ስምምነት የተፈራረምን ስለሆነ አመልካች የጉዳት ካሳውን ለመክፈል እንደማልገደድ በመጠቀስ ያቀረብኩትን ክርክር ፍርድ ቤቶቹ ሳይቀበሉት ያለፉት አግባብነት የለውም፤

አንድ መኪና ከአቅም በላይ ጭኖ ሲጓዝ እንደፈለጉት መሪም ሆነ ፍሬን መያዝ መቆጣጠር እንደማይቻል እና ከአቅም በላይ መጫን ለአደጋ ምክንያት እንደሚሆን የባለሙያ ምስክርነት በተሰጠበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ከአቅም በላይ መጫን ለአደጋ ምክንያት አይሆንም፣እንዲሁም በኢንሹርነስ ፖ/ሊሲው ላይ ከሳሾች ግዴታ ገብተው

የፈረሙት ነገር ስለሌለ የመኪናውን ግምት፤የጠበቃ አበል 10 ፐርሰንት ወጪ ኪሳራ ብር 500 ጨምሮ አመልካች ሊከፍል ይገባል ሲሉ የወሰኑት ተቀባይነት የለውም የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡-በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በተደረገው የኢንሹራንስ ዋስትና ውል የመድን ሽፋን የተሰጠው መኪና ትርፍ ሰው ከጫነ አመልካች ኃላፊነት አይኖረውም በሚል አልተስማማንም፣ በዚህ መልኩ ስለመዋዋላችን የሚገልጽ ማስረጃም አመልካች ለሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አላቀረበም፤አመልካች የኢንሹራንስ ፖሊሲ ነው በማለት ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበውም የፖሊሲ ቁጥር የሌለው ለማስታወቂያ ተብሎ የተዘጋጀውን ብሮሸር በመሆኑ ተጠሪዎችን የሚያስገድድ አይሆንም፤ እንዲሁም በተሸርከርካሪው ላይ አደጋ የደረሰው በፍጥነት በመንዳትና በአሽከርካሪው ማንቀላፋት ምክንያት መሆኑን በማረጋገጥ የትራፊክ ፖሊስ ማስረጃ የሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ አመልካች አደጋው የደረሰው ትርፍ ሰው በመጫኑ ምክንያት ነው ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች ላቀረቡት መልስም አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- ጉዳት ለደረሰበት መኪና ተጠሪዎች የጠየቁትን ገንዘብ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የንብረት ኢንሹራንስ ውል ስለመደረጉ በግራ ቀኙ የታመነ ጉዳይ ሲሆን አመልካችም የተጠሪዎች ንብረት ለሆነው ጉዳት ለደረሰበት ሚኒባስ መኪና የብር 350,000 የዋስትና ሽፋን ሰጥቷል፡፡ መኪናውም በደረሰበት አደጋ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን የግራ ቀኙን ወገን እያከራከራቸው የሚገኘው ደግሞ ኢንሹራንስ ሰጪው ለደረሰው ጉዳት በሰጠው ዋስትና ሽፋን መሰረት ኃላፊ የመሆኑና ያለመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በመኪናው ላይ ለደረሰው ጉዳት የዋስትናውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የለብኝም ሲል በዋናነት የሚከራከረው መኪናው ላይ አደጋ ሊደርስ የቻለው የመጫን አቅሙ 11 ሰዎች ሆኖ ሳለ በትርፍነት ሰባት ሰዎችን በመጫኑ ምክንያት ክብደት በመጨመሩ የመኪናው መሪና ፍሬን እንደልብ ባለመታዘዛቸው ነው፡፡ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ከተቀመጡት ጠቅላላ የማግለያዎች በአንቀጽ 6 የኢንሹራንስ ዋስትና ሽፋን የተሰጠው መኪና መጫን ከሚገባው የሰው ቁጥር በላይ በትርፍነት ጭኖ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ አመልካች ኩባንያ የዋስትናውን ገንዘብ የመክፈል ሀላፊነት እንደሌለበት ተመልክቷል በሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ግን በኢንሹራንስ ፖሊሲው ተጠቅሷል በሚል አመልካች ቢከራከርም በማስረጃነት የኢንሹራንስ ፖሊስ ነው በማለት ያቀረበው ለማስታወቂያ ሥራ ተብሎ የተዘጋጀ ብሮሸር እንጂ ትክክለኛ የኢንሹራንስ ፖሊሲ አይደለም፣እንዲሁም አመልካች የጠቀሰው የማግለያ ምክንያትም አመልካችና ተጠሪዎች በገባነው የኢንሹራንስ ውል ያልተጠቀሰ በመሆኑ የሚያስገድደን አይደለም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የንብረት ኢንሹራንስ ውል ከተለያዩ የውል አይነቶች አንዱ ሲሆን ውሉም ህጋዊ የሆኑ ተግባራት በሚከናወኑበት ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በዋስትናው ሽፋኑ መሰረት ለመካስ በማሰብ ሊደረግ የሚገባ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ህ/ቁ/1678 (ለ) እንደተመለከተው አንድ ውል በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ ለማከናወን ሊደረግ ይገባል፡፡ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የንብረት ኢንሹራንስ ውልም በህጉ መሰረት የተደረገ ነው፡፡ ሆኖም ህጋዊ ውል የሚደረገው በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደውን ድርጊት ወይም የህግ ክልከላ የተደረገበትን ጉዳይ በማከናወን ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ወይም በሚኖረው ፍላጎት መነሻ ሊሆን አይገባም፡፡ የተጠሪዎች መኪና ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውል መሆኑ የታመነ ጉዳይ ሲሆን ይህንኑ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜም የትርንስፖርት አዋጅ፣ደንብና መመሪያዎችን መከተል ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን አደጋው በደረሰበት ወቅትም መኪናው መጫን ከሚገባው 11 ሰዎች በላይ 7 ሰዎችን ጭኖ ሲጓዝ እንደነበር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን ተጠሪዎቹም ቢሆኑ መኪናው ትርፍ ሰዎችን አልጫነም ሲሉ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ መኪናው ከጫናቸው 18 ሰዎች ውስጥም በወቅቱ 14 ሰዎች መሞታቸው ከክርክሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ መኪናው በህጉ ከተቀመጠው የሰው ቁጥር በላይ መጫኑ የትራንስፖርት ህጉን የሚጥስ ሲሆን ህጉ ተጥሶ ከተፈቀደው የሰው ቁጥር በላይ ሰዎችን ጭኖ ሲጓዝ ለደረሰው አደጋ አመልካች የዋስትናውን ሽፋን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት ሊኖረው አይችልም፡፡

በአጠቃላይ በመኪናው ላይ ጉዳቱ የደረሰው ያለውን የትራንስፖርት ህግ በመጣስ ከወንበር በላይ በትርፍ 7 ሰዎችን ጭኖ ስለመሆኑ ለሥር ፍርድ ቤት የትራፊክ ፖሊስ በማስረጃነት ከላከው ሪፖርት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በመንገድ ትራንስፖርት ህግ ከሚፈቀደው ውጪ ትርፍ ሰዎችን ጭኖ ሲጓዝ በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት ሆኖ ባለበት የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች በኢንሹራንስ ውሉ መሰረት የዋስትና ሽፋን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል ሲሉ የወሰኑት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/15121 በቀን 14/08/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔና የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/161389 በቀን 15/08/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. ተጠሪዎች የትራንስፖርት ህጉን ጥሰው ከወንበር በላይ ትርፍ ሰዎችን ጭነው መኪናው እየተጓዘ በመኪናቸው ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች የዋስትናውን የሽፋን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አይኖርበትም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 78206

ሰኔ 20 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፉ አህመድ

አመልካቾች፡-1. ወ/ሮ ዩስራ አብዱልመኢን
2. አቶ ሁሴን አብዱልመኢን } ጠበቃ መሰረት ስዩም ቀረቡ
3. ዶ/ር አህመድ አብዱልመኢን

ተጠሪ፡- አቶ አብዱልቀኒ አብዱልመኢን ጠበቃ ጥጋቡ ጌጤ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 የተመለከተውን ድንጋጌ አተገባበር የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩም መነሻ የአሁን አመልካቾች በየመን አገር ፍ/ቤት በተሰጠ ፍርድ ባለመብት መሆናቸውን ገልፀው ይህንኑ በውጭ አገር ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያስፈጽምልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ሲሆን የአሁን ተጠሪም የመን አገር በተሰጠው ፍርድ የክርክር ተካፋይ ስላልነበርኩ መብቴን የነካ ፍርድ ስለሆነ ፍርዱ ሊፈፀም አይገባም በማለት ከዚህ በፊት በአመልካቾች ጥያቄ መሰረት ተሰጥቶ የነበረውን ፍርድ ተቃውሟል፡፡ አመልካቾችም ክርክሩ በየመን አገር ሲደረግ ተጠሪው ኢትዮጵያ ውስጥ ስለነበረ ፍ/ቤቱ ወኪል አቁሞለት በወኪል የክርክር ተከፋይ የነበረ መሆኑንና ይህንንም ክርክር ተጠሪው ማቅረብ የሚችለው ፍርዱን ለሰጠው ለየመን አገር ፍ/ቤት እንጂ ለዚህ ፍ/ቤት አይደለም በማለት መልሳቸውን የሰጡበት ስለመሆኑ የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሰጠው ብይን ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

ፍ/ቤቱም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳይ ተመልክቶ በከ/መ/ቁ 78860 በቀን 17/9/2003ዓ.ም በዋለው ችሎት ከዚህ ቀደም አመልካቾች በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ ይፈፀምልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456-461 የተመለከተውን ቅደመ ሁኔታ ያሟላ መሆኑ ታይቶና በፍርድ ባለዕዳነትም የተሰየሙት ወገኖች ያልተቃወሙት ስለሆነ ፍ/ቤቱ በዚሁ መዝገብ በቀን 25/2/02ዓ.ም በዋለው ችሎት በውሣኔው መሰረት እንዲፈፀም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤቱ የፍርድ ተቃዋሚ ሆኖ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

358 መሰረት ይፈጽም የተባለው ፍርድ ስህተት አለበት እኔ በክርክሩ ሳልሳተፍ የተሰጠ ፍርድም በመሆኑ መብቴን ተነክቷል በማለት የቀረበው ክርክር ሊቀርብ የሚገባው ጉዳዩን አከራክሮ ፍርዱን በሰጠው በየመን አገር ፍ/ቤት እንጂ ፍርዱ በሚፈፀምበት ፍ/ቤት አይደለም። ችሎቱ እያየ ያለው የአፈጻጸምን ጉዳይ እንደመሆኑ በዚህ የአፈጻጸም ጉዳይ ሊታይ የሚገባው የክርክር ዓይነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሰረት ፍርዱን ለማስፈፀም ሲባል በተያዘ ንብረት ላይ የሚቀርብ አቤቱታ የሆነ እንደሆነ ነው። የአሁን ተጠሪ የተቃውሞ ክርክር ያቀረበበት ጉዳይ በየመን ሀገር ፍ/ቤት ፍርድ ያረፈበት ንብረት የሚመለከት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሰረት የሚሸፈን አይደለም። በመሆኑም ተቃውሞው ተቀባይነት የለውም የሚለውን የፍርድ ትንታኔ ሰጥቶ ከዚህ በፊት እንደየመን አገር ፍ/ቤት ፍርድ ይፈፀም ሲል ሰጥቶት የነበረውን ትዕዛዝ አጽድቋል።

የአሁን ተጠሪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ላይ እኔ በክርክሩ ሳልካፈልበት የተሰጠው ፍርድና ለማስፈፀም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሀ/ መሰረት በሁለቱ አገሮች ፍርድን ለማስፈፀም ስምምነት ሣይኖር በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢት/ያ ፍ/ቤቶች እንዲፈፀም መበየኑ ተገቢ አይደለም ይሻርልኝ በማለት ባቀረበው ክርክር መነሻ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 70047 ጥር 30 ቀን 2004ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ፡-

በውጭ አገር የተሰጠን ፍርድ በኢት/ያ ለማስፈፀም የሚቻለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456-461 በተደነገገው መሰረት መሆን ይገባዋል። በተለይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ/ 458/ሀ/ በኢት/ያና ፍርዱን በፈረደው አገር መካከል ፍርዱን የማስፈፀም ስምምነት ሊኖር ይገባል። ኢት/ያና የመን በፍርዱ ላይ ማህተም ማድረጋቸው የፍርድ ሰነድ ከየመን ወደ ኢት/ያ ሲገባ የሰነዱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሲባል የተከናወነ የማስተባበል ስራ እንጂ በአገሮች መካከል ፍርድን ለማስፈፀም ስምምነት መደረጉን አያመለክትም። ስለሆነም ይኸው የህጉ ማሟያ ሣይሟላ የተሰጠው ፍርድ ተሸሯል። በማለት ከወጭና ኪሣራ ጋር ወስኗል።

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በዚሁ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በተሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ላይ የአሁን አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ነው።

በዚህ የሰበር ደረጃም ሁለቱም ወገኖች ያላቸውን ክርክር በጽሑፍ አቅርበው ክርክሩ ተጠናቋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ ባጭር ባጭሩ በይዘት ደረጃ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል።

በፍ/ብ/ሥ/ሥርአት ህጉ የተመለከተው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ በሁለት ዓበይት ምዕራፎች የተመለከተ ሲሆን በምዕራፍ 1 ላይ የተመለከተው በኢት/ያ ግዛት ውስጥ የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች ሲሆን በምዕራፍ 2 ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456 እስከ 461 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ደግሞ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ወይም ብይን የሚፈፀምበትን ሁኔታ የሚያመለክቱ ናቸው። ከዚህ ከህጉ አቀራረጽ መገንዘብ የሚቻለው ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይ በይዘቱ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት እንጂ ለአፈጻጸሙ ምክንያትና መነሻ ከሆነው ፍርድ ጋር በተያያዘ የሚነሣን ክርክር ለመጋበዝ ወይም ለማስተናገድ የሚያስችል አይደለም።

ሆኖም ምንም እንኳ ጉዳዩ በይዘቱ የአፈጻጸም ጉዳይ ቢሆንም ይፈፀም የተባለው ፍርድ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ከመሆኑ የተነሣ ይህንኑ ፍርድ በኢት/ያ ፍ/ቤቶች ዕውቅና ተሰጥቶት ለማስፈፀም የሚቻለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 የተመለከቱትን ቅደመ ሁኔታዎች መሟላታቸው የተረጋገጠ እንደሆነ ብቻ መሆኑን በግልጽ ተመልክቷል፡፡

እነዚህ በዚሁ ድንጋጌ የተመለከቱት ፍርዱን ለማስፈፀም የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውንና አለመሟላታቸውን አስመልክቶ ክርክር በቀረበ ጊዜም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 459 እና 460 በተደነገገው መሰረት ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርበውን ሙግት ሰምቶ ዳኝነት የሚሰጠው እራሱ የፍርዱን አፈጻጸም የያዘው ፍ/ቤት ነው፡፡

በህጉ የተመለከተው ትክክለኛ የጉዳዩ አካሄድ ይህ ሆኖ እያለ የአፈጻጸም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የክርክር አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 አንጻር በማየት ጉዳዩን ሰምቶ የመወሰን ስልጣኑ እና የዳኝነት ስራ ተግባሩ መሆኑ እየታወቀ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ፍርዱን በሰጠው በየመን አገር ፍ/ቤት ሊቀርብ የሚገባው እንጂ በዚህ ፍርዱን ለማስፈፀም ሲባል የአፈጻጸም ጉዳዩ በቀረበለት ፍ/ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የሰጠው ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን እና ከላይ የተመለከቱትን ስነ ስርአታዊ ድንጋጌዎች ትክክለኛ አፈጻጸም የተከተለ አይደለም፡፡

የአሁን ተጠሪም በመቃወሚያነት ካቀረባቸው ክርክሮች መካከል ይፈፀም በተባለው ፍርድ በተሰጠበት ጊዜ የመከራከር መብቴ አልተጠበቀም ይህንኑ ፍርድ በኢትዮጵያ አገር ፍ/ቤቶች ለማስፈፀም የሚቻል ስለመሆኑ በሁለቱ አገሮች መካከል ስለዚሁ ጉዳይ የተደረገ ስምምነት ስለመኖሩ አልተረጋገጠም የሚሉት ሁለቱ የመከራከሪያ ነጥቦች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 /ሀ/ እና /ሐ/ የሚወድቁ ሲሆኑ ሌሎች በተለይም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ በኢትዮጵያ በሚገኙ የኃይማኖት ፍ/ቤቶች ታይቶ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ በድጋሚ በየመን ሀገር ፍ/ቤት ሊስተናገድ አይገባም የሚለው ክርክሩ በዚህ በተያዘው የአፈጻጸም ጉዳይ ቀርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት ስርአት አልተዘረጋም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 ስር የተመለከቱትን ነጥቦች በይዞታቸው ማየት እንደሚቻለው በአለም አቀፍ ህግ የሁለት አገሮችን ግንኙነት ከሚገዛው የአለም አቀፍ ህግ መርህና በኢትዮጵያ ተቀብላ ባፀደቀቻቸው የሲቪልና የፖለቲካ አለም አቀፍ ስምምነት በአንቀጽ14 ስር የተመለከተውን በህግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ፊት የመዳኘት እና በክርክር በእኩል አይን የመታየት መብትን ለማስከበር ሲባል የተመለከቱትን መብቶች ተከብረውና ተጠብቀው የተሰጠ ፍርድ መሆኑ ታውቆ ማስፈፀም እንዲቻል በኢትዮጵያ ዝርዝር ህግ የተመለከቱ አንኳር ነጥቦች ናቸው እንጂ ማንኛውንም የክርክር ነጥቦች ባካተተ መንገድ የተቀረፀ ባለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው የክርክር ነጥብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 ስር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ጋር የተገናኘ መሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ የሚገባው በመሆኑ ነው፡፡

ከዚህም አንጻር የአሁን ተጠሪ በቁጥር 458/ሀ/ የተመለከተውን ድንጋጌ ተንተርሶ ፍርዱን በኢትዮጵያ አገር ባሉ ፍ/ቤቶች ለማስፈፀም የሚያስችል በሁለቱ አገሮች ተመሣሣይ ስምምነት ስለመኖሩ አልተረጋገጠም በማለት ሲከራከር የአሁን አመልካቾች በበኩላቸው በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ በሁለቱም አገሮች በሚመለከታቸው ክፍሎች ተረጋግጦ የገባ መሆኑን የሚያመለክቱ ሰነዶችን ከማቅረባቸውም ባሻገር ስለዚሁ ጉዳይ ተጨማሪ ማስረጃ ይቅረብልን በማለት እንደጠየቁ ከጉዳዩ አመጣጥ ተረድተናል፡፡ ይህ ጉዳይ በአገር ደረጃ የሚደረግ ስምምነት በመሆኑ ይህ አይነት ስምምነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለመኖሩና አለመኖሩ የማረጋገጥ ግዴታ እንደማንኛውም በተከራካሪ እጅ እንደሚገኝ ማስረጃ ተቆጥሮ መቅረብ በሚገባው ጊዜና አኳኋን ካልቀረበ በቀር ተቀባይነት የለውም የሚል የጠበቀ የስነ ስርዓት መስፈርትን የሚከተል አይደለም ይልቁንም ይህ አይነቱ የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345(1)ለ እንደተመለከተው የሚቀርበው ማስረጃ ለጉዳዩ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችል ከመሆኑ በላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተገቢ መስሎ ቢታየው በማናቸውም ምክንያት በተከራካሪው ወገን ጠያቂነትም ሆነ በእራሱ አነሣሽነት ይኸው አይነት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ለመፍቀድ ለማዘዝ ስልጣን ያለው በመሆኑ በዚህ አግባብ ይኸው የሁለቱ አገሮች ስምምነት ያለ መሆኑንና አለመሆኑን ለሚመለከታቸው መንግስታዊ ክፍሎች በትዕዛዝ ማጣራት እየተገባው በአመልካቾች የቀረበው ማስረጃ ስለማስረጃው ትክክለኛነት ከሚያረጋግጥ በቀር ስምምነት ስለመኖር ለማስረዳት ብቃት የለውም በሚለው ብቻ ተገድቦ የሰጠው ዳኝነት የማስረጃ አቀባበል ስርዓትን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ረገድ የአሁን ተጠሪ የተጨማሪ ማስረጃው ጥያቄ ስርዓቱን ጠብቆ በጊዜው የቀረበ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚለውም ክርክሩ በተመሣሣይ ምክንያት የህግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡

እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሀ/ በተመለከተው ድንጋጌ አፈጻጸም ላይ ብቻ ተወስኖ የሰጠው ዳኝነት በመሆኑ ምክንያት የአሁን ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሐ/ መሰረት ይፈፀም በተባለው ፍርድ አሰጣጥ ሂደት የክርክር ተካፋይ አልነበርኩም የመደመጥ መብቴ አልተከበረም በሚል ባነሳው ክርክር ሳቢያ አመልካቾችም በፍርዱ ሂደት ተጠሪው ኢት/ያ ውስጥ የነበረ በመሆኑ በሀገሪቱ ህግ መሰረት ወኪል በፍ/ቤቱ ቆሞለት የታየ ጉዳይ ነው በማለት በመከራከራቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሐ/ በዝምታ እንዳለፈው ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፍርድ ተረድተናል፡፡ ፍርድ ቤቱ ደርሶበት እንደነበረው መደምደሚያ ፍርዱን በዚህ አኳኋን መስጠት የሚቻል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 247/4/ እና 182/3/ የተደነገገ ቢሆንም በፍርዱ መሰረት አድርጎ በያዘው የህግ ጭብጥ ላይ የሰጠው ዳኝነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ መሰረት ያለው ሆኖ ባለመገኘቱ የአሁን ተጠሪ በተደራቢነት አቅርቦት የነበረውን ነገር ግን በዝምታ ያለፈው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሐ/ ጋር በተያያዘ የተነሣውን የመደመጥ መብት የመከበርና ያለመከበር ሚሚያ ሁኔታንም በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ እንደገና ተመልክቶ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 70047 ጥር 30 ቀን 2004ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. በፍርድ ሀተታው ላይ እንደተገለፀው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458/ሀ/ እና 458/ሐ/ በተመለከተ ግራ ቀኙ ባቀረቡት ክርክር ላይ ብቻ ተወስኖ እንዲሁም በቁጥር 458/ሀ/ን በሚመለከት በአሁን አመልካቾች በኩል የቀረበውን የተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ ጥያቄ ተቀብሎ በአመልካቾችም ሆነ በእራሱ አነሣሽነት ማስረጃውን በማየትና በማስቀረብ አስፈላጊውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መዝገቡን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የመስማሚያ ሀሣብ

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምጽ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን በደረሰበት መደምደሚያና በሰጠው ውሣኔ እስማማለሁ፡፡ ሆኖም ጉዳዩ መመለስ ያለበት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሣይሆን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆን ይገባዋል የሚል ሀሣብ ያለኝ በመሆኑና ጉዳዩ ሲመለስ በጭብጥነት ሊያዙ ስለሚገቡ ጉዳዬች ከአብላጫው ድምጽ የምለይባቸው ነጥቦች ያለ በመሆኑ ይህንን የመስማሚያ ሀሣብ ጽፌለሁ፡፡

1. የመጀመሪያውን የመስማሚያ ኃሣቤ መነሻ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ብይን ይዘትና ባህሪ ነው፡፡ አመልካቾች በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ በመቀበል የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጥቅምት 25 ቀን 2002ዓ.ም ውሣኔ ሲሰጥ የአሁን ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 459 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ቀርቦ አስተያየቱን አልሰጠም፡፡ ተጠሪ በእሱ በኩል የሚቀርቡ መከራከሪያዎች ሣይሰሙ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚ እንዲሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 460/1/ መሰረት የሰጠው ውሣኔ ተሰርዞ የመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባዋል ወይም አይገባውም? የሚለው ጭብጥ እሱ ባለበት ታይቶ እንዲወሰንለት ጥቅምት 10 ቀን 2003ዓ.ም የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ያቀረበ መሆኑን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 78860 ግንቦት 19 ቀን 2003ዓ.ም ከሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በክርክሩ ተካፋይ ሣይሆን የአመልካቾችን አቤቱታ በመቀበል በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚ እንዲሆን ጥቅምት 25 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በመሰረታዊ ይዘቱና ባህሪው በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 458 የተደነገጉትንና ሌሎች አስፈላጊ መስፈርቶች የሚያሟላ በመሆኑ ፍርዱ በኢትዮጵያ ግዛት ክልል ባሉ ፍርድ ቤቶች ሊፈፀም የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥና በፍርድ ዕውቅና ለመስጠት የተሰጠ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 460

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጸ 2 መሰረት የተሰጠ ውሣኔ ነው፡፡ ይህ ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ለመቃወምና እንዲሰረዝ ለማድረግ የሚቻልበት ስርዓት ከፍተሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 እስከ ፍታሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 460 ተዘርግቷል፡፡

3. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የተቃወመው በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈፀም የሚችል ነው በማለት ፍርድ ቤቱ ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 460 የሰጠውን ውሣኔ መሆኑን ሣያገናዝብና በየመን አገር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈፀም የሚችል መሆኑን የሚረጋገጥና ዕውቅና የሚሰጥ ውሣኔ እንጂ የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዳልሆነ ሣይገነዘብ ተጠሪ መቃወሚያውን ማቅረብ ያለበት ፍርዱን ለሰጠው የየመን አገር ፍርድ ቤት እንጂ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አይደለም፡፡ እንደዚሁም ክርክሩ የአፈጻጸም ክርክር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 ከተደነገገው ስርዓት ውጭ ተጠሪ ጥቅምት 25 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠሁትን የአፈጻጸም ውሣኔ መቃወም አይችልም የሚል ይዘት ያለው ብይን ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ.ም ሰጥቷል፡፡
4. ተጠሪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጥቅምት 25 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በመሰረዝ እኔ ባለሁበት ጉዳይ ታይቶ እንዲወሰን ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ ማድረጉን በመቃወም ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች እንዲፈፀምላቸው እየጠየቁ ያሉት በየመን አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ሊፈፀም ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም በማለት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358/ሀ/ መሰረት በማድረግ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በእኔ እምነት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ፍ/ቤቱ ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ያቀረበውን ክርክር በመቀበልና የአመልካቾችን ክርክርና ማስረጃ በመቀበል በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠት አለበት ወይም የለበትም? የሚለውን ጭብጥ በመመስረት የስር ፍ/ቤት የተጠሪን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻና የአመልካቾችን ክርክር በመስማትና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሰረት ጉዳዩን መመለስ ነበረበት፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍ/ቤት ወደ ይዘቱ ገብቶ ያላየውንና ውሣኔ ያልሰጠበትን ጭብጥ ማለትም በየመን አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ሊፈፀም ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የሰጠው ውሣኔ አመልካቾች በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈፀም ይገባል የሚሉበትን የተሟላ ክርክርና ማስረጃ የማቅረብ መብትና ተጠሪም በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈፀም አይገባውም የሚልበትን የተሟላ ክርክርና ማስረጃ የማቅረብ መብት የሚያጣብብ ነው፡፡ እንደዚሁም በዚህ ጭብጥ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ተከራካሪዎቹ ሊኖራቸው የነበረውን የይግባኝ መብት ያጣበበ ነው የሚል ሀሣብ አለኝ
5. ከዚህ አንጻር ከሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካቾች በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈፀምላቸው የጠየቁት የየመን ፍ/ቤቶች የሰጡት ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈፀም የሚችል ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ጭብጥ ላይ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሰረት መመለስ ነበረበት፡፡ ይህንን አለማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት በሰበር በመሻር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈፀም ይችላል ወይስ አይችልም? በሚለው ጭብጥ ላይ የአመልካቾችንና የተጠሪን የተሟላ ክርክርና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ ሰምቶ እንዲወሰን ሊመለስለት ይገባል፡፡ አብላጫው ድምጽ ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚው ችሎት መመለሱ አመልካቾችና ተጠሪ በስር ፍ/ቤት የተሟላ ክርክርና ማስረጃ የማቅረብ መብታቸውን የሚያሣጣና የይግባኝ መብታቸውንም የሚያጣብብ ነው የሚል ሀሣብ ያለኝ በመሆኑ ጉዳዩ መመለስ የሚገባው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ችሎት ሣይሆን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆን ይገባዋል በማለት ይህንን የመስማሚያ ሀሣብ ጽፌለሁ፡፡

6. ይህንን የመስማሚያ ሀሣብ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ሁለተኛው ምክንያት አብላጫው ድምጽ ጉዳዩን ወደ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የመለሰው አመልካቾች በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት በየመን አገር የተሰጠ ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358/ሀ/ እና /ሐ/ ድንጋጌዎች የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟላ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማጣራት ውሣኔ እንዲሰጥበት በማዘዙ ነው፡፡ በእኔ በኩል ይግባኝ ሰሚው ችሎት በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ከ/ሀ/ እስከ ከ/ሠ/ የተደነገጉትን ሁሉንም መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማጣራትና በማረጋገጥ ውሣኔ ሊሰጥበት ይገባል የሚል ሀሣብ አለኝ፡፡ በተለይም ተጠሪ አመልካቾች በየመን አገር በተሰጠ ፍርድ የፍርድ ባለመብት ሁነንበታል የሚሉት ጉዳይ በኢትዮጵያ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ታይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበትና በፍርድ ያለቀ ነው የሚል መቃወሚያና ክርክር እንዳቀረበ አብላጫው ድምጽ በውሣኔው ካሰፈረ በኋላ ይህን ጉዳይ በኢትዮጵያ ሸሪዓ ፍ/ቤት ውሣኔ ያገኘ ነው የሚለው መቃወሚያ ሊስተናገድ የሚችልበት ስርዓት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጠር 458 እንዳልተዘረጋ ውሣኔው በገጽ 17 በመጨረሻው ፖራግራፍ በመግለጽ የሰጠው ምክንያትና የሕግ አተረጓጎም አልተቀበልኩትም፡፡

7. ተጠሪ ጉዳዩ በኢትዮጵያ የሸሪያ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘና በፍርድ ያለቀ ነው በማለት ያቀረበው መከራከሪያ በየመን አገር የተሰጠው ፍርድ ይፈፀምልን በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን ጥያቄ ለመቃወምያ ሊሆን የሚችል መሰረታዊ መከራከሪያ ነው የሚል ሀሣብ አለኝ፡፡ በአገራችን በፍርድ በተቋጨ ጉዳይ ሌላ ክስ ማቅረብ እንደማይቻል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5/1/ ተደንግጓል፡፡ ይህም የአገሪቷ ፍ/ቤቶች በሕግ በተሰጣቸው የዳኝነት ስልጣን መሰረት በማድረግ አከራክረው የመጨረሻ ውሣኔ በሰጡት ጉዳይ የውጭ አገር ፍ/ቤቶት የሰጡት ውሣኔ አለና ይፈፀምልን የሚል ጥያቄ ቢቀርብ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ይህንን ጥያቄ የመቀበል የአገሪቱ ፍ/ቤቶች በፍርድ የሰጡት ጉዳይ ላይ የውጭ አገር ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ ተፈጻሚ እንዲሆን የሚፈቅዱበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ በእኔ እምነት ጥያቄው ከጅምሩ የአገሪቱን ፍርድ ቤቶች ብሄራዊ የዳኝነት ስልጣን የሚጋፋ ስለሆነ ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ነው የሚል ሀሣብ አለኝ፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ጉዳዩ በሸሪዓ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ነው የሚለውን ክርክር የቀረበ ቢሆንም ጉዳዩ በኢትዮጵያ የሸሪዓ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሰጥቶበታል ወይስ አልተሰጠበትም? ጉዳዩ በሸሪዓ ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ የተሰጠበት ከሆነ አመልካቾች በዚያው ጉዳይ በየመን አገር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ህጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች በመያዝ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማጣራትና በማረጋገጥ ውሣኔ እንዲሰጥበት የሰበር ችሎት መመሪያ /ትዕዛዝ/ ሊሰጥ ይገባዋል የሚል ሀሣብ አለኝ፡፡ ስለመሆኑም የሰበር ችሎት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 70047 ጥር 30 ቀን 2004ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሻርና ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን በደረሰበት መደምደሚያ የምስማማ ቢሆንም ከላይ በዝርዝር በገለጽኳቸው ነጥቦች ከአብላጫው ድምጽ የምለይ በመሆኑ ይህንን የመስማሚያ ሀሣብ አስፍሬአለሁ፡

የማይነበብ የአንድ ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 88867

ታህሳስ 28 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሰሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች:- ሪዬስ ኢንጂነሪንግ አክሲዮን ማህበር

ተጠሪ:- የአክሱም ኮንስትራክሽን ባለቤት አቶ ጌታሁን ሁሴን

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል::

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ አንድ የፍርድ ባለእዳ የሆነ ንብረት ከአንድ በላይ በሆኑ የፍርድ ባለገንዘቦች ለፍርድ አፈፃፀም በእያንዳንዳቸው በተናጠል እንዲከበር ተደርጉ በሚገኝበት ጊዜ አፈፃፀሙ በንብረቱ ላይ ሊቀጥል የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ባስከፈተው የአፈፃፀም መዝገብ መነሻነት ነው:: የጉዳዩ አጀማመርም አመልካች በተጠሪ ላይ የገንዘብ ክፍያ አስፈርደው የፍርድ ባለመብት ሲሆኑ አፈፃፀሙም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ 185082 በሆነው ቀርቦ እና አመልካችም ይዜንኑ ፍርድ ለማስፈፀም ሲባል የተለያዩ የፍርዱን ባለእዳ ንብረቶችን ያስከበረ ቢሆንም ሆኖም ግን እነኝህ ንብረቶች በሌላ የፍርድ ቤቱ መዛግብት ላይ በሌሎች ፍርድ ባለገንዘቦችም የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠባቸው በመሆኑ የአሁኑ አመልካች እግዱን አስነስተው ሲቀርቡ ወይም ሌላ የፍርድ ባለእዳ ንብረት አፈላልገው ሲቀርቡ አፈፃፀሙ ሊቀጥል ከሚችል በቀር በሌላ ጉዳይ የእግድ ትዕዛዝ በተሰጠባቸው ንብረቶች ላይ የይሽጡ ትዕዛዝ መስጠት አይቻልም በማለት የፍርድ ባለመብቱን ጥያቄ ባለመቀበል የአፈፃፀም መዝገብ ጉዳዩን ሲመራ በነበረው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በትዕዛዝ እንዲዘጋ ተደርጓል::

የአሁኑ አመልካችም በትዕዛዙ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተቀባይነት አላገኘም አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይዜንኑ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም አመልካች ያስከበረውን ንብረት በሌሎች መዛግብት ላይ ሌሎች የፍርድ ባለመብቶችም የእግድ ትዕዛዝ አሰጥተውበት ከሆነም ፍ/ቤቱ እነዚህን ፍ/ባለመብቶች አስቀርቦ በመመርመር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 403 ድንጋጌ ይዘት አኳያ በአፈፃፀም የተያዘውን ንብረት ለመከፋፈል የሚያበቃ ውሳኔ ካላቸው እንደየገንዘባችን መጠን ንብረቱ ተሸጦ እንድንከፋፈል መደረግ ሲገባ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይችልም በማለት ፍርዱ ሳይፈፀም የአፈፃፀም መዝገቡን መዝጋቱ በአግባቡ ባለመሆኑ የሥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ ተሽሮ አፈፃፀሙ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 403 ድንጋጌ ይዘት አኳያ እንዲፈፀም ይታዘዝልን የሚል ነው።

አቤቱታውም ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በዕሁፍ እና በቃልም በችሎት እንዲሰሙ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም በበኩላችን አመልካች በሌላ መዛግብት ላይ በሌሎች ፍርድ ባለመብቶች በንብረቱ ላይ የተሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ካላደረገ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይችልም ተብሎ የአፈፃፀም መዝገቡ በስር ፍ/ቤቶች መዘጋቱ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል።

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪ በ1993 ዓ/ም ወደ ብር 1,172,503.06 (አብዛኛው ገንዘብ በ10.5% እና የተወሰነው ቀሪ ገንዘብ ደግሞ በ9% ከሚታሰብ ወለድ ጋር) ለአመልካች ይክፈል ተብሎ ፍርድ የተሰጠበት መሆኑን፣ አመልካችም ይሄንኑ ፍርድ ለማስፈፀም ሲባል የፍርድ ባለእዳ የሆኑ የተለያዩ ንብረቶችን የዕግድ ትዕዛዝ ሲያሰጥባቸው የቆየ ቢሆንም እዳው እስከአሁንም ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ አለመጠናቀቁን፣ በመሆኑም የፍርድ ባለመብቱ በፍርድ ባለእዳ ባለቤት በወ/ሮ እፀገነት ታዬ ስም በካርታ ቁጥር 32435 ተመዝግቦ የሚገኘውንና የቤት ቁጥሩ 2089 የሆነውን መኖሪያ ቤት በአፈፃፀም ተሸጦ እዳው እንዲከፈለው ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን፣ ሆኖም ግን ይህ ንብረት ሌላ ባለገንዘብ በሆነው አንበሳ ኢንሹራንስም በተመሳሳይ ፍ/ቤት አፈፃፀም መ/ቁ 1251/92 በሆነው መከበሩንና እንዲሁም ይሄው መኖሪያ ቤት በዳሽን ባንክም በብድር ለተሰጠ እዳ በመያዣ ውል መያዙንም ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል። ይህ ችሎትም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መነሻ በማድረግ ጉዳዩን ከህጉ ጋር በማገናዘብ ተመልክቷል።

በመሰረቱ ፍርድ የተፈረደለት ሰው እንደፍርዱ እንዲፈፀምለት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት የአፈፃፀም ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚችል እና የአፈፃፀሙ ስነ-ስርዓትም የሚመራበት አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 378 እና የፍርድ አፈፃፀም ጉዳይን አስመልክቶ የተደነገጉ ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በዚሁ መሰረት በአንድ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ላይ ፍርዱ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁ የፍርድ ባለገንዘቦች ካሉም አፈፃፀሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 403 ድንጋጌ መሰረት ሊስተናገድ እንደሚችል ህጉ ያመላክታል። ይሄውም በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ተከብሮ የተያዘ ወይም በፍርድ ቤቱ ዘንድ ተቀማጭ የሆነ ሀብት ከመያዙ ወይም ከመቀመጡ በፊት ገንዘብ እንዲከፈላቸው በባለሀብቱ ላይ አስፈርደው እንደፍርዱ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁ የፍርድ ባለገንዘቦች ሲቀርቡ ፍ/ቤቱ በፍርዱ መሰረት ያለመፈፀሙን ካረገገጠ በኋላ ተገቢውን ኪሳራ እና ወጪ ቀንሶ የተያዘውን ሀብት በውሳኔው መሰረት እንዲከፋፈሉ ይደረጋል በሚል በተጠቃሹ ድንጋጌ ስር በግልፅ ተደንግጐ ይገኛል።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በተጠሪ ላይ የገንዘብ እዳ በ1993 ዓ.ም አስፈርደው እና ገንዘቡም ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኖሪያ ቤት በአፈፃፀም ተሸጦ እንዲከፈለው እየጠየቀ ያለ ሲሆን ሌላኛው የፍርድ ባለገንዘብ የሆነው አንበሳ ኢንሹራንስም ከዚህ የተለየ ነው በሚል ከግራ ቀኙ የቀረበ ክርክር የለም። ንብረቱም በፍ/ቤቱ ተከብሮ የተያዘ መሆኑ እስከተገለፀ እና እንዲሁም በድንጋጌው ስር የተመለከቱት ሌሎች መስፈርቶችም እስከተሟሉ ድረስ አመልካችን ጨምሮ የሁሉም የፍርድ ባለመብቶች የአፈፃፀም ጥያቄ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 403

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌ ይዘት አኳያ በንብረቱ ላይ ቀጥሎ ሊስተናገድ ይገባል እንጂ አመልካች ሌላ የፍ/ባለመብት በሌላ የፍ/ቤቱ አፈፃፀም መዝገብ ላይ ያሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ አስነስቶ ካልቀረበ በቀር አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይችልም መባሉ የስነ-ስርዓት ህጉን የተከተለ አካሄድ ሆኖ አላገኘንም፡፡ በሌላ በኩል በንብረቱ ላይ የመያዣ ውልን መነሻ በማድረግ ከሌሎች ፍርድ ባለገንዘቦቹ የተለየ ወይም የቀዳሚነት መብት አለን የሚሉ ወገኖችም ካሉ ጥያቄው ሲቀርብ እንደየአግባብነቱ ታይቶ ተገቢው ምላሽ የሚሰጥበት ይሆናል እንጂ አፈፃፀሙ በዚህ ምክንያት ከወዲሁ ሊቀጥል አይችልም መባሉም ተገቢ አይደለም፡፡

ስለሆነም አፈፃፀሙን ሲመራ የነበረው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችን ጨምሮ በተጠሪ ላይ የገንዘብ ክፍያ ፍርድ አሰጥተው እና ገንዘቡም እንዲከፈላቸው የአፈፃፀም ጥያቄ ያቀረቡ የፍርድ ባለገንዘቦችን አስቀርቦ ጥያቄያቸውን በመመርመር እና ጉዳዩንም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 403 ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ አኳያ አገናዝቦ በመመልከት አፈፃፀሙ ቀጥሎ እንደፍርዱ ሊፈፀም በሚቻልበት አኳኋን አፈፃፀሙን መምራት ሲገባ ጉዳዮቹ በየተናጠል በመምራት እና በስተመጨረሻም ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው የአፈፃፀም ጉዳይ ሊቀጥል አይችልም በማለት የአፈፃፀም መዝገቡን መዝጋቱ እና ይሄውም በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ታይቶ መታረም ሲገባ መዕናቱ ስለፍርድ አፈፃፀም የተመለከቱትን የፍ/ብሔር ስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 185082 በ12/2/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 128399 በ7/6/2005 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከዚህ በላይ በፍርዱ ክፍል እንደተጠቀሰው በኮ/መ/ቁ 185082 እንዲቋረጥ የተደረገው የአፈፃፀም ጉዳይ እንዲቀጥል በማድረግ እና ጉዳዩንም ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 403 እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አኳያ አገናዝቦ አፈፃፀሙ እንዲመራ በማድረግ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን የአፈፃፀም ውሳኔ እንዲሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 89088

ታህሳስ 17 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዩጵያ ንግድ ባንክ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡ -አቶ ሞላ እርቂ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለፍርድ አፈጻጸም የተያዘ ንብረት በሁለተኛ ጊዜ በሀራጅ ሊሸጥ የሚችልበትን ዋጋ መጠን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በኢሊባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባስከፈተው የአፈፃጸም መዝገብ ነው፡፡አመልካች ለተጠሪ ብድር ሰጥቶ በብድር ውሉ መሰረት ባለመከፈሉ ክስ መስርቶባቸው ተጠሪ የተበደሩትን ገንዘብና እና ወለድ ከወጪ እና ኪሳራ ጋር ለአመልካች እንዲከፍሉ ተብሎ ተወስኖ አፈፃጸሙ በዚህ ውሳኔ መሰረት ቀጥሎ የተጠሪ የተለያዩ ንብረቶች ተሸጠው ለእዳው ገቢ የሆኑ ቢሆንም ብር 209,000.00(ሁለት መቶ ዘጠኝ ሺህ ብር) በመቅረቱ ይህንኑ የገንዘብ መጠን ለማስፈጸም ንብረትነቱ የተጠሪ መሆኑ በተረጋገጠና በኢሊባቦር ዞን ጮራ ወረዳ ክልል ውስጥ የሚገኝ ባህርዛፍ አመልካች ለፍርዱ ማስፈፀሚያነት እንዲሸጥለት አመልክቶ ባህርዛፍ በብር 125,500.00(አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ብር) ተገምቶ ቀርቧል፡፡ከዚህም በኋላለ 1ኛ ጨረታ በቀረበው ግምት መሰረት በሐራጅ እንዲሸጥ አፈፃጸሙን የያዘው ፍርድ ቤት በማዘዝ በ1ኛ ጫረታ ሳይሸጥ ቀርቷል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ንብረቱ በሁለተኛ ጫረታ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ሰጥቶ ጫረታው ሳይከናወን ቀርቶ ይህንኑ መነሻ በማድረግ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሲሰጥ ባህርዛፉ በ2ኛ ጨረታ ባለሙያ ባቀረበው ግምት በላይ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች እንዲሸጥ በማለት ጠቅሷል፡፡በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪ ንብረት በሁለተኛ ጫረታ ሲሸጥ ከባለሙያ ግምት በላይ በተገኘ ከፍተኛ ዋጋ እንዲሸጥ ተብሎ መታዛዙ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 428 ድንጋጌን ያላገናዘበ እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ጫረታ የሚካሄድበትን አግባብ በተመለከተ ከፍተኛ ዋጋ ለአቀረበ የሚል ሁኖ እያለ ይኼው ትዕዛዝ በበላይ ፍርድ ቤት ባልተሻሻለበት በራሱ ችሎቱ መለወጡ ያላግባብ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምረናል፡፡እንደመረመረው እንዲሸጥ የታዘዘው የተጠሪ ንብረት በሁለተኛ ጫረታ የሚሸጥ ከሆነ ከግምት በላይ ከፍተኛ ዋጋ ነው መሸጥ ያለበት ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ለላባቸው እዳ ንብረታቸው የሆነው ባህርዛፍ እንዲሸጥ ትእዛዝ ተሰጥቶ በ1ኛው ጫረታ ገዥ ባለመገኘቱ በሁለተኛ ጫረታ እንዲሸጥ የታዘዘ መሆኑን፣በዚህ ጊዜ ንብረቱ ሲሸጥ ግን በ2ኛ ጫረታ ባለሙያ ባቀረበው ግምት በላይ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች ንብረቱ እንዲሸጥ ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የመጀመሪያ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዥ አለመቅረቡ ከተረጋገጠ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 428(1) እንደተመለከተው ድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡በመጀመሪያው ጫረታ ማስታወቂያ በተገለፀው የዋጋ ግምት መነሻ ተጫራች ካልቀረበ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 428(1) መሰረት ድጋሚ ማስታወቂያ በማውጣት በሁለተኛ ጨረታ እንደሚደረግ፣ንብረቱም የሚሸጠው በሁለተኛ ጨረታ ማስታወቂያ ጥሪ መሰረት ውድድር በማድረግ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራች እንደሆነ ተጠቃሹ ድንጋጌ ያሳያል፡፡በድንጋጌው *"--------ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርብ ተጫራች----------"* የሚለው ሐረግም የሚያስገነዝበው በመጀመሪያ ጫረታ ጊዜ በግምቱ መነሻ ተጫራች ያልቀረበ በመሆኑ የፍርድ ባለመብቱም በፍርድ ያገኘው ውሳኔ እንዲፈፀምለት፣ባለእዳውም ያለበትን ግዴታ እንዲወጣ ማድረግ ይቻል ዘንድ በሁለተኛ ጨረታ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ባለሙያ በገመተው ዋጋ መነሻ ሳይገደብና ከዚያም ባነሰ የዋጋ መነሻ ጫረታ ሊደረግ እንደሚችልና ንብረቱም ሊሸጥ የሚችለው ከተወዳዳሪዎች ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራቾች መሆኑን ነው፡፡ እንዲህም ሲሆን ይህ በውድድሩ ጊዜ የተገኘው ከፍተኛ የተባለው ዋጋም በመጀመሪያ ጫረታ ጊዜ ከተመለከተው የዋጋ መነሻ ዝቅ ሊል እንደሚችል መታወቅ አለበት እንጂ ፍርድ ቤት በሁለተኛ ጫረታ ጊዜም ዋጋው ከባለሙያው ግምት ሊያንስ አይገባም በማለት የሚገድበው አይደለም፡፡በሁለተኛ ጨረታ ባለሙያ ባቀረበው ግምት በላይ በተገኘ ከፍተና ዋጋ ላቀረበ ተጫራች እንዲሸጥ የግድ ማድረግ የንብረቱ ዋጋ የባለሙያውን ግምት ካልደረሰ ንብረቱ የሚሸጥበት ሁኔታ እንዳይኖር በማድረግ ባለገንዘቡ ገንዘቡን እንዳያገኝ፣ባለእዳውም ግዴታውን እንዳይወጣ የማድረግ ውጤትን የሚያስከተል በመሆኑ የፍርድ አፈፃጸም ስርዓት የሚቀበለው አካሄድ ነው ተብሎ አይታሰብም፡፡ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪ ንብረት በሁለተኛ ጨረታ ሲሸጥ ባለሙያ ባቀረበው ግምት በላይ በተገኘ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች እንዲሸጥ በማለት የሠጡት የአፈጻጸም ትዕዛዝ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 428(1) ድንጋጌ ያላስቀመጠው መስፈርት መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 06920 ሰኔ 25 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 153062 ጥር 14 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በሁለተኛ ጨረታ ጊዜ ለፍርድ አፈጻጸም የተያዘ ንብረት ሊሸጥ የሚገባው ባለሙያ ባቀረበው ግምት በላይ በተገኘ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች ሳይሆን ግምቱን ሳይጠብቅ ከተወዳዳሪዎች መካከል ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራች ነው ብለናል፡፡በዚህ መሰረት አፈጻጸሙን እንዲቀጥል ጉዳዩን ለኢሊባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 85764

መስከረም 21 ቀን 2006ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፉ አህመድ

አመልካቾች፡-1. አቶ ኃ/ሚካኤል ታደሰ የቀረበ የለም

2. ወ/ሮ ሸዋዬ አምደ ቀረቡ

3. አቶ ዮሴፍ ታደሰ ቀረቡ

4. ወ/ሪት አመቤት ታደሰ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ተስፉ ታደሰ የቀረበ የለም

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሸበደኖ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ የአፈፃፀም ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በፍርድ ባለመብትነት ቀርበው የፍርድ ባለዕዳው የአባታችንን ውርስ ሀብት እንዲያካፍል በተሰጠው ፍርድ መሰረት እንዲፈፅም ይወሰንልን በማለት ያቀረቡት የአፈፃፀም ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካች የፍርድ ባለዕዳ በመሆን ቀርቦ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተገቢ ነው የሚለውን አፈፃፀም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች የስር ፍርድ ቤት በሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ በሰበር ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡
2. አመልካች በ22/4/2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አፈፃፀም ክስ ያቀረበበትን ፍርድ የተሰጠው ሸበደኖ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ዋናው ፍርድ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድርስ ቀርቦ የፀና ነው፡፡ ይህንን ፍርድ ለማስፈፀም ክስ ስናቀርብ ጉዳዩ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሚታይ በመሆኑ ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በ1/8/2005 ዓ.ም ተጠሪዎች መልስ ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

3. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
4. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የአፈፃፀም ክስ ያቀረቡበት ፍርድ በሸበድኖ መጀመሪያ ፍርድ ቤት ውርሱ እንዲጣራ ተደርጎ የተወሰነና በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ታይቶ የፀና በመጨረሻም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44135 የካቲት 11 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የሸበድኖ መጀመሪያ ፍርድ ቤት ውሣኔና የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮ አመልካቾች የፍርድ ባለ መብት የሆኑበት ፍርድ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካቾች በሸበዲኖ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አፈፃፀም ክስ ያቀረቡት የሥር ፍርድ ቤትም አፈፃፀም ክሱን በመቀበልና በመመርመር 15/08/2004 ዓ.ም አፈፃፀም ትእዛዝ የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44135 የካቲት 11 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ መሠረት በማድረግ ነው፡፡
5. የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ የሚቀርበው ፍርዱን ለፈረደው ፍርድ ቤት እንደሆነና ፍርድ የማስፈፀም ስልጣን ያለው ፍርድን የፈረደው ወይም ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርድ እንዲያስፈጽም ውክልና የተሰጠው ፍርድ ቤት እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁ 378 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44135 የካቲት 11 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ የማስፈፀም ስልጣን ያላቸው የክልሉ ፍርድ ቤቶች እንጂ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አይደሉም፡፡ የአፈፃፀም ስልጣን መሠረቱ ፍርዱ መስጠት ወይም ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርድ ለማስፀም የሚያስችል ውክልና ማግኘት መሠረት ያደረገ እንጂ የፍርድ ባለእዳውን ወይም የፍርድ ባለመብቱ የሚኖሩበትን ክልል /የከተማ አስተዳደር/ መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡
6. ከዚህ አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤትም አፈፃፀም ክሱን በመቀበልና በመመርመር በ15/08/2004 ዓ.ም አፈፃፀም ትእዛዝ የሰጠውና በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ትእዛዙን በይግባኝ በማየት ያፀናው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁ 378 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ለአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2/ በተዛባ መንገድ በመተርጎም ጉዳዩን በሰበር ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 57927 መስከረም 30 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤትና የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን የአፈፃፀም ትዕዛዝ በሰበር አይቶ የመወሰን ሥልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡
3. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአምልካቾችን የሰበር አቤቱታ በመመርመር ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 81023

ግንቦት 05 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ገላና አልጅራ ጠበቃ አቶ ግርማ ሚደቅሳ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡ 1. አቶ ገዛኸኝ ፋይስ ጠበቃ አቶ ብርሃኑ ይማም ቀረቡ

2. አቶ ብርሃኑ ገመዳ

3. የለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ አስተዳደር

የመሬት አስተዳደርና አካባቢ ጥበቃ ጽ//ቤት } አልቀረቡም

አመልካች በሁለተኛ ተጠሪና በሶስተኛው ተጠሪ ላይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 81444 ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ሁለተኛና ሶስተኛ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር በፍታብሔር ስነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 11 ንዑስ አንቀፅ 5 መሰረት ከዚህ ከቀረበው ክርክር ጋር በማጣመር መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛ ተጠሪና በሶስተኛው ተጠሪ ላይ ያቀረብኩትን ክስ በመዝገብ ቁጥር 05753 በማየት ታህሳስ 13 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140154 አይቶ ሚያዝያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በዚህ መዝገብ ያቀረበውን ሰበር አቤቱታና አመልካች የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05762 የአመልካችን የሁለተኛውን ተጠሪና የሶስተኛውን ተጠሪ ክርክር ሰምቶ ጥር 8 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140153 ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት በሰበር መዝገብ ቁጥር 81444 ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል ለገዥው የሚያስገኘውን መብትና በገዥ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ሊያቀርባቸው የሚችለውን የመብት ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲታይ በመዝገብ ቁጥር 05753 አመልካች ከሳሽ አንደኛ ተጠሪና ሶስተኛ ተጠሪ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ እንደዚሁም በመዝገብ ቁጥር 05762

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ከሳሽ ሁለተኛ ተጠሪና ሶስተኛ ተጠሪ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል የክርክሩ መነሻ አመልካች ከላይ በተገለጹት መዛግብት በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ነው፡፡

1. አመልካች ለስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05762 በአንደኛ ተጠሪና በሶስተኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ አንደኛ ተጠሪ በስሙ የተመራውንና የካርታ ቁጥር L/x/L/D/132/00 የሆነውን በ140 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተሰራ ጅምር ቤት ሕዳር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በተደረገ የጅምር ቤት ሽያጭ ውል ብር 85,000 /ሰማኒያ አምስት ሺ ብር/ ሸጦልኛል አንደኛ ተጠሪ ጅምር ቤቱንና የቦታውን ካርታና ፕላን አስረክቦኛል፡፡ ቤቱን በስሜ ለማዛወር እንድችል ልዩ የውክልና ስልጣን ተሰጥቶኛል፡፡ እኔም የገዛሁትን ቤት የቦታውን ፕላን በማስቀየር ፎቅ ቤት ለመገንባት የሚያስችለኝ የስራ ፕላን ተሰጥቶኝ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር/ ወጭ በማድረግ የግንባታ ስራ በመስራት ግንባታውን በማጠናቀቅ ላይ እገኛለሁ ሆኖም አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ በሸያጭ ውል ለእኔ ያስተላለፈውን የጅምር ቤቱና የቦታው ካርታና ፕላን እንደጠፋበት ሀሰተኛ መግለጫ ለሁለተኛው ተከሳሽ /ሶስተኛ ተጠሪ/ በማቅረብ አዲስ ካርታና ፕላን ተሰጥቶታል አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ በሀሰት አጭበርብሮ ባገኘው ካርታና ፕላን መሰረት በውል ለእኔ የሸጠለኝንና ያስረከበኝን ጅምር ቤት እንድትሸጥ እንድትለውጥና ለሶስተኛ ወገን እንድታስተላልፍ የውክልና ስልጣን ለሌላ ሴት ወ/ሮ ትዕግስት ወርቁ በመስጠት ለእኔ የሰጠኝን ውክልና ስልጣን ሽሮታል፡፡ ስለሆነም ለእኔ በሸያጭ ውል ያስተላለፈውን ጅምር ቤት እንድትሸጥ እንደትለውጥና ለሶስተኛ ወገን እንድታስተላልፍ አንደኛ ተከሳሽ/አንደኛ ተጠሪ/ ለሌላ ሴት የሰጠው ልዩ የውክልና ስልጣን እኔ በቤቱ ላይ ያገኘሁትን መብት የሚጥስ በመሆኑ በፍርድ ፈራሽ ሆኖ እንዲሻርልኝ፡፡ አንደኛው ተከሳሽ/አንደኛ ተጠሪ/ በሸያጭ ውል ለእኔ ያስተላለፈውን የቦታውንና የቤቱን ካርታና ፕላን እንደጠፋበት ሀሰተኛ መግለጫ ለሁለተኛው ተከሳሽ በማቅረብ ያገኘው ካርታና ፕላን በማጭበርበር የተገኘ ካርታና ፕላን ስለሆነ እንዲሰረዝልኝ አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ የሸያጭ ውሉን የሚያፈርስ ተግባር የፈፀመ በመሆኑ በሸያጭ ውሉ የተቀመጠውን የመቀጫ ገንዘብ ብር 15,000 /አስራ አምስት ሺ/ ብር እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ሁለተኛው ተከሳሽ/ሁለተኛው ተጠሪ/ የቤቱን ስመ ሀብትና ካርታ በስሜ እንዲያዛውር ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡
2. አመልካች ለስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05753 /በሁለተኛ ተጠሪና በሶስተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስና የጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ ከላይ በዝርዝር ከተገለፀው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ ልዩነቱ አመልካች የካርታ ቁጥሩ L/x/L/D/1223/00 የሆነውን የሁለተኛ ተጠሪ ቤት ህዳር 12 ቀን 2001 ዓ.ም በብር 85,000 /ሰማንያ አምስት ሺ ብር/ የገዛ መሆኑንና ሁለተኛ ተጠሪ ጅምር ቤቱን የቦታውንና የቤቱን ካረታና ፕላን አስረክቦኝ ብር 250,000/ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ ብር/ በማውጣት ፎቅ ቤት ገንብቶ በማጠናቀቅ ላይ እያለ ሁለተኛው ተጠሪ የቦታውና የቤቱ ካረታና ፕላን የጠፋበት መሆኑን ሀሰተኛ መግለጫ ለሶስተኛው ተጠሪ አቅርቦ አዲስ ካርታና ፕላን ከወሰደ በኋላ ጅምር ቤቱን እንድትሸጥ እንድትለውጥና ለሶስተኛ ወገን እንደታስተላልፍ ለወ/ሮ ትዕግስት ወርቁ ልዩ የውክልና ስልጣን የሰጠ መሆኑ ነው፡፡ አመልካች ለሁለተኛ ተጠሪ ለትዕግስት ወርቁ የሰጠው ውክልና እንዲሻር በሀሰት መግለጫ የተሰጠው ካርታና ፕላን እንዲሰረዝና ሁለተኛ ተጠሪ 15,000/አስር አምስት ሺ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብር/መቀጫ ገንዘብ እንዲከፍልና ሶስተኛ ተጠሪ የቤቱን ሰመ ሀብት ካርታና ፕላን በስሙ እንዲያዛውር ፍርድ እንዲሰጥለት ጠይቋል፡፡

3. በሁለቱም መዛግብት ተጠሪዎች በተከሰሱበት መዝገብ በተከሳሽነት ቀርበው የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያዎችን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን የማየት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የለውም አንድ ሰው ለሌላው ሰው የሰጠው ውክልና እንዲሻር ጥያቄ ለፍርድ ቤት ሳይሆን ለሚመለከተው አካል መቅረብ ያለበት ነው የካርታ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ተቀብሎ ውሳኔ የመሰጠት የአስተዳደር አካላት እንጅ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የላቸውም የስም ይዛወርልኝ ጥያቄም ውሉን በተናጠል ለከሳሽ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ያፈረሰነው ስለሆነ የሕግ መሰረት የለውም የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡

4. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር ከመረመር በኋላ ከሳሽ ካርታና ፕላን እንዲሰረዝለት ያቀረበው ጥያቄ በአስተዳደር አካላት የሚወሰን እንጅ በፍርድ ቤት ታይቶ የሚወሰን አይደለም፡፡ ከሳሽ ልዩ የውክልና ስልጣን እንዲሻርለት ያቀረበውን ጥያቄ የመወሰን ስልጣን ያለው ውልን የሚመዘግበው አካል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ስልጣን አለው ቢባል እንኳን በመጨረሻ የጠየቀው ብር 15,000 /አስራ አምስት ሺ ብር/ ስለሆነ ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድቤት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ሳይሆን የወረዳ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት ሁለቱንም መዛግብት በመዝጋት አመልካችንና ተጠሪዎችን አስናብቷቸዋል፡፡

5. አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05762 ሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140153 የስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05753 የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140154 አቅርቧል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሁለቱ ይግባኝ መዛግብት አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታና የተጠሪዎችን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካችና ተጠሪዎች የኦሮሚያ ክልልና የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በመሆናቸውና አመልካች የጠየቀው ዳኝነት ብር 15,000 ብቻ እንዲከፈለው ባለመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት ስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው የውሣኔ ክፍል ስህተት ያለበት ነው ሆኖም በውጤቱ ደረጃ አመልካች ካርታ እንዲሰርዝለት እና ልዩ የውክልና ስልጣን እንዲሻርለት ያቀረበው ጥያቄ በሚመለከታቸው አስተዳደር ክፍሎች የሚወሰን እንጂ በዳኝነት የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም ያለው ውሣኔ ክፍል ትክክል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው በማለት በሁለቱም መዛግብት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የውሣኔ ምክንያት ብቻ በማሻሻል ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡

6. አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላል ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140154 የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም በሰበር መዝገብ ቁጥር 81023 ሀምሌ 26 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል እንዲሁም አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140153 የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም በሰበር መዝገብ ቁጥር 81444 ሀምሌ 10 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቀርቧል፡፡ አመልካች በሁለቱ መዛግብት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘት እኔ በውል የገዛሁትንና የተራከብኩት ጅምር ቤት ካርታና ፕላን እንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ለመሸጥ ለመለወጥ እንዲመቻቻው በማሰብ የቤቱና የቦታው ካርታና ፕላን እንደጠፋባቸው ሀሰተኛ መግለጫና ማስረጃ ለሶስተኛ ተጠሪ በማቅረብ የተሰጣቸው አዲስ ካርታና ፕላን የእኔን መብት የሚጎዳና በሀስትና በማጭበርበር የተሰጠ መሆኑ ተረጋግጦ በፍርድ እንዲሰረዝልኝ ያቀረብኩትን የዳኝነት ጥያቄ ፍርድ ቤቶች አከራክረው የመወሰን የዳኝነት ስልጣን አላቸው ስለዚህ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ በውል ለእኔ የሸጠልኝንና እኔ ከፍተኛ ገንዘብ ወጭ በማድረግ የገነባኃቸውን ቤቶች፣ በሀሰተኛ መግለጫና ሐሰተኛ ማስረጃ ተጠቅመው ያወጡትን አዲስ ካርታና ፕላን ጋር ወ/ሮ ትእግስት ወርቁ እንድትሸጥ እንድትለውጥና ለሶስተኛ ወገን ቤቶቹን እንድታስተላልፍ የሰጧት ልዩ የውክልና ስልጣን በንብረቴ የተሰጠና እኔ በቤቶቹ ላይ ያለኝን መብት የሚጎዳ ነው፡፡ የውክልና ስልጣኑ የውል ሰነድ ነው፡፡ ስለዚህ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረብኩት ጥያቄ የግራ ቀኞችንን ማስረጃ በመስማት ውሣኔ የሚሰጡት ፍርድ ቤቶች እንጂ የውልና ማስረጃ የመዝገባ ስልጣን ያለው አካል አይደለም፡፡ ስለዚህ ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ ለመወሰን ስልጣን እንደሌላቸው በመግለጽ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው በማለት አመልክቷል፡፡

7. አንደኛ ተጠሪ ሕዳር 7 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስና ሁለተኛው ተጠሪ ሕዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ተመሣሣይ ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡ የውክልና ስልጣን አንድ ወገን ወካይነት የማቋቋምና ሊሻር የሚችል በመሆኑ የውክልና ሰነዱን በመመርመር ፍርድ ቤቶች ሊሰርዙትና ሊሽሩት ይችላሉ በማለት አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያደረግነው ጅምር ቤት ሽያጭ ውል በሕጉ የተገለፀውን ፎርም እንደማያሟላ ገልፀን ውሉን ሰርዘነዋል አመልካች የወሰደውን ካርታና ፕላን እንዲመልስልን ስንጠይቀው ጠፍቶብኛል በማለት እንቢተኛ በመሆኑ ለሚመለከተው የፖሊስ ክፍል አመልክተንና በበከልቻ ኦሮሚያ ጋዜጣ ጥሪ በማስድረግ የቤት ካርታና ፕላን ሶስተኛው ተጠሪ ተሰጥቶናል ይህም በሀሰት የመጣ ካርታና ፕላን ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ነው ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲያፀናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሶስተኛ ተጠሪ በበኩሉ በሁለቱ የሰበር መዛግብት አመልካች ላቀረበው የሰበር አቤቱታ ጥቅምት 21 ቀን 2005 ዓ.ም እና ሕዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ሶስተኛው ተጠሪ አንደኛውን ተጠሪ ሁለተኛው ተጠሪና የቤትና የቦታ ካርታና ፕላን እንደጠፋባቸው በተናጠል በማመልከታቸው ጉዳዩ በፖሊስ በኩል የተሰጠውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ በጋዜጣ ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ ጥሪ አድርጌ ተቃዋሚ የልቀረበ በመሆኑ ለአንደኛና ለሁለተኛ ተጠሪዎች አዲስ የቤት የቦታ ካርታ ፕላን ሰጥቻለሁ፡፡ ይህንን የፈፀምኩት በሕጉ የተደነገገውን ሥርዓት በመከተል የሰበር አቤቱታውን ውድቅ ሆኖ በነፃ እንድሰናበት ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርቧል አመልካች ተጠሪዎች ለሰጡት መልስ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

8. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካች ተጠሪዎች በዚህ መዝገብና ከዚህ መዝገብ ጋር በተጣመረው በሰበር መዝገብ ቁጥር 81444 ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረባቸው የዳኝነት ጥያቄዎች በፍርድ የማያልቁ በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ውሣኔ የሚሰጥባቸው ናቸው በማለት ውድቅ ማድረጋቸውን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
9. ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ ለማቅረብ መነሻ የሆነውን መሠረታዊ ጉዳይና የክርክሩ ጭብጥ በፍተሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተደነገገው መሠረት በመለየትና በመመስረት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት በመመርመርና በመመዘን ውሣኔ ለመስጠት የዳኝነት ኃላፊነታቸውን የተወጡ መሆኑን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ጉዳይ አከራካሪ መሠረታዊ ጭብጥ አንደኛው ወገን የጠየቀውና ሌላኛው ወገን የካደው መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246 የሚደነግግ ሲሆን የአንድ ክርክር ጭብጥ የሚመሠረተው ከሣሽ በክስ በማመልከቻው የገለፀው እና ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ተከሣሽ ክሱን ለመከላከል ያቀረበውን የጽሑፍ መልስና ክሱን ለመከላከያ ያቀረበው የጽሑፍ ማስረጃና ተከራካሪዎች ለፍርድ ቤት የቃል ምርመራ የገለፁትን ፍሬ ጉዳይ መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍተሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ይደነግጋል፡፡
10. አመልካች በተጠሪዎች ላይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ መሠረታዊ መነሻ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ሕዳር 12 ቀን 2001 ዓ.ም ያደረገው የካርታ ቁጥሩ L/X/L/D/131/00 የሆነውን ጅምር ቤት በብር 85,000 /ሰማንያ አምስት ሺ ብር/ ለመግዛት የተዋዋለው ውልና ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር ሕዳር 19 ቀን 2001 ዓ.ም የካርታ ቁጥር L/X/L/D/1223/00 የሆነ ጅምር ቤት ለመግዛት የተዋዋለው ውል ነው አመልካች በውል የገባውን ግዴታ በመፈፀምና የገባቸውን የቤት ዋጋ በመክፈል የቤቶቹን ካርታዎች እና ጅምር ቤቶቹን ከአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ተረክቦ የጅምር ቤቶቹን ፕላን በማስቀየር ከፍተኛ ወጭ በማውጣት ፎቅ ቤቶችን በመገንባት በማጠናቀቅ ሒደት ላይ እያለ ተጠሪዎች በውል የገቡትን ግዴታ በመጣስና በውል ያገኘውን መብት ዋጋ ለማሣጣት የተለያዩ ተግባራትን ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በሽያጭ ውልና በፍተሐብሔር ሕግ ቁጥር 2879/1/ መሠረት ለእኔ ያስተላለፉትን ካርታ በሐሰት ጠፋቶብናል የሚል ማመልከቻና ማስረጃ ለሶስተኛው ተጠሪ በማቅረብ አዲስ ካርታ መውሰዳቸው በዚህ አዲስ ካርታ መሠረት እኔ የገዛሁትን እና ወጭ አውጥቼ የገነባኋውን ቤት ትእግስት ወርቁ እንድትሸጥ እንድትለወጥ ወይም ለሶስተኛ ወገን እንድታስተላልፍ ልዩ የውክልና ስልጣን የመስጠት ተግባር ፈጽመዋል እነዚህ ተግባራት በፍርድ ተመርምረው ይሰረዙልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስና ክርክር አቅርቧል፡፡
11. ተጠሪዎች በበኩላቸው ከአመልካች ጋር ውል ከተዋዋሉና የቤቱን ዋጋ ከተቀበሉ በኃላ ውሉ ጐድቶናል በሚል ሣጣብ የተቀበሉትን ገንዘብ የመለሱ መሆኑንና ውሉም የፈረሰ መሆኑን ገለፀው እንደተከራከሩ አመልካች የወሰደውን ካርታና ፕላን ጠፋቶብኛል ስላላቸው አዲስ ካርታ ፕላን የወጣ መሆኑ ቤቱ ንብረታቸው መሆኑን ገልፀው እንደተከራከሩ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በውሣኔው ካሠፈራቸው መሠረተ ሃሣቦች ተረድተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

12. ከላይ የገለጽናቸው አመልካችና አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር መሠረታዊ ጭብጦች

/ሀ/ አንደኛ ተጠሪ የካርታ ቁጥሩ L/X/L/D/131/00 የሆነውን ቤት ለአመልካች ለመሸጥ ሕዳር 12 ቀን 2001 ዓ.ም ያደረገውን የጅምር የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ ተጠሪ የተቀበለውን የቤቱን ዋጋ ለአመልካች መልሷል ወይስ አልመለሰም፣

/ለ/ ሁለተኛ ተጠሪ የካርታ ቁጥር L/X/L/D/1223/00 የሆነ ጅምር ቤት ለአመልካች ለመሸጥ ሕዳር 12 ቀን 2001 ያደረገው ውል ፈርሶ ሁለተኛ ተጠሪ የተቀበለውን የቤቱን ዋጋ ለአመልካቾች መልሷል ወይስ አልመለሰም?

/ሐ/ አመልካች ከአንደኛ ተጠሪና በሁለተኛ ተጠሪ ጋር በተናጠል ያደረገው የጅምር ቤት ግዥ ውል በሕጉ አግባብ አልፈረሰም ቢባል አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች የሽያጭ ውሉን ሲዋዋሉ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2879/1/ መሠረት ለአመልካች አሣልፈው የሱጡት የቤትና የይዞታ ካርታና ፕላን እንደጠፋባቸው ሀሰተኛ መግለጫ በማቅረብ አዲስ ካርታና ፕላን ከሶስተኛው ተጠሪ መወሰዳቸው ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም?

/መ/ ሶስተኛው ተጠሪ ለተጠሪዎች አዲስ የቤትና የቦታ ካርታና ፕላን ሲሰጥ የቀድሞው ካርታና ፕላን ተጠሪዎች ጠፍቶብናል በማለት ባቀረቡት ማመልከቻና ማስረጃ መሠረት መሠረዙ በሶስተኛ ወገን /አመልካች/ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለማስወገድ ተጠሪዎች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1197 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በቂ ዋስትና እንዲሰጡ አድርጓል ወይስ አላደረገም?

/ሠ/ አመልካች ከአንደኛ ተጠሪና ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር በተናጠል ያደረገው የቤት ሽያጭ ውል በሕጉ አግባብ አይፈረስም ከተባሉ ተጠሪዎች በውል ለአመልካች የሸጡትን ቤት ወ/ሮ ትእግስት ወርቁ እንድትሸጥ እንድትለውጥ በማናቸውም ወገን ለሶስተኛ ወገን እንድታስተላልፍ ልዩ የውክልና ስልጣን መስጠት ይችላሉ ወይስ አይችሉም? አይችሉም የሚባል ከሆነ ውጤቱ ምንድ ነው?

/ረ/ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ብር 150,000 / አንድ መቶ ሃምሣ ሺ ብር/ ከአንደኛ ተጠሪ በገዛው ጅምር ቤት 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሣ ሺ ብር/ ከሁለተኛው ተጠሪ በገዛው ጅምር ቤት ላይ ወጭ አውጥቶና የቤቱን ፕላን ወደ ፎቅ አስለውጦ የግንባታ ሥራ ሠርቷል? ወይስ አልሰራም? ሠርቷል የሚባል ቢሆን ውጤቱ ምን ይሆናል?

/ሰ/ ሶስተኛ ተጠሪ ለአንደኛ ተጠሪና ለሁለተኛ ተጠሪ የሰጠውን አዲስ ካርታና ፕላን በመሰረዝ የቤቱቹን ስመሃብት ወደ አመልካች እንዲዛወር ማድረግ ይገባዋል ወይስ አይገባውም? የሚሉት ጭብጦች ላይ በግራ ቀኙ የቀረቡ ማስረጃዎችን በመስማት በመመርመርና በመመዘን ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በፍርድ መወሰን የሚጠይቅ ነው። እነዚህን ከላይ የገለጽናቸውን ተያያዥነት ያላቸው ጭብጦች በፍርድ የሚያልቁ እንጂ የአስተዳደር ክፍሎች ግራ ቀኙን በማከራከርና ማስረጃ በመስማት በአስተዳደራዊ ውሣኔ የሚጨርሷቸው ጉዳዮች አይደሉም። በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጣመሩት የሰበር መዝገቦች የቀረበውን ጉዳይ በዳኝነት እንደማያልቁ በመግለጽ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05753 እና በመዝገብ ቁጥር 05762 የሰጣቸው ውሣኔዎች ተሽሯል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140154 እና በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 140153 የሰጣቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡
3. የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገበ ቁጥር 05753 እና የመዝገብ ቁጥር 05762 በማንቀሣቀስ ከላይ በተራ ቁጥር 12 የተገለፁትን ጭብጦች በመመስረትና ማስረጃ በመስጠት ሌሎች ተያያዥነት ያላቸወን ጉዳዩች በማጣራት በጉዳዩ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁ 341/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 80301

ሚያዝያ 24 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አንተነህ ሲሳይ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ - ነገረ ፈጅ አሸናፊ ስዩም ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17701 ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የዲስፕሊን ጥፋት የተፈፀመ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ በይግባኝ የታየው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው፡፡

1. ተጠሪ አመልካች ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የፈፀመ መሆኑ በቢሮው የዲስፕሊን ኮሚቴ የተረጋገጠ መሆኑን ገልፆ ከሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ከስራ የተሰናበተ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ ፅፏል፡፡ አመልካች በቢሮው የዲስፒሊን ኮሚቴና በቢሮ ኃላፊው የተሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካች ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ፈፅሟል ያለው አያት አክሲዮን ማህበር ከአዲስ አበባ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን ጋር የሊዝ ውል አፈፃፀም በተመለከተ አለመግባባት ተፈጥሯል፡፡ ሁለቱ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ለመጨረስ ከተስማሙ በኋላ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣንን የሚወክል የህግ ባለሙያ መወከል አስፈላጊ በመሆኑ አመልካች ውክልና ተሰጥቶታል፡፡ አመልካች ይህንን የስራ ግዴታውን በመደበኛ የመንግስት የስራ ሰዓት ሰርቷል፡፡ ለግልግል ዳኛ አበል እንዲከፍል ትዕዛዝ ሲሰጡ ከሌሎች የግልግል ዳኞች ጋር አብረው መወሰናቸው የመንግስት ሰራተኞችን ስነ ምግባር የጣሰ ነው፡፡ የግልግል ዳኛ በመሆናቸው የተከፈላቸውን አበል ለፍትህ ቢሮ ተመላሽ እንዲያደርጉ በቢሮው ኃላፊው ሲጠየቁ እንቢተኛ በመሆን ገንዘቡን ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸው ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት ነው በማለት ከስራ ያሰናበተው መሆኑን በመግለፅ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተከራክሯል፡፡ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አመልካች የፈፀመው የዲስፒሊን ጥፋት የሌለ መሆኑን በመዘርዘር የዲሲፕሊን ኮሚቴና የቢሮው ኃላፊ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች ያልተከፈለው ደመወዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከፍሎት ወደ ሥራው እንዲመለስ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠሪን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ግ/ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

2. ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የከተማው የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች የግልግል ዳኛ ሆኖ ለሰራበት አበል መቀበሉና አበሉን ለፍትህ ቢሮ እንዲመልስ ሲጠየቅ እንቢተኛ መሆኑ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ነው፡፡ አመልካች የበላይ ኃላፊውን ትዕዛዝ አላከበረም በማለት የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የዲስፒሊን ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡
3. አመልካች ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የግልግል ዳኛ ሆኖ እንዲሰየም ደብዳቤ ፅፏል፡፡ የግልግል ጉባኤው በፍ/ስ/ስ/ሕ/ግ/ቁጥር 318(5) በተደነገገው መሰረት የአበል ክፍያ ወስኗል፡፡ የግልግል ዳኛ ሆኜ ተሰይሜ ለሰራሁበት የተከፈለኝን አበል ለቢሮው እንዳስገባ የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ትዕዛዝ ሰጠኝ አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ ገቢ የማደርግበት ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ግዴታ የለብኝም፡፡ ስለዚህ አበል ለመመለስ ፈቃደኛ አይደለሁም በማለት የዲስፒሊን ጥፋት እንደፈፀምኩ የከተማው አስተዳደር የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡
4. ተጠሪ መስከረም 28 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ እያለ አበል መቀበል፣ አበልም ከተቀበለ በኋላ ወክሎ የላከው መስሪያ ቤት ለማስረከብ ፈቃደኛ አይደለም ይህም ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት በመሆኑ የከተማው አስተዳደር የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡
5. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት ፈፅሟል በማለት የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
6. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካችን የመደብኩት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን ከአያት አክሲዮን ማህበር ጋር በሊዝ ውል አፈፃፀም ጋር ባለው አለመግባባት፣ አመልካች የሙያ ምክርና ድጋፍ ለመሬት አስተዳደር ባለስልጣኑ እንዲሰጥ ነው በማለት ይከራከራል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ተጠሪ በፅሁፍ የገለፀልኝ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣንና የአያት አክሲዮን ማህበር አለመግባባት በግልግል አይቶ ውሳኔ የሚሰጠው የግልግል ጉባኤ አባልና የግልግል ዳኛ ሆኜ እንድሰራ ነው በማለት ይከራከራል፡፡ አንድ ጉዳይ በፍርድ ቤት ወይም በግልግል ጉባኤ በሚታይበት ወቅት ለአንደኛው ወገን የሕግ ምክርና ድጋፍ እንዲያደርግ የተመደበ ባለሙያ ያለበት ሙያዊ ኃላፊነትና ሊከተለው የሚገባው የስነ ምግባር ደንብ በሁለቱ ወገኖች መካከል የተነሳውን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት አይቶ ውሳኔ እንድሰጥ ከተመደበ ባለሙያ ካለበት ኃላፊነትና ሊከተለው ከሚገባው የስነ ምግባር ደንብ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ በመሆኑም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ተጠሪ አመልካችን የመደበው ለመሬት አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን የሕግ ድጋፍና ምክር አገልግሎት እንዲሰጥ ነው? ወይስ የግልግል ጉባኤ አባል ሆኖ የሁለቱን ተከራከሪ ወገኖች ክርክርና ማስረጃ ለመስማት ውሳኔ እንዲሰጥ የሚለው ነጥብ መለየት አለበት፡፡

7. ተጠሪ ለመሬት አስተዳደርና ግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን መጋቢት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤና ተጠሪ ሚያዝያ 26 ቀን 2002 ዓ.ም ለአያት አክሲዮን ማህበር በፃፈው ደብዳቤ፣ አመልካች የሁለቱን ጉዳይ በግልግል እንዲያይ በግልግል ዳኝነት የተሰየመ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የመሬት አስተዳደርና የግንባታ ፈቃድ ባለስልጣንና ለአያት አክሲዮን ማህበር መካከል የሊዝ ውል በተመለከተ የተፈጠረውን አለመግባባት በግልግል የሚያው የግልግል ጉባኤ አባል ሆኖ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ተጠሪ በፅሁፍ መድቦታል፡፡ የግልግል ዳኛ ሆኖ የተሰየመ ባለሙያ (የግልግል ዳኛ) ሆኖ የተሰየመበትን ስራ በሚሰራበት ጊዜ ሊከተለው የሚገባው የሙያ ስነ ምግባር ዳኛ የሚከተለውን ሥነ ምግባር እንደሆነና ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 351 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

አንድን ጉዳይ በግልግል አይቶ እንዲወሰን የተቋቋመው የግልግል ጉባኤ የግልግል ዳኛ በጉዳዩ ገለልተኛና ነፃ ሆኖ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በአግባቡ ሰምቶ የመወሰን ግዴታ እንዳለበትና ይህ በተጓደለ ጊዜ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ በይግባኝ ሊታረም እንደሚችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 351 ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ፡፡ በተለይም የአንቀጽ 351 ንዑስ አንቀጽ (2)(መ) የግልግል ወይም የሽምግልና ዳኝነት አባል የሆነ ሰው በስራው አፈፃፀም ላይ በዳኛ ሊፈፀም የማይገባውን የአድሏዊነት እና የመጥፎ ባሕሪይ ፀባይ ማሳየት እንደሌለበት የሚደነግግ ይዘት ያለው ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች የግልግል ዳኛ ሆኖ ከተሰየመ በኋላ የግልግል ጉባኤ አባልነቱ ግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ የመስማት የመመዘንና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁጥር 317 ድንጋጌዎች መሰረት ከማድረግ ክርክሩን የመምራትና የቀረበለትን ክርክርና ማስረጃ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ የመሰለውን ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

የግልግል ጉባኤው ከሚወስናቸው ውሳኔዎችና ከገላጋይ ዳኞቹ ሊከፈል የሚገባውን የአበል መጠን እንደሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 318 ንዑስ አንቀጽ 5 በግልፅ ተመልክቷል፡፡

አመልካች የግልግል ዳኛ ሆኖ ሲሰራ አንድ ዳኛ ማሟላት የሚገባውን የሙያ ስነ ምግባር ደንብ ማሟላት ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ የግልግል ዳኛ ሆኖ ተለይቶ የግራ ቀኙን ክርክር ማስረጃ መስማትና ውሳኔ መስጠት አመልካች ከተቀጠረበት መደበኛ ሥራ/ የህግ ምክርና ድጋፍ/ መስጠት በእጅጉ የተለየ ከባድ ኃላፊነት ነው፡፡ ከዚህ በላይ የግልግል ዳኛ ሆኖ የተሰየመ ሰው በግልግል ዳኝነቱ የተጣለበትን በአግባቡ ካልተወጣ ራሱን የቻለ የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት መሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 399(1) ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አመልካች የግልግል ዳኛ ሆኖ የተሰየመበት ጉዳይ በውሳኔ እስኪጠናቀቅ ድረስ ጉዳዩን ተከራካሪ ወገኖችን በእኩልነት የማየት ነፃና ገለልተኛ ሆኖ የመስማት የመመርመርና ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነቱን ያልተወጣ ስለመሆኑ ተጠሪ በክርክሩ አልገለፀም፡፡ ተጠሪ አመልካች የግልግል ዳኛ የሆነው የቢሮው ወኪል ሆኖ ነው በማለት ያቀረበው ክርክርም የህግ መሰረት የለውም፡፡ አመልካች በክርክሩ የግልግል ዳኛ እንዲሆን የተመረጠውና የተሰየመው በተጠሪ ፈቃድና ሥምምነት ነው፡፡ አመልካችና የግልግል ዳኛ ሆኖ ተሰይሞ ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግልግል ዳኝነት ማየት ከጀመረ በኋላ ተጠሪን እያማከረና በግልግል ዳኝነት አባልነቱ የሚሰጠውን ብይንም ሆነ ውሳኔ በተጠሪ እያፀደቀና እያስፈቀደ ሊሰራ አይችልም፡፡ አመልካች እንደማንኛውም ዳኛ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ጉዳዩን ማየትና የመወሰን ኃላፊነት አለበት፡፡

ከዚህ አንፃር ካየነው አመልካች በግልግል ዳኝነት ተሰይሞ የሰጠውን ብይን (ተከራከሪዎች የግልግል ጉባኤ ወጭና አበል እንዲሸፍኑ) የግልግል ጉባኤው ሲወስን፣ አመልካች መስማማቱን እንደ ድስፒሊን ጥፋት ማቅረቡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁጥር 351 ንዑስ አንቀጽ 2(መ) በአመልካች ላይ ከተጣለበት የዳኛ ሥነ ምግባር የመከተልና ገለልተኛ ሆኖ ብይንና ውሳኔ የመስጠት ግዴታን የሚፃረር ነው፡፡ የአበል ክፍያን በተመለከተ የግልግል ጉባኤው እንደ አንድ ፍርድ ሰጭ ተቋም፣ ተከራከሪዎች ካልተስማማቸው በይግባኝ ሊያስለውጡት የሚችሉበት ሥርዓት በተዘረጋበት ሁኔታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ/ቁጥር 318 ንዑስ አንቀጽ 2(5) የወሰነው እንጅ አመልካች በግሉ ከአያት አክስዮን ማህበር የተቀበለው ገንዘብ አይደለም፡፡ አበሉ ለአመልካች የተከፈለው አመልካች በተጠሪ ከተቀጠረበት የሕግ ምክርና ድጋፍ የመስጠት ስራ የተለየ ኃላፊነትና ሥልጣን ባለው የግልግል ጉባኤ የግልግል ዳኛ ሆኖ ለሰራው ስራና ለሰጠው ለአገልግሎት ነው፡፡

ስለዚህ አመልካች ለአንድ ልዩ ጉዳይ የግልግል ዳኛ ሆኖ ለሰጠው አገልግሎት እንደማንኛውም የግልግል ጉባኤ አባል የተከፈለው የአበል ክፍያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 6/2000 አንቀጽ 31 የሚጥስ የሥነ ምግባር ጥፋት ተደርጎ ሊያዝ የሚችል አይደለም፡፡

ተጠሪ አመልካች ሰራተኛው በመሆኑና የግልግል ዳኛ ሆኖ አመልካች በጉዳዩ የተሰየመው በእሱ ፈቃድና ስምምነት መሆኑን መሰረት በማድረግ የአበል ክፍያውን አመልካች ገቢ ሊያደርግ ይገባዋል በማለት የሚያቀርበው የሕግ መሰረት የለውም፡፡ ስለዚህ አመልካች በግልግል ዳኛ ሆኖ ለሰጠው ግልጋሎት እንደ ማንኛውም የግልግል ጉባኤ አባል የተከፈለውን አበል ለተጠሪ ገቢ አለማድረጉን ከባድ የስነ ምግባር ጥፋት ነው በማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሠጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች የግልግል ዳኛ ሆኖ ሲሰራ የፈፀመው ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት የሌለ በመሆኑ ተጠሪ የአመልካችን ውዝፍ ደመወዝ በሕጉ መሰረት ከፍሎ ወደ ስራ ሊመልሰው ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 88060

መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ አ/ማህበር ነ-ፈጅ አቶ አሰፋ ዓለሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ምስጋናው ጥሩነህ ጠበቃ አቶ ውቤ አለነ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት የለውም በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ዳኝነት አግባብነት በክርክር ሂደት ከተረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳዮችና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም የአሁን ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በሚል ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ወሰደ የሚባለው ከኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ መሆኑንና በዚህ ገንዘብ ምክንያት ክስ በቀረበበት ጊዜ ደግሞ የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ በሽያጭ ወደ አሁኑ አመልካች የተላለፉ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው በመንግሥት እጅ የነበረ የልማት ድርጅት ከመሸጡ በፊት በሦስተኛ ወገኖች ላይ አለኝ የሚለውን ገንዘብ የልማት ድርጅቱ በሽያጭ ከተላለፈ በኋላ የመሰብሰብ መብት ያለው ማን ነው? የሚለው ነው፡፡

ለዚሁ አከራካሪ ነጥብ አግባብነት ባለው የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ባለአደራ ቦርድን ለመቋቋምና ሥልጣንና ተግባሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 208/92 አንቀጽ 5 እና 6 ላይ "የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታነት፣ ወደ አክሲዮና ማህበር በሚለወጥበት ወይም ወደ ቀድሞ ባለሀብቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት የማይተላለፉ ተሰብሣቢ ሂሣቦችን ለመሰብሰብ፤ ዕዳዎችን ለመረከብና የፍርድ ቤት ጉዳዮችን ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

በዚህም ጉዳይ የመንግሥት የልማት ድርጅት የነበረው የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ በሽያጭ ወደ አሁን አመልካች በመተላለፉ ምክንያት የተሸጠው የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ ከመሸጡ በፊት የነበረው ተሰብሣቢ ሂሣብና የነበረበት ዕዳ

ወደ ገዥው የማይተላለፍ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ከላይ በተጠቀሰው ሕግ መሠረት ተሰብሣቢ ሂሣቡንም ሆነ ዕዳውን በሚመለከት ለመሰብሰብም ለመረከብም ኃላፊነት እና ግዴታ የተጣለበት ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እንደሆነ መደንገጉ እየታወቀ የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካን በሽያጭ ወደ አሁን አመልካች እንዲተላለፍ በተደረገበት የሽያጭ ውል አንቀጽ 4.5 ላይ " ገዥው የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር የሸጠውን የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካን ቋሚ ንብረትንና ዕዳን ሁሉ የመረከብ ግዴታ እንዳለበት ስለመደንገጉ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም።

ይህም መሆኑ ከተረጋገጠ በአዋጅ ቁጥር 208/92 አንቀጽ 5 እና 6 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የተሸጠው የመንግሥት የልማት ድርጅት ከመሸጡ በፊት የሚሰበስባቸው ተሰብሣቢ ሂሣቦች እና ዕዳዎች በሽያጭ ውል መሠረት ወደ ገዥው የማይተላለፉ ሆኖ በተመለከተ ጊዜ ብቻ ነው። በዚህ በተያዘው የሽያጭ ውል ላይ የተሸጠው ድርጅት የነበረው ዕዳ ሁሉ ወደ ገዥው እንደሚተላለፍ በግልጽ እስከተመለከተ ድረስ ዕዳውን ተሸካሚ ከሆነ በሽያጭ ውል ከተመለከተው የድርጅቱ ቋሚ ንብረት ባሻገር ተሰብሣቢ የሂሣብ ሰነዶችንም የመሰብሰብ መብትና ሥልጣን ብቻ ተነጥሎ ለባለአደራ ቦርድ ተሰጥቷል ወደ ሚል መደምደሚያ ሊያደርስ የሚቻል አይደለም። ይህ የሽያጭ ውል ከአዋጅ ዓብይ ዓላማ አንፃር ለሕግ ተፃራሪ ነው እስከልተባለ ድረስ የባለ አደራ ቦርድ ሥልጣንና ተግባር ወደ ገዥው ሊተላለፉ በማይችሉ የተሸጠው ድርጅት ውጤትና ግዴታ ላይ የተወሰነ ነው።

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግ ይዘቱን ግብር ዓላማውን ከሽያጭ ውሉ ይዘት ጋር በማገናዘብ ተመልክተው የሰጡት ትርጉም እንዳልሆነ ተገንዝበናል።

በመሆኑም የአሁን አመልካች ክስ የቀረበበት ጉዳይ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ እና ከሽያጭ ውሉ አንፃር ተገናዝቦ ከታዩ ክሱን በአሁኑ ተጠሪ ላይ ለማቅረብ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት አለው ከሚባል በቀር የተለዩ ትርጉም የሚያሰጥ ሆኖ አላገኘነውም።

ከዚህም የትርጉም መስመር ባሻገር የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ግዴታ በትክክል እና ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን ተመልክቶ ሕግን መሠረት ያደረገ ፍርድን መስጠት እንዲቻል ከተዘረጋው የክርክር አመራር ሥርዓት አንፃርም ይታይ ቢባል ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲመች የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.40/2/ በተመለከተው መሠረት ማድረግም እየተቻለ ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ ብቻ በመገደብ የአሁን አመልካች በጉዳዩ ላይ ክስ የማቅረብ መብት የለውም በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1/ የአሁን አመልካች በጉዳዩ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የለውም በሚል ተወስኖ የበላይ የሆነው በአማራ ብ/ክ/መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ጉዳዩን ተመልክቶ በመ/ቁ. 468/01 ታህሣሥ 10 ቀን 2005 ዓ.ም ይህንኑ ውሣኔ በማጽናት የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ተሽሯል፡፡

2/በጉዳዩ የአሁኑን አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተነሣው ክርክር የሚያመለክት በመሆኑና አስፈላጊም ሆኖ በተገኘ ጊዜ ባለጥቅሙ ነው የተባለውንም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር የሥነ ሥርዓት ሕጉ የሚፈቅድ በመሆኑ ይህንኑ ወገን የክርክር ተከፋይ በማድረግ ክርክሩ ቀጥሎ ይወሰን ዘንድ ጉዳዩን ወደ ክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት ወስነናል፡፡

3/ በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በማሰማት ውሣኔ እስኪሰጠው ድረስ ላወጡት ወጭና ኪሣራ በየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 88959

ህዳር 17 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ጽ/ቤት ነ/ፈጅ አባይነህ ዘውዱ

ተጠሪ፡- ደብረ አማን ተክለኃማኖት ቤተክርስቲያን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍረድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 190802 ጥቅምት 5 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 128307 ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወን ነው፡፡ ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክስን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በካርታ ቁጥር 11/35/77/00 በሚታወቀው ይዞታ ኃይማኖታዊ አገልግሎት ለህዝብ የምሰጥበት ህጋዊ ይዞታ ቦታ አለኝ፡፡ ከሳሽ ኃይማኖታዊ በዓላት የማከብርበት ምዕመናኑ መኪና የሚያቆሙበት በከፍተኛ ወጭ ያፀዳሁትና ከቀበሌ አስተዳደር በብሔራዊ ደህንነትና ከፖሊስ ጋር በመተባበር የፓርኪንግ አገልግሎት ሥር በሆኑ ወጣቶች የምሰጥበት ለአንድ መቶ አራት ዓመታት በያዝኩት ቦታ የፓርኪንግ አገልግሎት መስጠቴን እንዳቆም ተከሳሽ ታህሳስ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በዕለፍ ትዕዛዝ በመስጠት ሁከት የፈጠርብኝ በመሆኑ ሁከቱ እንዲወገድ ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርባለች፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ (ተጠሪ) የሁከት ክስ ያቀረበችበት ቦታ ከከሳሽ ህጋዊ ይዞታ እና አጥር ውጪ የሚገኝ ክፍት ቦታ ነው፡፡ ቦታው በካርታው ውስጥ የተጠቃለለ አይደለም፡፡ በቦታው ላይ ቀደም ሲል የኢትፍሩት ኮንቴነርና ተንቀሳቃሽ ሽንት ቤት ተቀምጦበት እንደነበር ከሳሽ ለክሳቸው ገልፀዋል፡፡ ተከሳሽ የመንግስት ቦታ የማስተዳደር ስልጣን በህግ ተሰጥቶታል፡፡ ከህብረተሰቡ በቀረበለት አቤቱታ መሰረት ከሳሽ የፓርኪንግ አገልግሎት እንዳትሰጥ መከልከሉ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ ቦታው ከአጥር ውጭ የሚገኝ ቢሆንም ከሳሽ በእጇ አድርጋ ይዛ ስትገለገልበት የኖረችው ይዞታዋ ነው፡፡ ተከሳሽ የዚህን ቦታ ከሳሽ የፓርኪንግ አገልግሎት እንዳትሰጥ የፃፈው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ የፓርኪንግ አገልግሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳትሰጥ የፃፈው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነው ስለዚህ የፓርኪንግ አገልግሎት እነዳይሰጥ የሰጠው ትዕዛዝና ክልከላ ተወግዷል፡፡ በከሳሽ ይዞታ ላይ የፈጠረው ሁከት ይወገድ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

3. አመልካች ሚያዝያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ቦታው የተጠሪ ይዞታ አይደለም በቦታው የነበረው የኢትፍሩት ኮንቴነርና ጊዜያዊ ሽንት ቤት የተነሳው በአስተዳደሩ ፈቃድ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ቦታውን የፓርኪንግ አገልግሎት እንዳትሰጥበት የፃፍኩት ደብዳቤ የሁከት ተግባር አይደለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 23 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ መሬቱ ለረዥም ዓመታት በእጃችን አድርገን ስንጠቀምበት የነበረ ህጋዊ ይዞታችን ነው፡፡ ስለዚህ በይዞታችን ላይ የተለያዩ ሃይማኖታዊ በዓላት እንድናከብር ለምዕመናን የፓርኪንግ አገልግሎት እንዳንሰጥ አመልካች የወሰነው ውሰኔ የሁከት ተግባር በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካች ሰኔ 13 2005 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ በመልስ መልሱ ውሳኔው ደንብ ቁጥር 14/1996 ድንጋጌዎችን ያገናዘብ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ በአጥር ካጠረውና በካርታ ቁጥር 01-11.35/77/00 ከሚታወቀው ቦታው ፊት ለፊት የሚገኘው ቦታ ላይ የምትሰጠውን የፓርኪንግ አገልግሎት እንድታቆም አመልካች የፃፈው ደብዳቤ የሁከት ተግባር ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ያቀረበችበት ቦታ ከቤተክርስቲያኑ አጥር ክልል ውጭ የሚገኝና የቤተክርስቲያኗን ህጋዊ ይዞታ በሚያረጋግጠው የካርታ ቁጥር ል11-35/77/00 የማይጠቃለል ነው፡፡ አከራካሪው ቦታ በቤተክርስቲያኗ ፊት ለፊት የሚገኝ ተጠሪ ከመቶ ዓመታት በላይ ኃይማኖታዊ በዓላትን ለማክበር ምእመናን ፀሎት ለማድረግና መኪኖቻቸውን ለማቆም ሲጠቀሙበት የኖሩ መሆኑን ተጠሪ ከስር ፍርድ ቤትና ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበችው ክርክር በግልፅ አስፍራለች፡፡ ከዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የከተማ ቦታ የማስተዳደርና የትኛው ቦታ ለምን አይነት አገልግሎት መዋል እንዳለበት የመወሰን ስለጣን ያለው የከተማው አስተዳደር ነው ወይስ የቦታው ተጠቃሚና ባለይዞታ ነን የሚለው ግለሰብ ድርጅት ወይስ ኃማኖታዊ ተቋም? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

6. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ማስተዳደር ሥልጣን ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንደሆነ በአዋጁ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 2(ሰ) በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ከወረዳው ክልል ሥር ያለውን ከተማ መሬት ማስተዳደር የትኛው ቦታ ለፓርኪንግ አገልግሎት የሚውል ስለመሆኑ የትኛው ለፓርኪንግ አገልግሎት እንደሚሆን የከተማዋን መሪ ፕላን የማህበረሰብ ደህንነትና የፀጥታና ሌሎች ቦታዎችን በማገናዘብ የመወሰን ሥልጣን ያለው አመልካች ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) እና አንቀፅ 38 ድንጋጌዎች ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

7. አመልካች ከላይ በገለጽነው ህግ ድንጋጌ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የወረዳ አስተዳደር ስልጣንና ኃላፊነት ለመወሰን የወጣውን አዋጅ መነሻ በመድረግ ተጠሪ ከይዞታው ፊት ለፊት ባለው ቦታ ላይ የፓርኪንግ አገልግሎት መስጠቷ ለህዝብ ደህንነትና ፀጥታ አስጊ በመሆኑ አገልግሎቱን እንድታቆም የፃፈው ደብዳቤ አመልካች በህግ የተጣለበትን ኃላፊነት እየተወጣ መሆኑን የሚያሳይ እንጅ የሁከት ተግባር አይደለም በመሆኑም አመልካች ተጠሪ በአጥር ከታጠረውና ከህጋዊ ይዞታው ፊት ለፊት ባለው ቦታ ላይ የምትሰጠውን የመኪና ፓርኪንግ አገልግሎት እንድታቋርጥ በቁጥር ል/ክ/ከ/ወ/አስ/624/2004 ታህሳስ 12 ቀን 2004 ዓ.ም የፃፈው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የሁከት ተግባር ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 2(ሰ) አንቀፅ 33 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የፃፈው ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ሁከት ተግባር አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች በወረዳው ክልል ውስጥ ያለውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ማስተዳደርና የከተማውን ፕላን መሰረት በማድረግ የትኛው ቦታ ለምን ዓይነት አገልግሎት መዋል እንዳለበት መወሰን ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 36/1995 እንደተሻሻለ ደብዳቤ መፃፉ ሁከት አይደለም በሚል ወስኗል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ል/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92546

ታህሣስ 18 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አሕመድ

አመልካች፡- አቶ አብዱራዛቅ ኢብራሒም ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ህግ ድንበሩ አንዳርጌ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፍትህ ሚኒስቴር ሚንስትር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣውን የዐቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 44/1991 ድንጋጌዎች በሚጥስ ሁኔታ ዐቃቤ ሕግነት ተመድቤ ሣገልገል የነበረኩትን አመልካች ከሥራ እንድሰናበት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሚኒስትሩ ውሣኔም በቁጥር 02/አሠአ.128/10/1 ግንቦት 8 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ተገልፆልኛል፡፡ የፍትህ ሚስቴር የአቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 44/1991 ከሚደነግገው ውጭ ካለአግባብ ስልጣኑን በመጠቀም ከሁለት ወር በላይ ከሥራና ከደመወዝ አግዶ አቆይቶኛል፡፡ ከሁሉም በላይ አመልካች ቀርቦብኝ የነበረውን የዲሲፕሊን ክስ በበቂ ሁኔታ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያላስረዳ በመሆኑ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሣያስፈልገኝ በነፃ የተሰናበትኩ መሆኑን በመግለጽ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤው ውሣኔ ሰጥቶ ውሣኔው በቁጥር 24/ሠ-16/91/4 ሕዳር 21 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ገልፆልኛል፡፡ ይህንን የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ሚኒስትሩ ሲሸር ለቀረበብኝ ይግባኝ መልስ እንድሰጥ እድል እልተሰጠኝም፡፡ እንደዚሁም የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ ከተሻረም ጉዳዩ ወደ ጉባኤው ተመልሶ የመከላከያ ማስረጃውን የማቅረብ መብቱ ሊጠበቅ ሲገባው የእኔን የመከራከርና የመከላከል መብት ሣይጠበቅ የተሰጠው ውሣኔ ደንብ ቁጥር 44/1991 እና የውሣኔ አሠጣጥ ስርዓትን የሚጥስ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይኸ የሰበር ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በሰበር አይቶ እንዲያርምልኝ በማለት ነሐሴ 6 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

2. አመልካች ከሰበር አቤቱታው ጋር በማያያዝ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ አመልካች የዲስፕሊን ጥፋት የፈፀመ ስለመሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ ከቀረበበት የዲስፕሊን ክስ የመከላከል ማስረጃ ማቅረቡ ሣያስፈልገው በነፃ የተሰናበተ መሆኑን በመግለጽ በቁጥር 24/ሠ-16/91/4 ሕዳር 21 ቀን 2005 ዓ.ም የፃፈውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደብዳቤና በፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ፊርማ አመልካች ከሥራ የተሰናበተ መሆኑን በመግለጽ በቁጥር 02/አሠደ-128/10/1 ግንቦት 8 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤ በማያያዝ አቅርቧል፡፡

3. አመልካች ላቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ መልስ በጽሑፍ እንዲያቀርብ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ተጠሪ መስከረም 30 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ የሻረው በአቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 44/1991 አንቀጽ 78 እና አንቀጽ 79 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ባስተላለፈው ውሣኔ መሠረት ነው፡፡ ውሣኔው በደንቡ መሠረት የተሰጠ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ጥቅምት 15 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. የጉዳዩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር የአቃቤ ሕግ አስዳደር ዋና ጉባኤ የሰጠውን ውሣኔ የሻረው አስገዳጅነት ያላቸውን የሕግ ሥርዓቶች በመከተልና የደንብ ቁጥር 44/9/ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የአቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ በመጣስ የዲስፕሊን ክስ የቀረበበት ዐቃቤ ሕግ በደንቡ የተጠበቁለት መሠረታዊ መብቶችን መመርመር አስፈላጊ ነው የዲስፕሊን ክስ የቀረቡለት አቃቤ ሕግ ላይ ያቀረበበትን የዲስፕሊን ክስ ለማጣራትና አቃቤ ሕጉ በሕጉ መጣራት ማስረጃዎችን ለማሠባሠብ አስፈላጊውን የአፈፃፀም ሥነ ሥርዓት መጠቀም እንዳለበት በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረታዊ መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ ጉባኤው ይህንን የማጣራት ግዴታውውን በመወጣት ከተገቢ የውሣኔ ሃሣብ ላይ ለመድረስ በዲስፕሊን የተከሰሰው አቃቤ ሕግና መሥሪያ ቤቱ እያንዳንዳቸው ጉዳያቸውን እንዲያስረዱ ማድረግ እንዳለበት በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ አቃቤ ሕጉ በመስሪያ ቤቱ የቀረበለትን ክስና ማስረጃ የማስተባበልና መከላከያ የሚሆኑት ነጥቦች የማቅረብና የመከላከያ ማስረጃ የመስማት መብት ያለው መሆኑ የሚደነግግ ነው፡፡

6. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ክስ የቀረበበት አቃቤ ሕግ ለቀረበበት ክስ መልስና መከላከያ ለማቅረብ እንዲቻል የቀረቡትን ክስ በዝርዝር የሚገልጽ የክስ ጽሑፍ ክሱን ለማረጋገጥ የቀረበበትን ማስረጃ መልስ የሚሰጥበት ቀን ሠዓት ቦታ ከሚገልጽ መጥሪያ ጋር እንዲደርሰው ማድረግ እዳለበት በደንቡ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ይህም አቃቤ ሕጉ የቀረበበትን የዲሲፕሊን ክስ ለመከላከል የሚችልበትንና ማስረጃ የሚሰማበትን ቀን የማወቅ መብት ያለው መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ የሰጠው የአመልካች የመከላከያ ማስረጃን በመስማትና በመመዘን እንዳልሆነና፣ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ የተጠሪን ምስክሮቹ ከሰማ በኃላ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ስለዚህ የአቃቤ ሕጉን /የአመልካችን/ መከላካያ ማስረጃ መስማት አስፈላጊ አይደለም በማለት ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ ሣይሰማ የተጠሪን ክስ በደንቡ አንቀጽ 84 ንዑጽ አቀጽ /ሀ/ በሚደነግገው መሠረት ውድቅ በማድረግ አመልካች በተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋት አልፈፀመም በማለት በነፃ ያሰናበተው መሆኑ ሕዳር 21 ቀን 2005 ዓ.ም በፃፈውና በአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ ይዘት በሚገልፀው ደብዳቤ ለመረዳት ይቻላል፡፡

7. በአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ክርክር ጉዳዮች ሚኒስትር ዴኤታ ይግባኝ ለፍትሕ ሚኒስትሩ ያቀረቡ መሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር ተረድተናል፡፡ የክርክር ጉዳዮች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚኒስትር ዴኤታ በአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሚኒስትሩ ማቅረቡ የደንቡን አንቀጽ 85 ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ በመሆኑ ሕጋዊነቱ ክርክር የሚያስነሣ አይደለም፡፡ አክራካሪው የሆነው ሚኒስትር ዴኤታው በአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉብኤ ውሣኔ ቅር በመሠኘት የቀረበውን ይግባኝ ሚኒስትሩ ያስተናገደበት ሥርዓትና ሚኒስትሩ አቃቤ ሕግ የአስዳደር ጉባኤ ውሣኔን በመሻር አመልካች ከሥራ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ በደንቡ አመልካች በአንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 1 የተሰጠውን ክስን የመከላከልና የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብት በጠበቀ ሁኔታ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ነው፡፡

8. ሚኒስቴር ከአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ የቀረበውን ይግባኝ የማያስተናግድበት ዝርዝር ሥርዓት በደንቡ አንቀጽ 85 አልተደነገገም፡፡ ሆኖም ይህ ማለት በአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በዲስፒሊን የሚያስከስስ በቂ ማስረጀ በሚንስትር መሥሪያ ቤቱ አልቀረበበትም ተብሎ በደንቡ አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ መሠረት የዲስፒሊን ክሱ የተሰራበትን አቃቤ ሕግ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ዝርዝር ይዘት አውቆ መልስ እንዲሰጥበት ሣያደርግ ሚኒስትሩ ሚኒስቴር ዴኤታው ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ብቻ በማየት ውሣኔ ይሰጣል ማለት እንዳልሆነ በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገው የአቃቤ ሕጉ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ የማወቅና የመከላከያ መልስን ማስረጃውን የማቅረብ መብት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሚኒስቴር አመልካች ተጠቃሚ የሆነበትን የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ በደንቡ አንቀጽ 85 መሠረት በይግባኝ አይቶ ውሣኔውን የሚያሻሽለው ወይም የሚሽረው በሆነ ጊዜ በደንቡ አንቀጽ 82 እና አንቀጽ 83 የተደነገጉት ሥርዓቶች በመከተል አቃቤ ሕጉ የቀረበበትን ይግባኝ ማመልከቱ በጽሑፍ እንደደረሰውና መልስ እንዲሰጥበት በማድረግ የአቀቤ ሕጉን የመከራከርና የመሰማት መብት የማክበር ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

9. ስለዚህ ምክንያቱ በደንቡ አንቀጽ 85 በሚኒስትሩ የተሰጠው የይግባኝ ስልጣን አስተዳደራዊ ስልጣን ሣይሆን የዳኝነት ነክ ስልጣን መሆኑ ነው፡፡ የዳኝነት ወይም ከፊል የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ክርክርና ክርክሩን የሚደግፉለትን ማስረጃ የማቅረብና ፍትሕ የማግኘት መብት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 እውቅናና ጥበቃ የተሰጠው መብት ነው የዳኝነት ነክ ስልጣን በሕግ የተሰጠው አካልም ለተከራካሪዎቹ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 25 የተደነገገው የእኩልነትና እኩል የሕግ ጥበቃና ዋስትና የማግኘት መብት በማክበር ተከራከሪዎቹ ክርክራቸውን እንዳያቀርቡ ማድረግና ለተከራካሪዎች እኩል እድል የመስጠትና ጉዳዩን ገለልተኛ ሆኖ የመመርመር ውሣኔ የመስጠት ግዴታ አለበት ከዚህ አንፃር በያዝነው ጉዳይ ሚኒስትሩ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም መስሪያ ቤት ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ለአመልካች እንዲደርሠውና መልስ እንዲሰጥበት ሣያደግ አመልካች የዲስፕሊን ጥፋት አልፈፀመም ተብሎ የተሰጠውን ውሣኔ መሻሩ ከላይ በዝርዝር የገለጽነውን አስገዳጅ የሆኑ ክርክር አሠራር ሥርዓትና ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. ሚኒስትሩ መሥሪያ ቤቱ በአንቀጽ 85 መሠረት የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ያቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ አመልካች ደርሶት መልስ እንዲሰጥበት ሣያደረግ ውሣኔውን መሻሩ የመጀመሪያ ክርክር አሠራር ሒደት የፈፀመው ስህተት መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሚኒስትሩ የሰጠውን ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ምክንያቱም የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በሚኒስተር መ/ቤቱ በአመልካች ላይ የቀረበውን የዲሲፕሊን ክስ ውድቅ ያደረገው የዲሲፕሊን ክስ የቀረበው መስሪያ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የዲስፕሊን ጥፋት የፈፀመ መሆኑን በማስረዳት ያቀረባቸው ምስክሮችና ማስረጃዎች ክሱን አላስረዱም የዲስፕሉን ክስ የቀረበው አላል ክሱን በበቂ ማስረጃ ያላስረዳ በመሆኑ ተከሣሹ /የአመልካቹ/ የመከላከያ ማስረጃ መስማት አስፈላጊ አይደለም በማለት አመልካች በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠበቀለትን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብና የማሰማት መብት በማለፉ እንደሆነ የሰበር አቤቱታው ጋር ተያይዞ የቀረበው የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔን በያዙት ከሚገለፀው ደብዳቤ ተረድተናል፡፡

11. ሚኒስትሩ በደንቡ አንቀጽ 85 መሠረት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የቀረበውን የተሰማው ማስረጃ የዲስፕሊን ክሱ በዚህ ሁኔታ ለማስረዳት የሚችል ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔ መሻር ጉባኤው ጉዳዩን እንደገና በማየትና አመልካች በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 3 በተሰጠው የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብና የማሰማት መብት ተጠቅሞ የሚያቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በማስማት ጉባኤው ውሣኔ እንዲሰጥ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ሚኒስትሩ ይህንን ሥርዓት ለመከተል ካልፈገለ አመልካች ለአቀቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በመከላከያ ማስረጃ አድርጎ የቆጠራቸው ምስክሮች እዲያቀረብና እንዲያሰማ በማድረግ ሌሎች የመከለካያ ማስረጃውን ተቀብሎ በመመርመር አመልካች በደንቡ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 የተሰጠውን የመከላከያ ማስረጃ የማቀረብ መብት በማክበርና በማስከበር ውሣኔ የመስጠት ኃላፊት አለበት ሚኒስተሩ የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብት የሚከበርበት ሁኔታ ሣይፈጥር ወይም አመልካች የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያቀርብ እድል ሣይሰጥ የአቀቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔን በመሻር አመልካች ከሥራ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ የአቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 44/1991 አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 አስገዳጅ ድንጋጌን የሚጥስ እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች ሚኒስትሩ የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ውሣኔን በመሻር አመልካች ከሥራ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ አስገዳጅ የሆኑ የክርክር አመራር ሥርዓት ያልተከተለና የአቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 85 ድንጋጌዎችን መሠረታዊ ይዘት መንፈስና አላማ ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 79/1/ ድንጋጌዎችን መሠረት ማድረግ ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ሚኒስትሩ የክርክር ጉዳዮች ዩኤታ ባቀረበው ይግባኝ ባይ አመልካች መልስ እንዲሰጥ ሣያደግርና የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብት ሣያከብርና እንዲከበር ሣያደርግ አመልካች ከሥራ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 75877

መስከረም 23 ቀን 2005 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡-የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር - ዜናዬ ታደሰ

አሰለፈች መርሻ } ጠበቆች ቀረቡ

ተጠሪ፡- የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ -ነገረፈጅ ሙዑዝ ገ/ልዑል ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በተጠሪ የታገደ ገንዘብ ይለቀቅልኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በይግባኝ ደረጃ የታየው በተጠሪ ቦርድ ነው፡፡ በዚህ ቦርድ አቤቱታ አቅራቢ የነበረው የአሁኑ አመልካች ሲሆን የአቤቱታው ዋና ሐሳብም አመልካች ማህበር ከውጭ ካገኘው እስከ 12,000,000.00 (አስራ ሁለት ሚሊዮን) ብር በጀት በመጠቀም በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው ደንብ መሰረት እስከ መጨረሻው ለመስራት ዝግጅት ሲያደርግ መቆየቱን፣ ኤጀንሲው ታህሳስ 14 ቀን 2002 ዓ/ም በጻፈው ደብዳቤ በበጎ አድራጎት ማህበሩ የባንክ አካውንት ውስጥ ከነበረው ከ10,000,000.00 (አስር ሚሊዮን) ብር በላይ እንዳገደበት እና 1,596,229.00 እንደለቀቀለት፣ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 ተፈጻሚነት ከየካቲት 06 ቀን 2002 ዓ/ም በኋላ እንደሚሆን በኤጀንሲው ተገልፆ እያለ የዝግጅት ስራ እስከዚያው ድረስ ለመጨረስ አመልካች እየተንቀሳቀሰ በነበረበት ወቅት በደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 10 የአዋጁ አፈፃፀም መሸጋገሪያ ጊዜ ተሰጥቶ ባለበት ሁኔታ፣ አዋጁ ነባር ድርጅቶችን ቀድሞ የነበራቸውን ሀብትና ንብረት ይዘው እንዲሸጋገሩ የሚከለክሉ ድንጋጌዎች ሳይኖሩበት፣ ማህበሩ ከኪራይ ነጻ ሆኖ ለተገልጋዮች ነጻ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችለውን ቤት ለመግዛት ብር 8,600,000.00 (ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ብር) እንደሚያስፈልገው ለኤጀንሲው አቅርቦ እያለና ቀድሞ ይህን እንዳያስፈጽም በፍትህ ሚኒስቴር የማህበራት ምዝገባና ጽ/ቤት የፈቃድ እድሳት ቆሞ በመቆየቱ አመልካች ማስፈጸም ያለመቻሉን፣ በመሸጋገሪያ ጊዜ ለመጠቀም አመልካች ያቀዳቸውን ተግባራት ለማከናወን የባንክ አካውንቱ በኤጀንሲው በመታገዱ ምክንያት ማህበሩ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መውደቁን በመዘርዘር ቦርዱ አመልካች በመሸገገሪያ ጊዜ ለማስፈጸም ያቀዳቸውን እቅዶችን ለማሳካት፣ የድርጅት ሰራተኞችን ደመወዝ በማማሸ እንዲቀንስ አድርጎ ባለበት ሁኔታና ለጋሾች ገንዘቡን አመልካች ድርጅት ባለመጠቀሙ መልሰው እንዲወስዱት ከማድረግ በሴቶች መብት ላይ የሚሰራው አመልካች ድርጅት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲጠቀምበት ይወስንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በአዋጁ መሰረት የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ መመዝገቡንና የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ደግሞ ከ10 ከመቶ በላይ ከውጭ ገቢ ምንጭ መጠቀም እንደማይችል አዋጁ የሚከለክል መሆኑንና ማኅበሩ ከውጭ የሰበሰበው በርካታ ገንዘብ የነበረው ከመሆኑም በላይ አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 በኋላም በርካታ ገንዘብ ከውጭ የገቢ ምንጮች የሰበሰበ መሆኑን፣ አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም በኋላ በቀድሞ ሕጎች የተገኙ መብትና ግዴታዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት አዋጁን የማይቃረኑ ከሆኑ ብቻ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 111(1) መደንገጉንና ድርጅቱ ኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ በመሆኑ ገንዘቡን ለተሰማራበት ዓላማ መጠቀም የማይችል መሆኑን፣ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከአገር ውስጥ 90% የሚያመነጭ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ መመዝገቡን ከመመዝገቡ በፊት ከውጭ ምንጭ የሰበሰበው ገንዘብ መጠቀም ስለማይችል በኤጀንሲው መታገዱን፣ በአዋጁ መሰረት ገንዘቡን ለሌላ ድርጅት ማስተላለፍ ቢቻልም ኤጀንሲው የወሰደው አቋም ግን በየአመቱ 90% ከአገር ውስጥ አመንጭቶ ለኤጀንሲው ሲያቀርብ ቀሪው 10% ደግሞ ከታገደው ገንዘብ ውስጥ እየተለቀቀለት መንቀሳቀስ እንዲችል የሚያደርግ መሆኑን ዘርዝሮ አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ቦርዱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ የተጠሪ እርምጃ ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 104 በተዘረጋው የይግባኝ ስርዓት መሰረት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የቦርዱ ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ አከራካሪውን ገንዘብ ለማገድ ሕጉ ስልጣን የማይሰጠው መሆኑና እገዳውም የተደረገው አመልካች ድርጅት ሕጉ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በልዩ ልዩ ሁኔታና ሕጋዊ መንገዶች ከውጭ ምንጭ የተገኘ ገንዘብ መሆኑና ለቤት መግዣ እቅድ ይዞ ፈቃዱ ባለመታደሱ ምክንያት እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ያልቻለ መሆኑን፣ የአመልካች የመከራከር መብት በቦርዱ በአግባቡ ያልተጠበቀለት መሆኑን ዘርዝሮ በጠቅላላው ገንዘቡ የሚታገድበት ሕጋዊ አግባብ ያለመኖሩንና የተጠሪ እርምጃም ሕገ መንግስቱንና አለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ስምምነትን የሚጻረር ስለመሆኑ ጠቅሶ ገንዘቡ የሚታገድበት ሕጋዊ አግባብ የለም ብሎ መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 111(1)፣ አዋጁን ለማስፈፀም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከወጣው ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 10(2) እና የፍትህ ሚኒስትር መጋቢት 16 ቀን 2001 ለተለያዩ የፌዴራልና የክልል አካላት በአዋጁ መሰረት የምዝገባና የድጋሚ ምዝገባ ሥርዓት እስከሚጀምር ድረስ ነባር የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቀደም ሲል ሲሰሩ በነበረበት ሁኔታ ስራቸውን መቀጠል እንደሚችሉ በመግለጽ ከፃፈው ደብዳቤ አንፃር ለመመርመር ሲባል ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለቦርዱ አቤቱታውን ሊያቀርብ የቻለው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመፅናቱ በፊትም ሆነ የምስክር ወረቀት እስከተሰጠበት እስከ ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ/ም ድረስ ከውጭ የተሰበሰበውን ገንዘብ ያላግባብ አግዶብኛል፣ ይህንን ለማድረግም አዋጁም ሆነ ደንቡ አይፈቅዱለትም፤ ስልጣን አይሰጡትም በሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው የሠበር ቅሬታም ተጠሪ በሕጉ ስልጣን ያልተሰጠው ከመሆኑም በላይ የአዋጁንና የደንቡን ዝርዝር ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍትህ ሚኒስቴር መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ/ም የተፃፈው ደብዳቤ ይዘት ባላገናዘበ መልኩ እገዳውን ማከናወኑንና በቦርዱ በነበረው ክርክርም የመከራከር መብቱ በስነ ስርአት ሕጉ መሰረት ሳይጠበቅለት የቀረ ስለመሆኑ ዘርዝሮ መከራከሩን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከውጪ የሚሰበሰበው ገንዘብን መሰረት በማድረግ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራት ትርጉም፣ አይነታቸውንና ዓላማቸውን ለይቶ ገደብ ያደረገ ስለመሆኑ የሚያመላክቱ ድንጋጌዎችን ይዞ ይገኛል፡፡ ይህንኑ መለኪያ መሰረት አድርጎም አዋጁ ሶስት አይነት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በአገሪቱ የህግ ማዕቀፍ የሚታወቁ መሆኑን የሚያሳዩ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 2 ንዑስ ቁጥር (2)፣ ንዑስ ቁጥር (3) እና ንዑስ ቁጥር (4) ድንጋጌዎች እንደየቅደምተከተላቸው ሲታዩም የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት እና የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት በሕጉ የሚታወቁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማህበራት አይነቶች መሆናቸውን በመጥቀስ ትርጓሜአቸውን አስቀምጠው እናገኛለን፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶና የማህበራት አይነት የሚወሰነው በመሰረታዊነት የገቢ ምንጭን በመመርኮዝ ስለመሆኑ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ኢትዮጵያዊ ነው ተብሎ ሊመደብ የሚገባው በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት መመስረቱ ብቻ ሳይሆን ከውጪ ምንጮች የሚገኘው የገቢ መጠን ከጠቅላላ ገቢው አስር ከመቶ (10%) የማይበልጥ ሲሆን ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ከጠቅላላ ገቢው ከአስር ከመቶ በላይ የሆነውን ገቢ ከውጭ ምንጮች ስለማግኘቱ ከተረጋገጠ የኢትዮጵያ ነዋሪ ተብሎ እንደማይመደብ በአዋጁ አንቀፅ 2(2) እና 2(3) የተቀመጡት የትርጓሜ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ሕጉ በዚህ ረገድ ያስቀመጠው የትርጉም መሰረት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚሰማራበትን ዓላማ ለመለየትም መለኪያ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 14 ድንጋጌ ከላይ ከተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር ተጣምሮ ሲነበብ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡

የአዋጁ አንቀፅ 14(2) የበጎ አድራጎት ዓላማዎችን የዘረዘረ ሲሆን በአንቀፁ ንኡስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ ስር ደግሞ ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ተለይተው የተሰጡትን ዓላማዎችን በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በዚህ ንኡስ ድንጋጌ መሰረት ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ብቻ ተለየተው የተሰጡት ዓላማዎች የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊነትን ማበረታታት፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጾታ እና የሐይማኖት እኩልነት መረጋገጥን ማበረታታት፣ የሕጻናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን ማበረታታት፣ የግጭት አፈታትን ወይም እርቅን ማስፋፋት እና የፍትህና የሕግ ማስፈጸም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት ማጠናከር ስለመሆናቸው በግልጽ ተለይቶ ተደንግጓል፡፡ አዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አይነትና ዓላማቸውን ለይቶ ከማስቀመጡም በላይ አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ እንደሚችል፣ ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች፣ የመሻሻገሪያ ድንጋጌዎች እንዲሁም አዋጁ የሚፀናበትን ጊዜ እንደየቅደምተከተላቸው በአንቀፅ 109፣ 110፣ 111 እና በአንቀፅ 112 ስር አስቀምጧል፡፡ በዚህ አግባብም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 168/2001 አውጥቶ ከጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን ያደረገ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 621/2001 ደግሞ ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 112 በግልጽ ያሳያል፡፡ የአዋጁ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111 ንዑስ ቁጥር (1) ድንጋጌ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግዴታ አዋጁን እስካልተቃረነ ድረስ ብቻ እንደሚቀጥል ሲደነግግ ንዑስ ቁጥር (2) ድንጋጌ ደግሞ ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አለባቸው በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ ደንግጓል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ድርጅት የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ/ም መመዝገቡንና አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከፀናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 በፊትና በኋላ በርካታ ገንዘብ ከውጭ የገቢ ምንጮች የሰበሰበ መሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው፤ አቤቱታውን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የተጠሪ መስሪያ ቤት ቦርድና ጉዳዩን በይግባኝ እንዲመለከት በአዋጁ አንቀፅ 104(3) መሰረት ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጧቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ አመልካችም በርካታ ገንዘብ ከውጭ ምንጮች አዋጁ ቁጥር 621/2001 ከመፅናቱ በፊትም ሆነ ከጸና በሁዋላ መሰብሰቡን ሳይክድ አንዱ የክርክር ነጥብ አድርጎ የሚያቀርበው ጉዳይ አመልካች ድርጅት ገንዘቡን የሰበሰበው ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ቤት ለመግዛት ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ በፊት በማህበርነት ተመዝግቦ ሲሰራ የነበረ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከወጣ በኋላ በአዋጁ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ዳግም የተመዘገበ በመሆኑ አዋጁ ከጸና በኋላ በአዋጁ ለኢትዮጵያ ማህበር የተፈቀዱትን ዓላማዎች መስራት ያለበት በአዋጁ መሰረት በመሆኑና ይህንኑ ዓላማ ለማስፈጸም ደግሞ ቀድሞ ከውጭ የገቢ ምንጭ ያገኘውን ገንዘብ ለመጠቀም የሚችልበት አግባብ የለም በማለት ቦርዱና ይግባኙን የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ ገንዘቡ ለቤት ግዥ ዓላማ የሚውል ነበር በማለት የሚያቀርበው ክርክር የክርክሩን ሂደት እና ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት የተሰጠውን የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ማረም ስልጣን ያላገናዘበ የፍሬ ነገር ክርክር ሁኖ ስለአገኘን የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

እንዲሁም አዋጁ በአንቀጽ 108 ስር አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወደ ሌላ በጎ አድራጎት ድርጅት አይነት ሊቀይር ከፈለገ የሚችል ስለመሆኑ የሚያሳይ ሲሆን አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 18(3) ድንጋጌ ስር ደግሞ አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ከውጪ ምንጭ ያገኘውን ገንዘብ ይዞ በሕጉ አግባብ ኢትዮጵያዊ ለመባል የማይችል ስለመሆኑ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች በአዋጁ መሰረት እንደገና መመዝገቡ ከውጭ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወደ ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንደተቀየረ አያስቆጥረውም በማለት የሚያቀርበው ክርክር በአዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅት ኢትዮጵያዊ ለመባል መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችና ለኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በሕጉ የተፈቀዱለትን ዓላማዎች አይነት ሳይለይ የቀረበ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ነጥብ ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18 ተፈጻሚነት የሚኖረው በአዋጁ መሰረት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ፈቃድ አግኝቶ ከተመዘገበ በኋላ ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች አዋጁ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ በፊት በሕጉ አግባብ ተመዝግቦ ሲሰራ የነበረ ሲሆን አዋጁ ከወጣ በኋላ ዳግም ተመዝግቦ በአዋጁ ለኢትዮጵያዊ ድርጅት ወይም ማህበር የተፈቀዱትን ዓላማዎችን ይዞ እንደሚንቀሳቀስ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አዋጁ ከፀናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ከውጭ ምንጭ ከ10% በጀት በላይ መሰብሰብ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን የአዋጁን አንቀጽ 2(2)(3)፣ 14(5) እና የደንብ ቁጥር 18(3) ድንጋጌዎችን አንድ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በምናነብበት ጊዜ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክርም የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ ስላላገኘን የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ከታገደው ገንዘብ ውስጥ ብር 4,987,781.20 ያህሉ አዋጁ ከመፅናቱ በፊት የተሰበሰበ መሆኑን፣ ቀሪው ገንዘብም በችሮታ ጊዜ የተሰበሰበ በመሆኑ አዋጁንና ደንቡን ይቃረናል ሊባል አይችልም፣ የምዝገባ ውጤቱም ከታህሳስ 07 ቀን 2002 በኋላ ነው በማለትም ክርክር አቅርቧል፡፡ ለዚሁ ክርክሩ መሰረት የሚያደርጋቸው የሕግ ድንጋጌዎቹም የአዋጁ አንቀፅ 111(1) የደንቡን አንቀጽ 10(2) ድንጋጌን ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 111 ርዕሱ "የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች" በሚል የተቀመጠ ሲሆን ከላይ እንደተጠቀሰው ንዑስ አንቀፅ አንድ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና ግዴታ አዋጁን እስካልተቃረኑ ድረስ እንደሚቀጥል ሲያስቀምጥ፣ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ ያለባቸው ስለመሆኑ በአስገዳጅ መልኩ ደንግጓል፡፡ የደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 10(2) ደግሞ የድጋሚ ምዝገባ ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከጸናበት ጊዜ ከአንድ አመት በኋላ ይሆናል ሲል አስቀምጧል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩ ቅራኔ ያላቸው ናቸው ለማለት የሚቻል ሳይሆን እርስ በእርሳቸው የተጣጣሙ ናቸው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በመሸጋገሪያ ጊዜው ውስጥ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በሕጉ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበሰብ የሚፈቀድበት አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም የመሸጋገሪያ ድንጋጌ አይነተኛ አላማ ቀደም ሲል በነበሩ ሕጎች የተገኙ መብቶች እና ግዴታዎች አዲስ ሕግ ሲወጣ አስራሪ እንዳይሆኑ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ግልጽ ምላሽ ለመስጠት ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲታዩም ቀደም ሲል ለተገኙት መብቶችና ግዴታዎች ተፈፃሚነት ያጣው ሕግ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ሳይሆን በአዲሱ ሕግ እንዲሸፈኑ መደረጉን የሚያስገነዝቡን ናቸው፡፡ እንዲሁም ቀደም ሲል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባ የሕግ ማዕቀፍ የሌለውና ከአዋጅ ቁጥር 621/2001 ዓላማ ጋር አንድ ላይ የማይሄድና የማይጣጣም በመሆኑና እንደ አይነታቸውና ባሕርያቸው በተለያዩ ድንጋጌዎች ስለሚገዙ አዋጁ በወጣ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አስፈላጊ መሆኑ መደንገጉ አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ በአዋጁ የተከለከሉ ዓላማዎችን በቀድሞው ሕግ መሰረት ማከናወን መቀጠል የማይቻል ስለመሆኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ/ም የፍትሕ ሚኒስቴር ዓፈ የሚለውን ደብዳቤ ይዘት ጠቅሶ ያቀረበውን ክርክር ስንመለከተውም የደብዳቤው ይዘት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መፅደቁን አስታውሶ መንግስት በአዋጁ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የሚመዘግብና የሚከታተል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ለማቋቋም በሂደት ላይ ያለ ስለመሆኑ ጠቅሶ ኤጀንሲው ተቋቁሞ በአዋጁ መሰረት የምዝገባና የድጋሚ ምዝገባ ሥርዓት እስከሚጀምሩ ድረስ ነባር የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከዚህ በፊት ይሰሩ በነበሩበት ሁኔታ እየሰሩ መቀጠል እንደሚችሉ ለሚመለከታቸው የአስፈጻሚ አካላት ስርኩላሩ መተላለፉን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ሰርኩላር ይዘቱ የሚያስገነዝበው የአዋጁን አፈጻጸም ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ኤጀንሲው እስከሚቋቋም ድረስ የሚመለከታቸው አካላት ሊያከናውኑ የሚገባቸውን ተግባራት የሚያሳይና አዋጁን ለማስፈፀም ይቋቋማል የተባለ ኤጀንሲ ከተቋቋመ በኋላ ግን ሁሉም ነገር በአዋጁ መሰረት መሰራት ያለበት መሆኑን የሚያስረዳ በመሆኑ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 2(2) እና 111(2)፣ በደንቡ አንቀጽ 10(2) ድንጋጌዎች መሰረት በችሮታው ጊዜ የራሱን አደረጃጀት በማስተካከል ያልተጠናቀቁ ስራዎችን ለማጠናቀቅ እንዲችል ሕጉ በሰጠው ችሮታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጊዜ መንቀሳቀስ የሚገባበት እንጂ ገቢውን ከአዋጁ ይዘትና መንፈስ ውጪ እንዲሰበስብ እድል የሚሰጠውና የአዋጁን አላማ ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ ተፈጻሚ የሚሆን አይሆንም፡፡

አመልካቹ ተጠሪ በአዋጁ አንቀፅ 90 ስር ሰፊ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን በማመን የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ነው በማለት የሚከራከረው ተጠሪ ገንዘቡን ማገድ የሚችለው አዋጁ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ጊዜ በኋላ ጀምሮ ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር ተፈጽሞ ሲያገኝና ድርጅቱን ከአደጋ ለመጠበቅ አስፈላጊ ሁኖ ሲያገኘው ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

ተጠሪ በሕግ ተቋቁሞ አዋጅ ቁጥር 621/2001 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በሕጉ አግባብ ስልጣን የተሰጠው አካል ያወጣቸውን ደንቦች ለማስፈጸም የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 6 ስር ከተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባራት ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን መፈጸም እንደሚችል በተጠቃሹ አንቀፅ ፊደል "ቸ" ስር ከተቀመጠው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ማየት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 90 መሰረት ለኤጀንሲው የተሰጠውን ስልጣን ስንመለከተው በተጠቃሹ የአዋጁ ድንጋጌ የንብረት ጥበቃ ወይም እገዳ ተግባር የሚፈፀመው ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም በማህበር መፈጸሙ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት ያሳያል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን ገንዘብ ያገደው በአዋጁ አንቀፅ 90 መሰረት ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር በአመልካች ተፈጽሟል በሚል አይደለም፡፡ ይልቁንም በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ዓላማ አመልካች ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚያደርገው ሁኖ እያለ አዋጁ ከጸናበት ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ ከውጪ ምንጭ በርካታ ገንዘብ ሰብስቧል፣ አመልካች ዓላማው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ሁኖ እስከተመዘገበ ድረስ ይህንኑ ከውጪ የተገኘውን ገንዘብ ለዓላማው ማስፈፀሚያነት ሊያውለው አይችልም በሚል ነው፡፡ እንዲህ አይነት ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ መፍትሔው ምን እንደሆነ አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18 ምላሽ ይሰጣል፡፡ ይህ የደንቡ ድንጋጌ በኢትዮጵያ ውስጥ በአዋጁ መሰረት ፈቃድ አግኝቶ የተመዘገበ የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በበላይ አካሉ ውሳኔ ወደ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ሊቀየርና የምስክር ወረቀት ሊያገኝ እንደሚችል በንዑስ ቁጥር አንድ በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን ማንኛውም የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ሲለወጥ በባለቤትነቱ ስር ያለን ከውጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት ለተለወጠው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሊያስተላልፍ እንደማይችል፣ በንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ መሰረት ወደ ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም ማህበርነት ለመለወጥ ያመለከተ የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የነበረው ከውጭ ምንጭ የተገኘን ሀብት በድርጅቱ የበላይ አካል ወይም **በኤጂንሲው ውሳኔ** ተመሳሳይ ዓላማ ላለው የውጪ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተላለፍ እንደአለበት የአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለትና ሶስት እንደየቅደምተከተላቸው ኃይለ ቃልን በያዘ አቀራረፅ ያስቀመጡት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካችን አይነት የበጎ አድራጎት ድርጅት ህጉ ከመፅናቱ በፊትም ሆነ በኋላ ከሕግ ውጪ ከውጭ ምንጭ የሰበሰበውን ገንዘብ ተጠሪ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተመሳሳይ ዓላማ ላለው ድርጅት ወይም ማህበር ማስተላለፍ እንደአለበት የደንቡ አንቀጽ 18(3) በግልጽ ያሳያል፡፡ እንግዲህ በአመልካች የተፈፀመው ተግባር ላይ ተጠሪ በሕጉ ሊያደርገው ይገባ የነበረው ገንዘቡን ከማገድ የበለጠ ውጤት ያለውን፤ ገንዘቡን ለሌላ ተመሳሳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድርጅት ወይም ማህበር ማስተላለፍን የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ከህጉ ከተቀመጠው ያነሰ እርምጃ ተጠሪ መውሰዱ አመልካችን የጠቀመ ነው ከሚባል በስተቀር ለተጠሪ በሕግ ከተሠጠው ስልጣን አድማስ ውጪ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ሊሆን የሚችለው በሕጉ ተለይቶ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር ውጪ ተፈጽሞ ሲገኝ እንጂ በውጤቱ በሕጉ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር ከሚያስከትለው ያነሰና ፍትሓዊ ነው የሚለውን አስተዳደራዊ እርምጃ በመፈፀሙ ተግባሩ ከስልጣኑና ከተግባሩ አድማስ ውጪ ነው ለማለት የሚያስደፍርበት ሕጋዊ ምክንያትና አግባብ የለም፡፡ በሕግ ያልተከለከለን ተግባር መፈፀም ተቀባይነት የማያገኝበት አግባብም የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ስልጣንና የተወሰደውን እርምጃ መሰረት አድርጎ ያቀረበው ክርክርም ከአዋጁ አንቀጽ 90 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም በደንቡ አንቀጽ 18(3) ስር ከተመለከቱት እርምጃዎች ውጤት አኳያ ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

እንዲሁም አመልካች የታገደውን ገንዘብ ለምን እንደሚያውለው የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቤ ተቀባይነት አላገኙም፣ የተጠሪ መልስም እንዲደርስ አልተደረገም በማለት ያቀረባቸው የቅሬታ ነጥቦች በሰበር አቤቱታው ላይ ያነሳ ሲሆን በአመልካች በኩል ለቦርዱ ቀርቦ ያልታየለት ማስረጃ ስለመኖሩና የመከራከር መብቱም የተጣበበት ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ ባለመሆኑ ይህ ችሎት በዚህ የክርክር ደረጃ የሚቀበላቸው የቅሬታ ነጥቦች ሁነው አልተገኙም፡፡ ይልቁንም አመልካች በቦርዱ የመከራከር እድል እንደተሰጠው ከቦርዱ ውሳኔ ማረጋገጡን፣ የአመልካች የቤት መግዛት እቅድም በቦርዱ መታየቱን፣ ሆኖም አመልካች ቀድሞ ሲል ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ መቋቋሙና ከአስራ ስድስት አመታት በላይ በሚቆይበት ጊዜ ስራውን የሚያከናውንበትን ቤት ሳይገዛ በአዋጅ ቁጥር 621/2001 እና በደንብ ቁጥር 168/2001 በተሰጠው የችሮታ ጊዜ ቤቱን ለመግዛት እቅድ ማቀዱንና ለቤት መግዣ ገንዘብ ከለጋሾች ጋር አዲስ ስምምነት በማድረግ በችሮታ ጊዜ ውስጥ እንደቀድሞው ስራውን መቀጠሉን አመልካች ራሱ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ያመነው ስለመሆኑ ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ በግልጽ ያሳፈረው ጉዳይ ስለሆነ የአመልካች ድርጅት የመከራከር መብት አልተጠበቀም፣ ገንዘቡን ለቤት ግዥ ለማዋል ይችል እንደነበር የሚያስረዱለት ማስረጃዎች አልታዩለትም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ አመልካች ማህበር ረዥም አመታት ያህል ስራ ላይ የነበረና ገንዘቡን ቀድሞ ያገኘው ከሆነ የፈቃድ መታደስ መዘገየት ከቤት ግዥ እና አፈጻጸም ጋር ተያያዥነት የሌለውና አሳማኝነት የሌለው ምክንያት ስለመሆኑ ፍሬ ነገሩን በሚያጣራውና ማስረጃዎችን በሚመዝነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፕሮክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠው ስልጣን አንፃር በዚህ ረገድ የቀረቡትን የአመልካችን የቅሬታ ነጥቦች የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዝና ጉዳዮች በመሆናቸው የሚቀበላቸው ሁነው አልተገኙም፡፡

ሲጠቃለልም የአመልካች ተግባር በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 2(2፣3፣እና 4)፣6፣ 14(5)፣90፣111 እና 112፣እንዲሁም በደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀፅ 10(2)፣18(3) እና 36 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ሲታይ ገንዘቡ በተጠሪ እንዳይታገድ የሚያደርግበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ ተጠሪ ገንዘቡን ማገዱም ሆነ አመልካች ከአገር ውስጥ የገቢ ምንጭ 90% ያህሉን መሰብሰቡ እየተረጋገጠ ከታገደው ገንዘብ ውስጥ 10% እንዲለቀቅለት መደረጉ ሕጋዊ ከሚባልና በውጤቱም ፍትሃዊ ነው ተብሎ ከሚደመደም በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ

1. በተጠሪ ቦርድ ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 108157 ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት በድምጽ ብልጫ ፀንቷል፡፡
2. የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ውሳኔው በ09/02/05 ዓ.ም ተነበበ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የሃሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በአራተኛው ተራ ቁጥር የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በሰጠው የህግ ትርጉምና ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ የስራ ባልደረቦች ከሰጡት የህግ ትርጉምና ከደረሱበት መደምደሚያ የተለየሁባቸው ዝርዝር ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 31 በተደነገገውና በወቅቱ ስራ ላይ የነበረውን የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የሴቶች መብት ማስከበርን መሰረታዊ ዓላማው አድርጎ ሲሰራና አገልግሎት ሲሰጥ የበጎ አድራጎት ድርጅት መሆኑ ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡አመልካች በመጀመሪያ ሲመሰረትና በመንግስት ተመዝግቦና ፈቃድ ተሰጥቶት ሲንቀሳቀስ በነበረበት ወቅት ተፈፃሚነት የነበረው የፍትሐብሔር ሕግ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት የወጣ ህግ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ህጉ ስለማህበራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች አመሰራረት፣ አሰራር፣ ተግባርና ኃላፊነት እንደዚሁም የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት የደነገጋቸው ድንጋጌዎች ክፍተት ያለባቸው አሁን ካለው ህገመንግስታዊ ስርዓትና ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም፡፡ የፍትሐብሔር ህጉ ድንጋጌዎች ያለባቸውን ክፍተቶችና ችግሮች እንደዚሁም በወቅቱ ያልሸፈኗቸውና ምላሽ ያልሰጣቸው ነባራዊ ችግሮችና ያለንበትን ዘመን በማገናዘብ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ለማስተዳደር አዋጅ ቁጥር 621/2001ን አውጇል፡ አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና እንደሚሆን በአንቀጽ 112 የሚደነግግ ሲሆን አዋጁ የካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም በነጋሪት ጋዜጣ ታውጆ ወጥቷል፡፡

   የፍታብሔር ህጉ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በአገሪቱ ሊቋቋሙና ተመዝግበው እና ፈቃድ አግኝተው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ማህበሮች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የአገር በቀል (ብሔራዊ) ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የውጭ አገር ማህበራት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚል መንገድ የሚከፈል የነበረ መሆኑን የፍታብሔር ህጉ አንቀጽ 404 እስከ አንቀጽ 549 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ አዋጅ ቁጥር 621/2001 በኢትዮጵያ ውስጥ ሊቋቋሙ ተመዝግበውና ፈቃድ አግኝተው ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ ሶስት አይነት ማህበሮችና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንደሚኖሩ ይደነግጋል፡፡ ከነዚሁም " የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅት" የኢትዮጵያ ነዋሪዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የበጎ አድራጎት ድርጅትና የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅት እንደሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2፤ ንዑስ አንቀጽ 3 እና ንዑስ አንቀጽ 4 ትርጓሜ ተሰጥታቸዋል፡፡

የፍትሐብሔር ህጉ አገር በቀል ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሊሰሯቸው የሚችሏቸውን ተግባራትና ተግባራቸውን ለማከናወን ጥቅም ላይ በሚያውሉት የገንዘብ ምንጭ ላይ የሚጥለው ገደብ አልነበረም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 621/2001 ህግ አውጭው የዜጎችን መደራጀትና ማህበር የመመስረት መብት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው ተግባራት ለህብረተሰቡ ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታና ማህበራቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚያከናውኑት ተግባር አገራዊ አጀንዳ በማራመድና የአገራቱን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅ አኳያ መከናወን እንዳለባቸው በማመንና ማህበራቱ የበጎ አድራጎት ድርጅት ዓላማቸውን ለማሳካት ጥቅም ላይ ሊያውሉት የሚገባውን የገንዘብ ምንጭ መወሰን አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት በአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል (በ) እስከ ፊደል (ነ) የተዘረዘሩት ተግባራት ለማከናወን የሚችሉት የኢትዮጵያ የበጎ አድጎት ድርጅቶች ብቻ እንደሆኑና የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከአስር ፐርሰንት በላይ ከውጭ የተገኘ የገንዘብ ምንጭ መጠቀም እንደማይችሉ በአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 የደነገገ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

አከራካሪ የሆነው ጉዳይ በአዋጁ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገጉት መሰረታዊ ሁኔታች ከመደንገጋቸው በፊት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 31 የተደነገገውን የመደራጀትና ማህበር የመመስረት መብትና ከላይ መሰረታዊ ባህሪያቸው የተገለጹትን የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ተቋቁሞ ለአመታት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ በነበረው አመልካቹ ላይ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ የሚሆነው አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ከየካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ነው፡፡ አብላጫው ድምፅ ከላይ የተጠቀሱትን የአዋጅ ቁጥር 621/2001 ድንጋጌዎችና ሌሎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን የደንብ ቁጥር 168/2002 ድንጋጌዎች በመጥቀስና በመተርጎም አዋጁ ከየካቲት 1 ቀን 2001 ጀምሮ በአመልካችና በሌሎች ነባር ማህበራት የበጎ አድራጎት ድርጅት ላይ ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ፣ተጠሪ አመልካች ከውጭ ምንጭ የሰበሰበውን ገንዘብ ማገዱ የአዋጁንና ከደንብ ቁጥር 168/2002 ድንጋጌዎች የተከተለ ነው ከሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

2. በእኔ እምነት ህግ አውጭው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ሲያወጅ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 31 እና በፍታብሔር ህጉ መሰረት ተቋቁመውና ተመዝግበው የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩት ማህበሮችና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ፈርሰው እንደአዲስ እንዲደራጁና እንዲመሰረቱ የሚያስገድድ ግልፅ ድንጋጌ አላካተተም፡፡ እንዲሁም ህግ አውጭው አዋጁ በመውጣቱ በፊት ተቋቁመው የተለያ ተግባራትን ሲፈፅሙ የነበሩ ማህበሮችና የበጎ አድራጎት ደርጅቶች፣ አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአዋጁ መሰረት ተመዝግበው ፈቃድ እስኪያገኙ ድረስ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተሰጣቸውን ፈቃድ በመጠቀምና አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የነበራቸውን መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ ማናቸውንም እንቅስቃሴ ከማድረግ ራሳቸውን ተገድበው ማቆየት ያለባቸው መሆኑን በግልጽ አልደነገገም፡፡ በአንፃሩ ህግ አውጭው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በነበረው ህግ መሰረት ተመዝግበውና ተቋቁመው የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ የነበሩ ማህራትና በጎ አድራጎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድርጅቶች አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደገና የመመዝገብ ግዴታ እንዳለባቸው በአዋጁ አንቀጽ 711 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ደንግጓል፡፡ ይህም ህግ አውጭው በአዋጁ መሰረት በሚመሰረቱ አዲስ ማህበሮችና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በአዋጁ መሰረት እንደገና በሚመዘገቡ ነባር ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በተመለከተ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ የተለያየ እንደሆነና አዋጁ ለነባር ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እስከ አንድ ዓመት የሚደርስ የችሮታ ጊዜ የሚሰጥ መሆኑን የሚያሳይ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይህንንም ሀሳብ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ለማስፈፀም የሚችል ደንብ የማውጣት ስልጣን በአዋጁ አንቀጽ 109 የተሰጠው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 168/2002 ድንጋጌዎች የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡

ደንብ ቁጥር 168/2002 በአዋጅ ቁጥር 621/2001 መሰረት የሚመሰረቱና የሚቋቋሙ ማህበራት የሚመዘገቡበትን መደበኛ የምዝገባ ስርዓት በደንቡ በአንቀጽ 3 እስከ አንቀጽ 9 ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል ደንቡ ከአዋጁ ከመውጣቱ በፊት ተቋቁመው የነበሩ ማህበራት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በድጋሚ ስለሚመዘገቡበት ሥርዓት በአንቀጽ 10 እና በአንቀጽ 11 ይደነግጋል፡፡ በተለይም ደንብ ቁጥር 168/2002 በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጁ ከመፅናቱ በፊት የተመዘገቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ያለምንም ክፍያ ኤጀንሲው በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በድጋሚ ይመዘግባሉ፡፡ የድጋሚ ምዝገባ የሚካሄድበት ዝርዝር በኤጀንሲው ይወሰናል "በማለት በአንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነገጋ ሲሆን፣" አዋጁ ከመፅናቱ በፊት በተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ በአዋጁ መሰረት የሚፈፀመው ድጋሚ ምዝገባ ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ከአንድ ዓመት በኋላ መሆኑን በደንቡ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ ደንግጓል፡፡

ይኽም በአዋጁ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 112 የተደነገገው አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ማለትም ከየካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና እንደሚሆን የደነገገው አጠቃላይ መርህ ቢኖርም አዋጅ ቁጥር 621/2001 አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ተመዝግበው ሲንቀሳቀሱ በነበሩ ማህበራትና የበጎ አድራጎት ላይ በአዋጁና በደንቡ መሰረት የሚከናወነው ድጋሚ ምዝገባ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው አዋጁ ከፀና ከአንድ ዓመት በኋላ ማለትም ከየካቲት 6 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ፣ የአዋጁን አንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 2ኛ አንቀጽ 109 እና ከደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች ጋር በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል የሚል ምክንያት አለኝ፡፡

3. አዋጅ ቁጥር 621/2001 በአመልካችና ሌሎች አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በህግ መሰረት ተመዝግበው ሲንቀሳቀሱ በነበሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበሮች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው አዋጁ ከወጣ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረስኩት ከላይ በዘረዘርኩት ምክንያት ብቻ አይደለም፡፡ በእኔ እምነት አዋጅ ቁጥር 621/2001 የደነገገው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እያንዳንዷን ድንጋጌ በጥንቃቄና አንድ ለዩ ሁኔታ ለመግለፅ ወይም ለመቆጣጠር በማሰብና አንድ አላማ ለማሳካት የሚል ደንግጎታል ተብሎ ሊታሰብ ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የህዝብ ከፍተኛ አደራና ኃላፊነት የተሸከመው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዋጁን ሲያውጅ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ድንጋጌዎች መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማድረግና በህገ መንግስቱ የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት በተሟላ ሁኔታ ለመወጣት ተገቢውን ሁሉ ጥንቃቄ በማድረግ በሰከነ ሁኔታ አስቦና አመዛዝኖ ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችለው መንገድ የአዋጁን ቅርፅና ይዘት አጽድቋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከላይ ከገለፅኳቸውን መሰረታዊ መነሻዎች በመያዝ ህግ አውጭው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ሲያውጅ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 31 እና በወቅቱ ስራ ላይ በነበረው የፍታብሔር ህግ መሰረት ተመዝግበውና ፈቃድ አግኝተው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች

- አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በመመሥረቻ ፅሁፋቸውንና መተዳደሪያ ደንባቸውን መሰረት በማድረግ ጀምረዋቸው የነበሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊያጠናቅቋቸው የሚችሏቸውን ተግባራት እንዲያጠናቅቁና የተሟላ የፋይናንስና የክንዋኔ ሪፖርታቸውን እንዲያዘጋጁ ለማድረግ
- በህግ ወይም በወል ያገኟቸውን መብቶች ለማስከበርና በህግ ወይም በውል የተጣለባቸውን ግዴታ እንዲፈፅሙ ለማስቻል፣
- አዋጁ ከመውጣቱ በፊትና አዋጁ መሰረት በድጋሚ ከመመዝገባቸው በፊት ያፈሩት እሴትና ያገኙት ገንዘብ በአዋጁ መሰረት በድጋሚ ለሚመዘገቡበት ዓላማ ሊያውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ ለምሳሌ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን እንዲያጠኑና ሰርተው በሚያገኙት ገቢ ላይ ተመስርተው ዓላማቸውን ለማሳካት የሚችሉበት ድርጅታዊ ሁኔታ እንዲያመቻቹ
- በድጋሚ ከመመዝገባቸው በፊት የከናወኗቸው ተግባራት፣ የሰበሰቡት ገንዘብና የላባቸውን ፅዳ በባለሙያ በማስጠናት በድጋሚ ምዝገባ ወቅት ግልፅና የተሟላ መረጃ ለማቅረብ እንዲችሉና ሌሎች እንዚህን መሰል ተግባራት በመፈፀም በአዋጁ መሰረት እንደገና ለመመዝገብና ተግባርና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በመሸጋገሪያነት የሚፈፅሙ ተግባሮችን ፈፅመው የሚያጠናቀቁበት የአንድ ዓመት የችሮታ ጊዜ ሰጥቷቸዋል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ በእኔ እምነት የአዋጁ አንቀጽ 211 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የደንብ ቁጥር 168/2002 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረታዊ ዓላማና ህጋዊ ውጤት ነባር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የድጋሚ ምዝገባው ውጤት ከማግኘቱ በፊት በሽግግር ወቅት ሊፈጸሙና ሊጠናቀቁ የሚገባቸው ተግባራት ለመፈጸም የሚችሉበት የችሮታ ጊዜ መስጠት ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ህግ አውጭው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ተዘግበው ሲንቀሳቀሱ የቆዩ ማህበራት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ፈርሰው እንደአዲስ መመስረትና መመዝገብ ይገባቸው መሆኑን በግልጽ የሚደነግግ ድንጋጌ ወይም ነባር ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በአዋጁ መሰረት በድጋሚ እስኪመዘገቡ ማናቸውም እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ የሚገደብ ግልፅ ድንጋጌ በአዋጁ ውስጥ በማካተት አዋጁን ያወጣው ነበር፡፡ ህግ አውጭው የተከተለው የህግ አቀራረፅና የድንጋጌዎቹ ይዘት ለነባር ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ምክንያታዊ የሆነ የአንድ ዓመት መሸጋገሪያ የችሮታ ጊዜ የሰጠ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው ብዬ ስለማሰብ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

4. ከላይ በገለፅኩት የህግ አተረጓጎም የምሰጠው ሌላም ተጨማሪ ምክንያት አለ፡፡ ይኸውም ህግ አውጭው አዋጅ ቁጥር 621/2001 ያወጀው ሶስት መሰረታዊ ዓላመዎችን ለማሳከት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ህግ አውጭው በአዋጁ ሊያሳካቸው የሚፈልጋቸው መሰረታዊ ዓላማዎች፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የተረጋገጠውን የዜጎች የመደራጀት መብት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ህግ ማውጣት
- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በኢትዮጵያ ህዝቦች ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለመደገፍና ለማሳለጥ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ማውጣት፣
- አዋጁን ለማስፈጸም የሚችል አስፈፃሚ አካል (የበጎ አድራጎት ማህበራት ኤጅንሲ) ማቋቋምና ስልጣንና ኃላፊነቱን ለመወሰን እንደሆነ ከአዋጁ መግቢያና ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ህግ አውጭው አዋጁን ሲያወጣ ሊያሳካቸው የሚፈልጋቸው እነዚህ መሰረታዊ ዓላማዎች ህግ አውጭው አዋጁን ሲያውጅ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 31 የተደነገገውን የመደራጀትና ማህበር የመመስረት መብት ለማስከበር የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ማውጣት ግዴታ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 የተጣለበት መሆኑን በማገናዘብ ህጉን ያወጣ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ህግ አውጭው አዲስና የተሟላ የህግ ማዕቀፎች ያወጣ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንደዚሁም ህግ አውጭው አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ለህገ መንግስቱ አንቀጽ 31 የተረጋገጠላቸውን መብት በመጠቀም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በነበረው ያልተሟላ የህግ ማዕቀፍ መሰረት ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት የመሰረቱት ዜጎች መብት የማክበር ግዴታና ኃላፊነት እንዳለበት ያውቃል፡፡ ስለዚህ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት በማቋቋም ህገ መንግስታዊ መብታቸውን ዕውን ሲያደርጉ የኖሩ ዜጎች ማህበራቸውን አዲስ ከወጣው ህግ ጋር በሚጣጣም መንገድ እንዲያደራጁ የአዋጁን መስፈርት ከማሟላትና በድጋሚ ለማስመዘገብ የሚያስፈለጋቸውን መስፈርት ለማሟላት የሽግግር ጊዜ /የችሮታ ጊዜ/ የመስጠት ኃላፊነት እንዳለበት በመረዳት የአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ በማካተት አዋጁን አውጥቷል የሚል እምነት አለኝ፡፡

አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስችል ደንብ እንዲያወጣ በአዋጁ አንቀጽ 109 ስልጣን የተሰጠው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት "የድጋሚ ምዝገባ ውጤት ተግባራዊ የሚሆነው ድጋሚ ምዝገባው በተጠናቀቀበት ጊዜ ሳይሆን አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ከአንድ አመት በኋላ ይሆናል" በማለት በደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልፅ የደነገገበት ምክንያት ህግ አውጭው አዋጁን ያወጣው የዜጎችን የመደራጀትና ማህበር የመመስረት ህገ መንግስታዊ መብት ማክበርና የማስከበር ግዴታውን ለመወጣት የሚችለውን ማናቸውንም ጥንቃቄ በማድረግ አዋጁን ያወጀና የአዋጁ አንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረታዊ ዓላማም ለነባር በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ የአዋጁን ተፈፃሚነት በአንድ ዓመት ያህል በማዘግየት በመሸጋገሪያ ጊዜ ማጠናቀቅ የሚገባቸውን ተግባርና እንዲያጠናቅቁ እድል ለመስጠት መሆኑን በአግባቡ በመገንዘቡ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለዚህ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ዓላማና መሰረታዊ ግብ በደንብ ቁጥር 168/2002 የተገለፀ ከመሆኑ በላይ የድንጋጌውን ነባራዊ ተፈፃሚነት የሚዘረዝር በመሆኑ የደንቡ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2፣ የአዋጁን አንቀጽ 112 እና አንቀጽ 111 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የሚቃረን አይደለም ብዬ አስባሁ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ በዝርዝር በገለፅኩት ምክንያት ተጠሪ አመልካች በቀድሞው ህግ በፊት በነበረው መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ለመፈፀም ያቀዳቸውንና የጀመራቸውን ተግባራት ለማጠናቀቅና ለአመልካች ጽ/ቤት መግዣ እንዲውል የሰበሰበውን ገንዘብ ለአመልካች በአዋጁ አንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 2 በደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 የተሰጠው የችሮታ ጊዜ ማለትም እስከ የካቲት 6 ቀን 2002 የተሰጠው ጊዜ ከማለቁ በፊት ማገዱ የህግ መሰረት የሌለው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

5. ከላይ በዝርዝር የገለፅኳቸው ጠቅላላ የህግ አተረጓጎም ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው ተጠሪ አምልካች በአዋጁ መሰረት በድጋሚ ከመመዝገቡ በፊት አመልካች ያፈራቸውን እሴቶችና ያጠራቀመውን ገንዘብ ምንጩን እንዲያስረዳ የመጠየቅና አመልካች በድጋሚ ሲመዘገብ፣ ለዓላማው ማስፈፀሚያ የሚሆነው የተጠራቀመ ገንዘብና ሌላ ንብረት መጠን ላይ ገደብ የመጣል ስልጣን በአዋጅ አልተሰጠውም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በአዋጁ መሰረት የሚመሰረት አዲስ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከመመዝገቡ በፊት የሚያሰባስበው ገንዘብ ወይም ንብረት ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) በላይ ሊሆን እንደማይችል የአዋጅ ቁጥር 61/2001 አንቀጽ 65 ንኡስ አንቀጽ 3 በግልፅ ይደነግጋል፡፡
   አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ተመዝግበው ለዓመታት ሲንቀሳቀስ የቆየ ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 111 አንቀጽ 2 እና በደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በድጋሚ ሲመዘገብ በንብረትነት ይዞት ሲመዘገብ ስለሚችለውን የገንዘብና የንብረት መጠን የሚገድብ ከአዋጁ አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ 3 ጋር ተመሳሳይ ድንጋጌ በአዋጁ አልተካተተም፡፡ ይህም በድጋሚ ምዝገባው ማህበሩ የነበረውን ንብረትና ያጠራቀመውን ገንዘብ ይዞ በድጋሚ ሲመዘገብ እበንደሚችልና ተጠሪ በህግ ያልተደነገገ ገደብ እና ሁኔታ አመልካች በድጋሚ ከመመዝገቡ ከአንድ ቀን በፊት በመጣል የአመልካች ገንዘብ ያገደ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንደዚሁም የአዋጁ አንቀጽ 90 እና የደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች በዚህ ጉዳይ በጭብጥነት የተያዘውን ጉዳይ ለመወሰን ተጠቃሽና ተፈፃሚ ሊሆኑ የማይችሉና ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው ድንጋጌዎች ናቸው ብዬ ስለማስብ አብላጫው ድምፅ ተጠሪ እነዚህን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ አመልካች በድጋሚ ከመመዝገቡ ከአንድ ቀን በፊት የአመልካችን ገንዘብ የማገድም ሆነ ለሌላ ተመሳሳይ ድርጅት የመስጠት ስልጣን እንዳለው በመተንተን በሰጠው የህግ ትርጉም አልተስማማሁበትም፡፡
6. ተጠሪ ካገደው አመልካች ካጠራቀመው ገንዘብ ውስጥ አመልካች አዋጅ ቁጥር 621/2001 ከመውጣቱ ማለትም ከየካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም በፊት ያሰባሰበው ገንዘብ እንደሚገኝበት በግራ ቀኙ ክርክር በከፍተኛው ፍ/ቤትና በአብላጫው ድምፅ ውሳኔ ተገልጿል፡፡ ይህም ተጠሪ አመልካች አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ሥራ ላይ በነበረው የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ያገኘውን ገንዘብ ወደኋላ በመሄድ ያገደና የአዋጅ አንቀጽ 111 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መሰረታዊ መርህ የሚጥስ ተግባር ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ በመሰረቱ በአዋጁ የኢትጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከካፒታላቸው አስር በመቶ በላይ ከውጭ ምንጭ እንዳይጠቀሙ ገደብ የተደረገበት ዋንኛ ምክንያት የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የተሰጣቸው የችሮታ ጊዜ ከማለቁ በፊትና አዋጁ ከመውጣት በፊት ያጠራቀሙትን ገንዘብ ለመሰረታዊ ዓላማቸው ማሳኪያ እንዳያውሉ ለመከልከል አይደለም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ በአዋጁ በውጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘብ ድጋፍ ላይ የተጣለው ገደብ ዋና ዓላማው ኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በውጭ ድጋፍ ላይ መንጠልጠላቸው አላማቸውን በራሳቸው አቋምና ገቢ ለማሳካት ጥረት እንዳያደርጉ የሚያደርግና አንድ አንድ ጊዜም የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት በለጋሽ ወገኖች የሚቀመጡ ምክንያታዊ ያልሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ለመቀበል የሚገደብበትና ለብሔራዊ አገራዊ ጥቅም እርባና የሌላቸው ነገርግን ለጋሾች እንዲፈፅሙ የሚፈልጓቸው ተግባራት እንዲፈፅሙ የሚገደዱበትን ሁኔታ ለመከላከልና ለማስወገድ በማሰብ ነው፡፡ አመልካች ለጽ/ቤት መግዢያነት ያጠራቀመውን ገንዘብ መጠቀሙ ወደፊት በራሱ አቅም ዓላማውን ለማሳካት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ከሚደግፈው በስተቀር አዋጁ ከመውጣቱ በፊትና አመልካች በድጋሚ ከመመዝገቡ በፊት የውጭ የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉለት ለጋሾች ሚጣልበት አስፈላጊ ቅድመሁኔታ ቢኖር ቅድመ ሁኔታውን እንዲቀበል የሚያስገድደው አይደለም የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለዚህ አመልካች በድጋሚ ምዝገባ በፊት የተጠራቀመውን ገንዘብ ለጽ/ቤት መግዣነት መጠቀሙ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 መሰረታዊ ዓላማ የሚጥስ እንደሆነ በማድረግ ተጠሪ የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሰረትና ድጋፍ የሌለው ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 6 በገለፅኳቸው ምክንያቶች አብላጫው ድምፅ ተጠሪ አመልካች አዋጁ ከመውጣቱ በፊትና ከወጣ በኋላ ከውጭ ያሰባሰበውን ገንዘብ ማገዱ ህግን መሰረት ያደረገ ነው በማለት የሰጠው የህግ ትርጉምና ውሳኔ ባለመስማማት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ2005 ዓ.ም. የሰበር ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አሠሪና ሠራተኛ		1		
1	በአሰሪ ከተደረገ የሥራ ቦታ ዝውውር ጋር በተያያዘ ሠራተኛው ወደነበረበት ሥራ ቦታና መደብ እንዲመለስ በፍ/ቤት ሲወሰን አሰሪው ሠራተኛው የሥራ ዝውውሩ ከመከናወኑ በፊት ይሰራበት ወደነበረበት ቦታና የሥራ መደብ በትክክል መመለስ ያለበት ስለመሆኑ፣	78536	በደሌ ቢራ አክሲዮን ማህበር እና አቶ አልማው ቤዛ	ታህሳስ 5/2005	2
2	ሠራተኛ ተቀጥሮ የሚሰራበትን አሰሪ ተቋም መልካም ስምና ዝና እንዲሁም ጥቅምና ህልውና አደጋ ላይ በሚጥሉ ተግባራት የሚፈጽመው ጥፋት መጠንና ደረጃ እና የሚወሰድበትን እርምጃ ለመወሰን ሠራተኛው ከሚሰራው የሥራ አይነትና ባህሪ እንዲሁም ከአሰሪና ሠራተኛ ህጉ መንፈስና ዓላማ አንፃር መታየት ያለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1)(ሸ)(ረ)	77134	ወሰኔ የህክምና አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ዶ/ር ክብረወሰን አለማየሁ	ጥቅምት 8/2005	5
3	የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ ሰው በሌላ የመንግስት ሥራ ተቀጥሮ ያለአግባብ የወሰደው የጡረታ አበል እንዲመለስ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ በአሥር አመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑና የይርጋ ጊዜውም ግለሰቡ በሌላ የመንግስት ሥራ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ መልሶ ደመወዝ በሚያስገኝ የመንግስት ስራ ከተቀጠረ የቅጥሩ ሁኔታ በቋሚነትም ይሁን በጊዜያዊነት እንዲሁም ደመወዙ ከጡረታ አበሉ ያነሰ ሆነም አልሆነ ከደመወዙና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ ያለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 46(1) (2) አዋጅ ቁ.209/55 አንቀጽ 30(2) የፍ/ብ/ህ/ቁ.1677(1)	72341	የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና አቶ ታዬ አበራ	ህዳር 21/2005	9
4	የሥራ ክርክር ችሎት አንድን ሠራተኛ ያለአግባብ የተሰናበተ ነው በሚል ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ወደኋላ ቀደም ብሎ ካለ ጊዜ ጀምሮ አሰሪው ወደ ሥራ እንዲመልስ በሚል ውሣኔ የሰጠ እንደሆነ ሠራተኛው ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ ውዝፍ ደመወዝ ለማግኘት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ፣	83012	ዝዋይ ሮዝ ድርጅት እና ወ/ሮ ፋንቱ ያሲን	ጥር 14/2005	14

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5	የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ያለው የህግ ባለሙያ በሙያው አገልግሎት ለመስጠት ከ3ኛ ወገን ጋር በሚያደርገው ውል የሚፈጠረው ግንኙነት በእውቀት ሥራ ውል ላይ የተመሠረተ እንጂ ሠራተኛውን እንደ የስራ መሪ ወይም ተቀጣሪ የማያስቆጥረው ስለመሆኑ፡ በአዋጅ ቁ.377/96 የማይገዛ ስለመሆኑ፣	81405	አቶ አህመድ ሲራጅ እና የአወሊያ ዋና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት	ጥር 29/2005	20
6	አንድ ሠራተኛ መብቱን ለማስከበር በአሰሪው ላይ በፍ/ቤት ክስ መመስረቱ ብቻ ከአሠሪው ጋር ለወደፊት የሻከረ ግንኙነት ይፈጥራል የማያስብልና የስራ ውሉ እንዳይቀጥል ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43(3)	82336	የአብጃታ ሶዳ አሸ አክሲዮን ማህበር እና ማርታ አበበ	ጥር 02/2005	22
7	ቀደም ሲል ስናገኘው የነበረው የደመወዝ መጠን የተቀነሠ ስለሆነ እንዲስተካከልልን በማለት በሠራተኞች የሚቀርብ ክስ የወል የሥራ ክርክር ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣	78865	የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት እና እነ አቶ ገ/ስላሴ ኃ/ማርያም (ስምንት ሰዎች)	ጥር 28/2005	26
8	•ከሥራ ቅጥር ግንኙነት ጋር በተገናኘ አንድ ሥራ "ቀጣይነት ያለው" ነው ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ • አንድ ሥራ በባህሪው "ቀጣይነት ያለው" ነው ለማለት ስራው ረዘም ላለ ጊዜ መስራቱን ብቻ ሣይሆን የሥራው ባህሪ ከአሠሪው ድርጅት (ተቋም) አይነተኛ ሥራ ጋር የሚዛመድና በመደበኛነት የሚከናወን መሆኑን ጭምር ማረጋገጥ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፣	80350	ሽራተን አዲስ እና እነ አቶ ገናናው ከበደ (ሃምሳ አንድ ሰዎች)	ጥቅምት 20/2005	29
9	የጡረታ መውጫ እድሜ ወሰንን በተመለከተ አሰሪው ከሠራተኛ ማህበር ጋር የሚያደርገው ስምምነት ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው በተመሣሣይ ጉዳይ ለሠራተኛ በህግ ከተደነገገው ይልቅ የህብረት ስምምነቱ የተሻለ (የበለጠ) ጥቅም የሚያስገኝ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 134(2),24(3) አዋጅ ቁ. 715/2003 አንቀጽ 17(1)	80079	የመቶ አለቃ ጥላሁን ታችበሌ እና ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር	ህዳር 19/2005	35
10	አንድ ሠራተኛ በባህሪው ቀጣይነት ባለው ሥራ ላይ መቀጠሩ መረጋገጡ ብቻ ሠራተኛው ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ የሚያስቆጥረው ስላለመሆኑ፡ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24(1)	79853	የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን እና እነ አቶ ጌታቸው ደበበ (14 ሰዎች)	ህዳር 04/2005	38
11	ሥራና ሰራተኛን ከመምራት እና ከመቆጣጠር ባለፈ በሠራተኛ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድም ሆነ	79212	ሮያል ከረሜላ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና	ጥቅምት 19/2005	43

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ከሥራ ለማሠናበት ስልጣን በሌለው የቅርብ አለቃ ሠራተኛው ሥራ እንዲለቅ የተነገረ መሆኑ የሥራ ውል ተቋርጧል ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 3(2)(ሐ)		ወ/ሪት ፀሐይ ብርሀኑ		
12	የሥራ ውል ወይም በሌላ ሠነድ ሠራተኛው ስምምነቱን ባልሰጠበት ሁኔታ አሰሪ የሆነው አካል እህት ድርጅት ወደ ሆነ ተቋም (ድርጅት) ሰራተኛውን አዛውሮ ለማሰራት አሠሪ መብት የሌለው ስለመሆኑ፣	83068	ዲ.ኤች.ገዳ ብርድልብስ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ወ/ሪት ቅድስት ጌታቸው	ታህሳስ 30/2005	46
13	አንድ ሠራተኛ በሥራው አፈፃፀም ምዘና ደካማ ነው በማለት የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚቻለው ምዘናውን ሠራተኛው በተቀጠረበትና በተመደበበት የሥራ አይነት (መስክ) ላይ በማድረግ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 42, 43(1)	82335	ሆሊ ኤንጀልስ ት/ቤት ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና መ/ር መልካም አለማየሁ	ጥር 01/2005	49
ውል			53		
14	በተዋዋይ ወገኖች በተደረገ የጽሁፍ ሰነድ ላይ የሚገኝ የስምምነት ቃል እንዲሁም በሰነድ ላይ ስለተመለከተው (ስለተፃፈው) ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ውሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው በሚል ለመደምደም የሚቻለው እንደ ውለታው አይነት የጽሁፉ ውል አደራረግን በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በተሟላ ሁኔታ የተዘጋጀና የያዘ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ውሉ በውል አዋዋይ ፊት በህጉ አግባብ ባልተደረገበት ሁኔታ በውሉ ላይ የሠፈሩት ማናቸውም የውል ቃሎች ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዳሉ የሚታመኑና በማናቸውም የሰው ምስክርነት ቃል ማስተካከል አይቻልም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ አንድ ውል በህግ ፊት የፀና ነው እንዲባል በህግ ውሉ የሚደረግበትን አግባብ በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በተመለከተ የተደረገ ካልሆነ በቀር ውሉን መሠረት በማድረግ እንደውሉ ይፈፀምልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ2005(1),1678(ሐ),1719(2,17	78398	እነ አቶ ሽፈራው ደጀኔ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሲሳይ አበቡ	ጥቅምት 19/2005	54

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	23)				
15	የአላቂ ነገር ብድር ውል ጋር በተገናኘ፣ የመመለሻ ጊዜው በግልጽ ተለይቶ የተሰጠን የገንዘብ ብድር በተመለከተ አበዳሪው በውሉ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላ ተበዳሪው የብድሩን ገንዘብ እንዲመለስ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ፣ የብድሩ ገንዘብ መክፈያ ጊዜው በተወሰነ የብድር ውል ስምምነት ገንዘብ የተበደረ ወገን የመክፈያ ጊዜው ካለፈበት (ካበቃበት) ጊዜ ጀምሮ ወለድ ለመክፈል ስምምነት ያልተደረገ ቢሆንም፣ በድሩን ከነ ህጋዊ ወለዱ ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2482(2)(3),2483, 2489(1),1676, 2478	74950	ወ/ሮ ዙብዳ ኑረ ኬርሰማ እና ወ/ሮ ሚሊዮን ዳግም ሙሴ (አራት ሰዎች)	ህዳር 5/2005	58
16	• ከውል አመሰራረትና መቋቋም ጋር በተገናኘ ዝምታ በመርህ ደረጃ ውልን እንደመቀበል ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑና አንድ ውል፣ ተሻሽሏል ለማለት የሚቻለው ማሻሻያው አስቀድሞ በተደረገው የአፃፃፍ ስርዓት አይነት የተከናወነ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ • የግልግል ጉባኤ አንድን ጉዳይ በማየት የዳኝነት መፍትሔ ሊሰጥ የሚችለው ተከራካሪ ወገኖች ከተስማሙበትና የሚፀና ወይም ዋጋ ያለው ግዴታ መኖሩን መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1682,1683,1684,1722,2001 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 356(ሀ)	63063	ኢትዮ ቴሌኮም እና ፒቲኢ ኢንተርናሽናል ኢንኮፖሬትድ	ህዳር 03/2005	62
17	ከውርስ ሽያጭና ከስጦታ ውል የመነጨን የባለቤትነት መብት አስመልክቶ በሚነሣ የንብረት ክርክር የይርጋ ጉዳይ በተነሣ ጊዜ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ለጉዳዩቹ አግባብነትና ተፈፃሚነት ባለው የህግ ክፍል እና የህግ ይዘት ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ	71537	እነ ወ/ሮ የሻረግ ከበደ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ የሺወርቅ መኮንን	ታህሳስ 02/2005	73
18	የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ አመዘጋገብ ጋር በተያየዘ በተፈፀመ ስህተት ንብረቱን በመያዣ የያዘው ወገን የሚደርስበትን ጉዳትና ኪሣራ ኃላፊነቱን በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመወጣት ስህተቱን የፈፀመው የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ጉዳትና ኪሣራውን በመያዣ በተያዘው ንብረት ዋጋ መጠን ለመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1640(2), 3052, 3053(1),3081	75743	የዳንግላ ማዘጋጃ ቤት ፍትህ ቢሮ፣ ዐ/ህግ እና እነ የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 17/2005	78

https://t.me/ethiopianlegalbrief

19	ከዋስትና ውል ጋር በተገናኘ ዋስ የሆነ ወገን በውሉ ላይ የተመለከተውን ፊርማ የእርሱ አለመሆኑን ወይም የውሉን ቃል በተመለከተ በመካድ በግልጽ ባልተከራከረበት ሁኔታ ውሉ በሁለት ምስክር ፊት የተደረገ አይደለም በሚል የሚቀርብ ክርክር የዋሱን ግዴታ ተፈፀሚነት የሚያስቀር ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1727(2) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.83,235	79907	ልዩ የገንዘብ እገዛ ተቋም እና እነ ወ/ሮ የወይንሐረግ ትዕዛዙ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 02/2005	82
20	ገቢ ለማስገኘት በተዘጋጀ ልዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን በተደረገ ጨረታ ተሣታፊ በመሆን የጨረታውን ገንዘብ በመክፈል መፌት ተረክቦ ለልማት ለማዋል በሚል ጨረታው ተወዳድሮ የጨረታው አሸናፊ የሆነ ወገን ጨረታውን ካዘጋጀው አካል ጋር የውል ስምምነት እንዳደረገ የሚቆጠር በመሆኑ በጨረታ ያሸነፈበትን የገንዘብ መጠን ለአዘጋጁ ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ፤ህ/ቁ.1771(1),1688(2),1757	76825	ጭላሎ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የአዳማ ከተማ የባኩ ሸነን ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት	ጥር 14/2005	85
21	በብድር የሚሰጥ ገንዘብ ላይ ተዋዋይ ወገኖች ሊያቋቁሙት ስለሚችሉት የወለድ ምጣኔ (መጠን)፣ የውል ግዴታውን ያልፈፀመ ወይም ያዘገየ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ስለሚከፍለው የኪሣራ መጠን፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1803(2),1790(2),1800,2479(3),2488, 2489	81857	አቶ አብዱልቃድር ጁሐር እና አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ጥር 13/2005	89
22	ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች በመካከላቸው የሚነሣን አለመግባባት (ክርክር) በግልግል ዳኝነት እንዲያይ በሚል በውሉ የተሰየመ አካል በከሰመ ጊዜ ተዋዋዮች በጋራ ስምምነት ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት የሚያይ አዲስ አካል ለመሰየም ከሚችሉ በቀር አስቀድሞ የተሰየመው አካል በመክሰሙ ምክንያት ፍ/ቤት ጉዳዩን በግልግል ለማየት የሚችል አካል ለመሰየም ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.3336(1),3328(2),3337,333 1,3325-3344,3329	80722	የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፓርትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት እና ዲ ኤም ሲ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር	ጥር 01/2005	93
23	ከግንባታ ሥራ ውል ጋር በተገናኘ የሚከፈል ክፍያ የሥራው ባለቤት የሆነው አካል በግንባታው ሂደት የሥራ ትዕዛዞችን እየሰጠ የሥራውን አካሄድ የመወሰንና ሥራውን በሚፈቅደው አይነት እንዲፈፀም የሥራ ተቋራጩን የማዘዝ ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ የሥራ ተቋራጩ ከሥራው ባለቤት ጋር	71972	አቶ ካሣሁን አያሌው እና የምስራቅ ጎጃም ጎዛምን ወረዳ ጤና ጽ/ቤት	ጥር 1/2005	97

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የተደረገውን የግንባታ ሥራ ውል፣ በሥራው ባለቤት በተሰጡት ፕላኖች፣ ግንባታ ዲዛይን አይነቶችና የዋጋና የሥራ ማስታወቂያ መሠረት ግንባታውን የማካሄድ ግዴታ ያለበት በመሆኑ የሥራው ባለቤት በግንባታው ሥራ ውል ሰነዱ ላይ ከተመለከተው ክፍያ ውጪ በተጨማሪነት በባለቤቱ ፈቃድና ትዕዛዞች መሠረት ለተሠሩ ሥራዎች ክፍያ ለመክፈል አልገደድም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በህጉ አግባብ በባለቤቱ የተሰጡ ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዞች የሥራ ውሉ አካል ተደረገው የሚወሰዱ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.3244,3225,(1)(2),3152(1),3266(1),3263,3265(3)				
24	በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት ከወጣው መመሪያ ቁ.3/2004 አፈፃፀምጋር በተገናኘ የንግድ ቤቱን በማከራየት ከሚያገኙት ገቢ ውጪ ሌላ ገቢ የሌለውና በእድሜ አዛውንት የሆነ ተከራይ የኪራይ ውል ሊቋረጥ የማይገባ ስለመሆኑ፣ መመሪያ ቁ.3/2004 አንቀጽ 6(1)	83448	እነ ወ/ሮ ሙሉወርቅ ኃ/ገብርኤል (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሪት ጽጌ መብራቱ	ጥር 30/2005	103
25	• በአንድ ውል የተመለከተን እዳ ለማረጋገጥ ሲባል አዲስ ሰነድ በተዋዋይ ወገኖች የማደራጀት ተግባር የውል መተካት አድራጐት ነው ለማለት የሚቻለው በሁለተኛው ውል በግልጽ የተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ • በባህር ላይ የሚደረግ የማጓጓዣ ውልን አስመልክቶ አጓዡ ለውሉ ምክንያት የሆነው እቃ (ንብረት) ጋር በተያያዘ የሚያቀርበው አቤቱታ ዕቃውን ከተረከበበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በስተቀር በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ፣ የባህር ህግ ቁ.146,203 የፍ/ብ/ህ/ቁ.1826,1828,1829(ሀ)	80642	የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት እና ባርጉባ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ታህሳስ 02/2005	109
26	አንድ ውል የአስተዳዳር ውል ነው ለማለት በህግ ወይም በተዋዋይ ወገኖች ግልጽ በሆነ ቃል የአስተዳደር መ/ቤት ውል ነው የተባለ እንደሆነ ወይም ደግሞ ተዋዋዮቹ ውል ያደረጉበት ጉዳይ ከህዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር ተያያዥና ለሥራ ውሉ አፈፃፀም የአስተዳዳር አካልን (ፍ/ቤትን) ተካፋይነት ያለማቋረጥ የሚጠይቅ መሆኑን እንዲሁም በአጠቃላይ የውሉን አይነትና	80464	ወይራ እንጨትና ብረት ሥራ ኃ/የተ/የሕብረት ሥራ ማህበር እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የንግድና ኢንዲስትሪ ልማት ቢሮ	ታህሳስ 16/2005	113

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ባህሪ፣ የውለታውን አይነተኛ ጉዳይ ብሎም የተዋዋዮችን ማንነት መመልከት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.3132 አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41(1)(መ)				
27	• የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ መብት ውጤት የሚኖረው ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አስር ዓመት ድረስ ነው በሚል የተደነገገው ድንጋጌ የይርጋ የጊዜ ገደብን የሚደነግግ ሣይሆን የመያዣ ውሉ ቀሪ የሚሆንበት ወይም በህግ ውድቅ የሚደረግበት (Lapse of Mortgage Right) ስለመሆኑ፣ • የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘ ባንክ በመያዣው ላይ ያለው መብቱ በይርጋ ቀሪ የሚሆነው የመያዣ ውሉ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ አስር ዓመት ከማለፉ በፊት በመያዣ መብቱ መገልገል ያልጀመረ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3058 (1)(3)	78444	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ ጥጋቡ ተፈራ	ጥቅምት 22/2005	116
28	•በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውል ባለመፈፀሙ ምክንያት የጉዳት ኪሣራ እንዲከፈል በሚል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ በውሉ ለዚሁ ዓላማ ተዋዋዮቹ ካመለከቱት የገንዘብ መጠን በላይ እንዲከፍል ለማስገደድ የማይቻል ስለመሆኑ፣ •የመልካም ሥራ አፈፃፀም ቦንድ መሰረታዊ ዓላማ በውል የተመለከተው ጉዳይ እንደውሉ ስለመፈፀሙ (የሚፈፀም ስለመሆኑ) ለማረጋገጥ ስለመሆኑ፣ •አንድን ዕቃ ማቅረብ ጋር በተያያዘ የተደረገ ውልን አስመልክቶ በአቅራቢው በኩል ከእቃው ዋጋ ጋር በተገናኘ በመንግስት የታወቀ የዋጋ ግሽበት መከሰቱ አቅራቢው ውሉን ሙሉ ለሙሉ ለማቋረጥ የሚያስችለው በቂ ምክንያት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3183(2),3188(1),1731,1734,1732,1889	69797	ወ/ሮ ሂላላ ሱሌማን እና ጎንደር ዩኒቨርስቲ	ታህሳስ 04/2005	121
የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት					**129**
29	አንድ ለእዳ መክፈያነት በአፈፃፀም በጨረታ እንዲሸጥ በተደረገ ንብረት ጨረታ ላይ በመካፈል የጨረታው አሸናፊ ከሆነ በኋላ የጨረታ ሽያጩን ለመፈፀም ያልቻለ ወገን ንብረቱ በቀጣይ	72017	አቶ ጉታ ኤጀታ እና አቶ መሀሪር ረዲ	ጥቅምት 20/2005	130

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በወጣ ጨረታ ቀርቦ ሲሸጥ የተገኘው የሽያጭ ዋጋ ዝቅተኛ የሆነ እንደሆነ የመጀመሪያው ጨረታ አሸናፊ ለተከሰተው የዋጋ ልዩነት ለፍርድ ባለዕዳው በካሣ መልክ እንዲከፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 429				
30	በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ተቋማት (ወገኖች) በድሀ ደንብ ዳኝነት ሳይከፍል በፍ/ቤት ለመስተናገድ የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቋሙ ከሚገኝበት የገንዘብ አቋም አኳያ ተገናዝቦ መታየት ያለበት ስለመሆኑና ተቋሙ የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም (Financial status) ለመለየት ተቀባይነት ስለሚኖረው የማስረጃ አይነት፣ ለዳኝነት የሚከፈለውን ገንዘብ ለመክፈል አልችልም በሚል በድሀ ደንብ ለመስተናገድ የህግ ሰውነት የተሰጠው ተቋም የሚያቀርበው አቤቱታ ሊስተናገድ ስለሚችልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 467	79555	ቤተልሄም ፋርማሲ ቲዩካል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ታህሳስ 02/2005	133
31	• በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43 መሠረት ወደ ክርክር እንዲገባ የተደረገ 3ኛ ወገን በክርክሩ ሂደት ሊያነሣ ስለሚችለው የክርክር አይነትና አድማስ፣ 3ኛው ወገን ሊያነሣ የሚችላቸው የክርክር ፈርጆች በአንድ በኩል ከተከሣሽ ጋር ሆኖ ድርሻ ክፍያ ወይም ስለተከሣሽ ሆኖ የካሣ ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ተቀብሎ በተከሣሽ እግር ተተክቶ ተከሣሽ ለከሣሽ ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን፣ ኃላፊነት አለበት የሚባል ቢሆን እንኳን ሊከፈል የሚገባው የካሣ ክፍያ መጠን ላይ ከከሣሽ ጋር ንጽጽር በማድረግ መሟገት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድርሻ ወይም ካሣ ለመክፈል ለተከሣሽ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም በማለት መከራከር ስለመሆናቸው፤ 3ኛ ወገን ጣልቃ ገብ በክርክር ሂደቱ መሟገት የሚችለው ከተከሣሽ ጋር ብቻ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 አስፈላጊነት ተከታታይ ክስ ሳይኖር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በአንድነት እንዲታዩ በማድረግ የኃላፊነት መጠኑን እንዲሁም ከፋዩን ወገን በመለየት የመጨረሻ እልባት ለመስጠት ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 መሠረት ጣልቃ	79465	ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ እና እነ አቶ አገኘው ገረመው (ሁለት ሰዎች)	ጥር 14/2005	136

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የሚገባ ወገን ከመነሻውም ከተከሳሹ ጋር የህግ ወይም የውል ግንኙነት የለኝም በማለት ክርክር ያቀረበ እንደሆነ በመሳሄድ ላይ ባለው ክርክር ተሣታፊ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የማይኖር ስለመሆኑና ይህን መሰል ክርክር ራሱን በቻለ ሌላ መዝገብ ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43(1),76 የፍ/ብ/ህ/ቁ.1896,1897,1908,1909 የንግድ ህግ ቁ.687,688,683				
32	• የወጪና ኪሣራ ክፍያ ጉዳይ ሊስተናገድ ሊወሰን የሚገባው በዋናው ጉዳይ ፍርድ (ውሣኔ) በተሰጠበት መዝገብ ስለመሆኑ፣ • ወጪና ኪሣራ ክፍያን በተመለከተ ማን መክፈል እንዳለበት በዋናው ጉዳይ ላይ ተለይቶ ከተወሰነ በኋላ ምን ያህል መክፈል እንዳለበት በተመለከተ ደግሞ ዋናው ፍርድ ባረፈበት መዝገብ የወጪና ኪሣራ ዝርዝር ቀርቦ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ስለቀረበው የወጪና ኪሣራ አስፈላጊነት ስለመጠኑ እና በእርግጥም ወጪና ኪሣራ ስለመውጣቱ በተመለከተ የበኩሉን ክርክር ካቀረበ በኋላ የወጪና ኪሣራ ልኩ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 183, 378, 462-464	83701	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት እና ወ/ሮ ህንደያ እንድሪስ ወኪል አብዲ ዓሊ	ጥር 27/2005	140
33	አንድን ክርክር ለማስረዳት የቀረበን ማስረጃ ህጋዊነት አስመልክቶ የሚቀርብ ክርክር ሊቀርብና ታይቶ ሊወሰን የሚገባው በዚያው ዋናው ጉዳይ በቀረበበት ፍ/ቤት ስለመሆኑ፣	74890	ወ/ሮ ሚስጢር ሰለሞን እና እነ አቶ ፍቃዱ ካሣሁን (አምስት ሰዎች)	ጥር 30/2005	142
34	• አንድ መዝገብ ላይ የተከሰሱ ሰዎች የኃላፊነት ምንጩ ከተለያየ የህግ ማዕቀፍ (ክፍል) በሆነ ጊዜ አንደኛው ወገን የተነሣው የይርጋ ክርክር በሌላኛው ወገን እንደተነሣ የማይቆጠር ስለመሆኑ፣ • በአንድ ክስ (መዝገብ) ተጣምረው በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊነት አለባችሁ ተብለው ከተከሰሱ ወገኖች መካከል አንደኛው ወገን የሚያነሣው የይርጋ መቃወሚያ ያለቅድመ ሁኔታ በሌላኛው ተጣምሮ የተከሰሰው ወገን ላይ ተፈፃሚነት አለው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ • በፍ/ብሔር ጉዳይ የአንድነትና የነጣላ ኃላፊነት ከተለያዩ የህግ ክፍሎች እና ከተለያዩ ምክንያቶች ሊመነጭ የሚችል ስለመሆኑ፣	80723	አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማህበር እና እነ ዋቅቶሉ አብደሳ (ሁለት ሰዎች)	ጥር 29/2005	145

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ህ/ቁ.1852 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.244(3),36				
35	• ለተሰጠ የብድር ገንዘብ አመላለስ በመያዣ የተያዘ በኪሣራ የፈረሰ ማህበር (ድርጅት) ንብረት በሀራጅ ጨረታ የተሸጠ በመሆኑ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ እና ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣ • በመያዣ የተያዘውን ንብረት በባንኩ በሀራጅ የተሸጠ በመሆኑ በባለዕዳው በኩል ቢሸጥ የተሻለ ዋጋ ያስገኝ ስለነበረ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ በህግ የተቋቋመ ባንክ በብድር የሰጠው ገንዘብ በአዋጅ ቁ.97/90 እና 216/92 መሠረት አስቀድሞ ለብድሩ አመላለስ ዋስትና ይሆን ዘንድ ከያዛቸው መያዣዎች መካከል አንዱን በመምረጥ በሐራጅ ሊሸጥ ይገባል፣ ለመሸጥ የተንቀሳቀሰበትን የመያዣ ንብረት ከመሸጥ ድርጊት ይታቀብ ይህም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ይሰጥልን በሚል የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ህግን ባለመከተል የፈፀመው ስህተት ቢኖርና በባለዕዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ግን ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባለዕዳው ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ እና ፍ/ቤቶችም ሀራጁን ለማስቆም ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣ • የሰበር ችሎት የሚሰጠው አስገዳጅነት ያለው የህግ ትርጉም አንድ ክርክር የቀረበበት ጉዳይ (ድርጊት) ከተፈፀመ በኋላ ስለሆነ የተሰጠው የህግ ትርጉም በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 394-449,224 አዋጅ ቁ.97/90 አንቀጽ 3,4 አዋጅ ቁ.216/92 አዋጅ ቁ.98/90 አዋጅ ቁ.2584	84353	ጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን አ/ማህበር ሒሣብ አጣሪ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ወጋገን ባንክ አ/ማህበር	ጥር 02/2005	149
36	• አንድ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ብይን መስጠቱ ፍርዱ ለከሣሽ በሚጠቅም መልኩ (መንገድ) የመወሰኑን ሁኔታ በአስገዳጅነት የሚያስከትል ነው ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣	82427	ዩኒስ ቡራሌ ሲ.ጋል የራይስ ጫት ላኪዎች ማህበር እና አቶ አብዲ አልሚ	ጥር 27/2005	155

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• የማህበር ሊቀመንበርን ከስልጣን ለማንሳት ስለሚቻልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 70(ሀ)		መሐመድ		
የንግድ ሕግ					**159**
37	የእሽሙር ማህበር ህጋዊ ሰውነት የሌለው እንዲሁም በጽሁፍ መረጋገጥና ሌሎች የንግድ ማህበሮችን በተመለከተ የተደነገጉት የማስታወቅና የማስመዝገብ ሥርዓቶች የማይፈፀምበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ የእሽሙር ማህበርን አስመልክቶ ማህበሩ እንዲፈረስ በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዬችን አስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የእሽሙር ማህበር የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያደርገው በሽሪኮቹ ስም ስለመሆኑና ሽሪኮቹም እንደተራ ተዋዋይ ወገኖች የሚታዩ ስለመሆናቸው የንግድ ህግ ቁ. 212(1),272	76394	አቶ ወርቁ ወ/ዓዲቅ እና እነ የአቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ወራሾች (ሰባት ሰዎች)	ህዳር 18/2005	160
38	አንድ የንግድ ማህበር (ድርጅት) የሚጨበጥና የማይጨበጥ እንዲሁም የሚንቀሣቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት መብቶች ምን ምን እንደሆኑ በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ስለመሆኑ አንድ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ሥራውን የሚያከናውንበት የንግድ ቦታ ኪራይ መብት የማህበሩ ህልውና ጋር የሚያያዝ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ •የንግድ ድርጅቱ የፈረሰ ቢሆንም የንግድ ሥራውን ሲያከናውንበት የነበረውን ቦታ በሌላ ጉዳይ በፍርድ እንዲለቅ በተወሰነ ጊዜ የማህበሩ ሒሳብ ተጣርቶ አለመጠናቀቅ ቦታውን ላለማስለቀቅ ምክንያት ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ፣	80599	ጀሽዋ ኢነድ ካሌቤ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ወ/ሮ እንቁጣጣሽ አሰፋ	ጥር 15/2005	164
ቤተሠብ					**168**
39	በአንድ ቦታ ከተደረገ በኋላ በሌላ ጊዜ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ እንዲረጋገጥና ማህተም እንዲደረግበት የተደረገ የኑዛዜ ሰነድ በህጉ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት እንደተደረገ ኑዛዜ የማይቆጠር ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.881,882	74734	ወ/ሮ ትዕግስት ሽባባው እና እነ እህት አለማው ወርቁ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 20/20085	169
40	• የኮንዶሚኒየም ቤትን በጋብቻ ወቅት እያሉ የደረሳቸው ባልና ሚስት የቤቱ ቅድመ ክፍያ በጋብቻ ወቅት ከተፈራ	74451	አቶ ደረጀ ማዘንጊያ እና ወ/ሮ ፍሬህይወት	ጥቅምት 20/2005	173

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የጋራ ሀብት የተከፈለ እንደሆነና ቤቱን ለማሳመርና ለሌሎች ተያያዥ ወጪዎች ከጋራ ሀብቱ ወጪ በማድረግ ጥቅም ላይ በዋለበት ሁኔታ ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ እንደሆነ ቤቱ ለተጋቢዎቹ፣ ሊከፋፈል ስለሚችልበት አግባብ፣ • በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን ቤተሰብ የመመስረት መብት በመጠቀም ጋብቻ የፈፀሙ ወንዶች እና ሴቶች በጋብቻው አፈፃፀም፣ በጋብቻው ዘመን እንዲሁም በፍቺ ጊዜ እኩል መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ፣ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 35(1)		ጴጥሮስ		
41	• የኑዛዜን ፎርማሊቲና የይዘቱን ህጋዊነት አስመልክቶ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ተቃውሞውን አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ወገን በሌላ ጊዜ በድጋሚ የኑዛዜው ይዘት ጋር በተገናኘ ተናዛዡ ከውርስ ነቅሎናል፣ እንዲሁም ሊደርሰን ከሚገባው ድርሻ ከ1/4ኛ በላይ ጉዳት ደርሶብናል በሚል ኑዛዜው እንዲሻር የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • ኑዛዜ የህጉን ፎርማሊቲ የጠበቀ ነው በሚል በፍ/ቤት መጽደቅ ኑዛዜው መብታችንን ይነካል በማለት ክርክር የሚያቀርቡ ወገኖች ክርክራቸውን ለዳኝነት አካል ከማቅረብ የማይከለክል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.51, 216, 217 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1123	77169	እነ አቶ ተሾመ ገበየሁ እና ወ/ሮ ሊሻንወርቅ ገበየሁ	ጥር 17/2005	176
42	የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው ቀደም ሲል ጋብቻ የነበረው እንደሆነ የጠፋው ሰው መመለስ በመጥፋት ውሣኔው የፈረሰውን ጋብቻ እንደገና ተመልሶ ህይወት እንዲዘራ (እንዲፀና) የማድረግ ውጤት አለው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ በፍ/ቤት የተሰጠ የመጥፋት ውሣኔ መሻር በመጥፋት ውሣኔው መሠረት የፈረሰን ጋብቻ ከፈረሰበት ቀን ጀምሮ (ግለሰቡ ከተመለሰበት ቀን ጀምሮ) መልሶ እንዲቋቋም (እንዲፀና) ለማድረግ የሚያስችል ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.170,171	74791	ወ/ሮ ውቢት ሕሩይ እና የሀዋሣ ከተማ ፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት	ጥር 17/2005	180
43	አንድ ወራሽ የወራሽነት መብት በሌለው ንብረት ላይ ከህግ ውጪ የወራሽነት ሠርተፍኬት መያዙ በተረጋገጠ ጊዜ ይኸው ማስረጃ እንዲሰረዝ አቤቱታ ሊቀርብ ስለመቻሉ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.998(1)	73247	አቶ ልዑል ኪዳነማርያም እና እነ ሰብለ ኪዳነማርያም	ጥር 14/2005	184

https://t.me/ethiopianlegalbrief

			(ሶስት ሰዎች)		
ጉምሩክ/ግብር/ ታክስ				**187**	
44	• በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቅቆ ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ወይም ወደ ውጪ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ የቀረበ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ • "የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተጠናቀቀ" ማለት ስለሚቻልበት አግባብ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 66(1), 2(17),66(29),66(2)	71070	ተሸአብ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን	መስከረም 21/2005	188
45	የተሸከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው በተሸከርካሪው የተፈፀመ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ህግን የመጣስ ወንጀል ከራሱ እውቀት ወይም ፈቃድ ወጪ መሆኑን ማስረዳት የቻለ እንደሆነ የተፈፀመው ወንጀል ክብደት እየታየ የገንዘብ መቀጮ ከፍሎ ተሸከርካሪው ሊለቀቅለት (ላይወረስ) የሚችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 109(1) የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መመሪያ ቁ.50/2003 አንቀጽ 6(2)	76976	የጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና አቶ ሊሻን ከተማ ገብሬ	መስከረም 22/2005	191
46	•የውጭ ምንዛሬ ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ አገር ያለህጋዊ እውቅናና ፈቃድ ማስወጣት የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣ •የወንጀል ድርጊትን የፈፀምኩት ባለማወቅ ነው በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለውና ህግን አለማወቅ ይቅርታ የማያሰጥ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 99 አዋጅ ቁ. 591/2000 አንቀጽ 20(3) የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22(1) የወንጀል ህግ አንቀጽ 2(2),25,23(2),81(1)(3)	80296	አቶ ሳምሶን መንግስቱ እና የፌደራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ጥር 30/2005	194
ንብረት				**199**	
47	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ህጋዊነትና ተቀባይነት ጋር በተናኘ የምስክር ወረቀቱ ሊሰጥ የቻለው የንብረት ባለሀብትነት መብትን ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው እንዴት መተላለፍ እንዳለበት በህጉ የተመለከተውን ደንብና ሥርዓት ሳይከተል ስለሆነ የንብረቱ ባለሀብት ስለመሆን የህግ ግምት መውሰጃ የሆነው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ቀሪ ነው፣ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት ሊረጋገጥ የሚችል	75414	ወ/ሮ ዋሪቴ ቡቡሳ እና እነ የጎልጆታ ከተማ አስተዳደር (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 22/2005	200

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የዳኝነት ጥያቄ እንጂ ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል አይደለም ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1195,1196				
48	በአንድ ወቅት የነበረን የተገነባ የመንገድ ደረጃ መነሻ (መሠረት) በማድረግ በመንገዱ ግራ ቀኝ አዋሣኝ በሆነ ይዞታ ላይ ተገቢውን ርቀት በመጠበቅ ንብረትን ያፈራ ሰው በሌላ ጊዜ የመንገዱ ደረጃ ከፍ እንዲል በመደረጉ የተነሣ በአዋሣኝ ይዞታው ላይ ግለሰቡ ያፈራቸው ንብረቶች ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ፣ ጉዳት ያደረሰው ወገን ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት (የሚኖርበት) ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 65/1936 አንቀጽ 2(ሀ) አዋጅ ቁ. 66/1936 አንቀጽ 1(ለ) አዋጅ ቁ. 455/1997,የኤ.ፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(8)	75343	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ በላይ ሀሰን	ህዳር 17/2005	204
49	አንድ ሰው የሌላ ሰው ንብረት ይዞ ሲጠቀም ከቆየና ንብረቱን በሚጠቀምበት ጊዜ ንብረቱን ከጥፋት ወይም ከብልሽት ለማዳን ሲል ተገቢውን ወጪ ያወጣ እንደሆነ ይኸው ወጪ በህጋዊ ባለሀብቱ እንዲተካለት ለመጠየቅ የሚችለው ወጪው የግድ አስፈላጊ ከሆነና በቅን ልቦና የተደረገ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ ወጪው በክፉ ልቦና የተደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ግን እቃውን (ንብረቱን) እንዲመልስ የተደረገው ሰው እንዲተካለት የጠየቀውን ወጪ መጠን ዳኞች ሊቀንሱት ወይም ጭራሹንም ሊያስቀሩት የሚችሉ ስለመሆኑ፣ በንብረቱ (እቃው) ላይ የተደረገው ወጪ «በክፉ ልቦና የተደረገ ነው» የሚባለው ወጪው በተደረገበት ጊዜ (ወቅት) ወጪው እንዲተካለት የሚጠይቀው ሰው ንብረቱን (እቃውን) ለባለቤቱ ለመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያወቀ እንደነበር ወይም ማወቅ ይገባው የነበረና ርትዕም ሲያስገድድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2172(1),2171(1),2168,2169	81081	ወ/ሮ ፍሬህይወት መብራህቱ ገ/መድህን እና እነ አቶ መብራህቱ ገ/መድህን /ሁለት ሰዎች/	ጥር 13/2005	207
50	• የመኪና ሽያጭ ውል መደረጉን (መኖሩን) ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት፣ • የመኪና /ተሽከርካሪ/ ባለሀብትነት (ስመ ሀብት) እንዲተላለፍለት የሚጠይቅ ሰው ሊያቀርባቸው ስለሚገቡና	81406	እነ አቶ አህመድ ኢብራሀም (ሁለት ሰዎች) እና አቶ አመሀ ተ/ወይኒ	ጥር 13/2005	211

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ተቀባይነት ስላላቸው ማስረጃዎች አንድ ግዴታ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ፣ • አከራካሪ ሆኖ የቀረበን አንድ ፍሬ ነገር ማስረዳት ስለሚቻልበት የማስረጃ አይነት አግባብነት ባለው ህግ በተለይ የተቀመጠ ግለጽ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ ማናቸውንም ዓይነት ማስረጃ አቅርቦ ጉዳዩን ለማስረዳት ስለመቻሉ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1186(1),(2),2001(1) ስለ ተሸከርካሪ መለያ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁ.681/2002 አንቀጽ 6(3)(4)				
51	የመሬት ባለ ይዞታ የሆነ አርሶ አደር ይዞታውን ላለበት እዳ ለ3ኛ ወገን በመያዣነት ለመስጠት ወይም በስጦታ የቤተሰብ አባል ላልሆነ ሰው ለማስተላለፍ መብት የሌለው ስለመሆኑ፣ በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ እና/ወይም የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ ከመነሻው ውጤት የሌለውና ፈራሽ ስለመሆኑ፣ • የውሉ መሠረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 130/99 አዋጅ ቁ.89/89 አንቀጽ 2(3) አዋጅ ቁ. 456./97 አንቀጽ 8(2),1)	79394	አቶ አብደላ ኢብራሒም እና አቶ ኡሶ አብዲ	ጥቅምት 06/2005	215
	ከውል ውጭ ኃላፊነት				**218**
52	• የፌዴራልና የክልል ከተማ አስተዳዳር አካላት የግንባታ ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት የቴሌኮሚኒኬሽን ወይም የኤሌክትሪክ ሀይል አውታር ስለመኖሩ እንዲሁም ፈቃድ ጠያቂው አካልም ግንባታን ከማካሄዱ በፊት በቴሌኮሚኒኬሽንና በኤሌክትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑና በዚህም የተነሳ በቸልተኝነት ግንባታ በማከናወን ጉዳት ያደረሰ ወገን በኃላፊነት የሚጠየቅ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.464/97 አንቀጽ 3(3) የፍ/ብ/ህ/ቁ.	77238	ኢትዮ ቴሌኮም እና አቶ ንጉሴ ተፈራ	ህዳር 03/2005	219

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	2027(1),2035(1),2028(1),2091 አዋጅ ቁ.49/89 አንቀጽ 23(1)				
የዳኝነት ሥልጣን			223		
53	• አንድ ሰው በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለማስወሰን የሚችለው ከህግ የመነጨ መብት ያለው መሆኑን በክሱ ውስጥ በዝርዝር በፍሬ ነገር ደረጃ ማመልከት የቻለ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ • ሀይማኖታዊ (መንፈሣዊ) ትምህርት ለመስጠትና ለማሰልጠን በሚል ከሚቋቁሙ ተቋማት ጋር በተገናኘ በተማሪነት ማን እንደሚመለመል፣ ምን ምን መስፈርቶች ሊሟሉ እንደሚገባ፣ የመሰፈርቶቹ መሟላትና አለመሟላት እንዲሁም በተቋሙ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች ከትምህርት አቀባበል ሂደት ወቅት ሊገልጿቸው ስለሚገቡ የዲሲፕሊን ጉዳዬች ወዘተ በሀይማኖት ተቋማቱ የሚወሰን ስለመሆኑና ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮችን መደበኛ ፍ/ቤቶች አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣ • የግለሰብ ፍትህ የማግኘት መብት በፍ/ቤቶች ተግባራዊ ሊደረግ የሚችለው በፍርድ ሊያልቁ የሚባቸው ጉዳዬችን በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37	77479	የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቅድስት ሥላሴ መንፈሣዊ ኮሌጅ እና አቶ አሰግድ ሣህሉ	ጥቅምት 06/2005	224
54	የፌዴሬሽን ምክር ቤት የኢፌዴሪ ህገ መንግስትን ለመተርጉም ባለው ስልጣን ተጠቅሞ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና ጉዳዩ በሚመለከተታቸው አካላት መከበርና መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ፣ የፐራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቦርድ የሚቀርብለትን አቤቱታ ህጋዊነት መርምሮ በመወሰን ሂደት ከፊል የዳኝነት ስልጣን ያለው አካል (quasi judicial body) እንደመሆኑ መጠን በህገ መንግስቱ የተጠበቁትን ፍትህ የማግኘት፣ የመሰማትና በእኩል ሚዛን የመታየት (የመዳኘት) መብት በሚያስከበር መልኩ ክርክሮችን ሊያስተናግድና ሊወስን የሚገባ ስለመሆኑ፣ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 62(1),37 አዋጅ ቁ. 251/93 አንቀጽ 3(1),56(1) አዋጅ ቁ. 87/86 አንቀጽ 8,9	43511	እነ የአቶ ዋሲሁን መኮንን ሚስትና ወራሾች /8 ሰዎች/ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ጥቅምት 23/2005	228

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337, 336, 339				
55	የአቃቤ ህግ ሙያን በሸመት የሚያከናውኑ ሰዎች ጋር በተገናኘ ቅጥር፣ ዝውውርና የደረጃ እድገትን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የተሰጠው አካል የአቃቤያነ ህግ አስተዳደር ጉባኤ ስለመሆኑና መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣ ደንብ ቁ.24/99 አንቀጽ 46(3), 41, 44, 2 (4) አዋጅ 568/2000 አንቀጽ 2(7),3,10(1),4,5 የአ/አ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁ.6/2000 አንቀጽ 2(5)(ሐ)	75034	አዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮ እና አቶ መኮንን ተክሉ	ህዳር 03/2005	234
56	• የፍ/ቤቶች የግዛት ስልጣን በዋነኛነት መሠረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረበት ቦታ ለተከራካሪ ወገኖች የሚኖረውን አመቺነት ሲሆን የሥረ ነገር ስልጣን መሠረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ይዘት፣ የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ጥቅም ክብደትና መጠን እንዲሁም የጉዳዩን የውስብስብነት ደረጃ ስለመሆኑ፣ • ፍርድን የማስፈፀም ጉዳይ በስረ ነገር ክርክር ተረጋግጠው የፍርድ ሀይል ያገኙትን የተከራካሪ ወገኖች መብቶችና ግዴታዎች በሥነ ሥርዓት ህጉ የተደነገገውን የአፈፃፀም ስርዓት ተከትለው እንዲፈፀሙ ከማድረግ ውጪ አዲስ መብትና ግዴታ የሚቋቋምበት ሂደት ስላለመሆኑና የማስፈፀም ስልጣን በመርህ ደረጃ የፍ/ቤቶች የሥረ ነገር ስልጣንን የሚከተል ስለመሆኑ፣ • አስፈላጊ እና ተገቢ በሆኑ ሁኔታዎች ሥረ ነገሩን የወሰነ ፍ/ቤት በአፈፃፀም ጉዳዮችን በውክልና የሥረ ነገር ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ሊያስተላልፍ ስለመቻሉ፡ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(2) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371, 372, 9, 10	75788	እነ አቶ በረከት ኃ/ኪሮስ (ሶስት ሰዎች) እና አቶ ጎይቶም ኃ/ኪሮስ	ህዳር 05/2005	238
57	የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ (የኮንትራት) ሠራተኞች ቅጥር ጋር በተገናኘ በሠራተኛ እና በቀጣሪው መካከል የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ የመደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በቀጥታ ክስም ሆነ በይግባኝ ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 22(3) ,2(1)	81963	አቶ አስፋው ጉደታ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	ታህሳስ 03/2005	242

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፌዴራል መንግስት ጊዜያዊ የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ				
58	በአዋጅ ቁ. 515/1999 መሠረት የተቋቋመና የሚተዳደር የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች የሚያቀርቡትን ክርክር በተመለከተ ተቋሙ በራሱ ገቢ የሚተዳደር በመሆኑ ምክንያት አዋጅ ቁ. 377/96 ን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን የመደበኛ ፍ/ቤቶች ለማየት ስልጣን አላቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አዋጁ ቁ. 515/99 አዋጅ ቁ. 553/99 አንቀጽ 6(1), 14(2)(ለ) አዋጅ ቁ. 545/99	80005	የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ እና አቶ ቦጋለ ዱንፋ	ጥቅምት 09/2005	245
59	የግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ መብት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ክርክርን ለማየት ስልጣን ያለው አካል የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ስለመሆኑ፣ • የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የቀረበላቸውን ጉዳይ በህጉ አግባብ ያስተናገዱና ውሣኔ የሰጡ መሆኑን የማረጋገጥና የመቆጣጣር ኃላፊነትና ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.9,231 አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10(22) አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2(1) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 142, 147 አዋጅ ቁ. 345/95 አዋጅ ቁ. 209/55 አዋጅ ቁ. 715/2003 ደንብ ቁጥር 202/2003	83425	አብጀታ ሻላ ሶዳ አክሲዮን ማህበር እና አብጃታ ሶዳ አሸ መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር	ጥር 02/2005	248
ወንጀል				**254**	
60	በወንጀል ጉዳይ የወንጀል ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር ጋር በተገናኘ ፖሊስ የወንጀል ድርጊቱን ፈጽሟል በሚል የተጠረጠረ ሰው ላይ የሚያደርገው ምርመራ የይርጋ ጊዜውን የሚያቋርጠው ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ.221 106(1), 420(2), 271 (1)(ሠ) 219 (2)	77097	እነ አቶ ሀይላይ ተክሉ (ሁለት ሰዎች) እና የመቀሌ ከተማ ሰሜን ምድብ ዐ/ህግ	ጥቅምት 20/2005	255
61	አንድ ተከሳሽ የተከሰሰበትን የወንጀል ክስ ይዘት በሚገባ ተረድቶና አድራጎቱን	77842	አቶ ሳሚ ሁሴን እና	ታህሳስ 03/2005	258

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በተመለከተም እንደቀረበበት የወንጀል ክስ በዝርዝር መፈፀሙን ገልፆ በማመን የእምነት ቃሉን ሰጥቷል በሚል መነሻ በተከሣሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ በአግባቡ ተሰጥቷል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ ፍ/ቤቶች ተከሣሹ የቀረበበትን ክስ በተመለከተ በድርጊቱ አፈፃፀም ረገድ የገለፀውን ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታ በመዝገብ ላይ ባለማስፈር በደፈናው ክሱን አምኗል በማለት የሚሰጡት የጥፋተኛነት ውሣኔ ተገቢ ስላለመሆኑ፣ የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ.134(1) የወ/ህ/አ.23		የፌዴራል ዐቃቤ ህግ		
62	• ተከሳሽ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ሊያቀርባቸው ስለሚችላቸው መከራከሪያዎች • ተከሳሽ በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት የሚያቀርባቸው መቃወሚያዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130 ላይ የተመለከተቱት ጉዳዬች ጋር ብቻ በተገናኘ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ • ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ የማይችልና ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ተፈፃሚ በነበረው ህግ ከተመለከተው የቅጣት ጣሪያ በላይ ሊቀጣ የማይችል ስለመሆኑ፣ • የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑና ዳኞች ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ክስ የቀረበበት ድርጊት ወንጀል ስለመሆኑ የሚደነግገው ህግ ፀንቶ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑን ከተረዱ በማናቸውም ጊዜ አንስተው ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉ ስለመሆኑ፣ • ፍ/ቤቶች በዐ/ህግ የቀረበ የወንጀል ክስ በህገ-መንግስቱና በወንጀል ህጉ የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር የተቀመጡ መርሆዎችና ድንጋጌዎችን የሚያሟሉ መሆን አለመሆኑን በመመርመር የመወሰን ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ፣ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 5(2) ,13(1), 22(1) የወ/ህ/አ. (414/96)3,402,419,5(2) የወ/ህ/ቁ.(214/74)	73514	ተስፋዬ ጡምሮ እና የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ	ህዳር 06/2005	261

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት (ICCPR) አንቀጽ 15(1) የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 130(2)(1)				
63	አንድ የንግድ ድርጅት (ማህበር) የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግንና ማሻሻያውን ተላልፏል በሚል በወንጀል ጥፋተኛ ሊሰኝና ሊቀጣ ስለሚችልበት አግባብ፣ የህግ ሰውነት የተሰጠው (legal personality) ድርጅት የወንጀል ተካፋይ ሊሆን የሚችልበት አግባብ፣ • የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው ኃላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም ህጋዊ ግዴታን በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ ስለመሆኑና የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተከስሶ የጥፋተኝነትና የቅጣት ወሣኔ እስከተሰጠበት ድርስ ድርጅቱ የወንጀሉ ተካፋይ እንደሆነ የሚቆጠር ስለሆነ ጥፋተኛ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ. 34(1),(2) አዋጅ ቁ. 285/95 አንቀጽ 56(1)	74237	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና አብካለ እንደሻው ጠቅላላ የንግድ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር	ጥቅምት 19/2005	266
64	• ፍ/ቤቶች በወንጀል ረገድ የሚሰጧቸው ማናቸውም ውሣኔ በወ/ህ/አ. 2 የተደነገገውን የህጋዊነት መርህ መሠረት በማድረግ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ • ፍ/ቤቶች በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በሚል ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉት በወንጀል ህግ በግልጽ የተደነገገ ድንጋጌ የተመለከተ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ • በወንጀል ጉዳይ አንድ ንብረት (ሀብት) እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ሊወሠን የሚችለው ንብረቱ (ሀብቱ) አንድን ሰው ለወንጀል ሥራ እንዲያነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳው ወይም ደግሞ ወንጀሉን ለፈፀመበት ዋጋ እንዲሆነው የተሰጠው ወይም ሊሠጠው የታቀደን ማንኛውም ጥቅም የተመለከተ ንብረት (ሀብት) ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ ወይም ንብረቱ (ሀብቱ) የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም ያገለገለ	75387	እነ አቶ ወርቁ ፍቃዱ (ሁለት ሰዎች) እና የቤ/ን/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ህግ	ጥር 17/2005	271

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ወይም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች ጋር የተያያዘ ወይም የተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ. 98,100,140, 2(1) (2)				
65	• በወንጀል ጉዳይ ተከሰሶ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በቅጣት አወሣሠን መመሪያው የተሸፈነ እንደሆነ ቅጣቱ በመመሪያው አግባብ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ • በወ/ህ/አ 539(1)(ሀ) ድንጋጌ ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን ሊቀነስለት የሚገባ ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ. 539(1)(ሀ) የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ቁ.1/2002 አንቀጽ 16(7)	82572	መሪጌታ ፍቅረማርያም ካሴ እና የቤንች ማጂ ዞን		274
ባንክና ኢንሹራንስ				**278**	
66	መድን ሰጪ የሆነ አካል በመድን ውሉ ለተመለከተው አደጋ ብቻ ለመድን ገቢው የመድን ሽፋን ለመስጠት የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁ. 663(1),665(1)	76977	ኒያላ ኢንሹራንስ (አ.ማ) እና እነ አዋሽ ኢንሹራንስ (አ.ማ) (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 07/2005	279
አፈፃፀም				**283**	
67	• በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰው ሰው ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ንብረቱ በቅጣት ለመንግስት እንዲወረስ በተወሰነ ጊዜ በአፈፃፀም ደረጃ ከአጥፊው (ወንጀለኛው) ንብረት ውስጥ ለቤተሰቡ ህይወትና መተዳደሪያ ሊውል የሚገባውን ድርሻ ለመወሰን ስለሚቻልበት አግባብ፣ • በውርስ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ከተወሰነው የአጥፊው (የወንጀለኛው) ሀብትና ንብረት ውስጥ ለቤተሰቡ ህይወት መተዳደሪያ ሊውል የሚገባው ድርሻ ሊሸፍናቸው የሚገባው የወጪ አይነቶችና መጠናቸው፣ • የአጥፊው (ወንጀለኛው) ጋር ጋብቻ የመሠረተ ሰው እንዲወረስ ከተወሰነው ንብረት ግማሽ ድርሻ የነበረው መሆኑን መሠረት በማድረግ በአፈፃፀም የሚያነሣው የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ጥያቄው እንደ መብት አቤቱታ	79860	ወ/ሮ ራኬብ መለሰ እና የፌደራል ዐቃቤ ሕግ	ህዳር 06/2005	284

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሊቀርብበት የማይችል ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 98(ለ)(መ), 98(3)(ለ)				
68	ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተገናኘ በአንድ በቀረበ የዋና ጉዳይ ክርክር ሒደት የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ንብረት በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ በአፈፃፀም ደረጃ በተጠቃሹ ንብረት ላይ አፈፃፀም እንዲቀጥል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ ቀደም ሲል በዋና ጉዳይ ክርክር በፍ/ቤት ትእዛዝ እንዲታገድ የተደረገ መሆኑ የታወቀ ንብረት ላይ በድጋሚ በተመሳሳይ ንብረት ላይ መብትን ለማስከበር በሚል በሌላ ጊዜ በአፈፃፀም ደረጃ የሚቀርብ ጥያቄ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣	81616	ወጋገን ባንክ አ.ማ. እና እነ ወ/ሮ ሠላማዊት ጥላሁን /ሁለት ሰዎች/	ጥር 15/2005	288
አእምሯዊ ንብረት				**291**	
69	ባለ ሶስት አውታር (three dimention) ቅርጽ ሥራ ከባለቤቱ ፈቃድና ፍላጐት ውጪ በወረቀት ላይ እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ማድረግ የቅጂ መብት ጥሰት የሚያስከትል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀጽ 34(4)	78856	የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወዳጆችና ቤተሰቦች ማህበር እና አቶ ኤሊያስ አሰጋሽኝ	ታህሳስ 15/2005	292
ልዩ ልዩ				**297**	
70	• ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተገናኘ በወንጀል ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ የተጣለበትን ቅጣት ፈጽሞ ያጠናቀቀ ሰው በፍርድ ቤት መሰየም በግለሠቡ የጡረታ መብት ላይ ስለሚኖረው ውጤት • በመሰየም ሊገኝ የሚችለው መብት ግለሰቡ ከመሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረውን መብት ሳይሆን ግለሰቡ ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ፊት ሊጠበቅለት የሚገባውን መብት በተመለከተ ብቻ ስለመሆኑ፣ • የመንግስት ሰራተኛ የነበረና የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሠው በወንጀል ጉዳይ ተከስሶና ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ በፍ/ቤት ቢያንስ የ3 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት የተወሰነበት በመሆኑ የጡረታ መብቱን እንዲያጣ የተደረገ ሠው ከቅጣቱ በኋላ በፍ/ቤት መሰየሙ አስቀድሞ በቅጣት ቀሪ ሆኖበት የነበረውን የጡረታ መብቱን መልሶ ለማግኘት የማያስችል ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አ. 231,235(1),232 አዋጅ ቁ. 209/55	61221	አቶ አክለ ምህረቱ እና የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	መስከረም 22/2005	298

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 5/67 አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 52/1/				
71	• ከጡረታ መብት ጋር በተገናኘ በሠራተኞች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ለማየት ስልጣን ያለው አካል የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተቋም ስለመሆኑና በኤጀንሲው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ሠራተኛ ቅሬታውን ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ • የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ በፍሬ ነገር ረገድ የመጨረሻ ስለመሆኑና በውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ቅሬታ ያለው ሠራተኛ አቤቱታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቀ. 714/2003 አንቀጽ 56(1) (4), 57	72928	አቶ አበራ ኪዳኔ እና የጋሞ ጎፋ ዞን አርባ ምንጭ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ቅ/ጽ/ቤት	ጥቅምት 09/2005	303
72	• ከጡረታ መብት አበል ተጠቃሚነት ጋር በተገናኘ የእድሜ አቆጣጠርና ውጤቱን በተመለከተ የሚቀርብ አቤቱታን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያለው የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ተቋም ስለመሆኑና በውሣኔው ቅሬታ ያለው ወገን ለኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ • በኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጥ ውሣኔ በፍሬ ነገር ደረጃ የመጨረሻ ስለመሆኑና በውሣኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለው በማለት አቤቱታ ያለው ሠራተኛ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 714/2003 አንቀጽ 4(1),54(3),56(4) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343, 9, 231	80964	የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና እነ አቶ አበረ ቦካን (ሶስት ሠዎች)	ጥቅምት 23/2005	305
73	የመንግስት ዩኒቨርስቲ መምህራንን በተመለከተ ከዲሲፕሊን ግድፈት ጋር በተገናኘ የሚሰጥ ውሣኔ በአስተዳደር ፍ/ቤት በይግባኝ ሊስተናገድ ስለሚችልበት አግባብ፣ አዋጅ ቁ. 515 /99 አንቀጽ 2(8),22(3),32(3) አዋጅ ቁ. 650/2001 አንቀጽ 44(ጎ)	78945	ደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ እና መምህር ባዬ ዋናያ የዳ	መስከረም 22/2005	311
74	• በባንክ በመያዣነት የተያዘ ተሽከርካሪ በሌላ በኩል የጉምሩክ ደንብ በመተላለፍ ወንጀል ባለቤቱ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦበት ተሽከርካሪውም	81215	ወጋገን ባንክ (አ.ማ.) እና የኢትዮጵያ	ጥር 03/2005	315

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በመንግስት እንዲወረስ ውሣኔ የተሰጠበት እንደሆነ በህግ ፊት ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊፈፀም ስለሚገባው ጉዳይ • በባንክ በመያዣነት የተያዘ ተሽከርካሪ ከመያዣው በኋላ በኮንትሮባንድ ወንጀል ምክንያት ለመንግስት ውርስ እንዲሆን በፍ/ቤት የመጨረሻ ፍርድ ባረፈበት ጊዜ ባለመያዣው በተሽከርካሪው ላይ ያለው የቀዳሚነት መብት እንዲሁም የውርስ ትዕዛዙ (ውሣኔው) ተፈፃሚ ሊደረጉ ስለሚችልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2828, 2857(1), 3059 አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 የወንጀል ህግ አንቀጽ 98(1) አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 91(2)		ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን		
75	• የሥራ ግዴታን ካለመወጣት ጋር በተገናኘ ሠራተኛ የሆነ ሰው ከአሰሪው የተረከበው ንብረት ላይ ጉዳት እንዲከሰት በማድረጉ ወይም ንብረቱ እንዲጐድል (እንዲጠፋ) በማድረጉ ምክንያት በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠ እንደሆነ በተመሣሣይ ጉዳይ ሠራተኛው በአሰሪው ንብረት ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠን በፍትሐብሔር ሊጠየቅ ስለመቻሉ፣ • ከአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሠራተኛው በአሰሪው ንብረት ላይ የደረሰ ጉዳትን በተመለከተ በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ ጉዳት የደረሰበትን ንብረት በተመለከተ በፍትሐብሔር ተጠያቂ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 515 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149	78414	የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እና እነ አቶ ቶላ መገርሣ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 07/2005	321
76	አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በህጉ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበስብ ሊፈቀድ የማይችል ስለመሆኑ፡ አዋጅ ቁ. 621/2001 አንቀጽ 2(2),(3)(4),14(5), 14(2), 6, 90, 111(2), 112,108,110, ደንብ ቁጥር 168/2001 አንቀጽ 18(3),10(2),36	74036	የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ እና የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ	መስከረም 23/2005	325

https://t.me/ethiopianlegalbrief



https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ - 16

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሣኔዎች ለፍ/ቤቶች፣ለሕግ ባለሙያዎች፣ ለሕግ ትምህርት ቤቶችና በአጠቃላይ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ጥረታችን ቀጥሏል።

በዚህ ቅጽ 16 በ2006 ዓ.ም. የተሰጡ ውሣኔዎችን በድረ ገጻችን አስቀምጠናል፤ ታትሞም በቅርቡ ይሠራጫል ቅጽ 15 የታተመው ሐምሌ 2006 ዓ.ም. በመሆኑ የዚህ የአሁኑ ዕትም ውሣኔዎች በአንባራዊነት ቶሎ ማሠራጨት ተችሏል። ከዚህ ባነሰ አጭር ጊዜያት ውስጥ ውሣኔዎችን አሣትሞ ለማሠራጨት ብርቱ ጥረት እያደረግን ሲሆን የዚህን ዕትምና የቀደሙትን ቅጾች ውሣኔዎች በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረ ገጽ (www.fsc.gov.et) ማግኘት እንደሚቻል እያስታወስኩ በውሣኔዎቹ ጥራትም ሆነ ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ገንቢ አስተያየቶች እና ትችቶች ለሥራችን መሻሻል ስለሚያግዙን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን በአክብሮት እገልጻለሁ።

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ2006 ዓ.ም. የሰበር ችሎት

የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
የፍትሐ ብሔር ህግ ሥነ-ሥርዓት					1
1.	አንድ ክስ እንደቀረበ የሚቆጠረው ክስ የቀረበበት ጽሁፍ በፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ በመሆኑ፡- የመስቀለኛ ይግባኝ ክርክር ስለሚመራበት የህግ አግባብ፣ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚቀርብን መስቀለኛ ይግባኝን በተመለከተ በህግ በግልፅ የተቀመጠ ድንጋጌ ባለመኖሩ ምክንያት በመደበኛነት የተቀመጡት የስነ ስርዓት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ መሆን ያለባቸው ስለመሆኑ፣መልስ ሠጪው ወገን የሚያቀርበው ይግባኝ ማመልከቻ ግልባጭ ለይግባኝ እንዲደርስ ሊደረግ የሚቻለው ይግባኙ ያልተሰረዘ ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 213(1) ፣337 ፣338 ፣ 340(2)	92043	ቱሌን ዩኒቨርሲቲ አሲስታንስ ፕሮግራም ኢትዮጵያ እና ዶ/ር ዮዲት አብርሃም	መጋቢት 22/2006	2
2	አንድን ሰው በመወከል በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመሟገት በህጉ የተቀመጠውን የዝምድና ደረጃ ወይም በህጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ የውክልና ስልጣን የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 58(ሀ)፣63	91493	አቶ አየለ ሚናሞ እና አቶ አሰፋ ባዩ	ሰኔ 03/2006	5
3.	በአንድ ክርክር ችሎት በመታየት ላይ ያለን ጉዳይ በሌላ ችሎት ተያያዥነት ባለው ጉዳይ ውሳኔ ተሠጥቶ ከሆነ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የተላለፈውን ውሳኔ በአግባቡ	94293	ሸዋ ንግድና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና	ሚያዝያ 9/2006	9

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	በማጨን በጭብጥነት ሊይዘው ስለሚችልበት አግባብ፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.247 እና 248		አቶ አሸብር አበበ		
4.	ከጭብጥ አያያዝ ጋር በተገናኘ በአንድ ወገን ተቆጥሮ የቀረበን ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በሚል ወይም ህጋዊ ተቀባይነት ባለው ሌላ ምክንያት መሰማት አይገባውም የሚል ግልፅ ትእዛዝ ሳይሰጥበት የክርክሩ ጭብጥ በአንደኛው ወገን ማስረጃ ላይ ብቻ ተመስርቶ ውሳኔ እንዲያገኝ መደረጉ ተገቢ የክርክር አመራር ስርዓት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 255፣257፣258፣259	95026	አቶ ዮናስ በቀለ እና አቶ ብርሃኑ ኩምሳ	መጋቢት 8/2006	13
5	ክስ በሚሰማበት ወቅት የቀረ ከሳሽ ፍ/ቤቱን በበቂ ሁኔታ የቀረበትን እክል ካስረዳ ፍ/ቤቱ መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ሊያደርግ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74(2)	97555	ወ/ሮ ሳኒያ ከድር እና የኮሪያ ዘማቾች ቤተሰቦች ሽመናና ስጋጃ ስራ	ሐምሌ 14/2006	15
6	ተሻሽሎ በቀረበው ክስ ላይ ግራ ቀኙ መልስ እንዲሰጡበት ሳይደረግ እና የመከላከያ መልሳቸውን ሳያቀርቡ ተሻሽሎ የቀረበውን ክስ መሰረት አድርጎ ፍርድ መስጠት ተገቢ ስላለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1)(ሠ)(መ)፣91(1)	95620	በቂርቆስ ክ/ከተማ የወረዳ 7 አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ ፤ አለቃ ከድር አህመድ (አራት ሰዎች)	ግንቦት 07/2006	18
7	በተከራካሪ ወገኖች በአንድ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የእርማት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው ውሳኔ ያረፈበት ነጥብ ላይ ብቻ ስለመሆኑ፣ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208	95649	ወ/ሮ ኢትዮጵያ ንጉሴ እና አዲስ ጡብ ማምረቻ ድርጅት	ሚያዝያ 6/2006	23

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
8	በሕግ ተለይቶ የተወሰነ የይርጋ ጊዜ የመቋረጥ እና ያለመቋረጥ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ ሊነሳ የሚችለው የይርጋውን መቆጠር ያቋርጠዋል የተባለው ምክንያት የተከሰተው የይርጋው ጊዜ ከመሙላቱ በፊት በሆነ ጊዜ እንጂ የይርጋው ጊዜ የሞላ ወይም ያለፈ በሆነ ጊዜ ጭምር ስላለመሆኑ ፡- የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.1851	90361	እነ ወ/ሮ አለዊያ ዑመር (ስድስት ሰዎች) እና አቶ ሐሺም ሁሴን	የካቲት 26/2006	26
9	የመቃወም አቤቱታ የሚመራው በመደበኛው የክርክር አመራር ሰርዓት ስለመሆኑ፡- - የመቃወም አቤቱታን የሚሰማው ፍ/ቤት ስላለው ስልጣን፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 222፣223፣234፣358፣359፣360(1) እና(2)	86398	ወ/ሮ አሰለፈች ይመር እና እነ ወ/ሮ አስመረት ተወልደ(ሶስት ሰዎች)	ሐምሌ 28/2006.	30
10	አንድ ክስ ሲቀርብ በክስ ማመልከቻው ላይ መገለፅ ከሚገባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የክሱ ምክንያት እና ለክሱ ምክንያት የሆኑት ነገሮችና እነዚሁ የተፈጠሩበት ጊዜና ስፍራ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ80(2)፣213(1)፣216(1)፣222(1)(ረ)	91329	ወ/ሮ አስመረት ኃ/ሚካኤል እና እነ አቶ ተስፋዬ ጥላሁን (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 24/2006	36
11.	የማይገባውን ክፍያ የከፈለ ሰው ገንዘቡን ከከፈለበት ቀን አንሥቶ ሕጋዊ ወለድ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችለው፣ ገንዘቡን የተቀበለው ሰው እምነትን በሚያጓድል ሁኔታ ክፍያውን ተቀብሎት በሆነ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2164(2)	91643	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ እና ካኪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	ጥር 15/2006	40

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
12	በህብረት ሥራ ማህበራትና በአባሎቻቸው ወይም በቀድሞ አባላቸው ወይም በህብረት ስራ ማህበር አባላት ወይም የቀድሞ አባላትና በማህበሩ አመራር መካከል የሚነሳ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የሸምግልና ጉባኤው ውሳኔ ሳይሰጥበት ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ዳኝነት ለማየትና ለመወሰን የማይችሉ ስለመሆኑ፣የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37፣ አንቀጽ 79(1) እና አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49	91745	አቶ ዳዊት አበበ እና አንድነት ቁጥር 4 የጋራ መኖሪያ ቤት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 12/2006	43
13	በውሳኔ በተቋጨ የክስ መዝገብ ላይ የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 31	93171	ወ/ሮ ሴቱ ከበደ እና እነ ወ/ሮ አስናቁ ፋንታዬ (ሦስት ሰዎች)	ግንቦት 8/2006	47
14	-በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር ስለዋናዎቹ ባለጉዳዮች በመሆን ሌሎች ሰዎች በተሟጋችነት ሊቀርቡ ስለሚችሉበት ስርዓት፣ በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ አለመገኘት የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 57፣ 58(1)፣ 60፣61፣62፣ 63 እና 197(1)	94302	ብርሃኑ አማረ ጠቅላላ ሕንፃ ስራ ተቋራጭ እና ፋርማ ብርብር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	ሚያዝያ 7/2006	50
15	በአንድ ክርክር ሂደት ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገ ተከራካሪ ወገን ጉዳዩን የፌዴራል የሚያደርገው የነበረ ሁኖ እያለ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ስልጣን ሳይኖረው ስረ ነገሩን አስተናግዶ ዳኝነት ከሰጠ በኋላ ይኼው ተከራካሪ ወገን በይግባኝ ደረጃ በነበረው ክርክር የተሠጠውን ዳኝነት ተቀብሎ ከወጣ	95033	አቶ ስንታየሁ ተፈሪ እና ወ/ሮ ማርታ በቀለ	መጋቢት 25/2006	54

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	በኋላ በሌሎች ጉዳዩን የፌዴራል ሊያደርጉ በማይችሉ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የተሰጠው ውሳኔ ከመነሻውም የፌዴራል ጉዳይ ነው ብሎ መወሰን አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43(1)፣ አዋጅ ቁ.25/88				
16	በክርክር ወቅት ጣልቃ ልግባ የሚለው ወገን በተከራካሪ ወገኖች መካከል ባለው ጉዳይ የሚሰጠው ውሳኔ የክርክሩ ተካፋይ ባይሆን በምን አግባብና መልኩ መብቱንና ጥቅሙን የሚጎዳ መሆኑንና አዲስ ክስ በማቅረብ ለማስቀረት የማይቻል መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41(2)	95934	አቶ አስፋው ንዳ እና ወ/ሮ እየሩሳሌም አየነ (ሁለት ሰዎች)	ግንቦት 18/2006	59
17	ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሚሰጠው የፍርድ ውሳኔ የመጀመሪያውን ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድን ካሻሻለው ወይም የለወጠው እንደሆነ በትችቱ ላይ ለይግባኝ ባዩ የሚገባውን ዳኝነት ዘርዝሮ መግለፅ ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182(1)፣348(1)	92903	ወ/ሮ ስላስ ረዳ እና ወ/ሮ ለተሚካኤል ገ/ሐዋሪያት (ሁለት ሰዎች)	ሚያዝያ24/2006	63
	የንግድ ህግ				**66**
18	ለቼኩ መሰጠት መሰረት የሆነውን ውል እና ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለውን ህግ ሳይመለከቱና በተገቢው የክርክር አመራር ስርዓት ፍሬ ነገሩን ሳያጣሩ የሚሰጥ ዳኝነት ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣	90434	ሉሃና አንጂነሪግ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር እና ማክሮ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ኃ.የተ.የግል ማህበር	ሰኔ 06/2006	67

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
አሰሪና ሰራተኛ					**72**
19	አንድ ሠራተኛ በስራ ውሉ እና በስራ ደንቡ መሠረት በአሰሪ የተሰጠውን ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታን አለመወጣቱ ስለሚያስከትለው ውጤት፣ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አንቀጽ 13(2)፣13(7)	90570	አቶ ፍፁም አስታጥቄ ወኪል እና የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት	ጥር 27/2006	73
20	በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የሚፈጠር የስራ ግንኙነትን መነሻ በማድረግ ሰራተኛው በሕግ የተሰጠውን መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት የህግ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑ፡- አዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 25(1)	92410	ቻይና ሀይ ቄይ ግሩፕ ሊሚትድ እና አቶ ውብሸት እንግዳው	ጥር 29/2006	77
21	የመድን ዋስትና የገባ የመንግስት የልማት ድርጅት በአንድ ሰራተኛው ላይ ለደረሰ የአካል ጉዳት ተጠያቂ የማይሆነው የተገባው የመድህን ሽፋን በአዋጁ የተጠበቀውን መጠን የሚሸፈን ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ በአዋጁ ስሌት ለአነሰ መጠን ያህል የመድህን ሽፋን አሰሪው ተጠያቂ ስለመሆኑ፣ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(1)፣ አንቀጽ 109(3) ,134(1)	97512	አቶ ምህረት አለነ ገረመው እና የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ስራ ድርጅት	ሐምሌ 29/2006	81
22	በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚደርግ የቅጥር ውሉ ላይ በግልፅ የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ካልተስማሙ በስተቀር አሰሪው የሙከራ ጊዜ ነው ብሎ በሚያስበው ጊዜ ውስጥ የሰራተኛውን የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የማይችል ስለመሆኑ፡-	98052	በርሄ ሐጎስ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ እና አቶ ገመቹ አዱኛ	ሐምሌ 14/2006	86

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	አዋጅ 377/1996 አንቀፅ 11(3)				
23	የአዋጅ ቁጥር 377/96 የተፈፃሚነት ወሰን በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚቋቋም በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ቢሆንም፤ በአዋጁ በግልጽ በተደነገጉ ሌላ ሕግ በሚገዛቸው ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 3	92152	ግርማ ደሳለኝ እና ወጣቶች ገነት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት	የካቲት 11/2006	89
24	የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ ሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ፣ የጳጉሜ ቀናት በይርጋ ቀናት የማይካተቱ ስመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(4)፣የፍ/ሕ/ቁ. 1860(3)	96458	ኢትዮጵያ የርቀት ትምህርት ኮሌጅ እና ዶ/ር ደግለኝ ተመስገን	ሐምሌ 29/2006	92
25	ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ በአሰሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ አሰሪው ለሰራተኛው መክፈል የሚገባውን ሒሳብ ካልከፈለ ክፍያ ለዘገየበት ጊዜ ለሰራተኛው እስከ ሶስት ወር የሚደርስ ደሞዙን ያህል አሰሪው እንዲከፍለው ሰራተኛው ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ላለው ፍ/ቤት በመጠየቅ ሊያስወስን የሚችል ስለመሆኑ- አዋጅ ቁ.377/ 1996 አንቀፅ 38	98724	ሙኒሽ ካፌ ድርጅት(ሙኒሽ ጀርመን ቤከር እና ካፌ) እና አቶ ዳዊት ፀጋው	ሐምሌ 14/2006	95
26	በአሰሪና ሰራተኛ መካከል ያለ የሥራ ግንኙነት በተቋረጠ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የክፍያ ጥያቄ ያለበት አካል መብቱን ካልጠየቀ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፣	92302	አቶ ርዕሶም እምባፍራሽ	ጥር 26/05/06	98

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	በተጨማሪነት ስድስት ወር ከሞላው(ካለፈው) በኃላ የሁለቱ የስራ ግንኙነት ቢቀጥል እንኳን አስቀድሞ የታገደውን የስንብት ክፍያ ጥያቄን ከአዋጁ ድንጋጌ ይዘት አኳያ የይርጋ ጊዜን ሊያቋርጥ የሚችል ስላለመሆኑ፣ አዋጅ 377 አንቀፅ 162(3)፣162(4)		እና ኢትዮ ቴሌኮም		
27	አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ በሚደርስበት የጤንነት ችግር ምክንያት አሰሪው የአንድ ወር የህመም ፍቃድ ሰጥቶት ነገር ግን በተሠጠው ጊዜ ውስጥ ከህመሙ ማገገም ካልቻለ ተጨማሪ የህመም ፍቃድ ከግማሽ ደመወዙ ጋር እንዲያገኝ ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ፡- አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 85(1)፣86(2)	99026	አቶ አብርሃም ታደለ እና ጥቁር አባይ ትራንስፖርት ኃላ/የግለ/ማህበር	ሐምሌ 17/2006	101
28	- የሥራ ውሉ ሊጠናቀቅ የአንድ ወር ጊዜ ብቻ የቀረው በሆነ ጊዜ አሰሪው የስራ ውሉ ከሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ ከ1ወር በፊት የሥራ ውሉን ያቋረጠ እንደሆነ ሊከፍል የሚገባው የ1 ወር ደመወዝ ብቻ እንጂ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሚገደድበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ፤ አዋጅ ቁጥር377/96 አንቀፅ 43(4)(ሀ)፣36	95392	የእንግሊዝ ሕፃናት አድን ድርጅት እና አቶ ሽመልስ አለሞ	ግንቦት 06/2006	104
29	-በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚደረግ የውል ግንኙነት ተዋዋይ ወገኖች የገቡትን ግዴታ በቅንነት ይፈፅማሉ ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ፣ - በአሰሪውና ሰራተኛው መካከል በሚደረግ የሥልጠናና የት/ት ውል መሰረት አሰሪው የሚጠበቅበትን ድጋፍ ለሰራተኛው የማድረግ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1732፣አዋጅ ቁጥር 377/96	92423	የሺሐረግ ታደሰ እና የአምቦ ማዕድን ውሃ አ/ማ	ጥር 16/2006	107

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	አንቀፅ 84፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 83 ንዑስ አንቀፅ 3				
30	- አንድ የስራ ውል በሰራተኛው አነሳሽነት እንደነገሩ አግባብ በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 31 እና 32	93511	አቶ ደረሰ ወርቁ እና በርሔ ሐጎስ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ	የካቲት 24/2006	111
31	-በፍትሐ ብሔር ክርክር አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር ማስረዳት እንደሚጠበቅበት እና በአንዳንም ግዴታ ፍርስ ነው ወይም ተለውጧል የሚለው ወገንም ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ ስለመሆኑ፣ ሠራተኛው በራሱ ጉድለት ባልሆነ ምክንያት ላልሰራው ስራ ደሞዝ ስለሚጠይቅበት አግባብ፣ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 54(1)፣54(2) በፍ/ሕ/ቁ. 2001(1) እና(2)	93532	አቶ በኃይሉ ደቦጭ አንበሴ እና ኢትዮጵያ ገብራት ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	ጥር 12/2006	115
32	በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚደረግ የስራ ግንኙነት የተነሳ ለተወሰነ ጊዜ ለፕሮጀክት ስራ መደብ የተቀጠረ ሠራተኛ ከአንድ የፕሮጀክት ወደ ሌላ የፕሮጀክት ስራ አዘዋውሮ ማሰራት በአሰሪውና ሰራተኛው መካከል ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ግንኙነት ተፈጥሯል ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ. 377/96 አንቀፅ 30፣ አንቀፅ 10	93813	ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ሙሉጌታ አምባዬ ጠበቃ አደም ታደለ	የካቲት 13/2006	119

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
33	አንድ ሰራተኛ ሲከፈለው የነበረው የደሞዝ መጠን ከፍተኛ መሆን የሥራ ስንብት ክፍያን ከመጠየቅ የሚያግደው ስላለመሆኑ፣ አዋጅ 377/1996 አንቀጽ 39 እና አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 2(2)(ሸ)	93828	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ካፒቴን እንድሪያስ ጀምሬ	የካቲት 11/2006	123
34	አንድ ሰራተኛ የሥራ ውሉ በሚቋረጥበት ጊዜ በስሙ የሚቀመጠው የፕሮቪደንት ፈንድ ለእዳ ማስቻያ ሊሆን የሚችለው ሰራተኛው ዕዳ እንዳለበት ያመነ እንደመሆኑ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 59(1)	95451	አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር እና አቶ መርዓዊ መስፍን	ሚያዝያ 06/2006	127
35	አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ የማጭበርበር ድርጊት በመፈፀሙ ምክንያት ያገኘው ጥቅም ባይኖርም፣ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ባያደርስም ወንጀልነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በቂ ስለመሆኑ፣ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ))	95522	የኢትዮጲያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን መሃል ሜዳ ደንበኞች አገልግሎት ዕ/ቤት እና አቶ ሙሉጌታ ወ/ጊዮርጊስ	መጋቢት 08/2006	131
36	በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በተነሳ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበው ለክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሆነ ጉዳዩ በተነሳበት ክልል የሰበር ችሎት የተደራጀ እስከሆነ ድረስ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታይ እና ውሳኔው የመጨረሻ መሆኑ ሳይረጋገጥ በቀጥታ ለፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ፣	94102	ኢትዮቴሌኮም ደቡብ ምዕራብ እና ጋምቤላ ሪጅን እና ወ/ሮ ሳባ መንገሻ	ሚያዚያ 21/2006	134

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(6)፣ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 138(1)፣				
37	-በሥራ ተከራካሪ ወገኖች ማንነት የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን (የክልል ወይም የፌዴራል) ብሎ ለመወሰን እንደወሳኝ መለኪያ ሊወስድ የሚገባ ስላለመሆኑ፣ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50፣ 51 እና 80 ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 14 እና 15፣አዋጅ ቁ.25/88አንቀፅ5	94839	መተሃራ ስኳር ፋብሪካ እና ጥበቡ እሸቱ (139 ሰዎች)	መጋቢት 22/2006	137
38	በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በሠራተኛ ዕድገት ዝውውርና ሥልጠና በሚመለከት አሠሪው የሚወስዳቸው እርምጃዎች በፍርድ ሊታዩና ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮች እንደሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀፅ 37፣ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 138፣142 ንዑስ አንቀጽ 1/ሰ/ እና ከአንቀጽ 147 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/	94889	ወ/ሮ አልማዝ ባዛ እና የደቡብ መንገዶች ባለስልጣን	መጋቢት 23/2006	144
39	የሥራ መሪ መብቱን ለማስከበር የሚችልበት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1846	94931	ወ/ሮ ጥሩቀርቅ መንግስቱ እና የተገጣጣሚ ህንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት	የካቲት 14/2006	150
40	የጡረታ እድሜያችን ሳይደርስ በጡረታ እንድንወጣ ተደርጐ የስራ ውላችን ከህግ ወጪ ተቋርጧል በማለት የሚቀርብ ክስን መደበኛ ፍ/ቤት ስንብቱ በህግ አግባብ የተደረገ መሆን አለመሆኑን የማጣራትና የመመርመር ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣	98099	እነ ወ/ሮ ደንቄ ከዳ (ሀያ ሰዎች) እና	ሰኔ 19/2006	153

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 23-27 (1)(ተ) እና 30፣40 አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7)		የኢትዮጵያ ፖልፕ እና ወረቀት አክስዮን ማህበር		
ከውል ውጭ ኃላፊነት					**158**
41	የጉዳት ካሳ አከፋፈልን በተመለከተ በአንድ ጊዜ ሊሆን የሚችል መሆን ያለመሆኑን ለመወሰን ለፍርድ ቤቱ የተተወ ስለመሆኑ፣ በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ ተቀጣሪ የሆነ ግለሰብ የአካል ጉዳት በሚደርስበት ወቅት የጉዳት ካሳው አሰላሉ የጡረታ መውጫ እድሜውን መሰረት ቢያደርግ ተገቢ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2154፣2090፣2091፣2095 አዋጅ.ቁ715/2003	92040	አቶ ጥምቀቱ ጋመነ እና ወ/ት ታገሰች ዮሐንስ	ሚያዚያ 09/2006	159
42	አንድ ሰው የሌላውን ሰው የሥራ ድካም ወይም በሌላው ሰው ሀብት በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ እንደሆነ አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሀብቱ ወይም በጉልበቱ ለደከመው ሰው የመመለስና የመካስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣ በፍ/ሕ/ቁ 2162፣2164(1)	93104	ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና አቶ ደስታ ጁላ ቤካሎ	ሚያዚያ 20/2006	165
43	ከሳሽ የጠየቀውን የካሳ ገንዘብ ተከሳሽ በግልጽ አለመካዱ የካሳውን መጠን ሙሉ ወይም በከፊል እንዳመነ የማያስቆጥር ስለመሆኑ፤ ሰዎች አንድ ሆነው በአንድ ጉዳይ ካሳ እንዲከፍሉ	94181	አቶ ሽኩር ጀማል እና	ግንቦት 18/2006	169

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	የተገደዱ እንደሆነ በአንድነት እያንዳንዳቸው ሀላፊ እንደሆኑና ለበደሉ ተግባር አነሳሽ በሆነው በዋና አድራጊው እና በተባባሪዎች መካከል ልዩነት የሚደረግ ስለመሆኑ፤ በፍ/ህ/ቁ 2155/1/ እና /2/ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 83		ወ/ሪት ኤደን ነጋሽ		
	ቤተሰብ			172	
44	የቀለብ ገንዘብ መጠን ስለሚወሰንበት አግባብ፤ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 አንቀጽ 2	98552	ሚ/ር አደም ሐሚድ እና ወ/ሮ ሐናእ አብዱልቃድር	ሐምሌ 4/2006	173
45	ይርጋ በተመለከተ የሚቀርብ መቃወሚያ ከመልስ ጋር መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፤ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 234(1)(ሐ) እና 244(2)(ሠ)	85815	አቶ ኢብራሀም መሀመድ ኑር እና እነ ወ/ሮ ጀሚላ መሐመድ (አራት ሰዎች)	ሐምሌ 17/2006	177
46	በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መመዘኛ የሚያሟላ አቤቱታ አቅራቢ (ፍርድ ተቃዋሚ) የሚቃወመው ፍርድ በይግባኝ ያልተሻረ (ዋጋ ያለው) እና ያልተፈፀመ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፤	93987	እነ አቶ ዳንኤል ወንዳፈራ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ አስናቀች ቦጋለ (አራት ሰዎች)	ሐምሌ 18/2006	181
47	የውርስ ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ በውርስ ህጉ የተመለከቱትን የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚገዙትን ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና አላማ የተከተለና ያገናዘበ መሆን ስላለበት፤ የፍ/ህ/ቁ 1079፣1082፣1083፣1086	94322	ወ/ሮ አልማዝ በቀለ እና አቶ ገዛኸኝ በቀለ	ሐምሌ 17/2006	186

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	፣1087(2)፣1092፣1093				
48	በህግ ፊት የሚፀና ስጦታ ለማድረግ ሰጪው ስጦታ በተደረገበት ንብረት ላይ መብት ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑ፤የባልና የሚስት የጋራ በሆነ ንብረት ላይ አንደኛው ተጋቢ ብቻውን የሚያደርገው ስጦታ ዋጋ የሌለው ስለመሆኑ፣	90959	ተክለፃድቅ ኤካ እና እነ አቶ መላኩ ፍሬው(2 ሰዎች)	ግንቦት 063/2006	192
	ንብረት			196	
49	ትዳር ያለው አንድ የመንግስት ቤት ተከራይ በሞት በተለየ ጊዜ የተከራይነት መብቱ ለሌላኛው ተጋቢ ሊተላለፍ የሚችለው አግባብነት ባለው መመሪያ ስለመሆኑ፣	93346	እነ ወ/ሮ ብርሃን ደሳለኝ(2 ሰዎች) እና ወ/ሮ ብርትኳን ዮሐንስ	ግንቦት 21/2006	197
50	አንድ ሰው በድልድል ያገኘውን መሬት ሌላ ሰው ሊወስድበት የሚገባው በሕጉ የተመለከቱ ምክንያቶች ሲኖሩ ብቻ ስለመሆኑ፣ የት/ቢ/ክ/መንግስት የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 136/2000 አንቀጽ 31፣5፣12፣14 እና 22 ደንብ ቁ. 48/2000 "ን" በደንብ ቁጥር 48/2000 14፣15፣16 አዋጅ ቁጥር 456/1997 በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣40(3) እና 79	95538	አብርሃ ሕሉፍ ገሰሰው እና ወ/ሮ ትበርህ ገብረሕይወት	ግንቦት 07/2006	200

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
51	ሁከት ፈጥረሀል ተብሎ የተከሰሰ ሰው ሁከት ፈጥረሀል በተባለበት ነገር ላይ በፍርድ የተረጋገጠ መብት ካለው ሁከት ፈጠረ ሊባል ስላለመቻሉ፣ የፍ/ህ/ቁ 1149(3)	94869	አቶ ሙሳ ደገፈ እና አቶ ጥላሁን ደስታ	ሰኔ 19/2006	204
52	የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሠው ባለማቋረጥ ለ 15 ዓመታት ግብር በስሙ መክፈሉ ከተረጋገጠ የዚሁ ንብረት ባለቤት መሆን ስለመቻሉ፣ የፍ/ህ/ቁ 1168(1)	89148	አቶ ክፍሉ ገ/ማርያም እና ወ/ሮ አስመረት መኮንን	ሰኔ 3/2006	208
53	ጉዳዩ ከይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ከሰነዶች ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብቻ በፍርድ ሊወሰን የሚችል አይደለም ሊባል ስላለመቻሉ፤ እንዲሁም የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካርታ ወይም ሌሎች ሰነዶች ተወስደውብኛል ተብሎ ክስ በሚቀርብበት ጊዜ የተወሰዱበት አግባብ ህጋዊ መሆን አለመሆኑ በፍርድ ቤት ሊጣራ የሚችል ጉዳይ ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 37(1)፣ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.4	97464	ወ/ሮ ዘይነብ ጀማል እና እነ የቦሌ ክፍለ ከተማ የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ጽ/ቤት (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 04/2006	213
	ውል			**217**	
54	አንድ ፍርድ ሊፈጸም የሚገባው በፍርድ ባለእዳውና በሕግ አግባብ እንዳይያዙ ከሚጠቀሱት ንብረቶች/መብቶች ውጪ ባሉት የፍርድ ባለእዳ ንብረቶች /መብቶች ስለመሆኑ፣ በህግ አግባብ መብቱን ባስተላለፈ ንብረት ላይ የቀድሞ	92290	ወ/ሪት ጦቢያው መኮንን እና	ሐምሌ 14/2006	218

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	ባለቤት በድጋሜ ሽያጭ የሚፈጽምበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378		እነ አቶ እርቁ ጎዳ (ሁለት ሰዎች)		
55	የዋስትና ግዴታ ግልፅ መሆን ያለበት ስለመሆኑ ኃላፊነቱም ግዴታ ከተገባለት እዳ ወሰን ለማለፍ እንደማይችል እና እንዲሁም ይህ ለአፈፃፀሙ ግዴታ የተገባለት የእዳመጠን ወይም የገንዘብ ልክ በዋስትና ውሉ ካልተገለፀ ዋስትናው ፈራሽ ስለመሆኑ፣ ከዚህ በተጨማሪ ገና ለወደፊት ሊደርስ ለሚችል ግዴታ አፈፃፀምም ዋስ ለመሆን እንደሚችል ነገር ግን በግልፅ ለምን ያህል እዳ ተጠያቂ ሊሆን እንደሚችል በግልፅ በውሉ ላይ መስፈር ያለበት ስለመሆኑ፣ ፍ/ብ/ህ/ቁ 1922(2)(3)፣ 1925(1)	94837	አቶ ልውል ዘወዴ እና አጀመራ የወርቅ ግብይት ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ሚያዝያ 22/2006	223
56	የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ በተመለከተ መንግስት ካለበት ኃላፊነት የተነሳ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውል እንዲዋዋሉ እና መዝገብ እንዲያደራጁ የተወሰነ አካልን ባላደረገበት ጊዜና ቦታ በአካባቢው የሚፈፀሙ ልማዳዊ አሰራሮችን ህጋዊ መሰረት የላቸውም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ ከፍ/ሕ/ቁ. 3364	98079	የቀይ አፈር ገዳሞች እና አቶ ኤርሚያስ ገሠሠ	ሰኔ 18/2006.	227
ወንጀል					**231**
57	በወንጀል ጉዳይ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሆኖ ያስገኘው ሕግ በፍርዱ ውስጥ መገለጽ እንደሚገባውና የጥፋተኝነት ውሳኔው የሚሰጥበት ድንጋጌ መፈጸሙ	94070	እነ አቶ ወልዱ ገ/አብዝጊ (ስድስት ሰዎች)		232

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	ከተረጋገጠው የወንጀል ፍሬ ነገር ጋር በጥንቃቄ መነጻጸር የሚገባው ስለመሆኑ፣ ወ/መ/ሕ/ስ/ስቁ. 149		እና የትግራይ ክልል ዐ/ሕግ	ሚያዝያ 22/2006	
58	አንድ ሰው በወንጀል ተከሶ በሌለበት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ጥፋተኛ የተባለው ሰው ቀርቦ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስነሳት ሳይሆን በዋናው ጉዳይ ላይ በቀጥታ ይግባኝ ከጠየቀ በኃላ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ ብሎ ቢያመለክት በፊት የጠየቀው ይግባኝ በህጉ ላይ የተቀመጠውን የ30 ቀን የጊዜ ገደብ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ፣ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.198	95875	እነ አቶ አዳሙ ዘለቀ(3 ሰዎች) እና የአማራ ክልል አቃቤ ሕግ	ሰኔ 17/2006	238
59	በተለያየ ጊዜና መዝገቦች የተለያዩ ቅጣቶች በአንድ ተከሳሽ ላይ በሚወሰንበት ጊዜ ተከሳሹ ይጣመርልኝ ብሎ በሚጠይቅበት ጊዜ ተደምረው የሚፈፀሙ ሲሆን የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ግን እንደገና በድጋሚ የሚታዩበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አንቀፅ 186(3)፣184(1)፣ 108(1)	96503	አቶ መኮንን ወለላው ካሳ እና የፌዴራል ሥነ ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ህግ	ሰኔ 19/2006	243
60	ከውል ግንኙነት ጋር በተያያዘ በህገ ወጥ መንገድ መብትን ማስከበር የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አንቀፅ 436(ለ)	98647	አቶ ፅጋቡ ወላይ ገብሩ እና የትግራይ ክልል ዐቃቤ ሕግ	ሰኔ 02/2006	248
61	አንድ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠበት ውሣኔ እንዲነሳለት የሚያቀርበውን ማመልከቻ በመቀበል ከሚቻልባቸው ምክንያቶች አንዱ መጥሪያ ለተከሳሹ ያለመድረስ ጉዳይ ስለመሆኑ፣	94227	አቶ ገ/መድህን ኃ/ማርያም እና	ግንቦት 05/2006	253

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	የወ/መ/ሕ/ሥ/ ሥ/ቁ. 199(ሀ)		ትግራይ ክልል ዐ/ህግ		
62	አንድ በወንጀል ድርጊት ቅጣት የተጣለበትን ተከሳሽ ቅጣቱ እንዳይፈፀም ፍርድ ቤቱ ለማድረግ የሚችለው ጥፋተኛው በመልካም ጠባይ እንደሚመራ ፣ እንዲፈፅም የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል ፣ በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጥፋቱ የደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍል እና ለዚሁ ጉዳይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ከሰጠ ስለመሆኑ፣ ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ለገባበት ግዴታ አፈጻፀም መተማመኛ ዋስትና የሚጠይቅ ስለመሆኑ፣ አንቀጽ 197/1/ እና/2/	94404	የደቡብ ብሔር በሔረሰቦች ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል አቃቤ ህግ እና አቶ መኩሪያ ቡሉ	መጋቢት 09/2006	257
63	የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በተፈፀመ ወንጀል ከተፈረደበት እና ሆኖም ግን ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ስራ ላይ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን ይልቅ የተሻሻለው መመሪያ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቀልለትና ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ይሄው የተሻሻለው መመሪያ ላይ ያለው ቅጣት የሚፈጽምበት ስለመሆኑ፣ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ የወንጀል ህግ አተረጓጎም መርሆን መከተል ያለበት ስለመሆኑ፣ ወንጀል ህጉ ቁ 6	95438	አቶ ሰለሞን ደሣለኝ እና የደቡብ ክልል ዐ/ህግ	ግንቦት 07/2006	262
64	አንድ ተከሳሽ በክስ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ እንደሆነ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል ሲል በመዝገብ ካሰፈረ	96954	ዘፈሩ ወልደ ትንሣኤ አብርሃ	ሚያዚያ 24/ 2006	267

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	በኃላ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠት የሚገባው ስለመሆኑ፣ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/አ 134(1)		እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ		
65	አንድ ሰው በአንድ አይነት የወንጀል አሳብ ወይም ቸልተኝነት የፈጸመው ወንጀል አንድን የሕግ ድንጋጌ ብቻ የሚጥስ ቢሆንም አንድ አይነት ጉዳት ያስከተለው ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ሲሆን እንደተደራራቢ ወንጀሎች ሊቆጠር የሚገባ ስለመሆኑ፣ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 27(1)፣60(ሀ) (ሐ) እና 598(1)	96078	ረዳት ሳጂን አህመድ ለገሰ እና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	መጋቢት 11/2006	270
የዳኝነት ስልጣን					**276**
66	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ የመመዘን እና ፍሬ ጉዳይን የማጣራት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፣ የአ.አ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 42(2)	93220	ግርማ አያሌው ዋልታንጉስ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት	መጋቢት 8/2006	277
67	በመንግስት በጀት በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚፈጠሩትን የመብት ጥያቄዎች መመራት ያለበት በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሆን አለበት፡፡ -በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 (2)(ሠ) ፣ አዋጅ 515/1999 አንቀጽ 3 በአዋጅ 650/2001፣ ደንብ ቁጥር 214/2003 እና	93358	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማርች ፕሮጀክት እና እነ ቤተልሔም ሽፈራ (ሶስት ሰዎች)	መጋቢት 26/2006	281

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	210/2003				
68	ከከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣን እና ተግባር ጋር እንዲሁም የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር እና የከተማው አስተዳደር አካልም በተከሳሽነት በሚቀርብበት ጊዜ የስረ ነገር ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ፣ በአንድ ክስ ውስጥ ብዙ አቤቱታዎች ቀርበው ከነዚሁ በከፊል ዋናውን ክስ የሚመለከቱ በከፊል ደግሞ ዋናውን ክስ መነሻ አድርገው ቅርንጫፍ ነገሮችን የሚመለከቱ በሆነ ጊዜ የፍርድ ቤቱ ስልጣን የሚወሰነው ከፍተኛ ግምት ያለውን አቤቱታ መሰረት አድርጎ በመከተል ስለመሆኑ፣ *መመሪያ* ቁጥር 4/2004 አዋጅ ቁጥር 361/1995 ፣ የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አንቀጽ 41(1) (ለ) እና (ረ) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 17(2)	96216	አቶ ተክለብርሃን ዘገየ እና እነ አቶ ሸምሰዲን አክመል (አራት ሰዎች)	ሐምሌ 29/2006	285
69	ከጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ጋር በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ሰው ለባለስልጣኑ አቤቱታ አጣሪ ቡድን ከዛም ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በየደረጃው ሳያቀርብ በቀጥታ ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት እንዲታይለት የሚጠይቅበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 89(2) እና ንዑስ አንቀፅ 3(ሐ)፣ አንቀፅ 89(2)(3)(ሐ) ፣(5) እና (6)	97372	ማም ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግል/ማህበር እና እነ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 29/2006	289

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
ጉምሩክ					294
70	በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለው አካል ያልተከፈለ ቀረጥና ታክ እንደተከፈለ የሚቆጠርበት የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ ---ቀረጥና ታክሱን የማስከፈል ስልጣን በህገ መንግስቱ ተለይቶ የተቀመጠ ስለመሆኑ፣ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 96(1) አዋጅ ቁጥር 578/2000 አንቀጽ 6(8)፣9 እና 10፣ ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2(6)፣(2(11)፣2(17) እና 91 ፣15(1)፣ 82 (1ሀ))((ለ))	97409	የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና እነ ጋርዊች ዋንግ (ሶስት ሰዎች)	ግንቦት 09/2006	295
71	አንድ የግብር ውሳኔ በግምት ስለሚወሰንበት አግባብ የግብር ህግ አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 69	88446	ሙሉ አሚን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን	ግንቦት 22/2006	302
72	ህጋዊ ቀረጥ የተከፈለበት ዕቃ ህጋዊ የጉምሩክ ስርዓት ካልተፈፀመበት ዕቃ ጋር ተቀላቅሎ ከተያዘ እና ከተወረሰ በህጋዊ መንገድ ዕቃው ሲገባ የተከፈለው ቀረጥ(tax) እንዲመለስለት የዕቃው ባለቤት የሚጠይቅበት የህግ ስርዓት ስላለመኖሩ፣ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 104(3)	92537	አዞ ግሎባል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን	ግንቦት 21/2006	307

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	አፈጻጸም				309
73	በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ሕጋዊ ባልሆነ እና ውሳኔውን ውጤት አልባ በሚያድርግ መልኩ ውድቅ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ ስላለመኖሩ፣ የአስተዳደር አካል በባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አሰጣጥ ላይ ፍጹም የሆነ አስተዳደራዊ ስልጣን ያለው ስላለመሆኑ፣ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378፣ 392 የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196	91622	ወ/ሮ አፍሪካ ታደሰ- እና ወ/ሮ ያለምወርቅ ታደሰ-ታልፏል የጎባ ከተማ አስተዳደር ፅ/ቤት	መጋቢት 12/2006	310
74	አንድ ንብረት ወይም ቤት የወቅቱ የገበያ ዋጋ ሊቆረጥ የሚችለው ከተቻለ በስምምነት ይህ ካልተቻለ ደግሞ ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ በሚያወጣው ከፍተኛ ዋጋ መሰረት ስለመሆኑ፣	94571	እነ ወ/ሮ የልፍኝ መኮንን (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ዘርሁን መኮንን	ሐምሌ 1/2006	315
75	ለፍርድ ማስፈጸሚያ የቀረበን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመጀመሪያ የሐራጅ ሽያጭ የሚቀርብበትን የዋጋ ግምትን አስመልክቶ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን፣ፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 423(2)(ሀ)	92035	ደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ. ዓድዋ ቅርንጫፍ እና እነ አቶ ሐጎስ ተስፋይ (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 24/2006	319
76	አንድ የፍርድ ባለገንዘብ በፍርድ ባለዕዳ ንብረት ላይ በህግ፣በውል ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ የቀደምትነት መብት ካላቋቋመ በቀር ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ጋር ደረጃቸው(መብታቸው) እኩል መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ባስፈረዱት የገንዘብ መጠን መቶኛ ስሌት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደውን ገንዘብ እንዲከፍሉ	97206	አቶ አማረ መልካሙ እና አቶ ካሌብ ሀሉፍ	ሐምሌ 28/2006	323

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ.	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገፅ
	ማድረጉ የህግ መሰረት ያለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ስ/ስህ/ቁ 403 የፍ/ህ/ቁ 3043፣3044፣3045፣2825				
ልዩ ልዩ					**327**
77	አግባብ ባለው የዩኒቨርስቲ አካል በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ቅሬታ ሲኖራቸው የይግባኝ መብት ያላቸው ስለመሆኑ፤ ይግባኙን የማስተናገድ ስልጣን የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት ስለመሆኑ፣	101271	መ/ር ግዛቸው ጥሪት እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ	ሐምሌ 30/2006	328
78	አንድ ሰው የፖሊስ ቅጥር ፎርም የሚል ስያሜ የያዘ ሰነድ ስለሞላ ወይም በቅጥር ፎርሙ በሕጉ አግባብ የሚገኙት ማዕረጎች ተሰጥተውት የጥቅማ ጥቅሙ ተጋሪ መሆኑ ብቻ ጉዳዩን በፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንዲዳኝ ማድረግ ተገቢ ስላለመሆኑ፡- አዋጅ ቁ.720/2004 አንቀፅ 2(1) የፌዴራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ የሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.268/2005 አንቀፅ 3፣4፣5፣6(1) እና 7	99367	ዶ/ር ሕሊና ፍቅሬ እና የፌዴራል ፖሊስ ሆስፒታል	ሐምሌ 29/2006	336

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍትሐብሔር

ሥነ-ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92043

መጋቢት 22 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ቱሌን ዩኒቨርሲቲ አሲስታንስ ፕሮግራም ኢትዮጵያ - ጠበቃ ሰማው ንጋቱ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ዶ/ር ዮዲት አብርሃም -ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ጋር የተያያዘ የይርጋ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ በ06/08/2004 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ ከሳሽ ከ20/01/2001 ዓ.ም ጀምሮ በሰው ኃይል ከፍተኛ አማካሪነት የስራ መደብ በተከሳሽ ድርጅት ሲያገለግሉ ቆይተው የስራ ውላቸውን በራሳቸው ፈቃድ ከ13/02/2004 ዓ.ም ጀምረው ማቋረጣቸውን እና ተከሳሽ ድርጅት የተለያዩ ክፍያዎችን ሊከፍላቸው ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን የሚገልጽ ሆኖ ያልተከፈላቸው የአራት ወር ደመወዝ፣የዓመት ዕረፍት ክፍያ፣የተጠራቀመ ፕሮፊደንት ፈንድ እና ክፍያ የዘገየበት ታስቦ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ተከሳሽ ድርጅት በ17/09/2004 ዓ.ም በሰጠው መልስ የይርጋ መቃወሚያ እና የፍሬ ጉዳይ መልስ ያቀረበ ሲሆን የይርጋ መቃወሚያው ይዘትም ከከሳሽ ጋር የነበረው በየጊዜው የሚታደስ የስራ ውል ለመጨረሻ ጊዜ ለሶስት ወር የተራዘመው በ22/07/2003 ዓ.ም በመሆኑ የከሳሽ የስራ ውል የተቋረጠው ከሳሽ እንደሚሉት ከ13/02/2004 ዓ.ም ሳይሆን ከ23/10/2003 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት 06/08/2004 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ደግሞ ከዘጠኝ ወር በላይ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ሊዘጋ ይገባል የሚል ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱን ከሰማ እና የመቃወሚያ ክርክሩን ከመረመረ በኃላ በግራ ቀኙ መካከል በ21/01/2001 ዓ.ም በተደረገው የመጀመሪያ ውል ላይ የስምምነቱ ጊዜ የሚራዘመው ሁለቱም ወገኖች በጊዜው ርዝማኔ ላይ በጽሁፍ በሚያደርጉት ስምምነት እንደሆነ መገለጹን፣ተከሳሽ በ22/07/2003 ዓ.ም ፃፍኩ የሚለው የማራዘሚያ ደብዳቤ ከሳሽ ያልተስማሙበት እና ማብራሪያም የጠየቁበት መሆኑን፣በዚህም ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል የውል ማራዘሚያ ስምምነት አለ ሊባል የማይችል መሆኑን እና ከሳሽ ስራቸውን መቀጠል በመፈለጋቸው ከ23/10/2003 ዓ.ም በኃላም ስራ ላይ መቆየታቸውን ተከሳሽ ድርጅት ክሱ በተሰማበት ወቅት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያመነ መሆኑን ገልጾ የከሳሽ የስራ ውል የተቋረጠው ከሳሽ እንደሚለው በ23/10/2003 ዓ.ም ጀምሮ ሳይሆን ከ13/02/2004 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን፣ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከ23/10/2003 ዓ.ም ጀምሮ ነው በማለት ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያጣ ቢሆንም ከሳሽ የስራ ውላቸውን ካቋረጡበት ከ13/02/2004 ዓ.ም ጀምሮ ፍ/ቤት ቀርበው ፋይል እስካስከፈቱበት 17/08/2004 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ ስድስት ወር ከአራት ቀን በመሆኑ እና በዚህም ሁኔታ ክሱ የቀረበው ይርጋው ከሞላ ከአራት ቀናት በኃላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መዝገቡን በብይን ዘግቶታል፡፡

በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት የስር ከሳሽ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 213(1) ድንጋጌ መሰረት አንድ ክስ እንደቀረበ የሚቆጠረው ክስ የቀረበበት ጽሁፍ በፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ በመሆኑ እና የክስ ማመልከቻው ለሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ ምልክት የተደረገበት በ12/08/2004 ዓ.ም ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት ፋይሉ የተከፈተበትን 16/08/2004 ዓ.ም ክስ የቀረበበት ቀን አድርጎ መውሰዱ ተገቢ እንዳልሆነ ገልጾ የስራ ውሉ ከተቋረጠበት ከ13/02/2004 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት 12/08/2004 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ስድስት ወር ያልሞላው በመሆኑ ክሱ በይርጋ አይታገድም ሲል ብይኑን ሽሮ የስር ፍ/ቤት የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን ሰምቶ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት በመመለስ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት አቅርቦት የነበረውን መስቀለኛ ይግባኝ ደግሞ በተመሳሳይ ቀን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ዘግቶ አሰናብቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እና መስቀለኛ ይግባኙን በትዕዛዝ በመዝጋት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች ባቀረበው መስቀልኛ ይግባኝ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሳይሰማ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/.ቁ. 337 መሰረት የመዝጋቱን አግባብነት ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 340 ድንጋጌ አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአንድ የይግባኝ ክርክር መልስ ሰጪ የሆነው ወገን በቀጥታ ይግባኝ ያላቀረበ ቢሆንም እንኳ ተገቢውን ዳኝነት ከፍሎ ይግባኝ ባዩ ባቀረበው የይግባኝ ክርክር በመልስ ሰጪነት ከሚያቀርበው ክርክር ጋር በፍርዱ ቅር የተሰኘበትን ጉዳይ በማቅረብ በይግባኝ ባይነትም ለመከራከር እንደሚችል እና በዚህ ሁኔታ የቀረበውን ይግባኝ መልስ ሰጪው ለይግባኝ ባይ ያደረሰ ስለመሆኑ መተማመኛ ካላቀረበ ማመልከቻው በመልስ ሰጪው ኪሳራ ተገልብጦ ለይግባኝ ባዩ እንዲደርስ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 340(1) እና (2) ተመልክቷል፡፡ በመሰረቱ አንድ ይግባኝ በሚቀርብበት ጊዜ ይግባኙ የተመሰረተው በስር ፍ/ቤት የመዝገብ ግልባጭ ላይ ብቻ ከሆነ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ባዩን ከሰማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኃላ መልስ ሰጪን መጥራት ሳያስፈልግ ይግባኙን ዘግቶ ማሰናበት የሚችል ስለመሆኑ እና መ/ሰጪው ወገን የሚጠራው ይግባኙ ባልተሰረዘ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 እና 338 ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡

መስቀለኛ ይግባኝ ስለሚስተናገድበት ስርዓት በሕጉ በተለየ ሁኔታ በግልጽ የተመለከተ ነገር እስከሌለ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 እና 338 ድንጋጌዎች የተመለከተው የክርክር አመራር ስርዓት ለመስቀለኛ ይግባኝም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚነት የሚኖረው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 340(2) በተመለከተው መሰረት መልስ ሰጪው ወገን የሚያቀርበው የይግባኝ ማመልከቻ ግልባጭ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ.338 መሰረት ለይግባኝ ባዩ እንዲደርስ ሊደረግ የሚችለው ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/.ቁ.337 መሰረት ያልተሰረዘ በሆነ ጊዜ ብቻ ነው፡፡በመሆኑም መልስ ሰጪው ወገን ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ከተሰማ በኃላ የሌላኛውን ወገን ክርክር መስማት ሳያስፈልግ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት እንዲሰረዝ በማድረግ የሚሰጥ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 340(2) የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት የሚቃረን ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ከአመልካች ክርክር አንጻር ጉድለት የሌለበት መሆኑን በማረጋገጥ የአሁኑ አመልካች በመልስ ሰጪነት አቅርቦት በነበረው ይግባኝ ላይ የሌላኛውን ወገን ክርክር መስማት ሳያስፈልግ መስቀልኛ ይግባኙን በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 337 መሰረት ዘግቶ በማሰናበት ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 78241 በ23/05/2005 ዓ.ም ሰጥቶ የነበረውን ብይን ሽሮ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ስላልሆነ የፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ታይቶ ሊወሰን ይገባል በማለት እና ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341(1) መሰረት ወደ ስር ፍ/ቤት በመመለስ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 132623 በ06/10/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአሁኑ አመልካች በመልስ ሰጪነት አቅርቦት የነበረውን ይግባኝ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 337 መሰረት ዘግቶ በማሰናበት የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 132623 በ06/10/2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 78241 የተያዘው ክርክር ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዘገብ በ04/03/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰኔ 03 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ረታ ቶሎሳ
አዳነ ንጉሤ
መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አየለ ሚናሞ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አሰፋ ባዩ -ተወካይ አቶ ዘርይሁን ሞገስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ ተጠሪ ተወካይ በጠበቃቸው አማካኝነት ግንቦት 7 ቀን 2004 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የአሁን አመልካች ተጠሪው በሌለበት የንብረት ግምት ክስ አቅርበው በመ/ቁ/06973 በቀን 15/01/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ብር 95,067. ተጠሪው እንዲከፍላቸው በማስወሰን የተጠሪን ይዞታ በስማቸው ማዛወራቸውን ሚያዚያ 22 ቀን 2004 ዓ/ም ተጠሪ ባቀረቡት ክርክር መነሻ አመልካቹ ውሳኔውን በማስረጃነት አያይዘው በማቅረባቸው የተረዱ ስለሆነ እና ውሳኔውም መብታቸውን የሚያሳጣ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 78(2) መሰረት ውሳኔው ተነስቶ ተወካዩ ወደ ጉዳዩ ገብቼ እንድከራከር ይታዘዝልኝ ብለዋል፡፡

ለአመልካችም የተጠሪው ተወካይ አቤቱታ እንዲደርሳቸው በተደረገው መሰረት ቀርበው በ06/10/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ባቀረቡት መቃወሚያ፡-ተጠሪው ለተወካዩ የሰጡት ውክልና በፍ/ሕ/ቁ/2205 መሰረት ንብረት እንዲያስተዳድሩ የተሰጠ እንጂ ተጠሪውን ወክለው በፍርድ ቤት ቆመው ለመከራከር የሚያስችላቸው ባለመሆኑ ውክልናው ተቀባይነት የለውም ሲሉ በመከራከራቸው ተወካዩም ለመቃወሚያው በሰጡት መልስ፡- ቀደም ሲል እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ በዚሁ የውክልና ማስረጃ ከአመልካች ጋር ስንከራከር ስለነበረ መቃወሚያው ውድቅ ተደርጎ ወደ ጉዳዩ ገብቼ እንድከራከር ይታዘዝልኝ ብለዋል፡፡

የወንዶ ገነት ወረዳ ፍርድ ቤትም፡- በ01/12/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን፡- አመልካች ቀደም ሲል ክሱን ሲያቀርቡ የተጠሪው አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 15 ቀበሌ 28 የቤት ቁጥሩ 171 በሚል በገለጹት መሰረት መጥሪያውን በአድራሻቸው ማድረስ ሲገባቸው ሳያደርሱ መጥሪያው ወደ ሌላ አድራሻ እንዲላክ በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደረጉ ስለሆነ ውሳኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78(2) መሰረት ተነስቶ የተጠሪው ተወካይ ወደ ጉዳዩ ገብተው ሊከራከሩ ይገባል ሲል በይኗል፡፡

ከዚህ ብይን በኋላ የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ፡- በዋናው ጉዳይ ላይ ተጠሪው በሌሉበት ክርክር ተካሂዶ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የአፈጻጸም ክስ አቅርቤ ተጠሪው በሌሉበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርዱ እንዲፈጸም ትዕዛዝ ተሰጥቶ ቤቱን እና ቦታውን ተረክቤ ወደ ስሜ ተዛውሮ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶኝ ጉዳዩ ተጠናቆ ሳለ በፍርድ በተጠናቀቀ ጉዳይ ክርክሩ ሊቀጥል አይገባም፣ለተጠሪው ተወካይ ተጠሪው ውክልና የሰጡት በ1996 ዓ.ም ሲሆን ክሱ በቀረበ ጊዜም ተጠሪው ቀርበው እንዲከራከሩ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ መቅረብ ስላልቻሉ በሕይወት መኖራቸውን ስለምጠራጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 65(1) መሰረት ራሳቸው እንዲቀርቡ ይታዘዝልኝ ሲሉ በመከራከራቸው የተጠሪው ተወካይም በጉዳዩ ለመከራከር የሚያስችለኝ ሙሉ ውክልና እያለኝ ዋናውን ባለጉዳይ ማቅረብ አስፈላጊ ስላልሆነ አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ሲሉ መልስ በመስጠታቸው ፍርድ ቤቱም 01/04/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን፡- ከመዝገቡ ማጣራት እንደተቻለው ተጠሪው ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ እንደገና እንዲከራከሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78(2) መሰረት የተፈቀደላቸው ሆኖ ሳለ የፍርድ ባለመብቱ (የአሁን አመልካች) እንደገና መቃወሚያ ማቅረባቸው ተገቢ ባለመሆኑ ተጠሪው በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/78(2) በተፈቀደላቸው መሰረት በተወካያቸው በዋናው ጉዳይ መከራከር ይችላሉ ሲል አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ አደርጓል፡፡

አመልካችም በዚሁ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ የወረዳውን ፍርድ ቤት ብይን ያጸናው ሲሆን ጉዳዩ በሰበር የቀረበለት የደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠ/ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በሥር ፍርድ ቤቶች ብይን ላይ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም ሲል አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም በዋናነት የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብ ሲጠቃለል፡- የተጠሪው ተወካይ ጠበቃ በንብረት ግምት ላይ ተጠሪው በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 78(1) መሰረት አቤቱታ አቅርበው መዝገቡ ከአመልካች በኩል የሚቀርበውን መልስ ለመቀበል እና የቃል ክርክር ለማድረግ በተቀጠረበት ቀን የተጠሪ ተወካይ በመቅረባቸው የውክልናው ማስረጃ በወካዩና በተወካዩ መካከል የዝምድና ትስስር ሳይኖር የተሰጠ መሆኑን፤እንዲሁም የውክልና ማስረጃው በፍ/ሕ/ቁ/2205(2) መሰረት ተወካዩ በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመከራከር በሚያስችል መልኩ የተሰጠ ባለመሆኑ ተወካዩ ተጠሪውን ወክለው ለመከራከር የሚያስችል ውክልና ማስረጃ የላቸውም በሚል ክርክር ከማቅረብም ሌላ ዋናው ባለጉዳይ በህይወት መኖር አለመኖራቸውን ስለምጠራጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 50(1) መሰረት ቀርበው እንዲከራከሩ እንዲታዘዝ በሚል ላቀረብኩት ክርክር የወረዳው ፍርድ ቤት የውክልና ማስረጃው ተወካዩ ክርክር ለማድረግ የሚያስችላቸው መሆን ስላለመሆኑ በዝምታ በማለፍ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 58(2) መሰረት በማንሳት ክርክሩ እንዲቀጥል መበየኑና በይግባኝ እና በሰበር በየደረጃው ያሉ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ማጽናታቸው ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

የተጠሪው ተወካይ በሰጡት መልስ፡- በውክልናው ማስረጃው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የተጠሪን ንብረት በተመለከተ ክስ እንዳቀርብ፣መልስ እንድሰጥ እና ክርክር ለማድረግ በግልጽ ሥልጣን የተሰጠኝ በመሆኑ፤ እንዲሁም በዚሁ የውክልና ማስረጃም ተጠሪውን በመወከል ያሰጠሁትን ውሳኔ መሰረት በማድረግ አመልካች ያቀረቡት ክስ በመሆኑ ቀደም ሲል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተደረጉት ክርክሮች አንድም ቀን የውክልና ማስረጃውን በመቃወም ያቀረቡት ክርክር ሳይኖር አሁን ግን ማስረጃው ተቀባይነት የለውም ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግባቸው ይገባል ብለዋል፡፡

አመልካችም ለተጠሪው የመልስ መልስ ከማቅረባቸውም ሌላ ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ወገኖች የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች የተጠሪው ተወካይ የያዙት የውክልና ማስረጃ ክርክሩን ለማድረግ የሚያስችላቸው አይደለም ሲሉ ያቀረቡትን ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች በማለፍ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ በማንሳት ተወካዩ ክርክሩን እንዲቀጥሉ ብይን የሰጡት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ባለጉዳዩ ራሱ ቀርቦ እንዲከራከር ፍርድ ቤቱ ካላዘዘ ወይም ራሱ እንዲቀርብ የሚያስገድድ ህግ ከሌለ ራሱ ለመቅረብ የማይችል ወይም የማይፈቅድ ሰው ሲሆን ነገሩን ለማስረዳት፣ለመከራከር፣ለሚጠየቀው ሁሉ በቂ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰው በዋናው ባለጉዳይ ተተክቶ በነገረ ፈጅነት፣በወኪልነት እና በጠበቃነት እንዲከራከር ለማድረግ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 57 ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪው ለተወካዩ በሰጡት ውክልና ሥልጣን መሰረት ተወካዩ ክርክር ሲያደርጉ የቆዩ ቢሆንም በዚህ ችሎት የቃል ክርክር በተደረገበት ወቅት በወካዩና በተወካዩ መካከል ዝምድና መኖሩን ወይም አለመኖሩ ተወካዩ እንዲገልጹ ተጠይቀው ወካዩ የአክስታቸው ልጅ እንደሆኑ የገለጹ በመሆኑ የአክስታቸውን ልጅ በመወከል ክርክር ለማቅረብም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 58(ሀ) መብት የሚሰጣቸው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በተጠሪውና በተወካዩ መካከል ያለው የዝምድና ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 58(ሀ) የዋናው ባለጉዳይ ተወካይ ሆኖ ለመከራከር ከተቀመጠው የዝምድና ደረጃ ውጪ ሆኖ በመገኘቱ የውክልናው ማስረጃው በዚህ ድንጋጌ መሰረት የተገኘ ነው ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ እንዲሁም ተወካዩ የውክልና ማስረጃ በፍ/ሕ/ቁ 205 መሰረት የተሰጠ ስለመሆኑ ጠቅሰው የሚከራከሩ ቢሆንም በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የተሰጣቸውን ተግባራት ለማከናወን ውክልናው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 58(ሀ) የተዘረዘረውን የዝምድና ደረጃ ተከትሎ የተሰጠ ለመሆኑ ስላላረጋገጡ ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 63 መሰረት መስፈርቱን አሟልተው በጠበቃነት የሚከራከሩ ስለመሆኑ በግልጽ ሳያመለክቱ በውክልና ማስረጃው ላይ የፍ/ህ/ቁ 205 በመጠቀሱ ብቻ ማስረጃው ተጠሪውን ተክቶ ለመከራከር ብቁ የሚያደርጋቸው አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል ተወካዩ ቀደም ሲል በይዞታ መብት ላይ ክርክር ሲደረግ ዋናው ባለጉዳይ በመወከል እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ስከራከር እንደነበር አመልካች እያወቁ በዝምታ ቆይተው አሁን ውክልናውን ሊቃወሙ አይገባም ያሉትም ቢሆን አመልካች ውክልናው ህጋዊ አለመሆኑን በመረዳት በንብረት ግምት ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ተጠሪው በተወካያቸው አማካኝነት ክርክር በማቅረባቸው ያነሱት የክርክር ጭብጥ መሆኑ መቃወሚያውን ከማቅረብ የሚያግዳቸው ነገር የለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪው ለተወካዩ የሰጡትን ውክልና ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመቃወም ያቀረቡትን ክርክር ተቀብለው ዋናው ባለጉዳይ ወይም ትክክለኛ ተወካይ ቀርቦ ክርክሩን እንዲቀጥል ማድረግ ሲገባቸው የውክልና ማስረጃው ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን ሳይመረምሩ በማለፍ ክርክሩ እንዲቀጥል ብይን የሰጡት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የወንዶ ገነት ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/6973 በቀን 01/04/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ብይን፣የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/27806 በቀን 05/06/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣እና የደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 59120 በቀን 27/09/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. ተጠሪው ለተወካያቸው የሰጡት ውክልና ተወካዩ ተጠሪውን ተክተው ለመከራከር የሚያስችላቸው አይደለም ብለናል፡፡ ይህ ውሳኔ ዋናው ባለጉዳይ ወይም ህጋዊ ወኪላቸው ወይም ጠበቃቸው ሊያቀርቡ የሚችሉትን ክርክር የሚያስቀር አይሆንም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94293

ሚያዝያ 9 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሽዋ ንግድና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፡- የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ አሸብር አበበ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ለፌዴራሉ መጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ፡-አመልካች ለ1ወር ከህግ ውጭ ከስራ አግዶኝ ካቆየኝ በኃላ ወደ ስራ እንዲመልሰኝ በተደጋጋሚ ብጠይቀውም ለመመለስ ፍቃደኛ ባለመሆን የስራ ውሌን ከህግ ውጭ ስላቋረጠ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት ካሳና የተለያዩ ክፍያዎች ይፈፅምላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ የአመልካች ድርጅትን ስም፤የስራ አስኪያጁን ፊርማና የድርጅቱን ማህተም አስመስለው ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት አዘጋጅተው በመገልገል የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት ፈፅመዋል በሚል በመጠርጠሩ ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ ለ1ወር ከስራ ታግደው የነበረ ቢሆንም ምርመራው ባለመጠናቀቁ ፖሊስ ጉዳዩን አጣርቶ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ተጠሪ ለጊዜው መደበኛ ስራውን እንዲቀጥል ቢነገረውም ፍቃደኛ ባለመሆኑና በዚህም መሠረት በስራ ገበታው ላይ በመደዳው ከ5 የስራ ቀናት በላይ ባለመገኘቱና በፈፀሙት የማጭበርበር ድርጊት የስራ ውላቸው በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ለ)(ሐ) መሠረት በህጉ አግባብ መቋረጡን በመግለፅ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመርያ ደረጃ የተመለከተው የፌደራሉ መጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክርና የአመልካችን ምስክሮች ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ክርክሩ ከተጀመረ በኃላ በፈፀሙት የማጭበርበር ድርጊት በወንጀል ችሎቱ ጉዳዩ ታይቶ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑን አመልካች ገልፀው መዝገቡ ቀርቦ እንዲታይላቸው ያመለከቱትን በተመለከተ ቀደም ሲል ጉዳዩን ሲመለከቱት በነበሩት ዳኛ በጭብጥነት የተያዘው ተጠሪ ከስራ ታግደው ከቆዩ በኃላ ወደ ስራ ለመመለስ ፍቃደኛ ነበሩ ወይስ አልነበሩም? የሚለው ነጥብ ብቻ በመሆኑና ክርክሩም የቀጠለው በዚሁ ነጥብ ላይ በመሆኑ በወንጀል ጥፋተኛ የመሆናቸው ጉዳይ የወንጀሉን መዝገብ በማስቀረብ ሊመረመር አይችልም በማለት ካለፈ በኃላ ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ እምቢተኛ ሆነው ከ 5 የስራ ቀናት በላይ ስለመቅረታቸው የአመልካች ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስላላስረዳ የተጠሪ ስራ ውል የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ አመልካች የ6ወር ደመወዝ የካሳ ክፍያ የ2ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የስራ ስንብትና የዓመት ረፍት ጊዜ ወደ ገንዘብ ተለውጦ በድምሩ ብር 13,296.33 የገቢ ግብር ቀንሶ ለተጠሪ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔም በፌዴራሉ ከፍተኛ/ፍ/ቤት በይግባኝ ታይቶ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሠረት ፀንቷል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን መሠረታዊ የቅሬታ ነጥቦችም የተጠሪ ስራ ውል የተቋረጠው በፈፀሙት የማጭበርበር ወንጀል ድርጊት ጭምር መሆኑን አመልካች ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ ማለትም የፅሑፍ መልስ ሲሰጥ ጀምሮ ክርክሩ ቀርቦ እያለ የስር ፍ/ቤቱ ግን ይሄንን በጭብጥነት ሳይዝ ማለፉ ስለጭብጥ አያያዝና አመሠራረት አስመልክቶ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.247 እና 248 የተደነገገውን የሚጥስ ነው፡፡ተጠሪ የአመልካችን ድርጅት ማህተምና የስራ አስኪያጁን ቲተር የሚመስል ሀሰተኛ ማህተም በራሳቸው ወይም በሌላ ሰው አማካኝነት የተዘጋጀውን በመገልገል በፈፀመው ወንጀል ድርጊት ተከሶ እና ጉዳዩም ተጣርቶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በስራ ክርክር ችሎት በክርክር ላይ እያለን የተጠሪ ስራ ውል ከተቋረጠበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ የተደረገበት ውሳኔ ቀርቦ ታይቶ እና ጉዳዩ ከዚህ አንፃር በጭብጥነት ተይዞና ተመርምሮ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰጠት ሲገባዉ ታልፎ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.247 እና 248 ድንጋጌዎች አኳያ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት ውሳኔዎቹ ተሽረው የተጠሪ ስራ ውል የተቋረጠው በህግ አግባብ ስለሆነ የካሳ ክፍያና ሌሎች ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ይወስንልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱም ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡበትን የወንጀል መዝገብ በትዕዛዝ አስቀርቦ እና አቤቱታውንም ከወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔ ጋር በማገናዘብ መርምሮ የግራ ቀኙን የክርክር ሂደት አመልካች ስለስንብቱ ጉዳይ ተጠሪ በፈፀመው ድርጊት በወንጀል ተከሶ ክርክሩ ተጠናቆ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቷል፣ ይህ የወንጀል ችሎት ጥፋተኝነት ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ስለሆነ ይታይልን በሚል አመልካች ላቀረበው ክርክር የስር ፍ/ቤት ከጭብጥ ውጭ ነው በሚል መታለፉ ስነ-ስርዓታዊ ነው?ወይስ አይደለም?የሚለውን ማየት እንዲቻል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን የግራ ቀኙን የሰበር ፅሑፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም አመልካች ተጠሪን ከስር ለማሰናበት በምክንያትነት የጠቀሰው የአንድ ወር እግዱ ጊዜ ካበቃ በኃላ ተጠሪ ወደ ስራቸው ለመመለስ ፍቃደኛ ባለመሆን በተከታታይ ከ5 የስራ ቀናት በላይ በስራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸውና እንዲሁም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የድርጅቱን ማህተም እና የስራ አስኪያጁን ቲተር አስመስሎ ሐሰተኛ የስራ ልምድ ሰርተው ወይም አሰርተው በመጠቀም በፈፀሙት የወንጀል ድርጊት ምክንያት ነው በሚል መሆኑንና እነዚህን ምክንያቶችም ለክሱ መልሱን ሲሰጥ ጀምሮ ስንብቱ ህጋዊ መሆኑን ለማሳየት በመከላከያነት አንስቶ መከራከሩን የስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ተጠሪ ለስራ ስንብቱ ምክንያት ከሆነው ጋር በተያያዘ በፈፀሙት የወንጀል ድርጊት ተከሰው በወንጀል ችሎት ጥፋተኛ ስለተባሉ እና ይህ የወንጀል ችሎት ጥፋተኝነት ውሳኔም ለጉዳዩ አግባብነት ስላለው ቀርቦ ይታይልን በማለት አመልካች ፍ/ቤቱን በክርክሩ ሂደት መጠየቁንም ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ በጭብጥነት የተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ ፍቃደኛ ነበሩ?ወይስ አይደለም?የሚል እንጂ የተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ መሆን ጉዳይ አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው አልፏል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ በወንጀል ችሎቱ በተጠሪ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ አመልካች ስር ፍ/ቤት ካቀረበው መከራከሪያ ነጥብ አኳያ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቱ አስቀርቦ ሳይመለከት እና ጉዳዩንም ከወንጀሉ ጥፋተኝነት ውሳኔ ጋር አገናዝቦ ከመረመረ በኃላ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ነበረበት፡፡

በመሠረቱ ተጠሪ የአመልካችን ማህተም እና እንዲሁም የድርጅቱን ስራ አስኪያጅ ቲተር አስመስሎ ሐሰተኛ የስራ ልምድ አሰርተው እና ይዤንኑ ሐሰተኛ ሰነድም ሌላ ቦታ ለስራ መወዳደሪያነት አለአግባብ በመጠቀም በፈጸሙት ወንጀል ድርጊት ተከሰው በኢ.ፌ.ዲ.ሬ የወንጀል ህግ አንቀጽ 378 ድንጋጌን በመተላለፍ በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው መቀጣቱ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ትዕዛዝ ቀርቦ ከዚህ መዝገብ ጋር እንዲያያዝ የተደረገው የወንጀል መዝገብም ይዤንኑን ያስገነዝባል፡፡

ይህ የተጠሪ ጥፋትም በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1)(ሐ) ስር እንደተመለከተው በስራ ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈፀም የሚለውን የሚያሟላ ከመሆኑም በላይ በአዋጁ አንቀጽ 27(1)(መ) ስር እንደተመለከተውም ተጠሪ የማይገባ ብልፅግና በመሻት የአመልካች ንብረት በሆነው ማህተም በድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ቲተር እና በድርጅቱ ስም አላአግባብ መጠቀም ድርጊት እና ጥፋት መፈፀሙን የሚያሳይ ሲሆን አመልካቹ ከዚህ ምክንያት ጋር በተያያዘ በተጠሪ ላይ የወሰደው የስንብት እርምጃም ከእነዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች አኳያ ህጋዊ ሊሆን የማይችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የተጠሪ ስራ ውል የተቋረጠው ከህግ አግባብነት ውጭ ነው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ ከዚህ በላይ በተገለፁት ምክንያቶች መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ.72453 በ29/8/05 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራሉ ከ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ.135773 በ23/11/05ዓ.ም. ይህንኑን በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1)መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የተጠሪ ስራ ውል የተቋረጠው በህጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች ለተጠሪ የ6ወር የካሳ ክፍያ፤የስንብት እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈል አይገባም ብለናል፡፡
4. ነገር ግን የስር ፍ/ቤቶች የዓመት ረፍት ፍቃድንና ምስክር ወረቀትን አስመልክቶ የሰጡት የውሳኔ ክፍል ብቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
5. ግራ ቀኙ የሰበር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

- ከስር ፍ/ቤት የቀረበው የወንጀል መዝገብ ይመለስ፡፡
- በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠው የአፈፃፀም እግድም ተነስቷል፡፡ይፃፍ
- የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95026

መጋቢት 8 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ዮናስ በቀለ-ከጠበቃ አያሌው ካሳዬ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ብርሃኑ ኩምሳ- ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከስራ ውል መቋረጥ ጋር የተያያዘ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ እና አመልካች እንደቅደም ተከተላቸው ከሳሽ እና ተከሳሽ በመሆን ያደረጉትን ክርክር የመረመረው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የተከሳሽን ክርክር ውድቅ በማድረግ ተከሳሽ የስራ ውሉን ያቋረጡት አላግባብ በመሆኑ ሕገወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች በድምሩ ብር 23,139 ከብር 200 ኪሳራ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት የፀናው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ ሲሆን እኛም በሰበር ክርክሩ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነጥብ የስር ፍ/ቤቶች የስራ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ውሳኔ የሰጡት ለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በግራ ቀኙ ማስረጃ እና በተገቢው ስነ-ስርዓታዊ አግባብ እንዲጣሩ ካደረጉ በኋላ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ በ28/06/2003 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ከሳሽ ከ01/04/1994 ዓ.ም ጀምሮ ከተከሳሽ ጋር የቅጥር ውል ፈጽመው በካሸርነት እና በአስተናጋጅነት ስራ ሲያገለግሉ እንደቆዩ እና ተከሳሽ በ26/06/2003 ዓ.ም የስራ ውላቸውን በሕገወጥ መንገድ እንዳቋረጡባቸው የሚገልጽ ሆኖ ሕገወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የጠየቁበት ሲሆን ተከሳሽ በበኩላቸው በ29/07/2003 ዓ.ም በሰጡት መልስ ከከሳሹ ጋር የአሰሪና ሰራተኛ አገናኝ የደላላነት ስራ በጋራ ሲሰሩ የነበረ ከመሆኑ ውጪ በቅጥር ውል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ያልነበራቸው መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቱ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው በግራ ቀኙ መካከል የቅጥር ውል አለ ወይስ የለም? የሚል ጭብጥ ይዞ ሲሆን ከሳሽ ምስክሮቻቸውን አቅርበው እንዲያሰሙ ካደረገ በኋላ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካች በስር ፍ/ቤት ምስክሮችን ቆጥረው የነበረ መሆኑን በሰበር አቤቱታቸው ላይ የገለጹ እና ይህም በተጠሪው ያልተስተባበለ ሲሆን አመልካች ምስክሮችን ቆጥረው የነበረ ስለመሆኑም ሆነ ምስክሮቹን ሳይሰማ ስለቀረበት ምክንያት ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ የገለጸው ነገር የለም፡፡የአመልካች ምስክሮች ሳይሰሙ የቀሩት አመልካች በተያዘላቸው ቀጠሮ ሳያቀርቧቸው ስለቀሩ ስለመሆኑ ተጠሪ በመልሳቸው የገለጹ ቢሆንም ይህ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያረጋግጥም፡፡ በመሰረቱ ከግራ ቀኙ የክርክር አቋም አንጻር ፍ/ቤቱ ለክርክሩ አወሳሰን የያዘው ጭብጥ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246-248 ድንጋጌዎች አንጻር ትክክለኛ ቢሆንም በሌላኛው ወገን የተቆጠረው ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በሚል ወይም ሕጋዊ ተቀባይነት ባለው ሌላ ምክንያት መሰማት አይገባውም የሚል ግልጽ ትዕዛዝ ሳይሰጥበት የክርክሩ ጭብጥ በአንደኛው ወገን ማስረጃ ላይ ብቻ ተመስርቶ ውሳኔ እንዲያገኝ መደረጉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.255፣257፣258፣259 እና ሌሎችም ድንጋጌዎች አንጻር ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት የተከተለ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በግራ ቀኙ ማስረጃ እና በተገቢው ስነ-ስርዓታዊ አግባብ እንዲጣሩ ሳያደርጉ ስንበቱ ሕገ ወጥ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የተሰጠው እና በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የስራ ስንብቱ ሕገ ወጥ መሆኑን በመግለጽ አመልካች ሕገወጥ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች በድምሩ ብር 23,139 ከብር 200 ኪሳራ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 40456 በ05/09/2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 134431 በ14/02/2006 ዓ.ም በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች የተቆጠሩትን ምስክሮች በመስማት እና የቀረበ ወይም የተቆጠረ ካለም የጽሁፍ ማስረጃ ጭምር በመመርመር በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 3(1) በተመለከተው መሰረት በግራ ቀኙ መካከል በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት መኖር አለመኖሩን አጣርቶ እና መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሰረት ጉዳዩ ለፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
3. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
4. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97555

ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ወ/ሮ ሳኒያ ከድር ጠበቃ ዘካርያስ መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኮሪያ ዘማቾች ቤተሰቦች ሽመናና ስጋጃ ስራ ጠበቃ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሣሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ይዘቱም በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የሁከት ይወገድልኝ ክርክር ክስ ለመስማት በተቀጠረበት ቀን እንደማንኛውም ሰው ፍርድ ቤት ቀርቤ ተራዬን እየጠበቅኩ ስሜ የተጠራ መስሎኝ በሌላ ሰው መዝገብ ችሎት ገብቼ የእኔ ያልሆነው መዝገብ ሲዘጋ የእኔ መስሎኝ በመሄድ የእኔ መዝገብ ሲጠራ ባለመቅረቤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይህ የሆነው ባለመስማትና ባለማሰብ በጥፋቴ ስለሆነ የተዘጋው መዝገብ ይንቀሳቀስልኝ በማለት ሲሆን ተጠሪዎችም የአመልካች ጥያቄ ደርሶአቸው በሰጡት መልስ(ሀሳብ)አመልካች በራሳቸው ጥፋት መዝገቡ መዘጋቱን ስለገለፀው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ እንደዚህ አይነቱን ጥፋት ይቅርታ የሚያደርግበት አግባብ ስለማይኖር መዝገቡን ለማስከፈት በቂ ምክንያት አይሆንም በቸልተኝነታቸው በመሆኑ ሊንቀሳቀስ አይገባም ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ክርክር ከፍ/ብ/ሥ/ሥህቁ. 74(2) አንጻር ለመመርመር ከላይ አመልካች ባለመቅረባቸው ምክንያት ነው ብለው የሰጡትን ሀሳብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጋችን በቂ የሆነ እክል ምክንያት ትርጉም ባይሰጠውም አመልካችን ከችሎት መቅረብ ያገደው ምክንያት በቂ እክል ሊሆን የሚችል አይደለም በማለት መዝገቡ ሊቀሳቀስ አይገባም በማለት ጥያቄው ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በይግባኝ የቀረበለትን መዝገብ በ22-4-2006 በዋለው ችሎት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡በአቤቱታቸውም ላይ የሥር ውሣኔዎች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን ቁጥር 74(2) አላማ ያላገናዘበ ትርጉም የተሰጠው ስለሆነና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልን ይገባል ሲሉ ጠይቋል፡፡

በዚህም የሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው አመልካች የሌላ ሰው ሥም ሲጠራ በስህተት ወደ ችሎት ገብተው መዝገባቸው የተዘጋ መስሏቸው መሄዳቸው በቂ እክል ምክንያት ነው?አይደለም የሚለውን ለመመርመር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካቀረቡት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንግዲህ አመልካች በዚህ ጉዳይ የሚሉት በፍ/ቤቱ ቅጥር ጊቢ መጥቼ ተራዬን በመጠባበቅ ላይ እያለሁ በስህተት የሌላ ሰው መዝገብ በተጠራበት ወደ ችሎት ገብቼ መዝገቡ የተዘጋ መስሎኝ መሄዴ በጉዳዩ መሣሣቴና ያለማሰቤን ይገልፃልና መዝገቡ ሊንቀሳቀስልኝ ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው እንደዚህ ያለው ስህተት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህጋችን እንደበቂ ምክንያት ሊቆጠር የሚገባው ነው አላለም ስለዚህ ሊንቀሳቀስላቸው አይገባም የሚል ነው፡፡የሥር ፍ/ቤቶችም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰሙ በኃላ አመልካች በንቃት መከታተል ነበረባቸው ጥፋት መሆኑን እራሳቸውም አምኗልና መዝገቡ ሊንቀሳቀስ አይገባም በማለት በብይን ዘግቶታል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የጉዳዩን አመጣጥ ሲመረምረው አመልካች ቀጠሮአቸውን አውቀው ወደ ፍ/ቤት ጊቢ መጥተው መሄዳቸው ተጠሪ በዕለፍ ከሰጡት መልስም ሆነ የሥር ፍ/ቤቶች የተቀበሉት እውነታ ነው ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች በስም ስህተትና ባለማስተዋል ችሎት ገብቶ መዝገባቸው የተዘጋ መስሏዋቸው መሄድ በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብለው ጉዳያቸውን ትተው የሄዱ ናቸው ወደ ሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ተጠሪ እንደሚሉትም አመልካች ጉዳዩን ለመጎተትና ተጠቃሚ ለመሆን ሲሉ እያዩ ሄዱ የሚለው ክርክርም ከግምትነት በዘለለ የተረጋገጠም አይደለም፡፡በመሆኑም ችሎቱ ይህን አባባል አልተቀበለውም፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.74(2) ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማም የአመልካችን አይነት ተከራካሪ ወገን ለመገደብ ተብሎ የተቀረፀ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻልበት ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

በመሆኑም አመልካች ለመዝገቡ መዘጋት እንደ ምክንያት ያቀረቡዋቸው ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. (74(2) ሥር እንደ በቂ የእክል ምክንያት ሊቆጠር አይችልም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ማጣቱ መሠረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርዓታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ብይንና የፌ/ከ/ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስላቸው ያቀረቡት ምክንያት በፍ/ስ/ሥ/ሥ/ቁ. 74(2)መሠረት በቂ ነው ብለናል፡፡
3. መዝገቡ እንደገና ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ ከቆመበት ይቀጥል ብለን ጉዳዩን ለስር ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ይፃፍ፡፡
4. የግራ ቀኙ ውጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 95620

ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ረታ ቶሎሳ
አዳነ ንጉሤ
መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- በቂርቆስ ክ/ከተማ የወረዳ 7 አስተዳደር ጽ/ቤት - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡-

1. ፤ አለቃ ከድር አህመድ } ቀረቡ
2. ወታደር ምትኩ ጀማል }
3. ፤ አለቃ ነጋሽ አሰፋ } አልቀረቡም
4. ፤ አለቃ ሳሙኤል በቀለ }

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ከሳሾች ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም አሻሽለው ባቀረቡት ክስ፡- ታህሳስ 01 ቀን 1996 ዓ/ም ከተከሳሽ ጋር ባደረግነው የአጭር ጊዜ የሊዝ ውል 128 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ 4 ክፍል የንግድ ቤቶችን በግል ገንዘባችን ሰርተን ስንጠቀምበት የቆየን ቢሆንም ቦታው ለሸራተን ሆቴል ማስፋፊያ ምክንያት እንዲፈርስ ተወስኖ ቤቶቹን ተከሳሽ ያስፈረሰ ቢሆንም ፍራሹን ለከሳሾች መስጠት ሲገባው ከሌሎች ከፈረሱት የመንግስት ቤቶች ጋር ተሸጧል በሚል ስለከለከለን ለቤቶቹ መሥሪያ የዋሉትን ቁሳቁሶች ዋጋ እና ቤቶቹን ለሰሩት ባለሙያዎች የተከፈለውን የእጅ ዋጋ በድምሩ ብር 130,000.00 ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልን ሲሉ የንብረቶቹን ዝርዝር እና ግምታቸውን በማስፈር ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽም ጥር 30 ቀን 2005 ዓ/ም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከማቅረቡም ሌላ በአማራጭ በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ ሰጥቷል፡፡ የመቃወሚያ ነጥቦቹም፡- በከሳሾች እና ተከሳሽ መካከል በተደረገው የሊዝ ውል አንቀጽ 12 በውሉ ትርጉምና አፈጻጸም ዙሪያ አለመግባባቶች ሲከሰቱ በስምምነት ሊፈቱ እንደሚገባ፤ካልተቻለም በሽምግልና ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶ እንደሚጠናቀቅ ስለተስማማን ከሳሾች በቀጥታ ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡትን ክስ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ለማከራከር ሥልጣን የለውም፤የሊዝ ውሉ ጊዜው የተጠናቀቀ በመሆኑ ቀሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሆነውን ውል መሰረት አድርገው ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም የሚሉ ናቸው፡፡ እንዲሁም በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው መልስ፡-በሊዝ ውሉ አንቀጽ 6(4) መሰረት ከሳሾች ቦታው ለልማት ተፈልጎ እንዲነሱ በሚጠይቁበት ጊዜ ለግል ሥራቸው ለገነቧቸው ግንባታዎች ወጪም ሆነ ካሳ ሊጠይቁ እንደማይችሉ የተደነገገ በመሆኑና ቦታውም ለልማት መፈለጉን ባልካዱበት ሁኔታ ያቀረቡት የንብረት ግምት ክስ አግባብነት የለውም ሲል ከመከራከሩም በተጨማሪ ከሳሾች ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው ጠይቀው በኮንቴይነር ኢንተርፕራዝ እንዲደራጁ ከተደረገ በኋላ የተሰጣቸውን የንግድ ማከናወኛ ቦታ ለ3ኛ ወገን አስተላልፈው በመገኘታቸው በመመሪያው መሰረት እንዲነጠቁ ተደርጓል፤ ብር 130,000.00 ለንብረታቸው ግምት እንዲከፈላቸው ጥያቄ ቢያቀርቡም ንግድ ቤቱ ሲሰራ የተሰራበት ዕቃ የወጪ ዝርዝር በማስረጃ አስደግፈው ካለማቅረባቸውም ሌላ ተከሳሽም ንብረቱን በምን ያህል ዋጋ እንደሸጠ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ በመሆኑም ከሳሾች ክሳቸውን በዝርዝር ማስረጃ አስደግፈው ስላላቀረቡ ውድቅ ሊደረግባቸው ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ያቀረባቸውን የመቃወሚያ ነጥቦች ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው ፍርድ፡- በከሳሾች እና ተከሳሽ መካከል ታህሳስ 01 ቀን 1996 ዓ/ም በተደረገው የአጭር ጊዜ የሊዝ ውል አንቀጽ 6.4 ውል ሰጪ ቦታውን ለሌላ ልማት ፈልጎት ውል ተቀባዩ እንዲለቅ ሲጠየቅ ውል ተቀባዩ ለግል ሥራው ይጠቅመኛል ብሎ ለገነባቸው ቤቶች ወጪም ሆነ ኪሳራ ሊጠይቅ እንደማይችል የተገለጸ ቢሆንም በአንቀጹ የሰፈረው ሁኔታ ከሳሾች ቦታውን ሲለቁ ለግንባታ የተጠቀሙባቸውን ንብረቶች የመጠየቅ እና ከተከለከሉም ግምታቸውን ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይደለም፣ተከሳሽም የከሳሾችን ቤቶች ስለማፍረሱ እና የቤቶቹን ፍራሽ አካላት መሸጡን በማመኑ ተከሳሾች በክሳቸው ለጠቀሷቸው ንብረቶች ግምታቸውን የማይከፍልበት ምክንያት አይኖርም ሲል ከሳሾች እንዲከፈላቸው ክስ ካቀረቡት የብር 130,000.00 የንብረት ግምት ውስጥ ብር 31,620.00 በመቀነስ ቀሪውን ብር 73,780.00 ፍርዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ተከሳሹም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከራቸው በኋላ በሰጠው ፍርድ፡-የሥር ፍርድ ቤት የተሻሻለ ክስ እንዲቀርብ የሰጠው ትዕዛዝ መልስ ሰጪዎች ግምቱን በተመለከተ ዘርዝረው እንዲያቀርቡ ከሚገልጽ በስተቀር ሌላ የተለየ ይዘት የለውም፣ይግባኝ ባይም ቀደም ሲል የቀረበው ክስ ግልጽ ባለመሆኑ ለመከላከል የሚያስችል አይደለም በማለት በዝርዝር እንዲቀርብ አለመጠየቁ በወቅቱ በቂና ለመከላከል የሚያስችል መሆኑን አምኖ መቀበሉን ስለሚያሳይ በተሻሻለው ክስ መልስ አልሰጠሁም ሲል ያቀረበው ቅሬታ መሰረታዊ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚገባ አይደለም፣እንዲሁም ይግባኝ ባዩ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ተገቢ ነው የሚላቸውን ክርክሮች በማቅረቡ ክርክሩን ለሥር ፍርድ ቤት መመለስ መልስ ሰጪዎችን ለመጉላላት ከሚዳርግ በስተቀር ጠቀሜታ የለውም ብሏል፡፡ በሌላ በኩል ይግባኝ ባዩ እንዲከፍል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ በተመለከተም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከብር 130.000.00 ውስጥ ብር 73,780 ይግባኝ ባዩ እንዲከፍል መወሰኑ ፍትህን የሚያጓድል አይደለም ሲል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ አጽንቷል፡፡

አመልካችም በሥር ፍርድ ቤቶች ፍርድ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡- ለአመልካች የደረሰው ክስ በ03/02/2005 ዓ/ም የተጻፈ ሲሆን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በራሱ አነሳሽነት አመልካችን ሳይጠራ ክሱ እንዲሻሻል በማዘዝ በ15/04/2005 ዓ/ም ተሻሽሎ በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንድሰጥበት ሳያደርግ እና የመከላከያ መልሴን ሳላቀርብ ተሻሽሎ የቀረበውን ክስ መሰረት አድርጎ ፍርድ መስጠቱም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ማጽናቱ ፍርድ ቤቶቹ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ህግ ጥሰት መፈጸማቸውን የሚያሳይ ነው፤ለአመልካች የተሻሻለው ክስ ቢደርስ ኖሮ በቀረበው የንብረት ግምት ዝርዝር እና ማስረጃ ዝርዝር አንጻር አመልካችም ንግድ ቤቶቹ ከመፍረሳቸው በፊት በባለሙያ የተሰራውን ግምት እና ቤቶቹ ሲፈርሱ የነበሩትን እማኞች በማቅረብ ማስተባበል የምችል ሆኖ ሳለ ክርክሩ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ማድረጉ ጠቀሜታ የለውም ሲል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በፍርዱ ያሰፈረው ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- በመጀመሪያው ክስ በጥቅል ቀርቦ የነበረው የንብረት ግምት ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም ተሻሽሎ በቀረበው ክስ በዝርዝር ከመቅረቡ ውጪ የተሻሻለው ክስ በመጀመሪያ ከቀረበው ክስ የፍሬ ነገር ልዩነት የለውም፡፡ የተሻሻለውና በዝርዝር የቀረበው ክስ ለአመልካች ቢደርስ ኖሮ አመልካቹ ምናልባት እንደገና ግምቱን ከመቃወም በስተቀር አስቀድሞ የንግድ ቤቶቹን ማፍረሱን በማመኑ ክዶ መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በመሆኑም ለአመልካች የተሻሻለው ክስ ቢደርሰውም እንኳን ውሳኔውን የሚያስለውጥ ክርክር ማቅረብ በማይችልበት ሁኔታ የመከላከል መብቱ አልተከበረም ሲል ያቀረበው ክርክር ውድቅ ሊደረግበት የሚገባ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም ተጠሪዎች ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-የሥር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ፍርድ የሰጡት አግባብነት ያላቸውን የፍትሃብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ጠብቀው ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍርዱ መግቢያ ላይ የአሁን ተጠሪዎች ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም የተጻፈ የተሻሻለ ክስ ማቅረባቸውን የገለጸ ሲሆን አመልካችም ጥር 30 ቀን 2005 ዓ/ም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ ማቅረቡን መዝግቧል፡፡ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ፍርድ የሰጠውም ይህንኑ የተሻሻለውን ክስ እና አመልካች ጥር 30 ቀን 2005 ዓ/ም ያቀረበውን መልስ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም በተሻሻለው የተጠሪዎች ክስ ላይ አመልካች መልስ ስለመስጠቱ የፍርድ ቤቱ ፍርድ አያመላክትም፡፡ ጥር 30 ቀን 2005 ዓ/ም አመልካች የሰጠው መልስ ለመጀመሪያው ክስ እንጂ ለተሻሻለው ክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለመሆኑን በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ከተደረገው ክርክር እና ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከሰጠው ፍርድ መረዳት ከመቻሉም ሌላ በዚህ በሰበር ደረጃም በተደረገው ክርክር ተጠሪዎች አመልካች ለተሻሻለው ክስ መልስ አለመስጠቱን በማመን ተከራክረዋል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሻሻለው ክስ ላይ አመልካች የበኩሉን መልስ እንዲሰጥበት ያላደረገው ምክንያት ግልጽ ባይሆንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን ለተሻሻለው ክስ አመልካች መልስ አለመስጠቱን ካረጋገጠ በኋላ አመልካች በተሻሻለው ክስ መልስ እንዲሰጥበት ማድረጉ የሚያመጣ ለውጥ አይኖረውም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪዎች አሻሽለው ያቀረቡት ክስ ግምቱን በተመለከተ በዝርዝር ማቅረባቸውን ከሚያሳይ በስተቀር ከመጀመሪያው ክስ የተለየ ይዘት ያለው ካለመሆኑም ሌላ አመልካችም ግምቱ ተገቢ እንዳልሆነ በመጀመሪያው ክስ ተከራክሯል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ መጀመሪያ በቀረበው ክስ ንብረቶቹ የሚያወጡት ዋጋ ግምት እና ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎች በዝርዝር አለመቅረባቸው ተረጋግጦ ክሱ ተሻሽሎ የንብረቶቹ ዝርዝር ከነግምታቸው እና የተለያዩ ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎች ተለይተው በዝርዝር እንዲቀርቡ እስከተደረገ አመልካችም የተሻሻለው ክስ ደርሶት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1)(ሠ) በተነገረው መሰረት የማያምናቸውን የንብረቶቹን ግምት እና ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎችም ካሉ በግልጽ እና በዝርዝር በመካድ እንዲከራከር፣ እንዲሁም በዚሁ የህግ ቁጥር በፊደል (መ) መሰረት የበኩሉን ማስረጃዎች በማቅረብ እንዲያስተባብል ዕድል መስጠት በድንጋጌው የተመለከተው መብቱ እንዲከበርለት የሚያደርግ ከመሆኑም ሌላ ትዕዛዙን የሰጠው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91(1) መሰረት ክሱ እንዲሻሻል በራሱ አነሳሽነት ሲያዝ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ይረዳል በሚል የያዘውን ዓላማ ከግብ እንዲያደርስ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡ በመሆኑም በተሻሻለው የተጠሪዎች ክስ ላይ አመልካች መልስ ሳይሰጥበት እና የበኩሉን የማስተባበያ ማስረጃዎችን ሳያቀርብ የሥር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ፍርድ የሰጡት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ደንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ፍርዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ የተደነገገውን የክርክር አመራር ሥርዓት መሰረት በማድረግ የተሰጠ አለመሆኑን ስለሚያሳይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ስንል ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 02230 በቀን 19/07/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/135414 በቀን 23/03/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. ተጠሪዎች ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም አሻሽለው ያቀረቡት ክስ ለአመልካች ደርሶት አመልካችም የበኩሉን መልስ እንዲሰጥበት ከተደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማት በጉዳዩ ላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የበኩሉን ፍርድ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ለቂርቆስ ምድብ ችሎት ትዕዛዝ ይጻፍ፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95649

ሚያዝያ 6 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኢትዮጵያ ንጉሴ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አዲስ ጡብ ማምረቻ ድርጅት - ጠበቃ ምናለ ዓለሙ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በአሰሪው የተወሰደበት የስራ ስንብት እርምጃ ሕገ ወጥነት በፍርድ ተረጋገጦ ወደስራው እንዲመለስ ለተወሰነለት ሰራተኛ ውዝፍ ደመወዝ መክፈል የሚገባው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) የተመለከተውን ድንጋጌ አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ተጠሪው የወሰደውን የስንብት እርምጃ በመቃወም አመልካች ባቀረቡት ክስ ሳቢያ ጉዳዩን የተመለከተው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ እንደሆነ መረጋገጡን ገልጾ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) መሰረት የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ቀድሞ ስራቸው እንዲመለሱ በመ/ቁ. 74375 በ02/08/2005 ዓ.ም ውሳኔ መስጠቱን፣በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪው ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይ/ሰሚው ከ/ፍ/ቤት አፈጻጸሙን አግዶ ካቆየ በኃላ በመጨረሻ ግን በመ.ቁ.133025 በ02/11/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/.ቁ. 337 መሰረት ዘግቶ ማሰናበቱን፣ከዚህ በኃላ አመልካች ጉዳዩ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት ለቆየበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ታስቦ እንዲከፈላቸው በመጀመሪያው የስረ-ነገር መዝገብ ላይ በ26/02/2006 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ለፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸውን፣ፍ/ቤቱም ጥያቄው መቅረብ የሚገባው ለይ/ሰሚው ፍ/ቤት እንደሆነ ገልጾ በ29/02/2006 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱን፣ቀጥሎም ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ባፀናበት ወቅት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) መሰረት የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ሳይወስንላቸው ያለፈው በስህተት በመሆኑ ውሳኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት እንዲታረምላቸው በ18/03/2006 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸውን፣ ፍ/ቤቱም አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት ነጥብ ውሳኔ ያላረፈበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ሊታረም የሚችል ጉዳይ አይደለም በማለት በ26/03/2006 ዓ.ም. ትዕዛዝ መስጠቱን እና አመልካች አቤቱታ ያቀረቡትም ሁለቱ የስር ፍ/ቤቶች በመጨረሻ የሰጧቸው ሁለት ትዕዛዞች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ስለፀና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) መሰረት ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈላቸው የዳኝነት ጥያቄያቸውን በግልጽ አቅርበው እያለ በአቤቱታው ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ተጠቅሷል በሚል አቤቱታው በሙሉ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካቿ መሰረታዊ የክርክር ነጥብ ይ/ሰሚው ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 133025 በ02/11/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ዘግቶ ያሰናበተው አፈጻጸሙን አግዶ ካቆየ በኋላ በመሆኑ በመ/ደ/ፍ/ቤት ከተወሰነልኝ የስድስት ወራት ውዝፍ ደመወዝ በተጨማሪ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) መሰረት ሌላ የስድስት ወራት ውዝፍ ደመወዝ ሊወሰንልኝ ይገባ ነበር የሚል መሆኑን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡እንደተባለው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው በ02/08/2005 ዓ.ም ሲሆን ይ/ሰሚው ከ/ፍ/ቤት ደግሞ አፈጻጸሙን አግዶ ካቆየ በኋላ ይግባኙን ዘግቶ ያሰናበተው በ02/11/2005 ዓ.ም በመሆኑ አፈጻጸሙ ለሶስት ወራት ያህል ታግዶ ቆይቷል፡፡ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን ዘግቶ ያሰናበተው አፈጻጸሙን ለሶስት ወራት አግዶ ካቆየ በኋላ በመሆኑ ይግባኙን በሰረዘበት ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) በተመለከተው መሰረት ተጨማሪ ውዝፍ ደመወዝ ሊወሰንልኝ ሲገባው በዝምታ ያለፈብኝ አላግባብ ነው የሚሉ ከሆነ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ተጨማሪ ውዝፍ ደመወዝ ሳይወስን ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበት በ02/11/2005 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ ላይ አመልካች ስርዓቱን ጠብቀው የሰበር አቤቱታቸውን ማቅረብ ይጠበቅባቸው የነበረ ሆኖ እያለ ይህንን አላደረጉም፡፡ይልቁንም የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክተው ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን ዘግቶ ካሰናበተ ከአራት ወር ከሶስት ሳምንት በኋላ አመልካች የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲታረምላቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ድንጋጌን በመጥቀስ ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረባቸውን ነው፡፡በመሰረቱ አንድ ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ውስጥ ውሳኔ ሊያሳርፍበት ይገባው የነበረውን መብት አላግባብ አልፎብኛል የሚል ተከራካሪ ወገን አላግባብ ታለፈብኝ የሚለውን መብት ማስከበር የሚችለው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ቀጥሎ ላለው የፍ/ቤት እርከን ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ በማቅረብ ከሚሆን በስተቀር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ድንጋጌን ጠቅሶ ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረብ አይደለም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ድንጋጌ ለተያዘው ዓይነት ክርክር አግባብነት/ተፈጻሚነት/የሌለው ስለመሆኑም ከድንጋጌው አነጋገር በግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት ነጥብ ውሳኔ ያላረፈበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ሊታረም የሚችል ጉዳይ አይደለም በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. ይ/ስሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ባጸናበት ወቅት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) መሰረት የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ሳይወስንልኝ ያለፈው በስህተት በመሆኑ ውሳኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ይታረምልኝ በማለት አመልካች በ18/03/2006 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ያቀረቡትን ጥያቄ የመረመረው የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት ነጥብ ውሳኔ ያላረፈበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ሊታረም የሚችል ጉዳይ አይደለም በማለት በመ.ቁ. 133025 በ26/03/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90361

የካቲት 26 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡-1. ወ/ሮ አለዊያ ዑመር

2. አቶ አህመድ ሁሴን

3 .ወ/ሮ ኑር ሁሴን

4. ወ/ት አስማ ሁሴን

5. አቶ መህሲን ሁሴን

6. ወ/ት አይዳ ሁሴን

ተጠሪ፡- አቶ ሐሺም ሁሴን

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ዕዳ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ተከሳሾች በነበሩት የአሁኖቹ አመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡በ17/10/2003 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-የ1ኛ ተከሳሽ ባለቤት የነበሩት እና የቀሪዎቹ ተከሳሾች አባት የሆኑት አቶ ሁሴን አህመድ በ28/09/1992 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ተከሳሾቹ የሚስትነት እና የወራሽነት ማስረጃ መውሰዳቸውን፣ሟች እና ሼህ አህመድ ሁሴን አል አሙዲ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የብርጭቆ ፋብሪካ በሽርክና ሲያቋቁሙ ከሳሽ ፋብሪካውን እንዲያስተዳድሩ ተስማምተው የነበረ መሆኑን፣ከሳሽም ከሶስት ዓመታት ያለምንም ስራና ክፍያ ሲጉላሉ መቆየታቸውን፣የፕሮጀክቱን ስራ ተግባራዊ ለማድረግ በሂደት ላይ እያሉ ሼህ አህመድ ሁሴን አል አሙዲ በገዛ ፈቃዳቸው ራሳቸውን ከፕሮጀክቱ ያገለሉ መሆኑን፣ከሳሽ ያለምንም ስራና ክፍያ ለቆዩባቸው ሶስት ዓመታት ክፍያና ካሳ የሚውል ብር 400,000 በሼህ አህመድ ሁሴን አል አሙዲ በስህተት ለሟች እንዲከፈል መደረጉን እና ሟችም ክፍያው የተከፈላቸው በስህተት መሆኑን አምነው በ10/05/1985 ዓ.ም በተጻፈ መተማመኛ በእማኞች ፊት አረጋግጠው እያለ ይህንን ክፍያ ሳይፈጽሙ በሞት መለየታቸውን የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሾቹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአውራሻቸው የሆነውን ይህንኑ ዕዳ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሾቹ በበኩላቸው በ14/11/2003 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ ሟች መተማመኛ ሰጡ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ከ18 ዓመት በላይ የሚሆነው በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፣1ኛ ተከሳሽ የሟች ባለቤት፣ቀሪዎቹ ተከሳሾች ደግሞ ወራሾች ስለመሆናቸው የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን፣ሟች በ10/05/1985 ዓ.ም ሰጡ በተባለው መተማመኛ ላይ ያለው ፊርማ የሟች አለመሆኑን፣2ኛ ተከሳሽ ዕዳውን አምነው የተቀበሉበት ነው በተባለው በ09/12/2001 ዓ.ም በተጻፈው ሰነድ ላይ ያለው ፊርማም የ2ኛ ተከሳሽ አለመሆኑን እና ውርሱ ሳይጣራ እና የውርስ ክፍያው ሳይፈጸም ወራሾች በሟች ዕዳ ሊጠየቁ የማይገባ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ፍ/ቤቱም ፊርማዎቹ በተካዱት ሁለቱ ሰነዶች ላይ የተመለከቱት ፊርማዎች ተመርምረው ውጤቱ እንዲገለጽ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በሟች ተሰጠ የተባለው መተማመኛ በአረብኛ የእጅ ጽሑፍ የተጻፈ በመሆኑ መመርመር እንዳልተቻለ የተገለጸ ሲሆን በ2ኛ ተከሳሽ የተሰጠ ነው በተባለው መተማመኛ ላይ ያለው ፊርማ ግን በ2ኛ ተከሳሽ የተፈረመ መሆኑ ተረጋግጦ ቀርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር ከመረመረ በኋላ 1ኛ ተከሳሽ የሟች ባለቤት፣ ቀሪዎቹ ተከሳሾች ደግሞ ወራሾች መሆናቸውን እንዳረጋገጠ፣ሟች መተማመኛ ሰጡ ከተባለበት ከ10/05/1985 ዓ.ም. ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት 17/10/2003 ዓ.ም ድረስ ከ18 ዓመት በላይ ያለፈው ቢሆንም 2ኛ ተከሳሽ በ09/12/2001 ዓ.ም በሰጡት መተማመኛ ሟች በሰጡት ማስረጃ መሰረት ብር 400,000 ፋብሪካው ከተሸጠ በኋላ የሚከፈል መሆኑን በማረጋገጥ መተማመኛ የሰጡ በመሆኑ እና ተከሳሾቹ በሰነዱ ላይ የተመለከተው ፊርማ የ2ኛ ተከሳሽ አለመሆኑን ክደው የነበረ ቢሆንም ፊርማው የ2ኛ ተከሳሽ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ በ2ኛ ተከሳሽ የተሰጠው የዕዳ ማረጋገጫ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1851(ሀ) መሰረት ይርጋውን የሚያቋርጥ እንደሆነ እና ተከሳሾቹ በወረሱት የገንዘብ መጠን የሟችን ዕዳ የመክፈል ግዴታ እንዳለባቸው በመግለጽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከወለድ እና ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተከሳሾቹ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሳሾቹ በስር ፍ/ቤት ለክሱ በሰጡት መልስ 2ኛ ተከሳሽ ዕዳውን አምነው የተቀበሉበት ነው በተባለው በ09/12/2001 ዓ.ም በተጻፈው ሰነድ ላይ ያለው ፊርማም የ2ኛ ተከሳሽ አለመሆኑን ክደው ከመከራከር ውጪ 2ኛ ተከሳሽ የሰጠው መተማመኛ ሌሎች ተከሳሾችን አይመለከትም በሚል ያቀረቡት ክርክር ባለመኖሩ በይግባኝ ክርክር ደረጃ 2ኛ ተከሳሽ የሰጠው መተማመኛ ሌሎች ተከሳሾችን አይመለከትም በሚል ያቀረቡት ክርክር በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ ምክንያት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾቹ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት ይዙቱ ከላይ የተመለከተው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካቾች ለሟች ዕዳ የአንድነት ባለዕዳዎች ናቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚባል ቢሆን እንኳ 2ኛ አመልካች በ09/12/2001 ዓ.ም. ብቻውን በግሉ ሰጠ የተባለው የባለዕዳነት መተማመኛ የተቀሩትን ባለዕዳዎች ሁኔታ ሊያከብድ የሚችል መሆን አለመሆኑን ከፍ/ሕ/ቁ.1906 አንፃር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ሕግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈጸም ወይም ካለመፈጸሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በአስር ዓመት ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን እና የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምረውም ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም ውሉ የሚሰጠው መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 1845 እና 1846 ላይ ተመልክቷል፡፡ አመልካቾቹ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት የሚከራከሩትም ሟች መተማመኛ ሰጡ ከተባለበት ከ10/05/1985 ዓ.ም. ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት 17/10/2003 ዓ.ም. ድረስ ከ18 ዓመት በላይ አልፎታል በማለት ሲሆን የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ይህን የይርጋ መቃወሚያ ላለመቀበል የሰጠው ምክንያት በ2ኛ ተከሳሽ በ09/12/2001 ዓ.ም. የተሰጠው የዕዳ ማረጋገጫ በፍ/ሕ/ቁ. 1851(ሀ) መሰረት ይርጋውን መቆጠር ያቋርጠዋል የሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ በሕግ ተለይቶ የተወሰነ የይርጋ ጊዜ የመቋረጥ እና ያለመቋረጥ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ ሊነሳ የሚችለው የይርጋውን መቆጠር ያቋርጠዋል የተባለው ምክንያት የተከሰተው የይርጋው ጊዜ ከመሙላቱ በፊት በሆነ ጊዜ እንጂ የይርጋው ጊዜ የሞላ ወይም ያለፈ በሆነ ጊዜ ጭምር አይደለም፡፡በተያዘው ጉዳይ ሟች መተማመኛ ሰጡ ከተባለበት ከ10/05/1985 ዓ.ም. ጀምሮ 2ኛ አመልካች መተማመኛ ሰጡ እስከተባለበት 09/12/2001 ዓ.ም. ድረስ 16 ዓመት ያለፈ በመሆኑ እና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ከተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ የሚበልጥ በመሆኑ 2ኛ አመልካች ሰጡት የተባለው መተማመኛ የይርጋውን መቆጠር የሚያቋርጥ ነው በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተያዘውን አቋም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሟች በሰጡት ማስረጃ መሰረት ብር 400,000 ፋብሪካው ከተሸጠ በኋላ የሚከፈል መሆኑን በማረጋገጥ 2ኛ አመልካች በ09/12/2001 ዓ.ም. መተማመኛ የሰጡ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በመሰረቱ የይርጋ ተጠቃሚ የሆነ ሰው የሞላውን ይርጋ ለመተው እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1856(1) የተመለከተ በመሆኑ አመልካቾቹ ሟች በ10/05/1985 ዓ.ም. ከሰጡት መተማመኛ አንጻር ሞልቶ የነበረውን ይርጋ በመተው አዲስ የመተማመኛ ሰነድ የሰጡ መሆኑ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ ይህ በ2ኛ አመልካች በ09/12/2001 ዓ.ም የተሰጠው መተማመኛ ይርጋን የሚያቋርጥ ሳይሆን አዲስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ የሚያመለክት በመሆኑ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ የመሆን አለመሆኑ ጉዳይ ሊወሰን የሚገባው የይርጋ ጊዜውን ከ09/12/2001 ዓ.ም. በመቁጠር ነው፡፡ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ይርጋው አልፏል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

አመልካቾቹ አጥብቀው የሚከራከሩበት ሌላኛው ነጥብ 2ኛ አመልካች በ09/12/2001 ዓ.ም. መተማመኛ የሰጡት በራሳቸው ሰም እንጂ በሌሎች አመልካቾች ስም ጭምር አይደለም የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡በመሰረቱ አመልካቾቹ ከስር ጀምሮ የሚከራከሩት በአንድነት ሲሆን በከ/ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ እንደተገለጸው በሰነዱ ላይ የተመለከተው ፊርማ የ2ኛ ተከሳሽ አይደለም ከማለት በስተቀር ይህን የክርክር ነጥብ በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት አንስተው አልተከራከሩበትም፡፡በመጀመሪያ ደረጃ ያልተነሳውን ክርክርና ያልቀረበውን አዲስ ነገር በይግባኝ ደረጃ መቀበል የማይቻል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329(1) ስር የተመለከተ በመሆኑ ይህ የክርክር ነጥብ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ 2ኛ አመልካች ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ ስለሌሎች አመልካቾች የውክልና ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ እና በ09/12/2001 ዓ.ም መተማመኛውን በፊረሙ ማግስት በግልግል ዳኞች ጉባኤ ዘንድ ቀርበው ስለሁሉም አመልካቾች የዕርቅ ሰነድ የፈረሙ ስለመሆኑ ተጠሪ በመልሳቸው ላቀረቡት ክርክር አመልካቾች ያቀረቡት የማስተባበያ ክርክር አለመኖሩን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ይህም 2ኛ አመልካች መተማመኛውን የፈረሙት በራሳቸው ስም ብቻ ሳይሆን በሌሎችም አመልካቾች ስም መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል በመሆኑ 2ኛ አመልካች መተማመኛውን የፈረሙት በራሳቸው ስም ብቻ ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር የሕግ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ሁሉ አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 185840 በ28/09/2004 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 125077 በ25/06/2005 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.86398

ሐምሌ 28 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልች፡- ወ/ሮ አስለፈች ይመር - ጠበቃ ችርነት ወርዶፋ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ አስመረት ተወልደ
2. አቶ ብርሃኔ ተወልደ
3. አቶ ናትናኤል ተወልደ

ጠበቃ ማርቆስ ወ/ሰንበት ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ጋብቻ ወይም የትዳር ሁኔታ መኖር አለመኖርን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረቡትን የመቃወሚያ ክርክር በመቀበል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች የአቶ ተወልደ ገብሩ ሕጋዊ ሚስት ናቸው፤ብርክቲ ተወልደ፣ሲሳያስ ተወልደ፣ዳንኤል ተወልደ እና ሄለን ተወልደ ደግሞ ከዚሁ ጋብቻ የተወለዱ የአቶ ተወልደ ገብሩ ልጆችና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ናቸው በማለት ቀደም ሲል በ22/03/1993 ዓ.ም. ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360(2) ድንጋጌ መሰረት አሻሽሎ የአመልካችን ሚስትነት የሚመለከተውን የውሳኔ ክፍል በመሰረዝ እና የተወላጆቹን ልጅነት እና ወራሽነት የሚመለከተውን የውሳኔ ክፍል ግን በማጽናት የሰጠው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 17 በቀበሌ 20 በቤት ቁጥር 1972 ሲኖሩ ቆይተው በ12/03/1991 ዓ.ም በሞት መለየታቸውን በመግለጽ አመልካች ሚስትነታቸው እና የአራቱ ልጆች ወራሽነት እንዲሁም አመልካች ለሁለቱ ልጆች ሞግዚት መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው በ29/03/1991 ዓ.ም አቤቱታ ማቅረባቸውን፣ለዚህ አቤቱታቸውም አራት ምስክሮችን መቁጠራቸውን እና ሚስትነታቸውን የሚያረጋግጥ ከወረዳ 2 ቀበሌ 11 ጽ/ቤት በቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ ላይ የተመዘገቡበትና ሌሎችም ማስረጃዎች በትዕዛዝ እንዲቀርቡላቸው መጠየቃቸውን፣በሌላ በኩል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቶ መስፍን ተወልደ፣ወ/ሮ ይህደጎ ተወልደ እና ወ/ሮ ፍሬ ወይኒ ተወልደ የተባሉ ሰዎች የሚች አቶ ተወልደ ገብሩ ልጆች መሆናቸውን ገልጸው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በጣልቃ ገብነት ለመከራከር ጠይቀው በተፈቀደላቸው መሰረት በ23/11/1991 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ሚች በአድራሻቸው ይኖሩ የነበሩት ከሕጋዊ ባለቤታቸው ከወ/ሮ አክበረት አስገዶም ጋር መሆኑን፣ሚች ከአመልካች ጋር አመልካች በጠቀሱት አድራሻ ኖረው የማያውቁ መሆኑን፣አመልካች ሚስት ስለመሆናቸው የቀረበ የጽሁፍ ማስረጃ አለመኖሩን፣ሌሎች አመልካቾችም በጋብቻ ውስጥ ስላልተወለዱ ልጅነታቸውን አረጋግጠው መቅረብ የሚጠበቅባቸው መሆኑን በመግለጽ መከራከራቸውን፣ለዚህ የጣልቃ ገቦች ክርክር አመልካቿ በ11/04/1992 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ሚች ከወ/ሮ አክበረት አስገዶም ጋር የነበራቸው ጋብቻ በስምምነት የፈረሰ መሆኑን፣የጋብቻ ሁኔታ መኖሩን በምስክሮች ማስረዳት የሚቻል መሆኑን፣ተወላጆቹም የተወለዱት በጋብቻ ውስጥ በመሆኑ ወራሽነታቸው ሊረጋገጥ የሚገባው መሆኑን በመግለጽ መልስ መስጠታቸውን፣ፍ/ቤቱም በሁለቱም ወገኖች አራት አራት ምስክሮችን ከሰማ በኃላ የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በምስክሮች ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር. 700(1) የተመለከተ መሆኑን እና በአንጻሩ የባልና ሚስትነት ሁኔታ አለመኖሩንም በምስክሮች ማስተባበል የሚቻል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 700(2) ተደንግጎ እንደሚገኝ፣ሚች እና አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 17 በቀበሌ 20 በቤት ቁጥር 1972 ውስጥ ከ20 ዓመት በላይ በባልና ሚስትነት የኖሩ፣አራት ልጆችን የወለዱ እና እስከ ሚች ሞት ድረስ ያልተለያዩ መሆኑ በአመልካች ምስክሮች እንደተረጋገጠ፣ በማስረጃነት በትዕዛዝ የቀረበው በዞን 5 የወረዳ 2 ቀበሌ 11 መስተዳድር ጽ/ቤት የስራ አስፈጻሚ አባላት ያስተላለፉት ውሳኔም ሚች የአመልካች ባለቤት መሆናቸውን የሚገልጽ እንደሆነ፣ጣልቃ ገቦች ያሰሟቸው ምስክሮች በአመልካች ማስረጃ የተመሰከረውን ፍሬ ነገር የሚያስተባብል እንዳልሆነ በዝርዝር ገልጾ የጣልቃ ገቦችን ክርክር ውድቅ በማድረግ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 699 መሰረት የአመልካችን ሚስትነት እና የሌሎችን አመልካቾች ልጅነት እና ወራሽነት በማረጋገጥ በ22/03/1993 ዓ.ም ውሳኔ መስጠቱን የውሳኔው ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት በዚሁ ውሳኔ ላይ ሲሆን በ28/08/2000 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ይዘትም ባጭሩ፡-ባለቤታቸው ወ/ሮ አክበረት አስገዶም ከሞቱበት ከ1973 ዓ.ም. ጀምሮ ሚች አቶ ተወልደ ገብሩ እስከ ሞቱበት ጊዜ ድረስ ሌላ ጋብቻ ያልመሰረቱ መሆኑን፣አመልካች ውሳኔ ያሰጡትም ጋብቻው በክብር መዝገብ ፊት ወይም በሀይማኖት ወይም በባህል መሰረት የተፈጸመ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ ሳይኖር መሆኑን እና ሌሎች አመልካቾችም በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ አለመሆኑን የሚገልጽ ሆኖ የሚስትነት እና የልጅነት ውሳኔው እንዲሰረዝ የተጠየቀበት ሲሆን ፍርድ ቤቱም በመቃወም አቤቱታው ላይ አመልካቿ መልስ እንዲሰጡበት ካደረገ እና የመቃወም አመልካቾችን ምስክሮች ከሰማ በኃላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. አመልካች ወ/ሮ አሰለፈች ይመር የሚች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ ሚስት ናቸው ወይስ አይደሉም?
2. ከወ/ሮ አሰለፈች ይመር የተወለዱት አመልካቾች የሚች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ ልጆች ናቸው ወይስ አይደሉም?

የሚሉ ጭብጦችን መስርቶ አጠቃላይ ክርክሩን በመመርመር **የመጀመሪያውን ጭብጥ** በተመለከተ አመልካቿ ሚስትነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ጋብቻቸው የተፈጸመው በየትኛው ስርዓት መሰረት እንደሆነ እንዳልገለጹ፣አመልካች ቀደም ሲል ያሰሟቸው ምስክሮችም አመልካች ከአቶ ተወልደ ገብሩ ጋር ሲኖሩ ነበር ከማለት ውጪ ጋብቻ የነበራቸው ስለመሆኑም ሆነ ጋብቻው በየትኛው ስርዓት መሰረት እንደተፈጸመ የገለጹት ነገር እንደሌለ፣የመቃወም አመልካቾቹ ምስክሮች በሁለቱ ተጋቢዎች ወይም በአንደኛቸው ባህል መሰረት የተፈጸመ ጋብቻ አለመኖሩን ወይም ጋብቻ አለመመስረቱን በተመሳሳይ ሁኔታ እንደገለጹ እና የጋብቻ ሁኔታ አለ የሚል ድምዳሜ በመያዝ ውሳኔ የተሰጠውም ባልተነሳ ጉዳይ ወይም ባልተጠየቀ ዳኝነት በመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደማይገባ ገልጾ የሚስትነት ውሳኔውን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 360(2) መሰረት በመሰረዝ እና **ሁለተኛውን ጭብጥ** በተመለከተ ግን አራቱ አመልካቾች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከሚች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ከክርክሩ መገንዘብ እንደቻለ እና ሚች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ በነበሩበት መረዳጃ ዕድር መሙያ ቅጽ ላይም ልጆች በሚለው ዝርዝር ውስጥ ተመዝግበው እንደተገኙ ገልጾ ብርክቲ ተወልደ፣ሲሳያስ ተወልደ፣ዳንኤል ተወልደ እና ሄለን ተወልደ ከሚች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ የተወለዱ ልጆች ናቸው በሚል ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 360(2) መሰረት በማጽናት ውሳኔ ሰጥቶአል።

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሚስትነት ውሳኔው መሰረዙን በመቃወም ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በአጣሪው ችሎት በተያዘው ጭብጥ እና ቀጥሎም በአጣሪው ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አገላለጽ ጋር ተያይዞ ተጠሪዎቹ ተጨማሪ ክርክር ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በመቀበል ይህ አምስት ዳኞች የሚሰየሙበት ችሎት በ22/01/2006 ዓ.ም በሰጠው ትዕዘዝ መሰረት ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል። የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ለክርክሩ ወደ ተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመገባቱ በፊት አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ የተሰጠው በሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት ተከትሎ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በቅድሚያ እልባት ማግኘት የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ጉዳዩን ከዚሁ ነጥብ አንፃር መርምረናል።

በዚህም መሰረት በፍርድ ቤት የሚደረግ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 1 የተመለከተ ሲሆን ተከራካሪ ወገኖች ወደ ክርክር የሚገቡትም በከሳሽነት፣ በተከሳሽነት፣ በጣልቃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገብነት፣በተቃዋሚነት፣በተተኪነት በመቃወሚያ አቅራቢነት፣በመቃወም ተጠሪነት እና በመሳሰሉ በሕጉ በተመለከቱ ሁኔታዎች ሊሆን እንደሚችል አግባብነት ካላቸው የስነ- ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡በእነዚህ የሕግ አግባቦች ከሚደረጉት የክርክር ዓይነቶች መካከል አንዱ ተካፋይ ባልሆኑበት ክርክር የተሰጠው ውሳኔ መብቴን ይነካል በማለት አስቀድሞ ለአንድ ወገን የተሰጠውን ውሳኔ ለማሰረዝ የመቃወም አመልካች በሆነው ወገን እና አስቀድሞ በተሰጠው ውሳኔ ተጠቃሚ በሆነው የመቃወም ተጠሪ በሚባለው ወገን መካከል የሚደረግ ክርክር ነው፡፡የዚህ ዓይነቱ ክርክር የሚቀርብበት እና የሚመራበት ስርዓት እንዲሁም የዚህ ዓይነቱን ክርክር የሚሰማው ፍርድ ቤት ስላለው ስልጣን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ከቁጥር 358 እስከ 360 የተመለከተ ሲሆን በተለይም የመቃወም አቤቱታው መቅረብ የሚገባው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 222 እና 223 ድንጋጌዎች መሰረት ክስ እና የማስረጃ መግለጫ የሚቀርብበትን ስርዓት መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ በግልጽ ተደንግጎአል፡፡የመቃወም አቤቱታው እና የማስረጃው ቅጂ የመቃወም ተጠሪ ለሆነው ወገን እንዲደርስ መደረግ የሚገባው መሆኑን ከመግለጽ በስተቀር የመቃወም ተጠሪው የጽሁፍ መልስ እና የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ እንደሚገባው በእነዚህ ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ የተጻፈ ባይሆንም የመቃወም ተጠሪ የሆነው ወገን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 234 ድንጋጌ መሰረት ለቀረበበት የመቃወም አቤቱታ ያለውን የመከላከያ መልስ እና ማስረጃ ማቅረብ የሚገባው ስለመሆኑ ከቁጥር 360(1) እና (2) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡በተለይም የመቃወሚያው ክርክር የሚሰማው የመጀመሪያው ክርክር በተሠማበት ስነ ስርዓት መሰረት ስለመሆኑ በቁጥር 360(2) የተመለከተው አስገዳጅ ድንጋጌ በቀጥታ የቀረበ ክስ እና ክርክር የሚስተናገድበትን ስርዓት በተመለከተ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከቱት መሰረታዊ ድንጋጌዎች የመቃወሚያ ክርክርን በማስተናገድ ረገድም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ሊደረጉ የሚገባቸው መሆኑን በግልጽ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው የክርክር አመራር ስርዓት ዓይነተኛ ዓላማ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች እኩል ዕድል እንዲኖራቸው እና በተለይም የመቃወም አመልካች የሆነው ወገን የክርክሩ ተካፋይ ባልነበረበት ጊዜ የቀረበውን የመቃወም ተጠሪ ወገን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በመስቀልኛ ጥያቄ እና በማስተባበያ ክርክር ጭምር የመፈተን ዕድል እንዲያገኝ ለማስቻል እንደሆነ ይታመናል፡፡በመጀመሪያ ደረጃ የሚደረግ የፍትሐብሔር ክርክር ከሚመራባቸው መሰረታዊ የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መካከል ደግሞ የመጀመሪያ ክስ ሲከፈት ስለሚፈጸም ስነ ስርዓት እንዲሁም ክርክሩን ስለመስማት እና ምስክሮችን ስለመመርመር በአራተኛ መጽሀፍ በምዕራፍ ሁለት እንደቅደም ተከተላቸው ከቁጥር 241 እስከ 256 እና ከቁጥር 257 እስከ 271 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም የቀረበ አንድ የመቃወም ክርክር በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት እንዲመራ ለማድረግ ተከራካሪ ወገኖች በተለይ ደግሞ ክርክሩ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመቃወም አመልካቾች በመቃወሚያችን መሰረት ያስረዱልናል ያሏቸውን ምስክሮች አቅርበው ያሰሙ ሲሆን የመቃወም ተጠሪዋ ግን በቀድሞው ክርክር ጊዜ ካሰሙት በስተቀር የመቃወም አቤቱታው ከቀረበ በኋላ ያሰሙት ምስክር አለመኖሩን ወይም በሌላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አነጋገር በቀድሞው ክርክር ጊዜ አሰምተዋቸው የነበሩትን ምስክሮች በድጋሚ አቅርበው የመቃወም አመልካቾች ባሉበት ያላሰሙ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር ተገንዝበናል፡፡ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች ቀደም ሲል ያሰጡት የሚስትነት ውሳኔ ሊነሳ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ነጥብ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የመቃወም አመልካቾች ብቻ ሳይሆን የመቃወም ተጠሪዋ ምስክሮች ጭምር ቀርበው እንዲሰሙ ማድረግ ሲገባው የመቃወም ተጠሪዋ ባሉበት የተሰሙትን የመቃወም አመልካቾች ምስክሮች ቃል ቀደም ሲል የመቃወም አመልካቾች በሌሉበት ከተሰማው የመቃወም ተጠሪዋ ምስክሮች ቃል ጋር በማነጻጸር የአመልካቿ ሚስትነት በተጠሪዎቹ ማስረጃ ተስተባብሏል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ እና ይህንኑ ድምዳሜ መሰረት አድርጎ የሚስትነት ውሳኔውን በመሰረዝ የሰጠው ውሳኔ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የክርክር አመራር ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡ይግባኙን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በስር ፍርድ ቤት የተፈጸመውን ይህንን ስነ ስርዓታዊ ግድፈት ማረም ሲገባው ውሳኔውን ያጸናው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የአመልካች የሚስትነት ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ጭብጥ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት የመቃወም ተጠሪዋ ምስክሮች ቀርበው የመቃወም አመልካቾች ባሉበት እንዲሰሙ ሊደረግ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት ተከትሎ ያልተሰጠ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 117112 በ01/02/2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 99599 በ14/12/2004 ዓ.ም በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ከአመልካቿ የተወለዱት አራት ልጆች ከሚች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ የተወለዱ ልጆች ናቸው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ የአመልካችን የሚስትነት ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 360(2) መሰረት በመሰረዝ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
4. የመቃወም ተጠሪዋ ቀደም ሲል ያሰሟቸውን ምስክሮች፣እነዚህ ምስክሮች ሊቀርቡ የማይችሉበት በቂና አሳማኝ ምክንያት ካለም የመቃወም ተጠሪዋ የሚቆጥሯቸውን ተለዋጭ ምስክሮች አስቀርቦ የመቃወም አመልካቾች ባሉበት ከሰማ እና የጽሁፍ ማስረጃም ካለ የመቃወም አመልካቾች አስተያየት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሰጡበት ካደረገ በኋላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ አመልካች ቀደም ሲል ያሰጡት የሚስትነት ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ነጥብ ላይ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሰረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡

5. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ መሰረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
አልማው ወሌ
ረታ ቶለሳ
አዳነ ንጉሴ
መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስመረት ኃ/ሚካኤል ጠበቃ ጌትነት የሻነህ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ተስፋዬ ጥላሁን
2. ወ/ሮ መቅደስ ፈቃደ } 1ኛ ተጠሪ እና ስለ ሶሱቱም
3. አቶ ደረጀ ተስፋዬ } ተጠሪዎች ጠበቃ ወንዳውክ አየለ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አላግባብ የተያዘ ነው የተባለን ቤት በፍርድ ኃይል ከማስለቀቅ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የአሁኖቹ አመልካች እና ተጠሪዎች ጉዳዩ በተጀመረበት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተላቸው ከሳሽ እና ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ከሳሽ በ16/03/2003 ዓ.ም.አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ከሳሽ ከአቶ ዘርዓይ ሐጎስ ጋር በ16/05/2002 ዓ.ም ባህላዊ ጋብቻ ፈጽመው በ04/02/2003 ዓ.ም ጋብቻውን በማስመዝገብ ማስረጃ የተሰጣቸው መሆኑን፣ በ18/05/1998 ዓ.ም በተጻፈ የኮንዶሚኒየም ቤት ሽያጭ ውል በቦሌ ክ/ከተማ በቀበሌ 01 ውስጥ በብሎክ 2 የሚገኝ ቁጥሩ ቢ.አር.አር.ቢ2-1/05 የሆነ ቤት ከቦሌ ክ/ከተማ ለአቶ ዘርዓይ ሐጎስ የተላለፈ መሆኑን፣ ከሳሽ እና ባለቤታቸው ይህንኑ ቤት በ16/05/2002 ዓ.ም በተጻፈ የጋብቻ ውል የጋራ ያደረጉት መሆኑን፣ ይህንን ቤት በተመለከተ ባለቤታቸው ለ1ኛ ተከሳሽ በ25/12/2002 ዓ.ም የተጻፈ የውክልና ስልጣን ሰጥተው የነበረ ቢሆንም የውክልና ስልጣኑን ከ24/01/2003 ዓ.ም ጀምሮ የሻሩ መሆኑን እና ተከሳሾቹ ምንም መብት ሳይኖራቸው ተከራዮችን በማስወጣት ቤቱን በሕገወጥ መንገድ ይዘው የሚገኙ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ እና ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ ኪራዩን እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በበኩላቸው በ12/04/2003 ዓ.ም.በተዘጋጀ ማመልከቻ ከሳሽ የአቶ ዘርዓይ ሐጎስ ባለቤት ስላልሆኑ ቤቱን በተመለከተ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቃወሚያ ካስቀደሙ በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጡት መልስ ክስ ያስነሳውን ቤት አቶ ዘርዓይ ሐጎስ በ25/12/2002 ዓ.ም. በተጻፈ ውል በብር 345,000 ለ1ኛ ተከሳሽ በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑን፣ ለዋስትና ይሆን ዘንድም አቶ ዘርዓይ ሐጎስ የብር 345,000 ብድር ውል በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ለ1ኛ ተከሳሽ የፈረሙ መሆኑን፣ የብድር ውሉን የፈረሙትም ትዳር እንደሌላቸው ከሚመለከተው ክፍል ማረጋገጫ በማቅረብ መሆኑን፣ ይህ በተደረገበት ጊዜም ከሳሽ የአቶ ዘርዓይ ሐጎስ የአክስት ልጅ እንደሆኑ በመግለጽ አብረዋቸው የነበሩ መሆኑን፣1ኛ ተከሳሽ ከአቶ ዘርዓይ ሐጎስ በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሰረት የቤቱን ጠቅላላ እዳ ከፍለው ከክፍለ ከተማው ጋር የሽያጭ ውል ያደረጉ መሆኑን እና ቤቱን የተላለፈባቸው በሽያጭ ውል በመሆኑ የውክልና ስልጣኑ የተሻረ የመሆን አለመሆን ጉዳይ የሚያስከትለው ውጤት አለመኖሩን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ የተከራከሩ ሲሆን 3ኛ ተከሳሽ በበኩላቸው ቤቱን ያልያዙና ተከራዮችንም ያላስወጡ መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን በ16/06/2003 ዓ.ም. በብይን አልፎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ቤቱን ይዘው የሚገኙት ከሳሽ እንደሚሉት ምንም ዓይነት መብት ሳይኖራቸው በሕገወጥ መንገድ ሳይሆን በአቶ ዘርዓይ ሐጎስ እና በ1ኛ ተከሳሽ መካከል በተደረገ የሽያጭ ውል መሰረት እንደሆነ መረጋገጡን፣ የሽያጭ ውል መኖሩ በከሳሽም ያልተካደ መሆኑን፣ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከሳሽ ቤቱን በተመለከተ ክስ ለማቅረብ መብት የሚኖራቸው የሽያጭ ውሉን ከማስፈረስ አንጻር ከሚሆን በስተቀር ተከሳሾቹ ምንም ዓይነት መብት ሳይኖራቸው ቤቱን በሕገወጥ መንገድ ይዘዋል በማለት እንዳልሆነ እና ከሳሽ የውል ይፍረስልኝ ክስ ባላቀረቡበት ሁኔታ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ መስርቶ በመዝገቡ ማከራከርና ውሳኔ መስጠት ስነ ስርዓታዊ አግባብነት እንደሌለው በመግለጽ ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪዎች በሕገ ወጥ መንገድ መያዛቸውን በገለጹበት እና የኮንዶሚኒየም ቤቶችን ከአምስት ዓመት በፊት ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የማይቻል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 19/1997 በተደነገገበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የያዙት በሽያጭ ውል በመሆኑ የሽያጭ ውሉን የማስፈረስ ክስ ካልቀረበ በስተቀር በዚህ ክስ የውሉ ሕጋዊነት ሊመረመር አይችልም በሚል አመልካች በሚስትነታቸው ያቀረቡትን የቤት ይልቀቁልኝ ጥያቄ ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ቀደም ሲል እንደተገለጸው ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በአመልካቾች በሕገ ወጥ መንገድ ተይዞአል በሚል አመልካች ያቀረቡትን ክስ ውድቅ ያደረገው ቤቱ በተከሳሾቹ የተያዘው ከሳሽ እንደሚሉት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕገ ወጥ መንገድ ሳይሆን በሽያጭ ውል መነሻ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ከሳሽ ቤቱ የተያዘው በውል መሆኑን እያወቁ በሕገወጥ መንገድ እንደተያዘ አድርገው ክስ ማቅረባቸው ተገቢውን የክስ አቀራረብ ስርዓት የተከተለ አይደለም በማለት ነው፡፡ በመሰረቱ ማናቸውም ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ክስ ሁሉ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን በሚገባ መርምሮ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችለው በዚያው ነገር ሌላ አከራካሪ ጉዳይ በማያስከትል ሁኔታ ግልጽ በሆነ አጻጻፍ መቅረብ እንዳለበት፣ በክስ ማመልከቻ ላይ መገለጽ ከሚገባቸው ነገሮች መካከልም አንዱ የክሱ ምክንያት እና ለክሱ ምክንያት የሆኑት ነገሮችና እነዚሁ የተፈጠሩበት ጊዜና ስፍራ እንደሆነ የክስ አቀራረብን ከሚመለከቱ የፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 80(2)፣213(1)፣216(1)፣222(1)(ረ) እና ሌሎችም ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ዓላማም የፍትሐብሄር ጉዳዮችን በተመለከተ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩት የግንኙነት ዓይነቶች፣ እንዲሁም እነዚህ ግንኙነቶች የሚገዙባቸው የህግ ድንጋጌዎች፣ ግንኙነቶቹን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮች የሚመሩበት ስርዓትም ሆነ የተለያዩ ግንኙነቶችን አስመልክቶ ከተከራካሪ ወገኖች የሚቀርቡት የክርክር ነጥቦች የተለያዩ በመሆናቸው ምክንያት እንደየግንኙነቱ እና ክርክሩ ዓይነትና ሁኔታ ለፍ/ቤት የሚቀርቡትን ክርክሮች በተቀላጠፈ ሁኔታ እና በተገቢው ስነ ስርዓታዊ አግባብ መርቶ እልባት ለመስጠት ማስቻል እንደሆነ የሚታመን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አቶ ዘርዓይ ሐጎስ በ25/12/2002 ዓ.ም. በተጻፈ ውል በብር 345,000 ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑ በአመልካች እንዳልተካደ እና ቤቱ በተጠሪዎች እጅ የገባው እና ይዘው የሚገኙት በዚሁ ውል ምክንያት እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በዚህ ሁኔታ በውል በተላለፈው ቤት ላይ መብት አለኝ የሚሉ ከሆነ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሰረት በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉትን መብት ማስከበር የሚችሉት ውሉን ከማስፈረስ አንፃር ከሚሆን በቀር በተጠሪዎች በውል የተያዘውን ቤት በሕገወጥ መንገድ እንደተያዘ አድርገው ክስ ለማቅረብ የሚችሉበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ አይኖርም፡፡ ቤቱ በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘ ነው ማለት እና ቤቱ የተያዘበት ውል የሕጉን መስፈርቶች አሟልቶ የተደረገ አይደለም ማለት ደግሞ የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ አመልካች ይህንኑ ተገንዝበው በፌ/ከ/ፍ/ቤት የውል ይፍረስልኝ ክስ አቅርበው በክርክር ላይ የሚገኙ ስለመሆኑ ተጠሪዎች የመዝገብ ቁጥሩን ጭምር ጠቅሰው ላቀረቡት ክርክርም አመልካች ያቀረቡት ማስተባበያ አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ያቀረቡት ክስ ተገቢውን የክስ አቀራረብ ስርዓት የተከተለ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. አመልካች ያቀረቡት ክስ ተገቢውን የክስ አቀራረብ ስርዓት የተከተለ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 69748 በ11/09/2003 ዓ.ም. የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 111732 በ23/04/2005 ዓ.ም. በፍርድ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች የውል ይፍረስልኝ ክስ ለማቅረብ ያላቸው መብት በዚህ ውሳኔ አልተነካም፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/ዘበ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 91643

ጥር 15 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነገረ-ፈጅ
ዕጌ መለሰ ቀረቡ

ተጠሪ:- ካኪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ሀጎስ አብርሃ ቀረቡ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 126221 ግንቦት 12 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ወጭና ኪሣራን በተመለከተ የተሰጠውን ውሣኔ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበው ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. ተጠሪ በመኪና አስመጭነት የሚሠራ ነጋዴ መሆኑን ገልፆ፣ ከውጭ ያስመጣቸው አሥር ትራክተሮች የሚገዛኝ በማጣቱ በንብረትነት በማስመዝገብ በግል ልገለገልባቸው ስለፈለግሁ የባለሀብትነት ስም ለማዛወር 422,604.22 /አራት መቶ ሃያ ሁለት ሺ ስድስት መቶ አራት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም/ ለተከሳሽ (አመልካች) በ3-10-2003 ዓ.ም ከፍያለሁ፡፡ ከሳሽ ይህንን ገንዘብ ከከፈልኩ በኋላ ትራክተሮቹን ጌትስ ኢንተርናሽናል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ገዝቶኛል፡፡ ተከሳሽ የከፈልኩትን ገንዘብ እንዲመልስ ብጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆነ ገንዘቡን ከነወለዱ እንደዚሁም ወጭና ኪሣራ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ገንዘቡን ከመመለሳችን በፊት የኢኮኖሚና ገንዘብ ሚኒስትር አስተያየት መጠየቅ ያለብን በመሆኑ ጠይቀናል ገንዘቡንም ለመመለስ በሂደት ላይ ስንሆን፣ ወጭና ኪሣራ ግን ልንከፍል አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ከሳሽ በክሱ የጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ወጭና ኪሣራን በተመለከተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽ ክሳሽን ለክርክርና ለወጭ ያልጋበዘ በመሆኑ፣ ወለድ ወጭና ኪሣራ ለክሳሽ ሊከፍል አይገባም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

2. ተጠሪ ወለድ ወጭና ኪሣራ የሥር ፍርድ ቤት አይገባህም ማለቱን በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ተጠሪን ስምንት ወራት ያህል ገንዘቡን አልመለሰለትም፡፡ ስለዚህ አመልካች ወለድ፣ ለዳኝነት የተከፈለ ገንዘብና የጠበቃ አበል የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች ተጠሪ የጠየቀውን ወለድ ፣ የዳኝነት ገንዘብ ፣ ይክፈል ፡፡ የጠበቃ አበል ተጠሪ ከጠየቀው ብር 44,000 ግማሹን ብር 22,000 /ሃያ ሁለት ሺ ብር/ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡
3. ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበው፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የወጭና ኪሣራ ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ራሱ አገልግሎት ለማግኘት ገንዘቡን በፈቃዱ ከፍሎ አገልግሎት ለመስጠት በሂደት ላይ እያለን፣አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ጥያቄ አቀረበ፡፡ ከዚያም የመንግሥት የፋይናንስ አሠራር በመጠበቅ ልንመልስለት በሂደት ላይ በነበርንበት ወቅት፣ ወለድ፣ወጭና ኪሣራ እንድንከፍለው ያቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ አመልካች ገንዘቡን በወቅቱ ያልመለሰ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡
4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ከዋናው ገንዘብ በተጨማሪ ወለድ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው፣ ተጠሪ ገንዘቡን ለአመልካች የከፈለው ገዥ ያጡ መኪናዎች በስሙ ለማዛወር በማሰብ እንደሆነ ክክስ ማመልከቻው ተገልጿል፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን ከከፈለ በኋላ መኪናዎቹ (ትራክተሮች) በመሸጣቸው፣ የመኪናዎቹ ስመሀብት በስሙ ለማዛወር ጠይቆት የነበረው አገልግሎት እንዲቋረጥና አገልግሎቱን ለማግኘት ለአመልካች የከፈለው ገንዘብ እንዲ መለስለት እንደጠየቀ፣ ግራቀኙ በበታች ፍርድ ቤቶች እና በሰበር ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል፡፡ ይህም የተጠሪ ጥያቄ ልከፍል የማይገባኝን ገንዘብ የከፈልኩ ስለሆነ ሊመለስልኝ ይገባል የሚል እንደሆነና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2164 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በማድረግ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን ገንዘቡን የተቀበለው ተጠሪ የጠየቀውን አገልግሎት ለመሥጠት የግድ መከፈል የነበረበት ክፍያ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን ገንዘቡን የተቀበለው እምነትን የሚያጓድል ተግባራትን በመፈፀም አይደለም፡፡ የማይገባውን ክፍያ የከፈለ ሰው ገንዘቡን ከከፈለበት ቀን አንሥቶ ሕጋዊ ወለድ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችለው፣ ገንዘቡን የተቀበለው ሰው እምነትን በሚያጓድል ሁኔታ ክፍያውን ተቀብሎት በሆነ ጊዜ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2164 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍትሐ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብሔር ሕግ ቁጥር 2164 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች ይዘት መሠረታዊ ዓላማና ተግባርና ተፈፃሚነት በአግባቡ ሣያገናዝብ፣ አመልካች ብር 38,034 (ሰላሣ ስምንት ሺ ሰላሣ አራት ብር) ወለድ ለተጠሪ መክፈል አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

6. ተጠሪ ገንዘቡ እንዲመለስለት ከጠየቀ በኋላ አመልካች ወዲያውኑ ባለመመለሱ፣ ተጠሪ ክስ ሲያቀርብ የዳኝነት ገንዘብ፣ ለጠበቃ አበልና ለቴምብር ቀረጥ ወጭ ያደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህንን ወጭ አመልካች እንዲሸፍን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 462 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ ወለድ እንዲከፍል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወሰነው የውሣኔ ክፍል ብቻ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ወለድ ብር 38,034 /ሰላሣ ስምንት ሺ ሰላሣ አራት ብር/ እንዲከፍል የሰጠው የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. አመልካች ተጠሪ ለዳኝነት የከፈለውን ብር 7,076 /ሰባት ሺ ሰባ ስድስት ብር/ ለቴምብር ቀረጥ የከፈለውን ብር 275 /ሁለት መቶ ሰባ አምስት ብር/ እና የጠበቃ አበል 22,000 /ሃያ ሁለት ሺ ብር/ እንዲከፍል በማለት የሰጠው የውሣኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገብ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 91745

የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ዳዊት አበበ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አንድነት ቁጥር 4 የጋራ መኖሪያ ቤት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

2. አቶ ካሚል ጀማል - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች፣ አመልካች በመጀመሪያ ክርክሩን ለሽማግሌ ዳኞች ያላቀረበ በመሆኑ፣ አከራክሮ ለመወሰን ሥልጣን የለንም በማለት የሰጡት ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች የአንደኛው ተጠሪ አባል የነበረ መሆኑን ገልፆ ሁለተኛው ተጠሪ የማህበሩ ሊቀመንበር ሆኖ ወርሃዊ መዋጮ መክፈል አቋርጠሀል በማለት አላግባብ ከአባልነት ያሰናበተኝ ስለሆነ የማህበር አባልነት መብቴ እንዳይሰረዝ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት በስር ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች ተከሳሽ ሆነው የአመልካች ክስ በግልግል መታየት ያለበትና ለፍ/ቤት መቅረቡ ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ጉዳዩን ለሽማግሌ ዳኞች ከሚያቀርብ ወይም ለሽማግሌ ዳኞች ቀርቦም ከሆነ ውጤቱን ጠብቆ በሕጉ መሰረት ይግባኝ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ከሚያቀርብ በስተቀር በቀጥታ ለፍርድ ቤት የማቅረብ መብት የለውም፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በመጀመሪያ አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡
3. አመልካች ሐምሌ 5 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች የክስ ምክንያት ያላግባብ ከማህበር አባልነቱ ተሰናበትኩ የሚል በመሆኑ በፍርድ ቤት የሚታይ እንጂ በሽማግሌ ዳኞች የሚታይ አይደለም፡፡ ክስ ከማቅረቤ በፊት በንፋስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት አመልክቼ አመልካች አንድ፣ ተጠሪዎች አንድ የሽማግሌ ዳኛ ከመረጥን በኋላ ተጠሪዎች ሰብሳቢ ዳኛ መርጠዋል፡፡ ሰብሳቢው ዳኛም አድሏዊነት የሚታይበት በመሆኑ እንዲቀየር በማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት አመልክቼ ዳኛ መቀየር የማይችሉ መሆኑን ማህበራት ማደራጃ ስለገለፀልኝ ክስ ለፍርድ ቤት አቅርቤያለሁ፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 70922 መጋቢት 10 ቀን 2004 በሰጠው ውሳኔ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ እንዲወስን የሰጠውን ውሳኔ ወደጎን በመተው የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጡት ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

4. ተጠሪዎች የስር ፍርድ ቤት ይህ ሰበር ችሎት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 73 የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራ ቀኞችንን ክርክር በመመርመር ውሳኔ እንዲሰጥበት በወሰነው መሰረት ተጠሪዎች ጉዳዩ በመጀመሪያ መታየት ያለበት በሽማግሌ ዳኞች ነው በማለት አዋጅ ቁጥር 147/91 ድንጋጌዎች በመጥቀስ ያቀረብነውን መቃወሚያ በመቀበል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ መልስ ተከራክረዋል፡፡አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
5. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ መጀመሪያ መቅረብ ያለበት ለሽማግሌ ዳኞች ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
6. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የአንደኛው ተጠሪ አባል እንደነበርና ሁለተኛ ተጠሪ የማህበሩ ሊቀመንበር ሆኖ ሲሰራ ወርሃዊ ክፍያ አልከፈልክም በማለት ከአባልነት እንዲሰናበት አላግባብ በሌላ ሰው እንዲተካ ያደረገ በመሆኑ የማህበሩ አባል ሆኜ እንድቀጥል ይደረግልኝ የሚል የዳኝነት ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔና በሰበር ከቀረበው ክርክር ተገንዝበናል፡፡ ይህም የሚያሳየው ክርክሩ የተነሳው በህብረት ሥራ ማህበሩና አላግባብ የማህበር አባልነት መብቴ ተቋርጧል በሚለው የቀድሞው የማህበሩ አባል በሆነው አሁን ግን አባልነቱ በአንደኛ ተጠሪ በመሰረዙ በአባልነት መጠቀስ ያለበት ወይም የሌለበት ስለመሆኑ ከፍሬ ጉዳይና ከህግ አንፃር ተመዝኖ ውሳኔ ሊሰጥበት ከሚገባው በአመልካች መካከል መሆኑን ነው፡፡ በአንድ ማህበር አቋም ስለ ስራው አካሄድ ወይም ስለስራው አፈፃፀም በአባላት ወይም በቀድሞ አባላት ወይም በቀድሞ አባላት ወኪሎች ወይም በሞት በተለዩ አባላት ስም ክርክር የሚያቀርቡ ሰዎች በማህበሩና በማህበሩ አመራር መካከል የሚነሳ ክርክር በመጀመሪያ ለሽማግሌ ዳኞች ቀርቦ መታየት እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 147/96 አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ አመልካች አንደኛ ተጠሪ አላግባብ ከአባልነት ሰርዞኛል ከማለቱም በተጨማሪ የማህበሩ አመራር የሆነውን ሁለተኛ ተጠሪም ላይ ክስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

7. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮችን ለፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ፍትህ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 ተደንግጓል፡፡ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተግባራዊ ተፈፃሚነትም የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 37 ድንጋጌዎች ውጤታማነት በሚያጎለብትና በሚያጠናክር መንገድ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በህብረት ሥራ ማህበራትና በአባሎቻቸው ወይም በቀድሞ አባላቸው ወይም በህብረት ስራ ማህበር አባላት ወይም የቀድሞ አባላትና በማህበሩ አመራር መካከል የሚነሳ ክርክር በመጀመሪያ አይቶ ውሳኔ ለመስጠት በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው የሽምግልና ጉባኤ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49 ሥልጣን ለተሰጠው ለሽምግልና የዳኝነት አካል ሳይቀርብ ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ዳኝነት ለማየትና ለመወሰን የማይችሉ መሆኑን የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 37፣ አንቀጽ 79(1) እና የአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49 ድንጋጌዎች በማየት መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ጉዳዩ በቀጥታ በፍርድ ቤት ሊታይ ይገባዋል በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

8. ሌላው አመልካች ያቀረበው መከራከሪያ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 70922 መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 70922 ያየው መሰረታዊ ጭብጥ ተካሳሾች የቃል ክርክር በሚያሰሙበት ቀን ከሳሽ የነበረው (አመልካች) ባለመቅረቡና ተከሳሾች (ተጠሪዎች) በመካዳቸው መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ አመልካች በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 74(2) መሰረት እንዲከፈት ሲጠይቅ በቀነ ቀጠሮው ያልቀረብከው በቂ በሆነ ምክንያት አይደለም በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይን በመስጣቸው ይህ ሰበር ችሎት ከሳሽ (አመልካች) በቀነ ቀጠሮው ያልቀረበው በበቂ ምክንያት በመሆኑ መዝገቡ ተከፍቶ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ እንዲወሰን ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት የመለሰበት ነው፡፡ ጉዳዩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341(1) የተመለሰ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ተከሳሾች (አመልካቾች) ያቀረቡትን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ በመመርመር የሰጠው ብይን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 244(1) ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ብይኑን የሰጠውም ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 70922 የሰጠውን ውሳኔ ይዘትና ሕጋዊ ውጤት መሰረት በማድረግ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታና መከራከሪያ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡

9. አመልካች የሽማግሌ ዳኞች በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት በኩል ተሰይሞ የነበረ መሆኑንና ሰብሳቢው ዳኛ አድሏዊ በመሆኑ ለፍርድ ቤት ክስ አቀረብኩ የሚለው መከራከሪያ ህግን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ የሽማግሌ ዳኞች ከተሰየሙ በኋላ አንድ ዳኛ እንዲለወጥ ማድረግ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ከተከራከሪዎች አንደኛው ዳኛው እንዲለወጥ የሚጠይቅበትን ምክንያት በመዘርዘር በመጀመሪያ የሽማግሌ ዳኞቹ ፣የሽማግሌ ዳኞቹ እንቢተኛ ከሆኑ ለፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄውን ማቅረብ እንደሚችል ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3340 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3342 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ህጉን በመከተል ጥያቄያቸውን ሳያቀርቡ ክሱን በቀጥታ ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ የአመልካችን መከራከሪያ አልተቀበለውም፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን ጉዳይ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ አይቶ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49 መሰረት በተቋቋመ የሽማግሌ ዳኞች ቀርቦ ውሳኔ ማግኘት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
4. ይህ ውሳኔ አመልካች የሽማግሌ ዳኞች እንዲቋቋምለት ጥያቄውን ለሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ወይም ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ከማቅረብ የሚገድበው አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93171

ግንቦት 8 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ወ/ሮ ሴቴ ከበደ - ተወካይ ወርቁ ከበደ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አስናቁ ፋንታዬ - ተወካይ መኩሪያ መኮንን ቀረቡ

2. አቶ ጣፋጭ ተሾመ- መብታቸው ታልፏል

3.የጉባ ላፍቶ ወረዳ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ጋር በጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00951 ያላቸው ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 31 መሠረት ወደ ሀከፋ ወረዳ ፍ/ቤት ተላውሮ እንዲታይ ያቀረቡትን የክስ ይላወርልኝ ጥያቄ የተመለከተው የሰሜን ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት አመልካች አቤቱታውን ያቀረቡት ቁጥር 00951 የሆነው መዝገብ በውሣኔ ከተቋጨ በኋላ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 መሠረት ዳግም ዳኝነት እንዲታይ የቀረበ ጥያቄም በሌለበት ሁኔታ በመሆኑ እንዲሁም የክስ ይላወርልኝ ጥይቄው በበቂ ምክንያት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት የክስ ይላወርልኝ አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም በማለት የሰጠው እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ስበር ችሎት በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት ዳግም ዳኝነት እንዲታይ መዝገቡ ተከፍቶ በ22/05/2004 ዓ.ም. ትዕዛዝ መስጠቱ በተመለከተበት ሁኔታ ተጠሪዎች ለክስ ይላወርልኝ አቤቱታው በሰጡት መልስ በወረዳው ፍ/ቤት የተከፈተ መዝገብ የለም በማለት የሰጡትን መልስ ተከትሎ የአመልካች አቤቱታ ሳይስተናገድ የተከፈተ መዝገብ የለም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለስበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ መብታቸው ከታለፈው 2ኛ ተጠሪ በስተቀር ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአንድ ወረዳ ፍ/ቤት በመታየት ላይ ያለ ጉዳይ ወደ ሌላ ወረዳ ፍ/ቤት ተዛውሮ እንዲታይ አንደኛው ወገን ሲያመለክት ተገቢ ምክንያቶች መኖራቸው ተረጋግጦ በክስ ይዛወርልኝ አቤቱታው እንደየሁኔታው አግባብነት ያለው ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 31 ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ለማቅረብ ጉዳዩ በክርክር ሂደት ላይ የሚገኝ መሆን ይኖርበታል፡፡በተያዘው ጉዳይ የዞኑ ከ/ፍ/ቤት የቀረበለትን የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ላለመቀበል የሰጠው ዋነኛ ምክንያት ግራ ቀኙ በጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት ክርክር ሲያደርጉበት የነበረው ቁጥሩ 00951 የሆነው መዝገብ በውሳኔ የተቋጨ መሆኑ እና መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ድንጋጌ መሰረትም ሆነ በሌላ ምክንያት ያልተንቀሳቀሰ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ ተችሏል የሚል ሲሆን አመልካች ለክስ ይዛወርልኝ አቤቱታቸው በቂ ምክንያት አላቀረቡም የሚለው ነጥብ በተጨማሪ ምክንያትነት በውሳኔው ይዘት ውስጥ የተገለጸ ከመሆኑ ውጪ ተፈጻሚነት ባለው የውሳኔ ክፍል ውስጥ ያልተጠቀሰ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡የጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት የቀረበለትን የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ለማየት መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ በ22/05/2004 ዓ.ም. ትዕዛዝ ሰጥቷል መባሉን በተመለከተ መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ተሰጠ የተባለውን ትዕዛዝ አመልካች በዞኑ ከ/ፍ/ቤት ስለማቅረባቸው የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታውን የተመለከተው የሰሜን ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት ተፈጻሚነት ባለው የውሳኔው ክፍል ላይ እንደገለጸው ጥያቄውን ሳይቀበል የቀረው የአመልካች የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የቀረበው በስር ፍ/ቤት ክስ ተመስርቶ ፋይል ባልተከፈተበት ወይም የቀድሞው መዝገብ ቁጥር 00951 ባልተንቀሳቀሰበት ሁኔታ ስለሆነ አቤቱታው የክስ ምክንያት የለውም በማለት በመሆኑ በመሰረቱ ይህ የከ/ፍ/ቤት ውሳኔ አመልካች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ የተደረገ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታቸውን በሌላ መዝገብ እንደ አዲስ ከማቅረብ የሚከለክላቸው አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የአመልካች የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የቀረበው በስር ፍ/ቤት ክስ ተመስርቶ ፋይል ባልተከፈተበት ወይም የቀድሞው መዝገብ ቁጥር 00951 ባልተንቀሳቀሰበት ሁኔታ ስለሆነ አቤቱታው የክስ ምክንያት የለውም በማለት በዞኑ ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአመልካች የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የቀረበው በወረዳው ፍ/ቤት ክስ ተመስርቶ ፋይል ባልተከፈተበት ወይም የቀድሞው መዝገብ ቁጥር 00951 ባልተንቀሳቀሰበት ሁኔታ ስለሆነ አቤቱታው የክስ ምክንያት የለውም በማለት የሰሜን ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 06041 በ12/03/2005 ዓ.ም. የሰጠው እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 01-00728 በ17/10/2005 ዓ.ም.በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የአመልካች የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ውድቅ የተደረገው የወረዳው ፍ/ቤት መዝገብ መንቀሳቀሱን የሚያረጋግጥ ትዕዛዝ አያይዘው ባለማቅረባቸው በመሆኑ ቀደም ሲል ያቀረቡት አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ተቀባይነት ማጣቱ የመዝገቡን መንቀሳቀስ የሚያረጋጥ ማስረጃ በማያያዝ የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄያቸውን በሌላ መዝገብ በድጋሚ ከማቅረብ የሚያግዳቸው አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበቡ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94302

ሚያዝያ 7 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሰሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ብርሃኑ አማረ ጠቅላላ ሕንፃ ስራ ተቋራጭ - ነ/ፈጅ አንተነህ ድንበሩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ፋርማ ብርብር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ ወነድወሰን ተ/ማርያም ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር ስለዋናዎቹ ባለጉዳዮች በመሆን ሌሎች ሰዎች በተሟጋችነት ሊቀርቡ የሚችሉበትን ስርዓት የሚመለከት ነው፡፡የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ክርክሩ በተጀመረበት በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽ በነበሩት በአቶ ብርሃኑ አማረ(በአሁኑ አመልካች) ላይ የመሰረተው ክስ በሌሉበት ተሰምቶ በተከሳሹ ላይ ውሳኔ መሰጠቱን፣ተከሳሹም ክሱ በሌሉበት ተሰምቶ ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው በተገቢው ስርዓት እንዲደርሳቸው ሳይደረግ በመሆኑ ውሳኔው ተነስቶ ክርክሩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው በፍ/ስ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሰረት አቤቱታ ማቅረባቸውን፣አቤቱታውን ያቀረቡትም ብርሃኑ አማረ ጠቅላላ ሕንፃ ስራ ተቋራጭ በሚል ስም መሆኑን፣ከሳሹም የአቤቱታው ግልባጭ ደርሶት በሰጠው መልስ ክሱን ያቀረበውም ሆነ ውሳኔ ያሰጠው በአቶ ብርሃኑ አማረ ላይ እንጂ በብርሃኑ አማረ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ላይ ባለመሆኑ ከከሳሹ ጋር የውል ግንኙነት በሌለው እና ውሳኔ ባልተሰጠበት ድርጅት ነገረ ፈጅ አማካይነት የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት መከራከሩን፣ ፍ/ቤቱም ወደአቤቱታው ፍሬ ጉዳይ ሳይገባ የአቤቱታ አቀራረቡን ስነስርዓታዊነት ከመረመረ በኋላ ተከሳሹ ግለሰብ ነጋዴ መሆናቸውን፣ከተከሳሹ ስም ቀጥሎ የተመለከተው ሐረግም የሚያመለክተው ተከሳሹ በሕግ መሰረት የተቋቋመ ድርጅት መሆኑን ሳይሆን የግለሰብ ነጋዴውን የንግድ ስም መሆኑን፣ነገረ ፈጅ መወከል የሚችለው በሕግ አግባብ የተቋቋመ ድርጅት እንጂ ግለሰብ(የተፈጥሮ ሰው) አለመሆኑን ገልጾ ተከሳሽ የሕጉን መመዘኛ ሳያሟሉ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶ መመለሱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሰረት አቤቱታ የቀረበው አመልካችን ወክሎ ለመከራከር በሚችል ሰው አይደለም መባሉ የመዝገብ መዘጋት ውጤትን የሚያስከትል መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሰረት የተዘጋጀ አቤቱታ ፈርመው በማቅረብ ስለአመልካቹ ሆነው በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀረቡት ተወካይ በአመልካቹ ስም በፍ/ቤት በተሟጋችነት ለመቆም በስነ ስርዓት ሕጉ የሚጠየቀውን መስፈርት የሚያሟሉ ስላልሆኑ አመልካቹን ወክለው ሊከራከሩ አይችሉም በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ ተገቢነት ያለው ነው ወይስአይደለም?
2. ተገቢነት ያለው ነው ከተባለ መስፈርቱን አለማሟላታቸው የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ምን ሊሆን ይገባል?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ጭብጦች አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪ ክሱን የመሰረተው እና ውሳኔ ያሰጠው የአመልካቹን ስም ብርሃኑ አማረ ገብረአብ ብሎ በመግለጽ ሲሆን አመልካች ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሰረት ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ስማቸውን የገለጹት ብርሃኑ አማረ ጠቅላላ የህንፃ ስራ ተቋራጭ በማለት ነው፡፡ በመሰረቱ ከአመልካቹ ስም ቀጥሎ "ጠቅላላ የህንፃ ስራ ተቋራጭ" በሚል የተመለከተው ሐረግ የተሞላው የአመልካቹን የንግድ ስራ ዘርፍ ወይም የንግድ ስም ለማመልከት ታስቦ ከመሆኑ ውጪ አመልካቹ ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ተቋም መሆኑን ለማመላከት እንዳልሆነ በግራ ቀኙ ያልተካደ ጉዳይ ስለመሆኑ ከክርክራቸው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ቀጥሎ መታየት የሚገባው ጉዳይ በስር ፍ/ቤት የአመልካቹ ነገረ ፈጅ ሆነው የቀረቡት ሰው በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር በተሟጋችነት ሊቆሙ ስለሚችሉ ሰዎች በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

በመሰረቱ በማናቸውም ፍ/ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ለመከራከር ባለጉዳዩ ራሱ እንዲቀርብ የሚያስገድድ ሕግ ወይም በፍ/ቤቱ የተሰጠ የተለየ ትዕዛዝ የሌለ በሆነ ጊዜ ባለጉዳዩ ራሱ ለመቅረብ የማይችል ወይም የማይፈቅድ ሲሆን ነገሩን ለማስረዳት፣ ለመከራከር፣ለሚጠየቀው ሁሉ በቂ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰው በዋናው ባለጉዳይ ተተክቶ በነገረ ፈጅነት፣ በወኪልነት፣ በጠበቃነት እንዲከራከር ለማድረግ እንደሚቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 57 ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በዚሁ ሕግ በቁጥር 60፣61 እና 62 ስር የተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አበል ሳይሰጣቸው ስለሌላ ሰው ሆነው በወኪልነት ወይም በነገረ ፈጅነት አቤቱታ ለማቅረብ፣ለመከራከር፣ለመሟገት እና ነገሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመከታተል የሚችሉት የዋናው ባለጉዳይ ባለቤት፣ወንድም፣እህት፣ልጅ፣አባት ወይም አያት ስለመሆናቸው በቁጥር 58(1) ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ስለአመልካቹ በመሆን በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት ሰው ከዋናው ባለጉዳይ ጋር በቁጥር 58(1) ከተመለከተው የዝምድና ግንኙነት መካከል አንዱን የሚያሟሉ ስለመሆኑ ወይም ዋናው ባለጉዳይ በቁጥር 60፣61 እና 62 ስር ከተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች መካከል በአንዱ የሚሸፈኑ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክር ካለመኖሩም በላይ የውክልና ሰነዱም ይህንን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ክርክሩን ራሳቸው ወይም በጠበቃ ወይም መስፈርቱን በሚያሟላ ተወካይ አማካይነት መከታተልና መምራት የሚችሉ ከመሆኑ ውጪ በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ስለአመልካቹ ሆነው የቀረቡት ሰው በክርክሩ ለመቀጠል የሚችሉበት ሰነ-ስርዓታዊ አግባብ አይኖርም፡፡በመሆኑም ስለአመልካቹ ሆነው በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀረቡት ተወካይ በአመልካቹ ስም በፍ/ቤት በተሟጋችነት ለመቆም በሰነ ስርዓት ሕጉ የሚጠየቀውን መስፈርት የሚያሟሉ ስላልሆኑ አመልካቹን ወክለው ሊከራከሩ አይችሉም በማለት የተሰጠው የትዕዛዝ ክፍል ሊነቀፍ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ስለአመልካቹ ሆነው የቀረቡት ተወካይ በፍ/ቤት በተሟጋችነት ለመቆም በሰነ ስርዓት ሕጉ የሚጠየቀውን መስፈርት የማያሟሉ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በሌላ በኩል ግን ከዋናው ባለጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 63 ድንጋጌ መሰረት በተገቢው ባለስልጣን ዘንድ ተረጋግጦ የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ክርክሩን ራሳቸው ወይም በጠበቃ ወይም መስፈርቱን በሚያሟላ ተወካይ አማካይነት መከታተልና መምራት እንዲችሉ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 197(1) በተመለከተው መሰረት ተለዋጭ ትዕዛዝ እና ቀጠሮ መስጠት ይገባው የነበረ ከመሆኑ ውጪ አመልካች ሙሉ በሙሉ አቤቱታ እንዳላቀረቡ ወይም ጉዳዩን እንዳልተከታተሉ በመውሰድ መዝገቡን ዘግቶ ማሰናበቱ የሰነስርዓት ሕጉን አጠቃላይ ዓላማ እና መርህ ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ትዕዛዝ በከፊል መሰረታዊ ሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. ስለአመልካቹ ሆነው የቀረቡት ተወካይ በአመልካቹ ስም በፍ/ቤት በተሟጋችነት ለመቆም በሰነ-ስርዓት ሕጉ የሚጠየቀውን መስፈርት የሚያሟሉ ስላልሆኑ አመልካቹን ወክለው ሊከራከሩ አይችሉም ሲል መዝገቡን ዘግቶ በማሰናበት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.100727 በ21/10/2005 ዓ.ም የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.149227 በ26/11/2005 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ በተ.ቁ. 1 ከተመለከተው ውሳኔ ውስጥ ስለአመልካቹ ሆነው የቀረቡት ተወካይ በአመልካቹ ስም በፍ/ቤት በተሟጋችነት ለመቆም በሰነ-ስርዓት ሕጉ የሚጠየቀውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መስፈርት የሚያሟሉ ስላልሆኑ አመልካቹን ወክለው ሊከራከሩ አይችሉም በማለት የተሰጠው የትዕዛዝ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

3. ከላይ በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ መዝገቡን ዘግቶ በማሰናበት የተሰጠው የትዕዛዝ ክፍል በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
4. አመልካች ክርክሩን ራሳቸው ወይም በጠበቃ ወይም መስፈርቱን በሚያሟላ ተወካይ አማካይነት መከታተልና መምራት እንዲችሉ ፍ/ቤቱ ተለዋጭ ትዕዛዝ እና ቀጠሮ በመስጠት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሰረት ከቀረበለት አቤቱታ ጋር ተያይዞ የግራቀኙን ክርክር መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት ለፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
5. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌ/የመ/ደ/ ፍ/ቤት ይላክ፡፡
6. በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም ዕግድ ተነስቷል፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95033

መጋቢት 25ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነንጉሴ

መስጠፋአህመድ

አመልካች፡- አቶ ስንታየሁ ተፈሪ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ማርታ በቀለ - ጠበቃ ሽመልስ መንግስቱ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 ድንጋጌ መሰረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገ ተከራካሪ ወገን ጉዳዩን የፌደራል የሚያደርገው የነበረ ሁኖ እያለ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ስልጣን ሳይኖረው ስረ ነገሩን አስተናግዶ ዳኝነት ከሰጠ በኋላ ይኼው ተከራካሪ ወገን በይግባኝ ደረጃ በነበረው ክርክር የተሠጠውን ዳኝነት ተቀብሎ ከወጣ በኋላ በሌሎች ጉዳዩን የፌደራል ሊያደርጉ በማይችሉ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የተሰጠው ውሳኔ ከመነሻውም የፌደራል ጉዳይ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኗ ተጠሪ ላይ በጨኮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች የክስ ይዘትም፡-የተጠሪ መኪና በአካላቸው ላይ ጉዳት ያደረሰባቸው መሆኑን ዘርዝረው ተጠሪ በድምሩ ብር 269,266.44 (ሁለት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ ስድስት ብር ከአርባ አራት ሳንቲም) የአካል ጉዳት ካሳ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ተጠሪም ለክሱ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑንና የጉዳት ካሳ መጠን ጥያቄው ተገቢነት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ከመከራከራቸውም በተጨማሪ በተጠሪ ላይ ጉዳት አደረሰ የተባለው መኪናቸው የመድን ሽፋን ከአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ያለው መሆኑን ጠቅሰው ይኼው አካል ወደ ክርክሩ እንዲገባ ይታዘዝላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ ክርክሩን ከመራ በኋላ ተጠሪንና ኡንሹራንስ ድርጅቱን ለክሱ ኃላፊ አድርጎ ኢንሹራንስ ድርጅቱ የውል ግዴታ ስላለበት የሞራል ካሳን ጨምሮ ለአመልካች ብር 98,750.00 እንዲከፍል፣ተጠሪ ደግሞ ብር 12,460.00 እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ ግራ ቀኙ ቅር በመሰኘት በየፊናቸው ይግባኛቸውን ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ለአመልካች የጉዳት ካሳ ይክፈል ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ ነው በማለት ከደመደመ በኋላ የጉዳት ካሳ መጠኑን በተመለከተ ግን የሥር ፍርድ ቤት ስህተት መፈፀሙን ገልፆ ለአመልካች ሊከፈል የሚገባው የጉዳት ካሳ መጠን ብር 143,016.44 (አንድ መቶ አርባ ሶስት ሺህ አስራ ስድስት ብር ከአርባ አራት ሳንቲም) መሆኑን ለይቶ ከወሰነ በኋላ መድን ሰጪ ድርጅት ሊጠየቅ የሚገባው ግን በመድን ውሉ መሰረት ነው በማለት ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) ብቻ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት አቅርበው ከአሁኑ አመልካች ጋር ብቻ ከተከራከሩ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ዳኝነት ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ከዚህ በኋላ ደግሞ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ከአሁኑ አመልካች ጋር ብቻ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ በወረዳው ፍርድ ቤት በጣልቃ ገብነት ገብቶ የተከራከረ ሲሆን ይህም ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የሚያደርገውና የወረዳው ፍርድ ቤት ደግሞ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የሌለው በመሆኑ ውሳኔው ከመነሻውም ሕጋዊ አይደለም በሚል ምክንያት ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ተቀብሎ ይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ ባልቀረበበት ሁኔታ ጉዳዩ የፌዴራል በመሆኑ ከመነሻውም በወረዳው ፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አልነበረም ተብሎ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ የስነ ስርዓት ሕጉን አላማ ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ለአመልካች የሰጡትን ውሳኔ መሻሩ የፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉን መሰረታዊ አላማ ያገናዘበ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ በይግባኝ ደረጃ በነበረው ክርክር የተሰጠውን ውሳኔ ተቀብሎ ከክርክሩ ውጪ መሆኑ መረጋገጡን፣አመልካችና ተጠሪ በክልሉ ነዋሪ ሁነው የክሱ መሰረትም የጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ተከሳሽ ከእሱ ጋር ኃላፊነት ሊወስድ ወይም ሊካፈል የሚችል ሦስተኛ ወገን ወደ ክርክሩ እንዲገባለት እንዲታዘዝ ማመልከት እንደሚችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ በዚህ ጥያቄ መነሻ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገ ተከራካሪ ወገን በክርክሩ ውስጥ ሊያነሳ የሚችለው የኃላፊነት እና የኃላፊነት መጠን አስመልክቶ የክርክሩ ዘንግ ከተከሳሽ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከከሳሽ ወይንስ ከሁለቱም ወገን ጋር ሊሆን ይገባል? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ በሁለት አቅጣጫ ምላሽ ሊያገኝ እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል። ይኸውም የጣልቃ ገብ ኃላፊነት ምንጭ ውል ወይንስ ሕግ የሚለው በመሠረታዊ ሕግ ድንጋጌዎች የሚወሰን መሆኑ እና በሌላ በኩልም የክርክሩ አቀራረብ እና ይዘት በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተደነገገው አግባብ መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል።

በዚህ ጉዳይ በወረዳው ፍርድ ቤት አዋሽ ኢንሹራንስ ጣልቃገብ ሁኖ የተከራከረ ሲሆን ጣልቃ ገብነት በፍትሓብሔር ስነስርዓት ሕጉአግባብ የተፈቀደ አንዱ የክርክሩ ተሳታፊ የሚሆንበትና ራሱን የቻለ መሰረታዊ አላማ ያለው፣ በስነ-ስርዓት ሕጉ የተዘረጋ ስርዓት መሆኑ የሚታወቅ ነው።በ1958ቱ ፍትሃብሄር ስነ-ስርዓት ሕግ ወደ ክርክሩ ሊገባ የሚችልበት ስርዓት የተለያየ ቢሆንም ይህ ስርዓት አገሪቱ ከምትከተለው የፌዴራል ስርዓትና በዚሁ ስርዓት ከተዘረጋው የፍርድ ቤቶች አደራጃጀት ጋር ተጣጥሞ በመታየት ስራ ላይ ሊውል የሚገባው መሆኑ ይታመናል።በመሆኑም አንድን ጉዳይ የፌዴራል ወይም የክልል ብሎ ለመለየት ይቻል ዘንድ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 የተቀመጠው መስፈርት ታይቶ የጉዳዩን የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣንም ከዚሁ አንጻር መለየት ያለበት ጉዳይ ነው።

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 ስር አንድን ጉዳይ የፌዴራል ጉዳይ ለማለት የሚያስችሉ ምክንያቶች ተገልጸዋል። አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ በፌዴራል መንግስት የተቋቋመና የተመዘገበ የልማት ድርጅት ሲሆን በፌዴራል መንግስቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶችና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን የማየት የስረነገረ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑ እና እስከ ብር 500,000 ግምት ያለው የገንዘብ ክርክር የማየት ስልጣን ደግሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/88 በአንቀጽ 5(6) እና በአንቀጽ 14 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(4) እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት በአንቀጽ 75(3) በተመለከተው የስልጣን ውክልና መሰረት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ በክልሉ የሚነሱ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የተሰጠው ለክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው። ስለሆነም ከመነሻው ሲታይ በእርግጥ የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን አልተሰጠውም። እንዲሁም የሥረ ነገረ የስልጣን ጥያቄ በማናቸውም የክርክር ደረጃ የሚነሳና ፍርድ ቤቱም በራሱ አነሳሽነት ጭምር ማየት የሚችለው ጉዳይ መሆኑ የሚታወቅ ነው።በመሆኑም የጨኩ የወረዳው ፍ/ቤት የአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ወደ ክርክሩ መግባቱ ጉዳዩን ከስረ ነገር ስልጣኑ ውጪ የሚያደርገው መሆኑን ተገንዝቦ ክሱ ጣልቃ ገቡን ባካተተ ሁኔታ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይቀርብ ዘንድ ጉዳዩን ዘግቶ ማሰናበት ሲገባው ክርክሩን ቀጥሎ በማየት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ያልነበረ ሲሆን የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቢሆን ጉዳዩን ከዚህ አንጻር በመመልከት በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ መሻር ይገባው ነበር።ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ ለማድረግ በሕጉ መለኪያ የተቀመጠው ተከራካሪ ወገን በይግባኝ ደረጃ የክርክሩ ተሳታፊ የነበረ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ረገድ በወረዳው ፍርድ ቤት የተፈጸመውን ስህተት ሳያርም መቅረቱ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(1(ለ))የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ይሁን እንጂ አንድን ክርክር የፌዴራል ብሎ ለመውሰድ ያስችል የነበረው የአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ተቀብሎ በስርዓቱ መሰረት ክርክሩን በበላይ ፍርድ ቤቶች ያልቀጠለ ከመሆኑም በላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያደረባቸው የአሁኗ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርቡ በመልስ ሰጪነት የሰየሙት የአሁኑን አመልካች ብቻ ነው፡፡ ተጠሪ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸው ተቀባይነት ሲያጣም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተጠሪነት የሰየሙት የአሁኑን አመልካች ብቻ እንጂ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያን ጭምር አይደለም፡፡ስለዚህ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው የክርክር ደረጃ ጉዳዩ የፌዴራል መሆኑን የሚያስገነዝብ ተከራካሪ ወገን የነበረ ሲሆን ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በኋላ በነበሩት የክርክሩ ሂደቶች ግን ይህ አካል ተሳታፊ አይደለም፡፡ይህም የሚያሳየው ጉዳዩን የፌዴራል ለማድረግ ይችል የነበረው የሕግ ምክንያት ቀሪ የሆነ መሆኑንና በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሚደረገው ክርክር ደግሞ በባሕርይው የፌዴራል ጉዳይ ለመሆን የሚያስችል የሕግ ምክንያት የሌለው መሆኑን ነው፡፡

የክርክሩ ሂደት የሚያስገነዝበው ከላይ የተገለጸውን ሁኔታ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ እልባት ማግኘት ያለበት ከስነ ስርዓት ሕጉ አላማ ጋር ተዛምዶና ታይቶ ሊሆን ይገባል፡፡ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ መሰረታዊ ዓላማ ክርክሮችን ፍትሃዊ በሆነ እና ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጭ ተገቢውን እልባት እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑ ይታመናል፡፡በተለይም የሥነ - ሥርዓት ድንጋጌዎችን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ እና በክርክሩ አመራር በህጉ በግልፅ ያልተሸፈኑትን ነገር ግን ፍ/ቤቱ በእራሱ በመሰለው እንዲወሰን፣ ትዕዛዝ እንዲሰጥ በሚያስችል አኳኋን በተደነገገ ጊዜ እንደቅደም ተከተሉ ከትክክለኛው ትርጉም ለመድረስና የተሰጠውንም ሥልጣን (Discretionary power) በአግባቡ ለመጠቀም ይህ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ ዓላማ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ጉዳዩን ማየቱ ጠቀሜታው የጎላ እንደሚሆን ይታመናል፡፡እንደሚታወቀው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረታዊ መብቶችንና ግዴታዎችን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል መሣሪያ በመሆኑ ይህንኑ ሂደት ውጤት እንዳይኖረው የሚያደርግ የስነ ስርዓት ሕግ አተገባበር ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው በተከራካሪ ወገን ማንነት የተነሳ አንድ ጉዳይ የፌዴራል ነው ለማለት የሚቻልበት የሕግ ምክንያት ባለበት ሁኔታ ጉዳዩን ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት አይቶ ዳኝነት ከሰጠና በይግባኝ የክርክር ሂደትም ይኼው ሳይታረም ቀርቶ ጉዳዩን የፌዴራል ነው ብሎ ለማለት የሚያስችል ተከራካሪ ወገን በፍሬ ጉዳዩ የተሰጠውን የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቀበል ከክርክሩ ውጪ ከሆነ እንዲሁም ክርክሩ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ ለማድረግ በማያስችሉ ተከራካሪ ወገኖች መካከል ከቀጠለ ስልጣን በሌለው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለው የስነ ስርዓት ሕግ ጥያቄን አዋጅ ቁጥር 25/1988"ም" ሆነ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ግልጽ ምላሽ የማይሰጡበት በመሆኑ ምላሽ ማግኘት ያለበት ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ መሰረታዊ አላማ አንፃር ሁኖ አግኝተናል፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ቀሪ የሆነውን የሕግ ምክንያት በመያዝ ጉዳዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመነሻውም ስልጣን በሌለው ፍርድ ቤት የተሰጠ ነው በማለት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተሰጠውን ዳኝነት መሻሩ የፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉን መሰረታዊ ዓላማ ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ መሻር እና በዋናው ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፀናው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አይቶ የመጨረሻ ዳኝነት እንዲሰጥበት ማድረጉ ስነ ስርዓታዊ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 59864 ጥቅምት 29 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩን በመ/ቁጥር 59864 በመቀጠል ተጠሪ ለአመልካች ካሳ እንዲከፍሉ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.95934

ቀን 18/09/2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አስፋው ንዳ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ እየሩሳሌም አየነው - ከጠበቃ እንዲለም በዕወቀቱ - ቀረቡ

2. አቶ መኮተ ሲሳይ - ከጠበቃ ጌታው ተስፋዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የጣልቃ ልግባ ጥያቄ የሚስተናገድበትን የህግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፊዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ የቤት ባለቤትነት መፋለም ክስ ያቀረቡባቸው ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ተወካይነት ጠበቃ ተወክሎላቸው ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካችና ወ/ሮ ፀሐይ ቸበራ የተባሉ ግለሰብ ወደ ክርክሩ ለመግባት እንዲፈቀድላቸው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአሁኑ ተጠሪዎች በጣልቃ እንግባ ጥያቄ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት ያደረግ ሲሆን የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የአሁኑ አመልካች የተከሳሽ ወኪል ሁነው ጠበቃ ወክለው ስለ ተከሳሹ ጥቅም ሁነው ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ወደ ክርክሩ ልግባ በማለት ጥያቄ ማቅረባቸው የስነ ስርዓት ህጉን አላማ ያልተከተለ መሆኑን ገልጸው የተቃወሟቸው ሲሆን ወ/ሮ ፀሐይ ቸበራ የተባሉትን ግለሰብ ደግሞ ለጣልቃ ልግባ ጥያቄአቸው ተገቢው ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን ገልፀው ወደ ክርክሩ ሊገቡ አይገባም ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ የስር ተከሳሽ የሆኑት የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ አመልካች በተከሳሽ በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሰረት አቶ ጌታሁን ተስፋዬ የተባሉትን ጠበቃ ወክለው ጠበቃው ቁጥሩ 3936 የሆነ ቤት የተከሳሽ የግል ቤት ሁኖ ቤቱን ተከሳሹ ለአሁኑ አመልካች የሸጡላቸውና ሰነዶቹም ቦታውን ለሚያስተዳድረው መሬት አስተዳደር ተመላሽ ሆኖ ቤቱን የአሁኑ አመልካች በእጃቸው አድርገውና ተገቢውን የይዞታ ማረጋገጫ አውጥተው የሚገለገሉበት መሆኑን በመጥቀስ የከሳሽ ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መከራከራቸውን፣የጣልቃገብነት ጥያቄው የአመልካቹ መብትና ጥቅም የሚነካበትን የህግ አግባብ የማያሳይ መሆኑን እንዲሁም አመልካች በተከሳሽነትም ሆነ በጣልቃ ገብነት በአንድ ጊዜ የሚከራከሩበት አግባብ የሌለ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ሲሆን የወ/ሮ ፀሐይ ችበራ ጥያቄ ደግሞ በማስረጃ ያልተደገፈ ነው በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ አልተቀበላቸውም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካች የተከሳሽ ወኪል መሆናቸው ስለወኪላቸው ጥቅምና ስለራሳቸው መብትና ጥቅም የሚያቀርቡትን ክርክር የማያግዳቸው ሁኖ እያለ ጉዳዩ በማስረጃ ሳይጣራ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ሊገቡ አይችሉም የተባለው ከህግ አግባብ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ከወኪላቸውና ለራሳቸው መብትና ጥቅም በአንድ ጊዜ ሊከራከሩ የሚችሉበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን፣ አመልካች አለኝ የሚሉት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርም በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ሰኔ 03 ቀን 2005 ዓ/ም የመከነ መሆኑን ዘርዝረውና ጥያቄያቸው ከስነ ስርዓት ህጉ መሰረታዊ አላማ ውጪ መሆኑን ጠቅሰው የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ አመልካችን ደግፈው መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካችም ለሁለቱም ተጠሪዎች መልስ የመልስ መልሳቸውን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቷል፡፡

በመሰረቱ ጣልቃ ገብነት አንድ በፍትሃ ብሔር ክርክር ተካፋይ ያልነበረ ሰው የክርክሩ ተካፋይ የሚሆንበትና መብቱንና ጥቅሙን ለማስከበር ተገቢውን ክርክር እንዲያቀርብ በህጉ የተዘረጋ ስርዓት ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ሰው ወደ ክርክሩ የሚገባው በተከሳሽ ጠያቂነት ወይም በራሱ አነሳሽነት ሊሆን እንደሚችል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 41 ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ በዚህ ድንጋጌ እንደተመለከተው ሌሎች ወገኖች በሚከራከሩበት ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሶስተኛ ወገን ከፍርድ ውሳኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር እንዲፈቀድለት ሊከራከር ይችላል፡፡ ሆኖም የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብ ለመሆን ሌሎች ሰዎች በሚከራከሩበት ጉዳይ የሚሰጠው ውሳኔ በቀጥታ መብቱንና ጥቅሙን የሚነካ መሆኑን የማስረዳት ግዴታውን መወጣት አለበት፡፡ በሌላ አገላለፅ ጣልቃ ልግባ ጥያቄ ተቀባይነት እንዲኖረው ውሳኔው የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነውን ሰው መብትና ጥቅም በሚጎዳ መልኩ በቀጥታ የሚፈጸም መሆኑንና ሌላ አዲስ ክስ በማቅረብ ለማስቀረት የማይቻል መሆኑን ማረጋገጥ የግድ ይላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ጣልቃ ገብ ልሁን በሚል ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ውሳኔው በቀጥታ መብቱንና ጥቅሙን የማይጎዳ ከሆነ እና አዲስ ክስ በማቅረብ ማስቀረት የሚቻልበት ሁኔታ ያለው ከሆነ ጥያቄው በህግ ፊት ተቀባይነት የሚያግኝበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን ነው።

ጣልቃ ልግባ የሚለው ወገን በተከራካሪ ወገኖች መካከል ባለው ጉዳይ የሚሰጠው ውሳኔ መብቱን በምን አግባብና መልኩ ሊነካ እንደሚችል ማሳየት እንደአለበት የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41(2) ድንጋጌ ያሳያል። በመሆኑም አመልካቹ ዝርዝር ምክንያቱን በማስፈር ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡ የጣልቃ ገብነቱ አቤቱታ ሊቀርብ የሚገባውም ጊዜ ለማራዘም፣ ክርክሩን ለማጓተት ሊሆን እንደማይገባውም ከተጠቃሹ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ህጉ መሰረታዊ አላማ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የስር ተከሳሽ ወኪል ሁነው ስለተከሳሹ ጥቅምና መብት ጠበቃ ወክለው ቤቱ የተከሳሹ የግል ቤትና ለአሁኑ አመልካች የተላለፈ መሆኑን ጠቅሰው ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ለራሳቸው ጥቅምና መብት ደግሞ የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል። አመልካች ስለተከሳሹ የወከሏቸው ጠበቃ ቤቱ የስር ተከሳሽ የግል ቤት መሆኑን ጠቅሰው ክርክር ከማቅረባቸው ውጪ ቤቱ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ነው ቢባል እንኳን በአመልካች እጅ የገባበት ሁኔታ ከስር ተከሳሽ ጋር ያደረጉትን ሽያጭ ህጋዊ ሊያደርግ የሚችልበት ምክንያት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41(2) በተመለከተው አግባብ ዘርዝረው አላቀረቡም። እንዲህ ከሆነ ደግሞ በስር ከሳሽ እና ተከሳሽ መካከል በሚደረገው ክርክር የሚሰጠው ውሳኔ ተከሳሽን የሚጠቅም ከሆነ የአሁኑን አመልካች ሊጎዳ ይችላል ተብሎ ሚታሰብበት አግባብ የለም። አመልካች ከስር ከሳሽ መብትና ጥቅም በተለየ ሁኔታ መብትና ጥቅማቸው ሊከበር የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት መኖሩን ዘርዝረው የጣልቃ ልግባ አቤቱታቸውን ስለማቅረባቸው የክርክሩ ሂደት አያሳይምና። አመልካች የመብታቸው ምንጭ የስር ተከሳሽ መሆናቸውን፤ የወኪላቸውን መብትና ጥቅም ከራሳቸው መብትና ጥቅም ጋር አዛምደው ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ማቅረባቸው ክርክሩን ለማጓተት ነው ተብሎ ከሚታሰብ ውጪ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም። እንዲህ አይነት የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ደግሞ የጣልቃ ልግባ አቤቱታዎች የሚስተናገዱበትን ስርዓት ከዘረጋው ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከፍትሐብሔር ስርዓት ህጉ መሰረታዊ አላማ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም።

ሲጠቃለልም አመልካች ተከሳሽ ለነበሩት ግልሰብ ወኪል ሁነው ጠበቃ ወክለው ጠበቃውም አከራካሪው ቤት የስር ተከሳሽና ለአመልካች የተላለፈ መሆኑን ጠቅሰው ሲከራከሩ ቆይተው ለአመልካች መብትና ጥቅም ማስከበር ሲባል ነው በማለት የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ማቅረባቸው የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 41 ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.74380 ሚያዝያ 22 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቀ.137867 ህዳር 17 ቀን 2006 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በ23/04/2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.92903

ሚያዝያ 24 ቀን ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ስላስ ረዳ - ጠበቃ ጠጅነሽ ሰይፉ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ለተሚካኤል ገ/ሐዋሪያት } አልቀረቡም

2. የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ }

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከንግድ መደብር ኪራይ ጋር ተያይዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው የሰበር አመልካች ከሳሽ ሆነው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ አመልካች በ14/06/2005 ዓ/ም በተሻፈ ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አቤቱታ፡- አመልካች ለንግድ ቤትነት ለመገልገል ከ 2ኛ ተጠሪ ተከራይተው በነበረው ቤት ላይ የፀጉር ስራ ንግድ ፈቃድ በማውጣትና ለስራው የሚያስፈልጉ ሌሎች ነገሮችንም ካሟላ በኋላ የንግድ ድርጅቱን ከነፈቃዱና ሙሉ እቃው ለ1ኛ ተጠሪ በወር ብር 4,000 ኪራይ ያካራዩ መሆኑን ጠቅሰው ሆኖም ግን 1ኛ ተጠሪ ከህግ አግባብ ውጭ በንግድ ድርጅቱ ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የኪራይ ውል አቋቁሜያለሁ በማለት ድርጅቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ስላልሆነ ተጠሪዎች ከህግ ውጭ በድርጅቱ ላይ ያደረጉት ኪራይ ውል ፈርሶ 1ኛ ተጠሪ ድርጅቱን ከነ ሙሉ እቃው ለአመልካች እንዲያስረክብ እንዲወሰንላቸው እና እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ከመሰከረም 2004 ዓ/ም ጀምሮ ያልተከፈለ የድርጅቱን ውዝፍ ኪራይ ገንዘብ ብር 24,000 መክፈል ከነበረበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ጉዳይን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ተከራይተው የነበረውን ንግድ ቤት በኪራይ ውሉ በገቡት ግዴታ መሰረት አስቀድመው አከራይን (2ኛ ተጠሪን) ሳያሳውቁ ለ1ኛ ተጠሪ አሳልፈው ማከራየታቸው የኪራይ ውሉን ስምምነት የጣሱ ስለሆነ እና 2ኛ ተጠሪም ይሄንኑ ተከትሎ ከአመልካች ጋር የነበረውን የቤቱን ኪራይ ውል አቋርጦ ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ ማከራየቱ መብቱና ተገቢ ስለሆነ ይህ በተጠሪዎች መካከል በቤቱ ላይ የተደረገው ኪራይ ውል ይፍረስልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልተቀበልኩም በማለት ጥያቄውን ወድቅ በማድረግ አልፏል፡፡ የንግድ መደብሩን ኪራይ ክፍያ ጥያቄ በተመለከተ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ ሊከፍሉ የሚገደዱት ኪራይ በአመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው ኪራይ ውል እስከተቋረጠበት (28/02/2004 ዓ/ም) ድረስ ያለው ኪራይ ብቻ ስለሆነ በዚህ መሰረት የመሰከረምና ጥቅምት ወር 2004 ዓ/ም የ2 ወራት ኪራይ ክፍያ ብር 8,000 ውሳኔ ከተሰጠበት ከ 15/06/04 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታዋን ለፌዴራል ከ/ፍ/ቤት አቅርበው እና ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች አሳልፈው ለ1ኛ ተጠሪ ያከራዩት ንግድ ቤቱን ሳይሆን ንግድ መደብር መሆኑን ከገለፀ በኋላ የንግድ መደብሩን ደግሞ በንግድ ህጉ ቁ.145(1) እና ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መ/ቁ.31264 አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት የአከራዩን ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልግ ማከራየት ስለሚችልና በዚህም መሰረት አመልካች ንግድ ድርጅቱን 2ኛ ተጠሪ ሳያሳውቁ ለ1ኛ ተጠሪ ማከራየታቸው ህጉን መሰረት ተደረጎ እንጂ ህጉን ያልተከተለ አድራጎት ባለመሆኑ በአመልካችና 2ኛ ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው የቤቱ ኪራይ ውል መቋረጡ በአግባቡ ስላልሆነ ውሉ ፀንቶ ሊቀጥል ይገባል በማለት ከወሰነ በኋላ በሌላ በኩል ግን በተጠሪዎች መካከል በቤቱ ላይ የተደረገው የኪራይ ውል ህጋዊ ባለመሆኑ ሊፈርስ ይገባል በማለትና እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ንግድ ድርጅቱን ቀድሞ በተረከበበት ሁኔታ መልሰው ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የተሰጠውን ውሳኔ በከፊል በመቃወም ሲሆን ቅሬታ ነጥቡም ባጭሩ፡- 1ኛ ተጠሪ ንግድ መደብሩን በወር ብር 4000 ተከራይተው የነበሩ መሆኑን ሳይክዱና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም በበኩሉ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር 1ኛ ተጠሪ ንግድ ድርጅቱን ከነ እቃው ለአመልካች እንዲያስረክቡ በማለት ከወሰነ በኋላ ኪራዩን በተመለከተ ግን ውሳኔ ሳይሰጥበት በገዘምታ ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት ውሳኔው ታርሞ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ አመልካች 1ኛ ተጠሪ የተከራዩትን የንግድ ድርጅት ኪራይ ይክፈሉኝ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በገዘምታ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙም ተከራካሪ ወገኖች ቀርበው በጉዳዩ ላይ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ እንደተቻለው አመልካች የንግድ ድርጅቱን ኪራይ ክፍያ በተመለከተ ስር ፍ/ቤት እንዲከፍላቸው ዳኝነት የጠየቁት ብር 24,000 ብቻ መሆኑን ፤ ከዚህ ውስጥም የመስከረምና ጥቅምት 2004 ዓ/ም የ2 ወራት የድርጅቱ ኪራይ ብር 8,000 በፌዴራል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለአመልካች መወሰኑን፤ የድርጅቱ ኪራይ መጠንም በወር ብር 4,000 መሆኑን፤ 1ኛ ተጠሪም የኪራይ መጠኑ ብር 4,000 አለመሆኑን ክዶ አለመከራከሩን፤ አመልካችም የስር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ሳይከፈላቸው ከቀረው የድርጅቱ ኪራይ ክፍያን ጨምሮ አለኝ ያሉትን ቅሬታቸውን በሙሉ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግን የንግድ መደብሩን ልረከብ ጥያቄን አስመልክቶ በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ክፍል ለውጦ አመልካች ድርጅቱን እንዲረከቡ በማለት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ሆኖም ግን ለአመልካች ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ወድቅ ተደርጎ የታለፈውን ኪራይ በተመለከተ ምንም አይነት ዳኝነት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ሳይሰጥበት በዝምታ መታለፉን ነው፡፡

በመሰረቱ በአመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው የድርጅቱ ኪራይ ውል ህጋዊና ተገቢ ነው በማለት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ተወስኗል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በተጠሪዎች መካከል በቤቱ ላይ የተደረገው ኪራይ ውልም ህገ-ወጥ ነው ተብሎ እንዲፈርስ ከመደረጉም በላይ 1ኛ ተጠሪም ድርጅቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ በማለት ጭምር ተወስኗል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በድርጅቱ ኪራይ ውል መሰረት እንዲከፍሉ የተጠየቁትን ቀሪ የድርጅቱን ኪራይ ክፍያ በተመለከተ ሊከፍሉ የማይገባበትን ህጋዊ የሆነ ክርክር ባላቀረብበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ቀሪው ኪራይ ለአመልካች እንዲከፈል ሳይወስን በዝምታ ማለፉ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182(1) እና 348(1) ድንጋጌዎች ይዘት አኳያ የውሳኔው በከፊል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላገኘን ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.128192 በ30/10/05 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ስር ፍ/ቤት እንዲከፈላቸው ዳኝነት ከጠየቁት ብር 24,000 የድርጅቱ ኪራይ ውስጥ የመሰከረምና ጥቅምት 2004 ዓ/ም ብር 8,000 በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተወሰነላቸው ሲሆን ቀሪው ብር 16,000ም ሊከፈላቸው የማይገባበት በቂና ህጋዊ ምክንያት ስላላገኘን ይሄው ገንዘብ ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ከ 24/08/06 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡
3. የሰበር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና እንዲሁም ፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በትዕዛዝ የቀረቡት መዝገቦች ይመለሱ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
- በተሻሻለው ውሳኔ መሰረት ይፈፀም ዘንድ የውሳኔ ግልባጩ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሉሃና አንጂነሪግ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ ፍሬው ካሳሁን ቀረበ

ተጠሪ፡- ማክሮ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ኃ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ ሰለሞን በዳኔ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የተጀመረው በተጠሪ ከሣሽነት አመልካች በቼክ ቁጥር C-1469751 ብር 462,518.04 እንዲከፈለው ከሰጠ በኃላ ክፍያው እንዳይፈጸም አመልካቹ ለባንኩ ትእዛዝ ሰጥቶ እንዲታገድ ከመደረጉም በላይ ገንዘቡን አመልካቹ ሊከፍል ፈቃደኛ አልሆነም በማለት ገንዘቡ በአመልካች እንዲከፈለው ይወሰን ዘንድ በተፋጠነ ስነ ስርዓት በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡

አመልካች እንዲከላከል ተፈቅዶለት ባቀረበው መልስም ቼኩ በተጠሪ እጅ ሊገባ የቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል መስከረም 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተፈፀመ የኮንስትራክሽን ንዑስ ስራ ተቋራጭነት ውል ስምምነት መሰረት አድርጎ ለሚፈጸመው ቅድመ ክፍያ ለዋስትና የተሰጠ መሆኑን ፣ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የስራ ውል ስምምነት ሲፈጸም አስቀድሞ እዳ አለብኝ ተብሎ የሚሰጥም ሆነ የሚገባ የውል ስምምነት የሌለ መሆኑን ፣ ቼኩ በተጠሪ እጅ የገባው ለተባለው አላማ ስለሆነ ተጠሪ እንዲፈጸምለት ለባንኩም ሆነ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄው ከማቅረቡ በፊት በውሉ አግባብ አመልካች ያልተወጣውን ግዴታ አረጋግጦ መሆን ሲገባው በቀጥታ በቼኩ ላይ የተገለጸውን ክፍያ እንዲፈጸምለት የዳኝነት ጥያቄ ማቅረቡ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ፣ ቼኩ የተሰጠው ለተባለው ዓላማ ወይም በተጠሪና በአመልካች መካከል በነበረው የግል ግንኙነት ከሆነ ደግሞ ቼኩ እንደቀረበ የሚከፈል ሰነድ ሳይሆን ተራ ሰነድ መሆኑን ፣ አመልካች ወደ ስራው ገብቶ ስራውን እያከናወነ እያለ ያልታሰበ ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ በመድረሱ ንብረቶች በመጎዳታቸው ምክንያት ለተጠሪ ቅድመ ሁኔታዎችን ሰጥቶ ስራውን በወቅቱ ለማቋረጥ መገደዱን ፣ ነገር ግን ተጠሪ ባለመስማማት ውሉን በራሱ ጊዜ ማቋረጡን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጎ ለክሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኃላፊ ያደረገው ሲሆን የኃላፊነት መጠኑን በተመለከተም በክሱ ላይ የገለጸውንና ሌሎች ወጪዎችን እንዲሁም የኮሚሽን ክፍያ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች ቼክ ለኮንስትራክሽን ስራ ለመያዣነት የተሰጠ መሆኑን ሳይገነዘቡና የተሰራ ስራ ስለመኖሩ እንዲሁም ተጠሪም ለተሰራው ስራ ከስራው ባለቤት ክፍያ መውሰዱ እየታወቀ ይህንኑ አልፈው አመልካች ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ እንዲከፍል መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው የኮንስትራክሽን ስራ ሁኔታ ሳይጣራ ቼኩ ለተጠሪ ለክፍያ መቅረብ አልነበረበትም በማለት ያቀረበው ክርክር ታልፎ በበታች ፍርድ ቤቶች ክፍያው እንዲፈጸም የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ በመሆኑ በዚህ አግባብ ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ቼክ የንግድ ወረቀት ከሚባሉ አንዱ ሲሆን እንደቀረበ የሚከፈል ፣ በባንክ ተቀማጭ ሂሳብ ያለው ሰው ገንዘቡ ለራሱ ወይም ለሌላ ወገን እንዲከፈል ሐተታ የሌለው ትእዛዝ የሚሰጥበት ፣ ገንዘብን ተክቶ ክፍያን የሚያቀላጥፍ የንግድ ወረቀት ወይም ሰነድ ስለመሆኑ ከን/ህ/ቁ.732፣827፣828 እና 854 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል የገንዘብ ሰነድ በመሆኑ በቼክ ገንዘብ ለመክፈል አውጭው በባንክ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተቀመጠ የቼኩን ዋጋ አጣርቶ የሚከፈል ፣ በቂ ስንቅ /ገንዘብ/ ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑም እርግጠኛ መሆን እንዳለበት የን/ህ/ቁ. 830(2) ድንጋጌ ያስቀምጣል፡፡ ይህንኑ በህግ የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ የቀረ አውጪ በቼኩ ላይ የተጻፈውን ገንዘብ /እዳ/ ለአምጪው እንዲከፍል የሚገደድ ስለመሆኑ የህጉ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ዕዳ ከፋዩ /አውጪው/ ግዴታውን እንዲወጣ የማይገደደው በህጉ የተቀመጡትን መቃሚያዎች /መከራከሪያ ነጥቦችን/ በአግባቡ ሲያስረዳ ነው፡፡ በህጉ እዳ ከፋዩ በአምጪው ላይ ሊያቀርብ ይችላል ተብለው የተቀመጡት መቃወሚያዎች በን/ህ/ቁጥር 717 ስር የተመለከቱት ናቸው፡፡ እነዚህም፡- በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ የተመሰረቱ ፣ በሰነድ አጻጻፍ ፎርምና በሰነዱ ላይ በተጻፉ ቃሎች ፣ እንዲሁም ፊርማን በማስመሰል የተሰራ ፣ ችሎታ ወይም ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ስልጣን ባለመኖሩ ወይም ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎችን ባለመሟላታቸው የሚነሱ መቃወሚያዎችና አምጭው ይህን ሰነድ ባገኘበት ጊዜ እዳ ከፋዩን ለመጉዳት እያወቀ ያደረገው መሆን ስለመሆናቸው የሚያሳዩ እንደሆነ ህጉ አስቀምጧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንግዲህ ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል እንደመሆኑ መጠን አውጪው ለቼኩ መውጣት ምክንያት የሆነውን ነገር የማስረዳት እና የማስተባበል ሸክም ያለበት ስለመሆኑ ከህጉ ቅርፅ ፣ ይዘትና መንፈስ በቀላሉ የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን በቼኩ የተጻፈውን ገንዘብ ለመክፈል አልገደድም የሚለው አውጪው ከላይ በን/ህ/ቁጥር 717 ስር የተመለከተቱትን ሁኔታዎች በበቂ እና አሳማኝ መንገድ ማስረዳት ግዴታውን ሲወጣ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የኮንስትራክሽን ስራን በተመለከተ ውል መኖሩ አልተካደም፡፡ ቼኩም ለዚህ ምክንያት የተሰጠ መሆኑን አመልካች ክርክርና ማስረጃ ያቀረበበት ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች በውሉ መሰረት የሰራው ስራ መኖር፣ የስራው መጠን ምን ያህል እንደሆነና በዚሁ ስራ መነሻ ተጠሪ ከስራው ባለቤት ክፍያ ያገኘ መሆን ያለመሆኑ በዚሁ መዝገብ ክርክር ተደርጎ በማስረጃ የማይነጥርበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

የአመልካች እና የተጠሪ ግንኙነት የተመሰረተው በመሃከላቸው በተደረገው የግንባታ ውል ላይ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል ክርክር ቀርቦ በተጠሪ እስካልተካደ ድረስ ተጠሪ በተፋጠነ ስነ ስርዓት ታይቶ ይወሰንለት ዘንድ ላቀረበው ክስ መሰረት ያደረገው ቼክ ቁጥር C-1469751 በግንባታ ውሉ መነሻ የተሰጠ ስለመሆኑ አመልካች የማስረዳት መብቱ በሌላ መዝገብ ሳይሆን በዚህ መዝገብ የማይታይበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች እነዚህን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ክሱን ይከላከል ዘንድ እንዲፈቀድለት ያቀረበው ጥያቄ ፍ/ቤቱ ከተቀበለው በኃላ የመከላከያ መልሱንና እና ማስረጃዎችን ሊታይለት ይገባል እንጂ በክሱ ቼክ በመጠቀሱ ብቻ ጉዳዩ ቼክን በሚመለከቱ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች አንጻር ብቻ በማየት በቼኩ የተመለከተው ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፈል ለመወሰን የሚያስገድድ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች አጥብቆ የተከራከረው ቼኩ ለተጠሪ የተሰጠው አመልካች በኮንስትራክሽን ንዑስ ስራ ስምምነት መሰረት በውሉ የገባውን ግዴታ ለመወጣት ፣ በውሉ ለተመለከተው የቅድሚያ ክፍያ በተወሰነ መጠን በመውሰዱ ለዚሁ ለመያዣነት እንዲሆን ነው የሚሉትን ነጥቦች በማንሳት ነው፡፡ ለዚህ የአመልካች ክርክር ግራ ቀኙ መስከረም 04 ቀን 2004 ዓ/ም ተፈረመ የተባለው የግንባታ የውል ስምምነት ቀርቦ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ስምምነት ቀርቦ ይዘቱና መንፈሱ ሊታይና የቼኩን መሰጠት ምክንያት ማጣራት የሚያስችል ነው፡፡ ተጠሪ ቼኩ የተሰጠው በቼክነቱ እንዲከፈል እንጂ ሁኔታ ላይ /ከአመልካች የውል ግዴታ መወጣት ጋር እየታየ የሚከፈል አይደለም/ የተመሰረተው አይደለም የሚል ክርክር በማንሳት በአመልካች በኩል እንዲፈጸም በውሉ የተቀመጠውን ግዴታ አመልካቹ ያለመወጣቱን እንዲያስረዳ አልተደረገም፡፡ የአመልካች ክርክር የግንባታ ውል ስምምነቱ እና የሲቪል ስራ ፕሮጀክቶች ግንባታ መደበኛ ሁኔታዎች /fidic/ ጋርም ተዛምዶ የማይታይበት ምክንያት የሌለ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከእነዚህ ሁኔታዎች አንጻር ያጣሩት አግባብ ያለመኖሩን ከክርክር ሂደት ተገንዝበናል፡፡

በንግድ ህግ ቁ.717/1/ እንደተመለከተው ዕዳ ከፋዩ ሰነዱን /ቼኩን/ በያዘው ሰው ላይ በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ የተመሰረቱት ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ መቃወሚያ ማቅረብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይችላል፡፡ በያዝነው ጉዳይም ከላይ እንደተገለፀው የግንባታ ውሉ የአመልካች እና የተጠሪ የግል ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡

የግንባታ ውል ስምምነት ደግሞ ሁለቱም ወገኖች በውሉ ያገኙትን መብት እና ከውሉ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ የያዘ ሰነድ ስለሆነ የገንዘብ ክፍያ የሚጠይቀው ተዋዋይ ወገን ገንዘቡን ያገኝ ዘንድ የበኩሉን ግዴታ ሊወጣ ይገባል፡፡ ግራ ቀኙ በውሉ ያላቸው ግዴታ ታይቶና ግዴታውን የተወጣ ወገን መኖር ያለመኖሩ በማስረጃ ከነጠረ በኃላ የቼኩ ክፍያ እልባት ይገባል እንጂ ይኼው ታልፎ ተጠሪ ቼክን መሰረት አድርጎ ክስ በማቅረቡ ብቻ የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ ሳይመዘን ውድቅ የሚሆንበትን አግባብ የን/ህ/ቁጥር 717፣732፣827፣828 እና 854 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አያሳይም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ለቼኩ መሰጠት መሰረት የሆነውን ውል እና ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለውን ህግ ሳይመለከቱና በተገቢው የክርክር አመራር ስርዓት ፍሬ ነገሩን ሳያጣሩ ዳኝነት መስጠታቸው ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡፡

አመልካች ለመከላከል ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን ግንኙነት እና ቼኩ የተወሰደበትን ምክንያት መሰረት አድርጎ ያቀረበው ክርክር ውድቅ ሆኖ ለገንዘብ ጥያቄው ኃላፊ መባሉ የአመልካች ማስረጃዎችን የስር ፍርድ ቤት ሳይሰማና የሰነድ ማስረጃዎችንም በሕጉ አግባብ ዝርዝር ምክንያት ሳይሰጥ ታልፎ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሕግ አግባብ የቀረበን ክርክርና የተቆጠረ ማስረጃ ደግሞ ያለ ሕጋዊ ምክንያት ሳይሰማና ሳይመዘን በዝምታ የሚታለፍበት፣ አግባብነት የሌለው ሕግ ተጠቅሶ ውድቅ የሚሆንበት፣ የሰነድ ማስረጃው ቀርቦ ደግሞ ይዘቱ ሳይታይ በደፈናው ውድቅ የሚደረግበት የማስረጃ አቀባበል እና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትና ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የክርክሩ ፍሬ ነገሮች አግባብነት ባላቸውና በሕጉ አግባብ በተቆጠሩ የተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ በፍርድ ቤቱ አነሳሽነትም ከሚመለከታቸው አካላት በሚቀርቡት ማስረጃዎች በተገቢው መንገድ ሳይጣሩ ዳኝነት መስጠት የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የማይቀበለው ጉዳይ ሲሆን የክርክሩ አካሄድ ሳይሟላ የሚሰጥ ዳኝነት ደግሞ በውጤቱ የተከራከሪ ወገኖችን የመደመጥ መብት እጅጉን የሚጎዳ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ሲጠቃለልም፡-

1. በአመልካችና በተጠሪ መካከል መስከረም 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተፈጸመ የኮንስትራክሽን ንዑስ ስራ ተቋራጭነት ውል ስምምነት ስለ አከራካሪው ቼክ የሚያሳየው ነጥብ ምን እንደሆነ፣
2. ቼኩ ከዚሁ ውል በመነጨ ስምምነት ለተጠሪ በአመልካች የተሰጠ ከሆነ በአመልካችና በተጠሪ መካከል መስከረም 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተፈፀመ የኮንስትራክሽን ንዑስ ስራ ተቋራጭነት ውል ስምምነት መሰረት አመልካች የሰራው ስራ መኖር ያለመኖር፣
3. ውሉ የተቋረጠበት ምክንያትና ውሉን ያቋረጠው ወገን የትኛው እንደሆነ ሕጋዊ ውጤቱ ምን እንደሆነ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. ተጠሪ በአመልካች በተሰራው ንዑስ የኮንስትራክሽን ስራ ከስራው ባለቤት ያገኘው ክፍያ መኖር ያለመኖሩና ካለም የክፍያው መጠን ምን ያህል እንደሆነ፣ ሌሎች ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነትና አስፈላጊነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች በአመልካች በተቆጠሩት ማስረጃዎች፣ ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 136 በሚመድባቸው ባለሙያዎች (በተለይ በአመልካች የተሰራው ስራ መኖር ያለመኖርና ተሰርቶ ከሆነም የስራው ዋጋ መጠን)፣ አመልካች ጉዳዩን ያስረዳሉ በማለት ያቀረቧቸው ሰነዶች ትክክለኛ መሆናቸውን፣ ይዘታቸው ምንን እንደሚገልጽና ለጉዳዩ ያላቸውን የማስረጃነት ዋጋ በዝርዝር በመመልከት አስፈላጊ ሲሆን ሌሎች ማስረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ፍርድ ቤቱ ራሱ በማስቀረብ ጭምር ጉዳዩን በተገቢው መንገድ አጣርቶና የፍሬ ነገሩን ክርክር አሚልቶ፣ በሕጉ የተመለከተውን የፍርድ አፃፃፍ ስርዓት በመከተል ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መመለሱ ስነ ስርዓታዊ ሆኖ አግኝተናል። በዚህም ምክንያት ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 200800 የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117557 ነሐሴ 16 ቀን 2004 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል።
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 200800 ክርክሩን እንዲቀጥል በማድረግ በፍርድ ሐተታው ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ ብቻ የአመልካችን ማስረጃዎችን በመስማትና በተገቢው መንገድ ሁሉ ፍርድ ቤቱ በሚያስቀርባቸው ማስረጃዎች ጭምር በማጣራት ጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል። ይፃፍ።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሰሪና ሰራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90570

ጥር 27 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓለ. መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአቶ ፍፁም አስታጥቄ ወኪል አቶ ታምራት አስታጥቄ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስራ ክርክር ችሎት በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ በአመልካች የቀረበው የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ፡- ከሣሽ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በኘሮጀክት አስተባባሪነት የስራ መደብ ላይ በ1/3/2001 ዓ.ም ተቀጥረው እያገለገሉ ሳሉ ተከሳሹ ድርጅት ያለአግባብ የስራ ውላቸውን ያቋረጡ መሆኑን ጠቅሰው ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲፈፀምላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ተከሳሹም በበኩሉ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ የስራ ውሉ በተከሳሽ አነሳሽነት ሊቋረጥ የቻለው በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ሆነው ድጋፍ የሚደረግላቸውንና በወሲብ ጥቃት ምክንያት ለስነ-ልቦና ቀውስ የተጋለጡ ህፃናትን ከሳሽ ያለተከሳሽ ድርጅት እውቅናና ፈቃድ በእንግዶች እንዲጐበኙ፣ እንዲጨፍሩ እና ፎቶግራፍ በእንግዶች እንዲነሱ በማድረጉና ይህ ድርጊትም ከከሳሹ የስራ ሙያ ውጭ ከመሆኑም በላይ የድርጅቱን የስራ ደንብም የጣሰ በመሆኑ ስንብቱ ህጉን ተከትሎ የተፈፀመ በመሆኑ ለከሳሹ የሚፈፀም ክፍያ የለም ሲሉ በመከራከር መልሱን ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ቃል ሰምቶ ጉዳዩንም ከቀረበው ማስረጃ እና ህጉ ጋር አገናዝቦ ተመልክቶ መመርመሩን ከገለፀ በኋላ ምንም እንኳ ጉብኝቱን ያለተከሳሹ እውቅና የፈቀዱ ስለመሆኑ እና እንዲሁም እነኝህ የወሲባዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑት ህፃናትን ያለጥንቃቄ እንዲጐበኙ ማድረግ፣ ከእንግዶቹ ጋር እንዲጨፍሩ ማድረግ እና ፎቶ ግራፍ እንዲነሱ ማድረግ በህፃናቱ ስነ-ልቦና ጤንነት ጋር በተያያዘ ችግር የሚፈጥርባቸው ስለመሆኑ በባለሙያ ምስክርነት ቃል ጭምር የተረጋገጠ ቢሆንም ሆኖም ግን ከሳሹ ጉብኝቱን የፈቀዱት ህፃናቱ ከእንግዶቹ ጋር እንዲጨፍሩና ፎቶግራፍ እንዲነሱ ጭምር ስለመሆኑ ባለመረጋገጡ እና እንዲህ ከሆነ ደግሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሳሽ ድርጊቱን በህፃናቱ ህይወት ላይ ጉዳት እንዲከተል ሆነ ብሎ የፈፀመው ነው ለማለት ስለማይቻል እና በአጠቃላይ የከሳሽ ስራ ውል የተቋረጠው በህጉ መሠረት ባለመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት ከወሰነ በኋላ የካሳ ክፍያ ብር 33,030 /ሠላሳ ሦስት ሺህ ሠላሳ ብር/፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 11,010/አሥራ አንድ ሺህ አሥር ብር/ እና ከወጪና ኪሳራ ብር 400/አራት መቶ ብር/ ጋር ተከሳሹ ለከሳሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡
በአሁኑ ተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች ከድርጅቱ እውቅና ውጭ የወሲብ ተጠቂ የሆኑት ህፃናት በእንግዶች እንዲጐበኙ ማድረጉ መረጋገጡን በመግለፅና ይህ በአመልካች የተፈፀመው ድርጊትም በድርጅቱ የተቀመጠውን የአሰራር ደንብ መጣስ ብቻ ሳይሆን ሙያው የሚጠይቀውን ልዩ ጥንቃቄንም አለማድረጉን የሚያስረዳ በመሆኑ እና ጥፋቱም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሠ) ስር የሚያስጠይቅ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ይሄንኑ ባለመገንዘብ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት መወሰኑ አለአግባብ ነው ሲል የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1/ መሠረት በመሻር ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ይፅናልኝ የሚል ይዘት ያለው አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን የግራ ቀኙን የሰበር ፅሑፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የሰበር አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የተጠሪ ድርጅት ከተቋቋመበት ዋና ዋና አላማዎች መካከል አንዱ እነዚሁኑ የወሲብ ጥቃት የደረሰባቸውን ህፃናት መንከባከብ እና በጥቃቱ ምክንያት ከደረሰባቸው የስነ-ልቦና ቀውስ እንዲድኑ እርዳታ ማድረግ መሆኑን፣ አመልካችም ይሄንኑ አላማ ለማስፈፀም ተቀጥሮ እነዚሁ ህፃናት ተጠልለው የሚገኙበት ማዕከል ኘሮጀክት አስተባባሪ መሆኑን፣ በዚህም መሠረት የህፃናቱን ጤንነት ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ ከስነ-ልቦና ቀውሱ እንዲያገግሙ የበኩሉን ሚና መወጣት ሚስጥራቸውን መጠበቅ እና እንዲጠበቅ ወይም እንዳይጋለጥ ለማድረግ በስራ ውሉ እና በድርጅቱ አሰራር ስርዓት መሠረት ከፍተኛ ግዴታ የተጣለበት መሆኑን፣ ሆኖም ግን አመልካች ከተጠሪ ድርጅት እውቅናና ፈቃድ ውጭ ህፃናቱ ያለጥንቃቄ በእንግዶች እንዲጐበኙ፣ እንዲጨፍሩ እና በእንግዶቹ ፎቶግራፍ እንዲነሱ ማድረጉን በሰውና ሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን፣ ይህ ድርጊትም የህፃናቱ ሚስጥር እንዲጋለጥ የሚያደርግ መሆኑንና ሚስጥራቸው በተጋለጠ ቁጥር ደግሞ በወሲብ ጥቃቱ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የደረሰባቸውን የስነ-ልቦና ቀውስ በማባባስ ከፍተኛ የጤንነት ችግር ውስጥ እንዲገቡና የወደፊት ማህበራዊ ህይወታቸውም እንዲጐዳ የሚያደርግ ስለመሆኑ በተጠሪ ድርጅት በኩል ተቆጥረው በስር ፍ/ቤት ቀርበው በተሰሙት የባለሙያዎች ምስክርነት ቃል መረጋገጡን ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል አንድ ሠራተኛ ደግሞ በስራ ውሉ እና በስራ ደንቡ መሠረት በአሰሪ የተሰጠውን ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታ እንዳለበት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አንቀጽ 13(2) ስር ተመልክቶ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የዚሁኑ አዋጅ ድንጋጌዎችን፣ የህብረት ስምምነትን፣ የስራ ደንብ እና በህግ መሠረት የሚተላለፉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን የማክበር ግዴታም እንዳለበት በንዑስ አንቀጽ 7 ስር ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች እነዚህ የወሲብ ተጠቂ የሆኑትን ህፃናት ጤንነት የመጠበቅ፣ የመንከባከብ፣ ከደረሰባቸው የስነ-ልቦና ቀውስ እንዲድኑ የበኩሉን እገዛ ማድረግ፣ ሚስጥራቸውንም የመጠበቅ እና እንዳይጋለጥ የማድረግ ግዴታ የተጣለበት ሆኖ ሳለ ያለድርጅቱ ፈቃድና እውቅና ውጭ ህፃናቱ ጥንቃቄ በጐደለ ሁኔታ በውጭ እንግዶች እንዲጐበኙ እና ፎቶግራፍም በእንግዶች እንዲነሱ በመፍቀድ ሚስጥራቸው እንዲጋለጥ ማድረጉ በአዋጁ አንቀጽ 13(2) እና 13(7) መሠረት በስራ ውሉ እና በድርጅቱ የአሠራር ስርዓት መሠረት እንዲፈፀም የተጣለበትን ግዴታ አለመወጣቱንና መጣሱን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ድርጊትም በመካከላቸው የተደረገውን የስራ ውሉን መሠረታዊ ስምምነት የሚጥስ በመሆኑ ተጠሪም ይህንኑ መነሻ በማድረግ የስራ ውሉን ማቋረጡ የአዋጁን አንቀጽ 13(2) እና 13(7) ድንጋጌዎች ይዘት፣ አላማ እና መንፈስ ያገናዘበ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘንም፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ለጉዳዩ በቀጥታ አግባብነት የሌለውን የአዋጁን አንቀጽ 27(1)(ሠ) ድንጋጌን ጠቅሶ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ሊስተካከልና ሊታረም የሚገባ ቢሆንም ሆኖም ግን በውጤት ደረጃ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የበታች ፍ/ቤቱን ውሳኔ ሽሮ በሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስላላገኘን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 95631 በ11/3/2005 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሸሯል፡፡
2. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 129923 በ20/07/2005 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት በተሰወጠ ምክንያት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
3. የሰበር ወጪና ኪሳራን ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡
የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፣

ዘ/ቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92410

ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ቻይና ሀይ ዌይ ግሩፕ ሊሚትድ- የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-አቶ ውብሸት እንግዳው - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡የክሱም ይዘት ባጭሩ ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከ30/08/2002 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 15/02/2005 ዓ.ም. ድረስ በወር የተጣራ ደመወዝ ብር 25,000 እያገኙ ሲሰሩ ቆይተው የስራ ውላቸው ሲቋረጥ ደመወዝ እና የስራ ስንብት ክፍያ የተፈጸመላቸው ቢሆንም የዓመት ዕረፍት፣የሳምንት ዕረፍት እና የሕዝብ በዓላት ክፍያ ያልተፈጸመላቸው በመሆኑ ይኸው ክፍያ ታስቦ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ ባቀረበው የመቃወሚያና የፍሬነገር መልስ ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ከሳሽ የስራ ውላቸውን በፈቃዳቸው ባቋረጡበት ጊዜ የሚገባቸውን ክፍያ በሙሉ ተሳስበው የተቀበሉ መሆኑን፣አሁን ጥያቄ ያቀረበባቸውን ክፍያዎች በወቅቱ መጠየቅ የሚችሉ ሆኖ እያለ ክፍያዎችን በመከፋፈል አሁን ያቀረቡት ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.216 መሰረት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣የዓመት ዕረፍታቸውን የተጠቀሙ መሆኑን፣የሳምንት ዕረፍት እና የሕዝብ በዓላት ክፍያ የየትኛው ዓመት እንደሆነና እና በማን ትዕዛዝ እንደሰሩ በክሳቸው ለይተው ያልገለጹ መሆኑን፣በሳምንት ዕረፍት እና በሕዝብ በዓላት ጊዜ ስራ የሚሰራ ከሆነ ክፍያ የሚፈጸመው ከየወሩ ደመወዝ ጋር ተጨምሮ በዚያው በተሰራበት ወር በመሆኑ ያልተከፈላቸው ክፍያ የሌለ መሆኑን፣ከሳሽ ቀደም ሲል ከተፈጸመላቸው ውጪ ከአሰሪው የሚጠይቁት ሌላ ክፍያ አለመኖሩን በማረጋገጥ ስምምነት ከፈረሙ በኋላ አሁን ያቀረቡት የተጨማሪ ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቱም የዳኝነት ጥያቄ ከቀረበበት ክፍያ ውስጥ በይርጋ ቀሪ የሚደረገውን መጠን በመለየት፣በቀሪው መጠን ላይ በተከሳሽ የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ባለመቀበል እና ሰራተኛው መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 25(1) መሰረት ሕጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን ገልጾ በዚህ ረገድ ከተከሳሽ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ስራው የመንገድ ስራ በመሆኑ ቻይናውያን የፕሮጀክቱ ኃላፊዎች በሚሰጡት የቃል ትዕዛዝ መሰረት ስራው ከሳምንት እስከ ሳምንት ይሰራ የነበረ መሆኑ እና የዓመት ዕረፍትም የሚጠየቀው በጽሁፍ መሆኑ በከሳሽ ምስክሮች መረጋገጡን እና በአንዳኑ ከሳሽ በትርፍ ሰዓት እና በበዓላት ቀናት ስላለመስራታቸው ወይም ለስራው ክፍያ የተፈጸመላቸው ስለመሆኑ እንዲሁም ከሳሽ የዓመት ዕረፍት የወሰዱ ስለመሆኑ የተከሳሽ ምስክሮች ማስረዳት እንዳልቻሉ ገልጾ የ13 ቀናት የሳምንት ዕረፍት እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 21,663 እና የ29 ቀናት የዓመት ዕረፍት ክፍያ ብር 24,167 በድምሩ ብር 45,830 ከ10% የጠበቃ አበል ጋር ተከሳሽ ድርጅት ለከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን ሳይቀበለው በመቅረቱ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው ከአመልካች የሚጠይቀው ቀሪ ክፍያ አለመኖሩን ተስማምቶ የፈረመ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በዚህ ረገድ የአመልካች መቃወሚያ ውድቅ ተደርጎ ለተጠሪው ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፈለው የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቹ የፈረሙት ስምምነት ስራቸውን በለቀቁበት ጊዜ ቀሪ የደመወዝ ክፍያ፣ የስራ ስንብት እና የካሳ ክፍያ በድምሩ ብር 60,000 የተከፈላቸው መሆኑ እና ከዚህ በኋላ በአሰሪው ላይ የሚያቀርቡት ሌላ የይገባኛል ጥያቄ አለመኖሩ የተገለጸበት ነው፡፡የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን መቃወሚያ ሳይቀበል የቀረው ተዋዋይ ወገኖች የስራ ውላቸውን በስምምነት ማቋረጥ እንደሚችሉ እና ሆኖም ግን ሰራተኛው በሕግ የተሰጠውን መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት የህግ ውጤት እንደማይኖረው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 25(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ ነው፡፡የትርፍ ሰዓት፣የበዓላት ቀናት እና የዓመት ዕረፍት ክፍያ ደግሞ ለሰራተኛው በሕግ የተጠበቁ መብቶች ስለመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 68(1)፣75(1) እና 77(5) ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቶአል፡፡በመሰረቱ ተጠሪው የፈረሙት ስምምነት ቀሪ የደመወዝ ክፍያ፣ የስራ ስንብት እና የካሳ ክፍያ በድምሩ ብር 60,000 የተከፈላቸው መሆኑን የሚገልጽ ከመሆኑ ውጪ የትርፍ ሰዓት፣የሕዝብ በዓላት እና የዓመት ዕረፍት ክፍያዎችን ጨምሮ ከአሰሪው የሚገባቸውን ክፍያዎች በሙሉ የተቀበሉ ስለመሆኑ ወይም እነዚህን ክፍያዎች ለመጠየቅ የሚያስችል የስራ ሁኔታ ያልነበረ ስለመሆኑ የተገለፀበት አይደለም፡፡በመሆኑም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ረገድ ከአመልካች የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ ሊነቀፍ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ግን ለተጠሪው የተወሰነው የዓመት ዕረፍት ክፍያ መጠን የግራ ቀኙን ክርክር እና የአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 77(1) የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑ መመርመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ በስራው ላይ የቆዩት ከ30/08/2002 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 15/02/2005 ዓ.ም. ድረስ መሆኑን በክስ ማመልከቻቸው ላይ የገለጹ ሲሆን ይህ ጊዜም 2 ዓመት ከ 6 ወር ከ15 ቀን ነው፡፡በመሰረቱ ከሰራተኛ የሚሰጠው የዓመት ዕረፍት ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት 14 ቀን መሆኑ እና ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ አገልግሎት በ14 ቀን ላይ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአገልግሎት ዓመት 1 የስራ ቀን እየታከለ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 77(1) (ሀ) እና(ለ) ስር ተመልክቷል፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ በግልጽ ላቀረበው ክርክር ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ላይ በዝምታ ከማለፍ በስተቀር የሰጡት ማስተባበያ የለም፡፡በመሆኑም ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የዓመት ዕረፍት ክፍያ የ15 ቀን ተኩል ሆኖ እያለ በ29 ቀን ታስቦ እንዲከፈል መደረጉ ከግራ ቀኙ ክርክር እና በሕጉ ከተመለከተው ውጪ ሆኖ በመገኘቱ በዚህ መጠን ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 82043 በ11/10/2003 ዓ.ም. የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.135827 በ18/11/2005ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ//ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ሰራተኛው መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 25(1) መሰረት ሕጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን በመግለጽና በዚህ ረገድ ከአመልካች የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የሳምንት ዕረፍት፣የሕዝብ በዓላት እና የዓመት ዕረፍት ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፈል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ስ/ሥ/ሕ.ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ከላይ በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ለተጠሪው የሚከፈለው የዓመት ዕረፍት ክፍያ መጠን የ29 ቀን ነው በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
4. ለተጠሪው ሊከፈል የሚገባው የዓመት ዕረፍት ክፍያ የ15 ቀን ተኩል ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. ለተጠሪው ሊከፈል የሚገባው የሳምንት ዕረፍት፣የትርፍ ሰዓት እና የዓመት ዕረፍት ክፍያ በድምሩ ብር 34,579.68(ሰላሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ከስድሳ ስምንት ሳንቲም) ከ10% የጠበቃ አበል ጋር ነው በማለት ወስነናል፡፡

6. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.84794 የተጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ29/11/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም ዕግድ ተነስቷል፡፡
7. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
8. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
9. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97512

ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ምህረት አለነ ገረመው - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ስራ ድርጅት - ነ/ፈጅ ፈለቀ ካሣሁን ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የቀረበውን የአካሉ ጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡,-አመልካች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በጋራዥ ኃላፊነት የስራ መደብ ላይ ተቀጥረው በወር ብር 3,460.00(ሶስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ ብር) እየተከፈላቸው ሲሰሩ የኮድ ቁጥሩ 3-08573 በሆነው የተጠሪ ድርጅት ተሽከርካሪ ለስራ እየተጓዙ ሚያዚያ 05 ቀን 2003 ዓ/ም በደረሰው የመኪና አደጋ በአካላቸው ላይ ጉዳት መድረሱንና በሕክምናም በአካላቸው ላይ የደረሰው የጉዳት መጠን የተረጋገጠ መሆኑን፣በደረሰው የአካል ጉዳት መጠን መሰረት ሊከፈላቸው የሚገባው ብር 171,600.00 (አንድ መቶ ሰባ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ብር) ሁኖ እያለ ተጠሪ ድርጅት ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጋር ባለው የኢንሹራንስ ውል መሰረት ከፍተኛው የመድን ሽፋን ብር 120,000.00 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) መሰረት ተደርጎና ከጉዳት መጠኑ ጋር ተሰልቶ ብር 36,000.00 (ሰላሳ ስድስት ሺህ ብር) ከሕግና ከድርጅቱ ህብረት ስምምነት ውጪ ክፍሉ ቀሪውን ያልከፈላቸው መሆኑን ጠቅሰው ብር 171,600.00 እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም፡- አመልካች የድርጅቱ ሰራተኛ በስራ ላይ እያሉ በአካላቸው ላይ ጉዳት መድረሱን ሳይክድ የአካል ጉዳት ካሳ ለአመልካች የተከፈለው ድርጅቱ ባለው የመድን ሽፋን መሆኑን፤ የመድን ሽፋን ላላቸው የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሰራተኞች በስራ ላይ ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሳ የሚከፈለው በመድን ፖሊሲው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(1) ድንጋጌ መጠቀሱን ገልጾ አመልካች በዚሁ አግባብ ብር 36,000.00 የተከፈላቸው በመሆኑ ቀሪ የሚከፈላቸው የአካል ጉዳት ካሳ ክፍያ የለም ሲል ተከራክሯል፡፡የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከተጠሪ ድርጅት ጋር ያለውን የመድን ፖሊሲውን እንዲያቀርብለት አድርጎ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ብር 36,000.00 የተከፈላቸው በመድን ፖሊሲው መሰረት በመሆኑና በዚህ አግባብ የአካል ጉዳት ካሳ የተከፈለው ሰራተኛ ደግሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዋጁ አንቀጽ 109(1) መሰረት አሰሪውን ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ የለም በሚል ድምዳሜ የአመልካችን ቀሪ የአካል ጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄን ውድቅ አድርጎ ወስኖታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በአመልካች ላይ በስራ ላይ ለደረሰው የ30% ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት በአዋጁ ሊከፍል የሚገባው የካሳ መጠን ብር 62,280.00(ስልሳ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ብር) ሁኖ እያለ አመልካች ተጠሪ ብር 36,000.00 በመድን ፖሊሲው መሰረት ተከፍሏል በማለት ቀሪውን ብር 26,280.00 ሊከፍል አይገባም ተብሎ መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109(3(ሀ)) እና ስራ ላይ ያለውን የድርጅቱን የህብረት ስምምነት አንቀጽ 25(2) ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ይገባል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት የድርጅቱ ነገረ ፈጅ ቀርበው በጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡በመልሳቸው ላይም ለአመልካች የአካል ጉዳት ካሳ የተከፈለው በሕጉ አግባብ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡እንደመረመርነውም አመልካች በደረሰባቸው የአካል ጉዳት ምክንያት የተከፈለው ካሳ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109(3(ሀ)) መሰረት የተሰላ አይደለም በማለት ያቀረበው ክስ የስር ፍርድ ቤቶች ከኢንሹራንስ የጉዳት ካሳ አከፋፈል አንጻር ብቻ በማየት ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካች ላይ የአካል ጉዳቱ በስራ ላይ መድረሱና የጉዳቱ መጠንም 30% ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት መሆኑን ግራ ቀኙን ያላከራከረ ነጥብ መሆኑን፣ግራ ቀኙን የሚያከራክረው የካሳው መጠን መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች በአካላቸው የደረሰውን የጉዳት መጠን መሰረት በማድረግ ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁትና የካሳውን መጠን ለማስላት መሰረት ያደረጉት በአካላቸው ደረሰ የተባለውን 30% ጉዳት መጠን መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 96(1) መሰረት በስራ ቦታ ላይ ለሚደርስ የአካል ጉዳት የካሳ መጠን የሚሰላበት አግባብን ሕጉ በአንቀፅ 109(3) ደንግጎ እናገኛለን፡፡በዚህም መሰረት በሰራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ከሆነ የሰራተኛው የአመት ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ የሚገኘው ውጤት እንዲሁም ሰራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ከዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መጠን በታች ከሆነ ከአካል ጉዳት ደረጃው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ እንደሚከፈለው የተጠቀሰው ድንጋጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይገልፃል፡፡በአመልካች ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት መሆኑን (30%) የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

በአንድ ሠራተኛ ላይ የሚደርሱት የጉዳት መጠን ደረጃዎች፡-ጊዜያዊ የአካል ጉዳት፣ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት፣ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት እና ሞት መሆናቸው በሕጉ ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ ይህን ደረጃ በመመሪያ በጉዳት መወሰኛ ሠንጠረዥ የሚያወጣው የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር መሆኑና ደረጃውን የሚያወጣውም ለዘላቂ ከፊል እና ሙሉ የአካል ጉዳት ብቻ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 102(1) ስር ተመለክቷል፡፡ በጊዜያዊ የአካል ጉዳት ሠራተኛው ቀድሞ የነበረውን የመሥራት ችሎታ መልሶ ስለሚያገኝ፤ ሞትም ቢሆን የጉዳቱ መጠን በራሱ የተገለጠ በመሆኑ ሚኒስትሩ ለእነዚህ ጉዳቶች ደረጃን የማይወሰን መሆኑን የሕጉ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ሚኒስትሩ ደረጃቸውን ለሚወስንላቸው ዘላቂ ሙሉ ወይም ከፊል ጉዳቶች ግን የጉዳቶቹ መጠን ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ጉዳቱ በደረሰ በአስራ ሁለት ወራት ውስጥ በተቻለ መጠን የጉዳቱን መጠን መወሰን ከሚኖርበት የህክምና ቦርድ ማስረጃ ማግኘት እንደሚያስፈልግ የአዋጁ አንቀጽ 102 (2) ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለውም አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ ጉዳት ሲደርስበትና ጉዳቱ ዘላቂ ሁኖ ጉዳቱ ያስከተለው የመስራት ኃይል ቅነሳ በተገቢው ባለሙያ ተረጋግጦ በደረሰው የጉዳት መጠን ሰራተኛው እንዲካስ ማድረግ የሕጉ ፍላጎት መሆኑን ነው፡፡የአዋጁ አንቀጽ 109(3(ሀ) ድንጋጌ ሲታይም ከስራ ላይ ለሚመጣ ጉዳት ምክንያት ዘላቂና ሙሉ የአካል ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ ሊያገኘው የሚችለው ከፍተኛው ክፍያ የሰራተኛው የአመት ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ የሚገኘው የብር መጠን መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ይሁን እንጂ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ከሆነ ሰራተኛው ሊያገኝ የሚገባው የካሳ ክፍያ መጠን በሰራተኛው አካል ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠን ደረጃ መሰረት አድርጎ የሚሰላ መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡

ሕጉ የካሳ መጠኑ የሚሰላበትን አግባብ ከመደንገጉም በተጨማሪም ሰራተኛው የአካል ጉዳት ክፍያ ተከፋይ የማይሆንባቸው አጋጣሚዎችም እንዳሉ ያሳያል፡፡ይኼውም፡ አንድ ሰራተኛ ሲሰራ የነበረው በመንግስት የልማት ድርጅት ሁኖ በመንግስት የጡረታ ሕግ የታቀፈ ከሆነ ወይም አሰሪው በገባለት የመድህን ዋስትና ተጠቃሚ ከሆነ በዘላቂ የአካል ጉዳት ክፍያ እንደማያገኝ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109(1) ስር የደነገገ ሲሆን የዚህ የድንጋጌው መሰረታዊ አላማም ሰራተኛው በደረሰበት ከባድ የአካል ጉዳት ምክንያት ከጡረታ ከወጣ ወዲያውኑ በመንግስት የጡረታ ክፍያ ስርዓት የሚታቀፍ በመሆኑ ከአንድ ምንጭ ሁለት ጊዜ የመካስ ሁኔታ እንዳይኖር ለመከላከል ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ እንዲሁም አንድ አሰሪ ለሰራተኞቹ በስራ ላይ ለሚደርስ አደጋ ዋስትና ገብቶላቸው የነበረ መሆኑና በፖሊሲው መሰረት ስለደረሰበት ጉዳት ሰራተኛው የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ አሰሪው የጉዳት ካሳ ለመክፈል የሚገደድበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሕጉ ይዘትና መንፈስ ያስረዳል፡፡ይሁን እንጂ ይህ የህጉ መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ሲታይ ሰራተኛው ተገቢውን ካሳ በደረሰው የአካል ጉዳት መጠን አንባር እየታዬ ሊያገኝ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም ቀጥሎ መታየት ያለበት ቁልፍ ጥያቄ ሰራተኛው በሕጉ የተጠበቀለትን የካሳ መጠን አሰሪው በመድን ፖሊሲው ሙሉ በሙሉ ሳይሸፈን እንዲቀር አድርጎ ቢገኝ የመድን ፖሊሲው መኖሩ ብቻውን ሰራተኛው በመድን ፖሊሲው ስሌት መሰረት ተሰልቶ የሚመጣውን ካሳ ብቻ ተከፍሎ እንዲሄድ ያስገድደዋል? ወይስ አያስገድደውም? የሚለው ነው፡፡በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(1) ስር የሰፈረው ድንጋጌ ሙሉ ይዘት ሲታይም "በሕብረት ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ ለሚሸፈኑ የመንግስት ድርጅቶች ሰራተኞች የሚሰጠው የጉዳት ካሳ አሰሪው በገባበት የመድህ ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ሕግ መሰረት ይሆናል፡፡ድርጅቱ መድህን ያልገባ ከሆነ በመንግስት የጡረታ ሕግ ለሚሸፈኑ ሰራተኞች የመንግስት የጡረታ ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡"በሚል የተቀመጠ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መረዳት የሚቻለው አንድ ሰራተኛ በመንግስት የጡረታ ሕግ የታቀፈ ከሆነ ወይም አሰሪው በገባለት የመድህን ዋስትና ተጠቃሚ ከሆነ የጉዳት ካሳውን አሰሪው እንዲከፍል የማይገደድ መሆኑን ነው፡፡ይህ ድምዳሜ የሚያዘው ግን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(3) ስር የተመለከተውን የካሳ ስሌት መሰረት አድርጎ የኢንሹራንስ ሽፋኑ ለሰራተኛው ካሳውን ለመክፈል የሚያስችል ሁኖ ሲገኝ ነው፡፡ይህ ካልሆነ ሰራተኛው በስራው ላይ ለደረሰበት ካሳ ተገቢውንና በሕጉ የተቀመጠለትን ካሳ አግኝቷል ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ከዚህ ውጪ አሰሪው የገባው የኢንሹራንስ ሽፋን ሰራተኛው በሕጉ በተመለከተው ስሌት መሰረት የሚያገኘውን የአካል ጉዳት ካሳ የሚቀንስ መሆኑ ቢረጋገጥም አሰሪው የመድን ሽፋን በመግባቱ ብቻ የጉዳት ካሳውን እንዲከፍል አይጠበቅበትም ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ ሁኖ አግኝተናል፡፡በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(1) መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅት ለሰራተኞቹ የገባው የአካል ጉዳት ዋስትና ሽፋን መኖሩ ድርጅቱን ተጠያቂ የማያደርገው ድርጅቱ ሰራተኛው በአዋጁ አንቀጽ 109(3) በተመለከተው ስሌት መሰረት ሊያገኝ የሚገባውን የአካል ጉዳት ለማስገኘት የሚያስችል የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንጂ በሕጉ ጥበቃ ከተደረገው የካሳ መጠን ያነሰ የሚያስገኝ የመድን ሽፋን ገብቶ በተገኘ ጊዜም ጭምር አይደለም፡፡ድርጅቱ በሕጉ ከተመለከተው የካሳ መጠን ያነሰ የኢንሹራንስ ሽፋን ገብቶ ሲገኝ ለቀሪው የጉዳት ካሳ ኃላፊነቱን የማይወስድበት ምክንያት የለም፡፡ግራ ቀኙ ለክርክራቸው መሰረት ያደረጉት የድርጅቱ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 25(2) ሲታይም በድርጅቱ ስራ ምክንያት አደጋ ለደረሰበት ሰራተኛ ድርጅቱ በገባው የኢንሹራንስ ፖሊሲ መሰረት ያሳክማል፣ደመወዙንም ይከፍላል፣ሆኖም መስራት የማይችል ከሆነ ስራው ላይ ባለው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ስለዚህ ጉዳይ የተደነገጉትን እና በጡረታ አዋጅ መሰረት መብቱ ይጠበቅለታል በሚል የሚያስቀምጥ ከመሆኑ ውጪ በስራ ላይ ለደረሰ የአካል ጉዳት ካሳ የሚከፍልበትን ስሌትና የአሰሪውን ከኃላፊነት ነጻ የሚሆንበትን አግባብ የማያስቀምጥ ሁኖ አግኝተናል፡፡ከሁሉም በላይ የሕጉ የጉዳት ካሳና ኃላፊነት ድንጋጌዎች የዝቅተኛ የስራ ሁኔታዎች (minimum labour conditions) አካል ናቸው ተብሎ የሚታሰቡ በመሆኑና ሕጉም የሚያስቀምጠው ዝቅተኛውን ጥበቃ ሁኖ በሕጉ ከተቀመጠው ሁኔታ በላይ ግን በህብረት ስምምነት ወይም በውል ሊወሰኑ የሚችሉ መብትና ጥቅሞች ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚታመኑ ሁኖ ሕጉ ካስቀመጠው ዝቅተኛው ሁኔታ በሕብረት ስምምነት መቀነስ የማይቻል መሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዋጁ አንቀጽ 134(1) በግልጽ የተቀመጠ ከመሆኑ ጋር ሁሉ ተዳምሮ ሲታይ ተጠሪ የሕብረት ስምምነቱን መሰረት አድርጎ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝበትን ህጋዊ አግባብ አላገኘንም፡፡

ከላይ ከተመለከቱት የሕግ ማእቀፎች አንፃር የአመልካችን ጥያቄ ስንመለከተው አመልካች 30% ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ ተጠሪም ማስተባበያ ክርክር ያቀረበበት ጉዳይ አይደለም፡፡እንዲህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(3(ሀ)) በአመልካች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት ሊከፍል የሚገባው ካሳ የወር ደመወዛቸው × በአስራ ሁለት ወራት × አምስት አመታት × የመስራት ኃይል ቅነሳ ተባዝቶ የሚመጣው የገንዘብ መጠን ነው፡፡በዚህ የሕጉ ስሌት መሰረት ለአመልካች ሊከፍል የሚገባው የአካል ጉዳት ካሳ መጠን፡ 3460.00×12×5×30%×=62,280.00 ሁኖ አግኝተናል፡፡ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ተጠሪ ድርጅት በገባው የመድን ሽፋን መሰረት ብር 36,000.00 በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 109(1) መሰረት ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል የሚይገደድበት ሁኖ ቀሪውን ብር 26,280.00 (ሃያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ብር) ግን ከሕጉ ስሌት ማስቀረት የሚችልበት ምክንያት ስላልተገኘ ለአመልካች ሊከፍል የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የቀሪ የአካል ጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄን ውድቅ ያደረጉት ተጠሪ በሕጉ አግባብ ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን የገባላቸው መሆኑን የመድን ድርጅቱም በስሌት መሰረት የከፈላቸው መሆኑን ሳያረጋገጡ በመሆኑ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 82946 ሐምሌ 24 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 136063 ታህሳስ 11 ቀን 2006 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት በሕጉ ስሌት መሰረት የሚከፈላቸው የካሳ መጠን በኢንሹራንስ ሽፋን ሙሉ በሙሉ ያልተከፈላቸው በመሆኑ ቀሪውን ብር 26,280.00 (ሃያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ብር) ለአመልካች ተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስነናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98052

ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-በርሄ ሐጎስ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ - ነ/ፈጅ ስዩም ረጋሳ ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ገመቹ አዱኛ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ክሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡በ30/08/2005 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-ከሳሽ ከ16/07/2005 ዓ.ም. ጀምሮ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በጀማሪ ነገረ ፈጅነት የስራ መደብ ላይ ተቀጥረው አንድ ወር ከ15 ቀናት የሰሩ መሆኑን፣የ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ እንዲኖር የተደረገ ስምምነት ሳይኖር ተከሳሽ ድርጅት የስራ አፈጻጸምህ ዝቅተኛ ነው፣ሰዓት አክብረህ ስራ አትገባም የሚል እና መሰል ምክንያቶችን በመዘርዘር የስራ ውላቸውን አላግባብ እንዳቋረጠ የሚገልጽ ሆኖ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተከሳሽ ድርጅት ከሕገወጥ የስራ ስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን እንዲፈጽምላቸው እና ቅጥሩም ቋሚ ቅጥር ነው ተብሎ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ13/10/2005 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ከሳሽ የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ መሆኑን፣በዚህ የሙከራ ጊዜ ውስጥ በፍ/ቤት ቀጠሮ በጊዜ ሳይቀርቡ ቀርተው መዝገቦች እንዲዘጉ በማድረግ፣በሰዓት ስራ ባለመግባት እና የመሳሰሉ ጥፋቶችን ከመፈጸማቸውም በላይ ማስጠንቀቂያ እና መልሶችን ራሳቸውን ችለው የማዘጋጀት ውስንነት የታየባቸው መሆኑን እና ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልግ እንዲሰናበቱ የተደረገውም የሙከራ ጊዜአቸው ባለማጠናቀቁ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሮአል፡፡

ፍ/ቤቱም የተከሳሽን ምስክሮች ከሰማ እና ከሳሽ ፈርመው ተቀብለዋል በተባለው ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑን በሚገልጸው ደብዳቤ ላይ የተመለከተው እና በከሳሽ የተካደው ፊርማ ተመርምሮ ውጤቱ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ከሳሽ የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ መሆኑን በሚገልጸው ደብዳቤ ላይ የተመለከተው እና በከሳሽ የተካደው ፊርማ የከሳሽ መሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ የተረጋገጠ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 11(3) በተመለከተው መሰረት ግራ ቀኙ በ16/07/2005 ዓ.ም. ባደረጉት የቅጥር ውል ላይ የሙከራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጊዜ እንዲኖር ስለመስማማታቸው ውሉ የማያመለክት መሆኑን፣ የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ግራ ቀኙ ስለመስማማታቸው በውሉ እስካላረጋገጡ ድረስ ቅጥሩ የተፈጸመው ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ ስለመሆኑ የሚገልጸውን ደብዳቤ ከሳሽ ፈርመው መቀበላቸው ብቻውን ከሳሽ በዚህ የውል ሁኔታ ስለመስማማታቸው የሚያረጋግጥ አለመሆኑን፣የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ግራ ቀኙ በውሉ ያልተስማሙ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ከሳሽ በተከሳሽ የተጠቀሱትን ድክመቶች አሳይተው ቢሆን እንኳ ተከሳሽ የከሳሽን የስራ ውል ማቋረጥ ይገባው የነበረው በማስጠንቀቂያ ሆኖ ሳለ ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጡ ስንብቱ የተከናወነው ከሕግ አግባብ ውጪ እንደሆነ የሚያመለክት መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ተከሳሽ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 2,500፣የስራ ስንብት ክፍያ ብር 273.97 እና የካሳ ክፍያ ብር 15,000 በድምሩ ብር 17,773.97(አስራ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ሶስት ከዘጠና ሰባት) የገቢ ግብር ቀንሶ ለከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይግባኝ ሰሚው ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የቅጥር ውሉ በተደረገበት በዚያው ቀን ተጠሪ የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ ስለመሆኑ የሚገልጸውን ደብዳቤ ፈርመው መቀበላቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ለሙከራ ጊዜ መቀጠራቸው የተገለጸበት ደብዳቤ በአመልካች ብቻ የተዘጋጀ ነው ተብሎ የአመልካች ክርክር በስር ፍ/ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ለሙከራ ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኛ ለስራው ተስማሚ አለመሆኑ ሲረጋገጥ አሰሪው የስራ ስንብት እና የካሳ ክፍያ ለመክፈል ሳይገደድ የሰራተኛውን የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 11(5) በግልጽ የተመለከተ ሆኖ እያለ እና ተጠሪውም ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ የተቀጠሩ ስለመሆኑ በቅጥሩ ዕለት በአድራሻቸው የተጻፈውን ደብዳቤ ፈርመው በመቀበል ያረጋገጡ ሆኖ እያለ አሰሪው ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ውሉን ያቋረጠው አላግባብ ስለሆነ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች እንዲፈጽም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ አይደለም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡እንደተባለው ተገቢ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ለሙከራ ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኛን በሙከራ ጊዜው ውስጥ አሰሪው ያለማስጠንቀቂያ ማሰናበት የሚችል ስለመሆኑ አዋጁ የሚደነግግ ቢሆንም የአዋጁ አንቀጽ 11(5) ድንጋጌ ተፈጻሚ ከመደረጉ አስቀድሞ ግን ተዋዋዮቹ የሙከራ ጊዜ እንዲኖር በቅጥር ውላቸው የተስማሙ መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ እንዳለበት የአዋጁ አንቀጽ 11(3) በግልጽ ያመለክታል፡፡በተያዘው ጉዳይ የቅጥር ውሉ የተደረገውም ሆነ ተጠሪው የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ ስለመሆኑ አመልካች ለተጠሪው በደብዳቤ የገለጸው በተመሳሳይ ቀን ነው፡፡ተጠሪ የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ የመሆን አለመሆኑ ጉዳይ ደግሞ መረጋገጥ ያለበት በአዋጁ አንቀጽ 11(3) መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቅጥር ውሉ እንጂ አመልካች በተናጠል ለተጠሪው በሚሰጠው ማስታወቂያ ባለመሆኑ ተጠሪው የሙከራ ጊዜውን የቅጥር ሁኔታ በውሉ ላይ በግልጽ የተቀበሉ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ በአመልካች የተጻፈላቸውን የቅጥር ደብዳቤ ፈርመው የተቀበሉ መሆኑ መረጋገጡ ብቻ የሙከራ ጊዜውን የቅጥር ሁኔታ ተስማምተው ተቀብለዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ በመሆኑ እና የተሰናበቱትም በስራ ላይ የተለያዩ ድክመቶችን በማሳየታቸው በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ለተጠሪው ተገቢ ክፍያዎችን እንዲፈጽም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 83708 በ21/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 139206 በ06/06/2006 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 86397 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ10/07/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92152

የካቲት 11 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ደሳለኝ – ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወጣቶች ገነት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ ቤት – ነ/ፈጅ አንዋር መስጠፋ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው አመልካች በተጠሪ መሥሪያ ቤት ያላግባብ ከሥራ የተሰናበቱ ስለመሆኑ ገልጸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁት ዳኝነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የሚታይ አይደለም ተብሎ ውድቅ በመደረጉ ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ መሥሪያ ቤት በጥበቃ ሠራተኛነት ተቀጥረው በመሥራት ላይ እንዳሉ ከሕግ ውጪ ተሰናብቼአለሁ በማለት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ መስርተው ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ጠርቶ ባለመቅረቡ በሌለበት አይቶና ጉዳዩን አጣርቶ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የወሰነ ሲሆን፤ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ትምህርት ቤት ከሕዝብ ትምህርት ቤትነት ወደ መንግሥት ከመዛወሩ በፊት ለሰሩባቸው ጊዜያት ተገቢ ክፍያ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሆኖ እያለ፤ ትምህርት ቤቱ ወደ መንግሥት ከተዛወረ በኋላ ሥራ ባልሰሩበት ሁኔታ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አይታይም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታቸውም ተመርምሮ አመልካች ቀደም ሲል ተጠሪ ከሕዝብ ወደ መንግሥት ትምህርት ቤት ሳይቀየር በማገልገል ላይ እያሉ ያላግባብ መሰናበታቸውን ገልፀው በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት የቀረበው ክስ ተጠሪ በአሁኑ ወቅት የመንግሥት እንጂ፣ የሕዝብ ተቋም አይደለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መመሪያ እንዲቀርብ ተደርጎ አመልካችም አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪ ተቋም ሲሰሩ በነበረበት ጊዜ ተቋሙ የሕዝብ የነበረ መሆኑን፤ ከሐምሌ 01 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ወደ መንግሥት የተዛወረ መሆኑን ፤ አመልካች ስንብቱ ተከናውኗል በማለት ክስ የመሰረቱት ደግሞ መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሕዝብ ጥያቄና ፍላጎት ከሕዝብ ይዞታነት ወደ መንግሥት ይዞታነት የሚዛወሩ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ሽግግር ለማስፈፀም የተዘጋጀው መመሪያ ደግሞ ተፈፃሚነቱ ከሰኔ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን ነው፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 የራሱ የሆነ የተፈጻሚነት ወሰን ያለው ስለመሆኑ አንቀጽ 3 የሚደነግግ ሲሆን፤ ይህ ድንጋጌ በአዋጁ የሚገዙትና የማይገዙትን የሥራ ግንኙነቶችን ይዞ ይገኛል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 3(1) በንዑስ አንቀጽ 2 ስር በስተቀር የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ይህ አዋጅ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ ስለዚህም በቅጥር ላይ የተመሰረተው ግንኙነት በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር ከተዘረዘሩት ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች የማይፈጸሙባቸው መሆኑን በአንድ መልኩ ከዚህ ድንጋጌ ስንረዳ በሌላ መልኩ ደግሞ ከነዚህ ውጭ ባሉ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚፈጠሩ ማንኛውም ግንኙነት ላይ አዋጁ ተፈጻሚነት እንደሚኖረው እንረዳለን፡፡ የአንቀጹ ሁለተኛው ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ ደግሞ ግንኙነታቸው በቅጥር ላይ የተመሰረተ ቢሆንም በዝርዝር በሚያስቀምጣቸው የሥራ ግንኙነቶች ላይ አዋጁ የማይፈጸም መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ እነዚህም ለአስተዳደግ ሲባል፣ ከሕመም ለመዳን፣ ወይም እንደገና ለመቋቋም፣ የትምህርትና ለሥልጠና (የሙያ መልመጃ ትምህርትን ሳይጨምር) የሚደረጉ የሥራ ውሎችን፣ የሥራ መሪን፣ ለትርፍ በሚካሔድ ሥራ ላይ ያልተመሰረተ የግል አገልግሎት ቅጥርን፣ በልዩ ሕግ የሚተዳደሩ እንደ የጦር ኃይል ባልደረቦችን፣ የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞችን፣ ዳኞችን፣ ዐቃቤ ሕጎችን፣ ፖሊሶችን እና ሌሎችንም እንዲሁም በራሱ የንግድ ሥራ ወይም በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሚሰራ ሥራ የሚያከናውን ተዋዋይ ያለበት ግንኙነቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም አዋጁ እነዚህ ግንኙነቶች ላይ የማይፈጸም መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለሆነም በአጭሩ ሲገለጽ አዋጁ በአጠቃላይ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚቋቋም በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ቢሆንም፤ በአዋጁ በግልጽ በተደነገጉ ሌላ ሕግ በሚገዛቸው ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ተጠሪ ተቋም ወደ መንግሥት ከሐምሌ 01 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ሲዛወር ከተጠሪ ጋር የሥራ ግንኙነት እንዳልነበራቸው የሚገልጹ ቢሆንም፤ መመሪያው ተፈጻሚ የሆነው ግን ከሰኔ 01 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ፤ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የሚታይበት ምክንያት የለም፡፡ መመሪያው ወደኋላ ሂዶ እንዲሰራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊደረግ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት አመልካች የሚያቀርቡት ክርክርም ሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ውስጥ ሥራ ላይ ያልነበሩ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አላገኘንም፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ባልቀረበበት ሁኔታ የሥልጣን ጉዳይ አንስቶና በተገቢው ማስረጃ በማጣራት ዳኝነት መስጠቱም ተካራካሪ ወገን ባይቀርብም ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነትም የስረ ነገር ሥልጣን ጥያቄን ማንሳት የሚችል ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9(1) እና 231(1)(ለ) ድንጋጌዎች የምንረዳው በመሆኑ፤ በዚህ ረገድ አመልካች የሚያቀርቡት ቅሬታም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(2) እና በአዲስ አበባ ከተማ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 መሠረት በመደበኛው ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ባለመሆኑ፤ የበታች ፍርድ ቤቶች ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሳይ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80282 የካቲት 21 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 132323 ሰኔ 18 ቀን 2005 ዓ.ም በውሣኔ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሚገዛ አይደለም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ሥልጣን ባለው አካል ጥያቄያቸውን ከማቅረብ ይህ ውሣኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዘ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96458

ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- ኢትዮጵያ የርቀት ትምህርት ኮሌጅ አልቀረበም

ተጠሪ፡- ዶ/ር ደሣለኝ ተመስገን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ተከሣሽ ሲሆን ተጠሪ ከሣሽ ነበሩ፡፡ከሣሹ (የአሁን ተጠሪ) ባቀረበው ክስ ታህሳስ 19/2005 ባቀረበው ክስ አመልካች ሰኔ 22/2004 በህገ ወጥ መንገድ ከሥራ ያሰናበተኝ በመሆኑ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ይክፈለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ተከሣሽ (አመልካች) ባቀረበው መልስ የተጠሪ ጥያቄ በ6 ወር የይርጋ ጊዜ የታገደ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 162(4) የሥራ ውሉ ለመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርቡት ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ ደንግጓል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪም ያቀረቡት ክስ የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት ሰኔ 22-2004 ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ 6 ወር ያለፈው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የክስ አቤቱታቸው በጊዜ ለማቅረብ ያልቻሉበት ምክንያትም በቂና አሣማኝ አይደለም፡፡በመሆኑም ጥያቄው በይርጋ ይታገዳል በማለት ተወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የከፍተኛ ፍ/ቤትም ውል ከተቋረጠ በኋላ የሚቀርቡ ክፍያዎች ከ6ወር በኋላ መቅረብ እንደሌለበት ቢደነግግም የፍትሀብሄር ሕጋችን በአንቀጽ 1860(3) ጳጉሜን እንደወር የማትቆጠር በመሆኗ የአመልካች ጥያቄ ከ22-10-2004 እስከ ታህሳስ 19-2005 በመቅረቡ 6 ወር ስላልሞላው በይርጋ ሊታገድ አይገባም በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት ብይን በመሻር በዋና ጉዳይ፤ በፍሬ ነገሩ አከራክሮ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.341(1)መሠረት መልሶታል፡፡

ለሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህን ለማረም ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታም ተጠሪ ሰኔ 22/2004 የሥራ ውላቸው መቋረጡን ጠቅሰው ታህሳስ 19/2005 ያቀረቡትን የክፍያ ጥያቄ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 162(4)መሠረት 6 ወር ካለፈ በኋላ ነው ብሎ ውድቅ የተደረገውን ጉዳይ የፌደራሉ የይግባኝ ሰሚ (ከፍተኛው) ፍ/ቤት በፍትሀብሔር ህጋችን ቁጥር 1860(3) ጳጉሜ እንደወር አትቆጠርም በማለት የሰበር ውሣኔን መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፤ሊታረም ይገባዋል በማለት ጠይቋል፡፡ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በፅሑፍ አቅርበው እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡

በዚህም መሠረት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍትሐብሔሩን ህግ ቁጥር 1860(3) ጠቅሶ ጳጉሜ እንደወር አትቆጠርም የክሱ ጊዜ 6 ወር አልሞላውም ብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት እንደ ጭብጥ ቀርቧል፡፡

በመሆኑም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካለው ህግ አኳያ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም እንዳየነው አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪ ያቀረቡት ክውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ ያቀረቡት ጥያቄ ጳጉሜ እንደወር ስለማትቆጠር 6ወር አልሞላም ተብሎ የይርጋ መቃወሚያው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉና በፍሬ ነገሩ እንድንከራከር መደረጉ በአግባቡ አይደለም የሚል ነው፡፡ከመዝገቡ መገንዘብ እንደቻልነው አከራካሪ የሆነው የህግ ጥያቄ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(4) የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ ሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል የሚለው ድንጋጌ “ጳጉሜን ያካትታል ወይስ አያካትትም? በሚል ነጥብ ነው፡፡እንግዲህ ይርጋ ማለት የመብት ጥያቄ ጊዜ በማለፉ ቀሪ የሚሆንበት ነው ባንባሩ መብት ላልነበረው የሚያጐናፅፍ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ አይቋረጥም የተባለበት ምክንያት የፍትሐብሔር ህጋችን አንቀፅ 1860(3) ጳጉሜን እንደወር ስለማይቆጥር እና የአሰሪና ሰራተኛ ህጉም “ወር”ን መሠረት አድርጐ ስለተደነገገ ነው፡፡

ጳጉሜ እንደ አስራ ሦስተኛ ወር የማትቆጠር መሆኑ ከታወቀና የሀገራችን የአንድ አመት ጊዜ 12 ወራቶች ከሆኑ ከዚህ አቆጣጠር ውጭ ያሉት ቀናት በግራ ቀኙ መሀከል መብትም ሆነ ግዴታ ሊፈጥር አይገባም፡፡ጳጉሜ ተጠሪ ሥራም ላይ ቢሆኑ የሚሰጣቸው ጥቅም ወይም በመብት ደረጃ የሚጠይቁትም ክፍያ የለም፡፡እንግዲህ እንደወር የማይቆጠረው “ጊዜ” ለቀረበው ክውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ የሚነሣው የክፍያ ጥያቄ ጳጉሜ ተሰልቶ የተጠሪን መብት ሊያጣብብ አይገባውም፡፡

ባጠቃላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያውን ደረጃ ፍ/ቤት ብይን ሽሮ የተጠሪ ጥያቄ የ6ወር ይርጋ ጊዜ አላለፈበትም በማለት ወደ ሥር ፍ/ቤት መዝገቡን መመለሱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀን 4/8/05 በመ.ቁ.07615 የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 16/12/2005 በመ.ቁ.133056 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. የግራ ቀኙ በፍሬ ነገር ደረጃ ክርክራቸው ይቀጥሉ ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.341(1)መመለሱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98724

ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-ሙኒሽ ካፌ ድርጅት(ሙኒሽ ጀርመን ቤከር እና ካፌ) ጠበቃ ወርቁ ፋንታሁን ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ዳዊት ፀጋው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡በ15/05/2005 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-ከሳሽ ከ24/01/2004 ዓ.ም. ጀምሮ በብር 900 የወር ደመወዝ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በባሬስታ የስራ መደብ ተቀጥረው በመስራት ላይ እያሉ ተከሳሽ ድርጅት ከ30/04/2005 ዓ.ም. ጀምሮ የስራ ውላቸውን አላግባብ እንዳቋረጠ የሚገልጽ ሆኖ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተከሳሽ ድርጅት ከሕገ ወጥ የስራ ስንብት ጋር የተያያዙትን እና ሌሎች ክፍያዎችን እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ16/07/2005 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ተከሳሽ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው ከ03/05/2005 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ዋናው መ/ቤት ተዛውረው እንዲሰሩ በ01/05/2005 በተጻፈ ደብዳቤ ተገልጸላቸው እያለ በተዛወሩበት ቦታ ከአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ በስራ ላይ ባለመገኘታቸው በሕጉ አግባብ መሆኑን ገልጾ ከዓመት ፈቃድ ክፍያ ብር 519 ውጪ ከሳሽ ጥያቄ ያቀረቡባቸው ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸው የክፍያ ዓይነቶች ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ አጠቃላይ ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ከሳሽ እንዲሰናበቱ የተደረገው በተዛወሩበት ቦታ በመደዳው ከአምስት የስራ ቀናት በላይ ከስራ በመቅረታቸው ምክንያት እንደሆነ በማስረጃ በመረጋገጡ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲፈጸሙላቸው አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ ሊከፈላቸው የሚገባው የ17.5 ቀን የዓመት ዕረፍት ክፍያ ብር 525.00 ብቻ መሆኑን፣ተከሳሽ ተገቢውን የስራ ልምድ የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ለከሳሽ መስጠት የሚገባው መሆኑን፣ከሳሽ ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ቢሆንም በእጃቸው የሚገኙ ንብረቶች ካሉ አስረክበው ክሊራንስ ከያዙ በኋላ ክፍያ እንዲፈጸምላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠይቀው የዘገየ ክፍያ ስለመኖሩ ስላላስረዱ ጥያቄአቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ የተከሳሽን የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ ጭምር ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በከሳሽ ጠያቂነት ይግባኙን የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አሻሽሎ ሌላውን የውሳኔ ክፍል ሲያጸና ክፍያ የዘገየበትን እና የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብትን በተመለከተ ግን ውሳኔውን ሽሮ በአዋጁ አንቀጽ 36 መሰረት የዓመት ዕረፍት ክፍያውን ተከሳሽ በሰባት ቀናት ውስጥ መክፈል የሚጠበቅበት ሆኖ እያለ ከሳሽ ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ክፍያውን ለመክፈል አዘጋጅቶ ከሳሽ በራሱ ጥፋት ሳይወስድ ያዘገየ ስለመሆኑ በማስረጃ አስደግፎ እንዳልተከራከረ ገልጾ በአዋጁ አንቀጽ 38 መሰረት ተከሳሽ ድርጅት ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ ለከሳሽ እንዲከፍል በማለት እና ለተከሳሽ ተጠብቆ የነበረውን የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመሰረዝ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስራ ውል ሲቋረጥ ለሰራተኛ ሊከፈል የሚገባው ክፍያ ዘገየ የሚባልበትን እና ዘገየ ለተባለ ክፍያ እስከ ሶስት ወር ደመወዝ የሚደርስ ክፍያ እንዲፈጸም የሚወሰንበትን አግባብ ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ ከአሰሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር በአንቀጽ 36 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ አሰሪው ለሰራተኛው መክፈል የሚገባውን ሂሳብ ካልከፈለ ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ ለሰራተኛው እስከ ሶስት ወር ለመድረስ የሚችል ደመወዙን ያህል አሰሪው እንዲከፍለው የስራ ክርክር ችሎት ሊወስን እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 38 የተመለከተ ሲሆን ክፍያውን በአዋጁ አንቀጽ 36 በተመለከተው የሰባት የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ መክፈል ያልተቻለው ከአሰሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት በተለይም በአንቀጽ 36 እንደተገለጸው ሰራተኛው ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት የማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማንኛውንም ሂሳብ የማወራረድ ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት ሆኖ ከተገኘ አሰሪው በአንቀጽ 38 የተጠቀሰውን ክፍያ የመክፈል ግዴታ የሌለበት መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች ክፍያ አዘግይቷል ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው የዓመት ዕረፍት ክፍያውን በሰባት ቀናት ውስጥ መክፈል የሚጠበቅበት ሆኖ እያለ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ክፍያውን ለመክፈል አዘጋጅቶ ተጠሪ በራሱ ጥፋት ሳይወስድ ያዘገየ ስለመሆኑ በማስረጃ አስደግፎ አልተከራከረም በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ክፍያ ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው በግልጽ ስለመጠየቃቸው ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በተጠሪው የተጠየቁ ሌሎች መብቶችን እና የክፍያ ዓይነቶችን ክዶ የተከራከረ ሲሆን የዓመት ዕረፍት ክፍያውን በተመለከተ ግን በክፍያው መጠን ላይ ከመከራከር ውጪ ይህ ክፍያ የማይገባቸው ስለመሆኑ እና ይህ በአሰሪው የታመነው የክፍያ ዓይነትም በአዋጁ አንቀጽ 36 መሰረት በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ለሰራተኛው ሳይከፈል የቀረው ሰራተኛው ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት የማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማንኛውንም ሂሳብ የማወራረድ ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት በመሆኑ ክፍያ ለዘገየበት በተጠሪ የተጠየቀውን ቅጣት የመክፈል ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ ገልጸ ያቀረበው ክርክር ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ተጠሪው የሚፈለግበትን ንብረት የማስረከብ እና ሂሳብ የማወራረድ ግዴታ አልተወጣም የሚለውን የክርክር ነጥብ አመልካች በሰበር ደረጃ ከማቅረቡ በቀር በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ቢሆን የዚህ ዓይነት ክርክር አቅርቦ የነበረ ስለመሆኑም መዝገቡ አያመለክትም፡፡የታመነውን ክፍያ ያዘገየሁት ተጠሪው የበኩሉን ግዴታ ባለመወጣቱ ነው በሚል አመልካች በሁለቱ የስር ፍ/ቤቶች አንስቶ ያልተከራከረበትን ነጥብ ደግሞ በሰበር ደረጃ በመከራከሪያነት ማንሳቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329(1) ድንጋጌ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡አመልካች በዚህ ነጥብ ላይ በስር ፍ/ቤቶች ያቀረበው መከራከሪያ የለም በማለት ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ያቀረቡትን ክርክርም አመልካች አላስተባበለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ክፍያ ላዘገየበት በአዋጁ አንቀጽ 38 መሰረት የሶስት ወር ደመወዝ ለተጠሪው በቅጣት መልክ እንዲከፍል በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሊነቀፍ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 07894 በ11/11/2005 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 136017 በ10/06/2006 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92302

ጥር 26 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ርዕሶም እምባፍራሽ – ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ኢትዮ ቴሌኮም – ነ/ፈጅ አቶ ፈቃዱ ኃይሌ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩም የተጀመረው የስር ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በፊደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ፡- በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከ27/1/1973 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/03/1991 ዓ.ም ስሠራ ከቆየሁኝ በኋላ በስህተት በመሰናበቴ በ5/07/1997 ዓ.ም ወደ ሥራ እንድመለስ ተደርጐ እስከ ሐምሌ 6 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 4,955 ደመወዝ እየተከፈለኝ ለ24 ዓመታት ከ6 ወር ሳገለግል ከቆየሁ በኋላ ተጠሪ የሥራ ውሌን ያለአግባብ ስላቋረጠ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲፈጸምለት እንዲወሰንለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ ከ27/1/1973 ዓ.ም እስከ 30/3/1991 ዓ.ም ያለው የሥራ ስንብት ክፍያ በይርጋ የታገደ መሆኑን፤ ይህ መቃወሚያው የሚታለፍ ከሆነም እስከ 30/3/1991 ዓ.ም ያለው የሥራ ስንብት የተከፈላቸው መሆኑን፣ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 16/10/2003 ዓ.ም ያለውን የሥራ ስንብት ክፍያ ደግሞ አመልካች እንዲወስዱ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ ስለቀሩ በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው መሆኑንና ከሥራ የተሰናበቱትም በሕጉ አግባብ በተፈፀመ ቅነሳ ምክንያት መሆኑን ጠቅሰው ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ይወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ከሰማ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር እስከ 30/3/1991 ዓ.ም ድረስ ያለው የስንብት ክፍያ በይርጋ የሚታገድ መሆኑንና የሥራ ውሉም ሊቋረጥ የቻለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/1/ (ሐ) መሠረት በተፈጸመ ቅነሳ ምክንያት መሆኑን ጠቅሶ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ከወሰነ በኋላ ከ5/7/1997 ዓ.ም ጀምሮ ያለው የሥራ ስንብቱ ክፍያ ብር 13,763.88፣ በሠራተኞች ቅነሳ ጊዜ በአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40(3) መሠረት ሊከፈል የሚገባ ክፍያ ብር 9,910፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 9,910፣ አመልካች ሥራ ሠርቶ ያልተከፈለው የ13 ቀናት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደሞዝ ብር 2,147.16 እና የ71 ቀናት የዓመት እረፍት ክፍያ ብር 11,726.83 በድምሩ ብር 47,457 ተጠሪ ለአመልካች ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ በአመልካች ይግባኝ አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የበታች ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት በማጽናት ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ሲሆን፤ አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች የሥራ ውሌ አላግባብ ተቋርጧል በማለት አቤቱታ ሲያቀርብ ቆይቶ በመጨረሻ ስንብቱ ሕገወጥ መሆኑ ተረጋግጦ በ5/7/1997 ዓ.ም ወደ ቀድሞው ሥራው እንዲመለስ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 164(3) መሠረት የይርጋውን ጊዜ ማቋረጡ እየታወቀ፤ አመልካች ወደ ሥራ ለመመለስ እየተከራከረ በነበረበት ሁኔታ የስንብት ክፍያ በወቅቱ አልወሰደም ተብሎ ከ1973 –1991 ዓ.ም ያለው የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን፣ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን፤ እኛም በበኩላችን አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሠረቱ የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሠራተኛውም ሆነ በአሠሪው የሚቀርብ ማናቸውም የክፍያ ጥያቄ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ በአዋጅ አንቀጽ 162(4) ስር ተደንግጐ ይገኛል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች የሥራ ውል ከ30/03/1991 ዓ.ም ጀምሮ ለ6 ዓመት ከ3 ወር ተቋርጦ የቆየ ስለመሆኑ ግራቀኙን ያላከራከረ ከመሆኑም በላይ በስር ፍ/ቤትም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የሥራ ውሉም በወቅቱ ሊቋረጥ የቻለው በመንግሥት ውሣኔ መነሻነት ነው ከሚባል በቀር በተጠሪ ጥፋት ምክንያት ስለመሆኑ ወይም ያለአግባብ በተጠሪ የተቋረጠ መሆኑን አመልካች አላስረዳም፡፡ የሆነ ሆኖ የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት እለት ከ30/3/1991 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት 6 ወራት ጊዜ ውስጥ የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄው ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ ግልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካቹ በ5/7/1997 ዓ.ም እንደገና በመንግሥት መመሪያ ወደሥራ እንዲመለስ መደረጉም አስቀድሞ በይርጋ የታገደውን የስንብት ክፍያ ጥያቄን (ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1991 ዓ.ም ያለውን የስንብት ክፍያ) ከአዋጁ አንቀጽ 164(3) ድንጋጌ ይዘት አኳያ የይርጋ ጊዜን ሊያቋርጥ የሚችል አይደለም፡፡ ምክንያቱም እንደድንጋጌው አነጋገር ተጠሪ የአመልካችን መብት በጽሑፍ አውቆለት ወይም በከፊል በራሱ የፈፀመለት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ አመልካች አላስረዳም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከ30/3/1991 ዓ.ም በፊት ያለው የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄ በአዋጁ መሠረት በስር ፍ/ቤቶች በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ እና አግባብነት ያላቸው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጁን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ከሚባል በቀር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላላገኘን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24120 በ18/6/2005 ዓ.ም ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 132709 በ25/10/05 ዓ.ም እንዲፀና የተደረገበት ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ የሰበር ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዘ.በ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 99026

ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተሽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ አብርሃም ታደለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጥቁር አባይ ትራንስፖርት ኃላ/የተ/የግል/ማህበር አልቀረብም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139116 ታህሳስ 4 ቀን 2000 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡በስር ፍርድ ቤት አመልካች በከሳሽነት ቀርቦ፤ተከሳሽ (ተጠሪ) ከህግ አግባብ ውጭ የስራ ውሌን በማቋረጥ ከስራ ያሰናበተኝ በመሆኑ፤ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ አመልካች ለአንድ ወር በህክምና ላይ ከቆየ በኋላ ወደ ስራ ባለመመለሱ የካቲት 21 ቀን 2005 ዓ/ም ማስታወቂያ አውጥተናል፡፡ከዚያም ከሳሽ ሪፖርት ካደረጉ በኋላ ቀላል ስራ ካልተሰጠኝ የሹፌርነት ስራ አልሠራም በማለት ለከሳሽ በማሳወቃቸው ከስራ በመቅረታቸው ከስራ የተሰናበት ስለሆነ ስንብቱ በህግ አግባብ የተደረገ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከሳሽ በስራ ላይ እያለ ጉዳት ከደረሰበት በኋላ ወደ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል ታክሞ በተሰጠው ማስረጃ ጉዳቱ መኪና ማሽከርከር እንደማይከለክለው ተገልጿል፡፡ ሆኖም ከሳሽ በህዳር ወር 2005 ዓ/ም መኪና ጅቡቲ ይዞ ከሄደ በኋላ ባደረበት ህመም ምክንያት መኪናውን ለመመለስ ባለመቻሉ መኪናው ሌላ ሹፌር ሄዶ እንዲያመጣ የተደረገ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተከሳሽ ድርጅት የህክምና ተቋም የሆነው ከሳሽ በአከርካሪ ዲስክና በእጅ ላይ ከባድ ጉዳት የደረሰበት ስለሆነ ቀለል ያለ ስራ ላይ እንዲመደቡ የሚገልፅ ማስረጃ ሰጥቷቸዋል፡፡ የደጃዝማች ባልቻ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠው ማስረጃም ይህንኑ የተከሳሹን የጤንነት ችግር የሚገልፅ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ከሳሽ በህመም ላይ መሆናቸውንና ጤንነታቸው ስላልተሻሻለ ህክምና በመከታተል ላይ ያሉ መሆናቸውን ተከሳሽ እያወቀ ቀላል ስራ ለመስጠት ፍቃደኛ ባለመሆኑ ከስራ ያሰናበተ መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ ስንበቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት ተከሳሽ ለከሳሽ የካሳ ክፍያና የሁለት ወር የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ መልስ ሰጪ (አመልካች) የይግባኝ ባይ ድርጅት ጥር 29 ቀን 2005 ዓ.ም የህክምና ማስረጃ ከሰጣቸው በኋላ ለሶስት ሳምንታት ያህል ለአሰሪያቸው (ይግባኝ ባይ) ሳያቀርቡና ስራ ሳይገቡ ቆይተው፤የካቲት 23 ቀን 2005 ዓ/ም የህክምና ማስረጃውን አቅርበዋል፡፡ይህም መልስ ሰጪ የተሰጣቸው የህክምና ፍቃድ ካለቀ በኋላ ለሃያ አንድ ቀናት ከስራ ቦታ የቀረ መሆኑን ስለሚያሳይ ይግባኝ ባይ የመልስ ሰጭ የሰራ ውል ያቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች መጋቢት 17 ቀን 2006 ዓም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ከደረሰብኝ የጤንነት ችግር እንዳላገገምኩ፤ለተጠሪ አሳውቄዋለሁ፡፡ አንድ የጤንነት ችግርና ህመም ያጋጠመው ሰራተኛ ፤አሰሪው ከስራ ከማሰናበቱ በፊት የሚወስዳቸው እርምጃዎች የሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 86 ነው፡፡ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ግን ለጤነኛ ሰራተኞች ተፈፃሚነት ያለውን እና በእኔ ጉዳይ አግባብነት የሌለውን አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በመጥቀስ የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ግንቦት 29 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ መልስ አመልካች የህክምና ፍቃዱ ካለቀ በኋላ ሃያ ቀናቶች ወደ ስራ ቦታው ያልመጣ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካች ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች ከስራ ያሰናበተው በሕግ አግባብ ነው፡፡ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በስራ ላይ ጉዳት የደረሰበት መሆኑንና በዚህ ምክንያት የጤና ችግር ስለገጠመው የአንድ ወር የህመም ፈቃድ በአሰሪው(ተጠሪ) ተሰጥቶት እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የተሰጠው የሕመም ፈቃድ እንዳበቃ ወደ ስራ ቦታ ባለመምጣቱ ተጠሪ ማስታወቂያ ማውጣቱንና አመልካችም ማስታወቂያው በወጣበት ቀን ማግስት ከስራ ቦታ በመገኘት ከህመሙ እንዳላገገመ ገልፆ፣ አመልካች ይሰራው የነበረውን የአሽከርካሪነት ስራ ለመስራት የማይችል በመሆኑ ቀላል ስራ ላይ እንዲመደብ በማለፅ የተጠሪ የጤና ተቋም የሰጠውን ማስረጃ እንዳቀረበ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ፣ አመልካችን እንደማንኛው ጤነኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰራተኛ በመቅጠር የተሰጠህ የህመም ፈቃድ ካለቀ በኋላ በተከታታይ አምስት ቀናት በስራ ቦታ አልተገኘህም በሚል ምክንያት የሚያባርርበት የሕግ መሰረት የለውም፡፡

አመልካች የደረሰበት ጉዳት መኪና ማሽከርከር የማይከለክለው መሆኑ በዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል በተሰጠ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በማለት ሲሆን፣ አመልካች ጅቡቲ እያሽከረከረ የወሰደውን መኪና መመለስ ባለመቻሉ ምክንያት ሌላ ሹፌር ተመድቦ መኪናውን ከጅቡቲ ያመጣ መሆኑ፣ አመልካችም የህመም ፈቃድ የተሰጠው መሆኑና አመልካች ያጋጠመው የአከርካሪ ዲስክ እና እጅ ላይ በመሆኑ መኪና ማሽከርከር እንደማይችል ተጠሪ በኃላፊነት የሚያስተዳድረው ክሊኒክ ጭምር በማረጋገጥ ማስረጃ እንደሰጠ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ፣ አመልካች ከሙሉ ደመወዝ ጋር የተሰጠውን የአንድ ወር የህመም ፈቃድ ጨርሶ ከህመሙ አገግሞ ስራ ቦታ መገኘት ካልቻለ፣ ተጠሪ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 85 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ተጨማሪ የህመም ፈቃድ መስጠትና በአንቀፅ 86 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ግማሽ ደመወዙን በመክፈል ተጠሪ ከህመሙ እንዲያገግም የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት ሲገባው፣ የአመልካችን የስራ ውል መሰረዙ አግባብነት ያለውን የሕግ ድንጋጌ መሰረት ያላደረገ ሕገ ወጥ ተግባር ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት፣ በስራ ላይ የደረሰበትን አደጋ አሰሪው አውቆ የአንድ ወር የህመም ፈቃድ የሰጠው ሰራተኛ ከህመሙ አገግሞ ስራ ቦታ ላይ ሳይገኝ በሚቀርበት ሁኔታ ተፈፃሚነት ያላቸው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 85 እና አንቀፅ 86 ድንጋጌዎች መሆናቸውን ሳያገናዝብ፣ አመልካችን እንደማናቸውም ጤነኛ ሰራተኛ በመቁጠር፣ የሕመም ፈቃድ ካለቀ በኋላ በተከታታይ ከአምስት ቀን በላይ ስለቀረ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን የስራ ውል ያቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139116 ታህሳስ 4 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09329 ሐምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95392

ግንቦት 06 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

አሊ መሀመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የእንግሊዝ ሕፃናት አድን ድርጅት ጠበቃ አቶ አይሸሽም መድፉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሽመልስ አለሙ አልቀረቡም

መዝገብን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአሳይታ ወረዳ ፍርድ ቤትና የአውሲረሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል ጊዜው ከመድረሱ በፊት መቋረጡ የሚያስከትለውን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1.የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ተጠሪ አመልካች በጊዜያዊነት የቀጠረው መሆኑንና የስራ ውሉም የሚጠናቀቀው ነሀሴ 25 ቀን 2004 ዓ.ም መሆኑን ገልፆ፤ የሥራ ውሉ የሚቋረጥበት ጊዜ ሳይደርስና በቂ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ ተከሳሽ (አመልካች)የሥራ ውሉን ያቋረጠው ስለሆነ የ6 ወር ደመወዝ የካሳ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ፣የአልጋ፣አበልና እና ሌሎች ወጪዎች ሊከፈሉኝ ይገባል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡አመልካች የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል መሆኑንና የሥራ ወሉን ያቋረጠውም ማስጠንቀቂያ በመስጠት መሆኑን ግልፆ፤ ስንብቱ ህጋዊ ነው፡፡ከሳሽ (ተጠሪ)ያቀረበው የጥቅማ ጥቅም እና ሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ የህግ መሰረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች የአስራ ሁለት ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት የስራ ውሉን ያቋረጠና የሥራ ውሉን ያቋረጠው በውሉ የተገለፀው ጊዜ ማለትም ነሀሴ 21 ቀን 2004 ዓ.ም ከመድረሱ በፊት በመሆኑ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ብሎ የስድስት ወር ደመወዝ ፤የካሳ ክፍያ፤የሶስት ወር ደመወዝ ክፍያ ለዘገየበት፤የማስጠንቀቂያ ክፍያና ሌሎች የጥቅማ ጥቅምና አበል ክፍያዎች በድምሩ ብር 107,823.73 (አንድ መቶ ሰባት ሺ ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከሰባ ሶስት ሳንቲም) አመልካች ለተከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ ስጥቷል ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2.አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ሀምሌ 25 ቀን 2004 ዓ.ም ነው፡፡ ከዚህ በፊት የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጽፈናል፡፡እንዲሁም ክፍያዎችን ፈጽመናል፡፡ በሌላ በኩል በማስረጃ ያልተረጋገጠ የአበልና እና የአልጋ ክፍያ ተወስኖብናል ስለዚህ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል ሆኖ እያለ ተጠሪ ከጠየቀው በላይ ገንዘብ በላይ እንድንከፍል የተሰጠው ውሳኔ መስረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው ከህግ ውጭና የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አላቀረበም፡፡

3.ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ለሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከህግ ውጭ ያሰናበተው ስለሆነ የስድስር ወር ደመወዝ የካሳ፡ ክፍያ የማስጠንቀቂያ ክፍያና ሌሎች ክፍያዎች እንዲከፍል በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ?የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

4. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪን ለተወሰነ ጊዜ የቀጠረው መሆኑንና የሥራ ውሉ የሚጠናቀቀው ነሐሴ 24 ቀን 2004 ዓ.ም እንደነበር፤ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረበው የክስ ማመልከቻ ገልጿል፡፡ አመልካች በስራ ውሉ የተገለፀው ጊዜ ሣይደርስና በቂ ምክንያት ሣይኖረው ሀምሌ 24 ቀን 2004 ዓ.ም የተጠሪን የሥራ ውል የአሰራ ሁለት ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ያቋረጠው መሆኑን የወረዳው ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ስለሆነም አመልካች ከነሐሴ 24 ቀን 2004 ዓ.ም በፊት ውሉን ለማቋረጥ የሚያስገድደው ምክንያት ወይም በተጠሪ በኩል ያልተፈፀመ ጥፋት ሣይኖርና ለተጠሪ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሣይሰጠው የስራ ውሉን ማቋረጡ ከሕግ ውጭ ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

5. አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል በውሉ የተገለፀው ጊዜ ከመድረሱ በፊት ያለበቂ ምክንያት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሣይሰጥ አቋርጧል ከተባለ ለተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ሊከፈል የሚገባው ክፍያ ምን መሆን አለበት የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ የተጠሪ የሥራ ውል የሚቋረጥበት ጊዜ የቀረው አንድ ወር ብቻ እንደነበረ ከግራ ቀኙ ክርክርና የበታች ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ውሳኔ ተረጋግጧል፡፡ይህ ከሆነ አመልካች ለተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(4)/ሀ መሠረት እንዲከፍል የሚገደደው ውሉ እስከ ሚቋረጥበት ድረስ ያለውና ተጠሪ ያቀረቡት የአንድ ወር ደመወዝ ማለትም ብር 8052.73 /ስምንት ሺ ሃምሣ ሁለት ብር ከሰባ ሶስት ሣንቲም/ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ውሉ ነሐሴ 24 ቀን 2004 ዓ.ም የሚጠናቀቅ መሆኑን ሣያገናዝቡ የበታች ፍርድ ቤቶች የስድስት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወር ደመወዝ ካሣ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

6. አመልካች የተጠሪ የሥራ ውል ከሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ ከአንድ ወር በፊት የሥራ ውሉን አቋርጧል፡፡ በዚህ ሁኔታ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው የአንድ ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንጂ የሶስት ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሚገደድበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ክፍያ ለዘገየበት በማለት የሶስት ወር ደመወዝ አመልካች እንዲከፍል የወሰነው የስራ ውሉ ከተቋረጠበት ሀምሌ 24 ቀን 2004 ዓ.ም በፊት ክፍያ ከፍለህ አላጠናቀክም በማለት ነው፡፡ ሆኖም አሠሪው ክፍያ እንዲከፍል የሚገደደው የሥራ ውሉ ከተቋረጠ በሰባት ቀናት ውስጥ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 የተደነገገ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ክፍያ ለዘገየበት በማለት አመልካች ለተጠሪ የሶስት ወር ደመወዝ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

7.የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ በመስክ ሥራ በሚቆይበት ወቅት የሚከፍለው የአልጋ ክፍያ ብር 6417(ስድስት ሺ አራት መቶ አስራ ሰባት ብር)እንደዚሁም የሃያ ቀን የውሎ አበል ብር 2970 (ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ሰባ ብር) በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን በመግለፅ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የክፍያ ውሳኔ በማሻሻል ፤አመልካች ለተጠሪ የአንድ ወር ደመወዝ የካሣ ክፍያ ፤የአንድ ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እና ለአልጋ ክፍያና የውሎ አበል በጠቅላላው በድምሩ ብር 25,492.16 /ሃያ አምስት ሺ አራት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም /ሊከፍል ይገባዋል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1.የአፋር ክልል አሳኢታ ወረዳ ፍርድ ቤትና የአወስራሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

2. የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪ ብር 107,823 .73 (አንድ መቶ ሰባት ሺ ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከሰባሶስት ሣንቲም) እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

3.አመልካች ለተጠሪ ብር 25,492.16 /ሃያ አምስት ሺ አራት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከአሥራ ስድስት ሣንቲም) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

4.በዚህ ፍርድ ቤት በ 23/04/2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡

5.በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92423

ጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ የሺሐረግ ታደሰ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአምቦ ማዕድን ውሃ አ/ማ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 130114 ግንቦት 5 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ ውል መቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የተያዘው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ በተከሳሽ ድርጅት ተቀጥራ በተለያየ የሥራ መደብ አገልግያለሁ፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ እየሠራሁበት ባለው የፋይናሻል ኮንትሮል የሥራ መደብ ከአዲስ አበባ ወደ ሰንቀሌ ተዛውሬ እንድሠራ ደብዳቤ ፅፎልኛል፡፡ ከሳሽ በተከሳሽ ፈቃድና ተከሳሽ ጋር ውል ተዋውዬ በደቡብ አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ ስከታተለው የነበረው የማስተርስ ትምህርት የመመረቂያ ጽሑፍ መስከረም 2003 ዓ.ም በፊት እንዳስረክብ ዩኒቨርሲቲው ያዘዘ መሆኑን ገልጬ ትምህርቴን ለሶስት ወር ዝውውሩን እንዲያዘገይልኝ ጠይቄው ተከሳሽ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ የመጀመሪያውን አማራጭ እንቢተኛ ከሆነ የዓመት ረፍቴ እንዲሰጠኝና ትምህርቴን እንዳጠናቅቅ በፅሑፍ ጠይቄለሁ፡፡ ከሳሽ ያልተጠቀምኩበት አንድ መቶ ሃያ ቀናት ረፍት አለኝ፡፡ ተከሳሽ ፈቃድ እንዲሰጠኝ ላቀረብኩት ጥያቄ መልስ ባለመስጠቱ ዝምታው ጥያቄውን እንደተቀበለው በመውሰድ ትምህርቴን በመከታተል ላይ እያለሁ ከአምስት ቀናት በላይ ከሥራ ቀርተሻል በማለት ትምህርት ስጀምር የተዋዋለውን ውል የሚቃረን ህገ ወጥ እርምጃ የወሰደ በመሆኑ ደመወዜን ከፍሎ ወደ ሥራ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርቦ በብይን ውድቅ አድርጐታል፡፡ የመከላከያ መልሱን በተመለከተ አመልካች ትምህርቷን እስክታጠናቅቅ ዝውውሩ እንዲዘገይላት ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ተገልፆላታል፡፡ የዓመት ፈቃድ በተመለከተ፣ ከሳሽ ፈቃድ የምትወጣበት ጊዜ በዕቅድ የተያዘው እንደአውሮፖዊያን አቆጣጠር በዲሴንበር 2010 ሆኖ እያለ፣ ከዚያ በፊት የዓመት እረፍት እንዲሰጣት ያቀረበችው ጥያቄ ተገቢነት የለውም፡፡ በግልፅ ፈቃድ ሣይሰጣት፣ ከሥራዋ ለአምስት ቀን የቀረች በመሆኑ፣ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ የመመረቂያ ፅሑፏን ለማጠናቀቅ የዓመት ፈቃድ እንዲሰጣት በፅሑፍ ጥያቄ አቅርባለች፡፡ ተጠሪ /ተከሳሽ/ ምላሽ ሣይሰጥ የቀረ መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከሳሽ የተከሳሽን ዝምታ የዓመት ፈቃድ ጥያቄውን እንደተቀበለው በመቁጠር ትምህርቷን ለማጠናቀቅ ከሥራ ቦታ ሣትገኝ መቅረቷ ያለ ምክንያት እንደቀረች የሚያስቆጥራት አይደለም፡፡ ተከሳሽ የሥራ ውሉን ያቋረጠው ከህግ ውጭ በመሆኑ የስድስት ወር ደመወዟን ከፍሎ ወደ ሥራ ይመልሳት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በግልፅ ፈቃድ ሣይሰጣት፣ ከሥራ ቦታ ያልተገኘች መሆኑ ስለተረጋገጠ፣ የሥራ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡
4. አመልካች ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ትምህርት የጨረስኩት ተጠሪ ጋር ውል ተዋውዬ ትምህርቴን ተከታትዬ ባላጠናቀቅ ለትምህርት ያወጣውን ወጭ ለመክፈል ተስማምቼ ነው፡፡ አመልካች የዓመት ፈቃድ እንዲሰጠኝ ስጠይቅ የመመረቂያ ፅሑፍ እንዳጠናቅቅ ዩኒቨርሲቲው ያስቀመጠውን ቀነ ገደብ በመጥቀስ ነው፡፡ ተጠሪ ለጥያቄው መልስ ሣይሰጥ ዝም ማለቱ እንደተቀበለው መቁጠር እንደ ጥፋት ሊያዝብኝ የሚገባ አይደለም፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በሰበር እንዲታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ የዓመት ፈቃድ የሚሰጥበት ሥርዓት ሣይሟላና በግልፅ ፈቃድ ሣይሰጣት ወደ ተዛወረችበት ቦታ ያልሄደች በመሆኑ፣ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1/ለ መሠረት ከሥራ መሰናበቷ ህጋዊ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡
5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበታት በህግ አግባብ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
6. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ በዚህ መዝገብ የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮችን መሠረታዊ ባህሪና ይዘት እንደዚሁም በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነትና አንፃራዊ ግዴታ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ፈቃድ ሰጥቶና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የድጋፍ ደብዳቤ ፅፎላት፣ ከተጠሪ ጋር ውል ተዋውላ የማስተርስ ትምህርት ስትከታተል እንደነበርና፣ ተጠሪ አመልካችን ከአዲስ አበባ ወደ ስንቀሌ ሲያዛውራት፣ አመልካች የመመረቂያ ፅሑፏን ለዩንቨርሲቲው የምታስረክብበት የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ ጋር ተገጣጣሚነት እንዳለው በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። አመልካች በተጠሪ ፈቃድና ስምምነት የጀመረችው ትምህርት እስክታጠናቅቅ ዝውውሩ እንዲዘገይላት ተጠሪ ጠይቃ ተጠሪ ጥያቄዋን የማይቀበለው መሆኑን እንዳሳወቃት ተረጋግጧል።

7. በተጠሪ ድጋፍና ፈቃድ ለሶስት ዓመት ያህል ስትከታተለው የነበረው የማስተርስ ትምህርት ለማጠናቀቅ ለተጠሪ ያቀረበችው የመጀመሪያ ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘው አመልካች፣ ዩንቨርስቲው ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ የመመረቂያ ፅሑፏን ለማቅረብና ትምህርቷን ለማጠናቀቅ እንድትችል ተጠሪ ያልተጠቀመችበትን የዓመት ፈቃድ እንዲሰጣት በፅሑፍ ጠይቃለች። ተጠሪ በዚህ አመልካች ላቀረበችው የዓመት ፈቃድ ጥያቄ በግልፅ አሉታዊ ምላሽ እንዳልሰጠ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። ይህም ያለበት አመልካችና ተጠሪ በሥራ ውል ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ብቻ ሣይሆን የአመልካችን የማስተርስ ትምህርት በተመለከተ፣ ከተጠሪ የሚፈለገውን ድጋፍ፣ ትብብርና እርዳታ አመልካች ትምህርቷን ስትከታተልና ትምህርቷን ተከታትላ ካጠናቀቀች በኋላ ያለባትን ግዴታና ኃላፊነት የሚወሰን ሌላ ልዩና ተጨማሪ የውል ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ተጠሪ ክዶ አልተከራከረም። በአንፃሩ አመልካች የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ፅውቅና በሰጠውና ከተጠሪ ጋር ባደረገችው ውል መሠረት ትምህርቷን ስትከታተል የቆየች መሆኑ ግራቀኙ በበታች ፍርድ ቤቶች እና ግራቀኙ በሰበር ደረጃ ካቀረቡት ክርክር ለመረዳት ችለናል።

8. አመልካች የዓመት ፈቃድ ተሰጥቷት፣ በተጠሪ ድጋፍ ስትከታተለው የነበረውን የማስተርስ ትምህርት ለማጠናቀቅ በፅሑፍና በግልፅ ላቀረበችው ጥያቄ ተጠሪ በግልፅ የሰጠው አሉታዊ መልስ አለመኖሩ፣ ከላይ ከገለፅነው አመልካችና ተጠሪ መካከል ስለአመልካች የማስተርስ ትምህርት ከተደረገው ልዩና ተጨማሪ ውል አንፃር መታየት የሚገባው ነው። ተጠሪ አመልካች ለደቡብ አፍሪካ ዩንቨርስቲ ከፍተኛ ክፍያ እየተከፈለ ስትከታተል የቆየችውና የማስተርስ ትምህርቷን በአግባቡ እንድታጠናቅቅ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ እና ትብብር ያደርጋል፣ አመልካችም ትምህርቷን ለማጠናቀቅ የምታቀርበውን ጥያቄ በቅንነት በመመልከት ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ይገመታል። ተዋዋይ ወገኖች በውል የገቡትን ግዴታ በመተማመንና በቅንነት ውሉን ይፈፅማሉ ተብለው ሊገመቱና በዚሁ መንገድ ትርጉም ሊሰጥ እንደሚገባው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1732 ተደንግጓል። ከዚህ አንፃር ሲታይ የተጠሪን ግልፅ የሆነ አሉታዊ ምላሽ ለመስጠት፣ አመልካች ጥያቄዎን እንደተቀበላት በመቁጠር ትምህርቷን ለማጠናቀቅ የግድ አስፈላጊ የሆነውን የመመረቂያ ፅሑፍ የማዘጋጀት፣ በሥራ ገበታዋ ላይ ሣትገኝ መቅረቷ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ1/ለ/ መሠረት ያለበቂ ምክንያት ከሥራ ቦታ እንደቀረች የሚያስቆጥር ሆኖ አላገኘነውም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

9. በአንዛሩ አመልካች ትምህርቷን ለማጠናቀቅ ያልተጠቀመችበት የዓመት ፈቃድ እንዲሰጣትና፣ የዓመት ፈቃዷን የምትፈልገው ዩኒቨርሲቲው ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ የመመረቂያ ፅሑፏን አጠናቅቃ ለማስረከብ እንደሆነ በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 84 መሠረት ለተጠሪ አሳውቃለች፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ባደረገው የሥልጠናና የትምህርት ውል መሠረት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 83 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት የትምህርት ፈቃድ በመስጠት አመልካች ትምህርቷን እንድታጠናቅቅ የመደገፍ ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች ትምህርቷን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ልዩ ፈቃድ ተጠሪ እንዲሰጣት ሣይሆን የዓመት ፈቃዷን በመጠቀም ትምህርቷን ለማጠናቀቅ ላቀረበችው ጥያቄ ግልፅ ምላሽ ሣይሰጥ አመልካች ከስራ ገበታዋ አልተገኘችም በማለት የሥራ ውሉን ማቋረጡ፣ ከላይ የገለፅናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚቃረንና የሕግ መሠረት የሌለው ተግባር ነው፡፡ በሌላ በኩል በዚህ መዝገብ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው የአሠሪና ሠራተኛ እና የትምህርትና ሥልጠና ውል ግንኙነትና አመልካች ከሥራ የቀረችበት ምክንያትና ሁኔታ ተጠሪ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የወሰደው እርምጃ ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 37778፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 37402 እና በሌሎች መዛግብት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሰጠባቸው ጉዳዮች የተለየ በመሆኑ፣ ተጠሪ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአግባቡ ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ የሥራ ውሉን ያቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 130114 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን ከሥራ ያሰናበታት ከሕግ ውጭ ነው በማለት በመዝገብ ቁጥር 57393 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
- ተጠሪ የአንድ ዓመት ደመወዝ በመክፈል አመልካችን ወደ ሥራ ሊመልሳት ይገባል በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 5 መሠረት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡
- በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡
የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93511

የካቲት 24 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ደረሰ ወርቁ ቀረቡ፤

ተጠሪ፡- በርሔ ሐጎስ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ጠበቃ ነገሠ ጋሹ ቀረቡ፤

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ፡- ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በቶንጎ-ቤጊ-ጊዳሚ የመንገድ ስራ ኘሮጀክት ከ10/02/2003 ዓ.ም ጀምሮ በክሊኒካል ነርስ የስራ መደብ በወር ብር 2,346.00 ደመወዝ ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበረ፣ ኘሮጀክቱ በመጠናቀቁ ተከሳሽ ድርጅት ሌሎች ሰራተኞችን በሙሉ ወደ ሌላ ቦታ ሲያዛውር ከሳሽን በባዶ ካምኘ ማስቀመጡ አግባብ እንዳልሆነ በመግለጽ ከሳሽ በ17/08/2004 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ለድርጅቱ በማሳወቃቸው ድርጅቱ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንደሰጣቸው፣ ከሳሽ ማስጠንቀቂያውን በመቃወም የጽሁፍ ምላሽ በመስጠታቸው ተከሳሽ ድርጅት በ17/09/2004 ዓ.ም የስራ ውላቸውን እንዳቋረጠባቸው የሚገልጽ ሆኖ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ ተከሳሽ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲፈጽምላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ13/10/2004 ዓ.ም በተዘጋጀ መልስ የቶንጎ-ቤጊ የመንገድ ስራ ኘሮጀክት ስራ ተጠናቆ ሰራተኞች ወደ ጊዳሚ-ሙጊ የመንገድ ስራ ኘሮጀክት ሲዛወሩ ከሳሽም አብረው የተዛወሩ መሆኑን፣ በወቅቱ ከሳሽ ዝውውሩን ተቀብለው ጊዳሚ-ሙጊ በሚገኘው የተከሳሽ ድርጅት ካምኘ ውስጥ ስራ ጀምረው የነበረ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ በዚህን ጊዜ ክሊኒኩን እየዘጉ ሌላ ቦታ በመዋላቸው አደጋና ጉዳት ለሚደርስባቸው ሰራተኞች የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ የሚሰጥ ባለሙያ ጠፍቶ የነበረ መሆኑን፣ ከሳሽ ለከፊሉ ሰራተኛ ህክምና በመስጠት እና ለከፊሉ ደግሞ በመከልከል በአንድ ድርጅት ሰራተኞች መካከል ልዩነትን እና መከፋፈልን የፈጠሩ መሆኑን፣ በመጨረሻም ከሳሽ ወደ ዋናው መስሪያ ቤት እንዲላኩ እና ከኘሮጀክቱም እንዲሰናበቱ በጠየቁት መሰረት የኘሮጀክቱን ክሊኒክ ከዘጉበት እና ስራ አልሰራም ብለው ካቆሙበት ከ12/08/2004 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቱም የተከሳሽን አንድ ምስክር ከሰማ በኋላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ከሳሽ በ29/08/2004 ዓ.ም የተሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ በመቃወም ለተከሳሽ ድርጅት በ01/09/2004 ዓ.ም የጻፉት ደብዳቤ ድርጅቱ "...መጀመሪያ ወደ ቀጠረኝ መስሪያ ቤት መላክ ይህ የማይሆን ከሆነ ማሰናበት ይችላል፡፡" የሚል አባባል ያዘለ ቢሆንም የደብዳቤው አጠቃላይ ይዘት ከሳሽ መሰናበት ስለምፈልግ አሰናብቱኝ ማለታቸውን የሚያመለክት አይደለም በማለት ይህንን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ ተከሳሽ ድርጅት የወሰደው የስንብት እርምጃ ሕገወጥ ነው፤ በመሆኑም ሕገወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች ተከሳሽ ለከሳሽ ሊከፍልና የምስክር ወረቀት ሊሰጣቸው ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በስር ተከሳሽ አቅራቢነት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ከሳሽ ኘሮጀክቱ በመጠናቀቁ ተከሳሽ ድርጅት ሌሎች ሰራተኞችን በሙሉ ወደ ሌላ ቦታ ሲያዛውር እኔን በባዶ ካምኘ አስቀምጦኛል በማለት የተከራከሩ ቢሆንም የኘሮጀክቱ ስራ አለመጠናቀቁን ራሳቸው በ20/06/2004 ዓ.ም ለተከሳሽ በጻፉት ደብዳቤ መግለጻቸውን፣ በቅጥር ውላቸው ተራ ቁጥር 15 በተመለከተው መሰረት ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽን አዛውሮ የማሰራት መብት ያለው ሆኖ እያለ ከሳሽ በ17/08/2004 ዓ.ም ለተከሳሽ በጻፉት ደብዳቤ አዲስ ድርድር እስካላደረግን ድረስ በሰራተኛው ላይ ለሚደርሰው ችግር ተጠያቂ አይደለሁም በማለት መግለጻቸው ክሊኒኩን ዘግተው ያለስራ የሚንቀሳቀሱበት ጊዜ እንደነበረ በተከሳሽ ድርጅት የቀረበውን ክርክር የሚያጠናክር መሆኑን፣ በመጨረሻም ከሳሽ በ01/09/2004 ዓ.ም ለተከሳሽ በጻፉት ደብዳቤ ማኔጅመንቱ ጥያቄዬን የመመለስ ብቃት የለውም፣ ወደቀጠረኝ መ/ቤት መመለስ አለብኝ፣ ይህ ካልሆነ ልሰናበት ይገባል በማለት መግለጻቸው የስራ ውሉ የተቋረጠው ከራሳቸው በቀረበ ጥያቄ መሰረት እንደሆነ የሚያመለክት መሆኑን ገልጾ የስንብቱን ሕገወጥነት በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ሲሽር የ43 ቀን ደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓት ማካካሻ አበል፣ የጉዞ አበል እና ክፍያ ለዘገየበት የተወሰነውን ገንዘብ በተመለከተ ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የይ/ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ በ01/09/2004 ዓ.ም ለተከሳሽ የጻፉትን ደብዳቤ ይዘት መሰረት በማድረግ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት በአግባቡ የሰጠውን ውሳኔ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ደብዳቤውን በአግባቡ ሳይተረጉም የሰጠው ውሳኔ ከሕግ ውጪ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡትን ቅሬታ ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የይ/ሰሚው ፍ/ቤት ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የተቋቋመ አንድ የስራ ውል በሰራተኛው አነሳሽነት እንደነገሩ አግባብ በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች በአዋጁ አንቀጽ 31 እና 32 ስር ተመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ከስር ጀምሮ የሚከራከረውም አመልካችን ከስራ ያሰናበትኩት በእነዚሁ ድንጋጌዎች መሰረት አመልካች የስራ ውሉ እንዲቋረጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል ነው በማለት መሆኑን የክርክሩ ይዘት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በ01/09/2004 ዓ.ም ለተጠሪ የጻፉት ደብዳቤ አጠቃላይ ይዘት ሲታይ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸውን የስራ ውል ለማቋረጥ ተነሳስተው በአዋጁ አንቀጽ 31 ወይም 32 በተመለከተው መሰረት የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ መወሰናቸውን የገለጹበት ሳይሆን በ29/08/2004 ዓ.ም የተሰጣቸውን የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመቃወም ለድርጅቱ ምላሽ የሰጡበት መሆኑን ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች በዚሁ በ01/09/2004 ዓ.ም ለተጠሪ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ተጠሪ ድርጅት በአመልካች ደብዳቤ ላይ የተጠየቀውን ጥያቄ ተቀብሎ ተገቢውን መፍትሔ እንዲሰጣቸው፣ ይህን የማያደርግ ከሆነ ግን ማሰናበት እንደሚችል የገለጹት ሀሳብም ቢሆን ተጠሪ ሌሎች መፍትሔዎችን መስጠቱን ትቶ ማሰናበቱን የሚመርጥ ከሆነ የማሰናበት እርምጃውን ከሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ጋር መቀበል እንደሚገባው መጠየቃቸውን የሚጠቁም ነው ከሚባል በቀር በራሳቸው አነሳሽነት የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ መፈለጋቸውን የሚያረጋግጥ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል በይ/ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ እንደሰፈረው አመልካች በስራው ላይ በነበሩበት ጊዜ የተጠሪን ጥቅም የሚጎዱ የተለያዩ ድርጊቶችን ይፈጽሙ የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪ ከስር ጀምሮ የተለያዩ የክርክር ነጥቦችን ያቀረበ መሆኑን ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ የተቻለ ቢሆንም በመሰረቱ ተጠሪ አመልካችን ከስራ ያሰናበተው በ01/09/2004 ዓ.ም ለተጠሪ በጻፉት ደብዳቤ የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ ጠይቀዋል በማለት እንጂ የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ የሚያስችል ጥፋት ፈጽመዋል በማለት ባለመሆኑ አመልካች በስራው ላይ በነበሩበት ጊዜ የፈጸሙት ጥፋት መኖር አለመኖሩ እና ካለም መጠኑ እና የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት በዚህ መዝገብ በተያዘው ክርክር ላይ ሊመረመር የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ከሳሽ በ01/09/2004 ዓ.ም ለተከሳሽ በጻፉት ደብዳቤ ማኔጅመንቱ ጥያቄዬን የመመለስ ብቃት የለውም፣ ወደቀጠረኝ መ/ቤት መመለስ አለብኝ፣ ይህ ካልሆነ ልሰናበት ይገባል በማለት መግለጻቸው የስራ ውሉ የተቋረጠው ከራሳቸው በቀረበ ጥያቄ መሰረት እንደሆነ የሚያመለክት ነው በማለት ለደረሰበት ድምዳሜ አመልካች በስራው ላይ በነበሩበት ጊዜ የተጠሪን ጥቅም የሚጎዱ የተለያዩ ድርጊቶችን ይፈጽሙ ነበር የመባሉን ጉዳይ በተጨማሪ ምክንያትነት በመቀበል በውሳኔው ላይ ማስፈሩ ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት የተከተለ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች በ01/09/2004 ዓ.ም ለተጠሪ የጻፉት ደብዳቤ የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ መፈለጋቸውን የሚያረጋግጥ ነው በማለት ይ/ሰሚው ፌ/ከ/ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ይህንኑ ድምዳሜ መሰረት በማድረግ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ሽሮ የስራ ስንብት እርምጃው ሕጋዊ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የደብዳቤውን እና የግራ ቀኙን አጠቃላይ የክርክር ይዘት ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት በመ/ቁ 78899 በ29/08/2005 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 135599 በ26/11/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የስራ ስንብት እርምጃው ሕገወጥ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ለአመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲፈጽም እና የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 78899 በ29/08/2005 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዘ/ቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93532

ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-አቶ በኃይሉ ደቦጭ አንበሴ..... ጠበቃ ገ/እግዚአብሄር ኪዳኔ ቀረቡ

ተጠሪ፡-ኢትዮጵያ ገብራት ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ተወካይ አቶ ግርማ መ·ለታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ ከሳሽ ከ20/05/2003 ዓ.ም.ጀምሮ በተከሳሽ ድርጅት በወር በብር 1,400 ደመወዝ ተቀጥረው በመስራት ላይ እያሉ ተከሳሽ ድርጅት ከ13/02/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ካለክፍያ እና ካለስራ እንዳስቀመጣቸው የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሽ ድርጅት የሰሩበትን የ4 ወር ደመወዝ እና ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ የስራ ስምሪት እንዲሰጣቸው፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነ ደግሞ የ4ወር ውዝፍ ደመወዝ፣የስራ ስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣የዓመት ዕረፍት ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት ተገቢውን ክፍያ እንዲፈጽም ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ ከሳሽን ደመወዝም ሆነ ስራ እንዳልከለከላቸው፣ከሳሽ የነሐሴ እና የመስከረም ደመወዝ ሳይቀበሉ የቀሩት ከጂቡቲ ዕቃ ጭነው ወደ ክልል ከተሞች ስለሚያዘዋውሩ በዚህ ሳቢያ በተፈጠረው ክፍተት እና በኋላም የሚፈለግባቸውን የ180 ሊትር ነዳጅ ጉድለት ገቢ እንዲያደርጉ በ14/02/2004 ዓ.ም. በተጻፈ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ስላልነበሩ እንደሆነ፣ከሳሽ የያዙት ተሽከርካሪ ችግር እንዳለበት በ12/11/2004 ዓ.ም. ባመለከቱት መሰረት ተሽከርካሪው ለጥገና ሲቆም ከሳሽ ጥገናውን መከታተል ሲገባቸው ትተው ወደ ቤታቸው እንደሄዱ፣ከሳሽ ከ14/02/2004 ዓ.ም. ጀምሮ በራሳቸው ምክንያት ከስራ የቀሩ ስለሆነ ላልሰሩት ስራ ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው፣ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽን ከስራ ባሳሰናበተበት ሁኔታ የስንብት እና ተያያዥ ክፍያዎችን ለመክፈል እንደማይገደድ እና ከሳሽ የነሐሴ እና የመስከረም ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ከፈለጉ ስራ ሊቀጥሉ እንደሚችሉ በመግለጽ መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱን ከሰማ በኋላ ሁለቱም ወገኖች ምስክሮቻቸውን ይዘው እንዲቀርቡ በሰጠው ቀጠሮ ተከሳሽ በትዕዛዙ መሰረት ባለመፈጸሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 199(1) መሰረት መብቱን በማለፍ በከሳሽ በኩል የቀረቡትን ምስክሮች ሰምቷል፡፡ከዚህ በኋላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሳሽ የስራ ውሉ ተቋርጦብኛል በማለት ያቀረቡት ክስ ባለመኖሩ የስራ ስንብት እና ተያያዥ ክፍያዎች እንዲፈጸሙላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ስነ ስርዓታዊ አግባብ እንደሌለው፣ከሳሽ ጥቅምት 15 እና 16 ቀን 2004 ዓ.ም. ወደ ድርጅቱ ግቢ እንዳይገቡ በድርጅቱ የጥበቃ ሰራተኞች መከልከላቸውን በምስክሮች ያስረዱ ቢሆንም የጥበቃ ሰራተኞቹ ክልከላውን የፈጸሙት ማን በሚባል ኃላፊ ትዕዛዝ እንደሆነ ከሳሽ እንዳላስረዱ በዝርዝር ገልጾ ተከሳሽ ድርጅት የነሐሴ እና የመስከረም ወር እንዲሁም ከሳሽ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን ባስረዱት መሰረት ከጥቅምት ወር 2004 ዓ.ም. ደመወዝ ውስጥ እስከ ማስጠንቀቂያው ቀን ማለትም እስከ ጥቅምት 21 ቀን ድረስ ያለውን ደመወዝ ከፍሎ ለከሳሽ ስራ እና የስራ ስምሪት እንዲሰጣቸው በማለት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ወደስራ ገበታቸው እንዳይገቡ በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች መከልከላቸው እና የስር ፍ/ቤት የስራ ውሉ ያልተቋረጠ መሆኑን በማረጋገጥ ለከሳሽ የስራ ስምሪት እንዲሰጣቸው መወሰኑ በተረጋገጠበት፣ነገር ግን አሰሪው በተግባር የስራ ስምሪት ባልሰጠበት ሁኔታ አመልካች ስራቸውን ተገደው ካቆሙበት ጊዜ ጀምሮ የተቋረጠባቸው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያቀረቡትን የመብት ጥያቄ የስር ፍ/ቤቶች ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 54(2) አንፃር ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በፍትሐብሔር ክርክር አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር ማስረዳት እንደሚጠበቅበት እና በአንፃሩም ግዴታ ፍርስ ነው ወይም ተለውጧል የሚለው ወገንም ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2001(1) እና(2) ድንጋጌዎች የተመለከተ ሲሆን ከዚህ ድንጋጌ አንፃር አመልካች በስራ ገበታቸው ላይ ለመገኘት ያልቻሉት ወደ ተጠሪ ግቢ ማለትም ወደ ስራ ቦታቸው እንዳይገቡ ጥቅምት 15 እና 16 ቀን 2004 ዓ.ም. በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች ስለተከለከሉ መሆኑን በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አቅርበው ባሰሟቸው ምስክሮች ማስረዳታቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በዚህ ረገድ ከአመልካች ለቀረበው የክርክር ነጥብ ተጠሪ በሰበር መልሱ ያቀረበው የማስተባበያ ክርክር የለም፡፡

አመልካች ከ14/02/2004 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ የቀሩት በራሳቸው ምክንያት በመሆኑ ላልሰሩበት ጊዜ ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ከማለት በስተቀር አመልካች ከ14/02/2004 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ የቀሩት በርግጥም በራሳቸው ምክንያት ስለመሆኑ ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ አለመኖሩን እና ይልቁንም ምስክሮቹን አቅርቦ እንዲያሰማ በተሰጠው ቀጠሮ ባለመቅረቡ መብቱ የታለፈ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት በመሆኑ ተጠሪ በሕግ የተጣለበትን ክርክሩን በማስረጃ የማስረዳት ግዴታ ተወጥቷል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ወደ ተጠሪ ግቢ ማለትም ወደ ስራ ቦታቸው እንዳይገቡ ጥቅምት 15 እና 16 ቀን 2004 ዓ.ም በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች እንደተከለከሉ ማስረዳታቸውን ተቀብሎ እያለ በተጠሪ ክልከላ ምክንያት በስራ ገበታቸው ላይ መገኘትና መስራት ላልቻሉባቸው ጊዜያት ያለው ደመወዝ ታስቦ እንዲከፈላቸው አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረገው የተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች የክልከላውን ድርጊት የፈጸሙት ማን በሚባል የስራ ኃላፊ ትዕዛዝ እንደሆነ አመልካች አላስረዱም በማለት መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያመለክታል፡፡ይሁን እንጂ ክልከላውን የፈጸሙት የጥበቃ ሰራተኞች የተጠሪ ሰራተኞች መሆናቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ስራቸውን የሚያከናውኑት ከአሰሪ በሚሰጣቸው ትዕዛዝ እንደሆነ የሚታመን በመሆኑ የክልከላ ድርጊቱን የፈጸሙት ከተጠሪ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት እንደሆነ ይገመታል፡፡ትዕዛዙን የሰጣቸው የተጠሪ የስራ ኃላፊ የሚያውቁት ትዕዛዙን የሰጡት የስራ ኃላፊ እና የተቀበሉት የጥበቃ ሰራተኞች ከመሆናቸው ውጪ አመልካች የትዕዛዝ ሰጪውን የስራ ኃላፊ ማንነት ሊያውቁ የሚችሉበት መንገድም ሆነ እንዲያስረዱ የሚገደዱበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

ወደ ስራ እንዳይገቡ በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች መከልከላቸውን ማስረዳታቸው ብቻ በቂ ሲሆን ይህንን ማስረዳታቸው ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በስር ፍ/ቤቶችም ቢሆን ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡ተጠሪም ቢሆን የጥበቃ ሰራተኞቹ የክልከላ ተግባሩን የፈጸሙት ከተጠሪ የስራ ኃላፊዎች የተሰጣቸው ትዕዛዝ ሳይኖር ነው በሚል ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ወደ ተጠሪ ግቢ እንዳይገቡ በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች እንደተከለከሉ ማስረዳታቸውን ተቀብሎ እያለ ከዚሁ ድምዳሜው ጋር በሚቃረን ሁኔታ የተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች የክልከላውን ድርጊት የፈጸሙት ማን በሚባል የስራ ኃላፊ ትዕዛዝ እንደሆነ አመልካች አላስረዱም በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሰረቱ ደመወዝ የሚከፈለው ለተሰራ ስራ ብቻ እንደሆን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 54(1) ስር በመርህ ደረጃ የተደነገገ ቢሆንም ሰራተኛው ለስራ ዝግጁ ሆኖ እያለ ለስራው የሚያስፈልገው መሣሪያ እና ጥሬ ዕቃ ሳይቀርብለት በመቅረቱ ወይም በሰራተኛው ጉድለት ባልሆነ ምክንያት ሳይሰራ ቢውልም ደመወዙን የማግኘት መብት እንደሚኖረው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ(2) ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በስራ ገበታቸው ላይ ለመገኘት ያልቻሉት በተጠሪው ክልከላ ምክንያት እንጂ የራሳቸው በሆነ ጉድለት ምክንያት አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የክልከላው ተግባር ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ በስር ፍ/ቤት ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 54(2) ድንጋጌ መሰረት ደመወዛቸውን እንዲያጡ ሊደረግ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ወደ ስራ ቦታቸው እንዳይገቡ በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች እንደተከለከሉ ማስረዳታቸውን ተቀብሎ እያለ የጥበቃ ሰራተኞቹ የክልከላውን ድርጊት የፈጸሙት ማን በሚባል የስራ ኃላፊ ትዕዛዝ እንደሆነ አመልካች አላስረዱም በማለት በክልከላው ምክንያት በስራ ገበታቸው ላይ መገኘትና መስራት ላልቻሉባቸው ጊዜያት ያለው ደመወዝ ታስቦ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲከፈላቸው አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው እና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 68705 በ15/01/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በ12/02/2005 ዓ.ም. የተነበበው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 129978 በ18/10/2005 በውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ አመልካች ወደ ስራ ቦታቸው እንዳይገቡ በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች እንደተከለከሉ ማስረዳታቸው በስር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ያገኘ ሆኖ እያለ የጥበቃ ሰራተኞቹ የክልከላውን ድርጊት የፈጸሙት በየትኛው የስራ ኃላፊ ትዕዛዝ እንደሆነ አመልካች አላስረዱም በማለት በክልከላው ምክንያት በስራ ገበታቸው ላይ መገኘትና መስራት ላልቻሉባቸው ጊዜያት ያለው ደመወዝ ታስቦ እንዲከፈላቸው አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
3. አመልካች በስራ ገበታቸው ላይ ለመገኘት ያልቻሉት በተጠሪው ክልከላ ምክንያት እንጂ የራሳቸው በሆነ ጉድለት ምክንያት እንዳልሆነ የተረጋገጠ በመሆኑ ከጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ማለትም እስከ ጥቅምት 12 ቀን 2005 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ደመወዝ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 54(2) መሰረት ለአመልካች የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት ወስነናል፡፡
4. ከላይ በተ.ቁ. 2 ስር ከተገለጸው ውጪ ያለው የስር ፍ/ቤቶች የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
5. ተጠሪ ለቀጣዩ የስራ ስምሪት እንዲሰጣቸው ይወሰን ዘንድ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በተመለከተ በስር ፍ/ቤቶች በተወሰነው መሰረት ከሚያስፈጽሙ በቀር በስራ ስምሪት ረገድ በዚህ ችሎት የሚሰጥ ውሳኔ አይኖርም፡፡
6. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ረታ ቶሎሳ
አዳነ ንጉሴ
መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር /ጠበቃ ማሞ ካሳ ቀረቡ/

ተጠሪ፡- ሙሉጌታ አምባዬ /ጠበቃ አምዶም ታደለ ቀረቡ/

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ክሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ በ20/07/2005 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሳቸውም ይዘት ባጭሩ ከሳሽ ከ18/12/2003 ዓ.ም ጀምሮ በተከሳሽ ድርጅት ብር 4,000 የወር ደመወዝ እየተከፈላቸው በጄኔራል ፎርማንነት ተቀጥረው እስከ 15/07/2005 ዓ.ም ድረስ ሲሰሩ እንደነበረ ተከሳሽ ድርጅት በ11/07/2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ስራው አልቋል በሚል ምክንያት ከ15/07/2005 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸው መቋረጡን እንደገለፀላቸው ይሁን እንጂ ተከሳሽ ድርጅት በተለያዩ ቦታዎች ኮንትራት የያዛቸው ስራዎች እንዳሉት ሲሰሩበት የነበረው የትግራይ ክልል ምክር ቤት ህንፃም እንዳልተጠናቀቀ፤ ርክክብም እንዳልተፈፀመ እና ስራው ባለማለቁ ከ70 በላይ ሰራተኞች በስራ ላይ እንደሚገኙ የተገለፀበት ሆኖ ስንብቱ ህገወጥ ነው ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት ህገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች እና የበዓላት ቀናት ክፍያ ተከሳሹ እንዲፈፅምላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ ከሳሽ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው የተቀጠሩበት የፕሮጀክት ስራ እየተገባደደና ለርክክብ እየተዘጋጀ በመሆኑ ምክንያት በአዋጁ አንቀፅ 30(1) እና (2) መሰረት በአግባቡ መሆኑን እና ሲሰናበቱ ተገቢ ክፍያዎች የተፈፀሙላቸው መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱንና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ተከሳሽ ሲሰራው ከነበረው የጎንደር ዩኒቨርስቲ ተዛውሬ ወደ መቐሌ ፕሮጀክት የመጣሁ ስለሆነ ቋሚ ሰራተኛ ነኝ በማለት ከሳሽ የተከራከሩ ቢሆንም ከጎንደር ፕሮጀክት ወደ መቐሌ ፕሮጀክት ተዛውረው እንዲመጡ የተደረገው የጎንደር ፕሮጀክት አልቆ ወደ መቐሌ ፕሮጀክት በመዛወራቸው ሳይሆን ስራ በማበላሸታቸው ጥፋቱ እንዳይደገም በማስጠንቀቂያ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ሰራተኛ ነኝ በማለት ከሳሽ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው፣ ከሳሽ የተቀጠሩት በአዋጁ አንቀፅ 10 መሰረት ለተወሰነ ስራ እንደሆነ ፣የተሰናበቱትም የፕሮጀክቱ የስራ መጠን ወደ መጠናቀቅ በመቃረቡና በከሳሽ ሲሰራ የነበረው ስራ በማለቁ መሆኑ በግራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀኙ ምስክሮች የተገለጸ በመሆኑ ምክንያት ስንብቱ ህጋዊ መሆኑን ገልፆ ክሱን ውድቅ በማድረግ የ18 ቀናት የበዓላት ቀናት ክፍያ ብር 4,799.99 ከ10% የጠበቃ አበል ጋር ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በውሳኔው ቅር በመሰኘት በስር ከሳሽ ጠያቂነት በቀረበለት ይግባኝ መነሻ የመቐሌ ከተማ ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአዋጁ አንቀፅ 30 ተፈፃሚነት የሚኖረው አናጢዎችን ግንበኞችን ለሳኞችን እና የመሳሰሉትን የጉልበት ሰራተኞች በተመለከተ እንጂ ከሳሹ በነበረበት የጀኔራል ፎርማን የስራ መደብ ላይ የተመደቡትን ዓይነት ሰራተኞች በተመለከተ ጭምር አለመሆኑን እና ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽን ከጎንደር ፕሮጀክት ወደ መቐሌ ፕሮጀክት አዛውሮ እንዳሰራው ሁሉ ወደሌላኛው ፕሮጀክት አዛውሮ ማሰራት የማይችልበት ምክንያት መኖሩን እስካላስረዳ ድረስ ስንብቱ ህጋዊ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን ገልጾ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ሽሮ ስንብቱ ህገ ወጥ በመሆኑ ተከሳሽ ድርጅት ህገ ወጥ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች ለከሳሽ እንዲፈጽም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች አስቀድሞ የጎንደር ዩንቨርሲቲ ህንፃ ኘሮጀክት እስከሚጠናቀቅ ብቻ ተቀጥሮ ሲሰራ ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ ወደ ትግራይ ክልል ምክር ቤት ሕንፃ ኘሮጀክት ተዛውሮ እየሰራ እያለ መሰናበቱ ሕገወጥ ነው በማለት ላቀረበው ክስ ስንብቱ የተደረገው የሕንፃው ስራ እየተጠናቀቀ በመሆኑ ነው በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር በስር ፍ/ቤቶች ሳይታይ ታልፎ አመልካች ዝውውር መፈፀሙ ተጠሪን ላልተወሰነ ጊዜ እንደቀጠረው ያስቆጥራል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሠረት ቀደም ሲል እንደተገለፀው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ውሳኔ ለመስጠት የቻለው ከሳሽ የተቀጠሩት በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት ለተወሰነ ስራ መሆኑን የተሰናበቱትም የኘሮጀክቱ የስራ መጠን ወደመጠናቀቅ በመቃረቡና በከሳሽ ሲሰራ የነበረው ስራ በማለቁ መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ መሆኑን እና የኘሮጀክቱ የስራ መጠን ወደመጠናቀቅ መቃረቡና በከሳሽ ሲሰራ የነበረው ስራ ማለቁ ደግሞ በከሳሽ ምስክሮች ጭምር የተገለፀ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ይ/ሰሚው የመቐሌ ከተማ ከ/ፍ/ቤት ይህንን የወረዳ ፍ/ቤት ሽሮ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው የአዋጁ አንቀጽ 30 ተፈፃሚነት የሚኖረው የጉልበት ሰራተኞችን በተመለከተ እንጂ ከሳሹ በነበረበት የጀኔራል ፎርማን የስራ መደብ ላይ የተመደቡትን ዓይነት ሰራተኞችን በተመለከተ ጭምር አለመሆኑን እና ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽን ከጎንደር ኘሮጀክት ወደ መቀሌ ኘሮጀክት አዛውሮ እንዳሰራው ሁሉ ወደሌላኛው ኘሮጀክትም አዛውሮ ማሰራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይችልበት ምክንያት መኖሩን እስካላስረዳ ድረስ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም በማለት ነው፡፡ በመሰረቱ አመልካች ተጠሪን ከጎንደር ወደ መቐሌ ፕሮጀክት ያዛወረው የጎንደር ፕሮጀክት በማለቁ ሳይሆን ተጠሪ ይሰሩበት በነበረው የጎንደር ፕሮጀክት ላይ የስራ አፈጻጸም ግድፈት በማሳየታቸው ከመሆኑ ውጪ የጎንደር ፕሮጀክት በማለቁ ምክንያት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ አልተረጋገጠም፡፡ ተጠሪ ወደ መቀሌ ፕሮጀክት እንዲዛወሩ የተደረገው ይሰሩበት በነበረው የጎንደር ፕሮጀክት ላይ የስራ አፈጻጸም ግድፈት በማሳየታቸው ስለመሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት የዝውውር ደብዳቤውን ጠቅሶ በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሯል፡፡

ይ/ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ ይህንኑ ደብዳቤ በመጥቀስ አመልካች ተጠሪን ከጎንደር ወደ መቀሌ ፕሮጀክት አዛውሮ ሲያሰራ ነበር ከማለት በስተቀር የዝውውሩ ምክንያት በወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ የተገለጸው ስላለመሆኑ የገለጸው ነገር የለም፡፡ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ለመሻር መነሻ ካደረጋቸው ምክንያቶች አንዱ የዝውውሩ ጉዳይ ከሆነ ደግሞ ዝውውሩን አስመልክቶ በወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ የተገለጸው ፍሬ ነገር ተቀባይነት የሚያጣበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ በግልጽ ማስፈር ይጠበቅበታል፡፡ በመሰረቱ በተቀጠረበት ፕሮጀክት ላይ የስራ አፈጻጸም ግድፈት የፈጸመን ሰራተኛ አሰሪው ሌላ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ወደ ሌላ ፕሮጀክት ማዛወሩ ሰራተኛውን የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ተግባር አይደለም፡፡ በመሆኑም ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የዝውውሩን ምክንያት ሳይጠቅስ ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽን ከጎንደር ፕሮጀክት ወደ መቀሌ ፕሮጀክት አዛውሮ የማሰራቱን ሁኔታ ብቻ ነጥሎ ለውሳኔው ምክንያት ማድረጉ ተገቢውን የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት የተከተለ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል የአዋጁ አንቀጽ 30 ተፈጻሚነት የሚኖረው የጉልበት ሰራተኞችን በተመለከተ እንጂ ከሳሹ በነበሩበት የጀኔራል ፎርማን የስራ መደብ ላይ የተመደቡትን ዓይነት ሰራተኞች በተመለከተ ጭምር አይደለም በማለት ይ/ሰሚው የደረሰበትን ድምዳሜ በተመለከተ በመሰረቱ የጀኔራል ፎርማን የስራ መደብ ከአመልካች ድርጅት አስተዳደራዊ ስራዎች ጋር የሚገናኝ ሳይሆን በቀጥታ በኮንስትራክሽን ወይም ከግንባታ ስራ ጋር የተያዘ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ተጠሪም ተሰማርተው የነበሩት በቢሮ ወይም በአስተዳደራዊ ስራዎች ላይ ሳይሆን በቀጥታ በፕሮጀክት ወይም በግንባታ ስራዎች ላይ ስለመሆኑ ያላስተባበሉት እና በክስ ማመልከቻቸውም ላይ የገለጹት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 30 በተመለከተው መሠረት የሚከናወን ቅነሣ የጉልበት ሰራተኞችን እንጂ እንደ አሁኑ ተጠሪ ዓይነት በጀነራል ፎርማን የስራ መደብ ላይ የተቀጠሩትን ሰራተኞች የሚመለከት አይደለም በማለት ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ የአዋጁን ድንጋጌ ይዘትም ሆነ በክርክሩ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች የተሰማራበት የኮንስትራክሽን ስራ ቀጣይነት ያለው በመሆኑ አንዱ ፕሮጀክት ሲያልቅ ተጠሪን ወደ ሌላኛው ፕሮጀክት አዛውሮ ሊያሰራው ይገባል በማለት በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተያዘውን አቋም በተመለከተ እንደተባለው አመልካች የተሰማራው በኮንስትራክሽን ስራ ላይ መሆኑ እና ስራውም ቀጣይነት ያለው መሆኑ የሚታወቅ እና በአመልካችም ያልተስተባበለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች እንደማንኛውም የኮንስትራክሽን ድርጅት ስራውን የሚያከናውነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፕሮጀክቶች በመከፋፈል ነው፡፡ ፕሮጀክቶቹን በውድድር የሚያገኛቸው እንጂ እራሱ ፈጥሮ የሚያከናውናቸው አለመሆኑም የሚታወቅ ነው፡፡ ይህም አመልካቹ የሚያከናውናቸውን ፕሮጀክቶቹ የሚጀምርበትን ጊዜ የሚወስነው በራሱ ሣይሆን በሚገባበት የውል ግዴታ መሠረት መሆኑን እና በተመሣሣይ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ ፕሮጀክቶች ሊኖሩት የሚችሉ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ በመሆኑም ለአንድ ፕሮጀክት የተቀጠረ ሰራተኛን ፕሮጀክቱ ሲያልቅ ወደ ሌላ ፕሮጀክት አዛውሮ ለማሰራት በኮንስትራክሽን የሰራ ዘርፍ በተሰማራ አሰሪ ላይ በሕግ የተጣለ ግዴታ አለመኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ማዛወር ቢኖርበት እንኳ ማዛወር የሚችለው በሌላኛው ፕሮጀክት ውስጥ በተመሣሣይ የሰራ መደብ ክፍት ቦታ በተገኘ ጊዜ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ ፕሮጀክት አዛውሮ ሊያሰራው ይችል ነበር ከማለት በስተቀር በሌላኛው ፕሮጀክት የተጠሪ የሰራ መደብ ክፍት ስለመሆኑ እንኳ አላረጋገጠም፡፡ በመሆኑም ተከሣሽ ድርጅት ከሣሽን ከጐንደር ፕሮጀክት ወደ መቐሌ ፕሮጀክት አዛውሮ እንዳሰራው ሁሉ ወደ ሌላኛው ፕሮጀክት አዛውሮ ማሰራት የማይችልበት ምክንያት መኖርን አላሰረዳም በማለት ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ በህግም ሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለል ይ/ሰሚው የመቀሌ ከተማ ከ/ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ለመሻር የሚያስችል በቂ የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት ሳይኖር በማስረጃ በተረጋገጠው መሰረት የህግ አግባብ የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በመቀሌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09635 በ06/09/2005 ዓ.ም የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የመቀሌ ከተማ ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13289 በ27/12/205 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ክሱን ውድቅ በማድረግ የ18 ቀናት የበዓላት ቀናት ክፍያ ብር 4,799.99 (አራት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ከ ዘጠና ዘጠኝ ሳንቲም) ከ10% የጠበቃ አበል ጋር ተከሻሽ ለከሳሽ እንዲከፍል የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09635 በ06/09/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348 (1)መሠረት ፀንቷል፡፡
3. የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10104 የተያዘው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ27/01/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ል/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93828

የካቲት 11 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ – ጠበቃ አውላቸው ደሣለኝ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ካፒቴን እንድሪያስ ጀምሬ – ጠበቃ ዶ/ር ያሬድ ለገሠ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን ከሰ/መ/ቁጥር 91872 ጋር አጣምረን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 494/1998 መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈልበትን ሕጋዊ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከመጋቢት 10 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በአውሮፕላን አብራሪነት የሥራ መደብ ተቀጥረው በወር ያልተጣራ ብር 91,623.60 እየተከፈላቸው ሲሰሩ ቆይተው የአንድ ወር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሰጥተው የሥራ ውላቸውን ያቋረጡና ንብረቶቹን ያስረከቡ ቢሆንም አመልካች ድርጅት ሕጋዊ ክፍያዎችን ያልፈፀመላቸው መሆኑን ጠቅሰው ክፍያዎቹ እንዲከፈሏቸው እና የሥራ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት በመጠየቅ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ አመልካችን በገበያ ውድድር ለመጣል በሚታገሉት ድርጅቶች ተጠቂ በመሆን ሥራቸውን የለቀቁ መሆኑን፤ ይህ ደግሞ አመልካች አብራሪዎችን ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ለማሰልጠን ከሚያስገበት መሰረታዊ ዓላማና ከአጠቃላይ የአገር ጥቅምና ደህንነት ጋር የማይሄድ መሆኑን፤ እንዲሁም ለአመልካች ድርጅት ሕልውና አደገኛ መሆኑን ዘርዝሮ የተጠሪን የማስጠንቀቂያ መስጠትን እና ሥራ መልቀቅን ሕጋዊነት የተቃወመ ሲሆን፤ ክፍያዎችን በተመለከተም ክፍያ ለዘገዩበት ጊዜ የሶስት ወር ደመወዝ የሚከፍልበት አግባብ ያለመኖሩን፣ የዓመት ፈቃድ ደግሞ በይርጋ የታገደ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ያላቸው የዓመት እረፍት ቀናት ብዛት በጥቅሉ 64 ብቻ መሆናቸውን፤ የሥራ ስንብት ክፍያም ተጠሪ ከሚሰሩበት ለየት ያለ የሥራ ሁኔታ ሊያገኙ ከነበረው ከፍተኛ ገቢ፣ ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር እና ሥራቸው በዓለም አቀፍ ዘርፍ ሳይቀር ካለው ተፈላጊነት አንፃር እንደሕጉ መንፈስ አሰሪው ሊሞላው የሚገባው ክፍተት አለ የሚያስብል ካለመሆኑ አንፃር ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ የስንብት ክፍያን በተመለከተ ተጠሪ እንደሚገባቸውና መጠኑም ብር 253,846.49 ክፍያ ለዘገዱበትም ሊከፈል የሚገባ ክፍያ ደግሞ የአንድ ወር ተኩል ደመወዝ ብር 144,935.40 የስልሳ አራት ቀናት የዓመት ፈቃድ ወደ ብር ሲቀየር ብር 206,129.92 በድምሩ ብር 604,911.81(ስድስት መቶ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ አንድ ብር ከሰማንያ አንድ ሣንቲም) አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካችም ሆነ ተጠሪ በከፊል ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የአመልካች ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 የተሰረዘ ሲሆን፤ በተጠሪ ይግባኝ ላይ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ለሥራ ስንብቱ መሠረት ያደረገው ስሌት ተገቢ ያለመሆኑን፣ ወጪና ኪሣራን በተመለከተም በስር ፍርድ ቤት የተወሰነበት አግባብ ሕጋዊ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ፍርድ ቤቱ ደምድሞ የሥራ ስንብቱ በጠቅላላው ብር 517,673.70 እንዲሆን፡፡ ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ደግሞ የተጠሪ ዝርዝር የማቅረብ መብታቸውን ጠብቆ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በእነዚህ ነጥቦች ብቻ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ 93,828 ክፍያ እንዲከፈል መደረጉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 39 እና አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 2(ሸ) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ፤ እንዲሁም ስለድንጋጌዎች ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ውጪ ነው ሲል፤ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈል መወሰኑ ስለሥራ ስንብት ክፍያ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን፤ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን፣ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው በወር ያልተጣራ ብር 91,623.60 ወርሃዊ ደመወዝ ሲከፈላቸው እንደነበር፤ ከቅጥር ጊዜው ጀምሮ ሥራውን እስከለቀቁበት ጊዜ ድረስ ያለው አገልግሎታቸውም ከአሥራ ሰባት ዓመታት በላይ መሆኑንና ሥራውንም በገዛ ፍቃዳቸው የለቀቁ መሆኑን ነው፡፡ ወደ ሕጉ ስንመጣ ቢያንስ አምስት ዓመት በአሠሪው ዘንድ የሥራ አገልግሎት ኖሮት በሕመም ወይም በሞት የሥራ ውሉ ሲቋረጥ፤ ወይም ሥራው ላይ የሚያስቆይ ከሥልጠና ጋር የተያያዘ ለአሠሪው የውል ግዴታ ሳይኖርበት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ሲለቅ ከሥራ የተገለለ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2(2)(ሸ) ተመልክቷል፡፡ ይህ ከሕጉ በስተጀርባ ያለው ምክንያት ሲሆን፣ የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የማያገኝበት አግባብ በሕጉ እንደተመለከተው ሠራተኛው ሥራው ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያስቆይ ከሥልጠና ጋር የተያያዘ ለአሠሪው የውል ግዴታ ያለበት ከሆነ ነው፡፡ ሕጉ የአገልግሎት ዘመኑ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ ሠራተኛው ግዴታውን ሳይወጣ የሥራ ስንብት ክፍያ መጠየቅ የማይችል መሆኑን በግልጽ ከሚያሳይ በስተቀር አንድ ሠራተኛ ከፍተኛ ደመወዝ ሲከፈል የነበረ ከሆነ የሥራ ስንብት ክፍያ አይገባውም በሚል ያስቀመጠው መለኪያ የለም፡፡ ሕጉ ግልጽ ከሆነ ደግሞ ሕጉን እንዳለ ከመተግበር ውጪ ትርጉም የሚሰጥበት አግባብ አይኖርም፡፡ አመልካች ድርጅት ከሠራተኞቹ ጋር ያለው ግንኙነት የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሆኑ ግልጽ እስከ ሆነ ድረስ በአዋጁ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ማድረግ የግድ የሚል መሆኑን ከአዋጁ ጠቅላላ ድንጋጌዎች እና ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79(3) እና በሥነ ሥርዓት ሕጉ ስለዳኝነት አሰጣጥ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 88739 የሥልጠና ግዴታ ያለበት ሠራተኛ ግዴታውን ሳይወጣ የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ ተቀባይነት እንደማይሰጠው፤ በሰ/መ/ቁጥር 35197 እና 37048 ደግሞ ስለሥራ ስንብት ክፍያ የሰጣቸው አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች የሥራ ስንብት ክፍያና የፕሮቪደንት ፈንድ አንድ ላይ ሊከፈሉ የሚችሉበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን ለማየት ይቻል ዘንድ የሁለቱን ክፍያዎች መሠረታዊ ዓላማ መመሳሰል ከማመላከቱ ውጪ የሠራተኛውን የደመወዝ መጠን ከፍተኛነት ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈልበትን አግባብ በተመለከተ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠ ባለመሆኑ በመዛግብቱ የተሰጠው ትርጉም ተጠሪ ከሥልጠና ጋር በተያያዘ ለአመልካች ግዴታ ያለባቸው ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ስለመሆናቸው ያልተረጋገጠ በመሆኑ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያላቸው አይደሉም፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን የደመወዝ መጠን ከፍተኛነት መሠረት አድርጎ ያቀረበው ቅሬታም ሆነ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ለማስቀረብ የጠቀሳቸው መዛግብት ውስጥ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው ምክንያቶች ተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁነው ያላገኘን በመሆኑ፤ በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ ክፍል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ ይገባቸዋል ተብሎ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81288 የካቲት 28 ቀን 2005 ዓ.ም የተወሰነውና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 132873 ሰኔ 11 ቀን 2005 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የሥራ ስንብት ክፍያ መጠኑን በተመለከተም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81288 የካቲት 28 ቀን 2005 ዓ.ም ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 132873 ሐምሌ 02 ቀን 2005 ተሻሽሎ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡ በወጪና ኪሣራ ላይ የተጠሪን የወጪና ኪሣራ ዝርዝር በመጠበቅ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው የውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክፍል ክፍያ ለዘገየበትና ለዓመት ፈቃድ ክፍያ ደግሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሙሉ በሙሉ የፀናው የውሣኔ ክፍል በዚህ ችሎትም አልተነካም፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው ይጻፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዘ.በ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 95451

ሚያዝያ 06 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ
አልማው ወሌ
ረታ ቶሎሳ
አዳነ ንጉሤ
መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር-ሠናይት ፋሲካ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መርዓዊ መስፍን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሆኖ በአሁን የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- በተከሳሽ አክሲዮን ማህበር ከህዳር 8 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ተቀጥሬ እያገለገልኩ ሳለሁ ተከሳሽ ሚያዚያ 13 ቀን 2004 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የህመም ዕረፍት ሳይሰጥህ ተሰጥቶኛል በሚል ለ10 ተከታታይ ቀናት ከሥራ ቀርተሃል በሚል ከሥራ አግዶኝ ለ32 ቀናት ያህል ከቆየ በኋላ ከሥራ ማሰናበቱን ስላስታወቀኝ ወደ ሥራ እንዲመልስ ካልሆነም በስሜ የተጠራቀመውን የጉድለት መጠባበቂያ ገንዘብ እና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

ተከሳሽ በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- ከሳሽ የህመም ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ማስረጃ ቢያቀርቡም ማስረጃውን ሰጥቷል የተባለው የሕክምና ተቋም ለከሳሽ የህመም ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሆኑን የገልጸ ሲሆን፤ ከዚሁ ማስረጃ ውጪ ለ15 ቀናትም ከሥራ ለቀረቡት አሳማኝ የሆነ ማስረጃ ባለማቅረባቸው በህጋዊ መንገድ ከሥራ እንዲሰናበቱ ተደርጓል፤ ወደ ሥራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄም ቢሆን ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡ በአማራጭ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁትን በተመለከተም፡- ስንብቱ ህጋዊ በመሆኑ የስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣እና ካሳ ሊከፈላቸው አይገባም፤የዓመት ፈቃዳቸውንም ተጠቅመው ስለጨረሱ በገንዘብ ተለውጦ የሚከፈላቸው የለም፣የፕሮቪደንት ፈንድም የአገልግሎት ዘመናቸው ከ5 ዓመት በታች በመሆኑ ሊከፈላቸው የማይገባ ከመሆኑም ሌላ ከሳሽ ያለባቸውን ዕዳ የማይሸፍን በመሆኑ የሚከፈል ገንዘብ አይኖርም፤የጉድለት ማሟያ ገንዘብም ቢሆን ለግል ጥቅም የሚከፈል ገንዘብ ካለመሆኑም በላይ ቀደም ሲል ከሚሰሩበት ከገንዘብ ቤት ክፍል ወጥተው በሌላ ክፍል እየሰሩ ከሥራ የተሰናበቱ ስለሆነ ገንዘቡን የመጠየቅ መብት የላቸውም ሲል ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በሰጠው ፍርድ፡- ከሳሽ ከሥራ የቀሩት የህመም ፈቃድ ሳይኖራቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ እና ከሥራ ለቀሩበትም በቂ ምክንያት ባለማቅረባቸው ስንብቱ ህጋዊ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ ከጠየቋቸው ክፍያዎች ውስጥም፡- ተከሳሽ የሥራ ውሉን ያቋረጠው ለከሳሽ ማስጠንቀቂያ ሊያሰጥ በሚችል ምክንያት ባለመሆኑ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም፤የዓመት ፈቃድ ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው የጠየቁትም ቢሆን ያልወሰዱትን የዓመት ፈቃድ በግልጽ ለይተው ባለመጠየቃቸው ተቀባይነት የለውም ሲል ውድቅ ያደረገባቸው ሲሆን የጉድለት ማሟያ ገንዘብ ብር 2,141 በተመለከተም፡- ገንዘቡ ከሒሳብ ሥራ ጋር በተገናኘ ለሚከሰት ጉድለት የሚውል ሆኖ ሳለ ተከሳሽ ከከሳሽ የሚፈለግባቸው ዕዳዎች ናቸው በማለት የጠቀሳቸው ከዓመት ፈቃድ እና ከትምህርት ወጪ ጋር የተያያዙ ዕዳዎች ለጉድለት ማሟያ ከሚጠራቀም ገንዘብ ዓላማ አንጻር ዕዳዎች ናቸው ተብለው ስለማይወሰዱ እና ከሳሽም ከሒሳብ ወይም ከገንዘብ ሥራ ጋር በተያያዘ ያጎደሉት ገንዘብ ስለመኖሩ ተከሳሽ ባለማስረዳቱ ይህንኑ የጉድለት ሟሟያ ገንዘብ ለከሳሽ ሊከፍል ይገደዳል ብሏል፡፡ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያን በተመለከተም ደግሞ ከሳሽ ልዩ ልዩ ዕዳዎች አለባቸው በሚል ተከሳሽ የፕሮቪደንት ፈንዱን መክፈል እንደማይገባው ቢከራከርም ከሳሽ ዕዳ ካለባቸው ክስ አቅርቦ ከመጠየቅ ውጪ ይህንኑ ገንዘብ በማቻቻያነት ሊይዝ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ የሥራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በማለት ተከሳሽ እንዲከፍሏቸው የጠየቋቸውን ሌሎች ክፍያዎች ግን ስንብቱ የተደረገው በህጋዊ መንገድ ስለሆነ ተቀባይነት የላቸውም ሲል ውድቅ አድርጓል፡፡

ተከሳሽም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት በማሰናበቱ የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

አመልካችም በሰበር አቤቱታው በዋናነት ያቀረበው ቅሬታ ነጥብ፡- ተጠሪው ያገለገሉት ከ5 ዓመት በታች በመሆኑ ያላቸው የፕሮቪደንት ፈንድ ራሳቸው ያጠራቀሙት ብር 4,828.03 ሲሆን ከአመልካች ባንክ የተበደሩት ገንዘብ፣ባንኩ በስማቸው በቅድሚያ የከፈለላቸው የዓባይ ግድብ ገንዘብ፣ መወሰድ ከሚገባቸው በላይ የወሰዱት ዓመት ፈቃድ በጥሬ ገንዘብ ተመላሽ መሆን ያለበት ፣ለትምህርት የተከፈለላቸው ገንዘብ በድምሩ ብር 12,397.54 እየተፈለገባቸው ሳለ እና ተጠሪውም አለባቸው ስለተባሉት ዕዳዎች መኖር እና አለመኖር በተመለከተ ምንም ዓይነት ተቃውሞ ባላቀረቡበት እንዲሁም ስለዕዳዎቹ በመካከላችን መካካድ በሌለበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤቶች በራሳቸው ጊዜ አንስተው የፕሮቪደንት ፈንድ ለዕዳው በማቻቻያነት ሊያዝ አይገባም ያሉት እና የጉድለት መጠባበቂያ ገንዘብም ለተጠሪው እንዲከፈላቸው የወሰኑት ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው ለሰበር አቤቱታው የበኩላቸውን መልስ እንዲሰጡበት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ቢደረግላቸውም ባለማቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- የጉድለት ሚሚያውን ገንዘብ አመልካች ለተጠሪው እንዲከፈላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት የሚነቀፍበት ምክንያት አለው? ወይስ የለውም?
- ፍርድ ቤቶቹ ከተጠሪው ላይ የሚፈለግባቸው ዕዳ ካለ አመልካች ክስ አቅርቦ ከሚያስወስን በስተቀር በተጠሪው ስም የተጠራቀመውን የፕሮቪደንት ፈንድ ገንዘብ አመልካች በራሱ ውሳኔ ለዕዳው ማቻቻያነት ሊያደርገው አይችልም በሚል የወሰኑት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች የጉድለት ማሚያ ገንዘብ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ሚያዚያ 24 ቀን 2005 ዓ/ም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጻፈው ማብራሪያ በባንኩ የሠራተኞች ጥቅማ ጥቅም መመሪያ መሰረት ለጉድለት ማሚያ ተብሎ ለገንዘብ ከፋይና ገንዘብ ተቀባይ ሠራተኛ በሠራተኛው ስም የሚጠራቀም ገንዘብ መኖሩን፣ ገንዘቡም ለሠራተኛው የሚከፈለው ሠራተኛው ከቦታው ተነስቶ በስመ ምንም ዓይነት ዕዳ አለመኖሩ ከተረጋገጠ ከ 6 ወር በኋላ እንደሆነ በመግለጹ ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ማብራሪያ እና በግራ ቀኙ በኩል በዚሁ ነጥብ ላይ የተደረጉትን ክርክሮች በመመርመር አመልካች በተጠሪው ላይ ይፈለግባቸዋል ሲል ከዘረዘራቸው የትምህርት፣ያለአግባብ ወስደዋል የተባሉት የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፍሉ ይገባል የሚለውን እና ለዓባይ ግድብ በተጠሪው ስም የተከፈለና ተጠሪው እንዲተኩ የሚፈለግባቸውን ዕዳዎች የጉድለት ማሚያ ገንዘብ ከሚጠራቀምበት ዓላማ አንጻር በመመርመር የተጠቀሱት ዕዳዎች ተጠሪው ከሚሰሩበት የገንዘብ ከፋይ ወይም ገንዘብ ተቀባይ ሥራ ጋር ተያይዞ ከሚመጣው ዕዳ የሚለይ በመሆኑ እንደጉድለት ማሚያ ዕዳ ተደርጎ አይወሰድም፣ እንዲሁም አመልካች ከሂሳብ ወይም ከገንዘብ ሥራ ጋር በተያያዘ ተጠሪው የገንዘብ ጉድለት ዕዳ ያለባቸው ስለመሆኑ አላስረዳም በሚል ፍርድ ቤቶቹ የደረሱበት ድምዳሜ የግራ ቀኙ ወገኖች ካደረጉት ክርክር እና አመልካች ለሥር የመ/ደ/ ፍርድ ቤት ከላከው ማብራሪያ ላይ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያደረገ በመሆኑ ፍርድ ቤቶቹ በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-ተጠሪው የተለያዩ ዕዳዎች ያሉባቸው ስለሆነ የተጠራቀመላቸውን የፕሮቪደንት ፈንድ የመክፈል ግዴታ የለብኝም ሲል አመልካች መከራከሩን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ከሚያመላክት በስተቀር አመልካች ከተጠሪው የሚፈለጉ ዕዳዎች ናቸው በሚል የዘረዘሯቸውን በመካድ ዕዳ የለብኝም ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ስለመኖሩ የሚያሳይ አይደለም፡፡ ሠራተኛው ያለበትን ዕዳ እስካልካደ ድረስም ደግሞ አሠሪው በሠራተኛው ስም የተጠራቀመውን የፕሮቪደንት ፈንድ ለዕዳው መክፈያ እንዲሆን የማድረግ መብት ያለው ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/71507 በቀን 10/07/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ዕዳዎቹን በግልጽ ክደው ባልተከራከሩበት ሁኔታ አመልካች በተጠሪው ላይ ክስ አቅርቦ ዕዳዎቹን እንዲከፈሉ ከሚያስወስን በስተቀር የፕሮቪደንት ፈንዱን ለዕዳው ማቻቻያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊያደረግ አይችልም ሲሉ የሰጡት የፍርድ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/06040 በቀን 01/09/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/135717 በቀን 03/03/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. ፍርድ ቤቶቹ አመልካች በተጠሪው ላይ ክስ አቅርቦ ከሚያስወስን በስተቀር በተጠሪ ስም የተጠራቀመውን ፕሮቪደንት ፈንድ በተጠሪው ላይ ለሚፈለግባቸው ዕዳ ማቻቻያ ሊያደርገው አይችልም ሲሉ የሰጡትን የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
3. የሥራ ውሉ የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ነው ሲሉ ፍርድ ቤቶቹ ከፕሮቪደንት ፈንድ ውጪ ያሉትን ሌሎች ክፍያዎችን በተመለከተ የሰጡትን የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348 (1) መሰረት አጽንተናል፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95522

መጋቢት 08 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን መሃል ሜዳ ደንበኞች አገልግሎት ጽ/ቤት -ነ/ፈጅ ተስፋዬ አያሌው ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-አቶ መሉጌታ ወ/ጊዩርጊስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት አድርጎ የቀረበን የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሓል ሜዳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪ የክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ግንኙነት ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ጠቅሰው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ከማህደራቸው ጋር አያይዘው መገኘታቸው በተደረገው መጣራት ተረጋግጦና የድርጅቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጠሪን ተገቢ ነው ያለውን ቅጣት በመቅጣት ወደ ስራ እንዲመለሱ ቢወሰንም የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የኮሚቴውን ውሳኔ ሽረው አመልካች ከስራ እንዲሰናበቱ መወሰናቸውን፣ውሳኔውም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) እና በድርጅቱ የህብረት ስምምነት አባሪ ቁጥር 4 አንቀጽ 2 ቁጥር 2.3 መሰረት ተጠሪ የማጭበርበር ወይም የማታለል ድርጊት መፈፀማቸው በመረጋገጡ የተሰጠ በመሆኑ ሕጋዊ ስለሆነ ወደ ስራ ሊመለሱ አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና የሰነድ ማስረጃ መርምሮ የአመልካች መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የኮሚቴውን ውሳኔ በደብዳቤ መሻራቸው ስለውሳኔ በሕጉ የተሰጠውን ትርጉም ያላገናዘበና ሕጋዊ ያለመሆኑን፣ተጠሪ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በማህደራቸው ተያይዞ የተገኘባቸው መሆኑ ቢረጋገጥም የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ የድርጊቱን ክብደትና ቅለት ያላገናዘበ ነው በማለት እርምጃውን ሕገ ወጥ ነው ብሎ ተጠሪ ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ወይም በአማራጭ ካሳ ተከፍሏቸው ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የድርጅቱን የበላይ ኃላፊ ውሳኔ የውሳኔ አጻጻፍ ስርዓትን የተከተለ አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የበላይ ኃላፊው በዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላቸውን ሥልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ የማይቀበለው መሆኑን ጠቅሶ ካለፈ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ውጤት በተመለከተ ግን ተጠሪ የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ ከማህደራቸው አያይዘው ከመገኘታቸው ውጪ ያገኙት ጥቅም ስለመኖሩ አመልካች ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ ያለመኖሩን ገልፆ አጽንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ አቅርበው በማህደራቸው አያይዘው መገኘታቸው ተረጋግጦ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያገኙት ጥቅም የለም ሲል የአመልካችን እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ወይም ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ሲል የሰጠውን ውሳኔ ማፅናቱ ያለግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የአመልካች የስንብት እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪ ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ወይም ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት ተጠሪ ከማህደራቸው የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ አያይዘው የተገኙ መሆኑን ተጠሪን ከስራ አግዷቸው በተገቢው መንገድ አጣርቶ ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን፣የዲሲፕሊኑን ጉዳይ ሲመለከት የቆየው የድርጅቱ ኮሚቴም ጉዳዩን አጣርቶ ተጠሪን የአንድ ወር ደመወዝ ቅጣት፣የአንድ አመት የደረጃ እድገትና የዝወውር ቅጣት አሳልፎ ተጠሪው ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ሲል የሰጠው ውሳኔ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ውድቅ ተደርጎ አመልካች ከስራ እንዲሰናበቱ መደረጉን፣ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል በሕግ አግባብ ሊቋረጥ ችሏል በማለት አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ በማህደራቸው አይይዘው የማጭበርበር ወይም የማታለል ድርጊት ለመፈጸም የሞከሩ መሆኑ በሚገባ በማስረጃዎች ተረጋግጧል በማለት መሆኑን፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለድርጊቱ ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ በተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ ከማህደራቸው ከማያያዛቸው ውጪ በማስረጃው ያገኙት ጥቅም የለም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

እንግዲህ ከላይ ከተገለፀው የፍርድ ቤቶች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በግል ማህደራቸው የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ አያይዘው መገኘታቸው በሁሉም ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ሁኖ በዚህ ማስረጃ ተጠሪ ጥቅም አግኝተዋል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ግን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግልጽ አንስቶ ተጠሪ ያገኙት ጥቅም የለም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ የአመልካችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ሲል የወሰነ መሆኑን ነው፡፡ይሁን እንጂ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር በሙከራ ደረጃ መቅረቱ የድርጊቱን ወንጀል መሆን ቀሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማያደርገው ሲሆን ጥቅም ማግኘት ወይም በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ ተግባሩ ከስራ ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የግድ መሟላት ያለባቸው ፍሬ ነገሮች መሆናቸውን የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) ድንጋጌ ይዘት አያሳይም፡፡በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ ያገኙት ጥቅም ስለመኖሩ አልተረጋገጠም የሚለውን ምክንያት የያዘው ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ሕግ በመመዘኛነት ያላስቀመጠው ነጥብ በመሆኑ ሕጋዊ አይደለም፡፡አመልካች ለጉዳዩ ተፈጻሚነት አለው በማለት የሚጠቅሰው የድርጅቱ የሕብረት ስምምነት ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ለተጠሪ የተሻለ ጥበቃ የሚያደርግ መሆኑም አልተረጋገጠም፡፡ይልቁንም የህብረት ስምምነቱ አባሪ ቁጥር 4 አንቀጽ ቁጥር 2.3 ስር አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት በማሰብ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር ፈጽሞ ሲገኝ የማይገባውን ጥቅም እንዲመልስ ተደርጎ እንዲሰናበት እንደሚደረግ እንጂ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር ጥቅም ካላስገኘ ስንብት እንደማይከናወን በግልጽ ያለማስቀመጡን ከክርክሩ ሂደት የተረዳን ሲሆን ተጠሪም በዚህ ረገድ ያቀረቡት ማስተባበያ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ማናቸውም ሰራተኛ የማጭበርበር ወይም የማታለል ሙከራ መፈፀሙ ከተረጋገጠ ድርጊቱ ሕገ ወጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27(1(ሐ)) ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን በአንቀጽ 27(1(ሐ)) ስር የተመለከቱትን ሕገ ወጥ ድርጊቶችን መፈፀም ደግሞ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡በመሆኑም ተጠሪ የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ በማህደራቸው አያይዘው መገኘታቸው በበታች ፍርድ ቤቶች በተደረገው የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና የተረጋገጠ ሁኖ እያለ በዚሁ በሕጉ ያልተመለከተውን መመዘኛ፤ በተሳሳተ ማስረጃ ተጠሪ ያገኙት ጥቅም የለም ተብሎ የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ መባሉ በሕጋዊ ምክንያት ያልተደገፈ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ስለሆነም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በአዋጁ አንቀፅ 27(1(ሐ)) ድንጋጌ መሠረት በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡በዚህም ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) ድንጋጌን የጣሰ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በመሃል ሜዳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0114277 መስከረም 03 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0112585 ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ/ም ምክንያቱ በከፊል ተለውጦ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 94102

ሚያዚያ 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም ደቡብ ምዕራብ እና ጋምቤላ ሪጅን -አልቀረበም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሳባ መንገሻ- አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ሆኖ በአሁን የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ከሳሽ አሻሽለው ባቀረቡት ክስ፡- በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከ29/02/1999 ዓ/ም ጀምሮ ተቀጥሬ እየሰራሁ የቆየሁ ቢሆንም በራሴ ፍላጎት የሥራ ውሌን ለማቋረጥ በ22/10/2004 ዓ/ም የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለተከሳሽ የሰጠሁ ሲሆን ተከሳሽ ድርጅትም ማስጠንቀቂያውን በጻፍኩበት ቀን የሥራ ውሌን በማቋረጡ በእጄ ያሉትን ንብረቶች ባስረክብም መክፈል የሚገባቸውን ክፍያዎች ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ በመሆኑም የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣በ2004 ዓ/ም የሥራ ዘመን ለቋሚ ሠራተኞች የከፈለውን ቦነስ የ2 ወር ደመወዝ፣የማስጠንቀቂያውን የአንድ ወር ጊዜ ሳይጠብቅ የሥራ መልቀቂያ በመስጠቱ በወሩ መክፈል የነበረበትን ደመወዝ፣የስንብት ክፍያ፣ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ፣የ56 ቀናት የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ፣ በድምሩ ብር 24,594 እንዲከፍል ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

ተከሳሹም ለክሱ የበኩሉን መልስ ከሰጠ በኋላ የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመመርመር ከሳሽ ከጠየቋቸው ክፍያዎች ውስጥ የተወሰኑትን ውድቅ በማድረግ በድምሩ ብር 12,593.74 ተከሳሽ እንዲከፍል የወሰነ ሲሆን በሥር ተከሳሽ ድርጅት ይግባኝ ጠያቂነት ጉዳዩን የመረመረው የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ጉድለት የለበትም ሲል በማጽናቱ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

ተጠሪዋም ለሰበር አቤቱታው የበኩላቸውን መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተገቢውን ደረጃ ጠብቆ የቀረበ ነው? ወይስ አይደለም?የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሰበር አቤቱታውን በቀጥታ ለዚህ ችሎት ያቀረበው የጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማጽናቱ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በሚቀርብ በግል የሥራ ክርክር ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 139(1) የተደነገገ ሲሆን ከአንቀጹ መረዳት የሚቻለውም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ ቢሰጥ እንኳን እንደሌሎች የፍትሃብሄር ጉዳዮች ለቀጣይ የይግባኝ ክርክር የማይቀርብ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአንቀጹ በዚህ መልክ መጠቀሱ ጉዳዩን በሰበር ችሎት ከመታየት የሚያስቀር አይደለም፡፡

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት እንደመሆኑ መጠን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በህግ የተሰጠውን ሥልጣን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ የማረም ሥልጣን ያለው መሆኑን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ለ) ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 64(ሐ)፣ እንዲሁም የክልሉን ፍርድ ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 26(1)(ሠ) በተመሳሳይ ሁኔታ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ጉዳዩ የቀረበላቸው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በሰበር እንዲታይለት አመልካች አቤቱታውን ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳያቀርብ በቀጥታ ለዚህ ችሎት ያቀረበበትን ምክንያት በአቤቱታው በግልጽ ባያሰፍርም አመልካች በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ አካል በመሆኑ እና በፌዴራል መንግስቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶችና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሡ ክርክሮችን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(6) በመደንገጉ፤ እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር ማየት የሚችለው ጉዳዩ የክልል በሆነ ጊዜ ብቻ ነው ከሚል ድምዳሜ በመነሳት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ጉዳዩን ይህ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር መ/ቁ/95298 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር መመርመር የሚገባ ነው፡፡ ችሎቱ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ በሰጠው ፍርድ፡- በፌዴራል መንግስቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች እና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(6) የተደነገገ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን በተመለከተ በክልሎች ውስጥ የሚነሱ የግል የሥራ ክርክር ጉዳዮችን ተቀብሎ የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የተሰጠው ለክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 138(1) በመደንገጉ እና ድንጋጌውም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 የተደነገገውን ዓይነት ተከራካሪ አካላትን ማንነት ግንዛቤ ውስጥ ካለማስገባቱም ሌላ ድንጋጌው የተካተተበት አዋጅ ቁጥር 377/1996 የወጣው፤ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 በኋላ ከመሆኑ አንጻር የአሠሪና እና ሠራተኛ ጉዳይ ክርክር የተለየ ባህርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ህግ አውጪው ማናቸውም በክልሎች ውስጥ የሚነሳ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በተከራካሪ ወገኖች (አካላት) ላይ ተመስርቶ ጉዳዩ የክልል እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል መሆኑ ከግምት ውስጥ ሳይገባ በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ መደንገጉን እንደሚያሳይ፤ አንድ ጉዳይ የተነሳው በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ በተነሳበት ክልል የሰበር ችሎት የተደራጀ እስከሆነ ድረስ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታይ እና ውሳኔው የመጨረሻ መሆኑ ሳይረጋገጥ በቀጥታ ለፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት እንደማይኖር አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይም ምንም እንኳን አመልካች የፌዴራል መንግስት አካል ቢሆንም ከዚህ በላይ በተሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት የሰበር አቤቱታውን ለፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከማቅረቡ አስቀድሞ ጉዳዩ በተጀመረበት ክልል ላለው ለኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረብ ያለበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘ በመሆኑ ተገቢውን ደረጃ ጠብቆ የቀረበ አይደለም ስንል ውድቅ አድርገናል፡፡
2. ይህ ውሳኔ መብቱን የሚጠይቅ ወገን በህጉ መሰረት አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከማቅረብ የሚያግደው አይደለም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94839

መጋቢት 22 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- መተሃራ ስኳር ፋብሪካ – ነ/ፈጅ አሉላ ድንቂሳ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ለራሳቸውና ለሌሎች ወኪል ጥበቡ እሸቱ ቀረቡ፡፡

1. አቶ ሳሙኤል ሰላሙ
2. ብርሃኑ ሃ/ማርያም
3. ወርቁ ጎበዜ
4. ሚቲዎስ ማሴቦ
5. ጀኻል ሸሪፍ
6. ጌታቸው እሸቱ
7. ተካ ባዲ
8. ወልዴ አሸቦ
9. ጀማል አደም
10. ፍራንሶ ዮሐንስ
11. ታገሰ አቦዬ
12. አየለ ጥላሁን
13. አህመድ ሃሰን ሁሴን
14. መሐመድ ሁሴን
15. ወልዴ ኦሎሮ
16. መለሰ እሸቱ
17. ሰለሞን ገብሬ
18. ሥራውብዙ አብሬ
19. ሽጉጤ ሌጆሶ
20. ምትኩ ነራሞ
21. ቀቀባ ጉተማ
22. መሐመድ ሸሪፍ
23. ጅባ አብደላ
24. ዳንኤል ደንታሞ
25. ቦሩ ፈንታሌ
26. አለማየሁ ጌታሁን
27. ሙሉጌታ በቀለ
28. ሳሙኤል ጌታ
29. መኮንን አስፋው
30. መሐመድ ሰይድ
31. አውላቸው ታደሰ
32. ሲሳይ አሰፋ
33. ሐሰን ሙኔ
34. ካሣ ኃይሌ
35. ማቴዎስ ጌቾሞ
36. አሸነ ተፈራ
37. አይረዲን መሐመድ
38. ሃይሉ ወልዴ
39. ከበደ መልኬ
40. እሸቱ ቡሽራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

41. ተከተል አናሞ
42. አምባው መኳንንት
43. መስቀሉ አበራ
44. ተሾመ ቲራሞ
45. ተስፋዬ ካሳ
46. ሃይሌ ሞሎሮ
47. እንድሪስ መሐመድ
48. አበበ በላይ
49. ሸምሱ ጀማል
50. ዘውዴ ደንታሞ
51. ተፈራ ሽመልስ
52. ግርማ አብዬ
53. ተሾመ ጃርሶ
54. ግርማ አብዬ
55. በልዳ ታደሰ
56. ጸጋዬ ታደሰ
57. ቦልጠና ወልዴ
58. ባዩ ክብረት
59. ወ/ሮ ፀሐይ ዋቆ
60. ሃይሉ ወልደየስ
61. ማቲዎስ ቡርቃ
62. አናሞ ላልንጎ
63. አበራ ይዘንጋው
64. ምህረቱ ይርዳው
65. ዳዲ ቱፋ
66. ደምሴ ግዴቦ
67. ረጋሳ ወልዴ
68. ታደሰ የሉች
69. ይመር አበበ
70. አሰፋ ጁዳ
71. አስቻለው ገረመው
72. ጥላሁን ጉልላት
73. ለማ ሀሰን
74. አሰፋ ረዲ
75. ፍቅሬ ደሳለኝ
76. አሊ ወሌ
77. ታደሰ ጅራ
78. ይዘንጋው አየለ
79. ስምኦን ሃቢብ
80. አብርሃም ጅማ
81. አለሙ አፈቦ
82. መላቱ ፈለቀ
83. አሰፋ አሼቦ
84. የኋላእሸት ደሳለኝ
85. ተፈራ ማደቦ
86. በቀለ ተፈራ
87. ተስፋዬ ሰላሙ
88. አሰፋ አድማሱ
89. አሊ ሰይድ ጸጋው
90. ድሪባ ዱባለ
91. ኢብሮ ሲራጅ
92. አለሙ ሰላቶ
93. ደሣለኝ ሰርካሞ
94. ሉባንጎ አላሮ
95. አድየስ አሸቦ
96. ተስፋዬ አሸቦ
97. አርቦዬ ወየሳ
98. ይገዙ ግምቶ
99. ከተማው አነሰኝ
100. ቶማስ ደንቃጎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

101. ጴጥሮስ አቡዬ
102. የርማኮ ጀኖሬ
103. አደም ዋዩ
104. አየለ ደገፋ
105. ንጉሤ በሻ
106. ጴጥሮስ አቡየ
107. ጥበቡ እሸቱ
108. ገናሞ ዱአና
109. ኤልሶ አንቀሞ
110. ጀማል ኡመር
111. አርፍጮ ሄኢሶ
112. አጋፋሪ ጀንባጋ
113. ማሀፋመ ታሰው
114. ተካ ባቴቦ
115. ለማንጎ ሐይሌ
116. አባቴ ዓለሙ
117. ተሰማ መርካኖ
118. ሐዋኖ አረዳ
119. ግርማ ጥላሁን
120. ተሰማ ቱሉ
121. ተስፋዬ አቡቶ
122. መሃጉ ላቴቦ
123. ጥላሁን አለሙ
124. ፀጋ በቀለ
125. ማደቦ ሻንካ
126. ማደቦ ሻንካ
127. ቀለመወርቅ በላይ
128. መካሻ ወርቁ
129. ሁሴን መሐመድ
130. አሸሮ አዋኖ
131. አዲፀፊ ዳንጎሬ
132. ሐይሉ መርጊያ
133. ፍቃዱ ማሙዬ
134. ተስፋዬ ማደቦ
135. ባቴ አነቦ
136. ታደሰ ገብሬ
137. ሰልበሳ ደጋሞ
138. አሊ ሀሰን
139. አያኖ አንቺ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሠረት አድርጎ የቀረበን የሥራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን፤ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች ላይ በምስራቅ ኦሮሚያ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪዎች የክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር መስርተው የነበረውን የሥራ ውል አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) ድንጋጌን በሚቃረን ሁኔታ ከሥራ የተቀነሱ መሆኑን ጠቅሰው እርምጃው ሕገወጥ ነው ተብሎ ወደ ሥራ እንዲመልሳቸው ወይም ሕጋዊ ክፍያዎችን እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ፣ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ በቦርዱ ሊታይ እንደማይገባ፤ ክሱም በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳ ሲሆን፣ በፍሬ ነገር ደረጃም ተገቢ ነው ያለውን የክርክር ነጥብ አንስቷል፡፡ ቦርዱም ጉዳዩን መርምሮ የአንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሰዎች ክስ ጥቅምት 09 ቀን 2005 ዓ.ም የተመሠረተ መሆኑን ጠቅሶና ጥያቄውም ከሥራ ያላግባብ ስለተቀነስን ወደ ሥራ ይመልሰን የሚል በመሆኑ፤ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን እንደአለው፣ ሆኖም እነዚህ ሰዎች ሐምሌ 25 ቀን 2005 ዓ.ም ከቀረበው የአሥራ አራት ሰዎች ክስ ጋር ተቀላቅሎ የሥራ ውሉ የካቲት 01 ቀን 2004 ዓ.ም ከተቋረጠ በኋላ መቅረቡ ተቀባይነት እንደሌለውና ክሱም በይርጋ የታገደ መሆኑን፤ የ14 ሰዎች ክስ ግን ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም መቅረቡንና ጊዜውን የጠበቀ ቢሆንም ጥያቄው በክፍያ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በቦርዱ ሥልጣን ስር እንደማይወድቅና የመደበኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን መሆኑን ጠቅሶ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በዚህ የቦርዱ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ከአከራከሩ በኋላ መርምሮ በሰጠው ውሣኔ የተጠሪዎች ጥያቄ ከራሳቸው አልፎ ሌሎች ሠራተኞችን የሚነካ ነው፡፡ ይህም የወል የሥራ ክርክር ያደርገዋል፡፡ ይርጋም ቢሆንም ክሱ መጀመሪያ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ሊታሰብ የሚገባውና ጊዜውም ያላለፈ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ የቦርዱን ብይን ሽሮ ቦርዱ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም ጉዳዩ የወል የሥራ ክርክር ነው፡፡ በይርጋው የሚታገድ አይደለም ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን፤ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የታዘዘ ሲሆን፣ ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን፤ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በቅድሚያ የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ጉዳዩ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለመታየት የመጨረሻ ፍርድ አግኝቷል? ወይስ አላገኝም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት በፌዴራል መንግሥት አካል ቢሆንም ግራ ቀኙን የሚያከራክረው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተመሰረተውን የቅጥር ውል መነሻ ያደረገ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች መዋቅሩን መሠረት በማድረግ የዳኝነቱም ሥልጣን በፌዴራል መንግሥት እና በክልል መንግሥታት መካከል እንደተከፋፈለ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50 እና 51 ሥር ተመልክቷል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 80 «የፍ/ቤቶች ጣምራነትና ሥልጣን» በሚል ርዕስ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በክልል ጉዳዮች ላይ በክልሉ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሥልጣኑ የተደነገገ ሲሆን፣ የክልል ፍ/ቤቶች በሕገ - መንግሥቱ የተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት ካልሆነ በቀር የፌዴራልን ጉዳይ ለማየት፤ እንዲሁም የፌዴራል ፍ/ቤቶች የክልልን ጉዳይ ለማስተናገድ የሚያስችል ሥልጣን የሌላቸውም መሆኑን በዚሁ ድንጋጌ ስር የተቀመጡት ንዑስ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ አንድ ጉዳይ የፌዴራል ነው? ወይስ የክልል? የሚለውን ለመለየትም መሠረቱ የአዋጅ ቁጥር 25/88 ሲሆን፤ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 5 ሥር በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የክልል ፍ/ቤቶች ሥልጣን የሚኖራቸው በሕገ-መንግሥቱ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን አግባብ ብቻ ነው፡፡ ይህ በግልጽ የሚያሳየው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 መሠረት የፍርድ ቤቶች ሥልጣን በጉዳዩ ባለቤትነት (Subject matter) የሥልጣን ክፍፍል እንደተጠበቀ ሆኖ ክሱም መቅረብ ያለበት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሥረ -ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ስለመሆኑ ነው፡፡ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8፣11፣14 እና 15 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ደግሞ አንዳንድ ጉዳዮች ሊያስነሱ በሚችሉት የክርክር ባህርይ ምክንያት ለተወሰኑ ፍ/ቤቶች እንዲቀርቡ በሕግ ተለይተው ከተመለከቱት በቀር የሥረ - ነገር ሥልጣን የተደለደለው በክሱ በተመለከተው የገንዘብ ወይም የንብረት ግምት መነሻ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 14 እና 15 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እና የክልል መንግሥታት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ሕጐች ያስረዳሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን አዋጅ ቁጥር 25/1988"ን" ያወጣው የፌዴራል መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሥራ ክርክሮች የሚመሩበትን ሥርዓት የዘረጋውን አዋጅ ቁጥር 377/1996 ከየካቲት 18 ቀን 1996 ዓ.ም ሥራ ላይ ያዋለ ሲሆን፤ በዚህ አዋጅ የሥራ ክርክር ሥልጣን ድልድል የተደረገው የግል የሥራ ክርክርና የወል የሥራ ክርክር የሚሉትን ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ ሲሆን፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከራካሪ ወገንን ማንነትን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ አይደለም፡፡ በመሆኑም ክርክሮቹ ክልል የተነሱ ቢሆንም ጉዳዩን የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም አግባብነት ያላቸው የቋሚ ወይም ጊዚያዊ ቦርዶች ሊመለከቱ እንደሚችሉ አድርጎ ሕጉን ሕግ አውጪው አውጥቷል፡፡ ይህ አዋጅ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 በኋላ ከመውጣቱም በላይ ለሥራ ክርክር ጉዳዮች ልዩ ሕግ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ለሥራ ክርክሮች ከሕገ መንግሥቱ በመለስ ባሉት ማናቸውም ሕጎች የበላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያስረዱን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በሥራ ተከራካሪ ወገኖች ማንነት የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን (የክልል ወይም የፌዴራል) ብሎ ለመወሰን እንደወሳኝ መለኪያ ሊወስድ የሚገባው አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ደግሞ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች ሳይመለከቱ የሥራ ክርክር ለዚህ ችሎት የሚቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን የምንገነዘበው ነው፡፡

በዚህም መሠረት አንድ የሥራ ክርክር ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ለመስተናገድ ይችል ዘንድ፣ በፍ/ቤቶች ወይም ክርክሮችን አይተው ለመወሰን ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት በተዋረድ ታይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት መሆኑ መረጋገጥ እንደሚገባው ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10(3) ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የምንችለው ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ክርክሩ የተጀመረውና በመጀመሪያ ውሣኔ የተሰጠበት በምስራቅ ኦሮሚያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን፣ ከዚህ በኋላ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ታይቶ የቦርዱ ውሣኔ ከመሻሩ ውጪ ጉዳዩ የተነሳው ከክልሉ በሚገኝ ቦርድ እንደመሆኑ መጠን በተሻሻለው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 64/2/ሐ/ እና የክልሉ ፍርድ ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 26(1)(ሠ) ድንጋጌ መሠረት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርቦ ውሣኔ የተሰጠበት መሆኑን መዝገቡ አያመላክትም፡፡ ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ የማይችልበት ሌላ ሕጋዊ ምክንያትም የለም፡፡ በዚህም ሁኔታ ጉዳዩ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊስተናገድ በሚችል ደረጃ የመጨረሻ ውሣኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ፣ ይህ ችሎት በተመሳሳይ የሥነ ሥርዓት ጥያቄ በሰ/መ/ቁጥር 95298 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት፤ይህ ጉዳይ በዚህ ችሎት ለመታየት ብቁ አይደለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በአመልካች ላይ ክስ የቀረበው አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሠረት በማድረግ በመሆኑ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡት የሥራ ክርክሮች የሚመሩትም በዚሁ አዋጅ በመሆኑ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ያልታየ ውሣኔን ይህ ችሎት የሚያስተናግድበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
2. አመልካች ጉዳዩን ለክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በሕጉ አግባብ የማቅረብ መብቱን ይህ ውሣኔ ቀሪ አያደርገውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዘ.በ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.94889

መጋቢት 23 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ባዛ - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- የደቡብ መንገዶች ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ፍፁም አዲስ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የደረጃ እድገት አላግባብና ከሕግ ውጭ ተከልክያለሁ በማለት የቀረበውን ጥያቄ የሚያመለክት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ በመስከረም 1 ቀን 2005 ዓ.ም የደረጃ እድገት ማስታወቂያ አውጥቷል፡፡ ተከሳሽ በማስታወቂያው የማኔጅመንት የመጀሪያ ዲግሪና ዜሮ አመት የሥራ ልምድ ያላቸው ሠራተኞች ለዕድገት መወዳደር እንደሚችሉ ገልጿል፡፡ እኔም በማኔጅመንት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪና አሥር አመት የሥራ ልምድ ያለኝ በመሆኑ ለእድገት ለመወዳደር ተመዝግቤ የተሰጠውን ፈተና አልፌና ተወዳድሬ በአንደኝነት አልፌአለሁ፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ያለምንም በቂ ምክንያት የተወዳደርኩበትን የሥራ መደብና እድገት እንዳላገኝ ያደረገኝ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በፍርድ መብቴን እንዲያስከብርልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ ክስ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ አመልካች የተወዳደረችበትን እድገት አለማግኘቷ ተገቢ ነው፡፡ የዕድገት ማስታወቂያው የወጣው ሥራ አስኪያጅ ሣያውቀውና ሣይፈርምበት ነው፡፡ የእድገት ኮሚቴው ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ሥራ አስኪያጅ አልተቀበለውም በመሆኑም የከሳሽ ክርክር የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ውድቅ አድርጐታል፡፡ የከሳሽን የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ ከሳሽ ተከሳሽ ባወጣው ማስታወቂያ መሠረት መስፈርቱን በማሟላት ከሌሎች ሁለት ተወዳዳሪዎች ጋር በድርጅቱ የተሰጠውን ፈተና ተፈትና ሌሎቹን ተወዳዳሪዎች በመብለጥ ያለፈች መሆኑ በእድገት ኮሚቴው ቃለ ጉባኤ በግልፅ ሠፍሯል፡፡ ከሳሽ በፈተናውና ሌሎች መስፈርቶችን በማሟላት የእድገት ማስታወቂያ ለወጣበት የሥራ መደብ መመደብ የምትችል መሆኑ ቢረጋገጥም የተከሳሽ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በቂና ቀጥተኛ የስራ ልምድና ብቃት ያለው ሰው ስላልተገኘና የእድገት ውድድሩም አራት ወራት ያህል እንደፈጀ በመግለጽ የእድገት ኮሚቴው ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ውድቅ ያደረገው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግና የህብረት ስምምነቱን በሚቃረን መንገድ በመሆኑ ተወዳድራ ባለፈችበት የሥራ መደብ እንዲመድባት በማለት ወስኗል፡፡ ከሳሽ በህግ መሠረት የደመወዝ ማስተካከያ እንዲደረግላት የጠየቀችውን ጥያቄም በአግባቡ በማጣራት የደመወዝ ማስተካከያ እንዲያደርግላትና ጥቅማጥቅም እንዲያከብርላት በማለት ወስኗል፡፡

3. ተጠሪ ይግባኝ ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ /አመልካች /ተወዳድራ ያለፈችበት እድገት በድርጅቱ ሥራ አስኪያጅነት ያልፀደቀ በመሆኑ ተጠሪ የደረጃ እድገቱ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት ክስ ለማቅረብ አትችልም በማለት የሥር ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

4. አመልካች 06/03/2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ሠራተኞችን ለማወዳደር አስቀድሞ ያወጣውንና በዕድገት ማስታወቂያው የዝርዝር መስፈርት ሳያገናዝብ ያለበቂ ምክንያት የዕድገት ኮሚቴው በተሰጠው መሥፈርት መሠረት አወዳድሮ ያቀረበለትን ውጤት ውድቅ ማድረጉ በፍርድ ታይቶ ሊታረም የሚገባው ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት እንደማይታይ አድርጐ የሰጠው ትርጉምና ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የክልሉ መንግስት ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ሊያደርግልኝ የሚገባውን የደመወዝ ማስተካከያ የነፈገኝ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክታለች ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ 22-04-2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የዕድገት ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ ተፈፃሚ የሚሆነው በሥራ አስኪያጁ ሲፀድቅ ነው፡፡ ይህም በሕብረት ስምምነቱ የተገለፀ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የእድገት ውድድሩን ያልተቀበለው በመሆኑ ከሳሽ እድገት ይሰጠኝ በማለት መጠየቅ አትችልም በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?የሚውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
6. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ለእድገት የተወዳደረችበት የሪከርድና ማህደር ሱፐርቫይዘር የሥራ መደብ በእድገት ለመወዳደር በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ ያለውና ዜሮ አመት የሥራ ልምድ የሚያስፈልግ መሆኑ ተጠሪ ከመስከረም 30 ቀን 2005 ዓ.ም ባወጣው የእድገት ማስታወቂያ ሰነድ የተገለፀ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪና የአስር አመት የስራ ልምድ ያላት በመሆኑ በእድገት ውድድር ተመዝግባ ከሌሎች ሁለት ሰራተኞች ጋር ተፈትና ብልጫ ያለው ውጤት በማግኘቷ እድገቱ እንዲሰጣት የተጠሪ ድርጅት የእድገት ኮሚቴ ቃለጉባኤ በማረጋገጥ የውሳኔ ሀሳብ ለድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ያቀረበ በመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡
7. የድርጅቱ ዕድገት ኮሚቴ ቃለጉባኤ የውሳኔ ሀሳብ የደረሰው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ “ውድድሩ ቀጥተኛ የሥራ ልምድ ያለውና ብቃት ያለው ሰው ያላስገኘና ጊዜውም ከአራት ወር በላይ ስለሆነው ውድቅ ቢሆን የተሻለ ነው” የሚል ይዘትም ያለው ውሳኔ በመስጠት አመልካች የተወዳደረበትንና ያለፈችበትን እድገት እንዳታገኝ ያደረጋት መሆኑን ከበታች ፍርድ ቤትቶች ውሳኔ ተረድተናል፡፡ አመልካች በዳኝነት ታይቶ እንዲታረምላት የምትጠይቀው የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ የእድገት ኮሚቴው አወዳድሮ ያቀረበውን ውጤትና የውሳኔ ሀሳብ ውድቅ ያደረገበት ምክንያት የሕግ መሠረት የሌለው ነው በማለት ነው፡፡
8. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካች በውድድሩ ያገኘችው ውጤትና የእድገት ኮሚቴው ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በድርጅቱ ያልፀደቀ በመሆኑ፣ ለተወዳደረችበት የሥራ መደብ አልፋለች ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ሥራ አስኪያጅ ያላፀደቀውን የእድገት ውድድር ውጤት መሠረት በማድረግ ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢ አይደለም በሚል ምክንያት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይህም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ውሳኔ፣ አንድ ድርጅት ለእድገት ባወጣው ማስታወቂያ መሠረት ተወዳድሮ በውጤቱ የእድገት ማስታወቂያ የወጣበትን የሥራ መደብ መመደብ የሚገባው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ፣ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ በቂና ምክንያታዊ ባልሆነ ማናቸውም ምክንያት የሠራተኛውን ውጤት አልቀበልም በማለት ቢወሰን ፍርድ ቤቶች የሥራ አስኪያጁ ውሳኔ የህግ መሠረት ያለው በቂና ምክንያታዊ መሆኑን የመመርመርና ሥራ አስኪያጁ ስህተት ሠርቶም ከሆነ በፍርድ የማረም ስልጣን የላቸውም የሚል አንድምታዎች ትርጉም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህም የአንድ ድርጅት የእድገት ኮሚቴ፣ የእድገት አሰጣጥ ደንብና ሥርዓት በመከተል ለእድገት ለመወዳደር ያቀረቡትን ሠራተኞች ዕውቀትና ክህሎት ለመመዘን ድርጅቱ ያስቀመጣቸውን የብቃት መመዘኛ መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ በውድድሩ ከፍተኛ ውጤት ያመጣውን ሰራተኛ በመለየት፣የቀረበለትን የእድገት ውድድር ውጤትና የውሳኔ ሀሳብ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ውድቅ ቢያደርገው ሠራተኛው ጉዳዩን በፍርድ እንዲታይለት ለመጠየቅና ክስ ለማቅረብ ይቻላል ወይስ አይቻልም? ፍርድ ቤቱስ ይህንን ጉዳይ በዳኝነት በማየት አስገዳጅነት ያለው ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚሉትን የሕግ ጥያቄዎች የሚያስነሳ ነው፡፡

9. በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በሠራተኛ ዕድገት ዝውውርና ሥልጠና በሚመለከት አሠሪው የሚወስዳቸው እርምጃዎች በፍርድ ሊታዩና ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮች እንደሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 142 ንዑስ አንቀጽ 1/ሰ/ እና ከአንቀጽ 147 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ድንጋጌዎች ይዘትና ይህ ሰበር ችሎት ስለ ግል የሥራ ክርክርና ስለ ወል የሥራ ክርክር፣ የክልልም ሆነ የፌዴራል የሥራ ክርክር ችሎቶች የግል የሥራ ክርክሮችን በዳኝነት አይተው የመወሰን ሥልጣን ያላቸው መሆኑን በማስፋፋት በሰር መዝገብ ቁጥር 18180 ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም ለመረዳት ይቻላል፡፡

10. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ሥራ አስኪያጁ የእድገት ውድድሩን ውጤት ያልተቀበለው ያለበቂ ምክንያትና ከሕግ ውጭ ነው በማለት በሥር ፍርድ ቤት ያቀረባቸው የዳኝነት ጥያቄ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 138፣አንቀጽ 142 ንዑስ አንቀጽ 1/ሰ/ እና አንቀጽ 147 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ እንዲሁም ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 18180 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ በመቀበል አመልካች የእድገት ውድድሩን ውጤት አልቀበልም፣ አመልካች ተወዳድራ ባለፈችበት የሥራ መደብ አልመድብም የሚልበትን ምክንያትና ማስረጃ እንዲያቀርብ በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ ከላይ የተገለፁትን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 መሠረት ሠራተኛው ያለህጋዊ በቂ ምክንያት አሠሪው በዘፈቀደ እድገት ሲከለክለው በፍርድ እንዲታይለት የመጠየቅና ፍትህ የማግኘት መብቱን የሚያስከብር ትክክለኛ የዳኝነት አካሄድ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

11. የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ፡ የዕድገት ኮሚቴው ያቀረበውን የሠራተኞችን የዕድገት ውድድር ውጤት ውድቅ ያደረገው፣ ኮሚቴው ሠራተኞችን ያወዳደረው የእድገት አሰጣጥ ደንብና ሥርዓትን ሣይከተል /ወይም / በመጣስ ነው፡፡ ወይም ኮሚቴው የእድገት ማስታወቂያ ለወጣበት የሥራ መደብ ሠራተኞች ሊኖራቸው የሚገባውን ዕውቀትና ክህሎት ለመመዘን ድርጅቱ ያወጣቸውን የብቃት መመዘኛ መስፈርቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሣይከተልና ሣያሟላ ነው፡፡ በሚል ምክንያት እንዳልሆነ የሥር ፍርድ ቤት በውሳኔው በግልፅ ያሰፈረው የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ የውሳኔ ሀሳብ ለመረዳት ችለናል፡፡

12. በአንዛሩ የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ፣ አመልካች የተወዳደረችበት የሪከርድና ማህደር ሱፐርቫይዘርነት የሥራ መደብ የሚያስፈልገው በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪና ዜሮ አመት የሥራ ልምድ መሆኑ ተገልፆ የእድገት ማስታወቂያው እንዲወጣ ያደረገና ውድድሩም በዚሁ መሠረት የተከናወነ ሆኖ እያለ በውድድሩ ቀጥተኛ የሥራ ልምድ ያለው ሠራተኛ አልተገኘም በማለት በመጀመሪያ በመወዳደሪያነት ያላስቀመጠውን መስፈርት ጠቅሶ የአመልካችን እድገትም በቂና ህጋዊ ምክንያት ሣይኖረው አልቀበልም በማለታቸው ጉዳዩን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

13. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ የእድገት ማስታወቂያ ለወጣበት የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጅት በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ መሆኑን ተጠሪ በማስታወቂያው የገለፀና አመልካችም በተጠሪ የተጠየቀውን ትምህርት ዝግጅት /በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ/ ያላትና መስፈርቱን ያሟላች ሆኖ እያለና፣ በተጠሪ አመልካች ዕውቀት ክህሎት ለመመዘን የራሱን ፈተና አውጥቶ አመልካች ከሌሎች ሁለት ሠራተኞች ጋር ተወዳድራ ማለፏ ተረጋግጦ እያለ፣ ሥራ አስኪያጁ ውድድሩ " ብቃት ያለው ሰው "አላገኘንም በማለት በውሳኔው መግለፁ፣ ተጠሪ ራሱ ያወጣቸው የብቃት መመዘኛዎችና የትምህርት ዝግጅት ለሚላቸው አመልካች እድገቱን ላለመስጠት ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት እንቢተኛ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የእድገት ውድድሩን ለማከናወን የእድገት ማስታወቂያው ከወጣ በኋላ ያለፉትን አራት ወራት እድገቱን በውድድሩ አሸናፊ ለሆነችው አመልካች ላለመስጠት እንደምክንያት ማቅረቡ፣ የሕግ መሠረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

14. በአጠቃላይ ተጠሪ አመልካች ለዕድገት ተወዳድራ ያለፈችበት የሥራ መደብ ላይ ላለመመደብና እድገቱን ላለመስጠት በሥራ አስኪያጁ በኩል ያቀረባቸው ምክንያቶች በበቂ ምክንያት የተደገፈና የህግ መሠረት ያላቸው አይደሉም፡፡ በአንዛሩ ተጠሪ የእድገት ማስታወቂያ ሲያወጣ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶችና መመዘኛዎች የሚጥሱ ናቸው፡፡ አሠሪው የሠራተኞችን ብሔረሰብ ፣ፆታ፣ሀይማኖት፣ፓለቲካ አመለካከትና ሌላም ሁኔታ መሠረት በማድረግ ልዩነት ማድረግ የማይፈቅድለት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ/2/ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ተጠሪ ሴት በመሆኗ ምክንያት ተጠሪ እድገቱን እንዳልሰጣት በመግለጽ የምትከራከር ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ እድገቱን ለአመልካች ያልሰጣት ሴት በመሆኗ ምክንያት ሣይሆን በሌሎች ተጨባጭና አሳማኝ ምክንያቶች መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነቱን ያልተወጣ መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸውም ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

15. በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት ከላይ የጠቀሳቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ግያገናዝብ፣የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ተወዳድራ ብልጫ ያለው ውጤት በማምጣት ልታገኝ የሚገባውን እድገት የሥራ መደብ፣ ሊሰጣት ይገባል በማለት የሰጡትን ውሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59766 ጥቅምት 12 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የደረጃ እድገቱን በተመለከተ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. ተጠሪ አመልካችን በእድገት ማስታወቂያ መሠረት ተወዳድራ ባለፈችበት የሥራ መደብ ሊመድባት እና የስራ መደቡ የሚያስገኘውን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ሊከፍላት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. አመልካች የጠየቀችው ውዝፍ የደመወዝ ማስተካከያ ጥያቄ በዚህ ሰበር ችሎት በጭብጥነት ያልተያዘ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94931

የካቲት 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጥሩወርቅ መንግስቱ - ጠበቃ አቶ ስዩም አዳሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የተገጣጣሚ ህንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት - ጠበቃ አቶ መንግስቱ ኃይሉ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክሩን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ-ነገርም ባጭሩ፡- ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በግዥ አቅርቦት እና ሽያጭ መመሪያ የሥራ ኃላፊነት ላይ ተመድበው በመስራት ላይ እንዳሉ ባላወቁትና ባልተረዱበት ሁኔታ የስራ ውላቸው ያለቅድመ ማስጠንቀቂያ ከ24/05/2004 ዓ/ም ጀምሮ የተቋረጠ ለመሆኑ በ25/05/2004 ዓ/ም የተፃፈ ደብዳቤ በ3/6/2004 ዓ/ም የደረሳቸው መሆኑን ጠቅሰው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ሲሆን የስር ተከሳሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ፡- ከሳሽ ሊከፍሉን ይገባል በማለት ያቀረቡት የተለያዩ ክፍያዎች ጥያቄ በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37 መሰረት የስራ ውሉ ከተቋረጠበት ከ24/05/04 ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት 30/11/2004 ዓ/ም ያለው ጊዜ ከ6 ወር በላይ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የመጀመሪያ መቃወሚያ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በበኩሉ የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ከድርጅቱ የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንቡ አኳያ አገናዝቦ መመርመሩን ከገለጹ በኋላ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በ24/05/04 ዓ/ም ስለመሆኑ በስር ከሳሽ ያልተካደ መሆኑን፣ ክሱ ደግሞ የቀረበው በ30/11/04 ዓ/ም መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘቡንና የተከሳሽ ድርጅት የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37(3) መሰረት አንድ የሥራ መሪ የስራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ካላቀረበ መብቱ በይርጋ እንደሚታገድ የተደነገገ መሆኑን ካሰፈረ በኋላ ከሳሽ ክሱን ያቀረቡት የስራ ውሉ ከተቋረጠ ከ6 ወር በኋላ ነው የሚል ድምዳሜ ሀሳብ ላይ ከደረሰ በኋላ ክሱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 244(2)(ሠ) እና 245(2) መሰረት በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት መዝገቡን በብይን ዘግቷል፡፡ በአሁኗ አመልካች ይግባኝ አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ይግባኙን ከመረመረ በኋላ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ብይንና ትዕዛዝ በመቃወም ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ደብዳቤ አመልካች የደረሰው በ3/6/2004 ዓ/ም መሆኑ እየታወቀ እና ከዚህ ቀን ጀምሮ ክሱ በስር ፍ/ቤት እስከቀረበበት ሐምሌ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ደግሞ 6 ወር የማይሞላ መሆኑ እየታወቀ ክሱ በስር ፍ/ቤቶች በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ እና ጉዳዩ ወደ ስር ፍ/ቤት ተመልሶ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ በፅሁፍ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን በአመልካች የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በስር ፍ/ቤቶች በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን መርምረናል፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው አመልካች የሚከራከሩት የይርጋ ጊዜው መቆጠር ሊጀምር የሚገባው የስራ ውሉ ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን የስራ ውሉ የተቋረጠበት ደብዳቤ ከደረሰኝ ከ3/6/2004 ዓ/ም ጀምሮ መሆን አለበት በሚል ሲሆን ተጠሪም በበኩሉ የሥራ ውሉ መቋረጫ ደብዳቤ ለአመልካች የደረሰው በ3/6/2004 ዓ/ም መሆኑን ሳይክድ ሆኖም ግን በተጠሪ ድርጅት የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37 ድንጋጌ መሰረት አንድ የሥራ መሪ የመብቱን ጥያቄ ለማቅረብ ከሚችልበት ቀን ጀምሮ እስከ 6 ወር ጊዜ ድረስ ጥያቄውን ካላቀረበ መብቱ በይርጋ ይታገዳል በሚል ስለሚደነግግ እና አመልካችም ከዚህ አኳያ አሉኝ የሚሉትን መብት ለማቅረብ የሚችሉት የስራ ውሉ ከተቋረጠበት ከ24/05/04 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑ በግልጽ በተደነገገበት ሁኔታ አመልካች የሥራ ውሉ መቋረጫ ደብዳቤ ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ መሆን አለበት በሚል ጠቅሰው ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም በሚል የሚከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ ማለትም የመብቱ ጥያቄ ስለሚቀርብበት የይርጋ ጊዜን አስመልክቶ ተፈፃሚነት ያለው ይሄው በተጠሪ ድርጅት የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተመለከተው የ6 ወራት የጊዜ ገደብ ስለመሆኑ አከራካሪ ባይሆንም ሆኖም ግን የይርጋ አቆጣጠሩን መነሻ ጊዜ በተመለከተ ተጠሪም በበኩሉ ለዚህ ሰበር ችሎት በሰጠው መልስ ይሄንኑን መነሻ በማድረግ ክርክሩን እንዳቀረበው የፍ/ብ/ህ/ቁ፣ 1846 ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይም አግባብነት ያለው ስለመሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ይህ የተጠቀሰው ድንጋጌም “የይርጋ መነሻ ጊዜ” በሚል ርዕስ የተሰየመ ሲሆን የድንጋጌው ሙሉ ይዘትም የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምረው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም ውሉ የሚሰጠው መብት ከተሰራበት ጀምሮ ነው የሚል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመረምረውም በመጀመሪያ ደረጃ የአመልካች ስራ ውል የተቋረጠው ከ24/05/04 ዓ/ም ጀምሮ ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የስራ ውሉ መቋረጫ ደብዳቤም ለአመልካች የደረሰው በ3/06/2004 ዓ/ም ስለመሆኑም እንዲሁ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ እና ከ3/06/2004 ዓ/ም በፊትም አመልካች የስራ ውሉን አስቀድሞ የተቋረጠ መሆኑን በሌላ አግባብ ታውቆ ነበር በሚል ከተጠሪ የቀረበ ክርክር በሌለበት ሁኔታ ደግሞ አመልካች የስራ ውሉ መቋረጡን መነሻ በማድረግ መብቷን የማስከበር እንቅስቃሴ ልትጀምር የምትችለው የስራ ውሉ የተቋረጠበት ደብዳቤ ከደረሳት እለት ጀምሮ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ከ3/6/2004 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ ክሱ ለስር ፍ/ቤት እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ (ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ/ም) ያለው ሲቆጠር ደግሞ 6 ወር ያላለፈ በመሆኑ በተጠሪ ድርጅት የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37 ድንጋጌ መሰረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ብይንና ይሄንኑን ብይን በማፅናት በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1846ና የተጠሪ ድርጅት ስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37 ድንጋጌን ይዘት፣ መንፈስና አላማን ያላገናዘበ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 32077 በ21/07/05 ዓ/ም የሰጠው ብይንና ይሄንኑን በማፅናት የፌዴራሉ ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 137495 በ11/02/06 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ 32077 የሆነውን በማንቀሳቀስና ግራ ቀኙን አስቀርቦ ክርክሩ ከቆመበት ጀምሮ በማከራከር በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ዘንድ ክርክሩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98099
ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡-

1. ወ/ሮ ደንቂ አዳ
2. አቶ በኃይሉ ዘለቀ
3. አቶ ነጋሽ ባልቻ
4. አቶ ዩሐንስ አፊቾ
5. አቶ ገመዳ በጅጋ
6. አቶ ገላዬ ገመቹ
7. ወ/ሮ በቀለች ያኢ
8. አቶ በላይ ገላ
9. አቶ ግዛው ታፈሰ
10. አቶ አበራ በየነ
11. ወ/ሮ ፈለቀች እሸቱ
12. ወ/ሮ ጌጤ በቀለ
13. ወ/ሮ እጅጋየሁ ኃይሌ
14. ወ/ሮ ትምህርተ ወልዴ
15. ወ/ሮ መሬማ ሁሴን
16. አቶ መሀመድ ዳምጠው
17. ወ/ሮ ማናለ ዘውዴ
18. ወ/ሮ የኔነሽ ኃይሉ
19. አቶ ሃብታሙ አበበ
20. አቶ ብርሃኑ ድረስ
21. ወ/ሮ የሺወርቅ ገ/ሚካኤል
22. ወ/ሮ ሳባ ጥሩነህ
23. ወ/ሮ ወይንሸት ወንድሙ
24. ወ/ሮ ሶፊያ መሀመድ
25. አቶ አድማሱ ያለው
26. ወ/ሮ ቀጸላ ታመነ
27. አቶ ሐሰን መሀመድ
28. ወ/ሮ እናኑ ወልደየስ
29. አቶ ተሸመ ተ/ፃዲቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ፐልፕ እና ወረቀት አክሲዮን ማህበር-ነገረ ፈጅ ጂብሪል አልቃድር ቀረ መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት አድርጎ የቀረበን የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባሁኑ በተጠሪ ላይ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካቾች የክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ከተጠሪ ጋር መስርተው የነበረውን የስራ ውል የአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) ድንጋጌን መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጡረታ መብት እንዲጠበቅላቸው መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ/ም ወስኗል በሚል ምክንያት ለአመልካቾች የስራ ውል ማቋረጫ ደብዳቤ የሰጣቸው መሆኑን፣እድሜአቸው ስልሳ አመት ሳይሞላ በጡረታ እንዲሰናበቱ መደረጉ ከሕግ ውጪ መሆኑን ጠቅሰው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) ድንጋጌ መሰረት በሚንኒስትሮች ምክር ቤት በተወሰነው መሰረት የጡረታ መብት ተጠብቆላቸው የተሰናበቱ ስለሆነና በዚህ አግባብ የተሰናበተ ሰራተኛ ደግሞ የስራ ስንብትም ሆነ ካሳ የሚከፈልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሠጠውን ውሳኔ እንዲቀርብ አድርጎ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች በጡረታ እንዲወጡ መደረጉ መረጋገጡንና በጡረታ የወጡት ሰራተኞች ደግሞ የሚተዳደሩት በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት መሆኑን ጠቅሶ ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት የተሰረዘባቸው ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግን ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾች ጥያቄ የጡረታ እድሜ ሳይደርስ ጡረታ እንድንወጣ ተደርጓል የሚል በመሆኑና ይህም በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል ያለመሆኑን ከጠቀሰ በኃላ የአመልካቾች ጉዳይ እድሜ ስላልደረሰ በጡረታ መውጣት አይገባንም የሚል በመሆኑ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን ውጤቱን አጽንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የአመልካቾች የክስ ይዘት ስንብቱ ከሕግ ውጪ ጡረታ እድሜ ደርሷል የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ለሕገ ወጥ የስራ ውል ማቋረጥ የሚከፈሉት ክፍያዎች እንዲከፈሉ ይወሰንልን ዳኝነት የሚጠይቅ ሁኖ ሳለ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በፍርድ ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊዳኝ የሚችል አይደለም ተብሎ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ክስ የመሰረቱት የሥራ ውሉ በዕድሜ ምክንያት እንዲቋረጥ መደረጉ ከሕግ ውጪ ስለሆነ ለሕገ ወጥ የሥራ ስንብት የሚከፈሉ ክፍያዎች እንዲከፍሉ ይወሰንልን በሚል መሆኑን፣ተጠሪ ደግሞ አመልካቾች መሰናበታቸውን ሳይክድ ስንብቱ ሕጋዊ ነው የሚልበትን ምክንያት ጠቅሶ በዚህ ረገድ ማስረጃ አቅርቦ መከራከሩን ነው፡፡ስለዚህ ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር በጭብጥነት ተይዞ ዳኝነት የሚፈልገው ጉዳይ ስንብቱ ሕጋዊ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የሥራ ስንብት የሚደረግባቸው ምክንያቶች ተለይተው የተቀመጡ ሲሆን ስንብቱ አከራካሪ ሁኖ ሲገኝም ዳኝነት የሚሰጡ አካላት የትኞቹ እንደሆኑ አዋጁ ያሳያል፡፡በአዋጁ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን አከራክሮ ለመወሰን ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚመለከታቸው የክርክር አይነቶች ተገልጸዋል፡፡መደበኛ ፍርድ ቤቶች የአሠሪና ሠራተኛን ክርክር በቀጥታ ሲቀርብላቸው ወይም ደግሞ በይግባኝ ሲመጣላቸው ለማስተናገድ እንደሚችሉ የአዋጁ አንቀፅ 138 እና 139 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡መደበኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ለማየት ሥልጣን የሚኖረው ግል የሥራ ክርክሮችን ሲሆን የግል የሥራ ክርክር የሚባለው በአዋጁ አንቀጽ 138 (1) ላይ የተገለፁት እና ተመሣሣይ ውጤት ያላቸው ክርክሮች ናቸው፡፡ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች በይግባኝ ሊታዩ የሚችሉት ጉዳዮች ደግሞ ቦርዱ ያያቸውን ጉዳዮች፣በሥልጣን ላይ የሚቀርብን መቃወሚያ፣የማህበር ምዝገባን ክልከላ፣ሚኒስቴሩ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ያለን ቅሬታ፣የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው በሰጠው ውሳኔ ላይ፣ ሚኒስቴሩ እገዳንና የማህበር ስረዛን በተመለከተ በሰጠው ውሳኔ ላይ ስለመሆኑ አዋጁ ያሳያል፡፡

ጉዳዩ የግል የስራ ክርክር ወይም የወል የስራ ክርክር መሆኑን መሰረት አድርጎ የሚለይበት የሕግ አግባብና በዚህ ረገድ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣንን መወሰን እንደተጠበቀ ሁኖ የስራ ውሉ የተቋረጠው በበቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑ ጉዳዩን ለመዳኘት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት ስልጣን በተሰጠው አካል የሚወሰን ይሆናል፡፡ሌሎች ሕጎችም የስራ ውል መቋረጥን ሊያስከትሉ የሚችሉ ምክንያቶችን በዝርዝር ደንግገው ሊያስቀምጡ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ከውሉ መቋረጥ ጋር ተያይዞ ክርክር ከተነሳ ይህንኑ ጉዳይ የሚዳኘው አካል ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ነገር መኖር ያለመኖሩን መመርመርን የግድ የሚለው ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአዋጅ ቁጥር 377/1996 የስራ ውል ስለሚቋረጥበት ምክንያቶችና ሁኔታዎችን በአንቀጽ 23፣ ከአንቀጽ 26 እስከ 30 ተደንግገው ይገኛሉ።በተጨማሪም በሕብረት ስምምነት መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ተደርጎ የተወሰደ ጉዳይም በአሰሪው ተነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 27/1/ተ/ ስር ተደንግጎ ይገኛል። በአዋጁ አንቀጽ 24 እንደተመለከተው ውሉ በሕግ የሚቋረጥበት ምክንያቶች በአብዛኛው ከሁለቱም ወገን ቁጥጥር ውጭ ያሉ ሲሆን የስራ ውል ሁለቱም ፈቃደኝነት የሚገበቡበት እንደመሆኑ ሁሉ ሁለቱም በፈቃደኛነት ከተስማሙ ውሉን ሊያቋርጡ የሚችሉበት ሁኔታም በአንቀጽ 25 ስር ሰፍሮ ይገኛል።ስለዚህ ከላይ በተገለጹት ቁጥሮች በተደነገጉት ምክንያቶችና ሁኔታዎች የሚፈጸም የስራ ውል መቋረጥ ሕጋዊ የስራ ውል መቋረጥ ሲሆን ከነዚህ ውጭ የሚደረጉ የስራ ውል መቋረጥ በሕገ ወጥነት የሚፈረጁ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 42 ድንጋጌ ስር ተመልክቷል። በዚህም ላይ በመመስረት የሚያስከትሉት ውጤቶች የሚለያዩ በመሆኑ በተናጥል የሚያስከትሉትን ውጤት ከሕጉ አግባብ በማየት ዳኝነትን መስጠት ይጠይቃል።

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከት የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው፣የጡረታ እድሜያችን ሳይደርስ በጡረታ እንድንወጣ ተደርጎ ውሉ ተቋርጧል የሚል ነው።አመልካች ደግሞ በሕጉ አግባብ የሥራ ውሉ መቋረጡን ጠቅሶ የስንብት እርምጃው ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል።ከዚህ መረዳት የሚቻለው የተጠሪ ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24 እና አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) መሰረት የቀረበ ሁኖ አመልካቾች ደግሞ እድሜያቸው ለጡረታ ስለመድረሱ ሳይክዱ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) መሰረት የስራ ውል የሚቋረጠው የሠራተኛው የአገልግሎት ዘመን 25 አመት ያላነሰና እድሜው ከሃምሳ አመት ያላነሰ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ህልውና በማክተሙ፣ የሰው ኃይል ብዛቱ ከሚፈልገው በላይ በመሆኑ ወይም ከፕራይቬታይዜሽን ጋር በተያያዘ ከሥራ እንዲሰናበት ከተደረገና አገልግሎቱ ከ25 ዓመት ያላነሰና ዕድሜው ከ50 ዓመት ያላነሰ ሆኖ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲወሰን ነው በሚል ነው። ይህም ስንብቱ ከህግ ውጪ የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው ክርክራቸውን ማቅረባቸውን የሚሳይ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ስንብቱ በሕግ አግባብ የተደረገ መሆን ያለመሆኑን ከመመርመር የሚያግደው አይደለም።ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) ድንጋጌ አግባብ አመልካቾች በጡረታ እንዲገለሉ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ማስወሰኑ የተካደ ፍሬ ነገር አይደለም።በዚህ ረገድ አመልካቾች በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡት የመልስ መልስ ይዘት ሲታይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉዳዩ መወሰኑን አምነው ተጠሪ ይህንኑ ውሳኔ አሳስቶ ያስወሰነ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ውሳኔው የለም በማለት ያቀረቡት ክርክር የለም።በመሆኑም አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) መሰናበታቸው ከተረጋገጠ ይኼው ውሳኔ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት እስካልተለወጠ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት የሚከራከሩበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብ የለም፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች ጥያቄ የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት ነው በሚል የቀረበና ውጤቱም በአዋጁ አንቀጽ 39 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብ እንዲታይ የቀረበ መሆኑን በማገናዘብ ጉዳዩ የመደበኛ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት የሚታይ ነው በማለት ክርክሩን ማየት ሲገባቸው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ይሁን እንጂ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) መሰረት ከስራ የተሰናበቱና የጡረታ መብታቸውም ተከብሮ አበሉን በመቀበል ላይ እንደሚገኙ በተጠሪ በኩል የቀረበውን ክርክር ግልጽ ማስተባበያ ያላቀረቡና በዚህ ረገድ ስልጣን ባለው አካል የተሰጠው ውሳኔም በስርዓቱ መሰረት ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ የሆነበት አግባብ ስለመኖሩ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ በመሆኑ የተጠሪ እርምጃ ሕጋዊ ነው? ወይስ አይደለም? በሚለው እና በውጤቱ ላይ ክርክር እንዲካሄድ ማድረግ የስነ ስርዓት ሕጉን አላማ ያገናዘበ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ ስላልተገኘ በዚህ ችሎት በዚህ ረገድ ድምዳሜ መያዙ ተገቢ ሁኖአል፡፡በመሆኑም አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) መሰረት በተሰጠ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ በጡረታ የተገለሉና የጡረታ መብትም ተጠቃሚ መሆናቸው ያልተካደ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው ከውጤት አንፃር ሲታይ የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 66514 ሀምሌ 11 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16522 ነሀሴ 09 ቀን 2005 በትዕዛዝ፣በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 173499 ታህሳስ 14 ቀን 2006 ዓ/ም ምክንያቱ ተለውጦ በፍርድ የፀናው ብይን በውጤት ደረጃ ሲታይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) አግባብ ተሰናብተው የእድሜ ልክ የጡረታ መብት ተከፋይ መሆናቸው የተረጋገጠ ስለሆነ የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችል አይደለም ብለናል፡፡በዚህም ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 35(1(ሀ) እና 44፣40(1) እና (2)፣36 እና 38 እንዲሁም 43(3) እና 44(4) ድንጋጌዎች አግባብ የጠየቋቸው የክፍያ አይነቶች ሊከፈሏቸው አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውልውጭ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92040

ሚያዚያ 09 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-አቶ ጥምቀቱ ጋመነ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-ወ/ት ታገሰች ዮሐንስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሰረት ያደረገን የጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካችና በአቶ ቢኒያም አሚቲ ላይ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ በገንዘብ ያሻቸነት ሥራ ተቀጥረው የተጣራ ብር 1717.054 በወር እየተከፈላቸው እንደሚሰሩ፣ነሐሴ 15 ቀን 2003 ዓ/ም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሰሌዳ ቁጥሩ 1-16423 አ.አ የሆነውና ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች የሆነ ሚኒባስ በአቶ ቢኒያም አሚቲ ይሽከረከር እንደነበርና ያለበቂ ጥንቃቄ እየተሽከረከረ ለእግረኛ ቅድሚያ መስጠት ሲገባው ይህንን ባለማድረግ በወቅቱ የዜብራ መንገድ ከቀኝ ወደ ግራ መንገዱን በማቋረጥ ላይ የነበሩትን ተጠሪን በመኪናው የፊት ለፊት አካል ገጭቶ በመጣል የግራ እጅ የላይኛው ክንድ አጥንት እንዲሰበር፣የቀኝ ትከሻ እንቅስቃሴ እንዲገደብ፣ሶስት ጥርሶች እንዲወልቁ የግራ እግር ቅልጥማቸው እንዲሰነጠቅ በማድረግ በአጠቃላይ የ30% ቋሚ የአካል ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት መሆኑን፣ጉዳቱ ሲደርስ እድሜአቸው 28 አመት ሁኖ ወደፊት ተጨማሪ 40 አመታት ለመኖር እንደሚችሉ ገልፀው በወር እየሰሩ እስከ አርባ አመታት ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን ገንዘብ አስልተውና የሞራልና የህክምና ወጪ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ወጪዎችን ደምረው በጠቅላላው ብር 269,344.50(ሁለት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ አርባ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ከወጪና ኪሳራ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ወደፊት ሰርተው ለመኖር የማይከለክላቸው እንዲሁም ደመወዛቸው ተብሎ የቀረበውም በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን ለጉዳቱ ኃላፊ በማድረግ የኃላፊነት መጠኑን ደግሞ ተጠሪ በወር ብር 1717.50 እንደሚያገኙ መረጋገጡን፣ተጠሪ የደረሰባቸው የአካል ጉዳትም 30% መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ ለወደፊትም አርባ አመት ሊኖሩ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ተጠሪ በወር ያገኙ የነበሩትን የተጣራ ገቢ በብር 1717.50(አንድ ሺህ ሰባት መቶ አስራ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) በአርባ አመት ሲሰላ ብር 247,320.00 (ሁለት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ብር) እንደሚመጣ፣ከዚህም በተጨማሪ በጉዳቱ ምክንያት ለህክምና የወጣው ወጪ መጠኑ ብር 13,024.00፣የሞራል ካሳ ብር 1000.00፣የትራንስፖርት ወጪ ብር 1000.00 መሆኑን ገልፆ በድምሩ ብር 261,544.00(ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ሺህ አምስት መቶ አርባ አራት ብር) አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ የተጠሪ የተጣራ ወርሃዊ ደመወዝ ብር 1617.50 መሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ የአካል ጉዳት መጠኑን በማሻሻል ብር 232,848.00 (ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ስምንት ብር) እንዲሆን አድርጎ ሌሎች ክፍያዎችን ግን ተቀብሎ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ተቀብሎ ዳኝነት ሰጥቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘቱም ባጭሩ፡-ተጠሪ በጉዳቱ ምክንያት የተቋረጠባቸው ገቢ ሳይኖር የጉዳት ካሳ ይገባቸዋል ተብሎ መወሰኑም ሆነ የጉዳት ካሳ ስሌቱ እንዲሁም ካሳው በቀለብ መልክ እንዲከፈል መደረግ ሲገባው በአንድ ጊዜ እንዲከፈላቸው መወሰኑ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም ይህ ችሎት እንዲመለከተው የተያዘው ጭብጥ፡-በተጠሪ ላይ ደርሷል ከተባለ የ30% የአካል ጉዳት አኳያ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው የካሳ መጠን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090 እና 2091 አንፃር ለመመርመር ሲባል ነው፡፡በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ ተብለው መወሰኑ ላይ ሳይሆን የካሳ ስሌቱን በተመለከተ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት የተገነዘብነው ተጠሪ ስራቸው ገንዘብ ያዥ ሲሆኑ ከጉዳቱ በሁዋላ ለዚህ ስራ ብቁ አይደሉም ባይባልም 30% ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሕክምና ቦርድ መቅረቡንና በዚህ ስራ ሲያገኙ የነበረው ያልተቋረጠ ስለመሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ነጥቦች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ነው።የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳቱ ምክንያት ወደፊት ተጠሪ የሚቀርባቸውን ገቢና ከጉዳቱ ጋር ተያይዘው የወጡትን ወጪዎች በመለየት የካሣ መጠኑንም መወሰናቸውን ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል።

በመሰረቱ ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን ፣መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣2091፣2092፣2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው።የበታች ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የካሳ መጠን ላይ ይግባኝ የሌለው መሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2152 ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኙ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 ስር ተገልጿል።

በተያዘው ጉዳይ በአመልካች በኩል የቀረበውን ቅሬታና በሰበር ችሎቱ የሕግ ትርጉም ያስፈልገዋል ተብሎ በጭብጥነት የተያዘውን ነጥብ መሰረት ስናደርግ በካሳ አተማመኑ ላይ በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ሳይገቡ በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ስለመሠጠቱ የሚያሳይ ነገር ያለ ሁኖ አልተገኘም።

ተጠሪ አካላቸው በሕገ መንግስቱም ጥበቃ የተደረገላቸው ሲሆን ካሳው ሲወሰንም ይህንኑና ጉዳቱ በአመልካች የወደፊት ኑሮ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው አጠቃላይ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ሊወሰን የሚችል እንጂ ተጠሪ 30%(ሰላሳ ከመቶ) ጉዳት ቢደርስባቸውም ይሰሩ የነበሩትን ስራ ላለመስራት ወይም ሌላ ስራ ላለመስራት እንቅፋት አይሆንባቸውም፣እንዲያውም ስራውን በመስራት ላይ የሚገኙ በመሆኑ የተቋረጠባቸው ገቢ የለም በሚል ምክንያት ብቻ ካሳው ሊቀነስ ይገባል፣ወይም ጭራሹን አይገባቸውም ሊባል የሚችል አይደለም።

ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ የሚገዙት የፍትሐብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች መንፈስ የጉዳትን ጠቅላላ ባህርይና የካሣ ልክ አተማመን ሁኔታዎችን ያስገነዝቡናል። በዚህም መሠረት ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ ችግር የሚያደርስ መሆኑን፣ ይህም ጥቅም ማቴሪያላዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራላዊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። የተጎዳ ሰው ደግሞ መካስ እንዳለበት ያስረዳሉ። የካሣውን አተማመን በተመለከተም መጠኑ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሁኖ መመዘን ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 ድንጋጌ ያሣያል።የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትን/future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል። በእነዚህ ድንጋጌዎች የጉዳት ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን ሕጉ በግልጽ ከማስቀመጡም በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብነት ሊለያይ የሚችል መሆኑን የሕጉ መንፈስ ያስገነዝባል። በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን የካሣ አከፋፈሉን ልክ በሚደነግገው የሕጉ ክፍል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ በሌላ በኩል የካሣ አተማመን ሥርዓት ጠቅላላ የመስራት አቅም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/General utility/ ሣይሆን ልዩ ጠቀሜታ/specific utility/ መርህን ቢከተል ፍትሐዊነት ያለው አሠራር መሆኑ ይታመናል፡፡ ይህም አሠራር በተጨባጭ የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የካሣውን ልክ ያላግባብ ከማጋነንና ከመቀነስ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡በመሆኑም ጉዳት መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠና ጉዳቱም በተጎጂው የወደፊት ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለመሆኑ ከተረጋገጠ ካሣ መወሰን ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ አኳያ አግባብነት ያለው ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተ በሕጉ ዳኞች በተሰጠው ሥልጣን ወይም በጉዳዩ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት በመተመን ለተጎጂው መፍረድ የሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መኖሩን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎችና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2101 እና 2102 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ ውጪ ጉዳቱ መድረሱ እየታወቀ የአሁንና የወደፊት ቁሣዊ ጉዳት /material damage/ ስለመኖሩ ተጎጂው አላስረዳም ተብሎ የመካስ መብት ማጣት ከአጠቃላይ ከውል ውጪ ኃላፊነትን ከሚገዛው ሕግ አላማ ጋር አንድ ላይ የሚሄድ አይሆንም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ንብረትነቱ የአመልካች በሆነው መኪና በዜብራ መንገድ ላይ በማቋረጥ ላይ በነበሩበት ጊዜ የመኪናው አሽከርካሪ ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ በፈጸመው ድርጊት ምክንያት በመኪናው ተገጭተው በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው ጉዳት መድረሱን፣በዚህ ጉዳትም በአካላቸው ላይ 30%(ሰላሳ ከመቶ) ጉዳት መድረሱ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳቱ ወደፊት ሊጠፋ የሚችል ስለመሆኑም የተገለፀ ነገር የለም፡፡በመሆኑም ተጠሪ በአመልካች ካሳ የማይከፍሉበት ምክንያት የለም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት የካሳ መጠኑን በተመለከተ የተጠሪ ወርሃዊ ደመወዝ በተገቢው ማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ፍሬ ነገሩን የማጣራት ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ተቀጥረው ሲሰሩ በወር ያገኙ የነበረውን የተጣራ የደመወዝ መጠን በማስረጃ ያረጋገጡት በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሆኖም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳቱ በደረሰ ጊዜ የተጠሪ እድሜ 28 አመት መሆኑን በማስረጃ አረጋግጠው ከተቀበሉ በኋላ ተጠሪ ወደፊት ሊኖሩ የሚችሉት አርባ አመት መሆኑን ግን በበቂ ምክንያትና ማስረጃ አስደግፈው የተቀበሉት መሆኑን ውሳኔው አያሳይም፡፡አንድ ሰው ወደፊት የሚኖርበትን የእድሜ መጠን በመግለጹ ብቻ ይሄው በተጎጂው የተገለፀው የእድሜ መጠን ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቶ የጉዳት ካሳ የሚሰላበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ በመሆኑም ወደፊት ለመኖር የሚገለፀው እድሜ በአጠቃላይ የአገሪቱን በተለይ ደግሞ የአካባቢውንና ተጨባጭ ሁኔታና በዚህ ረገድ የሚመለከተው አካል ያስቀመጠው ጥናታዊ መነሻ ካለ ይህንኑ መሰረት ማድረግ ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ወደ ፊት በሕይወት ልኖር እችላለሁ በማለት ያቀረቡት የእድሜ መጠን በአጠቃላይ የአገሪቱን ወይም በተለይ የሚኖሩበትን አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም የሚመለከተው አካል ይፋ ያደረገውን ጥናት መሰረት ያደረገ መሆኑን የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡በመሆኑም ተጠሪ አርባ አመት ወደፊት ሊኖሩ ይችላሉ ብሎ መያዝ የሕግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡት የእድሜ መጠን ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ከተባለ ደግሞ ምክንያታዊ የሆነ እድሜ መያዝ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ተጠሪ የግል ድርጅት ተቀጣሪ ሰራተኛ እንደመሆናቸው መጠን በስራው ላይ ሊቆዩ የሚችሉት ስልሳ አመት መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 17(1) ድንጋጌ ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም ተጠሪ ከዚህ አመት በላይ በቅጥር ላይ በተመሰረተ ግንኙነት ሊያገኙ የሚችሉት ገቢ ሊቋረጥ ወይም ሊቀንስ ይችላል ብሎ ለመውሰድ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪን የወደፊት እድሜ አርባ አመት ነው በማለት ካሳውን ከዚህ ጊዜ አንጻር በመመልከት ማስላታቸው ሊገምቱት የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያላግባብ በመያዝ ወይም ትክክለኛውን መንገድ ትተው ያላግባብ የሆነውን ያገማመት መንገድ መያዛቸውን የሚያሳይ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2253(ሀ) ድንጋጌ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የጣሰ ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህ አይነት ሁኔታ በሚወሰነው የካሳ መጠን ደግሞ ይግባኝ ማቅረብ እንዲሁም በሰበር ማሳረም የሚቻል መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2152 እና 2153 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡እንዲሁም አመልካች ተጠሪ ወደፊት የሚኖሩበትን እድሜ አስመልክቶ በግልጽ ክርክር አላቀረቡበትም ቢባል እንኳን ጉዳዩ የጉዳት ካሳ ክፍያ ይገባኛል የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን በፍርድ ቤቶቹ ጉዳዩ ከመታየት ሕጉ የማይከለክል መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 83 ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ነጥብ ነው፡፡ ስለሆነም በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰላው የካሳ መጠን በውጤት ደረጃ ሲታይ ከላይ የተመለከቱትን የካሳ አተማመን መንገዶችን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና ጉልሕ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት የጉዳት ካሳ አከፋፈሉ በቀለብ መልክ በየወሩ ሊሆን ሲገባ በአንድ ጊዜ እንዲከፈል መደረጉ ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2154 ድንጋጌ ሲታይ የጉዳት ካሳ አከፋፈል በአንድ ጊዜ ሊሆን የሚችል መሆን ያለመሆኑን በአቀራረፁና ይዘቱ ለፍርድ ቤቱ ፈቃድ የሠጠ ከመሆኑ አንፃር የካሣው አከፋፈል በጡረታ መልክ ሊሆን ይገባል የሚለው የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ክፍያው በአንድ ጊዜ ሊሆን እንደሚችልና ለፍርድ ቤቱ የተተወ ስልጣን መሆኑንም ይህ ችሎት በመ/ቁጥር 67225 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በካሳ ስሌት ደረጃ ሲታይ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 69127 ጥር 20 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 131954 ሐምሌ 08 ቀን 2005 ዓ/ም ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለጉዳቱ ከመኪናው አሽከርካሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የአካል ጉዳት ካሳ መጠን ግን መታሰብ ያለበት ተጠሪ ወደፊት ስልሳ አመት እስከሚሞላቸው ድረስ ሊኖሩ ይችላሉ ተብሎ ሊሆን ስለሚገባው ጉዳቱ ሲደርስ ተጠሪ የነበራቸውን እድሜ (28 አመት) መነሻ በማድረግ ወደፊት የሚቀራቸው 32 አመት መሰረት ተደርጎ ሊሰላ ይገባል ብለናል፡፡በዚህም መሰረት የተጠሪ የተጣራ ወርሃዊ ገቢ ብር 1617 መሆኑ ስለተረጋገጠ ይኼው ገንዘብ በአስራ ሁለት ወራት እና በሰላሳ ሁለት አመታት ሲባዛ የሚመጣው ውጤት (1617×12×32×30%=186,278.40) አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሰምንት ብር ከአርባ ሳንቲም) ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የአካል ጉዳት ካሳ ነው ብለናል፡፡ሌሎች የክፍያ አይነቶችን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አልተነካም፡፡ተጠሪ የዳኝነት መክፈል ያለባቸው በዚህ ችሎት በተወሰነው የካሣ መጠን ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በመዝገቡ ነሐሴ 09 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93104

ሚያዚያ 2 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር - ነ/ፈጅ ግርማ ሞገስ - ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ደስታ ጁላ ቤካሎ - ጠበቃ አንዱዓለም በእውቀቱ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያላግባብ ለውጭ አገር ጉዞ የተከፈለ የመንገዣ ወጪና አበል ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች የክስ ይዘትም፡-ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት የአንድ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆናቸው ለስራቸው ጠቃሚ የስራ ልምድ ገብይተው እንዲመለሱ አመልካች ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ ወደ አውስትራሊያ አገር ልኳቸው የተላኩበትን ትምህርት አጠናቅቀው ሃላፊነታቸውን መወጣት ሲገባቸው ከተላኩበት አገር ሳይመለሱ መቅረታቸውን ገልፆ ለአበል፣ለስልጠናና ለአውሮፕላን መንገዣ የተከፈላቸውን ብር 180,574.94 (አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ አምስት መቶ ሰባ አራት ብር ከዘጠና አራት ሳንቲም) ከእነ ወለዱ እንዲመልሱ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት ለክሱ በሰጡት መልስ ወደ ውጪ አገር የተላኩት ለስራ ጉብኝት እንጂ ለትምህርት አለመሆኑ ጠቅሰው ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ለመመለስ ከሕግም ሆነ ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ተጠሪ ገንዘቡን እንዲመልሱ እየጠየቀ ያለው ያላግባብ ስለመበልጸግ የተጠቀሱትን ድንጌዎችን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ በቃል ክርክር ጊዜ ግልጽ ያደረገ ቢሆንም ተጠሪ ያላግባብ ተገልግሏል በማለት አመልካች ከመግለጽ ውጪ ያገኘው ጥቅም ስለመኖሩ አላስረዳም በሚል ምክንያት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ የአመልካችን ክስ በከፊል ውድቅ አድርጎታል፡፡ እንዲሁም የተጠሪ ጠበቃ ተጠሪ በአገር ውስጥ እያለ ለአበል ወስደው ያላወራረዱት ብር 832.00 (ስምንት መቶ ሰላሳ ሁለት ብር) መኖሩን ያመኑ በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ በከፊል ቅር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ውስጥ የፌዴራል የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከፍተኛ ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ ለስራው ጠቃሚ የሆነ ትምህርታዊ እውቀት ገብይተው እንደሚመለሱ ወደ አውስትራሊያ አገር ሲላኩ ለአበል ለስልጠናና ለአውሮፕላን መንገዣ አመልካች ብር 180,574.94 ከፍሎላቸው ከሄዱና ስልጠናውን ከወሰዱ በኋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው በቀሰሙት ሙያ ለአገራቸው አገልግሎት መስጠትና ኃላፊነታቸውን መወጣት ሲገባቸው በዚያው ሳይመለሱ መቅረታቸው ተረጋግጦ እያለ ጥቅም ስለማግኘታቸው አልተረጋገጠም ተብሎ ክሱ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደረጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አመልካች ተጠሪው ለመንግስት ስራ እንዲረዳቸው ከውጪ አገር ልምድ ቀስመው እንዲመጡ ወጪ አውጥቶ ከላካቸው በኋላ ወደ አገራቸው ሳይመለሱ መቅረታቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ያገኙት ጥቅም ስለመኖሩ አልተረጋገጠም ተብሎ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው ተጠሪ ለመንግስት የስራ ጉዳይ ወደ ውጪ አገር ሂደው በዚያው ስለቀሩ ለጉዞና ለስልጠና የወጣ ወጪ ሊመለስልኝ ይገባል በሚል ሲሆን ተጠሪ በአመልካች የስራ ምክንያትና ወጪ ወደ ውጪ አገር መሄዳቸውን ሳይክዱ ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከሩት የተገኘ ጥቅም የለም፣ወደ ውጪ አገር የሄዱበትን ስራ ሰርተው ተገቢውን ሪፖርት አጠናቅረው ለአመልካች መስሪያ ቤት አስረክበዋል በሚሉ ምክንያቶች መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው የሌላውን ሰው የሥራ ድካም ወይም በሌላው ሰው ሀብት በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ እንደሆነ አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሀብቱ ወይም በጉልበቱ የደከመው ሰው የመመለስና የመካስ ግዴታ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 በመሠረታዊ መርህነት ተደንግጓል፡፡የዚህ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ሲታይ የሚከፈለው የካሳ መጠን የሚወሰነው ተከሳሹ ያገኘው ጥቅምና ከሳሹ የደረሰበት ኪሳራ ተመዛዝነው በመታየት ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም ለከሳሹ የሚወሰንለት ካሳ ተከሳሹ ካገኘው ጥቅምም ሆነ ከሳሹ ከደረሰበት ኪሳራ ሊበልጥ እንደማይገባ ሕጉ ያሳያል፡፡ሕጉ ተከሳሹ የሚያገኘው ጥቅም በንብረት ላይ የተቋቋመ ግዙፍ መብት ወይም ከአንድ ሰው ላይ የሚጠየቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብት ሊሆን እንደሚችል፣እንዲሁም ተከሳሹ የነበረበት እዳ ተሰርዞለት ወይም ግዴታው ቀርቶለት ወይም ኪሳራ ሳይደርስበት ቀርቶ ሊሆን እንደሚችል ያስረዳል፡፡ስለሆነም በተከሳሹ በኩል የተገኘው ጥቅም መኖር ብቻ ሳይሆን የተገኘው ጥቅም የሕሊና እርካታን የሚያስገኝና በገንዘብ ሊተመን የሚችል መሆን አለበት፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት በነበራቸው ኃላፊነት አበልና የአውሮፕላን ትራንስፖርት የስልጠና ወጪ ተከፍሎላቸው ወደ ውጪ አገር መሄዳቸውና በስራ ምክንያት ሂደው ሳይመለሱ መቅረታቸው ግራ ቀኙን ያላከራከሩ ፍሬ ነገሮች ሲሆኑ ተጠሪ የአመልካችን ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የሚከራከሩትና የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው ተጠሪ ጥቅም ማግኘታቸው አልተረጋገጠም በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ወደ ውጪ አገር ለመሄድ ለትራንስፖትም ሆነ ለተለየዩ ጉዳዮች የገንዘብ ወጪ የሚያስፈልግ መሆኑ ግልጽ ሲሆን ተጠሪ ወደ ውጪ አገር ሲሄዱ አመልካች ገንዘብ ማውጣቱ ተረጋግጧል፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ሰራተኛ ባይሆኑና ለስራ ምክንያት ወደ ውጪ አገር የማይሄዱ ቢሆኑ ኑሮ ለአውሮፕላን ትራንስፖርትና ተያያዥ ወጪዎችን መሸፈን የሚገባቸው ተጠሪ ራሳቸው መሆኑን ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ተጠሪ ጥቅም አላገኙም ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ምክንያቱም በአመልካች መስሪያ ቤት በነበራቸው የስራ ግንኙነት ወደ ውጪ የተላኩት አስፈላጊውን ልምድ ቀስመው አመልካችን ያገለግላሉ በሚል ሀሳብ ሲሆን ይኼው የአመልካች ሃሳብ ተጠሪ ከሄዱበት ባለመመለሳቸው ውጤት ሳይገኝ መቅረቱን የክርክሩ ሂደትና ይዘት ያሳያልና፡፡አመልካች ኪሳራ የደረሰበት፣ተጠሪ ደግሞ በአመልካች መስሪያ ቤት የተመቻቸላቸውን አጋጣሚ በመጠቀም በአመልካች ወጪ ወደ ውጪ አገር ሄደው የቀሩ በመሆኑ ለአውሮፕላን ትራንስፖርትና ለስልጠና በተከፈለው ገንዘብ መጠን ጥቅም አላገኙም ሊባል የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸውን የስራ ግንኙነት፣ወደ ውጪ ሊሄዱ የቻሉበትን ምክንያትና አንድ ሰው ወደ ውጪ ሲሄድ ደግም የግድ ወጪ የሚያስፈልገው መሆኑንና ተጠሪ በራሳቸው ወደ ውጪ ቢሄዱ ኑሮ የራሳቸውን ገንዘብ ሊከፍሉ ይችሉ የነበረ መሆኑን፣አመልካች ተጠሪ ከተላኩበት ተመልሰው ሊያገለግሉ ይችላሉ በሚል ሙሉ እምነት ወጪውን አውጥቶ ልኳቸው ተጠሪ ያለመመለሳቸው ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ገንዘብ በመገልገል ጥቅም ማግኘታቸውን የሚያረጋግጥ እና ይህም ጥቅም በገንዘብ ሊተመን የሚችል ሁኖ እያለ አመልካች ተጠሪ ጥቅም ማግኘቱን አላስረዳም በማለት የሰጡት ውሳኔ የክርክሩን ይዘትና ባህርይ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ጋር ያላገናዘበ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሣኔ የክርክሩን ይዘት፣ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2162 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2164 /1/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መሠረት ያላደረገ ስለሆነ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የአውሮፕላንና የስልጠና ወጪን አስመልክቶ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80127 ሚያዚያ 08 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 137281 ሐምሌ 23 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች ብር 179,742.94 (አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ አርባ ሁለት ብር ከዘጠና አራት ሳንቲም) ከዛሬ ሚያዚያ 20 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ 9%(ዘጠኝ ከመቶ) ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. ለአበል ወሰዱ በተባለው ብር 832.00 የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.94181

ግንቦት 18/2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አደነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ሸኩር ጀማል - ጠበቃ አቶ ሳሙኤል ደመቀ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ኤደን ነጋሽ ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ወረደ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በስርቆት ወንጀል ለተወሰደ ንብረት ግምት የቀረበን የአንድነት ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረባቸው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችና ቢኒያም ታደስ ግምቱ ብር 65,000 (ስልሳ አምስት ሺ ብር) የሚሆን ንብረት ሰርቀው የወሰዱ መሆኑ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06338 ነሐሴ 7 ቀን 2005 ዓ/ም በወንጀል ጥፋተኛ መሆናቸውን አርጋግጦ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለሱቅ የምከፍለው ኪራይና ዕቃዎች በመስረቃቸው የደረሰብኝ ኪሳራ ብር 20,000 (ሃያ ሺ በር) ጨምርው እንዲከፍሉ ይወስንልኝ በማለት ክስ ያቀረበች ሲሆን በቢኒያም ታደስ ላይ ያቀረበችው ክስ እንዲቋረጥ አመልክታ ክሱ ተቋርጧል፡፡ አመልካች ንብረቶች ባለሀብት ከሳሽ መሆኗና የንብረቶቹ ግምት በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ተከርክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በስርቆት ወንጀል ለተወሰዱት የተጠሪ ንብረቶችና በዚህ ምክንያት ለደረሰው ኪሳራ አመልካች የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት በማለት ብር 85,000 (ሰማኒያ አምስት ሺ ብር) እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች መሰከረም 30 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተሰረቁ የተባሉት ንብረቶች የተገዙበት ደረሰኝ አልቀረበም፡፡ በክርክሩ የግዴታ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወገን ተጠሪ ክሱ እንዲቋረጥ ጠይቃ እንዲቋረጥ አድርጋለች፡፡ ስለዚህ ተጠሪ የዕቃውን ዋጋና የደረሰባትን ኪሳራ ሳታስረዳና በክስ የጠየቀችውን ገንዘብ በሙሉ አመልካች የመክፍል ኃላፊነት አለበት መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የወንጀል ተካፋይ የነበረው ሰው አድራሻ አፈላልጌ ላገኘው አልቻልኩም፡፡ ዕቃው ተጭኖ የተወሰደው ከአመልካች ቤት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በስርቆት ለተወሰደው ንብረት ግምት የአንድነትና በነጣላ ኃላፊነት ያለበት ስለሆነ ውሳኔው ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

3. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በስበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ተጠሪ ክስ ያቀርበችበትን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

4. ጉዳዩን እንደመርመርነው አመልካችና የፍትብሔር ክስ በከሳሽ ጠያቂነት የተቋረጠበት ቢኒያም ታደሰ በወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1)ሀ እና አንቀጽ 665 የተመለከተውን በመተላለፍ፣ ግምታቸው ብር 65,000 (ስልሳ አምስት ሺ ብር) የሚሆኑ ንብረቶች ሰርቀው የወሰዱ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06338 ነሐሴ 7 ቀን 2005 ዓ/ም የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች የንብረቶቹ ዋጋ ብር 65,000 (ስልሳ አምስት ሺ ብር) መሆኑ አልተረጋገጠም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የፍትብሔር ህግ ቁጥር 2035 እና የፍትብሔር ህግ ቁጥር 2091 ድንጋጌን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

5. አመልካችና የወንጀል ስራ ተካፋይ የነበረው ቢኒያም የስርቁት ተጠሪ የንግድ ስራ የምታከናውንባቸውን ዕቃዎች እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ዕቃዎቹ በመሰረቃቸውና የንግድ ስራውን በአግባቡ ለማከናወን ባለመቻሏ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ኪሳራ የደረሰባት መሆኗን ገልጻለች፡፡ ተጠሪ ይህንን ያህል ኪሳራ የደርሰባት ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2141 የማስረዳት ግዴታ ያለባት ቢሆንም፣ ይህንን ለማስረዳት በስር ፍርድ ቤት ያቀረበችው ማስረጃ ስለመኖሩ በውሳኔው አልገለፀም፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ብር 20,000 (ሃያ ሺ በር) የጉዳት ካሳ እንዲከፍል የወሰነው አመልካች ክሱን በግልጽ ክዶ መልስ አልሰጠም በሚል ምክንያት መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም የካሳን ልክ በተመለከተ፣ ከሳሽ የጠየቀውን የካሳ ገንዘብ ተካሳሽ በግልጽ አለመካዱ የካሳውን መጠን በሙሉ ወይም በከፊል እንዳመነ እንደማያስቆጥረው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.83 ተደንግጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንጻር ስናየው ተጠሪ በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2141 መሰረት በማስረጃ ያላረጋገጠችውን የጉዳት ካሳ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) አመልካች ክዶ አልተከራከርም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.83 ድንጋጌ ይዘት ያላገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

6. አመልካች በስርቆት ወንጀሉ የተወሰዱ ንብረቶች ግምት እኔ ብቻ የመክፍል ኃላፊነት አለብህ መባሌ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የስርቆት ወንጀሉ ሙሉ ተካፋይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንድ ሰው ህግን በመጣስ በሌላ ሰው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2035 ተደንግጓል፡፡ ሆነ ብሎ ሰዎች አንድ ሆነው በአንድ ጉዳይ ካሳ እንዲከፍሉ የተገደዱ እንደሆነ በአንድነት እያንዳንዳቸው ኃላፊ እንደሆኑና ለበደሉ ተግባር አነሳሽ በሆነውና በዋና አድራጊው እና በተባባሪዎች መካከል ልዩነት እንደማይደረግበት በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2155 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ አመልካች በስርቆት ወንጀሉ ተካፋይ የሆነው ሁለት ሰዎች ሆነን እያለን እኔ የንብረቱ ሙሉ ዋጋ እንድከፍል መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር ከላይ የገለጽናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የጠየቀችውን ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) አመልካች እንዲከፍል የሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የተሰረቁትን የተጠሪ ንብረቶች ዋጋ ብር 65,000 (ስልሳ አምስት ሺ ብር) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪ የጠየቀችውን ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ካሳ ይክፈል በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል የፍትብሔር ህግ ቁጥር 2141 እና የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.83 ድንጋጌዎች የሚጥስ በመሆኑ ተሽሯል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለያራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98552

ሐምሌ 4 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማዉ ወሌ

አሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ሚ/ር አደም ሐሚድ - ጠበቃ አቶ ኪዳነማርያም ሃጐስ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ሐናእ አብዱልቃድር - ጠበቃ ደበበ መንግስቱ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137912 ታህሳስ 4 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ከህፃን ልጅ ማሣደጊያ የሚቆረጥ ገንዘብ መጠን የሚመለከት ክርክር ነው ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ /ከሳሽ/ ከተከሳሽ /አመልካች/ጋር የነበራት ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን ገልፃ ከሳሽና ተከሳሽ በጋብቻ ስንኖር ህፃን ሁዳ አደም የተባለች ልጅ ወልደናል፡፡ ህፃኗ አንድ ዓመት ከአስር ወሯ ነው፡፡ ስለዚህ ለህፃኗ ማሳደጊያ የሚሆን በወር ብር 94,927 /ዘጠና አራት ሺ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሰባት ብር /ተከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው ከሳሽ የጠየቀችውን ገንዘብ ተከሳሽ በየወሩ ለህፃኗ ማሳደጊያ ለመክፈል አልችልም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ስለተከራከሩ የሥር ፍርድ ቤት የተከሳሹን ገቢ ለማረጋገጥ የተለያዩ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው የመንግሰት አካላት ጠይቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሳሽ /ተጠሪ ህፃኗን ለማሳደግ የሚያስፈልጋት የትምህርትና ሌሎች ወጪዎች በሰንጠረዥ መልክ አዘጋጅታ ያቀረበችውን የወጭ ዝርዝር ተመልክቶ ተከሳሽ ለሕፃኗ ማሳደጊያ በወር ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር / እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
2. በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይግባኝ ባይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/አመልካች / ለህፃኗ ማሳደጊያ በወር 12,000 /አስራ ሁለት ሺ ብር / እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት መጋቢት 3 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች በኢትዮጵያ የኑሮ ደረጃ አንድ ህፃን ለማሳደግ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰነውን ከሚፈለገው መጠን በላይ ነው፡፡ የአመልካች ትክክለኛ ገቢ አልተረጋገጠም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ብር 12,000/ አስራ ሁለት ሺህ ብር/ እንዲከፍል የወሰነው ውሳኔውን ከሰጠበት ታህሳስ 4 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ይህም ማለት ከሐምሌ 19 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ለህፃን ማሳደግያ ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ ብር / እንዲከፍል የሰጠውን ውሳኔ ሳያሻሽለው አልፎታል፡፡ ስለዚህ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል በማለት አመልክቷል፡፡

3. ተጠሪ በሰበር አቤቱታው ሚያዚያ 20 ቀን 2006 ዓ.ም ፅፎ ያቀረባቸው መልስ የህፃን ማሳደጊያ ገንዘብ የጠየቅሁት ለህፃኗ የትምህርት ቤት የትራንስፓርት የአልባሣት የቀለብና ሌሎች ወጪዎችን በመዘርዘር ነው፡፡ አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገቢ በዓመት ያገኘ መሆኑ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በላከው መረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከኢትዮጵያ ውጭ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኙ የተለያዩ የንግድ ድርጅቶች እና የአክሲዮን ድርሻ ያለው ነው፡፡ አመልካች ከሌላ የወለዳቸውን ልጆቹን ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እየከፈለ እያሳደገ ነው፡፡ ስለዚህ የአመልካች ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለህፃን ማሳደጊያ አመልካች እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠው በሕግ የተመለከቱትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ነው ወይስ አይደለም ? የሚውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሣስሮ በነበረበት ወቅት ለወለዳት ህፃን ሁዳ አደም ለማሣደግ የሚያስፈልገውን ወጪ የመጋራትና የመሸፈን ግዴታ ያለበት መሆኑ አላከራከረም አመልካችንና ተጠሪ የሚያከራክረው አመልካች ለህፃኗ አስተዳደግ ሊከፍለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ ለህፃን ልጅ ማሳደጊያ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ወላጅ፣ የሚከፍለው የገንዘብ መጠን የሚወስነው እንደባለ ጉዳዩ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልምድ የሚስማማውን በመከተል በቀለብ ተቀባዩ ምግብ፣ መኖሪያ፣ ልብስ፣ ጤናውን የሚጠብቅበትና እንደ ሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑትን ወጭዎች የሚሸፍን መሆን እንደሚገባው በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመውና የአክሲዮን ባለድርሻ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሆኑበት የንግድ ድርጅት በሚሊዮን የሚቆጠር ገቢ በዓመት የሚያገኙ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል።

6. ይህም በመሆኑ ህፃኗን ለማሳደግ የሚያስፈልግ፣ የምግብ፣ የመኖሪያ፣ የጤና አጠባበቅና የትምህርት ወጭ ሲታሰብ፣ አንድ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ቤተሰብ፣ ህፃን ልጁን በጥሩ ሁኔታ ለመመገብ፤ በጥሩ መኖሪያ አካባቢ ለማኖርና ጤናው ለመጠበቅ እንዲሁም ጥሩ ትምህርት እንዲያገኝ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ወጭ መሠረት በማድረግ ሊወሰን ይገባዋል። ይህም ማለት አመልካች ለህፃኗ ማሳደጊያ የሚከፍለው ገንዘብ ገቢያቸው ስለማይፈቅድላቸው በህፃን አስተዳዳር አስፈላጊ የሆኑ የምግብ አይነቶች ንጥረ ነገሮች በተሟላ ሁኔታ ሣያቀርቡ፣ ህፃን ልጆቻቸው በየወቅቱ የጤና ክትትልና ምርመራ ሣያደርጉ ምቹና ፅዳት በጐደለው የመኖሪያ ቤት ውስጥ ህፃን ልጃቸው ለማኖርና ለማሣደግ ሁኔታው ያስገደዳቸዉን ወላጆች ለህፃን ልጆቻቸው የሚያወጡትን ዝቅተኛ ገንዘብ መሠረት በማድረግ ሊወሰን አይገባውም ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ህፃኗን ለማሣደግ ከብር 2000 በላይ አስፈላጊ አይደለም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም።

7. የአመልካች ከፍተኛ ገቢ ያለው መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። አመልካች ገቢውን በተመለከተ በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው ክርክር በሕገ መንግስቱን አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 20 ለዚህ ችሎት የተሰጠውን ሥልጣን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም። በሌላ በኩል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰነውን የቀለብ ገንዘብ ህፃኗን መዋለ ህፃናት ለማስገባትና ለማማላለስ ህፃኗን ለጤና ምቹ የሆነ መኖሪያ ቤት ውሰጥ ለማኖር ሕፃኗ የተሟላ ምግብ ፣ አልባሳትና መጫወቻ እንዲኖራት ለማድረግ ከሚያስፈልገው መጠን በላይ ስለመሆኑ አመልካች የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም። አመልካች በኢትዮጵያ ሁኔታ አንድ ህፃን ለማሳደግ ከብር 2000 በላይ አስፈላጊ እንደልሆነ በጥቅል አገላለፅ ተከራክሯል። ይህም አመልካቹ የህፃኗ አስተዳደግ ስስታዊ ሣይሆን ዝቅተኛ ገቢ ስላላቸው የልጆቻቸውን መሠረታዊ ፍላጉት የማያሟሉና የልጆችቻውን ፍላጐት ገድበው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በሚያሳድጉበት መንገድ እንዲሆንለት የሚያከራክር መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህ የአመልካች መከራከሪያ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 197 እና አንቀጽ 202 ድንጋጌዎችን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ አልተበቀልውም። በዚህ ምክንያት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለአመልካች ለህፃኗ አስተዳደግ እንዲከፍል የወሰነው የቀለብ ገንዘብ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 85815

ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ኢብራሂም መሐመድ ኑር - ጠበቃ አሸናፊ ወጂ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ ጀሚላ መሐመድ ኑር
2. አቶ ሰይድ መሐመድ ኑር
3. ወ/ሮ ነጃት መሐመድ ኑር
4. ወ/ሮ ሐያት መሐመድ ኑር

} የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የአሁኖቹ ተጠሪዎች የሚች አባታችን የአቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ይጣራልን ሲሉ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ውርሱ ተጣርቶ ውጤቱ እንዲቀርብ ከተደረገ በኃላ በውርስ አጣሪው የቀረበውን ሪፖርት አሻሽሎ በማጽናት የፊዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው እና በፊዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ተጠሪዎቹ የሚች አባታችን የአቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ይጣራልን ሲሉ በወ/ሮ ባህሯ አብዱ፣በአሁኑ አመልካች እና በአቶ ጀማል መሐመድ ኑር ላይ በ18/08/2002 ዓ.ም. የተጻፈ አቤቱታ ማቅረባቸውን፣1ኛ እና 3ኛተጠሪ የነበሩት ወገኖች ውርሱ ቢጣራ ተቃውሞ እንደሌላቸው የገለጹ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በበኩላቸው የሚች አቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ጉዳይ አስቀድሞ በሸሪዓ ፍ/ቤት በውሳኔ ያለቀ በመሆኑ በድጋሚ የውርስ ይጣራልን አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በፍሬ ጉዳዩ ረገድም መልስ ሰጥተው መከራከራቸውን፣ፍ/ቤቱም በ12/02/2003 ዓ.ም. በሰጠው ውሳኔ አመልካች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥብ ውድቅ አድርጎ በማለፍ ውርሱ ተጣርቶ ውጤቱ ይቀርብ ዘንድ አጣሪ እንዲመደብ ማድረጉን፣የማጣራቱ ሂደት መጀመሩን ተከትሎ አመልካች የውርስ ይጣራልን አቤቱታው በይርጋ የሚታገድ ነው የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ለአጣሪው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማቅረባቸውን፣አጣሪውም የዚህ ዓይነቱ መቃወሚያ መቅረብ የሚገባው ለፍርድ ቤቱ እንጂ ለአጣሪው አለመሆኑን በመግለጽ የማጣራቱን ሂደት አጠናቆ የወራሾችን ማንነት እና የውርሱን ሀብት በመለየት በ10/06/2003 ዓ.ም. የተጻፈ ሪፖርት ማቅረቡን፣ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን አስተያየት ከተቀበለ በኃላ ሪፖርቱን አሻሽሎ ማጽደቁን፣አመልካች በአጣሪው ሪፖርት ላይ ካቀረቡት አስተያየት መካከል የውርስ ይጣራልን አቤቱታው በይርጋ የሚታገድ ነው የሚል ነጥብ የሚገኝበት መሆኑን፣ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ አመልካች ይህንን የመቃወሚያ ነጥብ ማቅረብ ይገባቸው የነበረው ለውርስ ይጣራልን አቤቱታው የመከላከያ መልስ በሰጡበት ጊዜ እንጂ ውርሱ ተጣርቶ ውጤቱ ከቀረበ በኋላ አይደለም በማለት የይርጋ መቃወሚያውን ሳይቀበለው መቅረቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪው ሪፖርት ተሻሽሎ የጸደቀበትን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የታየው ክርክር በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሊታይ አይገባውም በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ እና የይርጋ መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ለክርክሩ በተያዘው ጭብጥ መሰረት በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች፡-

1. የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰጡት አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰጡት በይርጋ በታገደ ጉዳይ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በሕግ ስልጣን የተሰጠው ማንኛውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከሰጠ በኃላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ስረ ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸውንም ዓይነት ሌላ ክርክር ለማቅረብ እንደማይችሉ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 5(1) ስር የተደነገገ ሲሆን የዚህ ዓይነቱ መቃወሚያ በተከሳሽ ወገን ሊቀርቡ ከሚችሉ የመቃወሚያ ነጥቦች ውስጥ የሚካተት ስለመሆኑ፣ፍርድ ቤቱ ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ አስቀድሞ በመጀመሪያ ደረጃ ለቀረበለት መቃወሚያ ውሳኔ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፣እንዲሁም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቶ ባለጉዳዮችን ማሰናበት የሚገባው ስለመሆኑ እንደቅደም ተከተሉ በዚሁ ሕግ በቁጥር 244(2)(ለ)፣244(1) እና 245(2) ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎቹ የሚች አባታችን የአቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ይጣራልን በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ላቀረቡት አቤቱታ አመልካች በሰጡት የመከላከያ መልስ የሚች አቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ጉዳይ አስቀድሞ በክልል 14 መስተዳድር በ2ኛ ናዒባ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 1952/88 ታይቶ በ25/11/1988 ዓ.ም. እልባት ያገኘ በመሆኑ በድጋሚ የክርክር ምክንያት ሊሆን የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም ሲሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው የነበረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በዚህ የመቃወሚያ ነጥብ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ እንደተባለው የሸሪዓ ፍርድ ቤት በሚች አቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ጉዳይ ውሳኔ መስጠቱን ተቀብሎ ነገር ግን የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን የሰጠው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 34(5) እና የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 4(2) እና 5(1) መሰረት የአሁኖቹ ተጠሪዎች በሸሪዓ ፍርድ ቤት ቀርበው ለመዳኘት ፈቃደኞች መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ስለመሆኑ የውሳኔው ይዘት እንደማያረጋግጥ ገልጾ የአሁኑ አመልካች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በ12/02/2003 ዓ.ም. በነበረው ችሎት ውድቅ በማድረግ ውርሱ እንዲጣራ መወሰኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ ቅር በመሰኘት አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በመዝገብ ቁጥር 102345 በ27/03/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ማጽናቱን እና ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡት አቤቱታም በመዝገብ ቁጥር 77308 በ24/08/2004 ዓ.ም. በአጣሪ ችሎት ተቀባይነት ማጣቱን ከመዝገቡ ተገንዝበናል፡፡አመልካች ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ የሰበር አጣሪ ችሎትን ጨምሮ በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች አስቀድሞ ተቀባይነት ያጣ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ የመቃወሚያ ነጥቡ ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ ሊታይ የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል በማለት አመልካች በዚህ ችሎት ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የይርጋ መቃወሚያ በመከራከሪያነት ለማቅረብ ለተከሳሽ ወገን ከተሰጡት መብቶች ውስጥ የሚካተት ሲሆን የዚህ ዓይነቱ መቃወሚያ መቅረብ የሚገባውም ተከሳሽ ወገን ለቀረበበት ክስ የመከላከያ መልሱን በሚያቀርብበት ጊዜ በመከላከያ መልሱ ውስጥ በማካተት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 234(1)(ሐ) እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

244(2)(ሠ) ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡በዚህ ሁኔታ መቅረብ ከሚገባቸው መቃወሚያዎች ውስጥ ሳይቀርቡ የቀሩት ትክክለኛውን ፍርድ ለመስጠት የሚያስናክሉ እስካልሆነ ድረስ ባለጉዳዩ ራሱ ሆነ ብሎ ለማቅረብ ባለመፈለግ እንደተዋቸው የሚቆጠሩ ስለመሆኑም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 244(3) ድንጋጌ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ሳይቀበል የቀረው እና ይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን ቅሬታ ውድቅ ያደረገው ውርሱ እንዲጣራ ለቀረበባቸው ክስ መልስ በሰጡበት ጊዜ የይርጋ መቃወሚያ ሳያቀርቡ ቀርተው መቃወሚያውን በውርስ አጣሪው ዘንድ እና ቀጥሎም ውርሱ ተጣርቶ ውጤቱ ከቀረበ በኋላ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ አስተያየት እንዲያቀርቡ በተጠየቁበት ጊዜ ቀደም ሲል ያላነሱትን የይርጋ መቃወሚያ ማንሳታቸው ስነ ስርዓታዊ አለመሆኑን በመግለጽ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡የይርጋ መቃወሚያውን ለክሱ በሰጡት የመከላከያ መልስ አካተው ያላቀረቡ ስለመሆኑ ደግሞ አመልካች በሰበር አቤቱታቸውም ላይ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለክሱ በሰጡት የመከላከያ መልስ የይርጋ መቃወሚያ እንዳላቀረቡ የተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ከጊዜ በኋላ ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ አለመቀበላቸው ሊነቀፍ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 169123 በ06/09/2004 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 126004 በ26/03/2005 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ቁጥሩ 1952/88 የሆነው የሸሪዓ ፍርድ ቤት መዝገብ ተመላሽ ይደረግ፡፡
3. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93987

ሐምሌ 18 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- 1. አቶ ዳንኤል ወንዳፈራ

2. አቶ ቴዎድሮስ ወንዳፈራ } ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1.ወ/ሮ አስናቀች ቦጋለ

2.ማቆያ ቦጋለ

3.ስንቅነሽ ቦጋለ } የቀረበ የለም፡፡

4.ፋኖሴ ቦጋለ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ስለውርስ ንብረት ክፍፍል የተደነገጉትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን መሰረት አድርጎ የቀረበ የፍርድ መቃወሚያን የሚመለከት ነው፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ነገር ሟች አቶ ቦጋለ ታደሰ ጥቅምት 09 ቀን 1990 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በኋላ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ያፈሩት በበቆጂ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ በ147.4 ካ.ሜትር ቦታ የሰፈረውን አራት ክፍል ቤት የውርስ ድርሻ ይገባናል የሚለው የአመልካቾችና የአሁኑ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ጥያቄ ነው፡፡ ሁሉም ተጠሪዎች የሟች አቶ ቦጋለ ታደሰ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ደግሞ የተጠሪዎች እህት የሆኑትና የሟቹ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የነበሩት የወ/ሮ ደመቀች ቦጋለ ልጆች ሁነው እናታቸውን ተክተው አያታቸውን አቶ ቦጋለ ታደሰን ለመውረስ ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አሁን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የሌሙና ቢሊቢሎ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የሟቹን ውርስ ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የአሁኑ አመልካቾች በተተኪ ወራሽነት የሚያገኙትን መብት የሚነካ ነው በማለት የአሁኑ አመልካቾች ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ በወረዳው ፍርድ ቤት ውድቅ ተደርጎ በበላይ ፍርድ ቤቶችም ተቀባይነት ማጣቱ ያላግባብ ነው የሚለው አቤቱታ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ሶስት የተጠቁሰት ተጠሪዎች 4ኛ ተጠሪን በመክሰስ የሟች አቶ ቦጋለ ታደሰን የውርስ ንብረት እንዲካፈሉ በሌሙና ቢሊቢሉ ወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ እናታችን ወ/ሮ ደመቀች ቦጋለን በመተካት ልናገኝ የሚገባንን ድርሻ ያስቀረ ነው በማለት ፍርድ ለመቃወም አቤቱታቸውን ነሐሴ 17 ቀን 2004 ዓ/ም ፅፈው ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤትም የአሁኑ ተጠሪዎች በአመልካቾች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጡበት አድርጎ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የአመልካቾችን የፍርድ መቃወሚያ ደግፈው አመልካቾች የእናታቸውን ድርሻ ቢያገኙ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ሲሆን የአሁኗ 4ኛ ተጠሪ ግን በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠውና ለፍርድ መቃወሚያ መሰረት የሆነው ፍርድ በተጠሪዋ ይግባኝ ባይነት ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ በመ/ቁጥር 38439 ነሀሴ 18 ቀን 2004 ዓ/ም በተሰጠው ፍርድ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ የመጨረሻ ፍርድ ማግኘቱን ገልጻው መቃወሚያው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው ተከራክረዋል፡፡

የፍርድ መቃወሚያውን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው የሌሙና ቢሊቢሉ ወረዳ ፍርድ ቤትም 4ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን መቃወሚያ በመቀበል በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በተሻረ ውሳኔ የፍርድ መቃወሚያውን ለማስተናገድ ስልጣን የሌለው መሆኑን ጠቅሶ የአመልካቾችን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 245(2) ድንጋጌን ጠቅሶ ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በመ/ቁጥር 39725 ታህሳስ 05 ቀን 2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተዘግቶባቸዋል፡፡እንዲሁም አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በመ/ቁጥር 158733 በሆነው ሐምሌ 23 ቀን 2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች በሰጡት ብይን ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ አቤቱታቸው ውድቅ ሁኖባቸዋል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 38439 ነሀሴ 18 ቀን 2004 ዓ/ም ለፍርድ መቃወሚያ የሆነውን ፍርድ የሻረበት ፍርድ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 151765 በሆነው ህዳር 29 ቀን 2005 ዓ/ም ተሽሮ በጉዳዩ ላይ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ጸንቶ እያለ የፍርድ መቃወሚያ የሚቀርብበት ፍርድ የለም ተብሎ አቤቱታቸው ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውርስ ንብረት ድርሻ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ያጣውም አከራካሪውን ንብረት በእጃቸው አስገብተው ለብዙ አመታት ከተጠሪዎች ጋር እኩል ሲጠቀሙበት የነበረ ሁኖ እያለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ብይን ሕጉን መሰረት ያላደረገ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በዕሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡በዚህም መሰረት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ ያሉት ተጠሪዎች አመልካቾችን ደግፈው የሚከራከሩ ሲሆን 4ኛ ተጠሪ ግን አመልካቾች አለን የሚሉት ውሳኔ በተጠሪዋ አቤት ባይነት፣ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ በተጠቀሱት ተጠሪዎች ደግሞ ተጠሪነት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲታይ ቆይቶ በዚህ ችሎት ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ሶስት የተጠቀሱት ተጠሪዎች የውርስ ንብረት ይገባናል ጥያቄ በሕጉ አግባብ በተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ያልቀረበ ሁኖ ተገኝቷል በሚል ምክንያት ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነው ተብሎ በመ/ቁጥር 158019 መስከረም 13 ቀን 2006 ዓ/ም የተወሰነ ሲሆን በውጤቱም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 151765 ጥቅምት 29 ቀን 2002 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ የሻረ መሆኑን ገልፀው አመልካቾች የፍርድ መቃወሚያ የሚያቀርቡት ፍርድ የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከውርስ ሕጉ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር ሲባል የተያዘው ጭብጥ የአመልካቾች መቃወሚያ ጉዳዩ ተፈፅሟል ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ሲሆን እኛም ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር በማየት ጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚቻል መሆኑን ያለመሆኑን መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች በአሁኗ 4ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡት የውርስ ንብረት ይገባናል ክርክር በመጨረሻ ላይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ የከሳሾች ክስ በሶስት አመት የይርጋ ጊዜ የታገደ ነው ተብሎ በመ/ቁጥር 158019 በሆነው መስከረም 13 ቀን 2006 ዓ/ም ውሳኔ ያገኘ ሲሆን በዚህም ውሳኔ መሰረት በወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠና የአመልካቾችን መብት ይነካል የተባለ ውሳኔ ጭምር የተሻረ መሆኑን ውሳኔው የሚያሳይ መሆኑን፣ከዚህም በኋላ በዚህ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የአሁኑ 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አመልካች፣4ኛ ተጠሪ ደግሞ ተጠሪ ሁነው ተሰይመው ጉዳዩን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ የሥር ከሳሾች አቅርበውበት አጣሪ ችሎት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 158019 የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት በመ/ቁጥር 94954 በሆነው ህዳር 23 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የመጨረሻ ትዕዛዝ የሠጠበት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደ ሕጉ ስንመጣም በመሰረቱ አንድ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራበት ሥርዓት የሚገዛው በ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርኣት ሕጋችንና በክልሎች ስራ ላይ ባሉት አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሆኑ እሙን ነው፡፡ የ1958ቱ የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕጋችን ከያዛቸው ስርዓቶች መካከል በፍርድ ላይ የሚቀርበው ተቃውሞ እና በፍርድ አፈጻጸም ጊዜ በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ የሚቀርበው ጣልቃ ገብነትን የሚገዙት ድንጋጌዎች ይገኙበታል፡፡እነዚህ አቤቱታዎችን የሚገዙት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 እና 418 ስር የተመለከቱት ናቸው፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አንድ የክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚገባው ሰው የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ውሳኔ ተሰጥቶ ከሆነ እና ውሳኔውም ያረፈው በአንድ የክርክሩ ምክንያት በሆነ ንብረት ላይ ሁኖ ይህንኑ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገንን መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑ ከተረጋገጠ ፍርዱ ይሽው ወገን ባለበት እንዲታይና በሕግና በማስረጃ የተደገፈ ሁኖ ሲገኝ እንዲነሳለት የሚደነግግ ነው፡፡አቤቱታው የሚቀርብበት ሥርዓትም በቁጥር 359 ስር በተመለከተው መንገድ መሆን እንደአለበት የተቀመጠ ሲሆን ይህ ድንጋጌ የመቃወሚያ አቤቱታ አቀራረብ በክስ አመሰራረት አይነት ሁኖ ማስረጃ ዝርዝር ሁሉ ይህንኑ ስርዓት ማሟላት እንደአለበት ያስገነዝባል፡፡የዚህ ድንጋጌ ይዘቱና መንፈሱ ሲታይ ክርክሩ መኖሩን ከጅምሩ እያወቀ ውጤቱን በመጠበቅ ከፍርዱ በኋላ የፍርድ መቃወሚያ የሚያቀርበውን ወገን አቤቱታውን በመቀበል ለማስተናገድ አስፈላጊ ያለመሆኑን ሁሉ ያስገነዝባል፡፡ይህም የክርክር አቀራረብ በቅን ልቦና የተመሰረተ ሁኖ በአነስተኛ ወጪ፣ጉልበትና ጭር ጊዜ ፍትሐዊነት ያለውን ውሳኔ ለመስጠት የሚቻልበት አግባብ እንዲኖር እና ሕግ አውጪ ከፈለገበት አላማ ጋር መጣጣም ያለበት መሆኑም የሚታመን ነው፡፡ እንግዲህ አቤቱታውን የሚያቀርበው ወገን የቅን ልቦና ተከራካሪ ሁኖ መሰረታዊ መብቱን ማስከበር የሚችልበት የስነ ስርዓት ሕግ አግባብ እንዲኖር ሕግ አውጪ የፈለገ ሲሆን ይህንኑ መመዘኛ የሚያሟላ አቤቱታ አቅራቢ የሚቃወመው ፍርድ ዋጋ ያለው፣ያልተፈፀመ መሆን እንደአለበትም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ ይዘት ያስረዳል፡፡በሌላ አገላለፅ የፍርድ መቃወሚያ የሚቀርብበት ፍርድ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ያልተሻረና አፈጻጸሙም ያልተጠናቀቀ ሊሆን እንደሚገባ ሕጉ ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ደግሞ አመልካቾች በተተኪ ወራሽነት የምናገኘውን መብት የነካ ነው የሚሉት ፍርድ በመጨረሻ ላይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሻረ ከመሆኑም በላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ የመጨረሻ እልባት የተሰጠበት በመሆኑ የፍርድ መቃወሚያ የሚቀርብበት ፍርድ በወረዳው ፍርድ ቤት መዝገብ ላይ አለ ለማለት የሚቻልበት ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም ዋጋ ያለው ፍርድ በወረዳው ፍርድ ቤት የሌለ መሆኑ ከተረጋገጠ የአመልካቾች የፍርድ መቃወሚያ በወረዳው ፍርድ ቤት የሚስተናገድበት አግባብ የለም፡፡ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የበታች ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች ውሳኔ ውጤቱ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሌሙና ቢሊቢሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17198 ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39725 ታህሳስ 05 ቀን 2005 ዓ/ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 158733 ሀምሌ 23 ቀን 2005 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ብይን ውጤቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡበት ፍርድ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተሸሮ የመጨረሻ እልባት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎትም ያገኘ በመሆኑ አቤቱታቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የሚስተናገድ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94322

ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም
መስጠፉ አህመድ
ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ በቀለ - ወኪል ቅጅነህ ለማ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ገዛኽኝ በቀለ - ከጠበቃ በጅጋ ሶሬቻ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ስለውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዳአ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ፣ተከሳሽ ደግሞ የአሁኗ አመልካች ነበሩ፡፡ ተጠሪ ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም አሻሽለው ባቀረቡት ክስ ሲሆን ወላጅ አባታቸው አቶ በቀለ ባልቻ ከዚህ አለም በሞት ህዳር 20 ቀን 2003 ዓ/ም መለያታቸውንና በህይወት በነበሩት ጊዜ በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 07 ውስጥ በካርታ ቁጥር 7/17/1 የሚታወቀውንና ቁጥሩ 290 የሆነው መኖሪያ ቤት ያፈሩ ቢሆንም ተጠሪንና አመልካችን ጨምሮ ስድስት ሕጋዊ ወራሾች እያሉ የአሁኗ አመልካች ብቸኛ ወራሽ በመምሰል ቤቱን ይዘው እንደሚገኙና የቤቱ ግምት 80,000.00 (ሰማንያ ሺህ) መሆኑን ጠቅሰው ከቤቱ ግምት የተጠሪ ድርሻ የሆነውን ብር 13,000.00 (አስራ ሶስት ሺህ) ድርሻቸውን እንዲያገኙ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም፡- ክሱ በአስር አመት ይርጋ እንደሚታገድ፣ተጠሪ ድርሻዬ ይገባኛል ከማለት ውጪ ማስረጃ ያለማቅረባቸውን፣ወ/ሮ ጽጌ የሚች ልጅ ያለመሆናቸውንና እልፍነሽ፣ዝናሽ፣እና ፀሐይ ከተባሉት የሚች ወራሾች ጋር ፍርድ ቤት ቀርበው ስምምነት ማድረጋቸውን፣ በአከራካሪው ቤት ላይ በሚች ስም የባለቤትነት ደብተር የወጣው ተጠሪ ማዘጋጃ ቤቱን በማሳሳት መሆኑን፣ቤቱ ያለበት የቦታ ስፋትም 200 ካ/ሜትር ሳይሆን 400 ካ.ሜትር ሁኖ አከራካሪውን ቤት አባታቸው በሕይወት በነበሩበት ወቅት ሕዳር 27 ቀን 1985 ዓ/ም ከሃያ አመት በፊት ሰጥተዋቸው የሚቹ ወራሾችም ይኼው ተነግሯቸው ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን፣በቤቱ ላይ መብራት፣ስልክና ውሃ በስማቸው ማስገባታቸውንና ከሃያ አመት በላይ ሲጠቀሙበት ለነበሩት ንብረት ተጠሪ ወራሽ ነኝ በማለት ክስ ማቅረባቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችንም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክሮችን ውድቅ አድርጎ አመልካች ለተጠሪ ድርሻቸውን ብር 13,000.00(አስራ ሶስት ሺህ) እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡አመልካች ለተጠሪ ብር 13,000.00(አስራ ሶስት ሺህ) እንዲከፍሉ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው የውርስ ቤቱን የገበያ ዋጋን መሰረት ያደረገውን ድርሻ እንጂ በክሱ ጊዜ የተጠቀሰውን ግምት አይደለም በማለት ወስኗል፡፡የአሁኗ በዚሁ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤቱ የግሌ ነው የሚል ክርክር አቅርበው የነበሩ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር መስቀልኛ ይግባኝ የቀረበበት ባለመሆኑ ስነስርዓታዊ አይደለም ሲል አልፎታል፡፡ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-አከራካሪውን ቤት በ1985 ዓ/ም ከወላጅ አባታቸው ያገኙትና ከሃያ አመታት በላይ ሲጠቀሙበት የቆየ ሁኖ እያለ ተጠሪ ድርሻቸውን በገበያ ዋጋ እንዲወስዱ ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አከራካሪው ቤት በሚች አውራሽ ፈቃድ ለመሰራቱ በዕሑፍ ሰነድ በቀረበበት የበታች ፍርድ ቤቶች ለአመልካች ስለሚከፈለው ግምት ያለመወሰናቸው እንዲሁም ተጠሪን ሳይጨምር ሌሎች አራት ወራሾች ቀደም ሲል ውርሱ ሲጣራ ድርሻቸውን ለአመልካች መልቀቃቸው በስር ፍርድ ቤቶች ታልፎ የተጠሪ ድርሻ የቤቱ ግማሽ ነው ተብሎ መባሉና የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ቤቱን አስቀርተው የተጠሪን ድርሻ ይክፈሉ በማለት የወሰነው በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የመሻሩን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ተጠሪ በሰጡት መልስም አመልካች በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉትን መብት በተመለከተ ስርዓቱን ጠብቀው ይግባኝ ያላቀረበበት መሆኑን ጠቅሰው ቤቱ የግሌ ነው በማለት የሚያቀርቡት ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከውርስ ሕጉ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪውን ቤት የሚች በቀለ ባልቻ የውርስ ንብረት ነው በማለት ተጠሪ በልጅነታቸው ድርሻቸው በተጠሪ እንዲሰጣቸው ክስ አቅርበው አመልካች ቤቱ የግሌ ነው የሚል ክርክር አቅርበው በወረዳው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ካጡ በኋላ ፍርድ ቤቱ ለክሱ መሰረት ከሆነው የቤቱ ግምት ከብር 80,000.00(ሰማንያ ሺህ) ውስጥ ለስድስት ወራሾች እኩል ሲካፈል የሚመጣው ውጤት ብር 13,000.00(አስራ ሶስት ሺህ) አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪ እንዲከፍሉ መወሰኑን፣በዚህ ውሳኔ በከፊል ያልተስማሙት የአሁኑ ተጠሪ ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ድርሻዬን ላገኝ ይገባል በማለት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት ያገኙ መሆኑን፣አመልካች በስርዓቱ መሰረት ቤቱ የግሌ ነው የሚለውን ይግባኝ ከወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ያላቀረቡ መሆኑንና ባሁኑ የክርክር ደረጃ ደግሞ ቤቱ የግሌ ነው የሚለውን ክርክር አጥብቀው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በየርከኑ ባሉት ፍርድ ቤቶች የሚታየው ክርክር የሚመራው በስነ ስርዓት ህጉ በተዘረጋው ስርዓት መሆኑ ይታወቃል፡፡ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ በሰጠው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅሬታ ያለበት ወገን ቅሬታውን በይግባኝ ወይም በመስቀለኛ ይግባኝ ለማሳየት የሚችል ስነ ስርዓት ሕጉ ያሳያል፡፡እነዚህ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓቶች የየራሳቸው ሕጋዊ ውጤት ያላቸው ሲሆን በማን ሊቀርቡ እንደሚገባም ስነ ስርዓት ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ይግባኝ ማለት በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠው ፍርድ ቅሬታ ያለበት ወገን ይህንኑ ቅሬታውን በህጉ ስልጣን በተሰጠው የበላይ ፍ/ቤት አቅርቦ በማሣየት በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ እንዲሻሻል እንዲለወጥ፣ወይም ሙሉ በሙሉ ውድቅ እንዲሆን ዳኝነት የሚጠየቅበት ሥርአት ነው፡፡ ይግባኝ ለተከራካሪ ወገኖች የተሰጠ መብት ቢሆንም ገደብ የለሽ ግን አይደለም፡፡ በሌላ አገላለጽ በማናቸውም ፍርድ ወይም ትእዛዝ ላይ ሁሉ ይግባኝ ለማለት የማይቻልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህም በግልጽ በሕግ ሊመለከት ይችላል፡፡ ለዚህ ዓይነት ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320 ስር የተመለከተው ድንጋጌ በዋቢነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ በመሆኑም በአንድ ፍርድ ወይም ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ መለኪያው ሊሆን የሚገባው በተሰጠው ፍርድ ወይም ትእዛዝ ተከራካሪ ወገን መብት የሚጐዳ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠ ውሣኔ መብቱ ወይም ጥቅሙ የተነካ አሊያም ግዴታው ከፍ እንዲል የተደረገ ወገን የይግባኝ መብት ይኖረዋል፡፡ የይግባኝ ዓይነቱም ቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ(cross-appeal) ሊሆን ይችላል፡፡ የይግባኝ ዓይነቱ ቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሚቀርበው ፍርዱ የይግባኝ አቅራቢውን መብት በሚጐዳው መልክ የሚነካ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ከተከራካሪ ወገኖች የቀረቡለትን ሁሉንም የክርክር ነጥቦች መሰረት ያላደረገ ቢሆንም በውጤት ደረጃ ጠቃሚ ሁኖ ከተገኘ ለውሣኔው መሰረት ይሆን ነበር የሚባል ምክንያት ብቻ በመያዝ ይግባኝ ሊል ይገባል ማለት የይግባኝ ሥርአትን መሰረታዊ ዓላማና መመዘኛውን እንዲሁም የፍትሐብሔር ሕግ ሥነ ሥርአትን ዓላማ ያገናዘበ አይሆንም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመከራከሪያ ነጥቡን ያቀረበ እና ከመከራከሪያ ነጥቦቹ መካከል በአንዱም እንኳ ቢሆን በውሣኔው ውጤት ተጠቃሚ የሆነ ወገን በስር ፍ/ቤት ለውሣኔው መሰረት ባልሆነው መከራከሪያ ነጥብ ብቻ ቀጥታ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ ሣያቀርብ መከራከሪያ ነጥቡን በበላይ ፍ/ቤት በመልሱ እስከአቀረበ ድረስ ተቀባይነት አያገኝም የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ቤቱ የውርስ ንብረት አይደለም፤የግሌ ነው የሚል ክርክር ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ለተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የጠየቁት የአሁኑ ተጠሪ ሁነው አመልካች ቤቱ የግል ተብሎ መወሰን ሲገባ መታለፉ ያለግባብ ነው በማለት ቀጥተኛ ይግባኝ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ይግባኝ አላቀረቡም፡፡እንዲህ ሳያደርጉ ቤቱ የግሌ ነው በማለት በይግባኝ መልሳቸው ላይ ክርክር ማቅረባቸው ተቀባይነት የሚያገኙበት አግባብ የለም፡፡ምክንያቱም ከመሰረቱ በወረዳው ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ተጠቃሚ የነበሩ ስለመሆኑ ውሳኔው አያሳይም፡፡ስለሆነም ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ተቃውሞ በመቀበል አመልካች ቤቱ የግሌ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክርና የዚህ ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎትም በዚህ ረገድ የያዘው ጭብጥ የክርክሩን ሂደት ያላገናዘበ እና ስነ ስርዓታዊ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሌላው በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ነጥብ አከራካሪው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ መወሰኑ የውርስ ንብረት ሊከፋፈል የሚገባበትን የክፍፍል ስርዓት ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡በመሰረቱ የውርስ ንብረት ክፍፍል አሰራር የሚከናወንበትን መንገድ የፍትሐብሔር ሕጋችን ግልጽ ድንጋጌዎችን ይዞ እናገኛለን፡፡ የውርስ ንብረት ክፍፍል አሰራር በወራሾች መካከል በሚደረግ ስምምነት፣ ወራሾች ያልተስማሙ እንደሆነ ከእነርሱ መካከል አንዱ ተግቶ ያሰናዳው የክፍያ ሐሳብ እንዲፀድቅ ለዳኞች ቀርቦ በሚጸድቀው አግባብ ሊከናወን እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1079 ድንጋጌ ይዘት ያሣያል፡፡ ሕጉ የመከፋፈሉ አፈፃፀም ደንብንም በቁጥር 1082 አስቀምጧል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረት ክፍያው የሚፈፀመው ሟቹ በዓፈው የኑዛዜ ቃል እንደሆነ፣ ስለክፍያው አፈፃፀም የተዓፈ ኑዛዜ ቃል ከሌለ ደግሞ በሕጉ በተዘረጋ ስርዓት መሰረት መደረግ እንዳለበት ያሣያል፡፡ የክፍፍሉ ደንብ በሕጉ የሚከናወንበትን አግባብ የሚደነግጉት ድንጋጌዎች በቁጥር 1083 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መካከል አንዱ ቁጥር 1086 ሲሆን ይህ ድንጋጌ የውርስ ንብረት የሚከፋፈልበትን መርህ የሚያስቀምጥ ሲሆን ዝርዝር ይዘቱ ሲታይም ክፍያው በመሰረቱ የሚደረገው እያንዳንዱ ወራሽ ከውርሱ ውስጥ ንብረት እየተሰጠው በአይነት ስለመሆኑና በአይነት የተመደቡት ድርሻዎች ትክክል ያልሆኑ እንደሆነ ተጨማሪ ገንዘብ በመስጠት እንደሚስተካከሉ የሚገልጽ ነው፡፡ የድርሻዎቹን አመዳደብ ስርዓትም በተቻለ መጠን ለእያንዳንዱ ወራሽ በሚሰጠው የጎላ ጠቀሜታ ምርኩዝ ተደርጎ ሊከናወን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1087/2/ ድንጋጌ ስር በግልጽ ሰፍሯል፡፡ስለውርስ ንብረት ክፍፍል የሚደነግጉት ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ ሲታይ ክፍፍሉ በዓይነት እንዲሆን ማድረግ ቀዳሚ የክፍፍል ሥርዓት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም በጨረታ የውርስ ንብረት በመሸጥ ወራሾች እንዲከፋፈሉ የሚደረገው ሕጉ በአስገዳጅነት ያስቀመጠው በአይነት የማከፋፈል መንገድ የማይቻል መሆኑና በሕጉ በልዩ ሁኔታ የተቀመጡት ሁኔታዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡የውርስ ንብረት ወራሾች በአይነት እንዲከፋፈሉ ማድረግ ቅድሚያ የሚፈጸም የክፍፍል ስርዓት ስለመሆኑ ሕጉ ከአስቀመጠ ደግሞ ከወራሾቹ አንዱ ወይም ሌላው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ በመፈለጉ ብቻ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ ሊደረግ አይገባም፡፡ሕጉ ለውርስ ንብረት ክፍፍል በአይነት የመከፋፈል ስርዓት በቅድሚያ እንዲከናወን ወይም መርህ ሁኖ እንዲቀመጥ የፈለገውም ሕብረተሰቡ ለውርስ ንብረት የሚሰጠውን የተለየ ቦታ ግምት ውስጥ አስገብቶ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ የውርስ ንብረት በሐራጅ የመሸጥ ስርዓት ተግባራዊ የሚሆንበትን አግባብ ሕጉ በቁጥር 1092 ድንጋጌ ከአስቀመጠው ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የውርስ ሀብት ውስጥ ከፍ ያለ ጉዳት ሳይደርስባቸው ሊከፈሉ የማይችሉ ንብረቶች ያሉ እንደሆነና ከወራሾቹ መካከል ይህን የማይከፈል ሀብት ሊወስድ የሚገባው የትኛው እንደሆነ በስምምነት ለመወሰን ያልቻሉ ከሆነ ስለመሆኑ ድንጋጌው ያሳያል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ቀጣይ ስለመሆኑ የሚያስገነዝበው ቁጥር 1093 ድንጋጌ ሲታይም ከወራሾቹ መካከል አንደኛው ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ ሽያጩ በወራሾች መካከል በሐራጅ ሊደረግ እንደሚገባ፣ በወራሾች መካከል ስምምነት ከታጣም በሐራጅ ጨረታ ውስጥ ባዕድ ሰዎች እንዲገቡ ሊደረግ እንደሚገባ እንደ የቅደም ተከተላቸው በንዑስ ቁጥር አንድና በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌዎች ስር አስቀምጧል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ጠቅለል አድርገን ስንመለከት የውርስ ንብረት ክፍፍል ስርዓት በሕጉ የተመለከቱትን መንገዶች በመጠበቅ ሊከናወን ሊገባ ስለመሆኑና በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር ንብረቱ ከወራሾቹ እጅ በቀላሉ እንዲወጣ የማይደረግ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የውርስ ሀብት በጨረታ እንዲሸጥ ሊደረግ የሚገባው በፍ/ሕ/ቁጥር 1093 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች ሲኖሩ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የበላይ ፍርድ ቤቶች የውርስ ንብረት የሆነውን ቤት በጨረታ እንዲሸጥ የወሰኑት ከላይ የተመለከቱትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን ተከትለው ያለመሆኑን፣የወረዳው ፍርድ ቤትም ተጠሪ ድርሻቸውን እንዲያገኙ ያደረገው የገበያ ዋጋን መሰረት ባደረገ መልኩ ያለመሆኑን ከውሳኔዎቹ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች የውርስ ንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ክፍፍሉ ሊከተለው የሚገባውን ስርዓት ስንመለከተውም ተጠሪ ቤቱ በአይነት ሊካፈል የሚችል መሆኑን ጠቅሰው የክፍፍሉ ስርዓትም በውርስ ድንጋጌዎች መሰረት እንዲከናወን ዳኝነት ያለመጠየቃቸውን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ደግሞ ቤቱን እንዲያስቀሩ በወረዳው ፍርድ ቤትም ተወስኖላቸው የነበረ ሲሆን ቤቱ በጨረታ ሊሸጥ ይገባል ተብሎ ከተሰጠው ውሳኔም ስርዓቱም ጠብቀው በመከራከር ላይ የሚገኙ መሆኑንና የጠየቁት ከፍተኛው ዳኝነትም ቤቱ የግሌ ሊባል ይገባል የሚል መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተናል፡፡ በመሆኑም ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ወራሾች ድርሻቸውን እንዲከፋፈሉ ከማድረግ ይልቅ የቤቱን የገበያ ዋጋ መሰረት በአደረገ መልኩ ከአመልካች ውጪ ያሉት የሚቹ ወራሾች እንዲሰጣቸውና አመልካች ቤቱን እንዲያስቀሩ መወሰኑ በውርስ ህጉ የተመለከቱትን የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚገዙትን ድንጋጌዎችን ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለልም የሚች አቶ በቀለ ባልቻ ንብረት የሆነውን አከራካሪውን ቤት ወራሾች እንዲከፋፈሉ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም የአከፋፈል ሥርዓት ግን በውርስ ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ያልተከተለ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዳአ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 30082 የካቲት 06 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 33562 ሚያዝያ 10 ቀን 2005 ዓ/ም ተሻሽሎ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 161567 ሰኔ 04 ቀን 2005 ዓ/ም ፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 164191 መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የሚች አቶ በቀለ ባልቻ ንብረት የሆነውና በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 07 ክልል ውስጥ የሚገኘው፣በካርታ ቁጥር 7/17/1 ቁጥሩ 290 የሚታወቀው ቤት የውርስ ቤት ነው ተብሎ አመልካችንና ተጠሪን ጨምሮ ለስድስት ወራሾች እንዲከፋፈል ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ክፍፍሉን በተመለከተ ግን የቤቱ የገበያ ዋጋ ከታወቀ በኋላ የተጠሪንም ሆነ የሌሎች ወራሾችን ድርሻ አመልካች ከፍለው ቤቱን በአይነት እንዲያስቀሩ፣ይህን ማድረግ የማይችሉ ከሆነ ግን በጨረታ ተሽጦ ሁሉም ወራሾች ድርሻ ገንዘባቸውን እኩል እንዲከፋፈሉ በማለት ወስነናል፡፡ የአዳአ ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ ችሎት ውሳኔ እንዲያስፈጽም በማለት የውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍለት ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ትእዛዝ

ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90959

ግንቦት 06 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ተክለ ዓዲቅ ኤካ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ መላኩ ፍሬው
2ኛ. ወ/ሮ በየነች ታደሰ } የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የስጦታ ይፍረስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች ላይ በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው።የክሱ ይዘትም፡-ተጠሪዎችና ሌሎች ልጆች የሟች ፍሬው ቦጋለ ኤካ እና የወ/ሮ አበራሽ ዳደና ልጆች መሆናቸውና እነዚህ ወላጆቻቸው ተከታትለው ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን፣ በህይወት በነበሩበት ጊዜም በሟች አቶ ፍሬው ቦጋለ ስም ቦታ ተመርተው በሶዶ ከተማ ቤት መስራታቸውን፣ ይህንኑ ቤት የአሁኑ አመልካች ጥር 28 ቀን 2001 ዓ/ም በስጦታ ከሟቹ እንደአገኙና በሰነዱ ላይ የሟች ወ/ሮ አበራሽ ደደና ፊርማ በማስመሰል ጽፈው በሶዶ ከተማ ፍትህና ጸጥታ ጽ/ቤት በማስመዝገብ አስጸድቀው መገኘታቸውንና ይህም በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ስጦታ መደረጉንና ተወላጆችን የነቀለ መሆኑን እንደሚያሳይና የሰጪው ተግባር ሕገወጥ መሆኑን ዘርዝረው ስጦታው እንዲፈርስ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም፡- ክሱ በይርጋ እንደሚታገድና ስጦታውም በሕጉ አግባብ የተደረገና ስመ ሃብቱም ለስጦታ ተቀባዩ ዙሮ የሚገኝ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል።ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በአሁኑ አመልካች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥብ ውድቅ አድርጎና ፍሬ ነገሩን መርምሮ ስጦታው ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል። በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም።የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የስጦታ ውሉ በሕጉ አግባብ የተደረገና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስመ ሃብቱም ለስጦታ ተቀባዩ የዞረ ሁኖ እያለ የስጦታ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው።አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ ሁኖ አግኝቶታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት የሟች አቶ ፍሬው ቦጋለ እና የወ/ሮ አበራሽ ዳደና ወራሾች መሆናቸውን ጠቅሰውና ሟቾች በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ በጋራ ያፈሩትን ቤት ሕጋዊ ባልሆነ የስጦታ ውል አመልካች መብት አለኝ በማለት ይዘው እንደሚገኙና ሟች አቶ ፍሬው ቦጋለ መብት ሳይኖራቸው በሚስታቸው ድርሻ ስጦታ ከሕግ ውጪ ያደረጉ ከመሆኑም በላይ ከድርሻቸው ተወላጆችን መንቀላቸውን በመግለፅ ዘርዝረው የስጦታው ውሉ እንዲፈርስ ይወሰንልን በሚል መሆኑን ነው። የአሁኑ አመልካች በበኩላቸው ለተጠሪዎች ክርክር በሰጡት መልስ ከተጋቢዎች መካከል አንዱ ሲሞት በሕይወት የቀረው ተጋቢ በጋራ ንብረት ላይ ሙሉ መብት እንዳለውና በስጦታ ለሚፈልገው ሰው ቢያስተላልፍ በሕግ ክልከላ እንዳልተደረገበት እንዲሁም ስጦታው በሟቹ ሙሉ ፈቃድ ሕጉን ተከትሎ የተፈፀመ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት መከራከራቸውን ተረድተናል።ይህ ችሎት የቀረበለትን ጉዳይ ለስጦታ ውል አደራረግ አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምሮአል። በዚህም መሰረት ሟች አቶ ፍሬው ቦጋለ ያደረጉት ስጦታ በባልና ሚስት የጋራ ሃብት በሆነው ቤት ላይ የተደረገ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ስጦታው የሚያስከትለው የሕግ ውጤት ምንድነው? የሚለው የሕግ ነጥብ አስመልክቶ ሕጉ የሚለውን መመልከት ለውሣኔ አስፈላጊ ሆኖም አግኝቶታል።

ከሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪዎች ለስጦታው መፍረስ እንደ አንድ ምክንያት የጠቀሱት ቤቱ የባልና ሚስት የጋራ ሁኖ እያለ ባል ብቻ አደረጉ በተባለው ስጦታ ለአሁኑ አመልካች እንዲሰጥ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አመልካች በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች ባቀረቡት ክርክር ከተጋቢዎች አንዱ በህይወት ከቀረ የጋራ ንብረት መብትን ጠቅልሎ ስለሚወስድ ስጦታ ማድረግ በሕግ ክልከላ አልተደረገም የሚል እንጂ ቤቱ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት አይደለም በማለት ክደው ያለመከራከራቸውን ተረድተናል።ስለሆነም አከራካሪው ንብረት የባልና ሚስት የጋራ ንብረት መሆኑ በአመልካች በስርዓቱ መሰረት ማስተባበያ ክርክር ያልቀረበበት በመሆኑ በዚህ ሰበር ደረጃ አመልካች ቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጋብቻ ውጤት ስለመሆኑ ተጣርቶ አልተወሰነም በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ወደ ስጦታ ሕጋዊ መሆን ያለመሆን ነጥብ ስንመለስም፡- በመሰረቱ አንድ ሰው በራሱ ባልሆነና ሊያዝበት በማይችል ንብረቱ ስጦታ ያደረገ እንደሆነ ስጦታው የሚኖረው ሕጋዊ ሁኔታ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ በፍትሃ ብሔር ሕጉ ስለስጦታ በሚደነግጉ ከቁጥር 2427 እና ተከታይ ድንጌዎች በግልጽ ምላሽ ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2427 ስለ ሥጦታ ትርጉም ሲያስቀምጥም ስጦታ አንድ ወገን ተዋዋይ ማለት ሰጪው፤ተቀባይ ተብሎ ለሚጠራው ለሌላ ሰው ችሮታ በማድረግ አሳብ ከንብረቶቹ አንዱን የሚለቅበት ወይም ግዴታ የሚገባበት ውል መሆኑን እንደሚያሳይ፣በዚህ ትርጉም ውስጥም «ከንብረቶቹ» የሚለው ቃል ስጦታ በሚደረገው ንብረት ላይ ስጦታ ሰጪው የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን የሚጠቁም ከመሆኑም በላይ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2451 ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ስጦታ የሚደረገው ስጦታው በተደረገበት ቀን የሰጪው ገንዘብ ከሆነ ንብረት ላይ ብቻ መሆኑን መደንገጉም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በመርህ ደረጃ ማንም ሰው ምንም መብት በሌለው ንብረት ላይ የስጦታ ውል ያደረገ እንደሆነ የተሰጠው ስጦታ ዋጋ የማይኖረው መሆኑን ነው፡፡ስለሆነም በሕግ ፊት የሚፀና ስጦታ ለማድረግ ሰጪው ስጦታ በተደረገበት ንብረት ላይ መብት ሊኖረው ይገባል፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ስጦታው በሚስት ድርሻም ጭምር የተደረገ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስጦታውን ፈራሽ የሚያደርግ ነው በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ተገቢነት ያለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው መታየት ያለበት ነጥብ ስጦታው በሚስት ድርሻ ሕጋዊ ውጤት አያስከትልም ከተባለ በባል ድርሻ ወይም በስጦታ አድራጊ ድርሻ ላይ ያለው ውጤት ነው፡፡ተጠሪዎች ስጦታው በዚህ ረገድ ሊፈርስ ይገባል በማለት ከሚከራከሩባቸው ምክንያቶች አንዱ ሚች በህመም ውስጥ እንደነበሩ ገልፀው አመልካች የሚቹን መንፈስ ልልነትና አቅመ ደካማነቱን በመጠቀም ስጦታ አድራጊ ሕጻን የሆኑ ተወላጆቹን ያላግባብ ከውርስ ንብረቱ ላይ እንዲነቀሉ አድርገዋል በሚል ነው፡፡አመልካች ተጠሪዎችም ሆኑ ሌሎች የሚቹ ሕጋዊ ወራሾች ሌላ የውርስ ንብረት ያላቸው ስለመሆኑ ገልፀው ያቀረቡት ክርክርም የለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ ስጦታው ተፈፃሚነቱ ሚቹ ከሞቱ በኋላ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 እና 2438 ድንጋጌዎች አግባብ በውርስ ሕጉ ተወላጆቹን በተመለከተ በኑዛዜ ለመንቀል የሚቻል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ማድረግ የግድ የሚል መሆኑ ይታመናል፡፡ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤት ስጦታው ተወላጆቹን የውርስ ንብረት እንዳያገኙ የሚከለክል፣ከቅን ልቦና ውጪ የተደረገ መሆኑን ሚቹ የነበሩበትን የጤና ሁኔታ፣ስጦታው ከተደረገ በኋላ ሚቹ እስከ ሚያዝያ 13 ቀን 2001 ዓ/ም ብቻ የቆዩ መሆኑን ሁሉ ከክርክሩ ፍሬ ነገር ደምድሞ ስጦታውን ፈራሽ ነው ሲል መወሰኑን የውሳኔው ይዘት የሚያስገነዝብ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን አጣርቶ በዚህ ረገድ የደመደመውንና ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የተቀበለውን ይህንኑ የፍሬ ነገር ሁኔታ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ተለይቶ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር ሲታይ ለመለወጥ የሚያስችል መሰረታዊ የሆነ ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም ስጦታው ከቅን ልቦና ውጪ የተደረገ ነው እስከተባለ ድረስ በስጦታ አድራጊው ድርሻ ጭምር ፈራሽ የማይሆንበት ሕጋዊ ምክንያት ያለመኖሩን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2438(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ተገንዝበናል፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ነጥብ ስጦታውን መነሻ በማድረግ የቤቱ ስመሃብቱ ወደ አመልካች ዙሮ እያለ የተጠሪዎች ክርክር ተቀባይነት ማግኘቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ በአንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በአስተዳደር አካል የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የባለቤትነት ግምት መነሻ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ሲሆን ይህ ግምት ግን ደምዳሚ ያለመሆኑን የዚሁ ድንጋጌ ተከታይ የሆነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡በመሆኑም ስመ ሃብቱ የዞረበት መነሻ ያላግባብ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የባለቤትነት ደብተር የያዘ ሰው በፍርድ ቤት ሊከሰስ አይገባም የሚባልበት የሕግ አግባብ ስለሌለ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታም ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ስጦታው ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20819 ሰኔ 06 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 00064 የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በ28/05/2001 ዓ/ም በሚች ፍሬው ቦጋለ ኤካ ተደረገ የተባለው ስጦታ ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93346

ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሰሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡-

1. ወ/ሮ ብርሃን ደሳለኝ
2. ወ/ሮ የሺ ቸኮል

} ከጠበቃ አገኘሁ ዓይናለም ጋር ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡ ወ/ሮ ብርትኳን ዮሐንስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግስት ቤት የተከራይነት መብትን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ በአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በአሁኖቹ ተጠሪዎች እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ በነበረው እና የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ባልሆነው በኮ/ቀ/ክ/ከተማ የወረዳ 14 ኮንስትራክሽን እና ቤቶች ልማት ጽ/ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡በ02/08/2005 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-የከሳሽ ባለቤት የነበሩት ፱ አለቃ ከበደ ሬባ በኮ/ቀ/ክ/ከተማ በወረዳ 14 የሚገኘውን ቁጥሩ 512 የሆነውን ቤት እስከሞቱበት የካቲት 2 ቀን 2005 ዓ.ም. ድረስ ከመንግስት ተከራይተው ይኖሩበት እንደነበረ፣ሟች በሕይወት እያሉ ቤት አፈላልገው እስኪያገኙ ድረስ በማለት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾችን ለጊዜው አስጠግተዋቸው እንደነበረ፣ተከሳሾቹ ቤት አፈላልገው እንዲወጡ ቢጠየቁ ፈቃደኞች ሳይሆኑ እንደቀሩ እና 3ኛ ተከሳሽም አስገድዶ ሊያስወጣቸው ፈቃደኛ እንዳልሆነ የሚገልጽ ሆኖ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ቤቱን ለቀው እንዲወጡ እና 3ኛ ተከሳሽም እንዲያስለቅቅ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በ14/08/2005 ዓ.ም. በጋራ በሰጡት መልስ ከቤቱ ውስጥ ከሟች አንዳንድ ክፍሎችን በመከራየት በቤቱ መኖር የጀመሩት 1ኛ ተከሳሽ ከመስከረም 1991 ዓ.ም.፣ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ከሚያዝያ ወር 1994 ዓ.ም. ጀምረው መሆኑን፣ከሳሽ ከሟች ባለቤታቸው ጋር በቤቱ የኖሩት ከ19/08/2003 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 02/06/2005 ዓ.ም. ድረስ ለ22 ወራት በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን 3ኛ ተከሳሽ በበኩሉ በ21/08/2005ዓ.ም. በሰጠው መልስ በከሳሽ ላይ የፈጸመው ድርጊት አለመኖሩን በመግለጽ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ በመመሪያ ቁጥር 2/2003 መሰረት ትዳር ያለው አንድ የመንግስት ቤት ተከራይ በሞት ሲለይ የተከራይነት መብቱ ለሌላኛው ተጋቢ ሊተላለፍ የሚችለው ተጋቢው ለሁለት ዓመት በቤቱ መኖሩ በተረጋገጠ ጊዜ በመሆኑ እና ከሳሽም እስከ ባለቤታቸው ሞት ድረስ በቤቱ የኖሩበት ጊዜ ከሁለት ዓመት በታች በመሆኑ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ከሳሽ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የከተማው ይ/ሰሚ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በመመሪያው የተቀመጠው የሁለት ዓመት ጊዜ መሰላት የሚገባው ተከራዩ እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ ብቻ ሳይሆን ክርክሩ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ መሆኑን፣ጊዜው በዚህ አግባብ ሲቆጠር ደግሞ ከሳሽ በቤቱ የኖሩት ከሁለት ዓመት በላይ መሆኑን እና የአሁኖቹ አመልካቾች በቤቱ ውስጥ ለመቆየት የሚያስችል መብት የሌላቸው መሆኑን ገልጾ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ተጠሪዎቹ ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የከተማው ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት አቤቱታቸውን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ አመልካቾቹ ክርክር ባስነሳው የቀበሌ ቤት ውስጥ እንደቅደም ተከተላቸው ለ14 እና ለ11 ዓመታት መኖራቸው በተረጋገጠበት እና በቀጣይም በሚመለከተው አካል በኩል የተከራይነት መብት አግኝተው የኪራይ ውል በተዋዋሉበት ሁኔታ ቤቱን ለቀው እንዲወጡ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ለውሳኔው የሰጠው ምክንያት በመመሪያው የተመለከተውን የጊዜ አቆጣጠር ስርዓት እና የአሁኖቹ አመልካቾች በቤቱ ውስጥ ለመቆየት የሚያስችል መብት የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይህንን ውሳኔ የሰጠው በ26/11/2005 ዓ.ም. ሲሆን ሰበር ችሎቱም አቤቱታውን ዘግቶ ያሰናበተው በ04/13/2005 ዓ.ም. ነው፡፡በሌላ በኩል ግን በክርክሩ ላይ ሶስቱም ፍ/ቤቶች ውሳኔ ከሰጡ በኋላ ጉዳዩ የሚመለከተው የክ/ክ/ከተማ ወረዳ 14 ኮንስትራክሽን እና ቤቶች ልማት ጽ/ቤት ሁለቱም አመልካቾች ለሚኖሩባቸው ክፍሎች ከሁለቱም አመልካቾች ጋር የኪራይ ውል መዋዋሉን እና ኪራይም ማስከፈል መጀመሩን አመልካቾቹ በሰበር አቤቱታቸው ላይ በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዋም ቢሆን አስተዳደሩ ከአመልካቾቹ ጋር የኪራይ ውል የተዋዋለው አላግባብ ነው ከማለት ውጪ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ማስተባበያ የለም፡፡ተጠሪ ክሱን ያቀረቡት አመልካቾቹ ለጊዜው በጥገኝነት የገቡ በመሆኑ በቤቱ ክፍሎች የመኖር መብት የላቸውም በማለት ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን የኪራይ ውል ገብተው የተከራይነት መብት ያገኙ በመሆኑ አስተዳደሩ ከተጠሪዎች ጋር ውል የገባው ከሕግ ውጪ ነው የሚሉ ከሆነ አስተዳሩን በሕግ መጠየቅ የሚችሉ ከመሆኑ ውጪ ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ አመልካቾቹ በቤቱ የመቆየት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ጭብጥ ለክርክር ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የአ/አበባ ፍ/ቤቶች ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች አመልካቾች ክርክር ባስነሳው የቤቱ ክፍሎች ለመቆየት የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ውሳኔ የሰጡት አመልካቾቹ የተከራይነት መብት ከማግኘታቸው በፊት ሲሆን ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ ግን አመልካቾቹ በያዟቸው የቤቱ ክፍሎች ለመቆየት የሚያስችል የኪራይ ውል ተጠቃሚ መሆናቸው በመረጋገጡ የስር ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ውሳኔ ሊሻር እና በአንጻሩ የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ በውጤት ደረጃ ሊጸና የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 31918 በ27/10/2005 ዓ.ም. የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የከተማው ፍ/ቤቶች ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመ.ቁ. 20461 በ26/11/2005 ዓ.ም.በመ.ቁ. 20659 በ04/13/2005 ዓ.ም. የሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የተጠሪዋን ክስ ውድቅ በማድረግ የአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 31918 በ27/10/2005 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም ዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95538

ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አብርሃ ሕሉፍ ገሰሰው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ትበርህ ገብረሕይወት የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በእርሻ መሬት ላይ የቀረበውን የይገባኛል ክስ መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመሬት ዳኝነት ሰጪ ጣቢያ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት ተጠሪ ሲሆኑ አመልካችን የከሰሱት በእርሻ መሬት ደልዳዮች (አከፋፋዮች) ተሸንሽኖ የተሰጠንን 50X25 ሜትር የሆነ መሬት ይልቀቁልኝ በማለት ነው፡፡በዚህ መሠረትም የእርሻ መሬቱን ተገደው እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ለክሱ በሰጡት መልስ መሬቱን ከተጠሪ ቀድመው የተደለደሉትና በቋሚ ተክሎች አልምተው በመጠቀም ላይ የሚገኙት መሆኑንና ለተጠሪ የተሰጠበት አግባብም ሕጋዊ ያለመሆኑን በመቃወም ለሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት ጥያቄ አቅርበው መሬት ሽንሻኙ ክፍል ሳይቀበላቸው የቀረ መሆኑን ጠቅሰው መሬቱን እንድለቅ የሚደረግበት የሕግ ምክንያት የለም፤ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት የመሬት ዳኝነት ጣቢያ ተከሣሽ (የአሁን አመልካች) መሬቱ ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም ቀድሞ ለአሁኑ አመልካች የተሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የቀይ ተኽሊ ወረዳ ፍርድ ቤትም የመሬት ዳኝነት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ በማቅረባቸው በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቷል፡፡ የሰበር ችሎቱም ተጠሪ መሬቱን በድልድል ያገኙት መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች ቅሬታ ማቅረብና ጉዳያቸው መታየት ያለበት በአስተዳደሩ እንጂ በፍርድ ቤት ሊሆን አይገባም በሚል ምክንያት የመሬት ዳኝነቱና የወረዳው ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-አከራካሪውን መሬት በሕጉ አግባብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተጠሪ ቀድሞ ከተሰጣቸው በኋላ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለተጠሪ የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ክርክር ያስነሳው መሬት በመጀመሪያ ለአመልካች ከተሰጠ በኋላ እንደገና ለአሁኑ ተጠሪ ከተሰጠ በድጋሚ በላዩ ላይ ደርቦ ለሰጠው አካል ጥያቄው ከሚቀርብ በቀር በዳኝነት ሊታይ የሚችል ጉዳት አይደለም የሚለውን መሰረት በማድረግ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ዳኝነት አግባብነት ለማየት ተብሎ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት ቀደም ሲል የተሰጠው ለአመልካች እንደሆነ እና በሱ ይዞታ ሥር ስለመቆየቱ እንዳላከራከረ ከሥር ጀምሮ ከተደረገ ክርክር እና ከተሰጡት ውሣኔዎች ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የመሬት ዳኝነት ጣቢያ በሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካች መሬቱ ሊወሰድበት አይገባም (አይችልም) የሚል መደምደሚያ ላይ የተደረሰው መሬቱ በህጉ አግባብ ለአመልካች ጥር 08 ቀን 2002 ዓ.ም በተሰጠበት ሁኔታ ከሕግ ውጪ ለአሁኑ ተጠሪ ተደርቦ ነሐሴ 20 ቀን 2002 ዓ.ም መስጠቱ ያለአግባብ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ነው፡፡የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሁለቱም የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሻረው አመልካች የመሬት አስተዳዳሪዎች ይዞታዬን ወስደው ለሌላ ሰጥተውብኛል ካለ ማመልከት ያለበት በየደረጃው ለሚገኙ የአስተዳደር አካላት ነው ፤ ከዚህ ባለፈ ጉዳዩ በቀጥታ በፍ/ቤት የሚታይ አይደለም በማለት እንደሆነ ከውሣኔው ተገንዝበናል፡፡

እንደምናየው ጉዳዩ በፍ/ቤት እንዲዳኝ ክስ ያቀረቡት ተጠሪ ናቸው፡፡ አመልካች መሬቱን የምለቅበት አግባብ የለም የሚል ክርክር ያቀረበ ሲሆን በመከላከያነትም የሕግ እና የፍሬ ነገር ነጥቦችን አንስቷል ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የመሬት ዳኝነት ጣቢያ ፍ/ቤት እንደመሆኑ የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር ከሰማ በኋላ መሬቱ ለአሁኗ ተጠሪ መለቀቅ የለበትም ብሎ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በፍ/ቤት የተሰጠ እንደመሆኑ በውሳኔው ያልተስማሙት ተጠሪ ይግባኙን ማቅረብ ያለባቸው በደረጃው ለተዋቀረው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ነው፡፡ አከራካሪው ጭብጥ ተጠሪ መሬቱን የተሰጡበት በሕጉ አግባብ ነው ወይ? የሚል በመሆኑ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ሆነ ይግባኝ የሰሙት ፍ/ቤቶች ጭብጡን ከቀረበው የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር አንፃር በማየት የየበኩላቸውን ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ ጥር 8 ቀን 2002 ዓ/ም ለአመልካች የተሰጠው መሬት ነሐሴ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ለተጠሪ ሊሰጥ የቻለው በምን ሕጋዊ ምክንያት እንደሆነ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም ድልድሉ ተገቢ ያለመሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የመሬት ዳኝነቱና የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ድምዳሜ ያሳያል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እነዚህ የዳኝነት አካላት መሬቱ ለተጠሪ የተደለደለ ከሕግ ውጪ ነው የሚል ምክንያት የሰጡት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 136/2000 አንቀጽ 31 "ን" በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ በበኩላችንም አዋጁንና ለማስፈፀም የወጣው የተሻሻለው የትግራይ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን ደንብ ቁ. 48/2000 "ን" ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ተመልክተናል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 5፣12፣14፣22 በመሬት የመጠቀም መብት የሚል ድንጋጌ የተቀመጠ ሲሆን ዝርዝር ሁኔታው ወይም አሰራሩም በተጠቃሽ ድንጋጌዎች ስር በተመለከቱት ንዑስ ድንጋጌዎች ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በደንብ ቁጥር 48/2000 14፣15፣16 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ስር የገጠር መሬት መብት የሚገኝባቸውን መንገዶች የተዘረዘረ ሲሆን ከአንቀጽ 27 እስከ 29 ድረስም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የቦረቦር መሬት የማግኘት መብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተዘርዝረዋል፡፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ በድልድል ያገኘውን መሬት አንድ ሰው ሊወስድበት የሚገባው በሕጉ የተመለከቱ ምክንያቶች ሲኖሩ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ለአመልካች የተሰጠው ይዞታ ለተጠሪ ተደርቦ የተሰጠበት አግባብ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም፡፡

የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በውሳኔው እንዳመለከተው የገጠር መሬትን የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው በየደረጃው ለተዋቀሩ የአስተዳደር አካላት ቢሆንም እነዚህ አካላት የተሰጣቸውን ሥልጣን መተግበር ያለባቸው በአዋጁ እና በደንቡ በግልጽ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ከላይ ተደጋግሞ እንደ ተገለፀው አመልካች የእርሻ መሬቱን አለቅም ያለው በአዋጁ እና በደንቡ የተጠበቀለትን መብት መሠረት በማድረግ ሲሆን ተጠሪ ክስ የመሠረቱበት ደግሞ ይህ በሕግ የተጠበቀለትን የአመልካች መብት በፍ/ቤት ውሳኔ ቀሪ እንዲሆንና መሬቱ እንዲለቀቅላቸው ነው፡፡ ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሚሰጡት ሕግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ ደግሞ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 79(3) ከተቀመጠው ድንጋጌ እና የዳኝነት አመራር ስርዓትን በሚመለከት ከወጡት ህጎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የመሬት ዳኝነቱና የወረዳው ፍ/ቤት ለአመልካች የተሰጠው ድልድል ቀሪ የሚሆንበት አግባብ የለም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በዳኝነት እንደማይታይ አድርጎ መወሰኑ ከላይ የተጠቀሱትን የክልሉን የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕጎችን አዋጅ ቁጥር 456/1997 ስር የተረጋገጠውን የእርሻ መሬት ይዞታ መብትን እንዲሁም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣40(3) እና 79 ስር የተቀመጡትን ድንጋጌዎችንና በዚህ ረገድ በክልሉ ሕገ መንግስትም የሰፈሩትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ

1. የትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 60917 ነሐሴ 25 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በሳንታ ገለበዳ ቀበሌ መሬት ዳኝነት ግንቦት 07 ቀን 2005 ተሰጥቶ በቀይሕ ተክሊ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01471 ሰኔ 28 ቀን 2005 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡ በዚህ መሠረት አመልካች የእርሻ መሬቱን እንዲለቅ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94869

ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች ፡- አቶ መሳ ደገፈ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ጥላሁን ደስታ /ጠበቃ ሽመልስ ከፍያለሁ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርደ ተሰጥቷል

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው በስሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን አሌሊቱ ወረዳ ፍ/ቤት የሰበር አመልካች ከሳሽ በመሆን ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡

አመልካች ጥቅምት 4 ቀን 2000 ዓ/ም በተሻፈ ለስር ፍ/ቤት በቀረበው ክስ አቤቱታ፡-በ1993 ዓ/ም ከአቶ ደስታ አያኔ እና ወ/ሮ ሸዋዬ ቡልቻ በልዋጭ ባገኘሁት ይዞታ ላይ ባህር ዛፍ ተክዬ በእጄ ያለውን ተጠሪ በ27/01/2000 ዓ/ም እንዳልጠቀምበት በመከልከል ሁከት ስለፈጠረብኝ ሁከቱ እንዲቆም ይወሰንልት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪም በበኩል ቀርቦ በሰጠው መልስ፡- ይህ ክርክር የቀረበበት ይዞታም ሆነ ባህር ዛፍ የአባቱ መሆኑን፤ተጠሪም ወራሽ በመሆን ይዞታው የተላለፈለት መሆኑንና ይህ በውርስ ያገኘው ይዞታ ደግሞ እንዳይነካበት መከልከሉ መብት እንጂ ሁከት ሊባል እንደማይችል ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ የፈጠረውን ሁከት እንዲያቆም በማለት ውሳኔ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ቅሬታውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ እና ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ ከተጠሪ አባት በልዋጭ አግኝቸበታለሁ በማለት የጠቀሰው የውል ስምምነት ሰነድ (በ17/7/1993 ዓ.ም የተደረገ) ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ አባት አቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደስታ አያሌ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ውጤቱ ከታወቀ በኋላ በጉዳዩ ላይ ተገቢው ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ክርክሩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሶ ለወረዳ ፍ/ቤቱ ልኳል፡፡

የወረዳ ፍ/ቤቱም በበኩሉ በሰነዱ ላይ ያለው ፊርማ በፎሬንሲክ ሳይንስ እንዲመረመር ካደረገ በኋላ ፊርማው የተጠሪ አባት መሆን አለመሆኑን ለመለየት አልተቻለም በሚል የተገለፀለትን የምርመራ ውጤት ጭምር መሠረት አድርጐ ጉዳዩን መመርመሩን ከገለፀ በኋላ አመልካች ክርክር የቀረበበትን ይዞታ በልዋጭ አግኝቸበታለሁ በማለት የሚከራከረው ውል ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ አባት ፊርማ አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ላይ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካችም በበኩሉ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ቅሬታውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ደረጃውን ጠብቆ ያቀረበ ቢሆንም በሁለቱም ደረጃ ቅሬታው ተቀባይነት አላገኘም ሆኖም ግን ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ክርክር የቀረበበት ይዞታ ማን እጅ እንደነበር ማን ግብር ሲገብርበት እንደነበር በይዞታው ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር የተሰጠው ለማን እንደሆነ እና ተጠሪ ይዞታውን ሁከት ፈጥሮ መያዝ አለመያዙ በግራ ቀኙ የሰው ምስክሮች እና እንዲሁም ከሚመለከታቸው አስተዳደር አካላትም ተጠይቆ ተገቢ ማጣሪያ ከተደረገ በኋላ በጉዳዩ ላይ የመሰለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ክርክሩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) መሰረት በድጋሚ ወደ ወረዳ ፍ/ቤቱ መልሶታል፡፡ የወረዳ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ጉዳዩ በተመራለት መሰረት በግራ ቀኙ ምስክሮች እና እንዲሁም የክፍሉ ቀበሌ አስተዳደር እና የወረዳውን አካባቢ ጥበቃና መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ስለ ጉዳዩ ጠይቆ ካጣራ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በይዞታው ላይ የተከለውን ባህርዛፍ እንዳይጠቀምበት በተጠሪ የተፈጸመበት መሰናክል ሁከት አይደለም ሊባል የሚቻል ስለላልሆነ ተጠሪ ሁከቱን አቁሞ አመልካች ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ ያለውን መብት እንዲጠቀምበት በማለት ወስኗል፡፡፡

በተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ጉዳዩን መርምሮ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ ቀጥሎ 2ኛ ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማቸው በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት የበታች ፍ/ቤቶችን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ሆኖም ግን ጉዳዩን ቀጥሎ በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማቸው በኋላ ይህ ክርክር የቀረበበት ይዞታ ወደ ተጠሪ ተመልሶ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃም ተሰጥቶት ግብርም እየገበረበት በእጁ ባለው መሬት ላይ ተጠሪ ሁከት ፈጥሯል ለማለት የሚቻል ስላልሆነ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስሕተት ያለበት ነው በማለት ሽሮታል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ የክልሉ ሰበር ችሎት ተጠሪ ሁከት ፈጥሯል ማለት አይችልም ወደሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሳኔዎች መሻሩ መሠረታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የህግ ስህተት ስላለበት ታየቶ ይታረምልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው ይህ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታና ኋላም ባህር ዛፍ ተተክሎበታል የተባለው ይዞታነቱ በመጀመሪያ የተጠሪ አባት የአቶ ደስታ አያኔ የነበረ ስለመሆኑ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ግን በአመልካች ስም ግብር እየተገበረበት በእርሳቸው ይዞታ ስር መቆየቱን፣ መሬቱ በአመልካች ይዞታ ስር በቆየበት ጊዜ ባህር ዛፍ በአመልካች የተተከለበት መሆኑን፣ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትም በ1998 ዓ.ም በአመልካች ስም ተሰጥቶ የነበረመሆኑን፣ሆኖም ግን ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ተጠሪ ከአባቱ አቶ ደሰታ አያኔ በውርስ ሊተላለፍልኝ የሚገባ የውርስ ሀብት ነው በማለት እናቱ ወ/ሮ ሸዋዬ ቡልቻን በ1999 ዓ.ም ከሶ በ12/9/99 ዓ.ም ማስፈረዱን፣ በፍርዱ መሠረትም ይዞታውን በፍርድ አፈፃፀም ትዕዛዝ በ2001 ዓ.ም ውስጥ መቀበሉን ይዜንኑ ተከትሎም ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የይዞታው ግብር በተጠሪ ስም መገበሩንና እንዲሁም በ2002 ዓ.ም ውስጥ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትም በስሙ የሰጠው ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ መረጋገጡንና እንዲሁም በዚህ ሰበር ችሎት ክርክር ደረጃም ግራ ቀኙ ካደረጉት የጽሑፍ ክርክር ይዞታው በውርስ ለተጠሪ ይገባል ተብሎ በተሰጠው ፍርድ መሠረት ተጠሪ ይዞታውን በአፈፃፀም ለመረከብ በስር ፍ/ቤት አስከፍቶ በነበረው አፈፃፀም መዝገብ ላይ አመልካች በመቃወሚያ አቅራቢነት ጣልቃ ገብቶ በጉዳዩ ላይ ሲከራከሩበት ከቆዩ በኋላ እና በስተመጨረሻ የአመልካች የመቃወሚያ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ተብሎ መወሰኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሠረቱ ይዞታው የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተነሣበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንዲመለስለት ወይም የተነሣው ሁከት እንዲወገድለት እንዲሁም ስለደረሰበት ጉዳት ኪሣራ እንዲሰጠው ለመጠየቅ እንደሚቻል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. አንቀጽ 1149 ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ተከሣሹ ለፈፀመው ድርጊት የሚፈቀድ መብት እንዳለው ማስረዳት ከቻለ በክሱ ኃላፊ ሊሆን እንደማይገባ እንዲሁ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የሕጉ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 3 የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በ1993 ዓ.ም በልዋጭ ባገኘሁት እና በይዞታዬ ስር በቆየ መሬት ላይ የተከልኩትን ባህርዛፍ ተጠሪ እንዳልጠቀምበት በማድረግ በ27/1/2000 ዓ.ም ሁከት ስለፈጠረብኝ ሁከቱ እንዲቆም የሚል ዳኝነት ሊሰጠኝ ይገባል በሚል የሚከራከር ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ክርክር ያስነሣው መሬት የአባቱ የነበረ መሆኑን ጠቅሶ ሆኖም ግን ይዞታውን በውርስ ስላገኘሁ እና ይህም በፍርድ ተረጋግጦ በኋላም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ቤት ትእዛዝ በአፈፃፀም የተረከብኩት ይዞታ ስለሆነ ድርጊቱ ሁከት ሊባል አይችልም በሚል የሚከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በ1993 ዓ/ም በልዋጭ አግኝቼ በኋላም ባህርዛፍ ተክየበታለሁ የሚለውን ይዞታ በውርስ ለተጠሪ ይገባል ተብሎ በወረዳ ፍ/ቤቱ በ12/9/99 ዓ/ም ውሳኔ መሰጠቱ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ሁከት ተፈጥሯል በተባለበት ጊዜ ይዞታው በፍ/ቤት አፈፃፀም ትዕዛዝ በተጠሪ እጅ ባይገባም ተጠሪ በፍ/ቤት ውሳኔ የይዞታው ባለመብት ሆኗል፡፡ እንዲሁም ሁከት ተፈጥሯል ከተባለበት ጊዜ በኋላ ቢሆንም ተጠሪ በፍርዱ መሰረት ይዞታውንም በአፈፃፀም እጁ አስገብቶ እና የይዞታ ማረጋገጫም በስሙ ተሰጥቶ እስከ አሁን ግብር በስሙ እየገበረበትና እየተጠቀመበት ያለ ስለመሆኑም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ስለሆነም ሁከት ተፈጥሯል በተባለበት ጊዜም ቢሆን ተጠሪ አስቀድሞ በይዞታው ላይ በፍርድ የተረጋገጠ መብት ስለነበረው ይህ በተጠሪ ተፈፅሟል የተባለው ድርጊት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1149(3) ድንጋጌ ይዘት አኳያ ተገናዝቦ ሲታይ ይሄንኑ በፍርድ የተረጋገጠለትን መብት ከማስፈፀም ጋር በተያያዘ እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመሩን ከሚያሳይ በቀር ሁከት ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ በተጠሪ እጅ ገብቶ ባለበት ሁኔታ ሁከት አለ ማለት አይቻልም በማለት በውጤት ደረጃ በሰጠው ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላላገኘን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 149158 በ27/12/05 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ችሎት በውጤት ደረጃ ሁከት የለም ሲል የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 89148

ሰኔ 3 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡-አቶ ክፍሉ ገ/ማርያም - ጠበቃ አቶ መለሰ ጉርሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡-ወ/ሮ አስመረት መኮንን - ጠበቃ ጎሳዬ ጉርሙ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በቦረና ዞን በቡሌ ሆራ ወረዳ ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ላይ በ24/06/2002 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡2ኛ ተከሳሽ የነበረው የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ያልሆነው የከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት ነው፡፡የክሱም ይዘት ባጭሩ፡-ከሳሽ በቡሌ ሆራ ከተማ ከአባታቸው ከአቶ ገ/ማርያም ዳኜ በውርስ የተላለፈላቸው 900 ካ.ሜ ይዞታ ያለው ቤት እንዳላቸው፣1ኛ ተከሳሽ በዚሁ ቤት በዝምድና መልክ በከሳሽ ፈቃድ ገብተው ሲኖሩ ከሳሽ በማያውቁት ሁኔታ የቤቱን የባለቤትነት ስም ወደራሳቸው አዛውረው እንደተገኙ፣ከሳሽ ይህ መፈጸሙን ያወቁት በ15/06/2002 ዓ.ም እንደሆነ የሚገልጽ ሆኖ 2ኛ ተከሳሽ አላግባብ የፈጸመውን የስም ዝውውር ሰርዞ ወደነበረበት እንዲመልስ እና 1ኛ ተከሳሽም ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

1ኛ ተከሳሽ በ08/08/2002 ዓ.ም በሰጡት የተሻሻለ መልስ አባታቸው በ1972 ዓ.ም ከሞቱ ከ30 ዓመት በኋላ ከሳሽ ያቀረቡት የውርስ ቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ በይርጋ እንደሚታገድ፣በቤቱ የገቡት ከሳሽ እንደሚሉት በዝምድና መልክ ወይም በጥገኝነት ሳይሆን ከልጃቸው ዳኜ ክፍሉ ጋር በ1994 ዓ.ም ጋብቻ በመፈጸማቸው እንደሆነ፣በጋብቻውም ሁለት ልጆችን እንደወለዱ፣ዳኜ ክፍሉ በ1996 ዓ.ም በሞት እንደተለየ፣ከሳሽ ቤቱን ከእናታቸው እና ከወንድሞቻቸው መግዛታቸውን (ድርሻ መክፈላቸውን) ገልጸው ልጃቸው ጋብቻ ከመፈጸሙ አስቀድሞ በ1981 ዓ.ም በስጦታ እንደሰጡት፣ስጦታውን የሚቃወም ካለ እንዲቀርብ የከተማው አስተዳደር ቁጥሩ 489/1981 በሆነ እና በ04/03/1981 በወጣ ማስታወቂያ ጥሪ አድርጎ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ ስሙን ወደ ሟች ዳኜ ክፍሉ እንዳዛወረ፣ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ግብሩ ሲከፈል የነበረው በሟች ስም፣እርሱ ከሞተ በኋላ ደግሞ በ1ኛ ተከሳሽ ስም በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168 መሰረት በቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ መብት ያላቸው ሟች ልጃቸው እና 1ኛ ተከሳሽ እንጂ ከሳሽ እንዳልሆኑ በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ክሱ በተሰማበት ጊዜም ከጋብቻቸው በኋላ ሰባት ክፍል ቤቶችን ከሟች ባለቤታቸው ጋር መስራታቸውን በመግለጽ አስመዝግበዋል።2ኛ ተከሳሽ በበኩሉ በ30/06/2002 ዓ.ም በሰጠው መልስ ቤቱ ቀደም ሲል ጀምሮ በሟች ዳኜ ክፍሉ ስም ተመዝግቦ የነበረ መሆኑን እና ስሙን ወደ 1ኛ ተከሳሽ ስም ሊያዛውር የቻለው 1ኛ ተከሳሽ የሟች ልጆችን ወራሽነት እና የራሷን ሚስትነት በመ.ቁ. 84/96 በ07/04/1996 ዓ.ም በማረጋገጥ ከቡሌ ሆራ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረበችው ማስረጃ መሰረት መሆኑን ገልጾ ፍ/ቤቱ እንዲያሰናብተው ጠይቋል።

ፍ/ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ከሳሽ ክስ ያስነሳውን ቤት ለልጃቸው ዳኜ ክፍሉ በስጦታ በመስጠታቸው የከተማው አስተዳደር ቁጥሩ 489/1981 የሆነ እና በ04/03/1981 የወጣ ማስታወቂያ አውጥቶ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ በስጦታ ውሉ መሰረት የቤቱ የባለቤትነት ስም ወደ ዳኜ ክፍሉ ተዛውሯል ከማለት ውጪ ከ1ኛ ተከሳሽ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2444፣881፣882 እና 883 ድንጋጌዎች መሰረት የሕጉን መስፈርቶች አሟልቶ የተደረገ የስጦታ ውል በማስረጃነት ያላቀረቡ በመሆኑ ስጦታን አስመልክቶ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው፣የቤቱ ግብር ለ15 ዓመታት ሳያቋርጥ የተከፈለ ባለመሆኑ 1ኛ ተከሳሽ በመከራከሪያነት ያቀረቡት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1168 ድንጋጌ ለክርክሩ ተፈጻሚነት እንደሌለው እና የከሳሽ የወራሽነት መብትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1000(2) መሰረት በይርጋ የሚታገድ እንዳልሆነ ገልጾ 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ እና 2ኛ ተከሳሽም የባለቤትነት ስሙን በከሳሽ ስም እንዲመዘግብ ውሳኔ ሰጥቷል።

በ1ኛ ተከሳሽ ጠያቂነት ይግባኙን የተመለከተው የቦረና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ቤቱ በስጦታ የተላለፈ መሆኑን ስልጣን ያለው የከተማው አስተዳደር ማረጋገጡን፣ግብሩም በሟች ዳኜ ክፍሉ እና ከእርሱ ሞት በኋላ ደግሞ በ1ኛ ተከሳሽ ስም በአጠቃላይ ከ1988 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ የተከፈለ መሆኑን፣እነዚህ ማስረጃዎች ሀሰተኛ ስለመሆናቸው ከሳሽ አሳማኝ እና ተጨባጭ ክርክር አቅርበው ማስተባበል አለመቻላቸውን እና የከሳሽ የወራሽነት መብትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000(1) መሰረት በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ገልጾ የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን ሊለቁ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።ከሳሽ በተራቸው ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከሳሽ የክስ ነጥብ 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን አላግባብ ወደ ራሷ ስም አዛውራለች የሚል እንጂ የወራሽነት ክርክር ባለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000(1) የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ለክርክሩ አግባብነት እንደሌለው ጭምር በመግለጽ የዞኑን ከ/ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል። ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት ክርክሩን ከሰማ በኋላ ይርጋን አስመልክቶ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የያዘው አቋም የሚነቀፍ አለመሆኑን ገልጾ ነገር ግን ሟች ዳኜ ክፍሉ ቤቱን በስጦታ አግኝቷል ወይስ አላገኝም? የሚለው ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ ሟች ዳኜ ክፍሉ እና እርሱ ከሞተ በኋላ ደግሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1ኛ ተከሳሽ በአጠቃላይ ከ1988 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ የቤቱን ግብር ለ15 ዓመታት በተከታታይ ወይም ሳይቋረጥ የከፈሉ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168 መሰረት የቤቱ ባለቤት እንደሚሆኑ ገልጾ የይግባኝ ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ በመሻር የዞኑን ከ/ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን ቤት ለሟች ልጃቸው ዳኜ ክፍሉ በስጦታ እንዳልሰጡ በሚከራከሩበት እና የቤቱ ግብር ለ15 ዓመታት ተከፍሏል ለተባለውም የተከፈለው በተከታታይና ሳይቆራረጥ አለመሆኑን እና በክርክር ላይ የነበሩበትን ጊዜ(ዓመት) ጭምር ያካተተ መሆኑን በሚከራከሩበት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የይግባኝ ሰሚውን ችሎት ውሳኔ የመሻሩን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1168(1) ድንጋጌ አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ክስ ያስነሳውን ቤት ከእናታቸው እና ከወንድሞቻቸው መግዛታቸውን (ድርሻ መክፈላቸውን) ገልጸው ልጃቸው ጋብቻ ከመፈጸሙ አስቀድሞ በ1981 ዓ.ም በስጦታ አስተላልፈውለታል በማለት ተጠሪዋ የተከራከሩ ቢሆንም ስጦታውን የሚቃወም ካለ እንዲቀርብ የከተማው አስተዳደር በቁጥር 489/1981 በ04/03/1981 ያወጣውን ማስታወቂያ ከማቅረብ ውጪ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የስጦታ ውል ስለመኖሩ ተጠሪዋ የስጦታ ውሉን በማስረጃነት በማቅረብ ማስረዳት አለመቻላቸውን የመዘገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የይግባኝ ሰሚውን ችሎት ውሳኔ ሽሮ የከ/ፍ/ቤት ውሳኔን በውጤት ደረጃ ለማጽናት የቻለው ግብሩ ለ15 ዓመታት በተከታታይ የተከፈለ መሆኑ ሟች ባለቤታን እና ተጠሪዋን የቤቱ ባለቤት ያደርጋቸዋል በማለት ነው፡፡በ1988 ዓ.ም የተቆረጠው የግብር ካርኒ ግብሩ የተከፈለው ለ1988 ዓ.ም ብቻ ሳይሆን ከ1988 ዓ.ም በፊት ለነበሩት ሶስት ዓመታት ጭምር እንደሆነ ከግራ ቀኙ የሰበር ክርክር መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ የቤቱ ግብር በሟች ባለቤታ እና በተጠሪዋ ስም የተከፈለው ክርክሩ የተጀመረበትን 2002 ዓ.ም ሳይጨምር ከ15 ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ መሆኑን የመዘገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ግብሩ ለ15 ዓመታት ተከፍሏል የተባለው ግራ ቀኙ ክርክር የጀመሩበትን ዓመት ጭምር በመቁጠር ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር በግራ ቀኙ ክርክር የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ግብሩ ለ15 ዓመታት ተከፍሏል ቢባል እንኳ የተከፈለው በተከታታይ ወይም ሳይቋረጥ ባለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1168 ድንጋጌ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት አመልካች ያቀረቡትን የክርክር ነጥብ በተመለከተ እንደተባለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለእጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(ባለይዞታ) የሆነ ሰው የዚሁ ንብረት ባለቤት መሆን የሚችለው ግብሩን ባለማቋረጥ 15 ዓመት በስሙ ከከፈለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1168(1) በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግብሩ በሚች እና በተጠሪዋ ስም የተከፈለው ከ15 ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ ቢሆንም የተከፈለው ግን ለእያንዳንዱ ዓመት በተናጠል ብቻ ሳይሆን የተወሰኑ ዓመታትን አጠቃሎ በአንድ ደረሰኝ በመክፈል ጭምር መሆኑ ተረጋግጧል፡፡አመልካች የሚከራከሩትም የሁለት ወይም የሶስት ዓመታት ግብር ተጠቃሎ የተከፈለባቸው ደረሰኞች ተቀባይነት ያገኙት አላግባብ ነው በማለት ነው፡፡በመሰረቱ ባለይዞታው የንብረቱ ባለቤት መሆን የሚችለው ግብሩን ለ15 ዓመታት ባለማቋረጥ ከከፈለ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168(1) የተቀመጠው ድንጋጌ ዓይነተኛ ዓላማ ስውር ወይም አሻሚ በሆነ መንገድ የተደረገ ይዞታ ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው እንደማይገባ እና በአንጻሩ ባለይዞታው ግብሩን በተከታታይ የከፈለው በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብት እንዳለው በማመን እንዲሁም በሌሎች ዘንድም የዚህኑ ዓይነት ግምት ለማሳደር በሚያስችል ሁኔታ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ግብሩ በሚች እና በኋላም በተጠሪ በተከታታይ ሲከፈል የነበረው ቤቱ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ በሚች እጅ፣እርሱ ከሞተበት ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በተጠሪ እጅ መሆኑ በተረጋገጠበት እና በከተማው አስተዳደርም ቤቱ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ ተመዝግቦ የሚታወቀው በሚች እና ከእርሱ ሞት በኋላ ደግሞ በተጠሪ ስም መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በመሆኑ ይዞታው አሻሚ ወይም ስውር ነበር ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡ይህ ሁሉ ሲደረግ አመልካች ይኖሩ የነበረው በዚያው ከተማ እና ቀበሌ ክልል ውስጥ ስለመሆኑ በክርክሩ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ቤቱ በተጠሪ ስም መመዝገቡን እና ግብር መከፈሉን ያወቅሁት በ15/06/2002 ዓ.ም ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡በክርክሩ እንደተረጋገጠው የአመልካች አባት አቶ ገ/ማርያም ዳኜ በ1972 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ አመልካች የቤቱን ግብር በስማቸው የከፈሉት ከ1972 ዓ.ም እስከ 1975 ዓ.ም ድረስ ብቻ መሆኑም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የይግባኝ ሰሚውን ችሎት ውሳኔ በመሻር ሚች ዳኜ ክፍሉ እና ተጠሪ የቤቱን ግብር ለ15 ዓመታት ሳያቋርጥ የከፈሉ በመሆኑ እና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168 መሰረት በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት የሚያስገኝላቸው በመሆኑ ተጠሪ ቤቱን ለቀው ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 129921 በ20/05/2005 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97464

ሰኔ 04 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘይነብ ጀማል አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1.የቦሌ ክፍለ ከተማ የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ጽ/ቤት አልቀረበም

2. አብዱልወሃብ መሐመድ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኗ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኖቹ ተጠሪዎች ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ከሳሽ ነሐሴ 12 ቀን 2004 ዓ/ም ያቀረቡት ክስ፡- በብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ መጋቢት 19 ቀን 1993 ዓ/ም በወጣው 10ኛ ዙር የመኖሪያ ቤት የሊዝ ዕጣ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 አስተዳደር ክልል ውስጥ የመለያ ቁጥሩ BKB-17-B56 የሆነ 160 ካሬ ሜትር ቦታ ደርሶኝ ጥቅምት 17 ቀን 1995 ዓ/ም ለ99 ዓመት የሚቆይ የሊዝ ውል ፈጽሜ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠኝ ሲሆን በቦታው ብር 90,000.00 የሚያወጣ ግንባታ በማከናወን የፕላን ስምምነት እንዲሰጠኝ ለ1ኛ ተከሳሽ ሳመለክት የ1ኛ ተከሳሽ ባለሙያ የሆኑት 2ኛ ተከሳሽ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታዬን እና ሌሎች ሰነዶቼን (ዶክመንቶቼን) ከተቀበሉኝ በኋላ የከለከሉኝ በመሆኑ ተከሳሾቹ የፈጠሩት ሁከት ተወግዶ የተቀበሉትን የቦታውን ካርታ እና ሰነዶቹን እንዲመልሱ፣የግንባታ ማከናወኛ ፈቃድም 1ኛ ተከሳሽ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም፡-ከሳሽ ያቀረቡትን ክስ ከመረመረ በኋላ በሰጠው ትዕዛዝ የከሳሽ ጥያቄ ይዞታን የሚመለከት ሳይሆን በ2ኛ ተከሳሽ የተወሰዱባቸው ሰነዶች እንዲመለሱላቸው እንዲወሰን የሚል በመሆኑ ጥያቄያቸው በአስተዳደሩ በኩል ደረጃውን ጠብቆ መፍትሔ የሚያገኝ እንጂ በሁከት ይወገድልኝ ቀርቦ በፍርድ ቤት እልባት የሚያገኝ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተቀብሎ አከራክሮ ለመወሰን ሥልጣን የለውም ሲል የክሱን መዝገብ ዘግቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሳሽም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት በማለናበቱ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸውም በዋናነት የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብ፡- 1ኛ ተጠሪ የፕላን ስምምነት እንዲሰጠኝ በሚል ባቀረብኩት አቤቱታ መነሻ በእጄ የሚገኙትን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እና ሌሎች ሰነዶችን 2ኛ ተጠሪ ነጥቀውኝ ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አመልካችም በመሥሪያ ቤት ውስጥ በጉልበት ከ2ኛ ተጠሪ ለመቀበል ስለማልችል ያለኝ አማራጭ በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ማስወሰን ሆኖ ሳለ የሥር ፍርድ ቤቶች የሁከት ተግባር በመሬት ይዞታ ብቻ እንደሚፈጸም በመቁጠር ተጠሪዎቹ የፈጸሙት ሰነዶችን የመንጠቅ ተግባር በሁከት እንደማይጠቃለል በመቁጠር ሥልጣን የለንም ሲሉ ክሴን ውድቅ ያደረጉት ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ባለመስጠታቸው መልስ የመስጠት መብታቸው የታለፈ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት የባለይዞታነት መብት በሌላቸው ጉዳይ ላይ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣በሌላ በኩል የባለይዞታነት መብት ለማረጋገጥ የሚቻለው ለዚሁ ሲባል ከሚመለከተው መንግስት አካል በህጋዊ መንገድ የተሰጠ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በማቅረብ ሲሆን ከዚህ ውጪ የሚቀርቡ ሰነዶችን በተመለከተ ግን በመመርመር መፍትሔ ሊሰጥ የሚችለው የአስተዳደሩ መስሪያ ቤት እንጂ ፍርድ ቤት ባለመሆኑ እና ጉዳዩ በፍርድ ቤት ይታያል ቢባል የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ካርታ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ውሳኔ ስለሚሆን የሥር ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የለንም ሲሉ የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረጉት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ብሏል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለሰጠው መልስ አመልካችም የበኩላቸውን የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

- አመልካች ያቀረቡት ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ ሊወሰን የሚችል ነው ? ወይስ አይደለም?
- ጉዳዩ በፍርድ ቤት ቀርቦ ሊወሰን የሚችል ነው ቢባል የሥር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ተቀብለው ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን አላቸው ? ወይስ የላቸውም ?

የሚሉትን ጭብጦች ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1) ማንኛውም ሰው (የተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ያለው ድርጅት) በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ (justiciable matter) ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ ከመደንገጉም በተጨማሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 4 በቀጥታ ወይም በግልጽ ካልታገዱ በስተቀር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍትሃብሔር ጉዳዮች ለመደበኛው ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ስለመሆናቸው ተመልክቷል። ሆኖም በቀጥታ ወይም በግልጽ በወጡ ወይም በሚወጡ ህጎች ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጪ በህግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ተለይቶ የተሰጣቸውን ፍትሃብሔር ጉዳዮች ተቀብለው የመወሰን ሥልጣን ይኖራቸዋል።

በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረትም አንድ ጉዳይ በፍርድ ቤት ወይም በሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል ተቀብሎ አከራክሮ ውሳኔ ወይም ፍርድ ሊሰጥ የሚችለው ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በክሳቸው የፕላን ስምምነት እንዲሰጣቸው በሚል በእጃቸው የነበረውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እና የተለያዩ ሰነዶችን (ዶክመንቶችን) ከጻፉት አቤቱታ ጋር በማያያዝ የ1ኛ ተጠሪ ሠራተኛ ለሆኑት 2ኛ ተጠሪ መስጠታቸውን 2ኛ ተጠሪም ካርታውን እና ሌሎች ሰነዶችን ከተቀበሉ በኋላ ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመጥቀስ እንዲመለስላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን ክክሱ መገንዘብ የተቻለ ሲሆን ተጠሪዎችም ይዞታ ማረጋገጫ ካርታውን እና ሌሎች ሰነዶችን ከአመልካቿ የተቀበሉ መሆን አለመሆናቸውን፤ከተቀበሉ ደግሞ ለመመለስ እንቢተኛ የሆኑበት ህጋዊ ምክንያት ካላቸው ማስረዳት የሚጠበቅባቸው ሲሆን ይህ ደግሞ ውሳኔ ሊያገኝ የሚችለው ለመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦ እንጂ ፍርድ ቤቶቹ በሰጡት ትዕዛዝ እንዳሰፈሩት በአስተዳደር መስሪያ ቤቱ አይደለም። በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ከይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ከሰነዶች ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብቻ ተጠሪዎቹ ካርታውን እና ሠነዶቹን ወስደው ከሆነ የወሰዱበት አግባብ ህጋዊ መሆን አለመሆኑ በፍርድ ቤት ሊጣራ የሚችል ጉዳይ ሆኖ ባለበት ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚችል አይደለም ሲሉ መደበኛ ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን እንደሌለው በመቁጠር በሰጡት ትዕዛዝ ላይ ያሰፈሩት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው።

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች በክሳቸው የመሬት ይዞታውን ያገኙት በወጣው የሊዝ ጨረታ በመሳተፍ ዕጣው ደርሷቸው መሆኑን፤ በዚሁ የመሬት ይዞታ ላይ የሊዝ ውል መግባታቸውን የገለጹ ሲሆን ይህ ችሎትም በሰበር መ/ቁ/ 77175 ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ፍርድ የሊዝ ውሎች አስተዳደራዊ ውሎች ተብለው እንደሚወሰዱና በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(መ) የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ወይም የከተማው አስተዳደር በባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸውን አስተዳደራዊ ውሎች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮችን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል። በመሆኑም ጉዳዩን በየደረጃው ያዩት የሥር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አመልካች ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ በህጉ ለመዳኘት ከተሰጣቸው የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን ውጪ ሆኖ ሳለ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/9(1)፤ 231(1)(ለ) መሰረት የክስ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በሚል መመለስ ሲገባቸው ተቀብለው መመርመራቸው ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ድንጋጌዎች እና ይህ ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በስበር መዝገብ ቁጥር 77175 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ፍርድ ቤቶቹ የአመልካችን የክስ አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 198320 በቀን 28/09/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/140656 በቀን 10/03/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ ምክንያቱን ሳንቀበል በውጤት ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ ሊወሰን የሚችል ነው ብለናል፡፡
3. የሥር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡትን ክስ ተቀብለው የመረመሩት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን በሌላቸው ጉዳይ በመሆኑ ተገቢነት የሌለው ቢሆንም የክስ አቤቱታውን ውድቅ ማድረጋቸው በውጤት ደረጃ ሲታይ የሚነቀፍበት ምክንያት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡
4. ይህ ውሳኔ መብቱን የሚጠይቅ ወገን ሥልጣን ላለው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሊያቀርብ የሚችለውን ክስ የሚያግድ አይሆንም ብለናል፡፡
5. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ታ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92290

ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሪት ጦቢያው መኮንን -ጠበቃ ዘውዴ ሚናስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ እርቁ ጎዳ -ጠበቃ ውቤ ጓዴ ቀረቡ

2. አቶ የኔአየሁ ተስፋዬ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍርድ ቤት እግድ የሠጠበት የማይንቀሳቀስ ንብረት እግዱ ተጥሶ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት በተደረገ ሽያጭ ውል መብት በሌላቸው ሰዎች ለሶስተኛ ወገን ንብረቱ ተላልፎ ሲገኝ ያለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻና ይዘትም የሚከተለው ነው፡፡

የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ 2ኛ ተጠሪ ወርቅ ያልሆነውን እቃ ወርቅ ነው በማለት በተቀነባበረ የማታለል ዘዴ ብር 700,000.00 (ሰባት መቶ ሺህ) ተወስዶባቸው ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ መስርተው ይህንኑ ብር 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍላቸው ተወስኖላቸው ይህንኑ ገንዘብ ለማስከፈል በኮ/መ/ቁጥር 124978 በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደፍርዱ እንዲፈፅምላቸው የአፈጻጸም ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ አቅርበው አሁን ለክርክሩ መሰረት በሆነውና በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ክልል ውስጥ በሚገኘውና ቁጥሩ 711/3 በሆነው ቤት ላይ ሐራጅ ወጥቶ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ባቀረቡት ማመልከቻ መሰረት ፍርድ ቤቱ እግድ ተሰጥቶበት የነበረ መሆኑን ተገንዝቦ የሐራጅ ማስታወቂያውን አውጥቶ አፈጻጸሙን በመምራት ላይ እንዳለ የአሁኗ አመልካች ቤቱን ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ከእግድ ትዕዛዙ በፊት የገዛሁት ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት ሐራጁን ለማስቆም የተቃውሞ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ በቀረበው የአመልካች አቤቱታ ላይ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡

የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስም፡-የተቃውሞ ምክንያትና ለአፈጻጸሙ መሰረት የሆነው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 711/3 የሆነውን መኖሪያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ከአቶ ፍቅረስላሴ አየለ የገዙትና ስመ ሀብቱንም ለማዞር እንቅስቃሴ ላይ የነበሩና 2ኛ ተጠሪም ቤቱ የባለቤታቸው መሆኑን በፍርድ ቤት ችሎት ፊት ገልጸው እግድ የተሰጠበትና ለሚመለከታቸው አካላትም እግዱ የተላለፈ ሁኖ እያለ የወ/ሮ ማስተዋል መኮንን እህት የሆኑት የአሁኗ አመልካች ቤቱን ገዝቻለሁ በማለት ጥያቄ ማቅረባቸው አፈጻፀሙን ለማሰናከል ነው በሚል የአመልካችን አቤቱታ ተቃውመዋል፡፡2ኛ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ከእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ ባገኙት ውክልና መሰረት ለአሁኗ አመልካች በውልና ማስረጃ የሸጡ መሆናቸውን ስለማመናቸው የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች ቤቱን ገዛሁ የሚሉት በቤቱ ላይ በሽያጭ ምክንያት መብት ቀሪ የሆነባቸው ሰዎች ውክልና ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ሰጥተው በመሆኑና ይህ ደግሞ ሕጋዊ ጥበቃ የማይደረግለትና ጥያቄው በአጠቃላይ ከቅን ልቦና ውጪ የቀረበ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቧል በሚል ምክንያት የሀራጅ መቃወሚያ አቤቱታውን ውድቅ አድርጎ ቤቱ ለ2ኛ ተጠሪ እዳ ማስፈጸሚያነት ሊሆን ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበውም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች መቃወሚያ የቤተሰቦቻቸውን ጥቅም ለመከላከል የቀረበ እንጂ ሕጋዊ ገዥ ሁነው በቤቱ ላይ ያቋቋሙትን መብት ለመከላከል የቀረበ አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 22 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች 1ኛ ተጠሪ እግዱ እንዲነሳ በመ/ቁጥር 99833 በሆነው ተሰማምተው እግዱ በተነሳበት ሁኔታ እና በሕግ አግባብ የገዙት መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በማስረጃ ባልተደገፈ ምክንያትና ከዳኝነት አካሄድ ውጪ ተቃውሞው የቤተሰብን ጥቅም ለመከላከል የቀረበ ነው ተብሎ በግምት ተቀባይነት ማጣቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአከራካሪው ቤት ላይ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ እና የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ/ም የሽያጭ ውል ማድረጋቸውና በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ እና እነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ መካከል በመ/ቁጥር 99833 በተሰጠው ዋና ክርክር በመ/ቁጥር 118241 በነበረው የብር 840,000.00 የፍርድ አፈጻጸም ክርክር ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥና ለእዳው መክፈያ እንዲውል ታገዘ፡ ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ይህንኑ በመቃወም ቤቱን ከሽያጭ ለማዳን ሲባል ቀደም ሲል ከገዙበት ብር 880,000.00 (ስምንት መቶ ሰማንያ ሺህ) ብር 240,000.00(ሁለት መቶ አርባ ሺህ) በመጨመር ሰኔ 14 ቀን 2004 ዓ/ም ተጨማሪ የቤት ሽያጭ ውል ማድረጋቸው በውል ሰነዶች መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት መቀበሉን፣ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ/ም ደግሞ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ በሆኑበት መዝገብ ላይ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሁነው በጠበቃቸው አማካኝነት 2ኛ ተጠሪ ያላቸውን ንብረት በቃላ መሃላ ስር ሁነው እንዲገልጹላቸው አፈፃጸሙን ለያዘው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልክተው 2ኛ ተጠሪ ባለቤቱ ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ከአቶ ፍቅረስላሴ አየለ የገዙት በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ የሚገኝና ቁጥሩ 711/3 የሆነ ቤት መኖሩን በመግለጻቸው ምክንያት የፍርድ ባለመብት ይኼው ቤት እንዲታገድላቸው ቃለ መሃላ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ/ም የእግድ ትዕዛዝ ማስተላለፉን፣ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ/ም ደግሞ ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ለእዳ መክፈያ እንዲውል ፍርድ ቤቱ ማዘዙን፣የአሁኗ አመልካች ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተፈረመና በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ በተመዘገበ የቤት የሽያጭ ውል የአቶ ፍቅረስላሴ አየለና የወ/ሮ ትብይን ታደሰ ወኪል ከሆኑት ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ገዝቼአለሁ በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ ላይ በመ/ቁጥር 99833 በሆነው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስፈርደው በነበሩት መዝገብ አከራካሪውን ቤት ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም አሳግደው የነበረ ሲሆን ይህ እግድ ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ/ም የተነሳው የአሁኑ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ማስተዋል ብር 600,000.00 (ስድስት መቶ ሺህ) ለእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ እዳ መክፈያነት እንዲሆንና ቤቱ እንዳይሸጥ ለማስቆም በአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 118241 መክፈላቸውና ሰኔ 14 ቀን 2004 ዓ/ም መመዝገቡ መረጋገጡን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99833 ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ/ም ከመዘገበው ላይ ዋናውን መዝገብ በመመልከት ተረድተናል፡፡

በመሰረቱ በፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ የሚሰጠው በክርክሩ ሂደት ረቺ የሚሆነው ወገን ለፍርድ አፈጻጸም ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲያስችለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ደግሞ ሊከበር የሚገባ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ፍርድ ደግሞ ሊፈጸም የሚገባው በፍርድ ባለእዳውና በሕግ አግባብ እንዳይያዙ ከሚጠቀሱት ንብረቶች/መብቶች ውጪ ባሉት የፍርድ ባለእዳ ንብረቶች/መብቶች ስለመሆኑ በቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ከተመለከቱት የፍትሐ ብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡አንድ ሰው በሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብ ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ የሚችለው መብትም በሕግ አግባብ ገደብ ያልተደረገበትንና ያለውን መሆኑ እሙን ነው።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በቤቱ ላይ ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ/ም በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ስምምነት ጭምር የተነሳ ቢሆንም እኚህ ተጠሪ ባሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ ባስከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ ንብረት ሊያፈላልጉ ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ/ም በጠበቃቸው አማካኝነት አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ በመሃላ ስር ሁነው ንብረቶቻቸውን እንዲያሳውቁ ጠይቀው ተጠሪው አከራካሪውን ቤት ባለቤታቸው የገዙት መሆኑን በማረጋገጣቸው ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በቤቱ ላይ ፍርድ ቤቱ የእግድ ትዕዛዝ አስተላልፏል።አመልካች ቤቱን ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ገዛሁ የሚሉት በዚሁ ቀን ሲሆን ለውልና ማስረጃ የሀምሌ 04 ቀን 2004 ዓ/ም እግድ ይደርሳል ተብሎ የሚታሰብበት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ አይደለም።ይህ መሆኑ ግን አመልካች አለኝ የሚሉትን ግዥ ሕጋዊ ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም።ሽያጩ ሲከናወን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለቤት የቤቱ ሕጋዊ ባለሃብት ሲሆኑ በዚሁ ሰፊው መብታቸው ደግሞ በሕግ ያልተገደቡ መብቶቻቸውን መጠቀም የሚችሉ እኚህ ሰው ሴት ስለመሆናቸው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1204፣1184 እና 1185 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊቆጠር እንደሚገባ የተመለከተ ቢሆንም ወ/ሮ ማስተዋል ቤቱን ከእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ የገዙት መሆኑን በመግለጽ በፍርድ ቤት ቀርበው የቤቱ ስመ ሃብት የተመዘገበላቸው እነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለም የወ/ሮ ማስተዋልን ሕጋዊ ገዥ መሆናቸውን ፍርድ ቤት ፊት ቀርበው የተቀበሉ በመሆኑ የቤቱ ስመ ሃብት በወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ያለመገኘቱ በቤቱ ላይ ህጋዊ መብት የላቸውም ለማለት የሚያስችል አይደለም። በመሆኑም የቤቱ ሕጋዊ ባለሃብት ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ሁነው እያለ እነ አቶ ፍቅረስላሴ ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲሸጡ ውክልና መስጠታቸው በሌላቸው መብት ላይ በመሆኑ በሕግ ፊት ዋጋ የሚሰጠው አይደለም።2ኛ ተጠሪ በእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ ወኪልነታቸው በሕግ አግባብ ሊያስተላለፉ የሚችሉት ለሰዎቹ ሕግ ጥበቃ ሊያደርግላቸው የሚችለውን መብት ብቻ ነው።አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ ያልተደረገለትን መብት ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ መብት የለውምና።በዚህ መንገድ መብቱ የተላለፈለት ሰውም በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት አይገባም።

ሌላው አመልካች ሽያጩ ሕጋዊ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ውሉ ሕግ ስልጣን በሰጠው አካል ፊት የተረጋገጠ ነው በሚል ነው።በእርግጥ ውልና ማስረጃ በዚህ ረገድ ሕጉ ስልጣን የሰጠው አካል መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 334/1995 የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። በውልና ማስረጃ ጽ/ቤትም በሕግ የባለቤትነት መብት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸውን ንብረቶች ለማስተላለፍ የሚዘጋጁ ሰነዶች ከመዘጋጀታቸው በፊትም ሰነድ አረጋጋጩ ንብረቱ በመያዣነት ያልተሰጠ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም በፍርድ ቤት ያልታገደ መሆኑን ሊያረጋግጥ እንደሚገባ አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 15(2) ድንጋጌ በጎይለ ቃል አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ በመሆኑም አመልካች አከራካሪውን ቤት የገዙት በውልና ማስረጃ በተረጋገጠ ውል ቢሆንም የቤቱ ስመ ሃብት ከእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ ወደ ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ባለመዛወሩ ምክንያት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ከያዙት ግለሰብ ሽያጩን አግኝተዋል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የሌለ መሆኑን በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99833 እና 118241 የተሰጡ ትእዛዛት የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡

በአጠቃላይ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአከራካሪው ቤት ሕጋዊ ባለቤት የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን መሆናቸውንና እነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ ደግሞ በቤቱ ላይ የነበራቸውን መብት ለወ/ሮ ማስተዋል መኮንን በሽያጭ ማስተላለፋቸውን ፍርድ ቤት ቀርበው ከአረጋገጡ በኋላ ለወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ባለቤት ለሆኑት ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲሸጡ ውክልና መስጠት የማይችሉ ስለመሆናቸው በማረጋገጥ የሠጡት ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 124976 መጋቢት 09 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 88605 ሰኔ 27 ቀን 2005 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 711/3 የሆነውን መኖሪያ ቤት ላይ የአመልካች አይደለም ተብሎ አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ እንዲቀጥል መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች በሽያጩ ተግባር የደረሰባቸው ጉዳት ካለ የሚመለከተውን አካል በመክሰስ መብታቸውን ከማስከበር ይህ ውሣኔ አይገድብም ብለናል፡፡
4. ቁጥር 99833 የሆነው የስ/ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94837

ሚያዝያ 22 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ልዑል ዘወዴ - ጠበቃ አቶ ትዕዛዙ አበበ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አጀመራ የወርቅ ግብይት ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የዋስትና ግዴታ ውል ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ባአሁኑ አመልካችና የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ባልሆነውና የስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ገ/ኪዳን በርሄ በተባለ ግለሰብ ላይ በጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአኙዋሃ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አቤቱታ፡- የስር 1ኛ ተከሳሽ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በወርቅ ገዥነትና ተቆጣጣሪነት ሲሰራ በነበረበት ጊዜ ለወርቅ ግዥ ከማህበሩ ከወሰደው ገንዘብ ውስጥ ብር 57,406 አጉድሎ በመገኘቱ እና በዚህም ምክንያት ተከሳሹ ገንዘቡን ለማህበሩ ከከፈለ በኃላ ስራውን እንዲያቆም ተብሎ የነበር ቢሆንም ሆኖም ግን በመካከላቸው በቀን 25/12/2004 ዓ.ም በተደረገው ስምምነት መሰረት ተከሳሹ የጎደለውን ገንዘብ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለማህበሩ መልሶ ለመክፈልና ለወደ ፊቱም ስራውን በታማኝነት ለመስራት ተስማምተዋል፡፡ በተስማማው መሰረት ግዴታውን የማይወጣ ከሆነና በዚህ ምክንያት ለሚመጣው ኃላፊነትም የአሁኑ አመልካችን በዋስነት አቅረበዋል፡፡ ይህ እንዲህ ሆኖ ሳለ የስር ተከሳሹ አሁንም በድጋሚ ከማህበሩ ብር 80,000 በቀን 10/2/2005 ዓ.ም ከወሰደ በኋላ መጀመሪያ አጉድሎ ካልተከፈለው ጋር በድምሩ ብር 124,995 በገባው ግዴታ መሰረት ስላልከፈለ ይዜንኑ ገንዘብ ከዋሱ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሹም ቀረቦ በሰጠው መልስ፡- እዳው መኖሩን አምኖ ነገር ግን ከማህበሩ ያልተከፈለው ኮሚሽን ስላለ ሂሳቡ ተሰልቶ ከታወቀ በኃላ እዳው እንዲከፈል ይታዘዝልኝ የሚል ይዘት ያለው መከራከሪያ ማቅረቡን የውሳኔ ግልባጩ ያሳያል እንዲሁም የአሁኑ አመልካችም ቀረቦ በሰጠው መልስ፡- ለብር 57,406 ተራ የሆነ ዋስትና ግዴታ መግባቱን አምኖ ሆኖም ግን ዋና ባለ እዳ እያለ ለዚህም ቢሆን ልጠየቅ እንደማይገባና ለብር 80,000 ደግሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመጀመሪያውም የዋስትና ግዴታ አለመግባቱን ጠቅሶ መከራከሩን የስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአጉዋሃ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች ክርክር ከሰማ በኃላ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1776 በዋቢነት ጠቅሶ ሁለቱም የስር ተከሳሾች በተጠሪ ጥያቄ መሰረት ገንዘቡን ይክፈሉ በማለት ወስኖባቸዋል፡፡ በስር ተከሳሾች አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች አስቀርቦ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ ቀጥሎም በአሁን አመልካች የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ የተመለከተው የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ አቤቱታውን መርምሮ የሰበር ቅሬታው ለሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አሁን በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን የሰበር ቅሬታውም በዋናነት አመልካች የዋስትና ግዴታውን የፈረመው ለብር 57,406 እዳ ብቻ ሆኖ ሣለ የስር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1922 ድንጋጌን በሚጥስ መልኩ የዋስትና ግዴታ ከተገባበት እዳ መጠን በላይ ለሆነ ገንዘብና ለብር 124,995 አመልካችን ተጠያቂ ማድረጋቸው ተገቢ ካለመሆኑም በላይ አመልካች የገባው የዋስትና ግዴታ አይነትም ተራ ዋስትና ከመሆኑም አኳያ ዋናው ባለእዳ እዳውን መክፈል የማይችል መሆኑ ሣይረጋገጥ አመልካች ዋስትና የተገባበትን ገንዘብ እንዲከፍል በስር ፍ/ቤቶች መወሰኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1934 ድንጋጌ አኳያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ስህተቱ ታርሞ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች የዋስትና ግዴታ ከገባው ብር 57,406 በተጨማሪ ዋናው ባለእዳ ከዋስትና ውሉ በኋላ ላገዳለው ገንዘብ ብር 80,000 ኃላፊ ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1922 እና 1924/1/ ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጉ ተጠሪም ቀርቦ በቀረበው አቤቱታ ላይ በጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል መሠረታዊ ይዘቱም በአመልካች አስቀድሞ የተገባው የዋስትና ግዴታ ዋናው ባለእዳ በኃላ ላይ ላገዳላው ብር 80,000 ጭምር በፍ/ብ/ህ/ቁ.1925(1) ድንጋጌ መሠረት በዋሱ ላይ ኃላፊነትን የሚያስከትል በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጉ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጠረ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡አመልካችም በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመ/መልሱን ሰጥቶበታል ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሠረቱ የዋስትና ግዴታ ግልፅ መሆን እንዳለበት እና ኃላፊነቱም ግዴታ ከተገባለት እዳ ወሰን ለማለፍ እንደማይችል እና እንዲሁም ይህ ለአፈፃፀሙ ግዴታ የተገባለት የእዳ መጠን ወይም የገንዘብ ልክ በዋስትና ውሉ ካልተገለፀ ዋስትናው ፈራሽ እንደሚሆን ከፍ/ብ/ህ/ቁ1922(2)(3) ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ደግሞ ዋናው ባለእዳ የሆኑት አቶ ገ/ኪዳን በርሔ ያጉደሉትን ገንዘብ ብር 57,406 በተቀመጠው ቀን ገደብ መሠረት ለተጠሪ ካልከፈሉ የአሁኑ አመልካች ተያዥ ወይም ዋስ ሆኖ ገንዘቡን ለተጠሪ ለመክፈል በመስማማት የዋስን ግዴታ በቀን 25/12/2004 ዓ.ም በተፃፈ ውል መግባቱን ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል ፡፡

ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በገባው ዋስትና ውል (በ25/12/2004 ዓ/ም በተፈረመው ሰነድ) ላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ብር 57,406 ብቻ መሆኑን እንጂ ከዚህ ውጭ ዋስትና የተገባለት ሌላ የገንዘብ መጠን በዋስትና ውሉ ላይ አልተገለፀም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በግልፅ ለተጠቀሰው ገንዘብ ብር 57,406 ብቻ ካልሆነ ከዚህ ውጭ በዋስትና ውሉ ላይ ላልተመለከተው እና በኋላ ላይ ዋናው ባለዕዳ ከተጠሪ ማህበር በቀን 10/2/2005 ዓ/ም ወስዶ አጉድሏል ለተባለው ብር 80,000 አመልካች በዋስትና ውሉ መሰረት በኃላፊነት ሊጠየቅ እንደማይችል ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1922 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በእርግጥ ገና ለወደፊት ሊደርስ ለሚችል ግዴታ አፈፃፀምም ዋስ ለመሆን እንደሚቻል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1925(1) ስር የተመለከተ ቢሆንም እንኳ ይህም ከዋስትና ውል ፎርም ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1922 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን መስፈርት ሊያሟላ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ለወደፊቱ ለሚመጣ ግዴታም ለሚገባ የዋስትና ውል ለምን ያህል እዳ መጠን ወይም ገንዘብ ልክ እንደተገባ በውሉ ካልተገለፀ ዋሱንም ያለአግባብ ሊጎዳ የሚችል ከመሆኑም በላይ ይህ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1925(1) ድንጋጌም ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1922(3) ድንጋጌ ጋር በተጣጣመ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ በአመልካች የተፈረመው የዋስትና ውል ከብር 57,406 በስተቀር ገና ወደፊት ዋናው ባለእዳ ሊያጉድል የሚችለውን እዳንም ጭምር ሊያካትት ይችላል ቢባልም እንኳን ለምን ያህል እዳ መጠን ወይም የገንዘብ ልክ እንደሆነ በውሉ ስላልተገለፀ ተጠሪ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1925(1) ድንጋጌን በምክንያትነት ጠቅሶ ያቀረበው ክርክር ከዚህ በላይ በተገለፀው ምክንያት ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘንም በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አመልካችን በዋስትና ውሉ ላይ ከተገለፀው የገንዘብ መጠን ብር 57,406 ወሰን በማለፍ ኃላፊ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1922 ድንጋጌ ይዘት አኳያ ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ግን አመልካች ዋናው ባለ እዳ እዳውን መክፈል የማይችል መሆኑ ሳይረጋገጥ በእኔ ላይ በስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1934 ድንጋጌን ያገናዘበ አይደለም በማለት ያቀረበውን ቅሬታ በተመለከተ ይህ ክርክር እንደ አግባብነቱ በአፈፃፀም ጊዜ የሚታይ ከመሆኑም በላይ አመልካችም ባለገንዘቡ አስቀድሞ የዋናውን ባለእዳ ንብረት ለማፈላለግ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በእሱ ላይ ክርክሩን ለመቀጠል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1936(1) ስር እንደተመለከተው የሚያስፈልገውን ወጭ አስቀድሞ ለባለገንዘቡ መስጠቱ ባልተገለፀበት ሁኔታ ክርክሩ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአኙዋሃ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 0068/2005 በቀን 14/10/05 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 01482/05 በ17/11/05 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ እና እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 00300/05 በ6/2/06 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በገባው ዋስትና ግዴታ መሠረት ሊጠየቅ የሚገባው ለብር 57,406 (ሃምሳ ሰባት ሺህ አራት መቶ ስድስት ብር) ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡ አመልካች ከዚህ በላይ ላለው የዋናው ባለዕዳ ዕዳ በኃላፊነት ሊጠየቅ አይችልም ብለናል፡፡
3. አመልካች የገባው የዋስትና ግዴታ ዓይነት ተራ ዋስትና በመሆኑ አመልካች ይዜንን የተጠቀሰውን ገንዘብ (57,406) ብር ለመክፈል የሚገደደው ዋናው ባለዕዳ መክፈል ካልቻለ ብቻ ነው ብለናል፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- በዚህ መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረውን የአፈፃፀም እግድ ተነስቷል፡፡ መነሳቱም ተገልፆ አፈፃፀሙን ለያዘው ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡
- የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሻሻሉን እንዲያውቁ የውሳኔ ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98079

ሰኔ 18 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-የቀይ አፈር ገዳሞች አቶ ማሙዮ አበራፍ ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ኤርሚያስ ገሠሠ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ለተጠሪ በውርስ የተላለፈ ነው የተባለን እና በአመልካች አላግባብ የተያዘ ነው የተባለን ይዞታ በፍርድ ኃይል ለማስመለስ ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በራሳቸው እና በሁለት ሕጻናት ወንድሞቻቸው ስም በአሁኑ አመልካች ላይ በደቡብ ወሎ ዞን በጀማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሳቸውም ይዘት ባጭሩ፡- ከከሳሽ ወላጆች በውርስ ሊተላለፍላቸው የሚገባውን 600 ካ.ሜ የቦታ ይዞታ በላዩ ላይ ካለው የሳር ቤት እና የባህር ዛፍ አትክልት ጋር ተከሳሽ አላግባብ ይዞ እንደሚገኝ የሚገልጽ ሆኖ ይኸው ንብረት እንዲመለስላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ በበኩሉ ከይርጋ መቃወሚያ በተጨማሪ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ክስ ያስነሳውን ይዞታ የያዘው ከሳሽ እንደሚሉት በሕገወጥ መንገድ ሳይሆን የከሳሽ ወላጆች የወሰዱትን የብድር ገንዘብ መመለስ ባለመቻላቸው ክስ ያስነሳውን ይዞታ ከባህርዛፉ እና ሳር ቤቱ ጋር በሽያጭ ውል ለተከሳሽ በማስተላለፋቸው ምክንያት መሆኑን፣ተከሳሽ ሳር ቤቱን በቆርቆሮ ለውጦ ይዞታውንም ወደ ራሱ አዛውሮ በመጠቀም ላይ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ መከራከሩን እና ፍ/ቤቱ የተከሳሽን የይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ መዝገቡን በብይን ዘግቶ የነበረ ቢሆንም ብይኑ በከ/ፍ/ቤት ተሽሮ በፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ የተመለሰለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩ በተመለሰለት መሰረት በከሳሽ ወላጆች እና በተከሳሽ መካከል የተደረገው ውል ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም? ሟቾች ለአውራሾች የሚያስተላልፉት መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚሉ ጭብጦችን መሰረት አድርጎ የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ ከሳሽ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ዘንድ የተደረገ እስካልሆነ ድረስ ሕጋዊ አይደለም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከራከሩ ቢሆንም የከሳሽ ወላጆች ብድሩን ለመክፈል ባለመቻላቸው ክስ ያስነሳውን ይዞታ በ1985 ዓ.ም በተደረገ እና በደጎሎ ከተማ በቀበሌ 01 አስተዳደር በተመዘገበ ውል ለተከሳሽ ያስተላለፉ እና ተከሳሽም ይዞታውን ተረክቦ ይዞ የሚገኘው ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ መሆኑ፣ የከተማው መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮም የይዞታው ሕጋዊ ባለቤት ተከሳሽ መሆኑ ታውቆግብሩን በስሙ መክፈል የጀመረ መሆኑ፣ ውሉ በተደረገበት ጊዜ በደጎሎ ከተማ ውስጥ ማዘጋጃ ቤትም ሆነ ውል የሚያዋውል ሌላ አካል ያልነበረ መሆኑ፣ ተዋዋዮቹም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ውሉን በቀበሌው አስተዳደር ለማስመዝገብ ስለመስማማታቸው በውሉ ላይ ገልጸው የተስማሙ መሆኑ፣ የከሳሽ ወላጆችም ይህንኑ አውቀው በሞት እስከተለዩበት 1995 ዓ.ም ድረስ በዚህ ይዞታ ላይ ያቀረቡት የይገባኛል ጥያቄ አለመኖሩ፣ ማዘጋጃ ቤቱ በአዲስ መልክ በተደራጀበት በ1997 ዓ.ም ከሳሽ በይዞታው ላይ ግብር መክፈል ጀምሬአለሁ በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ግብሩ የተከፈለው ለአከራካሪው ይዞታ መሆኑን የግብር ሰነዱ የማያመለክት መሆኑ በክርክሩ መረጋገጡን በዝርዝር በመግለጽ ለከሳሾች በውርስ የሚተላለፍላቸው ንብረት የለም ሲል ክሱን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

የደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በተጠሪ የቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ ያሰናበተ ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ውሉ በስር ከሳሽ የተካደ መሆኑን፣የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ውል ለማዋዋል በሕግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም አለመሆኑን፣ውሉ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት በመሆኑ በፍ.ሕ.ቁ. 1723 በተመለከው መሰረት ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ የተደረገ ስላልሆነ እንደረቂቅ የሚቆጠር መሆኑን፣በ15/02/1985 ዓ.ም ተደረገ የተባለው ውል ረቂቅ ብቻ ነው የሚባል ከሆነ ደግሞ ግራ ቀኙ በፍ.ሕ.ቁ.1815 መሰረት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ መደረግ የሚገባው መሆኑን በዝርዝር ገልጾ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የስር ከሳሽ በ15/02/1985 ዓ.ም. ተደረገ በተባለው ውል ላይ መጠኑ የተመለከተውን ገንዘብ ብር 3,500 (ሶስት ሺህ አምስት መቶ) ለተከሳሽ እንዲመልሱ እና በአንፃሩ ተከሳሽም ይዞታውን ለከሳሽ እንዲመልስ እንዲሁም ቦታውን ለማልማት ያወጣውን ወጪ ክስ መስርቶ እንዲጠይቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታና ንብረት ከተጠሪ ወላጆች በ1985 ዓ.ም በውል ተረክቦ እና በስሙ አዛውሮ ሲጠቀምበት የነበረ መሆኑ እና የተጠሪ አውራሾችም ይህንኑ ተቀብለው በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ያቀረቡት ጥያቄ አለመኖሩ በተረጋገጠበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ችሎት ውሉ አልተመዘገበም በሚል አውራሾች አሳልፈው የሰጡት መብት ለወራሾች ሊተላለፍ ይገባል በማለት የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የተጠሪ ወላጆች ከአመልካች በብድር የወሰዱትን ገንዘብ መመለስ ባለመቻላቸው ከአመልካች ጋር በ15/02/1985 ዓ.ም በተደረገ ውል ክስ ያስነሳውን ይዞታ በሽያጭ ለአመልካች ማሳተላለፋቸው እና ማስረከባቸው፣ውሉም ግራ ቀኙ በተስማሙበት መሰረት በቀበሌው ጽ/ቤት ተመዝግቦ እንዲቀመጥ ማድረጋቸው፣ ይህንን ያደረጉትም ማዘጋጃ ቤትም ሆነ ውል የሚያዋውል ተቋም በወቅቱ በከተማው ውስጥ ስላልነበረ መሆኑ፣ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይዞታው የሚገኘው በአመልካች እጅ መሆኑ እና የተጠሪ ወላጆች በሕይወት እስከነበሩበት 1995 ዓ.ም ድረስ በውል ባስረከቡት ይዞታ ላይ ያነሱት የይገባኛል ጥያቄ አለመኖሩ በክርክሩ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ ተጠሪ ክስ ያቀረቡትም ክስ ያስነሳውን ይዞታ አመልካች አላግባብ ይዞ እንደሚገኝ በመግለጽ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ክስ ያስነሳውን ይዞታ አመልካች አንድም ጊዜ እንዳልያዘ እና በቁጥጥሩ ስር እንዳላደረገ በመግለጽ ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ያቀረቡት የክርክር ነጥብ የስር ክሳቸውን እና በመዝገቡ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የክልሉ ሰበር ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ለመሻር የቻለበት ዓቢይ ምክንያት የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ውል ለማዋዋል በሕግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም አይደለም የሚል ነው፡፡እንደተባለው የማይንቀሳቀስ ንብረትን ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎች በጽሁፍ እና በፍርድ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት መደረግ ያለባቸው ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) የተመለከተ ሲሆን የቀበሌ አስተዳደርም ውል ለማዋዋል በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል አለመሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሰረቱ የፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) ድንጋጌ ዓይነተኛ ዓላማ ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ያደረጉት በነፃ ፈቃዳቸው መሆኑን፣ ሻጩ በሚያስተላልፈው ንብረት ላይ ለማስተላለፍ የሚያስችል ሙሉ መብት ያለው መሆኑን እና መሰል የውል አደራረግ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በሕጉ የተመለከተውን ፎርም እና ስርዓት አሟልቶ የተደረገ ከመሆን በተጨማሪ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ መፃፍ (መግባት) ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1568(ሀ)፣ 2878 እና በሌሎችም ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ውሉ በተደረገበት ጊዜ እና ቦታ ውሎችን ለማዋዋል የሚችል የመንግስት ተቋምም ሆነ የተደራጀ የርስት መዝገብ ያልነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተዋዋይ ወገኖችም ይህንኑ ተገንዝበው ውላቸውን በወቅቱ ውሎችን ተቀብሎ ይመዘግብ ለነበረው የቀበሌ አስተዳደር በማቅረብ አስመዝግበዋል፡፡ የተጠሪ ወላጆችም በፍ/ሕ/ቁ. 2879 መሰረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ፈጽመዋል፡፡ አመልካችም ከሽያጩ ጊዜ ጀምሮ ንብረቱን በመረከብና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማልማት ላለፉት 18 ዓመታት ሲጠቀምበት ቆይቷል፡፡ የተጠሪ ወላጆች በዚህ ሁኔታ ውሉን ካደረጉበትና ንብረቱን ካስረከቡበት ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ በሞት እስከተለዩበት 1995 ዓ.ም ድረስ ባሉት አስር ዓመታት ውሉንም ሆነ ንብረቱን አስመልክቶ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳያቀርቡ የቀሩት ንብረታቸውን ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በሽያጭ ማስተላለፋቸውን በመቀበል ነው፡፡ በመሰረቱ መንግስት ባለበት ኃላፊነት መሰረት የርስት መዝገብ እንዲደራጅ ባላደረገበት ጊዜ እና ቦታ በተዋዋይ ወገኖች እና በአካባቢው ባሉ የመንግስት (የቀበሌ) አስተዳደር አካላት የሚፈጸሙ የዚህ ዓይነቶቹ ልማዳዊ አሰራሮች ሕጋዊ መሰረት የላቸውም ለማለት የሚቻልበት አግባብ አለመኖሩን ከፍ/ሕ/ቁ.3364 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት የቀበሌ አስተዳደር ውል ለማዋዋል በሕግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም አይደለም የሚለውን ነጥብ ብቻ ነጥሎ በመውሰድ ውሉ ረቂቅ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው በአግባቡ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሉ ረቂቅ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ በጅማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 90/2003 በ07/02/2004 ዓ.ም.ተሰጥቶ በደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 7588 በ16/02/2004 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናውን ውሳኔ በመሻር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 26285 በ03/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/.ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ በጅማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 690/2003 በ07/02/2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.7588 በ16/02/2004 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ታ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94070

ሚያዝያ 22 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡-

1. አቶ ወልዱ ገ/አብዝጊ
2. አቶ ጉዕሽ ገ/ስላሴ ተስፋዬ
3. አቶ በላይ ገ/ስላሴ ተስፋዬ
4. አቶ ገ/ኪዳን ገ/ስላሴ ተስፋዬ
5. አቶ ብርሃን ገ/ስላሴ ተስፋዬ
6. ቂስ ገ/መድህን ተስፋዬ መረሳ

ጠበቃ አብርሃም ገ/ወልድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ዐ/ሕግ - ተወልደ በርሔ በ V.c.ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የአሁኖቹ አመልካቾች ክሱ በቀረበበት በትግራይ ብ/ክ/መንግስት ማዕከላዊ ዞን በአብይ ዓዲ ከ/ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተላቸው 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ ተከሳሽ የነበሩ ናቸው፡፡

ተጠሪ በ06/02/2005 ዓ.ም. አሻሽሎ ያቀረበባቸው ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ተከሳሾቹ በወ/ሕ/አ. 32(3) እና 539(1)(ሀ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በ15/09/2004 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ሲሆን በኦምበራ መጠቃ ንዑስ ወረዳ ልዩ ስሙ ሳልጎል በሚባል ቦታ በግፍ ሰው ለመግደል አስበውና አቅደው ከበታች መሬት በኩል ስራ በመስራት ላይ በነበሩት ሰዎች ላይ የድንጋይ ናዳ እያወረዱ ሲያደናቅፉ ከቆዩ በኃላ በጉዳዩ ላይ ለመግባባት ከታች በኩል የነበሩት ሰዎች መጥተው ሲያናግሯቸው ምን አመጣችሁ? በሚል ምክንያት ሟች ነጋሽ መኮንን ይባል የነበረውን ሰው 1ኛ ተከሳሽ በድንጋይ ጭንቅላቱን መትቶ ከመሬት ላይ ሲጥለው 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ጭንቅላቱን በተለያየ ቦታ ላይ በድንጋይ በመምታት ከሃያ ሜትር በላይ ርቀት ወዳለው ገደል በእጁ ገፍትሮ በመወርወር፣ቀሪዎቹ ተከሳሾች ደግሞ ሟችን ከጥቃት ለማስጣል የመጡትን ሰዎች በመከላከል 3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች ገላጋዮችን በድንጋይ ጭንቅላታቸውን በተለያዩ ቦታዎች እየፈነከቱ በማባረር፣6ኛ እና 7ኛ ተከሳሾች ደግሞ አባዲ ስዩም፣ብርሃነ አሰፋ እና ገዳሙ ገ/እግዚአብሔር የተባሉትን ሰዎች በድንጋይ በመምታት፣ልብሶቻቸውን በመጨምደድ እና እጆቻቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጠምዘዝ እንዳያገላግሉ በመከልከላቸው፤ሟችም በደረሰበት ጉዳት ምክንያት በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ በ25/09/2004 ዓ.ም. ሕይወቱ በማለፉ ተከሳሾቹ አባሪ ተባባሪ በመሆን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ አሰቃቂ የግድያ ወንጀል አድርገዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾቹ ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ተደርጎ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ወንጀሉን አላደረግንም በማለታቸው ተጠሪ አራት ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ፍ/ቤቱም የተጠሪን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተጠሪ እንደክሱ አቀራረብ ያስረዳ መሆኑን ገልጾ 2ኛ አመልካች በክሱ በተጠቀሰበት ድንጋጌ ስር፤ቀሪዎቹ አመልካቾች ደግሞ በወ/ሕ/አ. 32(3) እና 540 ስር እንዲከላከሉ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 142 መሰረት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ መሰረት አመልካቾቹ ድርጊቱን ያልፈጸሙ መሆናቸውን እና ሟች የወደቁት በራሳቸው መሆኑን ያስረዱልናል በማለት በድምሩ ስምንት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ሲሆን ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የመከላከያ ምስክሮቹ ድርጊቱ ከመፈጸሙ በፊት እና ከተፈጸመ በኋላ የነበረውን ሁኔታ ገልጸው ከመመስከራቸው በስተቀር ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ በቦታው ያልነበሩ በመሆኑ ምስክርነታቸው የተጠሪን ማስረጃ ለማስተባበል የሚችል አይደለም በማለት ይከላከሉ በየተባሉበት ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡በመቀጠልም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ በ2ኛ አመልካች ላይ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት፣በ1ኛ እና በ6ኛ አመልካቾች በእያንዳንዳቸው ላይ የአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት፣በ3ኛ፣በ4ኛ እና በ5ኛ አመልካቾች በእያንዳንዳቸው ላይ የስድስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት መነሻ አድርጎ ከወሰነ በኋላ የቀረበባቸው የቀድሞ ሪከርድ አለመኖሩን በማቅለያ ምክንያትነት ይዞ ቅጣቱን በማቅለል በ2ኛ አመልካች ላይ የሃያ ዓመት ጽኑ እስራት፤በ1ኛ እና በ6ኛ አመልካቾች በእያንዳንዳቸው ላይ የአስራ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት፤በ3ኛ፣በ4ኛ እና በ5ኛ አመልካቾች በእያንዳንዳቸው ላይ የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት በመጣል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ይግባኝ እና አቤቱታ ሳይቀበሉ በመቅረታቸው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ለስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ከቀረበው ማስረጃ አንጻር 2ኛ አመልካች በወ/ሕ/አ. 539(1)(ሀ) ስር፤ቀሪዎቹ አመልካቾች ደግሞ በወ/ሕ/አ. 32(3) እና 540 ስር ጥፋተኛ ልንሰኝ አይገባም በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም መሰረት በክሱ በተገለጸው ዝርዝር መሰረት ሟች ነጋሽ መኮንን ይባል የነበረውን ሰው 1ኛ አመልካች በድንጋይ ጭንቅላቱን መትቶ ከመሬት ላይ ሲጥለው 2ኛ አመልካች ደግሞ ጭንቅላቱን በተለያየ ቦታ ላይ በድንጋይ የመታው ከመሆኑም በላይ ቀጥሎም ከሃያ ሜትር በላይ ርቀት ወዳለው ገደል በእጁ ገፍትሮ የወረወረው መሆኑ እና ተበዳዩም በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ በደረሰበት በዚሁ ጉዳት ምክንያት ለሞት የበቃ መሆኑ በተጠሪ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን እና አመልካቾቹ በመከላከያ ምስክሮቻቸው ከድርጊቱ መፈጸም በፊትና ከተፈጸመ በኃላ ስለነበረው ሁኔታ ከማስመስከር ውጪ ድርጊቱን ስላለመፈጸማቸው ያቀረቡት ቀጥተኛ መከላከያ አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በ2ኛ አመልካች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠው በወ/ሕ/አ. 539(1)(ሀ) ስር መሆኑን በተመለከተም ቢሆን አመልካቹ በ1ኛ አመልካች በድንጋይ ከጭንቅላቱ ላይ ተመትቶ ወድቆ የነበረውን ሟች በድንጋይ ከጭንቅላቱ ላይ ከመታው በኃላ ከሃያ ሜትር በላይ ርቀት ወዳለው ገደል የወረወረው መሆኑ እና ሟችም ለሞት የበቃው በዚሁ በሁለቱ አመልካቾች በደረሰበት ጉዳት ምክንያት እንደሆነ የተረጋገጠ በመሆኑ እና ይህ 2ኛው አመልካች የፈጸመው አድራጎት የአፈጻጸም ሁኔታ ደግሞ የአመልካቹን ጨካኝነት እና የአፈጻጸሙን አሰቃቂነት በግልጽ የሚያመለክት በመሆኑ ድርጊቱ የሚሸፈንበትን ድንጋጌ አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም በ1ኛ እና በ2ኛ አመልካቾች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ቀሪዎቹን ማለትም 3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾችን በተመለከተ እነዚህ አመልካቾች የተከሰሱት በወ/ሕ/አ. 32(3) እና 539(1)(ሀ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል ተብለው ሲሆን ይከላከሉ የተባሉትና የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸው ደግሞ በወ/ሕ/አ. 32(3) እና 540 ስር ነው፡፡እነዚህ አመልካቾች አድርገዋል ተብለው በክሱ የተጠቀሰባቸው ግዙፋዊ ድርጊት ሟችን ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ጥቃት ለማስጣል የመጡትን ሰዎች በመከላከል ልብሶቻቸውን እየጨመደዱና እጆቻቸውን እየጠመዘዙ እንዲሁም በድንጋይ ጭንቅላታቸውን በተለያየ ቦታዎች እየፈነከቱ አባረዋል የሚል ነው፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካቾቹ ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት የካዱ ቢሆንም ከበታች መሬት በኩል በስራ ላይ የነበሩትና ከላይኛው መሬት በኩል የድንጋይ ናዳ የወረደባቸው ሰዎች ከሟች ጋር ወደቦታው በመጡበት ጊዜ አመልካቾቹ በእነዚሁ ሰዎች ላይ በክሱ የተመለከተውን ድርጊት መፈጸማቸው በተጠሪ ምስክሮች የተረጋገጠባቸው መሆኑን እና ከ1ኛ እና ከ2ኛ አመልካቾች ጋር በተመሳሳይ ጭብጥ ያቀረቡት መከላከያ ከላይ ስለ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ከተገለጸው ጋር በተመሳሳይ ምክንያት ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱን ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ይሁን እንጂ በክስ ማመልከቻውም ሆነ በተጠሪ ምስክሮች በተገለጸው መሰረት በአንድ በኩል በ1ኛ እና በ2ኛ አመልካቾች፣በሌላ በኩል ደግሞ በቀሪዎቹ አመልካቾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መፈጸማቸው የተረጋገጠው ግዙፋዊ የወንጀል ድርጊቶች ከየተፈጸሙበት የጊዜ ቅደም ተከተል አንጻር ሲታዩ በ3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች መፈጸሙ የተረጋገጠው ግዙፋዊ የወንጀል ፍሬ ነገር በወ/ሕ/አ. 32 በተመለከተው መሰረት በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ በግድያ ወንጀሉ መሳተፋቸውን የሚያረጋግጥ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ መጤን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በ3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ሚችን ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ለማስጣል የመጡትን ሰዎች ደብድበው አባረዋል ከመባላቸው ውጪ እራሳቸው ሚችን በቀጥታ የመቱ ስለመሆኑ በክስ ማመልከቻው ላይ አልተገለጸም፡፡ ይህ ፍሬ ነገር በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.111(1)(ለ) እና 112 ስር በተመለከተው የክስ አቀራረብ ስርዓት መሰረት በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተ ወይም ክሱ እንዲሻሻል የተደረገ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ ሚችን የደበደቡት 3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ጭምር ስለመሆናቸው በተጠሪ ምስክሮች የተገለጸው ፍሬ ነገር በእነዚህ አመልካቾች ላይ ውጤት እንዲኖረው ሊደረግ የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡በክስ ማመልከቻውም ሆነ በተጠሪ ምስክሮች በተገለጸው መሰረት እነዚህ አመልካቾች ሚችን ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ለማስጣል የመጡትን ሰዎች ደብድበው አባረዋል የተባሉት 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች በሚች ላይ በክሱ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ከፈጸሙ በኋላ በመሆኑ 3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች መፈጸማቸው የተረጋገጠው ግዙፋዊ የወንጀል ፍሬ ነገር ራሱን የቻለ ሌላ ወንጀል የሚያቋቁም ነው ከሚባል በቀር ከ1ኛ እና ከ2ኛ አመልካቾች ጋር በየትኛውም ደረጃ ወይም ዓይነት የሚገለጽ የግድያ የወንጀል ሀሳብ በመጋራት ተጎጂዎቹ ሚችን ከጥቃት እንዳያስጥሉ ለመከላከል በማሰብ የተፈጸመ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሆኖ ያስገኘው ሕግ በፍርዱ ውስጥ መገለጽ እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 149 የተመለከተው ድንጋጌ የጥፋተኝነት ውሳኔው የሚሰጥበት ድንጋጌ መፈጸሙ ከተረጋገጠው የወንጀል ፍሬ ነገር ጋር በጥንቃቄ መነጻጸር እንደሚገባው የሚያስገነዝብ በመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤት 3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾችን በግድያ ወንጀል ጥፋተኛ በማድረግ የሰጠው ውሳኔም ሆነ ይህንኑ በማጽናት በክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በመዝገቡ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ለወንጀሉ ምክንያት የሆነው ግጭት የተፈጠረው በላይኛው የመሬት ክፍል በስራ ላይ የነበረው አመልካቾቹ የሚገኙበት ቡድን ከመሬቱ በታችኛው ክፍል በስራ ላይ በነበረው እና ተጎጂዎቹ በሚገኙበት ቡድን ላይ በተደጋጋሚ የድንጋይ ናዳ በማውረዱ ምክንያት ተጎጂዎቹ በዚሁ ድርጊት ተነሳስተው አመልካቾች ወደ ሚገኙበት አካባቢ በመምጣታቸው ምክንያት መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ይህም ግጭቱ የተከሰተው አመልካቾቹ ይገኙበት በነበረው ቡድን ጠብ አጫሪነት መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ አመልካቾቹ ድንጋዮችን በመያዝ በዚህ ዓይነቱ ድርጊት ውስጥ በመሳተፍ በተጎጂዎቹ ላይ ጉዳት ማድረሳቸውም በወ/ሕ/አ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

577(1) እና (3) ስር የተመለከተውን የአምባንሮ ወንጀል ማድረጋቸውን የሚያመለክት በመሆኑ በአመልካቾቹ መፈጸሙ በፍሬ ነገር ደረጃ በተረጋገጠው መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠበት ድንጋጌ ከወ/ሕ/አ. 32(3) እና 540 ወደ ወ/ሕ/አ. 577(1) እና (3) ሊለወጥ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ጥፋተኞች የተባሉበት የአምባንሮ ወንጀል በወቅቱ በስራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ደረጃ ካልወጣላቸው ወንጀሎች መካከል የሚካተት ሲሆን ድርጊቱ የተፈጸመው በሁለቱም ቡድኖች ውስጥ የሚገኙት ሰዎች በእርሻ ስራ ላይ ይገኙ በነበሩበት ጊዜ መሆኑን ከግምት በማስገባት በመመሪያው አንቀጽ 13(2) በተመለከተው መሰረት በአፈጻጸሙና በክብደቱ ወንጀሉ በዝቅተኛ ደረጃ ሊመደብ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በድንጋጌው ስር በዝቅተኛ ደረጃ ለተመደበ ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው የተቀመጠው ፍቅደ ስልጣን እስከ ሰባት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ሲሆን ከዚህ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው የቅጣት መጠን የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ የቅጣት መጠን በቅጣት መመሪያው አባሪ አንድ በእርከን 20 ስር የሚወድቅ ሲሆን ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ እንደሚቻለው በተጠሪ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፡፡ የቅጣት ማቅለያን በተመለከተ 3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች የቀረበባቸው ሪከርድ አለመኖሩን ገልጸው አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ማስመዝገባቸውን እና 6ኛ አመልካች የሰባት ቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን በመግለጽ ተጨማሪ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ማስመዝገባቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡የቅጣት መነሻው ከአንድ ዓመት በላይ እና ከሰባት ዓመት በታች በሆነ ጊዜ በእያንዳንዱ የማቅለያ ምክንያት መነሻ ተደርጎ የተያዘው የቅጣት መጠን በሁለት እርከን እንደሚቀነስ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በአንቀጽ 16(6) በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ የሚደረገው የቅጣት መጠን ሊወሰን የሚገባው 3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾችን በተመለከተ በእርከን 18 እንዲሁም 6ኛ አመልካችን በተመለከተ በእርከን 16 በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን መሰረት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል በአመልካቾቹ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በማዕከላዊ ዞን በአብይ ዓዲ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01450 በ24/05/2005 ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመ.ቁ.57452 በ08/09/2005 ዓ.ም. እና በመ.ቁ. 59621 በ23/11/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾችን በተመለከተ የተሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በ3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ላይ በወ/ሕ/አ. 32(3) እና 540 ስር ተሰጥቶ የነበረው የጥፋኝነት ውሳኔ ተሻሽሎ ተጠቃሾቹ አመልካቾች ጥፋተኞች ሊባሉ የሚገባው በወ/ሕ/አ. 32(1) (ሀ) እና 577(1) እና (3) ስር ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረት በዚህ ጉዳይ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሆኖ 3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች እያንዳንዳቸው በሶስት ዓመት ከሰባት ወር ጽኑ እስራት፤6ኛው አመልካች ደግሞ በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
5. በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ አመልካቾቹ ለሚገኙበት ማረሚያ ተቋም ይላክ፡፡
6. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95875

ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ
አልማው ወሌ
ረታ ቶሎሳ
አዳነ ንጉሴ
መ·ስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-1.አቶ አዳሙ ዘለቀ
2.አቶ ሽባባው ወሂሶ
3.አቶ ኃይሉ ሸበት
} የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-የአማራ ክልል አቃቤ ሕግ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የአንድ ወንጀል ጉዳይ በስነ ስርዓት ሕጉ መሰረት ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ ተደርጎ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ የተወሰነበት ሰው ውሳኔውን እንዲነሳለት ለመጠየቅ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ አተገባበርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡አመልካቾች በዚህ ፍርድ ቤት በዞኑ አቃቤ ሕግ የተከሰሱት ታደሰ ግዛት ከተባለ ግለሰብ ጋር ሁነው ገበየሁ ጋው የተባለ ሰው በግፍ ገድለዋል ተብሎ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) እና 539(1/ሀ) ተጠቅሶባቸው ነው፡፡የአሁኑ አመልካቾች በበኩር ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ሊቀርቡ አልቻሉም ተብሎ ጉዳዩ በሌሉበት የታየ ሲሆን የስር 4ኛ ተከሳሽ የነበረው ታደሰ ግዛት ግን ቀርቦ ተከራክሯል፡፡ፍርድ ቤቱም በአቶ ታደሰ ግዛት የቀረበውን ክስ በተመለከተ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የምስክሮች ቃልና ተከሳሹ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 27(2) መሰረት ለፖሊስ የሰጠው ቃል የማይጣጣም፣ እርስ በእራሱ የሚጋጭ ሁኖ ተገኝቷል በሚል ምክንያት ተከሳሹን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 መሰረት በነጻ ያሰናበተው ሲሆን የአሁኑ አመልካቾችን በተመለከተ ግን በአቃቤ ሕግ ምስክሮች የሠው ግድያ ወንጀል የፈፀሙ መሆኑ ተረጋግጦባቸዋል በማለት ለወንጀሉ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን አድራጎቱንም በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር ሳይሆን ተራ በሆነ የሰው ግድያ ወንጀል የሚሸፈን ነው በማለት በክስ ማመልከቻው ላይ የተጠቀሰውን ድንጋጌ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 113(2) መሰረት ወደ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1/ሀ) እና 540 ድንጋጌ ለውጦ አመልካቾችን እያንዳንዳቸውን በ18 (አስራ ስምንት) አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ከመጋቢት 29 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ፍርዱን መፈፀም መጀመራቸውንና በዋናው ጉዳይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በ01/08/2004 ዓ/ም ይግባኝ ጠይቀው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚገኙ ገልጸውና ቀድሞ መፈፀም ያለበት ስርዓት በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ማቅረብ መሆኑን መገንዘባቸውን ጠቅሰው በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ ውድቅ ሁኖ ክርክሩ ባሉበት እንደገና እንዲሰማ ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥያቄያቸውን አቅርበዋል፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በአሁኑ አመልካቾች ጥያቄ ላይ የዞኑ አቃቤ ሕግ አስተያየት እንዲሰጥበት ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የተወሰነ መሆኑን ያወቁት ከመጋቢት 29 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑን፣አንድ የወንጀል ጉዳይ በሌለበት ታይቶ እንዲወሰንበት የተደረገ ሰው ደግሞ ውሳኔው ውድቅ እንዲሆን ጥያቄ ማቅረብ ያለበት ውሳኔው መሰጠቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በሰላሳ ቀናት ውስጥ መሆኑን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 198 ስር የተደነገገ መሆኑን እንዲሁም አመልካቾች ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስርዓቱን ባለማወቅ አቅርበናል የሚሉት ምክንያትም ሕጋዊ ያለመሆኑን በምክንያትነት ይዞ የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ከተጠሪ ጋር እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ሰኔ 08 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰላሳ ቀናት ጊዜ ለመቁጠር መነሻ ያደረጉት ሁኔታ የአመልካቾችን በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ቆይተው በስነ ስርዓት ተገቢውን ለመፈጸም ጥያቄውን ማቅረባቸውንና የመከራከር መብት መከበር ያለበት መሆኑን በአግባቡ ሳይገነዘቡ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካቾች ጥያቄ በሰላሳ ቀናት ያልቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በሌሉበት እንዲታይ ተደርጎ የተወሰነባቸው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መኖሩን ያወቁት መጋቢት 29 ቀን 2004 ዓ/ም መሆኑን፣ሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም ደግሞ በዋናው ጉዳይ ላይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ማቅረባቸውን፣ በዚህ ሂደት ውስጥ ከቆዩ በኋላ በዋናው ጉዳይ ላይ ያቀረቡት ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 05102 ጥቅምት 30 ቀን 2005 ዓ/ም የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ስህተት ያልተገኘበት ነው ተብሎ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(1) ከመጽናቱ በፊት ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ/ም በዞኑ ከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ውድቅ እንዲሆንላቸው አቤቱታቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገገው ሥርዓት ጉዳዩን ተከሣሹ በሌለበት (default) በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው መሠረት አይቶ የተሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ውድቅ ለማስደረግ የሚያገለግሉ ድንጋጌዎችን ያካተቱ ሲሆኑ ድንጋጌዎች ጥያቄ መቅረብ ያለበት እና የጊዜ ገደብ፣ የጥያቄ አቅራቢ ማመልከቻ ምክንያት መግለጽ ያለበት መሆኑን፣ በጊዜ ገደቡ ውስጥ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የማያገኝበትንና የሚያገኝበትን አግባብና በዚህ አግባብ በፍርድ ቤቱ የሚሰጡ ትዕዛዛት ያላቸውን ሕጋዊ ውጤቶቻቸውን በተመለከተ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 198 በተደነገገው መሰረት በሰላሳ ቀናት ውስጥ አመልካቾች በሌሉበት የተፈረደውን ፍርድ ውድቅ ለማስደረግ ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ማመልከቻቸውን አላቀረቡም፣ ፍርዱን ያወቁት ከመጋቢት 29 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ሁኖ እያለ ጥያቄውን ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ/ም ማቅረባቸው ስነ ሥርዓታዊ አይደለም በማለት ነው፡፡ይህ መሆኑን አመልካቾችም የሚክዱት የፍሬ ጉዳይ ክርክር አይደለም፡፡አመልካቾች የሚከራከሩት በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ካሉ በኃላ ትክክለኛውን ስነ ስርዓት መከተል ያለባቸው መሆኑን በመገንዘብ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥያቄያቸውን ማቅረባቸውን በመግለጽ ነው፡፡ በእርግጥ ትክክለኛውን የህግ ስነ ስርዓት አለማወቅ ለአቤቱታው አቀራረብ በሕጉ የተደረገውን የጊዜ ገደብ ለመተው የሚያስችል ምክንያት ባይሆንም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 198 ስር የተመለከተው የጊዜ ገደብ ማቋረጫ ሕጋዊ ምክንያት በስነ ስርዓት ሕጉ በግልጽ ያለመመልከቱ ግን ይኼው ምክንያት መኖር ያለመኖሩን ከመከራከር አጠቃላይ መብትና ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 160 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማ አንጻር ፍርድ ቤቱ ከማየት የሚከለክል ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

የመከራከር መብት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20 ድንጋጌ እና በሌሎች የአገሪቱ የሕግ አካል በሆኑ አለም አቀፍ ስምምነቶች ጥበቃ ያገኘ መሰረታዊ መብት መሆኑ ይታወቃል፡፡የአለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 በጠቅላላውና ንዑስ አንቀጽ 3/መ/ በልዩ ሁኔታ በአቀራረቡም ሆነ በይዘቱ የወንጀል ክስ ተከሣሽ ባለበት መታየት ያለበት መሆኑን የሚደነግግና በወንጀል የተከሰሰ ሰው ሊከበርለት የሚችል ሰፊ መብት ያለው መሆኑን በዝርዝር ይደነግጋል፡፡ ይህ መብት ሊከበር የማይችለው በሕጉ የተዘረጋው ስርዓት መሰረት ተደርጐ ሲሆን ከእነዚህ በህግ ከተዘረጉ ስርዓቶች አንዱ የወንጀል ክስ ተከሣሹ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተመለከተው አግባብ እንዲታይ የተዘረጋው ስርዓት ነው፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማ ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች ከፍትህ ሸሽተው ተገቢውን ፍርድ ሳያገኙ እንዳይቀሩ ለማድረግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ድንጋጌዎቹን ተፈፃሚ የሚያደርገው ተገቢውን የመጥሪያ አደራረስ ስርዓት ተከትሎ መሆኑንም ያስገነዝባሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ የመጀመሪያው የወንጀል ክሱ በሌለበት የታየ ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ እንዲሆንለት ያቀረበው ማመልከቻ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 201 በተደነገገው ሥርዓት እንዲታይ መደረጉም የተከሳሽን የመከራከር መብት ከመጠበቅ አንጻር የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ስርዓት ሕጋዊ ምክንያት ያለውና ጥሪውን ለመስማት ያልቻለ ሰው ባለመቅረቡ ብቻ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተሰጥቶ እንዳይቀር ታስቦ የተቀመጠ ስርዓት ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለሆነም በዚህ አግባብ የሚቀርብ ጥያቄ ከመከራከር ህገ መንግስታዊ መብትና ከዝርዝር ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማ፣ ይዘትና መንፈስ ጋር ተዛምዶ መታየት ያለበት ጉዳይ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 198 ስር የተቀመጠው የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ድንጋጌ መተርጎም ያለበት የመከራከር መብትን በማያሣጣ ወይም በማያጣብብ መንገድ መሆን አለበት፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካቾች በዋናው ጉዳይ ላይ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ተቀብሎ በማየት ላይ እንዳለ ውጤቱን ሳይጠብቁ የመከራከር መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀረቡበት ሁኔታ ጥያቄያቸውን በሰላሳ ቀን የጊዜ ገደብ ውስጥ አላቀረቡም ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ እንደዚህ አይነት ጥረት የነበረው ሰው በሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄውን አላቀረበም ተብሎ አቤቱታውን ውድቅ ማድረግ የመከራከር መብትን በአግባቡ ለማስከበር የሚያስችል ነው ተብሎ የማይታሰብ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች ሕግን አለማወቅ ጥያቄያቸውን ለመቀበል የሚያስችል አይደለም፣ ጊዜው መቆጠር ያለበት ፍርዱ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ነው በማለት ያሰፈሩት ምክንያት ሕጋዊ ቢሆንም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 198 ስር የተመለከተው የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ሊቋረጥ የሚችልበትን ምክንያት ግን አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ቆይተው ውጤቱን ሳይጠብቁ ትክክለኛውን ስነ ስርዓት ከመከተላቸውና ይህም ከመከራከር መብት ጋር አንፃር ሲታይ የሰላሳ ቀናት ጊዜውን ቀሪ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሕገ መንግስቱ የተከበረው የመከራከር መብት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 198 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ አላማ ጋር አጣጥሞ በመተርጎም ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የፈፀሙ ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01346 ሰኔ 08 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 28404 መስከረም 28 ቀን 2006 ዓ/ም በሰጠው ፍርድ የጸናው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 198 መሰረት በሰላሳ ቀናት ይታገዳል መባሉ ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡
3. የአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ/ም ያቀረቡትን አቤቱታ የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ የማያግደው ነው ተብሎ መወሰኑን ተገንዝቦ ጥያቄያቸውን ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 199 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በመመርመር አመልካቾች በሌሉበት የተሰጠውን ፍርድ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ነጥብ በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ታ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96503

ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- መኮንን ወለላው ካሳ ጠበቃ ዘነበ አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ሥነ ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ህግ

ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

የአቤቱታው መነሻ የአሁኑ አመልካች የካቲት 27 ቀን 2005 ዓ/ም ለስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ማመልከቻ ሲሆን ይዘቱም፡- በመ/ቁጥር 65858፣ 66882፣ 71671 እና በመ/ቁጥር 87280 በሆኑ መዛግብት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተለያዩ መጠን ያላቸው የእስራት ቅጣት እና የገንዘብ መቀጮዎች እንደተወሰኑባቸው ገልጸው ቅጣቶች እንደገና ተጣምረው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 186 መሰረት በአንድነት ተጠቃለው ይወሰኑልኝ በማለት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችን ጥያቄ በኮ/መ/ቁጥር 87280 በመቀበል ከተመለከተው በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በአራቱም መዝገቦች በአመልካቹ ላይ ተወስነውበት የነበሩት ቅጣቶች በአንድነት ተጠቃለው ተደምረው በ24 አመት ከ3 ወር ጽኑ እስራት እና በብር 22,500 የገንዘብ መዋጮ እንዲቀጣ የሚል ውሳኔ በመስጠት ማረሚያ ቤቱንም በአንድነት ተጠቃሎ በተወሰነው ቅጣት መሰረት እንዲያስፈፅም አዟል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔን አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቹ የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-የበታች ፍርድ ቤቶች አራቱን መዝገቦች በማሰባሰብና በማጣመር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) መሰረት አይቶ መወሰን ሲገባቸው ያለአግባብ በመደመር ቅጣቱን ከፍ አድርጎ የወሰኑባቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሀ) ድንጋጌ ውጪ መሆኑንና ቅጣቱን በተመለከተውም በሕግ አግባብ ተቀባይነት ያገኙት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ግንዛቤ ውስጥ ገብተው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወጣው የቅጣት አወሳሰን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመሪያ መሰረት የቅጣት መጠኑ ያለመሰላቱን የሚገልፅ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም የበታች ፍርድ ቤቶች ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) የሰጡት ትርጉም ተገቢ መሆን ያለመሆኑንና የቅጣት መጠኑ የተወሰነው የቅጣት አወሳሰን መመሪያን መሰረት አድርጎ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) መሰረት የቅጣት ይጣመርልኝ ጥያቄ ከቀረበ በየመዝገቦቹ የተወሰኑትን ቅጣቶች መደመር ሳይሆን በአንድነት በማጠቃለል እንደገና በአዲስ መልክ ቅጣቱ ተሰልቶና ተቀባይነት ያገኙት የቅጣት ማቅለያዎች ሁሉ ታይተው ጉዳዩ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሀ) ለአንድ የወንጀል ሐሳብ አንድ ቅጣት ከመሆኑ እና ከቅጣት መመሪያ ድንጋጌዎች አንፃር ታይቶ ቅጣቱ ሊወሰን የሚገባው ነው በማለት ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በአራት የክስ መዝገቦች ቀርበውባቸው እንደነበር፣ በወ/መ/ቁ 66882 ቀርበውበት በነበሩት 2 ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነበት የ9 ዓመት ጽኑ እስራት እና የብር 15,000 መቀጮ፣ በወ/መ/ቁ 71671 በቀረበበት አንድ ክስ ጥፋተኛ ተደረጎ የተወሰነበት የ5 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት እና የብር 7000 መቀጮ እንዲሁም፣ በወ/መ/ቁ. 65858 በቀረቡበት ሁለት ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነበት የ10 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት እንዳለ የፀኑና ያለቀላቸው መሆኑን፣ በወ/መ/ቁ.87280 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቹ ላይ ቀርበው በነበሩ ሁለት ክሶች ጥፋተኛ አድርጓቸው የ2 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት እና የብር 1000 መቀጮ ወስኖባቸው የነበረ ቢሆንም አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው በአንዱ ክስ ብቻ ጥፋተኛ ተብለው የ6 ወር ቀላል እስራት ቅጣት እና የብር 500 መቀጮ የተወሰነባቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) በአንድነት ተጣምረው መታየት የነበረባቸው የወንጀል ክሶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች በተወሰኑ ጊዜ የጠቅላላ ቅጣቱ አወሳሰን ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል ብሎ ከተጠቃሹ ድንጋጌ በላይ ወደ ተገለፁት ድንጋጌዎች የሚያጣቅስ ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች ሲታዩ በተለያዩ ፍ/ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች ተወስነው በተገኙ ጊዜ እንደገና በአዲስ መልክ እያንዳንዱ ቅጣት ተሰልቶና የቅጣት ማቅለያዎች ሁሉ ታይተው መወሰን አለበት የሚል መንፈስ ያላቸው አይደሉም፡፡ይልቁንም ሕጉ ጥፋተኛው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ጊዜ ቢፈረድበት ኖሮ ሊወሰንበት ይችል ከነበረው ከፍተኛ ቅጣት ሳያልፍ እንደሚወሰን የሚያስረዳ ነው፡፡ ስለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን የሚመለከተው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184(1)(ለ)"ም" ሲታይም ጥፋተኛው ተደራራቢ ወንጀሎች ፈፅሞ በተገኘ ጊዜ በተደራራቢነት ለተፈፀሙ ለእያንዳንዱ ወንጀል በተናጠል ተገቢው የቅጣት መጠን ተወስኖ የሁሉም እንደሚደመር እና ቅጣቶችም ተደምረው ለወንጀሉ አይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት መብለጥ እንደማይችል ያስቀምጣል፡፡ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የፅኑ እስራት ከፍተኛው ቅጣት ሃያ አምስት አመት ስለሆነ በጽኑ እስራት የሚያስቀጡት ተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣቶች ተደምረው ከሃያ አምስት አመት ሊበልጡ እንደማይችሉ ደግሞ ይሄው ድንጋጌ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 108(1) ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ይዘቱና መንፈሱ ደግሞ ቅጣቶቹ ተደምረው ከሃያ አምስት አመት በሚበልጡበት ጊዜም ሃያ አምስት አመት ላይ እንዲያቆም ፍርድ ቤቱ እንዲቆም የሚያስገድድ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንግዲህ ከላይ ከተገለጹት ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ጥፋተኛው ከፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ የየትኛውም ወንጀል ቅጣት የቀሪዎችን ወንጀሎች ቅጣት የሚያጠቃልል ካልሆነና ወንጀሎቹ በእስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ከሆኑ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ ሁሉም እንዲደመር የሚደረግ መሆኑን እና ምንጊዜም ቢሆን ለእስራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ጣሪያ ቅጣት ማለፍ አይቻልም ተብሎ መደንገጉ ነው፡፡ይህም መታየት ያለበት አጥፊው ጥፋተኛ የተባለበት ልዩ ድንጋጌ የሚያስቀምጠው የቅጣት ጣሪያ ሳይሆን በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ጣሪያ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ እንዲሁም አንድ ሰው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ከፊሎቹ የሚያስቀጡት በቀላል እስራት፣ ከፊሎቹ ደግሞ በፅኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በሚሆኑበት ጊዜ የቅጣት አወሳሰኑ ቅጣቶችን ለመደመር እንዲያመች ሁለት ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ፅኑ እስራት ይቆጠራል ተብሎ በሕጉ በግልጽ ተቀምጧል፡፡
ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም ከላይ በተጠቀሱት አራት መዝገቦች በአመልካች ላይ በተለያየ ጊዜ ተነጣጥለው የተወሰኑበት የተለያዩ ቅጣቶች ተጣምረው ይወሰኑልኝ በሚል ያቀረበውን ጥያቄ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተወሰነበትን የ6 ወር ቀላል እስራት ወደ 3 ወር ጽኑ እስራት በመለወጥ የአራቱም መዝገቦች ቅጣቶች በአንድነት በማጠቃለል ደምሮ የ24 ዓመት ከ3 ወር ፅኑ እስራት ቅጣት እንዲፈፀም ከመወሰን ወጪ በሕጉ ስለጽኑ እስራት የተቀመጠውን ጣሪያ በማለፍ የወሰነው ቅጣት የለም፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ይህንኑ የቅጣቶች ይጣመሩልኝ ጥያቄ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ አመልካቹን ጥያቄውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብ አለብህ ብሎ የመለሰው ወይም የመራው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአራቱንም መዝገቦች ቅጣቶች አሰባስቦ እንደገና በመከለስ አዲስ የቅጣት ውሳኔ እንዲሰጥ ሳይሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) በተከተለ መንገድ እንዲያይ ስለመሆኑም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሳኔ በግልጽ ያሳያል፡፡ አስቀድሞ በየመዝገቦቹ ቅጣቶቹ በተናጠል በሚወሰኑበት ጊዜ ሁሉም ነገሮች ታይተው ለፈፀማቸው ወንጀሎች ይመጥናሉ ተብለው የተወሰኑ መሆናቸው በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን የቅጣቶች አፈጻጸምን በተመለከተም ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 186(3)፣ 184(1(ለ)) እና 108(1) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ተደምረው እንዲፈፀም ማድረግ የድንጋጌዎቹን ትክክለኛ ትርጉም አተገባበር የተከተለ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ሊባል የሚችልበትን ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩበትና ለዚህ ችሎት እንዲታይ የተያዘው ነጥብ የቅጣት አሰላሉን የሚመለከተው ነጥብ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኙት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መሰረት ተደርጎ ቅጣቱ ያለመሰላቱንና የቅጣት መጠኑ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው ውጪ ከፍ የተደረገባቸው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በተለያዩ ጊዜ ፣በተለያየ ሰነድና በተለያየ ቦታ ለፈጸሟቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በተለያዩ መዛግብት ጥፋተኛ ተብለው ቅጣቱ ሲወሰን አለኝ የሚሏቸው ሕጋዊ የቅጣት ማቅለያ ምክያንቶች ተይዘውላቸው ቅጣቱ መሰላቱን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሲሆን ቅጣቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 186(3) ድንጋጌ አግባብ ታይቶ እንዲወሰን ሲደረግ ወይም መዝገቦቹ ተነጣጥለው ሲወሰኑ የተያዙት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እንደገና የሚታዩበት የሕግ አግባብ የለም፡፡በአመልካች ጥያቄ አግባብ ቅጣቱ እንዲሰላ ማድረግ ለአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሁለት ጊዜ ዋጋ የመስጠት ውጤትን የሚያስከትል በመሆኑ በሕግ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን አመልካቹ መዝገቦቹ ተነጣጥለው ሲታይ ቅጣቱም ተነጣጥሎ ሲወሰን በተለያዩ መዝገቦች ተመሳሳይ የቅጣት ማቅለያ እንዲያዙ መደረጉ በውጤቱ አመልካችን ጠቅሟቸዋል ከሚባል በስተቀር የመብት መጣበብን አስከትሎባቸዋል ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቹ ቅሬታም የሕግ መሰረት ያለው ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87280 ሐምሌ 09 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 92594 ጥቅምት 04 ቀን 2006 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(መ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) ሲተርጉሙም ሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ተግባራዊ ሲያደርጉ የፈፀሙት ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት የጸና መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረሚያ ቤቱ ትዕዛዝ ይድረስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ታ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 98647

ሰኔ 02 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ፅጋቡ ወላይ ገብሩ- VC ስላልሰራ መቅረቡን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ዐቃቤሕግ - VC ስላልሰራ መቅረቡን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ከሚሊኒየም ዴቨሎፕመንት ፕሮጀክት ጋር ከመቐሌ ወደ ሓውዜን ሲሚንቶ እንዲያንገዝላቸው የማንገዝ ሃላፊነት ተሰጥቶት በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት አንገዞ በጊዜው ሊያስረክባቸውና ለህዝብ ልማት ላይ ሊያውል የሚገባውን እምነት አጉድሎ ሲሚንቶውን ሸጦ ለግል ጥቅሙ በማዋሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ድንጋጌን ተላልፏል የሚል ሲሆን የአሁኑ አመልካች ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ገልጾ የድርጊት አፈጻጸሙን በተመለከተ ግን በመንገዣ ዉሉ መሰረት ሲሚንቶውን መረከቡንና መሸጡን አምኖ ሆኖም አስጫኙ ያልከፈለው ገንዘብ ስለነበረ ይህንኑ ገንዘብ አስቀርተው ቀሪውን እንዲረከብ ጥያቄ ሲያቀርብ ተቀባይነት ያጡ መሆኑን ገልፀው ጉዳዩ በፍትሐብሔር እንጂ በወንጀል ሊያስጠይቀኝ አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የክልተ በለሳ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩ የፍትሐ ብሔር እንጂ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል አይደለም በማለት አመልካችን በነጻ አሰናብቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ሰሚንቶውን የሸጠው በውሉ መሰረት ሳያስረክበው የቀረ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት አመልካችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675(1) ስር ጥፋተኛ አድርጎታል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና ድንጋጌው ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ቅጣቱን ከአሰላ በኋላ አመልካች በሁለት አመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አድራጎቱ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው በማለት ድምዳሜ ላይ የደረሰው ከስልጣኑ ውጪ ማስረጃ መዝኖ ከመሆኑም በላይ በማስረጃ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የአመልካች አድራጎት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ስር የተመለከቱትን የወንጀሉን ማቋቋሚያዎችን የሚያሟሉ አይደሉም የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች አድራጎት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675(1) የሚያስጠይቅ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች አድራጎት የሚሸፈነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675 (1) ድንጋጌ ስር ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት አመልካች አልፈጸምኩም በማለት ያልተከራከረ ሲሆን አጥብቆ የሚከራከረው በመንገዣ ውሉ መሰረት ሊከፈለኝ የሚገባው ገንዘብ በሲሚንቶው አስጫኙ ድርጅት ስላልተከፈለ ሲሚንቶውን ሸጦ የመንገዣውን ገንዘብ አመልካች ከቀነሰ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ ከሰሚንቶ አስጫኝ ድርጅት ለመመለስ ጥረት አድርጎ ድርጅቱ ቀሪውን ገንዘብ ሊቀበለው ያልቻለ መሆኑን በመጥቀስ ጉዳዩ ፍትሐ ብሔራዊ እንጂ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስከትልም በማለት ነው፡፡በርግጥ አመልካች ይህንኑ ቃሉን በመከላከያ ማስረጃዎቹም ያረጋገጠው ፍሬ ነገር መሆኑን ክሱን የሰማው የወረዳው ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም እንደዚሁ የተሰማውን ማስረጃ በመመዘን ሲሚንቶው የተሸጠበትን ሁኔታ እርግጠኛ ሆኗል፡፡ የሲሚንቶው መሸጥ ድርጊት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም የሚለው ፍሬ ነገር በአመልካች ካለመካዱም በላይ የፍሬ ነገር ጭብጥን በማስረጃ የማጣራት እና የተሰማውን ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የወረዳው ፍርድ ቤት እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን በዚህ መልክ በመምራት መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡እነዚህ ፍርድ ቤቶች የአመልካች ድርጊት የወንጀል ተጠያቂነትን አያስከትልም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት አመልካች በመንገዣ ውሉ መሰረት ያልተከፈለውን ገንዘብ ለማግኘት ሲል ሲሚንቶውን ሸጦ ከመንገዣ ዋጋ የተረፈውን ለሲሚንቶው አስጫኝ ድርጅት ለመመለስ አመልካች ጥረት ቢያደርግም ድርጅቱ ገንዘቡን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግን አመልካች ሲሚንቶውን እንዲሸጥ የውል ስምምነት የተደረገው መጋቢት 10 ቀን 2003 ዓ/ም ሁኖ ከዚህ ቀን በፊት ያለው ውል ደግሞ ይህንኑ መብት እንደማይሰጠው፣ሲሚንቶውም የተሸጠው ከመጋቢት 10 ቀን 2003 ዓ/ም በፊት ሁኖ የቀደመው ሕጋዊ ውል ባለበት ሁኔታ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የአመልካች አድራጎት የእምነት ማጉደል ወንጀል ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ደምድሟል፡፡ይህ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድምዳሜ ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃውን በመመዘን የተያዘ ሳይሆን በክርክሩ ሂደት የቀረቡት ማስረጃዎች ያረጋገጧቸው ፍሬ ነገሮችን በመለየት የተያዘ በመሆኑና በክርክሩ ሂደት የቀረቡት ማስረጃዎች ያረጋገጧቸውን ፍሬ ነገሮች የበታች ፍርድ ቤቶች ባግባቡ ሳይዙና ሳይመለከቱ ቀርተው በዚህ ረገድ ቅሬታው በስርዓቱ መሰረት ለሰበር ሰሚ ችሎት ቢቀርብና ችሎቱም ይህንኑ ቅሬታ ተቀብሎ በዚህ ረገድ የተፈፀመውን ስህተት ቢያርም የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ አይደለም የሚል ቅሬታ የሚነሳበት ጉዳይ አይደለም፡፡ምክንያቱም የአንድ የህግ ድንጋጌ ትክክለኛ ትርጉም እና አተገባበር የሚኖረው በህጉ አግባብ የተቆጠሩት ማስረጃዎች ያረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ከእነ ሙሉ ይዘታቸው ታይተውና ተመዝነው እንጂ ማስረጃዎቹ ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር በመተው ሊሆን አይገባምና፡፡ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ ያነሳው ቅሬታ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ቀጥሎ መታየት ያለበት የሕግ ጥያቄ አመልካች በገባው የእቃ ማንገዝ ውል መሰረት ሲሚንቶውን በሙሉ በጥንቃቄ በማንገዝ፣ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን አለመወጣቱ አመልካችን በፍታሐብሔር ተጠያቂ ከመሆን አልፎ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ በእምነት ማጉደል ወንጀል የሚያስጠይቃቸው ነው ወይስ በሌላ ድንጋጌ? የሚለው መሠረታዊ ነጥብ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የወንጀል ህጉ በንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝርበት ምእራፍ ሁለት በልዩ ሁኔታ በተንቀሳቃሽ ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝረው ክፍል አንድ ሥር የተደነገገው የዕምነት ማጉደል ወንጀል መሠረታዊ ባህሪ ይዘትና የሚያስከትለው ኃላፊነትን የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ ሙሉ ይዘቱ ሲታይም፡

" ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ ፣ የወሰደ ፣የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል" በማለት ያስቀምጣል፡፡ የተጠቃሹ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተከሣሹ ወንጀል ሃጣብ ግምት የሚደነግግ ሲሆን ይዘቱም ተከሣሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ማስረዳት ካልቻለ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ማዋል ሃጣብ እንዳለው ይቆጠራል የሚል ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ ሙሉ ይዘት ሲታይ አመልካች በገባው የእቃ ማንገዝ ውል መሠረት ሲሚንቶውን በማንገዝ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ በእምነት ማጉደል ወንጀል ተጠያቂ የሚሆን ስለመሆኑ አይደነግግም፡፡የድንጋጌው ይዘት አንድ ሰው አንድን ንብረት ለአንድ አገልግሎት ለማዋል በኃላፊነት ተረክቦት ንብረቱን ለተባለው አገልግሎት ሳያውል ሲቀር በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቅ መሆኑን የሚመለከት እንጂ በማጓጓዝ ውል መሠረት በልምድ መሠረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ አድርጐ እቃውን በማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ያልተወጣ አጓዥ በዕምነት ማጉደል ወንጀል እንዲጠየቅ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ የማያሣይ በመሆኑ በዚህ በኩል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል በማጓጓዝ ውል መሠረት በልምድ መሠረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ በማድረግ እቃውን ማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ሳይወጣ አመልካች ሲሚንቶውን መሸጡና የሸጠውም ያልተከፈለውን የማጓጓጉ ዋጋ ለራሱ ለማድረግ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ማንም ሰው በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቀው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የተሰጠውን ዋጋ ያለው ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የአመልካች አድራጎት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገዉ የወንጀል ሃላፊነት ግምት የማይሸፈን መሆኑን ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ እንዲሁም በአመልካችና በሲሚንቶው አስጫኝ ድርጅት መካከል ከነበረው የውል ግንኙነት ለመረዳት የሚቻል ሁኖ አግኝተናል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የመጓጓጉ ዋጋውን ሲሚንቶውን ሸጦ ለራሱ ማድረጉ ከስምምነት የመነጨ አድራጎት ያለመሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ይህ የአመልካች መብት በሲሚንቶ አስጫኙ ድርጅት በውሉ መሰረት ካልተፈጸመም አመልካች ያላቸው መብት በሕግ አግባብ መብታቸውን ማስከበር ነው፡፡ከሕግ ውጪ መብት አለኝ በማለት የሌላውን ሰው መብት ለራስ ጥቅም ማዋል ደግሞ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር ሲሆን ይህም የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል አድራጎት መሆኑን ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 436(ለ) ስር ከተደነገገው ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው የህግ፣ የግዙፍ ተግባርና የሞራል ሁኔታ በአንድነት ተጣምረው መገኘታቸው ሲረጋገጥ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 23 ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ሰፍሯል፡፡ በያዝነው ጉዳይም የአመልካች አድራጎት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ስር የተዘረዘሩት የህግ የሃላፊ ሁኔታዎች ያልተሟሉ ቢሆንም አድራጎቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 436(ለ) ስር የሚሸፈን ሁኖ ስለአገኘነው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን የጥፋተኛነት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113(2) እና 195(2)(ለ)(2) ድንጋጌዎች አግባብ በማሻሻል አመልካች ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መብት ማስከበር ወንጀል የፈጸመ በመሆኑ ጥፋተኛ ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች መቀጣት ያለበት በዚህ ችሎት ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ ስር ሲሆን ድንጋጌው የሚያስቀጣው ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ሲሆን እኛም የአመልካችን አድራጎትና የቅጣትን መሰረታዊ ዓላማ እንዲሁም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያስያዛቸውን ሪከርድ ያልቀረበበት መሆኑንና የቤተሰብ አስተዳዳሪነቱን የሚመለከቱትን የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተናል፡፡ቅጣቱን ደረጃ ላልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎች ደረጃ የሚወጣበትን አግባብ መሰረት በማድረግ አስልተናል፡፡ይህን ሁሉ መሰረት ስናደርግ አመልካች የታሰረበት ጊዜ በቂ ሁኖ እንዲፈታ ማድረጉ አመልካችን የሚያርም ሌሎች መሰል ወንጀሎችን የሚያስጠነቅቅ ሁኖ አግኝተናል፡፡ሲጠቃለልም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የአመልካችን አድራጎት በሚሸፈነው ድንጋጌ ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 60228 ጥር 29 እና 30 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 195(2)(ለ(2)) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአመልካች አድራጎት በወንጀል የሚያስጠይቅ ሁኖ የሚሸፈነውም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ሳይሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 436(ለ) ስር ነው በማለት አመልካች ለዚሁ አድራጎቱ የታሰረው ጊዜ በቂ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች የታሰረው ጊዜ ለአድራጎቱ በቂ ነው ተብሎ በዚህ ችሎት መወሰኑን አውቆ በሌላ ወንጀል የማይፈለግ መሆኑን አረጋግጦ ከእስር እንዲፈታው ለመቐሌ ማረሚያ ቤት የመፍቻ ትዕዛዝ ይላክለት ብለናል፡፡ይፃፍ፤፤
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94227

ቀን 05/09/2006 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ገ/መድህን ኃ/ማሪያም - ቀረቡ(በV.c)

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ዐ/ህግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች በዚህ መዝገብ አቤቱታ ያቀረቡት ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገው መጥሪያው በመደበኛ መኖሪያ አድራሻቸው እንዲደርሳቸው ሳይደረግ በመሆኑ ክርክሩ በሌሉበት ታይቶ የቴሌኮምኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 464/1997 በአንቀጽ 4 ስር በ29/05/2005 ዓ/ም የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የአስር ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ እንደገና ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡትን ማመልከቻ እና ተጠሪው የሰጠውን መልስ ከመረመረ በኋላ የአመልካችን ጥያቄ ባለመቀበል የትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.50320 በ19/11/2005 ዓ/ም. በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.202 (2) መሰረት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ፍ/ቤት እንድቀርብ ባስመዘገብኩት አድራሻ የተላከ መጥሪያ የሌለ ከመሆኑም በተጨማሪ ለዋሴም በተመሳሳይ የደረሰ ነገር የለም በማለት በሌሉበት የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ላማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑ አለመሆኑ ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህ መሠረት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ያየው በፌ/ከ/ፍ/ቤት ስልጣኑ ሲሆን ጉዳዩ ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ የሰጠውም በተደጋጋሚ በፓሊስ ተፈልገው አልተገኙም፣ በጋዜጣም ተጠርተው አልቀረቡም በማለት ነው፡፡ ተከሳሽ በበኩላቸው በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳልኝ ይገባል በማለት የሚከራከሩት መጥሪያው በምርመራ ጊዜ ቃሌን ስሰጥ በገለጽኩት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና በዚሁ መሠረት ተጠሪው በክስ ማመልከቻው ላይ በገለፀው መደበኛ መኖሪያ አድራሻዬ አልደረሰኝም፣ ተከሳሽን ማግኘት አልቻልኩም በማለት ለፍ/ቤቱ የገለፀው ከመደበኛ መኖሪያ ቦታዬ ውጪ የሚገኝ የሌላ ወረዳ ፓሊስ ነው በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሰረቱ አንድ ከሳሽ በሌለበት የተሰጠበት ውሳኔ እንዲነሳለት የሚያቀርበውን ማመልከቻ ለመቀበል ከሚቻልባቸው ምክንያቶች አንዱ መጥሪያ ለተከሳሹ ያልደረሰው የመሆኑ ጉዳይ ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 199/ሀ/ ስር የተመለከተ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ለአመልካች መጥሪያው የተላከው የአመልካቹ መደበኛ መኖሪያ አድራሻ በሆነው ውቅሮ ወረዳ ፓሊስ በኩል ሳይሆን ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት ወረዳ በሚገኘው እና ምርመራውን አጣርቷል በተባለው አጽቢ ወንበርታ ወረዳ ፓሊስ በኩል ስለመሆኑ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡

የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ተከሳሹን በጋዜጣ ሊያስጠራ የቻለው እና ቀጥሎም ጉዳዩን አመልካች በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ የሰጠው የአጽቢ ወንበርታ ወረዳ ፓሊስ ቁጥር 1008/8/34 በ07/09/2004 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ተከሳሹ ከአካባቢያችን ውጪ ስለሆነ እና ዋሱም ተነግሮት ላቀርበው አልችልም ስላለ ልናቀርበው አንችልም ሲል በሰጠው ምላሽ ሳቢያ ስለመሆኑ አመልካች ከስር ጀምሮ እየተከራከሩ ሲሆን መጥሪያው በአመልካቹ የተመዘገበ የመኖሪያ አድራሻ ተልኮ የነበረ ስለመሆኑ ወይም አመልካቹ ከዚሁ አድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ ያልቻሉ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ የማያመለክት ከመሆኑም በላይ የአጽቢ ወንበርታ ወረዳ ፓሊስ በቁጥር 1008/8/34 በ07/09/2004 ዓ.ም የተሰጠውን ምላሽ አስመልክቶ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላቀረቡት ክርክር ተጠሪው ያቀረበው ግልፅ ማስተባበያ አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡ በመሰረቱ ባስመዘገቡት አድራሻ መጥሪያው ለአመልካቹ የተላከ መሆኑ ወይም አመልካቹ በዚህ አድራሻቸው ተፈልገው ያልተገኙ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወደ ጋዜጣ ጥሪ አማራጭ የሚኬድበት አግባብ ስለማይኖር የጥሪ ማስታወቂያው በጋዜጣ መነገሩ ብቻውን መጥሪያው ለአመልካች በአግባቡ እንዲደርስ ተደርጓል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ዋሱ ተከሳሹን ላቀርበው አልችልም ብለዋል መባሉም ኃላፊነት ሊያስከትል የሚችለው በዋሱ ላይ እንጂ በተከሳሹ ላይ አይደለም፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ማንኛውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸው ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 20(4) ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይህንን ሕገ መንግስታዊ መብት ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉት ደግሞ ክስ የቀረበባቸው መሆኑን በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 123 በተመለከተው መሰረት በሚላክ መጥሪያ እንዲያውቁት ሲደረግ ነው፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩ አመልካች በሌሉበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የአስር ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው ባስመዘገቡት የመኖሪያ አድራሻ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ ሆኖ እያለ እና ይህም በሌሉበት የተሰጠባቸውን ውሳኔ ለማንሳት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

199(ሀ) ድንጋጌ መሰረት በቂ ምክንያት ሆኖ እያለ ውሳኔው ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሌሉበት ታይቶ የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የአስር ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 50320 በ19/11/2005 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በሌሉበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የአስር ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው ባስመዘገቡት የመኖሪያ አድራሻ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ ወይም በዚሁ አድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ አለመቻላቸው ሳይረጋገጥ በመሆኑ እና ይህም በሌሉበት የተሰጠባቸውን ውሳኔ ለማንሳት በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 199(ሀ) ድንጋጌ መሰረት በቂ ምክንያት በመሆኑ ውሳኔው ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 202(1) በተደነገገው መሰረት ቀድሞ ጉዳዩን ያዩት ዳኞች በማይሰየሙበት ችሎት አመልካች ባሉበት ጉዳዩን እንደገና በማየት በስነ ስርዓት ሕጉ በተመለከተው መሰረት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚሁ መሰረት መፈፀም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እንዲሁም በሚገኙበት የመቀሌ ከተማ ማረሚያ ተቋም በኩል ለአመልካቹ ይላክ፡፡
5. ውሳኔው የተሰጠው በአብላጫ ድምጽ ነው፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የልዩነት ሀሳብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተጠቀሰው ዳኞች በአብላጫ ድምጽ በተሰጠው ፍርድ ሰላልተስማማን የልዩነት ሀሳባችን እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

በመሰረቱ ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነውን የኤሌክትሪክ ኃይል ሰርቆት ወንጀል ያጣራው የአፅቢ ወረዳ ፖ/ሊስ ሳይሆን የትግራይ ብ/ክ/መ/ፖ/ሊስ ኮሚሽን ስለመሆኑ የክልል ጠ/ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት አመልካችን የክልሉ ፖ/ሊስ ኮሚሽን እንዲያቀርበው በተደጋጋሚ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ፖ/ሊስ ከአድራሻው ፈልጎ ማጣቱን እና ማቅረብ አለመቻሉን ገልጾ ምላሽ የሰጠው የክልሉ ፖ/ሊስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኮሚሽን እንጂ የወረዳው ፖ/ስ ጽ/ቤት አለመሆኑን የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት የሠጠውና ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የትዕዛዙ ግልባጭ በግልጽ ያሳያል፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ለሰጠው ትዕዛዝ መነሻ ያደረገው አመልካች በሰበር አቤቱታው እንደገለጸው በወረዳ ፖ/ስ የተሠጠውን ምላሽ ሳይሆን ከክልሉ ፖ/ስ ኮሚሽን የተሰጠውን ምላሽ መሆኑን ነው፡፡የክልሉ ፖ/ስ ኮሚሽን ደግሞ አመልካችን ከአድራሻው ፈልጎ ማጣቱንና በዚህም ምክንያት ማቅረብ አለመቻሉን አረጋግጦ እስከገለጸ ድረስ ለአመልካች መጥሪያው በአድራሻው እንዲደርሰው ተገቢው ጥረት አልተደረገም ለማለት የሚቻል አይሆንም ፡፡

በአድራሻው ተፈልጎ ማግኘት ካልተቻለ ደግሞ የሚኖረው አማራጭ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 162(1) ሥር እንደተመለከተው የጥሪ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ማድረግ ሲሆን በጋዜጣም ጥሪ ተደርጎለት አመልካች ሊቀርብ አልቻለም፡፡እንዲሁም ዋሱም ተጠይቆ አመልካች በአድራሻው እንደሌለ እና ማቅረብ እንደማይችል ገልጿል፡፡ እነዚህም ጠቅላላ ሁኔታዎች አንድ ላይ ሲታዩም አመልካች በራሱ ምክንያት ፍርድ ቤት ቀርቦ ለመከራከር አለመፈለጉን መደምደም ከሚቻል በስተቀር ከመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት አንጻር የተፈጸመ ጉድለት የለም፡፡ በአጠቃላይ መጥሪያው በአድራሻ እንዲደርሰው ተገቢው ጥረት ተደርጎ ከታጣ በኋላ በጋዜጣም ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ የተነሳ ጉዳዩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መጥሪያው በአድራሻው እንዲደርሰው አልተደረገም በሚል ምክንያት እንዲነሳ ማድረግ በክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ አብላጫው ድምጽ መጥሪያው በአግባብ ለአመልካች እንዳልደረሰው ቆጥሮ በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ ባለማግኘታችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94404

መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- የደቡብ ብሔር በሔረሰቦች ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል አቃቤ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ መኩሪያ ቡሎ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ የእስር ቅጣት አፈፃፀሙ የሚገደብበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27(1) እና 540 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከሌላ ካልተያዘው ግብረ አበር ጋር በመሆን አቶ ላልሞ ላግዴ የተባለውን የግል ተበዳይ በክላሽ መሳሪያ አራት ጥይት ተኩሶ ስቷል፤ ከተሰወረ በኋላም ተይዟል በማለት ዘርዝሮ የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈፅሟል የሚል ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ክደው ተከራክረው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቶ ክሱን ማስረዳቱን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦ ተጠሪ ክሱን እንዲከላከሉ መብታቸውን ተጠብቆላቸው የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ በመጨረሻም ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን መርምሮ ተጠሪ የአመልካችን ማስረጃዎች በመከላከያ ማስረጃዎቹ አላስተባበሉም በማለት ተጠሪን ክስ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን አስተያየት ተቀብሎ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መመልከቱን ከጠቀሰ በኋላ በሶስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ሆኖም የእስራት ቅጣት አፈፃፀሙን በተመለከተ ተጠሪ ታማሚ መሆናቸውን ሐኪም አረጋግጧል፤ በግል ተበዳይም የደረሰ ጉዳት የለም በሚል ምክንያት በሁለት አመት ገደብ እንዲሆን ወስኗል፡፡ በዚህ የእስራት ቅጣት እንዲገደብ ተብሎ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከሩ በኋላ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 34280 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ/ም የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱ እንዲገደብ የሰጠውን ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጽንቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በተጠሪ ላይ የተጣለው የሶስት አመት ፅኑ እስራት ቅጣት የተገደበው ሕጉ የሚጠይቃቸው መስፈርቶች ሳይሟሉና አግባብነት የሌለው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተጠቅሶ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ከድርጊቱ አፈፃፀም እና ተጠሪ የግል ተበዳይን ይቅርታን ያልጠየቁ፣ ካሳም ያልከፈሉ ከመሆናቸው አንጻር ሲታይ የእስራት ቅጣቱ መገደቡ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ድንጋጌ አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ ድርጊቱን ያልፈፀሙ መሆኑን፣ ይግባኝ ያልጠየቁበት ምክንያትም በአቅመ ደካማነታቸው የተነሳ መሆኑንና የእስራት ቅጣቱ የተገደበው ባለባቸው በሽታ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ ነው በማለት ዘርዝረው ውሳኔው እንዲጸናላቸው ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ በተከሳሽ ላይ የተወሰነ የቅጣት ውሳኔ ከመገደቡ ወይም የገደብ ውሳኔው ከመሻሩ በፊት የቅጣት ገደብ ስለሚከለከልበትና ስለሚሻርበት ሁኔታ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 እና 197 ስር የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ በተወሰነ ገደብ ቅጣትን ማቆም የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ከአንቀጽ 190 እስከ 200 ስር አስፍሮ ይገኛል፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 190 ሲታይም ከእስር በገደብ መለቀቅ ማለት ፍርድ ቤት አንድ ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑን አረጋግጦ ከእስር እንዲፈታ የሚደረግበት አግባብ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሳሽ የቅጣት አፈፃፀም እንዲገደብ ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ መስጠት የማይችሉባቸው ሁኔታዎችም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡በሌላ አገላለፅ ፍርድ ቤቱ የቅጣት ውሳኔውን በገደብ የሚያስቆመው የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን እነዚህም፡- ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፣ ጥፋቱ በመቀጮ፣ በግዴታ ስራ ወይም ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል መሆኑና በዚህ ውሳኔ ብቻ እስከ መጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን ያመነበት እንደሆነ አስተያየት ከሰጠ በኋላ ቅጣት ሳይወስን የተወሰነ የፈተና ጊዜ ሊሰጠው የሚችልበት አግባብ መኖሩን ሕጉ ያሳያል፡፡ እንዲሁም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግም የሚታገድ መሆኑና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱ ከአፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝ እንደሚችል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከላይ የተመለከቱትን የገደብ አሰጣጥ ውሳኔዎች ተግባራዊ ለማድረግ ግን ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎችን በጥንቃቄ በማየት የተሟሉ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በዚህ አግባብ የገደብ ውሳኔ ካልተሰጠ የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ አላማ ለማሳካት የማይቻል መሆኑ ይታመናል፡፡

የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 196 ስር እንደአስቀመጠው ፍርድ ቤቱ ለጥፋተኛው የሚሰጠውን የፈተና ጊዜ የሚወሰነው የወንጀሉን ከባድነት፣ በወንጀል ድርጊት መደጋገም ሊደርስ የሚችለውን ጉዳትና በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚችለውን እምነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡ የተከሳሹን የገደብ ጥያቄ ፍርድ ቤቱ ከመቀበሉ በፊትም ተከሳሹ ቀድሞ የነበረውን ጠባይ ፣ የአኗኗርና የስራውን ሁኔታ ምን አይነት እንደነበር ፍርድ ቤቱ መረጀ መሰብሰብ እንደሚችልም ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197/1/ ሲታይም ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ እንዳይፈፀም ለማድረግ በቅድሚያ ሊሟሉ የሚችሉትን ሁኔታዎች አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ እነዚህም ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው በመልካም ጠባይ እንደሚመራ ካመነ፣ ጥፋተኛው እንዲፈፀም የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል ካረጋገጠ ፣ ጥፋተኛው በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጥፋቱ የደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍል እና ለዚሁ ጉዳይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ከሰጠ በኋላ ስለመሆናቸው ሕጉ በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ለገባበት ግዴታ አፈፃፀም መተማመኛ ዋስትና እዲያቀርብ እንደሚያደርግ ተጠቃሹ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር አስፍሮ ይገኛል፡፡

እንግዲህ ህግ አውጭው አንድ ሰው በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ቅጣት ሳይጣል ጥፋተኛ ነህ በማለት ብቻ ሊታለፍ የሚችልበትን እንዲሁም ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ቅጣቱ ከተጣለ በኋላ ደግሞ የእስራት ቅጣቱ ሳይፈፀም ተገድቦ የሚቆይበትን አግባብ በግልፅ የዘረጋ መሆኑን ከአንቀፅ 190 እስከ 200 ድረስ ያሉትን የወንጀል ህግ ድንጋጌዎችን በማየት የምንረዳው ጉዳይ ሲሆን አንድን ጥፋተኛ በተወሰነ ገደብ ከእስር ለመፍታት ግን በህጉ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆኑን ፍ/ቤቱ አስቀድሞ ማረጋገጥ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የገደብ ውሳኔው በዘፈቀደ የሚሰጥ ሳይሆን ህጋዊ ሁኔታዎች መሟላታቸው በሚገባ ተረጋግጦ የሚሰጥ ነው፡፡ በህግ ተለይተው የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ደግሞ የዳኝነት አካሄድ የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሰር ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ የጣለውን የሶስት አመት ጽኑ እስራት ቅጣት በሁለት አመት የገደበው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ስር የተመለከቱት ቅድመ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታዎች መሟላታቸውን መርምሮ ስለመሆኑ የውሣኔው ግልባጭ አያሣይም፡፡ ይልቁንም ፍርድ ቤቱ አጽንኦት የሰጠው የተጠሪን በሽተኛ መሆን በሐኪም መረጋገጡንና በግል ተበዳይ ላይ የደረሰ ጉዳት ያለመኖሩ ነው፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ ተጠሪ መልካም ጠባይ እንደሚመራ ስለማመኑ፣ ተጠሪ እንዲፈጽም የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል ማረጋገጡን፣ ተጠሪ በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጥፋቱ የደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍልና ለዚሁ ጉዳይ በተወሰነ ጊዜ ውሰጥ የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ስለመስጠቱ በቅጣት ፍርድ ላይ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 አግባብ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ የተጠሪ በሽተኛ መሆን ደግሞ ሕጉ ከአስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ በግልጽ ያልተጠቀሰ ሲሆን በግል ተበዳይ ላይ የደረሰ ጉዳት ያለመኖሩም ድርጊቱ ሙከራ ሁኖ አራት ጥይት ተተኩሶ የተሣተ እንደመሆኑ መጠን ለገደብ ውሣኔው የግድ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለበት ምክንያት አይደለም፡፡ ተጠሪ ከግል ተበዳይ ጋር ይቅርታ ማውረዳቸውም ያልተረጋገጠ ሲሆን ይልቁንም እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገው ክርክር ስለአጥፊነታቸው አምነው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ይህም ተጠሪ የተጣለባቸው ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶላቸው አመላቸው ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገዱ ናቸው ብሎ ለመደምደም የማይቻል መሆኑን በግልጽ የሚያሣይ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ለማጽናት መሠረት የደረገው የዚህ ችሎት አሰገዳጅ ትርጉም ሲታይም ከዚህ ጉዳይ በመሠረታዊ ነጥቦቹ ተመሣሣይነት የሌለው ነው፡፡ በሰ/መ/ቁ. 34280 የተሰጠው የሕግ ትርጉም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በገደብ አወሣሰን በሕጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች ባገናዘበ መልኩ ዳኝነት መስጠቱን የሰበር ሰሚ ችሎቱ በማረጋገጥ የሰጠው ከመሆኑ ውጪ በሕጉ የተመለከቱትን መሰፈርቶችን ሣይከተል የተሰጠ ውሣኔን የተቀበለ ባለመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች በተጠሪ ላይ የተጣለው የሶስት አመት ጽኑ እሰራት በሁለት አመት የታገደው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ስር የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ሣይሟሉ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቅጣት ገደብ የውሣኔ ክፍል ሕጉን ያልተከተለ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና የሰበር ችሎትም ይህንኑ የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሣኔ ክፍል ማረም ሲገባቸው ማለፋቸውና ውሣኔውን ሙሉ በሙሉ ማጽናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28009 መጋቢት 27 ቀን 2005 በተጠሪ ላይ የተወሰነው የሶስት አመት ጽኑ እሰራት ቅጣት ውሣኔ ሊገደብ ይገባል ተብሎ ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 59288 ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም በክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 59939 ነሐሴ 23 ቀን 2005 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፀናው የውሣኔ ክፍል ብቻ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/2/መ/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ለፍርድ ቤቶቹ የውሣኔው ግልባጭ ይድረሣቸው ብለናል፡፡

2. በዚህ በኩል የእሰራት ቅጣት ውሣኔው አፈፃፀም እንዲገደብ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ተሽሮ ተጠሪ የሶስት አመት ጽኑ እሰራት መፈጸም ያለባቸው በማረሚያ ቤት ነው ብለናል፡፡ የክፍሉ ፖ/ሊስ ተጠሪን ይዞ ለሀዋሣ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብ፣ የሀዋሣ ማረሚያ ቤትም ከክፍሉ ፖ/ሊስ ተጠሪን ተረክቦ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ ቀድሞ የታሰሩትን ጊዜ ታሣቢ በማድረግ የሶስት አመት ጽኑ እሰራት ቅጣትን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95438

ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ሰለሞን ደሣለኝ ጠበቃ ግደይ ገድሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የደቡብ ክልል ዐ/ህግ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በቼክ የማጭበርበር ወንጀልን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው በሀዋሳ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰበር ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ወንጀል ክስ መነሻነት ነው፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ በ3 መዝገቦች ያቀረበባቸው ክሶች ዝርዝር፤-

1) አመልካች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ወንጀል ህግ ቁ. 693(1) በመተላላፍ በ29/02/04 ዓ.ም ከጧቱ 4.00 ሰዓት ለግል ተበዳይ ጥላሁን ሰይድ የብር 12,786 ስንቅ የሌለው ቼክ ስለሰጠ፡
2) በቀን 5/03/2004 ዓ.ም ከቀኑ 5.00 ሰዓት ላይም ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ በመተላለፍ ለግል ተበዳይ ጌቱ ተዋታን የብር 20,000 ስንቅ የሌለው ቼክ ስለሰጠና፡-
3) እንዲሁም አሁንም ተመሳሳይ የወንጀል ህጉን ድንጋጌ በመተላላፍ ለግል ተበዳይ ግርማ ፈንዲጋን እንደ ቅደም ተከተላቸው በቀን 30/02/2004 ዓ.ም እና በቀን 25/03/2004ዓ.ም የብር 20,624 እና 17,328 ስንቅ የሌላቸው ቼኮች ወይም የሚያገበት ገንዘብ የሌለው መሆኑን እያወቀ ቼክ ስለሰጠ በቼክ የማጭበርበር ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡

አመልካችም ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት እንዲረዳ ከተደረገ በኋላ ክክሱ ላይ የሚያቀርበው መቃወሚያ እንደሌለው ገለፆ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኗል፡፡ሆኖም ግን ድርጊቱን የፈፀምኩት የግል ተበዳዮቹን ለማጭበርበር አስቤ ሳይሆን ጨረታ አሸንፌ ስለነበር ገንዘብ ከመንግስት እስኪለቀቅልኝ ድረስ ቼኩን በዋስትና ይዘው ገንዘቡ ሲለቀቅ እንዲወስዱ ተብሎ ነበር በማለት የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡በመቀጠልም ፍ/ቤቱ የዐ/ህግን የስነድና የሰው ምስክሮችን አድምጦ ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመረመረ በኋላ አመልካች ወንጀሉን እንዲከላከል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ግን አመልካች የበኩሉን መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ወንጀሉን ባለመከላከሉ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ በሦስቱም ወንጀሎች ስር አመልካችን ጥፋተኛ ካደረገ በኋላ ቅጣትን በተመለከተም ለእያንዳንዱ ወንጀል አመልካች በ5 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ከወሰነ በኋላ ቅጣቶቹም በማረሚያ ቤት በኩል ተጀምረው እንዲፈጸሙ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ እና ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች አስቀርቦ በጉዳዩ ላይ እንዲከራከሩ ካደረጋ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር የስር ፍ/ቤቱን የጥፋተኝነት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ካፀና በኋላ ቅጣትን በተመለከተ ግን በ2002 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሠረት በማድረግ ሦስቱም ወንጀሎች በተመሳሳይ በደረጃ 5፤የእስራት ቅጣት መነሻም እርከን 14 ስር ለእያንዳንዱ ወንጀል 2 ዓመት ከ6 ወር መነሻ ቅጣት ወስኖና እነዚህንም በአንድነት በመደመር ለሦስቱም ተደራራቢ ወንጀሎች 7 ዓመት ከ6 ወር የእስራት ቅጣት ወስኗል፡፡ በመቀጠልም የቅጣት ማክበጃ አሰተያየትን በተመለከተ ቅጣቱ እንዲከብድ ተብሎ በዓ/ህግ በኩል የቀረበ አስተያየት የለም በማለት ካለፈ በኋላ የቅጣት ማቅለያን ምክንያትን በተመለከተ ደግሞ የቀረበው አስተያየት በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው አልፎ በመነሻ ቅጣቱ 7 ዓመት ከ6 ወር እስራት እንዲቀጣ ሲል በበታች ፍ/ቤት የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል ይህ ውሳኔም በክልሉ ሰበር ችሎትም መሠረታዊ የህግ ስህተት የለውም ተብሎ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

አሁን ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይዜንኑ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጡት ውሳኔዎች ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታልና ስህተቱ ይታረምልኝ የሚል ሲሆን አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰው የጉዳት መጠን እና በስር ፍ/ቤት የተወሰነው ቅጣት ተመጣጣኝነት፤እንዲሁም በአመልካች የቀረቡት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የመታለፋቸውን አግባብነት ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ 2/2006 አኳያ ለመመርምር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ዐ/ህግም ቀርቦ የበኩሉን መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዐ/ህግ በኩል የቀረበው መልስ ይዘትም ፤- በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሻሽሎ የተወሰነውና በክልሉ ሰበር ችሎትም ተቀባይነት አግኝቶ በትዕዛዝ እንዲፀና የተደረገው የቅጣት ውሳኔ ተገቢ እና የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጐ እንዲወሰንለት ጠቅሶ መከራከሩን የሚያሳይ ሲሆን አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመ/መልሱን ሰጥቶበታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሠረቱ የቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰንን ትክክለኛነት እና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥም ሆነ ሰለመቆጣጠር እንዲቻል የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ (Manual) ማውጣት ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 88(4) ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም በዚህ መሠረት ከዚህ ቀደም የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.1/2002 አውጥቶ ከግንቦት 9 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ሲሰራበት የነበረ ስለመሆኑ ይታወቃል፡፡ሆኖም ግን በኋላ ላይ ይህን መመሪያ ማሻሻል በማስፈለጉ የተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 በምትኩ ወጥቶ ከ1/2/2006 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ መዋሉም የሚታወቅ ነው፡፡ቅጣትን በሚመለከት ደግሞ አዲሱ የወንጀል ህግ ከመውጣቱ በፊት በተፈፀመ ወንጀል ከተፈረደበት እና ሆኖም ግን ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ስራ ላይ ከነበረው ወንጀል ህግ ይልቅ አዲሱ ህግ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቀልለትና ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ይሄው በአዲሱ ህግ ላይ ያለው ቅጣት የሚፈጽምበት ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ ቁ. 6 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም ምንም እንኳ አመልካች እነኝህን ወንጀሎች የፈጸመው የተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 ዓ.ም ከመውጣቱ በፊት ቢሆንም ይህ ጉዳይ በዚህ ሰበር ችሎት ታይቶ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ከበፊቱ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 1/2002 ይልቅ በኋላ ተሻሽሎ ወጥቶ በአሁኑ ጊዜ ተፈፃሚነት ያለው የተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 አመልካች የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ይሄው በጉዳዩ ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው ስለሚገባ በዚሁ መሠረት በአመልካች ላይ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ተመርምሯል፡፡

አመልካች በሦስቱም ቼኮች የሚያዝበትን ገንዘብ ከባንክ ሳይኖረው የተለያዩ ቼኮችን በተለያየ ጊዜ ለተለያዩ ሦስት ግለሰቦች አውጥቶ ሰጥቷል ተብሎ ጥፋተኛ የተባለው የቼኮቹ ገንዘብ መጠን እንደቅደም ተከተላቸው ብር 12,786፤20,000 እና ብር 37,972 የያዙ ስለመሆናቸው የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ በግልፅ ያስረዳሉ፡፡ይህም በተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ መሠረት የእያንዳንዱ ተደራቢ ወንጀል ደረጃ እና የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን እንደቅደም ተከተላቸው በ1ኛ ና 2ኛ ተደራራቢ ወንጀሎች የተገለፀው የገንዘብ መጠን በደረጃ 3 እና የእስራት መነሻ ቅጣቱም በእርከን 9 ስር የሚወድቁ ሲሆን በ3ኛ ተደራቢ ወንጀል የተገለጸው የገንዘብ መጠን ደግሞ በደረጃ 4 እና እርከን 11 ስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚወድቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመመሪያው አንቀጽ 22(1)(ሀ) መሠረት ደግሞ ለእያንዳንዱ ተደራቢ ወንጀል ለብቻቸው ሊወሰን የሚገባው መነሻ ቅጣትም እንደቅደም ተከተላቸው 1 ዓመት ከ6ወር፤1 ዓመት ከ6 ወር እና 2 ዓመት እስራት ሆኖ ተወስኗል፡፡እነዚህ መነሻ የእስራት ቅጣቶችም በአንድ ላይ ሲደመር 5 ዓመት ሲሆን ይህም ከፍ ሲል በተገለፀው ተመሳሳይ የመመሪያው ድንጋጌ መሠረት በእርከን 20 ስር ይወድቃል፡፡

በሌላ በኩል የቅጣት ማክበጃ ምክንያትን በተመለከተ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ በዐ/ህግ አስተያየት አልቀረበም በሚል ምክንያት ሰላለፈ እና በዚህ ነጥብ ላይም በዐ/ህግ በኩል የቀረበ ቅሬታ ባለመኖሩ በዚሁ የሚታለፍ ይሆናል፡፡ የቅጣት ማቅለያን በተመለከተ ግን ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ሳይቀበለው ያለፈው የቀረበው ምክንያት በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ይሁን እንጂ አመልካች ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆኑትን ተደራራቢ ወንጀሎች ከመፈጸሙ በፊት የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበበት እና የዘወትር ፀባዩም መልካም ስለመሆኑና እንዲሁም ይዜንን ወንጀል ከፈፀመም በኋላ በመፀፀት ለግል ተበዳይ ገንዘብ መክፈል የጀመረ ስለመሆኑ በከፍተኛ ፍ/ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡እነዚህ በበታች ፍ/ቤት የተረጋገጡት ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 82(1)(ሀ)፣5(ሠ) እንዲሁም በመመሪያው አንቀጽ 23 መሠረት መነሻ የቅጣት እርከኑን ከእርከን 20 ወደ እርከን 18 እንዲቀል ያደርጋሉ፡፡ በመመሪያው መሠረት የእርከን 18 መነሻ ቅጣት 3 ዓመት ከ7 ወር ሲሆን መድረሻው ደግሞ 4 ዓመት ከ4 ወር በመሆኑ በዚሁ ፍቅደ ስልጣን ውስጥ ደግሞ የወንጀል አፈፃፀሙ ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ ገብቶ እንዲታይ ከተደረገ በኋላ አመልካች በ4 ዓመት እስራት ቅጣት ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለልም የአመልካች ቅጣት ውሳኔ ሊመረመር የሚገባው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ወንጀል ህግ አንቀጽ 6 ስር እንደተመለከተው በ2006 ዓ.ም ከጥቅምት ወር ጀምሮ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሻሽሎ በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት መሆን ስላለበት በዚህ መሠረት በስር ፍ/ቤቶች በአመልካች የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ብቻ አሻሽለን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ጉዳይ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 57677 በ7/09/05 ዓ.ም ተወስኖ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 58576 በ23/12/05 ዓ/ም በትዕዛዝ እንዲፀና የተደረገው የ7 ዓመት ከ6 ወር እስራት ወደ 4 ዓመት እስራት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ)(2) መሠረት ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
3. የቅጣት ውሳኔውም መሻሻሉ ታውቆ በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም ለስር ፍ/ቤቶችና ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት የውሳኔ ግልባጭ እና ትዕዛዝ ይተላለፍ መዝገቡ ተዘግቷል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 96954

ሚያዚያ 24 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ዘፈሩ ወልደ ትንሣኤ አብርሃ ጠበቃ ሽፈራው በላይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ህግ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል መፈጸም ጥፋተኛ በሆነ ሰው ላይ የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ህጋዊነት የሚመለከት ነው ከሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ከሳሽ ተከሳሹ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ የሰው ህይወት ጤናና ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ግዴታ ያለበት ሆኖ እያለ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት 25/01/2006 ዓ.ም ከምሽቱ አራት ሠዓት በየካ/ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13/14 ለም ሆቴል ፊት ለፊት አልኮል ጠጥቶ ሲያሽከረክር ለእግረኛ ቅድሚያ በመከልከል ሲያሽከረክር ከፊት በነበረው የሰሌዳ ቁጥር 2-42769 ለጊዜው ማንነቱ ያልታወቀው ገጭቶ የሞት አደጋ ያደረሰበት በመሆኑ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

ተከሳሽ የወንጀሉን ድርጊት ፈጽሜአለሁ ጥፋተኛ ነኝ፡፡ ሆኖም በወቅቱ መጠጥ አልጠጣሁም ነበር ፡፡ ሟችን የገጨሁት በላዳ መኪና ተከልሎ መንገድ ሲያቋርጥ ነው፡፡ ከዚያም ሟችን ወደ ሆስፒታል ወስጄው ነበር ሊተርፍ አልቻለም በማለት ተከራክሯል ፡፡ ዐቃቤ ህግ መጠጥ የመጠጣቱ ጉዳይ ወሳኝ ነጥብ አይደለም ፡፡ በእምነቱ መሠረት ፍርድ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል ፡፡ ፍርድ ቤቱ አመልካች /ተከሳሽ/ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543 (2) የተመለከተውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመተላላፍ ለእግረኛ ቅድሚያ በመከልከል በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ብሎ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል ።

የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሳሽ አልኮል ጠጥቶ ሲያሽከረክር አደጋ ሊያደርስ እንደሚችል ዕውቀት ያለው በመሆኑ የሞት አደጋውን ያደረሰው በታወቀ ቸልተኝነት ነው ብሎ በመደምደም በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በሁለት ዓመት ከስድስት ወር እስራትና ብር 3000 መቀጮ እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል ውሳኔውን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም አጽንቶታል። አመልካች ጥር 19 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ እኔ አደጋው በደረሰበት ጊዜ አልኮል መጠጥ የጠጣሁ መሆኑን በማመን የሰጠሁት የእምነት ቃል የለም። ዐቃቤ ህግም ይህንን የሚያሰረዳ ማስረጃ አላቀረበም። ዐቃቤ ህጉ በዕምነት ቃሉ መሠረት ጥፋተኛ ይባልልኝ ብሏል ። ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት በክርክሩ ሂደት ያልታመነ ወይም በማስረጃ ያልተረጋገጠ ጉዳይ (አልኮል ጠጥቶ ያሽከረከረ ስለነበረ) በማለት ቸልተኝነቱ የሚታወቅ ቸልተኝነት ነው በማለት ያወጣው ደረጃና የሠጠው የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል። ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ለእግረኛ ቅድሚያ በመከልከል የሞት አደጋ ያደረሰ በመሆኑ የቅጣት ውሳኔው የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል ።

ከሥር የክርክር አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አሻሽሎ ያወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ከምሽት አራት ሰዓት ሚች በላዳ መኪና ተከልሎ መንገድ ለማቋረጥ ሲሞክር የገጨው መሆኑን አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ከሰጠው የእምነት ቃል ይዘት ተረድተናል።አመልካች በወቅቱ የአልኮል መጠጥ ያልጠጣ መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት በግልጽ አስመዝግቧል።ተጠሪም አመልካች የአልኮል መጠጥ ጠጥቶ አላሽከረክረኩም በማለት የሰጠውን ቃል በመቀበል ማስረጃ ማቅረብ ሣያስፈልገኝ በእምነት ቃሉ መሠረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት እንዳሳሰበ ለመረዳት ችለናል፤ይህም አመልካች በዕምነት ቃሉ ያረጋገጠውን ወይም ዐቃቤ ህግ በማሰረጃ ያላስረዳውን ፍሬ ጉዳይ ማለትም አመልካች ሚችን ገጭቶ የሞት አደጋ ያደረሰበት የአልኮል መጠጥ ጠጥቶ ሲያሽከረክር ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት በቅጣት ውሳኔው መግለጹ በዚህ ምክንያት ቸልተኛነቱም በግልጽ የታወቀ ቸልተኝነት በማለት መፈረጁ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 134(1) ድንጋጌ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም።

የአመልካች የወንጀል አድራጊነት የፈጸመው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ (1)ሀ በተመለከተው ሁኔታ አይደለም። አመልካች በቸልተኝነት የሞት አደጋውን ያደረሰው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በተመለከተው ሁኔታ መሆኑን ለጥፋተኝነት ውሳኔው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት የሆነው አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የእምነት ቃል ያሳያል ። አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 134(1) መሠረት በሰጠው የእምነት ቃል መሰረት ከሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ከሰጠው የእምነት ቃል ውስጥ አመልካቹን የሚጠቅመውን ክፍል በመተው፤በአመልካች በዕምነት ቃሉ ያላስመዘገበውና ቅጣት የሚያከብድበትን ሁኔታ በቅጣት ውሳኔው በማሰፈሩ ቅጣቱን መወሰናቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አሻሽሎ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 134 (1) ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ አላማ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በወንጀል ህግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 2 በመተላለፍ ነው። አመልካች የወንጀል ድርጊቱን የፈጸመው በወንጀል ህግ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በተመለከተ ሁኔታ መሆኑ ተረጋግጧል። ይህም የአመልካች ቸልተኛነት የሚች አስተዋጾ በሌለበትና ባልታወቀ ቸልተኛነት የተፈጸመና በእስራት መቀጮ እርከን 8 በገንዘብ መቀጮ እርከን 4 ላይ የሚወድቅ ነው። ይህም ከአንድ ዓመት ከሁለት ወር እስከ አንድ ዓመት ከስምንት ወር ባለው የቅጣት ሬንጅ ውስጥ የሚያስቀጣ ነው። በመቀጮም እስከ ብር 5000 የሚያስቀጣ ነው። አመልካች ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሉት መሆኑን በውሳኔው አስፍሯል ። ይህም ሁለት እርከን ለመቀነስ የሚያስችል ነው።ስለሆነም ነፃነትን በሚያሳጣ ቅጣት እርከን ስድስት ሥር እና ገንዘብ መቀጮን በሚያስቀምጠው እርከን ሁለት ሥር የሚወድቅ ነው። በመሆኑም በዚህ ወንጀል ውስጥ በተሰጠው እርከን ሁለት ሥር የሚወድቅ ነው። በመሆኑም በዚህ ሬንጅ ውስጥ በተሰጠው ፍቅደ ሥልጣን መሠረት አመልካች በአንድ ዓመት እስራትና በብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ መቀጮ ሊቀጣ ይገባል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማፅናት የቅጣት ውሳኔውን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ(2))መሠረት በማሻሻል ውሳኔ ሰጥተናል ።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 125698 እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45874 የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በማፅናት የቅጣት ውሳኔውን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) መሰረት አሻሽለናል።

2. አመልካች በዚህ ጉዳይ እጁ ከተያዘችበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በአንድ ዓመት እስራትና በብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) መቀጮ እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥተናል ።

3.በዚህ ሰበር ችሎት የቅጣት ውሳኔው የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ ።

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።።

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96078

መጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች ፡- ረዳት ሳጂን አህመድ ለገሰ ---ጠበቃ አድምጠው በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ --- ዐ/ህግ መኩሪያ አለሙ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ክሱም በስር ፍርድ ቤት በስድስት ምድብ ተከፍሎ የቀረበ ሆኖ አመልካች ጥፋተኛ የተባለው በአምስት ክሶች ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተባለባቸው ክሶችም እንደሚከተለው በአጭሩ የተገለጹ ናቸው፡፡

የ1ኛው ክስ አመልካች በ1996 ዓ.ም. የወጣውን በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 27(1)እና 598(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን ወደ ውጪ ለመላክ የሚያስችል ምንም አይነት ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/06/07 ክልል ልዩ ቦታው ቂርቆስ ቴሌ አካባቢ ሚያዝያ 08 ቀን 2005 ዓ.ም. የግል ተበዳይ ራቂያ አደም የተባለችውን ከሰሜን ጎንደር ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ በማድረግ አመልካች በተከራየው ቤት ውስጥ ለሁለት ሳምንታት እንድትቀመጥ በማድረግ ወደ አረብ አገር እልክሻለሁ ብሎ ህክምና እንድትወስድ ከተደረገ በኋላ ከአመልካች ጋር በስር ፍርድ ቤት ተከሶ የነበረው 2ኛ ተከሳሽ የሕክምና ውጤቷን ፖስፖርትና የአሻራ ውጤት በመውሰድ ይኼው ተከሳሽ ቪዛውና የአየር ቲኬት በማምጣት ለመሄድ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ብር 800.00 ለአሁኑ አመልካች ሰጥታ ለመሄድ በመዘጋጀት ላይ ሳለች ሚያዚያ 11 ቀን 2005 ዓ.ም በደረሰ ጥቆማ ሳትሄድ የቀረች በመሆኗ ተከሳሾች ወንጀል ለማድረግ ጀምረው የወንጀሉ ድርጊት እስከ መጨረሻው ለመከታተል ያልቻሉ በመሆናቸውና በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጲያዊን ለስራ ወደ ውጪ አገር መላክ ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ 2ኛው ክስ ደግሞ አመልካቹ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27(1)እና 598(1)ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ኢትዮጵያዊያንን ወደ ውጪ አገር የመላክ ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ቦታ ቀኑ በውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባልታወቀበት መጋቢት ወር 2005 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 አካባቢ የግል ተበዳይ ናስራ መሐመድ ከትግራይ ክልል በማምጣት ወደ ውጪ አገር ለመሄድ እንደምትፈልግ ስትገልጽለት እኔ እልክሻለሁ በማለት በተከራየበት ቤት ውስጥ አንድ ወር ከአንድ ሳምንት አስቀምጧት የሜዲካል ውጤቷን ወስዶ ወደ ኦማን ነው የምትሄጂው ሲላት ወደዚያ አልሄድም ስትለዉ ቪዛው ለኦማን ነው የተሰራው በማለት የከለከላት እና ወደ ኦማን ለመሄድ በዝግጅት ላይ እንዳለች የአየር ትኬት ሲመጣ ብር 1000.00 እስከ 1500.00 እንድትከፈል በመግለጽ በመጠባበቅ ላይ እንዳለች በደረሰው ጥቆማ መሠረት ወንጀሉ ፍጻሜ ሳያገኝ የቀረ በመሆኑ አመልካቹ በፈጸመው በሕገ ወጥ መንገድ የኢትዮጵያዊያንን ለስራ ወደ ውጪ አገር መላክ ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው። ሌላው አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት 4ኛ ክስ ሲሆን የክሱ ይዘት ሲታይም፡- በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ቦታ መጋቢት 28 ቀን 2005 ዓ.ም. የግል ተበዳይ እሸቱ ቱፋን ከሳውዲ አረቢያ ወደ ኢትዮጵያ በምትገባበት ወቅት አመልካቹ ወደ ተከራየበት ቤት በመውሰድና ከዚያም ወደ ሆስፒታል በመውሰድ እንድትመረመር ካደረገ በኋላ ኩዋት ላከኝ ስትለው ሕክምና ያደረግሽው ለሳውዲ አረቢያ ስለሆነ ኦማን ነው የምልክሽ በማለት ፖስፖርት እና ሜዲካል ውጤቱን ከተቀበላት በኋላ ሞገስ ለተባለው ግለሰብ በመስጠት ይህ ግለሰብም ከዚያው ስለመጣ ውል እንዋዋል ብሏት ውል ለመዋዋል ለመሄድ በዝግጅት ላይ ሳለ ወንጀሉ ፍጻሜ ሳያገኝ የተቋረጠ መሆኑን ጠቅሶ አመልካቹ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 27(1) 598/1 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፏል የሚል ነው። ሌላው አመልካች ተከሶ ጥፋተኛ የተባለበት ክስ ደግሞ በ5ኛ ምድብ የተጠቀሰው ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካቹ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 27(1)እና 598(1) ድንጋጌዎች በመተላለፍ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ቦታ ሚያዝያ 11 ቀን 2005 ዓ.ም. የግል ተበዳይ ሕይወት ተስፋን ከሰሜን ጎንደር ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ በማድረግ ወደ ውጪ ለስራ እልክልሻለሁ በማለት የአሻራና የህክምና ምርመራ እንድታደርግ አድርጎ፣ የአሻራ ውጤት፣የህክምና ውጤት እንዲሁም ፖስፖርት በመቀበል ወደ ውጪ እልክሻለሁ፣ ስትሄጂ ብር 1500.00 ትከፍያለሽ በማለት ለመሄድ በመጠባበቅ ላይ ሳለች ለፖሊስ በደረሰው ጥቆማ መሠረት ወንጀሉ ፍጻሜ ሳያገኝ የቀረ መሆኑን ተጠቅሶ አመልካቹ በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያን ወደ ውጪ አገር የመላክ ሙከራ ወንጀል መፈፀሙን የሚገልጽ ነው። ሌላው ክስ በምድብ 6 ስር የተጠቀሰው ሆኖ አመልካቹ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 27 እና 598(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ቦታ ሚያዝያ 01 ቀን 2005 ዓ.ም. የግል ተበዳይ ሐጅራ ኡስማንን ከመተማ ከተማ ስትደውል ቪዛው መጥቶልሻል ነይ በማለት እንድትመጣ ካደረገ በኋላ ወደ ተከራየበት ቤት በመውሰድ ያለቀልሽ በመሆኑ ብር 800.00 ትከፍያለሽ በማለት ክፍያውን ለመክፈል በመስማማት ለመሄድ በዝግጅት ላይ ሳለች ለፖሊስ በደረሰው ጥቆማ ወንጀሉ ፍጻሜ ሳያገኝ የቀረ መሆኑ ተዘርዝሮ አመልካቹ በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ወደ ውጪ አገር የመላክ ሙከራ ወንጀል መፈፀሙን የሚያሳይ ነው። የአሁኑ አመልካችም ክሶቹን ክዶ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህም በኋላ አመልካች በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ወንጀሉን መፈፀሙ መረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ገልጾ አመልካች እንዲከላከል መብቱን ጠብቆለት አመልካችም የመከላከያ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ያስያዘው ጭብጥ እና የመከላከያ ማስረጃዎቹ አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ያስያዘው ጭብጥ እና የመከላከያ ማስረጃዎቹ እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ናቸው በማለት የመከላከያ ማስረጃዎችን ክብደት ሳይሰጥ አልፎ አመልካችን በአምስቱ ክሶች ጥፋተኛ አድርጓል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር በማገናዘብ በእያንዳንዱ ክስ ተገቢ ነው ያለውን የእስራት እና የገንዘብ መቀጮ ከአስቀመጠ በኋላ በድምሩ ደግሞ 25(ሃያ አምስት) አመት ፅኑ እስራት እና ብር 37,500.00 መምጣቱን ፣ ይህ የእስራት ቅጣት በእርከን 37፣ የገንዘብ መቀጮ ደግሞ በእርከን 9 የሚመደብ ሆኖ ወንጀሉ ተደራራቢ በመሆኑ ምክንያትም አንድ እርከን ከፍ እንደሚል ተቀብሎና በዚህም ስሌት መሠረት የእስራት ቅጣቱ በእርከን 38፣የገንዘብ መቀጮ ደግሞ በእርከን 10 ስር እንደሚወድቅ ደምድሟል፡፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ አመልካች ሪከርድ የሌለበት፣የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በቅጣት ማቅለያነት ይዞ እያንዳንዳቸው ምክንያቶች ሁለት ሁለት እርከን እንደሚያስቀንሱለት እንዲሁም ወንጀሉ ሙከራ መሆኑም ሁለት እርከን እንደሚያስቀንስ ገልጾና በአጠቃላይ በስድስት እርከን መቀነስ ያለበት መሆኑን ደምድሞ የእስራት ቅጣቱን በእርከን 32 ስር ባለው ፍቅደ ስልጣን ውስጥ በአስራ ሶስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ፣ የገንዘብ መቀጮ ደግሞ ብር 2000.00 ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(1)መሠረት ተሰርዟል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ድርጊቱ ስለመፈፀሙም በአግባቡ አልተረጋገጠም፣ በአንድ የወንጀል ማድረግ ሐሣብ በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ ለተፈፀመ ድርጊት ስድስት ክሶች ቀርበው በአምስቱ ጥፋተኛ ተብሎ ለእያንዳንዱ ክስ ቅጣት ተጥሎ መደመሩ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሀ)እና (ሐ)ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህን ችሎት ምላሽ እንዲያገኝ ተብሎ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ክሱ በግል ተበዳዮች ቁጥር መቅረቡንና ቅጣቱ በተደራራቢ ወንጀሎች አንጻር ታይቶ ከብዶ የመወሰኑን አግባብነት የሚመለከት በመሆኑ ከዚሁ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተከሰሰው በአንድ መዝገብ ሆኖ ክሶቹ በስድስት ምድብ የተከፈሉ መሆኑንና የተጠቀሰበት የሕግ ድንጋጌም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1)(ሀ)፣27 እና 598(1)ሆኖ የክሱ ዝርዝር ይዘቱም ባጭሩ ሲታይ አመልካች ምንም ሕጋዊ የሆነ ፈቃድ ሳይኖረው የግል ተበዳዮችን ከተለያዩ ቦታዎች በማምጣት ወደ ውጪ አገር እልካችኋለሁ፣ ስራም አስቀጥራችኋለሁ በሚል ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡና ከተከራየበት ቤት እንዲቆዩ በማድረግ የተለያየ መጠን ያለውን ገንዘብ ለመቀበል ጠይቆ ወደ ውጪ ለመላክ በዝግጅት ላይ እያለ በፖሊስ የተያዘ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ክሱን የካደ ሲሆን ዓቃቤ ሕግ አሉኝ ባላቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን ማስረዳቱን የስር ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጥብቆ የሚከራከረው በአንድ የወንጀል ሐሳብ በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ ለተፈፀመ ድርጊት በተለያዩ ክሶች ልጠየቅ አይገባም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ አመልካች በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ በርካታ ሰዎችን ጭኖ ወደ ውጪ አገር እልካችኋለሁ በማለት ማጓጓዝ ላይ እንዳለ መያዙን የክርክሩ ሂደት ያረጋግጣል፡፡

በመሠረቱ የተደራራቢ ወንጀሎች ትርጉም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሀ)እና (ለ)ስር የተቀመጠ ሲሆን የዚሁ አንቀጽ ፊደል “ሐ“ድንጋጌ ሙሉ ይዘት ሲታይም አንድ ሰው በአንድ አይነት የወንጀል ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት የፈጸመው ወንጀል አንድን የሕግ ድንጋጌ ብቻ የሚጥስ ቢሆንም አንድ አይነት ጉዳት ያስከተለው ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ሲሆን እንደተደራራቢ ወንጀሎች ሊቆጠር የሚገባ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ሕግ አውጪው ይህንኑ ድንጋጌ በ1949 ዓ.ም. የወንጀል ሕግ ያስቀምጥ ከነበረው ሁኔታ በተለየ መልኩ እንዲገባ ያደረገበት ምክንያትም ነባሩ የወንጀል ሕግ በዚህ ረገድ የነበረው ይዘትና መንፈስ በሕግም ሆነ በፍትህ ረገድ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደማይገባው ፣በነባሩ ህግ ማብራሪያ የጻፉት ምሁራንም የሕጉን አቋም ያልደገፉት ሆኑን መሠረት አድርጎ ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የተሻሻለው የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት ሰፍሮ የምናገኘው ጉዳይ ነው፣ ከዚህ ሕጉ ሲወጣ ከነበረው የሕግ አውጪ ሀሣብም ሆነ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሐ)ድንጋጌ በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው ሕጉ ጥበቃ የሚያደርገው የእያንዳንዱን ሰው መብትና ጥቅም መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በአንድ የወንጀል ማድረግ ሐሳብ ተመሳሳይ ድንጋጌ ተጥሶ በበርካታ ሰዎች ላይ ተመሳሳይ የሆነ ጉዳት መድረሱ ከተረጋገጠ የድርጊቱ ፈጻሚ በተደራራቢ ወንጀሎች የሚጠየቅ ሲሆን ሕጉ በዚህ ጊዜ ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ ያስቀመጠው በቅጣት አወሳሰን ጊዜ በጠቅላላው ሕግ ከተቀመጠው የቅጣት አይነት ጣሪያ ያለማለፍን ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184(1)(ሀ)ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሐ)ድንጋጌ ትርጉምና አተገባበሩ ከላይ በተመለከተው አግባብ ስለመሆኑም ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 83947 በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1)መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ሲጠቃለልም ፍሬ ነገሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን በበቂ ሁኔታ ያረጋገጡ መሆኑን በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ስር በተቀመጠው የማስረጃ ምዘና ስርዓት መሠረት መዝነው ከአረጋገጡና አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን በግልጽ ከአስታወቀ ይህንኑ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አመልካችን ለወንጀል ድርጊቶቹ ኃላፊ ነው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን መሠረት ያደረገ መሆኑን የውሳኔ አሰጣጡ ሂደት በግልጽ የሚያሳየው ጉዳይ ሆኖ ስለአገኘነውና አመልካቹ ለእያንዳንዱ ክስ ተጠያቂ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡

ቅጣቱን በተመለከተም ለእያንዳንዱ ክስ በተናጠል ተወስኖ በጠቅላላው ተደምሮ ከ25/ሃያ አምስት አመት/ ጽኑ እስራት እና ብር 37,500.00ተደርጎ መወሰኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2)፣58፣60፣(ሐ)፣92፣184(1)(ሀ)እና32(1)(ሀ)፣27(1)፣598(1)ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሰው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተገቢ እንጂ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የቅጣት መጠኑ ከብዶ የተወሰነ መሆኑን በቅሬታ ነጥብነት የጠቀሰ መሆኑን ስለተገነዘብን የስር ፍርድ ቤት ለአመልካች በቅጣት ማቅለያነት የያዛቸውን የሪከርድ ያለመኖርና የቤተሰብ አስተዳዳሪ የመሆኑ ምክንያቶች የሚያስቀንሱት የእርከን መጠን ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሠረቱ እንደ ቅጣት መመሪያው መወሰን እንዲቻል በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከግራ ቀኙ ቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ጥፋተኛ ከተባለበት ድንጋጌ እና ከአድራጐቱ አፈጻጸም አንጻር ሲታይ በቅጣት መመሪያው አንቀጽ 13 መሠረት የወንጀሉ ደረጃ ዝቅተኛ ሆኖ ተደራራቢ በመሆኑ ምክንያት በእርከን 38 ላይ የሚወድቅ ሲሆን የስር ፍ/ቤቱ እንዳረጋገጠው የአሁን አመልካች ወንጀል ሪከርድ ያልቀረበበትና የቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆኑ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ሊያዝለት ስለሚገባውና ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ከሚያስከትለው ቅጣት ዓይነትና መጠን አኳያ በእነዚህ ሁለት የማቅለያ ምክንያቶች መሠረት በድምሩ አራት እርከን እንደሚያስቀንስ የስር ፍርድ ቤት ገልጿል፡፡ ሆኖም በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በአንቀጽ 16(7)እና16(8)ስር እንደሰፈረው የቅጣት ዓይነትና መጠን ሬንጅ እድሜ ልክ በመሆኑ ለአንድ የቅጣት ማቅለያ መቀነስ ያለበት እርከን ሶስት ነው፡፡ ይህ ስሌት ሲያዝ በሁለት የቅጣት ማቅለያዎች መቀነስ ያለበት ስድስት እርከን ሆኖ ሙከራ በመሆኑ ደግሞ ሁለት እርከን መቀነስ ያለበት በመሆኑ በጠቅላላው ስምንት እርከን ሲቀነስ ከእርከን 38 ወደ እርከን 30 መውረድ የግድ የሚል ነው ፡፡ በዚህ እርከን ለፍ/ቤቱ የተሰጠው ፍቅደ ስልጣን ደግሞ ከአስራ አንድ አመት እስከ 13 ዓመት ከሁለት ወር እስራት ስለሆነ በዚህ መሠረት የአሁን አመልካች ለፈፀመው ጥፋት በ11 ዓመት /በአስራ አንድ ዓመት/ ጽኑ እስራት ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ ስላገኘነው የስር ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዳለ በመቀበል በእስራት ቅጣት አጣጣል ረገድ የፈፀሙትን መሠረታዊ የህግ ስህተትን ግን አርመን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13370 ነሐሴ 8 እና 10 ቀን 2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 94212 ህዳር 17 ቀን 2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የጸናው ውሳኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአሁን አመልካች በአምስት ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለዚህ ጥፋቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባወጣው ቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንጻር ታይቶ ሊቀጣ የሚገባው በ11 ዓመት /በአስራ አንድ ዓመት/ጽኑ እስራት እና በብር 2000.00የገንዘብ መቀጮ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-2)መሠረት አሻሽለን ወስነናል፡፡
4. በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለመ/ቤት ትዕዛዝ ይድረሰው ብለናል፡፡ ይጻፍ፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93220

መጋቢት 8 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንገሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ግርማ አያሌው ዋልታንጉስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ጽ/ቤት

ነ/ፈጅ ቁምነገር ደጉ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአ/አ/ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ነሐሴ 28 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ሰለጠየቁ ነው፡፡ ጉዳዩም የመንግስት ሠራተኞች የሰራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በአ/አ/ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍ/ቤት ነው በዚያ ደረጃ አመልካች ይግባኝ ባይ ተጠሪ ደግሞ መልስ ሰጪ በመሆን ተከራክሯል፡፡ አመልካች በ17/04/2005 ዓ.ም በተፃፈ ለአስተዳደር ፍ/ቤት ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ አመልካች ሠራተኞችን በስርዓት መምራት አልቻለም፣ የስራ ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም በሚል እና እንዲሁም ላፕቶፕ ኮምፒውተር ሣልረከብ ተረክበሃል በሚል የተጠሪ መስሪያ ቤት የዲሲፕሊን ኮሚቴ ያለምንም ማስረጃ ያለአግባብ ጥፋተኛ ካደረገኝ በኋላ ከስራ እንዲሰናበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ስህተት ያለበት መሆኑን ጠቅሰው ውሣኔው ተሽሮ ወደ ስራ እንዲመለስ ጠይቋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የአስተዳደር ፍ/ቤቱም በበኩሉ በቀረበው ይግባኝ አቤቱታ ላይ ግራ ቀኙን አስቀርቦ እንዲከራከሩ ካደረገና እንዲሁም በመስሪያ ቤቱ ዲስፕሊን ኮሚቴ ክርክር ደረጃ ተጠሪ አሰምቶ የነበረውን ምስክሮችም አስቀርቦ በድጋሚ ቃላቸውን ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አመልካች ፈጽመዋል ከተባሉት የዲስፕሊን ጥፋቶች ውስጥ ስለ ላፕቶፕ ኮምፒውተርን በተመለከተ አመልካች ኮምፒውተሩን ከመ/ቤቱ ተቀብሎ አለመመለሱ በበቂ ማስረጃ ስላልተረጋገጠ በዚህ ረገድ ለቀረበበት የዲስፕሊን ክስ ተጠያቂ ሊሆን አይገባም በማለት ከወሰነ በኋላ ሌሎች ጥፋቶችን በተመለከተ ግን ማለትም አመልካች ከሰራተኞች ጋር ያለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መልካም ግንኙነት አናሣ ስለመሆኑና ከሰራተኞች ጋር ተባብሮ በስምምነት መሰራት አለመቻል በሚመለከት የቀረበበትን የዲስፕሊን ጥፋቶች መፈጸሙ በሚገባ በማስረጃ ተረጋግጦበታል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ካሰፈረ በኋላ እና እነዚህን ጥፋቶች በተመለከተም በ2 ወር የደመወዝ ቅጣት እንዲቀጣ ሲል በተጠሪ መ/ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ የተሰጠውን የሰንብት ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

በአሁኑ ተጠሪ ቅሬታ አቅራቢነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከተማ አስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማ በኋላ የአስተዳደር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት በማጽናት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል አሁንም ባአሁኑ ተጠሪ ሰበር አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩን የተመለከተው የከተማ አስተዳደሩ ሰበር ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ እንዲከራከሩ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ላፕቶፕ ኮምፒዩተሩን ወስዶ አለመመለሱ የተጠሪ መ/ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ በሰነድና በሰው ማስረጃ በበቂ ሁኔታ አረጋግጦ እያለ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ግን ይሄንን አላአግባብ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ማስረጃን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑንና እንዲሁም የከተማ አስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ይሄንኑ ስህተት ማረም ሲኖርበት ማጽናቱ እንዲሁ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን ከገለፀ በኋላ የአስተዳደር ፍ/ቤቱንና የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል በተጠሪ መ/ቤት ዲስፕሊን ኮሚቴ የተሰጠውን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ በማጽናት ወስኗል፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በከተማ አስተዳደሩ ሰበር ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም፡- የስር አስተዳደር ፍ/ቤቱ የቀረበውን ማስረጃ በመመርመር እና በመመዘን አመልካች የመ/ቤቱን ላፕቶፕ መውሰዱ በማስረጃ በበቂ ሁኔታ አልተረጋገጠም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ የሰጠው ውሳኔ በከተማ አስተዳደሩ ሰበር ችሎት “አመልካች አከራካሪውን ላፕቶፕ ወስዶ አለመመለሱ ተረጋግጦበታል” በማለት የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መቀየሩ በህግ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ የማስረጃ ምዘናን ተግባር መሰረት በማድረግ ስለሆነና ውሳኔው ከዚህ አኳያ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተሽሮ በአስተዳደር ፍ/ቤቱ እና በከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ ይፅናልኝ የሚል ነው፡፡ አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን የከተማ አስተዳደሩ ሰበር ችሎት የአስተዳደር ፍ/ቤቱንና የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱን ውሳኔ የለወጠው በህግ ከተሰጠው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሳኔ የማረም ስልጣን ውጭ በማውጣት መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጀመሪያ ደረጃ የአ/አ/ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ካለ ይሄንኑን ለከተማ አስተዳደሩ ሰበር ችሎት ማቅረብ እንደሚችልና ሰበር ችሎቱም በበኩሉ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለ ይሄንኑን አይቶና መርምሮ ለማረም ስልጣን እንደተሰጠው ከተሻሻለው የአ/አ/ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 42(2) ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳዩ ነው፡፡

በሌላ በኩል በተያዘው ጉዳይ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ የተጠሪ መስሪያ ቤት ዲስፕሊን ኮሚቴ ላፕቶፕ ኮምፒውተርን በሚመለከት የቀረበውን የዲስፕሊን ክስ በተመለከተ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በይግባኝ ስልጣኑ ተጠቅሞ ሊለውጥ የቻለው ግራ ቀኙ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር መሰረት በማድረግ በዲስፕሊን ኮሚቴ ክርክር ደረጃ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተው የነበሩ የተጠሪ መ/ቤት ሰራተኞች በድጋሚ አስቀርቦ ቃላቸውን እንዲሰጡ ካደረገ በኋላ አመልካች አከራካሪውን ላፕቶፕ ስለመውሰዱ በማስረጃ ተረጋግጦበታል? ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ የነገር ጭብጥ በማስረጃ በድጋሚ እንዲጣራ በማድረግ እና እነዚህ የቀረቡትን ማስረጃዎችም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር አገናዝቦ በመመርመርና በመመዘን ተገቢ ነው ያለውን ክብደት ለማስረጃዎቹም በመስጠትና በስተመጨረሻም አመልካቹ ላፕቶፑን ስለመውሰዱ በበቂ ማስረጃ አልተረጋገጠም የሚል የፍሬ-ነገር ድምዳሜ ላይ ከደረሰ በኋላ ስለመሆኑ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ይህ የፍሬ-ነገር ድምዳሜም በአ/አ/ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ሆኖም የአ/አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ችሎት በበኩሉ ይሄንን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ላፕቶፕ ኮምፒውተር በአመልካች አለመወሰዱ በማስረጃ ተጣርቶና እንዲሁም ማስረጃውም ተመዝኖ የመጨረሻ ድምዳሜ ላይ የተደረሰበትን ፍሬ ነገር እንዳለ ተቀብሎ በህግ ረገድ ብቻ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ካለ ያንን ብቻ አይቶ ማረም ሲገባ በህግ ተወስኖ ከተሰጠው የስልጣን ገደብ ውጭ በመውጣትና የማስረጃ ምዘና ተግባር ውስጥ በመግባት አመልካች አከራካሪውን ላፕቶፕ ወስዶ አለመመለሱ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ በበቂ ሁኔታ ተረጋግጦበታል በማለት የፍሬ ነገር ክርክርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን በህግ ስልጣን ከተሰጠው የአስተዳደር ፍ/ቤቱ የተለየ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ በመድረስ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ለውጦ በተጠሪ መስሪያ ቤት ዲሲፕሊን ኮሚቴ የተሰጠውን የስንብት ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 42 (2) ድንጋጌ ይዘት ፣መንፈስና አላማ አኳያ ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአ/አ ክተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 2005 በ7/12/2005 ዓ.ም በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሠ/ሥ/ህ/ቁ.348(1)መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአ/አ/ከ/አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍ/ቤት በመ/ቁ.643/05/ በ2/72005 ዓ.ም ተወስኖ በአ/አ/አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ.17945 በ7/8/2005 በሰጠው ውሳኔ እንዲፀና የተደረገው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348 (1) መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ የሰበር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   - የውሳኔ ግልባጩ ለሰር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
   - መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93358

መጋቢት 26 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙሰጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማርች ፕሮጀክት፡- ነ/ፈጅ አላዮ አምበርብር ቀረቡ

ተጠሪ፣- 1. ቤተልሔም ሽፈራው
2. አሸናፊ ሀደራ
3. ሮማን ታደሰ
ጠበቃ ግንቡ መኮንን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት የሚገዛበትን የሕግና ዳኝነት የሚሰጠውን አካል በተመለከተ በግራ ቀኙ መካከል የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካችና በበሽታዎች መከላከል እና ቁጥጥር ማዕከል ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሳቸው ማመልከቻ ይዘትም ባጭሩ፡- በአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤቱ በተለያየ ጊዜና በተለያየ የስራ መደብ ተቀጥረው ሲሰሩ ቆይተው አመልካች የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረው የበሽታዎች መከላከልና ቁጥጥር ማዕከል የሰጠውን ውክልና በመጠቀም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ከተደነገገው ውጪ የስራ ቅነሳ ያደረገባቸው መሆኑን ዘርዝረው እርምጃው ሕገ ወጥ ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለተጠሪዎች ክስ በሰጠው መልስም፡- አመልካች መስሪያ ቤት በአዋጅ የተቋቋመና በመንግስት በሚመደብለት አመታዊ በጀት የሚተዳደር የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ነው፣ የፌዴራል መንግስት የአስተዳደር መስሪያ ቤቶችና ሰራተኞች የስራ ግንኙነትን በተመለከተ ደግሞ ራሱን የቻለ የሠራተኞች ሕግ እና አስተዳደር ፍርድ ቤት ያለ በመሆኑ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታይበት አግባብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው አካል ግን በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካች መስሪያ ቤት በበጀት የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት በመሆኑ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚዳኝና በመደበኛ ፍርድ ቤትም የሚታይ አይደለም በማለት መዝገቡን የዘጋው ሲሆን ተጠሪዎች በዚህ የስር ፍርድ ቤት ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በኤች.አይ.ቪ መከላከል ላይ ጥናት አድርጎ ባቀረበው የምርመራ ውጤት መሰረት በስር 1ኛ ተከሳሽ በነበረው አካል ፈንድ ተደርጎለት በራሱ ስራ የሚሰራ ተቋም እንጂ የአመልካች ወኪል አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች በመንግስት የተመደበለትን በጀት መሠረት አድርጎ መደበኛ የመማር ማስተማር፣ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድ አካል አይደለም፣ አመልካች ተጠሪዎችን በመንግስት ሰራተኝነት የቀጠራቸው መሆኑን በማስረጃ አስደግፎ አላስረዳም የሚሉትን ምክንያቶችን አስፍሮ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የማይሸፈንበት እንደዚሁም ክርክር የተነሳ እንደሆነ በመደበኛ ፍርድ ቤት የማይዳኝበት ምክንያት አይኖርም ሲል ደምድሞ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ ሠራተኞቹን የሚያስተዳድረው በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረታዊ መርሆዎች መሠረት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 ተመልክቶ እያለ እንዲሁም ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 515/1999 መሠረት መብቱን ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት ማቅረብ ሲገባቸው ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረባቸው ትክክል ነው ተብሎ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው በመባሉ ምክንያት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት የጽሑፍ መልስ፤ የአመልካች አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም፣ ተጠሪዎች የተቀጠሩት አመልካች በሚያከናውነው የፕሮጀክት ስራ በመሆኑ ጉዳዩ የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 377/1999 እንጂ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አይደለም፣ አመልካች በኮንትራት የተቀጠሩትን የመንግስት ሰራተኞችን ጉዳይ ለመግዛት በሚመለከተው አካል የወጣ መመሪያ ጉዳዩ ሊገዛ ይገባል በማለት የሚያቀርበው ክርክርም ተጠሪዎች በመመሪያው መሠረት የተቀጠሩት መሆኑን የቅጥር ውሉ በማያመላክትበት ሁኔታ የቀረበ የክርክር ነጥብ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጸው ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሚታይ ነው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መወሰኑ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ፡- የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን አመልካች ያነሳውን መቃወሚያ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ አድርጎ መወሰኑ ተገቢ ነው ? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሠረቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር በ214/2003 አንቀጽ 2(1) እና (3) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ የተቋቋመ መሆኑ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርስቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሰረት የሚተዳደር መሆኑን ተጠቃሹ ደንብ በግልጽ የሚደነግገው ጉዳይ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1)ደግሞ ዩኒቨርሲቲው በፌዴራል መንግስት በጀት የሚተዳደር መሆኑን፣ በአዋጁ አንቀጽ 29 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ደግሞ የተቋሙ ተቀጣሪ ሰራተኞች አይነትን የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች እንዲሁም ቅጥሩ ስለሚመራበት አግባብ የሚገልፁ ድንጋጌዎች ተቀምጠው እናገኛለን፡፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከተቋቋመባቸው ተግባሮች አንዱ ምርምርና ጥናት ማካሄድ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህን ለማከናወን ደግሞ ፕሮጀክት ቀርጾ ሰራተኛን ከመቅጠር ጀምሮ ተገቢውን ሁሉ የሚፈጽም መሆኑ ይታመናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ፕሮጀክት በዩኒቨርሲቲው የሚተዳደር እንጂ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት አለው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ፕሮጀክት በአዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በደንብ ቁጥር 210/2003 አግባብ የሚተዳደር ሆኖ እያለ ለምርምር ስራ የሚቀጠሩ ሰራተኞች የሚያቀርቡትን አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የመቀበልና ውሣኔ የመስጠት ስልጣን ለመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ለዩኒቨርሲቲው በሕጉ አግባብ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ባገናዘበ መልኩ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መደበኛ ፍርድ ቤቶች ለማየት እንደህጋዊ ምክንያት አድርጎ ከወሰደባቸው ምክንያቶች አንዱ አመልካች ተጠሪዎች በኮንትራት የተቀጠሩ ሰራተኞች ስለመሆናቸው በማስረጃ አላስደገፈም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ነጥብም ቢሆን የተጠሪዎች ግንኙነት በመንግስት በጀት በሚተዳደር መስሪያ ቤት ስር ባለው አካል ጋር የተመሰረተ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 እና በመንግስት የበጀት መስሪያ ቤቶች የቅጥር ሁኔታዎችን በሚደነግጉት ደንቦችና መመሪያዎች አንጻር ስልጣን ባለው አካል እንዲታይ ከሚደረግ በስተቀር ጉዳዩን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ለመዳኘት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ በመንግስት በጀት በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚተዳደሩ መስሪያ ቤቶች የተቀጠሩ ሰራተኞች ግንኙነታቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የማይገዛ መሆኑን የተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 3 (2)(ሠ) ድንጋጌ ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 3 ድንጋጌ ጋር አዛምደን ስንመለከተው የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመንግስት መስሪያ ቤት በኮንትራት የሚቀጠሩ ሰራተኞችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 22(3) የኮንትራት ሰራተኛ የቅጥር አፈጻጸም መመሪያ ያወጣል ተብሎ የተደነገገ ሲሆን በሕጉ ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት "የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሰራተኞች ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ" የሚል ርዕስ የተሰጠበትን ፣ በመግቢያውም ለፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ስለሚቀጠሩ ጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሠራተኞቹ አቀጣጠር፣ መብቶችና ግዴታዎች በግልጽ የሚያስቀምጥ መመሪያ ማውጣት ማስፈለጉን፣ የጊዚያዊ ሰራተኞች ምልመላና መረጣ በችሎታ፣ በግልጽነት ከአድሎ ነጻ በሆነ ውድድር ላይ እንዲመሠረት ለማድረግ፣ በቀጣሪና በተቀጣሪ መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች ፍትህ ለመስጠት እንዲረዳ እና በሁሉም የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ግልጽ የሆነ አፈጻጸም እንዲኖር ለማድረግ ተብሎ ዓላማው ተለይቶ የተቀመጠለት መመሪያን አውጥቶ ከህዳር ወር 2000 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ እንደሚውል አድርጓል፡፡ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት በዚህ መመሪያ የሚገዛ መሆን ያለመሆኑን ሊለይ የሚችለው ደግሞ ጉዳዩ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ ውጪ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ሲቀርብ ነው፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ጉዳዩ ሊታዩ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ሳይሆን በአዋጅ 650/2001፣ ደንብ ቁጥር 214/2003 እና ደንብ ቁጥር 210/2003 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 515/1999 በተዘረጋው ስርዓት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 130048 ሰኔ 13 ቀን 2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 መሠረት በተዘረጋው ስርዓት የሚታይ እንጂ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት በስራ ክርክር ችሎት የሚታይ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96216

ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-አቶ ተክለብርሃን ዘገየ /ጠበቃ መረሳ ፍስሐ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. አቶ ሸምሰዲን አክመል
2. አቶ ሬድዋን ኸይረዲን } 4ኛ ተጠሪ ከጠበቃ አበራ አንጃ
3. አቶ መሐመድ አክመል

4. በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 8 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፊጅ ፍጹም ካሳዩ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የመንግስት የንግድ ቤት የተከራይነት መብትን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ06/10/2004 ዓ.ም በተጠሪዎቹ ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች በወረዳ 8 የሚገኘውን ቁጥሩ 144/495/145/516 የሆነውን የንግድ ቤት ከ4ኛ ተጠሪ ተከራይተው የንግድ ስራ ሲሰሩበት መቆየታቸውን እና ይሁን እንጂ 4ኛ ተጠሪ ውሉን አላግባብ ያቋረጠባቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ 4ኛ ተጠሪ ውሉን ከአመልካች ጋር እንዲቀጥል እና ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች ደግሞ የንግድ ቤቱን እና በሱቁ ውስጥ የሚገኙትን ንብረቶች እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች ፍርድ ቤቱ ክሱን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል መቃወሚያ በማቅረባቸው ፍርድ ቤቱ ይህንኑ የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥብ መርምሮ ጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች የሚመለከት በመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች እንጂ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አለመሆኑን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34428 በ23/03/2001 ዓ.ም የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምም ይህንኑ የሚያስገነዝብ መሆኑን ገልጾ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት አመልካች ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል ያቀረቡትን ጥያቄ በተመለከተ መዝገቡ በሬጅስትራር ጽ/ቤት በኩል ጉዳዩን ለማየት ለተመደበው ችሎት እንዲያስተላልፍ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን የብይን ክፍል ሲያጸናው ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ በተመለከተ መዝገቡ በሬጅስትራር ጽ/ቤት በኩል ጉዳዩን ለማየት ለተመደበው ችሎት እንዲመራ የተሰጠውን የብይኑን ክፍል ግን በመሻሩ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች በተጠሪዎች ላይ የመሰረቱት ክስ ተጠሪዎቹ በአመልካች የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረትና ይዞታ ላይ በግብረአበርነት እየፈጸሙት ያለው ሁከት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1149(1) መሰረት ተወግዶ ሀብትና ንብረቱን ለቀው ያስረክቡኝ የሚል ሆኖ እያለ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህን መሰል ጉዳይ የማከራከር ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ነው በማለት የመወሰኑን እና ውሳኔው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጽናቱን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

1. ክስ የቀረበበት ጉዳይ የሚወድቀው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ነው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?
2. ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል አመልካች ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ከዋናው የዳኝነት ጥያቄ ተነጥሎ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲታይ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪዎቹ የሁከት ተግባር ፈጥረውብኛል በማለት አመልካች የሚከራከሩት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የንግድ ሱቃቸው ተቀጣሪዎች ሆነው እያለ መመሪያ ቁጥር 4/2004 መውጣቱን ምክንያት አድርገው የንግድ ሱቁን ከአመልካች የተከራዩ አስመስለው ለ4ኛ ተጠሪ በማቅረብ የተከራይነት መብቱ አላግባብ ወደ ራሳቸው እንዲዛወር አድርገዋል፤4ኛ ተጠሪም በአመልካች እና በሌሎች ተጠሪዎች መካከል ያለውን የግንኙነት ዓይነት በአግባቡ ሳያጣራ ከአመልካች ጋር የነበረውን ውል በማቋረጥ ውሉን ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር አድርጓል፤3ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ ወንድም በመሆን በሱቁ ውስጥ ተገኝቷል በማለት መሆኑን ከክርክራቸው ተገንዝበናል፡፡እንደሚታየው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በቀጥታ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻፀም ጋር የተያያዘ ነው፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የአመልካች ነበር በተባለው የንግድ ሱቅ የገቡት አመልካች እንደሚከራከሩት በሰራተኝነት ነው ወይስ ተጠሪዎቹ እንደሚከራከሩት የንግድ ቤቱን ከአመልካች በመከራየታቸው ነው? የሚለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አከራካሪ ጭብጥ ጭምር ከመመሪያው አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚታይ እና ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው።የንግድ ቤቱ ተከራይ ከነበሩት ከአመልካች እና እንደ አመልካች አባባል በሰራተኛነት፤እንደ ተጠሪዎች አባባል ደግሞ በተከራይነት ወደ ንግድ ሱቁ ገብተዋል ከተባሉት ተጠሪዎች መካከል በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት የተከራይነት መብት ሊያገኝ የሚገባው ማነው? የሚለው ጥያቄ በመሰረቱ በመመሪያው ላይ የተመለከቱትን ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት አድርጎ ምላሽ የሚያገኝ የመመሪያ አፈጻጸም ጉዳይ ከሚሆን ውጪ ከሁከት ድርጊት ጋር ግንኙነት ያለው ጉዳይ አይደለም።

መመሪያውን መሰረት አድርጎ የሚነሳ የንግድ ቤት የተከራይነት መብት ጥያቄ ከከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣን እና ተግባር ጋር እንዲሁም የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር የተያያዘ እስከሆነ እና የከተማው አስተዳደር አካልም በተከሳሽነት የተሰየመ እስከሆነ ድረስ ደግሞ የዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ተቀብሎ የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር በአንቀጽ 41(1) (ለ) እና (ረ) ስር በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ የዚህ ዓይነቱ ክስ የሁከት ስም ተሰጥቶት በመቅረቡ ብቻ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ሊወድቅ የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም።አመልካች ጠቅሰው የሚከራከሩበት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 64703 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይም ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር ግንኙነት ያለው ባለመሆኑ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር ተፈጻሚነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

በመሆኑም ክስ የቀረበበት ጉዳይ የሚወድቀው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ነው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የአመልካች ዋነኛው የዳኝነት ጥያቄ አላግባብ የተወሰደብኝ የንግድ ቤቱ የተከራይነት መብት ሊመለስልኝ ይገባል የሚል ሲሆን ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል የቀረበው ጥያቄ ዋናውን ጥያቄ ተከትሎ የቀረበ ተጨማሪ የዳኝነት ጥያቄ ነው።ይህ ተጨማሪ የዳኝነት ጥያቄ በመሰረቱ የሚወድቀው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ነው።ይሁን እንጂ የዳኝነት ጥያቄው የቀረበው ብቻውን ወይም ራሱን ችሎ ሳይሆን ዋነኛውን የዳኝነት ጥያቄ ተከትሎ ነው።የዚህ ዓይነት ጉዳዮችን በተመለከተ በአንድ ክስ ውስጥ ብዙ አቤቱታዎች ቀርበው ከነዚሁ በከፊል ዋናውን ክስ የሚመለከቱ በከፊል ደግሞ ዋናውን ክስ መነሻ አድርገው ቅርንጫፍ ነገሮችን የሚመለከቱ በሆነ ጊዜ የፍርድ ቤቱ ስልጣን የሚወሰነው ከፍተኛ ግምት ያለውን አቤቱታ መሰረት አድርጎ በመከተል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 17(2) ስር የተደነገገ በመሆኑ የአመልካች የንብረት ያስረክቡኝ ጥያቄ የንግድ ቤቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከራይነት መብት ከሚመለከተው ዋነኛው የዳኝነት ጥያቄ ተነጥሎ ለብቻው ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የንብረት ያስረክቡኝ የዳኝነት ጥያቄ ጭምር ከዋናው ጉዳይ ጋር በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየት እንደሚገባው ገልጾ መመለስ ሲገባው ተነጥሎ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ ትዕዛዝ መስጠቱም ሆነ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ ግልጽ የሆነ ውሳኔ አለመስጠቱ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 190432 በ07/03/2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 128776 በ04/02/2006 ዓ.ም ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ክስ የቀረበበት ጉዳይ የሚወድቀው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ነው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል አመልካች ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ከዋናው የክስ ምክንያት ተነጥሎ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲታይ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
4. ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል አመልካች ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 17(2) በተመለከተው መሰረት የንግድ ቤቱን የተከራይነት መብት ከሚመለከተው ዋናው የዳኝነት ጥያቄ ጋር በአንድነት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ በአንድነት ሊስተናገድ የሚገባው ነው በማለት ወስነናል፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
6. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97372

ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ማም ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግል/ማህበር አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ህግ ሜሮን አንማው ቀረቡ

2. አፍሮ ግሎባል የንግድ ማዕከል ሊሚትድ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በኮንቴነር ዲፖዚት ዋስትና የተያዘ ገንዘብ ይለቀቅልኝ ወይም ይከፈለኝ በሚል መንገድ የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ አንደኛ ተጠሪ /አንደኛ ተከሳሽ/ ሁለተኛ ተጠሪ /ሁለተኛ ተከሳሽ/ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ ያስገባቸው ዕቃዎች የታሸጉበት ኮንቴነር ለመመለስ ብር 22.836.32 /ሀያ ሁለት ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር ከሰላሳ ሁለት ሳንቲም/ የኮንቴነር ዲፖዚት ዋስትና መያዣ በማድረግ ለአንደኛው ተከሳሽ (አንደኛ ተጠሪ) በትራንዚተሩ ሁለተኛ ተከሳሽ (ሁለተኛ ተጠሪ) በኩል አስይዣለሁ፡፡ ኮንቴነሮቹ የተመለሱ ቢሆንም አንደኛ ተከሳሽ ገንዘቡን ያለ በቂ ምክንያት አለቅም በማለት ወስኗል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሾችም የትራንዚት ውል መሰረት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን አቅርቦ ገንዘቡን እንዲመለስ ማድረግ ሲገባው፤ ሰነዶችን በአንደኛ ተከሳሽ አቅርቦ ገንዘብ እንዲመለስ በማድረጉ በከሳሽ ላይ ለደረሰው ኪሳራ ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ ገንዘቡን በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ውሳኔ ቢሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆነው አንደኛ ተጠሪ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት ቅሬታውን በሚመለከተው ኃላፊ /የስራ ክፍል/ አቅርቦ ማሳየት ሲገባው በህጉ መሰረት አቤቱታውን ሲያቀርብ ቀጥታ በፍርድ ቤት ማቅረቡ የህግ መሰረት የለውም፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ይህንን የአንደኛ ተከሳሽ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ በመቀበል ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት በብይን መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 339 መሰረት ሰርዞታል፡፡
3. አመልካች የበታች ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን መቃወሚያ የተቀበለው በአዋጅ ቁጥር 622/2001 ከሚደነግገው ውጭ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ የማየት ስልጣን የለውም ቢባል እንኳን ሁለተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ ነጥሎ የማያይበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤት የፈፀሙት የህግ ስህተት ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ብይን አዋጅ ቁጥር 622/2001 መሰረት ያደረገ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው በመሆኑ፤ መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ባለማቅረቡ፤ የመልስ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡
4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን የህግ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች አንደኛ ተጠሪ ክስ ያቀረበበት ገንዘብ የመመለስ ኃላፊነት አለበት የሚለው አንደኛ ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 622/2001 ከሚደነግገው ውጭ ከኮንቴነር ዋስትና ያስያዝኩትን ገንዘብ አይመለስልህም ያለኝ በመሆኑ ገንዘቡን እንዲመልስ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ይህም አመልካች አንደኛ ተጠሪ ዋስትና ያስያዝኩትን ገንዘብ የመመለስ ህጋዊ ግዴታ አለበት የሚልና የአንደኛው ተጠሪ ኃላፊነት የሚመነጨው ከሕግ መሆኑን አመልካች በግልፅ ጠቅሶ የተከራከረ መሆኑን ያሳያል፡፡
6. አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ ዙሪያ የቀረበው ጥያቄ፤ ሁለተኛው ተጠሪ አስፈላጊ የግምሩክ ስርዓት እንዲፈጽምና የትራንዚት ሥራ እንዲሰራ ውክልና ተሰጥቶታል፡፡ በሁለተኛ ተጠሪ ለአመልካች ለመስጠት በተዋዋለው የትራንዚት አገልግሎት መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስፈላጊ ሰነዶችን በአንደኛ ተጠሪ በማቅረብ ገንዘቡን በወቅቱ መጠየቅና ማስመለስ ሲገባው ይህንን ግዴታውን ባለመፈጸም ገንዘቡን አንደኛ ተጠሪ ገቢ አድርጎታል። ስለዚህ የደረሰብኝን ኪሳራ የመተካት ኃላፊነት አለበት በማለት የሁለተኛው ተጠሪ ኃላፊነት ምንጩ በሁለተኛ ተጠሪ በአመልካች መካከል ያለው የትራንዚት አገልግሎት ውል መሆኑን በመግለፅ ክስ ያቀረበ መሆኑን ተረድተናል።

7. አንደኛ ተጠሪ አመልካች ዕቃ ላስገባባቸው ኮንቴነሮች በመያዝ እስከ ሚይዙ የነበረውን ገንዘብ መኖሩን የማይክድ አመልካች ተገቢውን የጉምሩክ ስርዓት በመፈፀም ኮንቴነሮቹን የመለሰ መሆኑን ገልፆ በወቅቱ ገንዘብ እንዲመለስለት ጥያቄ አላቀረበም። ስለዚህ ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ ሆኗል። አመልካች ቢያንስ አስተዳደራዊ ውሳኔ ስህተት ነው የሚል ከሆነ በመጀመሪያ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ያቋቋማቸው አቤቱታና ቅሬታ ሰሚ አካላት ማቅረብ አለበት በመሆኑ ይህ ስርዓት ሳይጠናቀቅ በፍርድ ቤት አይታይም በማለት መቃወሚያ አቅርቧል።

8. የአንደኛ ተጠሪን መቃወሚያ ስንመረምረው ጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ጋር በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ሰው ባለስልጣኑ አቤቱታ አጋር ቡድን ውሳኔው በተሰጠ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ማቅረብ እንደሚገባም ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 89 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3(ሐ) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል። በአዋጅ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 17 መሰረት የጉምሩክ ሥርዓት የሚለው ቃልና ወደ አገር የሚገባ፤ ወደ ውጭ አገር የሚላክ ወይም ተላላፊ ዕቃ ከጉምሩክ ወደብ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ከጉምሩክ ቁጥጥርም እስከሚወጣ ድረስ የሚከናወን ማናቸውንም የጉምሩክ አፈፃፀም ሂደት የሚጨምር ስለመሆኑ ተደንግጓል። ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ዕቃ አስቦ ያስገባቸውና ወደ ውጭ የሚመልስ ስለመሆኑ የዋስትና ገንዘብ ያስያዘባቸው ኮንቴነሮች ከጉምሩክ ቁጥጥር ስር የሚወጡበትን የሚሄዱበትን አመልካች መያዣውን የሚጠይቅበትን ሂደት የሚያካትት መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል።

9. አመልካች የመያዣ ገንዘቡን ለማስመለስ አስፈላጊውን ሥርዓት አሟልቶ ለባለስልጣኑ መስሪያ ቤት መጠየቂያና ባለስልጣኑ ለሚወሰነው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ አቤቱታ አጣሪ ቡድን ቅሬታውን ማቅረብ እንዳለበት የአቤቱታ አጣሪ ቡድን የሚያቀርበውን የውሳኔ ሀሳብ ተከትሎ ዳይሬክተሩ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር በተሰኘ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ እንደሚገባውና አመልካች በሰላሳ ቀናት ውስጥ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ካላቀረበ የዳይሬክተሩ ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 89 ንዑስ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 3(ሐ) ንዑስ አንቀፅ 5 እና ንዑስ አንቀፅ 6 ድንጋጌዎችና ከባለስልጣን በቦንድ ወይም በዋስትና ስለተያዘ ገንዘብ አመላላሽ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 37/2002 አንቀፅ 9 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንፃር ሲታይም አመልካች በዋስትና ያስያዝኩት ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት የስር ፍርድ ቤት ቀጥታ ክስ ያቀረበው በአዋጅ ቁጥር 622/2001 እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ቁጥር 37/2002 አንቀፅ መሰረት ሥልጣን ላላቸው አካላት ቅሬታውን ሳያቀርብና ሳይወሰን በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛው ተጠሪ ላይ ያቀረበውን የክስ በዳኝነትን አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ብይን ከላይ የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ ለማየት የዳኝነት ሥልጣን የሌለው መሆኑ፤ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ በዳኝነት አይቶ በመወሰን የሚገድበው አይደለም፡፡ አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ ሁለተኛው ተጠሪ የአመልካች ትራንዚተር ሆኖ ውክልና ወስዶ እያለ ተገቢውን የጉምሩክ ስርዓት ፈፅሞ በመያዣ የተሰጠውን ገንዘብ ባለማስመለሱ የደረሰብኝን ኪሳራ እንዲተካ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ይህ አመልካች በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በባህሪው አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተነጥሎ ሊታይና ሊወሰን የሚችል ዳኝነት የተጠየቀበት የገንዘብ መጠንም በስር ፍርድ ቤት የዳኝነት የስረ ነገረ ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ (ሀ) በአመልካች በሁለተኛው ተጠሪ መካከል የተደረገ የትራንዚት አገልግሎት ውል አለ ወይስ የለም (ለ) በሁለቱ መካከል የተደረገ የትራንዚት አገልግሎት ውል አለ ከተባለ ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች ለኮንቴነሮች ያሰያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስ የመጠየቅ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? ሁለተኛ ተጠሪ በዋስትና የተያዘውን ገንዘብ የመጠየቅ ኃላፊነት አለበት ቢባል፤ ሁለተኛ ተጠሪ ይህንን ኃላፊነቱን በአግባቡ ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚሉትንና ሌሎች አከራካሪ ጭብጦች በመጨረሻም ሁለተኛ ተጠሪ ገንዘቡን ለአመልካች የመተካት ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት መወሰን ሲገባው የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛው ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስና አመልካች በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ የተለያዩ መሆናቸውን ሳያገናዝብ፤ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን የአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 14 ድንጋጌዎች የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 198134 ሰኔ 19 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 140746 ህዳር 12 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው በመሆኑ፤ የአመልካችንና የሁለተኛ ተጠሪን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉሙሩክ/ታክስ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97409

ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ህግ - ምህረት ቁምላቸው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ጋርዊች ዋንግ

2. ሽመልስ አየለ

3. ሰለሞን ተሾመ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ እንደ ቅደም ተከተላቸው 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ክሱም፡- ተከሳሾች የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91(1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈጸመበትን እንዲሁም ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበትን ብር 250,759.16 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም) ለመንግስት መክፈል ሲገባው ይኼው ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበትን አርባ ስምንት በርሜል ነዳጅ እና አንድ መቶ ኩንታል ሲሚንቶ የታርጋ ኮድ ቁጥር 3-48079 ኢት በሆነ ኤርቴቾ የጭነት መኪና ላይ በመጫን ባሁኑ 2ኛ ተጠሪ አሽከርካሪነትና በአሁኑ ሶስተኛ ተጠሪ ረዳትነት የኢትዮጵያን መሬት ሙሉ በሙሉ ጨርሰው ሱዳን ሊገቡ ሲሉ በኢትዮጵያ ድንበር ላይ በምትገኘው ኩቡሪ ኬላ ላይ በፌዴራል ፓሊስ አባላትና በጉምሩክ ሰራተኞች ከእነ ሕገ ወጥ እቃዎቹ እጅ ከፍንጅ ሚያዚያ 07 ቀን 2005 ዓ.ም ከቀኑ ስድስት ሰዓት ሲሆን መያዛቸውን ዘርዝሮ ተጠሪዎች የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሾችም በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጉላቸው የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ግን ቀርቦ በክሱ የተጠቀሰውን ወንጀል ክደው በመከራከራቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአመልካችን ምስክሮች በመስማት እና ማስረጃዎቹን በመመርመር የአሁኑን 1ኛ ተጠሪ እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪው ከኑዌር ዞን ላሬ ወረዳ የተፃፈ ደብዳቤ እንዲሁም ጥቅምት 06 ቀን 2006 ዓ.ም በቁጥር 5/11/ ጋጉም የተፃፈ ደብዳቤ ሕጋዊ የጉምሩክ ክፍያ ከፍለው ሕጋዊ ደረሰኝ ያላቸው መሆኑና የገቢ ደረሰኝ ቁጥር 764/38 የመቶ ኩንታል ሲሚንቶ ወደ ደቡብ ሱዳን የገባበት የጉምሩክ ገቢ ደረሰኝ ለመከላከያ ማስረጃነት ማቅረባቸውን ጠቅሶ ተጠሪው በእነዚህ የሰነድ ማስረጃዎች የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ማስተባበላቸውን ገልፆ ሁሉንም ተከሳሾች ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙ ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦት የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው ጉዳያቸው በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ከሰጠና አመልካችንና የሁኑን 1ኛ ተጠሪን ግን አከራክሮ ጉዳዩን በመመርመር የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የነፃ መለቀቅ ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በድምፅ ብለጫ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- እቃው ከኢትዮጵያ ግዛት ወደ ሌላ አገር ግዛት ሕጋዊ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ሲጓጓዝ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ በክልሉ በሚገኘው የወረዳው የገቢ ጽ/ቤት የተሰጠው ደረሰኝ ቀረጥና ታክሱ መከፈሉን ያሳያል ተብሎ ተጠሪዎች በነፃ መሰናበታቸው በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን ያለው የፌዴራል መንግስት መሆኑን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው ሊሻር ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪዎች በሕጉ አግባብ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ፡-ተጠሪዎች ክስ የቀረበባቸውን የኮንትሮባንድ ወንጀል ስላለመፈፀማቸው በመከላከያ ማስረጃ አስረድተዋል ተብሎ በነፃ እንዲሰናበቱ መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል ፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት የመከላከያ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑንና 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ለክሱ መሰረት የሆኑትን እቃዎች ወደ ደቡብ ሱዳን ሊያስገቡ ሲሉ እቃዎቹ መያዛቸውን ሳይክዱ አጥብቀው ሲከራከሩ የነበሩት እቃዎቹ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተፈፀመባቸው ናቸው በሚል ምክንያት ሁኖ ይህንኑ ለማስረዳት በጋምቤላ ክልል የሚገኘው የላሬ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 600.00(ሰድስት መቶ ብር) የከፈሉ መሆኑን የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ያቀረቡ መሆኑንና የበታች ፍርድ ቤቶች ለተጠሪዎች ነፃ መለቀቅ መሰረት ያደረጉትም ይህንኑ የሰነድ ማስረጃ መሆኑን ነው፡፡አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚከራከረው ደግሞ ከኢትዮጵያ ግዛት ወደ ውጪ አገር በሚወጡ እቃዎች ላይ ቀረጥና ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን የፌዴራል መንግስት ከመሆኑም በላይ ተከፈለ የተባለው ገንዘብ በእቃዎቹ ላይ ሊከፈል ይገባ የነበረውን የቀረጥና ታክስ መጠን አይደለም፤ክልሎች በተሰምዶ ለኩቴ ብለው የሚያስከፍሉ ነው በማለት መሆኑንም ክክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል

በመሰረቱ ቀረጥና ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህግ መንግስት በአንቀጽ 96፤97እና 98 ድንጋጌዎች ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ እንዲሁም በእነዚህ የሕገ መንግስት ድንጋጌዎች አግባብ በፌዴራል መንግስት ስልጣን የሆኑትን የታክስ ጉዳዩችን በተመለከተ ስልጣን የተሰጠው አካል በሕግ ተቋቁሞ በሕጉ የተሰጠውን ስልጣንና ሐላፊነት በመውጣት ላይ የሚገኝ ሲሆን የአዋጅ ቁጥር 578/2000 በተለይ ሲታይም የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተሰጣቸው ኃላፊነቶችና ተግባሮች በአንቀጽ 6 ስር ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡ ከኢትዮጵያ ግዛት ወደ ውጪ አገር በሚላኩ ወይም ከውጪ አገር ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ እቃዎች ቀረጥና ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን ያለው የፌዴራል መንግስት መሆኑን የኢፌዲሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ከዚህ አንጻር ስንመለከተውም በፌዴራል መንግስት ታክስና ቀረጥ እንዲያስከፍል በሕግ ስልጣን ከተሰጠው ተገቢው ቀረጥና ታክስ መከፈሉን መቆጣጠርና በሕጉ የተሰጠውን ኃላፊነት ሁሉ መወጣት ያለበት ይኼው አካል መሆኑ ከዚሁ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ እና ከአዋጅ ቁጥር 578/2000 አንቀጽ 6(8)፣9 እና 10 ድንጋጌዎች እንዲሁም ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 15(1)፣ 82 (1ሀ))((ለ)) ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለው አካል ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ እንደተከፈለ የሚቆጠርበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በሕጉ አግባብ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን እቃ ወደ ውጪ ማስወጣትም ሆነ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2(6)፣(2(11)፣2(17) እና 91 ድንጋጌዎች መሠረት የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው፡፡ ቀረጥና ታክሱን የከፈለው ሰው ከሐሣቡ በላይ የወንጀል ተጠያቂነት የሌለበት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ወደዚህ ድምዳሜ የሚደረሰው ግን ተገቢው ቀረጥና ታክስ ከፋዩ ወገን መንግሥታዊ አካሉ ስልጣን ያለው መሆኑን በማመን ቀረጥና ታክሱን መክፈሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ እቃዎቹ ወደ ደቡብ ሱዳን ሊገቡ ሲሉ የተያዙ ሲሆን በእቃዎቹ ቀረጥና ታክስ የመሰብሰብ ሕጋዊ ስልጣን ያለው የፌዴራሉ መንግሥት መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን ሊከፈል ይገባ የነበረው ቀረጥና ታክስ መጠንም ብር 250,759.16 ሣንቲም መሆኑን አመልካች ጠቅሶ የተከራከረበትና ማስተባበያ ማስረጃዎች ያልቀረቡበት ጉዳይ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ከፈሉ የተባለው ገንዘብ በጉዳዩ ላይ ቀረጥና ታክስ ለመሰበሰብ ስልጣን በሌለው ለክልሉ የወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ገቢ የሆነ ከመሆኑም በላይ መጠኑም ብር 600.00 /ስድስት መቶ ብር/ ብቻ መሆኑን ተጠሪው ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያረጋግጣል፡፡ ይህ ደግሞ በእቃዎቹ ላይ ተገቢው ቀረጥና ታክስ በሕጉ ስልጣን በተሰጠው አካል ተሰብስቧል ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ 1ኛ ተጠሪ እቃዎቹ ከውጪ አገር የገቡና የተከፈለባቸው ቀረጥና ታክስ ምን ያህል እንደሆነ የሚታወቅ እንደመሆኑ መጠን ወደ ውጪ ሲወጡ ሊከፈል ይችል የነበረውን የቀረጥና ታክስ መጠን እንዲሁም ስልጣን ያለውን አካል አያውቁም ለማለት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ታክስና ቀረጥ የመሰብሰብና ሕጉን የማስከበር ኃላፊነት ያለውን አካል አግባብነት ካላቸው ሕጐች አንፃር ሣይመለከቱና 1ኛ ተጠሪ ከፊልኩ የሚሉት የገንዘብ መጠን በእቃዎቹ ሊከፈል ይገባ የነበረውን የገንዘብ መጠን ያህል ያለመሆኑን በማስረጃዎቹ መረጋገጡን ሣያገናዝቡ ተጠሪዎችን ነፃ ማሰናበታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ውሣኔ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የጋምቤላ ክተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 05823 በቀን 10/03/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 01557 በቀን 08/05/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የፀናው ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/.ቁ. 195(2)(ሀ) መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ ተጠሪዎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91(1) ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፉ ጥፋተኞች ናቸው በማለት ወስነናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ከተባለ በኋላ አቃቤ ሕግ ስለቅጣት አስተያየት ተጠይቆ መንግስት በከፍተኛ ወጪ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባውንና ወደ ውጪ የማይላከውን እቃ ተጠሪዎች ከወረዳው ገቢዎች ጽ/ቤት ጋር ተመሣጥረው ወደ ውጪ አገር መላካቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84/1/መ/ መሠረት ቅጣቱን የሚያከብድ ነው ወንጀሉም ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ መካከለኛ ተብሎ ተመድቦ ተገቢው ቅጣት በተጠሪዎች ላይ እንዲወሰን እናመለክታለን አሉ፡፡ ጉዳዩን መርምሮ የቅጣት ውሣኔ ለመስጠት ለ18/09/2006 ዓ.ም ተቀጠረ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 18 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

መሰጠፉ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሰልጣን ዐ/ሕግ ምህረት ቁምላቸው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ጋርዊች ዋንግ
2. ሽመልስ አየለ
3. ሰለሞን ተሾመ

በሌሉበት የሚታይ ነው

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን የቅጣት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ቅ ጣ ት

ተጠሪዎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91(1) ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፉ ጥፋተኞች ናቸው ተብሎ የተወሰነ ሲሆን ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠበት ሰው ደግሞ ተገቢውን ቅጣት ሊያገኝ ይገባል፡፡

ተጠሪዎች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው ወንጀሉ የተፈፀመባቸው እቃዎችና መሳሪያዎች እና የወንጀሉ ፍሬ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በእቃዎቹ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከሰባት እስከ አስራአምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ነው፡፡ድንጋጌው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት የወንጀል ደረጃ እርከን ያልወጣለት በመሆኑ በመመሪያው መሰረት በድንጋጌው የመነሻ ቅጣት ሰባት አመት እና በጣሪያው፤በአስራ አምስት አመት መካከል ያለውን ልዩነት በአራት በማካፈል የምናገኘው የመጀመሪያውና ቀላል ተብሎ የሚታወቅ ደረጃ ቅጣት ፍቅድ ስልጣን ከሰባት አመት እስከ ዘጠኝ አመት ሲሆን መካከለኛው ደግሞ ከዘጠኝ አመት እስከ አስራ አንድ አመት ነው፡፡ከባድ ተብሎ የሚለየው ደግሞ ከአስራ አንድ አመት እስከ አስራ ሶስት አመት ነው፡፡ በስሌቱ መሰረት የመጨረሻው ደግሞ ከአስራ ሶስት አመት እስከ አስራ አምስት አመት ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓቃቤ ሕግ ደረጃው መካከለኛ ተብሎ እንዲመደብ ያመለከተ ሲሆን ለዚሁ ምክንያት ያደረገውም የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 84(1(ሐ)) ድንጋጌ ነው፡፡ይሁን እንጂ የወንጀሉ አፈጻጸም ዘዴ፤ጊዜ ቦታና የአፈጻጸሙ አካኋን ሲሆን በዚህ ድንጋጌ በተመለከተው ይዘትና መንፈስ ነው ለማለት የሚቻል ያለመሆኑን ከድርጊቱ አጠቃላይ አፈፃጸም የተረዳን በመሆኑ የዓቃቤ ህጉን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ስልጣን ከሌለው አካል ደረሰኝ በመያዝና ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ያህል ሳይከፍሉ እቃውን ወደ ውጪ አገር በማውጣት ላይ ሳሉ መያዛቸው የወንጀሉን ደረጃ ዝቅተኛ ሊያደርገው የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡በዝቅተኛ የወንጀል ደረጃ ስር የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ከሰባት አመት እስከ ዘጠኝ አመት ሲሆን ይህ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በእርከን 23 ስር የሚወድቅ ነው፡፡ከዚሁ ውስጥ መነሻ ቅጣቱ ሰባት አመት ሊሆን እንደሚገባው ይዘናል፡፡ በዓቃቤ ሕግ በኩል በተጠሪዎች ላይ የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን ተጠሪዎች ሪከርድ ያልቀረበባቸው በመሆኑ ከዚህ ወንጀል በፊት መልካም ባህርይ የነበራቸው መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል፡፤ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ስራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 16(7) ደግሞ መነሻ ቅጣታቸው ሰባት አመት በላይ ለሆኑት ወንጀሎች አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የሚያስቀንሰው ሶስት እርከን መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ከእርከን 23 ወደ እርከን 20 አውርደናል፡፡ በዚሁ እርከን ውስጥ የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ ከአራት አመት ከአምስት ወር እስከ አምስት አመት ከአራት ወር ነው፡፡ ተጠሪዎች ስራቸው የተለያዩ ሲሆን በወንጀሉ የነበራቸው ሚናም ተመሳሳይ ነው ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ የእቃው ባለቤትና ቀረጥና ታክስ አከፋፈል ላይም ከሌሎቹ ተጠሪዎች የላቀ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ደግሞ የመኪናው ረዳት በመሆኑ ከሌሎቹ ያነሰ ተሳትፎ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ቅጣት ደግሞ መወሰን ያለበት የአጥፊዎችን የተሳትፎ ደረጃም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 41 ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በተጠሪዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት በአንደኛ ተጠሪ ጋርዊች ዋንግ አምስት አመት ጽኑ እስራት፣ በሁለተኛ ተጠሪ፣ ሽመልስ አየለ አራት አመት ከሰባት ወር፣ በሶስተኛ ተጠሪ፣ ሰሎሞን ተሾመ አራት አመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት ሆኖ አግኝተናል፡፡ የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተም እያንዳንዳቸው ብር 250,759.16 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም) እንዲከፍሉ፣ ለክሱ መሰረት የሆነው አርባ ስምንት በርሜል ነዳጅና አንድ መቶ ኩንታል ሲሚንቶ ደግሞ ለመንግስት ውርስ እንዲሆን ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ት ዕ ዛ ዝ

1. ተጠሪዎችን የፌዴራል ፖሊስ ከክፍሉ ፖሊስ ጋር በመተባበር ካሉበት በመያዝ ለጋምቤላ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር እንዲያስረክብ፣ ማረሚያ ቤቱም ተጠሪዎቹን ፖሊስ ይዞ ሲቀርብ በመረከብ በዚህ ችሎቱ በተወሰነው የቅጣት ውሳኔ መሰረትና በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ጊዜ ካለ በማሰብ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ብለናል፡፡ ይጻፍ፡፡
2. የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔውን እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 88446

ግንቦት 22 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሙሉ አሚን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር -ጠበቃ አቶ ገ/መድህን ረዳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን -ዐ/ሕግ አቶ ኃይለመለኮት አበበ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ለዚህ ለሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች ተጠሪው በወሰነበት የገቢ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን ላይ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቢያቀርብም ጉባኤው ቅሬታውን ውድቅ በማድረጉና ጉዳዩን በየደረጃው በይግባኝ ያዩት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጽናታቸው ነው፡፡

አመልካች ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታም፡- ይግባኝ ባይ የሚፈለግብኝን ግብር ከከፈልኩ ከ5 ዓመት በኋላ ያለአግባብ የተወሰነብኝ ግብር እና ታክስም በይርጋ የሚታገድ ነው፣የ1997 ዓ/ም የግብር ዘመን በይግባኝ ባይ ድርጅት ስም ገቢና ወጪ፣ትርፍና ኪሳራ በማስላት በሒሳብ መዝገብ መሰረት በማቅረብ ለግብር አስገቢ መስሪያ ቤት ካሳወቅሁ በኋላ ታህሳስ 23 ቀን 1998 ዓ/ም በድርጅቱ ላይ ባጋጠመው የእሳት አደጋ የሂሳብ እና መሰል ሰነዶች ተቃጥለው በመውደማቸው ይግባኝ ባይም ለሚመለከተው የመንግስት አካል አመልክቼ በክፍለ ከተማው ፖሊስ መምሪያ በኩል አደጋው ስለመጣራቱ ማስረጃ እያለኝ እና ግብር አስገቢው መ/ቤትም በዚሁ ምክንያት የ1997 ዓ/ም የግብር ዘመን በማገኘው 1.65% ኮሚሽን ሊገኝ የሚችለውን ትርፍ ማስላት ሲገባው በእሳት ቃጠሎው ንብረቱ እና ሰነዶቹ መውደማቸውን ቢቀበልም በእሳት አደጋው የወደመውን የሂሳብ መዝገብ ካላመጣህ በስተቀር በ1.65% አይሰላም በማለት ይግባኝ ባዩን በሚጎዳ መልኩ በ7.5% አማካይ የትርፍ መቶኛ በማስላት እጅግ የተጋነነ ግብርና ታክስ መጠየቁ ተገቢነት የለውም፤ በሌላ በኩል ይግባኝ ባይ ድርጅት ከኬኬ ኃ/የተ/የግል ማህበር የሚያገኘው የሱፍ ክር ሐምሌ 15 ቀን 1996 ዓ.ም በተፈራረምነው ውል አንቀጽ 5(5.3) መሰረት ማህበሩ ከሚሰጠው የጅምላ ዋጋ ላይ በፓኬት ከ1ብር እስከ 2 ብር ብቻ በመጨመር እንዲሸጥ የተስማማን ሲሆን ከተስማማነው በላይ የአገልግሎት ዋጋ በመጨመር ልሸጥ እንደማልችል፣ ሽጬ ብገኝም ለውሉ መፍረስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት እንደሚሆን በተስማማነው መሰረት ይግባኝ ባይም ይህንኑ የውል ግዴታ በማክበር በኮሚሽን የሚሸጠው ክር የትርፍ መቶኛው 1.65 በማይበልጥበት ሁኔታ ግብር አስገቢው መ/ቤት ግብር እና ታክስ በግምት ሲወስን 7.5% የትርፍ ህዳግ መያዙ ተገቢ አይደለም፣እንዲሁም በ1996፣ከ1998 እስከ 2001 ዓ/ም ግብር ዘመን ግብሩ በተሰላበት በ1.65% መሰረት የ1997 ዓ/ም ግብርም መሰላት ሲገባው መስሪያ ቤቱ በተሳሳተ መንገድ ማስላቱ ተገቢ አይደለም፣የግብር አስገቢው መ/ቤት በግብር ማስታወቂያዎቹ ላይ አስመጪ በሚል በመጻፍ በተሳሳተ የስሌት መነሻ ወለድ፣ግብር አሳንሶ በመክፈል እና ክፍያ በማዘግየት እንድከፍል የወሰነብኝ መቀጫ ተቀባይነት የለውም ሲል የግብርና ታክስ ውሳኔው ተሰርዞ አዲት በተደረጉት የሂሳብ ሰነዶች መሰረት ሂሳብ ተስተካክሎ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጪው መ/ቤትም በሰጠው መልስ፡- ይግባኝ ባይ የግብር ውሳኔው መቅረብ ከሚገባው ጊዜ በላይ ቆይቶ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው ቢልም ውሳኔው የደረሰው በ25/02/2003 ዓ/ም በመሆኑ የይርጋው ጊዜ ከማለፉ በፊት የቀረበ ነው፤ጊዜው አልፏል ቢባል እንኳን ግብር ከፋይ የተጭበረበረ ገቢ ያቀረበ እንደሆነም በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 71(3) መሰረት በማናቸውም ጊዜ ግብሩን መወሰን እንደሚቻል በመደንገጉ የይርጋው ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ይግባኝ ባይ መስከረም 19 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የሂሳብ መዝገቡን እንዲያቀርብ ተጠይቆ በእሳት አደጋ ምክንያት ንብረቱ የወደመ መሆኑን በመግለጽ ምንም ዓይነት ሰነድ ማቅረብ ባለመቻሉ በአዋጁ መሰረት በይግባኝ ባይ ግብሩ የተወሰነበት ሲሆን ግብሩ በግምት በሚወሰንበት ጊዜም መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት የዘርፉን ዝቅተኛ ትርፍ 7.5% መሰረት በማድረግ ተወስኗል፡፡ ግብሩ በመመሪያው መሰረት የተወሰነበት ሆኖ ሳለም ይግባኝ ባዩ ከአምራች ድርጅት ጋር በተዋዋልኩት መሰረት በ1.65% ዝቅ ተደርጎ ሊሰላ ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክርም የህግ መሰረት የለውም፤የ1996 ዓ/ም የግብር ዘመን ግብር የተሰላው ይግባኝ ባይ አምኖ በገለጸው መሰረት እንጂ በመልስ ሰጪው መ/ቤት አዲት ተደርጎ አይደለም፣የ1997 ዓ/ም ግብርም ሲወሰን በተመሳሳይ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ሲያተርፉ የነበረውን የትርፍ ህዳግ መሰረት አድርጎ በወጣው መመሪያ መሰረት ነው፡፡ መቀጫውን እና ወለድን በተመለከተም ማንኛውም ግብር ከፋይ በህጉ የተጣለበትን የግብርና ታክስ የመክፈል ግዴታ በአግባቡ ባልተወጣ ጊዜ ወለድም ሆነ መቀጫ በህጉ መሰረት የመክፈል ግዴታ ስላለበት መቀጫውንም ሆነ ወለዱን የማይከፍልበት ምክንያት የለም ሲል የግብር ውሳኔው እንዲጸናበት ጠይቋል፡፡

የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤውም ይግባኝ ባይ ያቀረበውን የይርጋ ክርክር በተመለከተ፡- መልስ ሰጪው የግብር ውሳኔውን ያስታወቀው በአዋጁ የተቀመጠው የ5 ዓመት የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ያለ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔ ደግሞ፡-በግብር ከፋዩ የሚቀርቡትን ሰነዶችና መዝገብ ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት በማናቸውም ምክንያት ያልተቀበለው እንደሆነ ግብሩን በግምት ሊወሰን እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

69(1) የተደነገገ ሲሆን መልስ ሰጪውም የይግባኝ ባይን የግብይት ሰነድ ውድቅ በማድረግ ግብሩን በግምት የወሰነው ህጉን መሰረት ያደረገ ነው፤ እንዲሁም የግምቱን አወሳሰን በተመለከተም በአዋጁ አንቀጽ 69(2) ስሌቱ የመልስ ሰጪው መ/ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እንደሚሆን በመደንገጉና መልስ ሰጪውም ግብሩን በግምት ስለሚወሰንበት ሁኔታ የገቢዎች ሚኒስቴር በ1997 ዓ/ም ባወጣው መመሪያ በተቀመጠው ስሌት መሰረት ግብሩን ስለመወሰኑ ስለተረጋገጠ ይግባኝ ባይ ያቀረባቸው የቅሬታ ነጥቦች ተቀባይነት የላቸውም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጓል። ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ እንደተጠቀሰውም ጉዳዩን በደረጃው ያሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ይግባኙን ውድቅ በማድረጋቸው አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን የቅሬታ ነጥቦቹም፡- ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በዝርዝር ያቀረባቸው ነጥቦች ሲሆኑ ተጠሪውም ለጉባኤው ያቀረበውን ተመሳሳይ ይዘት ያለውን መልስ ለዚህ ችሎትም አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች የ1997 ዓ/ም የግብር ዘመን የሂሳብ መዝገብ እና ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች በድርጅቱ ባጋጠመው የእሳት አደጋ በመውደማቸው ለተጠሪው መ/ቤት ማቅረብ አልችልም ሲል ያቀረበውን ክርክር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤና የሥር ፍርድ ቤቶች በማለፍ የዘመኑን ግብር ተጠሪው በግምት መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 69(1) እና በ1997 ዓ/ም የገቢዎች ሚኒስቴር ያወጣውን የግብርና ታክስ ስሌት መሰረት ያደረገ ነው ሲሉ በመቀበል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል የወሰኑት ይህንኑ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮች በአግባቡ በተረጋገጡበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል።

አመልካች የ1997 ዓ/ም የግብር ዘመን ገቢውን በማስታወቅ ግብሩን ለመክፈሉ በግራ ቀኙ የሚታመን ሲሆን ተጠሪው መስከረም 19 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ አመልካች የሂሳብ መዝገቡን እንዲያቀርብ በመጠየቁ አመልካችም መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ በድርጅቱ በደረሰው የእሳት አደጋ ምክንያት ንብረቱና የሂሳብ ሰነዶቹ መውደማቸውን በመጥቀስ ማቅረብ እንደማይችል በማስታወቁ ተጠሪውም የግብሩን መጠን በግምት ስለመወሰኑ የግብር የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በውሳኔ ላይ ካሰፈረው መገንዘብ ተችሏል። እንዲሁም በእሳት አደጋው ንብረቱ እና የሂሳብ ሰነዶቹ መውደማቸውን ለመንግስት አካል አስታውቆ የአደጋው ሁኔታ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ እንዲጣራ ስለመደረጉ እና ማስረጃም እንደተሰጠው አመልካች ከሥር ጀምሮ እየተከራከረ ይገኛል። ይሁን እንጂ ይህን አመልካች ያቀረበውን ምክንያት ተጠሪውም ሳይመረምር ግብሩን በግምት የወሰነ ሲሆን የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እና የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሳይመረምሩ ግብሩ በግምት መወሰኑ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 69(1) መሰረት ተገቢ ነው ሲሉ ተቀብለውታል። በእርግጥ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 69(1) ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብ እና ሰነድ ያልያዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሠነዱን የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ በዚህ ህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላስታወቀ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብሩን ልክ በግምት ለመወሰን እንደሚችል የተደነገገ ቢሆንም ግብር አስገቢው ባለሥልጣን በዚህ ድንጋጌ መሰረት ግብሩን በግምት ከመወሰኑ በፊት ግብር ከፋዩ የሂሳብ ሰነዱን ያልያዘበትን ምክንያት፣ወይም በህጉ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢውን ያላታስወቀበት ምክንያት ከህጉ ጋር አገናዝቦ በመመርመር ምክንያቱ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑን መወሰን ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም "...በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ..." በሚል በድንጋጌው የሰፈረው ሐረግም ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብ እና ሰነድ ባለመያዙ ወይም የሂሳብ መዝገቡንና ተያያዥነት ያላቸውን የሂሳብ ሰነዶች ማቅረብ ባለመቻሉ ብቻ በቀጥታ ግብሩ በግምት እንዲወሰን የሚያደርግ ሳይሆን በቅድሚያ ግብር አስገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ የሚያቀርበው ምክንያት በማስረጃ የተደገፈ መሆን አለመሆኑን፣ ምክንያቱ በማስረጃ የተደገፈ ሆኖ ቢቀርብ እንኳን ግብሩን በግምት ከመወሰን የማይከለክል መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ አመልካች በድርጅቱ ላይ በደረሰው የእሳት አደጋ ንብረቱና የሂሳብ ሰነዶቹ መውደማቸውን ገልጾ እስከተከራከረ ድረስም ተጠሪው አመልካች የሂሳብ መዝገብና ተያያዥነት ያላቸውን የሂሳብ ሰነዶቹ እንዲያቀርብ ታዞ አላቀረበም በሚል ግብሩን በግምት በአዋጁ አንቀጽ 69(1)መሰረት ከመወሰኑ አስቀድሞ የአመልካች ደርጅት በእሳት የተቃጠለ ስለመሆኑ፣ የእሳት ቃጠሎ ደርሶ ከሆነም ግብር እንዲከፈል በተጠየቀው ዘመን አመልካች የያዘው የሂሳብ መዝገብ እና የሂሳብ ሰነዶች መቃጠላቸውን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን አመልካች ካሉት ተቀብሎ በመመርመር እንዲሁም ተጠሪውም ከራሱ በኩል በሚኖረው የማጣሪያ መንገድ በማጣራት ማስረጃዎቹን መዝኖ ግብሩ በግምት ሊወሰን የሚገባ መሆን አለመሆኑን በመለየት የአመልካችን ክርክር የማይቀበልበት በቂ ምክንያት ካለው ግብሩን በግምት መወሰን ሲገባው ክርክሩንና ማስረጃዎቹን ሳይመረምር በአዋጁ አንቀጽ 69(1)መሰረት ግብሩን በግምት መወሰኑ ተገቢነት የለውም፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤም አመልካች ድርጅቱ በእሳት መቃጠሉንና የዘመኑ የሂሳብ መዝገቡም ሆነ ተያያዥነት ያላቸው የሂሳብ ሰነዶች በቃጠሎው ምክንያት መውደማቸውን በመግለጽ ግብሩ በግምት ሊወሰን አይገባም ሲል ያቀረበውን ቅሬታ በመመርመር አመልካች የጠቀሰው ምክንያት መኖር አለመኖሩን በማስረጃዎች በማጣራት መወሰን ሲገባው ተጠሪው በግምት ግብሩን የወሰነው ህጉን መሰረት ያደረገ ነው ሲል መቀበሉም ሆነ ጉዳዩን በየደረጃ ያዩት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪው የሰጠውን የግብር ውሳኔ ተገቢ ነው ሲሉ ማጽናታቸው ውሳኔውን ለመስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮች በአግባቡ ባልተረጋገጡበት ሁኔታ ከመሆኑም ሌላ የአመልካችን መሰረታዊ የሆነ የመሰማት መብት ባልተጠበቀበት ሁኔታ ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ስንል ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ

1. የፌዴራል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመ/ቁ/706 በቀን 21/05/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ውሳኔ፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/118346 በቀን 11/04/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/86148 በቀን 13/06/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. የፌዴራል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እና የሥር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጡት ውሳኔውን ለመስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮች ባልተሟሉበት፣ ባልተረጋገጡበት እና የአመልካች የመሰማት መብት ባልተከበረበት ሁኔታ ነው ብለናል፡፡
3. በአመልካች ድርጅት ታህሳስ 23 ቀን 1998 ዓ/ም የእሳት አደጋ መድረሱን እና በ1997 ዓ/ም የግብር ዘመን አመልካች የያዘው የሂሳብ መዝገብ እና ተያያዥነት ያላቸው የሂሳብ ሰነዶች በቃጠሎው ምክንያት ስለመውደማቸው የሚያቀርባቸውን ማስረጃዎች እንዲሁም ተጠሪውም በተቃራኒው የሚያቀርባቸው ማስረጃዎች ካሉ የፌዴራል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመስማት እና በመመዘን ግብሩ ስለሚወሰንበት ሁኔታ በግብር ህግ አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ህጎች አንጻር ጉዳዩን መርምሮ የበኩሉን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቁጥሩ 118346 የሆነው መዝገብ በመጣበት አካኋን ተመላሽ ይደረግ፡፡
- መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92537

ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች ፡- አዞ ግሎባል ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ ሙሉጌታ ወንድማገኝ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ኃ/መለኮት አበበ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ የጉምሩክ ሥርዓት አልተፈጸመበትም ተብሎ ለተወረሰ ንብረት የተከፈለ ታክስ እንዲመለስ በማለት የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

> የክርክሩ መነሻ አመልካች ከቻይና አገር ኒግቦ ኦቪል ባትሪ ኮ/ሊሚትድ ከሚባል ኩባንያ 100,800 ደርዘን ካርቶኖች የያዘ ባትሪ ወደ አገር ውስጥ አስገብቻለሁ፡፡ዕቃውን ወደ አገር ውስጥ ሳስገባ በደኅላራሲዮን ቁጥር C/D22074 ብር 473,799.65 ቀረጥ ከፍለናል፡፡ነገር ግን ከዚህ በኋላ ህገ ወጥ ተግባር ተፈፅሟል ተብሎ በወንጀል ተከሰን ዕቃው ተወርሶ እኛ በነፃ ወጥተናል፡፡ስለዚህ የከፈልነውን ብር 473,799.65 እንዲመልስ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ውርሱ የተከፈለውንም የቀረጥ ገንዘብ የሚያካት ነው፡፡ስለዚህ የምመልስበት ምክንያት የለኝም የሚልና ሌሎች ዝርዝር መከራከሪያዎች አቅርቧል፡፡
>
> የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ማመልከቻ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች ነሐሴ 3 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች እንዲመልስልኝ የጠየኩት ዕቃዎች የከፈልኩትን መደበኛ የቀረጥ ገንዘብ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን በዋስትና እንደተያዘ ገንዘብ በመቁጠር የሰጡት የህግ ትርጉም መሰረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ተጠሪ በበኩሉ ጥቅምት 7 ቀን 2005 ዓ/ም በሰጠው መልስ አመልካች ዕቃው ህገወጥ ተግባር ተፈፅሞበታል ተብሎ ሲወረስ ፤በህጋዊ መንገድ ዕቃው የተከፈለ ቀረጥ ውርሱ መጨመር የለበትም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካቹ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

በሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በዕሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተወረሱ ዕቃ የተከፈለው የቀረጥ ገንዘብ እንዲመለስለት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ህጋዊ የጉምሩክ ቀረጥ ከፍየበታለሁ የሚለው ዕቃ የተያዘውና የተወረሰው፤በአመልካች መጋዘን በተደረገ ብርበራ የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ ከገቡ ዕቃዎች ጋር ተቀላቅሎ በመገኘቱ እንደሆነ ይኸ ሰበር ችሎት መዝገብ ቁጥር 64115 ጥቅምት 8 ቀን 2004ዓ/ም በሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ህጋዊ ቀረጥ የተከፈለበት ዕቃ ህጋዊ የጉምሩክ ሥርዓት ካልተፈፀመበት ዕቃ ጋር ተቀላቅሎ በተያዘ ጊዜ፤በህጋዊ መንገድ ለገባው ዕቃ የተከፈለው ታክስ እንዲመለስለት የዕቃው ባለቤት የሚጠይቅበት ህጋዊ ሥርዓት የለም ፡፡የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3)(ሀ) ድንጋጌም በዚህ መንገድ እንዲተረጎምለት አመልካች ያቀረበው ክርክር አዋጅ ሊያስፈፅመው የሚፈልገውን ጠቅላላ አላማና የድንጋጌውን ይዘትና ግብ ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 91622

መጋቢት 12 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አፍሪካ ታደሰ-

ተጠሪ፡- 1.ወ/ሮ ያለምወርቅ ታደሰ-ታልፏል

2.የጎባ ከተማ አስተዳደር ፅ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በሚስትነትና በወራሽነት ድርሻ አለው ተብሎ ውሳኔ ያገኘ ሰው በንብረቱ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው እንዲታዘዝለት በአፈጻጸም ማመልከቻ ዳኝነት ቢጠይቅ ጥያቄው በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በጎባ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍ/ቤት የአሁኗ አመልካች የፍርድ ባለመብት የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለእዳ ሁነው ተከራክረው ነበር፡፡ አመልካች በአሁኑ ተጠሪና በወ/ሮ ያለምወርቅ ታደሰ ላይ የከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10883 የተሰጠ ውሳኔ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቅ ሲሆን አፈጻጸሙን የያዘው ፍርድ ቤትም ጉዳዩ እንዲጣራ ትእዛዝ ሰጥቶ የጎባ ከተማ ማዘጋጃ ቤትም በቁጥር 1109/2/4/184 በ14/9/2004 ዓ/ም ለፍርድ ቤቱ በጻፈው ደብዳቤ አመልካች እንዲፈጸምላቸው የሚጠይቁት ቤት ከሟች ባለቤታቸው ኢንስፔክተር ጥላሁን መለሰ ስም ወደ ወ/ሮ ያለምወርቅ ታደሰ (1ኛ ተጠሪ) የተዛወረ ስለሆነ የሚፈፀም ነገር የለም በማለት ገልጿል፡፡ከዚህም በኋላ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ይህንኑ ደብዳቤ መነሻ በማድረግ የአፈጻጸም መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ የአፈፃጸም ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ለተጠሪዎች ጥሪ አድርጎ 1ኛዋ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ጉዳዩን በሌሉበት እንዲታይ ያደረገ ሲሆን 2ኛው ተጠሪ ግን ቀርቦ ከአመልካች ጋር ከተከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነውና በመ/ቁጥር 10883 የተሰጠው ውሳኔ ይዘቱ አመልካችም ሆነ ህፃኑ ድርሻቸውን እንዲያገኙ የሚል እንጂ ስመ ሀብቱ እንዲዛወር የሚል አይደለም፣የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በሐሰተኛ የሚስትነት ማስረጃ ስመ ሃብቱ እንዲዞር ያደረጉ መሆኑ የተረጋገጠ ነው የሚል ክርክር ቢቀርብም ይህ ማስረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 998 መሰረት እንዲሰረዝ አልተደረገም የሚሉትን ምክንያቶችን አስፍሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10883 የተሰጠውን ውሳኔ የሚፈፀም አይደለም በማለት የአፈጻጸም መዝገብ መዝጋታቸው አንድ ውሳኔ የሚፈጸምበትን ስርዓት ባልተከተለ መንገድ መሆኑን ዘርዝረው አከራካሪው ቤት ስመ ሃብቱ እንዲዞርላቸው አድርገው ዋናውን ውሳኔ ያስፈጽሙ ዘንድ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው 1ኛዋ ተጠሪ ሊቀርቡ ባለመቻላቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው የታለፈ ሲሆን 2ኛው ተጠሪ ግን በመቅረቡ ከአመልካች ጋር በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች በመ/ቁጥር 10883 በ26/11/2003 በንብረቱ ላይ ድርሻ ያላት መሆኑ በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ድርሻዋ እንዲሰጣት ውሳኔ ተሰጥቶ እያለና ውሳኔውም ባልተሻረበት ሁኔታ ባፈፃጸም ችሎቱም ቢሆን 1ኛ ተጠሪ ንብረቱ ላይ አፈጻጸም ሊቀጥል አይችልም በሚል ያቀረቡት ተቃውሞ ሳይኖር የበታች ፍርድ ቤቶች ሊፈጸም የሚችል ነገር የለም በሚል አቤቱታውን ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም በመ/ቁጥር 10883 የተሰጠው ውሳኔ አስቀርበን ይዘቱን ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በአከራካሪው ቤት ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ጠቅሰውና ይኼው መብታቸው ተረጋግጦ ዳኝነት እንዲሰጥ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው የወረዳው ፍርድ ቤት ተገቢ ነው ያለውን ዳኝነት ከሰጠ በኋላ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ስመ ሃብቱን በስማቸው ያደረጉት ከቤቱ ባለቤት ውል አድርገው መሆን ያለመሆኑን፣የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የቤቱን ስመ ሃብቱን ከሕግ ውጪ ካዛወረ መከሰስ አለበት? ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦችን ለይቶና የአሁኗን 1ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ እንድትገባ አድርጎ ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወስን ለወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሶለት ጉዳዩ የተመለሰለት የወረዳው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን 1ኛ ተጠሪ በሌለችበት አይቶና አመልካችንና 2ኛ ተጠሪን ደግሞ በተገቢው መንገድ አከራክሮና ተገቢ ነው ያለውን ሁሉ ከአጣራ በኋላ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የሚች ኢንስፔክተር ጥላሁን መለሰ ሚስትነትን በማሳወጅ በያዙት ማስረጃ መሰረት ቤቱን ሙሉ በሙሉ በግላቸው የሚያዛወሩበት ምክንያት እንደሌለ፣ተጠሪዋ ድርሻዋን ብቻ የምታገኝ መሆኑን፣የአሁኗ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ደግሞ የሚቹ ሚስት መሆናቸው መረጋጡንና እርሳቸውም ድርሻቸውን ማግኘት ያለባቸው መሆኑን እንዲሁም አመልካች ከሚቹ የወለዱት ልጅ(ይዲድያ ጥላሁን) ደግሞ የሚቹን ድርሻ ላይ ሙሉ የወራሽነት መብት ያለው መሆኑን ገልፆና ይህንኑ ድርሻውን የማግኘት መብት የተጠበቀ መሆኑን ጠቅሶ በመ/ቁጥር 10883 ሐምሌ 26 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት ዳኝነት መስጠቱን፣ይህ ውሳኔ በየትኛውም እርከን ባለው ፍርድ ቤት ያልተለወጠ መሆኑንና ለአፈጻጸሙ መሰረት የሆነውም ይኼው የአመልካችና የልጃቸው ድርሻ ያለበት መሆኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተረጋገጠው ውሳኔ መሆኑን ነው።

በመሰረቱ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደ ፍርዱ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሳያሉ። በእነዚህ ድንጋጌዎች በተዘረጋው ስርአት አግባብ በመመራት ካልሆነ በስተቀር በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ሕጋዊ ባልሆነ እና ውሳኔውን ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ ውድቅ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ አይኖርም።ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያስገነዝቡት አቢይ ነጥብ የፍርድ አፈጻጸም ስርአት ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በእራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር ወይም ውጤት የሚለውጥበት ስርአት መሆኑን ነው። በሌላ አገላለጽ የድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘትና መንፈስ በጥንቃቄ ሲታይም የፍርድ አፈጻጸም ስለፍርድ አፈጻጸም የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመከተል ፍርድን በተግባር መተርጎም እንደመሆኑ መጠን የአፈጻጸም ስርአቱ ህጉን መሰረት ማድረግ ያለበትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን መሰረታዊ ዓላማ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአነስተኛ ወጪ ጊዜና ጉልበት በተፋጠነና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም በሚያስችል አግባብ ሕግ አውጪ ያስቀመጣቸው መሆኑን የምንረዳው ጉዳይ ነው።ውሳኔው የማይፈፀምበት ሕጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩም በፍርድ ቤቱ ታይቶ ተገቢው እልባት የሚሰጥበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው።ይህ ድንጋጌ አፈጻጸሙን የያዘው ፍርድ ቤት አፈፃፀሙን ምቹ ሁኔታዎች ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በተቻለ መጠን ፍርዱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ሊከተል የሚገባ መሆኑን ያሳያል።ስለሆነም አንድን ፍርድ እንደፍርዱ ይዘትና መንፈስ ውጤት ባለው መልኩ መፈጸም የግድ የሚል ሲሆን ይህ ደግሞ የፍርድ አፈጻጸምን በተመለከተ በስነ ስርዓት ሕጉ የተዘረጉት ስርዓቶች በአግባቡ በማየትና ተፈፃሚ በማድረግ የሚከናወን መሆኑን የድንጋጌዎቹ ይዘት የሚያሳይን ጉዳይ ነው።።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ለአፈፃጸም ማመልከቻቸው መሰረት ያደረጉትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት አያይዘው ያቀረቡት የወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10883 የሰጠውን ፍርድ ሲሆን ከላይ እንደተገለጸው በአከራካሪው ቤት ላይ መብት ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል። በአፈፃጸም ማመልከቻቸው የጠየቁት ዳኝነትም የቤቱ ስመ ሃብተ በስማቸውና የሚቹ ወራሽ መሆኑ ተረጋግጦ የሚቹን ድርሻ እንዲወርስ ለተወሰነለት አመልካች ሞግዚት ለሆኑት ሕጻን ልጅ ስም ነው፣የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ የአመልካችን የአፈጻጸም ዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት በመ/ቁጥር 10883 በተሰጠው ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስመ ሀብት እንዲኖር ለፍርድ ባለመብቶች አልተወሰነም በሚል ምክንያት መሆኑን ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የምንረዳው ጉዳይ ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤት ግን ቤቱ ወደ አሁኗ 1ኛ ተጠሪ ስም ተዛውሯል ተብሎ በማዘጋጃ ቤት በመገለጹ ብቻ የአፈጻጸም መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካችና ሕጻኑ በቤቱ ላይ መብት አላቸው የሚለው የዋናው ክርክር ውሳኔ ይዘት የሚያሳየው አመልካች እና ሕጻኑ በኢ/ፌ/ዲ/ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ስር የተከበረውን የንብረት ባለቤትነት ያረጋገጠ መሆኑን፣ በዚሁ ውሳኔ መሰረት የቤቱ ስመ ሃብት በአመልካችና በሕፃኑ ድርሻ መጠን ላይ እንዲመዘገብ የማይደረግበት አግባብ የሌለ መሆኑን ነው፡፡በዚህ አግባብ ውሳኔው እንዲፈፀም ካልተደረገ ደግሞ በዋናው ክርክር በሕጉ አግባብ ተጠርተው ያልቀረቡና ድርሻቸውን ብቻ እንዲያገኙ የተወሰነባቸው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ ተገቢ ያልሆነ ተግባር እንዲፈፅሙ የሚያደርግ ውጤት የሚያስከትል መሆኑ የሚታመን ነው፡፡በመሆኑም አመልካች በቤቱ ላይ መብት እንዳላቸው በዋናው ውሳኔ ተረጋግጦላቸውና በ1ኛ ተጠሪም ስመ ሃብቱ ሙሉ በሙሉ የተመዘገበው ያላግባብ መሆኑን በመ/ቁጥር 10883 የተሰጠው ውሳኔ በግልጽ የሚያሳይ ሁኖ እያለና 1ኛዋ ተጠሪም በፍርድ ባለእዳነታቸው ቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 386 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያቀረቡት መቃወሚያ ሳይኖር በፍርድ ኃይል የተረጋገጠውን የአመልካችን የንብረት ባለቤትነት መብት ዋጋ የሚያሳጣ የአፈጻጸም ትእዛዝ መስጠት ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ 2ኛ ተጠሪም በዋናው ክርክር ተሳታፊ ሁኖ የአመልካችንና የህፃኑን ድርሻ በ1ኛ ተጠሪ ስም እንዲመዘገብ ማድረጉ ተገቢ ያለመሆኑን በሚያስገነዘብ መልኩ በዋናው ጉዳይ ተወስኖበት እያለ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ስመ ሃብቱ በ1ኛ ተጠሪ ተዛውሯል በማለት በአፈጻጸም ጊዜ ለፍርድ ቤቱ በመግለፁ ብቻ የአፈፃፀም መዝገብ የሚዘጋበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ምክንያቱም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲነበቡም የአስተዳደር አካል በባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አሰጣጥ ላይ ፍጹም የሆነ አስተዳደራዊ ስልጣን ያለው ስለመሆኑ አያሳዩም፡፡ይልቁንም ድንጋጌዎች እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1198 ድንጋጌ ጋር ተዛምደው ሲታዩ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የሚሰረዘው በሕጉ በተመለከቱት ምክንያቶች ብቻ መሆኑን ከሕጉ ውጪ ተግባሩ ተከናውኖ ከተገኘም መብቱ የተነካው ሰው በኢ/ፌ/ዲ/ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣78 እና 79 ድንጋጌዎች መሰረት ጉዳዩን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቅርቦ አቤቱታው እንዲታይለት የሚያደርግበት ጉዳይ እንጂ አስተዳደር አካሉ የሰጠው ውሣኔ በፍርድ ቤት እንዳይታይ የሚገደብበት ስርአት የሌለ መሆኑን የምንገነዘበው ነውና፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ በሚስትነታቸው ባገኙት ማስረጃ መሰረት የቤቱን ስመ ሃብት እንዲዞር ባደረጉበትና ይኼው ማስረጃ ባልተሰረዘበት ሁኔታ የስመ ሃብት ምዝገባ ጥያቄ በአመልካች መቅረቡ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 998 ድንጋጌ አንፃር ተገቢነት የለውም በማለት በፍርድ ላይ ያሰፈረው ምክንያትም ቢሆን በዋናው ክርክር ጊዜ 1ኛ ተጠሪ ስመ ሃብት እንዲዞር ማድረግ የሚችሉት በሚስትነታቸው ባላቸው ድርሻ ብቻ ነው ተብሎ የተወሰነውን የውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክፍል ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ነው።በመሆኑም የ1ኛ ተጠሪ የሚስትነት ማስረጃ ያለመሰረዝ ውጤት ሊኖረው የሚችለው በድርሻቸው ብቻ እንጂ በአመልካችና በሟቹ ኢንስፔክተር ድርሻ ጭምር አይደለም።አመልካችም ሆነ 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ ድርሻ አላቸው ከተባለም ድርሻቸው ምን ያህል ነው?፤በቤቱ ግማሽ ነው ወይስ ከሟቹ ጋር ሶስቱም እኩል? የሚለው የሟቹን ድርሻ ህፃኑ እንዲወርስ ተብሎ ከተወሰነው የውሳኔ ክፍል እና አግባብነት ካላቸው የህገ መንግስት እና ከክልሉ የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝቦ በአፈፃፀሙ ጊዜም ቢሆንም ተገቢው ትዕዛዝ የሚሰጥበት ጉዳይ ነው።ይህም አካሄድ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንጻር የሚነቀፍበት አግባብ የለም።

በአጠቃላይ ተጠሪዎች በዋናው ጉዳይ በፍርድ ቤት በነበረው ክርክሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጎ 2ኛ ተጠሪ ቀርቦ ተገቢ ነው ያለውን ክርክር አቅርቦ አመልካችና ሕጻኑ በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ በተወሰነበት ሁኔታ በዋናው ጉዳይ ስመ ሃብቱ እንዲዞር አልተወሰነም ተብሎ የአፈጻጸም መዝገቡ መዘጋቱ ከላይ የተመለከቱትን ሕጋዊ ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ባላገናዘበ መንገድ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አፈፃጸሙ እንዲቋረጥ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. በጎባ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13408 ግንቦት 14 ቀን 2004ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝና ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት በባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14585 ጥቅምት 06 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል።
2. አመልካች እና ህፃን ይዲድያ ጥላሁን መለሰ በዋናው ክርክር በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑ እና 1ኛ ተጠሪም በድርሻቸው ብቻ ስመ ሃብቱን ማስመዝገብ ሲገባቸው በቤቱ ላይ ሙሉ መብት እንዳላቸው ተደርጎ ስመ ሃብቱ መዞሩ ተገቢነት የሌለው መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በቤቱ ላይ 1ኛ ተጠሪ ስመ ሃብት ማዞራቸው አፈጻጸሙን ለማስቆም በቂ ምክንያት አይደለም ብለናል። በዚህም ምክንያት አመልካች በራሳቸውና በህፃኑ ድርሻ ስመ ሃብቱ እንዲመዘገብላቸው ያቀረቡት የአፈጻጸም ጥያቄ ተገቢ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት አፈጻጸሙን በመ/ቁጥር 13408 ቀጥሎ በፍርድ ሐተታው ላይ በተመለከተው አግባብ እንዲያስፈፅም ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሰረት መልሰናል። ይጻፍ።

3.በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዘገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94571

ሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፉ አህመድ

አመልካቾች ፡- 1. ወ/ሮ የልፍኝ መኮንን } ጠበቃ አቶ ባንተአምላክ ብናልፈው ቀረቡ
2. ቄስ ደርሰህ መኮንን }

ተጠሪ፡- የአባ መኮንን እጅጉ ወራሽ አቶ ዘርሁን መኮንን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀም ክርክርን የሚመለከት ሆኖ አፈፃፀሙን ሲመራ የነበረው ፍ/ቤትም የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካቾች የአፈፃፀም ከሳሾች ደግሞ የአፈፃፀም ተከሳሽ ነበር፡፡

ለፍርድ አፈፃፀሙ ክርክር መነሻ የሆነው ፍርድ የተሰጠው በፊዴራሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 69209 የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ፡- የወቅቱ የቤቱ ግንባታ ዋጋ በወራሾች መካከል የእኩልነት መብትን ስለሚያረጋግጥ የሚያከራክረው የውርስ ንብረት ወይም ቤት ለክፍፍል በሚቀርብበት ወቅት በሚኖረው የገበያ ዋጋ መሰረት ግምቱ ሲቀርብ አመልካቾች (የአሁኑ አመልካቾች)የግምቱን ግማሽ ድርሻ እንዲያገኙ የሚል ነው፡፡ይህ ውሳኔው በአሁኑ አመልካቾች አማካኝነት በምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከ/ፍ/ቤት ለአፈፃፀም ቀርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ የአሁን ተጠሪን አስቀርቦ አስተያያቱን ከጠየቀ በኃላ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረት ለማስፈፀም ይችል ዘንድ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምት ምን ያክል እንደሆነ ግምቱ በደብረ ማርቆስ ከተማ አገልግሎት ፅ/ቤት በኩል በባለሙያ ተገምቶ ውጤቱ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት በብር 39,119.09 ተገምቶ መቅረቡን የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ግልባጭ የሚያስረዳ ሲሆን ፍ/ቤቱም በበኩሉ የቤቱ ጨረታ መነሻ ግምት ብር 39,119.09 መሆኑ ታውቋል በማለት ለአፈጻጸሙ መነሻ በሆነው ውሳኔ መሰረት የቤቱን የገበያ ዋጋ ግምት ለማወቅ ይቻል ዘንድ የፍ/ቤቱ ተወካይ በተገኙበት ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ የጨረታ አሸናፊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሆነው ዋጋ ታውቆ ለፍ/ቤቱ እንዲገለፅ የሚል ይዘት ያለው ትዕዛዝ ሰጥቶ ውጤቱን ለመጠባበቅም ቀጠሮ ለሐምሌ 2 ቀን 2004 ዓ/ም ይሟል፡፡

የአሁኑ ተጠሪም በዚህ ትዕዛዝ ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም በበኩሉ ቅሬታውን መርምሮ በሰጠው ትዕዛዝ ፡- በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው እንጂ የጨረታው የመጨረሻ ውጤቱ የታወቀ ስላልሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 320(3) መሰረት የይግባኝ አቤቱታ ሊቀረብበት የሚችል አይደለም በማለት ቅሬታውን ሰርዞታል፡፡ሆኖም ግን ቀጥሎ በአሁኑ ተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአከራካሪው ቤት የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምት በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት በደ/ማርቆስ ኢንዲስትሪ ልማት ከተማ አገልግሎት ፅ/ቤት ብር 39,119.09 መሆኑ ተገምቶ ውጤቱ ቀርቦ እያለ የስር ፍ/ቤት ቤቱ በጨረታ ተሸጦ ክፍፍሉ እንዲፈፀም በማሰብ የጨረታ ማስታወቂያ እንዲወጣ ትዕዛዝ መስጠቱ ለአፈፃፀም መነሻ የሆነውን ውሳኔ (በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን)ሙሉ ይዘት ያገናዘበ አይደለም የሚል ምክንያት ጠቅሶ የስር ፍ/ቤቱን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ህ/ስ/ስ/ቁ 348(2) መሰረት በመሻር የአሁኑ ተጠሪ ተገምቶ በቀረበው “የቤቱ ገበያ ዋጋ ግምት ብር 39,119.09” መሰረት ግማሹን ብር 19,559.55 ለአሁኑ አመልካቾች ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

አሁን በአመልካቾች የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ፡- የቤቱ ገበያ ዋጋ ግምት የሚታወቀው ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ በሚሰጠው ከፍተኛ ዋጋ መሰረት በማድረግ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም የጨረታ ማስታወቂያውን ያወጣው በዚሁ መሰረት የቤቱን የገበያ ዋጋ ግምት ለማወቅ እንዲቻል እንጂ ቤቱ ተሸጦ ከተጠሪ እጅ እንዲወጣ በማሰብ አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤትን ትዕዛዝ ሽሮ የውርስ ንብረት ድርሻችንን በባለሙያ ግምት መሰረት ግማሹን ገንዘብ እንድንቀበል በማለት የሰጠው ውሳኔ ለአፈፃፀም መነሻ የሆነው ውሳኔ ይዘት በትክክል ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ መብታችንም በእጅጉ የጐዳ በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ 3ኛ ወገን በሚያቀርበው የገበያ ዋጋ መሰረት ግማሹ እንዲከፈለን የሚያደርግ ውሳኔ ይሰጠን የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁ 69209 ለክርክሩ መነሻ የሆነው የውርስ ሀብት በወራሾች መካከል በእኩል ክፍፍሉ እንዲፈፀም በሚያስችል መልኩ የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግማሽ ድርሻ አመልካቾች እንዲያገኙ በማለት ከሰጠው ውሳኔ አንፃር የክልሉ ሰበር ችሎት ያሳለፈውን ውሳኔ ተገቢነተ ለማጣራት ሲባል አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ በፅሁፍ ሰጥቷል፡፡ይዘቱም ባጭሩ፡- የክልሉ ሰበር ችሎት አመልቾች ድርሻቸውን እንዲያገኙ የወሰነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወቅቱን የገበያ ዋጋ ግምት መሰረት ባደረገ መልኩ ስለሆነ ውሳኔው የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካቾችም የመልስ መልሳቸውን ሰጥተውበታል ፡፡

የጉዳይ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን የአንድ ንብረት የገበያ ዋጋ ግምቱ ምን ያህል እንደሆነ የሚወሰነው ወይም የሚታወቀው በምን አግባብ ነው?የሚለውን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሰረቱ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የውርስ ሀብት ወይም ቤት ግምት ግማሹን ድርሻ ለአመልካቾች ከፍሎ ቤቱን በቀዳሚነት ለራሱ እንዲያስቀር ተብሎ አስቀድሞ የተወሰነ በመሆኑ አመልካቾች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ የለም፡፡እንዲሁም ግምቱን በተመለከተም የውርስ ሀብቱን በወራሾች (በግራ ቀኙ)መካከል በእኩል ለማከፋፈል በሚያስችለው መልኩ በወቅቱ ገበያ የዋጋ መሰረት ግምቱ ሲቀርብ አመልካቾች የግምቱን ግማሽ ድርሻ እንዲያገኙ ተብሎም ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁ 69209 በሆነው ላይ በግራ ቀኙ መካከል የስረ ነገር ክርክርን አስመልክቶ በቀረበው ጉዳይ ላይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ተወስኗል፡፡ሆኖም ግን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀደም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ የውርስ ሀብቱ የገበያ ዋጋ በምን አግባብ ሊቆረጥ ወይም ተወስኖ ሊታወቅ እንደሚችል በግልፅ አለማመላከቱን ከውሳኔው ይዘት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ይሁን እንጂ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ በተጠቀሰው ውሳኔ ይዜንን ጉዳይ በግልፅ ባያመለክትም በሌሎች በርካታ መዝገቦች ላይ ግን በተለይም በሰበር መ/ቁ 37297 እና 37298 ላይ የአንድ ንብረት ወይም ቤት የወቅቱ የገበያ ዋጋ ሊቆረጥ የሚችለው ከተቻለ በስምምነት ይህ ካልተቻለ ደግሞ ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ በሚያወጣው ከፍተኛ ዋጋ መሰረት መሆኑን በአዋጅ ቁ 454/97 አንቀጽ 2(1) ድንጋጌ መሰረት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ይህ አስገዳጅ የሰበር ውሳኔም ለዚህ ለተያዘው ጉዳይም አግባብነት ያለው ሆኖ ስላገኘን አመልካቾች የውርስ ሀብቱን ግማሽ ድርሻቸውን የወቅቱን የገበያ ዋጋ ግምት ተቆርጦ ወይም ታውቆ ሊከፈላቸው የሚገባው በዚህ መሰረት ሆኑ አግኝተነዋል፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ተመልክቶ ውሳኔ መሰጠት ሲገባ በደ/ማርቆስ ከተማ አገልግሎት ፅ/ቤት ባለሙያ ተገምቶ የቀረበውን የቤቱን ግምት የገበያ ዋጋ ግምት እንደሆነ አድርጐ በመውሰድ እና አመልካቾች በዚህ መሰረት ግማሽ ድርሻቸውን ብር 19,559.55 እንዲያገኙ በማለት የሰጠው ውሳኔ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎችን ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1.የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 25073 በ5/02/06 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2.የምስራቅ ጉጃም አስተዳደር ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ግንቦት 28 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ለአፈፃፀሙ መሰረት በሆነው ውሳኔ መሰረት ለማስፈፀም እንዲቻል የቤቱ የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምት ተለይቶ እንዲታወቅ ይቻል ዘንድ ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ አሸናፊ የሆነው ከፍተኛ ዋጋ ለፍ/ቤቱ ይገለፅ በማለት የሰጠው ትዕዛዝ የሚነቀፍ ባለመሆኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

3. የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የአፈፃፀም መ/ቁ 18328 በማይንቀሳቀስ እና ግራ ቀኙ ተጠይቀው የቤቱ የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምት በስምምነት ሊቆረጥ ካልተቻለ ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ በሚያወጣ ከፍተኛ ዋጋ መነሻ በማድረግ ተጠሪ ግማሹን ለአመልካቾች እንዲከፍል እንዲደረግ ብለናል፡፡

4.ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92035

የካቲት 24 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ. ዓድዋ ቅርንጫፍ - ነ/ፈጅ ጥላሁን ይህደጉ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሐጎስ ተስፋይ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ክበይ ገ/ሊባኖስ - ተወካይ ሐጐስ ተስፋይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለፍርድ ማስፈጸሚያ የቀረበ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመጀመሪያ የሐራጅ ሽያጭ የሚቀርብበትን የዋጋ ግምት አስመልክቶ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አፈጻጸሙ በተጀመረበት የዓድዋ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኖቹ አመልካች እና ተጠሪዎች እንደቅደም ተከተላቸው የፍ/ባለመብት እና የፍ/ባለዕዳዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩን አመጣጥ እና ሂደት በተመለከተ በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የብድር ውል መሰረት አመልካች በተጠሪዎች ላይ ለሰጠው የብር 275,165.73 ፍርድ የፍርድ ማስፈጸሚያ ይሆን ዘንድ ለብድር ውሉ በመያዣነት የያዝኩት ነው ያለውን የተጠሪዎች ንብረት የሆነ ቤት(ሕንፃ) ለአፈጻጸም መምራቱን፣ ቤቱ አመልካች በጠየቀው መሰረት በከተማው ማዘጋጃ ቤት እንዲገመት በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ግምቱ ብር 1,525,354.85 መሆኑ መገለጹን፣ ግምቱ በቀረበበት በ26/04/2005 ዓ.ም. በነበረው ችሎት የቀረበው ግምት የተጋነነ በመሆኑ በገልተኛ መሐንዲስ እንደገና ተገምቶ እንዲቀርብ እንዲታዘዝለት አመልካች ጥያቄ ማቅረቡን፣ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ እስካልተስማሙ ድረስ ግምቱ በሌላ መሐንዲስ እንደገና እንዲከናወን ሊደረግ የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን እና በሌላ መሐንዲስ ተገምቶ የሚቀርበው ውጤት የተለየ ከሆነ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚገባው ግምት የየትኛው መሀንዲስ ወይም ባለሙያ እንደሆነ መወሰኑ አስቸጋሪ እንደሚሆን ገልጾ የዳግም ግምት ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ፣ በሌላ በኩል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግን ሕንፃው በመንገድ ስራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑ መገለጹን ጠቅሶ የጉዳቱ መጠን በዓድዋ ከተማ ንግድ ኢንዱስትሪና መሬት ልማት ጽ/ቤት ተገምቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱን፣ በትዕዛዙ መሰረትም የጉዳቱ መጠን ብር 54,000.35 መሆኑ መገለጹን፣ ይህ ውጤት መቅረቡ በተመዘገበበት በ08/05/2005 ዓ.ም. በነበረው ችሎት ተጠሪዎቹ ገንዘቡን ለመክፈል የሁለት ወር ጊዜ እንዲሰጣቸው፣ ይህ የማይቻል ከሆነ ግን በቀረበው ግምት መሰረት የሀራጅ ሽያጩ እንዲቀጥል መጠየቃቸውን፣ አመልካች የተጨማሪ ጊዜ ይሰጠን ጥያቄውን በመቃወሙ ፍ/ቤቱ በመንገድ ስራ ምክንያት በሕንጻው ላይ ደርሷል የተባለውን ጉዳት የዋጋ ግምት ቀደም ሲል ከማዘጋጃ ቤት ከተገለጸው የሕንፃው የዋጋ ግምት ቀንሶ በተገኘው ውጤት መሰረት ሕንጻው በብር 1,471,354.40 የዋጋ ግምት በሐራጅ ሽያጭ እንዲቀርብ በዚያው በ08/05/2005 ዓ.ም. በነበረው ችሎት ትዕዛዝ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ሕንጻው በገለልተኛ መሐንዲስ ወይም ባለሙያ በድጋሚ እንዲገመት አመልካች ያቀረበው ጥያቄ ውቅድ ተደርጎ የሐራጅ ሽያጩ የተጋነነ ነው በተባለው የዋጋ ግምት እንዲቀጥል በተሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካች ለክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች ያቀረበው ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ እንደቅደም ተከተሉ በፍርድ እና በትዕዛዝ ተቀባይነት በማጣቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች የንብረቱ የዋጋ ግምት የተጋነነ ነው በማለት ያቀረበው ተቃውሞ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በማዘጋጃ ቤት የቀረበው የሕንፃው ግምት የተጋነነ መሆኑን ገልጾ ግምቱ በድጋሚ በሌላ ገለልተኛ መሐንዲስ ወይም ባለሙያ እንዲከናወን እንዲደረግ አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች ተቀባይነትን ያገኘው የዓድዋ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአንድ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ላይ በትክክለኛ ሁኔታ መገለጽ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ የሚሸጠው ንብረት ዓይነት እና የግምቱ ልክ መሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 423(2)(ሀ) ስር የተደነገገ ሲሆን የድንጋጌው ዓላማም የሚሸጠው ንብረት ከትክክለኛ የዋጋ ግምት አላግባብ ከፍ ወይም ዝቅ ተደርጎ እንዳይገመት ለማድረግ እና በዚህ ሳቢያ በፍ/ባለገንዘቡም ሆነ በፍ/ባለዕዳው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል እንደሆነ ይታመናል፡፡ ፍ/ቤቱ በማስታወቂያው ላይ የሚሰፍረውን የንብረቱን የዋጋ ግምት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚችል የሚሸጠውን ዓይነት ንብረት ለመገመት ልዩ ችሎታ ያለውን ኤክስፐርት በማዘዝ ንብረቱ እንዲገመት ለማድረግ እንደሚችል በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 424(2) ላይ የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይ የሐራጅ ሽያጭ ትዕዛዝ የተሰጠበት የፍ/ባለዕዳዎች ቤት በፍ/ባለመብቱ ጥያቄ በከተማው ማዘጋጃ ቤት መሐንዲሶች በኩል በብር 1,525,354.85 የተገመተ ሲሆን አመልካች ይህ ግምት የተጋነነ መሆኑን ገልጾ ቤቱ በሌላ ገለልተኛ ባለሙያ እንዲገመት ይደረግ ዘንድ ያቀረበውን አቤቱታ የወረዳው ፍ/ቤት ሳይቀበለው የቀረው ከላይ እንደተገለጸው ሁለቱ ወገኖች እስካልተስማሙ ድረስ ቤቱ በድጋሚ ሊገመት የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን እና ይገመት ቢባል እንኳ የሚቀርበው ግምት ከበፊቱ የተለየ ከሆነ ተቀባይነት የሚኖረው የትኛው ግምት እንደሆነ ለመወሰን አስቸጋሪ ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁለቱ ወገኖች እስካልተስማሙ ድረስ ቤቱ በድጋሚ ሊገመት የሚችልበት አግባብ የለም በማለት በፍ/ቤቱ የተያዘው አቋም ሕጋዊ መሰረት የሌለው እና ፍ/ቤቱም የዚህ ዓይነት አቋም ለመያዝ ያስቻለውን ድንጋጌ በትዕዛዙ ላይ ያልጠቀሰ ከመሆኑም በላይ ቤቱ በድጋሚ በሌላ አካል ወይም ባለሙያ ተገምቶ የሚቀርበው ግምት ከበፊቱ የተለየ ከሆነ እንደየገማቹ አካል ወይም ባለሙያ ደረጃ እና ማንነት ከሁለቱ ግምቶች ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባው የትኛው ግምት እንደሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተገቢውን ትዕዛዝ ይሰጥበት የሚችል በመሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች ቤቱ በሌላ ገለልተኛ ባለሙያ እንዲገመት ይደረግ ዘንድ ያቀረበውን አቤቱታ ላለመቀበል የሰጠው ምክንያት ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በማዘጋጃ ቤት በኩል ቤቱ እንዲገመት የጠየቀው የፍ/ባለመብቱ ራሱ በመሆኑ በጥያቄው መሰረት ተሰርቶ የቀረበውን ግምት መልሶ ሊቃወም አይችልም በማለት በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተያዘውን አቋም በተመለከተ የቀረበው ግምት የተጋነነ ስለመሆኑ የፍ/ባለመብቱ ያቀረበው መከራከሪያ አሳማኝ ሆኖ አስከተገኘ ድረስ የግምቱ ስራ የተከናወነው የፍ/ባለመብቱ በጠየቀው አካል የመሆኑ ጉዳይ ብቻውን የፍ/ባለመብት ንብረቱ በሌላ ባለሙያ በድጋሚ እንዲገመት ጥያቄ ከማቅረብ ሊከለክለው የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

በሌላ በኩል በወረዳው ፍ/ቤት በነበረው የአፈጻጸም ክርክር በ08/05/2005 ዓ.ም. በነበረው ችሎት ተጠሪዎቹ ገንዘቡን ለመክፈል የሁለት ወር ጊዜ እንዲሰጣቸው፣ ይህ የማይቻል ከሆነ ግን በቀረበው ግምት መሰረት የሀራጅ ሽያጩ እንዲቀጥል መጠየቃቸውን የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት ሲሆን ተጠሪዎቹ አሁንም ድረስ የቤቱ ግምት የተጋነነ ስላልሆነ በግምቱ መሰረት የሐራጅ ሽያጩ ሊቀጥል ይገባል በሚል ከመከራከር በስተቀር ግምቱ የተጋነነ አይደለም የሚሉ ከሆነ ጠይቀው በነበረው መሰረት ቤቱን በራሳቸው ሸጠው ከቀረበው የቤቱ ግምት አንፃር ሲታይ አነስተኛ የሆነውን ዕዳቸውን ለመክፈል ስላልቻሉበት ምክንያት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ይህም በማዘጋጃ ቤቱ ተሰርቶ የቀረበው የቤቱ ግምት የተጋነነ በመሆኑ ቤቱ በሌላ ገለልተኛ አካል ወይም ባለሙያ ሊገመት ይገባል በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ምክንያታዊ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡

ሲጠቃለል በከተማው ማዘጋጃ ቤት መሐንዲሶች የቀረበው የቤቱ ግምት የተጋነነ መሆኑን ገልጾ ቤቱ በሌላ ገለልተኛ ባለሙያ እንዲገመት እንዲደረግ አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ካለበቂ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት ውድቅ በማድረግ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በከተማው ማዘጋጃ ቤት መሐንዲሶች የቀረበው የቤቱ ግምት የተጋነነ መሆኑን ገልጾ ቤቱ በሌላ ገለልተኛ ባለሙያ እንዲገመት እንዲደረግ አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በዓድዋ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06471 በ08/05/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በዓድዋ ከተማ ከ/ፍ/ቤት እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመ.ቁ 03638 በ06/07/2005 ዓ.ም. እና በመ.ቁ 59337 በ13/10/2005 ዓ.ም. በውሳኔ እና በትዕዛዝ የፀናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ለአፈጻጸሙ የተመራው የፍ/ባለዕዳዎች ቤት የግምት ስራ የማከናወን ስልጣን እና ሙያ ባለው የክልል ቢሮ ወይም የግምቱን ስራ የማከናወን በሚችል ሌላ ባለሙያ ወይም አካል አማካይነት በድጋሚ ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ፣ የሚቀርብለትን ግምት ከቀዳሚው ግምት ጋር በማገናዘብ እና የግራ ቀኙን አስተያየት ጭምር በመቀበል በሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያው ላይ መገለጽ የሚገባውን የቤቱን የዋጋ ግምት በተመለከተ ተገቢውን ትዕዛዝ በመስጠት የሐራጅ ሽያጩን እንዲያስቀጥል ጉዳዩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት ለዓድዋ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
3. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለወረዳው ፍ/ቤት ይላክ፡፡ ለዓደዋ ከተማ ከ/ፍ/ቤት እና ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዘቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97206

ሐምሌ 28 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

አለ. መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ አማረ መልካሙ ራሳቸው ቀረቡ በVC ከመቐለ

ተጠሪ፡- አቶ ካሌብ ሕሉፍ የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ በሰበር ችሎቱ ሊወሰን ይገባል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ አመልካች የተጠሪ ንብረት የሆነውን በትግራይ ክልል ኮንስትራክሽንና መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ካላቸው ገንዘብ 612,2005.57 ብር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 154/ለ/ መሠረት ማሳገዳቸው ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች የቀደምትነት መብት ያረጋግጥላቸዋል ወይ? የሚለው ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ የመሰረቱት ክስ ተከትሎ የፍርድ ባለገንዘብ መሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡ በአመልካች ጠያቂነት ከላይ በተጠቀሰው ቢሮ የነበረው ገንዘብም አሳግዷል፡፡ አመልካች ገንዘቡን ካሳገዱ በኋላ አሥራ ሰባት የፍርድ ባለገንዘቦች ከተወሰነ ቀን በኋላ በተመሳሳይ መንገድ የተጠሪ ገንዘብ ላይ ዕግድ እንዲሰጥ አመልክተው በፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ አመልካች በትግራይ ክልል መቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 14044 ባቀረቡት ክስ ያሳገዱትን ገንዘብ በቅድሚያ ለእሳቸው እንዲከፈል ጠይቋል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ለክርክር መነሻ የሆነውን ሀብት ገንዘብ መሆኑን መሠረት በማድረግ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደው ገንዘብ ከመሆኑ አኳያ እንደማይንቀሳቀስ ንብረት የማይወሰድ ነው፡፡ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደው ገንዘብ ለፍርድ ባለገንዘቦች ባስፈረዱት መጠን (በሬሽዎ) እንዲከፋፈል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተፈጽሟል ያሉትን የሕግ አተረጓጎም ስሕተት በመዘርዘር የሰበር አቤቱታቸውን በ26-05-2006 ዓ.ም አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው መሠረታዊ ይዘት የፍርድ ባለዕዳ ገንዘብ ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ቀድመው ማሳገዳቸውን መሠረት ተደርጎ የቀደምትነት መብት እንዲከበርላቸው፤ የቀደምትነት መብት በማይንቀሳቀስ ንብረት ብቻ ሳይሆን በሚንቀሳቀስ ንብረትም ማቋቋም እንደሚቻል፤ የሥር ፍርድ ቤቶችም ክፍያ ማስፈጸም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለባቸው የፍርድ ባለገንዘቦች ገንዘቡን ባስከበሩበት ቅደም ተከተል ሊሆን እንደሚገባ በመጥቀስ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲታረም ጠይቋል፡፡ ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ ከመጥሪያ ጋር የተላከላቸው ቢሆንም በአድራሻቸው ስላልተገኙ በፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ በሚለጠፍ መጥሪያ መሠረት እንዲቀርቡ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ባለ መቅረባቸው በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች በፍርድ ባለዕዳ ገንዘብ ላይ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማስከበራቸው የቀደምትነት መብት እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም በሥር ፍርድ ቤት ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረው ነገር ገንዘብ ነው፡፡ የፍርድ ባለገንዘብ በፍርድ ባለዕዳ ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት በሕግ፣ በውል እና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊያቋቁም ይችላል፡፡ ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የቀደምትነት መብት በጋራ የንብረት ባለሀብቶች፤ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንደውሳኔውን ለማስፈጸም እንዲሁም ግራቀኙ ባደረጉት ስምምነት ሊቋቋም እንደሚችል ከፍ.ሕ.ቁ. 3043፣3044 እና 3045 ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት ሊቋቋም የሚችለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2825 በሚያዘው አግባብ የፍርድ ባለዕዳው ንብረቱን ለፍርድ ባለገንዘብ ማስረከቡ ሲረጋገጥ መሆኑን ከሕጉ ንባብ የምንገነዘበው ነው፡፡ አመልካች የቀደምትነት መብት እንዲሰጣቸው መሠረት ያደረጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154/ለ/ ነው፡፡ የዚህ ሕግ አንቀጽ መሠረታዊ ይዘትና ዓላማ ስንመለከተው በክርክር ላይ ባሉ ጉዳዮች የፍርድ ባለገንዘብ በመጨረሻ የረታ ከሆነ ፍርዱን ለማስፈጸም የሚያስችል ንብረት ወይም ገንዘብ እንዳይታጣ ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154 ርዕስ እንደምንረዳው የማገድ ትዕዛዙ የሚሰጠው ለጊዜው ስለመሆኑ፤ በፍርድ ባለዕዳ ሥር ያለው ንብረት በየትኛው መልኩ ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ፤እንዳይበላሽ፤እንዳይጠፋ ፍርድ እስከሚሰጥ ተከብሮ እንዲቆይ የማድረግ ዓላማ ያለው ነው፡፡ አመልካች ከላይ በተገለጸው አግባብ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ማሳገዳቸው በማይንቀሳቀስና በሚንቀሳቀስ ንብረት የቀደምትነት መብት ማቋቋም በሚያስችል አግባብ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት አግኝቷል ወይ? የሚለውን የክርክር ነጥብ በአግባቡ መታየት አለበት፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ከፍርድ በፊት በማይንቀሳቀስ ሆነ በሚንቀሳቀስ ንብረት የቀደምትነት መብት ማቋቋማቸው የሚገልጽ ነገር አላቀረቡም፡፡ አመልካች በእጃችን ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ድንጋጌ ነው በማለት የጠቀሱት የሕግ አንቀጽ 2860 ከላይ በጠቀስነው አግባብ መያዣ/Pledge/ ያቋቋሙ የፍርድ ባለገንዘቦች ያላቸው መብት የሚያመለክት እንጂ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የቀደምትነት መብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማቋቋማቸው የገለጹ ቢሆንም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154/ለ/ ከሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ስንመለከተለው ከዚህ የተለየ ትርጉም የሚሰጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ንብረት ለማስከበር የሚቀርብ ማመልከቻ ሊያሟላቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 379 በዝርዝር ደንግጓል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረቱ ዓይነቱን በመለየት ማቅረብ ግዴታ መሆኑን፤ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሆነ ደግሞ ንብረቱን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ ምልክቶች መገለጽ እንዳለባቸው ንብረቱ የሚለየው በአካባቢው ውስጥ ወይም ርስተመዘገብ ከሆነ በተራ ቁጥር በሆነ ጊዜ የወሰኑ ምልክት ወይም በመዝገብ ላይ የተሰጠው ቁጥር መግለጽ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ አመልካች በፍርድ ባለዕዳ ንብረት ላይ የዕግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ማድረጋቸው ከላይ በተገለጸው አግባብ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ የቀደምትነት መብት አቋቁመዋል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ አንድ የፍርድ ባለገንዘብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154/ለ/ መሠረት የንብረት ዕግድ ቢያሰጥ የቀደምትነት መብት የሚያቋቁም ስለመሆኑና አለመሆኑ ከአሁን በፊት የሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 29269 እና 27808 የሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች ተመልክተናል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማድረግ ብድር በመስጠታቸው ምክንያት የሥር ፍርድ ቤቶች የቀደምትነት መብታቸው የነፈገ ውሳኔ በመስጠታቸው የእነዚህ አበዳሪ ተቋማት መብት የሚያስጠብቅ ውሳኔ መስጠቱ የሚያስረዱ ናቸው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔዎች በተናጠል ሲንመለከታቸው በሰ.መ.ቁ 27808 የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ግለሰቦች ሲከራከሩ በመያዣ የያዘው ቤት በማሳገዳቸው ዕግዱ እንዲነሳ ሲጠይቅ ጣልቃ ገብተህ አልተከራከርክም ዕግዱ አይነሳም የሚል ውሳኔ በመስጠቱ በቀረበው አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሯል፡፡ በሌላ በኩል በሰ.መ.ቁ 29269 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አስቀድሞ ንብረት ማስከበሩ ብቻውን የቀደምትነት መብት አያሰጥም ማለታቸው ከሕግ የመነጨ የቀደምትነት መብት የነፈገ ነው ተብሎ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል፡፡ በእነዚህ ሁለት የሰበር ውሳኔዎች አሁን በእጃችን ካለው ጉዳይ ያላቸው ተመሳሳይነት እንደተመለከትነው ከላይ የተጠቀሱ ተቋማት የቀደምትነት መብታቸው በማይንቀሳቀስ ንብረት ያቋቋሙት የቀደምትነት መብት የነበረ መሆኑ የሚያሳይ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ያቀረቡት ጉዳይ ግን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 154/ለ/ መሠረት በአንድ የመንግሥት ተቋም የተያዘው የሚንቀሳቀስ ገንዘብ የሚመለከት በመሆኑ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

የቀደምትነት መብት በሕግ፣ በውል ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ /ውሳኔ/ የሚቋቋም ስለመሆኑ ከላይ በተገለጸው የፍትሐብሄር ሕግ ተመልክቷል፡፡ አመልካች በፍርድ ባለዕዳ ላይ አስፈርደው ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ቀድመው የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ማግኘታቸው ከሕግ፣ ውል ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ የመነጨ የቀደምትነት መብት አቋቁመዋል ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የላቸውም፡፡አመልካች በተጠሪ ገንዘብ የሰጡት የዕግድ ትዕዛዝ ከሌሎች የፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለገንዘቦች የተሻለ መብት እንዳላቸው የሚያረጋግጥ አይደለም ከተባለ፤ቀጥሎ የሚነሳውን ጥያቄ በተራ የፍርድ ባለመብቶች መካከል ያለው የክፍፍል ሥርዓት ምንመሆን አለበት የሚል ነው፡፡ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው አመልካችን ጨምሮ በተጠሪ ገንዘብ ላይ 18 ግለሰቦች የዕግድ ትዕዛዝ አሰጥቷል፡፡ከአንድ በላይ የፍርድ ባለመብቶች ባሉበት ጊዜ የሀብትና የንብረት ክፍፍል ሥርዓት ምን መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 403 ያስቀመጣቸው ሁኔታዎች ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የፍርድ ባለገንዘቦች ተቀማጭ የሆነውን ሀብት በውሳኔው መሰረት እንዲከፋፈሉ እንደሚደረግ ተመልክቷል፡፡ አመልካች በተጠሪ ገንዘብ ላይ ቀድመው የዕግድ ትዕዛዝ ማሰጠታቸው ግልጽ ቢሆንም ሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦችም በተከታታይ ቀናት ይህንን የማሳገድ ተግባር አከናውነዋል፡፡አመልካች ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች የቀደምትነት መብት ያልተሰጣቸው ከሆነ ሁሉም የፍርድ ባለገንዘቦች እንደተራ ገንዘብ ጠያቂዎች የሁሉም መብት እኩል እንደሆነ የሕግ ግምት ይወሰዳል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አንድ የፍርድ ባለገንዘብ ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች አስቀድሞ የባለዕዳውን ንብረት በማስከበሩ ምክንያት ብቻ የቀደምትነት መብት አይሰጠውም፡፡በመሆኑም የፍርድ ባለገንዘቦች እንደተራ የፍርድ ባለመብቶች ተወስደው ደረጃቸው(መብታቸው)እኩል መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ባስፈረዱት የገንዘብ መጠን መቶኛ ስሌት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ ማድረጉ የሕግ መሰረት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 403 ይዘት ዓላማና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ከዚህ አንፃር የሥር ፍርድ ቤቶች የፍርድ ባለገንዘቦች በፍርድ ባለዕዳው ላይ ያላቸው የገንዘብ መጠን በሬሾዎ እንዲከፋፈሉ ትዕዛዝ መስጠታቸው መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ.መ.ቁ.14044 በ25/04/2006 የሰጠው ብይን፤የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ. 6365 በ12/05/2006 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

2. አመልካች እና ሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ባስፈረዱት መጠን ገንዘብ መቶኛ ስሌት (ሬሾዎ)ድርሻ ድርሻቸውን ይከፋፈሉ ብለናል፡፡

3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 101271

ሐምሌ 30 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- መምህር ግዛቸው ጥሪት - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወሎ ዩንቨርስቲ አያና ስማቸው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ወሎ ዩንቨርሲቲ ቦርድ የሰጠው የዲሲፕሊን ውሳኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ያቀረብኩትን የይግባኝ ቅሬታ በፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳዳር ፍርድ ቤት እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ወሎ ዩንቨርሲቲ ቦርድ የሰጠውን የዲስፕሊን ውሳኔ፣ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚታይና የሚታረም መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያለአግባብ የተማሪዎቹን ውጤት ቀይሯል ወይም ውጤት ሞልቷል በሚል መንገድ የቀረበውን የዲሲፕሊን ክስ፣ በዩኒቨርሲቲው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ ከቀረበለት በኋላ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ አመልካች ከሥራ እንድሰናበት የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው፣ ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ትምህርት ማቋቋሚያ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ድንጋጌዎች ያገናዘበ አይደለም፡፡ ውሳኔው አመልካች በሕገ መንግስት የተረጋገጠለትን ፍትህ የማግኘት መብት የሚያጣብብ ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ የሚል ይዘት ያለው የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ መንግስት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነት ለማረጋገጥ በአዋጅ የሰጣቸውን ሥልጣን ያገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይቀርብበት በመሆኑ፣ አመልካች የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይቀርብበት በመሆኑ አመልካች የዩኒቨርስቲው ቦርድ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በዘጠና ቀናት ውስጥ የሰበር አቤቱታውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማቅረብ ሲገባው ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ለሌላቸው አካላት ማቅረቡ የህግ መሰረት የለውም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ

አቅርቧል፡፡

3. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ይዘት ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የሕግ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

4. የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለዚህ ሰበር ችሎት አከራካሪ ጭብጥ ሆኖ የቀረበውን የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው የሚለውን የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የሰጡት የከፍተኛ ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በመንግስታዊ ተቋሙ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ መመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ የመሥጠት ስልጣን ያለው መሆኑን በግልጽ ደንግጓል በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. ይህም የከፍተኛ ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ መሰረታዊ ባህሪው ከልካይና የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ሰራተኞች እንደማንኛውም መንግስት ሰራተኛ ፣ የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ የበላይ አመመራር አካል የሆነው የዩኒቨርስቲው ቦርድ፣ የሚሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤትና ደረጃውን ጠብቀው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ የማይችሉ መሆኑን የሚደነግግ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ለድንጋጌው ትርጉም መስጠት የሚጠይቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) መሰረታዊ ባህሪና ዓላማ እንደዚሁም ድንጋጌው በአካዳሚክ ሰራተኞች የይግባኝ መብት ላይ የሚኖረውን ሕጋዊ ውጤት ለመረዳት የድንጋጌውን የተናጠል የቃል በቃል ንባብ ማየት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡

6. የአዋጁን አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ መሰረታዊ ባህሪና ዓላማ እንደዚሁም፣ ድንጋጌው በአካዳሚክ ሰራተኞች የይግባኝ መብት ላይ የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ለመገንዘብ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊያከብራቸውና ሊመሩባቸው የሚገቡ ቋሚና መሰረታዊ እሴቶች፣ በአዋጁ የተረጋገጠውን የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካዳሚክ ነጻነት ይዘትና የአካዳሚክ ሰራተኞች ስላላቸው መብትና ግዴታ እንዲሁም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አደረጃጀትና የዩኒቨርሲቲው ቦርድና ሰኔት በአዋጁ የተሰጣቸውን ጥቅልና ዝርዝር ስልጣንና ኃላፊነትና ግዴታ አግባብነት ያላቸውን የፌደራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ድንጋጌዎች ጋር በጣምራ መታየትና መተርጎም ይኖርበታል፡፡

7. የመንግስት ሆነ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ሰራተኞች፣ አስተዳደርና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችና የቴክኒክ ሰራተኞች ሊኖራቸው እንደሚችል ከአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 2፣ ንዑስ አንቀጽ 3፣ንዑስ አንቀጽ 13 ፣ ንዑስ አንቀጽ 15 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 4 የከፍተኛ ተቋማት ዓላማዎችን ይዘረዝራል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች አንደኛው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማዊ ነጻነት ከተጠያቂነት ጋር ማረጋገጥ እንደሆነና በከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንቅስቃሴ ፍትሕን፣ ፍትሐዊነትና የህግ የበላይነትን ማራመድና መጠበቅ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 5 እና ንዑስ አንቀጽ 6 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማናቸውም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ እውነትን የመሻትና እውነትን የመግለጽ ነጻነት፣ አሳታፊና የሕግ የበላይነት፣ፍትህንና ፍትሐዊነትንና ሌሎች በአዋጁ አንቀጽ 6 የተደነገጉ እሴቶች በቋሚነት የመያዝና ቋሚ እሴቶቹን ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንዑስ አንቀጽ 5፣ እና ንዑስ አንቀጽ 6፣ ንዑስ አንቀጽ 11 እና በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል።

8. ሕግ አውጭው የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችና ቋሚ እሴቶች በአዋጅ ቁጥር 650/2001 የደነገገው ያለ ምክንያት አይደለም። ሕግ አውጭው የግልም ሆነ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚፈጽሟቸው ትምህርትና ምርምር ተግባራትና ተቋማቱ ከአካዳሚክ ሰራተኞች፣ ከአስተዳደርና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች፣ከቴክኒክ ሰራተኞች እና ከተማሪዎች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነትና የሚከተሉት አስተዳደር ጥበብ ከላይ የተገለጹትን የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችና ቋሚ እሴቶች በሚያረጋግጥ መንገድ መሆን እንዳለበትና ተቋማቱ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችም ከላይ ከተገለጹት ዓላማዎችና እሴቶች አንጻር ሊመዘኑና ሊመረመር የሚገባው መሆኑን ግልጽ ለማድረግ በማሰብ ከላይ የተገለጹት ድንጋጌዎች በማካተት አዋጁን ያወጀ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል። ከዚህ አንጻር የዩኒቨርሲቲው በላይ አመራር የሆነው ቦርድ በዲስፕሊን ጉዳይ የሚሰጠው ውሳኔ በይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት የሚታይበትንና ስህተትም ካለው የሚታረምበት እድል በሚያጣብብ ሁኔታ የአዋጁን አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ መተርጎም ዩኒቨርሲቲው የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችና በቋሚነት ሊይዛቸው፣ ሊተገብራቸው የሚገባውን ቋሚ እሴቶች ለማስፈጸምና ለማጎልበት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ያለ መሆኑ መመዘን ይገባዋል።

9. ከላይ የተገለጹትና ሕግ አውጭው በተቋማቱ ውስጥ ፍትህን የማስፈን፣ ፍትሐዊነትና የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ዓላማና ቋሚ እሴት እንዲኖር የመድረግ መሰረታዊ ግብን ለማሳካት ከደነገጋቸው ድንጋጌዎች በተጨማሪ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነታቸው የተረጋገጠላቸው መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 በጥቅሉ አገላለጽ ይደነግጋል። የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአዋጁ የተረጋገጠላቸው አካዳሚክ ነጻነት አመላካች በሆነ መንገድ የሚዘረዝረው አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 የተቋማቱ የአካዳሚክ ነጻነት የአካዳሚክ ሰራተኞችና ሌሎች ሰራተኞች የመቅጠርና በሥራ አፈጻጸም ውጤታቸው መሰረት መድቦ የማሰራትንና የሰው ኃይሉን በአዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሰረት የሰው ኃይሉን የማስተዳደርንና ሌሎች ነጥቦችን የሚያካትት መሆኑን ከአንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) እና (ሐ) ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል።

10. እዚህ ላይ በትኩረት መታየት ያለበት ሕግ አውጭው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነት በሚደነግገው ድንጋጌ ሥር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ በአዋጁና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሰረት የሰው ኃይሉን የማስተዳደር ነጻነት ያላቸው መሆኑን በአንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ) የደነገገበት ምክንያት ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ አውጭው ይህንን ድንጋጌ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነት በሚያውጀው የአዋጁ ክፍልና ድንጋጌ ሥር ያካተተው ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 የተረጋገጠላቸው አካዳሚክ ነጻነት በውስጡ ተነጻጻሪ ግዴታንም የያዘ በተለይም ተቋማቱ አዋጁንና አዋጅ ለማስፈጸም የወጣውን የፌደራል የዩንቨርሲቲዎች ደንብ ቁጥር 210/2003 እና በአዋጅ ቁጥር 515/199 እንደ አግባብነቱ ሌሎች አግባብነትና ተፈፃሚነት ያላቸውን የፌደራል ሕጉች መሠረት በማድረግ የሰው ሀይላቸውን የማስተዳደር ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የሚያካትት እና ይህንን ለተቋማቱ የተሰጠው አካዳሚክ ነጻነት ይህንን ተቋማቱን መሰረታዊ ግዴታ የማያስቀር ወይም የማይቀንስላቸው መሆኑን በግልጽ ለማስቀመጥ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

11. አከራካሪውን ጭብጥ ለመወሰን መታየት ያለበት ሌላው ነጥብ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 የአካዳሚክ ሰራተኞች የተረጋገጠላቸውን መብትና የተጣለባቸው አንጻራዊ ግዴታ ነው፡፡ በመንግስት ከፍተኛ ተቋማት ተቀጥረው የሚሰሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች ያላቸውን መብት በአመላካች ሁኔታ የሚዘረዝረው የአዋጅ ቁጥር 650/2001፣ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) የአካዳሚክ ሰራተኞች ግልጽና ፍትሐዊ አስተዳደር የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን በዲሲፕሊን ጉዳይ የመስማት እድል የማግኘትና ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እንዲነሳላችው የመጠየቅና ፍትህ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1(ተ) በግልጽ ይደነግጋል ይህ ያአካዳሚ ሰራተኞች በአዋጅ ቁጥር 31 ንዑስ አንቀጽ 1(ተ) የተረጋገጠላቸው ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እንዲነሳላቸው የሚጠይቅ እና ፍትሕ የማግኘት መብት እስከምን ድረስ ነው የሚለው ነጥብ ከሕገ መንግስቱ መሠረታዊ መርሆና ድንጋጌዎች አንፃር መታየት እና መተርጎም እንዳለበት ግንዛቤ ሊያገበት የሚገባ ነው፡፡

12. ከላይ ከተገለጹት በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲ ቦርድ በዩኒቨርሲቲው ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ ከፍተኛውና የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥ አካል መሆኑን ከአዋጅ አንቀጽ 43 ድንጋጌዎችና ከአንቀጽ 44 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በተለይም ቦርዱ የተቋሙ የላይ አመራር መሆኑ በአንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ የሚደነግግ ሲሆን ቦርዱም ቀዳሚ ኃላፊነት አዋጁ መከበሩንና መልካም አስተዳደር መሰፈኑን የማረጋገጥ እንደሆነ በአንቀጽ 44 ንዑስ አንቀት 1(ሀ) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በተቋሙ ውስጥ አዋጁ መከበሩንና መልካም አስተዳደር መስፈኑን ለማረጋገጥ የተቋሙ የሥራ ኃላፊዎች የዩኒቨርሲቲው አመራር አማካሪ አካላት፣ የአካዳሚክ ሰራተኞች፣ የቴክኒክ ሰራተኞች፣ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች እና ተማሪዎች የከፍተኛ ክፍል ተቋማት አዋጅ የሚያከብሩና የሚተገብሩ መሆኑን መከታተልና መምራት ይጠበቅበታል፡፡ ቦርዱ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ለማረጋገጥ በዩኒቨርሲቲው ተፈጽመዋል የሚባሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በበላይነት በማየት የመልካም አስተዳደር ችግር አለበት የሚባለው አስተዳደራዊ ውሳኔ በማየት የማረም ሥልጣን ሊኖረው ይገባል፡፡ ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔም በተቋሙ በሌላ አካል ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ የማይችል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሆን ይገባል፡፡ የከፍተኛ ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ በመሰረታዊ ባህሪውና ይዘቱ ከላይ የገለጽነውንና ቦርዱ በተቋሙ ውስጥ አዋጁን ለማስከበርና ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ፣ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ለማረጋገጥ የሚያስችለውን በዩኒቨርሲቲው መዋቅራዊ እርከን፣ የቦርዱን የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጭነት የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡

13. የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በመንግስታዊ ተቋሙ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ መመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ይህ በተለየ ሁኔታ አካዳሚክ ሰራተኞች የተሰጠ የዲሲፕሊን ውሳኔ ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ የድንጋጌው አወቃቀር ጠቅላላና ሰፊ ነው፡፡ ድንጋጌው ማናቸውም የአካዳሚክ ሰራተኞች፣ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች፣ የቴክኒክ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው ጋር የአቅርቦት ወይም ሌላ የውል ግንኙነት ያላቸው ሶስተኛ ወገኖች በዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊ ወይም ሌላ አካል ደርሶብናል የሚሉትን የመልካም አስተዳደር በደል፣ በየደረጃው ባሉ የተቋሙ ኃላፊዎች ካልተፈታና ወይም ውሳኔያቸው ቅሬታ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ከሆነ፣ ጉዳዩን አይቶ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጠው ቦርዱ እንደሆነ የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡

14. ከዚህ አንጻር ሲታይ ቦርዱ ከፌደራል የመንግስት አዋጅ ቁጥር 515/199 አንቀጽ 2 ንዑስ 3 በሚሰጠው ትርጓሜ የዩኒቨርሲቲው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጭ አካል መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነዉ የሚለው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማዊ ነጻነት ከተጠያቂነት ጋር ማረጋገጥና የከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንቅስቃሴ ፍትሕን፣ ፍትሐዊነትና የህግ የበላይነትን የማራመድና የመጠበቅ ዓላማዎች በማሳካት አንጻር ሲመዘን ተገቢነት የሌለው በመሆኑና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሊያዳብሩት የሚገባውን እውነትን የመሻትና እውነትን የመግለጽ ነጻነት፣ አሳታፊና የሕግ የበላይነት፣ የፍትህንና ፍትሐዊነትን እሴቶች ለማረጋገጥ በጎ አስተዋጽኦ የማያበረክትና አዋጅ የደነገጋቸውን ቋሚና መሰረታዊ እሴቶች ግብና አላማ ጋር የማይሄድና አተረጓጎም መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

15. ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ የአካዳሚክ ሰራተኞችን የይግባኝ መብት ከልካይና ገዳቢ እንደሆነ የተሰጠው ትርጉም ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 የተረጋገጠላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አካዳሚክ ነጻነት በውስጡ ተነጻጻሪ ግዴታንም የያዘ፣ በተለይም ተቋማቱ አዋጁንና አዋጅ ለማስፈጸም የወጣውን የፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች ደንብ ቁጥር 210/2003 እና በአዋጅ ቁጥር 515/199 አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችና ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸውን የፌደራል ሕጎች መሰረት በማድረግ የሰው ኃይላቸውን የማስተዳደር ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑንና ተቋማቱ ይህን ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ በሕግ አግባብ ሊጠየቁ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚያካትት መሆኑን ያላገናዘበ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በአዋጁ ለተቋማቱ የተሰጠው የአካዳሚክ ነጻነት ተቋማቱን አዋጁንና ሌሎች ሕጎችን መሰረት በማድረግ የሰው ኃይላቸውን እንዲያስተዳድሩ የተጣለባቸውን መሰረታዊ ግዴታ የማያስቀር ወይም የማይቀንስላቸው መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

16. እንደሁም የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ የአካዳሚክ ሰራተኞችን የይግባኝ መብት ከልካይና ገዳቢ እንደሆነ የተሰጠው ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) የአካዳሚክ ሰራተኞች ግልጽና ፍትሐዊ አስተዳደር የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑንና በዲስኘሊን ጉዳይ የመስማት እድል የማግኘትና ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እንዲነሳላቸው የመጠየቅና ፍትህ የማግኘት መብት ያላቸዉ መሆኑ በግልጽ የሚደነግግ መሆኑን ያገናዘበ አይደለም፡፡ በመሰረቱ በአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1(ተ) የተገለጸው ፍትህ የማግኘት መብት፣ የአንድ ሰው ፍትህ የማግኘት መብት በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮችን ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ የዳኝነት ሥልጣን በሕግ ለተሰጠው አካል አቅርቦ የማስወሰን መብትን የሚያካትት መሆኑን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ከተደነገገው ጋር በሚጣጣም ሁኔታ መተርጎምና ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

17. የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በመንግስታዊ ተቋሙ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ መመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት የሚልና አግባብነት የተዋቀረ ድንጋጌ ነው ጥቅል የአካዳሚክ ስራተኞችን ጉዳይ ብቻ የማይመለከት ሌሎች ሠራተኞችና ሰዎች በዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊ ወይም አካል ደርሶብናል የሚሉትን የመልካም አስተዳደር በደል በየደረጃው ባሉ የተቋሙ ኃላፊዎች ካልተፈታና ቅሬታ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ከሆነ ጉዳዩን አይቶ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጠው ቦርዱ እንደሆነ የሚደነግግ ድንጋጌ መሆኑን ሣይመረምር የተሰጠ ትርጉምና ውሳኔ ነው፡፡

18. ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የዩኒቨርሲቲው ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ይኸ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 78945 በአካዳሚክ ሰራተኛ ላይ የተሰጠ የዲሲፕሊን የቅጣት ውሳኔ በዩኒቨርሲቲው ኘሬዝዳንት ከጸደቀ በኋላ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) መሠረት በቦርድ ቀርቦ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሳይሠጥበት በይግባኝም ሆነ በሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደማይገባው በመግለጽ የሰጠውን የሕግ ትርጉም በተዛባ ሁኔታ በመረዳት የሰበር ችሎት ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ እንደማይባልበት፣ የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ትርጉም እንደሰጠ አድርጎ በውሳኔው ማስፈሩ የተሳሳተና ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል።

19. የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሲመለከቱ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ያወጣውን አካዳሚክ ሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ተግባራዊነት በሚያረጋግጥ መንገድ መሆን እንደሚገባው ግንዛቤ ሊያዝበተ የሚገባው ነው።ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የዩኒቨርስቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው በማለት የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የህግ ትርጉምና ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።
2. የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን አለው በማለት ወስነናል።
3. የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት፣የአዋጅ ቁጥር 650/2001፣የፌደራል የዩኒቨርሲቲዎች ደንብ ቁጥር 210/2003፣ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ያወጣውን የአካዳሚክ ሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ እና የአዋጅ ቁጥር 515/1999 እንደ አግባብነቱ መሠረት በማድረግ በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341 (1) መሠረት መልስን ልከንለታል።
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ።

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 99367

ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ዶ/ር ሕሊና ፍቅሬ ጠበቃ ሶፊያ ክፍሌ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ፖሊስ ሆስፒታል ነገረ ፈጅ ረ/ኢንስፔክተር ወተቱ ተገኘ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የስራ መልቀቂያ ይሰጠኝ ጥያቄን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ለፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የአመልካች የይግባኝ አቤቱታቸው ይዘትም ባጭሩ፡ -ከጥር 03 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ በስራ ላይ ባለመሆናቸው በገዛ ፈቃዳቸው ስራ ስለለቀቁ የሥራ መልቀቂያ እንዲሰጣቸው የአሁኑን ተጠሪን ጠይቀው የተከለከሉ መሆኑን ገልጸው የስራ መልቀቂያ እንዲሰጣቸውና ከለቀቁበት ቀን ጀምሮ ለደረሰባቸው ኪሳራ ተሰልቶ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለይግባኙ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያስቀደመ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤት ከሚያዚያ 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ በኮንስታብል ማእረግ በመለዩ ለባሽነት ቅጥር የፈፀሙ በመሆኑ የሚተዳደሩት በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ደንብ ሳይሆን በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 268/2005 ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱም በዚህ መልክ የቀረበውን የተጠሪን መቃወሚያ መነሻ በማድረግና ከአዋጅ ቁጥር 720/2004 እና ደንብ ቁጥር 268/2005 ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤተ ተቀጥረው ለመስራት ማመልከታቸውን፣መብቶቻቸውና ጥቅሞቻቸው በፌዴራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 268/2005 መሰረት ሲጠበቁላቸው የነበረ መሆኑ መረጋገጡን፣የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት ለጡረታ ፈንድ መዋጮ ይዋጣላቸው የነበረው 20% መሆኑ መረጋገጡን፣አመልካች ሲቀጠሩ በሞሉት ፎርም ላይ በኮንስታብል ማዕረግ ለመስራት መፈረማቸውና በሕይወት ታሪክ ፎርሙም የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች ከሚሞሉበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፎርም የተለየና በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 2(1) ስር ስለመንግስት ሰራተኛ የተመለከተውን ትርጉም የማያሟሉ መሆኑን መረዳቱን ገልፆ የአመልካች ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት የሚታይ ሳይሆን በፌዴራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚታይ ነው በማለት በድምፅ ብልጫ ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካች አንድ ሰው የፌዴራል ፖሊስ አባል ለመሆን መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች በሕጉ በግልጽ በተቀመጡበት ሁኔታ አመልካች ለደመወዝ አከፋፈል ሲባል እንዲሞሉ በተደረገው ፎርም ላይ ኮንስታብል ተብሎ በመገለፁና ለፖሊስ የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞችን ሲቀበሉ ስለቆዩ ብቻ የፌዴራል ፖሊስ አባል ናቸው ተብሎ ጉዳዩ በፌዴራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንዲታይ ተብሎ መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 2(1) እና ደንብ ቁጥር 268/2005 አንቀጽ 5(1)፣6(1)፣7(1) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን አግባብ የጣሰና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች ጉዳይ በፌዴራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚታይ ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦ በሰጠው መልስ አመልካች የፖሊስ አባላቱ የሚያገኙትን ማዕረግና ጥቅማ ጥቅም እያገኙ ሲሰሩ የቆዩ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን ጠቅሶና አመልካች የፖሊስ መሰረታዊ ስልጠና ያልወሰዱት ለጊዜው መሆኑን ጠቅሶ አመልካች የፖሊስ አባል አይደሉም ተብሎ ሊወሰዱበት የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም ሲል የተከራከረ ሲሆን አመልካችም በመልስ መልሳቸውን ላይ የሰበር አቤቱታቸው አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪ ተቋም ሲቀጥረው የኮንስታብል ማዕረግ የተሰጣቸው መሆኑ፣ሲቀጠሩ የሞሏቸው ቅጾች ፖሊሳዊ ባህርይ ያላቸው መሆኑን፣ለፖሊስ አባላት የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች እና የጡረታ መዋጮ ለአመልካች ሲከፈልላቸው የነበረ መሆኑ በአስተዳደር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ከመሆናቸውም በላይ በግራ ቀኙ ያልተካዱ መሆኑን፣አመልካች እነዚህ ፍሬ ነገሮች መኖራቸውን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት እነዚህ የተጠቀሱት ተግባሮች ሊፈፀሙ የቻሉት በጁኒየር ጀኔራል ሚዲካል ፕራክቲሽነር የስራ መደብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠሪ መስሪያ ቤት ሲቀጠሩ የደመወዝ ቅጥራቸው ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የደመወዝ ስኬል ጋር አቻ እንዲሆን ታስቦና የአመልካችን ጥቅም ለመጠበቅ ታስቦ እንጂ ፖሊስ በመሆናቸው የተጠበቁላቸው ጥቅሞች ያለመሆናቸውን ጠቅሰው መሆኑን፣ተጠሪ በበኩሉ ይህንኑ የአመልካችን ክርክር የሚያስተባብል ማስረጃ ያለው ስለመሆኑ በግልጽ ሳይገልጽ አመልካች ወደውና ፈቅደው ፖሊስ ሁነው ስራቸውን መጀመራቸውንና የፖሊስ አባላቱ የሚያገኟቸውን ጥቅማ ጥቅሞችን ሲያገኙ የቆዩ በመሆኑ ፖሊስ ተብለው ሊወሰዱ ይገባል በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው።

በዚህ ጉዳይ በዋነኛነት የተያዘው ጭብጥ አንድ ሰው የፌዴራል ፖሊስ አባል ነው ተብሎ ጉዳዩ በዚህ ረገድ በተዘጋው የሕግ ስርዓት የሚታየው ምን ምን ሕጋዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው? የሚለው ነው።ይህንኑ ጥያቄ ለመመለስ ይቻል ዘንድም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸውን አዋጅ ቁጥር 720/2004 እና ደንብ ቁጥር 268/2005 ድንጋጌዎችን መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል።

አዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 2(1) "የፖሊስ አባል" ማለት መሠረታዊ የሆነ የፖሊስ ሙያ ስልጠና ተሰጥቶት በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተቀጥሮ የሚሠራ የፌዴራል ፖሊስ አባል ነው በሚል ትርጉም የሰጠ ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 27(1) እና በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 ድንጋጌዎች መሰረት አዋጁን ለማስፈፀም ደንብ ቁጥር 268/2005 ወጥቶ ስራ ላይ ውሏል።ይህ ደንብ የፌዴራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 268/2005 ተብሎ የሚጠቀስ ሲሆን ደንቡ የተፈፃሚነት ወሰኑን በአንቀጽ 3 ስር በግልፅ አስቀምጧል።በዚህም መሰረት ደንቡ ኮንስታብል እስከ ኮሚሽነር ማዕረግ ባላቸው የፌዴራል ፖሊስ አባት ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን በተጠቃሹ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር አንድ ያስቀምጣል።እንዲሁም የደንቡ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ስለፖሊስ ምልመላ፣ስልጠናና ምደባ የሚደነግግ ሲሆን የደንቡ አንቀጽ 5 ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ማንኛውም ምልምል ፖሊስ በፖሊስ አባልነት ከመቀጠሩ በፊት መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና መውሰድና የሚሰጠውን ፈተና ማለፍ አለበት በሚል በንዑስ ቁጥር አንድ ስር ሃይለ ቃል በያዘ አቀራረፅ ተቀምጦ ይገኛል።በደንቡ አንቀጽ 6(1) ደግሞ ማንኛውም ምልምል ፖሊስ መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና እንዳጠናቀቀ ስራ ከመጀመሩ በፊት ቃለመሐላ መፈፀም እንዳለበት እና ሊፈፀም የሚገባውን የቃለ መሐላ ይዘት አስፍሯል።እንዲሁም የደንቡ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሲታይም የቅጥር ውል የሚደረግበትን አግባብ ይደነግጋል።በዚህ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር አንድ መሰረት ምልምል ፖሊስ የፖሊስ አባል የሚሆነው መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና አጠናቅቆ ቃለ መሃላ ፈፅሞ የቅጥር ውል ከፈረመ በኋላ መሆኑን አስገዳጅነት ባለው መልኩ የሚያስቀመጥ ሲሆን የተጠቃሹ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌም ውሉ ከተፈረመበት በኋላ ስለሚኖረው የአገልግሎት ዘመን ለይቶ የሚደነግግ ነው።ደንቡ በትርጓሜ ክፍሉ አንቀጽ 2(2) በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለደንቡም ተፈፃሚ ይሆናል ሲል ያስቀመጠ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሆን በዚህ ደንብ አዋጅ ማለት ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚ አዋጅ ቁጥር 720/2004 ስለመሆኑ በአንቀጽ 2(1) በግልፅ ያሳያል፡፡በዚህ አግባብ ሲታይ ደግሞ ፖሊስ ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(1) የተሰጠውን ትርጉም የሚይዝ ሁኖ በደንቡ አንቀጽ 4፣5፣6 እና 7 ድንጋጌዎች መሰረት በሕጉ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ የተቀጠረ ሊሆን እንደሚገባው ከድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ይሆናል፡፡በመሆኑም በሕጉ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ አንድ ሰው የፖሊስ ቅጥር ፎርም የሚል ስያሜ የያዘ ሰነድ ስለሞላ ወይም በቅጥር ፎርሙ በሕጉ አግባብ የሚገኙት ማዕረጎች ተሰጥተውት የጥቅማ ጥቅሙ ተጋሪ መሆን እንደ ሕጉ አነጋገርና ይዘት ፖሊስ ነው ብሎ ትርጉም ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ስለመሆናቸው ጉዳዩን በተለይ እንዲገዙ የወጡ ሕጎች አያሳዩም፡፡

አዋጅ ቁጥር 720/2003 የወጣበት መሰረታዊ አላማ የፌዴራል ፖሊስ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያ ዊሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትንና ሕገመንግሥቱን መሠረት አድርገው የሚወጡህጎችን የማስከበር ተልዕኮውን በብቃት በመወጣት የዲሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባት፣ ሠላምን ለማስፈንና ልማትን ለማፋጠን በሚደረገው አገራዊ እንቅስቃሴ የበኩሉን ድርሻ ለማበርከት እንዲችል በተሻለ ሁኔታ እንዲደራጅ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የፌዴራል ፖሊስ ተቋም ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ገለልተኛ የሆነ፣ሕብረተሰቡን በእኩልነት የሚያገለግል፣ በፖሊሳዊ ሥነ-ምግባሩ የታነፀና ብቃትና ጥራትያለው አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ተቋም መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ስለመሆኑ አዋጁ በመግቢያው ላይ የሚገልፅ ሲሆን ይህንኑ አዋጅ በአግባቡ ለማስፈፀም ይቻል ዘንድ ደግሞ ደንቡ ወጥቷል፡፡በመሆኑም አዋጁ የራሱን አላማ እንዲያሳካ በአዋጁ የተቀመጡትና አዋጁን መሰረት አድርጎ በወጣው ደንብ ስር ያሉት ድንጋጌዎች በአግባቡ ሊከበሩና ሊተገበሩ ይገባል፡፡ከዚህ ውጪ ከአዋጁ የወጡ አሰራሮችና ልማዶች በአዋጁና በደንቡ ጥበቃ የሚያገኙበት አግባብ እንዲኖር ማድረግ ጉዳዩን ለመግዛት ታስቦ ስልጣን ባለው አካል የወጣውን ሕግ ትርጉም የሚያሳጣ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያደርግ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ያልወሰዱ፣በደንቡ መሰረትም ቃለ መሃላ ያልፈፀሙ ቅጥሩን የሞሉትም ምልምል ፖሊስ ሊወሰደው የሚገባውን መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና አጠናቅቀው ሳይሆን ምንም ስልጠና ሳይወስዱ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጡ ነጥቦች ናቸው፡፡ የፌዴራል ፖሊስ የፖሊስ አባላቱን የሚመለምለው የሚያሰለጥነው የሚቀጥረውና የሚያስተዳድረው በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 14 በግልፅ የተቀመጠ ሲሆን ደንቡን ለማውጣት በሕጉ ስልጣን የተሰጠው አካል ደግሞ ደንብ ቁጥር 268/2005 አውጥቶ ከህዳር 10 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ ሁኗል፡፡በደንቡ አንቀጽ 96(2) ድንጋጌ ስር ደግሞ ከደንቡ ጋር የሚቃረኑ ደንቦች፣መመሪያዎች ወይም የአሰራር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልማዶች በደንቡ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል፡፡በመሆኑም በአዋጁና በደንቡ ከተመለከቱት ሕጋዊ ስርዓቶች ውጪ የሚፈጸሙ የፖሊስ ቅጥሮች አንድን ሰው የፖሊስ አባል ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችሉ አይሆኑም፡፡

እንዲሁም ከጊዜ ቅደም ተከል አንፃር ይታይ ቢባል እንኳን አዋጅ ቁጥር 720/2004 ተፈፃሚ የሆነው ከሕዳር 18 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ነው፡፡አመልካች የቅጥር ፎርሙን የሞሉበት ጊዜ ሚያዚያ 01 ቀን 2002 ዓ/ም መነሻ ተደርጎ በጊዜው ተፈፃሚነት የነበራቸው ሕጎች አዋጅ ቁጥር 313/1995 እና ደንብ ቁጥር 86/1995 ድንጋጌዎች ሲታይም የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ያልወሰደ ሰው የፖሊስ አባል ነው የሚለውን ትርጓሜ ሊያገኝ የሚችልበትን አግባብ የሚያሳዩ ድንጋጌዎችን ይዘው አይገኙም፡፡ስለሆነም ተጠሪ ለአመልካች የፖሊስ ማእረግ ሰጥቶ ቅጥሩ ላይም ማእረጉ ተጠቅሶ ፎርሙ መሞላቱም ሆነ አመልካች የአንድ ፖሊስ ጥቅማ ጥቅሞችን ሲያገኙ መቆየታቸው በአዋጁ ጥብቅ አነጋገር ስንነሳ በማናቸውም መመዘኛ አመልካች የፖሊስ አባል ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ ለመውሰድ የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ተጠሪ አመልካች የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ያልወሰዱ መሆናቸውን አምኖ ወደፊት የሚወስዱበት ሁኔታ መኖሩን ጠቅሶ ያቀረበው ክርክርም የአዋጁንና የደንቡን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሚያገኝበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች የፖሊስ አባል ናቸው ተብሎ የሚደመደምበት አንዳችም የሕግ ምክንያትን በሌለበት ሁኔታ ማዕረጉ ተሠጥተው የፖሊስ አባል ጥቅማ ጥቅም ተጠቃሚ ነበሩ በሚሉ ምክንያቶች ብቻ ጉዳያቸው በፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ እንጂ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 በተዘረጋው ስርዓት የሚታይ አይደለም ተብሎ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ መወሰኑም ሆነ ይኼው ውሳኔ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በድምጽ ብልጫ መጽናቱ ከላይ የተመለከቱትን የሕግ ማዕቀፎችን ጥብቅ ስርዓት ያላገናዘበና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቭል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 162/2006 ጳጉሜ 04 ቀን 2005 ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 93890 ጥር 26 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በአዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 2(1)፣14(1) እና በደንብ ቁጥር 268/2005 አንቀጽ 4፣5፣6 እና 7 ድንጋጌዎች መሰረት የፌዴራል ፖሊስ አባል ናቸው ተብሎ የሚወሰዱ አይደለም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤት የነበራቸው ቅጥር ከፖ/ሊስ አባልነት ውጪ የነበረ በመሆኑ ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዋጅ ቁጥር 515/1999 በተዘረጋው አግባብ ነው በማለት በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ጉዳይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 162/2006 ክርክሩን ቀጥሎና በአግባቡ አጣርቶ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቅጽ 15 2005 እና 2006 ዓ.ም የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች

ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠት ቀን	ገጽ
	አሠሪና ሠራተኛ				
1.	• አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የደረሰበትን የአካል ጉዳት በተመለከተ የጉዳት ካሣ ክፍያ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችለው በአማራጭ አንድም በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ መሠረት አሰሪውን ያለጥፋት በሥራ ክርክር ችሎት ክሶ በመጠየቅ ወይም የአሰሪውን ጥፋት መነሻ በማድረግ የጉዳት ካሣ ክፍያ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በፍ/ሔር ችሎት በአሠሪው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ፣ • በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ የጉዳት ካሣን ለመጠየቅ በህጉ የተመለከቱትን መብቶች በአግባቡና በትክክል ተገንዝቦ እንደ ጉዳቱ ሁኔታ፣ አይነትና አግባብነት በተሻለ ሁኔታ የሚጠቅመውን የመብት አድማስ አውቆ በመለየት ተገቢው መብቱ ከመነጨበት የህግ አግባብ አንፃር ክሱን ሊያቀርብ የሚገባ ስለመሆኑ፣ • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5 ድንጋጌ ይዘት አድማሱ በግልጽ በተወሰኑ ጭብጦች ላይ ብቻ ሣይሆን በተከራካሪ ወገኖች ቢነሱ ኖሮ ሊወሰኑ ይችሉ የነበሩ ጭብጦችን ጭምር የሚያካትት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1)፣97 109፣ 138(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 80(2)	80343	ዋሊያ የቆዳ ማለስለሻ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ደረጀ ውለታው	ግንቦት 06/2005	2

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2.	አሠሪ ሠራተኛውን እንደ ሠራተኛ በመቀበል የሚሰራውን ሥራ ባልሰጠበት ሁኔታ ሠራተኛውን ከሥራ ገበታው ቀርቷል በሚል ያለ ማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1) ለ	82091	ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እና አቶ ለገሠ ደሣለኝ	መጋቢት 25/2005	9
3.	የሥራ መሪ የሆነ ሠራተኛ ያለ አግባብ ከሥራ መሰናበቱ ተረጋግጦ ሲወሰንና የአሰሪው የመተዳደሪያ ደንብ የሚፈቅድለት ከሆነ በአዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት ኪሣራ ታስቦ ሊከፈለው የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሀ/ቁ.2574(2) አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 43(4) (ሀ)	84661	አቶ ዳዊት ሸዋቀና እና ስኳር ኮርፖሬሽን	መጋቢት 27/2005	12
4.	ከሥራ ጋር በተገናኘ እንዲከፈል በሚል የሚቀርቡ የደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓት እና ሌሎች ክፍያዎች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው ሠራተኛው ክፍያዎቹን መጠየቅ ይችላል (ይገባዋል) ከሚባልበት ግዜ ጀምሮ እንጂ የሠራተኛው የሥራ ውል ከተቋረጠበት ግዜ ጀምሮ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(1-4)	79476	ኢትዩ ቴሌኮም እና እነ አቶ ዘሪሁን ታዬ (ዘጠና ስድስት ሰዎች)	የካቲት 12/2005	17
5.	የስራ ውል የሚመሠረተው ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሠነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሰሪው ለመስራት የተስማማ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 2(3),4	81814	እነ ወ/ት ፌቨን የሺጌታ (12 ሰዎች) እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ	ሐምሌ 18/2005	24
6.	በአሠሪው ንብረት ላይ ጉዳት በማድረሱ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የተሰናበተ ሠራተኛ ጉዳቱን ያደረስኩት በሥራ መደራረብ እና ከልምድ ማነስ ነው የሚል ምክንያት አቅርቦ የተከራከረ መሆኑ ስንብቱን ህገ ወጥ ነው ለማለት የሚያበቃ (የሚያስችል) ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96	86284	ሆራይዞን አዲስ ጎማ (አ.ማ) እና አቶ መኮንን ዓለሙ	መጋቢት 13/2005	27

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አንቀጽ 27(1)(ሸ), 13(3)				
7.	አንድ ሠራተኛ የቅጥሩ ውል አይነት ቋሚም ይሁን ግዜያዊ ለሠራተኛ በህጉ በተፈቀዱ ጥቅሞች የመጠቀምና ህጉ የሰጣቸውን ከለላዎች የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 42(2)	87338	ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር እና እነ አቶ ገብሬ በላይነህ (አምስት ሰዎች)	ግንቦት 21/2005	30
8.	አንድ ሠራተኛ ከሥራ መቅረቱ በህመም ምክንያት መሆኑ እንደበቂ ምክንያት ሊወሰድ የሚችለው በህጉ አግባብ፣ በህመሙ ምክንያት ስለመቅረቱ ለአሰሪው ያሳወቀና ፈቃድ ያገኘ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 85(4)	87285	ወ/ሮ የውብዳር ንጋቱ እና ገነት ሆቴል	መስከረም 23/2006	34
9.	የሥራ ኃላፊነቱን ባለመወጣት ተገቢነት የሌላቸው ሰዎችን ወደ አሰሪው ድርጅት ውስጥ ዘልቀው እንዲገቡ በማድረግ ጥፋት የፈፀመ የጥበቃ ሰራተኛ ወደ ድርጅቱ በገቡት ሰዎች ምክንያት የተፈጠረ የፀጥታና የደህንነት ችግር አልተከሰተም በሚል ምክንያት ብቻ አሰሪው በሰራተኛው ላይ የፈፀመውን የስራ ውል ማቋረጥ ተግባር ህገ ወጥ ነው ሊያስብል የሚችል ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሸ), 17(1)(ሸ)(ቀ), 14(2)(ሀ)	90389	የኢትዮጵያ ኤርፖርት ድርጅት እና አቶ በሪሁን በላይ	ጥቅምት 18/2006	38
10.	አንድን ሠራተኛ የሥራ መሪ ነው ለማለት የሚቻለው በህግ ወይም እንደ ድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሰሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈፀም እንዲሁም በተጨማሪነት ወይም ይህንን ሣይጨምር ሠራተኞን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ የማገድ፣ የመመደብ ወይም ሌሎች የሥነ-ሥርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውን እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3(2)(ሐ)	92466	ሳይግን ቴክስታይል ቢዩልዲንግ ኮንስትራክሽን ትሬድ ኢንዳሪኢንክ ኢትዮያ ብራንች እና አቶ ተስፋዬ ጥላሁን	ጥር 02/2006	41

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(1)(ሐ)				
	ውል				
11.	የንግድ ቤትን ከመንግስት የተከራየ ተከራይ ከአከራዩ እውቅና ውጭ ለ3ኛ ወገን የንግድ ቤቱን ማስተላለፉ አከራዩ የመጀመሪያውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ የሚያስችለው ስለመሆኑ፣ በዚሁ መሠረትም አከራዩ ቤቱን ለማስለቀቅ የሚያያደርግው እንቅስቃሴ ሁከት ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6 የፍ/ብ/ህ/ቁ.1140, 1149	82670	እነ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 አስተዳደር ፅ/ቤት (ሁለት ሰዎች) እና ዋጋዬ አሰፋ	መጋቢት 09/2005	46
12.	• አንድን በጽሁፍ የተደረገ ውል ዋና ሰነድ ጠፍቷል በማለት ክርክር በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤት በማስረጃነት በቀረበው የውሉ ሰነድ ኮፒን ተቀብሎ በውሉ የተመለከቱትን ምስክሮች ሊሰማ የሚገባው ጠፍቷል የሚለው ወገን ዋናው ሰነድ ስለመጥፋቱ በተመለከተ በአግባቡ ያስረዳ እንደሆነና የውሉንም ኮፒ አግባብነት ያለው አካል ዋናው የውል ሰነድ ጋር ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው እንደሆነ ስለመሆኑ፣ • የምስክሮቹ ቃል ሊሰማ የሚገባውም የውሉ ቃል ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2011(1),2003 ,1730(1)	84330	አቶ መንግስቱ አሾ እና እነ ወ/ሮ እመቤት ጥላሁን (አምስት ሰዎች)	ሚያዝያ 10/2005	50
13.	አስቀድሞ በተደረገ የኪራይ ውል መነሻነት አንድን የአከራይ ንብረት ይዞ ሲጠቀም የቆየ ተከራይ የኪራይ ውል ግዜው ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ አከራዩ የኪራዩን ዋጋ በመጨመር አዲስ የኪራይ ዋጋ እንዲከፈል ገልፆ እያለ ተከራዩ በቀረበው አዲስ የኪራይ ዋጋ ሳይስማማ ወይም እየተቃወመ በንብረቱ መገልገሉን በቀጠለ ጊዜ ተከራይ ለአከራዩ ሊከፍለው የሚገባውን የኪራይ ዋጋ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ፣	81163	አቶ ሲሳይ ረታ እና የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት	የካቲት 11/2005	55

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2950(1) (2), 1687				
14.	• ከውል አፈፃፀም ሂደት ጋር በተገናኘ በተዋዋይ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኪሣራ ሊሰላ ስለሚችልበት አግባብ፣ •የኪሣራው ልክ ከውል ውጪ የሚደርስ ኃላፊነትን መሠረት በማድረግ በርትዕ ሊወሰን ስለሚችልበት አግባብ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790, 1800, 2102(1)(2)	79794	የማይክሮሊንክ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ኃ.የተ.የግል ማህበር እና የፊደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	ሚያዝያ 22/2005	59
15.	አንድ ውል (ስምምነት) ህግ በጽሑፍ እንዲሆን ሲያስገድድ ውሉ በጽሁፍ መደረግ ያለበት እና በተዋዋይ ወገኖችና በሁለት ምስክሮች ፊርማ ሊረጋገጥ የሚገባ ስለመሆኑና መሀይማንና ማየት የተሳናቸው ሰዎች የሚያደርጉት ውል በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት የተደረገ ካልሆነ በቀር በውሉ የማይገደዱ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1727, 1728(3), 2005	83674	ወ/ሮ እቴነሽ ካሳ እና ሀጂ ጀማል ይማም	ግንቦት 19/2005	65
16.	በመያዣ ውል መነሻነት አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት ከነይዞታው የያዘ ሰው በይዞታው ላይ የንብረቱ ባለቤት ሳይቃወመው ግንባታ የፈፀመ ከሆነ ተጠቃሹ የመያዣ ውል አይፀናም በሚል ተዋዋዩቹ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ሲደረግ የንብረቱ ባለቤት በመያዣው ይዞታ ላይ የወጣውን የግንባታ ወጪ ግንባታውን ላካሄደው ወገን ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1818, 2162	90862	ወ/ሮ ተዋበች ኃይሌ እና ወ/ሮ አያንቱ በዬቻ	ታህሳስ 14/2006	69
17.	የማይንቀሣቀስ ንብረት ተከራይ የሆነ ሰው ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል ለ3ኛ ወገን በኪራይ ሊሰጥ የሚችለው ተከራዩ አስቀድሞ ለአከራዩ አሳውቆ አከራዩ የማይቃወም መሆኑ ሲታወቅ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2957(1)(2), 1731	86847	አቶ ፀጋዬ አማን እና እነ አቶ መሐመድ ነጋሽ (ሶስት ሰዎች)	ጥቅምት 18/2006	73

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	በአ.አ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ቢሮ ደንብ ቁጥር 3/2004, 4/2004				
18.	ከሠራተኛ ቅጥር ውል ጋር በተገናኘ የዋስትና ግዴታ የገባ ሰው የሠራተኛው የቅጥር ውል እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ ከተደረገ በኋላ ሠራተኛው ከተሻሻለው ወይም ከተለወጠው የቅጥር ውል ጋር በተያያዘ ያለበትን ተጠያቂነት አስመልክቶ አስቀድሞ በገባበት የዋስትና ግዴታ መሰረት ተጠያቂ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1827(1)	86813	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት እና እነ ሰሚር መላኩ (ሶስት ሰዎች)	መስከረም 22/2006	77
19.	ተከራካሪ ወገኖች በአንድ የሰነድ ማስረጃ ላይ የተመለከተን ፊርማ የማን ስለመሆኑ በሚመለከተው የመንግስት አካል ተጣርቶ ውጤቱ ከቀረበና ከታወቀ በኋላ ሰነዱ በውጭ አገር ተመርምሮ ውጤቱ እንዲታወቅ በማለት የሚያቀርቡት ጥያቄ በህግ አግባብ አጥጋቢና አሣማኝ ምክንያትን በመጥቀስና በማስረጃ አስደግፈው ያላቀረቡ እንደሆነ ጥያቄው ተቀባይነት ሊኖረው የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ቤት የተሰጠ ትእዛዘ /ውሣኔ/ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚቻለው በተከራካሪ ወገኖች ፍትህ የማግኘት መብት ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2008, 2007, 2001, 2005	86187	አቶ ዳንኤል ዘሚካኤል እና አቶ ቢሃሪ ባቡላል ሞዲ	ሰኔ 21/2005	80
የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት					
20.	• በፍ/ብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገሩ እንዲነጠር የሚደረገውም በማስረጃ የሚነጥረው ፍሬ ነገር ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ፣	77983	እነ አቶ እንድሪስ አደም (አምስት ሰዎች)	መጋቢት 24/2005	87

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ማስረጃ እንዲሠማ የሚፈልግ ወገን ማስረጃው የሚሰማበትን ነጥብ ለይቶ የማስረጃውን አይነትና የሚገኝበትን ቦታ ሁሉ በመጥቀስና በእጁ ላይ ያለውንም አያይዞ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.223,234,137(3),145,256,136-138,246,248		እና ወ/ሮ አስናቀች ጥላሁን		
21.	አንድን ጉዳይ በተመለከተ ተከራካሪ ወገኖች በየበኩላቸው በተለያዩ ፍ/ቤቶች (ችሎቶች) አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ክሶች ባቀረቡ ግዜ (የክርክሮቹ ደረጃ ምንም ይሁን ምን) ክሶቹ ተጣምረው ታይተው ሊወሠኑ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 8(1),11,244, 245	81275	ወ/ሮ ዘምዘም ወንድሙ እና አቶ አብዲሰቡር አብዱሰመድ	ሰኔ 05/2005	92
22.	ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ ጋር በተገናኘ መብቱን ለማስፈፀም ጠይቆ በአፈፃፀም በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ ውሣኔ ተሰጥቶ እያለ ባለመብት ነኝ የሚለው ወገን የሚያነሣው የመብት ጥያቄና ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ •በአንድ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በህግ አግባብ እስካልተሻረ ድረስ የውሣኔው አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት በባለጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ ሣይሆን በማናቸውም አስፈፃሚ አካላትና በማናቸውም ፍርድ ቤት ላይ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 79(2)	83007	እነ ወ/ሮ አልማዝ ገመቹ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ፋዩ ገመቹ	ሰኔ 03/2005	98
23.	በአንድ ጉዳይ ተከሣሽ የሆነ ወገን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ካቀረበ ፍ/ቤቱ ከቀረቡት ክሶች መካከል በሥረ-ነገር ስልጣኑ ሥር ያሉትን መርጦ ለማየትና ከሥረ-ነገር ስልጣኑ በላይ የሆነውን ጉዳይ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይቅረብ በማለት የከሣሽን ክስና የተከሣሽን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ተነጣጥለው እንዲታዩ በማድረግ የሚሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ስላለመሆኑ፣	83169	ፕሮፌሰር አደም ዓለ. አህመድ እና አዳማ ጠቅላላ ሆስፒታልና ሜዲካል ኮሌጅ ኃ/የተ/የግል	መጋቢት 28/2005	103

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 30(1)¸324(1)(ሀ),215(2)¸17(3)		ማህበር		
24.	አንድ ስምምነት በፍ/ቤት ሊፀድቅ የሚችለው ጉዳዩ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት በመታየት ሂደት ላይ እያለ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩን በስምምነት የጨረሱ መሆኑን ገልፀው ይኼው ስምምነት ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣ ከፍርድ ቤት ውጪ በሚደረግ እርቅ ወይም ግልግል መሰረት ያለመግባባትን ያስቀሩ ወይም ለጉዳያቸው እልባት ያገኙ ሰዎች የእርቁን ወይም የግልግሉን ስምምነት በፍርድ ቤት ማስመዝገብ ወይም ማስፀደቅ የማያስፈልጋቸው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3312 እና 3324	85873	እነ ወ/ሮ ኒኢማ አባድጋ አባዋጂ እና አቶ ጣሐ ጀማል አደም	መጋቢት 13/2005	108
25.	አንድን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የሚመለከት ፍ/ቤት በህጉ አግባብ ክስ ተሻሽሎ ከፍ ያለ ዳኝነት ባልተጠየቀበት ሁኔታ በግምት ላይ ተቃውሞ ቀርቦ ግምቱ እንዲጣራ ሲደረግ የንብረቱ ግምት ከፍ ማለቱ በመረጋገጡ ብቻ ቀድሞ ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1) ,92, 225, 226, 250,136	86551	ወ/ሮ ብዙነሽ ወ/ሚካኤል እና እነ አቶ ሽመልስ ቦጋለ	መጋቢት 25/2005	112
26.	ወራሽነትን በማረጋገጥ በተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ ላይ መብቴን ወይም ጥቅሜን ይነካል በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ የመቃወሚያ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ሥለመሆኑ እና ተረጋግጦ የተሰጠውን ማስረጃ በሌላ ክርክር መቃወም የሚችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358	79871	እነ ወ/ሮ የውብዳር ባንቱ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሎሚ ተሊላ (አምስት ሰዎች)	የካቲት 11/2005	116
27.	አንድን ጉዳይ አስመልክቶ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው እስከሆነና ጉዳዩን ለማየት በህግ በግልጽ	80202	እነ አቶ ሐጎስ ሽንፅ	የካቲ ት12/	120

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ሌላ አካል እስከሌለ ድረስ ጉዳዩ በቀጥታ በፍ/ቤት ቀርቦ ሊስተናገድና ውሣኔ ሊሰጥበት የሚችልና የሚገባ ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1), 79(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4		(ሁለት ሰዎች) እና የመሸነ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	2005	
28.	የክስ አቀራረብ ሥርዓቱን አሟልቶ ያልቀረበ ክስን ፍ/ቤቶች ሌላኛውን ወገን ሳይጠሩ ለመዘጋት ስለመቻላቸው፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 33, 80, 222, 225, 226 እና 231	83915	አቶ ዩሐንስ በቀለ እና የበንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	የካቲት 29/2005	123
29.	የማይንቀሳቀስ ንብረት የመፋለም ክስ ጋር በተያያዘ ክርክር ቀርቦ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በክርክሩ ተሣታፊ የነበረ ወገን ንብረቱን አስመልክቶ ተሰጥቶ የነበረው የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መክኗል በሚል የሚያቀርበው አዲስ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በፍርዱ መሠረት የተጀመረው አፈፃፀም ሂደትን ለማስቆም የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195,1196 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6,358,378 የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78(1), 79(1)(4) , 37	42501	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የአስር አለቃ ደምሴ ዳምጤ ወራሾች (ሶስት ሰዎች)	የካቲት 28 /2005	126
30.	የማይንቀሣቀስ ንብረት (ቤት) ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ በውሉ መሠረት የቤቱን ስመ-ንብረት የሚመለከተው አካል ወደ ገዢው ለማዞር እንዲችል በሚመለከተው ክፍል ቀርቦ ተገቢውን እንዲፈፀም በማለት ገዥ የሚያቀርበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(1)(ሀ), 33(2-3), 222, 224	82234	አቶ አየለ መኮንን እና እነ ወ/ሮ ጦቢያው ወንድም ገዛው (ስድስት ሰዎች)	የካቲት 26/2005	130
31.	ፍርድ ቤቶች ለቀረበላቸው ጉዳይ አወሣሠን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን የተገነዘቡ ከሆነ ይሄው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያሉትን ማጣራት	72980	ወ/ሮ ይርገዱ አዲሱ	ሐምሌ 06/2004	134

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ሁሉ ለማድረግ ስለመቻላቸው፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136, 137, 272, 327(3), 345		እና እነ ህጻን ምስጋናው ዘሪሁን (ሶስት ሰዎች)		
32.	ሚስትነትን በተመለከተ የአመልካችን ማስረጃ ብቻ በመቀበል ሚስትነትን በማረጋገጥ በፍ/ቤት የሚሰጥ ማስረጃ (Declaratory Judgment) በማናቸውም ጊዜ ተዓማኒነትና ክብደት የሌለው ማስረጃ መሆኑን ለማሳየት ክርክር ሊቀርብበትና ተቃራኒ ማስረጃ ተሰምቶ ውድቅ ሊደረግ የሚችል እንጂ ማስረጃውን በተሰጠው ፍ/ቤት ተቃውም በማቅረብ ያልተሻረ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣	82679	ወ/ሮ ከበቡሽ ሸዋረገድ እና ወ/ሮ እንዳገር ጌቱ	መጋቢት 27/2005	138
33.	በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ከነበረ ክርክር ጋር በተገናኘ በተከራካሪዎቹ ወገኖች አመልካችነት ጉዳይ በእርቅ በማለቁ የተከራካሪዎቹን የእርቅ ስምምነት ተቀብሎ በማጽደቅ እንዲመዘገብ በማለት በፍ/ቤት የተሰጠ ትእዛዝ ላይ መብቱ ወይም ጥቅሜ ተነክቷል የሚል ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚያቀርበው የመቃወሚያ አቤቱታ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ትእዛዙን የሠጠው ፍ/ቤት አቤቱታውን ተቀብሎ ሊያስተናግደው የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358,360,277(1)(2)	83582	ወ/ሮ ወርቅነሽ ውብነህ እና እነ ወ/ሮ አልማዝ ዓለሙ (ሶስት ሰዎች)	መጋቢት 27/2005	144
34.	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 ተፈፃሚነት በተከራካሪ ወገኖች መካከል በዋናው ጉዳይ ላይ ከላይ ወደ ታች በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች ከተደረገ ክርክርና ከተሰጠ ውሣኔ ጋር በተገናኘ እንጂ በአፈፃፀም ከተሰጠ ትእዛዝ (ውሣኔ) ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 32	84446	ጠበቃ አንበርብር ዓባይነህ እና ፍትህ ሚኒስቴር	ሚያዝያ 24/2005	149

https://t.me/ethiopianlegalbrief

35.	አንድን ጉዳይ ለማየት በህግ ስልጣን በሌለው ፍ/ቤት ታይቶ የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ካልደተረገ በቀር በጉዳዩ ላይ አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 212	85718	አቶ ቴዎድሮስ አማረ እና አቶ አዲሱ ፍሰሃ	ሰኔ 03/2005	153
36.	በአንድ የቀረበ ክስ በተከሣሽነት የተሰየመ ወገን በከሳሽ ከቀረበበት ክስ ጋር በተገናኘ ክስ በቀረበበት ንብረት (ጉዳይ) ጋር በተያያዘ የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ በህጉ አግባብ የተከሣሽ ከሣሽነት ክሱን ተገቢውን ዳኝነት በመክፈል ያቀረበ ካልሆነ በስተቀር ዳኝነት ሊሰጥ የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1) (ረ)(ሠ), 215(2), 235(2)	86454	እሪ ወ/ት ፍሬወይኒ አለም (ሶስት ሰዎች) እና አቶ አለም መሐሪ	ግንቦት 23/2005	156
37.	ከሣሽ የሆነ ወገን የሚያቀርበውን የዳኝነት ጥያቄ አይነትና መጠኑን በክሱ ማመልከቻ በግልጽ በማስፈር ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣ ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በህግ የተፈቀደን መፍትሔ ለማግኘት በግልጽ ዳኝነት መጠየቅ የሚገባቸው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241 ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማ ተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ያቀረቡት ክርክር ለማብራራት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 246-248 መሠረት ጭብጥ ለመመስረት እንዲያግዝ እንጂ በጽሁፍ ማመልከቻ ላይ ያልሰፈረን የዳኝነት ጥያቄ ተከራካሪዎች እንዲጠይቁ የሚያስችል ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 222, 234, 235, 236, 83, 224, 182, 241, 246-248, 251, 255	86510	ሙሉ ኤሌክሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል /አ.አ/	ሰኔ 18/2005	160
38.	በፍ/ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተመለከተው 60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ግዜ ታሳቢ የሚያደርገው እና ተፈፃሚ የሚሆነው ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት ውሣኔ መሰጠቱን ወይም ለውሣኔ የሚያበቃ ክርክር የተደረገ መሆኑን ተረድተው ቀርበው ለመከታተልና	87190	ቄስ ዳንኤል አርኬ እና የኮልፌ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን	መስከረም 21/2006	164

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የዳኝነቱን ውጤት ለመስማትና ለማወቅ ያልፈለጉትን ወይም ደግሞ የተከራካሪዎችን የመደመጥ መብት ማክበር ይቻል ዘንድ በህጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በአግባቡ ጥሪ ተደርጉላቸው በጥሪው መሠረት ክርክራቸውን በአግባቡ ለመምራት ባልቻሉ ወገኖች ላይ ስለመሆኑ፣		መካነ ኢየሱስ		
39.	• የኑዛዜ ህጋዊነት ጋር በተያያዘ በተካሄደ ክርክር ተሣታፊ ሆኖ ተቀባይነት ያጣና ኑዛዜው በፍርድ ቤት የፀደቀበት ሰው በሌላ ጊዜ የኑዛዜውን ህጋዊነት አስመልክቶ በመቃወሚያነት የሚያቀርበው ክርክር ወይም አዲስ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ዳኝነት መስጠት የሚገባው በስርዓቱ መሠረት የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ መሠረት በማድረግ እንጂ ቀድሞ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ተገቢ አልነበረም በሚል ምክንያት ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5,212 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881	85102	አቶ ሰንደቁ አበበ እና አቶ ሐብታሙ ቃበቶ	መስከረም 21/2006	168
40.	•በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ መደበኛውን የሙግት ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ መከናወን ያለበት ስለመሆኑ፣ •በፍርድ አፈፃፀም ደረጃ ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር በሚል የመቃወሚያ አቤቱታ በቀረበ ግዜ ጉዳዩን የያዘው የአፈፃፀም ችሎት በንብረቱ ላይ ተቀዳሚ መብት አለኝ በሚል የቀረበውን የመቃወም አቤቱታ በመደበኛው የሙግት ሥነ-ሥርዓት ሂደት ክርክሩን በማስተናገድ ንብረቱ እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የሚያደርግ ህጋዊና በቂ ምክንያት መኖር ያለመኖሩን በማስረጃ በማጣራት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፣	86133	እነ አቶ ፍቅሩ ከበደ (አስራ አንድ ሰዎች) እና ወ/ሮ አስቴር አርአያ (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 20/2006	172

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 419, 421				
41.	የፍርድ ቤትን እገዛ በመጠየቅ ማስረጃ ማስቀረብ የሚቻለው ጠያቂው ተከራካሪ ወገን እንዲቀርብ የተጠየቀውን ማስረጃ ትክክለኛ ግልባጭ በቅርብ ግዜ ለማምጣት የማይችልበትን ወይም ለማስገልበጫ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመክፈል የማይቻል መሆኑን እንዲሁም ማስረጃው ለክርክሩ ምን ያህል ጠቃሚነት እንዳለውና ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያስችል ስለመሆኑ በጽሁፉ ገልፆ ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 145(1)(2),	89494	የኢትዩጵያ መድን ድርጅት እና የሚች ዘካሪያ ኢብራሂም ባለቤት ሳዲያ ኢብሮሽ	ጥቅምት 19/2006	177
42.	• ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጋር በተገናኘ አንድ ሰው ሚች በተውት ኑዛዜ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ክፍያ እንዲከፈለው ክስ አቅርቦ ገንዘቡ እንዲከፈል ዳኝነት ከተሰጠ በኋላ በሌላ ግዜ የሚቹ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በማለት የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ • ኑዛዜን መሠረት አድርጐ የሚቀርብ የኑዛዜ ተጠቃሚት መብት ይረጋገጥልን ጥያቄና የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄዎች ተመሳሳይ የሆነ የፍሬ ነገርና የህግ ጥያቄ የሚያስነሱ ጉዳዬች ስለመሆናቸው፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(2)	90543	እነ አቶ ተሾመ አሰፋ (ሶስት ሰዎች) እና ወ/ሪት መስታወት አሰፋ	ጥቅምት 21/2006	183
43.	በችሎት በመገኘት ስልክን ማስጮህ ብሎም ፍርድ በሚነበብበት ጊዜ በችሎት ዳኛው ሥነ-ሥርዓት እንዲይዝ ሲነገረው ችሎቱ በሥነ-ሥርዓት ያናግረኝ በማለት ያልተገባ ባህሪ ማሣየት በችሎት መድፈር ወንጀል ሊያስቀጣ የሚችል ተግባር ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 481 የወንጀል ህግ ቁጥር 449(1)(ሀ)	92459	አቶ ፍጽም ብርሃን ገ/ክርስቶስ እና ተጠሪ፡ የለም	ጥቅምት 19/2006	186

https://t.me/ethiopianlegalbrief

44.	ከወጪና ኪሣራ አወሣሠን ጋር በተገናኘ ከቅን ልቦና ውጪ ለክርክር የተዳረገ ወገን የክርክሩ ረቺ መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ቅን ልቦና ከሌላው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት በሚል ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የወጪና ኪሣራ ጥያቄን አስመልክቶ ፍ/ቤቶች በመጠኑ ላይ ለመወሰን በህግ ስልጣን የተሰጣቸው ስለመሆኑና ረቺ የሆነ ወገን ሁል ግዜ ወጪና ኪሣራ እንዲተካለት ሊወሰን ይገባል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 462-464	91103	ዩቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር እና እነ የአቶ ፉአድ መሃመድ እናት ወራሽ ወ/ሮ ማሪያም አብዱላሂ (ሁለት)	ታህሳስ 16/2006	188
45.	በሌለበት የተሰጠ ውሣኔ እንዲነሣ በቀረበ አቤቱታ መነሻነት ፍ/ቤቱ አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ያነሳውና አቤቱታ አቅራቢው ክርክሩን እንዲያቀርብ በድጋሚ እድል ከተሰሠጠው በኋላ የጽሁፍ ክርክሩን ያላቀረበና ክሱ በሚሰማበት ቀጠሮ ያልቀረበ እንደሆነ ክርክሩን እንደገና ለመስማት በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት የከሣሽ ክስና ማስረጃ እንደገና ተመርምሮ ተገቢው ውሣኔ ከሚሰጥበት በቀር እንዲነሣ ትእዛዝ የተሰጠበት የቀድሞው ውሣኔ በቀጥታ ተመልሶ እንደገና እንዲፀና ሊደረግ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78(2), 70(ሀ)	90452	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ገ/ሥላሴ በርሄ	ጥር 14/2006	191
46.	ሀሰተኛ ማስረጃ ለፍ/ቤት በመቅረቡ የተነሣ የተወሰነበት ተከራካሪ ወገን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)ን መሠረት በማድረግ ፍርዱ በድጋሚ እንዲታይለት አቤቱታ ባቀረበ ጊዜ ሀሰተኛ ማስረጃውን የሰጠው አካል በምን ምክንያት በህገ ወጥ ተግባር ሀሰተኛውን ማስረጃ ሊሰጥ እንደቻለ የማስረዳት ግዴታ ጭምር አለበት ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣	91968	አቶ ግርማ ሰንበት እና ወ/ሮ አልማዝ ገብረየስ	ታህሳስ 15/2006	194

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) የወንጀል ህግ አንቀጽ 403፣405				
47.	• ተከራካሪ ወገኖች በቅድሚያ ሊያቀርቧቸው ሲችሉ ሆነ ብለው ወይም በቸልተኝነት ያላቀረቧቸውን ማስረጃዎች በክርክር ሂደት ሁሉ እያንጠባጠቡ ሊያቀረቡ ወይም የማስረጃ ማሰባሰብ ሥራውን ፍርድ ቤት እንዲያከናውን ሊጠይቁ የሚችሉበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ • በፍ/ቤት እገዛ ማስረጃ የሚቀርበው ተከራካሪ ወገን አጠቃቅሎ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ስለመሆኑና ፍ/ቤቱ የተጠየቀው ማስረጃ ለተያዘው ጉዳይ ያለውን አግባብነት በተመለከተ የተቀበለው እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1)	85468	ሣባ ኢንጂንሪግ ኃ.የተ.የግል ማህበር እና የፕራይቬታይዜሽን ና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጂንሲ	መስከረም 24/2006	197
48.	• ተከራካሪ ወገኖች ለክርክራቸው ምክንያት ሊሆን የሚችለውን ጉዳይ ወይም ያከራከራቸውን ጉዳይ በእርቅ ስምምነት የጨረሱ እንደሆነ የእርቅ ስምምነቱ ግብ ተከራካሪዎቹ (ታራቂዎቹ) በግላቸው ያላቸውን መብትና ግዴታ እንደሁኔታው በማስተካከል ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን ጉዳይ በስምምነት ማስቀረት ስለመሆኑና የእርቅ ስምምነቱ ውጤትና ተፈፃሚነቱ እርቁን ባደረጉት ተከራካሪ ወገኖች መካከል ብቻ ተገድቦ የሚቀር እንጂ የሌሎች 3ኛ ወገኖች መብትና ግዴታ ሁሉ በማካተት የ3ኛ ወገኖች መብትና ግዴታን አብሮ በእርቅ እንዳለቀ የሚያስቆጥር ስላለመሆኑ፣ • የተከራካሪ ወገኖች የእርቅ ስምምነት በፍ/ቤት ትእዛዝ (ውሣኔ) መጽደቅና መመዝገብ መብቴን ወይም ጥቅሜን ይነካል በሚል 3ኛ ወገኖች የሚያቀርቡት የመቃወም አቤቱታ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3311	87834	በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት እና ፀዳለ ካሣቀ (ሶስት ሰዎች)	መስከረም 21/2006	204

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358				
49.	አንድ ፍርድ ቤት ክርክርን በሚሰማበት ወቅት የሚሰጠው ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ (Interlocutory order) ላይ በመነጠል ክርክር የሚካሄድበት ዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችለው የተሰጠው ትእዛዝ በባህሪው የሰውን መታሰር ወይም የንብረት ማስተላለፍን ወይም ስም ማዞርን ጉዳይ በተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320(3)(4)	89893	ኮንቴክ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ወልዱ ሀሉፍ	መስከረም 24/2005	207
50.	የዳግም ዳኝነት (Review of Judgement) ዓይነተኛ ዓላማ ተገቢ ሁኔታዎችና ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸው ሲረጋገጥ በሀሰተኛ ማስረጃ፣ በመደለያና በመሰል ወንጀል ጠቀስ ድርጊቶች ምክንያት የተዛነፈን ፍትህ ወደ ነበረበት መመለስ ስለመሆኑ፣ የዳግም ዳኝነት ጥያቄ (አቤቱታ) ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ተግባራት የሚከናወንበት በመሆኑ ጥያቄው ለሰበር ችሎት በቀረበ ጊዜ ችሎት አቤቱታውን ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ላላቸው የስር ፍ/ቤቶች ሊመራውና ሊያስተላልፈው በሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)(ሀ)(ለ) አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ)	93137	ወ/ሮ ብጥር ታገለ እና ወ/ሮ አገር ተሰማ	የካቲት 11/2006	210
51.	በተከራካሪ ወገኖች ክርክር በሚካሄድበት ወቅት በፍ/ቤት ትእዛዝ በተከራካሪ ወገን ስም በባንክ የሚገኝ ገንዘብ ታግዶ እንዲቆይ ተደርጐ ትእዛዙ ፀንቶ በነበረበት ግዜ በገንዘቡ ላይ ወለድ ሊታሰብ ይገባል ወይስ አይገባም በሚል ክርክር የተነሣ እንደሆነ ከጉዳዩ ልዩ ባህሪ ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የልዩ አዋቂ ምስክርነትና የባለሙያ ማብራሪያን	83771	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ ወ/ሮ ዘነበች አለማየሁ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 10/2005	214

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አስቀርበው በማጣራት ሊወሰኑ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136				
52.	ባለ አምስት ዳኞች የሚሰየሙባቸው የክልል ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች በአጣሪው ችሎት ጉዳዩ ያስቀርባል በሚል በተመለከተው ነጥብ (ጭብጥ) ሳይገደብ ሌላ (ሌሎች) ጭብጦችን በመመስረት ክርክሩ እንዲሰማ በማድረግ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣	90298	አቶ ኃይሉ ደሬሳ እና ወ/ሮ ሱፊ አለሙ	የካቲት 10/2006	217
	የንግድ ህግ				
53.	• የንግድ መደብር ኪራይ ከንግድ ቤት ኪራይ የተለየ ስለመሆኑ፣ • የንግድ መደብር የተከራየ ሰው ያለአከራዩ እውቅና እና ፈቃድ መደብሩን ለ3ኛ ወገን በኪራይ አሳልፎ ለመስጠት ስለመቻሉ፣ የንግድ ህግ ቁ. 127 (ሐ),145(ለ),	79561	አቶ ፀጋዬ አማን ለኛ እና በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት	የካቲት 11/2005	221
54.	የንግድ ማህበር ሒሣብ ከተጣራና ትርፍና ኪሣራው ተለይቶ ከቀረበ በኋላ የማህበር አባል (ባለአክሲዮን) የሆነ ሰው ከትርፍ ሊደርሰው የሚገባውን የድርሻ ክፍያ በመለየት ክፍያ እንዲፈፀምልኝ በማለት የሚያቀርብው ጥያቄ ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁጥር 211, 517, 518, 532(1)	82503	እነ ወ/ሪት ቤዛ ዱጉማ (ሁለት ሰዎች) እና ዘሚሊ ቀለም ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ሚያዝያ 21/2005	224
55.	• የህብረት ሥራ ማህበራት ንብረት እንደ የአባለቱ የጋራ ሀብት (ንብረት) ተቆጥሮ ንብረቱን ለመሸጥ የሁሉም አባላት ስምምነት ያስፈልጋል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ • የህብረት ሥራ ማህበራት አሰራር ጋር በተያያዘ ውሣኔ ለማሳለፍ የሚችለው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስለመሆኑ፣	85009	ሃጅ ፈዬ ገመቹ ሄዳኡ እና እነ አቶ ዓለሙ በቀለ (አስራ አምስት ሰዎች)	መስከረም 21/2006	229

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ. 147/91 አንቀጽ 21, 18, 32, 19 ደንብ ቁጥር 106/96 አንቀጽ 20(2) 123				
56.	አበዳሪ የሆነ ባንክ ለተበዳሪው ላበደረው ገንዘብ በመያዣነት ለያዘው ንብረት የመድን ሽፋን የገባለት እና የአርቦን ክፍያን ለመክፈል የተስማማ እንደሆነ ለመድን አስገቢው ተቋም የአረቦን ክፍያውን ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ • የንግድ ህግ ቁጥር 657, 675	83489	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ግንቦት 19/2005	233
ቤተሠብ					
57.	ከሚች በስጦታ ወይም በኑዛዜ የተሰጠን ንብረት ወደ ውርስ መልሶ ማግባት (Collation) ስለሚከናወንበት ሥርዓት፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1065-1078	80920	ወ/ሮ ውድነሽ እሸቱ እና አቶ ፍቅረማሪያም ወርቁ	የካቲት 25/2005	237
58.	ኑዛዜ ፈራሽ ነው በሚል ስለሚቀርብ ክስ እና ክሱ ሊቀርብ ስለሚገባበት የጊዜ ገደብ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973, 974	82585	እነ ወ/ሮ ሱዛን ሞንታልባን (ሶስት ሰዎች) እና እነ አቶ መራድ አለ. (ስድስት ሰዎች)	የካቲት 13/2005	240
59.	ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጋር በተገናኘ የውርስ ሀብት ተጣርቶና ሪፖርት ቀርቦ በመጽደቁ መነሻነት ሀብቱ ተከፋፍሎ ከተፈፀመ በኋላ ወራሾቹ ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሣይኖራቸው ውርሱን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ አድርጓል በሚል እውነተኛ ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት የውርስ ንብረቶች እንዲመለሱለት በሚል ለመጠየቅ የሚችለው ተገቢውን የዳኝነት	89641	እነ ወ/ሮ ሐረገወይን ብርሃኑ(ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ አዜብ ብርሃኑ (ሁለት	ጥቅምት 21/2006	243

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ክፍያ በመክፈል አዲስ ክስ በመመስረት እንጂ ክፍፍሉ ተፈጽሞና ውሣኔ አግኝቶ የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996(1), 998(1), 999 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91, 6		ሰዎች)		
60.	ተጋቢዎች የጋብቻቸውን ፍቺ አስመልክቶ ጉዳዩ በመደበኛው ፍ/ቤት ቀርቦና ክርክር ተካሄዶ ውሣኔ ከተሰጠበት በኋላ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጉዳይ ሀይማኖታዊ ስርዓትን በመጠቀም በሸሪአ ፍ/ቤት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1)(2), 244(2)(ለ), 245(2) አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 5(4), 6(2) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 34(5)	93779	ወ/ሮ ጂአቶ ያሲን ሺበሺ እና አቶ ሐሰን መሐመድ	ታህሳስ 30/2005	247
61.	• የአባት ስም እንዲስተካከልልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ • አንድ ሰው አንድ የቤተዘመድ ስምና አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞችና የአባት ስም ሊኖረው ስለመቻሉና የአንድ ልጅ የአባት ስም የሚሆነው የአባቱ የግል ስም ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231 (1)(ሀ) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 32(1)፣ 36(1)	95995	ወ/ት ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ እና ተጠሪ፡- የለም	የካቲት 10/2006	251
62.	የቤተ ዘመድ ስም እንዲለወጥ በፍ/ቤት ጥያቄ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 42 , 33(1) , (2)	87420	ወ/ሪት ማህሌት ልዑለቃል እና ተጠሪ የለም	ሚያዝያ 24/2005	254
ጉምሩክ/ግብር/ታክስ					
63.	ግብር የተጣለበትን የካፒታል ንብረት ዝውውር	79189	የኮልፌ ቀራኒዮ	መጋቢት	258

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የመቀበል ወይም የመመዝገብ ወይም በማናቸውም መንገድ የማጽደቅ ስልጣን ያለው (የተሰጠው) የመንግስት አካል ግብሩ መከፈሉን ማያረጋግጥ ዝውውሩን እንዲቀበል፣ እንዲመዘግብ ወይም እንዲያፀድቅ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 37(7)		ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ባለስልጣን እና ጂ.ኤም.ቲ ኢንዱስትሪያል ኃ/የተ/የግል ማህበር	9/2005	
64.	• አንድ ሰው ለመንግስት ሊከፍል የሚገባውን ግብር ባለመክፈሉ በወንጀል ተግባር ሊጠየቅና ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚችለው ግብሩን ላለመክፈል በማሰብና ግብር አስገቢው መ/ቤትም ንብረቶቹን በመያዝና በመሸጥ የግብር ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ለማድረግና ግብር የመክፈል ኃላፊነቱን ለማምለጥ ንብረቶቹን ለማሸሽ፣ የመሰወር ወይም ሌሎች ተገቢነት የሌላቸው ህገ ወጥ ተግባራትን በመፈፀም ግብርን ያልከፈለ መሆኑ ሲረጋገጥ እንጂ በሌሎች በህግ ተቀባይነት ባላቸው ምክንያቶች ግብሩን ለመክፈል ሳይችል የቀረ እንደሆነ ስላለመሆኑ፣ • ማንኛውም ሰው በፍ/ብሔር ጉዳይ ያለበትን እዳ ለመክፈል ባለመቻሉ ምክንያት ብቻ በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የማይገባ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 49 አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 96, 162 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 13(2) ደንብ ቁጥር 78/94 ICCPR- አንቀጽ 11	84623	እነ ጅ. አግሪ ፖክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች) እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት	ሰኔ 04/2005	261
65.	የንግድ ሥራ ፈቃድ ኖሮት ነገረ ግን በህግ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፈቃዱ ሳይታደስ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የተገኘ ሰው የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ እንደሌለው ተቆጥሮ በወንጀል ኃላፊነት ጥፋተኛ ተደርጐ ሊያስቀጣው የሚችል	86388	አቶ ባዘዘው ይሁን እና የአ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ	ሰኔ 17/2005	268

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 2(10), 36, 60(1)				
66.	ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተገናኘ ከሚመለከተው የገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ፈቃድ ሳያገኝ ተገቢ ያልሆኑ ፓዶችን (የVAT ደረሰኞችን) ማሳተምና መገልገል በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑና የድርጅቱ ባለሀብት (ሥራ አስኪያጅ) ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው ያልነበረ መሆኑን በመግለጽ የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው ማንኛውም በጉ አሳቢ ሰው ሊያደርገው የሚችለውን ጥንቃቄ ያደረገና ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ድርጅቱን በመምራት ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን ማስረዳት የቻለ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56(3),(ለ), 3(1)(ለ), 2(11), 3(1)(ሀ) አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 2, 19(50) (ሐ)	86597	ግሎሪ ኢትዮጵያ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር እና አቶ በርሀ ረዳ ኪዳኑ	መስከረም 21/2006	271
67.	አንድ በንግድ ሥራ የተሰማራ ሰው (ድርጅት) በተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ አለበት ለማለት የሚቻልበት እንዲሁም መመዝገብ ሲኖርበት ሳይመዘገብ ቀርቶ ግብር ሊጣልበት ስለሚችልበት አግባብ፣ አዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 3(1)(3), 16(1)(ለ)	82061	አቶ አብዶልቀድር ሁሴን እና የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት	መስከረም 20/2006	274
68.	የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነ ነጋዴ (ሠው) ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሽያጭን አከናውኗል በሚል በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችልበት አግባብ፣ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 11(1)(2)፣ 22(1)(3) አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 11(1)	86672	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ እና አቶ በቀለ ተሰማ	መስከረም 22/2006	277

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2)፣ 58(3) ደንብ ቁጥር 139/1999		(ሁለት ሰዎች)		
69.	ከጉምሩክ ህግና አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በኮንትሮየባንድ ወንጀል ተጠርጥሮ በጉምሩክ ተቋም በቁጥጥር ሥር እንዲውል የተደረገ የንግድ ተሽከርካሪን አስመልክቶ ለንብረቱ ባለቤት የተቋረጠ ጥቅም (ገቢ) እንዲከፈል ሲወሰን የካሣውን መጠን ለመወሰን የተሽከርካሪውን ዓመታዊ የተጣራ ገቢ በተመለከተ ባለንብረቱ ለሚመለከተው የመንግስት አካል በህጉ አግባብ ያሳወቀውን የገቢ መጠን ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብና መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ በአንድ የመንግስት ባለስልጣን ተረጋግጦ የተሰጠ የሰነድ ማስረጃ በህጉ መሠረት ተቃውሞ ቀርቦበት ዋጋ የሌለው ስለመሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ማስረጃው በማስረጃነት ዋጋ ሣይሰጠው ሊታለፍ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2010, 2011, 2090, 2091, 2141, 2152, 2153 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136, 138, 180 (1)	89640	የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን እና ሰይፈዲን አብዱልቃድር	መስከረም 23/2006	281
	ንብረት				
70.	የአንድ እምነት ወይም ሐይማኖት ተከታይ ወይም አማኝ በመሆን በሐይማኖታዊ ተቋሙ ውስጥ የመቃብር ቤት ገንብቻለሁና የቤቱን ግምት ይከፈለኝ በሚል ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር በተገናኘ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179 ድንጋጌ ተፈፃሚ ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1179 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 11,27 (1-3) UDHR-Art. 18 ICCPR.Art. 18(1)	85979	የሐረር (ደ/ሳ) ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን እና ወ/ሮ ማንያህልሻል አበራ	መጋቢት 13/2005	286
71.	ከመንግስት የተከራየውን ቤት ከአከራዩ ፈቃድ	88798	አቶ መሉ አብርሃ	ሐምሌ 18/2005	291

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ውጪ ለ3ኛ ወገኖች አከራይቶ ሲገለገል የነበረ ሰው በመንግስት መመሪያ መሠረት ቤቱ ተከራይቶ ሲሰራበት ለነበረው ሰው በመተላለፉ ምክንያት የመጀመሪያው ተከራይ በመመሪያው መሠረት ቤቱ የተላለፈለት ሰው ላይ የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣		ገ/ሕይወት እና እነ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት (ሶስት ሰዎች)		
72.	• የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ነገር በቀጥታ ወይም በጥበቃ ሥር የሆነ ይዞታ ሲኖረው ስለመሆኑ፣ • የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም አይነት መብት በሌለው ሰው ላይ ስለመሆኑ፣ •የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርብ ሰው ንብረቱ በይዞታው ሥር የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚዉ የኃይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጥር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ፣ • የሁከት ተግባር ተፈጥሯል ለማለት ባለይዞታ የሆነው ሰው በይዞታው ሥር በሚገኘው ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ወይም ረብሻ የፈጠረበት ስለመሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፣ •በህግ አግባብ በተደረገ የኪራይ ውል መነሻነት ይዞታን በእጁ ያደረገ ሰው (ተከራይ) ላይ አከራይ የሚያቀርበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣	80241	ጽናት የሆቴል ቱሪዝም ስራዎች ኃ.የተ.የግል ማህበር እና እነ አቶ ዳመነ ነጋ (አምስት ሰዎች)	የካቲት 12/2005	295
73.	የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ጋር በተገናኘ ንብረትነቱ ከአገር የወጡ ኤርትራዊያን የሆነ ቤትን ለማስተዳደር ውክልና የተሰጠው ሰው የመሸጥ ውክልና በባለቤቱ ያልተሰጠ ቢሆንም እንኳን በሚመለከተው የመንግስት አካል በተሰጠ (በተላለፈ)	83060	ገ/ማሪም ገ/መድህን እና ጣዕመ ወ/ስላሴ	ሰኔ 21/2005	300

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	መመሪያ መሠረት ከተወካዩ ቤቱን የገዛ ገዥ ተወካዩ ቤቱን የሸጠለት በሌለው የውክልና ስልጣን ነው በሚል ገዝቶ ስመ ንብረቱ ከተላለፈለት በኋላ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ቤቱ ለባለቤቱ ሊመልስ ይገባል ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀጽ 2(1), 4(1), 5(1)(ሀ)				
74.	የውርስ ሀብትን እንዲያጣራ የተመደበ የውርስ ሀብት አጣሪ የንብረትነቱ የሚቸ የግል ሀብት መሆን በተመለከተ በሪፖርቱ ገልጿል በሚል ምክንያት ከንብረቱ ጋር በተገናኘ የባለሀብትነት ክርክር ያቀረበውን ወገን ጥያቄ በአግባቡ ባለማስተናገድ ውሣኔ ላይ መድረስ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መግስት አንቀጽ 40(1), 37 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 1206	83665	ወ/ሮ እታፈራሁ ፀጋዬ እና እነ ወ/ሮ መሰረት ግርማ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 22/2005	305
75.	• አንድ ሰው ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ የሚችለው በህግ ጥበቃ የሚደረግለትንና ያለውን መብት እንጂ የሌላውን መብት ስላለመሆኑ፣ • በህግ ጥበቃ የሚደረግለት መብት ሣይኖር በስሙ የተመዘገበ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀተ ከያዘ ሰው ንብረቱን በመንደር ውል የገዛ ገገር ተገቢውን ማጣራት በማድረግና፣ በጥንቃቄ፣ የገዛና የቅን ልቦና ያለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ • የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ደንብና አሰራርን መሠረት ያላደረገ እንዲሁም ከስልጣን ውጪ የተሰጠና በህግ ፊት የማይፀና ስለመሆኑ በማናቸውም ማስረጃ ለማረጋገጥ የተቻለ እንደሆነ በተሰጠው የምስክር ወረቀት የተፈጠረውን የህጉን የህሊና ግምት ማፍረስ የሚቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196, 2884, 2882-2884 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(1)(2)	88084	ወ/ሮ ወጋየሁ ታምሩ እና እነ የወ/ሮ አስካለ ወሰኔ ወራሽ ፍሬዘውድ ጌታቸው (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 19/2006	309

https://t.me/ethiopianlegalbrief

76.	ፍርድ ቤቶች ከሣሽ በክሱ ገልፆ በትክክል ዳኝነት የጠየቀበት ጉዳይ በቤት ላይ ያለውን የባለሀብትነት መብት ለማስከበርና የመፋለም ክስ ሆኖ እያለ ክሱ የቀረበው በአዋጅ የተወረሰ ቤት ወይም ከአዋጅ ውጪ በባለስልጣን ቃል ትእዛዝ ወይም በቀላጤ የተወሰደን ቤት ለማስመለስ ነው በሚል ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሚሰጡት ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 47/67 የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 2257	86049	አቶ ሻፊ አብዱራህማን አብዱ እና ወ/ሮ አንሻ እንድሪስ (ሶስት ሰዎች)	መስከረም 20/2006	313
ከውል ውጭ ኃላፊነት					
77.	ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት አንድ ሰው በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ባደረሰ ጊዜ ጉዳት የደረሰበት ንብረት ባለቤት ለንብረቱ የመድን ዋስትና የገባ ሆኖ የመድን ተቋሙ በመድን ውሉ መሠረት ጉዳት ለደረሰበት ወገን የጉዳት ካሣ በመክፈል በጉዳት አድራሹ ንብረት ባለቤት ላይ ብቻ ክስ በመመስረትና ጉዳቱን በቀጥታ ያደረሰውን ሰው በመተው ጉዳቱ ለደረሰበት ሰው የከፈለውን የጉዳት ካሣ ክፍያውን እንዲከፍለው ለመጠየቅ ስለመቻሉ፣ የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 1677, 1896, 2081, 18, 2156 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ. 36(2)	89504	አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና እነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን (ሁለት ሰዎች)	መስከረም 22/2006	317
78.	ባለፎቶግራፍ ወይም ባለስዕሉ ካልፈቀደ በቀር የማንም ሰው ፎቶግራፍ ወይም ስዕል በህዝብ አደባባይ ሊለጠፍም ሆነ ሊባዛ ወይም ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑና ፎቶው ወይም ስዕሉ ጥቅም ላይ ለዋለበት የማስታወቂያ ሥራ ባለፎቶው ወይም ባለስዕሉ ካሣ ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ፣ ለባለ ፎቶው ወይም ለባለስዕሉ የሚከፈለውን የካሣ መጠን ድርጊቱን የፈፀመው ሰው በዚሁ ድርጊት ያገኘው ሀብት (ጥቅም) ተመጣጣኝ በሚሆንበት	91710	ሕጻን ሪያን ሚፍታህ እና ኤልሲውዲ ኬብልስ ኃላፊነቱ የተ.የግል ማህበር	ህዳር 16/2006	319

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	መጠን በዳኛች ሊወሰን ስለመቻሉ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 28 29(2), 2142				
79.	• ጥቅምን መሠረት ባላደረገ ሁኔታ ህፃናትን (እድሜው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰውን) አሳፍሮ በመንዝ ወቅት በደረሰ አደጋ ምክንያት በህፃናቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ የተሸከርካሪው ባለቤትና በወቅቱ በተሸከርካሪው ሲገለገል የነበረ ወይም ሹፌሩ የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርባቸው ስለመሆኑ፣ • የተሸከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው ጥቅም በሌላው ግንኙነት መነሻ በተሸከርካሪው ተሳፍሮ ሲንዝ በነበረ ሰው ላይ ለሚደርስ የአደጋ ጉዳት ካሣ ለመክፈል የማይገደድ ቢሆንም ጉዳቱ የደረሰው ከፍተኛ ጥንቃቄና እንክብካቤ ሊደረግላቸው በሚገባ ህፃናት ላይ በሆነ ጊዜና ህፃናቱም ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ በተሸከርካሪው ላይ የተጫኑ (የተሣፈሩ) እንደሆነ የተሸከርካሪው ባለቤት የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 36(2), 15, 25 የህፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3, 6(1) የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 4(1), 5(1) የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2126(2), 2127, 2130 2131, 2089(2), 2081(1)	92020	እነ የኢ.ፌ.ዲ.ፌ ፌዴሬሽን ምክር ቤት (ሁለት ሰዎች) እና ቂስ ማሞ ይታፈሩ	ታህሳስ 15/2005	323
80.	አንድ ሠው በሰራው ሥራ ወይም በፈፀመው ድርጊትና ድርጊቱ በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ምክንያት በ3ኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በፍ/ብሔር ኃላፊነት ተጠያቂ የሚሆን ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2069	88432	ወጣት ደሣለኝ ወንታ እና አቶ ኡስማን መሐመድ	መስከረም 22/2006	327
81.	• አንድ የመንግስት መ/ቤት በሠራተኛው ተግባር በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው በሠራተኛው የተፈፀመው ጥፋት የሥራ ጥፋት ሆኖ ሲገኝ	82154	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	መጋቢት 24/2005	

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ስለመሆኑ፣ • አንድ ጥፋት የሥራ ጥፋት ነው ተብሎ የሚወሰደው ጥፋት አድራጊው በጥፋቱ ላይ የወደቀው በቅን ልቦና በስልጣኑ ለሥራው ክፍል መልካም ያደረገ መስሎት የፈፀመው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑና ከዚህ ውጪ በሆነ ጉዳይ ግን ጥፋቱ እንደ ግል ጥፋት የሚቆጠር ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2126, 2127 (1)(2)(3)		እና ተጠሪ፡ አቶ ፍቅሩ ኃይሌ		330
የዳኝነት ስልጣን					
82.	ከንግድ ምዝገባ ፈቃድ ጋር በተገናኘ የሚነሱ የፍሬ ነገር ክርክሮችን የመደበኛ ፍ/ቤቶች አይተው ለመወሰን ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 686/2002 አንቀጽ 61	81934	የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት እና 50 አለቃ ታምራት ከበደ	የካቲት 28/2005	336
83.	ከአስጎብኚና የጉዞ ወኪል የንግድ ሥራ ፈቃድ ጋር በተያያዘ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ መኪኖችን በተመለከተ የሚቀርብ ክርክርን መደበኛ ፍ/ቤቶች በቀጥታ ክስ ለማስተናገድ የሥረ ነገር ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 87(1), (5), (9), (10), ደንብ ቁጥር 146/2000	86817	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ግሎሪ ኢትዮጵያ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር	መስከረም 22/2006	338
84.	የክርክሩ ገንዘብ መጠን ከአምስት ሺህ ብር በታች በመሆኑ ምክንያት ብቻ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የሚቀርብን ክርክር የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች አይተው ለመወሰን ስልጣን አላቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣	89530	ቲኤንቲ ኮንስትራክሽንና የንግድ ስራዎች ድርጅት	ጥቅምት 21/2006	341

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 138, 142 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9(1), 231(1)(ለ), አዋጅ ቁ. 416/96 አንቀጽ 41(1),		እና አቶ እያዩ ደጀኔ		
85.	ከህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በተገናኘ የማህበር የሥራ ኃላፊዎችን በተመለከተ ገንዘብ አጉድለዋል በማለት ገንዘቡ እንዲከፈል ማህበሩ በኃላፊዎቹ ላይ የሚያቀርበው ክስ አስቀድሞ በእርቅ ካልተቻለ ደግሞ በሽምግልና ሊታይ የሚገባው እንጂ በቀጥታ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ሊቀርብበት አይችልም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑና መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49(1-4), 47(1), 26(2), 39(1)(ለ)(ሐ), 152 አዋጅ ቁጥር 402/96 አንቀጽ 46 ደንብ ቁጥር 106/96 አንቀጽ 14(ሀ)(ሐ)(መ)	90737	የንጋት ኮከብ ሸማቾች ኃ/የተ የግል ማህበር እና እነ አቶ የሴፍ እንድሪስ (አስር ሰዎች)	ህዳር 16/2006	344
86.	አንድን ክርክር በማስተናገድ ላይ ያለ የክልል ፍ/ቤት በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ተቋም (ድርጅት) አግባብነት ያለው የጣልቃ ገብ አቤቱታ በቀረበለት ጊዜ ጉዳዩን ጣልቃ ገቡን ወደ ክርክሩ በማስገባት አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሌለው በመሆኑ ክርክሩ ጣልቃ ገብን ባካተተ መልኩ ለማየት ወደሚችለውና ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ጉዳዩ ቀርቦ ሊታይ የሚገባ መሆኑን ገልፆ መዝገቡን መዝጋትና ተከራካሪዎችን ማሰናበት የሚገባ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(6),14 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(4) የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 64(4) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9, 231(1)(ለ)	90920	ዓባይ ኢንሹራንስ አ.ማ እና አቶ አለማየሁ አሰፋ	ህዳር 06/2006	347
	ወንጀል				
87.	አንድ ሠው በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከስሶ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በተመሳሳይ ማስረጃ በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ተጠያቂ	78470	አቶ ታሪኩ ጫኔ	ሚያዝያ 07/2005	35

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ነው (ኃላፊነት አለበት) ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149 የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 141		እና የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን		1
88.	አንድ ሠው በአንድ ወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ የሆነ ውሣኔ ተሰጥቷል በማለት በድጋሚ ልከሰስ አይገባም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ከዚህ ቀደም ተጣርቶ ክስ የቀረበበትና የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት የወንጀል ድርጊትን በድጋሚ (ለሁለተኛ ጊዜ) ክስ ቀርቦበታል ከተባለው የወንጀል ድርጊት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 2(5), 678, 696(ሐ) እና 378 ህገ መንግስት አንቀጽ 23	85237	ዘካሪያስ ገ/ጻዲቅ እና የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ	መጋቢት 27/2005	355
89.	በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሣሽ ላይ የሚወሰነው የእስራት ቅጣት አፈፃፀም እንዲገደብ ለማድረግ ስለማይችልባቸው ሁኔታዎች፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 194(1) እና (2)¸190¸192	85596	እነ ሰይፉ ደስታ እና የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ	መጋቢት 25/2005	359
90.	ህጋዊ መከላከል (Legitimate self-defense) በወንጀል የማያስቀጣው የራስን ወይም የሌላን ሰው መብት ህገ ወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ህገ ወጥ ጥቃት ለማዳንና ጥቃቱ እንዳይደርስ ከማድረግ ሌላ አማራጭ (መንገድ) ሣይኖር ከሁኔታው መጠን ባለማለፍ የተፈፀመ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 78 ,79	86570	ጌታቸው ገላዬ ፈረደ እና የደቡብ ክልል ዐቃቤ ሕግ	ሚያዝያ 07/2005	363
91.	• አንድ ሠው የአራጣ ወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችልበት አግባብ፣	80119	አቶ ተድላ ተገኝ እና	የካቲት 11/2005	367

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	• በወር 10% ወለድ ታስቦ እንዲከፈል በመስማማት ገንዘብ ማበደር በአራጣ የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ 667(1)		የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ		
92.	• በሌላ ሰው ጥቅም የሥራ አመራር ላይ ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ • በተከታታይ ለተፈፀመ ወንጀል ይርጋ ስለሚቆጠርበት አገባብ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/፣702/3/፣219/2/	79389	እነ ዶ/ር ታጀዲን ያህያ (ሁለት ሰዎች) እና የአማራ ክልል ዐ/ሕግ	መጋቢት 12/2005	371
93.	አንድ ሰው በስራው ስልጣን መሠረት በአደራ የተሰጠውን ወይም ሊጠብቀውና ሊከላከለው የሚገባውን የህዝብ ወይም የመንግስት ጥቅም የሚጐዳ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ በወንጀል ህግ አንቀጽ 411 መሠረት በወንጀል ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 411(ሐ), 407	86845	የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ እና አቶ ሰለሞን ዩሐንስ	መስከረም 22/2006	374
94.	የአንድ ደርጊት ወይም ግድፈት ወንጀልነት በህግ በግልጽ ተደንግጐ በማይገኝበት ሁኔታ የድርጊቱን ወይም የግድፈቱን ፈፃሚ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ፣ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክስ ስለ ድርጊቱና አፈፃፀሙ የሚሰጠው መግለጫ ድርጊቱን ወንጀል ከሚያደርገው ህግ አነጋገር በጣም የተቀራረበ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ፣ በንግድ ሥራ ለተሰማሩ ወይም ሌሎች ሰዎች በግለሰብ ደረጃ መጠኑ በርካታ የሆነ ገንዘብን በተደጋጋሚ በብድር የመስጠት ተግባር በህግ የተከለከለ ወይም በወንጀል የሚያስቀጣ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 2, 23(2), 3, 61	81178	የኢዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ እና እነ አቶ ከበደ ተሰራ (ሁለት ሰዎች)	መስከረም 21/2006	380

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወ/መ/ህ/ሥ/ቁ. 112 አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1), (ሸ), 2(ሀ),				
95.	ነፍሰጡር (እርጉዝ) የሆነች ሴትን ሆዷ ላይ በመምታት ጽንሱ እንዲሞት ማድረግ ድርጊቱን በፈፀመው ሰው ላይ በግድያ መከራ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 27(1), 581(ለ), 540	90089	ዘኒት አባቡ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ዐ/ህግ	ጥቅምት 20/2006	384
96.	አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈጽሟል ሊባል የሚችለው የድርጊቱን ውጤት እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ድርጊቱ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ማወቅ ይችል ነበረ ለማለት የሚቻል እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አንድ ሰው የፈፀመው ድርጊት በቸልተኝነት ነው ለማለት በመስፈርትነት ሊወሰድ የሚገባው የድርጊቱ ፈፃሚ በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ስለመሆኑና ይህም የድርጊቱ ፈፃሚ የነበረው እውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባውን እውቀትና ግንዛቤ መመዘን ያለበት ከግለሰቡ እድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ የትምህርት ደረጃ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 59(1), 543(2), 57	93741	አቶ አብነት ዋቆ ብሩ እና የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ	ታህሳስ 14/2005	387
97.	ፈቃድ የሌላቸው የጦር መሳሪያዎችና ጥይቶችን በቤቱ ውስጥ አከማችቶ የተገኘ ሰው መሣሪያዎቹን ለመነገድ በሚል ሀሳብ የያዘ መሆኑ የተረጋገጠ ካልሆነ በስተቀር ግለሰቡ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው በወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) ሣይሆን በአንቀጽ 809(ሀ) ሥር በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ስለመሆኑ፣	93173	እነ አቶ ተዋበ እስጢፋኖስ (ሁለት ሰዎች) እና የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ	ታህሳስ 17/2006	391

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	የወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ), 809(ሀ)				
98.	አንድ ሠው የአንድን ጉዳይ መከሰት በምክንያትነት በመግለጽ ከሌላ ሰው ገንዘብን ተበድሮ መውሰድ ተከስቷል የተባለው ጉዳይ ካለመከሰት ጋር በተገናኘ ተበዳሪው በእምነት ማጉደል ወንጀል ሊያስጠይቀው የሚችል ስላለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 675	89276	ተፈሪ ሚናሞ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ዐቃቤ ሕግ	መስከረም 23/2006	395
99.	• አንድ ሠው ወንጀል አደረገ የሚባለው ህገ ወጥነቱ እና አስቀጪነቱ በህግ የተደነገገ ድርጊት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ስለመሆኑና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ስለመሆኑ፣ • ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በሙላ አሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆኑ ድርጊቱን የራሱ ያደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 2፣23(1)፣ 32(1) የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 111፣112፣141፣142	91535	አቶ አህመድ አደም በሽር እና የአማራ ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ	የካቲት 12/2006	400
ባንክ እና ኢንሹራንስ					
100.	የመድን ዋስትና ሽፋን ውል ተደርጓል እንዲሁም ውሉ ተሻሽሏል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣ የንግድ ህግ፡ 657	78180	አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና ወ/ሮ አስቴር ንጉሴ	መጋቢት 09/2005	405
101.	•አንድ ውል በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ ለማከናወን ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ፣	90793	ግሎባል ኢንሹራንስ	ታህሳስ	410

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	•የመድን ዋስትና ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ ከትራንስፖርት ጋር በተገናኘ በወጡ ህጐች ከተፈቀደው የመጫን አቅም በላይ ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ መድን ሰጪው የዋስትናውን ሽፋን ገንዘብ ለመድን ገቢው የመክፈል ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678(ለ)		እና እነ አቶ ፍጹም ላቀው (ሁለት ሰዎች)	04/2006	
		አፈፃፀም			
102.	•በውጭ አገር የተሰጠን ፍርድ በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ለማስፈፀም ስለሚቻልበት አግባብ፣ •በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድን በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ከማስፈፀም ጋር በተያያዘ በአፈፃፀም ሂደቱ ክርክር በተነሣ ግዜ የፍርድ አፈፃፀሙን በያዘው ፍ/ቤት ክርክሩ ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 458-460	78206	እነ ወ/ሮ ዩስራ አብዱልመኢን (ሶስት ሰዎች) እና አቶ አብዱልቀኒ አብዱልሙኢን	ሰኔ 20/2005	415
103.	በአንድ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ላይ ፍርድ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁ የፍርድ ባለገንዘቦች ያሉ እንደሆነ አፈፃፀሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 መሠረት ሊስተናገድ የሚገባ እንጂ በሌላ የፍ/ባለመብት ምክንያት በሌላ የአፈፃፀም መዝገብ ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቶ የአፈፃፀም ጥያቄው ካልቀረበ በስተቀር ሊቀጥል አይችልም ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣ አፈፃፀሙ በሚካሄድበት ወቅት በንብረቱ ላይ የመያዣ ውልን መነሻ በማድረግ የቀዳሚነት መብት አለን የሚሉ ወገኖች ያሉ እንደሆነም ጥያቄው በቀረበ ጊዜ እንደየአግባብነቱ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ስለመሆኑ፣ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በንብረቱ ባለቤት ላይ የገንዘብ ክፍያ ፍርድ አሰጥተው እና ገንዘቡም እንዲከፈላቸው ጥያቄ ያቀረቡ የፍርድ	88867	ሪዬስ ኢንጂነሪንግ አክሲዮን ማህበር እና የአክሱም ኮንስትራክሽን ባለቤት አቶ ጌታሁን ሁሴን	ታህሳስ 28/2006	423

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ባለገንዘቦችን አስቀርቦ ጥያቄያቸውን በመመርመር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አኳያ አገናዝቦ በመመልከት አፈፃፀሙ ሊመራ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403, 378				
104.	ለፍርድ አፈፃፀም ከተያዘ የሀራጅ ጨረታ ሽያጭ ጋር በተገናኘ ለሁለተኛ ጊዜ በወጣው ጨረታ የተያዘው ንብረት ሊሸጥ የሚገባው ባለሙያ ካቀረበው የንብረቱ ግምት ዋጋ በላይ በተገኘ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች ብቻ ሣይሆን የባለሙያው ግምት ሳይጠበቅ በሁለተኛው ጨረታ ከተወዳዳሪዎች መካከል ከፍተኛ የሆነውን ዋጋ ላቀረበው ተጫራች ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 428(1)	89088	የኢትዩጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ሞላ እርቂ	ታህሳስ 17/2006	426
105.	አንድን የተሰጠ ፍርድ ከማስፈፀም ጋር በተገናኘ የአፈፃፀም ስልጣን መሰረቱ ፍርዱን መስጠት ወይም ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም የሚያስችል ውክልና ማግኘት እንጂ የፍርድ ባለዕዳውን ወይም ባለመብቱ የሚኖርበት ክልል (ከተማ) ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378	85764	እነ አቶ ኃ/ሚካኤል ታደሰ (አራት ሰዎች) እና አቶ ተስፉ ታደሰ	መስከረም 21/2006	429
ልዩ ልዩ					
106.	የመሬት አስተዳዳር ጽ/ቤት ቀድሞ የተሰጠን የቤትና ቦታ ካርታና ፕላን ጠፍቷል በሚል ሲጠየቅ በምትኩ ሌላ ሊሠጥ የሚገባው በ3ኛ ወገኖች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለማስወገድ በቅድሚያ ጠያቂው በቂ ዋስትና እንዲሰጥ በማድረግ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1197(2)	81023	አቶ ገላና አልጅራ እና እነ አቶ ገዛኸኝ ፋይስ (ሶስት ሰዎች)	ግንቦት 5/2005	433

https://t.me/ethiopianlegalbrief

107.	• አንድ የመንግስት ሠራተኛ መ/ቤቱን በመወከል ተቋሙ ከ3ኛ ወገን ጋር ካለው አለመግባባት ጋር በተገናኘ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት በዳኝነት ተሰይሞ ለጉባኤው የሚከፈለውን አበል ክፍያ መወሰኑ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሟል ሊያስብለው የሚችል ስላለመሆኑ፣ • በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ዳኝነት የተሰየመ ዳኛ በህግ ስላለበት ኃላፊነት፣ • የግልግል ዳኛ ሆኖ የተሰየመ ሰው በግልግል ዳኝነቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ በወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 351(2)(መ), 317, 318(መ) የወንጀል ህግ አንቀጽ 399 የአ.አ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አዋጅ ቁ. 6/2000 አንቀጽ 31	80301	አቶ አንተነህ ሲሳይ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ	ሚያዝያ 24/2005	440
108.	የመንግስት የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታነት፣ ወይም ወደ አክስዮን ማህበር፣ በሚለወጥበት ወይም ወደ ቀድሞ ባለሀብቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት የማይተላለፉ ሒሣቦችን ለመሰብሰብ ዕዳዎችን ለመረከብና የፍርድ ቤት ጉዳዮችን ለመከታተል ስልጣን የተሰጠው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 208/92 አንቀጽ 5፣6	88060	የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ አ/ማህበር እና አቶ ምስጋናው ጥሩነህ	መስከረም 23/2006	444
109.	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የማስተዳደር ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በህግ የተሰጠውን የማስተዳደር ስልጣን መሠረት በማድረግ በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬት በተመለከተ የከተማዋን መሪ ፕላን እንዲሁም የከተማውን ማህበረሰብ ፀጥታና ደህንነት ታሣቢ በማድረግ በከተማው የሚገኝ ቦታ (መሬት) ለምን ለምን አገልግሎት መዋል እንዳለበት የመወሰን ስልጣንና	88959	የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ጽ/ቤት እና ደብረ አማን ተክለኃማኖት ቤተክርስቲያን	ህዳር 17/2006	447

https://t.me/ethiopianlegalbrief

	ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑና ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደ የሁኔት ተግባር ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 11(2)(ለ)(ሰ), 38				
110.	በአቃብያነ ህግ ሙያ የተሰማሩ ሠዎች ላይ ከዲሲፒሊን ጉዳዬች ጋር በተያያዘ ክስ በቀረበ ጊዜ ጉዳዩ በተዋረድ በተቋቋሙትና ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ታይቶ ሊወሰን ስለሚችልበት አግባብ፣ የአቃቤ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁ. 44/1991 አንቀጽ 78, 79, 82(1)(2), 83(1)(3), 84(ሀ), 85, 86(ሀ) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 25, 37	92546	አቶ አብዱራዛቅ ኢብራሒም እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ህግ	ታህሳስ 18/2006	450
111.	አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በህጉ ከተመለከው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበሰብ ሊፈቅድ የማይችል ስለመሆኑ፡- አዋጅ ቁ. 621/2001 አንቀጽ2/2/፣3/4/፣14/5/፣14/2/፣6፣90፣111/2/፣112፣108፣110 ደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 18/3/፣10/2/፣36	75877	የኢትዮጲያ የህግ ባለሙያ ሴቶችማህበር እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	መስከረም 23/2005	454

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች



ቅጽ-17

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ-17

የኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲ ሪፐፐሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ጥቅምት 13, 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

የሰበር ውሳኔዎችን ለሕዝብ ለማዳረስ እየተደረገ ያለው ጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች እየታዩበት ነው። ከሰበር ውሳኔዎች አስገዳጅነት አንጻር ውሳኔዎቹ እንደተሰጡ ወዲያውኑ ለሥር ፍ/ቤቶች ሆነ ለሌሎች አካላት መድረስ ይኖርባቸዋል። አትሞ ማሰራጨት የቱንም ያህል ለማፋጠን ቢሞክር ጊዜ መውሰዱ አይቀርም ።በአሁኑ ጊዜ የኢንተርኔት አገልግሎት እስከ ወረዳ ድረስም ስለደረሰ ውሳኔዎቹ በተሰጡ ጥቂት ቀናት ውስጥ በፍ/ቤታችን ድረ ገጽ በመጫን ተደራሽ ለማድረግ እየሰራን ነው፤የዚህን እትም ውሳኔዎችና የበፊቶቹንም በድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል። እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ አገልግሎታችንን ለማሻሻል የሚረዱ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ ነን።

ተገኔ ጌታነህ

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2007 ዓ.ም. የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች

ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት					1
1.	ቤትና ይዞታን በሚመለከት በሚደረግ ክርክር አንድ ጣልቃ ገብ አመልካች ክርክር በሚደረግበትቤትና ይዞታ ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር መብት አለኝ በማለት መብቱን የሚያሳዩ ሰነዶችን አቅርቦ እያለ የባለይዞታነት ወይም የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አላቀረብክም ተብሎ ከወዲሁ ጣልቃ ገብተህ ልትከራከር አትችልም ተብሎ አቤቱታውን ውድቅ ማድረግ አግባብነት የሌለው ሥለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41	90713	ወ/ሮ አሚና ሰይድ እና እነ ወ/ሮ ወለላ ንጋቱ -/ሁለት ሰዎች/	መስከረም 29 ቀን 2007	2
2.	ተከራካሪ ወገኖች ለፍ/ቤት የሒሳብ አጣሪ ይሾምልን የሚል አቤቱታ ሲያቀርቡ በሒሳብ አጣሪዎች ሪፖርት አለመስማማት ቢኖር እንኳ ጉዳዩ የንግድ ህጉንና የፍትሐብሔር ሥነ-ስርዓቱን መሠረት በማድረግ ውሣኔ በዛው በኩል እንደሚሠጥ በግልጽ ከተስማሙ ይህ ግልጽ ስምምነት ባለበት ሁኔታ የሒሳብ አጣሪዎች የስራ ክንውን ግድፈት አለበት በማለት ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት የሚያቀርቡበት ህጋዊ	93239	የአቶ አበበ ክብረት ሚስትና ወራሾች እና አቶ ነጋ ቦንገር (አስር ሰዎች)	ጥቅምት 25/2007	5

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277(1)(2) ፣የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3312				
3.	በህግና በሚመለከተው መንግስት አካል እውቅና የተቋቋሙ ማህበራት የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት፣የአባላታቸውን መብትና ጥቅም ለማስከበርፍ/ቤት፣ለግልግል ተቋም ወይም ለሌሎች የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት የዳኝነት ጥያቄ የማቅረብ መብት ያላቸው ስለመሆኑ፣ የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 454(1) የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 35 አዋጅ ቁጥር 62/2001 አንቀፅ 55፣110	100631	ሮፓክ ነዋሪዎች ማህበር እና ሮፓክ ኢ/ኃ/የ/የግ/ማህበር	ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም	9
4.	በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 74(2) መሰረት ፍ/ቤቱ የተዘጋን የይግባኝ አቤቱታን እንደገና ስለሚያይበት አግባብ፣	94511	እነ ወ/ሮ ብዙ ሰንበታ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ታደሰ ሰንበታ	30/01/2007 ዓ.ም.	13
5.	የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የፍትሐብሔር ሥነ- ስርዓት ህጉ በሚያዘው መሰረት ሥርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ ከሆነ ዳኝነት ሊሰጥበት የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 234(1)፣(2)	94713	እነ ህፃን ሰኢድ ዘውዴ(ሦስት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ጥሩ ሰው ሞሳ (ዘጠኝ ሰዎች)	መጋቢት 16 ቀን 2007	16

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
6.	አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት (ሰበር ሰሚ ችሎት)የሥር ፍ/ቤት ጉዳዮን አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ሁሉ አጣርቶ እንዲወስን ብሎ አንድን ጉዳይ ሲመልስ ስለማስረጃ አቀራረብ በህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ሁሉ ባላገናዘበ መልኩ ማስረጃ ይቅረብ ማለት ስላለመሆኑ፡- ለአንድ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መቅረብ ያለባቸው ለህጉ የተዘረጋውን ሥርዓት ጠብቀው ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑና ተገቢውን የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ሳይጠብቅ የሚቀርብ ማስረጃ ግን ዋጋ ሊሰጠው የማይገባና ውድቅ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137(3) እና 256	97217	አቶ ባካፋ አንለይ እና አቶ ቴዎድሮስ አንለይ	መጋቢት 16 ቀን 2007 ዓ.ም	21
7.	በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ መብት አለን ብለው ተቃውሞ የሚያቀርቡ ሦስች በንብረቱ ላይ ያላቸውን የቀዳሚነት መብት ወይም ባለይዞታነት ለማረጋገጥ በጽሁፍ ማስረጃ ብቻ ሳይወሠኑ ሌላ ማስረጃም ሊያቀርቡ የሚችሉ ስለመሆኑ፣ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.418/3/ እና የፍ/ህ/ቁ 1193/1//2/	97094	ወ/ሮ አስቴር አምባው እና እነ አቶ አበባው ክፍሌ/ሁለት ሰዎች/	ሕዳር 08/2009	28
8.	በሞተ ሰው ስም ቀደም ብሎ የተሰጠን ውክልና በመያዝ የሚቀርብ ክስ ፣የሚደረግ ክርክር እና የሚሰጥ ውሣኔ እንዳልቀረበ እና ውሣኔም እንዳልተሰጠ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣	95587	ወ/ሮ ሀዋ በክር እና እነአቶቶፊቅመሐመድ(ሁለትሰዎች)	ጥቅምት 28/2007	31

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2232(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 57				
9.	የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሆነ ለፍርድ ማስፈፀሚያ ተብሎ በጨረታ ከተሸጠ በኋላ በሐራጁ ላይ ጉድለት አለ፣የጨረታ ሽያጩ ይሰረዝ የሚል አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ሽያጩ ሊሰረዝ ይገባዋል? ወይስ አይገባውም? በሚለው ላይ መከራከር ያለባቸው የፍርድ ባለዕዳና ባለገንዘብ ብቻ ሳይሆኑ ንብረቱን በሐራጅ አሸንፎ የገዛው 3ኛ ወገንም ጭምር ስለመሆኑ፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 32፣39፣40፣79 እና 370(3)	97332	አቶ ከይምር በላይ እና እነ አንዱአለም አሻግሬ	መጋቢት 30 ቀን 2007ዓ.ም	34
10.	ሌሎች ሰዎች በሚከራከሩበት መዝገብ ለክርክሩ መነሻ ከሆነው ንብረት ውስጥ በአንደኛው ወገን ጠያቂነት የታገደን ንብረት ሌላ ሶስተኛ ወገን ለሌላ እዳ አፈፃፀም ንብረቱን ሥለምንፈልገው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 158 መሰረት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ይነሳልኝ ብሎ አቤቱታ አቅርቦ ዕግዱ ሊነሳ አይገባም ተብሎበሚሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ በሚጠየቅበት ወቅት ከስረ ነገር ውሳኔ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም ሊባልየማይቻል ስለመሆኑ፡- የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320(3)	101632	አቢሲኒያ ባንክ እና ወ/ሮ ዘይቱ ከማል	መጋቢት 4 ቀን 2007	38

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
11.	በፍርድ የተከለለከለ ሰው የፍቺ ጥያቄ ስለሚያቀርብበት አግባብ	103781	ወ/ሮ አስካለ አሸኔ እና አቶ ታምራት ተስፋዬ	መጋቢት 17/2007 ዓ.ም	41
አሠሪና ሠራተኛ					**43**
12.	በስራ ክርክር የተከራካሪ ወገኖች ማንነት የፍርድ ቤቶችን ስልጣን (የክልል ወይም የፌዴራል)ብሎ ለመወሰን እንደወሳኝ መለኪያ ሊወሰድ የማይገባ ስለመሆኑ፤ የአሰሪው እርምጃ ህገ ወጥነት የተረጋገጠ እንደሆነ የክፍያ መጠኑ ሊሰላ የሚገባው አዋጁ ባስቀመጠው ስሌትና በማስረጃ በተረጋገጠ የደመወዝ መጠን መሆን ያለበት ስለመሆኑ፤ አዋጅቁጥር377/1996አንቀፅ 35(1(ለ))፣39(1(ለ))፣40(1)(2)፣43(4(ሀ)፣68፣71	95638	ኢስት ሲሜንት አክሲዩን ማህበር እና አቶ ዘላለም ታደሰ	መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ/ም	44
13.	በሠራተኛው የሚጠየቅ የውዝፍ ደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በአሠሪው የይርጋ መቃወሚያ ካልቀረበበት በስተቀር ተከፋይ ስለመሆኑ።።-	101020	አቶ ዳዊት ገ/ማርያም እና አቶ ሣህለማርያም ደግፌ	መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም	52
14.	አንድ ባለሙያ በአሠሪው ቁጥጥር ሳይሆን በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሙያ አገልግሎት ለመስጠት ከአንድ አሠሪ ጋር ውል ሲኖረው ጉዳዩ የሚገዛው በአሠሪና ሠራተኛ ህግ ስላለመሆኑ፤	101396	አዲስ አጠቃላይ ሆስፒታል እና ዶ/ር ምስራቅ ጥላሁን	ታህሳስ 21/2007	55

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	-ከአንድ ባለሙያ ጋር የሙያ ግልጋሎት ውል ያለው አሠሪ ውሉን በማናቸውም ጊዜ ማፍረስ ሥለመቻሉ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀስ /1//2/ የፍ/ህ/ቁ. 2140፣2646/1/፣ 2638/1/				
15.	ከአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ጋር በተነሳ ማንኛውም የሠራተኛ ክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የዕዳ ጥያቄ ቅድሚያ የሚኖረው ለሠራተኛ እንጂ ለስራ መሪዎች ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 2(2)(ሐ) (3)፣167	101913	አቶ መላኩ ሙሉጌታ እና አቶ አበበ አቡራ	የካቲት 17 ቀን 2007ዓ.ም	59
16.	አንድ ተማሪ በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ ህገመንግስታዊ መብት ያለው ስለመሆኑ፡- አንድ አስተማሪ የሚያስተምራቸውን ተማሪዎች በአግባቡ የመቆጣጠርና የመከታተል ህጋዊ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑና ይህንን ግዴታውን ተላልፎ ተማሪን ቢደበድብ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል በቂ ምክንያት ስለመሆኑ፡ የኢ.ፌ.ዲ.ራ ህገ መንግስት በአንቀፅ 16 የፍ/ሕ/ቁ 2124 እና 2125 አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27(1)(ቀ) ፣አንቀፅ 14(2)(ሀ)	103209	አትላስ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ት/ቤትእና ወ/ሪት መስታወት ስመኝ	የካቲት 16 ቀን 2007ዓ.ም	62

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
17.	የዓመት ዕረፍት ክፍያ አስፈላጊው የገቢ ግብር ተቀንሶ ለሠራተኛው ሊከፈለውየሚገባ ስለመሆኑ፡-አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27(ሐ)፣36፣37 የገቢ ግብር አዋጅ 286/94 እና ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀፅ 3	101040	አቶ አየለ መንግሥቱ እና የኢትዮጲያ እህል ንግድ ድርጅት	መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም.	66
18.	አንድ አሠሪ ለሙከራ የቀጠረውን ሠራተኛ በቀጠረው በ46ኛው ቀን ለስራው ብቁ አይደለም ብሎ የስንብት ደብዳቤ ቢጽፍለት ድርጊቱ ህገ ወጥ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(2)፣(3)	101890	የኢትዮጵያ አየር መነግድ እና ወ/ት ፍፁም ሀይሉ	ጥቅምት 24/2007	69
19.	“ስለሠራተኛ ዕድገት አሰጣጥ ስርዓት” በሚል በአዋጁ የተገለፀው ሀረግ ሊተረጎም የሚገባው ከአንድ የሠራተኛ የስራ መደብ ወደ ሌላ የሠራተኛ የስራ መደብ የሚፈፀም የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት በሚል መልኩ ስለመሆኑ፣ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 142(1)(ሠ)	101795	የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት እና አቶ አድማሱ አበበ	መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም.	72
20.	የአንድ ድርጅት የበላይ ኃላፊ ለሠራተኞች ለጡረተኞች የክፍያ ጭማሪን በተመለከተ በስሩ ለሚገኙ እንደየገቢያቸው መጠን እያስወሠኑና እያስፀደቁ የጭማሪ ክፍያ እንዲያደረጉ ያስተላለፈው ውሣኔ በሙሉ በስር በሚገኙት ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ሥለመሆኑ፣	101579	እነ አቶ ገ/መድህን አስፋው እና ትንሳኤ ጉባኤ ማተሚያ ቤት	ሕዳር 24/2007	76

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
21.	የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የወሰነውን ጉዳይ በይግባኝ ሲያይ የህግ ስህተት መኖሩን እና አለመኖሩን ከማረጋገጥ ባለፈ የፍሬ ጉዳይ እና የማስረጃ ምዘናን በተመለከተ የማየት እና የማረም ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፣ አንድ አሠሪ የሠራተኛ ቅነሳ በሚል ምክንያት ሠራተኞችን ከሥራ ሲያሰናብት በአዋጁ የሠራተኛን ቅነሳ በተመለከተ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መሠረት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28(2)(ሐ) ፣29፣140	102512	እነ ብርሀኑ ቢኒ (ሰላሳ አራት ሰዎች) እና የአርባ ምንጭ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ	ታህሳስ 10/2007	81
22.	አንድ ሠራተኛ የስራ ግዴታውን በአግባቡ ባለመወጣት በአሰሪው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ ከሆነ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ሥለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 (1)(ሸ)፣ 12(2)(7)	104294	ሀግቤስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ በላይ ገ/ማሪያም	መጋቢት 29 ቀን 2007ዓ.ም	85
23.	ከስራ በቅነሳ ምክንያት ለሚሰናበት ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የሚከፈል ስለመሆኑ፡- አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 39(1)(ሐ)፣40(1)(3)፣28(2)(ሀ)(3)	105620	እነ አቶ ሀብቴ ብርሃኔ (ስድስት ሰዎች) እና አቶ መሉነህ ቡና ላኪ ትራንስፖርትና ትሪንቢት አገልግሎት	ሚያዚያ 13 ቀን 2007	88

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
24.	አንድን ሰው ሠራተኛ ነው ለማለት በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት መኖር፣ሠራተኛው አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑ፣ ሊሰጥ የሚገባውን አገልግሎት መቼ ሊያከናውን እንደሚገባና እንዴት ማከናወን እንደሚኖርበት አሰሪው የመቆጣጠር ስልጣን ያለው ስለመሆኑ መረጋገጥ ያለባቸው ስለመሆኑ፣ አንድን አደጋ በስራ ላይ የደረሰ ነው ለማለት ሠራተኛው ስራውን በማከናወን ላይ እያለ ወይም ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ውጪ በሆነ ምክንያት ወይም በአካሉ በማንኛውም ክፍል ተፈጥሯዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት የደረሰበት ጉዳት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 2.4፣58.96፣97፣107፣110	105555	እነ መፍትሃ ሙሜ (ሶስት ሰዎች) እና አቶ ዑስማን አሊ	መጋቢት 18 ቀን 2007ዓ.ም	91
25.	አንድ ሠራተኛ በህግ የተቀመጠው የጡረታ መዉጫ ዕድሜው ደርሶ በስራው ገበታ ላይ ቢቆይና በኋላ የስራ ውሉ ቢቋረጥ በአሰሪው ላይ የተለየ ግዴታ የሚጥል ስላለመሆኑና የማስጠንቀቂያ ጊዜ አልሰጠህም ተብሎ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ክፈል ተብሎ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 24(3) አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀፅ 17(1)	101736	ግዮንኢንዱስትሪያል ኮሜርሻልኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ አዲስ ዓለም	መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም	97
ውል					**100**
26.	አንድ ቤት የተከራየ ሠው የኪራይ ዘመኑ ሲያልቅ አከራዩ ኪራዮን	96858	ወ/ሮ አብቢልክሽ ገለታ	ህዳር 26/2007	101

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መጨመሩን ማስጠንቀቂያ ከሠጠውና ተከራዩም ዝም ብሎ ቤቱን መጠቀም ከቀጠለአዲሱን የኪራይ ተመን ተከራዩ እንደተቀበለው የሚቆጠር ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 1684፣ 2952/2/		እና ዶ/ር ትግስት ቦርጋ		
27.	-ከአስተዳደር ውሎች አለመፈፀም ጋር ተያይዞ የወለድ ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ በውሉ በተመለከተው መሠረት ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ለተዋዋዩ ስለ ገንዘቡ አከፋፈል የሚያስፈልገውን የማረጋገጥ ሥራ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ወይም የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ የሚፈለግበትን ገንዘብ የማረጋገጥ ሥራ በተፈፀመ በ3 ወር ውስጥ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ስለመሆኑ፣ -ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም እንኳን ከአስተዳደር መስሪያ ቤት ጋር የተዋዋለው ሰው መስሪያ ቤቱ ሳይከፍል ለቆየበት ገንዘብ ወለድ ወይም ኪሣራ ለመጠየቅ የሚችለው ሳይከፈል የቆየበት ጊዜ ከ6 ወር በላይ ሲሆን ወይም ውሉን ያደረገው የአስተዳደር መስሪያ ቤት ተዋዋዩን ለመጉዳት ብሎ ያደረገው ወይም ከባድ በሆነ ቸልተኝነትና ወይም ጥፋት ያደረገ ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 3196፣3197	95797	ደበበ ደረሠ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭእና የፌንታሌ ወረዳ ውሃ መአድን ኢነርጂ ጽ/ቤት	ጥር 20 ቀን 2007 ዓ.ም	104

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
28.	አንድ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆነ ሰው ከመንግስት የተከራየውን ቤት ለሌላ ሰው አከራይቶ መጠቀምየሚችለው በመመሪያው የተመለከቱት ምክንያቶች ተጣምረው የተገኙ እንደሆነ ስለመሆኑ፡- መመሪያ ቁጥር 3/2004 አንቀጽ 6 መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 12	103704		ጥር 20/2007	107
29.	የባህር ላይ የእቃ ማጓጓዝ ውልን በተመለከተ የዕቃው ርክክብ ከተፈፀመበት ወይም የማስረከቡ ጉዳይ ሳይፈፀም ቀርቶ እንደሆነ እቃውን ማስረከብ ከሚገባበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ውስጥ ክስካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ፡- የባህር ህግ ቁጥር 203፤180፤162	98358	አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጂስቲክ አገልግሎት	ጥር 5 ቀን 2007ዓ.ም	110
30.	አንድ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ ለገዥ የሸጠ ሻጭ የገባው ውል እቃው ቢበላሽ ጥገና ለማድረግ እያለ ሆኖ እያለና ለድብቅ ጉድለቶች ኃላፊነት ሳይኖርበት ከውላቸው ውጭ እና ከህግ ውጭ እቃው ስላልሰራ እቃውን እንዲቀይር ወይም ገንዘቡን እንዲመልስ ሊደረግ የማይችል ስለመሆኑ፡- የፍ/ህ/ቁ 1731፤2266፤2288-2293፤2300	95072	ግሎርየስ ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና ሜሮን ጌትነት	ጥር 7 ቀን 2007 ዓ.ም	114

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
31.	-የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ ውልን በተመለከተ እዳው እንዲከፈል በተወሠነ ጊዜ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው የመያዣ መብት ያገኝበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይወስዳል በሚል የተደረገ ውል ፈራሽ ስለመሆኑ፣ -የብድር ውልን በተመለከተ ተዋዋዬች ወለዱ በወር እንዲታሠብ የሚዋዋሉት ውል ፈራሽ ስለመሆኑና በህጉ መሠረት ወለድ ሊታሠብ የሚችለው በዓመት ሥለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 3060/1/፣ 1711 እና 2479/1/	102711	ፈንታዮ ፍስሀ እና አቶ ደጀኔ ማርየ	ሕዳር 10/2007 ዓ.ም	117
32.	በግልፅ የሰፈረ የውል ቃል ባይኖርም ስጦታ ሰጪው በድህነት ላይ ወድቆ ሲገኝ ስጦታ ተቀባይ የመጦር ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣ ሥጦታ ተቀባይ ይህን ግዴታውን ካልፈፀመ ደግሞ ስጦታ ሰጪ ውሉ እንዲሻር መጠየቅ ስለመቻሉ፣ የፍ/ሕ/ቁ. 2458(1)፣ 2464(1)	107990	እማሆይ ወ/ገብርኤል እና ደረጀ ደስአለኝ	መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ.ም	121
ወንጀል					**124**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
33.	አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ወንጀል የሰራው አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ሲሆንና ቅጣቱ በሚወሰንበት ጊዜ ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን ማንዋል ይልቅ አዲሱ የቅጣት አወሳሰን ማንዋል(መመሪያ) ቅጣቱን የሚያቀልለት ሲሆን ተፈፃሚ መደረግ የሚገባው አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ስለመሆኑ፡- የወ/ሕ/ቁ. አንቀፅ 88(4)፣6	95440	አቶ ሰሚር ኢብራሂም ሂቡ እና የፌዴራል ዐ/ሕግ	ሰኔ 4 ቀን 2006 ዓ.ም.	125
34.	በማስረጃ በተረጋገጠ የወንጀል ፍሬ ነገር መፈፀሙ የተረጋገጠው የወንጀል ተጠያቂነትን በሚያስከትለው የህግ ድንጋጌ መሰረት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠጠት ያለበት ስለመሆኑ፡- የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 አንቀጽ 98(2)(ሀ)	96607	እነ አቶ ኤርሚያስ ካጢሶ (ሁለት ሰዎች)እና የከምባታ ጠምባሮ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ዋና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት	መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም.	129

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
35.	በወንጀል ክስ ክርክር የክስ ይሻሻል ጥያቄ ቀርቦ ጥያቄው ውድቅ ከተደረገ ጥያቄው ውድቅ የተደረገበት ትእዛዝ በድጋሚ ለክርክር ሊቀርብ የሚችልበት ዕድል የሌለ በመሆኑና ትእዛዙ የመጨረሻ እንጂ ጊዜያዊ አገልግሎት እንዳለው ተቆጥሮ በስረ ነገሩ ከሚሰጠው ፍርድ ጋር ተጠቃሎ ይግባኝ የሚባልበት ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑና በተሠጠው ትእዛዝ ላይ በስረ ነገሩ ከሚሰጠው ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ስለመሆኑ፡- የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 118፣184፣	93234	የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ እና አቶ ኃይለኪሮስ ወልደብርሃን ካሕሳይ	መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም.	134
36.	የወንጀል አድራጊው በአንድ ድርጊት ከአንድ ጊዜ በላይ አደራርቦ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የአካባቢ ሁኔታዎችን ሲመረምር በተለይም ወንጀለኛው አስቦና አቅዶ ህግ መጣሱን ወይም ግልጽ የሆነ መጥፎፀባይ ማሣየቱን ባመነ ጊዜ ቅጣቱን አክብዶ መወሠን ሥለመቻሉ፣ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የድምር ውጤት የቅጣት አወሣሠን መርህን ተፈጻሚ ማድረግ ያለባቸው ሥለመሆኑ፣ በተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሠነው ቅጣት ድምር ውጤት ከሃያ አምስት አመት ጽኑ እስራት ሊበልጥ የማይችል ሥለመሆኑ፣ የወ/ህ/ቁ. አንቀጽ 184/1/ለ/፣ 108/1/፣ 187/1/፣65	92296	እነ አንዷለም አራጌ/ሶሰት ሰዎች/ እና የፌዴራል ዐ/ህግ	ሕዳር 22/2007	137

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
37.	ከአንድ በላይ ሰዎች በወንጀል ተሳታፊ በሚሆኑበት ጊዜ ለወንጀሉ ድርጊት ኃላፊ ናቸው የተባሉት ወንጀለኞች የእያንዳንዳቸውን ተሳትፎ ህጉ ባስቀመጠው የማስረጃ መለኪያ መሰረት መለየት ያለበት ስለመሆኑ፦ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 141፣ የወ/ህ/ቁ. 40	97203	እነ አቶ ታምራት ደምሴ (ሦስት ሰዎች) እና የቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ሕግ	መስከረም 30 ቀን 2007	147
38.	ከዳኝነት ስራ ጋር ያልተያያዙ እና የአስተዳደር ስራ ሲያከናውኑ የሚፈፀሙ የወንጀል ጥፋቶች ዳኛውን ከተጠያቂነት የማያስቀሩ ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/ቁ. 402(1) እና (2) በትግራይ ክልል ዳኞች እና ሬጂስትራሮችን ለማስተዳደር ተሻሽሎ የወጣው ደንብ ቁጥር 1/2003	98283	አቶ ሐጐስ ገ/ብሄር መኮንን እና የትግራይ ክልል የስነ/ፀ/መ/ኮ	መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም	155
39.	የወንጀል ህጉ አንቀጽ 420 ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው የመወሰን ስልጣን በሌላቸው እና የሙያ አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸው በመንግስት ስራ ተመድበው ባሉበት ሁኔታ በመንግስት ንብረት ላይ የሥራ ኃላፊነት ወይም ግዴታቸውን ባልተወጡት ላይ ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/አንቀጽ 420/1/	92826	የደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና ወ/ሮ ፀሐይ ነጫሎ	ጥር 05/2007	158

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
40.	የማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርሆችን መሰረት ያላደረገ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለመሆኑ	89676	የፌደራል ዓቃቤ ህግ እና አቶ ሳሙኤል ፈቃዱ	ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም	162
41.	አንድ በወንጀል ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰው ቅጣት በሚያከብድ የህግ ድንጋጌ ስለተከሰሰኩ ክሱ ይሻሻልልኝ በማለት ተቃውሞ ካቀረበ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ፍ/ቤቱ የሚወስነው እንጂ ከጅምሩ ማስረጃ ሳይሰማ አቋም የሚወሰድበት እና ክሱ ይሻሻል ተብሎ የሚታዘዝ ስላለመሆኑ፣	103452	አቶ ጥዑም ተኪ ገብራይ እና የፌዴራል ሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ሕግ	ጥር 19/2007	170
42.	በወንጀል የቅጣት አወሳሰን ጊዜ የቅጣት መነሻ ለማግኘት ቀላል የእስራት ቅጣትን ወደ ፅኑ እስራት መለወጥ የሚያሥፈልገው ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለው በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወንጀሎች ሲሆንና አንዱ ወንጀል በቀላል እስራት ሌላው ደግሞ በፅኑ እስራት የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ፡- የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 የወ/ሕ/አንቀፅ 184(1(ለ))	103448	አቶ አገኘሁ አስፋው እና የፌደራል ዓቃቤ ህግ	የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም	174

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
43.	በአንድ ተከሳሽ ላይ ከቀረቡት ከአንድ በላይ ከሆኑት ክሶች መካከል ከፊሎች የሚወድቁት በፌዴራል ፍ/ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር ከፊሎቹ ደግሞ በክልል ፍርድ ቤት የስረ- ነገር ስልጣን ስር በሆነ ጊዜናበወንጀል ህግ ሥነ-ስርዓቱ የክስ አቀራረብ መርህ መሰረት በቀጥታም ሆነ በውክልና በፌደራል ፍ/ቤት ቀርበው እንዲታዩ ከተደረገ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የይግባኝ እና የሰበር ሥርዓታቸው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲቀርቡ እንደተደረገው ሁሉየፌደራል ፍ/ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ሥርዓት ተከትለውና ተጠቃለው መታየትያለባቸው ስለመሆኑ።- ወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 109(3)፣116(2) አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 4(4)፣15(1)	99883	አቶ ገ/ስላሴ ገብሩ እና የትግራይ ብ/ክ/መንግስት ፍትህ ቢሮ	ጥር 19/2007	178
44.	አንድ ወንጀል ከመስራት ሃሳብ የሚመነጨ የተለያዩ ድርጊቶች አንድ ወንጀል ከመስራት ሃሳብ የሚመነጨ ናቸው በማለት ተጠቃለው እንደ አንድ ወንጀል እንዲተገበሩ ማድረግ የህጉን አግባብ የተከተለ ስላለመሆኑ፡- በፅኑ እስራትና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው ሲገኙ የቀላል እስራት ወደ ፅኑ እስራት እንደሚለወጥ፣ስሌቱም የሁለት ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ፅኑ እስራት የሚቆጠር ስለመሆኑ፡- የወ/ሕ/ቁ/ 184 (1)(ለ)	104715	እንደሻው ይልማ ዳዲ እና የፌደራል አቃቤ ህግ	መጋቢት 02 ቀን 2007ዓ.ም	188

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
45.	አንድ የትራፊክ ባለሙያ የሚሰጠው ሙያዊ አስተያየት የማስረጃ ዋጋ የማይሰጠው አስተያየቱ ተገቢውን የሙያ ደንብ ተከትሎ ያልተሰጠና ያልቀረበ፣በጊዜውና በቦታው ከነበሩት የአይን ምስክሮች ቃል ጋር ተነፃፅሮ ሲታይ በመሰረታዊ ነጥቦች ላይ ልዩነት ያለበት መሆኑ ሲረጋገጥ እንጂ በጭፍጫፊ ነጥቦች ላይ ልዩነት ተከስቷል ተብሎ ሊሆን እንደማይገባ፣ የልዩ አዋቂዎች ምስክሮች ቃላቸውን ገለልተኛ ሆነው መስጠት እንደ አለባቸውና ቃላቸው ያለበቂ ምክንያት ልዩ አዋቂ ያልሆኑ ሰዎች በሚሰጡት የምስክሮች ቃል ውድቅ መሆን የሌለበት መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ህግ ደንቦች የሚያስገነዝቡ ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141፣142፣194 የወንጀል ህግ ቁጥር 24፣59፣239(2)፣57፣543(2)	92141	የደ/ብ/ብ/ህ/ክልል ዓቃቤ ህግ እና አቶ አለማየሁ አስፋው	መስከረም 30 ቀን 2007ዓ.ም	191
46.	በወንጀል የተከሰሰ ሰው ጉዳዩን በሌለበት ለማየት ፍ/ቤቱ በመጀመሪያ ለተከሣሹ ህጉ ያስቀመጠውን ጥብቅ መስፈርት በተከተለ መልኩ በአግባቡ ጥሪ ሊያደርግለት የሚገባ ስለመሆኑ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 161(1)(2) እና 162	93577	አቶ ዘውዴ ተስፋዬ ስመኝ እና የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ	ህዳር 22/2007	198

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
47.	አንድ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በምርመራ ሒደትም ሆነ ክሱን ለሚሠማው ፍ/ቤት የሚሠጠው የእምነት ቃል ውጤት በራሱ በቃል ሠጪው ላይ ተወስኖ የሚቀር ከመሆኑ ውጪ ወንጀሉን አልፈፀምኩም ብሎ በሚከራከር ሌላ ተከሣሽ ላይ ህጋዊ ውጤት ሊያስከትል የማይችል ሥለመሆኑ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 27፣35 እና 134	96310	አቶ ጉደና ለማ ገዛኸኝ እና የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል መንግስት የስ/ፀረ-ሙስና ኮሚሽን	ህዳር 26/2007	203
48.	ከስር ተከሳሾች መካከል ፍ/ቤት የሠጠው ውሣኔ ለአንዱየሚጠቅም በሆነ ጊዜና ይግባኝ ባዩ ጋር ተከሠውጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ሠዎች ይግባኝ ቢያቀርቡ ኖሮ በይግባኝ ሠሚው ፍቤት ውሣኔ ሊጠቅሙ ይችሉ የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ይግባኝ ሠሚዉ ፍ/ቤት የሠጠው ውሣኔ ይግባኝ ላላቀረቡት ተከሳሾች ጭምር ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባ ሥለመሆኑ፣ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 196/1/ /ሀ/ /ለ/	96378	ሀቡብ ጀማል እና የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ዐ/ህግ	ህዳር 25/2007	209
49.	የRTD ችሎት መከላከያ የማቅረብ መብትን የማያስነፍግ ስለመሆኑ	100712	አቶ ሽብሩ ጌቱ ሴንጫ እና የፌዴራል አቃቤ ሕግ	መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ/ም	213

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ጉምሩክ/ታክስ/					216
50.	በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ የተባለ ሠው በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዝለት ያቀረበውን ምክንያት በማስረጃ ማስደገፍ እንዲችል በቂ ጊዜ ባልተሠጠበት ሁኔታ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በሚል የማቅለያ ምክንያቱን ውድቅ በማድረግ የሚሠጥ የቅጣት ውሣኔ በወንጀል ህጉ እና በቅጣት አወሳሠን መመሪያው ሥለ ቅጣት አወሣሠን የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ስላለመሆኑ፣ የወ/መ/ሥ/ሥርዓት 149/3//4/	96168	አቶ አርአያ ኪዳኔ እና የኢትዮጵያገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን	ህዳር 9/2007	217
51.	የህግ ሰውነት ያለው የንግድ ድርጅት በህግ በግልፅ በተደነገገ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት ፣በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሊቀጣ የሚችል መሆኑ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ህጉ በወንጀል የሚጠየቁ እንደሆነ በልዩ ሁኔታና በግልፅ ባልደነገገባቸው ወንጀሎች የወንጀል ተጠያቂነት እንደማይኖርባቸው በወንጀል ህጉ የተደነገገ ስለመሆኑ፡- ህጋዊ ህልውና ያለው ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በኃላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት አለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት በአነሳሽነትና በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ መሆኑ በወንጀል ህጉ	100079	አቶ እቁባይ በረሃ ገ/እግዚአብሄር እና የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ዓ/ህግ	መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ/ም	221

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በግልፅ የተደነገገ መርህ ስለመሆኑ።- አንድ የንግድ ድርጅት የወንጀል ተግባር ከፈፀመና ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ከተረጋገጠ ለወንጀሉ አድራጎት ኃላፊ የሚሆኑት ሠራተኞችና ኃላፊዎች በወንጀል ከመጠየቅ ነፃ የማይሆኑ ሥለመሆኑ፡- የወንጀል ህግ አንቀፅ 34				
ከውል ውጪ ኃላፊነት					**231**
52.	ሁለት የሞተር ተሽከርካሪዎች ሲጋጩ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየራሱ አንዱ ከአንዱ ላይ ጉዳት እንዳደረሱ የሚቆጠረውና የእያንዳንዱ መኪና ባለሀብት ለአደጋው ኃላፊ የሚሆነው አደጋው የደረሠው ከአንደኛው መኪና አሽከርካሪ ስህተት መሆኑ በማስረጃ ያልተረጋገጠ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፡- *የፍ/ሕ/ቁ 2084*	95267	ናይል ኢንሹራንስ እነ ካሳሁን ወንድሙ (ሶስት ሰዎች)	ጥቅምት 28/2007	232
53.	የአንድ ግንባታ ባለቤት ግንባታውን ለሚያከናውነው የስራ ተቋራጭ ግንባታው ሲከናወን ለሚደርሱ ከውል ውጪ ኃላፊነቶች ወይም በህጉ የተጣለበትን ፍትሐ ብሄራዊ ግዴታዎች ለስራ ተቋራጩ በማስተላለፍ የሚያደርገው ስምምነት በህግ ጥበቃ የሚደረግለት ስለመሆኑ፡- የፍ/ሕ/ቁ.2027(1)፣2130፣2132(1)፣2131(1)፣2035(1)፣2141	93772	አቶ ሁሴን አምዴ እና እነ ኢትዮ ቴሌኮም (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 30 ቀን 2007ዓ.ም	235

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍ/ሕ/ቁ. 1675፣1716፣1731 አዋጅ ቁጥር 464/97 አንቀፅ 3(3)				
54.	አንድ ኢንሹራንስ ኩባንያ በውል የመነጨውን ግዴታውን በወቅቱባለመወጣቱ ለተከሰተው ተጨማሪ ወጪ ተጠያቂ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ የን/ሕ/ቁ 665	95751	ወ/ሮ እመቤት መኮንን እና እነ ወ/ሮ መሰረት አስናቀ (ሁለት ሰዎች)	መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም.	241
55.	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ያልተወረሰ ቤትን በህገወጥ መንገድ በመያዝ የተጠቀመበት ከሆነ የኪራይ ገንዘብና ያለአግባብ የበለፀገበትን ያህል ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ፡- ያለአግባብ በመንግስት ተይዞ ለቆየ ቤት የታጣ ጥቅም አይከፈልም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፡- የፍ/ሕ/ቁ 2162 አዋጅ ቁጥር 193/92 አንቀፅ 7(3) አዋጅ ቁጥር 192/92 አንቀፅ 3	97683	አክበር አሊ ካምሩዲን ኩባንያ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	መጋቢት 18 ቀን 2007ዓ.ም	243

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ባንክ እና ኢንሹራንስ		**247**			
56.	አንድ የባንክ ደንበኛ ከባንኩ ጋር በገባው ውል መሰረት የቁጠባ ሂሳቡን በኤ.ቲ.ኤ.ም ካርድ ሲያንቀሳቅስ ቆይቶ ነገር ግን በአጋጣሚ ካርዱ ቢጠፋ እና ይዜንኑ በፅሁፍ ለባንኩ ካሳወቀ ከዚያ በኋላ በሂሳቡ ላይ ለሚደርስ ጉድለት ባንኩ ኃላፊ ስለመሆኑ፡-	96309	ዳሸን ባንክ አክስዮን ማህበር እና አቶ አበባየሁ ግርማ	መስከረም 27/2007 ዓ.ም	248
የዳኝነት ስልጣን					**251**
57.	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ጋብቻን በተመለከተ የባልነት ወይም የሚስትነት የምስክር ወረቀት ከመስጠት ባለፈ በማስረጃው ላይ ክርክር ከተነሳበት ወይም የጋብቻ መኖር አለመኖርን ለመወሠን የስረ ነገር ሥልጣን ያልተሠጣቸው ሥለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀፅ 2 አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41/1/ /ሸ/	75560	ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም እና አቶ ገብረስላሴ ኃይሌ	ሐምሌ 26/2004	252

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
58.	የዲፕሎማቲክ ግንኙነቶችን ስምምነት ልምድን ለማክበር ሲባል የውጭ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችና ኢትዮጲያዊያን ሠራተኞቻቸው የሚያደርጉት የቅጥር ግንኙነት ላይ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ተፈፃሚ የማይሆን ስለመሆኑ፡- የተባበሩት መንግስታት አካል የሆነ ድርጅት የተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ በተደነገገ ሥምምነት በማንኛውም የመንግስት ፍ/ቤቶች ተከሶ መቅረብ የሌለበት ሥለመሆኑ፡- አፈፃፀም በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ትርጉም እንዲኖረው በማድረግ ውጤት ያለውና በተገቢው መንገድ መፈፀም ያለበት መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም ለማንኛውም ጉዳዮች ይሰራል ተብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ የማይቻል ስለመሆኑ፡- አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 3/3(ሀ) የተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀፅ 105 ከተባበሩት መንግስት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ የተደነገገው ሥምምነት አንቀፅ 2/2/ እና 3 የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 212	98541	አቶ አለማየሁ አላና እና የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት/UNDP/	ህዳር 10 ቀን2007 ዓ.ም	258

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
59.	የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን ትምህርት ለመማር ከአሰሪያቸው ተቋም ጋር የሚያደርጉትን ውል አፈፃጸምና ከውሉ ጋር ተያያዥ ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ክርክሮችን ለማየት ስልጣኑ ያላቸው የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆናቸው፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 79(1) የፌድራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515//1919 አንቀፅ 75(5)(6)	99717	አቶ ሲሳይ ይማነ እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	ጥር 20 ቀን 2007ዓ.ም	262
60.	በክልል በተነሳ ግምት በሌለው የመንገድ ይከፈትልኝ ጥያቄ ላይ ከተከራካሪ ወገኖች መሃል አንደኛው በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ማህበር ከሆነ ጉዳዩ በፌዴራል የፍ/ቤቶች ስልጣን ስር፣በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስረ ነገርሥልጣን ስር የሚወድቅ ሲሆን የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ስልጣኑ ጉዳዩን የሚመለከት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 5(2) እና 5(6)፣ አንቀፅ 14 በኦሮሚያ ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ 64(3) እንዲሁም በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 27(4)	105962	እነ ቢ.ኤም.ጂ ኃ.የተ.የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች) እና ፕሮፌሰር በደግ በቀለ	የካቲት 19/2007ዓ.ም	266

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
61.	የአዲስ አበባ መስተዳደር አስፈፃሚ አካላት በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል ካሳ ይክፈሉ ተብሎ የሚቀርብ ክስን በተመለከተ የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያላቸውየፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው፡- አዋጅ ቁጥር 361/1995፣ አዋጅ ቁጥር 408/1996 አዋጅ ቁጥር 25/88	99375	አቶ አምባቸው አለሙ እና እነየካ/ክ/ከተማ/ወ/01 አስተዳደር(አራት ሰዎች)	መጋቢት 15 ቀን 2007ዓ.ም	270
62.	የክርክሩ አጠቃላይ ይዘት የዕቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄን መሰረት አድርጐ የቀረበ በንግድ ህጉየተመለከቱትን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎችን አተገባበር ለመመርመር የሚያስችልና ቼክ እንደተራ ማሰረጃነት ሆኖ በክርክር ወቅት በቀረበበት ጊዜ ጉዳዩ የፌደራል ነው ተብሎ የማይወሰድ ሥለመሆኑ፡- አዋጅ ቁጥር 25/1988	104511	እነ አቶ ዳኜ ሃይሉ(ሁለት ሰዎች) እና እነ አለም ሰገድ ሃብታሙ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም	273
ቤተሰብ					**276**
63.	ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ ስም የነበረን የግል ንብረት በጋብቻ ወቅት በንብረቱ ላይ መሰረታዊ መሻሻል ቢደረግበትና ይዜው መሻሻል የተደረገው የባለንብረቱ የግል ገንዘብ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ህጉ ንብረቱ የጋራ ነው የሚል ግምት የሚወስድ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀፅ 63(1)	94952	ወ/ሮ ዙሪያሽ ተገኝ እና ወ/ሮ የሺ ውድዬ	መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም.	277

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
64.	በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ መሠረት ባልና ሚስቱ በየግል ያገኟቸውን ንብረትም ሆነ ገንዘብ በግል ይዘው መቀጠል እንደሚችሉ ሲደነገግ ይህ የግል የተባለው ንብረት የግል ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው የግል ይባልልኝ ተብሎ በፍ/ቤት ሲፀድቅ ስለመሆኑ፣ የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ህግ ቁ.69/1995 አንቀፅ 7410፣አንቀፅ 74/2/	95680	ወ/ሮ የሺ ተሾመ እና አቶ መስፍን ኃይሉ	መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ/ም	281
65.	የባልና ሚስት ጋብቻ ፈርሶ የጋራ የሆነ ንብረት ክፍፍል በሚፈፀምበት ጊዜ በፍ/ሕጉ ላይ የተቀመጡት በቅድሚያ የመግዛት መብት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሌላቸው ስለመሆኑ የፍ/ሕ.ቁ. 1386፣1388፣1391፣1392፣1393፣(1)፣1397	88275	አቶ ኃይለሚካኤል ልኬ ሉሉ እና እነ አቶ መኮንን በለጠ /ሁለት ሰዎች/	ጥር 19/2007	284
66.	የDNA ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ መሰጠቱ አንደኛው ወገን አሉኝ የሚላቸውን የመከላከያ ማስረጃዎች የማሰማት መብት የማይከለክል ስለመሆኑ፣ የDNA ምርመራ እንዲረግ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለሚሠጥበት አግባብ፣	90121		መስከረም 28/2007 ዓ/ም	289
67.	ሚች በህይወት እያለ ከይዞታ ቦታው ላይ ለሌላ ሠው ቤት እንዲሠራፈቅዶ ቢሰጠው ሚች በሚሞትበት ጊዜ በሚች ፈቃድ ቤት የሠራው የቤቱ ባለቤት እንደሚሆንና ከሌላው ቦታ ጋር ሆኖ የውርስ ክፍል የሚሆን ስላለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 826/2/፣1179/1/	96628	እነ አሳምነው ከበደ /አምስት ሰዎች/ እና አቶ ዳንኤል ከበደ	ሕዳር 08/2007	293

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
68.	አንድ ተናዛዥ ኑዛዜውን መሻር ሲፈልግ ሀሳቡን በማያሻማ አኳኋን በመግለጽ ከሻረ ኑዛዜዎች ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ በሚያስፈልገው ፎርም አይነት ግልጽ አድርጐአልሻረውም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 898(1)፣ 899(1)	96364	እልፍነሽ ወርቁ እና ኤልሳቤጥ አስራት	ጥቅምት 10/2007	298
69.	አንድ የቀበሌ ቤትን ተከራይቶ የነበረ ሠው ከዚህ አለም በሞት ሲለይ ወራሾቹ ወይም ቤተሠቦቹ የተከራይነት መብቱ ይተላለፍልን ብለው በሚጠይቁበት ጊዜ ከሕግ አኳያ ዳኝነት የሚሠጥበት እንጂ በፍርድ ቤት የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም ብሎ ጥያቄውን አለመቀበል አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 የፍ/ህ/ቁ. 826/2/ እህ 2928	97948	ወ/ሪት ሔለን ተክሌ እና ወ/ሮ ዘይድ አብርሃ	ታህሳስ 21/2007	301
70.	በጋብቻ ጊዜ የተፈራ የባልና ሚስት የጋራ የሆነ የአክስዮን ድርሻ በፍቺ ጊዜ በአይነት ሊከፋፈል የሚችል ስለመሆኑ፣ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 91 እና 92	102652	ወ/ሮ ሃቢባ መካ እና እነ ደሊል ሁሴን(ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 16 ቀን 2007	304

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
71.	አንድ ሰው ከህግ ውጪ የገጠር እርሻ መሬት ለመውረስ የሚያስችል የወራሽነት ማስረጃ ስላወጣ ይሰረዝበት የሚል አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ፍ/ቤት ጭብጥ ይዞ ውሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ እንጂ የመሬት ክርክር ሲነሳ የሚታይ ነው ተብሎ ክሱን ውድቅ ማድረግ አግባብነት የሌለው ሥለመሆኑ፣ የአ/ብ/ክ/መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 እና ደንብ ቁጥር 51/99	108539	አቶ አበባው አጥናፍ እና እነ ወ/ሮ የካባ ግዛው (ሶስት‹ሰዎች)	መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም	307
ንብረት					**310**
72.	በገጠር የእርሻ መሬት ላይ በተሠጠ ፍርድ የፍርድ መቃወሚያ ሲቀርብ ፍርድ ተፈፅሚል ሊባል የሚችለው የፍርድ ባለመብቱ በይዞታው ላይ ህጋዊ ማረጋገጫ ሲያገኝ ስለመሆኑ፣	101079	የይልማና ዲንሳ ወረዳ አከባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፅ/ቤት እና አቶ ውበት ገ/መድህን	ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም	311

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
73.	በአንድ ተቋም ውስጥ ተቀጥሮ ለሚሰራ ሠራተኛ አሰሪው ተቋም ለሰራተኛው ለመኖሪያ የሚሆን ክፍል ከሰጠው እና ሰራተኛው በአሰሪው ተቋም ፍቃድ ተጨማሪ ግንባታ በራሱ ወጪ ከገነባ እና አሰሪው ሰራተኛው እንዲወጣ ካስገደደው አሰሪው ተቋም ሰራተኛው ለተጨማሪ ግንባታ ያወጣውን ወጪ መክፈል ያለበት ወይም ሰራተኛው ተጨማሪውን ግንባታ አፍርሶ የመውሰድ መብት ያለው ስለመሆኑ፡- የፍ/ሕ/ቁ. 1446፣1454፣1455	96495	የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና አቶ ኃይሌ ብሩ	የካቲት 5 ቀን 2007ዓ.ም	315
74.	ለክርክሩ መነሻ የሆነ ሽጉጥ (የጦር መሳሪያ) የንምራ ቁጥር አከራካሪ በሆነበት ወይም የመጀመሪያው ንምራ ቁጥር በሌላ ተተክቷል የሚል ክርክር በተነሳ ጊዜ በመሳሪያው ላይ ያለው ንምራ ቁጥር ኦሪጅናል ነው? ወይስ በሂደት የተተካ ቁጥር ነው? የሚለውን አግባብነት ባለው አካል ሞያዊ አስተያየት/expert opinion/ አጣርቶ መወሰን አስፈላጊ ስለመሆኑ፣	97132	አቶ መሃመድ ከማል እና የከሚሴ ወረዳ ሚሉሻ ፅ/ቤት	መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም	318
ንግድ					**321**
75.	ክሱ የቀረበው በአንድ ተለይቶ በታወቀ ጊዜ ወይም ቀን የተፈጠረ ክስተትን መሠረት በማድረግ ሳይሆን በተለያየ ጊዜ ተከስተዋል የተባሉ የተለያዩ ችግሮችን መሠረት አድርጐ ሲሆን የማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄ ወይም ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚባልበት ምክንያት	94278	አቶ ሐሠን መሀመድ እና ማጅ አግሮ ፎረስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል	ሕዳር 11/2007	322

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሥላለመኖሩ፣ የን/ሕ/ቁ 218(1)፣541(1) የፍ/ሕ/ቁ 1835፣1845		ማህበር		
76.	ከውጪ አገር በዶላር የተላከ የውጭ ምንዛሬ ለተላከለት አላማ አልዋለም በሚል ገንዘቡ እንዲመለስ ክርክር ሲነሳ ገንዘቡ ሊመለስ የሚገባውዶላር በተላከበት ጊዜ በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ በተሠጠው ተመን መሠረት ስለመሆኑ፣ የፍ/ሕ/ቁ 1705፣1749፣1750፣1771	95069	እነ ስፍሜት አግሮ ቢዝነስ ኃ/የተ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ኤልሳቤት ብረቱ	ሕዳር 23/2007	325
አፈፃፀም					**332**
77.	በፍርድ ባለዕዳው ሥም የሚታወቅ ቤት ቤቱ በህጋዊ መንገድ የተገነባና የፍርድ ባለዕዳው እስከሆነ ድረስ ካርታና ፕላን የሌለው መሆኑ እና ለሌላ ሶስተኛ ወገን ተሠጥቷል መባሉ ስጦታው ህጋዊ በሆነ መንገድ እስካልተከናወነ ድረስ ቤቱ ለፍርድ አፈፃፀም እንዳይውል ሊያደረግው የሚችል ስላለመሆኑ፣ የፍ/ሕ/ቁ 276፣277	90722	ወ/ሮ መዓዛ መዝገቡ እና አቶ መሠለ ገላው	ጥቅምት 11/2007	333
78.	በፍርድ ውሣኔ በተሰጠበት ጉዳይ አፈፃፀምን ለማስቀረት በፍርድ ባለመብት እና በፍርድ ባለ ዕዳ የሚደረግ የእርቅ ውል በፍርድ ቤት ቀርቦ ካልፀደቀ በቀር አፈፃፀምን ሊያስቀር የሚችል ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 276፣277	98263	ወ/ሮ እናናይቱ ኢሳ እና ወ/ሮ አሲና ሁሴን	ጥር 06/2007	336

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
79.	የፍርድ ባለመብት ፍርዱን እንዲፈፀምለት ሲጠይቅ የፍርድ ባለዕዳው የፍርድ ባለመብቱ ተነፃፃሪ የሆነ ግዴታውን እንዲወጣ ትዕዛዝ ይሠጥልኝ በማለት ጥያቄ ለማቅረብ የሚችለው በአንድ ፍርድ ቤት ውስጥ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የፍርድ ባለመብት መሆናቸው ተረጋግጦ ውሳኔ ተሰጥቶበት እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፡- አንድ የፍርድ ባለእዳ እንደ ፍርዱ እንዲፈጽም ሲጠየቅ ፍርድ ያላረፈበትን ቅድመ ሁኔታ በማቅረብ በአፈፃፀም ሊከራከር ሥላለመቻሉ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 398፣ 378	99743	ንብ ኢንሹራንስ እና ራዲካል ኢንጅነሪንግ	መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም	341
ልዩ ልዩ					**344**
80.	አንድ የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ ዕድሜው ከደረሠ በኋላ አሠሪው መ/ቤት ፈቃድና ከየትኛውም አካል ተቃውሞ ሣይቀርብ የጡረታ ጊዜው ከተራዘመ ለተራዘመበት ጊዜ የሠራበት ለጡረታ ሊያዝ የሚገባው ሥለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 714/2003፣ አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 85፣89	96833	የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና አሥፋው ደነቀ	ታህሳስ 8/2007	345
81.	በአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም ውስጥ አንድን ጉዳይ በግልግል እንዲያይ የተቀመጠ የግልግል ዳኛ ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ እንዲነሳ አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ይነሳ የተባለው ዳኛ ልነሳ	99679	የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና	ታህሳስ 24/2007	348

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አይገባም ብሎ ጥያቄውን ካነሳው ወገን ጋር ሊከራከር የማይገባው ሥለመሆኑና ልነሳ አይገባም እያለ በሚከራከርበት ሆኔታም ጉዳዩን ገለልተኛ ሆኖ ያየዋል ተብሎ ሥለማይገመት መነሳት ያለበት ሥለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 እና 10 የፍ/ህ/ቁ.3342/ 3340/2/ የግልግል ተቋሙ የተሻሻለ ደንብ አንቀጽ 13 እና 15		አቶ በየነ ወልደገብርኤል		
82.	አንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ላስተማራቸው ተማሪዎች ጊዜያዊ ዲፕሎማ ከሠጠ በኋላ ዋናው ዲፕሎማ ሳይሠጣቸው የማስተማር ፈቃዱ ቢነጠቅ እንኳ ፈቃዱን ተነጥቂያለሁ፣ ዋናውን ዲፕሎማ ልሰጥ አልችልም የማለት መብት የሌለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 650/2001፣ ደንብ ቁጥር 199/2003	99689	የአዲስ አበባ ዩንቲል ባይንስ ኮሌጅ እና እነ መንግስቱ ጋሞ (ሰባት ሰዎች)	ታህሳስ 24/2007	351
83.	አንድ የንግድ ድርጅት ሊከስር የዕዳ ክፍያን በተመለከተ የድርጅቱን ንብረቶች በመያዣነት ከያዛቸው ባንክ ይልቅ የከሰረው ድርጅት ሰራተኞች የቀዳሚነት መብት ያላቸው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 167 አዋጅ ቁጥር 97/1990 እንደተሻሻለ	102061	የከሰረው ሆላንድካር ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ዘመን ባንክ	የካቲት 6 ቀን 2007 ዓ.ም	354

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
84.	በአንድ መተዳደሪያ ደንብ በማህበር አባላትና በድርጅቱ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በመጀመሪያ በእርቅ መፈታት አለባቸው የሚል ድንጋጌ ሲኖር ይኸው ሥርዓት ሳይፈፀም ወደ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ አግባብነትየሌለው ስለመሆኑ ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚነሳ አለመግባባትን በተመለከተ ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና እንዲታይ ሊሰማሙ ሥለመቻላቸው፣ የፍ/ሕ/ቁ. 1731(1)፣1732፣1736፣1738	106286	ቦሮ ትራቪል የግንባታ ሥራዎች የተ.የግ.ማህበር እና አቶ ኤፍሬም ሽብሩ	መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም	358

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90713

መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ አሚና ሰይድ ጠበቃ ይርሳው ጌትነት ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1 ወ/ሮ ወለላ ንጋቱ - ጠበቃ ዘርፉ ካብትይመር ቀረቡ

2. የዲላ ከተማ ማዘጋጃ ቤት - ነ/ፈጅ ማደቦ ዋንጮ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሰረት ያቀረቡትን የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መመስረታቸውን፣ የክሳቸው ይዘትም ከሳሽ ለኢንቨስትመንት ዓላማ ለማዋል በጨረታ ተወዳድረው እና አሸንፈው የገዙትን 602 ካሬ ሜትር የቦታ ይዞታ ተከሳሽ የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር ሊያስረክባቸው ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን የሚገልጽ ሆኖ ይህንኑ ቦታ ነጻ አድርጎ እንዲያስረክባቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት መሆኑን፣ተከሳሹም ርክክቡ የዘገየው የአሁኗ አመልካች በፈጠሩት ችግር ምክንያት መሆኑን እና በክሱ መሰረት ቦታውን ለማስረከብ ፈቃደኛ መሆኑን ገልጾ መልስ መስጠቱን፣አመልካች የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ያቀረቡትም ጉዳዩ በዚህ ደረጃ ላይ እያለ መሆኑን፣ፍርድ ቤቱም የጣልቃ ገብነት ማመልከቻውን እና አባሪ ሰነዶችን ከመረመረ በኃላ አመልካች በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያስችላቸውን በቂ ምክንያት አላቀረቡም በማለት የጣልቃ ገብነት ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉን እና አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም ለክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በተጠሪዎች መካከል ክርክር የተነሳበት ንብረት በሚች ባለቤታቸው ሐጅ መሐመድ ዑመር ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ መሆኑን እና የአመልካች ሚስትነት እና የልጆች ወራሽነት በፍርድ የተረጋገጠ መሆኑን የሚያሳዩ የተለያዩ ሰነዶችን አመልካች ከአቤቱታቸውጋር አያይዘው አቅርበው እያለ በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያስችላቸውን በቂ ምክንያት አላቀረቡም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት ከፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 ድንጋጌ አንጻር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአንድ ክስ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በክርክር ላይ ባሉበት ጊዜ ማናቸውም ሶስተኛ ወገን በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሲሆን ከፍርድ ውሳኔ በፊት ጣልቃ ገብ ሆኖ ለመከራከር እንደሚችል እና የጣልቃ ገብነት ማመልከቻው በክሱ ውስጥ ያገባኛል የሚልበትን ምክንያት የሚዘረዝርና በተለይም የመብቱን ሁኔታ የሚገልጽ መሆን እንዳለበት፣እንዲሁም የጣልቃ ገብነት ጥያቄ አቅራቢው በጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚያስችል መብት ያለው መሆን አለመሆኑ በቅድሚያ ሊወሰን እንደሚገባው፣ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል መብት የለውም በተባለ ጊዜ መሰናበት እንደሚገባው እና መብት አለው በተባለ ጊዜ ግን የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ከተደረገ በኃላ ከጣልቃ ገቡ መብት አንፃር ጭምር አጠቃላይ ክርክሩ ተመርምሮ ተገቢ ነው የሚባል ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 (1)፣ (2) እና (3) ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከቤተሰቦቻቸውጋር የሚኖሩበት በሚች ባለቤታቸው ስም እንደሚታወቅ እና 189 ካሬ ሜትር ይዞታ እንዳለው የተገለጸው ቤት የሚገኘው 1ኛ ተጠሪ በጨረታ ከ2ኛ ተጠሪ ገዝቸዋለሁ በሚሉት 602 ካሬ ሜትር የቦታ ይዞታ ውስጥመሆኑ በተጠሪዎቹም ያልተካደ ጉዳይ ሲሆን የጣልቃ ገብነት ማመልከቻው የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበል የቀረው አመልካች ከግብር ደረሰኞች በስተቀር ባለይዞታ ወይም ባለቤት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ሰነድ አላቀረቡም፣ደረሰኞቹም የሚታወቁት በአመልካች ስም አይደለም፣ሰነዶቹ የሚያመለክቱት ክስ ያስነሳውን ይዞታ ስለመሆኑም የቀረበ ማረጋገጫ የለም በማለት መሆኑን የብይኑ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ይሁን እንጂ አመልካች ለጣልቃ ገብነት ማመልከቻው ምክንያት ያደረጉት ቤትና ይዞታ በግብር ደረሰኞች የሚታወቀው በሚች ባለቤት ስም ቢሆንም አመልካች ሚስትነታቸውን እና የልጆችን ወራሽነት በፍርድ ቤት ያረጋገጡ መሆኑ በተረጋገጠበት እና የባለይዞታነት ወይም የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ ያልቻለ ተከራካሪ ወገን ክርክር ባስነሳው ቤት እና ይዞታ ላይ አለኝ የሚለውን መብት የባለይዞታነት ወይም የቤት ባለቤትነት ማረጋጫ ሰነድ በማቅረብ ካልሆነ በስተቀር በሌላ ማስረጃ ማስረዳት የማይችል ስለመሆኑ ግልጽ የሆነ የሕግ ክልከላ በሌለበት ሁኔታ የጣልቃ ገብነት ጥያቄው የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካች በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያስችላቸውን በቂ ምክንያት አላቀረቡም በማለት የሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ብይን ከላይ ከተጠቀሰው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ አንጻር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ የአመልካች የጣልቃ ገብነት ጥያቄ መሰረት የሚያደርገው የካሳ እና የምትክ ቦታ መብትን ብቻ ሳይሆን የኢንቨስትመንት የቅድሚያ መብትን ጭምር ስለመሆኑ ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለ ሲሆን አመልካች በጣልቃ ገብነት ሊያቀርቡ የሚችሉትን ክርክር ይዘት እና አድማስ በተሟላ ሁኔታ መገንዘብ የሚቻለው ጥያቄአቸው ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ጉዳዩ እንዲገቡ ሲደረግ ነው፡፡

በሌላ በኩል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በጣልቃ ገብነት መከራከር የሚቻለው ከፍርድ ውሳኔ በፊት መሆኑ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (1) የተመለከተ ሲሆን ጉዳዩ የፍርድ ውሳኔ ካገኘ በኃላ በሆነ ጊዜ ግን በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባውና ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቴን ይነካል የሚል ሰው ተነክቶብኛል የሚለውን መብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስከበር የሚችለው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ መሰረት ነው፡፡በመሆኑም አመልካች የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ በተጠሪዎች መካከል ክርክሩ ቀጥሎ ውሳኔ ተሰጥቶበት ከሆነ የአመልካች አቤቱታ ሊስተናገድ የሚገባው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡
ሲጠቃለል የአመልካችን የጣልቃ ገብነት ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአመልካችን የጣልቃ ገብነት ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ በዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09114 በ05/03/2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 06769 በ05/06/2005 ዓ.ም. በውሳኔ እና በመዝገብ ቁጥር 58897 በ13/07/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 በተደነገገው መሰረት በጉዳዩ በጣልቃ ገብነት ለመከራከር የሚያስችል መብት ነበራቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች የጣልቃ ገብነት ማመልከቻ ያቀረቡበት ተጠሪዎች ከሳሽ እና ተከሳሽ በመሆን የሚከራከሩበት ጉዳይ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚደርስበት ቀን ውሳኔ ያላገኘ ከሆነ አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 ድንጋጌ መሰረት የተሟላ ክርክር እንዲያቀርቡ በማድረግ፤ጉዳዩ ውሳኔ አግኝቶ ከሆነ ደግሞ አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ በተዘረጋው ስርዓት መሰረትየመቃወም አቤቱታቸውን አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በማድረግ የሶስቱንም ተከራካሪ ወገኖች አጠቃላይ ክርክር መርምሮ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት ወስነናል፡፡
4. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፤እንዲያውቁት ደግሞ ለጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 93239

ጥቅምት 25 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተሽሊት ይመሰል

አመልካቾች ፡- የአቶ አበበ ክብረት ሚስትና ወራሾች እነ ወ/ሮ ብርሃኔ መኮንን 10 ሰዎች

ጠበቃ አቶ አምሳሉ ባየ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ነጋ ቦንገር ዶ/ር ሸዋረጋ አስራት ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በሥር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ በኮ/መ/ቁ 06187 በ 13/07/2005ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ነው፡፡አመልካቾች እና ተጠሪ የነበራቸውን ክርክር በስምምነት ለመጨረስ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.277 መሠረት በፍ/ቤት የተመዘገበ መሆኑ መዝገቡ መዘጋቱን በሥር ፍ/ቤት መዝገብ የተገለጸ ሲሆን በስምምነቱ መሠረት የተሾሙት የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት ፍ/ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ በአሁኑ አመልካቾች ግንቦት 09 ቀን 2004ዓ.ም አቤቱታ ቀርቧል፡፡

የሥር ፍርድ ቤቱም የግራቀኙ የስምምነት ይዘት አጠር ባለመልኩ ከጠቀሰ በኃላ የግራ ቀኙ ጥያቄ ወይም ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ ሂሣብ አጣሪ ይሾምልን የሚል እንደነበር፤የሂሳብ አጣሪዎች ከተመረጡ በኃላ ሂሳቡ በምን መንገድ ተሠራ ወደ ሚለው ፍሬ ጉዳይ በመግባት የሂሣብ ሪፖርቱ የሚመረመርበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ፤የፍ/ቤቱ ሥልጣን የሂሳብ አጣሪ ኮሚሽም የዘለለ አለመሆኑና ሥልጣኑ አጣሪ ከመሾም የዘለለ ነው የሚባልቢሆን እንኳ ግራቀኙ በስምምነታቸው መሠረት የሂሣብ አጣሪው ውሳኔ እንደሚቀበሉ በስምምነታቸው ተራ ቁጥር 4(3)መመልከቱን ፤የሂሳብ አጣሪ በፍ/ቤት ትዕዛዝ መነሻነት ከሂሳብ አጣሪነት ሊነሳ እንደሚችል ፤ይሁንና በተያዘው ጉዳይ ሂሣብ ከተጣራ በኃላ የሂሣብ አጣሪዎች ሪፖርት ይፅደቅ ወይም አይፅደቅ ወደ ሚል ክርክር ውስጥ መግባት ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚሰጡበት አግባብ አለመኖሩን በመጥቀስ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ በትዕዛዝ ክፍሉ ግራቀኙ በስምምነቱ መሠረት ያልፈፀመ ወገን ካለ የአፈፃፀም ጥያቄ ማቅረብ እንደሚቻል አስፍሯል፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በመቃወም ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል ፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም ግራቀኙ ያደረጉት ስምምነት ህግና ሞራል የማይቃረን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑ ተረጋግጦ የተመዘገበ እና በይግባኝ ያልተሻረ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካቾች ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው በማለት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች በሥር የመጀመሪያ እና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ተፈጽሟል ያሉትን ስሕተት በመዘርዘር የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታቸው መሠረታዊ ይዘት በሂሣብ አጣሪዎች ተፈጽሟል ያሏቸውን ግድፈቶች ከዘረዘሩ በኃላ በግራቀኙ የተደረገው እና በፍ/ቤት የተመዘገበው ስምምነት ይዘት የሂሳብ አጣሪዎችን ምርጫ ብቻ እንደሚመለከት የሁለቱም ወገኖች መብትም ሆነ ግዴታ የሚመለከት ጉዳይ በስምምነቱ ሰነድ አለመካተቱን ፣የሂሳብ አጣሪዎች የሚያቀርቡት ሪፖርትም የስምምነቱ አካል አለመሆኑን፤የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ አስቀድሞ በስምምነት አልቋል ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ ትክክል ባለመሆኑ እንዲሻር እና በሂሣብ አጣሪዎች የቀረበው ሪፖርት ፍ/ቤቱ አሻሽሎ እንዲያፀድቀው ጠይቋል፡፡ተጠሪ በበኩላቸው መልስ ሰጥተዋል፡፡ ዋና ፍሬ ነገሩ በአመልካቾች የቀረበው አቤቱታ የግራቀኙ ስምምነት አለማገናዘቡን ፣የሂሳብ አጣሪዎችም ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ ግዴታቸውን የተወጡ ስለመሆናቸው የግራቀኙ ስምምነት በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 3312 መሠረት ሊነካ የማይችል እና ይግባኝ አልባ ውሳኔ መሆኑ ተረጋግጦ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡ በአመልካቾች የቀረበው የመልስ መልስ አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል ፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግራቀኙ ጉዳያቸው በግልግል ስምምነት ለመጨረስ ይችሉ ዘንድ ሂሳብ አጣሪዎች በመሾም ስልጣን እና ተግባራቸውን በመወሰን ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረጋቸው ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ግራቀኙ ያቀረቡትን የእርቅ ስምምነት ህግና ሞራልን የማይቃወም በመሆኑ ተቀብሎ ማፅደቁ ከመዝገቡ ጋር የተያያዘው ማስረጃ ያሳያል በዚህ ጉዳይ ለክርክሩ መሠረት የሆነው በግራቀኙ የተደረገው የግልግል ስምምነት የሂሣብ አጣሪዎች ሪፖርት በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች በፍርድ ቤት እየታዩ መፅደቅ አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚል ነው ፡፡አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት በሂሳብ አጣሪዎች ተፈጸመ የተባለው ግድፈት በፍርድ ቤት ስሕተቱ እንዲታረም ማድረግ እንደሚችሉ ሲገለጽ ተጠሪ በበኩላቸው የሂሣብ አጣሪዎች ውሳኔ የመጨረሻ እና ይግባኝ የማይጠየቅበት መሆኑን ነው፡፡

የግራቀኙ መሠረታዊ የልዩነት ነጥብ ለክርክሩ መሠረት የሆነውን የሂሣብ አጣሪዎች ሪፖርት ተገቢነት በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል ነው ወይስ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህንን መሠረታዊ የክርክር ነጥብ ይዘት በአግባቡ ለመረዳት በግራቀኙ የተደረገው ስምምነት ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው የስምምነቱ ክፍል ማየቱ ተገቢ ይሆናል ፡፡ ግራ ቀኙ ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓ.ም ተስማምተው የተፈራረሙት ሰነድ እንደሚያመለክተው በጋራ ማህበር ያቋቋሙት የናዝሬት የምግብ ዘይትና ሳሙና ኢንዱስትሪና የእህል ንግድ ማህበር ስለፈረሰ ሂሳቡን በአጣሪዎች ለማጣራት መስማማታቸውን ፣የሂሳብ አጣሪዎች በተሰጣቸው ኃላፊነት መሠረት ከ1990 ዓ.ም ወዲህ ያለውን ሂሣብ አጣርተው ዕዳ ጠያቂዎች የሚያቀርቡት ማስረጃ መርምረው ዕዳውን በመቀበል ወይም ስላለመቀበል ውሳኔ እየሰጡ በመጨረሻም የማህበሩ ንብረት በመሸጥ እዳውን ከከፈሉ በኃላ ቀሪው ለተገልጋይ ወገኖች እንደ አክስዮን መጠን እንዲያከፋፍሉ መስማማታቸው፤ሂሣብ አጣሪዎች የሂሳብ መጣራቱን በሚያካሂዱበት ወቅት ከተገልጋይ ወገኖች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚቀርቡ ሂሳቦች ቢኖሩ እንደሚቀበሉ፤ጉዳዩም በስምምነት ለመጨረስ ጥረት እንደሚያደርጉ፤ ጥረቱ ፍሬያማ ካልሆነ ግን በንግድ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጎች መሠረት የራሳቸውን ውሳኔ በማድረግ ሥራቸውን በትክክል አከናውነው ከፍጻሜ እንደሚደርስ መስማማታቸውን በስምምነቱ ተራ ቁጥር 4.2 እና 4.3 በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ግራ ቀኙ ካደረጉት የግልግል ስምምነት መገንዘብ እንደተቻለው የሂሳብ አጣሪዎች ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ይሁንና በስምምነት መቋጨት ካልተቻለ ግን የበኩላቸውን ውሳኔ እንዲሰጡ ነው፡፡አመልካቾች የሂሳብ አጣሪዎች የሥራ ክንውን ግድፈት አለበት በማለት ይከራከራሉ፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት ግራቀኙን የሚያስገድድ ይግባኝ የሌለበት ውሳኔ መሆኑን ይገልፃሉ ፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ስምምነት አፅድቆታል ፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሰፈረው የአመልካቾች ጥያቄ በፍ/ቤት ትዕዛዝ የተሾሙ የሂሳብ አጣሪዎች ከኃላፊነት ይነሱልን ጥያቄ አይደለም ፡፡ የሂሳብ አጣሪዎች ተገቢ ነው ያሉትን ተግባር አከናውነው ለግራቀኙ አቅርበዋል ፡፡ ግራቀኙ ከመጀመሪያውኑ ጉዳዩ ከፍርድ ቤት ውጭ በስምምነት ለመጨረስ ተስማምተዋል ፡፡ በግራቀኙ ስምምነት መሠረትም የሂሳብ አጣሪዎች ሥራቸውን አከናውነው ውጤቱ ለሚመለከታቸው ባለ ጉዳዬች ማቅረባቸው በሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ተመልክቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ስምምነት ከመዘገበ በኃላ መዝገቡን ዘግቶታል ስምምነቱ ህግና ሞራልን የማይቃረን መሆኑ በፍ/ቤት ታምኖበት ከተመዘገበ በኃላ ያለው ሕጋዊ ውጤት እንደማንኛውም ፍርድ እንዲፈጸም አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል መሆኑን ከፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.277(1)እና(2) እንዲሁም ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3312 ይዘትና የሕጉ መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ክርክራቸው የሂሣብ አጣሪዎች የግራ ቀኙ ስምምነት የጣሱ ስለመሆናቸው ወይም ከስምምነቱ ውጭ መሠረታዊ እና የሥነ ሥርዓት ሕጎች በሚቃወም አግባብ ስለመሥራታቸው የቀረበ ነገር የለም ፡፡ በአንፃሩ የሂሣብ አጣሪዎች ጉዳዩን በስምምነት መቋጨት ካልተቻለ የንግድ ህግና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጐች ተፈፃሚ በማድረግ የመጨረሻ ውሳኔ እንደሚሰጡ በግራቀኙ ስምምነት አንቀፅ 4.3 ተመልክቷል ፡፡ ይህ ግልፅ ስምምነት ባለበት ሁኔታ የሂሳብ አጣሪዎች የሥራ ክንውን ግድፈት አለበት በማለት ጉዳዩን በድጋሚ ወደ ፍርድ ቤት የሚያቀርቡበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ አመልካቾች የሂሳብ አጣሪዎችን የመጨረሻ ውሳኔ መሠረት በማድረግ ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ ይግባኝ ከሚጠይቁ በስተቀር የግራቀኙ ክርክር በሥር ፍርድ ቤት በተገለጸበት ሁኔታ የሂሳብ አጣሪዎች የሥራ ክንውን ሪፖርት በፍርድ ቤት እንዲሻሻል ያቀረቡት አቤቱታ ከግራቀኙ ስምምነት ውጭ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት ተገቢነት በፍርድ ቤት ይታይልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል ፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ የግራቀኙ አስገዳጅ ስምምነት ይዘትና መንፈስ ያልተከተለ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች የአመልካቾች የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት ተገቢነት ተመርምሮ ይሻሻልልን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስሕተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም ፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ.መ.ቁ.06187 በ 13/07/2005 ዓ.ም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ.መ.ቁ 137138 በ 5/10/2005 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት ተገቢነት በፍ/ቤት ተመርምሮ ይሻሻልልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል ፡፡ ይሁንና አመልካቾች በስምምነቱ መሠረት ያልፈፀመ ወገን ካለ የአፈፃፀም ጥያቄ የማቅረብ መብት የተጠበቀ ነው ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

ት/ቤ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 100631

ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- ሮፓክ ነዋሪዎች ልማት ማህበር - ጠበቃ አቶ ማርሻል ፍቅረ ማርቆስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሮፓክ ኢንተርናሽናል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር -ጠበቃ አቶ ያለለት ተሾመ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 128626 ጥር 30 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 98701 ሚያዝያ 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 197501 ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የግልገል ዳኛ እንዲሰየም ትእዛዝ ይስጥልኝ በሚል መንገድ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማመልከቻ ነው፡፡ ከሳሽ (አመልካች) ተከሳሽ(ተጠሪ) ከአባላቱ ጋር በተለያየ ጊዜ በተዋዋለው የመኖሪያ ቤት ግንባታ ውል ቤቶቹ ለሚሰሩበት መንደር የመሰረተ ልማት ግንባታና ልማት ስራ ለማከናወን ለነዋሪዎቹ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግየውል ግዴታ ገብቷል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ (ተጠሪ) በውሉ በገባው ግዴታ መሠረት የመሠረተ ልማት ግንባታ እንዲያከናውን ሲጠየቅ፤የግንባታ ስራውን ለመስራት ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ተከሳሽ ከከሳሽ አባላት ጋር ባደረገው ውል በአፈፃፀም ሂደት የሚፈጠር አለመግባባት ለግልግል ዳኛ የሚቀርብ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ የግልግል ዳኛ እንድንሰይም ባቀረባቸው ጥያቄ መሰረት የግልግል ዳኛ ለመሰየም ፍቃደኛ ባለመሆኑ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የግልግል ዳኛ እንዲሰይምና ስብሳቢ ዳኛ ሊሰየም በሚችልበት ሁኔታ ትእዛዝ እንዲሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡
2. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ፤ ከከሳሽ (አመልካች) ጋር ያደረኩት የውል ግንኙነት የለም፡፡ ከሳሽ አባላቱን ለመወከል በግልግል ጉባኤ ለመከራከር የሚያስችለው ልዩ ውክልና በአባላቱ አልተሰጠውም፡፡ ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው መብትና ጥቅም ወይም የውክልና ስልጣን የለውም፡፡ ስለዚህ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የተከሳሽን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግና ከሳሽ የተቋቋመበት አላማ በተከሳሽ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው በመሆኑ ተከሳሽ የግልግል ዳኛ እንዲሰይም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

3. ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኃላ መልስ ሰጭ(አመልካች) አባላቶችን በመወከል ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው የውክልና ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ፤ ይግባኝ ባይ (ተጠሪ) የግልግል ዳኛ እንዲሰይም ጥያቄ ለማቅረብ አይችልም በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካች ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 377 መሰረት ሰርዞታል፡፡
4. አመልካች ግንቦት 5 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ አመልካች የአባላቱን መብትና ጥቅም ለማስከበር የተቋቋመ ማህበር መሆኑን ተጠሪ አምኖ የተለያዩ ደብዳቤዎችን ሲፃፃፍ ቆይቷል፡፡ ተጠሪ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ያቀረበውን ክርክርና መቃወሚያ በመቀበል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲሻርልኝ የሚል ይዘት ያለው የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በተጠሪ ላይ የግልግል ዳኛ እንዲሰየምለት ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችለው ውክልና ወይም ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብትና ጥቅም የሌለው በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው መልስ ሐምሌ 22 ቀን 2006 ዓ/ም በፅሁፍ አቅርቧል፡፡ አመልካች ነሐሴ 13 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
5. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ችሎት ያቀረቡትን የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ለተጠሪ የግልግል ዳኛ እንዲሰይም ክስ ለማቅረብና ለመጠየቅ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት የሰጡት ብይን (ውሳኔ) የህግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
6. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች ህጋዊ ህልውና ሲያገኝ ሊያሳካቸው የሚችላቸው መሰረታዊ ዓላማዎችና አመልካች አላማዎቹን ለማሳካት ሊፈፅማቸው ስለሚችላቸው ህጋዊ ተግባራት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በኦሮሚያ ክልል በፊንፍኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ ሮፓክ ቀበሌ ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች የተመሰረተና የአካባቢ ብክለትና የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል፤ጎርፍለመከላከል፤ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ስራ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር፤ የልማት ስራ የመስራትና የመሰረተ ልማትና የማህበሩ የአገልግሎት ተቋማት በፕላን መሰረት መገንባታቸውን በአባላቶቹ ስም ለመከታተልና ይህ ግዴታ ያለበት ሶስተኛ ወገን በሕጉ መሰረት ግዴታውን እንዲወጣ ለማድረግ በአባላቱ ስም አስፈላጊውን ለመፈጸም ለማስፈፀምና ሌሎች አላማዎችን ለማሳካት የተቋቋመ ማህበር መሆኑን ከማህበሩ መመስረቻ ፅሑፍ አንቀጽ 5 የተዘረዘረ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ውሳኔና ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡
7. ይህም ከተጠሪ ጋር በተናጠል የቤት ግንባታና የማዘዋወር ውል የተዋዋሉ ግለሰቦች፣ተጠሪ በተናጠል በገባላቸው የውል ግዴታ በአንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት የመሠረተ ልማት ተቋማትን የመገንባትና የአገልግሎት ሰጭ ማዕከላትን የመገንባት ግዴታውን ያልተወጣ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ፣ ተጠሪን ከውል ወይም በሕግ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ የውል ግዴታውን እንዲወጣ ክስ የማቅረብና ተከታትሎ የማስፈፀም ዓላማና ሌሎች አላማዎችን የሚያሳካ ማህበር በመፍጠር፣ የፈጠሩት ማህበር፣ የማህበሩ አባላት በተናጠል ከውል የመነጨ መብታቸውን፣ለማስከበር ቢንቀሳቀሱ፣ የሚያወጡትን ወጭዎችና ጊዜ በሚቆጥብ ሁኔታ በተደራጀ መንገድ ማህበሩ ጥያቄ እንዲያቀርብላቸው ሙሉ ፈቃድና ስምምነታቸውን ሥልጣን ባለው የመንግስት አካል ፊት በመቅረብና የማህበሩን መመስረቻ ፅሑፍ በፊርማቸው በማፅደቅ የሰጡ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች በውሣኔያቸው ካሰፈሩትና ከደረሱበት የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ለመረዳት ይቻላል፡፡

8. አመልካች የተቋቋመበት አንደኛው መሰረታዊ ጉዳይ የማህበሩ አባላት አመልካችን ከማቋቋማቸው በፊት በተናጠል ከተጠሪ ጋር ባደረጉት የመኖሪያ ቤት ግንባታና የማዘዋወር ስምምነት መሰረት ተጠሪ ግዴታውን እንዲወጣ አባላቱን በመወከል አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ክስና ሌሎች የዳኝነት ጥያቄዎችን በማቅረብ ኃላፊነት ያለበት ሶስተኛ ወገን /ተጠሪ/ ግዴታውን እንዲፈጽም ለማድረግ መሆኑ በአመልካች መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 11 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ይህንንና ሌሎች ዓላማዎችን ለማሳካት እንዲንቀሳቀስ ዕውቅና ፈቃድ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተሰጥቶታል፡፡ይህም አመልካች በአላማነት ይዟቸው የተነሱ ተግባሮች ለመፈጸም የሚያስችልን ህጋዊ ተግባራት እንዲፈጽም አባላቱ ማህበሩን ሲመሰርቱ በሰጡት ፍቃድና ስምምነት መሰረት የመንቀሳቀስ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ከአዋጁ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 55 ድንጋጌዎችና ከአዋጅ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ይዘትና ውጤት ያላቸው የሌሎች ህጎች ተፈጻሚነት የሌላቸው መሆኑን ከሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 110 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት ህጋዊ ውጤት በማገናዘብ ለመረዳት ይችላል፡፡

9. ለዚህም ምክንያቱ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 110 ድንጋጌ፣ ከአዋጅ ጋር የማይቃረኑ የፍትሐብሔር ሕጉና የሌሎች ሕጐች ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚከለክል ይዘትም ሆነ ሕጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑ ነው፡፡ ይህም ስለ ማህበራት “ችሎታ” የሚደነግገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 454 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንድናገናዝብ የሚጠይቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለማህበራት ችሎታ የሚደነግገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 454 ንዑስ አንቀጽ 1 “ማህበሩ ከዓይነቱ ጋር የሚያስማማበትን ብሔራዊ የኑሮ ተግባሮች ሁሉ ለመፈፀም ይቻላል” የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ከዚል አንፃር ሲታይ፣ አመልካች የተቋቋመበትን መሠረታዊ ዓላማ ለማሳካት የሚያስችለውን የዳኝነት ጥያቄ የአባላቱን መብትና ጥቅም ለማስከበር በሚያስችለው አግባብ ለመጠየቅ ከአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 55፣አንቀጽ 110 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 454 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች የሚፈቅድለት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

10. ከዚህ በተጨማሪ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 ድንጋጌ፣ ከአንድ ሰው አንድ አይነት መብትና ጥቅም የሚጠይቁ ካሉ ከሳሾች፣ መብትና ጥቅማቸውን እነሡን በመወከል የሚጠይቅ በህግ ዕውቅና የተሰጠውና ህጋዊ ህልውና ያለው ማህበር በማቋቋም፣ በማህበሩ መብታቸውን እንዲጠይቅላቸው በማህበሩ መመሥረቻ ፅሑፍ በሙሉ ፈቃድና ስምምነት በማፅደቅ የሚሰጡትን ስምምነት ዋጋ በሚያሳጣ ሁኔታ መተርጐም ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአንፃሩ የህግ ህልውና ያገኙ የሲቪል ማህበራት ፣የተቋቋመለትን ዓላማ ለማሣካትና፣ ሲያከራክሩት የሚፈልጉትን የአባላታቸውን መብትና ጥቅም ለማስከበር፣ ለፍርድ ቤት ለግልግል ተቋም ወይም ለሌሎች የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት ጥያቄዎችን ለማቅረብ በሚያስችል መንገድ የሕጉን ድንጋጌዎች መተርጐም በግልና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተናጠል እንዲሁም በራሳቸው ችሎታ ተከራክረው መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር ከፍተኛ ወጭና ጊዜ የሚጠይቃቸው ግለሰቦች፣ ለዚህ ዓላማ በመሠረቱት ማህበር በኩል መብትና ጥቅማቸውን በቀላሉ ለማስከበር የሚችሉበትን ዕድል በሚያሰፋና የሰዎችን ፍትህ የማግኘት መብት የሚያረጋግጥ አግባብ መተርጎም ያለበት ሆኖ አገኘተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ በሕግና በሚመለከተው የመንግስት አካል ዕውቅና የተቋቋሙ ማህበራት፣ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት፣ የሚያስችላቸው የዳኝነት ጥያቄ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ያቀረበው መቃወሚያ ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና ተግባራዊ ተፈፃሚነት ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

11. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸውን ድንጋጌዎች ይዘትና ተግባራዊ ውጤት ሣያገናዝቡ አመልካች የግልግል ዳኛ እንዲሰየምለት ለማቅረብ አይችልም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 197501 ታህሳስ 1 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94511

30/01/2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ሕይወት

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካቾች፡-

1. ወ/ሮ ብዙ ሰንበታ
2. ወ/ሮ ባይሴ ሰንበታ

} ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ታደሰ ሰንበታ - መብታቸው ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይግባኙ ሊሰማ በተቀጠረበት ዕለት በቀጠሮው ሰዓት ለመድረስ ያልቻሉት ለጠበቃቸው የሰጡት የውክልና ስልጣን ማስረጃ በእጃቸው በመቅረቱ እና የሚመጡትም ከርቀት አካባቢ በመሆኑ ምክንያት መንገድ በመዘጋጋቱ በመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 73 መሰረት የተዘጋው የይግባኝ መዝገብ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 74(2) መሰረት ተከፍቶ እንዲታይላቸው ያቀረቡት አቤቱታ በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በውሳኔ የጸናው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካቾቹ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በነበራቸው ክርክር መዝገቡ በ4፡00 ሰዓት ተዘግቶ አመልካቾቹ በዚያኑ ቀን በ4፡30 ሰዓት በፍርድ ቤቱ የደረሱ መሆናቸውን እና በሰዓቱ ለመድረስ ያልቻሉትም በመንገድ ስራ ምክንያት መንገድ በመዘጋጋቱ መሆኑን ገልጸው በሚከራከሩበት ሁኔታ አመልካቾቹ ያቀረቡት ምክንያት በቂ ምክንያት የሚባል አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾቹን አቤቱታ ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት "በቀዳሚው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረው በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳው እንደሆነ" በሚል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 74(2) ስር ከተመለከተው ሐረግ ይዘት እና ተፈጻሚነት አንጻር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ የተላከላቸውን መጥሪያ ፈርመው ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸው በስርዓቱ መሰረት በመረጋገጡ የመከራከር መብታቸው እንዲታለፍ ተደርጓል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁኖቹ አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ለመስማት ለ18/03/2005 ዓ.ም. ከጠዋቱ በ3፡00 ሰዓት ተይዞ በነበረው ቀጠሮ በይግባኝ ባዮቹ በኩል የቀረበ ሰው ባለመኖሩ ተጠሪው ያቀረቡትን ክርክር በመቀበል ፍርድ ቤቱ መዝገቡን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 73 መሰረት የዘጋው መሆኑ፣አመልካቾቹ በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ላይ ቀርበው በሰዓቱ በቀጠሮ ሊገኙ ያልቻሉት ለጠበቃቸው የሰጡት የውክልና ስልጣን ማስረጃ በእጃቸው በመቅረቱ፣የሚመጡትም ራቅ ካለ አካባቢ በመሆኑ እና አዲስ አበባ ከተማ ከገቡ በኃላም ፍርድ ቤቱ የሚገኝበትን አካባቢ እና የታክሲ መያዣ ቦታውን በትክክል ባለማወቃቸው መሆኑንበመግለጽ መዝገቡ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 74(2) መሰረት ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው በጽሁፍ የጠየቁ መሆኑ በክርክሩ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ሲሆኑ ፍርድ ቤቱ በአቤቱታቸው ላይ የሌላኛውን ተከራካሪ ወገን አስተያየት ከተቀበለ በኃላ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል አመልካቾቹ ያቀረቡትን ጥያቄ ሳይቀበል የቀረው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው በአመልካቾቹ በኩል የቀረበው ምክንያት በቂ ሊባል የሚችል አይደለም በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ በአንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ እና ተከሳሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉም ሆነ በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሳሹ በሌለበትም ቢሆን ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በሙሉ ወይም በከፊል ላመነው ጉዳይ የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚችል እና ከሳሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን በመዝጋት እንደሚያሰናብተው በፍትሐብሄር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 73 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህ ድንጋጌ በይግባኝ ክርክር ጉዳዮች ላይ ጭምር ተፈፃሚነት ያለው መሆኑም በቁጥር 32(2) ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል በቀነ ቀጠሮው ሳይቀርብ የቀረበትን ምክንያት በመግለጽ ይግባኝ ባዩ መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ጥያቄውን ለፍርድ ቤቱ ሊያቀርብ የሚችል ስለመሆኑ እና ይግባኝ ባዩ በቀዳሚው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረው በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳው እንደሆነ ስለኪሳራው እና ስለ ማናቸውም ወጪ አከፋፈል ተስማሚ መስሎ የታየውን ውሳኔ ከሰጠ በኃላ የተዘጋው መዝገብ እንደገና ተከፍቶ ነገሩ እንዲቀጥል ትዕዛዝ መስጠት የሚችል ስለመሆኑ በቁጥር 74(2) ተደንግጓል፡፡እንደሚታየው ይህ ድንጋጌ ይግባኝ ባዩ በቀነ ቀጠሮው ሳይቀርብ የቀረበት ምክንያት በቂ ሆኖ የሚገመት እክል መሆን እንደሚገባው ከመግለጽ ውጪ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ውስጥ የሚካተቱት ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ የሚጠቁመው ነገር የለም፡፡ይህም በዚህ ረገድ የሚቀርብላቸውን አቤቱታ ከድንጋጌው ይዘት እና ዓላማ አንጻር መርምሮ ተገቢውን ዳኝነት የመስጠት ኃላፊነት የፍርድ ቤቶች መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾቹ ጉዳዩ እንዲንቀሳቀስላቸው አቤቱታ ያቀረቡት መዝገቡ በተዘጋ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መሆኑ እና ለጠበቃቸው የውክልና ስልጣን የሰጡትም ቀጠሮው ከመድረሱ ከስምንት ቀናት በፊት በ10/03/2005 ዓ.ም. በወልመራ ወረዳ ፍትሕ ጽ/ቤት በኩል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡አመልካቾቹ ለጠበቃቸው የሰጡት የውክልና ስልጣን ማስረጃም በእጃቸው የቀረ መሆኑን በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን በአንጻሩ የውክልና ስልጣን ማስረጃው አስቀድሞ ለጠበቃቸው ተሰጥቶ የነበረ ስለመሆኑ በተጠሪው በኩል የቀረበ ክርክር እና ማስረጃ የለም፡፡የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾቹ ያቀረቡት ምክንያት በቂ ሊባል የሚችል አይደለም ከማለት ውጪ በቂ ተደርጎ ሊወሰድ ያልቻለው በምን ምክንያት እንደሆነ በውሳኔአቸው ላይ በግልጽ አላሰፈሩም፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚሰጥ ውሳኔ ደግሞ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 182(1) ስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአስገዳጅነት የተቀመጠውን የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡ ይልቁንም አመልካቾቹ ጉዳዩ እንዲንቀሳቀስላቸው አቤቱታ ያቀረቡት መዝገቡ በተዘጋ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መሆኑ ሲታይ ጉዳያቸውን በአግባቡ በመከታተል ላይ የነበሩ መሆኑን እና በሰዓቱ በቀጠሮው ሳይገኙ የቀሩትም በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል በመሆኑ አመልካቾቹ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ያቀረቡት አቤቱታ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 74(2) መሰረት ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው ይገባ እንደነበረ ከክርክሩ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ሲጠቃለል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 73 መሰረት የተዘጋው የይግባኝ መዝገብ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 74(2) መሰረት ተከፍቶ እንዲታይላቸው አመልካቾቹ ያቀረቡት አቤቱታ በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በውሳኔ የጸናው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የተዘጋው የይግባኝ መዝገብ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል አመልካቾቹ ያቀረቡት አቤቱታ በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 141122 በ09/04/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 158692 በ13/01/2006 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾቹ በሰዓቱ በቀጠሮው ሳይገኙ የቀሩት በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ያቀረቡት አቤቱታ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 74(2) መሰረት ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. መዝገቡን አንቀሳቅሶ ክርክሩን ቀጥሎ በመስማት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት ወስነናል፡፡
4. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
5. ቁጥሩ 141122 የሆነው መዝገብ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይመለስ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ አመልካቾች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 94713

መጋቢት 16 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካቾች፡- 1. ህጻን ሲኢድ ዘውዴ
2. ህጻን ኑሩ ሁሴን ዘውዴ } ምግዚት ወ/ሮ ሙሉ ሞሳ - ጠበቃ ሆነልኝ ዋለ -
3. ህጻን አዲሱ ዘውዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1.ወ/ሮ ጥሩሰው ሞሳ
2. ሶፊያ አግማስ
3. ፋንታ አግማስ
4. አስጋርጅ አግማስ
5.ብርቁአግማስ
6. ሞሚና አግማስ
7. ጥጋቡ አግማስ
8. በላይ አግማስ
9. አለሚቱ ታደሰ

የ1ኛ፣2ኛ፣3ኛ፣5ኛ-8ኛ ጠበቃ አዲስ መንግስት ቀረቡ፡፡

ታልፏል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውርስ ንብረት ግምት ክፍያ ጋር ተያይዞ የቀረበ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ያሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት ላይ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደብረ ታቦር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት ተከሳሽ፣ አሁን ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ስምንት የተጠቀሱት ተጠሪዎች ከሳሾች፣9ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡

የክሱ ይዘትም፡-ከተጠሪዎች መካከል ከተራ ቁጥር ሁለት ጀምሮ ያሉት ከወላጅ አባታቸው ከሚች አቶ አግማስ አምባው ላይ በውርስ ያገኙትንና አዋሳኙ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን በ369 ካ/ሜትር ያረፈውን ቤት ከሚች ባለቤት ከወ/ሮ ጥሩሰው ሞሳ ጋር እኩል ተካፍለው ከይዞታው ውስጥ 184.57 ካ/ሜ ከወ/ሮ ጥሩሰው ሞሳ ድርሻ ውጪ ያለው ግማሹን በወ/ሮ ሙሉ ሞሳ ተይዞ እንደሚገኝ፣ይህንኑ ቤትና ቦታ የወ/ሮ ሙሉ ሞሳ ባለቤት አቶ ዘውዱ አግማስ እንደስር ከሳሾችና ሌሎች የሚች ወራሾች ሁሉ የሚቹ ልጅ በመሆናቸው በቤቱ ላይ ወርሃዊ ኪራይ ክፍያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እየከፈሉ ይዘው ቆይተው አቶ ዘውዱ አግማስ በመስከረም ወር 2001 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በኋላ ወ/ሮ ሙሉ ሞሳ ቤቱን ያለ ክፍያ ይዘው የተቀመጡ መሆኑን ዘርዝረው ከጥቅምት ወር 2001 ዓ/ም ጀምሮ የቤቱን ጥቅም በተመሳሳይ ቤት በአካባቢው ያሉ ቤቶች በሚያስገኙት ዋጋ መጠን እንዲከፍሉና ቤቱንም እንዲለቁ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ማለቁንና ጥያቄው ውርስ ሳይጣራ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚሉ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው በፍሬ ነገሩ ደግሞ አውራሹ ሳይሞቱ የነበረው ሙሉ ቤትና ቦታ በአንድ በኩል ከሞቱ በኋላ ለሁለት የተከፈለው ቤትና ቦታ ተይዞ ሁለቱ ቤትና ቦታዎች በገንዘብ እያንዳንዳቸው ያለመገመታቸውን፣ የቤት ኪራይ ውል በጽሑፍ ሳይኖር የክፍያ ጥያቄ መቅረቡ ያላግባብ መሆኑን፣ ቤቱን የያዙትም ባለቤታቸው አቶ ዘውዱ አግማስ የአውራሹ ልጅና ወራሽ በመሆናቸውና የአሁኑ አመልካቾችን የወለዱላቸው በመሆኑ አመልካቾች በተተኪ ወራሽነት በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን፣ ስለቤቱ ከአውራሹ ሞት በኋላ የተሰጡ የምስክር ወረቀቶችን በተመለከተ መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ/ም የተሰጠውን የሚስማሙበት ሆኖ የካቲት 15 ቀን 2001 ዓ/ም የተሰሩትን ግን ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላ የተሰሩ፣ ነገር ግን የእርሱ ስም የተጠቀሰባቸው የተተኪዎችን ጥቅምና መብት የማያስከብሩ በመሆናቸው ተቀባይነት ሊሰጣቸው እንደማይገባና ሊሰረዙ የሚገባቸው መሆኑን፣ የውርሱ ጉዳይ ስለቤቱ ብቻ ሳይሆን ስለሌሎች ተንቀሳቃሽ ንብረቶችም ጭምር በመሆኑ በአጣሪ ሊጣራ እንደሚገባ፣ የእርቁ ጉዳይን ለማረጋገጥ የቀረበው ሰነድም ባለቤታቸው ተስማሚ ያልሆኑበት ሰነድ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ፣ ክሱ የቀረበበት ቤት ሟች ባለቤታቸው ከአባታቸው ከአቶ አግማስ አምባው ለጎጆ መውጫ እንዲሆናቸው የተሠጣቸው መሆኑን፣ የውርስ ሃብት ክፍፍል ይደረግ ከተባለውም ተከሳሽ እና ሌሎች ወራሾች እየተጠቀሙበት ያለው የአቶ አግማስ አምባው ንብረቶች በአጣሪ ተጣርተው ሊካፈሉ ይገባል እንጂ ተከሳሽ የያዙትን ቤት ብቻ የሚያካፍሉበት አግባብ ያለመኖሩን ዘርዝረውና በውርሱ ሊካተቱ ይገባል ያሏቸውን የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን አይነታቸውና ግምታቸውን ጠቅሰው ክፍፍሉ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በተከሳሽ የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ውድቅ አድርጎ ከአለፈ በኋላ ፍሬ ነገሩ ላይም ግራ ቀኙን በቃል ከአከራከረና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ከአጣራ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ክርክር የተነሳበትን ቤት ተከሳሽ ይልቀቁ፣ ከአስሩ የሟች አቶ አግማስ ልጆች ጋር የተከሳሽ ልጆችበአባታቸው አቶ ዘውዱ እግር ተተክተው ተጠቃሚ ይሁኑ፣ ከጥቅምት 01 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ ወር 2002 ዓ/ም ድረስ ያለውንተከሳሽ ቤቱን ይዘው የተጠቀሙ በመሆኑበወር አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ቤቱ እንደሚከራይ በአካባቢው ግምት መነሻ ተረጋግጧል ብሎ ይህንኑ ስሌት መሰረት አድርጎ እስከ ታህሳስ ወር 2002 ዓ/ም ድረስ ያለውን የኪራይ ገንዘብ ብር 21,000.00 አንድ አስረኛ ድርሻ ትተው ተከሳሽ ለከሳሾች እንዲከፍሉ፣ጣልቃ ገብም አንድ አስረኛ ከቤቱም ሆነ ከኪራዩ ገንዘብ እንዲያገኙ፣ የዳኝነት ገንዘቡን በተመለከተም ተከሳሽ ለከሳሾች እንዲተኩ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካቾችም በተሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለደቡብ ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ያልተከፋፈለ የሟች አግማስ አምባው ንብረት በመሆኑ ወራሾች ባሉበት ሁኔታ ለመካፈል ካልተስማሙ በጨረታ ተሸጦ አንድ አስረኛ ድርሻ ለአሁኑ አመልካቾች ሁኖ ቀሪውን ተጠሪዎች በድርሻቸው እንዲከፋፈሉ፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተመለከተም ተጠሪዎች አመልካች የዳኝነት አልከፈሉም ከማለት በስተቀር ሌላ ክርክር አላቀረቡም፣ በይግባኝ ሰሚው ችሎት ያቀረቡት የይርጋ ክርክርም ተቀባይነት የሌለው ነው በሚል ምክንያት አርባ ሺህ የተገመተ አይነታቸው ሃያ የሆኑ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን ተጠሪዎች ለአመልካቾች በድርሻቸው እንዲከፍሉ በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በአመልካች መከላከያ መልስ ጋር በአማራጭ መልስነት የቀረበና ዳኝነት የተከፈለበት ስለመሆኑ የማያሳይ እና ክሱ ስርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ ሁኖ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስን ራሱ ከይግባኝ ክርክር ጋር ተቀብሎ ተጠሪዎች የሚንቀሳቀሱ ንብረቶቹን ግምት ለአመልካቾች ድርሻቸውን እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ አይደለም፣ የቤት ኪራዩንም አመልካች የሚከፍሉበት የሕግ አግባብ የለም በሚል ምክንያት በዚህ ረገድ የተሰጡትን የውሳኔ ክፍሎች የሻራቸው ሲሆን በአመልካቾች ሞግዚት ተያዘ የተባለውን ቤት በተመለከተ ግን እንዲለቀቅና ለወራሽ ልጆች እንዲያስረክቡና አከፋፈሉን በተመለከተም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1272 እና ተከታዩቹ መሰረት የሚፈጸም ሁኖ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት አጽንቶታል፡፡የዳኝነት ገንዘቡን በተመለከተ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍልንም አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት በዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው የውሳኔ ክፍል ቅር በመሰኘት የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-- አከራካሪውን ቤት እንዲለቁ መወሰኑ ከህፃናት መብትና ጥቅም አንፃር ተገቢ ያለመሆኑን፣ በጉዳዩ ላይ ያነሱት ይርጋ መታለፉም ያላግባብ መሆኑን፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስም ስርዓቱን ጠብቆ ስልጣን ላለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበ ሁኖ እያለ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ መሆኑን፣ ባልተከፋፈለ የጋራ ሃብት ላይ በቀረበ ክስ ረቺና ተረቺ በሌለበት ሁኔታ የዳኝነት ገንዘብ እንዲከፍሉ መደረጉም ከህግ ውጪ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ሊለወጥ ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ አይደለም ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ዳኝነት ሳይከፈል ክሱ ቀርቦ ከታየ በኋላ ፍርድ ቤቱ ሊከተለው ስለሚገባው ስርዓት ይህ ችሎት ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት የቀረበ ሲሆን ከ9ኛ ተጠሪ በስተቀር ሌሎች ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት በጭብጥነት የተያዘው ጉዳይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት የሚመለከት በመሆኑ የአመልካቾች ሞግዚት ቤቱን እንዲለቁ፣ በቤቱ ላይ ያነሱት የይርጋ መቃወሚያ፣ እንዲሁም የዳኝነት ገንዘብ እንዲከፍሉ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ያቀረቡት የሰበር ቅሬታ በዚህ ችሎት እንዲታይ ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ አመልካቾች በወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ታልፎ ቤቱን እንዲለቁ፣ የዳኝነት ገንዘቡንም እንዲከፍሉ ተወስኖባቸው ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ ክርክርም በዚህ ረገድ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ፀንቶባቸው ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረቡት የአሁኑ ተጠሪዎች መሆናቸውን የክርክሩ ሂደት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሚያሳይ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ደግሞ አመልካች በዚህ ረገድ መስቀለኛ ይግባኝ ወይም የመቃወሚያ ክርክር ያቀረቡ ስለመሆኑ ውሳኔው ስለማያሳይ በዚህ ችሎት በእነዚህ ነጥቦች ላይ የሚያቀርቧቸው ክርክሮች ተቀባይነት የሚያገኙበት የስነ ስርዓት ሕግ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረቡትን የአመልካቾችን የክርክር ነጥቦች ስርዓቱን ጠብቀው ያልቀረቡ በመሆኑ አልፈናቸዋል፡፡

ስለተከሳሽ ከሳሽነት የቀረበውን ቅሬታ በተመለከተ ከክርክር ሂደቱ መገንዘብ እንደሚቻለው ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት ከፍ ሲል እንደተገለፀው ዳኝነት ጠይቀው እየተከራከሩ ያለው አከራካሪ ከሆነው ቤት ጭምር ሌሎች የሚንቀሳቀሱ የውርስ ንብረቶች መኖራቸውን ገልጸውና የንብረቶችን አይነት፣ብዛትና ግምታቸውን ዘርዝረው እነዚህ ንብረቶች የውርሱ አካል ተደርገው ክፍፍሉ ሊፈፀም ይገባል በማለት ሲሆን ይህን የዳኝነት ጥያቄ በወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት ግን ተጠሪዎች ባቀረቡባቸው ክስ የመከላከያ መልስ ሲያቀርቡ በአማራጭ መልስነት ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን የመራበት ሁኔታም ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት ግራ ቀኙን በስር የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቀራረብ ስርዓት በሕጉ የተቀመጠውን አግባብ ያለመከተሉን በአቢይ ምክንያትነት ጠቅሶ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔውን መሻሩን ከውሳኔው ተገንዝበናል፡፡አመልካቾች በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃ አጥብቀው የሚከራከሩት ደግሞ በወረዳው ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ነበር ሳይሉ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጎ የንብረቱ ግምትም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን እንዲኖረው የሚያደርግ በመሆኑ ክርክሩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከይግባኝ ክርክር ጋር እንዲታይ ተደርጓል በሚል ነው፡፡ ሆኖም አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ተከሳሾች እንደመሆናቸውና እነሱም በበኩላቸው ከተጠሪዎች የሚጠይቁት መብት ካላቸው በህጉ አግባብና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 234/1/ /ረ/ መሰረት ከመከላከያ መልሳቸው ጋር የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 215/2/ ስር እንደተመለከተው በመፈፀም በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የተጠቀሱት የሚንቀሳቀሱት ንብረቶች ግምት እንዲከፈላቸው በሚል የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ የለም፡፡ በዚህ አግባብ ተሟልቶ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ በሌለበት ደግሞ ዳኝነቱ ሊሰጥ አይችልም፡፡ አመልካቾች በተከሳሽነታቸው በተሰጣባቸው ውሳኔ ይግባኝ ብለው በሄዱት ክርክር ላይ በስር ፍርድ ቤት በሕጉ አግባብ ያልቀረበ የተካሳሽ ከሳሽነት ክስ እንዲቀርብ ተደርጎ ከይግባኙ ጋር የሚወሰንበት አግባብ የለም፡፡ እንዲህ አይነት የክርክር አመራር የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትም የሚጎዳ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17352 የሠጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚመለከተው ተገቢው ዳኝነት ክፍያ ሳይፈፀም በፍርድ ቤት በቀጠለ ክርክር ስለሚፈፀም ስርዓት እንጂ ከመነሻው የክስ አቀራረብ ስርዓትን ሳይከተል የቀጠለውን ክርክር ሁኖ የሚመለከት አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ከፍ ሲል በተገለፁት ምክንያቶች የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች የዳኝነት አገልግሎት ፈፅመው የተከሳሽ ከሳሽ ዳኝነቱንም በስርዓቱ ባላቀረቡበት ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ግምት በተመለከተ ተጠሪዎች የአመልካቾችን ድርሻ እንዲከፍሉ ሊገደዱ አይገባም፣ አመልካቾች በሕጉ አግባብ ክስ ሊያቀርቡ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዕናቱ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መ/ቁ 31215 ሰኔ 05 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ 33634 ጥቅምት 15 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ አይደለም ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተሰጠውና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፀናው የውሳኔ ክፍል የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በሌሎች ነጥቦች ላይ የተሰጠው ውሳኔም አልተነካም፡፡
3. ለዚህ የሰበር ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

በዚህ መዝገብ ህዳር 04 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የ/ማ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ ቁጥር 97217

መጋቢት 16 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ባካፋ አንለይ -- ራሳቸው ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ቴዎድሮስ አንለይ - ጠበቃ ጌትነት አየለ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያለአግባብ የተያዘ የመኖሪያ ቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 08 ክልል ውስጥ የሚገኘውን፣ በካርታ ቁጥር 10/00/93 የሚታወቀውንና በ660 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ሰፍሮ በስማቸው ተመዝግቦ ያለውን መኖሪያ ቤት ተከሳሽ ምንም መብት ሳይኖራቸው ከህዳር ወር 1998 ዓ.ም ጀምሮ በመያዝ እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ገልፀው ቤቱ እንዲለቀቅላቸውና ያላግባብ ቤቱን ለተጠቀሙበት ጊዜ ደግሞ በወር ብር 2000.00(ሁለት ሺህ) ኪራይ ታስቦ እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተከሳሽ የሰጡት የመከላከያ መልስም፡- ከሳሽ ቦታውን የተመራበት ካርኒ አላቀረበም፡፡ ቤቱ በ1963 ዓ.ም የተሠራ ሲሆን ውሃና መብራት የገባው በወላጅ አባታችን በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም በመሆኑ ቤቱ የአባታችን ቤት ነው፡፡ በአባታችን ስም የተከፈተው የማህደር ቁጥር 1224 የአባታችን ቤት መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ማህደሩ በሙሉ ተዘርፏል፡፡ ግብርበአባታችን ስም የተገበረ ለመሆኑ የባህር መዝገብ ቁጥር 202 ስለሚያስረዳ ቀርቦ መታየት ይችላል፡፡ ቤቱ ከአባታችን ሞት በኋላ ከእናታችን ጋር የምንገለገልበት እንጅ ተከራይቶ አያውቅም፡፡ ከሳሽ ከአከራካሪው ቤት ጐን በሊዝ የተመራውን ቦታ አንድ ላይ በማድረግ የሚች አባታችንን ቤትና ቦታ አጠቃሎ ካርታ እና ፕላን አወጣበት እንጅ የእሱ አይደለም፡፡ ስለዚህ የወራሽነት ድርሻውን ከሚጠይቅ ውጪ የግሌ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ሐሰት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አከራካሪው ቤት የከሳሽ ለመሆኑ ከተከሳሽ በተሻለ አስረድተዋል በማለት በአብላጫ ድምጽ ተከሳሹ ቤቱን ለከሳሽ ሊያስረክብ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣የሰበር

አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሲያጡ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት አቅርበው ይህ ችሎትም ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 55907 አከራክሮ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩ በአግባቡ ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል ሲል ሊጣሩ የሚገባቸውን ነጥቦች ለይቶና ሊቀርቡ የሚችሉትን ማስረጃዎችን ጭምር ጠቁሞ ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡

ጉዳዩ የተመለሰለት የምዕራብ ጉጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም እንደገና ግራ ቀኙን በመጥራት አለኝ የሚሉትን የሰውና የሰነድ ማስረጃ አስቀርቦ በመስማትና ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን የሰነድ ማስረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካለት እንዲቀርቡና ማብራሪያም እንዲሰጥበት ጭምር ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ከ660 ካ/ሜትር ቤትና ቦታ ውስጥ በ440 ካ/ሜትር ክልል ውስጥ ያለው ቤት የአሁኑ ተጠሪ አይደለም፣ 220 ካ/ሜትር ቦታ ግን ተጠሪ በሊዝ የገዙት በመሆኑ የአሁኑ አመልካች ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ጉዳዩን በይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ 440 ካ/ሜትር ቤትና ቦታ የአሁን ተጠሪ ስለመሆኑ በሰውም ሆነ በሰነድ ማስረጃ ከአሁኑ አመልካች ክርክርና ማስረጃ በተሻለ መልኩ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ይዞ የአሁን አመልካች ቤትና ቦታውን ሙሉ በሙሉ ለቀው ለተጠሪው ሊያስረክቡ ይገባል፣ ያላግባብ ለተጠቀመበት የቤት ኪራይም በወር 2000.00 ታስቦ በድምሩ ብር 62,000 /ስልሳ ሁለት ሺህ ብር/አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካች ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን አቅርበው ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካች 440 ካ/ሜትር ቤትና ቦታ ጭምር እንዲለቁ መወሰኑ ባግባቡ ነው፣ የኪራይ ገንዘቡን በተመለከተ ግን ለተጠሪ ቀድሞ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያልወሰነው እና ጉዳዩ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊመለስም እንዲጣራ ያልታዘዘ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሚወስንበት የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የለም ብሎ በጉዳዩ ላይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አከራካሪው ቤትና ቦታ የሚች አባታችን ለመሆኑ በተገቢው መንገድና ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የተጠሪው ነው ተብሎ እንዳስረክብ የተወሰነው ያለአግባብ ነው፣ተጠሪው አለኝ ያሉት የኑዛዜ ሰነድም የማስረጃ አቀራረብ ስርዓትን ተከትሎ ያልቀረበና ሕጋዊ አይደለም፣በጉዳዩ ላይ ዳኝነት የተሠጠው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጣሩ የተለዩት ነጥቦችንና ጉዳዩ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተመለሰ በኋላ ከሚመለከታቸው አካላት የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችን ባለገናዘበ መልኩ ነው የሚል ሁኖ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከለተው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች 440 ካ/ሜትር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤትና ቦታ ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

በቅድሚያ ተጠሪ ጉዳዩ የፍሬ ነገር ክርክር ነው በማለት ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተመልክተናል፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ክርክር ከማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ጋር የተያየዘ ሲሆን በዚህ ችሎት ጉዳዩ የቀረበው ጉዳዩ በሕጉ አግባብ ተጣርቶ የተወሰነ መሆን ያለመሆኑንና የማስረጃ አቀራረብ ስርዓትን እንዲሁም የምዝና መርሁን ባገናዘበ መልኩ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጭብጥ የፍሬ ነገር ማጣራት ወይም የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ባለመሆኑ በዚህ ችሎት የማይታይበት አግባብ ስላላገኘን በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪን ተቃውሞ አልተቀበልነውም፡፡

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስም፡- ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ይህ ችሎት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ሲመልስ ሊጣሩ የሚገባቸውን ነጥቦችን የለየ መሆኑን ነው፡፡ይህ ችሎት ጉዳዩን ወደ ታች ሲመልሰው ለክርክሩ መነሻ የነበረውን ይዞታ ማነው የተመራው ፣ ቤቱን ማነው የሰራው፣በማን ገንዘብ ተሰራ የፅሁፍ ማስረጃዎችን በተመለከተ ካርታ በከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ስም የተሰጠ መሆኑ ከማስረዳት ባለፈ የከተማው አስተዳደርየቤቱንና የይዘታውን አመጣጥ በአግባቡ ያውቃል ተብሎ ስለሚገመት በስር ፍርድ ቤቱ በኩል ታዞ ተጨማሪ ማብራሪያዎችንእንዲሰጥበት ሊደረግ እንደሚገባ፣ ማብራሪያ ከሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች መካከልም በከተማ አስተዳደሩ የነበረውን የማህደር ቁጥሩ 1224 የሆነውና በደጃዝማች አንለይ ሃይል ስም የነበረው/ የተከፈተው ለየትኛው ይዞታና ቤት ነበር የውሃና መብራት ውል በስማቸው ሊዋዋሉ የቻሉበትን አግባብ እንዴት እንደነበር፣ ከማህደሩ ውስጥ ጠፍቷል የተባሉት ገፆች እንዴት ሊጠፉ እንደቻሉ ፣ጠፍተውም ከሆነ መጥፋታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጠፉት ገፆች ይዘታቸው ምን እንደነበር ያሁን ተጠሪ ካርታ 660 ካሬ ሜትር ላይ የወጣላቸው በአንድ ጊዜ ነው ወይስ አሁን ክርክር ካስነሳው ይዞታ ጎን የነበረውን 220ካሬ ሜትር ከተመሩ በኋላ ነው፣ አሁን ክርክር የተነሳበት ይዞታ ከ220 ካሬ ሜትር ጋር ተጠቃሎ የተሰራ ነው ወይስ አይደለም፣ ሒደቱስ እንዴት ነበር የሚሉት ነጥቦች ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ናቸው በማለት ዘርዝሯል እንዲሁም ሰበር ችሎቱ የግብር አከፋፈል ሂደቱ በተካራካሪዎች አባት ሲከፈል የነበረበትና በተጠሪም ሲከፈልበት የነበረበት አግባብ ሊጠራ የሚገባው ነጥብ መሆኑን በመግለፅ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በባህርዳር ከተማ ገቢ ፅ/ቤት የባህር መዝገብ ተራ ቁጥር 202 በአባታቸው ስም ይገበር የነበረ በመሆኑ ቀርቦ ይታይልኝ በሚል ጥያቄ ቀርቦ ፍ/ቤቱ ስለማየቱ በፍርዱ ውስጥ የተባለ ነገር ባለመኖሩ ማስረጃው ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባ ለስር ፍርድ ቤት መመሪያ ሰጥቷል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቤቱ ተሰራ ከተባለበት ከ1963 ዓ.ም ጀምሮ ግራ ቀኙም ሆኑ ሌሎች የቤተሰብ አባላት በተለይም እናትና አባት ከቤቱ ጋር ያላቸውና የነበራቸው ቁርኝት መታየትና መጣራት እንዳለበትም በውሳኔው ላይ አስፍሮ ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት የመለሰለት መሆኑን ተረድተናል፡፡

ከላይ የተመለከቱት ነጥቦች ይህ ችሎት በስር ፍርድ ቤት እንዲጣሩ የለያቸው ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ከተመለሰለት በኋላ ፍሬ ነገሩን ያጣራበትን መንገድ መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች የሰማ ሲሆን በሥር ፍ/ቤት የተሠሙት የተጠሪ ምስክሮች ቤቱን ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1965 ድረስ ባለው ጊዜ ተመርቶ የሠራው ተጠሪ መሆኑን፣ ቤቱን ሲሰራም ከተለያዩ ሰዎች ገንዘቡን ተበድሮ መስራቱን የሚያውቁ መሆኑን አስረድተው ቤቱን ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲሄድ አባቱ እንዲኖሩበት ፈቅዶላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይኖሩበት እንደነበር፣ በዚሁ ሁኔታ ውሀና መብራት በእሳቸው ስም መግባቱን መስክረዋል። ባንቺ ዓለም አንለይ የተባለችው የግራ ቀኙ እህት በሰጠችው ምስክርነትም ቤቱ የታላቅ ወንድማችን የቴዎድሮስ አንለይ ነው፣ አባታችን በሕይወት እያሉ ሁሉን ነገር ያንቀሳቅሱ የነበሩ እሳቸው ናቸው፣ በኑዛዜያቸውም ቤቱን የተጠሪ መሆኑን ገልፀዋል፣ እሳቸው በ1990 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ ቤቱ በብር 2000 ተከራይቶ ነበር፣ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ ቤቱ በአሁኑ አመልካች ይዞታ ስር መቆየቱንም ሁሉም ምስክሮች አስረድተዋል። የአመልካች ምስክሮች በበኩላቸው ቤቱን የሠሩት የግራ ቀኙ አባት ደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ናቸው፣ ቦታውን የተመሩት ደግሞ በተጠሪው ስም ነው፣ ግብር ይከፈል የነበረው ደግሞ በደጃዝማች አንለይ ስም ነበር በማለት መመስከራቸውን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል።

ከክፍሉ ማዘጋጃ ቤት የቀረበው የሙያ ምስክር የሰጠው ምስክርነትም የደጃዝማች አንለይ በልጃቸው ቴዎድሮስ አንለይ ስም ቦታ ተመርተው በራሳቸው ስም ሲገብሩ ቢኖሩም በኋላ ግን ቦታው በስሙ በተመራው ልጃቸው /በተጠሪ ስም/ ግብሩ ተስተካክሎ ሲገበር መቆየቱን፣ በፊት የነበረው ቦታ 440 ካሬ ሜትር ሲሆን በኋላ 220 ካሬ ሜትር ቦታ ሊዝ ገዝቶ ጨምሮበት 660 ካሬ ሜትር ቦታ በተጠሪ ስም ተጠቃሎ መስጠቱን መግለጹን የስር ፍርድ ቤት መዝግቧል።

የስር ፍርድ ቤት በሰነድ ማስረጃነት ያስቀረበው የባህር ዳር ከተማ አስተዳዳር ገቢዎች ጽ/ቤት ጥቅምት 11 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ቁጥር አዘል ደብዳቤ በባህር መዝገብ ቁጥር 202 በሆነ ግብር በተጠሪው ስም የማይገበር መሆኑንና መዝገቡ በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም መሆኑን የሚያሳየውን ሰነድ፣ በባህር ዳር ከተማ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ ቁጥር የያዘ ደብዳቤ ውሀ የገባው በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም መሆኑንና በመሥሪያ ቤቱ አሠራር ውሀ በስም ለማስገባት የሚቻለው ባለይዞታ መሆኑን ገልፆ በወቅቱ ደጃዝማች አንለይ ባለይዞታ ስለሆኑ ውሃው የገባላቸው መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠው ሰነድ፣በባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የማህደር ቁጥር 1224 የሆነውን በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም የነበረው ቦታ የሚያሳየው የተለያዩ ቦታዎችን ከሰዎች መግዛታቸውን፣ ይሁን እንጂ እነዚህ ቦታዎች የተወረሱባቸውና በተለያየ ምክንያት የፈረሱ መሆኑን፣ ህዳር 19 ቀን 1984 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ቦታ እንዳሌላቸውና በልጃቸው በቴዎድሮስ አንለይ ቤት በጊሰኝነት እንደሚኖሩና ቦታ እንዲሰጣቸው ያመለከቱበት ማመልከቻ መኖሩንና አቶ ቴዎድሮስ ፋይል ላይ ደግሞ ግንቦት 11 ቀን 1992 ዓ.ም በተዘጋጀ ሳይት ፕላን ባህር ዳር ከተማ 08 ቀበሌ የ440 ካሬ ሜትር ቦታ እንደነበራቸውና 220 ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ ጠይቀው ከሚያዚያ 24 ቀን 1993 እስከ ግንቦት 02 ቀን 1993 ዓ.ም እንዲወስዱ ተወሰኖላቸው የ660 ካሬ ሜትር ቦታ ካርታ መውሰዳቸውን የሚገልፅ ሰነድ ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በባህር ዳር ዲስትሪክት ቁጥር 2 አገልግሎት ማዕከል ጥቅምት 06 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤ መብራት በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም መግባቱን የሚያሳይ ሰነድ፣ የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም ይገበርበት የነበረ ምንም ዓይነት ካርታና ፕላን የለም ሲል የገለጸበት ሰነድ፣የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አከራካሪው ቤትና ቦታ በአቶ ቴዎድሮስ አንለይ ስም በካርታ ቁጥር 10100/93 በፋይል ቁጥር 291 ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን እንደሚያሳይ የገለፀበት ሰነድ ናቸው። ከእነዚህ የሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት የያዘው ሰነድ የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩ ወደ ስር ፍርድ ቤት ከተመለሰ በኋላ አገኘሁ ብለው በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲታይላቸው ያቀረቡት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰነድ ሲሆን ይህም ሟች ደጃዝማች አንለይ ኃይሌ መስከረም 06 ቀን 1984 ዓ.ም. አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ሁኖ ለጉዳዩ አግባብነት አለው የተባለው የኑዛዜው ክፍል ሟቹ ".....አሁን ያለንበት መኖሪያ ቤት በልጄ በቴዎድሮስ አንለይ ስም የተሠራ ነው፣ቤቱም የተሠራበት ቦታ በራሱ ስም የተገኘና የተያዘ ሥለሆነ ቤቱን ከነቦታው መረከብ ይችላል...." በማለት ማስፈራቸውን ያሳያል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች ተመዝግቧል። ከዚህ የሰውና ሰነድ ማስረጃ መገንዘብ የሚቻለው በአከራካሪው ቤትና ቦታ ውሀና መብራት በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም መግባቱንና በቤቱም ውስጥ እየኖሩ ግብር በህይወት እስከነበሩ ድረስ በእሳቸው ስም ይገበሩ የነበረ መሆኑን ሲሆን የቤቱን ካርታ እና ፕላን ግን በእሳቸው ስም የተመዘገበ አለመሆኑንና በተጠሪው ስም የተመዘገበ መሆኑን ነው።በተጠሪው ስም የተመዘገበበት ጊዜ በ1993 ዓ/ም ስለመሆኑ ክርክር የቀረበበት የፍሬ ነገር ነጥብ አይደለም።ይህ ምዝገባ የተከናወነው ቦታው በተጠሪው ስም የተመራ ነው በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ማዘጋጃ ቤቱ የሚከተለውን አሰራርን መሰረት በማድረግ ለስር ፍርድ ቤቱ ማብራሪያ እንደሰጡ የቀረቡት ሰራተኞች ከሰጡት የምስክርነት ቃል መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም በቤቱ ማህደር ውስጥ ሰነዶች እንደነበሩ ሳይካድ ሰነዶቹ የጠፉት ህጋዊ ምክንያት ግን በማስረጃ ያለመረጋገጡን የክርክሩ ሂደት ያሳያል። ማዘጋጃ ቤት ያለው የቤቱ ማህደር የአመልካችን አባት ስም የማይጠቀስ ነው የተባለ ቢሆንም ተመሳሳዩን ቤትና ቦታ በተመለከተ በግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ይገኛል የተባለው ማህደር ደግሞ የአሁኑን ተጠሪ ስም የማይገልፅ፣ይልቁንም የሟች ደጃዝማች አንለይ ኃይሌን ስም የሚገልፅ መሆኑን የሚመለከተው አካል ለፍርድ ቤቱ አረጋግጦ ልኳል።ይህ ማህደር ሰነዶቹ የጠፉት ስለመሆኑ በተጠሪ ክርክር ያልቀረበበትና ሕጋዊ ተቀባይነቱም ጥያቄ ውስጥ ያልገባ የሰነድ ማስረጃ መሆኑን ክርክሩ በግልጽ ያሳያል።

በመሰረቱ አንድ ሰው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1195 ድንጋጌ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍልየምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊገመት እንደሚገባ ተመልክቷል። ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳየው በአስተዳደር አካሉ የሚሰጥ ማስረጃ የመብቱ ባለቤት የሆነውን ሰው ለመለየት ግምት የሚወስድበት እንጂ አሳሪ ወይም ድምዳሜ ማስረጃ /conclusive evidence/ ያለመሆኑን ይልቁንም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 ስር በተመለከቱት ውስን ምክንያቶች አግባብ ሊስተባበል የሚችል ሕጋዊ ግምት /rebuttable legal presumption/ መሆኑን ነው። በመሆኑም በፍ/ብ/ህ/ቁ 1195 ስር የተመለከተው የህግ ግምት ፍጹም የሆነ ወይም ድምዳሜ ማስረጃ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ስለመኖራቸው በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት ነው። በመሆኑም አንድ ሰው በአስተዳደር አካል የተሰጠ ካርታ በመያዙ ብቻ በካርታው የተጠቀሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ህጋዊ ባለሃብት እንደሆነ ህጉ ግምት ቢወስድለትም ይህ ግምት ግን ካርታው የተሰጠበትን አግባብ ከደንቡ ከአስራሩና ከሰልጣኑ ውጪ እንዲሁም በማይረጋ የምስክር ወረቀት መሰረት ማስረጃው ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ የህጉን ሕሊናዊ ግምት ማፍረስ እንደሚቻል ፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል። ይህንኑ የህጉን ይዘትና መንፈስ ካርታው ከመሰረዝ ጋር አስተሳስረን ስንመለከተውም አንድ የአስተዳደር አካል በሕጉ አግባብ የተሰጠን የባለቤትነት ማስረጃ በሕጉ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ዋጋ አልባ የሚያደርገው ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን በቀላሉ የምንረዳው ጉዳይ ነው። አንድ ሰው በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የባለቤትን መብት አቋቁሟል ለማለት የሚቻለው በህግ አግባብ የተገኘውን ማስረጃ መሰረት አድርጎ የመፋለም ክስ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አቅርቦ በጉዳዩ የሚቀርቡት ማስረጃዎች በሕጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተዘረጋውን የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ተከትለው ሲቀርቡና ማስረጃዎቹ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ባለው የማስረጃ ምዘና መርህ መሰረት ክሱን ማስረዳታቸው ሲረጋገጥ ነው።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በ1993 ዓ/ም ከአስተዳደር አካሉ የባለቤትን ማረጋገጫ ደብተር አግኝተዋል ተብሎ ማስረጃው መቅረቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 መሰረት ማስረጃው የተሰጠበትን ንብረት ባለሃብት ናቸው ተብሎ የሚገመቱት ተጠሪ ናቸው ተብሎ ግምት ለመውሰድ የሚያስችል ቢሆንም የክርክሩ ልዩ ባህርይ ሲታይ በተለይም የአከራካሪው ቤት ማህደር ውስጥ ነበሩ የተባሉ ሰነዶች ከጠፉ በኋላ ማስረጃው ለተጠሪ መሰጠቱ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ አለኝ በማለት ያቀረቡት ይኼው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ሕጋዊ ተቀባይነት እንዲሰጠው የማያደርገው ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ይህንን ለማስተባበል በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1196 በተደነገገው አግባብ ለተጠሪውየተሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከደንብ ውጪ በሆነ አሠራር ወይም ሥልጣን በሌለው አስተዳዳር ክፍል ስለመሆኑ በሰውም ሆነ በሰነድ ማስረጃው ያስረዱት ነገር የለም በማለት መደምደማቸው በክርክሩ ሂደት የቀረቡትን ሁሉንም ማስረጃዎች ያገናዘበ ሁኖ አልተገኘም። ሟች ደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ግብር በስማቸው መገበራቸው ወይም ውሃና መብራት በስም ማስገባታቸው ከሚመለከታቸው አካላት በቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን እነዚህ ማስረጃዎች በአመልካችና በተጠሪ መካከል አይነት በተነሳው ክርክር የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ለማረጋገጥ አይችሉም ተብሎ ማስረጃዎቹ ውድቅ የሚሆኑበት የማስረጃ ምዝና መርህ የለም። የበታች ፍርድ ቤቶች የባህር ዳር ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ውሃ በስም ሊገባ የሚችለው የይዞታ ባለቤትነት ሲረጋገጥ ነው በማለት የሰጠውን የሰነድ ማስረጃም በደፈናው በምን እንዳረጋገጠው የገለፀው ነገር ባለመኖሩ የሰጠው ማረጋገጫ ተቀባይነት አለው ብሎ ለመውሰድ የሚቻል አይደለም በማለት ከማለፋቸው በስተቀር የመስሪያ ቤቱ የተለመደ አሰራር አለመሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲቀርብ ያላደረጉ በመሆኑ ማስረጃው ተቀባይነት ያጣበት አግባብ ሕጋዊ ምክንያትን መሰረት አድርጎ አለመሆኑን ተገንዝበናል።

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ቤትና ቦታው የሟች አባታችን ነው በማለት ሲሆን ሟች አባታቸው መስከረም 06 ቀን 1984 ዓ.ም ባላደረጉትና ስርዓቱን ጠብቆ ባልቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ክርክር ያስነሳው ቤት የተጠሪ ነው መባሉ ያላግባብ ነው በሚል ነው። የስር ፍርድ ቤቶች ይህ የኑዛዜ ሰነድ ለማስረጃነት የቀረበበትን አግባብ በውሳኔውአቸው ላይ በግልጽ ባያሰፍሩም የአሁኑ ተጠሪ በዚህ የሰበር ደረጃ በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር ሰነዱ ቀድሞ ሊገኝ ባለመቻሉ የቀረበና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት ሲመልስም ጉዳዩ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ማስረጃዎች ጭምር እንዲጣራ ብሎ ስለአዘዘ ማስረጃው መቅረቡ ተገቢ ነው በሚል ነው። ይሁን እንጂ ይህ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ሁሉ አጣርቶ እንዲወስን በማለት የሰጠው ውሳኔ ስለማስረጃ አቀራረብ በህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ሁሉ ባላገናዘበ መልኩ ማስረጃው እንዲቀርብ በማሰብ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚገባ አይደለም። በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መቅረብ ያለባቸው በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት ጠብቀው ሊሆን ይገባል። ከዚህ አንጻር ተጠሪ አለኝ የሚሉትን የኑዛዜ ሰነድ በተመለከተ ለማስረጃነት ያቀረቡት ጉዳዩ ከዚህ ችሎት ከተመለሰ በኋላ ሲሆን ሰነዱ በማስረጃነት እንዲቀርብ የጠየቁበት አግባብም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 137(3) እና 256 ድንጋጌዎች ይዘት ጋር የተገናዘበ መሆኑን ያረጋገጡት ነገር የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል። የተጠሪ ምስክር የሆኑት እህታቸው ቀድሞ ክርክሩ ላይ የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሆን በዚህ ጊዜ ስለኑዛዜ ሰነዱ የሰጡት የምስክርነት ቃል ሳይኖር ጉዳዩ ወደ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲመለስ ቤቱ የተጠሪ መሆኑን ሟች ደጃዝማች በኑዛዜ አረጋግጠውላቸዋል የሚለው ምስክርነታቸው ቀድሞውንም ኑዛዜ መኖሩ ይታወቅ የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ምስክርነት ነው ሊባል የሚችልና ተጠሪ ሰነዱን በጊዜው ተገቢውን ጥረት አድርገው ማቅረብ ይችሉ የነበረ፣ ማቅረብ የማይችሉበት ምክንያት ካለውም ይህንኑ ለፍርድ ቤቱ ማሳወቅና በሌላ አግባብ ማስረዳት ይችሉ የነበረ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም የኑዛዜው ሰነድ ለማስረጃነት የቀረበበት አግባብ ከተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ውጪ ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ሰነዱን ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው ሟቹ በኑዛዜው ላይ ቤቱ የልጅ ቴዎድሮስ አንለይ በስሙ ቦታ ተመርቶ የሠራው ስለሆነ ቤቱ ከነቦታው መረከብ ይችላልብለው ማስፈራቸውን፣የኑዛዜው ቃል ይዘት ቤቱ የሟች ነው ተብሎ አሁን የተከሰተው ዓይነት ክርክር እንዳይፈጠር አስቀድመው አስበው ያደረጉት መሆኑን ነው በሚል ምክንያት ሰነዱ የማስረጃነት ዋጋ መስጠታቸው ተገቢነት የሌለውን የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ተፈጻሚ በማድረግ የደረሱበት ድምዳሜ በመሆኑ በሕግ ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አከራካሪው 440 ካ/ሜትር ቤትና ቦታ የተጠሪ ሃብት ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ ጉዳዩ እንዲጣራ ሲመለስ በክርክሩ ላይ በህግ አግባብ የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችን ይዘት ከክርክሩ ልዩ ባህሪና ተገቢነት ካለው የማስረጃ ምዘና መርህ ጋር ባለማገናዘብ ሁኖ ስለአገኘው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34051 የካቲት 20 ቀን 2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 88365 ታህሳስ 02 ቀን 2006 ዓ/ም ተሻሽሎ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 25679 ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
3. አመልካች 440 ካ/ሜትር ቤትና ቦታ ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል የተባለው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ አመልካች ብር 62,000 /ስልሳ ሁለት ሺህ ብር/ የቤት ኪራይ ለተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም፣ 220 ካ/ሜትር ቦታ ሊለቁ ይገባል ተብሎ የተሠጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. ተጠሪ በውርስ አግባብ አለኝ የሚሉትን መብት ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 08 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የአፈፃፀም ዕግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 97094

ቀን 08/03/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ አስቱር አምባው - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ አበባው ክፍሌ የቀረበ የለም

2. ያሬድ አለማየሁ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በከፋ ዞን የቦንጋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በስር ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 418 በአፈፃፀሙ ጉዳይ ጣልቃ የገቡ ሲሆኑ 1ኛ ተጠሪ የአፈፃፀም ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ የአፈፃፀም ተከሳሽ ነበሩ የአፈፃፀም ከሳሽ /የአሁንተጠሪ/ ለአፈፃፀም ይውሉ ዘንድ 1. የልብስ ስፌት ማሽን፣ ኮንትሮል ብፌ፣ የሴቶች ፀጉር ቤት ካስክ፣ ስሶት የፀጉር ማሽን፣ የፀጉር ቤት መስታወት፣ የመቀመጫ ወንበር፣ ባለ 21 ኢንች ቴሌቪዥን እና አራት የሶፋ ወንበሮች ተሸጦ እዳው ይከፈለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የተጠቀሱት ንብረቶች ተገመተው እንዲቀርቡለት ትዕዛዝ በመስጠቱ ምክንያት የአሁን አመልካች ንብረቶች የግሌ ናቸው በማለት ሊፈፀም አይገባም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሰረት በመቅረቧ ፍ/ቤቱም አመልካች ተጠቃሹ ንብረቶች የራሳቸው ለመሆኑ ያቀረቡት የፅሁፍ ሰነድ የለም፣ በሰው ምስክር አስረዳለሁ ያሉትን ክርክር በስነ ስርዓት ህጉ 418/3/ መሰረት ተቀባይነት የለውም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ በየደረጃው ያሉትም የክፍሉ ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ተቀብለውታል፡፡

የአመልካች አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልፁ 2ኛ ተጠሪ በእኔ ድርጅት ተቀጥሮ የሚሠራ ነው፤ ተጠቃሾቹ ንብረቶች የግሌ እና መጠቀሚያዎቼ ናቸው ብዬ ብቀርብምበሰው ምስክር ማስረዳት አይቻልም፤የፅሑፍ ሰነድ ካልሆነ በቀር በማለት ላቀርብ እችላለሁ ያልኩትን ሰነድ ሳይቀበለኝ ጥያቄየን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረምልኝ ይገባዋል ሲሉ አመልክተዋል፡፡

በዚህም መሰረት እኛም አመልካች በሰውና በሰነድ ንብረቶቹ የእኔ መሆናቸውን ላስረዳ እያሉ በሰው ማስረጃ ብቻ ማሰረዳት አይቻልም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግራ ቀኙ በቀረበው አቤቱታ ላይ መልስና የመልስ መልስ በፅሑፍ እንዲቀባበሉ ተደርጐ ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ የሚሉት 2ኛ ተጠሪ የአመልካች ባል ናቸው በአካሌ ላይ ጉዳት አድርሶብኝ እንዲፈፀምልኝ ያቀረብኩትን ንብረቶች አመልካች ለማስቀረት በማሰብ ነው የእኔ ንብረቶች ናቸው የሚሉት የራሳቸው ለመሆኑ በሰነድ ማቅረብ ባለመቻላቸው እና በሰው ማስረጃ አስረዳለሁ ማለታቸው ውድቅ መደረጉ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ነው፡፡የሚከራከሩት አመልካች በበኩላቸው በ2ኛ ተጠሪ ፍቃድ እኔ ንብረቶቹን አቀርቤ ቀጥሬያቸው ነው የሚሰሩት እንጂ የጋብቻ ግንኙነት የለኝም በስር ፍ/ቤት በሰነድና በሰው ማስረጃ ላስረዳ ብዬ እያመለከትኩ ይህ ታልፎ በሰው ማስረጃ ማስረዳት አይቻልም ተብሎ መወሰኑ ንብረቴን የሚያሳጣኝ ውሳኔ በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል ሲሉ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሱትን ይመስላል፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አኳያ መርምሯል፡፡

እንግዲህ አመልካች ተጠቃሾቹ ንብረቶች የእኔ ለመሆናቸው “ሰነድ” ማቅረብም እችላለሁ ስል እንዳቀርብ ከተፈቀደልኝ በኋላ ነው፡፡ ይህ ታልፎ በፅሁፍ ማስረጃ ብቻ ነው እንጂ በሰው ማስረጃ ማስረዳት አትችይም የተባልኩት ነው የሚሉት፡፡ በመሰረቱ የፍ/ብ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 ድንጋጌ አስፈላጊነት የክርክሩ አካል ያልሆኑና ፍርድ ያላረፈባቸው የ3ኛ ወገን ንብረት ሳይረጋገጥ የፍርዱ ማስፈፀሚያነት እንዳይውሉ ለመከላከልና ባንጻሩ ፍርዱን የመፈፀም ለማስተጓጐል (እንዳይፈፀም ለሚቀርቡት በቂ ላልሆኑ አቤቱታዎችም (መቃወሚያ) እልባት የሚሰጥ ነው፡፡ በመሆኑም በተያዙት ንብረቶች ላይ መብት አለኝ የሚል ወገን የሚያቀርበውን መቃወሚያና አቤቱታ ተቀብሎ መመርመር እንዳለበት የተጠቀሰው ድንጋጌም በግልፅ ያሰፈረውነው፡፡ ይህ ከሆነ የዚሁ አንቀጽ 418(3) የአራተኛው ቅጂ ባለይዞታነትን ለማስረዳት የፅሁፍ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበትየሚደነግግ ቢሆንም የእንግሊዘኛው ቅጂ የስነ- ስርዓት ህጉደግሞ ይህንኑ አንቀጽ ሲገልጽ The Claimant or 0bjector Shall adduce evidence to Show that and the date of the attachment he had Some interest in or was possessed of the property attached ይላል፡፡ እንግዲህ ከዚህኛው የእንግሊዘኛ ቅጂ የምንረዳው “ማስረጃ በማቅረብ ለአፈጻጸም የቀረበውን ንብረት ማስረዳት እንደሚቻል የሚገልጽ ነው፡፡ የአማርኛው ቅጂም ቢሆን ከፍ/ህ/ቁ/1193 (1) እና (2) ድንጋጌዎች ጋር ተደምሮ ሲታይ ሌላውን የማስረጃ አይነት በግልጽ እንዳይቀርብ የከለከለው ሆኖ አይታይም፡፡በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አመልካች አካራካሪውን የሚንቀሳቀስ ንብረት በሰው ማስረጃ ሊያስረዱ አይችሉም ሲሉ ያደረሱበትን ድምዳሜ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 418 ድንጋጌ መሰረታዊ አላማና የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ሀብቶችን ባለ ሃብትነት ለማስረዳት የሚጠቅሰውን የማስረጃ ዓይነት ያገናዘበ ሁኖ አልተገኘም በመጨረሻ በስር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሰው ማስረጃ ከወዲሁ ሳይሰማ ሰነድ አልቀረበም በማለት ጥያቄያቸውን ውድቅ በማድረጉ የማስረጃ አቀራረብ ስርዓትን ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የከፋ ዞን ቦንጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06403 በቀን 11/04/2006 ዓ.ም የሰጠው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10082 በ30/04/2006 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01555 በቀን 09/05/2006 ዓ.ም የተሰጡት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የቦንጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በጉዳዩ የቀረበውን የሰው ማስረጃ በመስማት አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች በመመርመር ተገቢነት ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መዝገቡን መልሰን ልከናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የወጪ ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ. 95587

ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ወ/ሮ ሐዋ በከር አቶ ጀማል የሱፍ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ቶፊቅ መሀመድ } ጠበቃ አቶ ፋይሶ ከድር ቀረቡ
2. አቶ አብዱሰላም መሀመድ }

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በሐዋ በከር የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 164559 ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይወሰንልኝ በማለት የሐዋ በከር ጠበቃ ነኝ በማለት አቶ ራጅ ገመቹ በአመልካች ስም ዕፈውና ፈርመው ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሐሮማያ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአውዳይ ፍርድ ቤት ጥር 30 ቀን 2004 ዓ.ም በሀዋ በከር ስም የቀረበለት ክስ ላይ የተከሳሾችን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተከሳሾች በከሳሽ የይዞታ ቦታ ላይ ግንባታ በማከናወን ሁከቱ የፈጠሩበት ስለሆነ ሀከቱ እንዲወገድ በማለት በመዝገብ ቁጥር 24494 ታህሣሥ 15 ቀን 2005 ዓ.ም. ውሣኔ ሰጥቷል፡፡
2. ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችን (ሀዋ በከርን) በመልስ ሰጭነት በመሰየምና መልስ ሰጭ በወኪሏ በኩል መልሷንና ክርክሯን እንዳቀረበች በማስፈር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመዝገብ ቁጥር 34942 ግንቦት 19 ቀን 2005 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ሀዋ በከርን በተጠሪነት በመሰየምና ተጠሪ በወኪል በኩል እንደተከራከረች በውሣኔው ውስጥ በማስፈር የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡
3. ይህንን ውሣኔ በማስለወጥ በሀዋ በከር ስም ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታና መጋቢት 15 ቀን 2006 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ ለዚህ ሰበር ችሎት ጠበቃው ራጅ ገመቹ ያቀረቡ ሲሆን ሐምሌ 15 ቀን 2006 ዓ.ም ሀዋ በከር በህይወት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሌለች መሆኑ ለፍርድ ቤቱ በመግለፅ፣የሀዋ በከር ወራሽ የወራሽነት ማስረጃውን እንዲያያይዙ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ መሰረት አቶ ጀማል ዮሱፍ ጥቅምት 12 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሃረሚያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25234 መጋቢት 6 ቀን 2004 በተፃፈ መሸኛ ሀዋ በከር ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየች መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠውን ፍርድና የወራሽነት ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ የቀረበውና እስካሁን ክርክሩ በሀዋ በከር ስም የቀጠለው ሟች ከሞተች በኋላ በመሆኑ ጉዳዩ ሊሰረዝልን ይገባል በማለት ጥቅምት 18 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀዋል፡፡

4. ይህችሎትሀዋበከር ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም በሞት ከተለየች በኋላ በሀዋ በከር ስም ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ሰበር እንዴት ክርክር እንደ ቀረበ ለማጣራት ግራ ቀኙን በቃል እንዲከራከሩ በማድረግ አጣርቷል፡፡ ጠበቃው አቶ ራጅ ገመቹ በመጀመሪያ ፋይሉን የከፈተው ጀማል ዮሱፍ ነው፡፡ እኔ ክርክሩ ከተጀመረ በኋላ ነው ጉዳዩን የያዝኩት በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን አቶ ጀማል ዮሱፍ በሟች ስም ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረብኩት እኔ ነኝ፡፡ ባለማወቅ ነው ክሱን ያቀረብኩት በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡
5. አጠቃላይ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀ ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደመረመርነው በሀዋ በከር ስም ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ እዚህ ሰበር ችሎት ክርክር ሲደረግ የነበረው ሀዋ በክር ከዚህ አለም በሞት ከተለየች ከህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም በኋላ ነው፡፡ ሀዋ በከር በህይወት እያለች ለአቶ ጀማል ዮሱፍ የሰጡት ውክልና ሀዋ በከር ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ውጤት እንደማይኖረውበፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2232(1) ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ጀማል ዮሱፍ ሟች ሀዋ በከር በሕይወት እያለች የሰጠችውን ውክልና በመጠቀም ጠበቃ ወክሎ ሟች በህይወት እንዳለች በማስመሰል ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስና ክፍያ ከዚያም በኋላ በይግባኝና በሰበር ያቀረበው ክርክር የሞተችው ሀዋ በክር በህይወት እያለች ሆኖ የቀረበ፣እስከ ሐምሌ 15 ቀን 2006 ድረስ ለሌሎች ፍርድቤቶችም ሆነ ለዚህ ችሎት ያልተገለፀና፣ ሀዋ በክር በህይወት እንዳለች ጀማል ዮሱፍ ወኪሏ እንደሆነና ወኪሏ ደግሞ ጠበቃ እንደወከለ ተደርጐ የቀረበ መሆኑን በመዝገቡ የቀረቡ ውሳኔዎችንና ሌሎች ክርክሮችን በመመርመር ተገንዝበናል፡፡
6. በአንድ ሰው ስም ፍርድ ቤት ቀርቦ ክስ ለማቅረብና ለመከራከር የሚችለው ዋናውባለጉዳይ ወይም ለዋናው ባለጉዳይ የወኪልነት፣የጠበቃነት ወይም የነገረ ፈጅነት ሥልጣን ያለው ሰው እንደሆነ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 57 ይደነግጋል፡፡በያዝነው ጉዳይ ጀማል የሱፍ የሟች ወራሽ መሆኑን ገልፆ በወራሽነቱ ያቀረበው ክስና ክርክር የለም፡፡ጀማል የሱፍ ሀዋ በከር በህይወት እያለች የሰጠችውን የውክልና ሰነድ በመጠቀም የሀዋ በከር ወኪል በመሆንና ጠበቃ በመቅጠር በሀዋ በከር ሥም ሟች ከሞተች በኃላ ክስ አቅርቧል፡፡ይህም ጀማል የሱፍ ሀዋ በከር በመሞቷ ምክንያት የተሰጠው የውክልና ሥልጣን ቀሪ ከሆነ በኃላ በወኪልነት ሥልጣኑ በመጠቀም ጠበቃ ያቆመ በመሆኑና ጠበቃውም ሀዋ በከርን በመወከል ጠበቃ ለመወከል ሥልጣን በሌለው ሰው ተወክሎ ክርክሩ ያቀረበ በመሆኑ ከወረዳው ፍርድ ቤት ጀምሮ በሀዋ በከር ስም እስከዚህ ችሎት ያቀረቡት ክርክር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2232/1/ እና የፍታሐብሔር ሥነ -ሥርዓት ሕግ ቁጥር 57 ድንጋጌዎችን የሚጥስና ህጋዊ ዕውቅናና ውጤት ሊሰጠው የማይገባው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

7. በመሆኑም ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በተለየችው ሀዋ በከር ስም ለሥር ፍርድ ቤት የቀረበ ክስና ከዚያም በኃላ ፍርድ ቤቶቹ ሀዋ በከር በህይወት እንዳለች በመገመትና በውሣኔያቸው በመግለፅ የሰጡት ውሣኔና ህጋዊ ዕውቅና ውጤት ሊሰጠው የማይገባ በመሆኑ በአመልካች ስም የቀረበውን ክርክርና የተሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሠርዘናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ክሱ የተጀመረውና እስከዚህ ሰበር ችሎት ክርክሩ የተደረገው ሀዋ በከር ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም በሞት ከተለየች በኃላ በሀዋ በከር ስም በመሆኑ ይህም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2232/1 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 57 ድንጋጌን የሚጥስ በመሆኑ በሟች ሀዋ በከር ስም የቀረበውን ክርክርና በየደረጃው ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ተሰርዟል፡፡
2. ሀዋ በከር በሞት ከተለየች በኃላ በስሟ የቀረበው ክስ፣ክርክር እንዳልቀረበና በየደረጃው የተሰጡት ፍርዶች ሁሉ እንዳልተሠጡ ይቆጠራሉ ብለናል፡፡
3. በሞት በተለየችው ሃዋ በከር ሥም ክርክር በማቅረብ በተጠሪዎች ላይ ለደረሰው መጉላላትና ኪሣራ አቶ ጀማል የሱፍ ብር 2000/ሁለት ሺ ብር/ ኪሣራ ተጠሪዎች ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::
እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 97332

መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አይመረ በላይ - ጠበቃ ሙሉአለም ዘውዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. መሪጌታ ኮነ ንጋቱ - ጠበቃ ተሾመ መኮንን ቀረቡ

2. አቶ አንዷለም አሻግሬ - ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ በፍርድ ቤት የተደረገ የጨረታ ሽያጭ ውድቅ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 14450 በሆነው ህዳር 4 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ሲታይም የአሁን1ኛ ተጠሪ ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በነበረባቸውና በወረዳው ፍርድ ቤት በተወሰነው የብር 15,000.00 ዋና ገንዘብ፣ የዚሁ ገንዘብ ወለድና የተለያዩ ወጪዎች ዕዳ መክፈያ እንዲሆን በአሁን አመልካች ስም ይታወቅ የነበረው በአዴት ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቤት በምስራቅ መንገድ፣ በምእራብ 16 ቁጥር፣ በሰሜን 15 ቁጥር፣ በደቡብ 19 ቁጥር በሚያዋስኑት መካከል የሚገኝ ቤት ባለሙያ ተገምቶ በአከባቢ ማስታወቂያ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ የአሁኑ አመልካች የሃራጁ አሸናፊ ሁነው ከተሸጠ በኋላ የ1ኛ ተጠሪ እዳ ለ2ኛ ተጠሪ እንዲከፈል፣ የተረፈው ገንዘብ ደግሞ ለአሁኑ 1ኛ ተጠሪ እንዲቀመጥላቸው የወረዳው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲሰጥ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በሐራጅ ሽያጩ ጉድለት እንደአለ ገልጸው አቤቱታ ቢያቀርቡም የወረዳው ፍርድ ቤት ጥያቄአቸውን ባለመቀበል መዝገቡን የዘጋባቸው ሲሆን በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት ስለአጡ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበው ችሎቱ በ1ኛ ተጠሪ አመልካችነት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ (የስር የፍርድ ባለመብትን) ብቻ ተጠሪ አድርጎ ክርክሩን ከመራ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት የዋለው የ1ኛ ተጠሪ ንብረት የጨረሻ መነሻ ግምቱ ብር 76,354.30 ሁኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጨረታ የተሸጠው ግን በብር 76,358.60 መሆኑ ቤቱ በአከባቢ ማስታወቂያ ለሰላሳ ቀናት ማስታወቂያው አየር ላይ ሳይውል መሸጡ በሽያጭ አካሄዱ ላይ ጉድለት መኖሩን የሚያሳይ ነው የሚል ምክንያት ይዞ በወረዳው ፍርድ ቤት ትእዛዝ የተካሄደውንና የፀደቀውን የጨረታ ሽያጭን እንዲሰረዝ በማለት ወስኖታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የጨረታው አሸናፊ የሆኑትን አመልካች ሳይጠራና የሐራጅ ሽያጩም ጉልህ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ አመልካች በግልጽ ተወዳድረው አሸናፊ የሆኑበትን የጨረታ ውጤት መሰረዙ ያላግባብ ነው፣ንብረቱም በሕግ አግባብ ለሶስተኛ ወገን ተሸጦ የሀራጅ ሽያጩ ወደ ነበረበት ቦታ ሊመለስ በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ይገኛል የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ሊቀርቡ ባለመቻላቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው የታለፈ ሲሆን1ኛ ተጠሪ ግን በመቅረባቸው ከአመልካች ጋር በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁኑን አመልካች ወደ ክርክሩ ሳያስገባ ክርክሩን መርቶ ዳኝነት መስጠቱና አመልካች ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ነው በማለት ያለመቀበሉ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች በጨረታው አሸናፊ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን ሽያጩ የሽያጭ ስነ ስርዓት ጉድለት አለበት ተብሎ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበው የፍርድ ባለእዳ በሆኑትና ለእዳው ማስፈጸሚያ ተብሎ የተሸጠው ቤት ባለንብረት የሆኑት የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ መሆናቸውን፣ይኼው ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት የሽያጭ ይፍረስልኝ ጥያቄ ተቀባይነት ሲያጣ ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲያቀርቡ ተጠሪ ያደረጉት የአሁኑን 2ኛ ተጠሪ ወይም የስር የፍርድ ባለመብት መሆኑን፣በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው የ1ኛ ተጠሪ ይግባኝ የተሰረዘው ተጠሪዎች ክርክር ሳያደርጉበት መሆኑን፣ከዚህ በኋላ 1ኛ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲያቀርቡ ተጠሪ ያደረጉት የአሁኑን 2ኛ ተጠሪ ሁኖ የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ የሰጠው የጨረታውን አሸናፊ የሆነውን የአሁኑን አመልካች ወደ ክርክሩ ሳያስገባ መሆኑን ነው፡፡

በመስረቱ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ለ)) እና እና በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 67(2(ሐ)) ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ያለመሆኑ ተጠቃሽ የሕግጋተ መንግስታት ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡ ሲሆን የክልሉን ፍርድ ቤቶችን ያደራጀው የክልሉ አዋጅ ቁጥር 153/2000 በአዋጅ ቁጥር 169/2002 እንደተሻሻለ በአንቀጽ 8 ስር ሰበር ችሎቱ ያለው ስልጣን መስረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የማረም ስልጣን እንጂ ፍሬ ነገርን ማጣራትና ማስረጃን መመዘን ስልጣን ያለመሆኑን ያስረዳል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚመራው ከላይ በተጠቀሰው የክልሉ የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅና በ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት መሰረት መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም ችሎቱ የተለየ የክርክር አመራር ስርዓት የሌለው እስከ ሆነ በ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ ክርክሩን መምራትና ዳኝነት መስጠት ያለበት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በ1958ቱ የፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ከተካተቱት ጉዳዮች መካከል ደግሞ የአፈፃፀም ክርክር የሚመራባቸው ድንጋጌዎች በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡ እንዲሁም ይኼው ሕግ በአንቀጽ 32 እና 79 ድንጋጌዎች ስር የፍትሃ ብሔር ድንጋጌዎች በሕጉ በተመለከቱት ሁሉም ጉዳዮች ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን እነዚህ ድንጌጌዎች የቀጥታ ክስና የይግባኝ ክርክሮች ላይ በስነ ስርኣቱ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን፣ የይግባኝ መብት ደግሞ በፍርድ አፈፃጸም ፍርድ ቤቱ በሚሰጣቸው ትዕዛዛት ላይ በፍርድ አፈፃፀም ደንብ መሰረት ሌሎቹ ትዕዛዞች ይግባኝ እንደሚባልባቸው ሁሉ ስለ አፈጻጸሙ በሚሰጠው ትዕዛዝ ይግባኝ ማለት የሚቻል መሆኑን በአንቀጽ 370(3) ስር ደንግጓል፡፡ የቀጥታ ክስ ወይም ይግባኝ ክርክር ሲመራ ተግባራዊ መሆን ከአላባቸው የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መካከል ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39 እና 40 ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማ በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ሲቀርብና የክሱም ምክንያት የብዙ ሰዎችን መብትና ጥቅም የሚነካ ሆኖ ከእነሱ አንዱ ወይም ከፊሉ ክስ በቀረበ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ መብትና ጥቅም የሚነካ ሲሆን በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ በማድረግ መብታቸውን ለማስጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም ይኼው በሕጉ የተቀመጠው መመዘኛ መሟላቱ ከተረጋገጠ በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡

እነዚህ ወገኖች ተካፋይ ሳይሆኑ የሚሰጠው ውሣኔ ወይም ፍርድ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑም የተጠቃሽ ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በክሱ መግባት ያለበት ተከሣሽ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የክርክር ተካፋይ እንዲሆንና በቀረበው ክስና መልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ ሊያዘው የግድ የሚል ስለመሆኑ ሥነ ሥርአቱ ያሳያል፡፡ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ማለት ደግሞ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው፣መብታቸው ወይም ግዴታቸው የሚነካ፣በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች ስለመሆናቸውም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በይግባኝ ደረጃ በሚደረገው ክርክርም ይግባኝ በቀረበበት የበታች ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ውስጥ ተካፋይ የነበረ ማናቸውም ሰው በይግባኝ ክርክሩ ላይ ተካፋይ ሳይሆን የቀረበ እንደሆነ የይግባኝ ውጤት የሚመለከተው መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሲረዳው የይግባኝ ክርክር መስሚያ ቀነ ቀጠሮ በማስተላለፍ ተካፋይ ያልሆነውን ሰው በመልስ ሰጪነት አባሪ ሆኖ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት ያለበት መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 40(5) በግልጽ የተመለከተ ሲሆን የሰበር ችሎት የሚመራው በዚሁ በይግባኝ ስርዓት የክርክር አመራር በመሆኑና በዚህ ድንጋጌ የተቀመጠው መመዘኛ ደግሞ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 447(4) ድንጋጌ ይዘት ጋር ሲታይ በጨረታ አሸናፊ የሆነ ሰውን ወደ ክርክሩ እንዲገባ ሳያደርግ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በፍርድ ቤት የሚደረግ ጨረታ በሕግ አግባብ የሚቋቋም ውል በመሆኑ የጨረታ አሸናፊ የሆነ ሰው የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ውሉ ፈራሽ የሚሆንበት አግባብ ከውል አመሰራረት መሰረታዊ መርሆዎችም ሆነ ከፍርድ አፈጻጸም ስርዓት ጋር የማይሄድ ከመሆኑም በላይ የፍርድ ቤት ክርክሮች በግልጽ ታይተው መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ ሕገ መንግስቱ ስል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገልፅነትና ተጠያቂነት ከተደነገገው መርህ ጋርም አብሮ የማይሄድ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት አይደለም፡፡ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ ውል መኖሩ በፍርድ ቤት የጸደቀለት ሰው ይኼው ውል በሕግ አግባብ ያልተደረገ ነው ተብሎ ፈራሽ ነው የሚል ውሳኔ ሲሰጥበት በዚሁ ላይ የሚያቀርበው ክርክር የማስረጃ ምዘና ብቻ ነው ተብሎ አቤቱታዋው በሰበር ሰበር ስርዓት የማይስተናገድበት አግባብ የለም፡፡ችሎቱ የጨረታ አሸናፊ የሰበር ክርክር የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የማያሟላ ነው የሚለውን ዳኝነት መስጠት ያለበትም ክርክሩን በሕጉ አግባብ ከመራ በኋላ ሊሆን ይገባል እንጂ አቤቱታ አቅራቢው ወደ ክርክሩ ገብቶ ተገቢውን ክርክር ሳያሰማ ሊሆን አይችልም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አምስት ዳኞች ተሰይመው የሰጡት ዳኝነት የጨረታውን አሸናፊ የክርክሩ ተካፋይ ያላደረገ ነው የሚለውን የአመልካችን ክርክር የማስረጃ ምዘና ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የአመልካችን የመሰማት መብትንም የጎዳ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች የሰበር አቤቱታ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ቅሬታዎችን መሰረት ያደረገ እንጂ የመሰረታዊ ህግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ አይደለም በማለት ትዕዛዝ መስጠቱ ከመነሻውም ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት ተከትሎ ባልተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔም ሆነ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 14450 ህዳር 04 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ እና በዚሁ መዝገብ ቀኑ ሳይጠቀስ የአመልካች አቤቱታ ማስረጃን መስማትን የሚጠየቅ ነው ተብሎ የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽርዋል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁኑን አመልካች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ አድርጎ በ1ኛ ተጠሪ በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ ግራ ቀኙ በሕጉ አግባብ እንዲከራከሩ በማድረግ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.101632

መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ. - ነገረ ፈጅ ብርሃኑ አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘይቱ ከማል - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ተጠሪ እና የተጠሪ ባለቤት ናቸው የተባሉት አቶ ኑሪ ከማል እንደቅደም ተከተላቸው ከሳሽ እና ተከሳሽ በመሆን ከፍቺ ጋር ተያይዞ ክርክር እያካሄዱ በነበረበት መዘገብ የአሁኑ አመልካች በተከሳሹ ግለሰብ ላይ በሌላ መዝገብ ላስፈረደው የብድር ዕዳ በንብረቱ ላይ አፈጻጸሙን መቀጠል ያስችለው ዘንድ ከፍቺ ክርክር ጋር ተያይዞ በተከሳሹ ስም ተመዝግቦ በሚታወቀው ቤት ላይ በከሳሽ ጠያቂነት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳለት በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 158 መሰረት ያቀረበውን አቤቱታ እና በአቤቱታው ላይ የተሰጠውን መልስ የመረመረው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዕግዱ ሊነሳ አይገባም በማለት የሰጠው ብይን እና ብይኑ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው በመሆኑ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው በመሆኑ ሊታረሙ ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩን በተመሳሳይ ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አስቀድሞ በመዝገብ ቁጥር 86400 በ21/09/2005 ዓ.ም. ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባው ዕግዱ ሊነሳ አይገባም በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይንጊዜያዊ አገልግሎት ያለው በመሆኑ ከስረ ነገሩ በፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ነጥብ አንፃር መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም መሰረት በአንድ ፍርድ ቤት በተሰጠ የማገጃ ትዕዛዝ ላይ ቅሬታ የተሰማው ወይም አላግባብ ነው የሚል ወገን ለፍርድ ቤቱ አቤቱታውን ያቀረበ እንደሆነ እና የቀረበውም አቤቱታ በቂ ምክንያት የሚያስገኝ መሆኑን የተረዳው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሰጥቶት የነበረውን የማገጃ ትዕዛዝ እንዲሻሻል፣እንዲነሳ ወይም ጨርሶ እንዲሰረዝ ለማድረግ እንደሚችል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 158 ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን የማገጃ ትዕዛዝ ይነሳልኝ ጥያቄው በመዝገቡ ተከራካሪ በሆነ ወገን ወይም የክርክሩ አካል ባልሆነ 3ኛ ወገን ጭምር ሊቀርብ የሚችል ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ የዕግድ ይነሳልኝ ጥያቄው የቀረበው በአመልካች ባንክ ሲሆን ተጠሪዋ ባለቤቱ ናቸው ከሚሏቸው ግለሰብ ጋር በሚከራከሩበት መዝገብ ባንኩ ተከራካሪ ወገን አይደለም፡፡ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዙ ላይ እንደገለጸው በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (4) ስር በተጠቀሱት ትዕዛዞች ላይ ካልሆነ በቀር ማናቸውም ፍርድ ቤት ክርክሩን በሚሰማበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ሲሰጥ፣ቀነ ቀጠሮ ሲወስን፣በመጀመሪያ ደረጃ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ሲሰጥ በእንደእነዚህ ዓይነቶቹ ትዕዛዞች ላይ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ማለት የማይቻል ስለመሆኑ እና ነገር ግን ለክርክሩ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ከዚህ በላይ በተገለጹት ትዕዛዞች ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን በስረነገሩ ፍርድ ላይ ከሚያቀርበው ቅሬታ ጋር አጠቃሎ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 320(3) ስር ተደንጓል፡፡

ከድንጋጌው አነጋገር በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው ድንጋጌው ጊዜያዊ አገልግሎት ባላቸው ትዕዛዞች ላይ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ማቅረብን የከለከለው የስረ ነገሩ ጉዳይ ውሳኔ ባገኘ ጊዜ በስረ ነገሩ ፍርድ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን በስረ ነገሩ ፍርድ ላይ ብቻ ሳይሆን አስቀድሞ በተሰጠበት ጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትዕዛዝ ላይም ቅሬታውን አጠቃሎ የማቅረብ መብት ስለተጠበቀለት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ባንክ የስረ ነገሩ ጉዳይ ተከራካሪ ወገን ስላልሆነ የስረ ነገሩ ክርክርም ሆነ በክርክሩ መጨረሻ የሚሰጠው ውሳኔ አይመለከተውም፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ ሊነሳ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ጭብጥ ላይ የሚሰጠው ትዕዛዝ ከአመልካች አንጻር እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር እንጂ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ነው የሚባል አይደለም፡፡በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከዚህ አንጻር በመገንዘብ የቀረበለትን የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ ሊሰጥበት ሲገባ ብይኑ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው በመሆኑ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት መዝገቡን ዘግቶ መመለሱ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 320(3) ድንጋጌን እና ዓላማ እና ይዘት ያገናዘበ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የእግድ ትዕዛዙ ሊነሳ አይገባም በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው በመሆኑ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የዕግድ ትዛዙ ሊነሳ አይገባም በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 206422 በ03/07/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ብይን ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ስለሆነ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት በመዝገብ ቁጥር 150681 በ15/08/2006 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሮአል፡፡

2. የዕግድ ትዛዙ ሊነሳ አይገባም በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 206422 በ03/07/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ብይን ከአመልካች ባንክ አንጻር የመጨረሻ እንጂ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ይህንኑ ተገንዝቦ የቀረበለትን ይግባኝ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት ወስነናል፡፡በዚሁ መሰረት ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 103781

ቀን መጋቢት 17/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተሽሊት ይመስል

አመልካች ፡- ወ/ሮ አስካለ አሸኔ - ጠበቃ በርታ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ታምራት ተስፋዬ - ጠበቃ አሸናፊ ቦሻ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በመዝገብ ቁጥር 197469 ጥር 12 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150493 ግንቦት 5 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የፍች ውሳኔን በመቃወም የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ የአባቱ የአቶ ተስፋዬ ጉልማ አሳዳሪና ሞግዚት መሆኑን ገልፆ፣የአቶ ተስፋዬ ጉልማና አመልካች 1964 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሣስረው ኖረዋል፡፡በትዳራቸው ልጆች አላፈሩም ፡፡ አባቴና ሞግዚት አድራጊና በእድሜ በመግፋታቸው ምክንያት የአእምሮና የጤና መታወክ አጋጥሟቸዋል፡፡ ተጠሪ ባላቸውን ሊንከባከቡዋቸው አልቻለም በዚህ ምክንያት ሁለቱ ተለያይተው መኖር ከጀመሩ ረዥም ጊዜ ሆኗቸዋል ፡፡ ስለዚህ ሞግዚት አድራጊዬ ከተጠሪ /አመልካች /ጋር ያላቸው ጋብቻ በፍች እንዲፈርስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ የአሁን አመልካች /በሥር ተጠሪ/ለፍች የሚያበቃ ምክንያት የለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አቶ ተስፋዬ ጉልማ በአካል በተደጋጋሚ እያስቀረበ ካነጋገረ በኃላ በአቶ ተስፋዬ ጉልማና በአመልካች መካከል በፍች እንዲፈርስ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡
2. አመልካች ተጠሪ ፍች እንዲወሰን የማመልከት ስልጣን የለውም ፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የፍች ውሣኔ ህግን መሠረት ያደረገ አይደለም በማለት ነሐሴ 5 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ከሞግዚት አድራጊዬ ጋር የባልና የሚስት ግዴታ እየተወጡ አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠው ሞግዚት አድራጊዬን በተደጋጋሚ አስቀርቦ ሁኔታውን ከተረዳ በኃላና በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ መሠረት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪን የፍች ጥያቄ በመቀበል የሰጡት የፍች ውሳኔ ሕግን መሠረት ደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
4. በመርህ ደረጃ የፍች ጥያቄ ለማቅረብ የሚችሉት ባል ወይም ሚስት ወይም ሁለቱም በጋራ ጥያቄ በማቅረብ እንደሚሆን በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/992 አንቀፅ 81 ተደንግጓል ፡፡ ሆኖም አንድ ሰው ጋብቻ ፈፅሞና በጋብቻ ተሣሥሮ ከኖረ በኃላ በፍርድ ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜ የፍች ጥያቄ የሚያቀርበው በምን ሁኔታና እንዴት ነው የሚለው ጥያቄ ሲነሳ በፍታብሔር ሕግ በፍርድ ስለሚደረግ ክልከላና ክልከላው ስለሚያስከትለው ውጤት ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 351 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 389 የተደረጉትን ድንጋጌዎች መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይም የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 370 ንዑስ አንቀፅ 1 ፍች ወይም ከሕግ ውጭ የሚያደርገው የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲቀር ጥያቄ ለማቅረብ የተከለከለው ሰው ፈቃድ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ የአሳዳሪውም ፈቃድ የግድ አስፈላጊ ነው በማለት ይደነግጋል ፡፡
5. ከዚህ አንፃር የአቶ ተስፋዬ ጉልማ አሳዳሪና ሞግዚት ሆኖ የተሾመው ተጠሪ ሞግዚት ሆኖ የሚያስተዳድራቸው ወላጅ አባቱ ፤በእድሜ በመግፋታቸው ምክንያት ራሳቸውን ችለው ህጋዊ ተግባራት መፈፀም እንደማይችሉ በፍርድ ተረጋግጦ ክልከላ የተደረገባቸው መሆኑንና አመልካችና አቶ ተስፋዬ ጉልማ ተለያይተው ለረጅም ጊዜ መኖራቸውን በመግለፅ ፍች እንዲወሰን ጠይቋል፡፡ ይህም ተጠሪ የፍታብሔት ህግ ቁጥር 370 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ጋብቻው በፍች አንዲፈርስ ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን ያሳያል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ፤አቶ ተስፋዬ ጉልማ በተደጋጋሚ ችሎት በማስቀረብና ካናገረ በኃላ አመልካችና አቶ ተስፋዬ ጉልማ በቤተሠብ ህጉ በባልና ሚስት ላይ የተጣለውን እርስ በእርስ የመተጋገዝ የመረዳዳት ፣የመደጋገፍና የመተሳሰብ ግዴታ እየተወጡ አለመሆኑን በማረጋገጥ ጋብቻው በፍች እንዲፈርስ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ አመልካችና አቶ ተስፋዬ ጉልማ በሕግ ፊት ባልና ሚስት ናቸው ቢባልም በዕውኑ ግን በባልና ሚስትነት የመፈፀማቸውን ተግባራትን ግዴታዎች እየፈፀሙ የማይኖሩ መሆኑንና የጋብቻው በፍች መፍረስ በፍርድ ክልከላ የተደረገባቸውን አቶ ተስፋዬ ጉልማ መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠው ውሳኔ መሆኑን በውሣኔ ተረድተናል ፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል ፡፡
2. ይህ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 103781 ህዳር 17 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡ ይዛፍ፡፡
3. ግራቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስትዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሥሪና ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 95638

መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ሕይወት

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡-ኢስት ሲሜንት አክሲዩን ማህበር - ጠበቃ ዓለሙ ደነቀው - ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ዘላለም ታደሰ - ጠበቃ ገናናው ተሾመ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የቀረበውን የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረበት ፍርድ ቤት የሂደቡ አቦቴ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡በዚህ ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ሁኖ የክሱ ይዘትም፡-በተጠሪ ድርጅት በአስተዳደር ኃላፊነት እና ጉዳይ አስፈፃሚነት አምስት አመት ከዘጠኝ ወር ብር 6,410.90 በወር እየተከፈላቸው ማገልገላቸውንና የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ መቋረጡን ገልጸው ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ የነበረ ቢሆንም መጥሪያ ደርሶታል፣ግን አልቀረበም ተብሎ በሌለበት ጉዳዩእንዲታይ ተደርጓል፡፡የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ አመልካች ለክሱ ኃላፊ ነው ተብሎ ለከሳሽ ብር 277,294.00 (ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አራት) ብር እንዲከፈል ወሰኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሌለሁበት ታይቶ የተወሰነው ውሳኔ ተነስቶ ባለሁበት ይታይልኝ በማለት ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተጨማሪ ከሳሹ የአሰሪ ወገን ስለሆነ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ሊዳኙ አይገባም፣በአዋጁ መሰረት ሊዳኝ ይገባል ከተባለም የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጋዊ መንገድ ስለሆነ ሊፈጸም የሚገባ ክፍያ የለም፣ክፍያ ሊፈፀም ይገባል ከተባለም ከሳሽ ደሞዜ ነው ብሎ ያቀረበው መጠን ትክክል አይደለም፣በትክክል ደመወዙ ላይ ተመስርቶ ሊከፈል የሚገባውም የደመወዙን $\frac{1}{10}$ ኛውን ያህል ብቻ ነው ብሎ ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤት በአመልካች በሌለሁበት ታይቶ የተወሰነው ውሳኔ ይነሳልኝ ጥያቄ ላይ የአሁኑ ተጠሪ (የስር ከሳሽ) አስተያየት እንዲሰጡበት ያደረገ ሲሆን ተጠሪው በሰጡት አስተያየትም ለአመልካች መጥሪያውን ባቀረቡት የቃለ መሓላ አቤቱታ የተዘረዘሩ ምስክሮች የሚያረጋገጡ መሆኑን እና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው የተወሰነውም በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ጉዳዩ ባለሁበት ይታይልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፣በቃለ መሐላ ተረጋግጧል በማለት ውሳኔ ሰጠ ፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት አቅርቦ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ መጥሪያው በሕጉ መሰረት ለአሁኑ አመልካች የደረሰው መሆንያለመሆኑን የግራ ቀኙን ምስክሮችእንዲሰሙና ተገቢው እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡ በዚህ አግባብ ጉዳዩ የተመለሰለት የወረዳው ፍርድ ቤትም በ18/03/2004 ዓ/ም የአሁኑ ተጠሪ ለወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ቃለ መሃላ ላይ ያሉትን ምስክሮችን ከሰማ በኋላ የአሁኑ አመልካች ደግሞ የቀረቡት ምስክሮች ይበቁናል ስላለ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ መጥሪያው ለአመልካች መድረሱ ተረጋግጧል በማለት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ አይነሳም ሲል በ24/05/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት ወሰኗል፡፡በዚህ ውሳኔ ላይ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ይግባኙን አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ መሰማት የሚገባቸው ምስክሮች በ18/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ የተጠሪ ቃለ መሃላ ላይ ያሉት ምስክሮች ሳይሆኑ በ26/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ መሃላ ላይ ያሉት ምስክሮች ናቸው በማለት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መመሪያ መሰረት የወረዳው ፍርድ ቤት አልፈጸመም ሲል በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ በ28/06/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት ሽሮ በ26/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ መሃላ ላይ ያሉት ምስክሮች እንዲሰሙ ሲል ጉዳዩን ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡የአሁኑ ተጠሪ በዚህ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ችሎቱ መሰማት የሚገባቸው በ18/03/2004 ዓ/ም በተፃፈ ቃለ መሃላ ላይ የተዘረዘሩት ምስክሮች ናቸው? ወይስ በ26/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ መሃላ ላይ የተገለፁት ምስክሮች ናቸው? የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር የወረዳው ፍርድ ቤት በ12/03/2004 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ የተከሳሽን መልስ ለመቀበል ብሎ ለ18/03/2004 ዓ/ም መቅጠሩን፣በዚህ ቀን ከሳሽ ለተከሳሽ መጥሪያ ማድረሱን በመግለፅ በቃለ መሃላ የተከሳሽ መልስ የመስጠት መብት መታለፉን፣በ26/03/2004 ዓ/ም ደግሞ ከሳሽ ደመወዝ ሲበላበት የነበረ ፔሮል ለተከሳሽ ድርጅት እንዲያቀርብ የታዘዘ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳቱን ጠቅሶ መሰማት ያለባቸው ምስክሮች በ18/03/2004 ዓ/ም በተፃፈው ቃለ መሃላ ያሉት ምስክሮች እንጂ በ26/04/2004 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ መሃላ የተገለፁ ምስክሮች አይደሉም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በ20/01/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሠጠውን ውሳኔ ሽሮ የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲሆን የአመልካች የሠበር አቤቱታ ቅሬታ መሰረታዊ ነጥቦችም፡-የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለወረዳው ፍርድ ቤት የመለሰው በ26/03/2004 ዓ/ም በተፃፈ ቃለ መሃላ የተገለፁትን ምስክሮች እንዲሰሙ ሁኖ እያለ መልሶ መሰማት ያለባቸው በ18/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ መሃላ የተገለፁትን ምስክሮች ናቸው ማለቱ ተገቢነት የለውም፣የተጠሪው ደመወዝ ተጠሪው እንደገለፀው ብር 6,410.00 ሳይሆን ብር 3,230.70 ብቻ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የስራ ስንብት ክፍያ ብር 47,383.60 እንዲሆን መወሰኑ ያላግባብ ሲሆን የስራ ስንብት ክፍያው ብር 8,348.00 ብቻ ነው፣የካሳ ክፍያ ብር 19,384.00 መሆን ሲገባው ብር 25,849.60 መሆኑ ያላግባብ ነው፣የሳምንት የእረፍት ክፍያ ሊተመን በማይችል ስሌት ብር 188,784.57 ሁኗል፣የአምስት አመት በዓል በማለት ብር 16,357.00 እንዲከፍል መወሰኑ ያላግባብ ነው፣የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው የሚባል ከሆነም ሊከፈሉ የሚገባቸው ክፍያዎች፤-የአገልግሎት ክፍያ ብር 8,384.30፣የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ ብር 6,461.40፣የካሳ ክፍያ ብር 19,384.20 በድምሩ ብር 34,229.90 እንጂ ብር 277,294.00 እንዲከፈል መወሰኑ ያለአግባብ ነው በማለት በዚህ ችሎት እንዲወሰን የጠየቀው ዳኝነትም የአመልካች የመከራከር መብቱ እንዲጠበቅለት፣ይህ የሚታለፍ ከሆነ በአዋጁ መሰረት ክፍያዎቹ መወሰን አለባቸው የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡የሠበር አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ጉዳዩ እንዲታይ የተደረገው ከአመልካች ማንነት አንፃር ይህንኑ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀብሎ ማየቱ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው በሰጡት መልስም ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ስለሆነ አዋጁ ከወጣበት ጊዜ አንጻር በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የማይታይበት ምክንያት የለም፣ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ስለሆነ በዚህ ችሎት የሚታይ አይደለም፣በሌለበት በታየ ጉዳይ በስንብቱ እና በደመወዝ መጠኑ ሊከራከርአይችልም፣ተጠሪ የአሰሪ የአስተዳደር አካል ያለመሆናቸው በማስረጃ ተረጋግጧል፣በቃለ መሃላ ጉዳይ ላይ ማስተባበያ ማስረጃ አላቀረበም፣የተጠሪ ምስክሮች የእኔም ምስክሮች ናቸው በማለት መግለፁን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፣የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ራሱ የሰጠውን ውሳኔ አልሻረም፣በ26/03/04 በተጻፈ ቃለ መሃላ የተገለጹት ምስክሮች የሚሰሙበት ምክንያት የለም፣በዚህ ቀን የቀረበው ቃለ መሃላ የስር ተከሳሽ ከሳሽ የሚበላውን ደመወዝ መዝገቡን እንዲያቀርብ በ22/03/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ አዞት ስለነበር ተከሳሹ የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ አልፈፀመም፣የፍርድ ቤቱን መጥሪያአልወስድም ማለቱን ለማረጋጋጥ ነው፣ በማለት ዘርዝሮ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 163369 በ20/01/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካችም ያስቀርባል የተባለበትን ነጥብ በመደገፍና በሰበር አቤቱታው ላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦችን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

ከዚህም በኋላ ይህ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች መጀመሪያ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለት ለወረዳው ፍርድ ቤት አመልክቶ ተቀባይነት ካጣ በኋላ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ሲያቀርብ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ስርዓቱን ጠብቆ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መከራከሩን ለማወቅ ይረዳ ዘንድ የወረዳው ፍርድ ቤት መጀመሪያ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ ግልባጭ፣አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ግልባጮችን እንዲያያይዝ ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካችአሉኝ ያላቸውን ውሳኔዎችን አያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክርና ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩመርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች፡-

1. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ወይስ የለም?
2. የአመልካች የመከራከር መብት የታለፈው በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?
3. የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎችን ለተጠሪ እንዲከፍል በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም?

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ</u> በተመለከተ፡-በመሰረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግስትና በክልሎች መዋቀሩን መሰረት በማድረግ የዳኝነቱም ሥልጣን በፌዴራል መንግስቱ እና በክልል መንግስታት መካከል እንደተከፋፈለ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 50 እና 51 ሥር ተመለክቷል፡፡በኢ.ፌ.ዲ.ሪሕገ መንግስት በአንቀጽ 80 “የፍ/ቤቶች ጣምራነትና ሥልጣን” በሚል ርዕስ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻየዳኝነት ሥልጣኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት፣በክልል ጉዳዮች ላይ በክልሉ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሥልጣኑ የተደነገገ ሲሆን የክልል ፍ/ቤቶች በህገ-መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት ካልሆነ በቀር የፌዴራልን ጉዳይ ለማየት፣እንዲሁም የፌዴራል ፍ/ቤቶች የክልልን ጉዳይ ለማስተናገድ የሚያስችል ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን በዚሁ ድንጋጌ ስር የተቀመጡት ንዑስ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያሳያል፡፡አንድ ጉዳይ የፌዴራል ነው? ወይስ የክልል? የሚለውን ለመለየትም መሰረቱ የአዋጅ ቁጥር 25/88 ሲሆን፤በዚሁ ህግ አንቀጽ 5 ሥር በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የክልል ፍ/ቤቶችስልጣን የሚኖራቸው በህገመንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን አግባብ ብቻ ነው፡፡ይህ በግልፅ የሚያሳየው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 መሰረት የፍርድ ቤቶች ስልጣን በጉዳዩ ባለቤትነት (Subject matter) የሥልጣን ክፍፍል እንደተጠበቀ ሆኖ ክሱም መቅረብ ያለበት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ስለመሆኑ ነው፡፡የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8፣11፣14 እና 15 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ደግሞ አንዳንድ ጉዳዮች ሊያስነሱ በሚችሉት የክርክር ባህርይ ምክንያት ለተወሰኑ ፍ/ቤቶች እንዲቀርቡ በህግ ተለይተው ከተመለከቱት በቀር የሥረ-ነገር ሥልጣን የተደለደለው በክሱ በተመለከተው የገንዘብ ወይም የንብረት ግምት መነሻ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 14 እና 15 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌች ጣምራ ንባብ እና የክልል መንግስታት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ሕጎች ያስረዳሉ፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን አዋጅ ቁጥር 25/1988"ን" ያወጣው የፌዴራል መንግስት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የስራ ክርክሮች የሚመሩበትን ስርኣት የዘረጋውን አዋጅ ቁጥር 377/1996 ከየካቲት 18 ቀን 1996 ዓ/ም ስራ ላይ ያዋለ ሲሆን በዚህ አዋጅ የስራ ክርክር ስልጣን ድልድል የተደረገው የግል የስራ ክርክርና የወል የስራ ክርክር የሚሉትን ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ ሲሆን የተከራካሪ ወገንን ማንነትን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ አይደለም፡፡በመሆኑም ክርክሮቹ ክልል የተነሱ ቢሆንም ጉዳዩን የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም አግባብነት ያላቸው የቋሚ ወይም ጊዜአዊ ቦርዶች ሊመለከቱ እንደሚችሉ አድርጎ ሕጉን ሕግ አውጪው አውጥቷል፡፡ይህ አዋጅ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 በኋላ ከመውጣቱም በላይ ለስራ ክርክሮች ልዩ ሕግ ነው፡፡እንዲህ ከሆነ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ለስራ ክርክሮች ከሕገ መንግስቱ በመለስ ባሉት ማናቸውም ሕጎች የበላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያስረዱን ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም በስራ ክርክር ተከራካሪ ወገኖች ማንነት የፍርድ ቤቶችን ስልጣን (የክልል ወይም የፌዴራል) ብሎ ለመወሰን እንደወሳኝ መለኪያ ሊወሰድ የሚገባው አይደለም፡፡ከዚህ አንጻር ሲታይ ደግሞ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ ማየቱ ከላይ የተመለከተውን የህጉን ማዕቀፍ እና በዚህ ረገድ ይህ ችሎት በመ/ቁጥር 95298 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በአከራካሪው የህግ ነጥብ ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር የተጣጣመ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበትን አግባብ አላገኘንም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር94 ስር እንደተመለከተው መጥሪያ በቅድሚያ መድረስ ያለበት ለተከሰሰው ሰው ሲሆን የተከሰሰው ሰው የንግድ ድርጅት ከሆነ ደግሞ ከድርጅቱ ጸሃፊ ወይም ለድርጅቱ ኃላፊ መሰጠት ያለበት መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 97(1) ስር ተመልክቷል፡፡ሕጉ መጥሪያ አሰጣጥ ዘዴና ቅደም ተከተሉ እንዲሁም መጥሪያው ለማን እንደሚሰጥ የሚመለከተው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ክፍል ዓይነተኛ ዓላማ ከሆኑት መካከል አንዱ ተካራካሪ ወገኖችን እኩል የመከራከር መብት እንዲኖራቸው በማድረግ ጉዳዩን ፍትሐዊ በሆነ አኳኋን ለመወሰንማስቻል መሆኑን ይታወቃል፡፡በመሆኑም ፍርድ ቤቱ መጥሪያ የሚደርስበትን ተገቢ መንገድና ለማን መድረስ እንዳለበት ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡

መጥሪያ በተገቢው መንገድ ደርሶት ተከራካሪ ወገን ካልቀረበ ወይም መጥሪያን አልቀበልም ካለ ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ስርዓትም በሕጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህም ድንጋጌዎች መካከል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 70(ሀ)፣103፣104፣105፣ 106 እና 107 ስር የተመለከተው ሊጠቀሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችሉ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩ ታይቶ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው መጥሪያው በአግባቡ የደረሰው መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ ወይም ሊገኝ ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌዎቹ መጥሪያው በትክክል ያልደረሰው መሆኑ ከተረጋገጠ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ የማይታዘዝ ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 70(ሀ) ድንጋጌ ስር ላይ **"መጥሪያው በትክክል መድረሱ"** የሚለው ሐረግ መኖሩም የሚያሳየው ስለመጥሪያ አሰጣጥና አደራረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 94 እስከ 110 ድረስ የተመለከቱት ሁኔታዎች በአግባቡ መሟላታቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡አንድ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ ከተሰጠውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሰረት መፍትሔ መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት መፍትሔ ሊጠየቅ የሚችለው አቤቱታ አቅራቢው በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ የጥሪው ትዕዛዝ "በሚገባ ያልደረሰው" መሆኑን በመጥቀስ ይህንኑ ማረጋገጥ ሲችል ነው፡፡ከእነዚህ ሁሉ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው አንድ ሰው የመከራከር መብቱን እንደተወው የሚቆጠረው መጥሪያው በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓትና ቅደም ተከተል መሰረት ደርሶት ክርክር ያለው መሆኑን እያወቀሳይቀርብ ሲቀር ብቻ መሆኑን ነው፡፡ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትሎ አማራጭ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት ከፈጸመ መጥሪያው ለተከሳሹ እንደደረሰ እንደሚቆጠርና በቂና ሕጋዊ ምንክያት ካለው ብቻወደ ክርክሩ እንዲገባ የሚፈቀድ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም ማንኛውም ውሳኔ መሰጠት ያለበትም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት መጥሪያው መድረሱ በሚገባ የተረጋገጠና የተከሳሽ የመከራከር መብት የተጠበቀ መሆኑ ሲታወቅ ሊሆን ይገባል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በወረዳው ፍርድ ቤት በነበረው ክስ ተጠሪ ለአመልካች ድርጅት መጥሪያውን እንዲያደርሱ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ መጥሪያውን ይዘው "ለድርጅቱ ኃላፊ ልሰጥ ስል ኃላፊው አልቀበልም ብለውኛል" በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 103 መሰረት በቃለ መሃላ አረጋግጠው መጥሪያውን የመለሱ ሲሆን ለዚህም ምስክሮች ያላቸው መሆኑን ጭምር ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት በ18/03/2004 ዓ/ም እና በ26/03/2004 ዓ/ም የተጻፉ ሁለት ቃላ መሃላዎችን ያቀረቡ ሲሆን አሁን በዚህ ረገድ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው በየትኛው ቀን የተዘረዘሩት ምስክሮች ናቸው ስለመጥሪያው አደራረስ ሊመሰክሩ የሚገባቸው? የሚል ነጥብ ነው፡፡ከላይ እንደተገለጸው የተጠሪ የመጥሪያ አደራረስ በቃለ መሃላ ተደግፎ የቀረበ ቢሆንም መጥሪያውን ለአመልካች ድርጅት ያደረሱ መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ ምስክሮች እንዲሰሙ በማለት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 148159 ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ/ም ተወስኖ ጉዳዩ የተመለሰለት የወረዳው ፍርድ ቤትም በ18/03/2006 ዓ/ም በተፃፈው ቃለ መሃላ የተጠቀሱትን ምስክሮች የሠማና ምስክሮቹ መጥሪያውን ተጠሪ ለአመልካች ድርጅት ማድረሳቸውንና የአመልካች ድርጅት ኃላፊ አልቀበልም ማለታቸውን ማረጋገጣቸውን ምክንያት አድርጎ የአመልካችን በሌለሁበት ታይቶ የተወሰነ ውሳኔ ይነሳልኝ ጥያቄን ሳይቀበለው የቀረ ሲሆን ይኼው የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ በክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ እንግዲህ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 148159 በ26/02/2005 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ ስለመጥሪያው አደራረስ የግራ ቀኙ ምስክሮች እንዲሰሙ ተብሎ ለወረዳው ፍርድ ቤት ከመመለሱ ውጪ በ26/03/2004 ዓ/ም በተጠሪ ለወረዳው ፍርድ ቤት በቀረበው ቃለ መሃላ የተጠቀሱት ምስክሮች እንዲሰሙ በግልጽ የተሰጠ ውሳኔ የለም፡፡በ26/03/2004 ዓ/ም ቀረበ በተባለው ቃለ መሃላ ያሉት ምስክሮችም አመልካች የተጠሪን ደመወዝ መጠን ለማወቅ ይቻል ዘንድ መዝገቡን እንዲያቀርብ የወረዳው ፍርድ ቤት በ22/03/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቶ ስለነበር አመልካች የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ አልፈፀምም፣የፍርድ ቤቱን መጥሪያአልወሰድም ማለቱን ለማረጋጋጥ የቀረቡ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሁኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግኝተናል፡፡እንዲህ ከሆነ በ26/03/2004 ዓ/ም በቀረበው ቃለ መሃላ የተጠቀሱት የተጠሪ ምስክሮች ስለመጥሪያ አደራረስ የሚሰሙበት የሕግ አግባብ የለም፡፡አንድ ማስረጃ መሰማት የሚገባው ለጉዳዩ አግባብነት ሲኖረው ስለመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ሕግ ደንቦች የሚሳዩት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነምአመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡በ18/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ የተጠሪ ቃለ መሃላ የተጠቀሱት ምስክሮች መሰማታቸው ተገቢ ነው ከተባለ እነዚህ ምስክሮች አመልካች መጥሪያ ደርሶት አልቀበልምበማለት ተጠሪን የመለሳቸው መሆኑን ያረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳይ በመሆኑ የተጠሪ የመከራከር መብቱ መታለፉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 97(1)፣103፣70(ሀ) እና 78 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ተገቢ እንጂ የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡

<u>ሦስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>አመልካች ተጠሪን ያሰናበተበትን ሕጋዊ ምክንያት በዋናው ክርክር ያለበቂ ምክንያት ባለመቅረቡ አላስረዳም፡፡ይልቁንም ተጠሪ አመልካች ከህግ ውጪ ያሰናበታቸው መሆኑን በወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ማስረጃ ያረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡በመሆኑም የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት የሚለወጥበት አግባብ የለም፡፡በመሰረቱ አንድ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ በተሰጠው በዋናው ጉዳይ ላይ ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ የይግባኝ አቀራረብ አድማሱ በተወሰኑት ነጥቦች ላይ ብቻ መሆን እንዳለበት የይግባኝ አቀራረብን በተመለከተ የተደነገጉት ድንጋጌዎች መንፈስ እንደሚያስረዳና ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተወሰነበት ተከሣሽ ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ በስር ፍ/ቤት በተከራካሪነት ቀርቦ ያላነሣውን ነጥብ ማንሳት እንደማይችል፣እንደዚህ ዓይነት ተከራካሪ በፍ/ቤቱ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ክሱን፣የማስረጃዎችን አግባብነት ተቀባይነት እና ጥንካሬ ባግባቡ ያላገናዘበ ሁኔታ አለ የሚል ከሆነ ይግባኝ ሊያቀርብ እንደሚችል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 36412 በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም ፍ/ቤት ከሣሹ ያቀረበው ክስ አባሪ ሆነው ከቀረቡት ማስረጃዎች አግባብነት፣ተቀባይነትና ጥንካሬ አኳያ በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት አልሰጠም በሚል ይግባኝ የማቅረብና ወደ ቀጣዩ የሰበር ደረጃም ቅሬታውን ማድረስ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ ውሳኔ ለተሰጠበት ወገን በሕግ የተጠበቀለት መብት መሆኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የወረዳው ፍርድ ቤት በ29/03/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ብሎ ሲወሰን በዚህ ውሳኔ ተጠሪ የሚከፈለኝ ገንዘብ በግልጽ አልተቀመጠልኝም በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አይቶ ለስር የተጠሪ ደመወዝ ተጣርቶ ሊታወቅ ይገባል፣ከዚህ በኋላ የማስጠንቀቂያ፣የስራ ስንብት ክፍያ እና ካሳ፣የሳምንት፣የአመት እና የበዓል ቀናት ክፍያዎች እንዲሁም ያልተከፈለው ደመወዝ ታስቦ በግልጽ መቀመጥ አለበት በማለት በመ/ቁጥር 33824 በ17/05/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሶለት የወረዳው ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ግብር ሲከፍልበት የቆየበት ቦታ በደገም ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት እና በተከሳሽ ድርጅት እንዲቀርብ አዝዞ ደመወዝንና የትርፍ ሰዓት ክፍያ በጠቅላላው ብር 6410.92 መሆኑ በድጋሚ እንደቀረበለት ጠቅሶ እንዲሁም ከደገም ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ከሳሽ ደመወዝ ሲበላበት የነበረው እና ወሩ ያልታወቀ ፔሮል ቀርቦ በሁለቱም ወገኖች ስምምነት መደረሱን ገልፆ ውሳኔውን ወደ ገንዘብ ለውጦ ማስቀመጥ የአፈፀጸም ክስ ቡድን እንጂ የፍርድ ቤት ተግባር አይደለም፣ግን የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መከተል ተገቢ ነው ብሎ ተጠሪ በሰዓት የሚያገኘው ደመወዝ ብር 13.46.00፣በቀን ደግሞ 107.69 መሆኑን ማረጋገጡን ጠቅሶ የወር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደመወዙን ብር 3230.70 ይዞ ክፍያዎችን አስልቶ በጠቅላላው ብር 277,294.04 እንዲከፈለው ሲል በመ/ቁጥር 03756 የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡አመልካች በሌለበት ጉዳዩ በመታየቱ ላይ የይግባኝ ቅሬታና የሰበር አቤቱታ ለክልል ፍርድ ቤቶች ሲያቀርብ ለተጠሪ እንዲከፈሉ በተወሰኑ ክፍያዎች መጠን ላይም በሕግ አግባብ ያልተሰሉ መሆኑን ጭምር በመጥቀስ ቅሬታ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን የክርክር ሂደት የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪ በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር አመልካች በሌለበት በታየው ውሳኔ ላይ ይግባኝና የሰበር ክርክር ማቅረብ አይችልም የሚል መሆኑን ተረድተናል፡፡ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለጸው አመልካች በሌለበት ጉዳዩ ቢታይም ተጠሪ ያቀረቡት ክስ አባሪ ሆነው ከቀረቡት ማስረጃዎች አግባብነት፣ተቀባይነትና ጥንካሬ ያለመመርመሩንና እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 377/1996 ከአስቀመጠው የክፍያ ስሌት ውጪ መሆኑን በሚያሳዩት ነጥቦች ላይ በዚህ ችሎት ክርክር ከማቅረብ የሚያግደው የሥነ ስርዓት ህግ የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ሁኔታ ሣያጋጥመው ካቋረጠ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 39(1/ለ) መሠረት በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 2፣ በአንቀፅ 44 እና በአንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4(ለ) የተደነገጉትን ክፍያዎች ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት የዘረዘራቸው የክፍያ አይነቶች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ካሳ፣የስራ ስንብት ክፍያ፣የሳምንት እረፍት ክፍያ፣የአምስት አመት በዓላት ክፍያ ናቸው፡፡የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣የስራ ስንብት ክፍያና የካሳ ክፍያዎች የሚሰሉበት አግባብ በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠ ሲሆን ይህንኑ በሕጉ የተቀመጠውን ስሌት ተግባራዊ ለማድረግ ሰራተኛው በወር ሲከፈለው የነበረው ደመወዝ በሕጋዊ ማስረጃ መረጋግጥ የግድ ይላል፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 3230.70(ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ብር ከሰባ ሳንቲም) መሆኑን በመ/ቁጥር 03756 የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ አረጋግጧል፡፡በመሆኑም የተጠሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣የስራ ስንብትና የካሳ ክፍያዎች መሰላት ያለባቸው በዚሁ የተጠሪ ወርሃዊ ደመወዝ የተባለው መጠን መሰረት ተደርጎ በሕጉ የተቀመጠው ስሌት ባገናዘበ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

ይህንኑ መሰረት አድርገን እያንዳንዱን የክፍያ መጠን ስንመለከትም ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ያላቸው የአገልግሎት ዘመን አምስት አመት ከዘጠኝ ወርበመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 35(1)(ለ)) መሰረት ሊከፈላቸው የሚገባው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የሁለት ወር ደመወዝ ብር 6,461.40 (ስድስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ አንድ ብር ከአርባ ሳንቲም) ሁኖ አግኝተናል፡፡የስራ ስንብት ክፍያን በተመለከተም በአዋጁ አንቀጽ 39(1(ለ)) እና 40(1)(2) ድንጋጌዎች መሰረት የሚመጣው ውጤት ብር 8,384.30 (ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ሰማንያ አራት ከሰላሳ ሳንቲም) እንጂ ብር 47,383.60 ያለመሆኑን ተረድተናል፡፡እንዲሁም የካሳ መጠኑ በአዋጁ አንቀጽ 43(4(ሀ)) መሰረት ሲሰላ የወረዳ ፍርድ ቤት የተጠሪን አማካይ የቀን ደመወዝ ብር 107.69 ያደረገው በመሆኑ ይኼው የቀን አማካይ ደመወዝ በመቶ ሰማንያ ሲባዛ የሚመጣው ውጤት ብር 19,384.20(አስራ ዘጠኝ ሺህ ሶስትመቶ ሰማንያ አራት ብር ከሃያ ሳንቲም) እንጂ ብር 25,849.60 ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ሌላው የስር ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀጽ 71 እና 68 መሰረት የሳምንት እረፍት ክፍያ በማለት ያስቀመጠው ብር 188,784.57(አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) የስሌቱ መነሻ እና የመብቱ አድማስ ለጉዳዩ አግባብነትና ጥንካሬ ያላቸውን ማስረጃዎችን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውሳኔ ክፍል ሕግና ማስረጃን መሰረት ያደረገ ሁኖ አላገኘነውም፡፡የአምስት አመት በዓል ክፍያን በተመለከተ ግን አመልካች በስር ፍርድ ቤት በሌለበት የታየ በመሆኑና የይርጋ ክርክር ተነስቷል ለማለት ስለማይቻል እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ደግሞ ይርጋውን በራሱ ሊያነሳ የሚችልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ የገንዘቡ መጠን ብር 16,357.00(አስራ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሃምሳ ሰባት ብር) ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መቀመጡን የማንቀበልበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 163369 በ20/01/2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. በሂደቡ አቦቴ ወረዳ በመ/ቁጥር 03756 የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአመልካች የስንብት እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የፀና ሲሆን ውጤቱን በተመለከተ የሰጠው የውሳኔ ክፍል ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
3. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፣የአመልካች የመከራከር መብት የታለፈው ባግባቡ ነው፣የአመልካች እርምጃ ህገ ወጥ ነው በማለት መወሰኑም ተገቢ ነው በማለት ውጤቱን ግን አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በተቀመጠው ስሌትና በማስረጃ በተረጋገጠው የደመወዝ መጠን በመሆኑ፡-
    - 3.1 የስራ ስንብት ክፍያ ብር 8,384.30፣
    - 3.2 የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 6,461.40፣
    - 3.3 የካሳ ክፍያ ብር 19,384.20 እና
    - 3.4 የአምስት አመት የበዓል ቀናት ክፍያ ብር 16,357.00 ሁኖ በድምሩ ብር 50,586.90(ሃምሳ ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር ከዘጠና ሳንቲም) ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. የሳምንት ዕረፍት ቀናት ክፍያ ብር 188,784.57 በተመለከተ ግን በሕግ እና በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101020
መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
ሱልጣን አባተማም
መኮንን ገ/ህይወት
ሙስጠፋ አህመድ
ተሽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ዳዊት ገ/ማርያም - የቀረበ የለም፡፡
ተጠሪ፡- አቶ ሣህለማርያም ደግፌ - የቀረበ የለም፡፡
መዝገቡ ተመርምሯል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የሶማሌ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.05-0-60/06 መጋቢት 19 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ይታረምልን የሚል ሲሆን፤ይግባኝ ባይ በጠበቃቸው በኩል ግንቦት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ሦስት ገጽ ቅሬታ፡-
በሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኑ የሰበር አመልካች በተጠሪ ላይ በ17/10/2005 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ከተጠሪ ጋር በ30/09/2004 ዓ.ም በተዋዋሉት የሥራ ቅጥር ውል መሠረት አመልካች ሲሰሩ የቆዩ ቢሆንም ተጠሪ ክፍያ ባለመፈፀማቸው እና አመልካችን ከሥራ አላግባብ በማሰናበታቸው ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ፣ ካሣ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅም ለአመልካች እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡
ተጠሪ ለቀረበባቸው ክስ ከአመልካች ጋር የሥራ ቅጥር ውል የለንም ከማለት አልፈው በፍሬ ነገር ክርክሩ መልስ ባለመስጠታቸው ክሱ የቀረበለት የጅጅጋ ወረዳ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል የሥራ ቅጥር ውል አለ ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ብር 42,000 /አርባ ሁለት ሺህ/ አመልካች ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡
ተጠሪ በውሣኔው ቅር በመሰኘት ለፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የጠየቁት ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት ጥር 26 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡
የአሁኑ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው ግራ ቀኙን ያከራከረ ቢሆንም በሥር ፍርድ ቤት ያልቀረበ የይርጋ ክርክር በማንሳት የአመልካች ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/3 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በመሻር መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የፈፀመ በመሆኑ ችሎቱ የሥር ሰበር ችሎት ስህተት በማረም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲያፀናልኝ እና ወጪና ኪሣራዬን ይተካልኝ ዘንድ በመወሰን ያስናብተኝ የሚል ነው፡፡
የሰበር አቤቱታ አጣሪ ችሎቱ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ሰኔ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት መርምሮ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

“የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በይርጋ ላይ ተመርኩዞ የሰጠው ዳኝነት አግባብነት ከፍ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 244/3 አንፃር ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ” ሲል አዟል፡፡

ተጠሪ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ደርሷቸው በጠበቃቸው በኩል ሐምሌ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት መልስ፤ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት የቀረበባቸው ክስ ችግር የተሞላበት የነበር ቢሆንም በይግባኝ ደረጃ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ህገወጥነት ከመግለጽ አልፎ በቃል ክርክር ስለይርጋ በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ቢያጸናውም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መወሰኑ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ውሳኔው ስህተት የለበትም ተብሎ ችሎቱ ከበቂ ወጪና ኪሣራ ጋር ያሰናብተን የሚል ነው፡፡

አመልካች ሀምሌ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በሚያጠናክር መልክ የቀረበ ነው፡፡

እኛም በሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ የግራ ቀኙ ክርክር አግባብ ካላቸው ህጐች አንፃር መርምረናል ፡፡

አመልካች ለሰበር አቤቱታቸው ምክንያት ያደረጉት በሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያቀረብኩት ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም፤ በሥር ፍርድ ቤትም ያልቀረበ መቃወሚያ በሰበር ደረጃ ሊቀርብ አይገባም በሚል ሲሆን ተጠሪ መቃወሚያ በቃል ክርክር አቅርቤያለሁ ውሳኔው አግባብ ነው ባይ ናቸው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 244/3 መሠረት መቅረብ ከሚገባቸው መቃወሚያዎች ውስጥ ተጠቃለው ካልቀረቡ ያልቀረበው መቃወሚያ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያስናክል ከሆነ ባለጉዳዩ ራሱ ሆነ ብሎ ለማቅረብ ባለመፈለግ እንደተወው የሚቆጠር ለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ መቃወሚያ በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ አጠቃለው አለማቅረባቸው አሁን በሰበር ክርክር ያመኑ ሲሆን በሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ውሳኔም ስለመቅረቡም አልተመዘገበም፡፡ መቃወሚያ ካልቀረበም ተከሳሹ ሆነ ብሎ እንደተወው የሚቆጠር ከመሆኑም በላይ በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ክርክር ኋላ በማንሣት ለውሣኔ መሠረት ማድረግ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329/1 የሚፃረር ነው፡፡

የክልሉ ሰበር በሥር ፍርድ ቤት ያልቀረበውን መቃወሚያ በማንሳት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ሲል መወሰኑ የህግ ስህተት ሲሆን፤ አመልካች ሥራ ከተቀጠርኩ ጊዜ ጀምሮ ደመወዝ አልተከፈለኝም ውዝፍ ደመወዜ ይከፈለኝ በሚል ነው፡፡ አመልካች አስራ ሦስት ወር ለተጠሪ መስራታቸው ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የጠየቁት የውዝፍ ደመወዝ ክፍያ የይርጋ መቃወም በተጠሪ ካልቀረበበት የማይከፈልበት ምክንያት የለም፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአሁኑ ተጠሪ የተነሳ የይርጋ ጥያቄ ሳይኖር የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ማድረጉ የሕግ ስህተት ስለሆነ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቁጥር 05/1/60/06 ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፊፋን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.19-05-06 ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ እና የጅጅጋ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.M/D/J746/05

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሐምሌ 04 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 348/1 መሠረት ፀንቷል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸው ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101396

ታህሳስ 21 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተሻሊት ይመሰል

አመልካች፡- አዲስ አጠቃላይ ሆስፒታል ጠበቃ አብደላ ዓሊ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዶ/ር ምስራቅ ጥላሁን ጠበቃ አቶ ስመኘው አራጌ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 42275 ሐምሌ 9 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 135997 ግንቦት 18 ቀን 2006ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ ውል ከሕግ ውጭ በአሠሪው ተቋርጣል በማለት ያቀረቡትን ጥያቄየሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በወር ብር 8000,/ስምንት ሺ ብር/ እየተከፈለው በራዲያሎጅስት ሙያ ከጥር 1 ቀን 2000ዓ.ም ጀምሮ ሲያገለግሉ የቆዩ መሆኑን ገልፀው፤አሰሪው አመልካች ከሕግ አግባብ ውጭ ያቋረጠ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡
   አመልካች ተከሣሽ ሆኖ ቀርቦ ከከሳሽ/ተጠሪ/ጋር የሥራ ቅጥር ውል ግንኙነት የለንም፡፡ከሳሽ ጋር ያለን ግንኙነት፣ከሳሽ በትርፍ ሠዓታቸው የሙያ ግልጋሎት እየሰጡ ክፍያ የሚያገኙበት የውል ግንኙነት ነው፡፡ተከሳሽ ይህንን በትርፍ ሠዓት የሚሰጥ የሙያ ግልጋሎት ውል አላቋረጠም፡፡ ከሳሽ የሙያ ፈቃዳቸውን ከጤና ጥበቃ ሚኒስትር ያላሳደሱ በመሆኑ ፈቃዳቸውን አድሰው ሲቀርቡ ሥራ የሚጀምሩ ፤መሆኑን ተገልፆላቸዋል ከሳሽ በድርጅታችን ውስጥ በቀን ሁለት ሰዓት የሚሠራ ሲሆን በጡረታ የተገለሉ በመሆኑ ከከሳሽ ጋር ቋሚ የሆነ የአሠሪና የሠራተኛ ግንኙነት የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ከመረመረ በኃላ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የከሳሽን ስም በመጥቀስ ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤና ሌሎች የዕሑፍ ሰነዶች በማስረጃነት ያቀረቡለት መሆኑን ጠቅሶ በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል የአሠሪና ሰራተኛ ግንኙነት አለ ከሳሽ የተከሳሽን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጭ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ከሳሽ ለተከሳሽ የሥራ ስንብት ክፍያ የማስጠንቀቂያ ክፍያ የካሣ ክፍያና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያና የፅሁፍ ክፍያ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

3. አመልካች ግንቦት 28 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው ከአመልካች ዘንድ በቀን ሁለት ሠዓት ብቻ የሚያገለግሉራዲዮሎጂስት ናቸው፡፡ ይህ ፍሬ ጉዳይ በተጠሪ አልተካደም ይህም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(1) የሚሸፈንና በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የአሠራና እና ሠራተኛ ግንኙነት የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የሥራ ውል አላግባብ ተቋርጧል በማለት የተለያዩ ክፍያዎች እንድከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ሐምሌ 17 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ እኔ በራሴ ኃላፊነት ሳይሆን በአመልካች ኃላፊነትና ቁጥጥር ሥር ሆኜ ሥራ የምሠራ ሠራተኛ ነኝ፡፡ ሬዲዮሎጅስት አገልግሎት የሚሰጥበት የሙያ ዘርፍ ነው፡፡ አመልካች ከሚገኘው ደመወዝ በየወሩ የሥራ ግብር 2,433.65(ሁለት ሺ አራት መቶ ሰላሣ ሶስት ብር ከስልሣ አምስት ሣንቲም) እየቀነሰ ያስቀራል እንጅ በቀን ሁለት ሰዓት መስራት የአመልካችና የእኔን የስራ ውል ስምምነት የሚያሳይ እንጂ የአመልካች ሰራተኛ አለመሆኔን የሚያሳይ አይደለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በተጠሪ መካከል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚሸፈን የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት አለ፣ አመልካች ከሕግ አግባብ ውጭ የሥራ ውሉን አቋርጧል በማለት የተለያዩ ክፍያዎች አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው የሕግ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ “በሬድዮሎጂ” የሕክምና ሙያ የስልጠና በቂ ዕውቀትና ክህሎት ያለውና የደንብ ቁጥር 76/1994 አንቀፅ 20 በሚደነግገው መሠረት በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል በሙያው የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለሙያ መሆኑ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ ከጥር 1 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በአመልካች ድርጅት በቀን ለሁለት ሠዓት ያህል በመገኘት ከአመልካች ጋር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2641 በሚደነግገው መሠረት የሆስፒታል ውል ከተዋዋሉ የአመልካች ደንበኞች የሙያ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ መሆኑና ተጠሪ ለሚሰጠው አገልግሎት አመልካች በየወሩ ብር 8000 /ስምንት ሺ ብር/ክፍያ ሲከፍለው የኖረ መሆኑ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

6. አመልካች እና ተጠሪ ከላይ የተገለፀው አይነት የውል ግንኙነት የነበራቸው መሆኑ አያከራክርም፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ይኽ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ፀንቶ የኖረው ግንኙነት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ነው ወይስ የዕውቀትና የሙያ ሥራ ለማከራየት የተደረገ የውል ግንኙነት ነው? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ይህንን ጭብጥ ለመወሰን በአመልካች ተጠሪና የሕክምና አገልግሎት በሚሰጣቸው ህመማን /የአመልካች ደንበኞች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መካከል የሚኖረውን ግንኙነት መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች በደንብ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 20 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በሙያው የሕክምና ግልጋሎት ለመስጠት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያለው ባለሙያ ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2140 በሕክምና ባለሙያዎች ላይ የሚጥለው ግዴታና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2646(1) መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት የአመልካች ደንበኛ ከሚከፍለው ክፍያ ተጠሪ ምን ያህል ገንዘብ በወር ሊከፈለው እንደሚችል በውል በመስማማት፣ሙሉ በሙሉ በአመልካች ተቆጣጣሪነትና አሠሪነት እየተመደበ ሳይሆን ፣በቀን ለሁለት ሠዓቶች ሙያዊ አገልግሎትየሚሰጥ ባለሙያ መሆኑን የግራ ቀኙ ክርክርና በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡት ፍሬ ጉዳዮች ያሳያሉ፡፡

7. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የተፈፃሚነት ወሰን በዝርዝር የሚደነግገው በአዋጅ ቁጥር 397/96 አንቀፅ 3 ፣ንዑስ አንቀፅ (1) አዋጅ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን በመርህ ደረጃ ደንግጓል፡፡ አዋጅ በዚህ ጠቅላላ መርህ የማይካተቱና የቅጥር ላይ የተመሰረቱ የሥራ ግንኙነቶች በአዋጅ ቁጥር 377 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 በልዩ ሁኔታና በዝርዝር ደንግጓል፡፡ የአዋጅ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ ‹‹ይህ አዋጅ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት በቅጥር ላይ በተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም ›› የሚል ይዘት ያለው ሲሆን በአዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 በዝርዝር ከተደነገጉ አዋጅ ተፈፃሚነት ከማይሆንባቸው ግንኙነቶች ውስጥ፤አንድ ተዋዋይ ወገን ዋጋ እየተከፈለው በራሱ የንግድ ሥራ ወይም በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሚሠራ ስራ የሚያከናውን ሲሆን፣አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሌላቸው መሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(1) ተደንግጓል፡፡

8. ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ ሙሉ በሙሉ በአመልካች መሪነትና ቁጥጥር ሣይሆን በአመልካች ድርጅት ውስጥ በቀን ለሁለት ሠዓት ያክል ከአመልካች ጋር የሆስፒታል ውል ለተዋዋሉ የአመልካች ደንበኞች የራድዮሎጅ የሙያ ግልጋሎት በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሚሰጥ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ይህንን የሙያ ግልጋሎቱን ሌላ ቦታ የሚገኝ የህክምና ተቋም ወይም ከአመልካች ጋር ምንም አይነት የሆስፒታል ውል ግንኙነት ለሌላቸውና የአመልካች የህክምና ካርድ ላልያዙ ሰዎች እንዲሰጥናየሥራ ስምሪት መስጠትና አመልካችን ተቆጣጥሮ ማሠራት አይችልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 61 እና ተከታታይ ድንጋጌዎች መሠረት በቀን ሥምንት ሠዓት በሣምንት አርባ ሥምንት ሠዓት ከሥራ ቦታ እንዲገኝ ለማስገደድና ተቆጣጥሮ ማሰራት እንደማይችል የግራ ቀኙ ክርክርና ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተረድተናል፡፡

9. የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ በቀን ለሁለት ሠዓት ብቻ አገልግሎት መስጠቱ፤ ከአመልካች ጋር በአዋጅ ቁጥር 377/96 የሚሸፈን የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ከመመስረት አይገድበውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ይህ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ከአንቀፅ 61 እስከ አንቀፅ 64 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘትና ውጤት ያገናዘበ ካለመሆኑም በላይ ፣በአዋጅ አንቀጽ 65 ልዩ ድንጋጌ ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 65 መሠረት በሥራ ውሉ ወይም በህብረት ስምምነት በሌላ አኳኃን ካልተወሰነ በስተቀር ፣የአዋጁ የስራ ሰዓት የሚመለከቱት ከአንቀጽ 61 እስከ አንቀጽ 64 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የማይኖራቸው በንግድ መልዕክተኞች በንግድ ወኪሎች ላይ እንደሆነ በግልፅ ተደንግጎአል፡፡ ከዚህ አንፃር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ፍርድ ቤት የአዋጅ የሥራ ሠዓት ድንጋጌዎች ተጠሪ የአመልካች ቅጥር ሰራተኛ ነው ብሎ ለመወሰን ተፈፃሚነት እንደሌላቸው በመግለፅ የሰጠው ትርጓሜ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 65 ልዩ ድንጋጌ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. ከላይ በዝርዝር የተገለፁት ምክንያቶች ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀፅ 2/1) መሠረት ከአመልካች ቁጥጥርና የሥራ አለመረዳት ሣይገደብ በራሱ የሙያ ኃላፊነት በቀን ለሁለት ሠዓት የራዲዮሎጅ የሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ እንጅ የአመልካች ሠራተኛ አይደለም፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የሚሰጠው የእውቀት ግልጋሎት እና ሥራ ውል በመሆኑ አመልካች በማናቸውም ጊዜ ውሉን ለማፍረስ የሚችል መሆኑን በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2638 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ይህም በመሆኑ አመልካች አግባብነት ያለውንና ተፈፃሚነት ያለውን የህግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ አለኝ የሚለውን መብትና ጥቅም ከሚጠይቅ በስተቀር ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት የለውም ፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል ፡፡
2. ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 ንዑስ 2(1) መሠረት በራሱ የሙያ ኃላፊነት በቀን ለሁለት ሠዓት የሙያ አገልግሎት የሚሠጥ በመሆኑ የአመልካች ቅጥር ሠራተኛ ሣይሆን የዕውቀት ሥራና ግልጋሎት ለመሰጠት የተዋዋለ ባለሙያ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሙያ (ዕውቀት)ሥራ ግልጋሎት ውል ያቋረጠው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2637 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. ይኽ ውሣኔ ተጠሪ የሙያ ግልጋሎት ውሉ በመቋረጡ ምክንያት አለኝ የሚለውን የመብት ጥያቄ ከማቅረብ የሚገድበው አይደለም ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.101913

የካቲት 17 ቀን 2007

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ መላከ ሙሉጌታ - ጠበቃ ሙሉጌታ ወንድምአገኘሁ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አበበ አቡራ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 11115 ታህሳስ 21 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና ታህሳስ 28 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139436 ሰኔ 6 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውየአፈፃፀም ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በአፈፃፀም ሂደት የቀዳሚነት መብት ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡

1. የፍርድ ባለዕዳ የሆነው ዲማክዶ መስማት የተሳናቸው የተባለ ድርጅት በመክሰስ አመልካችና ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሆነዋል፡፡ ተጠሪ የድርጅቱ የሥራ መሪ ስለነበረ በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት የፍትሐብሔር ክስ አቅርቦ የፍርድ ባለመብት ሆኗል፡፡ የፍርድ ባለዕዳውንም ንብረት አስቀድሞ በማስከበር በአፈፃፀም እንዲሸጥ አድርጓል፡፡ አመልካች በፍርድ ባለዕዳው ላይ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ክስ አቅርቦ የፍርድ ባለመብት ሆኗል፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 167 መሠረትየቀዳሚነት መብት ያለኝ ስለሆነ በቅድሚያ ለእኔ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ጥያቄ አንስቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችም ሆነ ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳው ሠራተኞች በመሆናቸው የቀዳሚነት መብት ያለው ንብረቱን ቀድሞ በአፈፃፀም የሸጠው /ተጠሪ/ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሁለቱም የፍርድ ባለመብቶች የፍርድ ባለዕዳ ሠራተኞች በመሆናቸው ከይግባኝ ባይ /አመልካች/ የቀዳሚነት መብት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡
2. አመልካች የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ተሸጦ ከተገኘው ገንዘብ በቀዳሚነት ሊፈፀምልኝ ሲገባ የበታች ፍርድ ቤቶች በሕግ የተሰጠኝን ልዩ የቀዳሚነት መብት አሳጥተውኛል በማለት የስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ እኔም የፍርድ ባለዕዳው ተቀጣሪ ሠራተኛ በመሆኔ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን አፈፃፀም ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

3. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ የሕግ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
4. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳውን ትምህርት ቤት ከስድስት ዓመት በላይ በወር 250 /ሁለት መቶ ሀምሳ የአሜሪካ ዶላር/ እየተከፈለው ያገለገለ መሆኑን፣ ተጠሪ የድርጅቱ የሥራ መሪ በመሆኑም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቁራ ምድብ 2ኛ ፍትሐ ብሔር ችሎት ክስ አቅርቦበመዝገብ ቁጥር 01892 ግንቦት 29 ቀን 2004 ዓ.ም የፍርድ ባለዕዳው 12,000 /አስራ ሁለት ሺ የአሜሪካን ዶላር/ እንዲከፍለው ውሣኔ የሰጡለት መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካች በበኩሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቁራ ምድብ የሥራ ክርክር ችሎት ክስአቅርቦ የፍርድ ባለዕዳው ብር 28,173.33 /ሃያ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰባ ሦስት ብር ከሰላሳ ሦስት ሣንቲም / ለአመልካች እንዲከፍል በመዝገብ ቁጥር 09226 ሐምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡
5. ከላይ እንደተገለፀው በተጠሪና በፍርድ ባዕዳው መካከል የሥራ ቅጥር ውል መኖሩ ግልፅ ቢሆንም የፍርድ ባለዕዳው አመልካችን የቀጠረው በሥራ መሪነት በርዕሰ መምህርነት እንደሆነ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል በአመልካችና በፍርድ ባለዕዳው መካከል የነበረው ግንኙነት በአዋጅ ቅጥር 377/1996 መሠረት የተመሠረተ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንድ የሥራ መሪ የሆነ ሰው በአሠሪው ድርጅት በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት ሊከፍለው የሚገባውን ክፍያ እንዲከፍለው ክስ አቅርቦ የፍርድ ባለመብት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት አሠሪው የሚያስተዳድራቸው ሠራተኞች በፍርድ እንዲከፈላቸው ያስወሰኑት ክፍያ ከመክፈሉ በፊት ፍርድ ተፈፃሚ ሊሆንለት ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው የህግ ጥያቄ መታየት ያለበት ነው፡፡
6. ይህም ጥያቄ በቅጥር ላይ ከተመሠረተ የሥራ ግንኙነት የሚመነጭ ማናቸውም የሠራተኛ ክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የዕዳ ጥያቄ ቅድሚያ ይኖረዋል በማለት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 167 ድንጋጌ አንፃር መታየት ያለበት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ሠራተኛ ማለት በአዋጅ አንቀጽ 4 በተመለከተው መሠረት ከአሠሪው ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው እንደሆነ በአዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገ ሲሆን የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ በተገለፁት የሥራ መሪዎች ላይ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 167 የተደነገገው ልዩ የቀዳሚነት መብት የለውም፡፡ በመሆኑም ልዩ የቀዳሚነት መብት ያለው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ከፍርድ ባለዕዳው ጋር የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ያለው አመልካች እንጅ ተጠሪ አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የቀዳሚነት መብት አለው በማለት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 2፣ የአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 167 የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. በአፈፃፀም የቀዳሚነት መብት ያለው ተጠሪ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. በአፈፃፀም የቀዳሚነት መብት ያለው አመልካች ነው በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 167 መሠረት ወስነናል፡፡ የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ተሸጦ ከተገኘው ገንዘብ፣ አመልካች በቅድሚያ ሊከፈለው ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 103209

የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አትላስ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት - ጠበቃ መልካም ዓለማየሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት መስታወት ስመኝ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የቀረበውን የግል የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስም፡- ከአመልካች ጋር በሕግ አግባብ ያደረጉት የስራ ቅጥር ውል ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም፡- ተጠሪ ከስራ የተነሰናበቱት በአመልካች ንብረት ያላግባብ በመገልገላቸው ከስራ ባልደረባቸው ጋር በክፍል ውስጥ ግጭት በመፍጠራቸው ማስንጠቀቂያ እየተሰጣቸው ከስራ ገበታቸው ያለበቂ ምክንያት በመቅረታቸው እና ተጠሪ በሚያስተምሯቸው የክፍል ተማሪዎች ላይ የመግረፍና የማስደንገጥ ተግባር እየፈፀሙ በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የስነ ልቦና ችግር በማድረሳቸው ምክንያት ነው በማለት ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና የአመልካችን ምስክሮችን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ውጤቱን በተመለከተም የክፍያዎችን አይነትና መጠን በመዘርዘር በድምሩ ብር 14,988.33 (አስራ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከሰላሳ ሶስት ሳንቲም) አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከአስተማሪ ጋር በስራ ቦታ ተጣልተው በማስጠንቀቂያ የመታለፉቸውን ሁኔታ ለስንብት ምክንያት ሊሆን የሚችል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም በማለት ማለፉም ሆነ ተጠሪ ተማሪዎችን መደብደባቸውን በማስረጃ በአረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት አይደለም በማለት ስንብቱን ሕገ ወጥ ሲል መወሰኑና ይህም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መጽናቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡
አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው በሰጡት መልስም ጥፋቶቹ ያለመረጋገጣቸውንና ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ የሚችሉበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡ይህም ችሎት ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት የተከራከሩበትን መዝገብ እንዲቀርብ አድርጎ በአመልካች ምስክሮች የተነገረውንና የተረጋገጠውን የምስክርነት ቃል ይዘት ተመልክቷል፡፡
የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ ያገኘውን በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ጭብጥ ነው፡፡
ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት በዚህ ችሎት የሚከራከረው ተጠሪን ከስራ ባልደረባቸው በስራ ቦታ ጠብ ፈጥረው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል በተማሪዎች ላይ ሕገ ወጥ የሆነ የድብደባ ተግባር ፈጽመዋል በማለት መሆኑን ነው፡፡ተጠሪ በበኩላቸው ጥፋቶቹን መፈፀሜ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡
ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ስንብቱን ሕጋዊ ያደርጋሉ በማለት በመከላከያ መልሱ የጠቀሷቸውን ፍሬ ነገሮች ውድቅ ያደረጋቸው መሆኑን ሲሆን ለዚህም ያስቀመጣቸው ምክንያቶች ተጠሪ ከስራ ባልደረባቸው በስራ ቦታ ጠብ ፈጥረዋል ለተባለው አድራጎት በአመልካች በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ከታለፉ በኋላ ይኼው በማስጠንቀቂያ የታለፈው ጥፋት ለስንብቱ ምክንያት ሊሆን እንደማይችል ተማሪዎችንመደብደባቸውም ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ጥፋት ስላለመሆኑ በሕጉ አልተመለከተም የሚሉ ናቸው፡፡
የአዋጅ ቁጥር 377/1996 የስራ ውል ስለሚቋረጥበት ምክንያቶችና ሁኔታዎችን በአንቀጽ 23 ከአንቀጽ 26 እስከ 30 ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ሕብረት ስምምነት መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ተደርጎ የተወሰደ ጉዳይም በአሰሪው ተነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 27/1/ተ/ ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 24 እንደተመለከተው ውሉ በሕግ የሚቋረጥበት ምክንያቶች በአብዛኛው ከሁለቱም ወገን ቁጥጥር ውጭ ያሉ ሲሆን የስራ ውል በሁለቱም ፈቃደኝነት የሚገቡበት እንደመሆኑ ሁሉ ሁለቱም በፈቃደኝነት ከተስማሙ ውሉን ሊያቋርጡ የሚችሉበት ሁኔታም በአንቀጽ 25 ስር ሰፍሮ ይገኛል፡፡ስለዚህ ከላይ በተገለጹት ቁጥሮች በተደነገጉት ምክንያቶችና ሁኔታዎች የሚፈጸም የስራ ውል መቋረጥ ሕጋዊ የስራ ውል መቋረጥ ሲሆን ከነዚህ ውጭ የሚደረጉ የስራ ውል መቋረጥ በሕገ ወጥነት የሚፈረጁ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 42 ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህም ላይ በመመስረት የሚያስከተሉት ውጤቶች የሚለያዩ በመሆኑ በተናጥል የሚያስከትሉትን ውጤት ከሕጉ አግባብ በማየት ዳኝነትን መስጠት የሚጠይቅ መሆኑም ግልፅ ነው፡፡
ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች ከተጠሪ ጋር በሕግ አግባብ የመሰረተው የስራ ውል መኖሩንና ስንብት ማድረጉን ሳይክድ አጥብቆ የሚከራከረው ስንብቱ ሕጋዊ ነው በሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ለዚህም ተጠሪ በአመልካች ንብረት ያላግባብ መገልገላቸውን ከስራ ባልደረባቸው ጋር በክፍል ውስጥ ግጭት መፍጠራቸውን ተጠሪ ማስጠንቀቂያ እየተሰጣቸው ከስራ ገበታቸው ያለበቂ ምክንያት መቅረታቸውንና ተጠሪ በሚያስተምሯቸው የክፍል ተማሪዎች ላይ በመግረፍና በማስደንገጥ በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የስነ ልቦና ችግር ማድረሳቸውን የሚገልጹ ምክንያቶች ጠቅሶ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡አመልካች ያቀረባቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ተጠሪ ከስራ ባልደረባቸው ጋር በስራ ቦታ ፈጠሩ ለተባለው ጸብ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው የታለፉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በስራ ቦታ ጠብ መፍጠር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1(ረ) ድንጋጌ መሰረት እንደጥፋቱ ክብደት እየታየ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ተግባር መሆኑ የተደነገገ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪ ለጥፋቱ በማስጠንቀቂያ የታለፉ መሆኑን በሚገባ ተረጋግጧል፡፡በመሆኑም በማስጠንቀቂያ የታለፉበት ጉዳይ የማስጠንቀቂያውን ተደጋጋሚነትን በመግለጽ ሌላ ጥፋት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ለስንብት መሰረት ከሚሆን በስተቀር ራሱ በማስጠንቀቂያ ቀሪ የሆነ ጥፋቱ ግን ለስንብት መሰረት የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት የሚያገኝበትን አግባብ አላገኘንም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪ የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች መደብደባቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ እያለ አድራጎቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት አይደለም መባሉ ተገቢነት የለውም በሚል ነው፡፡በእርግጥ አንድ ተማሪ በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ ሕገ መንግስታዊ መብት ያለው መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 16 በግልጽ ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሆን ይህን ህገ መንግስታዊ መብት መጣስ ሕገ ወጥ ድርጊት በመሆኑ በሕግ ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑም የሚታመን ነው፡፡በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1(ቀ)) ድንጋጌ ስር በተመለከተው አግባብም በአዋጁ አንቀጽ 14(2(ሀ)) ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲታይ ከስራ ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል ምክንያት ነው፡፡

በሌላ በኩል አንድ አስተማሪ የሚያስተምራቸውን ተማሪዎች በአግባቡ የመቆጣጠርና የመከተታል ህጋዊ ግዴታ ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2124 እና 2125 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም እነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች ተጣጥመው በአግባቡ ተግባራዊ መሆን ያለባቸው መሆኑ እሙን ነው፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ ተማሪዎችን ደብድበዋል የተባለው ከአስተማሪነታቸው ከሚጠበቀው ኃላፊነት በላይ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ላይ የቀረቡትን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ይዘት በመመልከት ተገንዝበናል፡፡ ከሁሉም በላይ የአመልካች ሁለተኛ ምስክር በስር ፍርድ ቤት ቀርበው በሠጡት የምስክርነት ቃል ተማሪዎችን መግረፍ ክልክል መሆኑን ገልፀው እንደዚህ አይነት አድራጎት የፈፀመ አስተማሪ ለጥፋቱ ከምክር እስከ ማጠንቀቂያ የሚሰጥበት ሂደት መኖሩን መጨረሻ ላይም አስተማሪው ካልታረመ ጉዳዩን የበላይ አካል እንዲያውቀው ተደርጎ ተገቢው የሚወሰን መሆኑና ይህም በትምህርት ቤት መተዳደሪያ ደንብ ያለ መሆኑን ጭምር ዘርዝረው መግለጻቸው ሲታይ ትምህርት ቤቱ ሕገ ወጥ ተግባር ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑን ተገንዝቦ ይህንኑ ህገ ወጥ ተግባር ለመከላከልና ተፈጽሞ ሲገኝም አስተማሪው በዲሲፕሊን የሚጠይቅበትን ስርዓት ዘርግቶ እየሰራበት መሆኑ የሚያሳይ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ፈፀሙ የተባሉት አድራጎት ከአስተማሪነታቸው ኃላፊነት እና ግዴታ በላይ መሆኑንና ከትምህርት ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ውጪ መሆኑን ጭምር ያለማስረዳቱን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን የሚያስገነዝብ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ተማሪን መደብደብ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም በማለት ያስቀመጠው ምክንያት ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 16 ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1(ቀ) እና 14(2(ሀ)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ ቢሆንም ተጠሪ ፈጸሙ የተባለው ድርጊት ከአስተማሪነት ኃላፊነት እና ግዴታቸው የወጣና ያልተገባ ስለመሆኑ ባለመረጋገጡ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ግን በውጤት ደረጃ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አግኝተናል፡፡በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 36072 ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 140064 ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ የሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራን የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

ሐምሌ 16 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101040

መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ሕይወት

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡- አቶ አየለ መንግሥቱ

ተጠሪ፡- የኢትዮጲያ እህል ንግድ ድርጅት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሣሽ ሲሆን ተጠሪ ተከሣሽ ነበሩ አመልካች ባቀረበው ክስ ተጠሪ ያለምንም ምክንያት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ስላሰናበተኝ የአገልግሎት ካሣና ጉዳት ፣የስድስት ወር ደሞዝ፣ የአመት ዕረፍት ክፍያ እና የሥራ ልምድ ጨምሮ 51,778 ብር እንዲከፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ አመልካች የመጋዘን ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ 41.01 ኩንታል በቆሎ በጆንያ መሐከል ተደብቆ በዕዳት ሠራተኛ በኩል ተደረሰበት ይህንንም ያደረጉት ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል በማሰብ ነው፣በድርጊቱም ተጠይቀው በቀን ሰራተኛ ሲጫን ተዛብቶ ይሆናል በማለት ተናግሯል፡፡ ይሁንና ይህ ተግባራቸው ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የሚያሰናብት ነው በማለት ተከራክሯል፡- ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተገኘ የተባለው በቆሎ ማን እንደደበቀው በግልፅ ባልተረጋገጠበት ያለማስጠንቀቂያ መሰናበቱ ህገ ወጥ ነው በመሆኑም በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 36፣37 ሣያሚላ እርምጃ መወሰዱ አግባብ ስላልሆነ በአዋጅ አንቀጽ 43(1) መሰረት ካሳና ደሞዝ ጋር ተያይዘው የሚመጡትን ክፍያዎች ጨምሮ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 40(1-3) ባጠቃላይ 49,998.50 ይከፈለው ሲል ወሰነ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የከፍተኛው ፍ/ቤት በፍ/ህ/ስ/ስ/ቁ.337 ሰርዞታል፡፡ የክልሉም የሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማየት ጠፋ የተባለው በቆሎ በመጋዘን ውስጥ ተደብቆ እና ቁልፉም ከተጠሪ ሌላ ማንም እንማይዘው ተረጋግጧል፣ በመሆኑም ተጠሪ የማጭበርበር ድርጊት የፈጸመ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(ሐ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ የሚያሰናብት ነው ሲል የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታም ይህንን ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ በስር ፍ/ቤት ተጠሪ በሰጠው መልስ በመጋዘን ውስጥ የተደበቀ በቆሎ በመገኘቱ እንዳሰናበተኝ ቢገልጽም የደረሰ ጉዳት የለም በማለት አጣርቶ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያ እንዲከፈለኝ ቢወሰንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት የአመልካችን የመጋዘን ኃላፊ መሆኑን በመገልጽና ቁልፉም በእኔው እጅ እንደሚቀመጥ በመጥቀስ የማጭበርበር ድርጊት ተፈጸሟል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(ሐ) መሰረት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የተወሰነልኝን የዓመት ዕረፍት ጭምር የሰረዘ ውሳኔን መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋዋል፡፡

በዚህ መሰረት ይህ ችሎትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ስንብቱ ህጋዊ ነው ሲል ሲሽረው ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል የተወሰነውን የዓመት ዕረፍት ክፍያ ጭምር መሻሩን እንደ ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን አስቀርቦ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የዓመት እረፍት ሊከፈል እንደሚገባ ሳይክድ በትርፍነት የተከፈላቸውን ገንዘብ እንዲከፍሉ (እንዲመልሱ) በማለት ሲከራከር አመልካች በበኩላቸው የሚፈለግባቸው ገንዘብ የሌለና አዲስ ክርክር ሊነሳ አይገባም ሲሉ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በመሆኑም የግራ ቀኙ ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው ህግ አኳያ አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመሆኑም የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰውን ሲመስል እኛም ጉዳዩን እንዳየነው አመልካች በወረዳው ፍ/ቤት ከህግ ውጭ ተሰናበትኩ ሲል የዓመት ዕረፍትን ጨምሮ የተለያዩ ክፍያ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙን በማከራከር ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ የስራ ከህግ ውጭ መሰናበት ውጤት የሆኑት ክፍያ እንዲከፈል ወስኗል፡፡በይግባኝ ሰሚውም ይኸው ውሳኔ ጸንቷል፡፡ በቀጣይነት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ውሳኔን በመሻር አመልካች የመጋዘን ኃላፊ ሆኖ በሚሰሩበት ወቅት ተደብቆየተገኘ በቆሎ መኖሩ የተረጋገጠ በመሆኑ ድርጊቱ በአዋጅ 377/96 አንቀፅ 27(1(ሐ) ስር የሚወድቅ የማጭበርበር ድርጊት በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ይህ ችሎትም የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ስንብቱ ህጋዊ ነው ሲል የደረሰበትን ድምዳሜ የሚቀበለው ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የተጠየቀው የዓመት ዕረፍት ክፍያ ጥያቄን አስመልክቶ ሳይለይ በጠቅላላ መሻሩ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሠረቱ የዓመት ዕረፍት ክፍያ ሠራተኛ በሥራ ዘመኑ ሊጠበቁለት ከሚገቡ መብቶች መሀከል አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ክፍያ የሠራተኛው ውል በህግ ወይም ከህግ ውጭ እንዲሁም ሠራተኛው በራሱ ጊዜ ሲያቋርጥየዓመት ዕረፍትክፍያ ሊታለፍበት (ሊነፈግ) የሚችል አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ጥያቄው ከሚቀጥለው ሁለት አመት በላይ ሊራዘም እንደማይችል በአዋጅ አንቀጽ 79(5) ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህም የሆነው ሰራተኛው ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጠው ከሚጠይቅ ዕረፍቱን በአይነት ወስዶ በተሟላና አካሉን አሳርፎ በአዲስ ሀይል ሥራውን እንዲያከናውን ታስቦ እንደሚሆን ብዙ አያከራክርም፡፡ የህጉ አንቀጽ 76(1) ይህንኑ ሲያጠናክር በዚህ ረገድ ሰራተኛው የዕረፍት ጊዜውን ለመተው ሊስማማ የማይችል መሆኑን ክልከላ ያስቀመጠው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣም የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የአመት እረፍት ክፍያ ውድቅ ያደረገበት ምክንያት ግልፅነት የጐደለው ሲሆንአመልካችም ውሳኔው ቢሻርም በሥር ፍ/ቤትየታመነው የአመት እረፍት ክፍያ የ85 ቀን (5468.5) ብር ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ይከራከራሉ፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ይህ ክፍያ ለአመልካች ሊከፈል እንደሚገባው በማመን መጠኑን አስመልክቶ የ48 ቀን ብቻ ነው ሊከፍለው የሚገባው ሲል መነሻው ግብር ተቀንሶ ሊከፍል ይገባዋል በማለት ይከራከራል፡፡ እንግዲህ የቀኑን ብዛት አስመልክቶ የተነሳው ክርክር በሥር ፍ/ቤት ጉልቶ መከራከሪያ ሆኖ ያልመጣ በመሆኑ አልተቀበልነውም ሌላው ተጠሪ የሚያነሣው ክርክር የዓመት ዕረፍት ክፍያው ግብር ተቀንሶ ሊከፈል ይገባል የሚል ነው፡፡ በዚሁ ውሳኔ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው የዓመት ዕረፍትን ለሰራተኛው መክፈል የማስፈለጉ አላማ ግልፅ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመርህ ደረጃ በዓይነት የእረፍት ቀናትን ወስዶ እንዲወጣ ነው፡፡ በዚህን ጊዜ በህግ የተፈቀደለትን የዓመት ዕረፍቱን ወስዶ ከመውጣት በቀር ሌላ ሊያሟላ የሚጠበቅበት ነገር የለም፡፡ በሌላበኩል በተለያዩ በህጉ በተቀመጡት ምክንያቶች የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሲከፈል እንደሌሎች ከአሰሪና ሰራተኛ ህጉ የሚመነጩ መብቶች (ክፍያ) የዓመት ዕረፍት ክፍያም የገቢ ግብር ከተቀነሰ በኋላ የሚከፈል ክፍያ መሆኑን ይህ ችሎት የሚቀበለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የገቢ ግብር የአዋጅ ቁ.286/94 እና ደንብ ቁ.78/94 አንቀፅ 3 የዓመት እረፍትን ያለማግለሉ ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የገንዘብ መጠን በሥር ውሳኔ በግልፅ ተጠቅሶ ባይቀመጥም ተጠሪ ለመጠንና ስሌት ክርክር ውጭ አመልካች የአመት ዕረፍት ክፍያ የላቸውም የሚል ክርክር አላቀረቡም በመሆኑም በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 77፣78 እና 79 በተደነገጉት መሠረት አመልካች ያቀረቡትን የገንዘብ መጠን በሌላ ማስረጃ አላስተባበለም፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ሠበር ሰሚ ችሎት የሥር ውሳኔን ሲሽር የአመልካችን የአመት ዕረፍት ክፍያ ጭምር መሻሩ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 20962 በቀን 20/12/05 የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 18732 በቀን 27/01/06 እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 74447 በቀን 01/07/06 በማሻሻል ፀንቷል፡፡
2. አመልካች የጠየቁትን የዓመት ዕረፍት ክፍያ በህጉ መሰረት አስፈላጊው የገቢ ግበር ተቀንሶ ይከፈላቸው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካች በትርፍነት ከወሰዱት ገንዘብ ሊመልሱልኝ ይገባል የሚለውን በህግ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግድም፡፡
4. የወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101890
ጥቅምት 24 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም
መስጠፋ አህመድ
ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ- ጠበቃ አውላቸው ደሣለኝ ቀረቡ፡፡
ተጠሪ፡- ወ/ት ፍጹም ኃይሉ - የቀረበ የለም፡፡
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ የቀረበው ክርክር የሥራ ውሉ ማቋረጡን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ አመልካች ከግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ በዕቃ ግምጃ ቤት ተቆጣጣሪነት በቋሚ ደመወዝ ብር 2,639 የቀጠራቸው መሆኑና ያለማስጠንቀቂያ በ12/11/2005 የተፃፈ የቅጥር ውል ማቋረጫ ደብዳቤ በ15/11/2005 እንዲሰጣቸው በሕገወጥ መንገድ ከሥራ ሰለአሰናበታቸው የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ በትብብር በሚሰራ ድርጅት ተቀጥረው ሲሰሩ ስለነበር የተቀጠሩት በቋሚነት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ከቀረበው ማስረጃ አንፃር ተገቢነት የለውም በማለት የታለፈ ሲሆን በግራ ቀኙ የነበረው የሥራ ውል ግንኙነት በ29/09/2005 ዓ.ም በተፃፈው ደብዳቤ ከግንቦት 7 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ለ45 ቀናት የሙከራ ቅጥር ተቀጥረው ሲሰሩ እንደነበር መሠረት በማድረግ ታልፏል፡፡
አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ተጠሪ ሊመደቡበት ላቀደው የዕቃ ግምጃ ቤት የስራ መደብ ተስማሚ መሆናቸውን ለመመዘን ለ45 ቀናት የሙከራ ግዜ ተቀጥረው ለታቀደው ሥራ ተስማሚ ያለመሆናቸውን በማረጋገጥ ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ የሥራ ውል ማቋረጡን ገልጿል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ በማገናዘብ በሰጠው ውሣኔ ተጠሪ በሰጡት የምስክርነት ቃል የሥራ ውል ማቋረጫ ደብዳቤ የተሰጣቸው እ.ኤ.አ ጁላይ 22/2013 ወይም ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 15/11/2005 መሆኑን ፤ የአመልካች ምስክርም ደብዳቤው የተሰጣቸው ጁላይ 19 ቀን 2013 ወይም ሐምሌ 15 ቀን 2005 ዓ.ም ነው በማለታቸው የተጠሪ የሥራ ውል ማቋረጫ ደብዳቤ የተሰጣቸው በ46ኛው ቀን ሐምሌ 15/11/2005 ዓ.ም በመሆኑ ስንብቱ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ለተጠሪ ያልከፈላቸው የ22 ቀናት ቀሪ ደመወዝ እንዲሁም የካሣ ክፍያ እንዲከፍላቸው የሥራ ልምድ ማስረጃም እንዲሰጣቸውበማለት ወስኗል፡፡ በይግባኝ ሥልጣኑየተመለከተው ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞታል፡፡
አመልካችም በሥር ፍ/ቤቶች ፍርድ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የቅሬታ ነጥቡም ሲጠቃለል፡- በአመልካች እና ተጠሪ የነበረው የሥራ ግንኙነት ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ ጁላይ 19 ቀን 2013 እ.ኤ.አ በተፃፈ ደብዳቤ መቋረጡ፤ ይህ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 12 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን እየታወቀ የውል መቋረጫ ደብዳቤ በ43ኛው ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተድፎ ሳለ ስንብቱ በ46ኛው ቀን የተደረገ በመሆኑ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ በሥር ፍርድ ቤት መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከአሁን በፊት ለ5ወር ከ6 ቀን በማቴሪያል ኢንቨንተሪ ኮንትሮል ሥራ በአመልካች መስሪያ ቤት መሥራታቸው እየታወቀ ድጋሚ በዚያው ሥራ በሙከራ የቅጥር ውል መሥራታቸው ሕጋዊ አለመሆኑን ፤የሥር ፍ/ቤት ማስረጃዎች በመመዘን ውሣኔ መስጠቱ ፤የተጠሪ ምስክሮች የሥራ ውል ማቋረጫ ደብዳቤ እ.ኤ.አ ጁላይ 22 ቀን 2013 እንደተሰጣቸው ማስረዳታቸውአመልካች በሕግ የተቀመጠውን 45 ቀን አሳንሶ በ43ኛው ቀን የስንብት ደብዳቤ መስጠት እንደማይችል፤ ደብዳቤውም ከሥራ ሰዓት ውጭ የተሰጣቸው መሆኑንበመግለጽ የሥር ፍ/ቤት እንዲፀና አመልክቷል፡፡ አመልካችም ተጠሪ ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው በአመልካች እና ተጠሪ በሙከራ ጊዜ ላይ የተመሰረቱ የሥራ ቅጥር ውል መፈፀሙን ነው፡፡ ተጠሪ ከድርጅቱ ጋር ግንኙነት ባለው ሌላ ድርጅት በዚህ የሥራ መደብ ላይ ሲሰሩ እንደነበር በድጋሚ በተመሳሳይ የሥራ መደብ ለሙከራ መቀጠራቸው ሕጋዊ አለመሆኑን በመጥቀስ ቢከራከሩም የሥር ፍርድ ቤት ለሙከራ የተቀጠሩበት ደብዳቤ በማስረጃነት በመውሰድ ክርክራቸው አግባብነት የሌለው መሆኑን በውሣኔው አስፍሯል፡፡ ተጠሪ ይህንን ውሣኔ በመቃወም ያቀረቡት ይግባኝ ይሁን መስቀለኛ አቤቱታ የለም፡፡ በዚህ ረገድ በሰበር አቤቱታቸው በሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውድቅ የተደረገው ክርክር በሰበር ደረጃ ማቅረባቸው ሥነ-ስርዓታዊ አካሄድ የተከተለ አይደለም፡፡

አንድ ሠራተኛ ሊመደብበት ለታቀደው ቦታ ተስማሚ መሆኑና አለመሆኑን ለመመዘን ለሙከራ ጊዜ ሊቀጠር እንደሚችል፤ ይህ የግራ ቀኙ ስምምነትም በጽሑፍ መደረግ እንዳለበት፤ የሙከራ ጊዜውም ከ45 ተከታታይ ቀናት መብለጥ እንደሌለበት ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(1) ፣(2) እና (3) አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን ለሙከራ ጊዜ መቅጠሩ በሥር ፍ/ቤት የታመነበት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን በግዜ ገደቡ ውስጥ ማሰናበቱን ሲከራከር ተጠሪ ደግሞ በ46ኛው ቀን የተሰናበቱ መሆናቸው በመግለፅ ስንብቱ ህገ ወጥ እንዲባልላቸው አመልክተዋል፡፡ በስር ፍ/ቤት የአመልካች ምስክሮች ስንብቱ እ.ኤ.አ. ጁላይ 19 ቀን 2013 መሆኑን ይህ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 15 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ሰፍሯል፡፡ ተጠሪ በሰጡት የምስክርነት ቃል የስንብት ደብዳቤው እ.ኤ.አ. ጁላይ 22 ቀን 2013 መሆኑ፤የጊዜ ስሌቱ ሲሰራ ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ በ46ኛው ቀን መሆኑን ገልጿል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቱ የአመልካች ድርጊት ሕገወጥ ነው ለማለት እንደመነሻ የወሰደው ተጠሪን በ46ኛው ቀን ከሥራ አሰናብቷል በሚል ነው፡፡

አመልካች ተጠሪን ያሰናበታቸው በ43ኛ ቀን ነው?ወይስ በ46ኛው ቀን?በ46ኛው ቀን ሲሰናበቱ ሕጋዊ ውጤቱስ የተለየ ሊሆን ይችላል? የሚለው መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአመልካች ተሰጠ የተባለው ደብዳቤ እ.ኤ.አ አቆጣጠር ጁላይ 19 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ መሆኑ ወደ ኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ሲመለስ ደግሞ ሐምሌ 15 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን በውሣኔው አስፍሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እ.ኤ.አ. ጁላይ 19 ቀን 2013 ወደ ኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 15 ቀን 2005 ዓ.ም በማለት በውሣኔ የተጠቀሰው ተቀባይነት /conventional/ ካልሆነው የጊዜ አቆጣጠር ቀመር አኳያ ሲታይ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ከላይ የተገለፀው ጁላይ 19 ቀን 2013 ወደ ኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 12 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2005 ዓ.ም መሆኑን ተቀባይነት ካለው የጊዜ አቆጣጠር /ካላንደር/ አንፃር በማዛመድ በቀላሉ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ጁላይ 19 ቀን 2013 እ.ኤ.አ ወደ ኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 15 ቀን 2005 ዓ.ም ነው፡፡ በማለት ማስፈሩ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች ተጠሪን ሐምሌ 12 ቀን 2005 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የሙከራ ግዜ ቅጥር ውል እንዲቋረጥ የተደረገ ከሆነ በ45 ቀን ጊዜ ገደብ ውስጥ የተፃፈ ደብዳቤ መሆኑ መረዳት ይቻላል ፡፡ አመልካች ተጠሪ ሊመደቡበት ለታቀደው ቦታ ተስማሚ መሆኑን አለመሆናቸው በ45 ቀን ውስጥ ውሣኔ ማስተላለፍ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር የሚቃረን ውሣኔ አይደለም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የአመልካች ድርጊት ሕገወጥ ነው በማለት ለመወሰን እንደ መነሻ የወሰደው ስንብቱ በ46ኛው ቀን ተከናውኗል በሚል ነው፡፡አንድ አሠሪ የሙከራ ጊዜ ውል ያለአግባብ በማሳጠር ይሁን ከሚገባው በላይ ጊዜው በማራዘም የሠራተኛው የተረጋጋ የሥራ ዋስትና እንዳይኖር ማድረግ እንደሌለበት ከአጠቃላይ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅቁ. 377/96 ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁንና አሠሪው በ45ኛው ቀን መጨረሻ ይሁን በ46ኛው ቀን መጀመሪያ ሠራተኛው ለተመደበበት የሥራ ቦታ ተስማሚ አይደለም በማለት ከወሰነ የፈጠነ ወይም በጣም የዘገየ ውሣኔ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የሙከራ ግዜው በ45ኛው ቀን መጨረሻ የሚጠናቀቅ ከሆነ በ46ኛው የመጀመሪያ ቀን የስንበት ደብዳቤ መፃፉ የሠራተኛው የሥራ ዋስትና አደጋ ውስጥ አስገብቷል ለማለት የሚያስችል አሳማኝ ምክንያት የለውም፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተረጋግጧል የተባለው ፍሬ ነገር ተወስዶ ደብዳቤው በ46ኛው ቀን ነው የተፃፈው ቢባል እንኳ የአሠሪው የማሰናበት መብትና ሥልጣን ዘግይቶ ተግባራዊ የተደረገ ነው ሊባል አይችልም፡፡ የሙከራ ጊዜ ውል ለ 45 ተከታታይ ቀናት የሚቀጥል ከሆነ ግለሰቡ በመጨረሻው ቀን በመገምገም ለታቀደው ቦታ ተስማሚ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ውሣኔ ለማስተላለፍ የመጨረሻ ቀን የሥራ አፈፃፀም ውጤት ጭምር ታሳቢ መደረግ ያለበት በመሆኑ በ46ኛው ቀን የስንብት ደብዳቤ መፃፉ የሕጉን ይዘትና መንፈስ የሚቃረን አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለውን ጉዳይ በአግባቡ ሳያገናዝቡ የሙከራ ጊዜ ከ45 ቀናት መብለጥ የለበትም የሚለውን የሕጉ ይዘት ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ግብ ሳያገናዝቡ መወሰናቸው በአግባቡ አይደለም ብለናል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች ድርጊት ሕገወጥ ነው በማለት መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ አተረጓጎም ስህተት ፈጽመዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ.85529 በ18/07/2006 ዓ.ም እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ. 139947 በ19/07/2006 የሰጡት ፍርድ እና ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪ ያለማስጠንቀቂያ ማሰናበቱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለዚህ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ብ/ግ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101795

መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ሕይወት

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡-የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት ነገረ ፈጅ ፈለቀ እንግዳሸት- ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ አድማሱ አበበ ከጠበቃ ጥላሁን ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ነው በሚል የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ በ08/02/2006 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-ተከሳሽ ድርጅት ለሕዝብ ግንኙነት ደጋፊ የስራ ሂደት ላወጣው ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ የድርጅቱ ደንብ፣መመሪያ እና የህብረት ስምምነት በሚፈቅደው መሰረት ከሳሽ መስፈርቶቹን አሟልተው ለውድድር መመዝገባቸውን፣ይሁን እንጂ ድርጅቱ በማስታወቂያ የወጣውን የመወዳደሪያ መስፈርት በመተው መስፈርቱን የማያሟሉትን አቶ አወቀ በለጠ የተባሉትን የድርጅቱ ባልደረባ ለውድድር አቅርቦ እንዲያልፉ ማድረጉን፣ከሳሽ ይህንን በመቃወም ለድርጅቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት አግኝቶ መስፈርቱን የማያሟሉት አቶ አወቀ በለጠ ለውድድር እንዲቀርቡም ሆነ እንዲያልፉ የተደረገው አላግባብ መሆኑን ገልጸ ኮሚቴው በ13/01/2006 ዓ.ም. የተጻፈ የውሳኔ ሀሳብ ያቀረበ ቢሆንም ድርጅቱ ለውድድር በቀረበው የስራ መደብ ላይ ከሳሽን ለመመደብ ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን በዝርዝር የሚገልጽ ሆኖ መስፈርቱን ላላሟሉ ሰራተኛ የተሰጠው ምደባ ተሰርዞ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት የስራ መደቡ መስፈርቶቹን ላሟሉት ለከሳሽ እንዲሰጥ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ25/02/2006 ዓ.ም በሰጠው መልስ የመቃወሚያ እና የፍሬ ነገር የክርክር ነጥቦችን አቅርቧል፡፡የቀረቡት ሁለት የመቃወሚያ ነጥቦችም ክሱ የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት በመሆኑ እና ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያው የወጣበት የስራ መደብም የሚመለከተው የስራ መሪን እንጂ ሰራተኛን ባለመሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለውም የሚሉ ሲሆኑ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ የተሰጠው መልስ ይዘት ደግሞ ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያው የወጣው በስራ መሪዎች ምደባ መመሪያ መሰረት መሆኑን፣ጉዳዩም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚመለከተው ምደባን እንጂ የደረጃ ዕድገትን አለመሆኑን፣ የከሳሽ የምደባ ጥያቄ ተቀባይነት ያጣው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የመንግስትን ፖሊሲ እና መመሪያ በማስፈጸም ረገድ በከሳሽ ላይ እምነት ባለመጣላቸው መሆኑንየሚገልጽ ነው።ቦርዱም በቅድሚያ የመቃወሚያ ነጥቦቹን ከመረመረ በኃላ ከሳሽ ክሱን ያቀረቡት የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት ተጥሶብኛል በማለት በመሆኑ እና የሰራተኛ አቀጣጠር እና ዕድገት አሰጣጥ ስርዓትን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 142(1)(ሠ) ድንጋጌ መሰረት የተሰጠው ለቦርድ በመሆኑ ክሱ የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት መሆኑን ጠቅሶ ተከሳሽ ያቀረበው የስልጣን መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እና ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያው የወጣበት የስራ መደብየሚመለከተው የስራ መሪን እንጂ ሰራተኛን ባለመሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለውም በሚል የቀረበውን መቃወሚያ በተመለከተም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(2)(ሐ) ድንጋጌ መሰረት ለስራ መሪ የተሰጠው ትርጉም ቀድሞውንም ቢሆን የስራ መሪ ሆኖ በአንቀጹ ላይ የተዘረዘሩትን የስራ መሪ ተግባሮች ሲያከናውን የነበረን ሰው የሚመለከት እንጂ ሰራተኛ ሆኖ ለስራ መሪ በወጣ ክፍት የስራ መደብ ላይ ለውድድር የቀረበን እንደ ከሳሽ ዓይነት ሰውን የሚያጠቃልል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው መቃወሚያም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ መቃወሚያዎቹን በ11/03/2006 ዓ.ም በብይን ካለፋቸው በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ጉዳዩን ለክፍት የስራ ቦታው በወጣው ማስታወቂያ ላይ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች እና ከስራ መሪዎች ምደባ መመሪያ አንጻር መመርመሩን ገልጾ በውድድሩ 84.50% ውጤት አግኝተዋል የተባሉት አቶአወቀ በለጠ ወደ ውድድሩ የገቡት ተገቢ መመዘኛዎችን ሳያሟሉ በመሆኑ ለእርሳቸው የተሰጠው ምደባ ውድቅ ተደርጎ የስራ መደቡ እና የስራ መደቡ የሚያስገኘው ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ተገቢ የመወዳደሪያ መስፈርቶቹን አሟልተው ወደ ውድድሩ ለገቡት እና በውድድሩ 71% ውጤት ላገኙት ለከሳሽ ሊሰጥ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ለስራ መሪ የስራ መደብ ብቁ ሆኜ ሳለ ቦታው ለሶስተኛ ወገን የተሰጠው አላግባብ ነው በማለት ተጠሪ ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያቀረቡትን ክስ ቦርዱ የማየት ስልጣን የለውም በማለት አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት የማጣቱን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል።

በዚህም መሰረት አመልካች ላወጣው ክፍት የስራ መደብ ለውድደር በቀረቡበት ጊዜ ተጠሪ ይሰሩ የነበረው በሰራተኛነት መሆኑ፣ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያው የወጣው ለስራ መሪ የስራ መደብ መሆኑ፣በማስታወቂያው መሰረት በሰራተኞች እና በስራ መሪዎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ ለውድድር የተጋበዙት በሁለቱም የስራ ዘርፍ የሚገኙ የድርጅቱ የሰው ኃይል አባላት መሆናቸው፣በመወዳደሪያ መስፈርቶቹ መሰረት ውድድሩ እና አሸናፊውን ተወዳዳሪ የመምረጡ ስርዓት የሚከናወነው በድርጅቱ የስራ መሪዎች ምደባ መመሪያ መሰረት መሆኑ እና በዚህ ረገድ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 “ም” ሆነ የድርጅቱ የህብረት ስምምነት ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መሆኑ በግራ ቀኙ ክርክር ያልቀረበበት እና ቦርዱም ቢሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቀበለው ጉዳይ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው ቦርዱ በስረ ነገር ስልጣን ረገድ ከአመልካች የቀረበለትን የመቃወሚያ ነጥብ ውድቅ ያደረገው ክሱ የቀረበው የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት ተጥሶብኛል በማለት መሆኑን፣የሰራተኛ አቀጣጠር እና ዕድገት አሰጣጥ ስርዓትን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 142(1)(ሠ) ድንጋጌ መሰረት የተሰጠው ለቦርድ መሆኑን እና የስራ መሪ የስራ መደብም ተጠሪው የሚወዳደሩበት እንጂ ይዘው የሚገኙት የስራ መደብ አለመሆኑን በመግለጽ ነው፡፡

እንደሚታወቀው አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርገው የሚነሱ የስራ ክርክር ጉዳዮች የሚታዩት እንደ ጉዳዩ ዓይነት በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታዩት በአዋጁ አንቀጽ 138(1) ስር ከፊደል (ሀ) እስከ (ረ) የተዘረዘሩ የግል የስራ ክርክር ጉዳዮች መሆናቸውን እና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ የሚታዩት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 142(1) ከፊደል (ለ) እስከ (ሸ) የተዘረዘሩ የወል የስራ ክርክር ጉዳዮች መሆናቸውን ከላይ የተጠቀሱት እንዲሁም የአዋጁ አንቀጽ 142(3) እና 147(1)(ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ተጠሪ ክሳቸውን ለቦርዱ ያቀረቡትም የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት ተጥሶብኛል በማለት ነው፡፡የዚህ ዓይነቱ የስራ ክርክር ደግሞ በባህርይው የወል እንጂ የግል የስራ ክርክር አይደለም፡፡በዚህም ሁኔታ ከላይ የተጠቀሱትን የአዋጁን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ክሱ የቀረበው የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት ተጥሶብኛል በማለት መሆኑን እና የሰራተኛ አቀጣጠር እና ዕድገት አሰጣጥ ስርዓትን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 142(1)(ሠ) ድንጋጌ መሰረት የተሰጠው ለቦርድ መሆኑን በመግለጽ ቦርዱ የያዘው አቋም በራሱ የሚነቀፍ ባይሆንም ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አንጻር ለክርክር የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚሸፈን መሆን አለመሆኑ እና በዚህም ምክንያት በቦርዱ ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ መጤን የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የተፈፃሚነት ወሰን በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሰረተ የስራ ግንኙነት ጉዳዮች የተገደበ ስለመሆኑ እና በተለይም ከስራ መሪ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 3(1) እና (2)(ሐ) ስር የተመለከተ ሲሆን ተጠሪ የስራ መሪ ባይሆኑም ለውድድር የቀረቡት በስራ መሪ በሚሸፈን የስራ መደብ ላይ ለመመደብ ነው፡፡ዋነኛ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የቀረበውም በአዋጁ መሰረት የተጠሪው ሰራተኛ የመሆን አለመሆን ጉዳይ ሳይሆን በስራ መሪ ለሚሸፈን የስራ መደብ የሚደረግ ውድድር የሚመራበት ስርዓት ነው፡፡በመወዳደሪያ መስፈርቶቹ መሰረት ውድድሩ እና አሸናፊውን ተወዳዳሪ የመምረጡ ስርዓት የሚከናወነው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ እና በህብረት ስምምነቱ መሰረት ሳይሆን በድርጅቱ የስራ መሪዎች ምደባ መመሪያ መሰረት መሆኑ አላከራከረም፡፡የስራ መሪዎችን የምደባ መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን ደግሞ በአዋጁ መሰረት ለፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎቶችም ሆነ ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አልተሰጠም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 142(1)(ሠ) ድንጋጌ ስር ***"...ስለሰራተኛ...ዕድገት አሰጣጥ ስርዓት"*** በሚል የተገለጸው ሐረግ ሊተረጎም የሚገባው ከአንድ የሰራተኛ የስራ መደብ ወደ ሌላ የሰራተኛ የስራ መደብ የሚፈጸም የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት ተደርጎ እንጂ ከአንድ የሰራተኛ የስራ መደብ በስራ መሪ ወደሚሸፈን ሌላ የስራ መደብ የሚፈጸም የዕድገት አሰጣጥ ስርዓትን በሚያጠቃልል አግባብ አለመሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከድንጋጌው አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 142(1)(ሠ) ድንጋጌ ስር "...ስለሰራተኛ...ዕድገት አሰጣጥ ስርዓት" በሚል የተገለጸውን ሐረግ ከአንድ የሰራተኛ የስራ መደብ በስራ መሪ ወደሚሸፈን ሌላ የስራ መደብ የሚፈጸም የዕድገት አሰጣጥ ስርዓትን እንደሚያጠቃልል አድርጎ በመተርጎም ቦርዱ በስረ ነገር ስልጣን ረገድ በአመልካች የቀረበውን መቃወሚያ በብይን አልፎ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ የሰጠው ውሳኔ በሕግ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመዝገብ ቁጥር 498/ቀወ2/06 በ12/06/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139704 በ22/09/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ክርክር ያስነሳው ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚሸፈን ባለመሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን ተቀብሎ በማስተናገድ ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖረው ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ በ12/10/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም ዕግድ ተነስቷል፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እና ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101579

ህዳር 24 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ. መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካቾች፡-

1. አቶ ገ/መድህን አስፋው
2. አቶ ተ/ዓዲቅ ደምሴ
3. አቶ ዳኜ አየለ
4. አቶ ወ/ሚካኤል ዋቄ
5. አቶ አምሃ ኃ/ስላሴ
6. አቶ አመሃ መላኩ ኃ/ማሪያም
7. አቶ ደምሴ ድጋፌ
8. አቶ ግዛው አስረስ
9. አቶ ታደሰ ገ/መድህን
10. አቶ ወረደወርቅ ጥላሁን
11. አቶ ከበደ አወቀ
12. አቶ ይልማ ጨርቆስ
13. አቶ ዓለማየሁ ተሾመ
14. አቶ ላቀው እርገጤ
15. አቶ ተሾመ አግዴ
16. አቶ አየለ ይግለጡ
17. አቶ ይትባረክ ሰሜ
18. ወ/ሮ ፀሐይ አእምሮ
19. ወ/ሮ ብዙነሽ ማሞ
20. ወ/ሮ በቀለች ጐዳና
21. አቶ ኃ/ማሪያም ገና
22. አቶ ገብረ ተ/ኃይማኖት
23. አቶ ፍቃደስላሴ ርዳው
24. አቶ ሞገስ ኃ/መስቀል

ከጠበቃ መስፍን አለማየሁ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ትንሳኤ ዘገባኤ ማተሚያ ቤት ነ/ፈጅ ሳህለማሪያም ወዳጆ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 128430 ታህሳስ 7 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.96927 ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተሽሮ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ጉዳዩ የጡረታ ደመወዝ ማስተካከያ አስተዳደራዊ ውሳኔ ተግባራዊ ይሁንልን ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት ተከሳሾች ነበሩ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካቾች የክስ ይዘትም፡- መንግስት ለመንግስት ሰራተኞች እና ጡረተኞች ህዳር 23 ቀን 2003 ዓ/ም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባስተላለፈው ውሳኔ የደመወዝ ማስተካከያ ማድረጉን ተከትሎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅድስ ሲኖዶስም በስሩ ላሉት ሰራተኞች የደመወዝ ማስተካከያ እንዲደረግ ወስኖ ባለበት ሁኔታ የአሁኑ ተጠሪ እምቢተኛ መሆኑን ዘርዝረው የጡረታ ደመወዝ ማስተካከያ እንዲከፈል ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ የስር ተከሳሾች ጉዳዩ በፍርድ ሊታይ የማይችልበትን ምክንያትና አመልካቾች ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን የሚያሳዩ ነጥቦችን በመጥቀስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ለአመልካቾች የጡረታ ደመወዝ እንዲስተካከል የሚደረግበት የህግ ወይም የህብረት ስምምነት የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾች ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾች ጥያቄ በፍርድ ቤት ሊታይ እንደሚችል፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቋሚ ሲኖዶስ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም ባደረገው ስብሰባ ማስተካከያውን ለሰራተኞችና ለጡረተኞች በወሰነው መሰረት የአሁኑ ተጠሪም ለአሁኑ አመልካቾች ማስተካከያው ሊከፍል ይገባል በማለት ደምድሞና ሊጨመር የሚገባውን ማስተካከያ በመቶኛ ገልጾና ይኼው ማስተካከያ የሚመለከተውን የጡረታ ደመወዝ መጠን ለይቶ ለአመልካቾች ተጠሪ የጡረታ ማስተካከያውን ሊከፍል ይገደዳል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስር የሚተዳደር ነገር ግን በራሱ ገቢ ራሱን የሚያስተዳድር ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ጉዳይ መሆኑን፣ ለአመልካቾች ክስም ሆነ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሠራተኞቹና ጡረተኞቹ የደሞዝ ማስተካከያ አስመልክቶ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም ያስተላለፈው ውሳኔ መሆኑን በዚህ ውሳኔ ጥናት ተደርጐ የቀረበውን ጉባኤው ያፀደቀላቸው ሲሆን ሌሎቹ ማለትም በትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤትና ጮፋ ጥበበ እድ ካህናት ማስልጠኛ ለሚገኙት ሠራተኞችና ጡረተኞች እንደየገቢያቸው መጠን እየወሰኑ ለአስተዳደሩ አቅርበው እያስፀደቁ ተግባራዊ እንዲሆን ሲል ቋሚ ሲኖዶሱ መወሰኑን የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይዘት በግዴታ የማያመላክት መሆኑን ከዚህ መረዳት የሚቻለው የጉባኤው ውሳኔ የአሁኑን ተጠሪን በተመለከተ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት እና አስገዳጅነት ያለው የደመወዝ ማስተካከያ ያለማድረጉ መሆኑን ይልቁንም ተጠሪ በራሱ ገቢ የሚተዳደር ከመሆኑ አንፃር እንደራሱ ገቢ መጠን ጥናት አድርጐ በአስተዳደሩ አፅድቆ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል አቅጣጫ የተቀመጠለት መሆኑን እንጂ አስገዳጅ የሆነ ውሳኔ ያልተሰጠ መሆኑን የሚያስገነዝብ መሆኑን ደምድሞ አመልካቾች ባለው የቤተክርስቲያን መዋቅር መሰረት አቤቱታቸውን ከማቅረብ ውጪ በፍርድ ሃይል ተፈጻሚ የሚሆን ውሳኔ የላቸውም በማለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ በመቀበል አፅንቶታል ። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሲኖዶስ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም ያሳለፈው ውሳኔ ተጠሪ ገቢውን መሰረት በአደረገ መልኩ ለሰራተኞቹም ሆነ ለጡረተኞቹ በተሰራው ስኬል መሰረት ማስተካከያውን እንዲያደርግ የሚል ሁኖ እያለ ተጠሪ ለሰራተኞቹ ብቻ ማስተካከያውን አድርጐ ለጡረተኞቹ ሳያደርግ ሲቀር የቀረበውን ክስ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያላግባብ ተርጉሞ ተጠሪ የሚገደድበት ውሳኔ የለም በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው የሚል ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል ፡፡እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቋሚ ሲኖዶስ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የአሁኑን ተጠሪ በስም ጠቅሶ ለሠራተኞቹና ጡረተኞቹ እንደየገቢያቸው መጠን እየወሰኑ ለአስተዳደሩ እያስፀደቁ ክፍያው እንዲፈፀም በማለት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ለሰራተኞቹ የጭማሪውን ክፍያ እንደአደረገ ተጠሪ ግንቦት 27 ቀን 2005 ዓ/ም በሰጠው መልስ ማመኑ ከተረጋገጠ የሲኖዶሱ ውሳኔ ለጡረተኞች ብቻ ተፈፃሚነት የለውም በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር ብቻ መመርመሩን ተገቢነት ያለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሥር የሚተዳደር ነገር ግን በራሱ ገቢ ራሱን የሚያስተዳድር ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ጉዳይ መሆኑን፣ ለአመልካቾች ክስም ሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሠራተኞቹና ጡረተኞቹ የደሞዝ ማስተካከያ አስመልክቶ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም ያስተላለፈው ውሳኔ መሆኑን፣ በዚህ ውሳኔ ጥናት ተደርጎ የቀረበውን ጉባኤው ያፀደቀላቸው ሲሆን ሌሎቹ ማለትም በትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤትና በጎፋ ጥበብ እድ ካህናት ማሰልጠኛ ለሚገኙት ሠራተኞችና ጡረተኞች እንደየገቢያቸው መጠን እየወሰኑ ለአስተዳደሩ አቅርበው እያፀደቁ ተግባራዊ እንዲሆን ሲል ቋሚ ሲኖዶሱ መወሰኑና ይህንኑ ተከትሎም ተጠሪ ለሠራተኞቹ የጭማሪውን አስተካክሎ ክፍያውን ሲፈፅም ለአሁኑ አመልካቾች፤ የድርጅቱ ጡረተኞች ግን ማስተካከያውን ሳያደርግ የቀረ መሆኑን አምኖ የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የሲኖዶሱ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይዘት ተጠሪ ለጡረተኞች ማስተካከያ እንዲያደርግ በግዴታየሚያመላክት አይደለም የሚለውን ምክንያት በመያዝ መሆኑን ከውሳኔው ይዘት ተረድተናል፡፡

በመሰረቱ ተጠሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስር የሚተዳደር ከሆነ የቤተክርስቲያኗ የበላይ የሆነው አካል የሰጠውን ውሳኔ ያለምንም ልዩነት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ ተጠሪ ለአመልካቾች የጡረታ ደመወዝ የሚከፍለው በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ሲሆን ይህ ክፍያ የሚፈፀመውም የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነቱ በጡረታ ምክንያት በመቋረጡ ምክንያት በመሆኑና ገንዘቡም ከአሰሪውና ከሠራተኞቹ ደመወዝ ተቆርጦ ሲጠራቀም ከነበረው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የጡረታ ደመወዝ ሕጋዊ በሆነ የአስተዳደራዊ ውሳኔ መሰረት እንዲስተካከል ሲደረግ በሠራተኛው ስም የተቀመጠው ገንዘብ መኖሩን ብቻ በማረጋገጥ ነው ተብሎ አይታሰብም፡፡ ጡረታ አግባብነት ላላቸው የህብረተሰቡ ክፍሎች የኑሮ ዋስትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመስጠት እንዲያስችል ተብሎ ተግባራዊ የሚደረግ ማህበራዊ መድህን መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የኑሮ ዋስትና የመስጠት መሰረታዊ አላማው የሚሳካው ደግሞ ተጨባጭነት ያለውን ወይም የሕብረተሰቡን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ማስተካከያው ሲደረግ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ በዚህ አግባብ የጡረታም ሆነ የደመወዝ ማስተካከያም ተግባራዊ እየተደረገ ያለበት ሁኔታ መኖሩም ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡ የተጠሪ መስሪያ ቤት ባለቤት የሆነውና የበላይ የአስተዳደር አካሉ መንግስት ለሠራተኞቹና ለጡረተኞቹ ያደረገውን ማስተካከያ መነሻ በማድረግና በራሱ ፍላጎት ለተጠሪ ሠራተኞቹና ጡረተኞች ማስተካከያውን እንዲያደርግ፣ ማስተካከያው ደግሞ የተጠሪን ገቢ መሰረት አድርጎ ሊሰራእንደሚገባና በሚመለከተው አካል እየጸደቀ ተግባሪዊ እንዲሆን የሚገልፅ ውሳኔ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም መወሰኑም ይህንኑ የሚያሳይ ነው ።። ተጠሪ የሲኖዶሱ ውሳኔ በተጠሪ ላይ አስገዳጅነት የለውም በማለት የሚያቀርበውና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘው መከራከሪያ ነጥብ ሲታይም ተጠሪው ገቢውን መሰረት ያደረገ ጥናት አደርጎ ለቋሚ እና ለኮንትራት ሰራተኞቹ ማስተካከያውን አድርጎ ክፍያውን መፈጸሙን ያመነበትን አግባብ ክፍያውን ለጡረተኞቹ ላለማድረግ ህጋዊ ምክንያት የነበረው መሆን ያለመሆኑን አጣምሮ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ምክንያቱም የተጠሪ የበላይ አስተዳደር የሆነው አካል ለተጠሪ የሰጠው አስተዳደራዊ አቅጣጫ የማስተካከያው ክፍያ ተጠቃሚዎችን ሠራተኞች ወይም ጡረተኞች በሚል ጭምር ተለይቶ እንዲፈፀም የሚያሳይ ሳይሆን ለሠራተኞቹም ሆነ ለጡረተኞቹ ልዩነት ሳይደርግ የድርጅቱን ገቢ መሰረት አድረጎ ማስተካከያውን እንዲሰራና ተግባራዊ እንዲያደርግ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የበላይ አካልን ውሳኔ ተግባራዊ ላለማድረግ ሕጋዊ መከራከሪያ ሊሆነው የሚችለው የድርጅቱ የገቢ ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ሆኖም ተጠሪ ለሰራተኞቹ ማስተካከያውን ያደረገው የድርጅቱን ገቢ መሰረት አድርጎ ስላለመሆኑ ያቀረበው ክርክርና ማስርጃ የለም፡፡የተጠሪ የበላይ አካል የሆነው ሲኖዶሱ ማስተካከያው ለተጠሪ ድርጅት ሰራተኞች ጡረተኞች እንዲደረግ ውሳኔ ከሰጠና ለሠራተኞቹ የተጠሪን ገቢ መሰረት ባደረገ መልኩ ማስተካከያው መደረጉ እስከተረጋገጠ ድረስ ደግሞ ተጠሪ ጡረተኞችን ብቻ በመለየት የማስተካከያው ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም የሚልበት አግባብ የለም፡፡ተጠሪ የበላይ አካሉን ውሳኔ ተቀብሎ ለሠራተኞቹ ብቻ ማስተካከያ አድርጎ ለጡረተኞቹ ብቻ ማስተካከያውን የተወበት አካሄድ ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ በውጤት የጡረታ መብት ለኑሮ ዋስትና ያለው ሕጋዊ ፋይዳ ዋጋ የሚያሳጣው ነው፡፡

አመልካቾች ተጠሪ ላይ በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ የመሰረቱት ከተጠሪ ጋር መስርተው የነበሩት ሕጋዊ የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ተቋርጦ የአመልካቾች የጡረታ መብት ተከብሮላቸው የጡረታ መብት ተካፋይ ሁነው ባሉበት ሁኔታ በአስተዳደራዊ ውሳኔ መሰረት የተከበረላቸው የጡረታ ማስተካከያ ክፍያ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም በሚል በመሆኑ ጉዳዩ ኃይማኖታዊ ስርዓትን ተከትሎ ትርጉም የማያስፈልገው በመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ቤት መታየቱ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 11 ስር የተደነገገውን መርህ የማይነካ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ሕጋዊ የሆነ አስተዳደራዊ ውሳኔ ተግባሪዊ ሳይሆን ሲቀር በፍርድ ቤት ውሳኔ አስገዳጅነትአንዲኖረውማድረግም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 37 እና 25 የተረጋገጡትን ፍትህ የማግኘት መብትና የእኩልት መብት ውጤታማ የሚያደረግ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪ የበላይ አካል የሆነው ሲኖዶስ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሰኔ የአሁኑን ተጠሪ በስም ጠቅሶ ለሠራተኞቹና ጠረተኞቹ እንደየገቢያቸው መጠን እየወሱነ ለአስተዳደሩ እያስወደቁ ክፍያው እንዲፈፀም በማለት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ተጠሪ ለሰራተኞቹ የጭማሪው ክፍያ እንደ አደረገ ግንቦት 27 ቀን 2005 ዓ/ም በሰጠው መልስ ማመኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተረጋገጠበት ሁኔታ የሲኖዶሱ ውሳኔ ለጡረተኞች ብቻ ተፈፃሚነት የለውም የሚል ትርጉም የሚያሰጥ ውሳኔ መስጠቱ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ያላገናዘበ ሆኖ ስለአገኘነው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 96927 ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128430 ታህሳስ 07 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካች ጥያቄ ኃላፊ ነው ተብሎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም በወሰነው መሰረት ከጥር ወር 2003 ዓ/ም ጀምሮ የጡረታ ማስተካከያ አበል ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ ስሌቱን በተመለከተ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባስቀመጠው መሰረት ነው ብለናል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማአለበት፡፡

እ/እ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 102512

ታህሳስ 10 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካቾች፡-

1.አቶ ብርሃኑ ቢኔ
2. አቶ ሞላ ደሴ
3. አቶ ተስፋዬ ሐበና
4. ወ/ሮ ጀማነሽ መንገሻ
5. አቶ ገልትነህ ታደሰ
6. አቶ ወርቁ አይዴ
7. አቶ መኮንን መሉ
8. ወ/ሮ ክብነሽ ዋጤሮ
9. ወ/ሮ ታየች አሰፋ
10. አቶ አጫ አይሳሮ
11. ወ/ሮ ፀዳለ ቸችሮ
12. አቶ ሐይሌ አረጋዊ
13. አቶ ጠብቀው ሳንፎ
14. ወ/ሮ ለተብርሃን መኮንን
15. አቶ ዘሪሁን ደግፌ
16. አቶ በርሔ አሰፋ
17. ወ/ሮ አቦነሽ ሳካሎ
18. አቶ ዋህድ ካሳዬ
19. አቶ ግዛቸው ካሳ
20. አቶ አበራ ሐይሌ
21.አቶ ደምመላሽ ካሳዬ
22. ወ/ሮ መስከረም ካንኮ
23. አቶ ሙሉጌታ መቺሶ
24. አቶ ሱልጣን ሐሰን
25. አቶ ጌታሁን ሐይሌ
26. ወ/ሮ ዓለሚቱ ገብሬ
27. ወ/ሮ ባዩሽ በቀለ
28. አቶ ደሳለኝ ትንታግ
29. አቶ እንግዳ እሸቱ
30. ወ/ሮ ጀማነሽ መንገሻ
31. ወ/ሮ አየለች ባልቻ
32. አቶ መንበረ ጌታቸው
33. አቶ መተኪያ ፀጋዬ
34. አቶ አብዮት ጌታሁን

ደመነ ቱኔ የ34ቱም ጠበቃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ፡- የአርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካአ/ማ- ነ/ፈጅ ሹፋያን ሱልጣን ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139151 ግንቦት 25 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው። ጉዳዩ የስራ ውል መቋረጥን የሚመለከት ነው። ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በደቡብ ክልል የሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ነው። በክልሉ የሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል።

1. አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት ከሃያ ዓመት በላይ በታማኝነት ያገለገሉ መሆኑን ገልፀው ተከሳሽ (ተጠሪ) አዲስ መዋቅር አስጠንቻለሁ በማለት የስራ መደባችሁ ታጥፏል በሚል ሰበብ በሕግ አግባብ የሰራተኛ ድልድልና ምደባ ሳያደርግ ቅነሳ በሚል ሀሰተኛ ምክንያት መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ/ም እና ሚያዝያ 10 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የስራ ውላችንን ከሕግ ውጭ ያቋረጠ በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ይወሰንልን በማለት አመልክተዋል። ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታይ ነው በማለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን፣ በአማራጭ ሰራተኞቹ የተቀነሱት የድርጅቱ መዋቅር በገለልተኛ ባለሙያ ከተጠና በኋላ ከሳሾች መዋቅሩ የሚጠይቀውን መስፈርት ባለማሟላታቸው ያልተደለደሉ በመሆኑና ድልድሉ የሰራተኞች ተወካይ ባለበት በግልጽ መስፈርት ሰራተኞች ተወዳድረው የተመደቡ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል።
2. የክልሉ ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተጠሪ አመልካችዎችን ከስራ ያሰናበተበት አግባብ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 29 የተደነገጉትን መስፈርቶች የማያሟላና ከሕግ ውጭ በመሆኑ ተጠሪ በሕጉ መሰረት ሁሉንም ሰራተኞች ባሳተፈ መልኩ እንደገና የሰራተኛ ድልደላ ይፈፅም። ተጠሪ እንደገና ለመደልደል ካልፈለገ ስንብቱ ሕግን ያልተከተለ በመሆኑ ከሳሾችን/ አመልካቾችን/ ወደ ስራ ይመልስ። ተጠሪ ከሳሾችን ወደ ስራ ካልመለሰ በሕግ አግባብ ካሳ በመክፈል እንዲያሰናብታቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይግባኝ ባይ (ተጠሪ) ሠራተኞችን የደለደለው በትምህርት ደረጃ፣ በስራ ልምድ፣ በማህደር ጥራትና የስራ አፈፃፀም ውጤት በመሆኑ ስንብቱ በህግ አግባብ የተፈፀመ ነው በማለት የክልሉ ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል።
3. አመልካቾች ሰኔ 27 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ያስጠናው መዋቅር ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 20 የስራ መደብ ያለው ቢሆንም ሰራተኛ ድልድል የፈፀመው ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 12 ባለው የሥራ መደብ ላይ ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል። ተጠሪ ካሉት 674 ሠራተኞች አስር ፐርሰንት የሚሆኑ አልቀነሰም። መዋቅሩ ሠራተኞች ቁጥር እንዲጨምር የሚያደርግ ነው። ተጠሪ እኛን በሕግ አግባብ በማወዳደር ሠራተኞችን ያልደለደለ መሆኑን በማረጋገጥ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አላግባብ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል። ተጠሪ ጥቅምት 3 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 12 ባለው የስራ መደብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠራተኞች በአግባቡ ተወዳድረው ተመድበዋል፡፡ ከደረጃ 13 እስከ ደረጃ 20 ያለው የስራ መደብ የስራ መሪዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ከስራ የተሰናበቱት ሰራተኞች 10% በታች መሆኑ ስንብቱን ህገ ወጥ አያደርገውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች ጥቅምት 14 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ የመልስ መልስ ተጠሪ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 12 ሰራተኞች ተወዳድረው ተመድበዋል ያለው ሀሰት ነው፡፡ ምክንያቱም በድርጅቱ ንብረትና ፋይናንስ ዘርፍ የሥራ መደቦች ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች በድልድል አልተካተቱም፡፡ ተጠሪ ከደረጃ 13 እስከ ደረጃ 20 ያሉት የስራ መደቦች የስራ መሪ የስራ መደብ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር እውነትነት የሌለው ነው፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ የአመልካቾችን የስራ ውል ያቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን፣ በመጀመሪያ ፍሬ ጉዳይ የማጥራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን በሕግ የተሰጠው የሠራተኞች ጉዳዮች ወሳኝ ቦርድ የግራ ቀኙን የሰውና የፅሁፍ ማስረጃ ሰምቶ፣ መርምሮና መዝኖ የደረሰባቸውን የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያዎች ከሕጉ ድንጋጌ ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ የክልሉ ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪ ምርታማነትን ለማሳደግና አሰራር ለመለወጥ አዲስ መዋቅር ያስጠና መሆኑና በአዲሱ መዋቅር መነሻ በማድረግ አመልካቾችን ከስራ የቀነሰ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ካሉት 674 ሠራተኞች ቅነሳ በሚል ምክንያት ከስራ ያሰናበተው ከአስር ፐርሰንት የማይሆኑ ሠራተኞችን እንደሆነ አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስራ ምደባው ከተወዳደሩ በኋላ በውድድሩ ያላለፉ ሠራተኞችን ተጠሪ ከደረጃቸው ዝቅ አድርጎ የመደበና ያላሰናበተ መሆኑን በማስረጃ መረጋገጡንና የሥራ ድልድሉ ሁሉንም ሰራተኞች የማይመለከት በተለይ ንብረትና ፋይናንስ ክፍል የሚሰሩ ሰራተኞችን የማይመለከት መሆኑን በማስረጃ እንደተረጋገጠ ቦርዱ በግልጽ በውሳኔው ውስጥ አስፍሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከደረጃ 13 እስከ ደረጃ 20 ያሉ የስራ መደቦች ሰራተኞች በውድድር ያልተመደቡባቸው መሆኑን፣ በማስረጃ እንደተረጋገጠ በውሳኔው አስፍሯል፡፡ ይህም የሠራተኛ ቅነሳ ነው በማለት ተጠሪ ያከነወነው ተግባር የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት አያሟላም በማለት የሠራተኛ ውሳኝ ቦርዱ መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡
6. ከላይ የሰራተኛ ወሳኝ ቦርዱ በማስረጃ ያረጋገጣቸው ጉዳዬች አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንጻር መርምረናል፡፡ በመጀመሪያ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) አሰሪው የድርጅቱን አቋም ወይም የስራ እንቅስቃሴ ምክንያት በማድረግ በተለይም የድርጅቱን ምርታማነት የማሳደግ አሰራር ዘዴዎች ለመለወጥ ወይም አዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ሲባል ሠራተኞችን የመቀነስ ውሳኔ ሊያስተላልፍ እንደሚችልና ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ሰራተኞችን ሊያሰናብት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ መስረት የስራ መደብ መሰረዝ ሠራተኞችን የሚነካ ሲሆንና በአዋጁ አንቀጽ 29(1) መሰረት የሠራተኛ ቅነሳ የሚያስከትል ሲሆን የስራ ውሉ የሚቋረጠው በአዋጅ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 3 ሁኔታዎች በማሟላት መሆን እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡
7. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ባስጠናው አዲስ መዋቅር ምክንያት ካሉት ሠራተኞች አስር ፐርሰንት የሚሆኑትን የስራ ውል ያላቋረጠና ይህም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 29(1)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቀመጠውን መስፈርት የማያሟላ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ካሉት ሠራተኞች አምስት ፐርሰንት የማይሆኑትን የስራ ውል ለማቋረጥ በአዋጅ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት የመከተል ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ከአመልካቾች ያነሰና ዝቅተኛ የሥራ አፈጻጸም ያላቸውን ሠራተኞች በተጠሪ ኃላፊዎች ትዕዛዝ በስራ እንዲቀጥሉ አድርጎ አመልካቾችን ያሰናበተ መሆኑ የሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የግራ ቀኙን ምስክሮች የሰራተኛ ደልዳይ ኮሜቴ አባላት የምስክርነት ቃል በመስማትና በመመዘን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስራ ድልድልና ቅነሳው ተጠሪ ያሉትን ሁሉንም የስራ መደቦች የማያካትትና ሁሉንም የስራ ክፍሎች የማይመለከት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡በአጠቃላይ ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 29/3/ የተደነገጉትን መስፈርቶች በመጠቀም የአመልካቾችን የስራ ውል ያላቋረጠ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለው የሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ ተረጋግጧል፡፡

8. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያረጋገጣቸውን ፍሬ ጉዳዮች እና የደረሰበትን የፍሬ ጉዳይ እና የማስረጃ መደምደሚያ በመቀበል፤ሕጉን መሰረት ያደረገ መሆኑን ከመመዘን ያለፈ፣ የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ስህተት በይግባኝ የማየትን የማረም ሥልጣን ከአዋጅ አንቀጽ 140 ንዑስ አንቀጽ 1 አልተሰጠውም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 12 ሰራተኞች ለመደልደል በተጠቀማቸው አራት መስፈርት ከአመልካቾች ጋር ተወዳድረው ዝቅተኛ ነጥብ ያመጡ ሰዎች በስራ እንዲቀጥሉ ያደረገና የተሻለ ውጤት ያመጡትን አመልካቾች ያሰናበተ መሆኑን በማስረጃ እንዳረጋገጠ የገለጸውን የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያ የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤት ሳይመረምርና ሳይመዝን በማለፍ ተጠሪ ሠራተኞችን የደለደለው አራት መስፈርቶች ተጠቅሞ ነው በማለት ስንብቱ ህጋዊነው በማለት መወሰኑ በመዝገቡ የሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ በማስረጃ ያረጋገጣቸውን ፍሬ ጉዳዮች በማለፍ የተሰጠና የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) እና ንዑስ አንቀጽ 3 እንዲሁም የአዋጁን አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 40(1) ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሠራተኞች ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የአርባ ምንጭ ቅርንጫፍ በመዝገብ ቁጥር 0002/05 መስከረም 24 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 104294

ቀን 29/07/2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ሐግቤስ ኃ/የተ/የግል/ማህበር - ነ/ፈጅ ፀጋዬ መካሻ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ በላይ ገ/ማሪያም - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው በፌዴሬራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካች የስንብት እርምጃ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጽናቱ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 “ን” መሰረት ያደረገ የግል የስራ ክርክር ሁኖ አንድ ሰራተኛ ከአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል ተብሎ ከስራ ያለማስጠንቀቂያ የሚሰናበትበትን የህግ አግባብ ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የተጠሪ ክስ አመልካች ተጠሪን በጨረታ እንዳይሳተፍ የተደረገውን ጥፋት ሳይፈጽም ይህንኑ ጥፋት ፈጽመሃል በሚል ምክንያት የስራ ውል አላግባብ ያቋረጠ በመሆኑ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ የተጠሪ የስራ መዝርዝር በግልጽ የሚያሳየው የጨረታ ሰነድ አዘጋጅተው የጨረታውን ሂደት በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ መሆኑን ፣ ተጠሪ ይህንኑ የስራ ግዴታ በመተላለፍ የጨረታ ሰነድ ሳያስገቡ በቀሩት የማሽን ጉልበት አመልካች ድርጅት ከጨረታ እንዲሰረዝ በመደረጉ ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ቢሆንም አመልካች ድርጅት ተሳታፊ እንዲሆን በወሰነበት የትግራይ የውሃስራዎች ኮንስትራክሽን መጋቢት 05 ቀን 2005 ዓ/ም ባወጣው ጨረታ ጨረታውን ሳይከታተሉ በመቅረታቸው ድርጅቱ በጨረታው እንዳይሳተፍ አድርገው የጥቅም ማጣት እንዲደርስበት ያደረጉ መሆኑን ዘርዝሮ ስንብቱ በህጉ አግባብ የተደረገ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በፈጸሙት ከባድ ቸልተኝነት ምክንያት አመልካች ድርጅት በጨረታው ላይ ሳይሳተፍ የቀረ መሆኑ ቢረጋገጥም በዚህ ጥፋት ምክንያት በአመልካች ድርጅት ላይ የደረሰ ጉዳት መኖሩ አልተረጋገጠም የሚል ምክንያት አስፍሮ የአመልካች የስንብት እርምጃ ህገ ወጥ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎችን ሊከፍል ይገባል በማለት የክፍያዎችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይነትና መጠን በመዘርዘር በድምሩ ብር 72,000.00 (ሰባ ሁለት ሺህ) እንዲከፍል፣ የስራ ልምድ የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ እንዲሰጠው ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ በስራ መዘርዝራቸው መሰረት ግዴታቸውን ያለመወጣታቸውና ከባድ ቸልተኝነት የነበረባቸው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት አረጋግጦ ጉዳት ስለመድረሱ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት ብቻ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የወሰነው ከህጉ ይዘትና መንፈስ ውጪ ነው ፣ አመልካች በጨረታው ላይ ባለመሳተፉ ከብር ሃያ ሶስት ሚሊዮን በላይ የጥቅም ማጣት ደርሶበታል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ በፅሁፍ በሰጡት መልስም በአመልካች ድርጅት ላይ ጉዳት ያለመደረሱን ፣ በስራቸው የፈጸሙት ጥፋትም የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው ከህግ ውጭ በመሆኑ ፣ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የተጠሪ የስራ መዝርዝር በግልጽ የሚያሳየው የጨረታ ሰነድ አዘጋጅተው የጨረታውን ሂደት በመከታተል ሪፖርት ማቅርብ መሆኑንና ይህንኑ የስራ ግዴታ ባለመወጣታቸው አመልካች ቀድሞ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው እንደገና አመልካች ድርጅት ተሳታፊ እንዲሆን በወሰነበት የትግራይ የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን መጋቢት 05 ቀን 2005 ዓ/ም ባወጣው ጨረታ ጨረታውን ሳይከታተሉ በመቅረታቸው ድርጅቱ በጨረታው እንዳይሳተፍ ያደረጉ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም ይህንን ጥፋት ያልፈጸሙ መሆኑን በማስረጃዎቹ ያላስረዱ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃ ባቀረቡት መልስ በአመልካች ድርጅት ላይ በጨረታ ባለመሳተፉ የደረሰ ጉዳት የለም በማለት ከገለፁ በኋላ በአማራጭ ደግሞ ከባድ ቸልተኝነት እንዳልነበራቸውና ጥፋት እንዳልፈጸሙ ዘርዝረው በዚሁ በአማራጭ ባቀረቡት ክርክር መሰረት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ከባድ ቸልተኝነት እንዳልነበራቸው ፣ ጥፋት እንዳልፈጸሙ የሚያቀርቡት ክርክር በሰበር መልሳቸው የተገለፀ እንጂ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ነው ሊባል የሚችል ካለመሆኑም በላይ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን አጣርቶና ማስረጃን መዝኖ የደረሰበት ድምዳሜ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በከባድ ቸልተኝነት አመልካች ድርጅት በጨረታው ላይ እንዳይሳተፍ ያደረጉ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነው በሚል የምንቀበለው ነጥብ ነው፡፡

አመልካች ተጠሪን ለቀደመው ጥፋታቸው በማስጠንቀቂያ ያለፋቸው ቢሆንም መጋቢት 05 ቀን 2005 ዓ/ም በወጣው ጨረታ እንዳይሳተፍ የተደረገው በተጠሪ ጥፋት መሆኑ በመረጋገጡ ተጠሪን ከስራ ሊያስናብታቸው ችሏል፡፡ አመልካች በዚህ ጨረታ ያልተሳተፈው በተጠሪ ከባድ ቸልተኝነት መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የሚሰሩበት የስራ ባህርይ የጨረታ ሰነድ አዘጋጅተው የጨረታውን ሂደት በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ መሆኑንም በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ አመልካች ድርጅትን ጥቅም ለማስጠበቅ ከፍተኛ ጥንቃቄና ትጋት በማድረግ ግዴታቸውን መወጣት የሚገባቸውና የድርጅቱ ኢኮኖሚ ጥቅም ጉዳት እንዳይደርስበት የማድረግ የስራ ግዴታ አለባቸው፡፡ ተጠሪ ይህንን የስራ ተግባሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመፈጸማቸው አመልካች ድርጅት ከጨረታ መሰረዙ በድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ጉዳት አላደረሰም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ተጠሪ ጉዳዩን ጨረታን መሰረት ያደረገና በውድድር ላይ የተመሰረት መሆኑን ግልጸው የአመልካች ድርጅት የጨረታ ሰነድ ከሌሎች ተጫራቾች ጋር ሲነጻጸር ጨረታውን ሊያሸነፍ ይችል ያልነበረ መሆኑን ጠቅሰው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በጨረታው ውደድር በአመልካች ድርጅት ጥቅም የሚገኝበት አግባብ መኖሩ ግልጽ ከሆነና አመልካች በተጠሪ የስራ ግዴታቸውን በአግባቡ ባለመወጣት ከውድድሩ ውጪ መሆኑ ከተረጋገጠ በአመልካች ድርጅት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ጉዳት ያለመደረሱን የማስረዳት ግዴታ የተጠሪ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን ተጠሪ በአመልካች ላይ ጉዳት አልደረሰም ከማለት ውጪ ይህንኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ያለማቅረባቸውን ክክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ የፈጸሙት ጥፋት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1/ሸ/ የሚሸፈንና የተጠሪን የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ከባድ ቸልተኝነት ምክንያት በአመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት የለም በማለት ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)ሸ እና አንቀጽ 12(2)(7) ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት ፣ መንፈስና አላማ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች የተጠሪን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ በድጋሚ ጥፋት ሲፈጽሙ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሸ) እና 12(2)(7) ድንጋጌዎች መሰረት ህጋዊ እንጂ ህገ ወጥ ተግባር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው ከህግ ውጭ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10206 ሚያዚያ 30 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 140042 ሐምሌ 25 ቀን 2006 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ ህጋዊ ነው፣ አመልካች ለተጠሪ ካሳም ሆነ የሰራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡ የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት ግን ይስጣቸው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ. 105620

ሚያዝያ 13 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካቾች፡-1. አቶ ሀብቱ ብርሃኔ

2. አቶ በየነ ለሜቻ

3. አቶ ግርማ አንጉራ

4. አቶ ጌትነት ዘውዴ

5. አቶ ጥላሁን ተክለመድህን

6. አቶ ተመስገን ግርማ

ጠበቃ አቶ ሣሙኤል ሽፈራው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መሉነህ ቡና ላኪ ትራንስፖርትና ትሪንዚት አገልግሎት - ጠበቃ ፈጠነ ደረሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች መዝገብ ቁጥር 140043 ሐምሌ 3 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ ስንብት የሁለት ወር ደመወዝ ይከፈለን በማለት የቀረበ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፊዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾች ተከሳሽ በሹፌርነት ተመድባችሁ የምታሽከረክሩት መኪና ተሸጧል በሚል ምክንያት የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ ከሰጠን በኃላ የሥራ ውላችን አቋርጧል፡፡ ተከሳሽ የሥራ ውሉን በቅነሳ ምክንያት ማቋረጥ ሲገባው አላግባብ የሥራ መደብ ተሰርዟል በማለት ያቋረጠው በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ መሠረት ሊከፍል የሚገባውን የሁለት ወር ደመወዝ የሥራ ስንብት ክፍያ ያልከፈለ በመሆኑ እንዲከፍል ውሣኔ ይስጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖ ቀርቦ ከሳሾች የሚያሽከረክሯቸው መኪኖች በመሸጣቸው የሥራ መደቡ ተሰርዟል፡፡ ስለዚህ ተከሳሾች የስራ ስንብት ክፍያ የምንከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተከሳሽ ኪሣራ አልደረሰበትም፡፡ ኪሳራ የደረሰበት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የቡና ላኪ ድርጅት ላይ ነው፡፡ ከሳሾች የሚያሽከረክሯቸው መኪኖች የተሸጡትም የቡና ላኪ ድርጅት ዕዳ መክፈያነት ነው፡፡ ተከሳሽ የሥራ ውሉን ከሳሾች የሚያሽከረክሯቸው መኪኖች በቡና ላኪ ድርጅት ላይ በደረሰው ኪሣራ ምክንያት በዕዳ መክፈያነት በመሸጣቸው የሥራ ውሉን ያቋረጠ በመሆኑ፣የሥራ ውሉ የተቋረጠው በቅነሳ እንጂ የሥራ መደብ በመሠረዙ ምክንያት አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ከሳሽ በተከሳሾች የሁለት ወር ደመወዝና አገልግሎት ጊዜአቸውን አስልቶ የሥራ ስንብት ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ መልስ ሰጭዎች ያሽከረክሯቸውየነበሩት መኪናዎች መሸጣቸው ተረጋግጧል፡፡ መልስሰጭዎች ያሽከረክሯቸው የነበሩ መኪናዎች መሸጣቸው ከተረጋገጠ ይግባኝ ባይ ሌላ መኪና ገዝቶ እስኪተካ ድረስ የሹፌርነት የሥራ መደብ ተሰርዟል ለማለት ይቻላል፡፡ ይግባኝ ባይ መልስ ሰጭዎችን የሥራ መደብ በመሰረዙ ምክንያት ከሥራ ያሰናብታቸው በመሆኑ የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል አይገባም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

4. አመልካቾች መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ካሉት ከመቶ በላይ ከሚሆኑ ሹፌሮች ዝቅተኛ አገልግሎትና የሥራ ልምድ በመምረጥ ቀንሶ ከሥራ አሰናብቶናል፡፡ ከዚህ አንፃር የተጠሪ አድራጎት ቅነሳ እንጂ የሥራ መደብ መሠረዝ ነው ሊባል አይገባውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሰሪው ሠራተኛውን ከሥራ ሲያሰናብት የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል ሃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ስንብት ክፍያ አይገባችሁም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር እንዲታይልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ጥር 28 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች የተሰናበቱት የሥራ መደቡ የተሠረዘ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንን በማገናዘብ የሥራ ስንብት ክፍያ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችዎች የካቲት 14 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካቾች የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

6. አሠሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውል ለማቋረጥ የሚችልባቸውን መሠረታዊ ምክንያቶች አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 በሁለት ከፍሎ አስቀምጧቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ከሠራተኛው ችሎታ ማጣት ወይም ሁኔታ የሚመለከቱ ምክንያቶችም ሲሆኑ በአዋጅ አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ"ሀ" እስከ "መ" በዝርዝር ደንግጓል፡፡ ሁለተኛው ከአሠሪው ድርጅታዊ አቋም ወይም የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከቱ ምክንያቶች የሥራ ውል ሲቋረጥ መሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ አመልካቾች የሚያሽከረክሯቸው መኪኖች በዕዳ ምክንያት በመሸጣቸው የአመልካችዎች የሥራ መደብ በአዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 (መ) መሠረት ተሰርዟል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተጠሪ ከፈፀመው ተግባር አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

7. አመልካችዎች የሚያሸከረክሯቸው መኪኖች የተሸጡት በተጠሪ ድርጅታዊ አቋምና የሥራ እንቅስቃሴ ምክንያት በመሆኑና በተለይም ቡና የሚልከው የንግድ ድርጅት ኪሣራ ስለደረሰበት መኪኖቹ ተሸጠው ዕዳ መክፈያነት የዋሉ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል። አንድ ድርጅት ሠራተኞች የተሰማሩባቸው ሥራዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቀጥታና በሌላ ቦታው የሚያስቆምና የሠራተኞች ቅነሳ የሚያስከትል ሁኔታ ሲያጋጥመው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውሉን ሊያቋርጥ እንደሚችል በአዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) ተደንግጓል። የተጠሪም አድራጎት በዚህ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈን ሆኖ አግኝተነዋል።
8. ስለ ሥራ ስንብት ክፍያ የሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር 377/96 ምዕራፍ ሶስት በክፍል ሁለት የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሰራተኛ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት ከሥራ ሲቀነስ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ በአንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) በግልፅ ይደነግጋል። ከዚህ አንፃር ሲታይ በተጠሪ ድርጅታዊ አቋምና የሥራ እንቅስቃሴ ምክንያት ከሥራ የተቀነሱት አመልካቾች በአዋጁ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከቱትን የሥራ ስንብት ክፍያዎች የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መንፈስና ዓላማ የምንረዳው ጉዳይ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካችዎች የሚያሸከረክሯቸው መኪናዎች በዕዳ ምክንያት መሸጥ ከተጠሪ ድርጅታዊ አቋምና የሥራ እንቅስቃሴ ነጥሎ በማየት ተጠሪ ለአመልካችዎች የሥራ ስንብት ክፍያ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) ና ንዑስ አንቀጽ 3 አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) እና የአዋጁን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
2. ተጠሪ ለአመልካችዎች የሥራ ስንብት ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል።
3. ተጠሪ ለአመልካችዎች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በማስላት የሥራ ስንብት ክፍያ ይክፈላቸው በማለት ወስነናል።
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 105555

መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- 1.መፍትሃ መሜ
2. ናቶሊ መሃመድ ነጂብ
3. ሐናን መሃመድ ነጂብ

} የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ዑስማን ዓሊ - ጠበቃ ይማጅ ዮኒስ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሁኖ የጉዳት ካሣ ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ የ1ኛ አመልካች ህጋዊ ባለቤት የሌሎች አመልካቾች ወላጅ አባት የሆኑት ሟች መሃመድ ነጂብ በተጠሪ በሠራተኛነት ተቀጥረው በማገልግል ላይ እያሉ የተጠሪ ንብረት የሆነውንና የሻንሲ ቁጥር JAAKP-34HbB7P5165፣የሞተር ቁጥሩ 4HG1-865627 የሆነና የሰሌዳ ቁጥር ያልወጣለትን አይሱዙ ተሽከርካሪ ከድሬዳዋ አዲስ አበባ ለማድረስ በማሽከርከር ላይ እንዳሉ ተጠሪ በእሩምታ ጥይት ተተኩሶባቸው ሕይወታቸው በማለፉየጉዳት ካሳ 903.000.00(ዘጠኝ መቶ ሰለሳ ሺህ) ብር እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነት ቀርበው ከሟች ጋር የስራ ቅጥር ውል የሌላቸው መሆኑንና ሟቹ በራሳቸው ኃላፊነትና መሪነት ለተለያዩ ሰዎች የሙያ አገልግሎት የሚሰጡ እንጂየተጠሪ ተቀጣሪ ያለመሆናቸውን፣ግንኙነቱ የሙያ አገልግሎት በመሆኑ ሊገዛ የሚገባው በፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ነው በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር እና ማስረጃዎችን ከሠማ በኋላ በተጠሪ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረቡትን የክርክር ነጥቦች ውድቅ በማድረግ በሟችና በተጠሪ መካከል የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ደርሶ የጉዳት ካሣውን መጠንን በተመለከተም የሟቹ የወር ደመወዝ ብር 12,000.00(አስራ ሁለት ሺህ) መሆኑን መገንዘቡን ጠቅሶ በዚሁ ወርሃዊ የደመወዝ መጠን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(3) የሞት ጉዳት ካሳው ሲሳላ ብር 720,000.00 (ሰባት መቶ ሃያ ሺህ) እንደሚሆንና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀብር ማስፈጸሚያም የሁለት ወር ደመወዝ ብር 24,000.00 ሊያዝ እንደሚገባ ገልፆ በድምሩ ብር 744,000.00(ሰባት መቶ አርባ አራት ሺህ ብር) ካሳ ለአመልካቾች ሊከፈል እንደሚገባ፣ አከፋፈሉን በተመለከተም ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ 50% የሚች ሚስት ለሆኑት ለአሁኗ 1ኛ አመልካች፣ ቀሪው 50% ደግሞ ለሚች ተወላጆች ለአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሊከፈል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በጉዳት ካሳ መጠኑ ላይ 10% ደግሞ ለጠበቃ አበል እንዲከፈል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በሚች እና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የአሰሪና ሠራተኛ አይደለም፣ ሚች በራሳቸው ኃላፊነትና መሪነት ስራውን ሲሰሩ የነበሩ ናቸው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም በፃፉት 4/አራት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-ሚች ሹፌር ሁነው ለተጠሪ ሲሰሩ የነበሩ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በራሳቸው ኃላፊነትና መሪነት የሙያ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ናቸው ተብሎ ግንኙነቱ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ አይገዛም ሲባል የተወሰነው ውሳኔ ስለሙያ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጠውን መስፈርት ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ እና የቃል ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ከላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ጭብጦች፡-

1. በተጠሪ እና በሚች መካከል የነበረው ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች አግባብ የሚገዛ ነው? ወይስ አይደለም?
2. ከተባለስ የጉዳት ካሳ መጠኑ ምን ያህል ሊሆን ይገባል? የሚሉት ሁነው አግኝተናል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሚች ህይወታቸው ያለፈው በሹፌነታቸው የተጠሪ ንብረት የሆነውን መኪና ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ በማሽከርከር ላይ እንዳሉ በተከፈተባቸው እሩምታ ተኩስ መሆኑን፣ሚች አንድ ጊዜ መኪና ሲያደርስ ብር 800.00 (ስምንት መቶ) ብር ለመክፈል ተጠሪ መስማማታቸውን ተጠሪ ባቀረቡት ክርክርም ሆነ የአመልካቾች ምስክሮች መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ በግልጽ ያሰፈረው ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ በሚችና በተጠሪ መካከል እንደዚህ አይነት ስምምነት የተደረገው ከሚያዚያ ወር 2002 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑንና የሞት አደጋው የደረሰው ደግሞ የካቲት 08 ቀን 2003 ዓ/ም ስለመሆኑ በአመልካቾች ማስረጃዎች የተነገረ መሆኑንም ከስር ከበታች ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ይዘት ተመልክተናል፡፡

ይህንኑ ለመመለስም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አሰሪና ሰራተኛ ማን ነው የሚለውን ጉዳይ መመልከቱ የግድ ይላል፡፡ ይህ ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ የሚችለውም በአዋጁ የሚገዙት የትኞቹ አሰሪዎች እና ሰራተኞች ናቸው? የሚለው ጥያቄ መሰረት በማድረግ መሆኑ ይታመናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀፅ 2/3/ ስር ሰራተኛ ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 ስር በተመለከተው መሰረት ከአሰሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው በማለት በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ በመሆኑም ይህ ሰራተኛ ለአሰሪው በአሰሪው ቁጥጥር ስር ሁኖ አሰሪው በሚከፍለው ደሞዝ በራሱ የጉልበት ወይም የእውቀት አገልግሎት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚሰጥ መሆኑን አዋጅ ያስገነዝባል፡፡ በሌላ በኩል አዋጁ በአንቀፅ 2/1/ ስር አሰሪ ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 በተመለከተው መሰረት ቀጥሮ የሚያሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሊሆን እንደሚችል በመግለፅ ድርጅት የሆነውን አሰሪ በማየት አሰሪ ማን ነው? የሚለውን ጥያቄውን ለመፍታት የሚያስችል መሆኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ጥያቄውን ስንመለከተውም አሰሪው ግለሰብ ወይም ድርጅት ሊሆን የስራ ውሉ ግንኙነት በአዋጅ የሚገዛ መሆኑን፣ አሰሪው ከነዚህ ውጭ ከሆነ እንደሁኔታው የሌሎች ህጎች ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው መሆኑን ሕጉ የሚያመለክት መሆኑን መረዳት የምንችለው ጉዳይ ይሆናል፡፡ በአዋጁ ስለሰራተኛ የተቀመጠው ትርጉም የሚያሳየው በአዋጁ አንቀጽ 4 በተመለከተው መሰረት ከአሰሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ መሆኑን አንቀጽ 2(3) በግልጽ ያሳያል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ይዘት አንድን ሰው ሰራተኛ ነው ለማለት በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት መኖሩና በአዋጁ አንቀጽ 4 ድንጋጌ አግባብ መሰረት ሰራተኛው አገልግሎት ለመስጠት መስማማቱ፣ሰራተኛው አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑንና ሰራተኛው ሊሰጥ የሚገባውን አገልግሎት አይነት፣ የት አገልግሎቱን መስጠት እንደአለበት፣አገልግሎቱን መቼ ሊያከናውነው እንደሚገባና እንዴት ማከናወን እንደሚኖርበት አሰሪው የመቆጣጣር ስልጣን ያለው መሆኑ መረጋገጥ ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ አሰሪው ሰራተኛውን በዚሁ በህጉ በተቀመጠው አግባብ ተቆጣጥሮ ስራውን የሚያሰራ መሆኑ መረጋገጡ አንድ ተዋዋይ ወገን ዋጋ እየተከፈለው የንግድ ስራ ወይም በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሚሰራ ስራ ከሚያከናውን ወገን በትክክል ለመለየት የሚረዳ መሆኑም ተቀባይነት ያለው መለኪያ ነው፡፡በአዋጁ ለቅጥር ውሉ ከተሰጠው ትርጉም መካከል አንዱ የደመወዝ ጉዳይ ሲሆን ሰራተኛው ለአሰሪው በገባው ለአሰሪው ጥቅምና በአሰሪው ቁጥጥር ችሎታውንና ጊዜውን በመጠቀም ተገቢውን አገልግሎት ለአሰሪው ለመስጠት ግዴታ የሚገባው አሰሪው ለሰራተኛው ተገቢውን የድካም ዋጋ በደመወዝ መልክ የመክፈል ግዴታ ሲገባነው፡፡ ደመወዝ ደግሞ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት ሊሆን የሚችል ሁኖ የአከፋፈሉ ጊዜም አንደነገሩ ሁኔታ በየቀኑ፣በየሁለት ቀኑ፣ በየሁለት ሳምንቱ፣በየወሩ፣በተሰራው ስራ መጠን……ወዘተ ሊሆን እንደሚችል ከአዋጁ አንቀጽ 4 እና 58 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም በእነዚህ የአከፋፈል ጊዜያት ወይ ዘዴዎች ደመወዝ የመክፈሉ ሁኔታ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በተመሰረተው የቅጥር ሁኔታ ላይ በሕጉ ረገድ ለውጥ የማያስከትል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ሚቸ ተጠሪ ግለሰብ ከውጪ ከሚያስመጣቸው ተሽከርካሪዎች ውስጥ ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ በማመላለስ አገልግሎት ሲሰጡ እንደነበርና ስራውን የሚሰራው ጊዜና ቦታ መኖሩን፣ይህም በተጠሪው መሪነት ወይም ቁጥጥር ሲከናወን የነበረ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ተጠሪ ሚቸ ሲከፈላቸው የነበረው ደወመዝ በቁርጥ መሆኑን ጠቅሰው ከመከራከራቸው ውጪ ሚቸ የሚሰጡትን አገልግሎት በራሳቸው ቁጥጥር ስር ያልነበረ መሆኑን አላስረዱም፡፡ የደመወዝ አከፋፈል በቁርጥ መሆኑ ደግሞ የቅጥር ግንኙነት ከላይ በተመለከቱት የአዋጁ ድንጋጌ ስለ ሰራተኛ ማንነት የተቀመጠውን ትርጉም ላለመቀበል የሚያስችል አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ሚቸ በተጠሪ ቁጥጥር ስር ሁነው የሹፍርና አገልግሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሰጡ የነበረ መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ሁኖ እያለ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሚች በራሱ የሙያ ኃላፊነት ሲሰሩ የነበሩ ናቸው በማለት ግንኙነቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የሚገዛ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ በሕጉ ስለሰራተኛ ማንነት የተቀመጡ መለኪያዎችን በአግባቡ ባላገናዘበ መልኩ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 2(1)(2)፣3(2(ረ))፣ 4 እና 58 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ የጣሰ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ፡-</u>ሚች የተጠሪ ሠራተኛ ናቸው ከተባለ በስራ ላይ እያሉ ሕይወታቸው ማለፉ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ በስራ ምክንያት ለሚመጡ ጉዳቶች አሠሪው ሀላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ በስራ ምክንያት የሚመጣ ጉዳት ከሆነ አሠሪው ኃላፊነቱን እንዲወስድ የተደረገ ሲሆን በአዋጁም በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ መሆኑን በቁጥር 95(2) ደንግጓል በአዋጅ አንቀጽ 96(1) "አሠራው ጥፋት ባይኖረውም....." ተብሎ መመልከቱ የአሠሪው የኃላፊነት ዓይነት ጥፋት ሣይኖር ኃፊነት /Strict Liability or Liability in the absence of Fault/ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ አሠሪው ከዚህ ዓይነት ኃላፊነት የሚድነው ጉዳት የደረሠበት ሠራተኛ ሆነ ብሎ በራሡ ላይ ያደረሠው ጉዳት መሆኑን ማስረዳት ሲችል ስለመሆኑ አንቀጽ 98(2) ያስገነዝባል፡፡ሆነ ብሎ ያደረሠው ጉዳት የሚባሉት ሁኔታዎችም ሠራተኛው አስቀድሞ በግል የተሠጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎችን መጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን መተላለፍ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ እፅ ሠክሮ በሥራ ላይ መገኘት መሆናቸውን ህጉ በቁጥር 96(2(ሀ እና ለ)) ስር አመላክቷል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 97(1) ድንጋጌ ሲታይም አንድን አደጋ በስራ ላይ የደረሠ ነው ለማለት ሠራተኛው ስራውን በማከናወን ላይ እያለ ወይም ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሡ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ስራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ በማንኛውም ክፍል ተፈጥሯዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት የደረሠበት ጉዳት ስለመሆኑ መርሁን ያስቀመጠ ሲሆን ይኽው ድንጋጌ ከፊደል (ሀ) እስከ ፊደል (መ) በተመለከቱት ንዑስ ድንጋጌዎች የተመለከቱት ምክንያቶች በስራ ላይ የደረሠ አደጋ ተብለው የሚጨመሩ ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ ስለሆነም በመርሁ መሠረት ሠራተኛው የጉዳት ካሣ ለማግኘት ማሣየት የሚጠበቅበት አደጋው ስራውን በማከናወን ላይ እያለ የደረሠ መሆኑን፣ ወይም ደግሞ በራሡ ባልሆነ ምክንያት ግን ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው መልኩ የደረሠበት አደጋ መሆኑን ነው ፡፡ከላይ እንደተገለፀው ከስራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ህጉ አስቀምጧል፡፡ ለዚህ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በአንቀጽ 97(1(ሐ)) ስር የተመለከተው ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት አሠሪው በመደበው የመጓጓዝ አገልግሎት ሠራተኛው ሲጠቀም ጉዳት ከደረሠ አደጋው በስራ ላይ እንደደረሠ ተቆጥሮ ኃፊነቱን ከአሠሪው ሊወሰድ የሚገባ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይኽው ድንጋጌ አሠሪው የመደበው የመጓጓዝ አገልግሎት አደጋው ከደረሠበት በአሰሪው ስር ባለው ሌላ ሠራተኛ ወይም 3ኛ ወገን ከሆነ አሰሪው ለተጐጂው ሠራተኛ የጉዳት ካሣ ኃፊነት የሌለበት ስለመሆኑ አያሣይም ይልቁንም ድንጋጌው በአዋጁ አንቀጽ 96(1) ስር ከተመለከተው የአሠሪ አላፊነት ዓይነት ጋር ተዳምሮ ሲታይ አሠሪው አላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያጠናክር ነው በሌላ አገላለፅ በሠራተኛው ላይ ጉዳት ያደረሠው ሠራተኛው ወደ ስራ ሲሄድና ከስራ ወጥቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ አሠሪው በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ሲጠቀም አደጋ የደረሠበት መሆኑ ከተረጋገጠ 3ኛ ወገኖች ለአደጋው ያደረጉት አስተዋጽኦ ለአሰሪው መከላከያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም ሚች የተጠሪን መኪና በወቅቱ ሲያሽከረክሩ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡ ተጠሪን ነፃ ሊያደርገው የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት ስለሌለ ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊነት ያለባቸው ናቸው፡፡

ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊ ናቸው ከተባለ የጉዳት ካሣ መጠኑ ምን ያህል ሊሆን ይገባል?፣ ካሳው መክፈል ያለበት ለየትኞቹ የተጐጂ ጥገኞች ነው? የሚለው ጥያቄም በህጉ አግባብ መታየት ያለበት ነው፡፡ ለዚህጥያቄ ምላሽ የሚሠጠው ድንጋጌም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 107(1(ሐ) ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም በስራ ላይ የሚመጣ ጉዳት የደረሠበት ሠራተኛ የሞተ እንደሆነ ለጥገኞች የጡረታ አበል ወይም ዳረጐት ወይም ካሣ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡የአዋጁ አንቀጽ 110 ድንጋጌ ሲታይም ለሚች ሠራተኛ ጥገኞች የሚከፍሉትን የክፍያ ዓይነቶችንና ጥገኛ የሚባሉትን ወገኖች በንዑስ ቁጥር አንድና ሁለት በግልፅ ዘርዝሯል፡፡ በዚህም መሠረት ማንኛውም ሠራተኛ ወይም ለማጅ ሠራተኛ በስራ ምክንያት በደረሠበት ጉዳት የተነሣ የሞተ እንደሆነ የጉዳት ካሣ ለጥገኞች፣ የቀብር ሥነ ሥርዓት ወጪ እንደሚከፈልና ጥገኞች የሚባሉትም የሚች ህጋዊ ባል ወይም ሚስት፣ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ የሚች ልጆችና በሚች ሠራተኛ ድጋፍ ይረዱ የነበሩ የሚች ወላጆች ስለመሆናቸው ተመልክቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም 1ኛ አመልካች የሚች ሚስት፣ ሌሎች ተጠሪዎች ደግሞ ተወላጅ ናቸው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በህጉ አግባብም የሚች ጥገኛ መሆናቸው ስለተረጋገጠ የጉዳት ካሣ የሚገባቸው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የጉዳት ካሳ መጠኑም በሰራተኛው በስራ ላይ እያለ የሞተ እንደሆነ የሰራተኛው የዓመት ደሞዝ በአምስት ተባዝቶ የሚከፈል እንደሆነ አንቀፅ 110(3) ተመልክቷል፡፡ይህንኑ ለመወሰን ደግሞ የሰራተኛው ደመወዝ መጠኑ በትክክል ሊታወቅ ይገባል፡፡በተያዘው ጉዳይ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚችን ደመወዝ መጠን በወር 12,000.00 ያደረገው በወር ውስጥ አስራ አምስት ቀናትን ለተጠሪ አገልግሎት ለመስጠት ይችላሉ በሚል መነሻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ በግልጽ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠው ሚች ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ ለሚያደርሱት አንድ ተሽከርካሪ ብር 800.00(ስምንት መቶ) የሚከፈላቸው መሆኑ ነው፡፡ይህ ደግሞ ሚች በወር አስራ አምስት ቀናት ሙሉ ስራውን ይሰራሉ ተብሎ ስላልተረጋገጠ የወርሃዊ ደመወዝ መጠን በብር 800.00 ሊታሰብ የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም ይህ ችሎት የሚች ወርሃዊ ደመወዝ ከብር 3200.00 ሊበልጥ የሚችልበትን አግባብ አላገኘም፡፡ ይኼው የደመወዝ መጠን መሰረት ተደርጎ አመታዊ ደመወዝ ሲሰላ ደግሞ ብር 38,400.00(ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ብር) ሁኖ በአዋጁ አንቀጽ 110(3) መሰረት የአምስት ዓመቱ ሲሰላ ብር 192,000.00(አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ ብር) የጉዳት ካሳ ሊሆን የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

የቀብር ሥርዓት ማስፈፀሚያ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(1(ለ) መሠረት ሲሰላም የሁለት ወር ደመወዝ ብር 6,400.00(ስድስት ሺህ አራት መቶ ብር) መሆን ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

በአጠቃላይ 198,400.00 (አንድ መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አራት መቶ ብር) የሚች ጥገኛ ለሆኑት ለአሁኑ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(3) እና (4) ስር በተመለከተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብ የሚከፈል የጉዳት ካሣ መጠን ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ፣ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ደግሞ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 09770 ሐምሌ 23 ቀን 2006 ዓ/ም ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 38410 ጥር 26 ቀን 2006 ዓ.ም እና መጋቢት 29 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
3. በሚች እና በተጠሪ መካከል የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ውል አለ፣ ሚቹ የሞቱት በስራ ላይ እያሉ በመሆኑ ለሚቹ ጥገኞች የሞት ጉዳት ካሳ የሚቹ የአምስት አመት ደመወዝና የሁለት ወር ደመወዝ ለቀብር ስነ ስርዓት ማስፈፀሚያ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው ብለናል፡፡
4. ተጠሪ ለአመልካቾች የሚከፍሉት የካሳ መጠንም ብር 198,400.00(አንድ መቶ ዘጠናስምንት ሺህ አራት መቶ) ሁኖ አከፋፈሉም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(3(ሀ) ((ለ)) በተመለከተው አግባብ 50% ለ1ኛ አመልካች (የሚች ሚስት) ቀሪው 50% ደግሞ ለሚች ልጆች (2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች) ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡ የጠበቃ አበል በዚህ ችሎት በተወሰነው የገንዘብ መጠን 10% ተጠሪ ለአመልካቾች ሊተኩ ይገባል ብለናል፡፡
5. ሌሎች ወጪና ኪሳራዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር/መ/ቁ 101736

መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አለማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ግዮን ኢንዱስትሪያልና ኮሜርሻል ኃ/የተ/የግል ማህበር ነገረ ፈጅ በዛዬ ሲያምረኝ

ተጠሪ፡- አቶ አዲስ አለም ሀ/ኪሮስ ጠበቃ ውቤ አለነ አልቀረቡም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ከአሠሪና ሰራተኛ የስራ ውል መቋረጥ ጋር የተያያዘ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ አመልካች በሥር የፌዴራል የመጀመሪያ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት፡- በአመልካች ድርጅት ከመጋቢት 23/2005 ዓ/ም ጀምሮ በወር 2650 ብር እየተከፈላቸው በአሽከርካሪነት የስራ መደብ ሲሰሩ እንደ ነበር፣ አመልካች ያለ ምንም ጥፋትና ማስጠንቀቂያ የሥራ ውላቸውን ያቋረጡ በመሆኑ ስንበቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ በሕግ የተፈቀዱ ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲወስንላቸው ማመልከታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩም ተጠሪ በጡረታ የተገለሉ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው እንዲባልለት፤ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ስለሆነ የሥራ ስንብት ክፍያ የመጠየቅ መብት እንደሌላቸው የካሳ እና ወደ ሥራ ልመለስ ጥያቄ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በተጠሪ የቀረበው ወደ ሥራ ልመለስ ካሳም ይከፈልኝ ጥያቄ በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ፤ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ በመሆናቸው የሥራ ስንብት ክፍያ እንደ ማይገባቸው፤ የዘገየ ክፍያ ጥያቄ በተመለከተም በአመልካች የታመነው የፕሮፊደንት ፈንድ እና የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ የተከፈላቸው መሆኑ በመረጋገጡ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ተጠሪን በጡረታ የተገለሉ ናቸው ይበል እንጂ ከግል ድርጅቶች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በተገኘው መረጃ መሰረት በጡረታ መገለላቸው አናውቅም በማለት መልስ በመስጠቱ እና ያለ ማስጠንቀቂያ ከሥራ በመሰናበታቸው ምክንያት የ3 ወር ደመወዝ ብር 7950 እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡

አመልካች እና ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ የስር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መነሻም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ የቀረበ ነው፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው የጠቀሰው መሰረታዊ ነጥብ ተጠሪ በጡረታ የተገለሉ በመሆናቸው ሰንብቱ በሕግ አግባብ የተከናወነ መሆኑ እየታወቀ የማስጠንቀቂያ ጊዜ 3 ወር ደመወዝ እንዲከፈል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው 60 ዓመት ካለፈባቸው በኃላ በአመልካች ድርጅት ይሰሩ እንደነበር ለስንብቱ ምክንያት ጡረታ ሳይሆን በግብታዊ መንገድ የተወሰደ እርምጃ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና አመልክቷል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታው የሚያጠናክር ነው፡፡

የሥር የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ፤ ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር አግባብነት ከላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመረነውም አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የተጠሪ የቅጥር ውል በጡረታ በመገለላቸው ምክንያት በሕጉ አግባብ መቋረጡን መሠረት በማድረግ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ዕድሜያቸው 60 ዓመት ከሞላ በኋላም በሥራ መደባቸው ላይ መቀጠላቸውን እና ስንብቱ ግብታዊ መሆኑን ነው፡፡ የሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ አልተሰጣቸውም ለማለት እንደ መነሻ የወሰደው የግል ድርጅት ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በጡረታ የተገለሉ ስለመሆኑ አናውቅም የሚል መልስ በመስጠቱ ምክንያት ነው ተጠሪ 60 ዓመት የሞላቸው ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የስራ ውል በሕግ ከሚቋረጥባቸው መንገዶች እንደ ሠራተኛው አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በጡረታ ሲገለል እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/ 1996 አንቀጽ 24 (3) በግልጽ ተደንግል፡፡ የግል ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 17(1) የሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜ 60 ዓመት መሆኑን ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ 60 ዓመት የሞላቸው ቢሆንም የቅጥር ውሉ እስከ ቀጠለ ድረስ ከሥር ለማሰናበት ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ እየተከራከሩ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰራተኛ በሕግ የተቀመጠው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ካለፈ በኃላ ሥራ ቢቀጥል ወይም እንደገና ተቀጥሮ ቢሰራ ያለው ሕጋዊ ውጤት ምንድነው? የሚለውን ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ አመልካች ለሰንብቱ መነሻ ያደረገው ተጠሪ 60 ዓመት የሞላቸው በመሆኑ በጡረታ ተገለዋል በሚል ነው፡፡ ክፍያ በተመለከተም በአመልካች የታመነው የፕሮፊደንት ፈንድ እና የአመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ የተከፈላቸው ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ አንድ ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከለፈበት በኋላ በሥራው ቢቀጥል አሰሪው በሕጉ አግባብ ሠራተኛውን ማስናበት እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24(3) ተመልክቷል፡፡ አሰሪው ምርታማነቱ እና የገበያ ተዋዋዳሪነቱ ለማስቀጠል የሚችለው በጡረታ የተገለሉ ሠራተኞች በሕጉ አግባብ እያሰናበተ በአዲስ ኃይል እየተካ ሲሄድ መሆኑ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በጡረታ የተገለለ ሰው ስራ መስራት አይችልም የሚባል ባይሆንም አንድ አሰሪ በጡረታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተገለለን ሠራተኛ በድጋሚ ላልተወሰነ ጊዜ ቀጥሮ ያሰራል ለማለት እንደማይቻል የሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 18832 ህዳር 3 ቀን 2000 ዓ/ም አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ አስገዳጅ ውሳኔ ደግሞ በሁሉም ደረጃ ላይ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚነት እንዳለው በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ስር ተደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ድርጅት ከተጠሪ ጋር የነበረው ግንኙነት በሕጉ አግባብ አቋርጠዋል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ መስጠት ይገባው ነበር ለማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረው የቅጥር ውል ሕጉ በደነገገው የጡረታ መውጫ ዕድሜ መሰረት የተቋረጠ በመሆኑ ነው፡፡ በሕጉ አግባብ የተቋረጠው የቅጥር ውል ደግሞ አሰሪ የማሰጠንቀቂያ ጊዜ አልሰጠህም በሚል ምክንያት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል አይገደድም፡፡ ተጠሪ 60 ዓመት ከሞላቸው በኃላ በሥራ ገበታቸው መቆየታቸው በአመልካች የተለየ ግዴታ የሚጥል አይደለም፡፡

በዚህ መሠረት የስር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የ3 ወር ደመወዝ ብር 7950 እንዲከፈላቸው መወሰኑ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 31577 በ27/10/2005 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 136076 በ18/09/2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የተጠሪ የቅጥር ውል ያቋረጠው በሕጉ አግበብ ነው ብለናል፡፡ አመልካች ለተጠሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የ3 ወር ደመወዝ ብር 7950 ሊከፈል አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው·ል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ.96858

ቀን 26/03/2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ አብቢልክሽ ገለታ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዶ/ር ትግስት ቦርጋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የኪራይ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄን መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ ክስ መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ/ም የተጻፈ ሆኖ ይዘቱም ህዳር 19 ቀን 2003 ዓ/ም በተደረገ የኪራይ ውል አመልካች /የስር ተከሳሽ/ የተጠሪ /የስር ከሳሽ/ የሆነውን ንብረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በንፋስ ስልክ ክፍለ ከተማ 522 የሆነ መኖሪያ ቤት በየወሩ ብር 2000.00 /ሁለት ሺህ ብር/ እየከፈሉ ለሶስት ወር ተጠቅመው ሊለቁና የተጠቀሙበትን የውሃና የመብራት ወጪ ከፍለው ቤቱን ለማስረከብ ግዴታ የገቡ መሆኑን ገልጸውና በግዴታው መሰረት ቤቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን፣ በዚህም ምክንያት ተጠሪ በህጋዊ ወኪላቸው በኩል ለአመልካች ታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም ቤቱን አመልካች እንዲለቁ፣ የማይለቁ ከሆነ ደግሞ በየወሩ ብር 5000.00 /አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍሉ ማስጠንቀቂያ የሰጧቸው ቢሆንም ቤቱን ያልለቀቁላቸው መሆኑን ዘርዝረው አመልካች ያለባቸውን የሁለት ወር ከአስር ቀናት ውዝፍ ኪራይ ብር 13,499.00 እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስረክቧቸው፣ ቤቱን እስከሚያስረክቡ ድረስ ያለውን ኪራይም እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ህዳር 19 ቀን 2003 ዓ/ም የተደረገው የኪራይ ውል መኖሩን ሳይክዱ የቤቱን የኪራይ መጠን ብር 5000.00 ስለመሆኑ ተሰጠ የተባለውን ማስጠንቀቂያ ግን ከተጠሪ ህጋዊ ወኪል ያልተሰጣቸውና አስገዳጅነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ለአመልካች ታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጠ የተባለው ማስጠንቀቂያ በተጠሪ ህጋዊ ወኪል የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን ከአጣራ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ ማስጠንቀቂያ ለአመልካች ሲሰጥ የተጠሪ ጠበቃ ህጋዊ ውክልና ነበራቸው ባይባልም አመልካች የተጠሪ ፍላጎት መሆኑን ያወቁ መሆኑ መረጋገጡን ደምድሞ እና ከታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ያለው ግንኙነት ላልተወሰነ ጊዜ እንደታደሰ የሚቆጠር መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ህ/ቁ.2968(1) መደንገጉን ፣ በአከራይ ለተከራይ በፈለገው ጊዜ ቤቱን የማስለቀቅ ህጋዊ መብት ያለው መሆኑ በህጉ የተጠበቀለት መብት መሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2966 የተደነገገ መሆኑ በዋቢነት ጠቅሶ አመልካች ለተጠሪ ከታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን እስከሚያስረክቡበት ጊዜ ድረስ የሚታሰብ ወርሃዊ ኪራይ ብር 5000.00/አምስት ሺህ/ እንዲከፍሉ፣ የተጠቀሙበትን የውሃና የመብራት ወጪም እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ የተጠሪ መሆኑን በጊዜው ማወቃቸው በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ማስጠንቀቂያው ከተጠሪ ህጋዊ ወኪል አልተሰጠኝም የሚሉት ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ለአመልካች በህጉ አግባብ ማስጠንቀቂያ ባልተሰጠበት ሁኔታ የቤቱ ኪራይ በወር 5000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ የኪራይ ገንዘቡ በወር ከብር 2000.00 ወደ ብር 5000.00 ብር ከፍ ማለቱ ተረጋግጧል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ህዳር 19 ቀን 2003 ዓ/ም ያደረጉት የኪራይ ውል የተወሰነ የኪራይ ዘመን የተቀመጠለትና ይህ ጊዜም ያለፈ መሆኑን፣ ጊዜው ካለፈ ስለ ኪራዩ መጨመር ማስጠንቀቂያ ከደረሳቸው በኃላም አመልካች የተጠሪን መኖሪያ ቤት መጠቀም መቀጠላቸውን፣ ተጠሪ አመልካች የኪራይ ጊዜው ከአለፈ በኃላ መኖሪያ ቤቱን ለተጠቀመበት ጊዜ በአዲሱ የኪራይ ተመን መሰረት ኪራይ አልተከፈለኝም በማለት የሚከራከሩ መሆኑንና አመልካች አዲሱ የኪራይ ተመን ተጠሪ በወኪሉ በኩል አሳውቁአለሁ ቢሉም ወኪሉ ህጋዊ ውክልና ስላልነበራቸው አመልካች አዲሱን የኪራይ ተመን አውቀዋል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪ ህዳር 19 ቀን 2003 ዓ/ም ለሶስት ወራት ያደረጉት የኪራይ ውል ዘመን ተጠናቆ አመልካች የተጠሪን ቤት መጠቀም የቀጠሉ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ግንኙነት የፍ/ብ/ህ/ቁ.2968/1/ ድንጋጌን የሚያሟላ የኪራይ ውል ግንኙነት መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን ድምዳሜ ሲመለከተው የፍ/ብ/ህ/ቁ.2968/1/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ በመሆኑ እና አመልካችም በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ስለሌለ የሚመለከተው ሆኖ አላገኘውም፡፡

በዚህ ችሎት መታየት ያለበት አቢይ ነጥብ አመልካች እና ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ግንኙነት ነበራቸው ተብሎ ድምዳሜ ከተያዘ አመልካች መኖሪያ ቤቱን ለተጠቀመበት ጊዜ ሊከፍሉ የሚገባው የኪራይ ገንዘብ መጠን ምን ያህል ነው? የሚል ነው፡፡ አመልካች የኪራይ መጠኑንን ያሻሻለው የታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም ማስጠንቀቂያ ከተጠሪ ህጋዊ ወኪል የተሰጠኝ አይደለም ቢሉም ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው አመልካች የኪራዩ መጠን እንዲጨመር የተደረገው በአከራዩ ፍላጎት መሆኑን ከማስጠንቀቂያው በኃላ ያወቁ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን ደምድመዋል፡፡ ይህ ችሎት ደግሞ ይህን የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የያዙትን ድምዳሜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳለ የሚቀበለው መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የኪራይ ተመኑ ከብር 2000.00 ወደ ብር 5000.00/አምስት ሺህ/ ከፍ ስለማለቱ ተገቢው ማስጠንቀቂያ አልደረሰኝም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ወርሃዊ የኪራይ ተመኑ ከፍ መደረጉን አከራይ ያሳወቃቸው መሆኑን በሚገባ ያውቁ ነበር፣ ቤቱንም መጠቀም ቀጥለዋል ከተባለ ደግሞ አዲሱን የኪራይ ተመን መቀበላቸውን ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1684(1) ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በዚህ አግባብ የኪራይ ተመን መሻሻሉን ከአወቁ በኃላ ቤቱን መጠቀም የቀጠሉ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2952 (2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት በአዲስ የቤት ኪራይ ተመን መሰረት ለቤቱ ባለቤት ኪራዩን ለመክፈል የማይገደዱበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.70432 ጥር 20 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.131903 ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በግራ ቀኙ መካከል የህዳር 2003 ዓ/ም የኪራይ ውል ካበቃ በኃላ የኪራይ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ ተደርጓል ፣ የኪራይ ተመኑም ወደ ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ ከፍ ማለቱን አመልካች አውቀውታል ተብሎ ይህንኑ ገንዘብ ከታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ቤቱን እስከሚያስረክቡ ድረስ ለተጠሪ እንዲከፍሉ ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

ጥር 19 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር. 95797

ጥር 20 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተሽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ደበበ ድርሪሳ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ -ስራ አስኪያጆች ባለቤት ደበበ ድሪርሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፈንታሌ ወረዳ ውሃ ማእድን ኢነርጂ ፅ/ቤት - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ከንጹህ ውሃ ግንባታ ጋር ተያይዞ የተነሳውን የወለድ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ እና በፈንታሌ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት ላይ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር በ17/08/2002 ዓ/ም በተደረገ የውል ስምምነት መሰረት የንጽህ ውሃ ግንባታ በፈንታሌ ወረዳ ከኒፋ ቀበሌ ውስጥ ለማከናወን ግዴታ ገብቶ በውሉ መሰረት ስራው ተሰርቶና በባለሙያ ተለክቶ የ1ኛ የ2ኛ እና የ3ኛ ዙር የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ክፍያ የተፈፀመለት መሆኑን ከዚህ በኋላ የተሰራው ስራም ተለክቶ የ4ኛዙር ላይ ብር 239,828,88 የ5ኛ ዙር ሰርተፊኬት ላይ ብር 131,975,13 ለአመልካች ሊከፈል ይገባል በማለት በባለሙያ ሰርተፊኬት ተዘጋጅቶ ለሥር ከሳሾች ቢደርስም ክፍያውን ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆኑም በማለት የብር 371,803,88 ከተለያዩ የወጪና ኪሳራ ክፍያዎች እንዲሁም ከ20%ቅጣት ጋር ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቋል ። የአሁኑ ተጠሪም አመልካች ስራውን እንደውሉ ያለመፈጸሙንና ውሉን በጊዜ ገደቡ ያለማጠናቀቁን ጠቅሶ ለአመልካች ክፍያ ለመፈጸም የሚገደድበት አግባብ ያለመኖሩን ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካችን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ያደረገው ሲሆን የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑን አመልካች ለክሱ ኃላፊ አድርጎ ብር 412,668,41(አራት መቶ አስራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም)ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ወጪና ኪሳራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ያለ ሲሆን ወለድና ቅጣትን በተመለከተ ግን የአሁን አመልካች ጠይቆ ውሉ የተደናቀፈው በተጠሪ ስላልሆነ መክፈል ያለበትን ገንዘብ አለመክፈሉ ቅጣትን ወለድን የሚያስከፍለው አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ወለድና ቅጣትን እንዲሁም ወጪና ኪሳራን በተመለከተ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የአሁኑ አመልካች ቅር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ወጪና ኪሳራን በተመለከተ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር ይግባኝ ሰሚው ችሎት ወጪና ኪሳራውን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 462 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብ ግራቀኙ አከራክሮ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1)መሰረት መልሶለታል የአሁኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ወለድን በተመለከተ ዳኝነት ያለመስጠቱ ያላግባብ ነው በሚል ሲሆን ጉዳዩ ተመርምሮም የአመልካች የወለድ ይከፈልኝ ጥያቄ መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በገባው የውል ግዴታ መሰረት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ዙር ያሉትን ክፍያዎችን በአግባቡ የከፈለ ሁኖ በ4ኛ እና 5ኛ ዙር ክፍያዎች ግን ከአመልካች ጋር በውል በተቀመጡ መሰረታዊ ጉደዮች ላይ ወደ ክርክር የተገባ በመሆኑና የሥራው ጊዜም ከ72 ቀናት ያለፈ በመሆኑ ሳይከፈል ለቆየው ገንዘብ ወለድ የሚከፍልበት የሕግ ምክንያት የለም ሲል ተከራክሯል አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል ፡፡

አመልካች ለሰራው ስራ 4ኛ እና 5ኛ ዙር ክፍያ እንደሚገባው በባለሙያሰርቲፊኬት የተረጋገጠለት ቢሆንም ተጠሪ ጋር ውሉ በአግባቡ አልተከናወነም በሚል ወደ ክርክር የገቡ መሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሳይል አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ የሚከራከረው ተጠሪ ሕጋዊ ወለድ የማይከፍልበት አግባብ የለም በሚል ሲሆን ለዚህም እንደ ሕጋዊ ምክንያት የሚያቀርበው ክርክር የተነሳበት ገንዘብ መጠን ከተሰራው ስራ ጋር በማመዛዘን የመስሪያ ቤቱ ባለሙያና ምድብ ሰራተኛ የክፍያ ሰርተፊኬት አዘጋጅቶ ካቀረበው ጊዜ ጀምሮ የሚታወቅ እዳ ነው የሚል ነው፡፡

ይሁን እንጂ በውሉ መሰረት ስራው መሰራት ያለመሰራቱ ላይ ግራ ቀኙ ሊተማመኑ ባለመቻሉ ወደ ክርክር የገቡ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል ፡፡ ይህ ደግሞ በአመልካች ላይ የጥቅም መቀነስን የሚያስከትል መሆኑ ግልፅ ቢሆንም ስራው በውሉ መሰረት መሰራት ያለመስራቱ አከራካሪ እስከሆነ ድረስ የታወቀ እዳ እያለ ተጠሪ ለአመልካች ሳይከፍል ዘግይቷል ሊባል የሚችል አይደለም ፡፡ አመልካች ላይ በተጠሪ ያልተገባ የውል ተግባር ቀጥተኛ የሆነ የገንዘብ ኪሳራ የደረሰባቸው መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡

ወለድ በሕጉ አግባብ የተዘረጋው ስርዓት እንደተጠበቀ ሁኖ በስምምነት ወይም ያለስምምነት ሊከፍል የሚችል ገንዘብ ነው፡፡ወለድ ተበዳሪ የወሰደውን ገንዘብ ወይም እቃ በወቅቱ ባለመመለሱ የተነሳ የሚከፈል የገንዘብ ካሳ ነው፡፡ በኮንስትራክሽን ስራ ውልም ወለድ ሊጠየቅበት የሚችል አግባብ ያለ ሲሆን አላማውም የገንዘብ ኪሳራን ማካካሻ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ምክንያቱም ከላይ ከተገለጸው የወለድ አይነት ሌላው አይነት ወለድ አንድ ሰው ግዴታውን ባለመፈፀሙ ወይም በማዘግየቱ የተነሳ የሚከፈለው ካሳ እኩያ መሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1803 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ወለድ ለገንዘብ ብድር ብቻ እንዲከፈል የሚደረግ የካሳ የአይነት ሳይሆን ለግዴታ ባለመፈጸም ወይም ማዘገየት የተነሳ የሚከፈል ካሳ በመሆኑ ይህ ሲረጋገጥ ብቻ የሚከፈል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች የንጹህ ውሃ ግንባታ ውል ስምምነት ያደረገው ከአስተዳደር መስሪያ ቤት ጋር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከአስተዳደር ውሎች ያለመፈፀም ጋር ተያይዞ የወለድ ጥያቄ የሚቀርብበት አግባብ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3196 እና 3197 ድንጋጌዎች የሚታይ ነው ። የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3196 ድንጋጌ ይዘት ሲታይ የወለድ ጥያቄ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልግ ተገቢነት የሚኖረው የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ በውሉ በተመለከተው መሰረት ከአስራ አምስት ቀን በኃላ ለተዋዋዩ ስለ ገንዘቡ አከፋፈል የሚያስፈልገውን የማረጋገጡ ስራ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ወይም የአስተዳደር መ/ቤት የሚፈለግበትን ገንዘብ የማረጋገጡ ስራ በተፈፀመ በሶስት ወር ውስጥ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ስለመሆኑ ያስገነዝባል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3197 ድንጋጌ ደግሞ ተቃራኒ የውል ስምምነት ቢኖርም እንኳን ሳይከፈል የቆየበት ጊዜ ከስድስት ወር በላይ ሲሆን ወይም ውሉን ያደረገው የአስተዳደር መስሪያ ቤት ለመጉዳት ብሎ ያደረገው ወይም ከባድ በሆነ ቸልተኛነት ወይም ጥፋት ያደረገው የአስተዳደር መስሪያ ቤት ለመጉዳት ብሎ ያደረገው ወይም ከባድ በሆነ ቸልተኛነት ወይም ጥፋት ያደረገው ሲሆን ወለድ ሊጠየቅና ተቀባይነት ሊሰጠው እንደሚገባ አስቀምጧል። ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከወለድ አላማ አንፃር አሁን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከተው አመልካች ግዴታውን በውሉ በተቀመጠው አግባብ አልፈጸመም በሚል ምክንያት ተጠሪ ክፍያውን ሳይፈጽም የዘገዬ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የካሳ እኩያ የሆነውን ወለድ የሚያገኙበት የሕግ ምክንያት አላገኘንም ።

ሲጠቃለልም ከላይ በተገለፁት ሕጋዊ ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ፍርድ ቤት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስላላአገኘነው ተከታዩን ወስነናል ።

<u>ውሳኔ</u>

1. በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 159905 ጥቅምት 11 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል።
2. የአመልካች የወለድ ክፍያ ጥያቄ በመታለፉ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለናል።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፤ ብለናል። መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 103704
ጥር 20/ቀን 2007ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
ዓሊ መሀመድ
ሱልጣን አባተማም
መስጠፋ አህመድ
ተሽሊት ይመሰል

አመልካች፡- -------ቀረቡ

ተጠሪ፡- --------ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 2 ቤት.ቁ 1314 (ለ)የሆነውን የመንግስት ቤት አመልካች የተከራየውን ንግድ ቤት ለሶስት በመሸንሸን አንዱን በ8000 ብር አከራይቶኝ ሙዝ የመሸጥ ስራ እየሰራሁበት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በመመሪያ ቁ.3/2004 መሰረት የከተማው ግብረ ሀይል ተጠሪ አንዱን ክፍል በመያዝ ለአመልካች አንደኛውን ክፍል በመክፈል እንዲሰጠኝ ተወስኗል፤ ሆኖም የስር አንደኛ ተከሣሽ እኔ በሌለሁበት ዕቃዬን የታሸገውን ቤት በውስጡ ያለውን ንብረት ተጠሪ እንዲጠቀምበት አድርጓል ፤ንብረቴንም እየተጠቀመበት ነው፡፡ ቤቱንም ወደ መኖሪያ ቤት በመቀየር ይሟል ንብረቴን መረከብ እና የተቋረጠብኝ ገቢን ማስከፈል አልቻልኩም ስለዚህ የንብረት ግምት 4000 እና የተቋረጠ ገቢ ተከፍሎኝ የንግድ ቤቱን ያስረክቡኝ በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት መልስ ለተጠሪ ቤት ሸንሸኜ በ8000 አላከራየውም የሀሰት ክስ ነው፡፡ በመመሪያ ቁ.3/2004 መሰረት የኪራይ ውሉ ከእርሳቸው ጋር እንድቀጥል ጉዳዩን የሚመለከተው አካልም የተሳሳተ ግንዛቤ ውስጥ በመክተት ቢጠየቅም አመልካች ለማስፈጸም የተዋቀረውን ግብረሀይል ከቫይረሱ ጋራ መኖሬን የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረቤ የኪራይ ውሉን ከእኔ ጋርእንዲቀጥል ተደርጓል፤ በተጨማሪም ሌላ ገቢ የሌለኝና ወረዳው የወሰነልኝ በመሆኑ ቤቱን ለተጠሪ ላስረክብ አይገባም ፣ ቤት ውስጥ የነበረውን ንብረት ወይም ግምት እና ያጣሁትን ገቢ ይከፈለኝ ለተባለው ማስረጃ ያልቀረበበት በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል መልሱን ሰጥቷል ፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን በማከራከር አመልካች የኤች አይ ቪ ታማሚ በመሆናቸው ብቻ በመመሪያው ልዩ ድንጋጌ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም፤ በንግድ ቤቱ ቁጥር 1314 በአንደኛው ክፍል እየሰሩበት ገቢ በማግኘት ላይ መሆናቸውን በማረጋገጥ ተጠሪ የአከራካሪውን ቤት አንዱን ክፍል ሊያገኙ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ሌላውን የንብረት ግምትና የታጣ ገቢ ጥያቄ በማስረጃ አልተረጋገጠም ሲል ውድቅ አድርጎታል ፡፡ በቀጣይነት ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶችም የስር ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት አጽንቶታል፡፡

የአመልካች አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልጹ ፡- በመመሪያ ቁ. 3/2004 መሰረት የኤች.አይ.ቪ ታማሚ እና ሌላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገቢ የሌለኝ መሆኔን አረጋግጫለሁ፤1314(ሀ)(ለ) ሆኖ (ሀ) ለመኖሪያ እየተጠቀምኩበት የትኛውን እንደምካፈል እንኳ አልተለየም ፤በአጠቃላይ ሌላ የገቢ ምንጭ እንዳለኝ የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህ መሰረት ችሎቱም አመልካች ኤች አይ ቪ ታማሚ እና የገቢ ምንጭ የለኝም ሲሉ ያነሱት ጥያቄ ውድቅ መሆኑን ከመመሪያ ቁ. 3/2004 እና 4/2002 አንቀጽ 6 መሰረት ለማጣራት በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙን መልስና የመልስ መልስ በጽሑፍ በማቀባበል ተከራክረዋል ፡፡

ተጠሪ በሰበር አቤቱታቸው የሚከራከሩት አመልካች የቤት ቁ.1314ን ለመኖሪያነት ከተከራዩ በኃላ ሀ፣ለ፣ሐ በማለት ለተጠሪ 1314(ለ)"ን" አከራይቶኝ ለራሳቸውም ሲሰሩ ነበር ስለዚህ በመመሪያው ቁ.6 አንዣር ጠቅላላውን ያከራዩ ሳይሆን በሌላኛው ቤት ሲነግዱና የገቢ ምንጫቸው ያደረጉት በመሆኑ ኤች አይ ቪ ታማሚ በመሆናቸው ብቻ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይገባም ተብሎ አመልካች የያዙትን እንዲሰሩበት ተደርጎ እኔም በተከራየሁት ተጠቃሚ እንድሆን መወሰኑ ሊጸና ይገባዋል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው በሽተኛ መሆኔ አልተካደም በይዞታዬ ስር አድርጌ ከምጠቀምበት ንግድ ቤት በቀር ሌላ የገቢ ምንጭ የለኝም ፣በመሆኑም ውሳኔው ሊሻር ይገባዋል በማለት ክርክራቸውን አጠናክረዋል ፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር መርምረናል ፤ በዚህ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ በመነሳት እንዳየነው ከተጠቃሾቹ መመሪያዎች አንጻር ልዩ ተጠቃሚ ለመሆን መመሪያ 3/2004 እና ቁ.4/2004 የኤች አይ ቪ ታማሚን አስመልክቶ የተለያየ ድንጋጌ አይታይባቸውም ፡፡ አንድነታቸው ጎልቶ ከመታየቱ በቀር የመመሪያ ቁ.3 አንቀፅ 6 እና መመሪያ ቁ. 4/2004 አንቀጽ 12 የሚሉት ከመንግስት የተከራየው ሰው የኤች አይ.ቪ ታማሚ ሆኖ እና ሌላ የገቢ ምንጭ ሳይኖረው እና ሲጠቀምበት የነበረውን ቤት አከራይቶ ከተገኘ ይህንኑ አረጋግጦ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል በተያዘው ጉዳይ በተጠቃሹ ቤት ቁ.1314 "ን" አስመልክቶ አመልካች ሽንሽኖ ለተጠሪ አከራይቶና የቀረውን ክፋይ አመልካች ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ እውነታ ነው፤ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በአንደኛው ክፍል ቤት ላይ እየነገዱ መሆናቸውን ሳይክዱ ከዚህ የተለየ ሌላ የገቢ ምንጭ የለኝም ያለኝ ለመሆኑም አልተረጋገጠም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር መመሪያውን ያላገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ይዘውት ባሉት ክፍል ተከራይነታቸው ሲቀጥል ተጠሪም የአንደኛውን ክፍል ሊያገኙ ይገባል መባሉን ይህ ችሎትም የሚቀበለው ይሆናል ፡፡

በመጨረሻም ጉዳዩን ያዩት የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የይግባኝ ሰሚው አመልካች ሌላ የገቢ ምንጭ ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ የመመሪያው ልዩ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይገባም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም ፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 06479 በ 03/7/06 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ.ቁ.21839 በቀን 29/8/06 እና በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.22278 በሀምሌ 11 ቀን /2006 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች የገቢ ምንጭ ስላላቸው የኤች.አይ.ቪ.ታማሚ በመሆናቸው የመመሪያው ልዩ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይገባም መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ የወጪ ኪሳራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በነሀሴ 08 ቀን 2006 ዓ.ም በዚህ ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98358

ጥር 05 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ -ነገረ ፈጅ ኃይሉ ተሰማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዩጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ጠበቃ ማረን ወንደ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የመድን ውልን መሠረት አድርጎ የቀረበውን የገንዘብ ይተካልኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- የአሁኑ አመልካች ለደንበኛው ለነዳ ኃላፊነቱ የተ.የግል ማህበር ከቱርክ ሀገር ለሚያስመጣቸው 246 ጥቅል ብረቶች ከተጫኑበት ሀገር ተንቡዞ እስኪመጣ ድረስ ለሚያጋጥም ጉዳት በፖሊሲ ውል ቁጥር 01/ኤም አር አኤ/00001/07 የባህር ላይ የጉዞ መድን ሽፋን መስጠቱን፣ተጠሪ የመድን ሽፋን የተሰጣቸውን 246 ጥቅል ብረቶችን ተረክቦ ሆውማ ቤሊ ቪ.ኢ.ኤስቲአር53 በሚባለው መርከብ ከሊአጋ ኢዝሚር ቱርክ አንጉዞ ጅቡቲ ለማድረስ በባህር እቃ መጫኛ ሰነድ ቁጥር 305/ኤስሲ ግዴታ መግባቱን፣ተጠሪ ጅቡቲ ለማድረስ ግዴታ ከገባባቸው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ እቃው ጅቡቲ ወደብ ደርሶ ሲራገፍ 11(አስራ አንድ) ጥቅል ብረቶች መጥፋታቸውን፣ ከተንገዘበው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ የአመልካች ደንበኛ በ11/04/2004 ዓ/ም 226 ጥቅል አዲስ አበባ ላይ በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10431 መረከቡን፣ቀሪው 20 ጥቅል ብረት ውስጥ 9 ጥቅል ደግሞ ዘግይቶ በ05/06/2004 ዓ/ም በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10999 መረከቡን፣ይህ የተጫነ እቃ መጥፋትና መጉደሉ በጅቡቲ የሰርቬየር ስራ በሚሰራው ገልፍ ኤጀንሲ አገልግሎት የሚባል ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ማረጋገጡን ገልጾ አመልካች ለደንበኛው የከፈለውን ካሳ ብር 289,527.23 ተጠሪ እንዲተካለት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም፡-የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያስቀደመ ሲሆን በዚህም መሰረት የአመልካች ክስ እቃው በጅቡቲ ወደብ ላይ መራገፉ ከተረጋገጠበት ከጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ በሚታሰብ በአንድ አመት ይርጋ ጊዜ ውስጥ የሚታገድ መሆኑን የባህር ሕግ ቁጥር 203(1) ድንጋጌ እንደሚያሳይ እንዲሁም አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የሌለው መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍርድ ቤትም በዚህ መልክ የቀረበውን የይርጋ ክርክር በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በመመርመር እቃው በጅቡቲ ወደብ የተራገፈው ጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ/ም መሆኑን መነሻ አድርጎ ይርጋውን በመቁጠር የካቲት 05 ቀን 2005 ዓ/ም የቀረበው የአመልካች ክስ በባህር ሕግ ቁጥር 203(1) መሰረት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ የታገደ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የመጨረሻ ርክክብ የተደረገው የካቲት 05 ቀን 2004 ዓ/ም ሁኖ እያለና የደንበኛው እቃ መጉደሉም የተገለጸው ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ሁኖ እያለ የእቃው ርክክብ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ይርጋው ሊቆጠር ይገባል ተብሎ የአመልካች ክስ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ነጥብ የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ሊመስርት የቻለው ለደንበኛው ለነፃ ኃላፊነቱ የተ.የግል ማህበር ከቱርክ ሀገር ለሚያስመጣቸው 246 ጥቅል ብረቶች ከተጫኑበት ሀገር ተንጉዞ እስኪመጣ ድረስ ለሚያጋጥም ጉዳት በፖ.ሊሲ ውል ቁጥር 01/ኤም አር ኦኤ/00001/07 የባህር ላይ የጉዞ መድን ሽፋን መስጠቱን መሰረት አድርጎ ሲሆን በዚህ ጉዞ ሂደት ጠፉ ለተባሉት 11 ጥቅል ብረቶች ለደንበኛው ከፈልኩ የሚለውን ገንዘብ እቃዎቹን የማጓጓዝ ግዴታ አለበት የሚለው ተጠሪ እንዲተካለት ነው፡፡ስለሆነም ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ሕግ የባህር ህግ ሲሆን ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለውን የይርጋ ጊዜ የሚያስቀምጠው የህጉ ድንጋጌ ቁጥር 203 ሲሆን ድንጋጌው ሁለት ንዑስ ቁጥሮችን የያዘ ሁኖ የመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር ከማመላለሻው ውል ውስጥ የተገኙ መብቶች በይርጋ የሚታገዱት የንግድ እቃውን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ወይም የማስረከቡ ጉዳይ ሳይፈፀም ቀርቶ እንደሆነ እቃውን ማስረከብ ከሚገባበት ቀን አንስቶ የአንድ አመት ጊዜ ካለፈ በኋላ ነው በማለት አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ አስቀምጧል፡፡የተጠቃሹ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ከሂሳብ አከፋፋል ጋር ተያይዞ የሚነሳው ክርክር የሚታገድበትን አግባብ የሚያስቀምጥ ነው፡፡ የባህር ህግ ቁጥር 203 ድንጋጌ የሚገኘው በጭነት ማስታወቂያ የተረጋገጠ ደረሰኝ የማመላለሻ ውልን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች በሚገዛው ክፍል ሲሆን የድንጋጌዎችን ወሰን በተመለከተ በቁጥር 180 ስር ሕግ አውጪ አስቀምጧል፡፡ይህ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር አንድ ስር በክፍሉ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚፀኑት በተለይ በመርከብ ላይ በተጫኑት የንግድ እቃዎች የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን በመሰለ ሌላ አይነት ሰነድ በተረጋገጡ የጭነት ማመላለሻ ውሎች ላይ ብቻ መሆኑን ሲያስቀምጥ የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት እና ሶስት ደንጋጌዎች ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው የመርከብ መከራየት ውል ሰነድ ባለው ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ ሊሆኑ እንደማይችሉና በዚህ ጊዜም ድንጋጌዎቹ ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን ልዩ ሁኔታዎችን የሚያስቀምጡ ናቸው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ጅቡቲ ለማድረስ ግዴታ ከገባባቸው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ እቃው ጅቡቲ ወደብ ደርሶ የተራገፈው ጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ/ም ሁኖ በዚህ ጊዜ ከተጓጓዘው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ የአመልካች ደንበኛ በ11/04/2004 ዓ/ም 226 ጥቅል አዲስ አበባ ላይ በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10431 መረከቡን፣ቀሪው 20 ጥቅል ብረት ውስጥ 9 ጥቅል ደግሞ ዘግይቶ በ05/06/2004 ዓ/ም በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10999 መረከቡን ፣ይህ የተጫነ እቃ መጥፋትና መጉደሉ በጅቢቲ የሰርቬየር ስራ በሚሰራው ገልፍ ኤጀንሲ አገልግሎት የሚባል ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ማረጋገጡንና አመልካች ክስ የመሰረተው የካቲት 05 ቀን 2005 መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡አሁን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይ በባህር ህጉ ቁጥር 203(1) የተመለከተው የአንድ አመት የይርጋው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ ጀምሮ ነው? የሚለው ነው፡፡አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስህተት ነው በማለት የሚከራከረው የእቃዎቹ ርክክብ ጊዜ በማስጫኛ ውሉ ላይ አልተገለፀም፣በመጀመሪያው ዙር 226፣ቀጥሎ ደግሞ 9 ጥቅል ብረቶች የተላኩ መሆኑንና ለክሱ መነሻ የሆኑት ቀሪዎቹ 11 ጥቅል ብረቶች መጥፋታቸው የተረጋገጠው ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ነው በሚል ነው፡፡እንግዲህ ክርክሩ ይዘት በግልጽ መረዳት የሚቻለው እቃው በባህር ላይ ተጉዞ ጅቡቲ የተራገፈበት አግባብ በአንድ የማስጫኛ ሰነድ ያለመሆኑን ነው ፡፡በአንድ የማስጫኛ ሰነድ እቃዎቹን ተጠሪ ባልተረከበበት ሁኔታ የመጀመሪያው የማራገፊያ ቀን ማለትም ጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ/ም ከይርጋው መቆጠር መነሻ ቀን የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ የርክክብ ቀን የሆነው ታህሳስ 11 ቀን 2004 ዓ/ም ለይርጋው መነሻ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል ማለቱ እቃው በሙሉ አንድ አይነት፣በአንድ የጭነት ሰነድ በአንድ የማጓጓዣ ውል የተጓጓዘ መሆኑን ከክሱ መረዳት ይቻላል በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ከዚሁ ከመጀመሪያው ርክክብ በኋላ 9 ጥቅል ብረትን የአመልካች ደንበኛ የካቲት 05 ቀን 2004 ዓ/ም መረከቡ ያልተካደ ፍሬ ነገር ነው፡፡ስለሆነም ርክክቡ የቆመው ከዚህ ከየካቲት 05 ቀን 2004 ዓ/ም በኋላ በመሆኑ የአመልካች ደንበኛ እቃዎቹ መጥፋታቸውን እርግጠኛ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ የሚታሰበው ከዚህ ቀን በኋላ እንጂ የመጀመሪያው ርክክብ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም፡፡ተጠሪ የባህር ህግ ቁጥር 180(2) ድንጋጌን መሰረት አድርጎ የሚያቀርበው ክርክርም እቃዎቹ ከመርከቡ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ አስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ የበህር ህግ ቁጥር 203 ድንጋጌ ተፈፃሚ መሆኑን የሚያስቀምጥ ሲሆን ይህም እቃዎቹ ሙሉ በሙሉ ተጭነው ባልተቆራረጠ ሁኔታ ርክክቡ የሚፈፀምበትን አግባብ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተቀመጠ ድንጋጌ ነው ከሚባል በስተቀር በመርከብ ላይ የተጫኑት እቃዎች በተግባር በተለያዩ ጊዜያት እየተራገፉ ርክክቡም በተለያዩ ጊዜያት ሲደረግ የነበረበትን ሁኔታ ለመግዛት ታስቦ የተቀመጠ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡የአመልካች ደንበኛ እቃዎቹን በተለያዩ ጊዜያት ሲረከቡ የነበሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠ እቃዎቹ የተራገፉበትን ቀን ወይም የመጀመሪያ ርክክብ የተደረገበትን ቀን መነሻ አድርጎ ክሳቸው በይርጋ እንዲታገድ ማድረግ ከይርጋ ዕንሰ ሃሳብም ውጪ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡

የይርጋ ህግ መሰረታዊ አላማ ተገቢውን ጥረት የሚያደርጉ ገንዘብ ጠያቂዎችን ወይም መብት አስከባሪዎችን መቅጣት ሳይሆን መብታቸውን በተገቢው ጊዜ ለመጠየቅ ጥረት የማያደርጉትን ሰዎች መቅጣት መሆኑ ይታመናል፡፡ስለሆነም የአመልካች ደንበኛ መብታቸውን ማስከበር ሲችሉ ያላግባብ የዘገዩበት ሁኔታ መኖሩን የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡በባህር ህግ ቁጥር 162 ድንጋጌ ስር የይርጋ አቆጣጠር ጊዜ የሚጀምርበትን አግባብ ያስቀመጠ ሲሆን ለተያዘው ጉዳይ ግን ድንጋጌው ሙሉ በሙሉ አግባብነት አለው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ምክንያቱም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌው በንኡስ ቁጥር አንድ ስር ለመጫን ወይም ለማራገፍ የተወሰነው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ካፒቴኑ መርከቡን ሊጫን ወይም ሊራገፍ ተዘጋጅቷል ብሎ ካስታወቀበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ሲያስቀምጥ የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ጊዜም የሚታሰበው ካፒቴኑ ማስታወቂያውን ሰጥቶ ስራው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን ያሳያል፡፡በሌላ አገላለፅ ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው የመጫኛና የማራገፊያ ጊዜ የሚጀምርበት ጊዜ በግልጽ በታወቀበት ሁኔታ ነው እንጂ እቃዎቹ በተለያዩ ጊዜያት በተጫኑበትና በተራገፉበት ግንኙነት ውስጥ አይደለም፡፡የአመልካች ደንበኛ እቃዎች ሙሉ በሙሉ የተጫኑበት ቀንም ሆነ የሚራገፉበት ቀን ያለመታወቁን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡

አመልካች በእርግጥም መብቱን ማስከበር የሚችልበት ጊዜ የካቲት 05 ቀን 2004 ዓ/ም ከተባለ ይኼው ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1848(1) ድንጋጌ መሰረት ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ በባህር ህጉ አንቀጽ 203(1) የተቀመጠው የአንድ አመት ጊዜ የሚያበቃው ከየካቲት 06 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ ሲሆን አመልካች ግን ይሄው ጊዜ ከማለፉ በፊት የካቲት 05 ቀን 2005 ዓ/ም ክሱን ያቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ በአንድ አመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት የሰጡት ብይን ተገቢውን የይርጋ መቁጠሪያ ጊዜ መነሻ ያላደረገ ከመሆኑም በላይ የባህር ህግ ቁጥር 162 ድንጋጌን ይዘቱንና መንፈሱን ከተያዘው ጉዳይ ልዩ ባህርይ ጋር ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ብይኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 203024 ግንቦት 06 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 137802 ታህሳስ 08 ቀን 2006 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ አይደለም ብለናል፡፡
3. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 203024 ቀጥሎ በሌሎች የግራ ቀኙ የክርክር ነጥቦች ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት ተከትሎ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95072
ጥር 07 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሱልጣን አባተማም
ሙስጠፋ አህመድ
ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡-ግሎሪየስ ኃ.የተ.የግል ማህበር - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሜሮን ታምራት - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታተ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የማቀዝቀዣ(ፊሪጅ) ሽያጭን መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ከተጠሪ በብር 16,750.00 የገዙት ፊሪጅ አስፈላጊውን አገልግሎት መስጠት እንደማይችል እንደተረዱ ወደአመልካች ድርጅት አድርሰው ድርጅቱ እቃው እንደሚስተካከልላቸው ነግሯቸው እቃውን ተስተካክሏል በሚል ወደ ቤት ቢመልሱትም በተመሳሳይ ሁኔታ ለሁለተኛ ጊዜ ተበላሽቶ አገልግሎት መስጠት በማቆሙ እቃውን እንዲቀየርላቸው ድርጅቱን ቢጠየቁም ድርጅቱ ፈቃደኛ ያለመሆኑን ዘርዝረው አመልካች ድርጅት እቃውን እንዲቀይርላቸው ወይም የሸያጭ ገንዘቡን እንዲመልስላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከተጠሪ ጋር የፊሪጅ ሽያጭ ውል መኖሩን ሳይክድ ማቀዝቀዣው ተጠግኖ እንዲሰራ ማድረጉን፣ ለአንድ አመት ደግሞ የጥገና ዋስትና ግዴታ ከመግባቱ ውጪ ፊሪጁን ለመቀየር ወይም የሸያጭ ገንዘቡን ለመመለስ ግዴታ ያለመግባቱንና ባለው የጥገና ዋስትና መሰረት ማቀዝቀዣውን ጠግኖ አመልካች ለመውሰድ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆንይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤትም ፊሪጁ መስራት አለመስራቱን በቦታው ላይ ተገኝቶ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ፍሪጁ መስራቱን መመልከቱን ገልፆ አመልካች በውሉ ባለው የጥገና ዋስትና ውል ግዴታውን መወጣቱ መረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ፍሪጁ መስራት አለመስራቱ ከሁለት ድርጅቶች ባለሙያ ተመድቦ እንዲጣራ ትዕዛዝ ቢሰጥም አመልካች ድርጅት ከአሜዳድ ድርጅት የተላከውን ባለሙያ ማቀዝቀዣውን እንዳይመለከት አድርጎ ሳልኔት ከተባለው ድርጅት የተላከው ባለሙያ ብቻ እንዲመለከት አድርጎ ይህ ድርጅት ያቀረበውን ሪፖርት በመመርመር የአመልካች አካሄድ ከቅን ልቦና የሆነ ነው በሚል ድምዳሜ አመልካች ለተጠሪ ተመሳሳይ ሞዴል ማቀዝቀዣ እንዲቀይርላቸው ወይም ዋጋውን ብር 16,750.00 እንዲመልስላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኦሜዳድም ሆነ በሳልኔት ድርጅት ባለሙያዎች ማቀዝቀዣው መስራት ያለመስራቱ ተጣርቶ እንዲቀርብ አድርጎ ድርጅቶቹ ባቀረቡት ሪፖርት መሰረት ማቀዝቀዣ መስራቱ ቢረጋገጥም የባለሙያዎቹ አስተያየት እንደ አስገዳጅ ማስረጃ ሊወሰድ እንደማይችል፣እቃው ከሶስት ወራት በኋላ የማይበላሽ መሆኑን እርግጠኛ መሆን እንደማይቻል፣አዲስ የተገዛ እቃ ሁል ጊዜ እያስጠገኑ መጠቀም አለበት ሊባል እንደማይገባ በምክንያት ይዞ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ሙሉ በሙሉ አንጽንቶታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ለተጠሪ የተሸጠው ማቀዝቀዣ የተበላሸው በተጠሪ የአጠቃቀም ችግር የተከሰተ ሁኖ የሸያጭ ውሉም በአመልካች ላይ ለአንድ አመት የጥገና ግዴታ ከሚጥል በስተቀር እቃውን ለመቀየር ወይም የሸያጭ ገንዘቡን ለመመለስ የማያስገድድ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከውሉና ከሕጉ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በአመልካችና በተጠሪ የተገባውን የሸያጭ ውል ስምምነት መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

አመልካችና ተጠሪ የማቀዝቀዣ ሽያጭ ውል ማድረጋቸው፣አመልካች ማቀዝቀዣውን ቢበላሽ ለአንድ አመት የጥገና ዋስትና ግዴታ መግባቱን፣አመልካች እቃውን ለተጠሪ አስረክቦ ተጠሪ እቃውን በመጠቀም ላይ እንዳሉ መጀመሪያ ሲበላሽ አመልካች ባለው የጥገና ግዴታ እቃውን ጠግኖ ሲመልስ እንደገና በመበላሸቱ ተጠሪ እቃውን ለአመልካች መልሰው አመልካች እንደገና ጠግኖ እቃው እንዲሰራ ቢያደርግም ተጠሪ እቃው ካልተቀየረ አልረከብም ማለታቸው በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ጉዳዮች ናቸው፡፡

በመሰረቱ ሽያጭ ማለት ሻጭ የሆነው አንዱ ወገን ገዥ ለሆነው ሌላ ወገን ዋጋው በገንዘብ የተወሰነውን አንድ ነገር ገዥው ሊከፍለው ግዴታ በገባበት መሰረት ሊያስረክብና ሀብትነቱን ሊያስተላልፍ የሚገደድበት ውል መሆኑ በፍ/ሕ/ቁ.2266 ተመልክቷል ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ሻጭ የሆነ ወገን የሸያጨን ገንዘብ ከገዥ ወገን መጠየቅ መብት እንዳለው ሁሉ የተሸጠውን ነገር ደግሞ የማስረከብና ሀብትነቱን የማስተላለፍ ተነጻጻሪ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ሻጭ ያስረከበው ነገር በውሉ መሰረት ትክክል ለመሆኑና ጉድለት ስላለመኖሩ ለገዢው ኃላፊ ነው፡፡ ዕቃው እንደ ውሉ አይደለም የሚባለው ዋቢነት የሚሰጥባቸው ጉድለቶች እና ጉድለት ስለመኖሩ ፣ ጉድለት ያለ ከሆነ ደግሞ ጉድለቱ መቼ መመርመር እንዳለበት ፣ ገዢው የገዛው እቃ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ መቼ ማስታወቅ እንዳለበት እንዲሁም ጉድለትን አለማስታወቅና የሚያስከትለው ውጤትን አስመልክቶ በፍትሐብሔር ህጉ ከቁጥር 2288-2293 ድንጋጌዎች ስር በግልጽ ተመልክቷል ፡፡

ገዢ ጉድለቱን ካወቀበት ወይም ጉድለት ያለበት መሆኑን ካስታወቀበት ግዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ክስ ካላቀረበ መብቱ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298 የተመለከተ ሲሆን ይሁንና ሻጩ የደረሰውን ጉዳት የማስተካከል ወይም በአዲስ የመተካት መብቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2300 ድንጋጌ ተጠብቆለታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የእቃውን ጉድለት መመርመርን በተመለከተ ህጉ ገዢው ግልፅ ጉድለትን በተመለከተ እቃውን በተረከበበት ግዜ የመመርመር ኃላፊነት እንዳለበት ሲያስቀምጥ ሻጩ ደግሞ ለድብቅ ጉድለቶች /በርክክብ ወቅት ሊታዩ ወይም ሊገለጽ የማይችሉ/ ሃላፊነት / let the seller be aware of latent / hidden/ defects/ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡
ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያቀረቡት ጉድለት መኖሩን መሰረት አድርገው ሳይሆን ብልሽቱ እንዲጠገንላቸው ለአመልካች ጥያቄ አቅርበው አመልካች በግራ ቀኙ መካከለ ባለው ውል መሰረት ጠግኖ ከሰጠ በኋላ እቃው እንደገና በመበላሸቱ ምክንያት በድጋሚ ሲጠገን ለታሰበው አገልግሎት ሊውል አይችልም በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ማቀዝቀዣው የሚሰራ መሆኑ በባለሙያ የተረጋገጠ ሲሆን የባለሙያዎች አስተያየት ማቀዝቀዣው እስከመቼ እንደሚሰራ ባይረጋግጥም አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለው ውል እቃው ቢበላሽ ጥገና ማድረግ መሆኑ ያልተካደ ጉዳይ ነው፤ስለሆነም አመልካች ለድብቅ ጉድለት ኃላፊነት አለበት ተብሎ ክስ ባልቀረበበትና በህጉ አግባብ የተቋቋመው ውል ደግሞ አድማሱ ለአንድ አመት ያህል አመልካች በነፃ የመጠገን ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የሚገልጽ ሁኖ እያለ ከግራ ቀኙ የውል ስምምነት እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2300 ድንጋጌ ይዘት ውጪ አመልካች ማቀዝቀዣውን እንዲቀየር ወይም የሽያጭ ገንዘቡን እንዲመልስ ተብሎ የተወሰነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731፣2298 እና 2300 ድንጋጌዎችን የጣሰ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የግራ ቀኙን ስምምነት እና በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡትን ነጥቦችን ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14450 መጋቢት 05 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 160863 ነሐሴ 28 ቀን 2005 ዓ/ም ፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 174255 ህዳር 03 ቀን 2006 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.58788 ሰኔ 15 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. አመልካች በውሉ በገባው ግዴታ መሰረት ማቀዝቀዣውን ጠግኖ አግልግሎት እንዲሰጥ ከማድረግ ውጪ ማቀዝቀዣውን የመቀየር ወይም የሽያጭ ገንዘቡን የመመለስ ግዴታ የለበትም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102711

ህዳር 10 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ፋንታዬ ፍሰሐ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ደጀኔ ማርዬ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በግለሰቦች መካከል በተደረገ የብድር ገንዘብ ውልን መሰረት አድርጐ የቀረበውን የቤት ልረከብ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ ከአሁኑ አመልካች ጋር ጥር 15 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት የብድር ውል በወር አምስት በመቶ ወለድ ሂሳብ የሚታሰብ ሁኖ ብር 8000.00 (ስምንት ሺህ ብር) ለአሁኑ አመልካች እንደአበደሯቸው፣ የብድሩ መመለሻ ጊዜም ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም መሆኑን፣ በዚህ ጊዜ አመልካች የብድር ገንዘቡን ካልመለሱ በላስታ ወረዳ ላሊበላ ከተማ 01 ቀበሌ ልዩ ስሙ ሸብጽ ከተባለው ቦታ የሚገኘውንና በ200 ካ/ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ላይ የሰፈረውን ቆርቆሮ ቤትና ባህርዛፍ ተክል አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቧቸው መስማማታቸውን በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብና ወለድ ስሌት መሰረት በድምሩ ብር 9600.00 (ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ብር) አመልካች ያለመመለሳቸውን ዘርዝረው አመልካች በውሉ መሰረት ንብረቱን እንዲያስረክቧቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ፍርድ ቤት ቀርቦ በሰጡት መልስም ከተጠሪ ጋር ለክሱ መሰረት የሆነውን ውል ማድረጋቸውን በማመን ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ውሉን አምነዋል በማለትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ አመልካች ለክሱ መሰረት የሆነውን ቆርቆሮ ቤትና ባህርዛፍ ተክል ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የወሰነ ሲሆን በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ያጡ ሲሆን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የለም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ከአመልካች ጋር በተደረገው ውል የገንዘብ ብድሩ የተደረገ መሆኑን ሳይክዱ የመያዣውን ንብረት በተመለከተ ግን የባህርዛፍ ተክል ብቻ መያዣ አድርገው የተስማሙ ሁኖ እያለ ተጠሪ የአመልካችን መሃይምነት በመጠቀም የአመልካች መኖሪያ ቤት ለመያዣነት እንደተሰጠ አድርገው በውሉ ላይ አስፍረው መገኘታቸውንና ለብር 9600.00 የብድር ገንዘብ ግምቱ ከብር 150.000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) በላይ የሆነውን መኖሪያ ቤታቸውን እንዲያስረክቡ መወሰኑ ጉዳዩ በአግባቡ ባልተጠራበትና ሕጉን መሰረት ሳያደርግ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲታረምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበውም የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ያለመቅረቡን፣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክሱን ሳይክዱ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የንብረቱን ግምትና የመያዣውን አይነት መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክርክር ሥነ-ሥርዓቱን መሰረት አድርጐ ያልቀረበ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የለበትም ተብሎ ሊጸና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ችሎት እልባት ሊያገኙ የሚገባቸው ጭብጦች፡-

1. የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ የቀረበ ነው ወይስ አይደለም?
2. አመልካች ለተጠሪ ቤቱንና የባህር ዛፍ ተክል ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም የሚሉት ናቸው፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- አንድ የመጨረሻ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት በአዋጅ ቁጥር 25/1998 አንቀጽ 22(4) ባተመለከተው አግባብ በዘጠና ቀናት ውስጥ መሆኑን ሕጉ ያሳያል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት የመጨረሻ ፍርድ በመ/ቁጥር 03-08770 ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ/ም መሰጠቱን የሚያሳይ የትዕዛዝ ግልባጭ አያይዘው ያቀረቡ ሲሆን ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ደግሞ ሐምሌ 03 ቀን 2006 ዓ.ም ነው፡፡ ይህም የሰበር አቤቱታው በሕጉ የተመለከተው የዘጠና ቀናት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የቀረበ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 28950 መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ነው ውሳኔ የሰጠው በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ለመቃወም ያቀረቡት ምክንያት የክርክሩን ሂደት ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ከተጠሪ ገንዘብ ሲበደሩ ለገንዘቡም አመላለስ አመልካች ያላቸውን ቤትና ባህርዛፍ በመያዣ ለተጠሪ መስጠታቸውን ነው፡፡ ሆኖም መያዣ ውሉ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ አለመመዝገቡን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማናቸውም ዓይነት ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆን ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይነቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ ርስት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር በማንኛውንም ዓይነት ውጤት እንደማያስገኝ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3052 ስር በማያሻማ ሁኔታ ተደንግጐ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ህጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግልጽ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚመሰረተው መያዣ መመዝገብ እንዳለበት የደነገገውን አለመከተል የመያዣው አመሰራረት ጉድለት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በመያዣ ውሉም አመልካች የተበደሩትን ገንዘብ እስከ ጥር 14 ቀን 2001 ዓ/ም ባይመልሱ ተጠሪ በመያዣነት የያዙትን ቤትና ባህርዛፍ እንደሚረከቡ በግልጽ ተዋውለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ውሉ በህጉ አግባብ የተደረገ ሆኖ አላገኘንም፡፡ ምክንያቱም በፍ/ህ/ቁ 3060/1/ በተደነገገው መሰረት ዕዳው እንዲከፈል በተወሰነበት ጊዜ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው የመያዣ መብት ያገኘበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይወስዳል በሚል የተደረገ ውል ፈራሽ ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አይነተኛ አላማ ሰዎች ለጊዜው የገጠማቸውን የገንዘብ ወይም ኢኮኖሚያዊ ችግር ለማቃለል ሲሉ ተገቢውን መደራደር አድርገውና ነፃ የመዋዋል መብታቸውን ተጠቅመው ወደ ግዴታው በነፃ ፍላጎታቸው ይገባሉ ተብሎ ስለማይታሰብ በዚህ ሁኔታ ውሉ ተፈጽሞ ሲገኝ ሕጉ ለስምምነቱ ጥበቃ ባለማድረግ የተዋዋይ ወገኖችን የንብረት መብት ለመጠበቅ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ በማየት የተጠሪን የአመልካች ቤትና ባህር ዛፍ ልረከብ ጥያቄን ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች አምነዋል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ቀጥሎ መታየት ያለበት የህግ ነጥብ ተጠሪ ያላቸው መፍትሔ ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የገንዘብ ብድር ውል መደረጉ የተካደ ፍሬ ነገር አይደለም ፡፡ አመልካች ከተጠሪ ብር 8000,00 (ስምንት ሺህ) ተበድረው ወስደው በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ አልመለሱም፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731፣በፍ/ብ/ህ/ቁ.2471 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት አመልካች ለተጠሪ የተበደሩትን ገንዘብ መመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡አመልካች ይህንኑ ገንዘብ መመለስ ያለባቸው ከምን ያህል ወለድ ጋር ነው የሚለውን ስንመለከትም ወለድን በተመለከተ ገዥው መርህ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2478 የተቀመጠው ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌው ተበዳሪው ወለድ እንዲከፍል የውሉ ቃል ካልሆነ በቀር ለተበዳሪው ወለድ መክፈል የለበትም ተብሎ አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ወለድ የሚከፈለው በውሉ ወለድ ይከፈላል የሚል ቃል ሲኖር መሆኑን ድንጋጌው ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ተዋዋዬች በወለድ የሚከፈለውን ገንዘብ በዓመት ከመቶ አስራ ሁለት በላይ እንዲሆን ለመዋዋል እንደማይችሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2479(1) ድንጋጌ በጎይለ ቃል አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም ተዋዋይ ወገኖች በገንዘብ ብድር ወለድን ገልጸው መስማማት እንደሚችሉና መጠኑ ግን በአመት ከመቶ አስራ ሁለት በላይ ሊሆን አይችሉም፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት የውል ስምምነት ወለድ ለመክፈል ስምምነት የተደረገ ቢሆኑም የወለዱ መጠን ግን በወር ከመቶ አምስት ሁኖ የሚታሰበውም በወር መሆኑን በግልጽ ስምምነቱ እንደሚያሳይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ህጉ ለብድር ገንዘብ ሊከፈል የሚችል የወለድ መጠን በአመት ከመቶ አስራ ሁለት ነው በማለት ከደነገገው ጣሪያ በላይ ስምምነት መደረጉን ነው፡፡ ህጉ ወለድ በአመት ጊዜ እንዲታሰብ እንጂ በወር ጊዜ እንዲታሰብ አልፈቀደም፡፡ ስለሆነም አመልካች በወር አምስት ከመቶ ወለድ እየከፈሉ የብድር ገንዘቡን ለመመለስ ያደረጉት ስምምነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711 እና 2479(1) ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይም አመልካች ለተጠሪም በወር አምስት በመቶ እየታሰበ እንዲከፍሉ የሚገደዱበት የህግ አግባብ አላገኘንም ፡፡ ሆኖም አመልካች የብድር ገንዘቡን በጊዜ ገደቡ ያልመለሱ በመሆኑ በአመት የሚታሰበው ህጋዊ ወለድን (9%) ለተጠሪ የማይከፈሉበትን አግባብ ግን አላገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍርድ ቤቶች የመያዣ ውሉ ህጋዊ አድርገው በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ስላገኘን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00256 በ10/07/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ፣ የሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12151 ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-08770 ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች እና ተጠሪ የመሰረቱት የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ ውል ሕጋዊ ስላልሆነ ተጠሪ ቤትና ባህርዛፍ ሊረከቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው ዋናውን የብድር ገንዘብ ብር 8000.00 (ስምንት ሺህ) ገንዘብ መመለስ ከነበረበት ከጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ (9%) ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 107990

መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተሾሊት ይመሰል

አመልካች፡- እማሆይ ወ/ገብርኤል የቀረቡ የለም (ተወካይ)

ተጠሪ፡- ደረጀ ደሳለኝ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ በጉራጌ ዞን አቤሸጌ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ በ1997 ዓ/ም የባለቤቴ ልጅ ባል የሆነው ቁስ ሀይሉም ተስፋዬ ይዞታዬን ወሮ ይዞብኝ ተጠሪ ረዳት መስሎ ቀርቦኝ ቦታውን በትክክል በማላውቀው ቦታ ወስዶኝ ልጄ ነው ብለሽ ፈርሚልኝ ብሎ ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ በመሬቴ ላይ ያመረተውን ድርሻዬንና 1.65 ሄክታር ይዞታየን ነጥቆኛል በመሆኑም ይመልስልኝ በማለት ጠየቁ፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ አመልካች በ23/07/98 ዓ/ም በተደረገ የስጦታ ውል በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2443(1) እና በ881 መሠረት የተፈጸመ ስጦታ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን ያየው የወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን በማከራከር አመልካች የስጦታ ውሉ አልተመዘገበም በማለት ያቀረቡት ክርክር ውድቅ ነው፤ መሬቱን ወደውና ፈቅደው በስጦታ ውል ሰጡ እንጂ በማታለል መሆኑ አልተረጋገጠም፣ ስለዚህ ተጠሪ መሬቱን ሊለቁ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በመቀጠልም ጉዳዩን ያየው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ30/8/98 ለጉራጌ ዞን ፍትህ መምሪያ የቀረበው የስጦታ ውል እና የቀበሌ መስተዳደር የተጻጻፉት ደብደቤዎች ውሉ መመዝገቡን የሚይሳይ ካለመሆኑም በላይ በቀላጤ የሰው ንብረት ማስተላለፍ ስለማይቻል የስር ፍርድ ቤት አመልካች ወደውና ፈቅደው የሰጡት የስጦታ ውል ነው፤ በመሆኑም መሬቱን ተጠሪ ሊለቁ አይገባም በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የስጦታ ወሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2443 እና 881"ን" የተከተለ ባለመሆኑ ተንኮል ያለበት በመሆኑ ተጠሪ ሊለቁ ይገባል፤ የኪራይ ግምትም በአካባቢው ባህል መሠረት ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በመጨረሻም ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በመመርመር፤ በ23/7/98 የተደረገው የስጦታ ውል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 እና 2443 ተከትሎ የተከናወነ፤ እንከን የማይወጣለት፣ የመመዝገብ ግዴታ የማይጥል በመሆኑ ተጠሪ ከ1998 ጀምሮ በስጦታው መሰረት ወደስመ አዙሮ በጉልበቱ አለስልሶ፤ የሚጠቀምበትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይዞታ ግዴታህን አልተወጣህም ባልተባለበት ይልቀቅ መባሉ እንደማፈናቀል የሚቆጠር በመሆኑ ሊለቁ አይገባም በማለት የከፍተኛውን ውሳኔ በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎትም ቅሬታውን ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡

የአመልካችም አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልጹ፡- የስር ፍርድ ከጠየቅኩት ዳኝነት ውጭ ጭብጥ በመያዝ በወረራ ተያዘብኝ ያልኩትን ይዞታ፤በስጦታ አስታኮ መወሰናቸው፤ እንዲጦረኝ ሰጥቸው ሲጦረኝ ቆይቶ አታሎኝ ስጦታ አስፈረመኝ እያልኩ ከዚህ ጭብጥ ወጥቶ መወሰኑ እና ለረጅም አመታት ሲጠቀምበት የነበረውን ይዞታዬን እንዲነጠቅ መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡ በዚህም መሰረት ችሎቱም አከራካሪውን መሬት ባለይዞታው ማነው? የሚለውን ለማስረዳት የቀረበው የስጦታ ውል በማስረጃነት ያለውን ተቀባይነት ለመመርመር በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙ በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክሯል፡፡

ተጠሪም በሰበር መልሳቸው አመልካች የተገኘውን ምርት አላካፍል አለኝ አሉ እንጂ ስጦታ መስጠታቸውን አልካዱም፤ የቀበሌው አመራሮች ባሉበት በሰነዱ ላይ ወደው ፈቅደው ሰጥቶኛል፤ ግዴታህን አልተወጣህም ከተባልኩ እንድወጣ ማድረግ እንጅ ውሉን የማያፈርሰው ነው፡፡ በመሆኑም የወረዳውና የጠቅላይ ፍርድ ቤት፤ የይግባኝ ሰሚውና የሰበሩ ውሳኔዎች ሊጸና ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ከተጠሪ ጋር ዝምድና የሌላቸውና በቤተክርስቲያን ቀርበን አብረን ለመጠቀም ነበር የተስማማነው፤ የስጦታ ውሉ የማላውቀውና በተንኮል የተገኘነው፤ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀፅ 8/5,6 መሰረት ለቤተሰብ፤ ወይም ለወራሽ ካልሆነ በቀር ማስተላለፍ ስለማይቻል ሊሻር ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰው ሲመስል፡- እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አንፃር መዝገቡን መርመረናል፡፡

በመሆኑም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር የግራ ቀኙን ክርክር የተሰጠውን ዳኝነት እንዳየነው፤ የአመልካች ጥያቄ የነበረው ከሟች ባለቤታቸው የተላለፈላቸው የእርሻ መሬት ወሮ ይዞብኛል፤ በማላቀው ሰነድ አታሎም አስፈረመኝ ድርሻየን እና ምርቱን ያካፍለኝ በማለት በመጠየቃቸው ምክንያት መሆኑን ከተያዘው ክርክር የምንገነዘበው ሲሆን ተጠሪም፤ ይዞታውን አመልካች በ23/7/98 በተደረገ የስጦታ ውል መያዙን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡ እንግዲህ አመልካች እንዲመለስላቸው የሚጠይቁት 1.65 ሄ/ር ቦታን አስመልክቶ ይህ ተጠሪ ረዳት በመምሰልና ባልታወቀ ቦታ ወስዶአቸው አብረን እንበላለን ልጄ ነው ብለሽ ፈርሚ ብሎኝ ነው የፈረምኩት በማለት አሁን ተጠሪ የሚያቀርቡትን የስጦታ ሰነድ እየተቃወሙት ያሉት፤ በተጨማሪም ሲረዳኝ ቆይቶ አቅመ ደካማ መሆኔን አይቶ እርዳታውን በማቆሙ ረዳት አጥቼ ወደ ቤተክርስቲያን በመግባት በመጠለል እገኛለሁ በማለት ገልጸው በሰው ምስክርም አስረድቷል፡፡ ተጠሪ የሚለው አመራሮች ባሉበት ፈቅደው ሰጥተውኛል፤ ግዴታህን አልተወጣህም የሚባል ከሆነ ግዴታዬን ከመወጣት በቀር በፍ/ህ/ቁ 2442 መሰረት በይርጋ ይቀራል፣ ሊጠይቁኝ አይችሉም በስሜ አዙሬ እየተጠቀምኩበት ነው የሚል መከራከሪያ ነው የሚያቀርበው፤ ይሁን እንጂ ይህ የአመልካች ክርክር የሚያሳየው የተጠቀሰው ይዞታ በእጁ መሆኑን እና ከመሰረቱ የመጦር ግዴታ የለብኝም ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከአመልካች እድሜና አቅመደካማነትን፤ በአሁኑ ጊዜ ያለረዳት በረሀብ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳሉ ከተገለፀው ፍሬ ነገር አንፃር ስንመለከተው ተለማኝነት የለውም፤ ላለመጦር ይዞታቸውን ይለቃሉ ተብሎም አይገመትም፤ ሌላው፤ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2458/1/ ድንጋጌም እንደምንረዳው፤ በግልፅ የሰፈረ የዉል ቃል ባይኖርም ስጦታው ሰጪ በድህነት ላይ ወድቆ ሲገኝ፤ የመጦር ግዴታም እንደለበት ተደንግጎል፤ ይሁን እንጂ ተጠሪ ከዚህም አልፎ ይዞታውን ይዘው እንኳንስ መጦር በውለታ ቢስነት ይዞታውን ስመሃብቱን ወደስማቸው ያዞሩት መሆኑን ክርክሩ የምንረዳው ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ያለመጦራቸውን ባረጋገጡበት ጊዜ ይዞታቸውን ማስመለስና ስጦታውንም እንዲሻር የመጠየቅ መብቱን ሊነፈጉ አይችሉም የፍ.ብ.ህ.ቁ. 2464(1) ይህንኑ ያመላክታል አመልካች ከይዞታቸው ያለመፈናቀል ሕገመንግስታዊ መብትም አላቸው፡፡ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ ሃዋሳ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚውና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አከራካሪውን ይዞታ ተጠሪ በስጦታ ያገኙትና ጉልበታቸውን አፍሰው አለስልሶ ወደስማቸው አዙሮ እየተጠቀሙበት በመሆኑ በስጦታ ያገኙትን ይዞታ ሊለቁ አይገባም ሊፈናቀሉ አይገባም በማለት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ማጽናታቸው ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡

ባጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚውና የሰበር ሰሚው ችሎት ተጠሪው አከራካሪውን ይዞታ ሊለቁ አይገባም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የደ.ብ.ብ.ህ.ክ.መ. የአበሸጌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 06347 በቀን 15/05/06 የሰጠው የጉ/ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 08153 በቀን 28/06/06 የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ በመ.ቁ. 03248 በቀን 09/10/06 የስር ውሳኔን በመሻር የሰጠውና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 03727 በቀን 10/3/07 ቅሬታውን ባለመቀበል የሰጡት ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የጉ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08153 በቀን 28/06/06 የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ በስጦታ ውል ያገኩት የሚሉትን ይዞታ ለአመልካች ሊለቁ ይገባል ብለናል፡፡
4. የግራ ቀኙ የወጪ ኪሳራቸውን የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.95440

ሰኔ 4 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ሰሚር ኢብራሂም ሂቡ ጉዳይ ተከታታይ ነኝ በማለት አቶ ኢብራሂም ሂቡ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐ/ሕግ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን ሁለት የወንጀል ክሶች የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠባቸው እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በውሳኔ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸው ሁለት ክሶች ይዘት ባጭሩ፡- አመልካች የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ለመስጠት አስቦ በአንደኛ ክስ በ28/09/2005 ዓ.ምእና በሁለተኛ ክስ በ30/09/2005 ዓ.ምበየክሶቹ ላይ በተመለከተው ጊዜ እና ቦታ የግል ተበዳይ ለሆኑት አቶ አሩቅ መሐላ አባድር ቁጥሮቻቸው በየክሶቹ ላይ የተመለከቱትን በአጠቃላይ ብር 520,000 የያዙ ከሕብረት ባንክ የሚመነዘሩ ሁለት ቼኮችን በመስጠቱ እና ሁለቱም ቼኮች እንደቅደም ተከተላቸው በ06/10/2005 ዓ.ም.እና በ05/10/2005 ዓ.ም. ለክፍያ ለባንኩ ሲቀርቡ በቂ ስንቅ የላቸውም ተብሎ ክፍያ ሳይፈጸምባቸው በመቅረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 693(1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ የመስጠት ወንጀል አድርጓል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቀው በሁለቱም ክሶች የተመለከተውን ወንጀል ማድረጋቸውን ሙሉ በሙሉ ማመናቸው በመረጋገጡ ፍ/ቤቱ ማስረጃ መስማት ሳያስፈልግ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ.134 (1) መሰረት ላይ በሁለቱም ክሶች የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኃላ ለሁለቱም ክሶች በመመሪያው መሰረት የተሰላው መነሻ ቅጣት 11 ዓመት ጽኑ እስራት እና የብር 16,000 መቀጮ መሆኑን፣ ይህ የእስራት ቅጣት እና የመቀጮ መጠን በአባሪ አንድ እና ሁለት እንደቅደም ተከተሉ በእርከን 29 እና 7 ላይ የሚወድቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን፣ ወንጀሎቹ ተደራራቢ በመሆናቸው ምክንያት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 85 መሰረት እርከኑ በአንድ ማክበጃ ምክንያት ወደ 30 ከፍ የሚል መሆኑን፣ በሌላ በኩል አመልካች የቀረበባቸው ሪከርድ አለመኖሩ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው እና በችሎት ቀርበው ክሶቹን ማመናቸው በሶስት የማቅለያ ምክንያትነት ሲወሰዱ እርከኑን ከ30 ወደ 24 ዝቅ የሚያደርጉ መሆኑን፣ በአባሪ አንድ እርከን 24 ስር የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን ከ6 ዓመት ከ6 ወር እስከ 7 ዓመት ከ8 ወር መሆኑን እና በአባሪ ሁለት በእርከን 2 የተመለከተው የመቀጮ መጠንም እስከ ብር 2000 መሆኑን በመግለጽ በመጨረሻ አመልካች በስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እና በብር 700(ሰባት መቶ) መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች የተከሰሱበትን ወንጀል አምነው የግል ተበዳይን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ መመለሳቸው፣ የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበባቸው መሆኑን እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸውን የስር ፍ/ቤቶች በማቅለያ ምክንያትነት መያዛቸውን በገለጹበት ሁኔታ በአመልካቹ ላይ የጣሉት የቅጣት መጠን ተመዛዛኝ መሆን አለመሆኑን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች የቀረቡባቸውን ሁለት የወንጀል ክሶች ሙሉ በሙሉ በማመናቸው የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠባቸው በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 134(1) መሰረት በሰጡት የእምነት ቃል መሰረት ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠበት የተከሰሰበትን ወንጀል ሙሉ በሙሉ በማመኑ በሆነ ጊዜ ስለቅጣቱ ልክ ወይም ስለቅጣቱ ሕጋዊነት ካልሆነ በስተቀር በጥፋኝነት ውሳኔው ላይ ይግባኝ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.185(1) ተደንግጋል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች የተከሰሰኩባቸውን ወንጀሎች በተመለከተ ክሱን በሰማው ፍ/ቤት የእምነት ቃል አልሰጠሁም ወይም ያስመዘገብኩት ቃል በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.134(1) መሰረት የእምነት ቃልን የሚያቋቁም አይደለም በማለት በሰበር አቤቱታቸው ላይ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ለሰበር ክርክሩ በጭብጥነት የተያዘውም የቅጣት ውሳኔው አግባብነት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሊሻርልኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ ከወጣላቸው ውስጥ የሚካተት ሲሆን የፌ/ከ/ፍ/ቤት ቅጣቱን የወሰነው በቼኮቹ ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን አንጻር በሁለቱም ክሶች የተመለከቱት ወንጀሎች በደረጃ 7 የሚወድቁ ሆኖ የእስራት ቅጣቱ እና መቀጮው እንደቅደም ተከተላቸው በአባሪ አንድ በእርከን 22 እና በአባሪ ሁለት በእርከን 6 ስር የሚወድቁ መሆኑን በመግለጽ፣ አንድ የማክበጃ ምክንያት እና ሶስት የማቅለያ ምክንያቶችን ተቀብሎ ቅጣቱን በመመሪያው መሰረት በማስላት መሆኑን የመዘገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ፍ/ቤቱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 "ን" መሰረት በማድረግ የተከተለው ይህ የቅጣት አወሳሰን ስርዓት በመሰረቱ ተገቢ ቢሆንም በሌላ በኩል ግን አሁን በስራ ላይ ያለው የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ከወንጀል ደረጃው አመዳደብ አንፃር በቅጣት አወሳሰኑ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ መኖር አለመኖሩ እና ካለም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው የትኛው መመሪያ እንደሆነ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሰረቱ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎቹን ያወጣው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 88(4) ድንጋጌ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በመሆኑ ምክንያት መመሪያዎቹ እንደ ሕግ የሚቆጠሩ ናቸው። አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸውን ወንጀሎች ያደረጉት መመሪያ ቁጥር 1/2002 ስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሲሆን ይህ መመሪያ ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም.ጀምሮ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ተተክቷል። በሌላ በኩል አዲሱ የወንጀል ህግ እንዲጸና ከተደረገ በኃላ አድራጊው ህጉ ከመጽናቱ በፊት ላደረገው ወንጀል ሲፈረድበት ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው ሕግ ይልቅ አዲሱ ሕግ ቅጣትን የሚያቃልልለት ሲሆን ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተመለከተው ቅጣት ስለመሆኑ በወንጀለኛ ሕግ አንቀጽ 6 ተደንግጎ ይገኛል። በመሆኑም የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ከቀድሞው መመሪያ ይልቅ ለአመልካቹ የሚጠቅም መሆኑ ከተረጋገጠ በወ/ሕ/ አንቀጽ 6 የተመለከተው ድንጋጌ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው መደረግ ይኖርበታል።

ለአመልካቹ ቅጣቱን የሚያቀለው የትኛው መመሪያ ነው? የሚለውን ነጥብ በተመለከተ ለ1ኛ ክስ ምክንያት በሆነው ቼክ ላይ የተመለከተው የገንዘብ መጠን ብር 120,000 በቀድሞው መመሪያ መሰረት በደረጃ 7 ስር ይሸፈን የነበረ ሲሆን በአዲሱ መመሪያ ግን በደረጃ 6 ስር እንዲሸፈን የተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ በፍቅድ ስልጣን አወሳሰን ረገድም አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቃልልለት በመሆኑ ለቅጣት አወሳሰኑ መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሆኑን ተገንዝበናል። በዚሁ በአዲሱ መመሪያ መሰረት በ1ኛ ክስ ስር የተመለከተው ወንጀል በደረጃ 6 ስር የሚወድቅ ሆኖ የእስራት ቅጣቱ እና መቀጮው እንደቅደም ተከተሉ በአባሪ አንድ በእርከን 15 እና በአባሪ ሁለት በእርከን 4 ስር የሚሸፈን መሆኑን፣በ2ኛ ክስ ስር የተመለከተው ወንጀል በደረጃ 7 ስር የሚወድቅ ሆኖ የእስራት ቅጣቱ እና መቀጮው እንደቅደም ተከተሉ በአባሪ አንድ በእርከን 17 እና በአባሪ ሁለት በእርከን 5 ስር የሚሸፈን መሆኑን፣ በአባሪ አንድ በእርከን 15 እና በአባሪ አንድ በእርከን 17 ስር ከተመለከተው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ አነስተኛው የቅጣት መጠን ተወስዶ ሲደመር በሁለቱ ወንጀሎች የሚጣለው መነሻ ቅጣት 6 ዓመት መሆኑን፣ ይህ የቅጣት መጠንም በአባሪ አንድ በእርከን 21 ስር የሚወድቅ መሆኑን፣ ይህ እርከን በስር ፍ/ቤት ተቀባይነት ባገኙት አንድ የማክበጃ እና ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች ሲሰላ ወደ እርከን 19 ዝቅ የሚል መሆኑን መሰረት በማድረግ ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው የቅጣት መጠን በአባሪ አንድ በእርከን 19 ፍቅድ ስልጣን ስር የተመለከተው የቅጣት መጠን መሆኑን ተገንዝበናል።

ሲጠቃለል በሁለቱም ክሶች በተመለከቱት ወንጀሎች በፌ/ከ/ፍ/ቤት ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፌ/ጠ/ፍ/ቤት በውሳኔ የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ እና በቅጣት ውሳኔው ላይ ግን ከላይ በተገለጸው ምክንያት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 136445 በ13/10/2005 ዓ.ም. እና በ25/10/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 92629 በ20/01/2006 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በወ.መ.ሕ.ስ.ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተ.ቁ.1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በአመልካቹ ላይ በሁለቱም ክሶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በአመልካቹ ላይ በሁለቱም ክሶችበድምሩ ተጥሎ የነበረውን የስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካቹ በዚህ ጉዳይ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሆኖ በአራት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
4. ይህንኑ ተገንዝቦ በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም አመልካቹ ለሚገኙበት የአዲስ አበባ ማረሚያ ተቋም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክ፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት እና በማረሚያ ቤት በኩል ለአመልካቹ ይላክ፡፡
6. በፌ/ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው የብር 700(ሰባት መቶ) የመቀጮ ውሳኔ አልተነካም፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96607

መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ተክሊት ይመሰል

አመልካቾች፡- 1ኛ.አቶ ኤርሚያስ ካጢሶ
2ኛ. አቶ ዮሐንስ ላምቤቦ } ጠበቃ ፀጋዬ አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የከምባታ ጠምባሮ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ዋና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ገቢን አሳንሶ የማስታወቅ ወንጀል መፈጸማቸው በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠብን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካቾቹ ላይ በ08/8/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበው ክስ ተከሳሾቹ በከምባታ ጠምባሮ ዞን በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ጊዜ ደበኦ በተባለ ቀበሌ አሸዋ እና ድንጋይ ለማምረት ከመንግስት ጋር ውል አድርገው ስራውን እያከናወኑ በነበረበት ከ2004 ዓ.ም እስከ ህዳር ወር 2005 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ትክክለኛ የገቢ ግብር ላለመክፈል ሆን ብለው በማሰብ በኤንትሬ ገልባጭ መኪና በቢያጆ ከብር 300 እስከ ብር 360 ይሸጡ የነበረውን ነጭ ድንጋይ ከብር 40 እስከ ብር 100 የሸጡ አስመስለው፣እንዲሁም በፊያት ገልባጭ መኪና በቢያጆ ከብር 140 እስከ ብር 250 ይሸጡ የነበረውን ነጭ ድንጋይ ከብር 30 እስከ ብር 60 የሸጡ አስመስለው በመመዝገብ እና ገቢያቸውን በማሳነስ የመንግስትን እና የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ አድራጎት የፈጸሙ በመሆኑ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 በአንቀጽ 97 የተደነገገውን በመተላለፍ ግብር አሳንሶ የማስታወቅ ወንጀል አድርገዋል በማለት ክስ የመሰረተ ሲሆን ተከሳሾቹ ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለታቸው ተጠሪ ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ ሰነዶችን በማስረጃነት አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም የተጠሪን የሰው እና የጽሁፍ ማስረጃ መርምሮ በአመልካቾቹ ላይ በክሱ መሰረት ያስረዳ መሆኑን በመግለጽ ተከሳሾቹ መከላከያቸውን እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ ከሰጠ እና የተከሳሾቹን የሰው እና የጽሁፍ መከላከያ ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር በመመርመር ዐቃቤ ሕግ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ያስረዳባቸውን ፍሬ ነገር ተከሳሾቹ በመከላከያቸው ያላስተባበሉ መሆኑን ገልጾ በክሱ በተመለከተው ድንጋጌ ስር በሁሉቱም ተከሳሾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በመቀጠልም የግራ ቀኙን የቅጣት አወሳሰን ክርክር ከሰማ በኃላ የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት መሆኑን በመግለጽ፣ተከሳሾቹ ወንጀሉን የፈጸሙት ማስጠንቀቂያ እየተሰጣቸው መሆኑን በማክበጃ ምክንያትነት በመያዝ እና የቀረበባቸው የቀድሞ የወንጀል ሪከርድ አለመኖሩን ደግሞ በማቅለያ ምክንያትነት በመያዝ እንዲሁም የቤተሰብ ኃላፊዎች መሆናቸው በቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት እንዲያዝላቸው ተከሳሾቹ ያቀረቡትን ጥያቄ ባለመቀበል እያንዳንዳቸው በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሳሾቹ በተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት፤ዐቃቤ ሕግ ደግሞ በተሰጠባቸው የቅጣት ውሳኔ መጠን ቅር በመሰኘት ሁለቱም ወገኖች ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከሳሾቹን ቅሬታ መሰረት አድርጎ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ያቀረበው በተሻረ ሕግ መሆኑን እና ተከሳሾቹ ለነጭ ድንጋይ የዋጋ ተመን ከወጣ በኃላ ከተመን በላይ ሽያጭ ስለማከናወናቸው ዐቃቤ ሕግ ያላስረዳባቸው መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔውን ሽሮ ተከሳሾቹን በነጻ በማሰናበት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በክሱ የተጠቀሰው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 በአዋጅ ቁጥር 136/2003 በከፊል የተሻሻለ ከመሆኑ ውጪ ሙሉ በሙሉ ያልተሻረ እና ለክሱ መሰረት የሆኑት ድንጋጌዎችም በማሻሻያ አዋጁ ያልተነኩ ሆኖ እያለ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ክሱ የቀረበው በተሻረ ሕግ መሆኑን መግለጹ ተገቢነት የሌለው መሆኑን እና የተመን ጉዳይም በክርክሩ ሂደት በግራ ቀኙ ምስክሮች እግረ መንገድ የተነገረ ከመሆኑ ውጪ ለክሱም ሆነ ለወንጀሉ የማቋቋሚያ ምክንያት ባልተደረገበት ሁኔታ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተመንን ጉዳይም በምክንያትነት የጠቀሰው አላግባብ መሆኑን ገልጾ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር እና የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካቾቹ ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ የተሰረዘ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾቹ ላይ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ አንሷል የሚለውን ቅሬታ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በማድረሱ ሰበር ችሎቱ በዚህ ረገድ በሌላ መዝገብ በቀረበለት አቤቱታ ሳቢያ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነውን የቅጣት መጠን ከፍ በማድረግ ተከሳሾቹ እያንዳንዳቸው በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ተሻሽሎ እና ከፍ ተደርጎ የተሰጠባቸውን የቅጣት ውሳኔ ጨምሮ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ገቢያችንን አሳንሰን ያሳወቅንበት የግብር መጠን በገቢ ማስታወቂው ላይ በሌለበት ሁኔታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 በአንቀጽ 97 ስር ጥፋተኛ መባላችን የሕግ ስህተት ነው በማለት አመልካቾቹ ያቀረቡትን ቅሬታ ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቾቹ ሲጠየቁ ወንጀሉን አላደረግንም በማለታቸው ተጠሪ አቅርቦ ያሰማቸው የውሃና ማዕድን ሀብት ጥናት የስራ ሂደት አስተባባሪ መሆናቸውን የገለጹት 1ኛ ምስክር እና የድንጋይ ግኝ ከአመልካቾቹ ሲፈጽሙ እንደነበረ የገለጹት 2ኛ ምስክር አመልካቾቹ በሽያጭ ደረሰኞች ላይ የሚጽፉት ዋጋ ድንጋዩን ከሚሸጡበት ዋጋ እጅግ ዝቅ ያለ መሆኑን፣ ግብር ይከፍሉ የነበረውም በደረሰኙ ላይ በተመለከተው መሰረት ከሽያጩ ዋጋ 3% መሆኑን፣ በደረሰኞቹ ላይ የሽያጩን ትክክለኛ ዋጋ እንዲሞሉ በተደጋጋሚ ሲነገራቸው የቆየ ቢሆንም ፈቃደኞች ሳይሆኑ መቅረታቸውን፣በኃላ ግን በተደረገ አጠቃላይ ውይይት ድንጋዩን የሚሸጡበት ተመን ወጥቶ ተግባራዊ መደረጉን፣ተመን ከወጣ በኃላ የተከሰተ ችግር ስለመኖሩ የቀረበ ሪፖርት አለመኖሩን እና መሰል ፍሬ ነገሮችን በመግለጽ በተመሳሳይ ሁኔታ የመሰከሩ መሆኑን እና ተጠሪ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎችም የሽያጭ ደረሰኞችን ጨምሮ ይህንኑ ምስክርነት የሚያጠናክሩ መሆናቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካቾቹ እንዲከላከሉ በተሰጠው ብይን መሰረትም ድንጋዩን ለማምረት እና ለማስጫን ይወጣ የነበረውን ወጪ በአዋጁ አንቀጽ 20 በተመለከተው መሰረት ከአጠቃላይ የሽያጩ ገንዘቡ ላይ በመቀነስ በደረሰኙ ላይ ይጽፉ የነበረው የተጣራ ትርፋቸውን ወይም ገቢያቸውን ብቻ እንደነበረ ያውቁልናል በማለት እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ምስክሮችን ያሰሙ እና የተለያዩ ሰነዶችን በማስረጃነት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካቾቹ በተጠሪ ማስረጃ የተመለከረባቸውን የወንጀል ፍሬ ነገር በመከላከያቸው አላስተባበሉም በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ያስተላለፈባቸውም ሕጋዊ ወጪዎችን ተቀናሽ የማድረግ መብት ተግባራዊ የሚደረገው ገቢያቸውን በስርዓቱ መሰረት እያስታወቁ ግብር ለሚከፍሉ ነጋዴዎች እንጂ ገቢያቸውን አሳንሰው ለሚያስታውቁ ነጋዴዎች ጭምር አይደለም የሚል ነጥብ በዓቢይ ምክንያትነት በመያዝ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በመሰረቱ በአመልካቾቹ ላይ የቀረበው ክስ መሰረታዊ ይዘት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ አሳንሰው አስታውቀዋል የሚል ሲሆን"ግብር የሚከፈልበት ገቢ" ለሚለው ሐረግ ለክሱ በተጠቀሰው የክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 የተሰጠ ትርጉም የለም፡፡በሌላ በኩል በአዋጁ ውስጥ የተለየ ትርጉም በግልጽ ካልተሰጣቸው በስተቀር በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት በተተረጎሙበት ሕግ የተሰጣቸውን ትርጉም የሚይዙ ስለመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 2 መግቢያ ላይ የተመለከተ ሲሆን ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በአንቀጽ 2(11) ስር "ግብር የሚከፈልበት ገቢ" ማለት በአዋጁ እና በአዋጁ መሰረት በሚወጡ ደንቦች መሰረት ማናቸውም ወጪ እና ሌሎች ተቀናሽ ሂሳቦች ከተቀነሱ በኃላ የሚቀረው የገቢ መጠንስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት በእነዚህ የአዋጆቹ ድንጋጌዎች መሰረት ለምርት እና ለአገልግሎት ያወጣነውን ወጪ ከአጠቃላይ የሽያጭ ገንዘቡ ላይ ቀንሰን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ በደረሰኝ ላይ ከማስፈር ውጪ ግብር የሚከፈልበትን ገቢያችንን አሳንሰን አላስታወቅንም በማለት ነው፡፡ በሽያጩ ዋጋ እና አመልካቾቹ በሽያጭ ደረሰኞቹ ላይ በሚሞሉት የዋጋ መጠን መካከል ልዩነት መኖሩን ከማስረዳት ውጪ አመልካቾቹ ወጪዎቻችን ናቸው የሚሏቸውን የተለያዩ ሂሳቦች በመቀናነስ በደረሰኞቹ ላይ ይሞሉት የነበረው የገቢ መጠን ከእውነተኛው ገቢያቸው መጠን በታች ስለመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪው ባለበት የማስረዳት ግዴታ መሰረት በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያረጋግጥም፡፡

አመልካቾቹ መግለጽ ይገባቸው የነበረው ከተቀናሽ ወጪዎች በኃላ የሚገኘው እውነተኛው የገቢ እና በገቢው ላይ መከፈል ይገባው የነበረው የግብር መጠን ምን ያህል እንደነበረ በመወሰን ተጠሪው በአዋጁ በተሰጠው ስልጣን እና በተዘረጋው የግብር አጣጣል ስርዓት መሰረት በአመልካቾቹ ላይ የጣለው ግብር ስለመኖሩም የቀረበ ክርክር እና ማስረጃ የለም፡፡ተጠሪው በሕግ በተጣለበት የማስረዳት ግዴታ መሰረት እነዚህን መሰረታዊ የወንጀሉን ፍሬ ነገሮች ማስረዳቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ደግሞ አመልካቾቹ በተከሰሱበት እና ጥፋተኛ በተባሉበት የወንጀል ሕግ አነጋገር መሰረት ግብር አሳንሶ የማስታወቅ ወንጀል አድርገዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ ሕጋዊ መሰረት አለው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾቹ ለምርት እና ለአገልግሎት አውጥተናል የሚሏቸውን ወጪዎች የግብር አስገቢው መስሪያ ቤት በማያውቀው ሁኔታ በራሳቸው በመቀነስ በሽያጭ ደረሰኞቹ ላይ የተጣራ ነው የሚሉትን ገቢ ብቻ በመሙላት መፈጸማቸው የተረጋገጠው ድርጊት ራሱን ችሎ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ቀጥሎ መታየት እና ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጥያቄ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በዚህም መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ ግብር የሚከፈልበትን ከንግድ ስራ የሚገኝ ገቢ በሚመለከት በአዋጁ የተመለከቱት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ግብር ከፋዩ ወጪዎችን ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ለንግድ ስራው ገቢ ለማግኘት፣ለንግድ ስራው ዋስትና ለመስጠት እና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ የሚደረጉ ስለመሆኑ ከላይ በተጠቀሰው የክልሉ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ በአንቀጽ 20 ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ግብር የሚከፈልበት የንግድ ስራ ገቢ ተቀባይነት ያገኘውን የሂሳብ አያያዝ መርህ በመከተል የሚዘጋጀውን የትርፍና ኪሳራ ሂሳብ ወይም የገቢ መግለጫ ፣ አዋጁን እና የግብር ባለስልጣን የሚያወጣውን መመሪያ መሰረት በማድረግ በእያንዳንዱ የግብር ዘመን የሚወሰን ስለመሆኑ በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 18 ተመልክቷል፡፡

ከእነዚህ የአዋጁ ሁለት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻለውም ግብር ከፋዩ ለንግድ ስራው ገቢ ለማግኘት፣ለንግድ ስራው ዋስትና ለመስጠት እና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል ተደርገዋል የሚባሉት ወጪዎች ተቀናሽ የሚደረጉት በራሱ በግብር ከፋዩ ውሳኔ ሳይሆን ሕጋዊ ወጪዎቹ ናቸው የሚላቸውን ወጪዎች ጨምሮ አጠቃላይ የሂሳብ መግለጫውን ለባለስልጣኑ ካቀረበ እና የወጪዎቹ ሕጋዊነትና ተገቢነት በግብር ባለስልጣኑ ተረጋግጦ ተቀባይነት ካገኘ በኃላ ብቻ መሆኑን ነው፡፡አንድ ግብር ከፋይ ለግብር ባለስልጣኑ በሚያቀርበው መግለጫ ውስጥ መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች ያለበቂ ምክንያት ሳያካትት ያስቀረ በሆነ ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ድርጊት ራሱን ችሎ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 98(1)(ለ) ስር የተደነገገ ሲሆን ለወንጀሉ የሚጣለው ቅጣትም ሳይካተት በቀረው ነጥብ ምክንያት ሳይከፈል የቀረውን የግብር መጠን መሰረት በማድረግ በአንቀጽ 98(2) በፊደል(ሀ) እና (ለ) ስር በተለያየ መጠን ተደንግጎ ይገኛል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካቾቹ ሕጋዊ ናቸው የሚሏቸውን ወጪዎች ዝርዝር ለባለስልጣኑ ሳያቀርቡ በመቅረታቸው ምክንያት ሳይከፈል የቀረውን የግብር መጠን ተጠሪው ለይቶ ያላስረዳ በመሆኑ በአመልካቾቹ ድርጊት ምክንያት አነሶ እንዲከፈል የተደረገው የግብር መጠን በአንቀጽ 98(2)(ሀ) ስር የተመለከተው አነስተኛ መጠን ማለትም ከብር አንድ ሺህ የማይበልጥ ተደርጎ መወሰድ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም በአመልካቾቹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው በዚህ ድንጋጌ ስር ሲሆን ሊጣልባቸው የሚገባው የቅጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጠንም በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኙትን የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች መሰረት በማድረግ በድንጋጌው ስር የተመለከተው ከብር ሃያ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ እና ከአንድ ዓመት የማያንስ እና ከሶስት ዓመት የማይበልጥ እስራት ነው፡፡በአመልካቾቹ የወንጀል ድርጊት ምክንያት ሳይከፈል የቀረው የግብር መጠን ቀደም ሲል እንደተገለጸው አነስተኛ ነው ተብሎ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ ውሳኔው በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 13(2) እና (3) መሰረት መፈጸሙ የተረጋገጠው ወንጀል በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ ሊመደብ የሚገባው በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ የጥፋተኝነት ውሳኔው በተሰጠበት ድንጋጌ ስር በዝቅተኛ ደረጃ ለተመደበ ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው የተቀመጠው ፍቃድ ስልጣን ከአንድ ዓመት እስከ አንድ ዓመት ከሶስት ወር የሚደርስ እስራት ሲሆን ይህም በመመሪያው አባሪ አንድ በእርከን ሰባት ስር የሚወድቅ ነው፡፡የገንዘብ መቀጮ መጠኑም በአባሪ ሁለት መሰረት እስከ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ) የሚደርስ ነው፡፡

ሲጠቃለል በማስረጃ በተረጋገጠው የወንጀል ፍሬ ነገር መሰረት በአመልካቾቹ መፈጸሙ የተረጋገጠው ወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትለው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 አንቀጽ 98(2)(ሀ) ድንጋጌ ስር ሆኖ እያለ በአመልካቾቹ ላይ በክሱ በተጠቀሰው የአዋጁ በአንቀጽ 97 ስር የተሰጠው በጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥ~ል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06021 በ11/07/2005 ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 01611 በ01/02/2006 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 02314 በ29/02/2006 ዓ.ም በውሳኔ እና በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06021 በ11/07/2005 ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01612 በ29/02/2006 ዓ.ም. የተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏ~ል፡፡
2. አመልካቾቹ የወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በአመልካቾቹ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 97 ድንጋጌ ስር ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋኝነት ውሳኔ በማሻሻል የወንጀል ተጠያቂነታቸው የሚወድቀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 አንቀጽ 98(2)(ሀ) ድንጋጌ ስር ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በአመልካቾቹ ላይ በክልሉ ሰበር ችሎት ተሻሽሎ የተሰጠው የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ተሻሽሎ በዚህ በጉዳይ የታሰሩበት የሚታሰብላቸው ሆኖ አመልካቾቹ እያንዳንዳቸው በአንድ ዓመት እስራት እና በብር 1,000 (አንድ ሺህ) መቀጮ እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
5. በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ አመልካቾቹ ለሚገኙበት ማረሚያ ተቋም ይላክ፡፡ውሳኔው ዛሬ ጥቅምት 4 ቀን 2007 ዓ.ም ተነገረ፡፡
6. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት:: እ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93234
መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኰንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡- የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ኃይለኪሮስ ወልደብርሃን ካሕሳይ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረበው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ላይ አቅርቧቸው በነበሩት ሁለት የሙስና ወንጀል ክሶች ጉዳዩ የከሳሽን ምስክሮች ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት ምስክሮቹ እንዲሰሙ ከመደረጉ በፊት ተከሳሹ ከተከሰሱባቸው ሁለት የሙስና ወንጀሎች መካከል በሁለተኛው ክስ የተመለከተውን ወንጀል ያደረጉት ከሌላ ሰው ጋር በመተባበር ስለመሆኑ በሂደት የተደረሰበት መሆኑን ገልጾ የወንጀሉ ተካፋይ ነው የተባለውን ሌላኛውን ግለሰብ በክሱ በማካተት ክሱን አሻሽሎ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ያቀረበውን ጥያቄ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምጽ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን እና በብይኑ ቅር በመሰኘት አመልካች ያቀረበውን ቅሬታ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ባለመቀበል የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክስ ማሻሻል ጥያቄውን በአብላጫ ድምጽ ሳይቀበል የቀረው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 118 እና 119 ድንጋጌዎች መሰረት ክስ እንዲሻሻል ሊደረግ የሚችለው ክሱ ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችግር በሆነ ጊዜ መሆኑን እና ተጨማሪ ተከሳሽን በክሱ የማካተት ጉዳይ ለክስ ማሻሻል ጥያቄ በምክንያትነት መቅረቡ ሕጋዊ መሰረት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ሲሆን አነስተኛው ድምጽ በበኩሉ ክስ እንዲሻሻል የሚደረገው ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችግር በሆነ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በቁጥር 118 ድንጋጌ አነጋገር መሰረት በክሱ መገለጽ ይገባው የነበረ ነገር ግን ሳይገለጽ የቀረ መሰረታዊ ነገር መኖሩ ሲረጋገጥ ጭምር መሆኑን እና በወንጀሉ ተሳታፊ ነበረ የተባለ ሰው በማናቸውም ምክንያት በክሱ ውስጥ በተከሳሽነት ሳይካተት መቅረቱም ለክሱ መሰረታዊ የሚባል ነገር መሆኑን በመግለጽ ክሱ እንዲሻሻል ሊደረግ ይገባው ነበር በማለት የልዩነት ሀሳቡን አስፍሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት የማስረጃ ማሰማት ሂደቱን አቋርጦ አመልካች ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት የተያዘው ክርክር ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ይግባኝ ወደ ተባለበት ፍሬ ጉዳይ ሳይገባ በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው የይግባኝ አቀራረቡ ስነ ስርዓታዊ አግባብነት መሆኑን ገልጾ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 181(1) እና 184(መ) ድንጋጌዎች መሰረት ተከሳሹን ጥፋተኛ በማለት ወይም ነፃ በመልቀቅ ወይም ለጊዜው በመልቀቅ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በዋናው ጉዳይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ከሚቀርበው ይግባኝ ጋር በአንድነት ካልሆነ በቀር በዋናው ጉዳይ ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በክስ ማሻሻል ክርክር ረገድ በሚሰጥ ብይን ወይም ትዕዛዝ ላይ ይግባኙን ነጥሎ ማቅረብ የሚቻልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ አለመኖሩን በምክንያትነት በመጥቀስ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበውም የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት አቤቱታውን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ክስ አቅርቦ ማስረጃ ከማሰማቱ በፊት ከተጠሪ ጋር አብሮ መክሰስ ያለበት ሌላ ግለሰብ መኖሩን ስለደረስኩበት ግለሰቡን ጨምሬ ክስ ላቅርብ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ክስ ለማሻሻል የሚፈቀደው ክሱ ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ፍርድ ለመስጠት አስቸጋሪ ሲመስል ብቻ ነው በማለት ጥያቄውን ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 119 ድንጋጌ አንጻር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ለክርክሩ ወደ ተያዘው የፍሬ ጉዳይ የክርክር ጭብጥ ከመገባቱ በፊት እልባት ማግኘት የሚገባው በዋናው ጉዳይ ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በክስ ማሻሻል ክርክር ረገድ በሚሰጥ ብይን ወይም ትዕዛዝ ላይ ይግባኙን ነጥሎ ማቅረብ የሚቻልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ አለመኖሩን በምክንያትነት ጠቅሶ ይግባኙን ባለመቀበል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው እና በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለውሳኔው መሰረት ካደረጋቸው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕጉ ሁለት ድንጋጌዎች መካከል ከላይ ለተጠቀሰው ጭብጥ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ቁጥር 184 ድንጋጌ ሲሆን ይህ ድንጋጌም ተከሳሹን ጥፋተኛ በማለት ወይም ነፃ በመልቀቅ ወይም ለጊዜው በመልቀቅ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ በዋናው ጉዳይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ከሚቀርበው ይግባኝ ጋር በአንድነት ካልሆነ በቀር በቁጥር 94 መሰረት ቀጠሮ መስጠትን ወይም አለመስጠትን ወይም በቁጥር 131 መሰረት የሚቀርብ መቃወሚያን ወይም በቁጥር 146 መሰረት ማስረጃን መቀበልን ወይም አለመቀበልን አስመልክቶ በሚሰጡ ትዕዛዞች ላይ ይግባኙን ነጥሎ ማቅረብን የሚከለክል ነው፡፡

እንደሚታየው ይህ ድንጋጌ ትዕዛዞቹ መሰረት የሚያደረጓቸውን ድንጋጌዎች ጭምር በመጥቀስ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት የትዕዛዝ ይግባኝ ክልከላ የተጣለባቸውን ጉዳዮች የሚዘረዝር ሲሆን ከዝርዝሩ ውስጥ የክስ ማሻሻል ጉዳይም ሆነ የክስ ማሻሻል ጉዳይ መሰረት የሚያደርጋቸውን ቁጥር 118 እና 119 ድንጋጌዎች አልተካተቱም፡፡ይህም ሕጉ የትዕዛዝ ይግባኝ ክልከላ በግልጽ ከጣለባቸው ውጪ በሆኑ የመጨረሻ ትዕዛዝ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ (የክስ ማሻሻል ጥያቄን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውድቅ ከማድረግ ጉዳይ ጋር የተያያዙትን ጨምሮ) ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊትም ቢሆን ይግባኝ ማቅረብን አስመልክቶ የስነ ስርዓት ሕጉ ያስቀመጠው ክልከላ አለመኖሩን መገንዘብ የሚያስችል ነው።በተያዘው ጉዳይ የክስ ማሻሻል ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የተሰጠውን ትዕዛዝ በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ ፍርድ ቤት ቢሆን ከአሁኑ ተጠሪ ቀጣይ የወንጀል ክርክር ሂደት ጋር የሚያስተሳስረው ነገር ባለመኖሩ እና ትዕዛዙ የተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ ለክርክር ሊቀርብ የሚችልበት ዕድል የሌለ በመሆኑ ትዕዛዙ የመጨረሻ እንጂ ጊዜያዊ አገልግሎት እንዳለው ተቆጥሮ በስረ ነገሩ ከሚሰጠው ፍርድ ጋር ተጠቃሎ ይግባኝ የሚባልበት ነው ሊባል የሚችል አይደለም።በመሆኑም ይግባኙ የቀረበው በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የይግባኝ አቀራረብ ስርዓት መሰረት አድርጎ ባለመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 184 ድንጋጌ የትዕዛዝ ይግባኝ ክልከላን የሚጥለው ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት በሚሰጡ ሁሉም ትዕዛዞች ላይ እንደሆነ አድርጎ በመተርጎም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው እና በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57074 በ06/06/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 58589 በ12/10/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ ተሽሯል።
2. የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 184 ድንጋጌ የትዕዛዝ ይግባኝ ክልከላ በግልጽ ከጣለባቸው ውጪ በሆኑ የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊትም ቢሆን ይግባኝ ማቅረብን አስመልክቶ የስነ ስርዓት ሕጉ ያስቀመጠው ግልጽ ክልከላ ባለመኖሩ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር ምክንያት የሆነው የክስ ማሻሻል ጉዳይ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ነው በማለት ወስነናል።
3. ይህንኑ በመገንዘብ የቀረበለትን የይግባኝ ክርክር መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲላክ ወስነናል።
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.92296

ህዳር 22 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካቾች፡- 1. አንዱዓለም አራጌ
2. ናትናኤል መኮንን } ጠበቆች አቶ ደርበው ተመስገንና አቶ አበበ ጉታ ቀረቡ
3. ክንፈሚካኤል ደበበ

ተጠሪ፡- የፌደራል ዓቃቤ ህግ አቶ ወንድምአገኝ ብርሃኑ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች በየግላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 112546 የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔና፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 83593 ጉዳዩን በይግባኝ ካየ በኋላ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ሥለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ተጠሪ አመልካቾች የሽብርተኝነትና ከፍ ያለ የመክዳት ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ያቀረበውን የወንጀል ክስና ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በቀረበው የወንጀል መዝገብ ቁጥር 112546 ተጠሪ ከሳሽ፣አንደኛው አመልካች አንደኛ ከሳሽ፣ሁለተኛው አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ እና ሶስተኛው አመልካች አምስተኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. ከሥር የክርክሩን አመጣጥ ከመዝገቡ እንደተረዳነው፣ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾችና ሌሎች ተከሳሾች በአራት ወንጀል ክሶች የጠቀሳቸውን የወንጀል ሕግና የአዋጅ ቁጥር 652/2001 ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካቾችና በሌሎች ተከሳሾች ላይ ካቀረባቸው አራት ክሶች ውስጥ፣ አመልካቾች በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑት ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/፣ አንቀጽ 38 እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 252 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ በመተላለፍ ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ሚስጥሮችን በመሰብሰብ ለኤርትራ መንግስት አሳልፈው በመሰጠት የስለላ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት በአምስተኛው ተራ ቁጥር ያቀረበውን የወንጀል ክስ የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ ባለማቅረቡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾችና ሌሎቹ ተከሳሾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በነጻ እንዲሰናበቱ ውሳኔ ሰጥቷል። የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን ክስና ማስረጃ፣ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ በመስማት፣በመመርመርና በመመዘን በአመልካቾች ላይ ጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ የሰጠው ተጠሪ ባቀረበባቸው በሶስት የወንጀል ክሶች የተገለጹትን የወንጀል ድርጊቶች መፈጸማቸው በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል በማለት ነው።

2. የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 4፣ የተመለከተውን በመተላለፍ፣የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣የተመለከተውን በመተላለፍና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ክሱ የዘረዘራቸውን የወንጀል ድርጊቶች ዋና ወንጀል አድራጊና ተካፋይ በመሆን የፈጸሙ መሆናቸው በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል በማለት የጥፋኝነት ውሳኔ ሰጥቷል።

3. የሥር ፍርድ ቤት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002ን መሰረት በማድረግ አንደኛው አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘባቸው፣

ሀ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት፣

ለ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ ሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና፤

ሐ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248 (ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ሶስት ዓመት ጽኑ እስራት፣በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት ሲደመር ሰላሳ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚሆን በቅጣት ውሳኔው አመላክቷል። የስር ፍርድ ቤት የጽኑ እስራት ቅጣት ከሃያ አምስት የማይበልጥ መሆኑን በመግለጽ፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2005 ከፍተኛው ጣሪያ ሃያ አምስት ዓመት እርከን 37 ላይ ይወድቃል። አንደኛ አመልካች ከዚህ በፊት በጽኑ እስራት ተቀጥቶ የነበረ በመሆኑ አንድ እርከን ከፍ ብሎ እርከን 38 ላይ እንደሚወድቅ በውሳኔው አስፍሯል። የስር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች ተቀባይነት ያለው የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያላቀረበ በመሆኑ በእርከን 38 ከተቀመጠው ቅጣት በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በውሳኔ ሰጥቷል።

4. ሁለተኛው አመልካች በተመለከተ፣ የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘባቸው፤

ሀ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘውን ቅጣት ስምንት ዓመት ፅኑ እስራትና፣

ሐ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ሶስት ዓመት ጽኑ እስራት፣ መሆኑን በቅጣት ውሳኔው አመላክቷል። በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(1) መሰረት ሲደመር አርባ ዓመት እንደሆነ ነገር ግን የጽኑ እስራት ከሃያ አምስት የማይበልጥ መሆኑን በመግለጽ፤የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002 እርከን 37 ላይ የሚወድቅ መሆኑን፣ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቅጣት ማክበጃ ያልቀረበ መሆኑንና፤ሁለተኛ አመልካች ወንጀል ፈጽሞ የማያውቅ በመሆኑ አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያለው መሆኑን ገልጾ ሶስት እርከን ተቀንሶለት እርከን 34 ላይ ይወድቃል። በዚህ እርከን የተመለከተው የቅጣት ሬንጅ ከ 15 ዓመት እስከ 18 ዓመት የሚደርስ መሆኑን አስፍሮ ሁለተኛ አመልካች 18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል።

5. ሶስተኛው አመልካች በተመለከተ፣ የሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘባቸው፣

ሀ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ ሃያ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት፣

ለ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ ሥምንት ዓመት ጽኑ እስራትና፣

ሐ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት መሆኑንና፣በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት ሲደመር አርባ ዘጠኝ ዓመት መሆኑን ቅጣት ውሳኔው አመላክቷል። ነገር ግን የጽኑ እስራት ከሃያ አምስት ስለማይበልጥ፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002 እርከን 37 ላይ ይወድቃል። ሶስተኛ አመልካች በችሎት መድፈር ስምንት ወር በመቀጣቱ የዘወትር ጸባዩ መልካም ነው ብሎ ለመያዝ የማይቻል መሆኑን ገልጾ በእርከን 37 የተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ ከሃያ ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ነው። ሶስተኛ አመልካች የፈጸማቸው የወንጀል ክብደቶችና ግላዊ ሁኔታ በማየት በሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል።

6. አመልካቾች የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል።ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካቾችን ይግባኝ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑት ሌሎች ይግባኝ ባዮች ጋር በማጣመር አይቷል። ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣የተመለከተውን በመተላለፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ስህተት ያለበት ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔውን ሽሮ አመልካቾች በነጻ እንዲሰናበቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

7. ይግባኝ ሰሚው ችሎት አንደኛ፣ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበራቸው ተሳትፎ መካከለኛ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ሀ) አንደኛ አመልካች በሁለቱ ወንጀሎች መካከለኛ ደረጃ ላይ ተመድቦ በሥር ፍርድ ቤት የተወሰነበት 32 ዓመት ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት በወንጀል ሕጉ ከተመለከተው ከሃያ አምስት ዓመት በላይ በመሆኑ ቅጣቱ ከእርከን 37 እንደሚሆንና አንደኛ አመልካች ተቀባይነት ያለው የቅጣት ማቅለያ ያላቀረበና አንድ የቅጣት ማክበጃ ያለበት በመሆኑ በእርከን 38 መነሻ ተደርጎ ቅጣቱ ሲሰላ የሥር ፍርድ ቤት በአንደኛው አመልካች ላይ የሰጠውን የእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የቅጣት ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለ) ሁለተኛ አመልካችን በተመለከተም የሥር ፍርድ ቤት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ደረጃ እንደሆነና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ደረጃ ነው በማለት ያስቀመጠውን የቅጣት መነሻ እንዳለ በመቀበል፣ በሁለቱ ወንጀሎች የስር ፍርድ ቤት የወሰነው መነሻ ቅጣት ሲደመር ሰላሳ ሁለት ዓመት በወንጀል ሕጉ ከተደነገገው 25 ዓመት በላይ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱ እርከን 37 መነሻ በማድረግ ሁለተኛው አመልካች ያቀረበውን አንድ ቅጣት ማቅለያ በመቀበል በእርከን 34 ከተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ በ18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የስር ፍርድ ቤት የወሰነውን የቅጣት ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

ሐ) ሶስተኛ አመልካች በተመለከተ በችሎት መድፈር መቀጣቱ አመልካች የወንጀል ሪኮርድ የሌለበብኝ በመሆኑ በቅጣት ማቅለያነት ሊያገለት እንደሚገባ ያቀረበውን ጥያቄ፣ የሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛው አመልካች በችሎት መድፈር ወንጀል ተቀጥቷል በማለት በቅጣት ማቅለያነት አለመያዙ ስህተት መሆኑን ገልጾ ይህ ማቅለያ ሲያገ ደረጃው ከእርከን 37 ወደ እርከን 34 የሚቀንስ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የወሰነውና ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ተገቢ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ተሻሽሎ ሶስተኛው አመልካች በአሥራ ስድስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሌላ አነጋገር ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአንደኛና ሁለተኛ አመልካቾች ላይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አጽንቶ፣ በሶስተኛው አመልካች ላይ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡

8. አመልካቾች ሐምሌ 22 ቀን 2005 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ዝርዝር ይዘት ከላይ የተገለጸው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡ አመልካቾች በጋራ ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ጥፋተኛ ተብለን የተቀጣነው የግዙፍ ተግባር፣ ሃሳብና የህግ ሁኔታዎች ባልተሟሉበትና በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀሎቹን ለመፈጸማችን ከሳሽ በበቂ ማስረጃ ባላስረዳበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ሊሻር ይገባዋል፡፡አመልካቾች በይግባኝ ሰሚው ችሎት ጥፋተኛ የተባልንባቸው ሁለት የህግ ድንጋጌዎች በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሃሳብ የተፈጸሙ መሆኑን የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ የሚያሳይ በመሆኑ በሁለት ወንጀል ጥፋተኛ መባላችን የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ መርህና ይህ ሰበር ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሻረ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካችዎች በስር ፍርድ ቤት በሶስት ወንጀሎች ጥፋተኛ ናቸው ተብለን የተወሰነብን የቅጣት ውሳኔ፣በይግባኝ ሰሚው ችሎት በአንደኛው ወንጀል ነጻ ተብለን በሁለት ወንጀሎች ብቻ ጥፋተኛ በተባልንበት ሁኔታ ሳይሻሻል እንዳለ የሚጸናበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

9. ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች ላቀረቡት የሰበር አቤቱታ የካቲት 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የግዙፍ ተግባር፣ ሀሳብና የህግ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ጥፋተኛ ተብለናል በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡ አመልካቾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4 የፈጸሙት ወንጀል፣ አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ከፈጸሙት ከፍ ያለ የክዳት ወንጀል የተለያዩ ናቸው፡፡ ሁለቱም ወንጀሎች ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ወንጀሎች በመሆናቸው አመልካቾች በአንደኛው ወንጀል ብቻ ጥፋተኛ ልንባል ይገባል በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት የለውም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች ለፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ ጥፋተኛ መባል የለባቸውም በማለት ቢወስንም፣ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካቾች ላይ ባጸናቸው ሁለት የወንጀል ድርጊቶች በአንደኛና ሁለተኛ አመልካቾች ላይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም፡፡ ሶስተኛውን አመልካች በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አሻሽሎታል፡፡ ስለዚህ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች መጋቢት 11 ቀን 2006 በተጻፈ የመልስ መልስ በሰበር አቤቱታቸው ያነሷቸውን ነጥቦች በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

10. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት፣የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ላይ ካስተላለፋቸው ሶስት የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ውስጥ ለፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1፣ በመተላለፍ ወንጀል የፈጸሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ሽሮ፤ አመልካቾች ጥፋተኛ መባል የሚገባቸው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ የተመለከተውን በመተላለፍ በማሴር፣ በማነሳሳት፣በማቀድና በማዘጋጀት ወንጀልና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀፅ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ከፍ ያለ የክዳት ወንጀል ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰባተኛው አመልካች የሰጠውን ቅጣት ከማሻሻልና ከማስተካከል ውጭ በአመልካቾች ላይ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ሳያደርግ መወሰኑ ሕጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

11. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካቾች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት በተፈረጀውና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ የጦርነት፣የአመጽና ሌሎች የወንጀል ተግባራትን የሚፈጽመው የግንቦት 7 አሸባሪ ድርጅት ውስጥ አመራርና አባል በመሆን፣ በአገር ውስጥ ካሉት የድርጅቱ አመራሮች ጋር በሕቡዕ በመገናኘት፣ የሽብር ተልዕኮ በመቀበል ፣ለዚሁ የሽብር ተግባር አጋዥ የሚሆኑ ሰዎችን በመመልመል፣ ወደኤርትራ ለወታደራዊና ፖለቲካዊ ሥልጠና በመላክ እንደዚሁም ስለ ግንቦት 7 የፖለቲካ ዓላማ፣ጉዞ መመሪያና ወታደራዊ አደረጃጀት ለአባላት ገለጻ በመስጠት፣ የታቀደውን የሽብር ተግባር በቀጥታ በመምራት፣ በህቡዕ የሚተላለፈውን ገንዘብ ተቀብሎ የሽብር ወንጀል ፈጻሚዎች ያስተላለፉና የሽብር ዓላማ ያላቸውን ስብሰባዎችን በመጥራት፣ በመምራትና በተለያዩ የሽብር ተግባሮች ላይ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ ዋና ወንጀል አድራጊና ሙሉ ተካፋይ በመሆን፣በማሴር፣ በማነሳሳት፣በማቀድና በማዘጋጀት ወንጀል የፈጸሙ ስለመሆናቸው ፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጦባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ አመልካቾች ወሩና ቀኑ ተለይቶ ከማይታወቅበት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ የጦርነት፣ የአመጽና ሌሎች የወንጀል ተግባራትን የሚፈጽመው የግንቦት 7 አሸባሪ ድርጅት ውስጥ አመራርና አባል በመሆን፣ ኢትዮጵያ ጋር በሰላማዊ ሁኔታ ሳይሆን በጦርነት ሁኔታ ከሚኖረውና በጠላትነት በመሰለፍ በማናቸውም መንገድ ኢትዮጲያን የማተራመስ አጀንዳ ካለው የኤርትራ መንግስት ጋር በህቡዕ በመገናኘት፣ለኤርትራ መንግስት የሚጠቅሙ የተለያዩ ተግባራትን ይፈጽሙ እንደነበር ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጦባቸዋል።

12. እኛም አመልካቾች ከላይ የተገለጹትን ሁለት ወንጀል ድርጊቶች የፈጸሙ ስለመሆናቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የደረሱበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ሙሉ በሙሉ እውነት ናቸው በማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት በመቀበል እነዚህ አመልካቾች የፈጸሟቸው ሁለት ድርጊቶች ጥፋተኛ የሚያስብሉት በአንድ ወንጀል ነው ወይስ በሁለት ወንጀል የሚለውን ነጥብ መርምረናል። አመልካቾች በአሸባሪነት የተፈረጀው የግንቦት 7 ድርጅት ውስጥ አመራርና አባል በመሆን፣ በአገር ውስጥ ካሉት የድርጅቱ አመራሮች ጋር በሕቡዕ በመገናኘት፣የሽብር ተልዕኮ በመቀበል፣ለዚሁ የሽብር ተግባር አጋዥ የሚሆኑ ሰዎችን በመመልመል፣ ወደ ኤርትራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለወታደራዊና ፖለቲካዊ ሥልጠና በመላክ እንደዚሁም ስለ ግንቦት 7 የፖለቲካ ኣላማ፣ ጉዞ መመሪያና ወታደራዊ አደረጃጀት ለአባላት ገለጻ በመስጠት ፣ የታቀደውን የሽብር ተግባር በቀጥታ በመምራት፣ በህቡዕ የሚተላለፈውን ገንዘብ ተቀብሎ የሽብር ወንጀል ፈጻሚዎች ያስተላለፉና የሽብር ዓላማ ያላቸውን ስብሰባዎች በመጥራትና በመምራት በተለያዩ የሽብር ተግባሮች ውሳኔ በማሳለፍ የፈጸሙት የማሴር፣ የማነሳሳት፣የማቀድና የማዘጋጀት ድርጊት ራሱን የቻለ ወንጀል ድርጊት እንደሆነና ከአሥራ አምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት፣ በእድሜልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 4፣ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል።

13. አመልካቾች ኢትዮጵያ ጋር በሰላማዊ ሁኔታ ሳይሆን በጦርነት ሁኔታ ከሚኖረውና በጠላትነት በመሰለፍ በማናቸውም መንገድ ኢትዮጵን የማተራመስ አጀንዳ ካለው የኤርትራ መንግስት ጋር በህቡዕ በመገናኘት፣ ለኤርትራ መንግስት የሚጠቅሙ የተለያዩ ተግባራትን መፈጸማቸው ራሱን የቻለ የወንጀል ድርጊትና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) መሰረት ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት፣ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጓል። አመልካችዎች ሁለቱም የወንጀል ድርጊቶች የተፈጸሙት በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሃሳብ ማለትም ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል የመናድ ኃሳብ በመሆኑ በሁለቱ ወንጀሎች ጥፋተኛ መባላችንና የቅጣት ውሳኔ መሰጠቱ ሕጋዊ አይደለም በማለት ተከራክረዋል። የአመልካችዎች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙባቸው ተደራራቢ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የመጣስ አድራጎት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(ሀ) የተደነገገው መሰረታዊ መርህ ተፈጻሚ የሚሆንበት ሁኔታ የለም። በአንጻሩ ወንጀል አድራጊው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ አደራርቦ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 187(1) መሰረት እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 65 በግልጽ ይደነግጋል።

14. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 187(1) ወንጀል አድራጊው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ አደራርቦ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ (አንቀጽ 65) ፍርድ ቤቱ የአካባቢ ሁኔታዎችን ሲመረምር በተለይም ወንጀለኛው አስቦና አቅዶ ሕግ መጣሱን ወይም ግልጽ የሆነ መጥፎ ጸባይ ማሳየቱን ባመነ ጊዜ በአንቀጽ 184 መሰረት ቅጣቱን አክብዶ ለመወሰን እንደሚችል ይደነግጋል። ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ድንጋጌ ይዘት ስንመለከተው ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነጻነትን የሚያሳጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ እያንዳንዱ ተደራቢ ወንጀል ቅጣት ተወስኖ፣ ቅጣቱ እንደሚደመርና የቅጣቱ አይነት በሕጉ ከተመለከተው ከፍተኛ ቅጣት ሊበልጥ እንደማይችል ይደነግጋል። ከዚህ አንጻር አመልካቾች የወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(ሀ) በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 65፣ አንቀጽ 187(1) እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተደነገገውን የቅጣት አወሳሰን መርሆች ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም።

15. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ህጋዊነት በተመለከተም አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉበት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ ሕጉ መነሻ ቅጣት አድርጎ በደነገገው አሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራትና በሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት መካከል ያለው ልዩነት አስር ዓመት ነው። ይህም በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወራት፣ በመካከለኛ ደራጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወራት፣ እሰከ ሃያ አንድ አመት ከስምንት ወር፣ በከፍተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ ሃያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንድ አመት ከስምንት ወር፣ እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ካወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ለመረዳት ይቻላል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሶስቱም አመልካቾች በዚህ ወንጀል ያላቸው ተሳትፎ በመመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ መሆኑን በውሳኔው አስፍሯል፡፡

16. አመልካቾች ጥፋተኛ ሆነው በተገኙበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የቅጣት ዝቅተኛው መነሻ ሆኖ በተደነገገው አምስት ዓመት ጽኑ እስራትና እና ከፍተኛ በሆነው ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት መካከል ያለው ልዩነት ሃያ ዓመት ነው፡፡ይህም በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አንድ ዓመት ከሥምንት ወራት፣ በመካከለኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ አሥራ አንድ ዓመት ከስምንት ወራት እስከ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወር፣ በከፍተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወር፣ እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሰረት በማድረግ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሶስቱም አመልካቾች በዚህ ወንጀል ያላቸው ተሳትፎ በመመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ መሆኑን በውሳኔው አስፍሯል፡፡

17. የጽኑ እስራት ቅጣት ከሃያ አምስት አመት ሊበልጥ እንደማይችል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የመጨረሻው ፓራግራፍ እና ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ በመሆኑ የሶስቱም አመልካቾች ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያ 25 ዓመት ጽኑ እስራት ሲሆን ይህም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት እርከን 37 ላይ የሚወድቅ ይሆናል፡፡በይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሳኔ መሰረት ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያላቸው መሆኑ ተመልክቷል፡፡ አንደኛ አመልካች የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የሌለው መሆኑንና አንድ የቅጣት ማክበጃ የቀረበበት በመሆኑ በእርከን 38 ላይ የሚወድቅ መሆኑን የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተስማምተዋል፡፡ በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን የሚቀንስ መሆኑን፣የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በውሳኔያቸው አስፍረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ሶስት እርከን ተቀንሶላቸው እርከን 34 ላይ በማሳረፍ ፈቃደ ሥልጣናቸውን ተጠቅመዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በቅጣት አወሳሰን መመሪያው የተሰጣቸውን ፈቃደ ሥልጣንና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 88(2) የተደነገገውን መሰረት በማድረግ አንደኛ አመልካች በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣና ሁለተኛው አመልካች በአስራ ሥምንት ዓመት ጽኑ እስራት ያስተላለፉት የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤት በሶስተኛ አመልካች ላይ ያስተላለፈውን የሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት በማሻሻል በአስራ ስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

18. የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህን ተፈጻሚ ማድረግ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይህም አንድ ሰው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎችን ከፈጸመና ወንጀሎቹ ነጻነትን በሚያሳጣ ቅጣት የሚያስቀጡ ከሆነ ለእያንዳንዱ ወንጀል ሊቀጣ የሚገባውን ቅጣት በመወሰንና ቅጣቱን በመደመር በወንጀለኛው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ የሚወሰነውን ቅጣት ለማስላት የሚያስችል ቅጣት አወሳሰን መርህ ነው፡፡ በሌላ በኩል ድንጋጌው ድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህ የሚገድብና ውጤት አልባ የሚያደርግ ደንብ የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በያዝነው ጉዳይ በጽኑ እስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሁለት ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመዋል፡፡ እደዚህ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ለሁለቱ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰኑት ቅጣት የድምር ውጤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፍተኛ የጽኑ እስራት ቅጣት ሆኖ ከተደነገገው ሃያ አምስት አመት ጽኑ እሰራት ሊበልጥ እንደማይችል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ ገደብ ያስቀምጣል፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ የተቀመጠው ገደብ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቱ፣በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የመጀመሪያው ፓራግራፍ መሰረት በጥፋተኛው ላይ ሊወሰን የሚገባው ድምር የቅጣት ውጤት ከሃያ አምስት ዓመት በላይ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የቅጣት ድምር ውጤቱን ወደ ሃያ አምስት ዓመት ዝቅ በማድረግ እንዲወስኑ የሚያስገድድና ሕግ አውጭው በአዲስ መልክ በወንጀል ሕጉ ያስገባውን የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህን ውጤት አልባ የሚያደርግ ገደብ ነው፡፡

19. ይህም ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህን እንዲተገብሩ በሚደነግገው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ1(ለ) የመጀመሪያው ፓራግራፍና የቅጣቱ ድምር ውጤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ሃያ አምስት አመት ጽኑ እስራት ሊበልጥ እንደማይችል አስገዳጅ ገደብ በሚጥለው በወንጀል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ መካከል በይዘትም ሆነ በተግባራዊ አፈጻጸማቸው ክፍተትና አለመጣጣም ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሆኖም ህጉ ባለው ክፍተትና አለመጣጣም አመልካቾች ተጠቃሚ እንጅ ተጎጅ አይደሉም፡፡ ስለሆነም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በመጀመሪው ፓራግራፍ የደነገገውን የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህ ዋጋ በማያሳጣ ሁኔታ ለተደራራቢ ወንጀሎች ፍርድ ቤቱ የሚወስነው ድምር የቅጣት ውጤት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ሃያ አምስት ዓመት መብለጥ የለበትም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ የጣለውን አስገዳጅ ገደብ ማሻሻል ለህግ አውጭው የስራ ኃላፊነትና ተግባር ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ካላይ በገለጽናቸው ወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች የሚታየው ክፍተት አመልካቾችን መብት የሚያጣብብ ሳይሆን እነርሱን በሚጠቅም መልኩ የተተረጎመና ሥራ ላይ የዋለ በመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች ላይ የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ማጽናቱና በሶስተኛው አመልካች ላይ የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 83593 በአመልካቾች ላይ የወሰነው የቅጣት ውሳኔ የጸና መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 97203

መስከረም 30 ቀን 2007

ዳኞች፡-አልማው ወሌ
ሡልጣን አባተማም
መኮንን ገ/ሕይወት
መስጠፉ አህመድ
ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- 1.አቶ ታምራት ደምሴ
2.አቶ በሪሁን ደምሴ } የቀረበ የለም
3.አቶ ታደለ ሽቱ

ተጠሪ፡- የቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች እና አቶ አለኸኝ ጋሻው በተባሉት ግለሰብ ላይ የመሰረተው ክስ፡- በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና 539/1/ሀ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ታህሳስ 29 ቀን 2002 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 3፡00 በሚሆንበት ጊዜ ግልገል በለስ ከተማ ከወ/ሮ አለምፀሐይ ጌታሁን ሻይ ቤት አረቄ እየጠጡ በፈጠሩት ፀብ ለምንድን ነው የሰደብከን? በማለት የአሁኑ 1ኛ፣2ኛ አመልካቾች እና የስር 3ኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ አለኸኝ ሚች ኤርሚያስ ኃይሉን ሊደበድቡት ሲሉ በገላጋይ ከቤት ከወጡ በኋላ ከስር ሶስተኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን ተከታትለው በመሄድ ኤርሚያስ ኃይሉን በአንድ ላይ ተባብረው በዱላና በድንጋይ ግንባሩንና መላ ሰውነቱን ደብድበው በግፍ ገድለዋል የሚል ነው፡፡አመልካቾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልፀው የድርጊቱ አፈጻጸሙን በተመለከተም ክደዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን ያሰማ ሲሆን የስር ፍ/ቤትም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን መርምሮ አመልካቾች ድርጊቱን መፈፀማቸው በበቂ ሁኔታ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የአሁኑ አመልካቾችን እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቶ የስር 3ኛ ተከሳሽ የነበሩትን ግለሰብ ግን በነፃ አሰናብቷል፡፡በዚህ ብይን መሰረትም አመልካቾች የመከላከያ ማስረጃዎችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃነት ቃል ክብደት የማይሰጠው ነው በማለት ውድቅ ከአደረገ በኋላ አመልካቾችን በዓቃቤ ሕጉ በኩል ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማድረግ እያንዳንዳቸውን በ17 (አስራ ሰባት አመት) ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ከዚህም በኋላ አመልካች በጥፋተኝነትና በቅጣት ውሣኔው ላይ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን፣የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች ህዳር 23 ቀን 2004 ዓ.ም በተባፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱንም ባጭሩ፡- የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የሰጡት የጥፋተኛነት ውሣኔ አግባብነት የሌለውን ማስረጃ መሰረት ያደረገ ከመሆኑም በላይ ማስረጃውም ተገቢውን የማስረጃ ምዘና ስርዓት ተከትሎ ያልተመዘነ መሆኑን፣አድራጎቱ በአመልካቾች ተፈፅሟል ከተባለም አግባብነት ያለው ድንጋጌ ተራ በሆነ የሰው መግደል ወንጀል የሚሸፍን ነው እንጂ በግፍ ሰው መግደልን በሚሸፍነው ድንጋጌ ስር የሚወድቅ ያለመሆኑን፣ እንዲሁም የቅጣት ውሳኔውም የአመልካቾችን የእድሜ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና የበዛ መሆኑን በመዘርዝር ውሣኔው ሊለወጥ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካቾች ለወንጀል ድርጊቱ ተጠያቂ የመደረጋቸውን አግባብነት ከወ/ሕ/አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር ሲባል ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጉት አበይት ነጥቦች፡-

1. ከአመልካቾች ውስጥ ለሟች ሕልፈት ተጠያቂነት ያለበት የትኛው ነው?፣

2. ተጠያቂነት አለበት ሊባል የሚችለው አመልካች አለ ከተባለ አድራጎቱ የሚሸፈነው በየትኛው አንቀፅ ስር ነው? እና ቅጣቱስ ስንት ሊሆን ይገባል የሚሉት ሁነው ተገኝተዋል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በዓቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ ለህልፈት ተዳርገዋል የተባሉት ግለሰብ ለህልፈት የተዳረጉት በአመልካቾችና በስር 3ኛ ተከሳሽ በነበሩት ግለሰብ በግብረአበርነት በተፈፀመባቸው አድራጎት መሆኑን የተጠሪ ክስ የሚገልጸው ጉዳይ ሲሆን ተጠሪ በሟች ላይ ለህልፈተ ሕይወት መድረስ ምክንያት የሆነውን አድራጎት የፈፀሙት አመልካቾች መሆናቸውን ለማስረዳት አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን ማቅረቡን የውሳኔው ግልባጭ የሚያስገነዝብ መሆኑን ነው፡፡በዚህ ረገድ የተሰሙት ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሲታይም፡-1ኛው ምስክር ድርጊቱ የተፈፀመው በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ መሆኑን ጠቅሰው አመልካቾችና ሟች የምስክሩ ጎረቤት በሆኑት በወ/ሮ አለምፀሐይ ጌታሁን ሻይ ቤት ሲጠጡ እንደቆዩና ጎረቤታቸው ወደ ምስክሩ ቤት እራት ሊበሉ ሂደው አመልካቾችና ሟቹ እንደተጣሉና ምስክሩ እንዲያገላግሏቸው ለምስክሩ ሲነግሯቸው ምስክሩም ወደ መጠጥ ቤት ሂደው ሲመለከቱ ሁሉም ቁጭ ብለው እንደአገኟቸው፣ከዚያ በኋላ ሟቹ ቀድሞ ከቤቱ ሲወጣ አለኽኝ ጋሻው የተባለው የስር 3ኛ ተከሳሽ ሟችን ተከታትሎ መውጣቱንና ከአምስት ደቂቃ ቆይታ በኋላም የአሁኑ አመልካቾች ተከታትለው እንደወጡ፣በወቅቱ በመጠጥ ቤት ውስጥ ሟቹና የስር ተከሳሾች ሲጨቃጨቁ ምስክሩ መስማታቸውን፣ተከሳሾች ከቤት ከወጡ በኋላ ምስክሩ ወደ ቤታቸው ተመልሰው ሂደው ከተኙ በኃላ ከምሽቱ 7፡00 አከባቢ ጩኸት እንደሰሙና በበነጋታውም 2፡00 አከባቢ ሟቹ ሞተ ሲባል መስማታቸውን መስክረዋል፡፡አለምጸሐይ ጌታሁን የተባሉት 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር በበኩላቸው ድርጊቱ የተፈፀመው በዐቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ መሆኑን ጠቅሰው በሻይ ቤታቸው ሶስት ሰዎች ቀድመው ገብተው በብርሌ አረቄ ገዝተዋቸው እየጠጡ እያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማውራት እንደጀመሩና ከቆይታ በኋላ ስድብ ሲጀምሩ ምስክሯ ነገሩ ጠብ መሆኑን በመረዳት ጎረቤታቸው ለሆኑት ለዓቃቤ ህግ አንደኛ ምስክር ከሻይ ቤታቸው ወጥተው በመሄድ ስለጉዳዩ እንደነገሯቸውና ጎረቤታቸውም ወደ ምስክሯ ቤት መጥተው በመጠጥ ቤት የነበሩትን አመልካቾችን "ሌላ ሰው ለምን ትረብሻላችሁ?" በማለት ሲናገሯቸው ከመጠጥ ቤት የነበሩት ሰዎች ተከታትለው እንደወጡና ምስክሯም ከዚህ በኋላ የመጠጥ ቤቱን በር ዘግተው የተኙ መሆናቸውን መስክረዋል።ሦስተኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክርም የአቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክር ባለቤት መሆናቸውን ጠቅሰው የሰጡት የምስክርነት ቃል በይዘቱ ከ1ኛው ምስክር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው።4ኛው የአቃቤ ሕግ ምስክር ደግሞ ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ በግልገል በለስ ከተማ 02 ቀበሌ ግብርና ፅ/ቤት ወደታች ባላቸው የግል ሻይ ቤት የሥር 3ኛ ተከሳሽ አለኽኝ እና ኤርምያስ የተባሉት ሰዎች ሂደው የሚጠጣ ሻይ ከአዘዙ እና ሻሂውን ከጠጡ በኋላ ከምሽቱ 3፡00 አከባቢ ከቤት ወጥተው እንደሄዱ፣ከምሽቱ 4፡30 ሲሆን ደግሞ አለኽኝ የተባለው ተከሳሽ ተመልሶ ወደ ሻሂ ቤታቸው ገብቶ ጅን አረቄ እንዲሰጠው ሲጠይቃቸው ምስክሯ የለኝም የሚል ምላሽ ሲሰጡት ይሄው ግለሰብ ሻሂ ጠጥቶ ለብቻው ተመልሶ መሄዱን መስክረዋል።5ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር በሰጡት የምስክርነት ቃል፡-በዓቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ እንዳልነበሩ፣ድርጊቱ ከተፈፀመ በኃላ የወንጀል ክትትሉን እንደጀመሩ፣ከወንጀሉ መፈፀም በኃላ የደምሴ ልጆች መሰወራቸውን፣አባታቸውም ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ታስረው እንደነበር፣አቶ ደምሴ የተባሉት ግለሰብም "አይ እኔን ከእስር ቤት ፍቱኝና ሌሎች ልጆች ስላሉ አፈላልጌ ላምጣ!" ብለው ለፖሊስ አቤቱታ እንደአቀረቡ፣ከዚያም ሰውየው ፖሊስ ይሰጠኝ በማለታቸው ፖሊስና ልዩ ኃይል ተሰጥቷቸው ታምራት የተባለው ልጃቸው ከስራ ቦታ ተይዞ እንደመጣ፣በወቅቱ "ድርጊቱን ከወንድሜ በሪሁን ጋር የፈፀምኩት እኔ ነኝ፣ ታደለና አለኽኝም በድብደባው ላይ አሉ፤ድርጊቱን የፈፀምነው እኛ ነን!" በማለት ለፖሊስ መናገሩን፣ድርጊቱን አራት ሁነው የፈፀሙት መሆኑንና ሚቹ ይሞታል በሚል ሃሳብ እንዳልፈፀሙ፤ሚችን የመቱትም ታምራት በዱላ ግንባሩን፣ሌሎች በቡጢ እና በድንጋይየመቱት መሆኑን መግለፁንና ከዚያም እንደሸሹና እንደተበታተኑ እንዲሁም ጥዋት ወደ አዝመራ ቦታ ሂዶ ቆይቶ በልዩ ኃይል መያዙን ሲናገር መስማቱን የመሰከረ ነው።6ኛው ምስክር በበኩሉ በወቅቱ በሚች ለቅሶ ላይ እያሉ "የእናተ ቤተሰብ ነው!" በሚል ምክንያት ተይዘው በፖሊስ ጣቢያ እንደነበሩ፣ምሽት ላይ ታምራት የተባለውን ተከሳሽ ፖሊሶች ይዘው ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እያለ አንድ የፖሊስ አባል ታምራትን "ለምንድነው እንዲህ አድርጋችሁ የምትማቱት?" በማለት ሲጠይቀው ታምራት ጭንቅላቱን አልመታሁትም፤እኔ ጀርባውን ነው የመታሁት፣ጭንቅላቱን የመታው ሰው ሌላ ነው ብሎ ሲመልስለት መስማቱን መስክሯል።

እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾችን ጥፋተኛ ለማድረግ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡት ምስክሮች ቃል ይዘት ከላይ የተጠቀሰው መሆኑን በውሳኔው ላይ የገለፀት ጉዳይ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ ሐተታው በግልጽ ያስቀመጠው ድምዳሜውም ከዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል አመልካቾች ሚችን ሲመቱትና ሲገድሉት አየሁ በሚል ያልተገለጸ መሆኑን የሚያሳይ ነው።የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾችን ለወንጀል ድርጊቱ ኃላፊ ያደረጋቸው በክሱ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ በሚቹና በአመልካቾች መካከል ጠብ ተፈጥሮ ሚቹ ከስር ሶስተኛ ተከሳሽ ጋር በአንድ በኩል፣አመልካቾቹ ደግሞ በሌላ በኩል ተቀምጠው ሚቹ ምራቅ ሲተፋ አመልካቾች "ይህች ምራቅ ዛሬ ደም ትሆናለች!" በማለት ተናገረው ወዲያውኑ ሚቹና የስር 3ኛ ተከሳሽ ከአረቂ ቤቱ ወጥተው ሲሄዱ ወዲያውኑ የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙን ተረጋግጧል በሚል ድምዳሜ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች ከሚከራከርባቸው ነጥቦች ውስጥ የአመልካቾችን የድርጊት ፈፃሚነት በተገቢው መንገድ አቃቤ ሕግ በማስረጃ ያለማስደገፉንና የአቃቤ ሕግ የአይን ምስክሮች ድርጊት ፈፃሚዎችን በወቅቱ ስለመለየታቸው ሳይመሰክሩ ሰምተናል በማለታቸው ብቻ ጥፋተኛ መባላችን ያላግባብ ነው የሚለውን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ ከሚመዘንበት መርህ ጋር በማጣቀስ ነው፡፡

በመሰረቱ በአንድ የወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ በቂና አሣማኝ በሆነ ሁኔታ የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙንና የወንጀል ድርጊቱን ፈፃሚውን ማንነት በትክክል ለይቶ ማሳየት ያለበት ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትንና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡አንድ ሰው ለወንጀል ድርጊት ኃላፊ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚገባው ወንጀል መስራቱ ወይም መፈፀሙና ተሰራ ወይም ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4)፤32፣40፤57፣ 58(1) እና ከወ/መሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141፣142 እና 149 ድንጋጌዎች አገላለፅና መንፈስ መመልከት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ የሚቆጠረው ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ቢያደርግ ወይም በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ ሀሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተከፋይ በመሆን ወንጀሉን የራሱ ያደረገ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ለ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ከሳሽ የሆነው አቃቤ ሕጉም ይህንኑ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት አለበት፡፡

አመልካቾች ሟችን በቀጥታ መትተው ስለመግደላቸው አይተናል የሚል የአቃቤ ሕግ ምስክር ባይኖርም ሟች ጋር በእለቱ በአረቄ ቤት ሲጨቃጨቁ እንደነበር፣ሟች ምራቅ ሲተፋም ምራቁ ደም እንደሚሆን ተናግረው እንደነበር በአቃቤ ሕግ ምስክሮች ተገልፆአል፡፡ይሁን እንጂ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በወቅቱ ከሟች ጋር ጠብ አስነስተው የነበሩትን ሰዎች ማንነት የገለፁ ቢሆንም ለሟቹ ህልፈተ ሕይወት እያንዳንዱ አመልካች የነበረውን ተሳትፎ ያልተናገሩ ከመሆኑም በላይ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል በሁሉም አመልካቾች ላይ እንደ አከባቢ ማስረጃ የሚወሰድ ነው ቢባልም ማስረጃው በ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ላይ ግን ጥንካሬ የሌለው ሁኖ ተግኝቷል፡፡በሌላ አነጋገር የተጠሪ ምስክሮች በወቅቱ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ /Circumstantial Evidence/ የምስክርነት ቃል ሰጥተው የተመለሱ ቢሆንም ከጠቡ መነሻ ውጪ ከጠቡ በኋላ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የነበራቸውን ሚና በግልጽ የሚያሳዩ አይደሉም፡፡ በአገራችን የህግ ሥርዓት ምስክሩ ስለአጠቃላይ ሁኔታዎች በአይኑ የታዘበውን በጆሮው የሰማውንና የሚያውቀውን ፍሬ ጉዳይ ሊመሰክር እንደሚችልና የምስክሩም ቃል ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 137 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡ይሁን እንጂ በ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ላይ በአቃቤ ምስክሮች የተሰጠው የምስክርነት ቃል በአረቄ ቤት የነበረውን ጠብ እና ሟች ምራቅ ሲተፋ ይህ ምራቅ ደም ሊሆን እንደሚችል አመልካቾች ከመናገራቸው ውጪ በድርጊቱ ወቅት ወይም በኋላ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የፈፀሙትን አድራጎት የሚያሳይ አይደለም፡፡ስለሆነም በ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ላይ የቀረበው የአቃቤ ሕግ ማስረጃ በወንጀል ሕግ የሚቀርብ ማስረጃ ስለጉዳዩ ለማስረዳት በቂና አሳማኝ ማስረጃ ነው ብሎ ለመደመድም የሚያስችል ሊሆን ይገባል የሚለውን መለኪያ ያሟላ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ስለሆነም በእነዚህ አመልካቾች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1ኛውን አመልካች ታምራት ደምሴን በተመለከተ ግን 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች አመልካቹ በወቅቱ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ ከሰጡት የምስክርነት ቃል በተጨማሪ አመልካቹ ከወንጀል ድርጊቱ በኋላ በፖሊስ ተይዞ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተይዞ ከገባ በኋላ ወንጀሉን መፈፀሙንና እንዴት እንደፈጸመ ጭምር ሲገልፅ እንደነበር 5ኛ እና 6ኛ የአቃቤ ምስክሮች ከመሰከሩት ቃል መረዳት የሚቻል ሁኖ ስለተገኘ አመልካቹ በሚቹ ህልፈተ ሕይወት ተሳትፎ እንደነበረው በዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተደጋጋፊነትና ተመጋጋቢነት ባለው ጠንካራ የአከባቢ ማስረጃ የተረጋገጠ ሁኖ አግኝተናል፡፡በመሆኑም አመልካች ታምራት ደምሴ በቀጥታ የወንጀሉ ተሳታፊ ሁኖ በመላ ሀሳቡ የወንጀሉን ድርጊት እንዲሁም ውጤቱን የራሱ ያደረገ ስለሆነ አመልካቹ ለወንጀል ድርጊቱ ኃላፊ ልባል አይገባም በማለት ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡

አንደኛውን ጭብጥ በተመለከተ ስናጠቃልለው 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ለወንጀሉ ድርጊት ኃላፊ የተባሉት ዓቃቤ ሕግ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 በሚያስቀምጠው የማስረጃ መለኪያ መሰረት የአመልካቾችን ተሳትፎ ባላስረዳበትና በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ በመሆኑ በእነዚህ አመልካቾች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሲሆን 1ኛ አመልካች ግን ሟች ከመሞቱ በፊትና ሲሞት የነበረው የወንጀሉ ተሳትፎ በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ በሰው ግድያ ወንጀል ተጠያቂ መደረጉ የሚነቀፍ ሁኖ አይደለም ብለናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> የስር ፍርድ ቤቶች 1ኛ አመልካችን ተጠያቂ ያደረጉት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539(1(ሀ)) ስር ነው፡፡

በመሰረቱ የሰው ግድያ ወንጀል በወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በመዘጋጀት ሲፈፀም ወይም በአንቀጽ 84 ወይም 86 ስር የተመለከቱት አክባጅ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ስለመሆኑ ተጠቃሹ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች በየራሳቸው መቆም የሚችሉ ነጥቦች ስለመሆናቸው ነው፡፡

የወንጀል ህግ አንቀጽ 540 ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ፡-

"ማንም ሰው አገዳደሉ በአንቀጽ 539 የተመለከተውን ያህል ከባድ ወይም በአንቀጽ 541 የተመለከተውን ያህል ቀላል ባልሆነ ሁኔታ አስቦ ሌላ ሰውን የገደለ እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል በሚል አስቀምጧል፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 539 እና 540 መሠረት የሚፈፀሙ ግድያዎች ሆነ ተብሎ ወይም በማወቅ /አስቦ/ የሚሰሩ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ሁለቱ አንቀፆች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ነገር ግን ሁለቱን አንቀፆች የተለያዩ የሚያደርጓቸው መሰረታዊ ነጥቦች መኖራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ አንድ ሰው በወ.ህ.አንቀጽ 539/1/ሀ/ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ እንዲገኝ በዚሁ አንቀጽ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡እነዚህን ሁኔታዎች ደግሞ ሰውየው ድርጊቱን ለመፈፀም ካነሣሣው ሃሣብ እና ከድርጊቱ አፈፃፀም አንፃር በመመርመር የድንጋጌውን ትክክለኛ አፈጻጸም መለየት ይቻላል፡፡በድንጋጌው ስለሃሳብ ሁኔታ የሚገልጹትን ሁኔታዎች ስንመለከትም አስቀድሞ የማሰብ ሁኔታ፤ ቂም በቀል፤ጥላቻ፤ ቅናት ወዘተ----የሚሉ የሚገኙ ሲሆን ከባድ የድርጊት አፈፃፀም መኖርን የሚያመላክቱ ነጥቦች ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስር የተመለከቱትና በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ 86 መሠረት ከባድ ምክንያቶች ናቸው ብሎ የሚቀበላቸውን ሁኔታዎች የሚያካትቱ ናቸው።

አንድ ሰው ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት የሃሣብ ሁኔታዎች ወይም የድርጊት አፈፃፀም አንዱን እንኳ ፈጽሞ ቢገኝ እና ይህም ሁኔታ ሲታይ ገዳዩ "በተለይ" ጨካኝ፤ ነውረኛ ወይም አደገኛ የሚያሰኝ አይነት ሆኖ ከተገኘ በአንቀጽ 539/1/ሀ/ መሠረት ጥፋተኛ ሊሰኝ እና ለዚሁ አድራጎት በሕጉ የተመለከተው ቅጣት ውሳኔ ሊተላለፍበት ይገባል።

አንቀጽ 539/1/ሀ/ በቅድሚያ እንዲሟላ የሚፈልገው መሰረታዊ ነጥብ የአገዳደሉ ሁኔታ አድራጊው በተለይ ጨካኝ፤ ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ መገኘትን ነው።በድንጋጌው ስር "በተለይ" የሚለው ቃል የሚያስገነዝበው ከተራ አገዳደል ወይም የሃሣብ ሁኔታ ውጭ በሆነ አድራጎት ወይም ለጥቃት መገልገያ የተደረገው መሣሪያ በሚች ላይ ስቃይና መከራ ማሣደር እንዳለበት፣ ግድያውም ከተራው ሁኔታ የተለየ እንደነበር የሚያመለክት ነው ተብሎ ይታመናል።። በህጉ በተለይ ጨካኝ ነውረኛ ወይም አደገኛ መባሉ የአገዳደሉ ሁኔታና የመግደያው መሣሪያ አደገኛነት፣ ፍፁም ጨካኝነትን፤ ነውረኛነትን ወይም የተጋነነ አደገኛነትን ማሳየት እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው።ስለሆነም የወ.ሕ.አንቀፅ 539(1(ሀ)) የማክበጃ ልዩ ሁኔታዎች በመኖራቸው ምክንያት ሆን ተብሎ የተፈፀመው ግድያ "ከባድ የሰው ግድያ" የሚባልበትን ምክንያቶች የያዘ ነው።እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች በሌሉበት አንድን ተከሣሽ በዚህ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ሊባል የማይችል መሆኑን የሕጉ ይዘትና መንፈስ ያሳያል። ከእነዚህ እና በተጠቃሹ አንቀፅ በፊደል "ለ" እንዲሁም "ሐ" ስር ከተመለከቱት የድንጋጌዎቹ ማቋቋሚያዎች ውጪ ሆን ተብሎ የሚደረግ ሰው የመግደል ወንጀል የሚያስቀጣው በአንቀጽ 540 ስር ነው።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣም አመልካች ሟችን ለመግደል አስቀድሞ ሐሳብ ያልነበረው መሆኑ ግልጽ ሲሆን አፈጻጸሙ ሲታይም በተለይ ጨካኝነት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ስለመሆኑ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል አያሳይም።እንዲሁም የአገዳደሉ ሁኔታና የመግደያው መሣሪያ አደገኛነት ፍፁም ጨካኝነትን፤ ነውረኛነትን ወይም የተጋነነ አደገኛነትን አያሳይም።እንዲህ ከሆነ ደግሞ አድራጎቱ በእለቱ በተፈጠረው ያለመግባባት በቀላሉ ለህልፈት የሚዳረግ የሰውነት ክፍል በዱላ በመምታት የሆነው ይሁን በማለት የፈፀመውና በተራ የሰው ግድያ ወንጀል ስር የሚሸፈን እንጂ በግፍ ሰው የመግደል ወንጀል በሚያስጠይቅበት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) ድንጋጌ መሰረት የሚጠየቅበትን አግባብ አላገኘንም።ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች 1ኛ አመልካችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539(1ሀ) ስር ጥፋተኛ ያሉት አጠቃላይ የድርጊቱን አፈፃጸም ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ጋር ሳያገናዝቡ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-2) ድንጋጌ መሰረት በመለወጥ 1ኛ አመልካች(ታምራት ደምሴ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ድንጋጌን የተላለፈ ጥፈተኛ ነው በማለት ወስነናል።

ቅጣትን በተመለከተ 1ኛ አመልካች ሊቀጣ የሚገባው በዚህ ችሎት ጥፋተኛ በተባለበት የሕግ ድንጋጌ መሰረት ነው።አመልካች ተራ የሆነ የሠው ግድያ ወንጀል መፈፀሙ በሚገባ ተረጋግጧል።በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ስር ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ደግሞ ሊቀጣ የሚገባው ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት ጽኑ እስራት ነው።

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ "የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወሰነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሰን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ከላይ እንደተገለጸው የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2)ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤አመዛዝኗልም፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ድርጊቱ በተፈጸመበትና ክርክሩ በስር ፍርድ ቤት ታይቶ ዳኝነት በተሰጠበት ጊዜ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ደረጃ ያልወጣለት የነበረ ሲሆን በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ደግሞ ደረጃ የወጣለት ነው፡፡እኛም ጉዳዩን ከዚሁ ከአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንፃር ተመልክተናል፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች ከሟች ጋር ለጠብ የተዳረገው በሟቹ ስድብ ምክንያት ሲሆን ይህም ለወንጀል ድርጊቱ መንስኤው ሟቹ መሆናቸውን የሚያሳይ ሁኖ ለድርጊቱ አፈጻጸም አመልካች የተጠቀመበት መሳሪያም ዱላ የነበረ ሁኖ የዱላው አይነትና አደገኛነትም በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑ ሲታይ አፈፃፀሙ የራሱ የሆነ የተለየ ዘዴ የነበረው መሆኑን የማያሳይ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት የወንጀሉ ደረጃው 2 ሁኖ ይዜው ደረጃ በእርከን 23 ስር የሚወድቅ ነው፡፡በዚሁ እርከን ደግሞ የፍርድ ቤቱ የፍቃድ ስልጣን ከስድስት አመት እስከ ሰባት አመት ከሁለት ወር ነው፡፡ከዚሁ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ የመነሻ ቅጣቱን ይዘን የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን ባለመኖራቸው እርከኑን ከፍ ማድረግ ያለመቻሉን ተገንዝበናል፡፡በሌላ በኩል አመልካች ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያም ሆነ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሉት መሆኑን በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ተደግፎ የተመዘገበለት ያለመሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም በእርከን 23 ስር ካለው የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ 1ኛ አመልካችን (ታምራት ደምሴን) ያርማል፣መሰል ወንጀለኞችን ያስጠንቅቃል ያልነው የቅጣት መጠን ሰባት አመት ሁኖ ስለአገኘን አመልካች በጉዳዩ ላይ የታሰረው ካለ የሚታሰብለት ሁኖ በዚሁ የቅጣት መጠን እንዲቀጣ በማለት ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በማሻሻል ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ

1. በመተከል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04545 ሚያዚያ 5 እና 6 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02856 ግንቦት 02 ቀን 2003 ዓ/ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03200 መስከረም 11 ቀን 2004 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 2ኛ አመልካች በሪሁን ደምሴ፣3ኛ አመልካች ታደለ ሽቱ ሚች ኤርሚያስ ሃይሉን ስለመግደላቸው በበቂና አሳማኝ ሁኔታ ስላልተመሰከረባቸው በእነዚህ አመልካቾች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-1) መሰረት ሙሉ በሙሉ በመሻር አመልካቾቹን በነጻ እንዲሰናበቱ በማለት ወስነናል፡፡አመልካቾቹ በሌላ ወንጀል የማይፈለጉ መሆኑ ከተረጋገጠ ወዲያውኑ ከእስር እንዲፈቱ ተገልፆ የመፍቻ ትዕዛዝ ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይድረሰው ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡
3. 1ኛ አመልካች ታምራት ደምሴ በሚች ኤርሚያስ ኃይሉ ህልፈት ተጠያቂ መደረጉ በአግባቡ ተመስክሮበት ሲሆን የአመልካቹ አድራጎት የሚሸፈነው ግን በወ/ሕ/አንቀጽ 539(1(ሀ) ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 ስር ነው በማለት በዚሁ የሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማድረግ በጉዳዩ ላይ የታሰረው ማናቸውም ጊዜ የሚታሰብለት ሁኖ በሰባት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡
4. በ1ኛ አመልካች በዚህ ችሎት ተሻሽሎ በተወሰነው የቅጣት ውሳኔ መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይድረስ ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98283

መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ተሾሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ሐጐስ ገ/ሄር መኮንን

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል የስነ/ፀ/መ/ኮ - ዐ/ሕግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ፍርድ

የአሁኑ አመልካች በወንጀል ህጉ አንቀጽ 407(2) የተመለከተውን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በትግራይ ክልል በደቡብ ዞን አሰላ ወረዳ ፍ/ቤት ዳኛ ሆኖ ሲሰራ ሥልጣኑን አላግባብ በመጠቀም የመንግስት የአበል አከፋፈል ሥርዓት በመጣስ ለራሱና ለሥራ ባልደረቦች ሊከፈል የማይገባውን ብር 7653.4 እንዲከፈል በማድረጉ በፈፀመው በሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም ወንጀል ተከሷል ሲል የአሁን ተጠሪ ክስ አቅርቦበታል፡፡

ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የአላማጣ ማዕከላዊ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች በተዘዋዋሪ ችሎት ስም ከሥራ ቦታዬ ወደ ቀበሌዎች ሄጃለው በማለት በተሞክሮ ልውውጥ ስም፤ በመሀበራዊ ፍ/ቤትና የመሬት ዳኞች ሥልጠና ስም አበል አላግባብ መውሰዱ ፤ዳኞች ስልጠና ሰጥተዋል በማለት በፔሮል ወደ ቀበሌ እንደወጡ አሰመስሎ አበል መክፈሉ ፤ የሂሳብ መደብ በማይፈቅድበት ሁኔታ በራሱ ስም አበል ወጪ በማድረግ የፅሕፈት መሣሪያ መግዛት እና ከፋይናንስ ደንብ እና መመሪያ ውጭ ስለመስራቱ በራሱ በዝርዝር የተመለከተውን እና የቀረበበትን የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ ማስተባበል ባለመቻሉ እንደ ክሱ አቀራረብ ጥፋተኛ ነው በማለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ተቀብሎ በ1(አንድ) ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 2000 /ሁለት ሺህ /መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔው የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት ቅሬታውን ውድቅ አድርገዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቹ የካቲት 24 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ 5 (አምስት) ገጽ ዝርዝር ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ተጠቃሎ ሲታይ የፍርድ ቤቱ ሥራ እንዳይጐዳ ብሎ የፈፀምኩት መሆኑ እየታወቀ፤በአግባቡም ማይጣራ ተድበስብሶ የታለፈ በመሆኑ፤የቀረቡት ማስረጃዎች ከሚመለከታቸው ህጐች ሳይገናዘብ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑና ፤ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 33075 ባሳለፈው ውሳኔ የዳኝነት ሥራ በሚያከውኑበት ጊዜ የሚፈፅሙ ጥፋቶች እና ስህተቶች ዳኞች በስልጣን ያለ አግባብ መጠቀም በሚል ወንጀል ሊከሠሱ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሎ ተተርጉሞ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ በነፃ ልሰናበት ብለዋል፡፡

ቅሬታቸው ተመርምሮ ፈፀሙት የተባለው ድርጊት ጥፋተኛ በተባሉበት የህግ አንቀጽ ሥር የሚወድቅ መሆኑን ወይም ጉዳዩ ከዳኝነት ሥነ ምግባርና ዲሲፕሊን አኳያ የሚታይ መሆኑን ለማጣራት ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሠጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ሚያዚያ 9/2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በወ/ህ/ቁ.407(2) መከሰሱ እና ጥፋተኛ መባሉ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ፤አስቀድሞ በሰ/መ/ቁ. 33075 የተሰጠው ውሳኔም የዳኝነት ሥራ በመከናወን ላይ እያለ የሚፈፀሙ ጥፋትና ሥህተትን እንጅ መሠል ተግባርን የሚመለከት ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡ አመልካቹም ግንቦት 2/2006 ዓ.ም የተፃፈ ክርክራቸውን የሚያጠናክር የመ/መልስ አቅርበዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ ለመግለፅ የሞከርነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ ይዘን መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ፍሬ ነገሩን የማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣኑ የተሰጠው የሥር ፍ/ቤት አመልካቹ መንግስት የፋይናንስ ህጐች እና ደንቦች ከተፈቀደው ውጭ በአጠቃላይ ብር 7,650.40 እንዲወጣ በማድረግ ለራሱም ሆነ ለሥራ ባልደረቦቹ መጠቀሚያ በማድረግ በኃላፊነቱ አላግባብ መገልገሉን አረጋግጧል፡፡

ይኸው በማስረጃ ተረጋግጧል የተባለው አድራጐት በመንግስት ሥራ ላይ የተፈፀመ ከዳኝነት ሥራ ጋር ተቀላቅሎ ሊታይ የማይገባ የወንጀል ጥፋት ነው፡፡

አመልካቹ በዳኝነት ተሹመው በቋሚት የዳኝነት የመንግስት ሥራን የሚሰሩ የመንግስት ሠራተኛ በመሆናቸው እና ይሠሩበት የነበረው የወረዳ ፍ/ቤትም በመንግስት በጀት ተመድቦለት የዳኝነት መንግስታዊ ሥራ የሚከናወንበት መስሪያ ቤት በመሆኑ በመንግስት ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የሚመለከቱ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች በመሠል ጥፋቶች ላይም በተመሳሳይ ተፈፃሚነት የሚሆኑ ናቸው፡፡ /የወ/ህ/ቁ. 402(1) እና (2) ይመለከታል፡፡

ሌላው መከራከሪያ እና የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ለመባሉ ምክንያት የሆነው ጉዳዩን ከዳኝነት ሥነ ምግባር እና ዲሲፕሊን አኳያ የሚታይ መሆኑን የተመለከተ ነው ፡፡

በትግራይ ክልል ዳኞች እና ሬጅስትራሮችን ለማስተዳደር ተሻሽሎ የወጣው ደንብ ቁጥር 1/2003 በመንግስት ገንዘብ ወይም ንብረት በዳኞች የሚፈፀምን ያላግባብ መጠቀም እና መውሰድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዲስፒሊን ጥፋት አድርጐ ይዟል፡፡ ነገር ግን የዲስፒሊን ደንቡ መሠል ድንጋጌ መያዙ በወንጀል ገረድ የሚኖረን ኃላፊነት የሚያስቀር አይደለም፡፡

የዲስፕሊን ጉዳዩች የሚቋቋሙበት፣ የሚመሩበት ሥርዓት እና ከሚሠጠው ውሳኔ የወንጀል ጥፋቶች ከሚቋቋሙበት፣ከሚመሩበት ሥርዓት እና ከሚሰጠው ውሣኔ ተለይቶ ሊታይ ይገባል፡፡ ስለሆነም የተፈፀመው ጥፋት የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆን አለመሆኑ ከዲስፒሊን ጉዳዩ ጋር ሊያታይ አይገባም፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 33075 ዳኛ ብርቁ ባላዬ እና የአማራ ክልል ስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በተከራከሩበት ጉዳይ ጥር 13/2001 ዓ.ም ባሳለፈው ውሳኔ የዳኝነት ሥራን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚፈፅሙ ስህተቶች እና ጥፋቶች ሁሉ ዳኛን በሥልጣን አላግባብ መገልገል ወንጀል ሊያስጠይቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው መወሠኑ የዳኞችን ህገ መንግስታዊ የውሳኔ ነፃነት ለማጠናከር እንጅ በእጃችን እንዳለው ጉዳይ ከዳኝነት ሥራ ጋር ያልተያያዙ እና የአስተዳደር ስራ ሲያከናውኑ የሚፈፀሙ የወንጀል ጥፋቶች ሁሉ ተጠያቂነትን የሚያስቀር ትርጉም የሚሠጠው ባለመሆኑ አመልካቾች ይኸው ውሳኔ በማመሳሰል ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚ እንዲሆን ያቀረቡት ጥያቄ በህጉ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በአጠቃላይ አመልካቾች በነበራቸው የሥራ ኃላፊነት ምክንያት ሊጠብቅ እና ሊከላከሉት የሚገባን የህዝብ እና የመንግስት ንብረት ከህግ ውጭ ሥልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ለፈፀሙት ጥፋት በስር ፍ/ቤቶች የተላለፈባቸው ውሣኔ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰጠው መ/ቁ. 6111/06 ታህሳስ 3 ቀን 2006 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ ፤የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.58434 ግንቦት 13 ቀን 2005 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ እና በደቡባዊ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት የአላማጣ ምድብ ችሎት በወ/መ/ቁ.02867/05 የካቲት 26/2005 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.92826

ጥር 05 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- የደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀሐይ መጫሎ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ጉዳይ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች የክልሉን የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽንን በመወከል በአሁኗ ተጠሪና በሌሎች ሁለት ሰዎች ላይ በካፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች ክስ ይዘትም፡- ተጠሪና በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ኢምቶ ወ/ማሪያም አቶ ዳዊት ደስታ የተባሉት ግለሰቦች ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሳቸው ለማግኘት በማሰብ በዬቻ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ውስጥ የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ኢምቶ ወ/ማሪያም ዋና ገንዘብ ያዥ፣የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ የክፍያ ኦፊሰር፣ቼክ አዘጋጅና ፈራሚ፣የስር ሶስተኛ ተከሳሽ የነበሩትና በብይን በነፃ የተሰናበቱት አቶ ዳዊት ደስታ ደግሞ የክፍያ ሰራተኛ እና ቼክ ፈራሚ በመሆን እየሰሩ የአሁኗ ተጠሪ ከኢትዩጵያ ንግድ ባንክ ቦንጋ ቅርንጫፍ ከሂሳብ ቁጥር GOV 787 ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ) ብር ወጪ ተደርጎ ለስር አንደኛ ተከሳሽ እንዲከፈል ቁጥሩ 0741998 የሆነውን ቼክ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ.ም አዘጋጅተው ከስር ሶስተኛ ተከሳሽ ጋር ፈርማ በኃላፊ ሳይታዘዙ በመስጠታቸውና የስር 1ኛ ተከሳሽም ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ) ከተጠቃሹ ባንክ አውጥቶ ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ)) እና 676(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በግብረአበርነት ክባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ክሱን ክደው የተከራከሩ ሲሆን አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ ካሰማ በሁዋላ የተጠሪ የመከላከል መብታቸው ተጠብቆላቸው የመከላከያ ምስክሮችን አሰምተዋል፡፡የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ በመከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ አልቻሉም በሚል ምክንያት ክስ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጓል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት አስልቶ በአስራ አራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመት ፅኑ እስራት እና በብር 7000.00(ሰባት ሺህ) እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግን ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ተደርጎ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የወንጀል ድርጊት መፈፀማቸው መረጋገጡን ተቀብሎ አድራጎቱ የሚሸፈንበትን ድንጋጌ በተመለከተ አመልካች ተጠሪ ገንዘቡን ለግል ጥቅማቸው ስለማዋላቸው ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ስለማዋላቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት በዓቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ የተጠቀሰውን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113 (2) መሰረት ወደ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420(1) ለውጦ በዚሁ ድንጋጌ ስር የሙያ ግዴታ የመጣስ አድራጎት ፈጽመዋል በማለት ወስኗል፡፡ቅጣቱንም በተመለከተም በዚሁ በተለወጠው ድንጋጌ ስር በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ደረጃ ላልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎች ደረጃ የሚወጣበትን አግባብ ዘርዝሮና ከግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ጋር በማገናዘብ መመርመሩን ገልፆ ተጠሪ በአንድ አመት ቀላል እስራት እና በብር 5000.00 (አምስት ሺህ) ብር እንዲቀጡ ወስኗል፡፡የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-የተጠሪ አድራጎት ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ሁኖ እያለ የስራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የተፈፀመ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 676(1) ሳይሆን በአንቀጽ 420(1) ስር ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸውም ቀርበውም በፅሑፍ በሰጡት መልስ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ሕጋዊ ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 (2) በግልፅ ደንግጓል፡፡እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች የሚመለከት ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደምተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ አንቀፅ 24፣57 እና 58 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን የሚመለከቱ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉት በመንግስት መስሪያ ቤት በክፍያ ኦፊሰርነት፣ቼክ አዘጋጅነትና ፈራሚነት የስራ መደብ ላይ ተመድበው ሲሰሩ በቀን 30/10/2002 ዓ/ም ቁጥሩ 0741998 በሆነ ቼክ ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ) ለስር አንደኛ ተከሳሽ እንዲከፈል አዘጋጅተው በቼኩ ጉማጅና በባንክ ክፍያ ደረሰኝ ላይ ሳያስፈርሙ ሰጥተው የስር አንደኛ ተከሳሽ ከኢትዩጵያ ንግድ ባንክ ቦንጋ ቅርንጫፍ ከሂሳብ ቁጥር GOV 787 ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ) ብር ወጪ አድርጎ ለግል ጥቅሙ እንዲያውል አድርገዋል፣ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህንኑ ያደርጉትም ያዘዛቸው ኃላፊ ሳይኖር መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተጋግጧል በሚሉ ምክንያቶች መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ከክርክሩ አመጣጥና ከስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ይዘት አንጻር በዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈነው በየትኛው ድንጋጌ ስር ነው? የሚለው ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች የተከሰሱትና በስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባሉት የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 676/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከመንግስት የሂሳብ ቁጥር ብር 100,000.00 ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲውል በማድረጋቸው ከባድ የእምነት ማጉደልና የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል ተብሎ ነው፡፡የወንጀል ሕጉ 676 በወንጀል ሕግ 675 የሚፈፀመውን የእምነት ማጉደል ወንጀል የሚከብ ድበትን ሁኔታ የሚዘረዝር ነው፡፡የድንጋጌው መሰረታዊ ማቋቋሚያ ነጥቦች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675 ስር የተመለከቱት የእምነት ማጉደል ወንጀል ማቋቋሚያ ሁኔታዎች ስለመሆናቸው የሁለቱ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል የሚሆነው ደግሞ የመንግስት ሰራተኛ ወይም የመንግስት ሰራተኛ ያልሆኑት ሰዎች በመንግስት ንብረት ላይ የእምነት ማጉደል ተግባሩን መፈፀማቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡በወንጀል ሕጉ 675 ንዑስ አንቀጽ 3 ተከሣሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም ባደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሀሳብ እንዳለው የሚቆጠር መሆኑን በግልፅ ደንግጓል፡፡ይህ የህግ ግምት የሚስተባበለው ደግሞ በተከሳሹ ነው፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪን ተጠያቂ ያደረጋቸው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 420(1) ስር ነው፡፡በዚህ ድንጋጌ የወንጀል ተጠያቂነት የሚመጣው ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የሥራ ግዴታ ተግባሩን በአግባቡ ሳይፈጽም በመቅረቱ በመንግስት፣በህብረተሰብ ወይም በግለሰብ ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሶ የተገኘ እንደሆነ ነው፡፡የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 420 ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው የመወሰን ሥልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ባለባቸው ሰዎች ነው፡፡ስለሆነም በአንቀጽ 420 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት አንድን ሰው ተጠያቂ ለማድረግ የሙያ ተግባሩንና ሥራው በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመፈፀሙ ምክንያት በመንግስት ላይ ጉዳት መደረሱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉደይ ስንመለስ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተጠሪ አድራጎት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420(1) ስር የሚሸፈን ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ አድራጎቱን የፈፀሙት ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ለግል ጥቅሙ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ለማዋል በማሰብ መሆኑን በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል አቢይ ምክንያት ነው፡፡በእርግጥ ተጠሪ የተከሰሱት በከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል መሆኑ ሲታይ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 676(1) የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675 መሰረታዊ የወንጀል ማቋቋሚያ የያዘ በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675(3) በተመለከተው የሕግ ግምት መሰረት ተከሣሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም ባደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሀሳብ እንዳለው የሚቆጠር መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪ የክፍያ ኦፊሰር፣ቼክ አዘጋጅና ፈራሚ መሆናቸው እንጂ በመሰረታዊ የስራ ሂደት መሰረት በጉርዱ ላይ ለመመዝገብ የስራ ሂደቱን አስተባባሪ ትዕዛዝ መጠበቅ የግድ የሚላቸው መሆኑን የክርክሩ ሂደት ማስገንዘቡ ሲታይ ተጠሪ ብቻቸውን የመወሰን ሥልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ብቻ የነበራቸው ናቸው ለማለት የሚያስችል ሁኖ አግኝተናል፡፡በስራ መደባቸው ተጠሪ ብቻቸውን የመወሰን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጣን ሳይኖራቸው ባልተገባ መንገድ ቼኩን አዘጋጅተውና ፈርመው ለስር 1ኛ ተከሳሽ በመስጠት ከመንግስት የባንክ ሂሳብ ውስጥ ብር 100,000.00 ወጪ ሁኖ ለስር 1ኛ ተከሳሽ የግል ጥቅም እንዲውል ማድረጋቸው በመንግስት ሰራ ተመድበው በመስራት ላይ ባሉበት ሁኔታ በመንግስት ንብረት ላይ የስራ ኃላፊነት ወይም ግዴታቸውን ያለመወጣታቸውን የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420(1) የተፈፃሚነት አድማሱን ከተጠሪ የስራ ኃላፊነት ዝርዝር ይዘት እና በወቅቱ ከነባራቸው ተሳትፎ ጋር በማዛመድ የተጠሪ አድራጎት የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚፈፀም ወንጀል ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 00723 ሐምሌ 02 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-2)) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈነው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 420(1) ስር ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/89676

ጥር 4 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - ዐቃቤ ሕግ ምርምር ጥጋቡ ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ሣሙኤል ፈቃዱ ኃይሌ-ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ተጠሪው በተከሰሰበት በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል ክስ ባሰማው የመከላከያ ማስረጃ የዐቃቤ ሕግን ክስ እና ማስረጃ ከጥርጣሬ ላይ የጣለ በመሆኑ በወንጀሉ ጥፋተኛ አይደለም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪው ላይ በ04/07/2004 ዓ.ም.አዘጋጅቶ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ተከሳሹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በ08/06/2004 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት ከ10፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 03/09 ክልል ልዩ ቦታው ደጃች ውቤ ሰፈር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ውስጥ ሣህሊት ብርሃን የተባለችውንየሁለት ዓመት ከስምንት ወር ዕድሜ ያላትን የግል ተበዳይ ሕጻን የለበሰችውን ልብስ ዝቅ በማድረግ እግሩ ላይ አስቀምጦ የግብረ ስጋ ግንኙነት በመፈጸም የክብረ ንጽህናዋ የታችኛው የቀኝ ክፍል እንዲቀደድ ያደረገ በመሆኑ በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል አድርጓል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቆ መቃወሚያ እንደሌለው ገልጾ ወንጀሉን አላደረግሁም በማለቱ ፍርድ ቤቱ በተጠሪ በኩል የቀረቡ የግል ተበዳይ ሕጻንን ጨምሮ የአራት ምስክሮችን ምስክርነት ከሰማ እና በ09/06/2004 ዓ.ም. ከየካቲት 12 ሆስፒታል የተሰጠ የሕክምና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳበት መሆኑን ገልጾ አመልካች መከላከያውን ማሰማት እንዲጀምር በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚሁ መሰረት አመልካች በ08/06/2004 ዓ.ም. ከቀኑ 7፡00 ሰዓት ላይ ከእናቱ፣ከሕጻን ልጁ እና ከሰራተኞቹ ጋር ከእህቱ ቤት መጥተው ምሳ ከበሉ በኃላ ሰራተኛዋ ቡና አፍልታ እስከ 11፡00 ሰዓት ድረስ መቆየታቸውን፣ተከሳሽ በ11፡00 ሰዓት ወጥቶ ወደ ቤተክርስቲያን የሄደ መሆኑን፣በዚህ መሀል የግል ተበዳይ ሕጻን ወደ ቤቱ አለመምጣቷን፣በአካባቢው ሣሙኤል በሚባል ስም የሚጠራ ሌላ ሰው መኖሩን ያስረዱልኛል በማለት ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የመከላከያ ምስክሮቹም እናውቃለን ስላሏቸው ፍሬ ነገሮች በጭብጡ ከተገለጸው በተጨማሪ በተከሳሽ እና በግል ተበዳይ ቤተሰቦች መካከል የቆየ ቂም በቀል መኖሩን እና የግል ተበዳይ ሰራተኛ አባት የግል ተበዳይ ቤተሰቦችን ልጄን በሀሰት አስመስክራችኃል በማለት ተከሳሽ ከተያዙ በኃላ መጥተው ልጃቸውን የወሰዱ መሆኑን ጭምር እና እነዚህኑ ፍሬ ነገሮች ሊያውቁ ስለቻሉበት ሁኔታ በዝርዝር በመግለጽ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡የግል ተበዳይ በጋንዲ ሆስፒታል በድጋሚ እንድትመረመር ተጠሪው በጠየቀው እና ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረትም ምርመራው ተከናውኖ የሕጻኗ የድንግልና አካል የሆነው ክፍል የተጎዳ እና ጉዳቱም የቆየ መሆኑን የሚገልጽ ከሆስፒታሉ በ11/10/2004 ዓ.ም. የተጻፈ ማስረጃ ቀርቦ ተያይዟል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተጠሪው ባለማቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረበትን ፍሬ ነገር ከጥርጣሬ ላይ በሚጥል ሁኔታ አስተባብሏል በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 149(2) ድንጋጌ መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይግባኙን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195(1) ድንጋጌ መሰረት ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው የመድፈር ወንጀል አልፈጸመም ተብሎ በነጻ የመለቀቁን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በክሱ መሰረት ያስረዱልኛል በማለት ያሰማቸው አራት ምስክሮች በተሰሙበት በቅደም ተከተል መሰረት የግል ተበዳይዋ ሕጻን፣የሕጻኗ እናት፣የሕጻኗ የእናት ወገን አክስት እና የሕጻኗ ሞግዚት ሲሆኑ የምስክርነታቸው ይዘት ጠቅለል ተደርጎ ሲታይም የሕጻኗ ቤተሰቦች እና ተከሳሹ ጎረቤታሞች መሆናቸውን፣ሕጻኗ በ08/06/2004 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት ከ10፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ከተከሳሹ መኖሪያ ቤት ቆይታ ወደ ቤቷ የተመለሰች መሆኑን፣የተመለሰችውም እያለቀሰች መሆኑን፣ምን ሆና እንዳለቀሰች ሞግዚቷ የጠየቀቻት ቢሆንም ሕጻኗ አልናገርም ያለቻት መሆኑን፣በወቅቱ እናቷ ከቤት ያልነበረች መሆኑን፣ማታ ላይ አሞኛል በማለት ወደ ሀኪም ቤት እንድትወስዳት እናቷን የጠየቀቻት መሆኑን፣እናቷም ሕጻኗ እንደዚህ ያለቻት ቀደም ሲል ሀኪም ቤት ትወስዳት ስለነበረ እንደሆነ በመገመት ደህና ነሽ አላመመሽም ተኚ ያለቻት መሆኑን ሰውነቷን እንድትጠርግላት እና ተከሳሹ በጣቱ ወይም በሽንት መሸኛው ከሽንት መሸኛዋ ላይ የወጋት መሆኑን ሕጻኗ በነጋታው የጠየቀቻት እና የነገረቻት መሆኑን፣እናቷ ገልጣ ስትመለከት በሕጻኗ ብልት አካባቢ ቁስል እና የደረቀ የወንድ የዘር ፍሬ ያየችመሆኑን፣ወዲያውኑ ይዛት እህቷ ወደ ሆነችው 3ኛ ምስክር ወስዳ ያሳየቻት እና በመቀጠልም ወደ ሆስፒታል ወስደው ያስመረመሯት እና ውጤቱም መደፈሯን ያረጋገጠ መሆኑን፣ተከሳሹ የስድስት ወር ሕጻን ልጅ ያለው መሆኑን፣የግል ተበዳይ ሕጻን የተከሳሹን ልጅ ለማጫወት ሁሌም ወደተከሳሹ ቤት ትሄድ የነበረ መሆኑን፣ቤታቸው ቅርብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለቅርብ በመሆኑ የምትሄደው ብቻዋን መሆኑን፣ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ዕለትም ሕጻኗ የሄደችው በዚሁ ሁኔታ መሆኑን፣ሕጻኗ ወደ ተከሳሹ ቤት ሄዳ እዚያው በነበረችበት ጊዜ ሞግዚቷ የሆነችው 4ኛ ምስክር የሕጻኗን መኖር ለማረጋገጥ ወደ ተከሳሹ ቤት ሄዳ በሩን ስታንኳኳ ተከሳሹ እንደከፈተላት እና የሕጻኗን መኖር ስትጠይቀው መኖሯን የነገራት መሆኑን፣በወቅቱም ከተከሳሹ ቤት ውስጥ ከእርሱ እና ከግል ተበዳይዋ ህጻን በቀር ሌላ ሰው ያልነበረ መሆኑን እና መሰል ፍሬ ነገሮችን የሚገልጽ ነው፡፡ከየካቲት 12 ሆስፒታል በ09/06/2004 ዓ.ም. የተሰጠው የሕክምና ማስረጃም የሕጻኗ ድንግልና የታችኛው የቀኝ ክፍል ትኩስ መቀደድ የታየበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሕጻኗ ድርጊቱ ተፈጽሞባታል በተባለበት ጊዜ የሁለት ዓመት ከስምንት ወር ዕድሜ የነበራት ሲሆን በፍርድ ቤት ቀርባ ምስክርነቷን የሰጠችውም ድርጊቱ ተፈጸመ ከተባለበት ቀን አንስቶ ሁለት ወር ባልሞላው ጊዜ ውስጥነው፡፡በማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ እርዳታ እና በተመሳሳይ ዕድሜ አካባቢ ለሚገኙ ሕጻናት በሚያመች ሁኔታ በተዘጋጀ የችሎት ፋሲሊቲ በመታገዝ ሕጻኗ የሰጠችው ምስክርነት በተለይ ሲታይ አዋቂ ሰዎች በሚጠቀሙበት ዓይነት አነጋገር እና አገላለጽ የተሰጠ ባይሆንም የተፈጸመባትን ድርጊት ዓይነት፣ድርጊቱን የፈጸመባትን ሰው ማንነት፣ፈጻሚው ድርጊቱን የፈጸመው በየትኛው የአካል ክፍሉ በመጠቀም እና በየትኛው የአካል ክፍሏ ላይ መሆኑን በግልጽ መገንዘብ በሚያስችል ሁኔታ የተሰጠ መሆኑን እና ድርጊቱን ፈጽሞብኛል ያለችውን ሰው ለይታ እንድታሳይ ተጠይቃም ወደ ችሎቱ አዳራሽ በመምጣት የአሁኑን ተጠሪ ለይታ ያሳየች መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት አጠቃላይ ይዘቱ ከላይ የተመለከተውን የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተጠሪው ባለማቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከረበትን ፍሬ ነገር ከጥርጣሬ ላይ በሚጥል ሁኔታ አስተባብሏል በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 149(2) ድንጋጌ መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ለሰጠው ውሳኔ በመከላከያ ምስክሮች ከተሰጠው ምስክርነት ውስጥ መሰረታዊ ምክንያቶች አድርጎ የወሰደው፡-

1. የግል ተበዳይዋ ሕፃን ቤተሰቦች እና ተከሳሹ በሚኖሩበት አካባቢ ከተከሳሹ ጋር በተመሳሳይ ስም የሚጠራ በሃያ ዓመት ዕድሜ አካባቢ የሚገኝ ሌላ ሰው አለ መባሉን፣
2. በተከሳሽ ቤተሰቦች እና በግል ተበዳይ የእናት ወገን ቤተሰቦች መካከል የቆየ ቂም በቀል አለ መባሉን እና
3. የግል ተበዳይ ሰራተኛ (የሕጻኗ ሞግዚት) አባት የግል ተበዳይ ቤተሰቦችን ልጅን በሀሰት አስመስክራችኃል በማለት ተከሳሽ ከተያዘ በኃላ መጥተው ልጃቸውን ወስደዋል መባሉን እንደሆነ ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡

የግል ተበዳይዋ ሕፃን ቤተሰቦች እና ተከሳሹ በሚኖሩበት አካባቢ ከተከሳሹ ጋር በተመሳሳይ ስም የሚጠራ በሃያ ዓመት ዕድሜ አካባቢ የሚገኝ ሌላ ሰው አለ መባሉን በተመለከተ በመሰረቱ የድርጊቱን ፈጻሚ ማንነት በተመለከተ በአመልካች ምስክሮች የተሰጠው ምስክርነት ድርጊቱን የፈጸመው ሣሙኤል የሚባል በሕጻኗ ቤተሰቦች መኖሪያ አካባቢ የሚኖር ሰው ነው ተብሎ በደፈናው እና የድርጊቱን ፈጻሚ ማንነት ለይቶ ለማረጋገጥ በማያስችል ወይም በሚያጠራጥር ሁኔታ የተሰጠ ሳይሆን ድርጊቱን የፈጸመው የአሁኑ ተጠሪ ስለመሆኑ በስም፣በመኖሪያ ቤቱ ማለትም ድርጊቱ በተፈጸመበት ቤት ልዩ አድራሻ እና በአካላዊ መለያው ጭምር ተለይቶ እና ተረጋግጦ የተሰጠ መሆኑን ይዘቱ ከላይ የሰፈረው የምስክርነቱ ይዘት በግልጽ የሚያመለክት በመሆኑ በአካባቢው ከተከሳሹ ጋር በተመሳሳይ ስም የሚጠራ ሌላ ሰው የመኖሩ ወይም ያለመኖሩ ጉዳይ ለክርክሩ አግባብነት ያለው የመከላከያ ፍሬ ነገር ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብ የለም፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ለዚህ ዓይነቱ ለክርክሩ አግባብነት ለሌለው የመከላከያ ፍሬ ነገር ዋጋ ሰጥቶ ተጠሪው ባሰማው መሳለከያ ማስረጃ በአመልካች ማስረጃ የተመሰከረበትን ፍሬ ነገር ከጥርጣሬ ላይ በሚጥል ሁኔታ አስተባብሏል ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱም ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡

በተከሳሽ ቤተሰቦች እና በግል ተበዳይ የእናት ወገን ቤተሰቦች መካከል የቆየ ቂም በቀል አለ መባሉን በተመለከተ የግል ተበዳይ እናት የሆኑት 2ኛ ምስክር ተጠይቀው በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የቆየ ጥል ነበረ መባሉን እህታቸው ከሆኑት 3ኛ ምስክር የሰሙት ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ እንደሆነ፣ሌሎች የምስክሯ ቤተሰቦች በተለያየ ምክንያት አካባቢውን የለቀቁ መሆኑን እና አሁን በአካባቢው የቀሩት ምስክሯ ብቻ መሆናቸውን እና ድርጊቱ ከመፈጸሙ በፊት ነበረ ስለተባለው ጠብ የሚያውቁት ነገር ስላልነበረ ከከሳሹ ጋር በክፉ እና በደስታ ቀን ይደራረሱ እንደነበረ በመግለጽ የመሰከሩ ሲሆን 3ኛ ምስክር በበኩላቸው ጠቡ ተከስቶ የነበረው ከ35 ዓመታት በፊት መሆኑን እና የጠቡን መንስኤ ጭምር በመግለጽ መስክረዋል፡፡ተጠሪው እና የግል ተበዳይ ቤተሰቦች ጨርሰው የማይነጋገሩ እና 3ኛ ምስክር በገለጹት መሰረት በክፉ እና በደስታ ቀን የማይደራረሱ ስለመሆኑ በተጠሪው ምስክሮች የተነገረ ነገር የለም፡፡ምስክርነት በሰጡበት ጊዜ የ2ኛ እና የ3ኛ ምስክሮች ዕድሜ እንደቅደም ተከተሉ 30 እና 44 ዓመት መሆኑንም የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ተጠሪው በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የቆየ ቂም በቀል አለ በሚል ጭብጥ ዙሪያ መከላከያ ምስክሮችን ያሰማው የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የቆየውን ቂም በቀል መሰረት በማድረግ በሀሰት የመሰከሩበት መሆኑን ግምት ለማስወሰድ እንደሆነ የሚታመን ነው፡፡ይሁን እንጂ በተጠሪው ላይ ዋነኛ እና የዓይን ምስክር ሆና የቀረበችው የግል ተበዳይ ስለቂም በቀል ልታውቅ የማትችል የ2 ዓመት ከ8 ወር ሕጻን በመሆኗ እና የአካባቢ ማስረጃ የሆነችው የሕጻኗ ሞግዚት 4ኛ ምስክርም የ14 ዓመት ዕድሜ ያላት እና በግል ተበዳይ እናት ቤት የቆየችው ለጥቂት ዓመታት ብቻ እንደሆነ መዝገቡ የሚያመለክት በመሆኑ እነዚህ ሁለቱ ምስክሮች ምስክርነት የሰጡት በቂም በቀል ሊሆን የሚችልበት ዕድል ፈጽሞ አለመኖሩን ከምስክርነታቸው አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚያዳግት አይደለም፡፡ ምስክርነታቸውም በተጨባጭ የሀኪም ማስረጃ የተደገፈ ጭምር ነው፡፡በመሆኑም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት የተሰጠው በቂም በቀል ስለመሆኑ ምንም ዓይነት አመላካች ፍንጭ በሌለበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች ለደረሱበት ድምዳሜ ይህንን ያልተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሰረት ማድረጋቸው አጠቃላይ የማስረጃ ምዘና መርህን መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

የግል ተበዳይ ሰራተኛ አባት የግል ተበዳይ ቤተሰቦችን ልጇን በሀሰት አስመስክራችኃል በማለት ተከሳሽ ከተያዙ በኃላ መጥተው ልጃቸውን ወስደዋል መባሉን በተመለከተ በዚህ ረገድ ምስክርነት የሰጠችው 3ኛ የመከላከያ ምስክር ስትሆን የምስክርነቷ ይዘትም የሠራተኛዋ አባት ወደግል ተበዳይ እናት ስልክ ደውለው ልጃቸውን በሀሰት እንደዳስመሰከሯት ልጃቸው የነገረቻቸው መሆኑን እና የግል ተበዳይ እናትም የምትመሰክረው ነገር ስላለ መስክራ ትመጣልሃለች ብለው መመለሳቸውን የሚገልጽ ነው፡፡በመሰረቱ የመከላከያ ምስክሯ የመሰከረችው የስልክ ንግግሩን በቀጥታ ሰምቻለሁ በማለት ሳይሆን የስልክ ንግግሩን ከሰሙት የግል ተበዳይ ጎረቤቶች ሰማሁ በማለት ነው፡፡ተጠሪው ይህንን የስልክ ንግግር በቀጥታ ሰምተናል ያሉትን ጎረቤቶች አቅርቦ ማሰማት ያልቻለበት ምክንያትም ሆነ የጎረቤቶቹ ማንነት አልተገለጸም፡፡በሌላ በኩል ሠራተኛዋ በፍርድ ቤት ቀርባ ምስክርነቷን የሰጠችው የስልክ ንግግሩ ተደረገ ከተባለበት ጊዜ በኃላ ሲሆን በተጠሪው ጠበቃ ለቀረበላት መስቀልኛ ጥያቄ ምስክርነቷን እንድትሰጥ በግል ተበዳይ ቤተሰቦች በኩል የደረሰባት ምንም ዓይነት ተጽዕኖ አለመኖሩን በማረጋገጥ መመስከሯን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ከላይ በዝርዝር በተመለከተው አግባብ በከሳሽ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ወደጎን ትቶ በመከላከያ ምስክሮች የተነገሩ ነገር ግን ለክርክሩ አግባብነት የሌላቸውን እና ያልተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በዐቃቤ ሕግ የዓይን፣የአካባቢ እና የሀኪም ማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ጋር በመመዘን ተጠሪው ባሰማቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከረበትን ፍሬ ነገር ከጥርጣሬ ላይ በሚጥል ሁኔታ አስተባብሏል በማለት የደረሰበት ድምዳሜም ሆነ ይህንን ድምዳሜ መሰረት አድርጎ ተጠሪን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 149(2) ድንጋጌ መሰረት በነፃ በማሰናበት የሰጠው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ የማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርሆዎችን መሰረት ያላደረገ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 192326 በ30/11/2004 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 129168 በ28/05/2005 ዓ.ም. የጸናውን ውሳኔ በመሻር ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት በዓይን፣በአካባቢ እና በሀኪም ማስረጃ ያስረዳበትን የወንጀል ፍሬ ነገር በመካለከያው ያላስተባበለ በመሆኑ ተጠሪው በተከሰሰበት በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ሀ) መሰረት ወስነናል፡፡
2. ተጠሪው ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ በቁጥጥር ስር አቆይቶ እንዲያቀርበው ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየታቸውን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በቀጣይ ቀጠሮ በጽሁፍ ያቅርቡ፡፡
4. ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን የቅጣት አስተያየት ለመቀበል 20/05/07 ዓ.ም ተቀጠረ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 89676

ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - ዐ/ሕግ ምርምር ጥጋቡ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሳሙኤል ፍቃዱ ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡን የተቀጠረው የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ነው፡፡ በዚህም መሰረት መዝገቡን መርምረን ተከታዩን የቅጣት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ቅ ጣ ት

1. አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሁኖ ከተገኘ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ያለበት ሲሆን ቅጣቱ የሚወሰነው ደግሞ ስራ ላይ በዋለው በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ታይቶ ነው፡፡ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/1/ ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአስራ አምስት አመት እስከ ሃያ አምስት ለሚደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ነው፡፡
2. በመሰረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀፅ 1 ስር ሲደነግግ "የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል ህጉ በአንቀፅ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሰረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኽው አንቀፅ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሰብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃወች አወሳሰን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀፅ ስር ያሉ ንዑስ አንቀፆች የሚያሳዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድጋጌዎች መሰረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ የነሳሱትን ምክንያቶችና የአሳቡን አላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነ ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሰን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ ከላይ እንደተገለፀዉ የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 88/2/ ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ሁሉ ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም፡፡

3. እንደ ቅጣት መመሪያው መወሰን እንዲቻል ደግሞ በተጠሪ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከግራ ቀኙ ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህ አግባብ ቅጣቱ ከመሰላቱ በፊት ግን ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ክሱ ሲመረትም ሆነ በበታች ፍርድ ቤቶች ክርክር ሲካሄድ ደረጃ ያልወጣለት ቢሆንም በዚህ ችሎት ጉዳዩ በመታየት ላይ እያለና የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በመሆኑ በዚሁ መመሪያ መሰረት የወንጀል ህጉ አንቀፅ 627 ደረጃ የወጣለት ድንጋጌ ነው፡፡ ተጠሪ ድርጊቱን የፈፀሙት እድሜዋ ዘጠኝ አመት ካልሞላት ሴት ህፃን ላይ በመሆኑ የወንጀሉ ደረጃ 2 ሁኖ የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 35 ነው፡፡ በዚህ እርከን ለፍርድ ቤቱ የተተወው ፍቃደ ስልጣን ከአስራ ስድስት አመት ከስድስት ወር እስከ አስራ ዘጠኝ አመት ከስድስት ወር ነው፡፡ መነሻ ቅጣቱም በዚሁ ሬንጅ ውስጥ የሚያዝ ሲሆን በተጠሪ ላይ መጨረሻ ላይ የሚጣለው የቅጣት መጠን የሚታወቀው ግን የማክበጃ እና የማቅለያ ምክንያቶች ታይተው ስሌቱ ከተሰራ በኋላ ነው፡፡ በዚህም አግባብ የቅጣት መጠኑን ማስላት የግድ ሲሆን በተጠሪ ላይ በዓቃቤ ሕግ በኩል ቅጣቱን ሊያከብዱ ይገባል ተብለው የተጠቀሱት ምክንያቶች የድርጊቱ አፈፃፀም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84/1/ሀ/ የተጠቀሰው መጥፎ አመልካችና ወራዳነትን ያሳያል እንዲሁም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84/1/ሠ// መሰረት ድርጊቱ የተፈፀመው የተለዩ እንክብካቤ በሚያስፈልጋት ህፃን ልጅ ላይ ነው የሚሉት ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ ምክንያቶች ከወንጀል ሕጉ አንቀፅ 627 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጀውን ሲያወጣ እድሜን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ከመሆኑ አንፃር የወንጀሉ ድርጊት ማቋቋሚያ ነጥቦች ሊባሉ የሚችሉ በመሆኑና በወንጀል ህጉ አንቀፅ 82/2/ ድንጋጌ አንፃር በቅጣት ማክበጃ ምክንያትነት መያዙ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አቃቤ ሕግ በቂ ጊዜ ተሰጥቶት ባቀረበው የቅጣት አስተያየት ተጠሪ የወንጀል ሪኮርድ አለባቸው የሚል ግልፅ አስተያየት አላቀረበም፡፡ ይህም ተጠሪ ሪኮርድ ያልቀረበባቸው መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ በመሆኑ ይኼው ምክንያት በማቅለያነት እንዲያዝላቸው የሚያደርግ ነው፡፡ ሌላም ተጠሪ ያቀረቡት የቅጣት ማቀለያ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት ሲሆን ከራሳቸው ልጆች በተጨማሪ የዘመድ ልጅ የሆኑትን ሁለት ህፃናትን የሚያስተዳድሩ መሆናቸውን ገልፀው በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን አቃቤ ሕግ በዚህ በኩል ክርክር ካለማቅረቡም በላይ ችሎቱም እነዚህ ምክንያቶች የቤተሰብ አስተዳዳሪነት በጠቅላላ ቅጣት ማቅለያነት፣ የዘመድ ልጆችን በመንከባከብ የማስተማር ሰብዓዊነት ተግባር መፈፀማቸው ደግሞ በልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅጣት ማቅለያነት ሊያዝ የሚገባ ሁኖ አግኝቷል፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ተጠሪ ሶስት ህጋዊ የሆኑ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሏቸው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ድርጊቱን በተፈፀመበት የካቲት 08 ቀን 2004 እና ክሱ የካቲት 19 ቀን 2004 ዓ.ም ተመስርቶ ክርክሩ በስር ፍርድ ቤት ታይቶ ዳኝነት በተሰጠበት ጊዜ በነበረበት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ደረጃ ያልወጣለት የነበረ ሲሆን በተሻሻለውየቅጣት አወሳሰን መመሪያ ደግሞ ደረጃ የወጣለት ነው፡፡ እኛም የቅጣት ማቅለያ ዋጋ አያያዝን ከወንጀል ሕጉ አንቀን 6 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር ለተጠሪ የተሻለ ሁኖ ያገኘነው ነባሩ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በመሆኑ የቅጣቱን መጠን ከዚህ አንፃር ተመልክተናል፡፡

ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ እንዲቀጡ በመነሻነት የሚያዘው እርከን 35 በመሆኑ በዚህ እርከን መነሻ ሲያዝ የቅጣት መጠኑ ከሰባት አመት በላይ በመሆኑ ተጠሪ ያላቸው ሶስት የቅጣት ማቅለያዎች በመመሪያው ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 13/8/ ድንጋጌ መሰረት እያንዳንዳቸው ሶስት እርከን የሚያስቀንሱ በመሆኑ ከእርከን 35 ወደ እርከን 26 መውረድን፣ በዚህ እርከን ውስጥ ተገቢውን ቅጣት መወሰን የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ቅጣቱን ስናሰላው ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው በእርከን 26 ስር ለፍርድ ቤቱ በተተወው የፍቅድ ስልጣን ማለትም ከሰባት አመት ከስምንት ወር እስከ ዘጠኝ አመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራት ውስጥ ነው፡፡ ከእነዚህ የእስራት ጊዜያት ተጠሪን ያርማል፣ ሌሎች መሰል አጥፊዎችን ከወዲሁ ያስጠነቅቃል ብለን ያመነው ሰባት አመት ከስምንት ወር ፅኑ እስራት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች ተጠሪ በጉዳዩ ላይ የታሰሩት **<u>ማናቸውም ጊዜ ካለ</u>** የሚታሰብላቸው ሁኖ ተጠሪ **<u>በሰባት አመት ከስምንት ወር ጽኑ እስራት</u>** ሊቀጡ ይገባል በማለት በድምፅ ብልጫ ወስነናል፡፡

የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤትም በተጠሪ ላይ በዚህ ችሎት የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>የ ሃ ሳ ብ ል ዩ ነ ት</u>

በአብላጫ ድምፅ በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ የተጠሪው የዘወትር ፀባይ መልካምነት በማቅለያ ምክንያትነት ሊያዝ ይገባል የተባለው ዐ/ሕግ በቂ ጊዜ ተሰጥቶት እያለ ተጠሪ የወንጀል ሪኮርድ ያለባቸው ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም በማለት ነው፡፡ በርግጥ አመልካች ባቀረበው የቅጣት አስተያየት ላይ ተጠሪ የወንጀል ሪኮርድ ያለባቸው ስለመሆኑ የቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይሁን እንጅ ተጠሪው ከሌሎ ውጤቱ የታወቀ /የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት/፣ ከፊሉ ደግሞ የመጨረሻ ውጤቱ ያልታወቀ የኋላ የወንጀል ታሪክ የነበራቸው ስለመሆኑ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት መዝገብ በግልፅ ያመላክታል፡፡ ተጠሪው በኋላ የወንጀል ታሪክ የነበራቸው ስለመሆኑ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት መዝገብ በግልፅ ያመላክታል፡፡ ተጠሪው በኋላ የወንጀል ታሪክ የነበራቸው ሲሆን ደግሞ ይህ የኋላ የወንጀል ታሪክ ሕጋዊውን ስርዓት ተከትሎ የተሰረዘ መሆኑ ሳይረጋገጥ የተጠሪው የዘወትር ፀባይ መልካም ነበር የሚል ግምት መያዙ ተገቢነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የተጠሪው የዘወትር ፀባይ መልካምነት በቅጣት ማቅለያነት እንዲያጣ ከመደረጉ በፊት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት መዝገብ የሚያረጋግጠው የተጠሪው የኋላ የወንጀል ታሪክ ሕጋዊውን ስርዓት ተከትሎ የተሰረዘ መሆን አለመሆኑ አሰቀድሞ ሊጣራ ይገባው ነበር በማለት ስማችን በአራተኛ እና በአምስተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኞች ይህንን የልዩነት ሀሳብ አስፍረናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 103452

ቀን ጥር 19/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተሽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ጥዑም ተኬ ገብራይ ጠበቃ ሀብታሙ ንጉሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የዐቃቤ ሕግ የድሬደዋ ምድብ ዋልተንጉስ ፍቅሬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድሬደዋ ምድብ ችሎት ነው ፡፡ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ያቀረበው ክስ የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 408(2) የተመለከተውን በመተላለፍ ከግል ተበዳይ አቶ ንጉሴ ለማ ብር ሁለት ሺህ (2,000.00) ጉቦ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ ተይዟል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

አመልካች በአሁኑ ተጠሪ የተመሰረተበት የወንጀል ክስ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪም የበኩሉን መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረታዊ ይዘት በጉቦ መልክ ተቀብለው የተባለው የገንዘብ መጠን ትንሽ መሆኑ፤የሥልጣን ደረጃውም በአዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀፅ 2(5) እንደማይካተት በመግለፅ ክሱ በወ/ሕ/ቁ 408(1) ሥር እንዲቀርብ ዐቃቤ ሕግ ክሱን እንዲያሻሽል እንዲታዘዝለት አመልክቷል ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች ስራ አስኪያጅ መሆኑን ፤በአዋጅ ቁጥር 668/2002 መሠረት የመንግስት የልማት ድርጀት ስራ አስኪያጆች የመንግስት ባለ ስልጣን በሚል ሥር ያካተታቸው በመሆኑ መቃወሚያው ውድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች ከፍተኛ ባለ ስልጣን ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 433/97 አልተካተተም ፡፡ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 2/2006 ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 407(2) የወንጀል ደረጃ እና የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ሲያወጣ ከፍተኛ ሥልጣን ማለት በተሻሻለው የፌዴራል ስነ ምግባር እና ፀረሙስና ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2(5) ውስጥ የተካተቱ ባለሥልጣኖች ያላቸው ስልጣን ማለት እንደሆነ ተመልክቷል ፡፡ በወ/ህ/አ. 407(2) እና 408(2) ላይ የተቀመጡ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመሳሳይ በመሆናቸው ለቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 408(2)መወሰዱ ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ ተከሳሽ የመንግስት የልማት ድርጅት ስራ አስኬያጅ መሆናቸው የስልጣን ደረጃቸው ከፍተኛ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡ በጉቦ መልክ ተቀብለው የተባለው ገንዘብ ሁለት ሺህ ብር መሆኑ ሲታይ የተገኘው ጥቅም ዝቅተኛ ነው፡፡ ኃላፊነት ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ የከባድ የሙስና ወንጀል መለኪያ መስፈርቶችን የሚያሟላ ሆኖም አልተገኘም ፡፡ በመሆኑም ዓቃቤ ሕግ በወንጀል መቀጫ ሥነ ሥርዓት አንቀጽ 112 በሚያዘው መሠረት አሻሽሎ እንዲያቀርብ ብይን ሠጥቷል፡፡

ተጠሪ በሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይን ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታው ወደ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ የዓቃቤ ሕግ ክስ ስለ ወንጀሉ የሚዘረዝረው ዝርዝር መግለጫ ከህጉ ጋር በእጅጉ የተራራቀ እስካልሆነ ድረስ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ስም ገና ከጅምሩ አንቀጽ ቀይሩ እያለ መዘገብ የሚዘጋ ከሆነ ገና ክሱ ሳይጀምር ወደ ማያባራ ውዝግብ እና ይግባኝ የሚደረግ ነው፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተጠሪ ተከላከል የሚል ከሆነ ሊከላከል የሚገባውም ከተከሰሰበት የህግ አንቀጽ ያነሰ የሚያስቀጣ ነው ብሎ ካመነ በዛን ግዜ አንቀጽን መቀየር የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ዓቃቤ ሕግ በከሰሰበት የወ/ህ/አንቀጽ 408(2) ክሱ ሊቀጥል እና ማስረጃ ሊሰማ ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በሥር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተፈጽሟል ያሉትን የህግ አተረጓጎም ስህተት በዝርዝር ያቀረቡ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩ ፈጸሙት የተባለው ድርጊት በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ሥር የተቀመጡትን ማቋቋሚያ ፍፌ ነገሮች የማያሟላ በመሆኑ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዓቃቤ ሕግ ክሱን እንዲያሻሽል የተሰጠ ትዕዛዝ ተገቢ ሆኖ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር የሚጠይቅ ነው ፡፡ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና አመልክቷል ፡፡የአመልካች የመልስ መልስም የሰበር ቅሬታቸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥ በሰበር ግራ ቀኙ በዕሑፍ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የሥር ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይን በመሻር ዓቃቤ ሕግ በከሰሰበት የወ/ሕ/ቁ.408(2) ክሱ ሊቀጥል እና ማስረጃ ሊሰማ ይገባል በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ለተያዘው ጉዳይ ዕልባት መስጠት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው የተመደበበት የኃላፊነት ደረጃ ይሁን በወንጀል ድርጊቱ ተገኘ የተባለው ጥቅም አነስተኛ በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ ክስ ማቅረብ የነበረበት በወ/ሕ/ቁ. 408 (1) ሥር መሆን ነበረበት በሚል ነው ፡፡ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች ሥራ አስኪያጅ በመሆናቸው በከፍተኛ ሥልጣን ደረጃ የሚመደብ በመሆኑ የተገኘው ጥቅም አነስተኛ መሆን የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ለመቀየር የሚያስችል አይደለም በማለት ተከራክረዋል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ዓቃቤ ሕግ የሚያቀርበው ክስ ማሟላት ያለበት መሰረታዊ ነጥቦች ምን እንደሆኑ ደንግጓአል። ተከሳሹ የቀረበበት ክስና ማስረጃ ዝርዝር አውቆና ለይቶ እንዲከላከል በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 111፣112 የተዘረዘሩት መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች በዓቃቤ ሕግ ክስ መገለጽ አለባቸው። ዓቃቤ ሕግ የሚያቀርበው ክስ የወንጀል ድርጊት መሆኑ ብቻ ሳይሆን የወንጀል ድርጊት መሆኑ የሚደነግጉ ፍሬ ነገሮች ተከሳሹ ፈጸመው ከተባለው ድርጊት የሚዛመድ መሆኑ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል ። በእንግሊዘኛው (“such description shall follow as closely as may be the words of the law creating the offence`) በማለት ተገልጿል ። በአግባቡ የቀረበ ክስ ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ዝርዝር ጉዳይ አውቆ የመከላከያ ማስረጃው እንዲያዘጋጅ ፍርድ ቤትም የጠራ ግንዛቤ በመያዝ ክርክሩን በሕጉ መሰረት ለመምራት የሚያስችለው እንደሆነ ከወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ111፣112 እና ከአጠቃላይ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረታዊ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው።

አመልካች የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ዋና ሥራ አስኪያጅ ስለመሆናቸው በሙስና የተጠረጠሩትም ሁለት ሺህ ብር ጉቦ ሲቀበሉ እጅከፍንጅ የተያዙ እንደሆኑ መሰረት በማድረግ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 408(2) የተጠቀሰባቸው ስለመሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት መገንዘብ ይቻላል ። የአመልካች የኃላፊነት ደረጃ በአዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2(5) ሥር በግልጽ የተጠቀሰ ባይሆንም በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ኃላፊዎች በዚህ ትርጓሜ ውስጥ ሊካተቱ እንደሚችሉ በአዋጅ የተጠቀሰ በመሆኑ ከወዲሁ የኃላፊነት ደረጃቸው ከፍተኛ ነው ወይስ ዝቅተኛ ? የሚለው በግልፅ የተወሰነ አይደለም ። የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ምን እንደሚወሰን ስለማይታወቅ ከወዲሁ የአመልካች የኃላፊነት ደረጃ ወስኖ ወደ ክርክር መግባት ሥነሥርዓታዊ ነው ለማለት የሚቻል አይሆንም።በሌላ በኩል በወ/ሕ/ቁ/408(2) የተዘረዘሩት የማቋቋሚያ ነጥቦች ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ ፣የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት የኃላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ ፣በህዝብ ወይም በመንግስት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት ናቸው ። ከላይ እንደተመለከተው ዋና ሥራ አስኪያጅ ከፍተኛ ኃላፊ ነው ወይስ አይደለም የሚለው በአዋጅ በግልጽ ባልተሸፈነበት ፍርድ ቤቱ ክርክሩ ሲመረምር ግለሰቡ ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንፃር እንደየአግባብነቱ የሚወሰን እንጂ ከወዲሁ የሰበር ሰሚ ችሎቱ አቋም የሚወሰድበት አይሆንም ። ሌሎች የማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮችም መኖር አለመኖራቸው በክርክር ሂደት ነጥረው የሚወጡ እንጂ ከወዲሁ ድርጊቱ የተፈፀመው ለዚህ ዓላማ ነበር ተብሎ ድምዳሜ የሚያዝበት ሆኖ አልተገኘም።

ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ ምንድነው? የሚለው ምናልባት ለወደፊት ዓቃቤ ሕግ እንደክሱ የሚያስረዳ ከሆነ በሥር ፍርድ ቤት የሚታይ እንጂ ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ ድምዳሜ ላይ መድረስ አይቻልም ።በተያያዘው ጉዳይ ተፈፀመ በተባለው ድርጊት በግለሰብ ወይም በህዝብ ወይም በመንግስት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ምንድን ነው ? የሚለውም ዓቃቤ ሕግ እንደክሱ አቀራረብ የሚያስረዳ ከሆነ የሥር ፍርድ ቤት ክክርክር በኃላ የሚወሰነው እንጂ ከወዲሁ አቋም የሚያዝበት አይደለም ። እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ደምረን ስንመለከታቸው አቃቤ ሕግ ተፈፀመ ያለው የወንጀል ድርጊት በወ/ሕ/ቁ. 408(2) ሥር የሚወድቅ ነው ብሎ ካመነ እና ለዚሁም መነሻ የሆኑ ነጥቦች በክሱ መግለጹ ከተረጋገጠ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ከማስተናገድ ውጭ ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ የወ.ሕ..ቁ 408(2) ማቋቋሚያ ፍሬነገሮች አያሟላም ብሎ ክሱን ውድቅ የሚያደርግበት ሥርዓታዊ ሂደት አይኖርም። በሌላ በኩል የሥር ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ በሚመረምርበት ወይም ዓቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አስረድቷል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሰም የመከላከያ ማስረጃ በሚመረምረበት ጊዜ ሁሉ በአመልካች ላይ የተጠቀሰው የህግ አንቀጽ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ከመመርመር የሚገደበው ሥርዓት አይኖርም ። ይህ ከሆነ ደግሞ ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ ዓቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ በወ/ህ/ቁ.408(1) የተዘረዘሩት የማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮችን አያሟሉም ተብሎ ወደ ወ/ህ/ቁ.408(1) እንዲቀየር የሚያስችል የህግ መሰረት የለውም ። በመሆኑም የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክሩ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ መሰረት እንዲቀጥል መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል።

ሲጠቃለል አመልካች የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት በወ/ሕ/ቁ.408(2) እንዲቀጥል በፌዴራል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል ። የአመልካች የኃላፊነት ደረጃ ኃላፊነቱ እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ ፤በግለሰብ በህዝብ ወይም በመንግስት የደረሰው ጉዳት ምንድነው የሚለው ዓቃቤ ሕግ በሚያቀርበው ማስረጃ ይዘት የሚመዘን ምናልባት የሥር ፍርድ ቤት ድርጊቱ የተፈጸመበት ሁኔታ ከለየ በኋላ ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ከሆነ የሚያቀርቡት የመከላከያ ማስረጃ ተመዝኖ የሚወሰን እንጂ ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ አቋም የሚወሰድበት ባለመሆኑ የአመልካች ክስ ይሻሻልኝ ጥያቄ አልተቀበልነውም ። በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.101820 ሐምሌ 10 ቀን 2006ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይን በመሻር የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል።

2. ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው የወ/ሕ/ቁ.408(2)ሥር ክርክሩ እንዲቀጥል መታዘዙ በአግባቡ ነው ብለናል ።

3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የጸና ስለመሆኑ ለሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና አመልካች በሚገኝበት አድራሻ የፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ ይድረሳቸው ። ይፃፍ።መዝገቡ ተዘጋ፤ወደ መ/ቤት ተመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/103448

የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች:-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መ·ስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አገኘሁ አስፋው የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የፌዴራል አቃቤ ሕግ - ወይን ገ/እግኢአብሄር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በሰው ሕይወትና አካል ላይ በቸልለተኝት ጉዳት ማድረስን የሚመለከት የወንጀል ክርክር ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ የመሰረተው በአምስት ምድብ የተከፈለ ክስ ነው፡፡

1ኛክስ፡-በ1996 ዓ.ም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(3) እና የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 13(ሀ) የተመለከተዉን በመተላለፍ አመልካቹ አሽከርካሪ በመሆኑ የሌላን ሰዉ የሕይወት ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ግዴታ እያለባቸው በ03/06/2005 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 9፡40 ሲሆን በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከ/ወረዳ 01 ልዩ ቦታዉ ቻይና ካምፕ መታጠፊያ አካባቢ የሠሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-15006 ኦ/ሮ የሆነ ተሸከርካሪ ይዞ ከአየር ጤና ወደ ሳሪስ አቦ አቅጣጫ እያሽከረከረ ሲንዝ ከተሸከርካሪ መንገድ ዉጭ በመዉጣት በእግረኛ መንገድ ላይ ስትንዝ የነበረችዉን ህጻን ሕይወት ዳዲ የተባለችዉን በሚያሽከረክረዉ መኪና የፊት አካል ገጭቶ በመግደሉ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነዉ፡፡

2ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ክሶች በተመሳሳይ የወ/ሕ/ አንቀጽ 559(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተጠቀሰዉ ጊዜ፣ ቦታና እንዲሁም በቸልተኝነት የድርጊት አፈፃጸም በ2ኛ ክስ የግል ተበዳይ በነበረችው ህጻን ብሩክታዊት ተስፋዬ የጆሮ ታምቡር መቀደድ ጉዳት አድርሷል፣በ3ኛ ክስ ተበዳይ በነበረችዉ ህጻን ሳምራዊት በቀለ ላይ የለስላሳ ጡንቻ ጉዳት አድርሷል፤ በ4ኛ ክስ ተበዳይ በነበረችዉ ህጻን ቅድስት አስማማዉ ላይ የለስላሳ ጡንቻ ጉዳት አድርሷል፤ እንዲሁም በ5ኛ ክስ ተበዳይ በነበረችዉ ህጻን ዋጋዬ ወቼሬ ላይ የለስላሳ ጡንቻ ጉዳት አድርሷ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የቀረበባቸዉ ክስ ደርሷቸዉ በግልጽ ችሎት ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኃላ በሥር ፍርድ ቤት የእምነት ክህደት ቃል እንዲሰጡ ሲጠየቁ ጥፋተኛ አይደለሁም ሲሉ ክደው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪም አሉኝ ያላቸውን የሠውና የሠነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አቃቤ ሕግ እንደክሱ ማስረዳቱን በመገንዘብ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያስመ መብታቸውን የጠበቀላቸው ሲሆን አመልካችም አሉኝ ያሏቸውን ማስረጃዎች አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ሕግንና የአመልካችን የሰዉና የሰነድ ማስረጃዎች ሰምቶና መርምሮ አመልካችን የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃዎቹ ያለማስተባበላቸውን ጠቅሶ የመከላከያ ማስረጃዎቹን ክብደት ሳይሰጥ ያለፈ ሲሆን አመልካችን በዐቃቤ ሕግ ተጠቅሶ በቀረበባቸው ክሶች በመሉ ጥፋተኛ አድርጎ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለና ከወንጀል ሕጉ እንዲሁም ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ መመልከቱን ከጠቀሰ በኃላ አመልካችን በ6 ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 5,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱም ጉዳዩን መርምሮ 1ኛ ክስን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(3) ድንጋጌ ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) መሆኑን፣በ3ኛ እና 5ኛ ክሶችም በአቃቤ ሕግ ክሱ የተነሳ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ሊባሉ እንደማይችሉ፣በ2ኛ እና በ4ኛ ክሶች ጥፋተኛ የተባሉት ግን ተገቢ መሆኑን ገልፆ የጥፋተኝነት ውሳኔ በዚህ አግባብ ከአሻሻለ በኃላ ቅጣቱን በተመለከተም አመልካች የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበባቸው መሆኑና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው እንዲሁም ከግል ተበዳይ ህፃናት ወላጆች ጋር እርቅ መፈፀማቸውን በሶስት ቅጣት ማቅለያነት ሊያዝላቸው እንደሚገባ ጠቅሶ በአንደኛው ክስ በሶስት አመት እስራት፣በ2ኛ እና በ4ኛ ክሶች ደግሞ ለእያንዳንዳቸው አንድ አመት እስራት ይዞና እነዚህን ጊዜያት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1(ለ) ድንጋጌ ደምሮ መነሻ ቅጣቱን አምስት አመት አድርጎ ይኼው መነሻ ቅጣት በእርግ ሃያ እንደሚያርፍና በሶስት ማቅለያ ምክንያቶች ደግሞ ወደ እርከን አስራ ሰባት እንደሚወርድ ጠቅሶ በዚሁ የቅጣት እርከን ውስጥ ካለው ሬንጅ ውስጥ አመልካች ሊቀጡ የሚገባው ሶስት አመት ከስድስት ወር እስራት ነው፣ የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ ደግሞ ብር 2000.00 ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ በወንጀል ሕጉም ሆነ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ላይ የተቀመጠውን ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በአመልካች ላይ የተጣለው የቅጣት ውሳኔ ሕጉን የተከተለ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በዕሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆኑትን የበታች ፍርድ ቤቶችን የውሳኔ ክፍሎችን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስልጉ ጭብጮች፡-

1. አመልካች ለ2ኛ እና 4ኛ ክሶች ጥፋተኛ ተብለው በመነሻ ቅጣትን የተያዘው ጊዜ ወደ ፅኑ እስራት ሳይቀር ከ1ኛው ክስ ጋር ተደምሮ መነሻ ቅጣቱ መያዙ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. እያንዳንዱ ቅጣት ማቅለያ የሚያስቀንሰው 1 እርከን ወይስ 2 እርከን ነው? የሚሉት ሁነው አግኝቷል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

አመልካች በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባሉት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 559(2) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ተላልፈዋል ተብለው በሶስት ክሶች ነው፡፡እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያስቀጡት በቀላል እስራት መሆኑን ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡በመሆኑም የመነሻ ቅጣቱ ሲወሰን ለእያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌ ከተለየ በኋላ ተደምሮ የሚመጣው ውጤት ሲሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1(ለ)) ድንጋጌ መሰረት እንደተመለከተው በቅጣት አደማመር ጊዜ በጽኑ እስራትና ቀላል እስራት በሚያስቀጡ ድንጋጌዎች አንድ ሰው ጥፋተኛ ከተባለ በቅድሚያ የቀላል እስራት ቅጣት ወደ ጽኑ እስራት መለወጥ አለበት፡፡ይህ ስሌት ተፈጻሚ መሆን እንደአለበትም ተሻሽሎ የወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያም በአንቀጽ 22 ስር ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡የወንጀል ሕጉም ሆነ የቅጣት መመሪያው አንድ ሰው በቀላል እስራት በሚያስቀጡ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ አድራጎቶች ጥፋተኛ ከተባለ ለእያንዳንዱ አድራጎት የሚጣለው ቅጣት ወደ ጽኑ እስራት መለወጥ ያለበት መሆኑን አይገልፁም፡፡በመሆኑም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(2) እና 559(2) ድንጋጌ የሚያስቀጡት በቀላል አስራት በመሆኑ ለእያንዳንዱ ድንጋጌ መነሻ ቅጣቱ ተወስኖ ከሚደመሩ በስተቀር የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 559(2) ድንጋጌ ቅጣት ወደ ፅኑ እስራት ተቀይሮ ለወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) ለመነሻነት ከተያዘው ቅጣት ጋር የሚደመርበት የሕግ አግባብ የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው የህግ ድንጋጌዎች በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሻሽሎ በወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የወንጀሉ ደረጃ የወጣላቸው ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ቅጣቱን በዚህ መመሪያ መሰረት ማስላቱን ተመልክተናል፡፡በክስ አንድ አመልካች የፈፀሙት አድራጎት የወንጀሉ ደረጃ አራት ሲሆን ይህም የቅጣት መነሻ እርከኑ 16 ስር የሚወድቅ ነው፡፡ለ2ኛ እና 4ኛ ክሶች ደግሞ ደረጃ 1 እርከን 7 የሚያርፍ ነው፡፡በእነዚህ እርከኖች ፍርድ ቤቶች ለእያንዳንዱ መነሻ ቅጣት ከለየ በኋላ ድምሩ አምስት አመት እስራት መሆኑን የገለፀ ይህም በእርከን ሃያ ስር የሚወድቅ ሁኖ በዚህ እርከን ስር ደግሞ ለፍርድ ቤቱ የተተወው ፍቅድ ስልጣን አራት አመት ከአምስት ወር እስከ አምስት አመት ከአራት ወራት እስራት ነው፡፡ይህንኑ ይዘን ወደ ቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ስንመጣ በተጠሪ በኩል የቀረበ ማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን አመልካች ሪኮርድ የሌለባቸው መሆኑን፣ከግል ተበዳይ ህፃናት ወላጆች ጋር መታረቃቸውና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት ተይዞላቸዋል፡፡በመሆኑም አመልካች የሚኖራቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ብዛት ሶስት ይሆናሉ፡፡እነዚህ ማቅለያ ምክንያቶችም በመመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 23(4) ድንጋጌ መሰረት በጠቅላላው ሶስት እርከን የሚያስቀንሱ ይሆናል፡፡ ሆኖም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው ድንጋጌዎች ድርጊቱ በተፈጸመበት የካቲት 13 ቀን 2005 ዓ/ም ተፈጻሚነት በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት የቅጣት ማቅለያ ዋጋ አያያዝ ከተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የተለየ ነው፡፡በዚህም ምክንያት እኛም የቅጣት ማቅለያ ዋጋ አያያዝን ከወንጀል ሕጉ አንቀፅ 6 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንጻር ለአመልካች የተሻለ ሁኖ ያገኘነው ነባሩ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በመሆኑ የቅጣቱን መጠን ከዚሁ አንፃር ተመልክተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች እንዲቀጡ በመነሻነት የሚያዘው እርከን 20 በመሆኑ በዚህ እርከን መነሻ ሲያዝ የቅጣት መጠኑ ከአንድ አመት በላይ እና ከሰባት አመት በታች በመሆኑ አመልካች ያላቸው ሶስት የቅጣት ማቅለያዎች በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 16(6) ድንጋጌ መሰረት እያንዳንዳቸው ሶስት እርከን የሚያስቀንሱ በመሆኑ ከእርከን 20 ወደ እርከን 14 መውረድን፣ በዚህ እርከን ውስጥ ተገቢውን ቅጣት መወሰን የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ቅጣቱን ስናሰላው አመልካች ሊቀጡ የሚገባው በእርከን 14 ስር ለፍርድ ቤቱ በተተወው የፍቅድ ስልጣን ማለትም ከሁለት አመት ከስድስት ወር እስከ ሶስት አመት እስራት ውስጥ ነው፡፡ከእነዚህ የእስራት ጊዜያት አመልካችን ያርማል፣ሌሎች መሰል አጥፊዎችን ከወዲሁ ያስጠንቅቃል ብለን ያመነው ሶስት አመት ቀላል እስራት ሁኖ አግኝተናል፡፡ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 133523 ጥር 21 እና 29 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 98818 ግንቦት 29 ቀን 2006 ዓ/ም ተሻሻሉ የተወሰነው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በ1ኛ፣ በ2ኛ እና 4ኛ ክሶች በተናጠል ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ ነው ብለናል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም ለእያንዳንዳቸው መነሻ ቅጣቱ ከተለየ በኋላ ወደ ፅኑ እስራት ሳይቀየር መደመራቸው ተገቢ ነው ብለናል፡፡የቅጣት ማቅለያ ዋጋ አያያዝን በተመለከተ ግን ሶስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የሚያስቀንሱት ስድስት እርከን በመሆኑ ከእርከን 20 ወደ አርከን 14 በመውረድ በዚሁ እርከን ውስጥ በሶስት አመት እስራት እንዲቀጡ ብለናል፡፡የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. አመልካች በጉዳዩ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሁኖ በዚህ ችሎት በተወሰነው የእስራት ቅጣት መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይገለጽለት ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ 99883

ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ገ/ሥላሴ ገብሩ - ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ ቀረቡ፤ ጠበቃ ሐና ዲግራንዲ ከመቀሌ በV.C. ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የትግራይ ብ/ክ/መንግስት ፍትሕ ቢሮ - ዐ/ሕግ ገ/እግዚአብሔር ተወልደብርሃን ከመቀለ በV.C. ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ እና ቁጥራቸው 98349 እና 98350 በሆኑት በዛሬው ዕለት በዚሁ ችሎት ውሳኔ በተሰጠባቸው ሌሎች ሁለት መዝገቦች ለቀረበው የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው ተጠሪ በ19/08/2003 ዓ.ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ በትግራይ ክልል በመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች እና 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በነበሩት ሌሎች ሁለት ተከሳሾች ላይ ስድስት የወንጀል ክሶችን በማቅረቡ ሲሆን ይዘታቸውም በአጭሩ፡-

1. በአንደኛ ክስ ሶስቱም ተከሳሾች በገቢ ግብር አዋጅቁጥር 286/1994 በአንቀጽ 96 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በተለያየ የንግድ ስራ ዘርፍ ተሰማርተው ይሰሩ በነበረበት ጊዜ

    - 1ኛ ተከሳሽ አቶ ገ/ሥላሴ ገብሩ ከ1997 ዓ.ም. እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ መክፈል ይገባቸው የነበረውን ግብር ብር 1,973,389.10 ባለመክፈላቸው፤
    - 2ኛ ተከሳሽ ወ/ት ብርኽቲ ተስፋይ ከ1999 ዓ.ም. እስከ 2000 ዓ.ም. ድረስ መክፈል ይገባቸው የነበረውን ግብር ብር 1,209,320.17 ባለመክፈላቸው፤
    - 3ኛ ተከሳሽ አቶ ፍጹም አብርሃ ከ2000 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ መክፈል ይገባቸው የነበረውን ግብር ብር 25,102.93 ባለመክፈላቸው ሕግን በመጣስ ግብር ያለመክፈል ወንጀል አድርገዋል፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በሁለተኛ ክስ ሶስቱም ተከሳሾች በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 በአንቀጽ 49 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በተለያየ የንግድ ስራ ዘርፍ ተሰማርተው ይሰሩ በነበረበት ጊዜ፡-

    - 1ኛ ተከሳሽ በገዛ ገብረስላሴ ባህላዊ ምግብ ቤት የወ/ሮ ከለላ ሃደራ ወኪል ሆነው በሰሩበት ጊዜ ከሚያዝያ እስከ የካቲት ወር 1999 ዓ.ም. ድረስ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ይገባቸው የነበረውን ብር 2,195,929.51 የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ባለማድረጋቸው፤
    - 2ኛ ተከሳሽ ከሐምሌ 1999 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ይገባቸው የነበረውን ብር 3,094,268.85 የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ባለማድረጋቸው፤እንዲሁም ከሐምሌ 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ሲገባቸው ባለመመዝገባቸው፤
    - 3ኛ ተከሳሽ ከሐምሌ 2001 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ይገባቸው የነበረውን ብር 199,334.17 የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ባለማድረጋቸው፤እንዲሁም ከሐምሌ 2001 ዓ.ም. ጀምሮ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ሲገባቸው ባለመመዝገባቸው፤ሕግን በመጣስ ታክስ ያለመክፈል ወንጀል አድርገዋል።

3 በሶስተኛ ክስ 1ኛ ተከሳሽ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 98(1)(ሀ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በመቀሌ ከተማ ለሚያሰሩት ባለ አምስት ኮከብ ሆቴል ከቀረጥ ነጻ ያስገቡት የተለያየ መጠን ያለው የቀረጥ መጠኑ ብር 8,741,024.44 የሆነ ቴንዲኖ በባለሙያዎች ተፈትሾ ባለመገኘቱ ከቀረጥ ነጻ ሆኖ ወይም በቅናሽ ቀረጥ የገባን ዕቃ ከቀረጥ ነጻ መብቱ ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ ለሌላ አገልግሎት የማዋል ወንጀል አድረገዋል፤

4 በአራተኛ ክስ 1ኛ ተከሳሽ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 በአንቀጽ 60(1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ መጀመርያ በሕንጻ ማከራየት የንግድ ዘርፍ ፈቃድ አውጥተው ከ2001 እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ባለመክፈል እና ባለማደሳቸው፤በከብት ማድለብ የንግድ ዘርፍ ፈቃድ አውጥተው ከ2001 እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ባለመክፈል እና ባለማደሳቸው፤ እንዲሁም በምግብ ቤት የንግድ ዘርፍ ፈቃድ አውጥተው ከ2001 እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ሳይከፍሉ እና የጸና/የታደሰ/ የንግድ ፈቃድ ሳይዙ በንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው በመገኘታቸው የጸና የንግድ ፈቃድ ሳይዙ በንግድ ስራ ላይ የመሰማራት ወንጀል አድርገዋል፤

5 በአምስተኛ ክስ 1ኛ ተከሳሽ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 በአንቀጽ 50(3)(ለ) ስር የተደነገገውን ተላልፈው በክሱ ዝርዝር የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት በመፈጸማቸው የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ የማቅረብ ወንጀል አድርገዋል፤

6 በስድስተኛ ክስ1ኛ ተከሳሽ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በአንቀጽ 97(3)(ለ) የተደነገገውን ተላልፈው በክሱ ዝርዝር የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት በመፈጸማቸው የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ የማቅረብ ወንጀል አድርገዋል፤የሚሉ ናቸው።

1ኛ ተከሳሽ ያቀረቧቸው የመቃወሚያ ነጥቦች ውድቅ ከተደረጉ በኃላ ተጠይቀው ሶስቱም ተከሳሾች ወንጀሎቹን አላደረግንም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ በተጠሪ በኩል የቀረቡ በሁሉም ክሶች አዲተሮችን ጨምሮ በድምሩ የአስራ ሰባት ምስክሮችን ምስክርነት ከሰማ እና የአዲት ሪፖርትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጨምሮ የተጠሪን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተጠሪ በክሶቹ መሰረት አላስረዳባቸውም በማለት 1ኛ ተከሳሽን ከአምስተኛ እና ከስድስተኛ ክሶች በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 141 መሰረት በማሰናበት እና ቀሪዎቹን ክሶች በተመለከተ ግን ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ ሶስቱም ተከሳሾች መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ ሶስቱም ተከሳሾች የተለያዩ የመከላከያ ጭብጦችን በማስያዝ በጋራ እና በተናጠል በመሆን በድምሩ አስራ አምስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ ሰነዶችንም በመከላከያነት አቅርበዋል።

ፍርድ ቤቱም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በአንደኛ ክስ በተጠሪ የቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ በመከላከያቸው ያስተባበሉ መሆኑን ገልጾ በአንደኛ ክስ ከተመለከተው የወንጀል ክስ በነጻ ያሰናበታቸው ሲሆን ይከላከሉ በተባሉባቸው በቀሪዎቹ ክሶች ግን ሶስቱም ተከሳሾች ባሰሟቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከረባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት በየክሶቹ በተጠቀሱባቸው ድንጋጌዎች ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ በማስተላለፍ ግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጓል። በመቀጠልም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ካመዛዘነ በኃላ፡-

- 1ኛ ተከሳሽ በአንደኛ ክስ ስር በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት፤በሁለተኛ ክስ ስር በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት፤በሶስተኛ ክስ ስር በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት፤በአራተኛ ክስ ስር በአራት ዓመት ጽኑ እስራት በብር 200,000 መቀጮ በድምሩ በአስራ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እና በብር 200,000 መቀጮ፤
- 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች እያንዳንዳቸው በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት(የቅጣት መጠኑን በተመለከተ ብቻ በአብላጫ ድምጽ)፤እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሶስቱም ተከሳሾች በአንድነት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54809 ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ከተሰጠው ውሳኔ መካከል በከፊሉ ቅር በመሰኘት በመዝገብ ቁጥር 54810 ይግባኝ አቅርቦአል። ፍርድ ቤቱም በከፍተኛ ፍርድ ቤት በሁለተኛ ክስ በተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሶስቱም ተከሳሾች ያቀረቡትን ይግባኝ በትዕዛዝ የዘጋ ሲሆን በ1ኛ ተከሳሽ እና በተጠሪ መካከል በሁለቱም መዝገቦች የቀረበለትን ክርክር በተመለከተ ግን ክርክሩን በአንድነት ከመረመረ በኃላ በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን ይግባኝ ውድቅ አድርጎ የ1ኛ ተከሳሽን የይግባኝ ክርክር በመቀበል በከፍተኛ ፍርድ ቤት በአንደኛ፣በሶስተኛ እና በአራተኛ የወንጀል ክሶች ተሰጥቶባቸው የነበረውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሽሮ በነጻ አሰናብቷቸዋል።

ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ተጠሪ ባቀረበው አቤቱታ ሳቢያ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 98(1)(ሀ) ተጠቅሶበት የቀረበው ሶስተኛው ክስ ሁለተኛ ይግባኝ ያለው በመሆኑ ምክንያት በሰበር ሊያየው እንደማይችል ገልጾ በማለፍ በአንደኛ እና በአራተኛ የወንጀል ክሶች በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማጽናት እና በ4ኛ ክስ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ የተሰጠው የቅጣት መጠን አንሷል በሚል የቀረበውን የዐቃቤ ሕግ አቤቱታ በመቀበል እና ለ4ኛ የወንጀል ክስ ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት በማስላት የመቀጮ ውሳኔውን ሳይነካ 1ኛ ተከሳሽ በሁለተኛ ክስ የተሰጠባቸውን የሶስት ዓመት ጽኑ እስራት ጨምሮ በድምሩ በአስራ አራት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ በዚህ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 99883 አቤቱታ ያቀረቡትም ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ በስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጣምረው ከቀረቡት ክሶች መካከል አንዱ የተጨማሪ እሴት ታክስን የሚመለከት ከመሆኑ አንጻር ጉዳዩን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአመልካቹ ላይ ከቀረቡት ስድስት የወንጀል ክሶች መካከል ሶስቱ ማለትም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 ተጠቅሶበት የቀረበው ሁለተኛ ክስ፣ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 98(1)(ሀ) ተጠቅሶበት የቀረበው ሶስተኛ ክስ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 50(3)(ለ) ተጠቅሶበት የቀረበው አምስተኛ ክስ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4(4) እና 15(1) ድንጋጌዎች መሰረት የሚወድቁት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር መሆኑ፣እነዚህ ክሶች ለመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርቡ የቻሉትም በሕገ መንግስቱ በተሰጠው የስልጣን ውክልና መሰረት መሆኑ፣ቀሪዎቹ ሶስት ክሶች በክልሉ የወረዳ ፍርድ የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ ሆነው ነገር ግን በስልጣን ውክልና መሰረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ከቀረቡት ክሶች ጋር ተጠቃለው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የተደረገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) ድንጋጌ መሰረት መሆኑ እና ይህም ተገቢነት ያለው የክስ አቀራረብ ስርዓት መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ ይልቁንም አከራካሪ ሆኖ የቀረበው በአንድ ተከሳሽ ላይ ከቀረቡት ከአንድ በላይ ከሆኑ ክሶች መካከል ከፊሎቹ የሚወድቁት በፌዴራል ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር፣ከፊሎቹ ደግሞ በክልል ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር በሆነ ጊዜ እና ነገር ግን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) ድንጋጌ ስር በተመለከተው የክስ አቀራረብ መርህ መሰረት ተጠቃለው በቀጥታም ሆነ በውክልና በፌዴራል ፍርድ ቤት ቀርበው እንዲታዩ ተደርገው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ ከተሰጠባቸው በኃላ ወደ ይግባኝ እና ወደ ሰበር የክርክር ደረጃ ሲደርሱ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ እንደተደረገው ሁሉ ተጠቃለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው መጠናቀቅ አለባቸው ወይስ እንደየሚወድቁበት የስረ ነገር ስልጣን ሁኔታ ተነጣጥለው ከፊሎቹ የክልል ፍርድ ቤቶችን፣ከፊሎቹ ደግሞ በፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው መጠናቀቅ አለባቸው? የሚለው ዓቢይ ነጥብ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ የወጣው በሀገሪቱ ውስጥ የፌዴራል የአስተዳደር ስርዓት እና ይህንኑ ተከትሎ አዲስ የፍርድ ቤቶች አወቃቀር ስርዓት ከመዘርጋቱ ከበርካታ ዓመታት በፊት በመሆኑ የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች በዚህ መዝገብ አከራካሪ ሆኖ ለቀረበው ነጥብ ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉ አይደሉም፡፡ በመሆኑም የሀገሪቱን አዳዲስ ሁኔታዎች ያገናዘበ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ተቀርጾ ተግባራዊ እስከሚደረግ ድረስ አከራካሪ ሆኖ ከቀረበው ነጥብ ጋር ግንኙነት ያላቸው አሁን በስራ ላይ ያለው የወንጀል የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ከፌዴራሊዝም ስርዓት እና ይህንኑ ተከትሎ ከተዘረጋው የፍርድ ቤቶች አወቃቀር ጋር በተቻለ መጠን ሁሉ ሊጣጣም በሚችል ሁኔታ እየተተረጎሙ ተግባራዊ እንዲሆኑ ከማድረግ ውጪ የተሻለ አማራጭ አይኖርም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ በአንድ ተከሳሽ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ የወንጀል ክሶች በቀረቡ ጊዜ ክሶቹ በመርህ ደረጃ በአንድነት መታየት የሚገባቸው ስለመሆኑ በስነ ስርዓት ህጉ በቁጥር 116(2) ስር የተቀመጠው ድንጋጌ ዓይነተኛ ዓላማ በአንድ በኩል በተለያዩ ፍርድ ቤቶች እና መዝገቦች በአንድ ተከሳሽ ላይ ለየብቻ የቀረቡትን ከአንድ በላይ የሆኑ ክሶች በማስተናገድ ሊባክን ይችል የነበረውን ጊዜ እና ሀብት በማዳን ለተከራካሪ ወገኖችም ሆነ ለምስክሮች ምቹ በሆነ ሁኔታ የተቀላጠፈ ፍትሕ እንዲሰጥ ለማስቻል እና በሌላ በኩል ደግሞ በክሶቹ ተነጣጥሎ መታየት ሳቢያ በክሱ ክትትል ረገድም ሆነ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ በቅጣት አጣጣል ረገድ በተከሳሽ ወገን ላይ ሊደርስ የሚችለውን አላስፈላጊ ጉዳት በተቻለ መጠን ለማስወገድ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) ድንጋጌ ስር ከተመለከተው የክስ አቀራረብ መርህ አንጻር ከላይ የተጠቀሰው የቁጥር 116(2) ድንጋጌ ዓላማ ሊሳካ የሚችለው ደግሞ ተጠቃለው የታዩት ክሶች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ ከተሰጠባቸው በኃላ ወደ ይግባኝ እና ወደ ሰበር የክርክር ደረጃ ሲደርሱ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ እንደተደረገው ሁሉ ተጠቃለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው እልባት እንዲያገኙ ሲደረግ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሶቹን አጠቃሎ የተመለከተው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣኑ መሆኑን በመግለጽ የክልሉ ሰበር ችሎት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ ከአመልካች የቀረበለትን መቃወሚያ ሰበር ችሎቱ ሳይቀበል የቀረው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ናቸው ከተባሉት መካከል 2ኛውን ክስ አስመልክቶ የቀረበለት አቤቱታ አለመኖሩን እና 3ኛው ክስ ደግሞ የይግባኝ ስርዓቱ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ ምክንያት በሰበር ሊታይ የማይችል መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቋም ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት ተጠቃለው እንዲታዩ የተደረጉት የወንጀል ጉዳዮች በይግባኝ እና በሰበር የክርክር ደረጃ ሲደርሱ እንደየሚወድቁበት የስረ ነገር ስልጣን ሁኔታ ከፊሎቹ የክልል ፍርድ ቤቶችን፣ ከፊሎቹ ደግሞ በፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው እና ተነጣጥለው የሚታዩበትን አሰራር የሚፈጥር በመሆኑ እና የስነ ስርዓት ሕጉን ቁጥር 109(3) እና 116(2) ድንጋጌዎች ዓላማ የሚያሳካ ባለመሆኑ የተሻለ የክርክር አመራር አማራጭ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣኑ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) እና 116(2) ድንጋጌዎች መሰረት አጠቃሎ በማየት በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ የሰጠባቸው ከፊሎቹ በክልል፣ከፊሎቹ ደግሞ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣኑ በይግባኝ አይቶ በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ ቀጥሎ ባለው የክርክር ሂደት መታየት የሚገባቸው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ እንደተደረገው ሁሉ ተጠቃለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው መሆን ሲገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የቀረበለትን መቃወሚያ ባለመቀበል በክልሉ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ ናቸው በማለት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ተቀብሎ በከፊሎቹ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠቱ በክርክር አመራር ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63092 በ12/07/2006 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ከላይ በተጠቀሰው ስነ ስርዓታዊ ምክንያት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡
2. የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ከፌዴራል ጉዳይ ጋር በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) ድንጋጌ መሰረት አጠቃሎ ያየውን የክልል ጉዳይ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር የማየት ስልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡
3. በአንድ ተከሳሽ ላይ ከቀረቡት ከአንድ በላይ ከሆኑ ክሶች መካከል ከፊሎቹ የሚወድቁት በፌዴራል ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር፣ከፊሎቹ ደግሞ በክልል ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር በሆነ ጊዜ እና ነገር ግን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) ድንጋጌ ስር በተመለከተው የክስ አቀራረብ መርህ መሰረት ተጠቃለው በቀጥታም ሆነ በውክልና በፌዴራል ፍርድ ቤት ቀርበው እንዲታዩ ተደርጎ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ ከተሰጠባቸው በኃላ ወደ ይግባኝ እና ወደ ሰበር የክርክር ደረጃ ሲደርሱ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ እንደተደረገው ሁሉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው እና ተጠቃለው መታየት አለባቸው በማለት ወስነናል፡፡
4. እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የሃሳብ ልዩነት</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር ሁለት የተገለጸው ዳኛከአብላጫው ድምጽ በተሰጠው የህግ ትርጉምና ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡ የስራ ባልደረቦቼ ከሰጡት የህግ ትርጉምና ከደረሱበት መደምደሚያ የተለየሁባቸውምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ከአብላጫው ድምጽ በውሳኔ እንደተገለጸው፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ውክልና ያለው የክልሉ ዐቃቤ ህግ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 የተመለከተውን በመተላለፍ፣ ከግብር ነጻ ያስገባውን የግንባታ ማቴሪያል፣ ለሌሎች ሰዎች አሳልፎ በመስጠት ወይም በመሸጥ ወንጀል እንደፈጸመና፣ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋጌዎች እንደተሻሻሉና አዋጅ ቁ.286/1994 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመ መሆኑን፣የአዋጅ ቁጥር 686/2002 ድንጋጌ በመተላለፍ የጸና ንግድ ፍቃድ ሳይኖረው የንግድ ስራ በማከናወን ወንጀል የፈጸሙ መሆኑን የሚዘረዝር የወንጀል ክስ ለመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል የክልሉ አቃቤ ህግ በአመልካች ላይ ያቀረባቸው የወንጀል ክሶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መካከል ከፊሎቹ በፌዴራል ፍ/ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቁና ክፊሎቹ ደግሞ በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት /የወረዳ ፍ/ቤት/ የዳኝነት የስር ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ መሆናቸው የሚያከራክር አይደለም፡፡

2. እያከራከረ ያለው፣ የክልሉ አቃቤ ህግ በክልል ፍ/ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን ስር እና በወረዳው ፍ/ቤት የዳኝነት የስር ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁትን የወንጀል ክሶች፣ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 109 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 117 በሚደነገገው መሰረት በአንድ ላይ አጠቃልሎ ለመቀሌ ከተማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብና የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ያቀረበለትን የወንጀል ክሶች በመቀበል ፣የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ መስጠቱ፣ ጉዳዩ በይግባኝ እና በሰበር ታይቶ በሚወሰንበት ስርዓትና በክልል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ላይ የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡

3. ተጠሪ የፌዴራል ወንጀል የሆኑትንና የክልሉን ወንጀል የሆኑትን ጉዳዮች በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 109 ንዑስ አንቀጽ /3/ መሰረት በማጣመር ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንዑስአንቀጽ 4 ከክልል የዳኝነት ስልጣን በተጨማሪ የተሰጠው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስልጣኑ በመጠቀም የወንጀል ክሶቹን አይቶ እንዲወስንና ከዚህ ጎን ለጎን በኢፌዲሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 7 በክልሉ ህገ መንግስትና በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በተሰጠው ክልላዊ የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት የፌዴራሉንና የክልሉን የወንጀል ጉዳዮች ጎን በጎን እውነት ፍርድ እንዲሰጥባቸው በማሰብ እንደሆነ ተጣምረው ከቀረቡለት የወንጀል ክሶች ይዘት ሙሉ መሠረታዊ ባህሪ፤ ከሕገ መንግስቱና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

4. በእርግጥ የክልል ዐቃቤ ህግ የፌዴራል የክልል የወንጀል ጉዳዮች አጣምሮ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለማቅረብ መሠረት አድርጎ የሚከራከረው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ በጠቅላላውና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀፅ 3፣ አንቀፅ 117 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች አገራቱ፣ አህዳዊ ቅርፀ መንግስት ትተዳደር በነበረበት ጊዜና የዳኝነት ሥልጣንም በአንድ ማዕከላዊ መንግስት ተጠቃሎ ተይዞ በነበረበት 1954 ዓ/ም የታወጁ ናቸው፡፡ እነዚህን እድሜ ጠገብ ድንጋጌዎች የመንግስት ስልጣን በፌዴራልና በክልል በተዋቀረበትና የዳኝነት ሥልጣንም በፌዴራልና በክልል ደረጃ ተከፍሎ ተግባራዊ በሆነበት ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ውስጥ ተፈፃሚ ሲያረጉ በሕገመንግስቱ አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 7 አንቀጽ 78 እንደዚሁም የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 (ለ) ንዑስ አንቀጽ 3 እና ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገጉትን መሠረታዊ መርሆች በማይጥስ ወይም በማይሸራርፍ መንገድ መተርጎምና ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቃል የሚል እምነት አለኝ፡፡

5. ከዚህ አንፃር ሲታይ የመቀሌ ከተማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ንዑስ አንቀፅ 3 እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 117 መሠረት አጣምሮ ካቀረበለት የወንጀል ክሶች መካከል፣ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ስር የሚወድቁትን የወንጀል ክሶች በሕገመንግስት አንቀፅ 88 ንዑስ አንቀፅ 4 ካለው ክልልዊ የዳኝነት ሥልጣን በተጨማሪ ተደርቦ የተሰጠውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን በመጠቀም አይቶ አከራክሮና መርምሮ ፍርድ ሰጥቶበታል ተብሎ ሊያዝ የሚገባው ነው፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር ከሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮች ጋር በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ንዑስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀፅ 3 መሠረት ተጣምረው የቀረቡትን በክልል የዳኝነት ስልጣን ሥር የሚወድቁ የወንጀል ክሶች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 7 በክልሉ ሕገ መንግስትና ሌሎች ክልላዊ የሕግ ማዕቀፎች የተሠጠውን ክልላዊ የዳኝነት ስልጣን በመጠቀም ጉዳዮችን አይቶ አከራክሮና በማስረጃ አጣርቶ ፍርድ ሰጥቶበታል የሚል ግንዛቤ ሊይዝ ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

6. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያለውን የፌዴራልና የክልል የዳኝነት ስልጣን መሰረት በማድረግ የሰጠው ፍርድ በይግባኝ አይቶ የወሰነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፤ ይግባኙን መርምሮ ውሳኔ የሰጠው በሕገ መንግስቱና ሌሎች ሕጎች የተሰጠውን ድርብ የዳኝነት ሥልጣን መሰረት በማድረግ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 4 እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 የተሰጠውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣኑ አይቶ በሰጠው ፍርድ ላይ ተጠሪ ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 2 በተጨማሪነት በተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣኑንና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 5 የተሰጠውን የፌዴራል የይግባኝ የዳኝነት ስልጣን በመጠቀም ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በሌላ በኩል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከፌዴራል የወንጀል ክሶች ጋር ተጣምረው በቀረቡለት የክልል የወንጀል ክሶች ላይ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የቀረበለትን የይግባኝ ቅሬታ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 7፣ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 6 በክልሉ ሕገ መንግስትና በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ የሰጠውን ክልላዊ የይግባኝ የዳኝነት ስልጣኑን መሰረት በማድረግ መርምሮ ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

7. ተጠሪ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ላይ የቀረበውን ጥቅል የይግባኝ ቅሬታ አይቶ ውሳኔ ሲሰጥ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፌዴራል የይግባኝ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ተፈፅሟል የሚለውን መሰረታዊ የሕግ ስህተትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በክልል የይግባኝ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ በሰጠባቸው ክልላዊ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ፈፅሟል የሚለውን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት፣ በሰበር አይቶ እንዲያርምለት ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በተጠሪ በኩል የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ይዘትና ከላይ የገለፅናቸውን የሕገመንግስቱን ድንጋጌዎች በማገናዘብ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ የሰጠባቸውና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ይግባኝ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ ያሻሻላቸው ወይም በሻራቸው የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንዲታይለት ተጠሪ ማቅረቡ ህጋዊ መሰረት የሌለውና ተጠሪ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 5 በተደነገገው መሰረት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ እንዳለበት ገልፆ የተጠሪን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ያደረገው መሆኑን ፣የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተደራቢ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ በሰጠባቸው የፌዴራል ወንጀሎች ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በክልል የዳኝነት ሥልጣኑ በተጨማሪነት በተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል የይግባኝ ሥልጣኑ መሠረት አይቶ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል ዳኝነት ሥልጣኑ የሰጠውን ውሳኔ ባፀናባቸው ጉዳዮች ፣ጉዳዩን በሰበር አይቶ የመወሰን ሥልጣን የሌለው መሆኑንና የሰበር አቤቱታው መቅረብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚገባው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደሆነ በመግለፅ የወሰነ መሆኑን መዝገቡ ያሣያል

8. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ፣ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ካቀረበባቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍርድ ከሰጡባቸው የወንጀል ጉዳዮች ውስጥ በሰበር አይቶው ውሣኔ የሰጠበት ተጠሪ ከፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ጋር በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አጣምሮ ክስ ያቀረበባቸውን በክልሉ ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን ሥር የሚወድቁ ክልላዊ የወንጀል ጉዳዮች ላይ የሆኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክልላዊ የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑን በመጠቀም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ደግሞ ክልላዊ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣኑን በመጠቀም በሰጡት ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለመሆኑን በማጣራት ነው፡፡ ይህም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 የተሰጠውን በክልል ጉዳይ ላይ ያለውን የበላይና የመጨረሻ ሥልጣንና በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3(ለ) የተሰጠውን የሰበር ሥልጣን መሠረት ያደረገና የሕግ ስህተት የሌለበት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

9. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነውን ውሳኔ የሰጠው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ተጣምረው ከቀረቡላቸው የፌዴራልና የክልል የወንጀል ክሶች፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሕገ መንግስቱ ተደርቦ የተሰጣቸውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃና የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን መሠረት በማድረግ ፍርድ የሰጡባቸውን የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች በሰበር አይቶ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በግልፅ ለይቶ አውጥቶ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመወሰንና ከተጣመሩት የወንጀል ክሶች ውስጥ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በክልል የዳኝነት ሥልጣናቸው አይተው ውሣኔ የሰጡባቸውን የወንጀል ጉዳዮች ላይ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ብቻ በመመርመር ነው፡፡ በእኔ እምነት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ንዑስ አንቀፅ /3/ እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 117 መሰረት ተጣምረው ያቀረቡለትን የፌዴራልና የወንጀል ክሶችን በአንድ ላይ አይቶ የመወሰን ድርብ የዳኝነት ስልጣን ላለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጣምረው መቅረባቸው፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል የወንጀል ክሶችን ከክልል የዳኝነት ስልጣኑ በተጨማሪ በሕገ መንግስቱ በተሰጠው የፌዴራል የዳኝነት ስልጣኑ፣ የክልል የወንጀል ክሶችን ደግሞ በክልል የወንጀል የዳኝነት ስልጣን አይቶ ውሳኔ ለመስጠት፣ በሁሉም የወንጀል ጉዳዮች የሚቀርበውን ክርክር አንድ ላይና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመስማትና የመወሰን እድል ከመፍጠር ውጭ ከፌዴራል የወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ የወንጀል ክስ የቀረበበትን የክልል የወንጀል ጉዳይ ወደ ፌዴራል ወንጀልነት የመቀየር ውጤት አይኖረውም፡፡

10. የክልሉ ጉዳዮች ከፌዴራል የወንጀል ጉዳይ ጋር ተጣምሮ ክስ ያቀረበበት መሆኑ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልላዊ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ በሰጠባቸው የክልል የወንጀል ክሶች ላይ የሰጠውን ፍርድ፣ ክልላዊ የሆነ የይግባኝና የሰበር የዳኝነት ስልጣን ያላቸው የክልሉ ፍርድ ቤቶች፣ ክልላዊ የሆነ በይግባኝና በሰበር አይተው ጉዳዩን ከመወሰን የሚገድባቸው አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በዚህ ጉዳይ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ የተሰጠው ክልላዊ የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮች ላይ የሰጡት ውሳኔዎች በሰበር በማየትና ክልላዊ የዳኝነት ስልጣኑን በአግባቡ ከመጠቀም ውጭ የፈፀመው መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለ ብዬ ስለማላምን በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ጉዳይ የቀረበው አከራካሪና መሰረታዊ የክልልና የፌዴራል የዳኝነት ስልጣን ጭብጥ፣ ይኽ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 91327 ውሳኔ ከሰጠበት ጉዳይ የሚለይባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ይኽው የሰበር መዝገብ ቁጥር 91327 የቀረበውን ጉዳይ በመጀመሪያ አይቶ ውሳኔ የሰጠው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ተጣምረው የቀረቡለትን ሁሉንም የፌዴራልና የክልል የወንጀል ጉዳዮች በዳኝነት አይቶ ለመወሰን የማያስችለው ድርብ የዳኝነት ስልጣንና የስረ ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑ ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 240 ተጠቅሶና ከክልል የወንጀል ጉዳይ ጋር ተጣምሮ የቀረበለትን የወንጀል ክስ፣ አይቶ የመወሰን ስልጣን በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት ያልተሰጠው ቢሆንም፣ ከሌሎች የክልል ጉዳዮች ጋር አጣምሮ በማየት ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ይህንን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕግ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ የፌደራል ወንጀል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አይቶ መወሰኑ ስህተት መሆኑን በመረዳት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ስህተቱንየማረምስራባለመሻራቸውናበፍርድ የፈፀመውን ስህተት ባለማረማቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ዉሣኔ የዚህ ሰበር ችሎት ሙሉ በሙሉ እንዲሻር ውሣኔ የተሰጠበት መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡

11. በያዝነው ጉዳይ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ተጣምሮ የቀረበውን የወንጀል ክስ በዳኝነት አይተው ውሣኔ የሰጡት ፣ጉዳዩን ለማየት ክልላዊ የዳኝነት ሥልጣንና በተደራቢ የሆነ የፌደራል የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎትም በሰበር አይቶ የወሰነው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በክልል የዳኝነት ሥልጣናቸው አይተው የወሰኗቸዉን የክልል የወንጀል ጉዳዬች ብቻ ለይቶና መርጦ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ የወንጀል ክሱንም ሆነ የይግባኝ ቅሬታውን እንደወንጀሎች መሠረታዊ ባህሪ በመለየት፣በሁለት የተለያዩ መዝገቦች አለማቅረቡና የወንጀል ክሶችን አጣምሮ በአንድ ላይ ማቅረቡ ጉዳዬቹን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያላቸው የፌደራል ፍርድ ቤቶች ናቸው ከሚለው መደምደሚያ ላይ ያደርሳል የሚል እምነት የሌለኝ በመሆኑ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 7 የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 (ለ) መሠረት ያደረገ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 104715

መጋቢት 02 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- እንደሻው ይልማ ዳዲ - የቀረበ የለም
ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ አቶ ያሬድ አየለ - ቀረቡ
መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ክሳሽ አመልካች ተክሳሽ በመሆን ነው፡፡ ጉዳዩ የወንጀል ክርክር የሚመለከት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ሁለት ክሶች አቅርበዋል፡፡ አንደኛው ክስ አመልካች የወ/ሕ/ቁ 692(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ጉዳይ ፈፃሚ ነኝ የፍቺ የምስክር ወረቀት ላሰራልህ በማለት የግል ተበዳይ ወንድወሰን አራጋው እህት ለሆነችው ፍቅርተ አራጋው እና ባለቤቷ በማታለል በሁለት ጊዜ ክፍያ አርባ ሺህ ብር ከወሰደ በኃላ ለልደታ ክፍለ ከተማ ውልና ጋብቻ መዝገብ የተሰጠ በማስመሰል ሀሰተኛ የፍቺ የምስክር ወረቀት የሰጠመሆኑን፤ 2ኛ ክስ ደግሞ የወ/ሕ/ቁ 385(1)(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ በሀሰት የተዘጋጀ የፍቺ ምስክር ወረቀት በማዘጋጀት ለግል ተበዳይ የሰጠ በመሆኑ፤በምስክር ወረቀቶች ላይ በሚደረግ ወንጀል መከሰሱን የሚያሳይ ነው፡፡
የሥር ፍርድ ቤትም የአመልካች የእምነት ክህደት ቃል በሕጉ አግባብ ከመዘገበ በኃላ አመልካች ክዶ በመከራከሩ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል አዳምጧል፡፡ አመልካች በቀረቡ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ድርጊቱን የፈጸመ መሆኑን በመግለጽ በመመስከራቸው ምክንያት እንዲከላከል ታዞ የመከላከያ ምስክሮችን ቃል ሰምቷል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡ ምስክሮች የአሁኑ አመልካች 40 ሺህ ብር ተቀብሎ በሀሰት የተዘጋጀ የፍቺ ምስክር ወረቀት መስጠቱን የቀረቡት የሰው ምስክሮች እንዲሁም አመልካች ለፖሊስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27(2) በሰጠው ቃል ጭምር እንዳመነ፤በአመልካች በኩል የቀረቡ የመከላከያ ምስክሮች የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ አላስተባበሉም በማለት በተከሰሰባቸው ሁለቱም የህግ ድንጋጌዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 149(1) መሰረት ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ቅጣትን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከመዘገበ በኃላ አንደኛው ክስ የወ/ሕ/ቁ 692(1) የወንጀል ደረጃ፣ መነሻ የእስራት ቅጣት እና መቀጮ እርከን የወጣለት በመሆኑ የወንጀሉ ደረጃ 5 ተጓዳኝ የእስራት ቅጣት እርከን 14 መቀጮ ደግሞ 3 በመሆኑ ፍርድ ቤቱም መነሻ ቅጣቱ 2 ዓመት ከ 9 ወር እና 2,500.00 ብር መቀጮ እንዲሆን ወስኗል፡፡ 2ኛ ክስ የወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደረጃ እና የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ያልተዘጋጀለት በመሆኑ የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ ደረጃ በመመደብ አንድ ዓመት ቀላል እስራት በመነሻነት ይዟል፡፡ ሁለቱም መነሻ ቅጣቶችን በመደመር በእርከን 17 ሥር በመክተት ፍቅድ ሥልጣኑ 3 ዓመት ከ 3 ወር እስከ 3 ዓመት ከ 11 ወር ፅኑ እስራት እና 3000,00 ብር መሆኑን በመግለጽ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቅጣት ማክበጃ ምክንያት አልቀረበም፡፡ በአመልካች በኩል ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመቀበል በእርከን 14 ሥር 2 ዓመት ከ 9 ወር እና ብር 600.00 እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል የተባለ በመሆኑ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር ያደረጉ ሲሆን አመልካች በሰበር ቅሬታው የጠቀሰው መሠረታዊ ነጥብ የወንጀል ድርጊት በሁለት የህግ አንቀጾች የሚያስጠይቅ አይደለም፤ የቅጣት አወሳሰን ሥርዓቱም ቀላል እስራት ወደ ጽኑ እስራት ሳይለወጥ የተደመረ በመሆኑ የወ/ሕ/ቁ 184(1)(ለ) ያገናዘበ አይደለም የሚል ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ በሰጠው መልስ የማታለል እና የሀሰት ምስክር ወረቀት ማዘጋጀት ሁለቱም ድንጋጌዎች እራሳቸው የቻሉ እና አንደኛው ሌላኛውን የላካተተ በመሆኑ በሁለቱም የህግ አንቀጾች ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው፡፡ ቅጣት በተመለከተ የጽኑ እና ቀላል እስራት በወ/ሕ/ቁ 184 (1) (ለ) መሰረት ያልተሰራ በመሆኑ በህጉ አግባብ ተስተካክሎ በእርከን 12 ሥር ተሰልቶ ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌለው አመልክቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት መታየት ያለባቸው መሰረታዊ ጭብጦች፡- አንደኛ አመልካች ተጠሪ በቀረበው ክስ የተጠቀሱ የህግ ድንጋጌዎች ሥር በሁለቱም ጥፋተኛ መባሉ በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?ሁለተኛ የጥፋተኝነት ውሳኔው በአግባቡ ከሆነ የቅጣት አወሳሰን ሥርዓቱስ የወ/ህ/ቁ 184(1) (ለ) እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2005 ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፡

የመጀመርያው ጭብጥ በተመለከተ፡- በመሰረቱ አንድ ድርጊት አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ መሆኑ በሕጉ አገላለጽ የተረጋገጠ ከሆነ በአንድ ድንጋጌ ሥር ጉዳይ የሚታይ ስለመሆኑ ከወ/ሕ/ቁ 61 መሰረታዊ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በሌላ በኩል ተደራራቢ ወንጀሎች መፈጸማቸው ሲረጋገጥ ደግሞ ለሁለት እና ከሁለት በላይ ለሆኑ ድንጋጌዎች አጥፊው በሕጉ አግባብ የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ በወ/ሕ/ቁ 60፣63 ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የሚመነጩ ድርጊቶች ሕግ አውጪው ራሳቸው ችለው ወንጀል እንደሚያቋቁሙ ለወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የደነገገ ከሆነም ወንጀል ፈፃሚው በሁለቱም የሕግ አንቀጾች እንደሚቀጣ ግልጽ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች በአንደኛው ክስ የማታለል ወንጀል በ2ኛ ክስ ደግሞ ሐሰተኛ የምስክር ወረቀት ለግል ተበዳዮች መስጠቱን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በማታለል ድርጊቱ መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሁኖ በ2ኛ ክስም በተደራቢነት ሊጠይቅ እንደሚገባ በወ/ሕ/ቁ 699 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም አመልካች ሁለቱም ድርጊቶች በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚጠቃለሉ ናቸው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡

ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች በሁለት የህግ ድንጋጌዎች ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ የሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለመጀመሪያው ክስ የጽኑ እስራት አማራጭ የተወሰደ ሲሆን ለሁለተኛ ክስ ደግሞ የአንድ ዓመት ቀላል እስራት ወስደዋል፡፡ በጽኑ እስራት እና ቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው ሲገኙ የቀላል እስራት ወደ ጽኑ እስራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚለወጥ፤ስሌቱም የሁለት ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚቆጠር በወ/ህ/ቁ 184 (1) (ለ) ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሁለተኛው ክስ (ወ/ሕ/ቁ 385) የአንድ ዓመት ቀላል እስራት የወሰነ ቢሆንም ወደ ጽኑ እስራት ሳይለወጥ የሁለቱም ድንጋጌዎች መነሻ ቅጣት በመደመር መወሰኑ የወንጀል ሕጉ እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ያላገናዘበ ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት የተፈፀመው የሕጉን አተገባበር ስህተት ሳያርም ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእነዚህ ሁለቱ ምክንያቶች በሥር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመው የሕግ አተገባበር ስህተት በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን የሚያሳይ በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ በመሆኑም ከላይ በተመለከተው የህግ ድንጋጌ መሰረት የሁለቱም ድንጋጌዎች መነሻ ቅጣት ሲደመር 3 ዓመት ከ 3 ወር ጽኑ እስራት እንደሚሆን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው የቅጣት ስሌት የምንረዳው ነው፡፡ በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 26(3) መሰረት መነሻ ቅጣቱ በመወሰንና በመደመር በቅጣት እርከኑ ሠንጠረዥ የሚያርፍበት የቅጣት እርከን መለየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት መነሻ ቅጣቱ በእርከን 15 የሚካተት ሲሆን በአመልካች በኩል በሥር ፍ/ቤት ተቀባይነት ያገኙ ሦስት የቅጣት ማቅለያዎች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 23 (1) መሰረት በእያንዳንዱ ማቅለያ ምክንያት እርከን አንድ ወደታች ይቀንሳል፡፡ እንዲህ በመሆኑም ቅጣቱ በእርከን 12 ከተመለከተው ከ2 ዓመት እስከ 2 ዓመት ከ 6 ወር ባለው ፍቅድ ሥልጣን ፍርድ ቤት የመወሰን ሥልጣን አለው፡፡

ቅጣቱ ሲወሰን የወንጀል ሕጉ ዓላማ ግብ በአንድ በኩል በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል ፈፃሚው ግላዊ ሁኔታዎች፤ የወንጀል አፈፃፀም ሁኔታ እና ተዛማጅ ጉዳዮች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ላይ የሚወሰነው ቅጣት የሚያስጠነቅቀው፤ የሚያስተምረው፤ሌላ ወንጀል እንዳይፈፅም የሚያደርገው መሆን አለበት፡፡ በሌላ በኩል ማሕበረሰቡም በቂ ትምህርት በመውሰድ ከወንጀል ድርጊት እንዲርቅ የሚያደርገው መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም ከላይ የገለጽነው አጠቃላይ የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች መሰረት በማድረግ አመልካች በዚህ ጉዳይ ከአሁን በፊት የታሰረበት ካለ በቅጣቱ የሚካተት ሆኖ በ 2 ዓመት ጽኑ እስራት እና 600.00 ብር መቀጮ እንዲቀጣ ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 143927 በ5/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ደ/መ/ቁ 102208 በ 30-10-2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195(2) (ለ) (2) ተሻሽሏል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች በተከሰሰባቸው ሁለቱም ድንጋጌዎች ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የወሰኑት እስራት ቅጣት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 195 (2) (ለ) (2) በማሻሻል በሁለት ዓመት ጽኑ እስራት እና 600.00 ብር መቀጮ እንዲቀጣ ወስነናል፡፡ የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤትም በዚህ ችሎት በተሻሻለው ቅጣት መሰረት ተቆጣጥሮ እስራቱን እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92141

መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ሕይወት

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- የደ/ብ/ብ/ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትፍትሕ ቢሮ አቃቤ ሕግ

ተጠሪ፡- አቶ አለማየሁ አስፋው

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543/2/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በሾፌርነት ሙያቸው የሌላውን ሰው ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለባቸው መጋቢት 02 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀኑ 5፣30 ሲሆን ንብረትነቱ የድርባ ደፈርሻ የመንገድ ስራ ተቋራጭ የሆነውን፤ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-25709 ኦሮ የሆነውን ቶዮታ ሃይሉክስ መኪና ከአዲስ አበባ ከተማ ወደ አርባ ምንጭ መሰመር በከፍተኛ ፍጥነት እና የራሳቸውን መስመር በመልቀቅ በማሽከርከር ላይ እያሉ በምዕራብ አባያ ወረዳ ብርብር ከተማ የሰሌዳ ቁጥሩ 2-ደ/ሕ 11444 የሆነችውን ባለሁለት እግር ባጃጅ ሞተር ሲያሽከረክር የነበረውን ንጋቱ ሉቃስ የተባለውን ሰው በመግጨት የገደሉት በመሆኑ በፈፀሙት በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም የክስ ማመልከቻ ደርሷቸው ክሱን እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ በክሱ ላይ ተቃውሞ እንደሌላቸው የገለፁ ሲሆን የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተም ድርጊቱ መፈፀሙን አምነው አፈፃፀሙ ግን እንደ አቃቤ ህግ ክስ ያለመሆኑን ዘርዝረው የክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ አቃቤ ህግ በበኩሉ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው ሚች በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ሕይወታቸው ያለፈ መሆኑን አቃቤ ህግ በማስረጃዎቹ ያስረዳባቸው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ታምኖበት ይህንኑ እንዲያስተባብሉ የተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብታቸው ተጠብቆላቸው ተጠሪ አንድ የሰው መከላከያ ማስረጃዎችን አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ በሚች ላይ የሞት አደጋ የደረሰው በሚች ጥፋት መሆኑን ከማስረጃዎቹ መረዳቱን ገልፆና በአቃቤ ህግ ማስረጃዎችም ልዩነት መከሰቱን ዘርዝሮ ተጠሪ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎቹን በመከላከያ ማስረጃቸው አስተባብለዋል በሚል ድምዳሜ ክክሱ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙንና የሰበር አቤቱታውን እንደየቅደም ተከተላቸው ለክልሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅላይፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርብም ቅሬታው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(1) መሠረት ተሰርዞበታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚልባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ድርጊቱን የፈፀሙት ከጥንቃቄ ጉድለትና በከፍተኛ ፍጥነት ሲያሽከረክሩ ሆኖ እያለ በስር ፍርድ ቤቶች የሚች ጥፋት አለ ተብሎ የተጠሪ የወንጀል ተጠያቂነት የለባቸውም ሲባል መታለፉ ያላግባብ መሆኑን፣የትራፊክ ባለሙያዎች የሰጡት የትራፊክ ኘላንና የአደጋ መግለጫ የሰነድ ማስረጃዎች ውድቅ የተደረጉት ተገቢውን የማስረጃ ሚዛን ባለመከተል መሆኑን ዘርዝሮ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ በተጠሪው ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲሰጥ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪ በነጻ የመለቀቃቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 239(2) በግልጽ ደንግጓል፡፡እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው ከድርጊቱ ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ ናቸው፡፡በምክንያትነትና በውጤት መካከል ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 24 በተመለከተው አግባብ ግንኙነት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ወንጀሉ በተከሳሹ የተፈፀመ መሆኑን ከሳሽ የሆነው ወገን አሳማኝ እና በቂ በሆነ ሁኔታ የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑን ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141፣142 እና 194 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ ሲያሽከረክሩት የነበረው ተሽከርካሪ እና ሟች ሲያሽከረክር የነበረውን ተሽከርካሪ ተጋጭተው ሟች ላይ መጋቢት 02 ቀን 2004 ዓ.ም ጉዳት ደርሶ በዚሁ ጉዳት ምክንያት ሟቹ ለህልፈት የተዳረገ መሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ተጠሪ የሚከራከሩበት ነጥብ በወቅቱ ራሳቸው የሚያሽከረክሩትን መኪና በተገቢው ፍጥነትና ጥንቃቄ በተሞላበትሁኔታ ሲያሽከረክሩ እንደነበር ጠቅሰውና ይህንኑ አይተዋል ተመልክተዋል የሚሏቸውን አንድ የሠው መከላከያ ምስክራቸው አስረድተዋል ሟች የሞቱት በራሳቸው ጥፋት ምክንያት ነው የትራፊክፕላኑ አደጋው የደረሰው በተጠሪ ጥፋት ነው በሚል የቀረበው ተጠሪ ያልፈረሙበት በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም የሚሉ ነጥቦችን በማንሳት መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭና ከዋናው መዝገብ ከሰፈሩት የክርክር ሂደቶች ተገንዝበናል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ይህንኑ የተጠሪን መከራከሪያ ነጥብ የተቀበለው ሲሆን የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቃል ልዩነት ያለበት መሆኑን፣የትራፊክ አደጋ ፕላኑና የአደጋው መግለጫ ሰነዶች የማይታመኑ መሆኑና የተጠሪ መከላከያ ማስረጃ ግን የሚታመኑ መሆኑን በውሳኔ ላይ ጠቅሷል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

፡፡ ይሁን እንጂ የሥር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ቀጥተኛና አግባብነት ያለውን የባለሙያ የምስክርነት አስተያየት በአደጋው ቦታ የተነሳውን ፕላንና የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል መዝኖ ተጠሪ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ቀርተው አደጋው መድረሱን የዐቃቤ ህግ የሠውና የሰነድ ማስረጃዎች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ውድቅ ያደረገው መሰረታዊ ነጥቦች ላይ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል ልዩነት ማሳየቱን ፣የባለሙያ ምስክርነት ቃልም በተገቢው ማስረጃ የተስተባበለ መሆኑን በግልጽ ጠቅሶ ያለመሆኑን ከውሳኔው ግልባጭና ከዋናው መዝገብ ላይ ከሰፈረው የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል እንዲሁም ከሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች የተከሰሰው ሲያሽከረክሩት የነበረውን መኪና በከፍተኛ ፍጥነት እና የራሳቸውን የቀኝ መስመር በመልቀቅ ወደ ግራ መስመር በመግባት በጥንቃቄ ጉድለት ሟችን ገጭተዋል በሚል ምክንያት ሲሆን አመልካች ይህንኑ የድርጊት አፈፃፀም በተመለከተ በጊዜው እና በቦታው የነበሩትን የሰው ምስክሮች ስለአደጋው ሙያዊ አስተያየት መስጠት የሚችሉትን የትራፊክ ፖሊሶች የሰጡትን ሙያዊ መግለጫ ለማስረጃነት አቅርቦ ለፍርድ ቤቱ ከመስማቱ በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ የትራፊክ ፖሊሶች ችሎት ቀርበው ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጡበትም አድርጓል ፡፡ በአቃቤ ህግ በኩል የተሰሙት ሁለት ምስክሮች ተጠሪ ሲያሽከረክሩት የነበሩውን መኪና ፍጥነት ከሙያ አንፃር ሊመሰክሩ ይችላሉ ተብሎ የማይወሰዱ ቢሆንም ሟች በወቅቱ የነበረበትን ሁኔታና የደረሰበትን ጉዳት ከመመስከራቸውም በላይ ድርጊቱ ሲፈጸም የተጠሪ መኪና በከፍተኛ ፍጥነት ሁኖ ወደ ሟች ግራ መስመር አጥብቦ በመግባት ሟችን እንደገጨውና የተጠሪ መኪና የቆመበትን አጠቃላይ ሁኔታ እንደግንዛቤአቸው መጠን የገለጹ ሲሆኑ በምስክሮች ቃል ተከስቷል የተባለው ልዩነት ሟቹ ሲያሽከረክር የነበረው ባጃጅ ተሽከርካሪ ወደ ዋናው መንገድ የፊት ጎማው የገባ መሆን ያለመሆኑ እና የተጠሪ መኪና ከግጭቱ በኃላ የቆመበትን አግባብ የሚመለከት ነው፤ ስለጉዳዩ ሙያዊ አስተያየት በሰነድ ማስረጃዎቹ ላይ ያሰፈሩት የትራፊክ ፖሊሲዎች የተጠሪ የመኪና ማሽከርከር ሁኔታ የትራፊክ ደንቡን ተከትሎ የተከናወነ ያለመሆኑን ሟች ለግጭቱ መከሰት ያደረገው አስተዋጽኦ ያልነበረ መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ የመሰከሩ ሲሆን የእነዚህ ምስክሮች ቃል በስር ፍርድ ቤት ክብደት ሳይሰጠው የታለፈው የአደጋ ቦታ ፕላኑ ረቂቁ የአደጋ መነሻ ቦታ ላይ ምልክት ያለበት ሁኖ ዋናው ግን ይኼው ምልክት የለውም የሚለውንና ለመርማሪ ከሳሽ ሲላኩ የሰነዶቹን የገጽ ብዛት ፍርድ ቤት ከቀረበው ጋር የተለያዩ መሆናቸውን የሚገልፁ ምክንያቶች በማስፈር ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዋናው የአደጋ ቦታ ፕላን የትራፊክ አደጋ የሚነሳበትን ደንብ መሰረት አድርጎ ያልተነሳ መሆኑን በተጠሪ ማስተባበያ ክርክርና ማስረጃ ያልቀረበበት ከመሆኑም በላይ ተጠሪ በወቅቱ ያሽከረክሩት የነበረውን መኪና ከተገቢው ፍጥነት በላይ እና ከተገቢው መስመር በመውጣት ሲያሽከረክሩ የነበሩ መሆኑን ሰነዶቹ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገልፁት መሆኑን የሰነዶቹ ይዘት በግልፅ ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክር የተጠሪ መኪና ፍጥነት የለውም ብለው የሰጡት ምስክርነት የባለሙያዎችን የምስክርነት ቃል ሊያስተባብል የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አንድ የትራፊክ ባለሙያ የሚሰጠው ሙያዊ አስተያየት የማስረጃነት ዋጋ የማይሰጠው አስተያየቱ ተገቢውን የሙያ ደንብ ተከትሎ ያልተሰጠና ያልቀረበ፣ በጊዜውና በቦታው ከነበሩት የአይን ምስክሮች ቃል ጋር ተነጻፅሮ ሲታይ በመሰረታዊ ነጥቦች ላይ ልዩነት ያለበት መሆኑ ሲረጋጥ እንጂ በጭፍጫፊ ነጥቦች ላይ ልዩነት ተከስቷል ተብሎ ሊሆን አይገባም፡፡

በመሰረቱ ፍርድ ቤቱ የልዩ አዋቂዎችን የምስክርነት ቃል ጉዳዩን ለማብራራት ወይም ለክርክሩ ውሣኔ አሰጣጥ ተገቢ ነው ካለ ወይም ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸውን ለማስረዳት በሕጉ አግባብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከቆጠሩ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን ልዩ አዋቂዎች ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ሊያደርግ እንደሚችል ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የልዩ አዋቂዎች ምስክሮች ቃላቸውን ገለልተኛ ሆነው መስጠት እንደአለባቸውና ቃላቸው ያለበቂ ምክንያት ልዩ አዋቂ ያልሆኑ ሰዎች በሚሰጡት የምስክርነት ቃል ውድቅ መሆን የሌለበት መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ሕግ ደንቦች የሚያስገነዘቡን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የልዩ አዋቂዎች የምስክርነት ቃል በገለልተኛነት ሊሰጥ እንደሚገባ አዋቂ ያልሆኑ ሰዎች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ከልዩ አዋቂዎች የምስክርነት ቃል የተሻለ ክብደት ሊሰጠው የሚገባው ፍርድ ቤቱ በቂ የሆነ ምክንያት ሲያገኝ በመሆኑ የልዩ አዋቂዎች የምስክርነት ቃል እንደ ማንኛውም ማስረጃ በጥንቃቄ ሊመዘን የሚገባው እንጅ ሁል ጊዜ ክብደት ሊሰጠው የሚገባ የማስረጃ አይነት አይደለም፡፡ የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ፕላን ሪፖርትም የባለሙያ ሙያዊ አስተያየትን በወረቀት ላይ ስዕላዊ በሆነ መንገድ የሚያስቀምጥ በመሆኑ በባለሙያ የሚረጋገጥ ሰነድ በመሆኑ እንደ ማንኛውም የልዩ አዋቂ የምስክርነት ቃል በተገቢው መንገድ ሊመዘን የሚገባው የማስረጃ አይነት እንጅ ሁልጊዜ ድምዳሜ ማስረጃ (Conclusive Evidence) ያለመሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይም የትራፊክ ሰነዱ ይዘትና የትራፊክ ባለሙያዎች አስተያየት ተገቢውን የትራፊክ ደንብ ተከትሎ ያልተሰራ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ልዩ አዋቂ ባልሆኑት በተጠሪ መከላከያ ምስክር ቃል ተስተባብሏል ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን መሰረታዊ ነጥቦችን ያላገናዘበና የማስረጃ አቀባበልና ምዘና ስርዓትን ያልተከተለ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በአንድ ጉዳይ የቀረበን የሰነድ ማስረጃ ይዘት ሙሉ በሙሉ ሳይመዘን በመተው በጭፍጫፊ ነጥቦች ላይ ብቻ በማተኮር ማስረጃን ክብደት ሳይሰጡ ማለፍ ደግሞ የማስረጃ ምዘና መርህና የዳኝነት አካሄዱ የማይፈቅዱት በመሆኑም የመሰረታዊ ህግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ነው፡፡ አንድ ፍ/ቤት በህግ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎቹን ውድቅ ሊያደርግ የሚገባው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነገር ሙሉ በሙሉ ይዞ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የማስረጃ ምዘና መርህ ይዞ ማስረጃውን በመመዘን እንጂ ከማስረጃዎቹ ውስጥ ጭፍጫፊውን ወይም የተወሰነውን ፍሬ ነገር ብቻ በመያዝ ሊሆን እንደማይገባው ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ህግ ጽንሰ ሀሳቦች የሚያስገነዝቡን ሐቅ ነውና፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የዐቃቤ ህግ ማስረጃዎች ተጠሪ ጥፋት የፈጸመው መሆኑን አላረጋገጡም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ከሰጠ በኃላ ሁሉም የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል እና በሰነድ ማስረጃዎች የሰፈረውን ይዘት አንድ ባንድ ባለማየትና የልዩ አዋቂዎች ሙያዊ አስተያየትን ውድቅ ለማድረግ ለሚያስችል በቂና ህጋዊ ምክንያት ሳይኖር ነው፡፡በመሆኑ ተጠሪ የሹፍርና ሙያ የሚጠይቀውን ጥንቃቄ ባለማድረግ የወንጀል ድርጊቱን በቸልተኝነት ያደረጉ መሆኑ በዓቃቤ ህግ የአይን ምስክሮች እና በትራፊክ ፖሊሶች ሙያዊ አስተያየት ተረጋግጦባቸው እያለ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመተው ተጠሪውን የስር ፍ/ቤት በነጻ ማሰናበቱም ሆነ በክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች አለመታረም መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 57 በግልጽ እንደሰፈረው “ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆንም በአንጻሩ አንድ ሰው “የፈጸመው ድርጊት በህግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈጸመ ወይም የደረሰ ሁኖ ሲገኝ በወንጀል ህግ ሊፈረድበት አይገባም በማለት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 57/2/ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የህጉ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ከሳሽ የሆነው ዐ/ህግ ድርጊቱ የተፈጸመው ሆነ ተብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም በችልተኝነት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት መሆኑን ነው።ድርጊቱ ሆነ ተብሎ ወይም በችልተኝነት የተፈጸመ መሆኑን ማስረጃ የሚጠበቅበት መሆኑን ነው። ድርጊቱ ሆን ተብሎ ወይም በችልተኝነት የተፈጸመ መሆኑ ማስረጃ ካልቀረበ ወይም ድርጊቱ ከአቅም በላይ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈጸመ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በተከሳሽ በኩል ከቀረበ የተከሰሰውን ሰው በወንጀል ህግ ጥፋተኛ ብሎ መፍረድ ከህጉ መንፈስ ውጪ ነው። በወንጀል የተከሰሰ ሰው ችልተኛ ነበር? ወይስ አልነበረም? የሚለው ጥያቄ በወንጀል ህግ በአንቀጽ 59 የሰፈረውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የሚወሰን ነው። የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ አሁን ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው በመሆኑም የህጉን ይዘት እንዳለ ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው። ይኸውም፦ ማንም ሰው በችልተኝነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለው ፦

/ሀ/ ድርጊቱ በወንጀል ህግ የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዘን፣ ወይም (ለ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ አለበት ወይም እንዳለበት ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ነው።

በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው በችልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው ውጤቱን እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ደግሞ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ውጤቱን ማወቅ ይችል ነበር ማለት ሲቻል ነው። በመሆኑም ችልተኝነት አለ ለማለት ሕጉ የሚጠቀምበት ዋነኛ መስፈርት የተከሰሰው ሰው በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ነው። ድርጊቱን የፈፀመው ሰው የነበረው ዕውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባው ዕውቀትና ግንዛቤ የሚመዘነው የሰውዬው እድሜ ያለው የኑሮ ልምድ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃው ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነም የሕጉ አንቀጽ 59(1) ይደነግጋል።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስመለስም ተጠሪ በሙያቸው አሽከርካሪ ሆነው እያለና በአሽከርካነት ሙያቸው ደግሞ የሌላውን ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለባቸው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-25709 ኦሮ የሆነውን ቶዩታ ሃይሉክስ መኪና ከዲስ አበባ ከተማ ወደ አርባ ምንጭ ከተማ እያሽከረከሩ ተገቢውን ጥንቃቄ ከማድረግ ጉድለት መኪናው ሚች ሲያሽከረክር የነበረውን ባጃጅ በመግጨት ሚች የሞተ በመሆኑ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) ስር የማይጠየቁበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም። ስለሆነም ተጠሪ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23፣24፣57፣59(ለ) እና 543(2) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ አንፃር ሲታይ ለወንጀሉ ኃላፊ ሊባሉ የሚገባ ሆኖ ስለአገኘነው ተጠሪ ላይ የተሰጠውን የነፃ መለቀቅ ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት በመሻር ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) ሰር የተመለተውን ድንጋጌ በታወቀ ችልተኝነት የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብለናል።

ይህ ከተባለ በኋላ አመልካች ባለመቅረቡ የቅጣት አስተያየት መቀበል አልተቻለም።

<u>ትዕዛዝ</u>

አመልካች የሚቀርብ ከሆነ አስተያየቱን ለመቀበልና ተገቢውን ለመከተል ለ11/02/07 ዓ.ም ተቀጠረ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 92141

ጥቅምት 14 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- የደቡብ ክልል ዐ/ህግ

ተጠሪ፡- ዓለማየሁ አስፋው

መዝገቡ የተቀጠረው የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ነው፡፡ በዚህም መሰረት መዝገቡን መርምረን ተከታዩን የቅጣት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ቅ ጣ ት

1. **አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሁኖ ከተገኘ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ያለበት ሲሆን ቅጣቱ የሚወሰነው ደግሞ ስራ ላይ በዋለው በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ታይቶ፡፡ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እስራት ሁኖ የገንዘብ መቀጮ ደግሞ ከብር 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር) እስከ 6000.00 (ስድስት ሺህ) ብር ነው፡፡**

   እንደ ቅጣት መመሪያው መወሰን እንዲቻል ደግሞ በተጠሪ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔከግራ ቀኙ ቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህ አግባብ ቅጣቱ ከመሰላቱ በፊት ግን ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ክሱ ሲመሰረትም ሆነ በበታች ፍርድ ቤቶች ክርክሩ ሲካሄድ ደረጃ ያልወጣለት ቢሆንም በዚህ ችሎት ጉዳዩ በመታየት ላይ እያለና የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በመሆኑ በዚሁ መመሪያ መሰረት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 543 ደረጃ ድንጋጌ ነው፡፡ ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸሙት በታወቀ ቸልተኝነት ከመሆኑም በላይ የሟች አስተዋጽኦ ስለሌለና ተጠሪም በሙያቸው ሹፌር በመሆናቸው የወንጀሉ ደረጃ አራት ሆኖ የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 16 ነው፡፡ በዚህ እርከን የፍርድ ቤቱ የተተወው ፍቃደ ስልጣን ከሶስት አመት እስከ ሶስት አመት ከሰባት ወር ነው፡፡ መነሻ ቅጣቱም በዚሁ ሬንጅ ውስጥ የሚያዝ ሲሆን ተጠሪ ላይ መጨረሻ ላይ የሚጣለው የቅጣት መጠን የሚታወቀው ግን የማክበጃ እና የማቅለያ ምክንያቶች ታይተው ስሌቱ ከተሰራ በኃላ ነው፡፡ በዚህም አግባብ የቅጣት መጠኑን ማስላት የግድ ሲሆን በተጠሪ ላይ በዓቃቤ ህግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃው ምክንያት የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቃቤ ህግ ጥፋተኝነት ውሳኔ ሲሰጥም ሆነ የቅጣት አስተያየቱን የማቅረብ እድሉን ለመጠበቅ ቀጠሮ ሲያዝለት አልቀረበምና፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ሪኮርድ ያልቀረበባቸው መሆኑን የክርክሩ ሂደት ማሳየቱ ይኼው ምክንያት በማቅለያነት እንዲያዝላቸው የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ማቅለያ ምክንያት ደግሞ በመመሪያው አንቀጽ 23(4) ድንጋጌ መሰረት በተጠሪ ላይ የሚጣለውን ቅጣት ከእርከን 16 ወደ እርከን 15 ዝቅ የሚደረገው ነው፡፡ በዚሁ መጨረሻ እርከን ስር የተመለከተው የቅጣት ዓይነትና የእስራት መጠን ሬንጅ ከሁለት አመት ከዘጠኝ ወር እስከ ሶስት አመት ከስምንት ወር በመሆኑ በዚሁ ለፍ/ቤቱ በተሰጠው ፈቃድ ስልጣን መሰረት የአሁኑ ተጠሪ ለፈጸመው ጥፋት በሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ቀላል እስራት ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ ስለገኘነው ተጠሪ በጉዳዩ ላይ የታሰረው ካለ ማናቸውም ጊዜ የሚታሰብለት ሁኖ በሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ቀላል እስራት ሊቀጣ ይገባል ብለናል፡፡

1. የገንዘብ መቀጮን በተመለከተ ደግሞ ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው ብር በእርከን 4 ሁኖ ስለአገኘነው በብር 3500.00 (ሶስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ነው ብለናል፡፡
2. በአመልካች የሰበር አቤቱታ ላይ የተጠሪ መኖሪያ አድራሻ አዲስ አበባ መሆኑ ስለተጠቀሰ የፌዴራል ፖ/ሊስ ከደቡብ ክልል ፖ/ሊስ ጋር በመሆን ተጠሪን አፈላልጎ በመያዝ ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብ ፣የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤትም ተጠሪን ተረክቦ በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 93577

ህዳር 22 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ዘውዴ ተስፋይ ስመኝ ጉዳይ ተከታታይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ተጠሪ በአመልካች እና በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ በነበረው ካሳየ ጌጡ ያቀረበው ክስ ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ነው፡፡ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩ የተሰማው በሌለበት በመሆኑ ከመጥሪያ አደራረስ ጋር የተያያዘ ክርክር በማቅረቡ ነው፡፡

ዓቃቤ ህግ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ እና 1ኛ ተከሳሽ በነበረው ካሳየ ጌጡ ያቀረበው ክስ የወ/ሕ/ቁ.32(1)(ሀ) እና 539(1)(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስበው በ19/10/1997 ዓ.ም. ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ትግራይ ክልል አላማጣ ወረዳ ቀበሌ ማረዋ ሚች ሰመሀኝ አረቂ በክላሽ ኮኘ መሳሪያ አንድ ጥይት በመተኮስ ገድለዋል የሚል ነው፡፡

አመልካች ጉዳዩ ሊሰማ በተያዘው ቀጠሮ ባለመቅረቡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.161(1) በሚያዘው መሰረት በመኖሪያ አካባቢው በተለጠፈ መጥሪያ ጥሪ ቢደረግለትም ባለመቅረቡ በሌለበት ክርክሩን ቀጥሎ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ከተሰሙ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት ዐቃቤ ህግ እንደ ክሱ አቀራረብ አስረድቷል በማለት አመልካች ጥፋተኛ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ቅጣት በተመለከተም በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የወሰነ መሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት ይቻላል፡፡

አመልካች በፖሊስ ክትትል በቁጥጥር ስር ከዋለ በኃላ በማረሚያ ቤት በኩል በ15/09/2004 ዓ.ም. ውሳኔ ለሰጠው ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው አቤቱታ እና በፍርድ ቤት ባደረገው ክርክር ፈጸመው በተባለው የግድያ ወንጀል ክስ የተመሰረተበት መሆኑ አለማወቁን፤ በሚኖርበት አካባቢ ባህል በግድያ የተጠረጠረ ሰው ራሱ እና ቤተሰቡ ከአካባቢው ለቀው እንደሚሄድ፤ አመልካችም አካባቢው ለቆ በኦሮሚያ ክልል ሲኖር እንደነበር፤ ቀርቦ ቢከራከር እና ቢከላከል ከእሱ ጋር ተከሶ እንደነበረው ግለሰብ በነፃ ይለቀቅ እንደነበር በመግለጽ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ተነስቶለት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ መጠየቁን፤ ዐቃቤ ህግ በበኩሉ አመልካች ወደ ህግ መቅረብ ሲገባው ሆነ ብሎ ከአካባቢው በመሸሹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአካባቢውም ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ እና ቅጣት ሊጸና እንደሚገባ ተከራክረዋል፡፡

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር በመመርመር በሰጠው ብይን አመልካች የአካባቢው ባህል መሰረት በማድረግ ከአካባቢው ለቆመሄዱ ያቀረበው ምክንያት ተቀባይነት እንደሌለው፤ በአንዛሩ ጉዳዩ ወደ ፍትህ አካል ቀርቦ መጨረስ ይገባው እንደነበር፤ አመልካች ወደ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በአካባቢው የአስተዳደር ክፍል ቤተዘመዶቹ በሚገኙበት አካባቢ መጥሪያ ተለጥፎ መቅረብ አልቻለም፡፡ ፖሊስ በቁጥጥር ስር ካደረገኝ በኃላ ነው ፍርደኛ መሆኔን ያወኩት የሚለው ተቀባይነት የለውም፡፡ መጥሪያው በአካባቢው መለጠፉን ያውቀዋል ተብሎ ይገመታል፡፡ በወ.ሕ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 197 ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስነዋል፡፡

አመልካች ቅጣት በተመለከተ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ ተቀባይነት በማግኘቱ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት በማሻሻል በ20 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በሌለበት የተሰማው ጉዳይ ሊሻር ይገባል በማለት ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162(ሀ) እንደተመለከተው የጋዜጣ ጥሪ አስፈላጊ መሆኑ አስገዳጅ ድንጋጌ ቢሆንም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ለ) እንደተደነገገው ፍ/ቤቱ ለተከሳሽ ሊደርሰው ይችላል ብሎ በገመተው አግባብ ጥሪውን ማስተላለፍ እንደሚችል ስለሚገልጽ በአመልካች መኖሪያ አድራሻ መለጠፉ ስለተረጋገጠ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በማጽናት ወስነዋል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጸመዋል ያላቸውን ስህተቶች በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘቱ፡- የተጠረጠረበት ወንጀል ከተፈጸመ በኃላ ከአካባቢው ርቆ መሄዱ፤ በአካባቢው ባህልም የተለመደ መሆኑ፤ የተከሰሰ መሆኑ አለማወቁን፤ በአካባቢውም መከሰሱን ሊነግረው የሚችል ቤተሰብ አለመኖሩን፤ ሕጉም ጥሪ በጋዜጣ እንደሚደረግ እያዘዘ በአካባቢው በተለጠፈው ጥሪ ብቻ መጥሪያ ደርሶታል መባሉ በአግባቡ አለመሆኑን፤ ቀርቦ ባለመከራከሩ የመከላከል መብቱ መታለፉ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር አመልክቷል፡፡

ዐቃቤ ህግ የበኩሉን መልስ አቅርበዋል፡፡ ዐቃቤ ህግ የሰጠው መልስ ዋና ፍሬ ነገሩ፡- የስር ፍርድ ቤት ህጉ በደነገገው አግባብ በተሰጠው አማራጭ ጥሪ ማስተላለፉ፤ አመልካች በአካባቢው በተደረገለት ጥሪ አለመቅረቡን፤ በገጠር አካባቢ በጋዜጣ የሚወጣ ጥሪ እንደማይነበብ የተሻለ የሚሆነው በአካባቢው መጥሪያው መለጠፍ መሆኑ፤ የስር ፍርድ ቤትም ይህንን አማራጭ በመውሰድ ለአመልካች የተላለፈው ጥሪ በአግባቡ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ጉዳዩ እንደመረመርነው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው መሰረታዊ የክርክር ጭብጥ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ ሲታዘዝ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓቱ ምን መምሰል አለበት? የሚል ነው፡፡ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት መፍትሔ የሚሻው ጭብጥ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የተከሰሰበት የግድያ ወንጀል በሌለበት እንዲታይ ሲወስኑ መጥሪያው ተከሳሹ ይኖርበት ነበር በተባለው ቀበሌ እና አካባቢ ብቻ መለጠፍ በወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162 የተመለከተው ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት በአግባቡ ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከስር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች በከባድ የግድያ ወንጀል ክስ ቀርቦበት ጉዳዩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ባለመቅረቡ በሌለበት ክርክሩን ተካሂዶ ጥፋተኛ ተብሎ በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች እንዲቀርብ የሰጠው ትዕዛዝ ተፈፃሚ ባለመሆኑ መደበኛ መኖሪያው ነው በተባለው እና በአካባቢው አስተዳደር መጥሪያ በመለጠፍ በሌለበት ጉዳዩን እንዲሰማ አዟል፡፡ አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው የተከሰሰ ስለመሆኑ አለመሰማቱ፤ በአካባቢው ባህል በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ቀየውን ለቆ የሚሄድ መሆኑ እና የስር ፍርድ ቤትም ህጉ ያስቀመጠውን በጋዜጣ የመጥራት አስገዳጅ ድንጋጌ በአግባቡ አለመተርጎሙን ነው፡፡

በመርህ ደረጃ የወንጀል የክርክር ሂደት ተከሳሾች ባሉበት እንደሚደረግ በልዩ ሁኔታ ደግሞ የፈጸሙት ወንጀል ቀርበው መከራከር የማይፈለጉና ከፍትህ ስርዓቱ የሸሹ ግለሰቦች በፍትህ ስርዓቱ መጠየቅ ያለባቸው በመሆኑ በሌሉበት ነገሩ ሊሰማ እንደሚችል ከወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 161(1) እና (2(ሀ) ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት ንባብ የምንረዳው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም አንድን ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ለማየት እንዲችል ተከሳሹ በቀጠሮ ቀን ያለ በቂ ምክንያት መቅረቱን ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑ የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ያመለክታል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በሌለበት ነገሩ ለመስማት ትዕዛዝ ከሰጠ ጥሪው ተደራሽ በሆነ አግባብ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል፡፡ በወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162 እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ የሚያስተላለፈው ጥሪ ተከሳሹ ስለተጠረጠበት ጉዳይ ዝርዝር መግለጫ የያዘ እና ጥሪውም በጋዜጣ እንዲወጣ መታዘዝ እንዳለበት ከድንጋጌው ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ በሌላ በኩል ፍ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘም የመጥሪያ ማስታወቂያው በሌላ መንገድ ማስተላለፍ እንደሚችል የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ያሳያል፡፡

በስር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት እንደተገለጸው የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ አለማድረጉን ነው፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን እንዳሰፈረው አመልካች የአካባቢውን ባህል መሰረት በማድረግ መሸሹን ተቀባይነት የለውም በመኖርያ ቤቱ አካባቢ እና በአካባቢ አስተዳደር የተለጠፈው መመጥሪያ ጉዳዩ በሌለበት እንደሚታይ የሰማ መሆኑ ግምት ይወስዳል በማለት ከድምዳሜ ላይ መድረሱን በውሳኔው አስፍራው አምልካች የተጠረጠረበት ወንጀል ተፈጸመ ከተባለበት በኃላ ከአካባቢው ለቆመሄዱን በየትኛውም መልኩ መከሰሱን አለማወቁን እየተከራከረ ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አምልካች የተከሰሱበት ጉዳይ በሌለበት ለመስማት ትዕዛዝ ሲሰጥ በጋዜጣ የጥሪ ማስታወቂያ ለማስተላለፍ ያልቻለበት ሁኔታ ምን እንደነበር በውሳኔው ግልጽ አላደረገም ፡፡በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ማስረጃ ቀርበው የመከላከል መብት ያላቸው መሆኑ በሕገ መንግስቱ እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች የተረጋገጠ ስለመሆኑ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 20 (1)እና(4)እና የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አካል የሆነው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች አለማቀፍ ቃልኪዳን አንቀጽ 14(3)(ለ) እና (መ)መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በሕገ መንግሥቱ እና ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች የተረጋገጠው ፍትሐዊ የዳኝነት መብት በየትኛውም መልኩ ሳይሸራረፍ በፍርድ ቤቶች ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ በእጃችን ወደ አለው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች ጉዳዩን በሌለበት የታየው የጥሪ ማስታወቂያ በመደበኛ መኖርያ ቤት እና የአካባቢ አስተዳደር በመለጠፍ ብቻ ነው፡፡ በወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ162(1) እንደተመለከተው ተከሳሽ በሌለበት የሚደረገው ክርክር የመጥሪያ ማስታወቂያ በቅድሚያ በጋዜጣ መደረጉ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተከሰሰበት ጉዳይ ቀርቦ እንዲከራከር በጋዜጣ ጥሪ ለማድረግ ያልቻለበት ምክንያት ግልፅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አላደረገም ። የወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 161(ሀ) መሠረታዊ ይዘት እና አላማ እንደተመለከተው አንድ ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ ሲሰማ በፍ/ቤት ትዕዛዝ የሚሰጥ ከሆነ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ያለበት መሆኑ በአስገዳጅነት የተደነገገበት አግባብ ሰፊ ስርጭትና ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ የሚደረግ ጥሪ፤ጥሪ የሚደረግለት ተከሳሽ ፍርድ ቤት ቀርቦ ጉዳዩን ለመከታተል የሚያስችለው እንዲሆን ነው።

የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ፍርድ ተሸሮ ጉዳዩ ድጋሜ ይታይልኝ ጥያቄ ውድቅ ሲያደርጉ ያሰፈሩት ምክንያት የወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.162(ለ) ፍርድ ቤቱ መጥሪያው ለተከሳሹ ሊደርስ ይችላል ብሎ በገመተው አግባብ ማስተላለፍ እንደሚችል ፤በዚህ የሕግ ድንጋጌ ትርጉም መሠረትም ተከሳሽ እንዲቀርብ በአካባቢው አስተዳደር እና መኖሪያ ቤቱ መጥሪያ እንዲለጠፍ አማራጭ መውሰዱን በመግለጽ ነው። በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162(ሀ) እንደተመለከተው ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ከታዘዘ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ማዘዝ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። በወ.መሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162(ለ) የተመለከተው አገላለጽ ለተከሳሹ የሚደርሰ መስሎ ከታየው መጥሪያው የሚደርስበት ሌላ መንገድ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል “የሚለውን ፍሬ ነገር በንኡስ አንቀጽ “ሀ”ላይ ከተመለከተው የጥሪ አደራረስ ሥርዓት በተሻለ አግባብ እንዲሆን ከማድረግ ውጭ ከዚህ ያነሰ መብት ለመስጠት ታስቦ የተደነገገ ስለመሆኑ ከአጠቃላይ የድንጋጌ ይዘትና ዓላማ የምንረዳው ሆኖ አልተገኘም። የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት በፍርድ ቤቱ እይታ የጥሪ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከሚደረግ ጥሪ ለተሻለ አግባብ የሚደርስ ስለመሆኑ እርግጠኛ ከሆነ ነው እንጂ ሰፊ ስርጪት እና ተደራሽነት ካለው የጋዜጣ ጥሪ የጠበበ አማራጭ እንዲጠቀም የወ/መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162(ለ) የሚፈቅድ አይደለም ።

በአመልካች መኖሪያ አካባቢ ወይም በአስተዳደር አካባቢ የሚደረገው ጥሪ በወሰን ቋሚ አድራሻ የሚደረግ እንጂ እንደ ጋዜጣ አገራዊ /አካባቢያዊ ስርጭት እና ተደራሽነት ያለው አለመሆኑ ግልጽ ነው። ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ የሚታይበት የሙግት ሥርዓት ሕጉ ለይቶ በደነገጋቸው ጉዳዮች ብቻ የሚደረግ ሆኖ የአጠቃላይ መርሁን ልዩ ሁኔታ ነው። ከፍትሕ ሥርዓቱ ሸሽተው የሚደበቁ ተከሳሾች በሌሉበት ሁኔታም ጉዳያቸው የሚታይበት ሥርዓት መዘርጋት የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ ለማሳካት ተገቢ ቢሆንም ተከሳሽ በሌለበት የሚደረገው ክርክር የተከሳሽ የመከላከል ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚያጣብብ እንዳይሆን የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት ሕጉ የዘረጋውን ድንጋጌ በጥብቅ በመተግበር ነው። በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20(4) እና የሲቭልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 14(3) (ለ) እና(መ) የተደነገጉት ቀርቦ የመከራከር እና የመከላከል መብት ማስከበር ፍትሐዊ የወንጀል ፍትህ ሂደት እንዲኖር የሚደረግ ነው።

አመልካች ከሚኖርበት አካባቢ ከቤተሰብ ጋር ቀየውን ለቆ ስለመሄድ በሥር ፍርድ ቤት ከቀረበው ክርክር መረዳት ይቻላል። በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋለውም በኦሮሚያ ክልል መሆኑ እየተከራከረ ነው። አመልካች ራሱን ቤተሰቡን ከአካባቢው ለቆ መሄዱ በሚከራከሩበት በሚኖርበት ቀበሌ/አስተዳደር መጥሪያ መለጠፍ ለአመልካች በተሻለ አግባብ ጥሪ ተደርጎለታል ለማለት አይችልም። ከላይ እንደተመለከተው የወንጀል ጉዳይ የሙግት ሥርዓት ፍትሐዊ የክርክር ሂደት ያከበረ መሆን ይገባል። ፍትሐዊ የወንጀል ሙግት ሥርዓት ደግሞ በወንጀል ለተጠረጠረው ግለሰብ ቀርቦ ጉዳዩ እንዲከላከል በአግባቡ ጥሪ ሊደረግለት ይገባል። ከዚህ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች መደበኛ መኖሪያ ቤት እና ቀበሌ አስተዳደር ጥሪ መደረጉ በቂ ነው በማለት አቤቱታው ውድቅ ማድረጋቸው በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 162 የተመለከተውን አገላለፅ መሠረታዊ ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ ነው። የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች እንዲቀርቡ ጥሪ የተደረገበት ሥርዓት ሕጉ ያስቀመጠው ጥብቅ መስፈርት ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የተከሰሰበት የወንጀል ጉዳይ ቀርቦ እንዲከራከሩ ሕጉ በዘረጋው ሥርዓት አግባብ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ ሳያወጡ ተከሳሹ በሌለበት የክርክር ሂደቱን አጠናቅቀው አመልካች ጥፋተኛ ነው በማለት በ20 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ/መ/ቁ. 03870 በ24/09/2004 የሰጠው ብይን፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 58544 በ03/12/2005 ዓ.ም የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ሕጉ በዘረጋው የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት መጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ ሳይሰማ ክርክር ተካሄዶ መወሰኑ በአግባቡ አይደለም ብለናል፡፡
3. በአመልካች የቀረበው የወንጀል ክስ ግራ ቀኙ በተገኙበት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 202(1) በሚያዘው መሠረት በአካባቢው ባለው ሌላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማለትም የደቡብዊ ምስራቅ ከፍተኛ ፍርድ ቤት/በተመሳሳይ ደረጃ ባለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት/ ዐቃቤ ህግ ክሱን በማቅረብ ክርክሩን እንዲቀጥል አዘናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የስር ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ብይኖች የተሻሩ ስለመሆናቸው ለሁለቱም ፍ/ቤቶች ይድረሳቸው ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ለአመልካችም የፍ/ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ በትግራይ ክልል ማይጨው ማረሚያ ቤት በኩል ይድረሰው፡፡ ይፃፍ፡፡
6. ለተጠሪም የፍ/ቤቱ ውሳኔ በትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ በኩል ይድረሰው ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/እ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 96310
ህዳር 26 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም
መስጠፉ አህመድ
ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡-አቶ ጉዲና ለማ ገዛኸኝ - አባት ነኝ በማለት አቶ ለማ ገዛኸኝ

ከጠበቃ ልዑል አያለው ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት የስ/ፀ/ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም የመውሰድና የመሰወር ከባድ የሙስና የወንጀል ክስ የተመለከተው በቤንች ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠባቸው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች እና በሌሎች አምስት ሰዎች ላይ ያቀረበው አንደኛ ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ተከሳሾቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) (ለ)፣33 እና413(2) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በሚዛን አማን ሆስፒታል ውስጥ 1ኛ ተከሳሽ የዋናው መድኃኒት ቤት ጠባቂ፣2ኛ ተከሳሽ የመድኃኒት ማሰራጫ ክፍል ባለሙያ እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ የግዢና የፋይናንስ የስራ ሂደት ባለቤት ሆነው በመስራት ላይ በነበሩበት ጊዜ በወንጀሉ ስራና በሚሰጠው ውጤት በመስማማት 1ኛ ተከሳሽ ይሰራበት ወደነበረው የመድኃኒት መጋዘን በ13/03/2005 ዓ.ም. ገቢ የተደረጉትን ሁለት ዓይነት መድኃኒቶች 2ኛ ተከሳሽ ይሰራበት ወደነበረው የመድኃኒት ማሰራጫ እንዲገቡ ካደረጉ በኃላ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች እነዚህኑ መድኃኒቶች በ17/04/2005 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 1፡00 ሰዓት ላይከአማን ከተማ በሆስፒታሉ ተሽከርካሪ ጭነው በማውጣት እና ወደ ሚዛን ከተማ በማጓጓዝ ወደ ባጃጅ አዛውረው በማጓጓዝ ከ4ኛ እስከ 6ኛ ለተጠቀሱት ተከሳሾች በብር 23,200 ከሸጡ በኃላ መድኃኒቱ ከ5ኛ ተከሳሽ እጅ፣የሸያጩ ገንዘብ ደግሞ ከ2ኛ ተከሳሽ እጅ የተያዘ በመሆኑ በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም የመውሰድ እና የመሰወር ከባድ የሙስና ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን ሁለተኛ ክስ የቀረበው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) (ለ)እና 420(1)ተጠቅሶ መድኃኒቶቹ ወጥተዋል በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ በነበሩት የሆስፒታሉ የጥበቃ ሰራተኞች ላይ ነው፡፡አመልካች ተጠይቀው ወንጀሉን አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ የሌሎቹንም ተከሳሾች የእምነት ክደት ቃል ጠይቆ ከመዘገበ በኃላ በተጠሪ በኩል የቀረቡ በአንደኛ ክስ አስራ ሁለት፣በሁለተኛ ክስ ደግሞ አንድ በሁለቱም ክሶች በድምሩ የአስራ ሶስት ምስክሮችን ምስክርነት ከሰማ እና የተጠሪን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በሁሉም ተከሳሾች ላይ የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካች ከዋናው የመድኃኒት ስቶር የመድኃኒቶችን የአወጣጥ ስርዓት ያስረዱልኛል ያሏቸውን ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡

ከዚህ በኃላ ፍርድ ቤቱ የቀሪዎቹንም ተከሳሾች የመከላከያ ማስረጃ ከሰማ በኃላ በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካቹ ባሰሟቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረተባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት ከ1ኛ እስከ 3ኛ በተጠቀሱት ተከሳሾች ላይ በክሱ በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ በማስተላለፍ ግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየታቸውን በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡በመቀጠልም በክሱ የተመለከተው ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን ገልጾ ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች የተሰጣቸውን መንግስታዊ አደራ ወደ ጎን በመተው ወንጀሉን የፈጸሙት ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ወደ ሆስፒታሉ በገባው መድኃኒት ላይ መሆኑን በምክንያትነት ጠቅሶ ወንጀሉን በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ በከባድ ደረጃ በመመደብ ቅጣቱ በአባሪ አንድ በእርከን 29 ስር የሚወድቅ መሆኑን፣ተጠሪ በጠየቀው እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 84(1)(ሀ)(ለ)እና(መ) ስር በተመለከተው መሰረት በሶስት የማክበጃ ምክንያቶች እርከኑ ከ29 ወደ 32 ከፍ የሚል መሆኑን እና የአመልካች የቀድሞ ጠባይ መልካምነት በአንድ የማቅለያ ምክንያትነት ሲያዝ ቅጣቱ ከእርከን 32 ወደ 30 ዝቅ የሚል መሆኑን ገልጾ ቅጣቱን በመመሪያው መሰረት በማስላት በአባሪ አንድ በእርከን 30 ስር አመልካች በአስራ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች የቀረበላቸውን እንደቅደም ተከተሉ ይግባኝ እና አቤቱታ ዘግተው በማሰናበታቸው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስር 2ኛ ተከሳሽ የሰጠውን የተከሳሽነት ቃል መሰረት በማድረግ አመልካቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 413(2) ስር ጥፋተኛ የመባሉን እና የተጠቀሰበትን አንቀፅ አግባብነት ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ተጠይቀው ወንጀሉን አላደረግሁም በማለታቸው ተጠሪው አቅርቦ ካሰማቸው አስራ ሶስት ምስክሮች መካከል፡-

- 1ኛ ምስክር የሆስፒታሉ ሾፌር መሆኑን፣በዕለቱ ምስክሩ ይዞት የነበረውን ሌላ ተሽከርካሪ አቁሞ አምቡላንሱን እንዲይዝ 3ኛ ተከሳሽ ወደ አመሻሽ አካባቢ እንደነገረው፣በኃላም ጊዜው ያለፈበት ስለሆነ ችግር የለበትም በማለት 3ኛ ተከሳሽ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ሆነው 2ኛ ተከሳሽ ከሚሰራበት የመድኃኒት ማሰራጫ መጋዘን ውስጥ በሶስት ካርቶን ያሉ መድኃኒቶችን በአምቡላንሱ ውስጥ እንደጫኑ፣2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጥበቃዎቹ እንዳይጠረጥሩን በማለት በእግራቸው ወጥተው ውጪ እንደጠበቁት እና ከግቢው ውጪ እንደተሳፈሩ፣በመንገድ ላይ ሲደርሱ 2ኛ ተከሳሽ ከአምቡላንሱ ወርዶ በባጃጅ እንደተሳፈረ፣3ኛ ተከሳሽ ግን አብሮት መሄድ እንደቀጠለ፣ የተወሰነ ቦታ ሲደርሱ 3ኛ ተከሳሽ በጠየቀው መሰረት አምቡላንሱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳቆመው፣2ኛ ተከሳሽም በባጃጅ እንደደረሰባቸው፣ቀጥሎም መድኃኒቱን ሁለቱ ተከሳሾች ወደ ባጃጁ እንዳዛወሩት፣ምስክሩ በዚሁ እንደተለያቸው፣በሚዛን ከተማ ውስጥ ሲዘዋወር አደባባይ አካባቢ በዚያኑ ምሽት በፖሊሶች ተይዞ ስለጫናቸው መድኃኒቶች ሲጠየቅ ዝርዝሩን እንደነገራቸው በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤

- 7ኛ ምስክር የሆስፒታሉ የጥበቃ ሰራተኛ ሆኖ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ከስራ ሰዓት ውጪ ምሽት አካባቢ በግቢው ውስጥ 2ኛ ተከሳሽ ከሚሰራበት መድኃኒት ማሰራጫ አካባቢ መቆየታቸውን፣በወቅቱም 1ኛ ምስክር የሆስፒታሉን አምቡላንስ ይዞ እዚያው አካባቢ የነበረ መሆኑን እና በእለቱ 1ኛ ተከሳሽን በአካባቢው እንዳላየው በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤
- 2ኛ ምስክር በመንገድ ላይ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በአምቡላንስ ውስጥ የነበረውን መድኃኒት 2ኛ ተከሳሽ ተሳፍሮ ወደመጣበት ባጃጅ ሲያዛውሩ አይቶ ለፖሊሶች ጥቆማ እንደሰጠ በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤
- 11ኛ እና 13ኛ ምስክሮችም 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በአምቡላንስ ውስጥ የነበረውን መድኃኒት ወደ ባጃጅ ሲያዛውሩ ማየታቸውን በመግለጽ ምስክርነት መስጠታቸውን፤
- 3ኛ፣4ኛ፣እና 12ኛ ምስክሮች ከ2ኛ ምስክር በተሰጠው ጥቆማ መሰረት ተገቢውን ክትትል አድርገው መድኃኒቶቹን ከ5ኛ ተከሳሽ እጅ፤የሽያጭ ገንዘቡን ደግሞ በነጋታው ከ2ኛ ተከሳሽ ቤት መያዛቸውን በመግለጽ ምስክርነት መስጠታቸውን፤
- 8ኛ ምስክር ቃላቸውን የሰጡት በ2ኛ ክስ በተከሰሱት የጥበቃ ሰራተኞች ላይ መሆኑን፤
- 1ኛ ተከሳሽ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት የነበረው ስለመሆኑ ወይም በዕለቱ የወንጀሉ አፈጻጸም ተጀምሮ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከ2ኛ እና ከ3ኛ ተከሳሾች ጋር ታይቶ የነበረ ስለመሆኑ ከላይ ከተዘረዘሩት ምስክሮች መካከል አንዳቸውም የጠቀሱት ነገር አለመኖሩን፤

የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶችም ከላይ በተጠቀሱት ምስክሮች በ1ኛ ተከሳሽ ላይ የተሰጠ ምስክርነት ስለመኖሩ በውሳኔአቸው ላይ አልገለጹም፡፡

ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ግንኙነት ያለው ምስክርነት የሰጡት 5ኛ፣6ኛ፣9ኛ እና 10ኛ ምስክሮች ናቸው፡፡5ኛ እና 6ኛ ምስክሮች በሆስፒታሉ ውስጥ በቀን ሠራተኝነት የሚያገለግሉ ሲሆኑ እነዚህ ምስክሮች ወንጀሉ በተፈጸመበት ዕለት 1ኛ ተከሳሽ 5ኛ ምስክርን ጠርቶ መድኃኒቶቹን 2ኛ ተከሳሽ ወደሚሰራበት ማሰራጫ እንዲወስድ በነገረው መሰረት ሁለቱ ምስክሮች 1ኛ ተከሳሽ ወደሚሰራበት ዋና መጋዘን ሄደው በካርቶን የተደረጉ መድኃኒቶችን 2ኛ ተከሳሽ ወደሚሰራበት ማሰራጫ መውሰዳቸውን እና ይህ ስራ ሁል ጊዜም የሚያከናውኑት የተለመደ ስራ መሆኑን በመግለጽ የመሰከሩ ናቸው፡፡9ኛ ምስክር በሙያው ፋርማሲስት ሆኖ ቀድሞ የሆስፒታሉ ሰራተኛ የነበረ እና 10ኛ ተከሳሽ ደግሞ የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ሲሆን የሰጡት ምስክርነት ይዘትም በዕለቱ 1ኛ ተከሳሽ ከሚሰራበት መጋዘን ወጪ ተደርገው 2ኛ ተከሳሽ ወደሚሰራበት ማሰራጫ ከተወሰዱት መድኃኒቶች መካከል አንደኛው ዓይነት መድኃኒት ወጪ የተደረገው ማሰራጫ መቀመጥ ከሚገባው መጠን በላይ መሆኑን እና መድኃኒቶቹ ወጪ የተደረጉበት ሰነድም ስርዝ ድልዝ የሚታይበት መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡በተጠሪ በኩል የቀረበው አጠቃላይ የሰው ማስረጃ ከላይ የተመለከተው ሲሆን በማስረጃነት ከቀረቡት ሰነዶች መካከል 1ኛ ተከሳሽን የሚመለከተው መድኃኒቶቹ የተጠየቁበት እና ወጪ የተደረገበትሰነድ መሆኑንም ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሰረቱ 1ኛ ተከሳሽ የዋናው መድኃኒት ቤት መጋዘን ኃላፊ ሲሆኑ የስራ ድርሻቸውም በሆስፒታሉ የበላይ አመራር ተፈቅዶ፣ተፈርሞ እና ተረጋግጦ በሚደርሳቸው ሰነድ መሰረት መድኃኒቶችን ማስረከብ ከመሆኑ በቀር መድኃኒት ወጪ እንዲሆን የመፍቀድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም መጠኑን የመወሰን የስራ ድርሻ ያላቸው ስለመሆኑ፣ወንጀል ተፈጽሞባቸዋል የተባሉት መድኃኒቶች ከ1ኛ ተከሳሽ መጋዘን ወጪ የተደረጉት ይህንን የተለመደ አሰራር በሚጥስ ሁኔታ በሆስፒታሉ የበላይ አመራር በጽሁፍ የተሰጠ ትዕዛዝ ሳይኖር ስለመሆኑ እንዲሁም ወንጀል ተፈጽሞባቸዋል የተባሉት መድኃኒቶች 1ኛ ተከሳሽ ከተረከቧቸው መድኃኒቶች መካከል በጉድለት የተገኙ ስለመሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክርና ማስረጃ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡

ይልቁንም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ ክሱን እንዲከላከሉ ብይን የሰጠውም ሆነ ተከሳሹ የቀረበባቸውን ማስረጃ አላስተባበሉም በማለት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ያስተላለፈባቸው ወንጀሉን ስለማድረጋቸው በምስክሮች ወይም በሰነድ ማስረጃ ተመስክሮባቸዋል በሚል ሳይሆን 2ኛ ተከሳሽ ወንጀሉን ያደረገ ስለመሆኑ እና ያደረገውም በ1ኛ ተከሳሽ ጠንሳሽነት ወይም አነሳሽነት ስለመሆኑ በመግለጽ በምርመራ ጊዜ እንዲሁም ክሱ በተሰማበት ጊዜ የሰጠውን የእምነት ቃል ዋነኛ ማስረጃ አድርጎ በመቀበል ስለመሆኑ በውሳኔው ላይ በግልጽ ያሰፈረው ሲሆን በበኩላችን አንድ ተከሳሽ የሰጠው የእምነት ቃል በሌላኛው ተከሳሽ ላይ በማስረጃነት ሊወሰድ የሚችልበት የሕግ አግባብ መኖር አለመኖሩ እና በዚህ ዓይነቱ ማስረጃ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት አስረድቷል ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑ በአግባቡ መጤን የሚገባው ሆኑ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(1) እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑም በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 32(1) ስር ተደንግጓል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡በሌላ አነጋገር ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቷል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመለከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 141 ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

እንደሚታወቀው አንድ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በምርመራ ሂደትም ሆነ ክስ ከቀረበበት በኃላ ክሱን ለሚሰማው ፍርድ ቤት የሚሰጠው የእምነት ቃል በሕግ ተቀባይነት ካላቸው የማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓይነቶች ውስጥ የሚካተት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 27፣35 እና 134 ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የዚህ ዓይነቱን የእምነት ቃል የሚሰጠው የራሱን አጥፊነት አምኖ በመቀበል እንደሆነ የሚገመት በመሆኑ ሌሎች ተጠርጣሪዎች፣ተከሳሾች ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው በወንጀሉ አደራረግ ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በእምነት ቃሉ ውስጥ የሚገልጻቸው ፍሬ ነገሮች ምናልባት ለቀጣይ ምርመራ ፍንጭ ሊሰጡ ይችሉ ይሆናል ከሚባል በቀር በማናቸውም ሰው ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትሉ የሚችሉ ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡በሌላ አነጋገር አንድ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በምርመራ ሂደትም ሆነ ክሱን ለሚሰማው ፍርድ ቤት የሚሰጠው የእምነት ቃል ውጤት በራሱ በቃል ሰጪው ላይ ተወስኖ የሚቀር ከመሆኑ ውጪ ወደሌሎች ተጠርጣሪዎች ወይም ተከሳሾች ሊተላለፍ የሚችል አለመሆኑን ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች አነጋገር እና ይዘት መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ ወንጀሉን የፈጸሙት በጋራ ወይም በመተባበር መሆኑን በማመን አንደኛው ተከሳሽ የሚሰጠው የእምነት ቃል ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ በሚከራከረው ሌላኛው ተከሳሽ ላይ ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትል የማይችል ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 94450 በ25/07/2006 ዓ.ም. የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በተያዘው ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ የስነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ በአመልካቹ ላይ ባቀረበው በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም የመውሰድና የመሰወር ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መሰረት ለማስረዳት በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ባልወጣበት ሁኔታ ክሱን የተመለከተው በቤንች ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ ወንጀሉን ያደረገው በ1ኛ ተከሳሽ አነሳሽነት መሆኑን ገልጾ የሰጠውን የእምነት ቃል በሕግ ከተደነገገው ውጪ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ጭምር በማስረጃነት በመያዝ 1ኛ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሰጠው ትዕዛዝም ሆነ በመጨረሻ የሰጠውና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች በትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በቤንጅ ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 11935 በ21/09/2005 ዓ.ም. ከሰጠው እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 00918 በ28/10/2005 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 01110 በ22/02/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ ከጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ውስጥ የስር 1ኛ ተከሳሽ (የአሁኑ አመልካች) አቶ ጉዲና ለማ ገዛኸኝን የሚመለከተው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ክፍል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195(2)(ለ)(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ባቀረበው የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ አመልካች ወንጀሉን ማድረጋቸውን ያላስረዳ እና በሕግ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታ ያልተወጣ በመሆኑ አመልካች አቶ ጉዲና ለማ ገዛኸኝ ከተከሰሱበት በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም የመውሰድና የመሰወር ከባድ የሙስና የወንጀል ክስ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. በአመልካች ላይ ተጥሎ የነበረው የአስራ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት የተሻረ በመሆኑ የሚፈለጉበት ሌላ ጉዳይ አለመኖሩን አረጋግጦ አመልካች አቶ ጉዲና ለማ ገዛኸኝን ወዲያውኑ ከእስር እንዲለቃቸው አመልካቹ ለሚገኙበት በኦሮሚያ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ለኢሉባቦር ዞን ማረሚያ ቤቶች ጽ/ቤት ትዕዛዝ ይተላለፍ፡፡ይፃፍ፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ በቤንጅ ማጂ ዞን ለቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድቤት፣ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ለኢሉባቦር ዞን ማረሚያ ቤቶች ጽ/ቤት ይላክ፡፡ለአመልካቹም በማረሚያ ቤት በኩል ይድረስ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.96378

ህዳር 25 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ሀቢብ ጀማል

ተጠሪ፡- የደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ -

አቤቱታ አቅራቢዎች፡- 1.ረዳት ሳጅን መሐመድ እንድሪስ
2. አብዱ ኡመር
3. ደግፌ አለሙ
} ጉዳዩን ተከታታዮች ተስፋዬ አለሙ እና ወሰላ ከድር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን መዝገቡ የተከፈተው በሀቢብ ጀማል አመልካችነት ሁኖ ከተጠሪ ጋር ክርክሩ ተካሂዶ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዚህ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በስር ፍርድ ቤት ከሀቢብ ጀማል ጋር ተከሳሽ የነበሩትን የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎችንም የሚጠቅም በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196 ድንጋጌ መሰረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል በማለት ህዳር 02 ቀን 2007 ዓ/ም ማመልከቻ ስለአቀረቡ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የአቤቱታ አቅራቢዎችን ጥያቄ ለማስተናገድ ይቻለው ዘንድ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደረገ ሲሆን ተጠሪ ህዳር 19 ቀን 2007 ዓ/ም ባቀረበው አስተያየት አቤቱታ አቅራቢዎቹ ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸው መሆኑን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 196 ከአስቀመጠው ድንጋጌ የሚገነዘበው መሆኑን ዘርዝሮ አቤቱታ አቅራቢዎች አቶ ሀቢብ ጀማል ጥፋተኛ በተባሉበት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 422(1) ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብለው በስር ፍርድ ቤት የቀረቡባቸው የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሰረት ተደርገው ቅጣት ሊወሰንባቸው እንደሚገባ ገልፆ አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

እኛም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ መነሻ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት የስልጤ ዞን ዐ/ሕግ ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የጥፋተኝነት እና ተገቢውን የቅጣት ውሳኔ በሰጣቸው አቶ ሃቢብ ጀማልና በአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ላይ አራቱም ተከሳሾች በወ/ህ/ቁ 32/1//ሀ/፣ 37፣ 27/1/ እና 671/1/ሀ/ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የማይገባቸውን ብልፅግና ለማግኘትና ለሌላውም ለማስገኘት በማሰብ በስልጤ ወረዳ ውስጥ አሻኖ ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ከወራቤ ወደ ቡታጅራ በሚወስደው አስፋልት መንገድ ላይ ሚያዚያ 08 ቀን 2005 ዓ/ም ከምሽቱ 5:00 ሰኣት እስከ 7:30 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ የውንብድና ወንጀል ተግባር ለመፈፀም አስቀድመው በማሰብ በቡድን /ህብረት/ ሁነውና ተደራጅተው የጦር መሳሪያና ለዚሁ ተግባር የሚያግዛቸውን ተሽከርካሪ ጭምር በማዘጋጀት በመንገዱ ላይ ከአዲስ አበባ ወደ ወራቤ ምርጥ ዘር እና ሰዎችን ጭኖ ይጓዝ የነበረውንና በአቶ አብዱረዛቅ ዑመር አማካኝነት የሚሸከረከረውን ኤፍ.ኤስ.አር መኪና በማስቆም ከባድ የሆነ የውንብድና ወንጀል ለመፈፀም ሞክረዋል የሚል ሁኖ እያንዳንዱ ግብረ አበር በወቅቱ ፈፀመ የተባለውን ድርጊትም ክሱ ይዘረዝራል፡፡

የአሁን አቤቱታ አቅራቢዎች በተከሳሽነታቸው ቀርበው ድርጊቱን አልፈፀምነም፤ ጥፋተኛም አይደለንም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ በአቃቤ ሕግ በኩል በማስረጃነት የሰው ማስረጃና የሰነድ ማስረጃዎች ቀርበዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ሁሉም ተከሳሾች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ተካሳሾቹ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው በአቃቤ ሕግ ተነግሮባቸው በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አላስተባበሉም በሚል ምክንያት በአቃቤ ሕግ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎአል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን አስተያየት ተቀብሎ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ መመርመሩን በማጣቀስ አቶ ሀቢብ ጀማልንና የአሁኑ አቤቱታአቅራቢ ከሆኑት 1ኛውን (የሥር 1ኛ ተከሳሽ) እና 2ኛውን (የሥር 2ኛ ተከሳሽን) እያንዳንዳቸውን በሰባት ዓመት፣ የስር 3ኛ ተከሳሽን (የአሁኑን ሶስተኛ አቤቱታ አቅራቢን) ደግሞ በስድስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አቶ ሀቢብ ጀማል ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣ የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ግን በዚህ አግባብ የይግባኝና የሠበር አቤቱታቸውን ስለማቅረባቸው የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡

ሆኖም ከአቤቱታ አቅራቢዎች ጋር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ4ኛ ተከሳሽነት ተሰይሞ የነበረውና በበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠበት አቶ ሃቢብ ጀማል በሕጉ አግባብ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ለዚህ ችሎት የሠበር አቤቱታ አቅርቦ ጉዳዩ ተጠሪ ባለበት ከተጣራ በኋላ ተጠሪ አድራጎቱ የሚሸፈንበትን የሕግ ድንጋጌ በመለየትና የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጡበት ድንጋጌ ለስር ተከሳሾች አድራጎት አግባብነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ በሰጠው መልስ መነሻ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ተከሳሾች አድራጎት የሚያቋቁመው በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 32(1(ለ)፣ 33 እና 422(1) ድንጋጌ መሆኑን ገልፆ አቶ ሀቢብ ጀማልን በዚሁ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ የቅጣት ውሳኔውንም በዚሁ ድንጋጌ አግባብ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በሕግ አተገባበርና አተረጓጎም ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የፈጸሙበትን ስህተት ከማረሙም በላይ በውጤቱ ደግሞ አቶ ሀቢብ ጀማልን የጠቀመ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከስር ተከሳሾች መካከል አንዱ ይግባኝ ጠይቆ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ለይግባኝ ባዩ የሚጠቅም በሆነ ጊዜና ከይግባኝ ባዩ ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ሰዎች ይግባኝ ቢያቀርቡ ኑሮ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊጠቀሙ ይችሉ የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ላላቀረቡት ተከሳሾች ጭምር ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደሚገባ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196(1(ሀ) እና(ለ) ድንጋጌዎች ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ ለዚህ ችሎት የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትም ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም ችሎቱ የሚመራበት የተለየ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ የለምና፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ከአቶ ሀቢብ ጀማል ጋር ለዚህ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡ ኑሮ የፍርዱ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችሉ የነበረ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አቶ ሀቢብ ጀማልን በተመለከተ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 196(1))(ሀ) (ለ) መሰረት ለአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ላይም ተፈጻሚነት አለው ብለናል፡፡

ቅጣቱን በተመለከተ ግን አቶ ሀቢብ ጀማል ላይ የተሠጠው እንዳለ ተግባራዊ ይሁን የሚል ግልፅ ድንጋጌ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196 ድንጋጌ ስር አለ ለማለት ስለማይቻልና በመርህ ደረጃም እያንዳንዱ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው በተሳትፎውና ግላዊ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕጉ አንቀጽ 40 ድንጋጌ እና ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን መርሆዎች የምንገነዘበው በመሆኑ የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ላይ የሚጣለው የቅጣት መጠንን መመልከቱ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ከአሁኑ ጥያቄ አቅራቢዎች ውስጥ 1ኛው ረዳት ሳጅን መሀመድ እንድሪስ፣ እና 2ኛው አብዲ አሙር ከሀቢብ ጀማል ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ የተቀጡ በመሆኑ በአቶ ሀቢብ ጀማል ላይ በዚህ ችሎት የተጣለው ቅጣት ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነት ያለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በጥያቄ አቅራቢዎች ላይ በቅጣት ማክበጃነት በስር ፍርድ ቤት የተያዙት ምክንያቶች እንዲያዙ የጠየቀ ቢሆንም ይህ ችሎት በአቶ ሀቢብ ጀማል ላይ የቅጣት ውሳኔ ሲሰጥ በከፊል ውድቅ ያደረጋቸው በመሆኑ በአሁኑ ጥያቄ አቅራቢዎች ላይም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት የሚያገኙበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘም፡፡

3ኛውን ጥያቄ አቅራቢ አቶ ደግፌ አለሙን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተያዙለት የቅጣት ማቅላያ ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ ይሄውም ሪኮርድ የሌለበት መሆኑና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ናቸው፡፡ ይህንኑ ይዘን የቅጣት እርከኑን ስንመለከተው በአንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ከእርከን 11 ወደ እርከን 12 ከፍ የሚል ሲሆን ጥያቄ አቅራቢው አቶ ደግፌ አለሙ ሁለት የቅጣት ማቅላያ ምክንያት ስላላቸው በመመሪያው አንቀፅ 13(5) መሰረት በጥያቄ አቅራቢው ላይ ሊጣል ይችል የነበረው ቅጣት በአራት እርከን እንዲወርድ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረትም ከእርከን 12 ወደ እርከን 8 የሚወርድ ሁኖ በዚሁ መጨረሻ እርከን ስር የተመለከተው የቅጣት አይነትና የመጠን ሬንጅ ከአንድ አመት ከሁለት ወር እስከ አንድ አመት ከስድስት ወርበመሆኑ ለፍ/ቤቱ በተሰጠው ፍቅድ ስልጣን መሰረት አቶ ደግፌ አለሙ ለፈፀሙት ጥፋት ተመጣጣኝ፣ ለመሰል አጥፊዎችን ደግሞ አስተማሪ ነው ብለን ያገኘነው አንድ አመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራት ነው፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች በጥያቄ ባሁኑ ጥያቄ አቅራቢዎች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09466 ሰኔ 28 ቀን 2005 ዓ/ም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196/1/ /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት ተሻሽሎ ጥያቄ አቅራቢ በሆኑት፡-
   ሀ/ ረዳት ሳጅን መሐመድ እንድሪስ

   ለ/ አብዱ ኡመር

   ሐ/ ደግፊ አለሙ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በአቶ ሀቢብ ጀማል በሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተፈፃሚነት አለው ብለናል፡፡ ስለሆነም ጥያቄ አቅራቢዎቹ ሊጠየቁ የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33፣ 32(1(ለ) እና 422(1) ድንጋጌ ስር ነው ብለናል፡፡

2. ቅጣቱን በተመለከተም ረዳት ሳጅን መሐመድ እና እንድሪስ አብዱ ኡመር እያንዳንዳቸው በጉዳዩ የታሰሩት ማናቸውም ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ ሊቀጡ የሚገባው በአንድ አመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት ነው በማለት ወስነናል፡፡ ደግፊ አለሙን በተመለከተ ደግሞ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሁኖ በአንድ አመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለወራቤ ማረሚያ ተቋም ይገለጽለት ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 100712
መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም
መስጠፉ አህመድ
ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ሽብሩ ጌቱ ሴንጫ - ጠበቃ ወይሽት ከበደ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የፌዴራል አቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 669(2)ን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በ18/02/06 ዓ/ም በግምት ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ሲሆን በኮ/ቀ/ክ/ከ/ወረዳ 02 ልዩ ቦታው ካራቆሬ ደጋማን የፕላስቲክ ውጤቶች ማምረቻ ድርጅት ውስጥ በስራ አስኪያጅነት ተቀጥሮ እየሰራ ባለበት የግል ተበዳይ አማረ አብርሃም የድርጅቱ ባለቤት የሆኑትን ንብረት አንድ መቶ ሃምሳ ከረጢት የጫማ ጥሬ እቃ ፕላስቲክ የአንድ ከረጢት ግምት ብር 1100.00 (አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር) የጠቅላላው ግምት ብር 165,000.00 (አንድ መቶ ስልሳ አምስት ብር) የሚያወጣውን ወስዶ ለስር 2ኛ ተከሳሽ አቶ ደረጀ ፍቃዱ የሸጠና የተያዘ በመሆኑ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ አመልካችም ፍርድ ቤት ቀርቦ የአቃቤ ሕግ የክስ ቻርጅ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በሁዋላ እምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ የወንጀል ድርጊቱን ያለመፈፀሙን በመግለጹ አቃቤ ሕግ አሉኝ የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ አሰምቷል፡፡

ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ አመልካች ድርጊቱን ስለመፈፀሙ በአቃቤ ማስረጃዎች የተነገረበት መሆኑን ተገንዝቦ የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብቱን በአመልካች ፍላጎት ማለፉን ጠቅሶ አመልካችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበበት አንቀጽ ስር ጥፋተኛ አድርጎ ቅጣቱንም ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ ማየቱን ገልጾ በስምንት አመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማቱ ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ የጸና ሲሆን የቅጣት ውሳኔው ግን በማክበጃ እና በማቅለያ ምክንያቶች አያያዝ ላይ የስር ፍርድ ቤት ስህተት መፈፀሙ የተረጋገጠበት ነው በሚል ምክንያት ስህተቶቹን ለይቶና ማረሙን ገልፆ የስር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ መጠን ዝቅ በማድረግ አመልካች በስድስት አመት ከስድስት ወራት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም፡- የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ሳይሰማ ያለፈው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የመከላከያ ማስረጃ አለኝ እያልኩ ነው፣የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙን አቃቤ ሕግ አላስረዳም፣ ተፈፀመ የተባለው የወንጀል ድርጊትና የተጠቀሰው ድንጋጌ አብረው የማይሄዱና የቅጣት ውሳኔ አሰጣጥም ተገቢነት የሌለው ነው የሚሉ ምክንያቶችን የያዘ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብት የታለፈው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለማጣራት ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባለው ዐቃቤ ሕግ ያቀረባቸውን ማስረጃዎች የመከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለት በቃልና በፅሑፍ ለስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል ተብሎ ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ አሁን በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃ ደግሞ አመልካች ይህ የሥር ፍርድ ቤት አገለላጽ ከፍላጎታቸው ውጪ መመዝገቡንና የመከላከያ ማስረጃ ላሰማ ጥያቄ አቅርበው የነበረ መሆኑን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ የተከሰሱ ሰዎች በሕግ ከተጠበቁላቸው መብቶች አንዱ የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸውን ቀርበው እንዲሰመሉላቸው የመጠየቅ መብት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20(4) የተደነገገ ሲሆን ይህ መብት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(4) ድንጋጌ አግባብ የአገሪቱ የሕግ አካል በሆኑት የአለም አቀፍ ስምምነቶችም ጥበቃ ያገኘ ስለመሆኑ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን 14(3(ለ)) ድንጋጌን በመመልከት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው የተከሳሽ መብት የሚያስገነዝበው አንድ ተከሳሽ ተገቢ ባልሆነ ማስረጃ ጥፋተኛ እንዳይባልና በከሳሹ ወገን ማስረጃ ቀርቦ ከሆነም በበኩሉ ምንም ጥፋት ያልፈፀመና ንፁህ መሆኑን የማስረዳት ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ለቀረበበት ክስ መከላከያ ለማዘጋጀት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮችንና በቂ ጊዜ ማግኘት እንደሚገባው ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ተከሳሹ ይህንኑ በሕገ መንግስቱ ጥበቃ ያገኘውን የመከላከል መብት በአግባቡ እንዲጠቀም ማድረግ የፍርድ ቤት ኃላፊነት መሆኑንም ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) እና (2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የተከሳሽ ክስን የመከላከል መብት ሊታለፍ የሚገባው ተከሳሹ መብቱን የማይጠቀምበት መሆኑን በግልፅ ለፍርድ ቤቱ ሲያረጋግጥለት ብቻ መሆኑን ከድንጋጌዎች መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ ተከሳሹ መብቱን ስለመተው ባልተረጋገጠበት አግባብ ግን የተከሳሽን የመከላከል መብት ተከሳሹ ትታል የሚል አገላለፅ በፍርድ ሐተታው ላይ በማስፈር ብቻ ዳኝነት መስጠት ተገቢነት የሌለው አካሄድ ነው፡፡

የጉዳዮችንመራዘምለማስቀረትየተቀየሰውየተፋጠነየወንጀልአሰጣጥ (RTD) መሰረታዊ ኣላምምበማስረጃደረጃውስብስብነትየሌላቸውንጉዳዮችበቀላሉለመወሰንአዲስአሠራር ለመዘርጋት ማስቻል ከሚሆን በስተቀር በሕገ መንግስቱና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች የተጠበቁትን የተከሳሽን መብቶች በሚጎዳ አኳኃን ለመተግበር አለመሆኑ ይታወቃል፡፡በመሆኑም በሕጉ የተጠበቁት መብቶችና የዳኝነት አካሄዶች በሕጉ አግባብ ተተግብረው ዳኝነት ከሚሰጥ በስተቀር አንድ ጉዳይ የተፋጠነየወንጀልአሰጣጥን (RTD) መሰረት አድርጎ በመቅረቡ ብቻ ቀሪ የሚሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደሉም፡፡ የተፋጠነየወንጀልአሰጣጥ (RTD) አሰራርን መሰረት አድርጎ የሚታይ ጉዳይ የተከሳሹን የመከላከል መብት ለመተው የሚያስችለው ተከሳሹን ይህንኑ መብቱን በማሻያማ አኳኃን የተወው መሆኑን ሲያረጋገጥ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉደይ ስንመለስ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ያየው የተፋጠነየወንጀልአሰጣጥ (RTD) አሰራርን ተከትሎ ሲሆን አመልካችን ጥፋተኛ ያደረገው ተከሳሽ ድርጊቱን መፈፀሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተነግሮበት የመከላከያ ምስክር እንዳለው ተጠይቆ የመከላከያ ማስረጃ "አለኝ በማለት በችሎት በዕሑፍ በቃል ያረጋገጠ" ስለሆነ ነው በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ተመልክተናል፡፡ ይህ የስር ፍርድ ቤት አጻጻፍ በአንድ በኩል አመልካች በቃልም ሆነ በዕሑፍ የመከላከያ ማስረጃ "አለኝ" ያለ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድምዳሜው አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን መግለፁን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህን ግልጽነት የጎደለውን የስር ፍርድ ቤትን አጻጻፍ ትክክለኛነቱን ለመረዳት ይቻል ዘንድም ዋና መዝገቡን አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ የስር ፍርድ ቤትን መዝገብ እንደተመለከትነውም የሥር ፍርድ ቤት አመልካች እንዲከላከል ጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ብይን ሲሰጥ ብይኑ ቀድሞ የተዘጋጀውን ቅጽ/ፎርም/ በመሙላት የተሰጠ ሲሆን በይዘቱም አመልካች መከላከያ ማስረጃ "የለኝም" በማለት መግለፁን፣ ይህንኑ የገለፀው ደግሞ በችሎት በዕሑፍና በቃል መሆኑን የሚጠቅስ ቢሆንም አመልካች በቃል የገለጸ ስለመሆኑ ከብይኑ ውጪ በእለቱ የችሎቱ የወረቀት ስራ ያልተመዘገበ፣ "በዕሑፍ አረጋግጧል" የሚለው አባባልም ከመዝገቡ ውስጥ ካሉት ሰነዶች ሲታይ ሰነዱ የሌለ መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ቀድሞ የተዘጋጀውን የብይንና የፍርድ ፎርም ሲሞላ በአማራጭ የተቀመጡትን ቃላትና ሐረጎችን በእስክርቢቶ እየሰረዘ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የለኝም ብሎ በቃልና በዕሑፍ አረጋግጧል በማለት የመከላከያ ማስረጃ መስማትን ያለፈ ቢሆንም ይህንኑ የሚያረጋገጥ ማስረጃ ያለመኖሩን ከስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ተረድተናል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች በሕጉ የተጠበቀላቸውን የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብት የስር ፍርድ ቤት ያለፈው አመልካቹ በግልጽ በመብቱ የማይጠቀምበት መሆኑን ሳያረጋገጥ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 34797 ጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 144019 የካቲት 14 ቀን 2006 ዓ/ም ተሻሻሎ የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-1)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብት የታለፈው ያላግባብ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 34797 ቀጥሎ የአመልካችን የመከላከላያ ማስረጃ በሕጉ አግባብ ሰምቶ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. የስር ፍርድ ቤት አመልካችን የብር 10,000 (አስር ሺህ) ዋስ እንዲጣራና ጉዳዩን በውጪ ሆኖ እንዲከታተል እንዲደረግም ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡

ትዕዛዝ

የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በአስቸኳይ ይመለስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉምሩክ/ታክስ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.96168

ህዳር 9 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አርአያ ኪዳነ ቤተሰብ ነኝ በማለት መምህር ፍሰሐ ገ/መስቀል ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን የኮንትሮባንድ የወንጀል ክስ የተመለከተው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠባቸው እና በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው የጥፋተኝነት እና የተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች እና የዕቃዎቹ ባለቤት ናቸው ተብለው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በብይን በተሰናበቱት 2ኛተከሳሽ ላይበ07/06/2005 ዓ.ም.አዘጋጅቶ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ተከሳሾቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(3) እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 91(2) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈጸመባቸውን የቀረጥ እና የታክስ መጠናቸው ብር 136,657 የሆነ እና ንብረትነታቸው የ2ኛ ተከሳሽ የሆኑ የተለያዩ ዕቃዎችን 1ኛ ተከሳሽ ሲያሽከረክሩ በነበረው የሰሌዳ ቁጥሩ 2-A06860 አ.አ. በሆነ ተሽከርካሪ ለዕቃ መሸሸጊያ ተብሎ በተሰራ የመኪና አካል (ሻማ) ውስጥ ጭነው ከባሌ ሮቤ ወደ ሻሸመኔ በመጓዝ ላይ እያሉ በ15/05/2005 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 9፡00 ሰዓት በአዳባ ኬላ ላይ የተያዙ በመሆኑ የኮንትሮባንድ ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቀው ወንጀሉን አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ በተጠሪ በኩል የቀረቡ ሁለት የጉምሩክ ፖሊስ አባላትን ምስክርነት ከሰማ እና የተጠሪን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ 2ኛ ተከሳሽ የነበሩትን ግለሰብ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነጻ በማሰናበት አመልካችን ግን ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካች የተሳቢ መኪና ሾፌር መሆናቸውን እና የተከለከሉ ዕቃዎችን ጭኖአል የተባለውን ተሽከርካሪ በዕለቱ ሊይዙ የቻሉት ብር 500

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከፍሎአቸው ተሽከርካሪውን ሻሸመኔ ድረስ እንዲያደርሱ ደላሎች በነገሯቸው መሰረት መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቹ ባሰሟቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት በክሱ በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ ግራ ቀኙ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡በመቀጠልም በክሱ የተመለከተው ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን ገልጾ በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ በመካከለኛ ደረጃ መድቦ አመልካች የቀድሞ ፀባያቸው መልካምነት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው በማቅለያ ምክንያትነት እንዲያዙላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በሚል ምክንያት ሳይቀበል ቀርቶ ቅጣቱን በመመሪያው መሰረት በማስላት በአባሪ አንድ በእርከን 27 ስር በአስር ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 15,000 መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካቹ የዘወትር ፀባይ መልካምነት በማቅለያ ምክንያትነት ሳይያዝ የቀረው አላግባብ መሆኑን ገልጾ የጽኑ እስራት ቅጣቱን በሶስት እርከን ዝቅ በማድረግ በእርከን 24 ስር ወደ ሰባት ዓመት አሻሽሎ ቀሪውን ውሳኔ በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የጥፋተኝነት ውሳኔውን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመከለተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በክሱ የተመለከተውን ወንጀል አላደረግሁም በማለት ክደው የተከራከሩ ቢሆንም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በአመልካቹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠው ተጠሪ ባሰማቸው ሁለት ምስክሮች እና ባቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 ስር በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አመልካቹን ጥፋተኛ በሚያደርግ ደረጃ በክሱ መሰረት ማስረዳቱን፣አመልካች መከላከያቸውን እንዲያሰሙ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት በተሰጠው ትዕዛዝ አመልካች አቅርበው ያሰሟቸው ሁለት የመከላከያ ምስክሮች የምስክርነት ቃል በተጠሪ ምስክሮች እና ሰነዶች በአመልካቹ ላይ የተመለከተውን የወንጀል ፍሬ ነገሮች ማስተባበል ያልቻለ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ነው፡፡አመልካች ሲያሽከረክሩት በነበረው ተሽከርካሪ የተጫኑ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በጉምሩክ ኬላ መያዛቸውን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት ተሽከርካሪውን ከባሌ ሮቤ እስከ ሻሻመኔ ለማድረስ በብር 500 ተስማምቼ ከማሽከርከር በቀር ተሽከርካሪው የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈጸመባቸውን ዕቃዎች ጭኖ የነበረ ስለመሆኑም ሆነ የዕቃ መደበቂያ ሻግ የነበረው ስለመሆኑ የማውቀው ነገር ያልነበረ በመሆኑ በወንጀሉ ጥፋተኛ የተባልኩት አላግባብ ነው በማለት መሆኑን የአቤቱታው ይዘት ያመለክታል፡፡

ይሁን እንጂ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ያስተላለፈው አመልካች በክሱ የተመለከተውን ወንጀል ማድረጋቸው በተጠሪ ማስረጃ ተረጋግጦባቸው እያለ ይህንኑ በመከላለከያ ማስረጃ አለማስተባበላቸውን መሰረት በማድረግ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በጥፋተኝነት ውሳኔው ላይ ያቀረቡትን ቅሬታ ሳይቀበል የቀረው ዕቃዎቹ ስለመጫናቸው የማውቀው ነገር የለም ይበሉ እንጂ 1ኛ የተጠሪ ምስክር በሰጡት ምስክርነት ቃል ውስጥ አመልካች በተሸከርካሪው ላይ የዕቃ መሸሸጊያ ቦታ (ሻማ) ካለ ተጠይቀው ሌላ ሻማ ከተሸከርካሪው ሳልቫቲዮ ውስጥ መኖሩን አሳይተውኛል የሚል ምስክርነት እንደሰጡ ከይግባኙ ግልባጭ መገንዘቡን ጭምር በመጥቀስ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ተጠሪ ይህንኑ ሁኔታ በመጥቀስ በሰበር መልሱ ላቀረበው ክርክር የምስክሩ ቃል እርስ በርሱ የሚጋጭ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ከማለት በቀር የዚህ ዓይነት ምስክርነት ስለመሰጠቱ አመልካች ያቀረቡት ማስተባበያ አለመኖሩን ከመልስ መልሳቸው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገርን አጣርተው እና ማስረጃን መዝነው በአመልካች በኩል የቀረበውን መከላከያ ውድቅ በማድረግ የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚያስችል አሳማኝ ምክንያት ባለመገኘቱ አመልካች የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠብኝ አላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ በነጻ እንድሰናበት ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክሱ የተመለከተው ወንጀል በወቅቱ በስራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን ገልጾ በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ በመካከለኛ ደረጃ ለመመደብ ምክንያት ያደረገው ዕቃዎቹ በተሸከርካሪው ውስጥ ተደብቀው የተገኙት ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ልዩ የመሸሸጊያ ስፍራ መሆኑን ነው፡፡በመዝገቡ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ወንጀሉን በመካከለኛ ደረጃ መመደቡ የመሰረታዊ የሕግ ስህተት ጥያቄን የሚያስነሳ ባለመሆኑ ወንጀሉ ሊመደብ ይገባው የነበረው በዝቅተኛ ደረጃ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአመልካቹ ላይ የቀረበ የማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን የቀድሞ ፀባያቸው መልካምነት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው በማቅለያ ምክንያትነት እንዲያዙላቸው አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በሚል ምክንያት ሳይቀበል የቀረ ቢሆንም በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ ተቃራኒ ክርክር እና ማስረጃ እስከሌለ ድረስ የአመልካቹ የቀድሞ ጸባይ መልካምነት ግምት የሚወሰድበት መሆኑን ገልጾ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቅለያ ምክንያትነት ተቀብሎ ቅጣቱን አሻሽሏል፡፡

ይሁን እንጂ የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው በማቅለያነት ሊያዝላቸው እንደሚገባ አመልካች አሁንም ድረስ እየተከራከሩ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ያለፈው በምን ምክንያት እንደሆነ ውሳኔው በግልጽ አያመለክትም፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይቀበል የቀረው የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረቡም በማለት ነው፡፡የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔው የተሰጠው በአንድ ቀን ስለመሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያመለክት በመሆኑ አመልካች አለኝ የሚሉትን የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በማስረጃ ለማስደገፍ ጊዜ ወይም ቀጠሮ ተሰጥቷቸው የነበረ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ግራ ቀኙ አሉን የሚሏቸውን የማክበጃ እና የማቅለያ ምክንያቶች የማቅረብ እና አስፈላጊ ሲሆንም በማስረጃ የማስደገፍ መብት ያላቸው ስለመሆኑ ከወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 149 (3) እና (4) ድንጋጌ አጠቃላይ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ፍርድ ቤቶችም የእነዚህን መብቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ያስችል ዘንድ ለተከራካሪ ወገኖች ጊዜ ወይም ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡በመሆኑም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቶ አመልካች የቤተሰብ አስተዳዳሪታቸውን በማስረጃ ማስደገፍ የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን ሳያረጋግጥ የማቅለያ ምክንያቱ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ወዲያውኑ የቅጣት ውሳኔ ወደ መስጠት ማምራቱ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ የተባለ ሰው በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዝለት ያቀረበውን ምክንያት በማስረጃ ማስደገፍ እንዲችል በቂ ጊዜ ባላገኘበት ሁኔታ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በሚል የማቅለያ ምክንያቱን ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ የቅጣት ውሳኔ ደግሞ በወንጀል ሕጉ እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ስለ ቅጣት አወሳሰን የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል በቅጣት አወሳሰን ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17056 በ13/12/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 168474 በ12/03/2006 የተሻሻለው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካቹ ላይ የተጣለው የቅጣት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
4. የአመልካቹ የዘወትር ጸባይ መልካምነት በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅለያ ምክንያትነት የተያዘው በአግባቡ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች የቤተሰብ አስተዳዳሪ ስለመሆናቸው አለኝ የሚሉትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ ካደረገ በኃላ ተገቢውን - የቅጣት ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በውሳኔው መሰረት ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፤እንዲያውቁት ደግሞ ለኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በሚገኙበት ማረሚያ ተቋም በኩል ለአመልካቹ ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 100079

መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ዕቁባይ በርሀ ገ/እግዚአብሔር - ጠበቃ ደሳለኝ መስፍን ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐ/ህግ ወንድዬ ብርሃኑ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176025 ታህሳስ 19/2005 ዓ/ም የሰጠው ፍርድና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 131320 ጥር 21 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታርምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው ጉዳዩ ተጠሪ አመልካች የአንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ ለግብር ስብሳቢው መሥሪያ ቤት አሳሳች ማስረጃ የማቅረብና ተጨማሪ እሴት ታክስ የማሳወቅና የመክፈል ኃላፊነቱን ባለመወጠት ወንጀል ፈፅሟል በማለት ያቀረበውን ክስና ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በሜጋ ኪነ ጥበብ ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና በአመልካች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ
   - በሥር አንደኛ ተከሳሽ የሆነው ሜጋ ኪነ ጥበብ ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 96 እና የወንጀል ህጉን አንቀፅ 34/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከሀምሌ 1996 ዓ/ም እስከ 2002 ዓ/ም ባደረገው የንግድ እንቅስቃሴ ለመንግስት ገቢ ማድረግ የነበረበት ብር 39,801.32 /ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አንድ ብር ከሰላሣ ሁለት ሳንቲም/ በማሣወቅ መክፈል ሲገባው ግብሩን ያላሳወቀ በመሆኑ ወንጀል ፈፅሟል ሁለተኛው ተከሳሽ (አመልካችም) የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 86 እና አንቀፅ 102(1) በመተላለፍ የንግድ ድርጅቱ ሥራ-አስኪያጅ ሆኖ የንግድ ድርጅቱን ገቢ ባለማሣወቁ ወንጀል ፈፅሟል፡፡
   - አንደኛ ተከሳሽ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286 /1994 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ 1997 ዓ/ም ባከናወነው የንግድ እንቅስቃሴ ትርፍ አግኝቶ እያለ፤ ወጭውን ከፍ አድርጎ በማቅረብ ኪሣራ እንደደረሰበት አድርጎ በማሳወቁ፤ ለግብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት አሳሳች ማስረጃ የማቅረብ ወንጀል ፈፅሟል ሁለተኛው ተከሳሽ (አመልካች) የአንደኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 96 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) አንቀፅ 102(1) የተመለከተውን በመተላለፍ አሳሳች ማስረጃ የማቅረብ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

- አንደኛ ተከሳሽ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285 /94 አንቀፅ 49 እና በወንጀል ህግ አንቀፅ 34(ሀ) የተመለከተውን በመተለለፍ ከ1996 ዓ/ም እስከ 2002 ዓ.ም ባደረገው የንግድ እንቅስቃሴ የሰበሰበውን ብር 426.229.03 /አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር ከዜሮ ሶስት ሣንቲም) ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት አሳውቆ ባለመክፈሉ ወንጀል ፈፅሟል፡፡ሁለተኛ ተከሳሽ (አመልካች) የአንደኛ ተከሳሽ ሥራ-አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ አንደኛ ተከሳሽ የሰብሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት አሳውቆ እንዲከፈል ባለማድረጉ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 ዓንቀፅ 49 እና 56(1) በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

2 አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት የቀረበበትን ክስ ክዶ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የአንደኛ ተከሳሽ የንግድ ፈቃድ፤ ሜጋ ኪነጥበብ ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የመመሥረቻ ፅሑፍና መተዳደሪያ ደንብ የድርጅቱ ገቢ ኦዲት የተሰራበት ሪፖርትና የትርፍ ማስታወቂያ፣ ደረሰኝ የተተመበትን ሰነድና የሰው ምስክሮችን በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ያቀረባቸው ሁለት ምስክሮች አንደኛ ተከሳሽ የመፍረስ ጥያቄ በማቅረቡ ከሳሽ መሥሪያ ቤት የድርጅቱን ሒሳብ ኦዲት እንዲያደርጉ መድቧቸው ሒሳቡን ኦዲት ያደረጉ መሆኑን ሂሳቡን ኦዲት ያደረጉት የአንደኛ ተከሳሽ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ሁለተኛ ተከሳሽ ያቀረበውን የሂሳብ ሰነድና አንደኛ ተከሳሽ ለከሳሽ መሥሪያ ቤት ሲያቀርብ የነበረውን የሂሳብ ሪፖርት መሠረት በማድረግ እንደሆነ ገልፀው 1997 ዓ/ም አንደኛ ተከሳሽ ብር 15,748 /አስራ አምስት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ስምንት ብር/ ኪሳራ የደረሰበት መሆኑን ለከሳሽ አሳውቋል፡፡ ሆኖም 1997 ዓ/ም አንደኛ ተከሳሽ ብር 132,673.06/አንድ መቶ ስላሣ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከዜሮ ስድስት ሣንቲም/ አግኝቶ የነበረ መሆኑንና 1997 ዓ/ም አንደኛ ተከሳሽ 39.801 /ስላሳ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አንድ ብር) የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር መክፈል የነበረበት መሆኑን በማረጋገጥ ወስነናል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ኪሣራ ደርሶብኛል በማለት ሪፖርት ያደረገው የድርጅቱ ሠራተኞች ባልሆኑ ሰዎች የከፈለው ደመወዝ የስልክ ወጭና የሌላ ድርጅት ንብረት የሆኑ መኪኖች የተሞላ ነዳጅ በወጭነት በማቅረብ ነው፡፡ ይህም የገቢ ግብር አዋጅንና አዋጁን ለማስፈፀም የወጣውን መመሪያ መሠረት ያላደረገ በመሆኑ በወጭነት አልያዝነውም፡፡ እኛ ሂሳብ ስንሠራ ወድቅ አድርገነዋል፡፡

3 ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ አንደኛ ተከሳሽ ለከሳሽ ባሣወቀውና አንደኛ ተከሳሽ ባከናወነው ግብይት ወይም የንግድ እንቅስቃሴ መካከል ልዩነት መኖሩን አንደኛ ተከሳሽ ብር 429,172 /አራት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሰባ ሁለት ብር/ ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት አሳውቆ መክፈል ሲገባው፤ ይህንን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት ያልከፈለ መሆኑን ባከናወኑት የኦዲት ሥራ ማረጋገጣቸውን ለሥር ፍርድ ቤት ያስረዱ መሆኑን በውሣኔው አስፍሮታል፡፡ ሶስተኛው የተጠሪ ምስክር አንደኛ ተከሳሽ የሂሳብ ሠራተኛ መሆኑን ገልፆ ሁለተኛው ተከሳሽ የአንደኛ ተከሳሽ ሥራ አስኪያጂ በመሆን 1997 ዓ/ም እስከ 2002 ዓ/ም የሠራ መሆኑንና 1ኛ ተከሳሽ 1998

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓ/ም ከሜጋ ማስታወቂያ ጋር ሲዋሀድም 2ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሰራ መሆኑን እንደመሰከረ የሥር ፍርድ ቤት በውሳኔው ፅፎታል፡፡

4 ሁለተኛ ተከሳሽ /አመልካች/ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሂሳብ ሠራተኞች በየወሩ ለከሳሽ /ተጠሪ/ ሪፖርት ያደርጉ የነበረ መሆኑንና ገቢን አለማሳወቅና አሳሳች ማስረጃ ማቅረብ የተባለውም ገቢን አለማሣወቅና አሳሳች ማስረጃ የማቅረብ ወንጀል አልፈፀምኩም በኦዲት ተገኘ የተባለው የሂሳብ ልዩነት የተፈጠረው አንደኛ ተከሳሽና ሜጋ ማስታወቂያ 1998 ዓ/ም ጀምሮ በአንድ ሥራአስኪያጅ እየተመሩ አንድ ላይ ስራ ሲሳሩ የነበረ በመሆኑና በሜጋ ማስታወቂያ ሠረተኞች የስልክ ወጭና የሜጋ ማስታወቂያ መኪኖች ነዳጅ የወጣ ውጭ በመኖሩ ምክንያት ነው በማለት አምስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ አንደኛው የአመልካች የመከላከያ ምስክር የአንደኛ ተከሳሽ ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኖ ሲሳራ ከፋይናንስ ክፍል ይሰጠው የነበረውን የተጨማሪ እሴት ተክስ ሪፖርት ለከሳሽ /ለተጠሪ/ ሲያደርስ እንደነበረና አንደኛ ተከሳሽ 1998 ጀምሮ ከሜጋ ማስታወቂያ ጋር ሲሰራ የሜጋ ማስታወቂያና መኪኖች በትውስት በመውሰድ ነዳጅ በመሙላት ሲጠቀም እንደነበረ የመሰከረ መሆኑን ሁለተኛ መከላከያ ምስክር የሒሳብ ባለሙያ መሆናቸውን ገልፀው ለአንደኛ ተከሳሽ የሂሳብ ሠራተኞች በ1996 ዓ/ም የሂሳብ አያያዝ ሥልጠና የሰጡ መሆኑን እንደመሰከረ፣ ሶስተኛ መከላከያ ምስክር የአንደኛ ተከሳሽ የሂሳብ ሠራተኛ እንደነበር 1997 ዓ/ም ጀምሮ የሽያጭ ወጭ ደረሰኞችን በመቀበል በየወሩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሪፖርት ያዘጋጅ እንደነበር እንደመሰከሩ፤ አራተኛ የመከላከያ ምስክር የአንደኛ ተከሳሽ ሹፌር የነበረ መሆኑን ገልጾ፣ 1ኛ ተከሳሽ ይጠቀምበት የነበረውን ላንድክሩዘር ኮድ ሁለት የሆነ መኪና ያሽከረክር እንደነበርና ወጭውንም የሚሸፍነው አንደኛ ተከሳሽ እንደነበር እንደመሰከረ፣ 5ኛ የመከላከያ ምስክር የፋሲል ኮንሰልት ኃላ/የተ/የግል ማህበር የሂሳብ ሰራተኛ በመሆን የአንደኛ ተከሳሽ የሁለት አመት 1996ዓ.ም እና 1997ዓ.ም ሂሳብ የሰራ መሆኑንና የሂሳብ ሰነድ ወጭና ገቢ አያያዙ ጥሩ ሆኖ ማግኘታቸውንና ተከሳሽ ድርጅትም በኪሳራ ይንቀሳቀስ እንደነበር ያስረዱ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው አስፍሮታል፡፡

5 የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽና ሜጋ ማስታወቂያ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ያልተቀላቀለ መሆኑ፣ አንደኛ ተከሳሽ በሜጋ ማስታወቂያ ሰራተኞች የከፈለው ደመወዝና የስልክ ወጭ የአንደኛ ተከሳሽ ሕጋዊ ወጭ ተደርጎ ሊያዝ የማይችል መሆኑን የተሸከርካሪ ትውስት የተባለውም ተቀባይነት ያለውን የሂሳብ አሰራር ያልተከተለ በመሆኑ ተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ፣ በየወሩ ሪፖርት ይደረግ የነበረ መሆኑን በመከላከያ ማስረጃ ከማስረዳት ውጭ አንደኛ ተከሳሽ የሰበሰበውን ብር 426,229.03 ተጨማሪ እሴት ታክስ ለከሳሽ መስሪያ ቤት ያላሳወቀና ገቢ ያላደረገ መሆኑን በማረጋገጥ በከሳሽ (ተጠሪ) በኩል ያቀረበውን ማስረጃ የሚያስተባብል ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ስለዚህ አንደኛ ተከሳሽ 1997ዓ.ም ትክክለኛ ገቢውን ባለማሳወቁና ኪሳራ እንደደረሰበት ሪፖርት በማድረጉ እንደዚሁም አንደኛ ተከሳሽ ከ1996ዓ.ም እስከ 2002ዓ.ም የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ሙሉ ለሙሉ ለተጠሪ (ለከሳሽ) ባለማሳቁና ገንዘቡንም ገቢ ባለማድረጉ ሁለተኛ ተከሳሽ በስራ አስኪያጅነቱ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 97 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍና በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት የቅጣት ውሳኔ በመወሰንና በመገደብ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

6 በዚህ ውሳኔ አመልካችና ተጠሪ ቅር በመሰኘት አመልካች በመዝገብ ቁጥር 131320 ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 131160 ያቀረቡትን ይግባኝ ቅሬታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመዝገብ ቁጥር 131320 በማጣመር፣ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል።

7 አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ ለማስለወጥ ሚያዚያ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የወንጀል ክስ ከመመስረቱ በፊት የንግድ ድርጅት ስራ አስኪያጅነት መልቀቂን ሰነዶች ያረጋግጣሉ። እኔ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ በወንጀል ጥፋተኛ ልባል ከሚገባው በመጀመሪያ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የንግድ ድርጅት ተጠርቶ፣ ቀርቦ ተከራክሮ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ነው። አንደኛ ተከሳሽ የሌለ መሆኑን ተጠሪ የወንጀል ክስ ሲመሰርት ያውቃል። አንደኛ ተከሳሽ የፈረሰና ህጋዊ ህልውና የሌለው በመሆኑ በወንጀል ሊከሰስና ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ አይችልም። አንደኛ ተከሳሽ በወንጀል ሊጠየቅ የማይችል ከሆነ ስራ አስኪያጅ በወንጀል ሊጠየቅ አይችልም ። የአንደኛ ተከሳሽ ሂሳብ ኦዲት የተደረገው በ2003 ዓ.ም ነው። ይህም አመልካች ድርጅቱን ከለቀቀ ከአስር ወር በኋላ ነው። ሜጋ ማስታወቂያና ሜጋ ኪነጥበባት፣ በኋላ የተቀላቀሉ መሆኑ ተረጋግጧል። ስለዚህ ስራ አስኪያጅ የነበረው አመልካች በተጨባጭ ለስራ ያወጣው ወጭ ውድቅ ተደርጎ አሳሳች ማስረጃ አቅርቧል፣ ተጨማሪ እሴት አሳውቆ ገቢ አላደረገም ተብሎ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል።

8 ሰኔ 27 ቀን 2006ዓ.ም በተጻፈ መልስ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት በራሱ ወንጀል የመፈጸም ሃሳብ የሚፈጥር ባለመሆኑ፣ ድርጅቱ ወንጀል የሚፈጽመው ከድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሰራተኞች አንዱ የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ ባለመወጣት ወይም የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ ተንቀሳቅሰው በተገኙ ጊዜ ነው። ከስር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት አመልካች አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ በነበሩበት ጊዜ ለተፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ መሆናቸው በወንጀል ሕጉ የተቀመጠውን መርህ የተከተለ ነው። ከስር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት በህጋዊ መንገድ የፈረሰ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም። ተጠሪ የወንጀል ክሱንና መጥሪያውን ለማድረስ ጥረት አድርጎ ሊያገኘው አልቻለም። ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በጋዜጣ ጥሪ አድርጎለት አልቀረበም ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤት በጋዜጣ አለመጥራት እንደ ስነ-ስርዐት ስህተት ከሚታይ በስተቀር በአመልካች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም። የድርጅቱም ሂሳብ በአግባቡ የተጣራና ወንጀሉ የተፈጸመ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ የአመልካች፣ የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካች ነሐሴ 23 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ ሁለተኛ ተከሳሽ (አመልካች) በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ የሚረጋገጠው አንደኛው ተከሳሽ በአግባቡ ተጠርቶ፣ ተከራክሮ ጥፋተኛ ነህ ተብሎ ሲፈረድበት ነው። ይህ ሳይደረግ ሁለተኛው ተከሳሽ ጥፋተኛ ተብሎ ሊፈረድበት አይችልም። የስር ፍርድ ቤት ድርጅቱንና ሁለተኛ ተከሳሽን ጥፋተኛ ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። ይህ ተገቢ ያልሆነና የወንጀል ህግን መሰረታዊ መርህ የሚጻረር ውሳኔ ነው። ምክንያቱም በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽን በመጥሪያም ይሁን በጋዜጣ አልተጠራም፣ አልቀረበም በሌለበት ይታያል ተብሎ አልተያዘም። 1ኛ ተከሳሽ ያፈረሰ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ሁለተኛ ተከሳሽ የለብኝም የሚልና ሌሎች በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን መከራከሪያዎች የሚያጠናክር ክርክር አቅርቧል።

9 ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የሜጋ ኪነጥበባት ኃላፊነቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተወሰነ የግል ማሕበር ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ፣ የንግድ ትርፍ ገቢ በትክክል አለማሳወቅና የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር አለመክፈል፣ አሳሳች ማስረጃ የማቅረብና የንግድ ድርጅቱ በፈጸማቸው ግብይቶች ወይም የንግድ እንቅስቃሴ የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ በተሟላ ሁኔታ አለማሳወቅና ገቢ ያለማድረግ ወንጀል ፈጽሟል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

10 ጉዳዩን እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆነው ሜጋ ኪነጥበባት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር በንግድ ህግ አንቀጽ 542 እና አንቀጽ 543 መሰረት ያልፈረሰ ወይም የንግድ ህጉ ከአንቀጽ 544 እስከ አንቀጽ 554 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሰረት ከሌላ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር በተለይም ከሜጋ ማስታወቂያ ጋር በሕግ የተደነገገውን ስርዓት በማሟላት ያልተቀላቀለ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው በማረጋገጥ ውሳኔ ሰጥቷል የስር አንደኛ ተከሳሽ በህግ አግባብ ካልፈረሰ ወይም ከሌላ የንግድ ድርጅት ጋር አለመቀላቀሉ ካልተረጋገጠ፣ ህጋዊ ህልውና ያለው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ እንደሆነ ከህጉ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ የስር አንደኛ ተከሳሽ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመሆኑ ከመፍረሱ ወይም ከሌላ ድርጅት ጋር ከመቀላቀሉ በፊት ይከናወን ያላቸው ተግባራት አሉ፡፡ ከእነዚህ ተግባራት መካከል የማጎበሩ ሒሳብ የማጣራት ስራ ነው፡፡ ተጠሪ የአንደኛ ተከሳሽ ሂሳብ ኦዲት ያደረገው አንደኛ ተከሳሽ የመፍረስ ጥያቄ በማቅረቡ እንደሆነ፣ ተጠሪ ያቀረባቸው ምስክሮችና የአንደኛ ተከሳሽን ሒሳብ ያጣሩት ባለሙያዎች የገለጹ መሆኑን በስር ፍርድ ቤት በግልጽ ሰፍሯል፡፡ ይህም የአንደኛ ተከሳሽ ሒሳብ በተጣራበት ጊዜ አንደኛ ተከሳሽ የመፍረስ ጥያቄ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም በሕግ አግባብ ሒሳቡ ተጣርቶ የመፍረስ ውሳኔ ያልተሰጠና ህጋዊ ሕልውና ያለው ድርጅት የነበረ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣናቸው ያረጋገጡት በመሆኑ አመልካች አንደኛ ተከሳሽ ሕጋዊ ሕልውናው የከተመ ወይም የፈረሰ ድርጅት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

11 .አንደኛ ተከሳሽ የሕግ ሰውነት ያለው የንግድ ድርጅት ነው፡፡ የሕግ ሰውነት ያለው የንግድ ድርጅት በሕግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሊቀጣ የሚችል መሆኑ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ሕጉ በወንጀል የሚጠየቁ እንደሆነ በልዩ ሁኔታና በግልጽ ባልደነገገባቸው ወንጀሎች የወንጀል ተጠያቂነት እንደማይኖርባቸው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ማንኛውም የንግድ ድርጅት በዓመት ውስጥ ያገኘው ትክክለኛ ትርፍ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የማሳወቅ ግብር የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበትና ይህንን ኃላፊነቱን በመጣስ በተለይም አሳሳች የሆኑ ማስረጃዎችን በማቅረብ ግብር የማጭበርበር ተግባር ከፈጸመ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን ከአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 97(1) ድንጋጌዎች ተደንግጓል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ በ1997ዓ.ም ብር 132673.06 /አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺድስት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከዜሮ ስድስት ሳንቲም/ ከንግድ ስራ ትርፍ አግኝቶ እንደነበር ነገር ግን አንደኛ ተከሳሽ በሕግ አግባብ ላልተቀላቀለው ሜጋ ማስታወቂያ ሰራተኞች የከፈለውን ደመወዝ በስልክ ክፍያና የነዳጅ ወጭ አንደኛ ተከሳሽ ለእራሱ ስራ ያወጣው ህጋዊ ወጭ አስመስሎ በማቅረብና 1997ዓ.ም ከንግድ ስራ ትርፍ እንዳላገኘና ኪሳራ እንደደረሰበት ለተጠሪ ያሳወቀ መሆኑ ተጠሪ ባቀረበው የጽሑፍና የሰው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንደኛ ተከሳሽከ1996 እስከ 2002 ዓ.ም ባከናወነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግብይት ብር 426299.03 /አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ብር ከዜሮ ሶስት ሳንቲም/ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ለተጠሪ ይህንን ተጨማሪ እሴት ታክስ ገንዘብ የሰበሰበ መሆኑን እንዳላሳወቀና ገንዘቡንም ገቢ እንዳላደረገ ተጠሪ ባቀረባቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ሕግን በመጣስ የሰበሰበውን ታክስ ያላሳወቀ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ እስከ አምስት አመት ሊቀጣ የሚችል መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 የተደነገገ ሲሆን የንግድ ድርጅት ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ለሚፈጸመው ጥፋት የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት ስለመሆኑ ከአዋጁ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

12 .በስር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የንግድ ድርጅት ለሌላ ድርጅት ሠራተኞች ሜጋ ማስታወቂያ ሠራተኞች የከፈለውን ደመወዝና የስልክ ወጭ የንግድ ተግባሩን ሲያከናውን ያወጣው ወጭ መሆኑን በሚገልጽ መንገድ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ሪፖርት በማቅረብ 1997ዓ.ም ትርፍ አግኝቶና ካገኘውም ትርፍ 39,801.32 የንግድ ስራ ትርፍ ገቢ ግብር መክፈል ሲገባው ኪሳራ እንደደረሰበት አድርጎ ሪፖርት ማቅረቡና ይህም ሪፖርት ለሌላ ንግድ ድርጅት ወጭ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ለመሸፈን የወጣ ወጭ እንደ ሕጋዊ ወጭ በማቅረብ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት የተረጋገጠ መሆኑን እንደዚሁም አንደኛ ተከሳሽ ከ1996 እስከ 2002 ዓ.ም የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ለተጠሪ ያላሳወቀና ገንዘቡንም ገቢ ያላደገረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

13 .አመልካች 1997ዓ.ም አንደኛ ተከሳሽ ትርፍ አግኝቶ እያለ ትርፍ እንዳላገኘና ኪሳራ እንደደረሰበት ሪፖርት በማድረግ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 97 (1) (ሀ) የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶች ሲፈጽም የአንደኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ የነበረ መሆኑ በተጣራ ማስረጃ ብቻ ሳይሆን አመልካች ባቀረባቸው የመከላከያ ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ያሳያል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ከላይ የጠቀስናቸውን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመ መሆኑ ከተረጋገጠ ስራ አስኪያጁ በወንጀሉ ተጠያቂ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም አንደኛ ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 የተመለከተውን በመተላለፍ ከ1996 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ባከናወነው ግብይት የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ለተጠሪ ያላሳወቀና ገንዘቡንም ገቢ ያላደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 ድንጋጌ የሚጥስ የወንጀል ተግባር በፈጸመበት ጊዜ አመልካች የአንደኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ እንደነበር በተጣራ ማስረጃ ብቻ ሳይሆን አመልካች ባቀረባቸው የመከላከያ ማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ወንጀሉን የፈጸመው ከ1996ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በመሆኑ አመልካች የአንደኛ ተከሳሽ ሂሳብ በተጠሪ በሚጣራበት 2003ዓ.ም እኔ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ አልነበርኩም በማለት የሚያቀርበው ክርክር አንደኛ ተከሳሽ በስራ አስኪያጅነት በሚሰራበት ወቅት ለተፈጸመው ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተጠያቂ መሆኑን የሚያስቀር ባለመሆኑ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

14 .የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከክርክሩ ውጭ እንዲሆን አላደረገም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአንደኛ ተከሳሽ ላይ እና በአመልካች ላይ የቀረበውን የወንጀል ክስ እና ማስረጃ ከሰማና የአመልካችን መከላከያ ከመረመረ በኋላ "ስለሆነም ተከሳሹ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የሚያስተባብል ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ በ1997ዓ.ም 1ኛ ተከሳሽ ባከናወነው የንግድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንቅስቃሴ ገቢን አሳውቆ ባለመክፈልና ተከሳሾች አሳሳች መረጃ በመስጠትና ኪሳራ ሪፖርት በማድረግና ከ1996ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውንየተጨማሪ እሴት ታክስ የሰበሰቡትን በሙሉ ሪፖርት ባለማድረጋቸው ሁለተኛው ተከሳሽ (አመልካች) በስራ አስኪያጅነታቸው አንደኛ ተከሳሽ ለፈጸመው ድርጊት ተጠያቂ በመሆናቸው ተከሳሾች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 97 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) አንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ናቸው" በማለት ውሳኔ እንደሰጠ ከስር ፍርድ ቤት ከሰጠው ፍርድ በስምንተኛው ገጽ በአራተኛው ፓራግራፍ በግልጽ ሰፍሯል፡፡

15 ይህም የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከላይ በገለጽናቸው አዋጆች የተመለከቱትን የሕግ ድንጋጌዎችና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመ መሆኑን በማረጋገጥ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠ መሆኑንና አንደኛ ተከሳሽ ወንጀሉን በሚፈጽምበት ጊዜ ሁለተኛ ተከሳሽ አመልካች የአንደኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 102 እና የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56 ድንጋጌዎች መሰረት ሜጋ ኪነጥበባት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በስራ አስኪያጅነት ሲመራ በነበረበት ጊዜ በድርጅቱ ለተፈጸመው ወንጀል በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን በማረጋገጥ የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች የንግድ ድርጅቱ ወንጀሉን የፈጸመ መሆኑ ሳይረጋገጥ እና ለወንጀሉ ኃላፊ ተብያለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር በመዝገቡ ያለውን እውነታ የሚያንጸባርቅ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ከአመልካች ጋር ለተፈጸመው ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176025 ታህሳስ 19 ቀን 2004ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በግልጽ የሚታይ ነው፡፡

16 አመልካች የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽን በአግባቡ ሳይጠራ አንደኛ ተከሳሽ በክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ወይም ጉዳዩ አንደኛ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ ትእዛዝ ሳይሰጥ የወንጀል ክሱን ሰምቶ የወሰነ መሆኑ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን መከራከሪያ አድርጎ አቅርቧል፡፡ አመልካች ከ 2003ዓ.ም ጀምሮ የአንደኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ እንዳልሆነና አንደኛ ተከሳሽንም ወክሎ ክርክር ለማቅረብ እንደማይችል በስር ፍርድ ቤት የገለጸ መሆኑን ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ተገንዝበናል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ የወንጀል ጉዳይ የታየው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ አንቀጽ 162 አንቀጽ 167 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ከሚደነግጉት ውጭ ነው ብሎ ካለ የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ በሌለበት አይቶ የሰጠው ፍርድ እንዲነሳለት ከሚያመለክት በስተቀር አንደኛ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ መወሰኑን አመልካች መከራከሪያ አድርጎ ሊያቀርብ የሚችል አይደለም፡፡ አንደኛ ተከሳሽ በመወከልም አንደኛ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ ለመከራከር የሚያስችለው ውክልና ወይም ስልጣን የለውም ስልጣንም ቢኖረው ክርክሩ መቅረብ የሚገባው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 102 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ መሆን የሚገባው በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

17 አንደኛ ተከሳሽ አግባብነት ባላቸው የንግድ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት መፍረሱ ወይም ከሌላ ድርጅት ጋር መቀላቀሉን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ይህም አንደኛ ተከሳሽ ሕጋዊ ህልውና ያለው ድርጅት መሆኑን ያሳያል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ በህግ አግባብ ሳይፈርስ ወይም ሌላ ድርጅት ጋር ተቀላቅሎ ህጋዊ ህልውናውን ሳያጣ አንደኛ ተከሳሽ በእውን እንዳይኖር የፈጸመበትን የንግድ ዓላማ የማይፈጽምና ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዳያደግ በማድረግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቁመ- ማክሰም የሚቻል መሆኑና አመልካችም አንደኛ ተከሳሽ በህግ አይን የፈረሰ ድርጅት ነው ባይባልም በእውኑ ዓለም የሌለና የከሰመ ድርጅት ነው የሚል መከራከሪያ ያቀረቡ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በመሰረቱ አንድን ድርጅት በቁመ- አንዲከስም በማድረግ ድርጅቱ ህጋዊ ህልውና ኖሮት ተግባራዊ የንግድ እንቅስቃሴ ሲያደርግ በነበረበት ጊዜ ለተፈጸመ ወንጀል የንግድ ድርጅቱንም ሆነ በወቅቱ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ የነበረውን ሰውና የሌሎች ሰራተኞች የወንጀል ተጠያቂነት ለማስቀረት አይቻለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሕጋዊ ህልውና ያለው ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በሃላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞች አንዱ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት አላግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት በአነሳሽነትና በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ መሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ የተደነገገ መርህ ነው፡፡ አንድ የንግድ ድርጅት የወንጀል ተግባር ከፈጸመና ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ከተረጋገጠ በኋላ ድርጅቱ የወንጀሉን ፍርድ ሊፈጽም የማይችልበት ሁኔታ በቁም እንዲከስም መደረጉ ለወንጀሉ አድርጎት ኃላፊ የሚሆኑትን ሰራተኞችና ኃላፊዎች በወንጀል ከመጠየቅ ነጻ የማያወጣ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በአመልካች ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) 2 መሰረት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴረል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት በድምጽ ብልጫ ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>የልዩነት ሐሳብ</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር አምስት የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ ከሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት የሚከተለው የልዩነት ሐሳብ አስፍሬአለሁ፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ አንደኛ ተከሳሽ ሜጋ ኪነጥበብ ማዕከል ኃ/የተ/የግል ማህበር 2ኛ ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች በማድረግ ስድስት ክሶች ያቀረበ ሲሆን በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ገቢን አለማሳወቅ፣ ትርፍ አሳውቆ አለመክፈል፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አለመክፈል የሚሉ ናቸው፡፡ አመልካች ድርጊቱን ክደው በመከራከራቸው የግራ ቀኙ ማስረጃዎች ተሰምተው ጥፋተኛ ተብሎው የእስራት ቅጣት ተወስኖ የተገደበላቸው ስለመሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በየደረጃው ጉዳዩን በተመለከቱት ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ቅሬታ መሠረታዊ ይዘት በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ጥፋተኛ ሳይባል መቀጣታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑ የሚያሰይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አንደኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ እንደተባለ እና ስለ መፍረሱ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን አመልካች ድርጁቱን ወክለው ባይከራከሩም ለምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ በማቅረብ የተከራከሩ በመሆኑ የተጣበበ መብት የለም የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሥር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ሜጋ ኪነጥበብ ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ቀርቦ እንዲከራከር በሕጉ አግባብ ጥሪ የተደረገለት ስለመሆኑ ጉዳዩም በሌለበት እንዲታይ ግልጽ ትዕዛዝ የተሰጠ ስለመሆኑ የወሳኔው ይዘት አያሳይም ።

ጉዳዩ በይግባኝ ሥልጣኑ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የሜጋ ኪነጥበባት ማዕከል በሕጉ አግባብ እንዳልተጠራ በዚህ ምክንያት መዝገቡ ወደ ሥር ፍርድ ቤት መመለሱ ውጤት እንደሌለው በመግለጹ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች በሕግ በግልጽ በተመለከተ ጊዜ የወንጀል ተጠያቂነት ያለባቸው ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 ተመልክቷል። የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 102 እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285 /1994 አንቀጽ 56(1) እንደተመለከተው ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት የወንጀል ጥፋት ከፈፀመ የድርጅቱ ስራአስኪያጅ ተጠያቂ እንደሚሆን ተደንግጓል። የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዝኛ ትርጉም ``subject to sub-Article (3) where an entity commits an offence every person who is manager of that entity at that time is treated as having committed the offence and is liable penalty under this proclamation`` የሚል ነው። ከዚህ የህግ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት ዓላማና መንፈስ መረዳት የሚቻለው የአንድ ድርጅት ሥራአስኪያጅ ኃላፊ የሚሆነው ድርጅቱ በሕግ አግባብ ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። ወደ ተያዘው ጉዳይ ሲንመጣ ድርጁቱ በህግ አግባብ መጥሪያ የደረሰው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም። የአሁኑ አመልካችም ድርጅቱ ከለቀቁ ከአንድ ዓመት በኃላ ክስ የተመሰረተባቸው ስለመሆኑ እየተከራከሩ ነው። የስር ፍርድ ቤቶች የአሁኑ አመልካች ጥፋተኛ ከተባሉ ድርጅቱም ጥፋተኛ ነው በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ከውሳኔያቸው ይዘት መረዳት ይቻላል። ይሁንና የስር ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ የህግ መሰረት ያለው አይደለም። ሕግ አውጪው ከላይ በጠቀሱኩዋቸው አዋጆች ላይ በግልጽ እንዳመለከተው ቅድሚያ መረጋገጥ ያለበት የድርጅት ጥፋት መኖር ያለመኖር ነው። አንድ ድርጅት ጥፋተኛ ነው ወይስ አይደለም ወደ ሚለው ድምዳሜ ለመድረስም በህጉ የተዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት በጥብቅ ተግባራት መደረግ ነበረበት። የስር ፍርድ ቤቶች አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት ሕጋዊ ሰውነት ያለውና ያልከሰመ መሆን ያለመሆኑን በአግባቡ ሰያጣሩ ጥሪ ቢደረግለትም አይቀርብም በሚል ሰበብ እውነት የማፈለግ ግዴታቸው (truth finding) ወደ ጎን በመተው ሕጉን የዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት ሳይከተሉ ከውሳኔ ላይ መደረሳቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸማቸውን የሚያሳይ ነው። ከላይ እንደተመለከተው ድርጅቱ ጥፋተኛ ሳይባል ስራአስኪያጅ ነበሩ የተባሉ የአሁኑ አመልካች በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ በአዋጅ ቁጥር 285 እና 286/1994 የተደነገገው የድርጅት እና ሥራአስኪያጅ የተጠያቂነት አወሳሰን ቅደም ተከተል ያዛባ ሂደት ነው። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ይሁን አብላጫው ድምጽ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የገቢ አዋጆች ስለ ድርጅት እና ሥራአስኪያጅ የወንጀል ተጠያቂነት አወሳሰን ማለትም የድርጅቱ ጥፋተኝነት በቅድሚያ የማረጋገጥ ሕጋዊ ግዴታ ታልፎ አመልካች ጥፋተኛ ናቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ የአዋጆች ዓለማና ግብ ያላገነዘበ ነው የሚል እምነት አለኝ።

በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት /ሜጋ ኪነጥበባት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በዚህ አገር በንግድ ህግ ተመዝግቦ የሚሰራ ድርጅት ከነበረ ስለ ድርጅቱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው መሆን ያለመሆን ከከሰመም መቼና በማን ውሳኔ የሚሉ ነጥቦች ሊጣሩ የሚገባቸው ነጥቦች ናቸው። ምክንያቱም አመልካች ድርጅቱ ከመሰከረም 5/2002 ጀምሮ የፈረሰ ስለመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩሉ ድርጅቱ አልፈረሰም ተሰውሯል በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ ሕግና ሥርዓት ባለበት አገር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት በእርግጥ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ህያው ድርጅት ከሆነ ከሚመለከታቸው አካላት በማጣራት እውነት የማፈላላግ ሥራ መከናወን ነበረበት፡፡ በሌላ በኩል ድርጅቱ ሜጋ ማስታወቂያ ከተባለው ድርጅት የተዋሃደ/የተቀለቀለ / Amalgamation merge /ስለመሆኑ በክርክር ሂደት ተነስቷል፡፡ ይህ በተመለከተም ሁለቱም ድርጅቶች ተዋህደው ከሆነ መቼ እና በማን ውሳኔ ሰሚነት ተዋሀዱ የሚለው መጣራት ነበረበት፡፡ አመልካች እንደሚሉት በክርክር ጊዜ አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ለማግኘት እንደተቸገሩ በተለይም ድርጅቱ ህያው ካልሆነ እና የድርጅቱ ሕጋዊ ሠራሽ የሆነው ድርጅት ወይም ግለሰብ በጉዳዩ ጣልቃ በመግባት ካልተከራከሩ ዞሮዞሮ የአመልካች የመከላከል ሕግ መንግስታዊ መብት ማጣበቡ የማይቀር ነው፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ምስክሮች መሰቀለኛ ጥያቄ በማቅረብ ስለተከራከሩ የተጣበበ መብት የለም በማለት በውሳኔው ያሳፈረ ቢሆንም ክርክሩ ግለሰባዊ ጉዳይ ሳይሆን የአንድ ድርጅት ጥፋተኛ መሆን ያለመሆን ብሎም የድርጅቱ ሥራአስኪያጅ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ጉዳይ በመሆኑ ድርጅቱ እና የአሁኑ አመልካች ፈጸሙት የተባለው የወንጀል ድርጊት ለመከላከል መቅረብ ያለባቸው ሕጋዊ ሰነዶች እና የክርክር ነጥቦች ከድርጅቱ የተያያዙ አይደለም የሚለው ድምዳሜ የህጉን አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የሥር ፍርድ ቤት ይሁን ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት ህያው ድርጅት ነው ወይስ የከሰመ ድርጅት? የከሰመ ድርጅት ከሆነ መብትና ግዴታው ለማን ተላለፈ? የሚሉትና ተያያዥ ነጥቦች በማጣራት ድርጅቱ ጥፋተኛ ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለው በቅድሚያ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸው ነበር፡፡

በማጠቃለል በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ሜጋ ኪነጥበበት ማዕከል ኃ/የተ የግል ማህበር በቅድሚያ በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎለት ራሱ ወይም ህልውናው የከሰመ ከሆነ መብትና ግዴታው የወረሰው ድርጅት/ተቋም/ ግለሰብ ሳይጣራ እና በአግባቡ ተጣርቶ ጥፋተኛ ሳይባል አመልካች ጥፋተኛ ናቸው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ አይደለም፡፡ በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት ህልውና ካበቃ ወይም መብቱና ግዴታው የተላለፈለት ድርጅት/ግለሰብ ከሌለ በእርግጥ በሥራ አስኪያጅ የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል ወይ የሚለውም ከወንጀል ቅጣት ዓላማና ግብ መታየት ነበረበት፡፡ ሜጋ ኪነጥበባት ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ሜጋ ማስታወቂያ ድርጅት በሕጉ አግባብ ያልተዋሀዱ ከሆነ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትለው ውህዳቱን የወሰኑ እና ያስፈጸሙ የየድርጅቱ ባለቤቶች ናቸው ወይስ ሥራ አስኪያጅ ነው ተጠያቂ መሆን ያለበት? የሚለውን በአግባቡ የተጣራ ጉዳዩ አይደለም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባ ነበር በማለት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጭ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95267
ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም
መስጠፉ አህመድ
ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡-ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር ነገረ ፈጅ ይነበብ ደርስህ-ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ካሣሁን ወንድሙ- ቀረቡ
2. አቶ ግርማ ታጳኖ- ከክርክሩ ውጭ ተደርገዋል
3. ኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር- ነገረ ፈጅ ዮሴፍ ገብሬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥ~ል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ በተጀመረበት የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች በዚህ መዝገብ አቤቱታውን ያቀረበው በተሸከርካሪዎች ግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰበትን የደንበኛውን ተሸከርካሪ አስጠግኖ ወደ ነበረበት ለመመለስ ያወጣውን ወጪ ለማስተካት ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ24/04/2004 ዓ.ም.አዘጋጅቶ ባቀረበው ክስ ንብረትነቱ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ሆኖ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በመሸከርከር ላይ የነበረ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02598 ደ/ሕ. የሆነ ተሽከርካሪ በሾፌሩ ጥፋት ንብረትነቱ የአድቫንስድ ኢንጂነርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሆኖ በአመልካች የኢንሹራንስ ሽፋን የተሰጠውን የሰሌዳ ቁጥሩ 3-3277 የሆነ ተሽከርካሪ ገጭቶ ያደረሰበትን ጉዳት አስጠግኖ ወደ ነበረበት ለመመለስ አመልካች ያወጣውን ወጪ ብር 441,213.17 (አራት መቶ አርባ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አስራ ሶስት ከአስራ ሰባት) 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ የጠየቀ መሆኑን፣1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲሁም ለ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ የመድን ሽፋን የሰጠው እና በተጠሪው ጠያቂነት ወደ ክርክሩ የገባው 3ኛ ተጠሪ ከመቃወሚያ በተጨማሪ በኃላፊነት እና በመጠን ረገድ ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር ማቅረባቸውን፣ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ውሳኔ መስጠቱን፣በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የተጠሪዎቹ ማስረጃ ሳይሰማ ውሳኔ መሰጠቱ እና የ3ኛ ተጠሪ ኃላፊነትም ተለይቶ አለመወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን ገልጾ ውሳኔውን በመዝገብ ቁጥር 51395 በ30/11/2004 ዓ.ም. በመሻር ጉዳዩን በነጥብ የመለሰው መሆኑን፣ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በተመለሰለት መሰረት የተጠሪዎችን ማስረጃ ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን ማስረጃ መዝኖ የሁለቱ ተሽከርካሪዎች ግጭት የደረሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአመልካች ደንበኛ ተሸከርካሪ ሾፌር ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተጠሪዎቹ ለክሱ ኃላፊነት የለባቸውም ሲል በነጻ ያሰናበታቸው መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ነው፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት እንደደረሰበት መደምደሚያ ለጉዳቱ መንሰኤ ለሆነው ጉዳት የሁለቱም ወገኖች ጥፋት የለም፣የመኪኖች ግጭት ጉዳይ ነው ከተባለ የአሁኑ አመልካች ያቀረበው የጉዳት ካሳ ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2084(2) ድንጋጌ አንጻር ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ አመልካች ከ1ኛ እና ከ3ኛ ተጠሪዎች ጋር የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ ሲሆን ለ2ኛ ተጠሪ መጥሪያውን ተከታትሎ ማድረስ ባለመቻሉ አቤቱታውን እንደተወው ተቆጥሮ 2ኛ ተጠሪ ከክርክሩ ውጪ እንዲሆን በ15/08/2006 ዓ.ም.ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የግጭት አደጋው የደረሰው በ1ኛ ተጠሪ ተሸከርካሪ ሾፌር ጥፋት ምክንያት አይደለም በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተደረሰበት ድምዳሜ እና ይህንን ድምዳሜ መሰረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኙ የቀረበውን አጠቃላይ ክርክርና ማስረጃ ያገናዘበ አይደለም፤የ1ኛ ተጠሪ ተሸከርካሪ ሾፌር ጥፋት አልነበረውም ቢባል እንኳ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2084(1) እና (2) ድንጋጌዎች መሰረት ተጠሪዎቹ ያወጣነውን ወጪ አጋማሽ የመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት መሆኑን የክርክሩ ይዘት ያመለክታል፡፡እንደተባለው ሁለት ባለሞተር ተሸከርካሪዎች ሲጋጩ እያንዳንዱ ተሸከርካሪ በየራሱ አንዱ በአንዱ ላይ አደጋ እንዳደረሰ የሚቆጠር ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ በቁጥር 2084 (1) ስር፣የእያንዳንዱ ተሸከርካሪ ባለሀብት ወይም ለአደጋው ኃላፊ የሆነው ሰው በአደጋው ምክንያት ከደረሰው ጠቅላላ ጉዳት ገሚሱን መክፈል የሚገባው ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 2084 (2) ስር እና አደጋው የደረሰው በተለይ ወይም በጠቅላላው በአንደኛው መኪና ነጂ ስህተት መሆኑ በማስረጃ በተገለጸ ጊዜ ግን ከዚህ በተጠቀሱት ሁለቱ ንዑሳን ቁጥሮች የተመለከተው ደንብ የማይጸና ስለመሆኑ በቁጥር 2084 (3) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ ወገኖች የቀረቡትን የሙያ እና የዓይን ምስክሮች ቃል እንዲሁም የትራፊክ ፕላንን ጨምሮ የቀረቡለትን ሰነዶች አገናዝቦ ከመረመረ እና ከመዘነ በኃላ ተጠሪዎቹ ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ውሳኔ የሰጠው አመልካች እንደሚከራከረው ጥፋቱ የ1ኛ ተጠሪ ተሸከርካሪ ሾፌር መሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ሳይሆን ይልቁንም የግጭት አደጋው የደረሰው የአሁኑ አመልካች የመድን ሽፋን በሰጠው ተሸከርካሪ ሾፌር ስህተት ነው በማለት መሆኑን የውሳኔው ይዘት በግልጽ ያመለክታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው ቁጥር 2084 (1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ጉዳቱን የመጋራት ደንብ ተፈጻሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (3) ስር በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች ያወጣውን ወጪ አጋማሽ ተጠሪዎቹ እንዲሸፍኑ መወሰን ነበረበት በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ ለጉዳቱ መንስኤ ሁለቱም ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው የየራሳችንን ጉዳት እንድንችል መደረግ ይገባዋል በማለት ተከራክረው እያለ አመልካች ያወጣውን ወጪ አጋማሽ እንዲጋሩ ሳይወሰን የቀረው አላግባብ ነው በማለት አመልካች ያቀረበውን የክርክር ነጥብ በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት መልስ ላይ ለጉዳቱ መንስኤ ሁለቱም ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው የየራሳችንን ጉዳት እንድንችል መደረግ ይገባዋል በማለት የተከራከሩት በራሳቸው ተሽከርካሪ ላይም በተመሳሳይ ሁኔታ ጉዳት መድረሱን እና ለጥገና ወጪ ማውጣታቸውን ለመግለጽ እንጂ ጥፋቱ በራሳቸው ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ነው በሚል የቀረበባቸውን ክስ በማመን ካለመሆኑም በላይ በመልሳቸው መጨረሻ ላይ ለክሱ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ የተከራከሩ መሆኑን አመልካች አቅርቦ ያያዘው የ1ኛ ተጠሪ መልስ ይዘት የሚያመለክት በመሆኑ እና ቀደም ሲል እንደተገለጸው ግጭቱ የተከሰተው አመልካች የመድን ሽፋን በሰጠው ተሽከርካሪ ሾፌር ስህተት መሆኑ በማስረጃ የተረጋጠ እስከሆነ ድረስ በቁጥር 2084(1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ጉዳቱን የመጋራት ደንብ ተፈጻሚነት የማይኖረው በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው የክርክር ነጥብም ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል ከላይ ከተመለከተው አጠቃላይ የክርክሩ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው ፍሬ ነገርን በማጣራት እና ማስረጃን በመመዘን ረገድ በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት መሆኑን ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃ የመዘነበት አግባብ ደግሞ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 በአንቀጽ 10 እንደተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ መርምሮ በማረም የተገደበ በመሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ አግባብነት በዚህ ሰበር ችሎት ሊመረመር የሚችልበት ስርዓት የለም። በሕግ ረገድ ደግሞ ውሳኔው መሰረታዊ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 24449 በ26/07/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59437 በ23/12/2005 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል።
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 93772

የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፦ ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ሁሴን አመዶ - ጠበቃ ጌታቸው ቅጣው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.ኢትዩ ቴሌኮም - ነ/ፈጅ ዘለቀ ሰይፉ ቀረቡ

2 ድርባን ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግ/ማ...ጠበቃ ጋዲሳ ጉታ-ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኮንስትራክሽን ስራ በኮንትራክተር ሲሰራ ደረሰ ለተባለ የቴሌኮሚኒኬሽን ኬብል መበጠስ ጉዳት የጉዳት ካሳ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽነት፣ በአሁኑ አመልካች ተከሳሽነት እና ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብነት በምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና ይዘትም ባጭሩ የሚከተለው ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ በስር ተከሳሽ ላይ ባቀረበው ክስ ተከሳሹ የአመልካች ንብረት በሆነው የአለም አቀፍ ግንኙነት በተሸከመ የኦፕቲካል ፋይበር ኬብል ላይ በሕግ የተጣለበትን ግዴታ በመጣስ ህዳር 30 ቀን 2002 ዓ/ም የብር 123,710.7234፣ ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ደግሞ የብር 374,754.2334 ጉዳት የ2ኛ ተጠሪን ፋብሪካ አጥር ግንባታ ሲያከናውን አድርሷል በሚል በድምሩ ብር 498,465.10(አራት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አራት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከአስር ሳንቲም) ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም የሲሚንቶ ፋብሪካ አጥር ግንባታውን ያከናወኑት ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የግንባታ ውል መሆኑን፣ አሰሪ የሆነው 2ኛ ተጠሪ በሰጣቸው ንድፍ መሰረት ስራውን በማከናውን ላይ እያሉ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳት እንደደረሰና ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው ሲሰሩ ለደረሰው ጉዳት በሕግም ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን፣ ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ደረሰ ለተባለው ጉዳትም የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ሠራተኛ የሆኑት ከ23 ሜትር በኋላ ቆፍሩ ብለው ምልክት አድርገውላቸው 25.10 ሜትር ርቀት ላይ ሲቆፍሩ ጉዳቱ የደረሰ በመሆኑ ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ወድቅ እንዲሆን ከመከራከራቸው በተጨማሪ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ እንዲገባም ጥያቄ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ከተደረገ በኋላ በሰጠው መልስም ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም የሚል ሁኖ ለዚሁ መልሱ መሰረት ያደረጋቸው ምክንያቶችም ከአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው የግንባታ ውል ኃላፊነቱን ለ1ኛ ተጠሪ ማስተላለፉንና የግንባታ ፈቃድን ከሚመለከታቸው አካላት አግኝቶ ተገቢውን የፈፀመ መሆኑን የሚገልጹትን ነጥቦችን ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካችንና የአሁኑን 2ኛ ተጠሪ ለክሱ ኃላፊ አድርጎ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ብር 498,465.10(አራት መቶ ዘጠና ስንምት ሺህ አራት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከአስር ሳንቲም) ከመስከረም 10 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም ለክርክሩ የወጡትን ወጪና ኪሳራ በአንድነትና በነጠላ ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአሁኑ አመልካችየአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ለአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የሚከፈላቸውን የጉዳት ካሳ ገንዘብም ሆነ ወጭና ኪሳራ በሙሉ የአሁኑ አመልካች ለጣልቃ ገብ ሊሸፍኑ እንደሚገባ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የአሁኑ ተጠሪዎች በመልስ ሰጪነት ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በህዳር 30 ቀን 2002 ዓ/ም ከአመልካች ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ መሆናቸው በአግባቡ ነው በማለት ሙሉ በሙሉ ያጸናው ሲሆን የታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ጉዳትን በተመለከተ ግን የአሁኑ አመልካች ሰራተኛ ቁፋሮው ከመንገዱ ከሃያ ሶስት ሜትር ርቀት በኋላ መቆፈር እንደሚችል ለአሁኑ አመልካች እስከቦታው ሂዶ በገለጸው መሰረት ቁፋሮው ከመንገዱ ከሃያ አምስት ሜትር ርቀት በላይ ሲከናወን የደረሰ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ ለጉዳቱ መድረስ አስተዋፅኦ ነበረው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ በዚህ ቀን ደረሰ ከተባለው የብር 374,754.3734 ጉዳት ውስጥ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ለግማሹ ብር 187,377.19(አንድ መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከአስራ ዘጠኝ ሳንቲም) ኃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በሁለቱም ቀናት ደረሰ ለተባለው ጉዳት አመልካች ኃላፊነት የለብኝም በማለት በመቃወም ውሳኔውን ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ለደረሰው የንብረት ጉዳት ግማሽ ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ ለጉዳቱ መድረስ አስተዋጽኦ አደረገ የተባለው የ1ኛ ተጠሪ ሠራተኛው መሆኑን ተቀብሎ እያለ ሰራተኛው መስሪያ ቤቱን በመወከል በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ስራውን እንዲያከናውን ስምምነት መግለጽ የሚያስችል የስልጣን ውክልና የለውም ብሎ አመልካች በከፊል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ እንዲሁም አመልካችና 2ኛ ተጠሪ አደረጉ የተባሉት ስምምነት የተተረጎመበት አግባብም የግራ ቀኙን ውል፣እንዲሁም የኮንስትራክሽን መመሪያውን ይዘትና ተፈፃሚነትን ባገናዘበ መልኩ ያልተገናዘበ መሆኑን ዘርዝረው አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነትአለባቸው ተብሎ የወሰነው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው አመልካች በሁለቱም ቀናት በ1ኛ ተጠሪ ንብረት ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለደረሱት ጉዳቶች ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ጭብጥ ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ ሁኖ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የብር 498,465.10 የንብረት ጉዳት ካሳ ክስ ያቀረበው ጉዳቱ በተለያዩ ቀናት መድረሱንና በእያንዳንዱ ቀን የደረሰውን የጉዳት መጠን ለይቶ ክስ ያቀረበ ሲሆን የስር ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በእያንዳንዱ ቀን ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ የማይሆኑባቸውን ምክንያቶችን ጠቅሰው የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ተደርጎ ከአሁኑ አመልካች ጋር ባደረገው የግንባታ ውልም ሆነ ለጉዳዩ አግባብነት ካላው ሕግ አንጻር በ1ኛ ተጠሪ ንብረት ላይ ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ አመልካችንና 2ኛ ተጠሪን በሁለቱም ቀናት በአመልካች ንብረት ላይ ለደረሱት ጉዳቶች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ አድርጎ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ወስኖባቸዋል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ የስር ፍርድ ቤት በሃላፊነት ላይ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል አሻሽሎአል፡፡ ከዚህ ጋር አያይዞም የጉዳት ካሳ መጠኑን ቀንሶ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ለአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው የጉዳት ካሳ መጠን ብር 311,087.91 (ሶስት መቶ አስራ አንድ ሺህ ሰማንያ ሰባት ብር ከዘጠና አንድ ሳንቲም) ነው ሲል ወስኗል፡፡ ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ይዘት የሚያስገነዝበው አመልካች የሕዳር 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጉዳትን በ2ኛ ተጠሪ በተሠጣቸው ንድፍ መሰረት ስራውን ሲሰሩ ጉዳት ደርሷል ብለው ያቀርቡት ክርክር በማስረጃ ያለመደገፉን፣ ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ደረሰ ለተባለው ጉዳት ለአመልካች የስራ ትዕዛዝ አስተላለፉ የተባሉት ሰራተኛ ሕጋዊ ውክልና ሳይኖራቸው መሆኑ ተረጋግጦ የተወሰነ መሆኑን ነው፡፡ እንግዲህ ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ የተያዘው በሕጉ የተሰጣቸውን ስልጣን መሰረት በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና ፍሬ ነገሩን በማጣራት ስለመሆኑ የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡ በመሆኑም ይኼው የበታች ፍርድ ቤቶች የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ በዚህ ችሎት የሚለወጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው በመሆኑ ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን ድምዳሜ በመያዝ በበታች ፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ወይም አተገባበር ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው አመልካች የግንባታው ባለቤት የሆነው የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ከሚመለከተው የመንግስት አካል በወሰደው የኢንቨስትመንት ቦታ ላይ አጥር ለማጠር ቁፋሮ ሲያካሂድ የ1ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነው ፋይበር ኬብል መበጠሱን ነው፡፡ አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጥብቆ የሚከራከረው ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ደረሰ ለተባለ ጉዳት የ1ኛ ተጠሪ ኃላፊነት ነው፣ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የግንባታው ባለቤት ሁኖ በአዋጁ መሰረት ፈቃድ ባለማውጣቱ የደረሰ ጉዳት በመሆኑ አመልካች በውልም ሆነ በሕግ ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆኑበት አግባብ የለም በማለት ነው፡፡ እኛም እነዚህን በአመልካች የቀረቡትን ክርክሮች ሕጋዊ መሆን ያለመሆናቸውን ከቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌትሪክ ሐይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 464/1997 እና አግባብነት ካላቸው የፍትሐ ብሔር ህግ ድንጋጌዎች አንጻር መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 464/1997 በአንቀጽ 3(3) ሥር የፌዴራልና የክልል ከተማ አስተዳደር አካላት የግንባታ ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት የቴሌኮሙኒኬሽን ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኤሌትሪክ ሀይል አውታር ስለመኖሩ እና ፈቃድ ጠያቂው አካልም ግንባታ ከማካሄዱ በፊት በቴሌኮሙኒኬሽን ወይም በኤሌትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ተደንግጓል። ድንጋጌው በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌትሪክ ሀይል አውታሮች ላይ በግንባታ ወቅት ጉዳት እንዳይደርስ አስቀድሞ እንዲያረጋግጡ ግዴታ የጣለው በፈዴራልና በክልል አስተዳደር አካላት ብቻ ሳይሆን የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ላይ ጭምር ነው። 2ኛ ተጠሪውም በዚህ የህግ ድንጋጌ መሰረት በቴሌኮሙኒኬሽን አውታር ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የማድረግና በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት አስቀድሞ የማረጋገጥ ግዴታ በመወጣት ቦታውን ላይ ተገቢው ስራ እንዲሰራ ማድረግ ያለበት መሆኑን የድንጋጌው ይዘት ያስገነዝባል።

በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌትሪክ ሀይል አውታሮች ላይ እያወቀም ሆነ በቸልተኝነት ጉዳት ያደረሰ ሰው የሚቀጣ ስለመሆኑም ተደንግጓል ። ወደ ፍትሐብሄር ህጉ ስንመለስ አንድ ሰው በራሱ በኩል ምንም የገባው ግዴታ ሳይኖር በራሱ ጥፋት(አስቦ ወይም በቸልተኝነት) በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ኃላፊ እንደሆነ በቁጥር 2027(1) ከተደነገገው መገንዘብ ይቻላል። እንዲሁም በህግ በትክክል ተገልጾ የተመለከተውን ልዩ ድንጋጌ፣ ልዩ ደንብና ሥርዓት የጣሰ ሰው ደግሞ ጥፋተኛ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ህ/ቁ 2035(1) ተመልክቷል። በአዋጁም ሆነ በፍትሐብሔር ህጉ የተዘረጋው ስርዓት ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን አመልካች በዚህ ችሎት በሕግ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር ሶስት አበይት ምክንያቶችን መሰረት ያደረገ ነው። ይኸውም ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ደረሰ የተባለው ጉዳት በ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ስራው ሲከናወን ጉዳቱደርሷል፣ የሕዳር 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጉዳትም 2ኛ ተጠሪ የግንባታ ፈቃድ ባላወጣበት ሁኔታ የተከናወነ በመሆኑ ጉዳቱ ሙሉ በሙሉ የሚመለከተው 2ኛውን ተጠሪ ነው፣2ኛ ተጠሪ ግዴታውን በውሉ ለአመልካች ማስተላለፍ አይችልም የሚሉ ናቸው።

ይሁን እንጂ አመልካች ስለታህሳስ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጉዳት የሚያቀርቡት ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች ከአረጋገጡት ፍሬ ነገር ውጪ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ የለም። ምክንያቱም ለአመልካች የስራ ትዕዛዝ ሰጠ የተባለው የ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ በሕግ አግባብ ያከናወነው የሰራተኛ ግዴታ ስለመሆኑ ካለመረጋገጡም በላይ አመልካች ራሳቸው ሰራተኛው ሰጠ ካሉት ርቀት ውጪ ሂደው ቁፋሮውን ሊያከናውኑ የቻሉበት ሕጋዊ ምክንያትም በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልጽ ያሳያልና። በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው ሁኖ አግኝተናል። 1ኛ ተጠሪ በአሰሪነቱ ሰራተኛው በሰራው ጥፋት ለሚደርስ ጉዳት ተጠያቂነት የሚኖርበት ሰራተኛው ስራውን በሚሰራበት ጊዜ ጥፋት የሰራ የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2130 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል። አመልካች የ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ የሆኑት ግለሰብ የሥራ ተግባሩን ሲያከናውን ጥፋቱ የተፈፀመ መሆኑን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2131/1/ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2032/1/ መሰረት ሊያረጋግጥ የሚገባው መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 ድንጋጌ ይዘት የሚያስገነዝብ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ሰራተኛው የስራ ተግባሩን ሲያከናውን ያደረሰው ጥፋት የሌለ መሆኑን ማስረዳት እንደሚጠበቅበት የድንጋጌዎቹ ይዘት ያስገነዝባል። ከላይ እንደተገጸው የ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ የሆነው ግለሰብ ለአመልካች ሰጠ የተባለው የስራ መመሪያ ተገቢውን ስራ እንደደንቡ ለማከናወን ተብሎ ስራው ሲሰራ የደረሰ አለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል። በመሆኑም አመልካች የታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ጉዳት ኃላፊነቱ የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የግንባታ ውል ያላቸው መሆኑን ሳይክዱ በውሉ በግንባታው ጊዜ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነቱ የአመልካች ተብሎ ስምምነት መደረጉ በ2ኛው ተጠሪ ላይ አዋጅ ቁጥር 464/97 አንቀጽ 3(3) ድንጋጌ የጣለውን ግዴታ በግለሰቦች ስምምነት እንደመለወጥ የሚቆጥር ነው በማለት ተራክረዋል፡፡ ሆኖም አዋጅ ቁጥር 464/97 አንቀጽ 3(3) ተጠሪ የግንባታው ባለቤት በመሆኑ ምክንያት ግንባታውን ከማከናወኑ በፊት በቴሌኮሚኒኬሽን ወይም በኤሌትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት የሚያሳይ ቢሆንም ግንባታው የተከናወነው በሕግ አግባብ በተቋቋመ የአመልካችና የ2ኛ ተጠሪ ስምምነት መሰረት በአመልካች ስራ ተቋራጭነት ነው፡፡ አመልካች በስራ ተቋራጭነቱ ግንባታውን የሚያከናውን ከሆነ ደግሞ ጉዳቱ እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ/ም የተደረገው የግንባታ ውሉም በአንቀጽ 12.1.5. ሀ እና 12.1.6 ስር አመልካች ግንባታ ከማከናወኑ በፊት ከመብራት ኃይል ባለስልጣናትና ከ1ኛ ተጠሪ ፈቃድ መውጣት እንዳለበት ግራ ቀኙ መስማማታቸውን፣ በውሉ በግንባታው ጊዜ ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግም አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የተስማማ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ አመልካች ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሕዝብ መጠቀሚያ የሆነ ንብረት ኬብል እንደማይነካ፣ እንክብካቤ እንደሚደረግለት፣ ንብረቱ ያለባለቤቱ ፈቃድ በምንም ሁኔታ እንደማይነካ፣ በንብረቱ ላይ ምንም አይነት ጉዳት ቢደርስ ተጠያቂው ኮንትራክተሩ ስለመሆኑም ስምምነቱ ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም የቁፋሮ ስራ ሲካሄድ ኬብሉን ሊነካ ስለሚችል የ1ኛ ተጠሪን ፈቃድ አመልካች ማግኘት እንደለበት፣ ኬብሉ ላይ ጉዳት እንዳይደረስ ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነትም የአመልካቹ መሆኑንና ማንኛውም ጉዳት ከደረሰ ተጠያቂ ኮንትራክሩ ስለመሆኑም የግራ ቀኙ የግንባታ ውል ስምምነት ያስረዳል፡፡

አመልካች ይህን የግራ ቀኙን የሥምምነት ይዘት መኖሩንና በነዛ ሐሳቡና ፈቃዱ መፈረሙን ሳይክድ ስምምነቱ ሕገ ወጥ ነው በሚል ያቀረበው ክርክር የአዋጅ ቁጥር 464/97 አንቀጽ 3(3) ድንጋጌን ሙሉ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የግንባታው ባለቤት በቴሌኮሚኒኬሽን ወይም በኤሌትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት የሚያሳይ ከመሆኑ ውጪ ይኼው ግዴታ ግንባታውን ለሚያከውነው የሥራ ተቋራጭ በስምምነት እንዳይተላለፍ ግልፅ ክልከላ የሚያስቀምጥ አይደለም፡፡ የድንጋጌው መሰረታዊ አላማም የሕዝብ መጠቀሚያ የሆነ ንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደረስ ግንባታ ሲከናወን ሊወሰዱ የሚገባቸውን ቅድመ ጥንቃቄዎችንና ጥንቃቄውን ሊያደርጉ የሚገባቸው ወገኖች የትኞቹ እንደሆነ የሚያመላክትና ጥንቃቄ ባለመደረጉ በንብረቱ ላይ ለሚደረስ ጉዳት ደግሞ ካሳ ሊከፍል የሚችልበት አግባብ መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 464/97 የግንባታው ባለቤት ግንባታውን ለሚያከናውነው የስራ ተቋራጭ ግንባታው ሲከናወን በሕጉ የተጣሉበትን ፍትሓ ብሔራዊ ግዴታዎች ለስራ ተቋራጩ የሚያስተላልፍ ስምምነት አድርጎ ቢገኝ ሕጉ ስምምነቱን ጥበቃ የማያደርግበት ምክንያት የሌለ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1675፣ 1716 እና 1731 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር አጣምረን በማየት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ ግዴታውን ለአመልካች በስምምነት ማስተላለፉ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ጉዳቱ በ2ኛ ተጠሪ ወይም ሰራተኛ ወይም ወኪሉ ስለመድረሱም እንዲሁም አመልካች ጉዳቱን ለመከላከል በማይችልበት ሁኔታ የደረሰ መሆኑም በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ/ም በአደረጉት የግንባታ ውል የውሉ አካል በሆነው በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በወጣው መመሪያ (Standard Conditions of

https://t.me/ethiopianlegalbrief

Contract for Construction of Civil Work Project) አንቀጽ 22 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መሰረት አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ የማይሆኑበት ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ያደረጓቸው በሕጉ አግባብ ነው ከሚባል በስተቀር ውሳኔያቸው የሚነቀፍበትን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በምስራቅ ጎጃም አሰተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር1914 መስከረም 10 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 32796 ሰኔ 03 ቀን 2005 ዓ/ም ተሻሽሎ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ለጉዳቱ ኃላፊ አድርገው በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95751
መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
ሱልጣን አባተማም
መኮንን ገ/ህይወት
ሙስጠፋ አህመድ
ተሽሊት ይመስል

አመልካች፡- ወ/ሮ እመቤት መኮንን - ቀረቡ፡፡
ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ መሰረት አስናቀ
2. ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ ሲሆኑ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ ከሳሽ በቀረቡት ክስ ባለቤቱ ሟች ወንደሰን ከፍያለው በተከሳሽ መኪና የታርጋ ቁጥሩ 323459 በሆነው ላይ በአሽከርካሪነት ተቀጥሮ በወር 1000 እየተከፈለው ሲሰራ በደረሰው የመኪና አደጋ ህይወቱ አልፏል በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 110/1/ ለከሳሽ እና የሟች ልጅ ለሆነው (ዳግም ወንድወሰን) ጭምር በድርጅታችን 60,000 (ስልሳ ሺ) ይከፈለኝ በተጨማሪም የጠበቃ አበል 10% እና ውጪ ኪሣራ ይከፈለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በሰጡት መልስ ተጠቃሹ መኪና የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው መሆኑን በመግለፅ ግሎባል ኢንሹራንስ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በጠየቁት መሠረት ይኸው አካል ወደ ክርክሩ በመግባት እስከ 60,000 ብር ድረስ ሽፋን መስጠቱን በመጥቀስ ከውላቸው ውጭ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡
ጉዳዩን ያየው የወረዳው ፍ/ቤት ግሎባል ኢንሹራንስ በሰጠው ሽፋን ልክ ይክፈል፡፡ በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያት ለደረሰው ወጪና ኪሣራ እና የጠበቃ አበል ይክፈል በማለት ወሰነ፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ለደረሰው ጉዳት ይከፈል የተባለውን 60,000 በማጽናት የጠበቃ አበል፣ የወጪና ክሣራ አስመልክቶ ሊከፍል አይገባም በማለት አሻሽሎ አፀና በመጨረሻም 1ኛ ተጠሪ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ቅሬታዋን በማቅረብ የሰበር ሰሚውም ሽፋን ከተሰጠው በላይ የአሁን 2ኛ ተጠሪ /ግሎባል/ ሊከፍል አይገባም ከሽፋኑ በላይ የሆነውን የአሁን አመልካች ተተክተው ሊከፍሉ ይገባል ሲል አሻሽሎ አፅንቷል፡፡
የአመልካች የሰበር አቤቱታም ይህንኑ የሰበር ውሣኔ ለማሳረም ነው፡፡
አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ 2ኛ ተጠሪ (ግሎባል ኢንሹራንስ) ለደረሰ ጉዳት ተተክቶ ሊከፍልእና በውላችን መሠረት ግዴታውን ለመወጣት ተስማምቷል (ውል ገብቷል) ይሁን እንጂ 2ኛ ተጠሪ በፍርድ ካልተገደደ በማለት በወቅቱ ግዴታውን ባለመወጣቱ ለቀረበዉ ክስ ሽፋንከሰጠው በላይ ልገደድ አይገባውም ተብሎ አመልካች የወጪ ኪሣራና የጠበቃ አበል ትክፈል ተብሎ መወሰኑ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ጠይቀዋል፡፡
በመሆኑም የግራ ቀኙ ለአመልካች አቤቱታ መልስ በፅሑፍ በማቅረብ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚሁ መሠረት 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች ከሰጠው ሽፋን በላይ የወጪ ኪሣራ እና የጠበቃ አበል ሊከፍል አይገባም ተብሎ አመልካች እንዲከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት በጭብጥነት ተይዞ ቀርቧል፡፡

ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካለው ህግ አኳያ መርምረናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል፡፡ እንግዲህ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የሥር ከሳሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሆኑት በባለቤታቸው ላይ በደረሰው የሞት አደጋ ምክንያት የአዋጅ 377/96 አንቀጽ 110(2) ሀ,ለ መሠረት 60,000 ብር እንድከፍላቸው በአሁኑ አመልካች ላይ ክስ በማቅረባቸው ምክንያት የአሁን 2ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 43 መሠረት ወደ ክርክሩ እንድገባ ተደርጐ ለደንበኛው በሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን መሠረት 60,000 ብር እና የጠበቃ አበል 10% እና የወጪ ኪሣራ 1000 ብር እንዲከፍል በመወሰኑና በየደረጃው ባሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች እያዩት የክልሉ ሰበር ሰሚ ደረሶ ግሎባል ኢንሹራንስ ከሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን በላይ የጠበቃ እና የወጪ ኪሣራ ልከፍል አይገባም የአሁን አመልካች ኢንሹራንስ ከከፈለው በላይ ያለውን 8000 ብር ይክፈሉ በመባሉ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር አመልካች ሊከፍሉ ይገባል ሲል የሠጠው የአሁን 2ኛ ተጠሪ (ግሎባል ኢንሹራንስ የንግድ ህጉን አንቀጽ 665(2) መሠረት ግዴታው ከውላችን ላይ ካለው የሽፋን መጠን ልበልጥ አይገባውም የሚለውን ክርክር በመቀበል መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ እንግዲህ የግራ ቀኙ መብትና ግዴታ የሚመነጨው በመሀከላቸው ከተቋቋመው ውል መሆኑ ይህ ችሎትም የሚቀበለው ጉዳይ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ደንበኛ (ግሎባል ኢንሹራንስ) በአመልካች መኪና በደረሰው የሞት አደጋ በወቅቱ አግባብነት ያለውን ክፍያ ባለመፈፀሙ ምክንያት የአሁን 1ኛ ተጠሪ የመኪናውን ባለቤት የሆኑትን አመልካች ለመክሰስ ተገደዋል፡፡ ስለሆነም ለተለያዩ (ላልታሰበ) ወጪ መዳረጋቸው ያልተካደና የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በመሆኑም ግሎባል ኢንሹራንስ ምንም እንኳ የሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን የተገለፀ ቢሆንም ከውል የመነጨውን ግዴታውን በወቅቱ ባለመወጣቱ ለተከሰተው ተጨማሪ ወጪ የአሁን አመልካች የሚቀጡበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የሞት ካሣውን የገንዘብ መጠን 60,000 ብር ላይ የጠበቃ እና የወጪ ኪሣራውን ግሎባል ኢንሹራንስ ሊከፍል የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ባጠቃላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ውሳኔዎችን በማሻሻል ከ60,000 ብር በላይ የተጠየቀውን ተጨማሪ ወጪ አመልካች ሊከፍሉ ይገባል ማለቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ.63103 በቀን 27/3/05 የልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.15437 በ29/08/05 እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 164154 በቀን 23/03/2006 የሰጡት ውሣኔዎች ተሻሽሎ ፀንቷል፡፡
2. የጠበቃ አበል እና የወጪ ኪሣራን ግሎባል ኢንሹራንስ /8000/ብር ለ 1ኛ ተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡

የሰበሩን ክርክር አስመልክቶ ግራ ቀኙ የወጪ ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97683

መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተሽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አክበር አሊ ካምሩዲን ኩባንያ

ተጠሪዎች ፡- 1) የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ

2) የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የቀጠና 4 ጽ/ቤት

3) በመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የአ/አ ቅ/ጽ ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ የቤት ቁ.868 እና 872 ሁከት በመፍጠር በመያዝ 2ኛ ተጠሪ በቤት ውስጥ የነበሩትን ልዩ ልዩ ዕቃዎች እና ሰነዶች በ3ኛ ተጠሪ መጋዘን የተቀመጠ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ዕቃውን እንዲመልስ ቢጠየቅ ለመመለስ ፍቃደኛ አልሆነም በተጨማሪም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የአመልካችን ቤት ለተለያዩ ግለሰቦች እያከራዩ ብር 149,294,00 (አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ዘጠና አራት ብር) ተጠቅመውበታል፡፡ አመልካች ቤቱን ስረከብ 5000 ብር ወጪ አድርጌያለሁ ፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ቤቱን አከራይተው ለለአግባብ የበለጸጉበትን እና ቤቱን ለማሳደስ ያወጣሁትን ወጪ በድምሩ 154,294,00 (አንድ መቶ ሀምሳ አራት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና አራት ብር) የስር 4ኛ፣5ኛ ፣6ኛ ተከሳሾች ጭምር የአሁን ተጠሪዎች የአመልካችን ንብረት ይመልሱ ፣ካልሆነ ግምቱን ብር 124,786.(አንድ መቶ ሀያ አራት ሺ ሰባት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር) እንዲከፍሉኝ ባጠቃላይ ተጠሪዎች 279,080.00(ሁለት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ሰማንያ ብር) ከእነወለዱ እንዲከፍሉ፣ወጪና ኪሳራ እንዲተኩ ተብሎ ይወሰንልኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በማየት የስር 4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች ክሱ በማሰናበት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ያሉት ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካች ተጠሪዎች ያለአግባብ የበለጸጉበትን ኪራይ ገንዘብ ይከፈለኝ በማለት መጠየቅ አይችሉም መጠየቅ ቢችሉም በመንግስት እጅ የቆየን ንብረት የሚጠየቅ ጉዳትም ሆነ ኪራይ የለም ተጠሪ ንብረት ተረክቧል ቢባል እንኳ ንብረቶቹ ያልተመዘገቡና እርጅና ያልተቀነሰ እንዲሆን ቁሳቁሶቹን በመጋዘን ለማስቀመጥ የፈጀው ጊዜ ከቀረበው ዋጋ በላይ ነው ሌላው አመልካች 5000 ብር ወጪ አደረግኩ የሚሉት ቤቱን ለማበላሸታችን ባለ ማስረዳታቸው ጥያቄው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባጠቃላይ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል ። ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ግራቀኙን በማከራከር አመልካች ያቀረቡትን የታጣ ገቢና የኪራይ ጥቅም አስመልክቶ በአዋጅ ቁ.192/92 በአንቀጽ 3 ላይ በመንግስት እጅ በቆየበት ጊዜ ለታጣ ጥቅም(ገቢ) ማናቸውም የጉዳት ካሳ መጠየቅ እንደማይቻል የሚደነግግ በመሆኑ የተጠየቀው የቤት ኪራይ ይከፈለኝ በማለት አመልካች የጠየቁትን ዳኝነት ውድቅ በማድረግ የንብረትን ጥያቄ በተመለከተ ተጠሪ እርጅናቸው አልተቀነሰም በማለት ተከራክረዋል። ይህ ደግሞ የአመልካችን የንብረት መጠየቅ መብት አያስቀረውም።ሌላው አመልካች ቤቱን ቀለም ለማስቀባት አወጣሁት የሚሉት 5000 ብር ተጠሪዎ በቤቱ ላይ ጉዳት ያድርሱ ወይም በራሱ ጊዜ ቀለም የፈለገ ስለመሆኑ የሚያሳይ አይደለም በማለት አልፎታል።

በአጠቃላይ ንብረትን በተመለከተ በተጠሪ ተዘርዝረው የቀረቡትን የንብረት በአይነቶች እነዲያስረክቡ ካልሆነ ግምቱን 124,786.000(አንድ መቶ ሀያ አራት ሺ ሰባት መቶ ሰማኒያ ስድስት ብር) ከነወለዱ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ይክፈል በማለት ወስኗል። በቀጣይነት ጉዳዩን ያየው ከፍተኛው ፍርድ ቤትም መዝገቡን በመመርመር ክርክር የተነሳበት ቤት በተመለከተ የተወረሰ አይደለም ከህግ ውጭ ተይዟል በሚል ምክንያት ሁከት ይወገድ ተብሎ አመልካች ቤታቸውን የተረከቡ መሆኑን የበፊት መዝገብ ያመላክታል ይህ ከሆነ ደግሞ የአዋጅ ቁጥር 193/92 አንቀጽ 7/3 ከአዋጅ ውጭ በመንግስት እጅ የቆየ ንብረት ለታጣ ገቢ ወይም ለደረሰ ጉዳት ካሳ ክፍያ መጠየቅ አይችልም ስለሚል በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም ። ንብረትን አስመልክቶ ግምቱን ወይም በአይነት ያስረክቡ የሚለው የውሳኔ ክፍልም ስህተት የለበትም በማለት ባጠቃላይ አጽንቶታል።

የአመልካች አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልጹ፡- የአመልካች ጥያቄ ተጠሪዎች ቤቱን ሁከት በመፍጠር ይዘው አከራይተው የተቀበሉትን ገንዘብ ሊከፍሉኝ ይገባል የሚል ሆኖ ሳለ ለአዋጅ ቁጥር 193/92 የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ሊከፈልህ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ሊታረም የሚገባው ነው። ተጠቃሹ አዋጅ ቁ.193/92 የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ለሚያስተናግደው ክርክር የወጣን ወጪን እንጂ በፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት ውሳኔያገኘ አይነት ባለመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በአጠቃላይ መንግስት (ተጠሪ) ማከራየታቸውን ባልካዱበት የሰበሰቡትን ገንዘብ ሊመልሱ አይገባም መባሉና ብር 5000 ጥያቄ ውድቅ መደረጉም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት አመልክቷል።

በዚህም መሰረት ችሎቱም የአዋጅ ቁጥር 193/92 ተጠቅሶ ተጠሪ የአመልካችን ቤት ሁከት በመፍጠር ይዞ አከራይቶ እየተጠቀመበት ሊመልሱ አይገባም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙን በጹሁፍ በማከራከር መልስ እና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክሯል።

ተጠሪዎች በሰበር መልሱ የሚሉት በአዋጅ 47/67 የተወረሰ ቤት አይደለም ሁከት ፈጥራችው የያዛችሁት ነው ተብሎ ተወስኖ የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ስለዚህ መንግስት በእጁ ይዞ ሲያስተዳድር በነበረበት ጊዜ አመልካች ያጣውን ገቢ ወይም ጥቅም በአዋጁ ቁጥር 193/92 አንቀጽ 3 መሰረት ሊጠይቅ አይችልም ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም ሌላው በስር ፍርድ ቤት ሁከት ፈጥሮ መያዝና ወርሶ መያዝ አንድ ናቸው አላለም ስለዚህ በዚህ ረገድ የተነሳው ክርክር ተቀባይነት የለውም። ባጠቃላይ ተጠቃሹ አዋጅ በአግባቡ የተተረጎመ በመሆኑ የአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄዬ አግባብነት የለውም፡፡ ሌላው አመልካች ለእድሳት አወጣሁ የሚሉት 5000 ብር(አምስት ሺ) ብር ውድቅ መደረጉ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የስር ውሳኔ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊጸና የሚገባው ነው በማለት ተከራክረዋል አመልካች በበኩሉ የስር ክርክሩን በማጠናከር ተጠሪዎች ለ 11 አመታት ቤቶቹን አከራይተው የተጠቀሙበትን እና ያሳደስኩበትን ወጪ ነው የጠየቅኩት እንጂ የጉዳት ካሳ ከገንዘባቸው ክፈሉኝ የሚል ክስ የቀረበበት ሁኔታ የለም ስለዚህ ጉዳይ በማይመለከተው አዋጅ ቁ.193/92 ተጠቅሶ ገንዘብህን ሊከፈልህ አይገባም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡
በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል፡፡ እኛም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል ፡፡
በመሆኑም ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የክርክሩን አመጣጥ አንዳየነው የአመልካች ጥያቄ የነበረው ተጠሪዎች ሁከት ፈጥረው የያዙትን ቤት ለቀው ሁከት ይወገድ በመባሉ ለቀዋልና ያለአግባብ ይዘው በነበሩበት ወቅት ለግለሰቦች ቤቱን በማከራየት የሰበሰቡትን ገንዘብ ይመልሱልኝ በውስጡ የነበረውን ንብረት እና ያሳደስኩበትን ይተኩልኝ የሚል መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት የሚቻል ነው፡፡
እንግዲህ በተያዘው ጉዳይ ያከራከረው ተጠሪ አዋጅቁጥር 193/92 ጠቅሶ በመንግስት የቆየን ንብረት ጥቅም ወይም ጉዳት መጠየቅ ስለማይቻል ልንጠየቅ አይገባም በማለቱ እና የስር ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪን መከራከሪያ በመቀበል በተጠቃሹ አዋጅ መሰረት አመልካች መጠየቅ አይገባውም በማለት በመወሰናቸው እና የእድሳት ገንዘቡን ውድቅ በማድረጋቸው ነው፤ይህ ችሎትም አመልካች በተጠቀሰው አዋጅ መሰረት በኪራይ ተጠሪዎች የሰበሰቡትን ገንዘብ ሊመልሱ ይገባል? ወይስ በተጠቃሹ አዋጅ መሰረት መከፈል የለበትም? የሚለው ነጥብ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ሆኖ አግኝቷል፡፡ በመሆኑምከስር ክርክር እንደተገነዘብነው ተጠሪ ያልተወረሰ ቤት በመያዙ ምክንያት በፍርድ ሀይል ሁከት መፍጠሩ ተረጋግጦ ቤቱን መልቀቁ የተረጋገጠና በግራቀኙ ያልተካደ ነው በተጨማሪም ተጠሪም ተጠቃሹን ቤት አላከራየሁም በማለት የተከራከረው ነገር የለም በስር ፍርድ ቤቶች የፍርድ ሀተታም ቢሆን ቤቱ አልተከራየም በሚል የተጠቀሰ ነገር የለም ፡፡ በመሆኑም መከራየቱ ያላከራከረ ፍሬ ነገር በመሆኑ በዚህ ረገድ ተጠሪም የዚህ ችሎት መከራከሪያው አላደረገም ፡፡ ይልቁንም የተጠየቀውን ገንዘብ ልንከፍል አንገደድም የሚል መሆኑን አጉልቶ የሚከራከረው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከተጠቃሹ አዋጅ ቁ.193/92 ድንጋጌ በመንግስት እጅ በቆዩ ንብረት ለታጣ ገቢ ወይም ለደረሰ ማንኛውም ጉዳት ካሳ ክፍያ መጠየቅ አይቻልም የሚል ነው፡፡ እንግዲህ ከፍ ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው ቤቱ በተጠሪ በመያዙ ብቻ ሊያገኙ የነበሩትን ጥቅም በማጣታቸው የደረሰባቸውን ካሳ ከምንም ተነስቶ ተጠሪ እንዲከፈላቸው ሳይሆን በህገወጥ መንገድ ቤቱን ይዞ በእውነቱ ሲያከራየው የነበረውን እና ቤታቸው የፈጠረላቸውን የራሳቸውን ገንዘብ እንጂ ቤቱ ተወርሶ ተይዞ በመቆየቱ በካሳ መልክ ከመንግስት የሚከፈላቸው ማካካሻ አይደለም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ያልተወረሰ ቤት በህገወጥ መንገድ በመያዝ የበለጸገበትንና አላከራየሁም በሚል ያላስተባበለውን የኪራይ ገንዘብ ለመክፈል አልገደድም ማለቱ እና ፍርድ ቤቶቹም ተጠሪዎች ያቀረቡትን መቀበላቸው የአዋጁን አላማ እና ሊያሳካ የፈለገውን ግብ ያገናዘበ አይደለም አዋጅ ቁጥር 193/92 ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ ሊሆን የማችልበት ምክንያት የለም ፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ቤቱን ይዘው ለሰበሰቡት ኪራይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ኃላፊ ሊሆኑ ይገባል ብለናል ፡፡ ይህን ካልን በስር ፍርድቤት ተጠሪዎች በምን ያህል እንዳከራዩ፤ቤቱ ለስንት አመታት እንደተከራዬ ጭብጥ ተይዞና በማስረጃ ተለይቶ ክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያልተደረገበት በመሆኑ በዚህ ዙሪያ ያሉት ነጥቦች ተጣርተው ሊወሰኑ የሚገባቸው በመሆኑ ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት መመለሱ ስነ ስርዓታዊ ሁኖ አግኝተናል ።

ሌላው የአመልካች ቅሬታ ቤቱ የታደሰበትን 5000 ብር አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ሲሉ የሰጡትን ውሳኔ ተገቢ አይደለም ብለው አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩን አጣርተውና ማስረጃውን መዝነው ውድቅ ያደረጉት ስለሆነ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ስልጣን አንፃር የሚታይ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም።

በአጠቃላይ የፌዴራል የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 193/92 መሰረት በማድረግ በመንግስት እጅ ለቀዩ ንብረት ተጠሪዎች የሰበሰቡትን ኪራይ ሊከፍሉ አይገባም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል ። በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥተዋል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 175802 በቀን 04/08/2004 ዓ/ም እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት በ125972 በቀን 25/03/2006 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።
   - አመልካች ያቀረቡት የ 5000 ብር የእድሣት ክፍያ እና ንብረትን አስመልክቶ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል።
2. ተጠሪዎች ከአከራካሪው ቤት ላይ የሰበሰቡትን የኪራይ ገንዘብ የመመለስ ሀላፊነት አለባቸው ብለናል ። በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አከራካሪው ቤት በምን ያህል የኪራይ ገንዘብ ሲከራይ እንደነበር ፤ እና ከመቼ ጀምሮ ሲከራይ እንደነበር በጭብጥነት ይዞ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን በመስማትና እና አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነም ፍርድቤቱ በራሱ አነሳሽነት በሚያስቀርባቸው ማስረጃዎች አጣርቶ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እነዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል ። ይፃፍ።
3. የግራቀኙ የወጪኪሳራቸውን ይቻቻሉ ብለናል። መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል።

ት/ቤ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባንክና ኢንሹራንስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ 96309

መስከረም 27 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡- ዳሽን ባንክ አ/ማ - ነ/ፈጅ ሠለሞን አያኖ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አበባየሁ ግርማ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታቸው የቀረበው የፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 189176 የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ በኮ/መ/ቁ/132422 ህዳር 23 ቀን 2006 ዓ.ም ማዕናቱን በመቃወም ነው፡፡ ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

በሥር ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በባንኩ ደንበኛ ሆነው በማጠራቀሚያ ሂሳብ ቁጥር 50100055 02016 ገንዘብ በባንኩ ተቀማጭ አድርገው የቁጠባ ሂሳቡን በኤ.ቲ.ኤም ካርድ ሲያንቀሳቅሱ ከቆዩ በኃላ የኤቲ.ኤም ካርዱ ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም የጠፋ በመሆኑ ለባንኩ ጥር 25/2003 ዓ.ም በፅሑፍ ያሳወቁ ቢሆንም ባንኩ ሂሳቡን መዝጋት እያለበት ባለመዝጋቱ ሪፖርት ከተደረገበት ከ25/5/2003 ዓ.ም እስከ 09/6/2003 ዓ.ም ድረስ ለማይታወቁ 3ኛ ወገኖች 40,300.00 (አርባ ሺህ ሶስት መቶ) ወጪ ሆኖ የተከፈለ በመሆኑ ይህን ገንዘብ ከነወለዱ ወጪና ኪሣራ ጋር ይከፈለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ በሠጠው መልስ ካርዱ የጠፋ መሆኑን ማሳወቃቸውን ሳይካድ ነገር ግን የጠፋ መሆኑን ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን በባንኩ አሠራር መሠረት ሂሳቡ እንዲዘጋ የመጠየቅ ግዴታ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ግራ ቀኙ በገቡት ውል መሠረት የሚስጥር ቁጥሩን ለሌላ ወገን እንዳያሳውቁ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑና የሚስጥር ቁጥሩ ካልታወቀ ደግሞ ገንዘቡ ወጭ ሊሆን የማይቻል በመሆኑ እንዲሁም የሂሳብ ይዘጋልኝ ጥያቄ ባልቀረበበት ሁኔታ ተከሳሽ ሂሳብ ሊዘጋ የማይችል በመሆኑ ላቀረበው ክስ ኃላፊነት እንደሌለበት በመግለፅ መልስ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ በቅድሚያ የተመለከተው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ከሳሽ እና ተከሳሽ በገቡት የካርድ ክፍያ አገልግሎት ውል አንቀፅ 2(2) መሠረት ካርዱ መጥፋቱን በጽሁፍ ከማሳወቁ በፊት ለተደረገ ማንኛውም የክፍያ ትዕዛዝ ባለካርዱ ኃላፊነት እንዳለበት የሚያመለክት በመሆኑና የዚህ የውል ክፍል ተቃርኖ ትርጉም ባለካርዱ በፅሑፍ ካሳወቀ በኃላ በተደረገ የክፍያ ትዕዛዝ ባንኩ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ፤ የውሉ ድንጋጌዎች የመብት እና ግዴታ ዝርዝር ውስጥ ኃላፊነት ለመውሰድ ባለካርዱ ሂሳብ እንዲዘጋለት ማመልከት እንዳለበት ያልተካተተ በመሆኑ ከሳሽ ካርዱ መጥፋቱን ለባንኩ ባሳወቀበት እለት ባንኩ ባዘጋጀው ፎርም ላይ የሚስጥር ቁጥሩን መፃፉ የታመነ በመሆኑ የካርዱን የሚስጥር ቁጥር የተከሳሽ ሰራተኞች በቀላሉ የማያውቁበት ምክንያት ባለመኖሩ የተከሣሽ መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም ስለሆነም የክሱን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል በማለት ተወስኗል፡፡

የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ እና ተጨማሪ የሙያ ምስክሮችን ከሰማ በኃላ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ታህሳስ 23 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ ክርክር የሰበር ቅሬታቸውን አቅርበዋል ቅሬታቸው ተመርምሮ ክርክር ያስነሳውን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑን አግባብ ለማጣራት ሲባል ለሠበር እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ በቅሬታው ላይ መልስ ሰጥተዋል ተጠሪ ጥር 27/2006 ዓ.ም የሰጡት መልስ የስር ክርክራቸውን የሚያጠናክር እና የሰበር ቅሬታው ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲጸና የሚጠይቅ ነው፡፡ አመልካችም የካቲት 21/2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከላይ በአጭሩ ለመግለፅ የሞከርነው የነገሩን አመጣጥ ሲሆን የሥር ፍ/ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ የተፈፀመው የህግ ስህተት ቢኖር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ካርዱ የጠፋ መሆኑን በፅሑፍ ለአመልካቾቹ ማሳወቁ፤ክርክር ያስነሳው ክፍያ የተፈፀመው ካርዱን መጥፋቱን ካሳወቀ በኃላ መሆኑ ግራቀኙ ባደረጉት ውል ካርዱ ከጠፋ በኃላ ለሚደረግ ክፍያ ባንኩ ኃላፊነት ይኖርበት ዘንድ ደንበኛው (ተጠሪ) ሂሳቡ በሙሉ እንዲዘጋለት የመጠየቅ ግዴታ እንደሌለበት፤ ተጠሪ ካርዱ መጥፋቱን በፅሑፍ ባሳወቀ ጊዜ በፎርሙ ላይ የሚስጢር ቁጥሩን መጻፉ ሁሉ ግራ ቀኙ የሚካካዱበት አይደለም፡፡

ከዚህም ሌላ ፍሬ ነገር ለማጣራትና ማስረጃ ለመመዘን ስልጣኑ የተሰጠው የስር ፍ/ቤት የሙያ ምስክሮችን በመስማት ተጠሪ በስህተት እንኳ የሚስጢር ቁጥሩን በፎርሙ ላይ ጽፎ ቢገኝ ይህ ቁጥር የተመዘገበበት ፎርም መቀመጥ እንደሌለበት ሙያዊ ምስክርነት እንዲሠጡ አረጋግጧል፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የሂሳብ ይዘጋልኝ ጥያቄ ባልቀረበበት ሁኔታ የተጠሪ ሂሳብ ሊዘጋ የማይችል መሆኑን እና ተጠሪ የሚስጥር ቁጥሩን በመግለፅ ግዴታውን መጣሱን በማንሳት ነው፡፡ነገር ግን ካርዱ መጥፋቱን ካሳወቀ በኋላ የሂሳብ ይዘጋልኝ ጥያቄ አልቀረበም በሚል ከኃላፊነት መዳን ስለመቻሉ በግራ ቀኙ ውል ካለመመልከቱም በላይ ተጠሪ በባንኩ ፎርም ላይ የሚስጥር ቁጥሩን ከሞላ በኋላ ሚስጥርነቱ ስለሚቀር ተገቢ ያልሆነ ተግባር እንዳይፈፀምበት በባንኩ በኩል ስለተደረገው ጥንቃቄ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡

ከባንኩ የሚጠበቀው በተለመደው የባንክ ሥራ አካሄድ ጥንቃቄ ማድረጉን እና ጥፋት አለመሰራቱን ማሳየት ነው፡፡ይህን ሳያሳይ ደንበኛው የሂሳብ ይዘጋልኝ ጥያቄ አላቀረበም በሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከኃላፊነት የሚድንበት የህግም ሆነ የውል አግባብ ባለመኖሩ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 189176 የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 132422 ህዳር 13/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ
3. የተጀመረው አፈፃፀም እንዲታገድ በዚህ ፍ/ቤት ታህሳስ 28/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 75560
ሐምሌ 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ነጋ ዱፊሳ
አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማሪያም - ጠበቃ ዮሴፍ አእምሮ ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ገብረ ስላሴ ሃይሌ- ወኪል ወርቅነሽ መንግስቱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልነት ማስረጃን መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ መነሻ ነው፡፡አመልካች የመቃወም አቤቱታ ሊያቀርቡ የቻሉት የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የሚች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ባል ነኝ በማለት በሐሰት የወሰዱት ማስረጃ ያላግባብ ነው በማለት የተወሰደው ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረና የምስክሮች ቃል ከሰማ በኋላ በተጠሪና በሚች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ መካከል ጋብቻ ስለመፈፀሙ በትዳር ሁኔታ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የአመልካችን አቤቱታ ባለመቀበል ቀድሞ ተጠሪ የሚች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ናቸው በማለት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 360(2) መሰረት በማጽናት ወስኗል፡፡ከዚህም በኋላ አመልካች የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ጉዳዩን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የባልነት ጉዳይ አከራካሪ በሆነበት ሁኔታ ጉዳዩ በበታች ፍርድ ቤቶች የታየው ያለስልጣናቸው መሆኑንና የተጠሪ የባልነት ማስረጃ ከመጀመሪያውም የተሰጠው ተገቢ ያልሆነ አቤቱታ ቀርቦና በሕግ አግባብ መቅረብ ያለበት ማስረጃ ሳይቀርብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ለማየት ስልጣን ያላቸው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን አላቸው? ወይስ የላቸውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥረ ነገር ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና 408/1996 ስር ተመልክቷል፡፡በዚህም መሰረት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና አዋጅ ቁጥር 408/1996 ከተሰጧቸው ስልጣኖች መካከል የወራሽነት ምስክር ወረቀት መስጠት፣የባልና ሚስትነት፣የሞግዚትነት ማስረጃ መስጠት ይገኙበታል፡፡በዚህ ረገድ የተሻሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀጽ 2 በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሸ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሰርዞ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የወራሽነት፣የባልና ሚስትነት እና የሞግዚትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ ላይ የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው መሆኑ ተደንግጓል፡፡የድንጋጌው የእንግሊዝኛው ቅጂም "application for certification of succession,marriage and guardianship."በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ከእነዚህ የድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች ስለጋብቻ በሚሰጡት ማስረጃ ላይ በሚቀርብ ክርክር የሚኖራቸው የዳኝነት ሥልጣን አድማሱ እስከምን ድረስ መሄድ አለበት? የሚለው ጥያቄ የሚነሳ መሆኑን ነው፡፡በሌላ አገላለጽ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የባልና ሚስትነት ማስረጃ ለመስጠት ነው ተብሎ የተቀመጠው የሕጉ አገላለፅ ፍርድ ቤቶቹ የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ ከሰጡ በኃላ በማስረጃው ተቃውሞ ቢቀርብ እና የተቃውሞው መሰረት የሚሆኑት ምክንያቶች የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃው የተሰጠው በቤተሰብ ሕጉ ስለጋብቻ መኖር ያለመኖር ሊቀርቡ የሚገባቸው የማስረጃ አይነቶች ሳይቀርቡ ነው፣ጋብቻ ሳይኖር ነው፣የቀረበው አቤቱታ ከሕጉ ስርዓት ውጪ ነው፤ሕጉን በሚጻረር መልኩ ነው የሚል ከሆነ ማስረጃዎች በማስረጃነቱ ከመስጠት ባለፈ በተጠቀሱት ነጥቦች ክርክር እንዲካሄድ በማድረግ ዳኝነት ሊሰጡ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚል ነው፡፡ይህንኑ ጥያቄ ለመመለስ የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ ምንነት፣ማስረጃው የሚሰጥበትን ሁኔታ፣የማስረጃውን ይዘት፣አቤቱታው የሚስተናገድበትን ሥርዓት መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

የጋብቻ ምስክር ወረቀት ስለሚሰጥበት ሁኔታና ስለይዘቱ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግአዋጅ ቁጥር 213/1992 ይደነግጋል፡፡ ይሄው ህግ ለጋብቻ መኖር መቅረብ ያለባቸውን የማስረጃ አይነቶች ቅደም ተከተል እንዲሁም በማስረጃው ሊረጋገጡ ስለሚገባቸውሁኔታዎች አስፍሮ እናገኛለን፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ፍርድ ቤቱ በሕጉ በተመለከተው አግባብ መረጋገጡን በቂ ነው ብሎ የገመተውን ያህል ማስረጃ ተቀብሎና መዝኖ ጋብቻ መኖር ያለመኖሩን የሚያረጋገጥ መሆኑን፣ጋብቻው አለ ወይም የለም ተብሎ ሊሰጥ የሚችለውም በሕግ የተቀመጠውን መመዘኛ በማሟላታቸው በመለየት ስለሆነ ይህንኑ የሚገልፅ ወይም የሚያሳይ ምክንያት በመስጠት ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ነው፡፡በአንፃሩ የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ መስጠት ግን ከላይ የተመለከቱት ሕጋዊ ክርክሮች በሌሉበት ሁኔታ የሚሰጥ ማስረጃ እንጂ ጋብቻ ስለመኖሩ ያለመኖሩ ክርክር ተደርጎ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ በሕጉ አይን ተመዝኖ የሚሰጥ አይደለም፡፡ፍርድ ቤቱ ጥያቄው ሲቀርብ የሚሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስለውሳኔ የተቀመጠውን ትርጉም የሚያሟላ ነው ሊባል የሚችል ሳይሆን የባልነት ወይም የሚስትነት የምስክር ወረቀቱን ስለሕጋዊ ማስረጃነቱ የሚያረጋገጥበት ነው፡፡ ይህን አይነት ውሳኔ ለመስጠት ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ስነ ሥርዓት ሲታይም ተከራካሪ ወገን የሌለበት፣አቤቱታ አቅራቢው ብቻ በማስረጃ በተደገፈ አቤቱታ መሰረት ይገባኛል የሚለውን መብት ወይም ጥቅም ትክክለኛነቱን፣ሕጋዊነቱን እንዲረጋገጥለት የሚያቀርብ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 305 መሰረት የተፋጠነ ሥርዓት ነው ሊባል የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ ይሰጠኝ አቤቱታ ይዘቱና ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ስነ ሥርዓት ሲታይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የማስረጃ ይሰጠኝ ጥያቄውን ተገቢነቱን፣ ትክክለኛቱንና ሕጋዊነቱን ከማረጋገጥ ባለፈ ጋብቻ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘው በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመስማት፣ጉዳዩን በማጣራት እና ሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ክርክር ሲኖር አቤቱታውን ተቀብሎ ለማስተናገድ የዳኝነት ሥረ ነገር ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡በጉዳዩ ላይ ሚስትነት ወይም ባልነት የለም የሚልና ተቃውሞውን ለማቅረብ መብትና ጥቅም ያለው ወገን ጋብቻው ያለመኖሩንና እና ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ሕጋዊ ክርክሮችን መሰረት በማድረግ ተቃውሞ በማቅረብ ሕጋዊ መፍትሔ ሊያገኝ የሚገባው ጥያቄውን ወይም አቤቱታውን ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ለማቅረብ እንጂ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በማቅረብ አይደለም፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ ወረቀት ላይ ውሳኔ ሰጥተዋል በሚል ምክንያት ብቻ ተቃውሞ ያለው ወገን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358"ን" መሰረት በማድረግ የተቃውሞ አቤቱታ ሲያቀርብና ፍርድ ቤቶቹም አቤቱታውን ተቀብለው የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ ትክክለኛነቱንና ሕጋዊነቱን ከማረጋገጥ ባለፈ ተከራካሪ ወገኖችን በማከራከር ስለጋብቻ መኖር ያለመኖር ላይ ማስረጃ ሳይሆን በጋብቻ ውጤት ላይ የራሱ የሆነ ትርጉም ያለውንና ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ሲሰጡ በተግባር ይስተዋላል፡፡ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የተቃውሞ አቤቱታ የሚቀርበው በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተሰጠው የውሳኔ ትርጉም(አንቀፅ 3 ይመልከቷል) መሰረት ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ከተሰጠ እና ውሳኔው የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑ ሲረጋገጥና አቤቱታው ውሳኔው ከመፈፀሙ በፊት ከቀረበ ነው፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አይነተኛ አላማ ማስረጃው ትክክለኛነቱና ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ በማስረጃነቱ (Declaratory Judgement) በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ሳይሆን ከላይ እንደተገለፀው ሊፈፀም በሚችል ውሳኔ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን መብትና ጥቅምን ማስከበር ነው፡፡በአጠቃላይ የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ አቤቱታ ስለሚሰጥበት ሁኔታና ስለይዘቱ እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ተቃውሞ የሚቀርብበት ሥርዓት በአንድነት ሲታዩ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የማስረጃው ይሰጠኝ ጥያቄ /አቤቱታ/ ትክክለኛነቱንና ሕጋዊነቱን በማረጋገጥ ለማስረጃነት ውሳኔ ከመስጠት ባለፈ ማስረጃውን ትክክለኛነቱንና ሕጋዊነቱን የሚቃወም ወገን አቤቱታ ሲያቀርብ ለተቃውሞው መሰረት ሊሆኑ በሚችሉት ጋብቻ የለም፣ተገቢው ማስረጃ አልቀረበም፣የቀረቡት ማስረጃዎችም ሐሰተኛ ናቸው በሚሉት ነጥቦች ላይ ክርክር በመስማት ዳኝነት ለመስጠት በአዋጅ ቁጥር 361/1995"ም" ሆነ የዚሁ አዋጅ ማሻሻያ በሆነው አዋጅ ቁጥር 408/1996 መሰረት ሥልጣን ያልተሰጣቸው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሲያቀርቡ መሰረት ያደረጉት ከሚች ወ/ሮ ኪሮስ ጋር በጋብቻ ተሳስረው የነበሩ መሆኑን ጠቅሰው የባልነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ሲሆን ይህ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ሲያመለክቱም አቤቱታቸውን በቃለ መሃላ ያስደገፉ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ለተጠሪ በተጠየቁት አግባብ ማስረጃ ከሰጠ በሁዋላ የአሁኗ አመልካች ተጠሪና ሚች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ባልና ሚስት አይደሉም፣ጥያቄውና ማስረጃው የተሰጠበት አግባብ ሕጋዊ አይደለም የሚል ይዘት ያለው ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ይህ በግልፅ የሚያሳየው የአመልካች የተቃውሞ አቤቱታ ተጠሪ ያገኙት የባልነት ማስረጃ ከማስረጃነቱ ባለፈ ሌሎች የቤተሰብ ሕግ ክርክሮችን የሚያስነሳ መሆኑን ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የከተማው ፍርድ ቤትም የተሻሻለውን የፌዴራሉን የቤተሰብ ሕግ ሁሉ በመጥቀስ ውሳኔ መስጠቱን ከውሳኔው ተመልክተናል፡፡የአዲስ አበባ ከተማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና 408/1996 መሰረት ካገኟቸው ሥልጣኖች መካከል ከመሰረታቸው የፌዴራል ጉዳዮች የሆኑት የሚገኙት ሲሆን እነዚህ ጉዳዮች ለእነዚህ ፍርድ ቤቶች ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ተቆርሰው ሲሰጡ በሕግ አውጪው የታሰበው በባሕርያቸው ውስብስብ ያልሆኑ ናቸው በሚል ነው፡፡የጋብቻ መኖር ያለመኖር ውስብስብ ያልሆነ ክርክር የማይቀርብበት ሳይሆን ክርክር ተደርጎበት ውስብስብ የሕግ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥበት ነው፡፡በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የጋብቻ መኖር ያለመኖርን ለመወሰን ሥረ ነገር ስልጣን ያልተሰጣቸው በመሆኑ ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች መስተናገዱ ያላግባብ ነው፡፡ተጠሪ ያገኙትን ማስረጃ አመልካች ሊቃወሙት የሚገባቸው ስልጣን ባለው የፌዴራል ፍርድ ቤት ነው፡፡ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረቡት ምክንያቶችን በመመልከት ጉዳዩን ለማስተናገድ ስልጣን የሌለው መሆኑን ገልፆ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(1(ለ)) መሰረት መዝገቡን መዝጋት ሲገባው ጉዳዩን ማስተናገዱም ሆነ የበላይ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ሳያረጋግጡ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በትእዛዝ ማፅናታቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 961/02 ጥቅምት 16 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17036 ሕዳር 25 ቀን 2004 ዓ/ም፣በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 17119ታህሳስ 13 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ በተመለከተ የቀረበው ጥያቄ ትክክለኛነቱንና ሕጋዊነቱን በማረጋገጥ በማስረጃነቱ ውሳኔ (Declaratory Judgement) ከመስጠት ውጪ ማስረጃው የተሰጠበትን ውሳኔ መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የተቃውሞ አቤቱታ መቀበልና ጋብቻ መኖር ያለመኖርን ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ክርክሮችን ለማስተናገድ የሥረ ነገር ሥልጣን የላቸውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ አለኝ የሚሉትን ማስረጃ አመልካች በተጠሪና በሚች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ጋር ጋብቻ የላቸውም የሚሉበትን ምክንያት መሰረት አድርገው ሊቃወሙ የሚችሉት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ሳይሆን በሌላ ክስ ሁኖ ስልጣን ባለው በፌዴራሉ ፍርድ ቤት ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሃሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በሰጠው የሕግ ትርጉምና ከደረሰበት መደምደሚያ የማልስማማ በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የወራሽነት፣ የባልና ሚስትነት የሞግዚትነትና የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ አከራክረው የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑ አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41/ሸ/ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀጽ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡

የባልና ሚስትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ፣ ባል ወይም ሚስት ነኝ በማለት አንድ ሰው የሚያቀርበውን ማመልከቻና መግለጫ ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ የባልና ሚስትነት ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ ማናቸውም ያገባኛል የሚል ሰው ባል ወይም ሚስት አይደለም በማለት የሚያቀርበውን ተቃውሞና ክርክርን የሚጨምር እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 1 "የአቤቱታ ፅሁፍ ማለት ከሳሽ የሚጠይቀውን ሁሉ ዘርዝሮ የሚገልፅ ፅሁፍ፣ ተከሳሽ የሚሰጠው የመከላከያ ፅሁፍ፣ የተከሳሽ ክሳሽ የሚያቀርበው ፅሁፍ የይግባኝ ማቅረቢያ ፅሑፍ ወይም በሌላ አይነት ተፅፎ ለፍርድ ቤትና ክስ መነሻ ወይም ለዚሁ መልስ የሚመለከት ማናቸውም ፅሑፍ ነው በማለት የሰጠውን ሰፊ ትርጉም በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀጽ 1 የባልና ሚስትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች እንደሆነ ሲደነግግ፣ አንዲት ሴት የአንድ ሰው ሚስት መሆኔ ተጣርቶና በማስረጃ ተረጋግጦ ይወሰንልኝ በማለት የምትጠይቀውን የዳኝነት ጥያቄ ወይም አንድ ሰው የአንዲት ሴት ባል መሆኔ ተጣርቶና በማስረጃ ተረጋግጦ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት በሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ ላይ ባል ነው የተባለው ሰው ወይም ሚስት ናት የተባለችው ሰው በህይወት ያለች ከሆነ የመከላከያ መልሷንና ማስረጃዋን እንድታቀርብ በማድረግ፣ ፍሬ ጉዳይ በማጣራት፣ ማስረጃ በመመርመርና በመመዘን በሁለቱ ተከራካሪዎች መካከል ህጋዊ ዕውቅና ያለው ጋብቻ መኖሩን ወይም አለመኖሩን የመወሰን ሙሉ ሥልጣን ያላቸው መሆኑን የሚያጠቃልል ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የባልነት ወይም ሚስትነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥና አቤቱታ የቀረበው አንደኛው ወገን ላይ የመጥፋት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ወይም አንደኛው ወገን ከሞተ በኋላ እንደሆነ፣ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው የመከራከር መብት ያላቸው ሰዎች የሚያቀርቡትን ክርክርና የመከላከያ ማስረጃ በተሟላ ሁኔታ በመስማት ተገቢውን ውሳኔ የመስጠት ሥልጣንን የሚያካትት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀጽ 1 ድንጋጌ ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 41 ድንጋጌ ጋር በማጣመር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ባል ወይም ሚስት መሆናቸውን የሚያረጋገጥ ማስረጃ ከመስጠታቸው በፊት፣ ተገቢውን የፍሬ ጉዳይ ማጣራት በማድረግ፣ አስፈላጊም በሆነ ጊዜ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 145/1/ እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 264 መሠረት ተጨማሪ የሰነድና የሰው ማስረጃ በማስቀረብ ፣ ውሣኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸው የከተማው ፍርድ ሰጭ ተቋማት መሆናቸውን በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 39 ተደንግጓል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ባል መሆኑ ወይም ሚስት መሆኗ ተጣርቶና ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው የቀረቡ የዳኝነት ጥያቄዎችን ፣ ለጉዳዩ መልስ መስጠት ያለበት - የትዳር አጋር /ባለ/ች/ መልስ እንዲሰጡና መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ በራሳቸው አነሳሽነት ተጨማሪ የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ በማስቀረብ ወይም በጉዳዩ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገን ሊሆን የሚችል ሰው ሲቀርብ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሠረት የጣልቃገቡን ክርክርና ማስረጃ በመስማት በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ጋብቻ መኖሩን ወይም በጋብቻ አለመኖሩን በማረጋገጥ የሰጡት ውሣኔ መብቴንና ጥቅሜን ይነካብኛል፤ በክርክሩ ተካፋይ መሆን ነበረብኝ የሚለው ሰው በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ሰው ቀደም ብሎ የተሰጠውን ውሣኔ ለማሰረዝ የፍርድ መቃወሚያ የሚያቀርበው ቀደም ብሎ ጋብቻ መኖሩን ወይም አለመኖሩን አከራክሮና አጣርቶ ለወሰነው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት እንደሆነ የአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀፅ 1 ድንጋጌና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 359 ንዑስ አንቀፅ 1 "መቃወሚያው የሚቀርበው በአቤቱታ አቀራረብ መልክ ሆኖ ተገቢው ዳኝነት ተከፍሎበት፣ መቃወሚያ ያቀረበለትን ለወሰነው ፍርድ ቤት ነው" በማለት በግልፅ የደነገገውን ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የባል ወይም ሚስት ስለመሆን የቀረበላቸውን አቤቱታ ተቀብለው አጣርተው በሰጡት ውሣኔ ላይ የሚቀርብን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ተቀብሎ የማስተናገድ ሙሉ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡ አብላጫው ድምፅ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ጋብቻ አለ ወይም የለም በሚለው ጭብጥ ላይ መከራከር ያለባቸውን ሰዎች ክርክር በመስማት አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ውሣኔ እንደማይሰጡና ሥልጣን እንደሌላቸው በመቁጠር፣ የፍርድ መቃወሚያው መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆን አለበት በማለት የሰጠው ትርጉም የአዋጅ ቁጥር 408/96 አንቀፅ 1፣ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር አንቀጽ 80/1/፣ አንቀጽ 41 እና አንቀጽ 358፣ አንቀጽ 359/1/፣ ድንጋጌዎች ይዘትና ተግባራዊ ተፈፃሚነት መሠረት ያደረገ ነው የሚል እምነት የሌለኝ በመሆኑ፣ በጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የፍርድ መቃወሚያውን በመቀበል የማከራከርና የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ ጭብጥ በተያዘበት በዳኝነት ሥልጣንን መሠረት በማድረግ ሳይሆን የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች የተጠሪን የፍርድ መቃወሚያ በመቀበል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ነጥብ ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር ውሣኔ ሊሰጠው ይገባ ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ 98541

ህዳር 10 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አለማየሁ አሳና - ቀረቡ

ተጠሪ፡-የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት (UNDP) ታልፏል ።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው አመልካች በተጠሪ ላይ የአሠሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎችን መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክስ ተጠሪ በሌለበት ታይቶ በክርክሩ ከተረጋገጠበት የፍሬ ነገር ጉዳዮች በመነሳት የአሁኑ አመልካች የተለያዩ ክፍያዎች በተጠሪ እንዲከፍሏቸው በወረዳው ፍርድ ቤት በተወሰነው መሰረት የአፈጻጸም መዝገብ ከፍተው ክርክሩ በመታየት ላይ እያለ ተጠሪ የመከሰስ መብት የለውም ተብሎ የአፈጻጸም መዝገቡ በሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች መዘጋቱ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡

የአሁን አመልካች ተጠሪ ከህግ ውጪ ከስራ አሰናብቶኛል በማለት ካሳና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ በያበሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው የአሁኑ ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ተደርጎ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ስንብቱ ሕገ ወጥ መሆኑን በመደምደም ለአመልካች ካሳና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ በማለት ወስኗል፡፡አመልካች ይህንኑ ውሳኔ ለማስፈፀም በወረዳው ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ክስ ከፍተው ጉዳዩ መታየት ከጀመረ በኋላ የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የተባበሩት መንግስታት ኮንቬንሽንን አንቀፅ 2(3) በዋቢነት ጠቅሶ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የአፈጻጸም መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበውም ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ሊቀርብ ባለመቻሉ መልስ መስጠቱ የታለፈ ሲሆን ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሁኖ አመልካች የሚከራከሩት የተባበሩት መንግስታት አካል ከሆነው ድርጅት ጋር መሆኑን፣ ከእንደዚህ አይነት ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የማይገዛ መሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 3(ሀ) ስር መመልከቱን፣ተጠሪና መሠል አካላት በሕግ የተለየ ከለላ ያላቸው መሆኑ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀጽ105፣በተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ ለመንደንገግ በወጣው ስምምነት አንቀጽ 2(2) እና 3 ስር መደንገጉን፣ኢትዮጵያም ይህንኑ ስምምነት መፈረሟን በዋቢነት ጠቅሶ ከመነሻውም ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት መከሰሱ ተገቢነት እንደሌለው፣አመልካች ያላቸው መፍትሔም በ"United Nations Commission on International Trade Law (UNCITRAL)" ደንቦች መሰረት ከተጠሪ ጋር ባላቸው ስምምነት መሰረት በእርቅ መጨረስ መሆኑን፣በዋናው ጉዳይ ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ መወሰኑን ከተጠሪ ጥቅምና ከባለ መብቶች አንፃር ሲታይ ዋናውን ውሳኔ ሕጋዊ የማያደርገው መሆኑን ዘርዝሮ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለንም በማለት የአፈጻጸም መዝገብ መዝጋታቸውን በመቀበል የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በዋናው ጉዳይ ላይ ተጠሪ ቀርቦ ባልተከራከረበት ሁኔታ በአፈጻጸም መዝገብ የተጠሪን ያለመከሰስ ከለላ በመጥቀስ ዋናውን ውሳኔ ውድቅ ማድረግ ሥነ ሥርዓታዊና የሕግ የበላይነት እንዲሁም አመልካች እንደ ዜጋ ፍትህ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ በጽሑፍ መልስ መስጠቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት ጉዳዩን ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ግንኙነት የቅጥር ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ዋናው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ ታይቶ ዳኝነት ማግኘቱን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የተለያዩ ዓይነት በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የስራ ግንኙነቶች የሚኖሩ ሲሆን ግንኙነቶቹ የሚገዙበት የሕግ አግባብም ይለያያል፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ግንኙነቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ይህ አዋጅ በየትኞቹ ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደሚችል በዋነኝነት የሚመራው የአዋጁን የተፈጻሚነት ወሰን የደነገገው አንቀጽ 3 ነው፡፡ለዚህ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የአንቀጹ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሶስት በፊደል "ሀ" ስር የተመለከተው ሲሆን በዚህ ንዑስ ድንጋጌ ስር የስራ ግንኙነቱ በንዑስ አንቀጽ ሁለት ስር የሚወድቁ ባለመሆናቸዉ በአዋጁ አንቀጽ 1 መሰረት በቀጥታ ሊፈጸምባቸው የሚችል ቢሆንም በንኡስ አንቀጽ 3 ስር በተገለጹት ሁኔታዎች መሰረት ከአዋጁ ሽፋን ውጭ ሊደረጉ የሚችሉ የስራ ግንኙነቶችን የሚመለከት ነው፡፡በዚሁ መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰሩ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ወይም አለም አቀፍ ድርጅቶች ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚመሰርቱት የስራግንኙነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ወይም ኢትዮጵያ በምትፈርማቸው አለምዓቀፍ ስምምነቶች መሰረት በአዋጁ ሊሸፈኑ እንደማይችሉ ተመልክቷል፡፡በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ሲታዩ አዋጁ በአጠቃላይ በአሰሪና ሰራተኛ መካካል በሚቋቋም በቅጥር ላይ በተመሰረተ የስራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ቢሆንም በአዋጁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግልጽ በተደነገጉ ሌላ ህግ በሚገዛቸው ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖረው ያስገነዝባሉ፡፡ በተጨማሪም አሁንም አዋጁ የሚሸፍናቸው የስራ ግንኙነቶች ሊሆኑ ቢችሉም ነገርግን የሚኒስትሮች ምክርቤት ወይም ኢትዮጵያ የምትፈርማቸው አለምአቀፍ ስምምነቶች በሚወስኑት መሰረት ከአዋጁ ሽፋን ውጭ ሊደረጉ የሚችሉ መሆኑን ተመልክቷል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ሕግ አውጪው የዲፕሎማቲክ ግንኙነቶችን ስምምነትና ልምድን ለማክበር ሲባል የውጭ ዲፕሎማቲክ ሚስዮኖቹና ኢትዩጵያውን ሠራተኞቻቸው የሚያደርጉት የቅጥር ግኙነት ላይ የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ ተፈጻሚ እንዳይሆን ያደረገ መሆኑን ነው፡፡በመሆኑም በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ወይም ኢትዩጵያ ከውጭ ድርጅቶች ጋር በምትፈራረምባቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት አዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚደረግበት አግባብ መኖሩን ሕግ አውጪ በግልፅ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(3((ሀ)) መሰረታዊ አላማ የውጭ አገር መንግሥታት ተወካዮችን ሉአላዊነት እና አለምአቀፍ ስምምነቶችን ለማክበር ተብሎ ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን በተጨባጭ ባለው ሁኔታ ደግሞ የውጪ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችና አለም አቀፍ ድርጅቶች ከኢትዩጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ጋር ስምምነት ተፈራርመው ይኼው የመንግስት አካል በእነዚህ ተቋሞች ተቀጥረው የሚሰሩት ኢትዩጵያውንን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ በአለም አቀፍ ስምምነቶች በተካተተው አግባብ የተፈጠረው አለመግባብት ሰላማዊ በሆነ መንገድ በማግባባትና በድርድር እንዲፈታ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ የሚታወቅ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ክርክር ያቀረቡት ግንኙነቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(3(ሀ)) መሰረት ሊገዛ ከማይችል አካል ጋር ነው፡፡ተጠሪ የተባበሩት መንግስታት አካል ሲሆን የተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ በተደነገገ ስምምነትም በማንኛውም መንግስት ፍርድ ቤቶች ተከሶ መቅረብ የሌለበት መሆኑን በተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀፅ 105 እንዲሁም ከተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ በተደነገገው ስምምነት አንቀጽ 2(2) እና 3 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር የሌለ ቢሆንም አሁን አጥብቀው የሚከራከሩት በዋናው ጉዳይ ውሳኔ ከአረፈ በውሳኔው መሰረት ከሚፈጸም በስተቀር የተጠሪ በሕግ ያለው የተለየ ከለላ እንደ አቢይ ምክንያት ተወስዶ አፈፃጸሙ ሊቆም የሚችልበት አግባብ የለም በሚል ነው፡፡በሕግ አግባብ የተሰጠ ፍርድ ዋጋ እንዳይኖረው የሚደረገው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተገቢነት እንደሌለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠን ውሳኔ በሕጉ አግባብ ማስፈፀም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78(1) እና 79(1) እና (4) ስር የተረጋገጠውንና የተከበረውን የነጻ ፍርድ ቤት መኖርንና የዳኝነት ስልጣን በአግባቡ ተግባራዊ የሚያደርገው እና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ስር የተረጋገጠው የዜጎች ፍትህ የማግኘት መብትም ውጤት ባለው መልኩ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡አፈጻጸም በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ትርጉም እንዲኖረው የማድረግ ውጤት ያለውና በተገቢው መንገድም መፈፀም ያለበት መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ይህ ግን ለማንኛውም ጉዳዮች ሁሉ ይሰራል ብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ ተገቢ ያልሆነ ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል መሆኑ እሙን ነው፡፡በእርግጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 ድንጋጌ ስር በስነ ስርዓት ጉድለት አንድ ፍርድ ውድቅ ሊሆን እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን ይህ ግን የሚሰራው የፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ ተፈፃሚነት ወሰንን መሰረት በማድረግ በሌላ አካታን እንዲፈፀም በሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባልተደነገገበት ሁኔታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡በመሆኑም ከመነሻውም ኢትዮጵያ በፈረመችው አለም አቀፍ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ላለመዳኘት ነገር ግን ከኢትዮጵያ ዜጎች ጋር ለመሰረተው ግንኙነት በሌላ አግባብ ጉዳዩን ለመጨረስ የሚያስችል ስርዓት ያለው ወገን በዋናው ክርክር ጊዜ ቀርቦ ባለመከራከሩና በይግባኝ ጉዳዩን ባለማሳረሙ ምክንያት ብቻ ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲፈጽም የሚገደድበት አግባብ የለም፡፡ስለዚህ ከዚህ ጉዳይ የተለየ ባሕርይ ስንነሳ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 እና 4 ድንጋጌዎች አንድ ላይ ተጣምረው ሲታዩ አፈፃጸሙ ዋጋ ያለውን ፍርድ መሰረት ያደረገ ነው፣ጉዳዩ ከስነ ስርዓት ጉድለት ጋር የተያያዘ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አላገኘነም፡፡ተጠሪ በሕግ የተጠበቀለት የከለላ መብትና ጥቅም እያለው ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲፈጽም ማድረግ ሕግ አውጪው የዲፕሎማቲክ ግንኙነቶችን ልምድን ለማክበር ሲባል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(3(ሀ)) ስር ያስቀመጠውን ድንጋጌ ዋጋ የሚያሳጣው እና በዲፕሎማቲክ ግንኙነቱም አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ተመራጭ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ሲጠቃለልም የጉዳዩ ልዩ ባህርይ ሲታይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 ድንጋጌን ጠቅሶ አፈፃጸሙን ማስቀጠል የሚቻልበት አግባብ ስለሌለና አመልካችም እንደዜጋ መንግስት በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በኩል በዘረጋው ስርዓት መሰረት መብትና ጥቅማቸውን የሚያስከበሩበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ የሕግ የበላይነት አልተከበረም፣ የዜጋ ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት ተጥሷል ለማለት ስላልተቻለ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 163639 ታህሳስ 07 ቀን 2006 ዓ/ም የበታች ፍርድ ቤቶችን ትዕዛዝ በማፅናት የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የአፈጻጸም ክስ መዘጋቱ ተገቢ ነው ብለናል፡፡አመልካች አለኝ የሚሉትን መብትና ጥቅም በሌላ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

መ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 99717

ጥር 20 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች ፡- አቶ ሲሳይ ይማነ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ነገረ ፈጅ አቶ መስፍን ጌታቸው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 41105 ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 143053 ጥር 13 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የዳኝነት ስልጣን ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች /ከሳሽ/ ከተከሳሽ ጋር የአካዳሚክ ሰራተኛ የነበረ መሆኑን ገልፆ፣ ግንቦት 9 ቀን 2001 ዓ/ም ከሳሽና ተከሳሽ ባደረጉት ስምምነት መሰረት በሌክቸረርነት አገልግያለሁ፣ ከሳሽ የማስተርስ ድግሪ ትምህርት በመማር ውጭ ሃገር ሄጀ ተመልሻለሁ፡፡ ከዚያም የዶክትሬት ድግሪ ትምህርት ለመከታተል ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ተከሳሽ ከነሀሴ 19 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ለሶስት ዓመታት የሚታሰብ ፍቃድ ሰጥቶኝ የዶክተሬት ትምህርቴን በመከታተል ላይ እገኛለሁ ትምህርት ፍቃድ የተሰጠኝ ሀምሌ 4 ቀን 2001 ዓ/ም ባወጣውና ህዳር 7 ቀን 2002 ዓ/ም በተሻሻለው መመሪያ መሰረት ነው፡፡ በመመሪያው መሰረት በሁለት የትምህርት ፈቃዶች መካከል አንድ አመት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ እንዳለ የተገለጸ ሲሆን ይህን የማያሟላ የአካዳሚክ ተቀጣሪ ፈቃዱን ማግኘት የሚችለው ፈቃድ በሚሆንበት ጊዜ ጥቅማ ጥቅሞቹን መብቶቹን /ደመወዙን ጨምሮ/ ላለመጠየቅ ሲስማማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው ሆኖም የአካዳሚክ ሰራተኛው የተሰጠው ፈቃድ ከመጠናቀቁ በፊት ወደ ዩኒቨርስቲው ተመልሶ ያላሟላውን የአንድ አመት አገልግሎት ከሰጡ፣ ቀደም ሲል በስምምነት መነሻነት የተዋችው ጥቅማ ጥቅም የማግኘት መብት እንደሚኖረው በመመሪያው ተደንግጓል ። በዚህ መሰረት ከሳሽ የተሰጠኝ የትምህርት ፈቃድ ከማለቁ በፊት ተመልሼ የአንድ አመት አገልግሎት የሰጠሁት ግዴታን የተወጣሁ በመሆኑ ተከሳሽ በስምምነታችን መሰረት ሊከፍለኝ የሚገባውን ደመወዝ ጥቅማ ጥቅም የአየር መጓጓዣ ወጭ እንዲከፍል ብጠይቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ እነዚህን ክፍያዎች ከህጋዊው ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል ።

2. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 515/99 እና በደንቡ ቁጥር 77/94 የሚተዳደር በመሆኑ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የስረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል ከሳሽ ተከሳሽ ባቀረበበት ጥያቄ መሰረት ከነሀሴ 19 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ የሶስት ዓመት ተሰጥቶ የስራ ውል ተቋርጧል። ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር ያለው ስምምነት ከጥር 6 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ የተቋረጠ በመሆኑ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው መብትና ጥቅም የለውም የሚልና ሌሎች መከራከሪያዎቹን አቅርቧል።የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር የመነጨው በቅጥር ላይ ከተመሰረተ ግንኙነት ነው የስራ ውሉም የተደረገው የመንግስት ተቋም ከሆነው አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ጋር ነው። ተከሳሽ መንግስት በሚበጅትለት የሚተዳደር ነው። ከሳሽና ተከሳሽ ያደረጉት ውል፣ የውሉን አፈጻጸም አስመልክቶ ያለመግባባት ቢፈጠር በፍርድ ቤት ቀርቦ እንደሚታይ የሚገልጽ ቢሆንም ይህ አገላለጽ የግራ ቀኙ ክርክር የሚዳኘው በአስተዳደር ፍ/ቤት መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ጉዳዩ ለመደበኛ ፍ/ቤት የሚቀርብ መሆኑን የሚያመላክት አይደለም ስለዚህ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ብይን ሰጥቷል።አመልካች ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል።

3. አመልካች አከራካሪው ጭብጥ የአካዳሚው ሰራተኛ የትምህርት ፈቃድ የሚያገኝበትንና የትምህርት እቅድ በተሰጠው ጊዜ መፈጸም የሚገባውን የአንድ ዓመት አገልግሎት የፈጸመ በሆነ ጊዜ ከዩኒቨርሲቲው ሊከፈለው ስለሚገባው ደመወዝ ፤ ጥቅማ ጥቅምና የትራንስፖርት ወጭ የሚመለከት በሌላ አነጋገር የውል አፈጻጸም የሚመለከት ሆኖ እያለ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ብይን መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ሚያዝያ 7 ቀን 2006 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል። ተጠሪ በበኩሉ ግንቦት 19 ቀን 2006 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤት እንደሆነ የሚገልጽ መከራከሪያ አቅርቧል።አመልካች ሰኔ 2 ቀን 2006 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤት ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለንም በማለት የሰጡት ብይን የህግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል ።

5. ከላይ የተያዙት ጭብጥን ለመወሰን፣ በመጀመሪያ አመልካች ተጠሪ የሚያከራክራቸው መሰረታዊ ጉዳይ ባህሪና ይዘት የግራ ቀኙ ክርክር የሚፈታበትን መንገድ መመርመር አስፈላጊ ነው። ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ለስር ፍ/ቤት ክስ ያቀረበው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተጠሪው ጋር በተዋዋልነው የመግባቢያ ስምምነት መሰረት የተሰጠኝ የትምህርት ፈቃድ ከማለቁ በፊት፣ ተመልሼ መጥቼ አንድ አመት አገልግሎት የመስጠት ግዴታዬን ተወጥቻለሁ።ተጠሪም በውሉ የገባውንና ደመወዝ፣ጥቅማ ጥቅምና የአየር ትራንስፖርት ወጭ የመሸፈን ግዴታውን እንዲወጣ በፍርድ ተጣርቶ ይወሰንልኝ በማለት ነው። ይህም

/ሀ/በተጠሪ ፈቃድና ይሁንታ የዶክትሬት ድግሪ ትምህርቱን ለመከታተል የተፈቀደለት አመልካች፣ ደመወዝ ጥቅማ ጥቅምና የአየር ትራንስፖርት ወጭ ክፍያ ሳይጠይቅ የትምህርት ፈቃድ እንዲሰጠው ያቀረበው ጥያቄ በመቀበል ተጠሪ የሰጠው የትምህርት ፈቃድ መሰረታዊ ይዘትን ባህሪ እንደዚሁም ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው

/ለ/ አመልካች ተጠሪ የሰጠው የትምህርት ፍቃድ ከመጠናቀቁ በፊት ተመልሶ በመምጣት በመመሪያው የተገለጸውን አገልግሎት የሰጠ በሆነ ጊዜ ቀደም ብሎ ላለመጠየቅ ተስማምቶ የተወውን ደመወዝ ጥቅማ ጥቅም እና የአየር የትራንስፖርት ወጪ ክፍያ ለመጠየቅ የሚችልበት ሁኔታ አግባብነት ባለው መመሪያ አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት የመግባቢያ ስምምነት ተደንግጓል ወይስ አልተደነገገም?

/ሐ/ ተጠሪ አመልካች የትምህርት ፈቃድ በነበረበት ጊዜ ደመወዝ ጥቅማ ጥቅም እና አየር ትራንስፖርት ወጭ ክፍያ የመክፈል ከውል ወይም ከህግ የመነጨ ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦች መርምሮና በማስረጃ አጣርቶ መወሰን የሚጠይቅ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር ለመረዳት ይቻላል።

6. አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩባቸው በላይ የተገለጹበት መሰረታዊ የፍሬ ጉዳይ እና የህግ ጭብጦች አመልካችና ተጠሪ የትምህርት ፈቃድንና አመልካች በትምህርት ፈቃድ ባለበት ጊዜ ተጠሪ ለአመልካች የደመወዝ ጥቅማ ጥቅምና የአየር ትራንስፖርት ወጭ የሚከፍልባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ቅደመ ሁኔታዎቹ ባልተሟሉ ጊዜ ተጠሪ እነዚህን ክፍያዎች ከመክፈል ነፃ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች የሚመለከት ነው። ከዚህ በተጨማሪ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ጉዳይ አመልካች በትምህርት ፈቃድ ለቆየበት ደመወዝ ጥቅማ ጥቅምና የአየር ትራንስፖርት ወጭ ክፍያ ለማግኘት የሚያስችሉትን ቅድመ ሁኔታዎች አመልክቷል። ወይስ አላመለከተም? አመልካች ቅድመ ሁኔታዎቹን አሟልቷል የሚባል ቢሆን ተጠሪ ለአመልካች መክፈል ያለበትም ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጭብጦች የሚያካትት ነው። ጠቅለል ባለ አነጋገር አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት በመካከላቸው ስላለው የሥራ ቅጥር ውል፣እድገት ወይም ዝውውር ሳይሆን ተጠሪ ለአመልካች የትምህርት ፈቃድ ሲሰጠው በተዋዋሉት የመግባቢያ ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች ያላቸው መብትና ግዴታን ተዋዋይ ወገኖች በውል የገቡትን ግዴታ በአግባቡ የፈጸሙ መሆን አለመሆናቸውና ውል የሚተረጎምበትንና የሚፈጸምበትን አግባብ የሚመለከት ነው።

7. ከዚህ አንጻር የሲቪል ሰርቪስ የአስተዳደር ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩባቸውን ከላይ የተገለጹትን የህግና የፍሬ ጉዳዩን ጭብጦች በመመስረት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት በመመርመርና በመመዘንና በማጣራት ውሳኔ የመስጠት የዳኝነት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ መመርመር ይጠይቃል። የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 75 የሚታዩ ጉዳዮችን በዝርዝር ደንግጓል በዚህ ድንጋጌ መሰረት በአስተዳደር ፍ/ቤት ታይተው ውሳኔ የሚያገኙት ከህግ ውጪ ከስራ መታገድ ወይም አገልግሎት መቋረጥ ጉዳይ ከባድ የዲስፒሊን ቅጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተወሰነባቸው ጉዳዮች ሰራተኛው ከህግ ውጭ ደመወዝ ወይም ሌሎች ክፍያዎች የተያዘበት ወይም የተቆረጠበት የሚመለከት ሲሆን በእንግሊዘኛው “an illegal attach ment or deduction of his salary or other payment” ሰራተኛው በስራው ምክንያት በደረሰበት ጉዳት ጋር በተያያዘ መብቱ መጓደልን የሚመለከቱ ጉዳዮች እና ሌሎቹ በአዋጅ አንቀጽ 75 ንዑስ ከአንቀጽ 5 እና ንዑስ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን ጉዳዬች እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

8. ይህም የአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 75 ድንጋጌዎች ይዘት ተጠሪ አካዳሚክ ሠራተኞች የትምህርት ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ፣በትምህርት ፈቃድ የወሰዱ የአካዳሚክ ሰራተኞች ጋር ባደረገው የመግቢያ ውልና ይህንን በሚመለከት በወጣው መመሪያ መሰረት ለአካዳሚክ ሰራተኞች ስለሚከፍለው ደመወዝ ጥቅማ ጥቅምና የትራንስፖርት ውጭ እና እነዚህን ክፍያዎች ለማግኘት የአካዳሚክ ሰራተኛው ማሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆናቸውን በማጣራት በአካዳሚክ ሰራተኛው የሚቀርበውን ክስ በቀጥታ ተቀብሎ ማስረጃ ሰምቶ መርምሮ፣ መዝኖና ፍሬ ጉዳይ አጣርቶና አግባብነት ያለውን የውል ስምምነትና የህግ ድንጋጌዎች በመተርጎም የአስተዳደር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚሰጥ መሆንን የሚደነግግ አይደለም የክርክሩ ይዘት ባህሪ ክርክሩ የሚያቀርብበትና የሚወስንበት ስርዓት የአስተዳደር ፍ/ቤት የአመልካችና የተጠሪን ጉዳዩ ተቀብለው ለማየትና አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችለው አይደለም፡፡

9. ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን ጭብጥ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ስልጣን ያላቸው በህግ መንግስቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች በተጠሪና በአመልካች መካከል የሚደረገውን ክርክር መሰረታዊ ይዘትና ባህሪ ሳይመረምሩ፣ ተጠሪ የመንግስት ተቋምና በመንግስትን በጀት የሚተዳደር መሆኑን በመመልከት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለንም በማለት የሰጡት ውሳኔ ከላይ የገለጽናቸው የህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል ፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል
2. የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር በዳኝነት አይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችና የተጠሪ ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልስን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ያወጡትን ውጭና ኪሳራ በየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገቡ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 105962

ቀን የካቲት 19/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- 1. ቢ.ኤም.ጂ ኃ.የተ.የግል ማህበር
2. ዜድ ኤ.ዲ.ኤስ ኃ.የተ.የግል ማህበር
} ጠበቃ ሰለሞን እምሩ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ፕሮፌሰር ባደግ በቀለ - ወኪል ተካልኝ በቀለ ቀረቡ፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ከመንገድ ይከፈትልን ጥያቄ ጋር ተያይዞ በኦሮሚያ ክልል የተነሳን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የቀረበው በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል የተነሳውን ክርክር ለመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን ያለውን ፍርድ ቤትን ለመለየት እና ስልጣን ሳይኖር ዳኝነት ተሰጥቶ ሲገኝ ውሳኔው ሊኖረው ስለሚኖረው ዋጋ ለመወሰን ይቻል ዘንድ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሚያ ልዩ ዞን ሰበታ አዋስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካቾች ክስ ይዘትም፡- ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰበታ ከተማ ወስጥ አንደኛው አመልካች 7939 ካ/ሜትር፣ ሁለተኛው አመልካች ደግሞ 8589 ካሬ ሜትር ቦታ ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዲስትሪ ልማት በኢንቨስትመንት መወሰዳቸውን፣ በዚህ ቦታ ላይ ለመውጫና መግቢያ የሚጠቀሙበትን መንገድ የአሁኑ ተጠሪ በመዘጋት መንገዱ እንዲከፈትላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ በሕግ አግባብ ለኢንቨስትመንት ቦታውን መውሰዳቸውንና የዘጉት መንገድ ያለመኖሩን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚህ መልክ ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ከአጣራ በኋላ ተጠሪ አመልካቾች በኢንቨስትመንት በወሰዱት ቦታ ላይ ያለውን መውጫና መግቢያ መንገድ መዘጋታቸው ተረጋግጧል በሚል ድምዳሜ ተጠሪ ለመኪና ተቆፍሮ በተሰራው መንገድ ላይ የሰሩትን አጥር አንስተው መንገዱን እንዲከፍቱ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ አቅርበው ግን ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ መንገድ ይከፈትልኝ የሚል በመሆኑ ይህንን አይነት ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ያለው የወረዳው ፍርድ ቤት ሳይሆን የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በክልሉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 128/1999 ተደንግጓል በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካቾች በፌዴራል መንግስት የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶች በመሆናቸው ክርክሩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፣ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ለክልሉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት አግባብ የሌለ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ ወረዳ ፍርድ ቤት መጀመሩ ስህተት ነው ቢባል እንኳን በይግባኝ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ታይቶ የጸና በመሆኑ ውሳኔው ሙሉ በሙሉ ዋጋ የለውም ተብሎ ውድቅ ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ የለም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በፌዴራል መንግስት የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶች መሆናቸውን፣ ተጠሪም ከክልሉ መንግስት ለኢንቨስትመንት በወሰዱት ቦታ ላይ በሕግ አግባብ ስራቸውን ከማከናወናቸው ውጪ የዘጉት መንገድ የሌለ መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን፣ ክርክሩ የመንገድ ይከፈትልን የዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ቢሆንም ከተከራካሪ ወገኖች መካከል በፌዴራል መንግስት የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶች ያሉበት መሆኑንና በክልሉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 128/1999 መሰረት የመንገድ ይከፈትልኝ ጥያቄን በመጀመሪያ ደረጃ የስረ ነገር ስልጣን አይቶ ዳኝነት መስጠት የሚችሉት የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች መሆናቸው በግልጽ የተደነገገ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግስትና በክልሎች መዋቀሩን መሰረት በማድረግ የዳኝነቱም ስልጣን በፌዴራል መንግስቱ እና በክልል መንግስታት መካከል እንደተከፋፈለ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 50 እና 51 ስር ተመልክቷል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80 "የፍ/ቤቶች ጣምራነትና ስልጣን" በሚል ርእስ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፤ በክልል ጉዳዮች ላይ በክልሉ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ስልጣኑ የተደነገገ ሲሆን የክልል ፍ/ቤቶች በህገ-መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሰረት ካልሆነ በቀር የፌዴራልን ጉዳይ ለማየት ፤ እንዲሁም የፌዴራል ፍ/ቤቶች የክልልን ጉዳይ ለማስተናገድ የሚያስችል ስልጣን የሌላቸውም መሆኑን በዚሁ ድንጋጌ ስር የተቀመጡት ንዑስ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ አንድ ጉዳይ የፌዴራል ነው? ወይስ የክልል? የሚለውን ለመለየትም መሰረቱ የአዋጅ ቁጥር 25/88 ሲሆን፤ በዚሁ ህግ አንቀጽ 5 ስር በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ብቸኛ ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የክልል ፍ/ቤቶች ስልጣን የሚኖራቸው በህገ-መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጣን አግባብ ብቻ ነው፡፡ ይህ በግልጽ የሚያሳየው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 መሰረት የፍርድ ቤቶች ስልጣን በጉዳዩ ባለቤትነት (subject matter) የስልጣን ክፍፍል እንደተጠበቀ ሆኖ ክሱም መቅረብ ያለበት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የስረ-ነገር ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ስለመሆኑ ነው፡፡ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8፣11፣14 እና 15 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ደግሞ አንዳንድ ጉዳዮች ሊያስነሱ በሚችሉት የክርክር ባህርይ ምክንያት ለተወሰኑ ፍ/ቤቶች እንዲቀርቡ በህግ ተለይተው ከተመለከቱት በቀር የስረ-ነገር ስልጣን የተደለደለው በክሱ በተመለከተው የገንዘብ ወይም የንብረት ግምት መነሻ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 14 እና 15 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እና የክልል መንግስታት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ሕጎች ያስረዳሉ፡፡

አመልካቾች በፌዴራል መንግስት የተመዘገቡ የንግድ ማህበራት እንደመሆናቸው መጠን ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2) እና 5(6) መሰረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ሆኖ ክርክሩ የተነሳው በክልል ሲሆን የክርክሩ መሰረት ግምት በሌለው የመንገድ ይከፈትልኝ ጥያቄ ላይ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 14 መሰረት ጉዳዩን የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የሆነውን ጉዳይ በውክልና ስልጣን በመጀመሪያ ደረጃ የስረ ነገር ስልጣን የሚመለከተው የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(4) ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 64(3) እንዲሁም በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 27(4) ድንጋጌዎችም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና የማየት ስልጣን እንደአለው ተመልክቷል፡፡

የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(5) በግልጽ ያሳያል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ህገ መንግስትም በአንቀጽ 64(4) ይህንኑ አስቀምጧል፡፡ ይህ በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሰረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ባልተቋቋሙባቸው ክልሎችም የሚሰራ ስርዓት ነው፡፡

ይህንኑ በህግ የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት አድርገን ጉዳዩን ስንመለከተው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዩች በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ወይም በወረዳ ፍርድ ቤት የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ በክልሉ መንግስት ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው የመንገድ ይከፈትልኝ ክርክር ከሚያነሱ ወገኖች መካከል አንዱ በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ይኼው አካል/ተቋም/ የክርክሩ ተካፋይ መሆኑ ብቻውን ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የሚያደረገውበመሆኑ በክልሉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት ጉዳዩ እንዲታይ የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ጉዳዩ የፌዴራል መንግስት አወቃቀርን መሰረት አድርጎ ያልታየ መሆኑና በስርዓቱ መሰረት በክርክር ላይ ባለበት ሁኔታ የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ጉዳዩን በመጀመሪያ የስረ ነገር ስልጣን የሚመለከተው ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ አጽንቶታል በሚል ምክንያት ብቻም ውሳኔው ዋጋ እንዲኖረው ማድረግ ከይግባኝ መብት እንዲሁም የፍርድ ቤቶች የስልጣን ድልድል መነሻ ከሚያደርጋቸው ምክንያቶች አንጻር ሲታይም ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም አመልካቾች በፌዴራል መንግስት የተመዘገቡ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ እና ክርክሩን ያስነሳው ጉዳይም ግምት የሌለው ሁኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የመንገድ ይከፈትልኝ የሚል ነው በሚል ምክንያት ብቻ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ቢሆንም ከላይ እንደተመለከተው ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ሁኖ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ ሲሆን በህገ መንግስቱ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ መታየት ያለበት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሻሩ በውጤት ደረጃ የሚነቀፍ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 180394 ነሐሴ 12 ቀን 2006ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ጉዳዩን በቀጥታ አይቶ የመዳኘት ስልጣን ያለው የክልሉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት አይደለም ብለናል፡፡ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(4) ፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 14፣ በኦሮሚያ ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ 64(3) እንዲሁም በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 27(4) ድንጋጌ መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመልስ ብለናል::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.99375

መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አምባቸዉ አለሙ - ጠበቃ ፋሲል ቀረበ

ተጠሪዎች፡-1ኛ የካ/ክ/ከ/ወ/01/አስተደር - የቀረበ የለም

2ኛ አቶ አሸናፊ መንገሻ

3ኛ አቶ አገስት አድነዉ

4ኛ አቶ አድማሱ አንጀሎ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሾች ነበሩ። አመልካች ባቀረቡት ክስ በተለምዶ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ በግምት 5 ሄክታር የተጎዳ መሬት በ 1985 ዓ/ም ተረክቤ የተለያዩ የዉጭ እና የሀገር ዉስጥ ዛፎች አልምቼ ዙሪያዉን በግንብና በሽቦ አጥር በመከለል፤ በርካታ የንብ፤ እንስሳት እርባታ፤ የእንግዳ መቀበያ እና መዝናኛ ቤቶች የሚገኙበትን የተሟላ መናፈሻ አቋቁሜ እያለሁ ተጠሪዎች እኔ በማላዉቀዉ ሁኔታ በመምጣት መናፈሻዉን በዉስጡ የነበሩትን ንብረቶችን አዉድመውብኛል ፤ግምቱንና የተቋረጠ ገቢ ብር 30,822,160.00(ሰላሳ ሚሊዩን ስምንት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ብር) ከፍለዉኝ ድርጅቱን እንዲያስረክቡኝ ሲል ጠይቋል።

1ኛ ተጠሪ በሰጠዉ መልስ አመልካች ይዞታዉን በህጋዊ መንገድ አልተረከበም፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና በደንብ ቁ.14/96 መሰረት ያቀረበዉ ማስረጃ የለም፣ ወደመ የተባለዉም ንብረት ስለመኖሩም አልተረጋገጠም፣ አመልካች ይዞታን አለቅም የሚል ሲሆን ተጠሪ በህግ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ያከናወነው ተግባር በመሆኑ ሊከስ መብት የለዉም፣ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ተከራክሯል። ፍርድ ቤቱም ከክርክሩና ከቀረበዉ ማስረጃ አመልካች ድርጅቱን በእጃቸዉ አድርገዉ የተለያዩ ስራዎችን እየሰሩበት የነበረ መሆኑ አልተካደም፣ ንብረት መዉደም ያለመዉደሙ በፍሬ ነገር ክርክር ወቅት የሚታይ በመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ የሰረ ነገር ስልጣን ያለዉ መሆኑን ስናይ በአዋጅ ቁ.361/1995 አንቀጽ 41(1) ((ረ))

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት የአዲስ አበባ መስተዳድር አስፈጻሚ አካላት በህግ በተሰጣቸዉ ስልጣንና ተግባር ጋር በተያያዙ ለሚነሱ ክርክሮች ስልጣን ያላቸዉ የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች በመሆኑ የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት በፍ.ብ/ሥ.ሥ.ህ.ቁ 244(2)((ሀ)) መሰረት ሳይቀበለዉ ቀርቷል፡፡የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎትም የአመልካችን ቅሬታ ባለመቀበል ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአመልካች አቤቱታም የቀረበዉ ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ ፡፡በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸዉን ሲገልጹ፡- ለደረሰብኝ ጉዳት ካሳ ገንዘቡን ገምቼ አቅርቤ እያለሁ ፍርድ ቤቱ የአዲስ አበባ አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ጋር የዳኝነት ጥያቄዬን በማገናኘት በአዋጅ ቁ. 361/95 41(1)(ሀ) መሰረት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ብለዋል ፤የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41 ስር ከተዘረዘሩት ዉስጥ አስተዳደሩ በግለሰቦች ላይ ለሚያደርሰው የንብረት ጉዳት ላይ የሚቀርብየካሳይከፈለኝ ጥያቄ አይቶ ለመወሰን ስልጣን እንዳላቸዉ አይገልጽም፤ በመሆኑም የደረሰብኝንጉዳት ገልጬ ያቀረብኩትን ክስ ተጠቃሹን አዋጅ መሰረት በማድረግ ስልጣን የለኝም ማለቱ አግባብነት የለዉም፤ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን በአዋጅ 25/88 መሰረት የፌደራል ፍርድ ቤቶች በመሆኑ የቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የተሰጠዉ ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በዚህም መሰረት ችሎቱም የቀረበዉን ካሳ ክፍያ ጥያቄ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማየት ስልጣን የለኝም ብለዉ የመወሰናቸዉን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ 1ኛ ተጠሪ እና አመልካችን በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክሯል፡፡ከ2ኛእስከ 4ኛ ተራ ያሉትን ተጠሪዎችን አስመልክቶ ጥሪ ቢደረግላቸዉም ባለመቅረባቸዉ በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

ተጠሪ በሰበር በሰጠዉ መልስ የሚለዉ ጉዳዩ በቀጥታ ከተጠሪ ጋር ግንኙነት ያለዉና የክርክሩም መሰረት መሬት በመሆኑ ከአንድ ስረ ነገር የሚመነጩትን ጥያቄ በአንድ ቦታ መቅረቡ እና ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ብይኑ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ አመልካች መሬቱን የያዙት በህጋዊ መንገድ ባለመሆኑ በፍ.ብ.ህ.ቁ.1178 መሰረት ካሳ ሊጠይቁ አይገባም፤ በህግ ባልተፈቀደላቸዉ ቦታ ላይ ያሰፈሩትን መጠየቅ መብት የላቸዉም፡፡ የተሰጣቸዉን ማስጠንቀቂያ ወደጎን በማለት ሲጠቀሙበት የነበረ በመሆኑ የወሰድነዉ እርምጃ ሊነቀፍ አይገባም፤ ስለዚህ የተሰጠዉ ብይን ተገቢ ነዉ ይባልልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩላቸዉ ይዞታዉን እንድለቅ ሳልጠየቅ ደብዳቤ ሳይደርሰኝ ለ16 አመታት ስገብርበት የያዝኩትን ድርጅትና ንብረት አዉድሞብኛል ፤ጉዳዩ የቦታ ማስለቀቅ ጉዳይም አይደለም፤ ስለዚህ በስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲስ አበባ ፍርድ ቤት ነዉ መባሉ ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን በአዋጅ ቁ.361/95 በአንቀጽ 41 የተዘረዘረ ሲሆን ከከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን እንዳለው በአዋጁ አንቀጽ 41/1/ለ/ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አኳያ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች ከሕግ ውጪ ተያዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተባለውን ቦታ በሕግ በተሰጠው ስልጣን አግባብ መቆጣጠር፣ተገቢውን ክትትል ማድረግና አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝም ተገቢውን እርምጃ መውሰድ የሚችሉ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ ጉዳይ የቀረበውን ክርክር ይዘቱን እንዳየነዉ የአመልካች ጥያቄ የነበረዉ ተጠሪዎች ተረክቤ በይዞታዬ ስር የሚገኘዉን እና አልምቼ የምገለገልልበትን መናፈሻ እና በዉስጡ የሚገኙትን የተለያዩ ንብረቶች እኔ በሌለሁበት ከሕግ ውጪ አዉድመውብኛል፣ በመሆኑም በግምት ብር 30,822,160 ያለው ንብረት የወደመብኝ በመሆኑ ገቢዬ ተቋርጧል፣ ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዙ ድንጋጌዎች አግባብ ካሳ ይክፈሉኝ የሚል መሆኑን ከመዝገቡ የምንረዳዉ ነው፡፡ይሁንና ጉዳዩ የቀረበለት ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፤አዋጅ ቁ 361(41) ለ በመጥቀስ የአዲስ አበባ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት በህግ በተሰጣቸዉ ስልጣንና ተግባር ስር የሚቀርቡትን ጉዳዮች የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት በብይን መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ስለዚህ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነዉ የአመልካች ዋና የዳኝነት ጥያቄ የነበረዉ በንብረታቸዉ ላይ ለደረሰዉ የጉዳት ካሳና የቀረ ጥቅም ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ የአስተዳደር አካል የክርክሩ ተሳታፊ በመሆኑ ብቻ በተጠቃሹ አዋጅም ሆነ የአዋጁ ማሻሻያ በሆነው በአዋጅ ቁጥር 408/1996 ድንጋጌዎች ስር በግልጽ እንዲህ አይነት የካሳ ጥያቄ ለመዳኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስልጣን መሰጠቱ ሳይደነገግ የቀረበለትን ጉዳይ ተጠቃሹን አዋጅ በመጥቀስ ስልጣን የለኝም ሲል በብይን መዝገቡን መዝጋታቸው ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ባጠቃላይ የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአዋጅ 25/88 መሰረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን መሆኑን አዉቆ በፍሬ ነገር ደረጃ መርምሮ አስፈላጊዉን ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ በብይን መዝጋቱና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎትም ሳይታረም መቅረቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.108063 በቀን 08/05/2006 ዓ/ም የተሰጠዉና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በመ.ቁ. 97764 በቀን 26/6/2006 ዓ/.ም የጸናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማከራከር (ማየት) ስልጣን እንዳለዉ አዉቆ አግባብነት ካላቸዉ ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. የግራቀኙ የዚህን ችሎት የወጪ ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል::

መዝገቡ ዉሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 104511

መጋቢት 30 ቀን 2007

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡-1. ዳኜ ሀይሉ } ጠበቃ ታየ ቀረበ

2. በከልቻ መኮንን }

ተጠሪዎች፡-1. አለምሰገድ ሀብታሙ - የቀረበ የለም

2. ታሪኩ ተክሌ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን ቡሌ ሆራ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካቾች ተከሳሽ ተጠሪዎች ከሳሾች ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ 1ኛ አመልካች የዕቁብ ሰብሳቢ 2ኛ ተጠሪ ዳኛ እና ጸሀፊ፤ ተጠሪዎች አባል በመሆን1ኛ ተጠሪን በ01/01/2005 ብር 50000 ደርሶአቸዉ 2ኛ ተጠሪን 08/07/2005 ዓም ብር 60,000 ደርሷቸዉ ከቡሌ ሆራ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክእንዲወስዱ ቼክ ተሰጥቷቸዉ ወደ ባንክ ሄደዉ በቂ ገንዘብ የለም በመባላቸዉ አመልካቾች በጋራ እና በተናጥል ይክፈሉንበማለት ጠይቋል፡፡አመልካቾች ባለመቅረባቸዉ በሌሉበት በማየት ተጠሪዎች የእቁቡ አባል መሆናቸዉን በማረጋገጥ በተጠቃሹ ቼክ ባንክ ቤት ሄደዉ ገንዘቡን በማጣታቸዉና አመልካቾችም የዕቁቡ ሀላፊዎች በመሆናቸዉ 110,000.00 ብር ለተጠሪዎች የመክፈል ሀላፊነት አለባቸዉ በማለት ወስኗል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማከራከር የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡በመጨረሻም ጉዳዩን ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የቼክ ክርክር በመሆኑ በአዋጅ ቁ. 25/1988 መሰረት የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታም የቀረበዉ ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ፡፡በመሆኑም አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸዉን ሲገልጹ፡-በስር የቀረበዉ ክስ የነበረዉ ያልተከፈለኝ የእቁብ ገንዘብ እንዲከፈለን፤ የሚል ሆኖ ሳለ ክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ የቼክ ክርክር በመሆኑ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የአዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 5(7) መሰረት መዝጋቱ ባግባቡ አይደለም፤ አመልካቾች የእቁብ ጸሀፊና ሰብሳቢ ናቸዉ በማለት፤ በምስክር ሳይጣራ ክፈሉ መባላችን ሊታረም ይገባል፤ ቼኩ የተፈረመዉ በስር ተከሳሽ በነበሩት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቶ ቦጋለ ግዛዉ ስም ነዉ፤አመልካቾች ከቼኩ ጋር ግንኙነት የለንም፤ አልሰበሰብንም፤ የዕቁቡ ዳኛ መሆኑንና የሚመለከተዉ መሆኑን አዉቆ ጠፍቶ እያለ የአሁን አመልካቾችን ሀላፊ ናችሁ መባላችን ስህተት ነዉ፣ የዕቁብ ደንብ ለዕቁብተኞች ዉል ነዉ ፤እኛ ደግሞ ከዉልም ሆነ ከህግ የመነጨ ግዴታ የለብንም፣ ስለዚህ ገንዘቡን የመክፈል ሀላፊነት አለባችሁ ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካቾች እና ተጠሪዎች ክርክር በቼክ አማካኝነት የተሰጠን የዕቁብ ገንዘብ በቂ ስንቅ ባለመኖሩ ሊከፈለን ባለመቻሉ ይከፈለን በማለት የጠየቁት ዳኝነት የክልሉ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁ.25/88 መሰረት ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ ተጠሪዎች ባለመቅረባቸዉ መልስ መስጠት መብታቸዉ ታልፎ በአመልካቾች የቀረበዉን ቅሬታ እና የስር ክርክርን አይተናል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተጠቀሰዉን ይመስላል፡፡ በመሆኑም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንግዲህ ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር የስር ክርክርን እንዳየነዉ ተጠሪዎችባቀረቡት ክስ በአመልካቾች ሰብሳቢነት፤ ጸሀፊነት እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ዳኛ በሆኑበት የእቁብ አባል በመሆን እቁብ ደርሷቸዉ ተጠቃሹን ገንዘብ እንዲወስዱ ቼክ ተሰጥቷቸዉ ወደ ቡሌ ሆራ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በመሄድ በቂ ስንቅ ባለመኖሩ መዉሰድ ባለመቻላቸዉ አመልካቾች በቼክ የተጠቀሰዉን ገንዘብ በአንድነትና ነጠላ እንዲከፍሏቸዉ በጠየቁት መሰረት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማከራከር ዳኝነት ቢሰጡም በመጨረሻ ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት ክርክሩ ከቼክ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት አዋጅ ቁ 25/88 5(7) በመጥቀስ ቅሬታዉን ሰርዞታል፡፡በዚህም ችሎት ሊታይ የሚገባዉ ነጥብ ሆኖ የተገኘዉ የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን ያለማስተናገዱን አግባብነት ነዉ፤ በመሆኑም የግራቀኙ መሰረታዊ ክርክር ዕቁብን ተከትሎ ያዋጡት ገንዘብ የመክፈያ ቀኑ ደርሶ አመልካቾች የእቁቡ አመራር በመሆናቸዉ ተጠቃሹን ገንዘብ የመክፈል ሀላፊነት ስላላቸዉ ቼክ ቆርጠዉ በሰጧቸዉ መሰረት ወደ ባንክ ቤት በመሄድ ገንዘባቸዉን ባለማግኘታቸዉ የዕቁቡን ግንኙነታቸዉን መሰረት አድርጎ እንዲመለስላቸዉ የቀረበ ዳኝነት እንጂ የክርክሩ መሰረት ቼክ ነዉ በማለት አይደለም፡፡ ቼክ የዕቁብ ገንዘቡ ላለመከፈሉ ማረጋገጫ ሆኖ በተራ ሰነድ ማስረጃነት የቀረበ እንጂ በዋናነት ቼኩ ራሱ በንግድ ሕጉ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን አተገባበር ለመመርመር የሚያስችል ክርክር በሚያስነሳ መልኩ የቀረበ ያለመሆኑን ከክርክሩ ይዘት ለመረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የክርክሩ አጠቃላይ ይዘት የእቁብ ገንዘብን ይከፈለኝ ጥያቄ መሰረት አድርጎ ቼኩን በተራ የሰነድ ማስረጃነት የቀረበበት ሁኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ችሎት የግራቀኙን የተጠየቀዉን ዳኝነት እና የክርክሩን አቅጣጫ ባላገናዘበ መልኩ ጉዳዩ በአዋጁ ቁ.25/88 ስር የሚታይ ነዉ ሲል የሰበር አቤቱታውን ሳይመለከተው መዝገቡን መዝጋቱ ስነ ስርዓታዊ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ባጠቃላይ ክልሉ ከፍተኛ እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቀረበላቸዉ የዳኝነት ጥያቄ አከራክረዉ ዉሳኔ ላይ ቢደርሱም የክልሉ ሰበር ችሎት የቀረበለትን የዳኝነት ጥያቄ ከወዲሁ ስልጣኔ አይደለም ,በማለት መዝገቡን መዝጋቱ የክርክሩን ይዘት ያላገናዘበ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ ትዕዛዙ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል የቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 08843 በቀን 18/10/2005 ዓ/ም እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 168299 በቀን 26/9/2006 ዓ/ም የሰጡትን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 34(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ጉዳዩ በክልሉ የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት በክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታዬ በመሆኑ የክርክሩ ይዘትም የፌዴራል ጉዳይ ሊባል የማይችል፣የቼክ ጉዳይ ባለመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎት በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይባፍ፡፡

3. የግራቀኙ የወጪ ኪሳራቸዉን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94952

መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኰንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዙሪያሽ ተገኝ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የሺ ውድዬ - ረ/ኢንስፔክተር ይመር ዮሴፍ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሞት የተለየው ተጋቢ የግል ንብረት ነው የተባለን ቤት ከሌላኛዋ ተጋቢ ለማስለቀቅ ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበሩት በአሁኗ አመልካች ላይ በ08/02/2003 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱይዘትም ባጭሩ፡-ከሳሽ የሟች ልጃቸው አቶታደሰ የሱፍ እናት እና ወራሽ መሆናቸውን፣ሟች እና ተከሳሽ በ17/09/1997 ዓ.ም. በባህላዊ ስርዓት ጋብቻ ፈጽመው አብረው ይኖሩ የነበረ መሆኑን፣በን/ስ/ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 09/14 የሚገኘው ቁጥሩ አዲስ የሆነው መኖሪያ ቤት ከጋብቻው በፊት የተፈራ የአቶ ታደሰ የሱፍ የግል ሀብት ስለመሆኑ ጋብቻውን በፈጸሙበት ጊዜ ባደረጉት የጋብቻ ውል ማረጋገጣቸውን፣ይሁን እንጂ ጋብቻው በልጃቸው ሞት ምክንያት መፍረሱን ተከትሎ ተከሳሽ ቤቱን እና በክሱ የተጠቀሱ የቤት ቁሳቁሶችን ለከሳሽ እንዲያስረክቡ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሽ የዋጋ ግምቱ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ) የሆነውን ቤት እና የብር 10,000 (አስር ሺህ) የዋጋ ግምት ያላቸውን የቤት ቁሳቁሶች ለከሳሽ እንዲያስረክቡ እና ለስምንት ወራት ከቤቱ ኪራይ የሰበሰቡትን ገንዘብ ብር 8,000 (ስምንት ሺህ) ለከሳሽ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ በበኩላቸው በ09/07/2003 ዓ.ም. በሰጡት መልስ ከጋብቻው በፊት ሟች የሰሩት አንድ ሳሎን እና አንድ መኝታ ያለው ሁለት ክፍል ቤት ሆኖ ከጋብቻቸው በኃላ ሶስት ተጨማሪ ክፍሎችን ከሟች ጋር የሰሩ በመሆኑ ቤቱ በሙሉ የሟች የግል ሀብት እንደሆነ ተደርጎ የቀረበው ክስ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣የቤት ቁሳቁሶቹ ግምት ከብር 1,000 የማይበልጥ መሆኑን እና ከቤቱ ኪራይ የተሰበሰበው የገንዘብ መጠንም ከቀለብ አልፎ ሊጠራቀም የማይችል መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቱ ውርሱ ተጣርቶ ሪፖርት እንዲቀርብለት ጉዳዩን ለውርስ አጣሪ የመራው ሲሆን አጣሪው ውርሱን ማጣራቱን ገልጾ ነገር ግን ቤቱ ሰነድ አልባ ስለመሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑ በመሆኑ የውርስ ሀብት ነው ለማለት ያልተቻለ መሆኑን በመግለጽ ሪፖርት አቅርቧል፡፡ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ቤቱ ሰነድ አልባ መሆኑ ክርክሩን አይቶ ውሳኔ ከመስጠት የማይከለክል መሆኑን እና በመዝገቡ የሚሰጠው ውሳኔ ተፈጻሚነት የሚኖረው የቤቱን ሕጋዊነት በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ተመስርቶ መሆኑን ገልጾ ተጋቢዎቹ ከጋብቻቸው በኃላ የሰሩት ተጨማሪ ግንባታ መኖር አለመኖሩን ለማጣራት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ቤቱ የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ስለመሆኑ ተከሳሽ በፈረሙት የጋብቻ ውል በማረጋገጣቸው ከቤቱ ድርሻ አላቸው ማለት ያልተቻለ መሆኑን፣ቤቱ በጋብቻ ውሉ ላይ የተገለጸው "ቤት" ተብሎ እንጂ የተከሳሽ ምስክሮች እንደገለጹት "የሸራ ወይም የላስቲክ ቤት" ተብሎ አለመሆኑን፣ስለቤት ቁሳቁሶች በከሳሽ ምስክሮች የተገለጸ ነገር አለመኖሩን እና ከቤቱ ኪራይ ይሰበሰብ የነበረው የገንዘብ መጠንም ከቀለብ አልፎ ሊጠራቀም የሚችል አለመሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ተከሳሽ ክስ ያስነሳውን ቤት ለከሳሽ ለቀው እንዲያስረክቡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በጋብቻ ውሉ ላይ ቤቱ የአቶ ታደሰ የሱፍ የግል ንብረት ነው ተብሎ መጠቀሱን ብቻ መሰረት በማድረግ በጋብቻው ጊዜ በሁለቱ ተጋቢዎች በጋራ ከታደሰው ቤት እና በጋራ ከተሰሩት ተጨማሪ ክፍሎች ውስጥ አመልካች ድርሻ የላቸውም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ክርክሩ የታየበትን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ጭምር ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡
በዚህም መሰረት አመልካች አድራሻው በክሱ የተጠቀሰው ቤት ከጋብቻው በፊት የተፈራ የተጠሪ አውራሽ የግል ንብረት መሆኑን በማረጋገጥ ጋብቻው በተፈጸመበት ጊዜ የጋብቻ ውል የፈረሙ መሆኑ በአመልካች ያልተካደ እና የጋብቻ የውል ሰነዱን ጨምሮ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የጋብቻ ውሉ በተፈረመበት ጊዜ የነበረው ከላስቲክ እና ከሸራ የተሰራ ዳስ ሆኖ እያለ ቤት እንደሆነ አድርገው ያስፈረሙኝ አላግባብ ነው በማለት አመልካች በሰበር ማመልከቻቸው ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡
በሌላ በኩል ግን በጋብቻው ወቅት ተጨማሪ ክፍሎች የተገነቡ ወይም የተሰሩ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ቤቱ ሙሉ በሙሉ የሚች የግል ሀብት እንደሆነ ተደርጎ ለተጠሪ እንድትለቅ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት የአቤቱታ ነጥብ በክርክሩ ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች አንጻር በአግባቡ ሊጤን እና ሊመረመር የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በዚህም መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሚያየው ፍርድ ቤት በፍትሐብሄር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 246፣247 እና 248 ድንጋጌዎች መሰረት ለጉዳዩ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በማስረጃ ካጣራ በኃላ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ በክርክሩ የተያዘው ጭብጥ ምን እንደሆነ፣ጭብጡ እንዴት እንደተወሰነና በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የተወሰነው በምን ምክንያት እንደሆነ በፍርድ ሀተታው ውስጥ መግለጽ እንዳለበት በቁጥር 182 (1) ስር በአስገዳጅነት ተደንግጎአል፡፡
በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት እና የተከራከሩት በጋብቻ ውሉ መሰረት ክርክር ያስነሳው ቤት የልጃቸው የግል ሀብት መሆኑን በመግለጽ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው መልስ የሰጡት እና የተከራከሩት ከተጠሪ ልጅ ጋር በጋብቻ ውስጥ በኖሩባቸው ከ1997 ዓ.ም.እስከ 2002

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓ.ም.ድረስ ባሉት ጊዜያት ቀደም ሲል ከነበሩት ሁለት ክፍል ቤቶች በተጨማሪ ሶስት ክፍል ቤቶችን በጋራ መስራታቸውን በመግለጽ ነው፡፡ከዚህ የግራ ቀኙ የክርክር አቋም በመነሳት በማስረጃ ሊጣራ የሚገባው ተጋቢዎቹ ከጋብቻቸው በኃላ የሰሩት ተጨማሪ ግንባታ አለ ወይስ የለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመግለጽ ፍርድ ቤቱ ለክርክሩ የያዘው ጭብጥ ተገቢነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ ጭብጥ ላይ የተሰሙት የግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል ሲታይም በአሁኗ አመልካች በኩል የተሰሙት ሁለት ምስክሮች ሟች ከቀድሞ ሚስታቸው ጋር የሰሩትን አንድ ክፍል ቤት አመልካች እና የተጠሪ ልጅ በጋብቻቸው ጊዜ አፍርሰው ቤቱን እንደ አዲስ ሶስት ክፍል አድርገው መስራታቸውን በተመሳሳይ ሁኔታ የገለጹ መሆኑን እንዲሁም በአሁኗ ተጠሪ በኩል ከተሰሙት ሁለት ምስክሮች መካከል 2ኛው ምስክር ቤቱ ጎርፍ የሚገባበት በመሆኑ አጥሩ ሲፈርስ የተጠጋገነ ከመሆኑ ውጪ ከጋብቻው በኃላ የተሰራ ቤት አለመኖሩን በመግለጽ የመሰከሩ ቢሆንም የተጠሪ 1ኛ ምስክር ግን ሟች ከቀድሞ ባለቤታቸው ጋር የሰሩት ዋናውን ቤት መሆኑን እና ከአመልካች ጋር ጋብቻ ከፈጸሙ በኃላ ደግሞ ሁለት ክፍል ቤት እና ኩሽና በጋራ መስራታቸውን በመግለጽ መመስከራቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ፍርድ ቤቱም ከላይ በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 182 (1) አስገዳጅ ድንጋጌ መሰረት ውሳኔውን በሚሰጥበት ጊዜ ይህንን የግራ ቀኙን ምስክሮች የምስክርነት ቃል መዝኖ የአንደኛውን ወይም የሌላኛውን ወገን ምስክሮች የምስክርነት ቃል የተቀበለበትን ወይም ያልተቀበለበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ ማስፈር የሚጠበቅበት ሆኖ እያለ ቤቱ የሟች የግል ሀብት ነው በማለት ለደረሰበት ድምዳሜ እና ለሰጠው ውሳኔ መሰረት ያደረገው የጋብቻ ውሉን ብቻ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያመለክታል፡፡
ይህም በአንድ በኩል ተጋቢዎቹ ከጋብቻቸው በኃላ የሰሩት ተጨማሪ ግንባታ አለ ወይስ የለም? በሚል ፍርድ ቤቱ በጭብጥነት የያዘው ነጥብ ከግራ ቀኙ የክርክር አቋም አንጻር ተገቢነት ያለው ቢሆንም በሌላ በኩል ግን ቤቱ በጋብቻ ውሉ መሰረት የሟች የግል ሀብት ነው በማለት የደረሰበት ድማዳሜ እና የሰጠው ውሳኔ ከላይ የተጠቀሰውን ጭብጥ ለማጣራት በተሰሙት የግራ ቀኙ ምስክሮች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡የዚህ ዓይነቱ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ደግሞ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 182 (1) አስገዳጅ ድንጋጌን እና በአንድ ክርክር በመዝገቡ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36848 በ11/02/2001 ዓ.ም. እና በሌሎችም መዝገቦች የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡

በክርክሩ በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ከጋብቻው በፊት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት መሆኑ በጋብቻ ውሉ ከተረጋገጠው አንድ ክፍል ዋናው ቤት በተጨማሪ ተጋቢዎቹ በጋብቻቸው ጊዜ ሶስት ተጨማሪ ክፍሎችን መስራታቸው ከሆነ ደግሞ ይህ ሁኔታ በግራ ቀኙ መብትና ግዴታ ላይ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት መታየት ይኖርበታል፡፡በመሰረቱ ተጋቢዎች ከጋብቻቸው በፊት በየግል የነበሯቸው ንብረቶች የየግላቸው ሆነው እንደሚቀሩ እና ከጋብቻቸው በኃላ ያፈሯቸው ንብረቶች ግን የጋራቸው እንደሚሆኑ በአዋጅ ቁጥር 213/1992 በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 57 እና 62 ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡በተያዘው ጉዳይ ከጋብቻው በፊት የነበረው እና በጋብቻ ውሉ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት ነው ተብሎ የነበረው አንድ ክፍል ዋናው ቤትም ቢሆን በጋብቻው ውስጥ ፈርሶ እንደ አዲስ መሰራቱ እና ኩሽናውን ጨምሮ ሶስት ተጨማሪ ክፍሎች በጋብቻው ውስጥ መሰራታቸው በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ከጋብቻው በፊት የነበረው ቤት ፈርሶ እንደ አዲስ የተሰራ እና ሶስት ተጨማሪ ክፍሎች የተሰሩ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ እነዚህ ስራዎች የተከናወኑት በጋብቻው ውስጥ እስከሆነ እና እነዚህ ተጨማሪ ስራዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከናወኑት በሚች የግል ገንዘብ ነው በሚል የቀረበ ክርክር እና ማስረጃ እስከሌለ ድረስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 63 (1) መሰረት ክርክር ያስነሳው ቤት የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ የሕግ ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡

ሲጠቃለል ከጋብቻው በኃላ ስለተከናወኑት ተጨማሪ ስራዎች በግራ ቀኙ ምስክሮች የተመሰከረውን ፍሬ ነገር በዝምታ አልፎ በጋብቻ ውሉ ላይ ብቻ በማተኮር ክርክር ያስነሳው ቤት ከጋብቻው በፊት የተፈራ የሚች የግል ንብረት ነው በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው ውሳኔ በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ የተሰጠ እና መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58686 በ02/07/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 135319 በ22/02/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በን/ላ/ክፍለ ከተማ በቀበሌ 09/14 የሚገኘው ቁጥሩ አዲስ የሆነው መኖሪያ ቤት ከጋብቻው በፊት የተፈራ የአቶ ታደሰ የሱፍ የግል ንብረት በመሆኑ አመልካች ቤቱን ለቀው ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
3. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው በን/ላ/ክፍለ ከተማ በቀበሌ 09/14 የሚገኘው ቁጥሩ አዲስ የሆነው መኖሪያ ቤት ሚች አቶ ታደሰ የሱፍ እና አመልካች በጋብቻው ጊዜ ያፈሩት የጋራ ሀብት ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. ከላይ ከተጠቀሰው ቤት ውስጥ ግማሹ የአመልካች በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ሀብት፣ቀሪው ግማሽ ደግሞ የተጠሪ የውርስ ሀብት በመሆኑ ግራ ቀኙ የሚቻል ከሆነ በዓይነት፣የማይቻል ከሆነ በስምምነት አንዳቸው ለሌላኛው የዋጋ ግምት ድርሻ ከፍሎ በማስቀረት፣በዚህ የማይስማሙ ከሆነም በሐራጅ እንዲሸጥ ተደርጎ የሽያጩን ገንዘብ እኩል እንዲካፈሉ በማድረግ ሊካፈሉት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
5. ከላይ በተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰው የክፍፍል ውሳኔ አፈጻጸም ጉዳዩ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል የቤቱን ሕጋዊነት አስመልክቶ ሊያነሳ የሚችለውን ጥያቄ የሚያስቀር አይሆንም በማለት ወስነናል፡፡
6. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ የቤት ቁሳቁሶችን እና ከቤቱ ኪራይ የተገኘውን ገቢ አስመልክቶ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
7. ጥያቄው ሲቀርብለት ከላይ በተራ ቁጥር 3፣4 እና 5 በተጠቀሰው ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
8. ቁጥሩ 58686 የሆነው መዝገብ ተመላሽ ይደረግ፡፡
9. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
10. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ **ብ/ግ**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95680

መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ የሺ ተሾመ

ተጠሪ፡- አቶ መስፍን ኃይሉ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የሎሜ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሣሽ ሲሆኑ የአሁን ተጠሪ ተከሣሽ ነበሩ አመልካች ባቀረቡት ክስ፡- ከተጠሪ ጋር የነበረው ጋብቻ የፈረሰ መሆኑን በመግለፅ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ንብረት ያካፍለኝ በማለት በኤጀሬ ከተማ የሚገኝ በ198 ካ.ሜ.ላይ ያረፈ ቤትና ኩሺና፣ ዲናሞ ብቻውንና የወፍጮ ዲናሞ በንግድ ባንክ ያለ ገንዘብ በ369 ካ.ሜ. ላይ 90 ቆርቆሮ የተሠራ ቤት የሞተር ቤት 2 ክፍል በልማት የተከፈለ 80,000 ብር እና የተሸጠ የወፍጮ እና ጀኔሬተር ገንዘብ(13,000) ያካፍለኝ ብላለች በ198 ካ.ሜ.ላይ ያረፈው ቤት በ1982 ከጋብቻ በፊት (በ17/02/82) የገዛሁትን ነው፡፡በ369 ካ.ሜ. ላይ ያለው ቤት 85 ቆርቆሮ እንጂ 90 አይደለም በመንገድ ሥራ የመኖሪያ ቤት ፈርሶ የተከፈለኝ 54,000 ባገኘሁት ካሣ ከአቶ መለሰ ጫካ ከተባለ ሰው ገንዘብ ተበድሬ የሰራሁት የግል ንብረት ነው፡፡ የካሣ ገንዘቡም ብር 80,000 ሣይሆን ብር 54,000 ነው፡፡ በናፍጣ የሚሠራ ሁለት ወፍጮና ጀኔሬተር 13,000 የተገዛ ቢሆንም 11,495.55 ተጨምሮበት በ24,495.85 ወደ ኤሌክትሪክ ተቀይሮ በሥራ ላይ የሚገኝ እንጂ በጥሬ ገንዘብ የለም፡፡ በተጨማሪም የጋራችን የሆነ የላሜራ ሱቅ ሸቀጥ ግምቱ 60,000 በከሣሽ እጅ ይገኛል፡፡ የመብራት ሀይል ዕዳ (የወፍጮ) 21,000 የጋራችን ነው በመጨረሻም በ369 ካ.ሜ. ቦታ ላይ ያለውም ቤት የግሌ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም በግራ ቀኙ የተማመኑትን ንብረት በማለፍ አከራካሪ የሆኑትን ፍሬ ነገሮች በመለየት ንብረቶችን አስመልክቶ መስተዳደሩና የአካባቢ ሽማግሌዎች እንዲያጣሩ በማድረግ ተከሣሽ (ተጠሪ) ተበደርኩ የሚለውን 60,000 አመልካች የማታውቀውና ያልተረጋገጠ ነው፡፡ባንክ ቤት አለ የተባለው ገንዘብ በአመልካች በኩል እንዲያረጋግጡ አልተደረገም በማለት ውድቅ ካደረገው በኃላ የተቀሩትን ንብረቶች በቀረበው ማስረጃ በማረጋገጥ እኩል እንዲካፈሉ ሲል በተለይ በ198 ካ.ሜ. ቦታ ላይ ያለው ቤት የተጠሪ በግል ገንዘባቸው ገዝተው በ369 ቦታ ላይ ቤት መስራታቸውን የካሣ ገንዘብ 54,000 ይክፈሉ ሲል በ369 ላይ ያረፈውን ቤት እኩል ይካፈሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ወስኗል፡፡የይግባኙም ፍ/ቤት የግራ ቀኙን በማከራከር አጣርቶ ሲያፀናው በክልሉ ሰበርም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 ተሰርዟል፡፡

የአመልካች አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማሳረም ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤት ከተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት ለ23 አመት ስንኖር ያፈራነውን ወፍጮ ከነ ቤቱ መኖሪያ ቤት አንድ ኩሽና አንድ ሽንት ቤት በ198 ካ.ሜ. ላይ ሰፍሮ የሚገኝ ጠጅ ቤት ፈርሶ መሬቱም ሲወሰድ የተከፈለውን ካሣ ገንዘብ 54,000 ብር በ369 ካ.ሜ ቦታ ላይ የተሰራውን ቤት አመልካች 54,000 ለተጠሪ ከፍላ ቤቱን በጋራ ትካፈል መባሉ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል ሲሉ አመልካች ጠይቀዋል፡፡

በዚህም መሠረት ይህ ችሎትም አመልካች 54,000 ብር ከፍላ በ369 ካ.ሜ.ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት ትካፈል መባሉና በ198 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያለው ቤት በላዩ ላይ የተተከለው ወፍጮ ቤት በግል የተሰራነው?ወይስ በጋብቻ ውስጥ? የሚለው ወደ ድርጅትነት የተለወጠው መቼ ነው?የሚለው እና ለመብራት ሀይል የተከፈለው 24,000 መቼ ነው?የሚሉት ነጥቦች እንዲጣሩ በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙ በቀረበው አቤቱታ ላይ መልስና የመልስ መልስ በመቀባበል እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡

በመሆኑም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል፡፡እኛም እንዳየነው አመልካች ጋብቻ መፍረሱን ጠቅሰው የጋራ ንብረታችን ነውና ልንካፈል ይገባል የሚሉትን የንብረት ዝርዝር በማቅረብ የጠየቁ ሲሆን የሥር ወረዳ ፍ/ቤትም በዝርዝር የቀረበለትንና የዳኝነት ጥያቄ የታመነውንና ተቃውሞ በተጠሪ የቀረበበትን ነጥብ በመለየት በማስረጃ አጣርቶ ውሣኔ አሳርፎበታል፡፡

እኛም በማስረጃ ረገድ ተጣርቶ ውሳኔ ያገኘውን በመቀበል በጭብጥነት በተያዙት ነጥቦችን ስናየው ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ ከአመልካች ጋር በነበረበት ጊዜ የነበረው ወፍጮ አብረው ሲጠቀሙበት የነበረ የመብራት ኃይል የአገልግሎት ዋጋ ብር 24.000.00 መክፈላቸውን አረጋግጠው የጋራ ዕዳቸው መሆኑንና በድርሻቸው አመልካች እንዲከፍሉ ጠይቋል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተጠቀሙበት መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ቤት በነበሩበት ወቅት የቆጠረ የመብራት ዋጋ በመሆኑ ዕዳውን ሊከፈሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ እንግዲህ አመልካች ከወፍጮ ገቢ ተጠቃሚ አይደለሁም ሲሉ ባልተከራከሩበት የዕዳው ተጋሪ መሆን የለብኝም በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የለውም በመሆኑም ይኸኛውም የውሳኔ ክፍል ባግባቡ ተጣርቶ የተወሰነ በመሆኑ ተቀብለነዋል፡፡

ሁለተኛውን አከራካሪውን በ198 ካ.ሜ ይዞታ አስመልክቶ ተጠሪ ከጋብቻ በፊት ገዝቼ እያለሁ በመንገድ ምክንያት ፈርሶ ያገኜሁትን ካሳ ገንዘብ 54.000 ብር በመያዝ ከአመልካች ጋር ተጋብተው በ369 ካ.ሜ ቦታ ላይ የሰፈረውን ቦታ ሰራን ፣ ስለዚህ ንብረቶቹ የግል ንብረት ነው በማለት ሲከራከሩ አመልካች በበኩላቸው ይዞታው የተገዛውና የተሰሩት አንድ ክፍል ቤት ብቻ መሆኑንና ይህ ፈርሶ ተስፋፍቶ በ369 ካ.ሜ ቤት ተሰርቶ የጠጅ ቤት ድርጅት ስንጠቀምበት የነበረና የፈረሰ በመሆኑ ከ23 አመት በኃላ ተጠሪ የግሌ ነው ሲል መከራከሪያ ሊያደርጉት አይገባም ይላሉና እኛም ተጠሪ ተቀበልኩ የሚሉትን ገንዘብ ከጋብቻ በፊት ያገኜሁት ነው ቢሉም ከአመልካች ጋር የ369 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ቤት በመስራት አስፋፍቶ ለረዥም ዓመታት መኖራቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላከራከረ ነው፡፡ እንግዲህ በእነዚህ ባለፉት አመታት በግራ ቀኙ አስተዋጽኦ ቤቱ ከተገነባ በቀጣይነት የሚገኙት ገቢዎች የሉም ማለት አይቻልም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ንብረቶች መቀላቀላቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ተጠሪ ተጠቃሹ ገንዘብ የግሌ ነው የሚሉበት ምክንያት ከጋብቻ በፊት ያገኘሁትና በዚሁ ገንዘብ በ369 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ቤት ሰርተናል በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ ቁ.69/1995 አንቀፅ 74/1/ መሠረት ባልና ሚስቱ በየግል ያገኟቸውን ንብረትም ሆነ ገንዘብ በግል ይዘው መቀጠል እንደሚችሉ ሲደነገግ ይህ የግል የተባለው ንብረት የግል ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው በተጠቃሹ ህግ አንቀፅ 74/2/ ስር የግል ይባልልኝ ተብሎ በፍ/ቤት ሲፀድቅ መሆኑን በግልጽ ደንግጐታል፡፡ ይህ ደግሞ በህጉ እንደዋነኛ መስፈርት የተቀመጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ በዚህ መልኩ ተጠቃሹን ንብረት ወይም ገንዘብ አስመዝግቤያለሁ ሲሉ ያቀረቡት ክርክር አልነበረም፡፡ ይህ ሆኖ ግለ በስር ፍ/ቤቶች አመልካች 54,000 ብር በመክፈል ቤቱን ይካፈሉ የሚለውን የውሣኔ ክፍል ባለመቀበል፡፡ የተቀሩትን የውሣኔ ክፍሎች ባልነካ መልኩ በ369 ይዞታ ላይ ያረፈውን ቤት 54,000 አመልካች ይክፈሉና ቤቱን ይካፈሉ መባሉና በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች ያለመታረሙ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 34054 በቀን 23/07/05 የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ 33974 በቀን 06/12/2005 እና የክልሉ ሰበር ሰሚ በመ.ቁ 173245 በቀን 28/02/2006 የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሎ ፀንቷል፡፡

2. አመልካች አከራካሪውን ብር 54,000.00 ለተጠሪ ግይከፍሉ የጋራ ነው የተባለውን ቤት ሊካፈሉ ይገባል ብለናል፡፡

3. የወጪ ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ውሣኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስ/መ/ቁ.88275
ጥር 19 ቀን 2007.ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም
መስጠፉ አህመድ
ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ኃይለሚካኤል ልኬ ሎሶ - የቀረበ የለም

ተጠሪ ፡- 1. አቶ መኮነን በለጠ - ጠበቃ መለሰ ጦና ቀረቡ

2. ወ/ሮ አምሳለች ዘበን - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የቅድሚያ ግዥ መብት ጥያቄ የሚስተናገድበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአፈፃጸም ከሳሽ የሆኑት የአሁኗ 2ኛ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በዋናው ፍርድ መሰረት እንዲፈፅምላቸው ባቀረቡት የአፈጻም ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ባልና ሚስት የነበሩ ሲሆን ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈርሶ የጋብቻ ውጤት ከሆኑት ንብረቶች መካከል ለአሁኑ ክርክር መነሻ የሆነውን መኖሪያ ቤት በክልሉ የቤተሰብ ሕግ መሰረት የተቀመጡት የክፍፍል ስርዓቶችን መሰረት በማድረግ ቤቱ በግልጽ ጨረታ መሸጥ እንደአለበት ፍርድ ቤቱ ውሳኔ አሳርፎ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪተወዳድረው የጨረታ አሸናፊ በመሆን የቤቱ ገዥነታቸው ከታወቀ በኋላ የአሁኑ አመልካች ቤቱን የመልሶ መግዛት መብት እንደአላቸው ጠቅሰው ቤቱን እንዲያስቀሩ እንዲወሰንላቸው ለፍርድ ቤቱ አመልክተው የአሁኑ ተጠሪዎች ይህንኑ የአመልካችን ጥያቄ ተቃውመው የመልሶ መግዛት መብት ለአመልካች ሊሰጣቸው አይገባም የሚለውን መከራከሪያ ሁለቱም ተጠሪዎች ከማቅረባቸውም በተጨማሪ የአሁኗ 2ኛ ተጠሪ አመልካች አዲስ አበባ ውስጥ መንግስት በሰጣቸው ደረጃውን በጠበቀ ቤት እንደሚኖሩና ራሳቸው ግን ሁለት ልጆችን ይዘው ቤት የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው የመልሶ መግዛት መብት ለራሳቸው እንዲጠበቅላቸው ጭምር ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካች ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ውደቅ አድርጎ የጨረታውን ውጤት እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡በዚህ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ የሚገዛ ቢሆንም የክልሉ የቤተሰብ ሕግ ስለመልሶ የመግዛት መብት የሚደነግገው ጉዳይ ያለመኖሩንና በዚህ ሁኔታ ደግሞ በፍትሐ ብሔር ሕጉ የጋራ ንብረትን መልሶ ስለመግዛት የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ተፈፃሚ ማድረግ በሕግ አተረጓጎም መርህ ተገቢ መሆኑን ጭምር ዘርዝሮ የአመልካች ቤቱን መልሶ የመግዛት መብታቸው ሊጠበቅ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ ሽሮታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበው ተቀባይነት ያጡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን በተናጠል ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ መዝገቦችን አጣምሮ በመመርመር የአሁኑ አመልካች የመልሶ መግዛት መብት አላቸው ተብሎ የተሰጠውን የከተማውን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ ያጸናውን የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ሽሮ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቶታል።የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የጋብቻ ውጤት የሆነውን ቤት መልሶ ለመግዛት በፍትሃ ብሔር ሕጉ በአንቀጽ 1261፣ከአንቀፅ 1386- 1409 ስር የተጠቀሱት ድንጋጌዎች መብት የሚሰጣቸው ሁኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ መሰረት የሚዳኝ እንጂ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች የሚዳኝ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢውን የሕግ አተረጓጎምና አተገባበር ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ በዚህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37297 የተሠጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው።የሰበር አቤቱታቸው ተመርምሮም ከተጠቃሽ ድንጋጌዎችና ክክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንጻር የአመልካች ጥያቄ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የአሁኑ አመልካች የጋራ ንብረት ነው የሚለውን ቤት ከ1ኛ ተጠሪ መልሶ የመግዛት መብት ያለው መሆኑ አለመሆኑን፣ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1394፣ ከቁጥር 1405-1408 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እና የፍትሐብሔር ሕጉ ስለ ጋራ ባለሃብትነት በቁጥር 1257 እና የሚቀጥሉት አንቀጾች የደነገገውን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 103(2) እና 102 ድንጋጌዎች አኳያ ለመመርመር ተብሎ በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል።

በክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ እኩል መብት ያላቸው መሆኑን፣የቤቱ የክፍፍል ስርዓት እንዲፈጸም የተደረገውም የክልሉን የቤተሰብ ሕግ መሰረት በማድረግ መሆኑን፣አመልካች አሁን አጥብቀው የሚከራከሩት የክልሉ የቤተሰብ ሕግ ስለመልሶ መግዛት የሚያስቀምጠው መፍትሄ ስለሌለ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ያሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ሊኖራቸው ይገባል በማለት መሆኑን፣2ኛ አመልካችም ቤቱን መልሶ የመግዛት መብት ሊጠበቅልኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት ጥያቄ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን የሰ/መ/ቁጥር 90586 የሚያሳይ መሆኑን፣1ኛ አመልካች አከራካሪውን ቤት የገዙት በግልጽ በተደረገው ጨረታ ተወዳድረው ጨረታው ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ መሆኑን ከመሆኑም በላይ በዚህ የጨረታ ሂደት አመልካችም ሆነ የአሁኗ 2ኛ ተጠሪ እንዲሳተፉ ጨረታው እንዲከናወን ያዘዘው የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያልሰጠበት ጉዳይ መሆኑን ነው።

በመሰረቱ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ስርዓት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትም ሆነ በክልል ሕግጋት መንግስታት የተረጋገጠውን የእኩልነት መብት መሰረት አድርጎ መከናወን ያለበት ጉዳይ ነው። የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ስርዓት የሚከናወንበትን መንገድ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 በቅደም ተከተል ያስመቀጣቸው መንገዶች ከአንቀፅ 90 እስከ 93 ድረስ ባሉት የሰፈሩ ሲሆን ስራ ላይ ያሉት የክልል የቤተሰብ ሕግጋትም አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን ይዘው እናገኛለን። ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 ሲታይም የባልና ሚስት ንብረት የሚከፋፈልበትን ሥርዓት ከአንቀፅ 101

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እስከ 105 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች አካቶ ይዟል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለውም የጋብቻ ውጤት የሆነው የጋራ ንብረት ክፍፍል ሊከናወን የሚገባው የእኩልነት መርህን መሰረት አድርጎና የተጋቢዎችን ፈቃድ በመመርኮዝ መሆኑን ነው፡፡የተጋቢዎች ስምምነት ከሌለ ደግሞ ክፍፍሉ መፈፀም ያለበት በሕጉ የተመለከተውን ቅደም ተከተል መሰረት አድርጎ ሊሆን እንደሚገባ ሕጉ ያስገነዝባል፡፡በመሆኑም የጋብቻ ውጤት የሆነውን ንብረት ለማከፋፈል የበላይነት ያለው የቤተሰብ ህጉ ነው፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1386 እና ተከታዩቹ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው የጋራ ባለሐብቶች ለሆኑ ወገኖች እንዲሁም የጋራ ባለሐብት የሆኑ ወራሾች መካከል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1388 እና 1392 ይዘት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ የመግዛት መብት በሕግ ጥበቃ የተደረገለት መብት ሲሆን ሕጉ ሊያሳካ ያሰበው አላማም ከዘር የወረደ ንብረትን በተመለከተ ዘመዳሞች የሚኖራቸውን ስሜት ለመጠበቅና ከቤተሰቡ እጅ ወጥቶ ወደ ሌላ ወገን እንዳይተላለፍ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡በዘመዳሞች መካከል ይህ መርህ ተፈጻሚ የሚሆነው በውርስ ሀብት ላይ ሲሆን መብቱን ተግባራዊ የሚያደርጉትም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1391 ስር እንደተመለከተው በወራሽነት ቅደምተከተላቸው መሰረት ነው፡፡ ለቅድሚያ ግዥር መብት የሚወዳደሩት በእኩል የዝምድና ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች የሆኑ እንደሆነ በመሬቱ ላይ የሚኖረውና የሚጠቀምበት ሰው ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1392 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህ ካልተቻለ ደግሞ መሬቱን በአንድነት እንደሚሰሩበት እኩል በሆነ ድርሻ የጋራ ባለሃብቶች እንደሚሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1393(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡በሌላ በኩል ሕጉ በባለጥቅሞቹ ላይ ያስቀመጠው ገደብም ያለ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1397 ድንጋጌ ያሳያል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ባለጥቅሞቹ በቀዳሚነት የመግዛት መብትን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፉ እንደማይችሉና እንዲሁም በእዳ ሊያዝ እንደማይችል አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ተቀምጧል፡፡ሌላው ስለቅድሚያ የመግዛት መብት በሕጉ የተቀመጠው ጉዳይ የመብቱ የተፈፃሚነት ጊዜ ነው፡፡በዚህም መሰረት በቅድሚያ የመግዛት መብት ተፈጻሚ የሚሆነው ባለሃብቱ ሀብቱን ወይም የሀብቱን አላባ በዋጋ በሚሸጥበት ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1398 ድንጋጌ የሚያመላክት ሲሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1407(1) ድንጋጌም ንብረቱ የተላለፈው ያለ ዋጋም ቢሆንም ግምቱን በመክፈል ይገባኛል ባዩ ሊገለገልበት እንደሚችል ያስረዳል፡፡እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1400 ድንጋጌ ማንም ሰው በቀዳሚነት ይገባኛል በማለት መብት ሊገለገልበት የፈለገ እንደሆነ ንብረቱ በሀብትነት ወይም በአላባነት ለገዥ ወይም በሐራጅ ለሚገዛው ሰው የተላለፈ መሆኑ ለይገባኛል ባዩ ከተነገረበት ቀን አንስቶ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በመብቱ ሊገለገልበት የፈለገ መሆኑ ካስታወቀ መብቱ እንደሚቀርበት አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1401 ደግሞ በቀዳሚነት ይገባኛል በማለት መብት እንዲገለገልበት ለመጠየቅ የማስተላለፍያ ማስታወቂያ ሳይነገር የቀረ እንደሆነ የጋራ ባለሃብቶቹ በማያጠራጥር አኳኋን ንብረቱ ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑን ካወቁበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በቀዳሚነት ይገባኛል በማለት በመብታቸው ሊገለገሉበት የፈለጉ መሆናቸውን ማስታወቅ እንደአለባቸውና የስጋ ዘመዳሞች ከሆኑ ደግሞ አዲሱ ባለሃብት ወይም የአላባ ጥቅም ተቀባዩ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት እጅ ካደረገበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በቀዳሚነት ይገባናል በማለት መብታቸውን ሊገለገሉበት የፈለጉ መሆናቸውን ማስታወቅ እንደአለባቸው እንደቅደምተከተሉ በተጠቃሹ ቁጥር ንዑስ አንቀጽ አንድ እና ንዑስ አንቀጽ ሁለት ድንጋጌዎች ስር በሕጉ የተመለከተውን ጊዜ ያለማስታወቅ እና ውጤቱን በተመለከተ ደንግገው እናገኛለን፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንግዲህ በቀዳሚነት የመግዛት መብትን አድማስ በተመለከተ በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዎች ከላይ የተቀመጡ ከሆኑ አሁን የተያዘው ጉዳይም እልባት ማግኘት ያለበት ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መሰረታዊ አላማ እንዲሁም ጉዳዩን በተለይ ለመግዛት የወጣው ህግ ድንጋጌዎች አንፃር ነው፡፡ከዚህ አኳያ ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ እኩል መብት ያላቸው ቢሆንም አንዱ ከሌላው በቅድሚያ ቤቱን መልሶ የመግዛት መብት የሚያገኝበት አግባብ የለም፡፡ የክልሉ የቤተሰብ ሕጉ በአንቀጽ 102 ስር ክፍፍሉ መሰረት ከሚያደርግባቸው ሁኔታዎች አንዱ ንብረቱ የተለየ ጥቅም የሚሰጠውን ተጋቢ መለየት እንደሆነ በተመለከተው አግባብም ለአመልካች ቤቱ እንዲሰጥ የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት መኖሩ አልተረጋገጠም፡፡ጉዳዩን የሚገዛው ልዩ ሕግ ስለ አንድ ክርክር መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል ድንጋጌ ባልያዘበት ሁኔታ አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች ስር ያሉትን ድንጋጌዎችን መሰረት አድርጎ ለአንድ የክርክር ጭብጥ መፍትሔ መስጠት ተገቢ መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የህግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ግን በክልል የቤተሰብ ሕግ የጋብቻ ውጤት የሆነው ንብረት ክፍፍል የሚፈፀምበትን አግባብ በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑና ተጋቢዎች ግራ ቀኙ በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት ክፍፍሉ ሊፈጸም ያልቻለ ከመሆኑም በላይ 2ኛ ተጠሪም የመልሶ መግዛት ጥያቄ ያቀረቡ በመሆኑ የአሁኑ አመልካች ንብረቱን መልሰው የመግዛት መብት የሚያገኙበት አግባብ ከፍትሃ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች አንፃር የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ጨረታው እንዲከናወን ያደረገው የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ተጋቢዎች መብት አነጻጽሮ በጨረታው ላይ እንዲሳተፉና መልሶ የመግዛት መብት እንደሚኖራቸው ከመነሻውም ግልጽ ትዕዛዝ ያልሰጠበት መሆኑን ክርክሩ ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ በጨረታው ላይ ተወዳድሮ የጋብቻ ውጤት የሆነውን ንብረት የገዛ ተጫራች የጨረታው ውጤት ከታወቀ በኋላ ንብረቱን ለጋራ ባለሃብት መልሶ እንዲሸጥ ማድረግ የባልና ሚስት ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በሚደረግበት ጊዜ ተወዳዳሪ እንዲቀርብ ያለማድረግ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ተቀባይነት አግኝቶ ሊተገበር የሚገባው አይደለም፡፡ስለሆነም ጉዳዩ ልዩ ሕግ በሆነው የክልሉ የቤተሰብ ሕግ የሚዳኝ እና በዚህ ሕግ የተቀመጡ የክፍፍል ስርዓቶች ደግሞ የጋራ ባለሃብት መብቱን እንዲጠቀም የሚያስችሉ ቅደም ተከተል ያላቸው በመሆኑ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በዚህ በህጉ በተቀመጡ ቅደም ተከተሎች መጠቀም ሳይችሉ ከቀሩ በኋላ በጨረታው ላይ የመልሶ መግዛት መብት እንዳላቸው ባልተቀመጠበት ሁኔታ ሶስተኛ ወገኖች ተወዳድረው አሸናፊው ከተለየ በኋላ ንብረቱን መልሰን እንግዛ ሲሉ ጥያቄው በዚህ ረገድ በተደነገጉት የፍትሐ ብሔር ድንጋጌዎች የሚታይበት አግባብ የሌለ ሁኖ አግኝተናል፡፡ሲጠቃለለም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58418 መጋቢት 06 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች አከራካሪውን ቤት የመልሶ መግዛት መብት የላቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ውጪ እና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

ነሐሴ 07 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

መ/ቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመለስ

አመልካች፡- አቶ .....ጠበቃ ሀይልዩ ሰሀለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ .....- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

በዚህ በመዝገብ የቀረበው ክርክር የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በአመልካች ላይ ያቀረቡትን ክስ እናታቸው ወ/ሮ ..... ከአመልካች ጋር ከጥር ወር 1973 ዓ/ም እስከ ህዳር ወር 1974 ዓ/ም ድረስ ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት አብሮው በመቂ ከተማ ድግዳቦራ ወረዳ ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 190 ወስጥ ሲኖሩ መቆያታቸውን ገልጸው በዚህ ግንኙነታቸው መሰረት ተጠሪ በጋንዲ ሆስፒታል ሚያዝያ 02 ቀን 1974 ዓ/ም የተወለዱ መሆናቸውን በመግለጽ አመልካች የተጠሪ አባት ነው ተብሎ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነው የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ ልጅነት የሚረጋገጠው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀፅ 154 እና 155 ላይ እንደተመለከተው የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ መሆኑን፤ተጠሪ ያቀረቡትማስረጃ አለመኖሩ አመልካች መቂ ከተማ ኑረው እንደማያወቁ ተጠሪም አንድም ቀን እራሳቸውም ሆነ በሰው የአመልካች ልጅ መሆናቸው ጠይቀው እንደማያውቁ በመጥቀስ ክሱ ውድቅ ተደርጐ እንዲሰናበቱ አመልክተዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የተጠሪ ሁለት ምስክሮች በማዳመጥ በሰጠው ውሳኔ በአሁን አመልካች እና የተጠሪ እናት እንደ ባልና ሚስት አብረው ይኖሩ ነበር በሚል ስላልተረጋገጠ የአመልካች ምስክር መስማት አያስፈልግም፡፡ የአመልካች እና የተጠሪ እናት ግንኙነት በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 143 በሚያዘው አግባብ ሳይረጋገጥ የደም ምርመራ (የDNA ምርመራ) ማድረግ ተገቢ ስላልሆነ ፍ/ቤቱ የተጠሪ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉን በመግለጽ አመልካች በነጻ ይሰናበቱ በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታውን ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በቃል ክርክር የድኤንኤ ምርመራ እንዲደረግለት ጠይቋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ምርመራውን ለማዘዝ የልጅ አባት ነው የሚያሰብል ግምት መያዝ አለበት በማለት መደምደሙ ከሰ/መ/ቁ.63195 አኳያ ተገቢነት የለውም፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በማስረጃነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጠቀሰውን የዲ.ኤን.ኤ ምርምራ ጥያቄ ሳይቀበለው አልፎ የሰጠው ውሳኔ የህግ አግባብ ባለመሆኑ ምርመራ ተደርጎ በምርምራው ውጤት የመስለውን እንዲወሰን ውሳኔውን በማሻር በነጥብ መልሶታል፡፡

የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም አመልካች ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ይግባኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ተሰርሟል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽሟል ያሉትን የህግ ስህተት እንዲታረም ግንቦት 13 ቀን 2005 ዓ/ም የተጻፈ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ዋና ፍሬ ነገሩ፡- የሰበር ውሳኔው ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የለውም ፤ የስር ፍርድ ቤት የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ጥያቄ የተቀበለው ስርዓቱን ጠብቆ አይደለም ፤ ከአመልካች ስለመወለዱ አልተረጋገጠም በማለት ስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሻር አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በስጡት መልስ በአመልካች እና የተጠሪ እናት ግንኙነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ የዲኤንኤ ምርመራ በመጀመሪያ ቀጠሮ መጠየቃቸው፤ ምርመራውም ጉዳዩን ግልጽ የሚያደረግ መሆኑ በመጥቀስ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ህዳር 05 ቀን 2006 ዓ/ም ግራ ቀኙ በችሎት በቃል አከራክሮ ውጤቱን መዝግበዋል፡፡

የክርክሩ አጭር ይዘትና አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም መዝገቡን በአጣሪ ችሎቱ ያስቀርባል ከተባለው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አኳያ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን ተጠሪ በአመልካች እና እናቱ መካከል የነበረው ግንኙነት ለማስረዳት ምስክሮች በማቅረብ ያስማ መሆኑ ከመዝገቡ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የስር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዲኤንኤ ምርምራ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በአመልካች እና የተጠሪ እናት ነበረ የተባለው ግንኙነት በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 መሰረት ከተመለከቱት ግምት የሚያሰጡ ምልክት ሰጪ ነገሮች በአንዱ አልተረጋገጠም የሚል ነው፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዲኤንኤ ምርምራ በተጠሪ በቃል ክርክር ወቅት የተጠየቀ በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.259(1) መሰረት እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ. 63195 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አኳያ ዲኤንኤ ምርመራ ይደረግ ጥያቄ ተቀብሎታል፡፡ የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ በአንዱ በኩል አባት የማግኘት መብት ሲያረጋግጥ በሌላ በኩል ደግሞ አባት ያልሆኑ ግለሰቦች አባት ነህ ተብሎ እንዳይወሰን ለመከላከል የተበጀ ህጋዊ ስርዓት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የዲኤንኤ ምርመራ ይደረግልኝ ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት ማቅረቡ አልተካደም፡፡ የዲኤንኤ ምርመራ እንደ አንድ የማስረጃ ይዘት እንዲታይለት መጠየቁ እና ይህንን ጥያቄም ስርዓቱን ጠብቆ ማቅረቡ በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ መነሻ ያደረገው የደም ምርመራ ለማድረግ አመልካች የዲኤንኤ ምርምራ እንዲያደርጉ ለማስገደድ ተጠሪ እናትና አመልካች በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 መሰረት ግንኙነት የነበራቸው መሆኑ እና ተጠሪም በዚህ ግንኙነት የተወለደ መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁንና ይህ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ማጣራትና ማስረጃ ምዘና ስርዓት ተገቢ አይደለም ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ከተሻረ በሰበር ችሎቱ የማስረጃ ምዘና ሂደቱ የሚታይበት ስርዓት አይኖርም፡፡

በአመልካች እና ተጠሪ እናት መካከል ግንኙነት ነበረ ወይስ አልነበረም የሚለው የፍሬ ነገር ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች የየራሳቸው አቋም የወሰዱበት መሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ ከመስጠት ውጪ ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃ ምዘና ረገድ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር የሚያስችል ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ ከኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ የቤተሰብ ህጉ የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ በግልጽ አልተገደበም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ከ30 ዓመት በኃላ የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ማቅረቡ የጥያቄውን ህጋዊነት ከወዲሁ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ሆኖ አልተገኘም፡፡ የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 63195 የዲኤንኤ ምርመራ ወጪ ከመሸፈን ጋር በተያያዘ የሰጠው ትርጉም በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደ አስገዳጅ ውሳኔ መጠቀሱ የክርክር ምክንያት ቢሆኑም በዚህ ጉዳይ በዋናነት መታየት ያለበት ይህ ሰበር ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የዲኤንኤ ምርመራ እንዳይደረግ የክልከላ ውጤት ያለው ውሳኔ ከመስጠቱ አንፃር ብቻ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሰበር ችሎቱ ከኤክስፐርት ምርመራ ውጤትና የማሳረዳት ብቃቱ በተያያዘ የተሰጠ ትርጉም መኖሩ ግልጽ ቢሆንም በእኛችን ከተያዘው ጉዳይ ጋር በፍሬ ነገርና በጭብጥ ረገድ አንድና ተመሳሳይ የሆነ ምርምራ የሚከለክል ውሳኔ ያልተሰጠ ከመሆኑ አንፃር የስር ፍርድ ቤት ከላይ የተጠቀሰው መዝገብ በአስገዳጅ ውሳኔ መመዝበሩ የውሳኔውን ህጋዊነት ጥያቄ ውስጥ የሚከተው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አባትነት የሚረጋገጥባቸውን መንገዶች አስቀምጧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የሚጠቀሱት አባትነት በህግ ግምት የሚወሰድባቸው ሲሆኑ በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ ልጆች እንዲሁም እንደባልና ሚስት ሆነው ከኖሩ ግለሰቦች የተወለደው ህፃን የሚመለከት መሆኑ ከቤተሰብ ህግ አንቀጽ 126 እና 130 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ወጪ አባትነት እውቅና በመስጠት ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ከላይ በተጠቀሱ ምክንያቶች ማረጋገጥ በማይቻልበት ሁኔታ በፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ እንደሚታይ ነው፡፡ በፍርድ ቤት አባትነት ለማረጋገጥ መነሻ ነጥቦች በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 የተዘረዘሩት ሲሆኑ በዚህ ረገድ የሚነሳው ክርክር ወይም ግምትና ምልክት ሰጪ ግምቶች ለማስተባበል የሚያስችሉ ምክንያቶች በዚህ ህግ አንቀጽ 144 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበው የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ በአመልካች ተክዷል፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የዲኤንኤ ምርመራ እንዲታዘዝለት ጠይቋል፡፡ የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥያቄውን ውድቅ ቢያደረገውም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የጥያቄው ተገቢነት በመቀበል ምርመራው እንዲደረግ አዟል፡፡ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተጠሪ የዲኤንኤ ምርመራ ይታዘዝልኝ ጥያቄ በወቅቱ የቀረበ መሆኑ በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንዲመለከተው መልሶ መላኩ በህግ አተረጓጎም ረገድ የፈጸመው ስህተት አለ ማለት አልተቻለም፡፡ የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት በማንኛውም ሁኔታ እንዲደረግ የሚጠይቅ አለመሆኑ ችሎቱ የሚገነዘብ ቢሆንም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር የመጀመሪያ ደረጃ የፍሬ ነገር ድምዳሜና የማስረጃ ምዘና ባለመቀበል ምርምራ እንዲደረግ ማዘዙ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ የተደነገጉት የክርክር አመራር መሰረታዊ የስነ ስርዓት ድንጋጌዎች በአግባቡ አልተተረጎሙም ለማለት የሚያስችል ነገር አልቀረበም፡፡ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ የዲኤንኤ ምርመራ ተደረጎ የስር ፍርድ ቤት የመሰለውን እንዲወሰን መታዘዙ ፤ የምርመራ ወጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መተንበይ በማይቻልበት ሁኔታ አመልካች ለመጉዳት ታስቦ የተደረገ ነው የሚያስብል የህግ ምክንያት የለውም፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው አባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ለመወሰን የዲኤንኤ ምርምራ አስፈላጊ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከታመነበት የፍ/ቤቱ ትእዛዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተፈጻሚ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የዲኤንኤ ምርመራ እንዲደረግ ማዘዛቸው በአግባቡ ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በስር ፍርድ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ እንደሚችሉ ግልጸዋል፡፡ የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ የመከላከያ ማስረጃ አለማዳመጡን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች የዲኤንኤ /DNA/ ምርምራ ቢደረግም አለኝ የሚሉትን የመከላከያ ማስረጃ የማስማት መብታቸው የሚከለክል አይሆንም፡፡

በማጠቃለል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የዲኤንኤ ምርመራ እንዲደረግ ማዘዙ እና ውሳኔው በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ መሰረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 57163 በ1/09/2004 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 126002 ጥር 30 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.87769 የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. የስር ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የዲኤንኤ ምርመራ እንዲደረግ ማዘዙ በአግባብ ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በትእዛዙ መሰረት ይፈጸም ብለናል፡፡ አመልካችም አለኝ የሚሉትን መከለከያ ማስረጃ የማሰማት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡
4. በዚህ ጉዳይ ክርክሩ ለጊዜው እንዲቆም ግንቦት 28 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
5. በዚህ የሰበር ጉዳይ ክርክር የተነሳ የግራ ቀኙ ላወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96628

ህዳር 8 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- 1. አሳመነው ከበደ

2. ወ/ሮ ፍቅርተ ከበደ ጠበቃ አቶ ፍሰሀ አለማየሁ ቀረቡ፡፡

3. አቶ ምንተስኖት ከበደ - ቀረቡ

4. ተማሪ ቀንአየሁ ከበደ

5. ተማሪ ብሩክ ከበደ

ተጠሪ፡- አቶ ዳንኤል ከበደ- ጠበቃ አቶ በየነ ታደሰ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 38926 ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137992 ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ንብረት ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች አመልካቾች ተጠሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ ወላጅ አባቱ አቶ ከበደ ሰለሞን ጥቅምት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በሞት ተለይቶ ወራሽነታችንን አረጋግጠናል፡፡ ስለዚህ ውርስ አጣሪ ተመድቦ ውርሱ እንዲጣራ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካቾች ውርስ አጣሪ ቢመደብና የውርሱ ንብረት ተጣርቶ ቢቀርብ አንቃወምም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ውርስ አጣሪ ከመደበ በኋላ ውርሱ ሲጣራ ተጠሪ ሚች በ 24/11/1980 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል በ210 ካሬ ሜትር ላይ ያረፉ አንድ ክፍል ቆርቆሮ በቆርቆሮ ቤት ሰጥቶኝ አባታችን በህይወት እያለ ቆርቆሮ ቤቱን በማፍረስ ሁለት ክፍል የጭቃ ቤት ሠርቼ እየኖርኩበት እገኛለሁ፡፡ ቤቱ ዋናውን 568

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካሬ ሜትር ግቢው ውስጥ የሚገኝና ቦታውም ራሱን የቻለ ካርታ የሌለው በመሆኑ ሁለት ክፍል የጭቃ ቤት 210 ካሬ ሜትርይዞታ ከውርስ ንብረቱ ተለይቶ እንድያዝልኝ በማለት ለውርስ አጣሪው ጥያቄ አቅርቧል፡፡አመልካቾች የይርጋ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ስጦታው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 መስፈርቶች የማያሟላ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ስጦታው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን መስፈረት ስለማያሟላ፣ ስጦታው ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ሆኖም ሁለት ክፍል ጭቃ ቤት የሥር አመልካቹ የአሁን ተጠሪ ያሰራው መሆኑን በሰውና በፅሑፍ ማሥረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ በ201 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የተሠራው ሁለት ክፍል ቤት የውርስ ንብረት ሣይሆን የአመልካች /የተጠሪ/ የግል ንብረት ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

2. አመልካቾች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካቾች ጥር 8 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በ210 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ አንድ ክፍል ቤት እንድሰራ በሰጦታ ተሰጥቶኝ ቤቱን አፍርሽ ሁለት ክፍል ቤት ሠርቻለሁ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ የስጦታ ውሉ የሕጉን ፎርም አያሟላም ተብሎ ውድቅ ተደርጓል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ አማራጭ የዳኝነት ጥያቄ ያላቀረበበትን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179 ጠቅሶ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ ቤቱን መሥራቱን አመልካቾች አላመኑም፡፡ ቤቱን መስራቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ስለዚህ ቤቱን ያሠራው ተጠሪ ነው መባሉ ስህተት ነው፡፡ ተጠሪ ሠራሁ የሚለውን ቤት ከ30 ካሬ ሜትር በማይበልጥ ቦታ ላይ ያረፈ ሆኖ እያለ 210 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ የውርስ ንብረት ክፍል እንዳልሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

3. ተጠሪ የካቲት 21 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች ቤቱንና ሽንት ቤቱን በግል የሠራሁት መሆኔን ገልጨ ያቀረብኩትን ክስ በግልፅ ክደው ክርክር አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ 1179 ድንጋጌን በመጥቀስ በቃል ክርክርና በፅሑፍ ለሥር ፍርድ ቤት አማራጭ ክርክር አቅርቤያለሁ፡፡ አመልካቾች ቤት ያረፈበት በ30 ካሬ ሜትር የሚሆነው ይዞታ እንጅ 210 ካሬ ሜትር አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀናልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 429 ግቢና ስፋቱ 568 ካሬ ሜትር ቦታ ውስጥ የሚገኘው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤትና ቤቶቹ የተሰሩት 210 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ የውርስ ንብረት ሣይሆን የተጠሪ የግል ቤትና ይዞታ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ መሠረታዊ ይዞታና በተጠሪና በአመልካቾች ክርክር ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተረጋገጡትን መሠረታዊ ፍሬ ጉዳዮች መመርመር ያስፈልጋል፡፡ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤትና ለውርስ አጣሪው ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ሁለት መሠረታዊ መብቶች ተረጋግጠው በፍርድ እንዲወሰንለት የሚጠይቅ ነው፡፡ የመጀመሪያው ሟች ወላጅ አባቱ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 429 ግቢ ውስጥ ሰርቶት የነበረውን አንድ ክፍል ቆርቆሮ በቆርቆሮ ቤት ሐምሌ 24 ቀን 1980 ዓ.ም ባደረገው የስጦታ ውል ሰጥቶኛል፡፡ ከዚህ በኋላ ሰጭው ወላጅ አባቴ በህይወት እያለ የሰጠኝን አንድ ክፍል ቆርቆሮ በቆርቆሮ ቤት በማፍረስ ፣ በራሴ ወጪ ሁለት ክፍል ሰርቪስ የጭቃ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤት ገንብቼ የኖርኩበት ስለሆነ ሁለቱ ክፍል ሰርቪስ ቤቶችና አንድ ክፍል ሽንት ቤት የሟች የውርስ ንብረት ክፍል አለመሆኑ ተረጋግጦ ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ሁለተኛ የዳኝነት ጥያቄ ወላጅ አባቴ ሐምሌ 24 ቀን 1980 ዓ.ም ባደረገው የስጦታ ውል አንድ ክፍል ቆርቆር በቆርቆሮ የተሰራ ቤት ሣይሆን ሟች ከነበረው 568 ካሬ ሜትር የይዞታ መሬት210 ካሬ ሜትር ይዞታ በስጦታ ያስተላለፈልኝና ይህ የይዞታ መሬት ከጠቅላላው 568 ካሬሜትር ይዞታ ያልተለየ በመሆኑ ተለይቶና ተከልሎ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

6. ተጠሪ መብት አግኝበታለሁ የሚሉት የስጦታ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገጉትን መስፈርቶች የማያሟላ መሆኑ ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ምክንያት ተጠሪ የግል ንብረቴ ናቸው የሚላቸውን ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶችና አንድ ክፍል ሽንት ቤት ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሥጦታ ውሉ መሠረት እንደማይሆንና የሥጦታ ውሉ ህጋዊ መብት እንደሌለው የበታች ፍርድ ቤቶች ወስነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የውርስ ንብረት ከሆነው የቤት ቁጥር 429 አጠቃላይ 568 ካሬ ሜትር ስኩየር የይዞታ ቦታ 210 ካሬ ሜትር ስኩዌር በስጦታ ይተላለፍልኝ የግል ይዞታዬ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የስጦታ ውሉ ፈራሽ ነው በመባሉ ምክንያት የሕግ መሠረት የሌለው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ተጠሪ የስጦታ ውሉን መነሻ በማድረግ ሰርቪስና ሽንት ቤቱ በ 210 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ ያቀረበው የመብት ጥያቄ፣የስጦታ ውሉ የሕጉን ፎርም ያላሟላ ፈራሽ ነው በመባሉ ምክንያት ውሉ በሙሉ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

7. የሥር ፍርድ ቤት በሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና በአንድ ክፍል ሽንት ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት መደምደሚያ ላይ የደረሰው፣ ተጠሪ ቤቶቹን የአመልካችዎች አውራሽና ወላጅ አባት ሣይቃወመው በራሱ ወጭና ገንዘብ የሠራቸው መሆኑ በማስረጃ ተረጋጋጧል በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤት የአመልካቾችና የተጠሪ ወላጅ አባትና አውራሽ ፈቃድና ያለምንም ተቃውሞ ተጠሪ በራሱ ውጭ የገነባቸው መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች በማስረጃ አረጋገጠዋል፡፡ በአንድ ሰው የይዞታ መሬት ላይ ባለይዞታው ሣይቃወም ህንፃ የገነባ ሰው የህንፃው ባለቤት እንደሚሆን፣ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሁለቱ ክፍል ሰርቪስ ቤቶችና አንድ ክፍል ሽንት ቤት ከጅምሩ የአመልካቾች አውራሽ የግል ሀብት ሣይሆኑ የተጠሪ የግል ንብረት መሆናቸውን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ በማጣመር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሟች ሲሞት ለሟች ወራሾች የሚተላለፈው በሟች መሞት ምክንያት የማይቋርጡ መብቶችና ግዴታዎች መሆናቸው በፍትሐበሐር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የአመልካችዎች አውራሽ ተጠሪ በራሱ ወጭ በሰራቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች እና አንድ ክፍል ሽንት ቤት ላይ የባለሀብትነት መብት የሌለው በመሆኑ፣ አውራሻቸው የሌለው መብት ለአመልካች ወራሾች ሊተላለፍ የሚችልበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ የሠራቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሰርቪስ ቤት የውርስ ንብረት ክፍል ሣይሆን የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) ድንጋጌ መሠረት ያደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ቤቶቹን የሠራኃቸው እኔ ነኝ የሚል ጥያቄ ያቀረበ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የሕግ ድንጋጌ ማለትም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) በመጥቀስ የሰጡት ውሳኔ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182(2) ድንጋጌ የሚጥስ ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም ፡፡

8. ተጠሪ የውርስ ንብረት በሆነው የቤት ቁጥር 429 ግቢ ውስጥ የሠራቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤት የግል ባለሀብት ነው የተባለው በስጦታ ውሉ ሳይሆን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) መሠረት ባለይዞታው ሣይቃወመው በግል ገንዘቡ የሠራው ነው ተብሎ ነው፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) መሠረት ባለመብት የሚሆነው የአመልካቾች አውራሽ ሳይቃወመው በራሱ ወጭ በሠራቸው ቤቶችና ቤቶቹ በተሰሩበት ወይም ባረፉበት ቦታ ላይ እንጅ፤ ቤቶቹን ከሠራበት ቦታ ውጭ ባለው የይዞታ ቦታ ላይ ባለመብት የሚሆንበት ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በግቢው ውስጥ በ 210 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ መብት አግኝቼበታለሁ የሚለው የስጦታ ውል ፈራሽነው በማለት ከወሰኑ በኃላ ተጠሪ 210 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የይዞታ መብት እንዳለው ገልፀው የሰጡት ውሳኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826(2) ድንጋጌ መሠረት ያላደረገና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

9. ከዚህ አንፃር ቢታይ ተጠሪ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤት ግንባታ ካከናወነበትና ቤቱ ካረፈበት ቦታ ውጭ በ210 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ባለይዞታ የሚሆንበት የሕግ መሠረት የሌለ በመሆኑ ፣የበታች ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179 (1) ድንጋጌ ይዘት በአግባቡ ሣይገነዘቡ ተጠሪ በራሱ ወጭ የሰራቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤት፣ አንድ ክፍል ሽንት ቤትና 210 ካሬ ሜትር ይዞታ የውርስ ንብረት አይደለም በማለት የሰጡት ውሣኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በራሱ ወጭ የሠራቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤት የውርስ ንብረት ክፍል ሣይሆኑ የተጠሪ የግል ንብረት ናቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) መሠረት ያደረገ በመሆኑ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ በቤት ቁጥር 429 ግቢ ውስጥ 210 ካሬ ሜትር ቦታ ባለ ይዞታ ሆኜበታለሁ የሚለው የስጦታ ውል ፈራሽ የሆነ በመሆኑና ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሽንት ቤት ከገነባበትና ቤቱ ካረፈበት ውጭ ያለው 210 ካሬ ሜትር ቦታ የውርስ ንብረት ክፍል አይደለም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

4. ተጠሪ ሰርቪስ ቤቱና ሽንት ቤቱ ከገነባበትና ቤቱ ካረፈበት ቦታ ውጭ ባለው ይዞታ ቦታ ላይ የይዞታ መብት የለውም ብለናል፡፡ ተጠሪ ሰርቪስ ቤትና ሽንት ቤት ከገነባበትና ቤቱ ካረፈበት ቦታ ውጭ ያለው የቤት ቁጥር 429 ይዞታና ቤቱ ላይ አመልካችና ተጠሪ እኩል የወራሽነት መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
6. ይህ ውሣኔ ተጠሪ በአፈፃፀም ወቅት የመውጭያና የመግቢያ መብት ይከበርልኝ የሚለበትን ጥያቄ ከማቅረብ አያግደውም፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96364

ጥቅምት 10 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- እልፍነሽ ወርቁ ጠበቃ አሳምነው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ኤልሳቤጥ አስራት ጠበቃ መስፍን ጌታቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የመ/አመልካች፣ተጠሪ ደግሞ የመ/ተጠሪ ነበሩ የመ/አመልካች የነበሩት የአሁን አመልካች ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ የመቃወም ተጠሪ ሚች ወ/ሮ አስረስ እሸቱ መስከረም 28/2000 ዓ.ም. ያደረጉትን ኑዛዜ ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሻሩት መሆኑን እያወቁ በተሻረው ኑዛዜ የወራሽነት ማስረጃ መውሰዳቸው ተገቢነት ስለሌለው ማስረጃው ይሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል፤ተጠሪም በሰጡት መልስ ሚች መፃፍ እና መፈረም ይችላሉ መስከረም 28/2000 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜም ላይ ስማቸውን ጽፈው የፈረሙ ሲሆን አመልካች የኑዛዜ መሻሪያ ብለው ያቀረቡት ሰነድ ላይ ግን የሚች ፊርማ ተብሎ የተቀመጠው የጣት ምልክት ሲሆን ከምልክቱ በላይ ግን የሚች ስም ተፅፏል፡፡ በመሆኑም መሻሪያ የተባለው ሰነድና መስከረም 28/2000 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ ከፍተኛ ልዩነት አለው፡፡ ሚችም ለረዥም አመት ታመው ፓራላይዝ ሆነው የሚያደርጉትን አያውቁም ባጠቃላይ መሻሪያ ተብሎ የቀረበው ሰነድ የኑዛዜን ፎርማሊቲ የማያሟላና ህጉን ተከትሎ የተፈፀመ አይደለም፣ንብረቱንም ቢሆን ተጠሪ ወደ ስሜ አዙሬዋለሁ፣ ተቃወሞዋቸው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም፡- ሚች መስከረም 28/2000 ዓ.ም ያደረጉትን ኑዛዜ በግልፅ የሻሩት መሆኑን ነሐሴ 23/2003 ዓ.ም. ባስመዘገቡት መሻሪያ ሰነድ ገልጸዋል፤ፎርሙን አስመልክቶ አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡ሚች ወ/ሮ አስረስ እሸቱ በፍ.ብ.ሕ.ቁ.898 ላይ በተቀመጠው መሰረት መስከረም 28/2000 ዓ.ም ያደረጉትን ኑዛዜ የሻሩት መሆኑን ስለገለፀ አመልካች በተሻረ የኑዛዜ ሰነድ የተሰጣቸው የወራሽነት ማስረጃ ተሰርዟል ሲል ወሰነ ፡፡የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም የአመልካችን ይግባኝ ሳይቀበለው አፀንቶታል፡፡ በመጨረሻ ጉዳዩ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የኑዛዜ መሻሪያ ሰነዱ ተናዛዥና በቦታው ለነበሩ ምስክሮች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተነበበላቸው ስለመሆኑ የሚያመለክት ቃል በሰነዱ ላይ አይታይም፡፡የፍ.ብ.ሕ.ቁ. 881 እና 898(1) ላይ የተጠቀሰውን የመሻሪያ ሰነዱ አያሟላም ሲል የሥር ውሣኔዎችን ሽሮታል፡፡
የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማሳረም ነው፡፡
አመልካች በሰበር አቤቱታው ቅሬታውን ሳያቀርብ በፍ.ሕ.ቁ. 898 መሠረት የግልፅ ኑዛዜ በሚያደርገው አይነት ኑዛዜን መሻር ይቻላል፡፡ በቀጣይ የፍ/ሕ/ቁጥር 899 መሠረት ደግሞ ተናዘዥ ያለውን የኑዛዜ መሻር ሀሳብ በቂ አድርጎ በመግለፅ አይነት የኑዛዜው አነጋገር በመሰረዝ ኑዛዜውን በማጥፋት በመቅደዱ ኑዛዜውን መሻር እንደሚቻል ህጉ እያመላከተ ፎርማሊት አላሟላም ተብሎ መወሰኑ እና ተናዛዥ ኑዛዜውን በፈለገው ጊዜ የመሻር መብቱን ያጣበበ በመሆኑ የፍ.ሀ.ቁ. 881 አልተሟላም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት አመልክተዋል፡፡
በዚህም መሰረት ይህ ችሎት ኑዛዜ ሲሻር ኑዛዜው በተሰጠበት አግባብ ብቻ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 898,899 እና 900 አኳያ ለመመርመር በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙን መልስና የመልስ መልስ በፅሑፍ እንዲቀባበሉ በማድረግ አከራክሯል፡፡
አመልካች ክርክራቸውን በማጠናከር የሟች የመሻሪያ ኑዛዜ ሰነድ በአግባቡ የተከናወነ እና የፍ.ሀ.ቁ. 881 (ፎርማሊትን) ሊከተል የሚገባው አይደለም በመሆኑም የፍ.ሕ.ቁ. 898 መሰረት አድርጐ መሻሩበተረጋገጠበት የከተማው ሰበር ችሎት የሥር ውሳኔን መሻራቸው አግባብነት የለውም ሲሉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በተቃራኒው የሥር ውሳኔ መሻሩ በአግባቡ ነው ሲሉ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡
ባጠቃላይ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰው ነው፡ በመሆኑም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረናል፡፡
በመሰረቱ የተያዘውን ጉዳይ ጠቅለል ባለመልኩ ስናየው እያከራከረ ያለው የህግ ጥያቄ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ ሲጤን ተጠሪ ከሟች መስከረም 28/2000 ዓ.ም አገኘሁት የሚሉት ኑዛዜ በድጋሚ ሟች በህይወት እያሉ ነሐሴ 23/2003 ዓ.ም. በውል አዋዋይ ጽ/ቤት ያደረጉት የመሻርያ ሰነድ በቀጥታ የመጀመሪያውን ኑዛዜ ዋጋ አልባ ያደረገዋል ወይስ የኋለኛው የመሻሪያ ሰነድ ሊከተለው የሚገባው ልዩ ስርዓት አለው የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ከተጠቀሱት የፍ/ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ሆኗል፡፡በመሠረቱ ኑዛዜ የሟች ጥብቅ የሆነ የግል ጠባይ ያለው እና ራሱ የሚተገብረው ነው በመሆኑም የተናዛዥ ሀሳብና ፍላጐት በጥንቃቄ ልንከተለው የሚገባው ነው፡፡ ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የፍ.ሀ.ቁ. 898(1)ተናዛዥ ኑዛዜዎቹ ዋጋ ያላቸው እንዲሆኑ በሚያስፈልገው ፎርም ዓይነት ግልፅ አድርጎ በማስታወቅ ኑዛዜውን የሻረ እንደሆነ በጠቅላላው አኳኃን የሚሻር ይሆናል ይላል፡፡በዚሁ ህግ አንቀፅ 899(1) ተናዛዥ የተናዘዘውን ለመሻር ወይም ለመለወጥ ያለውን ሀሳብ በቂ አድርጎ በመግለፅ ይህንንበኑዛዜው የተመለከተውን ቃል መሻር ይችላል በማለት ተደንግጓል፡፡
በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ሁለቱንም ድንጋጌዎች ስናይ አንዱ ሌላኛውን በሚያጠናክር መልኩ የተቀመጠ እንጂ የሚቃረኑ አይደለም፡፡
ይህም ሲባል ሁለቱም አንቀፆች ተናዛዥ ያደረጋቸው ኑዛዜ መሻር ሲፈልግ ሀሳቡን በማያሻማ አኳኋን ግልፅ በሆነ መንገድ መሻር እንደሚችል የሚገልፅ ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ሟች (ተናዛዥ) ከዚህ ውጭ ሊከተላቸው የሚገባው ሥርዓት መኖሩን አይደለም፡፡ ይልቁንም ተናዛዥ ኑዛዜውን ለመሻር ሊከተላቸው የሚገባውን አማራጮች የሚያመለክት (የሚገልፅ) ነው፡፡ እንግዲህ በያዝነው ጉዳይም ሟች ነሐሴ 23/2003 ዓ.ም.ባደረጉት የመሻሪያ ሰነድ ተጠሪ (ተሻሪዋ) ከዚህ ቀደም እንደተገበሩት የተሰጣቸውን ሀላፊነት ባለመወጣታቸው እና ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት በትክክለኛ አእምሯቸውና በፍላጐታቸው የመጀመሪያውን የኑዛዜ ሰነድ በግልፅ ቃልና አነጋገር የሻሩት መሆኑን ነው፡፡ ይህም የተፈፀመው በውል አዋዋይ ጽ/ቤት መሆኑም ተመልክቷል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የግድ ሚች የመስከረም 28/01/2000 የፈፀሙትን ሥርዓት ሊከተሉ አይገባቸውም፡፡ ይህን ኑዛዜ ለመሻር በቂና ግልፅ ቃል መሻራቸውን መግለፃቸው የመጀመሪያውን ያስቀረዋል፡፡ የፍ/ህ/ቁ. 881ን አልተከተለም በማለት ብቻ የሚችን የግል ሀሳብና ፍላጎት መቃረን አይገባም፡፡

በመጨረሻም በሥር (ከተማው የሰበር ሰሚ ችሎት ሚች በመስከረም 28/01/2000 ዓ.ም.ያደረጉት ኑዛዜ በነሐሴ 23/2003 ዓ.ም. በተደረገው ሊሻር አይገባውም (ሊሽረው) አይችልም፤መባሉን ይህ ችሎት የሚቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለዚህ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የከተማውን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የይግባኝ ሰሚውን ውሣኔዎች መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 927105 3/11/05 እና የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 20673 በቀን 10/01/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 21133 በቀን 27/3/2006 የተሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. ለተጠሪ በመስከረም 28/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ኑዛዜ ነሐሴ 23/2003 ዓ.ም. በተደረገው የመሻሪያ ሰነድ ተሽሯል (ቀሪ) ሆኗል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ በውሣኔ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ኢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97948

ታህሳስ 21 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-ወ/ሪት ሄለን ተክሌ - ቀረቡ

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ዘይድ አብርሃ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች የሚች አባታቸው የአቶ ተክሌ ነጋሽ የውርስ ንብረት እንዲጣራላቸው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የውርስ አጣሪው በፍርድ ቤቱ ተቋቁሞ የማጣራት ስራውን ከአጠናቀቀ በኋላ ሪፖርቱ ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ግራ ቀኙ አስተያየት ከሰጡበት በኋላ የውርስ አጣሪው ሪፖርት ተሻሽሎ በስር ፍርድ ቤት ፀድቋል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካች ሶፋውን ከእነ ሙሉ ጠረጴዛ የግል ንብረቴ ነው በማለት ጠይቀው እያለ በንብረቱ ላይ የግል ወይም የጋራ ነው ተብሎ ዳኝነት ሳይሰጥበት መታለፉ እና የቀበሌ ቤት የተከራይነት መብትን በተመለከተም አመልካች በወራሽነታቸው የሚገባቸው ስለመሆኑ በፍርድ ቤት መወሰን ሲገባው በቤቱ አካራይ የሚወሰን ነው ተብሎ መታለፉ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ ተጠሪ እንዲቀርቡ ተደርጎ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች፡-

1. ሶፋውን ከእነ ሙሉ ጠረጴዛ ዳኝነት ሳይሰጥ መታለፉ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ክልል ውስጥ በሚገኘውና በቁጥር 009 በሚታወቀው የቀበሌ ቤት የሚች አባት የነበራቸው የተከራይነት መብት ለአመልካች ሊተላለፍ የሚችል መሆን ያለመሆኑ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉ ሁነው ተገኝተዋል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡-አመልካች የሚች አቶ ተክሌ ነጋሽ ወራሽ መሆናቸውን ጠቅሰውና የሚቹ ንብረት እንዲጣራ የውርስ አጣሪ በፍርድ ቤት እንዲሾም ጠይቀው ፍርድ ቤቱም የውርስ አጣሪው እንዲቋቋም አድርጎ አመልካች ሊጣራ የሚገባቸውን የውርስ ንብረቶች ህዳር 05 ቀን 2005 ዓ/ም በፃፉት ማመልከቻ ዘርዝረው ያቀረቡ መሆናቸውን፣በዚህ የንብረት ዝርዝርም ከሚቹ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ናቸው በሚል ወደ 48 የሚሆኑ የቤት መገልገለያ እቃዎችን መጥቀሳቸው የውርስ አጣሪው ከአቀረበው የውርስ ማጣራት ሪፖርት መጠቀሱን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የተመለከተን ሲሆን በዚህ የንብረት ዝርዝር ውስጥ አመልካች በሚቹ መኖሪያ ቤት ሶፋ ከእነ ሙሉ ጠረጴዛ አለ በማለት የጠቀሱት ነገር እንደሌለ ግልባጩ የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ከዚህም መረዳት የሚቻለው አመልካች ይህንኑ ንብረት የውርስ ንብረት ነው በማለት በዚህ ረገድ ተገቢው መጣራት እንዲደረግላቸው የማጣራት ስራውን እንዲያከናውን በፍርድ ቤት ለተሾመው የውርስ አጣሪ ጥያቄ ያላቀረቡ ከመሆኑም በላይ የማጣራት ስራውን ሲከታተል ለነበረው ፍርድ ቤትም በተገቢው ጊዜ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ጥያቄ ያለመኖሩን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡እንዲህ ከሆነ አመልካች ሶፋው ከእነ ሙሉ ጠረጴዛ ዳኝነት ተጠይቆበት የግል ወይም የጋራ ነው ተብሎ ውሳኔ ሳያርፍበት ቀርቷል በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታ በስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ጥያቄ ያልቀረበበት በመሆኑ እና የስር ፍርድ ቤት ደግሞ ባልተጠየቀ ጉዳይ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182 (1) ድንጋጌ ስር የተመለከተ በመሆኑ ይህ ችሎት በዚህ ረገድ አመልካች የሚያቀርቡትን ቅሬታ የሚቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- አመልካች የሚች አቶ ተክሌ ነጋሽ ወራሽ መሆናቸውንና ሚቹ ከቀበሌ ተከራይተው ይኖሩበት የነበረ መኖሪያ ቤት እንዳላቸው ጠቅሰው የሚች አባታቸው የተከራይነት መብት እንዲተላለፍላቸው ዳኝነት እንዲያርፍበት ጥያቄ ማቅረባቸውን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ያለፉት ጉዳዩ በቤቱ ባለቤት የሚወሰን እንጂ በፍርድ ቤት የሚወሰን አይደለም በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ የቀበሌ ቤት የተከራይነት መብት ተከራይ ሲሞት ለወራሾቹ ወይም ለቤተሰቦቹ የሚተላለፍ መሆን ያለመሆኑ በፍ/ብ/ሕጉ ስለማይንቀሳቀስ ንብረት የኪራይ ውል የተመለከቱትን ድንጋጌዎች፣የቀበሌ ቤትን የኪራይ መብትና ግዴታ ለመግዛት በሚመለከተው አካል በወጡት ደንብና መመሪያዎች አንጻር ታይቶ በፍርድ ቤት ዳኝነት የሚሰጥበት እንጂ የቤቱ አስተዳዳሪ የሆነ ቀበሌ ለፈለገው ሰው የሚያከራየው ነው ተብሎ በፍርድ እንዳያልቅ የሚደረግ ጉዳይ አይደለም፡፡የቀበሌ ቤት የተከራይነት መብት የሚሰጥበት አግባብ በሕግ ስርዓት የሚዘረጋለትና የራሱ የሆነ አሰራር ያለ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡መብቱ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓትና አሰራር መሰረት መፈፀሙ ያለመፈፀሙ ላይ ክርክር ሲነሳ ደግሞ ነፃና ገለልተኛ በሆነ አካል፤በፍርድ ቤት ታይቶ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን፣ህጎችንና አሰራሮችን መሰረት በማድረግ ዳኝነት የሚሰጥበት እንጂ ጉዳዩ የቤቱ አስተዳዳሪ ለሆነው አካል የሚተው አይደለም፡፡የቀበሌ ቤት የተከራይነት መብት ላይ ክርክር ሲነሳ ጉዳዩ ለቤቱ አስተዳዳሪ ለሆነው ለቀበሌ የሚተው ነው ከተባለ የቀበሌ ቤት የተከራይነት መብት ማግኘት ያለባቸው ግለሰቦችም መብታቸውን በአግባቡ ለማስከበር የሚችሉበት አግባብ ይኖራል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች አንድ የቀበሌ ቤትን ተከራይቶ የነበረ ሰው ከዚህ አለም በሞት ሲለይ ወራሾቹ ወይም ቤተሰቦቹ የተከራይነት መብቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አግባብ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 37፣ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826(2) እና 2928 ድንጋጌዎች እንዲሁም በዚህ ረገድ የወጣውን መመሪያና ተቀባይነት ያለውን አሰራር በመመልከት የራሳቸው በቂ መተዳደሪያ የሌላቸው ዜጎች ከመንግስት ሊደረግላቸው ከሚገባው ድጋፍ ጭምር በመመርመር ዳኝነት መስጠት ሲገባቸው ጉዳዩ በፍርድ ቤት የሚያልቅ አይደለም በማለት የአመልካችን የቀበሌ ቤቱን የተከራይነት መብት የውርስ ጥያቄ ማለፋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75418 መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 135521 ታህሳስ 22 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 06 ክልል ውስጥ በሚገኘው ቁጥሩ 009 በሆነው የቀበሌ ቤት ላይ አመልካች ተከራይ የነበሩትን ሟች አባታቸውን አቶ ተክሌ ነጋሽ መብት ለመውረስ ያቀረቡት ጥያቄ በፍርድ ቤት የሚወሰን አይደለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡በቤቱ ላይ የቀረበው የተከራይነት መብት የውርስ ጥያቄ በፍርድ ቤት የሚያልቅ ነው በማለት በዚህ ነጥብ ላይ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን ቀጥሎ በፍርድ ሐተታው ላይ በተመለከተው አግባብ ጉዳዩን አጣርቶና ተገቢውን የክርክር አመራር ሁሉ በመከተል ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. ሶፋን ከእነ ሙሉ ጠረጴዛ በተመለከተ የበታች ፍርድ ቤቶች ማለፋቸውም ሆነ በሌሎች ንብረቶች ላይ የሰጡት የውሳኔ ክፍል ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውንወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102652

መጋቢት 16 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-ወ/ሮ ሀቢባ መካ -ከጠበቃ ዘውዱ ተሾመ ጋር ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ደሊል ሁሴን - ቀረቡ
2. ኢትዮ የአሽከርካሪዎች እና መካኒኮች ማሰልጠኛ ማዕከል ኃ. የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ ስንታየሁ ብርሃኑ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የአክሲዮን ድርሻ በተጋቢዎቹ መካከል የሚከፋፈልበትን ስርዓት አስመልክቶ የተነሳ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በነበረው የንብረት ክፍፍል ክርክር በ2ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው 162 የአክሲዮን ድርሻ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ንብረት መሆኑ ተረጋግጦ እኩል እንዲካፈሉ በስረ ነገሩ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ይህንኑ ውሳኔ ለማስፈጸም አመልካች ባቀረቡት የአፈጻጸም ክስ ላይ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 418 ድንጋጌን ጠቅሶ መቃወሚያ አቅርቦ የነበረ መሆኑን፣ፍርድ ቤቱም መቃወሚያው ወደፊት የሚታይ ነው በማለት የጋራ ናቸው የተባሉትን ሌሎች ንብረቶች በተመለከተ አፈጻጸሙን መቀጠሉን፣ከዚህ በኃላ የአክሲዮን ድርሻውን በተመለከተ እንደ ፍርዱ እንዲፈጸምላቸው አመልካች አቤቱታ ማቅረባቸውን፣ፍርድ ቤቱም የአክሲዮን ድርሻው የሚገኝበት ማህበር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ለአፈጻጸሙ ያመች ዘንድ በአፈጻጸም ጥያቄው ላይ ማህበሩ አስተያየት እንዲሰጥ ትዕዛዝ መስጠቱን ተከትሎ ከቀድሞ ተጋቢዎች መካከል አንዳቸው ለሌላኛው ድርሻውን ለቆ አንደኛው ወገን በማህበሩ አባልነት መቀጠል የሚችል ከመሆኑ ውጪ ሁለቱን ወገኖች በአንድነት በማህበሩ ውስጥ የማይፈልጋቸው መሆኑን ገልጾ አስተያየት ማቅረቡን፣ግራ ቀኙ የዋጋ ግምቱን ተቀብለው አንዳቸው ለሌላኛው ድርሻውን ለመልቀቅ መስማማት ያልቻሉ መሆኑን እና የማህበሩ አባላት ባልተስማሙበት ሁኔታ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ሌላ ሰው በማህበሩ ውስጥ አባል እንዲሆን መወሰን የማይችል መሆኑን ገልጾ የአክሲዮን ድርሻው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሸጦ ገንዘቡን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ እኩል እንዲከፋፈሉ ትዕዛዝ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት አክሲዮኖች በዓይነት መካፈል የሚችሉ ሆነው የ2ኛ ተጠሪ መተዳደሪያ ደንብም ሳይከለክል አክሲዮኖቹ በሐራጅ ተሸጠው ክፍፍሉ እንዲፈጸም የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በ2ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው 162 የአክሲዮን ድርሻ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት መሆኑ በስረ ነገሩ ፍርድ ተረጋግጧል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የአክሲዮን ድርሻው በሐራጅ ተሸጦ ክፍፍሉ በገንዘብ እንዲደረግ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው ከቀድሞ ተጋቢዎች መካከል አንዳቸው ለሌላኛው ድርሻውን ለቆ አንደኛው ወገን በማህበሩ አባልነት መቀጠል የሚችል ከመሆኑ ውጪ ሁለቱን ወገኖች በአንድነት በማህበሩ ውስጥ የማይፈልጋቸው መሆኑን ገልጾ 2ኛ ተጠሪ ማህበር አስተያየት አቅርቦአል በማለት ነው፡፡አመልካች ከስር ጀምረው የሚከራከሩት ደግሞ አክሲዮኖቹ በዓይነት ሊካፋፈሉ የሚችሉ በመሆኑ ሕጻናት ልጆቻቸውን ለማሳደግ ጭምር እንዲረዳቸው የአክሲዮኖቹ ክፍፍል በዓይነት እንዲደረግ በመጠየቅ ነው፡፡በመሰረቱ የጋብቻ መፍረስን ተከትሎ የጋራ ሀብት እንዲከፋፈል የሚደረገው እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ ስለመሆኑ እና ክፍፍሉ በሽያጭ ሊደረግ የሚችለው ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ ንብረቱ ከሁለት ለአንዳቸው እንዲሰጥ ባልና ሚስቱ ሳይስማሙ በቀሩ ጊዜ ስለመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 91 እና 92 ስር በዝርዝር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 2ኛ ተጠሪ ማህበር ከአመልካች እና ከ1ኛ ተጠሪ መካከል አንዳቸውን እንጂ ሁለቱን በማህበሩ ውስጥ አልፈልጋቸውም ከማለት በቀር አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ አክሲዮኖቹን በየድርሻቸው በዓይነት በመከፋፈልየማህበሩ አባላት መሆን የማይችሉበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክርክር እና ማስረጃ የለም፡፡በሰበር ደረጃም ቢሆን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ አክሲዮኖቹን በዓይነት ተከፋፍለው በአባልነት ይቀጥሉ መባሉ በማህበሩ ውስጥ ብርቱ ጭቅጭቅን እና አለመግባባትን የሚያስከትል ነው ከማለት ውጪ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሊከሰት ስለሚችልበት ምክንያት ያቀረበው አሳማኝ መከራከሪያ የለም፡፡ የአክሲዮኖቹ በዓይነት የመከፋፈል ጉዳይ የሚመለከተው በመሰረቱ አመልካችን እና 1ኛ ተጠሪን እንጂ 2ኛ ተጠሪን ባለመሆኑ አክሲዮኖቹ ሊከፋፈሉ የሚገባቸው በሽያጭ ነው በማለት 2ኛ ተጠሪ መቃወሚያ አቅርቦ ለመከራከር የሚያስችል መብት እና ጥቅም አለው ለማለትም የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል በ2ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው 162 የአክሲዮን ድርሻ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የአክሲዮን ድርሻውን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በዓይነት እንዲከፋፈሉ ለመወሰን የሚከለክል ሕጋዊ ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ 2ኛ ተጠሪ ማህበር የሰጠውን አስተያየት ብቻ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት በማድረግ የአክሲዮን ድርሻው ክፍፍል በሽያጭ አማካይነት እንዲፈጸም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 91 እና 92 ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በ2ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግበው የሚገኙት 162 የአክሲዮኖች ለአመልካች እና ለ1ኛ ተጠሪ ሊከፋፈል የሚገባው በሐራጅ ሽያጭ ነው በሚል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 206322 በ25/07/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150907 በ30/08/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በ2ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግበው የሚገኙት 162 አክሲዮኖች በዓይነት ሊከፋፈሉ የማይችሉበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ እነዚህን አክሲዮኖች አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 91(1) ድንጋጌ መሰረት እያንዳንዳቸው 81 አክሲዮኖችን በዓይነት ሊከፋፈሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በውሳኔው መሰረት እንዲያስፈጽም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ እንዲያውቀው ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 108539

መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አበባው አጥናፉ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ የካባ ግዛው - ወኪል ተሻገር ካሜ - ቀረበ

2. አቶ ጌቴ ግዛው - ቀረቡ

3. ወ/ሮ ምሳዬ ግዛው - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት መብት በውርስ የሚተላለፍበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በመቄት ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች የአሁኑ ተጠሪዎች የሚች እማሆይ እቴ አለማየሁ የገጠር መሬት ይዞታ ሕጋዊ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋገጥ ማስረጃ በወረዳው ፍርድ ቤት ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ/ም መውሰዳቸው ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ ውጪ ነው በማለት ተጠሪዎች የወሰዱት ማስረጃ እንዲሰረዝ መስከረም 20 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪዎች የገጠር መሬት ይዞታ ውርስ ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲሰረዝ መሰረት ያደረጉት ምክንያት የሚች እማኝይ እቴ አለማየሁ የቤተሰብ አባልና የራሳቸው መሬት ይዞታ የሌላቸው ሁኖ እያለ ተጠሪዎች የሚቺ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች በመሆናቸው ብቻ መሬቱን ሊወርሱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም የሚል ሲሆን ተጠሪዎች ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርበው በሰጡት መልስ የሚች ልጆች ሁነው በሕጉ አግባብ የወራሽነት ማስረጃውን መውሰዳቸውን ፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ የሚቺ የቤተሰብ አባል ቢሆኑም እማሆይ እቴ አለማየሁ ከነበራቸው ሁለት ቃዳ መሬት ከመሞታቸው በፊት እኩሌታውን ከፍለው ለአሁኑ አመልካች የሰጧቸውና አመልካቹ የራሳቸው የሆነ ይዞታ እያላቸው የሚቺን ድርሻ ለመውሰድ ጥያቄ ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ በዚህ መልክ ክርክር የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳዳር አዋጅና ደንብ መሰረት ሳይናዘዝ የሞተ አርሶ አደር ይዞታ መብት የሚተላለፍበትን የሕግ አግባብ ዘርዝሮ ከአስቀመጠ በኋላ አመልካች መሬት ያላቸው የሚች የቤተሰብ አባል ሲሆኑ ተጠሪዎች ደግሞ መሬት ላቸው የሚች ልጆች ናቸው የሚል ምክንያት ይዞ ተጠሪዎች ይዞታውን ለመውረስ ማስረጃ መውሰዳቸው በአግባቡ ነው በማለት የአመልካችን ተቃውም ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሰሜን ወሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስተዳዳር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው በፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮይዞታውን የመውረስ መብት ያላቸው የአሁኑ አመልካች እንጂ የአሁኑ ተጠሪዎች አይደሉም በማለት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኝቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች ያወጡት የወራሽነት ማስረጃ በደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/7/ሐ// መሰረት መሬት ያላቸው የሟች ልጆች መሆናቸውን የሚገልጽ ነዉ ፣ የአሁኑ አመልካች ያወጣው የወራሽነት ማስረጃ በደንቡ አንቀጽ 11/7/ለ// መሰረት የሟች የቤተሰብ አባል መሆኑን የሚገልጽ ነው የሚል ምክንያት ጠቅሶና ማስረጃው የሟችን መሬት ለመውረስ ያላቸውን ደረጃ የሚገልጽ ገላጭ የሆነ ማስረጃ ነው ፣ በመሬቱ ላይ ያላቸውን የመውረስ ቅደም ተከተል ደግሞ በመሬቱ ላይ ክርክር በተደረገ ጊዜ የሚታይ እንጂ የማስረጃ ይሰረዝልኝ ጊዜ የሚታይ አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ውጤቱን አጽንቶታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት የሠበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች የሚች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ በመሆናቸው ብቻ በመሬቱ ላይ ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እነዲታይ በመደረጉ 1ኛ እና 3ኛተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው ሊቀርቡ ባለመቻላቸው በጹሑፍ መልስ የመሰጠት መብታቸው የታለፈ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ግን ቀርበው ከአመልካች ጋር በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን በሥር በሚገኙት በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ያደረጉትን ክርክር እና በእነዚህ ፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ዳኝነት አግባብነት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው ህጎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነው ክርክር ያስነሳው የእርሻ መሬት ይዞታ ሟች እማሆይ እቴ አለማየሁ ኑዛዜ ሳይተው ከዚህ አለም በመለየታቸው ምክንያት አመልካችና ተጠሪዎች የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ መሰረት አድርገው የውርስ ይገባናል ጥያቄ አቅርበው የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕጉ ያለውን የገጠር መሬት የውርስ ቅደም ተከተል መሰረት አድርገው ተገቢ ነው ያሉትን ዳኝነት የሰጡ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን የቅደም ተከተሉን ጉዳይ እልባት ሳይሰጠው በመሬት ላይ ክርክር በተደረገ ጊዜ የሚታይ ነው በሚል ያለፈው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ይሄው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተገቢነት ነው፡፡

በአንድ ክርክር ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባው የክርክሩን አርእስት በማየት ሳይሆን ዝርዝር ይዘቱን በአግባቡ በመለየትና ተገቢነት ያለውን ህግ መሰረት በማድረግ መሆኑን የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ክርክር የሚመራው ደግሞ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ነው፡፡ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራው በ1958 ዓ/ም በወጣው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግና ተፈጻሚነት ባላቸው ሌሎች የክልል ሕግጋት መሆኑ ይታወቃል፡፡ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ መሰረታዊ ዓላማም ክርክሮች በአነስተኛ ወጪ፣ ጉልበት እና በአጭር ጊዜ ታይተው ፍትሓዊና ትክክለኛ ዳኝነት ለመስጠት ማስቻል መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ክርክር ይህንኑ የክርክር አመራር መሰረታዊ አላማ በሚያሳካ መልኩ ሊመራ ይገባዋል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከተውም አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳዳር ሕግ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ ተጠሪዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚቺን ይዞታ ለመውረስ የሚያስችላቸው ማስረጃ መሰጠቱን ገልጸውና ይዞታውን በህጉ አግባብ መውረስ የሚችሉት አመልካች መሆኑን ጠቅሰው ለተጠሪዎች የተሰጣቸው ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ የአከራካሪው ይዞታ ህጋዊ ወራሾች መሆን የሚገባቸው ተጠሪዎች እንጂ አመልካች አለመሆናቸውን ገልጸው ማስረጃው ሊሰረዝ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በጭብጥነት ይዞ እልባት የሚሰጥበት ጉዳይ ይዞታውን መውረስ የሚችለው ወገን የትኛው ነው የሚለው ነው፡፡ የዚህ ጭብጥ እልባት ማግኘት ደግሞ ይዞታው ላይ መብት ያለውን ሰው የሚለይ በመሆኑ መብቱ የተረጋገጠለት ሰው አዲስ የመሬትይዞታ ይገባኛል ክርክር የሚያቀርብበት አግባብ ሳይኖር ውሳኔውን መሰረት አድርጎ አፈጻጸሙን የሚቀጥልበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህም አላስፈላጊ ወጪና የጊዜ ብክነት በማስቀረት ለክርክር እልባት ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ተጠሪዎች ከገጠር መሬት ይዞታ ውጪ በሌሎች የሚች ንብረቶች ማስረጃውን የወሰዱ መሆኑን አመልካች ገልጸው የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ያለማቅረባቸውን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ማስረጃውን መሰረት አድርጎ የሚቀርብ የክፍፍል ጥያቄ በሌለበት ሁኔታ ወይም የገጠር መሬት ይዞታ ላይ የተሰጠውን የወራሽነት ማስረጃ መሰረት አድርገው ግራቀኙ የድርሻ ወይም የክፍፍል ጥያቄ ሊያነሱ የሚችሉበት አግባብ ሳይኖር ከክርክሩ ባህርይና ከፍትሃብሄር ስነ ስርዓት ውጪ የማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ላይ የመሬት ይዞታ ወራሽነት ቅደም ተከተል የመሬት ክርክር ሲነሳ የሚታይ ነው ተብሎ መወሰኑ የሕግ መሰረት የሌለውና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-07895 ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 03-09360 ህዳር 03 ቀን 2007 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሚች እሚኃይ እቴ አለማየሁ የገጠር እርሻ መሬት ሊወርስ የሚገባው ማን ነው? የሚለው ጥያቄ እልባት ማግኘት ያለበት በሌላ መዝገብ በሚከፈተው የመሬት ክርክር ሳይሆን አመልካች ባቀረቡት የክርክር አግባብ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ክርክሩን በመ/ቁጥር 03-07895 ቀጥሎ የወረዳው ፍርድ ቤት እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ አዋጅ ቁጥር 133/98 እና በደንብ ቁጥር 51/99 የተደነገገውን አግባብ መሰረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን መርምሮ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ምክንያት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 101079

ጥር 22 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች:- የይልማና ዴንሳ ወረዳ አስባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፅ/ቤት

ከክልል ፍትህ ቢሮ አይናዲስ አሰጋህኝ - ቀረቡ

ተጠሪ :- አቶ ውበት ገ/መድህን - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የገጠር የእርሻ መሬት የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በይልማና ዴንሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአቶ ልንገርህ ውበት ላይ የእርሻ መሬት ይዞታዬን ያላግባብ ይዞብኛል በማለት ክስ መስርተው ፍርድ ቤቱን የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አከራካሪውን መሬት አቶ ልንገርህ ውበት ለአሁኑ ተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቶ የአሁኑ ተጠሪ በዚሁ ፍርድ መሰረት እንዲፈጸምላቸው የአፈጻጸም ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡በዚህ ሂደት የአሁኑ አመልካች አከራካሪውን ይዞታ ይዘው የነበሩት አቶ ልንገርህ ውበት የመንግስት ሰራተኛ ስለሆኑና አመልካችም የይዞታ ባለመብት ስላልሆኑ ይዞታውን ሊረከቡ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፣ ውሳኔው የህዝብንና የመንግስት ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ሊነሳ ይገባል በማለት አቤቱታውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች የፍርድ መቃወሚያ ላይ መልስ እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ላይ በሰጡት መልስም የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አቀራረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ስር የተመለከተውን አግባብ ያልተከተለ መሆኑን፣አቶ ልንገርህ ውበት የተባሉት ግለሰብ መሬቱን ከተጠሪ በስጦታ ስለመቀበሉ ምንም ማስረጃ ባልቀረበበትና ራሱ የፍርድ ተቃዋሚ ወገን ባለሙያ መድቦ ይህንኑ ባረጋገጠበት ሁኔታ ፍርዱን መቃወሙ ያላግባብ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የተጠሪን መከራከሪያ ነጥብ ውድቅ አድርጎና የቀድሞውን ውሳኔ በመሻር መሬቱ ለክፍሉ ቀበሌ የመሬት አስተዳደር ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ የቀረበው ተጠሪ የመሬት ይዞታውን ከተረከቡ በኋላ በመሆኑ መቃወሚያው ዋናው ፍርድ ከተፈጸመ በኃላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የሚቀርብበትና የሚስተናገድበት አግባብ የለም በማለት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሮታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች የፍርድ መቃወሚያውን ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት ማቅረቡን፣ የአከራካሪው መሬት ይዞታ ስም በተጠሪ ሳይመዘገብ ርክክቡ ተፈፅሟል የሚባልበት አግባብ ያለመኖሩን ዘርዝሮ መቃወሚያው በሕግ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የቀረበ ሁኖ እያለ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- በሚያከራክረው የገጠር መሬት ይዞታ ላይ አመልካች ያቀረበው የፍርድ መቃወሚያ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ አይደለም ተብሎ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪ በልጃቸው ይዞታ ስር የነበረውን መሬት ልጃቸው ሕጋዊ መብት ሳይኖራቸው ይዘው እንደሚገኙ ገልፀው ባቀረቡት ክስ ከልጃቸው ጋር ተከራክረው መሬቱን እንዲለቀቅላቸው በተወሰነው መሰረት መሬቱን የተረከቡ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡አመልካች አሁን አጥብቆ የሚከራከረው የክርክሩ ምክንያት የሆነው የገጠር የእርሻ መሬት እንደመሆኑ መጠን አመልካች መሬቱን ተረክበዋል ሊባል የሚችለው የይዞታ ማረጋገጫ ሲያገኙ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ተጠሪ በበኩላቸው ይህ አይነት አሰራር በተለያዩ የአስተዳደር አሰራሮች ሊዘገይ የሚችል በመሆኑ ተጠሪ መሬቱን አልተረከቡም ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የተዘረጋው ሥርዓት አስቀድሞ በተሰጠው ውሣኔ መብቱ የሚነካበት ወገን ባለበት ውሣኔ እንዳልተሰጠበት ተቆጥሮ እንደገና ክርክር የሚጀምርበት ሥርዓት ነው፡፡ መሰረታዊ አላማም ቅን ልቦና ያላቸው ወገኖች በመሰረታዊ ሕግ የተጠበቀላቸው መብት ባለመከራከር ዋጋ እንዳያጣ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ድንጋጌው በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ወገን አቤቱታውን ለማቅረብ መብት እንደአለው በመለኪያነት ያስቀመጠ ሲሆን ይኼው የድንጋጌ ይዘትም የተቃውሞ አቤቱታውን ለማቅረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39፣40 እና 41 አግባብ የክርክሩ ተካፋይ ሊሆን ይገባው የነበረውንና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33 አግባብ ደግሞ በጉዳዩ መብትና ጥቅም ያለው ወገን መሆን እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ የተቀመጠው የሕጉ ሐሳብ በተቃውሞ አቤቱታ አቀራረብ ስርዓት መብቱ ሊከበርለት የሚገባው ወገን ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ክፍል አንፃር ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ ያለው የመሚገት መብት የተጠበቀ ነው ለማለት እንጂ በማንኛውም ጉዳይ ቢሆን በአንድ ጉዳይ አፈፃፀሙ ማለቁ የተረጋገጠበት ወገን አፈጻፀሙ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከአፈፃጸሙ መዘገብ መዘጋት በኃላ የፍርድ መቃወሚያ በማቅረብ የመሚገት መብት አለው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 ሰፊና የፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ አላማ ውጤት አልባ የሚያደርግ ትርጉም ለመስጠት ተፈልጎ አይደለም፡፡ይህ ዓይነት አተረጓጎም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግን መሠረታዊ ዓላማ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሚያግኝበት አግባብ የለም፡፡አፈጻጸም የፍርድ ቤት ውሳኔ ትርጉም የሚያገኝበት ሂደት በመሆኑ አፈጻጸሙ በሕጉ አግባብ ከተጠናቀቀ በኋላ ይህንኑ ሂደት ወደ ኃላ መመለስ የአፈጻጸም ስርዓት የሚፈቅደው አይደለም፡፡በመሆኑም አንድ ፍርድ ከተፈፀመ በኃላ የፍርድ መቃወሚያ ማቅረብ የማይቻል መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ በቀላሉ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡አከራካሪው ጉዳይ አንድ ፍርድ ተፈፀመ የሚባለው መቼ ነው? የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡ይህ ጥያቄ እንደ ለክርክሩ መነሻ እንደሆነው ንብረት ልዩ ባህርይ ታይቶ ሊመለስ የሚችል ነው፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለሰው የፍርድ ባለመብት ፍርዱ ተፈጽሞለታል የሚባለው ጥሬ ገንዘብ ከሆነ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ ሲመለስለት፣የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሆነ ደግሞ ንብረቶቹን ተረክቦ በይዞታው ላይ ሲያደርግ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ መሬቱን ከልጃቸው መረከባቸውን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ይሁን እንጂ ተጠሪ በመሬቱ ላይ ያላቸው መብት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትም ሆነ በክልሉ ህገ መንግስት እንዲሁም የገጠር የእርሻ መሬት አስተዳደርን አጠቃቀምን በተመለከተ በፌዴራሉ መንግስት በወጣው አዋጅ ቁጥር 456/1997 እንዲሁም ይህንኑ አዋጅ ተከትሎ በወጣው የክልሉ አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ደንብ ቁጥር 51/1999 አግባብ የይዞታ መብት ሲሆን ነው፡፡በመሆኑም መሬቱ ላይ ያላቸው የባለይዞታ መብት የሚረጋገጠው መሬቱን እንዲያስተዳደር በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል በሕጉ አግባብ ሲያስረክባቸውና በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የባለይዞታ መብት ማረጋገጫ ደብተር ሲያገኙ ነው፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ መሬቱን ከልጃቸው ተረክበዋል ከመባሉ ውጪ ርክክቡ መሬቱን የሚያስተዳድረው የመንግስት አካል እውቅና ሰጥቶ የተፈፀመ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲሰጣቸው በተገቢው ጊዜ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ጥያቄ አቅርበው በአስተዳዳራዊ አሰራር ችግር የዘገዬ ስለመሆኑም የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ስለሆነም ተጠሪ በሕጉ የተጠበቀላቸውን የባለይዞታነት መብት ተረክበዋል ሊባል የሚችለው ይዞታውን ከግለሰብ እንዲረከቡ በመደረጉ ብቻ ሳይሆን ሕጋዊ ማረጋገጫ ሊሆን የሚችል ማስረጃ ሲያገኙ ነው፡፡የገጠር መሬትን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮችን መሰረት አድርጎ የሚቀርብ የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አቀራረብ፤ ፍርድ ከተፈጸመ በኃላ የቀረበ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ መለኪያ ሕገ መንግስቱን መሰረት አድርገው ጉዳዩን ለመግዛት የወጡ ሕጎችን፣ደንቦችንና መመሪያዎችን በሚያሳካ መልኩ ካልተተረጎመና ተግባር ላይ ካልዋለ ግለሰቦች ተገቢ ያልሆነ ክርክር በማቅረብ አንዱ ላንዱ ይዞታውን አስረክቤለሁ በማለቱ ብቻ የገጠር መሬትን የሚያስተዳድረው የመንግስት አካል የሕዝብና የመንግስት ጥቅም ለማስከበር እንዳይችል የሚያደርግ ውጤትን የሚያስከትል በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ ሁኖአግኝተናል፡፡ሲጠቃለልም አመልካች የፍርድ መቃወሚያውን ያቀረበው ፍርዱ ሙሉ በሙሉ ተፈጽሚል ሊባል በማይችልበት ሁኔታ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 52990 የካቲት 07 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 35349 ግንቦት 16 ቀን 2005 ዓ/ም ፣የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 32961 መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. በገጠር የእርሻ መሬት ላይ በተሰጠ ፍርድ የፍርድ መቃወሚያ ሲቀርብ ፍርዱ ተፈጽሟል ሊባል የሚችለው የፍርድ ባለመብቱ በይዞታው ላይ ሕጋዊ ማረጋገጫ ሲያገኝ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች በሚያከራክረው መሬት ላይ የፍርድ መቃወሚያው ያቀረበው ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት መሆኑን አውቆ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የይልማና ዴንሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ታህሳስ 11 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በሕግም ሆነ በፍሬ ነገሩ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን መርምሮ ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

መ/ት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96495

ቀን 05/06/2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት - ነገረ ፈጅ ወይንሽት እንድሪስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሌ ብሩ - ተወካይ ዓመተ ኃይሌ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 46873 በ30/08/2005 ዓ/ም የተሰጠው ፍርድ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በአመልካች ፈቃድ ተመስረተው ተጠሪ የገነቡት ቤት የሚኖረው ህጋዊ ውጤት የተመለከተ ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ ሲሆኑ የአሁኑ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ባጭሩ፡- በአመልካች ተቀጥረው ሲሰሩ በ1967 ዓ/ም አንድ ክፍል መኖሪያ ቤት እንደተሰጣቸው በሒደት የቤተሰባቸው አባላት ቁጥር በመጨመሩ በራሳቸው ወጪ ተጨማሪ ክፍል 2 መኝታ ፤ ሳሎን ፤ 2 ክፍል ኩሽና መስራታቸው በሰሩት ቤትም ከ1975 ዓ/ም ጀምሮ ለ 30 ዓመታት ሲጠቀሙ እንደነበር አሁን ግን አመልካች ቤቱን እንዲለቁ እያስገዳዳቸው በመሆኑ ድርጊቱ እንዲቆም ወይም ቤቱን የተሰራበት አርባ አምስት ሺህ ብር እንዲከፍላቸው ጠይቋል፡
የአሁኑ አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪ ቤቱን ያገኙት በስራ ምክንያት ነው ፤ ቤቱ የተገነባው ለህዝብ ጥቅም ሲባል የተቋቋመ በመሆኑ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በተቋቋመ ንብረት ላይ የይዞታ መብት ማቋቋም ስለማይቻል ክስ ማቅረብ አይችሉም፡፡ ቤቱም የገነቡት አመልካች እየተቃወመ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ማስረጃ እና ክርክር ከመረመረ በኃላ በአሰሪና ሰራተኞች ማህበር በተፈረመው የህብረት ስምምነት መሰረት የተቋመ ሰራተኛ በጡረታ ወይም በሌላ ምክንያት ከስራ ገበታው ሲገለል የተረከበው ቤት በነበረበት ሁኔታ ሊያስረክብ እንደሚያስገደድ በመጥቀስ ተጠሪ ቤቱን ለቀው ያስረክቡ፡፡ ቤቱን ለመስራት ያወጡት ወጪም አመልካች የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ቤቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰሩት በ1975 ዓ/ም ሲሆን የህብረት ስምምነቱ የተቋቋመው በ1989 ዓ/ም ነው። አመልካች ተጠሪ ቤቱን ሲሰሩ ምንም ተቃውሞ አላቀረቡም። ተጠሪ በተጨማሪነት ሁለት ክፍል ቤቶች መኝታ ቤት ሳሎን ኩሽና በቤት ቁጥር 420 ላይ ሲገነቡ አመልካች ምንም ያቀረበው መቃወሚያ የሌለ መሆኑን ፍርድ ቤቱ መገንዘቡን ፤ በዚሁም የተነሳ ተጠሪ ለእነዚህ ተጨማሪ መኖሪያ ቤቶች ባለሀብት ሆነዋል። አመልካች ለተጠሪ ግምቱን ሰጥቶ ማሰናበት አሊያም ደግሞ ተጠሪ ቤቱን አፍርሰው እንዲሄዱ መብት አላቸው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔውን ሽረዋል። የአሁኑ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 ተሰርሏል። የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ለማስለወጥ ነው።ግራ ቀኙ ከዚህ ችሎት የጽሁፍ ክርክር አድርገዋል። አመልካች በዋናነት የሚከራከረው አመልካች ድርጅት ለህዝብ ጥቅም የተቋቋመ በመሆኑ በነዚህ ይዞታዎች ላይ ግዙፍ መብት በማቋቋም ባለመብት ለመሆን እንደማይቻል በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1446፣1454 እና 1455 በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ የስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔዎች እንዲሻሩ የሚያመለክት ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በአመልካች ፈቃድ የገነቡት መሆኑን በድርጅቱ ለረጅም ዓመታት ሲያገለግሉ ቆይተው በጡረታ ተገለው እየኖርበት እንደነበር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል። አመልካች የሰበር አቤቱታው የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረነውም አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው ለመኖሪያነት ተፈቅዶ በነበረው ይዞታ ላይ ተጨማሪ ቤቶች በመሰራታቸው ተጠሪ በቤቱ ላይ ያለቸው ህጋዊ መብትና ጥቅም በአመልካች ክርክር እንደተነሳው ለህዝብ ጥቅም በተቋቋመ ድርጅት መብት ማቋቋም አይችልም የሚለው የፍ/ህ/ቁ. 1454 እና 1455 መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ከአጠቃላይ የህጉ ዓላማና መንፈስ ተገናዝቦ መታየት አለበት። በስር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነገር ቢኖር ተጠሪ የአመልካች ሠራተኛ በነበሩበት ጊዜ ለመኖሪያነት በተሰጣቸው ይዞታ ላይ ተጨማሪ ክፍሎች ሲገነቡ በአመልካች በኩል የቀረበ ተቃውሞ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም። ተጠሪ ቤቱን ሰሩት የተባለው እና በአመልካች ድርጅት እና ሠራተኞች የተፈረመው የህብረት ስምምነት ቤቱ ከተገነባ በኃላ ስለመሆኑ በአመልካች የተካደ ጉዳይ አይደለም። ተጠሪ በሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት መልስ ቤቱን በአመልካች የጽሁፍ ፈቃድ የተገነባ ስለመሆኑ የገለጹ ሲሆን አመልካች ለተጠሪ ፈቃድ እንዳልተሰጠ የመልስ መልሱ ላይ አላስተባበለም። ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት ላይ ጡረታ ከወጡ በኃላም እየኖሩበት እንደሆነ አልተካደም።

አመልካች ከስር ፍርድ ቤት አንስቶ አጽንኦት በመስጠት የሚከራከረው ለህዝብ ጥቅም በተቋቋመ የመንግስት ይዞታ ላይ መብት ማቋቋም አይቻልም በሚል ነው። በእርግጥ ለህዝብ በተቋቋም መንግስት ይዞታ ላይ መብት ማቋቋም እንደማይቻል በፍ/ህ/ቁ. 1454 እና 1455 በግልጽ ተመልክቷል። ይሁንና የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት ፣ ዓላማና ግብ መታየት ያለበት መብቱን ባቋቋመ ግለሰብ እና መንግስት የነበረው ህጋዊ ግንኙነት መሰረት በማድረግ ነው። አመልካች እና ተጠሪ የስራ ውል ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፤ አመልካች ለተጠሪ መኖሪያ ቤት የሰጣቸው መሆኑን ፤ በሂደት ቤተሰብ መስርተው የቤተሰብ አባላት ቁጥር በመጨመሩ ምክንያት ተጨማሪ ቤት እንዲገነቡ በአመልካች በጽሁፍ ፈቃድ መሰጠቱ በአመልካች አልተካደም። አመልካች እና ተጠሪ ህጋዊ ግንኙነት የነበራቸው በመሆኑ ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቱን የገነቡት ከአመልካች ፈቃድና እውቅና ውጭ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ህጋዊ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች የተቋቋመው መብትና ግዴታ ምንም ህጋዊ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች እንደተገነባ ጥቅም መታየት የለበትም፡፡ ከላይ የተመለከትነው የህግ ድንጋጌም ህጋዊ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች የተገነባ ጥቅም /መብት/ ካለ የህግ ጥበቃ የሚሰጠው መብት ማቋቋም እንደማይችሉ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል ግንኙነት መሰረት በማድረግ በአመልካች ፈቃድ ተጠሪ የግል ሀብታቸው በማውጣት የገነቡትን ቤት አፍርሰው ለመውሰድ አልያም የቤቱን ግምት የመጠየቅ መብት ሊነፈጉ አይገባም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ተጠሪ አመልካች ሳይቃወም ለገነቧቸው ተጨማሪ ቤቶች ያወጡት ወጪ ብር 45,000 (አርባ አምስት ሺህ) ይክፈሉ ወይም ደግሞ ቤቱን አፍርሰው ይውሰዱ በማለት መወሰኑ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሄር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔውን ማጽናቱ ህጉን በአግባቡ ተግባራዊ አድርገዋል ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 127167 በ12/11/2005 ዓ/ም የፌዴራል የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 46873 በ30/08/2005 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በመሻር የሰጠው ፍርድ ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 93048 በ22/02/2006 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪ አመልከች ሳይቃወም ለገነቧቸው ተጨማሪ ቤቶች ያወጡትን ወጪ ብር አርባ አምስት ሺህ /45,000.00/ ይክፈላቸው ወይም ቤቱን አፍርሰው እንዲሄዱ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመልስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.97132

መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ መሀመድ ከማል ሀምዛ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡-1ኛ የከሚሴ ከተማ ወረዳ ፖሊስ
2ኛ የከሚሴ ከተማ ወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት
} ተወካይ አይኔ አዲስ አሰጋኸኝ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በኢግዚቢት ተይዞ ነበር በተባለው እስታር ማክሮቭ ሽጉጥ አመላለስ ጋር በተያያዘ የቀረበ ሲሆን በሥር የደ/ሥ/ፌ/ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ውድቅ የተደረገባቸው በመሆኑ በሰበር ተጣርቶ እንዲወሰን የቀረበ ነው፡፡ አመልካች በሥር ወረዳ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት፡- ቁጥሩ 635 የሆነው እስታር ማክሮቭ ሽጉጥ ከ8 መሰል ጥይቶች ጋር ህገ ወጥ መሣሪያ ይዘሃል ተብሎ በፖሊስ ተጠይቀው መሣሪያውም በኢግዚቢት ተይዞ ምርመራ ከተጠናቀቀ በኋላ ሽጉጡ ፈቃድ ያለው የግላቸው መሆኑ ቢከራከሩም የሥር ፍርድ ቤት ሳይቀበል ጥፋተኛ ያላቸው መሆኑን፤ ለአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ በነፃ እንደተለቀቁ፣ በኢግዚቢት የተያዘው ሽጉጥ በፍትሐብሄር መጠየቅ እንደሚችሉ ሰበር ሰሚ ችሎቱ መብታቸው የጠበቀላቸው በመሆኑ፣ በኢግዚቪት ተያዘ የተባለውን ሽጉጥ ላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ አለመስጠቱን፤ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊዎች በመሆናቸው ሽጉጡ ከመሰል ጥይቱ በዓይነት እንዲመልሱ፤ በዓይነት ማስረከብ የማይችሉ ከሆነም በድምር 33,400 ብር እንዲከፈሉ እንዲወሰንላቸው የሚጠይቅ ነዉ፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ ከአመልካች የተያዘው ሽጉጥ ቁጥር 635 ሳይሆን ቁጥር 165231 መሆኑን፤ ሽጉጥ የተያዘው መሃመድ ከማል የተባለው ግለሰብ ሲያስፈራሩበት የነበረ ስለመሆኑ በመግለጽ ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱ ማመልከታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ የቃል ክርክር እንዲሁም የተጠሪዎች የሰው ምስክሮች ካደመጠና የአመልካች የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ፖሊስ ከአመልካች የያዘው ሽጉጥ ቁጥሩ 635 የሆነ ማክሮቭ ሽጉጥ ሳይሆን ፈቃድ የሌለው ማክሮቭ ሽጉጥ ቁጥር 165231 ከሁለት መሰል ጥይቶች ጋር መሆኑን በወቅቱ ጉዳዩን ያጣራው መርማሪ ፖሊስ እና ሽጉጡን በኤግዚቢት ገቢ ያደረገው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከሚሴ ከተማ ፖሊስ ጽ/ቤት የግምጃ ቤት ሠራተኛ አስረድቷል በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጐታል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ የሰበር ቅሬታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው በመሰረታዊነት ያነሳቸው ዋና ዋና ነጥቦች፡- ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ቀን ይዘውት የነበረው ሽጉጥ ፈቃድ ያለው ነው፡፡ የንምራ ቁጥር 635 የነበረው በመፋቅ ሌላ ተለጣፊ ቁጥር ተደርጎበት በፎርጅድ ቁጥር ሌላ ባለሥልጣን የታጠቀው ስለመሆኑ፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ሽጉጥ ንምራ ቁጥሩ 635 ነው ወይስ 165231 የሚለው በፎረንሲክ የባለሙያ/expert/ ምርመራ ያልተደረገበት ስለመሆኑ፤ የሰበር ሰሚ ችሎት ንብረት የመጠየቅ መብታቸው መጠበቁ በመሆኑም በባለሙያ ምርመራ ተደርጎ ቁጥሩ መረጋገጥ እንደሚገባ ማመልከታቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ደግሞ የተያዘው ሽጉጥ 635 ሳይሆን 165231 መሆኑን የሰው ምስክር በቂ እንደሆነ የፎረሲንክ ምርመራ አግባብነት እንደሌለው የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና መጠየቁን የሚያመለክት ነው፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታቸው የሚያጠናክር ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በአመልካች የቀረበው የጦር መሣሪያ ፈቃድ የመሣሪያው ዓይነት ስታር ሽጉጥ የወግ ቁጥር 635 መሆኑን የሚያመለክት፤ እንዲሁም የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 24840 ህዳር 28 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ከአመልካች ተያዘ የተባለው ሽጉጥ የንምራ ቁጥር 165231 ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አለመቅረቡን፤ አመልካች የንምራ ቁጥር 635 የሆነ ማክሮቭ ሽጉጥ ፈቃድ እንዳለው ማስረጃ በማቅረባቸው ምክንያት ከወንጀል ድርጊቱ በነፃ እንዲሰናበቱ በኤግዝቢትነት የተወሰደባቸው ሽጉጥ በፍትሐብሔር ክስ አቅርበው የመጠየቅ መብታቸው መጠበቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩት በኢግዚቢት ተያዘ የተባለው ሽጉጥ ንምራ ቁጥር 635 እንጂ 165231 አይደለም፡፡ የንምራ ቁጥር 165231 የተባለው ፎርጅድ ቁጥር ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሽጉጥ የንምራ ቁጥር 635 ይሁን 165231 በባለሙያ /expert/ ምርመራ ተደርጎበት ውጤቱ አልቀረበም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በአንፃሩ ከአመልካች የተያዘው ሽጉጥ ንምራ ቁጥር 165231 ስለመሆኑ በሰው ምስክሮች ተረጋግጧል የፎረንሲክ ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ንምራ ቁጥር 165231 አመልካች ይዘው ስለመገኘታቸው አልተረጋገጠም በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ ሽሯል፡፡ በአንፃሩ አመልካች ፈቃድ ያለው ንምራ ቁጥር 635 የሆነ ማክሮቭ ሽጉጥ እንደነበራቸው በውሳኔው አስፍሯል፡፡

የሥር ወረዳ እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች አመልካች ይዘውት ተገኙ የተባለው ሽጉጥ ንምራ ቁጥር 165231 ስለመሆኑ በሰው ምስክር ተረጋግጧል የሚል ነው፡፡ ይሁንና ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት መገንዘብ እንደተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ሽጉጥ ከተያዘ በኋላ በወ.መ.ሥ.ሕ.ቁ 33/4/ እና 97 መሰረት የተመዘገበ እና ከአመልካች የተያዘ ስለመሆኑም በሰነድ የተደገፈ ክርክር አልቀረበም፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቁጥር 635 እና 165231 በተለምዷዊ የዓይን ምልከታ መለየት የሚቻል ስለመሆኑ በሕጉ አግባብ የተረጋገጠ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ንምራ ቁጥሩ ተፍቶ ፎርጅድ ቁጥር ተለጥፎበታል በማለት ይከራከራሉ፡፡ ይህ ጉዳይ በተጠሪዎች የተካደ ቢሆንም በኤግዝቪት ተያዘ በተባለው ሽጉጥ ንምራ ቁጥር 165231 ተብሎ የተመዘገበው ቁጥር በእርግጥ ኦርጅናል /ዋና/ ቁጥር ስለመሆኑ በልዩ ባለሙያ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ሽጉጥ ላይ የተፃፈው ቁጥር ኦርጂናል /ዋና/ መሆን ያለመሆን ደግሞ በቀላል የዓይን እይታ/ምልከታ/ የሚረጋገጥ ሳይሆን በመሣሪያ እውቀት ባላቸው የፎርንሲክ ምርመራ ባለሙያዎች ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሽጉጥ ላይ የተፃፈው ቁጥር ሽጉጡ በሰራው ኩባንያ /ተቋም/ የተሰጠው ንምራ ቁጥር መሆን ያለመሆኑን በባለሙያ /expert/ ሳይረጋገጥ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ግራቀኙ እያከራከረ ያለው ሽጉጥ ላይ የተፃፈው ንምራ ቁጥር 165231 በእርግጥ በእናት ኩባንያው የተሰጠው ቁጥር ነው ወይስ በጊዜ ሂደት የተተካ ቁጥር ነው? በአከራካሪው ሽጉጥ የተፃፈው ንምራ ቁጥር 635 ነው ወይስ 165231 ነው? የሚሉ መሰረታዊ ነጥቦች አግባብነት ካለው አካል በሚቀርበው ሙያዊ አስተያየት /expert opinion/ መሰረት ተደርጎ ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች ተሽሮ ጉዳዩ ደግሞ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ሥር ፍ/ቤት ሊመለስ የሚገባው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በአብክመ የኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር የደዋ ጤፋ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 02932/05 በ04/10/2005 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳዳር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0101458 በ26/11/2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጠ/ፍ/የሰ/ይ/መ/ቁ 03-06689 በ 27/03/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የደዋ ጤፋ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍርድ ይዘቱ እንደተገለጸው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሽጉጥ ንምራ ቁጥር 635 ነው ወይስ 165231? ንምራ ቁጥሩ 165231 የተባለው ሽጉጥ ኦርጂናል ቁጥር ነው ወይስ በሂደት የተተካ ቁጥር ነው? የሚሉና ተዛማጅ ነጥቦች በፎረንሲክ ባለሙያዎች ተመርምሮ ውጤቱ ከታወቀ በኋላ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይፃፍ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘጋ፡፡ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንግድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 94278

ህዳር 11 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ሐሰን መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ማጂ አግሮ ፎረስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ ዶ/ር አሸናፊ ማሞ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

በስር ፍርድ ቤት ክሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በዚህ መዝገብ አቤቱታ ያቀረቡት በተከሳሽነት ተሰይመው የነበሩት የማጂ አግሮ ፎረስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ በማህበሩ የመመስረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጡ ባለመቻላቸው ምክንያት የማህበሩ ሕልውና አደጋ ላይ የወደቀ መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ በንግድ ሕግ ቁጥር 218 እና 542 መሰረት ማህበሩ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1835 መሰረት በአስር አመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ክሱ የቀረበለት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት የማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የፀናው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ እንደተቻለው ክሱ የቀረበለት የማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተከሳሽ የቀረበለትን የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር. 1835 ድንጋጌን ጠቅሶ ክሱ በአስር ዓመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን የሰጠው የማህበሩ የመመሰረቻ ፅሁፍ ከተፈረመበት ከ19/06/1991 ዓ.ም ጀምሮ ማህበሩ እንዲፈርስ ክስ እስከቀረበበት 03/10/2005 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር አስር ዓመት አልፎታል በማለት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ማህበሩ የተመሰረተበትን ጊዜ መነሻ አድርገው በማስላት አመልካች መስራች ሆነው አቋቁመውት ሲንቀሳቀስ የነበረው ማህበር ሒሳብ በአዲት ተመርምሮ ድርሻቸው እንዲታወቅ እና ማህበሩ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርቡ በመደረጉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ የፀናው ብይን ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. በከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ተገቢውን የክስ አቀራረብ ስርዓት ተከትሎ የቀረበ አይደለም በማለት ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ያቀረቡት ክርክር ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ በዚህ ሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ አለ ወይስ የለም? የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ጭብጦች አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህ መሰረት የመጀመሪያው ነጥብ በተመለከተ አመልካች ለማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘት የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በማህበሩ የመመስረቻ ውሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጡ ባለመቻላቸው ምክንያት የማህበሩ ሕልውና በአደጋ ላይ የወደቀ በመሆኑ ሂሳብ ተጣርቶ ማህበሩ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ የሚል መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ እና የግራ ቀኙ የክርክር ይዘት ያመለክታል፡፡ አመልካች የማህበሩ መስራች አባል መሆናቸው እና በ1995 ዓ.ም ከማህበሩ የስራ አስኪያጅነት ስልጣን ተነስተዋል ከመባሉ በቀር ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ የማህበሩ አባልነታቸው ያልተቋረጠ ስለመሆኑ በተጠሪው አልተካደም፡፡ የማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ በአስር ዓመት ይርጋ ይታገዳል ለማለት የቻለውም ጊዜውን የማህበሩ የመመስረቻ ፅሁፍ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ በመቁጠር ስለመሆኑ የብይኑ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በመሰረቱ አንድ የንግድ ማህበር በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፈርስ የሚደረገው ጥያቄ ስለቀረበ ብቻ ሳይሆን ማህበሩን ለማፍረስ የሚያስችሉ ትክክለኛ ምክንያቶች ስለመኖራቸው በማስረጃ ተረጋግጦ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በንግድ ሕጉ ዕውቅና የተሰጣቸው የንግድ ማህበራት ከአባላቱ በአንዱ የይፍረስልኝ ጥያቄ ሊቀርብባቸው የሚችል ስለመሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር. 218(1) ስር ተደንግጐ የሚገኝ ሲሆን የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበርን በተመለከተ በንግድ ሕግ ቁጥር 542(1) ስር የተመለከተው ድንጋጌም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው፡፡ እንደሚታወቀው የንግድ ማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄ በውል ከተቋቋመ የማህበርተኝነት መብት የሚመነጭ እና በማህበሩ እንቅስቃሴ ሂደት የሚፈጠሩ የተለያዩ ችግሮችን መሰረት አደርጐ የማህበሩ ህልውና አስካለ ድረስ በማንኛውም ጊዜ ሊቀርብ የሚችል ነው ከሚባል በቀር በታወቀ የይርጋ ጊዜ የሚታገድ ስለመሆኑ የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች አያመለክቱም፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለብይኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር. 1835 ድንጋጌን በምክንያትነት የጠቀሰው አለቦታው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በንግድ ሕጉ የተደነገገ የተለየ የይርጋ ዘመን በሌለ ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር. 1845 በተመለከተው ጠቅላላ የይርጋ ጊዜ ይታገዳል ሊባል ይችል የነበረውም የይፍረስልኝ ጥያቄው የቀረበው ተለይቶ በታወቀ ቀን የተፈጠረ ክስተትን ጠቅሶ ወይም መሰረት አደርጐ ቢሆን ኖሮ እና ክሱ የቀረበው ክስተቱ ከተፈጠረ አስር ዓመት ካለፈው በኋላ ቢሆን ኖሮ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክሱን ያቀረቡት በአንድ ተለይቶ በታወቀ ጊዜ ወይም ቀን የተፈጠረ ክስተትን መሰረት በማድረግ ሳይሆን ይልቁንም በማህበሩ እንቅስቃሴ ሂደት በተለያየ ጊዜ ተከስተዋል የተባሉ የተለያዩ ችግሮችን በምክንያትነት በመጥቀስ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብታቸው በይርጋ ይታገዳል የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የማህበሩ የመመስረቻ ፅሁፍ የተፈረመበት ቀንም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን በማህበሩ እንቅስቃሴ ሂደት በተለያየ ጊዜ የተፈጠሩ የተለያዩ ችግሮችን መሰረት አድርጐ ለሚነሳ የማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄ ለይርጋው አቆጣጠር የመነሻ ቀን ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር. 1835 ድንጋጌን አለቦታው በመጥቀስ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የፀናው ብይን ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛው ነጥብ በተመለከተ ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ላይ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ተገቢውን የክስ አቀራረብ ስርዓት ተከትሎ የቀረበ ባለመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን አመልካች ክሱን ያቀረቡት በራሳቸው ስም ብቻ ነው ወይስ በሌሎች ሰዎች ስም ጭምር ነው? እንዲሁም ክሱን ያቀረቡት በማህበሩ ላይ ነው ወይም በማህበሩ ስራ አስኪያጅ ላይ ነው? በሚሉት ነጥቦች ላይ ግራ ቀኙ የአቋም ልዩነት ያላቸው መሆኑን በሰበር ደረጃ ከተለዋወጡት የፅሁፍ ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በብይን የተዘጋው በይርጋ ምክንያት በመሆኑ በሰበር ክርክራቸው ላይ ግራ ቀኙ የተለያዩባቸውን ጨምሮ ቀሪዎቹ የክርክሩ ነጥቦች በስር ፍርድ ቤት ተጣርተው ውሳኔ የሚያርፍባቸው ከሚሆን በቀር ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ በዚህ ሰበር ችሎት ሊስተናገዱ የሚችሉበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት በማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 19372 በ20/12/2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01174 በ15/01/2006 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የማህበር ይፍረስልኝ ክስ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. በግራ ቀኙ የቀረበውን ቀሪ ክርክር መርምሮ እና አጣርቶ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር. 341(1) መሰረት ለማጂ አካባቢ ከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ በዚህ ውሳኔ መሰረት ተገቢውን መፈፀም ያስችለው ዘንድ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ለማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፤ እንዲያውቀው ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95069

ህዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- 1. ሴፍሜት አግሪ ቢዝነስ ኃ.የተ.የግ.ማህበር
2. አቶ ወንድምአንተነህ መሸሻ } ጠበቃ ውቤ አለነ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ብረቱ ሱኬሱ ጠበቃ ወንድአወክ አየለ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገንዘብ ይመለስልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁኗ ተጠሪ የአሁኑ አመልካቾችን እንደቅደምተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች፣ ወ/ሮ ትግስት ድረስ የተባሉትን ግለሰብ ደግሞ 3ኛ ተከሳሽ በማድረግ መጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው። የተጠሪ የክስ ይዘትም፡- 2ኛው ተከሳሽ 1ኛ ተከሳሽን በአሸሙር ማህበር በመመስረት የጥቁር ድንጋይ ማምረቻ እናቋቁም በማለት ተጠሪዋን ባግባቧቸው መሰረት በሚኖሩበት ከኬኒያ ናይሮቢ ከተማ ሆነው በተለያዩ ጊዜያት ማለትም ነሐሴ 06 ቀን 2001 ዓ.ም 10,000 የአሜሪካ ዶላር፣ ነሐሴ 07 ቀን 2001 ዓ/ም 70,000 የአሜሪካ ዶላር፣ ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም ደግሞ 67,000 የአሜሪካ ዶላር በ1ኛ አመልካች ስም ናይሮቢ ከተማ በሚገኘው ዲያመንድ ትረስት ባንክ አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኘው በአቢሲኒያ ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ በኩል እንደላኩና ለእነዚህ በተለያዩ ጊዜያት ለተላኩት ገንዘቦች ደግሞ በተከታታይ 204 ዶላር፣ 1429 ዶላር፣ 1367 ዶላር ኮሚሽን እንደከፈሉባቸውና በአጠቃለይም 150,000 የአሜሪካን ዶላር ልከው 2ኛው አመልካችም ይህን ገንዘብ መቀበላቸውን በደረሰኝ ያረጋገጡላቸው መሆኑን እንዲሁም እርሳቸው ወደ አዲስ አበባ በመጡበት ወቅት የአሸሙር ማህበሩን ለማቋቋም ተጨማሪ ገንዘብ መስጠት አለብሽ በማለት 2ኛው አመልካች በጠየቋቸው መሰረት ጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ደረሰኝ አማካኝነት ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺህ የኢትዮጵያ ብር) የሰጧቸው መሆኑን፣ ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን 2ኛ አመልካችን ለማግኘት እንደተቸገሩና ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ አግኝተዋቸው ሲጠይቋቸው ገንዘቡን ለሌላ ፕሮጀክት እንዳዋሉት እንደገለፁላቸው፣ እርሳቸውን በደንብ የሚያውቋቸውን የ2ኛ አመልካች ባለቤት የሆኑትን የሥር 3ኛ ተከሳሽ የነበሩትን ግለሰብ ሲጠይቋቸውም "ገንዘብሽን አንክድሽም፤ ጊዜ ስጭንና ከባንክ ተበድረን እንሰጥሻለን" እንዳሏቸውና እርሳቸውም ባዶ እጃቸውን ወደ ኬኒያ እንደተመለሱ እና አመልካቾችም ሆነ የሥር 3ኛ ተከሳሽ ገንዘባቸውን ሊመልሱላቸው እንዳልቻሉ በመዘርዘር አመልካቾች የወሰዱትን 150,000 የአሜሪካ ዶላር ክስ በቀረበበት ከመጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ/ም በነበረው የአንድ ዶላር ምንዛሬ ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

16.7293 ሂሳብ ብር 2,509,395 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ብር) እንዲሁም የዚህን ገንዘብ የመጨረሻ ክፍያ (67,000 ዶላር) ከተከፈለበት ከነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት እስከ መጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ 9% ወለድ ብር 368,159.20 ተጨምሮበት እንዲከፈላቸው፣ እንዲሁም ብር 800,000.00 (ስምንት መቶ ሺህ የኢትዮጵያ ብር) እና ይህ ገንዘብ ከተወሰደበት ከጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት እስከ መጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ 9% ወለድ ብር 112,636.60 (አንድ መቶ አስራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር ከስልሳ ሳንቲም) እንዲከፈሏቸው ጠቅሰው በአጠቃላይም ከላይ የተዘረዘረውን ገንዘብ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ያለው ብር 3,790,189.82 (ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ሺ አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ ሁለት ሳንቲም) ክሱ ከቀረበበት ከመጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ወለድ ጋር በውጭ ምንዛሬ የወሰዱትም በሚከፍሉበት ወቅት በሚኖረው ምንዛሬ ታስቦ እንዲከፍሏቸው፣ የጠበቃ አበል በውላቸው መሰረት፣ ሌሎች ወጪና ኪሳራዎች ደግሞ በሚያቀርቡት ዝርዝር መሰረት እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

የአሁኑ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስም፦ ከሳሿ የክስ ምክንያት የሌላቸው መሆኑን፣ ከሳሿ ገንዘቡን ያዋጡት ለአሸሙር ማህበር መዋጮ በመሆኑ 1ኛ አመልካችን የሚመለከት ክስ ከሚሆን በስተቀር 2ኛ አመልካችን እና የሥር 3ኛ ተከሳሽን በሚመለከት የመክሰስ ጥቅም እንዳላቸው ያለማረጋገጣቸውን፣ ገንዘቡ ገቢ የተደረገውና በ2ኛ አመልካች ወጪ የሆነው በኢትዮጵያ ብር በመሆኑ እርሳቸው ባሉበት የዶላር ምንዛሬ ሊጠይቁ እንደማይገባ፣ ገንዘቡን የላኩት በመዋጮ መልክ በመሆኑ ወለድ ሊታሰብላቸው እንደማይገባ፣ ከሳሽ በአጠቃላይ ያዋጡት ገንዘብ ብር 2,634,089.73 ሁኖ ከዚህ ገንዘብ ውስጥም ብር 139,200.75 ከሳሿ መልሰው የወሰዱ በመሆናቸው ይህ ተቀንሶ የሚቀራቸው ብር 2,494,888.98 መሆኑንና ይህን ገንዘብ ብቻ ለመውሰድ ፈቃደኛ ባለመሆን በመሰረቱት ክስ ወጪና ኪሳራ ሊከፍሉ እንደማይገባ ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል። የሥር 3ኛ ተከሳሻም የአሁኑ 2ኛ አመልካች ባለቤት ከመሆናቸው ውጪ ለክሱ ኃላፊ የሚሆኑበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካቾች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ ፍሬ ነገሩን በተመለከተም ጉዳዩን መርምሮ ከሳሿ (ተጠሪ) በዶላር የላኩት ገንዘብ 2ኛ ተከሳሽ (የአሁኑ 2ኛ አመልካች) የተቀበሉት በብር ስለሆነ አሁን ባለው የብር ምንዛሬ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ክስ ውድቅ ነው፣ ከሳሿ ገንዘቡን የላኩት በራሳቸው ፈቃድ የአሸሙር ማህበር ለመመስረት አስበው ስለሆነ የወለድ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም፣ ተከሳሾቹ ባቀረቡት ክርክር ከሳሿ ብር 139,200.75 መልሰው ወስደዋል የሚለውም ተቀባይነት የለውም፣ 3ኛዋ ተከሳሽ ለከሳሿ ገንዘብሽን እንመልስልሻለን ከማለት ውጭ በክሱ ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ነገር ስላልተገኘ ከክሱ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል፣ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ግን ከከሳሽ የተቀበሉትንና የወሰዱትን ብር 2,634,089.43 ዳኝነት ከፍለው መዝገቡን ካስከፈቱበት ከሚያዝያ 10/2003 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር በአንድነትና በነጠላ ለከሳሽ እንዲከፍሏቸው በማለት ወስኗል፣ እንዲሁም ከሳሿ በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ላይ 3ኛዋ ተከሳሽ ደግሞ በከሳሿ ላይ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብትም ጠብቋል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ በከፊል በመቃወም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኞቸው መሰረታዊ ነጥብም፡- በኬኒያ አገር ናይሮቢ ከተማ ሆነው በዶላር የላኩላቸው ገንዘብ ለእኔ ጥቅም ባላገለገለበት ማለትም ለአሸሙር ማህበሩ በመዋጮ መልክ ባልዋለበትና እቃም ባልተገዛበት በወቅቱ በነበረው የብር ምንዛሬ ብቻ እንዲከፈላቸው ተብሎ መወሰኑ የደረሰባቸውን ጉዳት ያላገናዘበ ነው፤ የሥር ተከሳሾችም ገንዘቡን ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ወለድ ሊታሰብልኝ እየተገባ ክሱ ከቀረበበት ከሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እንዲታሰብ መደረጉ ስህተት ነው፣ የስር 3ኛዋ ተከሳሽም ከሌሎች ተከሳሾች ጋር እኩል ኃላፊነት እንዳላቸው ሊወሰን ሲገባ መታለፉ ያላግባብ ነው የሚሉትን ነጥቦችን ዘርዝረው ይግባኙን ለማቅረብ የከፈሉትን ዳኝነት፣ የጠበቃና ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች የስር ተከሳሾች እንዲከፍሉ ሊወሰን ይገባል በማለት ዳኝነት መጠያቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ መልስ ሰጪዎች ለይ/ባይ ሊከፍሉት የሚገባው የዶላር ምንዛሬ መቼ በነበረው ነው? የሚለው ጭብጥ በተመለከተከፍ/ብ/ህ/ቁ 1750 ጋር አመሳስሎ በመተርጎም የአሁኑ አመልካቾች ለተጠሪ ሊከፍሏቸው የሚገባው የዶላር ምንዛሬ የስር ፍርድ ቤቱ ፍርድ በሰጠበት በታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም በነበረው የዶላር የብር ምንዛሬ ተመን መሆን ይገባዋል በማለት የወሰነ ሲሆን አመልካቾች ገንዘቡን ከወሰዱት ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ ክስ እስከመሰረቱባቸው ድረስ ላለው ጊዜ ወለድ ሊከፍሉ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪ ገንዘባቸው ከእጃቸው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ ገንዘብ ያገኙት ምንም አይነት ጥቅም እንደሌለ፣ በአንፃሩ ደግሞ የገንዘቡ ተጠቃሚዎች አመልካቾች የነበሩ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ ወለዱ የማይከፈልበት ምክንያት የለም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ተጠሪ በክሳቸው እንደጠየቁት 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር) በሚመለከት ከነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ክስ ወደ ፍርድ ቤት እስከቀረበበት እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ ላለው ጊዜም 9% ወለድ ሊከፈላቸው ይገባል፤ በተመሳሳይም አመልካቾቹ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺህ ብር) ከተጠሪ ከወሰዱበት ከጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ተጠሪ ክሱን በሬጅስትራር እስካስከፈቱበት እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ 9% ወለድ ሊከፍሏቸው ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ እንዲሁም የሥር 3ኛ ተከሳሽን በተመለከተም በባለቤታቸው በሁለተኛው አመልካች በቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎች መሰረት ተጠያቂ ሊያደርጋቸው የሚችል ሁኔታ ካለ ከተጠያቂነት የማያመልጡበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ለተጠሪ ክስ ግን በቀጥታ ፍርዱ ሊያርፍባቸው የሚያስችል ነገር የለም፣ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአመልካቾች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተገቢውን ጭብጥ ለጉዳዩ ሳይዝና አግባብነት የሌለውን ድንጋጌን መሰረት አድርጎ አመልካቾች ከኬንያ ናይሮቢ በአሜሪካን ዶላር ተልኮ በ2ኛ አመልካች ከአቢሲኒያ ባንክ በወቅቱ በነበረው የውጭ ምንዛሬ ተመን መሰረት ለተወሰደው ገንዘብ ለተጠሪ ገንዘቡን ሊመልሱ የሚገባው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በሰጠበት ጊዜ ባለው የውጭ ምንዛሬ ተመን ነው በማለት መወሰኑ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ ተጠሪ ወለድ የሚያገኙበት ሕጋዊ ምክንያትም የሌለ መሆኑን ዘርዝረው በዚህ ረገድ የተሰጠው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በአንፃሩ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች፡-

1. አመልካቾች ለተጠሪ ሊከፍሉት የሚገባው ገንዘብ በውጪ ምንዛሬ ነው? ወይስ በኢትዮጵያ ብር ነው?፣
2. አመልካቾች ገንዘቡን ከወሰዱት ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ ክስ እስከመሰረቱባቸው ድረስ ላለው ጊዜ ወለድ ሊከፍሉ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚሉት ሆነው ተገኝተዋል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- አመልካቾች ለተጠሪ የኢትዮጵያ ብር 800,000 እና 150,000 የአሜሪካን ዶላር በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ ሊከፍሏቸው እንደሚገባ ክርክር ያቀረቡበት ጉዳይ አይደለም፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው አመልካቾች ለተጠሪ መክፈል ያለባቸው 150,000 ዶላር ይኼው ገንዘብ በ2ኛ አመልካች ከአቢሲኒያ ባንክ ወጪ ሲሆን በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ በተሠጠበት መጠን ነው? ወይስ በዶላር ነው? የሚል ሲሆን ይህ ጭብጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246፣ 247 እና 248 ድንጋጌዎች አግባብ ሊመሰረት የሚገባው እና ተጠሪ በዶላሩ ነው ሊከፈላቸው የሚገባው የሚል ምላሽ ከተሰጠ ደግሞ ቀጥሎ የሚመጣው ጥያቄው የዶላሩ ምንዛሬ መሆን ያለበት አመልካቾች ገንዘቡን በወሰዱበት ጊዜ ባለው የውጪ ምንዛሬ ተመን ነው?፣ ተጠሪ ክስ በመሰረቱበት ጊዜ ባለው የውጭ ምንዛሬ ተመን ነው?፣ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በሰጠበት ጊዜ ባለው የውጭ ምንዛሬ ተመን? ወይስ አመልካቾች ገንዘቡን ለተጠሪ በሚከፈሉበት ጊዜ ባለው የውጭ ምንዛሬ ተመን ነው? የሚሉትና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው ተጠሪ ገንዘቡን ከኬኒያ ወደ ኢትዮጵያ ለአመልካቾቹ የላኩላቸው አብረው የንግድ ማህበር ለማቋቋም በመዋጮነት ቢሆንም ማህበሩም አልተመሰረተም፣ ገንዘቡም ለአመልካቾች ጥቅም የዋለ ነው ከሚባል በስተቀር ተጠሪ በዚህ ገንዘባቸው ያገኙት እንዳችም ጥቅም የሌለ መሆኑን፣ ተጠሪ በገንዘባቸው ምንም አይነት ጥቅም ሳያገኙ በአንፃሩ ግን አመልካቾች ይህንን ገንዘብ ከተጠሪ ከተቀበሉበት ጊዜ ጀምሮ ለራሳቸው ጥቅም በማዋል ከፍተኛ ገቢ እንዳገኙበት የሚገመት መሆኑን፣ ተጠሪ ገንዘቡ ለራሳቸው ንግዳዊ ስራ ወይም ለሌላ አገልግሎት አውለውት ቢሆን ኖሮ በወቅቱ ከፍተኛ ጥቅም ሊያገኙበት ይችሉ እንደነበር የሚገመት መሆኑን፣ ተጠሪ የገንዘባቸው ዋጋ ሳይወርድ አቻው የብር ምንዛሬ እስካላገኙበት ድረስ ገንዘባቸውን በተሟላ ሁኔታ አግኝተዋል ሊባሉ የሚችሉ ያለመሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በምክንያትነት ይዞ የስር ፍ/ቤቱ አመልካቾች ለተጠሪ የብር ምንዛሬው መክፈል ያለባቸው ገንዘቡን ሲወስዱ በነበረው የብር ምንዛሬ ነው ማለቱ የተጠሪን ጥቅም የሚያጓድል፣ አመልካቾችን ደግሞ አላግባብ ጥቅም እንዲያገኙ የሚያደርግ መሆኑን ደምድሞ እና ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1750 ጋር አመሳስሎ በመተርጎም አመልካቾች ለተጠሪ ሊከፍሏቸው የሚገባው የዶላር ምንዛሬ የስር ፍርድ ቤቱ ፍርድ በሰጠበት በታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም በነበረው የዶላር የብር ምንዛሬ ተመን መሆን ይገባዋል በማለት መወሰኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ተጠሪ እንዲመሰርት የፈለጉትና ጥቅም አገኝበታለሁ ብለው የነበሩት ድርጅት ባለመቋቋሙ አመልካቾች ገንዘቡን እንዲመልሱላቸው ዳኝነት መጠየቃቸው ግልጽ ሲሆን ዶላሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከኬንያ አገር ወደ ኢትዮጵያ ቢልኩም 2ኛ አመልካች ገንዘቡን ከባንክ ወጪ አድርገው ሲወስዱ የተከፈላቸው በወቅቱ በነበረው የምንዛሬ ተመን ወደ ኢትዮጵያ ብር ተለውጦ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ከውጪ አገር የተላከ የውጭ ምንዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በጊዜው በነበረው ተመን ታስቦ ክፍያ የተፈፀመበት ከሆነ ዶላሩ ለተላከበት አላማ አልዋለም በሚል ክርክር ሲነሳ ገንዘቡ ሊመለስ የሚገባው ዶላሩ ሲላክ በነበረበት የውጪ ምንዛሬ ተመን ሊሆን አይገባም የሚል የሕግ መሰረት የለም፡፡ ተጠሪ ከአመልካቾች ጋር ያለው ውል በመፍረሱ ምክንያት የደረሳባቸውን የጉዳት አይነትና መጠን በግልጽ ጠቅሰውም አልተከራከረም፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1750 ድንጋጌ ከገንዘብ እዳ ጋር ተይይዞ የሚነሳውን የውል አፈፃጸም ለመግዛት ታስቦ የወጣ ድንጋጌ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1749 ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲነበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1749(1) ድንጋጌ ገንዘብን የሚመለከት እዳ ሲሆን እዳው የሚከፈለው በአገሩ መገበያያ ገንዘብ መሆኑን በመርህ ደረጃ የደነገገ ሲሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1750 ድንጋጌ ደግሞ እዳው በሚከፈልበት ቦታ ውሉ ሕጋዊ ዋጋ የሌለው ገንዘብ ጠቅሶ እንደሆነ ውሉ ቃል በቃል እውነተኛ ዋጋ ወይም ይህንኑ የመሰለ ቃል ከሌለበት በቀር እዳው በሚከፈልበት ቀን ዋጋ ልክ በአገሩ ገንዘብ ሊከፈል እንደሚችል የሚያስቀምጥ ነው፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1750 ድንጋጌ በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል ላለው ጉዳይ ቀጥታም ሆነ በማመሳሰል የትርጉም መርህ ተፈፃሚ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ የገንዘብ ክፍያ ውል መሰረት ያደረገ የገንዘብ እዳ ክፍያን የሚመለከት ካለመሆኑም በላይ አመልካቾች ከተጠሪ የተላከላቸውን የአሜሪካን ዶላር በቀጥታ የተቀበሉ ሳይሆን ዶላሩ በጊዜው በነበረው የአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ተመን መሰረት ተሰልቶ ወደ ኢትዮጵያ ብር ተመልሶ አመልካቾች መቀበላቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ነውና፡፡ በአገሪቱ የገንዘብ ስርዓት መሰረት መንግስትና ሕዝብ በጊዜው በነበረው የውጪ ምንዛሬው ተመን ላገኙት ጥቅም ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ብር የተመነዘረ ዶላር ለተጠሪ ሊያስገኝ ይችል የነበረው ጥቅም ግምት ውስጥ ገብቶ ምንዛሬው ተመን የሚታሰብበት የሕግ አግባብም የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካቾች ያላግባብ ጥቅም ሊያገኙ የሚችሉበትን አጋጣሚ ግምት ውስጥ አስገብቶ ዶላሩ በተላከበት ጊዜ በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ ለአመልካቾች መሰጠቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ ለተጠሪ ዶላሩ ከተላከበት ጊዜ በኋላ ያለው የምንዛሬ ተመን በከፍተኛ ሁኔታ የተለዋወጠ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገባ ተመኑ ለተጠሪም የሚያስገኘው ጥቅም ሕጋዊ አድርጎ መውሰዱ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይመሰርትና በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር በመተው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1750 ድንጋጌን ያለቦታው ጠቅሶ አመልካቾች 150,000.0 የአሜሪካን ዶላር ለተጠሪ ሊመልሱ የሚገባው በታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም ባለው የውጪ ምንዛሬ ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካቾች ይህንኑ ዶላር ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው 2ኛው ተጠሪ ከአቢሲኒያ ባንክ ሲወስዱ በተከፈላቸው የውጪ ምንዛሬ ተመን ሊሆን የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> ተጠሪ ገንዘባቸው ከእጃቸው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ ገንዘብ ያገኙት ምንም አይነት ጥቅም ያለመኖሩ፣ በአንፃሩ ደግሞ የገንዘቡ ተጠቃሚዎች አመልካቾች በመሆናቸው ተጠሪ ይህ ገንዘብ ከእጃቸው አላግባብ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ያጡት ጥቅም በወለድ ክፍያ ሊካካስላቸው የሚገባ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካቾች በዚህ ሰበር ደረጃ የሚከራከሩት ለተጠሪ ሕጋዊ ወለድ የሚታሰብበት አግባብ የለም በሚል ሲሆን ለዚህም እንደ ሕጋዊ ምክንያት የሚያቀርቡት ተጠሪ ለአመልካቾች ማስጠንቀቂያ ያልሰጡ መሆኑንና ጉዳዩ የገንዘብ ብድርን መሰረት ያላደረገ መሆኑን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይሁን እንጂ ይመሰረታል የተባለው ድርጅት ሳይመሰረት መቅረቱን አመልካቾች የሚክዱት ፍሬ ነገር አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ በተጠሪ ቋሚ ሃብት ወይም ጥቅም ላይ መቀነስን የሚያስከትል መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በተጠሪ ላይ ቀጥተኛ የሆነ የገንዘብ ኪሳራ የደረሰባቸው መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተጠሪ ለአመልካቾች ማስጠንቀቂያ የሚሰጡበት ምክንያት የለም፡፡ አመልካቾች ያመኑትን ገንዘብ ያህል ተጠሪ ለመውሰድ ፈቃደኛ ሊሆኑ ያለመቻላቸውንም በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጡት ጉዳይ አለመሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ይመሰረታል በማለት የጠበቁት ድርጅት ሳይመሰረት ከቀረ ለአመልካቾች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1771 እና 1705 ድንጋጌዎች አግባብ ማስጠንቀቂያ ሊሰጡ ይገባ ነበር ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ እንዲሁም የወለድ ገንዘብ በብድር ጊዜ ብቻ ተፈፃሚነት የሚሆን ነው በሚል የቀረበው የአመልካቾች ክርክር ሲታይም የሕግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ወለድ በሕጉ አግባብ የተዘረጋው ስርዓት እንደተጠበቀ ሁኖ በስምምነት ወይም ያለስምምነት ሊከፈል የሚችል ገንዘብ ነው፡፡ ወለድ ተበዳሪ የወሰደውን ገንዘብ ወይም እቃ በወቅቱ ባለመመለሱየተነሳ የሚከፈል የገንዘብ ካሳ ነው፡፡ ሌላው አይነት ወለድ አንድ ሰው ግዴታውን ባለመፈፀሙ ወይም በማዘገየቱ የተነሳ የሚከፈለው ካሳ እኩያ ነው፡፡ ስለሆነም ወለድ ለገንዘብ ብድር ብቻእንዲከፈል የሚደረግ የካሳ አይነት አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1803(3) ድንጋጌ አንፃር ሲታይም ተጠሪ አመልካቾች የውል ግዴታቸውን ባለመፈመፀማቸው የተነሳ የካሳ እኩያ የሆነው ወለድ የማያገኙበት የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቱ ገንዘቡ ለተጠሪ ጥቅም ያለማዋሉን አረጋግጦ እያለ ገንዘቡን የላኩት ለንግድ ማህበር ማቋቋሚያ በመዋጮነት በመሆኑ ወለድ አይገባቸውም የሚል ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያለመቀበሉ ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በክሳቸው እንደጠየቁት 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር) በሚመለከት 2ኛ ተጠሪ ከአቢሲኒያ ባንክ ወጪ አድርገው ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ክስ ወደ ፍርድ ቤት እስከቀረበበት እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ ላለው ጊዜም 9% ወለድ ሊከፈላቸው ይገባል፤ በተመሳሳይም አመልካቾቹ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺህ ብር) ከተጠሪ ከወሰዱበት ከጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ ክሱን በሬጅስትራር እስካስከፈቱበት እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ 9% ወለድ ሊከፍሏቸው ይገባል በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተገለፁት ሕጋዊ ምክንያቶች የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻሻል የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 88280 ጥቅምት 08 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች 150,000 የአሜሪካን ዶላር ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው ይኼው ዶላር ከኬንያ ናይሮቢ ወደ ኢትዮጵያ ተልኮ በአቢሲኒያ ባንክ በኩል በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ በተሰጠው ተመን መሰረት ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ለተጠሪ በሚከፍሉት ገንዘብ ላይ ክሱ ከቀረበበት ከሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ከሚታሰብ 9% ወለድ አክለው እንዲከፍሉ የሚለውን የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል የሠጠውን ውሳኔ ይህ ችሎትም በማሻሻል አመልካቾች 150,000 ዶላሩን በሚመለከት ከላይ በተራ ቁጥር 2 መሰረት በሚገኘው የብር ስሌት ላይ ከነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ 9% ወለድ በማከል እንዲሁም ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺህ ብር) በሚመለከት ደግሞ አመልካቾች ገንዘቡን ከወሰዱበት ከጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሏቸው ወስነናል፡፡
4. የሥር 3ኛ ተከሳሽን በሚመለከትይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ አልተነካም፡፡
5. በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ በሚመለከት አመልካቾች ለተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት በተወሰነው የገንዘብ መጠን መሰረት የዳኝነት ገንዘብ ይክፈሏቸው ብለናል፡፡ ሌሎች ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና በዚህ ችሎት ክርክር የወጡትን ወጪና ኪሳራዎችን የያራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ዘግቶን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90722

ጥቅምት 11 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ መዓዛ መዝገቡ - VC ሰላልሰራ መቅረባቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ መሰለ ገላነው - VC ሰላልሰራ መቅረባቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በስር የፍርድ ባለመብት (በአሁኑ ተጠሪ) እና በስር የፍርድ ባለዕዳ (የአሁኗ አመልካች የቀድሞ ባለቤት በአቶ ሰመረ ኃይሉ) መካከል በነበረው የአፈጻጸም ክርክር የአማራ /ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ በፍርድ ባለዕዳው ስም የሚታወቀው ቤት ካርታ እና ፕላን የሌለው መሆኑ እና የቀድሞ ተጋቢዎች የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ ቤቱን ለልጆቻችን ሰጥተናል በማለት በንብረት ክርክሩ መዝገብ ላይ ማስመዝገባቸው ቤቱ ለፍርድ አፈጻጸም እንዳይውል ሊያደርገው የሚችል ባለመሆኑ አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ ሊቀጥል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ በስረ ነገሩ ክርክር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በስረ ነገሩ 1ኛ ተከሳሽ እና የአሁኗ አመልካች ባለቤት ከነበሩት ከአቶ ሠመረ ኃይሉ ጋር በ22/06/2000 ዓ.ም. ጋር አቋቁመውት በነበረው ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው አቶ ሠመረ ኃይሉ ጉዳት አድርሰውብኛል በማለት ብር 270,926.50 እንዲከፍሏቸው በሁለቱ ተጋቢዎች ላይ በባህር ዳር ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ መመስረታቸውን፣2ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች በሰጡት መልስ በውሉ ተዋዋይ ወገን ባለመሆናቸው በውሉ አለመፈጸም ሳቢያ በከሳሽ ላይ ደርሷል ለተባለው ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት የሕግ አግባብ አለመኖሩን በምክንያትነት በመጥቀስ ፍርድ ቤቱ ክሱ እንዲያሰናብታቸው መጠየቃቸውን፣ፍርድ ቤቱም ጥያቄቸውን ተቀብሎ 1ኛ ተከሳሽ ለክሱ ኃላፊ የሚደረጉ ከሆነ 2ኛ ተከሳሽ ተጠያቂ ሊደረጉ የሚችሉበት ሁኔታ መኖር አለመኖሩ በአፈጻጸም ጊዜ ከሚታይ በስተቀር 2ኛ ተከሳሽ በስረ ነገሩ ሊከሰሱ የሚችሉበት አግባብ የለም ሲል 2ኛ ተከሳሽን አሰናብቶ 1ኛ ተከሳሽን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ብር 198,371.40 ለከሳሽ እንዲከፍሉ በመዝገብ ቁጥር 17174 በ30/04/2002 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣ከሳሽ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ የተሰጠላቸውን ፍርድ ለማስፈጸም በዚያው የስረ ነገሩ መዝገብ የአፈጻጸም ማመልከቻ ባቀረቡበት ጊዜ ከስረ ነገሩ ክስ የተሰናበቱትን አመልካች በ2ኛ የፍ/ባለዕዳነት አካተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማቅረባቸውን፣አመልካቿ በስረ ነገሩ ኃላፊ ተደርጌ የተሰጠብኝ ፍርድ ሳይኖር የፍ/ባለመብቱ በፍ/ባለዕዳነት ሰይሞ ያቀረበኝ አላግባብ በመሆኑ ከአፈጻጸሙ ልሰናበት ይገባል የሚል ክርክር በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ይህንኑ ተቀብሎ አመልካች ከአፈጻጸም ክስ ነፃ ናቸው በማለት በ05/05/2003 ዓ.ም. በተሰጠ ትዕዛዝ ያሰናበታቸው መሆኑን፣ከዚህ በኃላ የፍ/ባለመብቱ ለአፈጻጸሙ ይውል ዘንድ በባህር ዳር ከተማ በቀበሌ 16 የሚገኝ የፍ/ባለዕዳውን ቤት መምራታቸውን፣ቤቱ ተከብሮ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ለሰጠው ትዕዛዝም የክፍሉ ቀበሌ ቤቱ የሚታወቀው በፍርድ ባለዕዳው በአቶ ሰመረ ኃይሉ ስም ቢሆንም የተገነባው በጊዜያዊ ይዞታ ላይ በመሆኑ እና ካርታ እና ፕላን የሌለው በመሆኑ ምክንያት ለማስከበር እንደሚቸገር በ20/11/2002 በተጻፈ ደብዳቤ መግለጹን፣የቤቱ ሁኔታ ተጣርቶ እንዲቀርብለት እና ተከብሮ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ በድጋሚ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረትም የፍርድ ባለዕዳው እና ባለቤታቸው ፍቺ በፈጸሙበት ጊዜ ቤቱ ለልጆቻቸው እንዲሆን ለፍርድ ቤት አቅርበው ማስወሰናቸውን በመግለጽ የክፍሉ ቀበሌ በ15/06/2003 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ መስጠቱን፣ፍርድ ቤቱም ከቀበሌው የተገለጹለትን ሁለት ምክንያቶች መሰረት በማድረግ የፍርድ ባለመብቱ ሌላ ንብረት አፈላልገው ማቅረብ የሚችሉ ከመሆኑ ውጪ አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ አለመኖሩን ገልጾ በ21/06/2003 ዓ.ም.የአፈጻጸም መዝገቡን በብይን መዝጋቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በብይኑ ቅር በመሰኘት የአሁኑ ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የወረዳውን ፍርድ ቤት ብይን ያጸናው ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ቤቱ የሚታወቀው በፍርድ ባለዕዳው ስም መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ካርታ እና ፕላን የሌለው መሆኑ ለፍርድ አፈጻጸም እንዳይውል ከማድረግ የማይከለክል መሆኑን እና የቀድሞ ተጋቢዎች ቤቱን ለልጆቻቸው ሰጥተዋል መባሉን በተመለከተም ስጦታው ሕጉ እንደሚያዘው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 በተመለከተው ስርዓት መሰረት የተከናወነ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ተጋቢዎቹ በፍቺ ውሳኔ መዝገቡ ላይ ቤቱ ለልጆቻቸው እንዲሆን መስማማታቸው እና ስምምነታቸው የፍቺ እና የንብረት ውሳኔውን ባጸደቀው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ ቤቱ በሕጉ አግባብ በስጦታ ተላልፏል የሚያሰኝ አለመሆኑን እና ከፍቺ ጋር የተያያዘ ክርክር የቀረበለት ፍርድ ቤት ፍቺን እና የፍቺ ውጤቶችን ከመወሰን በቀር ስጦታን የማጽደቅ ስልጣን የሌለው መሆኑን ገልጾ የሁለቱን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ እንዲቀጥል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ የተደረገው በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ሲካሄድበት ከነበረው ቁጥሩ 90723 ከሆነው መዝገብ ጋር ተጣምሮ እንዲታይ ተብሎ ቢሆንም በሁለቱ መዝገቦች ተከራካሪ ወገኖቹ ተመሳሳይ ቢሆኑም ለክርክር የቀረቡት ጭብጦች ግን የተለያዩ መሆናቸው በመረጋገጡ ቁጥሩ 90723 በሆነው መዝገብ የቀረበው ክርክር ተነጥሎ ውሳኔ የተሰጠበት ሲሆን በዚህ መዝገብ የቀረበውን አቤቱታ በተመለከተ ግን ለአፈጻጸሙ የተያዘው ቤት የተገነባው በጊዜያዊ ይዞታ ላይ መሆኑ እና በተጨማሪም በአመልካች እና በአቶ ሰመረ ኃይሉ መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሷል መባሉን ተከትሎ ቤቱ ለቀድሞ ተጋቢዎች ልጆች የተሰጠ መሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ ቤቱ ለአፈጻጸሙ ሊውል ይገባል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ የአቤቱታውን ግልባጭ ከመዝገቡ ወስደው መልስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሰጡበት በቪዲዮ ኮንፈረንስ በችሎት ተነግሯቸው መልስ ሳይሰጡ በመቅረታቸው የመከራከር መብታቸው እንዲታለፍ ተደርጓል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ለአፈጻጸሙ የተያዘው ቤት በጊዜያዊ ይዞታ ላይ የተገነባ እና ካርታ እና ፕላን የሌለው ቢሆንም በሌላ በኩል ግን ተመዝግቦ የሚታወቀው በአቶ ሰመረ ኃይሉ ስም መሆኑን ጉዳዩ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ለወረዳው ፍርድ ቤት በጽሁፍ አረጋግጧል፡፡ በሌላ አነጋገር ቤቱ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ዕውቅና ውጪ በሕገወጥ መንገድ የተገነባ ስለመሆኑ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ይልቁንም አመልካች እና በፍቺ ተለያይተዋል የተባሉት የቀድሞ ባለቤታቸው አደረጉት በተባለው እና በፍርድ ቤት በተመዘገበው የፍቺ ስምምነት ቤቱ ለልጆቻቸው እንዲተላለፍ መስማማታቸው እና ጉዳዩ የሚመለከተው የአስተዳደር አካልም ቤቱ በቀድሞ ተጋቢዎች ስምምነት ለልጆቻቸው የተሰጠ በመሆኑ የፍርድ ቤቱን የማስከበሪያ ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚችገር ገልጾ አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት ምላሽ መስጠቱ ካርታ እና ፕላን የሌለው ከመሆኑ ውጪ የቤቱ ሕጋዊነት ጉዳይ በአስተዳደር አካሉ ዘንድ ጥያቄ ያላስነሳ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡

ቤቱ ለቀድሞ ተጋቢዎች ልጆች ተሰጥቷል በማለት የቀረበውን ክርክር በተመለከተም አመልካች እና ፍቺ ፈጽመዋል የተባሉት የቀድሞ ባለቤታቸው የፍቺ ክርክሩን በተመለከተው ፍርድ ቤት ቤቱን ለሕጻናት ልጆቻቸው መስጠታቸውን ገልጸው የፍቺ ስምምነት ከማስመዝገባቸው ውጪ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በውሳኔው ላይ እንደገለጸው ስጦታውበሕጉ በተደነገገው ስርዓት መሰረት የተደረገ ነው የሚባል ካለመሆኑም በላይ የፍቺ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ተመዝግቧል የተባለውም ተጠሪው ክስ ከመመስረታቸው ከአምስት ቀናት በፊት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክርም ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የሁለቱን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በባህር ዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17174 በ21/06/2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 45472 በ29/05/2004 ዓ.ም. የጸናውን ብይን በመሻር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 20652 በ07/09/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀን~ል፡፡
2. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭለባህር ዳር ወረዳ ፍርድ ቤት፣ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98263

ጥር 06 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- ወ/ሮ እናናይቱ ይሳ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ወራሽ መክያ ከንዙ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34482 የካቲት 13 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35608 የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በአፈፃፀም ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ አፈፃፀሙ በመጀመሪያ የታየው በፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ የአፈፃፀም ከሳሽ አመልካች የአፈፃፀም ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 11394 በተሰጠው ፍርድ መሰረት በመሬቱ ላይ የገነባቸውን ንብረት በማንሳት ቦታውን እንድታስረክብ ይወሰንልኝ የሚል የአፈፃፀም ክስ ለወረዳው ፍርድ ቤት በማቅረቧ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርባ፤ የፍርድ ባለመብት ከነበረችው ከሟች ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም የዕርቅ ውል ተዋውለናል፡፡ በዕርቁም የፍርድ ባለዕዳ ለፍርድ ባለ መብት ብር 6000 /ስድስት ሺ ብር/ ለመክፈልና ቦታውንና ቤቱን ባለበት ሁኔታ ይኸር ለመቆየት ተስማምተናል፡፡ የዕርቅ ውሉን ለማስመዝገብ መጋቢት 27 ቀን 2002 ዓ.ም ፍርድ ቤት ማመልከቻ ይዘን ቀርበን፣ በቀጠሮው ቀን ቅረቡ ተብሎ የተመለስን ሲሆን ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን የቀጠሮው ቀን ከመድረሱ በፊት በመሞታቸው ምክንያት የዕርቅ ውሉ፣ በፍርድ ቤት ሣይመዘገብ ቀርቷል፡፡ ጉዳዩ በዕርቅ ያለቀ ስለሆነ ቤቱን አፍርሼ ቦታውን እንዳስረክብ አልገደድም በማለት ተከራክራለች፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳ መከራከሪያ ያደረገችው የዕርቅ ውል በመዝገቡ ያልተያያዘና ያልተመዘገበ በመሆኑ ፍርድን ባለመፈፀም መከራከሪያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም በማለት አመልካች አዋሳኝ ምልክቱ በተገለፀው ቦታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ የሰራችውን ቤት አፍርሳ ለፍርድ ባለመብት ታስረክብ ማለት ጥቅምት 7 ቀን 2005 ዓ.ም የአፈፃፀም ትዕዛዝ ሰጥቷል።

2. አመልካች በዚህ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፍርድ ባለመብትና የፍርድ ባለዕዳ የካቲት 28 ቀን 2006 ዓ.ም በፍርድ ቤት የተሰጠዉን ፍርድ ቀሪ በማድረግ የተስማሙ በመሆኑ ተጠሪ እንደ ፍርዱ እንዲፈፀምላት ያቀረበችውን ጥያቄ በመቀበል የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢነት የለውም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ሽሮታል። በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርባለች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዕርቅ ውሉ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277 መሰረት በፍርድ ቤት ተመርምሮ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ያልተመዘገበና በዕርቅ ውሉ ሰበብ፣ የመሬት ሽያጭ የሚመስል ስምምነት የተደረገ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ተፈፃሚነት የሌለው ነው በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ አፅንቷል። አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርባለች። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም።

3. አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት የካቲት 17 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበችው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡትን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው። አመልካች ቤት አፍርሽ ቦታ እንዳስረክብ በወረዳው ፍርድ ቤት ተወስኖብኝ ይግባኝ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቤ ጉዳዩ በቀጠሮ ላይ እያለ ከፍርድ ባለመብት ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም የዕርቅ ውል አድርገናል። ቦታው የከተማ ቦታ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉ የመሬት ሽያጭ የሚመስል ነው በማለት የዕርቅ ውሉን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው። የዕርቅ ውሉ ይፍረስልኝ የሚል ክስ ሣይቀርብ ዕርቅ ውሉን ማፍረስ ተገቢ አይደለም። አመልካች በርካታ ገንዘብ በማውጣት የገነባሁት 56 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት እንዳፈርስ የተሰጠው ውሳኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ተከራክራለች። ተጠሪ በበኩሏ፣ ሚያዝያ 13 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ከአውራሽ ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር ያደረገችው የዕርቅ ውል የለም። የቀረበው ሰነድ በሀሰት የተዘጋጀ የዕርቅ ሰነድ ነው። አውራሽ ወዳና ፈቅዳ የፈረመችው ሰነድ አይደለም። ዕርቁ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ያልተደረገና ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት መልስ ሰጥታለች። አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርባለች።

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ለዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት አመልካች የአፈፃፀም ክስ የቀረበበትን ውሳኔ ገዥነትና አስገዳጅነት ለማስቀረት ከተጠሪ አውራሽ ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር የዕርቅ ስምምነት አድርገናል በማለት ያቀረበችውን ክርክር ውድቅ ያደረጉት በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው በወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪ አውራሽ ወ/ሮ ሀሲና ሁሴንና አመልካች ተከራክረው፣ አመልካች በአከራካሪው ቦታ ላይ የሰራችውን ቤት በማፍረስ ቦታውን እንድታስረክብ ፍርድ የተሰጠበት መሆኑን ግራ ቀኙ አይካካዱም። የወረዳው ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት በሰጠው ፍርድ የተጠሪ አውራሽ የፍርድ ባለመብት፣ አመልካች የፍርድ ባለዕዳ ሆነዋል። ተጠሪ ለፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነውን የአፈፃፀም ክስ ያቀረበችው አውራጁ የፍርድ ባለመብት የሆነችበት ፍርድ እንዲፈፀምላት ነው። አመልካች ተጠሪ ያቀረበችው የአፈፃፀም ክስ የማትፈፅምበት ምክንያት እንዳላት መከራከሪያ አድርጋ ያስቀረበችው፣ የወረዳው ፍርድ ቤት ቤቱን አፍርሽ ቦታውን እንዳስረክብ የሰጠውን ውሳኔ ተፈፃሚነትና አስገዳጅነት ለማስቀረት የፍርድ ባለመብት ከነበረችው ሚች ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 የዕርቅ ስምምነት አድርገናል በማለት ነው።

6. አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ጋር አድርገነዋል በማለት ያቀረበችውን የዕርቅ ስምምነት ሰነድ በተጠሪ በኩል የታመነ አይደለም። በአንፃሩ ተጠሪ የዕርቅ ስምምነት የተደረገ መሆኑን ያሳያል በማለት አመልካች ያቀረበችው ሰነድ፣ በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው። በሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የአውራሽ የወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ፊርማ አይደለም። ሰነዱ በፍርድ ቤት ያልተመዘገበና ያልፀደቀ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የተከራከረች መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ግራ ቀኙ ለዚህ በሰበር ችሎት ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል። ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ ሰነዱን ለመቃወም የአውራሽ ፊርማ አይደለም ብላ መከሪከሯ በቂ እንደሚሆን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2007 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም ባደረገችው የዕርቅ ውል የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ተፈፃሚ እንዳይሆን የዕርቅ ስምምነት አድርጋለች የሚል ውሳኔ የሰጠው፣ አመልካች የዕርቅ ውል ነው ካለ ባቀረበችው ሰነድ ላይ ተጠሪ ያቀረበችውን መቃወሚያ በመቀበል፣ ፊርማው ለምርመራ ወይም በሌላ መንገድ እንዲጣራ በማድረግና የሰነዱን ትክክለኛነት በማስረጃ በማረጋገጥ እንዳልሆነና የአመልካችን መከራከሪያ ዕውነት ነው ብሎ በመቀበል እንደሆነ ከውሳኔው ተረድተናል። ይህም ተጠሪ የዕርቅ ውል ነው ተብሎ የቀረበውን ሰነድና በሰነዱ ላይ ያለውን ፊርማ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2007 ንዑስ አንቀፅ 2 በተደነገገው መሰረት ክዳ ተከራክራ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰነዱን ትክክለኛነት በፍትሐብሔርሕግ ቁጥር 2008 በተደነገገው መሰረት ተገቢው ማጣራትና ምርመራ ሳያደርግ፣ ሰነዱን ትክክለኛ የዕርቅ ውል ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ መሆኑን ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል። ከዚህ አንፃር ሲታይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2007 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2008 ድንጋጌዎች መሰረት የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

7. ከላይ የገለፅነዉ ተጠሪ የሰነዱን ትክክለኛነትና ፊርማውን በመካድ ያቀረበችው ክርክር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሣያጣራና በማስረጃ ሳያረጋግጥ ማለፉ የመጀመሪያው የሕግ ስህተት ሆኖ፣ አመልካች ከተጠሪ ወራሽ ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም አድርጌዋለሁ በማለት ያቀረበችው የዕርቅ ውል፣ ትክክለኛና ሚች የፈረመችበት ሰነድ ነው ቢባል ተጠሪ ያቀረበችውን የአፈፃፀም ክስ ቀሪ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ ወይም አለመሆኑ መመርመር ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል። አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም የዕርቅ ስምምነት ፈፅመናል በማለት ያቀረበችው ሰነድ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት የተፈረደባት ፍርድ አፈፃፀም ቀሪ ለማድረግና በምትኩ ብር 6000 /ስድስት ሺህ ብር/ ለተጠሪ አውራሽ ለመክፈል፣ የተስማሙ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ሰነዱ አመልካች የተጠሪ ወራሽ ተከራክረው የተሰጠን ፍርድ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት ለማስቀረት የተደረገ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ የዕርቅ ስምምነት ሰነድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈረመው በወቅቱ አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርባ በክርክር ላይ በነበረበት ወቅት እንደሆነ አመልካች ለስር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ችሎት ካቀረበችው የፅሁፍ ክርክር ተረድተናል፡፡

8. ይህም አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ጋር አድርጌዋለሁ የምትለው የዕርቅ ውል በፍርድ የተሰጠ ውሳኔ ተፈፃሚነት ቀሪ የማድረግ ዓላማና ይዘት ያለው ከሆነ፣ በሕግ ፊት ውጤት እንዲኖረው ምን ምን መስፈርቶችን አሟልቶ መገኘት አለበት የሚለውን ነጥብ እንድንመረምር የሚያስገድድ ነው፡፡ የዕርቅ ውሉ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ተፈፃሚ እንዳይሆን የማድረግ ይዘት እና አላማ ካለው፣ ከሌሎች የዕርቅ ስምምነቶች ለየት ባለ መንገድ የተደረገና ይዘቱ ተመርምሮ የፀደቀ መሆን እንዳለበት ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 274 እስከ ፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 279 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሰረታዊ ዓላማና ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ በተለይም የዕርቅ ውሉ በፍርድ የተወሰነ ውሳኔ አፈፃፀም ቀሪ ለማድረግ የተደረገ በሆነ ጊዜ፣ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 276 እና በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ የተቀመጡ መስፈርቶች በጥብቅ የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በፍርድ የተወሰነ ጉዳይ ተፈፃሚነት ለማስቀረት የሚደረግ የዕርቅ ውል፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 መሰረት ተደርጉና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277/1/ መሰረት ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ቀርቦ ካልፀደቀ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በፍርድ የተወሰነ ውሳኔ ተፈፃሚነት ለማስቀረት የፍርድ ባለመብትና የፍርድ ባለዕዳ ያደረጉት ስምምነት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 በሚደነግገው መሰረት ተዘጋጅቶ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277/1/ መሰረት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ባልፀደቀበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች እየተቀበሉ የሚያከራክሩና ህጋዊ ውጤት የሚሰጡ ከሆነ፣ በዳኝነት አካሉ ክስ ቀርቦባቸው ተከራክረው በፍርድ ውሳኔ የተሰጠባቸው ሰዎች፣ የፍርዱን ውሳኔ ተፈፃሚነት ለማስቀረት ከፍርድ ቤት ዕውቅና ውጭ የዕርቅ ውል ተዋውለናል የሚል መከራከሪያ እያቀረቡ የፍርድ አፈፃፀም ስርዓቱን እንዲያጓትቱና እንዲያስተጓጉሉ ሰፊ ዕድል፣ የሚፈጥር አጠቃላይ የስነ ስርዓት ሕጉን አላማ የሚፃረርና ጉዳዮች በፍርድ ከተቋጨ በኋላ እንደገና ማቆሚያ የሌለው ክርክር እንዲቀርብላቸው የሚያደርግ ይሆናል፡፡

9. በመሆኑም በፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ አፈፃፀም ለማስቀረት የፍርድ ባለመብት እና የፍርድ ባለዕዳ የሚያደርጉት የዕርቅ ውል፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277/1/ የተደነገገውን ጥብቅ መስፈርት የሚያሟላ ባልሆነበት ጊዜ፣ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት እንደማይኖረው የሚያረጋግጥ፣ ጥብቅ የሆነ የሕግ አተረጓጎም መርህ መከተል የፍርድ አፈፃፀም ስርዓቱን ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ እንዲከናወን ለማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም አድርጌዋለሁ በማለት ያቀረበችው የዕርቅ ውል ሰነድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277/1/ መሰረት ፍርድ ቤት ቀርቦ ያልፀደቀ በመሆኑ ከጅምሩ ተጠሪ ያቀረበችውን የአፈፃፀም ክስ ለማቋረጥ መከራከሪያ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ሰነድ በመቀበል አፈፃፀሙ እንዲቋረጥ የሰጠው የሕግ ትርጉምና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዕርቅ ሰነዱን አፈፃፀሙን ለማቋረጥ ሊቀርብ የሚችል ማስረጃ አድርጎ ከወሰደ በኋላ፣ የሰነዱን ይዘት መርምሮ ሰነዱ በይዘቱ የመሬት ሽያጭ የሚመስል በመሆኑ ለህግ ተቃራኒ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ከላይ በዝርዝር የገለፅነውን የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 277/1/ በፍርድ የተወሰነ ውሳኔ ተፈፃሚነት ቀሪ በማድረግ በሚደረጉ የእርቅ ስምምነት ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን ጥብቅ ተፈፃሚነት ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው፡፡

10. ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻራቸው ተገቢነት ያለው ቢሆንም፣ በፍርድ የተወሰነ ውሳኔ ተፈፃሚነት ለማሰቀረት የፍርድ ባለመብትና የፍርድ ባለዕዳ ከፍተኛ ዕውቅና ማረጋገጫ ሣይሰጠው አድርገነዋል የሚሉት የዕርቅ ውል ህጋዊ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው አድርገው የሰጡት የሕግ ትርጉም፣ ስህተት ያለበት በመሆኑ፣ ምክንያቱን ለውጠንና አሻሽለን፣ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም ተዋውለናል በማለት ያቀረበችው የዕርቅ ስምምነት ሰነድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277/1/ መሰረት በፍርድ ቤት ያልፀደቀ በመሆኑ ተጠሪ ያቀረበችውን የአፈፃፀም ክስ ለማሰቀረት ህጋዊ ተፈፃሚነትና ውጤት የለውም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዝ የተነሳ መሆኑ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ/ሰ/መ/ቁ 99743

መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ንብ ኢንሹራንስ (አ.ማ) - ነገረ ፈጅ ተስፋሁን ሽብሩ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ራዲካል ኢንጅነሪንግ ኃላ/የተ/የግል ማህበር - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 147896 መጋቢት 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 99409 ሚያዝያ 3 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ፍርድ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የአፈፃፀም ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች ወጪና ኪሣራን ጨምሮ አመልካች በፍርድ የተወሰነበትን ብር 589880/ አምስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሰማኒያ ብር / እንዲከፍል የአፈፃፀም ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ለሥር ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ክስ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በፍርዱ መሠረት የማይፈፀምበትን ምክንያት ቀርቦ እንዲያስረዳ ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች የፍርድ ባለመብት /ተጠሪ/ የሚከናወን ቅሪት ለመሸጥ የሚያስፈልግ ሊብራና ውክልና እንዲሰጠን ብንጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆኑ በፍርድ የተወሰነብኝን ገንዘብ አልከፈልኩም የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበው መከራከሪያ በፍርድ የተወሰነበትን ገንዘብ ባለመክፈል በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም በማለት አመልካች እንደ ፍርዱ እንዲፈፅም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡
2. አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ሚያዝያ 6 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች በመኪናው ላይ የደረሰውን ጠቅላላ ጉዳት ብር 450,000 በመክፈል ተሸከርካሪውን የማስቀረት መብት በመድን ውሉ ውስጥ ተሰጥቷል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ በፍርድ የተወሰነበትን ገንዘብ እንዲከፈለው ጉዳት የደረሰበትን ተሸከርካሪ ለአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲያስረክብ፣ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ አስጠግኖ ለመሸጥ፣ለመለወጥ የሚያስችል ውክልና የመኪና ሊብሬና ተሽከርካሪ ከዕዳና እገዳ እንዲሁም ከግብር ዕዳ ነፃ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃና ክሊራንስ ለአመልካች የመስጠት ግዴታውን መወጣት ይገባዋል፡፡ ተጠሪ ይህንን ሳይፈፅም ገንዘቡን ክፈል መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

3. ተጠሪ ግንቦት 5 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ፣ፍርድ የሚፈፀመው የተሰጠው ፍርድ ይዘት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች በአፈፃፀም ወቅት ካነሳቸው መከራከሪያዎች በዋናው ጉዳይ ስንከራከር አንስቶ ፍርድ አላረፈበትም ይህ ከሆነ አመልካች በፍርድ የተወሰነበትን እንድፈጽም ስጠይቅ በፍርድ ተረጋግጦ ውሣኔ ያላረፈበትን ቅድመ ሁኔታ በመደርደር ፍርዱን ለመፈፀም እንቢተኛ መሆኑ የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ግንቦት 27 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪ ብር 589,850 / አምስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ ብር/ ለተጠሪ እንድከፍል በፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑንና የፍርድ ባለመብቱ ተጠሪ በፍርድ የተወሰነለትን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍለውና ፍርዱ እንዲፈጽምለት ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን ግራቀኙ በሥርና በሰበር ደረጃ ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል፡፡ አመልካች በፍርዱ መሠረት ፍርድ የማይፈፀምበትን ቀርቦ እንዲያስረዳ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 383 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት እንዲያቀርብ የተጠሪው አመልካች ከተጠሪ ጋር ባለው የመድን ውል መሠረት በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት ሰባ አምስት ፐርሰንት ከሆነ የመኪናውን በመድን ውሉ የተመለከተውን ሙሉ ዋጋ ከፍሎ የመረከብ መብት እንዳለው ገልፆ፣ገንዘቡን ለመክፈል በመጀመሪያ የመኪናውን ቅሪት፣ተጠሪ ሊያስረክበኝ ይገባል፡፡ የመኪናውን ሊብሬና ውክልና ሊሰጠኝ ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ አመልካች በመድን ውሉና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት አለኝ የሚለው የመኪናውን ቅሪትና ሌሎች መኪናውን ለማስጠገንና ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች የመረከብ መብት፣የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 30 እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 215(2) መሠረት የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ በማቅረብ በፍርድ ያስወሰነ ስለመሆኑ ያቀረበው የፍርድ ቤት ውሣኔ የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በአፈፃፀም ወቅት መከራከሪያ አድርጎ ያቀረባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች የክስ መከላከያ አድርጎ አቅርቦ፣ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት በጭብጥነት ይዞ፣ውሣኔ የሰጠባቸውና ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ የፍርድ ቤት ውሣኔ አላቀረበም፡፡

6. ፍርድ የሚፈፀመው በፍርድ ውስጥ በተገለፀው ውሳኔ መሰረት መሆኑን የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 378 ንዑስ አንቀጽ 1 ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፍርድ ባለመብት ፍርዱን እንዲፈፀምለት ሲጠይቅ፣የፍርድ ባለዕዳው፣የፍርድ ባለመብቱ ተነጻጻሪ የሆነ ግዴታውን እንዲወጣ ትዕዛዝ ይስጥልኝ በማለት ጥያቄ ለማቅረብ የሚችለው በአንድ ፍርድ ውስጥ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የፍርድ ባለመብት መሆናቸው ተረጋግጦ ውሳኔ ተሰጥቶበት እንደሆነ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 398 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከመድን ውሉና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ሊፈፅምልኝ የሚገባው ግዴታ አለ በማለት በአፈፃፀም መከራከሪያ አድርጎ ያቀረባቸው ነጥቦች በዋናው ጉዳይ መከራከሪያ ሆነው ቀርበው ፍርድ የተሰጠባቸው አይደሉም ይህ ከሆነ አመልካች ከተጠሪ የሚጠይቀው መብት ካለ፣በሕግ አግባብ ክስ አቅርቦ በፍርድ ተረጋግጦ እንድንወስንለት ከሚጠይቅ በስተቀር፣ፍርድ ያላረፈበትን ቅድመ ሁኔታ በአፈፃፀም ክርክር በመደርደር ፍርዱን የመፈፀም ግዴታ የለብኝም በማለት ያቀረበው መቃወሚያ የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ፍርዱን የማይፈፅምበት በቂ አሳማኝና ህጋዊ ምክንያት አላቀረበም በማለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ከላይ የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 9 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጭ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.96833
ህዳር 08 ቀን 2007 ዓም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ
ዓሊ መሀመድ
ሱልጣን አባተማም
መስጠፋ አህመድ
ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ቀረቡ /ነ-ፈጅ/

ተጠሪ፡- አቶ አስፋዉ ደነቀ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ ጉዳይ በማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጀመረዉ ተጠሪ አቶ አስፋዉ ደነቀ የተራዘመዉ አገልግሎት ለጡረታ ተግባር እንዲያዝላቸዉ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ነዉ፡፡ ተጠሪ የሚጠይቁት ተጠቃሹ መስሪያ ቤት በወቅቱ በነበረበት የሰዉ እጥረት የጡረታ ጊዜዬን ለ5 ዓመታት እንዲራዘም በጻፈዉ ደብዳቤ ለማ/ዋ/ቅ/ጽ/ቤት ሲጻፍ ለእኔም ግልባጩ ደርሶኝ በተከፈተዉ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት የውሃ ጽ/ቤት ተጠባባቂ ኃላፊነት ተመድቤ በ6 ወረዳዎች ሰራሁ፣በድጋሜ የጡረታ ግዜ ለ5 ዓመታት እንዲራዘም ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ተጽፎ የስምምነቱ ደብዳቤ ለመ/ቤቱ ሲደርስ ግልባጩ ለክልሉ ማ/ዋ/ኤ/ጽ/ቤት ደርሷል፣ የዉሃ ሀብት ቢሮ ባዘጋጀዉ አዲስ መዋቅር የተደረገዉ ስምምነት 2 ዓመት ሲቀረኝ እርምጃ ወስዷል፣ስለዚህ ከየካቲት 1995 እስከ ጥር 30 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ የተራዘመዉ የ8 ዓመታት አገልግሎቴ እንዲያዝልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በሰጠዉ መልስም፡- አቶ አስናቀ ደነቀ የትዉልድ ዘመናቸዉ ጥር 13 ቀን 1940 ዓ.ም ሲሆን በጡረታ መገለል የሚገባቸዉ ከየካቲት 01 ቀን 1995 ዓም ጀምሮ ነዉ፣አሰሪዉ መ/ቤቱ መረጃ እንዲልክ በ2/9/95 ዓ.ም ቢጠየቅም የአገልግሎት ማራዘሚያ ጥያቄ ለሱማሌ ክልል መላኩ ስልጣኑ እንዳልሆነ በማሳወቅ የባለመብቱ መረጃ ተሟልቶ እንዲላክ በድጋሚ በ15/11/95 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የተጠየቀና የመጀመሪያ አምስት አመታት የጡረታ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ በሚመለከተዉ አካል ባልቀረበበት ሁኔታ በተጨማሪ ከ1/8/2000 እስከ 30/05/2005 ዓም እንዲራዘም የተደረገዉ የጡረታ መዉጫ ጊዜያቸዉ ካለፈና የጡረታ አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 11(ሀ) መሠረት የጡረታ መዉጫ ጊዜያቸዉ ካለፈ አገልግሎታቸዉ እንዲራዘም የተፈቀደበት መረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ከእድሜ ጣሪያ በላይ ላገለገሉበት የመዋጮ ተመላሽ ከሚከፈላቸዉ/ከሚጠይቁት በስተቀር የተራዘመዉ አገልግሎት ሊያዝላቸዉ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን ያየዉ ማህበራዊ ዋስትና ጉባኤም ከሱማሌ ክልል መንግስት የዉሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ በ12/10/1995 ዓም ለማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በጻፈዉ ደብዳቤ የተጠሪ የአገልግሎት ጊዜ እንዲራዘም ጥያቄ ያቀረበ መሆኑ ከቀረበዉ መረጃ ለመረዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተችሏል፣በተጨማሪም በ18/7/1995 ዓ.ም በቁጥር ሠአር ከሰ/2145/95 ከክልሉ የዉሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ የድሬዳዋ ጽ/ቤትን በመደበኛ ስራ ለማስጀመር የጽ/ቤቱ ጊዜያዊ ኃላፊ በመሆን የተሾሙ መሆኑን ከቀረበዉ ማስረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፣የሸንሌ ዞንም ከፍተኛ ድርቅ ተከስቶበት ስለነበር ችግሩን ለመቅረፍ ሲሰሩ እንደነበር እና ከፍተኛ ባለሙያ መሆናቸዉን ገልጸ በክልሉ የዉሃ ሀብት ኃላፊ ሆነዉ በሹመት ወደ ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ተዛዉረዉ በኃላፊነት ሲሰሩ እንደነበር ለጉባዔዉ ገልጸዋል የሚሉ ምክንያቶችን ይዞ በሹመት የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን እንዲሰሩ የተመደቡ በመሆናቸዉ ከእድሜ ጣሪያ በላይ የፈጸሙት አገልግሎት ሊያዘላቸዉ እንደሚገባ በጉባኤዉ ታምኖበታል በማለት የኤጀንሲውን ዉሳኔ ሽሮ ተጠሪ ከዕድሜ ጣሪያ በላይ የፈጸሙት አገልግሎት ለጡረታ ተግባር እንዲያዘላቸዉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ኤጀንሲዉ ይግባኝ በማለቱ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎትም ቅሬታዉን በአዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 76 መሰረት ባለመቀበል ዘግቶታል፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታም ቅሬታዉን ሲገልጽ፡- ተጠሪ በክልሉ የዉሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ ሥር ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን ሲሰሩ የቆዩት በስራ ሀላፊነት እንጂ በሹመት አይደለም፣ ሃላፊ ተብለዉ መስራታቸዉ ሹመት ሊባል አይችልም፣ የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁ. 515/99 ድንጋጌን በመጥቀስ የተጠሪ አገልግሎት ከተቋረጠ 5 ዓመታት በኋላ እንዲራዘም መፍቀዱ ህግን የተከተለ አይደለም፣ የጡረታ አዋጅ ቁ.710/2003 አንቀጽ 17(4)(ሀ) መሠረት ማንኛዉም የመንግስት ሰራተኛ በህጉ መሰረት አገልግሎቱ ካልተራዘመ የጡረታዉ መዉጫ እድሜዉ ከደረሰበት ከሚቀጥለዉ ወር አንስቶ የሚሰጠዉ አገልግሎት ለጡረታ ተግባርአይያዝም እያልንኤጀንሲዉና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የተጠሪ አገልግሎት እንዲራዘምና እንዲያዘላቸዉ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህም መሰረት ችሎቱም ተጠሪ ከጡረታ መዉጫ በኋላ የአገልግሎት ዘመኑ ለተጨማሪ 5 ዓመታት ተራዝሟል መባሉን ከአዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 89 ድንጋጌና ከዚሁ አዋጅ አንቀጽ 85/1 ድንጋጌ አንጻር ለማጣራት የግራ ቀኙ የመልስና መልስ መልስ በጽሑፍ ተቀባብለዉ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች የሚለዉ የአዋጅ ቁ.515/99 ተጠቅሶ ተጠሪ አገልግሎት ከተቋረጠ ከ 5 ዓመታት በኋላ እንዲራዘም መፈቀዱ ህግን የተከተለ አይደለም ፣በህጉ መሠረት ማንኛዉም የመንግስት ሰራተኛ አገልግሎት ካልተራዘመ በስተቀር የጡረታ መዉጫ ዕድሜዉ ከደረሰበት ከሚቀጥለዉ ወር አንስቶ የሚሰጠዉ አገልግሎት ለጡረታ ተግባር አይያዝም፣በመሆኑም ህጋዊነቱ ሳይረጋገጥ ተራዝሟል መባሉ ሊታረም ይገባዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በወቅቱ በነበረዉ የዉሃ አጥረት የተነሳ እንዳገለግል ፈቅዶ ሲያሰራኝ ቆይቶ መራዘሙን አላዉቅም ማለቱ የራሱን የመረጃ አያያዝ ድክመት መኖሩን የሚያሳይ ነዉ፣ አመልካች ማገልገሌን ሳይቃወም ዉሳኔዉን መንቀፉ አግባብ ባለመሆኑ የስር ዉሳኔ ስህተት የለበትም በማለትተከራክሯል፡፡

በመሰረቱ የአዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 89 እና አንቀጽ 85(1) ድንጋጌዎች ከተያዘዉ ክርክር አንጻር ስንመለከታቸው አንቀጽ 89(2) ሠ እና 85(1) በመርህ ደረጃ የጡረታ ጊዜ አገልግሎት ሊራዘም የሚችለዉ ለኤጀንሲዉ ቀርቦ በህጋዊ መንገድ መፈቀድ እንዳለበት ይህ ካልሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለተጨማሪ ስነ-ስርዓት አገልግሎት የሚቋረጥ መሆኑን እና የአገልግሎት መራዘም ከ10 ዓመት የማይበልጥ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች በመርህ ደረጃ ጡረታ መውጫ ጊዜ ከደረሰ በኋላ አገልግሎት ዘመን ለማራዘም ሊከናወኑ የሚገባቸዉን ህጋዊ አካሄድን የሚያመላክቱ መሆናቸዉን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በእጃችን ወዳለዉ ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በክልሉ የዉሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ ሲያገለግሉ የነበሩና አስፈላጊ ባለሙያ በመሆናቸዉ ከጡረታ መዉጫ ጊዜያቸዉ በኋላ ተጨማሪ አገልግሎት እንዲሰጡ በመፈለጉ ምክንያት በ12/10/95 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ማሳወቁን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ላለፉት 8 ዓመታት የውሃ አጥረት በገጠማቸዉ አካባቢዎች ተዘዋውረው ሲሰሩ እንደነበሩና ለስራቸዉም ክፍያ ሲያገኙ እንደነበሩ የምንገነዘበዉና በስር ፍርድ ቤትም ተረጋግጦ እና በአመልካችም ያልተካደ ጉዳይ ነዉ፡፡ አከራካሪ የሆነዉ ጉዳይ ተጠሪ ይሁንታ ሳያገኙ የአዋጅ ቁ.714/2003"ን" መንፈስ ተከትሎ አስፈላጊውን ቅደመ ሁኔታ ሳያሟሉ (ጥያቄያቸዉ ተቀባይነት ሳያገኙ) በመስራታቸዉ ብቻ የተራዘመ አገልግሎት ለጡረታ አገልግሎት እንዲያዘላቸው መጠየቅ አይችሉም በማለት ነዉ፡፡ እንግዲህ ተጠሪ ለተጨማሪ ግዜ አገልግሎት መስጠታቸዉ ባልተካደበት አስፈላጊዉን አስተዳደራዊ መጻጻፍ በማድረግ ጉዳዩን ወደ ህጋዊነት የማምጣት ኃላፊነት እና ግዴታ ያለበት አመልካች እንጂ ተጠሪ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ምክንያቱም አሰሪዉ አካል እያወቀና ተቃዉሞ ከየትኛዉም አካል ሳይገጥማቸዉ ተጠሪ ስራቸውን መስራታቸዉን ማረጋገጣቸዉ በቂ ነዉ፡፡

በአጠቃለይ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በስር በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን በመቀበል ተጠሪ ከዕድሜ ጣሪያ በላይ ያገለገሉት ጊዜ ለጡረታ አገልግሎት እንዲያዘላቸዉ መወሰኑ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡

በመጨረሻም ማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚዉ ጉባዔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በመ.ቁ.ጤ/ይ/1/1/43/2006 በቀን 29/02/2006 ዓ/ም እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.95017 በቀን 30/04/2006 ዓ.ም የሰጡት ዉሳኔ ጸንቷል፡
2. ተጠሪ ከዕድሜ ጣሪያ በላይ የፈጸሙት አገልግሎት ለጡረታ ተግባር እንዲያዘላቸዉ መባሉ ባግባቡ ነዉ ብለናል፡፡
3. የግራቀኙ የወጪና ኪሳራቸዉን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም
መስጠፉ አህመድ
ተሻሊት ይመሰል

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤርፓርቶች ድርጅት - ጠበቃ አቶ ሚካኤል ጉንታ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ በየነ ወልደገብርኤል - ጠበቃ ኃይሉ ብርሃኑ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 96130 ጥር 6 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የግልግል ጉባኤ ዳኛና ሰብሳቢ ሆኖ የተሰየመ ሰው ጉዳይን ከማየት ይነሳልኝ በሚል መንገድ በቀረበ ጥያቄ የተሰጠን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡

1. ጉዳዩ የተጀመረው ለአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤትና የዘርፍ ማህበራት የግልግል ተቋም አመልካች ባቀረበው ጥያቄ ነው፡፡ በግልግል ተቋሙ መልስ ሰጭ የሆነው አመልካችና የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ የሆነው ጂአሜትሪ ሉዊጅ ቫርኔሮ አምፕራስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመካከላቸው የተፈጠረው አለመግባባት በግልግል ዳኞች እንዲቀርብ በመስማማታቸው የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤትና የማህበራት ዘርፍ የግልግል ዳኝነት ተቋም የግልግል ዳኞች ጉባኤ ተቋቁሟል፡፡ የግልግል ዳኞች ጉባኤ ሰብሳቢ ተጠሪ እንዲሆን ሰይሞታል፡፡ የግልግል ዳኞች የተከራካሪዎችን ክርክር በማየት ሂደት ላይ እያሉ አመልካች ታህሳስ 04 ቀን 2006 ዓም በተፃፈ ማመልከቻ የግልግል ዳኞች ጉባኤ ሰብሳቢ የሆኑት ተጠሪ ጉዳዩን ከማየት እንዲነሱለት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የግልግል ተቋሙ የግልግል ዳኞች ጉባኤው በአመልካች ጥያቄ ላይ አስተያየት እንዲያቀርብ በማድረግ፣ የግልግል ዳኞች በአመልካች ማመልከቻ ላይ ዝርዝር አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ የግልግል ተቋሙ፣ የግልግል የዳኝነት ጉባኤው ሰብሳቢ የሆኑት የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩን ከማየት እንዲነሳለት አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ያልተቀበለው መሆኑን በመግለጽ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡
2. አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ግልግል ዳኝነትና ከሰብሳቢነት ሊነሳ ይገባል የሚልባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር የሰበር አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ ከግልግል ዳኝነቱ እንዲነሳ የተጠየቀው ተጠሪ ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከግልግል ዳኝነት አልነሳም የሚልበትን ዝርዝር ምክንያት በመግለፅ ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ሐምሌ 8 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

3. የሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ሂደት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ ከዚህ በኋላ የግልግል ዳኛና ሰብሳቢ ሆኖ ለመቀጠል ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
4. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከህዳር 16 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው የአዲስ አበባ ንግድ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የግልግል ተቋም የተሻሻለ የግልግል ደንብ ስለዳኞች መነሳትና መተካት በአንቀፅ 15 የደነገገ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በግልግል ደንቡ አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ በአንደኛው ተከራካሪ ወገን አቤቱታ ወይም ጥቆማ መሠረት የግልግል ዳኛ እንዲነሳ ጥያቄ ሲቀርብ፣ ተዋዋዮችና ወይም የይነሳልን ጥያቄ ያልቀረበባቸው የግልግል ችሎት ሌሎች አባላት የፅሑፍ አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ተቋሙ ውሣኔ እንደሚሰጥ ይገልፃል፡፡
5. አከራካሪው ጉዳይ ተቋሙ ከግልግል ችሎቱ እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት ዳኛ፣ ከግልግል ችሎቱ መነሳት የለበትም በማለት በሰጠው ውሣኔ ላይ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 9 እና አንቀፅ 10 መሠረት የይግባኝና የሰበር አቤቱታ ሲቀርብበት ወይም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3342 መሠረት መቃወሚያ ሲቀርብበት የተቋሙን ውሣኔ በመደገፍ ተከራካሪ ሆኖ መቅረብ ያለበት ማን ነው? ከጉዳዩ እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት ዳኛ፣ ጉዳዩን ከማየት እንዳልነሳ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢነት ያለው ነው በማለት ጉዳዩን ለግልግል ዳኝነት ካቀረበውና ጥያቄውን ካነሳው ተከራካሪ ወገን ጋር መልስ ሰጭ ወይም ተጠሪ ሆኖ ቀርቦ ዝርዝር ክርክር ካቀረበ በኋላ፣ በፍርድ ቤት ተከራካሪ ሆኖ በቀረበበት ጉዳይና በተከራካሪነት ቀርቦ ሲሞግተው የነበረውን ተከራካሪ ወገን ለግልግል ዳኞች የሚያቀርበውን ክርክርና ማስረጃ በገለልተኝነት ስምቶ ሊወስን ይችላል ተብሎ በግልግል ዳኝነት እንዲሰየም ማድረግ የግልግል ዳኝነቱን ዓላማ የማያሳካ ነው ወይ? የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
6. የአዲስ አበባ ንግድ ዘርፍ ማህበራት የግልግል ተቋም የግልግል ደንብ፣ ተቋሙ ጉዳዩን ከማየት እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት የግልግል ዳኛ ጉዳዩን ከማየት አይነሳም በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ አንደኛው ተከራካሪ ወገን መቃወሚያ ፣ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ በሚያቀርብበትና አቤቱታው ተቀባይነት አግኝቶ መልስ እንዲቀርብ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ፣ የግልግል ተቋሙ ዳኛው ጉዳዩን ከማየት የሚነሳበት በቂ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ በዝርዝር ለማስረዳት ክርክሩን በማን በኩልና እንዴት እንደሚያቀርብ በግልፅ ያስቀመጠው ስርዓት የለም፡፡ ሆኖም በመርህ ደረጃ የግልግል ተቋሙ ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት (ሰብሳቢነት) ተሰይሞ ከማየት የሚከለክል በቂ ምክንያት የለም በማለት የሰጠውን ውሳኔ ለማስረዳት ከሚያቀርብ በስተቀር፣ጉዳዩን ከማየት እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት የግልግል ዳኛ በተከራካሪነት ቢቀርብና፣የግልግል ዳኛውን ከዳኝነት የሚያስነሳው በቂ ምክንያት አለ ወይስ የለም በሚለው ጭብጥ ዙሪያ ተከራካሪ ሆኖ መሰለፍና ዝርዝር ክርክር የሚያቀርብበት ሁኔታ መኖር የለበትም፡፡
7. ከዚህ አንጻር ስናየው ተጠሪ በጉዳዩ ተከራካሪ ሆነው መጠራታቸው ስህተት ነው፡፡ አመልካች ለግልግል ተቋሙ ተጠሪ ከግልግል ዳኝነትና ሰብሳቢነት እንዲነሳ ያቀርብኩት ምክንያት አላግባብ ውድቅ ተደርጎብኛል የሚል የሰበር አቤቱታ ሲደርሳቸው ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጉዳዩ የተለየ ጥቅምና ፍላጎት የሌላቸው መሆኑንና ጉዳዩን በዳኝነት እንዳያይ ወይም ከግልግል ዳኝነት እንዲነሳ በህግ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ጉዳዩን አጣርተው የሚሰጡትን ውሳኔ በፀጋ እንደሚቀበሉ ከመግለጽ ማቆም ይገባዋል፡፡ ተጠሪም ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት ተሰይሜ ማየት አለብኝ የሚል አቋም በመያዝ ሰፊና ዝርዝር ክርክር እንዳቀረቡ ለዚህ ሰበር ችሎት ካቀረቡት ክርክር ተርድተናል፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ይዘት የቀረበውን ሙግት በመቃወም ፣ ተከራካሪ ሆነው ተሰልፈው ሰፊና ዝርዝር ክርክር ባቀረቡበት ሁኔታ የአመልካችንና በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆነውን "ቫርኔሮ" እየተባለ የሚጠራውን ድርጅት ጉዳይ ከዚህ በኋላ በግልግል ዳኝነት ተሰይመው እንዲያዩ መፍቀዱ ከመሰረታዊነትም ሆነ ከዕይታ አንጻር ሲመዘን ፣ የግልግል ዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነት መርህ የሚያስከበር ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይህ ሁኔታ በራሱ በሶስተኛ ወገን የተመረጠ ዳኛ ባለማዳላቱ ወይም በነጻነቱ ላይ ጥርጣሬ ለማስገባት የሚችል አንድ አንድ የአካባቢ ሁኔታ ምክንያት በሚኖርበት ጊዜ ዳኛው ከግልግል ዳኝነቱ ሊነሳ እንደሚችል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3340 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የሚያሳይ ነው፡፡

8. ተጠሪ በጉዳዩ መልስ ሰጭ አድርጎ ሰይሞ በማቅረብ አመልካች በፈጸመውና ፍርድ ቤቱም ተጠሪን በተከራካሪነት በመጥራቱ ምክንያት በተፈጸመ ስህተት ፣ አመልካች ተጠሪ በአንድ አከራካሪ ጭብጥ ላይ በተከራካሪነት ተሰልፈው ሰፊ የሆነ ክርክር አቅርቧል፡፡ በሌላ አነጋገር በግልግል ዳኝነት አካሉ መልስ ሰጭ የሆነው አመልካችና የግልግል ዳኛ ሆኖ ጉዳዩን ከማየት የሚከለክለኝ ምክንያት የለም የሚል ክርክር ያቀረበው የግልግል ችሎቱ ሰብሳቢ ዳኛ የሆኑት ተጠሪ "ዳኛው ከግልግል ችሎቱ መነሳት አለበት ወይስ የለበትም" በሚለው ጭብጥ ላይ ሁለት ተቃራኒ አቋም በመያዝ ግራናቀኝ በተከራካሪነት ቆመው ተሟግተዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ተጠሪ የግልግል ጉባኤው ዳኛና ሰብሳቢ ሆኖ እንዲቀጥል ቢደረግ የግልግል ዳኛ ሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ጋር የነበረው ያለውና የሚኖረው ግንኙነት በገለልተኝነትና በነፃነት መርህ ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል የሚለውን የግልግል ተቋሙ የተሻሻለ ደንብ አንቀፅ 13 ድንጋጌና ሌሎች ሕጎች የተደነገገውን መርህ የሚጥስ በመሆኑ ተጠሪ የግልግል ዳኛና ሰብሳቢ ሆኖ መቀጠል አይገባውም በማለት በተሻሻለው የግልግል ደንብ ከአንቀፅ 13 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3340 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በማድረግ ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ተጠሪ በግልግል ዳኝነትና ሰብሳቢነት መቀጠል እንደሌለበት የተወሰነ መሆኑን አውቆ ተገቢውን እንዲፈፅም ለአዲስ አበባ ንግድ ዘርፍ ማህበራት የግልግል ተቋም ውሣኔው ይተላለፍለት፡፡
2. ግራቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 99689

ታህሳስ 24 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡-ዶ/ር መኮንን ንዋይ የአዲስ አበባ ዩንታል ሳይንስና ኮሌጅ ባለቤትና ዲን - ጠበቃ ግርማ ኃይሌ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. መንግስቱ ጋሞ
2. አቶ እንዳለ አለማየሁ
3. አቶ ኢሳያስ አበራ
4. አቶካሊድ አባስ
5.ወ/ሮ መሰረት መላኩ
6. አቶ አዲስአለም አለማየሁ

} ሌሎች አልቀረቡም

7. አቶ ታዬ አዱኛ.....ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ኦርጂናል ዲፕሎማ ይሰጠኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪዎች የክስ ይዘትም፡-አመልካች በ1999 ዓ/ም አዲስ አበባ ዩንታል ሳይንስ ኮሌጅውስጥ ለማስተማር ተቀብሎ ለሶስት አመታት የጥርስ ህክምና ትምህርት አስተምሮ በ2002 ዓ/ም ካስመረቀ በኋላ ትራንስክርቢትና ጊዚያዊ ዲፕሎማ የሰጣቸው ቢሆንም ኦርጂናል ዲፕሎማውን ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ገልጸው ይህንኑ ማስረጃ እንዲሰጧቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ተጠሪዎች ትምህርቱን ጨርሰው ጊዜያዊ ዲፕሎማ መውሰዳቸውንአምነው ዋናውን ዲፕሎማ ለመስጠት ኮሌጁ ዝግጅት ላይ እንዳለ የመንግስት ክልከላና የፈቃድ ስረዛ በማጋጠሙ የተነሳ ማህተምም ሆነ ፊርማ የሚፈርም ባለስልጣን ባለመኖሩ ለተጠሪዎች ኦርጂናል ዲፕሎማ እንዳልተሰጠና በፍርድ ቤት ቢወሰንም ሊፈጸም የማይችል መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ከሚመለከተው አካል ስለ ጉዳዩ አጣርቶ የተጠሪዎችን ኦርጂናል ዲፕሎማ አመልካች ሊሰጥ የማይችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ማስረጃውን አመልካች ለተጠሪዎች ሊሰጥ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በስር ፍርድ ቤት ያቀረባቸውን የክርክር ነጥቦችን የሚያሳይ ሁኖ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች በአመልካች ባለቤትነትና በሚታወቀውና አመልካቹ በዲንነት ያስተዳድሩት ኮሌጅ ውስጥ ተመዝግበው በተገቢው መንገድ ትምህርታቸውን መከታተላቸውና መጨረሳቸው ተረጋግጦ ትራንስክርቢትና ጊዜያዊ ዲፕሎማ በአመልካቹ የተሰጣቸው መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ከመሆኑም በላይ ኮሌጁ በመንግስት ክልከላና ፈቃድ ስርዛ ምክንያት ስራውን ያቆመ ቢሆንም ትምህርታቸውን በአግባቡ ተከታትለው ላጠናቀቁት ተማሪዎች ዋናውን ዲፕሎማ እንዳይሰጥ የሚከለክል መመሪያ የሌለ መሆኑና ኮሌጁ ዲፕሎማውን የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጂንሲ በቁጥር ኤ./4015/ተስጥመ/12/67 በቀን 17/10/2005 ዓ/ም ለስር ፍርድ ቤት በጻፈው ደብዳቤ መረጋገጡን ነው፡፡በመሆኑም ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ኮሌጅ በመንግስት ስልጠና ለመስጠት መከልከሉና ፈቃድ መሰረዝ ከዚህ የመንግስት እርምጃ በፊት ስልጠናውን በአግባቡ ተከታትለው የጨረሱ ተማሪዎች ኦርጂናል ዲፕሎማ እንዳያገኙ የማያደርግ መሆኑን ከሚመለከተው አካል ምላሽ ተሰጥቷቸው በሚገባ አረጋግጠዋል፡፡አመልካች ማህተም የሌለው ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ካለመረጋገጡም በላይ ማህተም ያለመኖሩ ወይም ቀድሞ ለተጠናቀቀ የትምህርት ስልጠና በፊርማ አረጋግጦ ማስረጃ ለመስጠት በወቅቱ የነበረው ኃላፊ ያለመኖሩ ተፈፃሚነትባላቸው ሕጎች መሰረት ኦርጂናል ዲፕሎማውን ለተጠሪዎች ላለመስጠት የሚያስችለው መሆኑን አላስረዳም፡፡ይልቁንም አግባብነት ያለው አካል ኦርጂናል ዲፕሎማውን ማግኘት መብታቸው መሆኑን፣ማስረጃው መስጠት ደግሞ የአመልካች ግዴታ መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ አረጋግጧል፡፡በመሆኑም አመልካች ከአዋጅ ቁጥር 650/2001፣ደንብ ቁጥር 199/2003 እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተጣለበትን ኃላፊነት ያልተወጣ መሆኑ በአንጻሩ ተጠሪዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገብተው ለመማር የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተውና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ስርዓቱን በተከተለ አግባብ ስልጠናውን ተከታትለው የጨረሱ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህንኑ የሚያረጋግጥላቸውን ማስረጃ ከአመልካች የማግኘት መብት ያላቸው ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩን በአግባቡ አጣርተውና አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ተጠሪዎች ኦርጂናሉ ዲፕሎማ ሊሰጣቸው ይገባል በማለት መወሰናቸው ሕጋዊ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81505 ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር143008 መጋቢት 23 ቀን 2006 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች ኦርጂናል ዲፕሎማ የመስጠት ግዴታ አለበት ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች አለበት

የ/ባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 102061
የካቲት 06 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
ዓሊ መሀመድ
ሱልጣን አባተማም
መስጠፉ አህመድ
ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የከሰረው ሆላንድ ካር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ግርማ አለሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዘመን ባንክ /አ.ማ/ ነገረ ፈጅ አቶ አዳም ሰገድ በላይ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 140316 ግንቦት 5 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101131 ግንቦት 28 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የእግድ ትእዛዝ መነሳትን የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 200820 ተጠሪ የከሰረው የሆላንድ ካር ኃ/የተ/የግል ማህበር ንብረት ታግዶ እንዲቆይ የሰጠውን ትእዛዝ እንዲያነሳለት ጥያቄ አቅርቦ የስር ፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ የሚነሳበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡ አመልካች የስር ፍ/ቤት የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሲነሳና በመያዣነት የያዝኳቸውን ንብረቶች በአዋጅ ቁጥር 97/1990 እንደተሻሻለው በተሰጠኝ ስልጣን መሠረት ንብረቶቹን በሀራጅ ለመሸጥ ለብድሩ መክፈያነት ላውል ይገባል በማለት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍ/ቤት የፅግድ ትእዛዝ ተነስቶ ተጠሪ በመያዣነት የያዘውን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/1990 በአዋጅ ቁጥር 216/1992 እንደተሻሻለው በተደነገገው መሰረት ንብረቶቹን በሀራጅ ሽጦ ለዕዳው መክፈያ ሊያደርግ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡
2. አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2006 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና አዋጅ ቁጥር 216/1992 ስለመክሰር የሚደነግግ ድንጋጌዎች የሉትም፡፡ በመክሰር ጉዳይ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው የንግድ ህጉ ነው፡፡ የከሰረው ድርጅት ንብረት በንግድ ህጉ መሰረት እንዲጣራና እንዲሸጥ መደረጉ፣ የሁሉንም ገንዘብ ጠያቂዎች መብትና ጥቅም የሚያስከብርና ተጠሪም በመያዣው ላይ አለኝ የሚለውን መብት የማያሳጣው በመሆኑ በተናጠል ንብረት ለመሸጥ ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል፡፡ ባለዕዳው የተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እዳ ከመክፈሉ በፊት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ሊከፈሉ የሚገባ የሰራተኞች ደመወዝ ሌሎች ክፍያዎችና የመንግስት ግብር በአግባቡ ተጣርቶ ባልተለየበት ሁኔታ፣ ተጠሪ መያዥርያ በተናጠል እንዲሸጥ ያቀረበውን ጥያቄ መፍቀድ የህጉን ዓላማ የማያሳካ በመያዥርያ ያልተያዙ የባለ እዳውን ንብረቶች ለብክነት የሚዳርግና ጥበቃው ከፍተኛ ወጪ እንዲያስወጣ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ እግዱ እንዲነሳ የተሰጠው ውሳኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

3. ተጠሪ ነሀሴ 27 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ መልስ አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና አዋጅ ቁጥር 216/1990 አንድ የንግድ ድርጅት ሳይከስርም ሆነ መክሰሩ በፍርድ ከተረጋገጠ በኃላ ባንኮች ብድር ሲያበድሩ በመያዣነት የያዙትን ንብረት በሀራጅ ሽጠው የዕዳው መክፈያ እንዲያደርጉ ታስበው የታወጁ ህጎች ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠሪ ለከሰረው ሆላንድ ካር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ገንዘብ ሲያበድር በመያዣነት የያዘውን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በሀራጅ ለመሸጥ ያቀረበውን ጥያቄ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ትእዛዝ ስህተት የለበትም የሰራተኞች ደመወዝና የመንግስት ግብርን በተመለከተ ተጠሪ በሀራጅ ንብረቱን ሲሸጥ በራሱ የሚከፍላቸውና የሚፈጽማቸው ግዴታዎች በመሆናቸው አመልካች መከራከሪያ አድርጎ ማቅረቡ የህግ መሰረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ተጠሪ በመያዥርያነት ይዥርዋለሁ የሚለውን ፋብሪካ ህንጻና ማሽነሪዎች በተናጥል ከሸጠ፣ ያልተገጣጠሙ መኪናዎችን ገጣጥሞ ለመሸጥና ለእዳው መክፈያ ለማድረግ የማያስችል ነው፡፡ የሰራተኞቹን የቀዳሚነት መብትና የመንግስትን ግብር በቀዳሚነት የመክፈል ግዴታ ለመወጣት የማያስችል በመሆኑ የዕግድ ትእዛዝ ጸንቶ ሊቆይ ይገባል በማለት መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከስር የክርክር አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጹሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የከሰረው ሆላንድ ካር መኪና መገጣጠሚያ ድርጅት የሚንቀሳቀስ ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥና ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የስር ፍ/ቤት የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቶ ተጠሪ በተናጥል በመያዥርያ የያዘውን የፋብሪካ ህንፃና ማሽነሪ በሀራጅ እንዲሸጥ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ባንኮች ያበደሩት የብድር ገንዘብ በወቅቱ ሳይከፈላቸው በሚቀርበት ጊዜ በመያዥርነት የያዙትን ንብረት በሀራጅ በመሸጥ ብድራቸውን እንዲከፈል ለማድረግ የሚያስችላቸው ስልጣንና ስርዓት በአዋጅ ቁጥር 90/1997 በአዋጅ ቁጥር 216/1998 እንደተሻሻለ በአዋጅ ህግ አውጭው ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል አንድ የንግድ ድርጅት መክሰሩ በፍርድ ተረጋግጦ ከተወሰነ በኃላ ከከሰረው የንግድ ድርጅት ገንዘብ የመጠየቅየቀዳሚነት መብት ያላቸው አበዳሪዎች እና ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት ዝርዝር አሰራር በንግድ ህጉ በአምስተኛው መፅሐፍ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡

6. በያዝነው ጉዳይ አመልካችንና ተጠሪ የሚከራከሩበት በጉዳዩ ተፈፃሚነት ሊሰጠው የሚገባው አዋጅ ቁ.97/1990 እንደተሻሻለ መሆን ይገባል? ወይስ በንግድ ህጉ አምስተኛው መጽሐፍ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ሊሆን ይገባዋል የሚለውን መከራከሪያ በማንሳት ነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍ/ቤት የሰጠው የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ውሳኔ የሰጠው አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና አዋጅ ቁጥር 216/1992 ከንግድ ህጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አምስተኛ መጽሀፍ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች በኃላ የወጡ ስለሆነ ተፈፃሚነትና ገኖርነት አላቸው በማለት ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው ከአዋጅ ቁጥር 97/1990 እና አዋጅ ቁጥር 216/1992 ስለመክሰር የሚመለከት ድንጋጌ የላቸውም የከሰረ የንግድ ድርጅት ንብረት ስለሚሸጥበትና የቀዳሚነት መብት ላላቸው ለሌሎች የገንዘብ ጠያቂዎች የሚከፍልበትን ስርዓት የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎችን የያዘው የንግድህጉ አምስተኛው መጽሀፍ በመሆኑ፣ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ሊኖራቸው የሚገባው የንግድ ህጉ ልዩ ድንጋጌዎች ናቸው በማለት ነው፡፡ ይህም ተጠሪ በኃላ የወጣው ህግ በፊት ከወጣው ህግ ላይ የበላይነትና ተፈፃሚነት አለው የሚለውን የህግ አተረጓጎም መርህ መሰረት በማድረግ የሚከራከር መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ልዩ የህግ ድንጋጌዎች በጠቅላላ የህግ ድንጋጌዎች ላይ የበላይነትና ተፈጻሚነት አላቸው የሚለውን የህግ አተረጓጎም መሰረት በማድረግ የሚከራከር መሆኑን ተረድተናል፡፡

7. በእኛ በኩል በዚህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ ለሚከራከሩበት ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 97/1990 እንደተሻሻለ መሆን ይገባዋል ወይስ የንግድ ህጉ አምስተኛው መጽሀፍ የሚለው ምርጫ ከመምረጥና አመልካችና ተጠሪ ከጠቀሳቸው የአተረጓጎም መርሆች በላይ የሆኑ በርካታ ሁኔታዎቹን በመመርመር እና መመዘን የሚጠየቅ ሆኖ አግኝተነዋል ይኸውም ተጠሪ በተናጥል የከሰረውን የሆላንድ ካር የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ ህንጻና ማሽነሪዎች በሀራጅ እንድሸጥ ቢደረግ የከሰረው የሆላንድ ካር ንብረት ተሸጦ በሚገኘው ገንዘብ ላይ ከተጠሪ በፊት የቀዳሚነት መብት ያላቸውን የሰራተኞችና የመንግስት የግብር ዕዳ ለማጣራትና ለመክፈል የማያስችል መሆኑን አለመሆናቸውን የከሰረው ድርጅት ንብረት ጠባቂና መርማሪ ዳኛ ተጣርቶ እንዲሸጥ መደረጉ ተጠሪ በመያዣነት በያዘው ንብረት ላይ ያለውን ልዩና የቀዳሚነት መብት የሚያሳጣ መሆኑን ወይስ አለመሆኑን እንደዚሁም የከሰረው ድርጅት ንብረት በንብረት ጠባቂና መርማሪ ዳኛ በኩል ተጣርቶ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በፍርድ ቤት ፈቃድና ትዕዛዝ መሰረት እንዲሸጥ መደረጉ የቀዳሚነት መብት የሌላቸውን ገንዘብ ጠያቂዎች መብትና ጥቅም በተሻለ ሁኔታ ለማስከበርና ዕዳቸው እንዲከፈላቸው ለማድረግ የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መንገድ ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

8. ከዚህ አንጻር ሲታይ፣ተጠሪ በመያዣነት የያዘውን የፋብሪካ ህንጻና የመኪና መገጣጠሚያ ማሽነሪ በተናጥል የሀራጅ ማስታወቂያ አውጥቶ እንዲሸጥ ቢደርግ የከሰረው ድርጅት ሰራተኞች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 167 የተሰጣቸውን የቀዳሚነት መብት በተሟላ ሁኔታ ለማጣራትና የሰራተኞች ጥያቄ ከተጠሪ በፊት ተከፋይ እንዲሆን በማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 በተናጠል የሚያከናውነው የሀራጅ ሽያጭ፣ መንግስት ከከሰረው ሆላንድ ካር መኪና መገጣጠሚያ ድርጅት የሚጠይቀውን ትክክለኛ የግብር ዕዳ በተሟላ ሁኔታ ለማጣራትና ለመወሰን እንደዚሁም ከድርጅቱ ሰራተኞች ቀጥሎ ከተጠሪ በፊት መንግስት ያለውን የቀዳሚነት የግብር እዳ የመጠየቅ መብት የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በተናጥል የሚያከናውነው የሀራጅ ሽያጭ ለሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች እዳ መክፈያ ሊሆኑ የሚችሉ ያልተገጣጠሙ መኪናዎች እና ሌሎች ንብረቶች ባለበት ሁኔታ በመጠበቅ ሽጦ የሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎቹን ዕዳ ለመክፈል የማያስችል መሆኑን ተጠሪ በመያዣነት ያልያዛቸውን የከሰረው ሆላንድ ካር ንብረቶች ለማጓጓዝና ለማስቀመጥ ተጨማሪ ወጪ የሚጠይቅና የሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች መብትና ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

9. በአንጻሩ ተጠሪ በመያዣነት የያዘው የፋብሪካ ህንጻና ማሽነሪዎች ከሌሎች የከሰረው ሆላንድ ካር ንብረት ጋር ተጣርተው እንዲሸጡ ቢደረግ አመልካች በመያዣነት ይዟቸው የነበሩት ንብረቶች ተሸጠው በሚገኘው ገንዘብ ላይ ያለውን የቀዳሚነት መብት የማያሳጣው መሆኑን ከንግድ ህጉ አንቀጽ 104 እና ሌሎች ተከታይ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሂደቱ ከንብረት ጠባቂና መርማሪ ዳኛ በላይ የሆኑ ጉዳዮች ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እየታዩ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለማድረግ የሚያስችል አማራጭ እንደሆነ ከንግድ ህጉ አንቀጽ 989 እና አንቀጽ 990 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የማጣራትና የሽያጭ ሂደቱ፣ ተጠሪ በመያዣነት የያዘው የፋብሪካ ህንጻና የመኪና መገጣጠሚያ ማሽነሪ በተናጠል ይሆን ከሌሎች የከሰረው የሆላንድ ካር ንብረቶች ጋር በአንድ ላይ የሚጣራበት የሚከናወነበትንና በመጀመሪያ ከተጠሪ በፊት የቀዳሚነት መብት ያላቸው የድርጅቱ ሰራተኞች ጥያቄና የመንግስት የግብር ዕዳ ተከፍለው የተጠሪ ቀዳሚነት መብት ተጠብቆ መያዣው ተሸጦ የተገኘው ገንዘብ እንዲከፈለው መደረጉ ከተጠሪ በፊት የቀዳሚነት መብት ያላቸውን ገንዘብ ጠያቂዎች የተጠሪንና የሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች መብትና ጥቅም የሚያስከብርበመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት አዋጅ ቁጥር 97/1990 በንግድ ህጉ አምስተኛ መጽሀፍ በኃላ የታወጀ ነው በሚል ምክንያት የዕግድ ትእዛዝ እንዲነሳ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በመያዣነት በያዛቸው የፋብሪካ ህንፃና የመኪና መገጣጠሚያ ማሽነሪዎች በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ለመሸጥና ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ የስር ፍ/ቤት የሰጠው የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳለትያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡ ንብረቶቹ እንዲከበሩየስር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ በመያዣው ላይ ያለው መብት እንዲከበር የከሰረው ሆላንድ ካር ሂሳብ ተጣርቶ ንብረቶቹ ተሸጠው በመያዣው ላይ ያለው የቀዳሚነት መብት እንዲከበርለንብረት ጠባቂ ለመርማሪ ዳኛና ስልጣን ላለው ፍ/ቤት በህግ አግባብ የማቅረብ መብቱን ይህ ውሳኔ የሚገድበው አይደለም ብለናል፡፡
4. ጉዳዩ የተጠሪ የመያዣያ መብት ያለበት በመሆኑ በተቀላጠፈ መንገድና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊፈጸም ይገባል ብለናል ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 106286

መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ቦሮ ትራቪል የግንባታ ሥራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ነገረ ፈጅ ም/ስ አስኪያጅ

ታከለ ንጉሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኤፍሬም ሽብሩ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የሥር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው ጉዳይ በመጀመሪያ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዱ በፊት በሽምግልና ዳኞች መታየት ነበረበት የሚለውን የአመልካች ክርክር ነጥብ ውድቅ በማድረግ ጉዳዩ በፍርድ ቤት እንዲታይ ብይን የመስጠታቸው አግባብነት አመልካች ከመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41(1) አንፃር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ለመመርመር ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ያቀረቡት ክስ ከማህበሩ መሥራች አባልነት ያለአግባብ መሰረዛቸው እና የቼክ ፈራሚነታቸው ያለአግባብ እንደተነቀሉ የሚገልጽ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች ጉዳይ ከአሁኑ በፊት በፍርድ ያለቀ ነው፤ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና ዳኞች መታየት አለበት የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው የሚል ክርክር ውድቅ ያደረገ ሲሆን፤ ጉዳዩ በመጀመሪያ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና ዳኞች መታየት አለበት የሚለውን የአመልካች ክርክር በመቀበል በማህበራቸው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 መሰረት በሽምግልና ዳኞች መታየት እንዳለበት ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራቀኙ በማከራከር የግራ ቀኙ መተዳደሪያ ደንብ ሽምግልናን እንደ አንድ አማራጭ ማስቀመጡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት እንዲታይ መስማማታቸውን አያሳይም በማለት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በማለት መወሰኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር ያደረጉ ሲሆን አመልካች በሰበር አቤቱታው የጠቀሳቸው አንኳር ነጥቦች፡- መተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 41 በአባላት መካከል የሚፈጠር አለመግባባት በእርቅ፣በሽምግልና እንዲታይ የተደነገገው በሥር ፍርድ ቤቶች መታለፉ አለአግባብ መሆኑን፤የግራቀኙ ስምምነት ደግሞ ሕግ መሆኑን ለመግለጽ ውሳኔ እንዲሻር መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን የተጠሪ መልስ መሠረታዊ ይዘትም፡- በማህበሩ እና አባላት መካከል የሚነሳው ክርክር በሽምግልና እንደሚፈታ የተገለጸ ቢሆንም ብቸኛ አማራጭ አለመሆኑን፤ በክልሉ መንገዶች ባለሥልጣን የበኩሉን ጥረት ማድረጉን፤አዋጅ ቁጥር 147/91 ተፈፃሚነት እንደሌለው፤ ማህበሩም ሕልውና እንደሌለው ጉዳዩም በሽምግልና እንደሚይፈታ በመግለጽ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸው ተገቢ መሆኑን ተከራክሯል። አመልካች የመልስ መልስ ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸው የሚጠናከር ነው።

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር፣ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ፤አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከሥር የክርክር ሂደት መረዳት እንደተቻለው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የግራ ቀኙ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና ዳኞች መታየት ነበረበት በሚል ነው። ተጠሪ በበኩሉ ጉዳዩ በቀጥታ ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ የሚከለክል ስምምነት የሌለ መሆኑን ነው። የግራ ቀኙ መሰረታዊ የክርክር ነጥብ እልባት ለመስጠት የቦሮ ትራቭል የግንባታ ሥራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መተዳደርያ ደንብ አግባብነት ያለው ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል። የአመልካች ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 በአባልነትና በማህበሩ መካከል የሚነሱ ክርክሮች የሚፈቱበትን አግባብ ደንግጓአል። በዚህ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 1 ሥር እንደተመለከተው አከራካሪ ጉዳዮች የሚነሱ ከሆነ የድርጅቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ በሚያመቻቸው በአስታራቂ ሽማግሌዎች በዕርቅ እንዲያልቅ እንደሚደረግ ተመልክቷል። ክርክሩ በዕርቅ ያላለቀ እንደሆነ ጉዳዩ በሽምግልና ዳኞች ይታያል። ጉዳዩ በሽምግልና ዳኞች የማይፈታ ከሆነ በአገሪቱ በህግአግባብ እንደሚታይ በዚህ ደንብ አንቀጽ 42.2 ሥር በግልጽ ተጠቅሷል።

ከአመልካች የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 እና 42 ለመረዳት እንደተቻለው በአባልነትና በማህበሩ መካከል የሚነሱ ክርክሮች ለመፍታት ሦስት መንገዶች የሚከተል መሆኑን ነው። የመጀመሪያው እርቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሽምግልና ዳኞች አማካይነት ነው። ሦስተኛ እና የመጨረሻው አማራጭ በአገሪቱ በህግ አግባብ የሚል ሲሆን ይህ አማራጭ በቀጥታ ፍርድ ቤት የሚል ግልጽ መልስ የሚሰጥ ባይሆንም በሌሎች ሕጎች ጉዳዩ ለሌላ ተቋም ካልተሰጠ በስተቀር የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ከመሆኑ አኳያ ፍርድ ቤት የሚል ትርጉም ሊሰጠው የሚችል ስለመሆኑ ከአጠቃላይ የድንጋጌው መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው። ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ተጠሪ ጉዳዩን በቀጥታ ፍርድ ቤት ማቅረቡ ደንቡን የሚቃረን አለመሆኑን እየተከራከረ ነው። አመልካች በአንፃሩ ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና መታየት ነበረበት የሚል ክርክር በአፅንኦት አቅርበዋል። በመሰረቱ ተዋዋዮች ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና ለማየት ከስምምነት ላይ ሊደርሱ ይችላሉ የተዋዋይ ወገኖች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስምምነት በሕጉ አግባብ የተቋቋመ ከሆነ አስገዳጅ ስለመሆኑ በፍ/ህ/ቁ 1731(1) ተመልክቷል። በተዋዋይ ወገኖች የሚነሳው የውል አተረጓጎም ክርክርም የውሉ መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ መሰረት በማድረግ መታየት እንዳለበት በፍ/ህ/ቁ 1732፣ 1736 እና 1738 በግልጽ ተደንግጓል ። በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 በማሕበሩ አባላት እና ድርጀቱ ሊነሱ የሚችሉ ክርክሮች በመጀመሪ በዕርቅ መፈታት እንዳለባቸው የተደነገገ ሲሆን የዕርቅ ስምምነቱ ውጤት ካላመጣ ደግሞ የሽምግልና ዳኞች እንደሚሰየሙ ተመልክቷል ። እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ውጤት ካላስገኙ የመጨረሻው አማራጭ ጉዳዩ በአገሪቱ ሕግ የሚፈታ መሆኑ ተገልጻዋል።

የአሁኑ ተጠሪ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ጉዳዩ በዕርቅ ለመጨረስ ጥረት ስለማድረጋቸው የቀረበ ክርክር የለም። በእርግጥ የቤንሻንጉል ጉምዝ መንገዶች ባለሥልጣን በፃፈው ደብዳቤ ጉዳዩ በሕግ አግባብ እንዲታይ መግለጽን ተጠሪ ቢከራከሩም የተጠሪ ክርክሩ በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 መሰረት በዕርቅ ለመጨረስ የተደረገ ጥረት ስለመኖሩ የሚያሳይ አይደለም ። ተጠሪ ሌላ ያነሱት ነጥብ ማህበሩ ሕጋዊ ሰውነቱን አጥቷል የሚል ቢሆንም አመልካች ወክለው እየተከራከሩ ያሉት ምክትል ስራ አስኪያጅ እና ባለአክሲዮን መሆናቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም ። የማህበሩ ሕልውና በሕግ አግባብ ስለመክሰሙም በሕግ የተደገፈ ክርክር አልቀረበም።ተጠሪ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 የተዘረጋውን ሥርዓት በአግባቡ ሳይጠቀሙ እና አለመግባባቱን ለመፍታት ጥረት ሳያደርጉ ጉዳዩን በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት መውሰዳቸው ከላይ የተመለከተው መተዳደሪያ ደንብ ያላገናዘበ ነው።

የሥር ፍርድ ቤት ሽምግልናን እንደ አማራጭ የተወሰደ ነው በማለት በውሳኔው የገለጸ ቢሆንም የአመልካች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 እንደተመለከትነው በድርጅቱ እና በማህበሩ የሚከሰት አለመግባባት የሚፈታበት ሥርዓት ቅደም ተከተል ማስቀመጡን መገንዘብ ይቻላል። ተጠሪ በደንቡ የተዘረጋውን የክርክር አፈታት ሥርዓት ሳይከተል በቀጥታ በፍርድ ቤት ክስ ማቅረቡ የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ያላገናዘበ ነው። በመሆኑም የግራቀኙ ክርክር በመጀመሪያ በእርቅ፣በሽምግልና ሳይታይ በቀጥታ በፍርድ ቤት መታየት ይችላል ተብሎ በሥር ጠቅላይ ፍርድ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መወሰኑ እና በሰበር ሳይታረም መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል።

በማጠቃለል የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ጉዳዩን በዕርቅ እና በሽምግልና ሳይታይ በቀጥታ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል በማለት የሰጡት ብይን የአመልካች መተዳደርያ ደንብ አንቀጽ 41 እና 42 ያስቀመጣቸው የክርክር አፈታት ቅደም ተከተል ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 05440 በ 07-11-2006 ዓ.ም የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 08575 በ 21-09-2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በመሻር የሰጠው ፍርድ፣የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 05591 07/02/2007ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) ተሽሯል። ይፃፍ።
2. የአሶሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 08575 በ 21/09/2006 የሰጠው ብይን ጸንቷል። ይፃፍ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው ጉዳይ በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 መሰረት በተዘረጋው ሥርዓት በዕርቅ፤ሽምግልና ሳይታይ በቀጥታ ፍርድ ቤት መቅረብ አይችልም በማለት ወስነናል፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- በዚህ ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
- መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ቅጽ-18

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ችሎት ውሳኔዎች





ቅጽ 18

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴሬሽን ጠቅላይ

ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች

ቅጽ-18

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ጥር 13, 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



<u>የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

የሰበር ውሳኔዎችን ለሕዝብ ለማዳረስ እየተደረገ ያለው ጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች እየታዩበት ነው። ከሰበር ውሳኔዎች አስገዳጅነት አንጻር ውሳኔዎቹ እንደተሰጡ ወዲያውኑ ለሥር ፍ/ቤቶች ሆነ ለሌሎች አካላት መድረስ ይኖርባቸዋል። አትሞ ማሰራጨት የቱንም ያህል ለማፋጠን ቢሞክር ጊዜ መውሰዱ አይቀርም ።በአሁኑ ጊዜ የኢንተርኔት አገልግሎት እስከ ወረዳ ድረስም ስለደረሰ ውሳኔዎቹ በተሰጡ ጥቂት ቀናት ውስጥ በፍ/ቤታችን ድረ ገጽ በመጫን ተደራሽ ለማድረግ እየሰራን ነው፤የዚህን እትም ውሳኔዎችና የበፊቶቹንም በድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል። እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ አገልግሎታችንን ለማሻሻል የሚረዱ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ ነን።

ተገኔ ጌታነህ

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ /ቅፅ 18/

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አሠሪና ሠራተኛ				1
1.	አንድ ሰራተኛ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ካለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረቱ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ አሰሪው በዚሁ ምክንያት ሰራተኛውን ካለማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበተው ስለመሆኑ በደብዳቤ ሳይገልፅ መቅረቱ የሥራ ውሉ በሕግ አግባብ አልተቋረጠም ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1) (ለ)	104862	አቶ መልካሙ አረጋ እና ተስፋዮ ለገሰ ጠቅላላ ስራ ተቋረጭ	መጋቢት 3 ቀን 2007ዓ.ም	2
2.	አንድ አሠሪ ሠራተኛው ህጋዊ የመብት ጥያቄ በማቅረቡ ምክንያት የስራ ውሉን ማቋረጥ ህገወጥ ተግባር ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 26(2)(ሐ)	105921	ፒተርድስ ፕሮዳክተስ ማኑፋክቸሪንግ (አ.ማ) እና እነ ይፍቱ ስራ ነጋሽ (ሁለት ሰዎች)	መጋቢት 14 ቀን 2007ዓ.ም	6
3.	የአንድ ድርጅት ሠራተኛ በሠራው ጥፋት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉ ቢቋረጥም ያልወሰደው የዓመት እረፍት ካለ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈል የሚገባው ስለመሆኑና የፕሮቪደንት ፈንድም በከፈለው ልክ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ፣	102994	ዳሽን ባንክ እና እነ ተፈሪ አሳልፈው /ሦስት ሰዎች/	ሚያዚያ 30 ቀን 2007	10

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
4.	የአንድ ድርጅት ሠራተኛ ለአሰሪው የስራ መልቀቂያ አስገብቶ የስራ መልቀቂያው በአሰሪው ምክንያት በወቅቱ ሣይሠጠው ቆይቶ ሰራተኛው የስራ ግዴታውን እየተወጣና የስራ ግንኙነታቸው በተግባር ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ ከረጅም ጊዜ በኋላ አሰሪው ሰራተኛው ቀደም ብሎ ያስገባውን የስራ መልቀቂያ መሰረት በማድረግ የስራ ውሉን ቢያቋርጥ የስራ ውሉ የተቋረጠው በህገወጥ መንገድ ነው ሊባል የሚችል ስለመሆኑ፣ አዋጁ ቁ.377/96 አንቀፅ 4/1/፣23፣26፣30፣31፣33፣39፣40/2/፣43/4/ሀ/፣ 35/1/ለ/፣38	104465	ወ/ሪት ሽዊት ሀይሉ እና መከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ	መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም	16
5.	አንድ ሠራተኛ በአሰሪው የሚሰጠውን ትእዛዝ የመፈጸም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑና ሳይፈጽም ቢቀር ካለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብት በቂ ምክንያት ስለመሆኑ አዋጅ 377/1996 አንቀፅ 13/1/2/ እና /7/ እና 27/1/ ሸ/	108789	ሴንቸሪ ጀኔራል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ገስጥ ንጉሴ	ሚያዚያ 10/ ቀን 2007 ዓ.ም	20
6.	በየመስሪያ ቤቱ የሚቋቋሙ የዲሲፕሊን ኮሚቴዎች በህግ አግባብ የሚቋቋሙና የሰራተኛው ጥቅም ያለአግባብ እንዳይጎዳ ተገቢው መጣራት ተደርጎ እርምጃ እንዲወሰድ እገዛ የሚያደርጉ ናቸው ተብሎ የሚታመን ስለሆነ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ ዋጋ ሊያጣ የሚገባው ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ህጋዊ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 1/ሸ/ እና አንቀፅ 12/2/(7)	105834	የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት ኮንፌደሬሽን እና ወ/ሮ እመቤት ኤርሚያስ	ሚያዚያ 28 ቀን 2007ዓ.ም	24

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
7.	አንድ አሰሪ ሰራተኛው ያቀረበውን የስራ መልቀቂያ ጥያቄ ተቀብሎ ሰራተኛውን ካሰናበተ በኋላ የተለያዩ የክፍያ ጥያቄዎች በሰራተኛው ሲቀርብለት ወደኋላ ተመልሶ የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያት አግኝቻለሁ በማለት ሌላ ደብዳቤ በመጻፍ ለሰራተኛው የሚገባውን ክፍያ አልፈፅምም ማለት አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1/ለ/፣25	106610	አቶ ካብራክ ተኮላ እና የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጂስቲክስ	ግንቦት 14 ቀን 2007 ዓ.ም	31
8.	በአንድ አሰሪ ድርጅት መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ መሠረት በአንድ የሥራ መደብ ላይ የውጪ ሰው የሚቀጠረው መጀመሪያ ለቦታው የሚመጥን የውስጥ ሠራተኛ ካለ ለውስጥ ሠራተኛው እድል ከሰጠ ለኋላ ከሆነ አሠሪው ድርጅት ይኽን ደንብና መመሪያ ተላልፎ የውስጥ ዕድገት ማስታወቂያ ሣያወጣና ለሠራተኞች ዕድል ሳይሰጥ የውጪ ቅጥር ቢፈጸም ድርጊቱ ህገወጥ ተግባር ስለመሆኑና ቅጥሩ ሊሠረዝ የሚገባው ስለመሆኑ፣	107002	ሲስተር ትዕግስት ፈቃድ እና የኤድስ መከላከያ ማህበራዊ አገልግሎት ድርጅት	ግንቦት 14 ቀን 2007 ዓ.ም	35
9.	አንድ በሾፌርነት የተቀጠረ ሠራተኛ አሰሪው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ጥንቃቄ ማድረግ ከሚገባው ነገር አንዱ መኪናውን የሚያሽከረክርበት አግባብ ከአካባቢው አየር ሁኔታና ከመልከዓ ምድሩ ጋር ባገናዘበ መልኩ መሆን ያለበት ስለመሆኑና ይህንን ሳያደርግ ቀርቶ አደጋና ጉዳት ቢደርስ ከባድ ቸልተኝነት እንዳደረሰ ተቆጥሮ የስራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13/3/፣27/1/ሸ/	111839	ፒ ኤስ አይ ኢትዮጵያ እና አቶ እሸቱ ካሣ	ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም	41

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
10.	የቅርብ አለቃውን ሰብአዊ ክብርና ሞራል የሚነካ የስድብና ማዋረድ የፈጸመ እና በስራ ቦታ የጠብ አጫሪነትን የፈጠረ ሰራተኛ የሥራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ አዋጅ 377/96 አንቀፅ 32/1/ሀ አዋጅ 377/96 አንቀፅ 13/2/ እና 27	110615	ኃብተሚካኤል ኃ/የተ/የግል/ማሕበር እና አቶ ታመነ ታደሰ	ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም	45
11.	አንድ ሠራተኛ መብትና ጥቅሙን ሳይነካ ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ወይም የስራ መደብ በማዛወር ማሠራት የአሰሪው አስተዳደራዊ ሥልጣን ነው ሲባል ዝውውሩ ያለህጋዊ ምክንያትና በህብረት ስምምነቱ ከሠፈረው አሰራር ውጪ ይከናወናል ተብሎ ሊተረጎም የማይገባው ስለመሆኑ፣	105997	ወ/ሪት ሉሊት አያሌው እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሚያዚያ 26 ቀን 2007 ዓ.ም	50
12.	ሰራተኛው በስራ ላይ በደረሰበት የሞት አደጋ ምክንያት የሰራተኛው ባለቤትና ሌሎች ጥገኞች የሚያቀርቡት የካሣ ክፍያ ጥያቄ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ 1	108785	ዩሴፍ ተክሌ ህንፃ ሥራ ተቋራጭ እና ወ/ሮ ወርቅነሽ ጌታቸው በራሳቸው እና ሞግዚት በሆኑላቸው /እነ ሕፃን ረዲኤት/	ሐምሌ 21 ቀን 2007 ዓ.ም	54
13.	አንድ ሰራተኛ በስራ መዘርዝሩ በግልጽ የተሰጠውን /የተቀመጠለትን/ ግዴታዎቹን አለመወጣቱ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ፡-	108933	ሠላም ቦሌ ሸማቾች ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር እና	ሐምሌ 30 ቀን 2007ዓ.ም	56

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13(2) እና (7)		አቶ እሸቱ አደፍርስ		
14.	አንድ ሰራተኛ ለአሠሪው በሥራ ክርክር ምክንያት ያወጣውን ወጭና ኪሳራ የመክፈል ግዴታ የሚጣልበት በክርክሩ ተረች በመሆኑ ምክንያት ብቻ ሳይሆን ሠራተኛው በአሠሪው ላይ ያቀረበው ክስ ሀሰተኛና በተጭበረበረ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ስለመሆኑ የፍትሐ ብሔር ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 463 ፣465 (1) አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 161	109055	አቶ ጌትነት ከበደ እና ሃያት ሜድካል ከሌጅ	ሐምሌ 29 ቀን 2007 ዓ.ም.	60
15.	አንድ የመንግስት ሠራተኛ በአሠሪው የመንግስት መ/ቤት ጥፋት በሆነ ምክንያት የስራ ውሉ ተቋርጦ ቆይቶ በኋላ በፍርድ ሠራተኛው ወደ ስራው ሲመለስ ውሉ ተቋርጦ በቆየበት ጊዜ ያለው ደሞዝ ጭምር ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ፣ የተሻሻለው የአ/ብ/ክ/መ/የመግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 አንቀጽ 81/2/፣87/1	104351	ወ/ት ክምክም እማኛው እና የደቡብ አቸፈር ወረዳ ሲቪልሰርቪስ ጽ/ቤት	ሠኔ 9 ቀን 2007 ዓ.ም	64
የፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት					**69**
16.	አንድን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከት ፍርድ ቤት በቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ አግባብነት ያላቸው ምስክሮች ሳይሰሙ ወይም አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ሳይቀርቡ በመቃወሚያው ላይ ውሳኔ መስጠት የማይቻል በሚሆን ጊዜ ፍ/ቤቱ እነዚህ ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት ትእዛዝ መስጠት የሚችል ስለመሆኑ፡- የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(1) እና 245(1)	105869	አቶ ደብሬ ቡልቲ እና ዳንሹቱ ዋጋሪ	መጋቢት 15 ቀን 2007ዓ.ም	70

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
17.	ለክርክሩ መነሻ የሆኑ እና በተከሳሽ እጅ የሚገኙ ንብረቶች እንዳይሸጡ፣ እንዳይለወጡና በማንኛውም መንገድ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ በታገዱበት ሁኔታና ተከሳሽ በንብረቶች ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተከሳሽን ተጨማሪ ዋስ አቅርብ ማለት አግባብነት የሌለውና የስነ ስርዓት ህጉን ዓላማ ያላገናዘበ ስለመሆኑ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 151	99642	ቴራ ኮንስትራክሽን እና አቶ ሚካኤል ነገሠ	ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም	75
18.	አንድ ተከራካሪ ወገን ሌላ ተከራካሪ ግለሰብ ወደ ክርክር እንዲገባ በህጉ አግባብ መጠየቁ ተገቢ ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት ከግለሰቡ መብት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት ህጉ ዓላማና ግብ አንፃር ጭምር ስለመሆኑ፣	96943	እነ አቶ ተስፋዬ ወርቁ /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ የምስራች ገ/መስቀል /አራት ሰዎች/	ሚያዚያ 16 ቀን 2007 ዓ.ም	78
19.	በመርህ ደረጃ በህግ አግባብ የተቋቋመ ፍ/ቤት የሠጠው ውሳኔ በህግ አግባብ በተቋቋመ የበላይ ፍ/ቤት በህጉ በተዘረጋው ስርዓት እስካልተለወጠ ድረስ የማይፈጸምበት ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378፣372፣392	101345	አቶ ፀጋዬ ብርሃኑ እና ወ/ሮ መሠረት ተገኘ	መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም	83
20.	ለአንድ የመንግስት ተቋም የተላከ መጥሪያ መጥሪያው በአግባቡ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ካልደረሰ በስተቀር መጥሪያው ለተቋሙ መዝገብ ቤት ገቢ በመሆኑ ብቻ መጥሪያው እንደደረሠ ተቆጥሮ ክርክሩ ተቋሙ በሌለበት ሊታይ የማይገባ ስለመሆኑ፣	100673	አቶ አዳነ መንገሻ እና የጋሪ ማዘጋጃ ቤት	ሠኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም	88

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍ/ሥ/ህ/ቁ 70/ሀ/፣78/2/፣96፣102				
21.	በሌለሁበት የተሰጠ ውሳኔ /ትእዛዝ/ ይነሳልኝ በማለት የቀረበ አቤቱታው ውሳኔው/ትእዛዙ ከተሰጠ በ30 ቀን ውስጥ በቃለ መሀላ ለሬጅስትራር የቀረበ ሆኖ እያለ አቤቱታው ለችሎት የቀረበው ከ30 ቀን በኋላ መሆኑ በህግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ /ይርጋ/ አላሟላም ሊያስብል የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78/1/	101478	የረር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ተስፋዬ ባልቻ	ሰኔ 29 ቀን 2007ዓ.ም	92
22.	በወጪና ኪሳራ ጉዳይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 466	98593	አቶ ክንፈ ወልደሰንበት እና እነ አቶ ስለሺ በቀለ (ሰበት ሰዎች)	ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም	96
23.	በካሳ ጉዳይ ካሳ የጠየቀው ወገን ገንዘቡን በማስረጃ ባላረጋገጠበት ሁኔታ ሌላኛው ተከሳሽ ወገን ዝም በማለቱ ብቻ እንዳመነ ተቆጥሮ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢ ያለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 83	111599	እነ አቶ መላኩ ካሳዬ እና ወ/ሮ ሱሲ አሲ	ቀን 29/11/2007 ዓ.ም	100
24.	የአንድ ክስ ዝርዝር ይዘቱ ሳይታይ እርስቱ ብቻ ታይቶ የፍርድ ቤት የሥረ ነገር ዳኝነት የሚወሰንበት የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ ስርዓቱን ጠብቆ አቤቱታ እስከቀረበበት ድረስ ሊፀና የማይገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(ለ)	102543	ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 አስተዳደር ፅ/ቤት እና ወ/ሮ አሰለፈች ወልዴ	ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም.	104

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
25.	የፍትሐ ብሔር ክርክር በሂደት ላይ እያለ ከሰሽ ወይም ተከሳሽ በሞት ሲለይ የክርክሩ አካሄድ በምን አኳኃን መመራት እንዳለበት ልንከተለው ስለሚገቡ ሁኔታዎች የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 48፣49 እና 50	105626	አቶ ለገሰ ደበባ ተተኪ ሚስት ወ/ሮ ክቡ ዳሜ እና ኢትዮጵያ ሜዲዬስ ኃለ/የተ/የግ/ማህበር	ሐምሌ 28 ቀን 2007ዓ/ም	108
ቤተሰብ					**112**
26.	ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ለሚኖሩ ሰዎች የሚፈለገው ማስረጃ ወንዱና ሴትየዋ የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሠቡ እንደተጋቢ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው የሚገምቷቸው መሆን ያለባቸው ስለመሆኑ፣ በአንድ ወንድና ሴት መካከል ለተወሰነ ጊዜ የፍቅር ግንኙነት መኖሩ ብቻ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ናቸው ሊያስብል የማይችል ስለመሆኑ ፣ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 97፣98፣99 እና 106/2/	96853	አቶ ጆቫኒ ላሮዛ እና ወ/ሮ አዳነች ተስፋዬ	መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም	113
27.	አንድ ወንድና ሴት ሲጋቡ በጋብቻ ውላቸው ንብረትን በተመለከተ ካደረጉት ስምምነት ላይ “ከወለደች የግል የለባትም ” ፣ “ ሀብትሽ ሀብቴ ነው “ ተብሎ የተፈጸመው የውል ሀረግ ካለና ልጅ ከወለዱ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን የግል ንብረት የጋራ ለማድረግ እንደተስማሙ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣	98029	ወ/ሮ ልዩሴት ሥዩም እና አቶ ሸዋፈራ ንጉሴ	ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ.ም	121
28.	በጋብቻ ፍቺ ጊዜ ለፍችው ምንክያት የሆነው በደል ተፈጽሞባታል ተብሎ ለአንደኛው ወገን ካሣ የሚከፈለው እንዲከፍለው ዳኝነት ሲጠይቅና	101552	ወ/ሮ ትርንጎ መስፍን እና	ሠኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም	126

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ካሣውም የሚወሰነው ለፍትህ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ስለመሆኑ፣ የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 81/2/፣84		አቶ መሉጌታ መኳንንት		
29.	አንድ ልጅ ሲወለድ ከልጇ እናት ጋር በጋብቻ ተሳስሮ የነበረው ሠው በህጉ ግምት መሠረት የልጁ አባት ስለመሆኑና ይህን የህጉን ግምት ማስተባበል የሚችለው እሡ ወይም በህግ የተፈቀደላቸው ሰዎች አባት አለመሆኑ እንዲወሰን የመካድ ክስ በማቅረብ ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 682፣741፣ የፌደራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 167	99954	እነ ህጻን ዘውዴ ሚካኤል እና አቶ ገዛኸኝ ወ/ሚካኤል	ሠኔ 5 ቀን 2007 ዓ.ም	130
30.	አንድ ሞግዚት አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ በማስተዳደር ስልጣኑ ክርክር የሚደረግበት ጥቅም ከ300 ብር ያነሰ ካልሆነ በቀር ያለ ቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ፈቃድ ምንም ግልግል መፈጸም የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 301	100426	እነ ዶ/ር ጥላሁን ኪሮስ /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ህጻን ሰናይ የማነኪሮስ /2 ሰዎች/	ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም	135
31.	ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ባንደኛው ተጋቢ ተገዝቶ ነገር ግን ስመሀብቱ ከ3ኛ ወገን ሻጭ ሳይዛወር የቀረ መሆኑ ንብረቱ የተጋቢዎች የጋራ ሀብትነው ከመባል የሚያስቀረው ስላልመሆኑ፣	94811	አቶ ታረቀኝ ጥሩነህ እና ወ/ሮ ሰናይት ታደሰ	ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም.	141
32.	ባል እና ሚስቶች ሲጋቡ ለጎጆ መውጫ ተብሎ በቤተሰባቸው ፍቃድ የተሰጣቸው መሬት ሲገለገሉበት የቆዩ በሆነ ጊዜ ንብረቱ የጋራ ሀብት ሀኖ በፍቺ ጊዜ እኩል ሊካፈሉት የሚገባ ስለመሆኑ፣ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የመሬት አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀጽ 5/5/,2/7/	107840	ወ/ሮ ዘምዘም ሸረፋ እና እነ ወ/ሮ አታላ ሐሰን	ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም	145

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
33.	አንድ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ስምምነት ፈርሶአል ሊባል የሚችለው የፍቺ ስምምነቱ ተደርጎአል በተባለበት ቀን ሳይሆን የፍቺ ስምምነቱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ባገኘበት እና በጸደቀበት ጊዜ ስለመሆኑ፡- የተሸሻለው የፌድራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 76(1)	109731	ወ/ሮ ሃና አሰፋ እና አቶ ክፍይበሉ አሰፋ (ሁለት ሰዎች)	ሐምሌ 1 ቀን 2007ዓ.ም	148
ውርስ					**153**
34.	በአንድ የጋራ የሆነ የውርስ ንብረት ላይ አንደኛው ወራሽ ብቻውን ያወጣው ወጪ ካለ ወጪውን ሁሉም ወራሾች ሊጋሩት የሚገባ ስለመሆኑ፣ የጋራ የሆነ የውርስ ንብረትን በተመለከተ ወራሾች የሚስማሙ ከሆነ ክፍያው በስምምነታቸው መሠረት የሚፈጸም ስለመሆኑ፣ ወራሾች ንብረቱን ስለሚካፈሉበት ሁኔታ ካልተስማሙና ንብረቱ በአይነት ለወራሾች ለማካፈል የማይቻል ከሆነ ንብረቱ በሀራጅ ተሸጦ ሊከፋፈሉ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ 1079/1/፣ 1086/1/፣1092፣1093	102932	እነ አቶ አፈወርቅ ደረጫ /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ሠራዊት ደረጫ	ሠኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም	154
35.	የውርስ የይዞታ መሬትን እኩል መብት ካላቸው ወራሾች መካከል አንደኛው አስቀድሞ ይዞ ወደ ልጁ ስም ማዞር የወራሾችን መብት መንጠቅ ስለመሆኑ፣ የኦሮሚያ የመሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 ደንብ ቁጥር 151/2005	108106	አቶ አዱኛ ጉታ እና እነ ወ/ሮ በሻዱ ጉደታ	መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ.ም	159

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
36.	ፍ/ቤቶች የወራሽነት ማስረጃ ወይም የምስክር ወረቀት ብቻ አንዲሰጡ ማመልከቻ ሲቀርብላቸው ውርስ እንዲጣራ የሚሰጡት ትእዛዝ የማይገባና አላስፈላጊ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሕ/ 996/1/	110022	አ/ቶ ትሻገር ምህረቱ እና የለም	ሐምሌ 29 ቀን 2007 ዓ.ም	163
37.	በስጦታ ሰጪ ላይ በተደረገ የመንፈስ መጫን የተደረገ የስጦታ ውል ይፍረስልን ጥያቄ መቅረብ ያለበት ስጦታው በተደረገ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ አጠቃላይ የሥጦታ ውልን በመቃወም የይፍረስልን ጥያቄ መቅረብ ያለበት በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ.2441፣በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1845	105652	እነ ወ/ሮ አሰፉ ዘለቀ (ሰባት ሰዎች) እና አቶ ዳዊት በርሄ	30/11/2007ዓ.ም	166
38.	ለክርክር ምክንያት በሆነው መሬት ወራሽ መሆኑን በማስረጃ ያረጋገጠ ሰው ከአውራሹ ተነጥሎ ለጊዜው ውጭ ሀገር ሄዶ መመለሱ በሕጉ “ለቤተሰብ አባል” የተቀመጠውን ትርጉም አላሟላም በሚል በቤተሰብ አባልነት መሬቱን ሊወርስ አይገባም ማለት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የአ/ብ/ክ/መ አዋጅ ቁጥር 133/98 ፣ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/7/ሀ/	109697	ዘመ· አስፋው እና መሀመድ አስፋው	ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም	170

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ውል					**173**
39.	አንድ ሥራ ተቋራጭ በሠራው ህንጻ ላይ የተከሠተ እርግጠኛ የአሰራር ጉድለት በሌለበት ሁኔታ ወደፊት የሚታይና የሚከሰት የአሰራር ጉድለት ሊኖር ይችላል በሚል ምክንያት ሥራ ተቋራጮች ለሰሩት ሥራ የመጨረሻ ክፍያ የማግኘት መብት መከላከል አግባብነት የሌለው ስለመሆኑና የህንጻ ተቋራጩን በፍትሐብሄር ጉዳይ ማንም ሰው ኃላፊ ነው ተብሎ ያለመገመት /presumption of non liablity/ መሠረታዊ መርህ ስለመሆኑ፣ የፍትሐብሔር ህግቁጥር 3268፣3282/1/ የመሠረት ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በ1996 ዓ.ም አሻሽሎ ያወጣውን የመንግስት ግንባታ ስለ አፈጻጸም መመሪያ አንቀፅ 8፣	101378	የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና ናሰው ኮንስትክሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር	ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም	174
40.	ተወካይ የጥቅም ግጭት ባለበት አኳኋኑን የፈጸመውን ተግባር ለማፍረስ ወካዩ ይኸው ድርጊት መፈጸሙን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ሕ/ቁ 2187	82725	እነ አቶ ከበደ ተሰማ /ሁለት ሰዎች/ እና እነ ወ/ሮ ፀሀይነሽ ገ/አምላክ /ሁለት ሰዎች/	ሠኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም	181

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
41.	አንድ የሽያጭ ውል በፍርድ ፈራሽ ነው ተብሎ ተዋዋዮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ከተወሰነ ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰው ንብረቱን ለውጦ ወይም በዚህ ላይ ወጪ አውጥቶ ከሆነ ከዚህ መለዋወጥ ወይም ወጪ የተነሳ ያለውን መብት በተመለከተ አለአግባብ መበልጸግ በሚለው የህጉ ክፍል መሠረት የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ 1818፣የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 392/1/	99634	አቶ ተስፋአለም አረፋ እና እነ ወ/ሮ አማረች ጉደታ /ሁለት ሰዎች/	ሠኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም	185
42.	ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚፈጠርን አለመግባባት በዘመድ ዳኛ የመጨረስ ስምምነት ማድረግ የሚችሉ ስለመሆኑ፡- የዘመድ ዳኛ አለመግባባቶችን አይቶ የመወሰን ስልጣን የሚመነጨው ተገልጋዮቹ በግልፅ እና በማያሻማ ሁኔታ በሚሰጡት ሥምምነት ላይ ብቻ ስለመሆኑ፡- የፍ/ሕ/ቁ 3325፣3326-3346	97021	መርዕድ ታደሰ ገ/መደህን ህንፃ ተቋራጭ እና አክስፎርድ አመልጌት ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ሐምሌ 28 ቀን 2007ዓ.ም	190
43.	የማማከር የስራ ውል ልዩ ፎርም የሚያስፈልገው ሥለመሆኑ፡- የፍ/ሕ/ቁ 1719፣2612(1)፣1882	103541	ቢውቲ ግሪን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግ/ማህበር እና ቪክስ ሰመር ፍላወር	ሐምሌ 3 ቀን 2007ዓ.ም	196
44.	ባዶ መሬትን ለማስተላለፍ የሚደረግ የሽያጭ ውል /የመሬት ግብይት ውል/ ፍሬ ነገሩ ሕገወጥ ሥለመሆኑና እና የዚህን አይነት ውል ከጅምሩ እንደሌለ ወይም እንዳልተደረገ የሚቆጠር ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ህገመንግስት አንቀፅ 40(3) የፍ/ሕ/ቁ.1716(1)	100671	I አለቃ ጌትነት ርቆ እና ወ/ሮ ጀሚላ አሊ	ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም	200

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
45.	በተዋዋይ ወገኖች የነበረን ውል አንዱ ለሌላኛው የውል መለዋወጥ ጥያቄውን ማቅረቡ በፍሬ ነገር ደረጃ ሳይረጋገጥ ውሉ ተራዝሟል ሊባል የማያስችል ስለመሆኑ፡- የውሉ አጻጻፍ ፎርም ወይም ዓይነት በሕግ የታዘዘ ሆኖ እንደ ትዕዛዙ ባይፈጸም ፈራሽነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ሕ/ቁጥርየፍ/ሕ/ቁ 1684፣1722፣1678(ሐ))	102778	ስማድል ኮሙኒኬሽን ተርሚናል ፋብሪካ ኃ.የተ.የግል ማህበር እና አቶ የሺጥላ ደሳለኝ	ሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም	204
ከውል ውጭ ኃላፊነት					**211**
46.	ለአንድ ጉዳት ወይም አደጋ መድረስ ጉዳት የደረሰበት ሰው አስተዋፅዖአ ካለው የጉዳት አድራሹ ኃላፊነት በከፊል ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ 2098/1/፣ 2097/2/፣2095	106450	የኢት/ኤሌ/ኃይል አገልግሎት ትመቂ ዲስትሪክት እና እነ በሳናናማ /ሦስት ሰዎች/	ሚያዚያ 15 ቀን 2007 ዓ.ም	212
47.	በአንድ ንዑስ የስራ ተቋራጭ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራ ሰራተኛ ለሚደርስበት ጉዳት ዋናው ሥራ ተቋራጭ ከውል ውጪ በኃላፊነት የሚጠየቅበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ./ቁ 2027-2136	106147	እሸት ኢንጂነሪንግህ /የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ፋንታዬ ቢያድግልኝ	ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም	216
48.	በአንድ ተቋም /መንግስታዊም ሆነ በባለስልጣን የተፈቀደለት/ ባለቤትነት የሚያካሄደው አደገኛ ተግባራት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ በሆነ ጊዜ ድርጅቱ ስራው በህግ የሚጠበቅበትን ደረጃ ያሟላ ስለመሆኑ እና በከፊልም ሆነ በሙሉ የተጎጂ ጥፋት መኖሩን እስካላስረዳ ድረስ ለደረሰው ጉዳት	101229	የኢት/ኤሌ/ኃ/ኮ እና አቶ ጣሂር ሣፋይ	ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም	219

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2069/1/ /2/ እና 2086/2/				
49.	በሌላ ሰው የስራ ድካም ወይም የሌላ ሰው ሃብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አለአግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠን ለባለሃብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው ይህ አድራጎት ባደረሰበት ጉዳት መጠን ኪሳራ መክፈል የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ.2162	90529	አቶ ኃ/እየሱስ መንግስቱ እና አማኑኤል ፀጋ የከተማ ሱቅ ቤቶች ልማት አክሲዮን ማህበር	ሐምሌ 2 ቀን 2007 ዓ.ም	224
ወንጀል					**232**
50.	አንድ ሰው የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመው ከሌላ ሰው ስምምነት በማድረግ ከሆነ እንደማክበጃ የሚወሰድ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 ከመውጣቱ በፊት በተፈፀመ ወንጀል ቅጣትን ለመወሰን ለተከሳሹ የሚጠቅመውን የቅጣት መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ ወ.ሕ/ቁ. 38(1) እና 84(1)(መ)	105289	አቶ ተፈሪ ጥላሁን እና የፌዴራል ዓቃቢ ህግ	መጋቢት 15 ቀን 2007ዓ.ም	233
51.	በተደጋጋሚ በተፈፀመ የወንጀል ድርጊት የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የመጨረሻው የወንጀል ድርጊት ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ የወንጀል ድርጊት ለረጅም ጊዜ ሲፈፀም የቆየ ከሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የወንጀል ድርጊቱ ካቆመበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ ወንጀል ህግ ቁጥር 219(2)	105406	አቶ ሃይሉ ወልደ መኮንን እና የፌዴራል ዓቃቢህግ	መጋቢት 14 ቀን 2007ዓ.ም	238

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
52.	በወንጀለኛ ህግ አንቀፅ 692(1) መሰረት የማታለል ተግባር ተፈፅሟል ለማለት መሟላት ስላለባቸው ሁኔታዎች አንድ ሰው ለወንጀል ድርጊት ኃላፊ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚገባው ወንጀሉ መሰራቱ ወይም መፈፀሙና ተሰራ ወይም ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 23(4)፣32፣40፣57 እና 58(1) የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ/. 141፣142 እና 149	104923	ወ/ሮ አበባ አረፋይኔ እና የትግራይ ክልል ዓቃቢ ህግ	መጋቢት 28 ቀን 2007ዓ.ም	243
53.	የተከሰሱ ሰዎች በህግ የተጠበቀላቸው የመሰማት መብት ቀሪ የሚሆነው ህጉ በዘረጋው ስርዓት ባለመብቱ ሳይጠቀምበት ሲቀር ብቻ ስለመሆኑ በህግ የተዘረጋ የክርክር አመራር ሳይሟላ የሚሰጥ ዳኝነት የግልፅነት መርህን የሚቃረንና በውጤቱም የተከራካሪ ወገንን መሰረታዊም ሆነ ሥነ-ሥርዓታዊ መብት የሚጎዳ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ስላለመሆኑ ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 20/4/፣9/4/፣13/1/2/ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች አለም አቀፍ ቃልኪዳን አንቀፅ 14/3/ለ/	95921	አቶ ብርሃኑ ኑርጋ እና የፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን	ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ.ም	249
54.	አንድ በወንጀል የተከሰሰ ተከሳሽ መጥሪያ ባስመዘገበው የመኖሪያ አድራሻ እንደደረሰው ሳይደረግ ወይም በዚሁ አድራሻ ተፈልጎ ሊገኝ አለመቻሉ ሳይረጋገጥ መጥሪያ በጋዜጣ እንዲወጣ አድርጎ ጉዳዩን በሌለበት ማየት የስነ ስርዓት ህጉን ያልተከተለ ስለመሆኑ፣ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረበባቸውን ምስክሮች የመስየት፣ ለመከላከል	104220	አቶ አታክልቲ አብርሃ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሁመራ ቅርንጫፍ	ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም	255

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰመላቸው የመጠየቅ መብት ያላቸው ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀፅ 20/4/ የወ/መ/ሥ/ሥነሥርዓት አንቀፅ 199 /ሀ/ ፣ 123፣202/3/፣				
55.	አንድ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠበት የህግ ድንጋጌ ስር ከተቀመጠው የቅጣት አማራጭ ውጪ የሚሰጠው የቅጣት ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ፣	97291	አቶ ጎሹ ዮሐንስ እና የፌ.የሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ	ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም	259
56.	በወንጀል ጉዳይ መነሻ ቅጣቱ በቅጣት መመሪያው ውስጥ በተለያዩ እርከኖች የሚወድቅ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ፍ/ቤቱ ዝቅተኛውን እርከን መምረጥ ያለበት ስለመሆኑ፣ የቅጣት መመሪያ 2/2006 አንቀጽ 19/11/	103775	ሀብቱ ቱሉ ዳዲ እና የፌደራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	ሰኔ 15 ቀን 2007ዓ.ም	267
57.	አንድ ሰው በሌለበት በወንጀል የተፈረደበት እንደሆነ ፍርድን ባወቀ በሠላሳ ቀናት ውሥጥ ፍርዱ ወድቅ እንዲደረግለት የማቅረብ መብቱን ሬጂስትራሉ አቤቱታውን አልቀበልም በማለት ሊከለክለው የማይችል ስለመሆኑ፡- የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.198፣200 እና 201 የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 20	98014	አቶ ያረጋል ተስፋ አባተ እና ቤንሻንጉል ጉምዝ ክ/ዓ/ህግ	ሐምሌ 14 ቀን 2007ዓ.ም	273

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
58.	አንድ የወንጀል ድርጊት ሊወድቅ የሚችልበት የህግ ድንጋጌ የተለያዩ የማክበጃ ነጥቦች በያዘ ጊዜ እና ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት አንቀጽ /ድንጋጌ/ ስር ያሉት ንዑስ ድንጋጌዎች የሚደነግጉት የቅጣት መጠን ተመሳሳይ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በዚያው የህግ ድንጋጌ ስር ድርጊቱ በይበልጥ ያሟላቸውን የማክበጃ ነጥቦች ወደ ያዘው ንዑስ ድንጋጌ መለወጥ የሚችሉ ስለመሆኑ፣	107219	አቶ አህመድ ሰይድ መሀመድ እና የፌደራል ዐ/ህግ	ሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም	280
59.	ደረጃ እና እርከን ላልወጣላቸው ወንጀሎች ቅጣት ስሌት ሲሠራ በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል ስር ያሉት አንቀጽ 106/1/ እና 109/1/ ድንጋጌዎች ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው ስለመሆኑ፣ አንድ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ የተባለ ሰው ወንጀሉን ስለመፈጸሙ ሙሉ በሙሉ ባላመነበት ሁኔታ በከፊል ማመኑ ብቻ ራሱን ችሎ እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ ሊወሰድለት የማይችል ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/ቁ 82/ ሠ	111006	ዲቦ ገልግሎ ቱራ እና የፌ/ን/ስ/ላ ዐ/ሕግ	ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም	286
60.	ፍርድ ቤቶች በተከሳሽ ላይ በዕምነት ክህደት ላይ በመመስረት የጥፋተኝነት ውሳኔን ከመወሰናቸው በፊት ቃሉ ከወንጀሉ ዝርዝር እና ከተከሰሰበት የህግ ድንጋጌዎች አነጋገር አንጻር ወንጀሉን ማድረጉን ሙሉ በሙሉ አምኗል የሚያስብል እና ቃሉ የእምነት ክህደትን ቃል የሚያቀቋቁም መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባቸው ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 132/1/ እና /3/	111742	እነ ኮሎኔል ተክሉ ፍሰሀ እና የኦሮሚያ ክልል ዐ/ሕግ	ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም	290

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
61.	ፍ/ቤቶች የተከሳሽን የመከላከል መብት የማክበርና የማስከበር ህገ-መንግስታዊ ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ህገ መንግስት አንቀፅ 13(1)፣13(2)፣20(4) የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 142(1) ዓለም አቀፍ የማህበራዊና ፖለቲካ መብቶች ሥምምነት አንቀፅ 14(3)(ረ)	100860	አቶ ፋንቱ ቡቼ እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ዓቃቤ ህግ	ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም	294
62.	የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196(1) ለሰበር ሥርዓትም ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑ	101056	አቶ አይሸሽም ገብሬ እና የፌዴራል የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	ሐምሌ 30 ቀን 2007ዓ.ም	299
63.	የወንጀለኛ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 75 (1)ዋስትናን በመፍቀድ በሚሰጥ ትዕዛዝ ላይ ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ እንዳያቀርብ ሕጉ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ክልክሏል በሚል አግባብ መተርጎም የሌለበት ስለመሆኑ ዋስትናን በመፍቀድ በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ከሳሽ /ዐቃቤ ህግ/ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ	110969	አቶ ሀብታሙ ደጁ እና የፌደራል ዐቃቢ ሕግ	ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም.	309
ጉሙሩክ/ታክስ					**312**
64.	ገቢውን በሚደብቅ ፣አሳንሶ በሚያሳውቅ፣ በሚያጭበረብር ወይም በማናቸውም መንገድ ግብር ሳይከፍል በሚቀር ግብር ከፋይ ላይ በተጨባጭ መረጃ በመደገፍ ሪፖርት ያቀረበ ሰው ከተደበቀው ግብር እስከ 20% ድረስ ግብሩ ሲሰበሰብ ማግኘት የሚገባው ስለመሆኑ፡- አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀፅ 84(1)	95157	የኢትዮ.ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን እና እነ አቶ ቅባቱ ወ/ሰንበት(ሦስት ሰዎች)	ሐምሌ 15 ቀን 2007ዓ.ም	313

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
65.	አንድ ተከሻሽ የጉሙሩክ አዋጅን በመተላለፍ በፈፀመው ድርጊት ጥፋቱ የመጨረሻ ውሳኔ አስከላገኘ ድረስ ሥራ ላይ ከነበረው የጉሙሩክ አዋጅ ይልቅ አዲሱ የጉሙሩክ አዋጅ ለተከሳሽ ቅጣትን የሚያቀል በሚሆን ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ የተሻለው ህግ ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ የኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀጽ 22 /2/ ፣የወ/ህ/ቁ/ 6 የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001፣ አዲሱ የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007	112032	የኑስ አህመድ /ሁለት ሰዎች/ እና የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት	ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ/ም	319
የዳኝነት ሥልጣን					325
66.	አንድ በፌደራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ድርጅት በክልል ቅርንጫፍ ከፍቶ የንግድ ሥራ መሰራቱና ቅርንጫፍ በክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ፅ/ቤት መመዝገቡ በፌደራል መንግስት የተቋቋመ የንግድ ድርጅት በመሆኑ ላይ የሚያሳድረው ለውጥ የሌለ ሥለመሆኑና ድርጅቱ ተካፋይ የሆነበትንም ክርክር በዳኝነት አይቶ ለመወሰን ሥልጣኑ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀፅ 6/2/ /3/ /4/ ፣ አንቀፅ 5/2/ አዋጅ ቁጥር 25/1988/6/ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀፅ 80/2/ /4/	97083	ገአትኮ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና የትግራይ ክልል መንገድ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ	ሚያዚያ 14 ቀን 2007	326

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
67.	የግለሰብ ዓለምአቀፍ ህግን / private international law/ የሚመለከቱ ጉዳች ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988 /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ 11/2/ /ሀ/	100290	ወ/ሮ መሠረት አለማየሁ እና እነ ወ/ሮ እመቤት ሙሉጌታ /ሁለት ሰዎች/	ሚያዚያ 1 ቀን 2007 ዓ.ም	330
68.	የአንድ የእምነት ተቋም አስተዳደራዊ ስራዎችን ለማከናወን የተሰጠ ሹመትና የሽረት ጉዳይ ከሀይማኖት ተቋሙ መሰረታዊና ተፈጥሯዊ ባህሪ ተነጥለው ለብቻቸው ሊታዩና ሊወሰኑ የማይችሉ በመሆናቸው በፍርድ ሊወሰኑ የማይገባቸው ስለመሆኑ፣ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገመንግስት አንቀፅ 11 እና 37	97009	አቶ ኤልያስ አዳሙ /ሁለት ሰዎች/ እና የኢ/ትዮጵያ ብርሃን ቤተ/ክርስቲያን	ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ.ም	335
ንብረት					**341**
69.	በገጠር የእርሻ ይዞታ የመጠቀም መብትን ከባለይዞታው ጋር የስጋ ዝምድና ለሌለው ሰው ማስተላለፍ የማይቻል ስለመሆኑ የስጦታ አደራረግን አስመልክቶ በፍትሐ ብሔር የተመለከቱ ድንጋጌዎች በገጠር የእርሻ ይዞታ የመጠቀም፣የማስተላለፍ እና አስተዳደር ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ክርክሮች ተፈፃሚነት የሌላቸው ስለመሆኑ፡- የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ. 130/1999 አንቀፅ 6 የፌድራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር አጠቃቀም አዋጅ.ቁ 456/19	105092	አቶ ብርሃኑ ከበደ እና አቶ ኢብራሂም ሹካ	መጋቢት 1 ቀን 2007ዓ.ም	342

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
70.	ከቤተሰባዊ ቅርርብ የተነሳ ውለታ ላደረገ ሰው አንደኛው ወገን ካለው መሬት ውርስ ቆርሶ በስጦታ መልክ እንዲጠቀም ሰጥቶት በሁለቱ መካከል አለመግባባት ቢፈጠር በሥጦታ ተቀባዩ ወገን በመሬቱ የመብት ክርክር ቢያነሳ የመሬት ይዞታ ስጦታው ሊፀና የሚችለው የክልል የመሬት አዋጅ በሚፈቅደው መሠረት ሥልጣን ባለው አካል ዘንድ ቀርቦ የስጦታ ውሉ መመዝገቡ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ /የኦሮሚያ ክልል የመሬት አዋጅ ቁጥር 130/99	109829	አቶ ረታ አበበ እና ወ/ሮ ተሬ ደማ ተወካይ ሙሉጌታ አበበ	ግንቦት 18 ቀን 2007 ዓ.ም	346
71.	የገጠር መሬት ወራሽነትን በሚመለከት በአንድ ወቅት በቤተሰብ አባልት መመዝገብ ብቻውን የሚችን የእርሻ መሬት በቀዳሚነት የመውረስ መብትን የማያጎናጽፍ ስለመሆኑ በውርስ ለማግኘት ወራሹ አርሶ አድርና ከእርሻ መሬቱ ከሚገኘው ገቢ የሚተዳደር የቤተሰብ አባል መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ 456/97 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 5 የኦሮሚያ የመሬት አዋጅ 130/99 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 13 እና 16/	109776	እነ ወ/ሮ ይርጋለም እና ወ/ሮ አሰፉ ዘውዴ	ግንቦት 13 ቀን 2007 ዓ.ም	350
72.	ፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ክፍል የተሰጠ የቤት ካርታ የተሰጠበት ወይም የተሻረበት ስርዓት እና አስተዳደራዊ ውሳኔው ህግና መመሪያ ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን በማጣራት ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ 1196፣የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 32	99071	ወ/ሮ አብረኸት ድክሪያ እና እነ ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል	ሠኔ 19 ቀን 2007 ዓ.ም	355

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ንግድ					**359**
73.	የሽርክና ማህበር በህግ አግባብ ተቋቁሞ እየሠራነው ለማለት በጽሁፍ ውል መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ተዋዋይ ወገኖች በጋራና በተናጥል በመተባበር በመስራት ከጥቅሙም ይሁን ከእዳው በጋራ ሲጋሩ እንደነበር መረጋገጥ ያለበት ሥለመሆኑ፣ አንድ የሽርክና ማህበር በህጉ አግባብ ተቋቁመ ለማለት የሚቻለው ተዋዋይ ወገኖች ተነጻጻሪ ጣይሆን ተደጋጋፊ የሆነ ግብ ይዘው መዋጮ በማውጣት አብረው በመስራትና በመተባበር ትርፍና ኪሣራም በህጉ አግባብ እየተጋሩ ኢኮኖሚያዊ ተግባር ማከናወናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁጥር 211፣229፣269/1/	94481	ወ/ሪት ፀሐይነሽ በቀለ እና ወ/ሪትንግስት ተክላይ	ሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም	360
74.	የሽርክና ውል ስምምነት አለ ለማለት መሟላት ሥለሚገባቸው መስፈርቶች የንግድ ህግ 5፣10(1)፣210(1)፣211፣215 እና 229(2)	96990	አቶ አያሌው ወልዴ ዮሃንስ እና አቶ ጀማል ሰማን ኑር	ሐምሌ 01 ቀን 2007ዓ.ም	365
75.	በሞተ ሰው ሥም የተመዘገበን የአክስዮን ድርሻ ላይ ሚቹ እንደተገኘ ተቆጥሮ የሚተላለፍ ውሳኔ አግባብነት የሌለው ሥለመሆኑ እና ተፈፃሚነት ያለው በንግድ ህጉ የተቀመጠው የሦስት ወር ጊዜ ሳይሆን በፍ/ሕ/ቁ 1845 የተመለከተው የአስር ዓመት ይርጋ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ.416 የፍ/ሕ/ቁ.1845	100621	አቶ ልዑልሰገድ ሞጆ እና እነ አንድነት ቅቤና ቅመማ ቅመም ነጋዴዎች	ሐምሌ 3 ቀን 2007 ዓ.ም	369

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
76.	በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት በልዩ ሁኔታ በንግድ ቤት ተጠቃሚ ለመሆን ሊሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔዎች	102725	እነ አቶ ዲንሳፋ ያዕቆብ/ሦስት ሰዎች/ እና ወ/ሮ አየለች በቀለ	ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም	373
77.	የህብረት ሥራ ማህበራት በመሰረታዊነት ለትርፍ ተብሎ የሚቋቋሙ ሳይሆን የአባላቱን ፍላጐት በአነስተኛ ወጪ ለሚሟላት የሚቋቋሙ በመሆኑ ለትርፍ ስራ የሚሰሩ የንግድ ስራዎች የሚያስፈልጋቸውን የንግድ ፋቃድ እንዲያወጡ የሚገደድበት አግባብ የሌለ ሥለመሆኑ የኃብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ማሻሻያው አዋጅ ቁ. 402/96 አንቀጽ 6	103717	የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሰራተኞች ሸማቾች ህብረት ስራ ኃ.የተ.የግል ማህበር እና የአዳማ ወረዳ ንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት	ሐምሌ 03 ቀን2007 ዓ.ም	379
አፈፃፀም					**385**
78.	ለአፈፃፀም መነሻ የሆነን ፍርድ ይግባኝ በመጠየቅ ሳያሸሩ ወይም ሳያሻሽሉ በዋናው ጉዳይ ሊነሱ የሚገባቸውን የክርክር ነጥቦች በአፈፃፀም በተያዘው መዝገብ የክርክር መሰረት ማድረግ ተገቢ ስላለመሆኑ	98347	ወ/ሮ በድሪያ መሐመድ እና አቶ አደም ዑመር	ሐምሌ 13 ቀን 2007 ዓ.ም	386
79.	በሃራጅ ጨረታ ያሸነፈ አንድ አካል ያሸነፈውን ንብረት በስሙ ካዘወረና ካስተላለፈ በኋላ የሃራጅ ሽያጩ ሙሉ በሙሉ ከተፈፀመለት በኋላ፣ ንብረቱ በሃራጅ ከተሸጠበት ዋጋ ላይ እንዲቀነስለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፡- የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.429፣441 እና 447	96588	እነ ወ/ሮ አልማዝ አርዓያ(አራት ሰዎች) እና አቶ አሸናፊ አልታየ	ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም	390

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
80.	የአፈፃፀም ችሎቶች ስለፍርድ አፈፃፀም የተዘረጉትን ሥርዓቶች በመከተል እንደ ፍርዱ ከመፈፀም በቀር የአንድ ፍርድ ይዘትን በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆነ በማስፋት ረገድ ፍርድን የመተርጎም ሥልጣን የሌላቸው ሥለመሆኑ፡- የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 372፣378	96814	አቶ አብዶሽ አዲሽ እና ወ/ሮ ሰብለ ዘውዴ	ሐምሌ 14 ቀን 2007ዓ.ም	395
81.	እኩል እንከፋፈል በሚል በፍ/ቤት የፀደቀን የቦታና ቤት ስምምነት እኩል ለማካፈል የከተማ አስተዳደሩ የፕላን ስታንዳርድን አያሟላም በተባለ ጊዜ የባልና ሚስትን የጋራ ሀብት በሀራጅ ተሸጦ ይካፈሉ ብሎ መወሰን የግራ ቀኙን በቤቱ የመጠቀም ፍላጎት /ነጻነት የሚገደብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ 277/1/,325,392 የአማ/ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ 79/95 አንቀጽ 73,74 101-103	104521	ወ/ሮ ታንጉት ሠጠ እና አቶ ፋንቱ ትኩ	ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም	401
ልዩ ልዩ					**406**
82.	ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦታ በሊዝ ለገዛ ሰው ቦታውን ለግንባታ ምቹ አድርጎ ማስረከብ ያለበት ስለመሆኑና በወቅቱ ካላስረከበ ካስረከበበት ጊዜ ጀምሮ የሁለት አመት የችሮታ ጊዜ ለገዥው ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ፣ መመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 14/3/ ፣ 37/6/ለ/ ፣ 38/8/ ደንብ ቁጥር 48/2004 አንቀፅ 11/1/ ፣ አንቀፅ 12/2/	97829	አቶ ሁሴን ሰይድ እና የየካ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ፅ/ቤት	ሚያዚያ 30 ቀን 2007 ዓ.ም	407

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
83.	የጥብቅና አገልግሎት የሚሠጥ ጠበቃ በደንበኛው የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጸምለት ለተፈጸመው ክፍያ ደረሰኝ አለመስጠት የዲሲፕን ግድፈት ስለመሆኑ አዋጅ 199/92 አንቀፅ 30/2/ ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 8/1/	107442	አቶ ሞገስ ናደው እንዳይላሉ እና የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር	መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም	412
84.	የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ ለመወሰን በልምድ የዳበረውና በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘው የአከፋፈል መርህ ጉዳዩ የወሰደው ጊዜ፣ የሚጠይቀው ድካም፣ የጉዳዩ ውስብስብነት የክርክርን ግምት ታሳቢ በማድረግ ስለመሆኑ፣ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ ያለምንም ገደብ ስምምነት የሚደረግበት አለመሆኑን ከስነ ህግ እና የፍርድቤቶች አሰራር የዳበረ ስለመሆኑ፣ የአብክመ የጥብቅና ስራ ፈቃድ አሰጣጥ ምዝገባ የጠበቆች ስነ-መግባር ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 75/1994 አንቀፅ 50፣51፣52 የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 462	105765	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ግርማ ሞገስ	ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም	418
85.	አንድ የፖለቲካ ድርጅት የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባል የሆኑ ሰዎችን አባልነታቸው ህጋዊ በሆነ መልኩ ሳይቋረጥ ወይም ቀሪ ሳይሆን እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ፣ አንድ ሰው በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ የሁለት የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን የማይችል ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 532/199 አንቀፅ 46፣102/4//ለ/፣አዋጅ ቁጥር 632/2002 አንቀፅ 7	112091	አንድነት ለፍትህና ዲሞክራሲ እና ሠማያዊ ፓርቲ	ሚያዚያ 28 ቀን 2007 ዓ.ም	422

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሣሬና ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.104862

መጋቢት 3 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡-አቶ መልካሙ አረጋ - ቀረቡ

ተጠሪ፡-ተስፋዬ ለገሠ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ - ጠበቃ ይትባረክ መኮንን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በ09/12/2005 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሳቸውም ይዘት ባጭሩ፡-ከሳሽ ከጥር 30 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 8,076 ደመወዝ እና ብር 100 አበል እየተከፈላቸው በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በዶዘር ኦፕሬተርነት የስራ መደብ ተቀጥረው በመስራት ላይ እያሉ ተከሳሽ ከ01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ በእርሳቸው ምትክ ሌላ ሰራተኛ በመቅጠር የስራ ውላቸው በቃል ያቋረጠባቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ የስንብት እርምጃው ሕገወጥ ነው ተብሎ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች እና ያልተጠቀሙበትን የዓመት ዕረፍት ክፍያ በድምሩ ብር 106,381.00 ተከሳሽ እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ11/02/2006 ዓ.ም በሰጠው መልስ ከሳሽ በራሳቸው ከስራ ከመቅረታቸው ውጪ ተከሳሽ ያላሰናበታቸው መሆኑን፣ሁሉም ሰራተኞች ለተረከቡት የድርጅቱ ንብረት ዋስትና እንዲያቀርቡ ተከሳሽ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ ከሳሽ ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን፣ዋስትና ለማቅረብ ያላቸውን ፈቃደኝነት ከ21/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/10/2005 ዓ.ም ድረስ እንዲያስታውቁ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ቢገለጽላቸውም ከሳሽ ይህንን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከማድረግ ፋንታ ከ21/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/10/2005 ዓ.ም ድረስ በተከታታይ ከስራ መቅረታቸውን፣በ03/11/2005 ዓ.ም ቢሮ ተገኝተው ተመሳሳይ መልዕክት ቢነገራቸውም ያልፈጸሙ እና እንደገና ከ03/11/2005 ዓ.ም እስከ 08/12/2005 ዓ.ም ድረስ ስራ ላይ አለመገኘታቸውን፣ከዚህ በኃላ ከሳሽ በ08/12/2005 ዓ.ም ቢሮ ቀርበው ስራቸውን በፈቃዳቸው መልቀቃቸውን በመግለጻቸው የተዘጋጀላቸውን ክፍያ እና የስራ ልምድ እንዲወስዱ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን፣በከሳሽ ምትክ ሌላ ሰራተኛ የተቀጠረው ከዚህ ሁሉ በኃላ በ05/01/2006 ዓ.ም. መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ የከሳሽ ምስክሮች ቃል ተከሳሽ ከሳሽን በቃል ከስራ እንዳሰናበተ የሚያስረዳ አለመሆኑን፣ከሳሽ ዋስ የሚጠሩ መሆን አለመሆኑን እስከ 30/10/2005 ዓ.ም ድረስ እንዲያስታውቁ፣ይህ ካልሆነ ግን ስራቸውን በራሳቸው ፈቃድ እንደለቀቁ ተቆጥሮ የስራ ግንኙነቱን እንደሚያቋርጥ ተከሳሽ በ21/10/2005 ዓ.ም የሰጠው ማስታወቂያ በይዘቱ ከሳሽ እስከተባለው ቀን ድረስ ሀሳባቸውን ካልገለጹ ተከሳሽ ከ30/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሉን እንደሚያቋረጥ የሚያመለክት መሆኑን፣የስራ ውላቸው ከ30/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ እንደተቋረጠ የሚቆጠር ከሆነ ደግሞ ከዚህ ቀን በኃላ ከሳሽ በስራ ቦታው የሚገኙበት ምክንያት ስለማይኖር ከሳሽ በተጨማሪ ከ03/11/2005 ዓ.ም እስከ 08/11/2005 ዓ.ም ድረስ ስራ ላይ አልተገኙም በማለት ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ከሳሽ ከ21/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/10/2005 ዓ.ም ድረስ በመደዳው ከስራ መቅረታቸው የተረጋገጠ ቢሆንም ተከሳሽ ይህንን ድርጊት የማሰናበቻ ምክንያት አድርጎ በደብዳቤ እስካልገለጸ ድረስ ከሳሽ የተሰናበቱት በመደዳው ከአምስት የስራ ቀናት በላይ ከስራ በመቅረት በራሳቸው አነሳሽነት ነው ሊባል የሚችል አለመሆኑን፣በአጠቃላይ ከሳሽም በራሳቸው አነሳሽነት ሰራቸውን ስላልለቀቁ እና ተከሳሽም ስላሰናበታቸው ስንብቱ ሕገወጥ መሆኑን ገልጾ በክሱ ከተጠየቀው ክፍያ ውስጥ ተከሳሽ ብር 79,189.66 ግብር ከተቀነሰ በኃላ ለከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተከሳሹ ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተከሳሽ በ21/10/2005ዓ.ም የሰጠው ማስታወቂያ በማስረጃነት የቀረበው በከሳሽ ሳይሆን በተከሳሽ በኩል ሆኖ እያለ እና የማስታወቂያው ይዘትም የስራ ውሉ በተከሳሽ አነሳሽነት መቋረጡን የማያረጋግጥ ሆኖ እያለ እንዲሁም ከሳሽ በመደዳው ከአምስት የስራ ቀናት በላይ ከስራ መቅረታቸው ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው በተከሳሽ አነሳሽነት ነው፣ስንብቱም ሕገወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልጾ ውሳኔውን በማሻሻል ተከሳሽ ከሕግ ውጪ የስራ ውሉን አቋርጧል በሚል የተሰጠውን እና ሕገወጥ የስራ የስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል

የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሽሮ የዓመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ብቻ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች ዋስ ካልጠሩ ተጠሪው የስራ ውላቸውን እንደሚያቋርጥ ገልጾ የጻፈላቸው መሆኑ በተረጋገጠበት እና አመልካች ዋስ አለማቅረባቸው ባልተካደበት ሁኔታ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ክስ ያቀረቡት ተጠሪው ከ01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ በእርሳቸው ምትክ ሌላ ሰራተኛ በመቅጠር የስራ ውላቸውን በቃል ያቋረጠባቸው መሆኑን በመግለጽ ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ አመልካችን እንዳላሰናበተ እና በራሳቸው ከስራ እንደቀሩ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡በመሰረቱ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ለክርክሩ ምክንያት የሚያደርጋቸውን ፍሬ ነገሮች የማስረዳት ሸክም እንዳለበት የሚታወቅ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ የአመልካች የምስክሮች ቃል ተጠሪው አመልካችን በቃል ከስራ እንዳሰናበተ የሚያስረዳ አለመሆኑን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተቀብሎ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በክሳቸው መሰረት አስረድተዋል ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡በአሰሪው በቃል ከስራ ተሰናብቻለሁ በሚል ክስ የሚያቀርብ ሰራተኛ ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43610 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ጉዳይ ተፈጸሚነት ሊኖረው የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪው ከ 01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ እንደሚያሰናብተኝ በ 21/10/2005 ዓ.ም በጻፈው ማስታወቂያ አረጋግጦ እያለ ስንብቱ ሕገወጥ አይደለም ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ አይደለም በማለት አመልካች ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ከ21/10/2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/10/2005 ዓ.ም ድረስ ከስራ መቅረታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ፣በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ያለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1)(ለ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል ምክንያት በመሆኑ፣በዚህ ምክንያትም አመልካች የስራ ውላቸውን ከ30/10/2005 ዓ.ም በፊት በራሳቸው አነሳሽነት እንዳቋረጡ የሚቆጠር በመሆኑ እና ይህም ተጠሪው በ21/10/2005 ዓ.ም የሰጠው ማስጠንቀቂያ ከ01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ የአመልካችን የስራ ውል እንዳቋረጠው የሚያመለክት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ የማንሳትን እና የመመርመርን አላስፈላጊነት የሚያስከትል በመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪው የስራ ውሌን ከ01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ እንዳቋረጠው ሊቆጠር ይገባል በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡አንድ ሰራተኛ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ካለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረቱ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ አሰሪው በዚሁ ምክንያት ሰራተኛውን ካለማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበተው ስለመሆኑ በደብዳቤ ሳይገልጽ መቅረቱ በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) (ለ) መሰረት የስራ ውሉ በሕግ አግባብ አልተቋረጠም ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተደረሰበትን የተሳሳተ መደምደሚያ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማረሙ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል ይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 80816 በ 30/03/2006 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139450 በ 12/12/2006 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከለተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105921

ቀን 14/07/2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- ፒተርድስ ፕሮዳክስት ማንፋክቸሪንግ (አ.ማ) አልቀረቡም

ተጠሪች፡- 1. ወ/ሮ ይፍቱስራ ነጋሽ } ጠበቃ ኤሊያስ አበበ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ገነት ወንድሙ }

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ አንደኛ ከሳሽ ፤ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆነችው ወ/ሪት መድሀኒት ሙቃ ሁለተኛ ከሳሽ ሁለተኛ ተጠሪ ሶስተኛ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾች ተከሳሽን ለምንድን ነው ለእኛ የቦነስ ክፍያ የማይከፈለን በማለት በእረፍት ሰዓት በመጠየቃችን ከስራ አግዶ አቆይቶ ሚያዝያ 2 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ከህግ ውጭ ያሰናበተን ስለሆነ የካሳ ክፍያ ፤ የማሰጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ፤ ክፍያ የዘገየበት ክፍያና ወጭና ኪሳራ እንዲከፍል ይወስንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ሆኖ ቀርቦ ከሳሾች ህገ ወጥ የስራ አድማ እንዲያደርጉ ሌሎች ሠራተኞችን በማስተባበርና በመቀሰቀስ ፤ የአድማ ስራ በመሆንና ረብሻና ሁከት የመፍጠር ሙከራ ማድረጋቸው ተረጋግጦ ከስራ የተሰናበቱ በመሆኑ ስንብቱ ህግን መሰረት ያደረገ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የስር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ በኩል ያቀረቡትን ምስክሮች ከሰማ በኃላ ተከሳሽ ከሳሾችን ከስራ ያስናበታቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ሸ) መሰረት በመሆኑ ስንብቱ ህግን መሰረት ያደረገ ነው በማለት የከሳሾችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ተጠሪዎች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት አቅርበው የሰማቸውን ምስክሮች ቃል በሰፊው ፤ ከዘረዘርና ከመርመር በኃላ አመልካች የቦነስ ክፍያ የማይከፈል መሆኑን በማስታወቂያ በመግለጽ ፤ ሰራተኞች ለምን አይከፈለንም የሚል ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን ፣ አመልካች ሰራተኞችን በሁለት ከፍሎ ማነጋገር እንደጀመርና ይግባኝ ባዮች (ተጠሪዎች) መብታችን ይከበር በማለት መግለፃቸውን ፣ አመልካች ይህንን በመናገራቸው ምክንያት አድማ ቀስቅሰዋል በማለት ይግባኝ ባዮችን (ተጠሪዎችን) ከስራ ያገደና ያስናበታቸው መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ እንደሆነ ገልፆና አንደኛ ይግባኝ ባይ (አንደኛ ተጠሪ) ዘግይተው ወደስራ የገባች መሆኑና እሷ ስራ ከመግባቷ በፊት ሌሎች ሰራተኞች ቦነስ ለምን አይከፈለንም የሚል ጥያቄ ማንሳታቸውን በአመልካች (መልስ ሰጭ) ምስክር የተረጋገጠ መሆኑን በውሳኔው አስፍሮ ፣ በዕለቱ ይግባኝ ባዮች ፣ የተናገሩት ንግግር የመብት ጥያቄ እንጅ ህገ ወጥ የስራ ማቆም አድማ ቅስቀሳ አይደለም፡፡ ይግባኝ ባዮች ረብሻና ሁከት የመፍጠር ተግባር አልፈፀሙም በማለት ስንብቱ ህገ ወጥ ስለሆነ መልስ ሰጭ (አመልካች) ለይግባኝ ባዮች (ለተጠሪዎች) የስራ ስንብት ክፍያ ፣ የካሳ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች ጥቅምት 3 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ፣ በዕለቱ አመልካች ምርት ባለማምርቱ ፣ ኪሳራ እንደደረሰበት ተረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች ምስክሮች ቃል ተዓማኒነትና ክብደት በአግባቡ ሳይመዝን ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች ጥር 12 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ ተጠሪዎች ህገወጥ አድማ ሰራተኛ ያነሳሳን ስለመሆኑ በማስረጃ እንዳላስርዳ በማረጋገጥ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የካቲት 5 ቀን 2007 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ያስናበተው ከህግ አግባብ ውጭ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የህግ መሰረት አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ፣ ማስርጃ የመመርመርና የመመዘን ስልጣኑን በመጠቀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የደርሰበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ህገ ወጥ አድማ ተደርጓል በሚልበት ቀን ፣ የቦነስ ክፍያ እንደማይከፍል ማስታወቂያ በመለጠፍ ፣ የድርጅቱ ሰራተኞች ለምን ቦነስ አይከፈለንም? የሚል ጥያቄ ማንሳታቸውን ፣ አመልካችም በሰራተኞች ጥያቄ ምላሽ በመስጠትና ሰራተኞችን በሁለት ከፍሎ ያነጋገረ መሆኑን ፣ አመልካች ሰራተኞችን በሚያነጋግርበት ጊዜ ተጠሪዎች ፣ መብታችን ይከበር በማለት መናገራቸውን ፣ ከዚህ ውጭ ተጠሪዎች የፈጸሙት ፣ ተግባር የሌለ መሆኑንና አንደኛ ተጠሪ ወደ ስራ የገባችው ዘግይታ እንደሆነ አመልካች በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ስህተት በይግባኝ የመመርመርና የማረም ስልጣኑን በመጠቀም የደረሰበት የፍሬ ጉዳይና የማስርጃ ምዘና መደምደሚያ ያሳያል፡፡

6. ይህንን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የደረሰበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያን አመልካች ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል ተአማኒነትና ክብደት ሲመዝን ፈጽሞታል የሚለውን ስህተት ፣ በሰበር ፣ የማየትና የማረም ስልጣን ለዚህ ሰበር ችሎት በህገመንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 አልተሰጠውም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የደርሰበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ዕውነት ነው ብለን በመቀበል ፤ ተጠሪዎች አመልካች ሰራተኞች በሁለት ቡድን ከፍሎ ሲያወያይ ፣ መብታችን ይከበር በማለት ሀሳባቸውን መግለፃቸው ወይም መናገራቸው የህገወጥ የስራ ማቆም አድማ መሪና የረብሻና የሁከት መፍጠር ሙከራ ነው ተብሎ ተጠሪዎችን ያለማሰጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያበቃ ምክንያት መሆኑን አግባብነት ካላው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

7. ሰራተኞችን አመልካች ቦነስ ክፍያ ስለማይከፈልበት ምክንያት በሁለት ከፍሎ በሚያነጋግርበት ወቅት ተጠሪዎች መብታችን ይከበር የሚል ንግግር መናገራቸው ፤ ህጋዊ መብታችን ነው የሚሉት የቦነስ ክፍያ እንዲከፈላቸው ሀሳባቸውን የገለጹ መሆኑን እንጅ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ሸ) መሰረት በአሰሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው በማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት የማድረስ ጥፋት የፈፀመ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ አንድ አሰሪ ሰራተኛው ህጋዊ የመብት ጥያቄ በማቅረቡ ምክንያት የስራ ውሉን የሚያቋርጥ ከሆነ ህገወጥ ተግባር እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 26(2) ሐ) ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ያስናበተው ከህግ አግባብ ውጭ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪዎች የካሳ ክፍያ ፣ የስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ ከላይ የጠቀሳቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139262 ሀምሌ 30 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 15 ቀን 2007 ዓ/ም የፅሁድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገበ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአመስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102994

ሚያዝያ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ዳሽን ባንክ አክሲዮን ማህበር - ነ/ፈጅ ሰለሞን አያኖ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ተፈሪ አሳልፈው
2. አቶ አየለ ገብረሃና
3. አቶ በኃይሉ ዓለማየሁ

} ከጠበቃ ሳህሉ ሀብቴ ጋር - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሾች የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ በ07/08/2005 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡የክሳቸውም ይዘት ባጭሩ፡-ከሳሾች በተከሳሽ ድርጅት ተቀጥረው ቂራ አካባቢ በሚገኘው መጋዘን በመስራት ላይ እያሉ ከመጋዘኑ ግቢ ያልወጣን ንብረት "ለግል ጥቅማችሁ አውላችኃል" በማለት ከ13/07/2005 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸውን ያቋረጠ መሆኑን፣ከሳሾቹ ንብረት ከመመዝገብ በስተቀር ንብረት የመያዝም ሆነ የመጠበቅ ኃላፊነት እና የስራ ድርሻ የሌላቸው መሆኑን፣ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠው ሠራተኛ በስሩ የሚገኘውን ንብረት ለአጠባበቅ ያመቸኛል በማለት ከመደበኛ ቦታ ውጭ በማስቀመጡ ድርጅቱ እርምጃ መውሰድ የሚገባው ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘው ሠራተኛ ላይ ብቻ ሆኖ እያለ ከሳሾቹን ጭምር በማሰናበት የወሰደው እርምጃ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27 (1) (መ) እና የድርጅቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 36 (1.3) የሚቃረን መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ የስራ ስንብት እርምጃው ሕገወጥ ነው ተብሎ ድርጅቱ ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደስራ እንዲመልሳቸው፣ይህ የሚታለፍ ከሆነም ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን እና ተዛማጅ ክፍያዎችን እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው።

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ17/10/2005 ዓ.ም በሰጠው መልስ ከሳሾቹ ከብር 180,000 በላይ ዋጋ ያላቸውን የተለያዩ ዕቃዎች እርስ በርስ በመመሳጠር በስቶር ክለርክነት ከሚሰሩበት የዕቃ ግምጃ ቤት ሰርቀው በመውሰድ በመጸዳጃ ቤት ውስጥ በመደበቅ እና የመጸዳጃ ቤቱን በመቆለፍ የቆጠራ ሠራተኞች እንዳያገኟቸው ያደረጉ መሆኑን፣ንብረቶቹ ለተለያዩ የአካባቢ ባንኮች እና የስራ ክፍሎች የተሰራጨ ተደርገው የሚታወቁ መሆኑን፣ከሳሾቹ ንብረቶቹን ከሚሰራጩት ዕቃዎች ቀንሰው ያጠራቀሟቸው እንደሆነ መረጋገጡን፣ስለጉዳዩ ሲጠየቁም እርስ በርስ የሚጋጭ መልስ መስጠታቸውን፣እንዲሰናበቱ የተደረገውም በፈጸሙት የስርቆት እና የማጭበርበር ድርጊት በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) (ሐ) እና (ተ) እና በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 36 /1.1 እና 36 /1.2/ መሰረት በአግባቡ መሆኑን፣የሚፈለግባቸውን ዕዳ በማቻቻል ተራፊ ገንዘብ ካለ ከሁለት ዓመት በላይ ያልተላለፍ የዓመት ዕረፍታቸውን ድርጅቱ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆኑን፣የፕሮቪደንት ፈንድ የለም እንጂ አለ ከተባለ ድርጅቱ ክፍያውን ለመክፈል የሚገደደው ከሳሾቹ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ በመወጣት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ብቻ በመሆኑ ከሳሾቹ ይህንን ግዴታ ተወጥተው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጥያቄ ባላቀረቡበት ሁኔታ ድርጅቱ የሶስት ወር ደመወዝ ለመክፈል የሚገደድበት ምክንያት አለመኖሩን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል።

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የተከሳሽ ድርጅትን ሶስት ምስክሮች ከሰማ በኃላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ በስቶር ውስጥ በነበረው ዕቃ ጉድለት ያልተገኘ ቢሆንም ከሳሾች በመመካከር ዕቃዎቹ ከመጸዳጃ ቤት ውስጥ እንዲቀመጡ ማድረጋቸውን ተከሳሽ ድርጅት ያስረዳ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ይህ መሆኑ ከሳሾቹ ዕቃዎቹ ትርፍ መሆን አለመሆናቸው ወይም በመጠየቂያ መሰረት ያልተሰጡ ዕቃዎች መሆን አለመሆናቸው እስኪለይ ድረስ አስቀምጠናቸዋል በማለት ለተከሳሽ ድርጅት ምስክሮች በቃል እና በጽሁፍ ከሰጡት መግለጫ አንጻር ከሳሾቹ ዕቃዎቹን ከመደበኛ ቦታቸው ውጪ መጸዳጃ ቤት ውስጥ ማስቀመጣቸው አግባብ አይደለም ከሚባል በቀር ከሳሾቹ በመመካከር ዕቃዎቹን ለግል ጥቅማቸው ለማዋል በማሰብ ከሚላኩ ዕቃዎች ቀንሰው አውጥተው ወስደዋል ለማለት የሚያስችል አለመሆኑን ገልጾ ከሳሾቹ የስርቆት እና የማጭበርበር ድርጊት ፈጽመዋል በማለት ተከሳሽ ድርጅት የወሰደው የስንብት እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት ለእያንዳንዳቸው የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመልሳቸው ውሳኔ ሰጥቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩል የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የተሰጠውን ውሳኔ ሲያጸናው ተጠሪዎቹ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራ እንዲመለሱ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ግን በመሻር ሕገወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸው ክፍያዎች፣የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲሁም ያልተጠቀሙበት የዓመት ዕረፍት ክፍያ ለ1ኛ ተጠሪ የ27 ቀናት፣ለ2ኛ እና ለ3ኛ ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው የ15 ቀናት ክፍያ ተፈጽሞላቸው እንዲሰናበቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪዎች በነበራቸው የስራ ግንኙነትና አጋጣሚ የአመልካች የሆኑ ለልዩ ልዩ ቅርንጫፎች የሚታደሉ በመጋዘን ውስጥ የነበሩ ንብረቶችን ከመጋዘን አውጥተው በግቢው ውስጥ ባለ መጸዳጃ ቤት ውስጥ አስቀምጠውት የነበረው ንብረት በጠቋሚዎች አማካኝነት በፍተሻ መያዙን የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማስረጃ ካረጋገጠ በኃላ ንብረቶቹን መጋዘኑ ካለበት ግቢ አውጥተው ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ አድራጎታቸው እንደስርቆት እንደማይቆጠር ገልጾ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት የመወሰኑን እና ውሳኔውም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጽናቱን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈለኝ የሚገባው የዓመት ዕረፍት የ71 ቀናት ሆኖ ሳለ የ27 ቀናት ብቻ ታስቦ የ44 ቀናት የታለፈብኝ አላግባብ ነው በማለት 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መስቀልኛ የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች መልስ እንዲሰጥበት በ13/06/2007 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በመስቀልኛ አቤቱታው ጉዳይም አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች፡-

1. አመልካች አቤቱታ ያቀረበበት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?
2. 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መስቀልኛ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡበት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ ጉዳዩን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪዎቹ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ይሰሩ የነበሩት በስቶር ክለርክነት መሆኑ፣በዚሁ የስራ መደብ ከሚሰሩበት የዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ ተደርገው ለባንኩ የተለያዩ አካባቢዎች እና የስራ ክፍሎች እንደተሰራጩ ተደርገው የተመዘገቡትን የተለያዩ ዕቃዎች ከንብረት ጠባቂው ጋር በመተባበር ከሚሰራጩት ዕቃዎች ቀንሰው በመጸዳጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ውስጥ በመደበቅ እና የመጸዳጃ ቤቱን በመቆለፍ የቆጠራ ሰራተኞች እንዳያገኟቸው ያደረጉ መሆኑ፣ንብረቶቹን ለተለያዩ የአካባቢ ባንኮች እና የስራ ክፍሎች የተሰራጨ እንደሆኑ አድርገው የመዘገቡትም እነዚሁ ተጠሪዎች መሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች መሆናቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።ተጠሪዎቹም እኛ ንብረት ከመመዝገብ ባለፈ ንብረቱን የመያዝ እና የመቆጣጠር የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት የሌለን ስለሆነ ለዕቃዎቹ በመጸዳጃ ቤት ውስጥ ተደብቀው መገኘት በኃላፊነት የምንጠየቅበት ምክንያት የለም፣ዕቃዎቹም የተገኙት ከግቢው ሳይወጡ ነው፣በግቢው መውጫ ላይ የሚደረገው ፍተሻ ዕቀዎቹን ከመጋዘኑ ግቢ ለማውጣት የሚያስችል አይደለም በሚል ከመከራከር በቀር በስር ፍርድ ቤቶች ስለተረጋገጡት ከላይ ስለተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች ያቀረቡት የማስተባበያ ክርክር የለም።ከንብረት ጠባቂው ጋር በመሆን ዕቃዎቹን ከመደበኛ ቦታቸው ውጭ በመጸዳጃ ቤት ውስጥ ቆልፎ ለማስቀመጥ ያስቻላቸው ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ምክንያት ስለመኖሩም ገልጸው አልተከራከሩም።

የስር ፍርድ ቤቶች ይዘቱ ከላይ የተመለከተው ፍሬ ነገር መረጋገጡን ከተቀበሉ በኃላ ስንበቱ ሕገወጥ ነው ለማለት የቻሉት በዋነኛነት ዕቃዎቹ የተገኙት በግቢው ውስጥ እንዳሉ በመሆኑ ተጠሪዎቹ ዕቃዎቹን ወስደዋል ማለት አይቻልም በማለት መሆኑን ከውሳኔዎቹ ይዘት ተገንዝበናል።በእርግጥ ዕቃዎቹ በመጸዳጃ ክፍል ውስጥ ተቆልፈው እንዳሉ በጥቆማ ተይዘዋል ከመባሉ በስተቀር ከግቢ ውጪ አልተወሰዱም።አመልካችም ቢሆን ዕቃዎቹ ከግቢ ውጪ ተወስደዋል በማለት አልተከራከረም።ይሁን እንጂ ተጠሪዎቹ ዕቃዎቹን ወጪ ተደርገው ለተለያዩ የባንኩ ቅርንጫፎች እና የስራ ክፍሎች እንደተሰራጨ አድርገው በመመዝገብ እና ከተሰራጩት ዕቃዎች በመቀነስ ከመደበኛ የዕቃ ማከማቻ ቦታ ውጭ በመጸዳጅ ክፍል ውስጥ ቆልፈው ያስቀመጡበት ሕጋዊ ምክንያት መኖሩን አስካላስረዱ ድረስ የፈጸሙት አድራጎት በድርጅቱ ላይ የተፈጸመ የማጭበርበር ድርጊት ነው ሊባል የማይችልበት ምክንያት የለም።ዕቃዎቹ ከግቢው ሳይወጡ ድርጊቱ በሙከራ ደረጃ ላይ እንዳለ የተደረሰበት መሆኑ እና በግቢው መውጫ ላይ ፍተሻ የሚደረግ መሆኑም ተጠሪዎቹ ዕቃዎቹን ከግቢው አውጥተው ለግል ጥቅማቸው የማዋል ሀሳብ አልነበራቸውም ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል አይደለም።በመሆኑም ተጠሪዎቹ ዕቃዎቹን ከመደበኛ ቦታቸው ውጪ መጸዳጃ ቤት ውስጥ ማስቀመጣቸው አግባብ አይደለም ከሚባል በቀር በመመካከር ዕቃዎቹን ለግል ጥቅማቸው ለማዋል በማሰብ ከሚላኩ ዕቃዎች ቀንሰው አውጥተው ወስደዋል ለማለት እና በስራቸው ላይ የስርቆት እና የማጭበርበር ድርጊት ፈጽመዋል ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በክርክሩ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጭ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም። እንደጥፋቱ ክብደት ሰራተኛው በስራው ላይ የሚፈጽመው የማታለል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም የማጭበርበር ተግባር ደግሞ ካለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 27 (1) (ሐ) ስር ተመልክቷል፡፡በመሆኑም የመጀመሪያው ጭብጥ ሲጠቃለል ስንብቱ ሕገወጥ ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለ1ኛ ተጠሪ የ27 ቀናት የዓመት ፈቃድ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል በሚል ውሳኔ የሰጠው ተጠሪው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ላይ ያላቸው የዓመት ፈቃድ ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው በደፈናው ከመጠየቅ ውጭ ያላቸውን የዓመት ፈቃድ መጠን ጠቅሰው እና ለይተው አለማቅረባቸውን በመግለጽ እና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 77 (1)፣(5) እና 79 (5) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ ተገቢ ነው ያለውን ግምት በመውሰድ ነው፡፡በሰበር ክርክራቸውም ቢሆን ያላቸውን የዓመት ፈቃድ መጠን በክሳቸው ለይተው አቅርበው የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገቡን ግልባጭ እና የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት አድርጎ ለተጠሪው ሊከፈል የሚገባው የዓመት ዕረፍት መጠን የ27 ቀናት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 08897 በ15/04/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139478 በ09/10/2006 ዓ.ም. ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች የተወሰደው የስንብት እርምጃ ሕገወጥ ነው በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. በተጠሪዎቹ መፈጸሙ የተረጋገጠው ጥፋት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 27 (1) (ሐ) ድንጋጌ መሰረት የስራ ውላቸውን ካለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. ስንበቱ ሕጋዊ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪዎቹ የካሳ ክፍያ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል አይገባም በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. አመልካች ለተጠሪዎቹ የዓመት ዕረፍት ወደገንዘብ ቀይሮ እንዲከፍላቸው የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
6. አመልካች ለተጠሪዎቹ የፕሮቪደንት ፈንድ ሊከፍል የሚገባው ተጠሪዎቹ ባዋጡት መጠን ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡
7. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14377 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ17/11/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
8. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
9. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
10. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰመ/ቁ/ር 104465

መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሪት ሽዊት ኃይሉ - VC - ስላልሰራ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተጠሪ፡- መከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራዝ - ነ/ፈጅ ደረጀ ከበደ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሰረት አድርጎ የቀረበ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በደጉዓ ተምቤን ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በካሼር የስራ መደብ ላይ በወር ብር 1744.00 እየከፈላቸው ከሰኔ 27 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሀምሌ 25 ቀን 2005 ድረስ ቀጥሮ ሲያሰራቸው እንደቆዩና ከህግ ውጪ የስራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ በአሰሪው ድርጅት የተቋረጠ መሆኑን ገልጸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም፡- የስራ ውሉ የተቋረጠው አመልካች ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም ባቀረቡት መልቀቂያ መሰረት መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር አመልካች ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም ባስገቡት የስራ ውል መነሻ ግንኙነቱ መቋረጡን ገልጾ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁኗ ተጠሪ ለምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበውም ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ስንብቱ በአመልካች ጥያቄ መሰረት የተደረገ በመሆኑ ሕጋዊ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በድምጽ ብልጫ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም ስራውን ለመልቀቅ ለተጠሪ ድርጅት መልቀቂያ አስገብተው ቆይ ተብለው ለሰባት ወራት ያህል ስራ እንዲሰሩ ከተደረገ በኋላ የስራ ውሉን ከሰባት ወራት በፊት በቀረበ ማመልከቻ መነሻ ተቋርጧል ተብሎ ስንብት መደረጉና ሁሉም ክፍያዎች ውድቅ መደረጋቸው ያላግባብ ነው የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረውን የስራ ውል ያቋረጠው በአመልካች የስራ መልቀቂያ ጥያቄ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ17/04/2005 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ የስራ መልቀቂያ እንዲሰጣቸው ለተጠሪ ጥያቄ አቅርበው ተጠሪም የአመልካችን ጥያቄ አቆይቶ አመልካች ለሰባት ወራት ምድብ ስራቸው ላይ እየተገኙ ስራውን እንዲሰሩና ግዴታቸውን እንዲወጡ ሲያደርግ ቆይቶ ከነሐሴ ወር 2005 ዓ/ም ጀምሮ የአመልካች የወር ደመወዝ ሳይያዝና ስማቸው ከአቴንዳንስ ተሰርዞ በአመልካች የስራ መደብ ላይ ሌላ ገንዘብ ያኘን በመመደብ አመልካች በ17/04/2005 ዓ/ም ያስገቡትን የስራ መልቀቂያ በመጥቀስ የስራ ውሉን ያቋረጠ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የስራ ውል ሁለት ወገኖች አንዱ አሰሪ ሌላኛዉ ሠራተኛ ሆነው በአሠሪው ቁጥጥር እያደረገ ሠራተኛው ለሚሰራለት የጉልበት ወይም የዕወቅት ስራ ደሞዝ የሚከፍልበት የስራ ግንኙነት የሚፈጥር ስምምነት ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 4/1/ ስር ከተደነገገው ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ የህጉ የትርጉም ይዘት መሰረት ከሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች አንዱ በሕጉ መሰረት አሠሪ ነው ተብሎ የሚወሰድ ሲሆን ይህ ወገን ለሚያገኘው አገልግሎት ተገቢውን ደሞዝ የሚከፍልና አገልግሎቱም በእርሱ ቁጥጥር የሚመራ መሆኑ፣ሠራተኛ ደግሞ በአሠሪው ቁጥጥር መሠረት አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስራ ውሉ መኖሩ ደግሞ በማናቸውም አይነት ሊረጋገጥ የሚችል ነው፡፡ በሕጉ አግባብ የተመሰረተ የስራ ውል ደግሞ የሚቋረጥባቸው መንገዶች ስለመኖራቸው ሕጉ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የስራ ውል ስለሚቋረጥበት ምክንያቶችና ሁኔታዎችን በአንቀጽ 23 ስር ተመልክተዋል፡፡ እነዚህም በሰራተኛው አነሳሽነት የሚደረግ፣ በሕግ በተደነገገው መሰረት፣በህብረት ስምምነት መሰረት እና በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የሚደረግ የውል ማቋረጥ ሲሆኑ ዝርዝር ምክንያቶቻቸውና ሁኔታዎችንም ህጉ አስቀምጧል፡፡ በአሰሪው አነሳሽነት የሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ እንደየሁኔታው በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ ሊደረግ የሚችል ሆኖ የምክንያቶቹ ዝርዝር እና አፈጻጸሙ በአዋጁ አንቀጽ 26 እስከ 30 ባሉት ድንጋጌዎች ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ሌላው በህጉ በዝርዝር የተቀመጠው የስራ ውል ማቋረጥ ስርዓት በሰራተኛው አነሳሽነት የሚደረገው ሲሆን ይህም በአሰሪው አነሳሽነት ሊደረግ እንደሚችለው በማስጠንቀቂያ እና ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ሰራተኛው የሚያቋርጥበት መንገድ ስለመኖሩና ውሉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማቋረጥ የሚቻልባቸው ሁኔታዎቹና ምክንያቶቹን ዘርዝሮ የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎችና ምክንያቶቹ በአዋጁ ከአንቀጽ 31 እስከ 33 ድንጋጌዎች ስር በግልጽ ተደንግገው ይገኛሉ፡፡

እንግዲህ ሕጉ የስራ ውሉ ሊቋረጥ የሚችልባቸውን መንገዶች በዝርዝር ከአስቀመጠ በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ሲነሳም ውሉ የተቋረጠበትን መንገድ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ ተለይቶ ዳኝነት መሰጠት ያለበት በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ ከሰኔ 27 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ህጋዊ የስራ ውል መኖሩ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ሲሆን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይ ይኼው ውል የተቋረጠው በማን አነሳሽነት ነው? የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም ያስገቡትን የስራ መልቀቂያ መሰረት አድርጎ የስራ ውሉን ማቋረጡን ያልካደው ሲሆን አመልካችም ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም የስራ መልቀቂያ ማስገባታቸውን ሳይክዱ መልቀቂያው ሳይሰጣቸው ቆይቶ የስራ ግዴታቸውን እየተወጡ እስከ ሰኔ ወር 2005 ዓ/ም ድረስ ያለው ደመወዝም እየተከፈላቸው ስራቸውን ሲሰሩ የቆዩ መሆኑን ገልጸው የስራ መልቀቂያ ጥያቄአቸው በተጠሪ ምክንያት ተግባራዊ ያለመሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የተጠሪ የስራ ስንብት የተከናወነው አመልካች የስራ መልቀቂያ ከአስገቡ ከሰባት ወራት በኋላ መሆኑንና መልቀቂያው ለሰባት ወራት የቆየው በአመልካች ፍላጎት ስላለመሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ አመልካች መልቀቂያውን ያነሱ ስላለመሆናቸው በተጠሪ በኩል የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ የአመልካች የስራ መደብ ላይ ተገቢው ሰራተኛ ባለመገኘቱ ሰራተኛ እስከሚገኝ ድረስ አመልካች በስራቸው ላይ እንዲቆዩ የተደረጉ ስለመሆኑና ስራተኛው ሲገኝ መልቀቂያው የሚሰጣቸው ስለመሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረበ ግልጽ ክርክርና ማስረጃ ያለመኖሩን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አመልካች የስራ መልቀቂያ ከአስገቡ በኋላ ለረዥም ወራት እንደ ሰራተኛነታቸው በሕጉ የተጣለባቸውን የስራ ግዴታ ሲወጡ መቆታቸውና ተጠሪም ለአመልካች ስራ እየሰጠና ደመወዝም እስከ ሰኔ ወር 2005 ዓ/ም ድረስ እየከፈለ መቆየቱ ሲታይ ግራ ቀኙ በነጻ ፍላጎታቸው የቀደመውን የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት እንዲቀጥል የተስማሙ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ አግባብ እንዲቀጥል የተደረገ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ደግሞ በተግባር ቀሪ በሆነው የስራ መልቀቂያ ጥያቄ በሕጉ የተቀመጠውን ስርዓት ሳይከተል ሊቋረጥ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አንፃር መመልከት ሲገባቸው አመልካች ስራውን የለቀቁት በራሳቸው ተነሳሽነት ነው በሚል የሰጡት ውሳኔ የስራ ውል አመሰራረት፣ውሉ የሚቋረጥባቸውን ሁኔታዎችና ምክንያቶችን እንዲሁም በሕጉ የተቀመጡትን ስርዓቶችን ያላገናዘበ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በደጉዓ ተምቤን ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02582 ህዳር 23 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥ 06144 ጥር 01 ቀን 2006 ዓ/ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 64078 ግንቦት 23 ቀን 2006 ዓ/ም በአብላጭ ደምጽ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ አመልካችን ያሰናበተው በራሱ ተነሳሽነት እና ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠሪ ለአመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39 እና 40(2) መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ፣ በአንቀጽ 43(4(ሀ)) መሰረት የካሳ ክፍያ፣ በአንቀጽ 35(1(ለ)) መሰረት የማስጠቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና በአንቀጽ 38 መሰረት ክፍያ ለዘገዱበት ክፍያ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፍል ብለናል፡፡
3. ሌሎች ክፍያዎች ማለትም ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተጠየቁት የትርፍ ሰዓት እና ህዝባዊ ባዕላት ክፍያዎች ግን በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያልተጣሩ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና በማስረጃ አጣርቶ ተገቢውን ሊወሰን ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይፃፍ፡፡
4. ብር 518.00 የዳኝነት ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ሊተኩ አይገባም ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚያዝያ 13 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፦-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡-ሴንቸሪ ጂኤራል ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ አሰፋ ዓሊ ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ገስጥ ንጉሴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በ11/09/2006 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሳቸውም ይዘት ባጭሩ፡-ከሳሽ ከ09/03/2006 ዓ.ም ጀምሮ በአሽከርካሪነት የስራ መደብ ላይ በወር ያልተጣራ ብር 1,900 (አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ) ደመወዝ እየተከፈላቸው በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በመስራት ላይ እያሉ ተከሳሽ ድርጅት ካለአንዳች ምክንያት በ19/07/2006 ዓ.ም ከስራ ካገዳቸው በኃላ በ24/08/2006 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ የስራ ስንብት እርምጃው ሕገወጥ ነው ተብሎ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን እና ተዛማጅ ክፍያዎችን በድምሩ ብር 21,850 (ሃያ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ) ድርጅቱ እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ26/09/2006 ዓ.ም. በሰጠው መልስ የከሳሽ የስራ ውል እንዲቋረጥ የተደረገው ከሳሽ ስራቸውን ለመስራት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፣አሮጌ ተሽከርካሪ አላሽከረክርም በማለታቸው፣ከድርጅቱ ሰራተኞች ጋር ለመስራት ባለመቻላቸው፣በዚህም ምክንያት የድርጅቱ ሰራተኞች በከሳሽ ሾፌርነት በድርጅቱ ተሽከርካሪ ከመጠቀም ይልቅ በታክሲ መጠቀም ይሻለናል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለታቸው እና ከሳሽ ተደጋጋሚ ምክር እና ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ሊታረሙ ባለመቻላቸው በመሆኑ የስራ ውላቸው የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13(2) መሰረት በአግባቡ ነው፣እስከሰሩበት መጋቢት 19 ቀን 2006 ዓ.ም. ድረስ ያለው ደመወዝ ተከፍሏቸዋል ፣ያልሰሩበት የሚያዝያ ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፣የዘገየ ክፍያ የለም፣ በመሆኑም ክሱ ውድቅ ሊደረግልን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ከሳሽ ባላቸው የማሽከርከር ሙያ በተቀጠሩበት የስራ መደብ ሰራተኞችን ወደ ስራ ቦታ በሰዓቱ ወስደው በሰዓቱ መመለስ እና የሚሰጣቸውን ትዕዛዝም መፈጸም እንዳልቻሉ እንዲሁም ተሽከርካሪው መስራት የሚችል ሆኖ እያለ በአሮጌ ተሽከርካሪ አልሰራም በማለት አቁመው እንደሄዱ ከግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል መገንዘብ መቻሉን፣አንድ ሰራተኛ በአሰሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ የመፈጸም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13 (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑን፣ይሁን እንጂ ከሳሽ መፈጸማቸው የተረጋገጠው ጥፋቶች በአዋጁ አንቀጽ 27 መሰረት ካለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብቱ አለመሆኑን ገልጾ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት ተከሳሽ ድርጅት ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች ለከሳሽ እንዲከፍል እና የስራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13 የተመለከተውን ግዴታ ሊፈጽም ያልቻለ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም የዚህ ግዴታ መጓደል ካለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 27(1) ስር ስላልተካተተ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ትርጉም አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በአንድ በኩል ተጠሪው ባላቸው የማሽከርከር ሙያ በተቀጠሩበት የስራ መደብ ሰራተኞችን ወደ ስራ ቦታ በሰዓቱ ወስደው በሰዓቱ መመለስ እና የሚሰጣቸውን ትዕዛዝም መፈጸም እንዳልቻሉ እንዲሁም ተሽከርካሪው መስራት የሚችል ሆኖ እያለ በአሮጌ ተሽከርካሪ አልሰራም በማለት አቁመው እንደሄዱ በግራ ቀኙ ምስክሮች መረጋገጡን እና አንድ ሰራተኛ በአሰሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ የመፈጸም ግዴታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለበት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13 (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑን በውሳኔው ላይ ከገለጸ በኃላ በሌላ በኩል ግን ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት ለተጠሪው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ ውሳኔ የሰጠው ተጠሪው መፈጸማቸው የተረጋገጠው ጥፋቶች በአዋጁ አንቀጽ 27 መሰረት ካለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብቱ አይደሉም በማለት ነው፡፡በመሰረቱ የስራ ውል ማለት ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአሰሪው ለመስራት ግዴታ የሚገባበት ውል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 4 (1) ስር የተመለከተ ሲሆን የዚህ ዓይነት የውል ግዴታ የገባ ሰራተኛ በስራ ውሉ ላይ የተመለከተውን ስራ ራሱ የመስራት፣በስራ ውሉ እና በስራ ደንቡ መሰረት በአሰሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ መፈጸም እና የአዋጁን ድንጋጌዎች፣የሕብረት ስምምነትን፣የስራ ደንብን እና በሕግ መሰረት የሚተላለፉ መመሪያዎችን እና ትዕዛዞችን የማክበር ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 13 (1) (2) እና (7) ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ በተጠሪው መፈጸማቸው በግራ ቀኙ ምስክሮች እንደተረጋገጡ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተገለጹት ፍሬ ነገሮችም ተጠሪው ከላይ በተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ግዴታዎች መፈጸም አለመቻላቸውን በግልጽ የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ተጠሪው እነዚህን ግዴታዎች ለመፈጸም ፈቃደኛ አለመሆናቸው ደግሞ ከአመልካች ጋር የገቡትን የስራ ውል መሰረታዊ ዓላማ እና ይዘት የሚጻረር እና የስራ ውሉን ተግባራዊነት የሚያሰናክል ከመሆኑም በላይ ድርጊቶቹም በባህሪያቸው ሆን ተብለው የሚፈጸሙ በመሆኑ እንደተራ ጥፋት ተቆጥረው በቀላሉ ሊታለፉ የሚገባቸው አይደሉም፡፡ በተጠሪው መፈጸማቸው የተረጋገጡት ጥፋቶች ካለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብቱ ናቸው ተብለው በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) ስር ከተዘረዘሩት ጥፋቶች ውስጥ በግልጽ ባይጠቀሱም በአሰሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው በማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ካለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናበት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) (ሸ) ስር ተመልክቷል፡፡በመሰረቱ ...”የአሰሪው ንብረት...” በሚል በዚህ ድንጋጌ ስር የተቀመጠው አገላለጽ መተርጎም የሚገባው ግዙፍነት ያለው ቁሳዊ አካል ብቻ ተደርጎ ሳይሆን ለአሰሪው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሌላ ነገር በሚያካትት አግባብ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ በተጠሪው መፈጸማቸው የተረጋገጡት ጥፋቶች የአሰሪውን የስራ እንቅስቃሴ የማስተጓጎል ውጤት ያስከተሉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ይህ መሆኑ ደግሞ ተጠሪው ሆነ ብለው በአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በመሆኑም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ተጠሪው በአዋጁ አንቀጽ 13 (1) (2) እና (7) ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ግዴታዎች አለመወጣታቸው የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤት በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) (ሸ) ስር ከተመለከተው ድንጋጌ አንጻር አይቶ መተርጎም ሲገባው ተጠሪው በአዋጁ አንቀጽ 13(2) ስር የተመለከቱትን ግዴታዎች አለመፈጸማቸው ካለማስጠንቀቂያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችሉ ናቸው ተብለው በአዋጁ አንቀጽ 27 (1) ስር ከተዘረዘሩት ጥፋቶች ስር በግልጽ አልተጠቀሱም ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የሰጠው እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት ሕገ ወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች አመልካች ለተጠሪው እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት ሕገ ወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች አመልካች ለተጠሪው እንዲከፍል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13619 በ29/11/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 155925 በ20/04/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች የተወሰደው የስራ ስንብት እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13 (1) (2) እና (7) እና 27 (1) (ሸ) መሰረት ሕጋዊ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የተጠሪውን የስራ መደብ፣የደመወዝ መጠን እና የአገልግሎት ዘመን በመጥቀስ አመልካች የስራ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105834

ሚያዚያ 28 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት ኮንፌደሬሽን -

ጠበቃ እሸቱ ጓንጉል - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እመቤት ኤርሚያስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካች የስንብት እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጽናቱ በውሳኔው ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 “ን” መሰረት ያደረገ የግል የስራ ክርክር ሁኖ አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ የዲስፕሊን ጥፋት ፈፅሟል ተብሎ ከስራ ያለማስጠንቀቂያ የሚሰናበትበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የተጠሪ ክስ በአመልካች ማህበር ውስጥ በወር ብር 4,500.00 (አራት ሺህ አምስት መቶ) እየተከፈላቸው በሂሳብ ሰራተኝነት የስራ መደብ ከመስከረም 05 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ ሲያገለግሉ ቆይተው አመልካች ማህበር የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽመዋል በሚል ምክንያት በሕገ ወጥ መንገድ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ዘርዝረው ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የካሳ፣የስራ ስንብት፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ እና ክፍያ ለዘገዱበት ክፍያ እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን ያሳያል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ የተለያዩ የዲስፕሊን ጥፋቶችን መፈፀማቸውን በመግለጽ ጥፋቶችም፡- ተጠሪ የስራ መደባቸው አካውንታት ሆኖ እያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከስራ ድርሻቸው ውጪ መጠኑ ብር 9000.00 (ዘጠኝ ሺህ ብር) የሆነ ገንዘብ ከአምስት ወራት በላይ በእጃቸው ላይ ያቆዩ መሆናቸውን፣ተጠሪ ይህን በእጃቸው ያቆዩትን ብር 9000.00 (ዘጠኝ ሺህ ብር) በስራ ላይ እንደዋለ በማስመሰል የተሳሳተ ሪፖርት ማቅረባቸውንና ይህንኑ በእጃቸው የቆየውን ገንዘብ ባንክ እንዲያስገቡ ሲታዘዙ ትዕዛዝ ያለመቀበላቸው፣የስራ አመራር ቦርድ ሳይፈቅድ የአመልካች ማህበር ተ/ዋና ስራ አስኪያጅ ለሆኑት አቶ ተሾመ ደሬሳ በየወሩ ከሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 2005 ዓ.ም ድረስ ብር 430.00 በድምሩ ለአራት ወራት ብር 1720.00 (አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ብር) መክፈላቸው፣ለፌዴሬሽኑ አትክልተኛ ለአቶ መዝገቡ ገላው ሐምሌ ወር 2004 ዓ.ም ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) መክፈላቸው፣ለአመልካች ማህበር የሕዝብ ግንኙነት ሰራተኛ አቶ ደረሰ ታደሰ ከሰኔ ወር 2004 ዓ.ም እስከ መስከረም 2005 ዓ.ም ብር 130.00 በየወሩ በድምሩ 520.00 (አምስት መቶ ሃያ ብር) ጭማሪ በማድረግ መከፈላቸው፣በአመልካች የክልሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስተባባሪዎች እጅ ብር 9000.00 (ዘጠኝ ሺህ ብር) የያዘ ሰደን ከሚያዝያ 19 ቀን 2004 ዓ.ም እስከ ህዳር 14 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ ሳያወራረድ እንዲቆይ በቃል መፍቀዳቸው፣ተጠሪ በተለያዩ ግለሰቦች ክፍያ ሲፈፅሙ ተቀናሽ የሚደረግ ዊዝሆልዲንግ ታክስ 2 %) ከሐምሌ ወር 2003 ዓ.ም እስከ መስከረም ወር 2005 ዓ.ም ድረስ ብር 17,092.70 (አስራ ሰባት ሺህ ዘጠና ሁለት ብር ከሰባ ሳንቲም) በወቅቱ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ገቢ ያለማድረጋቸው፣ህዳር 04 ቀን 2005 ዓ.ም ከቀኑ 11፡00 ከአስተደደርና ፋይናንስ ኃላፊ ቢሮ በኮምፒዩተር ላይ ተሰክቶ የነበረ 4GB የፍላሽ ዲስክ ያለ አመልካች ማህበር ፈቃድ መውሰዳቸው፣የቅጥር ውል ላልተፈፀመላቸውና ላልታደሰላቸው ሰራተኞች ደመወዝ መክፈላቸው፣ግኝዖች በእቅድ ከተያዘው በጀት በላይ እንዲፈፀሙ ማድረጋቸው፣ከፋይናንስ ውጪ ሰነድ ማዘጋጀታቸው፣ከአለም አቀፍ የሥራ ድርጅት የተገኘውን ብር 184,206.00 “ወርልድ ለርኒግ” ከተባለ ድርጅት የተገኘ በማስመሰል በጀት ምንጩን በማሳሳት መመዝገባቸው፣አመልካች ድርጅት ምንም እዳ ሳይኖርበት በስራ ማስኪያጃ 19,000.00 (አስራ ዘጠኝ ሺህ ብር) ከተለያዩ ወጪዎች ብር 162,000.00 (አንድ መቶ ስልሳ ሁለት ሺህ) እዳ ያለበት መሆኑን አስመስለው መግለፃቸው፣ተጠሪ የአመልካችን ብር 500.00 እዳ እያለባቸው ለአንድ አመት ያህል ገቢ ያለማድረጋቸው ስለመሆናቸው ዘርዝሮ እና ከእነዚህ ጥፋቶች በዲስፕሊንና ኮሚቴ ውሳኔና በኦዲት ሪፖርት መረጋገጣቸውን ጠቅሶ የስራ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የፌዴሬሽን ተ/ዋና ስራ አስኪያጅና አትክልተኛ ደመወዝ እንዲጨመር ከሚመለከታቸው አካላት የደረሳቸውን የደመወዝ ዝርዝርና በአመልካች መስሪያ ቤት ይገኛል የተባለውን ሰነድ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሰነዱ ከቀረበለትና ከተጠሪ እጅ ያለውን ቀሪ ሁሉ ከተመለከተ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የፈፀሙት የዲስፕሊን ጥፋት የለም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደ ሚለው ድምዳሜ ደርሶ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት የካሳ ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ክፍያ ለዘገዩበት ክፍያና የሁለት አመት ፈቃድ እንዲከፍላቸው፣የስራ ስንብት ግን የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚና የተከፈላቸው በመሆኑ አይከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው፡፡ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈል ተብሎ በተወሰነው የውሳኔ ክፍል ቀጥተኛ የይግባኝ አቤቱታ፣ተጠሪ ደግሞ በድርጅቱ ከአስራ አምስት አመት በላይ አገልግለው ለሰባት አመታት ለአገለገሉት ጊዜ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆናቸው ለቀሪዎቹ አመታት የሥራ ስንብት ክፍያ እንዳገኙ መደረጉና የአመት ፈቃድም ሲተላለፍ የቆየ ሁኖ እያለ የሁለት አመት ብቻ ታስቦ እንዲከፈላቸው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው በሚል መስቀለኛ የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ ስራቸውን ሲሰሩ ከአስራ አምስት በላይ የዲስፕሊን ግድፈት የፈፀሙ ስለመሆኑ በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጦ እያለ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ በስራቸው ላይ ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆኑ በኦዲት ሪፖርትና በአመልካች መስሪያ ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ ተረጋግጦ ሳለ የሥር ፍርድ ቤቶች ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎች ለተጠሪ እንዲከፈሉ የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ከግራ ቀኙ ክርክር፣ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪን አሰናበትኩ የሚለው አስራ አምስት ያህል የዲስፕሊን ግድፈቶችን ተጠሪ ስለመፈጸማቸው ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ሲሆን ይህንኑ ለማስረዳትም የፌዴሬሽኑ የአስተዳደር ማኑዋል በሚያዘው መሰረት የተቋቋመው የዲስፕሊን ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔና የኦዲት ሪፖርት ሰነድ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል የቀረቡትን እነዚህን የሰነድ ማስረጃዎች የማስረጃነት ዋጋ ሳይሰጡ አልፈዋል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የዲስፕሊን ኮሚቴውን የውሳኔ ሰነድ ያልተቀበሉት ተጠሪ ሰነዱን ባለማመን ፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸውን በመጥቀስ ሲሆን የኦዲት ሪፖርቱን ደግሞ የስራ ስንብቱ ከተደረገ በኃላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠቃለለ በመሆኑ የተጠሪ የዲስፕሊን ግድፈት መኖሩ ታውቆ ስንብቱ ተደርጓል በማለት የሚያስችል አይደለም የሚለውን አብይ ምክንያት ከአሰፈሩ በኃላ በተጨማሪነት የኦዲት ሪፖርቱ ከቀድሞ ሰራተኛ ያልተሰራ ስራ መኖሩን ገልጾ በተተኪ ሰራተኛ ሊሰራ እንደሚገባ መገለጹ ከሂሳብ አሰራር ጉድለት ጋር ተያያዥ የሆኑትን ሰራተኛ ማንነት የማይገልጽና የማያብራራ ነው፣ኦዲት ሪፖርቱ በተራ ቁጥር 4.8፣4.3 እና 4.9 የተዘረዘሩት ካልሆነ በስተቀር ቀሪዎቹ የኦዲት ሪፖርት ይዘቶች ከቀረቡት መከራከሪያ ነጥቦች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ተያያዥነት የሌላቸው ናቸው፣የኦዲት ሪፖርት ተራ ቁጥር 5 ስር የሂሳብ ሰራተኛዋ የብቃት ችግር ያለባቸው መሆኑን መግለጹም ለስንብቱ ምክንያት የተባለው የዲስፕሊን ጉድለት በመሆኑ አግባብነት የሌለው ነው የሚሉትንና የደመወዝ ጭማሪ አከፋፈል በተመለከተ ደግሞ ተጠሪ በሚመለከተው አካል ተፈቅዶ የፈፀሙት መሆኑን አረጋግጠዋል የሚሉ ምክንያቶችን አስፍሮ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድን ፍሬ-ነገር ለማስረዳት በተከራካሪ ወገኖች ተቆጥሮ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ በህጉ ተቀባይነት የለውም (inadmissible) ወይም ከተያዘው ፍሬ-ነገር ጭብጥ ጋር አግባብነት የለውም እስካልተባለ ድረስ ሰነዱ በማስረጃነት ተመርምሮ እንዲሁም ከሌሎች ማስረጃ አይነቶች ጋርም በአንድነት ታይቶና ተመዝኖ የሚገባው ዋጋ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ምክንያቱም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 138 ስር እንደተመለከተው በህግ አግባብ የተቆጠረው ማስረጃ በዝምታ የሚታለፍበት ወይም ከሕግ ውጪ የማስረጃነት ዋጋ ሳይሰጥ ውድቅ የሚሆንበት አግባብ የለምና፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንኑ በፍትሐብሄር ስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ደንብ ያለፈው በአመልካች በኩል የቀረበው የዲስፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ የሰነድ ማስረጃ በተጠሪ እምነት ያላገኘና ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበበት ጉዳይ ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ያቀረበው ይኼው ሰነድ የፌዴሬሽኑ የአስተዳደር ማኑዋል በሚያዘው መሰረት በተቋቋመው ኮሚቴ ተጠሪ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡበት ተደርጎና ተገቢነት አላቸው የሚሏቸው ማስረጃዎች ቀርበው በተጠሪ ተፈጸሙ የተባሉትን ጥፋቶች መኖራቸውን፣ተጠሪም በዲስፕሊን ኮሚቴው ጥፋቶችን ማመናቸውን በማረጋገጥ የተሰጠ መሆኑን የሰነዱ ይዘት በግልፅ ያሳያል ፡፡ ይህ ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ ሲሆን የማስረጃነት ዋጋ ሊያጣ የሚችለው ተጠሪ በፍርድ ቤት ክስ በማቅረባቸው ወይም ሰነዱን ባለማመናቸው ሳይሆን ሰነዱ በፌዴሬሽኑ የአስተዳደር ማኑዋል መሰረት ባልተቋቋመ የዲስፕሊን ኮሚቴ የተዘጋጀ፣ወይም ዲስፕሊን ኮሚቴው ከሕግ ውጪ ማስረጃውን በመስማትና በመመዘን ያልተገባ ድምዳሜ ይዞ የሰጠው ውሳኔ መሆኑን ተጠሪ በፍርድ ቤት ላይ በሚያቀርቡት ክርክርና ማስረጃ የአመልካችን ማስረጃ ሲያስተባብሉ እንጂ እንዲሁ በደፈናው ማስረጃውን አላመኑም፣ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል በሚል ምክንያት አይደለም፡፡ በየመስሪያ ቤቱ የሚቋቋሙ የዲስፕሊን ኮሚቴዎች በሕግ አግባብ የሚቋቋሙና የሰራተኛው ጥቅም ያላግባብ እንዳይጎዳ ተገቢው መጣራት ተደርጎ እርምጃ እንዲወሰድ እገዛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያደርጉ ናቸው ተብሎ የሚታመን ሲሆን የዲስፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ በማስረጃነት ዋጋ ሊያጣ የሚገባው ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ሕጋዊ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች መስሪያ ቤት ያቀረበውን የዲስፕሊን ኮሚቴ የውሳኔ ሰነድ የማስረጃነት ዋጋ ያሳጡት ተጠሪ ተገቢውን ማስረጃ አቅርበው ሰነዱ ሕገ ወጥ መሆኑን ሳያስረዱና ይህንኑ ለማስረዳትም በሕግ አግባብ የቆጠሩት ማስረጃዎች ሳይኖር ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ አስቀርበን ከጠቅላላ የግራ ቀኙ የክርክር ሂደት ተገንዝበናል፡፡

የኦዲት ሪፖርቱን በተመለከተም ኦዲት የተደረገው እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1/2011 እስከ ኦክቶበር 31/2012 ድረስ ያለው የአመልካች ማህበር ዝርዝር ሂሳብ ሁኖ ሪፖርቱ በተጠቀሱት 22 ወራት ውስጥ የታዬውን የሂሳብ አያያዝ ችግር ከዝርዝር ከማስቀመጡ በፊት የ2012 በቀድሞዋ የሂሳብ ሰራተኛ ያልተሰራ መሆኑ፣በተተኪው ሰራተኛ ሊሰራ የሚገባ እና ይህም የተጀመረ መሆኑን በመግቢያው ላይ ያሰፈረ መሆኑን ሰነዱ ያሳያል፡፡ የኦዲት ሪፖርቱ የተጠቃለለው በእርግጥ ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም ስለመሆኑ ሰነዱ የሚገልጽ ሲሆን ስንብቱ የተከናወነው ደግሞ ጥር 10 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን የስንብት ደብዳቤው ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት በተደረገበት ጊዜ የሂሳብ ስራው የሚመለከተው ተጠሪን ስለመሆኑ አመልካች በክሱ የጠቀሰ ሲሆን ተጠሪም ቢሆኑ የኦዲት ስራው ራሳቸውን የሚመለከት ሁኖ በውጤቱ ግን ተጠያቂ ያላደረጋቸው መሆኑን ጠቅሰው አመልካች አለኝ የሚለው ይዜው የሰነድ ማስረጃ በፍርድ ቤት እገዛ እንዲቀርብላቸው በማስረጃ ዝርዝር መግለጫቸው ላይ የጠቀሱ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ውስጥ ያሉት ሰነዶች የሚያሳዩት ሐቅ ሲሆን የስንብት ደብዳቤው መሰረት ያደረገው የዲስፕሊን ኮሚቴውን ውሳኔ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሲታይ በዚህ ውሳኔ መሰረት ተጠሪ በ17 የዲስፕሊን ክሶች ተከሰው በ15ቱ ጥፋተኛ ሁነው የዲስፕሊን ኮሚቴ ማግኘቱን፣ጥፋቶቹም ከባድ መሆናቸውን ጭምር የሚገልጽ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ላይ ክስ ያቀረቡት መጋቢት 09 ቀን 2005 ዓ.ም እንደመሆኑ መጠን አመልካች ስንብቱ ሕጋዊ ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች በዲስፕሊን ኮሚቴው ውሳኔና ይህንኑ የሚደግፉትን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎችን በማስረጃነት ቢያቀርብ ከስንብቱ በኃላ የተገኘ ማስረጃ ነው ተብሎ የማስረጃነት ዋጋ የሚያጣበት የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ደንብ የለም፡፡ አንድ ማስረጃ ለአንድ ጉዳይ ሊቀርብ አይገባም ተብሎ ውድቅ መደረግ ያለበት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሁኖ ሲገኝ ወይም በሕጉ ለማስረጃነት እንዲቀርብ ተለይቶ የተቀመጠ የማስረጃ አይነት መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪን የዲስፕሊን ኮሚቴ ውሳኔን እና የኦዲት ሪፖርት ማስረጃዎችን ውድቅ ያደረጉት ተገቢውን የማስረጃ አቀራረብና አቀራረብ ስርዓት ተከትሎ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች የማስረጃነት ዋጋ አላቸው ከተባሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደግሞ በማስረጃዎቹ የተረጋገጡት የዲስፕሊን ጥፋቶች ከባድ መሆናቸውንና የተደጋገሙ መሆኑን የሚገልፁና ተጠሪ ስራቸውን በአግባቡ የማይወጡ የነበሩ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ተጠሪ ከባድ የዲስፕሊን ግድፈቶች ሲፈጽሙ የነበረ ከሆነና ጥፋቶችም ተደጋጋሚ መሆናቸው ግልጽ ከሆነና አመልካች በተጠሪ የስራ ግዴታቸውን በአግባቡ ባለመወጣት ስራው በአግባቡ ያልተሰራለት፣በገንዘብ ጥቅሙ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ከተረጋገጠ በአመልካች ማህበር የገንዘብ ጥቅም ላይ ጉዳት ያለመደረሱን የማስረዳት ግዴታ የተጠሪ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን ተጠሪ የአመልካች የሠነድ ማስረጃዎች የተጠሪን ጥፋት የሚያረጋግጡ አይደሉም ከማለት ውጪ ይህንኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ያለማቅረባቸውን የሥር ፍርድ ቤትን ዋና መዝገብ በማስቀረብ ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ የፈፀሙት ጥፋት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1/ሸ/ የሚሸፈንና የተጠሪን የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በተጠሪ የተፈፀመ ጥፋት የለም በማለት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲሉ የሰጡት ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/ እና አንቀጽ 12(2) (7) ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት፣መንፈስ አላማ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የተጠሪን የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1(ሸ)) እና 12(2)(7) ድንጋጌዎች መሰረት ሕጋዊ እንጂ ሕገ ወጥ ተግባር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42383 ህዳር 19 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 139394 ሐምሌ 30 ቀን 2006 ዓ.ም ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ ሕጋዊ ነው፣አመልካች ለተጠሪ ካሳም ሆነ የሥራ ስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡
3. የዓመት እረፍት የ57 ቀናት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ብር 8,550.00 (ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ብር) እና ይህንኑ ክፍያም ያላግባብ ያዘገዩ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ መሰረት የአንድ ወር ደመወዝ ብር 4,500.00 (አራት ሺህ አምስት መቶ) ይክፈል ብለናል፡፡
4. ለክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ት እ ዛ ዝ

ጥቅምት 26 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል። ይፃፍ።

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ106610

ግንቦት 14 ቀን 2007

ዳኞች - አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መ·ስጠፋ አህመ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ካብራክ ተኮላ - ጠበቃ ጋር ቀረበ

ተጠሪ ፡-የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጀስቲክስ - ነ/ፈ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ በተጠሪ ድርጅት ከታህሳስ 26/2000 - ጥር 29/2005 ዓ.ም ድረስ ለ5 አመት ከ1 ወር ስሰራ ቆይቼ ስራዬን በራሴ ፍቃድ ብለቅም፤ የስንብት፤ ለዘገየበት እና አበል አልተከፈለኝም በማለት እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ አመልካች ያለደሞዝ የወሰዱት እረፍት ከተጠናቀቀ ከህዳር 17/2005 ዓ/ም ጀምሮ ወደ ሥራ ያልገቡ መሆኑን በመረዳቱ ከህዳር 17 /2005 ዓ/ም ጀምሮ ውላቸው መቋረጡን ፤ እና 5 አመት ያልሞላቸው በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ስለሆነ ስንብት አይገባቸውም፤ ይገባቸዋል ከተባለም የማስጠንቀቂያ ግዜ 1 ወር ደሞዝና የቦንድ መግዣ ተቀንሶ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤትም ተጠሪ የአመልካችን የስራ መልቀቅ ጥያቄ ከ29/6/2005 ጀምሮ ከተቀበለ እና ካሰናበታቸው በኋላ የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያት መፈጸሙን አረጋግጫለሁ በማለት ሌላ ደብዳቤ በመጻፍ ክፍያ አልፈጽምም የሚልበት ምክንያት አይኖርም በመሆኑም የ5 አመት ከ1 ወር የስንብት ክፍያ የቦንድ ተቀንሶ ተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በቀጣይነት ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤትም ተጠሪ አመልካችን የመልቀቂያ ጥያቄ ተቀብሎ ቢያሰናብተውም፤ ድርጊቱ ስህተት ነው ብሎ ካመነበት ስህተቱን ለማረም ይችላል፤ አመልካችም ከህዳር 17 ቀን 2005 ጀምሮ በስራ ላይም አልተገኙም፤ በመሆኑም ተጠሪ ውል ማቋረጫ ምክንያት አግኝቻለው በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስንብት አልከፍልም ማለቱ ባግባቡ ነው፤ በማለት የስር ውሳኔን ሽሮታል፡፡ የአመልካች አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልጹ፤ ስራዬን የለቀቅኩት በጥር 29/2005 በጻፍኩት ደብዳቤ ሲሆን ተጠሪም የስንብት ደብዳቤ በሚያዝያ 11/2005 ሰጥቶኛል፡፡ ይሁን እንጂ በ17/03/2005 ነበር ወደ ስራ መመለስ የነበረብህ፤ ግንቦት 8/2005 ስህተት መፈፀሜን ተረዳሁ በማለት ጥር 29/2005 ያስገባውን ደብዳቤ አልቀበልም በማለት ከእረፍት በኋላ ወደስራ አልገባህም በማለት ከ ህዳር 17/2005 ጀምሮ ነው፤ መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ የተጠቀሰውም የሰበር ውሳኔ ቁ 45889 ከተያዘው ጉዳይ አይመሳሰልም፡፡ ሰራተኛውና አሰሪው የስራ ውላቸው ጸንቶ ባለበት የሚደረግ እርምት እንጂ፤ ከስራ በገዛ ፍቃዱ ለለቀቀ ሰራተኛ ኪሊራንስ ተሰጥቶት ከ4 ወር በኋላ ስህተትን ማረም አይደለም፡፡ በመሆኑም በፍቃዱ ከተሰናበትኩ በኋላ ግንቦት 8/2005 የተጻፈውን፤ የተጠሪን ደብዳቤ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተቀብሎት፤ አመልካች ከህዳር 17/2005 በኋላ ወደስራ ያለመግባቱ ተረጋግጦ እርማት መደረጉ ባግባቡ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡

በዚህም መሰረት ችሎቱም አመልካች የሥራ መልቀቂያ ለተጠሪ ሚያዝያ 11/2005 ዓ.ም ከሰጠው በኋላ፤ እንደገና ያለደሞዝ የወሰድከው ዕረፍት የተጠናቀቀው በ17/3/2005 ሆኖ ወደሥራ አልገባህም በማለት ከዚሁ ግዜ ጀምሮ የስራ ውሉን ማቋረጡ፤ እና ጥር 17/2005 ክሊራንስ እንዲያዞር ከመፍቀዱ አኳያ ስንብቱ ህጋዊ ነው መባሉን በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙ በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ እንዲቀባበሉ በማድረግ አከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በሰበር መልሱ የሚከራከረው፡- አመልካች እረፍታቸውን ጨርሰው ካልተመለሱ ማስታወቂያ በማውጣት ጥሪ በማድረግ ካልመጡ ውል ማቋረጡ የተሻለ ይሆን ነበር፤ ይህ ያለመደረጉ ምንም መብት አይፈጠርላቸውም እንጂ፤ ሌላው ኪሊራንስ የተሰጣቸው አስተዳደሩ ስራ ላይ ነበሩ በሚል እምነት ነው፤ አመልካች ወደ ስራ መመለስ ከነበረባቸው 17/3/05 ጀምሮ እስከ ጥር 30/2005 ድረስ ወደስራ አልተመለሱም፤ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 27/1/ ለ መሠረት ከ5 ቀን በላይ ስለቀሩ መሰናበታቸው ባግባቡ ነው፤ በመሆኑም ተጠሪ የፈጸመውን ስህተት ባወቀበት ጊዜ ማረሙና አመልካችን ማሰናበቱ አግባብነት ያለው በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው መባሉ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት ይከራከራል፡፡ አመልካች በበኩሉ፡- ከተጠሪ ጋር በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 25 መሰረት በስምምነት የስራ ውላችንን ካቋረጥን በኋላ እና ተጠሪ ጥያቄዬን ተቀብሎ፤ ክሊራንስ አዞሬ እንድወጣ ከፈቀደና ውሉ ከተቋረጠ ወድያ የሚታረም ነገር አይኖርም በማለት የስር ክርክሩን በማጠናከር የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ እኛም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

በመሆኑም ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የክርክሩን አጠቃላይ ሂደትና የስር ውሳኔዎችን እንዳየነው አመልካች በራሳቸው ፍቃድ የስራ መልቀቂያ በመጠየቅ ተጠሪም በጥያቄው መሰረት እንዲፈጸም ፈቅዶና አመልካችን ካሰናበተ በኋላ፤ ያለማስጠንቀቂያ የሚያሰናብት ምክንያት አገኘሁ በማለት አስፈላጊውን ክፍያ አልከፍልም በማለቱ ነው፡፡ እንግዲህ ተጠሪ የሚለው አመልካች እረፍት በ17/2/2005 ወስደው ወደስራ መመለስ የነበረባቸው በ17/3/2005 ሆኖ ሳለ በቦታው ተገኝተው ስራ ባለመጀመራቸው እና በስህተት በጥር 30/2005 የቀረበውን የአመልካች መልቀቂያ ጥያቄ ተቀብለን ሚያዝያ 11/2005 እንዲፈጸም ብናደርግም ስህተት መሆኑን በመረዳታችን ከህዳር 17/2005 ጀምሮ ማሰናበታችን ባግባቡ ነው የሰበር ሰሚው ውሳኔ 45889 አሰሪው ስህተቱን ማረም የሚችል መሆኑን ወስኗል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ያየው ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የስራ መልቀቂያ ተቀብሎ ካሰናበተው በኋላ ሌላ ምክንያት አገኘሁ በማለት ድጋሜ ደብዳቤ መጻፍ ተገቢነት የለውም በማለት የስንብት ክፍያ ለአመልካች እንዲከፈላቸው ቢወስንም፤ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ካየው በኋላ ተጠሪ ስህተቱን ማረም ይችላል ሲል የአመልካች ስንብት ባግባቡ ነው በማለት የስር ውሳኔን ሽሮታል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ ሊያርሙት የሚችሉት ስህተት የትኛውን አይነት ስህተት ነው የሚለውን ስናይ የሰበር ውሳኔ ቁ. 45889 ከተያዘው ጉዳይ የማይገናኝ በመሆኑ መከራከሪያ ሊሆን አይገባም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን የመልቀቂያ ጥያቄ ተቀብሎና ለአግባብነቱም ምላሽ ሰጥቶ ካሰናበታቸው እና የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለት ከወራት በኋላ ወደኋላ ተመልሶ ስህተት መፈጸሜን ተረዳሁ ማለቱ ባለቀ ጉዳይ ስህተት ማፈላለግ ካልሆነ በቀር፤ ተጠሪን የመሰለ ድርጅት አስተዳደራዊ ስራውን ባግባቡ ባለመወጣት በፈጸመው ጉዳይ የአዋጁን ቁ 377/96 አንቀጽ 27/1//ለ/ን ጠቅሶ ለመከራከር መሞከሩ አግባብነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ እረፍት የሰጠውን ሰራተኛ በተባለው መመለሻ ጊዜ ካልገባ ምን ሊደረግ እንደሚገባ ሳያውቅ የአመልካችን መልቀቂያ ያስተናግዳል ተብሎም የሚታሰብ አይሆንም፡፡ ባጠቃላይ የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ በፍሬ ነገር ደረጃ በማረጋገጥ ክፍያ እንዲከፈላቸው የወሰነው ውሳኔ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አግባብነት የሌለው አሰሪ ስህተቱን ማረም ይችላል ተብሎ የተወሠነው አስገዳጅ ውሣኔ ተጠቅሶ መሻሩ ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡

በመጨረሻም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከስንብት በኋላ የተሰጠውን የውል ማቋረጫ ምክንያት በመቀበል ተጠሪ ስህተቱን ማረም ይችላል በማለት የስር ውሳኔን መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.139381 በቀን 13/12/06 ዓ/ም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 09937 ህዳር 16/2006 የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለአመልካች የስንብት ክፍያ ብር 7,540.50 ይከፈላቸው በማለት የወሰነው ጸንቷል፡፡
3. የግራቀኙ የወጪ ኪሳራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 107002

ግንቦት 14 ቀን 2007ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተሻሊት ይመሰል

አመልካች፡- ሲስተር ትዕግስት ፈቃድ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኤድስ መከላከያ ማህበራዊ አገልግሎት ድርጅት አልቀረበም

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 177544 መስከረም 22 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 197235 ህዳር 17 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣራቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ መደብ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በምዕራብ ኦሮሚያ አሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ውሳኝ ቦርዱ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል ፡፡

1- አመልካች በተከሳሽ (ተጠሪ) ድርጅት በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በነርስ ካውንስለር ሰባተኛ ደረጃ ተቀጥሬ በመሥራት ላይ እያለሁኝ የቤተሰብ ችግር ስላጋጠመኝ በራሴ አቤቱታ አቅራቢነት በደረጃ ሶስት የነርስ ካውንስለር የሥራ መደብ ወደ ነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተዛውሬና ተመድቤ በመሥራት ላይ እገኛለሁ ፡፡ ሆኖም ተከሳሽ እኔ በፊት ተቀጥሬበት የነበረው ሰባተኛ ደረጃ ነርስ ካውንስለር ለመመደብ መስፈርቱን የሚያሟላ የውስጥ ሠራተኛ የለም አግባብ ባልሆነ መንገድ የመሥሪያ ቤቱን መተዳደሪያ ደንብ በመጣስ ከአምስት ዓመት በፊት የሥራ ስንብት ክፍያና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ከፍሎ ያሰናበታትን ሠራተኛ በመጥራት ያለምንም ውድድር በመቅጠር ደረጃ ሰባት ነርስ ካውንለር አድርጎ መድቧታል፡፡ ከሳሽ መስፈርቱ የሚማላ የውስጥ ሠራተኛ እያለሁ የውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠራተኞች ተወዳድረው በእድገት በሚመደቡበት የሥራ መደብ ላይ የነቀምቴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እኔን በቦታው ላይ መመደብ ሲገባው የውጭ ማስታወቂያ በማውጣት ቅጥር መፈፀሙ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ የሚጥስና የእኔን መብት የሚያጣብብ በመሆኑ፣ቅጥሩን በመሰረዝ እኔን በቦታው ላይ እንዲመድቡኝ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት የምዕራብ ኦሮሚያ አሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ክስ አቅርባለች፡፡

2- ተከሳሽ (ተጠሪ በበኩሉ ከሳሽ በሶስተኛ ደረጃ ነርስ ካውንስለር የሥራ መድብ ተመድባ የምትሠራ ሠራተኛ ናት ከሳሽ አራት ደረጃዎችን በመዝለል ደረጃ ሰባት ነርስ ካውንስለር ሥራ መደብ ላይ መመደብ አለብኝ በማለት ያቀረበችው ክስ የህግ ስህተት የለውም ፡፡ ከሳሽ ለደረጃ ሰባት የሚመጥን የሙያ ብቃት ስነምግባርና የሥራ አፈፃፀም የላትም ፡፡ ባለው የሥራ መደብ ፤ሥራውን ለመሥራት የሚችል ሠራተኛ በዕድገት ወይም በቅጥር የመመደብ መብት ያለው አሠሪው (ድርጅቱ) እንጅ ሠራተኛው አይደለም ፡፡ ከሳሽ ያለምንም ውድድር የሥራ መደቡ እንዲሰጣት ያቀረበችው ክስ ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

3- የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ ከሳሽ በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ፣ተመድባ ስትሠራ የነበረ መሆኑ በተከሳሽ አልተካደም ከሳሽ ወደ ወለጋ ቅርንጫፍ የተዛወረችውና በደረጃ ሶስት የሥራ መደብ ላይ ተመድባ ለመሥራት የተስማማችው በቤተሰብ ችግር ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል ፡፡ ተከሳሽ ከሳሽ በዲሲፒሊን ችግር ምክንያት ወደ ደረጃ ሶስት ብቅ ብላ የተመደበች ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ስለዚህ ተከሳሽ ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ተመድባ ስትሠራ የነበረችውን ተከሳሽን ሣያሳውቅ ከውጭ ሌላ ሰው የቀጠረው ከሳሽ ቦታውን እንዳታገኝ ለማድረግ በማሰብ በክፋ ልቦና ነው፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ከሳሽን በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ መድቦ የደመውዝን ልዩነት አስቦ ሊከፍል ይገባል በማለት በድምፅ ብልጫ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4- የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሠኘት ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ መልስ ሰጭ (አመልካች) ያለውድድር በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ እንድትመደብ የሰጠው ውሳኔ የመሥሪያ ቤቱን የሥራ አመዳደብ መመሪያ መሠረት ያላደረገ ነው በማለት ቦርዱ የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል ፡፡ አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርባለች ፡፡ የክልሉ የሰበር ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም ፡፡

5- አመልካች ህዳር 18 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በአንድ የሥራ መደብ ላይ የውጭ ሰው የሚቀጠረው በመጀመሪያ ለቦታው የሚመጥን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውስጥ ሠራተኛ ካለ እድል ከሰጠ በኃላ መሆን እንዳለበት በግልፅ ያስቀምጣል ። አመልካች በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ተመድቤ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ስሰራ እንደነበር ተረጋግጧል ። ይህ ሆኖ እያለ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት አመልካች በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ልትመደብ አይገባትም በማለት የሰጡት ውሳኔ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክታለች ። ተጠሪ መጋቢት 23 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ያለውድድር በቀጥታ ለመመደብ ጥያቄ ያቀረበችበት ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ለመወዳደር የሚስፈልገው የትምህርት ደረጃ አድቫንስድ ዲፕሎማ ሲሆን አመልካች ያላት ድፕሎማ በመሆኑ ለቦታው ለመወዳደር አትችልም አመልካች አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ደረጃ ሰባት ተመድባ የነበረው በድሮው መዋቅር ነው። ስለዚህ ያለምንም ውድድር በደረጃ ሰባት እንድትመደብ የተሰጠውን ውሣኔ መሻሩ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል። አመልካች ሚያዚያ 8/ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ በነርስ ሙያ ዲፕሎማና ዲግሪ የትምህርት መርሃ ግብር እንጂ አድቫንስድ ዲፕሎማ የሚባል የትምህርት መረሃ ግብር የለም በነርስ በአድቫንስ ዲፕሎማ የተመረቀ ባለሙያ የለም ። ተጠሪ ዕውነትነት የሌላቸውን መስፈርቶች በማንሣት የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክራለች።

6- ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ለዚህ ሰበር ችሎት ግራቀኙ በዕሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት አመልካች በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መስፈርቱን የማሟላው ሠራተኛ ሣልወዳደር የደረጃ እድገት ሣይሰጠኝ ተጠሪ ቅጥር በመፈፀም የሥራ መደቡን ማስያዙ ሕገ ወጥ ስለሆነ ቅጥሩ ተሰርዞ እኔ በቦታው ላይ እንድመደብ በማለት ያቀረበችውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምረናል ።

7- ጉዳዩን እንደመረመርነው በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ክፍት የሥራ መደብ ሲኖር ድርጅቱ ሌላ ሠራተኛ ከመቅጠሩ በፊት መስፈርቱን የሚያሟሉ የድርጅቱ ሠራተኞች ካሉ ተወዳድረው በእድገት በቦታው ላይ እንዲመደቡ እድል መስጠት ያለበት መሆኑ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና የሰው ሀይል አመዳደብ መመሪያ በግልፅ የተደነገገ በመሆኑን አመልካችና ተጠሪ የሚተማመኑበት ነጥብ ነው። አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ጭብጥ አመልካች ተጠሪ የመተዳደሪያ ደንቡንና መመሪያውን በመጣስ ለደረጃ ሰባት የሚያስፈልገውን መስፈርት የማሟላ ሠራተኛ እኔ እያለሁ ለእኔ እድል ሣይሰጠኝ ከውጭ ሠራተኛ በመቅጠር የስራ መደቡን ማስያዙ ህገወጥ ነው በማለት ያቀረበችውን ክስ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ በመካድ በነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የነበረውን ደረጃ ሰባት የስራ መደብ በቅጥር ሰው ያሟላሁት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካሉኝ ሠራተኞች ለሥራ መደቡ የሚያስፈልገውን መስፈርት የሚያሟላ ሠራተኛ ስለሌለኝ ነው፡፡ አመልካችም ለደረጃ ሰባት የሚያስፈልገውን መስፈርት አታሟላም የሚል ክርክር በማቅረቡ ነው፡፡ ይህም የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 በሚደነግገው መሠረት ፣ተጠሪ ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ በውጭ ቅጥር ያሟላው የሥራ መደቡ የሚያስፈልገውን መስፈርት የሚያሟሉ ሠራተኞች እንዲወዳደሩ እድል ከሰጠ በኋላ መስፈርቱን የሚያሟላ ሠራተኛ ባለማግኘቱ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው አከራካሪ ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡

8- ተጠሪ በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ላይ የውጭ ቅጥር በመፈፀም በሥራ መደቡ ላይ ሠራተኛ ከመመደቡ በፊት የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና የሰው ሀይል ምደባ አፈፃፀም መመሪያ በሚደነግጉት መሠረት በሥራ መደቡ የሚያስፈልገውን የትምህርት ዝግጅት፣የሥራ ልምድና ሌሎች መስፈርቶች የሚያሟሉ ሠራተኞች ማስረጃውን በማቅረብ እንዲወዳደሩ እና እንዲመዘገቡ የእድገት ማስታወቂያ ያላወጣና መስፈርቱን የሚያሟሉ ሠራተኞች እንዲወዳደሩ እድል ያልሠጠ መሆኑን የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሣኔ ተረድተናል ፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ አመልካችና ሌሎች የድርጅት ሠራተኞች ለደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ለመወዳደር የሚያስችላቸውን ማስረጃ በማቅረብ እንዲወዳደሩ የውስጥ የእድገት ማስታወቂያ ሣያወጣና መስፈርቱን ለሚያሟሉ ሠራተኞች እድሉን ሣይሰጥ ፣ሠራተኛ በመቅጠር በደረጃ ሰባት ላይ መመደቡ የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብና የሰው ሀይል አመዳደብ መመሪያ መሠረታዊ መርህ የሚጥስና ህጋዊ ፅውቅና ሊሰጠው የማይገባው ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡

9- ተጠሪ የራሱ የሆነ የሥራ መዋቅር ፣አደረጃጀትና የሥራ መደብ ያለው ድርጅት መሆኑ አያከራክርም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ በተለያዩ አካባቢዎች በራሱ የሆኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያሉት መሆኑንና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹም ያላቸው ተመሳሳይ የሥራ መደቦች የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጅት፣የሥራ ልምድና ሌሎች መስፈርቶች ተመሣሣይነት ያላቸው እንደማይሆኑና በተመሣሣይ የሥራ መደብ ተመድበው ለሚሠሩ ሠራተኞች የሚከፈለው ደመወዝና ሌሎች ሁኔታዎች ተመሣሣይነት ያላቸው እንደሚሆኑ ከተጠሪ ድርጅታዊ ተፈጥሮአዊ ባህሪና መተዳደሪያ ደንብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ ሰባት ነርስ ካውንስለር የሥራ መደብ ላይ ለመመደብ የሚያስፈልገው መስፈርትና በነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ ሰባት ነርስ ካውንስለር የሥራ መደብ የሚያስፈልገውን መስፈርት አንድ አይነትና ተመሣሣይ መስፈርቶች መሆናቸውን በመካድ ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ አመልካች በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ መስፈርት በሚሟላት ተመድባ ስትሠራ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ አዲስ አበባ የነበራትን ደረጃና ደሞወዟን በመቀነስ ወደ ነቀምት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅርንጫፍ የተዛወረችው በነበረባት የቤተሰብ ችግር ምክንያት አመልካች ጥያቄ በማቅረቧ ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተመድባ ስትሠራበትና ደመወዝ ስትበላበት ለነበረው ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ለመወዳደር የሚያስፈልገውን መስፈርት አታሟላም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሠረት ያለው መከራከሪያ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ ለአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ያላቀረበውን አዲስ የፍሬ ጉዳይ መከራከሪያ በዚህ ሰበር ችሎት በማንሣት ለደረጃ ሰባት የሚያስፈልገው የነርስ አድቫንስድ ዲፕሎማ ነው የሚልና መዋቅሩ ስለተለወጠ መስፈርቱም ተለውጧል በማለት ያቀረባቸው መከራከሪያዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329 ንዑስ አንቀፅ/1/ የሚጥስ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው መከራከሪያ ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ተጠሪ የነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ባለው ደረጃ ሰባት ክፍት የሥራ መደብ ለመወዳደር አትችልም በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

10- አመልካች በተጠሪ ድርጅት ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ላይ ተመድባ በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስትሠራ የነበሩ መሆኑንና አመልካች ይህንን የሥራ መደብ ለቅቃ በነቀምት ጽ/ቤት በደረጃ ሶስት የሥራ መደብ የተመደበችው በራሷ ጥያቄ አቅራቢነት መሆኑ ፣ተጠሪ በነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ላለው ክፍት ቦታ ለመወዳደር የሚያስችላት ቢሆንም ፣ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ሣትወዳደር የሥራ መደቡን ለማግኘት የሚያስችላት አይደለም ፡፡ ከዚህ አንፃር የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ አመልካች ከሌሎች ሠራተኞች ጋር በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ የመወዳደር እድል እንዲሰጣት ውሣኔ መስጠት ሲገባው አመልካች ያለምንም ውድድር ደረጃ ሰባት ላይ እንድትመደብ የሰጠው ውሳኔ የተጠሪን መተዳደሪያ ደንብና የሰው ሀይል አመዳደብ መመሪያ ያልተከተለ በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት አሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ አመልካች ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ላይ ያለምንም ውድድር እንድትመደብ የሰጠውን ውሣኔ መሻራቸው ተገቢ ቢሆንም ፣ተጠሪ አመልካችና ሌሎች ሠራተኞችን በማወዳደር የውስጥ እድገት ማስታወቂያ ሣያወጣና ለሠራተኞች እድል ሣይሰጥ የውጭ ቅጥር መፈፀሙ ህገወጥ ተግባር በመሆኑ ፣ተጠሪ የፈፀመው ቅጥር ተሰርዞ አመልካችንና ሌሎች ሠራተኞችን በማወዳደር በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ በእድገት እንዲመደብ ውሣኔ ሣይሰጡ ማለፋቸው አመልካች ያቀረበችውን ግልፅ የዳኝነት ጥያቄና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀፅ 2 ያላገናዘበና በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የምዕራብ ኦሮሚያ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ የውስጥ እድገት ማስታወቂያ ሣያወጣና አመልካችና ሌሎች ሠራተኞች ተወዳድረው በደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ለማደግና ለመመደብ የሚያስችላቸውን እድል ሣይሰጥ የውጭ ቅጥር በመፈፀም ደረጃ ሰባት የሥራ መደብ ላይ መመደቡ ሕገወጥ ተግባር በመሆኑ ተጠሪ በደረጃ ሰባት ላይ የፈፀመው ቅጥር ሊሠረዝ ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች በደረጃ ሰባት የስራ መደብ ለመወዳደር የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን የምታሟላ በመሆኑ ፣ተጠሪ አመልካችንና ሉሎች መስፈርቱን የሚያሟሉ ሠራተኞችን በማወዳደር የውስጥ እድገት ሊሰጥ ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለያራሳቸው ይቻሉ ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 111839

ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ፒ.ኤስ አይ ኢትዮጵያ - ጠበቃ አላምነህ ስንሻው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ እሸቱ ካሳ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ሐምሌ 24 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ክስ በአመልካች ድርጅት በሹፌርነት ተቀጥረው እየሠሩ ባለበት ሁኔታ ያላግባብ ከስራ መሰናበታቸውን ገልፀው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተጠሪ የድርጅቱን መኪና ባግባቡ የመንዳት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ.ም ሰው ገጭቶ ጉዳት ማድረሱንና ከዚህ በኋላም ሰኔ 08 ቀን 2006 ዓ/ም ከደሴ ወደ መቐሌ በሚሄድበት ጊዜ በግድየለሽነት በማሽከርከር በመኪናው ላይ ጉዳት ከማድረሱም በላይ በተሽከርካሪው ውስጥ በነበሩት የድርጅቱ ሰራተኞች ላይ ቀላል የመቁሰል አደጋ ማድረሱንና ይህም በክፍሉ የትራፊክ ፖሊስ መረጋገጡንና አመልካችም ተገቢውን ኮሚቴ አቋቁሞ በማጣራት ከአረጋገጠ በኋላ ስንብቱን ያከናወነ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ/ም ደረሰ የተባለው አደጋ በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ የስራ ስንብት ማከናወኛ ምክንያት ያልሆነ በመሆኑ በይርጋ እንዲሚታገድ፣ ሰኔ 08 ቀን 2006 ዓ/ም ደረሰ የተባለው አደጋ ደግሞ በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት በመኖሩ የደረሰ ነው ቢባልም በከባድ ቸልተኝነት የደረሰ ነው ሊባል የሚችል ያለመሆኑን ጠቅሶ የአመልካችን የስንብት እርምጃ ሕገወጥ መሆኑን በመደምደም ተጠሪ የአምስት ወር ከስድስት ቀናት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 24 ቀን 2007 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የተጠሪ ድርጊት በሕጉ አግባብ ሲጣራ ቆይቶ ተጠሪ ከባድ ቸልተኝነት ያለባቸው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ለተፈፀመው እርምጃ ድርጊቱ በይርጋ የታገደ ነው መባሉ አሰሪ የሰራተኛውን ጥፋት በትክክል አወቀ ሊባል የሚችልበትን አግባብና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/1/ ስር ስለ ከባድ ቸልተኝነት የተመለከተውን የህጉን ድንጋጌ ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ሰኔ 08 ቀን 2006 ዓ.ም ደረሰ ለተባለ አደጋ የተጠሪ ቸልተኝነት ከባድ ሊባል የሚችል አይደለም ተብሎ የስንብቱ እርምጃ ሕገወጥ ነው መባሉ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በሹፌርነት ተቀጥረው እየሠሩ ባለበት ወቅት ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ.ም መንገደኛ በነበረው ሰው ላይ ጉዳት አድርሰዋል፣ሰኔ 08 ቀን 2006 ዓ.ም ደግሞ የአመልካች ድርጅት ሰራተኞችን ከደሴ ወደ መቐሌ ለስራ ይዞ በመሄድ ላይ እያለ መንገዱ ጠመዝማዛና የአየሩ ሁኔታም ዝናብማ ሁኖ እያለ ከጥንቃቄ ጉድለት መኪናውን እንዲወድቅ በማድረግ በመኪናው ላይ ጉዳት አድርሷል፣በሰራተኞች ላይም ቀላል የመቁሰል አደጋ አድርሷል ተብሎ ስንብቱ የተከናወነ መሆኑንና የስር ፍርድ ቤቶች ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ.ም ተፈጸመ የተባለው ጥፋት በሰላሳ ቀን የይርጋ ጊዜ መታገዱን፣የሰኔ 08 ቀን 2006 ዓ.ም ጥፋት ግን በወቅቱ ዝናባማ የአየር ሁኔታ በነበረበትና መንገዱ እርጥበታማና ቁልቁለታማ በሆነበት አካባቢ የተፈፀመ ቢሆንም በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት ነበር ከሚባል በስተቀር በአዋጁ በተመለከተው አግባብ ከባድ ቸልተኝነት ነበር ሊባል የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች የወሰኑ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የተጠሪ አድራጎት በከባድ ቸልተኝነት ስር ሊወድቅ ይችላልን? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ሠራተኛ ለስራው የተሰጡትን መሣሪያዎችና እቃዎች ሁሉ በጥንቃቄ የመጠበቅ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 13/3/ ስር የተመለከተ ሲሆን በአሠሪው ንብረት ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 27/1/ሸ/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ሆኖም ከባድ ቸልተኝነት የሚለውን ቃል መለኪያ በተመለከተ ሕጉ በግልጽ አያሣይም፡፡ ይሁን እንጂ ቸልተኝነት የጥንቃቄ ጉድለት እንደመሆኑ መጠን የጥንቃቄ ዓይነትና ደረጃ እንደየድርጊቱና አድራጊው የስራ ድርሻ አኳያ በመመልከት ምላሽ ለማግኘት እንደሚገባ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 41115 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የጥፋት ደረጃ "ከባድ ቸልተኝነትን" ሊያቋቁም የሚችል መሆን አለመሆኑን ከስራቸው ባህርይ አንፃር መመልከቱ የግድ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ስራቸው ሹፌር ሲሆኑ ከስራቸው በተያያዘ ሁኔታ ጥንቃቄ ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ መኪናውን የሚያሽከረክሩበትን አግባብ ከአከባቢው አየር ሁኔታ እና ከመልክዓ ምድሩ ጋር በአገናዘበ መልኩ መሆን ያለበት መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡በመሆኑም በዝናባማ የአየር ሁኔታና ጠመዝማዛና ቁልቁለታማ በሆነ መንገድ በዝግታና በጥንቃቄ ተሽከርካሪን ማሽከርከር ከአንድ አሽከርካሪ የሚጠበቅ ሙያዊ ግዴታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ መኪናውን ዝናባማ በሆነ የአየር ሁኔታ ውስጥ በጠመዝማዛና ቁልቁለታማ በሆነ መንገድ ላይ ተጠሪ ማርሹን በተመጣጣነ ማርሽ አስሮ ባለማሽከርከሩ አደጋው መደረሱ በክፍሉ ፖሊስና አመልካች ባቀረባቸው ሌሎች ማስረጃዎች የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ማስተባበያ ማስረጃ ያላቀረበበት ጉዳይ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶችም ተጠሪ ሲያሽከረክሩት የነበረው መኪና በተጠቀሰው የአየር ሁኔታና መልክዓ ምድር ላይ ሲሽከረከር ተጠሪ ተገቢውን ማርሽ አስሮ ሲሽከረክር ነበር በማለት የደመደሙት ፍሬ ነገር ያለመኖሩን የውሳኔያቸው ይዘት ያስገነዝባል፡፡

ተጠሪ መኪናውን ሲያሽከረክሩ የነበረበት ሁኔታ ከላይ የተገለጸው ነው ከተባለ ደግሞ ትክክለኛ አእምሮ ባለው ሰውና በተጠሪ የግል ሁኔታ መመዘኛ መሠረት ከባድ ቸልተኝነትን ሊያሣይ የሚችል አይደለም ሊባል የሚችልበትን አግባብ አላገኘንም፤፤ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪ ጥፋት ከባድ ቸልተኝነት አይደለም ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ሁኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.10762 ታህሳስ 06 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.19554 የካቲት 19/ 2007 ዓ.ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-10681 መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. በዚህ ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 110615

ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ኃብተሚካኤል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር -

ሥራ አስኪያጅ አቶ ተካልኝ ሁንዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ታመነ ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌንፌኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22279 ሐምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 187457 የካቲት 9 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው የሰበታ ሀዋሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሕግ አግባብ ውጭ የሥራ ውሌ ተቋርጧል በማለት ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ አመልካች ሆነው ተከራክረዋል፡፡

1. ከሳሽ (ተጠሪ) ከተከሳሽ (አመልካች)ድርጅት ጋር በሠራተኝነት ተቀጥሮ ሲሰራ ተከሳሽ ከሕግ አግባብ ውጭ የሥራ ውሉን ያቋረጠው መሆኑን ገልፆ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡
   አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ በጥቅምት 2 ቀን 2006 ዓ.ም አደም ገረመው ከሚባል ሠራተኛ ጋር በመደባደብ በሥራ ቦታ ሁከት የፈጠረ መሆኑንና ህዳር 25 ቀን 2006 ዓ.ም የድርጅቱን ሥራ አስኪያጅ አልታዘዝም ከማለቱም በላይ “ዝም በል አንተ አሸሸም ፡፡ አሸሸ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጭስህ መጥተሕ አፍህን አትክፈት፡፡ አእምሮ የሚያደነዝዝ አሸሸ ወስደህ ደንዝዘህ መጥተህ አታደንዝዘን" በማለት የተሳደበና ችግር የፈጠረ መሆኑ ከሥራ የተሠናበተ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል ፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የከሳሽንና የተከሳሽን ምስክሮች ሰምቷል የከሳሽ አንደኛው ምስክር ከሳሽ ከቅርብ አለቃው ጋር መጣላቱን የመሰከረ መሆኑንና የተከሳሽ ምስክሮች ጥቅምት 7 ቀን 1986 ዓ.ም ከሳሽ የድርጅቱን አንድ ሠራተኛ የደበደበ መሆኑንና 25/03/2006 ዓ.ም ከሳሽ የቅርብ አለቃውን ሀሸሻም ሀሸሽ አጭሰህ መጥተህ ትናገረናለህ ጠብ እና ግርግር ያነሳ መሆኑን በማረጋገጥ እንደመሰክሩ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሮ ተጠሪ /ከሳሽ/ አለቃውን አልታዘዘም ማለቱንና መስደቡ የተረጋገጠ በመሆኑ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት የተጠሪ /ከሳሽን/ ክስ ውድቅ አድርጎታል ፡፡

2. ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል ፡፡ የልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክረክር ከሰማ በኃላ አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው ተጠሪ አለቃውን ሰብዓዊ መብቱን በሚነካ መልኩ ስለሰደበው መሆኑ እንደተረጋገጠ ገልፆ አመልካች ተጠሪው ለፈፀመው ለዚህ ጥፋት ማስጠንቀቂያ መስጠት ሲገባው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጡ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 4 ድንጋጌ መስፈርት የሚያሟላ አይደለም በማለት ስንብቱ ከሕግ አግባብ ውጭ የተፈፀመ ነው ተብሎ አመልካች ብር 8,284.24 /ስምንት ሺ ሁለት መቶ ሰማንያ አራት ብር ከሃያ አራት ሳንቲም) ለተጠሪ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል ፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የተጠሪ አድርጎት "ጠብና"አንባጓሮ ማንሣት ነው ተብሎ ሊያዝ አይገባም በማለት የልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል ፡፡

3. አመልካች የካቲት 24 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የቅርብ ኃላፊውን አንድ ሠራተኛ ወደሌላ ቦታ ሄዶ እንዲሠራ ትዕዛዝ ሲሰጥ ትዕዛዙን ከመቃወም አልፈው የቅርብ አለቃውን አንተ ሀሸሻም በማለት የተሳደበና አምባጓሮ የፈጠረ፤ በዚህ ምክንያት የምርት ሥራው እንዲገታ ያደረገ መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል ፡፡ ይህ የተጠሪ አድራጎት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1/ረ መስፈርት አያሟላም በማለት የልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት የሕግ ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል ፡፡ተጠሪ በበኩሌ ሚያዚያ 6 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ እኔ አለቃዬን አልተሳደብኩም ፡፡ ሁከትም አልፈጠርኩም ፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል ፡፡ አመልካች ሚያዝያ 20 ቀን 2007 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጭ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕጉን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ተጠሪ ህዳር 25 ቀን 2006 ዓ.ም በሥራ ቦታ ያሳየውን ባህሪይና የፈፀመውን አድራጎት በተመለከተ ፍሬጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የወረዳው ፍርድ ቤትና የልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደረሱበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ ህዳር 25 ቀን 2006 ዓ.ም ተጠሪና ሌሎች አራት ሠራተኞች ሥራ እየሰሩ እያለ የቅርብ አለቃቸው ከእነሡ መካከል አንድ ሠራተኛ ወደ ሌላ የሥራ ክፍል እንዲሄድና ቀሪዎች አራቱ ቀሪውን ሥራ እንዲያከናውኑ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑ በዚህ ጊዜ ተጠሪ የቅርብ አለቃውን የሥራ ትእዛዝ ከመቃወም አልፎ ሀሸሽም ሀሸሽ አጭስህ መጥተህ ትናገረናለህ በማለት የተሳደበ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑንና የተጠሪ ማስረጃ ይህንን በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ ያላስተባበለ መሆኑን የወረዳው ፍ/ቤት በውሣኔው በግልፅ አስፍሮታል ፡፡
6. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው ተጠሪ የሥራ ትዕዛዝ ባለመቀበሉና የቅርብ አለቃውን ክብረ ነክ የሆነ ስድብ በመሳደቡ ምክንያት ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የደረሰበትን የፍሬ ጉዳይ ማጣራትና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው በማለት የልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተቀበለው መሆኑን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22279 ሀምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ በአራተኛው ገፅ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ይዘት ከተነተነ በኃላ ‹‹ በአጠቃላይ የመልስ ሰጭ ድርጅት ይግባኝ ባይን ከሥራ ያባረረው እሱ አለቃውን ሰብዓዊ ክብሩን መንካቱን በሚነካ መልኩ ስለሰደበው እንደሆነ ከመዝገቡ ውስጥ የምንረዳው ጉዳይ ነው በማለት በመጨረሻው ፓራግራፍ ካሰፈረው የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ለመረዳት ይቻላል፡፡
7. ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ ህዳር 25 ቀን 2006 ዓ.ም በቅርብ አለቃው የተሰጠውን የሥራ ትዕዛዝ ከመቃወም አልፎ የቅርብ አለቃውን አንተ ሀሸሽ አጭስህ መጥተህ አትናገረን “በማለት የተሣደበ መሆኑን ፍሬጉዳይ ያማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዩነት የላቸውም፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተለያዩት ይኸ የተጠሪ አድርጎት አመልካች ህዳር 26 ቀን 2006 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ በማቋረጥ ለወሰደው እርምጃ በቂና ህጋዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው የህግ ጥያቄ በሚመረምሩበትና መዝነው ውሣኔ በሰጠበት ጊዜ እንደሆነ ከውሣኔያቸው ለመረዳት ችለናል ።

8. ሠራተኛው ከሥራ ውል የተመለከተውን ሥራ ራሱ የመሥራትና የሥራ ውሉና ደንቡ መሠረት በአሠሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታ ያለበት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1(1)እና ንዑስ አንፅ 2 ተደንግጓል ።ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰራተኛ እንደጥፋቱ ክብደት በስራው ቦታ አንባጓሮ ወይም ጠብ አጫሪነት ጥፋት በፈፀመ ጊዜ አሰሪው ሰራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብተው የሚችል መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ(1)ተደንግጓል። ተጠሪ የቅርብ አለቃው ከተጠሪ ጋር ከሚሠሩት አምስት ሠራተኞች አንድ ሠራተኛ ወደ ሌላ ሥራ ክፍል ለማስማራት የሰጠውን ትዕዛዝ የተቃወመና በአዋጅ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 አሠሪው በሥራ ውሉና ደንቡ መሠረት የሰጠውን የሥራ ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ና አሠሪው ሌሎች ሠራተኞች የሥራ ትዕዛዝና ስምሪት የመስጠት መብት በመጋፋት የቅርብ አለቃውን "አንተ ሀሸሻም ሀሸሸ አጭሰህ መጥተህ አትናገረን "በማለት የተሳደበ መሆኑ ተረጋግጧል።

9. አመልካች የቅርብ አለቃው ላይ የስድብና ማዋረድ ተግባር የፈፀመው በወንጀል ሕግ ማንም ሰው እንዳይዘውና እንዳይጠቀም ክልከላ የተደረገበትን ሀሸሸ አጭሰህ መጥተህ ነው የምትናገረን በማለት እንደሆነ ተረጋግጧል ። ተጠሪ በቅርብ አለቃው ላይ የፈፀመው የስድብና ማዋረድ ተግባር፣በህግ የተከለከለ ተግባር ፈጽመሀል በማለት ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡም የሚያወግዘውንና የሚጠየፈውን ተግባር የቅርብ አለቃው ፈጽሞ መጥቶ ሰራተኞችን እንደሚበጠብጥ አድርጎ ሌሎች ሰራተኞች እየሰሙ በመግለፅ እንደሆነና ይህም የተጠሪ አድርጎትና ተግባር የአሠሪው ወኪል የሆነውን የቅርብ አለቃውን ሰብዓዊ ክብር በሚነካ ሁኔታ ተጠሪ የስድብና ማዋረድ ተግባር የፈፀመና በዚህ ምክንያት የተጠሪ የቅርብ አለቃ ስሜት ውስጥ እንደገባና ለጠብና ለድብድብ እንዲነሳሳ ለማድረግ አስቦና መርጦ የተናገረው መሆኑን ከግራቀኙ ክርክርና ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ለመረዳት ይችላል ። ይህንን የተጠሪ አድርጎት በአዋጅ ቁጥር 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ድንጋጌ ጋር በማነፃፀር ስንመለከተው "አሠሪው የሠራተኛውን ሰብዓዊ ክብርና ሞራልን የሚነካ ወይም በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሠረት የሚያስቀጣ ሌላ አድርጎት የፈፀመ እንደሆነ ሠራተኛው የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ እንደሚችል ይደነግጋል

10. በዚህ መዝገብ እየታየ ያለው ጉዳይ ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ የተገለፁት ተግባራት በአሠሪው ሣይሆን በሠራተኛው የተፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ተጠሪ የቅርብ አለቃው የሠጠውን የሥራ ትዕዛዝ አልፈፅምም ከማለት አልፎ አንተ ሀሸሻም ሀሸሸ አጭሰህ መጥተህ አትናገረን በማለት የቅርብ አለቃውን የሰደበና ያዋረደ መሆኑን በዚህ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከቅርብ አለቃው ጋር ጠብ የተፈጠረ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሳያል ከዚህ አንፃር በአዋጅ ቁጥር 32 ንዑስ አንቀፅ 1(ሀ) የተገለፀ ሁኔታ ሠራተኛው የቅርብ አለቃውን ሰብዓዊ ክብርና ሞራል የሚነካ የስድብና የማዋረድ ተግባር በመፈፀሙ ወይም ሌላ ህገወጥ ተግባር በመፈፀሙ ምክንያት በሥራ ቦታ በሠራተኛውና በቅርብ የሥራ ሀላፊው መካከል ጠብ የተነሳ መሆኑ ከተረጋገጠ አሠሪው በአዋጅ ቁጥር 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) በተደነገገው መሠረት የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ እንደሚችል የአዋጁን አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2፣የአዋጅ አንቀጽ 32(2) ሀ ከሚደነግገው በሚቃረን ሁኔታ ሠራተኛው የቅርብ የሥራ ሀላፊውን ሰብዓዊ ክብርና ሞራል የሚነካ ተግባር መፈፀም ሊያስከትል የሚችለውን ህጋዊ ውጤትና የአዋጁን አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 1(ረ) ድንጋጌ ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪ በቅርብ አለቃው የተሰጠውን የሥራ ትዕዛዝ ከመቃወም አልፎ የቅርብ የሥራ ሃላፊውን አንተ ሀሸሻም ሀሸሽ አጭሰህ መጥተህ እኛን አትናገረን በማለት በመሳደቡና ከቅርብ አለቃው ጋር መጣላቱ የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በቂና ህጋዊ ምክንያት አይደለም በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰበታ ሀዋሳ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል የቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 እና በአንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 1(ረ) መሠረት በመሆኑ የሥራ ስንብቱ በሕግ አግባብ የተከናወነ ነው በማለት ወስነናል ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 105997

ሚያዚያ 26 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሪት ሉሊት አያሌው ማሞ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ማህሌት ዓለሙ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሰራተኛ የስራ መደብና ቦታ ዝውውር ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም፡- የተጠሪ ድርጅት አመልካች የኢንዲስትሪ ሰላም አላግባብ ንትርክ እየፈጠሩ መረባሻቸውን ሳያረጋግጥ በ26/08/2005 ዓ/ም በፃፈው የአመልካችን የግል ታሪክ በሚያጎድፍ ደብዳቤ ከኦዲት ወደ ማርኬቲንግ ክፍል ያላግባብ በማዘዋወር እርምጃ መውሰዱን ጠቅሰው የተወሰደው እርምጃ እንዲነሳና ወደ ኦዲት ክፍል እንዲመለሱ እንዲሁም የዝውውሩ ደብዳቤ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም፡- አመልካች ከኦዲት ሰራተኞች ጋር ባላቸው አለመግባባት የተነሳ የኢንዲስትሪ እና የስራ ቦታ ሰላም ለመጠበቅ ሲባል የአመልካች የስራ ደረጃ እና ደመወዝ ሳይነካ ዝውውሩ መፈፀሙንና ክሱ ከተመሰረተ በኋላም የአመልካችን ደመወዝ ብር 10,759.00 ማድረጉን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን በመመርመር የሥራ መደብ ዝውውሩ ሕጋዊ ነው፣ የዝውውር ደብዳቤም ሊሰረዝ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካች ለኢንዲስትሪ ሰላም የፈጠሩት ችግር ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ እና በስራው ላይ ያስከተሉት ችግር መኖሩ በተጠሪዎች ምስክሮች ባልተነገረበት ሁኔታ ዝውውሩ ህጋዊ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ በዕሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክርና ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ ዝውውሩ ሕጋዊ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት አመልካች ከአቀረበው ክርክር ይዘትና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ለማየት ይቻል ዘንድ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር ብቻ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁን አመልካች ሥራዬን በአግባቡ እየተወጣሁ እያለ አሠሪው ወደ ሌላ የሥራ መደብ ተዛውረሻል በማለት ደብዳቤ ጽፎልኛል፣ ዝውውሩ ከፍላጎቴና ከህብረት ስምምነቱ ውጪ የተደረገ ከመሆኑም በላይ በግል ማህደሬ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል ነው በማለት ገልጸው ተከራከረው ተጠሪ ዝውውሩ የተደረገበትን ምክንያቶችን ዘርዝሮ በሕግ ከተሠጠው ስልጣን የመነጨ መሆኑንም ጭምር ጠቅሶ መከራከሩን ነው፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የተጠሪ ምስክሮች ቃል አመልካች ከሰራተኞች ጋር ብሎም ከሃላፊዎች ጋር ግጭት የሚፈጥሩ፣የሚሰጣቸውን ስራውም በአግባቡ የማይሰሩ ስለመሆኑ፣የስራ ባልደረቦቻቸው አብረዋቸው ለመስራት የማይመርጧቸው ሰው እንደሆኑ፣ ስራቸውን በአግባቡ ስለማይሰሩ የጊዜ ብክነት፣ አላስፈላጊ ውጪና ያልተቃና ስራ መከሰቱን መመስከራቸውን፣ የአመልካች ምስክር ደግሞ አመልካች በስተመጨረሻ የአዲት ስራ የሰሩባቸው ሶስት ቅርንጫፎች አስመልክቶ የተፈጠረ ችግር ሳይኖር ስራውን ከአመልካች ጋር መስራታቸውን ገልጸው መመስከራቸውን በውሳኔ ላይ ከአሰፈረ በኋላ የአመልካች ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል አመልካች አሉባቸው የተባሉትን ከስራው ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮችን ፈጽሞ የሌሉባቸው ስለመሆኑ አስረድተዋል ለማለት የሚያስችል አይደለም፣ አመልካች ስራው ላይ ያሳያሉ የተባሉት ባህርይ በስራ ቅልጥፍና፣ በውጤታማነትና በኢንዲስትሪ ሰላም ላይ አሉታዊ ተእዕኖ የሚፈጥሩ በመሆናቸው ተጠሪ ድርጅት የአመልካችን ደመወዝ፣ የስራ ደረጃና ሌሌች ጥቅማጥቅሞችን ሳይነካ የፈፀመው የሥራ መደብ ዝውውር ሕጋዊ ነው በማለት ደምድሟል፡፡

ከተጠሪ የሥር ክርክርም ሆነ በዚህ ሰበር ደረጃ ከሰጠው መልስ መገንዘብ የተቻለው ደግሞ በአንድ በኩል ዝውውሩ የተፈጸመው በአመልካች ጥያቄ መነሻ መሆኑን ጠቅሶ የተሻለ ደመወዝ አመልካች እንዲያገኙ ማድረጉን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአመልካችን ተገቢ ያልሆነ ባህርይ መነሻ በማድረግ ለኢንዱስትሪና ለስራ ቦታ ሰላም የተደረገ ነው በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ አንድ አሰሪ አንድን ሰራተኛ ከአንድ የስራ መደብ ወደ ሌላ የስራ መደብ የማዛወር አስተዳደራዊ ስልጣኑ ነው ተብሎ የሚታመነው አሰሪው ስራንና ሰራተኛን ለማገናኘት የሚችልበት አግባብ ነው በሚል ምክንያት ሆኖ ዝውውሩም ተቀባይነት የሚያገኘው የሰራተኛውን መብትና ጥቅም በማይነካ መልኩና ተመሳሳይ ወደሆነው የስራ መደብ ተከናውኖ ሲገኝ እንጂ ይህንኑ በሚቃረን መልኩ ሊሆን እንደማይገባ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎችን በመመርመር በሰ/መ/ቁጥር 40938 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ የፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የህግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ አመልካችን ከአዲት ክፍል ወደ ማርኬቲንግ የስራ መደብ ያዛወራቸው መሆኑን ሳይክድ አዲሱ የስራ መደብ አመልካች ቀድሞ ይሰሩበት ከነበረው የስራ መደብ ጋር ተመሳሳይ የሆነና የአመልካችን መብትና ጥቅም በማይነካ መልኩ መከናወኑንና ለዝውውሩ አብይ ምክንያትም የአመልካች ባህርይ ሁኖ ለኢንዲስትሪ ሰላም ሲባል አመልካች እንዲዛወሩ ከተደረገበት የስራ ቦታ በጡረታ የወጣ ሰራተኛ አመልካች እንዲተኩ ለማድረግ ሲባል መከናወኑን ጠቅሷል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ድርጅት ለዝውውሩ ምክንያት ያደረጋቸው እነዚህ ምክንያቶች ባንድ በኩል ከአመልካች ባህርይ ጋር እንደተያያዙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአመልካች ጥያቄ መነሻና በጡረታ የተገለሉ ሰራተኛን የሥራ መደብ እንዲሸፈኑ ለማድረግ ታስቦ የተደረገ መሆኑን የሚገልጹ በመሆናቸው ይዘታቸው ሲታይ እርስ በራሳቸው የሚቃረኑ ምክንያቶች መሆናቸውን የሚያስገነዝብ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ አንድ ሰራተኛ በባህርይ ችግር ለኢንዲስትሪ ሰላም አስቸጋሪነቱ ከተረጋገጠ በሕጉ አግባብ ተገቢው ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ተደርጎ እንዲታረም ማድረግ የሚቻልበት አግባብ መኖሩ የሚታወቅ ሲሆን በባህርይ ችግር ተዛወረ የተባለን ሰራተኛ ደግሞ የስራ መደቡ ክፍት በመሆኑ እንዲዛወር ተደርጓል በሚል የሚቀርብ ክርክር ዝውውሩ ስራንና ሰራተኛን ለማገናኘት የተደረገ ነው ብሎ ለመደምደም የማያስችል ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን በየጊዜው የሚያዛውራቸው ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት መገለጹም ሲታይ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ስራንና ሰራተኛን ለማገናኘት ሲባል ባልተደረገ የሥራ ውል ደግሞ የስራ ውል የሚሻሻልበት አግባብ ያለመኖሩን ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 15 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪ የስራ መደቡ ዝውውሩ ሕጋዊ ነው ብሎ የሚያቀርባቸው ምክንያቶች እርስ በራሳቸው የሚቃረኑ በመሆናቸው ተጠሪ ዝውውሩ በህጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያከናወነው ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ዝውውሩ ሕጋዊ መሆኑን ያሳያሉ የተባሉት የተጠሪ ምክንያቶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ናቸው ከተባለ የአሰሪው የዝውውሩ እርምጃ የአስተዳዳሪነት ሥልጣኑን በዘፈቀደ ለማከናወን መነሳቱን ያሳያል ከሚባል በስተቀር የዝውውሩን ህጋዊነት በምንም መመዘኛ አያሳዩም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም አንድን ሰራተኛ መብትና ጥቅሙን ሳይነካ ከአንድ የስራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ወይም የስራ መደብ በማዛወር ማሰራት የአሰሪው አስተዳደራዊ ሥልጣን (Administrative prerogative) ነው ሲባል ዝውውሩ ያለ ሕጋዊ ምክንያትና በሕብረት ስምምነቱ ከሰፈረው አሰራር ውጪ ይከናወናል ተብሎ ሊተረጎም የማይገባው ስለመሆኑ ከአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ አጠቃላይ መሰረታዊ አላማና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 57117፣77113 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ሁኖ ስለአገኘን ተጠሪ አመልካችን ያዛወረበት ሁኔታ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መሰረዝ ሲገባው በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ ያከናወነው ዝውውር ሕገ ወጥ ነው ከተባለም የአመልካችን ባህርይ በተመለከተ በዝውውር ደብዳቤው የገለፀበት አግባብ ከአመልካች የግል ማህደር ጋር ሊኖር የማይገባ በመሆኑ ሊሰረዝ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10179 መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 139826 ነሐሴ 07 ቀን 2006 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ዝውውር ሕገ ወጥ ነው፣ ሊሰረዝ ይገባል ብለናል፡፡ አመልካች ይሰሩበት ከነበረው የኦዲት የስራ መደብ ወደ ማርኬቲንግ የስራ መደብ ሊዛወሩ አይገባም፣ የዝወውሩ ደብዳቤም ሙሉ በሙሉ ሊሰረዝ ይገባል ከአመልካች ማህደር ሊያያዝ አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 108785

ሀምሌ 21 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነአ ቂጣታ

አመልካች ፡- ዩሴፍ ተክሌ ህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጠበቃ ብሥራት መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ ጌታቸው በራሳቸው እና ሞግዚት በሆነችላቸው እነ ሕፃን ረዲኤት ታምራት ከጠበቃ አቶ ፋንቱ አስፋው ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

? ? ?

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ለሚስትና በሌሎች ጥገኞች የሚከፈል የካሣ ገንዘብ ጥያቄ የይርጋ የጊዜ ገደብ የሚመለከት ነው ተጠሪ ባለቤታ የሁለት ልጆች አባት የሆነው ታምራት ሀይሌ አሠሪው በመደበው መኪና ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ሲጓዝ መኪናው ተገልብጦ ሚያዝያ 23 ቀን 2005 ዓ.ም ህይወቱ ያለመሆኑን ገልፆ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ለእርሷና ለህፃናቱ ካሣ እንዲከፈላቸው ውሣኔ እንዲሰጥላት ጥር 25 ቀን 2006 ዓ.ም ጠይቃለች ፡፡
2. አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገው የስድስት ወር የይርጋ የጊዜ ገደብ አልፏል በማለት መቃወሚያ አቅርቧል ፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ብይን ሰጥቷል ፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባ፣ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ ነው ፡፡ ስለዚህ ክሱ የቀረበው በዚህ ድንጋጌ የተጠቀሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የይርጋ የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በመሆኑ በይርጋ አይታገድም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ሽሮታል ።

3. አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ይህንን የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ተጠሪ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን የሕግ ስህተት የሌለበት መሆኑን ገልፃ ተከራክራለች እኛም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይርጋ አይታገድም በማለት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሰጠውን ብይን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል ።

4. ጉዳዩን እንደመረመርነው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገው የስድስት ወር ይርጋ ተፈፃሚ የሚሆነው አሠሪው በሠራተኛው ላይ ወይም ሠራተኛው በአሠሪው ላይ ለሚያቀርበው የደመወዝ፣ የትርፍ ሠዓት ሥራ ክፍያ፣በአል ቀናት ክፍያ ጥያቄና ለመሳሰሉት የክፍያ ጥያቄዎች መሆኑን ከድንጋጌው አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት ይቻላል በአዋጅ አንቀፅ 4 በይዘቱም ሆነ በአቀራረፅ ፣የሰራተኛው በስራ ላይ የደረሰበት የሞት አደጋ የሰራተኛው ባለቤትና ሌሎች ጥገኞች በአዋጁ አንቀጽ 110 መሠረት የሚያቀርቡትን የካሣ ክፍያ ጥያቄ በስድስት ወር የይርጋ የጊዜ ገደብ ለመገደብ ታስቦ የተደነገገ ድንጋጌ አይደለም ። ከዚህ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በአዋጅ አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው።ተጠሪ ክስ ያቀረበችው በአዋጁ አንቀጽ 162 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በመሆኑ የተጠሪ ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል ።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139907 ህዳር 25 ቀን 2007 ዓ.ም የሰ ጠውን ውሣኔ ፀንቷል ።
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ወስነናል ።
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ይቻቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።።

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 108933

ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ሠላም ቦሌ ሸማቾች ኃ.የተ.የህብረት ስራ ማህበር - የቀረበ የለም ከተባለ በኃላ ጠበቃ መለሰ ግርማይ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ እሸቱ አደፍርስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግል ስራ ክርክር ሲሆን የተጀመረውም ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ሰኔ 02 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ፡-ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከ7/00/2003 ዓ/ም ጀምሮ በጉልበት ሰራተኝት የስራ መደብ ተቀጥረው በወር ብር 770.00 እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እንዳሉ የአሁኑ አመልካች ከስራ መደባቸው ውጪ የሆነ ስራ ተጠሪ እንዲሰሩ በማድረጉ ተጠሪ የአመልካችን ትዕዛዝ ከስራ መዘርዝራቸው ውጪ ነው በሚል በመቃወማቸው ምክንያት ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ዘርዝረው ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ የታዘዙት ከስራ መደባቸው ጋር ተያያዥነት ያለውንና በስራ መዘርዝሩ በተጠቀሰው አግባብ መሆኑን እንዲሁም በተደጋጋሚ በቅርብ አለቃቸው ሲታዘዙ ትዕዛዙን የማይቀበሉ መሆኑን ጠቅሶ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርን ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ከአሰሪው የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ያለመፈጸማቸው አከራካሪ ያለመሆኑን፣ተጠሪ የሚፈፅሟቸው ተግባራት በስራ መዘርዝሩ በግልጽ መመልከታቸውን፣በዚህም መሰረት ተጠሪ ውሃ ያላቸውን ለስላሳ ጠርሙሶችን ከስቶር ወደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባር፣ባዶ ጠርሙሶችን ደግሞ ከባር ወደ ስቶር እንደሚመልሱ በስራ መዘርዝሩ ላይ ከመገለፁም በላይ በዚሁ ሰነድ ተራ ቁጥር 8 ስርም ከቅርብ አለቃቸው ሲታዘዙ ማንኛውንም የጉልበት ስራ ሊሰሩ እንደሚችሉ መጠቀሱን ከሰነዱ ይዘት መመልከቱንና ከዚህም ተጠሪ የታዘዙት ከስቶር ወደ ባር ውሃ ያለበትን ጠርሙስ ወስደው ከባር ወደ ስቶርም ውሃ ያለበትን ጠርሙስ እንዲመልሱ በመሆኑ ስራው የስራ ድርሻቸው የሆነው የጉልበት ስራ መሆኑን መረዳቱን ከአረጋገጠ በኋላ ይህ ተግባር የስራ ውልን ያለማስንጠቀቂያ ሊያቋርጥ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለውን ጥያቄ በማንሳት በስራ መዘርዝሩ መሰረት ያለመስራት ስራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት አይደለም በማለት ደምድሞ የአመልካችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 1540.00፣የካሳ ክፍያ ብር 4620.00፣የስራ ስንብት ክፍያ ብር 781.25፣የአመት ፈቃድ ክፍያ ብር 377.3 የገቢ ግብር ተቀንሶ እንዲከፈላቸውና የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-ተጠሪ በስራ መዘርዝራቸው መሰረት የታዘዙትን ስራ ለመስራት ፈቃደኛ ያለመሆናቸው ተረጋግጦ እያለ ተግባሩ ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል አይደለም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች የተወሰነው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 13(2) ድንጋጌን ያላገናዘበ ነው የሚል ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ በመሆኑ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ተጠሪ በስራ መዘርዝሩ መሰረት ስራቸውን ያለመስራታቸው ተረጋግጦ እያለ ተግባሩ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል አይደለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡

የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን በተመለከተ አመልካች አላግባብ ከስራ አስናብቶኛል በማለት ተጠሪ ላቀረቡት ክስ አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪው ከስራ ማሰናበቱን አምኖ ያሰናበተው ግን ተጠሪው እንደሚሉት አላግባብ ሳይሆን የተጠሪ የቅርብ አለቃ በሰጣቸው ትዕዛዝ እና በስራ መዘርዝሩ መሰረት ተጠሪ የስራ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪው የተሰናበቱት በስራ መዘርዝሩ በተገለፀው አግባብ የስራ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው በመሆኑ ውጤቱ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13(2) እና (7) ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ እንዲሁም አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረታዊ አላማ መታየት ያለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ ተጠቃሹ አዋጅ መሰረታዊ አላማ ከያዛቸው ነገሮች ውስጥ የኢንዱስትሪ ሰላምን በማስፈን ምርትና ምርታማነትን በማሳዳግ ለአገር ኢኮኖሚ እድገት አስተዋፅኦ ማድረግ መሆኑን የአዋጁ መግቢያ ያሳያል፡፡ ይህንኑ ለማሳካትም ሕጉ በአሰሪውም ሆነ በሰራተኛው ላይ ለይቶ ያስቀመጣቸው ግዴታዎች መኖራቸውን የአዋጁ አንቀጽ 12 እና 13 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም አሰሪውም ሆነ ሰራተኛው በሕጉ የተጣለባቸውን ግዴታ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለውና ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለውን ነጥብ በተመለከተ ስናይም አዋጁ ሰራተኛው በአሰሪው የተሰጠውን ሕጋዊ የስራ ትዕዛዝ በአግባቡ የመወጣት ግዴታ ያለበት መሆኑን በአንቀፅ 13(2) እና (7) ስር ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ሌላው አዋጁ አካቶ ከያዛቸው ጉዳዮች መካከል የስራ ውል የሚቋርጥባቸው መንገዶችና ምክንያቶች ይገኙበታል፡፡ የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ የሚችልባቸው ምክንያቶች በአዋጁ አንቀፅ 27(1) ስር በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የተመለከቱት የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያቶች ግን አንድ ሰራተኛ የስራ ግዴታውን ያለመወጣቱ ሲረጋገጥ የስራ ውሉን ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ መስጠትን በቅድመ ሁኔታነት የሚያስቀምጡ አይደለም፡፡ ስለሆነም ግልጽ ደንብ ወይም መመሪያ መኖሩ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሰራተኛው የስራ ግዴታውን ካልተወጣ አሰሪው ሰራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ የማያሰናብትበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም ተጠሪ በስራ መዘርገዘራቸው በግልጽ የተቀመጠመውን ግዴታቸውን ያለመወጣታቸው ተረጋግጦ የተከናወነው ስንብት ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13(2) እና (7) ድንጋጌዎች እና ከአዋጁ መሰረታዊ አላማ አንፃር ሲታይ ህጋዊ ነው ከሚባል በስተቀር ሕገ ወጥ የሚባልበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አንፃር መመልከት ሲገባቸው ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሰረታዊ አላማ በመውጣት የስራ ግዴታውን ያለመወጣቱ የተረጋገጠውን ተጠሪ መሰናበት የነበረበት በማስጠንቀቂያ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 90184 ሐምሌ 03 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 155790 ታህሳስ 20 ቀን 2007 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ስንብቱም ህገወጥ ነው በማለት በስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የውሳኔ ክፍል ተሽሮ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች ለተጠሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣የስራ ስንብት ክፍያና የካሳ ክፍያ ለመክፈል አይገደድም፣ የአመት ፈቃድ ክፍያ ብር 377.3 ግን ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል፣የስራ ልምድ ምስክር ወረቀትም ሊሰጥ ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.109055

ሐምሌ 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተክሊት ይመሰል

አዳነ እንደሻው

ቀነዓ ቂጤታ

አመልካች ፡- አቶ ጌትነት ከበደ - ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- ሃያት ሜድካል ከሌጅ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የአመልካች የጠበቃ አበልና ወጭና ኪሳራ ብር 6000/ስድስት ሺ ብር/ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የስራ ውሉ ከህግ አግባብ ውጭ ተቋርጧል የሚል ክስ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርቦ፣ተጠሪ የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ በሚደነግገው መሰረት መሆኑን ገልጾ በመከራከሩ፣ የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተጠሪ የአመልካችን የስራ ውል ያቋረጠው በህግ አግባብ ነው በማለት አመልካች /ከሳሽ/ ለተጠሪ ለተከሳሽ የጠበቃ አበል ብር 5000 / አምስት ሺ ብር/ እና ኪሳራ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ በድምሩ ብር 6000 /ስድስት ሺ ብር/ ይክፈል ማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
2. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ /ተጠሪ/ ለአመልካች የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ የስራ ውሉን አቋርጧል፡፡ ስለዚህ መልስ ሰጭ /ተጠሪ/ ለአመልካች የሁለት ወር ደመወዝ ብር 10,697.96 /አስር ሺ ስድስት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከዘጠና ስድስት ሳንቲም/ ግብር ተቀንሶ የመክፈል ሃላፊነት አለበት፡፡ በሌሎች ነጥቦች የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ አልተነካም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች ጥር 17 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው በህግ ከተደነገገው ውጭ መሆኑን ካረጋገጠ በኃላ የሁለት ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ብቻ እንዲከፈለኝ የሰጠው ውሳኔና የስር ፍርድ ቤት ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነብኝን የጠበቃ አበል እና ኪሳራ ሳይሻር መቅረቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 13 ቀን 2007 ዓ/ም በሰጠው መልስ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 161 ሰራተኞቹን የዳኝነት ክፍያ ከመክፈል ነፃ የሚያደርግ እንጂ በአሰሪው ወጭና ኪሳራ እንዳይከፍሉ የሚያደርግ ድንጋጌ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
4. ጉዳዩ በዚህ ሰበር ችሎት የተያዘው ጭብጥ፤ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ይዘትና ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ ማለትም አመልካች ለተጠሪ ብር 6000 /ስድስት ሺ ብር/ የጠበቃ አበልና ኪሳራ እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ ነጥብ መርምረናል፡፡
5. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ለያዝነው ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን የፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ እና የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር ተራቸው ስራቸው ኪሳራና ወጭ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ሊያዝ እንደሚችልና ኪሳራ በቁጥር የተወሰነለት ወገን የተወሰነለትን የኪሳራ ገንዘብ፣ የወጭ ዝርዝር እንደሚያቀርብ የተፈቀደለት ደግሞ የወጭና ኪሳራ ዝርዝር አቅርቦ ለመጠየቅ የሚችል መሆኑን ከፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 463 ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸ የሥነ - ሥርዓት ህጉ ድንጋጌ አዋጅ 377/96 ቁጥር 161 ንዑስ አንቀጽ 2 “ማንኛውም ሰራተኛ ወይም የሰራተኛ ማህበር ፍርድ ቤት ለሚያቀርበው የስራ ክርክር ጉዳይ ክክፍያ” ነፃ ነው በማለት ካስቀመጠው ድንጋጌ ጋር ተጣጥሞ መታየት ያለበት ነው፡፡
6. የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ከዳኝነት ክፍያ ነፃ ነው በሚል መንገድ ሳይሆን “ከክፍያ ነፃ ነው” በማለት የሚደነግግ መሆኑን ከድንጋጌው አቀራረጽና አውድ ንባብ ለማየት ይቻላል፡፡ ድንጋጌው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ህጋዊና ሰላማዊ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የመፍጠር፤ የኢንዱስትሪ ሰላምን የመፍጠር፤ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የሚነሳ ክርክር በተቀላጠፈ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝ የማድረግ አላማዎቹን በሚያሳካ ሁኔታ መተርጎምና ስራ ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ ከላይ የተገለጹትን አላማዎች ለማሳካት፤ ሠራተኞች በግልም ሆነ በጋራ መብታችን በአሠሪው ተጥሶብናል ብለው ሲያስቡ ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ለሚሰጥ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰጭ አካል ከህግ አግባብና ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲታይላቸው ለመጠየቅ የሚችሉበትን ተደራሽና ቀልጣፋ የዳኝነት ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

7. ከዚህ አንፃር ሲታይ ሠራተኛው በፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ 465 ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት ሠራተኛው ሀሰተኛና የተጨበረበረ ክስና ማስረጃ በአሰሪው ላይ ማቅረቡ ካልተረጋገጠ በስተቀር ከህግ አግባብ ውጭ ተጥሶብኛል የሚለውን የመብት ጥያቄ ለፍ/ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል /አሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ/ አቅርቦ በሙሉ ወይም በከፊል ተረች በሆነ ጊዜ ሁሉ አሰሪው ለክርክሩ ያወጣውን ወጭና ኪሳራ እንዲከፍል በሚያስገድድ መንገድ የአዋጅ አንቀጽ 161 ድንጋጌዎች ከተተረጎሙት ሠራተኞች ተጥሶብናል የሚሉትን መብት ለማስከበር ክስ አቅርበን በፍርድ ቤት ተከራክረን ብንረታ አሰሪው ለጠበቃና ለክርክሩ የወጣውን ወጭ እንድንከፍል ሊወሰንብን ይችላል በሚል ፍራቻና ስጋት መብታቸውን በፍርድ ከመጠየቅ የሚገደቡበትን ሁኔታ የሚፈጥር ይሆናል፡፡ ይህም ከላይ የገለጽናቸውን የአዋጁን መሰረታዊ ዓላማዎች የሚያሳካ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሰራተኛ ለአሰሪው በስራ ክርክር ምክንያት ያወጣውን ወጭና ኪሳራ የመክፈል ግዴታ የሚጣልበት በክርክሩ ተረች በመሆኑ ምክንያት ብቻ ሳይሆን ሰራተኛው በአሰሪው ላይ ያቀረበው ክስ ሀሰተኛና በተጭበርበረ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ሲገኝ መሆን እንዳለበት የፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 463 የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 465 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 161 ድንጋጌ ጋር በሚጣጣም መንገድ በመተርጎም ለመረዳት ይቻላል፡፡

8. በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከህግ አግባብ የስራ ውሉ ተቋርጦብኛል በሚል እምነት ክስ ያቀረበ መሆኑና በክርክር ሂደት አሰሪው /ተጠሪ/ያቀረበው ማስረጃ ከሰራተኛው /አመልካች/ የተሻለ ሆኖ ስለተገኘ የስር ፍርድ ቤት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የወሰነ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካችንና የተጠሪን ክርክር በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን የስራ ውል ከማቋረጡ በፊት የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ መስጠት ነበረበት በማለት ተጠሪ ለአመልካች የሁለት ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የወሰነ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሳኔ ተረድተናል፡፡ ይህም አመልካች በክርክሩ ሙሉ ለሙሉ ተረች አለመሆኑንና በከፊል መብት ያለው መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ የተሰጠለት መሆኑን ያሳያል፡፡

9. ከላይ በዝርዝር ከሰጠነው የህግ ትርጉምና አመልካችና ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ካቀረቡት ክርክር መሰረታዊ ባህሪ አንፃር ሲታይ፣ አመልካች ለተጠሪ የጠበቃ አበል ብር 5000/ አምስት ሺ ብር/ ኪሳራ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ በድምሩ ብር 6000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/ስድስት ሺ ብር/ እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139696 ታህሳስ 8 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች የሁለት ወር ደመወዝ ብር 10697.96/ አስር ሺ ስድስት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከዘጠና ስድስት ሳንቲም/ ግብር ተቀንሶ እንዲከፍል በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ የጠበቃ አበል ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ኪሳራ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ በድምሩ ብር 6000 /ስድስት ሺብር/ እንዲከፍል የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ አመልካች ይህንን ገንዘብ ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.104351

ሰኔ 9 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ት ክምክም እማኛው - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የደቡብ አቸፈር ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት - ዐ/ሕግ ዘላለም ተስፋዬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ቅጥር ውሉ የተሰረዘው አላግባብ ነው ተብሎ ወደ ስራው እንዲመለስ የተወሰነ የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛ ውዝፍ ደመወዝ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡-አመልካች በደቡብ አቸፈር ገ/ኢ/ል/ጽ/ቤት በ10/02/2004 ዓ.ም ተቀጥረው ሲያገለግሉ ከቆዩ በኃላ በቅጥር ውድድሩ ጊዜ ያቀረቡት የስራ ልምድ ማስረጃ ለተቀጠሩበት ፕሳ-3 የስራ ደረጃ የሚጠየቀውን አግባብነት ያለው የስምንት ዓመት የስራ ልምድ መስፈርት የሚያሟላ አይደለም በሚል የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ በ04/12/2004 ዓ.ም. የአመልካችን ቅጥር መሰረዙን፣አመልካች በዚህ የስረዛ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ማጣቱን፣ ይግባኙ ቀጥሎ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅጥሩን የሰረዘው የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ መጥሪያ ደርሶት መልስ ባለማቅረቡ በሌለበት ጉዳዩን መርምሮ ቅጥሩ ከተፈጸመ ከዘጠኝ ወራት በኃላ ቢሮው የቅጥር ፎርማሊቲ አልተሟላም በሚል ምክንያት ቅጥሩን በመሰረዝ የወሰደው እርምጃ ከክልሉ አዋጅ ቁጥር 171/2002 ውጭ መሆኑን፣ አመልካች ያቀረቡት የስራ ልምድ ማስረጃ ሀሰተኛ ነው ያልተባለ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 23 የተመለከተው ድንጋጌም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን ገልጾ ውሳኔውን በመሻር አመልካች ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ውሳኔ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታቸውን ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ያቀረቡት አመልካቿ ሲሆኑ የአቤቱታቸው ይዘትም ቅጥሩ የተሰረዘው ከሕግ አግባብ ውጭ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ስራዬ እንድመለስ ተወስኖልኝ እያለ ቅጥሩ ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ስራ እንድመለስ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለኝ ሳይወሰን የታለፈው አላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ አመልካች ለሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀረቡበት ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ጭምር እንዲከፈላቸው አለመጠየቃቸውን፣ ይግባኙ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሚቀርበውም በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ብቻ መሆኑን እና በዚህም ምክንያት ለአስተዳደር ፍርድ ቤት በቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ላይ ዳኝነት ያልተጠየቀበትን ጉዳይ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ ሰበር ችሎቱ ተቀብለው ውሳኔ ሊያሳርፉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ አለመኖሩን ገልጾ አቤቱታውን ባለመቀበል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ለሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ቅጥራቸው ፀንቶ እንዲቀጥል ከመጠየቃቸውም በተጨማሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ላይ በክርክር ላይ ለነበሩበት ጊዜ ያለው ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት ጥያቄ አቅርበው እያለ ዳኝነት አልተጠየቀበትም ተብሎ የውዝፍ ደመወዝ ጥያቄው ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. አመልካች ለክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀረቡበት ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ጭምር እንዲከፈላቸው ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የለም በማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም?
2. ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ወደስራቸው እንዲመለሱ ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ያለው የአመልካች ደመወዝ ሊከፈላቸው የማይችልበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ቅጥሩ አላግባብ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ወደ ስራ እንዲመለስ ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ያለው ደመወዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲከፈለኝ ያቀረብኩትን ጥያቄ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያለፈብኝ አላግባብ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ሳይቀበል የቀረው ደመወዙ ሊከፈል የማይችልበት ሕጋዊ ምክንያት መኖሩን መሰረት በማድረግ ሳይሆን ይልቁንም አመልካች ለክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀረቡበት ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጭምር ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የለም በማለት መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ቅጥሩ የተሰረዘባቸው አላግባብ መሆኑን ገልጸው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው ካቀረቡት ጥያቄ በተጨማሪ ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጭምር ለክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት በ24/12/2004 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ በተራ ቁጥር ስምንት ላይ ጠቅሰው መጠየቃቸውን እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በ19/02/2005 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ በተራ ቁጥር አስራ ሁለት ላይም ተመሳሳይ ዳኝነት መጠየቃቸውን በመግለጽ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ ላቀረቡት ክርክር ተጠሪው በመልሱ የሰጠው ግልጽ ማስተባበያ ካለመኖሩም በላይ በአጣሪው ችሎት በኩል ከዚህ መዝገብ ጋር እንዲያያዙ የተደረጉት ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ እና ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረቡት የሁለቱ የይግባኝ ማመልከቻዎች ይዘትም የአመልካቿን የክርክር ነጥብ የሚያረጋግጥ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀረቡበት ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጭምር ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የለም በማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከላይ በመጀመሪያው ጭብጥ ትችት ላይ እንደተገለጸው አመልካች ቅጥሩ የተሰረዘባቸው አላግባብ መሆኑን ገልጸው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው ካቀረቡት ጥያቄ በተጨማሪ ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጭምር በአስተዳደር ፍርድ ቤትም ሆነ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዳኝነት መጠየቃቸው የተረጋገጠ ሲሆን የአስተዳደር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ ቅጥሩ የተሰረዘው አላግባብ መሆኑን በመግለጽ አመልካች ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ውሳኔ የሰጠው የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጥያቄ አቅርበው የነበረ ስለመሆኑም ሆነ ጥያቄውን አቅርበው ነበረ ከተባለም ውሳኔ ሳያሳርፍበት የቀረው በምን ምክንያት እንደሆነ በውሳኔው ላይ የገለጸው ነገር አለመኖሩን ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት በሰጠው መልስ የስራ ቅጥሩ የተሰረዘበት ሰራተኛ በፍርድ ቤት ወደ ስራው እንዲመለስ ቢወሰንለት ቅጥሩ ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደመወዝ ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 ላይ የተደነገገ ነገር አለመኖሩ ሕግ አውጭው የዚህ ዓይነቱ ውዝፍ ደመወዝ እንዳይከፈል መፈለጉን የሚያሳይ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ እንደተባለው ቅጥሩ ለተሰረዘበት እና በፍርድ ቤት ውሳኔ ወደ ስራው እንዲመለስ ለተወሰነለት ሰራተኛ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ በአዋጁ በግልጽ የተቀመጠ ፈቃጅ ድንጋጌ የሌለ ሲሆን በአንጻሩ የዚህ ዓይነቱ ደመወዝ ሊከፈል የማይገባው ስለመሆኑም በአዋጁ በግልጽ የተቀመጠ ክልካይ ድንጋጌም የለም፡፡ይልቁንም ከዲሲፕሊን ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ሁኔታ የመንግስት ሰራተኛው የተሳለፈበት ውሳኔ በይግባኝ ከተሻሻለለት ወይም ከተሰረዘለት ውሳኔው ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ታስቦ ያለወለድ የሚከፈለው ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 81 (2) ስር የተመለከተው ድንጋጌ የሠራተኛው የስራ ውል ተቋርጦ የቆየው የሠራተኛው ባልሆነ እና ይልቁንም የመንግስት መስሪያ ቤት በሆነ ጥፋት ምክንያት መሆኑ በፍርድ ተረጋግጦ ሰራተኛው ወደ ስራው እንዲመለስ ሲወሰን የስራ ውሉ ተቋርጦ በቆየበት ጊዜ ያለው ደመወዝ ጭምር ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ በአዋጁ ተቀባይነት ያገኘ መርህ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ በአዋጁ መሰረት የቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ ወይም ሌላ ጥቅም የተሰረዘበት የመንግስት ሠራተኛ በማታለል ወይም በማጭበርበር ያገኘው ካልሆነ በቀር የስረዛው እርምጃ እስከተወሰደበት ጊዜ ድረስ የተከፈለውን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች እንዲመልስ የማይጠየቅ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 87 (1) የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ቅጥሩ የተሰረዘበት ሠራተኛ ወደስራው እንዲመለስ በፍርድ ቤት ሲወሰን ውዝፍ ደመወዙ ጭምር እንዲከፈል ሕግ አውጭው አለመፈለጉን አዋጁ ያመለክታል በማለት በደፈናው ከመከራከር በቀር የዚህ ዓይነት ትርጉም የሚሰጠው ወይም የዚህ ዓይነት ግምት ለመውሰድ የሚያስችለው የአዋጁ ድንጋጌ የትኛው እንደሆነ ተጠሪው በግልጽ ለይቶ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡በመሆኑም ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ወደስራቸው እንዲመለሱ ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ያለው የአመልካች ደመወዝ ሊከፈላቸው የማይችልበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ስራቸው እስኪመለሱ ደረስ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ በዝምታ በማለፍ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. አመልካች ለክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀረቡበት ጊዜ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ጭምር እንዲከፈላቸው ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የለም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 30581 በ21/09/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤትም ሆነ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻ ላይ ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጭምር የዳኝነት ጥያቄ አቅርበዋል በማለት ወስነናል፡፡
3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34488 በ05/06/2005 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
4. በተራ ቁጥር ሶስት ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ቅጥራቸው የተሰረዘው አላግባብ በመሆኑ አመልካች ወደስራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
5. በተራ ቁጥር ሶስት ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸው አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ በዝምታ በማለፍ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
6. ቅጥራቸው ከተሰረዘበት ከ04/12/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ እስከተወሰነበት 05/06/2005 ዓ.ም. ድረስ ያለው የአመልካች ደመወዝ ያለወለድ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
7. የውሳኔው ግልባጭ በውሳኔው መሰረት ማስፈጸም ያስችለው ዘንድ ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤት፣ እንዲያውቁት ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና አመልካች ለሚሰሩበት የመንግስት መስሪያ ቤት ይላክ፡፡
8. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
9. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትሐ ብሔር

ሥነ - ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105869

መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ደበሬ ቡልቲ - ተወካይ ታከለ ደበሬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዳንሹቴ ዋጋሪ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጋራ የእርሻ ይዞታ ላይ የተደረገ ውል የይፍረስልኝ ጥያቄን መሰረት አድርጎ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት እና የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ባልተደረጉት ባለቤታቸው እና 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ በ07/10/2005 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-በወንጪ ወረዳ በደጎዬ ጋለይ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው እና አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰው ሁለት ጥማድ መሬት የከሳሽ እና የባለቤታቸው የ1ኛ ተከሳሽ የጋራ ይዞታ ሆኖ እያለ ከከሳሽ እውቅና ውጪ ተከሳሾቹ በ21/01/2004 ዓ.ም.የከሳሽን መብት የሚጋፋ የመሬት ቅያሪ ውል ማድረጋቸውን የሚገልጽ ሆኖ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ በክሱ መሰረት ቢወሰን ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡2ኛ ተከሳሽ በበኩላቸው በ25/10/2005 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ በተከሳሾቹ መካከል በ21/01/2004 ዓ.ም የተደረገው ውል የድንበር ግጭት ማስወገጃ ስምምነት እንጂ የመሬት ቅያሪ ውል አለመሆኑን፣ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የመሬት ቅያሪ ያደረጉት በ1994 ዓ.ም መሆኑን፣2ኛ ተከሳሽ በቅያሪ ባገኙት መሬት ላይ አንድ የሳር ቤት የሰሩበት እና በርካታ አትክልት ያለሙበት መሆኑን፣1ኛ ተከሳሽም በቅያሪ ባገኙት መሬት ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንድ የሳር ቤት የሰሩበት መሆኑን እና የመሬት ቅያሪው ከተደረገ ከአስራ አንድ ዓመታት በኃላ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና በ21/01/2004 ዓ.ም በተደረገው ውል ላይ የነበሩትን ሶስት ምስክሮች አስቀርቦ ከሰማ በኃላ የ1ኛ ተከሳሽ ባለቤት ከሆኑት ከከሳሽ ስምምነት ውጪ ሁለቱ ተከሳሾች በ21/01/2004 ዓ.ም ያደረጉት ውል ሕጋዊ አለመሆኑን ገልጾ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ሁለት ቀርጥ መሬት ከሳሽ ይጠቀመበት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት 2ኛ ተከሳሽ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ከሳሽ ክሱን ያቀረቡት ለክሱ መነሻ የሆነው የመሬት ለውጥ ውል መደረጉን ካወቁ ስድስት ወር ካለፈው በኃላ መሆኑን ገልጾ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ክሱ በስድስት ወር ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የስር ከሳሽ በዚህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ባለመስማማት በተራቸው ያቀረቡትን ይግባኝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዘግቶ ያሰናበተው ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ተከሳሾች ሁለት ጥማድ መሬት የተቀያየሩ መሆኑ እና የመሬት ቅያሪ ውሉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 “ም” ሆነ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 መሰረት ስልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበ መሆኑ በግራ ቀኙ ያልተካደ መሆኑን፣የስር ከሳሽ በ21/01/2004 ዓ.ም. የተደረገውን ውል ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስካቀረቡበት ቀን ድረስ ስድስት ወር ያለፈው ስለመሆኑ የስር 2ኛ ተከሳሽ ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን፣የመሬት ቅያሪ ውል የይፍረስልኝ ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበትን የይርጋ ዘመን የሚያመለክት በክልሉ የቤተሰብ ሕግም ሆነ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 እና ደንብ ቁጥር 151/2005 ውስጥ የተካተተ ድንጋጌ አለመኖሩን ገልጾ የሁለቱን የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር እና በአንጻሩ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ችሎት ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የሁለቱን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከሻረ በኃላ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በአሁኑ አመልካች የቀረበውን ክርክር አጣርቶ ይወስን ዘንድ ጉዳዩን ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይመልስ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ጭምር ውሳኔ የመስጠቱን አግባብነት ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 ድንጋጌ አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባው የስር ፍርድ ቤቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ የሰጡት ለጉዳዩ አወሳሰን አስፈላጊ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በአግባቡ እንዲጣሩ ካደረጉ በኃላ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪዋ በወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት ባለቤታቸው 1ኛ ተከሳሽ ከአመልካቿ እውቅና ውጪ ከአሁኑ አመልካች ጋር ያደረጉት የሁለት ጥማድ የእርሻ መሬት ቅያሪ ውል በፍርድ ኃይል እንዲፈርስላቸው በመጠየቅ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው ክይርጋ መቃወሚያ በተጨማሪ መሬቱን የተለዋወጡት በ1994 ዓ.ም መሆኑን፣ በ2004 ዓ.ም የተደረገው የድንበር ስምምነት እንጂ የመሬት ቅያሪ ውል አለመሆኑን፣ሁለቱም ወገኖች በ1994 ዓ.ም በተደረገው ለውጥ መሰረት በእጃቸው በገባው መሬት ላይ የሳር ቤት መስራታቸውን እና አመልካች በተጨማሪም በመሬቱ ላይ ቋሚ አትክልቶችን ማልማታቸውን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡በሌላ በኩል በ21/01/2004 ዓ.ም በተደረገው ውል ላይ የነበሩት ምስክሮች ውሉ የመሬት ቅያሪ ውል መሆኑን እና የተደረገውም በአንድ ጥማድ መሬት ላይ መሆኑን በመግለጽ የመሰከሩ ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው ደግሞ ተጠሪዋ በሁለቱ ጥማድ እንዲጠቀሙ በማለት ከመሆኑም በላይ የተጠሪዋ ባለቤት በቅያሪ አግኝተዋል ስለተባለው መሬት በውሳኔው ላይ ያሰፈረው ነገር አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡የመሬት ቅያሪው የተደረገው በ1994 ዓ.ም ስለመሆኑ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መሬቱ የሚገኘው በአመልካች እጅ ስለመሆኑ የወረዳው መሬት አስተዳደር እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በቁጥር WLBEN/525/06 በ25/02/2006 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ የገለጸ ስለመሆኑ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የገለጹትን ፍሬ ነገር ተጠሪዋ በመልሳቸው በዝምታ ከማለፍ በቀር ማስተባበያ ያልሰጡበት ከመሆኑም በላይ የወረዳው መሬት አስተዳደር እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ቁጥሩ እና ቀኑ ከላይ በተጠቀሰው ደብዳቤ ሰጠ ስለተባለው መግለጫ ሁሉም የስር ፍርድ ቤቶች በውሳኔያቸው ላይ የገለጹት ነገር የለም፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም ፍርድ ቤት ባለጉዳዮችን ማከራከር የሚገባው የተለያዩበት የሕግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ምን እንደሆነ አረጋግጦ ለጉዳዩ ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ ስለመሆኑ፣የነገር ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ተከራካሪ ወገን ያመነውን የሕግ ወይም የነገር አግባብ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በማስተባበል የካደ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ፣ፍርድ ቤቱ ጭብጥን ለመመስረት የሚችለውም ከግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሰረት በሚደረግ ምርመራ በተከራካሪ ወገኖች የሚሰጠውን መልስ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የጭብጥ አመሰራረትን በሚደነግጉ ከቁጥር 246 እስከ 248 በተመለከቱት የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በክርክሩ የተያዘው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጭብጥ ምን እንደሆነ እና ጭብጡ በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የተወሰነበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ የፍርድ አጻጻፍን በሚመለከተው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 182(1) ስር በአስገዳጅነት ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከተው ፍርድ ቤት ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ አስቀድሞ በመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦች ላይ ውሳኔ መስጠት ያለበት ቢሆንም ለመቃወሚያ ክርክሩ አወሳሰን አግባብነት ያላቸው ምስክሮች ሳይሰሙ እና አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ሳይቀርቡ በመቃወሚያው ላይ ውሳኔ ለመስጠት የማይቻል በሆነ ጊዜ ግን ፍርድ ቤቱ በመቃወሚያ ነጥቦች ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ተገቢ መስሎ የሚገምተው ማስረጃ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ የሚሰጥ ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 244(1) እና 245(1) ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡በተያዘው ጉዳይም አግባብነት ያለውን የይርጋ ዘመን ከመለየት በተጨማሪ ይርጋው መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ለይቶ ለማወቅ የሚቻለው የመሬት ለውጡ የተደረገው መቼ ነው? የሚለው የክርክር ነጥብ በማስረጃ ተጣርቶ ከታወቀ በኃላ ነው፡፡የክልሉ ሰበር ችሎት ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በሁለቱ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ ያልተቀበለው ከሆነም ውሳኔውን ሽሮ በፍሬ ጉዳይ ረገድ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመለስ የሚገባው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 ድንጋጌ የሚያመለክት ሆኖ እያለ አመልካች በፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ረገድ ያላቸውን የይግባኝ መብት በሚያጣብብ ሁኔታ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ጭምር ጉዳዩን አጠቃሎ ውሳኔ መስጠቱ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ያልተደረጉት ከአመልካች ጋር ውሉን አድርገዋል የተባሉት የስር 1ኛ ተከሳሽም የክርክሩ ውጤት በቀጥታ የሚመለከታቸው በመሆኑ በቀጣይ የክርክር ሂደት የክርክሩ አካል መደረግ የሚገባቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ አወሳሰን አስፈላጊ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በተገቢው ስነ ስርዓታዊ አግባብ እንዲጣሩ ሳይደረግ የስር ፍርድ ቤቶች በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. አመልካች ሁለት ጥማድ መሬት ለተጠሪ እንዲለቁ በወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10986 08/12/2005 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ፣ይህንን ውሳኔ በመሻር ክሱ በስድስት ወር ይርጋ የታገደ ነው በማለት በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 29851 በ03/04/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት በመዝገብ ቁጥር 170870 በ02/07/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ እና የሁለቱን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሽሮ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 184750 በ26/01/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. ከላይ በውሳኔው ይዘት ውስጥ በተገለጸው መሰረት በአከራካሪው የቅያሪ ውል መሰረት በአመልካች እጅ የገባው መሬት ምን ያህል ነው? አንድ ጥማድ ወይስ ሁለት ጥማድ? ቅያሪው የተደረገው አመልካች እንደሚሉት በ1994 ዓ.ም. ነው ወይስ ተጠሪ እንደሚሉት በ21/01/2004 ዓ.ም. በተደረገው ውል ነው? ከይርጋ አቆጣጠር አንጻር ተጠሪ የለውጥ ውል መደረጉን ያወቁት ወይም አውቀዋል ሊባሉ የሚችሉት መቼ ነው? የቅያሪውን ጊዜ አስመልክቶ በማስረጃ በሚረጋገጠው እና ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው ወይስ አይደለም? የመሬት ቅያሪ ውሉ በሚመለከተው አካል የተመዘገበ እና ዕውቅና የተሰጠው ነው ወይስ አይደለም? አመልካች እና የተጠሪ ባለቤት የተቀያየሩትን መሬት በይዞታቸው ስር አድርገው የቆዩት ለምን ያህል ጊዜ ነው? በተለዋወጡት መሬት ላይ አመልካች ቤት መስራታቸው እና ቋሚ አትክልቶችን ማፍራታቸው የሚረጋገጥ ከሆነ ይህ ሁኔታ በጉዳዩ አወሳሰን ላይ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት አለ ወይስ የለም? በ21/01/2004 ዓ.ም. የተደረገው ውል ሙሉ ይዘት ምንድነው? ቅያሪው የተደረገው በ1994 ዓ.ም. መሆኑ የሚረጋገጥ ከሆነ በ21/01/2004 ዓ.ም. የተደረገው ውል ዓላማ ምንድ ነው? የቅያሪ ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚባል ከሆነ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? የሚሉትን እና ከእነዚሁ የሚመነጩ ተያያዥ ነጥቦችን እንደየአግባብነቱ በግራ ቀኙም ሆነ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በሚቀርቡ ማስረጃዎች በማጣራት እና የስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ታከለ ደበሬ የክርክሩ ተካፋይ ሆነው እንዲቀጥሉ በማድረግ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሰረት ወስነናል፡፡

3. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲሁም እንዲያውቁት ለደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 99642

ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፣- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- ቴራ ኮንስትራክሽን ባለቤቱ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ሚካኤል ነገሰ ደበበ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዮን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዮ በክርክር ባለው ጉዳይ ዋስ እንዲጠራ በተሰጠው ትዕዛዝ ተገቢነት የተመለከተ ነው፡፡ በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን እየተከራከሩ ነው፡፡ አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ በሆኑ ማሽነሪዎች ሊያደርሰው ይችላል የተባለውን ጉዳት ለመከላከል ወይም ለማካካስ የብር 8 ሚሊዮን ዋስ እንዲጠራ የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ የሚል አቤቱታ በማቅረቡ ምክንያት የዚህ ትዕዛዝ ሕጋዊነት ለመመርመር የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ ክፍሉ ያሰፈረው ፍሬ ነገር ግራ ቀኙ እያከራከሩ ያሉትን ማሽነሪዎች በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ በአመልካች ይዞት ሥር ያሉ ናቸው፡፡ ምንአልባት ተጠሪ እንደሠጋው የማሽነሪዎቹ የተለያዩ ወሳኝ አካላቶች ቢፈታቱ ወይም ከጥቅም ውጪ ቢሆኑ በእርግጥም በተጠሪ ላይ ከፍ ያለና የማይተካ ጉዳት ሊደርስ የሚችል በመሆኑ ማሽነሪዎችን በተመለከተ አመልካች ለብር 8 ሚሊዮን /ስምንት ሚሊዮን/ የሚበቃ ዋስ እንዲጠራ ወይም ገንዘቡን በሞዴል 85 እንዲያሲዝ ማዘዙን ያሳያል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ከዚህ በተጨማሪ ለክርክሩ መነሻ የሆኑ ማሽነሪዎች እንዳይሸጡ እንዳይለወጡ እንዲሁም በማናቸውም መንገድ ለሌላ 3ኛ ወገን ሳይተላለፉ ታግደው እንዲቆዩ መታዘዙን የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካችም የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘት ማሽነሪዎቹ በታገዱበት ሁኔታ ተጨማሪ ዋስትና እንዲጠራ መደረጉ ተደራራቢ ዋስትና መሆኑ፣ የተጠቀሰው ገንዘብ ማስያዝ እንደማይችል የጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ ይግባኝ የለም በማለት ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ጥሪ ተደርጐለት ቀርቦ በሰጠው መልስ አመልካች ዋስ እንዲጠራ መታዘዙ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ለመከላከል አስፈላጊ መሆኑ፣ ገንዘብ የሚያስያዝ በቂ ሀብት ያለው ስለመሆኑ ትዕዛዙ ሊጸና የገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ በዋናነት አቤቱታውን የሚያጠናክር ቢሆንም በሰበር ከተያዘው ጭብጥ በዘለለ በፍሬ ነገር ክርክር ሲነሱ የሚገባቸው ነጥቦች ያካተተ በመሆኑ ታልፏል፡፡

ከሥር የጉዳይ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመላኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያደረጉት ክርክር በሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ትዕዛዝ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር ለማዛመድ እንዲሁም ጉዳዮ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዮን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው ማሽነሪዎች ባሉበት ሁኔታ በፍ/ቤት ትዕዛዝ የታገዱ በመሆኑ በድጋሚ ዋስ እንዲጠሩ ወይም ገንዘቡ በሞዴል 85 እንዲያሲዝ መታዘዙ ድርብ ዋስትና እንዲጠራ የሚያስገድድ ትዕዛዝ መሆኑን ይገልፃል፡፡ ተጠሪ በአንፃሩ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ማሽነሪዎች በአመልካች እጅ የሚገኙ በመሆናቸው በመጨረሻ ረቺ መሆኑ በፍ/ቤት ቢወሰን ጉዳዩን ለማስፈፀም የሚያስችል ሀብት ከሌለ የተጠሪ ክርክር መና የሚያስቀር በመሆኑ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ተገቢ መሆኑን ይከራከራል፡፡

በመሰረቱ ከፍርድ በፊት ንብረት የሚከበርበት ወይም ዋስ የሚጠራበት ሥርዓት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 151 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ተፈላጊው ዕቃ ወይም ንብረት ለማቅረብ የሚሰጠው ዋስትና ከተከሳሽ ድርጊት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች መፈፀማቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.151/1/ እንደተመለከተው ተከሳሽ /አመልካች/ ክሱን ለማሰናከል ማቀድ ወይም የተሰጠው ትዕዛዝ እንዳይፈፀም ዘዴ መፍጠሩ የሚመለከት በቃለ ማህላ የተደገፈ አቤቱታ ከቀረበ ፍ/ቤቱም በድንጋጌው የተዘረዘሩትን መሰረታዊ ነጥቦች አንደኛው አመልካች ንብረቱ በሙሉ ወይም በከፊል ለማሸሽ ወይም ለማባከን ማቀዱን ፣ሁለተኛ ከፍ/ቤቱ የዳኝነት ክልል ንብረቱ ለማሸሽ ማቀዱን ሲረዳ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆኑ ማሽነሪዎች እንዳይሸጡ፣ እንዳይለወጡ፣ እንዲሁም በማንኛውም መንገድ ለሌላ 3ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገን እንዳይተላለፉ ታግደው እንዲቆዮ ክርክሩ እየተመለከተ ያለው ፍ/ቤት አዟል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች እጅ ያለውን ንብረት ከማሳገድ በተጨማሪ ዋስ እንዲጠራ የተጠየቀበት ምክንያት ምንአልባት አመልካች የማሽነሪዎቹ የተለያዩ ወሳኝ አካላቶች ቢፈታቱ ወይም ከጥቅም ውጭ ቢሆኑ የሚል ስጋት በመኖሩ ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ የተነሳው ግምታዊ ስጋት ወደ እውነታ የተጠጋ ስለ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ስለመሆኑ የሰጠው ትዕዛዝ አያሳይም፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ማሽነሪዎች በማናቸውም ሁኔታ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፉ በታገዱበት ሁኔታ ወይም ንብረቱ በተከበረበት ሁኔታ በተጠሪ ላይ ተጨማሪ ኪሳራ እንደሚደርስ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች የብር ስምንት ሚሊዮን ዋስ እንዲጠራ ወይም በሞዴል 85 እንዲያሲዝ ማዘዙ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 151 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ ያገናዘበ አይደለም ብለናል፡፡ በዚህ ሁሉ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ዋስ እንዲጠራ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ አተገባበር ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዮን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 138130 ጥር 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.99240 መጋቢት 29 ቀን 2006 ዓ.ም የስምንት ሚሊዮን ዋስትና በተመለከተ የሰጠው ትዕዛዝ ክፍል ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች የብር ስምንት ሚሊዮን ዋስ እንዲጠራ ወይም በሞዴል 85 እንዲያሲይዝ አይገደድም ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤት በሌሎች ጉዳዮች የሰጠው ትዕዛዝ አልተነካም፡፡
4. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 96943

ሚያዝያ 16 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካቾች፡- 1ኛ አቶ ተስፋዬ ወርቁ ጠበቃ በረከት ቡሽራ - ቀረቡ

2ኛ ተስፋሽ ሪል እስቴት ኃ/የተ- የግል ማህበር

ተጠሪዎች፡- 1ኛ ወ/ሮ የምስራች ገ/መስቀል

2ኛ ሰመረ ባህሩ ወ/ሩፋኤል - ቀረቡ

3ኛ መቅደስ ባህሩ ወ/ሩፋኤል

4ኛ ህፃን በረከት ባህሩ ወ/ሩፋኤል

መዝገቡ መርምራን ተከተዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ ጉዳይ በሰበር ሰሚ ችሎት ሊመረመር ይገባል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ አንደኛ አመልካች በተከሰሱበት በንብረት ላይ ደረሰ በተባለው ጉዳይ ካሣ ጥያቄ ግንባታውን ፈፅመዋል የተባለው ብራይት የኮንስትራክሽን ድርጅት የክርክሩ ተካፋይ ሊሆን ይገባ ነበር በማለት ያቀረቡት ጥያቄ የመታለፉ አግባብነት ከፍ/ሀ/ቁ. 2136 አንፃር ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካቾች ተከሳሾች ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሾች ነበሩ፡፡ ጉዳዩም በመኖሪያ ቤት ላይ በደረሰው ጉዳት ቤቱን በድጋሚ ለመገንባት የሚያስፈልግ የገንዘብ መጠን የተመለከተ ክርክር ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ዋና ይዘቱ፡- በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 21 የቤት ቁጥር 711/2 የሆነ በካርታ ቁጥር 20521 በሚች አቶ ባህሩ ወ/ሩፋኤል ስም የተመዘገበው እና 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት እንደሆኑ ከ2-3 ያሉት ደግሞ የሚች ወራሾች መሆናቸው በመ/ቁ. 854/93 እና 206/93 ያረጋገጡበት ቤት የተከሳሾች ይዞታ ከከሳሾች ይዞታ ጋር ወሰንተኛ /ኩታ ገጠም/ በመሆኑ ተከሳሾች በቦታቸው ላይ ህንፃ ለመሥራት ላደረጉት ቁፋሮ መሬቱ ተንዶ የከሳሾች ቤት መሠረቱ በመጋለጡ ያለድጋፍ በመንጠልጠሉ እና ቤቱ ስለተሰነጣጠቀ ቤቱ ከመደርመሱ በፊት ተከሳሾች በራሳቸው የቀጠሩት አማካሪ መሃንድስ ባቀረበው ሐሳብ መሰረት ችግሩ ወደ ባሰ ደረጃ ሳይደርስ የመከላከያ ዕርምጃ እንዲወሰዱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ልማት ቢሮ አሳውቋል፡፡ ተከሳሾች በመሃንዲስ የቀረበው ምክረ ሐሳብ ባለመሥራታቸው ቤቱ መደርመሱ፣ ሳሎኑ ደግሞ ያለድጋፍ መንጠልጠሉ በአጠቃላይ ቤቱ ከጥቅም ውጭ በመሆኑ ከሳሾች ቤቱን መልቀቃቸው፤ የአዲስ አበባ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ልማት ቢሮ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በመጀመሪያ የድጋፍ ግንቡን ከሰሩ በኃላ ቀጥሎ የከሳሾች ቤት እንዲሰሩ የተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ተግባራዊ አላደረጉም፡፡ በወንጀል ያቀረቡት ክስም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የፈረሰውን ቤት መልሶ ለመሥራት ብር 764,154.20 /ሰባት መቶ ስልሳ አራት ሺ አንድ መቶ ሃምሳ አራት ከሃያ ሳንቲም/ እንደሚያስፈልግ በቦታው ተገኝቶ ኢትዮ አማካሪ አርክቴክቶችና መሐዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተባለ ገለልተኛ ድርጅት ስለአረጋገጠ ይህንኑ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ተከሳሾች እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው ከሳሾች ቤቱ ተሰርቶ እስከሚገቡ በየወሩ ብር 8,000 የቤት ኪራይ እንዲወሰንላቸው ወጪና ኪሳራ የጠበቃ አበል ጭምር መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡

ተከሳሾች የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ፤ በፍሬ ጉዳዩ መልስ እና የተከሳሽ ከሳሽነት ይዘው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው መቃወሚያ ሥራውን የሚሠራው ብራይት ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ ማህበር በመሆኑ በክሱ ገብቶ እንዲከራከር የሚል ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ከሳሾች ክስ ያቀረቡት ቤቱን አንገዛም ስላልናቸው ከቅን ልቦና ውጭ በለቀቁት ጎርፍ መሆኑን፣ የወንጀል ክስም ማቅረባቸው ተጠሪዎች ከቤቱ ውስጥ እየኖሩ ነው፡፡ በአካባቢው የተመሳሳይ ቤት ኪራይ ከ1000-2000 ብር ብቻ ነው፡፡ በተከሳሽ ከሳሽነት ቤቱ ለአደጋ የተጋለጠው ከሳሽ በለቀቁት ፈሳሽ መሆኑን በከሳሽ በተፈፀመው ድርጊት ምክንያት የቤቱ መሠረት ሲፈርስ አንድ ሠራተኛ መሞቱ፣ መከላከያ ግንብ ለመገንባት፤ ለድንጋይ ለጠጠር፣ ለአናጢ፣ ሚስማር በድምሩ 200,000 እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው የተከሳሽ ከሳሽነት አቅርበዋል፡፡

ከሳሾች ለቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት መልስ ያቀረቡ ሲሆን የከሳሾች ቤት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ መሆኑ በባለሙያ መረጋገጡ፤ ጉዳት የደረሰውም በተከሳሾች ጥፋት መሆኑን የወንጀል ክስም ውድቅ መደረጉ ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙ የቃል ክርክር አዳምጧል፡፡ ተገቢ ነው ያለውን ጭብጥ (ቤቱ በማን ጥፋት ፈረሰ? ተከሳሾች ኃላፊ ሊሆኑ ይገባል? ኃላፊነት አለባቸው ከተባለ መጠኑ ምን ያክል ነው?) በመመስረት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ቤቱ ሊፈርስ የቻለው የተከሳሾች የግንባታ ሥራውን ለማከናወን ባደረጉት ቁፋሮ በፍ/ህ/ቁ.1210 የተጣለባቸው ግዴታ ወደ ጎን በመተው እና አስፈላጊ ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው በፈጸሙት ጥፋት እንደሆነ ፍ/ቤቱ መገንዘቡን፤ ተከሳሾች ቤቱን ሊፈርስ የቻለው በአንደኛ ከሳሽ ጥፋት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የተከሳሽ ከሳሽነትን በተመለከተም ተከሳሾች ወጪ አውጥተው የድጋፍ ግንብ መሥራታቸውን ገልፀዋል ይህ የሚያመለክተው ደግሞ የከሳሽ ተከሳሾች ቤቱ ለአደጋ የተጋለጠው እነሱ በፈጸሙት ጥፋት መሆኑን እምነው መቀበላቸው ነው፡፡ በዚህ አግባብ የፈጸሙት ክፍያ የመጠየቅ መብት የላቸውም፡፡ ቤቱ መልሶ ለመሥራት የሚያስፈልገው ወጪ ብር 764,154.20 መሆኑን ኢትዮ አማካሪ አርክቴክቶችና መሐንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተባለ ገለልተኛ አካል ገምቶ አቅርበዋል፡፡ የግምቱ መጠን የተጋነነ ነው የሚለው መከራከሪያ በብይን ውድቅ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በገለልተኛ አካል ተገምቶ የቀረበው ብር 764,154.20 ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ የቤት ኪራይ በተመለከተ በራሳቸው ቤት ስለሚኖሩ አልተቀበለውም ፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ፍርድ ቤቱ ቤቱ የፈረሰው በአመልካቾች ጥፋት መሆኑ የክርክሩ ተካፋይ ሊሆን ይገባ ነበር የተባለው የስራ ተቋራጭ ከሰው ከሚጠይቁ በስተቀር አሁን ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት የሚመለስበት የህግ ምክንያት እንደሌለ፣ የካሳ መጠኑም በገለልተኛ ባለሙያ ተገምቶ የቀረበ ነው የሚነቀፍ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ካነሱዋቸው መሠረታዊ ነጥቦች፡- ህንፃው ገና ያልተገነባ በመሆኑ የኃላፊነት መሰረቱ በአግባቡ ያልታየ መሆኑን፤ የስራ ተቋራጩ ጣልቃ እንዲገባ የቀረበው ጥያቄ መታለፉ ተገቢ አለመሆኑን፤ የካሳው አወሳሰን ሥርዓትና መጠን አወሳሰን የተጋነነ ስለመሆኑ የሚገልጽ ነው፡፡ ተጠሪዎች የበኩላቸውን መልስ አቅርበዋል ፡፡ ዋና ፍሬ ነገሩ ቤቱ እየተገነባ ያለው በአመልካቾች መሆኑን ቤቱን በሙሉ ለመገንባት ግዴታ ገብቷል፡፡ ቤቱ የፈረሰው በቁፋሮ ላይ ነው የህንፃ ተቋራጩ መሥራቱን አያሳይም፡፡ የተከሳሽነት ከሳሽ ያቀረቡት በራሳቸው ስለሚሰሩት ነው፡፡ በአስተዳደሩ የድጋፍ ግንብ እንዲሰሩ ታዘው ነበር፡፡ የወንጀል ክስም ውድቅ ተደርጓል፡፡ የካሳው ዘዴና መጠን አሁን ቤት ለመሥራት የሚያስፈልገውን ወጭ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ቤቱ ለመሥራት ግዴታ ገብቷል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታቸው የሚያጠናክር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው የጉዳት ካሳ ጥያቄ በተመለከተ ግንባታ ለማከናወን የሥራ ተቋራጭ የነበረው ብራይት ኮንትራክሽን የክርክሩ ተካፋይ ሊሆን ይገባ ነበር የሚል ክርክር በአመልካች ቀርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካቾች ግንባታው በራሳቸው የሚያከናውኑት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አጣርቶ በመወሰኑ አመልካች መክሰሳችን በአግባቡ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

ከሥር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት ለመረዳት እንደተቻለው አመልካቾች የተጠሪዎች ቤት ላይ የመከለከያ ግንብ እንዲገነቡ፤ ጉዳት ከደረሰ በኃላም ቤቱን ሙሉ በሙሉ እንዲገነቡ በአዲስ አበባ አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ ልማት ቢሮ መታዘዛቸው፤ አመልካቾችም ቤቱን ለመገንባት ግዴታ መግባታቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ሥልጣናቸው የተጠሪዎች ቤት ሊፈርስ የቻለው በአመልካቾች ጥፋት ስለመሆኑ አረጋግጠዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የፍሬ ነገር ማጣራት እና ማስረጃ ምዘና ውጤት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳለ የሚቀበለው ነው፡፡ ምክንያቱም የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሕግ ተሰይቶ የተሰጠው ሥልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን ያለመሆኑን መመርመር ብቻ ስለመሆኑ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የሥር ፍርድ ቤቶች ከሁለቱም ለጉዳዩ ኃላፊ ማን ነው? የሚለው በሥር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር እና የቀረበው ማስረጃ መሠረት በማድረግ አመልካቾች ቤቱን በማፍረስ ረገድ ጥፋት መፈጸማቸው ከድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም ቤቱን አፍርሰዋል ባሉት ግለሰብ ላይ ክስ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራቀኙ ክርክር ማስረጃ በመመዘን ኃላፊ መሆናቸው ካረጋገጠ ግንባታው ለመሥራት ውል ገባ የተባለው የስራ ተቋራጭ የክርክሩ ተካፋይ ካልሆነ ልንጠይቅ አይገባም የሚለው ክርክር ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ድርጊት የተፈጸመው በሥራ ተቋራጭ ነው የሚሉ ከሆነም ለተጠሪዎች ተገቢ ተብሎ የተወሰነው ካሣ ከፍለው በሥራ ተቋራጩ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚከለከሉበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡

የአመልካቾች የስራ ተቋራጭ የክርክሩ ተካፋይ ይሁን ጥያቄ በፌዴራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ተደርጓል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍርድ ሐተታው ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱ ተገቢነት እንደሌለው ገልጸዋል፡፡ አንድ ተከራካሪ ወገን ሌላ ተከራከሪ ግለሰብ ወደ ክርክሩ እንዲገባ በሕጉ አግባብ መጠየቁ ተገቢ ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከግለሰቡ መብት አንጻር ብቻ ሳይሆን ከፍትሐብሄር ስነሥርዓት ሕግ ዓላማ ግብ ጭምር ነው፡፡ የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ዓላማና ግብ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ፍትሐዊ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ ውሳኔ እንዲያገኙ/ economic and efficient resolution of dies puts/ ማድረግ ስለመሆኑ ከአጠቃላይ የህጉ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በተጠሪዎች የቀረበው የቤታችን ፈረሰብን ጥያቄ እንደገና በሥር ፍርድ ቤት ክርክር ቀርቦ እንዲወሰን ማድረግ ጉዳዮች ከበቂ ጊዜ በላይ እንዲጓተቱ በማድረግ በተከራካሪዎች ጊዜ፤ ወጪና ጉልበት ከፍተኛ ጉዳት ማድረስ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች የሥራ ተቀራጩን ለመጠየቅ የሚከለክል የህግ አግባብ በሌለበት ሁኔታ ጉዳዩን በአዲስ ክርክር እንዲመራ መጠየቅ ከላይ የተመለከተው የፍትሐብሔር ህግ ዓለማና ግብ የሚያሳካ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች የሥራ ተቋራጭ የክርክሩ ተካፋይ ይሁንልን ጥያቄ ውድቅ ማደረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳይ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍረድ ቤት በመ/ቁ. 108002 በ18/05/2005 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 88156 በ30/03/2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች የተጠሪዎች ቤት መልሶ ለመሥራት የሚያስፈልገውን ብር 764,154.20 ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ገንዘብ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% ህጋዊ ወለድ ጋር በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. በዚህ ፍ/ቤት የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101345

መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ፀጋዬ ብርሃኑ - ወኪል ይርጋ ብርሃኔ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መሰረት ተገኝ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍትሐብሔር ጉዳይ ፍርድ እና አፈጻጸሙን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ለአፈጻጸሙ መሰረት የሆነው ውሳኔ የተሰጠው ደግሞ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 128082 ነው፡፡ በዚህ መዝገብ የተሰጠው የውሳኔ ይዘት ዋናው ክርክር የጀመረው በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት የአመልካች ክስና የዳኝነት ይዘቱ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 166 የሆነ የመንግስት ቤት ከአሁኗ ተጠሪ ተከራይተው ሲሰሩበት የነበረ መሆኑ በመመሪያው መሰረት ክፍለ ከተማው አምኖበት የኪራይ ውል በስማቸው አዙሮ ካበቃ በኋላ ቤቱን እንድትለቅ በማለት ሁከት የፈጠረባቸው መሆኑን ዘርዝረው ሁከቱ እንዲወገድላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ክሱን መጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም የአራዳ ክፍለ ከተማውን በተከሳሽነት ፣ የአሁኗን ተጠሪ ደግሞ በጣልቃ ገብነት አከራክሮ ጉዳዩን መርምሮ ጣልቃ ገብ በመመሪያው መሰረት ልዩ ተጠቃሚ መሆናቸውን የማስረዳት ሸክም ያለባቸው መሆኑን፣ ይህን የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው ህጋዊ ተቋም የተሰጠ ማስረጃ ስላላቀረቡ ቤቱንም የእድሳት ፈቃድ አውጥተው በማደስ እየሰሩ እያለ ለጣልቃ ገብ ይገባል በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተረጋግተው እንዳይሰሩ ማድረጉ ሁከት ተግባር በመሆኑ ሁከቱ ሊቆም ይገባል በማለት የወሰነ ሲሆን በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪና ክፍለ ከተማው ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በመ/ቁጥር 128082 እና 128271 በሆኑት የአሁኑን አመልካች በመልስ ሰጪነት ሰይሞ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮ ተፈጻሚነት ባለው የውሳኔው ክፍል በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 166 የሆነውን ክርክር የተነሳበትን ቤት ለወ/ሮ መሰረት ተገኝ ይመለስላቸው፣የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ወስኗል፡፡

ይህንኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመያዝና የፍርድ ባለመብት በመሆን የአሁኑ ተጠሪ በመ/ቁጥር 213768 በሆነው አፈፃፀሙን የቀጠሉ ሲሆን የአሁኑ አመልካችም በፍርድ ባለእዳነታቸው ቀርበው ፍርዱን እንዲፈፅሙ ተጠይቀው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊፈጸም አይችልም በማለት መዝገቡን የዘጋበትን ማስረጃ አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በችሎቱ አፈጻጸሙ አይቀጥልም በማለት የገለፀ መሆኑ አፈጻጸሙን አያግድም በማለት በመ/ቁጥር 128082 የተሰጠው ውሳኔ እንዲፈጸም ለአፈጻጸም መምሪያ ውሳኔውን በማያያዝ ትዕዛዙን አስተላልፎአል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128082 የሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድ ቤት ያለ ስልጣኑ ሁከት ነው ተብሎ የተሰጠ ነው የሚል ሆኖ እያለ የሚፈጸም ውሳኔ አለ ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ፍርድ ያረፈበት ንብረት ማዕድ ቤት እንጂ ስድስት ክፍል ቤቶች፣ ባህር ዛፎችና ጽድ ያለበት ቦታ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍርድ መፈፀም ያለበት እንደ ፍርዱ መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 ድንጋጌ መረዳት የምንችለው ጉዳይ ሲሆን ደረጃውን ጠብቆ በቀረበው የአፈፃፀም ጉዳይ ላይ በአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውን የፍርድ ይዘት አድማስ በማስፋት ወይም በማጥበብ ፍርድን ለማስፈፀም የሚያስችል የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ስለፍትሐብሔር ጉዳይ አፈጻጸም ከተደነገጉትና የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ በአንድ የፍትሐብሔር ጉዳይ ፍርድ የሚሰጠው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182 እና 183 በተደነገገው አግባብ ሲሆን በዚህ አካኃን የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 እና 372 መሠረት ሥልጣን ያላቸው የአፈፃፀም ችሎቶች ስለ ፍርድ አፈፃፀም የተዘረጉትን ሥርዓቶችን በመከተል እንደ ፍርዱ ከመፈፀም በቀር የአንድ ፍርድ ይዘትን በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆን በማስፋት ረገድ ፍርድን የመተርጎም ሥልጣን ያልተሰጣቸው መሆኑም ግልፅ ነው፡፡ ድንጋጌዎች በግልፅ የሚያስገነዝቡት አቢይ ነጥብ የፍርድ አፈፃፀም ስርዓት ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ በእራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር ወይም ውጤት የሚለውጥበት ሥርዓት መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የድንጋጌዎች አቀራረፅ፣ ይዘትና መንፈስ በጥንቃቄ ሲታይም የፍርድ አፈጻጸም ስለፍርድ አፈጻፀም የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመከተል ፍርድን በተግባር መተርጎም እንደመሆኑ መጠን የአፈጻጸም ሥርዓቱ ህጉን መሰረት ማድረግ ያለበትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን መሠረታዊ ዓላማ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአነስተኛ ወጪ፣ጊዜና ጉልበት በተፋጠነና ፍትሓዊ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም በሚያስችል አግባብ ሕግ አውጪ ያስቀመጣቸው መሆኑን የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም በሕግ አግባብ የተቋቋመ ፍርድ ቤት አከራክሮ መወሰን ብቻ ሳይሆን የወሰነው ውሳኔ ውጤት ባለው መልኩ ወደ ተግባር መለወጡን ጭምር ማረጋገጥ አቢይ ሐላፊነትና ተግባሩ በመሆኑ ይህንኑ በሕግ የተሰጠውን ስልጣን ተግባራዊ ሲያደርግ ግን ሕጉንና ሕጉን ብቻ መሠረት ማድረግ አለበት፡፡ የአፈጻጸም ጉዳይ ደግሞ የሚመራበትን አግባብ ሕጉ ዘርግቷል፡፡ በሕጉ ከተዘረጉት ስርዓቶች አንዱ ደግሞ አፈጻጸሙ ሊመራ የሚገባው እንደዋናው ፍርድና ተገቢ ሁኖ ሲገኝም ፍርዱን ለማስፈፀም በሚያስችል አግባብ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና 392 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም በሕግ አግባብ የተቋቋመ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በሕጉ አግባብ በተቋቋመ የበላይ ፍርድ ቤት በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሠረት እስካልተለወጠ ድረስ የማይፈፀምበት አግባብ የለም፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው በመርህ ደረጃ የተሰጡት የፍርድ ቤት ውሣኔዎች እንደፍርዱ ተፈፃሚነት እንዲያገኙ ማድረግ ህጉ የግድ የሚለው ጉዳይ ሲሆን አልፎ አልፎ ሊፈፀም የማይቻል ፍርድ ሊኖር እንደሚቻል ከፍታሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392(1) መሠረት አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ሊፈፀም የሚቻል ውሣኔ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ማረጋገጥ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ ፍርዱ የማይፈፀምበት ህጋዊ ምክንያት ካለ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.392(2) መሠረት ይዜንኑ በማመልከት ሊፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚቻል ያስገነዝባል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንጻር የተያዘው ጉዳይ ስንመለከት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ዋና ክርክር በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሁከት ይወገድ ተብሎ ከተወሰነ በኃላ ጉዳዩ በይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በመ/ቁጥር 128082 እና 128271 በሆኑት የአሁኑን አመልካች በመልስ ሰጪነት፣ የአሁኗን ተጠሪ እና ክፍለ ከተማውን ደግሞ በይግባኝ ባይነት ሰይሞ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮ ተፈፃሚነት ባለው የውሳኔው ክፍል ደግሞ በአራዳ ክፍለ ከተማ 5 የቤት ቁጥር 166 የሆነውን ክርክር የተነሳበት ቤት ለወ/ሮ መሰረት ተገኝ ይመለስላቸው፣ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት በግልጽ ወስኗል ። ይህ ውሳኔ በግለጽ የሚያሳየው ቤቱ ለተጠሪ እንዲመለስላቸው እንጂ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ያለስልጣኑ የታየ ነው በሚል የተደመደመ ያለመሆኑን ነው። ውሳኔው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት ስለመለወጡ በአመልካችም በኩል የቀረበ ክርክር የለም እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ራሱ አፈጻጸሙን የማይመራ መሆኑን ጠቅሶ አመልካችን ከማሰናበቱ በስተቀር በመ/ቁጥር 128082 የሰጠው ውሳኔ የማይፈፀም መሆኑን ገልፆ አፈጻጸሙን ማቆሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አለማቅረቡን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳይል ። በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ትዕዛዝ ለአፈጻጸም መነሻ ከሆነውና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128082 ከተሰጠው ዋና ውሳኔ ይዘት እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር የተጣጣመ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም ። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 213768 መጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 150831 ግንቦት 04 ቀን 2006 ዓ/ም በተሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል።
2. ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128082 በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ሊፈጸምላቸው ይገባል ተብሎ አፈጻጸሙ ለአፈፃጸም መምሪያ መመራቱ በአግባቡ ነው ብለናል።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ት ዕ ዛ ዝ

ሰኔ 02 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 100673

ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አዳነ መንገሻ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የጋዘር ማዘጋጃ ቤት ተወካይ ዓ/ሕግ አሰግድ አድማሱ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ይግባኝ ባይ ተጠሪ መልስ ሰጪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ተነስቶ ወደ ክርክር እንዲገባ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በሚል ያቀረበው ቅሬታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

ለዚህ አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የንብረት ግምት የተመለከተ ሲሆን አመልካች የጋዘር ማዘጋጃ ቤት ባለሙያ ባልሆነ ግለሰብ የአትክልት ግምት ብር 14,772 መወሰኑ በሕጉ አግባብ ባለመሆኑ ለደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረቡ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የአመልካች ይግባኝ ያስቀርባል ያለው በመሆኑ ለተጠሪ መጥሪያ ልከዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ 08867 በ09/05/2005 ዓ.ም በተፃፈ የላከው መጥሪያ ለተጠሪ ጽ/ቤት መዝገብ ቤት ገቢ የተደረገ ሲሆን የመዝገብ ቤቱ ሠራተኛ የሆኑት ወ/ሮ ዘውዲቱ ፀጋዬ ፈርመው እንደተቀበሉት እንዲሁም መተማመኛ ሰጥተው ከፍ/ቤቱ መዝገብ ተያይዟል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.70 /ሀ/ መሠረት ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከተው ሲሆን በባለሙያ ተሰራ የተባለው ግምት ውድቅ በማድረግ ተጠሪ ብር 128,700.00 ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች በክርክር ሂደት አወጣሁት ያለውን ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለው ጉዳዩን ለወሰነው ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የመከላከያ መልሱ እንዲያቀርብ መጥሪያ የተላከለት ሲሆን በ25/06/2005 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው አቤቱታ አቅርበው አመልካችም መልስ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ለሥልጠና ሄደው እንደነበር፤ የኃላፊ ተወካዩም ቀበሌዎች ለማስፋፋት ሥራ የሄዱ በመሆኑ በሌሉበት የተሰጠው ፍርዱ ሊነሳ እንደሚገባ ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ለተጠሪ ጽ/ቤት መዝገብ ቤት ገቢ የሆነውን መጥሪያ በጽ/ቤቱ የመዝገብ ቤት ሠራተኛ ተፈርሞ መተማመኛ የተሰጣቸው በመሆኑ ተጠሪ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ የሚነሳበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብሏል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አንድ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ሊነሳ የሚችለው በቂ ምክንያት መኖሩን ሲረጋገጥ ነው፡፡ የተጠሪ ጽ/ቤት ኃላፊ ባይኖርም ሌላ ሰው ተወክሎ መከራከር ይችል ነበር፡፡ የተጠሪ ጽ/ቤት የመዝገብ ቤት ሠራተኛ የሆኑት ወ/ሮ ዘውዲቱ ፀጋዬ መጥሪያው በ10/05/2005 ፈርመው ከተቀበሉ በኋላ ፈቃድ የወጡት በ13/05/2005 ዓ.ም ነው፡፡ ጽ/ቤቱ ለሠራተኛዋ የዓመት ፈቃድ ስትወጣ ተተኪ ሠራተኛ መኖሩን ሳያረጋግጥ ፈቃድ እንደማይሰጥ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የሚያሳምን በቂ ምክንያት አልቀረበም በማለት የተጠሪ አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ብይን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙ ካከራከረ በኋላ መጥሪያው ለጋዘር ማዘጋጃ ቤት መዝገብ ቤት ገቢ መደረጉን አልተካደም፡፡ ጉዳዩ ተቋማዊ ይዘት ያለው በመሆኑ የጽ/ቤቱ ሠራተኛ የተቀበለችው ቢሆንም ለጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊ መጥሪያው አልደረሰም፡፡ መጥሪያው የተቀበለችው ሠራተኛ በሎከር ውስጥ የቆለፈችው እና ለሌሎች ሠራተኞች ወይም የበላይ አመራር ካላደረሰች መ/ቤቱ በቸልተኝነት ወይም ህግን በመናቅ ትተዋል ለማለት አልተቻለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በጥልቀት መርምሮ አስፈላጊ ከሆነ ተጠሪ በቂና ተመጣጣኝ ኪሳራ እንዲከፈል ተደርጎ ወደ ክርክር ሊገባ ይገባ ነበር፡፡ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78/2/ መሠረት ወደ ክርክር ለመግባት ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ መደረጉ ተቀባይነት የለውም በማለት ሽሮታል፡፡ አመልካች የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ በመሆኑ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ቀርቦ የበኩሉን መልስ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረታዊ ይዘት፡- ከፍርድ ቤት ወጭ የተደረገው መጥሪያ ለተጠሪ ጽ/ቤት መድረሱ፤ በጽ/ቤቱ ማህተም የተረጋገጠ መተማመኛ አቅርቦ ሳለ ፍርድ ተሸሮ ተጠሪ ወደ ክርክር እንዲገባ መደረጉ አግባብነት የለውም የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል የቀረበው መልስ ዋና ፍሬ ነገሩ፡- ከፍ/ቤት የላከው መጥሪያ ለሚመለከተው ኃላፊ አለመድረሱ፤ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን እንዳልነበረው፤ መጥሪያው የሥነ ሥርዓት ሕጉ በደነገገው አግባብ አለመድረሱን መሠረት ተደርጎ ውሳኔው መሻሩ በሕጉ አግባብ ነው ሊጸና ይገባል የሚል መሆኑን ተረድተናል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም አቤቱታውን የሚደግፍ ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፍ/ቤት የተላከው መጥሪያ ለተጠሪ በሕጉ አግባብ አልደረሰውም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስለመጥሪያ አደራረስ የተመለከቱት መሠረታዊ ድንጋጌዎች ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፍ/ቤት መጥሪያ ለተጠሪ ጽ/ቤት ገቢ መሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክርክር መጥሪያው ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች እንዲቀርብ አልተደረገም፡፡ የሥራ ኃላፊዎቹ መጥሪያ መድረሱን ሳያውቁ ቀጠሮ አክብረው አልቀረቡም ሊባል አይቻልም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች መጥሪያ ማድረሱና ስለመድረሱም በተጠሪ ጽ/ቤት ክብ ማህተም የተረጋገጠ መተማመኛ ለፍ/ቤት ማቅረቡ መሠረት በማድረግ በሌሉበት የተሰጠው ፍርድ ለመሻር የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የለም የሚል ክርክር ስለማቅረቡ ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሰረቱ አንድ ተከሳሽ የፍርድ ቤት መጥሪያ ተልኮለት መጥሪያውም በአግባቡ ስለመድረሱ ሲረጋገጥ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይና የሚወሰን ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70/ሀ/ ሥር ተመልክቷል፡፡ የፍ/ቤት መጥሪያ ለሚመለከተው ተከራካሪ ወገን የሚሰጥበት ሥርዓትም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 96 እና 102 ሥር ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል ከፍ/ቤት የተላከው መጥሪያ በሕጉ አግባብ ለሚመለከተው ተከራካሪ ወገን ካልደረሰ በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ የሚነሳበት ስርዓት መኖሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78/2/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ለጽ/ቤት መጥሪያ መድረሱ በማመን ነገር ግን መጥሪያው ተቀበሉ የተባሉት የመዝገብ ቤት ሠራተኛ መጥሪያ ስለመቀበላቸው ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ባለማቅረባቸው ምክንያት ቀርበው ለመከራከር አለመቻላቸውን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡ ኩነቶች /facts/ የተጠሪ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ትዕዛዙን ገቢ በሆነበት ጊዜ በሌላ ቦታ ስልጠና እና ሥራ የነበሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች መጥሪያው ለጽ/ቤቱ መዝገብ ቤት ገቢ አድርገው መተማመኛ ከመውሰዳቸው በቀር መጥሪያ ለመቀበል አግባብ ላለው ሰው መጥሪያውን ስለማደረሳቸው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በፍርድ ሐተታው እንደገለጸው መጥሪያውን የተቀበለችው ዘውዲቱ ፀጋዬ የተባለችው የተጠሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ መሆኗ ከመገለጹ ውጭ ነገረ ፈጅ ወይም መዝገብ ቤት ሹም መሆኗ አልተረጋገጠም፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ እንደተረዳነው መጥሪያው አግባብነት ያለው ሠራተኛ ተቀብሎት ለመሥሪያ ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች መቅረቡን የተረጋገጠ አለመሆኑን ነው፡፡ ከፍርድ ቤት የተላከው መጥሪያ ለሚመለከተው ተከራካሪ ወገን በሕጉ በተዘረጋው የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት መደረሱን ካልተረጋገጠ በስተቀር በሌለበት የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ ተደርጎ መሠረታዊ የሆነውን መከራከር መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል፡፡ የክ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎት ለተጠሪ የተላከው መጥሪያ በአግባቡ አልደረሰም በማለት የደረሰበት ድምዳሜው እና ለድምዳሜው መነሻ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣኑ መሰረት ያደረገ በመሆኑ በዚህ ችሎት በድጋሜ የሚመረመርበት ሥርዓት አይኖርም፡፡ ምክንያቱም ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሕግ ተሰይቶ የተሰጠው ሥልጣን መሠረታዊ የህግ አተረጓጐም ስህተት የተፈጸመባቸው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች ብቻ መርምሮ መወሰን ስለመሆኑ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80/3//ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ በመሆኑም የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ወደ ክርክሩ እንዲገባ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን አያሳይም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍረድ ቤት የደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. ተጠሪ በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክር እንዲገባ መወሰኑ በሕጉ አግባብ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.101478

ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- የረር ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ ጌታቸው ለማ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ባልቻ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ አንድ ተከሳሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ እንዲነሳለት አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ክርክር ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡-ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በፊዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት ተከሳሽ በነበረው የአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች የጽሁፍ መልሱን እንዲያቀርብ በተያዘለት የ30/07/2005 ዓ.ም ቀነ ቀጠሮ መልሱን ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ መሆኑን፣ ክሱን ለመስማት አስቀድሞ በተያዘው የ17/08/2005 ዓ.ም ቀነ ቀጠሮ በአመልካች በኩል የቀረበው ሰው ተገቢ ተወካይ ባለመሆኑ ፍርድ ቤት ለመከራከር የውክልና ስልጣን የተሰጠው የአመልካች ተወካይ እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠት ለ01/09/2005 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱን፣ በዚህ ቀነ ቀጠሮም የአመልካች ተወካይ ባለመቅረቡ ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 70 (ሀ) መሰረት አመልካች በሌለበት ክሱን ከሰማ በኃላ የተጠሪውን ምስክሮች ለመስማት ለ19/10/2005 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱን፣በዚህ ቀነ ቀጠሮ የአመልካች ተወካይ አመልካች በሌለበት የተሰጠበት ትዕዛዝ ተነስቶ ወደ ጉዳዩ ገብቶ ለመከራከር እንዲፈቀድለት በ30/09/2005 ዓ.ም የተጻፈ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቃለ መሀላ ስለመፈጸሙ በዚሁ ዕለት ምልክት የተደረገበትን ማመልከቻ ይዞ እንደቀረበ በችሎት መመዝገቡን፣ፍርድ ቤቱም የተጠሪው ምስክሮች እንዲመለሱ አድርጎ በቃለ መሀላ አቤቱታው ላይ የተጠሪውን የጽሁፍ አስተያየት ከተቀበለ በኃላ አቤቱታውን መርምሮ አመልካች የቃለመሀላ አቤቱታውን ያዘጋጀው እና በሬጅስትራር ጽ/ቤትም ቀርቦ የመሀላ ቃል የፈጸመው በ30/09/2005 ዓ.ም ቢሆንም የቃለ መሀላ አቤቱታውን ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው ግን በ19/10/2005 ዓ.ም. መሆኑን እና ይህም ጉዳዩ አመልካቹ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ ከተሰጠበት ከ01/09/2005 ዓ.ም ጀምሮ ሲቆጠር የአንድ ወር ጊዜ ያለፈው መሆኑን ገልጾ የቀረበውን የቃለመሀላ አቤቱታ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 78 (1) መሰረት በ01/11/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትዕዛዝ ውድቅ በማድረግ የተጠሪውን ምስክሮች ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በሌለበት የተሰጠበት ትዕዛዝ እንዲነሳለት ትዕዛዙ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አላመለከተም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትዕዛዝ በሬጅስትራሩ ፊት የተመዘገበውን ማስረጃ መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታው የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ እና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አንድ ተከሳሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ውሳኔው ወይም ትእዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትዕዛዙ ወይም ውሳኔው እንዲነሳለት ሊያመለክት እንደሚችል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 78 (1) ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ጉዳዩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠው በ01/09/2005 ዓ.ም ሲሆን አመልካቹ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ የተሰጠበት ትዕዛዝ እንዲነሳለት የቃለ መሀላ አቤቱታ ያዘጋጀውም ሆነ በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ በተወካዩ አማካይነት የመሀላ ቃል የፈጸመው በ30/09/2005 ዓ.ም መሆኑ የተረጋገጠ እና የስር ፍርድ ቤትም የተቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ጥያቄው በቁጥር 78 (1) ድንጋጌ መሰረት በአንድ ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ የቀረበ አይደለም ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው አመልካች አቤቱታውን ያዘጋጀውም ሆነ በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ በተወካዩ አማካይነት የመሀላ ቃል የፈጸመው በ30/09/2005 ዓ.ም ቢሆንም አቤቱታውን ለፍርድ ቤቱ (ለችሎቱ) ያቀረበው ግን በ19/10/2005 ዓ.ም መሆኑን እና ከአንድ ወር የጊዜ ገደብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኃላ የቀረበው አቤቱታ ሊስተናገድ የማይገባው መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ የሚከራከረው በአቤቱታው ላይ በ30/09/2005 ዓ.ም በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ በተወካዩ አማካይነት መሀላ ከፈጸመ እና ቀኑን ጭምር የሚገልጽ ምልክት ካስደረገበት በኃላ የቃለ መሀላ አቤቱታውን ለችሎቱ ያቀረበው በዚያኑ ዕለት መሆኑን እና የችሎቱ ዳኛ የቃለ መሀላ አቤቱታውን ከተቀበሉ እና ከመሩበት በኃላ በዕለቱ ስራ በዝቶባቸው ስለነበረ በ19/10/2005 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ እንዲቀርቡ ነግረው ያሰናበቷቸው መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡የቃለ መሀላ አቤቱታው ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ለችሎት እንዲቀርብ በቃለ መሀላ አቤቱታው ላይ በዳኛው በጽሁፍ የተመራበት እና የተፈረመበት መሆኑን እና የተመራበትን ቀን ግን ያልተገለጸበት መሆኑን አመልካች አቅርቦ በአጣሪው ችሎት ካያያዘው የቃለመሀላው ቅጂ እና ቀርቦ በተያያዘው ዋናው መዝገብ ውስጥ ከሚገኘው የቃለመሀላው ቅጂ መገንዘብ ተችሏል፡፡በመሰረቱ እያከራከረ ያለው የቃለ መሀላ አቤቱታው ለችሎት የቀረበው መቼ ነው? የሚለው የጊዜ ጉዳይ ሲሆን የችሎቱ ዳኛ የቃለመሀላ አቤቱታውን ተቀብለው ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ እንዲቀርብ የመሩበትን ቀን በመሩበት ጽሁፍ ላይ ካልገለጹ ቃለመሀላው ለችሎቱ ዳኛ የቀረበው በ19/10/2005 ዓ.ም መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻልበት አግባብ አይኖርም፡፡ ይልቁንም አመልካች የቃለመሀላ አቤቱታውን በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ መሀላ የፈጸመው በ30/09/2005 ዓ.ም መሆኑ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ አመልካች የቃለመሀላ አቤቱታውን ለችሎቱ አቅርቧል ተብሎ ሊወሰድ የሚገባው ቀን ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ነው፡፡ ጉዳዩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ የተሰጠው በ01/09/2005 ዓ.ም ሲሆን አመልካቹ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ የተሰጠበት ትዕዛዝ እንዲነሳለት የቃለ መሀላ አቤቱታውን ያዘጋጀውም ሆነ በሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ በተወካዩ አማካይነት የመሀላ ቃል የፈጸመው እና ለችሎቱም ያቀረበው በ30/09/2005 ዓ.ም. መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ አቤቱታው የቀረበው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 78 (1) ስር የተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ ከማለፉ በፊት በመሆኑ አመልካች አቤቱታውን ያቀረበው የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኃላ ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 82332 በ01/11/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139139 በ21/09/2006 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሮአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች የቃለ መሀላ አቤቱታውን ያቀረበው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 78 (1) ስር የተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ ከማለፉ በፊት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች በክርክሩ ሊሰማ በተያዘው ቀጠሮ ቀርቦ መከራከሪያውን ያላሰማው ወይም መልስ ያልሰጠው በቂ በሆነ ምክንያት መሆን አለመሆኑን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 78 (2) መሰረት መርምሮ ተገቢውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 (1) መሰረት ወስነናል፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በውሳኔው መሰረት ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለፈዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.98593

ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲር.ጋ.ጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ክንፈ ወልደሰንበት - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ስለሺ በቀለ - የቀረበ የለም
2. ወ/ሮ ፍቅርተ በቀለ - ቀረቡ
3. አቶ ልየው መብራቱ - ቀረቡ
4. አቶ አስረስ አሊ - ተወካይ ወ/ሮ ወርቁ ግዛው ቀረቡ
5. አቶ አሰፋ በቀለ - ቀረቡ
6. አቶ ኃይሉ ቸርነት - የቀረበ የለም
7. የካ ክፍለ ከተማ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተዘጋ ነው የተባለን መንገድ በፍርድ ኃይል ለማስከፈት ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደቅደም ተከተላቸው ከ1ኛ እስከ 6ኛ ተከሳሾች በነበሩት የአሁኖቹ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ተጠሪዎች ላይ በ11/10/2004 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የአሁኑ 7ኛ ተጠሪ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ ወደ ጉዳዩ እንዲገባ የተደረገ ተከራካሪ ወገን ነው፡፡ከሳሽ ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ተከሳሾቹ ከይዞታቸው ውጪ በመውጣት አስር ሜትር ስፋት ያለውን መንገድ አጥረው በመያዝ በከሳሽ ላይ ችግር መፍጠራቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚገልጽ ሆኖ በክፍለ ከተማው ፕላን መሰረት የያዙትን አስር ሜትር መንገድ እንዲለቁ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው።ተከሳሾቹ በበኩላቸው የመንገዱ ስፋት አስር ሜትር ሳይሆን ስምንት ሜትር መሆኑን እና ከሕጋዊ ይዞታቸው በመውጣት አጥር በማጠር መንገድ ያላጣበቡ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል።ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት ውሳኔውን ሽሮ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ የሚመለከተውን የአሁኑን 7ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ በማስገባት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ በመለሰው መሰረት ጣልቃ ገቡ በ26/04/2005 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ከሳሽ በቂ መተላለፊያ መንገድ ያላቸው መሆኑን፣በፕላኑ ላይ ያለውን መንገድ ለመስራት በቂ የሆነ ዝግጅት የሚፈልግ እና በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን፣ከሳሽ አቤቱታቸውን ማቅረብ የነበረባቸው ለአስተዳደሩ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል።

ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ከሚመለከተው የክፍለ ከተማው የአስተዳደር ክፍል ተገቢው ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኃላ ተከሳሾቹ ለውስጥ ለውስጥ መንገድ የተጠናውን አስር ሜትር አጣብበው ወደ ይዞታቸው ያጠሩ መሆኑን፣ይሁን እንጂ መንገዱ የተጠናው ተከሳሾቹ ቦታውን በሕጋዊ መንገድ ከያዙ በኃላ እንደሆነ እና በካርታ ተከልሎ ከተሰጣቸው ይዞታ ውጪ የያዙት ቦታ እንደሌለ ከሚመለከተው የአስተዳደሩ አካል ተጣርቶ በተላከው ደብዳቤ የተረጋገጠ መሆኑን፣በፀደቀው የክፍለ ከተማው ፕላን መሰረት የተጠናውን መንገድ ወደ ተግባር ለመለወጥ እንደወሰን ማስከበር፣የካሳ ክፍያ እና መሰል የቅድመ ዝግጅት ተግባራት መከናወን የሚገባቸው መሆኑን፣እንደነዚህ ዓይነት ተግባራትን ደግሞ አስተዳደሩ የሚያከናውነው በራሱ ዕቅድ እና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንጂ በግለሰቦች አነሳሽነት አለመሆኑን ገልጾ ክሱን ውድቅ በማድረግ እና ለተከሳሾቹ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ ጭማሪ ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የከተማው ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች የቀረበላቸውን እንደቅደም ተከተሉ ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ዘግተው በማሰናበታቸው ሲሆን ለዚህ ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ዳኝነት የተጠየቀበት መንገድ አላግባብ መዘጋቱ ተረጋግጧል ከተባለ በኃላ ተጠሪዎቹ ሊለቁ አይገባም መባሉ፣እንዲሁም አመልካች በመንገዱ መዘጋት ተጎጂ መሆናቸው ከታወቀ ተጠሪዎቹ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር እንዲያቀርቡባቸው የመወሰኑን ተገቢነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም መሰረት አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው ለግዴታው መኖር ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2001 (1) እንዲሁም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 258 እስከ 261 ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳይ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በክርክሩ ረቺ ሊሆን የሚችለው በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ክርክሩን ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን በተሻለ ሁኔታ አስረድቶ በተገኘ ጊዜ መሆኑም የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክስ የመሰረቱት ከ1ኛ እስከ 6ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከይዞታቸው ውጪ በመውጣት አስር ሜትር ስፋት ያለውን መንገድ አጥረው በመያዝ በከሳሽ ላይ ችግር መፍጠራቸውን በመግለጽ ነው፡፡ይሁን እንጂ በጸደቀው የክፍለ ከተማው ማስተር ፕላን መሰረት አስር ሜትር የውስጥ ለውስጥ መንገዱ የተጠናው ተጠሪዎቹ አሁን ይዘው የሚገኙትን ይዞታ በሕጋዊ መንገድ ከያዙ በኃላ መሆኑ እና ይዘው በሚገኙት የይዞታ መጠን ላይም በሚመለከተው አካል የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ የተሰጣቸው መሆኑ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡ይህም ተጠሪዎቹ አስር ሜትር መንገዱን አጥረው የያዙት ከሕጋዊ ይዞታቸው ውጪ በመውጣት ስለመሆኑ አመልካች በክሳቸው መሰረት ማስረዳት ያልቻሉ መሆኑን ነው፡፡ክስ ካስነሰው መንገድ ውጪ አመልካች በቂ የመተላለፊያ መንገድ ያላቸው መሆኑም በክርክሩ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች በዚህ ረገድ በሰበር አቤቱታቸው ያቀረቡት ግልጽ የማስተባበያ ክርክር የለም፡፡በማስተር ፕላኑ መሰረት የውስጥ ለውስጥ መንገዱ የጸደቀ ቢሆንም ተግባራዊ የማድረግ ስራው የስር ፍርድ ቤቶች እንደገለጹት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል አማካይነት ዝግጅት ተደርጎበት እና አስፈላጊ የቅደመ ሁኔታ ስራዎች ከተከናወኑ በኃላ የሚፈጸም እንጂ ማስተር ፕላኑን መሰረት አድርገው ግለሰቦች የጸደቀው የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጉዳይ በሕግ አግባብ እንደተሰጠ በሚገመተው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በተረጋገጠው ሕጋዊ ይዞታቸው ውስጥ በሚገኝ ሌሎች ግለቦች ላይ በሚያቀርቡት የመንገድ ይከፈትልኝ ክርክር እልባት ማግኘት የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡የተጠናው አስር ሜትር መንገድ በተጠሪዎቹ የተያዘ መሆኑ መረጋገጡ ደግሞ ብቻውን መንገዱ ወዲያውኑ እንዲከፈት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል አይደለም፡፡በመሆኑም የአመልካቹን ክስ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

የወጪና ኪሳራ ጉዳይን በተመለከተ በሌላ አካኃን እንዲፈጸም በግልጽ ካልተደነገገ በቀር በክስ ምክንያት ስለሚከፈለው ስለማናቸውም ወጪና ኪሳራ የሚከፍለውን ወገን፣የወጪንና የኪሳራውን ልክ፣የሚከፈልበትን ሀብት ምንጭ፣የአከፋፈሉን ሁኔታ እና ሌላውንም ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ፍርድ ቤቱ ትክክል መስሎ በሚገምተው ሁኔታ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 462 ስር ተመልክቷል፡፡ይህም የተከራካሪ ወገኖችን የክርክር አቋም፣የረቺ እና ተረቺ ወገኖችን ማንነት እና መሰል ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወጪና ኪሳራን የመወሰን ስልጣን በመሰረቱ ጉዳዩን ለሚወስነው ፍርድ ቤት የተሰጠ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በወጪና ኪሳራ ጉዳይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑም በስነ ስርዓት ሕጉ ቁጥር 466 ስር ተመልክቷል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች በክርክሩ ተረቺ ወገን መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡የተጠሪዎቹን የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ጭምር ተቀባይነት አግኝቷል፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በሕግ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት በአግባቡ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05149 በ21/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በከተማው ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 21346 በ17/04/2006 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 21533 በ27/05/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ111599

ቀን 29/11/2007

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፉ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃም መሠለ

አመልካቾች፡- 1ኛ. አቶ መላኩ ካሳዬ

2ኛ. አቶ ደነቀው ደሳለው

3ኛ. አቶ ጋሻው ፀሐይነው

4ኛ. አቶ ሳንጃው አየለ

5ኛ. ወ/ሮ የሮም ካሳዬ

ጠበቃ አቶ አላና ፉፋ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሱሲ አለ. ጠበቃ አቶ ኤቢሳ ሶቦቅሳ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የእርሻ መሬትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል አመያ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት ከባለቤቴ እቶ ሸለማ አንገሣ ጋር በፍቺ ምክንያት በፍ/ቤት መዝገብ ቁጥር 12615 ተወስኖልኝ በ6/12/2003 እጄ ገብቶ የይዞታ ምስክር ወረቀት ያለኝን 5.5 ሄክታር መሬት የማሣ ኮድ ቁ. 2020፣2022፣2025 እና 2029 የሚታወቀውን ይዞታ መሬቴን አመልካቾች በጉልበት ይዘውብኛል የማሳ ኮድ 2025 የሆነውን መሬት 2004 ለ 2005 ዓ.ም የምርት ዘመን ለራሳቸው አርሰውታል የዚህ የምርት ዘመን ውጤት 32 ኩንታል ጤፍ ብር 30,000 ከፍለውኝ መሬቱ እንዲለቁልኝ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች በበኩላቸው ተጠሪ ክስ የመሰረተችበትን መሬት ይዛው አታውቅም የተፈጠረ ሁከት የለም የሷ አይደለም የእሷ ቢሆን የመሬቱን አዋሳኝ አልጠቀሰችም፡፡
የምርት ውጤት መጠየቁ ስህተት ነው ከባለቤታ በውሳኔ የተከፈላት መሬት 4.5 ሄክታር ነው ድርሻዋ 2.5 መሆኑን ውሳኔው እና አፈፃፀሙ ተመልክቶ እያለ ያቀረበችው አቤቱታ ተገቢ አይደለም ብለው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ካሳ እንድትከፍል ተደርጋ ከተራ ቁ.1-4 የተጠቀሱ አመልካቾች ቀደም ሲል ከሰጡት መልስ ጋር በተመሣሣይ መልስ ማቅረባቸው በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ 5ኛ አመልካች ወደ ክርክሩ የገቡት በጣልቃ ገብነት ተጠሪ ክሱ የመሰረቱት የጣልቃ ገብን ይዞታ በመጨመር መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪ የፍ/ቤቱ ውሳኔን ሽፋን በማድረግ ያልተወሰነላትንና ያልተፈፀመላት ፍ/ቤት የወሰነላት በማስመሰል እጅ ገብቶ ያላዘዘችበትን መሬት ጨምራበት ሌሎች ሰዎች የፈጠሩትን ሁከት አመልካቾች (የስር ተከሳሾች) እንደፈፀሙ አስመስላ ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ለደቡብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አዋሳኙን ጠቅሳ ክስ የመሠረተችበት በኮድ 0220፣2022፣2025 እና 2029 የሚታወቀው መሬት ተጠሪ ከባለቤታቸው ጋር በመ/ቁ.12615 በሆነው መዝገብ በነበራቸው ክርክር የመሬት ስፋት 4.5 ሄክታር ነው ተብሎ መሬቱን እኩል እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡ ይህን ውሳኔ መሠረት በማድረግ በአፈፃፀም በ/መ/ቁ. 12837 ተጠሪ ውሳኔው እንዲፈፀምላቸው በስር ፍ/ቤቱ ጠይቀው በውሳኔው መሰረት በማስፈፀም ውጤቱን ለፍ/ቤቱ እንዲያሳውቁ በፍ/ቤቱ የታዘዙ የቀበሌው አስተዳደር የሚመለከታቸው አካላት በአዋሳኝ ተጠቅሶ ውሳኔ የተሰጠበትን መሬት ለተጠሪ እና ለባለቤታቸው እኩል ለማካፈል ሲለኩት ውሳኔው ላይ እንደተመለከተው 4.5 ሄክታር መሬት ሳይሆን 11 ሄክታር መሬት መሆኑን ለፍ/ቤቱ አሳውቀው እንዲካፍሉ በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት ለተጠሪ 5.5 ሄክታር መሬት አካፍለው ለክተው ለፍ/ቤቱ ሪፖርት በማድረግ የአፈፃፀሙን መዝገብ የዘጋው መሆኑን ከስር ፍ/ቤት መዝገብ እንዳረጋገጠ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ገልፆ በውሳኔ ላይ የተጠቀሰው ይዞታ መሬት አዋሳኝ እና ኮድ ቁጥሩ ባልተቀየረበት ውሳኔው ላይ ከተመለከተው ስፋት በላይ ስለሆነ በማለት የተጠሪ አቤቱታ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ አይደለም የአሁኑ አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት ይቁም፡፡ በማሣ ኮድ 2029 ከሆነው የተጠሪ ይዞታ መሬት ተጠሪ ያጣችውን የአንድ ዓመት ምርት ብር 30,000 ከ1-6ኛ ያሉት (የስር መልስ ሰጭዎች) ይክፈሉ በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ የአሁን አመልካች ቅሬታቸውን ለማሳረም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ በመቀጠልም የሰበር አቤቱታቸውም ለሰበር ሰሚው ችሎት ቢያቀርቡም ከፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ተፈፀመ ያሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመጥቀስ እንዲታረምላቸው አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ ይገባል የተባለው ለተጠሪ የተወሰነው 2.5 ሄክታር ነው ተብሎ የተፈፀመው 5.5 ሄክታር ድርሻ አለኝ በሚል መነሻ ከእጁ ያልገባ ይዞታ ላይ አመልካቾች ሁከት ፈጥረዋል መባላቸውንና ካሳ እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡
ግራ ቀኙ የፅሑፍ ክርክር አድርገዋል፡፡
ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሊመረመር ይገባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ ጋር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ መሬት በአዋሳኝ ተጠቅሶ እና በኮድ ቁጥር ተለይቶ (ተጠቅሶ) ተጠሪ ከባለቤታቸው ጋር ቀደም ሲል በነበራቸው የጋብቻ ፍቺ ውጤት ክርክር የመሬቱ ይዘት 4.5 ሄክታር መሆኑ ተገልፆ ተጠሪ ከባለቤታቸው ጋር እኩል እንዲካፈሉ በፍ/ቤት ውሳኔ አግኝቷል፡፡ ይህን ውሳኔ ተከትሎ ተጠሪ እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም ፋይል ፍርድ ቤት አስከፍተው በውሳኔው መሠረት ለማስፈፀም የተላኩ የአስተዳደር አካላት በውሳኔ ተለይቶ የተመለከተውን መሬት ሲለኩ ስፋቱ በውሳኔው ላይ የተጠቀሰው 4.5 ሄክታር ሳይሆን 11 ሄክታር መሆኑንና ለፍ/ቤቱ ገልፀው 11 ሄክታር መሬት ለተጠሪ እና ለባለቤታቸው እኩል እንዲካፈል በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት ለተጠሪ 5.5 ሄክታር መሬት በድርሻ የተሰጣቸው መሆኑ ከስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተመልክቷል፡፡ በአንፃሩ የአሁን አመልካቾች ለክርክር ምክንያት የሆንው ይዞታ መሬት ሕጋዊ ይዞታ መሬታቸው መሆኑን የሚያስረዳ የተሻለ ማስረጃ አቅርበው አልተከራከሩም ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት በአዋሳኝ እና በኮድ ቁጥር ተለይቶ ይዞታው የተጠሪ እና የባለቤታቸው ነው እኩል ይካፈሉ ተብሎ ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ ውሳኔው ላይ የተመለከተው እና እንዲፈፀም በተደረገው መሬት ላይ የይዞታ መብት አለን የሚሉ ከሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ ላይ በተመለከቱ አግባብነት ባላቸው ድጋጌዎች መሠረት አመልካቾች መብታቸውን ጠብቀው ሳይከራከሩ በውሳኔው ላይ የተመለከተው የመሬት ስፋት እና በአፈፃፀም የተከፈለው የመሬት ስፋት ልዩነት አለው በሚል ያደረጉት ክርክር ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች ይህን ይዞታ መሬት አልያዝንም ወይም በሕጋዊ መንገድ ያገኘነው ነው ብለው ያቀረቡት መከራከሪያም የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለዚህ በተጠሪ ይዞታ ላይ የአሁን አመልካች ሁከት መፍጠራቸውን ገልፆ የክልሉ ከፍ/ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚቻል አይደለም ብለናል፡፤

ሌላው በወረዳ ፍ/ቤት ላይ በማሣ ኮድ 2025 በሚል በተጠቀሰው በከፍ/ፍ/ቤት መዝገብ ውሳኔ ላይ ደግሞ በማሣ ኮድ 2029 በሚል በተጠቀሰው ይዞታ መሬት ላይ 2004 -2005 ዓ.ም የምርት ዘመን ተጠሪ ያጡት ምርት ብር 30,000 አመልካቾች ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነውን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 83 የካሳ ጉዳይ ካልሆነ እና ካልተካደ በስተቀር በክሱ የተጠየቀው ገንዘብ እንዲተመን ይጣራል በሚል ከተመለከተው የሕግ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው በካሣ ጉዳይ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ዝም ማለቱ እንደታመነ ተቆጥሮ በካሣ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሚያሰጥ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶችም ይህን ሥነ-ሥርዓታዊ ድንጋጌ በማለፍ የአሁን አመልካቾች በካሳው ጉዳይ ክደው አልተከራከሩም እንዳመኑ ይቆጠራል በማለት ተጠሪው ገንዘቡን በማስረጃ ባላረጋገጡበት ሁኔታ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. ለተጠሪ አመልካቾች ብር 30,000 ካሣ ይክፈሉ በማለት የተሰጠው የስር ፍ/ቤቶች የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
   አመልካቾች የተጠቀሰውን የካሳ ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም፡፡ ብለናል፡፡
2. የክልሉ ከፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ/ 32269 በቀን 8/12/2006፣ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ቁ. 196121 እና በመ/ቁ. 20370 በቀን 8/07/07 በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ ከዚህ በላይ በተራ ቁ. 1 ከተጠቀሰው የውሳኔ ክፍል ውጭ ያለው አስራካሪው ይዞታ መሬት የአሁኑ አመልካቾች ሁከት ድርጊት ፈፅመዋል ብለው የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ወጪ ግራ ቀኙ ያወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102543

ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡-ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 አስተዳደር ፅ/ቤት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-ወ/ሮ አሰለፈች ወልደ - ጠበቃ ሙሉጌታ ዱላ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግስት የንግድ ቤት የተከራይነት መብትን የሚመለከት ክርክር ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ3/03/2005 ዓ.ም በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ፡- ተጠሪ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 123 የሆነውን የንግድ ቤት ከአመልካች ተከራይተውና በቤቱ ላይ የንግድ ፈቃድ አውጥተው ይነግዱ ከነበሩት ከወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረጋ ገርቢ ተከራይተው ክስ እስከአቀረበቡት ጊዜ ድረስ ሲነግዱበት የነበረ መሆኑን፣በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት ተጠሪ ተጠቃሚ መሆናቸውን፣ሆኖም የአሁኑ አመልካች ተጠሪን የመመሪያው ተጠቃሚ መሆናቸውን እየገለፀ ሲያመላልሳቸው ከቆየ በኋላ ሕዳር 01 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ ማስጠንቀቂያ የቤቱን የተከራይነት መብት ለተጠሪ ማከራየት እንደማይችል በመግለፅ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ቤቱን እንድታስረክቢ በማለት ያሳወቃቸው መሆኑን፣ከአመልካች ጋር የኪራይ ውል አድርገው የነበሩት ግለሰብ አመልካችን ሳያሳውቁ ለሶስተኛ ወገን ቤቱን አከራይተው መገኘታቸው ተጠሪን በመመሪያው መሰረት ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውና አመልካችም ከተጠሪ ጋር በመመሪያው መሰረት ውል የመዋዋል ግዴታ ያለበት መሆኑን፣በመመሪያው መሰረት አመልካች ከተጠሪ ጋር የኪራይ ውል የመዋዋል ግዴታ እያለበት ቤቱን አስረክቢ በማለት የገለጸላቸው የሁከት ተግባር መሆኑን ዘርዝረው የተፈጠረው ሁከት ተወግዶላቸው አመልካች ከተጠሪ ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመመሪያው መሰረት ውል እንዲዋዋል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም አከራካሪው ቤት አብነ ቡድን ለተባለ የጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት የተሰጠ እንጂ ተጠሪ መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑንና የአመልካች ተግባር ሁከት ነው ሊባል የማይችል መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ አመልካች ቤቱን ለፈለገው ሰው የማከራየት መብት ያለው መሆኑን፣የአብነ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት አባል የነበሩት ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረጋ የተባሉ የማህበሩ አባል የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የተቋቋሙበትን ዓላማ በሚፃረር መልኩ ለተጠሪ አስተላለፈው የተገኙ በመሆኑ ቀድሞውኑም ባልነበራቸው መብት ሊሰሩበት የሚችሉበት አግባብ የለም የሚሉትን ምክንያቶችን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አልፎ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ደግሞ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ቤቱን ከአመልካች እውቅና ውጪ ከወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረጋ ተከራይተው ሲሰሩበት የነበረ መሆኑ መረጋገጡንና መመሪያው ደግሞ በዚህ አግባብ የመንግስት ቤትን ተከራይቶ ሲሰራ የነበረ የተከራይ ተከራይ ተጠቃሚ እንደሚሆን የደነገገ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ አመልካች የሁከት ተግባር ፈፅሟል፣ሁከቱ ሊወገድ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ አሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ተግባር የሁከት ተግባር ነው በማለት መወሰናቸው የአመልካችን ቤት ለፈለገው ሰው የማከራየት መብቱን ያላገናዘበና ቤቱ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተሰጥቶ እነዚህ ድርጅቶች ወደ መካከለኛ ደረጃ ሲተላለፉ በሌላ ተቋም አግባብነት ባለው መመሪያ መሰረት የሚተላለፍ ሁኖ እያለ ይህ ታልፎ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መመሪያ መሰረት ተደርጎ የተጠሪ የተከራይነት ተጠቃሚነት ሊረጋገጥላቸው ይገባል ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-ክስ የቀረበበት ጉዳይ የሚወድቀው በፌደራል ፍርድ ቤቶች ነው? ወይስ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ነው? የሚለውን ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም አመልካች የሁከት ተግባር ፈጥሮብኛል በማለት ተጠሪ የሚከራከሩት ተጠሪ አከራካሪውን የንግድ ቤት የአመልካች ተከራይ ከሆኑት ከወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረጋ ተከራይተው በመሰራት ላይ እያሉ መመሪያ ቁጥር 4/2004 መውጣቱንና በዚህም ምክንያት የተከራይነት መብት ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት ተጠሪ ሁነው እያለ አመልካች ተጠሪን ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ በማለት ማስጠንቀቂያ መፃፉ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሁከቱ ሊወገድ ይገባል፣የመመሪያው ተጠቃሚነትም ሊረጋገጥልኝ ይገባል በማለት ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶችም የግራ ቀኙን ክርክር መርምረው የአከራካሪው ቤት ተከራይ ማን እንደሆነ፣ ወደ ተጠሪ ይዞታ የገባበት አግባብ ምን እንደሆነ፣ተጠሪ ቤቱን የተከራዩበት አግባብ ከአመልካች እውቅና መሆኑ፣በዚህ አግባብ የተላለፈ የንግድ ቤት የተከራይነት መብት ተጠቃሚ የሚሆነው ደግሞ የተከራይ ተከራይ ስለመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6 ስር መመልከቱን መሰረት በማድረግ የአመልካችን ተግባር ሁከት ነው በማለት መወሰናቸውን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በቀጥታ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ የአመልካች ነበር በተባለው የንግድ ሱቅ የገቡት አመልካች እንደሚከራከሩት በቤቱ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት በተመደበበት ነው? ወይስ የንግድ ቤቱ ለጥቃቅን አነስተኛ ተቋማት አገልግሎት ከተመደበበት አላማ ውጪ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረጋ ወይም የእብነ በድን አባላት በመከራየታቸው ነው?የሚለው አከራካሪ ጭብጥ ጭምር ከመመሪያው አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚታይ እና ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ አመልካችም ሆነ ተጠሪ ግንኙነቱ የንግድ መደብር ኪራይን መሰረት ያደረገ ነው የሚል ክርክርም የላቸውም፡፡ የንግድ ቤቱ ተከራይ ከነበሩት ከወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረጋ ከእብነ በድን አባለት እና ከተጠሪ መካከል በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት የተከራይነት መብት ሊያገኝ የሚገባው ማነው? የሚለው ጥያቄ በመሰረቱ በመመሪያው ላይ የተመለከቱትን ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት አድርጎ ምላሽ የሚያገኝ የመመሪያ አፈጻጸም ጉዳይ ከሚሆን ውጪ ከሁከት ድርጊት ጋር ግንኙነት ያለው ጉዳይ አይደለም፡፡ የአንድ ክስ ዝርዝር ይዘቱ ሳይታይ እርስቱ ብቻ ታይቶ የፍርድ ቤት የሥረ ነገር ዳኝነት የሚወሰንበት የሕግ አግባብ የሌለ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በጉዳዩ ላይ የሥረ ነገር ዳኝነት ያለው መሆን ያለመሆኑን ተከራካሪ ወገን ባያነሳውም ራሱ ማረጋገጥ ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ//ቁጥር 9 እና 231(ለ) ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ክስ እርስቱ የሁከት ይወገድልኝ የሚል ቢሆንም ዝርዝር ይዘቱ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሲሆን መመሪያውን የሚያስፈጽሙት ደግሞ እንደ አመልካች ያሉት የከተማው አስፈጻሚ አካላት ናቸው፡፡

መመሪያውን መሰረት አድርጎ የሚነሳ የንግድ ቤት የተከራይነት መብት ጥያቄ ከከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣን እና ተግባር ጋር እንዲሁም የከተማው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር የተያያዘ እስከሆነ እና የከተማው አስተዳደር አካልም በተከሳሽነት የተሰየመ እስከሆነ ድረስ ደግሞ የዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ተቀብሎ የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር በአንቀጽ 41(1) (ለ) እና (ረ) ስር በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ የዚህ ዓይነቱ ክስ የሁከት ስም ተሰጥቶት በመቅረቡ ብቻ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ሊወድቅ የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡

በመሆኑም ክስ የቀረበበት ጉዳይ የሚወድቀው በፌደራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ሁኖ እያለ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን አይቶ ዳኝነት መስጠቱ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑና ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ ደግሞ ስርዓቱን ጠብቆ አቤቱታ እስከቀረበበት ድረስ ሊፀና የማይገባው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 200149 በ17/08/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137735 በ02/08/2006 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጥያቄው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ብለናል፡፡ ተጠሪ በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ጥያቄአቸውን ከማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. የዚህን ችሎት ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105626

ሀምሌ 28 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መለሰ

አመልካች፡- አቶ ለገሰ ዲባባ ተተኪ ሚስት ወ/ሮ ክቡ ደሜ ጠበቃ አብዲ ፈይሳ ቀርቡ

ተጠሪ፡- ኢትዮጵያ ሜዲዬስ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ጠበቃ አቶ ሚሊዮን አለሙ ቀረቡ

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ጋር የተያያዘ የጉዳት ካሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ላይ በ27/01/2006 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በአጭሩ ከ01/01/2000 ዓ/ም ጀምሮ በግሪን ሃውስ በብረት ስራ ተመድበው በቀን ደመወዝ ብር 20 እየተከፈላቸው በወር 600 እየሰሩ በጨመሩት 8 ሜ. ብረት ላይ የግሪን ሃውስ ላስቲክ እየሰሩ እያሉ በ17/09/2005 ዓ/ም ብረቱን ወይም ላስቲኩን እንስተው ሁለት እግራቸው ሽባ ሆኖ ተሰብሮ መራመድ ያልቻሉና የጀርባ አጥንታቸው ተሰብሮ ሽንትም ሆነ ሰገራ መቆጣጠር ያልቻሉና ካሳና ሞራል ክፍያ እንዲሁም የተቋረጠባቸው ደመወዛቸውና ካሳ ከልዩ ልዩ ክፍያዎች ጋር ተጠሪ ሊከፍላቸው ሲገባ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ውሃ እንኳን የሚገዙበት አጥተው አልጋ ላይ ሁለት ሰዎች ተሸክመው የሚያስተኟቸው እና የሚያነሷቸው መሆኑን እያወቀ ሃኪም ቤት ሳይወስዳቸው በመቅረቱ ተከሳሽ ድርጅት በአሰሪ እና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 494/98 የስራ ስንብት ክፍያ ክፍያ ለዘገየበት የሦስት ወር ደመወዝ የጉዳት ካሳ የህክምና ወጪ ለወደፊት ህክምና ወጪ የሞራል ካሳ የተለያዩ ክፍያዎች በድምሩ 289,390 ብር ተከሳሽ ድርጅት እንዲከፈላቸው ክስ አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በቀን 21/02/2006 ዓ/ም የተፃፈ መልስ ደግሞ ድርጅቱ አደጋ እንዳይደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ የሚያስፈልጉ ቀበቶ የሰጠ እና ስልጠና በየወቅቱ እንደሰጠ ከሳሽ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ሆን ብሎ በራሱ ጉዳት ያደረሰ ስለሆነ ልጠየቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይገባም፡፡ ሃላፊነት አለ ካለ ደግሞ የጡረታ ተመዝጋቢ ስለሆኑ የተከፈለ መዋጮ ያለ ስለሆነ ተጠያቂ ሰራተኞች ጡረታ ኤጀንሲ ነው፡፡ አደጋው የደረሰው 2005 ዓ/ም ሳይሆን 2004 ዓ/ም ግንቦት 17 ቀን ነው፡፡ ጉዳት ከደረሰባቸው ቀን ጀምሮ የአንድ ዓመት ሙሉ ደሞዛቸው የከፈላቸው መሆኑ የህክምና ወጪ የሸፈነ መሆኑ የዘገየ ክፍያ እንደሌለ የዓመት እረፍት 24 ቀን አላቸው ግን 37 አይደለም፡፡ የህክምና ክፍያ በማስረጃ የተረጋገጠ አይደለም በማለት ክሳቸው ውድቅ ተዳርጎ በነፃ እንድሰናበት ብለዋል፡፡ ከሳሽም የመልስ መልስ የሰጡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ መዝኖ አጣርቶ በከሳሽ የደረሰው ሙሉ ዘላቂ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ተከሳሽ ሃለፊነት እንዳለበት በማረጋገጥ በድምሩ ብር 288,940 እንዲሁም የወጪና ኪሰራ ብር 500 እንዲከፈላቸው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ቅሬታ በይግባኝ ለፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር ከሰማ በኃላ የወረዳ ውሳኔ አፅንቷል፡፡

ተጠሪ አሁንም ቅሬታው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ተቀባይነት ስላገኘ ከሰሽ መልስ እንዲሰጥበት ትዕዛዝ ተሰጥቶበት ነገር ግን በሞት ስለተለዩ ባለቤታቸው የሚሰነትታቸው አረጋግጠው ስለቀረቡ መልስ እንዲሰጡና የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናላቸው በመልሳቸው ገልፀዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ክርክሩ ከቀጠለ በኃላ ፍርድ ቤቱ የሚች ባለቤት ስለሆኑ ሊከፈላት የሚገባው ካሳ መሆን አለበት ወይ የሚለው ጭብጥ በመያዝ ጉዳት የደረሰባቸው መደበኛ ስራቸው እየሰሩ በዚህም አደጋ የሞቱ ስለሆነ ተጠሪ ሃላፊነት አለበት በማለት አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 110 በመጥቀስ ብቸኛ ጥገኛ ስለሆነች ለጥገኞች ከሚከፈላቸው 50% የወር ደመወዝ 600x12x5x50/100 =18,000 ብር ድርሻቸው ብቻ ነው፡፡ ባለቤታቸው ስለሞቱ የስር ፍርድ ቤት የስራ ስንብት ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 40 የመዘግየት ክፍያን በአንቀፅ 36 እና 38 መሰረት የእረፍት ክፍያ በአንቀፅ 77 ቀርቷል የተባለውን ደመወዝ ለወደፊቱ ህክምና የሚያስፈልጋቸውን ክፍያ በአንቀፅ 106 እና የሞራል ካሳን አስመልክቶ የሰጡት ውሳኔ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ እንደተደረገ ነው፡፡

በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ለሰበር በቀን 04/05/2007 ዓ/ም የተፃፈ አቅርበው ተቀባይነት ስለአገኘ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በማድረግ ክርክር ተካሂዷል፡፡ ባለቤታቸው ተተክተው ያቀረቡት አቤቱታ ባለቤቱ እየተከራከረ የነበረውን በሞት ምክንያት እንዳይቋረጥ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.49 መሠረት ተክቼ የገባሁ ሲሆን የተጠየቀውን ወደ ጎን በመተው ማንም ተከራካሪ ባላነሳው በፍ/ብ/ስ/ስ/ሀ/ቁ.182 (2) በሚቃረን መልኩ የጥገኞች ነው በማለት የሞት ካሳ ክፍያ ላይ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ በንብረት አስተዳዳሪነቴ ሥነ-ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት ተክቼ ነው የገበሁት ባለቤት ያልጠየቀውን ዳኝነት ጠይቄ የራሴ መብትና ጥቅም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማስከበር አይደለም፡፡ የጥገኞች የሞት ካሳ አልነበረም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናልኝ ነበረ የጠየቅሁት በስር ፍርድ ቤት የነበረውን በመተው ክርክር ያልተከሄደበት ጉዳይ ራሱ ማንሳቱ ስህተት ነው፡፡ በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ እንዲሻር አመልክቷል፡፡

በተጠሪ በኩል የቀረበ መልስ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182 (2) የሚቃረን አይደለም ካመነበት ማናቸውም ሌላ ማንሳት ይችላል፡፡ ጉዳት ከደረሰበት ግዜ ጀምሮ የአንድ ዓመት ደመወዝ የተከፈላቸው ስለሆነ ያልተከፈላቸው ክፍያ የለም የዘገየ ክፍያ የለም፣ የህክምና ወጪ ተሸፍኗል፡፡ የ100,000 ካሳ ክፍያ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2116(3) መሠረት የለውም ብለን ተቃውሞ አቅርበናል፡፡ የአመልካች ባለቤት መሞቱ የክርክሩ ጭብጥ መቀየሩ ስህተት የለውም ለአመልካች የሚከፈሉ ክፍያዎች ውስጥ መካተት ስለሌለባቸው የሰበር ሰሚ ችሎት ክፍያዎችን ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ የመስቀለኛ ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ጥያቄያቸው በትዕዛዙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በሰበር አጣሪ እንዲመረመር የተያዘው ነጥብ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚች ወራሾች ካሉ ጠርቶ ሳያከራክር የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለውጦ መወሰኑ ሥነ-ሥርዓታዊ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉ እና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦችን ለመመርመር እንዲቀርብ የተደረገው ::

የክርክሩ አመጣጥ እና ይዘት ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ሥነ-ሥርዓታዊ ግድፈት አለ ወይ የለም የሚሉና ተያያዥ ጉዳዩች እንደሚከተለው ተመርምረዋል፡፡

ሚች ከተጠሪ ድርጅት ሰራተኛ እንደነበረ እና መደበኛ ስራተኛው እየሰሩ እንዳሉ በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ዘላቂ ሙሉ አካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ በፍሬ ነገር የማጠራት ስልጣን ባለባቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነው፡፡ ተጠሪ ለጉዳቱ ሃላፊነት እንዳለበት የተለየዩ ክፍያዎች እንደተወሰነ ነው፡፡

ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከደረሰ በኃላ ከሳሽ የነበሩት መልስ ሳይሰጡ በመሞታቸው ነው ባለቤታቸው ተክተው በክርክሩ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

በክርክሩ ሂዳት እያለ ከሳሽ ወይ ተከሳሽ በሞት ብለይ የክርክሩ አካሄድ በምን አኳኃን እንደሚመራ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 48,49,50 ተመልክቷል፡፡ ፍ/ብ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 48(1) ክርክሩ እንዲቀጥል የሚያስችለው መብት የሚያቋርጥ ከሆነ የከሳሽ ወይ የተከሳሽ መሞት ክርክሩ እንዲቆም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አያደረገውም እንዲሁም አንቀፅ 49 50 የሚች መብት የሚታለፈው ከሆነ የሚች ከሳሽ ተከሳሽ ንብረት አስተዳደር ተተክቶ ክሩክሩ እንዳሚቀጥል ተደንግጓል፡፡

ስለዚህ ከዚህ የሥነ -ሥርዓት ድንጋጌ የምንረዳው የተጀመረው ክርክር የሚቋረጠው የሚተላለፍ መብት ከሌላ የሚተላለፍ ከሆነ ደግሞ ክርክሩ እንደሚቀጥል ነው ከዚህ ውጭ አዲስ ጭብጥ ተመስርቶ ክርክር ይዘት የሚለውጥበት ምክንያት የለም ክርክር የሚቀጥል ከሆነ በቀረበው ቅሬታ መሠረት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተፈፀመ ስህተት አለ የለም የሚለው ነው መጣራት የሚኖርበት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአሁኑ ተጠሪ የቀረበው አቤቱታ ሀላፊነት የለብኝም የተለያዩ ክፍያዎች በአግባቡ አልተወሰነም በማለት ነው መልስ ሰጪ የነበሩት መልስ እንዲሰጥበት ትዕዛዝ በተሰጠበት ሂዳት በሞት መለየታቸው በስር ፍርድ ቤቶች የነበረው ጭብጥ ተለውጦ ጉዳዩ የጥገኞች ክስ የሚመለከት ሆኖ ተገኝቷል በማለትና የተቀሩት የተለያዩ ክፍያዎች ውድቅ በማድረግ ውስኗል ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅሬታ የተነሳባቸው የተፈፀመ የህግ ስህተት አለ የለም ብሎ መወሰን ሲገባው ከባለ ዋና ጉዳዩ (ሟች) መብት የሚተላለፍ ወይ የማይተለለፍ መሆናቸው አረጋግጦ የሚተላለፍ መብቶች አሉ ከተባለ በተጀመረው ክርክር መርምሮ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 48፣49፣50፣ በሚፈቅደው መሠረት ማጣራት ሲገባው በስር ፍርድ ቤት ክርክር ባልተነሳበትና ባልተካሄደበት ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182(2) በሚቃረን መልኩ ለለሞት ክፍያ መሰረት አድርጎ የተሰጠ ውሳኔ ሥነ-ሥርዓቱ በሚፈቅደው ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህታት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ፣ 185129 በቀን 05/01/2007 ዓ/ም የተሰጠ ውሳኔ በወ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348 (1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. በጉዳዩ ከተጠሪ ሌላ የሚገቡ ወራሾች ካሉ በማስገበት የከፍተኛ እና ወረዳ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ቅሬታ የቀረበበት ላይ መሠረት በማድረግ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖሩን ወይም አለመኖሩን መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348 (1) መሠረት ጉዳዩ ለኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲመለስ ወስነናል፡፡ በዚሁ ውሳኔ እንዲፈፀም ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርም አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተክህነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96853

መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ጀቫኒ ላሮዛ - ጠበቃ ስንታየሁ ብርሃኑ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አዳነች ተስፋዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል በሕግ ጥበቃ ሊደርግለት የሚችል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አለ ለማለት የሚቻልበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ የክስ ይዘትም ከአሁኑ አመልካች ጋር ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ እስከ መስከረም ወር 2003 ዓ/ም ድረስ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ቆይተው መስከረም ወር 2003 ዓ/ም ግንኙነቱ መቋረጡንና ልጅ ባይወልዱም የተለያዩ የሚንቀሳቀሱም ሆነ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በግንኙነቱ ጊዜ ያፈሩ መሆኑን ጠቅሰውና የንብረቶቹን አይነትና ብዛት ዘርዝረው አመልካች ንብረቶቹን እኩል እንዲያካፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጡት መልስም በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የጀመሩት ከጥር 1999 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑን፣በዚህ ጊዜም ተጠሪ ይኖሩ የነበሩት በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/112 የቤት ቁጥር 539 እና 612 ውስጥ ሁኖ አመልካች ደግሞ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 14/15 በቤት ቁጥር አዲስ ውስጥ መሆኑንና አብረው እንደባልና ሚስት ሁነው አለመኖራቸውን፣አመልካች በቱሪስት ቪዛ በ1998 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሐምሌ 21 ቀን 1998 ዓ/ም ተመልሰው መውጣታቸውን፣ነሐሴ 27 ቀን 1998 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ደግሞ ጥቅምት 11 ቀን 1993 ለሶስተኛ ጊዜ ሲመጡ ያረፉት በሴንትራል ሸዋ፣በሀሌዳይ፣በገነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆቴል፣በጊዩን ሆቴሎች እና ለሶስት ወራት በአቶ ሽመልስ ወ/ስላሴ ቤት መሆኑን፣ ከተጠሪ ጋር ጓደኝነት የጀመሩት ታህሳስ 29 ቀን 1999 ዓ/ም ሁኖ የቆዩትም እስከ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ/ም ድረስ መሆኑን፣ግንኙነታቸውም አልፎ አልፎ እንደነበርና ተጠሪ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ/ም በኃላ ጣሊያን አገር አመልካች እንዲወስዷቸው ጠይቀው አመልካች ወስዷቸው ሳለ ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ፈጥረው ለመመለስ ባለመፈለጋቸው በመሀከላቸው ያለመግባባት በመፈጠሩ ግንኙነቱ መቋረጡንና ይህንም ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ/ም ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኃላ ለጣሊያን ኢምባሲ አመልክተው ከዚያ በኃላ ነሐሴ 1999 ዓ/ም እስከ ሚያዚያ 2001 ዓ.ም ድረስ በፍቅር ጓደኝነት ከወ/ሮ መቅደስ አራጌ ጋር ለሁለት አመታት ከቆዩ በኃላ ከወ/ሮ እመቤት ጋሻው ጋር በፍቅር ጓደኝነት እየኖሩ እንደሚገኙ ዘርዝረው ከተጠሪ ጋር ከአምስት ወር በላይ በጓደኝነት ባልቆዩበት ሁኔታ በጣሊያን አገር እያሉ ያፈሩት ገንዘብ በኢትዮጵያ ባንክ በኩል ተላልፎላቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ያፈሩትን የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት ተጠሪ ሊካፈሉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከ1999 ዓ/ም እስከ መስከረም 2003 ዓ/ም ድረስ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ይዞ ንብረቶቹን በተመለከተም ግራ ቀኙ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ተጨማሪ ማስረጃ ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የለም ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ ከዚህም በኃላ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ይዞ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የተጠሪ ምስክሮች ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭና ታዓማኒነት የሌለው ከመሆኑም በላይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ግንኙነት እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ነው ተብሎ የሚወሰድ አለመሆኑን እንደ ህጉ የማያስረዳ ሁኖ እያለና እንዲሁም የአመልካች ምስክሮች በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ግንኙነት በተመለከተ የሰጡት የምስክርነት ቃል ያላግባብ ውድቅ መደረጉ ተገቢውን የማስረጃ ምዘና ስርዓት ያልተከተለ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡እንዲሁም የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዋና መዛግብት እንዲመጡ ተደርገው የግራ ቀኙ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘቱ ታይቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በአመልካችና በተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አለ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ዋና ነጥብና ውጤቱ ምንድነው? የሚለው ተያያዥ ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ክስ ሲመሰርቱ በመካከላቸው ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ እስከ መስከረም ወር 2003 ዓ/ም ድረስ እንደባልና ሚስት አብረው መኖራቸውን የገለፁ ሲሆን አመልካች ደግሞ ከተጠሪ ጋር ከአምስት ወር በላይ በጓደኝነት ያለመኖራቸውን ጠቅሰው ግንኙነቱ የሕግ ጥበቃ የሌለው መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ መልሳቸውን ሰጥተው ግራ ቀኙ አሉን ያሏቸውን ማስረጃዎችን አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ የግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል የሰጡት የምስክርነት ቃልም በአጭሩ እንደሚከተለው የተመዘገበው ነው፡፡

ወ/ሪት ሳራ ተስፋዬ የተባሉት የተጠሪ 1ኛ ምስክር የተጠሪ እህት መሆናቸውን ገልጸው አመልካችና ተጠሪ ከ1998 ዓ/ም ክረምት ወራት ጀምሮ እስከ 2003 ዓ/ም ድረስ ለአምስት አመታት ያህል በትዳር መቆየታቸውን፣ይህንኑ ሊያውቁ የቻሉትም አመልካችና ተጠሪ ወደ ምስክሯ ቤት አብረው ሲሄዱና አመልካችና ተጠሪ አብረው ሲኖሩ ስለነበር መሆኑን፣አመልካች ወደ ውጪ ይሄዱ በነበሩበት ጊዜ ምስክሯ ይሄዱ እንደነበርና አመልካች ውጪ ሂደውም ሁለት፣ሶስት ወራት ይቆዩ እንደነበር፣አመልካችና ተጠሪ ቤት ገዝተው እስከ ተጣሉበት ጊዜ ድረስ አንድ ቤት ሲኖሩ እንደነበር፣አመልካችና ተጠሪ አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ቤት፣መኪና እና የቤት ቁሳቁሶችን ገዝተው እንደነበር፣አመልካችና ተጠሪ ከክረምት 1998 ዓ/ም ጀምሮ በጓደኝነት መስሪያ ቤት መጥተው እንደተዋወቁ እንደሚያወቁና ለአምስት ተከታታይ አመታት ያለማቋረጥ መኖራቸውን፣ቤት፣መኪና እና የቤት ቁሳቁሶች ሲገዙ ምስክሯ እንዳልነበሩ ገልፀው መስክረዋል፡፡ወ/ሮ እቴነሽ ተስፋዬ የተባሉት ሁለተኛ የተጠሪ ምስክርም የተጠሪ እህት መሆናቸውን ገልጸው የሰጡት የምክርነት ቃል በይዘቱ ከ1ኛ ምስክር ቃል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ወ/ሮ ዳግማዊት ደርቡ የተባሉት የተጠሪ ሶስተኛ ምስክር የተጠሪ የአክስት ልጅ መሆናቸውን ገልጸው ከውጪ አገር ቆይተው በ1999 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ተጠሪ ከጣሊያን አገር የመጣ የውጭ ሰው አግብተው እየኖሩ መሆኑን ወላጅ እናታቸው የነገሯቸው መሆኑን፣አመልካችና ተጠሪ በምስክሯ ወላጅ እናት ቤት በ2000 ዓ/ም እራት ሲጋበዙ አንድ ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመልከታቸውንና አመልካችና ተጠሪ አንድ ላይ በአንድ ቤት ሲኖሩ እንደነበር ራሳቸው ተመልክተው የተረዱት ሳይሆን ሰው ነግሯቸው ያወቁት ሁኔታ መሆኑን፣አመልካችና ተጠሪን እንደባልና ሚስት መኖራቸው ሊያውቁ የቻሉት በቤተሰብ ሰርግም ሆነ ለቅሶ ወይም ልደትና ክርስትና ላይ እንደባልና ሚስት ሁነው በመሆኑ ምክንያት መሆኑን መስክረዋል፡፡ ወ/ሮ ሀረጓ በየነ የተባሉት የተጠሪ 4ኛ ምስክር በበኩላቸው በግራ ቀኙ መካከል ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ገልጸው አመልካችንና ተጠሪን በ1999 ዓ/ም ክረምት ውስጥ አግኝተዋቸው ተጠሪ አመልካችን ለምስክሯ ባለቤቱ ነው ብላ ያስተዋወቃቸውና አመልካችም ይህንኑ የተጠሪዋን ንግግር ይሰማና አመልካችም ጆቫኒ እባላለሁ ብሎ የመለሰላቸው መሆኑን እንዲሁም ቀኑን፣ወሩንና አመተ ምህረቱን በማያስታውሱት ጊዜ አመልካችና ከሌሎች ሴቶች ጋር ሲመለከቷቸው እንደነበር ገልጸው የመሰከሩ ናቸው፡፡ አቶ ተፈራ ሲሳይ የተባለው የተጠሪ አምስተኛ ምስክር በበኩላቸው በግራ ቀኙ መካከል ዝድምና የሌላቸው መሆኑን ገልፀው አመልካችና ተጠሪ መኪና ለመከራየት ወደ ምስክሩ በ1999 ዓ/ም መሄዳቸውን መኪና ተከራይተው መሄዳቸውን፣ከዚያ በኋላም በሚያዚያ ወር 2002 ዓ/ም መኪናቸውን በብር 80,000.00 ሸጠው ቴሮስ መኪና በብር 172,0000.00 የገዙ መሆኑን እንደሚያውቁ፣አመልካችና ተጠሪ በሚጠቡበት ጊዜ እንደባልና ሚስት ሁነው እንደሚረዷቸው የመሰከሩ ናቸው፡፡ወ/ሮ አስናቀች ደስታ የተባሉት የተጠሪ ስድስተኛ ምስክር ደግሞ ከግራ ቀኙ ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ተጠሪ የጓደኛቸው እህት መሆናቸውንና እርሳቸውም ከተጠሪ ጋር ጥቂት ጊዜ አብረው የሰሩ መሆኑን፣ጽጌ የተባለችው የተጠሪ እህት ተጠሪ ከውጭ ሀገር ዜጋ ጋር ተዋውቃ አብራ መኖርም የጀመሩ መሆኑን ለምስክሯ የነገረቻቸው መሆኑን፣ከዚህ በኋላ 1999 ዓ/ም ገና አልፎ በሳምንቱ ዕጌ ቤት በእንግድነት ሂደው ለመጀመሪያ ጊዜ አመልካችና ከተጠሪ ጋር መጥተው እንደተመለከቷቸውና ከዚያ በኋላ ወንድሟ ተስፋዬ ሲያገባ አመልካችና ተጠሪ አብረው በሰርጉ ላይ በ2000 ዓ/ም መጥተው እንደነበር በሳምንቱ በሙሽሪት ቤት መልስ ላይ ተገናኝተው እንደነበር፣አመልካችና ተጠሪ ቤት እንዳላቸው የሰሙ መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ በተለያዩ ዝግጅቶች ሲመጡ ባልና ሚስት ተብለው መሆኑን እንደሚያውቁ መስክረዋል፡፡ወ/ት ሽዋእመቤት ተስፋዬ የተባሉት የተጠሪ 7ኛ ምስክር የተጠሪ እህት መሆናቸውን ገልጸው የሰጡት የምስክርነት ቃልም በይዘቱ ከተጠሪ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ቃል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች አሉኝ ያሏቸው ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሲታይም እንደሚከተለው የተመዘገበው ነው፡፡

አቶ ማርቆስ የተባለው የአመልካች 1ኛ ምስክር ከግራ ቀኙ መካከል ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ገልጸው አመልካችንና ተጠሪን ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ ጎረቤቶቻቸው ሁነው እንደሚያውቋቸው ጠቅሰው ለተወሰኑ ወራት ብቻ ተጠሪን ከአመልካች ጋር ከአዩ በኋላ ከአመልካች ጋር መቅደስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚባሉ ሴት ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ እንደሚያዩ እና ወደ እርሳቸው ቤትም እኚህ ሴት ሲሄዱ የነበሩ መሆኑን፣አመልካች በራሳቸው ስም በሚታወቅ ቤት ሲኖሩ ምስክሩ ደግሞ ከወንድማቸው ቤት ከአመልካች ጋር በጉርብትና ይኖሩ እንደነበር እንዲሁም አመልካችና ተጠሪ በ2000 ዓ/ም መጀመሪያ አከባቢ አንድ ሲመለከቷቸው የነበሩ ከመሆኑ ውጪ አመልካችን ከወ/ሮ መቅደስ እና ከወ/ሮ እመቤት ጋር ሲመለከቷቸው እንደነበር የመሰከሩ ናቸው።አቶ አሊ ሰይድ የተባሉት የአመልካች ምስክር ደግሞ ግራ ቀኙን ያወቁበትን ጊዜ ለይተው አመልካችና ተጠሪ ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ በጓደኝነት እንደሚኖሩ የሚያውቁ መሆኑን፣ይህንኑ ሊያውቁ የቻሉትም ወደ ጣሊያን አገር ሲሄዱ ምስክሩ በአመልካች ቤት ውስጥ የጥበቃ ስራ ሲሰሩ ስለነበሩ መሆኑን፣የጥበቃ ስራውን የሰሩትም እስከ 2001 ዓ/ም ሁኖ አመልካች በሰኔ ወር 1999 ዓ/ም ከጣሊያን አገር ከተመለሱ በኋላ ከተጠሪ ጋር ያላዩዋቸው መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ በነበሩበት ጊዜ ተጠሪ ወደ አመልካች ቤት መጥተው የሚሄዱ መሆኑንና ብዙ ጊዜ ተጠሪ በአመልካች ቤት ውስጥ ያልኖሩ መሆኑን እንዲሁም አመልካችን ከወ/ሮ መቅደስ ጋር ምስክሩ እንደሚያያቸው እና በ2001 ዓ/ም ግን ምስክሩ ከጥበቃ ስራ ስለለቀቁ የሚያውቁት ነገር ያለመኖሩን ገልጸው የመሰከሩ ናቸው።ወ/ሪት ተሰረ አሰግደው የተባሉት የአመልካች ምስክር ደግሞ ከግራ ቀኙ ጋር ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው ግራ ቀኙን ከመስከረም ወር 2001 ዓ/ም ጀምሮ በቤት ሰራተኝነት በአመልካች ቤት ገብተው ስለነበር እንደሚያውቋቸው ገልጸው አመልካችና ተጠሪ አብረው ሁነው ከደላላው ቤት ምስክሯን ማስመጣታቸውን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ ከአመልካች ቤት ውስጥ ያልነበሩ፣የማይመጡ የነበረ መሆኑን፣ ምስክሯ በአመልካች ቤት እስከ መስከረም ወር 2004 ዓ/ም ድረስ እንደቆዩ፣በዚህ ጊዜ ውስጥም መቅደስ የሚባሉ ሴት ከአመልካች ጋር ይኖሩ እንደነበርና እኚህ ሴትም ከአመልካች ጋር ምስክሯ እስከ ቆዩበት ጊዜ እንዳልቆዩና እመቤት የተባሉ ሴት ከአመልካች ጋር እንደነበሩ የመሰከሩ ናቸው። ወ/ሮ እመቤት ጋሻው የተባሉት የአመልካች 4ኛ ምስክር በበኩላቸው የአመልካች የፍቅር ጓደኛ መሆናቸውን ገልጸው አመልካችን ከመጋቢት ወር 2002 ዓ/ም ጀምሮ እንደሚያውቋቸውና ከአመልካች ጋር አብረው የማይኖሩ ቢሆንም በሳምንት ሶስት ቀንና እረፍት በሚሆንበት ጊዜ ከቤቱ ሄደው እንደሚያድሩ፣ስራ በሌላቸውና ስራ ባቆሙ ጊዜም ሁለት ወር የሚሆን ከአመልካች ቤት ሂደው እንደሚቆዩና በዚህ ጊዜ ተዘሩ የምትባል የቤት ሰራተኛ እንደነበረችና የአሁኗ ተጠሪ ወደ ቤቱ መጥተው እንደማያውቁ እንዲሁም ከአመልካች ጋር ጓደኝነት ከጀመሩ ጊዜ ጀምሮ ግንኙነቱ ቀጥሎ ያለ መሆኑን የመሰከሩ ናቸው።አቶ ግዛቸው አምደ የተባለው የአመልካች አምስተኛ ምስክር ደግሞ ከግራ ቀኙ ጋር ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው አመልካችና ተጠሪ ከሐምሌ ወር 1999 ዓ/ም ጀምሮ በጉርብትና እንደሚያውቋቸውና ተጠሪን ደግሞ ከ1999 ዓ/ም መጨረሻ ጀምሮ እስከ ጥር ወር 2000 ዓ/ም ድረስ ብቻ እንደሚያውቋቸው ገልጸው በዚህ ጊዜ ውስጥም ተጠሪን ሁለት ጊዜ ብቻ ያገኟቸው መሆኑን፣ ከአመልካች ጋር ከጥር ወር 2000 ዓ/ም በኋላ የሚያገኟቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወ/ሮ መቅደስን ስለመሆኑና እሳቸውም ቢሆን ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2003 ዓ/ም ድረስ አልፎ አልፎ እንደሚመለከቱ ገልፀው መስክረዋል፡፡ ዋና ሳጅን እልፍነሽ ግርማ የተባሉት የአመልካች 6ኛ ምስክር ደግሞ አመልካች ሲ.ኤም.ሲ አካባቢ ቤት ተከራይተው በነበሩበት ጊዜ ተጠሪን እስከ ሰኔ ወር 1999 ዓ/ም የተመለከቷቸው መሆኑን በግንቦት ወር 1999 ዓ/ም አመልካች ተጠሪን ወደ ጣሊያን አገር ይዘው ሂደው ከሁለት ወር ቆይታ በኋላ አመልካች መምጣቱን ለምስክሯ ከነገሯቸው በኋላ ምስክሯ አመልካችን ተጠሪ ደህና መሆናቸውን ሲጠይቁ አመልካች ከተጠሪ ጋር ተጣልተው እንደተለያዩ አመልካች ለምስክሯ የነገሯቸው መሆኑን፣ምስክሯ ከተጠሪ ጋር አንድ ቀበሌ ይኖሩ ስለነበርም ከአመልካች ጋር ለማስታረቅ በሚፈልጉበት ጊዜ ተጠሪ ከአመልካች ጋር መታረቅ የማይፈልጉ መሆኑን ለምስክሯ እንደነገሯቸው፣ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አመልካችና ተጠሪ ተገናኝተው እንደማያውቁና ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ አመልካች መቅደስ ከምትባል ሴት ጋር ተዋውቀው ወደ ምስክሯ ቤት ይዘው ሂደው እንደነበርና መቅደስ ጋር ደግሞ አመልካች በግምት ለሁለት አመታት ያህል አብረው የቆዩ መሆኑንና ከመቅደስ ጋር ከተለያዩ በኋላ ደግሞ እመቤት የሚባሉ ሴት ጋር በጓደኝነት እየኖሩ እንደሚገኙ መስክረዋል፡፡አቶ ወንደወሰን ተሰማ የተባሉት የአመልካች ሰባተኛ ምስክር በበኩላቸው ከግራ ቀኙ ጋር ዝምድና የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው በአከባቢው የጥበቃ ኃላፊ ሁነው ሲሰሩ አመልካችንና ተጠሪን ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ እንደሚያውቋቸው፣ተጠሪ አመልካች ወደ ገዙት ቤት 1999 ዓ/ም መጨረሻ አካባቢ ከተጠሪ ጋር አልፎ አልፎ ሲመጡ እንደነበር፣ተጠሪ እስከ መስከረም 2000 ዓ/ም ድረስ ያዩአቸው እንደነበርና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ ከአመልካች ጋር እንዳላያቸውና አመልካች ከሌሎች ሴቶች ጋር ይታዩ የነበረ መሆኑን የመሰከሩ ናቸው፡፡የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለተጨማሪ ማስረጃነት የሰማቸው ምስክሮች ቃልም በይዘቱ ከላይ የተጠቀሱት የአመልካች ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል የሚደግፍ መሆኑን መዝገቡ የሚያሳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡እንግዲህ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች እነዚህ ከሆኑ ከሕጉ አገናዝቦ ግንኙነቱ በሕጉ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል መሆን ያለመሆኑን መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

በመሰረቱ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 98፣ 99 እና 106 በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ አለ የሚባለው መቼ እንደሆነና የግንኙነቱ መኖር በምን አይነት መንገድ ማስረዳት እንደሚቻል ያመላክታል፡፡የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 106/2/ ድንጋጌ ሲታይም ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ለሚኖሩ ሰዎች የሚፈለገው ማስረጃ ወንዱና ሴትየዋ የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው የሚገምቷቸው መሆኑን ማሳየት እንደአለበት ያመለክታል፡፡በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የሚቀርበው ማስረጃ ጋብቻ መፈፀሙን እንዲያረጋግጥ የማይጠበቅ ሲሆን ሕጉ ለይቶ ያስቀመጠው የማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይነት ስለሌለ በማናቸውም ማስረጃዎች ስለግንኙነቱ ማስረዳት ይቻላል፡፡ በጉዳዩ ላይ የሚቀርቡ ማስረጃዎች ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የሚያሳዩ፣ሕጋዊ ውጤቱ የሚኖረው ሶስት አመትና ከዚያ በላይ አብሮ መኖሩ ሲረጋገጥ መሆኑና ምስክሮች የሚያረጋግጡት ሶስት አመትና ከዚያ በላይ አብሮ መኖራችንና በትዳር መልክ አብሮ መኖርን ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች እና ተጠሪ የነበራቸው ግንኙነት ከሕጉ ይዘትና መንፈስ ሲታይ በተጠሪ ምስክሮች ቃል አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የማያሳዩ፣ በሕጉ ግንኙነቱ ሕጋዊ ውጤቱ የሚኖረው ሶስት አመትና ከዚያ በላይ አብሮ መኖሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የተመለከተውን የተጠሪ ምስክሮች ጊዜውን በትክክል ለይተው ያልመሰከሩ እና አመልካችና ተጠሪ በትዳር መልክ አብሮ መኖርንም ያላረጋገጡ መሆኑን ከአመልካች ምስክሮች ጋር ተዳምሮ ሲታይ የምንገነዘበው ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ህጉ ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ለሚኖሩ ሰዎች የሚፈለገው ማስረጃ ወንዱና ሴትዩዋ የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው የሚገምቷቸው መሆኑን ማሳየት እንደአለበት የሚያመላክት ሲሆን አመልካችና ተጠሪ ይኖሩበት ነበር በተባለ አከባቢ ያሉት የአመልካች ምስክሮች ቃል አመልካችና ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ ግንኙነት እንደነበራቸው፣አመልካች ከሌሎች ሴቶች ጋር አንድ ላይ ይኖሩ እንደነበር፣ተጠሪ ከሌሎች ሴቶች ጋር የቀጠለው የአመልካች ግንኙነት እያለ ከአመልካች ግንኙነት ያልነበራቸው መሆኑን ጭምር የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጠሪ ምስክሮች ቃል በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው ግንኙነት በትዳር መልክ ቀጣይነት የነበረው መሆኑን ባልመሰከሩበትና በአንፃሩ የአመልካች ምስክሮች ስለጉዳዩ የሰጡት የምስክርነት ቃል የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት በትዳር መልክ ሳይሆን ጊዜያዊ የፍቅር ግንኙነት የነበረ መሆኑን በአረጋገጡበት አግባብ የተጠሪ ምስክሮች የተጠሪ ቤተዘመድ በመሆናቸው ብቻ አይታመኑም ሊባሉ የሚችሉበት አግባብ የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢውን የማስረጃ ምዘና መርህ መሰረት ያላደረገና በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 97፣98፣99 እና 106(2) ድንጋጌወች መሰረታዊ አላማ፣ይዘትና መንፈስ ውጪ ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 88241 ጥቅምት 09 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 91809 ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 128087 ሰኔ 28 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በአመልካችና በተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 98029

ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ ልዩሴት ሥዩም ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሽዋፈራ ንጉሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በበረኸት ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው አመልካች የነበሩት የአሁኑ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የመሠረቱት ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ ይፍረስልኝ እና የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ መነሻ ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው የቆዩና አንድ ልጅ የወለዱ ቢሆንም ጋብቻው ውስጥ ተግባብተው መኖር ያልቻሉ መሆኑን ጠቅሰው ጋብቻው ፈርሶ የጋራ ንብረት ያካፍለኝ በማለት የንብረቶቹን አይነት እና ብዛት ዘርዝረው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው መኖራቸውንና ልጅ መውለዳቸውን ሳይክዱ የጋራ ንብረትን በተመለከተ በአመልካች ተዘርዝረው ከቀረቡት ውስጥ መኖሪያ ቤቱንና ካዝናው ከጋብቻ በፊት የተፈሩ መሆናቸውን ገልጸው የግሌ ናቸው ያሉ ሲሆን ሌሎችን የጋራ መሆናቸውን አምነው መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች ተጠሪ የግሌ ናቸው በማለት የጠቀሷቸው ንብረቶች ግራ ቀኙ ሐምሌ 23 ቀን 1997 ዓ/ም ባደረጉት የጋብቻ ውል ሀብትሽ በሃብቴና ከወለደች የግል የለባትም በማለት መስማማታቸውን ገልጸው ንብረቶች የጋራ ናቸው ሲሉ ተከራክሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የጋብቻ ውሉ ይዘት አመልካች "ከወለደች የግል የለባትም" የሚል ሐረግ መያዙ ንብረቶቹን የጋራ ሊያደርግ የማይችል መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም የክፍሉን ማዘጋጃ ቤት ጠይቆ አከራካሪው ቤት በ1995 ዓ/ም መሰራቱን ያረጋገጠ ሲሆን የጋብቻ ውሉን ይዘትና መንፈስ ለመረዳት ደግሞ በውሉ ያሉትን የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ከተሰሙት ሶስቱ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ከጋብቻ በፊት የተፈራውን ንብረት የማይመለከት መሆኑን የሚያሳይ ስለመሆኑ ጠቅሶ በጋብቻ ውሉ ላይ አመልካች "ከወለደች የግል የለባትም" የሚለው ሐረግ ቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከጋብቻ በፊት የተፈራ የተጠሪ የግል ንብረት በመሆኑ ለአመልካች ተጠሪ የሚያካፍልበት ምክንያት የለም ሲል በዚህ ንብረት ላይ የቀረበውን የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ካዝናውንና ሌሎች ንብረቶችን የጋራ ናቸው በማለት ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ የወሰነ ሲሆን የልጅ ቀለብን በተመለከተም ተጠሪ በየወሩ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የወረዳው ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ያለመሆኑን ምክንያቱን ዘርዝሮ ያጸናው ሲሆን የልጁን ቀለብ በተመለከተ ግን መጠኑ ያነሰ መሆኑን ገልፆ ተጠሪ በየወሩ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ከዚህም በኋላ አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ግራ ቀኙ ባደረጉት የጋብቻ ውል "ሀብትሽ ሀብቴ ነው አመልካች ከወለደች የግል የለባትም" ተብሎ የተቀመጠው ሐረግ ከጋብቻው በፊት የተፈራውን የተጠሪን ንብረት የጋራ ለማድረግ ታስቦ የገባ ሁኖ እያለ በውሉ ላይ ያለው ይኼው ሐረግ ከጋብቻ በኋላ የሚገኘውን ንብረት የጋራ ለማድረግ ታስቦ የተደረገ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች መተርጎሙ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረት የጋራ ስለመሆኑ ሕጉ ጥበቃ ያደረገውን መብት ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ በ18/08/95 ዓ.ም በተደረገ የፍቺ ስምምነት አንጻር ሊፈጸም የሚገባው እንጂ ዳግም ዳኝነት የሚጠየቅበት አይደለም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ሐምሌ 23 ቀን 1997 ዓ/ም ባደረጉት የጋብቻ ውል "ሀብትሽ ሀብቴ ነው አመልካች ከወለደች የግል የለባትም" የሚል ሐረግ አስገብተው ስምምነት መደረጉን፣ ጋብቻው በዚህ እለት ተፈጽሞም አመልካችና ተጠሪ አንድ ላይ ሲኖሩ አመልካች አንድ ልጅ ለተጠሪ የወለደችላቸው መሆኑን፣ ተጠሪ ቤቱን ከጋብቻ በፊት ያፈሩት መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን፣አሁን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይም የጋብቻ ውሉ ላይ " ከወለደች የግል የለባትም" ተብሎ የተቀመጠው ሐረግ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪ ልጅ ሰለወለዱላቸው ከጋብቻ በፊት የተፈሩ ንብረቶችን የጋራ የማድረግ ውጤት ያለው መሆን ያለመሆኑን ነው።

በመሰረቱ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኃላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው የሚያገኟቸው ንብረቶች በጋብቻ ዘመንም የግል ሆነው እንደሚቀሩ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 68(1) በግልጽ ያሳያል። ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት ንብረቶቹ በጋብቻ ውል የጋራ እንደሆኑ ስምምነት ከሌለ ብቻ ነው። አመልካችና ተጠሪ ሐምሌ 23 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የጋብቻ ውል ስምምነት "ሀብትሽ ሀብቴ ነው ልጅ ከወለደች የግል የለባትም" የሚል ሐረግ የያዘ ነው።

ተጠሪ ከአመልካች ጋር በዚህ መልኩ ያደረጉት የጋብቻ ውል ስምምነት ውጤቱ ከጋብቻ በኋላ የሚፈሩትን ንብረቶች የጋራ የሚያደርግ ነው ይበሉ እንጂ የውሉ ይዘትና መንፈስ እንደ አመልካች ክርክር ነው እንዳይባል የቤተሰብ ሕጉ ባልና ሚስት ንብረታቸውንና የግል ግንኙነታችን በተመለከተ የሚያደርጓቸው ስምምነቶች በህጉ በአስገዳጅነት የተቀመጡ ድንጋጌዎችን በሚፃረር መልኩ ሊሆን አይገባም ተብሎ በሕጉ ከተቀመጠው ድንጋጌ ጋር አብሮ የማይሄድ ነው። ሕጉ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረትን በተመለከተ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በሚል በአስገዳጅ መልኩ ደንግጓልና። በመሆኑም በሕጉ ጥበቃ በተደረገው መብት ላይ የጋብቻ ውል ስምምነት ሕጉን በሚፃረር መልኩ ማድረግ በሕጉ የሚፈቀድ አይደለም። ከዚህ አንጻር የውል ስምምነቱ በግልፅ በጋብቻ በፊት በተፈሩት ንብረቶች ላይ መደረጉን የሚያሳይ መሆኑን ከግራ ቀኙ ስምምነት ይዘት፣ የቤተሰብ ሕጉ በጋብቻ ጊዜ ስለሚፈሩ ንብረቶች ከአደረገው ጥብቃና ከውል ሕግ የአተረጓጎም ደንቦች መንፈስ የምንረዳው ነጥብ ነው። የጋብቻ ውል ስምምነት ይዘት ትርጉም አከራካሪ ከሆነ ስምምነቱ የግራቀኙን የንብረትን መብት የሚገዛ እንደመሆኑ መጠን ከውል አይነቶች አንዱ ሊባል የሚችል ስለሆነና አተረጓጎምን በተመለከተ ልንከተለው የሚገባ ደንብ በቤተሰብ ሕጉ በግልፅ የተቀመጠ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677/1/ ድንጋጌ መሠረት በጠቅላላ ውል ስለውሎች አተረጓጎም የተቀመጡትን ደንቦች ማለትም ከፍ/ሕ/ቁጥር 1731 እና ተከታዩቹን ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ የግራቀኙ ሐሳብና ፍላጐት ምን እንደነበር መመርመር የግድ የሚል ነው።

በመሰረቱ በውል ውስጥ የተጠቀሱት ቃላትና ድንጋጌዎች ግልጽ ባልሆኑ ጊዜ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1732፣ 1735-1738 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር በሰፈሩት ደንቦች መሠረት መተርጎም የተፈቀደ ነው። በዚህም መሠረት ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ደንቦች በፍ/ሕ/ቁጥር 1734 እና 1736 ሲሆኑ ተዋዋዩች ውላቸውን ከመዋዋላቸው አስቀድሞ ወይም ከተዋዋሉ በኃላ የነበሩበትን ሁኔታዎች የፈጸሙትን ተግባር በማመዛዘንና ሐሳባቸው ምን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደነበር ለማወቅ መሞከር እና የውሎችን ቃሎች አንዱን ከአንዱ ጋር እያዛመዱ በመመልከት ለውሉ ጉዳይ አግባብ ያለውን ትርጉም በመስጠት አዎንታዊ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ በ23/11/1997 ዓ.ም አደረግን የሚሉት የጋብቻ ውል ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተፈራ የተጠሪ የግል ንብረት መሆኑን ተጠሪ እያወቁ አመልካች ጋር ሲጋቡ ግን "ሀብትሽ ሀብቴ ነው ልጅ ከወለደች የግል የለባትም" በማለት ስምምነት ማድረጋቸው አስቀድሞም ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት የግል ስለመሆኑ በህግ የተጠበቀላቸውን መብት በመተው አመልካች ልጅ እስከወለዱላቸው ድረስ የተጠሪን የግል ንብረት የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ለማድረግ አምነው ልጅ ከማግኘት በመነጨው ፍላጐት የግል ንብረታቸውን የጋራ ለማድረግ ተስማምተዋል ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ አገላለፅ በጋብቻ ውሉ አመልካች ልጅ ከወለደች የግል የለባትም ተብሎ የተቀመጠው ሐረግ ሀብትሽ ሀብቴ ነው ከሚለው ሐረግ ጋር ተሳስሮ ሲታይ ግራቀኙ የነበራቸው ሀሳብ አመልካች ልጅ በመውለድ ሁኔታ ላይ የተገደበ ሁኖ ልጅ ከወለዱ ግን ከጋብቻ በፊት የተፈራ የተጠሪ የግል ሀብት የግላቸው ሁኖ የሚቀር ንብረት ስለመሆኑ የሚያሳይ ሳይሆን የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ስለመሆኑ መስማማታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ "ሐብትሽ ሀብቴ ነው" የሚለው የአማርኛ ሐረግም የሚታወቀው ተጋቢዎች በግል የነበራቸውን ሀብት የጋራ ለማድረግ በማሰብ የሚጠቀሙበት ስለመሆኑ ከነባራዊ ሁኔታ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ "ከወለደች የግል የለባትም" የሚለው ሐረግ በጋብቻ ጊዜ የሚፈራውን ንብረት የጋራ ለማድረግ ታስቦ የተደረገ ነው እንዳይባል በጋብቻ ወቅት የሚፈሩ ንብረቶቹን ሕጉ የጋራ ስለመሆናቸው በአስገዳጅ ሁኔታ የደገገ በመሆኑ የጋብቻ ውል ሲደረግ ይኼው በሕጉ አስቀድሞ በአስገዳጅ ሁኔታ ጥበቃ ያገኘ ጉዳይ በስምምነት ውስጥ የሚካተትበት አግባብና በህግ ጥበቃ የሚያገኝበት ምክንያት አይኖርም፡፡ተጠሪ ከጋብቻ በፊት ያፈሯቸው ንብረቶች የግላቸው ሁነው የሚቀጥሉ መሆኑም በሕጉ የተደገገ በመሆኑ ይህንኑ በህግ ጥበቃ ያገኘ መብት መኖሩን እያወቁና ውጤቱን እየተረዱ የጋብቻ ውል ስምምነቱ ሲደረግ "ሀብትሽ ሀብቴ ነው" "ከወለደች የግል የለባትም" የሚሉትን ሐረጋትን በስምምነቱ እንዲገቡ ያደርጋሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡

ሲጠቃለልም ስምምነቱ መኖሩ ግራ ቀኙን ያላከራከረና ይዘቱም አንዱ ሀረግ ከአንዱ ጋር ተሳስሮ ሲታይ ከጋብቻ በፊት የተፈሩ ንብረቶችን የጋራ የሚያደርግ መሆኑን የሚያሳይ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ስምምነቱ በጋብቻ ውስጥ ለተፈራ ንብረት ተፈፃሚነት ያለው እንጂ ከጋብቻ በፊት ለተገኘ ንብረት አይደለም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. አከራካሪውን ቤት አስመልክቶ በበረኸት ወረዳ ፍ/ር/ቤት በመ/ቁጥር 01316/05 ጥቅምት 25 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0113001 ጥር 09 ቀን 2006 ዓ/ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 030-4591 የካቲት 19 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት "በድምፅ ብልጫ" ተሽሯል፡፡

2. አመልካችና ተጠሪ ሐምሌ 23 ቀን 1997 ዓ/ም ባደረጉት የጋብቻ ውል አመልካች "ከወለደች የግል የለባትም" በማለት ያስቀመጡት የውሉ ሐረግ በውሉ ሀብትሽ ሀብቴ ነው ተብሎ ከተቀመጠው የውሉ ሀረግ ጋር ተሳስሮ ሲታይ አመልካች ለተጠሪ ልጅ ከወለዱ ከጋብቻ በፊት በነበረው የተጠሪ የግል ንብረት ላይ የጋራ ባለሃብት እንዲሆኑ በማሰብ ያስቀመጡት ነው በማለት አመልካችና ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን ቤት እኩል ሊካፈሉ ይገባል፣ ክፍፍሉም በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በተቀመጠው ስርዓት ሊሆን ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ በሌሎች ንብረቶች በወረዳው ፍርድ ቤት፣ ስለ ልጅ ቀለብ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች አልተነኩም፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሀሳብ ልዩነት

እኔ በሁለተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተገለፀው ዳኛ አመልካች እና ተጠሪ ያደረጉት የጋብቻ ውልና የተሰሙት ምስክሮች ቃል የጋብቻ ውላቸው አመልካች ልጅ ከወለደች ተጠሪ ከጋብቻ በፊት ያፈራውን የግል ንብረቱን የጋራ ሀብት እንዲሆን የተስማማ መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ አይደለም ፡፡ የጋብቻ ውሉ የተጠሪን ግልፅ ስምምነት የማያሣይ ከሆነ ፤የጋብቻ ውሉ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1738 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በማድረግ ባለዕዳውን የተጠሪን በሚጠቅም መንገድ መተርጎም ይኖርበታል ብዬ ስለማስብ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101552

ሰኔ 01 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ ትርንጎ መኮንን - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሙሉጌታ መኳንንት - ታልፏል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና የሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ክርክር ሲጀመር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ እንዲፈርስ በፍርድ ቤቱ ከተወሰነ በኋላ አመልካች ጥር 18 ቀን 2001 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 553/ለ/ የሆነና በተጠሪ ስም የተመዘገበ ቤት፣ በተጠሪ ስም የተመዘገበና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-205229 አ.አ የሆነ ተሽከርካሪ፣ በተጠሪ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቀመጠ ጥሬ ገንዘብ፣ የቤት ቁሳቁሶች /ሙሉ ሶፋ፣ ኮንትሮል ቡፌ፣ ፍሪጅ፣ አንድ ዘመናዊ አልጋ፣ ባለቀለም ቴሌቪዥን ከእነ ዲሽ/፣ 35 ግራም የአንገት ሃብል በተጠሪ እጅ የሚገኝና ከወላጆች በውርስ ያገኙት ብር 40,000.00 /አርባ ሺህ/ በተጠሪ እጅ የሚገኘው ንብረቶችን ዘርዝረው የጋራ የሆኑትን ቤት፣ መኪና፣ባንክ ውስጥ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብና የቤት ቁሳቁሶችን እንዲያካፍሏቸው፣ የግል የሆኑትና 35 ግራም ወርቅና 40,000.00 ጥሬ ገንዘብ ደግሞ ተጠሪ እንዲመልስላቸው እና ካሳም እንዲከፈል ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ቤቱ የጋራ መሆኑን፣ መኪናውን አሰርተው ለጋራ እዳ መክፈያነት የሸጡ መሆኑን፣ ባንክ ውስጥ ያለው ገንዘብ 320.667 መሆኑን፣ የቤት ቁሳቁሶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአመልካች እጅ እንደሚገኙ፣ 35 ግራም ወርቅና ብር 40,000.00 በተመለከተ ግን የሚያውቁት ነገር የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ስለመኪናው ተገቢውን አካል ጠይቆ ማስረጃ እንዲቀርብለት ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ቤቱን በተመለከተ አመልካች ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት አመልካች ልጆችን ይዛ እንድትጠቀምበት እና በኋላ ለልጆቻችን እንዲተላለፍ ተስማምተናል ቢሉም ስምምነቱ የቴምበር ቀረጥ ያልተከፈለበትና ፈቃደኝነታቸውን የገለፁበት ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ግራቀኙ እኩል እንዲካፈሉ፣ የቤት ቁሳቁሶችንም ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በማለት የወሰነ ሲሆን መኪናው የግራ ቀኙ ጋብቻ ጸንቶ ባለበት ጊዜ የተሸጠና በሌላ ሰው ስም የሚገኝ መሆኑ መረጋገጡን፣ የካሳ ጥያቄ ፍቺ ሲወሰን ያልቀረበ የዳኝነት ጥያቄ መሆኑን፣ ወርቅና የውርስ የተባለውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ ያለመኖሩን ጠቅሶ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የልጅ ቀለብን በተመለከተም ተጠሪ ሊቆርጡ የሚገባውን ቀድሞ ወስኖና ተጠሪ ስራ በማቋረጣቸው ምክንያት ቀለብ የመቁረጥ ግዴታ ቀሪ እንዲሆንላቸው ቢያመልክቱም ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም፡፡ አመልካች ቤቱ ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በተወሰነውና መኪናውን፣ ወርቁንና የውርስ የተባለውን ጥሬ ገንዘብ በተመለከተ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ መኪናው ላይ ብቻ የቀረበውን ቅሬታ በመቀበል መኪናው በብር 70,000.00 /ሰባ ሺህ/ የተሸጠ መሆኑ ቢረጋገጥም ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም እንዳልዋለ ተረጋግጧል፡፡ በሚል ምክንያት ተጠሪ ለአመልካች ብር 35,000.00 /ሰላሳ አምስት ሺህ/ እንዲተኩላቸው ሲል ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ቤቱ የጋራ ቢሆንም ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት አመልካች እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ ድረስ ተጠቅመው ከዚያ በኋላ ለጋራ ልጆቻችን እንዲተላለፍ ስምምነት ተደርጎ እያለ መታለፉ ያላግባብ ነው፣ ካሳውን በተመለከተም ተጠሪ በሴሰኝነት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ መባላቸው ተረጋግጦ እያለ በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 84 መሰረት ካሳ እንዲከፈል የቀረበው ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሁለቱም ነጥቦች ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ይዘት ተገቢነት በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በሕግ አግባብ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በመኖሪያ ቤቱና ካሳን አስመልክቶ በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው የውሳኔ ክፍል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ በሕጋዊ ጋብቻ ተሳስረው ቆይተው ጋብቻው በፍቺው ውሳኔ ታህሳስ 24 ቀን 2001 ዓ/ም መፍረሱን፣ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ቁጥሩ 553/ለ የሆነና በተጠሪ ስም የተመዘገበ ቤት የጋብቻ ውጤት መሆኑ ተረጋግጦ የግራ ቀኙ ነው ተብሎ የተወሰነ ሲሆን አሁን አመልካች ቅሬታ የሚያቀርቡት ቤቱ የጋራ ቢሆንም ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት አመልካች ቤቱን ልጆችን ይዘው እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ እንዲጠቀሙበትና በኋላም ለልጆች እንዲተላለፍ የተደረገ ሁኖ እያለና ተጠሪም በዚህ ረገድ ሰነዱን በመካድ ያቀረበው ክርክር ሳይኖር በአመልካች በተጠሪ መካከል ክፍፍል እንዲደረግ ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን፣ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር ያለፉት ስምምነቱ የቀረጥ ቴምብር ያልተከፈለበትና በነጻ ፈቃዳቸው የተደረገ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የተጋቢዎች የፍቺ ውጤቶች በስምምነት፣ በሽማግሌዎች ወይም ባለሙያዎች ሊወሰን እንደሚችልና በዚህ አግባብ የተወሰነ የፍቺ ውጤት ተፈጻሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ስለመሆኑ የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀጽ 77 እስከ 80 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 83/3/ ድንጋጌ በጣምራነት ሲነበቡ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጋቢዎቹ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን መኖሪያ ቤት በተመለከተ ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም ስምምነት ያደረጉ መሆኑን አመልካች ቢከራከሩም የፍቺ ውሳኔ በ24/04/2001 ዓ/ም ከተሰጠ በኋላ የተደረገና ስምምነቱ ፍርድ ቤት ቀርቦ ያልጸደቀ፣ ይህን የንብረት ክፍፍል ስምምነት አስመልክቶ በግልጽ ፈቃዳቸውን ሰጥተው ስለመስማማታቸው ያልተረጋገጠ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ ተጠሪም በስር ፍርድ ቤት የክፍፍል ጊዜ ቤቱ የጋራ መሆኑን ጠቅሰው ክፍፍል እንዲደረግ ዳኝነት የጠየቁበት ከመሆኑም በላይ በይግባኝ ደረጃም በቤቱ ላይ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ክፍል ተገቢ ነው በማለት ሲከራከሩ የነበሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ ስለሆነም አመልካች አለ የሚሉት ሰነድ በፍርድ ቤት ያልጸደቀና የግራ ቀኙን ፈቃዳቸው መኖሩ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ቤቱን አስመልክተው የሚያቀርቡት ቅሬታ ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚራከሩት የካሳ ጥያቄ መታለፉ ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ያለፉት አመልካች የፍቺ ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሰጣቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ይህንኑ አልገለፁም በሚል ነው፡፡ በእርግጥም አመልካች የፍቺ ጥያቄ ሲያቀርቡ የካሳ ጥያቄ አላቀረቡም፡፡ ሆኖም ሕጉ የፍቺ ጥያቄ ሲቀርብ ለፍቺ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ መግለፅ የሌለባቸው መሆኑን በአንቀጽ 81/2/ ስር የተደነገገ ቢሆንም ካሳውን ግን በንብረት ክፍፍል ጊዜ ዳኝነት ሊያቀርቡ የሚችሉ መሆኑን ይህንኑ ድንጋጌ ከአንቀጽ 84 ጋር አገናዝበን ስንመለከተው የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ለፍቺ ምክንያት የሆነውን በደል ለፍቺ ምክንያትነት መጥቀስ በሕጉ ግዴታ ያልተጣለባቸው ቢሆንም ካሳ የሚወሰነው ለፍትህ አስፈላጊ ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲያምንበት መሆኑን አንቀጽ 84 በግልጽ ስለሚደነግግና የበታች ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ ካሳ መወሰኑ ለፍትህ አስፈላጊ መሆኑን ያላመኑበት መሆኑን በተለይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍርዱ ላይ የገለፀ ስለሆነ በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ ከአንቀፁ አቀራረፅና ይዘት አንጻር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 64612 ታህሳስ 26 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 119293 ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ/ም ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.99954

ሰኔ 5 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መ·ስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- 1. የህፃን ዘውዴ ወ/ሚካኤል

2. የህፃን አስቴር ወ/ሚካኤል

3. የህፃን አስንቀ ወ/ሚካኤል

4. የህፃን እመቤት ወ/ሚካኤል

ጠበቃ አቶ ዘውዱ ከበደ ቀረቡ

5. የህፃን ሰላም ከልሴ ሞግዚት ወ/ሮ አስናቀች አሰፋ

ተጠሪ፡- አቶ ዝናየ ወ/ሚካኤል - ጠበቃ ደምሰው ዘገየ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 178480 ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 117887 ጥር 23 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዮ ከህጋዊ ጋብቻ የተወልድኩ የሚች ወልደሚካኤል ታረቀኝ ልጅ መሆኔ በፍርድ ተረጋግጦ ይወሰንልኝ በማለት የቀረበን ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ /አመልካች/ተጠሪዎች ተከሳሽ /ተቃዋሚ/ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም ፅፎ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ አባታቸው አቶ ወልደሚካኤል ታረቀኝና እናታቸው ወ/ሮ እቴነሽ ወ/ፃድቅ ሚያዝያ 18 ቀን 1971 ዓ.ም የጋብቻ ሥርዓታቸውን ፈፅመው በትዳር ተሣስረው አብረው እየኖሩ እያለ መጋቢት 7 ቀን 1972 ዓ.ም ተወልጃለሁ፡፡ ስለዚህ የአቶ ወልደ ሚካኤል ታረቀኝ ልጅ መሆኔ ይወሰንልኝ የሚል የዳኝነት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ተጠሪዎች በተከሳሽነት ቀርበው ሟችና የከሳሽ እናት ሚያዝያ 18 ቀን 1971 ዓ.ም አድርገውታል ተብሎ በቀረበው የጋብቻ ውል ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የሟች ፊርማ መሆኑን ስለምንክድ ይመርመርልን ፡፡የአርሲ ነገሌ ማዘጋጃ ቤት ከሳሽ የሟች ልጅ መሆናቸውን በመግለፅ የሰጠው የልደት ማስረጃ ተገቢነት የለውም፡፡ከሳሽ በጋብቻ ውሉ ስማቸው ያልተጠቀሱ ሰዎች በምስክርነት መቁጠሩ ተገቢ አይደለም፡፡የኦርቶዶክስ ቤቴክርስቲያን ስለከሳሽ ልደትና ጥምቀት የሰጠችው ማስረጃ ተገቢነት የለውም በማለት ከሳሽ/ተጠሪ/ የሟች ልጅ አለመሆኑንና ሟች ልጅ የሌላቸው መሆኑን ገልፀው ያደረጉት ግልፅ ኑዛዜ የሚያሳይ እንደሆነ በማንሳት ተከራክረዋል፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ህጋዊ ጋብቻ የተወለደ የሟች ወ/ሚካኤል ታረቀኝ ልጅ መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት ወላጅ እናቱንና ወ/ሮ እቴነሽ የተባሉ ሴት በምስክርነት አቅርቦ አሰምቷል ተጠሪዎች ምስክሮቻቸውን ባለማቅረባቸው ምስክር የማሰማት መብታቸውን በማለፍ፣የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረና ከመዘነ በኃላ በጋብቻ ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የሟች ወልደሚካኤል መሆኑን በፎረንሲክ ለማስመርመር በቂና አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤቴክርስቲያን ስለ ከሳሽ ልደት ፣ጥምቀት የሰጠው ማስረጃና የአርሲ ነገሌ ማዘጋጃ ቤት የሰጠው የልደት ማስረጃ ተዓማኒነት ያላቸውና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ናቸው፡፡የከሳሽ እናትና አባት ከሚያዝያ 18 ቀን 1971 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1978 በጋብቻ ተሳስረው መኖራቸውና ከሳሽ አባትና እናቱ በፀና ጋብቻ በነበሩበት ወቅት መጋቢት 2 ቀን 1972 ዓ.ም የተወለደ በመሆኑ የሟች ወልደሚካኤል ታረቀኝ ልጅ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል ፡፡

3. በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካቾች ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ተጠሪ /መልስ ሰጭ/ መልስ እንዲሰጡ ካደረገና የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የጋብቻ ውሉ ሲፈረም ምስክር የነበሩ ሰዎች እንዲቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቶ፣ምስክሮቹ በሞት የተለዩ በመሆኑ ስለተገለፀለት ለሎች ጋብቻቸው ሥርዓት ላይ ነበሩ የተባሉ ምስክሮች ቃልና የተጠሪን ወላጅ እናት የምስክርነት ቃል በድጋሚ ሰምቷል፡፡ወ/ሮ ጥጋብነሽ ሙላቱ የተባሉ ሴት ሟችና የተጠሪ ወላጅ እናት የጋብቻ ሥርዓት ሲፈፅሙ እንደነበሩና ተጠሪ ጋብቻው ከተፈፀመ በኃላ መወለዱን እንደመሠከሩ ሁለተኛው ተጨማሪ ምስክር ሆነው የተሰጡት አቶ የማታው ወርቁ የሟች አክስትና የልጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልጅ መሆናቸውን ገልፀው ሚች የተጠሪን እናት በደብረብርሃን ከተማ እንዳገባቸውና ተጠሪን እንደወለዱ የነገሯቸው መሆኑን ገልፀው መስክረዋል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡ ማስረጃዎችና በትዕዛዝ አስቀርቦ የሰማቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎች ቃል ከመዘነ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሚች ወ/ሚካኤል ታረቀኝ ልጅ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

4. አመልካቾች 12/07/2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ሚች ልጅ የሌላቸው መሆኑን በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት ግልፅ ኑዛዜ አድርገዋል፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች በጋብቻ ውሉ ላይ ያሉው ፊርማ እንዲመረመር ያቀረብነውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግና ሌሎች አግባብነት የሌለባቸውን ከኦርቶዶክስ ቤቴክርስቲያን እና ሌሎች ማስረጃዎች በመቀበል የDNA /ዲኤንኤ/ ምርመራ ሳይደረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ሰኔ 13 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሚች በጋብቻ የወለደው ልጅ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ ልጅነቱን ያስረዳ መሆኑን ገልፃ አመልካችዎች ያቀረቡት የፊርማና ዲኤንኤ ይመርመርልን ክርክር የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካችዎች ሰኔ 26 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ከዚህ በፊት ተስፋዬ ወልደሚካኤል የተባለ የሚች ልጅ መሆኑን ገልፆ የልጅነት ክስ አቅርቦ ይኽ ሰበር ችሎት የሚች ልጅ ነው በማለት ወስኗል፡፡ሚች በአንድ ከተማ ውስጥ ሁለት ሴቶችን አግብቶ በተመሣሣይ ጊዜ የሁለት ልጅ አባት የሚሆንበት አጋጣሚ የተጠሪን ጥያቄ እጅግ አጠራጣሪ የሚያደርገው በመሆኑ ዲ.ኤን.ኤ ሊመረመር ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ የሚች አቶ ወ/ሚካኤል ታረቀኝ ልጅ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ሕግን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ለመያዝ ጉዳዩን ምርምረናል፡፡

6. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የተወለደው አባቱ አቶ ወልደሚካኤል ታረቀኝና እናቱ ወ/ሮ እቴነሽ ወ/ፃድቅ ሚያዚያ 18 ቀን 1971 ዓ.ም የጋብቻ ሥርዓታቸውን ፈፅመው በጋብቻ ተሣስረው በሚኖሩበት ወቅት መሆኑ ነው ተጠሪ ባቀረባቸው ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑ ለፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡የጋብቻ ሥርዓቱ ለሕዝብ ይፋ በሆነበት ፣የአካባቢው ነዋሪዎች በተጋበዙበትና በተሳተፉበት ሁኔታ የተከናወነ መሆኑን በተጠሪ እናትና አባት የሠርግ ሥርዓት ላይ የተገኙትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረባቸው ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ የተጠሪ ወላጅ እናት ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የምስክርነት ቃልና ሌሎች ደጋፊ የሰነድ ማስረጃዎች የተጠሪ ወላጅ እናትና አባት ሚያዚያ 18 ቀን 1971 ዓ.ም የጋብቻ ሥርዓታቸውን ፈፅመው እስከ 1978 ዓ.ም ድረስ በጋብቻ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሣስረው እንደኖሩ ተጠሪ መጋቢት 12 ቀን 1972 ዓ.ም የተወለደ መሆኑና እናቱና አባቱ የሚከተሉት የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ቀኖና በሚያዘው መሠረት በአርባ ቀኑ የጥምቀት ሥርዓት የተከናወነበት መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡የተጠሪ እናትና አባት የጋብቻ ውል ሲዋዋሉ ምስክር የነበሩት ሰዎችን በሕይወት የሌሉ በመሆናቸው የምስክርነት ቃላቸውን ለመቀበል ያልተቻለ ቢሆንም በጋብቻ ሥርዓት ላይ የነበሩ ሰዎችም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰማ በመሆኑ አመልካችዎች በጋብቻ ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የሚች መሆኑ በፎርንሲክ አልተረጋገጠም በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

7. ተጠሪ የተወለደው አባቱና እናቱ በጋብቻ ተሣስረው በሚኖሩበት ጊዜ ውስጥ መሆኑ ከተረጋገጠ፣የተጠሪ አባት ተጠሪ ሲወለድ ከተጠሪ እናት ጋር በጋብቻ ተሣስሮ ሲኖሩ የነበሩት አቶ ወልደሚካኤል ታረቀኝ ናቸው ብሎ ሕግ ግምት የሚወስድ መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀፅ 741 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ የሚች ልጅ ነው የሚለውን የህጉን ግምት ለማስተባበል የሚቻለው ሚች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት ባደረገው ግልፅ ኑዛዝ እኔ ከአብራኬ የወጣ ልጅ የለኝም በማለት ያደረገውን ግልጽ ኑዛዜ ሣይሆን፣በወቅቱ ሥራ ላይ በነበረው የፍትሐ ብሔር ሕግ 682 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እና በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 167 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት የመካድ ክስ በማቅረብ ተጠሪ የሚች ወ/ሚካኤል ታረቀኝ ልጅ አለመሆኑን በፍርድ በማስወሰን ነው ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ የሚች ልጅ አለመሆኑ እንዲወሰንለት ሚች ወይም የመካድ ክስ እንዲያቀርቡ በሕግ የተፈቀደላቸው የሚች የቅርብ ዘመዶች ለፍርድ ቤት አቅርበው የተወሰነ ውሣኔ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ የሚች ልጅ መሆኑን በሕግ ግምት የተረጋገጠው ልጅነት ከአብራኬ የወጣ ልጅ የለኝም ብሎ የኑዛዜ ቃል ተናገዘዞ በመሞቱ ብቻ የሚስተባበል አይደለም፡፡

8. ከዚህ አንፃር ሲታይ ይኸ የአመልካችዎች መከራከሪያ የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑና አንድ ሰው በኑዛዜ የሚፈፅማቸው ተግባራት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 909 የተደነገጉ በመሆናቸው የአመልካችዎችን መከራከሪያ አልተቀበልነውም፡፡

9. አመልካዎች በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት የመልስ መልስ በመዝገብ ቁጥር 95410 አቶ ተስፋዬ ወልዴሚካኤል የተባለ ሰው የተሰጠን ውሣኔ በማንሣት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችዎች በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ይህንን ፍሬ ነገር መከራከሪያ አድርገው ያላቀረቡትና በማስረጃ ያላረጋገጡት አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329/1/ መሠረት አልተቀበልነውም፡፡ በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የሚች ወልደሚካኤል ታረቀኝ በህጋዊ ጋብቻ የተወለደ ልጅ ነው በማለት አግባብነት ያለውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቤተሠብ ሕግ ድንጋጌ የሕግ ግምት መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 100426

ሰኔ 17 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካቾች፡- 1ኛ ዶ/ር ጥላሁን ኪሮስ
2ኛ አቶ ሐዱሽ ኪሮስ
} ጠበቃ ፅጌ ሐዋስ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ ህፃን ሰናይ የማነ ኪሮስ
2ኛ ህፃን ፍዩሪ የማነ ኪሮስ
} ሞግዚት ወ/ሮ ሄለን ያቆብ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉደዩ የውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ የመንግስት የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካቾች ተከሳሾች ተጠሪዎች ከሳሾች በመሆን ነው የተከራከሩት፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ የሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን የሚለውን ክርክር አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት ወላጅ አባታቸው አቶ የማነ ኪሮስ በ17/01/1996 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩ ሟች አባታቸው ከወላጅ እናታቸው ወ/ሮ ደስታ ረታን ተክተው ከእህት ወንድሞቻቸው የወረሱት ቤትና ቦታ አዋሳኙ በምስራቅ አቶ በላይ አርአያ በሰሜን ወ/ሮ ኪሮስ ታደሰና ወ/ሮ በላይነሽ ታረቀ፣ በምእራብ መንገድ፣ በደቡብ መንገድ የሚዋሰን ስፋቱ 333 ካሬ ሜትር ተከፍሎ እንዲሰጣቸው የማይካፈል ከሆነ በጨረታ ተሸጦ እንዲካፈሉ የሚጠይቅ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች በተጠሪዎች ለቀረበው ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ዋናው ፍሬ ነገሩም፡፡ የተጠሪዎች ሞግዚት በስ/ፍ/መ/ቁ. 52/97 በ30/02/97 ዓ.ም ሞግዚትነት በፍርድ ቤት አጽድቀው ቤቱና ቦታው በሽማግሌ ወደ አንድ መቶ ሺህ ተገምቶ ከ1ኛ አመልካች ብር 25,000.00 /ሃያ አምስት ሽህ ብር / ተቀብለዋል፡፡ በውልና ማስረጃ በ06/01/1997 ዓ.ም ጽድቋል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ በዕርቅ እልባት አግኝቶ ያደረ መሆኑን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244/2//1/ መሠረት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ በተጠሪዎች ጠበቃ በሰጡት መልስም ዕርቁን ፈጽመዋል የተጠሪዎች ወ/ሮ ሄለን ያዕቆብ የፈፀሙት ዕርቅ በ6/01/97 ዓ.ም ነው፡፡ ሞግዚት ሆነው የተሾሙት በ30/02/97 ዓ.ም በመሆኑ ዕርቁን በፈፀመበት ወቅት ሕጋዊ ተግባር ለመፈፀም መብት አልነበራቸውም ሞግዚቱ ሳይሾም ሕጋዊ ተግባር መፈፀም ስለማይችሉ እርቁ ከሕግ ውጭ ነው፡፡ ዕርቅ የመፈፀም ሥልጣን አላቸው ቢባል እንኳ አንድ ሞግዚት ከ300 ብር በላይ በሆነው የንብረት ጥቅም ላይ ስለህፃን ሆኖ መዋዋል አይችልም፡፡ የፍ/ሕ/ቁ. 301 እና 3307 ጋር የሚቃረን ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ አመልካቾች እና የተጠሪዎች ሞግዚት በሽማግሌዎች በ6/01/97 ዓ.ም ባደረጉት ስምምነት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የ4 ወራሾች የነበረ በዘመድ ሽማግሌ ብር 100,000.00 ተገምቶ የከሳሾች ሞግዚት የአመልካች ድርሻ 25,000.00 በተጠሪዎች ስም ተቀብለው ለወደፊቱ ምንም ዓይነት መብት እንደሌላቸው በሽማግሌዎች ፊት ተስማምተው ፊርመው በመቀሌ ከተማ ውልና ማስረጃ ቀርቦ ለህግና ሞራል ሰለማይቃረን ፀድቋል የተጠሪዎች ሞግዚት ከዚህ በኃላ በ30/02/97 ዓ.ም ሞግዚትነት አረጋግጠዋል በ6/01/97 ዓ.ም የተደረገው ስምምነት ለህግና ለሞራል ይቃረናል ተብሎ እንዲፈርስ የቀረበ ጥያቄ የለም፡፡ የተጠሪ ልጆች እናት ባለቤታቸው እንደሞቱ በሕግ እንደ ሞግዚት ነው የምትቆጠረው በፍ/ህ/ቁ.205 በተሰጣቸው ስልጣን የአውራሻቸው የውርስ ሀብት እንደምትቀበል በፍ/ህ/ቁ.298 ተመልክቷል፡፡ በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተፈፀመ ጉዳይ ደግሞ ለክርክር መነሻ ሊሆን ስለማይችል ክሱ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2//ረ/ መሠረት በዕርቅ እልባት አግኝቶ ያደረ ነው ፡፡ በማለት ክሱ በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ወ/ሮ ሄለን ያዕቆብ ዕርቅ የፈፀሙት በ06/01/07 ዓ.ም ሲሆን ሞግዚት ሆነው የተሾሙት ደግሞ በ30/02/97 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ደግሞ በሞግዚትነት ስልጣን ከመውሰዳቸው በፊት እርቁን መፈፀማቸው ነው፡፡ የተጠሪዎች እናት በፍ/ህ/ቁ.205 በህግ ሞግዚቶች እንደሆኑ ይሁን እንጂ የተጠሪዎች የውርስ ሀብቱ አስመልክተው ዕርቅ ለማድረግ የቤተዘመድ ጉባኤ የሰጣቸው ስልጣን የለም፡፡ የቤተዘመድ ጉባኤ ሥልጣን ቢሰጣቸው እንኳን ከብር 300 በላይ ከህፃናቱ ጥቅም ጋር በተያያዘ ክርክር ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከገባ በሽምግልና መስማማት እንደማይችሉ በፍ/ሕ/ቁ.301 በአስገዳጅነት መልኩ ተቀምጠዋል፡፡ ወ/ሮ ሄለን ያዕቆብ የፈፀሙት ስምምነት መጠኑ ብር 25,000.00 ነው ይህ የሚያሳየው ደግሞ ወ/ሮ ሄለን ያዕቆብ ከስልጣናቸው ውጭ የተጠሪዎች የውርስ ሀብት ስምምነት እንደፈጽሙ ነው፡፡ ወ/ሮ ሄለን ያዕቆብ ፈጽሙት የተባለው የሽምግልና ስምምነት ከሥልጣናቸው ውጭ በቤተዘመድ ጉባኤ ባልተፈቀደላቸው ነው፡፡ ባልተሰጣቸው ስልጣን ለፈጸሙት ስምምነት ደግሞ ውጭ ተጠሪዎች / ህፃናት / ስምምነቱ ይፍረስልን ብለው አስቀድመው የሚጠይቁበት ምክንያት የለም፡፡ ስምምነቱ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠው የህፃናት መብት የሚጋፉ ፈራሽ ነው፡፡ ስምምነቱ ፈራሽ ነው፡፡ ከተባለ ደግሞ ህፃናቱ ስምምነቱ ይፍረስልን የሚሉበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ አከራክሮ ውሳኔ ይስጥበት በማለት ብይኑ ለመሻር በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 በነጥብ ለሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ በጽሑፍ ክርክር አድርጓል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ያነሱዋቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች የተጠሪዎች እናት ሕጋዊ ሞግዚት ናቸው ሰምምነቱም እንዲፈርስ ጥያቄ አልቀረበም ተጠሪዎች በሸማግሌዎች ግምት መሠረት ድርሻቸውን ወስደዋል የሚል ይዘት አለው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በግራ ቀኙ የዕርቅ ስምምነት ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም አለመጠናቀቁ የእርቅ ስምምነቱም የህፃናት መብትና ጥቅም የሚጎዳ ስለመሆኑ የተጠሪዎች ሞግዚት ዕርቅ ለማድረግ የቤተሰብ ጉባኤ ፍቃድ አልሰጣቸውም ተጠሪዎች የጠየቁት ሀብት ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት መሆኑ በፍ/ህ/ቁ 205 መሠረት ከወላጆቹ አንዱ በማይኖርበት ወይም ችሎታ ባጣበት ወቅት የማሳደግ፣ የማሰተማር፣ የመንከባከብና የማሰተዳደር ስልጣን እንጂ ንብረት የማሰተላለፍ ሀላፊነት እንደማይሰጠው በመጥቀስ መልሰ አቅርበዋል የአመልካቾች የመልሰ መልሰም የሰበር አቤቱታው የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ለማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመረውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚያስፈለገው ጭብጥ የሥር ፍርድ ቤቶች በተጠሪዎች ሞግዚት ተደረገ የተባለው የዕርቅ ስምምነት ከመሾማቸው በፊት የተደረገ በመሆኑ ተጠሪዎችን የሚያስገድዱ አይደለም በማለት መወሰናቸው በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከክርክር ሂደቱ መረዳት እንደተቻለው አመልካቾች ከተጠሪዎች ሞግዚትነት ጋር ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት መስከረም 6 ቀን 1997 ዓ.ም ዕርቅ ስምምነት አድርገው በሽማግሌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግምት መሠረት 25.00.00 ብር እንደወሰዱ እና ሌላ እንደማይጠይቁ መግለፃቸው፤ተጠሪ የሞግዚትነት ስልጣን የወሰዱትም ጥቅምት 30 ቀን 1997 ዓ.ም ስለመሆኑ ነው፡፡ አመልካቾች ተጠሪዎች ሞግዚት ያደረጉ ስምምነት ለህግና ሞራል የማይቃረን መሆኑን ተረጋግጦ በሚመለከተው አካል ቀርቦ መመዝገቡን ይከራከራሉ ተጠሪዎች በበኩላቸው ሞግዚቱ እንደገና ሞግዚቶቻቸው በቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ያልጸደቀ በመሆኑ አደረጉት የተባለው ዕርቅ እንደማያስገድዳቸውና የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለመሆኑ መከራከራቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው የተጠሪዎች ሞግዚት የሞግዚትነት ሥልጣን ከማግኘታቸው በፊት ከአመልካች ጋር ዕርቅ ማድረጋቸው ነው፡፡ በተጠሪዎች ሞግዚት የተደረገው ስምምነትም ለቤተዘመድ ምክር ጉባኤ አቅርቦ ስለመጽደቁም በአመልካቾቹ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ አመልካቾች ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩት በተጠሪዎች ሞግዚት የተደረገው ስምምነት ለህግና ለሞራል የሚቃረን አይደለም በሚል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዕርቅ ስምምነቱ እንዲፈርስ ክስ እንዳልቀረበ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ያቀረቡት ቅሬታ ያመለክታል፡፡ በመሠረቱ የልጅ አስተዳደግ እና ንብረት አስተዳደር ባልና ሚስት በጋብቻ ተሳስረው በሚኖርበት ጊዜ በጋራ እንደሚያከናውኑት በማንኛውም ምክንያት ከወላጆች አንዱ ተግባሩን ማከናወን ካልቻለ ሌላኛው ኃላፊነቱን እንደሚሸከም ከፍ/ህ/ቁ.204 እና 205 ጭምር ጥምርንባብ የምንረዳው ነው፡፡

ሞግዚት አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት በማስተዳደር ሥልጣን እንዳለው ከፍ/ህ/ቁ. 280 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ሞግዚቱ የልጅን ሀብት በሚያስተዳድሩበት ጊዜ እና ሁኔታ በፍ/ህ/ት የተመለከቱትን መሠረታዊ ድንጋጌዎች ባስከበረ መልኩ መሆን እንዳለበት ከድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት አላማና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የውርስ ሀብት ያገኘ እንደሆነ ሞግዚቱ ከቤተዘመድ ምክር አባሎች መካከል ምስክሮች ባሉበት ንብረቱም የዋጋ ግምት መግለጫ ሊዘጋጅለት እንደሚገባ ልጅ ከውርስ ሀብት የሚደርሰው መጠን ጉድለት እንዳይኖርበት ሞግዚቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ልጅን ወክሎ እንደሚቀበል፤ ለአውራሽ ዕዳ የማይበቃ ካልሆነ በቀር አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ በውርስ የደረሰው ሀብቱ የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ካልተፈቀደለት በቀር ሞግዚቱ ለመተው እንደማይችል ከፍ/ህ/ቁ. 282/1/ ፤/2/ እና 298/1/ እና /2/ ጥምር ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ከላይ የተመለከተናቸው ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና አላማ መረዳት እንደተቻለው ሕግ አውጭው የህፃናት መብት በተመለከተ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረጉን የሚያሳይ መሆኑን ነው ከዚህ ጋር በተያያዘም ሞግዚቱ የልጅን መብትና ጥቅም በተመለከተ የሚያደርገው ሕጋዊ ግንኙነት የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ፍቃድ የሚጠይቅ ስለመሆኑ ነው፡፡ የፍ/ህ/ቁ.301 ድንጋጌ ሙሉ ይዘቱ ሞግዚቱ ክርክር የሚደረግበት ጥቅም ከሦስት መቶ የኢትዮጵያ ብር ያነሰ ካልሆነ በቀር አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅሞች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚመለከት ነገር ከቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ካልተፈቀደለት ምንም ግልግል ለመፈፀም አይችልም፡፡ በማለት ደንግጓል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪዎች ሞግዚት ለዕርቅ ስምምነት አድርጉ የተባለው በቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ከመሾማቸው በፊት ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ በአመልካቾች እና በተጠሪዎች ወኪል ተደረገ የተባለው የገንዘብ መጠንም ከ25,000.000 ብር ያላነሰ ነው፡፡ በአንጻሩ ሕግ አውጭው ሞግዚቱ ስለ ህፃኑ የሚያደርገው ግልግል ከ300.00 ብር በላይ ከሆነ የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ይሁንታ እንደ ቅድመ ሁኔታ መቀመጡን ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ በተያያዘው ጉዳዩ የተጠሪዎችም ሞግዚት ዕርቅ ለማድረግ ቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ፋቃድ ስለማግኘታቸው አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ነገር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የህፃናቱ መብትና ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ሞግዚቱ ከ3ኛ ወገን በሕጉ ከተፈቀደው ውጭ የመስማማት ሥልጣን አልተሰጠውም የተጠሪዎች ሞግዚት በሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣን ውጭ የተደረገ የቤተዘመዱ ምክር ጉባኤ ፍቃድ ሲያገኙ ተጠሪዎች ከአውራሻቸው የሚያገኙት የውርስ ሀብት ድርሻ በተመለከተ ያደረጉት ስምምነት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪዎችም በሞግዚታቸው የተደረገው ዕርቅ መጀመሪያ እንዲያፈርሱ የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች ከዚህ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት አለው በማለት የጠቀሱት አስገዳጅ የሰበር ውሳኔ ሰ/መ/ቁ. 43226 በክርክሩ ይዘት ባህሪ እና ለውሳኔ የተያዘው ጭብጥ ከዚህ ጉዳይ ጋር የሚዛመድ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥር ወረዳ እና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ግራ ቀኙ በፍሬ ጉዳዩ እንዲከራከሩ የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

- የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ. 61548 በ23/03/2006 የሥር የወረዳና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 96934 በ10/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጽንቷል፡፡
- የተጠሪዎች ሞግዚት ከአመልካች ጋር አደረጉት የተባለው ስምምነት የሞግዚትነት ሥልጣን ሳይሰጣቸው እና በቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ፍቃድ ያላገኘ በመሆኑ በሕግ ፊት የሚጸና አይደለም ተብሎ በሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
- የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ት ዕ ዛ ዝ

- በዚህ ፍ/ቤት 03 ሰኔ 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይባፍ፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

ወ/ክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.94811

ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ታረቀኝ ጥሩነህ - የቀረበ የለም
ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሰናይት ታደሰ - የቀረበየለም
} በአካልም በV.C ም ከሀዋሳ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ የቀረበ የጋራ ንብረት ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በዚህ መዝገብ አከራካሪ ሆኖ ከቀረበው ጉዳይ መካከል በጭብጥነት የተያዘው ተጋቢዎቹ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት ነው የተባለ የአንድ ባጃጅ ተሽከርካሪ ጉዳይ እና ተጠሪዋ በ02/07/2004 ዓ.ም.ከባንክ ውጪ አድርገው መውሰዳቸው የተረጋገጠው የብር 34,000 (ሰላሳ አራት ሺህ) ጉዳይነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/ መንግስት በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ተከሳሽ በነበሩት በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ጋብቻቸው በተከሳሹ ጥፋት እና በካሳ ውሳኔ ጭምር የፈረሰ መሆኑን ገልጸው በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ ናቸው ያሏቸው የማይንቀሳቀስ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ለክሱ መልስ ከመስጠታቸው በተጨማሪ በተጠሪዋ እጅ የሚገኝ ነው ያሉት ጥሬ ገንዘብ በድርሻቸው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው የበኩላቸውን የዳኝነት ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ በመዝገብ ቁጥር 00906 በ05/09/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ የክፍያ ጥያቄ ለቀረበባቸው ንብረቶች ሁለት የተለያዩ ውሳኔዎችን ሰጥቷል፡፡ በአሁኗ ተጠሪ ጠያቂነት ውሳኔ ከተሰጠባቸው ንብረቶች መካከል ለሰበር ክርክሩ ለተያዘው ጭብጥ ምክንያት የሆነው ጋብቻው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፀንቶ ባለበት ጊዜ የአሁኑ አመልካች ገዝተው ስመሀብቱን ሳያዛውሩ ሲሰሩበት ነበር የተባለው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 1-1420 ደሕ የሆነን ባጃጅ ተሽከርካሪ ሲሆን በአሁኑ አመልካች ጠያቂነት ውሳኔ ከተሰጠባቸው ንብረቶች መካከል ለሰበር ክርክሩ ለተያዘው ጭብጥ ምክንያት የሆነው ደግሞ ተጠሪዋ በ02/07/2004ዓ.ም.ከአቢሲኒያ ባንክ ወጪ አድርገው መውሰዳቸው የተረጋገጠው የብር 34,000 (ሰላሳ አራት ሺህ) ጉዳይ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. አመልካች ገዝተው ስመ ሀብቱን ሳያዛውሩ ሲሰሩበት ነበር የተባለው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ1-1420 ደሕ የሆነው ባጃጅ ተሽከርካሪ የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ነው በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
2. ተጠሪዋ በ02/07/2004 ዓ.ም. ከአቢሲኒያ ባንክ ወጪ አድርገው መውሰዳቸው የተረጋገጠው ብር 34,000 (ሰላሳ አራት ሺህ) ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠር ነው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ጋብቻው ጸንቶ በነበረበት ጊዜ አመልካች አንድ ባጃጅ ተሽከርካሪ ገዝተው ነገር ግን ስም ሳያዛውሩ ሲሰሩበት የነበረ ስለመሆኑ ገልጸው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ተጠሪዋ ላቀረቡት ክስ አመልካች ስለተባለው ባጃጅ ተሽከርካሪ የሚያውቁት ነገር አለመኖሩን እና ባጃጁ የተገዛበትን ውልም ሆነ በአመልካች ስም የተመዘገበበትን የባለቤትነት ማስረጃ ሳያቀርቡ ተጠሪ ያቀረቡት የድርሻ ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ገልጸው በመሸሸ መልክ መልስ ከመስጠታቸው በቀር ባጃጅ ተሽከርካሪውን ያልገዙ እና ሲሰሩበትም ያልነበሩ ስለመሆኑ በግልጽ የሰጡት የማስተባበያ መልስ አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ባጃጁን በተመለከተ ተጠሪዋ ስለራሳቸው 1ኛ ምስክር በመሆን በሰጡት ምስክርነት አመልካች አንድ ባጃጅ ተሽከርካሪ ገዝተው ነገር ግን ስም ሳያዛውሩ ሲሰሩበት የነበረ ስለመሆኑ ገልጸው መመስከራቸውን ፣የተጠሪዋ 2ኛ ምስክር አመልካች ባጃጁን ሲገዙ እንዳላዩ፣ነገርግን ያሽከረክሩ እንደ ነበረ እና ያሳድሩ የነበረውም በግቢአቸው ውስጥ እንደሆነ በመግለጽ መመስከራቸውን እና የተጠሪዋ 3ኛ ምስክር ደግሞ አመልካቹ ባጃጁን ያሽከረክሩ እና በቤታቸው ያሳድሩ የነበረ ከመሆኑ በተጨማሪ ባጃጁን የገዙት ስለመሆኑም ጭምር እንደነገሯቸው ገልጸው መመስከራቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች ስለባጃጅ ተሽከርካሪው የማውቀው ነገር የለም፣በስሜም አልተመዘገበም፣የሽያጭ ውሉም አልቀረበም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት በደፈናው ከመከራከር በቀር በተጠሪዋ ምስክሮች የተሰጠውን ምስክርነት ለማስተባበል ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ባጃጅ ተሽከርካሪ የእኔ ነው በማለት የቀረበ ወገን ስለመኖሩም የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም። እንዲህ ከሆነ ደግሞ በአመልካቹ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 235 መሰረት በመሸሸ መልክ የተሰጠውን የመከላከያ መልስ እና በተጠሪዋ ምስክሮች የተሰጠውን ምስክርነት መሰረት በማድረግ አመልካች ጋብቻው ጸንቶ በነበረበት ጊዜ ገዝተው ነገር ግን ስም ሳያዛውሩ ሲሰሩበት የነበረው ባጃጅ ተሽከርካሪ የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ሕጉን እና የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መሰረት አድርጎ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም።

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት የዳኝነት ጥያቄ ያቀረቡት ተጠሪዋ ከአቢሲኒያ ባንክ ብር 34,000 በ02/07/2004 ዓ.ም.ወጪ አድርገው በዚያኑ ዕለት የተለያዩ ዕቃዎችን ይዘው ከቤት የወጡ በመሆኑ ከዚህ ገንዘብ ወስጥ ግማሹን ሊያካፍሏቸው የሚገባ መሆኑን በመጠየቅ ሲሆን ተጠሪዋ በበኩላቸው መልስ የሰጡት አመልካች የእናታቸውን ለቅሶ ጎንደር ደርሰው ከተመለሱ በኃላ የገንዘብ እጥረት እንዳጋጠማቸው በመግለጽ ለሚያካሄዱት የበርበሬ ንግድ ስራ ለማዋል ያስችላቸው ዘንድ ገንዘቡን ወጪ አድርገው እንዲሰጧቸው ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ተጠሪ ገንዘቡን በ02/07/2004 ዓ.ም. ወጪ አድርገው በዚያኑ ዕለት የሰጧቸው መሆኑን እና አመልካቹም ለበርበሬ ግዥ ያዋሉት መሆኑን፣ገንዘቡ ከባንክ ወጪ ተደርጎ ከተሰጣቸው ከአምስት ቀናት በኃላ በ07/07/2004 ዓ.ም አመልካች ጠብ ፈጥረው ተጠሪዋን ከቤት ያባረሩ መሆኑን በመግለጽ እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል። ይህንን የክርክር ነጥብ ለማስረዳት ግራ ቀኙ ካቀረቡት ማስረጃ መካከል በተጠሪዋ በኩል የቀረበው ማስረጃ የራሳቸው ምስክርነት ሲሆን በአመልካቹ በኩል የቀረበው ማስረጃ ደግሞ ከአመልካቹ ምስክርነት በተጨማሪ ተጠሪዋ ከቤት የወጡት በ05/07/2004 ዓ.ም ስለመሆኑ በሌሎች ሁለት ምስክሮች የተሰጠው ምስክርነት ነው። ተጠሪዋን ብረት ይዘው ከቤት የወጡት በ02/07/2004 ዓ.ም.ስለመሆኑ አመልካች በ03/07/2004 ዓ.ም.ለአካባቢው ፖ/ስ ጽ/ቤት አመልክቻለሁ በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ለፖ/ስ ያመለከቱት በርግጥም በ03/07/2004 ዓ.ም.መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ የቀረበ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም። በመሰረቱ አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው ለግዴታው መኖር ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2001(1) እንዲሁም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 258 እስከ 261 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት አመልካች እንደ አቤቱታቸው አስረድተዋል ሊባል የሚችለው ተጠሪዋ ከቤት የወጡት ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ብር 34,000 ከባንኩ ባወጡበት በ02/07/2004 ዓ.ም. መሆኑን ማስረዳት ቢችሉ ኖሮ ነው። ቀደም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲል እንደተገለጸው ይህንን ነጥብ ደግሞ ማስረዳት አልቻሉም፡፡ ይልቁንም አመልካች ያሰሟቸው 2ኛ እና 3ኛ ምስክሮች ያረጋገጡት ተጠሪዋ ከቤት የወጡት በ05/07/2004 ዓ.ም.መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ብር 34,000 አስመልክቶ አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ሳይቀበሉ የቀሩትም ከግራቀኙ ማስረጃ መካከል የተሻለ ክብደት ያለው ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ገንዘቡን ለትዳር ጥቅም ያዋሉ ስለመሆኑ በተጠሪዋ በኩል የቀረበው ማስረጃ መሆኑን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪዋ በ02/07/2004 ዓ.ም. ከአቢሲኒያ ባንክ ውጪ አድርገው መውሰዳቸው የተረጋገጠው ብር 34,000(ሰላሳ አራት ሺህ) ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠር ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 00906 በ05/09/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በሀዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14065 በ23/11/2005ዓ.ም. በፍርድ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59978 በ15/02/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓትሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01512 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ05/03/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 107840

ቀን ሐምሌ 28/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘምዘም ሸረፋ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ኢታለ ሐሰን -ቀረቡ

2. አቶ ተቂቶ መሐመድ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባል እና ሚስት ንብረት ክርክር መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በወረዳ ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል ፡፡ በ1ኛ ተጠሪ የቀረበው ክስ በቀን 03/06/2006 ዓ.ም የተፃፈ ክስ ዝርዝር ይዘቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን በመግለፅ የተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የመሬት ይዞታ አንድ የቆርቆሮ ቤት አንድ የሳር ክዳን ቤት እንዲሁም በንሮ የጫት ተክል ፣ቡና ፣ሙዝ ተክል ያለበት አንድ በሬ አንድ ጊደር አንድ ጥጃ እና የውሃ ጀኔሬተር የጋራ የባል እና ሚስት ስለሆነ 2ኛ ተጠሪ ድርሻቸውን እንዲያካፍሏቸው የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡

በ2ኛ ተጠሪ የተሰጠ መልስ የጋራ ንብረት የለንም በክሱ የተጠቀሱት የእናታቸውን ወይም የጣልቃ ገብ መሆኑ በመግለፅ መልስ ሰጥቷል፡፡በአሁን አመልካች ጣልቃ ገብተው ለክርክር ምክንያት ሆኑት የመሬት ይዞታ ፣ ቀንድ ከብቶች እና የውሃ ጀኔሬተር የራሳቸው መሆናቸው የከሳሽ እና የተከሳሽ ንብረት አይደሉም በማለት መቃወሚያ አቅርበው የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ተሰምቶ ክርክሩ ተጠናቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤትም በመ/ቁ. 08575 በቀን 25/07/06 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሁለት ጥማድ በጣልቃ ገብ ለጎጆ መውጫ የተሰጣቸው መሆኑ በማረጋገጥ እኩል ባልና ሚስት እንዲካፈሉ አንድ በሬ አንድ ጊደር አንድ ጥጃና የውሃ ጀነሬተር ተጠሪዎች በእኩል እንዲካፈሉ ተወሰነ፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታ በአመልካች በመቅረቡ፤ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር እንዲካሄድ በማድረግ በመ/ቁ. 10375 በቀን 19/10/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት በውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አሁንም አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ችሎቱ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

አመልካች በቀን 13/04/2007 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ በማድረግ የፅሑፍ ክርክር አድርገዋል፡፡ ከአመልካች ክርክር ይዘት ተጠሪዎች እንዲከፈሉ የተወሰነው የመሬት ይዞታ፣ቀንድ ከብቶችና የውሃ ጀነሬተር የግሌ ንብረቶች ናቸው፡፡ ተጠሪዎች ምንም መብት የላቸውም ሲሉ የመሬት ይዞታው በስሜ ግብር ካርኒ የሚቆረጠው በሌለባቸው ንብረት የተሰጠ ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአንደኛ ተጠሪ የተሰጠ መልስ ጎጆ ስንወጣ በአካባቢው ባህል የተለመደ 4 ጥማድ ይዞታ ሰጥተውን አንድ አነስተኛ የሳር ቤት ሰርተን ቋሚ ተክሎች በመትከል ለ 11 ዓመት ባልና ሚስት በጋራ ስንጠቀምበት የነበረ ነው፡፡ ይህንን በማስረዳት ነው የተወሰነው፡፡ ቀንድ ከብቶች ጀነሬተር የባልና ሚስት የጋራ ሃብቶችን በትዳር ውስጥ ያፈራናቸው መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ የተወሰነ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስለሌለው በውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ በ2ኛ ተጠሪ የተሰጠ መልስ ደግሞ የጋራ የሆነ መሬትና ንብረት የለንም፡፡ አብረን ባልና ሚስት የተጠቀምንበት ሁኔታ የለም፡፡ ለጎጆ መውጫ ተብሎ ከአመልካች የተሰጠ ስጦታ የለም፡፡ የምንተዳደረው የነበረው ለእኩል እርሻ እያረስኩ በማገኘው ገቢ ቤተሰቤን አስተዳድር ነበር፡፡ በአመልካች የቀረበ አቤቱታ በአግባቡ ነው በማለት መልሳቸው አቅረበዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪዎች ለ11 አመታት በጋብቻው ቆይታው ጋብቻው በፍቺ በመፍረሱ ምክንያት በ1ኛ ተጠሪ በጋራ ያፈሩትን ሃብት ድርሻቸው እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ክስ በ2ኛ ተጠሪ የጋራ የሚባል ሃብት እንደሌላቸው ሲከራከሩ የአሁኑ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ በመግባት ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ንብረት የግላቸው መሆኑን ተከራክሩ በፍሬ ነገር ደረጃ ማጣራት የሚገባው በክሱ የተጠቀሱትን ንብረቶች የባልና ሚስት ናቸው ወይስ የአመልካች ናቸው የሚለውን ጭብጥ በማስረጃ ማረጋገጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለበት ሆኖ በመገኘቱ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ማስረጃ ያቀረበ መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘብ ይችላል፤ አመልካች ለተጠሪዎች ጎጆ መውጫ ከይዞታቸው የሰጡ መሆናቸው ተጠሪዎችና በዚሁ የተሰጣቸው በጋራ ይጠቀሙበት እንደነበር በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ነው፡፡

የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ/ የመሬት አዋጅ ቁ 110/1999 አንቀፅ 5/5/ ላይ የተደነገገው ባልና ሚስት ጋብቻው ወቅት አብረው ይጠቀሙ የነበረው ይዞታ በፍቺ ጊዜ የመጠቀም መብት አይከላከልም፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 2/7/ በጋራ ይጠቀሙበት የነበር ይዞታ በፍቺ ወቅት እኩል የመካፈል መብት ይሰጣል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት በአመልካች ለተጠሪዎች ለጎጆ መውጫ የተሰጣቸው መሆኑን በስር ፍርድ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለዚህ አመልካች በፍቃዳቸው የሰጡት ይዞታ ተጠሪዎች በጋራ 11 አመት ይጠቀሙበት የነበር ይዞታ

በእኩል እንዲካፈሉ እንዲሁም የቀንድ ከብቶችና የውሃ ጀነሬተር የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ናቸው በማለት በተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በዚህ ጉዳይ በስር ፍርድ ቤቶች ማለትም የደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 62532፣ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 08575 በቀን 19/10/06ዓ.ም እና የስልጤ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 08575 በቀን 25/07/06/ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ያደረጉት ወጪና ኪሳራ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በቀን 27/04/2007ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተነስተዋል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ109731

ሐምሌ 1 ቀን 2007ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች ፡- ወ/ሮ ሃና አሰፋ -ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ከፍይበሉ አሰፋ -ቀረቡ

2. አቶ ሽፈራው ከበደ---መብታቸው ታልፎአል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት ለስረ ነገሩ ፍርድ ምክንያት የሆነው የብድር ገንዘብ ባለቤታቸው በነበሩት በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የተወሰደው ጋብቻቸው ከፈረሰ በኃላ በመሆኑ የአመልካቿ የግል ንብረት የሆነው የሰሌዳ ቁጥር 2-38341 ተሸከርካሪ ለአፈጻጸሙ የተያዘው አላግባብ መሆኑን ገልጸው ተሸከርካሪው እንዲለቀቅላቸው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 418 መሰረት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡- 2ኛ ተጠሪ በ05/13/2000 ዓ.ም. ከ1ኛ ተጠሪ የወሰዱትን የብድር ገንዘብ መመለስ በነበረባቸው ጊዜ ሳይመልሱ በመቅረታቸው 1ኛ ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 104139 ክስ መስርተው 2ኛ ተጠሪ ብር 41,000 (አርባ አንድ ሺህ) ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ በ30/05/2005 ዓ.ም ውሳኔ ማሰጠታቸውን፣ይህንን ፍርድ ለማስፈጸም 1ኛ ተጠሪ ባስከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 108770 ላይ የ2ኛ ተጠሪ ባለቤት ናቸው በተባሉት የአሁኗ አመልካች ስም ተመዝግቦ የሚታወቀው የሰሌዳ ቁጥር 2-38341 ተሸከርካሪ ለአፈጻጸሙ እንዲውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያቀረቡትን ጥያቄ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ተሽከርካሪው በሐራጅ ተሸጦ ለዕዳው መክፈያ እንዲውል በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተሽከርካሪ ለአፈጻጸሙ የተያዘ መሆኑን፣አመልካቿ የአፈጻጸም ትዕዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት መቃወሚያ ያቀረቡትም ይህንን ትዕዛዝ በመቃወም መሆኑን፣በ24/11/2006 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት መቃወሚያ ይዘትም የአመልካች እና የ2ኛ ተጠሪ ጋብቻ በመዝገብ ቁጥር 74753 በ08/03/2002 ዓ.ም. በተሰጠ ውሳኔ የፈረሰ በመሆኑ በማይመለከታቸው ዕዳ የተያዘው የአመልካቿ የግል ንብረት የሆነው ተሽከርካሪ እንዲለቀቅ የተጠየቀበት መሆኑን፣በመቃወሚያው ላይ 1ኛ ተጠሪ በ16/03/2007 ዓ.ም. በሰጡት መልስ የብድር ዕዳው የተገባው አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ በጋብቻ ተሳስረው በነበረበት ጊዜ መሆኑን እና የንብረት ክፍፍልም ያላደረጉ መሆኑን በመግለጽ መቃወሚያው ውድቅ ተደርጎ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል መጠየቃቸውን፣2ኛ ተጠሪ በሞት ተለይተዋል በመባሉ በእርሳቸው በኩል የቀረበ አስተያየት አለመኖሩን፣ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ የብድር ዕዳው በ2ኛ ተጠሪ የተገባው በ05/13/2000 ዓ.ም. ሆኖ ጋብቻው የፈረሰው ደግሞ በመዝገብ ቁጥር 74753 በ08/03/2002 ዓ.ም. በተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ መሆኑን፣አመልካቿ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ የተጋቢዎቹ የጋራ ዕዳ አይደለም የሚል እና የፍርድ ባለዕዳው ዕዳውን ለመክፈል የሚያስችል አቅም አላቸው የሚል ዝርዝር ክርክር ያላቀረቡ መሆኑን፣ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ እያሉ ለጋራ ጥቅም የተበደሩት ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው ሊከፈል እንደሚችል፣ ከጋራ ሀብታቸው ሊከፍሉ ካልቻሉ ዕዳው ከአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት ሊከፈል እንደሚችል እንዲሁም አንደኛው ተጋቢ በግሉ የተበደረውን ገንዘብ በግል መክፈል ካልቻለ ከተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ላይ እንደሚከፈል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 70 የተደነገገ መሆኑን እና በአጠቃላይ ተሽከርካሪው ለዕዳው መክፈያ ሊውል የማይችልበትን ሕጋዊ ምክንያት አመልካች ያላስረዱ መሆኑን ገልጾ የቀረበለትን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ከቀድሞ ባለቤታቸው 2ኛ ተጠሪ ጋር የፍቺ ስምምነት ያደረጉት በ15/08/2000 ዓ.ም. መሆኑን እና ፍርድ ቤቱም በ08/03/2002 ዓ.ም. ያጸደቀው ይህንኑ ስምምነት ከመሆኑ አንጻር እና ብድሩ በ2ኛ ተጠሪ ተወስዷል የተባለው ደግሞ የፍቺ ስምምነቱ ከተደረገ በኃላ በ05/13/2000 ዓ.ም ከመሆኑ አንጻር የብድር ውሉ አመልካችንም የሚመለከት ነው ተብሎ አፈጻጸሙ በግል ንብረታቸው ላይ እንዲቀጥል የተሰጠውን ትዕዛዝ አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ የ2ኛ ተጠሪ መልስ የመስጠት መብት የታለፈ ሲሆን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ግን የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ፍርድ ቤቱ በ08/03/2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ያጸደቀው በ15/08/2000 ዓ.ም. የተደረገውን የፍቺ ስምምነት በመሆኑ ጋብቻው በስምምነት ፈርሷል ሊባል የሚችለው ስምምነቱ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ እንጂ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ከጸቀበት ቀን ጀምሮ አይደለም፣2ኛ ተጠሪ የብድር ውሉን አድርገዋል የተባለውም ጋብቻው በስምምነት ከፈረሰ በኋላ በመሆኑ ብድሩ አመልካችን የሚመለከት ሊሆን አይችልም በማለት መሆኑን የክርክራቸው ይዘት ያመለክታል፡፡አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ጋብቻችንን በስምምነት አፍርሰናል በሚሉበት ቀን እና ስምምነታቸውን ለፍርድ ቤት አቅርበው ባጸደቁበት ቀን መካከል ያለው ጊዜ አንድ ዓመት ከሰባት ወር መሆኑን ከላይ ከተመለከተው የጊዜ ቅደም ተከተል መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሰረቱ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ሊወሰን ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሲወስኑ እና ለፍርድ ቤት አቅርበው ውሳኔያቸው ተቀባይነት ሲያገኝ ስለመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 76 (1) ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አነጋገር በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው አንድ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ስምምነት ፈርሷል ሊባል የሚችለው የፍቺ ስምምነቱ ተደርጓል በተባለበት ቀን ሳይሆን የፍቺ ስምምነቱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ባገኘበት እና በጸደቀበት ቀን መሆኑን ነው፡፡ብድሩ በ2ኛ ተጠሪ ተወስዷል የተባለው ደግሞ የፍቺ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ቀርቦ ከጸደቀበት ቀን ከአንድ ዓመት ከሶስት ወራት በፊት መሆኑ አላከራከረም፡፡በመሆኑም ጋብቻው በስምምነት ፈርሷል ሊባል የሚችለው ስምምነቱ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ እንጂ ስምምነቱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ አይደለም በማለት አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ የፍቺ ስምምነትን ሲያጸድቅ ተጋቢዎቹ ስለፍቺው ውጤት ያደረጉትንም ስምምነት አብሮ የሚያጸድቅ ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 80 (2) ስር ተመልክቷል፡፡ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ የመሰረቱት በ1994 ዓ.ም. እንደሆነ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ያቀረቡት የፍቺ ስምምነት የሚያመለክት ሲሆን በፍቺ ስምምነቱ ላይ ተጋቢዎቹ ልጅ እንዳላፈሩ ከመገለጹ በቀር የጋራ ንብረት ያፈሩ ወይም ያላፈሩ ስለመሆኑ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ይህም በፍርድ ቤት ቀርቦ ጸድቋል የተባለው የፍቺ ስምምነት የተሟላ አለመሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡አመልካች የጋራ ንብረት ያላፈራን ስለመሆኑ በፍቺ ስምምነቱ ላይ ተገልጿል በማለት በሰበር አቤቱታቸው ላይ ያቀረቡት ክርክርም የስምምነቱን ይዘት መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ የፈረሰበት ስምምነት በፍርድ ቤት ጸድቋል ከተባለበት ቀን ከአንድ ዓመት በኃላ 2ኛ ተጠሪ እና አመልካች ባልና ሚስት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆናቸውን በመግለጽ ከሶስተኛ ወገን ጋር የንግድ ድርጅት ሽያጭ ውል የፈጸሙ ስለመሆኑ 1ኛ ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ያቀረቡትን የክርክር ነጥብ በተመለከተ ባልና ሚስት ከተፋቱ በኃላ እንደገና ከመጋባትም ሆነ የጋራ ንብረት ከማፍራት የሚከለክላቸው ነገር የለም ከማለት በቀር አመልካች ግልጽ የማስተባበያ ክርክር ያላቀረቡበት መሆኑን የክርክራቸው ይዘት ያመለክታል፡፡

የስር ፍርድ ቤት በትዕዛዙ ላይ እንደገለጸው አመልካች የብድር ዕዳው የተገባው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የነበረን ጋብቻ በስምምነት ከፈረሰ በኃላ በመሆኑ ዕዳው አይመለከተኝም ከማለት በቀር 2ኛ ተጠሪ የወሰዱት ብድር ለትዳር ጥቅም የዋለ አይደለም በማለት አልተከራከሩም፡፡የዚህ ዓይነት ክርክር በሰበር አቤቱታቸውም አላቀረቡም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ በአንቀጽ 71 በተመለከተው መሰረት ዕዳው ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ ግምት የሚወሰድበት ይሆናል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ እንደገለጹት ለአፈጻጸሙ የተያዘው ተሽከርካሪ አመልካች ከጋብቻው በፊት ያፈሩት የግል ሀብታቸው መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ዕዳው የመጣው ለትዳራቸው ጥቅም ነው እስከተባለ እና ለፍርዱ አፈጻጸም ሊውል የሚችል የ2ኛ ተጠሪ የግል ወይም የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብትም ቢሆን ለአፈጻጸሙ ሊውል የሚችል ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 70 (2) ድንጋጌ ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ሲጠቃለል በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘው የሰሌዳ ቁጥር 2-38341 ተሽከርካሪ ለአፈጻጸሙ ሊውል አይገባም በማለት አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 108770 በ09/04/2007ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 163553 በ15/05/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 108770 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ20/06/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ይጻፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠርክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102932

ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካቾች፡-1. አቶ አፈወርቅ ደርጫ ቀረቡ

2. አቶ አበባው ደርጫ ወኪል አንደኛ አመልካች ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሠራዊት ደርጫ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የአርባምንጭ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15601 ጥቅምት 29 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታህሣሥ 1 ቀን 2006 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 23114 የሰጠው ትዕዛዝና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03770 ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው የተከራከሩ ሲሆን፣ ጉዳዩ የውርስ ሀብት ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካቾች ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አመልካቾች ወላጅ እናታቸው ሟች ብዙነሽ በየነ በአርባ ምንጭ ከተማ ውሃ ምንጭ ቀበሌ በካርታ ቁጥር 2689 የሚታወቅና የቤት ቁጥሩ 911 የሆነ ቤት ሠርታ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየች መሆኑን ገልፀው፣ የቤቱ ግምት ብር 60,000 /ስልሣ ሺ ብር/ በመሆኑ ለተከሳሽ /ተጠሪ/ የሚደርሳትን ብር 20,000/ሃያ ሺ ብር/ ከፍለናት ቤቱን እንድታስረክበን ውሣኔ ይስጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርባ እናቷ ቤት ስትሠራ በገንዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያገዝኳትና ቤቱን በጋራ ተጋግዘን የሠራነው በመሆኑ የከሳሾች ክስ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ሟች ቤት ስትሠራ ተከሳሽ በግሏ አውጥቻለሁ የምትለው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ በውርስ አጣሪ በኩል ተጣርቶ እንዲቅርብለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የውርስ አጣሪው ተጠሪ ብር 13,284.50 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ሟች ቤት ስትሰራ ከግል ገንዘቧ አውጥታ እናቷን የረዳች መሆኑን በማረጋገጥ መግለጫ አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ከሳሾች/አመልካቾች/ ገምተው ካቀረቡት ብር 60,000 /ስልሣ ሺ ብር/ ውስጥ ተጠሪ ያወጣችው ብር 13284.50 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ተቀንሶ ብር 46715.50 /አርባ ስድስት ሺ ሰባት መቶ አስራ አምስት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ለአመልካቾችና ለተጠሪ/ሶስቱ ወራሾች እኩል ይካፈሉ፡፡ ተከሳሽ /ተጠሪ/ የአመልካቾችን ድርሻ ብር 31143.66 /ሰላሣ አንድ ሺ አንድ መቶ አርሳ ሶስት ብር ከስልሣ ስድስት ሣንቲም/ ከፍላ ቤቱን ታስቀር በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

2. አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በፎርም በሰጠው ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካቾች ሀምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ተጠሪ ቤቱ ስትሰራ አውጥቻለሁ በማለት የጠየቀችው ገንዘብ የአባታችን ገንዘብ እንጂ የተጠሪ ገንዘብ አይደለም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ከግል ገንዘቧ አውጥታለች በማለት ከውርሱ ንብረት ዋጋ ላይ ተቀንሶ እንድከፈላት የተሰጠው ውሣኔ እውነታውን የማያንፀባርቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች ያቀረብነው የዳኝነት ጥያቄ እኛ ለተጠሪ ድርሻዋን ከፍለናት ቤቱን ትልቀቅልን የሚል ሆኖ እያለ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ድርሻችሁን ትክፈላችሁና ቤቱን ታስቀር በማለት የሰጡት ውሣኔ፣ እኛ ያቀረብነውን የዳኝነት ጥያቄ ያላገናዘበና የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ እንዲሻርልን በማለት አመልክተዋል ፡፡

3. ተጠሪ ህዳር 5 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠችው መልስ ቤቱ እድሳት የተደረገበት በእኔ ገንዘብ እንደሆነ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ቤቱን እኔ ይገፍ ስኖርበት ቆይቻለሁ፡፡ ተጠሪ አዲስ ቤት በገንዘቤ ሠርቻለሁ፡፡ ቤቱን በአመልካቾች ፈቃድና ስምምነት የሰራሁ በመሆኑ ቤቱን መያዝ የሚገባኝ እኔ ነኝ፡፡ ቤቱን ብር 60,000/ስልሣ ሺ ብር/ ገምተው ያቀረቡት አመልካቾች ናቸው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀናልኝ በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካቾች ታህሣሥ 4 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ እናታችን ቤቱ ውስጥ ልጆቹ ይኑሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚል ኑዛዜ ትታለች፡፡ ተጠሪ አወጣሁ ያለችው ወጭ አመልካችዎች በሌለንበት የወጣ ዕውነትነት የሌለው ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ የአመልካችዎችን ድርሻ ከፍላ የውርስ ቤቱን እንድታስቀር የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በሟች ስም ያለውን የውርስ ቤት ለማደስ ጠቅላላ ዋጋው ብር 13284.50 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ያወጣች መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውርስ አጣሪ በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ አረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ የውርስ ንብረቱን ለማደስ ብር 13,284.50 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ከግል ገንዘቧ አውጥታለች በማለት የደረሰበትን መደምደሚያ፣ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተስማምቶበት በትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡ ይህም ተጠሪ የውርስ ቤቱን ለማደስ ብር 13,284.50 ከግል ገንዘቧ ማውጣቷ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካችዎች የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን የደረሱበት መደምደሚያ ስህተት መሆኑንና ቤቱ አባታቸው በላከው ገንዘብ የታደሰ መሆኑን በመግለፅ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም አመልካችዎች ያቀረቡት ይህ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር ለዚህ ሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 የተሰጠውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በሰበር አይቶ የማረም ሥልጣን ያላገናዘበና የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የውርሱን ንብረት ለማደስ ከግል ገንዘቧ ያወጣችው ብር 13,284.50 የውርስ ንብረት ክፍፍል ሲደረግ ሊተካለት ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረተዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

6. በዚህ መዝገብ መታየት ያለበት አከራካሪ የሰበር ጭብጥ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የአመልካችዎችን ድርሻ ከፍላ ቤቱን እንድታስቀር የተሰጡት ውሣኔ የውርስ ሃብት ክፍያ ደንቦችን የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ከሳሽ የሆኑት አመልካችዎች ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ፣ ከእናታቸው በውርስ ያገኙት ቤት ግምቱ ብር 60,000 መሆኑን ገልፀው ለተጠሪ ድርሻዋን ብር 20,000 /ሃያ ሺ ብር/ ከፍለናት ቤቱን እንድታስረክበን ይወሰንልን የሚል ይዘት ያለው መሆኑን ከወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ ተረድተናል፡፡ ይህም አመልካችዎች የውርሱን ንብረት ተጠሪ የእነርሡን ድርሻ ከፍላ እንድታስቀር የዳኝነት ጥያቄ ያላቀረቡ መሆኑንና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በበኩሏ ቤቱን ማስቀረት ያለብኝ እኔ ነኝ በማለት የተከራከረች መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም አከራካሪውን የውርስ ንብረት አመልካቾችና ተጠሪ ለማስቀረት ፍላጎት ያላቸው በሆነበት ሁኔታ የውርሱ ንብረት /ቤቱ/ የሚች ወራሾች እንዴትና በምን ሁኔታ ሊካፈሉ ይገባል የሚለውን ነጥብ መመርመር ይጠይቃል፡፡

7. የውርስ ንብረት የሚከፈለው በወራሾቹ መካከል በሚደረግ ስምምነት እንደሆነ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1089 ንዑስ አንቀፅ 1 የሚደነግግ ሲሆን ውርሱ በአይነት መከፋፈል ከሆነ ወራሾቹ የውርሱን ንብረት በአይነት የሚካፈሉ መሆኑ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1086 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡ የውርሱ ሀብት በአይነት ለመከፋፈል የማይችል በሆነ ጊዜና ከወራሾቹ መካከል ይህንን ሊካፈል የማይችለውን ንብረት ሊወስድ የሚገባው የትኛው እንደሆነ በስምምነት ለመወሰን ያልቻሉ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ ገንዘቡ ለወራሾቹ የሚከፋፈል መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1092 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች ከላይ በገለፅናቸው የውርስ ንብረት ክፍያ ደንቦች ሣይከተሉ፣ አመልካቾች ተጠሪ የውርሱን ቤት እንድታስቀር ባልተስማሙበት ሁኔታ፣ ተጠሪ የአመልካቾችን ድርሻ ከፍላ ቤቱን እንድታስቀር የሰጡት ውሣኔ ከላይ የገለፅናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚቃረንና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፣ በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአርባ ምንጭ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ፣ የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የውርሱን ንብረት ለማደስ ከግል ገንዘቧ ያወጣችው ብር 13,284.50 /አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ አራት ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ከውርስ ንብረት ዋጋ ተቀንሶ ለተጠሪ እንዲተካለት የሰጡት የውሣኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. የውርስ ንብረት የሆነውን ቤት ክፍያ በተመለከተ፡ ተጠሪ የአመልካቾችን ድርሻ ከፍላ ቤቱን እንድታስቀር በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

   3/ሀ/ የውርስ ንብረት የሆነው ቤት የሶስቱም ወራሾች ስለሚካፈልበት ሁኔታ አመልካቾች እና ተጠሪ የሚስማሙ ከሆነ ክፍያው በስምምነታቸው መሠረት እንድፈጽም በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1079 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ወስነናል፡፡

   /ለ/ አመልካቾችና ተጠሪ ቤቱ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ካልተስማሙና ቤቱ በአይነት ለአመልካቾችና ለተጠሪ ለመካፈል የሚችል ከሆነ፣ አመልካቾች ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቱን የጠገነችበትን ገንዘብ ሁለት ሶስተኛውን ለተጠሪ ከፍለው ቤቱን በአይነት እንዲካፈሉ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1086 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ወስነናል፡፡

/ሐ/ አመልካችዎና ተጠሪ ቤቱን ስለሚከፈልበት ሁኔታ ካልተስማሙና ቤቱ በአይነት ለወራሾቹ ለማካፈል የማይቻል ከሆነ ቤቱ በሀራጅ ከተሸጠ በኋላ፣ ተጠሪ የውርስ ቤቱን ለማደስ ያወጣችው ገንዘብ በመጀመሪያ ተከፍሎ፣ ቀሪውን የቤቱን ዋጋ አመልካችዎችና ተጠሪ ለሶስት እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1092 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1093 መሠረት ወስነናል፡፡

4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 108106

መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ አዱኛ ጉደታ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ በሻዱ ጉደታ - የቀረበ የለም

2. ወ/ሮ ባንቼ ጉደታ

3. ወ/ሮ መሉ ጉደታ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ፤ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጣልቃገብ ነበሩ፡፡ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ እናቴ ወ/ሮ ኩሊ ቦኩ በ10/03/04 ዓ/ም ባደረባት ህመም ሞተዋል፤ በህይወት በነበሩበት ወቅት በተለያዩ አካባቢዎች የመሬት ይዞታ የነበረ ሲሆን መሬቱ በአመልካች እጅ የሚገኝ በመሆኑ የሌሎች ወራሾች ድርሻ ወጥቶ ድርሻዬን ያካፍለኝ በማለት በመጠየቃቸው፤ አመልካች በሰጡት መልስ የግል እንጂ የውርስ ንብረት አይደለም፡፡ ከ1967 ጀምሮ ከእጄ ሳይወጣ ስጠቀምበት ቆይቻለሁ በማለታቸው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ይዞታው የቤተሰቦቻችን እንጂ የአመልካች ብቻ አይደለም በማለት ጣልቃ ገብተው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን በማከራከርና ምስክሮችን በመስማት ተጠቃሹ ይዞታ 6.5 ሄክታር መሆኑን እና ይዞታውም በሚቾች ስም የነበረ እና ከእናታቸው ሞት በኃላ (2004) መሬቱን አመልካች በልጃቸው ስም አስመዝግቦ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ መስተዳድሩ ጭምር በመግለፁ በገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ.130/99 አንቀጽ 16 እና በደንብ ቁ.151/2005 መሠረት ከሚቾች ጋር አብረው ሲኖሩ የነበሩት አሁንም እዛው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያሉት አመልካች ናቸው፡፡ ተጠሪዎች በአሁኑ ጊዜ ሌላ ቦታ ወጥቶ ያሉ በመሆኑ በይዞታው ላይ የቅዲሚያ መብት ያላቸው አመልካች በመሆኑ የተጠሪዎች ክስ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ በቀጣይነት ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤትም ተጠሪዎች የቤተሰብ አባል በመሆን በይዞታው ሲጠቀሙ ያልነበሩ ሲሆን አመልካች አሁንም በይዞታው እየተጠቀሙ በመሆኑ አመልካች ተጠቃሚ ሲሆኑ ይገባል መባሉ ባግባቡ ነው በማለት የስር ውሳኔን አጽንቶታል፡፡ በመጨረሻም ጉዳዩን ያየው የክልሉ ሰበር ችሎትም መዝገቡን በመመርመር፤ አመልካች ይዞታው የግላቸው መሆኑን እነጂ የቅድሚያ መብት እንዳላቸው አልተከራከሩም፤ ተጠቃሹም ደንብ ቢሆን ቅድሚያ የሚሰጠው አመልካች ድርሻን እንዲወስዱ እንጂ ተጠሪዎችን መብት የሚከለክል አይሆንም፣በመሆኑም አመልካች ለብቻቸው 6.5 ሄክተር ተጠቃሚ መድረጉ ከአዋጁ አላማ ውጭ በመሆኑም ተጠሪዎች ወራሾች በመሆናቸው እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ በመሆኑም አመልካችም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልፁ፡- ይዞታው የተጠሪዎች እናት ሳይሆን በአዋጅ ቁ.31/67 መሰረት በ1967 ዓ/ም በምሪት ያገኘሁት ነው፡፡ በስሜም ተመዝግቦ በእጄ ተለክቶ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ከተጠሪዎች ጋር ተካፈሉ መባሉ ባግባቡ አይደለም፡፡ በመሬቱ ብቸኛ ተጠቃሚ እና ከዚህ ገቢ የሚተዳደር መሆኔ እየታወቀ ከአዋጅ ቁ.130/99 አንቀጽ 9(2) ውጭ የተወሰነ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህም መሠረት ችሎቱ የደንብ ቁ.151/2005 አንቀፅ 10(10) መሠረት አመልካች የቅድሚያ መብት ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት አላነሳም ተብሎ መታለፉን በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙን በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በሰበር መልሳቸው የሚሉት፡- አመልካች ያቀረቡት መልስ ይዞታው የግላቸውና በ1967 በህግ ተመርተው ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን ነው፡፡ በምስክር እና በመስተዳደሩ የተረጋገጠው ግን የቤተሰባችን እና ሟች እስከ 2004 ዓ/ም ድረስ የሚጠቀሙ መሆኑን ነው? አመልካች ቤት ስለቀሩ እና እኛ ባል በማግባታችን የቤተሰባችን ንብረት ልናጣ አይገባም የደንብ ቁ151/2005 አንቀፅ 10(10) ትክክለኛ ፍቺ ያለማወቅ የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ሊፀና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በደንብ ቁ.151/2005 አንቀጽ 10(10) መሠረት ብቸኛ ተጠቃሚ መሆን ሲገባኝ ከተጠሪዎች ጋር ተካፈል መባሉ ሊታረም ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ይህን ይመስላል፡፡ እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አንፃር መዝገቡን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ያከራከረውን የይዞታ ጉዳይ እንዳየነው የአመልካች አብይ ክርክር የነበረው ይዞታውን በ1967 በአዋጅ በእጁ አስገብቹ ስጠቀምበት የነበረና የውርስ ንብረት ሳይሆን የግሌ ይዞታ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን ከክርክር ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ይዞታው የግራቀኙ ወላጅ እናታቸው እስከ እለተሞታቸው 2004 ዓ/ም ድረስ ስጠቀሙበት የነበረና አመልካች በልጃ ስም (በአስናቀ) ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን በመስተዳደሩ የተገለጸ ነው፡፡ እንግዲህ ከጅምሩም በአመልካች የውርስ መሆኑ ባልታመነበትና በክርክር ሂደት የተጣራ መሆኑ እየታወቀ በስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ይዞት ቆይቷል ቤተሰብ ሆኖ ሲጠቀምበት ነበር በማለት የክልሉን ደንብ ቁ.151/አንቀጽ 10(10) በመጥቀስ የቅድሚያ መብት ያለው አመልካች ነው በማለት ይዞታውን ጠቅልሎ እንዲወስድ በመወሰናቸው ምክንያት የክልሉ የሰበር ችሎት ጉዳዩን በማጣራት አመልካች ባላነሳው ክርክር የቅድሚያ መብት አለው ተብሎ 6.5 ሄክታር ለብቻው እንዲወስድ መወሰን የለበትም አከራካሪው ይዞታ የግራ ቀኙ ወላጆች መሆኑ እስከ ተረጋገጠ ድረስ ድርሻቸውን ሊነፈጉ አይገባም፡፡ ተጠቃሹ ደንብ ቁ. 151/ 10(10) ለአመልካች መብት ይሰጠዋል ቢባልም እንኳ እንዲቀር የመውሰድን እንጂ ተጠሪዎችን በማሳጣት ባጠቃላይ ይዞታውን ለአመልካች እንዲቀር የሚያደርግ ሊሆን ተደርጎ ሊቆረጎም የሚገባው አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማረም ተከራካሪዎች ከአመልካች ጋር እኩል ድርሻ አላቸው ተብሎ መወሰኑ ይህ ችሎትም የሚቀበለው ነው በአጠቃላይ አመልካች ከሟች ጋር እስከ 2004 ዓ/ም በመኖሩ ብቻ አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች ሌላ ገቢ ይኑራቸው አይኑራቸው ባልተረጋገጠበት አመልካች ቀድሞ ይዞ ወደ ልጅ ስም ማዞሩ ብቸኛ ተጠቃሚ ሊያደርገው አይገባም የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ 130/99ም ሆነ ተጠቃሹ ደንብ ቁ. 151/2005 በዚህ መልኩ ሊተረጎሙ የሚገባቸው አይደሉም፡፡

በመጨረሻም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የወረዳውን እና የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ተጠሪዎች በአከራካሪው የውርስ መሬት እኩል ድርሻ አላቸው ሲል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል የሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 32850 በቀን 1/7/06 ዓ/ም የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 22061 በ20/8/2006 የሰጡትን ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተሸሮ የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር እኩል ድርሻ አላቸው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የግራ ቀኙ የወጪ ኪሳራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.110022

ሐምሌ 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ትሻገር ምህረቱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት የሟች እናቴ የወ/ሮ ማሚቴ ደሳለኝ ወራሽ መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ ጥያቄው የቀረበለት አምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ በትዕዛዝ ውድቅ ያደረገው የሚወረስ ንብረት ስለመኖሩ ተጣርቶ የቀረበ ነገር የለም በማለት ሲሆን የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም እንደቅደም ተከተላቸው በፍርድ እና በትዕዛዝ ያጸኑት ይህንኑ ትዕዛዝ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ቀድሞ የወሰድኩት የወራሽነት ማስረጃ ስለጠፋብኝ በድጋሚ ወራሽነቴን ላረጋግጥ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት አጣርቶ ለመወሰን ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የአመልካች ጥያቄ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ መሰረት አመልካች ለወረዳው ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው በመጠየቅ ሲሆን ጥያቄውን ሊያቀርቡ የቻሉት ደግሞ የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ እንደማይነበብ ተደርጐ ስለተበላሸ መሆኑን በመግለፅ ያቀረቡት ክርክር የተመዘገበው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የቀድሞ የወራሽነት ማስረጃ የተሰጠበት መዝገብ ቁጥር 76/83 መጥፋቱ በመረጋገጡ ምክንያት ለአመልካቿ የቀድሞው የወራሽነት ማስረጃ ቅጂ እንዲሰጥ ማድረግ ያልተቻለ ስለመሆኑም ይግባኝ ሰሚው የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሣኔው ላይ አመልክቷል፡፡ በመሰረቱ ወራሽ የሆነው ሰው ለሟቹ ወራሽ መሆኑ እና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመለክቱ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጡት ዳኞችን ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 996(1) ይደነግጋል ፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እንዲሰጣቸው ጥያቄው ያቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ ብቻ ነው፡፡ ከውርሱ ላይ የሚያገኙት ድርሻ የሚያመለክት የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ የለም፡፡ አንድ ሰው ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመለክት የምስክር ወረቀት ጥያቄ መስጠት የሚቻለው ውርሱ እንዲጣራ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን የወራሽነት ማስረጃ ወይም የምስክር ወረቀት ለመስጠት ግን የውርስ ማጣራት ሂደት በቅድሚያ መከናወን የሚገባው ስለመሆኑ ሕጉ የሚጥለው ግዴታ የለም፡፡ ወራሽ የሆነው ሰው ለሟቹ ወራሽ መሆኑ እና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመለክት የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጡት ዳኞችን ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 996/1/ የተመለከተው ድንጋጌም የሚች ወራሽ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ ብቻ እንዲሰጠው ወይም ደግሞ ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ ጭምር የሚያመላክት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጠው የመጠየቅ አማራጭ ለጠያቂው ወገን የተተወ እንጂ ሕጉ ሁለቱም አይነት ማስረጃዎች ሊጠየቁ እና በፍርድ ቤት ሊሰጡ የሚችሉት ሳይነጣጠሉ በአንድነት ስለመሆኑ በአስገዳጅነት አልደነገገም፡፡ የወራሽነት የምስክር ወረቀት የማግኘት እና የውርስ ማጣራት ሂደት ሁለት የተለያዩ ሂደቶች ስለመሆናቸው እና የተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 996/1/ ድንጋጌው ውርሱ ካልተጣራ በቀር የወራሽነት ማስረጃ ሊሰጥ አይችልም በሚል አግባብ ሊተረጎም የሚገባው ስላለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35657 በ06/02/2001 ዓ.ም የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ለቀረበው ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታው የቀረበለት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 39306 በ11/03/2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 02827 በ08/05/2007 ዓ.ም በፍርድ እና በመዝገብ ቁጥር 202020 በ05/06/2007 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ውርሱ እንዲጣራ ሳይደረግ የወራሽነት የምስክር ወረቀት መስጠት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 996 (1) ድንጋጌ አይከለክልም በማለት ወስነናል፡፡
3. የአመልካቿን ጥያቄ አስተናግዶ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1)መሰረት ለአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
4. የውሣኔ ግልባጭ ተገቢውን መፈፀም ያስችለው ዘንድ ለአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲያውቁት ደግሞ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. ውሣኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105652

ቀን 30/11/2007ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲ.ር.ጋ.ጋ

አብርሃም መሰለ

አመልካቾች፡- 1ኛ. ወ/ሮ አሰፉ ዘለቀ

2ኛ. ወ/ሮ ብርቱካን ዘለቀ

3ኛ. ወ/ሮ ሰላማዊት ዘለቀ

4ኛ. ወ/ሪት አምሳሉ ዘለቀ

5ኛ. ወ/ሮ ተስፋነሽ ዘለቀ

6ኛ. ወ/ሪት ወርቁሀ ዘለቀ

7ኛ. ተማሪ ራሄል ዘለቀ

ጠበቃ አበበ ደጉ

ተጠሪ፡- አቶ ዳዊት በርሄ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የይርጋ ተፈጻሚነትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ሃዋሳ ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች በተጠሪ እና 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት ወላጅ እናታቸው ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የአመልካቾች የክስ ይዘት፡- ሟች አባታችን አቶ ዘለቀ ባዲቦ በንግድ ስራ ተሰማርቶ እያለ በሞት ሲለይ ለአቅመ ሄዋን አልደረስንም፡፡ እናታችን ሞግዚት ሆና የካቲት ወር 1988ዓ.ም ወራሽነታችንና የሷን ሞግዚትነት በፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ በአባታችን የውርስ ሃብት ስታስተዳድረን ነበር ተጠሪ የእናታችን ወንድም ልጅ በመሆኑ ቤተሰብ ነው፡፡ 1ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽ (ተጠሪ) ከ2ኛ ተከሳሽ (የአመልካቾች እናት) ጋር በመመሳጠር የውርስ ሃብታችን እንደሆነ እያወቀ በአመልካቾች የውርስ ሀብት ላይ የመዋዋል ስልጣን ሳይኖረው ሃምሌ 2ቀን 1999 ዓ.ም 2ኛ ተከሳሽ ከሆነችው እናታችን ጋር የስጦታ ውል እንደተዋዋሉ ተረድተናል፡፡ የስጦታ ውሉ በተደረገበት ጊዜ ሁለት አመልካቾች ለአቅመ ሄዋን አልደረስንም፡፡ 2ኛ ተከሳሽ ከንብረቱ ግማሹ የአመልካቾች የውርስ ንብረትን በስጦታ የማስተላለፍ ስልጣን አልነበራትም በራሷም መብት ሲሆን ልጆቿን አለአግባብ ከውርስ መንቀል አትችልም፡፡ በተጠሪው እና በ2ኛ ተከሳሽ (የአመልካቾች ወላጅ እናት) መሀከል የተደረገው የስጦታ ውል ለህግና ለሞራል ተቃራኒ እና 2ኛ ተከሳሽ የግል ንብረቷ ባልሆነ ንብረት ላይ የተደረገ የስጦታ ውል በመሆኑ በህግ ፊት የማይጸና ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልን፡፡ በ2ኛ ተከሳሽ ስም የተዘዋወረው ንብረት ስመ ባለቤትነት ተሰርዞ ወደ አመልካቾች ይዛወርልን የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም የሚል እና ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭ መልሳቸው ክርክር ያስነሳው ቤት በስጦታ ውል ለ1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) በተላለፈበት ጊዜ ንብረትነቱ በ2ኛ ተከሳሽ በስማቸው የባለሃብትነት ማስረጃ አውጥተው የአመልካቾች አባት ባለቤት ናት ወደ 2ኛ ተከሳሽ ከተዛወረ በኋላ የስጦታ ውሉ የተደረገ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ለህግም ሆነ ለሞራል ተቃራኒ ነው ሊባል አይገባም፡፡ 2ኛ ተከሳሽ ባለሃብትነቱን በስማቸው አዛውረው ለባንክ ያስያዙትን ንብረት እዳውን ከፍዬ ስጦታውን እንድቀበል ሳደርግ አመልካቾች ሳይቃወሙ የስጦታ ውሉ ተደርጎ 7ዓመት ከሆነ በኋላ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም የሚል ነው ፍ/ቤቱ በተጠሪ የተነሳውን መቃወሚያ በብይን አልፎ የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ለክርክር ምክንያት ከሆነው ሆቴል ግማሹን 50% 2ኛ ተከሳሽ ለተጠሪ በስጦታ ማሳለፋቸው ወይም መስጠታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአመልካቾች የውርስ ድርሻ የሆነውን ግማሹን 50% የአመልካቾች ያልተከፋፈለ የውርስ ሃብትን ጠቅላላው ለ1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) የሰጡ በመሆኑ የሥጦታ ውሉ በከፊል ይፍረስ፡፡ ወደ ነበሩበት መመለስ የማይቻል ስለሆነና ንብረቱን በስምምነት መካፈል የሚችሉ ከሆነ ይካፈሉ ካልቻሉ በሃራጅ ሽጠው እኩል ይካፈሉ ከባንክ በብድር የተወሰደውን ብር 600,000 አመልካቾች 300,000 ብር ለተጠሪ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኝ ቅሬታቸውን ለሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የለውም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 377 መሰረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በስር ፍ/ቤቶች በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ይታረምልኝ በማለት ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የተጠሪዎች (የአሁኑ አመልካቾች) ጥያቄ ይዘት በእናታቸው የተደረገ የሥጦታ ውል እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡ ተጠሪዎች ስጦታው ከተደረገበት ቀን አንስቶ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ያላቀረቡ በመሆኑ ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441(1) መሰረት በሁለት አመት ይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በዚህ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈጸመ ያሉትን መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመጥቀስ አመልካቾች አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ያስቀርባል የተባለው የአመልካቾች የስጦታ ውል ይፍረስልን ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441 (1) ውሉ ከተደረገ ጀምሮ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ አልቀረበም በይርጋ ይታገዳል የይርጋው ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 በ10ዓመት የይርጋ ጊዜ አይታይም መባሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው የግራ ቀኙን ክርክር ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንዲሁም አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር የአመልካቾች የመብት ጥያቄ የሚች አባታችን የውርስ ድርሻ እና በስር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ የሆነችው ወላጅ እናታችን የሚስትነት ድርሻ ያለበትን ንብረት የስር 2ኛ ተከሳሽ የወንድሟ ልጅ ለሆነው ተጠሪ በስጦታ ውል አሳልፋ መስጠት አትችልም የተደረገው የስጦታ ውሉ ለሞራል እና ለሕግ ተቃራኒ በመሆን ይፍረስልን የሚል ነው፡፡ አንድ ሰው በስጦታ ለሌላ ሰው መስጠት የሚችለው የራሱ የሆነውን ንብረት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2427 ተመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካቾች የስጦታ ውሉ ይፍረስልን በሚል ክስ የማቅረብ መብታቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441(1) መሰረት በሁለት አመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል በሚል የሰጠው ውሳኔ የተጠቀሰው የፍ/ሕግ ድንጋጌ መነሻ የሚያደርገው ፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 2439 ስለመንፈስ መጫን የሚለውን በመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በስጦታ ሰጪ ላይ በተደረገ የመንፈስ መጫን የተደረገ የስጦታ ውል ይፍረስልን የሚል ባለመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው ይርጋ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1845 የተመለከተው መሆን ሲገባው የፍ/ሕ/ቁ. 2441(1) ጠቅሶ የአመልካቾች አቤቱታ በሁለት አመት ይርጋ ታግዷል (ቀሪ ሆኗል) በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የደ/ብ/ብ/ከ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ር ሰበር 62649 በቀን 21/01/2007ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441(1) ሳይሆን በፍ/ሕ/ቁ. 1845 የተመለከተው ነው ብለናል፡፡
3. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ከይርጋ ክርክር ውጭ ባሉ በግራ ቀኙ ክርክሮች የመሰለውን ውሳኔ ይስጥበት ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ቅጂ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይላክ

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.109697

ቀን 30/11/2007

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃም መሠለ

አመልካች፡- ዘመ አስፋው አልቀረቡም

ተጠሪ፡- መሀመድ አስፋው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ይዞታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው አማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ሀብሩ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች በተጠሪ ላይ አቅርበውት የነበረው ክስ ይዘት አያቶቹ ከሆኑት ሟቾች አቶ አስፋው ሸኩር እና እናት ሠይድ ጋር በ1983 ዓ.ም መሬት በተሰጣቸው ወቅት በቤተሰብ አባልነት ተመዝግቤ እኖር ነበር፡፡ ለአያቶቹ በተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ላይ ስሜ በቤተሰብነት ተመዝግቧል፡፡ የቤተሰብ አባል ስለሆንኩ ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ ተጠሪ /ተከሳሽ/ ድርሻ ይዞታ መሬት ያካፍልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች መሬት የተተመነችው ከአያቶቿ ከእኔ ወላጆች ሳይሆን ከወላጆቿ ጋር ነው፡፡ የወላጆቼ ወራሽ በመሆኔ ይዞታው በስሜ ተዛውሯል አመልካች ለክስ ምክንያት ከሆነው መሬት ድርሻ የላትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ለክርክር ምክንያት በሆነው ይዞታ ደብተር ላይ በቤተሰብ አባልነት የተመዘገበች በመሆኑ እና የወራሽነት ማስረጃ ያቀረበች በመሆኑ ከተጠሪ ጋር መሬቱን የመካፋል መብት አላት ብሎ ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ያለውን ቅሬታ ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በይግባኝ አቅርቦ ግራቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ስር ፍ/ቤት ከሳሽ /የአሁኑ አመልካች/ የሚቾቹን ገቢ በቋሚነት እየተጋራች የምትኖር መሆኑን የራሷ ገቢ ያልነበራት መሆኑን ማጣራት ሲገባ ክክርክሩ መሬት እንደተቻለው መልስ ሰጭ በራሳቸው የሚተዳደሩ እና የራሳቸውን ገቢ ለማግኘት ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ከሚቾች በመለየት ሣውዲ አረቢያ የኖሩ መሆኑ ራሳቸው ያመኑት ፍሬ ነገር በመሆኑ በአ.ቁ.133/98 ለቤተሰብ አባል የተሰጠውን ትርጉም የማያሟሉ በመሆናቸው የሚቾችን መሬት በቤተሰብ አባልነት ስም ሊወርሱ አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ችሎት አያስቀርብም በማለት ተዘግቶባቸዋል፡፡

አመልካቿ በስር ፍ/ቤቶች ተፈፀመ ያሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመጥቀስ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲታረምላቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አቤቱታቸው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል የተባለው አመልካች በቤተሰብ አባልነት መመዝገቡ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግንዛቤ ከተወሰደ በኋላ ወደ ሣውዲ አረቢያ መሄዷን ብቻ ምክንያት በማድረግ ቋሚ ስራ እንዳላት አድርጐ መወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡

ግራቀኙ የፅሑፍ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ ጋር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች ስለክርክር ምክንያት በሆናቸው ይዞታ መሬት የይዞታ ደብተር ላይ በቤተሰብ አባልነት የተመዘገበች መሆኑ እና አረብ ሐገር እስከሄደችበት 1996 ዓ.ም ድረስ ከሚች አያቶቿ ጋር ትኖር የነበረ መሆኑ አረብ ሐገር እንዳለች አያቶቿ የሞቱ መሆኑ እና ከአረብ ሀገር ተመልሳ ለክርክር ምክንያት በሆነው መሬት ወራሽ መሆኗን በአዋጅ ቁጥር 133/98 እና ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀፅ 11/7//ሀ/ መሠረት በማረጋገጥ ማስረጃ ያቀረበች መሆኑ ደርሶናል ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች በ1996 ዓ.ም ከአያቶቿ ተለይታ ሣውዲ አረቢያ የኖረች መሆኑ ሌላ ማስረጃ ሳያስፈልገው አመልካች በአዋጅ ቁ.133/98 ለቤተሰብ አባል የተሰጠውን ትርጉም አታሟላም በማለት መደምደሚያ ላይ መድረሱ ከአዋጁ ትርጉምና ዓላማ የራቀ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ለጊዜው ወደ አረብ ሐገር መሄዷ በአዋጁ አንቀፅ 133/98 ለቤተሰብ ከተሰጠው ትርጉም ውጭ የሚያደርጉት አይሆንም ከአረብ ሐገር ከተመለሰች በኋላ ቀደም ሲል ስትኖርበት በነበረው ይዞታ መሬት ድርሻዋን ወስዳ በግብርና ለመተዳደር መብቷን ለማስከበር ያቀረበችው አቤቱታ አረብ ሐገር ሄዳ በመመለሷ ብቻ የራሷ መተዳደሪያ እንዳላት እና ለክርክር ምክንያቶች ከሆነው መሬት መጠቀሟ ተቋርጧል የቤተሰብ አባል አይደለችም። ለክርክር ምክንያት በሆነው መሬት ድርሻ የላትም ተብሎ መወሰኑ የክልሉን አዋጅ ቁ.133/98 ዓላማን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ በስር ከፍ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይህን ተከትሎ በይግባኝ እና በሰበር ችሎቱ የተሰጡ ውሳኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው ብለናል።

ው ሳ ኔ

1. የሰሜን ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.11603 በቀን 19-11-03 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በ/ይ/መ/ቁጥር 03-09093 በቀን 1/03/07 ዓ.ም እና ጠ/ፍ/ቤት በጠ/ፍ/ሰ/ይ/መ/መ/ቁ. 03-09714 በቀን 24/4/2007 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል። ብለናል።
2. የወረዳው ፍ/ቤት በመ/ቁ.11-902 በቀን 7/08/2006 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ --- ቁ.348/1/ መሠረት ፀንቷል ብለናል።
3. ግራቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል። የውሳኔው ትክክለኛ ቅጅ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ።
   - መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠዓሊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ.101378

ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ነገረ ፈጅ አርአያ ካሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ናሰው ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር -ጠበቀ ውቡ አስነቀው - ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 134164 ሚያዚያ 2 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 100813 ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የግንባታ ሥራ የመጨረሻ ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. ከሳሽ (ተጠሪ) የተከሳሹን የምስራቅ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትና የሰሜን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ህንፃ ሰርቶ ለማስረከብ ውል የተዋዋለና ከውሉ በተጨማሪ የስሚንቶ የብረትና የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ መሠረተ ልማት ባወጣው መመሪያ መሠረት ክፍያ እንደሚፈፀም መስማማቱን በደብዳቤ ቁጥር W5PP/861/08 ህዳር 23 ቀን 2001 ዓ/ም በደብዳቤ ገልፆልን ዋናውን ውል እንድንፈርም የቀረበልኝን ጥያቄ ተቀብዬ ውሉን በመፈረም በውሉ መሠረት የህንፃዎቹን ግንባታ አጠናቅቄ ህንፃዎቹን ለከሳሽ /አመልካች/ አስረክቤያለሁ ተከሳሽ ከሳሽ የሠራቸው ሥራዎች በተቆጣጣሪ መሀንዲስ ተረጋግጦ እየቀረበለት ክፍያ ሲፈፅም ቆይቷል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ሰኔ 26 ቀን 2004 ዓ/ም በአማካሪ መሀንዲስ ተረጋግጦ የቀረበለትን ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4,623,938.76 (አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሰባ ስድስት ሣንቲም) አልከፈለም፡፡ ከሳሽ ተከሳሹ ክፊያውን እንድፈፅም ማስጠንቀቂያ ብሰጠውም ያልከፈለ ስለሆነ ከሰኔ 26 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

2. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ተከሳሽ በዋናው ውል ያልተፈቀደ ለነዳጅ ለሲሚንቶና ብረት የዋጋ ጭማሪ የከፈለው ብር 1,829,661.15 (አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺ ስድስት መቶ ስልሣ አንድ ከአሥራ አምስት ሣንቲምና) እና ለተጨማሪ ሥራዎች የከፈለው ብር 3,696,219.55 (ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺ ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ አምስት ሣንቲም) የፋይናንስ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አሳውቋል፡፡ ስለዚህ ይኽ ገንዘብ ሊቻቻልልን ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሽና ከሳሽ የህንፃውን የመጨረሻ ርክክብ ያልፈፀመ በመሆኑ ከሳሽ የመጨረሻ ክፍያ ሊጠይቀኝ አይገባም የሚል የመከላከያ መልስ አቅርቧል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቷል የሥር ፍርድ ቤት የተከሳሽ (አመልካች) አማካሪ መሃንድስ ቀርቦ የሰጠውን የምስክርነት ቃል ከሰማ በኃላ አመልካች ያቀረበውን የመቻቻል ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የመጨረሻ ርክክብ ሣይደረግ ክፍያ አልከፍልም በማለት ያቀረበው ክርክር የህንፃ ሥራ ውሉ የሚተዳደርበት የኮንስትራክሽን ዘርፍ መመሪያ መሠረት ያላደረገ ክርክር መሆኑን ገልፆ ተከሳሽ ከሳሽ ለሠራውና ሥራው ተረጋግጦ በአማካሪ መሃንድሱ ፀድቆ የቀረበለትን ክፍያ የማይከፍልበት ህጋዊ ምክንያት የለበትም በማለት ተከሳሽ ከሳሽ በክሱ የጠየቀውን ገንዘብ ክስ በተመሠረተበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

4. አመልካች ግንቦት 28 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አማካሪ መሃንድስ ሳይወስን የተደረገው የዋጋ ንረት ስምምነት መሠረት የተከፈለው ክፍያና ለተጨማሪ ሥራ የተከፈለው ክፍያ የፋይናንስን ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ ተጠሪ ከቀረበው ጥያቄ ጋር ተቻችሎ ቀሪው ተራፊው እንዲመለስልን ያቀረብነው ጥያቄ አላግባብ ውድቅ ተደርጎብናል፡፡ ተጠሪና አመልካች የመጨረሻ ርክክክብ ሣያደርጉ የመጨራሻ ክፍያ እንድንከፍል የተወሰነው ውሳኔ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1757 ድንጋጌን የሚጥስ ነው፡፡ አመልካች ስህተቱን ማረም እንደሚችል ይኽ ሰበር ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም የበታች ፍርድ ቤቶች ማለፋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መስከረም 28 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪ ክፍያ የከፈለው ተጠሪ የሠራው ሥራ ተቆጥሮ፣ ተለክቶና ተረጋግጦ አማካሪ መሀንድሱ ባፀደቀው ክፍያ ሰነድ መሠረት ነው፡፡ አመልካች ያልተሠራ ሥራ የከፈለው ክፍያ የለም፡፡ የዋጋ ንረት ሥምምነቱም አመልካች ስምምነቱን ሰጥቶ የውል ግዴታ የገባበት ነው፡፡ ተጠሪ ከህግ አግባብ ውጭ ከአመልካች የተከፈለው ክፍያ ሌላ በመሆኑና አመልካች ያቀረበው ይቻቻልልኝ ጥያቄ የህግ ሥርዓቱን የማያሟላ ሆኖ በመገኘቱ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ የመጨረሻ ክፍያ የሚፈፅመው የህንፃው የመጨረሻ ርክክብ ሲደርግ ነው በማለት ተጠሪ ያቀረበው መከረከሪያ የህግ መሠረት የለውም አመልካች ህንፃዎቹን ተረክቦ እየተጠቀመ ይገኛል፡፡ በህንፃ ላይ ለሚከሰት ጉድለት ማስተካከያ የሚሆን የመያዣ ክፍያ ይዟል፡፡ ከዚህ ውጭ የመጨረሻ ክፍያ የመጨረሻ ርክክብ እስኪደረግ አልከፍልም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የሌለው ስለሆነ ውድቅ ይደረግልኝ፡፡ አመልካች ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ለዚህ ሰበር ችሎት ከግራ ቀኙ የቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የመቻቻልና የመጨረሻ ርክክብ ካልተፈፀመ የመጨረሻ ክፍያ እንድከፍል አልገደድም የሚል መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ለተጠሪ በክሱ የጠየቀውን ገንዘብ እንድከፍል የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

6. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ከአመልካች ጋር ህዳር 30 ቀን 2001 ዓ/ም የግንባታ ሥራ ውል ከመዋዋሉ በፊት የግንባታ ዕቃ ላይ በሚፈጠር የዋጋ ግሽበት ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች አሠሪው (አመልካች) የሚሸፍንበት ድንጋጌ በዋናው ውል እንዲካተት ህዳር 19 ቀን 2001 ዓ/ም ጥያቄ አቅርቦ፤ አመልካች ተጠሪ ባቀረበው ሀሳብ የሚስማማ መሆኑን ህዳር 23 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ በመግለፁ ህዳር 30 ቀን 2002 ዓ/ም በዋጋ ግሽበት ምክንያት በሚፈጠረው ጭማሪ ላይ ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች የጋራ መግባባት ኖሯቸው የግንባታ ሥራ ውሉ የተፈረመ መሆኑን አመልካችና ተጠሪ አልተካካዱም፡፡ የህንፃው አሰሪ የሆነው አመልካች በግንባታ ዋጋ ንረት የሚመጣን ጭማሪ ዋጋ ለመሸፈን ሙሉ ስምምነቱን ከሰጠ በኃላ፣ ስምምነቱን ከመሰጠቱ በፊት ያላሟላው ሥርዓት ያለ መሆኑ በኦዲተር በመተቸቱና አመልካች በተጨማሪ ሥራዎች እንዲሠሩ የሥራ ትዕዛዝ ሲሰጥና ክፍያ ሲፈፅም አንድ የአሠራር ጉድለት ያለ መሆኑ በድርጅቱ የበጀት አጠቀቀምና የፋይናንስ አያያዝና አወጣጥ ሥርዓት በመጀመሩ ኦዲተሮች መተቸቱ አመልካችና ተጠሪ ዋናውን የሥራ ውል ከመዋዋላቸው በፊት ባደረጉት የደብዳቤ ልውውጥ የተስማሙበትን የዋጋ ንረት ጭማሪ ክፍያ ስምምነትና በአመልካችና በአማካሪ መሀንዲስ በተሰጠው ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዝ መሠረት ተጠሪ ሥራው የግንባታ ሥራ መጠንና ጥራትና ዋጋ ተረጋግጦ ለሠራው ሥራ የተከፈለውን ገንዘብ ህገ ወጥ የማድረግ ውጤት የሚያስከትል አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው የግንባታ ዕቃዎች የዋጋ ንረት ጭማሪ ክፍያ ስምምነትና ተጠሪ በተሰጠው ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዝ መሠረት ለሠራው ተጨማሪ ሥራ የተከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ያቀረበው የመቻቻል ጥያቄ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀፅ 1 ገዥ መርህ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3252 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍተብሔር ህግ ቁጥር 3266 ንዑስ ድንጋጌዎች ይዘትና ህጋዊ ውጤት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

7. አመልካች ተጠሪ ግራ ቀኙ ካደረጉት ውል ውጭ በተጭበረበረ ሀሰተኛ የክፍያ ሰነድ ተጠሪ ክፍያ የወሰደ መሆኑን ወይም ተጠሪ በግንባታ ሥራ ውሉና ከውሉ ጋር በአባሪነት በተያያዘው የግንባታ ሥራ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ግንባታውን በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ባለማጠናቀቁና ግንባታው በመዘግየቱ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ኪሣራ ወይም ቅጣት ገንዘብ ያለ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው በቂ የህግና የክስ ምክንያት ያለው የበሰለ የመብት ጥያቄ ሳይኖር ከተጠሪ ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት በማድረግ ለተጠሪ የዋጋ ንረት ጭማሪ ክፍያና የተጨማሪ ሥራ ክፍያ ተጠሪ እንዲመለስ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የፍተብሔር ስነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 236 እና በፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 238 ንዑስ አንቀፅ 2 መስፈርት የማያሟላ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የቀረበውን የመቻቻያ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 30 እና የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሠረት ከተጠሪ የሚጠይቀውን የገንዘብና ተጠሪ ገንዘቡን እንዲመልስ ኃላፊ የሚሆንበትን ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ኃላፊነት በመግለፅ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አላቀረበም፡፡ በመሆኑም አመልካች አለኝ የሚለውን መብት በፍርድ ለማስወሰን ሕጉ የዘረጋቸውን ሥርዓት ያሟላ ክርክርና የመብት ጥያቄ ያላቀረበ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

8. አመልካች አማካሪ መሀንድሱ ለተጠሪ ያፀደቀለትንና ተጠሪ ክስ ያቀረበበትን የመጨረሻ ክፍያ የህንፃው የመጨረሻ ርክክብ ከመደረጉ በፊት የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት ያቀረብኩት ክርክር ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል የሰበር አቤቱታና ክርክር አቅርቧል፡፡ ይህንን የአመልካችን ክርክር ህጋዊነት ለመመርመር አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የሥራ ውል ልዩ ሁኔታና የግንባታ ሥራው የሚመራበትን ጠቅላላ ሁኔታ እንደዚሁም ስለ መጨረሻ ርክክብና የክፍያ አፈፃፀም የተደነገጉትን አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች መመርመር ያስፈልጋል፡፡

9. አመልካች ተጠሪ የገነባቸውን ህንፃዎች ተረክቦ እየተገለገለባቸው መሆኑን ግራ ቀኙ በሥር ፍርድ ቤትና ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ያሳያል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው ልዩ የግንባታ ሥራ ውል ሁኔታ፣ ለህንፃው ተቋራጭ ለተጠሪ የመጨረሻው ክፍያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚከፈለው የህንፃው የመጨረሻ ርክክብ ከተፈፀመ በኃላ መሆኑን ተስማምተው ስምምነታቸውም በውሉ ልዩ ሁኔታ ውስጥ የተገለፀ መሆኑን በመግለፅ የቀረበው ክርክር የለም እንደዚሁም አመልካች ህንፃውን በጊዚያዊነት ከተረከበ በኃላ በህንፃው ላይ የሚታይ ጉድለት መኖሩንና በህንፃው ላይ የሚታየውን ጉድለት ለማስተካከል በግንባታ ሥራ ውሉና በግንባታ ሥራዎች ላይ ተፈፃሚነት ባላቸው ደንቦች መሠረት በየወቅቱ ተጠሪ ከሚከፈለው ክፍያ እየቀነሰ በመያዣነት የያዘው የጉድለት ማስተካከያ የመያዣ ገንዘብ የሚይበቃው መሆኑንና ጉደለቱን ለማስተካከል ለተጠሪ ከሚከፈለው የመጨረሻ ክፍያ ክፊሉን ወይም ሙሉን የሚጠይቅ ስለመሆኑ የቀረበው ክርክር የለም፡፡

10. አመልካች ከላይ የተገለፁትን ሁለት መከራከሪያዎች ሳያቀርብ ተጠሪ ህንፃዎቹን ሥራ ለማጠናቀቅና ህንፃዎች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የሥራው የማጠናቀቂያ ሥራዎች መጠንና ጥራት ዋጋ በአማካሪ መሀንድሱ ተረጋግጦ የፀደቀውን ክፍያ አልከፍልም በማለት ይዞ የሚቆይበት በቂ ምክንያት ያለው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር ክፍያ ለመፈፀም ተጠሪ የሠራቸው ሥራዎች አመልካች በመደበው አማካሪ መሀንድስ መመርመር መለካትና በሥራው የሚከፈለው ነጠላዎች ጥቅል ዋጋ በአማካሪ መሀንድስ ፀድቆ መቅረቡ አስፈላጊ ሁኔታ መሆኑን አመልካችና ተጠሪ ከተዋዋሉት የግንባታ ስራ ውል እና ግራ ቀኙ ከሚያቀርቡት ክርክር የተረዳ መሆኑን ገልፆ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔው አስፍሮታል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ተጠሪ ሥራውን ከሠራ በኃላ ክፍያ ለመፈፀም አስፈላጊ የሆነውን የምርመራና የማረጋገጡ ሥራ በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ መፈፀምና ክፍያውም የምርመራና የማረጋገጡ ውጤት እንዲታወቅ መፈፀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 3268 ድንጋጌዎች እና የመሠረተ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር 1996 ዓ/ም አሻሽሎ የወጣውን የመንግስት ግንባታ ሥራ አፈፃፀም መምሪያ አንቀጽ 8 በጣምራ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከላይ ከጠቀስናቸው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ አመልካች የመጨረሻ ርክክብ ሣይደረግ ለተጠሪ የመጨረሻ ክፍያ የመፈፀም ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

11. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ተጠሪ የገነባቸውን ህንፃዎች ለተጠሪ አስረክቦ ህንፃዎቹ በተጠሪ ቁጥጥርና ይዞታ ስር ሆነው እየተገለገለባቸው እንደሚገኝ ተረጋግጧል አመልካች ከተጠሪ ጋር የመጨረሻ እርክብክብ ለማድረግ ያላስቻለው በቂ ምክንያት ያለ ስለ መሆኑ በክርክሩ አልገለፀም፡፡ የህንፃው የመጨረሻ ርክብክብ ተጠሪ ስለሚፈልገው የሚፈፀም ተግባር አይደለም፡፡ አመልካች የመጨረሻ እርክብክብ በማድረግ ሊስተካከል ይገባቸዋል የሚላቸውን ጉድለቶች ለተጠሪ የማሳወቅ እንዲስተካከሉ ማድረግና ርክብክቡን በህጉ መሠረት ለመፈፀም ፍቃደኛና ዝግጁ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡ ተጠሪ በገነባቸው ህንፃዎች ላይ ለሚከሰት የአሠራር ጉድለት አመልካች ህንፃዎቹን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አስር ዓመት መድህንና ኃላፊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚሆን በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3282 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል ይህም አመልካች የመጨረሻ ርክክብ ለመፈፀም ያጋጠሙትን ችግሮች ሣያስረዳ የመጨረሻ ርክክብ ሣይደረግ ቀሪ ክፍያ አልከፍልም የሚለው ክርክር ህጋዊ ዕውቅናና ውጤት ከተሰጠው በአራቱ የሚገኙ የሥራ ተቋራጮች ከባንክ ወይም በሌላ መንገድ ያገኙትን ካፒታል በመጠቀም ለሠሩት ሥራ ወዲያውኑ ክፍያ እንዳያገኙ የማያደርግና ይህም በምላሹ በህንፃ ተቋራጩና በኮንስትራክሽን እንዱስትሪ ላይ የፋይናንስና የኢንቨስትመንት እጥረት እንዲከሰት የሚያደርግ ይሆናል፡፡ የሥራ ተቋራጩ በሠራው ህንፃ ላይ የተከሰተ እርግጠኛ የአሠራር ጉድለት በሌለበት ሁኔታ ወደ ፊት የሚታይና የሚከሰት የአሠራር ጉድለት ሊኖር ይችላል በሚል መነሻና ግምት ሥራ ተቋራጮች ለሠሩት ሥራ የመጨረሻ ክፍያ የማግኘት መብት አግባብ መከልከል ገንዘቡ በህንፃ አሠሪዎች በእጅ ያለ በቂ ምክንያት ታስሮ እንዲቀመጥ የሚያደርግና የህንፃ ተቋራጩን በፍትሐብሔር ጉዳይ ማንም ሰው ኃላፊ ነው ተብሎ ያለመገመት /presumption of non liablity) መሠረታዊ መርህ የሚጥስ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የመጨረሻ ርክክብ ያልተፈፀመ በመሆኑ ተጠሪ የጠየቀውን ክፍያ መክፈል የለብኝም ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በትዕዛዝ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

12. አመልካች ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57049 የሰጠውን የሕግ ትርጉም በመጥቀስና ለሥር ፍርድ ቤትና ለዚህ ሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ ሆኖም በሰበር መዝገብ ቁጥር 57049 የተነሳው የተረጋገጡ የፍሬ ጉዳይና የህግ ጭብጦች ከዚህ መዝገብ ጋር ተመሣሣይነት የሌላቸው ናቸው በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57049 የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመግለፅ የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በትዕዛዝ ማፅናቱ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከላይ በዝርዝር ለገለፅናቸው ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ ለሠራው ሥራ መክፈል የሚገባውንና በክሱ የተገለፀውን ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ይህ ፍርድ ቤት ግንቦት 29 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ የተነሳ መሆኑ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ረታ ቶሎሳ
ሙስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ከበደ ተሰማ } ጠበቃ አቶ ሰለሞን ሐብቴ ቀረቡ
2. ወ/ሮ መሰሉ አበበ }

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ፀሐይነሽ ገ/አምላክ - ቀረቡ
2. አቶ መኮንን ኃ/ጽዮን - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የይርጋ ድንጋጌዎችን አፈፃፀም የሚመለከት ነው። ለይርጋ ድንጋጌዎች አፈፃፀም መነሻ የሆኑት የፍሬ-ነገር ክርክሮች ሁለቱም ወገኖች እንደ ክርክር አቅጣጫቸው በስር ፍ/ቤቶች አቅርበዋል።

እኛም በዚህ ረገድ ግራ ቀኙ በሥር ፍ/ቤቶች ሲከራከሩ በክርክር ሂደት በስር ፍ/ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች በመነሳት ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የይርጋ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የድንጋጌዎችን አፈፃፀም እንደሚከተለው መርምረናል።

የጉዳዩ መነሻ የሆነው ክስ በአሁን ተጠሪዎች በፌዴራል የከፍተኛ ፍ/ቤት አማካኝነት የቀረበው ሲሆን፤ ይዘቱም በድንገት ወደ ኤርትራ ስወጣ በአ/አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 20 በቤት ቁጥር 2024 በካርታ ቁጥር 12926 የታወቀውን እና በ520 ሜትር ካሬ ስፋት በ175 ሜትር ካሬ ላይ ያረፈውን ባለ ቤዝመንት ባለ አንድ ፎቅ ከፅቃው ጋር ለአሁን 1ኛ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውክልና አስረክቤ ከአገር ከወጣሁ በኋላ በግንቦት 01/2001 መንግስት ባወጣው መመሪያ መሰረት ወደ አገር ተመልሼ እንዲያስረክበኝ ብጠይቀው ንብረቱን ለመሸጥ ያስገደደው ሁኔታ ሳይኖር በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2208 እና 2211 ከተደነገገው ውጭ ሚስቱ ለሆኑት ለአሁን 2ኛ አመልካች በብር 380,000.00 /ሶስት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር/ በሆነ ዋጋ በሽያጭ ስም የእራሳቸው የጋራ ያደረጉ በመሆኑና እንደገናም ሁለቱም በአንድነት ሆነው ጥር 19 ቀን 2000 ዓ.ም በብር 3,300,000.00 /ሶስት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺህ ብር/ በስር ፍ/ቤት ሁለተኛ ጣልቃ ገብ ለሆኑት ለወ/ሮ ደስታ ተመስገን ሸጠው የተጠቀሙ ስለሆነ ሁለቱም የሽያጭ ውሎች ፈራሽ ሆነው ንብረቱ ካስገኘው የኪራይ አላባ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካቾችም ለቀረበባቸው ክስ በመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ክርክርነት ካቀረቧቸው የመከራከሪያ ነጥቦች አንዱ ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው የይርጋ ክርክር ሲሆን ይዘቱም ከሀገር እንዲወጡ ባደረገው መመሪያ መሰረት ንብረቱ በወከላቸው በአሁን 1ኛ አመልካች አማካኝነት የተሰጠው ጥቅምት 01 ቀን 2003 ዓ.ም ነው፡፡ በነበረን የስልክ ግንኙነት እንዲያውቁትም ተደርጓል፡፡ የውል ይፍረስልኝ ክስ የቀረበውም ታህሳስ 12 ቀን 2003 ዓ.ም ስለሆነ ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845 መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው የሚለውን በመጥቀስ የቀረበ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ከዚህ በላይ በተመለከተው የይርጋ ጉዳይ ላይ ተመርኩዞ

1ኛ ተከሣሽ የነበሩት የአሁን አመልካች በተሰጣቸው ልዩ የውክልና ስልጣን መሰረት ንብረቱን የሸጡት ጥቅምት 01 ቀን 1993 ዓ.ም ሆኖ እያለ ይህንኑ የሽያጭ ውል ለማስፈረስ ክስ የቀረበው ደግሞ ታህሳስ 12 ቀን 2003 ዓ.ም ስለሆነ በሁለቱ ጊዜያቶች መካከል ያለፈው ጊዜ ሲሰላ የ10 ዓመት ጊዜ አልፎታል 1ኛ ተከሣሽ የፈፀመውን የሽያጭ ድርጊት በመቃወም የሽያጭ ውሉን ለማስፈረስ የሚቀርበው ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 መሠረት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ሲገባው ይህ ጊዜ ካለፈ በኃላ የቀረበ ክስ ሆኖ ስለተገኘ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ብይን ሰጥቶበታል፡፡

ይህንኑ ብይን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የሥር ፍ/ቤት ስለይርጋው ክርክር የሰጠውን ዳኝነት አግባብነት በሚመለከት ጉዳዩን መርምሮ፤

1ኛ አመልካች ስለ ቤቱ ጉዳይ ልዩ የውክልና ስልጣን የተሰጠው ለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም ሆኖም በዚህ የውክልና ስልጣን መሠረት ተክቶ ቤቱን የሸጡ መሆኑ ከሣሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ወደ ኢትዮጵያ ሐገር ከመግባታቸው በፊት ሻጩ ያሣወቋቸው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ 1ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ቤቱ መሸጡን ያወቁት ኢት/ያ ውስጥ ከገቡ በኃላ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ስለመሆኑ በማስረጃ ያልተደገፈ እና ማስተባበያ ያልቀረበበት ስለሆነ ቤቶቹን መሸጡን ካወቀበት፤ ወደ ሀገር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከተመሠረበት እስከ ታህሣስ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ያለው ጊዜ ሲሰላ 6 ወር ብቻ መሆኑን 10 ዓመት ይቀርና 1 ዓመት የሞላው አይደለም ስለዚህ ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን ሽሮ በቀሪዎች ክርክሮች ላይ አስፈላጊውን ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት መዝገቡን በመመለስ ዳኝነት ሰጥቶበታል፡፡

ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውም ይኸው የጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ በጉዳዩ ላይ የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ሲሆን የዚሁኑ ፍርድ አግባብነት ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ባቀረቡት የጽሑፍ ክርክር እና ከላይ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች ከተሰጠው ዳኝነት ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ በሆነው ክሣቸው ላይ ለክሱ መሠረት አድርገው ያቀረቡት የክስ ምክንያትና ለጠየቁት ዳኝነት እንደ ክሣቸው በማስረጃ ቢያረጋገጡ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ክፍል በውክልና ሕግ ሥር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2187 እና 2188 የተመለከተውን ስለመሆናቸው በክሣቸው ዝርዝር የጠቀሷቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2208 እና 2211 ጠቅሰው ማቅረባቸው አስረጂ ከመሆኑም በላይ ተወካዩ ከቤቱ ትክክለኛ ዋጋ በታች ለሚስታቸው ሸጠው የጋራ ተጠቃሚ ከሆኑ በኃላ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ዋጋ መልሶ ለሶስተኛ ወገን ሸጠዋል የሚለው የፍሬ ነገር ክርክራቸውም አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም በግራ ቀኙ መካከል ለተነሣው የይርጋ ክርክር ጉዳይ አግባብነት እና ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ በውክልና ሕግ የተመለከተው የፍ/ሥ/ሕ/ቁ. 2187 እንጂ ውሎች በጠቅላላው በተመለከተው የሕግ ክፍል የሚገኘው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1845 ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህም ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ድንጋጌ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2187 ድንጋጌ መሠረት ተወካዩ የጥቅም ግጭት ባለበት አካኃን የፈፀመውን ተግባር ለማስፈረስ ወካዩ ይኸው ድርጊት መፈፀሙን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ተመልክቷል፤

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የቀረበለትን የይግባኝ ጉዳይ ተመልክቶ ዳኝነት በሚሰጥበት ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ የክርክር ሂደት በሙግት የክርክር ደረጃ በግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች ከቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ የተረጋገጠበትን ፍሬ ነገሮች ለይቶ ለማውጣት በተሰጠው ማስረጃን የመመዘንና የማስረጃን የማስረዳት ክብደት የመለካት ዳኝነታዊ ተግባሩ ተጠቅሞ የአሁን ተጠሪ ቤታቸው የተሸጠ መሆኑን መቼ አወቁ መቼ ተረዱ? የሚለውን ለድንጋጌው አፈፃፀም መነሻ የሆነው የፍሬ ጉዳይ ያረጋገጠው መሆኑን ተረድተናል፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ረገድ የአሁን አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ እንዲታረምላቸው ያቀረቡት እና የጠየቁት ክርክር እና ዳኝነት ከላይ በተመለከተው የፍሬ ነገር እና ማስረጃ ጉዳይ ላይ ያተኮረ እንጂ ከህግ ጥያቄ ጋር የተገናኘ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ሊታገድ የሚችል አይደለም በሚል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፤

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ77515 ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ፀንቷል፡፡
2. ስለይርጋ ጉዳይ የአሁን አመልካች ያቀረቡት ክርክር የህግ መሰረት ያለው ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤
3. የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፤

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፤

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ል/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.99634

ሰኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ተስፋዓለም አረፋ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አማረች ጉደታ ┐ ጠበቃ እዮኤል ጀረነ -ቀረቡ
2. አቶ ጫላ ኃይሌ ┘

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 181329 ሚያዝያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 135064 ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ በአፈፃፀም የተሰጠን ትእዛዝ ህጋዊነት የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ የአፈፃፀም ከሳሽ ፣አመልካች የአፈፃፀም ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

1. የፍርድ አፈፃፀም ሂደቱ ወደ ፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ከተመራ በኃላ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ፍርዱን ለማስፈጸም እየተከተለ ያለው ሂደት ተገቢነት የሌለው ስለሆነ፣ሂደቱ እንዲለወጥ ትእዛዝ ይሰጥልን በማለት ለሥር ፍርድ ቤት አመልካች /የፍርድ ባለዕዳ/ ጥያቄ አቅርቦ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ሚያዝያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ አፅንቶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች ሚያዝያ 3 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ውሳ ፈርሶ አመልካችና ተጠሪዎች ወደነበርንበት እንድንመለስ ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ይህም ውሣኔ የተሰጠው እኔ ድርጅቱን ከተረከብኩበት ሚያዝያ 24 ቀን 1998 ወዲህ ልዩ ልዩ ንብረቶችን በቦታው በማስፈር ምክንያት ነው የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሚያዚያ 24 ቀን 1995 በቦታው ላይ ያሰፈርኩትን ንብረት ዘርዝሬ እንዳቀርብ ካደረገ በኃላ በቦታው ላይ አመልካች አፍርቻለሁ በማለት የጠየቅሁትን ንብረት በተመለከተ አዲስ ክሰ አቅርቤ እንድጠይቅ የሰጠው ትአዛዝ የሰበር ችሎት የሰጠውን ውሣኔ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንድታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በእኛና በአመልካች መካከል ተደርጎ የነበረው የድርጅት ሽያጭ ውል ከማድረጋችን በፊት ወደ ነበርንበት ሁኔታ እንድንመለስ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡አመልካች ድርጅቱን ከእኛ የተረከበው ድርጅት እንጂ ባዶ ቦታ አይደለም ስለዚህ ፍርድ አፈፃፀም መምሪያ አመልካች ድርጅቱን ከእኛ ከተረከበ በኃላ ያፈራው ንብረት የሌለ መሆኑን በማረጋገጥ ድርጅቱን ለእኛ እንዲያስረክብ የተሰጠው ትእዛዝ በዋናው ጉዳይ የተሰጠውን ፍርድ መሠረት ያደረገና የሕግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ የሰበር አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግልን በማለት አመልክተዋል፡፡አመልካች ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

3. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ በዋናው ጉዳይ የተሰጠውን ፍርድ ይሽ ከሰበር ችሎት የሰጠውን ውሣኔና አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

4. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪዎች ሻጭ አመልካች ገዥ በመሆን ሚያዚያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም የቡልኬት ማምረቻ ድርጅት ውል ተዋውለው የነበረ መሆኑንና በአንደኛ ተጠሪ ክስ አቅራቢነት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 152619 ህዳር 12 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ፍርድና ውሣኔ የድርጅት ሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ ስም የሚገኘውን የሲሚንቶ ውጤቶች አምርቶ መሸጫ የንግድ ድርጅት ከሚያዝያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት ከነበረበት ሁኔታ በአንደኛ ተጠሪ/ከሳሽ/ እንዲያስረክብ ከሳሽ አንደኛ ተጠሪ በቅድሚያ ክፍያ የወሰዱትን ብር 10,000/አሥር ሺ ብር / እስከ ቀረበበት ሀምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ግምት ወለድ ጋር ለተከሳሽ / አመልካች/ እንዲከፍሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

5. ከዚህ በኃላ አንደኛ ተጠሪ ድርጅቱን ከቦታው ላይ ካለው አጥርና ቤት ድረስ እንድረከብ ትእዛዝ ይሰጥልኝ የሚል ጥያቄ አቅርባ ውሉ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ይመለሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተባለ እንጅ ከሳሽ በተከሳሽ የተመራን ንብረት ሊረከቡ አይገባም በማለት በመዝገብ ቁጥር 152619 የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት በተከሳሽ /በአሁን አመልካች/ ጥያቄ አቅራቢነት፣አመልካች ሚያዚያ 24 ቀን 1998 በተደረገው ውል የገዛው የድርጅት ቦታ እንጅ ንብረት የሌለበት በመሆኑ ውሣኔውን በዚህ መልኩ እንዲፈፅም በማለት ታህሣሥ 22 ቀን 2003 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

6. የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት አንደኛ ተጠሪ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው፣የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በመዝገብ ቁጥር 108282 ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በማፅናቱ አንደኛ ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች፡፡ይህ የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር በሰበር መዝገብ ቁጥር 72262 ሀምሌ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ፍርድ ሰጥቷል፡፡ይህ የሰበር ችሎት በሰጠው ፍርድ የሥር ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመብት /አንደኛ ተጠሪን/ ክርክር ሣይሰማ ታህሣሥ 18 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝ በማረም ታህሣሥ 24 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን የመጀመሪያ ጭብጥ አድርጎ በመያዝ ፍርድ ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ከሚያዝያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ የያዘውን ንብረት የማስረከብ ግዴታ ያለበት መሆኑንና ሌሎችን ጉዳዬች በተመለከተ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 392/1/ መሠረት ማዘዝ እንደሚገባቸው ገልፃ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡትን የአፈፃፀም ትእዛዝ ሽሮታል፡፡

7. ከዚህ በኃላ አፈፃፀሙን የቀጠለው የሥር ፍርድ ቤትና ፍርዱን የሚያስፈፅመው የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 152619 የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 108282 ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠውን ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ በመሻር የአሁኑ አመልካች /ተጠሪ/ ለአመልካች ለማስረከብ የሚገደዱት ከሚያዝያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት በሽያጭ ውል ምክንያት የያዙትን ንብረት ነው በማለት በመዝገብ ቁጥር 72262 ሀምሌ 2 ቀን 2004 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት አጣርቶ አመልካች ለተጠሪዎች ቦታ ብቻ ሣይሆን በቦታው ላይ ያለውን ንብረት እንዲያስረክብና አመልካች ሚያዝያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በቦታው ላይ አፍርቻለሁ የሚለውን ንብረት ውሃና መብራት ለድርጅቱ ወጭ አውጥቼ አስገብቻለሁ የሚሉትን በተመለከተ በሌላ መንገድ ይጠይቁ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

8. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው የድርጅት ሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ በፍርድ ተወስኗል፡፡አመልካች የገዛሁት ባዶ ቦታ ስለሆነ እንድመልስ የምገደደው ባዶ ቦታ መሆን አለበት በማለት ጠይቆ ፣ይህንን ጥያቄውን የሥር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ታህሣሥ 24

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች በሽያጭ ያስረከብኩትን ድርጅትና ንብረት እንድረከብ ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበችውን ጥያቄ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ በማድረግ የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በዚህ ሰበር ችሎት ተሸሮ አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች የሸጠችውን ድርጅትና ንብረት የመረከብ መብት ያላት መሆኑ ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡ከዚህ አንፃር አመልካች በቦታው ላይ በራሱ ወጭ ያፈራሁት ንብረት አለ በማለት የሚከራከር ቢሆንም፣ይህ የአመልካች ክርክር ጥያቄ በፍርድ ባለመብቷ አንደኛ ተጠሪ የታመነ አይደለም፡፡

9. አመልካች ድርጅቱን ሚያዚያ 24 ቀን 1998 ከተረከበ በኃላ ድርጅቱ ውሃ መብራት ለማስገባት ያወጣው ወጭ አለ ወይስ የለም?አመልካች ድርጅቱን ከተረከበ በኃላ በገንዘቡ የሠራው የግንባታ ሥራ አለ ወይስ የለም?አመልካች የሠራው የአጥርና የቤት ግንባታ ሥራ አለ ቢባል በአመልካች የተሠሩ ሥራዎች በወቅቱ በነበረው የግንባታ ዋጋ ምን ያህል ያወጣሉ?የሚሉት ጭብጦች በአፈፃፀም ሂደት በተደረገው ማጣራት ግልፅ የሆነ ምላሽ ለማግኘት የማይቻል በሆነ ጊዜና እነዚህ ጭብጦች የግራ ቀኙን ሙሉ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ ሊወሰኑ የሚገባቸው ሆነው አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ቢያገኛቸው አመልካች ቦታው ላይ ካለው ንብረት ጋር ድርጅቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ ትእዛዝ በመስጠት የፍርድ ባለዕዳው የፍርድ ባለመብት ከተረከባቸው ንብረት ውስጥ ሚያዚያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በኃላ በአመልካች ወጭ ያወጣበትና የተሠራ ነው የሚለውን ራሱን የቻለ ክስ አቅርቦ እንድጠይቅ የሰጠው ትእዛዝ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር.392 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መሠረታዊ ዓላማ ያገናዘበ የአፈፃፀም ትእዛዝ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. አመልካች ድርጅቱን ከተረከበ በኃላ ለመብራትና ለውሃ አውጥቻለሁ ያለው ወጭ ሠርቻለሁ የሚለው ተጨማሪ ግንባታ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠውን ውሣኔ የማያስለውጥ ወይም የፍርዱን ተፈፃሚነት የሚያስቀር ምክንያት አይደለም በአንፃሩ ውሉ ከመፍረሱ ወይም ከመሰረዙ በፊት የተነሳ ንብረት የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰው ንብረቱን ለውጦ ወይም በዚሁ ላይ ወጭ አድርጎ እንደሆነ ከዚህ መለዋወጥ ወይም ወጭ የተነሳ ያሉት መብቶች ወይም ግዴታዎች በዚህ ሕግ አላግባብ በመበልፀግ በሚመለከተው ምዕራፍ ውስጥ በተወሰኑት ድንጋጌዎች መሠረት የሚመራ መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1818 በግልፅ ተደንግጓል፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የአፈፃፀም ትእዛዝ አመልካች ውሉ ፈርሶ ተጠሪዎች ድርጅቱን በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረት ሲረከቡ፣እሱ ድርጅቱን ሚያዝያ 24 ቀን 1998 ሲረከብ ያልነበረ ንብረት ወይም በአመልካች ወጭ መብራትና ውሃ የገባ ተጠሪዎች አላግባብ የበለፀጉ መሆኑን በዝርዝር ገልፆ መብቱን እንዲጠይቅ የሚያመላክትና ውሉ ፈራሽ በመሆኑ አመልካች በሽያጭ ውል መነሻ የተረከበውን ድርጅትና ንብረት እንዲፈፅም የሚያስገደድ ትእዛዝ በመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 392 ንዑስ አንቀፅ 1 መሥፈርት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያሚላ ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የአፈፃፀም ትእዛዝና ውሣኔ መሠታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 181329 ሚያዚያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 135064 ጥር 16 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. ይህ ውሣኔ አመልካች ተጠሪዎች በአፈፃፀም በተረከቡት ድርጅት ላይ አውጥቸዋለሁ የሚለውን ወጭና ተጠሪዎች አላግባብ በልፅገዋል የሚልበትን ምክንያት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1818 እና ለሎች አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ጥያቄ ከማቅረብ የሚገድበው አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97021

ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተሻገር ገብረሥላሴ

መስጠፉ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡-መርዕድ ታደሰ ገብረመድህን ህንጻ ስራ ተቋራጭ - ጠበቃ ጸጋዬ አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡-ኦክስፎርድ አመልጌትድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የቀረበ የለም ከተባለ በኋላ ጠበቃ ታረቀኝ ተፈራ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረበው በፍርድ ባለመብትነት ተሰይሞ በነበረው የአሁኑ ተጠሪ እና በፍርድ ባለዕዳነት ተሰይሞ በነበረው የአሁኑ አመልካች መካከል የነበረውን የፍርድ አፈጻጸም ክርክር የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕግ አግባብ የተሰጠብኝ እና የምፈጽመው የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የለም በማለት በፍርድ ባለዕዳነት ተሰይሞ በነበረው የአሁኑ አመልካች ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ ባለዕዳው በግልግል ዳኝነት ውሳኔው መሰረት ፈጽሞ እንዲቀርብ የሰጠው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አሰሪ በሆነው የአሁኑ ተጠሪ እና የስራ ተቋራጭ በሆነው የአሁኑ አመልካች መካከል በታህሳስ ወር 2004 ዓ.ም በተደረገው የጫማ ማምረቻ ፋብሪካ ህንጻ የግንባታ ውል መሰረት በአሰሪው በአማካሪ መሀንዲስነት የተሰየሙት እና በገላጋይ ዳኝነት ጭምር እንዲያለግሉ በውሉ ተመርጠዋል የተባሉት ግለሰብ የስራ ተቋራጩ በውሉ መሰረት ባለመፈጸሙ ምክንያት አድርሶብኛል ላለው ጉዳት ተቋራጩ በድምሩ ብር 14,391,813.61 (አስራ አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሶስት ከስድሳ አንድ ሳንቲም) ካሳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲከፍለው ለማስወሰን አሰሪው ያቀረበውን ክስ የተከሳሽ ስራ አስኪያጅ መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነም በሚል አማካሪ መሀንዲሱ ጉዳዩን ተቋራጩ በሌለበት ከተመለከተ በኃላ

1. ተቋራጩ ካከናወነው የስራ መጠን በላይ በእላፊ የወሰደውን ገንዘብ ብር 691,625.56/ ስድስት መቶ ዘጠና አንድ ሺ ስድስት መቶ ሃያ አምስት ከሀምሳ ስድስት ሳንቲም/
2. ተቋራጩ ለፈጸመው የውል አፈጻጸም መዘግየት በውሉ መሰረት ኪሳራ እና የገደብ መቀጫ ብር 1,287,692.80 / አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ሰባት ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከ80/100
3. ተቋራጩ ሳያጠናቅቅ የቀረውን ስራ በሌላ ተቋራጭ ለማሰራት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ወጪ ብር 1,072,495.25
4. ተቋራጩ ስራውን በወቅቱ ቢያጠናቅቅ ኖሮ አሰሪው ሊያገኝ ይችል የነበረውን የታጣ ገቢ ብር 1,701,000

በድምሩ ብር 4,752,813.61 (አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሶስት ከስልሳ አንድ ሳንቲም) ክሱ ከቀረበበት ከ06/12/2005 ዓ.ም.ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ እና ከ10% የጠበቃ አበል ጋር የስራ ተቋራጩ ለአሰሪው እንዲከፍል በ09/02/2006 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣ተጠሪው በከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲፈጸምለት ያቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ መሆኑን፣አመልካች በበኩሉ አማካሪ መሀንዲሱ ውሳኔ የተሰጠበትን ዓይነት ጉዳዮች አይቶ ለመወሰን በግንባታ ውሉ ላይ በገላጋይ ዳኝነት ያልተመረጠ በመሆኑ በግራ ቀኙ ስምምነት በገላጋይነት ያልተሰየመ ሰው የሰጠውን ውሳኔ ለመፈጸም እንደማይገደድ እና ውሳኔው ተሰጠ የተባለውም የስራ ተቋራጩ ሳይጠራ እንደሆነ በመግለጽ የአፈጻጸም አቤቱታው ውድቅ ተደርጎ መዝገቡ እንዲዘጋ መከራከሩን፣ፍርድ ቤትም ክርክሩን ከሰማ በኃላ የፍርድ ባለዕዳው ያቀረበው ክርክር ሊስተናገድ የሚገባው በስረ ነገሩ ክርክር ጉዳይ ላይ እንጂ በአፈጻጸም ደረጃ አለመሆኑን ገልጾ ክርክሩን ውድቅ በማድረግ እንደፍርዱ ፈጽሞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱን እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይግባኙን ዘግቶ ማሰናበቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መሰረት አማካሪ መሀንዲሱ በሁለቱ ወገኖች በገላጋይ ዳኝነት ሳይመረጥ ሰጠ በተባለው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም የተሰጠው ትዕዛዝ ከሕግ እና ከውል ስምምነታችን ውጪ ነው በሚል በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ ከመሆኑም በላይ በ20/06/2007 ዓ.ም በተለዩት ነጥቦች ላይ በ29/7/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቃል እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በሕግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ሊቋቋሙ እንደሚችሉ በአንቀጽ 37 (1) እና 78 (4) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀጽ 79 (1) ስር የተደነገገ ሲሆን ከዝርዝር ሕጎች መካከልም በሌላ አኳኃን እንዲፈጸም በሕግ ካልተገለጸ ክስን ተቀብሎ ለማከራከር ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ብቻ ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 4 ይደነግጋል፡፡ይህ ማለት ግን በሰዎች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች የሚነሱ አለመግባባቶች ከፍርድ ቤቶች ውጪ በሌላ አግባብ ሊስተናገዱ እና እልባት ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ አይኖርም ማለት አይደለም፡፡ይልቁንም ግልጽ የሕግ ክልከላ ካለባቸው ጉዳዩች ውጪ ሰዎች በመካከላቸው የተነሱ ወይም የሚነሱ አለመግባባቶች ከፍርድ ቤቶች ውጪ እልባት እንዲያገኙ በስምምነት ሊወስኑ ይችላሉ፡፡በዚህ አግባብ ከሚደረጉ ስምምነቶች መካከል አንዱ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3325 ስር ትርጉም የተሰጠው ክርክርን በዘመድ ዳኛ የመጨረስ ስምምነት ነው፡፡የዚህ ዓይነቱ ስምምነት አፈጻጸምም ከቁጥር 3326 እስከ 3346 ባሉት ድንጋጌዎች የተመለከተ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች ከተመለከቱት መሰረታዊ መርሆዎች እና መብቶች አንዱ እና ዋነኛው የተገላጋዮቹ የየራሳቸውን የዘመድ ዳኛ የመምረጥ መብት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ በመካከላቸው ካቋቋሙት የግንባታ ውል አፈጻጸም የሚመነጩ አለመግባባቶችን በዘመድ ዳኛ ለመጨረስ በግንባታ ውሉ በአንቀጽ 38 ስር ስምምነት ማድረጋቸው ያልተካደ ጉዳይ ሲሆን አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የአንቀጹ አነጋገር አተረጓጎም፣በተለይም የአንቀጹ አነጋገር በአሰሪው የተሰየመው አማካሪ መሀንዲስ በአማካሪ መሀንዲስነቱ ከሚያከናውናቸው መደበኛ የምህንድስና ሙያ ተግባራት በተጨማሪ የዘመድ ዳኛ ስልጣን ጭምር እንዲኖረው ግራ ቀኙ ስምምነት ማድረጋቸውን የሚያመለክት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ዓቢይ ነጥብ ነው፡፡

“አለመግባባትን በግልግል ስለመፍታት” የሚል ርዕስ የተሰጠው የውሉ አንቀጽ 38 “ከውሉ በመነጨ ወይም ውሉን በማስተካከል ምክንያት ወይም ማንኛውንም ዓይነት አለመግባባቶች ወይም ልዩነቶች በሚከሰትበት ወቅት በስራው አፈጻጸም ሂደት ወቅት ስራው ከተጠናቀቀ በኃላ ወይም ከተቋረጠ በኃላ ወይም ውል የማፍረስ ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት በመሐንዲሱ አማካኝነት ከሁለቱ አካላት በአንዱ የጽሁፍ ማስታወቂያ በደረሰ በ21 ቀናት ውስጥ ሁኔታውን ለመፍታት ይሞክራል፡፡ውሳኔውንም ለቀጣሪው እና ለኮንትራክተሩ የሚያሳውቅ ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ውሳኔ በቀጣሪው እና በኮንትራክተሩ መሀል ያለው አለመግባባት የመጨረሻ ውሳኔ ሲሆን በውሳኔው መሰረት ከውሳኔው በኃላ ሌላ የገላጋይ ሂደትን ቢፈልጉም እንኳን ኮንትራክተሩም ሆነ ቀጣሪው ስራውን ማስፈጸም መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡

አማካሪው ውሳኔውን ለቀጣሪው በጽሁፍ ካሳወቀ በኃላ እና ኮንትራክተሩም ሆነ ቀጣሪው ማስታወቂያ በደረሳቸው በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኝ ካልጠየቁ የተወሰነው ውሳኔ የመጨረሻ እና በቀጣሪና በኮንትራክተሩ መካከል የጸና ይሆናል፡፡መሀንዲሱ ይህንን ውሳኔ በተጠየቀ በ21 ቀናት ውስጥ ያላሳወቀ እንደሆነ ወይም ኮንትራክተሩም ሆነ ቀጣሪው በውሳኔው ያልተስማሙ ከሆነ ቀጣሪው ወይም ኮንትራክተሩ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሳቸው ወይም የመጀመሪያው 90 ቀናት ካለፉ በኃላ ጉዳዩ ወይም ጉዳዮቹ ለሚመለከተው ኮሚቴ በመምራት መፍትሄ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ኮሚቴው አምስት አባላትን የያዘ ሲሆን እያንዳንዱ ወገን ሁለት ሁለት አባላትን ያቀርባል፡፡ሊቀመንበር ከሁለቱ ወገኖች መሀል በስምምነት የሚሾም ይሆናል፡፡የዚህ ኮሚቴ ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሆን ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ለውሳኔው ተገዢ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡"በሚል የሚነበብ ሲሆን "Settlement of Disputes Arbitration" የሚል ርዕስ ያለው የአንቀጹ የእንግሊዝኛ አነጋገርም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው፡፡

እንደሚታየው የድንጋጌው አነጋገር በአንድ በኩል ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት በአማካሪ መሀንዲሱ እንዲወሰን የተስማሙት በስራው አፈጻጸም ሂደት ወይም ስራው ከተጠናቀቀ በኃላ ወይም ከተቋረጠ በኃላ ወይም ውል የማፍረስ ሁኔታ ከተከሰተ በኃላ የሚነሳ ማናቸውም ዓይነት አለመግባባት እንደሆነ የሚያመለክት ሲሆን በሌላ በኩል ግን አለመግባባቶችን አይቶ የሚወስን በግራ ቀኙ በጋራ የሚመረጥ የግልግል ኮሚቴ ስለመኖሩ በውሉ ተገልጾ መገኘቱ፣እንዲሁም ከአማካሪ መሀንዲሱ ውሳኔ በኃላ "...ሌላ የገላጋይ ሂደትን ቢፈልጉም እንኳን ኮንትራክተሩም ሆነ ቀጣሪው ስራውን ማስፈጸም መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡" በሚል የተቀመጠው የውሉ ኃይለ ቃል ግራ ቀኙ የተስማሙበት የአማካሪ መሀንዲሱ ስልጣን የግንባታ ውሉ አፈጻጸም በሂደት ላይ በሚገኝበት ወቅት የሚነሱ እና በዘርፉ በተለመደው አግባብ በአማካሪ መሀንዲስ የሚወሰኑ የምህንድስና ዘርፍ ውሳኔ የሚሹ አለመግባባቶችን መርምሮ በመወሰን የተገደበ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ውለታዎች ግልጽ ባልሆኑ እና የሚያሻሙ በሆነ ጊዜ ደግሞ ለክርክሩ ውሳኔ መስጠት የሚቻለው በታወቁ እና በፍትሐብሔር ሕግ በቁጥር 1732 እስከ 1739፣እንዲሁም በሌሎች ድንጋጌዎች በተመለከቱት የውል አተረጓጎም መርሆዎች መሰረት ውሉን ውጤት ባለው አግባብ በመተርጎም ነው፡፡አመልካች በሰበር አቤቱታው ላይ አማካሪ መሀንዲስ የግልግል ዳኝነት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በተመሳሳይ ጉዳይ በመዝገብ ቁጥር 36577 በ16/10/2001 ዓ.ም የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ክርክር ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ በመሰረቱ አስቀድሞ በቀረበለት ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ቀጥለው በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው በሁለቱ ጉዳዮች ለክርክር የቀረቡት የሕግ እና የፍሬ ነገር ነጥቦች ተመሳሳይነት ባላቸው ጊዜ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በተጠቀሰው መዝገብ ቁጥር 36577 አማካሪ መሀንዲሱ የግልግል ዳኝነት ስልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም? የሚለው ነጥብ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ተዋዋዮቹ የውላቸው አካል ካደረጉት የባትኮዳ ደንቦች አንጻር ሲሆን በዚህ መዝገብ በተያዘው ጉዳይ ግን ግራ ቀኙ ስለአማካሪ መሀንዲሱ የስልጣን ወሰን የሚከራከሩት ውላቸውን መሰረት አድርገው በመሆኑ እና የባትኮዳ ደንቦችንም የውላቸው አካል ያላደረጉት በመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 36577 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ለቀረበው ክርክር ተፈጻሚነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ግራ ቀኙ አለመግባባቶች እንዲወሰኑ የተስማሙት በአማካሪ መሀንዲሱ እና በግራ ቀኙ በጋራ በሚመረጥ ኮሚቴ ነው፡፡በአማካሪ መሀንዲሱ የሚሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኙ በጋራ ለሚመረጥ ኮሚቴ በይግባኝ የሚቀርብ ስለመሆኑ ስምምነቱ አያመለክትም፡፡ይልቁንም የአንቀጹ አነጋገር የሚያስገነዝበው ኮሚቴው አለመግባባቶችን አይቶ የሚወስነው በመጀመሪያ ደረጃ ክርክር መሆኑን ነው፡፡ይህም በአንድ በኩል በአሰሪው በተሰየመው አማካሪ መሀንዲስ እና በሌላ በኩል ደግሞ በግራ ቀኙ በጋራ በሚመረጠው ኮሚቴ ታይተው እንዲወሰኑ ግራ ቀኙ የተስማሙት የተለያዩ ጉዳዮችን መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በሌላ አነጋገር የውሉ አንቀጽ 38 አቀራረጽ እና ይዘት ግራ ቀኙ የአማካሪ መሀንዲሱ ስልጣን የግንባታ ውሉ አፈጻጸም በሂደት ላይ በሚገኝበት ወቅት የሚነሱ እና በዘርፉ በተለመደው አግባብ በአማካሪ መሀንዲስ የሚወሰኑ የምህንድስና ዘርፍ ውሳኔ የሚሹ አለመግባባቶች በአሰሪው በተሰየመው አማካሪ መሀንዲስ ታይተው እንዲወሰኑ እና የውል ግንኙነቱ በቀጠለበት ጊዜም ሆነ ከተቋረጠ በኃላ የሚነሱ ሌሎች አለመግባባቶች ግን በግራ ቀኙ በጋራ በሚመረጠው ኮሚቴ ታይተው እንዲወሰኑ መስማማታቸውን የሚያመለክት ነው፡፡የውሉን አንቀጽ 38 ይዘት በዚህ አግባብ መተርጎሙ ከአንቀጹ ዓላማ እና አነጋገር ጋር ብቻ ሳይሆን ክርክርን በዘመድ ዳኛ የመጨረስ ስምምነትን አስመልክቶ በፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ካሉት ድንጋጌዎች ጋርም የሚጣጣም በመሆኑ ተገቢነት ያለው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አማካሪ መሀንዲሱ ውሳኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች ዓይነት እና ይዘት በግራ ቀኙ ስምምነት መሰረት ለአማካሪ መሀንዲሱ ቀርበው እንዲታዩ የተወሰኑ የምህንድስና ዘርፍ ውሳኔ የሚሹ አለመግባባቶች ሳይሆኑ ይልቁንም ከዚህ ያለፉ እና ከምህንድስና ውጪ የሌላ ዘርፍ ዕውቀትን የሚሹ በግራ ቀኙ በጋራ በሚመረጠው ኮሚቴ ታይተው እንዲወሰኑ ግራ ቀኙ የተስማሙባቸው አለመግባባቶች ናቸው፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዘመድ ዳኛ አለመግባባቶችን አይቶ የመወሰን ስልጣን የሚመነጨው ተገላጋዮቹ በግልጽ እና በማያሻማ ሁኔታ በጽሁፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚሰጡት ስምምነት ነው፡፡በመሆኑም በውሉ እንዲወስናቸው ከተመለከቱት አለመግባባቶች ዓይነት እና ወሰን በማለፍ እና የዘመድ ዳኛ አድርጎ ባልመረጠው አማካሪ መሀንዲስ ተሰጠ በተባለው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጽም አመልካቹ ሊገደድ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ፍርድ ቤቶች በፍርዱ መሰረት እንዲፈጸም ትዕዛዝ ከመስጠታቸው አስቀድሞ በሕግ አግባብ የተሰጠ የሚፈጸም ውሳኔ መኖሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 392 (1) ድንጋጌ አነጋገርም ይህንኑ የሚደግፍ ነው፡፡ባልተስማማበት እና ባልመረጠው የዘመድ ዳኛ ተሰጠበት የተባለውን ውሳኔ ለማስለወጥም አመልካች ይግባኝ እንዲያቀርብ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 350 ድንጋጌ ግዴታ አይጥልበትም፡፡

ሲጠቃለል የአመልካቹን ክርክር ውድቅ አድርጎ አመልካች በግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ መሰረት እንዲፈጽም ይገደዳል በማለት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142388 በ23/03/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 95728 በ18/04/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ በግራ ቀኙ ስምምነት እና በሕጉ የተመለከተውን ስርዓት ተከትሎ የተሰጠ ሊፈጸም የሚችል የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 103541

ሐምሌ 3 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ቢውቲ ግሪን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ እንየው ለማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ቪክስ ሰመር ፍላወር ኃ/የተ/የግ/ማህበር አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 197636 ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 147228 ሰኔ 9 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በውል መሰረት ለተሰራ ስራ ክፍያ እንዲፈፀም ይወሰንልኝ በማለት የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ ከተከሻሽ ጋር ባደረገው የስራ ስምምነት መሰረት ለተከሳሽ የምክር ስራ ለመስራትና ተከሻሽም በወር 4000 ዩሮ /አራት ሺ ዩሮ/ ሊከፍለኝ ተስማምተን እንደአውሮፖዊያን አቆጣጠር 15/10/2011 እስከ 16/01/2012 አገልግሎት ሰጥቻለሁ፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ በውሉ መሰረት መክፈል ያለበትን ክፍያ ከነ ተጨማሪ እሴት ታክስ በወቅቱ በነበረው ምንዛሬ ታስቦ ብር 313,200 /ሶስት መቶ አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ብር/ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቀርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከከሳሽ ጋር ያደረግነው የፅሁፍ ውል የለም፡፡ ውል ነው ተብሎ የቀረበው ሰነድ በሁለት ምስክሮችና በተዋዋይ ወገኖች አልተፈረመም፡፡ የውሉ አለመፈረም ተዋዋይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገኖች ያልተስማሙ መሆናቸውን የሚያመለክት በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

2. የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ ይዘት ከመረመረ በኋላ በግራ ቀኙ መካከል በቃል የተደረገ የማማከር ስምምነት አለ፡፡ በዚህ ስምምነት መሰረት ከሳሽ ሠራተኞችን ቀጥሮ የተከሳሽን እርሻ የማስተዳደር ስራ የሰራ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ከሳሽ በውሉ መሰረት ለሰጠው አገልግሎት ተከሳሽ መክፈል የሚገባውን ገንዘብ፣ ማለትም ከሳሽ በክሱ የገለፀውን የገንዘብ መጠን ተከሳሽ ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

3. አመልካች ሀምሌ 25 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ የማማከር ውል የለም፡፡ አመልካችና ተጠሪ የማማከር ውል ለመዋዋል በፅሁፍ ረቂቁን ካዘጋጀ በኋላ ባለመስማማታቸው፣ ረቂቁ ሣይፈርም ቀርቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህንን በማለፍ በመካከላቸው በቃል የተደረገ ውል አለ በማለት የሰጠው ውሳኔ እርስ በርሱ የሚቃረን የተጠሪን ምስክሮች ቃል መሰረት በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ህዳር 24 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካችና ተጠሪ የተስማሙት በፅሁፍ ሣይሆን በቃል መሆኑን በማስረጃ አስረድተናል፡፡ ቀደም ብለን በቃል ባደረግነው ስምምነት መሰረት ስራዎችን እየሰራን፣ ስምምነቱን ወደ ፅሁፍ ለመቀየር ረቂቅ ውል ተዘጋጅቶ የአመልካች ስራ አስኪያጅ ወደ ኢትዮጵያ ባለመምጣታቸው ረቂቁ ሣይፈረም መቅረቱ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ታህሳስ 23 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቀርቧል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሁፍ ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ከሳሽ /ተጠሪ/ ከአመልካች ጋር በቃል ባደረገው የምክር ግልጋሎት የመሰጠን የስራ ውል መሰረት ከሳሽ /ተጠሪ/ የሰራው ስራ ተከሳሽ ክፍያ ይፈፀም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ከአመልካች ጋር የማማከር ስራ ውል በቃል ተዋውሎ በጉራጌ ዞን በሚገኘው የአመልካች እርሻ ቦታ የመገኘት የማማከር ስራውን የሚሰሩ ሰራተኞች ቀጥሮ ሰራተኞች የማማከር ስራ የሰሩ መሆኑንና ለሰራተኞች የአራት ወር ደመወዝ የከፈለ መሆኑን፣ ረቂቅ የፅሁፍ ውል ተዘጋጅቶ የነበረው በቃል የነበረውን ውል በፅሁፍ አድርገው ለማስቀጠል በመስማማታቸው መሆኑንና ረቂቁ የፅሁፍ ውል ያልተፈረመው የተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ወደ ኢትዮጵያ ባለመምጣታቸው መሆኑን በማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያረጋገጠ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። አመልካች ረቂቅ የውል ሰነዱ አመልካችና ተጠሪ የማማከር ስራ ውል ለመዋዋል በሚያደርጉበት ወቅት፣ ባለመስማማታቸው ረቂቁ ያልተፈረመ መሆኑን የሚያስረዳ ነው በማለት ይከራከራል። ሆኖም አመልካች ከተጠሪ ጋር የማማከር ስራ ውል ለመዋዋል ድርድር ጀምሮ እንደነበር፣ በድርድሩ ሂደት ስምምነት ላይ ባለመደረሱ ረቂቁ ሊፈረም የቀረ በመሆኑና ረቂቅ ውሉ ከመዘጋጀቱ በፊት በቃል ያደረጉት የስራ ውል የሌለ መሆኑንና ተጠሪም በስራ ውሉ መሰረት የፈፀማቸው ተግባራት የሌሉ መሆኑን የሚያስረዳ በቂና አሳማኝ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል።

6. አመልካችና ተጠሪ በቃል ያደረጉት የማማከር ስራ ውል መኖሩ ብቻ ሊይሆን በተጠሪ በቃል በተደረገው የማማከር ስራ ውል መሰረት ለአራት ወራት ያህል ሰራተኞች ቀጥሮ ደመወዝ እየከፈለ የአመልካችን እርሻ ያስተዳደረና ሌሎች የምክር አገልግሎቶችን የሰጠ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። አመልካች ተጠሪ በዚህ መዝገብ የሚከራከሩበትን አይነት የስራ ውል ለመዋዋል፣ የአሰሪው /የአመልካች/ ጥያቄውን ማቅረብና የተጠሪ ጥያቄውን መቀበል ብቻ በቂ እንደሚሆን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1779፣ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2610 እና ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2612 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ አንፃር አመልካች የማማከር የስራ ውል በፅሁፍ ካልተደረገ በስተቀር ተዋዋይ ወገኖች በቃል ባደረጉት ስምምነት ሊቋቋሙት እንደማይችሉ በመግለፅ የሚያቀርበው ክርክር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1882 ንዑስ አንቀፅ 1፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2610፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2612 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን ይዘት ያላገነዘበና የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም።

7. ተጠሪ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2610 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ከአመልካች ጋር በቃል ባደረገው የስራ ውል መሰረት የማማከር ስራውን ከሰራ፣ አመልካች በስራ ውሉ ላይ በቁርጥ የተወሰነውን ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2624 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል። ከዚህ አንፃር ተጠሪ ለአመልካች በውሉ መሰረት ለአራት ወራት ያህል ለሰጠው የማማከር ስራ በቁርጥ የተወሰነውን ገንዘብ እንዲከፍል የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያላቸውንና ከላይ የተገለፁትን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል። ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች አመልካች ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበውን ክስና ማስረጃ በቂና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ የማስተባበል ግዴታውን በአግባቡ ያልተወጣ መሆኑን የአመልካች የውሉን ፎርም አለተሟላም በማለት ተጠሪ ለሰራው ስራ ክፍያ ለመፈፀም እንቢተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ የሰጡት ውሳኔ ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 100671

ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ሻለቃ ጌትነት ታርቆ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ጀሚላ አሊ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው፡፡ ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 08573 በቀን 21/10/2003 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞር ከፍተኛ ፍርድ ቤ.ያፀናውም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 2665 በዐ9/08/2006 ዓ.ም በመለወጥ በሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካች መሰረታዊ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የውል መፍረስን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በጎንደር ከተማ ቀበሌ 17 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር 7662/03 በእኔና በባለቤቱ ወራሾች በሆኑት ህፃናት ልጆች ስም የተመዘገበ ቤትና ቦታ ላይ እኔ ቦታ ተጠሪ ደግሞ ገንዘብ ችሎ ባለ 3 ፎቅ ህንፃ ሰርተን እኩል ልንካፈል እና ተጠሪ ከፎቅ ጀርባ መኖሪያ ቤት ሰርቶ ሊሰጠኝ በ21/06/03 ውል አድርገን እሱባለው ሆነ ኃ/የተ/የግ/ማ በማቋቋም ተስማማን፡፡ በውሉ መሰረት እንዲፈፀም በወረዳ ፍርድ ቤት ክሶኝ ውሳኔ አሰጥቶብኛል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካች የቤትና ቦታው ካርታ ወደ ማህበሩ እንዲዞር የሽያጭ ውል መፈፀም አለብን በሚል የአሁኑን ተጠሪ አታሎ የልጆቼን መብት በሚጎዳ መልኩ የሽያጭ ውሉ ላይ አስፈርሞኛል በመሆኑም ውሉ የፈቃድ ጉድለት ያለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ ይፍረስልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነት ቀርቦ በሰጠው መልስ ቀደም ሲል በ21/06/03 ዓ.ም የተደረገው ውል በ2/07/03 ዓ.ም በተደረገው ውል ተተክቷል የአሁኑ ተጠሪ ጋር ውል አልፈፀምኩም በ8/07/03 ዓ.ም የተደረገውን ውል የአሁን ተጠሪ የማድረግ ስልጣን አላት ምክንያቱም የልጆቹ ሞግዚትና ብቸኛ ወኪል ነች ውሉን ያደረግነው በአሁን ተጠሪ ጠያቂነት ነው ውሉ ፀድቆ ተመዝግቦ ስም ተዛውሯል፡፡ በአሁኑ ተጠሪ ስም የነበረው ካርታ ቁጥር 7662/03 በአዲስና በአሁን አመልካች ስም በወጣና ቁጥር 7668/03 በሆነ ካርታ ተለውጧል፡፡ በመሆኑም ክሱ በሌላ መብት የቀረበ ነው ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የአሁን ተጠሪ በ25/06/03 ዓ.ም የመንደር ውል ካደረጉ በኋላ በ8/7/03 ዓ.ም የአሁኑ አመልካች ጋር የሽያጭ ውል በማድረግ ውሉን አስመዝግበው ስም ወደ አሁኑ አመልካች እንዲዛወር አድርገዋል፡፡ ይህንን ሲያደርጉ ደግሞ ተገደው መሆኑን አላስረዱም ወደውና ፈቅደው መዋዋላቸውን ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም በ8/7/03 ዓ.ም የተደረገው ውል ሊፈርስ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁኑ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኙን በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይኸው ፍርድ ቤት በ8/10/04 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከዚህ በኋላም የአሁኗ ተጠሪ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረሙ ይገባል በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርባ ይኸው ችሎትም በዋናነት የሽያጭ ውሉ ህጋዊነት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አከራካሪ የሆነው የሽያጭ ውል የተደረገው በ7/7/03 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ ቤትና ቦታ ላይ ቀደም ሲል በአሁን ተጠሪ ባለቤት ስም የነበረው ካርታ በአሁን ተጠሪና ልጆቻቸው ስም ዞሮ ቁጥር 7662/03 የሆነው ካርታ የተሰጣቸውም በዚሁ ዕለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ከ1 ወር ከ15 ቀናት በኋላ ይኸው የሽያጭ ውል ተደረገበት በተባለ ቦታ ላይ በግራ ቀኙ ስም ሻለቃ ጌትነት ታርቆ እና ጀሚላ ዓሊ /PIC/ በሚል ስም በ23/7/03 ቁጥር 7668/03 የሆነ ካርታ ተሰጥቷል ይህም የሆነው ግራ ቀኙ በ23/5/03 ዓ.ም በተፈራረሙበት የንግድ ድርጅት የጋራ ሕንፃ በመገንባት ውል መሰረት እና ማህበሩም እሱባለው ሆነ ኃ/የተ/የግ/ማ ተብሎ እንዲመዘገብ በጋራ በ24/08/03 ዓ.ም እና በ02/06/03 ዓ.ም ለሚመለከተው አካል ካመለከቱ በኋላ ነው፡፡ ይህንንም የአሁኑ አመልካች ራሱ በስር ፍ/ቤት ካቀረባቸው ሰነዶች ማየት ይቻላል የአሁን አመልካችም ቦታውን በ7/7/03 ዓ.ም በተደረገ ውል ቢገዛ ኖሮ ከዚህ በኋላ ይኸው ቦታ ላይ የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት በሆነ ድርጅት ስም ካርታ ሲወጣ ዝም ይላል ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም የሽያጭ ውሉ በክፉ ልቦና የአሁን ተጠሪን በመደለል የተደረገ ውል ነው፡፡ የሽያጭ ውሉም የተደረገው በባዶ ቦታ ላይ በመሆኑ ሕገ/ወጥ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም ቢሆኑ የሕፃናት ልጆቻቸውን ድርሻ የሆነን ቦታ የመሸጥ ከሕግ የመነጨ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብት የላቸውም የሚሉ ምክንያቶችን በማስቀመጥ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ ባለመስማማት መሰረታዊ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሞባቸዋል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የሽያጭ ውሉ በተጠሪ ፈቃድ የተደረገና በሚመለከተው አካል ተረጋግጦ የተመዘገበ መሆን ውሉ የተደረገው ቤት የነበረው ቦታ ላይ እንጂ ባዶ ቦታ ላይ አለመሆኑን የሽያጭ ውሉ ከመደረጉ በፊት የተቋቋመ ማህበር አለመኖሩን ተጠሪ የሸጡት የራሳቸውን ድርሻ ብቻ መሆኑን ተጠሪ የሽያጭ ዋጋውን ፈርመው መቀበላቸውን ዘርዝረው ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርመሮ አመልካች የሸያጭ ውል የፈፀመው በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ሆኖ ካርታ በስሜ ዞሮ የግንባታ ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ የስር ሰበር ችሎት ውሉ የተደረገው ባዶ ቦታ ላይ በመሆኑ ፈራሽ ነው በማለት ያልተከራከርንበትን ነጥብ በማንሳት መወሰኑን ያለአግባብ ነው በማለት ያቀረበውን ቅሬታ ለመመርመር በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የአሁን ተጠሪ የተጠሩ ሲሆን ቀርበው ሐምሌ 4 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በግራ ቀኙ መካከል በ22/05/03 ዓ.ም የንግድ ድርጅት የጋራ ህንፃ ግንባታ ውል መዋዋላቸውን ይህም ውል የተመዘገበ መሆኑን ይህንን ውል ለማስፈፀም ሲባል ህንፃው የሚሰራበት ቦታ ላይ የነበረው ቤት ፈርሶ ነፃ መሆኑን ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካች የቦታውን ስመ ሀብት ወደ ጋራ ማህበሩ ለማዞር የሸያጭ ውል መደረግ አስፈላጊ ነው በማለት በ7/7/03 ዓ.ም የባዶ ቦታ ሽያጭ ውል እንዲፈርሙ ያደረጋቸው መሆኑን በኋላ የተሰጠው ካርታ ቁጥር 7668/03 ግን በአመልካች ስም ሳይሆን በድርጅቱ ስም መሆኑን የሸያጭ ውሉን የገቡት የቦታውን ስመ ሀብት ወደ ድርጅት ዞሮ ግንባታ ይጀመር በማለት አመልካች ስለደለላቸው እንጂ የመሸጥ ሀሳብ ኖሯቸው አለመሆኑን ዘርዝረው የስር ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ራሱ አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ያቀረበውን ማስረጃዎች መርምሮ በመሆኑ የፈፀመው የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል አመልካችም ሐምሌ 7 ቀን 2006 ዓ.ም የመልስ መልሳቸውን አቤቱታቸውን በማጠናከር ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርመሮታል፡፡ እንደመረመረውም የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው በግራ ቀኙ መካከል የሽያጭ ውሉ ከመደረጉ በፊት የአሁኑ ተጠሪ የሚኖሩበት ቤት ፈርሶ በቦታው ላይ የአሁኑ አመልካች ህንፃ ግንባታውን ለመጀመር ተዘጋጅተው እንደነበር በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ውሉ የተደረገው /የሽያጭ ውሉ/ በባዶ ቦታ ላይ መሆኑን ያሳያል፡፡ ባዶ መሬት ደግሞ የማይሸጥ የማይለወጥ መሆኑና የኢትዮጵያ ብሔርብሔረሰቦች ሕዝቦች የጋራ ንብረት መሆኑ ሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 40/3/ የተመለከተ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ድንጋጌ በመተላለፍ የተደረገ የመሬት ግብይት ውል ፍሬ ነገሩ /Object/ ሕገ ወጥ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ውል ደግሞ ከጅምሩ የሌለ ወይም ያልተደረገ /Voide/ ውል መሆኑን የፍ/ህ/ቁ 1716/1/ ያስቀምጣል፡፡ በዚህ ሁኔታ ደግሞ ፍርድ ቤት ህግን የማስከበር ኃላፊነትም ጭምር ያለበት በመሆኑ ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም እንኳን ሕገ- ወጥ ውል ሲያጋጥመው ውሉ ከጅምሩ ፈራሽ መሆኑን በመግለፅ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኞችን ያልተከራከርንበትን ጉዳይ በራሱ በማንሳት ውሉ ከጅምሩ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ አይደለም የሚለው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም መሰረት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሉ ከጅምሩ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 26665 በቀን 09/08/06 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102778

ሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ስማድል ኮሙኒኬሽን ተርሚናል ፋብሪካ ኃ.የተ.የግል ማህበር

ተጠሪ፡- አቶ የሺጥላ ደሳለኝ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በሰ/መ/ቁጥር 102777 ከቀረበው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት ስላለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 11 መሰረት መዝገቦችን አጣምረን በመመርመር ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ የውል ክርክር በፍርድ ቤት የሚታይበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥር 10 ቀን 2005 ዓ/ም በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም፡-አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገጣጥማቸውን ስማድል ተንቀሳቃሽ ስልኮችን የአሁኑ ተጠሪ ለአንድ አመት ብቸኛ ወኪል በመሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ለማከፋፈል በ03/12/2003 ዓ/ም በተፈረመ ውል ስምምነት መደረጉን፣አመልካችም የሚያመርተውን ምርት ለተጠሪ የንግድ መደብር የሺጥላ ሞባይል ሴንተር እያስረከበ ተጠሪ እቃዎቹን እየሸጠ ክፍያውንም እየፈፀመ ቀሪ ሒሳብ ማመዛዘኛ(ባላንስ) እየተሰራ የውሉ ዘመን መጨረሻ ድረስ እቃ እየወሰደ የውሉ ጊዜ መጠናቀቁን፣ ተጠሪ በውሉ ዘመን የተረከባቸውን እቃዎችን ዋጋ ቀስ በቀስ ለአመልካች ገቢ እያደረገ እስከ ውሉ ዘመን ማብቂያ ማለትም እስከ 03/13/2004 ዓ/ም ድረስ ያለውን ሒሳብ አጠናቅቆ መከፍሉን፣ተጠሪ የብቸኛ ወኪልነቱን ዘመን ከተጠናቀቀ በኋላ ከ05/13/2004 ዓ/ም ጀምሮ የማከፋፈል ሰራውን እስከአቋረጠበትና የመጨረሻ ክፍያ እስከተፈፀመበት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ የብር 4,663,730.00(አራት ሚሊዩን ስድስት መቶ ስልሳ ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ብር) እቃዎችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በንግድ መደብሩ ሰራተኞች መረከቡን፣ ተጠሪ ከውሉ ዘመን ማብቂያ በኋላ ለወሰደው እቃ የመጨረሻ ሂሳብ ጥቅምት 03 ቀን 2005 ዓ/ም ገቢ አድርጎ በልዩነት የተገኘው ተራፊ ገንዘብ ብር 131,155.00(አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ብር) ታሳቢ ተደርጎ እስከ ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ ብር 2,322,815.80(ሁለት ሚሊዩን ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አስራ አምስት ብር ከሰማንያ ሳንቲም) ገቢ ማድረጉን፣ ይህ ገንዘብ ከብር 4,663,730.00 ላይ ተቀናሽ ሲደረግ በልዩነት ብር 2,340,914.50 (ሁለት ሚሊዩን ሶስት መቶ አርባ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ተጠሪ ለአመልካች መክፈል ይጠበቅበት እንደነበር፣አመልካች በወቅት ባልተሸጡ እቃዎች ላይ የዋጋ ቅነሳ ስላደረገ ያልተሸጡ እቃዎች ላይ ቆጠራ ተደርጎ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 05 ቀን 2012 ብዛታቸው 1000 ለሆኑ ሞባይል ስልኮች ለተጠሪ የብር 52,425.00(ሃምሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ ሃያ አምስት ብር) ተቀናሽ መደረጉን፣ተጠሪ ቅናሽ ከተደረገለት በኃላ ለአመልካች ብር 2,288,489.40(ሁለት ሚሊዩን ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከአርባ ሳንቲም) እንዲከፍል የሚጠበቅበት መሆኑንና የወሰዳቸውን እቃዎችን እንዲመልስ ወይም ገንዘቡን እንዲከፍል ቢጠየቅ ፈቃደኛ ያለመሆኑን ዘርዝሮ ተጠሪ የሚፈለግበትን ብር 2,288,489.40 ከ18/03/2005 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ፣ከክሱ ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ተከሳሽነቱ ቀርቦ ለአመልካች ክስ በሰጠው መልስም፡- የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበው ነጥብ የፍርድ ቤቱን ስልጣን የሚመለከት ሲሆን ይኼውም በግራ ቀኙ መካከል በ03/12/2003 ዓ/ም በተደረገ ስምምነት በውሉ አፈጸጸም ጋር በተያያዘ አለመግባባት ቢፈጠርና ይህም አለመግባባት በስልሳ ቀናት ውስጥ በስምምነት መፍትሔ ሊያገኝ ካልቻለ ጉዳዩ ሶስት ገላጋይ ዳኞች(አርቪትሬተርስ) ለሚሰየመው አለም አቀፍ የንግድ ምክር ቤት ቀርቦ መፍትሔ እንደሚሰጠው፣የግልግል ዳኝነቱ የሚደረገውም በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሆንግ ኮንግ እንደሚሆንና ጉባኤውም የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን በውሉ አንቀፅ 10 ስር ስምምነት መደረጉን፣ከዚህም በተጨማሪ አለመግባባቱ የሚታየው በኢትዩጵያ ሕግ እንዳልሆነና በ2000 ዓ/ም አለም አቀፍ የንግድ ድንጋጌዎች(ኢንተርናሽናል ኮሜርሺያል ተርምስ፤ኢንኮተርምስ) አማካኝነት እንደሆነ ተፈፃሚነት ስላለው ሕግ በሚደነግገው የውሉ አንቀጽ 11 ስር ግራ ቀኙ መስማማታቸውንና ይኼው በውሉ የተመለከተው የአለመግባባት አፈታት መንገድ በውሉ በተመለከተበት አግባብ ከሚታይ በቀር ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት የሚወሰድበት አግባብ ያለመኖሩና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 16896 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠበት መሆኑን ጠቅሰው ጉዳዩን ፍርድ ቤቱ ሊመለከተው አይችልም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በዚህ የተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ በግልግል እንደሚታይ ግራ ቀኙ በውላቸው ላይ ያስቀመጡ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጎ አመልካች የከፈለውን የዳኝነት ገንዘብ በደንቡ መሰረት እንዲመለስለት፣ተጠሪ ደግሞ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት አለው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ወጪና ኪሳራን በተመለከተም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች ለተጠሪ ብር 37,760.07(ሰላሳ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም) እንዲከፍል በማለት ጥር 14 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡ስልጣንን አስመልክቶ በተሰጠ ብይን አመልካች፣ በወጪና ኪሳራ ላይ በተሠጠው ውሳኔ ደግሞ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዛግብት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ችሎቱ ስልጣኑን አስመልክቶ የቀረበውን ክርክር መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ያለው ውል ተራዝሟል፣ያለመራዘሙን አመልካች አልካደም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሲያፀናው ወጪና ኪሳራን በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች ለተጠሪ በክሱ ገንዘብ መጠን 3% የጠበቃ አበል እንዲከፈል በማለት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ብይንና ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ03/12/2003 ዓ/ም በተደረገ ውል ያለመግባባቱ የሚፈታበት አግባብ የተቀመጠው እስከ 03/13/2004 ዓ/ም ላለው ጊዜ ተፈፃሚነት ለሚኖረው ውል ሁኖ እያለና በዚህ ጊዜ ውስጥ ደግሞ ውሉ አብቅቶ የግራ ቀኙ በፅሑፍ ያደረጉት ስምምነት ሳይኖር ግንኙነቱ ከ05/13/2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ/ም በመቀጠል ለተፈፀመ የሞባይል ግብይነት የቀረበውን የክፍያ ጥያቄ የቀደመው ውል እንዲቀጥል በግራ ቀኙ መካከል በጽሑፍ የተደረገ ውል በሌለበትና ቀዳሚው ውል ጊዜው ባበቃበት ሁኔታ የመጀመሪያው ውል ተፈጻሚነት እንዳለው ተደርጎ ያለመግባባቱ በፍርድ ቤት ሳይሆን በግልግል የሚታይ ነው መባሉም ሆነ ወጪና ኪሳራን በተመለከተ አመልካች ለተጠሪ እንዲተካ ተብሎ መወሰኑም ረቺና ተረቺ ባልተለየበት ሁኔታ በመሆኑ ያላግባብ የተወሰነ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥም፡- በአመልካችና በተጠሪ መካከል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደረገው ውል ጳጉሜ 03 ቀን 2004 ዓ/ም ከተጠናቀቀ በኃላየተደረጉ ግብይቶችን አስመልክቶ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት የመዳኘት ስልጣን በፍ/ብ/ቁጥር 1684 መሰረት ውሉ የተራዘመ በመሆኑ የሽምግልና ዳኞች ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለኝም ያለበትን አግባብነትና እንዲሁም በግልጽ በውሉ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1684 ትርጉም ተሰጥቶ ውሉ መራዘሙ በሽምግልና ዳኝነቱ ስልጣን የሚኖረውን ውጤት ለመመርመር ተብሎ በመሆኑ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች የክስ ይዘት አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገጣጥማቸውን ስማድል ተንቀሳቃሽ ስልኮችን የአሁኑ ተጠሪ ለአንድ አመት ብቸኛ ወኪል በመሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ለማከፋፈል በ03/12/2003 ዓ/ም በተፈረመ ውል ስምምነት የተደረገ ሲሆን የውሉ ዘመን ማብቂያ እስከ 03/13/2004 ዓ/ም ድረስ ስለመሆኑ፣በመጀመሪያ ውል መሰረት መከፈል የሚገባውን ሂሳብ ተጠሪ አጠናቅቆ ለአመልካች ከፍሏል በማለት አመልካች ክሱን መመስረቱን፣ተጠሪ የብቸኛ ወኪልነቱን ዘመን ከተጠናቀቀ በኋላ ከ05/13/2004 ዓ/ም ጀምሮ የማከፋፈል ሰራውን እስከአቋረጠበትና የመጨረሻ ክፍያ እስከተፈፀመበት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ ያለው ግብይት ላይ ያልተከፈለው ሒሳብ መኖሩን ዘርዝሮ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ መመስረቱና ተጠሪም የመጀመሪያው የውሉ ጊዜ ከአበቃ በኋላ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ግንኙነት ቀድሞ በጽሑፍ በተደረገው ውል አግባብ ሊገዛ ይገባል በሚል ምክንያት ጉዳዩ በግልግል እንጂ በፍርድ ቤት የሚታይበት አግባብ የለም የሚል ክርክር አንስተው የበታች ፍርድ ቤቶችም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት ውሉ በመራዘሙ ምክንያት ቀድሞ በተደረገው የውል ግንኙነት አግባብ መገዛት አለበት በሚል ድምዳሜና የፍ/ሕ/ቁጥር 1684 እና 1731(1) ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ጉዳዩን ፍርድ ቤት ለማየት ስልጣን የለውም ሲሉ የወሰኑ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር የሚዋዋሉትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት ያላቸው መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1711 በግልጽ የደነገገ ሲሆን በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ደግሞ ባቋቋሚቸው ሰዎች ላይ የሕግን ያህል ኃይል ያላቸው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ስር ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም በሕግ እስካልተከለከለ ድረስ ተዋዋይ ወገኖች አንድን ጉዳይ ከፍርድ ቤት ውጪ በሌላ የሙግት መፍቻ ዘዴ ለመፍታት ስምምነት ማድረግ እንደሚችሉና ስምምነቱ መኖሩና ሕጋዊ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ደግሞ ተዋዋዮቹ በስምምነታቸው መሰረት መገዛት እንደአለባቸው፣ፍርድ ቤቱም ሕጋዊ ውል መኖሩን አረጋግጦ ውሉ እንዲፈጸም ማድረግ ያለበት መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት በግልፅ መገንዘብ የሚቻለው በ03/12/2003 ዓ/ም በግራ ቀኙ በጹሑፍ የተገባው ውል የተሻሻለ ስለመሆኑ አለመረጋገጡን ነው፡፡የውል መለወጥ ሥርዓት በሕጉ የተዘረጋ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1722 ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት ዋናውን ውል የመለወጥ ጉዳይ በዚሁ ውል በተደነገገው አፃጻፍ (ፎርም) መሰራት ያለበት መሆኑ በተጠቃሹ ድንጋጌ ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በጹሑፍ ያደረጉትን ውል በፁሑፍ የለወጡ መሆኑን አላስረዱም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ በዚህ ረገድ የሚከራከሩትና የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር የቀድሞ ውል ጊዜው ከአለቀ በኋላ ሁለቱ ወገኖች በቀድሞ ውል መሰረት ግንኙነታቸውን የቀጠሉ መሆኑ እንጂ አመልካች ወይም ተጠሪ ያቀረቡት የውል አቀራረብ ጥያቄ ኑሮ ሌላኛው ወገን በዝምታ ግንኙነቱን የቀጠለ ስለመሆኑ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ወይም ተጠሪ አንዱ ለሌላኛው የውል መለዋወጥ ጥያቄውን ማቅረቡ በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳየው ጉዳይ ከመሆኑም በላይ የውል መለወጥ ሊከተለው የሚገባውን ስርዓት በመከተል ውሉ ስለመለወጡ ያልተረጋገጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው የተጠሪ ክርክርም ሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም በ03/12/2003 ዓ/ም የተደረገው ውል በአመልካችና ለተጠሪ መካከል ከ05/13/2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 18/03/2005 ዓ/ም ድረስ ነበረ ለተባለ ግንኙነት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም፡፡

በሌላ በኩል ግን በ03-12-2003 ዓ.ም የተደረገው ውል እና በውሉ የተቀመጠው የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ በሕጉ አግባብ አልተለወጠም፣ ቀዳሚው ውል ተጠናቋል ከተባለ ተጠሪ በ03-12-2003 ዓ.ም በተደረገው ውል ከገባው ግዴታ በኋላ ነበር ለተባለ የግራ ቀኙ ግንኙነት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ውል አለ ተብሎ የ03/12/2003 ዓ/ም ተደረገ የተባለውን ውል ለክሱ ምክንያት ሊሆን የሚችልበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ውል ተራዝሟል ብሎ ለመደምደም መነሻ ያደረገው በ03/12/2003 ዓ/ም ተደረገ የተባለውንና አመልካች ለማስረጃነት ያቀረበውን ሰነድ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ እንዲሁም አመልካች ይህ ውል ከተጠሪ ጋር ከ5/13/2004 ዓ/ም በኃላ የፅሑፍ ውል የለም ብሎ ለመከራከር እንደማያስችለውና ውል የለም ካለ ደግሞ ክሱን የመሰረተበት አግባብ ምን እንደሆነ ጠቅሶ ያቀረበው ክርክር የለም በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በውሳኔው ላይ ማስፈሩን ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ የአንድ ግዴታ ምንጭ ውል ወይም ሕግ ሲሆን አንድ መብት አለኝ በማለት ክስ የሚያቀርብ ሰውም የመብቱን ምንጭ ማሳየት እንደሚጠበቅበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33፣80፣231 እና በሌሎች ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው የክስ አመሰራረት ስርዓት ያስገነዝባል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካችም በተጠሪ ላይ ክስ ሲመሰርት በመካከላቸው ቀድሞ በፅሑፍ የሆነ ውል የነበረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑና በዚያ ውል ተጠሪ ያለባቸውን ግዴታ የተወጡ መሆኑን አሳይቶ ለክሱ መሰረት የሆነው ግን ከቀዳሚው ውል ጊዜ ማብቃት በኋላ በነበራቸው ግንኙነት መሰረት ተጠሪ አልተወጡም የተባለው ግዴታ ነው፡፡ በመሰረቱ በጠቅላላ ውል በሕግ ፊት የጸና ውል አለ ለማለት መሟላት ከአለባቸው ነገሮች አንዱ በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠ ፎርም ካለ ይህንኑ ማሟላት ሲሆን በአመልካችና በተጠሪ መካከል ነበር የተባለው የተንቀሳቃሽ ስልክ በወኪልነት የማከፋፈል ውል ፎርምን በተመለከተ በሕጋችን ለተዋዋይ ወገኖች ነፃነት የተተወ ነው፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1719(1) በሁለቱ ወገን ተዋዋዮች በማናቸውም ሁኔታ የተደረገ ስምምነት ውል ለማድረግ በቂ ነው በማለት የተቀመጠው ድንጋጌ የሚያስገነዝበውም ሕጉ ይህን ነፃነት መጠበቁን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የውሉ አጻጻፍ ፎርም ወይም ዓይነት በሕግ የታዘዘ ሆኖ እንደ ትዕዛዙ ባይፈጸም ፈራሽነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ሐ)) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ሆኖም የተንቀሳቃሽ ስልክ በወኪልነት የማከፋፈል ውልን በተመለከተ ግን በግልጽ የተቀመጠ የፎርም ግዴታ ባለመኖሩ ተዋዋይ ወገኖች በመሰላቸው መልኩ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የተንቀሳቃሽ ስልክ በወኪልነት የማከፋፈል ውል በቃል፣ በድርጊት፣ ወይም በጽሑፍ ሊፈጸም ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች አቀረበ የተባለውን ሰነድ ከ05/13/2004 ዓ/ም በኋላ እስከ 18/03/2005 ዓ/ም ድረስ ላለው ጊዜ የቀረበ ማስረጃ ስለመሆኑ ሳያረጋግጥና የውሉ ጊዜ ያበቃ ስለመሆኑ አመልካች ጠቅሶ እየተከራከረ የግራ ቀኙ ግንኙነት በፅሑፍ ያለውን ውል መሰረት ያደረገ ነው፣ ውሉ ተራዝሟል በማለት ያሰፈረው ድምዳሜ የአመልካችን የክርክር ይዘትና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1719 ድንጋጌን ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 16896 የተሠጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምም በመዝገቡ ተከራካሪ የነበሩ ወገኖች በመካከላቸው የተሻሻለ ውል መኖር ያለመኖሩ አካራካሪ ባልሆነበትና በሕግ ፊት የፀና አንድ ውል መኖሩና በዚህ ውል ደግሞ ግራ ቀኙ ያለመግባባትን በግልግል ለመፍታት የተስማሙ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ በመሰረታዊ የክርክር ነጥቦች አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት የሌለው በመሆኑ በዚህ ረገድ ተጠሪ የሚያቀርቡት ክርክር ከአስገዳጅ የሕግ ትርጉም አተገባበር አንፃር ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ሲጠቃለልም በአመልካችና በተጠሪ የተነሳው ክርክር በ03/12/2003 ዓ/ም የተደረገው ውል ከአበቃ በኋላ ግራ ቀኙ በዚሁ ውል ለመገዛት በፍ/ሕ/ቁጥር 1684 እና 1722 ድንጋጌዎች አግባብ ያራዘሙት ውል ሳይኖር በአዲስ መልክ የተፈጠረውን ሌላ ውል መሰረት ያደረገ በመሆኑ በ03/12/2003 ዓ/ም በተደረገ ውል መሰረት በግልግል እንዲታይ የሚደረግ ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፤፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 130429 በ06/03/2006 እና 14/06/2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 96463 በ24/8/2003 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 97137 በ24/08/2006 ዓ/ም የተሻሻለው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከ05/13/2004 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 18/03/2005 ዓ/ም ድረስ ያለውን ግንኙነት የመዳኘት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካችን የዳኝነት ገንዘብ ተመልሶለት ከሆነ ተገቢውን እንዲፈጽም በማድረግ ክርክሩን በመ/ቁጥር 130429 እንዲቀጥል አድርጎ ጉዳዩን በሕጉ አግባብ አጣርቶ ተገቢውን ሊወሰን ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. ወጪና ኪሳራን በተመለከተ ተጠሪን ለወጪና ኪሳራ ዳርጓል የተባለና በጉዳዩ ላይ የተሰጠ ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ አሁን ባለው የክርክር ደረጃ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የሚገደድበት ወጪና ኪሳራ የለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሙሴ ሙሴ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 106450

ሚያዝያ 15 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፉ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ኢትዮጵያ ኤ.ን/አገልግሎት መቂ ዲስትሪክት - ነ.ፈ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ በሳ ናናማ - ጠበቃ - ደነቡ ጠይሶ - ቀረቡ

2. አቶ ባንቂ መኤሶ

3. ወ/ሮ አዩሌ መገርሳ

መዝገቡ መርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪዎች ከሳሽ ነበሩ፡፡ተጠሪዎች የሚች ቱፋ ቤንቂ ቤተሰብ መሆናቸዉን በመግለጽ በመኖሪያ ቤቱ አጠገብ ባለዉ የኤሌክትሪክ ሽቦ መሀከል ትልቅ ዛፍ በመኖሩ ድርጅቱ (አመልካች) በተለያዩ ጊዜ ቆርጦ እንዲያነሳለት ቢጠይቅም ባለማንሳቱ ሚች በልጆቹ ላይ ሊወድቅ እና ሊይዝብኝ ይችላል በማለት ዛፉን ሲቆርጥ ኤሌክትሪኩን በመንካቱ ሊገድለዉ ችሏል፡፡ ሁለት ቀርጥ መሬት እያከራዩ ከአንዱ ቀርጥ ላይ 10 ኩንታል ቦቆሎ ሲያገኝ ከሁለቱም ቀርጦች 20 ኩንታል የሚያገኝ ሲሆን የ1 ኩንታል በቆሎ ዋጋ 500 ብር ሲሆን በ1 አመት 10,000 ብር ያገኝ ነበር፣ ለወደፊቱ ሊኖር የሚችለዉ ለ36 አመት ስለሚሆን በዚህ ሂሳብ 360,000 ብር እንዲከፈለን በማለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በሰጠዉ መልስ ፤ሚች ከኤለክትሪክ ርቆ ቤቱን መስራት ሲኖርበት የአዋጅ 464/97 ድንጋጌን በመተላለፍ፤እራሱ የተከለዉን እንጨት አጥር ለመስራት ሲቆርጥ ጥንቃቄ ባለማድረጉ በመሞቱ ልንጠየቅበት አይገባም፤ይህ የኤሌክትሪክ መስመር ለብዙ አመት አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ እና እስካሁን ችግር ፈጥሮ አያዉቅም፣በመሆኑም ተጠያቂ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልንሆን አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡በመቀጠልም ሚች ያገኝ ነበር የተባለዉም ገቢ የተጋነነ ነዉ ፤የወንድ አማካይ እድሜም 55 አመት በመሆኑ ሚች ለወደፊት ይኖራል ተብሎ የቀረበዉ ትክክል አይደለም፤ ዉድቅ ሊሆን ይገባል ብሏል፡፡ ጉዳዩን ያየዉ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት እንዲሁም ተገቢ ነው ያለውን ማጣራትም ከአደረገ በኋላ ሀላፊነትን በተመለከተ አመልካች የኤሌክትሪኩ ሽቦ ከሚች ቤት 4 ሜትር ርቆ የነበረና መቁረጥ የማያስፈልግ ነበር ቢልም፤ በተደረገዉ ማጣራት ሚችን የገደለዉ የኤሌክትርክ ሽቦ 2.85 ርቆ እንዳለ በማረጋገጥ አመልካች እንጨቱን መቁረጥ ነበረበት፣ ይህን ባለማድረጉ ለደረሰዉ አደጋ ተጠያቂነት አለበት በማለት የፍ.ህ.ቁ 2095 ድንጋጌን ጠቅሶ ወስኗል፡፡በመቀጠልም የታጣን ገቢ በተመለከተ ሚች ሁለት ቀርጥ መሬት አከራይቶ በአመት 20 ኩንታል ያገኝ ነበር ቢባልም ተጠሪዎች መሬቱ በእጃቸዉ ስለሚገኝ ሰራተኛ ቀጥረዉ መጠቀም ስለሚቻል በርትዕ በወር 200 ብር መቅጠር ስለሚችሉ፤እና የሚችም ዕድሜው 24 አመት የነበረና ለወደፊቱ 32 አመት ሊኖር ይችላል ተብሎ ስለሚገመት 32×12×200 = 76,800 ብር እና የሞራል 1000 ብር ጨምሮ 77,800.00 ብር ለተጠሪዎች ይከፈላቸዉ በማለት ወስኗል፡፡በቀጣይነት ጉዳዩን ያየዉ ፍርድ ቤትም ቅሬታዉን ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡

የአመልካች አቤቱታም የቀረበዉ ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ቅሬታዉን ሲገልጽ፡- የኤሌክትሪክ መስመሩ ከ1972 ጀምሮ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ነዉ፤ ሚች ኤሌክትሪክ በእርጥብ እንጨት ከነኩት ሊገድል እንደሚችል በሚገባ ያዉቃል 4 ሜትር ርቆ ያለዉን መስመር በቸልተኝነት እንጨት በመቁረጥ በተፈጠረዉ አደጋ የሞተ በመሆኑ ሀላፊነት የለብንም ፤ሚች እንጨቱ እንድቆርጥለት ድርጅቱን በተደጋጋሚ ጠይቋል ቢባል እንኳ የሰዉን ንብረት ለመቁረጥ መብትም የለንም፤ ባጠቃላይ ተጠሪዎችም ቢሆኑ እራሳቸዉን ችለዉ ሰርተዉ መኖር የሚችሉ በመሆኑ ተጠቃሹን ገንዘብ እንድንከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡

በዚህም መሰረት ችሎቱ ጉዳቱ የደረሰዉ ሚች በፈጸመዉ ጥፋት ነዉ ሲል አመልካች ያቀረበዉ ክርክር ታልፎ የመወሰኑን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙን በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በሰበር መልሳቸዉ የሚሉት የተቆረጠዉ ዛፍ ከመስመሩ 4 ሜትር ርቆ ነዉ ያለዉ የሚለዉ ክርክር ሀሰት ነዉ በስር ፍርድ ቤት 2.85 በአጣሪዉ ኮሚቴ በመረጋገጡ ክርክሩ ውድቅ ሊሆን ይገባል፤ሚች በተደጋጋሚ አመልካች ዛፉን እንዲቆርጥ አመልክቷል፤ የመቁረጥም ሀላፊነት ነበረበት፤ ይህን ባለማድረጉ ሀላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ይከራከራሉ፤፤ አመልካች በበኩሉ ሚች ዛፉን ሲተክልና ቤቱን ሲሰራ በኤሌክትርክ መስመር አጠገብ መስራት አልነበረበትም ፤ዛፉም ቢሆን ባይቆረጥም አደጋ አያመጣም ነበር፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያመጣል ብሎ ቢያስብም ለመቁረጥ ሙያ ያላቸዉን ማማከር ነበረበት ይህን ባላደረገበት ኃላፊነት አለባቸዉ ልንባል አይገባም ዉሳኔዉ ሊሻር ይገባዋል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸዉን ሲመስል፡- እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

በመሆኑም ከተያዘዉ ጭብጥ አኳያ አጠቃላዩን የክርክሩን ይዘት እንዳየነዉ፡- ተጠሪዎቸ የሚች ሚስትና ወላጆች በመሆናቸዉ በመተዳደሪያ ረገድ ለሚደርስባቸዉ ጉዳት ካሳ ጠይቀዋል፡፡ እንግዲህ የተያዘዉም ጉዳይ ሚች ቤቱ አጠገብ የነበረዉ የኤሌክትርክ መስመርና ዛፉ በቅርበት በመኖሩ ቢወድቅ በልጆቹ ላይ ሊያደርስ የሚችለዉን ጉዳት በማሰብ ድርጅቱ (አመልካች) ቆርጦ እንዲያነሳለት ቢጠይቁም ባለመቆረጡ በራሳቸዉ ጊዜ በመቁረጥ ላይ እያሉ ኤሌክትሪኩን በመንካት ሕይወታቸዉ አልፏል፡፡ይህን ተከትሎ በተጠየቀዉ የካሳ ክፍያ ሚች 32 አመት ሊኖሩ ይችላል፤በርትዕ ተጠሪዎች በወር በ2ቱ ቀርጥ መሬት ሰራተኛ 200 ብር ቀጥረዉ ሊያሰሩ የሚችሉ መሆናቸዉን በመጥቀስ ባጠቃላይ የሞራል ካሳን ጨምሮ ብር 77,800 የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት በመወሰኑ፤ አመልካችም ሀላፊነት የለብኝም ሚች አደጋ የማያደርስና ከመስመሩ የማይገናኘዉን ዛፍ ሲቆርጥ ነዉ የሞተዉ መቁረጥ እንኳ አስፈላጊ ቢሆን እንኳ ሙያ ያለዉን ቆራጭ በማማከር በጥንቃቄ መቁረጥ ሲገባዉ ለብዙ አመት ያለችግር አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘዉን የኤሌክትርክ መስመር መንካቱ የራሱ ጥፋት እንጂ ሊያስጠይቀን የሚገባ አይደለም፤ ሚች ቤቱን ሲሰራም ሆነ ዛፉን ሲተክል ወደ መስመሩ መጠጋት አልነበረበትም፤በተጨማሪም ሚች የተከለዉን ዛፍ እንድንቆርጥ አልጠየቁም እንጂ ቢጠይቁም የሰዉ ንብረትን የመቁረጥ መብት የለንም በዚህ ሁሉ ምክንያት ሚችን የመካስ ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክረዋል፡፡እንግዲህ የአመልካችን ኃላፊነት በተመለከተ መስመሩ 2.85 ቅርበት ላይ መኖሩ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ አመልካች እንደሚለዉ በ 4 ሜትር ላይም አይደለም፤ሊደርስ ይችላል ተብሎ የተገመቱትን ነገሮች ረፖርት ሲደርሰዉም ሆነ በራሱ ክትትል አደጋን የማስቀረት ወይም የመቀነስ ሙሉ ኃላፊነት እና የህግ ግዴታ ያለበት መሆኑ ግልጽ ነዉ በመሆኑም የቤቱን ግንባታና የመስመሩን ቅደም ተከተል እንደዋነኛ መከራከሪያ ሊያቀርበዉ የሚገባ አይደለም፤ኃላፊነት የለኝም ሲል አመልካች የሚያቀርበዉን የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ረገድ አጣርቶ ኃላፊነት አለበት ማለታቸዉ የሚነቀፍ አይደለም ብለናል ፡፡ይሁን እንጂ ሚችም ቢሆን በዛፉ ምክንያት ኤሌክትሪክ አደጋ ሊያደርስ ይችላል በማለት ያሰበዉን ከመቁረጡ በፊት ሊያደርስ የሚችለዉን ጉዳት ማሰብና አግባብ ያለዉን ቆራጭ በመያዝ ሊቆርጥ ሲገባ በእርግጥ አደጋ ስለማድረሱ ሳያረጋግጥ ዛፉን በቸልተኝነት መቁረጡ የሚች አስተዋጽኦ የለበትም ለማለት አይቻልም በመሆኑም የፍ.ህ/ቁ 2097(2) መሰረት ተበዳዩ በማስተዋል ቢሰራ ኖሮ የደረሰበትን ጉዳት ሊያቀለዉ ወይም ሊያግደዉ የሚችል ሲሆን በደረሰበት ጉዳት በሙሉ ካሳ መጠየቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይችል መሆኑን ይደነግጋል ፤በተያዘውም ጉዳይ ጥንቃቄ በተሞላበት እና በማሰተዋል ቢሰራ ኖር አደጋዉን ይቀንስ ነበር የሚለዉን ግንዛቤ ይዘናል፡በዚህ ሁሉ ምክንያት ለደረሰዉ አደጋ የሚች አስተዋጽኦ አለ፤ ካልን በፍ.ብ/ህቁ. 2098 (1)መሰረት በከፊል ሀላፊነት አለበት ማለት ነዉ፤ በመሆኑም አመልካች አለበት የተባለዉን የጉዳት ካሳ መጠን በማሻሻል 38,400 ሊሆን የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡የሞራል ጉዳት ካሳው ግን የሚነካ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ፡፡

በመጨረሻም በኦሮሚያ ክልል አዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሚችን ለጉዳቱ መድረስ የነበረዉን የቸልተኝት ከፊል አስተዋጽኦ ሳያገናዝቡ አመልካችን ሙሉ በሙሉ ሀላፊ በማድረግ ተጠቃሹን የገንዘብ መጠን ካሳ እንዲከፍል መወሰናቸዉ በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ፡፡በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ክልል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 37792 በቀን 05/13/2006 እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በመ.ቁ.189401 በቀን 4/2/07 የሰጡት ዉሳኔዎች ተሻሽሏል፡፡
2. ሟች ለደረሰበት አደጋ በከፊል ሃላፊነት ነበረበት ብለናል፡፡በመሆኑም አመልካች ለተጠሪዎች ሊከፈል የሚገባው የጉዳት ካሳ መጠን ብር 38,400.00፣ የሞራል ካሳ ደግሞ ብር 1000.00 በድምሩ ብር 39,400.00 (ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ብር) ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የግራቀኙ የወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
4. በህዳር 08/2007 ተሰጥቶ የነበረዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 106147

ቀን ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- እሸት ኢንጅነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ፋንታዬ ቢያድግልኝ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የአውሲረሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 4585 ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3033 መስከረም 5 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ክስ የአመልካች ሠራተኛ የሆነ ልጃቸው አመልካች የንፅህና መጠበቂያ ውሃ ባለማቅረቡ ምክንያት፣ሥራ ውሉ፣ አዋሽ ወንዝ ውስጥ ገብቶ ሲታጠብ ስለመሆኑ በሥራ ላይ እያለ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ስለዚህ የአምስት ዓመት ደመወዝ ብር 270,000 /ሁለት መቶ ሰባ ሺ ብር/ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ሚች የድርጅቱ ሠራተኛ አይደለም ሚች ከአመልካች ንዑስ የሥራ ውል ተዋውሎ የሚሠራው ድርጅት ሠራተኛ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ከንዑስ የሥራ ተቋራጭ ሠራተኞች ውሃ የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት ተከሳሽ /አመልካች/ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ሚች የሥራ ውል ግንኙነት የላቸውም፡፡ ሆኖም ከንዑስ ተቋራጩ ሠራተኞች ውሃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት አመልካች መሆኑ በውሉ የተገለፀ በመሆኑ፣ ተከሳሽ ለሚች ከውል የመነጨ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብሎ ብር 31,000 /ሰላሣ አንድ ሺ ብር/ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡
3. አመልካች ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ሚች የተጠሪ ሠራተኛ አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ባልተከራከርንበት እና በማስረጃ ያልተረጋገጠ ጭብጥ በማንሣት፣ አመልካች፣ ውሃ የማቅረብ ግዴታውን አልተወጣም ብለው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ አመልካች በውል የገባውን ውሃ የማቅረብ ግዴታ መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች የተጠሪ ልጅ በአዋሽ ወንዝ ገብቶ ሲታጠብ ለደረሰበት የሞት አደጋ ኃላፊ ነው ተብሎ ካሣ እንድከፍል የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ክስ ያቀረበው ሚቹ ልጁ የአመልካች ሠራተኛ ነው፡፡ በሥራ ላይ እያለ ጉዳት ደርሶበታል በማለት ነው፡፡ የተጠሪ ልጅ የአመልካች ሠራተኛ አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የተጠሪ ልጅ የአመልካች ሠራተኛ ሣይሆን ከአመልካች ንዑስ የሥራ ውል ተዋውሎ የሚሠራው ንዑስ የሥራ ተቋራጭ ድርጅት ሠራተኛ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ መሆኑን ውሣኔው ያሳያል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 110 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አመልካች ካሣ እንድከፍለው ለመጠየቅ የሚችልበት የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ተጠሪ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ መሠረት በማድረግ የቀረበው የካሣ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡
6. የተጠሪ ልጅ የንዑስ ሥራ ተቋራጭ ሠራተኛ ነው ከተባለ፣ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚችለው በንዑስ ሥራ ተቋራጩ ላይ እንጅ በአመልካች ላይ ሊሆን አይችልም፡፡ አንድ ሰው በአንድ ጉዳት ኃላፊ የሚሆነው፣ ከሕግ ከውልና ከውል ውጭ ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆንበት ህጋዊ መሠረት ሲኖር ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ለንዑስ ተቋራጩ ሠራተኞች ውሃ የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት አመልካች ነው በማለት አመልካች በተጠሪ ልጅ ላይ ለደረሰው ጉዳት ከውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመነጨ ኃላፊነት እንዳለበት በመግለፅ ወስነዋል፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቶቹ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሱት በአመልካች በንዑስ ሥራ ተቋራጩ መካከል የተደረገውን ውል በዝርዝር ሣያዩና፣ ተጠሪ በንዑስ ሥራ ተቋራጩ ላይ የቀረበው ክስ ሣይኖር፣ ንዑስ ሥራ ተቋራጩ ክስ ቀርቦበት አመልካች ውል ጋር ያደረገውን ውል እንደመከላከያ ባላቀረበበት ሁኔታ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በውል የገባውን ግዴታ ባለመወጣቱና በተጠሪ ልጅ ሞት መካከል፣ ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት ያለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በተጠሪ በኩል ስለመቅረቡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ አያሳይም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ልጅ ሞት ከውል የመነጨ ኃላፊነት አለበት በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

7. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ በተጠሪ ልጅ ላይ የሞት አደጋ የደረሰበት አመልካች ከውል ውጭ ስለሚመጣ ኃላፊነት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2027 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2136 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት፣ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ አያሳይም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የተጠሪ ልጅ አዋሽ ወንዝ ገብቶ ሲታጠብ ለደረሰበት የሞት አደጋ ከውል ውጭ በኃላፊነት የሚጠየቅበት የሕግ መሠረት የሌለ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካች ከሕግ፣ ከውልና ከውል ውጪ የተጠሪ ልጅ አዋሽ_ወንዝ ገብቶ ገላውን ሲታጠብ ለደረሰበት የሞት አደጋ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ምክንያት ሣይኖር፣ የአውሲረሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ ከላይ የጠቀስናቸውን ድንጋጌዎች የሚጥስ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአውሲራሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.101229

ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች ፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የኢት/ኤሌ/ኃ/ኮ/ ነገሌ ቦረና ዲስትሪክት - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ጣሂር ሣፋይ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ክሳሽ፣ የአሁኑ አመልካች የስር 2ኛ ተከሳሽ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ ደግሞ የቻይና ኤም.ሲ.ሲ 17 መንገድ ስራ ድርጅት ነበር፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ፡- በአመልካች ድርጅት እየሰራሁ ሳለ ሳፋ በሚባል ዕቃ መንገድ እያሳየሁ እያለሁ ይህ ብረት የኤሌክትሪክ ሽቦ በመንካት ባደረሰብኝ ጉዳት ግራ እግሬ ተቆርጦ በሌላ አካሌ ላይ ጉዳት ስላደረሰብኝ ሰርቼ የመኖር አቅም ሙሉ በሙሉ አጥቻለሁ፡፡ በመሆኑም የስር 1ኛ ተከሳሽ በአዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 27(3) 96(3) ፣ 97(መ) ፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ በፍ.ብ.ሀ.ቁ 2027፣ 2028 መሰረት ኃላፊነታቸው እንዲለይላቸው፣ የካሳውን መጠን በተመለከተም በቀን 35 ብር እንደሚያገኙና ዕድሜአቸዉ 20 ሲሆን እስከ 40 አመት ሊኖሩ እንደሚችሉ ዘርዝረው ባጠቃላይ ብር 499,996.80 እና የሞራል ካሳ ይከፈላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ ሀላፊነት የለበትም ተብሎ ክሱ ሲወጣ አመልካች በሰጠዉ መልስ፡- የኤሌክትሪክ መስመሩ ደረጃዉን የጠበቀ ነው፣ተጠሪ ስራዉን ሲሰራ ጥንቃቄ ባለማድረጉ እና የያዘዉን ብረት ወደ የኤሌክትሪክ ከፍ በማድረግ ያስነካዉ መሆኑን አልካደም፣ በመሆኑም በፍ.ብ.ሀ.ቁ 2086 (2) መሰረት አያስጠይቀኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮና አመልካች የኤሌክትሪክ ሽቦዉን በምን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያክል ከፍታ ላይ እንደዘረጋ እና መዘርጋት ያለበት በምን ያክል ከፍታ እንደሆነ የቅርንጫፉ ድርጅት እንዲገልጽ ከአደረገው በኋላ ፍርድ ቤቱ በጠየቀዉ መሰረት ከቀበሌዉ መስተዳድር ጋር በመሆን በቦታዉ በመገኘት የከፍታዉ ስታንደርድ 5.2 ሜትር ሲሆን አደጋዉ ሲደርስ በ5 ሜትር ከፍታ ላይ እንደነበረ አጣርቶ በደብዳቤ ቁ 397/7/05 በቀን 21/6/ 05 ዓ/ም ከተገለፀለት በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ስታንደርዱን ጠብቆ ሽቦዉን ባለመዘርጋቱ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ በፍ.ብ.ህ.ቁ 2069 (1) (2) መሰረት ኃላፊነት አለበት በማለት ጀምሮ የካሳውን መጠን በተመለከተ ደግሞ የጉዳት መጠኑ 45% መሆኑ በመረጋገጡ ይሄው የጉዳት መጠን ከተጠሪው የወደፊት አማካይ እድሜ 40 አመት ጋር ተነጻጽሮ ሲታይ ብር 219,373.6 እንደሚሆን፣ በዚሁ ገንዘብ የሞራል ካሳን 1000 ብር ሲጨመር ባጠቃላይ ብር 220,378.60(ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከስልሳ ሳንቲም) እንዲከፈለዉ ወስነዋል። በቀጣይነት ጉዳዩን ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን በማከራከር በድምጽ ብልጫ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ባግባቡ ነዉ በማለት አጽንቶታል።

የአመልካች ቅሬታም ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ። በመሆኑም አመልካች ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ቅሬታዉን ስገልጽ ፡- የኤሌክትሪክ ሽቦ ከምሰሶ ወደ ምሰሶ በአግባቡ የተወጠረ ሲሆን የመጣዉ ልዩነት የ 20 ሳንቲ ሜትር ደግሞ ከመሬት አቀማመጥ ሊከሰት ይችላል፣ ፍርድ ቤቱ ይህን ከግምት ሳያስገባ መወሰኑ እና ተጠሪ በራሱ ጊዜ አቅጣጫ ማሳያ ወደ ኤሌክትሪክ ሽቦ ያስጠጋዉ እና የተበጠሰ ሽቦ ሳይኖር ተጠሪ ጥፋተኛ ሆኖ ሳለ ሙሉ በሙሉ አመልካችን ሀላፊ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል።

ተጠሪ በሰበር መልሳቸዉ የሚሉት፤- ሽቦ በምሰሶ ሲወጠር በዳገት ወይም በገቅተኛ ቦታ ቢሆንም በዛዉ ልክ ከፍ ብሎ ስለሚወጠር የመሬት አቀማመጥ ልዩነት አያመጣም፣ ሽቦዉ አልተበጠሰም በማለት ብቻ በእኔ ጥፋት መፈጸሙን ሳያረጋግጥ አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር አግባብነት የለዉም፣ የቀረበዉም ሪፖርት ሽቦዉ ስታንደርዱን ጠብቆ ያለመወጠሩን አረጋግጧል፣ በመሆኑም በቀን የሚገኘዉን ገቢና የደረሰብኝን የጉዳት መጠን የመስራት አቅሜ እንዲቀንስ ያደረገ መሆኑ ተረጋግጦ ካሳው መወሰኑ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክሯል። አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ ፡-ተጠሪ ለደረሰዉ አደጋ ቸልተኝነት አለበት፣ ስራዉን እንዲያከናዉን ያዘዘዉ የለም፣ ባጠቃላይ ጉዳት ካሳ መጠየቅ አይችልም፣ ከፍ.ብ.ህ.ቁ.2086 (2) ጋር ይቃረናል፣ በፍ.ብ/ህ.ቁ 2155(3) መሰረት ሊታይ ሲገባ የታለፈ በመሆኑ ዉሳኔዉ ሊሻር ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀዉን ይመስላል።እኛም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር የክርክሩን አጠቃላይ ይዘት እንዳየነዉ የጉዳዩ መነሻ የነበረዉ ተጠሪ በምሰራበት የመንገድ ስራ ድርጅት በመሰራት ላይ ባለዉ መንገድ ሳፋ(ጠቋሚ) መሳሪያ በመያዝ በማገልገል ላይ እያለ የተወጠረዉን የኤሌክትርክ ሽቦ በመንካት በደረሰዉ አካል ጉዳት የግራ እግሩ መቆረጡን በማረጋገጥ እና 45% ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ጠቅሶ የጉዳት ካሳ እና የሞራል ካሳ ይከፈለዉ ዘንድ በመጠየቁ ሲሆን አመልካችም የተዘረጋዉ የኤሌክትሪክ ሽቦ ስታንደርዱን ጠብቆ የተዘረጋ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም፣ ጉዳቱ በተጠሪ ጥፋት የደረሰ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን ያዩት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉዳት መድረሱን በማረጋገጥ ኃላፊነትን በተመለከተ የተወጠረዉ የኤሌክትሪክ ሽቦ ስታንደርዱን ጠብቆ የተዘረጋ መሆኑን ለማጣራት ሲባል የቀበሌዉ መስተዳደር እና የግራ ቀኙ ባሉበት የቅርንጫፍ ድርጅቱ ስለሁኔታዉ እንዲገልጽ በማድረግ በተረጋገጠዉ መሰረት መስመሩ (ምሶሶው) በ5.20 ሜትር ርቀት ሊኖረዉ ሲገባ በ5 ሜትር ርቀት ላይ የተገኘ መሆኑን በማረጋገጥ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2069(1)(2) መሰረት በተፈለገዉ ጥራት ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነዋል፡፡ እንግዲህ አመልካች መከራከሪያዉ ያደረገዉ የተደረገዉ የመስመር መወጠር ልኬት የመሬቱን አቀማመጥ አላገናዘበ፣ የተበጠሰ ሽቦ ሳይኖር በተጠሪ ጥፋት ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም የሚለውን ነው፡፡

ይሁን እንጂ የመስመር ዝርጋታው ስንታደርዱን ያለመጠበቁ በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ በተረጋገጠበት ሁኔታና ጉዳቱም በተጠሪ ጥፋት ስለመድረሱ ያቀረበዉ ማስረጃ ሳይኖር በዚህ ረገድ ለዚህ ችሎት የሚያቀርበው የፍሬ ነገር ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ መስመሩ ደረጃውን ጠብቆ የተዘረጋ መሆን ያለመሆኑና በተጠሪ በኩል ጥፋት የነበረ መሆን ያለመሆኑ በማስረጃ የሚጣሩ ነጥቦች ሲሆኑ በዚህ ረገድ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ደግሞ ፍሬ ነገሩን አጣርተውና ማስረጃዎቹን መዝነው የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርገዋል፡፡ ይህ ለሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገሩን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ስርዓቱን ጠብቀው ያጣሩትና የደመደሙትን የፍሬ ነገር ክርክር እንደ እውነት የምንቀበለው ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች የመስመሩ ዝርጋታ ደረጃውን የጠበቀ ነው፣ በተጠሪ በኩል ጥፋት ነበር በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው የለውም በማለት አልፈነዋል፡፡

ሌላዉ ተጠሪ በቀጣሪው ስራ ላይ ሳይታዘዝ ስለመስራቱም የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አግባብ በተመሰረተ የስራ ግንኙነት ስራ ላይ እያሉ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ መረጋገጡም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 96(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስን በማመሳሰል የትርጉም ደንብ ስናየው በአመልካች በተፈጸመ ጥፋት ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዙ ድንጋጌዎች አግባብ ካሳ ከመጠየቅ የማይከለክላቸው ሁኖ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው የሚፈነዱ ወይም መርዝ የሚሆኑ ቅመማት ሥራ ላይ ማዋል ወይም በማከማቸት ወይም ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር በመዘርጋት ወይም መሬትን የተፈጥሮ መልክ በመለወጥ ወይም በተለይ አደገኛ የሆነ የኢንዱስትሪ ሥራ በማካሄድ ይህ ሥራው በሌላው ሰው ላይ አደጋ ያደረሰ እንደሆነ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2069/1/ የሚደነግግ ሲሆን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ተግባራትን በመፈፀም በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰው መንግሥትም ቢሆን ወይም ሥራውን እንዲሠራ በባለሥልጣን የተፈቀደለት መሥሪያ ቤት ቢሆንም በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2069(1) የተደነገገው ደንብ ተፈፃሚ የሚሆን መሆኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2069(2) በግልፅ ይደነግጋል፡፡ከዚህ ከሕጉ ይዘትና መንፈስ አንጻር ሲታይም ተጠሪ ከላይ በተገለፁት የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ለደረሰው ጉዳት የኤሌክትሪክ መስመሩ ባለሀብት በመሆኑ ብቻ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተገቢነት አይኖረውም፡፡ አመልካች ለደረሰው ጉዳት በኃላፊት የማያስጠይቀው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2086(2) በሚደነግገው መሠረት ጉዳቱ የደረሰው በሙሉ ወይም በከፊል በተጠሪ ጥፋት መሆኑን በማስረጃ በማስረዳትና በማረጋገጥ ነው፡፡አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ አለመሆኑን ለማስረዳትም በመጀመሪያ የኤሌክትሪክ መሥመሩን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስለ ኤሌክትሪክ ሥራዎች የወጣው ደንብ ቁጥር 49/1991 አንቀጽ 35 ስለ ኤሌክትሪክ መስመሮችና መሣሪያዎች ደህንነት የደነገገውን በሚያሟላ ሁኔታ ተዘርግቶ የነበረ መሆኑን ሊያስረዳ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን መሰረት አድርገን ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች ለክሱ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡

ባጠቃላይ በተጠሪ ላይ የእግር መቆረጥ ደርሶበታል፣ በዚህም የተነሳ የመስራት አቅሙ በ45% መቀነሱ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ሊያገኝ የነበረዉ እና ለወደፊት የሚያገኘዉ ገቢ/ጥቅም የቀረበት በመሆኑ የጉዳት ካሳው ከደረሰዉ ጉዳት መጠን ጋር ተመዛዝኖ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2090 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የሚደነግጉትን መሰረት ተደርጎ የሞራል ካሳን ጨምሮ ብር 220,378.60 (ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከስልሳ ሳንቲም) ሊከፈለዉ ይገባል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ሊነቀፍ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የህጉንም አላማ ስናይ የተጎዳ (ጉዳት የደረሰበት) ሰዉ በጉዳት አድራሹ ሊካስ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ በህገ መንግስታችንም አንቀጽ 14 ሥር ማንኛዉም ሰዉ ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና ነጻነት መብት አለዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም መንግስትም ሆነ ማንኛውም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ የአካል ደህንነት የመጠበቅ የህግ ግዴታ አለበት፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይም የሰበር ችሎቱ በመ.ቁ 42962 እና በሌሎችም መዝገቦች ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ዉሳኔ በአዋጅ ቁ454/97 አንቀጽ (2) (1) መሰረት በሀገሪቱ ባሉት ፍርድ ቤቶች አስገዳጅነት ያለዉ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የደረሰዉን ጉዳት በማረጋገጥ የተጠቀሰዉን የጉዳት ካሳ እና የሞራል ካሳ ክፍያ መወሰናቸዉ አግባብነት ያለዉ ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለልም የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በተጠሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት አመልካችን ኃላፊ በማድረግ የጉዳት ካሳ እና የሞራል ካሳ ብር 220,378.60(ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከስልሳ ሳንቲም) ሊከፈለዉ ይገባል በማለት የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመቁ 06611 በቀን 10/10/2005 ዓ/ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 168406 በቀን 25/6/2006 ዓ/ም የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ህ/ስ/ስ ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰዉ የአካል ጉዳት ሀላፊ ነዉ ተብሎ ጉዳት ካሳ ብር 220,378.60(ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከስልሳ ሳንቲም) ይክፈል መባሉ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የግራ ቀኙ የወጪ ኪሳራቸዉን ይቻቻሉ ብለናል፡፡
4. ግንቦት 27 ቀን 2006 ዓ.ም በዚህ ችሎት ተሰጥቶ የነበረዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተዉ አካል ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 90529

ሐምሌ 2 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ኃይለየሱስ መንግስቱ ይግዛው - ጠበቃ ውብሰራ ሹመቴ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አማኑኤል ፀጋ የከተማ ሱቅ ቤቶች ልማት አክሲዮን ማህበር-

ጠበቃ ደረጀ ኢቲቻ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከንግድ ቤት ኪራይ ውል አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሽ በ01/11/2003 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በአዲስ ከተማ ከፍለ ከተማ በቀበሌ 08/09/18 ከሚገኙት የተከሳሽ ድርጅት ሱቆች መካከል ከሳሽ በ01/11/2001 ዓ.ም በተደረገ ውል በምድር ቤት የሚገኝ 345 ካ.ሜ ስፋት ያለው አንድ የንግድ ሱቅ በካሬ ሜትር በብር 30 (ሰላሳ) ሂሳብ ለአምስት ዓመት ተከራይተው የምግብ እና መጠጥ ቤት ንግድ ፈቃድ በማውጣት እየሰሩበት እያለ ተከሳሽ ድርጅት ከ22/09/2003 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሱቁ የሚመጣውን የኤሌክትሪክ እና የውሃ መስመር በማቋረጡ የኤሌክትሪክ መስመሩ በፖሊስ እና በኤሌክትሪክ ኃይል ባለስልጣን ትብብር እስከተከፈተበት 22/10/2003 ዓ.ም ድረስ ከሳሽ ከንግድ ቤቱ ስራ በየቀኑ ያገኙ የነበረውን የተጣራ ትርፍ ብር 10,000 (አስር ሺህ) ለ31 ቀናት በማጣታቸው የብር 310,000 (ሶስት መቶ አስር ሺህ) ጉዳት እንደደረሰባቸው፣ ተከሳሽ የውሃ መስመሩን በኋላም ቢሆን እንዳልከፈተው፣ ከ22/10/2003 ዓም ጀምሮ እስከ 30/12/2003 ዓ.ም ድረስ ባሉት 68 ቀናት ደግሞ ገቢው በግማሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀነሰ እና ከሳሽ በየቀኑ የብር 5000 (አምስት ሺህ) ገቢ እንዳጡ፣በእነዚህ 68 ቀናት ከሳሽ ያጡት ገቢ ብር 340,000 (ሶስት መቶ አርባ ሺህ) እንደሆነ የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሽ ድርጅት በከሳሽ ላይ ላደረሰው ጉዳት በድምሩ ብር 650,000 (ስድስት መቶ ሃምሳ ሺህ) ለከሳሽ እንዲከፍል ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ26/11/2003 ዓ.ም በሰጠው መልስ ተከሳሽ የንግድ ሱቁን ያከራየው አቃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለተባለ ተከራይ እንጂ ለከሳሽ አለመሆኑን፣ ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ንብረት የተገለገሉት የኪራይ ውል እና መብት ሳይኖራቸው መሆኑን፣ ከሳሽ ከተከሳሽ ማህበር ጋር በራሳቸው ስም ያደረጉት የኪራይ ውል ባለመኖሩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33 (2) መሰረት በተከሳሽ ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችል መብት እና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን፣ተከሳሽ ማህበር የውሃም ሆነ የኤሌክትሪክ መስመር ያላቋረጠባቸው መሆኑን፣የኤሌክትሪክ መስመሩ አውቶማቲክ የጠፋው በራሱ ችግር መሆኑን፣ተከሳሽ ማህበር የኤሌክትሪክ መስመሩን አቋርጦት ቢሆን ኖሮ እንኳ ከሳሽ ጀኔሬተር ገዝተው ጉዳቱን መቀነስ ሲችሉ የብር 650,000 ጉዳት ደርሶብኛል በማለት ክስ ማቅረባቸው ተገቢነት የሌለው መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

በሌላ በኩል ከሳሽ ከተከሳሽ ማህበር ጋር ያደረጉት ውል ሳይኖር በስራ አስኪያጅነት በሚመሩት አቃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም በተከራዩት የተከሳሽ የንግድ ቤት ውስጥ የንግድ ፈቃዱን በራሳቸው ስም አውጥተው የንግድ ስራ በማከናወን በተከሳሽ ማህበር ንብረት አላግባብ የበለጸጉ መሆኑን ገልጾ በአቃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም የንግድ ቤቱን ከያዙበት በ01/11/2001 ዓ.ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት 26/11/2003 ዓ.ም ድረስ በካሬ ሜትር በአነስተኛ ዋጋ በብር 50 (ሃሳብ) የ345 ካ.ሜ ስፋት ያለው የንግድ ቤት ኪራይ ብር 638,250 (ስድስት መቶ ሰላሳ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ) ከነወለዱ እንዲከፍሉ፣ክሱ ከቀረበበት ቀን በኃላ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ ያለውን ኪራይም በተመሳሳይ ስሌት መሰረት ከነወለዱ እንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንለት ዘንድ በ26/11/2003 ዓ.ም የተዘጋጀ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ ለዚህ ክስ ከሳሹ በ08/03/2004 ዓ.ም በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጡት መልስ በካሬ ሜትር ብር 50 ሂሳብ ለመክፈል ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር ያደረጉት ስምምነት አለመኖሩን፣ከአቃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር ውሉ የተደረገው በካሬ ሜትር በብር 30 ሂሳብ መሆኑን፣ አስቀድሞ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ሳይኖር ኪራዩ ተከፍሎት ቤቱን ለማስለቀቅ ተከሳሽ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቱም ከሳሽ የንግድ ቤቱን ከተከሳሽ ማህበር ስለመከራየታቸው ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን እና ከተከሳሽ ማህበር የንግድ ቤቱን የተከራየው አኃኔ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደሆነ በማስረጃ መረጋገጡን ገልጾ ከሳሽ ከተከሳሽ ማህበር ጋር ያደረጉት ውል ባለመኖሩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33 መሰረት በተከሳሹ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ዋናውን ክስ በ24/09/2004 ዓ.ም. በትዕዛዝ ውድቅ አድርጓል፡፡ ቀጥሎም የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን በተመለከተ ክሱን ከሰማ በኃላ የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦቹን በ03/03/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውድቅ አድርጎ በማለፍ በ02/05/2005 ዓ.ም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የከሳሽ ተከሳሽ ከተከሳሽ ከሳሽ ጋር በራሳቸው ስም ያደረጉት የኪራይ ውል ሳይኖር በማህበር ስራ አስኪያጅነታቸው የኪራይ ውሉን በአኃኔ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም ከተዋዋሉ በኃላ በራሳቸው ስም የንግድ ፈቃድ አውጥተው የንግድ ስራ ሲያከናውኑ መቆየታቸው መረጋገጡን፣ይህም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2162 ስር እንደተመለከተው በተከሳሽ ከሳሽ ንብረት አላግባብ መበልጸጋቸውን የሚያመለክት መሆኑን፣የግራ ቀኙ ምስክሮች በተሰሙበት ጊዜ አካባቢ በ3ኛ ፎቅ ላይ የሚገኙት የንግድ ቤቶች በወር በካሬ ሜትር በብር 120 ሂሳብ እንደሚከራዩ በተከሳሽ ከሳሽ ምስክሮች የተገለጸ መሆኑን፣የከሳሽ ተከሳሽ የያዙት የንግድ ቤት የሚገኘው በምድር ቤት ላይ በመሆኑ ኪራዩ በፎቅ ላይ ከሚገኙት የንግድ ቤቶች በላይ እንደሆነ ግምት የሚወሰድበት መሆኑን እና በዚህም ምክንያት በተከሳሽ ከሳሽ የተጠየቀው በካሬ ሜትር በወር ብር 50 የኪራይ ስሌት ተቀባይነት ያለው እና ምክንያታዊ መሆኑን በዝርዝር ገልጾ የከሳሽ ተከሳሽ ይዘውት የሚገኙትን የንግድ ቤት ለተከሳሽ ከሳሽ እንዲያስረክቡ፣ በአኃኔ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም የንግድ ቤቱን ከያዙበት በ01/11/2001 ዓ.ም ጀምሮ ውሳኔው እስከተሰጠበት 19/06/2005 ዓ.ም. ድረስ ላለው የ43 ወራት ከ19 ቀናት ጊዜ ኪራዩን በካሬ ሜትር በብር 50 እና በየወሩ በብር 17,250 (አስራ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ) ሂሳብ በድምሩ ብር 752,675 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ አምስት) ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለተከሳሽ ከሳሽ እንዲከፍሉ፤ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ ያለውን ኪራይም በተመሳሳይ ስሌት በወር ብር 17,250 (አስራ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ) ሂሳብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በአከራካሪው ቤት የምግብና የመጠጥ የንግድ ፈቃድ አውጥተው ሲሰሩበት የነበረው በስራ አስኪያጅነት ሲመሩት በነበረው አኃኔ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስምም ቢሆን ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባውን የአንድ ዓመት ከሶስት ወር ቅድሚያ ኪራይ ከፍለው መሆኑ ባላከራከረበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና በስሙ ኪራዩ የተከፈለበትን ቤት አመልካች ለማላቸው አላግባብ እየሰሩበት ነው በማለት አቃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሳይቃወም አመልካችን ሕገወጥ ብልጽግና አግኝተሃል በሚል በግራ ቀኙ መካከል ጭቅጭቅ ከተፈጠረ እና የአመልካች የንግድ እንቅስቃሴ ከቆመ በኃላ ያለውን የቤት ኪራይ ከነወለዱ እንዲከፍሉ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ያላግባብ ስለመበልጸግ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2162 ከተመለከተው ድንጋጌ አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. አመልካቹን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
2. አመልካቹ ኃላፊ የተደረጉበት የኪራይ ገንዘብ መጠን ተገቢነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ከተጠሪ ጋር የንግድ ቤት ኪራይ ውል የገባው አመልካች ሳይሆኑ አቃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሆኑ፣አመልካች የአቃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ መሆናቸው፣አቃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በውል ከተጠሪው በተከራየው የንግድ ቤት ውስጥ የምግብ እና የመጠጥ አገልግሎት ንግድ ፈቃድ አውጥተው የንግድ ስራ ሲያከናውኑ የነበሩት አመልካች መሆናቸው፣አመልካች የንግድ ፈቃድ አውጥተው የንግድ ስራ ሲያከናውኑበት ለነበረው የተጠሪ ቤት ከተጠሪው ጋር የገቡት የኪራይ ውል አለመኖሩ በአመልካቹ ያልተካዱ እና በስር ፍርድ ቤትም የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡በመሰረቱ አቃጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከአመልካቹ የተለየ የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው በመሆኑ አመልካቹ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ መሆናቸው በንግድ ቤቱ የንግድ ስራ ሲያከናውን የነበረው አመልካች በስራ አስኪያጅነት የሚመሩት ማህበር ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡በሌላ ሰው የስራ ድካም ወይም የሌላ ሰው ሀብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ጥቅም ባገኘበት መጠን ለባለሀብቱ ወይም ጉልበቱ ለደከመው ሰው ይህ አድራጎት ባደረሰበት ጉዳት መጠን ኪሳራ መክፈል የሚገባው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2162 ይደነግጋል፡፡አመልካች በተጠሪው ሀብት መገልገላቸው የተረጋገጠ ሲሆን በተጠሪው ሀብት ለመገልገል ያስቻላቸው ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ ማስረዳት እንዳልቻሉ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት በተጠሪው ሀብት አላግባብ በመገልገል ባገኙት የማይገባ ብልጽግና መጠን ለተጠሪው ኃላፊ የማይደረጉበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም አመልካቹን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የሌላ ሰው ሀብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው ለባለሀብቱ ኪሳራ ለመክፈል የሚገደደው ከዚሁ ተግባሩ ባገኘው ጥቅም መጠን እና በአንጻሩ በባለሀብቱ ላይ ባደረሰው ጉዳት መጠን ስለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ተጠሪው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ ቤት ለአጎጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ያከራየው ከ01/11/2001 ዓ.ም ጀምሮ ለአምስት ዓመታት በካሬ ሜትር በብር 30 (ሰላሳ) ሂሳብ ስለመሆኑ ተጠሪው ራሱ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ያቀረበው የኪራይ ውል ያመለክታል፡፡ የኪራይ ተመኑን በመካከል ተጠሪ የመጨመር መብት ያለው ስለመሆኑም የኪራይ ውሉ አያመለክትም፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በኪራይ ውሉ መሰረት አጎጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የንግድ ቤቱን ይዞ ለአምስት ዓመታት ተገልግሎበት ቢሆን ኖሮ ተጠሪው ሊያገኝ ይችል የነበረው ገቢ በወር በካሬ ሜትር 30 ሂሳብ ተሰልቶ የሚገኘውን ጥቅም መጠን ነው፡፡ አመልካች የንግድ ቤቱን አላግባብ ይዘው በመገልገል ተጠሪውን ላሳጡት ጥቅምም ለተጠሪው ኪሳራ መክፈል የሚገባቸው ተጠሪው ባጣው ገቢ መጠን በመሆኑ አመልካች ኪሳራውን በካሬ ሜትር በብር 50 (ሃምሳ) ሂሳብ ለመክፈል የሚገደዱበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ አመልካቹ በስራ አስኪያጅነት በሚመሩት አጎጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስምም ቢሆን የአንድ ዓመት ከሶስት ወር ኪራይ የከፈሉ በመሆኑ ይኸው የኪራይ ገንዘብ ተጠሪው ከአመልካች ከሚፈልገው ገንዘብ ተቀናሽ መደረግ ይገባው ነበር በማለት አመልካች ያቀረቡትን እና በአጣሪው ችሎትም በጭብጥነት የተያዘውን የአቤቱታ ነጥብ በተመለከተ አመልካቹ በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር እና ጥያቄ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ ይህ የክርክር ነጥብ የቀረበው አሁን በሰበር ደረጃ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው እንደማይገባ ገልጾ ተጠሪው በሰበር መልሱ ያቀረበውን ክርክርም አመልካች በመልስ መልሳቸው አላስተባበሉም፡፡በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ የክርክር ነጥብ ደግሞ በበላይ ፍርድ ቤቶች ሊስተናገድ እንደማይገባው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 329 (1) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጎጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስምም ቢሆን የአንድ ዓመት ከሶስት ወሩ የኪራይ ገንዘብ ተከፍሏል ወይስ አልተከፈለም? የሚለው ጥያቄ አሁንም ድረስ አከራካሪ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን ገንዘቡ ተከፍሏል የሚባል ቢሆን እንኳ በዚህ ገንዘብ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ገንዘቡን ከፍያለሁ የሚለው ማህበር እንጂ አመልካቹ አይደሉም፡፡በመሆኑም በአጎጌ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም የተከፈለው ገንዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተወሰነብኝ የገንዘብ መጠን ላይ ተቀናሽ ሊደረግልኝ ይገባ ነበር በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በንግድ ቤቱ መገልገል የጀመሩት በ01/11/2001 ዓ.ም መሆኑ ያልተካደ ሲሆን በፌዴራል የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት አማካይነት ለተጠሪው ያስረከቡት ደግሞ በ11/10/2005 ዓ.ም ስለመሆኑ ተጠሪው በሰበር መልሱ ላይ ገልጿል፡፡አመልካችም በመልስ መልሳቸው ይህንን አላስተባበሉም፡፡ ተጠሪው የኤሌክትሪክ እና የመብራት መስመሮችን በማቋረጡ ምክንያት አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል እንዳልቻሉ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከቤቱ ያገኙት ጥቅም አለመኖሩን በሰበር አቤቱታቸው ላይ የገለጹ ሲሆን ተጠሪው በሰጠው መልስ አመልካቹ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት የኤሌክትሪክ እና የመብራት መስመሮች ስለተቋረጡባቸው ሳይሆን በአዲሱ የንግድ ምዝገባ አዋጅ አግባብ እንደገና ለመመዝገብ እና ፈቃዳቸውን ለማሳደስ የኪራይ ውል ማቅረብ ስለነበረባቸው እና ማቅረብ ስላልቻሉ መሆኑን ገልጾ ከመከራከር በቀር አመልካች በንግድ ቤቱ መገልገል ያቆሙት ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ስላለመሆኑ የማስተባበያ ክርክር አላቀረበም፡፡በመሆኑም አመልካች በካሬ ሜትር በብር 30 ሂሳብ ኪሳራውን ለመክፈል የሚገደዱት ከ01/11/2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 22/09/2003 ዓ.ም ድረስ ላለው ጊዜ ነው፡፡

ከ22/09/2003 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን ለተጠሪው እስካስረከቡበት 11/10/2005 ዓ.ም ድረስ ላለው ጊዜ አመልካች ለተጠሪው ኪሳራ የመክፈል ግዴታ አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚለውን ነጥብ በተመለከተ በዚህ ነጥብ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት በምን ምክንያት እንደሆነ በቅድሚያ ተገቢው ማጣራት ሊደረግ ይገባል፡፡በከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች በቤቱ መገልገል ያቆሙት ተጠሪው የኤሌክትሪክ እና የመብራት መስመሮችን ስላቋረጠባቸው እንደሆነ በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪው ይህንን አድራጎት እንዳልፈጸመ ክዶ ተከራክሯል፡፡ በመሰረቱ አንድ ሰው ለባለንብረቱ ኪሳራ ሊከፍል የሚገደደው በሌላ ሰው የስራ ድካም ወይም የሌላ ሰው ሀብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ቀደም ሲል በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2162 ላይ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት በተጠሪው ጥፋት መሆኑ የሚረጋገጥ ከሆነ ጥቅም ባላገኙበት እና ጥቅሙን ሳያገኙ የቀሩትም በተጠሪው ጥፋት በሆነበት ሁኔታ ለተጠሪው ኪሳራ እንዲከፍሉ ሊገደዱ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት ተጠሪው እንደሚከራከረው የተጠሪው ባልሆነ እና ይልቁንም የራሳቸው የአመልካቹ በሆነ ምክንያት ከሆነ ደግሞ ቤቱን በወቅቱ ለተጠሪው ማስረከብ ሲገባቸው አላግባብ ይዘው በመቆየት ተጠሪውን ላሳጡት ጥቅም አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኪሳራ የማይከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት በማን ጥፋት ወይም የትኛው ወገን ኃላፊ ለሚሆንበት ድርጊት ነው? የሚለውን ነጥብ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጭብጥነት ይዞ ያጣራው ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም በዚህ የክርክር ነጥብ ላይ ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት ያስችል ዘንድ ጉዳዩ ወደ ስር ፍርድ ቤት ተመልሶ ተገቢው ማጣራት ሊደረግ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 108108 በ19/06/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 89369 በ30/08/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተጠሪው ንብረት አላግባብ ለበለጸጉበት አመልካቹን ኃላፊ በማድረግ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. አመልካች የኪሳራ ገንዘቡን መክፈል የሚገባቸው በካሬ ሜትር በብር 50 (ሃምሳ) ሂሳብ ነው በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. አመልካች የኪሳራ ገንዘቡን መክፈል የሚገባቸው በካሬ ሜትር በብር 30 (ሰላሳ) ሂሳብ ነው በማለት ወስነናል፡፡
5. በንግድ ቤቱ መገልገል ከጀመሩበት ከ01/11/2001 ዓ.ም. ጀምሮ በቤቱ መገልገል እስካቆሙበት 22/09/2003 ዓ.ም. ድረስ ላለው የ22 ወራት ከ21 ቀናት ጊዜ በካሬ ሜትር በብር 30 (ሰላሳ) እና በወር በብር 10,350 ሂሳብ ተሰልቶ የሚገኘውን ውጤት ብር 234,945 (ሁለት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት) አመልካቹ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ከ19/06/2005 ዓ.ም. ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪው እንዲከፍሉ ወስነናል፡፡
6. ከላይ በውሳኔው ክፍል ውስጥ በተመለከተው መሰረት አመልካች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ በንግድ ቤቱ መገልገል ያልቻሉት በምን ምክንያት ወይም ከግራ ቀኙ መካከል የትኛው ወገን ኃላፊ በሚሆንበት አድራጎት ምክንያት እንደሆነ በግራ ቀኙ እና ተገቢ ሆኖ ባገኘው ማስረጃ ሁሉ ካጣራ በኃላ አመልካች ከ22/09/2003 ዓ.ም. ጀምሮ ቤቱን ለተጠሪው እስካስረከቡበት 11/10/2005 ዓ.ም. ድረስ ላለው ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪው ኪሳራ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ወስነናል፡፡

7. እንዲያውቀው እና ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
8. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 134825 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ05/11/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡ ይጻፍ፡፡
9. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
10. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መንጃፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105289

መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ተፈሪ ንጉሴ ጥላሁን - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ህግ /ዐ/ህግ በላይ ወርቅነህ ቀረቡ/

የመዝገብ ቁጥር 105290 ከዚህ መዝገብ ጎን ለጎን ተመርምሮ ተጣምሮ ተወስነኗል፡፡ መዝገቦቹ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የህግ ስህተት የፈጸሙ በመሆኑ በሰበር ይታረምልኝ የሚል አቤቱታ በማቅረቡ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ የማታለል ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በመ/ቁ. 136720 ሁለት ክሶች አቅርቧል፡፡ አንደኛው ክስ የወ/ህ/ቁ 692(1) የተመለተከውን በመተላለፍ ከግበረ አበሩ በመመሳጠር ባልሽ ጥር 2005 ይሞታል ከመሞቱ በፊት ገንዘብ አምጪ በማለት አሳሳች ነገሮችን በመናገር ከግል ተበዳይ መሰረት ስንታየሁ አንድ መቶ ሰላሳ ሺህ ብር እና ዋጋው ሀያ አምስት ሺህ ብር የሆነ ወርቅ በማታለል መወሰዱ ፤ ሁለተኛው ክስ የወ/ህ/ቁ.692(1) የተመለከተውን በመተላለፍ የግል ተበዳይ ወ/ሮ አጸደ ስንታየሁ ባለቤትሽ ይህንን ሱስ የሚያቆመው ገንዘብ እና ጌጣጌጥ ስትስጪኝ ነው ፤ ገንዘቡ እና ጌጣጌጡም ተፀልዮበት ሲመልስ ነው የሚድነው በማለት ሀምሳ ሺህ ብር እና ዋጋው ዘጠና ሁለት ሺህ ብር የሆነ ወርቅ ከእነ መጫወቻው መወሰዱን የሚያሳይ ነው፡፡ ሌለው ክስ በመ/ቁ. 136734 የቀረበ ሲሆን አመልካች ግበረ አበሩ መላከ ገነት ሳሙኤል አስፋው የተባሉ ግለሰብ የግል ተብዳይ የሆነችው ወ/ሮ ዘበናይ ከበደን የተሳሳተ እምነት በመጠቀም የሚያድንሽን ሰው አውቃለሁ ላገናኝሽ በማለት ከአሁኑ አመልካች ካገናኙዋት በኋላ ፤ ከያዘሽ በሽታ በህክምና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አትድኝም እኔ ነው የሚያድነሽ ለዚህም አንድ መቶ ስልሳ ሺህ ብር እና ዋጋው ስልሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር የሚሆን ወርቅ ተቀብሎ በመሰወሩ ወ/ህ/ቁ. 692(1) የተመለከተውን ተላልፏል የሚል ነው፡፡

አመልካች የቀረበበት ክስ ክዶ በመከራከሩ ፍ/ቤቱ የዐ/ህግ ምስክሮች አዳምጧል፡፡ አመልካችም የበኩሉን የመከላከያ ማስረጃ በማስቀረብ አሰምቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በዐ/ህግ የቀረቡ ምስክሮች አመልካች የተለያዩ የማታለያ ዘዴዎች ተጠቅሞ በሁለቱም መዝገቦች የተጠቀሱትን የግል ተበዳዮች ገንዘብ እና ወርቅ መወሰዱ ፤ የማታለል ድርጊቱ ሲፈጸም ዋና ወንጀል አድራጊ በመሆን የተሳተፉት የግል ተበዳይ አፀደ ስንታየሁ የነፍስ አባት የሆኑት መላከ ገነት የተባሉትን ግለሰብ አመልካች በሽታን የመፈወስ ችሎታና አቅም እንዳለው በመግለጽ የግል ተበዳዮች የተሳሳተ እምነት እና ግምት እንዲይዙ ማድረጋቸው ፤ በአመልካች በኩል የቀረበው አንድ የመከላከያ ምስክርም ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ እና ቦታ አመልካች ከአዲስ አበባ ውጭ የነበረ ስለመሆኑ የሰጠው የምስክርነት ቃል ተአማኒነት የሌለው እና የዐ/ህግ ክስና ማስረጃ የማያስተባብል ነው በማለት በሶስቱም ክሶች ጥፋተኛ ነው በማለት ፈርደዋል፡፡ ቅጣት በተመለከተም በዓቃቤ ህግ በኩል የቀረበው አንድ የቅጣት ማክበጃ እንዲሁም በአመልካች በኩል ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች በመቀበል በመ/ቁ. 136720 በሁለቱም ድርጊቶች በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 6,000 እንዲሁም በመ/ቁ 136734 በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 2,000 የሁለቱም ድምር በወ/ህ/ቁ 186 መሰረት በስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 8,000 መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በሁለቱም መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ የጠየቀ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ወደ ጉዳዩ ለመግባት የሚያስችል በቂ ምክንያት ባለመገኘቱ ይግባኙን በማሰናበት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ በመሆኑ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር አደርገዋል፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት፡- የወንጀል ድርጊቱን አለመፈጸሙን ፤ ተፈጸመ የተባለው ድርጊት አንድ ወንጀል ከመስራት ሐሳብ የመነጨ መሆኑን ፤ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የቅጣት መመሪያ አዲስ ሳይሆን የቀደም መሆን እንዳለበት ወንጀሉ ከሌላ ግብረ አበር በመሆን ፈጸመዋል መባሉ በአግባቡ አለመሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የሰጠው መልስ ያስቀርባል ከተበለው ነጥብ አንፃር ሆኖ ወንጀሉ ከብዶ መወሰኑ በህጉ አግባብ መሆኑ ፤ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የቅጣት መመሪያ ግን ለአመልካቹ የሚጠቅም የቀደሞ የቅጣት መመሪያ ከሆነ ቢወሰድለት እንደማይቃወም ገልፀል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከስር የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረነውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚሹ መሰረታዊ ነጥቦች አንደኛው የስር ፍርድ ቤቶች ወንጀሉ በግብረ አበርነት የተፈጸመ ነው በማለት በወ/ህ/ቁ. 84(1)(መ) ጉዳዩን በማክበድ መወሰናቸው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? ሁለተኛ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው ወይስ ቁጥር 2/2006? የሚሉ ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ነጥብ በተመለከተ፡- አመልካች በሶስት የግል ተብዳዮች የማታለል ወንጀል በመፈጸም ጥሬ ገንዘብና ወርቅ መውሰዱ የስር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ስልጣናቸው ከድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ለመፈጸም ግብረ አበር ሆነዋል የተባሉት መላከገነት የተባሉ የቤተክርስትያን ሰው ነኝ ባይ ሲሆኑ አፀደ ስንታየሁ የተባለችው ተባዳይ የነፍስ አባት መሆናቸው የተካደ ጉዳ አይደለም፡፡ የግል ተበዳዮች አለን የሚሉት የጤና ችግር ፤ ሊመጣ ከሚችለው አስደንጋጭ ችግር ለመታደግ ወይም ባለቤታቸው ከነበራቸው የባህሪ ችግር ለማስተካከል ገንዘብና ወርቅ በማስያዝ ፀሎት ማድረግ እንደ ብቸኛ አማራጭ መወሰዱ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡ የግል ተብዳዮች ገንዘብና ወርቅ እንዲሰጡ የማሳመን ሚና የተጫወቱት የግል ተበዳይ አፀደ ስንታየሁ የነፍስ አባት ሲሆኑ በሶስቱም የግል ተበዳዮች ከፍተኛ የመንፈስ ተፅዕኖ የፈጠሩት እኚሁ የነፍስ አባት መላከገነት መሆናቸው ከአጠቃላይ የመዝገቡ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ ከህጉ ጋር ስናገናዝበው አንድ ሰው የወንጀል ድርጊቱ የፈጸመው ከሌላ ሰው ስምምነት በማድረግ ከሆነ እንደ ማክበጃ እንደሚወሰድ በወ/ህ/ቁ. 38(1) እና 84(1)(መ) ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እና ግበረ አበር የነበሩት ግለሰብ የግል ተበዳዮች በማታለል ገንዘብና ወርቅ ለመውሰድ አስቀደመው በመስማማት ድርጊቱ ስለመፈጸማቸው ከቀረበው የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የምንረዳው ነው፡፡ አመልካች እና ግበረ አበር የተባሉትን መላከገነት የግል ተበዳዮች ሊያሳምን ይችላል ብለው ያቀዱትን ስልት ወደ ተግባር በማሸጋገር የግል ተበዳዮች ማህበራዊ ችግር ፤ የጤና ችግር እንደምክንያት ተጠቅመው ሃይማኖታቸውን መሰረት በማድረግ ከፍተኛ የማታለል ድርጊት ፈጸመዋል፡፡ የግል ተበዳይ አፀደ ስንታየሁ የነፍስ አባት የሆኑትን መላከገነት የተባሉትን ግለሰብ የግል ተበዳዮች በአመልካች ላይ እምነት ኖሯቸው ገንዘብና ወርቅ እንዲሰጣቸው ያላቸው ሀይማኖታዊ ግንኙነት ያለአግባብ ተጠቅመውበታል፡፡ ይህ ደግሞ በወ/ህ/ቁ. 84(1) (መ) እንደተመለከተው ወንጀሉ በሁለት ሰዎች ስምምነት (prior agreement) የተፈጸመ መሆኑ የሚሳይ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች እንደ ማክበጃ መውሰዳቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን አያሳይም፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ቅሬታ የህግ መሰረት የለውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁለተኛው ነጥብ በተመለከተ፡- አመልካች የተከሰሰባቸው የማታለል ወንጀሎች በ 2005 ዓ/ም የተፈጸሙ ናቸው፡፡ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ስራ ላይ የነበረው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002 ስለመሆኑ ግራ ቀኙ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 95438 እና ሌሎች መዝገቦች በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለተከሳሽ የሚጠቅም የቅጣት መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ ወስኗል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ድርጊቱ ሲፈጸም በተግባር ላይ በነበረው የቅጣት መመሪያ መሰረት ለእያዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሁለት እርከን የሚቀነስለት መሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በመ/ቁ 136720 በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ የሁለቱም ድንጋጌዎች ቅጣት ተደምሮ በእርከን 22 የሚወድቅ ሲሆን በሁለተኛው መዝገብ የመ/ቁ. 136734 እርከን 17 ስር የሚወድቅ ነው፡፡ በሁለቱም መዝገቦች ቅጣት ተነጣጥሎ የተወሰነ ሲሆን አፈጻጸም በተመለከተ ግን ተጣምሮ እንዲፈጸም የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው የመዝገብ ቁጥር 136720 አመልካች ሁለት የማቅለያ ምክንያቶች በማቅረቡ በእያዳንዱ ማቅለያ በቀድሞ የቅጣት መመሪያ አንቀጽ 17 መሰረት ሁለት እርከን ዝቅ የሚል በመሆኑ በአጠቃላይ ከመነሻ እርከኑ አራት እርከን ወደታች ዝቅ ይላል፡፡ በዚህ መሰረት በእርከን 18 ሥር የሚወድቅ ነው፡፡ ሁለተኛው የመዝገብ ቁጥር 136734 በእርከን 15 ሥር የሚወድቅ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የወንጀል ድርጊቱ በ 2005 ዓ.ም የተፈፀመ መሆኑን ፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁ 95438 የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ በየትኛውም ደረጃ ባሉ ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) የተደነገገ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 6(1) እና በቀድሞ የቅጣት መመሪያ መሰረት ያቀረበው ማቅለያ የበለጠ ዝቅ የሚያደርግለት ነበሩ ፣የቅጣት መመሪያ መሆኑ እየታወቀ መታለፉ በአግባቡ ባለመሆኑ ፤ በቅጣት ረገድ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማሻሻል መወሰኑ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች የፈጸመው የማታለል ወንጀል ያስከተለው ጉዳት በሌላ በኩል አመልካች ሊያስተምር ሊያስጠነቅቅ የሚያስችል የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ የሚያሳካ ቅጣት መወሰን ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች በ መ/ቁ 136720 የተወሰነበትን ቅጣት በማሻሻል በእርከን 18 ከተደነገገው 4 ዓመት ጽኑ እስራት በመውሰድ በመ/ቁ 136734 በእርከን 13 ከተደነገገው ሁለት ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራት በመውሰድ በድምር በስድስት ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራት እና 8,000 ብር መቀጮ እንዲቀጣ የሚከተለው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1 የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 136720 በ 08/04/2006 የሰጠው ፍርድ ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 101684 በሰኔ 30/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡ ይፃፍ፡፡

2 አመልካች በተከሰሰባቸው የወ/ሕ/ቁ 692(1) ሥር ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡

3 የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት አመልካች ከአሁኑ በፊት የታሰረበት ካለ በቅጣቱ የሚካተት ሆኖ እጁ ከተያዘበት ጀምሮ በስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነ መሆኑን አውቆ እስራቱን ተቆጣጥሮ እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

4 የዚህ ፍርድ ግልባጭ በሰ/መ/ቁ 105290 ይያያዝ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 105406

መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ኃይሉ ወልደ መኮንን - ጠበቃ ጳውሎስ ተሰማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን ለእርሳቸው አገልግሎት ባልታሰበ ወይም እርሳቸውን በማይመለከት ሰነድ የመገልገል የወንጀል ክስ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠባቸው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡-አመልካች ጥቅምን ወይም መሻሻልን ለማግኘት በማሰብ ትክክለኛ ስማቸው ኃይሉ ወልደ ሆኖ እያለ ሰይፉ ወልደ እንደሆነ አድርገው በመግለጽ ለእርሳቸው አገልግሎት ያልታሰበውን ወይም እርሳቸውን የማይመለከተውን እና የወንድማቸው ሰይፉ ወልደ የሆነውን ከመድኃኒዓለም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተሰጠ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ የምስክር ወረቀት (ትራንስክሪፕት) እና ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መልቀቂያ የምስክር ወረቀት በማቅረብ በየካቲት ወር 1977 ዓ.ም. በኢትዮጵያ አየር መንገድ የተቀጠሩ በመሆኑ፣ ከተቀጠሩ በኃላ ወንጀሉን ለመደበቅ በማሰብ ህዳር 30 ቀን 1979 ዓ.ም ፍርድ ቤት ቀርበው ሰይፉ ወልደ እና ኃይሉ ወልደ በሚሉ ሁለት ስሞች ሲጠሩ እንደነበረ እና አሁን ግን ኃይሉ ወልደ በሚለው ስም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብቻ ለመጠራት እንደሚፈልጉ በመግለጽ በፍርድ ቤት በማስወሰን ይህንን የፍርድ ቤት ውሳኔ ለተቀጠሩበት መስሪያ ቤት አቅርበው ከማህደራቸው ጋር እንዲያያዝ በማድረግ እስከ ህዳር 19 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ አየር መንገድ በበረራ አስተናጋጅነት እና በመሪ የበረራ አስተናጋጅነት ሲሰሩ የቆዩ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 385(1)(ለ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ሀሰተኛ በምስክር ወረቀት የመገልገል ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቀው በክሱ የተመለከተውን ወንጀል አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ያቀረባቸውን ሶስት ምስክሮች ምስክርነት ከሰማ እና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ አመልካች መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካች የሰው መከላከያ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ መግለጫው ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 ዘርዝሮ በማስረጃነት ካቀረባቸው ሰነዶች መካከል ሶስቱን በመከላከያነት ጭምር የጠቀሱ ከመሆኑም በላይ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ኃይሉ ወልዴ በሚል ስም የተሰጠው የምስክር ወረቀቶችን፣የስራ እድገት ደብዳቤን እና በዚሁ ስም የተሞላ የጡረታ ቅጽ በመከላከያ ማስረጃነት አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቹ በተጠሪ የቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ አስተባለዋል ሊባሉ የሚችሉት በወንድማቸው ሰይፉ ወልዴ ስም በተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች ለስራ ቅጥር ስላለመገልገላቸው ወይም የትምህርት ማስረጃዎቹ የሌላ ሰው ሳይሆኑ የራሳቸው ስለመሆናቸው በማስረዳት መሆኑን እና ይሁን እንጂ አመልካች ያቀረቧቸው የመከላከያ ሰነዶች ከላይ ከተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች አንዱንም የማያስረዱ መሆኑን ገልጾ አመልካች ባቀረቡት የሰነድ መከላከያ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት በክሱ በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን፣ድንጋጌው የሚያስቀጣው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ መሆኑን፣ አመልካች ሰነዱን በመገልገል ከሃያ ዓመት ላላነሰ ረጅም ጊዜ ያልተቋረጠ ጥቅም ያገኙ እና ፍርድ ቤትን ሳይቀር አሳስተው የመጀመሪያውን ወንጀል ለመሸፈን ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸው በድርጊቱ አለመፀፀታቸውን የሚያሳይ ነው በማለት የእስራት ቅጣቱን አማራጭ በመውሰድ እና ወንጀሉንም በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ በከባድ ደረጃ በመመደብ፣በድንጋጌው ስር በከባድ ደረጃ ለተመደበ ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ከተቀመጠው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ የሁለት ዓመት እስራት መነሻ አድርጎ በመያዝ፣ይህ የቅጣት መጠን በመመሪያው አባሪ አንድ በእርከን 10 ስር የሚወድቅ መሆኑን፣በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት አለመኖሩን፣የአመልካቹ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዘወትር ጠባይ መልካምነት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው በሁለት የማቅለያ ምክንያትነት ሲያዙ ፍቅድ ስልጣኑን ከእርከን 10 ወደ እርከን 8 ዝቅ የሚል መሆኑን በዝርዝር ገልጾ በመጨረሻ አመልካች በእርከን 8 በተቀመጠው ፍቅድ ስልጣን መሰረት በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ወንጀሉን ፈጽመዋል ከተባለበት ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ሲቆጠር ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት አመልካች ላቀረቡት መቃወሚያ የስር ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ድርጊቱ ከቆመበት ህዳር ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ እንጂ ድርጊቱ መፈጸም ከጀመረበት ከ1977 ዓ.ም. ጀምሮ አይደለም በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 219(2) ድንጋጌ አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ በአብላጫ ድምጽ በተሰጠ ትዕዛዝ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

1. በአመልካች የቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?
2. በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች የተከሰሱበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ሲሆን በሕጉ በተለየ ሁኔታ በግልጽ ካልተደነገገ በቀር ቀላል እስራት ከአስር ቀን እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 106(1) ተመልክቷል፡፡በሌላ በኩል የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜን አስመልክቶ ከአንድ ዓመት በላይ በቀላል እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል የክስ ማቅረቢያው የይርጋ ጊዜ አምስት ዓመት ስለመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 217(1)(ሠ) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡የክስ ማቅረቢያ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በመርህ ደረጃ ጥፋተኛው ወንጀሉን ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ እና ይሁን እንጂ የወንጀሉ ድርጊት እየተደጋገመ ተፈጽሞ እንደሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የመጨረሻው የወንጀል ድርጊት ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ ስለመሆኑ፣እንዲሁም የወንጀሉ ድርጊት ለረጅም ጊዜ ሲፈጸም የቆየ ከሆነ የይርጋ ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው የወንጀሉ ድርጊት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካቆመበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 219(2) ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ አመልካች በአየር መንገዱ የተቀጠሩት በወንድማቸው ሰይፉ ወልዴ ስም የተሰጠውን የትምህርት ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ እና እስከ ህዳር ወር 2005 ዓ.ም. ድረስ በአየር መንገዱ ውስጥ በስራ ላይ ሊቆዩ የቻሉትም በእነዚሁ የትምህርት ማስረጃዎች አማካይነት እና መነሻ በተፈጠረ የስራ ቅጥር ግንኙነት ወይም የስራ ውል መሰረት መሆኑ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡ የይርጋ ጊዜው መቆጠር መጀመር የሚገባው ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ነው በማለት አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት አመልካች ለወንድማቸው ለአቶ ሰይፉ ወልዴ የተሰጠውን የትምህርት ማስረጃ በ1977 ዓ.ም ለኢትዮጵያ አየር መንገድ አቅርበው የተመዘገቡ ቢሆንም የተቀጠሩት ግን ፈተናውን አመልካች ራሳቸው ተፈትነው በመሆኑ እና የተቀጠሩበትን ስራ ለረጅም ጊዜ ሲሰሩ የነበረውም አየር መንገዱ በሰጣቸው ስልጠና ባገኙት ዕውቀት እንጂ በምዝገባ ጊዜ ባቀረቡት የትምህርት ማስረጃ ባለመሆኑ ስልጠናውን አጠናቀው ስራ ከጀመሩ እና በተለይ ደግሞ ኃይሉ ወልዴ በሚለው ስም ብቻ እንዲጠሩ በፍርድ ቤት ካስወሰኑበት ከ1979 ዓ.ም. ጀምሮ በሰይፉ ወልዴ ስም በተሰጠው የትምህርት ማስረጃ ተገልግለዋል ወይም ጥቅምን ወይም መሻሻልን አግኝተዋል ሊባሉ አይገባም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ይሁን እንጂ አመልካች ለስራው የተመዘገቡትም ሆነ ፈተናውን ወስደው ለስልጠና እና ለስራ ቅጥር የበቁት የእርሳቸው ባልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች በመገልገል በመሆኑ አመልካች ስልጠናውን ካጠናቀቁበት ቀንም ሆነ ስራ ላይ ከተሰማሩበት ቀን ጀምሮ የትምህርት ማስረጃዎቹ አገልግሎት ተቋርጧል ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ለስራው የተቀጠሩት የራሳቸው ባልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች በመገልገል መሆኑን ስልጠናውን ባጠናቀቁበት ቀን ወይም ስራ ላይ በተሰማሩበት ቀን ለአየር መንገዱ አስታውቀው የነበረ ስለመሆኑ እና በዚህም ምክንያት የእርሳቸው ባልሆኑ የትምህርት ማስረጃዎች የመገልገላቸው ሁኔታ እንዲያበቃ ወይም እንዲቋረጥ የተደረገ ስለመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ለረጅም ጊዜ ሲፈጸሙ የቆዩትን ወንጀሎች የይርጋ ዘመን አቆጣጠር በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 79389 በ12/07/2005 ዓ.ም. የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት አመልካች ወንጀሉን አላደረግኩም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም የራሳቸው ያልሆኑትን እና ሰይፉ ወልዴ ለተባሉ ወንድማቸው የተሰጡትን የትምህርት ማስረጃዎች የራሳቸውን ፎቶግራፍ በመለጠፍ የራሳቸው እንደሆኑ አስመስለው ለኢትዮጵያ አየር መንገድ በማቅረብ በ1977 ዓ.ም ለስራ ቅጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተገለገለበት መሆኑ እና በዚህ ሁኔታ በተቋቋመ የስራ ውል መሰረት እስከ ህዳር ወር 2005 ዓ.ም ድረስ ጥቅም ሲያገኙበት የነበረ መሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን እና አመልካች በቤተሰብ ውስጥ ሰይፉ በሚል ሌላ ስም ተጠርተው የማያውቁ፣ ይልቁንም ሰይፉ ወልዴ ከኢትዮጵያ ውጭ በመኖር ላይ የሚገኙ የአመልካች ታላቅ ወንድም ስለመሆናቸው የአመልካች ወንድም መሆናቸውን በገለጹት 2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጭምር የተመሰከረ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካች ያቀረቧቸው የሰነድ ማስረጃዎች ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች በወንድማቸው ሰይፉ ወልዴ ስም በተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች ለስራ ቅጥር ስላለመገልገላቸው ወይም የትምህርት ማስረጃዎቹ የሌላ ሰው ሳይሆኑ የራሳቸው ስለመሆናቸው የማያስረዱ መሆኑንም መዝገቡ ያመለክታል፡፡ወንጀሉን ስለመፈጸሜ በማስረጃ አልተረጋገጠብኝም ወይም የተጠሪን ማስረጃ በመከላከያዬ አስተባብያለሁ በማለት አመልካች በሰበር አቤቱታቸው በግልጽ ያቀረቡት ክርክርም የለም፡፡የቅጣት ውሳኔውም ቢሆን ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው የወንጀሉን አፈጻጸም ሁኔታዎች፣ሕጉን እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሰረት በማድረግ በአግባቡ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 114900 በ16/10/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 152347 በ13/12/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች እንዲሁም አመልካች ለሚገኙበት ማረሚያ ተቋም ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 104923

መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-ወ/ሮ አበባ አረፋይኔ ጠበቃ መረሣ ፍሰሃ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የትግራይ ክልል አቃቤ ሕግ - ተልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ አመልካች በአድዋ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጸናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ባለመስማማት ቅሬታቸዉ በሰበር እንዲታይላቸው ሐምሌ 30 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

በአድዋ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበዉ ክስ በ1996 ዓ.ም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692/1/ ሥር የተመለከተዉን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ከፍ ያለ ጥቅምና ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት አስበው ከስር 1ኛ ተከሳሽ ከነበረው ከአቶ ተክለማሪያም ገ/ማርያም ጋር አባሪ ተባባሪ ሁነው ወደ ግል ተበዳይ መኖሪያ ቤት ድረስ ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ/ም ከቀኑ 7፡00 ሲሆን በመሄድ ከበሽታሽ የሚፈውስ ደብተራ አለ በሚል የአሁኗ አመልካች የሥር 1ኛ ተከሳሽን ወደ ግል ተበዳይ ቤት ልካባት የሥር 1ኛ ተከሳሽም ወደ ግል ተበዳይ ቤት ገብቶ ስሜ ይትባረክ ሽፈራው እባለላሁ ብሎ በሽታሽ በወርቅሽ ስለሆነ ወርቅሽን ሁሉ አቅርቢ፣አንድ አንዳታስቀሪ ብሎ ሎሚ፣ዶሮና አረቄ አቅርቢ ብሎአት ወርቁን ከአቀረበችለት በአቦጀዲ ጠቅልሎ መድሃኒት አድርጌበታለሁ በማለት ሌላ ተመሳሳይ አቦጀድ የተጠቀለለ ቆርኪ ጠቅልሎ አስቀምጦ ወርቁን መድሃኒት አድርጌበት ስለሆንኩ በኃላ መጥቼ ራሴ እስከምፈታው እንዳትነኩ ብሎ ባለ ሃያ አራት ካራት ወርቅ ግምቱ ብር 447,000.00 የሆነ 447 ግራም የሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወርቅ ይዞ መሰወሩን ዘርዝሮ አመልካችና የስር 1ኛ ተከሳሽ በግብረአበርነት የማታለል ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች የዕምነት ክህደት ቃል እንዲሰጡ ሲጠየቁ የቀረበባቸውን ክስ አልፈጸምኩም፤ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ዐቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸዉን የሠነድና የሰዉ ማስረጃ በማቅረብ አሰምቷል፡፡ አመልካች እንዲከላከሉ በተሰጠዉ ብይን መሠረት አሉኝ ያሏቸውን ማስረጃዎችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን የመረመረዉ የወረዳው ፍርድ ቤትም አመልካች በክሱ ላይ ተጠቅሶ የቀረበባቸውን የሕግ አንቀጽ በመተላለፍ ጥፋተኛ ናቸዉ በማለት ፍርድ ከሰጠ በኃላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ መመልከቱን ጠቅሶ አመልካችን በሶስት አመት ከአምስት ወር ቀላል እስራት እና በብር 500.00(አምስት ሺህ) እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፣ የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ አቤቱታቸው ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በወረዳው ፍርድ ቤት የታየው ከስልጣኑ ውጪ መሆኑን፣ አቃቤ ሕግ አመልካች በወንጀሉ የነበራቸውን ተሳትፎ እንደ ክሱ ያለማስረዳቱን፣ በዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የግል ተበዳይ እና የስር 1ኛ ተከሳሽ ቀደም ብለው የሚተዋወቁ መሆናቸው መነገሩም አመልካች በወንጀሉ አፈፃጸም ተሳትፎ ያልነበራቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፣ የቅጣት ውሳኔም ተገቢውን የቅጣት አወሳሰን ስርዓት ተከትሎ የተወሰነ አይደለም የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ምክንያት በዕሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን እንደሚከተለዉ መርምሯል፡፡ በዚሁ መሠረት የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልጉ አበይት ጭብጦች፡-

1. አመልካች በክስ ቻርጁ ላይ የተገለጸውን የወንጀል ተግባር ፈጽመዋል ተብሎ ጥፋተኛ መባላቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?፣
2. አመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት አወሳሰን ረገድ የደረጃ አወሳሰን አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤት የወሰነዉ ቅጣት ተገቢነት አለው? ወይስ የለውም? የሚሉት ናቸዉ፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ የመሠረተዉን የማታለል ወንጀል ለማስረዳት የግል ተበዳይንና ሌሎች ምስክሮችን በምስክርነት ያቀረባቸዉ ሲሆን ምስክሮቹም ቀጥተኛ የሆነ የምስክርነት ቃል የሰጡና የአካባቢ ምስክሮች ናቸው፡፡ የአይን ምስክር የሆኑት 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ሲሆኑ አመሰካከራቸውም የስር አንደኛ ተከሳሽ በአሁኗ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አማካኝነት በክሱ በተጠቀሰው ጊዜ ወደ ግል ተበዳይ ቤት ሂዶ ስሜ ይትባረክ ሽፈራው እባለላሁ ብሎ በሽታሽ በወርቅሽ ስለሆነ ወርቅሽን ሁሉ አቅርቢ፣አንድ አንዳታስቀሪ ብሎ ሎሚ፣ዶሮና አረቄ አቅርቢ ብሏት ወርቁን ከአቀረበችለት በኋላ በአቦጀዲ ጠቅልሎ መድሃኒት አድርጌበታለሁ በማለት ሌላ ተመሳሳይ አቦጀዴ የተጠቀለለ ቆርኪ ጠቅልሎ አስቀምጦ ወርቁን መድሃኒት የአድርግሁበት ስለሆነ በኃላ መጥቼ ራሴ እስከምፈታው እንዳትነኩ ብሎ ባለ ሃያ አራት ካራት ወርቅ ግምቱ ብር 447,000.00 የሆነ 447 ግራም የሆነ ወርቅ ይዞ መሰወሩን፣አመልካች ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ወደ ግል ተበዳይ ከሄዳቸውም በተጨማሪ የስር 1ኛ ተከሳሽ በግል ተበዳይ ቤት ውስጥ እያለ አመልካች ስልክ እንደደወሉለትና ለምስክሮቹ ገልጾ ከግል ተበዳይ ቤት ወጥቶ ወደ አመልካች ደርሶ መመለሱንና አመልካች ልጃቸውን እየላኩ ሁኔታውን ሲከታተሉ የነበሩ መሆኑን ዘርዝረው የመሰከሩ መሆናቸውን ከውሳኔው ግልባጭ ተረድተናል፡፡ ምስክሮቹ ይትባረክ ሽፈራው የተባለውና ወርቁን የወሰደው የስር 1ኛ ተከሳሽ አመልካች የአጎቴ ልጅ ነው ብለው መሄዳቸውንም መመስከራቸውን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ሌሎች ምስክሮች የአከባቢው ምስክሮች ሲሆኑ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ወደ ግል ተበዳይ ሲገባ፣ ከጊዜ በኋላ የግል ተበዳይ ግለሰቡ ሲሰወሩ የሚያውቁት መሆን ያለመሆኑን ሲጠየቁቸው እንደነበርና ወርቅ ዘርፎ የተሰወረባቸው መሆኑን 1ኛ እና 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የነገራቸው መሆኑን የገለፁ ምስክሮች ናቸው፡፡

እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ጥፋተኛ ለማድረግ በአቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡትን የሰው ምስክሮች አመሰካከር ይዘት ከላይ የተጠቀሰው መሆኑን በውሳኔው ላይ የገለፁት ጉዳይ ሲሆን ፍርድ ቤቶቹ በፍርድ ሐተታው በግልጽ ያስቀመጡት ድምዳሜውም ከአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል አመልካች የስር 1ኛ ተከሳሽ የግል ተበዳይን ከበሽታ እፈውሳለሁ በሚል ወርቃቸውን አታልሎ ሲወስድባቸው ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑን አየን፣ ወርቁን ይዞ የተሰወረው ሰው የአመልካች ትክክለኛ ዘመዳቸው ሳይሆን የአጎታቸውን ልጅ መሆኑንና ስሙን ሁሉ ቀይሮ ከግል ተበዳይ ጋር ሲተዋወቅ አመልካች ይህንኑ ለግል ተበዳይና ለ2ኛ ምስክር ሊታመን በሚችል ሁኔታ የገለፁ መሆኑን መመልከታቸውንና ሁኔታውን እውነት መስሏቸው መቀበላቸውን መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የወረዳው ፍርድ ቤትም ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን የደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ የሆነ ስልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡በመሆኑም አመልካች በማታለል ድርጊቱ አፈጻጸም ቀጥተኛ ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑ፣በስር 1ኛ ተከሳሽ ሲፈጸም የነበረውን ሁኔታ ልጃቸውን እየላኩ መከታተላቸው ውጤቱን በመቀበል የራሳቸው ማድረጋቸው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

10 ድንጋጌዎች መሰረት ከተሰጠው ስልጣን አኳያ አመልካች በወንጀል ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑን በስር ፍርድ ቤቶቹ የተደረሰውን ድምዳሜ እንዳለ የሚቀበለው ነው፡፡

አመልካች ከሚከራከሩባቸው ነጥቦች ውስጥ አመልካች የድርጊቱ ተሳታፊ መሆናቸው በአቃቤ ህግ ማስረጃዎች አልተገለፀም በሚል ነው፣የግል ተበዳይ የስር 1ኛ ተከሳሽን ቀደም ብለው ያውቁት ነበር በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ በአንድ የወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ በቂና አሣማኝ በሆነ ሁኔታ የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙንና የወንጀል ድርጊቱን ፈፃሚውን ማንነት በትክክል ለይቶ ማሳየት ያለበት ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትንና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡አንድ ሰው ለወንጀል ድርጊት ኃላፊ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚገባው ወንጀሉ መስራቱ ወይም መፈፀሙና ተሰራ ወይም ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ሲጋገጥ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4)፣32፣40፣57፣58(1) እና ከወ/መሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141፣142 እና 149 ድንጋጌዎች አገላለፅና መንፈስ መመልከት የምችለው ጉዳይ ነው፡፡ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ የሚቆጠረው ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ቢያደርግ ወይም በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ ሀሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተከፋይ በመሆን ወንጀሉን የራሱ ያደረገ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ለ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ከሳሽ የሆነው አቃቤ ሕጉም ይህንኑ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት አለበት፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን የማታለል ተግባር ከግብረ አበራቸው ጋር ሁነው በቀጥታ ተሳትፈውና ውጤቱንም የራሳቸው በማድረግ ወንጀሉን የፈፀሙ መሆኑን የተነገረባቸው በጊዜውና በቦታው በነበሩት ምስክሮችና በጠንካራ የአካባቢ ምስክሮች መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃልም በመከከላከያ ማስረጃዎች ያልተስተባበለ መሆኑን ፍሬ ነገሩን አጣርተውና ማስረጃዎቹን መዝነው አረጋግጠዋል፡፡ስለሆነም አመልካች ለወንጀል ድርጊቱ ተሳታፊ የነበሩ መሆኑ በበቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የወንጀል ተጠያቂነት የለብኝም በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(2)፣32(1(ሀ)(ለ)፣58 እና ስለ ማታለል ወንጀል የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ሁኖ ሰላሳገኘነው አልተቀበልነውም፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692(1) ስር ማታለል ተፈጽሟል ለማለት አራት መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች መረጋገጥ አለባቸዉ፡፡ እነዚህም፡- አጥፊዉ ሆን ብሎ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባዉን ነገር በመደበቅ ወይም ሌላዉን ሰዉ የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ መግለጽ ይኖርበታል፣ ተበዳዩ መታለል ይኖርበታል ወይም በአጥፊዉ የተገለጸለትን አምኖ ሊቀበል ይገባል፣ በሀሰት የተገለጸለትን በማመን የፈጸመዉ ተግባር መኖር አለበት፣ እንዲሁም የግል ተበዳይ በመታለሉ ያጣዉ የገንዘብ ጥቅም ሊኖር ይገባል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስም እነኚህ በሕጉ የተመለከቱት መመዘኛዎች የተሟሉ በመሆናቸው አመልካችን ከወንጀሉ ተጠያቂነት የሚድኑበትን አግባብ አላገኘንም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692/1/ በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ ደረጃ የወጣለትና እርከኑ የተለየ ነዉ፡፡የግል ተበዳይ በተፈጸመባቸዉ የማታለል ወንጀል ምክንያት 447,000.00 ብር በጥሬ ገንዘብ አጥተዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን እድሜና የጤና ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በቀላል እስራት ሊቀጡ እንደሚገባ ከለየ በኋላ የቅጣት መጠኑን አሰልቷል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ አመልካች የብር 447,000.00 ያለአግባብ ብልጽግና የማግኘት ሀሳብ የነበራቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም 447,000.00 ብር ደረጃ 6 ስር የሚወድቅ ሲሆን በእስራት እርከን 16፣ በገንዘብ መቀጮ ደግሞ እርከን 4 ላይ ያርፋል፡፡ በቅጣት ማክበጃነት በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ አንድ ማክበጃ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን ይህም የስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ቅድመ ስምምነት አድርገው ወንጀሉን መፈፀማቸውን የሚገልጽ ሲሆን ከድርጊቱ አፈፃጸም እና ከማታለል የወንጀል ድርጊት ባህርይ አንጻር ሲታይ ምክንያቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1(መ))ስር የሚወድቅ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ላይ አንድ ማቅለያ ምክንያት መያዙ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ለአመልካች በቅጣት ማቅለያነት ያለፈ ባህሪያቸው መልካም የነበረ መሆኑ በወ/ሕግ አንቀጽ 82/1/ሀ/ እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው በአንቀጽ 86 መሠረት ተይዞላቸዋል፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህን ቅጣቶች እንደ ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች እንዳሉ ተቀብሏቸዋል፡፡

ይህ ችሎት አመልካች በቀላል እስራት አማራጭ መቀጣት ይገባቸዋል በሚል የስር ፍርድ ቤት ማመኑን ቢገነዘብም የስር ፍርድ ቤት መነሻ ቅጣቱን የያዘበት ሁኔታ ሕጉ ስለ ቀላል እስራት የጊዜ ገደብ በአንቀጽ 106 ከአስቀመጠው ጋር አብሮ የሚሄድ ሁኖ አላገኘውም፡፡ ይልቁንም የሥር ፍርድ ቤት በግል ተበዳይ ላይ ደረሰ የተባለውን የገንዘብ ጥቅም ጉዳት መጠን መሰረት አድርገን እርከኑ ሲታይ እርከን 16 ማረፉ ተገቢ ሁኖ በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ምን ያህል እርከን ሊቀንስ ይገባዋል? የሚለውን ጥያቄ ወንጀሉ የተፈፀመው ነባሩ መመሪያ ስራ ላይ በነበረበት ጊዜ መሆኑን ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 6 ይዘትና መንፈስ አንጻር ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቢመለከተውም ከነባሩ መመሪያ አንቀጽ 16(6) ድንጋጌ አንፃር ለውጥ የሚያመጣ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ሁለት ማቅለያ ምክንያቶች እንዳሏቸው ከገለፀ በኃላ የቅጣት ማክበጃውን ይዞ እርከኑን ከእርከን 16 ወደ እርከን 17 ከፍ ከአደረገ በኋላ በዚሁ እርከን ለፍርድ ቤቱ በተተወው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ(ከሶስት አመት ከሶስት ወር እስከ ሶስት አመት ከአስራ አንድ ወራት) ሶስት አመት ከአምስት ወር ቀላል እስራት ወስዶ አመልካች በዚሁ የእስራት ቅጣት ጊዜ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ ሆኖም በመመሪያው መመሰረት የቅጣት ማክበጃ ከተወሰነ በኋላ ህጋዊ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ሳይሰሉ አጥፊው በማረሚያ ቤት ሁኖ የሚታሰረው የእስራት ጊዜ መጠን ሊወሰን እንደማይችል በአንቀጽ 19 ሰር የተመለከተው የቅጣት አሰላል ስርዓት ያሳያል፡፡ በመመሪያ መሰረት በድምሩ አራት እርከን ሲቀነስላቸዉ የእስር ቅጣቱ ከእርከን 17 ወደ እርከን 13 ስለሚወርድ በዚሁ እርከን ውስጥ የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ ከሁለት አመት ሶስት ወር እስከ ሁለት አመት ዘጠኝ ወር እስራት ነው፡፡

ከዚህ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ አመልካችና ያርማል፤ ለፈጸሙት አድራጎት ያስተምራታል፣ ሌሎችን ደግሞ ያስጠነቅቃል ባልነዉ በ2(ሁለት)አመት እንዲቀጡ መወሰኑ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁም መሠረት የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአድዋ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06997 የካቲት 25 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04714 ሚያዚያ 08 ቀን 2006 ዓ/ም ፣በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 66316 ሰኔ 26 ቀን 2006 ዓ/ም በአመልካች ላይ ያስተላለፈዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2(ለ-2) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለድርጊቱ ጥፋተኛ መባላቸው በአግባቡ ነው፣ ቅጣቱን በተመለከተ ግን ተገቢውን የቅጣት አወሳሰን መርህ ያልተከተለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች በዚህ ጉዳይ የታሰሩት ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ በ2 (ሁለት) አመት ቀላል እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. የክፍሉ ማረሚያ ቤት በዚህ ችሎት በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሰረት ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የቅጣት ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን እንዲያውቁት የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡

መዝገቡን ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ **ሩ/ለ**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95921

ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ/ ም

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ብርሃኑ ኑርጋ - ጠበቃ አመሃ መኮንን - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሙስና ወንጀል የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 29 እና 31 ድንጋጌዎች አግባብ የቀረበውን የውርስ ማመልከቻ መነሻ አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች እና ከእኚህ አመልካች ጋር በሙስና ወንጀል ተከሰው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠባቸው ሌሎች ስድስት ግለሰቦች ላይ ባቀረበው የንብረት ውርስ ጥያቄ ነው፡፡

የዋናው ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ተከሳሾች ከ1999 ዓ/ም እስከ 2000 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ የመንግስት ሰራተኛ፣ አስመጪና የእቃ አስተላላፊ ሁነው ሲሰሩ ሕገ ወጥ ጥቅም ለማግኘት አስበው በተለያዩ ዲክላራሲዩን ቁጥሮች ከአሳወቋቸው እቃዎች እና ከውጪ ለአስመጧቸው እቃዎች መክፈል የሚገባቸውን ብር 13,457,694.40 (አስራ ሶስት ሚሊዩን አራት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአርባ ሳንቲም) ቀረጥና ታክስ ሳይከፈሉ የከፈሉ አስመስለው ከመቅረጫ ጣቢያ እቃዎቹን እንዲለቀቁ እና የፈፀሙት ወንጀል እንዳይደርስባቸው ለማድረግ እቃዎቹን የሚይዘውን መረጃ ከመስሪያ ቤቱ "አሲኩዳ" የመረጃ ሲስተም በማጥፋት የመንግስት ቀረጥ እንዳይሰበሰብ በማድረጋቸው በግብረአበርነት በስልጣን ያላግባብ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ሲሆን የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ አመልካችና ሌሎች የስር ተከሳሾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥፋተኛ ተብለው የእስራት ቅጣት የተወሰነባቸው መሆኑን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ቁጥር 66892 ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ያሳያል፡፡

ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ በዋናው የወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበባቸው ሰዎች ጥሬ ገንዘብና ሌሎች ንብረቶች ታግደው እንዲቆዩ አድርጎ የነበረ መሆኑን ጠቅሶ በእያንዳንዱ አጥፊ ስም የታገደውን የንብረት አይነትና የጥሬ ገንዘብ መጠን ዘርዝሮ በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ የተባሉት ግለሰቦች በድርጊታቸው በመንግስት ላይ ለደረሰው ጉዳት ማካካሻነት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ያለባቸው ናቸው በማለት ጠቅሶ በአመልካችና በሌሎች ግለሰቦች ስም በባንክ የሚገኝ ገንዘብ ለመንግስት በውርስ ገቢ እንዲደረግ፣ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታግዶ የሚገኘው የስር 7ኛ ተጠሪ(አቶ ነብዩ በድሩ) ጅምር የመኖሪያ ቤትና መጋዝን በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ እንዲደረግ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ በአሁኑ አመልካች ስም በባንክ ይገኛል የተባለው የገንዘብ መጠን በንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ተክለሐይማኖት ቅርንጫፍ በሒሳብ ቁጥር 179 ብር 123,738.52 (አንድ መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም) እና በንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ተክለይሐይማኖት ቅርንጫፍ በሒሳብ ቁጥር 221 ደግሞ ብር 1,020,095.80 (አንድ ሚሊዩን ሃያ ሺህ ዘጠና አምስት ብር ከሰማንያ ሳንቲም) ስለመሆኑ በተጠሪ የውርስ ማመልከቻ ላይ ተጠቅሷል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ የውርስ ጥያቄ ላይ በሰጡት መልስም በመንግስት ላይ ደርሷል በማለት በማመልከቻው ላይ የተጠቀሰው ብር 13,457,694.40 (አስራ ሶስት ሚሊዩን አራት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአርባ ሳንቲም) በእርግጥ ለመድረሱ በሚያሳምን ሁኔታ ተጣርቶ ያለመቅረቡን፣ በማካካሻነት ንብረት ሊወረስ የሚገባው በመንግስት ላይ በእርግጥ ለደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ መሆን እንደአለበት በጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ስርዓትና የማስረጃ ሕግ መደንገጉን፣አመልካቹ ጥፋተኛ የተባሉት በዲክሊራሲዩን ቁጥር 19225 በደግፍ ይርጋ ስም ያስገቡት ሁኖ ንብረቱ በዋናው መዝገብ አራተኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ነብዩ በድሩ በመሆኑ ቀረጡን መክፈል የሚገባቸው ይኼው ግለሰብ መሆናቸውን፣ እንዲወረስ የተጠየቀውና በፍርድ ቤት የታገደው በባንክ የሚገኘው ገንዘብ አመልካቹ ጥፋተኛ የተባሉበት ድርጊት ከመፈጸሙ በፊት በተከፈተ ሒሳብ ውስጥ የተገኘና መጠኑም በእንቅስቃሴ ከፍ ዝቅ ሲል የቆየ በመሆኑ በስራ እንጂ በሕገ ወጥ መንገድ ያላገኙት መሆኑን፣ጥፋተኛ የተባሉት የጉምሩክ ስነ ስርዓት በመጣስ እንጂ በዋናው ወንጀል ተሳትፎ ኑሯቸው ባለመሆኑና በወንጀል ቀጥተኛ ተሳትፎ አድርገዋል ተብለው ጥፋተኛ ከተባሉት ተከሳሾች በመንግስት ላይ ደረሰ ለተባለው ጉዳት ለማካካስ በቂ ንብረት የተያዘ መሆኑን ዘርዝረው የተጠሪ የውርስ አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ሌሎች የሥር ተከሳሾችም አሉን የሚሏቸውን ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡ ክርክሩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በተከሳሾች ላይ የውርስ ጥያቄ መቅረብ የሚገባው እያንዳንዳቸው በወንጀል ድርጊት ምክንያት ሳይከፍሉ በቀሩት የታክስና ቀረጥ መጠን እንጂ በወንጀሉ ድርጊት ላልተሳተፉበትና ጥቅም ላላገኙበት የገንዘብ መጠን ሊሆን አይገባም የሚለውን ድምዳሜ ይዞ ተጠሪ ተከሳሾች በመንግስት ላይ የደረሰውን ብር 13,457,694.40 (አስራ ሶስት ሚሊዩን አራት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና አራት ብር ከአርባ ሳንቲም) በአንድነትና በነጠላ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ባቀረበው አቤቱታ ሁሉም አጥፊዎች የሚገደዱበት ምክንያት የለም፣ አመልካች አድራጎት በዲክላራሲዩን ቁጥሮች 19225፣21702፣23132 በገቡት እቃዎች ሳይከፈል የቀረው ግብርና ታክስ መጠኑ ብር 2,539,233.00 (ሁለት ሚሊዩን አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) መሆኑን፣ ይህንኑ ገንዘብ ተጠቃሚ የሆኑትም አመልካች ሳይሆኑ የስር ተከሳሽ የነበሩት አቶ ነብዩ ብድሩ መሆናቸውን፣ አመልካች በጉምሩክ አስተላላፊነታቸው ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያልተጣለባቸውና ግብሩንና ታክሱን የመክፈል ኃላፊነት የአቶ ነብዩ ብድሩ ሽፋ በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የአቶ ነብዩ በድሩ ብቻ ነው በማለት ወስኗል፡፡በሌሎች ተከሳሾችም ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ አቶ ነብዩ ብድሩ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱ አቶ ነብዩ ብድሩንና የአሁኑን ተጠሪ በመልስ ሰጪነት ሰይሞ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አቶ ነብዩ ብድሩ ለብቻቸው እንዲከፍሉ የተወሰነው የሕግ መሰረት በሌለበት አግባብ ነው በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ ብር 2,539,239.50 (ሁለት ሚሊዩን አምስ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) መክፈል ያለባቸው አቶ ነብዩ ብድሩ ሺፋ ብቻ ሳይሆኑ በወንጀል ድርጊቱ አብረውት ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡት ተከሳሾችሽ ጭምር ናቸው በማለት ገንዘቡን በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የሃላፊነት አይነትና መጠን አመልካች በወንጀሉ የነበራቸውን የተሳትፎ ደረጃ ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው መሆኑን እንዲሁም ውሳኔው የአመልካችን መብትና ጥቅም የሚነካ ሁኖ እያለ በይግባኝ ክርክሩ ላይ አመልካች እንዲካፈሉ ሳይደረግ መወሰኑ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ በይግባኝ ሰሚው ችሎት በነበረው ክርክር ተጠሪ ይግባኝ ባይ ባልሆነበት ሁኔታ በሰበር ክርክሩ ተሳታፊ ሊሆን የሚችልት አግባብ ያለመኖሩንና አመልካች ይነሳልን ለሚሉት የእግድ ትዕዛዝም ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ጠቅሶ ከክርክሩ ውጪ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለበት ቀዳሚው ነጥብ አመልካች የይግባኝ ክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆኑ ገንዘቡን በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ መመርመሩ ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡

አመልካች ከአቶ ነብዩ ብድሩ ጋር ብር 2,539,239.50 (ሁለት ሚሊዩን አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ተብሎ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ የተሰጠው አመልካቹ የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ መሆኑን ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ አሁን በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃ ደግሞ አመልካች ይህ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መብትና ጥቅማቸውን የሚነካ ሁኖ እያለ የክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆኑ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ የተከሰሱ ሰዎች በሕግ ከተጠበቁላቸው መብቶች አንዱ የመሰማት መብት ነው፡፡ ይህ መብት በመጀመሪያም ሆነ በሌሎች የክርክር ደረጃዎች በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት በመከተል ሊጠበቅ የሚገባ ነው፡፡መብቱ ቀሪ የሚሆነው ሕጉ በዘረጋው ስርዓት ባለመብቱ ሳይጠቀምበት ሲቀር ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የመሰማት መብት ተከሳሾች የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸውን ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20 (4) የተደነገገ ሲሆን ይህ መብት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(4) ድንጋጌ አግባብ የአገሪቱ የሕግ አካል በሆኑት የአለም አቀፍ ስምምነቶችም ጥበቃ ያገኘ ስለመሆኑ የሲቭልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን 14(3(ለ)) ድንጋጌን በመመልከት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ በአንቀጽ 10 ያስቀመጠው ድንጋጌም ማንም ሰው በተከሰሰበት ወንጀል ውሳኔ ለማግኘት ሙሉ የእኩልነት መብቱ ሊጠብቅለት እንደሚገባና ሚዛናዊና ይፋ የሆነ ፍርድ የማግኘት መብት እንደአለው ያሳያል፡፡ ይህ መብት የሚጠበቀው የመከራከር መብቱ በአግባቡ ሲጠበቅ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው የተከሳሽ መብት የሚያስገነዝበው አንድ ተከሳሽ ተገቢ ባልሆነ ማስረጃ ጥፋተኛ እንዳይባልና በከሳሹ ወገን ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀርቦ ከሆነም በበኩሉ ምንም ጥፋት ያልፈፀመና ንፁህ መሆኑን የማስረዳት ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚችል መሆኑንና ክርክሩ የእኩልነት መብቱ ተጠብቆ በግልጽና ተከሳሹ በይፋ በሚያውቀው አግባብ መሆን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ለቀረበበት ክስም ሆነ ይግባኝ ተገቢውን ክርክርና ማስረጃ ለማዘጋጀት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ተደርጎ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮችንና በቂ ጊዜ ማግኘት እንደሚገባው ሕጉ ያስገነዝበል፡፡ ተከሳሹ ይህንኑ በሕገ መንግስቱ ጥበቃ ያገኘውን የመሰማት መብታቸውን በመጀመሪያ ደረጃ ክርክርም ሆነ በይግባኝ ደረጃ በሚደረገው ክርክር በአግባቡ እንዲጠቀም ማድረግ የፍርድ ቤት ኃላፊነት መሆኑንም ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) እና (2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የተከሳሽ የመሰማት መብት ሊታለፍ የሚገባው ተከሳሹ መብቱን የማይጠቀምበት መሆኑን በግልፅ ለፍርድ ቤቱ ሲያረጋግጥለት ወይም በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት ክርክር መኖሩን እንዲያውቀው ተደርጎ ይህንኑ እያወቀ ፍርድ ቤት ለመቅረብ ፍቃደኛ ሳይሆን መቅረቱ በእርግጥ ሲታወቅ ብቻ መሆኑን ከድንጋጌዎች መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ ተከሳሹ የመሰማት መብቱን ስለመተው ባልተረጋገጠበት አግባብ ግን የተከሳሽን መብትና ጥቅም የሚነካ ውሳኔ ፍርድ ቤት መስጠት ተገቢነት የሌለው አካሄድ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉደይ ስንመለስ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ያየው አመልካችንና ተጠሪን እንዲሁም በወንጀሉ ጥፋተኛ የተባሉትን ሁሉንም ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ አድርጎ ሲሆን አመልካች ለተጠሪ የውርስ ጥያቄ አለኝ ያሉትን የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አቅርበዋል፡፡አመልካቹ ያቀረቡትን ክርክርም የስር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ለአመልካች መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት የማያደርስ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ በውጤቱ ተጠቃሚ መሆኑን ተገንዝቦ ይግባኝ ያልጠየቀ ቢሆንም ገንዘቡን ለብቻቸው ለተጠሪ እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው የወንጀሉ ተሳታፊ ነበር የተባሉ ግለሰብ(አቶ ነብዩ በድሩ) ግን ገንዘቡን ብቻዬን ልከፍል አይገባም በማለት አመልካችንና ሌሎችንም ግለሰቦች ሊጨምር ይገባል በማለት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ክርክሩን የአሁኑ አመልካች ሳይጠራ በመምራት ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች የንብረት ጥቅምና መብት የሚነካ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካችን ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ያላደረገበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩም በውሳኔው ላይ አልገለጸም፡፡ይህም አመልካች የይግባኝ ክርክሩ የሚመለከታቸው መሆኑን እንዲያውቁ ተደርጎ የክርክሩ ተሳታፊ ለመሆን ፍላጎት የሌላቸው መሆኑ ሳይረጋገጥ ክርክሩ መመራቱን የሚያረጋግጥ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በክርክር አመራር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በሕግ የተዘረጋ የክርክር አመራር ሳይሟላ የሚሰጥ ዳኝነት የግልጽነት መርህን የሚቃረንና በውጤቱም የተከራካሪ ወገንን መሰረታዊም ሆነ ስነ ስርዓታዊ መብት የሚጎዳ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች በሕጉ የተጠበቀላቸውን የሰውነት መብት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያለፈው አመልካቹ በግልጽ በመብታቸው የማይጠቀሙበት መሆኑን ሳያረጋገጡ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 91921 ሕዳር 06 ቀን 2006 ዓ/ም ብር 2,539,239.50 (ሁለት ሚሊዩን አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) አመልካች ከአቶ ነብዩ በድሩ ሽፋ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የይግባኝ ክርክሩ ተካፋይ ሁኖ የመሰማት መብት የታለፈው ያላግባብ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ክርክሩን በመ/ቁጥር 91921 ቀጥሎ የአመልካችን የመሰማት መብት በሕጉ አግባብ ሰምቶ አቶ ነብዩ ብድሩና ሌሎች የክርክሩ ተካፋይ ሊሆኑ የሚገባቸው ሰዎች ካሉም ወደ ክርክሩ እንዲገቡ አድርጎ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.104220

ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አታክልቲ አብርሃ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገ/ት/ባለስልጣን የሁመራ ቅርንጫፍ ዐቃቤ ሕግ -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገው ክሱ እና መጥሪያው በመደበኛ መኖሪያ አድራሻቸው እንዲደርሳቸው ሳይደረግ በመሆኑ ክርክሩ በሌሉበት ታይቶ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 91 (2) ስር የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የስድስት ዓመት ከአስር ወር ጽኑ እስራት እና የብር 5,500 የቅጣት ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ እንደገና ባሉበት እንዲታይ እንዲደረግ ያቀረቡትን ማመልከቻ እና ተጠሪው የሰጠውን መልስ ከመረመረ በኃላ የአመልካችን ጥያቄ ባለመቀበል በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 91 (2) ስር ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ጉዳይ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 161 (2) መሰረት በሌለበት ሊታይ የሚችል መሆን አለመሆኑን እና አመልካች በሌሉበት የተሰጠባቸው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡት ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሆን እኛም በሌሉበት የተሰጠባቸው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ጉዳዩን አመልካች በሌሉበት አይቶ የጥፋተኝነት ውሳኔውን የሰጠው የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሁመራ ምድብ ችሎት ጉዳዩ ተከሳሹ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ የሰጠው የፌዴራል ፖሊስ ተከሳሹን አላገኝኃቸውም በማለት ምላሽ ሰጥቷል፣ተከሳሹ በክልላዊ ጋዜጣ በወጣ ማስታወቂያም ተጠርተው አልቀረቡም በማለት ነው፡፡ተከሳሽ በበኩላቸው በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳልኝ ይገባል በማለት የሚከራከሩት በጎንደር በሕክምና ላይ የነበሩ መሆኑን እና ከሕክምና ክትትሉ በኃላም በመደበኛው መኖሪያ ቦታቸው የነበሩ ሆኖ እያለ የፍርድ ቤቱ ክስ እና መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ ፖሊስ አላገኘሁትም ብሏል በማለቱ እና በጋዜጣ ማስታወቂያ ተጠርተው አልቀረቡም በማለት ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገው አላግባብ ነው በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡አመልካቹ በጎንደር ከተማ በህክምና ክትትል ላይ ነበርኩ የሚሉበት ጊዜ ፍርድ ቤት መቅረብ ነበረባቸው ከተባለበት ጊዜ በፊት እንደሆነ ከጊዜው ቅደም ተከተል መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ አመልካች በህክምና ክትትል ላይ ነበርኩ የሚሉበት ጊዜ ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለው አይደለም፡፡በሌላ በኩል ግን አንድ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠበት ውሳኔ እንዲነሳለት የሚያቀርበውን ማመልከቻ ለመቀበል ከሚቻልባቸው ምክንያቶች አንዱ መጥሪያው ለተከሳሹ ያልደረሰው የመሆኑ ጉዳይ ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 199 (ሀ) ስር የተመለከተ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል ፖሊስ በደፈናው ተከሳሹን አላገኝኃቸውም ብሏል ከመባሉ ውጭ ተከሳሹን አላገኝኃቸውም በማለት ፖሊስ ምላሽ የሰጠው በርግጥም በምርመራ ጊዜ ከሰጡት መደበኛ የመኖሪያ አድራሻቸው ተገቢውን ፍለጋ አድርጎ ሊያገኛቸው እንዳልቻለ ተገቢውን ማረጋገጫ በመስጠቱ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ የፌዴራል ፖሊስ እንዳላገኛቸው አረጋግጧል ከማለት ውጭ ጉዳዩ በሌሉበት የታየው መጥሪያው በመደበኛ የመኖሪያ አድራሻዬ እንዲደርሰኝ ሳይደረግ ነው በማለት አመልካች ባቀረቡት የክርክር ነጥብ ላይ ተጠሪው ያቀረበው ግልጽ ማስተባበያ አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡ አመልካቹ በምርመራ ጊዜ ከገለጹት መደበኛ የመኖሪያ አድራሻቸው ተፈልገው የታጡ ስለመሆኑም ተጠሪው በግልጽ አልተከራከረም፡፡ባስመዘገቡት አድራሻ መጥሪያው ለአመልካቹ የተላከ መሆኑ ወይም አመልካቹ በዚሁ አድራሻቸው ተፈልገው ያልተገኙ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወደ ጋዜጣ ጥሪ አማራጭ የሚኬድበት አግባብ ስለማይኖር የጥሪ ማስታወቂያው በክልላዊ ጋዜጣ መነገሩ ብቻውን መጥሪያው ለአመልካች በአግባቡ እንዲደርስ ተደርጓል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ማንኛውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀጽ 20 (4) ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይህንን ሕገ መንግስታዊ መብት ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉት ደግሞ ክስ የቀረበባቸው መሆኑን በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 123 በተመለከተው መሰረት በሚላክ መጥሪያ እንዲያውቁት ሲደረግ ነው።አመልካቹ መጥሪያው በሕግ አግባብ የደረሳቸው መሆኑን ደግሞ የመዝገቡ ገልባጭ አያረጋግጥም።

በሌላ በኩል አንድ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሳኔ ተነስቶ ባለበት በድጋሚ እንዲታይ ያቀረበውን ማመልከቻ ባለመቀበል በሚሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት የማይቻል ስለመሆኑ እና ይግባኝ ማለት የሚቻለው በቅጣቱ መጠን ላይ ብቻ ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 202 (3) ስር በግልጽ የተመለከተ ሆኖ ሳለ እና አመልካች ለትግራይ ብ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቅጣቱ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ሳይኖር የቀድሞው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በሚል በተሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበለትን ቅሬታ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ አስተናግዶ ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195 (1) ድንጋጌን ጠቅሶ የሰጠው ትዕዛዝ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል ጉዳዩ አመልካች በሌሉበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የስድስት ዓመት ከአስር ወር ጽኑ እስራት እና የብር 5,500 የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው ባስመዘገቡት የመኖሪያ አድራሻ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ ሆኖ እያለ እና ይህም በሌሉበት የተሰጠባቸውን ውሳኔ ለማንሳት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 199 (ሀ) ድንጋጌ መሰረት በቂ ምክንያት ሆኖ እያለ ውሳኔው ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. አንድ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተሰጠበት ውሳኔ ተነስቶ ባለበት በድጋሚ እንዲታይ ያቀረበውን ማመልከቻ ባለመቀበል የሚሰጥ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 202 (3) ስር በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን አስመልክቶ የቀረበለትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ በማስተናገድ የትግራይ ብ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 67114 በ 09/10/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

2. በሌሉበት ታይቶ የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የስድስት ዓመት ከአስር ወር ጽኑ እስራት እና የብር 5,500 የቅጣት ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡትን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁመራ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 09566 በ05/09/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች በሌሉበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የስድስት ዓመት ከአስር ወር ጽኑ እስራት እና የብር 5,500 የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው ባስመዘገቡት የመኖሪያ አድራሻ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ ወይም በዚሁ አድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ አለመቻላቸው ሳይረጋገጥ በመሆኑ እና ይህም በሌሉበት የተሰጠባቸውን ውሳኔ ለማንሳት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 199 (ሀ) ድንጋጌ መሰረት በቂ ምክንያት በመሆኑ ውሳኔው ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁመራ ምድብ ችሎት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 202(1) በተደነገገው መሰረት ቀድሞ ጉዳዩን ያዩት ዳኞች በማይሰየሙበት ችሎት አመልካች ባሉበት ጉዳዩን እንደገና በማየት በስነ ስርዓት ሕጉ በተመለከተው መሰረት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁመራ ምድብ ችሎት እንዲሁም በሚገኙበት የሁመራ ማረሚያ ተቋም በኩል ለአመልካቹ ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.97291

ቀን ሰኔ 17/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

መስጠፉ አህመድ

ተሽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ጎሹ ዮሐንስ ገብሩ ጠበቃ ወንድ ይፍራው አረፈ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል የሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓ/ሕግ የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስልጣን አለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ከሳሽነት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ ያልሆኑትን ጨምሮ በሦስት ግለሰቦች ላይ የቀረበው ክስ 1ኛ ተከሳሽ አደምኑር ፣2ኛ ተከሳሽ አዳነ ይርዳው 3ኛ ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች በመሆን ነው ፡፡ የአሁኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች እና በዚህ ጉዳይ ተከራካሪ ያልሆኑ ግለሰቦች ሁለት ክስ ያቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ክስ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በነበሩት አደም ኑር ገበያው እና አዳነ ይርዳው የቀረበ ነው ፡፡ የክሱ አጭር ይዘትም ፡- በ 1997ዓ.ም የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) (ለ) እና 379(1)(ሀ)እና (ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በመንግስት ንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ እና ለራሳቸው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ 1ኛ ተከሳሽ በግብርና ምርት ላኪነት የተሰማራ ባለሀብት /ኢንቨስተር /2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ወኪል መስለው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ለመቅረብ እና ከድርጅቱ በርካታ ኩንታል ማዳበሪዎች ለመውሰድ ያመቻቸው ዘንድ በሀሰት የተዘጋጀ በአማራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክልል በምሥራቅ ጎጃም ዞን በሰሊቨን ወረዳ መሬት ለማልማት የተደረገ የመሬት ኪራይ ውልና ተዛማጅ ደብዳቤ ፣በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንደተሰጠ ተደረገው ተመሳስለው የተሠሩ የንግድ ፈቃዶች በአማራ ክልል መንግስት እንደተሰጠ ተደርጎ ተመሳስሎ የተሠራ የኢንቨስትመንት ፈቃድና የውክልና ማስረጃ እንዲሁም ትክክለኛው ከባንክ ገቢ የተደረገው የገንዘብ መጠን 914.55 ሆኖ እያለ ብር 914,355.00 ያክል ገንዘብ እንዳለው የሚገልጽ ሀሰተኛ የባንክ ሲ.ፒ.ኦ.እና ሌሎች ሰነዶች በመያዝ ሰኔ 23 ቀን 2001 እና በተከታዮች ቀናት በግብርና ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በመቅረብ ገቢ በማድረግ አላግባብ የተጠቀሙና በ2ኛ ክስ የተመለከተውን የመንግስት ንብረት ሐምሌ 03 ቀን 2001 ዓ.ም በመወሰዳቸው ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት በፈጸሙት በሀሰተኛ ሰነድም መገልገል የሙስና ወንጀል እንደተከሰሱ፤

ሁለተኛው ክስ በሁሉም ተከሳሾች የቀረበ ሲሆን ዋና ይዘቱ ፡- በ1997 ዓ.ም የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) (ለ) 33 እና 407(1)(ሀ)(ለ)እና (2) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ 3ኛ ተከሳሽ(የአሁኑ አመልካች) በ1ኛ ክስ በተመለከቱት ቀናት የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የድርጅቱ የሽያጭና ገበያ ጥናት ዋና ክፍል ኃላፊ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ለራሱ እና ለሌሎች ተከሳሾች የማይገባ ጥቅም ለማግኘት እንዲሁም ለማስገኘት እና በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ፡-

ሀ. 2ኛ ተከሳሹ ከ1ኛ ተከሳሽ የሚገለገልበትን በርካታ ሰነዶች ይዞ በማዳበሪያ ግዥ ሲጠየቅ በመመሪያ መሠረት 3ኛ ተከሳሽ እንደ ኃላፊነታቸው ከዋናው ጋር ማመሣከር ሲገባቸው ይህንኑ ባለማድረጋቸው የማዳበሪያ ግዥ ጥያቄውን በስሙ በቀጥታ ያቀረበው 2ኛ ተከሳሽ ሆኖ እያለ ይኸው ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ የፈጠራ ድርጅት /አደም ኑር ገበያው ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ንብረት መስለው የቀረቡትን በ1ኛ ክስ የተመለከቱትን ሐሰተኛ ሰነዶች ይዞ ሲቀርብ 3ኛ ተከሳሽ የዋጋ ማሣወቂያ ከመፍቀዳቸው በፊት የራሱ ሰነዶች መሆናቸውን ሳያረጋግጡ ላላመለከተ (ግዥ ላልጠየቀ) አካል ከመመሪያው ውጭ መፍቀዳቸው ፡- 2ኛ ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ወኪል ናቸው ቢባል እንኳ የተያዘው የውክልና ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ ያልተሟላና ለዚህ በቂ አለመሆኑ እየታወቀ እንዲታረምና በመመሪያው መሠረት የውክልና ደብዳቤ እንዲቀርብና የግዥ መጠየቂያ ማመልከቻው እንዲስተካከል አለ ማድረጋቸው እንዲሁም በቀን 02/11/2000 ዓ.ም በቁጥር 89/008-12/00 ከዋናው መሥርያ ቤት ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአድራሻ እና ለንግድ መመሪያ በግልባጭ የተፃፈው የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ለሰፋፊ የግል እርሻዎች የሚፈቀደው የማዳበሪያ የሽያጭ መጠን ለአንድ ሄክታር መሬት አንድ ኩንታል ዳፕና አንድ ኩንታል ዮሪያ በጠቅላላው ከ 500 ኩንታል ሣይበልጥ የሚሸጥ መሆኑ እየገለጹ ተከሳሽ ከመመሪያው ውጭ 3,000 ኩንታል ማዳበሪያ በመፍቀዱ፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾችም በመግቢያው ላይ በተጠቀሰው የወንጀል ሐሳብ በመነሳት ከ3ኛ ተከሳሽ በመመሣጠርና በመንግስትና በህዝብ ሐብት ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው የመንግስት የልማት ድርጅት የሽያጭ ህጋዊ አሠራሮችና መመሪያዎች እንዲጣሱ በማድረግ ባለሀብትና ወኪል በመምሰል በ1ኛ ክስ የተገለጹትን ሐሰተኛ ሰነዶች ይዘው በመቅረብ ግምቱ ብር 913,440.45 የሆነ ማዳበሪያ ከተጠቃሹ የመንግስት የልማት ድርጅት ላይ ወስደዋል ። በመሆኑም ተከሳሾቹ የሽያጭና የአሠራር መመሪያዎች በአግባቡ ከማከናውን በመታቀብ እና እርስ በርስ የጥቅም ተከፋይ ለመሆን በመመሳጠር በዋና ወንጀል አድራጊነት ተሳታፊ በመሆን ድርጊቱን በመፈፀማቸው በስልጣን ያለ አግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው።

በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች (አመልካች) ቀርበው በጉዳዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው በተሰጠው ብይን እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሁለቱም ክሶች ተነጣጥለው እነዲታዩ ትዕዛዝ ተሰጥቷል ። አንደኛ ተከሳሽ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ታዟል ። 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች (አመልካች) ክሱን ክደው በመከራከራቸው የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ተሰምቷል ። 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችም የበኩላቸው የመከላከያ ማስረጃ አቅርበዋል ። የሥር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ 2ኛ ተከሳሽ የነበረው በተመለከተ የዓቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃ በሁለቱም ክሶች የተጠቀሱትን ፍሬ ነገሮች የፈፀመ ስለመሆኑ መስክሯል ። የ2ኛ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ ያስረዱት ፍሬ ነገር ተከሳሹ የድለላ ሥራ የሚሠራ ስለመሆኑ እንጂ ለተከሰሰበት ጉዳይ ባስያዘው ጭብጥ መሠረት ድርጊት ያልፈጸመ ስለመሆኑ የመሰከሩት ነገር የለም ። 2ኛ ተከሳሽ በሰነድ ማስረጃነት የቆጠረው በአንደኛ ተከሳሽ ለ2ኛ ተከሳሽ ተሰጠ የተባለውን የውክልና ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው ስለመሆኑ ለግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የፃፈው ማመልከቻም በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጉዳዩ ለማስፈጸም የተዋዋለበት ሰነድ የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ የሚያጠናክሩ ናቸው ከሚያሰብል በስተቀር የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ተከላክሏል የሚያስብሉ አይደለም ። ስለሆነም በቀረበበት 1ኛ ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 379(1)(ሀ) በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/ቁ. 32(1)(ሀ)(ለ)፤33 እና 407(1) (ሀ)(2)በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.113(2) መሠረት አንቀጽን በመቀየር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ)(ለ) እና 407(1)(ሀ) በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.149(1)መሠረት ጥፋተኛ ነው ተብሏል።

የአሁኑ አመልካች (3ኛ ተከሳሽ) በተመለከተም የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ እንዲከለከሉ በተሰጠው ብይን መሠረት በድርጅቱ የሚወጡ የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ወሰን በተመለከተ በዓቃቤ ሕግ ክስ የተጠቀሰው መመሪያ ተፈፃሚነት ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንጂ ለዋናው መ/ቤት ተከሳሽ ለሚሰሩበት ለሽያጭና ገበያ ጥናት ዋና ክፍል አለመሆኑን በዝርዝር ያስረዱና በክሱ የተጠቀሰው የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ በአድራሻ የተፃፈው ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ 3ኛ ተከሳሽ በኃላፊነት ተመድበው ለሚሰሩበት የሽያጭና የገበያ ጥናት ዋና ክፍል በዓቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ የተጠቀሰውና በድርጅቱ ሐምሌ 02 ቀን 2000 ዓ.ም ተላለፈ የተባለው መመሪያ ከወጣ በኃላ ሚያዝያ 19 ቀን 2001 ዓ.ም ተከሳሹ በኃላፊነት ተመድበው ለሚሰሩበት ለሽያጭና ገበያ ጥናት ዋና ክፍል በአድራሻ የተላለፈው የማዳበሪያ ሽያጭ መመሪያ በተሰጣቸው ስልጣን መጠኑ እስከ 10,000 ኩንታል የሚደርስ የማዳበሪያ ሽያጭ ለግል ስፋፊ የእርሻ ልማት ባለሃብት መፍቀድ እንደሚችሉ ሥልጣን የተሰጣቸው ለመሆኑ የሚያረጋግጥ የመከላከያ የሰነድ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ይህም ተከሳሽ በዓቃቤ ሕግ ከመመሪያ ውጭ የማዳበሪያ ግዥ ፈቅደዋል በሚል የተጠቀሰባቸው የክስ ፍሬ ነገር በተመለከተ በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው ተከላክለዋል የሚያስብል ሆኖ ተገኝቷል ። 3ኛ ተከሳሽ በዓቃቤ ሕግ ከተጠቀሰባቸው የክስ ፍሬ ነገሮች ውስጥ 2ኛ ተከሳሽ ከ1ኛው ተከሳሽ ጋር የሚገለገሉባቸው ሐሰተኛ ሰነዶች ይዞ የማዳበሪያው ግዥ በቀጥታ የጠየቀው 2ኛ ተከሳሽ ሆኖ የማዳበሪያው ግዥ ከመፍቀዳቸው በፊት 2ኛ ተከሳሽ ግዥው እየጠየቀ ያለው የራሱን ሰነዶች ይዞ እንደሆነ ሣያረጋግጡ ግዥው ላልጠየቀ አካል ፈቅደዋል ። 2ኛው ተከሳሽ የ1ኛው ተከሳሽ ወኪል ነው ቢባል እንኳ ተያይዞ የቀረበው የውክልና ሰነድ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው መሆኑን እያወቁ የማዳበሪያው ግዥ እንዲፈጸም ፈቅዷል በሚል ሲሆን በዓቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች 2ኛ ተከሳሽ ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም የማዳበሪያ ግዥ በራሱ ስም የጠየቀና የቀረቡት ሰነዶች አደም ኑር ገበያው ኃ/የተ.የግ ማህበር የሚል ሆኖ እያለና የቀረበው የውክልና ሰነድ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው ስለሆነ በግልጽ በቀላሉ ችግሩን መለየትና ማጣራት የሚያስችል ሆኖ እያለ ይህንን ሳይፈጽሙ ከድርጅቱ ማዳበሪያ ግዢ እንዲፈፅም መፍቀዳቸው የተመሰከረባቸው በመከላከያ ማስረጃዎች የተከለከሉ ሆነው አልተገኘም ። በዚህም መሠረት በ3ኛ ተከሳሽ (አመልካች) ላይ ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 33 እና 407(1)(ሀ)(ለ) (2) ተላልፏል በማለት የቀረበው ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.113(2) መሠረት አንቀጹን በመቀየር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)(ለ) እና 33 እና 407 (1)(ሀ) ሥር በወ/መ/ሥ/ሥ/ህቁ 149(1) መሠረት ጥፋተኛ ነው በማለት ተወስኗል።

ቅጣት በተመለከተም 1ኛ ተከሳሽ በሌለበት የታየ በመሆኑ የቅጣት ማቅለያዎች ግምት ውስጥ ሳይገባ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በተመለከተም በግራ ቀኙ የቀረቡት የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በማገናዘብ 1ኛ ተከሳሽ በ 13 ዓመት ጽኑ እስራት እና 6,000 ብር መቀጮ 2ኛ ተከሳሽ በ 8 ዓመት ጽኑ እስራት 5000 ብር መቀጮ 3ኛ ተከሳሽ (አመልካች) ደግሞ በ 4 ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራትና ብር 2500.00 እንዲቀጡ ተወስኗል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና ቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ይግባኝ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታው ወደ ጉዳዩ ለመግባት የሚያስችል በቂ ምክንያት የለውም በማለት ውድቅ ተደርጓል ። የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራቀኙ የጹሑፍ ክርክር አድርገዋል ። የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት ፡- የዋጋ ማሳወቂያ መስጠት መደበኛ ሥራቸው እንደሆነ ፤የቀረበላቸው የሐሰት የሰነድ ማስረጃ የተባለው ሐሰተኛ ስለሀመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚችሉበት አግባብ እንዳልነበረ ሽያጭ የፈቀደው የሌላ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ነው። የዋጋ ማሳወቂያ የተሰጠው ለ 5 ቀን የሚያገለግል ስለመሆኑ ፤የዋጋ ማሳወቂያ መስጠት ለመሸጥ ሐሳብ ማቅረብ እንጂ ሽያጭ መፈጸም አይደለም ። እቃ ለመሸጥ አሳብ መቅረብ የወንጀል ድርጊት አይደለም ። በሲ.ፒ.ኦ ደረሰ የተባለው ጉዳት በቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ትዕዛዝ የተከናወነ እንጂ አመልካች ተሳትፎ እንዳልነበራቸው በድርጊቱ ምክንያት እና ውጤት ግንኙነት የለውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል የሚል ስለመሆኑ ተረድተናል። ተጠሪ በበኩሉ በአመልካች በኩል መጣራት የገባቸው የነበሩ ነገሮች ባለ መጣራታቸው ከመመሪያው ውጭ ሽያጭ ተከናውነዋል ።አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሾች በነበሩ ግለሰቦች የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ሳያጣራ በማሳለፍ ምክንያት ድርጊቱ የወንጀል ውጤት ያስገኘ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እነዲጸና መጠየቁን ተመልክተናል ። አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታው በማጠናከር ተከራክሯል።

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ፤ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ፍርድ አግባብነት ካላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች በማዛመድ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው በአመልካች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ የወ/ሕ/ቁ 32(1)(ሀ)(ለ)፣33እና 407(1)(ሀ)(ለ)እና (2) የተመለከተውን በመተላለፍ በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በነበሩ የቀረቡ ሐሰተኛ ሰነዶች የዋጋ ማሳወቂያ ከመፍቀዳቸው በፊት የ2ኛ ተከሳሽ የራሱ ሰነዶች መሆናቸው አላረጋገጡም ። ግኝር ላልጠየቀ ግለሰብ ከመመሪያው ውጭ ፈቅደዋል። 2ኛ ተከሳሽ በአንደኛ ተከሳሽ ወኪል ነው ቢባል እንኳ የተያዘው የውክልና ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ የለም።ከዋናው መሥሪያ ቤት የተፃፈው የማዳበሪያ ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ለሰፈራ እርሻዎች የሚፈቀደው የማዳበሪያ ሽያጭ መጠን በሄክታር አንድ ኩንታል ዳፕና አንድ ኩንታል ዮሪያ በጠቅላላው ከ 500 ኩንታል እንደማይበልጥ የሚሸጥ መሆኑ እየታወቀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3000 ኩንታል መዳበሪያ እንዲሸጥ ፈቅደዋል የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ፤የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ሥልጣኑ የደረሰበት ድምዳሜ አመልካች በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት መጠኑ እስከ 10,000 ኩንታል ማዳበሪያ መሸጥ እንደሚችሉ ይሁንና 2ኛ ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ተወካይ እነደሆነና የቀረቡ የግዥ ሰነዶች አደም ኑር ገበያው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት የሚል ሆኖ ሳለ 2ኛ ተከሳሽ በራሱ ስም ግዥ መጠየቁ የቀረበው የውክልና ሰነድም የወካይ ስምና ፊርማ የሌላው እንደሆነ ፤ይህም በቀላሉ ችግሩን መለየትና ማጣራት የሚቻል እንደነበር ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥልጣኑ ያለአግባብ የተገለገለ ከሆነ በወ/ሕ/ቁ.407 ሥር ተጠያቂ እንደሚሆን ግልጽ ነው ፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ እንደሆነ ፤የድርጊቱ አፈፃፀምም የተሰጠው ሹመት ወይም ሥልጣን በግልጽ ተግባር ወይም ግድፈት ከተሰጠው ስልጣን አልፎ በመሥራት ወይም ሥልጣኑ በማይፈቅደለት በተለይም ሥልጣን ሳይኖረው ወይም ከሥራ ከታገደ ከተነሣ ፤ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱ ከተወ በኃላ የተፈጸመ ከሆነ የወንጀል ድርጊቱ ለማቋቋም በአማራጭ የተዘረዘሩ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ እንደ ወንጀሉ ክብደትም ከወንጀል ፈፃሚው ኃላፊነት፤የደረሰው ጉዳት ወይም የተገኘው ጥቅም ወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓላማ መሠረት በማድረግ ወንጀሉ እንደሚከብድ የወ/ሕ/ቁ. 407(2) እና (3) ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት ዓላማና መንፈስ መረዳት ይቻላል ፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግ ክስ በማሻሻል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) (ለ) እና 407(1)(ሀ) ሥር ጥፋተኛ ያላቸው ስለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል ፡፡ የዚህ ድንጋጌ ሙሉ ይዘት ፡ የተሰጠው ሹመት ወይም ሥልጣን በግልጽ ተግባር ወይም ግድፈት ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ “የሚል ነው ፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ለማለት እንደመነሻ የወሰደው ግዥው የተጠየቀው ለአደም ኑር ሆኖ እያለ 2ኛ ተከሳሽ በራሱ ስም የራሱ ሰነዶች ይዞ እየጠየቀ መሆን ያለመሆኑን አላጣሩም ፤2ኛ ተከሳሽ የ1ኛ ተከሳሽ ተወካይ ነው ቢባል እንኳ የውክልና ሰነዱ የወካይ ስምና ፊርማ ያለው ነው በቀላሉ መለየት ይቻል ነበር በሚል ነው ፡፡ አመልካች የዋጋ ማሳወቂያ ሰነድ የሰጡ ስለመሆኑ አላከራከረም ፡፡ በዋጋ ማሳወቂያው መሠረት ሽያጭ መፍቀድና ማከናወን ደግሞ በሌላ የሥራ ክፍል የሚደረግ ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር መረዳት ይቻላል ፡፡ አመልካች በኃላፊነት እንዲጠየቁ በመሠረታዊነት የተያዘው ምክንያት የውክልና ሰነዱ የተሟላ ባለመሆኑ ችግሩን በቀላሉ መለየትና ማጣራት ይቻል ነበር በሚል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት መሠረታዊ ነጥብ አመልካች በውክልና ሰነዱ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወካይ ስምና ፊርማ የሌለ መሆኑ እየታየ የዋጋ ማሳወቂያ ሰነድ መስጠታቸው በወ/ሕ/ቁ 407(1)(ሀ) ሥር ጥፋተኛ ሊያሰኛቸው ይችላልን ? የሚል ነው።

ከክርክር ሂደቱ መረዳት እንደተቻለው አመልካች የቀረቡ ሰነዶች በጥንቃቄ ለይተው ማጣራት የማይችሉበት ሁኔታ እንደነበር በግልጽ የቀረበ ክርክር ባይኖርም በወ/ሕ/ቁ.407(1)(ሀ) እንደተመለከተው ግን የተሰጣቸው ኃላፊነት ያለአግባብ የተገለገሉ ስለመሆናቸው የወንጀል ሕጉ እንደ መሠረታዊ ማቋቋሚያ የዘረዘረው ፍሬ ነገር ስለመረጋገጡ ከሳሽ ወገን የማስረዳት ሸክሙ ስለመወጣቱ የሚያሳይ ነገር በሥር ፍርድ ቤት አልቀረበም ። ይህ ከሆነ ደግሞ በአመልካች የተፈጸመው ድርጊት ስልጣን አላግባብ መገልግል ሳይሆን የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚፈጸም ወንጀል መሆኑን መረዳት ይቻላል ። አመልካች የሥራ ግዴታቸው ሲወጡ ከእሳቸው የሚጠበቀውን ግብይት ለማካሄድ እንደቅድመ ሁኔታ የሚወሰዱ የቀረቡ ሰነዶች በተገቢው መንገድ ተፈረመው የቀረቡ መሆን ያለመሆናቸው ፤የውክልና ስጪ ስምና ፊርማ መኖር ያለመኖር የድርጅቱን አሠራር በሚፈቅደው አግባብ በጥንቃቄ ባለማጣራታቸው በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በቀረቡት ሐሰተኛ ሰነድ ተጠቅመው ከግብርና ምርት ማሳደጊያ አቅራቢ ድርጅት ማዳበሪያ ወስደዋል ። በዚህም በድርጅቱ የገንዘብ ጥቅም ላይ ጉዳት ደርሰዋል ። በመሆኑም አመልካች የሥር ፍርድ ቤት በወ/ሕ/ቁ 407(1)(ሀ) ሥር ጥፋተኛ ማለቱ የወንጀል ድርጊቱ ይዘትና ባሕሪ ያላገናዘበ ነው። አመልካች ጥፋተኛ ሊሆኑ የሚገባው ከፈጸሙት የወንጀል ድርጊት በተጣጣመ መልኩ መሆን ይገባዋል ። በዚህም አመልካች የሥራ ኃላፊነታቸው ሲወጡ ተገቢው ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው በሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የወካይ ስምና ፊርማ የሌለው ። ንብረት እንዲገዛ የጠየቀው 1ኛ ተከሳሽ ሆኖ ሳለ 2ኛ ተከሳሽ በስሙ ግዥ መጠየቁ የቀረቡ ሰነዶች አግባብነትና አስፈላጊ ፎርማልቲዎች የሚሉ መሆን ያለመሆናቸው የተለመደው አሠራር ተከትለው ባለማጣራታቸው ምክንያት የሥራ ኃላፊነትን ያለመሠጠት ወንጀል ፈጽመዋል ። ስለሆነም የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/ሕ/ቁ/32(1)(ሀ)(ለ)፤33እና 407(1)(ሀ)ሥር ጥፋተኛ ማለቱ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱ በአግባቡ ባለመሆኑ አመልካች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው አግባብነት ባለው የወንጀል ድንጋጌ በመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113(2) በሚያዘው መሠረት ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 407 (1) (ሀ) ወደ ወ/ህ/ቁ.420/1/ሥር በመለወጥ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል ።

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ በመለወጡ በሥር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው ቅጣት ተገቢነት መርምረናል ። የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2002 ወይም ቁጥር 2/2006 መሠረት በማድረግ ነው። አመልካች ጥፋተኛ የተሰኙበት የሕግ አንቀጽ የወንጀል ደረጃ እና መነሻ የእስራት ወይም መቀጮ እርከን የወጣለት አይደለም ። አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 420(1) ከአንድ ሺህ ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው በ2001 ዓ.ም በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የቅጣት መመሪያ 1/2002 ነው፡፡ የወንጀል ቅጣት ሲወሰን የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ በአንድ በኩል የወንጀል ፈፃሚው ግላዊ ሁኔታዎች በሌላ በኩል ግምት ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ከወ/ሕ/ቁ 1 እና 88 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና ዓላማ የምንረዳ ነው ፡፡ በተያዘው ጉዳይ ፍርድ ቤቱ የእስራት አማራጭ ወስዷል ፡፡ አመልካች የፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ክብደትና ባህሪ መሠረት በማድረግ የስድስት ወር ቀላል እስራት መነሻ ይዘናል ፡፡ መቀጮ በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በ 2500 ብር እንዲቀጡ የወሰነ ቢሆንም በዚህ ድንጋጌ የቀላል እስራት አማራጭ ብቻ የተወሰደ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የጣለው መቀጮ የሕግ መሠረት የሌለው ስለሆነ ሊነሳ የሚገባው ነው፡፡በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካች ሊያርምና ሊያስተምር ይችላል ፤መሰል አጥፊዎችን ያስጠነቅቃል ብለን ያመነበት አመልካች በስድስት ወር ቀላል እስራት ሊቀጡ ይገባል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካች የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ዓይነት በአግባቡ ሳያገናዝቡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ)እና (ለ) 407(1)(ሀ)ሥር ጥፋተኛ ማለታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በማረም በወ/ሕ/ቁ.32(1)(ሀ)(ለ)፤33 እና 420(1) ሥር ጥፋተኛ ናቸው በማለት ተከታዩን ወስነናል ፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.94053 በ 2/09/2005ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና ቅጣት ፤የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ.92016 በ 29/02/2006ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.195(2)(ለ)መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው በሥልጣን ያለአግባብ በመገልገል የወ/ህ/ቁ 407(1)(ሀ)ሥር ሳይሆን የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት ወንጀል የወ/ህ/ቁ.420(1) ሥር ነው በማለት ወስነናል ፡፡
3. አመልካች ለፈጸሙት ወንጀል በስድስት ወር ቀላል እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት የተወሰነባቸው ብር 25000/ሁለት ሺህ አምስት መቶ /መቀጮ ለመንግስት ገቢ አድርገውት ከሆነ ወጪ ሆኖ እንዲከፈላቸው ታዟል፡፡ ይፃፍ ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.103775

ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ተሽሊት ይመስል

አመልካች፡- ሀብቱ ቱሉ ዳዲ -ጠበቃ በቃሉ ያለው ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የፌደራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን - ዐ/ህግ ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ መነሻ ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በመዝገብ ቁጥር 104519 በአመልካች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመዝገብ ቁጥር 100951 ሰኔ 18 ቀን 2006 ዓ.ም አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የበታች ፍርድ ቤቶች በአምስተኛ ክስ ላይ የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በሁሉም ክሶች ላይ ደግሞ የቅጣት አሰላልን በተመለከተ ተፈፃሚነት ያለውን መመሪያ ለይቶ ለማሳረም ነው፡፡

በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ከሌሎች አምስት ሰዎች ጋር ክስ የቀረበባቸው ሲሆን በአሁኑ አመልካች ላይ የቀረበው ክስ በአራት ምድብ የተከፈለ ነው፡፡

ተጠሪ ያቀረበው 1ኛ ክስ ይዘት፡- አመልካችን ጨምሮ የስር 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)((ለ)) እና አንቀፅ 379 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ የተደነገገውን በመተላለፍ የመንግስት ሰነድ አሰመስሎ የማዘጋጀትና መገልገል የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡ 2ኛው ክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደግሞ አመልካችና የስር 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ)(ለ)) እና 696(ሀ) ስር የተደገገውን በመተላለፍ የከባድ አታላይነት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ 3ኛው ክስ ደግሞ የአሁኑን አመልካች ጨምሮ የስር 1ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ) (ለ)) እና 379(1(ሀ)) ስር የተደገገውን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት አስበው ሐሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ 4ኛ ክስ ደግሞ አመልካች ከስር 1ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች ጋር ሁነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ)(ለ) እና 696(ሀ) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የአታላይነት ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ በአመልካች ላይ ብቻ የቀረበውና የመጨረሻው ክስ በተራ ቁጥር አምስት የተጠቀሰው ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካቹ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1(ሀ)(ለ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት እና ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እ.ኤ.አ ኦገስት 23 ቀን 2005 በፐርሶኔል ማኔጅመንት በመጀመሪያ ዲግሪ መመረቁን የሚገልፅ ሀሰተኛ ጊዜያዊ ዲፕሎማ እና ደጅኔ ተሊላ አሊ የተባለ ግለሰብ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ፋኩሊቲ በመካኒካል ኢንጂነሪንግ እ.ኤ.አ ጁላይ 24 ቀን 2004 ዓ/ም በአድቫንስድ ዲፕሎማ መመረቁን የሚገልፅ ሀሰተኛ ጊዜያዊ የምረቃ የምስክር ወረቀት ተመሳስሎ የተሰራ ሐሰተኛ የዩኒቨርሲቲውን ማህተም በመጠቀምና የኃላፊዎችን ፊርማ አስመስሎ በመፈረም አዘጋጅቶ ካስቀመጠበት በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ውስጥ በሚገኘው የተከሳሽ መኖሪያ ቤት በ2/06/2003 ዓ/ም በተደረገው ብርበራ የተገኘ መሆኑን በመዘርዝር አመልካቹ ሐሰተኛ ሰነድ የማዘጋጀት የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም አመልካች የቀረበባቸውን ክስ እንዲረዱት ከአደረገ በኋላ በስርዓቱ መሰረት በቅድመ ክስ ሂደት ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ አድርጎ በቅድመ ክስ ጊዜ አመልካች ያቀረቧቸውን መቃወሚያዎችን ውድቅ አድርጎ ጉዳዩን ወደ መደበኛው የክርክር ሂደት በመግባት ክርክሩን መርቷል፡፡ ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት አሉኝ ያላቸውን የሰውና የፅሁፍ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች መከላከያ እንዲያቀርቡ ተደርጎ ማስረጃዎቻቸው ተሰምተዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ከመረመረ በኋላ አመልካች በተጠሪ የክስ ዝርዝር የተገለፁትን ተግባራት መፈጸማቸው በተጠሪ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠና በመከላከያ ማስረጃዎችም ያላስተባበሉ ናቸው በማለት አመልካች በቀረበቡባቸው አምስት ክሶች ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የሙስና ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በመቀጠል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሻሽሎ የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት አድርጎ ለወንጀሎቹ ደረጃ በመለየትና ለእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት የሁለት አመት እስራት መነሻ ቅጣት በማስቀመጥ ለአምስቱም ክሶች ይህንኑ የሁለት አመት እስር ጊዜ ደምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መነሻ ቅጣቱን አስር አመት እንደሚሆን ጠቅሶ ይኼው የቅጣት መጠን የሚወድቅበትን የእስራት ቅጣት እና የገንዘብ መቀጮውን እንደየድንጋጌዎቹ ይዘት በመለየት የእስራት ቅጣቱ በእርከን 29፣ የገንዘብ መቀጮው ደግሞ በእርከን 8 ስር እንደሚወድቅ ወስኗል፡፡ ከዚህም በኃላ በግራ ቀኙ የቀረቡትን የቅጣት አስተያየቶችን በመመርመር በአመልካች ላይ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በተጠሪ በኩል ያለመቅረባቸውን ጠቅሶ በአመልካች በኩል ግን ከዚህ በፊት በወንጀል ተክሰው ተቀጥተው የማያውቁ መሆኑን አመልካች የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን የሚያሳዩ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መቅረባቸውን ገልጾ በመመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 23(4) መሰረት እያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሁለት ሁለት እርከን ሲያስቀንስ የእስራት ቅጣቱ ከእርከን 29 ወደ እርከን 27 እንደሚወርድ፣ የገንዘብ መቀጮው ደግሞ ከእርከን 8 ወደ እርከን 6 እንደሚወርድ ገልፆ በእነዚህ እርከኖች ለፍርድ ቤቱ በተተወው ፍቅድ ስልጣን መሰረት አመልካች በስምንት አመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 10,000.00 (አስር ሺህ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንን ፍርድ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

አመልካች ሐምሌ 24 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ ሰባት ገፅ የሰበር አቤቱታ በ5ኛ ክስ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 379(1(ሀ)) ተጠቅሶ ጥፋተኛ የተባሉት ድንጋጌው ከአድራጎታቸው ጋር ባልተጣጣመበት ሁኔታ መሆኑን፣ የቅጣት ውሳኔውም መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት መሰላት ሲገባው የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት መደረጉ ያላግባብ መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት በእያንዳንዱ ሕጋዊ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መቀነስ የነበረበት የሶስት እርከን ቅጣት ሳይቀነስ የታለፈና በሕግ ፊት እኩል ሁኖ የመታየት መብታቸው የተነካ መሆኑን፣ ለእያንዳንዱ ክስ መነሻ ቅጣት ከተለየ በኋላ ድምሩ የሚወድቅባቸው እርከኖችም ሶስት ሁነው እያለ በመመሪያው መሰረት ዝቅተኛው እርከን መያዝ ሲገባው ያላግባብ የታለፈ መሆኑን ዘርዝረው 5ኛ ክስ ስር የተጠቀሰው ድንጋጌ እንዲቀየርና ቅጣቱም አመልካችን በሚጠቅመው የቅጣት አወሳሰን መመሪያና ድንጋጌዎቹ ተሰልቶ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ተገቢውን የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የሰጡትን የቅጣት ውሳኔ ተገቢነት ለመመርመር በመሠረታዊ ጭብነት መታየት ያለባቸው ሁነው ያገኘናቸው ነጥቦች፡-

1. የቅጣት ውሳኔው መሰላት ያለበት የወንጀል ክስ በቀረበበት ጊዜ ተፈፃሚነት በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ነው? ወይስ የጥፋተኛነት ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ ተፈፃሚነት በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ነው?፣
2. የሥር ፍርድ ቤት የእስራት ቅጣት መነሻ የሚወድቅበትን እርከን በተገቢው መንገድ ለይቶአል ወይስ አልለየም? እና
3. አመልካች ሊቀጡ የሚገባው የቅጣት መጠን ምን ያህል ሊሆን ይገባል? የሚሉ ናቸው፡፡

<u>የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ</u>፡- የበታች ፍርድ ቤቶች ቅጣቱን የወሰኑት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበት የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ወጥቶ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያቀረበውም ይህ መመሪያ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበት ወንጀል ክስ ሲቀርብ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም ለወንጀሉ ቅርበት ያለውና ተፈፃሚነት የነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነበር፡፡ በአመልካች ላይ የቅጣት ውሣኔ ሲወሰን ተፈፃሚ የነበረው የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ይህም በአመልካች ላይ የቅጣት ውሳኔ ሊወሰን የሚገባው አመልካች ወንጀሉን በፈጸመበትና ተገቢው ክስ በቀረበበት ጊዜ ተፈጻሚነት የነበረውን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት በማድረግ ነው? ወይስ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊወሰን ተፈጻሚነት ያለውን የተሻሻለውን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማድረግ ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ ይህንኑ የሕግ ጥያቄ በተመለከተ ይህ ችሎት በወንጀል ጉዳይ ገዥ መርህ ሆኖ ከተደነገገው ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 22 እና የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 6 ድንጋጌ አንጻር በመመርመር ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው ተከሳሹን የሚጠቅመው መመሪያ ነው በማለት በሰ/መ/ቁጥር 95438 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት አመልካች ወንጀሉን ሲፈጽም ወይም ክስ በቀረበበት ጊዜ ያልነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በአመልካች ላይ የቅጣት ውሳኔ ሊወሰን ተፈጻሚ የሚሆነው ይህ መመሪያ አመልካችን የሚጠቅመው ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከትአመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የወንጀል ድርጊት ሲፈጽም ያልነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አመልካች በወንጀሉ ድርጊት ሲከሰሱ ስራ ላይ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እርከን አቀናነስ ላይ ከመመሪያ ቁጥር 1/2002 በተሻለ ሁኔታ የአመልካችን መብት የሚያስከብር አይደለም፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቅጣት ውሳኔ ውሳኔውን የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማድረግ መወሰናቸው ከላይ የገለጽነውን የሕገ መንግስት ድንጋጌዎች ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95438 ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያትም በጉዳዩ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> የስር ፍርድ ቤት አመልካችን በአምስት ክሶች ጥፋተኛ ከአደረጋቸው በኃላ የወንጀሎቹን ደረጃ በመለየት ለእያንዳንዱ ክስ የሁለት አመት እስራት በመነሻነት ይዞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184(1(ለ)) መሰረት ደምሮ አስር አመትን በመነሻነት የያዘ ሲሆን ይህ የመነሻ ቅጣት የሚያፍርበት እርከን 29 መሆኑን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ ሆኖም አስር አመት መነሻ ቅጣት በመመሪያ ቁጥር 1/2002ም ሆነ በመመሪያ ቁጥር 2/2006 በሶስት ተከታታይ እርከኖች ያለ ሲሆን እንዲህ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ዝቅተኛ እርከንን እንደሚይዝ በመመሪ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 13(9)፣ በመመሪያ ቁጥር 2/2006 ደግሞ በአንቀጽ 19(11) ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ ሁለቱም መመሪያዎች በዚህ ረገድ ልዩነት የሌለባቸው በመሆኑ በአመልካች መብት አከባበር ላይ የሚያስከትሉት ችግር የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ጥፈተኛ የተባሉባቸው ድንጋጌዎች ድምር ቅጣት መነሻው የሚወድቅበትን እርከን ይህንኑ መሰረት አድርጎ መያዝ ሲገባው ከፍተኛ እርከን መያዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት የአምስቱ ክሶች ድምር የሆነው የአስር አመት ጽኑ እስራት የሚወድቅበት እርከን 27 ተደርጎ መያዝ ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

<u>ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- በቅጣት ማቅለያ አያያዝ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ስንመለከትም አመልካች ሪኮርድ የሌለባቸው መሆኑ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን የሚያሳዩትን ነጥቦች በሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት ይዞላቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ያልቀረበባቸው ሲሆን ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተይዞላቸው ድርጊቱ ከተፈፀመበትና ክሱ ከቀረበበት ጊዜያት አንፃር ሲታይ በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 16(7) ድንጋጌ መሰረት እያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሶስት ሶስት እርከን የሚያስቀንስ በመሆኑ በድምሩ ስድስት እርከን መቀነስ ስለአለበት ከእርከን 27 ወደ እርከን 21

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መውረድንና በዚህ እርከን ውስጥ ተገቢውን ቅጣት መወሰን የሚጠይቅ ነው፡፡ በእርከን 21 ስር የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ ከአምስት አመት እስከ ስድስት አመት ነው፡፡

ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሰረት ቅጣቱን ስናሰላው አመልካችን ያርማል፣ሌሎች መሰል አጥፊዎችን ከወዲሁ ሊያስጠነቅቅ ይችላል ብለን የገመትነው የቅጣት መጠን በእርከን 21 ስር በአምስት አመት ጽኑ እስራት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢ ቢሆንም የቅጣት ውሳኔው ግን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 104519 ጥር 01 እና መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ፣ ይህንኑ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 100951 ሰኔ 18 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195 (2)(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በአምስቱም ክሶች ጥፋተኛ መባላቸው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለእነዚህ ወንጀሎች ቅጣቱን በተመለከተ ግን አመልካች ሊቀጡ የሚገባው በ5 (አምስት) አመት ጽኑ እስራት ነው ብለናል፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች ገንዘብ መቀጮ ውሳኔ አልተነካም፡፡
4. በአመልካች ላይ የተሰጠው የእስራት ቅጣት ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን አውቆ አመልካች በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ማናቸውም ጊዜ ታስቦላቸው በዚህ ችሎት በተወሰነባቸው የቅጣት መጠን መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ትዕዛዝ ይድረስ ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98014

ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ያረጋል ተስፋ አባተ ጠበቃ አዳነ ታረቀኝ ቀረበ

ተጠሪ፡- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክ/ዐ/ቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁን አመልካች የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ.03468 በ04/05/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በ20/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ እኔ እና ሌሎች 5 ሰዎች በተከሰስኩበት በግብረ አበርነት ሰው በግፍ መግደል ወንጀል ተከስሼ ክሱ በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲታይ ቆይቶ ፍ/ቤቱ በመዝገብ ቁ.01597 በግንቦት 3 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከክሱ ነፃ የተሰናበትኩ መሆኔን እና ከአሶሳ ዞን ማረሚያ ቤት እንድለቀቅ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን፣ ከዚህ በኋላ የደረሰኝ መጥሪያ ሳይኖር እኔ ቀርቤ ሳልከረከር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሌሎች ተከሳሾች ቅጣት ሲጥል በእኔ ላይ የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት የወሰነብኝ መሆኑን በቅርብ ጊዜ ተነግሮኛል፡፡ ስለዚህ እኔ የህግ ታራሚ ስለሆንኩ የፍትህ መጓደል እንዳይደርስብኝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.191 /3/ መሰረት እኔ በሌለሁበት እና ከአቅሜ በላይ በሆነ ምክንያት ማለትም በነጻ ስለቀቅ ወደ ትውልድ ቦታዬ ጎጃም በመሄድ በእርሻ ተሰማርቼ 3 ሕፃናት ልጆቼን በማሳደግ ላይ የቆየሁ መሆኔንና በቲቪ ስለቃይ፣ በባህርዳር ፈለገ ሕይወት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆስፒታል ስታክም የቆየሁና በስንት መከራ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተርፌያለሁ፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ችግሬን ከግንዛቤ ውስጥ አስገብቶልኝ የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻዬን ተቀብሎ ይግባኝ ተከፍቶልኝ ህጋዊ መብቴ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩ እንዲሰማልኝ በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የነበረ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ከሰማ በኋላ በመዝገብ ቁ 03468 በ04/05/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ አመልካች የይግባኝ ጊዜ ያለፈባቸው በእውነት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ አመልካች የጠቀሰው ምክንያት ህመም ሲሆን በህክምና ወረቀት ካለመደገፉ በተጨማሪ ለአምስት አመታት ከነበረበት እና ጉዳዩ ከሚታይበት አከባቢ በመሰወር በመጨረሻም በፖሊስ ክትትል መያዙ የምክንያቱን በቂነትና ተቀባይነት ያሳጣዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ጊዜው ያለፈበት እና በበቂ ምክንያት ያልተደገፉ ነው ሲል የይግባኝ ማስፈቀጃውን ሳይቀበል መቅረቱ በህግ አግባብ እንጅ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም በማለት አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ይህን ትዕዛዝ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ፡-

1. እኔ አመልካች ከሌሎች ሰዎች ጋር ከተከሰስኩበት በሰው መግደል ወንጀል የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ወንጀሉን አለመፈጸሜን አረጋግጦ ግንቦት 3 ቀን 1999 ዓ.ም በነጻ ሲያሰናብተኝ፤ ይግባኝ ልጠራ ይችላል በሚል ሀሳብ ጉዳዩ በታየበት አከባቢ በመሆን የይግባኝ ውጤት እንድጠብቅ በሕግ የተጣለብኝ ግዴታ ሳይኖር፤ ወደ ሌላ አካባቢ በመሄዴም ከሕግ ተሰወረ ሊባል ስለማይችል፤ ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀርቦ ሲታይ አመልካች የማውቀው ነገር የሌለና የደረሰኝ መጥሪያ ሳይኖር፤ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የወሰነብኝ መሆኑን ያወቅኩት ፍርዱ ከተሰጠ ከ4 ዓመት በኋላ በፖሊስ ሲያዝ ነው፡፡ እኔ እንደተያዝኩ በ6 ቀን ውስጥ በ14/03/2004 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ "በሌለሁበት የተሰጠብኝ ፍርድ ውድቅ እንድደረግልኝ" በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.197 እና 198 መሰረት የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ስጠይቅ፤ አቤቱታው በሕግ የተደገፈ ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቱ እንደገና አላይም ማለቱ፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ስህተቱን አርሞ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ መፍቀድ ሲገባው አቤቱታውን ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጅስትራር የአመልካችን አቤቱታ አልቀበልም ያለው ፍርድ የተሰጠበትን ጊዜ በመቁጠር የይግባኝ ጊዜው አልፏል በሚል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ፍርድ የተሰጠው እኔ በሌለሁበት ስለሆነ ተፈጻሚ ሊሆን የሚገባው የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.191/1/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይሆን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.197 እና ተከታዮቹ የተመለከተው ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በሌለበት የተፈረደበት ሰው ፍርዱን ካወቀበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ፍርዱ ውድቅ እንዲደረግለት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ማመልከት እንደሚቻል፤ ማመልከቻው ተቀባይነት ባያገኝ ደግሞ ማመልከቻው ተቀባይነት ካጣበት ቀን አንስቶ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 197፣198 እና 202/3/ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ፍርዱን እንዳወቅኩኝ በ6 ቀን ውስጥ ሥርዓቱን ጠብቄ ማረሚያ ቤት ሆኜ ተደጋጋሚ አቤቱታ ባቀርብም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ፍርድ የተሰጠበትን ቀን በመቁጠር ሁሉንም አቤቱታዎች አልቀበልም በማለቱ በሕጋዊ መብቱ እንዳልጠቀም ከመከልከሉም በላይ የሬጅስትራር ክልከላ እንዲወገድልኝ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ባቀርብም የሬጅስትራሩን ድርጊት እንደህጋዊ ተግባር በመቁጠር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማስፈቀጃ አለመቀበሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ነው፡፡

3. አመልካች የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻ የማቀርብበት ሁኔታ አልተፈጠረም እንጅ ማቅረብ አለበት ቢባል እንኳ ማስፈቀጃው የሚቀርበውም የሚፈቀደውም ሆነ ተቀባይነት ሊያጣ የሚችለው ፍርዱን በፈረደው ፍ/ቤት ሬጅስትራር ውሳኔ ሳይሆን ፍርዱን በይግባኝ ወይም በሰበር የማየት ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ነው፡፡ ሬጅስትራሩ በማይመለከተው የዳኝነት ሥራ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የአመልካች አቤቱታ ለፍ/ቤት ችሎት ቀርቦ እንዳይታይ ያደረገው ሕጋዊ ተግባር ፈጽሟል ተብሎ አቤቱታው ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

4. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በ04/05/2004 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት ለይግባኝ ግልባጭ እንዲሰጠኝ በተደጋጋሚ ባመለክትም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሬጅስትራር በመከልከሉ ለሁለት ዓመት መብቴን እንዳልጠቀምና ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ሳላቀርብ ከፍ ያለ በደል ተፈጽሞብኝ መቆየቱ ሕገ መንግስቱ ለተከሰሱ ሰዎች በአንቀጽ 20/6/ የሰጠውን ይግባኝ የማቅረብ መብት የሚጥስ ነው፡፡ ስለዚህ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሻርልኝ፤ አመልካች የሰበር አቤቱታ ጊዜው ያለፈው በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ችግር ፈጣሪነት ምክንያት ነው ተብሎ አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ እንዲታይ እንዲፈቀድልኝ፤ እኔ በሌለሁበት ተገቢውን መከራከርያ ሳላቀርብ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወሰነብኝ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት እጅግ ከባድ ቅጣት በመሆኑ ጉዳዩ አመልካች ባለበት እንደገና ታይቶ እንዲወሰን በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ግልባጭ በማስቀረብ ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመመርመር "አመልካች በሌለበት የተፈረደበት ፍርድ እንዳወቀ ፍርዱ ተነስቶ ባለሀብት እንዲታይልኝ በማለት ያቀረበው አቤቱታ እና የይግባኝ ማስፈቀጃው ተቀባይነት ማጣቱ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? " የሚለውን ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ታዝዞ፤ ተጠሪ በዚህ ጉዳይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት መጥሪያ ደርሶት መልሱን ይዞ ባለመቀረቡ በጽሁፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ ጉዳዩም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማየት አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው እና ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካችን ጨምሮ አምስት ሰዎች በግብረ አበርነት በግፍ ሰው መግደል ወንጀል ተከሰው በአሶሳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲከራከሩ ቆይተው ፍ/ቤቱ በግንቦት 3 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ተከሳሾቹን በነጻ ስላሰናበታቸው በዚሁ ዕለት ተከሳሾቹ ከማረሚያ ቤት እንዲወጡ መደረጉን የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረቡ፤ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ሲያይ ቆይቶ በ17/11/1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ መሰረት አመልካች በሌለበት የዕድሜ ልክ እስራት እንደተፈረደበት መዝገቡ ያመለክታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አግባብነት ፖሊስ አመልካችን በ09/03/2004 ዓ.ም በቁጥጥር ስር በማዋል ማረሚያ ቤት እንዲገባ መደረጉ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በ14/03/2004 ዓ.ም ጽፎ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ እኔ ከተከሰስኩበት የወንጀል ክስ ፍ/ቤት በነፃ ካሰናበተኝ በኋላ ወደ አማራ ክልል በመሄድ ኑሮዬን የመሰረትኩ ሲሆን እኔ በሌለሁበት መጥሪያ ሳይደርሰኝ በፍ/ቤቱ የተፈረደብኝ የዕድሜ ልክ እስራት ፍርድ ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.199 መሰረት ማመልከቻዬን ተቀብሎኝ በቁ.202/1/ መሰረት ፍርዱ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ማመልከቱን፣ አመልካች እንደገና በድጋሚ በ02/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ እርሱ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ እንዲደረግለት መጠየቁን፣ ነገር ግን አመልካች አቤቱታው ጊዜው አልፎበታል ተብሎ ማረሚያ ቤት ስለተመለሰበት ድጋሚ በ02/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የይግባኝ መብቱ እንዲጠበቅለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ማመልከቱን፣ አመልካች አሁንም በ17/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የይግባኝ ጊዜው ያለፈው በእኔ ጥፋት ስላልሆነ ክርክሩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲታይለት የመዝገብ ግልባጭ እንዲሰጠው መጠየቁን ከስር ፍርድ ቤት ከመጣው መዝገብ ጋር ተያይዘው የሚገኙ ሰነዶች የሚያሳዩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ከላይ እንደተመለከተው በ20/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የደረሰበት ከፍተኛ ሰቆቃና ችግር ከግንዛቤ ውስጥ ገብቶ የይግባኝ ጊዜው ያለፈው በእርሱ ጥፋት እንዳልሆነ በመጥቀስ የይግባኝ ማስፈቀጃ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ ይሁን እንጂ የክልሉ ሰበር ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት የቀረበው የይግባኝ ማስፈቀጃ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ በማድረጉ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ምክንያት ሆኗል፡፡

በመሰረቱ አንድ የወንጀል የሚመራው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ነው፡፡ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት የቀረበውን ክርክር ደግሞ መምራትና በሕጉ አግባብ ዳኝነት መስጠት ያለበት በሕግ አግባብ የተቋቋመው ፍርድ ቤት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የክልሉ ዐቃቤ ሕግ የቀረበውን የወንጀል ይግባኝ ማመልከቻ ለአመልካችም ሆነ ለሌሎች መልስ ሰጭዎች እንዲደርሳቸው ማድረግ እንዳለበት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.187/4/ ሥር ተደንግጓል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ለአመልካች መጥሪያ እንዲደርሰው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በመጠቀም ተገቢውን ትጋት አድርጎ ነበር ወይ? የሚለው አሁን የሚታይ ስላልሆነ በዚህ ረገድ ምንም ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት የወንጀል ይግባኙን አይቶ በ17/11/99 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የፈረደበት መሆኑን ከቀረበው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በዚህ ፍርድ አማካይነት በ09/03/2004 ዓ.ም በፖሊስ ተይዞ በማረሚያ ቤት እንዲታሰር ከተደረገ በኋላ በ5 ቀናት ውስጥ በ14/03/2004 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.197 እና በተከታዮቹ ድንጋጌዎች ታይቶ እርሱ በሌለበት የተፈረደበት ፍርድ እንዲነሳለት የጠየቀ ስለሆነ፤ ይህ ጉዳይ በዚህ ድንጋጌ አግባብ የሚታይ ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሬጅስትራር የይግባኝ ጊዜው አልፎበታል በማለት አቤቱታውን አልቀበልም በማለት ጉዳዩ ለዳኞች ቀርቦ እንዳይታይለት የሚያደርግበት የህግ አግባብ የለውም፡፡ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.198 እንደሚደነግገው አንድ ሰው በሌለበት በወንጀል የተፈረደበት እንደሆነ ፍርዱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ፍርዱ ውድቅ እንዲደረግለት ማመልከት እንደሚችል እና በቁ.200 መሰረት የማመልከቻው ግልባጭ ለዐቃቤ ሕግ ደርሶ ለመስማት ቀጠሮ እንደሚያገዝ ነው እንጂ ሬጅስትራር ማመልከቻውን አልቀበልም በማለት እንቢ የሚልበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ ይህ ማመልከቻ ከተሰማ በኋላ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.201 መሰረት ፍ/ቤት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ጉዳይ ነው እንጂ ሬጅስትራር አልቀበልም በማለት ውሳኔ ሊሰጥበት በሕግ የተሰጠው ስልጣን የለም፡፡ አመልካች የአቀረበው ማመልከቻ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀርቦ በዳኞች ታይቶና ክርክሩ በሕግ አግባብ ተሰምቶ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በሌለበት የተፈረደበት ቅጣት ነጻነትን የሚያሳጣ ከባድ የእስራት ቅጣት ሆኖ ሳለ አቤቱታው ተቀባይነት ቢያገኝም ቢያጣም ለፍ/ቤት ቀርቦ በዳኞች ውሳኔ ሊሰጥበት ሲገባው ሬጅስትራሩ ይህን መብት መገደቡ የህግ መሰረት የለውም፡፡ ይህ ድርጊት ደግሞ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 መረዳት እንደሚቻለው "የተከሰሱ ሰዎች ክርክራቸው በፍ/ቤት ታይቶ ተሰምቶ ፍርድ ሊያገኙ ይገባል" የሚለውን ሕገ መንግስታዊ መብቱን የሚሸራርፍ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ በእንዲህ እንዳለ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ያቀረባቸው አቤቱታዎች የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የቀረበውን የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻ በማየት ከላይ የተጠቀሱትን አመልካቹ ላይ የደረሰውን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት በሬጅስትራሩ ምክንያት የተፈጠረውን የአካሄድ ችግሮችን በማረም፣ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሬጅስትራር አመልካች በሌለሁበት የተፈረደብኝ ፍርድ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት የቀረበው ማመልከቻ ለዳኞች ቀርቦ እንዲታይለት እንዲያደርግ ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው የሬጅስትራሩን ድርጊት ሕጋዊ እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ አድርጎ መተው ከላይ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎችን የሚጻረር በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

ከዚህም በላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ይግባኝ ማስፈቀጃ የጠየቀው እርሱ በሌለበት የተሰጠበት ፍርድ ላይ መሆኑ እየታወቀ፣ አመልካች በዚህ ላይ ምን ዓይነት የይግባኝ ጥያቄ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሊያቀርብ እንደሚችል ሳይጣራ፣ እንዴትስ ከዚህ ዓይነት ፍርድ ይግባኝ ማለት እንደሚቻል ሳይመረመር፣ በሌለበት ፍርድ የተሰጠበት ሰው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.197 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብነት መብቱን መጠየቅ እንደሚችል መገንዘብ ሲገባው፣ የሬጅስትራሩን ከሕግ ውጭ የሆነ ድርጊት ሕጋዊ ሽፋን በመስጠት የሰጠው ትዕዛዝ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈጠረውን የአካሄድ ችግር ተገቢውን ማስተካከያ ሳያደርግ ከመቅረቱም በላይ አመልካቹ የጠቀሰው " ምክንያት ህመም ሲሆን በህክምና የምስክር ወረቀት ካለመደገፉ በተጨማሪ ከአምስት ዓመታት በላይ ከነበረበት እና ጉዳዩ ከሚታይበት አካባቢ በመሰወር በመጨረሻም በፖሊስ ክትትል መያዙ የምክንያቱን በቂና ተቀባይነት ያሳጣዋል" በማለት የደረሰበት ድምዳሜ፣ አመልካቹ አቤቱታው በፍ/ቤት/በዳኞች/ ታይቶ ተሰምቶ ተገቢ ማጣሪያ ተደርጎ ፍርድ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብቱን የሚያጣብብ በመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ስለዚህ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሬጅስትራር የፈጠረውን የአካሄድ ችግር ማስተካከል ሲገባው አመልካች በሌለሁበት የተፈረደብኝ ፍርድ ውድቅ እንዲሆንልኝ በማለት ያመለከተው አቤቱታ በፍ/ቤት ታይቶ ተሰምቶ ውሳኔ ሳይሰጥበት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ሁኖ ስለአገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ.03468 ላይ በ04/05/2004 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በ14/03/2004 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ መሰረት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.197 እና ተከታይ ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌለበት የተፈረደበት ፍርድ ውድቅ ሊሆን ይገባል? ወይስ አይገባም? በሚለው ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች፣ አመልካች በታሰረበት ማረሚያ ቤት በኩል ለአመልካች ይድረስ ብለናል፡፡
4. ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቀረበው የመዝገብ ቁ.03488 እና የአቤቱታዎች ግልባጭ በመጣበት አካኋን ይመለስ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. መዝገቡ ውሳኔ ስለአገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 107219

ሐምሌ 1 ቀን 2007ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መ·ስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-አቶ አህመድ ሰይድ መሐመድ ጠበቃ መሳይ ተድላ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ በተጀመረበት ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ከነበሩት ሌሎች ሁለት ግለሰቦች ጋር በመሆን ከባድ የስርቆት ወንጀል መዋል በማለት ተጠሪ ያቀረበባቸውን የወንጀል ክስ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠባቸው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡-አመልካች ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ከመስከረም ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት ወር 2005 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በተለያዩ ቀናት ሰዓቱ ተለይቶ ባልታወቀበት የምሽት የጊዜ ክፍል በን/ላ/ክ/ከተማ በቀበሌ 13 ክልል ልዩ ቦታው የኔታ አካዳሚ በሚባል አካባቢ የግል ተበዳይ መሐመድ አብደላ በሆነ መጋዘን ተቀጥረው ይሰሩ በነበረበት ጊዜ ስማቸው በክሱ የተዘረዘረውን እና በካርቶኖች ታሽገው ተቀምጠው የነበሩትን አጠቃላይ የዋጋ ግምታቸው ብር 373,080 (ሶስት መቶ ሰባ ሶስት ሺህ ሰማንያ) የሆነ የተለያዩ ቢንቧ ዕቃዎችን ከመጋዘን እያወጡ 2ኛ ተከሳሽ ለሆነው ግለሰብ የሰጡ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 669 (2) (መ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ከባድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስርቆት ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቀው በክሱ የተመለከተውን ወንጀል አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ በሶስቱም ተከሳሾች ላይ የግል ተበዳይን ጨምሮ ተጠሪ ያቀረባቸውን አራት ምስክሮች ምስክርነት ከሰማ እና አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 27 መሰረት ለምርመራ ክፍል የሰጡትን ቃል ጨምሮ ተጠሪው ያቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ አመልካች በተከሰሱበት ድንጋጌ ስር መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካች ለምርመራ ክፍል ቃላቸውን የሰጡት በደረሰባቸው ድብደባ ምክንያት ተገደው መሆኑን ያውቁልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ወንጀሉን ያልፈጸምኩ መሆኑን ያስረዳልኛል በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 35 መሰረት ለፍርድ ቤት የሰጡትን ቃል እና የየኔታ አካዳሚ የጥበቃ ሰራተኛ እንጂ የግል ተበዳይ ሰራተኛ አለመሆኔን ያስረዳልኛል በማለት ይህንኑ የሚያስረዳ ማስረጃ በመከላከያነት አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ቀሪዎቹ ሁለት ተከሳሾችም እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ከሰጠ እና መከላከያቸውን ከሰማ በኃላ በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካቹ ባሰሟቸው የመከላከያ ምስክሮች እና ባቀረቡት የሰነድ መከላከያ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከረተባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት ደንጋጌውን ግን ለውጦ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 (3) (ለ) ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ የቅጣት አወሳሰኑ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት እንዲመራ በአመልካቹ ጠበቃ የቀረበውን ጥያቄ ባለመቀበል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ውሳኔው በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ በሚገኘው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ተቀብሎ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም እስከ አስራ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት መሆኑን፣ወንጀሉ በመመሪያ ቁጥር 2/2006 ደረጃ የወጣለት መሆኑን፣በወንጀሉ የተወሰደው ንብረት ግምት ከብር 100,000 በላይ በመሆኑ እና አንድ ማክበጃ የተገኘ በመሆኑ የሚወድቀው በደረጃ 7 በእርከን 26 ስር መሆኑን፣በእርከን 26 ስር ከተመለከተው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ተደርጎ የተያዘው የስምንት ዓመት ጽኑ እስራት መሆኑን፣የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ያልተገኘ ሲሆን ተቀባይነት ባገኙት ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች የፍቅድ ስልጣኑ እርከን ከ26 ወደ 23 ዝቅ የሚል መሆኑን በዝርዝር ገልጾ በዚሁ እርከን ስር አመልካቹ በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 669 (2) (መ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ እንዲጠብቅ በኃላፊነት የተሰጠውን ንብረት ሰርቋል ተብሎ ክስ ተመስርቶበት አመልካች የግል ተበዳይ ተቀጣሪ አይደለሁም፣ወንጀሉንም አላደረግሁም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክዶ በመከራከሩ የግል ተበዳይ ተቀጣሪ አለመሆኑን፣ብቸኛውን የተጠሪ ማስረጃ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 27 መሰረት የተሰጠ ቃል እና የደረጃ ምስክሮችን የምስክርነት ቃል ለመከላከል አመልካቹ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 35 መሰረት የሰጠውን ቃል እና የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቶ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች በክሱ የተመለከተውን ድንጋጌ ወደ አንቀጽ 669 (3) (ለ) በመቀየር የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የመስጠታቸውን አግባብነት ከማስረጃ ምዘና መርህ እና ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 113 (2) ድንጋጌ አፈጻጸም አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

3. በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
4. የቅጣት ውሳኔው በሕጉ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ወንጀሉን አላደረግሁም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም በክሱ የተዘረዘሩት የዋጋ ግምታቸው ብር 373,080 የሆነ የተለያዩ የቧንቧ ዕቃዎች ከግል ተበዳዩ የተሰረቁ መሆኑ እና የተሰረቁትም ከሚቀመጡበት መጋዘን ውስጥ ለጊዜው ባልታወቀ ሁኔታ እየተወሰዱ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡የዚህ ዓይነት የስርቆት ወንጀል የተፈጸመባቸው ስለመሆኑም የግል ተበዳይ ለአካባቢው ፖሊስ በወቅቱ ሪፖርት ያደረጉ መሆኑም ተረጋግጧል፡፡ የወንጀሉ ፈጻሚዎች ማንነት ለጊዜው ሳይታወቅ የቆየ ቢሆንም የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በተመሳሳይ ሌላ ወንጀል ተጠርጥረው የግል ተበዳይ የወንጀል አቤቱታ ባላቀረቡለት በአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ በኩል በቁጥጥር ስር በነበሩበት ጊዜ የግል ተበዳይን የቧንቧ ዕቃዎችም ከአሁኑ አመልካች ጋር በመተባበር መስረቃቸውን በመግለጻቸው ምክንያት አመልካቹ ጭምር ተይዘው ተጠያቂ መደረጋቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካቹ የግል ተበዳዩ ሰራተኛ ባይሆኑም መጋዘኑ በሚገኝበት ግቢ ከግል ተበዳይ ቤት ተከራይቶ ስራውን ለሚያከናውነው የትምህርት ተቋም በጥበቃ ስራ ሲያገለግሉ የነበሩ መሆናቸውን አልካዱም፡፡ከስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር የስርቆት ወንጀሉን የፈጸሙ ስለመሆኑም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 27 መሰረት ለምርመራ ክፍል በሰጡት የእምነት ቃል አረጋግጠዋል፡፡ይህንን የእምነት ቃል የሰጡት በፈቃዳቸው መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካቹ በሌላ ጊዜ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 35 መሰረት ለፍርድ ቤት ባስመዘገቡት ቃል የፈጸሙት ወንጀል አለመኖሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መግለጻቸው ብቻውን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ እንደገለጸው ቀደም ሲል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 27 መሰረት ለምርመራ ክፍል የሰጡትን የእምነት ቃል ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡ አመልካች ለምርመራ ክፍሉ የእምነት ቃል የሰጠሁት ተገድጄ ነው በማለት ያስያዙትን የመከላከያ ጭብጥ በምስክሮቻቸው ማስረዳት አለመቻላቸውን ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው ሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ሁኔታ በውሳኔያቸው ላይ ገልጸዋል፡፡አመልካች ከሌሎች ተባባሪዎቻቸው ጋር የስርቆት ወንጀሉን ያደረጉት በሌሊት እና ዕቃዎቹ የሚቀመጡበትን መጋዘን ባልታወቀ ሁኔታ ከፍቶ በመግባት በመሆኑ እና እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ራሳቸውን ችለው በስርቆት ወንጀል ማክበጃነት አመልካቹ ጥፋተኛ በተባሉበት አንቀጽ 669 (3) (ለ) ስር የተካተቱ በመሆኑ፣እንዲሁም አመልካቹ የተከሰሱበት እና ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌዎች የሚደነግጉት የቅጣት መጠን ተመሳሳይ በመሆኑ አመልካቹ ጥፋተኛ የተባሉት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 (3) (ለ) ስር መሆኑም በአግባቡ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን ማስረጃ መዝኖ በመከላከያነት የቀረበውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ውድቅ በማድረግ በአመልካቹ ላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ደረጃ ከወጣላቸው ወንጀሎች ውስጥ የሚካተት ሲሆን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቅጣቱን የወሰነው በተጠሪው በኩል የቀረበ የማክበጃ ምክንያት አለመኖሩን እና በአመልካቹ በኩል ተቀባይነት ያገኙ ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች መገኘታቸውን ገልጾ ቅጣቱን የጥፋተኝነት ውሳኔው በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ ባለው አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማስላት ነው፡፡ ግን አመልካቹ ወንጀሉን አድርገዋል የተባሉት ከመስከረም 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት ወር 2005 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካች ወንጀሉን ባደረጉበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በቅጣት አወሳሰኑ ረገድ ከተሻሻለው መመሪያ በተለየ ሁኔታ የሚያስከትለው ለውጥ መኖር አለመኖሩ እና ካለም ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው የትኛው መመሪያ እንደሆነ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡በመሰረቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎቹን ያወጣው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 88(4) ድንጋጌ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በመሆኑ ምክንያት መመሪያዎቹ እንደ ሕግ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበትን ወንጀል ያደረጉት መመሪያ ቁጥር 1/2002 ስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሲሆን ይህ መመሪያ ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ተተክቷል፡፡ በሌላ በኩል አዲሱ የወንጀል ሕግ እንዲጸና ከተደረገ በኃላ አድራጊው ሕጉ ከመጽናቱ በፊት ላደረገው ወንጀል ሲፈረድበት ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ በስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ ከነበረው ሕግ ይልቅ አዲሱ ሕግ ቅጣትን የሚያቃልለት በሆነ ጊዜ ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተመለከተው ቅጣት ስለመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 ተደንግጐ ይገኛል፡፡

ለአመልካቹ ቅጣቱን የሚያቃልለው የትኛው መመሪያ ነው? የሚለውን ነጥብ በተመለከተ በቀላል እና በጽኑ እስራት ለሚያስቀጡ ወንጀሎች ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን ወደታች የሚቀንሰው አንድ እርከን ብቻ ስለመሆኑ በተሻሻለው መመሪያ አንቀጽ 23 (4) ስር የተመለከተ ሲሆን በአንጻሩ መነሻ ቅጣታቸው ሰባት ዓመት ጽኑ እስራት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ወንጀሎች ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን የቅጣቱ ፍቅድ ስልጣን ዝቅ የሚደረገው በሶስት እርከን ስለመሆኑ በቀድሞው መመሪያ በአንቀጽ 16 (7) ስር ተመልክቷል፡፡ይህ ብቻ ሳይሆን አመልካቹ ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል በአዲሱ መመሪያ የሚወድቀው በደረጃ 7 በእርከን 26 ስር ሲሆን በቀድሞው መመሪያ ግን በደረጃ 7 በእርከን 21 ስር በመሆኑ ወንጀሉ ከሚወድቅበት እርከን አንጻርም ያነሰ ቅጣት የሚደነግገው የቀድሞው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ነው፡፡ወንጀሉ የተፈጸመው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሆኖ የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠው ግን የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በስራ ላይ ከዋለ በኃላ በሆነ ጊዜ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ለተከሳሽ ወገን የተሻለ ጥቅም የሚሰጠው መመሪያ ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 95440 እና በሌሎችም መዝገቦች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠ መሆኑም የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም ለአመልካቹ ቅጣቱን የሚያቃልለው የቀድሞው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ ቅጣቱን በአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት አስልቶ መወሰኑ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው በአመልካቹ ላይ የቀረበ የማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኙት ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች ለደረጃ 7 በተቀመጠው እርከን 21 ላይ የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን በዘጠኝ እርከን ዝቅ ሲደረግ የሚወድቀው በእርከን 12 ስር ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካቹ ላይ ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው ቅጣት በአባሪ አንድ በእርከን 12 ፍቅድ ስልጣን ስር የተመለከተው የቅጣት መጠን መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች በተከሰሱበት የከባድ ስርቆት የወንጀል ክስ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ እና በቅጣት ውሳኔው ላይ ግን ከላይ በተገለጸው ምክንያት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111142 በ09/08/2006 ዓ.ም. እና በ12/09/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 152298 በ11/02/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በአመልካቹ ላይ ተጥሎ የነበረውን የስድስት ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካቹ በዚህ ጉዳይ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሆኖ በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
4. ይህንኑ ተገንዝቦ በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም አመልካቹ ለሚገኙበት የአዲስ አበባ ማረሚያ ተቋም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክ፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና በማረሚያ ቤት በኩል ለአመልካቹ ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ።።

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 111006

ቀን 14/11/2007

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲ.ር.ጋ.ጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ዲቦ ገልገሎ ቱራ ጠበቃ ትዕግስት ጫንያለው

ተጠሪ፡- የፌ/ን/ስ/ላ/ዐቃቤ ሕግ ተወካይ ሕይወት አዳና

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ 2/2006 ደረጃና እርከን ላልወጣላቸው ወንጀሎች የሚደረገውን ስሌት እና የቅጣት ማቅለያ ምክንያትን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው "ተከሳሽ የወ/ሕ/ቁ.676(2) (ሀ) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ወይም ለሌላ ሠው ለማስገኘት በማሰብ በስራ አስኪጅነት ተቀጥሮ ሲሰራ ከነበረበት ፍቅር ለሕፃናት በጎ አድርጎት ድርጅት ለስራ የተሰጠውን 1ኛ ቶሺባ ላፕቶፕ 2ኛ አሴር ላፕቶፕ 3ኛ. ለሲዲ መግዣ የተሰጠውን ብር 3000 አጠቃላይ ግምቱ ብር 24,000 (ሀያ አራት ሺህ ብር) የሚገመት ንብረት በስራው ሃላፊነት ምክንያት እጁ የገባ ንብረት ይዞ በመሰወሩ በፈፀመው ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ነው፡፡"

ተከሳሹ (የአሁኑ አመልካች) ላፕቶፖቹን እህቱ ላይ በደረሰ የመኪና አደጋ ምክንያት ገንዘብ ቸግሮት የወሰደ መሆኑን ብቻ ያመነ ሲሆን የፍ/ቤቱ እንደ ክሱ ሙሉ በሙሉ አላመነም በማለት መዝግቦ የዓ/ሕግ ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተከሳሽ በተከሰሰበት አንቀጽ እንዲከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለቱ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ ክስ በተመሠረተበትና የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት የወ/ሕ/አ 676(2) (ሀ) ስር የፅኑ እስራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አማራጭ በመውሰድ የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ከግምት በማስገባት ተከሳሽ በ3 ዓመት ከ3 ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙ ካከራከረ በኃላ የስር ፍ/ቤት ደረጃውን መካከለኛ ማለቱንና ተከሳሽ በፈፀመው አድራጎት የተመለከተውን የገንዘብ መጠን አንፃር የፅኑ እስራት አማራጭ መውሰድ ተገቢ አለመሆኑን በማተት የቀላል እስራት አማራጭን ወስዶ ደረጃውን ዝቅተኛ ብሏል፡፡ ተከሳሽ ወንጀሉን ያመነ እና በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝለት የሚገባ ቢሆንም በወ/ሕ/አ. 663(2) እና 82(1) (ሠ) መሠረት ተከሳሽ የወሰደው ንብረት ስለተመለሠ ብሎ የስር ፍ/ቤት ቅጣት ማቅለያ የተቀበለ በመሆኑ በአንድ የቅጣት ማቅለያ አንቀጽ 82(1) ሠ ተጨማሪ ቅጣት ማቅለያ ሊወሰድ አይገባም በማለት መነሻ ቅጣት 3 ዓመት ከ6 ወር እስራት ወስዶ የተከሳሽን የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ከግምት በማስገባት ተከሳሽ በ2 ዓመት ከ7 ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን፤የሰበር አቤቱታው ይዘትም “ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የእስራት ቅጣት አማራጭን ከያዘ በኃላ ቅጣቱን ሲያሰላ በልዩ ሕጉ የተደነገገውን የ1 ዓመት እስራት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106 የተመለከተውን የእስራት ቅጣት መድረሻ ጣራ ያለአግባብ በማለፍ 15 ዓመት መያዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ሌላው በስር ፍ/ቤት ወንጀሉን ማመኔን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቱ ተቀብሎ በወ/ህ/ቁ. 82(1) ሠ ስር በድጋሚ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝ አይገባውም ማለቱ ሊታረም ይገባዋል በሚል ነው፡፡”

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በወ/ሕ/አ. 676(2)(ሀ) የቀላል እስራት አማራጭን ከወሰደ በወ/ህ/ቁ 106 ቀላል እስራት ከ10 ቀን እስከ 3 ዓመት ነው ተብሎ ተደንግጎ እያለ የመድረሻ ቅጣቱን 3 ዓመት በመያዙ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያት ከግምት በማስገባት ቅጣቱን ማስላት ሲገባው መነሻ ቅጣት 3 ዓመት ከስድስት ወር ማለቱ ከወ/ህ/ቁ. 106(1)፣ ከተከሰሰበት አንቀጽ እንዲሁም ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንፃር የቅጣት አወሳሰኑን አግባብነት ግራ ቀኙ ባሉበት ለማየት ሲባል የቀረበ የሰበር ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪም ከስር ዓ/ሕ ቀርቦ ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ የስር ፍ/ቤት የቀላል እስራት አማራጭ ወስዶ አመልካችን ሲቀጣው በወ/ሕጉ አንቀጽ 106(1) መሠረት መሆን እንዳለበት እናምናለን፡፡ የወ/ሕጉ አንቀጽ 106(1) ቀላል እስራት መነሻ 10 ቀናት መድረሻው 3 ዓመት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የተነሳው ይታረምልኝ ጥያቄ ላይ ተቃውሞ የለንም፡፡

የስር ፍ/ቤት የወ/ሕጉ አንቀጽ 663(2) እና 82(1) (ሠ)ን በመጥቀስ አመልካች ድርጊቱን ማመኑን እንደአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሊያዝለት አይገባም ማለቱ ተገቢ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ተከሳሽ እንደመነሻ አድርገው ቢወሰድም የወ/ሕጉ አንቀጽ 663(2) እና 82(1) (ሠ) ተጣምረው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲታዩ አመልካች በስር ፍ/ቤት በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት ሙሉ በሙሉ ማመን እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ ተከሳሽ ሙሉ በሙሉ ባለማመኑ ዐ/ሕግ ማስረጃ አሰምቶ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ባለመከላከሉ ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ አመልካች በወ/ሕጉ አንቀጽ 82(1) (ሠ) ስር ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም፡፡ በወ/ሕጉ አንቀጽ 663 (2) መሠረት የወሰደውን ዕቃ ሙሉ በሙሉ ያልመለሰና የተከሰሰበትን ወንጀል ሙሉ በሙሉ ያላመነ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ቅጣት ሲጣል ከግምት ሊያስገባው የሚችል በመሆኑና ፍ/ቤቱ ሲያምንበት ብቻ እንደሆነ መረዳት የሚቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት በፅሑፍ መልሱን አቅርቧል፡፡ እኛም የአመልካችን አቤቱታ አግባብነት ካለው የወ/ሕጉ ድንጋጌ እና ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 እንዲሁም ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጋር ከዚህ በላይ ሰበር ችሎቱ ከያዘው ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም፤

የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ተቀብሎ የአመልካችን የወንጀል አፈጻጸምን መሠረት በማድረግ በአመልካች ላይ ሊወሰን የሚገባው በቀላል እስራት ቅጣት ነው ብሎ ካመነበት አመልካቹ ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕግ አንቀጽ 676(2) (ሀ) ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ወይም ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ የተመለከተ በመሆኑ፣ቀላል እስራትን አስመልክቶ በወ/ሕጉ አንቀጽ 106(1) ከ10 ቀን እስከ 3 ዓመት እንደሆነ የተመለከተ ስለሆነ እና የወ/ህጉ አንቀጽ 676(2)(ሀ) ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 19(6) መሠረት ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት ያለውን እስራት ለአራት እኩል በመክፈል የቅጣት እርከኑን በመለየት መነሻ ቅጣት መወሰን ሲገባው የስር ፍ/ቤት (ፌ/ከፍ/ፍ/ቤት) መነሻ ቅጣቱን ስለቀላል እስራት በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጽ 106(1) ከተመለከተው 3 ዓመት ጣሪያ አልፎ መነሻ ቅጣቱ 3 ዓመት ከ6 ወር መያዙ የወንጀል ሕጉን እና የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሠረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የተከሳሽ (አመልካች) ወንጀል አፈፃፀም እና በእምነት ማጉደል ከወሰዳቸው ንብረቶች የመለሰው ንብረት መኖሩን ከግምት በማስገባት አመልካች ጥፋተኛ በተባለበት የወ/ሕግ አንቀጽ 676(2) (ሀ) የቀላል እስራት አማራጭ መወሰዱ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት ሲሆን ከወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጽ 106(1) ጋር በማገናዘብ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 19(6) መሠረት እርከን አንድ ከ1 ዓመት እስከ 1 ዓመት ከ6 ወር ይሆናል የወንጀሉን አፈፃፀምና ክብደት መሠረት በማድረግ ቀላል ወንጀል ደረጃ የተሰጠው በመሆኑ በዚህ እርከን አንድ ውስጥ መነሻ ቅጣቱ 1 ዓመት ከ4 ወር እንዲሆን ወስነናል መነሻ ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው የቅጣት ሠንጠረዥ እርከን 7 ከ1 ዓመት እስከ 1 ዓመት ከ6 ወር በሚለው ስር ይወድቃል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዐ/ሕግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ባለመኖሩ ቅጣቱ የሚከብድ አይሆንም በሌላ በኩል አመልካች ለሰበር ችሎት እንደ አንድ ቅሬታ ምክንያት በማድረግ ወንጀሉን መፈፀሜን ማመኔ በወ/ሕጉ አንቀጽ 82(1) ሠ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝልኝ ሲገባ በሥር ፍ/ቤቶች ታልፎብኛል በማለት የተከራከረ ቢሆንም፤ አመልካች በስር ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የወ/ሕጉን አንቀጽ 676(2) (ሀ) በመተላለፍ ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅሟል በሚል በክሱ ዘርዝሮ ከተመለከተው ብር 3000 (ሦስት ሺህ ብር) መውሰዱን ሳያምን ላብቶፖቹን ብቻ ወስጃለው በማለት ያመነ በመሆኑ የእምነት ቃሉ ከወንጀሉ ዝርዝር ጋር ሲታይ ወንጀሉን ስለመፈፀሙ ሙሉ በሙሉ ያመነ ባለመሆኑ በከፊል ማመኑ በቅጣት ፈቅደ ስልጣን ከግምት ሊገባ ከሚችል በቀር ራሱን ችሎ አንድ ቅጣት ማቅለያ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች ይህንን በወ/ህ/አንቀጽ 82(1)(ሠ) እንደ አንድ ቅጣት ማቅለያ ምክንያት አለመውሰዳቸው በአግባቡ ስለሆነ በዚህ ላይ አመልካች ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

በስር ፍ/ቤቱ ተከሳሻ (አመልካች) የዘወትር አመሉ መልካም እንደነበረ ግምት በመውሰድ በወ/ሕጉ አንቀጽ 82(1) (ሀ) እና ንብረቶቹ በመመለሳቸው በወ/ህ/አ 663(2) እና 82(1) (ሠ) መሠረት የተያዘለትን ሁለት ቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመውሰድ መነሻ ቅጣት ካረፈበት እርከን 7 በሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ወደ እርከን 5 ዝቅ ይላል በዚህ እርከን 5 የተመለከተው የቅጣት ፈቅድ ስልጣን ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት እስራት ሲሆን ተከሳሹን ያርማል ለሌላው ማስተማሪያ ይሆናል ብለን ባመንበት በ1 ዓመት እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 88912 በቀን 3/03/07 ዓ.ም በዋለ ችሎት፤የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 145151 በቀን 3/07/07 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጡት የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ቁ. 195(2) (ሰ) (2) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
- ተከሳሽ (አመልካች) በዚህ ወንጀል ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ በአንድ ዓመት እስራት እንዲቀጣ የስር ፍ/ቤቶች የቅጣት ውሳኔን በማሻሻል ወስነናል፡፡ እንደ ተሻለው የቅጣት ውሳኔ ይፈፀም ዘንድ ተከሳሹ ታስሮ ለሚገኝበት መ/ቤት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 111742

ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካቾች፡- 1. ኮሎኔል ተክሉ ፍስሐ
2.ኮሎኔል ፀሐይ ዋሉ } ስለሁለቱም ጠበቃ ረጋሳ ሽጋ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክሱ በቀረበበት የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኖቹ አመልካቾች እንደቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የነበሩ ናቸው፡፡ ተጠሪ በ29/01/2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ ያቀረበባቸው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ተከሳሾቹ በክልሉ የደን አዋጅ ቁጥር 72/1995 በአንቀጽ 13 (1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በ27/01/2007 ዓ.ም ከጠዋቱ 1፡30 ሰዓት ላይ 1ኛ ተከሳሽ የዋጋ ግምቱ ብር 5,400 የሆነ 60 ማዳበሪያ ከሰል፣ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ የዋጋ ግምቱ ብር 4,590 የሆነ 51 ማዳበሪያ ከሰል በሚያሽከረክሯቸው ሁለት ተሽከርካሪዎች ጭነው በቢሾፍቱ ከተማ ውስጥ በመያዛቸው የደን ውጤቶችን ያለፈቃድ የማዘዋወር ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን ተከሳሾቹ ተጠይቀው በክሱ ላይ መቃወሚያ እንደሌላቸው ከገለጹ በኃላ ድርጊቱን መፈጸማቸውን፣ ከሰሉን የጫኑት ለቤተሰቦቻቸው እንጂ ለንግድ አለመሆኑን፣ድርጊቱን መፈጸማቸው በርግጥ ጥፋት መሆኑን አምነው በማስመዝገባቸው ዓቃቤ ህግ በጠየቀው መሰረት ፍርድ ቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 134 (1) መሰረት በተከሰሱበት ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ እያንዳንዳቸው በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ተከሳሾቹ ያቀረቡትን ይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከተው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ የቀረበውን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ የቅጣቱን መጠን ብቻ አሻሽሎ እያንዳንዳቸው በሶስት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች የቀረበላቸውን እንደቅደም ተከተሉ ይግባኝ እና አቤቱታ ዘግተው በማሰናበታቸው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካቾቹ እንደክሱ በዝርዝር ወንጀሉን የፈጸሙ ስለመሆናቸው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሳይክዱ አምነዋል ተብለው በዚህ መነሻነት በስር ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰጠቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሠረት አንድ ተከሳሽ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ ሙሉ በሙሉ ያመነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል ሲል በመዝገብ ከጻፈ በኃላ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚሰጥ ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁጥር 134(1) ስር የተመለከተ ሲሆን በዚህ አግባብ በእምነት ቃሉ መሰረት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠበት ተከሳሽ ስለቅጣቱ ልክ ወይም ስለቅጣቱ ህጋዊነት ካልሆነ በቀር በጥፋተኝነት ውሳኔው ላይ ይግባኝ ማለት የማይችል ስለመሆኑም በስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 185(1) ስር ተመልክቶአል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የወረዳው ፍርድ ቤት በአመለካቾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠው የተከሰሱበትን ወንጀል ሙሉ በሙሉ አምነዋል በማለት ሲሆን ይግባኙን የተመለከተው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾቹ በጥፋተኝነት ውሳኔው ላይ ያቀረቡትን ቅሬታ ሳይቀበል የቅጣት ውሳኔውን ብቻ በማሻሻል ውሳኔ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠው በአመልካቾች የእምነት ቃል መሠረት በመሆኑ በጥፋተኝነት ውሳኔው ላይ ይግባኝ ሊያቀርቡ የሚችሉበት የህግ አግባብ አለመኖሩን በምክንያትነት በመጥቀስ ነው፡፡

በመሠረቱ ከላይ በተጠቀሰው የወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 134 (1) መሰረት በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው ተከሳሹ ያስመዘገበው የእምነት ቃል በክስ ማመልከቻው በተገለፀው የወንጀል ዝርዝር መሰረት ወንጀሉን ማድረጉን ሙሉ በሙሉ ያመነ መሆኑን የሚያረጋግጥ በሆነ ጊዜ ነው፡፡ ተከሳሹ እንደ ሕጉ አነጋገር ወንጀሉን መፈፀሙን ሙሉ በሙሉ ያመነ መሆኑን ለማረጋገጥ ያስችል ዘንድ የሚያስመዘግበው የእምነት ቃል መነሻበር የሚገባው ከወንጀሉ ዝርዝር ጋር ብቻ ሳይሆን በክሱ ተላልፎታል ከተባለው የሕግ ድንጋጌ አነጋገር ጭምር ነው፡፡ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል እያንዳንዱ ክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀሉን እና ሁኔታውን በዝርዝር መግለፅ ያለበት ስለመሆኑ፣ እንዲሁም ስለ ወንጀሉ እና ስለ ሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ የፈፀመውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ በስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 112 የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነው።

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾቹ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ካቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩት ለወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠነው ቃል በአግባቡ እና በዝርዝር አልተመዘገበም• የመከላከያ ማስረጃ አቅርበን ክሱን እንድንከላከልም ዕድል አልተሰጠንም በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመላክታል። ተከሳሾቹ ወንጀሉን መፈፀማቸውን አምነዋል በሚል መዝግቦ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከመስጠቱ በቀር ተከሳሾቹ ተላልፈዋል ተብለው የተከሰሱት የትኛውን ሕግ እና ድንጋጌ እንደሆነ እንኳ የወረዳው ፍርድ ቤት በጥፋተኝነት ውሣኔውም ሆነ በቅጣት ውሣኔው ላይ አላሰፈረም። ተላልፈውታል የተባለው ሕግ እና ድንጋጌ የተጠቀሰው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ላይ ነው። ተከሳሾቹ አስመዝግበውታል የተባለው የእምነት ቃል ከተከሰሱበት ድንጋጌ ጋር ተነፃፅሮ በስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 134(1) ድንጋጌ መሰረት የእምነት ቃልን የሚያቋቁም መሆን አለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተከሳሾቹ ወንጀሉን መፈፀማቸውን ሙሉ በሙሉ አምነዋል በማለት የጥፋተኝነት ውሣኔ መስጠቱ ደግሞ የቁጥር 134 (1)ድንጋጌ ዓላማ እና መንፈስ መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም።

ሲጠቃለል አመልካቾች ያስመዘገቡት ቃል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ሥርዓተ ቁጥር 134 (1) ድንጋጌ አነጋገር መሰረት የእምነት ቃልን የሚያቋቁም መሆን አለመሆኑን ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ወንጀሉን መፈፀማቸውን አምነዋል ተብሎ በአመልካቾቹ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 45255 በ29/01/2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 39258 በ17/03/2007 ዓ/ም በውሳኔ የተሻሻለው እና በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 200050 በ02/04/2007 ዓ/ም እና በመዝገብ ቁጥር 199366 በ08/07/2007 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሯል።
2. አመልካቾቹ ያስመዘገቡት ቃል በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁጥር 134/1/ ድንጋጌ አነጋገር መሰረት የእምነት ቃልን የሚያቋቁም መሆን አለመሆኑ ሳይረጋገጥ የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰጠቱ የስነ ስርዓት ህጉን መሰረት ያደረገ አይደለም በማለት ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካቾቹ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 132 /1/ እና /3/ መሰረት ቃላቸውን እንዲያስመዘግቡ ካደረገ በኃላ የሚያስመዘግቡት ቃል ከወንጀሉ ዝርዝር እና ከተከሰሱበት የህግ ድንጋጌ አነጋገር አንጻር ወንጀሉን ማድረጋቸውን ሙሉ በሙሉ አምነዋል የሚያሰኝ መሆን አለመሆኑን መርምሮ እና የሚያስመዘግቡት ቃል የእምነት ቃልን የሚያቋቁም አይደለም የሚል ከሆነም ጉዳዩን በስነ ስርዓት ህጉ መሰረት በማስረጃ አጣርቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለአደአ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
4. የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩን አንቀሳቅሶ መጥሪያ እስኪልክላቸው እና ክርክሩ እንዲቀጥል እስካደርግ ድረስ አመልካቾቹ በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት ባለመገኘቱ ከእስር እንዲለቃቸው ለሚገኙበት የምስራቅ ሸዋ ዞን ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ትእዛዝ ይተላለፍ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለአደአ ወረዳ ፍ/ቤት፣ እንዲያውቁት ደግሞ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 100860

ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች ፡- አቶ ፋንቱ ጉቼ - የቀረበ የለም

ተጠሪ ፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ዐቃቢ ሕግ - ወ/ት ፍጹም ደጉ ቀርበዋል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁን አመልካች የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 61059 ላይ በ18/06/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት በ22/07/2006 ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን ተጠሪ / የሥር ከሳሽ/ የዳራ ወረዳ ዐቃቢ ሕግ በዳራ ወረዳ ፍ/ቤት በቀረበው የማታለል ወንጀል ክስ የአሁን አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ አቶ ፋንቱ ቡቼ የ/ወ/ሕ/ቁ. 692/1/ ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ የግል ተበዳይ አቶ ቾቼ ላሚሶ በፍ/ቤት ላለው የመሬት ክስ ዳኞችን ይገፎ ነገርን አስጨርሼልሃለሁ በማለት ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ጊዜያት በአጠቃላይ ብር 25,000/ ሃያ አምስት ሺህ/ በማታለል በመውሰድ ተከሷል የሚል ነው ፡፡ ተከሳሽ አቶ ፋንቱ ቡቼ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል “ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ቃሉን ሰጥቷል” ፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግል ተበዳይን ጨምሮ የዐቃቢ ህግ ሶስት የሰው ምስክሮች ተሰምተዋል ፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ ተከሳሹን ተከላከል ማለቱን ክሱን ተከላከል ብሎ ከሆነ የመከላከያ ምስክሮች ለምን ቀርቦ እንዳልተሰሙ በምን ምክንያት እንደታለፈ በውሳኔው ላይ የጠቀሰው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን የወረዳው ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመዝገብ ቁ. 11973 በ22/12/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የዐቃቢ ህግ ምስክሮችን ቃል በመመዘን እንደክሱ አረጋግጧል በማለት ተከሳሹን በወ/ሕግ አንቀጽ 692/1/ ሥር ጥፋተኛ በማድረግ የዐቃቤ ሕግን የቅጣት አስተያየት በመቀበል የወንጀሉን ደረጃ 5 አድርጎና የቅጣት እርከን 14 በመያዝ በ3 ዓመት እስራት እና 1000 ብር እንዲቀጣ ወስኗል ።

የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታውን ለሶዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በመዝገብ ቁጥር. 30133 በ30/01/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195 /2/ለ-2/ መሰረት የቀረበውን ይግባኝ ውድቅ በማድረግ የሥር ውሳኔን በማጽናት ወስኗል ። አመልካች አሁንም ይህን ውሳኔ በመቃወም አቤቱታውን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም፣ ችሎቱ በመዝገብ ቁ. 61059 በ18/06/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሌለ አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም በማለት ወስኗል ። አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ሊያቀርብ የቻለው ይህ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው።

አመልካች በ22/072006 ዓ.ም በተጻፈው አቤቱታ የዐ/ሕግ የሰው ምስክሮች እንደክሱ ጭብጥ የአስረዱት ነገር የለም ። ክሱ ራሱ በሰዎች ቅንብር በውሸት የቀረበብኝን ነው። እኔ ይህን ገለሰብ አምስት ጊዜ ወደ ቤት በመጥራት የተጠቀሰውን ገንዘብ ስቀበል ምንም አይነት ውል ወይም ተጨባጭ ማስረጃ በሌለበት ይህን ብር ሰጥቼዋለሁ ያለው አግባብነት የለውም። ዐ/ህግ የማስረዳት ሃላፊነቱን አልተወጣም ። የዐ/ህግ ምስክሮች ከጥርጣሬ ውጭ ስላላስረዱ በነጻ መሰናበት ነበረብኝ። እኔ የተከሰስኩበት ወንጀል የዋስትና መብት የማያስከለክለኝ ቢሆንም የወረዳው ፍ/ቤት አሳስሮኝ መከላከያዬን እንዳላቀርብ ስላደረገኝ በሕገ መንግስት አንቀጽ 19-20 የተደነገገውን የመከላከል መብቴን ያጣበበብኝ በመሆኑ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ግድፈት ተፈጽሟል በማለት በዝርዝር አቅርቧል ። ስለዚህ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ተመልክቶ የሥር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር በነጻ እንዲያሰናብተኝ በማለት አመልክቷል ።

ከዚህ በኋላ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በመመርመር አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በማለት ተጠሪው መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት በ07/11/2006 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አመልካች ብር 25000 ከግል ተበዳይ በማታለል በተለያየ ጊዜ መውሰዱን የዐ/ህግ ማስረጃዎች በተገቢ ሁኔታ ከጥርጣሬ በላይ መስክረዋል የመከላከል መብት በተመለከተ የወረዳ ፍ/ቤት ሕገ መንግስትና የወንጀል ህግ ስነ ስርዓትን መሰረት በማድረግ የዐ/ህግ ማስረጃዎች በ15/12/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከሰማ በኋላ ፣ ከጥርጣሬ በላይ ስለተመሰከረበት ተከሳሹ እንዲከላከል ትእዛዝ በመስጠት የመከላከያ ምስክሮች ስም ዝርዝር አቅርቦ በ16/12/2005 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀርቦ እንዲከላከል ወስኖ በእለቱ በዋለው በወንጀል ችሎት መከላከያዎቹን ባለማቅረቡ በድጋሚ እድል በመስጠት በ20/12/2005 ዓ.ም አቅርቦ እንዲከላከል ህገ መንግስታዊ የመከላከል መብቱ ቢጠበቅለትም በራሱ ፈቃድ መብቱን አለመጠቀሙ ፍ/ቤቱ መብቱን አጣቧል ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ አመልካች የህግ ስህተት አለባቸው ብሎ ያቀረባቸው ነገሮች የህግ ስህተት የሌለበትና ተገቢ የሆነ ውሳኔ የተሰጠበት ነው በማለት በዝርዝር የተለያዩ ነጥቦችን በማንሳት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል ፡፡

አመልካች በ02/04/2006 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አመልካች የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ የመከላከል መብት የታለፈው በህግ አግባብ ነው? ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው ምርምረናል ፡፡

ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው የዳራ ወረዳ ዐ/ህግ በዳራ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የማታለል ወንጀል ፈጽሟል በማለት የወ/ሕ/ቁ. 692/1/ በመጥቀስ የቀረበውን ክስ በተመለከተ አመልካች ፍ/ቤት ቀርቦ በሰጠው ቃል የተጠቀሰውን ወንጀል አልፈጸምኩት በማለት ክዶ ተከራክሯል ፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሶስት ምስክሮችን መስማቱን በውሳኔው ላይ ጠቅሷል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ የዐ/ህግ ምስክሮች እንደክሱ ስላረጋገጡ አመልካችን ተከላከል ማለቱን አመልካች በምን ምክንያት የመከላከያ ማስረጃውን እንዳላቀረበና እንደታለፈ በውሳኔው ላይ የጠቀሰው ነገር የለም የወረዳው ፍ/ቤት የውሳኔ አጻጻፍ ችግር እንደተጠበቀ ሆኖ ፍ/ቤቱ ለዚህ መብት ተገቢ ግምት ሰጥቷል ወይ? የሚል የሕግ ጥያቄ የሚያነሳ ነው፡፡

በዚህ አግባብ ሲታይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 142/1/ እንደሚደነግገው የዐ/ህግ ህግና የተበዳይ ማስረጃ እንደክሱ ጭብጥ የመሰከሩ ወይም ያረጋገጡ ከሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ማሰማት እንደሚጀምርና መንገር እንደሚችል ነው፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የመከላከያ ማስረጃን አቅርቦ ማሰማት የተከሳሹ መብትና ግዴታ መሆኑን ነው ፡፡ ፍ/ቤቱ ግን ተከሳሽ በዚህ መብቱ እንዲጠቀም የነገረው መሆኑን በውሳኔው ማመልከት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ በላይ የተከሰሱ ሰዎች በህገ መንግስቱ ከተከበረላቸው ሰብዓዊ መብቶች መካከል “ የመከላከል መብት” አንዱ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20/4/ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሰረት የተከሰሱ ሰዎች “ የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡበትን ምስክሮች የመጠየቅ ፣ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርቦ እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው"። ስለዚህ የመከላከል መብት ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ ያገኘ መብት መሆኑን ያስገነዝባል።

ከዚህም በላይ ይህ " የመከላከል መብት " በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሰነዶች ጥበቃ የተደረገለት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው እ.ኤ.አ በ1976 በጸደቀው ዓለም አቀፍ የማህበራዊ እና የፖለቲካ መብት ስምምነት አንቀጽ 14/3ረ/ እንደሚደነገገው የተከሰሰ ሰው የራሱን ምስክሮች አቅርቦ የመጠየቅ መብት እንዳለው ነው ። ይህ ደግሞ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13/2/ ሽፋን ያገኘ ጉዳይ ነው።

ይህ " የመከላከል መብት" በተመለከተ ፍ/ቤት ያላቸው ሚና ሲታይ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13/1/ መሰረት " የማክበርና የማስከበር ሃላፊነትና ግዴታ አለባቸው" ከዚህ አኳያ ፍ/ቤት የተከሰሱ ሰዎች የመከላከል መብታቸውን በሚገባ መጠቀም እንዲችሉ አስፈላጊውን ሁኔታ ለማመቻቸት በሕግ አግባብ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል እንጂ በምንም መልኩ ይህን መብት ለሚገድብ ድርጊት አስተዋጽኦ ማድረግ የለበትም ፍ/ቤት የተቀላጠፍ ፍትህ አሰጣጥን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተከሰሰው ሰው ምስክሮቹን ለማቅረብ ያለው አቅም እና የተመቻቸ ሁኔታ፣ በማረሚያ ቤት መሆኑን እና አለመሆኑን፣ የመከላከያ ማስረጃና ምስክሮችን ለማቅረብ የሚጠይቀውን እገዛ፣ በቂ ነው ሊባል የሚችል ጊዜ እና አጠቃላይ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ መብት ተጠቃሚ እንዲሆን አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል። ስለዚህ ፍ/ቤት ይህን ሕገ መንግስታዊ ሃላፊነትና ግዴታውን በአግባቡ መወጣት አለበት።

ከዚህ አንጻር አሁን የያዝነው ጉዳይ ስንመለከት የዳራ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች የዐ/ህግ ምስክሮች እንደክሱ ስለመሰከሩበት እንዲከላከል ብይን መስጠቱን አመልካች የመከላከያ ምስክሮቹን ከማቅረብ አንጻር የጠየቀውን መብት የመከላከያ ምስክሮችን ሳይሰማ ለምን እንደታለፈ በውሳኔው ውስጥ የጠቀሰው ነገር የለም። የወረዳው ፍ/ቤት ይህን ያህል በዓለም አቀፍ ሰነዶች እና በሕገ መንግስቱ ጥበቃ የተደረገለትን የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ክስ የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ " የመከላከል መብት " በውሳኔው አለማካተቱ በሕገ መንግስቱ የተጣለበትን ሃላፊነት በሚገባ ተወጧል ብሎ ለመናገር የሚያስችል አይደለም። የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የሰበር ሰሚ ችሎት የወረዳውን ውሳኔ ማስተካከል ሲገባቸው ውሳኔውን ማጽናታቸው ከዚህ አንጻር የሚጠበቅባቸውን ሚና ተወጥቷል ለማለት አያስደፍርም።

በዚህ በኩል ተጠሪ ያቀረበው መልስ ሲታይ ፍ/ቤት በ15/12/2005 ዓ.ም የዐ/ህግ ምስክሮችን እንደሰማ አመልካች በ16/12/2005 ዓ.ም የመከላከያ ምስክሮቹን እንዲያቀርብ መታዘዙን ፣ በድጋሚ ተለዋጭ ቀጠሮ ለ20/12/2005 ዓ.ም እንደተሰጠ በመጥቀስ አመልካቹ በራሱ ፈቃድ መከላከል እንዳልፈለገ በመጥቀስ ተከራክሯል ። አመልካች ደግሞ ባቀረበው ክርክር ፍ/ቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማረሚያ ቤት እንዲታሰር አድርጎኝ በሁለት ቀን ውስጥ እንዲከላከል ትእዛዝ መስጠቱ እንዳልከላከል እንደማድረግ ይቆጠራል፡፡ በማለት የመልስ መልሱን ሰጥቷል ፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ተከሳሹ የመከላከያ ምስክሮችን እንዲያቀርብ የሰጠው ጊዜ በአጠቃላይ ከ4 ቀናት የሚበልጥ አይደለም ከዚህ ክርክር መረዳት እንደሚቻለው ፍ/ቤቱ አመልካች በማረሚያ ቤት ታስሮ መገኘቱን እያወቀ የመከላከያ ምስክሮቹን አቅርቦ በማሰማት ሕገ መንግስታዊ መብቱን በሚገባ እንዲጠቀምበት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በቂ ነው ሊባል የሚያስችል ጊዜ ሰጥቷል ለማለት አይቻልም ፡፡ ፍ/ቤቱ አመልካቹ ያለበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ምስክሮቹን እንዲያቀርብ በማዘዝ፣ ምስክሮችን አላቀረብክም በማለት ማለፍ መብቱን እንዳይጠቀም እንደመከልከል የሚቆጠር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የስር ፍ/ቤቶች አመልካቹ “የመከላከል መብቱን እንዲጠቀም ተገቢና አስፈላጊ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ረገድ በህገ መንግስቱም ሆነ በወንጀል መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ግዴታ በሚገባ ተወጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ የስር ፍ/ቤቶች አመልካች የመከላካ ምስክሮችን አቅር እንዲያሰማ በማድረግ፣ የመከላከል መብቱን ያለ የሕጋዊና በቂ ምክንያት በማለፍ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ ይደነበት አግባብ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል ፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

- የዳራ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 11973 በ22/12/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 30133 በ30/01/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 61059 በ18/06/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተሽሯል ፡፡
- የዳራ ወረዳ ፍ/ቤት ይህ ጉዳይ ድጋሚ በማየት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስ በማስገባት በቂ ነው ሊባል የሚችል ጊዜ በመስጠት አመልካች የመከላከያ ምስክሮቹን አቅርቦ እንዲያሰማ በማድረግ በሕጉ አግባብ በማጣራትና በመመዘን ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ይሰጥ ብለናል፡፡ ይጻፍ፡፡
- የዳራ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች ብር 1000/ አንድ ሺህ/ የሚሆን በቂ ዋስትና ካቀረበ ወይም ይህን ገንዘብ በወረዳው ፋይናንስ በሞዴል ካስያዘ ከማረሚያ ቤት ውጭ ሆኖ እንዲከራር እንዲያደርግ ታዟል ፡፡ ይጻፍ ፡፡ ጉዳዩን ባለ 5 ዳኛ እንዲታይ ተብሏል ፡፡
- የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ለማረሚያ ቤት እና ለአመልካች ይድረስ ብለናል፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.101056

ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተሽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጤቻ

አመልካች፡- አቶ አይሸሽም ገብሬ - ጉዳዩ ተከታታይ ቤተሰብ ቀረበች

ተጠሪ፡- የፌዴራል የሥነ - ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1በዋና ወንጀል ሠሪነትና በግብረአበርነት አንድ የወንጀል ድርጊት መፈፀማቸው በፍርድ ተረጋግጦ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየው ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት /ይግባኝ ሰሚ ችሎት/ተመሣሣይ ፍርድና የቅጣት ውሣኔ የተሰጠባቸው ሰዎች በተለያየ መዝገብ የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበው•የአንደኛው የሰበር አቤቱታ አቅራቢ የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቅጽ 22 መሠረት ቢዘጋና የሌላኛው የሰበር አቤቱታ አቅራቢ የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ወይም ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሣኔ ቢሻሻልና የሰበር ችሎት በማሻሻል የሰጠው ፍርድ ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎት ለሰበር የሚያስቀርብ ነጥብ የለውም ተብሎ የተዘጋበትን አቤቱታ አቅራቢ የሚጠቅመው ሆኖ ቢገኝ• የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም?የሚለውን አከራካሪ የህግ ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡
2. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች አንደኛ ተከሳሽ በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 አመልካች የነበረው አክሊለብርሃን አባቡ ሁለተኛ ተከሳሽ ሆነው በወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1)ሀ እና አንቀጽ 408 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ከፍተኛ ግብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፋዮች ቅርንዛፍ ጽ/ቤት አዲተሮች ሆነው ሲሰሩ አዲት እንዲያደርጉ ከተመደቡበት ኦትራክን/ ጀኔራል ኢትዮጵያ ሰርቪስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የቆዳና ሌጦ ፋብሪካ ግብይት አቅራቢ ድርጅት ሂሳቡ አምስት ሚሊዮን ብር ብር / 5000,000/ጉድለት ያሳያል በማለት ከድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ጋር በአካልና በስልክ በመደራደር ብር 600,000 /ስድስት መቶ ሺህ እንዲከፍላቸው በመስማማት ሰኔ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀኑ አስራ ሁለት ሠዓት ከድርጅቱሥራ አስኪያጅ ጋር ቀጠሮ በያዙበት ቦታ ተገኝተውና ከድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ መኪና ውስጥ ገብተው በተደራደሩበት ገንዘብ ውስጥ ብር 100,000/አንድ መቶ ሺህ/ አንደኛ ተከሳሽ የአሁኑት አመልካች በጥቁር ፌሰታል እንደተጠቀለለ ተቀብሎ ሲወርድ ሁለተኛ ተከሳሽ /በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013/አመልካች የነበረው አክሊለብርሃን አባቡ መኪናው ውስጥ ተቀምጦ ቀሪውን ገንዘብ ለመቀበል በመጠባበቅ ላይ እያለ የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በመደባቸው የክትትል አባሎች እጅ ከፍንጅ መያዛቸውን በማረጋገጥ• የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሾች የተከሰሱበትን የህግ ድንጋጌ በመተላለፍ ከባድ የጉቦ መቀበል የሙስና ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት በመዝገብ ቁጥር 123410 የጥፋተኝነት ውሣኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

3. የቅጣት ውሣኔውን በተመለከተ• ወንጀሉ በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ነው በማለትና የቅጣት ደረጃው ከሰባት ዓመት እስከ ዘጠኝ ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት መሆኑን ገልፆ በሁለቱም ላይ የመነሻ ቅጣቱ ስምንት ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 4000/አራት ሺህ ብር/ መቀጮ እንደሆነ ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች አራት ታናናሽ እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑን በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዝለት ያቀረበውን ጥያቄ አስተዳድራቸዋለው ያልከው ልጆችህን ወይም ሚስትህን አይደለም በሚል ምክንያት ውድቅ ካደረገ በኃላ አመልካች የወንጀል ሪከርድ የሌለበት መሆኑንና እና ፀባያቸው መልካም የነበረ መሆኑን አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያትን በመቀበል በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በእያንዳንዱ ማቅለያ ምክንያት አንድ እርከን በመቀነስ ከእርከን ሃያ ስድስት ወደ እርከን ሃያ አምስት ዝቅ በማድረግ ተከሳሾች በስድስት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እሰራትና በብር 3000/ሶስት ሺህ ብር/መቀጮ እንዲቀጡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት የቅጣት ውሣኔ በመቃወም የአሁኑ አመልካች የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 96631 ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ•ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ጉዳዩ የሚያስገባ ምክንያት የለም በማለት የካቲት 20 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ/ትዕዛዝ/ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 አቤቱታ ያቀረበው የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ በበኩሉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመቃወም በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 96526 ይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ጉዳዩ የሚያስገባ ምክንያት የለም በማለት የካቲት 25 2006 ዓ.ም በሠጠው ውሳኔ/ ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

5. የአሁን አመልካች የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም ግንቦት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በዚህ መዝገብ አቅርቦ፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታውንና መዝገቡን ከመረመረመ በኃላ በቀረበው ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተሰርቷል ማለት አልተቻለም በመሆኑም መዝገቡ ለሰበር አያስቀርብም ብለናል በሚል ትዕዛዝ ቅጥምት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶበት ተዘግቷል፡፡

6. ከአመልካች ጋር በወንጀል ተካፋይነት የተከሰሰውና ጥፋተኛ የተባለው እንደዚሁም ይግባኙ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 95526 ይግባኝ ሰሚው ችሎት የካቲት 25 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ /ውሣኔ/ ውድቅ የተደረገበት አክሊለብርሃን አባቡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ግንቦት 11 ቀን 2006 ዓ.ም ፅፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በመመርመር የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የጥፋተኝነት ቅጣቱን የወሰንኩት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ለሰበር ችሎት በመቅረቡ፣ ይኸ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሣኔ አፅንቶ የቅጣት ውሣኔውን በማሻሻል መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

7. በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም የቅጣት ውሣኔውን ሲያሻሽል የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሁለት መሠረታዊ የህግ ስህተቶች ሠርተዋል፡፡ የመጀመሪያ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት በተለይም እናት አባት ወንድም እህት ማስተዳደርና መርዳት /ልጅና ሚስት/ባልሆነ በስተቀር በወንጀል ህግ አንቀጽ 86 የሚሸፍን ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሊሆን አይችልም በማለት የሰጡት የህግ ትርጉም ስህተት ያለበት መሆኑን በመተንተን• ተከሳሹ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ወንድሞቹን እህቶቹን እናትና አባቱን እየረዳና እያስተዳደረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከቀረበ በወንጀል ህግ አንቀጽ 86 ሥር የሚሸፈን ልዩ የቅጣት ምክንያት እንደሚሆን ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛው ቅጣቱ መሠላት ያለበት መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት በመተንተን• በመዝገብ ቁጥር 101013 አመልካች የነበረው ሰው• እናቱን አባቱን ወንድምና እህቶቹን የሚረዳ መሆኑ በልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት እንዲያዝለትና•በሁለቱ የቅጣት ምክንያቶች በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 7 መሠረት ሶስት እርከን በአጠቃላይ ስድስት እርከን ሲቀንስ ከእርከን ሃያ ስድስት ወደ እርከን አስራ ዘጠኝ ዝቅ የሚል በመሆኑ አመልካች አክለስብርሃን አባቡ በእርከን አስራ ዘጠኝ ከተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአራት ዓመት ፅኑ እስራትና በብር 3000/ሶስት ሺ ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101013 መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል ።

8. ከዚህ በኋላ አመልካች በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ ከነበረው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 የቅጣት ውሳኔ ከተሻሻለበት አክሊብርሃን አባቡ ጋር ተመሣሣይ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያቀረቡ መሆኑን ገልፆ እህቶችህን የማስተዳድር መሆኑ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አይሆንም በማለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚችሎት የሰጡት የህግ ትርጉም ስህተት ያለበት መሆኑ በሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑና በጉዳዩም ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሆኑ በሰበር ችሎት የተወሰነ ሆኖ እያለ• የእኔ የሰበር አቤቱታ የሰበር አጣሪ ችሎት ለሰበር የሚቀርብ ነጥብ የለውም በሎ ስለዘጋው ብቻ የእኩልነትና ፍትህ የማግኘት መብቴ ተገድቦ ሊቀር ስለማይገባው• የሰበር ችሎት መዝገብ ቁጥር 101013 የሰጠው ፍርድ የሚጠቅመኝ በመሆኑ በፍርድ ተጠቃሚ ሊሆንና የቅጣት ውሣኔው ሊሻሻልልኝ ይገባል በማለት አቤቱታውንና ክርክሩን አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በራሱ መንገድ ይግባኝና የሰበር አቤቱታ አቅርቦ እድሉን አሟጥጦ የጨረሰና የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠበት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በሰበር ማጣሪያ ችሎት ያፀናበት በመሆኑ• ይኸ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101013 በሰጠው ውሣኔ የሚጠቀምበት የህግ ሥርዓት የለም፡፡ ፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 የሰበር አቤቱታ ላላቀረቡ ተከሳሾች እንጅ በአመልካች ጉዳይ ላይ ተፈፅሚነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል ።

9. መዝገቡ በዚህ ሰበር ችሎት የቀረበበት መሠረታዊና አከራካሪ የህግ ጭብጥ አመልካች በዚህ መዝገብ• ከአመልካች ጋር በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከሳሽ የነበረው ሰው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ያለፈበት ሂደትና የተሰጡ ትዕዛዝና ውሣኔ ይዘት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 196 ንዑስ አንቀፅ 1 በአመልካች ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ወይም የለውም? የሚለውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 የተሰጠው ፍርድ አመልካችን የሚጠቅመው ነው ወይስ አይደለም? የአመልካች ጉዳይ ለሰበር ችሎት ቢቀርብ ኖሮ በአመልካች ላይ የተሰጠው የቅጣት ውሣኔ ሊሻሻልለት ይችል ነበር ወይስ አልነበረም? የሚሉትን ነጥቦች መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. አመልካችና በመዝገብ ቁጥር 101013 አመልካች የሆነው ሰው በወንጀል ህግ አንቀፅ 32/1/ሀ እና አንቀፅ 408 ንዑስ አንቀፅ 1 በመተላለፍ፣ በዋና ወንጀል ሠሪነት አንድ ላይ ከአንድ ሰው ከባድ ጉቦ የመቀበል ወንጀል የፈፀሙ ጥፋተኛ መሆናቸው እስከሰበር ችሎት ድረስ በተሰጠው ፍርድ ተረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለቱም ተከሳሾች ከዚህ በፊት ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፈፅመው የማያውቁና የዘወትር ባህሪያቸው መልካም የነበረ መሆኑን አንድ የቅጣት ማቅለያ አድርጎ የያዘላቸው ሲሆን ይህንኑ ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተቀብሎታል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለቱም ተከሳሾች በወንጀል በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በሁለቱም ተከሳሾች ለአንድ የቅጣት ማቅለያ አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ በእርከን ሃያ አምስት የተመለከተው ሁለቱም ስድስት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራትና በብር 3000/ሶስት ሺ ብር/ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ተከሳሾቹ በተናጠል ያስከፈቱትን የይግባኝ መዝገብ መርምሮ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

11. ይህም የሚያሳየው ከአመልካች ጋር በዋና ወንጀል ተካፋይነት ጥፋተኛ የተባለው በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበረው ሰው ለሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በአራት ዓመት ፅኑ እስራትና በሶስት ሺ ብር/3000 ብር/ መቀጮ እንዲቀጣ የተወሰነው፣ ከአመልካች ያነሰ የወንጀል ተሣትፎ ስለነበረው አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው ችሎትና የሰበር አጣሪ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የወሰነውን የቅጣት ውሣኔ ያፀኑት በወንጀል ህግ አንቀፅ 41 በሚደነግገው መሠረት ቅጣቱን በአመልካች ላይ ለይቶ ለመወሰንና ለማፅናት የሚያስችሉ የግል ምክንያቶች ያሉ መሆናቸውን በማረጋገጥና ይህንንም በሰጡት ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ በግልፅ በማስፈር እንዳልሆነ ተረድተናል፡፡

12. በአንፃሩ የአሁን አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ጉዳዩ ታይቶ የቅጣት ውሳኔው ከተሻሻለለትና በወንጀል ተካፋይነት አብሮት ጥፋተኛ ከተባለው ሰው፣ የተለየ ቅጣት እንዲፀናበት የተደረገው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 41 ወይም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 88 በተደነገጉና በግልፅ ተለይተው በሚታወቁ ምክንያቶች ሣይሆን፣ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ልጅና ሚስት ካልሆነ በስተቀር ወንድምና እህት እናትና አባት መርዳትና ማስተዳደር በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 የሚሸፈን ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አይሆንም በማለት በሰጡት የተሣሣተ ትርጉምና ይኸ ሰበር ችሎት 101013 እህትና ወንድም አባትና እናት መርዳትና ማስተዳደር በወንጀል ህግ አንቀፅ 86 የሚሸፈን ልዩ የቅጣት ማቅለያ ይሆናል በማለት በሰጠውና አመልካችን ተጠቃሚ በሚያደርገው ትርጉም ውሳኔ፣ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ባለመቅረቡ ተጠቃሚ ሣይሆን በመቅረቱና አመልካች እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑ በልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት ሣይያዝለት በመቅረቱ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95438 ግንቦት 7 ቀን 2006 በቅጣት አወሳሰን ሂደት የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 2/2006 ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር፣ ቅጣት ለመወሰን፣ ተፈፃሚነት ያለው የወንጀል ድርጊት ሲፈፀም ስራ ላይ የነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው በማለት የሕገ መንግስቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀፅ 22 እና የወንጀል ህግን አንቀፅ 5 መሰረት በማድረግና ይኽ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95438 ግንቦት 7 ቀን 2006 የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም የስር ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባለመከተላቸውና መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመፈፀማቸው ምክንያት ነው።

13. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑ በልዩ የቅጣት ማቅለያ ተይዞለት፣ ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች ያሉት መሆኑንና በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 7 መሰረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሶስት እርከን በድምሩ ስድስት እርከን ሲቀነስ በእርከን አሰራ ዘጠኝ ከተገለፀት የቅጣት ሬንጅ ውስጥ የሚወድቅ መሆኑና በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በተሰጠው ፍርድ የሚጠቀም መሆኑ የሚያከራክር ሆኖ አላገኘነውም።

14. አመልካች በወንጀል ተካፋይነት አብሮት በተከሰሰውና ጥፋተኛ የተባለው ሰው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ፍርድ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል ከተረጋገጠ አመልካች በተናጠል በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ታይቶ ጥቅምት 7 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ውድቅ መደረጉ አመልካች የሰበር አቤቱታ ባያቀርብ ኖሮ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሊያገኝ የነበረውን ጥቅምና መብት የሚያስቀርበት ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ፣ ጉዳዩ የወንጀል ጉዳይ ከመሆኑ አንፃር በፌዴራል ደረጃ ከተዘረጋው የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማና ግብ መሠረት በማድረግ መመርመሩ አስፈላጊ ነው።

16. ሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) የተዘረጋው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሣኔ በሰበር አይቶ በማረም በአገር ውስጥ ሕጎች ወጥ በሆነ መንገድ እንዲተርጎምና ተፈፃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የህግ የበላይነትንና ፍትህን ማስፈን ነው። የሰበር ሥርዓት ከይግባኝ እና ሌሎች የፍርድ ላይ የሚፈፀሙ ስህተቶች ማረሚያ መንገዶች የተለያየና የራሱ የሆነ ባህሪ ያለው በመሆኑ ይህንኑ ባህሪውን ያገናዘበና ዓላማውን ለማሣካት የሚያስችል የሥነ ሥርዓት ሌሎች አሠራሮች ያስፈልጉታል።

17. በአገራችን የሰበር ሥርዓቱ የሚመራበት ሰበር የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ የሥነ ሥርዓቱ ህግ የለም። የሰበር ችሎት እየሠራ የሚገኘው ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ በሚታዩበት ወቅት እንዲያገለግሉ ታስበው ከግማሽ ምዕተዓመት በፊት የወጡና ሌሎች የሥነ ሥርዓት ሕግ ማዕቀፎችን ነው። ይህም በመሆኑ በሥራ ላይ ያሉትንና የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ባህሪና አላማ ግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባ ህግ አውጭው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወደዳቸውን የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ከሰበር ሥርዓቱ መሠረታዊ ባህሪ ጋር በማጣጣምና የሰበርን መሠረታዊ ዓላማ ለመስማት በሚያስችል መንገድ በመተርጎም በማጣጣም ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡

18. ለያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ክርክር ያስነሳው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ 196 ንዑስ አንቀፅ 1 ህግ አውጭው የደነገገውና በሥራ ላይ እንዲውል ያደረገው በአገራችን የሰበር ሥርዓት ባልዘረጋበት ጊዜና የይግባኝ ሥርዓቱ በፍርድ የሚፈጸም የፍሬ ጉዳይ ብቻ ሣይሆን መሠረታዊ የህግ ስህተት ማረሚያ ዋና ሥርዓት ተደርጎ በተዘረጋበት ወቅት መሆኑን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት የታወጀበትን ጥቅምት 23 ቀን 1954 ዓ.ም መመልከቱ ብቻ በቂ ነው፡፡በዚያን የታወጀው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት አንቀጽ 196 “የተፈረደባቸው ሰዎች ሆነው አንድ ብቻ ይግባኝ ሲያቀርብ” የሚል እርዕስ ያለው ሲሆን የደነገገው ንዑስ አንቀጽ 1 ቃል በቃል ሲነበብ “ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበው ይግባኝ ስለተፈረደባቸው ብዙ ሰዎች የሚመለከት ሆኖ ይግባኝ ያለው ግን የተፈረደበት አንድ ሰው ብቻ በሆነ ጊዜ ከዚህ በታች የተመለከተው ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሚሰጠው ፍርድ ይግባኝ ላሉትም ሰዎች ይግባኝ እንዳለ ተቆጥሮ ይፈጸምላቸዋል ለማለት የሚችለው /ሀ/ በይግባኝ የተሰጠው ፍርድ ይግባኝ ባዩን የሚጠቅም በሆነ ጊዜና /ለ/ ተከሳሾች ይግባኝ ቢሉ ኖሮ በፍርድ እነርሱም ሊጠቀሙ ይችሉ ነበር የሚያሰኝ ሆኖ ሲገኝ ነው” የሚል ይሁንታ ያለው ነው፡፡

19. ይህንን ድንጋጌ አሁን ላለው የሰበር ስርዓት ለመጠቀም ካለው የሰበር ችሎት አደራጃጀትና አሰራር ጋር በሚጣጣምና የሰበርን መሰረታዊ ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መንገድ መተርጎምና ስራ ላይ ማዋል ይጠይቃል፡፡ የመጀመሪያው ብዙ ተከሳሾች አንድ ወንጀል የወንጀል ስራው ተካፋይና ግብረ አበር ሆነዋል ተብለው ክስ ቀርቦባቸውና፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ባየው ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ባዩው ፍርድ ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አንደኛው ተከሳሽ የሰበር አቤቱታ አቅርቦ፣ አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ በሰበር ችሎት ታይቶ፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በይግባኝ አይቶ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት የጥፋተኝነት ወይም የቅጣት ውሳኔ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔው መሰረታዊ ህግ ስህተት አለበት ተብሎ ከተሻረ፣ ከተሻሻለ ወይም ከተለወጠና የሰበር ችሎት በመሻር፣ በማሻሻል ወይም በመለወጥ የሰጠው ውሳኔ የሰበር አቤቱታ ያላቀረቡትን ሌሎቹ በአንድ ጉዳይ የተከሰሱ ሰዎችን የሚጠቅም ሆኖ በተገኘ ጊዜ፣ ሰዎቹ ፍርድን በመቃወም የሰበር አቤቱታ ባያቀርቡም ሰበር ችሎት በሰጠው ውሳኔ ወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

196 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተጠቃሚ እንደሆኑ በሚያደርግ አግባብ ድንጋጌው መተርጎምና ስራ ላይ መዋል አለበት የሚለው ነው።

20. ሁለተኛው በአንድ ወንጀል አድራጎት በወንጀል ህግ ስለወንጀል ተካፋይነት አድራጊነት ወይም ስለግብረአበርነት በተደነገጉት መሰረት በአንድ ላይ ፈጽመዋል ተብለው ክስ ከቀረበባቸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ባየውና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተወሰነባቸው ሰዎች ብዙ ሰዎች ሁሉም በግላቸው የሰበር አቤቱታ አቅርበው የሰበር መዝገብ አስከፍተው ከፊሎቹ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታና የስከፊቱት የሰበር መዝገብ በሰበር ችሎት የሚቀርብ መሠረታዊ የህግ ስህተት ጭብጥ የለውም ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 22 መሠረት በሰበር አጣሪ ችሎት ውድቅ ቢደረግና ቢዘጋ የከፊሎቹ ወይም አንደኛው ተከሳሽ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰበር የሚጣራ መሠረታዊ የህግ ጭብጥ አለው ተብሎ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሰበር ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የጥፋተኝነት ውሣኔውን ወይም የቅጣት ውሳኔውን ወይም የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔውን መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር ችሎት ከሻረው ካሻሸለው ወይም ከለወጠውና ውሳኔው የሰበር አቤቱታ አቅርበው የሰበር ማጣሪያ ችሎት የሚጣራ መሠረታዊ የህግ ስህተት ጭብጥ የለውም ብሎ አቤቱታውን ውድቅ ያደረገባቸውን ሰዎች የሚጠቅም ሆኖ በተገኘ ጊዜ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል የሚለው ነው።

21. ለዚህም ምክንያቱ ለይግባኝ ሥርዓት ታስቦ የተደነገገው የወንጀለኛ መቅጫ ሥርዓት ህግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 አሁን ያለውንና በአዋጅ ቁጥር 25/88 የተደነገገውንና የተዘጋውን የሰበር ችሎት አደረጃጀት ጋር በሚጣጣም መንገድ ሥራ ላይ ካልዋለና• አሁን በመዝገቡ ለያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚ የማይሆን ከሆነ አንድ የወንጀል ድርጊት በአንድ ላይ ፈፅማችኃል ተብለው ተከሰው ቢኖር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከተመሣሣይ የወንጀል ህግ ድንጋጌ ጥፋተኛ ተብለውና በወንጀሉ የነበራቸው ተሣትፎ እና ሌሎች ግላዊ ሁኔታዎች ተመሣሣይ ሆኖ በመገኘቱ ተመሣሣይ የሆነ የቅጣት ውሣኔ የተላላፈባቸው ሰዎች፣ የአንደኛው የሰበር አቤቱታ የሚጣራ የህግ ነጥብ ያለው መሆኑ ተገልፆ ለሰበር ችሎት ስለቀረበና በውሣኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑ ተገልጾ በሚሰጠው ፍርድ ተጠቃሚ የሚሆንበት የሌላኛው የሰበር አቤቱታ የሰበር አጣሪ ችሎት ለሰበር የሚቀርብ የለውም ተብሎ ውድቅ ስለተደረገበት ብቻ የፍርዱ ተጠቃሚ የማይሆንበትን አግባብ መከተል በህገ መንግስቱ አንቀፅ 25 እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 4 የተደነገገውን የእኩልነት መርህ የሚጥስና የሰበርን መሠረታዊ ዓላማ የማያሳካ ይሆናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

22. ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ወንጀል በጋራ ፈፅማችኋል ተብለው የተከሰሱና ጥፋተኛ ተብለው ከተቀጡ ሰዎች መካከል፣ ሌሎቹ ሰዎች መብታቸውን ለሰበር ችሎት ለማቅረብ ዳኛ ሆነው አንደኛው ተከሳሽ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሰበር ችሎት በሰጠው ፍርድ ሌሎቹ ተከሳሾች በሚጠቅሙበት አግባብ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196 ንዑስ አንቀጽ 1 ጥቅም ላይ የሚውሉና የሚፈፀም ከሆነ፣ በአንድ የወንጀል ድርጊት የተከሰሱ ሁሉም ሰዎች መብታቸውን ለሰበር ለማቅረብ ተገቢውን ትጋት አሳይተው ለሰበር ችሎት በማቅረባቸውና የከፊሎቹ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመደረጉና የከፊሎቹ ለሰበር የሚቀርብ ነጥብ የለም ተብሎ በመዘጋቱ•የሰበር ችሎት የሰጠው ፍርድ የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ የተደረገባቸውን ሰዎች የሚጠቅም ሆኖ እያለ በፍርዱ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማድረግ፣ በአጠቃላይ የሰበር ሥርዓቱን መሠረታዊ አላማና ሕግ አውጭው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 196 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ሊያወጣ የፈለገውን ግብ፣ አሁን ካለው የሰበር አደረጃጀት ጋር በሚጣጣም መንገድ ሥራ ላይ እንዳይውል የሚደረግና ሰዎች ተግተው የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ምክንያት ብቻ የድንጋጌው ቱርፋት እንዳይደርሳቸው የሚያደርግ በመሆኑ፣ ይህንኑ ድንጋጌ ይህንኑ ሁኔታ በሚሰጥበት አግባብ መተርጉም ሥራ ላይ መዋል ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

23. አመልካች የሰበር አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ውድቅ ባይደረግ ኖሮ ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በሰጠው ፍርድ እና ከአመልካቹ ጋር ዋና ወንጀል አድራጊ ሆኖ በተከሰሰው ሰው፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪነቱ በልዩ ቅጣት ማቅለያነት እንዳይዝለት ይኸ ሰበር ችሎት በሰጠው የህግ ትርጉም ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2001 አንቀጽ 17 ፀዑስአንቀጽ 1መሠረት ለአንድ የቅጣት ማቅለያ ሶስት እርከን መቀነስ እንዳለበት ይጭ ሰበር ችሎት መሠረታዊ ዓላማ፣ ለማሳካት ፣ በህገ መንግስቱአንቀጽ 80 ፀጉስ አንቀጽ 3ን/ሀ/የተደነገገውን የሰበር ችሎት መሠረታዊ ዓላማ፣ ለማሳካት፣ በህገመንግስቱ አንቀጽ 25 እና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 4 የተደነገገውን የእኩልነት መርህ ተግባራዊ ለድረግ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 196ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ከስር አደረጃጀትና አሠራር ጋር በማጣጣም መተርጉምናአመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 101013 በተሰጠው ፍርድ ተጠቋሚ ማድረግ አስፈላጊ ነው በማለት ወስነናል።

24. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች እህቶቹን የሚያስተዳድር መሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 86 ልዩ የቅጣት ማቅለያ ሆኖ ሲያዝለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከያዙለት አንድ የቅጣት ማቅለያ ጋር ተደምሮ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ይኖረዋል ። የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወሰኑት የቅጣት መነሻ ከሚገኝበት እርከን ሃያ ስድስት እያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 7 መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሶስት እርከን ሲቀነስ በአመልካች ላይ የሚወሰነው ቅጣት እርከን አስራዘጠኝ ላይ የሚወድቅ ይሆናል ። በመሆኑም በእርከን አስራዘጠኝ ከተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ ፈቃደ ስልጣናችንን ተጠቅመን አመልካች በቀሩት ዓመት ፅኑ እስራት እና ብር 3000 /ሶስት ሺ ብር/ መቀጮ ይቀጣል በማለት ወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 196 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በአመልካች ላይ የተሰጠውን የቅጣት ውሣኔ አሻሽለን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 123410 የሰጠው የቅጣት ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 93631 የሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/196 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ተሻሽሎአል።
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ማጣሪያ ችሎት ጥቅምት 10 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በዚህ ፍርድ ተለውጧል።
3. አመልካች በዚህ ጉዳይ ተጠርጥሮ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ አራት ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 3000 /ሶስት ሺ ብር/ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ወስነናል ።
4. የቅጣት ውሣኔ የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ሊክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ።
5. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቡ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 110969

ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገብረሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ሀብታሙ ደጁ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቢ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሆኖ የዋስትና መብት አፈጻጸምን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረውም ተጠሪው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች እና በሌላ አንድ ግለሰብ ላይ ባቀረበው ክስ መነሻ ተከሳሾቹ ባቀረቡት የዋስትና መብት ጥያቄ ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡-ክሱ የቀረበው ተከሳሾቹ በአዋጅ ቁጥር 761/2004 በአንቀጽ 9 (1) (ሀ) እና (ለ) ስር የተደረነገገውን በመተላለፍ የቴሌኮም የማጭበርበር ወንጀል አድርገዋል ተብለው ሲሆን የዋስትና መብታቸው እንዲከበር ተከሳሾቹ ባቀረቡት አቤቱታ ሳቢያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዋስትና ጥያቄው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በክሱ የተጠቀሰው ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከ10 እስከ 20 ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት እና በወንጀሉ የተገኘውን ሕገወጥ ጥቅም አስር እጥፍ መቀጮ መሆኑን፣ተከሳሾቹ የተከሰሱበት ድንጋጌ የዋስትና መብትን የሚከለክል አለመሆኑን እና አመልካቹ የተሟላ አድራሻ ያላቸው እና በንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ በመሆኑ በዋስትና ቢወጡ ግዴታቸውን አክብረው አይቀርቡም በማለት ተጠሪው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 67 (ሀ) ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ አመልካች ለብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ)፣2ኛ ተከሳሽ የነበሩት ግለሰብ ደግሞ ለብር 80,000 (ሰማንያ ሺህ) ዋስትና አቅርበው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዋስ ሆነው እንዲከራከሩ በመዝገብ ቁጥር 153018 በ27/05/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ መስጠቱን፣በትዕዛዙ ቅር በመሰኘት ተጠሪው ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ተከሳሾቹ ከሚጠብቃቸው ቅጣት ከባድነት አንጻር በዋስ ቢወጡ ግዴታቸውን አክብረው አይቀርቡም የሚለው ግምት ሚዛን የሚደፋ ሆኖ ማግኘቱን ገልጾ የከፍተኛ ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ በመሻር ተከሳሾቹ ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከታተሉ በመዝገብ ቁጥር 109570 በ17/06/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሳኔ መስጠቱን፣አመልካች ይህንን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለአመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተፈቀደው የዋስትና መብት በተጠሪው ይግባኝ ባይነት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሻሩ ከወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 75 (1) አንጻር ሲታይ ዐቃቤ ሕግ ለምን ዋስትና ተፈቀደ በሚል ይግባኝ የማለት መብት ያለው መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የዋስትና መብት ቢኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስትም ሆነ በዝርዝር ሕጎች ከተረጋገጡት የተከሳሽ መሰረታዊ መብቶች መካከል አንዱ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም በማናቸውም ጊዜ እና ሁኔታ የሚረጋገጥ ሳይሆን ይልቁንም በሕግ በተመለከቱት ምክንያቶች ሊገደብ የሚችል ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካቹ የተከሰሱበት ወንጀል በመሰረቱ የዋስትና መብትን የሚፈቅድ ቢሆንም ተጠሪው የአመልካቹን የዋስትና መብት ጥያቄ የተቃወመው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 (ሀ) የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ሲሆን የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝን በመሻር አመልካቹ ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከታተሉ ውሳኔ የሰጠው ይህንኑ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

የዋስትና ጥያቄን ባለመቀበል በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የሚባልበትን ሁኔታ በተመለከተ በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የቀረበውን ማመልከቻ ፍርድ ቤቱ ያልተቀበለው እንደሆነ ተከሳሹ በቁጥር 182 (1) ለተመለከተው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሃያ ቀን ውስጥ ማመልከቻውን ሊያቀርብ የሚችል ስለመሆኑ በወንጀለኛ ሥነ ሥርዓት ሕጉ በቁጥር 75 (1) ስር ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ ወገን ዋስትናን በመፍቀድ በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ የስነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስርዓት ሕጉ በተለየ ሁኔታ ያካተተው ድንጋጌ የለም፡፡ይህ መሆኑ ግን የስነ ስርዓት ሕጉን ቁጥር 75 (1) ድንጋጌ አነጋገር ዋስትናን በመፍቀድ በሚሰጥ ትዕዛዝ ላይ ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ እንዳያቀርብ ሕጉ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ክልክሏል በሚል አግባብ ለመተርጎም የሚያስችል አይደለም፡፡የዚህ ዓይነቱ አተረጓጎም በስነ ስርዓት ሕጉ ከተመለከተው አጠቃላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት ጋርም የሚጣጣም አይደለም፡፡ይልቁንም የዋስትና መብት በተከለከለ ጊዜ ተከሳሽ ወገን ይግባኝ የማለት መብት ያለው ስለመሆኑ ሕግ አውጪው በቁጥር 75 (1) ለይቶ የደነገገው የዋስትና መብትን መሰረታዊነት ከግምት በማስገባት ለጉዳዩ አጽንኦት ለማስጠት በማሰብ እንደሆነ ከድንጋጌው ይዘት እና በስነ ስርዓት ሕጉ ከተመለከተው አጠቃላይ የይግባኝ መብት መርህ መገንዘብ ይቻላል፡፡በወንጀል ስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 75 (1) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ዋስትናን በመፍቀድ በተሰጠ ትዕዛዝ ላይ የከሳሽን ይግባኝ የማቅረብ መብት በተዘዋዋሪ መንገድ እንደሚከለክል ተደርጎ መተርጎም የሚገባው ስላለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በቀረበለት ተመሳሳይ ጉዳይ በመዝገብ ቁጥር 113436 የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም በዚህ መዝገብ በጭብጥነት ተይዞ ለቀረበው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ትዕዛዝ በመሻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 75 (2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በማረሚያ ቤት በኩል ይደረስ፡፡
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉሚዱክ/ታክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 95157

ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን -ዐ/ህግ ኃ/መለኮት አበበ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- 1. አቶ ቅባቱ ወ/ሰንበት

2. አቶ ኤልያስ አሰፋ -ጠበቃ ተሻገር ደሳለኝ ቀረቡ፡፡

3. አቶ አብርሃ ስዩም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በገቢ ግብር አዋጅ አግባብ የሚቀርበውን የጥቆማ አበል ክፍያ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡

ተጠሪዎች ሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ.ም ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የተሻሻለ ክሣቸው ቢ.ጂ.አይ የተባለው ማህበር ለደንበኞቹ የሚሸጥላቸውን የድራፍት መጠጥ መጠን ለመንግስት አሣንሶ ስለሚገልጽ ደንበኞቹ ሊከፍሉ የሚገባቸውን ግብር እየሠወሩ እንደሚገኙ በጥቆማ መቀበያ ቅጽ ሴሪ ቁጥር 016294 ሕዳር 16 ቀን 2002 ዓ.ም ለአመልካች መስሪያ ቤት እንዳቀረቡለት ፣አመልካችም ጥቆማቸውን መሠረት በማድረግ የግብር ስወራው የሚከናወንባቸው ኮምፒውተሮች፣ ፍላሽ ዲስኮች፣ ዶክሜንቶች የተግባሩ ፈፃሚ ማንነትና እና የ3ኛ ወገኖች የሽያጭ ሁኔታ የሚያሣዩትን እቃዎች አመልካቹ ባደረገው ምርመራ ፍሬ ግብር ወለድና መቀጮን ጨምሮ በጠቅላላ ብር 72,467,971.65 /ሰባ ሁለት ሚሊዮን አራት መቶ ስልሣ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አንድ ብር ከስልሣ አምስት ሣንቲም/ መጠን ያለው ገንዘብ እንዲሠወር ያደረገ መሆኑን ያረጋገጠ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሆን ማህበሩም የወንጀሉ ክስ አመልካቹ እንዲተውለት በማስደረግ ገንዘቡን ግን እንዲከፍል የተደረገ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 እና ሃምሌ 1996 ዓ.ም በወጣው መመሪያ ቁጥር 3.3 መሠረት አመልካቹ ካገኘው ፍሬ ግብር 29,433,465.71 /ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሣ ሶስት ሺህ አራት መቶ ስልሣ አምስት ብር ከሰባ አንድ ሣንቲም/ 20% የጠቋሚ አበል /ሽልማት/ ብር 5,886,693.14 /አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሶስት ብር ከአስራ አራት ሣንቲም/ የሚገባን በመሆኑ እና ከዚሁ ውስጥም አመልካቹ ብር 1,471,672.84 /አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰባ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከሠማኒያ አራት ሣንቲም/ የከፈለን ሲሆን ቀሪው ብር 4,415,020.30 /አራት ሚሊዮን አራት መቶ አስራ አምስት ሺህ ሃያ ብር ከሰላሣ ሣንቲም/ አመልካቹ ይክፈለን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለተጠሪዎች ክስ ሃምሌ 08 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን የሰጠ ሲሆን ዝርዝር ይዘቱም፡-ተጠሪዎቹ ክሣቸውን ከማሻሻላቸው በፊት ያቀረቡት ክስ ቢ.ጂ.አይ ማህበር ግብር ሠውሯል የሚል ቢሆንም ይህ አባባላቸው በመረጃ ያልተደገፈ መሆኑን፣ የ3ኛ ወገኖች ግዢ ማስተላለፊያ ሠነድ የተገኘው በኦዲተሮች እንጂ በተጠሪዎች /ጠቋሚዎቹ/ እንዳልሆነ፣ የተጠሪዎች ጥቆማው ሕጉን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ሽልማቱ እንደማይገባቸው፣ተጠሪዎች በጥቆማቸው ቢ.ጂ.አይ የግብር ስወራ እንደሚያደርግ እንጂ 3ኛ ወገንኖቹ ግብር እንደሚያጭበረብሩ ጥቆማ ያላቀረቡ መሆኑን ዘርዝሮ ተጠሪዎች ሽልማቱ እንማይገባቸው በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ እንዲሁም የተከሳሽ ከሳሽነት ሐምሌ 19/2003 ዓ.ም አሻሽሎ አቅርቧል፡፡ በዚህ ክሱም፡- ተጠሪዎች በስህተት የተሠጣቸውን ገንዘብ ብር 1,471,672.84 እንዲመልሱለት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪዎች በአመልካች በቀረበባቸው ክስ ግንቦት 23 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ መልሣቸው አመልካቹ ተጠሪዎች የሰጡትን ጥቆማ መሠረት በማድረግ የተጭበረበረና የተሰወረ ግብር የሠበሠበ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ክሱን እና የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን በመስማት ተጠሪዎች በሰጡት ጥቆማ መነሻነት ብር 72,467,971.65 ፍሬ ግብር ወለድና መቀጮ መሠብሠቡን አመልካች የሚክደው ባለመሆኑና ከዚህ ውስጥም ብር 29,433,456.71 ፍሬ ግብር ሲሆን አመልካቹ ለተጠሪዎቹ ብር 1,471,672..84 የከፈለ በመሆኑ ይህም አመልካች በተጠሪዎቹ ጥቆማ እምነት ያሣደረ መሆኑን እንደሚያሳይ፣ አመልካቹ በጠቋሚዎቹ መረጃ መሠረት ከሚሠበሠበው ግብር 20% ለጠቋሚቹ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ሕግ የሚያስገድደው መሆኑን በምክንያትነት ይዞ አመልካቹ ያቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ባለመቀበል ቀሪውን የጥቆማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አበል ገንዘብ ብር 4,415,020.30 ለዳኝነት ከከፈሉት ከ5% የጠበቃ አበልና ሌሎች ወጪና ኪሣራ በቁርጥ ብር 5000.00 ጋር አመልካቹ ለተጠሪዎች ሊከፍላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፈዬራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በጉዳዩ ላይ በስር ፍርድ ቤት የተሠጠው ውሳኔ የፍሬ ነገርም ሆነ የህግ ስህተት የለበትም በሚል ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የስር ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን የክስ እናሻሽል ጥያቄ የተቀበለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 91 ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማ ውጪ መሆኑን፣የተጠሪዎች ክስ በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን፣ግብሩ የተሰበሰበው በተጠሪዎች ጥቆማ መነሻ ሳይሆን በአመልካች መስሪያ ቤት ባለሙያዎች ጥረት መሆኑን፣ተጠሪዎች የሠጡት ጥቆማ በሕጉ አግባብ የጠቋሚ አበል የማያሰጥ መሆኑን ያሳያሉ ያላቸውን ምክንያቶችን በሰፊው ዘርዝሮ የተጠሪዎች የጠቋሚ ገንዘብ ይከፈለን ጥያቄ ውድቅ መሆን እና ያላግባብ የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ መወሰን ሲገባ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ከ5% የጠበቃ አበልና ከሌሎች ወጪዎች ጋር እንዲከፈላቸው መወሰኑ በሕግና በማስረጃ አግባብ ባለመሆኑ ውሳኔው ሊሻር ይገባዋል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎች እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዙትን ነጥቦች ተመልክተናል፡፡
ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ተለይተው ከተያዙት ጭብጦች አንዱ የተጠሪዎች የክስ ማሻሻል ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 91 ድንጋጌ አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ በመሰረቱ ፍርድ ቤት አንድ ተከራካሪ ያቀረበውን ክስ እንዲያሻሽል ትዕዛዝ የሚሰጥባቸው ምክንያቶች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 91 ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ ከሣሽ ያቀረበውን ክስ እንዲያሻሽል ትዕዛዝ የሚሰጠው ከሣሽ ያቀረበው ክስ ጉዳዩን ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እንደሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር አንቀጽ 91 ንኡስ አንቀጽ 1 ስር ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ/ም ያቀረቡትን ክስ አብራርተው ለማቅረብ ይፈቀድላቸው ዘንድ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቱን ጠይቀው ፍርድ ቤቱም የተጠሪዎችን ጥያቄ በመቀበል ተጠሪዎች ሰኔ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ክሳቸውን አሻሽለዋል፡፡ ተጠሪዎች አስቀድመው ባቀረቡት ክስ ቢ.ጂ.አይ ግብር እንዲሰወር ያደርጋል በማለት የገለፁትን የክሱን ፍሬ ነገር በተሻሻለው ክስ ደግሞ ይኼው ቢ.ጂ.አይ የተባለው የአክሲዩን ማህበር የቢራና ድራፍት ምርቶችን በሚሸጥበት ወቅት የሽያጭ ዝርዝሩን ለአዲስ አበባ ፋይናንስ ቢሮ ሲያስተላልፍ እውነተኛውን የሽያጭ መጠን ሳይሆን አሳንሶ ስለሚያቀርብ መንግስት ማግኘት ያለበትን ግብር እንዳይሰበስብ ሆኗል የሚለውን የክሱን ፍሬ ነገር በማካተት ክርክራቸውን ማቅረባቸውን የክርክሩ ሒደት ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ ክሱ እንዲሻሻል ተደርጎና በአመልካች በኩል ደግሞ ተገቢ ነው የተባለው ተቃውሞ ቀርቦ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ያለውን ብይን በመስጠት ታህሳስ 27 ቀን 2004 ዓ/ም ክሱ ሲሰማም ሆነ ሰኔ 29 ቀን 2004 ዓ/ም ምስክሮች ሲሰሙ በተጠሪዎች የተሻሻለ ክስ የተጠቀሰው ፍሬ ነገር መሰረት ተደርጎ ክርክሩ መመራቱንና በማስረጃዎቹ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር መሰረት ተደርጎ ዳኝነት መሰጠቱን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ ጥቆማ አድርገናል በማለት ሊከፈላቸው የሚገባውን የጠቋሚ ገንዘብ ተገቢውን የክስ ምክንያትና የክሱ ፍሬ ነገር በክሳቸው ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ እንዲያቀርቡ ሊፈቀድ እንደሚችልና የክሱ መሻሻል መሰረታዊ አላማም ጉዳዩን ለመወሰን አስፈላጊ ሁኖ መገኘት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 91 ስር የተመለከተ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከርበትና በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገው ነጥብ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ተጠሪዎች የጥቆማ አበል እንዲከፈላቸው የሚያስችሉ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ባላቀረቡት ክስ አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪዎቹ የግብር መሠወር ተግባር ፈጽሟል በማለት ጥቆማ ያቀረቡት በቢ.ጂ.አይ ላይ እንጂ በ3ኛ ወገኖች ላይ ባለመሆኑ የጥቆማ ፎርሙ ይዘትና የተጠሪዎች ጥቆማ አይስማማም፣ የተሠወረው ገንዘብ የተገኘው በአዲተሮቹ ጥረት ነው በማለት ቢከራከርም የአመልካች የ"ኢንተለጀንስ" ባልደረቦች የሆኑት እነ ቁምላቸው ሻምበል ስሜነህ ለሥር ፍ/ቤቱ ቀርበው በሰጡት ምስክርነት ተጠሪዎቹ በወቅቱ ያቀረቡት ጥቆማ ቢ.ጂ.አይ ለደንበኞቹ የሚያቀርብላቸውን የመጠጥ መጠን በመቀነስ ለአመልካቹ ሪፖርት ስለሚያደግ የግብር ስወራ እንደተደረገ የሚገልጽ ነው፣ የመጠቆሚያው ፎርም የጥቆማው ይዘት መዘርዘሪያ በጣም አጭር በመሆኑ በአጭሩ በመፃፉ የተጠሪዎቹ ዝርዝር የጥቆማ ይዘት ለማስፈር እንደሚያስቸግር፣ በተጠሪዎች ጥቆማ መሠረት ኦፕሬሽን መካሄዱን በግልጽ እንደሚያሳይ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ ስልጣን ያለው ይግባኝ ሰሚው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይህንኑ የፍሬ ነገር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ ተቀብሎታል፡፡ ይህ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ድምዳሜ የሚያስገነዝበውም ተጠሪዎች የሰጡት ጥቆማ በእርግጥም ለምርመራው መነሻ ሁኖ መንግስት ሊሰበስበው የሚገባውን ግብር ለመሰብሰብ ያስቻለ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የተጭበረበረው ገንዘብ የተገኘው በኦዲተሮች ጥረት ነው በማለት አመልካቹ ያቀረበው ክርክር የተጠሪዎች ጥቆማ ለኦዲት ምርመራ መነሻነቱ ያልተካደ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡አመልካቹ የተጭበረበረ ግብሩን የሠበሠበው ተጠሪዎቹ ባቀረቡት ጥቆማ መሠረት መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ይህን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ደግሞ ይህ ችሎት የማይቀበልበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ዲፕብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡የሥር ፍ/ቤቱ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች የጠየቁት ቀሪ የጠቋሚ ገንዘብ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ተገቢነት ያለውና የሕጉንም አላማ የሚያበረታታ ሲል ይግባኝ ሰሚ ችሎት መደምደሙም በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ከሕጉ ጋር ያገናዘበ ነው፡፡

ወደ ህጉ ስንመጣም በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 84(1) እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ገቢውን በሚደብቅ፣አሳንሶ በሚያስታውቅ፣በሚያጨበርብር ወይም በማናቸውም መንገድ ግብር ሳይከፍል በሚቀር ግብር ከፋይ ላይ በተጨባጭ መረጃ በመደገፍ ሪፖርት የቀረበ እንደሆነ የተደበቀው ግብር እስከ 20% ድረስ ግብሩ ሲሰበሰብ ሲጠቃለልም በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ላይ ዳኝነት የሠጡት የግራ ቀኙን ክርክር በሕጉ አግባብ በመምራትና ፍሬ ነገሩን በሚገባ በማጣራት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን እንደሚከፈል ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 96 ድንጋጌ ሲታይ ሕግን በመጣስ የሰበሰበውን ግብር ያላሣወቀ ወይም የሚፈለግበትን ግብር ያልከፈለ ወይም መንግስትን ለማጭበርበር በማሠብ የማይገባውን ተመላሽ ታክስ የጠየቀ ማናቸውም ሰው ወንጀል እንደፈፀመ እንደሚቆጠርና የወንጀል ተጠያቂነትንም እንደሚያስከትል ከአዋጁ አንቀፅ 49 ጋር ተዳምሮ ሲነበብ ያስገነዝባል፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይም የተጠሪዎች ጥቆማ ቢ,ጂ.አይ የተባለው አክሲዩን ማህበር በ3ኛ ወገኖች ሊከፈል ይገባ የነበረውን ግብር እንዳይከፈል የሚያደርግ ተግባር መፈጸሙና በተለይም ራሱ አክሲዩን ማህበሩ የወንጀል ክስ እንዲቀርስት ተደርጎ ሳይከፈል ቀርቷል የተባለውን ግብር መክፈሉ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርበውን ክርክር ለመቀበል የሚያስችል የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶቹ ፍሬ ነገሩን አጣርተው ማስረጃውን መዝነው የደረሱበት ድምዳሜ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 84 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን የህጉን ይዘት፣መንፈስና መሰረታዊ አላማ ያገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በከ/መ/ቁጥር 99932 የካቲት 08/2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 88152 መስከረም 28 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች ብር 4,415,020.30 /አራት ሚሊዮን አራት መቶ አስራ አምስት ሺህ ሃያ ብር ከሰላሣ ሣንቲም/ ከ5% የጠበቃ አበል ጋር ይክፈል፣ተጠሪዎች ብር 1,471,672..84 ለአመልካች ሊመልሱ አይገባም ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

ትእዛዝ

- ታህሳስ 14 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ 112032

ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተክሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጠታ

አመልካች፡- 1ኛ የኑስ አህመድ } የቀረበ የለም

2ኛ. ግዛቸው አየለ }

ተጠሪ ፡- የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓቃቤ ህግ ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት

ዓ/ህግ ኤርሚያስ ታደሰ - ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በቤንሻንጉል ጉምዝ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአሁኑ ተጠሪ ከሳሽነት ነው፡፡ አመልካቾች ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የስር ፍ/ቤቶች ያስተላለፉት የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ መሰረታዊ ይዘቱ፡- አመልካቾች ህጋዊ ፈቃድ ከሌለ በስተቀር በግለሰብ መያዝም ሆነ ማዘዋወር የተከለከለ በቁጥር 903 /ዘጠኝ መቶ ሶስት / ህገ ወጥ የከሳሽ ጥፋት በሁለት ማዳበሪያዎች ቋጥረው በጉዞ ሻንጣ ውስጥ በመክተት ንብረትነቷ የ2ኛ አመልካች የሆነችው የታርጋ ቁጥር ኮድ 2-0705 ቤጉ በሆነች የሞተር ሳይክል በመጫን ከአል መሃል አቅጣጫ ወደ መንጉሻ አቅጣጫ በማንዣዝ ላይ ሳሉ በቀን 03/11/2006 ዓ/ም ከቀኑ በ11፡30 አካባቢ ማንኩሻ ላይ እጅ ከፍንጅ በመያዛቸው 1ኛ ተከሳሽ /አመልካች/ የህገ ወጥ ዕቃ ባለቤት 2ኛ አመልካች የሞተር ሳይክሉ አሽከርካሪ በመሆን በፈጸሙት ህገ ወጥ ዕቃ መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈጸሙት የኮንትሮባንድ ወንጀል የወ/ህ/ቁ/32/1/ሀ/ እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ የተመለከተውን ወንጀል ተላልፏል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ፍርድ ቤት ቀርበው የተጠሪ ክስ እንዲደርሳቸው ተደርጎ ስለጉዳዩ እምነት ክህደት ተጠይቀው 1ኛ አመልካች እንደ ተጠሪ /ዓቃቤ ህግ/ ክስ አቀራረብ ማመኑ በማስመዝገብ ጥፋተኛ ነኝ ያለ ሲሆን 2ኛ አመልካች መካዱ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው ተሰምቷል፡፡ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው በሰጡት የምስክርነት ቃል የ1ኛ አመልካች መሆኑን የተረጋገጠው 903 ጥይት በ2ኛ አመልካችም ሞተር ሳይክል ተጭኖ ሲመጣ ኬላ ላይ መያዙን አስረድቷል፡፡ 2ኛ አመልካች እንዲከላከል ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም የመከላኪያ ማስረጃ እንደ ሌለው በመግለጽ ፍ/ቤቱ በቀረበው ማስረጃ እንዲሁም 1ኛ አመልካች ቀድሞ በሰጠው የእምነት ቃል መሰረት በማድረግ ሁለቱም አመልካቾች በተከሰሱበት የህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት መዝግበዋል፡፡ በተጠሪ /የዐቃቤ ህግ/ በኩል የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ ሆኖ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በእርከን 28 ስር ቅጣት እንዲወሰን፤ መቀጮም እንዲወሰን፤ ንብረቱ እንዲወርስ ጠይቋል፡፡ አመልካቾቹም የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች መሆናቸው ግምት ውስጥ እንዲገባ አመልክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የወንጀል ድርጊቱ በሀገሪቱና በህዝብ ደህንነት ላይ አደጋ የሚጥል ስለመሆኑ ድርጊቱም ሆን ተብሎ የተፈጸመ በመሆኑ በከባድ ደረጃ መድቦታል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ ሆን ተብሎ መፈጸሙ፤ አመልካቾች ድርጊቱን በስምምነት መፈጸማቸው ሁለት ማክበጃ ምክንያት እንደሆነ፤ በአመልካቾች በኩል 1ኛ የዘወትር ጸባያቸው መልካም መሆን፤ 2ኛ ድርጊቱ የፈጸሙት ከህግ እውቀት ማነስ መሆኑ 1ኛ አመልካች የወንጀል ድርጊቱ ማመኑ 3ኛ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን በቅጣት ማቅለያነት ተይዘላቸዋል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተሰኙበት ወንጀል ከ7 ዓመት እስከ 15 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና የወንጀል ድርጊቱም በከባድ ደረጃ በመመደቡ የቅጣቱ መነሻ እና መድረሻ ለአራት እኩል ሲከፈል ከ11 ዓመት -13 ዓመት ጽኑ እስራት ባለው ፍቅድ ስልጣን በማካተት የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 29 እንደሆነ በመለየት ሁለት ማክበጃዎች በመውሰድ እርከን 31 የወደቀ ሲሆን በአመልካቾች በኩል እያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ማቅለያዎች የተያዘላቸው በመሆኑ በእርከን 28 ከተደነገገው ቅጣት 1ኛ አመልካች 10 ዓመት 2ኛ አመልካች 9 ዓመት ጽኑ እስራት፤ እንዲሁም በመቀጮ ረገድ የወ/ህ/ቁ/ 90/2/ መሰረት በማድረግ እያንዳንዳቸው 6670 ብር እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በኢግዚቢትነት የተያዘው ጥይት እንዲሁም የወንጀል መፈጸሚያ የተባለው ሞተር ሳይክል ለመንግስት ውርስ ይሁን በማለት አዟል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ በሰበር እንዲመረመር በመቅረቡ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ አመልካቾች የስር ፍ/ቤት ወንጀሉ በከባድ ደረጃ መመደቡ እና የቅጣት ማቅለያዎች አያያዝ ላይ የፈጸመው ስህተት እንዲታረምላቸው ሲጠይቁ፤ ተጠሪ በበኩሉ የስር ፍርድ ቤት የወንጀል ድርጊት አፈፃጸም መሰረት በማድረግ በከባድ ደረጃ መድቦ ቅጣት መወሰኑ በአግባቡ ነው የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥ በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ጭብጦች 1ኛ አመልካቾች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው በቀድሞ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ነው ወይስ በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168/2/ 2ኛ የስር ፍርድ ቤቶች የወንጀል ድርጊቱ ከባድ በማለት መመደባቸው በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? 3ኛ በስር ፍርድ ቤት እንደ ቅጣት ማክበጃ የተወሰዱ ነጥቦች የህግ መሰረት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚሉ ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

ከስር የክርክር ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካቾች 1ኛ አመልካች ገደብ የተደረገበት /ህገ ወጥ/ ጥይት ባለቤት፤ 2ኛ አመልካች ንብረቱ የጫነችው ሞተር ሳይክል ባለቤትና ሹፌር በመሆን በ03/11/2006 ዓ/ም ከቀኑ 11፡30 ሰዓት በመንኩሻ ከተማ መግቢያ እጅ ከፍንጅ እንደተያዙ፤ 1ኛ አመልካች ሙሉ በሙሉ ማመኑ፤ 2ኛ አመልካችም የዐ/ህግ ክስና ማስረጃ አለማስተባበሉን የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ስልጣኑ ከድምዳሜ ላይ የደረሰ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንደተቀበለው ነው፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የስር ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር ማጣራት እና ማስረጃ ምዘና ስርዓት እንዳለ የሚቀበለው ነው፡፡ ምክንያቱም ችሎቱ በህግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች ማረም ስለመሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር ማጣራት እና ማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ይዘን ከላይ የተመለከቱት ጭብጦች ከህግ አንጻር እንደሚከተለው መርምረናል

<u>የመጀመሪያው ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> አመልካቾች ጥፋተኛ የተሰኙት የኮንትሮባንድ ወንጀል በመፈጸም ነው፡፡ ይህ ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 622/ 2001 አንቀጽ 91/2/ ስር የተመለከተ ሲሆን የሚያስቀጣው በእቃዎቹ ላይ ሊከፍል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር የሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከ7 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም ይህንን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት በማድረግ 1ኛ አመልካች በ10 አመት 2ኛ አመልካች በ9 አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 ተሽሮ በአዋጅ ቁጥር 859/2007 ተተክቷል፡፡ የአመልካቾች የክስ ሂደት እስከ ሰበር ደረጃ ደርሶ ሳይጠናቀቅ አዲስ አዋጅ የወጣ ሲሆን በዚህ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168/2/ መሰረት የኮንትሮ ባንድ ወንጀል የፈጸመው ግለሰብ ከሶስት ዓመት በማያንስና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና በብር 50 ሺህ በማያንስና ከብር 100,000 የማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል፡፡ በተሻረው እና በአዲሱ አዋጅ በአመልካቾች ላይ በሚጣለው እስራት እና መቀጮ መሰረታዊ ልዩነት እንዳለው ከድንጋጌዎቹ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ወንጀሉ ሲፈጸም ስራ ላይ ከነበረው ህግ ይልቅ የኋላኛው /አዲሱ/ ህግ ቅጣት የሚያቃልለት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ /አመልካቾች/ የተሻለው ህግ ተፈፃሚ እንደሚያደርግ ከወ/ህ/ቁ/ 6 እና ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 /2/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የተቀጡት በነባሩ /የቀደም/ አዋጅ ከመሆኑ አንፃር በቅጣት ረገድ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው አዋጅ ቁጥር 859/2007 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168/2/ ስር ነው ብለናል፡፡

<u>ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> የስር ፍ/ቤት የግራቀኙ የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኃላ የወንጀል ድርጊቱ ክብደትና አፈፃጸም መሰረት በማድረግ ቀላል /ዝቅተኛ/ ተብሎ እንዲመደብ ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ዓቃቤ ህግ እንዳለው በመካከለኛ ደረጃ ሊመደብ እንደሚገባ ተከራክሯል፡፡ በመሰረቱ ደረጃ ያልወጣላቸው ወንጀሎች የወንጀል ደረጃ እና የቅጣት መነሻ እርከን በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 19 ስር በተመለከቱት መስፈርቶች መሰረት እንዲሁም ፍ/ቤቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19/5/ የተመለከቱት መመዘኛዎች ብቻ ሳይታጠር ሌሎች መስፈርቶች ተጠቅሞ የወንጀሉ ደረጃ እንደሚመደብ በአንቀጽ 19/6/ ስር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የወንጀሉ አይነትና ክብደት አፈፃጸም፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ መዝኖ ከባድ ነው ማለቱ የሚነቅፍ ሆኖ አልተገኘም ፡፡ አመልካቾች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

<u>3ኛ ጭብጥ በተመለከተ</u> ፡- የስር ፍርድ ቤት ቅጣት ሲወሰን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ከግራ ቀኙ የመዘገበ ሲሆን ዐ/ህግ የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ እንዲሆን ከመጠየቅ ውጭ ፍ/ቤቱ እንደ ማክበጃ የወሰዳቸው 1ኛ የወንጀል ድርጊቱ ሆነ ተብሎ መፈጸሙ፤ 2ኛ የወንጀል ድርጊቱ በህብረት ስምምነት የተፈጸመ ነው በማለት የወንጀል ህግ አንቀጽ 84/1/ሀ/ እና /መ/ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካቾች ጥፋተኞች የተሰኙበት አዋጅ ቁጥር 168/2/ ስር እንደተመለከተው ድርጊቱ የተፈጸመው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው በማለት የተደነገገ ሲሆን የስር ፍ/ቤት የወንጀል ህግ አንቀጽ 84/1/ሀ/ በመጥቀስ እንደማክበጃ መውሰዱ የድንጋጌው መሰረታዊ ይዘት ያላገናዘበ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ተረድተናል፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት የወንጀል ድርጊቱ በስምምነት የተፈጸመ ነው በሚል እንደ ማክበጃ የወሰደው ቢሆንም በወንጀል ህግ አንቀጽ 37 /1/ እና 84/1/መ/ እንደተመለከተው ወንጀል ለመስራት አስቀድመው በመስማማት /Prior meeting of mind/ የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈጸማቸው የሚያሳይ ሳይሆን 1ኛ አመልካች የህገ ወጥ ዕቃ ባለሌት 2ኛ አመልካች ደግሞ የሞተር ሳይክል ባለቤት በመሆን የኮንትሮባንድ ዕቃው መጫኑን ከመረጋገጡ ውጭ ወንጀሉን ከመጀመሪያው አቅደው ፤ጊዜ እና ሁኔታ አመቻችተው ስለመፈጸማቸው በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ እንደ ህጉ አነጋገር ቅጣት የሚያከብዱ ሁኔታዎች ሳይኖሩ ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መውሰዱ የህግ መሰረት የለውም ብለናል፡፡

በመጨረሻ መታየት ያለበት ጉዳይ ቅጣት ነው፡፡ በተጠሪ በኩል በህግ አግባብ ተቀባይነት ያለው የቅጣት ማክበጃ አልቀረበም፡፡ በአመልካቾች በኩል ሶስት ሶስት የቅጣት ማቅለያዎች ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ አመልካቾች ጥፋተኛ የተሰኙበት አዋጅ ቁጥር 859/2007/ አንቀጽ 168/2/ 3-5 ዓመት ጽኑ እስራት በገንዘብ ረገድ ደግሞ ከ50,000-100,000 ብር የሚያስቀጣ ነው፡፡ የወንጀሉ ደረጃ ከባድ የተባለ በመሆኑ የቅጣት መነሻና መድረሻ ለአራት እኩል ሲከፈል የከባድ ወንጀል ከ4 ዓመት እስከ 4 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 26/2/ሐ/ መሰረት መነሻ ቅጣት በሁለት እርከኖች ስር የሚወድቅ ከሆነ ዝቅ ብሎ ያለው የሚያዝ በመሆኑ በአንቀጽ 19/1/ በመመልከቱ በእርከን 18 ስር ይወድቃል፡፡ ፍ/ቤቱ በተሰጠው ፍቃድ ስልጣን መነሻ ቅጣቱ 4 ዓመት ጽኑ እስራት በመያዝ የቅጣት ማቅለያዎች ተመልክተናል፡፡ በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅሊያ አንድ እርከን ዝቅ የሚል በመሆኑ ቅጣቱ በሶስት እርከን ዝቅ የሚል በመሆኑ በእርከን 15 ይካተታል፡፡ መቀጮ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የወ/ህ/ቁ/90/2/ መሰረት በማድረግ እያንዳንዳቸው ብር 6670 እንዲቀጡ ወስነናል፡፡ ይህ ችሎትም አዲሱ አዋጅ በዚህ ረገድ አመልካቾች የማይጠቀም በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የወሰነው መቀጮ እንዳለ ተቀብሎታል፡፡

ቅጣት ሲወሰን የወንጀል ህጉ ዓላማ ግብ የሚያሳካ መሆን እንዳለበት በወንጀል ህግ አንቀጽ 1 እና 87 በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካቾች የተፈጸመው ወንጀል ክብደት በህ/ሰብ/ ሊያደርስ የሚችለው አደጋ በአንድ በኩል፤ የአመልካቾች የመታረም ዕድል በሌላ በኩል ግምት ውስጥ በማስገባት አመልካቾች የሚያረምና የሚያስተምር እንዲሁም መሰል ወንጀል ፈፃሚዎች የሚያስጠነቅቅ ነው ብለን ያመንበት በእርከን 15 በተመለከተው ፍቃድ ስልጣን ስር በመሆን እያንዳንዳቸው 2 አመት ከ9 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ በመለየት እና ሁለቱ ፍርድ ቤት የቅጣት ማክበጃዎች አወሳሰድ ላይ የፈጸሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የስር መተከል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 10407 በ28/11/2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድና ቅጣት፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/05758 በ06/05/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 195/2/ለ/2/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾች ጥፋተኛ መሆን ያለባቸው በአዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 168 /2/ ስር ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካቾች በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ካለ በእስራት ቅጣቱ የሚካተት ሆኖ እጃቸው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ እያንዳንዳቸው በ2 አመት ከ9 ወር /ሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር/ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡ አመልካቾች የሚገኙበት ማረሚያ ቤት በተሻሻለው የእስራት ቅጣት መሰረት ያስፈጽሙ ብለናል፡፡ የእስራት ቅጣቱ መሻሻሉ አመልካቾች ባሉበት ማረሚያ ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
4. በስር ፍ/ቤት የተወሰነው መቀጮ እና የንብረት ውርስ የተመለከተ የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጽኑነት ሥልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 97083

ሚያዝያ 14 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ገኣትኮ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡-የትግራይ ክልል መንገድ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ -አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 60677 ታህሳስ 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የዳኝነት ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. አመልካች/ከሳሽ/ ተከሳሽ /ተጠሪ/ በሚካሄደው ጨረታ ለአንድ ዓመት እንዳልሣተፍ ከህግ ውጭ ዕገዳ ጥሎብኛል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ በፍርድ ተጣርቶ እገዳው እንዲነሳ ይወሰንልኝ በማለት ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካች በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ድርጅት በመሆኑ ጉዳዩ ሊቀርብ የሚገባው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተደራቢ የዳኝነት ሥልጣን ላለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው የሚል መቃወሚያና ሌሎች መከረከሪያዎችን አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪን መቃወሚያ በማለፍ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስራጃ ከመዘነ በኃላ ተጠሪ በሚያካሄደው ጨረታ አመልካች ለአንድ ለአመት ያህል እንዳይሳተፍ የሠጠው ዕገዳ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ይነሳ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት የተጠሪን ይግባኝ ሰርዞታል፡፡

2. ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ አመልካች በፌዴራል መንግስት ተመዝግቦ የተቋቋመ የንግድ ድርጅት ነው፡፡ በፌዴራል መንግስት ተመዝግቦ የተቋቋመ የንግድ ድርጅት ተካፋይ የሆነበትን ክርክር በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የፌዴራል ፍርድ ቤት ነው፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጉዳይ በዳኝነት አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው ተደረቢ ወይም በውክልና የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን የለውም፡፡ በማለት የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡
3. አመልካች ጥር 21 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አመልካች ቅርንጫፍ ከፍቶ በሚነግድበት ቦታ እንዲመዘገብ የሚያስገድድ በመሆኑ አመልካች ቅርንጫፍ በከፈትኩበት መቀሌ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በመዝገብ ቁጥር 0041/2003 ተመዝግቤ የንግድ ምዝገባ ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠኝ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት አመልካች በፌዴራል የተቋቋመ የንግድ ድርጅት ነው የሚለውን ብቻ በመመልከት የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዳኝነት የማየት ሥልጣን የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በመቀሌ ቅርንጫፍ ከፍቶ የሚነግድ መሆኑ መመዝገቡ የክልል የንግድ ተቋም አያደርገውም፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው መልስ መጋቢት 8 ቀን 2006 ዓ/ም በፅሁፍ አቅርቧል:: አመልካች ሚያዚያ 3 ቀን 2006 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራቀኙ የቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ በሰበር አጣሪ ችሎት አመልካች የቀረበውን ክስ የወረዳው ፍርድ ቤት በዳኝነት አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም በማለት የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የመመሥረቻ ፅሑፍ መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች በንግድ ሕጉና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የሕግ ማዕቀፎች የተደነገጉትን መስፈርቶች አሟልቶ ለፌዴራል መንግስት በማቅረብ፣ በፌዴራል መንግስት ህጋዊ ዕውቅና ተሰጥቶት የተመዘገበ የንግድ ድርጅት መሆኑን በመካድ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ አመልካች የመመሥረቻ ፅሑፉን መተዳደሪያ ደንቡንና ሌሎች ህጋዊ ሕልውና ለማግኘት አስፈላጊ የሆነ ፎርማሊቲዎች በማሟላት፣ በፌዴራል መንግስት ህጋዊ ህልውና ያለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ድርጅት መሆኑ አከራካሪ ካልሆነ፣ አመልካች በመቀሌ ከተማ ቅርንጫፍ በመክፈቱ በአዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት በንግድ መዝገብ መመዝገቡ የአመልካችን የክልል የንግድ ድርጅት ወይም የክልልና የፌዴራል ህጋዊ ሰውነት ያለው የንግድ ድርጅት የሚያደርገው አይደለም።

6. ማንኛውም ሰው በንግድ መዝገብ የሚመዘገበው ዋና መሥሪያ ቤቱ ባለበት ሥፍራ መሆኑንና ማንኛውም ሰው በተለያዩ ክልሎች የተለያየ ንግድ ሥራ በሰራም በንግድ መዝገብ የሚመዘግብ የሚመዘገበው አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 686 /2002 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል። በአዋጅ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 የተለያያ ቅርንጫፍ ያለው የንግድ ድርጅት ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቱ በሚገኝበት ስፍራ ላለው መዝጋቢ መሥሪያ ቤት አግባብነት ያለውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላትና የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ በማያያዝ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን አድረሻና ልዩ የምዝገባ የመለያ ቁጥር የማሳወቅ ግዴታ የተጣለበት ሲሆን፣ አዋጁ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 ያጣለው ይህ ግዴታ በፌዴራል መንግስት ህጋዊ ዕውቅና ተሰጥቶት የተቋቋመን የንግድ ድርጅት የክልል የንግድ ተቋም ወይም የክልልና የፌዴራል ህጋዊ ሰውነት ያለው የንግድ ድርጅት የማድራግ ህጋዊ ውጤት የለውም።

7. በአዋጅ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 4 የተቀመጠውና ቅርንጫፍ የማሳወቅ ግዴታ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ከፍቶ የሚነግድ የፌዴራል ወይም የክልል የንግድ ድርጅት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን ከፍቶ የንግድ ሥራ በሚሠራባቸው ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች የሚሠራው ሥራ ህጋዊ ህልውናና የንግድ ፈቀድ ካገኘበት የንግድ ሥራ ጋር ተመሣሣይ መሆኑን ለመረጋገጥና ቅርንጫፎቹ ጎጅና ተገቢ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር መሆኑ የአዋጅን አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 4 እና የአዋጅን አንቀፅ 3 ድንጋጌዎች በጣምራ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል። ከዚህ በተጫማሪ የንግድ ድርጅቱ ቅርንጫፍ በከፈተባቸው ሥፍራ ያሉ መዝጋቢ አካለት፣ ቅርንጫፍ የሚመዘግቡት በአዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ሚኒስትር በሚሰጣቸው ውክልና መሠረት መሆኑ ተደንግጓል። በመሆኑም አመልካች በመቀሌ ከተማ ቅርንጫ ስለከፈትኩና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ በመቀሌ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ያልተመዘገበ በመሆኑ እንደ አንድ የክልሉ የንግድ ድርጅት ስለምቆጠር የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው በማለት ያቀረበውን ክርክር የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም።

8. አመልካች በመቀሌ ከተማ ቅርንጫፍ ከፍቶ የንግድ ሥራ መሥራቱና ቅርንጫፉ በመቀሌ ከተማ ንግድና እንዱስትሪ ቢሮ የንግድ መዝገብ የተመዘገበና ፈቃድ የተሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑ አመልካች በፌዴራል መንግስት የተቋቋመ የንግድ ድርጅት በመሆኑ ላይ የሚያሳድረው ለውጥ የለም ከተባለ በፌዴራል መንግስት ዕውቅና የተቋቋመ የንግድ ድርጅት ተካፋይ የሆነበትን ክርክር በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 6 ተደንግጓል፡፡ በክልል የዳኝነት ሥልጣናቸው በተደራቢነት የፌዴራል ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 4 የተሰጣቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ናቸው፡፡

9. አመልካች ለወረዳ ፍርድ ቤት ክስ የቀረበበት ጉዳይ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተደራቢ የዳኝነት ስልጣን ላለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ መወሰን ሲገባው በወረዳው ፍርድ ቤት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 (2) የሚጥስ መሆኑን በመረጋገጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሻረው በህግ አግባብ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል ፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ግራቀኙ ለያራሳቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.100290

ሚያዝያ 1 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ መሰረት አለማየሁ - ጠበቃ መላኩ አየነው

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ እሙሽት ሙሉጌታ - ጠበቃ አባይነሽ ማሙዬ ቀረቡ
2. አቶ ፀጋዬ ደመቀ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጋር በአሜሪካን አገር የተፈጸመ ጋብቻ መኖሩን ያስረዳልኛል በማለት ያቀረቡት የጋብቻ ማስረጃ በአዋጅ ቁጥር 334/2004 አንቀጽ 26(1) ድንጋጌ መሰረት በአሜሪካን አገር በሚገኘው የኢትዮጲያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ያልተረጋገጠ እና ወደ አገር ውስጥ ከገባ በኃላም ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ መሰረት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቀርቦ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካቿ የዚህ ዓይነቱን ሰነድ መሰረት በማድረግ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ መሰረት ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ከጋብቻ እና በጋብቻው የተፈራ ነው ከተባለ ንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ ጉዳይ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ክስ አቅርበው ውሳኔ ማሰጠታቸውን፣በጋብቻው ውስጥ የተፈራ ነው ተብሎ ውሳኔ ካረፈበት ንብረት ውስጥ አንዱ በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኝ ባለሶስት ፎቅ ሕንጻ መሆኑን፣የአሁኗ አመልካችም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ መሰረት መቃወሚያ ያቀረቡት በዚሁ ውሳኔ ላይ መሆኑን፣በ20/02/2006 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ አጭር ይዘትም:- ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጋር በአሜሪካን አገር በ1993 ዓ.ም. ጋብቻ መስርተው አንድ ልጅ እንዳፈሩ፣1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር አብሮ ከመኖር በቀር የፈጸሙት ጋብቻ እንደሌለ፣ተጠሪዎቹ በጋብቻ ያፈሩት ነው የተባለው በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኝ ባለሶስት ፎቅ ሕንጻም የተሰራው በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ የጋራ ገንዘብ እና አመልካች ከአሜሪካን አገር በላኩት ገንዘብ እንደሆነ የሚገልጽ ሆኖ ሕንጻው ለአመልካቿ እና ለ2ኛ ተጠሪ እኩል ከተካፈለ በኃላ 1ኛ ተጠሪ ከፈለጉ ከ2ኛ ተጠሪ ድርሻ እንዲካፈሉ እንዲደረግ እና 2ኛ ተጠሪ የልጅ ቀለብ እንዲከፍሉ የተጠየቀበት መሆኑን፣1ኛ ተጠሪ በመቃወም አቤቱታው ላይ በሰጡት መልስ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተፈጸመ ጋብቻ አለመኖሩን እና የጋብቻ ማስረጃ ነው ተብሎ የቀረበው ሰነድም በአሜሪካን አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ያልተረጋገጠ እና ወደ አገር ውስጥ ከገባ በኃላም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቀርቦ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አለመሆኑን በመግለጽ መከራከራቸውን፣2ኛ ተጠሪ በመቃወም አቤቱታው ላይ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ ስለመሆኑ በብይኑ ላይ የተገለጸ ነገር አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካቿ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው በመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ የማስተናገድ ስልጣን የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው ወይስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው? የሚለውን ነጥብ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11 (2) (ሀ) አንጻር እንዲሁም አመልካች በማስረጃነት ያቀረቡትን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ የሰጠውን ማረጋገጫ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት ስለማረጋገጫው ሕጋዊነት ጉዳይ በአግባቡ አጣርተው መሆን አለመሆኑን ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመቃወም አቤቱታውን አስተናግዶ ብይን የሰጠው ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን ኖሮት ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የስረ ነገር ስልጣን ጉዳይ በተከራካሪ ወገኖች ባይነሳም ማንኛውም ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ አስተናግዶ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጣን ያለው መሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት መሆኑ፣ስልጣን የሌለው በሆነ ጊዜ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 9(1) እና 231(1)(ለ) እንደተመለከተው ተገቢውን ትዕዛዝ ወይም ብይን ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑ እና የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን የሚያረጋግጠውም በክስ ማመልከቻው ላይ ከተገለጸው ዝርዝር መሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡በሌላ በኩል አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ክስ የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆኑን አረጋግጦ ጉዳዩን ማስተናገድ በቀጠለበት ጊዜም ሆነ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኃላ ክርክሩ ይመለከተናል ወይም የተሰጠው ውሳኔ መብታችንን የሚነካ ነው በማለት በስነ ስርዓት ሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት እንደ የአግባብነቱ የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ወይም የመቃወም አቤቱታ በሚያቀርቡ ሰዎች ማንነት ወይም በሚያቀርቡት የዳኝነት ጥያቄ ባህርይ ላይ ተመስርቶ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የክርክሩ ተካፋይ ያልነበሩ ሰዎች ወደ ጉዳዩ መግባት ጉዳዩን አስቀድሞ ማየት ከጀመረው ወይም ውሳኔ ከሰጠው ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ውጪ ሊያደርግ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡የእንደዚህ ዓይነቶቹ አጋጣሚዎች መፈጠር አንዱ መንስዔ አገሪቱ መከተል የጀመረችውን የፌዴራሊዝም ስርዓት መሰረት በማድረግ በአገሪቱ ያለው የዳኝነት ስልጣን በፌዴራል እና በክልል የተከፋፈለ መሆኑ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአሁኖቹ ተጠሪዎች መካከል የተነሳውን ክርክር የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስተናግዶ ውሳኔ የሰጠው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት ሲሆን አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ ያቀረቡትም ተካፋይ ባልሆንኩበት ክርክር ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ መብቴን ይነካል በማለት ነው፡፡በመሰረቱ የመቃወም አቤቱታ የሚቀርበው መቃወሚያ የቀረበበትን ፍርድ ለሰጠው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 359(1) ስር ተመልክቷል፡፡ይሁን እንጂ የስነ ስርዓት ሕጉ የወጣው አገሪቱ የፌዴራሊዝም ስርዓት መከተል ከመጀመሯ እና በአገሪቱ ያለው የዳኝነት ስልጣንም በፌዴራል እና በክልል ከመከፋፈሉ ከረጅም ዓመታት በፊት በመሆኑ ድንጋጌው መተርጎም የሚገባው የፍርድ ቤቶችን የስረ ነገር ስልጣን አስመልክቶ አዲስ ከወጡት የሕግ ማዕቀፎች ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ የተደረገው የስረ ነገር ስልጣን ያለውን ፍርድ ቤት ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 11(2)(ሀ) ደንጋጌ አንጻር ለማጣራት ሲሆን የተጠቀሰው የአዋጁ ድንጋጌም የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን(ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው) የሚመለከቱ ጉዳዮችን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጉዳዩ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር እንዲወድቅ የሚያደርገው መሰረታዊ ጉዳይ የተከራካሪ ወገኖች ወይም ከእነዚህ አንዱ የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸው ሳይሆን ይልቁንም ለክርክር የቀረበው ጉዳይ የተለያዩ ሀገሮች ሕጎችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈጻሚነት ጥያቄ የሚያስነሳ መሆኑ ነው።ክርክሩ መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች የሰዊድን፣2ኛ ተጠሪ ደግሞ የአሜሪካን ዜግነት ያላቸው ሲሆን አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ፈጽመን ስንኖር ነበር የሚሉትም በአሜሪካን አገር ነው። በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ ኢትዮጵያዊት ሲሆኑ ክርክሩ የቀረበውም ለኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ነው።ይህ ብቻ ሳይሆን አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ያፈራሁት ነው የሚሉት የማይንቀሳቀስ ንብረትም የሚገኘው በኢትዮጵያ ውስጥ ነው። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎችም፡-

1. የአመልካችን የዜግነት አገር ሕግ
2. የ2ኛ ተጠሪን የዜግነት አገር ሕግ
3. የአመልካች እና የ2ኛ ተጠሪን መደበኛ የመኖሪያ አገር ሕግ
4. የአመልካች እና የ2ኛ ተጠሪ ጋብቻ ተፈጽሟል የተባለበትን አገር ሕግ
5. ክርክሩ የቀረበለትን ፍርድ ቤት ሀገር ሕግ
6. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚገኝበትን አገር ሕግ እና
7. ተከራካሪ ወገኖች የሚስማሙበትን አገር ሕግ

የተፈጻሚነት ጉዳይ የሚያስነሱ ናቸው።አከራካሪ ሆኖ ለቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ውሳኔ ለመስጠት ደግሞ የእነዚህ ሀገሮች ሕጎች ለክርክር የቀረበውን ጉዳይ የሚፈቱበትን አግባብ መለየትን፣ለክርክር የቀረበውን ጉዳይ በመፍታት ረገድ በእነዚህ ሀገሮች ሕጎች መካከል አለመጣጣም (Conflict) መኖር አለመኖሩን መለየትን፣አለመጣጣም የሚኖር ከሆነ አለመጣጣሙ የሚፈታበትን አግባብ መለየትን እና በመጨረሻም ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለውን ሕግ መምረጥን ይጠይቃል።ይህም የአሁኗ አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን (ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው) የሚመለከት መሆኑን እና ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣንም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 11(2)(ሀ) ድንጋጌ መሰረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሆነ መገንዘብ የሚያስችል በመሆኑ የመቃወም አቤቱታው የቀረበለት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ ገልጾ የመቃወም አቤቱታውን መመለስ ሲገባው ተቀብሎ በማስተናገድ ውድቅ ያደረገው የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖረው መሆኑን ተገንዝበናል።በሌላ በኩል ጉዳዩ የተነሳው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(2) በተሰጠው የስልጣን ውክልና፣በክልሉ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 64 (2) (ለ) እና የክልሉን ፍርድ ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/2000 በአንቀጽ 26 (1) (ለ) በተመለከተው መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኗ አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ ተቀብሎ በማስተናገድ የሰጠው ብይን የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖረው የተሰጠ እና በዚህም ምክንያት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአሁኗ አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ ተቀብሎ በማስተናገድ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26729 በ11/07/2006 ዓ.ም. የሰጠው እና በኦሮሚያ ብ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 186043 በ25/07/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ብይን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን (ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው) የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የማየት የስረ ነገር ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 11(2)(ሀ) ደንጋጌ መሰረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣በሕገ መንግስቱ በተሰጠው የስልጣን ውክልና መሰረት ደግሞ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት በተመለከተው መሰረት አመልካች ተጥሶብኛል የሚሉትን መብት ለማስከበር ክሳቸውን ማቅረብ የሚገባቸው ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97009

ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካቾች፡- 1. አቶ ኤልያስ አዳሙ ጠበቆች ክፍሌ ታደሰና አቶ ጅማ ድልቦ ቀረቡ

2. ሐዋሪያው ዳንኤል መኮነን

ተጠሪዎች፡- የኢትዮጵያ ወንጌል ብርሃን ቤቴክርስቲያን - ደረጀ አበበ የቦርድ ተወካይ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 08477 ሐምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142307 ታህሣሥ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በተጠሪ አንድ አጥቢያ ላይ የተፈጠረ ሁከት እንዲቆምና እንዲወገድ ውሣኔ ይሰጥልን በሚል መንገድ የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቾች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በጠበቃ ተወክላ ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፣ ከሳሽ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመች ናት፡፡ ተከሳሾች የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም በከሳሽ አንድ አጥቢያ ላይ ሁከት በመፍጠር የከሳሽን ቢሮ ውክልና አለን በማለት አሽገዋል የካቲት 29 ቀን 2005 ዓ.ም ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት በመምጣት ከሌሎች ግብረአበሮቻቸው ጋር በመሆን የሁከት ተግባር ፈፅመዋል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ /ሁለተኛ አመልካች/ ከሥልጣናቸው መነሳታቸውን እያወቁት ለሌሎች ሠራተኞች የሥራ አመራር ትዕዛዝ በመስጠት በከሳሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተክርስቲያን ላይ ችግር ፈጥረዋል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ አመልካች/ አላግባብ ከሁለተኛ ተከሳሽ ባገኘው ውክልና በከሳሽ ላይ የፈጠረው የሁከት ተግባር እንዲወገድና የውክልና ስልጣኑ እንዲሰረዝልን ሁለተኛ ተከሳሽ ከኃላፊነታቸው ስለተነሡ የሥራ አመራር ተግባር መሣተፋቸው የሁከት ተግባር በመሆኑ ከተግባራቸው እንዲቆጠቡ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

2. አንደኛ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው የፅሑፍ መልስ ቤተክርስቲያን በመወከል በቤተክርስቲያኗ ስም ክስ ለማቅረብ የሚችሉት መስራች ሀዋሪያው ናቸው፡፡ የሥራ አመራር ቦርዱ ቤቴክርስቲያኗን ወክሎ ክስ ለማቅረብ አይችልም፡፡ ክሱ የቀረበብኝ ቤቴክርስቲያኗን ወክለው ክስ የማቅረብ ሥልጣን በሌለው አካል በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት፣ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሁለተኛ አመልካች መልስ በፅሑፍ ባለማቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኋላ፣ክሱ የቀረበው ቤተክርስቲያኗን ወክሎ ክስ ለማቅረብ ተገቢው ውክልና ባላቸው ሰው ነው ወይ? ተከሳሾች በቤተክርስቲያን ላይ የፈጠሩት የሁከት ተግባር አለ ወይ? የሚሉትን ጭብጦች መሥርቷል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት በቤተክርስቲያኑ መተዳደሪያ ደንብና በቤተክርስቲያኗ የመዋቅር መግለጫ ተዋረድ መሰረት ሀዋሪያው ከሥራ አመራር ቦርዱ ሥር የተቀመጡ መሆኑንና መሥራች ሀዋሪያው አስተዳደራዊና መንፈሳዊ ሥልጣን በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 18 እንደተሰጣቸው ገልፆ፣ የመስራች ሀዋሪያውን የመንፈሣዊ ሥልጣን በዳኝነት አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለኝም፡፡ መሥራች ሀዋሪያው በመተዳደሪያ ደንቡ፣ አንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ 6 የተሰጠውን አስተዳደራዊ ሥልጣን በተመለከተ በዳኝነት አይቼ መወሰን እችላለሁ፡፡ ከዚህ አንፃር መስራች ሀዋሪያው /ሁለተኛ ተከላሽ/ ከአስተዳደራዊ ሥልጣናቸው በሥራ አመራር ቦርዱ የተነሱ ስለሆነ በአንደኛ ተከሳሽ የውክልና ሥልጣን መስጠት አይችሉም፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ ተከሳሽ ከአስተዳደራዊ ሥልጣናቸው የተነሱ ስለሆነ በአስተዳደር ሥራ እንዳይሣተፉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካችዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የአመልካችዎችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

4. አመልካችዎች ጥር 20 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የኢትዮጵያ ወንጌል ብርሀን ቤተክርስቲያን በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ሃይማኖት መሠረት የተቋቋመች፣ የራሷን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አውጥታ የምትተዳደር ቤቴክርስቲያን ነች፡፡ ቤተክርስቲያኗ ነሐሴ 2 ቀን 2000 ዓ.ም ያፀደቀችው መተዳደሪያ ደንብ እስካሁንም ድረስ በሥራ ላይ ያለና የምትተዳደርበት ደንብ ነው፡፡ የቤቴክርስቲያኗን መተዳደሪያ ደንብ በሚመለከት የሚነሳ ጥያቄና ክርክር ሀይማኖታዊ ባህሪ፣ ይዘት ያለው በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይና ሊወሰን የሚችል አይደለም፡፡ ለሥር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ይዘትም ጭብጥም የሥራ አመራር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቦርዱ ቤተክርስቲያኗ በመተዳደሪያ ደንቡ መሪ አድርጋ የሾመቻቸውን ሁለተኛውን አመልካች ከአስተዳደር ሥልጣናቸው አንስቻለሁ በማለት የሰጠው ውሣኔ በቤተክርስቲያኗ ተፈፃሚነት የሚሰጠው መሆኑን የሚመለከት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የውክልና ስልጣን ሰጥቶኛል የሚለው የቀድሞው የሥራ አመራር ቦርድ በቤተክርስቲያኒቱ ላይ በፈጠራው ረብሻ ምክንያት ጠቅላላ ጉባኤው ተሰብስቦ ከኃላፊነታቸው እንዲነሡ የወሰነባቸውና በሌላ ሥራ አመራር ቦርድ የተተካ ቤተክርስቲያኗን ወክሎ ክርክር ለማቅረብ ህጋዊ ህልውና የሌለው አካል ነው። ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የማይችል ጉዳይ በዳኝነት ተቀብሎ በማየት የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 37/1/ እና ስለመንግስትና ኃይማኖት መለያየት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 11 የተደነገገውንና ይኸ ሰበር ችሎት የሰጣቸውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች በመጣስ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል።

5. ተጠሪ የካቲት 28 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤተክርስቲያኗ የምትተዳደረው ግንቦት 2 ቀን 2000 ዓ.ም በወጣው መተዳደሪያ ደንብ መሆኑን ገልፀውና የመተዳደሪያ ደንቡን ድንጋጌዎች በሰፊው ዘርዝረው የሥራ አመራር ቦርዱ ከአስተዳደር ሥልጣናቸው ካነሳቸው በኋላ ሁለተኛ አመልካች አንደኛ አመልካችን መወከላቸው የሁከት ተግባር ነው። የሁከት ተግባር መሆኑም የወንጀል ምርመራ ተጣርቶ፣ የወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል። ስለዚህ ሁለተኛ አመልካች ከአስተዳደራዊ ሥልጣኑ ከተወገደ በኋላ ሁከት መፍጠሩን በማስረጃ በማረጋገጥ ሁከቱ እንዲወገድ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉዳዩ በዳኝነት የሚያልቅ መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠው በመሆኑ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያስናብተን በማለት መልስ ሰጥተዋል። አመልካቾች መጋቢት 29 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል።

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት በዕሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ሁለተኛ አመልካች ከአስተዳደራዊ ሥልጣናቸው በቤtክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ የተነሱ በመሆኑ፣ የቤተክርስቱያኗ የአስተዳደራዊ ሥራ ውስጥ መግባታቸው የሁከት ተግባር ነው። ስለዚህ ሁለተኛ አመልካች በቤተክርስቲያኗ አስተዳደራዊ ተግባር እንዳይሣተፉ በማለት የሰጡት ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርመረናል።

7. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን አመልካቾችና ተጠሪ የሚከራከሩበት መሠረታዊ ጉዳይ ባህሪና ይዘት ምንድን ነው? ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ መሠረታዊ ይዘት ምንድን ነው የሚሉትን ነጥቦች በመመልከቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል። ጉዳዩን እንደመረመርነው ለሥር ፍርድ ቤት ክሱ ሲቀርብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተክርስቲያኗን በመወከል ለጠበቃ የወኪልነት ሥልጣን የሰጠው የሥራ አመራር ቦርድ፣ የቤተክርስቲያኗ "መሥራች ሀዋሪያ " መሆናቸው በግንቦት ወር 2000 ዓ.ም በወጣው ደንብ ስማቸው የተገለፀውን ሁለተኛ አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ ቤተክርስቲያኗን የማስተዳደር ሥልጣናቸውን በማንሣት በመንፈሳዊ ሥልጣናቸው ብቻ እንዲገደቡ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ በቤተክርስቲያኗ የአስተዳደር ሥራዎች እየገቡ ችግር እየፈጠሩ ነው፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ አመልካች በሌላቸው ስልጣን ቤተክርስቲያኗን እንዲያስተዳድር ለአንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ አመልካች/ የሰጠው ውክልና እንዲሰረዝና ሁለተኛ ተከሳሽ በአስተዳደራዊ ሥራዎች ጣልቃ እንዳይገባ ይወሰንልን የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

8. አንደኛ አመልካችና በጅምሩ የሥራ አመራር ቦርዱ ቤተክርስቲያኗን ወክሎ ክስ ለማቅረብና ለመከራከር የሚያስችለው ሥልጣን የለውም፡፡ በመተዳደሪያ ደንቡ የሥራ አመራር ቦርድ በመሥራች ሀዋሪያው /ሁለተኛ አመልካች/ የሰጠውን ስልጣን መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ብሎ የመክፈልና የመሥራች ሀዋሪያውን ሥልጣን ለመቀነስ ወይም የመስራች ሀዋሪያው ቤተክርስቲያኗን የማስተዳደር ሥልጣኑ የማንሣት ስልጣን የለውም፡፡ ስለዚህ የሥራ አመራር ቦርድ መሥራች ሀዋሪያው /ሁለተኛ አመልካች/ በቤተክርስቲያኗ የአስተዳደር ሥራ እንዳይሳተፍ የሰጠው ውሣኔ የቤተክርስቲያኗን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ተፈፃሚነት የለውም በማለት አንደኛ አመልካች በፅሑፍና በቃል ባቀረበው ክርክር ሁለተኛ አመልካች የግራቀኙ ክርክር በሚሰማበት ቀን ተገኝቶ በቃል ባቀረበው ክርክር የገለጹ መሆናቸውን፣ ለመረዳት ችለናል፡፡

9. አንድ ክርክር መሠረታዊ ጭብጦች የሚመሰረቱት ከሳሽና ተከሳሽን የሚካካዱበትን የሕግ ነጥብ፣ ከሳሽ በክሱ የገለፀውን ፍሬ ነገር እና በማስረጃነት የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ይዘት፣ ተከሳሹ በመከላከያ መልሱ የገለፀውን ፍሬ ነገርና በመከላከያ ማስረጃነት የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ይዘትና ፍርድ ቤቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241 መሠረት የግራቀኙን የቃል ክርክር ሲሰማ የተገለፁትን ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ መሆን እንዳለበት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246/1/፤የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 247/1/ እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 248 ድንጋጌዎች ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ አመልካችና ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር መሰረታዊ ጭብጦች የስራ አመራር ቦርድ ቤተክርስቲያኗን በመወከል ክስ ለማቅረብ ይችላል ?ወይስ አይችልም? የስራ አመራር ቦርድ የመስራች ሐዋሪያውን በቤተክርስቲያኑ መተዳደሪያ ደንብ የተሰጠውን የቤቴክርስቲያን አስተዳደር የመምራት ስልጣን እንዲቀንስ ወይም እንዲሸር የመወሰን ስልጣን አለው ወይስ የለውም? በቤተክርስቲያን አደረጃጀትና የስልጣን ተዋረድ እርከን፣ ከፍተኛ ስልጣን ያለው መስራች ሐዋሪያው ነው ወይስ የስራ አመራር ቦርዱ? የስራ አመራር ቦርዱ መስራች ሐዋሪያው የቤተክርስቲያን አስተዳደር ስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳይሰራ በማለት የሰጠው ውሳኔ በቤተክርስቲያን የውስጥ አስተዳደር ጉዳይ ውጤትና ተፈፃሚነት ያለው ውሳኔ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸው።

10. ከላይ የተገለፁትንና ግራ ቀኙ የሚከራከሩባቸው መሰረታዊ ጭብጦች በመሰረታዊ ባህሪያቸው 1987 ዓ.ም ህጋዊ ህልውና አግኝታ የተቋቋመችው የኢትዮጵያ የወንጌል ብርሃን ቤተክርስቲያን፣ የተቋቋመችበትን መመስረቻ ፅሁፍ፣ ቤተክርስቲያኗ ኃይማኖታዊ አላማ ለማሳካት፣ የፈጠረቻቸውን መዋቅራዊ አደረጃጀቶች፣ ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ ያወጣችውንና በፍትህ ሚኒስቴር ግንቦት 2 ቀን 2000 ዓ.ም ቀርቦ የተመዘገበውን መተዳደሪያ ደንብና የቤተክርስቲያን የተለያዩ አካላት ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት መመርመርና መተርጎም የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። በዚህ አይነት መንገድ የተቋቋመ አንድ ሀይማኖታዊ ተቋም፣ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት የሚያደራጃቸውን አደረጃጀቶች፣ የሚከፍታቸው ቅርንጫፎች፣ የሚፈጥራቸውን መዋቅሮች እንደዚሁም ለተለያዩ የኃይማኖት ተቋሙ አካላት የሚሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት፣ በኃይማኖት ተቋም የተለያዩ አካላት መካከል ስለሚኖረው የስልጣን ተዋረድና የእምነት ተቋሙ ኃይማኖታዊ ዓላማውን ለማሳካት ስለሚሰራቸው መንፈሳዊ ተግባራትና የቤተክርስቲያን አስተዳደር ተግባራት እንደዚሁም መንፈሳዊ አስተዳደርና ተግባሩ በየትኛው የኃይማኖች ተቁሙ አካል በኩል መከናወን እንዳለበት የሚነሱ ክርክሮች በመሰረታዊ ይዘታቸውና ባህሪያቸው የኃይማኖት ተቋሙን የተቋቋመበትን መሰረታዊ አላማ የተቋሙን መመስረቻ ፅሁፍ፣ የኃይማኖት ተቋሙ የሚመራባቸውን መሰረታዊ የእምነት ህጎችና ቀኖናዎችና የኃይማኖት ተቁሙን መተዳደሪያ ደንብ በጥልቀት መረዳትና መተርጎምና ተፈፃሚ እንደሆኑ ማድረግ የሚጠይቅ ከኃይማኖት ተቋሙ መሰረታዊና ተፈጥሯዊ ባህሪ ተነጥለው ለየብቻቸው ሊታዩና ሊወሰኑ በፍርድ ሊወሰኑ የሚችሉ ጉዳዮች አይደሉም። ከዚህ አንፃር ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ጭብጥ በዳኝነት የማያልቅ ከቤተክርስቲያኑ መሰረታዊ ተፈጥሯዊ ባህሪ ተነጥሎ ሊታይ የማይችል ጉዳይ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት የቤተክርስቲያኑን አስተዳደራዊ ስራዎች ለማከናወን የተሰጠ የሹመትና የስርአት ጉዳይ በዳኝነት አይቶ መወሰን የምችለው ጉዳይ ነው። የቤተክርስቲያኑን መንፈሳዊ ሹመት ስራና ኃላፊነት በተመለከተ በዳኝነት የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ይዘት ያላገናዘበ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

11. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 11 መሰረታዊ መርህ ሆኖ የተደነገገው የመንግስትና የኃይማኖት መለያየት መሰረታዊ መርህ፣ በይዘቱም ሆነ በተግባራዊ ተፈፃሚነቱ የአንድ ኃይማኖታዊ ተቋም የተቋቋመበትን ኃይማኖታዊ ዓላማ ለማሳካት በመመስረቻ ፅሁፍና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የዘረጋውን አደረጃጀት፣ የከፈታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅርንጫፎች፣ ያዋቀራቸውን የተለያዩ አካላትና ያላቸው መንፈሳዊና አስተዳደራዊ የስልጣን ደረጃ እርከንና ተዋረድ፣ እንደዚሁም በኃይማኖት ተቋሙ የተለያዩ አካላት መካከል የሚነሱ የስልጣን፣ የኃላፊነትና የተጠሪነት ጉዳይ በዳኝነት አይቶ በማስረጃ አጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥና በኃይማኖት ተቋሙ መሰረታዊ ተፈጥሯዊ ጉዳይ ገብቶ ዳኝነት እንዲሰጥ የሚፈቅድለት አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ይኽ ሰበር ችሎት በኃይማኖት ተቋማት የተለያዩ አካላት፣ መሪዎችና ኃላፊዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮች በራሱ በኃይማኖትታዊ ተቋሙ መመስረቻ ፅሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብና የፅምነቱ መሰረታዊ ህግጋትና ቀኖናዎች መሰረት የሚፈቱ መሆናቸውንና ፍርድ ቤቶች እንደዚህ አይነት ክርክሮችን አይተው ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችላቸውን የዳኝነት ስልጣን የሌላቸው መሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 66957 በሌሎች መዛግብት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች ሕገ መንግስቱን አንቀፅ 11 የተቀመጠውን መሰረታዊ መርህን ይኽ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 66957 በሌሎች መዛግብት የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉምና የአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች ወደ ጎን በመተው ጉዳዩን በዳኝነት አይተው ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ዝርዝር ምክንያቶች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዳኝነት አይተው የመወሰን ስልጣን የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጎዝቲት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.105092

መጋቢት 1 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ብርሃኑ ከበደ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኢብራሂም ሹካ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በገጠር የእርሻ ይዞታ ላይ የተነሳ የውርስ ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በአርሲ ዞን በዲገሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ከሳሽ በ08/11/2005 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ በ2001 ዓ.ም በሞት የተለዩት የከሳሽ አባት አቶ ሹካ ቃሉ በሕይወት እያሉ በኪራይ ለተከሳሽ ሰጥተው የነበረውን እና በውርስ ለከሳሽ ሊተላለፍ የሚገባውን አወሳኞቹ በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለጸውን ሶስት ጥማድ የእርሻ ይዞታ ተከሳሽ እንዲለቁ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን የሚገልጽ እና ይህንኑ መሬት ለቀው ለከሳሽ እንዲያስረክቡ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ በበኩላቸው በ18/11/2005 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ተከሳሽ የከሳሽን እናት እና አባት ሲጦሩ የነበረ መሆኑን ምክንያት በማድረግ የከሳሽ ወላጆች በእርሻ ይዞታው የመጠቀም መብታቸውን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2427 መሰረት በ26/02/1999 ዓ.ም በተደረገ ውል በስጦታ ያስተላፉላቸው መሆኑን፣ተከሳሽም ውሉን በሚመለከተው አካል አስመዝግበው የከሳሽ ወላጆች በሕይወት እያሉ የባለይዞታነት ስሙን ወደ ራሳቸው አዛውረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን እና በዚሁ ይዞታ ጉዳይ የከሳሽ ወንድሞች በተከሳሽ ላይ በሌላ መዝገብ ክስ መስርተው መዝገቡ በዕርቅ የተዘጋ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በግራ ቀኙ ማስረጃ እና ከሚመለከተው አካል ማጣራቱን፣የከሳሽ ወላጆች በእርሻ ይዞታው የመጠቀም መብታቸውን በ26/02/1999 ዓ.ም በተደረገ ውል በስጦታ ለተከሳሽ ማስተላለፋቸው እና ተከሳሽም የባለይዞታነት ስሙን ወደራሳቸው አዛውረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ በክርክሩ መረጋገጡን ገልጾ ሟቾች በሕይወት እያሉ ለተከሳሽ ያስተላለፉት በይዞታው የመጠቀም መብት የውርስ ንብረት ሊሆን የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎ ተከሳሽ ይዞታውን እንዲለቁ አይገደዱም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን ያጸና ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በገጠር የእርሻ ይዞታ የመጠቀም መብትን ከባለይዞታው ጋር የስጋ ዝምድና ለሌለው ሰው ማስተላለፍ የማይቻል ስለመሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 6 ስር ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑን በምክንያትነት ጠቅሶ የሁለቱን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር አመልካች ክስ ያስነሳውን ይዞታ ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች አከራካሪውን መሬት በተመለከተ ህዳር 28 ቀን 1999 ዓ.ም ሕጋዊነቱ የተረጋገጠላቸው መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ እያላቸው የክልሉ ሰበር ችሎት በሀምሌ ወር 1999 ዓ.ም የወጣውን የገጠር መሬት አዋጅ ወደ ኃላ ወስዶ አመልካች የቤተሰብ አባል ስላልሆኑ መሬት በስጦታ የማግኘት መብት የላቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን ሽሮ አመልካች ክስ ያስነሳውን ይዞታ ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የተጠሪው ወላጆች ክርክር ባስነሳው የእርሻ ይዞታ የመጠቀም መብታቸውን በ26/02/1999 ዓ.ም በተደረገ ውል በስጦታ ለአመልካቹ ማስተላለፋቸው፣ አመልካችም የባለይዞታነት ስሙን ወደ ራሳቸው አዛውረው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ እና አመልካች ለስጦታ አድራጊዎቹ ተወላጅም ሆነ በመሬቱ ገቢ የሚተዳደሩ የቤተሰብ አባል አለመሆናቸው ያልተካደ እና በክርክሩም የተረጋገጠ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔን በመሻር ስጦታው ሕጋዊ ውጤት ያለው አይደለም ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው በገጠር የእርሻ ይዞታ የመጠቀም መብትን ለተወላጅ ወይም ከመሬቱ በሚገኝ ገቢ ለሚተዳደር የቤተሰብ አባል ካልሆነ በቀር በስጦታ ማስተላለፍን የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አይፈቅድም በማለት ነው፡፡አመልካችም ቢሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት የሚከራከሩት ስለ ስጦታ ውል አደራረግ እና ስለሕጋዊ ውጤቱ በፍትሐብሔር ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት አድርገው ከመሆኑ ውጪ ስጦታው በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 “ም” ቢሆን ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡

በመሰረቱ በገጠር የእርሻ ይዞታ የመጠቀም መብትን በስጦታ የማስተላለፍ ጉዳይን ጨምሮ ከገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ክርክሮች በመሰረታዊነት ተፈጻሚነት የሚኖራቸው የፌዴራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 እና ይህንን አዋጅ ተከትለው በየክልሉ የወጡ አዋጆች እና ደንቦች እንጂ የስጦታ አደራረግን አስመለክቶ በፍትሐብሔር ሕጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ባለመሆናቸው በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 በስራ ላይ ባለበት ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ ውሉ ተደረገ የተባለው አዋጁ ከመጽናቱ ከስምንት ወራት በፊት መሆኑ ለክርክሩ ምክንያት ከሆነው ጉዳይ ልዩ ባህርይ አንጻር ተጠቃሹን አዋጅ ለክርክሩ ተፈጻሚ ከማድረግ የሚያግድ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የሁለቱን የሰር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር አመልካች ክስ ያስነሳውን ይዞታ ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በዲገሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17089 በ30/01/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62601 በ09/04/2006 ዓ.ም. የጸናውን ውሳኔ በመሻር የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 179508 በ19/12/2006 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዲገሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20831 የተጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ29/01/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 109829

ግንቦት 14 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ረታ ከበበ ቀረቡ

ተጠሪ ፡-- ወ/ሮ ቱሬ ደማ ተወካይ መልዜታ ከበበ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመሬት ይዞታ ክርክር የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የወረጃርሶ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረው በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኗ ተጠሪ በሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ልጃቸው እንደሆነ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የመሬት ይዞታ በፍርድ ቤት አስወስነው የተረከቡት ከቦቤ ሊበን ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው በአጠቃላይ 0.9 ሄክታር መሬት በክርክር ላይ እያለ በቀጣይነት ይዘው እየተጠቀሙበት ስለሆነ ከዚህ መሬት ላይ አርሰው ያገኙት አላባ እና ግጦሽ በአጠቃላይ 6500 የሚያስገኝ ስለሆነ አላባውን ከፍሎው መሬቱን እንዲለቅላቸው መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በሰጡት መልስ ክስ ከቀረበበት ይዞታ ሁለት ቦታ ላይ የሚገኘው በስጦታ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ይኸውም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት በሌላ ሰው የተያዘባቸው በመሆኑ ተከራክረው በማስለቀቃቸው መብታቸውን ያስከበሩላቸው በመሆኑ እንደተሰጣቸው በ3ኛ ቦታ የሚገኝ መሬት በተመለከተ ግን የተጠሪ ከብቶች የበሉት ስለሆነ ሊጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክርና እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ለክርክሩ መነሻ ከሆነው ይዞታ ተጠሪ ለአመልካች 3 ገመድ መሬት በስጦታ መስጠታቸው በ22/06/2006 የተፃፈ ስጦታ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር መያያዙን፣ በመሆኑም ተጠሪ መሬቱን ይዞብኛል በማለት ያቀረቡት በስጦታ የተሰጠውን 3 ገመድ መሬት የአመልካች መሆኑን፤ ሌሎች ይዞታዎች በተመለከተ ግን ለቀው እንዲያስረክቡ ለግጦሽ አላባ በተመለከተ የተጠሪ ከብቶች የበሉት መሆኑ ምስክሮች አረጋግጠዋል በማለት ያለፈው መሆኑን በመጥቀስ ውሳኔ ሰጥተዋል። ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም። ተጠሪ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት በማግኘቱ ግራቀኙ አከራክሮ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ አጭር ይዘት፡- ግራቀኙ እያከራከረ ያለው የመሬት ይዞታ ውሳኔ አግኝቶ ተጠሪ ከተረከቡት በኋላ አመልካች መያዙን፤ አላባ እና ግጦሽ በተመለከተም አመልካች መሬቱን አርሶ ያመረተበት መሆኑን፤ ግጦሽም በከብቶች መበላቱን በምስክሮች መረጋገጡን በመግለጽ አመልካች ሁሉም ክስ የቀረበበት መሬት እንዲለቅ፤ ምርቱ ምን ያህል እንደሆነ፤ የተባለው ግጦሽም ምን ያህል ዋጋ ማውጣት እንደሚችል ተገምቶ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፈል ጉዳዩም በወረጃርሶ ወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 343(1) የመለሰው መሆኑን የሚያሳይ ነው።

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። ጉዳዩ በሰበር ይታይ በመባሉ ምክንያት ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርገዋል። አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት የምስክሮች ቃል ቀይሮ መተርጎሙን፤ ለክርክሩ መነሻ ከሆነው መሬት 0.5 ሄክታር መሬት በስጦታ ውል የተሰጣቸው መሆኑን የግጦሽ መሬት የበሉት የተጠሪ ከብቶች መሆናቸውን ተረጋግጦ እያለ ይክፈል መባሉ በአግባቡ አለመሆኑን መሠረት ተደርጎ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል። ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- አመልካች መሬቱን በስጦታ አገኘሁት የሚሉት ከሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ያልተመዘገበ፤የስጦታ ውል የተባለው በራሱ ጊዜ ያዘጋጀው መሆኑን፤ አላባና ግጦሽ በተመለከተ ተጣርቶ እንዲወሰን መመለሱ በአግባቡ ነው የሥር ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሊጸና እንደሚገባ ተከራክረዋል። የአመልካች የመልስ መልስም ቀርቧል።

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ በሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ እንደመረመርነው አመልካች ከሥር ፍርድ ቤት አንስተው አጥብቀው የሚከራከሩት ለክርክሩ መነሻ ከሆነው የመሬት ይዞታ 0.3 ሄክታር ከተጠሪ በስጦታ ያገኙት መሆኑ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ለአመልካች የመሬት ይዞታ ስጦታ አለማድረጋቸው፤ የስጦታ ውል የተባለውም እንደማያውቁት በመጥቀስ መከራከራቸውን ተገንዝበናል፡፡ ከሥር የክርክር ሂደት መረዳት እንደተቻለው ግራቀኙ እያከራከረ ያለው ይዞታ የተጠሪ ስለመሆኑ የተካሄደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይሁንና አመልካች መሬቱን ከሌላ ግለሰብ ተከራክረው ያስመለሱት በመሆኑ እናታቸው /ተጠሪ/ የድካማቸው ዋጋ ይሆን ዘንድ መሬቱን በስጦታ እንደሰጧቸው አፅንኦት በመስጠት መከራከራቸው ከውሳኔ ይዘት መረዳት ችለናል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች መሬቱን ከሌላ 3ኛ ወገን ማስመለሳቸው የገለጹ ቢሆንም ከማን ጋር ተከራክረው መሬቱን እንዳስመለሱት ያቀረቡት ግልጽ ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ በአንፃሩ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት ከአሁኑ አመልካች ይሁን ከሌላ ሰው ተከራክረው መሬቱ እንዳስመለሱት ግልጽ ባይሆንም በተያዘው ጉዳይ መታየት ያለበት እና መፍትሄ የሚያሻው መሠረታዊ ነጥብ መሬቱን ያስመለሱት ከአሁኑ ተጠሪ አመልካች ይሁን ሌላ ሦስተኛ ወገን አመልካች አለኝ የሚሉት የስጦታ ውል የኦሮሚያ የመሬት አዋጅ በሚፈቅደው አግባብ ሥልጣን ባለው አካል ቀርቦ ተመዝግቧል ወይስ አልተመዘገበም? የሚለው ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ እንዳረጋገጠው የመሬቱ ባለ ይዞታ ተጠሪ ስለመሆናቸው ተጠሪ ለአመልካች 0.3 ገመድ በስጦታ መስጠታቸው የተገለጸ ቢሆንም በማይንቀሳቀስ ሥልጣን ባለው አካል ቀርቦ የተመዘገበ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር ሕጋዊ ሰነድ የለም፡፡ በገጠር የመሬት ይዞታ ተጠቃሚዎች የመሬት ይዞታቸው ለ3ኛ ወገን በስጦታ የማስተላለፍ መብት ያላቸው ቢሆንም ስጦታው በሕግ ፊት የሚጸናው በሚመለከተው አካል ቀርቦ መመዝገቡን ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ አመልካች አለኝ የሚሉት የስጦታ ውል በተጠሪ የተካደ ሲሆን በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የስጦታ ውል ስለመሆኑ በሕግ የተደገፈ ክርክር አልቀረበም፡፡ የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሻረው ተሰጠ በተባለው ስጦታ ሕጋዊነት መሠረት በማድረግ ሳይሆን ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ ከአመልካች በክርክር አሸንፈው እንደወሰዱት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ከሥር የወረዳ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ መረዳት እንደተቻለው መሬት የማስመለስ ክርክሩ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል እንደነበር በግልጽ አያሳይም፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የጉዳዩን ክርክር ባሕሪ እና አግባብነት ያለው ጭብጥ ከመመስረት አኳያ ግድፈት ያለበት ቢሆንም በውጤት ደረጃ አመልካች በመሬት ይዞታው መብት እንደሌላቸው የሚያረጋግጥ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች በተጠሪ ተሰጠኝ የሚሉት የመሬት ይዞታ ሕጉ በዘረጋው ሥርዓት በሚመለከተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አካል ቀርቦ የተመዘገበ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በተጠሪ ተሰጠ የተባለው የመሬት ይዞታ ስጦታ በሕጉ አግባብ መቋቋሙ ካልተረጋገጠ በተጠሪ ላይ ሕጋዊ ግዴታ የሚጥል ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካችም ከተጠሪ የመሬት ይዞታ የመጠየቅ መብት የሚሰጠው አይደለም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የወረጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር አመልካች በመሬት ይዞታው መብት የለውም ብሎ መወሰኑ በተለየ ምክንያት በውጤት ደረጃ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 186103 በ02/06/2007 ዓ.ም የወረጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 27904 በ12/09/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በማሻሻል፤ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 47208 በ21/09/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በተለየ ምክንያት በውጤት ደረጃ በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ አገኘሁት የሚሉት የመሬት ይዞታ ስጦታ፤ ስጦታ ለመመዝገብ ሥልጣን ባለው የመሬት አስተዳዳር ጽ/ቤት ቀርቦ ያልተመዘገበ በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት ወስነናል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች 0.3 ገመድ መሬት እንዲያስረክብ አይገደድም ብለናል፡፡ የውሳኔ ግልባጭ ለሚመለከተው ይተላለፍ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከትለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- በዚህ ችሎት መጋቢት 8/2007 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
- መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት የዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 109776

ግንቦት 13 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አበተማም

መስጠፋ አህመድ

ተሻሊት ይመሰል

አመልካቾች፡- 1- ወ/ሮ ይርጋዓለም ዘውዴ - አልቀረቡም

2- ወ/ሪት ስንቅነሽ ክፍሌ

3- ወ/ሪት ወላንሳ ዘውዴ

4- አቶ ኃይለሚካኤል ክፍሌ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አሰፉ ዘውዴ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የጊምቢቹ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17681 ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 38944 መስከረም 14 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 197346 ህዳር 18 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የእርሻ መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት በውርስ የማግኘት ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ለወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1- የክርክሩ መነሻ ከሳሾች (አመልካቾች)ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾች የሚች ወ/ሮ ካሰች ዘውዴ ልጆች መሆናቸውን ገልፀው የእናታችን እናት ወ/ሮ የሺ ወልደየስ ታህሣሥ 19

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀን 2005 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፡፡ አያታችን በተለያዩ ስፍራ የእርሻ መሬትና ይዞታ ያላት ሲሆን እኛም በቤተሠብ አባልነት አስመዝግባናለች ፡፡ አያታችን በተሰጣት የይዞታ መሬት ማረጋገጫ ደብተር በቤተሠብ አባልነት የተመዘገበ ነው ከሳሾች ስለሆን መሬቱን የመውረስ የቀዳሚነት መብት አለን፡፡ ሆኖም ተከሳሽ የሚች ወ/ሮ የሺወልደየስ ወራሽ መሆኑን በፍርድ ቤት አስወስና፣ የያዘች በመሆኑ የተሰጣት የወራሽነት ማስረጃ ተሰርዞ መሬቱን የመውረስ መብት ያለን እኛ መሆናችን ተረጋግጦ ይወሰንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

2- ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርባ ሚች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ ወላጅ እናቴ ናት ተከሳሽ የወላጅ እናቴ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆኔ በማረጋገጥ ማስረጃ ያገኘሁት በሕግ አግባብ ነው፡፡ ከሳሾች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡ ከሳሾች የሚችን መሬት በቀዳሚነት የመውረስ መብት የላቸውም በማለት ተከራክራለች፡፡ አመልካቾችና ተጠሪ እየተከራከሩ እያሉ ፣የወ/ሮ ዘነበች ዘውዴ ልጅ መሆኑን ገልፆ እናቴን ተክቼ የአያቴን የእርሻ መሬት የመውረስ መብት አለኝ በማለት አቶ ሰለሞን መርሻ ጣልቃ ገብቷል፡፡

3- የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክር ሰምቷል በአመልካቾች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ተጠሪ የሚች የሺ ወልደየስ ልጅ መሆኗን አናውቅም በማለት የመሠከሩ መሆኑንና ተጠሪ የሚች የሺ ወልደየስ ልጅ መሆኗን የሚያውቁ አምስት ምስክሮች በማቅርብ እንዳስመሰከረች ከዚህ በተጨማሪ አንደኛ ከሳሽ ከአምስት ዓመት በፊት አግብታ ከሁለተኛ ከሳሽ ጋር በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ መሆኑን ሦስተኛና አራተኛ ተከሳሽም በአዲስ አበባ ከተማ ከአባታቸው ጋር የሚኖሩ መሆኑን ተከሳሽ ባቀረበቻቸው ምስክሮች የተረጋገጠ መሆኑን በውሣኔው ገልፆ የሚች የሺ ወልደየስ መሬት ለሶስት ተከፍሎ ከሳሾች የእናታቸውን ድርሻ አንድ እጅ እንዲወስዱ ጣልቃ ገቡ የእናቱን ድርሻ አንድ እጅ እንዲወስድና ተጠሪ አንድ እጅ ድርሻዋን እንድትወስድ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4- አመልካችዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል ፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችዎችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል አመልካችዎች የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጎባቸዋል ፡፡አመልካችዎች ተጠሪ ከስልሣ አንድ ዓመት በፊት ለሌላ ሰው በጉድፈቻ ተሰጥታ ከጉድፈቻ ከተሰጠችበት አደአ አካባቢ አግብታና መሬት ተመርታ እየኖረች ያለች ናት ፡፡ ተጠሪ አንድ ቀንም ከወላጅ እናቷ የእርሻ መሬት ተጠቅማ አታውቅም ፡፡በሌላ በኩል እኛ የሚች የሺ ወልደየስ የቤተሠብ አባል መሆናችን በመሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ሚች አስመዝግባናለች ይህም ሆኖ እያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ መሬት እንድትወርስ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ጥር 27 ቀን 2007ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ በሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡

5- ተጠሪ መጋቢት 11 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ተጠሪ የሚች ልጅ መሆኔ በርካታ ማስረጃ ያለኝ ቢሆንም አመልካችዎች የሚች እናቴ ወራሽ ስለመሆኔ ተረጋግጦ የተሰጠኝ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ ከሕግ ውጭ ጥያቄ አቅርበዋል ፡፡ አመልካቿ ለዚህ አሰበር ችሎት ተጠሪ በጉዲፈቻ እንዳደኩ አድርገው በሥር ያላነሱትንና እውነትነት የሌለውን ክርክር አቅርበዋል፤ክርክራቸውም ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ነው፡፡ ተጠሪ የእርሻ መሬቱን ከዚህ በፊትም ስጠቀምበት የቆየሁ ስሆን አሁንም ድርሻዬን በስሜ አዛውሬ እየተጠቀምኩ እገኛለሁ ፡፡ በሌላ በኩል የሚችን የእርሻ መሬት የመውረስ መብት የሌላቸው አመልካቾች የእኔን ወራሽነት በመቃወም ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሬለች ፡፡ አመልካችዎች የካቲት 8 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

6- ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ የሚች እናቷን የእርሻ መሬት ከሌሎች ወራሾች ጋር እንድትካፈል የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል ፡፡

7- ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የግራቀኙን ማስረጃ መዝነው የደረሱበት የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ ሚች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ፤በሥር ፍ/ቤት ከሳሾች እናት የወ/ሮ ካሰች ዘውዴ ወላጅ እናት መሆኗ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሚች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ የተጠሪ ወላጅ እናት መሆኗ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሚች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ የሚች ዘነበች ዘውዴ ወላጅ እናትና በሥር ፍ/ቤት ጣልቃገብ ተከራካሪ የሆነው ሰለሞን መርሻ አያታቸው መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

8- ከዚህ አንፃር ሲታይ የሚች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ የእርሻ መሬትና ንብረት አመልካቾች እናታቸውን ወ/ሮ ካሰች ዘውዴ በመተካት ተጠሪ የወላጅ እናቷ አንደኛ ደረጃ ወራሽ በመሆኗና ሰለሞን መርሻ እናቱን ዘነበች ዘውዴን በመተካት የመውረስ መብት ያላቸው መሆኑንን ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሚች የሺ ወልደየስ ልጅ አይደለችም በማለት የተከራከሩና ይህንን ክርክራቸውን ለማስረዳት ምስክሮች አቅርበው እንደነበርና አመልካቾች ማስረጃ ታአማኒነት የሌለው መሆኑን ተረጋግጧል ፡፡ አመልካቾች በዚህ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የሚች የሺ ወልደየስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥጋ ልጅ መሆኗን አምነው ተጠሪ በጉዲፈቻ ሌላ ሰው አሳድጓታል የሚል በሥር ፍርድ ቤት ያላነሱትን አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል ሆኖም አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት ተጠሪ በጉድፈቻ ሌላ ሰው ነው ያሳደጋት በማለት ያቀረቡት አዲስ የፍሬ ጉዳይ ክርክር የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ያላገናዘበና የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም ።

9- አመልካቾች ተጠሪ የእናቷን ወ/ሮ የሺ ወልደየስ የእርሻ መሬት የመውረስ መብት የላትም ። የእርሻ መሬቱን የመውረስ የቀዳሚነት መብት ያለን እኛ ነን በማለት የሚከራከሩት ሟች ወ/ሮ የሺ በህይወት እያለች እኛን በቤተሠብ አባልነት አስመዝግባናለች በማለት ነው። ሆኖም ሟች ወ/ሮ የሺ አመልካቾችን በቤተሠብ አባልነት ማስመዝገቧ የበታች ፍ/ቤቶች ለማስረጃ ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ መሆኑን ተረድተናል እንደዚሁም ሟች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ አመልካቾችን በአንድ ወቅት በቤተሰብ አባልነት ማስመዝገቧን የሚያሳይ ማስረጃ ቢኖር እንኳን አመልካቾች የሟች የቤተሠብ አባል ሆነው መመዝገባቸው ብቻውን የሟችን የእርሻ መሬት በቀዳሚነት የመውረስ መብት የሚያጎናፅፋቸው አይደለም።

10- ለዚህም ምክንያቱ የእርሻ መሬት በውርስ ለማግኘት ወራሹ አርሶ አደርና ከእርሻ መሬቱ ከሚገኘው ገቢ የሚተዳደር የቤተሰብ አባል መሆን እንዳለበት የፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 5 እና የኦሮሚያ ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 13 እና 16 በግልፅ ተደንግጓል።

አመልካቾች ሟች ወ/ሮ የሺ ወልደየስ የእርሻ መሬት ከሚገኘው ገቢ የማይተዳደሩ በአዲስ አበባ ከተማ የየራሳቸውን ኑሮ መሥርተው የሚኖሩ መሆናቸው በማስረጃ ተረጋግጧል። ይህ ከሆነ አመልካቾች የህጉን መስፈርት የማያሟሉ ሆነው እያለ ሟች የሺ ወልደየስ የቤተሰብ አባል ናቸው ብላ ማስመዝገቧ፣አመላከቾች የሟችን የእርሻ መሬት የመውረስ ቀዳሚ መብት አለን በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም ። በአንፃሩ ተጠሪ በእርሻ ሥራ የምትተዳደር አርሶ አደር መሆኗ ተረጋግጧል ። በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ተጠሪ የሟች እናቷን የእርሻ መሬት ልትወርስ አይገባም በማለት ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

<u>ው ሣ ኔ</u>

1- የጊንቢቹ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

2- በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ በየራሳቸው ይቻሉ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 99071

ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ አብረኽት ዲክሪያ ቁምጆን ጠበቃ መስፍን አስፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል

2ኛ አቶ ያሲን ጀማል

3ኛ አቶ ናስር ጀማል

4ኛ የልደታ ክፍለ ከተማ ማሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ነገረ ፈጅ ንጉስ ከበደ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቤት ክርክር የተመለከተ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቀርቦለት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማስተናገድ ሥልጣን እንዳለው ትዕዛዝ ከሰጠ በኃላ አመልካች የክስ ላሻሽል ጥያቄ አቅርበው በፍ/ቤት ፊታድ ክሱን ተሻሽሎ ከቀረበ በኃላ በተመሳሳይ ችሎት በመጀመሪያ ውድቅ የተደረገው መቃወሚያ በድጋሚ ቀርቦ ፍ/ቤቱ ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በቀረቡት ክስ የአመልካች እና ከ1-3 የተጠቀሱት ተጠሪዎች የጋራ ሀብት የሆነው በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 327 ለሆነው ቤት ያለአግባብ 4ኛ ተጠሪን በማሳሳት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለወሰዱ ካርታው ተመላሽ እንዲደረግ ይወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በሰጡት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመከላከያ መልስ ከ1-3 የተመዘገቡት ተጠሪዎች የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ የሚታገድ ነው የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቀወሚያ ሲያቀርቡ 4ኛ ተጠሪዎች የአመልካች ክስ መቅረብ ያለበት ከርታ ለሰጠው አስተዳደር ክፍል እንጂ ለፍርድ ቤት አይደለም በማለት መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከመረመረ በኃላ ፍርድ ቤቱ ተሰጠ የተባለው ካርታ የተሰጠበት አግባብ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የማጣራት ስልጣን እንዳለው፤ ለክርክሩ መሠረት የሆነውን ቤት የማን ነው? የሚለው ፍሬ ነገር በማጣራት ሂደት ነጥሮ እንዲመወጣ ይርጋ በተመለከተም የባለቤትነት ክርክር በይርጋ እንደማይታገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በስ/መ/ቁ. 43600 የሰጠው ገዥ ውሳኔ መሠረት በማድረግ ውድቅ እንዳደረገው እና ፍሬ ጉዳዩን ለመስማት ለ25/08/2007 ዓ/ም ቀጠሮ መያዙን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

አመልካች ግን በ7 ቀን 2004 ዓ/ም ክሱን አሻሽሎ የቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ከ1-3 የተመዘገቡ ተጠሪዎች ክስ የማቅረብ መብታቸው በይርጋ ከታገደ በኃላ 4ኛ ተጠሪ ከርታ አዘጋጅቶ መስጠቱ ተገቢ አለመሆኑን፤ በየደረጃው ያሉ የአስተዳደር አካላትም አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ መፍታት ስላልቻሉ ተጠሪዎች የወሰዱት ካርታ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲመክን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ 4ኛ ተጠሪ አመልካች አሻሽለው ላቀረቡት ክስ በሰጠው የመከላከያ መልስ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ የመስጠት ስልጣን የአስተዳደሩ በመሆኑ የመሰረዝ ሥልጣንም የአስተዳደሩ እንጅ የፍርድ ቤት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የ4ኛ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀብሎ የባለቤትነት ካርታ የመሰረዝ ሥልጣን የተሰጠው ለአስተዳደር ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.245(2)(መ) መሠረት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የዚህ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ያቀረቡት ይግባኝም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ የተባለ በመሆኑ ግራ ቀኙ የፅሑፍ ክርክር ያደረጉ ሲሆን ይህ ችሎትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት ተደርጎ ከተሰጠው ብይን አንፃር የቀረበው የሰበር አቤቱታና መልስ እንደተመለከተው፤ በአመልካች በኩል የቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት በብይን ያለፈው ጉዳይ በተመሳሳይ ችሎት እንደገና ተቀብሎ ማስተናገዱ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን 4ኛ ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች አቤቱታ ከተሻሻለ ቀደሞ የተሰጠው ብይንም ሕጋዊ ውጤት አይኖርም የሚል ይዘት ያለው መልስ ሰጥቷል፡፡ ከ1-3 የተጠቀሱት ተጠሪዎችም የስር ፍርድ ቤት ብይን እንዲፀና ጠይቋል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታቸው የሚያጠናክር ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የጉዳዩ አመጠጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ብይን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች በማገናዘብ ጉዳዩን መርምሮታል፡፡ እንደመረመረነውም በዚህ ችሎት እልባት የሚያሰፈልገው ጭብጥ የሥር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሥረ ነገር ስልጣን ጋር በተያያዘ የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ ጉዳዩን ለመስማት ከተቀጠረ በኃላ ክሱን በድጋሜ ተሻሽሎ በመቅረቡ ምክንያት በተመሳሳይ ችሎትና ፍ/ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም ተብሎ መዘገቡን በብይን መዘጋቱ በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከክርክር ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካች ባቀረቡት ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቀርቦ ፍርድ ቤቱም ካርታው የተሰጠበት ትዕዛዝ የማጣራት ስልጣን አለኝ በማለት በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የፍ/ቤቱ ብይን ተከትሎ የተጠየቀ ይግባኝ የለም፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ አመልካች ክሳቸውን ለማሻሻል ያቀረቡት ጥያቄ በፍ/ቤቱ ተቀባይነት በማግኘቱ አሻሽለው አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ካርታ የተሰጠበት አግባብ የማጣራት ስልጣን አለኝ በማለት የሰጠው ብይን በመሻር ካርታ የመስጠትና የመሰረዝ ሥልጣኑ የአስተዳደር ክፍል ነው በማለት በአንድ ጉዳይ ሌላ ብይን ሰጥቷል፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበው የክስ ላሻሽል አቤቱታ የክርክሩ መሠረታዊ ይዘት የለወጠ ሳይሆን የተጠሪዎች መብት በይርጋ የታገደ ነው አስተዳደሩም ውሳኔ ማረም አልቻለም የሚል አዲስ ፍሬ ነገር በማካተት የቀረበ ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት የብይን ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡ የሥር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ4ኛ ተጠሪ መጀመሪያ የቀረበው የፍርድ ቤቱ ሥልጣን ጥያቄ በተመለከተ በብይን ውድቅ ከተደረገ በኃላ አመልካች ክሳቸው በማሻሻላቸው ምክንያት ብቻ የራሱ ብይን መልሶ የሚሽረበት ሥርዓት አይኖርም፡፡ የስር ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቀርቦ ውድቅ ካደረገው በኃላ የመቃወሚያው ባሕሪ ዓይነትና ይዘት ሳይለወጥ በተመሳሳይ ጉዳይ የራሱ ብይን መልስ በመሻር ጉዳዩን ለማየት የስር ነገር ሥልጣን የለኝም በማለት የመወሰን ሥልጣን የለውም፡፡

በዚህ ጉዳይ ሌላ መታየት ያለበት መሠረታዊ ነጥብ የአሁኑ 4ኛ ተጠሪ ባቀረበው ክርክር ካርታ ከመስጠት እና ከማምከን ጋር የተያያዘ ጉዳይ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም የሚል ነው፡፡ አስተዳደራዊ ተቋማት በሕግ ተለይቶ የተሰጣቸው ጉዳይ የመወሰን ሥልጣን እንዳላቸው የታወቀ ነው፡፡ ይሁንና ለአንድ ባለ ጉዳይ የተሰጠው ከርታ የተሰጠበት እና የተሻረበት አግባብ በሕግ አግባብ መሆን ያለመሆኑን አጠርቶ የመወሰን ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለ መሆኑን አጣርቶ የመወሰን ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታን የመሰረዝ ሥልጣን የአስተዳደሩ ክፍል ነው፣ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የጉዳዩ የክርክር ባህሪ እና ይዘት ያላገናዘበ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ክፍል የተሰጠው ካርታ የተሰጠበት ወይም የተሸረበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥርዓት እና አስተዳደራዊ ውሳኔው ሕግና መመሪያ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን በማጣራት ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን እንዳላቸው ከፍ/ሀ/ቁ.1196 በህገ መንግስቱ ስለ ንብረት መብት ከአደረገው ድንጋጌና በፍርድ የሚያልቁ ጉዳዮችን በተመለከቱ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

በማጠቃላል፡- የሥር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን እንዳለው መጀመሪያ ብይን መስጠቱ እየታወቀ ክስ ተሻሽሎ ከቀረበ በኃላ በዚህ ችሎት የተሰየሙት ሌላ ዳኛ በተመሳሳይ ምክንያት የችሎቱ ትዕዛዝ እንደ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመሆን ሽሮታል፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ስ/ስ//ሕ/ቁ. 244 እና 245 የተመለከቱት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ብይን አሰጣጥ እና ጉዳይ አመራር ሥርዓት ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች አቤቱታ በማሻሻላቸው ምክንያት ብቻ የክርክሩ ይዘት ሳይለወጥ ብይኑ አጥሮ እንደሚሻር በሚያስቆጥር አግባብ የመጀመሪያ ብይን እንደ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመሆን የሻረው በመሆኑ በሕጉ የተዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት የተከተለ አይደለም ብለናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤት የራሱ የሰጠው ብይን መልሶ መሻሩ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ይህንን ብይን ሳያርም በትዕዛዝ ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ጉዳይ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 191377 በ27/05/2005 ዓ/ም የሰጠው ብይን፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 134095 በ13/5/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የስር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት ራሱ የሰጠው ብይን መልሶ የመሻር ስልጣን የለውም ብለናል፡፡ ካርታ የተሰጠበት እና የተሻረበት ሁኔታ በሕግ አግባብ መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ የመወሰን ሥልጣን የፍርድ ቤት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤት የተዘጋው መዝገብ ቁጥር 191377 በማንቀሳቀስ በተሰጠው ብይን መሠረት ክርክሩን ከቆመበት ቀጥሎ ተገቢ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ ::
4. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ተመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጎጎጵ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.94481

ሐምሌ 01 ቀን/2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ወ/ሪት ፀሀይነሽ በቀለ ጠበቃ ደረጀ ኢተቻ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- ወ/ሪት ንግስት ተክላይ ጠበቃ ሌ/ክ/ስንታየሁ ደመቀ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሽርክና ውል መሰረት በማድረግ የቀረበ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን አመልካች የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት ፡- በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተፈረመ የሽርክና ውል መኖሩን፤ ተጠሪ በሽርክና ውል ስምምነት መሰረት ለትርፍ ክፍፍል እንዲያመች የወጪና ገቢ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ እያላቸው አላቀረቡም ፡፡ ተጠሪ በውል የተረከቡትን የንግድ ድርጅት ሽርክና ውሉ ጊዜ ያለው በመሆኑ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 014 የሆነው የከሳሽ ድርጅትን እንዲያስረክቡ፤ የድርጅቱ ገቢና ሂሳብ ተሰርቶ በሂሳብ ስራው ውጤት ለአመልካች የሚደርሳቸው ትርፍ ወይም አመልካች በክሳቸው ባቀረቡት ግምት ብር 150,000 ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፈላቸው የጠየቁ መሆኑን የሚሳይ ነው፡፡

ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የመከላኪያ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩ፡- የሽርክና ውል የተባለው በህጉ የተቀመጠው መስፈርት አያሟላም፡፡ የንግድ ቤቱ ከሚመለከተው አካል የተከራዮት በመሆኑ አመልካች መጠየቅ አይችሉም፡፡ የመንግስት ቤት ለ3ኛ ወገን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማከራያታቸው የተወሰደ እርምጃ ህጋዊ ነው፡፡ የሽርክና ውሉ የማስመሰል ውል ነው፡፡አከራይ የሆኑት አመልካች የጉልበትም ሆነ የገንዘብ አስተዋፆኦ ሳያደርጉ በመንግስት ቤት ብቻ ትርፍ ይክፈሉ የሚለው ውል ስለ ኪሳራ ተጠያቂነት የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡ የሽርክና ማህበር ለማቋቋም የተቀመጡ መሰረታዊ ነጥቦች አልተሟሉም ሊጠየቅ አይገባም በማለት የተከራከሩ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ የንግድ ማህበር በንግድ ህጉ መሰረት የሚቋቋምበት አግባብ በመለየት የንግድ ማህበር ስለመኖሩ የማስረዳት ግዴታው የሽርክና ማህበር ተመስርቷል፡፡ የሚል ወገን መሆኑ በመግለጽ፤ የሽርክና ውል ስምምነት በወረቀት ላይ መፃፍ ብቻውን የሽርክና ማህበር አለ ሊባል አይችልም፡፡የግራ ቀኙ ማስረጃዎች እንዲመዘንና የአመልካችም ምስክሮች የሽርክና ማህበር በውል ግንኙነት አለ ቢሉም የዚህ አይነት ግንኙነት መመስረት መሟላት አለባቸው የተባሉትን ሁኔታዎች በሙሉ ባሟላ መልኩ የተመሰረተ ግንኙነት ያላቸው መሆኑ ምስክሮች አላስረዱም፡፡አብሮ የመስራትና የመተባበር፣ትርፍ መከፈል የሚሉት ሁኔታዎች በግራ ቀኙ ያልነበሩ በመሆናቸው በዚህ የመንግስት ቤት የሚሰሩት ተከሳሽ /ተጠሪ/ ብቻ መሆናቸው ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ያቀረቡት የሽርክና ውል ስምምነት የተፈረመው ተከሳሽ /ተጠሪ/ቤቱን የተከራዩት በ2003 ዓ/ም ሆኖ እያለ ወደ ኋላ በመመለስ መሆኑን ተጠሪ በዚህ የንግድ ቤት የሚሰሩት የንግድ ቤቱን ተከራይተው መሆኑን የተከሳሹ /ተጠሪ/ ምስክሮች በተሻለ ሚዛን አስረድተዋል ፡፡ውሉ የሽርክና ውል ተብሎ መፃፍ ብቻውን ደግሞ ውሉ ወደ ኋላ ሳይሰራበት ተጽፎ እያለ በእርግጥ በግራ ቀኙ መካከል የሽርክና ማህበር ውል ተመስርቷል፡፡ ሊባል አይችልም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ/337 መሰረት ተሰርሟል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ የተባለ በመሆኑ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አድርጓል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ያነሱት መሰረታዊ ነጥብ የሽርክና ውል መቅረብ ባልተካደበት በሰው ምስክር ሰነዱን ማስተባበል ህጋዊ አለመሆኑን፣ በሽርክና ውል አብሮ መስራት እንደመስፈርት እንዳልተወሰደ፤ ሽርክና በቀጥታ በስራ ሳይሳተፉ አብሮ በሽርክና መስራት እንደሚችል አመልካች ከመንግስት የተከራዩት ቤት በመዋጮነት በማቅረብ /በመስጠት/ መስራታቸው ህጋዊ ነው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከራቸውን ያሳያል፡፡ተጠሪ በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ ተደረገ የተባለው የሽርክና ውል ከመንግስት ተጠያቂነት ለማምለጥ የተደረገ ወደ ኋላ ተመልሶ የተፈረመ መሆኑን ተጠሪ ቤቱን በ2000 ብር ተከራይተው 4,000 መክፈላቸው፤ የአስተዳደር አካልም ጉዳዩ በማጣራት የአከራይ ተከራይ ግንኙነት መኖሩን ማረጋገጡን፤ ተዋጣ የተባለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካፒታል እና የተጠየቀው ትርፍ /300,000 ብር/ የማይገናኝ ፣መሆኑ፤ ቤቱ የመንግስት ሲሆን አመልካችም ውጭ አገር የሚኖሩ፤ የመንግስት ቤት በመዋጮ መስጠት እንደማይቻል፤ ተደረገ የተባለው ውልም የሽርክና ውል በንግድ ህግ ቁጥር 211 የተመለከተው አስገዳጅ መስፈርት እንደማያሟላ በመግለጽ የስር ፍርድ ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ በአመልካች የቀረበው የመልስ መልስ አቤቱታውን የሚያጠናክር ነው፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የታዘዘ ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች ከተጠሪ አደረኩት ያሉትን የሽርክና ስምምነት በንግድ ህጉ የተጠቀሱትን መሰረታዊ መመዘኛዎች አያሟሉም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ በአግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ግንኙነት በሽርክና ውል ላይ የተመሰረቱ ስለመሆኑ አጥብቀው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው በግራ ቀኙ መካከል ያለው ግንኙነት አከራይ ተከራይ እንጂ በህግ አግባብ የተቋቋመ የሽርክና ውል የለም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ የሰውና የሰነድ ማስረጃ መመዘኑን በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ የነበራቸው ግንኙነት በሽርክና ውል ላይ የተመሰረቱ ሳይሆን የአከራይ ተከራይ ግንኙነት ነው፡፡በሽርክና ውል መሰረት መተባበርና አብሮ የመስራት፤ ትርፍ መከፈል የሚሉት የሽርክና ማህበር ለማቋቋም እንደ መሰረታዊ መመዘኛ የሚወስዱት ነጥቦች አልተሟሉም፡፡ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው የንግድ ቤት ተጠሪ ብቻ እንደሚሰሩ አረጋግጧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ስልጣኑ የደረሰበት ድምዳሜ ይዘን ጉዳዩን ከህግ አንፃር መርምረናል፡፡

በመሰረቱ የሽርክና ማህበር በውል የሚቋቋም ሲሆን መሰረታዊ የማህበሩ ባህርያትም በአንቀጽ 211 ስር እንደተመለከተ ህጋዊ ሰውነት ያለው፤ በሽሪኮቹ የውል ስምምነት የሚቋቋም፤ ዓላማው ኢኮኖሚያዊ ተግባር ለማከናወን /ንግድ/፤ ሽሪኮች አብረው ለመስራትና ለመተባበር ተስማሙ፤ ከድርጅቱ የሚገኘው ትርፍም ሆነ ከሚመጣው ዕዳ ተከፋፋይ እንደሚሆኑ የሚስማሙበት ውል ስለመሆኑ ከላይ ከተመለከተው የህግ አንቀጽ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው ። የሽርክና ማህበር ሲቋቋም ሽሪኮቹ መዋጮ የማውጣት ግዴታ የተጣለባቸው ሲሆን መዋጮው በገንዘብ፣ በአይነት ወይም በጉልበት ሊሆን እንደሚችል በንግድ ህግ አንቀጽ 229 ስር የተመለከተ ሲሆን መዋጮውም ብዛታቸው እኩል እንደሆኑ እና ለማህበሩም የሚስማሙ መሆን እንዳለባቸው የዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ ያመላክታል፡፡ ማህበሩ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት ካለው በአይነት /ንብረት/ የተደረገው መዋጮ መልሶ መውሰድ እንደማይችል በንግድ ህግ አንቀጽ 269 /1/ ስር ተደንግጓል፡፡ አንድ የሽርክና ማህበር በህጉ አግባብ ተቋቋመ ለማለት የሚቻለው ተዋዋይ ወገኖች ተነፃፃሪ ሳይሆን ተደጋጋፊ የሆነ ግብ ይዘው መዋጮ በማዋጣት አብረው ከመስራትና በመተባበር፤ ትርፍና ኪሳራም በህጉ አግባብ እየተጋሩ ኢኮኖሚያዊ ተግባር ማከናወናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ከተጠሪ ጋር መሰረትኩት በሚሉት የሽርክና ማህበር በአዲስ ከተማ ክፍለ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 014 የሆነው የመንግስት ቤት በመዋጮነት በማዋጣት ፤ ተጠሪ ደግሞ በእራሳቸው ገንዘብ የተዘጋጁ ልብሶችና ጫማዎች ገዝቶ በማምጣት በጋራ ተቀናጅቶ ለመስራት የተስማሙ ስለመሆኑ በመዝገቡ ከተያዘው የሽርክና ውል መረዳት ይቻላል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ እንዳረጋገጠው ተጠሪ ቤቱን የተከራዩት በ2003 ዓ/ም ሁኖ ሳለ ውሉ ወደ ኋላ ተመልሶ 2002 ዓ/ም እንደተደረገ፤ ተጠሪ የንግድ ቤቱን ተከራይተው ተመስርቷል፡፡ ሊባል እንደማይችል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ያመላክታል፡፡ በአመልካችና ተጠሪ ተፈረመ የተባለው ሽርክና ውል በጽሁፍ ብቻ መሆኑ የሽርክና ማህበር መቋቋሙን የሚያሳይ አይሆንም፡፡ የሽርክና ማህበር የንግድ ህግ አንቀጽ 211 እንደደነገገው በህጉ ተለይተው የተቀመጡ መሰረታዊ መስፈርቶች ማለትም አብሮ መስራትና መተባበር፤መዋጮ መኖር የትርፍና ኪሳራ ክፍፍል ስርዓት የተመለከቱ ነጥቦች በመሰረት ላይ በትስስር ሊገኙ ይገባል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ የሽርክና ውል ማቋቋሚያ ነጥቦች በተግባር አልተረጋገጠም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በድጋሚ የሚመረምር አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የሰበር ሰሚ ችሎቱ በህግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን ያለመሆኑን ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 /3/ /ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በግራ ቀኙ ተደረገ /ተፈረመ/ የተባለው የሽርክና ውል እና ይህንን ተከትሎ መሬት ላይ ያለው እውነታ በስር ፍርድ ቤት እንደተጠራው የሽርክና ውል በጽሁፍ ከመደረጉ ውጭ የሽርክና ውል የሚጠይቃቸው መስፈርቶች አሟልተው ሲሰሩ እንደነበር አልተረጋገጠም ፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የሽርክና ማህበር በህግ አግባብ ተቋቁሞ እየሰራ ነበር ለማለት የሚቻለው የጽሁፍ ውል መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ግራ ቀኙ በጋራና በተናጥል በመተባበር በመስራት ከጥቅሙ ይሁን ዕዳው በጋራ ሲጋሩ እንደነበር በውል መንፈስና ይዘት የሚፈጽሙበት አግባብ የነበረ ስለመሆኑ የሽርክና ማህበሩ የነበረበት ነባራዊ ሁኔታ ይህንን እንደማያሳይ የስር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን በስልጣናቸው ከድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተመሰረተ የሽርክና ማህበር ውል የለም ማለታቸው በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን የማያሳይ ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/197575 በ19/07/2005 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/135286 በ30/11/2005 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ ጸንቷል፡፡
2. በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተመሰረተ የሽርክና ማህበር ውል የለም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.96990

ሐምሌ 01/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አያሌው ወልዴ ዩሐንስ - ጠበቃ ስንታየሁ ባሕሩ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጀማል ሰማን ኑር - ጠበቃ አማኑል ኩመራ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የሽርክና ውል ስምምነት የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካች የቀረበው ክስ ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታይልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከነበረው በአዲስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 1088 ተከራይተው ሲሰሩ እንደቆዩ፤በዚህ ቤት በሥር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ /የአሁኑ ተጠሪ/ ከነበረው ሰኔ 21 ቀን 2002 ዓ.ም በተፈፀመ የሽርክና ውል የቁርስ ቤት ንግድ ሥራ በጋራ ሲሰሩ የነበሩ ሲሆን አስተዳደሩ የአከራይ ተከራይ መመሪያው ያለአግባብ በመተርጎም ለተጠሪ አከራይተሃል በማለት የኪራይ ውል ማቋረጡን በአግባቡ አይደለም፡፡ተጠሪም የንግድ መደብሩ ያለአግባብ ይዘው ስለሚገኙ እንዲለቁ፤በተፈፀመው የሽርክና ውል ግዴታ መሠረት ውሉን ለማፍረስ የሞከሩ ስለሆነ የገደብ መቀጮ ለአመልካች ብር 10,000.00 ለመንግሥት ብር 5,000 እንዲከፍሉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት የመከላከያ መልስ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱ ፡- በአመልካች እና ተጠሪ ተደረገ የተባለው የሽርክና ውል በንግድ ሕጉ መሠረት የማይታወቅ ነው፡፡ የተደረገ መዋጮ የለም፡፡የንግድ ቤቱን ሰኔ 21 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገው ውል መከራየታቸው ፤በየወሩም 2500 ብር እንደሚከፍሉ፤የሽርክና ውል የፈረሙት አመልካች ስለአስፈራሩዋቸው በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም ?የሚለው በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካች እና ተጠሪ ተደረገ የተባለው የሽርክና ውል በሕጉ አግባብ የተመሰረቱ ስለመሆኑ ጉዳዩን ለማጣራት የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ የሰውና የሰነድ ማስረጃ መርምሮ የሽርክና ውል የለም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጣቸው መሠረታዊ ነጥቦች የሽርክና ስምምነቱ በጽሑፍ ከመደረጉ በቀር አብሮ የመሥራት የመተባበር እንዲሁም የትርፍና ኪሣራ ክፍፍል ሥርዓት ምን እንደነበር የተገለጸ ነገር የለም ሲል በውሳኔው አስፍሯል፡፡ በመሠረቱ አንድ የሽርክና ማህበር የሚቋቋመው በንግድ ሕግ አንቀጽ 10/1/ እንደተመለከተው የንግድ ሥራ ለማከናወን ሲሆን ፣ የንግድ ሥራ ምን እንደሆነም በዚህ ሕግ አንቀጽ /5/ ሥር ተዘርዝሯል፡፡ የንግድ ማህበር /ሽርክና/ትርጓሜ መሠረታዊ ባህርያት በንግድ ሕግ አንቀጽ 210/1/ እና 211 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የሽርክና ማህበር ሕጋዊ ሰውነት ያለው በሽርኮቹ ውል የሚቋቋም ዓላማውም ኢኮኖሚያዊ ተግባር ለማከናወን ስለመሆኑ፤ሽርኮቹም አብረው ለመሥራትና ለመተባበር የተስማሙ፤ከሚገኘው ተርፍም ሆነ ከሚመጣው ዕዳ ተከፋይ እንደሚሆኑ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 211፣215 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ ሽሪኮቹ የመዋጮ ዓይነት ልክ መወሰን እንደሚችሉ፤መዋጮው በገንዘብ ፣በዓይነት ወይም በጉልበት ሊሆን እንደሚችል ፤ይሁንና የመዋጮው ዓይነት ልክ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር መዋጮዎቹ ብዛታቸው እኩል እንደሚሆን፤ለማህበሩ ዓላማ የሚስማሙ እንዲሆኑ እንደሚያስፈልግ የንግድ ሕግ አንቀጽ 229/2/ በግልጽ ደንግጓል ፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመልስ የሥር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ሥልጣኑ በአመልካች በኩል የቀረቡ ምስክሮች ከተጠሪ ጋር የሽርክና ውል ተፈራርመዋል ያሉ ቢሆንም ውሉ ሲፈረም የሽርክና ውል ስምምነቱ መዋጮ ምን ያህል እንደሆነ እንደማያውቁ በአንፃሩ በተጠሪ በኩል የቀረቡ ምስክሮች ከ1997 ዓ.ም እስከ አሁን ድረስ ሱቁን ተከራይቶ ይሰራ እንደነበር የሽርክና ውሉም ሊዋዋል መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ውድቅ እንዲሆን ማመልከታቸውን ያሳያል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል በሕግ አግባብ የተቋቋመ የሽርክና ማህበር የለም ። በተጠሪ የቀረቡ ምስክሮች የግራ ቀኙ ግንኙነት የአከራይ ተከራይ መሆኑን ሚዛን በሚደፋ መልኩ ማስረዳት የቻሉ መሆናቸው ችሎቱ መገንዘቡን በመግለጽ የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጐታል። አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም ። ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓል።አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የግራ ቀኙ ግንኙነት በሽርክና ውል የተመሰረቱ ስለ መሆኑ አመልካች ድርጅቱ ከነ ፊቃድ እና መልካም ስምና ዝናው ሊያዋጡ ተጠሪ ደግሞ የመነገኛ ገንዘብ እንዳቀርቡ ፤የሽርክና ውሉ አለመመዝገቡ ውድቅ እንደማይሆን እንደ የአሸሙር ማህበር ሊወሰድ እንደሚገባ፣የ73 ዓመት ዕድሜ ባለጸጋ እና ሌላ የገቢ ምንጭ የሌላቸው መሆናቸው የአከራይ ተከራይ ግንኙነት መመሪያ ቁጥር 4/2004 ዓመት ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባቸው በመግለጽ ተከራክሯል። ተጠሪ በበኩላቸው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው ግንኙነት የአከራይ ተከራይ መሆኑን አስተዳደሩ ማጣራቱ ፤አመልካች የሽርክና ማህበር ለመመስረት የሚያስችል ምንም ያዋጡት ነገር አለመኖሩን ፣የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በማጣራት መወሰኑ ፤የመመሪያ ቁጥር 4/2004 ተጠቃሚነኝ የሚለው ክርክር መቅረብ የነበረበት ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች መሆኑን፤የሥር ፍርድ ቤቶች የሽርክና ውል የለም በማለት መወሰናቸው በአግባቡ ነው፣ሊጸና ይገባል በማለት መልስ ያቀረቡ መሆኑን ተረድተናል ።የአመልካች የመልስ መልስም አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ነው።

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር፤ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመርነውም የሥር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል ተፈረመ የተባለው የሽርክና ውል በንግድ ሕግ የተመለከቱት መሠረታዊ መመዘኛዎች ያሟላ አይደለም በማለት ውድቅ ሊያደርግ የቻለው ከሳሽ/አመልካች/ ውሉን ካልፈረምክ ከሱቁ አስወጣሃለው በሚል አስገድደውት እንደሆነ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት የአከራይ ተከራይ ግንኙነት መሆኑን የሽርክና ስራ እንደማይሰሩ መመስከራቸውን ውሣኔው ማስፈሩን ተረድተናል።የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ያረጋገጠውን ጉዳይ ይዘን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር ስናገናዝበው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የንግድ ሕጉ በደነገገው አግባብ በጋራ መስራትና መተባበር ፤መዋጮ ስለመኖሩ ፤ከድርጅቱ ከሚገኘው ትርፍ የተደረገ ክፍፍል ስለመኖሩ የቀረበ ክርክር የለም። እንዲህ ከሆነ ደግሞ በግራ ቀኙ የተደረገው የሽርክና ውል በንግድ ሕግ አንቀጽ 211 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተመለከቱት አስገዳጅ መመዘኛዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለመሟላታቸው በሕጉ አግባብ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ተመሰረቱ የተባለው የሽርክና ማህበር በንግድ ሕጉ በተመለከተው የሽርክና ማህበር ማቋቋሚያ መስፈርት ያልተቋቋመ በተግባርም መሬት ላይ የሌለ መሆኑ ከአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ግንኙነት በሽርክና ውል ላይ የተመሰረተ ሳይሆን የሥር ፍርድ ቤት እንዳለው የአከራይ ተከራይ ግንኙነት ነው፡፡

አመልካች በሰበር ቅሬታቸው የተደረገ መዋጮ መኖሩ፣የትርፍ ክፍፍል ስለመደረጉ እና ሽርክናው በ 3ኛ ወገን አለመታወቁ ውጤቱ የአሸሙር ማህበር የሚመለከት እንደሆነ ፍርድ ቤት ግንዛቤ አለመወሰዱን ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ግራ ቀኙ ግንኙነት በሽርክና ውል ላይ የተመሰረቱ ስለመሆኑ ተደረገ የተባለው ስምምነትም አረጋጋጭ በማድረግ አቅርበዋል፡፡የአመልካች የክርክር መስመር ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ ከተያዘው ጭብጥ የሚጣጣም ካለመሆኑ በተጨማሪ የሽርክና ውል በቀረበበት ሁኔታ ስለመዋጮ እና የትርፍ ክፍፍል ሥርዓት በተመለከተ ግን ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደ እሽሙር ማሕበር ግንዛቤ እንዲወሰድ ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የለውም፡፡በሌላ በኩል አመልካች አቅመ ደካማና የ73 ዓመት ዕድሜ ባለፀጋ በመሆናቸው የመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6.1 ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚገባ በሰበር አቤቱታቸው ገልጸዋል፡፡ በመሠረቱ አመልካች ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329(1) ሥር የተመለከተው ፍሬ ሐሳብ ያላገናዘበ ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የመመሪያው ልዩ ተጠቃሚ መሆን ነበረብኝ በማለት ያቀረቡት ክርክር በግራ ቀኙ ነበረ ከተባለው የሽርክና ውል ስምምነት የማይጣጠም ነው፡፡ጉዳዩም መቅረብ ከነበረበትም ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ነው በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ ማድረጋቸውን በሕግ አተረጓጎምና አተገባበር ረገድ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸማቸውን አያሳይም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.194434 በ12/09/2005 የሰጠው ፍርድ፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.138064 በ 21/02/2006 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ጸንቷል ፡፡
2. በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተመሰረቱ የሽርክና ማሕበር የለም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ት እ ዛ ዝ</u>

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 100621

ሐምሌ 3 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ሉልሰገድ ምጆ- ጠበቃ ደሳለኝ ድረስ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. አንድነት ቅቤና ቅመማቅመም ነጋዴዎች /አ.ማ/ ጠበቃ ይልማ አቻሜ ቀረቡ

2. ወ/ሮ አለምፀሐይ ሞጆ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 205328 ህዳር 13 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150124 መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ይርጋ የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ የሚወለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ እናቱን ወ/ሮ አማራች ኦዳ በቀድሞው ወረዳ 5 ቀበሌ 06 በአዲሱ አጠራር አዲስ ከተማ 10/11/12/ የመደብ ቁጥሩ 1 የሆነ የቅቤ ንግድ ችርቻሮ የሚነግድበት መደብ ነበራቸው በአካባቢው ያሉ ነጋዴዎች ተደራጅተው አክሲዮን ማህበር 1990 ዓ.ም ሲመሰርቱ እና የአንደኛ ተከሳሽ መሥራች አባል ሆነው አንድ የአክሲዮን ድርሻ ነበራቸው፡፡ እናቱ ወ/ሮ አማረች ኦዳ ታህሳስ 27 ቀን 1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፡፡ ሆኖም እናቱ ታህሳስ 27 ቀን 1997 ዓ.ም መሞቷ እያታወቀ አንደኛ ተከሳሽ መጋቢት 24 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የአክሲዮን ማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በህይወት እንደለች በማስመሰል ስሜን በአባላት ሥም ዝርዝር ላይ በመፃፍና ሀሰተኛ ቃለ ጉባኤ በማዘጋጀት በአክሲዮን ማህበሩ የነበረትን አንድ የክሲዮን ድርሻ ለሁለተኛ ተከሳሽ እንደሸጠች አድርጉ የአክሲዮን ባለቤትናቱን ለሁለተኛ ተከሳሽ አዛውሯል፡፡ ይህንን በሀሰት የተከናወነ ተግባር የተፈፀመ መሆኑን ያወቅሁት በጥቅምት ወር 2005 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ ሀሰተኛ ቃለ ጉባኤ ተሸሮ የአክሲዮን ድርሻው የወ/ሮ አማረች አዳ ወራሽ በሆንኩት በከሳሽ ስም እንድመዘገብ ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

2. ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በተከሳሽነት ቀርበው የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በከሳሽ እናት ስም የነበረው የክሲዮን ድርሻ ለሀለተኛ ተከሳሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ የተወሰነው መጋቢት 24 ቀን 1998 ዓ.ም ነው፡፡ የአንደኛ ተከሳሽ ባለ አኪስዮኖች ጉባኤ ቃለ ጉባኤ የካቲት 9 ቀን 1999 ዓ/ም በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ቀርበው ተመዝግቧል፡፡ ከሳሽ ቀለ ጉበኤው እንዲሻር መጠየቅ የሚችለው መጋቢት 24 ቀን 1994 ዓ/ም ጀምሮ ወይም ቃለ ጉባኤው በተመዘገበበት የካቲት 9 ቀን 1999 ዓ/ም ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ነው ከሳሽ ጥያቄ ያቀረቡት ሚያዚያ 15 ቀን 2005 ዓ/ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተከሳሾች ያቀረቡት መቃወሚያ የንግድ ህግ ቁጥር 4/6(2) መሠረት ያደረገ ነው በማለት የከሳሽ ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

3. አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በንግድ ሕግ ቁጥር 416 ንዑስ አንቀጽ 2 በያዝነው ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ጉዳዩ የወንጀል ድርጊት የተፈፀመ መሆኑን የሚያሳይና የወንጀል ምርመራ እየተጠራ በመሆኑ የይርጋው የጊዜ ገደብ በወንጀል ህጉ የተመለከተው አስራ አምስት ዓመት መሆን አለበት ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በስር ታይቶ ይሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች ሀምሌ 02 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት መልስ የሚች እናት አክሲዮኑን የሸጡት የካቲት 21 ቀን 1996 ዓ/ም ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በንግድ ህጉ ቁጥር 416 (2) የተመለከተው የሶስት ወር የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሀምሌ 22 ቀን 2006 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጡት ብይን ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ክስ ያቀረበው፣ አንደኛ ተጠሪ ተህሳስ 27 ቀን 1997 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችውን ወላጅ እናቴ፣ በህይወት ያለች በማስመሰልና መጋቢት 24 ቀን 1998 በተደረገው የባለአክስዬኖች ጉባኤ ስሜን በመመዝገብ ሀሰተኛ የሆነ ቃለ ጉባኤ በማዘጋጀት የእናቴን ድርሻ ለሁለተኛ ተጠሪ እንዲተላለፍ በመወሰን የአክሲዮን ድርሻዎን ለሁለተኛ ተጠሪ አስተላልፏል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ይህንን ተግባር የፈፀመ መሆኑን ያወቅሁት በጥቅምት ወር 2005 ዓ/ም በማለት ነው፡፡ ይህም የአመልካች ጥያቄ አንድ ሰው የሲቪል መብትና ግዴታ የሚኖረው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ መሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1 የተደነገገ ሆኖ እያለ አንደኛ ተጠሪ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለያች በኃላ እናቴን በባለአክሲዬኖች ጉባኤ ላይ እንደተገኘች አድርጎ በሀሰት በመመዝገብ የአክሲዬን ድርሻ ዝውውር ፈፅሟል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

6. አንድ ሰው የሲቪል መብትና ግዴታ የሚኖረው በህይወት ባለበት ጊዜ መሆኑ ሟች ከዚህ ዓለም በሞት ከተለያየ በኃላ በሟች መሞት የማይቋረጡ መብቶችና ግዴታዎች ለወረሾቹ የሚተላለፍ መሆኑ በፍተብሔር ህግ ቁጥር 1 እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ ማናቸውም አክስዬን ማህበር፤ በመመሥረቻ ፅሑፍም ሆነ በመተዳደሪያ ደንቡ ወይም በባለአክሲዬኖች ጉባኤው በህይወት የሌለ የአክስዮን ባለ ድርሻ በህይወት አንዳለ ተደርጎ በባለአክሲዮን ጉባኤ ላይ ስመ እንዲመዘገብና በለ አክሲዮኑ ከሞተ በኃላ የባለ አክሲዮኖች ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ በህይወት እንዳለ ተቆጥሮ እንዲፈፀምበት ለመደንገግ መብትና ሥልጣን የለውም፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካች የሚያቀርበው ጥያቄ በሟች ምትክ የሟችን ወራሽ መጥረትና በባለአክሲዮኖች ጉባኤ እንዲሳተፍ ማድረግ ሲገባው የአክሲዮን ማህበሩ መሥራች የሆነችው ወላጅ እናቴ በሞት የተለያች መሆኑን እያወቀ በሞት ከተለየች ከአንድ ዓመት በኃላ በግል አክሲዮኖች ጉባኤ ላይ እንደተገኘች አድርጎ ስሟን በመመዝገብና የሀሰት ቀለ ጉባኤ በማዘጋጀት የፈፀመው የአክሲዮን ድርሻ ዝውውር ፈራሽ ይሁንልኝ በማለት ነው፡፡

7. ይህ የአመልካች ጥያቄ ህግ አውጭው በንግድ ህግ ቁጥር 416 ንዑስ አንቀፅ 2 የሶስት ወር የይርጋ የጊዜ ገደብ ሲደነግግ ተሳቢ ካደረጋቸው ጉዳዮች ጋር አንድ አይነት ካለመሆኑም በላይ አንድ አክሲዮን ማህበር ባለ አክሲዮኑ ሲሞት የባለአክሲዮኑ ወራሾች ሣይጠራ የሞተውን ባለ አክሲዮን በባለአክሲዮን ጉባኤ ላይ የተገኘ በማስመሰል የወራሾቹን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ውሣኔ ቢወሰን ወራሾች የባለአክሲዮን ጉባኤ የተደረገ መሆኑንና የባለአክሲዮኖች ጉባኤ የእነርሱን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ውሣኔ መወሰኑና ቃለጉባኤውን ማስመዝገቡን እንዴትና በምን ሁኔታ ያውቃሉ? ወራሾች ይህንን ሣያውቁ በንግድ ህግ ቁጥር 416 ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተው የጊዜ ገደብ ቢያልፍ ሁኔታውን ለማስቀየር በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ አለባቸው የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሣ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

8. አንድ ሰው በፍርድ መብቱን ለማስከበር ጥያቄ የሚያቀርበው መብቱ ከተጣሰበት ወይም በመብቱ ሊሰራበት ከሚችልበት ቀን ጀምሮ መሆኑን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1846 ተደንግጓል ። በያዝነው ጉዳይ አመልካች ያቀረበው ጥያቄ በንግድ ህግ ቁጥር 416 ንዑስ አንቀፅ 2 በተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ ቀሪ የሚሆን አይደለም ። ከዚህ አንፃር አመልካች ጉዳዩን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር ዓመታት ውስጥ የአክሲዮን ማህበሩን ጥያቄውን በማቅረብና በክፉ ልቦና የአክሲዮን ድርሻው ተላልፎላቸዋል የሚላቸውን ሰዎች ላይ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻል መሆኑ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1677 ንዑስ አንቀፅ 1 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1845 በጣምራ በመተርጎም ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ አንፃር አመልካች ጥያቄውን ያቀረበው ከላይ የገለፅነው የአስር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ሳያልፍበት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ላቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አግባብነት የሌለውን የንግድ ህግ ቁጥር 416 ንዑስ አንቀፅ 2 በመጥቀስ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል ።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይንና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።
2. የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ወስነናል ።
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ አመልካችና ተጠሪ በሌሎች ነጥቦች ያቀረቧቸውን ክርክሮችና የማራቀኙን ማስረጃ በመስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል ።
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ።

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102725

ሐምሌ 14 ቀን2007ዓ.ም

ዳኞች:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች- 1.አቶ ዲንሳፋ ያዕቆብ - ከጠበቃ ታረቀኝ ተፈራ ጋር - ቀረቡ

2. ወ/ሮ መሰለች አባመላ - ቀረቡ

3. የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ጽ/ቤት

ኃ/ፊጅ ሽመልስ ኃ/ጊዮርጊስ - ቀረቡ

ተጠሪ:- ወ/ሮ አየለች በቀለ - ከጠበቃ ግርማ ዘመድኩን ጋር - ቀረቡ

በዚህ መዝገብ እና ቁጥሩ 103457 እንዲሁም 103944 በሆኑት መዛግብት የቀረቡት ክርክሮች በበታች ፍርድ ቤቶች አንድ ላይ የታዩና የሚያስነሱት የሕግ ጥያቄም ተመሳሳይ በመሆኑ ተጣምረው ተመርምረው የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁኖቹ አመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ ሲሆን የክሱም ይዘት ባጭሩ ከ3ኛ ተከሳሽ የንግድ ቤት ከ1967 ዓ/ም ጀምረው ተከራይተው እየሰሩበት ያሉትን የንግድ ድርጅት ከመስከረም ወር 2000 ዓ/ም ጀምሮ ለአቶ ዲንሰፋ ያእቆብ በወር ብር 3500.00፣ለአሁኗ 2ኛ አመልካችም በወር በብር 800.00 ያከራዩ መሆኑን፣የአሁኑ 3ኛ አመልካች ደግሞ ከተጠሪ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል አቋርጦ ለ1ኛ አመልካች ኪራዩን ማስተላለፉን፣ተጠሪ ለ1ኛ አመልካች ያከራዩት የንግድ ድርጅት እንደሆነና ይህም በሕጉ የተፈቀደ ከመሆኑም ንግድ ቤቱን ያከራዩት ባለባቸው የጤና ችግር ተንቀሳቅሰው ሊሰሩ ባለመቻሉና በዚህ ንግድ ቤት በሚገኝ ብቻ የሚተዳደሩ መሆኑን ጠቅሰው 3ኛ አመልካች የፈጠረው ሁከት ተወግዶ በቤቱ ላይ የተከራይነት መብት ተጠብቆላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጠቀም እንዲቀጥሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ 1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ተጠሪ በቤቱ ላይ የነበራቸው የኪራይ ውል የተቋረጠ በመሆኑ ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ከአስቀደሙ በኋላ በፍሬ ነገሩ ደግሞ ከተጠሪ የተከራዩትን ቤት ለሁለት ከፍለው በማከራየታቸው በመመሪያ ቁጥር 4/2004 ተግባራዊ ሲደረግም በቤቱ እየተጠቀሙ የነበረ በመሆኑ ተከራይነታቸው የተረጋገጠላቸው መሆኑን፣የአሁኗ 2ኛ አመልካች ሲሰሩበት የነበረው ክፍል ደግሞ ለተጠሪ እንዲሆን የተደረገ መሆኑንና ይህን ደብቀው ምንም ገቢ የለኝም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢነት የሌለው መሆኑንና 3ኛ አመልካችም ያስተላለፈላቸው በመመሪያው አግባብ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፤፤ 2ኛ አመልካች በበኩላቸው ተጠሪ የቤት ቁጥር 073 የሆነውን በከፊል አከራይተዋቸው ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ እየተገለገሉበት ያለ መሆኑን፣3ኛ አመልካችም በወረደው ዲዛይንና ግንባታ ፅ/ቤት በኩል ቤቱን ለተጠሪ፣ለ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ሊተላለፍ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ወደ ጎን በመተው ለ1ኛ አመልካች እንዲተላለፍ መወሰኑ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፤፤

የአሁኑ 3ኛ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ውል የሌላቸው በመሆኑ ክስ ለመመስረት መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን፣ተጠሪ ሁከት እንዲወገድላቸው ያቀረቡት ሱቅ በክሱ ጊዜ በይዞታቸው ስር ያልነበረ በመሆኑ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ፣ተጠሪ ቁጥሩ 073 የሆነው ቤትን ሽንሽነው ለሶስተኛ ወገን ያስተላለፉ በመሆኑ አንደኛውን የተሸነሸነውን ተጠሪ እንዲሰሩበትና በሌላው ላይ የአሁኑ 1ኛ አመልካች እንዲሰሩበት የተደረገው መመሪያውን መሰረት በአደረገ መልኩ መሆኑን፣ተጠሪ በመመሪያው በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ስለመሆኑ ማስረጃ ያለማቅረባቸውንና አቅመ ደካማ ቢሆኑ እንኳን በመመሪያው መሰረት ራሳቸው የሚሰሩበትን ክፍል ብቻ እንዲፀድቅላቸው የሚያደርግ ስለመሆኑና በዚህም መሰረት አመልካች ተጠሪ አንድ ሽንሻኖ ላይ እንዲሰሩበት ተወስኖ የኪራይ ውል እንዲዋዋሉ ያደረገ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም በ1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የቀረቡትን መቃወሚያዎችን ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክርና የተጠሪን ምስክሮችን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ ለ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ያከራዩት የንግድ መደብር ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ያለፈው ሲሆን የኪራይ ውል ተጠቃሚነትን በተመለከተ ግን ተጠሪ አቅመ ደካማ፣የቤተሰብ አስተዳዳሪና ሌላ ገቢ የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጦአል በሚል ድምዳሜ እና የ3ኛ አመልካች ተግባርም በመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀፅ 6(2) ስር በልዩ ሁኔታ የተቀመጠውን የተጠሪን ተጠቃሚነት የሚፃረርና የሁከት ተግባር ነው በማለት ተጠሪ ቁጥሩ 073 የሆነውንና በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቤት ተጠሪ በመሉም ሆነ በከፊል እንዲለቁ የተደረገው ተግባር እንዲቆምና ለተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲመለስላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለየብቻቸው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የአሁኗ 2ኛ አመልካች ግን መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ መዝገቦቹን በተናጠል መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፤፤ የ1ኛ እና 2ኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ሲታይም ተጠሪ ከ3ኛ አመልካች የተከራዩትን የንግድ ቤት ሽንሽነው አከራይተው በመገኘታቸው በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት አንድ ሽንሻኖ ክፍል እንዲቀርላቸው ተደርጎ በመስራት ላይ የሚገኙ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ቁጥሩ 073 የሆነው ቤት ሙሉ በሙሉ ለተጠሪ እንዲመለስላቸው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን 2ኛ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ደግሞ በመመሪያው መሰረት ተጠቃሚ መሆን ሲገባቸው ይኼው ታልፎ የተከራይነት መብቱ ለ1ኛ አመልካች ብቻ ተጠብቆ በሌላኛው ክፍል ተጠሪ እንዲሰሩበት በአስተዳደሩ መወሰኑ ተገቢነት የሌለው ነው የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ሲቀርብ ከተያዙት ጭብጦች አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ ጉዳዩ ሲቀርብ የተያዙት ጭብጦች፡-

1. ጉዳዩ በሁከት ይወገድልኝ ክስ መቅረቡና በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመታየቱን አግባብነት እና
2. ተጠሪ ከሽነሽኑት ቤት በአንዱ እንዲጠቀሙ የተመለሰላቸው ሁኖ እያለ ገቢ የላቸውም ተብሎ አከራካሪውን የንግድ ቤት ሙሉ በሙሉ ሊጠቀሙ ይገባል ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?የሚሉት ናቸው፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ጭብጦች አንፃር አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ክስ የመሰረቱት ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ጋር ያለኝ ግንኙነት የንግድ መደብር ኪራይ ውል ከመሆኑም በላይ በመመሪያ ቁጥር 4/2004 ተጠቃሚነቱ ሊጠበቅልኝ ይገባል በማለት ነው፡፡1ኛ እና 3ኛ አመልካች ደግሞ ተጠሪ ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ጋር በቤት ቁጥር 073 ያላቸው ግንኙነት የንግድ መደብር ኪራይ ውል አለመሆኑንና በመመሪያው መሰረትም ልዩ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠላቸው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በቀጥታ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር የተያያዘ ቢሆንም 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በመካከላቸውን ያለውን ግንኙነት የንግድ መደብር አይደለም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ግንኙነቱ የንግድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መደብር ኪራይን መሰረት ያደረገ ነው የሚል ክርክር አቅርበው ይሄው ጭብጥ ተይዞ የተጠሪ የመመሪያ ቁጥር 4/2004 ተጠቃሚ መሆን ያለመሆን ጭምር እልባት ያገኘ መሆኑን የክርክሩ ይዘት ያስገነዝባል፡፡

መመሪያውን መሰረት አድርጎ የሚነሳ የንግድ ቤት የተከራይነት መብት ጥያቄ ከከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣን እና ተግባር ጋር እንዲሁም የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር የተያያዘ እስከሆነ እና የከተማው አስተዳደር አካልም በተከሳሽነት የተሰየመ እስከሆነ ድረስ ደግሞ የዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ተቀብሎ የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር በአንቀጽ 41(1) (ለ) እና (ረ) ስር በግልጽ የተመለከተ ነው፡፡

የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በቀጥታ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪን የመመሪያ ቁጥር 4/2004 ተጠቃሚት ጥያቄን ከንግድ መደብር የዳኝነት ጥያቄ ጭምር በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየት እንደሚገባው ተገንዝቦ ጉዳዩን መመልከቱ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም የክሱ ዝርዝር ይዘት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች አግባብ የሚታይ የሁከት ጉዳይ ሳይሆን ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈፃጸም ጋር የተያያዘና በዋንኝነትም የንግድ መደብር ኪራይ መኖር ያለመኖሩን ሁሉ የሚያካትት ክርክር በመሆኑ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ መታየቱ ከውጤት አንጻር ሲታይ የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፦-ተጠሪ ከ3ኛ አመልካች የተከራዩትን የንግድ ቤት ከአከራዩ ፈቃድና እውቅና ውጪ ለ1ኛ አመልካች አከራይተው መገኘታቸው ተረጋግጦአል፡፡ አመልካች ለ1ኛ አመልካች አከራየሁ የሚሉት የንግድ መደብሩን ነው ይበሉ እንጂ ይህ ስለመሆኑ ማስረዳት አለመቻላቸውን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ 2ኛ አመልካች የተጠሪ ልጅና ቤቱ ተሸንሽኖ ከተገኘው አንዱ ክፍል በተጠሪ ንግድ ፈቃድ የሚሰሩና የተጠሪ ልጅ መሆናቸው ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ የተደረገው ክርክር፣በሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር የሚያስረዳ ሲሆን 2ኛ አመልካች የተጠሪ ልጅ ያለመሆናቸውንና ይሰሩበት የነበረው የንግድ ፈቃድም የተጠሪ ያለመሆኑን በሚመለከት የቀረበ ክርክርና ማስረጃ የለም፡፡ እንዲሁም 2ኛ አመልካች በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር መልስ ሰጪ የሆኑት የአሁኑ 1ኛ አመልካች ባስከፈቱት የይግባኝ መዝገብ ሲሆን በዚህ መዝገብ በሰጡት መልስም 1ኛ አመልካች በመልስ ሰጪነት ያስጠሩት በማይመለከታቸው ጉዳይ ስለመሆኑ ጠቅሰው ይግባኙ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልስ ከመስጠታቸው በተጨማሪ በመስቀለኛ ይግባኝ ደግሞ ቤቱ ለሶስት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከፍሎ ራሳቸው የያዙት ክፍል ግን በራሳቸው ይዞታ እንዲቀር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 142239 ከተሰጠው ውሳኔ ይዘት ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም 2ኛ አመልካች የተጠሪ ልጅ ከመሆናቸውን በላይ በተጠሪ የንግድ ፈቃድ የሚሰሩ መሆናቸውንና እንዲሁም ከተጠሪ ጋር ያላቸው የተከራይነት ግንኙነት ስላለመሆኑ በግልጽ ያልተካደ ጉዳይ መሆኑን ከክርክር አቀራረብ ሂደት ተገንዝበናል፡፡በሌላ በኩል 1ኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያላቸው ግንኙነት የተከራይ ተከራይነት መሆኑና የሚሰሩትም በራሳቸው የንግድ ፈቃድ መሆኑ አከራካሪ የሆነ አይደለም፡፡3ኛ አመልካችም ተገቢው ግብረሃይል ተቋቁሞ ጉዳዩን አጣርቶ ባቀረበትና በመመሪያው መሰረት በተዘረጋው ስርዓት አግባብ በጸደቀው የአስተዳደር ውሳኔ መሰረት 1ኛ አመልካች የያዙት ክፍል በመመሪያው መሰረት ተላልፎላቸው ቀሪውን ክፍል በተመለከተ ግን ተጠሪ እንዲጠቀሙ ያደረገ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በመመሪያው በተዘረጋው ስርዓት መስረት የተሰጠውን አስተዳደራዊ ውሳኔ በአስተዳደር አካሉ አልተወሰነም ወይም በበላይ አካል የተሻረ ነው በማለት ክርክር ሳያቀርቡ አጥብቀው የሚከራከሩት አቅመ ደካማና ገቢ የሌለኝ በመሆኑ 1ኛ አመልካች የያዙት ክፍል ጭምር ሊወሰድብኝ አይገባም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ተጠሪ አቅመ ደካማና ከአስተዳደሩ በተከራዩት ቤት አከራይተውና ሰርተው ከሚያገኙት ገቢ ሌላ ገቢ የሌላቸው መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማሰረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዳለ የሚቀበለው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አቅመ ደካማና ገቢ የሌላቸው መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ የምንቀበለው ሲሆን ይህ ነጥብ ተይዞ በሕግ ጥያቄነት ሊታይ የሚገባው ግን አከረካሪው ቤት ለተጠሪ ሊመለስላቸው የሚገባው ሙሉ በሙሉ ነው ወይስ በከፊል ነው የሚለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ተጠሪ አድራጎታቸው በመመሪያው አግባብ በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ ሊያደርገኝ ይገባል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ምንም ገቢ የሌለኝ ስለመሆኑ ተረጋግጧል የሚል ምክንያት ነው፡፡ይሁን እንጂ በተጠቃሹ የመመሪያው ድንጋጌ ከተመለከተው ዝርዝር የልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ የሆነው ምንም ገቢ የሌለው መሆን ብቻውን ተቀባይነት የለውም፣ምንም ገቢ የሌለው መሆን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሁኔታዎችም ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡በዚሁ ድንጋጌ አቅመ ደካማ፣አዛውንት፣ወይም ወላጅ ያጡ ሕጻናት፣የኤች አይ፣ቪ ህመምተኞችና የአልጋ ቁራኞች የሚሉት ሁኔታዎች ተዘርዝረው ሌሎች የገቢ ምንጮች እንደሌላቸው ከሚመለከተው ሕጋዊ ተቋም ማስረጃ ካቀረቡ" ከሚለው ዓረፍተ ነገር ጋር “ከሆኑና” በሚለው ቃል ጭምር መያያዛቸው ገቢ ያለመኖር ብቻውን የልዩ ተጠቃሚነት መብትን የማያስገኝ መሆኑን የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡በመሆኑም ምንም ገቢ ካለመኖር በተጨማሪ አቅመ ደካማ፣አዛውንት፣ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወላጅ ያጡ ሕጻናት፣የኤች አይ፣ቪ ህመምተኞችና የአልጋ ቁራኞች ከሚሉት ሁኔታዎች አንዱ ተሟልቶ መገኘት አለበት፡፡ስለሆነም ምንም ገቢ ያለመኖር ከሌሎች ሁኔታዎች ጋር ድርብ ማሟያ ምክንያት እንጂ ብቻውን መገኘቱ በቂ ያለመሆኑን የድንጋጌው ይዘት የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ምንም ገቢ ያለመኖር ብቻውን በቂ ነው ተብሎ እንዲወሰድ ማድረግም መመሪያው የወጣላትን መሰረታዊ አላማ ያሳካል ተብሎ የማይታሰብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡የመመሪያው መሰረታዊ አላማ በመንግሰት ቤቶች ላይ በተከራዮች የተፈጠረውን ችግር መቅረፍና የመላውን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ መሆኑን የመመሪያው መግቢያ ያስረዳል፡፡ ገቢ የሌለውና ከላይ የተመለከቱትን የመመሪያውን መስፈርቶችን የሚያሟላ ተከራይ የመንግስትን ቤት ሸንሽኖ ማከራየቱ ከተረጋገጠ ደግሞ አፈጻጸሙ ከኑሮው መተዳደሪያ ሊሆን የሚችል ክፍል ቀርቶ ሌላው የተሸነሸነ ክፍል ከተከራዩ ለተከራዩት ሰዎች ሊሆን እንደሚገባ የመመሪያው አንቀፅ 6(1) እና (2) ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ገቢ የለኝም በማለታቸው ራሳቸው ያሰሩበት የነበረው ክፍል እንዲቀርላቸው ተደርጎ ሌላው ክፍል ለ1ኛ አመልካች እንዲተላለፍ መደረጉ የመመሪያውን ትክክለኛ አፈፃጸም የሚያስገነዝብ እንጂ ሕገ ወጥ ተግባር አይደለም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አንጻር መመልከት ሲገባቸው ከተጠሪ ገቢ ያለመኖር ብቻ በመመልከት የሰጡት ውሳኔ የመመሪያውን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም መሰረታዊ አላማ ያላገናዘበ ነው፡፡በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 196499 በ23/11/05 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 142245 በ24/10/2006፣በመ/ቁጥር 142239 በ24/10/2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 1ኛ አመልካች አቶ ዲንሰፋ ያዕቆብ ከተጠሪ የተከራዩትን ክፍል ሊለቁ አይገባም ብለናል፡፡
3. 2ኛ አመልካች ወ/ሮ መሰለች አባመላ የያዙት ክፍል ለተጠሪ እንዲሆን የተወሰነ በመሆኑ ተጠሪ በዚሁ ክፍል ተጠቃሚነታቸው ሊቀጥል ይገባል ብለናል፡፡

4.. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/103717

ሐምሌ 03 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሰራተኞች ሸማቾች ህብረት ስራ ኃ.የተ.የግል ማህበር

ተወካይ ጥላሁን ንዋይ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- የአዳማ ወረዳ ንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርመሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉደዩ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 መሠረት የተቋቋመ ሸማቾች ህብረት ስራ ኃ.የተ.የግል ማህበር በአዋጅ የንግድ ፋቃድ የሚያስፈልገው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክር የጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁን ተጠሪ እና በአቶ ዘላለም ታዬ በወ/ሮ በድሪያ ሁሴን እና በአቶ ዮናስ አስፋው ላይ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም አመልካች ቁጥራቸው 205 በሚሆኑ አባላት በአዋጅ ቁጥር 14791እና 402/96 ድንጋጌዎች አግባብ የተቋቋመ ሆኖ ከሚመለከተው አካል ህጋዊ ሰውነት አግኝቶ የማህበሩን አባላትና የአካባቢው ህብረተሰብ እያገለገለ መቆየቱን በወንጅ አካባቢ ወፍጮ ቤትና ዳቦ ቤት ከፍቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ እያለ የተጠሪ ሰራተኞች የሆኑትና የስር ከ2ኛ እስከ 4ኛ የተጠቀሱት እነ አቶ ዘላለም ታዩ አመልካች እየሰራ ያለውን ሰራ ንግድ ፍቃድ እንደሚያስፈልገው አመልካች እንደማያስፈልገው አመልካች እየነገራቸው ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ.ም ወፍጮ ቤትንና ዳቦ ቤቱን ያለአግባብ ያሸጉት መሆኑን በዚህ አድራጉት ምክንያትም አመልካች ሲያገኝ የነበረውን ገቢ ያሳጡና ለሰራተኞቹም ያለ ምንም ገቢ ደመወዝ እንዲከፍል ያደረጉ መሆኑን በዚህ ምክንያት የታጣ ገቢ መጠንና አመልካች ላይ የደረሰውን ወጪ አይነቱንና መጠኑን በመጥቀስ ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕገወጥ መንገድ ያሸገውን የወፍጮ ቤትና የዳቦ ቤት እንዲከፍት የተቋረጠ ገቢና ያለአግባብ ወጪ የሆነ ገንዘብ በድምሩ ብር 34.982.28 ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁ የሚያሳይ ነው ። የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 147/91 የተቋቋመ ቢሆንም ከዚህ አዋጅ በኃላ የወጣው አዋጅ ቁጥር 686.2002 ማንኛውም የንግድ ስራ የንግድ ፍቃድ የሚያስፈልገው መሆኑ መደንገጉን በመቀነስ ከህግ የአወጣጥ ጊዜ ቅደም ተከተል አንፃር ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሆኑን አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረት የመቆጣጠር ስራ ደግሞ የተጠሪ መሆኑ እና ተጠሪ በሠራተኞቹ አማካኝነት ኃላፊነቱን ሲወጣ ላከናወነው የማሸግ ስራ ለታጣ ጊዜ የሚጠየቅበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የሥር 2ኛ 3ኛ፣ እና 4ኛ ተከሳሾች የተጠሪ ስራተኞች በመሆናቸው በግላቸው የሚከሰሱበት አግባብ የለም በማለት ክሱ ውጪ ከአደረጋቸው በኃላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለውን ክርክር መርምሮ ከሕግ አወጣጥ የጊዜ ቅደም ተከተል አንፃር በኃላ የወጣው አዋጅ ቁጥር 686/2002 ሆኖ ይህ አዋጅ በአንቀጽ 31/2/ እና 42 ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ ማንኛውም የንግድ ስራ የሚሰራው በንግድ ፍቃድ መሆኑን የሚደነግግ መሆኑን እንደሚያስገነዝብና ይህ አዋጅ የአዋጅ ቁጥር 147/91 በአዋጅ ቁጥር 402/96 እንደተሻሻለው አዲስ አዋጅ በመሆኑ የበላይ ተፈፃሚነት አለው በማለት አመልካች ያለ ንግድ ፍቃድ የወፍጮ ቤትና የዳቦ ቤትን ስራ ሊሰራ አይችልም የንግድ ስራን የመቆጣጠር ኃላፊነት ደግሞ የተጠሪ በመሆኑና ተጠሪ ይህንኑ በሕጉ የተሰጠውን ኃላፊነት ሊወጣ ለታጣ ገቢ ኃላፊ የሚሆንበት አግባብ የለም በማለት የአመልካችን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጐታል በዚህ ውሳኔ የአሁን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም። አመልካች የሰበር አቤቱታውን በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ተብሎ አቤቱታው ተሰርዞበታል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም በጉዳዩ ልዩ ህግ የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 በአወጅ ቁጥር 402/96 እንደተሻሻለ ሆኖ እያለ የበታች ፍ/ቤቶች አግባብነት የሌለውን አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረት በማድረግ አመልካች ለሚያከናውናቸው የወፍጮ ቤትና የዳቦ ቤት ስራዎች የንግድ ፍቃድ ያስፈልገዋል። በማለት መወሰናቸው ያለአግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲያከራክር አድርጓል።

በክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታም መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር ጉዳዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ለጉዳዩ ያዘገት ያለው ህግ የትኛው ነው? የሚለው ነጥብ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ለክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቸለው አመልካች በአዋጅ ቁጥር 147/91 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 402/96 የተቋቋመ መሆኑንና የወፍጮ ቤትና የዳቦ ቤት ክፍቶ ሲሰራ መገኘቱ ግራ ቀኙን ያላከራከሩ ጉዳዩች መሆናቸውን ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው የሕግ ነጥብ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 686/2002 በተደነገገው አግባብ የንግድ ፋቃድ የሚያስፈልገው መሆን ያለመሆን የሚመለከት ነጥብ ስለመሆን ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 686/2002 በአዋጅ ቁጥር 147/91 እና አዋጅ ቁጥር 402/96 በኃላ የወጣ አዲስ አዋጅ መሆኑና ይህ አዋጅ በማንኛውም የንግድ ስራ የንግድ ፋቃድ የሚያስፈልገው መሆኑን መደንገጉን መሠረት በማድረግ አዲስ አዋጅ ለጉዳዩ የበላይ ተፈፃማነት አለው በማለት ወስነዋል፡፡ በመሆኑም ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህን አተረጓጐምና አተገባበር የተጠቃሽ ሕጐችን ሙሉ ይዘትና መንፈስ የተከተለ መሆን ያለመሆን እንደሚከተለው አይተናል፡፡

በመሠረቱ የህብረት ስራ ማህበት የፌዴራል ደረጃ አዋጅ ቁጥር 147/1991 እና በማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 402/1996 እንዲሁም በደንብ ቁጥር 106/1996 መሠረት የተደራጀ ሲሆን፡፡ ክልሎቹም የየራሳቸውን አዋጆች ቀርፀው እነዚህ ማህበራት የሚገዙበትን ስርዓት ዘግተዋል፡፡ ፌዴራልም ሆነ በክልል የተቋቋመበት የንብረት ሥራ ማህበራት በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዩች ላይ በመሳተፋ ለአባባሎቻቸውና ለጠቅላላው ሕብረተሰብ የራሳቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ መሆናቸው የሚታወቅ ነው፡፡ እነዚህን አካላት ያደራጀ ህጐች ይዞታቸውና መንፈሳቸው ሲታይም ማህበራቱ የራሳቸውን የቻለ አደረጃጀትና ልዩ ባህሪያት ያላቸው መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991አንቀጽ 2/2/ ሲታይ የህብረት ሥራ ማህበር ማለት ሰዎች በፍቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታታ የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በህግ መንገድ የሚያስተዳድሩት ማህበር ነው፡፡ በሚል ትርጉም ያስቀመጠ ሲሆን የድንጋጌ ይዘቱና መንፈስ ሲታይ በሕብረት ስራ ማህበራት ለማህበራዊነት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ሲባል የሚደራጅ መሆኑን ያሳያል፡፡ አዋጅ ቁጥር 147/91 እና በዚሁ አዋጅ ማሻሻያ የሆነው አዋጅ ቁጥር 402/97 ድንጋጌዎች ሲታይ የንብረት ሥራ ማህበራት ከበጐ አድራጐት ድርጅቶችም ሆነ ከንግድ ማህበራት የሚለዩበት ባህሪያት ያሏቸው መሆኑን ያሳያሉ፡፡ በህጐቹ ከተቀመጡት መለያ ባህሪያት አንዱ ማህበራት የሚቋቋሙበት ዓላማ ሲሆን የህብረት ሥራ ማህበራት የሚቋቋሙበት ዓላማ የአባላትን ተመሳሳይ ፍላጐት በአነስተኛ ወጪ ለማሟላት እንጅ በአባላት ትርፍ ለማስገኘት ተብሎ የማይቋቋም መሆኑን ያሳያል፡፡ አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 4 በተለይ ሲታይም የህብረት ስራ ማህበራት የሚቋቋሙበትን ዓላማዎች የዘረዘረ ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዝርዝሩ ውስጥ ለአባላት ትርፍ ለማስገኘት የሚያስችል ሥራ እንደሚሳተፍ አይገልጽም፡፡ የተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 35 ድንጋጌ አንድ ማህበር ለአባላት ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመ ሌላ ማህበር ካልሆነ በቀር ብድር መስጠት እንደሚችል የደነገገው ሲሆን ይህም ማህበር በትርፍ ተብሎ የሚቋቋሙና መሠረታዊ ግባቸው የአባላቱን ፍላጐት በአነስተኛ ወጪ ማሟላት ነው የሚለውን ድምዳሜ የሚያጠናክር ነው፡፡ የህብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ሲታይ የህብረት ሥራ ማህበር አባል ለመሆን አንድ ሰው 14 ዓመት የሞላው የማህበሩን ዕጣ ለመግዛትና የመመዝገቢያ ክፍያ ለመክፈል የሚችልና የማህበሩ ደንብና የተለያዩ አዋጆችን ለማክበር ፍቃደኛ ሊሆን እንደሚገባ ሕጉ የሚያሳይ ሲሆን የማህበራት ስያሜም አዋጅ በአንቀጽ 8 ማንኛውም ማህበር መመሪያ ስም ሲኖረው እንደሚገባ ስሙ በመጨረሻ ኃላፊነቱ ስያሜም አዋጅ በአንቀጽ 8 ማንኛውም ማህበር መጠሪያ ስም ሊኖረው እንደሚገባ ስሙ በመጨረሻ ኃላፊነት የተወሰነ የኃብረት ሥራ ማህበር የሚሉ ቃላት መያዝ እንደሚገባ አንድ ማህበር በተመዘገበበት ስምና ምልክት ሌላ ማህበር ሊጠቀምበት እንደማይችል ሕጉ አስቀምጧል፡፡ ሌላው ስለ ህብረት ስራ ማህበር በሕጉ የተቀመጠው ጉዳይ ማህበራቱ ያላቸው ልዩ መብቶች ናቸው፡፡ አዋጅ ቁጥር 147/1991 እና የዚሁ አዋጅ ማሻሻያ የሆነው አዋጅ ቁጥር 402/96 ድንጋጌወች ሲታዩ ለህብረት ሥራ ማህበራት ልዩ መብቶች እንዳሏቸው ያሳያሉ፡፡ በሕጐቹ ከተመለከቱት ልዩ መብቶች የማህበራት ዕዳ በቀዳሚነት እንዲከፈል የተቀመጠው ደንብ የህብረት ሥራ ማህበራት የአለበትን ዕጣ ወይም ጥቅም የማቻቻል የኃብረት ሥራ ማህበራት በመንግስት የሚሰጧቸው ልዩ ልዩ ድጋፎችንና የንግድ ፍቃድን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚሸፈኑ መሆኑን አዋጆቹ ያሳያሉ፡፡ ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ ተግባራት ያለው የንግድ ፍቃድን የሚመለከተው ልዩ መብት ሲሆን አዋጅ ቁጥር 402/96 አንቀጽ 6 ስር ማህበራት ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ተጨማሪ የንግድ ፍቃድ ሳያስፈልጋቸው በማንኛውም የንግድ ሥራ ላይ መሰማራት ይችላሉ በሚል ተቀምጧል፡፡ በዚህ ረገድ የተቀመጠው ድንጋጌ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም የንግድ ፈቃዱ ልዩ መብት ንግድን ያለንግድ ፋቃድ ለማከናወን የሚፈቅድ በመሆኑና ማህበራቱ ከሚሰሩት ስራ ውጭ ባሉ የንግድ ሥራዎችም ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 እና 813/2006 ሊገዙ ያሰቡትን የንግድ ውድድርን ትርጉም ሊያሳጣው ይችላል የሚል ክርክር ሊቀርብበት የሚችል መሆኑ እሙን ነው፡፡

ወደ አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረታዊ አላማ ስንመጣ የንግድ ዘርፍ የሀገሪትን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚደግፍበትን ሁኔታ የማጠናክር የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፋቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን በአግባቡ በሚደራጁት የንግዱን ዘርፍ ጉጂና ተገቢ ያለሆኑ እንቅስቃሴዎችን መከላከል በንግድ ዘርፍ መንግስት ሊኖረው የሚገባውን መረጃ ሰበአግባቡ ለመያዝ የሚያስችለውን ሁኔታ ማመቻቸት እና ለንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ምቹ ሆኔታዎችን መፍጠር ስለመሆናቸው በአዋጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 3 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የአዋጅ ተፈፃሚነትን በተመለከቱም የንግድ ፈቃድን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 ንዑስ ለአንቀጽ /1/ ከተመለከቱት የንግድ ስራዎች በስተቀር በሌላ ማናቸውም የንግድ ሥራ በተሰማራ ሰው ላየ ተፈፃሚ ይሆናሉ ሲል የደነገገው ሲህን በአዋጅ አንቀጽ 30/1/ ስር የተመለከቱት የንግድ ስራዎች ደግሞ በማዕድን ፍለጋና ልማት የውሃ ነክ ስራወች ግንባታ አገልግሎትን ሳየጨምር በልዩ ለዩ ውሃ ነክ ሥራዎች በባንክ መድን እና ማይክሮ ፋይናንስ ንግድ ሥራወች በአየር ማመልከቻና አገልግዘለት ስራ ሬዲዮ አክቲብ ቁሶዎችንና ጨረር አመንጪ መሳሪያወችን በሚመለከቱ የንግድ ስራዎች በቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት የኤሌክትሪክ ማመንጨት ማስተላለፍ አከፋፈል ወይም መሸጥ ንግድ ሥራ በቀርና ተኩል መስሪያወች ጥገና እድሳትና ፈንጅ ሽያጭ ሥራ በባህርና የሃገር ውስጥ የውሃ ትራንስፖርት ንግድ ሥራ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ንግድ ሥራ የዕቃ ማከማቻ ቤት ንግድ ሥራ እና በትምባሆና የትምባያ ውጤቶች ንግድ ሥራ መሆናቸውን የዘረዘረ ሲሆን አግባብ ላቸው ሌሎች መስሪያ ቤቶች ከሚሰጡ ፋቃዶች በስተቀር ሌሎች የንግድ ስራ ፋቃዶች የሚሰጡት እንደአግባቡ በሚኒስተሩ ወይም በቢሮው ወይም በኢትዮጵያ ኢንበስትመንት ኤጀንሲ ስለመሆኑም ይህው ድንጋጌ ያሳያል፡፡

የአዋጅ አንቀጽ 31/1/ ማንኛውም ሰው የፀና የንግድ ስራ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ሰራ መሥራት እንደሚይችል በኃይል ቃል የደነገገ ሲሆን የአዋጅ አንቀጽ 42 ድንጋጌም ተገቢው የንግድ ሥራ ፋቃድ ሳይኖረው በሌላ አይነት ፋቃድ ይህ አዋጅ ፈፃሚ የሚሆንበት የንግድ ሥራ ሲካሄድ የነበረ ማገኛውም ሰው ይህንኑ ሥራ ለማካሄድ ይህ አዋጅ ከመጣበት ቀን ጀመሮ በ12 ወራት ውስጥ አግባብ ያለውን ቅጽ ሞልቶ ማመልከቻ በማቅረብ ተገቢውን የንግድ ሥራ ፋቃድ ማውጣት እንዳለበት በአስገዳጅነት ደንግጓል፡፡

እነዚህን የአዋጅ ቁጥር 686/2002 ድንጋጌዎች ስንመለከት በሕጉ ንግድ ፋቃድ የሚያስፈለጋቸው ተግባራት ተለይተው የተቀመጡ በመሆኑ በህጉ ተዘርዝረው የተቀመጡ ውጪ ያሉት የንግድ ስራዎች ፋቃድ የሚያስፈለጋቸው መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው በማለት መደምደሚያ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የድንጋጌወቹን ተፈፃሚነት በአወጅ ቁጥር 147/91 እና በአዋጅ ቁጥር 402/96 መሠረታዊ አላማና ከማህበራት ልዩ ባህር አንፃር ማየቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ማህበራት በመሰረታዊነት ለትርፍ ተብሎ የሚቋቋሙ ሳይሆን የአባላቱን ፍላጉት በአነስተኛ ወጪ ለሚሟላት የሚቋቋሙ በመሆኑለትርፍ ስራ የሚሰሩ የንግድ ስራዎች የሚያስፈልጋቸውን የንግድ ፍቃድ እንዲያወጡ የሚጋደድበት አግባብ የለም፡፡ አዋጅ ቁጠር 402/96 አንቀጽ 6 ድንጋጌም በዚህ ረገድ ግልጽ የሆነ ይዘት ያለው በመሆኑ ማህበራት የንግድ ፍቃድ አያስፈልጋቸውም በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 31/1/ እ 42 ድንጋጌዎች ስር ማንኛውመ የንግድ ስራ የንግድ ፍቃድ እንደሚያስፈልገው የተቀመጠው ድንጋጌ ከማህበራቱ መሠረታዊ አላማና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባህርይ አዋጅ ቁጥር 686/2002 ሊያሳካው ካሰበው ግብ አንፃር ታይቶ ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው እንጂ አዋጅ የወጣበትን ጊዜ ብቻ መሠረት በማድረግ ለማንኛውም የንግድ ስራ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ሊደረግ የሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 147/91 እና በማሻሻያው የሚገዛ ነው፡፡ ከተባለ ደግሞ የተጠሪ አድራጉት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027/2028 እና 2035 መሠረት ሕገ ወጥ በመሆኑ በአመልካች ላይ ለደረሰው የጉዳት ካሳ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ የጉዳት ካሳ መጠኑ ግን በስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ያልታየ በመሆኑ በዚህ ችሎት እልባት የሰጠው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዮን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16938 ግንቦት 01 ቀን 2006 ዓ.ም ተሠጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 187476 ግንቦት 22 ቀን 2006 ዓ.ም በክለሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 185055 ሰኔ 26 ቀን 2006 ዓ.ም የሆነው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በአወጅ ቁጥር 147/91 እና በማሻሻው በተቋቋመና የሚገባ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረት የንግድ ፋቃድ እንዲወጣ አይገደድም ብለናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ እርምጃ ሕግ ነው ብለናል፡፡ ተጠሪ እሽጉን ሊያሳይ ይገባል በአመልካች ላይ የደረሰውን የጉዳት ካሳ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027/2028 እና 2035 የመክፈል፡፡ ሀላፊነት አለበት ብለናል፡፡ የጉዳት ካሳ መጠኑን በተመለከተ ግን የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ሊወሰን ይገባል በማለት በዚህ ነጥብ ብቻ ጉዳዩን በስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክፈል ፴፯

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98347

ሐምሌ 13 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተክሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቁጠታ

አመልካች፡- ወ/ሮ በድሪያ መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አደም ዑመር ቀረቡ

መዝገቡን መርመረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መቋረጡን ተከትሎ የተነሳው የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ አመልካች አመልካች ደግሞ ተጠሪ በመሆን ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ ከ1980 እስከ 2001 ዓ.ም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖርበት ጊዜ የአመልካች አባት አሮጌ አፈር ቤት ሊሾ በማድረግ እና ደረጃው 12 በረንዳ ቆርቆሮ በመቀየር ተጠሪ ማሳደሳቸው እንዲሁም ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤት እንዲሰሩ አብረው ሲኖሩ የተለያዩ የቤት መገልገያ ዕቃዎች ማፍራታቸውን መሠረት በማድረግ ንብረቱ የሚቻል ከሆነ በዓይነት እንዲከፈሉ የማይቻል ከሆነ በሀራጅ ተሽጦ እኩል እንዲካፈሉ ተጠሪ በዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት የመከላከያ መልስ በወላጅ አባታቸው ቤት የተደረገ እድሳትም ሆነ የተቀየረ በረንዳ እንደሌለ የተሰሩ ሁለት ሰርቪስ ቤቶች መኖራቸው አምነው ተጠሪ ተክተው አፍርሰው መውሰድ እንደሚችሉ ዛፎች የአመልካች አባት የተከሉዋቸው እንደሆነ፣ አመልካች በተጠሪ ከሚከራየው ቤት ድርሻቸው እንዲያካፍላቸው ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል የቀረበ ምስክሮች ያዳመጠ ሲሆን አመልካች ግን ማስረጃ አለማቅረባቸውን በውሳኔው ገልጾ በፍሬ ጉዳዩም ሁለት ሰርቪስ ቤቶች ግራ ቀኙ በጋራ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የተሰሩ የጋራ ንብረት መሆናቸው እንደታመነ መዝግቦ፤ በአመልካች በኩል በቀረበው ክርክር ተጠሪ የተሰራውን ሰርቪስ ቤት አፍርሰው ይውሰዱ የሚለውን ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40/3/ እንደተመለከተው መሬት የመንግስትና የህዝብ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ እንዳልተቀበለው የአመልካች አባት አሮጌ ቤት በጋራ ማደሳቸው ከ30-40 የሚሆኑ ዛፎች በጋራ መትከላቸው መረጋገጡን እንደሁም የጋራ የተባሉትን የቤት ዕቃዎች በመለየት ሁለት ሰርቪስ ቤቶች አንድ የደጅ ሽንትቤት ቧንቧ እና በግምት ከ30-40 ዛፎች የጋራ ንብረት ስለሆነ በዓይነት መክፈል የሚቻል ከሆነ በዓይነት ይህ ካልተቻለ ዋጋ በማይቻል ይህ ካልተቻለ በስምምነት በመሸጥ ይህ ካልተቻለ በሐራጅ በመሸጥ ሽያጩ እኩል እንዲከፈሉ ቀደም የነበረው ሳሎንና መኝታ ቤት በ12 ቆርቆሮ በረዳ የተሰራበት እና በአብጆዳድ እና በሸራ ኮርኒስ የተሰራበት ገንዘብ በባለሙያ ተገምቶ የግምቱ ግማሽ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ ሌሎች የቤት ዕቃዎችም እንዲከፈሉ ወስኗል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት በከ.መ.ቁ.28071 በ24/07/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ማብራሪያ የሚፈልግ በመሆኑ በፍርድ አፈፃፀም መመሪያ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት ፍርድ ቤቱ በ30/08/2005 ዓ.ም መብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ በሰጠው መብራሪያም ባህርዛፍን የተተከለበት ቦታ መምራ እኩል እንዲካፈሉ በአጠቃላይ ውሳኔ ያረፈባቸው ሰርቪስ ቤቶች ቧንቧ እና ባህርዛፎች ከእነ ይዞታቸው ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ አሏል፡፡ አመልካች ይህንን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥነው ጉዳዩ የሰበር ይመርመር በመባሉ በግራ ቀኙም የጽሑፍ ክርክር አደርጓአል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዋና ፍሬ ነገር ለክርክሩ መነሻ የሆነውን በአባታቸው የመሬት ይዞታ የተሰሩትን ሰርቢስ ቤቶችን እና ተተክሉ የተባሉ ዛፎች ተጠሪ አፍርሰው ወይም ግምት ወስደው ከሚሰናበቱ በቀር አኩል የሚካፈሉበት ምክንያት አይኖሩም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ለአፈፃም መነሻ የሆነውን ፍርድ የግባኝ ጠይቀው ሳያሸሩ በአፈፃፀም ጊዜ የክፍፍል ሥርዓቱ መቃወም እንደማይችሉ ሰርቪስ ቤቱም በደመወዛቸው እንዲሰሩት የሥር ፍርድ ቤት ከነይዞታው እኩል እንዲከፍሉ የሰጠው ትዕዛዝ የሚነቀፍ ነጥብ የለም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ፍርዱን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ይዘት ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በሥር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደገለፀው ግራ ቀኙ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ እንደነበር ከአብራካቸው ሐዋን አዳም የተባለችው ልጅ እንደተወለደች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ሰርቪስ ቤቶች የደጅ ሽንት ቤት ቧንቧ እና ግምቱ ከ30-40 የሆኑ ዛፎች የጋራ ንብረት እንደሆኑ፤ የክፍፍል ሥርዓቱም ከተቻለ በዓይነት፤ ካልተቻለ ዋጋ በማቻቻል ካልተቻለ በስምምነት በመሸጥ ይህ ካልተቻለ በሀራጅ በመሸጥ እኩል እንዲከፍሉ በኮ.መ.ቁ. 28071 በ24/07/2004 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ውሳኔ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወይም ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ የተሻረ የተሻሻለ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክር የለም፡፡ የፍርድ አፈፃፀም የሚመራው ፍርድ ቤት እንደ ፍርዱ የማያስፈፀም ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ባስቀመጡት አግባብ የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤትም መጀመሪያ በሰጠው ፈርድ መሠረት እንዲፈፀም በ30/08/2005 ዓ.ም በሰጠው የመብራሪያ ትዕዛዝ ግልጽ አደርጓአል፡፡ የአሁኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አልነበረም የሚል ቅሬታ ከነበራቸው በሕጉ የተዘረጋው የይግባኝ ሥርዓት ተጠቅመው መብታቸው ሊያስከብሩ ይገባ ነበር ለአፈፃፀም መነሻ የሆነውን ፍርድ ይግባኝ በመጠየቅ ሳይሻሩ ወይም ሳያሻሽሉ በዋናው ጉዳይ ሲነሱ የሚገባቸው የክርክር ነጥቦች በአፈፃፀም በተያዘው መዝገብ የክርክር መሠረት ለማድረግ የሚያስችላቸው ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በእርግጥ አመልካች በአፈፃፀም የተያዘው ጉዳይ በአፈፃፀም ጊዜ እንደ ፍርዱ ለመፈፀም የሚያስችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች መኖራቸው ካሳዩ ሥርዓቱን ጠብቀው አቤቱታ የማቀርብ መብት አላቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በዋናው ጉዳይ ሰርቪስ ቤቶች፣ የደጅ ሽንት ቤት እና ባህር ዛፎች እኩል እንዲካፈሉ ግልጽ ውሳኔ በተሰጠበት ሁኔታ በአፈፃፀም ወቅት ሰርቪስ ቤቶቹ የተሰሩት በአባቴ ይዞታ ነው በማለት ብቻ የአፈፃፀም ሂደቱን ለማቆም የሚያስችል የሕግ መሠረት የላቸውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙ ከመረመረ በኃላ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392/1/ እና /2/ መሠረት እንደ ፍርድ እንዲፈፀም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች በመ/ቁ 28071 በ24/07/2004 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ መሠረት በማድረግ የተከፈተው አፈፃፀም እንደ ፍርዱ እንዲፈፀም ትዕዛዝ መሰጠታቸው ሕጉን ተግባራዊ አድርጓል ከሚባል በቀር የፈፀሙት መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1/ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.28071 በ30/08/2005 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 13773 በ1/4/2006 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ ጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2/ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች እና ተጠሪ የሚከራከረው የሰርቪስ ቤቶች የደጅ ሽንት ቤት እና ባህር ዛፍ እንደ ፍርዱ እንዲፈጽሙ የሰጠው ትዕዛዝ ፍርዱን መሠረት ያደረገ ነው በማለት ወስነናል፡፡ አመልካች በፍርድ አፈፃፀም ጊዜ እንደ ፍርዱ እንዳስፈጽም የሚገድብ ሕጋዊ ምክንያት ካለ ሥርዓቱን ጠብቀው አቤቱታ የማቅረብ መብታቸው በዚህ ፍርድ አልተገደቡም /አልተነካም/፡፡

3/ የሰበር ችሎት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙን የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1/ ከዚህ ችሎት ታህሳስ 15 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 96588

ሐምሌ 17 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጤታ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ አልማዝ አርዕያ - ተወካይ ለማ ሀይሌ ቀረቡ

2. አቶ ፍቀሩ አርዕያ ቀረቡ

3. አቶ ደረሰ አርዕያ ቀረቡ

4. ወ/ሮ አለምነሽ መኮነን ተወካይ ሁለተኛ ተጠሪ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አሸናፊ አልታየ ጠበቃ እዩኤል ጀረኔ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የሶዶ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 09284 ሐምሌ 5 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የደቡብ ብሔርብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25570 ጥቅምት 13 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03219 ታህሳስ 1 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ውሳኔ በሀራጅ የተሰጠበት ዋጋ ተቀንሶ እንዲከፈል የተሰጠ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢነት የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ እነ አልማዝ አርዕያ የአፈፃፀም ከሳሾች፣ አንተነህ አሰፋና ፍቀሩ አርዕያ የአፈፃፀም ተከሳሾች ሆነው በሚከራከሩበት የአፈፃፀም መዝገብ የውርስ ንብረት የሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይንቀሳቀስ ንብረት በሀራጅ እንዲሸጥ በአፈፃፀም ትዕዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪ በሀራጅ ጨረታው አሸናፊ በመሆን ንብረቱን በብር 1,573,000 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባ ሶስት ሺህ ብር/ ለመግዛት ተስማምቶ፣ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ፣ የንብረቱን ሰባ ፐርሰንት በቼክ ገቢ በማድረግ፣ ገዝቷል። የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በሀራጅ የገዛው ቤት ስመ ንብረት፣ በጨረታ አሸናፊው በተጠሪ ስም እንዲዛወር፣ ሰባ ፐርሰንቱ የቤቱ ዋጋ ክፍያ እንዲፈፀምና፣ ታግዶ ያለው የቤቱ ሰላሣ ፐርሰንት ዋጋ የማዛወር ሒደቱ ሲለቀቅና በያዘው ቦታ ላይ መንግስት ከውራሾች ወይም ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የሚፈልገውን ዕዳ ከፍለው ሲጨርሱ ወይም ሽያጭ የተፈፀመበትን ንብረት ነፃ ሲያደርጉ ክፍያው እንዲፈፀም በማለት የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቷል።

2. ከዚህ በኋላ አመልካቾች ግንቦት 27 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የጨረታ አሸናፊው በጨረታ የገዛውን ንብረት በስሙ አዛውሮ የጨረሰ በመሆኑ ቀሪውን ሰላሳ ፐርሰንት እንዲከፍል ትዕዛዝ ይሰጥልን በማለት አመልክተዋል የስር ፍርድ ቤት የጨረታው አሸናፊ /ተጠሪ/ የአመልካቾችን ቀሪ ክፍያ ይዞ እንዲቀርብ ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቷል። ተጠሪ ሰኔ 10 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በአራት አቅጣጫ አዋሳኝ ምልክቶቹ ተገልፀው በጨረታ አሸንፌ የገዛሁት ቤት በ1340 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው መሆኑን ሰነዶቹ ያሳያሉ። ነገር ግን ስም ለማዛወር ቦታው ሲለካ 1130 ካሬ ሜትር ብቻ ሆኖ ስለተገኘ የ210 ካሬ ሜትር ቦታ ዋጋ ይቀነስልኝ በማለት ጥያቄ አቅርቧል። አመልካቾች ይኽ የአመልካች ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም ካልሆነ የሀራጅ ሽያጩ ፈርሶ ንብረታችንን ያስረክቡን፣ ገንዘቡን እንመልስ በማለት ተከራክረዋል። የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የ210 ካሬ ሜትር ቦታ ዋጋ ብር 246515 /ሁለት መቶ አርባ ስድስት ሺ አምስት መቶ አሰራ አምስት ብር/ ተቀንሶለት ሌላውን ገንዘብ ይክፈል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል።

3. አመልካቾች ይህንን የአፈፃፀም ትዕዛዝ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበዋል። ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቷል። አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበዋል። የሰበር ችሎቱ የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም።

4. አመልካቾች ጥር 7 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም በተደረገው የሀራጅ ሽያጭ ከዘጠኝ ሰዎች ጋር ተወዳድረው አሸናፊ ሆነዋል። የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም የገቡት ስመ ሀብት እንዲዛወርላቸው እና ሰባ ፐርሰንት ክፍያ እንዲከፈለን ትዕዛዝ ተጥቷል። ተጠሪ የሀራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ያቀረቡት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ የለም፡፡ ከዚያ በኋላ ዋጋ እንዲቀነስላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የሕግ ስርዓቱን ያልተከተለ ሆኖ እያለ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን ጥያቄ ተቀብለው የሰጡት ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በሀራጅ የገዛሁት ቦታና ንብረት ስም ሲዛወር ተለክቶ የተገኘው ቦታ ልዩነት ያለበት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ሊዝ ዋጋ አስልተው ከቤቱ ዋጋ መቀነሳቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የካቲት 19 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ መልሶ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች መጋቢት 5 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅረበዋል፡፡

5. ከስር የክርክሩ አመጣጥ በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በሀራጅ ጨረታ ንብረቱን ከገዛበት ዋጋ ተቀንሶ ሊዝ ዋጋ ሒሳብ 210 ካሬ ሜትር ቦታ ለአመልካችዎች እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
6. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም በተደረገው የሀራጅ ሽያጭ ተወዳዳሪ ሆኖ ቀርቦ በብር 1,573,000 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባ ሶስት ሺ ብር/ የሀራጅ ሽያጭ አሸናፊ ሆኗል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሀራጅ ሽያጩን ዋጋ ተጠሪ በቼክ እንዳስያዘ ገልፆ፣ ሰባ ፐርሰንቱ ለአመልካችዎች እንዲከፈል፣ ሰላሳ ፐርሰንቱ ስመ ሀብቱ እስኪዛወር እንዲቆይ የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካችዎች ግንቦት 27 ቀን 2005 ዓ.ም አፈፃፀሙን ለያዘው የስር ፍርድ ቤት፣ የንብረቱ ስመ ሀብት ወደ ተጠሪ የተዛወረና ተጠሪ ንብረቱን የተረከበ በመሆኑ ቀሪ ሰላሳ ፐርሰንት የንብረቱን ዋጋ እንዲከፈል ትዕዛዝ ይሰጥልን በማለት ነው፡፡
7. በመሰረቱ የስር ፍርድ ቤት የሀራጅ ሽያጭ አሸናፊ የሆነው ተጠሪ የጨረታው አሸናፊ ከሆነበት፣ ከየካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 26 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ ባሉት አስራ አምስት ቀናት፣ የገዛውን ንብረትሙሉ ዋጋ በፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 441 መሰረት ሙሉ በሙሉ ገቢ እንዲያደርግ ማድረግ ሲገባው፣ ሰባ ፐርሰንቱን የንብረቱን ዋጋ ብቻ ተጠሪ በቼክ እንዲከፍል አድርጎ ሰላሳ ፐርሰንቱ የንብረቱ ዋጋ በተጠሪ እጅ እንዲቆይ ማድረጉ፣ ተጠሪ ንብረቱን የገዛው ፍርድ ቤት ባወጣው ሀራጅ ማስታወቂያ ፍርድ ቤት በመደበው ሀራጅ ባይ በኩል ከፍርድ ቤቱ ሆኖ እያለ፣ በሀራጅ ሽያጩ ውስጥ ምንም አስተዋፅኦ የሌላቸውንና ፍርድ ቤት የሸጠውን የቤት ዋጋ በሕግ አግባብ ተቀብሎ ሊከፍላቸው ከሚገባቸው አመልካችዎች፣ ከተጠሪ ጋር አላስፈላጊ ክርክር ውስጥ እንዲገቡና በዚህም መጉላላትና ኪሳራ እንዲደርስባቸው የሚያደርግ ስርዓት የስር ፍርድ ቤት የተከተለ መሆኑን ያሳያል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

8. የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በሀራጅ የገዛውን ንብረት ሙሉ ዋጋ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 441 በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ገቢ እንዲያደርግ አድርጎ ቢሆን ኖሮ፣ የቤቱ ስመ ሀብት ለተጠሪ መዛወሩን እንዳረጋገጠ፣ ተጠሪን ማይጠራ፣ ቀሪው የቤቱ ዋጋ ለአመልካቾች እንዲከፈል ትዕዛዝ ይሰጥ ነበር፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን አስገዳጅ ስርዓት ባለመከተሉ ተጠሪ በሀራጅ የገዛውን ቤት ሙሉ ዋጋ የመክፈል ግዴታውን የሚቀንስለት ወይም የሚሻሻልለት፣ አይሆንም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሀራጅ ሽያጩ የተከናወነው የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም ነው፡፡ ተጠሪ የገዛሁት ንብረት የይዞታ መጠን በሰነድ ከተገለፀው 1340 ካሬ ሜትር ማይሆን 1130 ካሬ ሜትር ሆኖ ተገኝቷል በማለት አቤቱታ ያቀረበው፣ የቤቱ ስመ ሀብት በስሙ ካዛወረና ንብረቱን ከተረከበ እንደዚሁም አመልካችዎች ቀሪው የቤቱ ዋጋ ይከፈለን ብለው ግንቦት 27 ቀን 2005 ጥያቄ አቅርበው፣ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ቀሪውን የቤቱን ዋጋ ገቢ እንዲያደርግ ግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ሰኔ 11 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡

9. ተጠሪ ሰኔ 11 ቀን 2005 ዓ.ም ላቀረበው ጥያቄ እድል የሰጠው የስር ፍርድ ቤት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 441 አስገዳጅ ድንጋጌ በጥብቅ ባለመከተሉና በድንጋጌው መሰረት አፈፃፀሙን ባለመምራቱ ነው፡፡ እንደዚሁም ተጠሪ በሰነድ የሚታየው በሀራጅ የተሸጠለት ቤት የይዞታ መጠንና ቦታው፣ ሲለካ የተገኘው የይዞታ መጠን ልዩነት አመልካችዎች በፈፀሙት የተንኮል ድርጊት የደረሰ ስለመሆኑ የገለፀውም ሆነ ያስረዳው ነገር የለም፡፡ ተጠሪ አዋሳኝ ምልክቶቹ በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 228 ንዑስ አንቀፅ 2 ተለይተው በሀራጅ ማስታወቂያ ተገልፆ፣ ካርታውና ኘላኑ ላይ የቦታው ስፋት 1340 ካሬ ሜትር መሆኑ ተገልፆ፣ ፍርድ ቤቱ በሀራጅ የሸጠለት ንብረት ይዞታ፣ ስም በማዛወር ልኬት ሲፈፀም 1130 ካሬ ሜትር ብቻ መሆኑን እንደተረዳ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 447 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሰረት የሀራጅ ሽያጩ እንዲሰረዝ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው ማመልከቻ የለም፡፡ ይህ ከሆነ፣ ተጠሪ ንብረቱን በስሙ ካዛወረና፣ ከተላለፈ በኋላ የሀራጅ ሽያጩ ሙሉ በሙሉ ከተፈፀመለት በኋላ፣ ንብረቱ በሀራጅ ከተሸጠበት ዋጋ ላይ እንዲቀነስለት ያቀረበው ጥያቄ የስነ ስርዓት ሕጉን ያልተከተለና ሕጋዊ ዕውቀትና ውጤት ሊሰጠው የማይገባው ነው፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የ210 ካሬ ሜትር ቦታ ዋጋ በሊዝ ሒሳብ ብር 246515 /ሁለት መቶ አርባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ አስራ አምስት ብር/ ተቀንሶለት፣ ቀሪውን ገንዘብ ይክፈል በማለት የሰጡት ውሳኔ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አንቀፅ 441፣ አንቀፅ 447 እና አንቀፅ 429 ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የሶዶ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሐምሌ 5 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ታህሳስ 1 ቀን 2006 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካችዎች ሊከፍል የሚገባው በሀራጅ ጨረታ ቤቱን አሸንፎ የገዛበትን ብር 1,573,000 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባ ሶስት ሺ ብር/ ሰላሳ ፐርሰንት ሙሉ በሙሉ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ ይህንን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ አጠቃልሎ ለመከፈል ፈቃደኛ ካልሆነ የስር ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 429 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ማድረግ ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 96814

ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ አብዶሽ አዲሽ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሰብለ ዘውዴ -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው የአሁኗ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በሐረሪ ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ06/08/2002 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ የአፈጻጸም ክስ መሰረት ያደረገውም በሐረር ከተማ ከፍተኛ 2 ቀበሌ 17 ክልል ውስጥ የሚገኘው፣ በ1280 ካ/ሜትር ስፋት ባለው ቦታ የሰፈረና ቁጥሩ 668 የሆነ፣ በካርታ ቁጥር 1035 የሚታወቀው የመኖሪያ ቤት ሲሆን ይህን ቤት በተመለከተ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት መሆኑን፣ለሁለት መከፈል የሚችል መሆኑን በተገቢው ባለሙያ አረጋግጦ ለተጠሪ በእጣ ምድብ "B" በ640 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን ሶስት ክፍል ቤት፣ለአሁኑ አመልካች ደግሞ በምድብ "A" 640 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን አምስት ክፍል ቤት እንዲወስዱ መወሰኑን ነው፡፡ በዚህ አግባብ እንዲፈፀምላቸው አፈፃጸሙን ለስር ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱን ግራ ቀኙን እንዲከራከሩ ከአደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ሌላ ባለሙያ መድቦ ቤቱ በአይነት ሊከፈል የሚችል መሆን ያለመሆኑንና ግምቱ ምን ያህል እንደሆነ አጣርቶ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአፈፃጸም ችሎት የመደበው ባለሙያም ቤቱ በአይነት ሊከፈል የማይችል መሆኑንና ቀድሞ የቀረበው የአይነት ክፍፍል የባለሙያ ሐሳብ ቤቱን ሙሉ በሙሉ ዋጋ የሚያሳጣ መሆኑን፣ ግምቱም በፍሬ ነገሩ ጊዜ የተገመተው ብር 520,683.18 ሳይሆን ብር 365,080.60 መሆኑን ዘርዝሮ ሪፖርቱን ለፍርድ ቤቱ የላከለት ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በፍሬ ነገሩ ጊዜ የተሰጠው የባለሙያ አስተያየት ስህተት መሆኑ በአፈፃጸም ጊዜ ከሚመለከተው አካል በተመደበ ባለሙያ አስተያየት መረጋገጡን፣ በአፈጻጸም ጊዜ የተመደበው ባለሙያ ቤቱ በአይነት ቢከፈል ቤቱ እንደሚጎዳና ግምቱም ብር 365,080.60 መሆኑን ማረጋገጡን፣ይህ ከተረጋገጠ ደግሞ በዋና ፍርድ ቤት ጊዜ የተሰጠውን ውሳኔ በአፈጻጸም ጊዜ አመቺ በሆነ መንገድ ማስፈፀም እንደሚቻል በሕጉ የተፈቀደ መሆኑን፣ይዞታውን እኩል ማካፈል የሚቻል ቢሆንም ቤቱን ግን ጉዳት ሳይደርስበት በእኩል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማካፈል የማይቻል መሆኑን ጠቅሶና በአማራጭነትም ክፍፍሉ በቀድሞው ክፍፍል ጊዜ አብዛኛው ቤት ያለበት ይዞታ ለአሁኑ አመልካች ደርሶ የነበረ መሆኑን፣አመልካች ከአስራ አምስት አመታት በላይ በቤቱ እየኖሩ ያሉ መሆኑን፣በቀዳሚነት የግዥ መብት ስርዓትም ሁለት ሰዎች በእኩል ደረጃ የሚገኙ ሲሆን በይዞታ ላይ ላለው ሰው የቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑ በሕጉ መመልከቱን መሰረት በማድረግ ቤቱ ያለበትን የይዞታ ክፍል የአሁኑ አመልካች እንዲወስዱ፣ ቤቱ የሌለበትን የይዞታ ክፍል ደግሞ ተጠሪ እንዲወስዱ፣ በአፈጻጸም ጊዜ ተገምቶ በቀረበው ብር 365,080.64 ግማሹን ብር 182,540.32 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት አፈጻጸሙን የመራው ከዋናው ፍርድ ውጪ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን የአፈጻጸሙን ውሳኔ በመሻር አፈጻጸሙ በዋናው ጉዳይ ላይ በመ/ቁጥር 01280 በ01/07/2002 ዓ/ም በተሰጠው አግባብ ሊመራ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አፈፃጸሙን የመራው ቤቱ በአይነት ቢከፈል ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ የሚሆን ስለመሆኑና በዋናው ክርክር ጊዜ የቀረበው የባለሙያ አስተያየት ስህተት መሆኑን በማረጋገጥ እንዲሁም አመልካችም ከውጪ አገር መጥተው በቤቱ ላይ ለረዥም አመታት የኖሩበት መሆኑን በመገንዘብ አግባብነት ካላቸው ሕጎችና አስገዳጅነት ካለው የሰበር ውሳኔ አንጻር ሁኖ እያለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አፈፃጸሙ በዋናው ፍርድ መሰረት መመራት አለበት ብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በነበረው የዋናው ክርክር የአሁኗ ተጠሪ ከሳሽ፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሁነው መከራከራቸውን፣ የግራ ቀኙን ክርክር የሰማውና ተገቢውን ማጣራት ያደረገው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ተገቢ ነው ያለውን ፍርድ መስጠቱን፣ፍርድ ቤቱ በሰጠው ፍርድ ክርክር የተነሳበት ቤት ለአመልካች ቤቱን የሸጡትና የተጠሪ ወላጅ አባት (ኮሎኔል ዘውዴ ወ/ማርያም) ሚስት የነበሩት ወ/ሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እታፈራሁ ፈጠነ እና ተጠሪ (የሥር ከሳሽ) ያልተከፋፈሉ የጋራ ሀብት መሆኑን ከዚህ ቀደም በመ/ቁ/00923 ታህሳስ 01 ቀን 2000 ዓ/ም ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ከመሆኑም ሌላ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የሚያምኑት ጉዳይ መሆኑን፣ በዚሁ መሰረት ቤቱንና ቦታውን ለሁለት ማካፈል የሚቻል መሆኑንና አለመሆኑን፤ የሚካፈል ከሆነ የሚደርሳቸውን መጠን ገምቶ እንዲገልጽ የከተማው ማዘጋጃ ቤት በታዘዘው መሰረት በሰጠው ምላሽ ቦታውን ምድብ " A" ምድብ "B" አድርጎ በማካፈል ምድብ " A" 5 ክፍሎች ያሉበት ቤት ሆኖ ስፋቱም 640 ካሬ ሜትር መሆኑንና ግምቱም ብር 115,983.96 እንደሆነ፣ ምድብ " B " ደግሞ ስፋቱ 640 ካሬ ሜትር ሆኖ 3 ክፍሎች ያሉበት ቤት ሆኖ ግምቱም ብር 96,820 መሆኑን የገለጸ ስለሆነና ተከሳሽም ክርክር የተነሳበትን ቤት አጠቃልለው ይዘው የሚገኙ በመሆኑ ከሁለቱ ምድቦች መርጠው እንዲወስዱ ዕድል ቢሰጣቸውም ለመውሰድ ፈቃደኛ ካለመሆናቸውም ሌላ ዕጣ ተጥሎ የደረሳቸውን እንዲወስዱ ቢደረግም ዕጣ ማንሳት እንደማይፈልጉ በመግለፃቸው ከሳሽ ዕጣ እንዲያነሱ ተደርጎ ምድብ "B" የደረሳቸው ስለሆነ የሁለቱን ምድቦች ድምር ግምት 212,803.96 ለሁለት ሲካፈል ብር 106,401 ስለሚሆን ተከሳሽ ልዩነቱን ብር 9,581 ለከሳሽ ከፍለው በምድብ "A" ያለውን ቤት እና ቦታ እንዲወስዱ ሲል መወሰኑን፣ 166 ወራት የቤት ኪራይ በተመለከተም ተከሳሽ ቤቱን የገዙት ከከሳሽ የጋራ ባለሀብት ከሆኑት ከወ/ሮ እታፈራሁ ፈጠነ ሚያዚያ 30 ቀን 1987 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ሆኖ እስካሁን ድረስ ቤቱን ይዘው የሚገኙ ሲሆን ከሳሽም ከቤቱ ድርሻ ያላቸው መሆኑን በፍርድ ቤት እስከሚወሰን ድረስ ሊያውቁ የሚችሉበት ሁኔታ አልነበረም፣ ከሳሽ በቤቱ ላይ ግማሽ ባለመብት መሆናቸውን በፍርድ ከታወቀ በኋላም ከቤቱ የሽያጭ ገንዘብ ግማሹ ብር 65,000 ለከሳሽ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ክርክሩ ስለሚያሳይና ቤቱን በቅን ልቦና ይዘው ቆይተዋል ለማለት ስለሚቻል ሊከፈሉ አይገባም ሲል የወሰነ መሆኑን፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን በማከራከር የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍ አይደለም በሚል ያፀናው መሆኑን፣ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካችም በሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታቸውን፣ተጠሪዋ ደግሞ የሰበር መስቀለኛ አቤቱታ ለዚህ ችሎት በመ/ቁጥር 68291 አቅርበው ይህ ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን በ25/01/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት መርምሮ የሐረሪ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 01280 በቀን 01/07/2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/62252 በቀን 12/07/2003 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348 (1) መሰረት በማሻሻል የአሁኑ አመልካች የአሁኗን ተጠሪን የውርስ ድርሻ ይዘው ለተጠቀሙበት ጊዜ ኪራዩን ሊከፍሉ አይገባም፣ እንዲሁም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪዋ ምድብ "B" ውስጥ ያለውን የቤት ግምት በምድብ "A" ውስጥ ካለው የቤት ግምት ጋር ለማመጣጠን የልዩነት ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም፣የአሁኗ ተጠሪ የአሁኑ አመልካች ላከናወኑት ተጨማሪ የአራት ክፍሎች ግንባታ የወጣውን ወጪ በድርሻቸው መጠን ለመክፈል አይገደዱም በማለት ወስኖ ከዚህ በፊት በስር ፍርድ ቤት ተጀምሮ በነበረው የአፈጻጸም መ/ቁ/ 0547 ክርክር ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቶ በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት አፈጻጸሙ እንዲቀጥል በማለት ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደ ፍርዱ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች በተዘረጋው ስርአት አግባብ በመመራት ካልሆነ በስተቀር በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ሕጋዊ ባልሆነ እና ውሳኔውን ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ ውድቅ ሊደረደግ የሚችልበት አግባብ አይኖርም፡፡ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያስገነዝቡት አቢይ ነጥብ የፍርድ አፈጻጸም ስርአት ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በእራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር ወይም ውጤት የሚለውጥበት ስርአት መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘትና መንፈስ በጥንቃቄ ሲታይም የፍርድ አፈጻጸም ስለፍርድ አፈጻጸም የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመከተል ፍርድን በተግባር መተርጎም እንደመሆኑ መጠን የአፈጻጸም ስርአቱ ህጉን መሰረት ማድረግ ያለበትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን መሰረታዊ ዓላማ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአነስተኛ ወጪ ጊዜና ጉልበት በተፋጠነና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም በሚያስችል አግባብ ሕግ አውጪ ያስቀመጣቸው መሆኑን የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ውሳኔው የማይፈፀመበት ሕጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩም በፍርድ ቤቱ ታይቶ ተገቢው እልባት የሚሰጥበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ይህ ድንጋጌ አፈጻጸሙን የያዘው ፍርድ ቤት አምፃፀሙን ምቹ ሁኔታዎች ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በተቻለ መጠን ፍርዱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ሊከተል የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡ስለሆነም አንድን ፍርድ እንደፍርዱ ይዘትና መንፈስ ውጤት ባለው መልኩ መፈጸም የግድ የሚል ሲሆን ይህ ደግሞ የፍርድ አፈጻጸምን በተመለከተ በስነ ስርዓት ሕጉ የተዘረጉት ስርዓቶች በአግባቡ በማየትና ተፈፃሚ በማድረግ የሚከናወን መሆኑን የድንጋጌዎቹ ይዘት የሚያሳይን ጉዳይ ነው፡፡በህግ አግባብ የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 372 መሠረት ሥልጣን ያላቸው የአፈፃፀም ችሎቶች ስለ ፍርድ አፈፃፀም የተዘረጉትን ሥርዓቶች በመከተል እንደ ፍርዱ ከመፈፀም በቀር የአንድ ፍርድ ይዘትን በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆነ በማስፋት ረገድ ፍርድን የመተርጎም ሥልጣን የሌላቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡ የአፈጻጸም ክስ መቅረብ ያለበትም እንደ ፍርዱ እንዲፈፀም ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ለአፈፃጸም ማመልከቻቸው መሰረት ያደረጉትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት አያያዘው ያቀረቡት አከራካሪው ቤትና ቦታ ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን የክፍፍል ውሳኔ እና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 68291 በ25/01/2005 ዓ/ም ተሻሽሎ የፀናውን ውሳኔ ነው፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ምድብ "B" የደረሳቸው መሆኑ ተረጋግጦ ከምድብ "A" ቦታ ጋር ያለው ድምር ግምት ብር 212,803.96 ሁኖ ይህ ገንዘብ ለሁለት ሲካፈል ብር 106,401.00 ስለሚሆን የአሁኑ አመልካች ልዩነቱን ብር 9,581.00 ለተጠሪ ከፍለው በምድብ "A" ያለውን ቤት እና ቦታ አመልካች ሊወስዱ እንደሚገባ ተወስኗል፡፡ ይህ የሚያሳየው በዋናው ክርክር ጊዜ ተገቢው መጣራት ተደርጎ በክፍፍሉ ስርዓትና ቅደም ተከተል ላይም ግራ ቀኙ ስምምነት ሊያደርጉ ባለመቻሉ የስር ፍርድ ቤት ተገቢ ነው ባለው መንገድ የቤቱና ይዞታው ግምት፣ግራ ቀኙ በንብረቱ ላይ ያላቸው ድርሻ እና ክፍፍሉ በእጣ ሲከናወኑንም ግራ ቀኙ የደረሳቸው ቤትና ይዞታው አቅጣጫ ጭምር ተለይቶ መወሰኑን ነው፡፡ በመሆኑም ቤቱና ይዞታው በዋናው ክርክር ጊዜ ምን ያህል ግምት እንዳለውና በምን አግባብ ክፍፍል እንደሚደረግ የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ታይቶና ተገቢው መጣራት ተደርጎ ከተወሰነ በኃላ በዋናው ክርክር ጊዜ ያለቀ የፍሬ ነገር ክርክር እንደገና በአፈጻጸም ተነስቶ በዋናው ክርክር ጊዜ የቀረበው ማስረጃ ሐሰተኛ/ተገቢነት/ የሌለው ነው ተብሎ የሚቀርበው ክርክርም ሆነ አፈጻጸም ችሎቱ በዚህ ረገድ የሚቀርበውን ክርክር ተቀብሎ ሌላ ማጣራት በማድረግ የቀደመውን ማስረጃ ሐሰተኛ ነው በማለት የሚቀርበውን የባለሙያ አስተያየት የሚቀበልበት የአፈጻጸም ክርክር አመራር ስርዓት የለም፡፡ በዋናው ክርክር ጊዜ ስለ ቤቱና ቦታ ክፍፍል የቀረበው የባለሙያ አስተያየት በንብረቱ የአይነት ክፍፍል የሚያመጣውን ጉዳት ያለማገናዘቡ በዋናው ክርክር ጊዜ ይታይ ይችል የነበረ እንጂ በዋናው ክርክር ጊዜ ተቀባይነት ከአገኘ በኃላ በአፈፃጸም ክርክር የሚታይ አይሆንም፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁኑን አመልካች በቤቱ ላይ ረኽቦም አመታት መኖራቸውን መሰረት አድርጎ የቀደምትነት መብት እንዳላቸው በማድረግ መወሰኑም ተገቢውን የክርክር ደረጃ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ በእርግጥ ሕጉን መሰረት አድርጎ የተሰጠ የንብረት ክፍፍል ውሳኔ በአፈፃጸም ጊዜ የንብረቱ ኢኮኖሚያዊ ዋጋ ትርጉም እንዳያጣ ተደርጎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አግባብ አመቺ በሆነ ሁኔታ ተመርቶ መፈፀም ያለበት መሆኑ እሙን ነው፡፡ ይህ ግን ተከራካሪ ወገኖች ሕጉ በዘረጋው ስርዓት ክርክር አቅርበውና ፍርድ ቤቶቹም በሕግ አግባብ አጣርተው የወሰኑትን የዋና ክርክር ውሳኔ በሚሸር መልኩ ሊከናወን የማይገባ መሆኑን ስለአፈጻጸም ስርዓት ከሚደንግጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘብ ጉዳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዋናው ውሳኔ ውጪ እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ ጋር ባልተገናዘበ መልኩ የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመሻር አፈጻጸሙ በዋናው ክርክር ጊዜ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ሊፈጸም ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጌዎች ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት ስላለገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ጠቅላይ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 90407 ጥቅምት 13 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አፈጻጸሙ በዋናው ጉዳይ ላይ በመ/ቁጥር 01280 በ01/07/2002 ዓ/ም በተሰጠው አግባብ ሊመራ ይገባል በማለት መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዘገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 104521

ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ ታንጎት ሰጠ

ተጠሪ፡- አቶ ፈንታው ትኩ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በአ/ብ/ክ/መ/ በሰሜን ወሎ ወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካችና ተጠሪ ባልና ሚስት የነበሩና ጋብቻቸው በፍቺ በመፍረሱ የዚሁ ውጤት በሆነዉ የጋራ ንብረትን አስመልክቶ በተደረገው ክርክር፤- አመልካች አከራካሪው ቤትና መሬት የግሌ እንጂ የጋራ ንብረት አይደለም በማለታቸው ምክንያት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ካዩ በኋላ ንብረቱን አስመልክቶ ተጣርቶ ይወሰን ዘንድ ወደ ወረዳ ፍርድ ቤት በመመለሱ ምክንያት ጉዳዩን በተመለሰለት መሰረት በተጠቃሾቹ ንብረት ላይ በማከራከር ንብረቱ በአንደኛዉ ተጋቢ ስም መመዝገቡ ብቻውን በክልሉ የቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 74(1) መሰረት የግል አያደርገውም፣ በመሆኑም ቤቱ የጋራ ንብረት ሲሆን የእርሻ መሬቱ የአመልካች የግል ንብረት መሆኑን በማረጋገጥ ወስኗል፡፡ ቤቱን አስመልክቶ አመቺ በሆነ መንገድ ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚሁ መሰረት ለማስፈጸም በተያዘው ቀን የግራቀኙ ቤቱን አስመልክቶ በእርቅ ለሁለት ተካፍለን ለመኖር ተስማምተናል በማለት ወደ ፍርድ ቤቱ ቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህ/ቁ. 277(1) መሰረት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪ የይግባኝ ጊዜ ካለፈ በኋላ ቅሬታቸዉን ለከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ጥያቄያቸዉ ተቀባይነት በማጣቱ በፍ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ ቁ 325 መሰረት መዝገቡ በመዘጋቱ በቀጣይነት ጉዳዩን ያየው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ቅሬታውን ባለመቀበል በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት የጸደቀው ስምምነትን አስመልክተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአፈጻጸም መ/ቁ 04586 ላይ ማዘጋጃ ቤቱ የአንደኛው ድርሻ ከ100 ካ.ሜ ያነሰ በመሆኑ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ነው በማለቱ ቤቱ በመነሻ ዋጋ እንዲሸጥ ትእዛዝ በመሰጠቱ አመልካች አፈጻጸሙን አስመልክቶ በእርቅ ስምምነት መሰረት ባለመፈጸሙ ክፍፍሉ በእርቁ መሰረት ሊፈጸም ሲገባ ቤቱ እንዲሸጥ መባሉ ዋናዉን ፍርድም ሆነ እርቁን የሚጻረር ነው በማለት ወደ ክልሉ ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልክተዉ ጉዳዩን ያየው ችሎትም በእርቁ ስምምነት መሰረት በአይነት መካፈል የማይቻል መሆኑን የከተማው ማዘጋጃ ቤት በሰጠው መረጃ መሰረት መሆኑ በመረጋገጡ የተሰጠ ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልጹ፡- ከተጠሪ ጋር አከራካሪውን ቤት መጋቢት 13 ቀን 2000 ዓ/ም ባደረግነው የእርቅ ስምምነት ክፍፍል አድርገን በፍርድ ቤት መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ/ም ጸድቋል፡፡ ቤቱን ስጠቀምበት ቆይቼ ተጠሪ በቤቱ ካርታ ሊያሰራ ጠይቆ ቦታህ 100 ካ.ሜ በታች በመሆኑ ሊሰራልህ አይችልም ስለተባለ ፍርድ ቤቱ እኔን ጠርቶ ቦታቻው ተሸጦ እንድትካፈሉ ተባለ ፣በውላችን መሰረት ካርታ ማሰራት ሲገባው፤ ቦታው ተሸጦ እንድንካፈል መወሰኑ የሚጎዳኝ ነው፤ ከ100 ካ.ሜ በታች ቦታ ካርታ ይሰራላቸው ነበር፤ ተጠሪ በራሳቸው ቦታ ካርታ ያላሰሩት በቸልተኝነታቸዉ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህም መሰረት ችሎቱም የግራ ቀኙ በስምምነት ጨርሰው ፍርድ ቤቱም ይህንኑ መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ/ም ተቀብሎ በስምምነታቸው መሰረት መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ በተጠሪ አመልካችነት በ26/4/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሀራጅ እንዲሸጥ መወሰኑን በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙን በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክሯል፡፡

ተጠሪ በሰበር መልሳቸው የሚሉት ፡- አመልካች እኩል አላካፍልህም በማለታ 100 ካ.ሜ ደግሞ መውጫ መግቢያ ሊኖረዉ አይችልም በሚል ተሸጦ እንድንካፈል መወሰኑ ባግባቡ ነዉ፣ ስምምነታችን እኩል ለመካፈል እንጂ ለአንዱ ያነሰ የሚል አይደለም፣ ባጠቃላይ ቤትና ቦታዉ 250 ካ.ሜ ነው፣ አመልካች ቦታዉን ተካፍለን የየራሳችንን ካርታ እንዳንይዝ የተጠሪ ድርሻ 100 ካ.ሜ ብቻ ነዉ በማለታቸው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ በስምምነታችን መሰረት መዝገቡን ዘጋው ማለት፣ ቤትና ቦታው ክፍፍል ተጠቃሎ ተፈጽሟል ማለት አይደለም፣ በስምምነቱ መሰረት ተካፍሎ ካርታ በእጃችን አልገባም፤ መሀንዲስ በቦታው ተገኝቶ መካፈል እንደማይመች ገልጿል፡፡ በመሆኑም የስር ውሳኔ ሊጸናልኝ ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው በስምምነት ባለቀ ጉዳይ ድጋሚ ይሸጥ መባሉ ስህተት ነው፣ አመልካች 100 ካ.ሜ. ነው አላልኩም፣ የተጠሪ ድርሻ 76.88 ካ.ሜ ብቻ ነዉ፡፡ ተጠሪ ስምምነቱን በማፍረሱ 5000 መቀጮ ያለበት በመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህን ለመንግስት እንዲከፍል ይወሰን፣በመሆኑም የስር ዉሳኔ ሊሻር ይገባል ሲሉ ተራክረዋል፡፡ ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተጠቀሰዉ ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መርምረናል፡፡

እንግዲህ ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር አጠቃላይ የክርክሩን ይዘት እንዳየነዉ የግራቀኙ ጋብቻ በፍቺ በመፍረሱ ምክንያት ይህን ተከትሎ በተጀመረዉ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ በዋናው ክርክር አከራካሪዉ ቤት የተጋቢዎቹ የጋራ ንብረት ነዉ፣ የእርሻ መሬቱ የአመልካች የግል ሀብት ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ በአፈጻጸም በተጀመረዉ ክርክር ቤትና ቦታዉን እኩል ለመካፈል ተስማምተው ስምምነቱን መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ/ም በፍርድ ቤት ካጸደቁ በኋላ በተግባር ለመከፋፈል አመቺ ያለመሆኑ በመረጋገጡ ታህሳስ 6 ቀን 2005 ዓ/ም ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ባልና ሚስቱ እንዲካፈሉት ተወስኗል፡፡

በመሰረቱ ባልና ሚስቱ በጋብቻ ጸንተዉ ባሉበት ጊዜ ባፈሩት ንብረት ላይ የጋራ ባለሀብቶች እንደሚሆኑ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 73 እና 74 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡በተያዘዉ ጉዳይ አከራካሪዉን ቤትና ይዞታ አስመልክቶ የጋራ ሀብት ነዉ ተብሎ ተወስኖ ያለቀ ሲሆን እያከራከረ ያለዉ አፈጻጸምን አስመልክቶ በእርቅ ለመካፈል የግራ ቀኙ ከተስማሙ በኋላ በማዘጋጃ ቤቱ በአይነት መካፈል አለመቻሉን በተገለጸዉ መሰረት ፍርድ ቤት በሀራጅ ተሸጦ ሊካፈሉ ይገባል በማለት የሰጠው ትዕዛዝ ነዉ፡፡ አከራካሪዉ ንብረት ላይ ተከራካሪዎቹ የጋራ ባለሀብት ነው ተብሎ ከተወሰነ ክፍፍሉ መደረግ ያለበትም በዋናው ውሳኔ፤ስለባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል በሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስለ አፈፃጸም የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በዚህ አግባብ አፈጻጸሙን ከመምራት በተጨማሪ የግራ ቀኙ ያደረጉትና በፍርድ ቤት ያጸደቀ የእርቅ ስምምነት መኖሩ ከተረጋገጠም እርቁ እንደ ፍርድ የሚቆጠርና ሊፈፀም የሚገባው ሲሆን አፈጻጸሙ የሚመራውም በሕጉ አግባብ ነው፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ ሊካፈሉትም የሚገባዉ በተስማሙት መንገድ ነዉ፡፡ በስምምነቱ መሰረት ሊፈፀም ካልተቻለ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ባለው መሰረት ማስፈፀም እንዲሚችል ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ ይዘት መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ደግሞ በቤተሰብ ህጉ በተቀመጠው መፍትሄ መሰረት አፈጻጸሙን ለመምራት የሚያስችል፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር እንደተገነዘብነዉ ተጠሪና አመልካች በጋራ ሀብታቸዉ ክፍፍል መጠን ላይ በፍርድ ቤት የጸደቀ ስምምነት መኖሩ ሳይክዱ በዚህ ስምምነት መሰረት ንብረቱ በአይነት ሊካፈል የሚችል በመሆኑ ላይ ግን ስምምነት ላይ ያለመድረሳቸዉን ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ክፍፍሉ አመቺ በሆነ መንገድ እንዲያልቅ ሊያደርግ (ሊያስፈጽም)የሚችል መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍ.ብ.ሥ.ሥ/ህ ቁ 392 እና ከክልሉ ቤተሰብ ህጉ ከአንቀጽ 101፣102 እና 103 ስር ክፍፍል እንዴት ሊፈጸም እንደሚችል ሰፍሯል። እንግዲህ እያከራከረ ያለዉ የአንደኛዉ ወገን ድርሻ በማነሱ ምክንያት ካርታ ሊወጣለት አልተቻለም የሚል በመሆኑ ክፍፍሉ አጠቃላይ የንብረት መጠን ማእከል በማድረግ በእኩልነት መርህ የሚከናወን መሆኑ ተጠቃሹ ህግ ግዴታ የጣለ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ቤቱንና ይዞታዉን በመለየት የእርሻ መሬቱ የአመልካች የግል ንብረት ነዉ ሲሉ የወሰኑት በዚህ ችሎትም አከራካሪ ባለመሆኑ የሚነካ አይደለም። የቤቱን ክፍፍል አፈጻጸም አስመልክቶ ቤቱ የጋራ በመሆኑና ክፍፍሉ ላይ ስምምነት ባለመኖሩ በሀራጅ ተሸጦ ይካፈሉ የተባለዉ የክልሉን የቤተሰብ ህጉን መርህ ሊከተል ስለሚገባዉ ከአንቀጽ 101-103 በተጠቀሰዉ መሰረት ኣጠቃላይ ይዞታዉ 250 ካ.ሜ ለመሆኑ ያላከራከረ በመሆኑ ባልና ሚስቱ በፍርድ ቤት በፀደቀው ስምምነት መሰረት ይካፈሉ፣በዚህ መሰረት ክፍፍሉ የማይቻል ከሆነ አንዱ ላንዱ በስምምነቱ ድርሻ መጠን(Proportion) ከፍሎ እንዲያስቀር፣ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ቤቱ በገበያ ዋጋ ተሸጦ በስምምነቱ ድርሻ መጠን(Proportion) መሰረት የሽያጭ ገንዘብ እንዲካፈሉ ማድረግ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቤቱ ማካፈል አልተቻለም፣ ስለተባለ ብቻ ህጉ ያስቀመጠዉን ቅደም ተከተል ባለማገናዘብ በሀራጅ ተሸጦ ይካፈሉ መባሉ የግራ ቀኙን በቤቱ የመጠቀም ፍላጉት (ነጻነት) ስለሚገድብ ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ በመሆኑ ያለቅድመ ሁኔታ በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠዉን ትእዛዝ ክፍል ሊታረም የሚገባዉ ነዉ ብለናል።

ባጠቃላይ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለአፈጻጸም የቀረበዉን አከራካሪዉን ቤትና ይዞታ በመቁ.04585 በእርቁ መሰረት ሊፈጸም ባለመቻሉ አከራካሪዉ ንብረት አመቺ በሆነ መንገድ ሊካፈል ሲገባ በሀራጅ ይሸጥ ተብሎ መወሰኑ የቤተሰብ ህጉን የክፍፍል እኩልነት መርህ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. በአ/ብ/ክ/መ/ የወልድያ ወረዳ ፍርድ ቤት በአፈጻጸም መ.ቁ 04586 መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ,የሰሜን ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት 08157 በ26/04/2005 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰብ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 35229 ሰኔ 24ቀን2006 የሰጠው ወሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ዉሳኔ ተሻሽሏል።
2. አከራክሪውን ቤትና ይዞታ የግራቀኙ የጋራ ሀብት በመሆኑ ክፍፍሉን አስመልክቶ በክልሉ የቤተሰብ ህግ ከአንቀጽ 101 እስከ 103 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት 250 ካ.ሜ ለመሆኑ ያላከራከረ በመሆኑ ባልና ሚስቱ በፍርድ ቤት በፀደቀው ስምምነት መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይካፈሉ፣በዚህ መሰረት ክፍፍሉ የማይቻል ከሆነ አንዱ ላንዱ በስምምነቱ ድርሻ መጠን(Proportion) ከፍሎ እንዲያስቀር፣ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ቤቱ በሓራጅ ተሸጦ በስምምነቱ ድርሻ መጠን (Proportion)፣ ስምምነት አለመኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ በእኩልነት መርህ መሰረት የሽያጭ ገንዘብ እንዲካፈሉ ብለናል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሰረት የወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት አፈጻጸሙን እንዲያስቀጥል በፍ.ብ.ሥ.ሥ..ህ.ቁ 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡

3. የግራ ቀኙ የወጪ ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

መስከረም 12 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97829

ሚያዝያ 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ሁሴን ሰይድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የየካ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት ጽ/ቤት አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05348 ጳግሜ 5 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21044 ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና፣ የሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 21382 ታህሳስ 23 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲተረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በሊዝ የተገዛ ቦታ ክፍያ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ ባቀረበው ክስ፣ ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር ጥቅምት 8 ቀን 1998 ዓ.ም በተዋዋለው የሊዝ ውል መሰረት በቀድሞው ቀበሌ 16/17/18 ክልል ስፋቱ 425 ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ በመግዛት ቦታውን ተረክቧል፡፡ የቦታው ጠቅላላ ዋጋ ብር 430312.80 /አራት መቶ ሰላሳ ሺህ ሶስት መቶ አስራ ሁለት ብር ከሰማንያ ሳንቲም/ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ተከሳሽ 20% ከፍሏል፡፡ ተከሳሽ የሁለት አመት የቸሮታ ጊዜ ተሰጠቶት ቀሪውን የሊዝ ዋጋ ከ2002 ዓ.ም እስከ 2020 ዓ.ም በየአመቱ ከፍሎ ለመጨረስ ግዴታ ገብቷል፡፡ ተከሳሽ በሊዝ ውሉ መሰረት የ2001 ዓ.ም የሊዝ ክፍያ ወለድና ቅጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ2003 ዓ.ም የሊዝ ክፍያ ወለድና ቅጣትና የ2003 ዓ.ም የ275 ቀናት የሊዝ ክፍያ ወለድና ቅጣት በድምሩ ብር 153,820.29 /አንድ መቶ ሃምሳ ሶስት ሺ ስምንት ሃያ ብር ከሃያ ዘጠኝ ሣንቲም/ አልከፈለም፡፡ ከሳሾች ተከሳሽ ገንዘቡን እንዲከፍል ቢጠየቅ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገንዘቡን ከባንክ ወለድ ጋር እንዲከፍል ዉሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

2. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ጉዳዩ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ታይቶ የተወሰነ ስለሆነ በፍርድ ቤት መታየት የለበትም በማለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርቦ ፍ/ቤቱ በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተከሳሽ /አመልካች/ ለክሱ ባቀረበው የመከላከያ መልስ ከሳሽ በሊዝ የሸጠልኝን ቦታ በመናፈሻ ክልል ውስጥ ሆኖ በመገኘቱ ቦታው እንዲቀየር ተወስኖ ቦታውን በመቀየር አንድ አመት ከአምስት ወራት ወስዶበታል ከሳሽ ከአንድ አመት ከአምስት ወራት በኋላ ቀይሮ የሰጠኝ ቦታ ባለሶስት መዓዘን ከመሆኑም በላይ የስልክና የመብራት ፖል /ምሰሶ/ የነበረበት በመሆኑ መሰሶው እንዲነሳ ጥያቄ አቅርቤ ከሳሽም ምሰሶው እንዲነሳ ሲፃፃፍ ቆይቶ፣ የምሰሶውን ማስነሻ ወጭ ተከሳሽ ክፍያ ቦታውን ግንባታ ለመጀመር በሚያመች ሁኔታ የተረከብኩት፣ ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ነው፡፡ ከሳሽ በሊዝ ውሉ መሰረት ቦታውን ለግንባታ ምቹ አድርጎ ማስረከብ ስላልቻለ፣ ቦታውን ካስረከበበት ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የሁለት ዓመት የችሮታ ጊዜ፣ የግንባታ መጀመሪያና ማጠናቀቂያ ጊዜ የሊዝ ውሉን በማሻሻልና በሊዝ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር አንቀፅ 14/3/ አንቀፅ 36 /7/ የተደነገገ በመሆኑ፣ ይኽም የአዲስ አበባ አስተዳደር ባወጣው የቅሬታ ማቅረቢያ ስርዓት መሰረት አቅርቤ ያስወሰንኩ በመሆኑ የከሳሽን ክስ ውድቅ በማድረግ ያሰናብተኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

3. የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከሳሽና ተከሳሽ ግንቦት 6 ቀን በ1999 ዓ.ም ያደረጉት የሊዝ ውል መሰረት ተከሳሽ እስከ 2001 ዓ.ም የችሮታ ጊዜ ተሰጥቶታል፡፡ የመመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 37/6/ የግንባታ መጀመሪያና ማጠናቀቂያ ጊዜ ስለማራዝምበት ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን፣ የችሮታ ጊዜ የሚራዘም ስለመሆኑ አይደነግግም ተከሳሽ የአስተዳደሩ የህዝብ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወስኖልኛል ቢልም ውሳኔ አስገዳጅነት የለውም፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ክስ የቀረበበትን የሊዝ ኪራይ ከቅጣትና ከወለድ ጋር ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች ለከተማው ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጎበታል፡፡

4. አመልካች የካቲት 13 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ተጠሪ ቦታውን ነፃ አድርጎ ያስረከበኝ ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ነው፡፡ ተጠሪ ቦታውን ለግንባታ ምቹ አድርጎ የማስረከብ ግዴታውን ሣይወጣ አመልካች የሊዝ ክፍያ እንዲከፍል የመጠየቅ መብት የለውም፡፡ ጉዳዩ በደንብ ቁጥር 48/2004 መሰረት ታይቶ፣ ተጠሪ የሊዝ ውሉን በማደስ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቸሮታ ጊዜ፣ የግንባታ መጀመሪያና ማጠናቀቂያ ጊዜ እንደሰጠኝ አስተዳደራዊ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 14 /3/ እና አንቀፅ 37 /6/ መሰረት ተጠሪ መፈፀም ሲገባው የሊዝ ክፍያ እንዲከፍል በማለት ያቀረበው ክስ የሕግ መሰረት የለውም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

5. ተጠሪ መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓ.ም ባቀረበው መልስ አመልካች የሊዝ ውሉ ከነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ይታሰብልኝ በማለት የሚከራከረው ከግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለው መመሪያ ቁጥር 11/2004 ወደ ኋላ ሄዶ እንዲሰራለት በመጠየቅ ነው፡፡ ሆኖም ለአመልካች ጉዳይ ተፈፃሚነት ያላቸው በወቅቱ ስራ ላይ የነበሩት መመሪያዎች እንጅ መመሪያ ቁጥር 11/2004 ስላልሆነ የአመልካች ክርክር የሕግ መሰረት የለውም፡፡ በደንብ ቁጥር 48/2004 መሰረት ታይቶ የተሰጠ የቅሬታ ሰሚ ውሳኔ አስገዳጅነት ያለው አይደለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሚያዝያ 1 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ መመሪያ ቁጥር 11/2004 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ያለው በመሆኑ የተጠሪ ክርክር ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

6. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪ የጠየቀውን የሊዝ ክፍያ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕግ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን፣ መርመረናል፡፡

7. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን፣ በአመልካችና ተጠሪ ክርክር የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች አግባብነት ካላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር የሕግ ማዕቀፎች ጋር በማገናዘብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካችና ተጠሪ የሊዝ ውል የተዋዋሉት ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ በገለፀው ጊዜ፣ ማለትም ጥቅምት 8 ቀን 1998 ዓ.ም ቢሆንም፣ ተጠሪ በሊዝ ውሉ መሰረት ለተጠሪ የሸጠው ቦታ የመናፈሻ ክልል ውስጥ ሆኖ በመገኘቱ፣ ቦታ መቀየሩን፣ ቦታውንም ለመቀየር አንድ አመት ከአምስት ወራት የወሰደ መሆኑን አመልካች ያቀረበውን ክርክር ተጠሪ ክዶ አልተከራከረም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአመልካች ተቀይሮ የተሰጠው ቦታ ላይ የመብራትና የስልክ ምሰሶዎች የነበሩ መሆኑንና አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1862 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ጉዳቱን ለመቀነስ የስልክ እና የመብራት መሰሶ ከቦታው ለማንሳት የሚያስፈልገውን ወጭ በራሳቸው ሸፍነው የስልክና የመብራት ምሰሶዎቹ ተነስተው ቦታው ለግንባታ ዝግጁ ሆኖ የተሰጣቸው ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሊዝ ለአመልካች የሸጠውን ቦታ ነፃ አድርጎና ለግንባታ ዝግጁ አድርጎ የማስረከብ ኃላፊነት ተጠሪ ያለበት መሆኑ፣ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጭብጥ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይህም ተጠሪ በሊዝ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከተውን ቦታውን ነፃ በማድረግ በተከራዩ /አመልካች/ የማስረከብ ግዴታውን የተወጣው ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም መሆኑን ያሳያል፡፡

8. ተጠሪ እስከ ሚያዝያ 23 ቀን 2003 ዓ.ም በሊዝ ውሉ የተመለከተውን መሰረታዊ ግዴታ አለመወጣቱ፣ የሚኖረውን ውጤት በተመለከተ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ መሬት ሊዝ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 3 በጨረታ የተሰጡ ቦታዎች በመስሪያ ቤቱ ችግር ምክንያት በውሉ መሰረት ማስረከብ ካልተቻለ ውሉ እንደገና ይታደሳል፣ የችግር ጊዜና የግንባታ መጀመሪያ ጊዜ፣ የሊዝ ማጠናቀቂያ ጊዜ እንደገና እንደ አዲስ የሚወስን መሆኑን ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም የመመሪያ ቁጥር 37 አንቀፅ 6/መ/ መሰረት ቦታውን ለማስረከብ ካልተቻለ፣ ተጨማሪ የግንባታ መጀመሪያ ጊዜ ሊሰጥ እንደሚችል የሚደነግግ ሲሆን በአንቀፅ 38 ንዑስ አንቀፅ 3 ተጨማሪ የማጠናቀቂያ ጊዜ ሊፈቀድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡
9. የስር ፍርድ ቤት የመመሪያውን ቁጥር አንቀፅ 37 ብቻ በማየት፣ መመሪያው የቸሮታ ጊዜ የማራዘም ድንጋጌ የለውም በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ለማየት ይቻላል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በዚህ ሰበር የሚከራከረው መመሪያው ወጥቶ ስራ ላይ የዋለው ግንቦት 16 ቀን 2004 ዓ.ም ስለሆነ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ነው፡፡ ሆኖም ይህ የተጠሪ ክርክር በመመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 83/ሀ/ ይህ መመሪያ ከመወጣቱ በፊት በአስተዳደሩ ቦርድ ወይም በመሬት አስተደደር ግንባታ ፈቃድ ባለስልጣን የተፈረሙ ውሎች ወይም የተከናወኑ ስራዎች ህጋዊነታቸው ተጠብቆ በዚህ መመሪያ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል በማለት በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ፣ የተጠሪ ክርክር፣ ይህን የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና ህጋዊ መሰረት የሌለው ክርክር በመሆኑ አልተቀበለነውም፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው የህግ ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ውሉን በማደስ፣ ከሁለት አመት የሊዝ ክፍያ የቸሮታ ጊዜ፣ የሊዝ ክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜና የግንባታ መጀመሪያና የግንባታ ማጠናቀቂያ የጊዜ የሚያሳይ ሌላ ውል ሳያቀርብ፣ አመልካች የሊዝ ክፍያ እንዲከፍል ያቀረበው ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ ማድረግ ሲገባው አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ክፍያ፣ እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔና ይግባኝ ሰሚው ችሎትና የሰበር ችሎቱ ይህንን ውሳኔ በትዕዛዝ ማፅናታቸው አመልካች በመመሪያ ቁጥር 11/2004 የተረጋገጠላቸውን መብት የሚያጣብብና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
10. የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ሊዝ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 11/2004 በአንቀፅ 14/3/፣ በአንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ 6/ለ/ እና በአንቀፅ 38 ንዑስ አንቀፅ 8 የሚጥስ ከመሆኑ በተጨማሪ የከተማው ምክር ቤት ባወጣው ደንብ ቁጥር 48/2004 መሰረት በክፍለ ከተማው የህዝብ አቤቱታና ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የካቲት 8 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2005 የሰጠው ውሳኔ አስገዳጅነት የሌለው ነው በማለት የሰጠው የህግ ትርጉም ስህተት ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ አተረጓጎም፣ በደንብ ቁጥር 48/2004 አንቀፅ 11/1/ እና አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 ቅሬታና አቤቱታ ሰሚ የስራ ሂደቱ የቀረበለትን ጉዳይ በማጣራት የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ውሳኔ እንደሚሰጥ፣ የተደነገገውን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ የስር ፍርድ ቤት ትርጉም በደንብ ቁጥር 23 ድንጋጌዎች ያላገናዘበና በአጠቃላይ የከተማው አስተዳደር ደንብ ቁጥር 48/2004 የወጣለትን መሰረታዊ ዓላማና ደንቡን በማውጣት ሊያሳካው የሚፈልገውን ግብ የማያገናዘብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

11. ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያትና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የከተማው የሰበር ችሎት የአመልካች የሊዝ ክፍያ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የከተማው አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 11/2004 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ከነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የሁለት አመት የሊዝ መክፈያ የቸሮታ ጊዜ፣ የማግኘት መብት ያለው በመሆኑ፣ ተጠሪ የጠየቀውን የ2002 ዓ.ም የ2003 ዓ.ም እና የ2004 ዓ.ም የሊዝ ክፍያ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 107442

መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተክሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ሞገስ ናደው እንዳይላሉ

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስተር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከጥብቅና የዲሲፕሊን ጋር የተያያዘ ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤ 78/06 ግንቦት 22 ቀን 2006 ዓ.ም አመልካች ለአንድ ዓመት ከጥብቅና ሙያ እንዲታገዱ በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በሚኒስትሩ ጸድቆ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ወ/ሮ አስቴር ወ/ሚካኤል ለዲሲፕሊን ጉባኤው ታህሳስ 30 ቀን 2006 ዓ.ም ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡የግለሰቧ አቤቱታ ይዘትም የአሁኑ አመልካች ከግለሰቧ ጋር በገቡት የጥብቅና አገልግሎት ውል መሰረት ጉዳዩን በመደበኛው የክርክር ሂደት ክስ ማቅረብ ሲገባቸው በተፋጠነ ስርነ ስርዓት ክስ አቅርበው ግለሰቧን ለተጨማሪ ወጭና ጉዳት መዳረጋቸውን፣ የአሁኑ አመልካች ከግለሰቧ ለቅድሚያ ክፍያ ብር 20,000.00(ሃያ ሺህ) ተቀብለው ደረሰኝ የከለከሏቸው፣ውሉ ከተቋረጠ በኋላም ገንዘባቸውን አልመልስም ያሏቸው መሆኑን መዘርዘራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም በመጀመሪያ ከግለሰቧ ጋር በሚገባ ተመካክረውና ግለሰቧ አሉኝ በአሏቸው ማስረጃዎች መሰረት ክሱን በተፋጠነ ስነ ስርዓት መሰረት አቅርበው ለክሱ መነሻ የሆነው ቼክ ለመያዣነት የተሰጠ መሆኑ ሲገለጽላቸው የክስ ማሻሻል ጥያቄ ክሱ ከመሰማቱ በፊት ማቅረባቸውን፣የቅድሚያ ክፍያው ብር 20,000.00 ሳይሆን ብር 10,000.00 መሆኑንና ጉዳዩ በጅምር ላይ እንዳለ ውክልናው የተሻረ በመሆኑ ሊጠየቁ የማይችሉ መሆኑን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡ በዚህ መልክ የግራ ቀኙ ክርክር የቀረበለት ጉባኤውም አመልካች የግለሰቧን ክስ በመደበኛ ክስ ማቅረብ ሲገባቸው በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት ክስ ማቅረባቸው ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ የቅድመ ክፍያውን በተመለከተ አመልካች በክሬል ክደው ቆይተው ምስክሮች ሊሰሙ ሲሉ ማመናቸው የግለሰቧን ምስክሮች ጊዜ ከማባከኑም በላይ በጉባኤው ስራ ላይም ከፍተኛ ጫና የፈጠረና ከአንድ ጠበቃ የማይጠበቅ ተግባር መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሁም አመልካች በክርክሩ ሂደት ግለሰቧን ከጉባኤው አዳራሽ ውጪ ምንም ልታደርጊኝ አትችይም አስር ሺህ ብር ከፍዬ ከሁለት ሳምንት በኋላ ወደ ስራ እገባለሁ በማለት የዛቻ አነጋገር መናገራቸው ከጠበቃ የማይጠበቅ ተግባር ሁኖ መገኘቱን ዘርዝሮ አመልካች ክሱን ያቀረቡበት አግባብ በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 30(2)፣ለጥብቅና አገልግሎት ለተቀበሉት ገንዘብ ደረሰኝ አለመስጠታቸው ደግሞ በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 8(1) ከጉባኤው አዳራሽ ውጪ በግለሰቧ ላይ ለተናገሩት ንግግር ደግሞ በደንብ ቁጥር 52/92 አንቀጽ ቁጥር 24(3(ለ)) ((2)) መሰረት ለአንድ ዓመት ከጥብቅና ስራቸው እንዲታገዱ በማለት የውሳኔ ሃሳብ አቅርቦ ይኼው የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስትሩ ጸድቋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የክስ አመሰራረቱ ግለሰቧ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሁነው በሰጡት ማስረጃ መሰረት ሙያውን ተመርኩዘው ያቀረቡት ሁኖ እያለ እና በኋላም ቼኩ በመያዣነት የተሰጠ መሆኑ ሲገለጽላቸው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የክስ ማሻሻል ጥያቄ ለፍርድ ቤቱ አቅርበው ተቀባይነት ያጡ መሆኑን፣ለጥብቅና አገልግሎት ክፍያም ደረሰኝ ያልተሰጠው ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ ከግለሰቧ ጋር በተፈጠረው አለመግባባት መሆኑንና አመልካች ግለሰቧ ላይ ከጉባኤው አዳራሽ ውጪ ዛቻ ፈጽመዋል የተባለው የአንድ ወገን የቃል አቤቱታ ተሰምቶና በማስረጃ ሳይጣራ መሆኑን ዘረዝረው በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔ እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም አመልካች የዲሲፒሊን ጥፋት ፈፅመዋል ተብሎ ለአንድ ዓመት ከጥብቅና ስራ እንዲታገዱ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ መሰረት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የታቻለው የጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤ አመልካች የስነ ምግባር ጥፋት ፈፅሟል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰበት የመጀመሪያው ምክንያት አመልካች የአቤቱታ አቅራቢዋን ግለሰብ ክስ ለፍርድ ቤት ሲያቀርቡ በተፋጠነ ስነ ስርዓት መሰረት ሊያቀርቡ አይገባም ነበር በሚል ነው፡፡አመልካች ይህንኑ የጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት የለውም የሚሉት ክሱ ሊመሰረት የቻለው ግለሰቧ ለጠበቃው በሰጧቸው ማስረጃዎች አግባብ ነው፣ክሱ ከቀረበ በኋላ ግለሰቧ ለአመልካች በአሳወቁት ማስረጃ መሰረትም የክስ ላሻሻል ጥያቄ ለፍርድ ቤቱ በጊዜው አቅርበው የነበሩ መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ የጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤ፣በጠበቃ ላይ ያቀረበውን የዲስፒሊን ክስ ሊወስን የሚገባው በጠበቃው ላይ የቀረበውን የዲስፒሊን ክስና ማስረጃ እንደዚሁም በጠበቃው በኩል የቀረበውን መልስና ማስረጃ በመመርመር እንደሆነ በፌዴራል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቶች የጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 109/1992 አንቀፅ 24(3) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የዲሲፕሊን ጉባኤው ከአንድ ጠበቃ በክስ አቀራረብ ሂደት የሚጠበቁ ሙያዊ ግዴታዎች ምን እንደሆኑ ከዘረዘረ በኃላ አመልካች የዲሲፕሊን ጥፋት ፈፅመዋል ያለው ጉዳዩ በጅምር ላይ ከማለት ያለፈ በመልሳቸው ላይ በቀጥታ የካዱት ነጥብ የለም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ለጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባኤ የካቲት 07 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት የመልስ ማመልከቻ ክሱ መቅረብ የሚገባውን ስርዓት ከግለሰቧ ጋር ተማምነው በስርዓቱ መሰረት ማቅረባቸውን በተራ ቁጥር አንድ ስር፣እንዲሁም ግለሰቧ ክሱ ከቀረበ በኋላ በዋስትና በተያዘው ቼክ ምክንያት በመኖሪያ ቤታቸው ላይ ሀራጅ መውጣቱን እና እዳ መክፍል መጀመራቸውን ለአሁኑ አመልካች ሲያሳውቋቸው በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት አድርገው ክሳቸው ተሻሽሎ እንዲቀርብ ግለሰቧ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ተስማምተው ክስ ከመሰማቱ በፊት አስቀድመው ለፍርድ ቤቱ የክስ ማሻሻያ አቤቱታ ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ ጥያቄውን ማቅረባቸውን በመልሳቸው ተራ ቁጥር ሶስት ስር የዘረዘሩ መሆኑን ከመልስ ማመልከቻቸው ይዘት ተመልክተናል፡፡ ይህንኑ ክርክራቸውን በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሐምሌ 05 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት የይግባኝ ማመልከቻም ያቀረቡት መሆኑን ከማመልከቻው ይዘት ተመልክተናል፡፡ ይህ የአመልካች ክርክር ይዘት በግልጽ የሚያሳየው ደግሞ አመልካች ከመነሻውም ክሱን ያቀረቡት አግባብ የሙያው ስነ ምግባር በሚፈቅደው ስርዓት መሆኑን እንጂ ከደንቡ ውጪ መሆኑን አምነዋል የሚያሳየኝ አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ከስር ጀምሮ ባቀረቡት ክርክር ክሱን ያቀረቡበትን ስርዓት ግለሰቧ ጋር በግልጽ ተማምነውና በእጃቸው ላይ ባሉት ማስረጃዎች ስለመሆኑ ገልጸው እያለ አልካዱም በማለት በዲሲፒሊን ጉባኤው አመልካች አልካዱም ተብሎ የተመዘገበው ተገቢውን የክርክር አመራር የተከተለ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም የዲስፒሊን ጉባኤው በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 3 በጠበቃው ላይ የሚቀርበውን ክስና ማስረጃ ብቻ ሣይሆን በጠበቃው የሚሰጠውን መልስና የመከላከያ ማስረጃ በመመርመር ውሣኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የተደነገገውን ድንጋጌ የጣሰ ነው፡፡ እንግዲህ አንድ ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ የሚያቀርብበት ሕጋዊ አግባብ ምንድነው? የሚለውን ስንመለከትም ሙያው የሚፈቅደውን የስነ ምግባር ደንብ ተከትሎ መሆን እንደአለበት የሚታወቅ ነው፡፡

በመሰረቱ በማንኛውም ጠበቃ ሕግን ለማስከበርና ፍትህን ለማስገኘት የፍትህ አስተዳደሩን የሚገባ ኃላፊነት ያለበት መሆኑንና ጠበቃው ልዩ ደንበኛውን ለሌሎች የሕግ ባለሙያዎች ተከራካሪ ወገኖች ለፍርድ ቤት፤ለሙያውና ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ያለበትን የሙያ ኃላፊነት በቅንነት፤ በታማኝነትና በእውነተኝነት የመወጣት ሙያዊ ግዴታ ያለበት መሆኑ በደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 3 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ማንኛውም ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ በትጋት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመከታተል አፋጣኝና ፍትሀዊ ውሳኔ ለማግኘት ሊወሰድ የሚገባውን እርምጃ ሁሉ በጥንቃቄና በወቅቱ የመፈፀም ሙያዊ ግዴታ ያለበት መሆኑ በደንብ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከደንበኛቸው ጋር ተነጋግረው ክሱን በተፋጠነ ስነ ስርዓት ማቅረባቸውን ገልጸውና በኋላም ግለሰቧ እዳውን መክፈል መጀመራቸውን ለአመልካች ሲገልፁ ክሱን ለማሻሻል ጥረት ያደረጉ መሆኑን አመልካች ጠቅሰው የተከራከሩ ሲሆን አመልካች ክሱን ያቀረቡት ለሙያውና ለግለሰቧ ያላቸውን የሙያ ኃላፊነት በአጓደለ መልኩ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ አመልካች ለሙያውና ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ያለባቸውን የሙያ ኃላፊነት በአጓደለ መልኩ ክሱን አቅርበዋል ሊባል የሚችልው በተገቢው መንገድ ከደንበኛቸው የቀረበላቸውን ሕጋዊ ማስረጃ መሰረት በአላደረገ መልኩ ክስ አቅርበው ስለመሆኑ በሚገባ ከተረጋገጠ ነበር፡፡ አመልካች ደንበኛቸውን በቅድሚያ የሰጡትን ማስረጃ መሰረት አድርገው ክስ ማቅረባቸውና በኋላም ግለሰቧ እዳውን መክፈል መጀመራቸውን ሲገልፁላቸው ክሱን ለማሻሻል ተገቢውን ጥረት ማድረጋቸው በደንብ ቁጥር 57/1992 አንቀጽ 3 እና 8 ድንጋጌዎች መሰረት ሙያዊ ኃላፊነቱን የተወጡ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የዲስፒሊን ጉባኤ ክስ አቀራረቡ በተፋጠነ ስነ ስርዓት ማቅረብህ ያላግባብ መሆኑን አመልካች አምነዋል ያለበት ድምዳሜ የአመልካችን የመልስ ይዘት ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ አመልካቹ ከደንበኛቸው የተቀበሏቸው ማስረጃዎች፣ከግለሰቧ ጋር ቅድሚያ ስለ ክስ አቀራረብ ስርዓት የተስማሙ መሆን ያለመሆኑንና በኋላም ግለሰቧ ለአመልካች የገለጹት እዳ መክፍል መጀመራቸው ጉዳይ መኖር ያለመኖሩንና ይህንኑ ተከትሎ አመልካች የክስ ማሻሻል ጥያቄ ማቅረባቸው ከሙያው ስነ ምግባር፤ ቅንነትና እውነትነት አንፃር ሲታይ ተቀባይነት ያልነበረው መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ሳያረጋገጥ የአመልካች የክስ አቀራረቡ ብቻውን የዲስፒሊን ጥፋት ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ ህጋዊ መሰረት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡በመሆኑም አመልካች ለክስ አቀራረቡ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽመዋል የተባሉት ያላግባብ ነው ብለናል፡፡

ሌላው የዲስፕሊን ጉባኤው አመልካች የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽመዋል ያለው ለጥብቅና አግልግሎት ለተቀበሉት ገንዘብ ደረሰኝ ለደንበኛቸው ያለመስጠታቸው ተረጋግጧል በሚል ነው፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ማስተባበያ ክርክርና ማስረጃ ያለመኖሩን በዲሲፕሊን ጉባኤው የግለሰቧ ምስክሮች የምስክርነት ቃል ለመስጠት ከቀረቡ በኋላ አመልካች አስመዘገቡ ተብሎ ከተመዘገበው ቃል ይዘት ተረድተናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ደረሰኝ ያለመስጠታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 8(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የጣሱ በመሆኑ ለዚህ አድራጎታቸው በዲሲፕሊን ተጠያቂ መደረጋቸው በአግባቡ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ነጥብ የዲስፕሊን ጉባኤው አመልካች ግለሰቧን ከዲሲፕሊን ጉባኤው አዳራሽ ውጪ ዛቻ ፈጽሞባቸዋል በማለት ያስተላለፈው ውሳኔ የአንድ ወገን አቤቱታን መነሻ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያደረገና በሌላ ማስረጃ ያልተደገፈ ነው በሚል ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን እንዳየነው ድርጊቱ መፈጸሙን የዲሲፕሊን ጉባኤው ያረጋገጠው ሲሆን ጉባኤው ለአመልካች በጉባኤው ፊት ተግሳጽ የሰጠ መሆኑን ከገለፀ በኃላ እንደገና በውሳኔው እለት ደግሞ ለዚህ አድራጎት የዲሲፕሊን ጥፋት ነው ከስራ ለማገድም ምክንያት አድርጎታል፡፡ይህ ደግሞ አመልካች ለአንድ ጥፋት ሁለት አይነት ቅጣት የተወሰነባቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡የዲሲፕሊን ጉባኤው ይኼው የአመልካች አድራጎት በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 57 ድንጋጌን የጣሰ መሆኑን በውሳኔ ላይ የገለፀ ቢሆንም ይኼው ተጠቃሽ ድንጋጌ ግን አመልካቹን ለሁለት ጊዜ ሊያጠይቅ የሚችልበትን አግባብ ስለመኖሩ ያስፈረው ምክንያት የለም፡፡ አንድ ጠበቃ ለፈፀመው የዲሲፕሊን ግድፈት ተገቢ ነው የተባለውን የዲሲፕሊን ቅጣት ከአገኘ በኋላ በተመሳሳይ የዲሲፕሊን ጥፋት ድጋሚ እንዲቀጣ ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለውና ከጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ መሰረታዊ ዓላማም ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ሲጠቃለልም የዲሲፕሊን ጉባኤው አመልካችን ለክስ አመሰራረቱና አመልካች ግለሰቧን ከዲሲፕሊን ጉባኤው አዳራሽ ውጪ ዛቻ ፈጽሞባቸዋል በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለው ሁኖ አመልካች ደረሰኝ ያለመስጠታቸውን በማረጋገጥ የሰጠው ውሳኔ ግን ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ሊቀጡ የሚገባው ደረሰኝ ባለመስጠታቸው ምክንያት በደንብ ቁጥር በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 30(2) ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 8(1) እና በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24(3(ለ)) ድንጋጌ አግባብ አመልካች ከጥብቅና ስራ ሊታገዱ የሚገባው ለስድስት ወር ብቻ ሊሆን የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፍትህ ሚኒስቴር የጠበቆች የዲስፕሊን ጉባኤ በመ/ቁጥር 78/06 ግንቦት 22 ቀን 2006 ዓ/ም የውሳኔ ሃሳብ ቀርቦ በሚኒስትሩ ሰኔ 06 ቀን 2006 ዓ/ም የፀደቀውና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡፡
2. የጠበቆች የዲስፕሊን ጉባኤና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የክስ አቀራረብ እና የዛቻ ተግባር የሥነ ምግባር ጥፋት ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ ህጋዊ አይደለም በማለት ሽረናል፡፡
3. አመልካች ከደንበኞቸው ለተቀበሉት ገንዘብ ደረሰኝ ያለመስጠታቸው ግን በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 30(2) ድንጋጌን የጣሰ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 24(3)(ለ))) መሰረት ከጥብቅና ስራ ለስድስት ወር ሊያሳግዳቸው የሚገባ ነው በማለት ወስነናል፡፡ይህ ጊዜ አመልካች ከዚህ በፊት የታገዱበትን ጊዜ መነሻ አድርጎ ሊቆጥር ይገባል ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. በዚህ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ግልባጩ ይላክ ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105765

ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ነገረ ፈጅ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ግርማ ሞገስ 8 ሰዎች - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩ ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ አወሳሰን ሥርዓት የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በአብክመ ደቡብ ወሎ ዞን ደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በክርክር ሂደቱ ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካች ተከሳሽ በመሆን የተሳተፉ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤትም አመልካች ተጠሪዎች ለጥብቅና ሙያ አገልግሎት የከፈሉት 40,000 እንዲከፍል ተወስኗል፡፡ ጉዳዩ በአፈፃፀም የተመለከተው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በዋናው ፍርድ በመ/ቁ 0180/8 በነበረው ክርክር የተደረገው ወጪ በደረሠኝ እንዲተካላቸው መወሰኑን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከጠበቃቸው በተናጠል ባደረጉት ውል እያንዳንዳቸው 5,000 ብር ለመክፈል መስማማታቸው ያሳያል፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤትም በቀረበው ሰነድ መሠረት አመልካች በድምር 40,000 እንዲከፈል ወስኗል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ ለአፈፃፀም ክስ መነሻ በሆነው መዝገብ ላይ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ በቀረበው ደረሰኝ እንዲከፍል መወሰኑን በመግለጽ፤ምንም እንኳ የተጠሪዎች የክርክር ጭብጥ አንድና ተመሳሳይ ነው ቢባልም አንኳ የተሰጠው መብትና በተጣለው መብት ተጠቃሚዎች ቁጥር ሲታይ 8 ተከራካሪዎች ናቸው፡፡ የፈጀው ጊዜም ሲታይ ከጥር 20/2005

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓ.ም ጀምሮ ጉዳዩ በይግባኝ እስከሚታይበት ጊዜ 1 ዓመት ከ 6 ወር ዕድሜ አስቆጥሯል፡፡ ተጠሪዎች የጠበቃ አበል በማለት የተዋዋሉት 40,000 በዝቷል ለማለት የሚቻል አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓል፡፡ የአመልካች ቅሬታ መሠረታዊ ይዘት የተጠሪዎች ክስ በህብረት የቀረበ ስለሆነና ለእያዳንዳቸው የተደረገ ክርክር የሌለ ስለሆነ የጠበቃ አበልን በተናጠል 5000 ማድረጋቸው፤ፍ/ቤቱም እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን በማጣራት የወሰነው በመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የመልስ መልስ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች በማዛመድ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ግራቀኙ እያከራከረ ያለው ጉዳይ ለጥብቅና ሙያ አገልግሎት ተከፈለ የተባለው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ አመልካች ክፍያው የተጋነነ ነው ክሱ በሕብረት የቀረበ ከመሆኑ አንፃር 40,000 እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት የተከራከረ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው ክርክሩ ረጅም ጊዜ የወሰደ ከመሆኑ አንፃር የተከፈለው ገንዘብ የተጋነነ የሚባል አይደለም በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡

በመሰረቱ የወጪና ኪሳራ አከፋፈል ሥርዓት በፍርድ ቤቶች የመወሰን ሥልጣን የተመሰረተ ስለመሆኑ ከፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 462 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ ተጠሪዎች በጠበቃ ተወክለው የተከራከሩ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ክሱ የቀረበውም በአንድ ድርጅት በተመሳሳይ የሕግ ጭብጥ በአንድ ጊዜ ስለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡ የአብክመ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ምዝገባ የጠበቆች ሥነ ምግባር ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 75/1994 ዓ.ም የአገልግሎት ክፍያ በግራ ቀኙ ስምምነት እንደሚፈጸም፤መጠኑ ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ ከሆነ በመቶኛ ስሌት እንደሚውል፤በባልና ሚስት ክርክር ፍቺ ቀለብ በተመለከተ፤በወንጀል ጉዳዮች በሚሰጠው ውሳኔ እና ቅጣት ያልተወሰነ የአገልግሎት ክፍያ እንደማይደረግ ከአዋጅ አንቀጽ 50፣51 እና 52 ጥምር ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ተገቢ የድካም ዋጋ የሚሰጠው መሆን እንዳለበት የታመነ ቢሆንም ከሚገባው በላይ የናረ መሆን የለበትም፡፡ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመወሰን በልምድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዳበረው እና በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘው የአከፋፈል መርህ ጉዳዩ የወሰደው ጊዜ፣የሚጠይቀው ድካም፣የጉዳዩ ውስብስብነት፤የክርክሩ ግምት ታሳቢ የሚደረጉ ናቸው፡፡

የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ ሥራውን ያለውን ውጣ ውረድ ድካምና ያስከተለው ወጭ ታሳቢ መደረግ አለበት፡፡ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ክፍያ ያለምንም ገደብ ስምምነት የሚደረግበት አለመሆኑን ከሥነ ሕግ እና የፍ/ቤቶች አሰራር የዳበረ ልምድ ነው፡፡ በመሆኑም የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ ፍትሐዊ እና ሚዛናዊ ሊሆን ይገባል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ተገቢ የሆነውን የአገልግሎት ዋጋ ለመወሰን የተደረገው ጥረት (ድካም)፣የወሰደው ጊዜ እና የጉዳዩ ውስብስብነት ታሳቢ ማድረጉ ሚዛናዊ የሆነ ክፍያ ለመወሰን እንደ መስፈርት የሚወሰድ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ ያከራከረው ነጥብ የሥራ ክርክር ሲሆን ተጠሪዎች በአንድ ዘንግ ቁመው የሕብረት ክስ ማቅረባቸው አልተካደም፡፡ ጉዳዩ የያዙት ጠበቃ የሚያስፈልጋቸው ጊዜ፤የሚነሳው የሕግና ፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይነት ያለው ከመሆኑ አንፃር ብዙ ጥረት ይጠይቃል ተብሎ አይገመትም፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ እንደተመለከትነው ጠበቃው በችሎት የቆሙባቸው ጊዜያት የተወሰኑ ስለመሆናቸው ተመልክተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች በተናጠል 5,000 በድምር 40,000 መክፈላቸው ጠበቃው በክርክሩ ያጠፉት ጊዜ፣ጉዳዩ ከወሰደው ጊዜ ግምቱ የክርክሩ ባሕሪ እና ይዘት አንፃር የተጋነነ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ያደረጉት የጥብቅና አገልግሎት ውል ከጉዳዩ ክብደት እና ውስብስብነት፤ግምቱ የወሰደው ጊዜ አንፃር መዝነው ትክክለኛ ወይም ተቀራራቢ ዋጋ መወሰን ሲገባቸው በተጠሪዎች የቀረበው ውል እንዳለ ወስደው አመልካች 40,000 ብር እንዲከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች መክፈል ያለበት የጥብቅና አገልግሎት ዋጋ ከተሰጠው አገልግሎት መጠን አንፃር በዳኝነት የተወሰነው ብር 145,360 አሥር ፐርሰንት (10%) አሥራ አራት ሺ አምስት መቶ ሰላሳ ስድስት ነው ብለናል፡፡ በእዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍርድ ቤቶች የፈጸሙት ስህተት በማረም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደሴ ወረዳ ፍ/ቤቶች በመ/ቁ. 36/018018 ግንቦት 01/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 17030 በ9/11/2006 የሰጠው ፍርድ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0309036 በ27/01/2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች መክፈል የሚገባው በዳኝነት የተወሰነው ብር 145,360 10% ብር 14,536 ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ት ዕ ዛ ዝ

- በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.112091

ሚያዝያ 28 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡-መድህን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

አመልካች፡- አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ወኪል መልካሙ መጩየ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- ሠማያዊ ፓርቲ ወኪል ወረታው ዋሴ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 46744 መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ነው፡፡ በምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አመልካች አቤቱታ አቅራቢ ተጠሪ መልስ ሰጭ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ በግንቦት ወር 2007 ዓ/ም በሚካሄደው ጠቅላላ ምርጫ የተጠሪ በምርጫ ክልሉ እጩ አድርጎ ያስመዘገባቸውን ሰዎች በመቃወም የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡

1. አመልካች በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪ ደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል እጩ አድርጎ ያቀፈረባቸው አቶ ግርማ ቢተው፣ አቶ መለስ ዘለቀ፣ ወ/ሮ የርጋዱ ታደገ እና አቶ ይሁኔ ጥላሁን የአመልካች ድርጅት አባላት እንጂ የተጠሪ አባላት አይደሉም፡፡ ተጠሪ ፓርቲውን እንዲወክሉ በእጩነት አቅርቦ በቅጽ 003 ያስመዘገባቸው ግለሰቦች በእጩነት እስከ ተመዘገቡበት ጊዜ ድረስ የአመልካች አባልና አመራር ሆነው ተልዕኮ ሲያስፈጽሙ የቆዩ በመሆናቸው ግለሰቦቹ ተጠሪን (ሠማያዊን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፓርቲን) በመወከል እጩ ሆነው ሊወዳደሩ አይገባቸውም በማለት በጽሑፍ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ ከላይ ስማቸው የተገለፁት ግለሰቦች የሌላ የፖለቲካ ፓርቲ (አመልካች) አባል በመሆናቸው ተጠሪን በመወከል እጩ ተወዳዳሪ ሆነው መቅረብ አይችሉም በማለት የካቲት 10 ቀን 2007 ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

2. ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተጠሪ ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታና ደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሠጠውን ውሳኔ ከመረመረ በኋላ የመርዓዊና ገርጨጭ ምርጫ ክልል ቢሮ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ የሚያስለውጥ ምክንያት የለም በማለት የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. ተጠሪ የደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴና የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 39918 የቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ ከመዝገብ ቁጥር 39919 ጋር በማጣመር በመዝገብ ቁጥር 39919 ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይግባኝ ባይ (ተጠሪ) እጩ ተወዳዳሪ ሆነው ሊመዘገቡልኝ ይገባል የሚላቸው ግለሰቦች የፓርቲ አባል በነበሩበት አንድነት ለፍትህና ዲሞክራሲ ፓርቲ (አመልካች) መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አቤቱታ አቅርበው የተሰናበቱ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ እንደዚሁም የይግባኝ ባይ (ተጠሪ) አባል ለመሆን መጠበቅ የሚገባቸውን ጊዜ ያህል ጠብቀው በመተዳደርያ ደንቡ መሠረት አባል ስለመሆናቸው ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም መርዓዊና ገርጨጭ ምርጫ ክልል ቢሮ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴና የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

4. ተጠሪ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መርዓውና ገርጨጭ ምርጫ ክልል ቢሮ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴና የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጡትን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር በሰበር መዝገብ ቁጥር 46743 ከሰማ በኋላ ጉዳዩን በሰበር አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በእጩ ተወዳዳሪነት ያቀረባቸው ሰዎች የሌላ ፖለቲካ ድርጅት አባል ለፍትህና ዲሞክራሲ ፓርቲ (አመልካች) የነበሩ ቢሆንም በማናቸውም ጊዜ አባልነት መብታቸውን በመተው የሌላ ፖለቲካ ድርጅት አባል የመሆን መብት አላቸው፡፡ ስለዚህ ተቃውሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበባቸው ሰዎች ለፍትህና ዲሞክራሲ ፓርቲ (አመልካች) አባላት የነበሩ ቢሆንም የሠማያዊ ፓርቲ አባልና እጩ ተወዳዳሪ የመሆን መብት አላቸው፡፡ ተቃውሞ የቀረበባቸውን ሰዎች በአባልነት የተቀበላቸውና ዕጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ሰማያዊ ፓርቲ ግለሰቦቹ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ የተደነገገውን ስድስት ሳምንት የመጠበቂያ ጊዜ ሳይቆዩ የፓርቲው ሙሉ አባልና እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ማቅረብ እንደሚችል በመተዳደሪያ ደንቡ የተደነገገ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመርዓዊናገርጨጭ ምርጫ ክልል ቢሮ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴና የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ግለሰቦቹ በእጩነት አይመዘገቡም በማለት የሰጡትን ውሳኔ ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ሽሮ ግለሰቦቹ ተጠሪን ወክለው በምርጫ ለመወዳደር ይመዝገቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. አመልካች መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ግለሰቦች የአመልካች አመራርና አባላት የነበሩ ናቸው፡፡ ተጠሪ ግለሰቦቹ የአመልካች አባልነታቸውን የተውት መሆኑን ለአመልካችና ለሕዝብ አሳውቀው የለቀቁ መሆኑን ሳያረጋግጥ የሌላ የፖለቲካ ድርጅት እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ሰዎች በአመለካች ያላቸውን አባልነት መብት በፈቃዳቸው የተውት ስለመሆኑ በጽሁፍ አላሳወቁም፡፡ አንድ ፓርቲ አባል በአባልነትና በአመራርነት ሲሳተፍ ለነበረበት ፖለቲካ ድርጅት ሳያሳውቅ የሌላ ፖለቲካ ድርጅት አባል ነኝ ብሎ እንዳሻው በሌላ ፖርቲ አባልነት መመዝገብና የሌላ ፓርቲ እጩ ሆኖ መቅረብ አይችልም፡፡ በመሆኑም የአመልካችን አባላት ተጠሪ በተወዳዳሪነት ለማቅረብ ህጉ እንደሚፈቅድለት በመግለጽ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በድምጽ ብልጫ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

6. ተጠሪ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ደርሶት ሚያዚያ 20 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የመምረጥና የመመረጥ መብት ሕገ መንግስታዊ ዕውቅና የተሰጠው መብት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው የፖለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን የሚያስፈልገውን መሰፈርት እስካሟላ ድረስ በፍላጎቱ የአንድ ፖለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የሌላ ፖለቲካ አባል የነበረን ሰው ከነበረበት የፖለቲካ ድርጅት በአግባቡ ሳይሰናበት የሌላ ፖለቲካ ድርጅት አባል ለመሆንና እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ አይችልም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህገ መንግስቱን ድንጋጌ የሚቃረን ነው፡፡ ተጠሪ እጩ ተወዳዳሪ ያደረጋቸው ሰዎች የተጠሪ መተዳደሪያ ደንብ ያሰቀመጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት የሰማያዊ ፓርቲ አባል ሆነዋል፡፡ ሰዎቹ ከዚህ በፊት የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባል የነበሩ መሆናቸው የተጠሪ አባላት ከመሆን አይገድባቸውም፡፡ እንደዚሁም የአመልካች ክርክር ተጠሪ እጩ ተወዳዳሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያደረጋቸው ሰዎች የፖለቲካ ድርጅት አባልነታቸውን በማናቸውም ጊዜ የመተው መብት ያላቸው መሆኑንና የፖለቲካ ፓርቲው ይህንን መብት በመተዳደሪያ ደንቡ መገደብ እንደሌለበት በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ የተደነገገውን ግልጽ ድንጋጌ የሚጥስ ነው፡፡ ሰዎች ከነበራችሁበት የፖለቲካ ድርጅት በአግባቡ አልተሰናበታችሁም በሚል ህጋዊነት የሌለው ምክንያት በማይፈልጉት የፖለቲካ ድርጅት በአባልነት እንዲቆዩ ሊደረጉ አይገባም፡፡ ስለዚህ የአመልካች ክርክር ውድቅ ተደርጎ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠውን ውሳኔ እንዲያፀናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ መስጠት አያስፈልገኝም ብሏል፡፡

7. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ለዚህ ሰበር ችሎት አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለጸው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርፍ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን በሰበር አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማየት ሥልጣን አለው ቢባል ተጠሪ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን መርዓዊናገርጨጭ ምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ሰዎች በእጩ ተወዳዳሪነት ሊመዘገቡ ይገባል በማለት የሰጠው የህግ ትርጉምና ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

8. የመጀመሪያውን ጭብጥ ለመወሰን ከምርጫ ሂደት የሚቀርቡ አቤቱታዎች ስለሚስተናገዱበት ሥርዓትና ጉዳዩን በዳኝነት አይተው ውሳኔ የመስጠት የዳኝነት ሥልጣን ስላላቸው የክልልና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 532/1999 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘትና የድንጋጌቹን አቀራረጽና መሰረታዊ ባህሪ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በምርጫ ሂደት ስለሚነሱ አቤቱታዎች ክርክሮች አቀራረብና አወሳሰን መሰረታዊ መርሆችን የሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 6 እና ንዑስ አንቀጽ 10 የክልል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በይግባኝ አይተው የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጡባቸውን ጉዳዮች ገልጿል፡፡

9. የአዋጁ አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 11 እና አንቀጽ 95 ንዑስ አንቀጽ 3 እና ንዑስ አንቀጽ 5 የወረዳው ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በእጩ ምዝገባ ሂደት አከራካሪ ጉዳይ ሲያጋጥም በመጀመሪያ ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ ሊቀርብ እንደሚገባውና የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሃያ አራት ሰዓት ውሳኔ እንደሚሰጥ በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 94 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 4 ያሉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወገን በሰባ ሁለት ሰዓት ውስጥ ለክልሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ሊያቀርብ እንደሚችልና ይግባኙም ለክልሉ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ታይቶ ውሳኔ ሰለሚሰጥበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር. 532/1999 አንቀጽ 94 ከንዑስ አንቀጽ 5 እስከ ንዑስ አንቀጽ 10 ባሉት ድንጋጌዎች ተደንግጓል፡፡

10. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በይግባኝ አይቶ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አርባ ስምንት ሰዓታት ማቅረብ እንደሚችልና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 11 ይደነግጋል፡፡ ከላይ የገለጽናቸው የአዋጅ ቁጥር 532/1999 ድንጋጌዎች ሕግ አውጭው የክልሉ ፍርድ ቤቶች በይግባኝ አይተው የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጡባቸውን ክልላዊ ባሕሪ ያላቸውን ጉዳዩች በግልፅ በመደንገግ ለክልል ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን የሚሰጡ ናቸው፡፡ አዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 6 በሌሎች ጉዳዮች የሚቀርቡ የምርጫ አቤቱታዎች ሰምቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከላይ የገለጽነው የህጉ ድንጋጌዎች አቀራረጽ የክልል ፍርድ ቤቶች በይግባኝ አይተው የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጡባቸው በአዋጁ በግልጽ ያልተደነገጉ ቀሪ የዳኝነት ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው የሚለውን መርህ የሚያራምድ ነው፡፡
11. ይህም ለክልሉ ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 532/1999 በግልጽ ተለይቶ የተሰጣቸው የዳኝነት ሥልጣን ክልላዊ ባህሪ ያላቸውና በክልል ፍርድ ቤቶች በይግባኝ ታይተው የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጡባቸው ሙሉ በሙሉ በክልሉ የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቁ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን እንዳለው በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 11 እና አንቀጽ 95 ንዑስ አንቀጽ 3 እና ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የወረዳው ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥባቸውን ጉዳዩችና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ወገን የሰበር አቤቱታውን በመጀመሪያ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማቅረብ እንዳለበት ከሕግ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) እና የተሻሻለው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 /ሐ/ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን አለኝ በማለት ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ ተገቢና የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

12. ከላይ በሁለተኛነት የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ለአመልካችና ለተጠሪ ክርክር መነሻ የሆኑትንና በየደረጃው ባሉ የምርጫ አቤቱታና ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችና ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና በህገ መንግስቱ ህጋዊ እውቅናና ጥበቃ የተሰጠው የመምረጥ፣ የመመረጥና የመደራጀት መብት መሰረታዊ ይዘት፣ መብቶቹ ተግባራዊ ለማድረግ የወጡ ዝርዝር ህጎች መሰረታዊ ግብ፣ እነዚህን መብቶች ተግባራዊ በሚደረጉበት ጊዜ ግለሰቦችም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ዝቅተኛ መስፈርቶች ወይም ቅድመ ሁኔታዎችና ግለሰቦች ወይም የፖለቲካ ድርጅቶቹ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ዝቅተኛ መስፈርቶች ወይም ቅድመ ሁኔታዎች አለማሟላታቸው የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

13. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን መርዓዊና ገርጨጭ ምርጫ ክልል እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ሰዎች፣ ከዚህ በፊት አመልካች አባልና አመራር የነበሩ መሆኑ ተረጋግጧል። ተጠሪ በምርጫ ክልሎቹ እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ሰዎች እስከቀርብ ጊዜ ድረስ የአመልካችን የፖለቲካ ተልዕኮ ሲያስፈጽሙ የነበሩ መሆኑን ተጠሪ ማስተባብያ ያላቀረበበት ዕውነታ መሆኑን ተረድተናል። ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ እጩ አድርጎ ያቀረባቸው ሰዎች የተጠሪ እጩ ሆነው ከመቅረባቸው በፊት አባልና አመራር ሆነው ለኖሩበት የፖለቲካ ድርጅት ማለትም አመልካች የድርጅቱ አባል ሆነው የማይቀጥሉና አባልነታቸውን በፈቃዳቸው የተው ስለመሆናቸው በጽሁፍ ያሳወቁ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው።

14. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ማናቸውም አይነት ልዩነት ሳይደረግበት በቀጥታ እና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በህዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣ አስራ ስምንት ዓመት ሲሞላው በህግ መሰረት የመምረጥ፣ በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው የመምረጥና የመመረጥ መብት ያለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ ማናቸውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት ያለው መሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 31 ተደንግጓል። እንደዚሁም የፖለቲካ ድርጅቶች በሠራተኞች ፣ በንግድ፣ በአሰሪዎችና በሙያ ማህበራት ለመሳተፍ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማናቸውም ሰው በፍላጎቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን ያለበት መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል። እነዚህ በህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች የዜጎች የመምረጥ የመመረጥና የፖለቲካ ድርጅት የመመስረትና የፖለቲካ ድርጅት አባል የመሆን መብትን ጨምሮ ሌሎች የመደራጀት መብቶች ዕውቅናና ጥበቃ የሚሰጡ የህገ መንግስት ድንጋጌዎች ናቸው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

15. ከላይ የተገለጹት ህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች መብቶቹን በጥቅል አገላለጽ የሚደነግጉ በመሆናቸው ማናቸውም ዜጋ የመምረጥ፣ የመመረጥና የመደራጀት መብት ዝርዝር ይዘትና መብቶቹ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ስርዓቶች አካትተው የሚይዙ አይደሉም፡፡ ከህገ መንግስቱ መብቶቹን በመርህና በጥቅሉ ከመደንገግ አልፎ የመብቶቹን ዝርዝር ይዘትና መብቶቹ ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ስርዓት በዝርዝር እንዲደነግግ አይጠበቅበትም፡፡ ይህም በመሆኑ ዜጎች በህገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን የመምረጥ፣ የመመረጥና የመደራጀት መብት የሚዘረዝሩ፣ መብቶቹ ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ስርዓትና መብቶቹን ተግባራዊ በሚደረጉበት ጊዜ ግለሰቦችም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊያሟላቸው የሚገቡ ዝቅተኛ መስፈርቶች ወይም ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር የሚያስቀምጡ ሌሎች ህጎች ማለትም አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ወጥተው ስራ ላይ ውለዋል፡፡

16. ከላይ የተገለጹትን የዜጎች መሰረታዊ የመምረጥ የመመረጥና የመደራጀት መብት ተግባራዊ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ወጥተው ስራ ላይ ከዋሉት የህግ ማዕቀፎች የተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 የመጀመሪያው ተጠቃሽ ነው፡፡ ህግ አውጭው አዋጁን በማወጅ ለማሳካት ከሚያስባቸው ግቦች መካከል፣ የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች የሚሳተፉበትና ዓላማቸውን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለመራጩ ህዝብ የሚገልጹበት መራጩ ህዝብም በመረጃ ላይ በመመስረት ፈቃዱን በነፃት በመግለጽ ወኪሎቹን የሚመርጥበትን የምርጫ ስርዓት መዘርጋት፣ በምርጫው ተሳታፊ የሚሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የግል እጩዎች ለፍታሀዊ ሰላማዊ ነጻና ዲሞክራሳዊ የምርጫ ስርዓት መስፈን ገንቢ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ግልጽ አሰራር መዘርጋትና ህገ መንግስቱን መሰረት በማድረግ ነጻ ገለልተኛና ፍታሀዊ ምርጫ በማካሄድ በህዝብ ድምጽ የተመረጠ መንግስት እንዲቋቋም ማድረግ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 532/1999 መግቢያ አራተኛውና አምስተኛው ፓራግራፍና ከአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

17. ከላይ የተገለጹትን ህገ መንግስት መሰረታዊ መብቶች ተፈፃሚ ለማድረግ የወጣው ሌላው የህግ ማዕቀፍ የፖለቲካ ፓሪቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000 ነው፡፡ በዚህ አዋጅ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ማለት ከህብረተሰቡ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎችን በማሰባሰብ የራሱን የፖለቲካ እምነትና ዓላማ የሚያንጸባርቅ ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በዴሞክራሳዊ ስርዓት የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ በአዋጁ መሰረት የተቋቋመና የተመዘገበ ልዩ ባህሪና ተልዕኮ ያለው ማህበራዊ ተቋም እንደሆነ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ ህግ አውጭው አዋጅ ቁጥር 573/2000 ያወጀው በህገ መንግስቱ መሰረት ዜጎች የመደራጀት መብታቸውን ተጠቅመው በሰላማዊና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህጋዊ የፖለቲካ እንቅሳቁሴ በመሳተፍ የሚይዙበትን ሁኔታ በህግ ለመደንገግ፣ ዜጎች የፖለቲካ ፓርቲ ሲመሰርቱና በአባልነት ሲንቀሳቀሱ ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊከተሏቸው ስለሚገቡ መርሆች ለመደንገግና የፖለቲካ ፓርቲዎች በመዋሃድ ወይም ግንባር በመፍጠር ወይም በመቀናጀት ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበትን ሁኔታ ግልጽ ለማድረግ እንደሆነ በመግቢያው በግልጽ አስቀምጧል።

18. በህገ መንግስቱ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 አንድ ዜጋ በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄደው ምርጫ በተመራጭነት ለመቅረብና በህገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን የመመረጥ መብት ለመጠቀም ሊያሟላቸው የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በዋናነት በአዋጅ ቁጥር 532/1999 ከአንቀጽ 44 እስከ አንቀጽ 57 ተደንግጓል። በተለይም የአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 45 እና አንቀጽ 46 እጩዎች በህግ የተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም በግላቸው ተወዳዳሪ ሆነው ለመቅረብ የሚችሉበትን ህጋዊ ሁኔታ በዝርዝር ያስቀምጣሉ። የአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 የፖለቲካ ድርጅት በመወከል ወይም በግላቸው ተወዳዳሪ ለእጩነት የሚቀርቡ ሰዎች ሁሉም በጋራ ሊያሟላቸው የሚገቡና ለእጩነት የሚያበቁ መመዘኛዎች የሚደነግጉ ናቸው። አዋጁ ቁጥር 532/1999 የአንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 3 በግል እጩ ሆኖ የሚቀርብ ተወዳዳሪ በልዩ ሁኔታ ሊያሟላው ስለሚገባው ተጨማሪ መስፈርት፣ ማለትም በግል እጩ ሆኖ ለመቅረብ በምርጫ ክልሉ ኗሪ የሆኑ ከአስራ ስምንት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸውና የመምረጥ መብታቸውን ያልተከለከሉ ከአንድ ሺ የማያንሱ ሰዎች የድጋፍ ፊርማ የግል ተወዳዳሪው የማቅረብ ግዴታ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል።

19. በአንፃሩ በህግ አግባብ የተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት መስፈርቱን የሚያሟላ እጩ በማቅረብ ሊወዳደር እንደሚችል፣ የፖለቲካ ድርጅቱን ወክለው የሚወዳደሩ እጩዎች ዝርዝር ለቦርዱ የሚያሳውቀው የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር እንደሆነና የፖለቲካ ድርጅት ወክሎ ለሚቀርብ እጩ በፓርቲው መወከሉንና በእጩነት ለመቅረብ መሰማማቱን የሚገልጽ ማስረጃ ከእጩነት ማስረጃው ጋር መቅረብ እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 46 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 3 በቅደም ተከተል ደንግጓል። እዚህ ላይ የሚነሱት ጥያቄዎች በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት የፖለቲካ ድርጅቶች እጩ ተወዳዳሪ አድርገው የሚያቀርቧቸው ሰዎች በአዋጁ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ሊያሟላቸው የሚገቡና ለእጩነት የሚያበቁ መመዘኛዎች በተጨማሪ የፖለቲካ ድርጅቱን ወክለው በእጩነት ለመቅረብ በልዩ ሁኔታ ሊያሟሉ የሚገባቸው ተጨማሪ መስፈርት አሉ ወይስ የሉም? የፖለቲካ ድርጅት ወክለው የሚቀርቡ እጩዎች ከግል ተወዳዳሪዎች በተለየ ሁኔታ የሚያሟላቸው ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ የሚባል ከሆነ መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው? በተለይም የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባላት የነበሩ ሰዎችን በእጩ ተወዳዳሪነት ያቀረበ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፖለቲካ ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 46 መሰረት የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባላት የነበሩ ሰዎች እጩ አድርጎ ሲያቀርብ ሊያረጋግጣቸውና በማስረጃ አስደግፎ ሊያቀርባቸው የሚገቡት ተጨማሪ ፍሬ ጉዳዮች ወይም መስፈርቶች ምንድን ናቸው? የፖለቲካ ድርጅት ወክለው የሚቀርቡ እጩዎች ተጨማሪ መስፈርቶቹን ባያሟሉ ህጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው? የሚሉት ናቸው።

20. ከላይ የተገለጹትን ጥያቄዎች ለመመለስ በአዋጅ ቁጥር 532/1999 ከአንቀጽ 44 እስከ አንቀጽ 57 የተደነገጉትንና ሌሎች የአዋጁን ድንጋጌዎች መመልከት ብቻውን በቂ አይደለም። በአንባሩ በመጀመሪያ ደረጃ የእነዚህን ድንጋጌዎች ይዘት ህግ አውጭው አዋጅ ቁጥር 532/1999 ካወጀበት መሰረታዊ ምክንያትና በአዋጁ ሊያሳካቸው ከሚፈልጋቸው ግቦች ጋር በጣምራ መመርመርና ለድንጋጌዎቹ ትርጉም መስጠት ይጠይቃል። በሁለተኛ ደረጃ የአዋጅ ቁጥር 532/1999 ድንጋጌዎች፣ ህግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 573/2000 ለፖለቲካ ፓርቲ ከሰጠው ትርጓሜ፣ አዋጅ ቁጥር 573/2000 ካወጀበት መሰረታዊ ግብና ዓላማ ከአዋጁ ድንጋጌዎች ይዘት ጋር ማገናዘብና ህግ አውጭው እነዚህን የህግ ማዕቀፎች በማሟላት ሊያሳካው ከፈለገው መሰረታዊና አገራዊ ግብ አንፃር ጉዳዩን መመርመርና የህግ ትርጉም መስጠት ያስፈልጋል።

21. ከዚህ አንፃር ስናየው አዋጁ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች መሰረት የፖለቲካ ድርጅቶች እጩ ተወዳዳሪ አድርገው የሚያቀርቧቸው ሰዎች፣ አዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከተደነገጉት መመዘኛዎች በተጨማሪ፣ የፖለቲካ ድርጅቱን ወክለው በእጩነት ለመቅረብ በልዩ ሁኔታ ሊያሟሉ የሚገባቸው ተጨማሪ መስፈርቶች ያሉ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል። የፖለቲካ ድርጅቱን ወክለው በእጩነት የሚቀርቡ ሰዎች በልዩ ሁኔታ የሚያሟሉት መስፈርት እጩ ተወዳዳሪዎቹ በህግ አግባብ የተመዘገቡና በእጩነት ያቀረባቸው የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መሆን ያለባቸው መሆኑን ከአዋጁ ቁጥር 573/2000 መግቢያ፣ አዋጅ 573/2000 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል።

22. የፖለቲካ ድርጅቶች ወክለው የሚቀርቡ እጩዎች በግላቸው እጩ ሆነው በተወዳዳሪነት እንዲሚቀርቡ ዜጎች የሚወዳደሩበት የምርጫ ክልል ኗሪዎች የድጋፍ ፊርማ አሰባስበው እንዲያቀርቡ በህጉ የማይጠየቁት በእጩነት የወከላቸው የፖለቲካ ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 የሚጠይቀውን የመስራች አባላት ድጋፍና ድምጽ በማሟላት የተመዘገበ መሆኑን ህግ አውጭው ከግንዛቤ በማስገባቱ ነው። ህግ አውጭው ፖለቲካ ድርጅቶቹን ወክለው የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎች የመራጭ ድጋፍ የማሰባሰብ ግዴታ እንዳይኖርባቸው ያደረገው የፖለቲካ ድርጁቱን በመወከል በእጩነት የሚቀርቡት ሰዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህጋዊ መስፈርቶችን ያሟሉ የፓርቲው ትክክለኛ አባላት ይሆናሉ በሚል ዕምነት እንደሆነ፣ የአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 45 እና አንቀጽ 46 ድንጋጌዎችና የአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 ድንጋጌዎች በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር የፖለቲካ ድርጅቶች ወክለው የሚቀርቡ እጩዎች ሁሉንም ህጋዊ ሁኔታዎች አሟልተው በእጩነት የሚወክሉት የፖለቲካ ድርጅት አባላት መሆን አለባቸው፡፡

23. የፖለቲካ ድርጅቶች የተለያየ አመለካከት ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች የሚወክሉ፣ የራሳቸው የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራምና ዓላማ ያላቸው፣ የፖለቲካ ዓላማቸውን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለማሳካትና በምርጫ የመራጩን ህዝብ ዓመኔታ፣ ድጋፍና ድምጽ አግኝተው፣ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚወዳደሩ ለየት ያለ ባህሪና ተልዕኮ ያላቸው ማህበራዊ ተቋማት መሆናቸው በሁለቱም አዋጅዎች በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህም በመሆኑ አንድ ሰው በአንድ ጊዜ የአንድ የፖለቲካ ፕሮግራምና ዓላማ ያለው ህጋዊ የፖለቲካ ድርጅት አባል የመሆን መብት ይኖረዋል፡፡ ከዚህ አሰራር በሚቃረን ሁኔታ አንድ ሰው በተመሳሳይ ጊዜ የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች አባል የመሆን መብት እንደሌለው ከአዋጅ ቁጥር 573/2000 መግቢያ፣ ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2፣ አንቀጽ 13፣ አንቀጽ 14ና አንቀጽ 15 ድንጋጌዎች ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

24. በአዋጁ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የአንድ የፖለቲካ ድርጅት አባል የነበረ ሰው አባል ሆኖ የተደራጀበትን የፖለቲካ ድርጅት አባልነት መብት የሚያጣው በሁለት መሰረታዊ ሁኔታዎች መሆኑን በአዋጁ ቁጥር 573/2000 በምዕራፍ ሶስት የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መብትና ግዴታ በሚል ርዕስ ከአንቀጽ 28 እስከ አንቀጽ 31 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመመልከት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የፖለቲካ ፓርቲው በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ከአባልነት እንዲወገድ ሲወሰንበት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ፓርቲው አባሉ ከፖለቲካ ድርጅት አባልነቱ እንዲወገድ የተወሰነበት ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ውጭ ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ ከፖለቲካ ድርጅት አባልነት እንዲወገድ የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ ተደንግጓል፡፡

25. ሁለተኛው የፓለቲካ ፓርቲ አባል የሆነ ሰው የፓርቲው አባል መሆኑ ቀሪ የሚሆንበት መንገድ አባሉ በአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 የተሰጠውን የፓለቲካ ፓርቲ አባልነት የመተው መብቱን ተጠቅሞ የፓለቲካ ድርጅት አባልነቱን ሲተወው መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡እዚህ ላይ መታየት ያለበት አንድ ሰው የፓለቲካ ፓርቲ አባልነቱን በፈቃዱ ትቷል የሚባልበት ህጋዊ መስፈርት ምንድን ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አንድ ሰው የፓለቲካ ፓርቲ አባልነቱን በፈቃዱ ትቷል የሚባለው በማያሻማ ሁኔታ የፓርቲ አባልነቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፈቃዱ የተወው መሆኑን ለፓርቲው ሲያሳውቅ እንደሆነና አንድ ሰው የፓርቲ አባልነቱን በማያሻማ ሁኔታ ገልፆ ትቷል ለማለት አባል የሆነበት የፓለቲካ ድርጅት፣ በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 12 መሰረት አቅርቦ ባስመዘገበውና በጸደቀው የፓለቲካ ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አባልነቱን በፈቃዱ የተወው መሆኑን ሲያሳውቅ እንደሆነ የአዋጁን አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 ፣አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) እና አንቀጽ 12 ድንጋጌዎች ጋር በጣምራ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

26. ይህም የአንድ የፓለቲካ ፓርቲ አባል የሆነ ሰው የፓለቲካ ድርጅቱ የአባልነት መብት በፈቃዱ የተወው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ በአባልነት ለሚሳተፍበት የፓለቲካ ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ሳይገልፅና ሳያሳውቅ፣ በአባልነት ስሳተፍበት የነበርኩትን የፓለቲካ ፓርቲ አባልነት በፈቃዴ ትቼ የሌላ ፓለቲካ ድርጅትአባል ሆኛለሁ ስለዚህ ለሁለተኛ ጊዜ የተደራጀሁበትን የፓለቲካ ድርጅት ፓርቲ ወክየ በእጩነት ለመመዝገብና ለመወዳደር እችላለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር ከላይ የገለጽናቸውን የፓለቲካ ድርጅት የአባልነት መብት ሊቋረጥ ስለሚችልባቸው ሁለት መሰረታዊ ሁኔታዎችና የአዋጅ ቁጥር 573/2000 ድንጋጌዎች መስፈርት የማያሟላና የህግ መሰረት የሌለው ክርክር ነው፡፡

27. ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን መርዓዊና ገርጨጭ ምርጫ ክልል ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ለአማራ ክልል ምክር ቤት እጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ያቀረባቸው ግለሰቦች፣ አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ በመባል የሚታወቀው የፓለቲካ ድርጅት(አመልካች)አባል መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ግለሰቦቹን በእጩነት አቅርቦ ለማስመዝገብ ጥያቄ ሲያቀርብ ሰዎች አባል ከሆኑበት የፓለቲካ ድርጅት(አመልካች)በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በዲስፒሊን ጥፋት ከአባልነት የተወገዱ ወይም አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 12 መሠረት አመልካች ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አቅርቦ ባስመዘገበውና ባጸደቀው የፓለቲካ ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ የተቀመጠውን ግልጽ መስፈርት በማሟላት የአመልካች አባልነቻቸውን የተውት መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ይህም ማለት ተጠሪ እጩ አድርጐ ያቀረባቸው ግለሰቦች በአባልነት ለተደራጁበት አመልካች አባልነታቸውን በፈቃዳቸው የተውት ስለመሆኑ በጽሑፍ ያሳወቁ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት አያይዞ በማቅረብ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡

28. በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በእጩነት ያቀረብኳቸው ሰዎች የአመልካች አባል ሆነው መቀጠል እንደማይፈልጉ በጽሑፍ በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አሳውቀዋል የሚል መከራከሪያ አላቀረበም፡፡ ተጠሪ የሚከራከረው በእጩነት ያቀበረብኳቸው የአመልካች አባል ሆነው መቀጠል እንደማይፈልጉ በጽሑፍ በአመልካች መተዳዳሪያ ደንብ መሰረት ባያሳውቁም ግለሰቦቹን የተጠሪ አባልና እጩ ከመሆን የሚከለክላቸው ህግ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አብላጫው ድምፅ ይህንን የተጠሪን ክርክር በመቀበል ማናቸውም ሰው አባል ሆኖ በተደራጀበት የፓለቲካ ድርጅት መተዳዳሪያ ደንብ መሰረት የድርጅት አባልነት መብቱን የተወው መሆኑን በጽሑፍ ሳያሳውቅ የሌላ የፓለቲካ ድርጅት አባል ሆኖ ከተመዘገበና የሌላ የፓለቲካ ድርጅት እጩ ሆኖ ከቀረበ በፊት ተደራጅቶ ሲሳተፍበት የነበረውን የፓለቲካ ድርጅት የአባልነት መብቱን እንደተወው ይቆጠራል፣ በዚህ መንገድ ለምንም ቅድመ ሁኔታ ቀድሞ አባል የሆነበት የፓለቲካ ድርጅት አባልነት በመተው ለሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባልና እጩ ተወዳዳሪ መሆን ይችላል በማለት የህግ ትርጉም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

29. ሆኖም ይህ ትርጉም ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 573/2000 መሰረት የአንድ ሰው ተደራጅቶበት በነበረው የፓለቲካ ፓርቲ አባልነት መብት ቀሪ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በዲስፒሊን ጥፋት በአባልነት ሲወገድ ወይም አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 12 መሰረት በተመዘገበው የድርጅቱ መተዳዳሪያ ደንብ መሰረት የአባልነት መብቱን የተወው መሆኑን ግልፅ አድርጎ በጽሑፍ ሲያሳውቅ ብቻ መሆኑን ያገናዘበ አይደለም፡፡ አንድ ሰው በአባልነት የሚሳተፍበት የፓለቲካ ፓርቲ መተዳዳሪያ ደንብ በሚደነግገው መሰረት የአባልነት መብቱን በፈቃዱ የተወው መሆኑን ግልፅ አድርጎ በጸሑፍ ሳያሳውቅ የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባል ሆኖ ተመዝግቦ መገኘቱ በመጀመሪያ ተደራጅቶበት የነበረውን ፓለቲካ ፓርቲ አባልነት ትቶታል ከሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በአንፃሩ ፓርቲው አባሉ ከህግና ከሥርዓት ውጭ ከአንደኛው የፓለቲካ ድርጅት ጋር የነበረውን የአባልነት ትስስር በሕግ አግባብ ሳያቋርጥ በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ የሌላ ድርጅት አባል መሆኑ በሌላ አነጋገር በአንድ ጊዜ የሁለት የፓለቲካ ድርጅቶች አባል በመሆን ተመዝግቦ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የሚያሳይና ህጋዊ ውጤት ሊሰጠው የማይገባ አድራጐት ሆኖ አግኝተዋል፡፡

30. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አብላጫው ድምፅ በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 4 የሰጠው ትርጉምም የህጉን ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም የአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ" የፓለቲካ ድርጅቶች መተዳዳሪያ ደንብ የዚህን ምዕራፍ ድንጋጌዎች የሚቃረን መሆን የለበትም" የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የፓለቲካ ፓርቲዎች አባላቶችቻቸው በራሳቸው ፈቃድና ፍላጐት አባልነት መብታቸውን የተውት ስለመሆኑ ለፓርቲው የሚያሳውቁትን ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንባቸውን እንዳያካትቱ የሚከለክል ድንጋጌ አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ተጠሪ በእጩነት ያቀረባቸው ሰዎች አባል ሆነው የተደራጁበት የፓለቲካ ፓርቲ(አመልካች) በመተዳደሪያ ደንብ የድርጅቱ አባል ሆኖ መቀጠል የማይፈልግ አባል አባልነቱን የተወው መሆኑን ለድርጅቱ በጽሑፍ የማሣወቅ ግዴታ እንዳለበት ያስቀመጠውን ድንጋጌ ህጋዊነት የሌለው ገደብ የማድረግ ይዘት የለውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደዚሁም ይህ የደንቡ ድንጋጌ አዋጅን የማስፈፀም ኃላፊነት በህግ ሥልጣን በተሰጠው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ተመርምሮ በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 ለድርጅቱ አባላት የተሰጠውን መብት የማያጣብብ መሆኑ ተረጋግጦ በአዋጁ አንቀጽ 12 መሰረት የተመዘገበና የጸደቀ ነው።

31. ከዚህ በተጨማሪ የፓለቲካ ድርጅት አባል የሆነ ሰው የድርጅቱ አባል ሆኖ መቀጠል እንደማይፈልግ በግልፅ በማሳወቅ አባልነቱን የመተው መብት ያለው በማናቸውም ጊዜ በምርጫ ወቅት የድርጅቱ እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ከተመዘገበ በኋላ ጭምር እንደሆነ የአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 54 ድንጋጌዎች በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ አንፃር በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ የተገለፀው አባልነትን የተወ የፓርቲ አባል አባልነቱን የተወው መሆኑን በጸሐፍ የማሳወቅ ግዴታ ህግ አውጭው በአዋጅ ቁጥር 352/1999 አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገገው መስፈርት ጋር ተመሳሳይነት ያለውና ይህንን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አብላጫው ድምፅ አመልካች በመተዳደሪያ ደንቡ ያስቀመጠው አባልነት መቀጠል የማይፈልግ የድርጅቱ አባል ይህንኑ በጽሑፍ የማሳወቅ ግዴታ ያለበት መሆኑን በመተዳደሪያ ደንቡ ያስቀመጠው መስፈርት በአዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 4 የሚጥስ ነው በማለት የሰጠው የህግ ትርጉም ከላይ የገለፅናቸውንና ሕግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 የደነገገውን መስፈርት ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል።

32. ከላይ በዝርዝር ከተገለፁት የህግ ትንተናዎች በተጨማሪ የህዝብ ሉዓላዊ ስልጣን በምርጫ ተወዳድሮ ለማሸነፍና ለመረከብ በህጋዊ መንገድ በተቋቋመ የፓለቲካ ፓርቲ አባል የሆነ ሰው፣ አባል ሆኖ ለኖረበት ፓርቲ ሳያሳውቅ የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባል ሆኖ የመመዝገብና በእጩነት የመቅረብ መብት አለው፣ የሌላ የፓለቲካ ድርጅት አባል የነበረን ሰው በአባልነት የሚመዘግብና በእጩነት የሚያቀርበው የፓለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን የተቀበለውና እጩ ያደረገው ሰው አባል ሆኖበት ከነበረው የፓለቲካ ድርጅት ጋር የነበረውን የፓለቲካ ትስስር ለመተው ያለውን ፍላጐት በግልፅ ያሳወቀ መሆኑን ሳያረጋግጥ አባል አድርጐ መመዝገብና በእጩ ተወዳዳሪነት ማቅረብ ይችላል በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አብላጫው ድምፅ የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ ሕግ አውጭው በሁለት አዋጆች የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፓለቲካ ድርጅቶች የሚሳተፉበትና ዓላማቸውን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ለመራጩ ሕዝብ የሚገልጹበት መራጩ ህዝብም በመረጃ ላይ በመመስረት ፈቃዱን በነፃነት በመግለፅ ወኪሎቹን የሚመርጥበት ሥርዓት ለመዘርጋት ያሰበውን ዓላማና ሌሎች ከላይ የገለፅናቸውን መሰረታዊ ግቦች የሚያሳካ አይደለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

33. በተቃራኒው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አብላጫው ድምፅ የተከተለው አተረጓጐም በምርጫ ወቅት የአንደኛው የፓለቲካ ድርጅት አባላት አባል ለሆኑበት የፓለቲካ ድርጅት አባልነታቸውን የተውት መሆኑን ሳያሳውቁ፣ የፓለቲካ ድርጅታቸውን የሚከዱበትና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ዘልለው በመሄድ የሌላ የፓለቲካ ድርጅት አባልና እጩ ሆነው የሚቀርቡበትን አሰራር የሚያበረታታ ነው። ይህ አሰራር ህጋዊ እውቅና ከተሰጠው በፓለቲካ ድርጅቶችና በአባላቶቻቸው መካከል መተማመን እንዳይኖር የሚደረግ፣ የፓለቲካ ድርጅቶች የአባልነት መብታቸውን በፈቃዳቸው የተውትንና በአባልነት ለመቀጠል ቁርጠኛ የሆኑትን ለመለየት የሚያስችለው ማስረጃ ኖሮት የምርጫ ዝግጅት እንዳያደርግ እንቅፋት የሚፈጥር፣ በፓለቲካ ድርጅቶች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት አንደኛው የፓለቲካ ፓርቲ አባላትና እጩ የፓለቲካ ድርጅቱ ሳይሰማና ሳያውቅ ሌላው የፓለቲካ ድርጅት በማስከዳት ወይም በመቀበል በሰዓታትና በቀናት ልዩነት የራሱ አባልና እጩ አድርጐ እንዲያቀርብ ሰፊ እድል የሚፈጥርና በፓለቲካ ድርጅቶች መካከል የሚኖረው ግንኙነት በጥራጣሬና በሽኩቻ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ የሚያደርግ ነው። ይህም ሕግ አውጭው በህገ መንግስቱ መሰረት ዜጐች የመደራጀት መብታቸውን ተጠቅመው በሰላማዊና ህጋዊ የፓለቲካ እንቅስቃሴ በመሳተፍ የመንግስት ስልጣን የሚይዙበትን ሁኔታ ለማረጋገጥና በፓለቲካ ድርጅቶች መካከል እንዲኖር የሚፈልገውን ሰላማዊና ፍትሐዊ ህጋዊ የፓለቲካ ውድድር በእጅጉ የሚጎዳና በአዋጅ ቁጥር 632/2002 አንቀጽ 7 የተደነገገው የምርጫ ሕግ ማክበር ግዴታ የሚሰጥና በአዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 4(ለ) ማንኛውም የፓለቲካ ድርጅት በምርጫ ከሚወዳደሩ ሌሎች የፓለቲካ ድርጅቶች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲፈጥር የተጠቀመውን የሥነ ምግባር ግዴታ ውጤት አልባ የሚያደርግ ነው።

34. በምርጫ ወቅትና ከተመረጡ በኋላ የፓለቲካ ድርጅቶች አባላት የሚፈጽሙትን የክዳት ተግባር ለመቆጣጠርና ለማስቀረት የዳበረ ዲሞክራሲ ሥርዓት ያላቸው እንደ እስራኤል ያሉ ሌሎች አገሮች በሕገ መንግስታቸውና በሌሎች የሕግ ማዕቀፎች ከልካይ የሆኑና ይህንን ተግባር በሚፈፅሙ ላይ ተጠያቂነት የሚያስከትሉ የህግ ድንጋጌዎችን በመደንገግ ተግባራዊ አድርገዋል። እኛም አገር የምርጫና የፓለቲካ ድርጅቶች ምዝገባ አዋጆች የአንድ የፓለቲካ ድርጅት አባል የነበሩ ሰዎች አባል ሆነው ለተደራጁበት የፓለቲካ ድርጅት አባልነታቸውን መቀጠል የማይፈልጉ ስለመሆኑ ሳያሳውቁና አባል ከሆኑበት የፓለቲካ ድርጅቶች ጋር የነበራቸውን ትስስር በህግ አግባብ ለማቋረጥ ያላቸውን ሀሳብ ሳይገልፁና በምርጫ ወቅት ዘለው የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባልና እጩ ሆነው የሚቀርቡበትን ሁኔታ በሚፈቅድና በሚያበረታታ መንገድ ታልመው የታወጁ አለመሆናቸውን ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸው የህግ ማዕቀፎቹን ድንጋጌዎች ይዘቶችና መሰረታዊ ዓላማዎች በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

35. ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች ተጠሪ የሌላ ፓለቲካ ድርጅት(አመልካች) አባልነታቸውን በህግ አግባብ እንዲቋረጥ በጽሑፍ ያላሳወቁ የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባል የሆኑ ሰዎች ተወዳዳሪ አድርጐ እንዲያቀርብ አዋጅ ቁጥር 532/199 አንቀጽ 46 እና አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 4(ለ) የማይፈቅድለትና አድራጐቱም በአዋጅ ቁጥር 662/2002 አንቀጽ 7 ተደነገገውን ሕግ ማክበር ግዴታ የሚሰጥ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ ያቀረባቸው እጩ ተወዳዳሪዎች እንዲመዘገቡ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ ሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

36. ተጠሪ እጩ አድርጐ ያቀረባቸው ግለሰቦች በህግና አባል በሆኑበት የፓለቲካ ድርጅት መተዳዳሪያ ደንብ የተጣለባቸውን አባልነታቸውን የተውት መሆኑን በጽሑፍ የማሳወቅ ዝቅተኛ መስፈርት ያላሟሉ በመሆኑ ወይም በአባልነት ተደራጅተውበት የነበረው የፓለቲካ ድርጅት በዲስፒሊን ጥፋት ከባልነታቸው እንዲሰረዙ የሰጠው ውሣኔ የሌለ በመሆኑ አሁንም ቢሆን የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አባላት ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር አንድ ሰው በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ የሁለት የፓለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን የማይችል በመሆኑ ተጠሪ ግለሰቦቹ በድርጅቱ መተዳዳሪያ ደንብ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልተው ስላገኘኋቸው በአባልነት ተቀብያቸዋለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሰረት ያለው አይደለም፣ ከላይ በዝርዝር በተቀመጡት ምክንያቶች የአማራ ክልል ሰበር ችሎት ተጠሪ በእጩነት ያቀረባቸው የሌላ ፓለቲካ ድርጅት (አመልካች)አባላት የተጠሪ እጩ ሆነው እንዲመዘገቡ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 46744 መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ታይቶ ተሽሯል፡፡
2. በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ተጠሪ በደጋ ዳሞት ምርጫ ክልል እጩ አድርጎ ያቀበባቸው አቶ ግርማ ቢተው፣ አቶ መለሰ ዘለቀ፣ ወ/ሮ ይርገዱ ታደገ እና አቶ ይሁኔ ጥላሁን የአመልካች ድርጅት አባላት በመሆናቸው የተጠሪ እጩ ተወዳዳሪዎች ሆነው ሊመዘገቡ አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 9 ቀን 2007 የተሰጠው የእግድ ትዕዘዝ ተነስቷል፡፡ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ **ሩ/ለ**

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



ቅፅ19

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌደራል ጠቅላይ

ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ-19

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ነሃሴ 19, 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ



<u>የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

በተሻሻለው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሠበር ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙ የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል ተብሎ መደንገጉ ፍርድ ቤቶች የሠበር ችሎቱ የሰጠውን የህግ ትርጉም ተከትለው በመስራት ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተመሳሳይ ውሳኔዎች እንዲሰጡ ለማስቻል ነው።

በሀገሪቱ ያሉ ፍርድ ቤቶች ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተመሳሳይ ውሳኔዎችን መስጠት መቻላቸው የዳኝነት አገልግሎቱ ተገማች እንዲሆን ከማስቻሉም በላይ ባለጉዳዮችን ካልተገባ ወጭና ከእንግልት ሊያድናቸው እንደሚችልም ይታመናል። ይህን እውን ለማድረግ በተቻለ መጠን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች በአግባቡ ታትመው በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶችና ለተለያዩ አካላት እንዲሁም ለህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሰራጩ ይደረጋል።

በሌላ በኩል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች በጥራዝ መልኩ መዘጋጀታቸው ጥናትና ምርምር ለሚካሄዱ የህግ ተመራማሪዎች፣ ለህግ ባለሙያዎች ለጠበቆች፣ ለምሁራንና በጠቅላላው ለህብረተሰቡ ውሳኔዎችን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑም ስለ ታመነበት ጭምር ነው።

ዳኜ መላኩ

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ /ቅፅ 19/

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
አሠሪና ሠራተኛ					
1					
1.	አንድ ሠራተኛ ከአንድ ዓመት በታች አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ ተመጣጣኝ የሆነ የረፍት ጊዜ በአገልግሎት ጊዜው ልክ (proportion to the length of his service) የሚሰጠው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 77(6)	112583	የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ጅማ ቅርንጫፍ እና አቶ ብሩክ አበራ	ጥቅምት 5 ቀን 2008ዓ.ም	2
2.	በውጭ ሃገር ስለሚኖር የስራ ውል የግል አገልግሎት(በውጭ ሃገር ለተሰጠው አገልግሎት) ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ህግ ስለስራና ሰራተኛ ማገናኘት አገልግሎት የወጣ አዋጅ 632/2001 ስለመሆኑ በዚህ አይነት የውል ግንኙነት ውስጥ የሚቀርብ የክፍያ ጥያቄ በአስር አመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 1677(1) እና 1845	101675	ወ/ሮ መስከረም ሞጋ እና ወ/ሮ ትግስት አረጋ	ጥቅምት 24 ቀን 2008ዓ.ም	6
3.	አንድ ሠራተኛ በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን በላይ መታሰሩ እና ከስራ ገበታው መቅረቱ ከ30 ቀናት የሚበልጥ እስራት እንደተወሰነበት ተቆጥሮ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ ተገቢ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/ለ/	114669	የኢትዮጲያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ አስማረ ፈጠነ	ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም	12
4.	አሠሪው ሠራተኛው በሚፈጽመው የሥራ ጥፋት ማስጠንቀቂያ በሰጠው ጊዜ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ የሚችለው በ30 ቀናት ውስጥ	118263	ወ/ሮ ሙሪዳ ኑረዲን እና	ጥር 18 ቀን 2008 ዓ.ም	16

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሲሆን ይህ ቀን ካለፈ በኋላ የሚያደርገው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ማቋረጥ የሥራ ውል የሚቋረጥባቸውን ሕጋዊ ሥርዓቶች ያላገናዘበ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(3) አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሀ/3/፣43/2/		አቡል ኬስ ሀ/የተ/የግ/ማህበር		
5.	አንድ ሠራተኛ ከስራ ከተሰናበተ በኋላ የአገልግሎት ክፍያ ከሚያገኝባቸው ሕጋዊ ምክንያቶች አንዱ በድርጅቱ ከ5 ዓመት በላይ አገልግሎ በገዛ ፈቃዱ ስራ መልቀቁ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2/ሸ/	112956	መስጠፋ ኑር ትዕም እና የኦሮሚያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ	ጥቅምት 22 ቀን 2008 ዓ.ም	21
6.	ውዝፍ ያልተከፈለ ደሞዝ ከስራ ስለተሰናበተ ሠራተኛ የሚከፈል ሳይሆን ወደ ስራ እንዲመለስ ለተወሰነበት ሰራተኛ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43(5)	116002	የአንቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን እና አቶ ጨመዳ መገርሳ	ህዳር 6 ቀን 2008ዓ.ም	25
7.	አንድ ሠራተኛ የሥራ መሪ ሆኖ የሚቆጠረው እንደ ድርጊቱ የሥራ ፀባይ ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንጻር መታየት ያለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 3/2/ሐ/	117076	የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት የቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ እና አቶ ዮሐንስ ብዙነህ	ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም	29
8.	አሰሪው በሰራተኛው ህይወት ላይ አደጋ ሊያደርስ በሚችል አኳኋን እንዲሰራ ማድረግ ህገ ወጥ ተግባር ሲሆን ይህም ሰራተኛው የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለመቋረጥ በቂ ምክንያት ነው ይህ ከተረጋገጠ ደግሞ ሠራተኛው በአዋጅ መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን የማግኘት መብት ያለው	117517	ሬድ ፎክስ ኢትዮ.ኃ/የተ/የግ/ማህ እና ወ/ት ጃለኔ ጌታቸው	ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም	34

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 14 (1) (ሠ)፣32(1)(ለ)				
9.	የአንድ ድርጅት ከሌላ ጋር መቀላቀል ወይም መከፋፈል ወይም የባለቤትነት መብት ወደ ሌላ መተላለፍ የስራ ውልን የማቋረጥ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/1996 አንቀፅ 23(2)	119734	ይርጋ ትራዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህ እና እነ አቶ በዛብህ መኮንን (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ.ም	38
የፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት **41**					
10.	በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነውን ወገን የሚጎዳ ውሳኔ የተላለፈው ጉዳዩን በተዋረድ ባየው የሰበር ችሎት በሚሆንበት ጊዜ ይህ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነው ወገን አለኝ የሚለውን መብት ለማስከበር ይችል ዘንድ መብቱን ተጋፍቷል በሚለው ሰው ላይ በስሙ ቀጥታ ክስ በመመስረት መብቱን ከማስከበር ውጪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት ተቃውሞውን ለሰበር ችሎቱ ሊያቀርብ የሚችል ስላለመሆኑ	102056	አቶ ሳምሶን ካሳዬ እና ወ/ሮ መሰረት ግርማ (አራት ሰዎች)	ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም	42
11.	አንድ ተከሳሽ በከሳሽ በመጀመሪያ ክስ ሲቀርብበት መጥሪያ ደርሶት በተከራከረበት እና ከሳሽ ክስ ያሻሻለ ተብሎ በተዘጋ መዝገብ ላይ ክሱ ተሻሽሎ መዝገቡ ከተከፈተ በኋላ ለተከሳሽ በተገቢው መንገድ መጥሪያ ሳይደርስ የሚሰጥ ውሳኔ ስነ- ስርዓታዊ ስላለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. አንቀጽ 94-110	107838	እነ አቶ ታከለ አርአያ እና አቶ ደጀን ገ/እግዚአብሔር	ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም	46
12.	በክስ ማሻሻል ሥርዓትና ዓላማ ቀድሞ ዳኝነት ከተጠየቀበት ጉዳይ ፈጽሞ የተለየ ጥያቄ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ፣ ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 91	100475	አቶ ሳምሶን አበራ እና ወ/ሮ ፀሐይ አበራ	ታህሳስ 20 ቀን 2008 ዓ.ም	50

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 342				
13.	ፍ/ቤቱ የግዛት ስልጣን የለውም በማለት ለሚቀርብለት መቃወሚያ የሚሰጠው ውሳኔ ፍትህን የሚያጓድል ካልሆነ በቀር ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ቁ. 10(2)	109383	ሳሊሆም ከፍተኛ ክሊኒክ እና ዶ/ር ዘመኑ ዮኃንስ	የካቲት 2 ቀን 2008 ዓ.ም	54
14.	ተከሳሽ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለፀ እንደሆነ በእምነቱ መሰረት ይገባኛል የሚለው ማናቸውም ዳኝነት እንዲሰጠው አመልካች(ከሳሽ) ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ	109206	አቶ ፍስሃ እርቅ እና አቶ ኪሮስ ስዩም	የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ.ም	59
15.	ፍ/ቤት በተዋዋዮች መሃል የተደረገን ውል (የእርቅ ስምምነት) ህጋዊነታቸውን ሳይረጋገጥ ሊያፀድቅበት የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ.1731 የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.277	109497	አቶ አግማስ ኡመር (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ኡመር አሳዮ	የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ.ም	63
16.	ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ለሚደርሰው ኪሳራ ዋስ እንዲያሲዝ የሚጠየቀው ከሳሽ በክሱ ምክንያት በተከሳሽ ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመክፈል የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሚያጠራጥር ሲሆንና ኪሳራውንም ለመክፈል የሚያስችል ሃብት ወይም ገንዘብ የሌለው በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 200	110150	አቶ ገ/መድህን ወ/ሚካኤል እና እነ አቶ ግርማይ ፍትዊ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም	66
17.	ከሳሽና ተከሳሽ ያልተካካዱበትና ከሳሽ በክሱ ገልፆ ተከሳሽ ባመነው ነጥብ ላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ማስረጃ በመመዘን ሳይሆን ተከሳሹ በሰጠው የእምነት ቃል ወይም መልስ መሰረት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242	112927	የማር ዘነብ እቁብ ዳኛ እና እነ አቶ ዋለልኝ ተመስገን	የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም	70
18.	የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለሚሉ ስለሚገባቸው ጥብቅ	104028	ወ/ሮ ብዙአየሁ ያለው	የካቲት 17 ቀን	74

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መስፈርቶች;- አንድ ክስ በይርጋ መዘጋቱ ዳግም ዳኝነት ጥያቄውን ለማስተናገድ እንደበቂ ምክንያት/እንደመመዘኛ/ የማይወሰድ ስለመሆኑ፡- የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6		እና አቶ ሲሳይ ካሴ	2008ዓ.ም	
19.	በጊዜያዊ ትእዛዝ ላይ በሚሰጥ ብይን ቅር የተሰኘ አካል የስረ ነገሩ ክርክር የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ እስካልተገኘ ድረስ ይግባኝ (የሰበር) አቤቱታ ሊቀርብ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320(3)	116209	የኢት/መንገዶች ባለስልጣን እና ወ/ሮ ምዕላል አብርሃ	የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ.ም	79
ቤተሰብ **82**					
20.	በገጠር መሬት ላይ የሚኖረው መብት የመጠቀም መብት ሲሆን ይህንን መብት ለ3ኛ ወገን /ለሌላ/ ሰው ለረጅም ጊዜ ሰጥቶ ተጠቃሚነቱ የተቋረጠበት ባለመብት መልሶ መጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ፣ የኦሮሚያ ክልለ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1997 አንቀፅ 9(5)	113973	ወ/ሮ ጠጅቱ ኩርጋ እና አቶ ገመዳ ሆባ	ታህሳስ 21 ቀን 2008 ዓ.ም	83
21.	አንድ ጋብቻ ሲፈርስ ንብረት ክፍፍልን በሚመለከት በእርቅ ውል ስምምነት በሽማግሌ የተደረገው እርቅ በፍ/ቤት ተመዝግቦ ከተዘጋ በኋላ እንደገና እንደ ባልና ሚስት አብረን እየኖርን ስለነበር በድጋሚ የንብረት ክፍፍል ይደረግ የሚል ጥያቄ አግባብነት ያለው ስላለመሆኑ፣	105054	ወ/ሮ ጌጤ እጅጉ እና አቶ ብርሃኑ ተሠማ	ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም	87
22.	ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ሊባልባቸው ስለሚችሉባቸው ሁኔታዎች ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ ከሚታሰብበት ጊዜ አንስቶ በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ካልቀረበ በይርጋ	102662	ወ/ሮ አልማዝ ለሼ እና አቶ በቀለ በላቸው	የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም	90

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የሚታገድ ስለመሆኑ				
23.	አንድ ሰው በወላጅ አባቱ ስም መጠራቱ ቀርቶ በአሳዳጊዬ ስም እንድጠራ ብሎ የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ በሕጉ ስለስም ለውጥ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች የማያሟላ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ጉዳይ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ.32(1)፣36(1)	116977	ወ/ት ሃና ታምራት እና የለም	የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም	94
24.	በተሻሻለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የቤተሰብ ህግ መሰረት ባልና ሚስት የጋራ ንብረታቸውን እኩል የማስተዳደር መብት ያላቸውና የጋራ ስምምነት ሳይኖር ንብረትን ለሌላ 3ኛ ወገን በአንደኛው ተጋቢ ፍቃድ ብቻ የተላለፈ ከሆነና ይህንን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ በህጉ በተፈቀደለት ጊዜ ገደብ ውስጥ የይፍረስልኝ ጥያቄውን ካላቀረበ የተፈፀመው ተግባር እንደፀና የሚቆይ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 68፣69	103721	ወ/ሮ ሰሚራ ጀማል እና እነ አቶ ጀማል እንድሪስ (ሦስት ሰዎች)	የካቲት 29 ቀን 2008 ዓ.ም	97
ውርስ					
25.	ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ፈጽሞ ሲገኝ ሊወሰዱ ስለሚገቡ ዝርዝር ሁኔታዎች የሕግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች፤ ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሠራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.213/1992 አንቀጽ 306፣277 የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2207/1	103151	አቶ ግርማ ብሩ እና አቶ መርዕድ ብስራት	መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ.ም	108
26.	የወራሾች ድርሻ በክፍያ ጊዜ ሊገመትበት ስለሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1083	103049	ወ/ሮ ሊዕማ ሓዲሽ እና አቶ አንዋር ሓዲሽ	መስከረም 28 ቀን2008 ዓ/ም	114

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
27.	እብደቱ በግልጽ ያልታወቀ ሰው ወራሾች ወይም ባለገንዘቦች ይህ ሰው የፈጸመው ውል ጉድለት የሌለበት ፈቃድ አልሰጠበትምና ውሉ ሊፈርስ ይገባል ሲሉ እብደቱን ምክንያት በማድረግ የውሉን መፍረስ መጠየቅ የማይችሉ ስለመሆኑ፡- የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውልን ዋጋ ተጎዳሁ በሚል ምክንያት ሊፈርስ የማይችል ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕ/ቁ. 348፣347/1//2/፣349፣350፣341፣342 የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2887	100931	አቶ ጥላሁን አለሙ እና አቶ ደረጀ ማሞ	ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም	117
28.	የሚች ወራሾች ተመላሽ የሚያደርጉት ንብረት ስለሚመለስበት ሥርዓት የፍ/ሕ/ቁ. 1074 እና 1076	106856	ወ/ሮ እየሩሳሌም ገመቹ እና ወ/ሮ ሮማን ገመቹ	ጥር 16 ቀን 2008ዓ.ም	125
29.	የሚች ንብረት (የውርስ ሃብት) ወደ ወራሾች የሚተላለፈው በመጀመሪያ የሚች እዳ ከተከፈለ ብቻ ስለመሆኑ፤- ሚች ከሞተ በኋላ ለቀብር ማስፈፀሚያ የሚወጡ ወጪዎች ከውርሱ ክፍፍል በፊት መከፈል ያለባቸው ስለመሆኑ፡- የፍ/ሕ/ቁ.1014	111216	ወ/ሮ ኤልሳቤት አህመድ እና ወ/ሮ ማፈኛ አባዬ	የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም	130
30.	ተተኪ ወራሽ ለመሆን ሊሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች የፍ/ሕ/ቁ. 842(3)	110040	እነ ወ/ሮ እሌተማርያም አክሎግ (ሦስት ሰዎች) እና የለም	የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ.ም	133
ውል 136					

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
31.	የመጓጓዣ ውልን መሰረት ያደረገ የካሳ ጥያቄ ሲቀርብ ጉዳዩ በየትኛው የህግ ማዕቀፍ እንደሚገዛ መለየት የይርጋውንም ሆነ የካሳ ስሌቱን በአግባቡ ለመዳኘት የሚያስችል ስለመሆኑ የን/ሕ/ቁጥር 587፣595 ፣597፣599 እና 603 የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143፣ 2090	95922	እነ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ(ሁለት ሰዎች) እና እነ ሃምሳ አለቃ ለገሰ ክፍለይ(ሁለት ሰዎች)	መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ/ም	137
32.	ተወካይ የውክልና ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ከሶስተኛ ወገን ጋር የሚያደርገው ውል ከወካይ ጋር የጥቅም ግጭት ተፈጠሯል ብሎ ወካይ ካወቀ ይህንን ለመቃወም /ለመስፈረስ/የሚችለው ወካይ ይህንን ሁኔታ መፈጠሩን ካወቀበት እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ድረስ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 2187(1)(2)	98961	አቶ ኡመር መሃመድ እና ሻ/ባሻ ከድር ሼህ አብድላሂ	መስከረም 24 ቀን 2008ዓ.ም	144
33.	አንድ የዋስትና ውል ዋሱ ግዴታ የገባበትን ኃላፊነት መጠን ወይም ልኩ ምንያህል እንደሆነ በዋስትና ውሉ ላይ በገንዘብ ካልተገለፀ በስተቀር ዋስትናው ፈራሽ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ-1922(3)	104061	አቶ ፍቅሬ ግርማ እና አቶ ደስታ ጫምሶ	መስከረም 25 ቀን 2008 ዓ.ም	148
34.	የአንድን የውል ሰነድ እርግጠኛ ቀን የሚባለው ሰነዱን የፃፈው ወይም የተቀበለው እንደ ሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ፅ/ቤትን የመሰለ የመንግስት መስሪያ ቤት ሲሆን የፃፈበት ወይም የተቀበለበት ቀን ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ.2015(ሀ)	98583	እነ ወ/ሮ ኤደን ሲሳይ(ሁለት ሰዎች) እና አቶ ሰይፉ አለሙ	መስከረም 27ቀን 2008ዓ.ም	151

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
35.	የተዋዋዮች የውል ግንኙነት መሰረት ያደረገው ፕርፎርማን ሳይሆን ፕሮፎርማን ተከትሎ በፅሑፍ የተደረገን ውል በሆነ ጊዜ በፕሮፎርማው ላይ ተጠቅሶ ነገር ግን ተዋዋዮቹ የውላቸው አካል አድርገው ያልተስማሙበት ጉዳይ በፕሮፎርማ ላይ የተጠቀሰ በመሆኑ ብቻ እንደውሉ አካል ተቆጥሮ በተዋዋዮቹ (ከተዋዋዮቹ) በአንዱ ላይ አስገዳጅነት እንዳለው አድርጎ መውሰድ ተገቢ ስላለመሆኑ የፍ/ሕ/ሥ/ሥ ቁጥር 2287-2300 ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በተሸጠው እቃ ላይ የተገኘው ጉድለት መኖሩ በገዥው የታወቀው ከርክክቡ በኋላ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ	99667	ቻክ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ናሽናል ሞተርስ ኮርፖሬሽን	መስከረም 27 ቀን 2008ዓ.ም	155
36.	አንድ የሽያጭ ውል የእጅ በእጅ ሽያጭ ውል ነው ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ አንቀጽ 2278(1)	97797	ናሽናል ስሚንቶ አ/ማህበር እና አቶ ብርሃኑ ግደይ	መስከረም 28 ቀን 2008 ዓ/ም	162
37.	አንድ ውልን ለመተረጎም አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም የውሉ ድንጋጌ መተርጎም ያለበት በውሉ አስገዳጅ የሆነው ወገን በሚጠቀምበት ሁኔታ ሳይሆን በውሉ ተገዳጅ ለሆነው ሰው ምቹ በሚሆንበት አኳኋን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1738(1)	103910	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና አቶ ሀብታሙ ተመስገን	መስከረም 28ቀን 2008 ዓ/ም	165

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
38.	የኮንዶሚኒየም ቤት የደረሰው ሰው ሌላ የኮንዶሚኒየም ቤት ከደረሰው ሰው ጋር እጣው ከደረሰው አምስት ዓመት ባይሞላውም በልውውጥ(በስምምነት ሊቀያየሩ የሚችሉ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 14(2)	105919	ወ/ሮ መኪያ አብደላ እና አቶ ጣሰው ሸምሱ	ጥቅምት 4 ቀን 2008 ዓ.ም	169
39.	ለመልካም ሥራ አፈጻጸም ለዋስትና የተያዘ ገንዘብ ውሉ እንደውሉ ሳይፈጸም ሲቀር ዋስትና አስያዡ የተያዘውን ገንዘብ በውል ለተጎዳው ወገን መክፈል የሚገባው ስለመሆኑ ለመልካም ስራ አፈፃፀም የሚሰጥ ዋስትና ዓይነተኛ ዓላማው በተሰራው ነገር ጉዳት የደረሰበት ተዋዋይ ወገን በገንዘቡ ረገድ ለመካስ ስለመሆኑ ፍ/ሕ/ቁ. 1815	98348	እነ አቶ ዘርይሁን የኔነህ /አመስት ሰዎች/ እና ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ	ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም	173
40.	በአከራይና ተከራይ መካከል በሚደረግ የኪራይ ስምምነት መሠረት አከራዩ ለተከራዩ ባከራየው ቤት ላይ ስለተደረገው ጥገና /ማሻሻያ/ አከራይ የሰጠው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አከራዩ ለተከራዩ አወጣሁ ያለውን ወጪ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6/3/ የፍ/ብ/ሕ/ቁ አንቀጽ 2917፣2973/1/፣2912	101053	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እነ አቶ የምሩ ነጋ	ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም	180
41.	የዋስትና ውል በግልፅ መደረግና ዋሱ ለግዴታው ዋስ የሆነበት የገንዘብ ልክ በዋስትናው ውል መገለጽ ያለበት ስለመሆኑ ለዋስትናው መሠረት የሆነው ዋናው ጉዳይም ሕጋዊና ግራ ቀኙን የተስማሙበትና የሚታወቅ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፡- ፍ/ሕ/ቁ 1928፣1922 አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/	111778	ወ/ት ገንዘብ ስጦታ እና የሊያ ቆቦ ወረዳ ፍ/ቤት ዐ/ህግ	ጥር 16 ቀን 2008 ዓ.ም	186

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
42.	በጽሑፍ የተደረገ ውል ውስጥ እማኞች በመሆን የፈረሙ ምስክሮች ስለ ውሉ መኖር አለመኖር እንዳያስረዱ ክልከላ ማድረግ ተገቢ ስላለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ.2005	106535	አቶ ረዲ ተፈራ እና እነ አቶ ረዲ ተፈራ/ሁለት ሰዎች/	ጥር 17ቀን 2008 ዓ/ም	191
43.	አንድን ንብረት የሸጠ ሰው የሸጠውን ንብረት ባለሃብትነት ለገዥው የማዛወር ግዴታ ያለበትና ይህንን ለመፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ተግባራቶችን የማከናወን ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ.2273፣2281፣1771(1)፣1757	112328	መገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይዝ እና አቶ ኤፍሬም እሸቱ	የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም	195
44.	ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው በባለእዳው በምንም መልኩ በቅድሚያ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የሚያስችል ክስተት ሲፈጠር ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 1792 በየብስ የእቃ ማጓዝ ስራን ለመደንገግ ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ ቁ. 547/1999	112168	የሺ ትራንስፖርት የጭነት ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር እና አቶ አስክንድር ዘርፉ	የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ.ም	200
45.	በማጓጓዝ ውል ግንኙነት በደረሰ የሕይወት ሕልፈት የሚከፈል ካሣ በንግድ ህጉ መሰረት ስለመሆኑ	99447	አቶ ተፈራ ጣሰው እና ወ/ሮ ፋንታዬ በንቲ	ጥቅምት 26 ቀን 2008 ዓ.ም	206

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
46.	ተዋዋዮች የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ሲተላለፍ በህጉ በተደነገገው መሰረት ውል ለመዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርቦ የማስመዝገብ ግዴታን ስምምነታቸው ላይ ካካተቱና ነገር ግን ይህንን ተፈፃሚ ማድረግ ካልተቻለ የተዘጋጀው ስምምነት ረቂቅ እንጂ ከጅምሩ ውል ነው ተብሎ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሊነሱ የሚገባቸውን ጉዳዮች ማንሳት ሰህተት ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ.1723፣1810፣1885(1)	99124	ወ/ሮ ሰብለ ማሞ (ሁለት ሰዎች) እና የ ፤ አለቃ ተስፋዮ በዛብህ ወራሾች (ሁለት ሰዎች)	የካቲት 28 ቀን 2008ዓ.ም	211
ከውል ውጭ ኃላፊነት 215					
47.	አንድ ሰው በህግ ወይም የሚፀና ውል የሚሰጠው አንዳች መብት እንደሌለ እያወቀ የሌላ ሰው የሆነን ንብረት በእጁ ባደረገ ጊዜ ንብረቱ ሊያፈራ የሚችለውን የገንዘብ ግምት እንዲመልስ ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2178	100651	ወ/ሮ መንበረ ሰፈርህ እና ወ/ሮ ብርሃኔ ጌቱ (ሦስት ሰዎች)	መስከረም ቀን 2008 ዓ/ም	216
48.	በወሊድ ወቅት በህክምና ተቋሙና በሙያው ባለቤት ዘርፉ የሚጠይቀውን ጥንቃቄ ሳይደረግ በሚወለደው ህፃን ላይ የአካል ጉዳት ከደረሰ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1790፣2028፣2031፣2647 /2/ እና 2651	96548	ሐያት ሆስፒታል እና ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን	መስከረም 24 ቀን2008 ዓ.ም.	220
49.	በውል የተገባ አንድ ግዴታ መፈጸም ያለመፈጸሙን ለማጣራት የግራ ቀኙ ተዋዋይ ወገኖች የገቡት ግዴታ እና ያላቸው መብት የሚገልጽ የሰነድና የሰው ማስረጃ እንዲሁም የግዴታ ልዩ ባህርይ መሰረት በማድረግ ልምድን መዳሰስ የሚጠይቅ ስለመሆኑ ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ 246፣247፣248 እና 249	96041	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና ወ/ሮ አልማዝ ግዛው	ጥቅምት 26 ቀን 2008 ዓ.ም	231

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
50.	የካሳን መጠን በርትዕ ለመወሰን የሚያስገድድ ሁኔታ በገጠመ ጊዜ መጠኑን ለመወሰን የጉዳት ካሳው መጠን ከጉዳቱ ተመጣጣኝ ይሆን ዘንድ ሚዛን ላይ ሊቀመጡ የሚገባቸው መለኪያዎች ሊኖሩ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ሕ/ቁ.2102 እና 2153	108251	የኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን እነ አቶ አመኸክ ከሊፋ	ጥር 5 ቀን 2008 ዓ.ም	235
ወንጀል					
51.	በወ/መ/ህ//አ/ቁ. 676(1) የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው የዋስትና መሰጠት (መፈቀድ) ጥያቄ የሚሰጠው በጉዳዩ ላይ በአግባቡ ተመርምሮ እንጂ ከወዲሁ ስላለመሆኑ አዲሱ የፀረ ሙስና ህግ አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀፅ 31	117383	አቶ አዲስ ዋለልኝ በላይ እና የፌ/ሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዓ/ህግ	መስከረም 6 ቀን 2008ዓ.ም	240
52.	በወንጀለኛ ህግ ቁጥር 627(2) መሰረት በክብረ ንህዕና ላይ የሚደረግ ድፍረት የተበዳይ ክብረ ንዕህና በጥቃቱ መገርሰስ ወይም አለመገርሰስ እንደ መስፈርት ሊቆጠር የሚገባው ስላለመሆኑ	107166	መኳንንት ግርማ እና የኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ	ጥቅምት 4 ቀን 2008 ዓ.ም	244
53.	አቃቤ ህግ በዋስትና መለቀቅ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ ፍርድ ቤት የዋስትና መብትን የሚከለከልበቻው ምክንያቶች ከተለየዩ ሁኔታዎች በመመልከት ሊመዘናቸው የሚገባቸው ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር67፣75	112725	አቶ ሀሰን አብዳል እና የፌዴራል ማዕከል ዐቃቤ ህግ	ጥቅምት 22 ቀን 2008 ዓ/ም	246

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
54.	የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ የአስረጅነት ብቃት ያለው ተአማኒነት ያለው ማስረጃ ተደርጎ እንዲወሰድ ሚዛን ላይ ሊቀመጡ ስለሚገባቸው ነገሮች	109441	ፈይሳ ማም ማሩ እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ	ጥር 17 ቀን 2008 ዓ/ም	250
55.	በወንጀል ጉዳይ ከአንድ በላይ ሰዎች የተከሰሱ እንደሆነ የእያንዳንዱ ተከሳሽ ሚና እና ተሳትፎ ደረጃው በቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ በክሳሽ ወገን በኩል በሚቀርበው ማስረጃ ነጥሮ ሊወጣ የሚገባ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 32፣40 የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 ተያያዥነት የሌላቸው ፍሬ ነገሮችን መሰረት ተደርጎና የአንድን ነገር መኖር ያለመኖር ሣይረጋገጥ ለአካባቢ ማስረጃ ክብደት መስጠት የማስረጃው አይነት የምዘና መርህን መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ስላለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.173(1)	113464	እነ እናት ሁናቸው(አራት ሰዎች) እና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዓቃቤ ህግ	ህዳር 22 ቀን 2008 ዓ.ም	258
56.	በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 188/5/ መሰረት አንድ ፍርድ በተከሳሽ ላይ ከተሰጠ ተከሳሹ ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብሎ ሲቀርብ የበታች ፍርድ ቤትን ውሳኔ የበላይ ፍርድ ቤቱ ማገድ የሚችልበትን አግባብ የሚያሳይ ድንጋጌ ከመሆኑ ውጪ ከሳሽ ወገን በተከሳሽ ነፃ መለቀቅ ላይ ይግባኝ ብሎ ሲሄድ ፍርዱ እንዳይፈፀም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመስጠት መነሻ የሚያደርገው ስላለመሆኑ	118252	ሀብታሙ አያሌው እና የፌዴራል ዐቃቤ ህግ	ጥር 24 ቀን 2008 ዓ/ም	268

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
57.	በወንጀል ክርክር ሂደት ፍ/ቤት በማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ሂደቶች ውስጥ ሊኖረው(ሊያደርገው) ስለሚችለው ሚና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 136(4)፣137፣138፣143(1)፣145፣194	111498	የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ዓቃቤ ህግ እና አቶ ሃብታሙ ካርሎ	የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም	275
58.	በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ጠበቃ ብቻውን ሊቀርብ አይችልም የሚለው ጉዳይ ተፈፃሚ የሚሆነው ለተፈጥሮ ሰዎች እንጂ የህግ ሰውነት ላላቸው ሰዎች ስላለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.127	120762	የፌድራል ዓቃቤ ህግ እና እነ አቶ ዱባይ አውቶ ጋለሪ(ሁለት ሰዎች)	የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም	279
59.	ህጉ በሚጠይቀው አግባብ ፈቃድ ሳያወጣ ወይም የጸና ፈቃድ ሳይኖረው ከቴሌኮሚኒኬሽን እውቅናና ፈቃድ ወጭ ሶፍትዌሮችን በመገልግል በኢንተርኔት ስልኮች ማስደወል ሊያስከትለው ስለሚችለው ኃላፊነት የቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 13	103940	ወ/ሮ አመለወርቅ ጌታነህ እና የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	ጥር 24 ቀን 2008 ዓ/ም	285
60.	አንድ ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ የሚቆጠረው ከኃላፊዎች አንዱ ወይም ከሠራተኞች አንዱ ከድርጅቱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት ወይም አነሳሽነት ወይም አባሪነት ወንጀል ሲፈጸም ብቻ ስለመሆኑ፣ የወ/ሕግ አንቀጽ 23 እና አንቀጽ 34/1/ ጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93/1ሀ/ እና 93/2/	94913	የኢ/ገ/ን/ባ/ቅ /ጽ/ቤት እና እነ ጀሳቢን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/	ህዳር 24 ቀን 2008 ዓ.ም	290

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
61.	አንድ ሰው በሀሰት የተዘጋጀን ወይም የተለወጠን ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት ካልሆነ በቀር የወንጀል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ፣ የወ/ሕ/ቁ 378	101618	የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ፀረ ሙስና ኮሚሽን እነ መስከረም ፋንታዬ	ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም	295
ጉምሩክ /ታክስ					
62.	የቲ.ኦቲ /ተርን ኦቨር ታክስ/ ተመዝጋቢ የሆነ ሰው በህግ ፊት እንደ መረጃ /ማስረጃ / ሊያቀርብባቸው የሚገቡ ደረሰኞች ከባት በተቀበለው የቲ.ኦ.ቲ ደረሰኝ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ /ታክስ የቲ.ኦቲ አዋጅ ቁጥር 285/194 አንቀጽ 21/	95941	ሐኤስትራቭል ሀ/የተ/የግ/ማህበር እና እነ የኢት/ገ/ን/ባለስልጣን	ታህሳስ 7 ቀን 2008 ዓ.ም	300
63.	በተሻሻለው የጉምሩክ አዋጅ መሰረት የጉምሩክ ቁጥጥርን አሰናክለሃል ተብሎ ሊጠየቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ መፈፀሙን አቃቢ ህግ በበቂ ሁኔታ ሲያስረዳ ስለመሆኑ የጉሙሩክ አዋጅ ቁ. 859/2006 አንቀፅ 166	114043	የኢት.ገ/ን/ባለስልጣን ዓ.ህግ እና አብዲ ሞገስ	የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም	304
64.	በቀድሞ ህግ እንደ ወንጀል የሚቆጠር ድርጊት በአዲሱ ህግ የወንጀል ድርጊት መሆኑ ቀሪ ከሆነ ጉዳዩ በወንጀል የሚታይበት አግባብ ስላለመኖሩ በአዲሱ የገቢዎችና ጉምሩክ አዋጅ መሰረት ከቀረጥ በነፃ በገባ እቃ አላግባብ መገልገል የወንጀል ተጠያቂነት ሳይሆን አስተዳደራዊ ተጠያቂነት ብቻ የሚያስከትል ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 5(3) አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀፅ 98(1)(ሀ)(ለ) የጉሙሩክ አዋጅ ቁ.859/2006 አንቀፅ 163(1)(ሀ)(ለ)	111086	የኢትዮ.ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን እና አሚኮ/ሸማቾች የህ/ስራ ማህበር	የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም	308
65.	ማንኛውም እቃ ወይም መጓጓዣ ሊወረስ በሚችል ወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ ተጨማሪ ትእዛዝ መስጠት ሳያስፈልግ እቃው ወይም መጓጓዣው እንዲወረስ የሚደረግ ስለመሆኑ	117065	የኢት/ገ/ን/ባለስልጣን ዓ.ህግ እና አቶ ሚፍታህ ከማል	የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ.ም	311

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀፅ 104(1)				
አእምሮዊ ንብረት 315					
66.	በቅጂና ተዛማጅ መብቶች መጣስ /ለሚደርስ ለጉዳት ካሳ/ ወይም የሞራል ካሳ ዋጋው በተዋዋዮች ወገን ካልተቆረጠ የወቅቱን ዋጋ አጣርቶ መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ የሞራል ካሳ አከፋፈል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ ውጪ መወሰን የሌለበት ስለመሆኑ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች አዋጅ ቁ 410/96 አንቀጽ 7፣8፣37 የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2102	99082	ወ/ሮ ፍሬሕይወት ደመቀ እና ቤሩት ዳዊት	ጥቅምት 23 ቀን 2008 ዓ.ም	316
የዳኝነት ሥልጣን 324					
67.	የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች አስቀድመው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት በቀረበ አቤቱታ ላይ ባሳለፉት ውሳኔ የሚነሳን ተቃውሞ አቤቱታ ተቀብለው ለማስተናገድ የሥረ ነገር ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቀ/361/1995 አንቀጽ41/ሸ/ አዋጅ 408/96 አንቀጽ 2/ንኡስ ቁ፣1	105211	እነ አቶ እንዳለ ደንቦባ (አራት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ አልማዝ ደንቦባ (አራት ሰዎች)	ጥቅምት 1 ቀን 2008ዓ.ም	325
68.	ካሳ አነሰኝ ወይም ተከለከልሁ ካልሆነ በቀር በኢንቨስትመንት የሚቀርቡ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር ይግባኞች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 138 አንቀጽ 6/5/	92991	አቶ ተፈራ ተሰማ እና የአርሲ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት	ጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም	329
69.	ከመንግስት ገዥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ክርክር በመጀመሪያ ስልጣኑ የማየት መብት ያለው የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ እንጂ የመደበኛ ፍ/ቤት ስላለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 75(1)	107805	ጀዳው አርክቴክቶችና መሃንዲሶች እና የፌድራል ስፖርት	ጥቅምት 04 ቀን 2008ዓ.ም	332

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው መመሪያ አንቀፅ 49(1)		ኮሚሽን		
70.	በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ስራቸውን የሚያከናውኑት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ጋር የሚመሰረቱት የሥራ ግንኙነት ስምምነት ያለ እንደሆነ ጉዳዩ የሚዳኘው በዓለም አቀፍ ስምምነቱ መሠረት ስለመሆኑ፡-	117390	አቶ አለማየሁ መኮንን እና የምስራቅ አፍሪካ የበረሃ አንበጣ መከላከያ ድርጅት	ታህሳስ 21 ቀን 2008 ዓ.ም	337
71.	በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በምትክ ቦታ ይሰጠኝ ጥያቄ ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ፍርድ የሠበር አቤቱታ ለከተማው ፍ/ቤት ሳይቀርብ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የከተማው ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 43(5)፣ አንቀጽ 42(2) አንቀጽ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 29(6)	104858	አቶ ታደሰ ካሣ እና ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 አስተዳደር/ሁለት ሰዎች/	ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም	340
72.	አዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የጉዲፈቻ ስምምነትን ማስረጃን ተመልክቶ የወራሽነት ማስረጃን የመስጠት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 361/1995 አንቀፅ 41(ሸ)	112575	አቶ አፈወርቅ መኩሪያ እና ወ/ሮ ማደሊና ፍራንሲኔት	የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ.ም	343
ንብረት					
73.	በኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት ይዞታን የመጠቀም መብት የሚተላለፈው በውርስ ሕግ መሰረት በይዞታው የመጠቀም መብት ላለው የቤተሰብ አባል ሲሆን በዚሁ አግባብ ቅድሚያ የውርስ መብት የሚሰጠው ከመሬቱ በሚያገኙት ገቢ ለሚተዳደሩ(ሌላ መተዳደሪያ)ገቢ ለሌላቸው ወራሾች ሥለመሆኑ የኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 130/1999 አንቀፅ 9(1)(2) አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 10(1)	108335	እነ አቶ አለሙ ስሜ(ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ብዙነሽ ስሜ (ስድስት ሰዎች)	የካቲት 4 ቀን 2008ዓ.ም	347

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
74.	በትግራይ ክልል ገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ መሰረት ባለይዞታ አርሶ አደር ይዞታውን የመሸጥ መብት የሌለውና የኸው ተፈፅሞ ሲገኝ ይህ ውል እንዳይረጋ በማንኛውም ጊዜ ተቃውሞ ሊነሳና ጉዳዩ የቀረበለትም ፍ/ቤትም ውሉ ከጅምሩ ህገወጥ መሆኑን አውቆ ውሉ ህጋዊና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ የትግራይ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 55/1994፣ አዲሱ አዋጅ ቁ. 236/2006 የፍ/ሕ/ቁ. 1678፣1716፣1718፣1195 እና 1196	110549	ወ/ሮ ደመቀች ንርኢ እና አቶ ጋለመ ረብሶ	የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም	352
75.	አንድ አርሶ አደር የሚጠቀምበት ይዞታ (መሬት) በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠው መሆኑን እስካላረጋገጠ ድረስ የመንግስትና የህዝብ መሬትን ለረሻም ዓመት ይገፍዋለሁኝ ስለዚህ ይርጋ አይመለከተኝም ብሎ የሚያነሳው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	112906	ማንአህሎህ አንተነህ እና የማቻካል ወረዳ አከባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ፅ/ቤት	የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም	357
የንግድ ህግ 360					
76.	በውል መሰረት ከተቋቋመ የሽርክና ማህበር ውስጥ አንድ የማህበር አባል ከማህበሩ ሊወጣበት ስለሚችልበት አግባብ የንግድ ህግ 227 እና ተከታዮቹ	99900	አቶ ኃይሉ መንግስቱ እና አቶ ሬገን መሐመድ (ሁለት ሰዎች)	መስከረም 25 ቀን 2008 ዓ.ም	361
77.	በአንቺዖ ጥፋት በደረሰ አደጋ ምክንያት በተንገፍ(መንገደኛው) ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ ለመወሰን ልንከተላቸው ስለሚገቡ የካሳ አከፋፈል መርሆች የን/ሕ/ቁ. 599፣ የፍ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092	97760	ወ/ሮ ንግስቲ አትክልቲ እና አቶ አበባው ሽፈራው	ታህሳሥ 19 ቀን 2008 ዓ.ም	365

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
78.	የህንጻ ኪራይ ውል ካለቀ በኋላ የታጣ ገቢ የኪራይ ዋጋ በሚያጠራጥር ጊዜ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣኖች በወሰኑት ታሪፍ መሠረት ወይም ታሪፍ የሌለ እንደሆነ የቦታዎች ልማድ በመከተል መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ሕ/ሕ/ቁ. 2950/2/	105628	ዩኒቨርሳል ሜታልስና ሚኒራልስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና በስፋት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም	372
አፈፃፀም 378					
79.	አንድ ፍርድ የማይፈፀምበት ምክንያት ያለመኖሩ ሲረጋገጥ ለአፈፃፀም ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርድ እንዲፈፀም ትእዛዝ መስጠት የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392(1)	101631	የባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ፅ/ቤት እና አቶ በየነ አሸናፊ	ጥቅምት 2 ቀን 2008ዓ.ም	379
80.	የአፈጻጸም ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለአፈጻጸሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርድ እንዲፈጸም ትዕዛዝ የሚሰጠው የፍርድ ባለዕዳውን ጠርቶ ከመረመረው በኃላ እንደፍርዱ የማይፈጸምበት ምክንያት አለመኖሩን ካረጋገጠ በኃላ ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 207 እና 320(2) መሰረት በተሰጠው ትእዛዝ ላይ ቅሬታ አቅርቦ ነገር ግን ቅሬታው ተቀባይነት ቢያጣ የይግባኝ መብቱን (የይግባኝ ጊዜ ሊሰላበት) ስለሚችልበት አግባብ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 392 (1)	95537	ክራውን ቴክስታይል ዊቪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ሚድሮክ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች)	ጥቅምት 3 ቀን 2008 ዓ.ም.	382
81.	በአፈጻጸም ወቅት አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ ተሸጦ ከእዳ መክፈያ /ከግራ ቀኙ/ ይካፈሉ በተባለበት ጊዜ የሐራጅ ማስታወቂያ የፍ/ባለመብትን ጥቅም ላይ በቀጥታ ጉዳት እስካላደረሰ ወይም የሚያደርስ	110681	ወ/ሮ ሃዋ ጆሬ ተወካይ ታጅዢሆ እና አቶ አብዲ ቀንጨራ	ታህሳስ 8 ቀን 2008 ዓ.ም	388

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የሐራጅ ማስታወቂያው ተገቢ ለሆነ ቀን በአየር ላይ አልዋለም ወይም በጨረታው ለሚሳተፉ ሰዎች በቂ ጊዜ አልተሰጠም የሚባልበት ሁኔታ አለመኖሩ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. አንቀጽ 445				
82.	በፍርድ ባለመብት አማካኝነት የተፈረደን ፍርድ ለማስፈጸም የቀረበው የአፈጻጸም የክስ ማመልከቻ ይፈጸም የተባለውን ፍርድ ብቻ መሰረት ሊያደርግ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378	103787	የኢት/ገ/ት/ባለስልጣን ሚሌ ቅ/ጽ/ቤት እና ፉአድ ደኑር ሀሰን	ታህሳስ 21 ቀን 2008 ዓ.ም	392
ልዩ ልዩ 396					
83.	የትራፊክ ደንብን በመጣስ የሚተላለፍ ቅጣትን ለአፈፃፀሙ ፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችል ስላለመሆኑ *የትራፊክ ፍሰትን ለመቆጣጠር የወጣው ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 85*	103826	አንዋር አህመድ እና የቤ/ት/ክ/መ/ፍ/ህ ቢሮ	መስከረም 25 ቀን 2008 ዓ.ም	397
84.	የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 የተፈፃሚነት ወሰን	103458	አቶ ጋረድ ለበሰ እና የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	መስከረም 27ቀን2008 ዓ.ም	400
85.	የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ፈቃድ ሳይዝ ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን ማመንጨት፣ ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ማምከን ወይም ማስወገድ የተከለከለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 300/95 አንቀጽ 4/1/	104512	አቶ አባስ ኢብራሂም እና ሐረር ቢራ አ/ማህበር	መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ/ም	403

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
86.	የድለላ አበል ክፍያ መጠን ከተሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ በድለላ አበል መጠን ላይ በሚደረገው ክርክር እንደ ጉዳዩ ዓይነት እና የተሰጠው አገልግሎት እየተገናዘበ የሚወሰን ስለመሆኑ የን/ሕ/ቁ. 59(3)	109535	ሳልቫቶሪ ዴቤታ ኮምፕሌክስ እና ሃብታሙ አባዲ	የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ.ም	406

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሠሪና ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 112583

ጥቅምት 5 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመካው

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መለሰ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ጅማ ቅ/የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ብሩክ አበራ- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረባቸውን ጉዳይ የሥራ ውል መቋረጥ ተከትሎ ሊከፈል የሚገባ ልዩ ልዩ ክፍያ ክርክር የሚመመለከት ነው፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረው የሥራ ውል ማቋረጥ ተከትሎ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን የጠየቀ ሲሆን የጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ተጠሪ የሠራበት የእሁድ ቀን ክፍያ የ2006 ዓ.ም የአመት ዕረፍት እና የጥር ወር 2006 ዓ.ም ሙሉ ደመወዝ እንዲከፈለው ወስኗል፡፡

ይግባኙ ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል የቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም

አመልካች ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረቡ ችሎቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ የጥር ወር 2006 ዓ.ም ደመወዝ ለተጠሪ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ፕሮፌደንት ክፍያ ጉዳይ እንዲጣራ ለሥር ፍርድ ቤት በነጥብ እንዲመለስ ሌላው የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናት ፍርድ ሰጥቷል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ሲሆን የአመልካች የቅሬታ ነጥብ የእሁድ ቀን ሥራ ተጠሪ ሳይሰራ እንዲከፈለው መወሰኑ እና የ2006 ዓ.ም ተጠሪ አገልግሎት (የሥራ ውል) የተቋረጠው ጥር ወር 2006ዓ.ም አገልግሎት እንደሰጠ ተቆጥሮ የዓመት እረፍት ሙሉ ታስቦ እንዲከፈል መወሰኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ አቤቱታውን ከመረመረ በኃላ የእሁድ ቀን ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፈል መወሰኑን እና የ2006ዓ.ም ሙሉ የዓመት እረፍት ተብሎ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የሥር ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ በሕግ አግባብ የተወሰነ ነው በማለት ተከራክሯል ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የአመልካች አንደኛው የቅሬታ ነጥብ እሁድ ቀን ተጠሪ ይሰራበት የነበረው ፋርማሲ ዝግ ስለነበር ተጠሪ እሁድ ቀን መሥራቱን ሳያረጋግጥ የሥር ፍርድ ቤት እሁድ ቀን ለሰራበት ይክፈሉ ማለቱ አግባብ አይደለም የሚል ሲሆን በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት ላይ እንደተገነዘብነው የአመልካች ነ/ፈጅ በወረዳ ፍርድ ቤት በቃል ክርክርና ሲያደርግ ተጠሪ ለስራው ተከፍሎታል በማለት ስለመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገቡ አስፍሯል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም ተጠሪ እሁድ ቀን መሥራቱን የአመልካች ነ/ፈጅ ሳይክድ ነገር ግን ተከፍሎታል እያለ ስለተከራከረ የክፍያ ፔሮል አስቀርቦ መርምሮ በፔሮል የተከፈለው ወርሃዊ የደመወዝ እንጂ የትርፍ ቀን ክፍያ ስለመክፈሉ አላስረዳም በሚል በእሁድ ቀን ለሰራበት እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው ቅሬታ የፍሬ ነገር ክርክር ከመሆኑም ባሻገር ተጠሪ እሁድ ቀን አልሰራም በማለት በሥር ፍርድ ቤት ያላቀረበውን የክርክር ነጥብ በዚህ ችሎት ደረጃ አንልቶ ማቅረቡ ሲታይ ለዚህ ሰበር ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት ከተሰጠ የሰበር ሥልጣን እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ ውጪ ከመሆኑም ባሻገር በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ 329/1/ መሠረትም በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳም የክርክር ነጥብ በየትኛውም ደረጃ ባለው የበላይ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ስለሌለው ቅሬታው የሕግ መሠረት የለውም ብለናል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የቀረበው ነጥብ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረው የሥራ ውል ጥር ወር 2006 ዓ.ም መቋረጡ ተረጋግጦ እያለ በ2006ዓ.ም በጀት ዓመት ሙሉ አገልግሎት እንደሰጠ ታስቦ የዓመት እረፍት በገንዘብ ተሰልቶ እንዲከፈል መደረጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 77 (1)(ሀ) ላይ እንደተመለከተው ለአንድ ዓመት አገልግሎት የ14 የሥራ ቀናት በቃድ ይሰጣል፡፡አንድ ሰራተኛ ከአንድ አመት በታች አገልግሎት የሰጠ እንደሆነም በዚሁ ልክ ተመጣጣኝ የሆነ የእረፍት ጊዜ እንደሚሰጠው አንቀጽ 77(6) ላይ ተደንግጓል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በ2006 ዓ.ም የበጀት ዓመት በአመልካች መ/ቤት ያገለገለው እስከ ጥር ወር 2006ዓ.ም ሲሆን የአገልግሎት ጊዜው በበጀት ዓመቱ ሲሰላ 7 ወራት ብቻ ያገለገለ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም አገልግሎት በሰጠበት ጊዜ ልክ ያልተጠቀመበት የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው የሚገባው በ2006 ዓ.ም የበጀት ዓመት ሙሉ እንዳገለገለ ሳይሆን በአዋጅ አንቀጽ 77(6) በተደነገገው አግባብ በአገልግሎት ጊዜው ልክ (proportion to the length of his service) የሚለውን መርህ ተከትሎ መሆን አለበት፡፡

በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ በአግባቡ ሳይመለከቱ የአንድ ዓመት ሙሉ አገልግሎት እንደሰጠ በመቁጠር የሙሉ ዓመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈል መወሰናቸው የሕጉን ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ ሆኖ ስላገኘነው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ በ1/2006ዓ.ም በአመልካች መ/ቤት የሰጠው አገልግሎት 7 ወራት ብቻ በመሆኑ ይኸው አገልግሎቱ የሚያሰጠው የዓመት ፈቃድ 8 ቀናት ብቻ ሲሆን ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መረዳት እንደተቻለው ተጨማሪ የሁለት ዓመት አገልግሎት ስላለው ሁለት ቀናት ሲደመርለት ሊያገኝ የሚገባው የዓመት ፈቃድ አሥር ቀናት (10) ይሆናል ፡፡

በዚሁ መሠረት ስዓቱ ሲሰራ (2576*30) X10 = 858.66 ያልተጠቀመው የዓመት እረፍት ክፍያ ሆኖ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው ይገባል ብለናል ፡፡

በዚሁ መሠረት ተከታዩ ተወስኗል ፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 1202 153በ07/07/07ዓ.ም የሥር ፍርድ ቤት ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሻሽሏል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የዓመት እረፍት ክፍያ ብር 1,373.86 ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ፍርድ ክፍል ብቻ ተሻሽሎ ብር 858.66(ስምንት መቶ ሃምሳ ስምንት ብር ከ66/100) ነው ተብሎ ተወስኗል ።
3. ሌላው የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ክፍል ፀንቷል ።
4. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገው ክርክር ግራቀኙ የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለናል ።

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101675

ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ መስከረም ሞጋ ጠበቃ መስፍን ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ትዕግስት አረጋ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የስራ ውል መነሻ ያደረገ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በአሁኗ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሰረቱት ክስ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች በየደረጃው ጉዳዩን የተመለከቱት ፍ/ቤቶች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ የሚል አቤቱታ በማቅረባቸው አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡ በአሁኗ ተጠሪ የቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- በፈረንሳይ ሀገር በአመልካች መኖሪያ ቤት ውስጥ በየወሩ 1200 /አንድ ሺህ ሁለት መቶ ዩሮ/ ደመወዝ እየተከፈላቸው በሞግዚትነት እንዲሰሩ በ19/02/2001 ዓ.ም በተፃፈ ውል በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09 በሚገኘው በአመልካች ወላጆች ቤት ውስጥ ተፈራርመው ከመጋቢት 02/2001 ዓ.ም እስከ መጋቢት 08/2002 ዓ.ም ድረስ ለአንድ አመት ሲሰሩ እንደቆዩ፣ የስራ ውሉም አመልካች ፈረንሳይ አገርን ለሁል ጊዜ ሲለቁ የሚቋረጥ ስለመሆኑ፣ አመልካች የተጠሪ ደመወዝ ሳይከፈሉ እንዳሰናበቷቸው የዓመት ረፍት ጊዜም አምስት ሳምንት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በውሉ የተመለከተ ቢሆንም እንዳልተሰጣቸው፣ አመልካች ደመወዛቸውን እንዲከፍሉዋቸው በውጭ ጉዳይ ሚኒስተር በኩል፣ በሽምግልና ጥረት ቢያደርጉም ሊከፈላቸው እንዳልቻለ፣ 1200 ዩሮ ወደ ኢትዮጵያ ገንዘብ ሲመነዘር 20.80 /ሀያ ሺህ ሰማንያ ሳንቲም/ በመሆኑ፣ ደመወዝ 299,520.00 የአምስት ሳምንት የእረፍት ጊዜ 29,120.00 በድምሩ 328,640.00 /ሶስት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ

አርባ ብር/ እና ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ገንዘብ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 9% ወለድ ጋር እንዲከፈላቸው፣ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች የበኩላቸውን መልስ ያቀረቡ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩ፡- የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በፍሬ ነገሩ በሰጡት መልስ ክሱ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቀርቦ የተዘጋ ስለመሆኑ፤ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንደሌለው፣ የተጠሪ የደመወዝ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በፍሬ ጉዳዩም ተጠሪ ያልተከፈላቸው ደመወዝ አለመኖሩን፤ ደመወዝ ካልተከፈላቸው ውሉ ለመዘገበዉ የፈረንሳይ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያቀረቡ እንደነበር፣ በመግለፅ መከራከራቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ በ18/06/2006 ዓ.ም ብይን የሰጠ ሲሆን ጉዳዩን ተመልክቶ የመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን እንዳለው በመጥቀስ የአመልካች መቃወሚያ ውድቅ አድርጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና የቀረቡ ምስክሮች የሰጡት ቃል ከመረመረ በኋላ በግራ ቀኙ የተፈረመው የስራ ቅጥር ውል መኖሩን ተቀብሎ የተጠሪ የወር ደመወዝ 1200 ዩሮ እንደነበር በአመልካች ከቀረበው ማስረጃ ፍ/ቤት የተቀበለው የክፍያ መጠን በድምሩ 6,408 ብር ብቻ እንደሆነ፤ ተጠሪ የሚገባቸው ቀሪ ክፍያ ብር 293,112.00 መሆኑን፤ የአምስት ሳምንት የእረፍት ክፍያ በድምር ብር 29,120.00 እንደሆነ በአጠቃላይ አመልካች ለተጠሪ ብር 322,232.00 /ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ብር/ እንዲከፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር አድርገአል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የተጠሪ የክፍያ ጥያቄ በፍ/ሕ/ቁ.2601 እና 2023/ሀ/ መሰረት በይርጋ የሚታገድ ነው፤ ጉዳዩ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የሚዳኝ አይደለም፤ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች መቅረብ ከነበረበትም በሥራ ክርክር ችሎት መቅረብ ነበረበት የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ክሱን በወቅቱ ማቅረባቸው እና በይርጋ የሚታገድበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች ያቀረቡት የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታውን የሚደግፍ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ነጥቦች፡-

1. ግራ ቀኙ በሚከራከሩበት ጉዳይ አግባብነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ የትኛው ነው?
2. የደመወዝ ክፍያ ግምት በተመለከተ የተነሳው የይርጋ ክርክር ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ በአጣሪ ችሎቱ የተጠቀሰው የፍ/ሕ/ቁ.2023/ሀ/ ነው ወይስ አይደለም?
3. አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሏቸው የሚገባ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው የገንዘብ መጠን ምን ያህል ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች እና ተጠሪ የሥራ ውል ግንኙነት እንደነበራቸው፤ ውሉም ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈርሞ በፈረንሳይ አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደተመዘገበ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት እንደነበራቸው ሳይክዱ ሁሉም ክፍያዎች በወቅቱ እንደተከፈሉ፣ አልተከፈለም የሚባል ገንዘብ ካለም በይርጋ እንደሚታገድ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በአመልካች ቤት በሞግዚትነት ለአንድ አመት ማገልገላቸው እና የጠየቁት ክፍያ እንዳልተፈፀመላቸው እንዲሁም ክሱን በወቅቱ ስለማቅረባቸው በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው መሰረታዊ ጭብጥ እንደሚከተለው መርመሮታል፡፡

<u>የመጀመሪያው ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- አመልካች የተጠሪ የስራ ቅጥር ውል ከፍ/ሕ/ቁ. 2601 አንፃር እንዲታይ በሰበር አቤቱታቸው አመልክተዋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት በቤተሰብ አስተዳደር ውስጥ ስለሚኖር አሽከር የስራ ውል፤ ሰራተኛውን የሚኖሩት መብትና ግዴታዎች የሚመለከት ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ድንጋጌ ያለው የተፈፃሚነት ወሰን ሲታይ በአገር ውስጥ በሚቀጠሩ ሰራተኞች ስለመሆኑ የሚያከራክር ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች እና ተጠሪ የስራ ውል በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈፅሞ በፈረንሳይ አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፀድቆ አመልካች እና ተጠሪም በፈረንሳይ አገር ሲኖሩ እንደነበር ባለተካደበት ሁኔታ ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል ስለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የወጣው አዋጅ ቁጥር 377/96 እና የዚህ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 494/1998 ዓላማና ግብ በሀገር ውስጥ ስለሚኖረው የስራ ስምሪት የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ፤ ሊሟሉ የሚገባቸው አነስተኛ መመዘኛዎች ማለትም የስራ ሰዓት፤ የእረፍት ጊዜ፣ የሕመም ፈቃድ ወዘተ ያካተቱ ሕግ እንጂ በውጭ አገር ተቀጠረው ስራ ሲሰሩ የነበሩ ሰዎች የሚያነሱት የመብት ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አመልካች እና ተጠሪ በሚከራከሩበት ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሕግ /Governing Law/ በሀገር ውስጥ ባለው የስራ ስምሪት የግራ ቀኙ አንፃራዊ መብትና ግዴታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚደነግጉ የፍ/ሕ/ቁ.2601 እና የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የሚመለከት አዋጅ 377/96 አለመሆኑን ተረድተናል፡፡ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ስለስራና ሰራተኛ ማገናኘት አገልግሎት የወጣ አዋጅ ቁጥር 632/2001 ነው፡፡ የዚህ አዋጅ መግቢያ፤ የተፈፃሚነት ወሰን የሚመለከት አንቀፅ 3/2/ “የግል አገልግሎት ስራ ላይ ለመቀጠር ወደ ውጭ አገር በሚሄዱ ኢትዮጵያ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል” በማለት ደንግጓአል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች እና ተጠሪ የስራ ውል የግል አገልግሎት /personal service/ ስራ ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ አዋጅ ቁጥር 632/2001 ነው ብለናል፡፡

<u>ሁለተኛ ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው መሰረታዊ ነጥብ አንዱ ይርጋን የተመለከተ ነው፡፡ አመልካች የተጠሪ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በ6 ወር የሚታገድ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ችሎት እንዲመረመር የተያዘው ጭብጥም የይርጋ ጥያቄው ከፍ/ሕ/ቁ.2023/ሀ/ አንፃር እንዲታይ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ከፍ/ሕ/ቁ.2601 በማጣመር ስንመለከተው በሀገር ውስጥ በቤት አገልጋይነት የተቀጠሩ አሽከሮች በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያ ካልተጠየቁ እንደተከፈለ የሕግ ግምት ይወሰዳል የሚል ይዘት ያለው ስለመሆኑ ተመልክተናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የፍ/ሕ/ቁ. 2601 ይሁን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በሀገር ውስጥ የስራ ስምሪት ላይ በሚነሱ ክርክሮች እንደነገሩ ሁኔታ ተፈፃሚ ከሚሆኑ በስተቀር በውጭ አገር ለተሰጠው አገልግሎት እና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የክፍያ ክርክር አግባብነት ያላቸው የሕግ ማዕቀፎች ባለመሆናቸው አመልካች የተጠሪ የመብት ጥያቄ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ የሚታገድ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሰረት የለውም ብለናል፡፡

አዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀፅ 3/1/ የአዋጁን የተፈፃሚነት ወሰን አንቀፅ 20 ስለ ሰራተኛው መብት፣ አንቀፅ 24 ስለ አነስተኛ ደመወዝ መጠን የሚመለከቱ መሰረታዊ ድንጋጌዎች ያካተተ ቢሆንም በአሰሪና ሰራተኛው የሚነሳው የክፍያ ጥያቄ በተለይም የመብት ጥያቄ ለማቅረብ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው የይርጋ ጉዳይ መታየት ያለበት ከአጠቃላይ የውል ድንጋጌዎች አንፃር ስለመሆኑ ተቀባይነት ያለው የሕግ አተረጓጎም ስርዓት ነው፡፡ የፍ/ሕ/ቁ. 1677/1/ “ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም የዚህ አንቀፅ ደንቦች ይፈፀሙባቸዋል” በማለት የደነገገ ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ተዛማጅ የሆነው የእንግሊዘኛው ትርጉም” 1677/1/ the relevant provisions of this title shall apply to obligations not withstanding that they do not arise out of a contract” በማለት የተደነገገ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው የክፍያ ጥያቄ ክርክር ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ከፍ/ሕ/ቁ. 1677/1/ እና 1845 አንፃር መታየት ያለበት ነው፡፡ የአመልካች እና ተጠሪ የስራ ውል ግንኙት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት በማድረግ የሚነሳው ክርክር በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው የውል ግንኙነት የተቋረጠው መጋቢት 2002 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ እስከቀረበበት መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያለው ጊዜ ሲታይ በፍ/ሕ/ቁ. 1845 የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ሳይጠናቀቅ ክስ መቅረቡን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የማያነሱት የይርጋ ጥያቄ ተፈፃሚነት ካለው የይርጋ ድንጋጌ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡

<u>የመጨረሻው ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በወር 1200 ዩሮ እየተከፈላቸው ይሰሩ እንደነበር አረጋግጧል፡፡ አመልካች ክፍያ መፈፀማቸው ቢከራከሩም የሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተደገፈ ነው በማለት የተቀበለው ክፍያ 6,408 ብር ብቻ መሆኑ ከውሳኔው ግልባጭ መረዳት ተችሏል፡፡ ተጠሪ ያልተከፈላቸው አጠቃላይ ደመወዝና የዓምስት ሳምንት የእረፍት ጊዜ ክፍያ ወደ ኢትዮጵያ ገንዘብ ሲመነዘር /6,408 ተቀንሶ/ 322,232.00 መሆኑን በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተመልክቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መዝኖ አመልካች ለተጠሪ ብር 322,232.00 ይክፈሉ በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍልም የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ከፍተኛ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔዎች በውጤት ፈርጆ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው መሆኑ የሚያሳይ ነገር ያልተገኘ በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 99933 በ12/07/2006 የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 99977 ግንቦት 6/2006 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች እና ተጠሪ የሚከራከሩበት የይርጋ ጊዜ የሚገዛው በፍ/ሕ/ቁ 1677/1/ እና 1845 ነው ብለናል፡፡ በዚህ መሰረት የተጠሪ የመብት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ ብር 322,232.00 /ሶስት መቶ ሀያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት/ ከ13/07/2003 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ እንዲከፍሉ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. በዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያወጡት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- በዚህ ፍ/ቤት ሐምሌ 30 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መ/ቁ.114669

ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተሽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የኢትዮጲያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፓሬሽን የደብረ ማርቆስ መንገዶች ጥገና ዲስትሪክት ነገረ ፈጅ መሰረት አበራ

ተጠሪ፡- አቶ አስማረ ፈጠነ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ የስራ ውል ማቋረጥ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአ.ብ.ክ.መ.የደብረማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ከሚያዚያ 21 ቀን 1984 ዓ/ም ጀምሮ በጠቅላላ 22 ዓመት ሲያገለግሉ እንደቆዩ፤ መስሪያ ቤቱም በየጊዜው እድገት ይሰጣቸው እንደነበር፤ በሹፍርና ሙያ የስራ መደብ እስከ መጋቢት 10 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ ስራቸውን በተገቢው መንገድ እየፈጸሙ በነበሩበት ሁኔታ አመልካች ከመጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ምንም ዓይነት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸው ክስ እስካቀረቡት ድረስ ከስራ ያገዳቸው በመሆኑ የስራ ውሉ የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው ተብሎ ወደ ስራ ገብታችሁ እንዲመለሱ፤ ይህ የማይወሰን ከሆነ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተፈቀዱትን የስራ ስንብት ክፍያ የ6 ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ደመወዝ በወቅቱ ባለመክፈሉ በድምር 60,601.70 /ስልሳ ሺህ ስድስት መቶ አንድ ብር ከሰባ ሳንቲም ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፈል እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ባቀረበው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ ከስራ ገበታቸው ከ30 ቀን በላይ የቀሩ በመሆኑ ስንብቱ በህጉ አግባብ የተከናወ ነው ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄም የህግ መስረት የለውም፡፡ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉአቸው ያቀረቡት ጥያቄም በአግባቡ አይደለም፡፡ የአመት እረፍት በተመለከተ የቀረበ የክፍያ ጥያቄም ተገቢነት የለውም፡፡ የስራ ልምድ የተሰጣቸው በመሆኑ ድጋሜ ሊጠይቁ አይገባም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የስር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር መርምሮ ተገቢ ነው ያለው ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት መዝገቡ ከመረመረ በኃላ የአሁን ተጠሪ ከባህር ዳር ወደ ደብረ ማርቆስ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነው ሌላ አሽከርካሪ ከእንጅባራ ወደ ደብረማርቆስ በሚነዱበት ጊዜ የመኪና ግጭት ተከስቶ የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩ እስከሚጣራ በጊዜ ቀጠሮ ለ4 ወር ከ11 ቀን መታሰሩን ዓቃቤ ህግ ጉዳዩን ካጣራ በኃላ በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ አያስከስስም በማለት በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/42/1/ሀ/ መሰረት የዘጋው ሲሆን ተጠሪ ማረሚያ ቤት የገቡት ፍ/ቤት ጥፋተኛ ተብሎው ተፈርዶባቸው ሳይሆን በጊዜ ቀጠሮ እስከ ሆነ ድረስ በተባለው ጉዳትም ተጠያቂ የሆነው ሌላ መኪና ሲነዳ የነበረ ሹፌር በመሆኑ አመልካች ተጠሪን የ6 ወር ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመለስላቸው ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም አቤቱታው ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/በ/ በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን በላይ ለሚታሰሩ ሰራኞች የሚመለከት አይደለም፡፡ ተጠሪ በጊዜ ቀጠሮ መታሰራቸው ፍርዱ ወይም ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው የሚያስብል አለመሆኑን ገልጾ የ6 ወር ውዝፍ ደመወዝ ይከፈላቸው የሚለውን የውሳኔ ክፍል በማሻሻል ወደ ስራ እንዲመለሱ የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በድምጽ ብልጫ ውድቅ ተደርጓል፡፡ ሰበር ችሎቱ በፍርድ ወይም በውሳኔ ከ30 ቀን በላይ ያልታሰረው ሰራተኛ ስራ ሲሰራ በተፈጠረ አደጋ በምርመራ ላይ በእስር የቆየ ለመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የስራ ውል መቋረጥ ከህግ ውጭ ነው ወደ ስራ ይመለስ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔዎች አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አድርጓል /ተሰዋውሟል/፡፡ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት፡- ተጠሪ በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን በላይ ታስረው ከስሩ የቀሩ መሆኑን ተረጋግጦ ስንብት መከናወኑ በአግባቡ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ውሳኔዎች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/37256 የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ያላገናዘበ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች የስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሉ ያቋረጠው ከህግ ውጭ ነው፡፡ የሰበር ውሳኔው በጭብጥ ከተያዘው ጉዳይ ግንኙነት እንደሌለው፤ በጊዜ ቀጠሮ ታስረው እንደተለቀቁ ጉዳዩም አያስከስስም ተብሎ በዓ/ህግ መወሰኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም አቤቱታውን የሚያጠናክር ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ፡- ተጠሪ ፈጸሙት በተባለው ወንጀል ተጠርጥረው በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን በላይ ታስረው ከተፈቱ በኃላ ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/በ/ ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከክርክር ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከባህር ዳር ወደ ደብረማርቆስ በሚያሽከርክሩበት ጊዜ ከሌላ መኪና ጋር ግጭት በመፍጠሩ ጉዳዩ ለማጣራት በጊዜ ቀጠሮ 4 ወር ከ11 ቀን ከታሰሩ በኃላ የዓቃቤ ህግ ጉዳዩን በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/42/1/ሀ/ አያስከስስም በማለት የዘጋው በመሆኑ ከእስር እንደተለቀቁ እና በፍርድ ቤት ክስ አቅርበው በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን መታሰር የሰራተኛው የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም ተብሎ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪ በወንጀል ተከሰው ጥፋኛ መሆን አለመሆናቸው ሳይሆን ከ30 ቀን በላይ ከስራ በመቅረታቸው ምክንያት ከስራ ለማሰናበት በቂ ስለመሆኑ ነው፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ ተጠሪ በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን በላይ ከመታሰራቸው ውጭ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ጥፋተኛ አልተባሉም፡፡

አንድ አሰሪ ሰራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከሚያሰናብትባቸው ምክንያቶች አንዱ ሰራኛው ከ30 ቀን በላይ የእስራት ፍርድ ተወስኖበት ከስራ መቅረቱን ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/በ/ ተመልክቷል ፡፡ የድንጋጌው ሙሉ ይዘት “በሰራተኛው ላይ 30 ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የእስራት ፍርድ ተወስኖበት ከስራ ሲቀረ” የሚል ሲሆን የእንግሊዘኛው ቅጂ ደግሞ “absence from work due to sentence of imprisonment passed against the worker for more than 3 days” በማለት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋ መረዳት የተቻለው አንድ ሰራተኛ ከ30 ቀናት የሚበልጥ እስራት ተወስኖበት ከስራ መቅረቱን ሲረጋገጥ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ እንደሚሰናበት የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከስራ መቅረታቸው ሳይካድ የቀሩበት ምክንያት ግን በወንጀል ተጠርጥረው በጊዜ ቀጠሮ ታስረው ስለነበር ነው፡፡ ስልጣን ያለው የዐቃቤ ህግም የወንጀል ክስ ለመቀጠል የሚያስችል ነገር የሌለው በመሆኑ ጉዳይ አያስከስስም በማለት ስለ መዝጋቱ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት የወንጀል ክስ ቀርቦባቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥፋተኛ ተብለው አልታሰሩም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከ30 ቀን በለይ ከስራ መቅረቱን ተረጋግጦ ያልተወሰነበት ሰራተኛ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ማሰናበት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/በ/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች በተሰጣቸው ኃላፊነት ሙያዊ ግዴታቸው ሲወጡ በተከሰተው የመኪና ግጭት ተጠርጥረው በመታሰራቸው ምክንያት ብቻ ፍ/ቤት ጥፋተኝነታቸው ሳያረጋግጥ አመልካች በራስ አነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችለው የህግ መሰረት የለውም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/37256 ህዳር 4 ቀን 2001 ዓ/ም የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪ የስራ ውል ከህግ ውጭ ማቋረጡን በማረጋገጥ ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰናቸው በአግባቡ መሆኑ ከሚያሳይ በቀር የፈጸሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው አይደሉም ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአብክመ የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0119921 በ27/04/2007 ዓ/ም የደብረማርቆስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/10694 በ20/20/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ፍርድ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/44956 በ26/09/2007 ዓ/ም በድምጽ ብላጫ የሰጠው ፍርድ ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ወደ ስራ እንዲመልሰው መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ችሎት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- ሰኔ 30/2007 ዓ/ም በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ አግኝቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 118263

ቀን ጥር 18/2008ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሪዳ ኑረዲን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቡልኬስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ በሰበር እንዲታይ የቀረበው መሰረታዊ የክርክር ነጥብ የአሁኑ ተጠሪ የወሰደው ከስራ የማሰናበት እርምጃ በሕጉ አግባብ መሆን ያለመሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኗ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ በመ.ቁ. 39053 ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ በየደረጃው የተመለከቱት የስር ፍ/ቤቶች በአሁኑ ተጠሪ የተወሰደው ከስራ የማሰናበት ተግባር በሕጉ መሰረት ነው በማለታቸው በሰበር እንዲታረም ያቀረበው አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች በስር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ባጭሩ፡- በተጠሪ ድርጅት በመጋዘን ሃላፊነት ከታህሳስ 06 ቀን 2004ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸው እስከተቋረጠበት ግንቦት 21ቀን 2006ዓ.ም ድረስ በወር 3386.32 (ሶስት ሺህ ሶስት መቶ ሰማንያ ስድስት ከሰላሳ ሁለት ሳንቲም) እየተከፈላቸው ስራቸውን ሲሰሩ እንደነበር፤ የአሁኑ ተጠሪ የስራ ውላቸው ከሕግ ውጪ ያቋረጠው በመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ የስራ ስንብት ካሳ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የግንቦት ወር የ21ቀን ደመወዝ፣ የ4ቀን የዓመት ረፍት ክፍያ እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ የመከላከያ መልስ ያቀረበ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩ፡- አመልካች እቃ እያለ የለም እያሉ፤ ከድርጅቱ ሰራተኞች ባለመግባባት እና በተደጋጋሚ ከስራ በማርፈድ ጥፋት ፈጽመው ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም አላሻሻሉም፡፡ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ አይገባቸውም የ4ቀን እረፍት ወስደውታል፤ የግንቦት የ21ቀን ደመወዝ በሂሳብ ቁጥራቸው ገቢ ሆነዋል፡፡ ስንብቱ በሕግ አግባብ የተከናወነ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤትም የተጠሪ ምስክሮች አድምጧል፡፡ የሰነድ ማስረጃም ተመልክተዋል፡፡ በተጠሪ የቀረቡ ምስክሮች አመልካች የድርጅቱ የስራ መግቢያ ሰዓት አያከብሩም፡፡ ከ2፡00 — 2፡30 ሰዓት ድረስ የስራ መግቢያ መሆኑን እየታወቀ ከ3፡00 - 3፡30 ይገባሉ፡፡ ከጥበቃና ሌሎች ሰራተኞች ይጋጫሉ፡፡ ፈጸሙት ለተባለው ጥፋት በ03/03/2005ዓ.ም ፣ በ12/03/2005ዓ.ም እና በ29/02/2006ዓ.ም ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው በ12/03/2005ዓ.ም የሁለት ቀን ደመወዝ ተቀጥቷል፡፡ አመልካች የተጠሪ ማስረጃ አላስተባበሉም፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1(ሀ) እና (ረ) መሰረት ማስጠንቀቂያ እየተሰጣቸው በተደጋጋሚ ከስራ የቀሩ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው፡፡ የስራ ስንብት ካሳ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ አይገባቸውም፡፡ የእረፍት ጊዜ በተመለከተ መውሰዳቸው የተረጋገጠ ሲሆን የግንቦት ወር 21ቀን ደመወዝ ፈርመው መውሰዳቸው አልተረጋገጠም ብር 2370.59 ይክፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ግራቀኙ በማከራከር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓአል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ለስንብቱ ምክንያት የተባለው ነገር በስንብት ደብዳቤ እንዳልተገለጸ፤ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው በኋላ ከስራ የሚያሰናብት ጥፋት መፈጸማቸው ሳይረጋገጥ የስራ ውል መቋረጡ ሕገወጥ ነው ሊታረም ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው በስንብት ደብዳቤው ላይ ምክንያት አለመገለጹ ስንብቱ ሕገወጥ አያደርገውም ውሳኔው ሊነቀፍ አይገባም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከለይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚጠይቀው ጭብጥ የአሁኑ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጡ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረታዊ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ሆኖ አግኝቶታል፡፡

አመልካች የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ በሆነ አግባብ ነው በማለት አጥብቀው ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው በፈጸሙት ጥፋት ነው የሚል መልስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማቅረቡን መዝገቡን ያሳያል፡፡ በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋገጠ የተባለው አመልካች እቃ የለም እንደሚሉ፤ ከስራ ባደረቦቻቸው እንደማይግባቡ እና በ03/05/2005 ፣ በ12/03/2005 ፣ እና በ29/02/2006 ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው የሚገልጽ ነው፡፡ ከዚህ መዝገብ ጋር የተያያዘው እና በተጠሪ ተጻፈ በተባለው ደብዳቤ የአመልካች የስራ ውል ከ21/09/2006ዓ.ም ጀምሮ የሁለት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው እንደሚቋረጥ የሚገልጽ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በስንብት ደብዳቤው ምክንያት ሳይገልጽ ፍሬ ነገሩ በማስረዳት የስራ ውል ማቋረጥ እንደሚችል ግልጽ ቢሆንም ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ጥፋት መቼ እንደተፈጸመ ማጣራትና ግልጽ ማድረግ ግን የአሰሪው ግዴታ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ አመልካች ጥፋት ፈጽመዋል በማለት የተከራከረ ቢሆንም እስከ ጥቅምት 29ቀን 2006ዓ.ም ተፈጸሙ የተባሉ ጥፋቶች መሰረት በማድረግ ቅጣት ወስኖ እንደነበር የስር ፍ/ቤት መዝገብ የሚያሳይ ቢሆንም ለመጨረሻ ጥፋት ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ጥፋት ስለመፈጸማቸው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡

በመሰረቱ አንድ አሰሪ ሰራተኛው ያለበቂ ምክንያት ማስጠንቀቂያ እየተሰጠው በመደጋገም የስራ ሰዓት የማያከብር ሰራተኛ የስራ ወሉ ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ እንደሚችል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሀ) ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተያያዘ እንደጥፋቱ ክብደት በስራ ቦታ አምባጓሮ መፍጠር ወይም ጠብ አጫሪነት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ እንደሚያሰናብት ከላይ በተመለከተው ሕግ አንቀጽ 27(1(ረ) ስር ተደንጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት አመልካች በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ እየተሰጣቸው አርፍደዋል ከተቋሙ ሰራተኞች አይግባቡም ያለ ቢሆንም ድርጊቱ የተፈጸመበት ጊዜ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው ጊዜ በኋላ ስለመሆኑ አላረጋገጠም፡፡ አንድ አሰሪ በሰራተኛው ተፈጸመ ያለው ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ድርጊት የስራ ውሉ ለማቋረጥ ያለው መብት ድርጊቱ መከሰቱ ከታወቀበት ከ30ቀናት በኋላ በይርጋ እንደሚታገድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27(3) ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ተፈጸመ ያለው በተደጋጋሚ ማርፈድ፤ ከድርጅቱ ሰራተኞች ያለመግባባት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው ከጥቅምት 2006ዓ.ም በኋላ የተፈጸሙ እና ድርጊቱ መከሰቱ በታወቀ በ30ቀናት ውስጥ ህጋዊ እርምጃ ስለመወሰዱ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ የአመልካች የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ያቋረጠው የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሀ)፣ (ረ) እና (3) ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ሳይከተል ነው ብለናል፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም በተጠሪ የተወሰደው የስራ ውል ማቋረጥ ተግባር በሕጉ አግባብ ነው ማለታቸው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የተደነገጉትን የስራ ውል የሚቋረጥባቸው ሕጋዊ ስርዓቶች ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው በሕጉ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ ነው ከተባለ የሕገወጥ ሥራ ውል ማቋረጥ ሕጋዊ ውጤት ምንድነው? የሚለው ነጥብ ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ የስራውሉ በሕገወጥ መንገድ ሲቋረጥ በሕጉ የተቀመጠው መፍትሔ በሕጉ የተፈቀደው ውዙፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራ መመለስ ወይም ልዩ ልዩ ክፍያዎች ተፈጽመውለት ከስራ ማሰናበት ናቸው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(1) እንደተመለከተው የስራ ውሉ ከሕግ ውጭ የተቋረጠበት ሰራተኛ ወደ ስራ የመመለስ መብት አሰሪው ደግሞ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡ ሰራተኛው ወደስራ የመመለስ ካልፈለገ/ች ካሳ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ይሁንና ፍርድ ቤት አንድ ሰራተኛ ወደስራ ሊመለስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው አንኳር ነጥብ ሲወሰን የስራው ባህሪ የግራቀኙ ግንኙነት እና የኢንዱስትሪ ሰላም ታሳቢ መደረግ አለባቸው፡፡ ፍ/ቤቱ ሰራተኛው ወደስራ ቢመለስ ከአሰሪው ጋር ከፍተኛ ችግር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ ብሎ ካመነ ሰራተኛው በሕጉ አግባብ ካሳ ተከፍሎት ከስራ እንዲሰናበት ሊወሰን እንደሚችል ከላይ በተመለከተው አዋጅ አንቀጽ 43(2) ስር ተመልክቷል፡፤ በተያዘው ጉዳይ የአሁኗ አመልካች በድርጅቱ ሲኒየር እስቶር ኪፐር /የመጋዘን ኃላፊ/ የነበሩ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የመጋዘን ሃላፊ የሚሆነው ሰራተኛ ከፍተኛ የሆነ እምነት የሚጣልበት ስራ ከመሆኑ አንጻር ከአሰሪው ጋር ጥሩ የስራ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ አሁን ያላቸው ግንኙነት ከፍተኛ እምነት በሚጠይቀው የስራ መደብ አመልካች በነበሩት የስራ መደብ እንዲቀጥሉ ማድረግ በኢንዱስትሪ ሰላም እና የድርጅቱ ውጤታማነት የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጠር እንደሚች ግምት ወስደናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ወደ ስራ ከሚመለሱ ይልቅ በሕጉ የተፈቀዱላቸው ክፍያዎች ተከፍሏቸው ከስራ ቢሰናበቱ ለሁለቱም ተከራካሪዎች ጠቃሚ ነው ብለናል፡፡

የአመልካች የስራ ውል ከሕግ ውጭ በመቋረጡ ምክንያት በሕጉ የተፈቀዱ ክፍያዎች የስራ ስንብት ክፍያ፣ የካሳ ክፍያ እና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ስለመሆናቸው ከላይ በተመለከተው አዋጅ አንቀጽ 39፣40፣43 እና 44 ተመልክቷል፡፡ የአመልካች የወር ደመወዝ 3386.38 መሆኑ በቀረቡት ክስ የተጠቀሰ ሲሆን ተጠሪም የደመወዝ መጠኑ በመካድ ያቀረበው ክርክር የሌለ በመሆኑ ለሚወሰነው ካሳ መነሻው ይህንን የደመወዝ መጠን ይዘናል፡፡ አመልካች በተጠሪ ድርጅት ከታህሳስ 06 ቀን 2004 እስከ ግንቦት 21ቀን 2006ዓ.ም የሰሩ መሆናቸውም አላከራከረም፡፡ የአመልካች የአገልግሎት ዘመን 3 አመት ከ 7 ወር ከ 16 ቀን ነው፡፡ በመሆኑም የስራ ስንብት ክፍያ በአንቀጽ 40(1) እና (2) መሰረት ብር 6,349.44፤ የካሳ ክፍያ በአንቀጽ 43(4)(ሀ) መሰረት 20,318.28 ብር፤ ተጠሪ የአመልካች የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ በማቋረጡ በአንቀጽ 35(1)(ለ) መሰረት የሁለት ወር ደመወዝ ለመክፈል የሚገደድ ይሆናል፡፡ ይሁንና የአሁኑ ተጠሪ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲወስዱ በደብዳቤ የገለጸ በመሆኑ ይህንን በደብዳቤው የገለጸውን መጠን ገንዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካልከፈለ ይክፈል ብለናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ፍ/ቤቶች በተጠሪ የተወሰደው የማሰናበት እርምጃ በሕጉ አግባብ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 39053 በ14/04/2007ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 156383 በ4/12/2007ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የአመልካች የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ያቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ የአመልካች የስራ ውል ከሕግ ውጭ በማቋረጡ የስራ ስንብት ክፍያ፣ ብር 6,349.44፤ የካሳ ክፍያ ብር 20,318.28 እና የማስጠንቀቂያ የሁለት ወር ደመወዝ ያልተከፈለ ከሆነ እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡ በድምር ብር 26,667.72 (ሃያ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስድሳ ሰባት ከሰባ ሁለት ሳንቲም) እንዲሁም በስንብት ደብዳቤ የተገለጸው የሁለት ወር ደመወዝ ስራ ማፈላለጊያ የተባለው የ2ወር የማስጠንቀቂያ ደመወዝ የሚተካ ነው ብለናል፡፡ ገንዘቡ ያልተከፈለ ከሆነ ተጠሪ አሁን ከተወሰነው ገንዘብ ደምሮ መክፈል አለበት ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 112956

ጥቅምት 22 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- መ/ስጠፋ ኑር ትዕም ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ነ/ፈጅ ጋሻው ቡልቶ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ የስራ ቅጥር ውል ማቋረጥን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በተመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ከ1976 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ተቀጥሮ በመስራት ላይ እያለ ወደ ኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን ተለውጦ፣ ይህም ድርጅት ወደ ኢንተርፕራይዝ ተቀይሮ ብር 3666.00 በማግኘት ለ28 አመታት የሰራ ቢሆንም ከስራ ሳይቀር፣ ከስራ ለቀረበት ቀንም የሃኪም ማስረጃ አቀርቦ ሳለ ደመወዝም እየተከፈለው በነበረበት ሁኔታ በ18/12/2004 በፅሁፍ ከስራ መሰናበቱ እንደተገለፀለት፤ የተጠሪ ድርጊት ሕገ ወጥ በመሆኑ ወደ ስራ እንዲመለስ እንዲወሰንለት ዘርዝሮ በአጠቃላይ 89,328.20 ከወጪና ኪሳራ ከጠበቃ አበል ጭምር እንዲከፈለው ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ከስራ የተሰናበተው ከ20/9/2004 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ ለአምስት የስራ ቀናት ከስራ የጠፋ ስለሆነ ምክንያቱና ማስረጃውን በወቅቱ ባለማቅረቡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1//ለ/ የስራ ውል ማቋረጥ ሕጋዊ ነው፡፡ የስራ ስንብት ክፍያ አይመለከተውም በአዲሱ ድርጅትም 5 አመት አላገለገለም፡፡ የማስጠንቀቂያ ክፍያም አይገባውም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረ ደመወዝ የለውም፣ በአንዛሩ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ከስራ በመቅረቱ የአንድ ወር ደመወዝ በካሳ መልክ እንዲከፍል እንዲወሰን በማለት አቅርበዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ከስራ የቀረበት በቂ ምክንያት የማቅረብ ሕጋዊ ግዴታ እንዳለበት የሕክምና ማስረጃ ለተጠሪ አስተዳደር የስራ ክፍል መስጠቱን፤ ከታመመ በኋላ ተመልሶ ስራ መጀመሩን የተከራከረ ቢሆንም አላረጋገጠም፤ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው፡፡ ክፍያ በተመለከተ ከ5 አመት በላይ በማገልገሉ እንዲሁም ክፍያው በወቅቱ ባለመፈፀሙ የአገልግሎት ክፍያ 36,660 እና ቅጣት 10,998 በድምር 47,658.00፣ የጠበቃ አበል 10% ወጪና ኪሳራ 500.00 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም የይግባኝ ቅሬታው ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ አመልካች የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ካከራከረ በኋላ አመልካች በራሱ ፍላጎት 5 አመት ካገለገለ በኋላ መልቀቁን ያልተረጋገጠ መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች ሽሮ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያ ይሁን ክፍያ ለዘገየበት ተብሎ የሚከፈለው ነገር የለም ብሎዋል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተለዋውጧል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ነጥብ፡- በተጠሪ ድርጅት ለረጅም ዓመታት አገልግሎት የአገልግሎት ክፍያ አይገባውም መባሉ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2/ሸ/ ያላገናዘበነው የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ ለ5 ቀናት ከስራ በመቅረቱ ምክንያት ከስራ በመሰናበቱ የአገልግሎት ይሁን ክፍያ ዘገየበት ለተባለው ጊዜ የሚከፈለው ነገር የለም ተብሎ መወሰኑ የአዋጁን መንፈስ የተከተለ ነው የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ በአመልካች የቀረበው የመልስ መልስም አቤቱታውን የሚደግፍ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር፤ ለሰበር ችሎት መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እንዲሁም ጉዳዩ በሰበር ይመርመር ተብሎ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመርነውም አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው መሰረታዊ ጭብጥ የሰራተኛውን በተከታታይ ለ5 ቀናት ከስራ መቅረት ተከትሎ የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በአመልካች የቀረበው የክፍያ ጥያቄ ሕጋዊ መሰረት ያለው መሆን ያለመሆኑን ነው። አመልካች በሕመም ምክንያት ከስራ የቀረ ቢሆንም ከሕመሙ አገግሞ ወደ ስራ እንደተመለሰ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ያለ በቂ ምክንያት ለተከታታይ 5 የስራ ቀናት ከስራ በመቅረቱ በሕጉ አግባብ ከስራ ተሰናብቷል የሚል መልስ አቅርበዋል። በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ፍ/ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ አመልካች ለተከታታይ 5 የስራ ቀናት ከስራ የቀረበት በቂ ምክንያት ስለመኖሩ አላስረዳም የሚል ነው። አመልካች ከስራ የቀረበት ምክንያት በጤና እክል ስለመሆኑ በቅሬታ ከመግለፅ ውጪ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር መጣራትና ማስረጃ ምዘና እና ድምዳሜ ተገቢ አለመሆኑን ስልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማስቀረብ የሻረ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም። የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር እና ማስረጃ ምዘና ስርዓት እና ድምዳሜ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በድጋሚ የሚመረመር ባለመሆኑ እንዳለ የምንቀበለው ነው። ምክንያቱም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ጉዳዮችም መርምሮ ማረም ስለመሆኑ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80/3//ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 መሰረታዊ ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳነው ነው። በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ አመልካችን ያለበቂ ምክንያት ተከታታይ 5 የስራ ቀናት ከስራ መቅረቱን በማረጋገጥ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ እንዲሰናበት መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1//ለ/ መሰረት ያደረገ ነው።

የአመልካች የስራ ስንብት በሕጉ አግባብ የተደረገ መሆኑ ከተረጋገጠ ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለተሰናበተ ሰራተኛ የአገልግሎት ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት በቅጣት መልክ የ3 ወር ደመወዝ ሊከፈል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው ነው። በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው አመልካች ለተከታታይ 5 የስራ ቀናት በስራ ገበታው ባለመገኘቱ ያለማስጠንቀቂያ ነው። አመልካች ያለማሰጠንቀቂያ ከስራ ቢሰናበትም የአገልግሎት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው አጥብቆ እየተከራከረ ነው። አንድ ሰራተኛ ከስራ ከተሰናበተ በኋላ የአገልግሎት ክፍያ ከሚያገኝባቸው ሕጋዊ ምክንያቶች አንዱ በድርጅቱ ከ5 አመት በላይ አገልግሎት በገዛ ፈቃዱ ስራ መልቀቁን ሲረጋገጥ ብቻ ነው። የአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2/ሸ/ "ቢያንስ አምስት አመት በአሰሪው ዘንድ የስራ አገልግሎት ኖሮት በሕመም ወይም በሞት የስራ ውሉ ሲቋረጥ ወይም ስራው ከስልጠና ጋር የተያያዘ ለአሰሪው የውል ግዴታ ሳይኖርበት ስራው በገዛ ፈቃዱ" የለቀቀ የአገልግሎት ክፍያ እንደሚያገኝ ደንግጎአል። በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከስራ የለቀቀው በገዛ ፈቃዱ /on his own initiative/ ሳይሆን አሰሪው ያለማሰጠንቀቂያ ከስራ ስለአሰናበተው ነው። አመልካች ከስራው በገዛ ፈቃዱ የለቀቀ መሆኑ ካልተረጋገጠ ደግሞ የስንብት ክፍያ የሚያገኝበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም። በተያያዘ ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁ 25511 እና ሌሎች መዝገቦች አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የስር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች ስራውን በገዛ ፈቃዱ አለመልቀቁን በማረጋገጥ የስራ ስንብት ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሻሩ ሕጉን በአግባቡ ተርጉሟል ከሚባል በስተቀር በጉዳዩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አያሳይም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች የፈፀሙት ስህተት ማረሙ በአግባቡ በመሆኑ ጉዳዩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው ለማለት የሚችል ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 181962 በ2/06/2007 ዓ.ም የስር የአዳማ ልዩን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 18244 በ08/09/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በመሻር፤ የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 73239 በ30/07/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ በድምፅ ብልጫ ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው ያለማስጠንቀቂያ መሆኑ በመረጋገጡ በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2/ሸ/ የተመለከተው ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት አይመለከተውም ተብሎ መወሰኑ በሕጉ አግባብነት ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ያወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 116002

ቀን 6/3/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

መ.ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- የአንቦ የገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩንየን አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ጨመዳ መገርሳ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር የአሁኑን አመልካች የአንቦ የገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩንየን በቀን 13-11-2007 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የኤሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 202963 በቀን 29-10-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ቅሬታውም የስር ፍ/ቤት የ12 ወር ውዝፍ ደሞዝ ለከሳሽ /ለአሁን ተጠሪ/ሊከፍለው ይገባል ብሎ ቢወስን ምንም ነገር ማሳመኛ ምክንያት ሳይጠቅስ ነው፡፡ ከሳሽ / የአሁን ተጠሪ/የአሁን አመልካች ንብረት መጥፋቱን ባልካደበትና የአሁን አመልካች ተጠሪ ወደ ስራ እንዳይመለስ ተከራክሮ እያለ አመልካች የተጠሪን ወደ ስራ መመለስ አልቃወምም ብሏል በማለት ወደ ስራ እንዲመለስ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፡፡፡ ውዝፍ የዓመት ዕረፍት ለተቋረጠ የስራ ውል የሚከፈል እንጂ በህጉ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 77/5/ መሠረት ወደ ስራ እንድመለስ ለተወሰነ ሠራተኛ አይደለምና በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች የወሰደው የስንብት እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያ ተከፍሏቸው ወደ ስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይመለሱ የመባሉን አግባብነት ከሰበር ውሳኔ መ.ቁ.106371 አንፃር ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስ ተሰጥቶበታል፡፡

የአሁን ተጠሪ በቀን 14 12 2007 በተፃፈ መልስ አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ቅሬታና ሙሉ ሃሳብ እንዲሁም የተያዘው ጭብጥ በዚህ ችሎት የሚታይ ስህተት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 183802 በቀን 22-3-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ እና ወደ ስር ፍ/ቤት በተመለሰው ላይ የአሁን አመልካች በወቅቱ ይግባኝ ያላለበት በመሆኑ አሁን እንደ ቅሬታ ልያነሳ አይችልም፡፡ አመልካች የአሁን ተጠሪን የዓመት ፋቃድ 76 ቀን መሆኑንን አልካደም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ቅር የሚያሰኝ ባለመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይሁንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁን አመልካችም በቀን 29/12/2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የቀረበውን አቤቱታ በማጠንከር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 183802 ወደ ስር ፍ/ቤት በውሳኔ የመለሰው የይርጋን ጉዳይ ጭብጥ ይዞ በመሆኑ ይርጋን በበተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ አይደለምና አሁን ቢነሳ ስህተት አይደለም፡፡ ተጠሪ ጥፋት መፈፀሙ እየታወቀ ወደ ስራ እንዲመለስ መወሰኑ ስህተት በመሆኑ ልታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

በዚሁ መሠረት መዝገቡን እንደመረመርነው ክርክሩ የጀመረው ከኦሮሚያ ክ/መ/የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ አቶ ጨመዳ መገርሳ ያቀረበው ክስ በተከሳሽ የአምቦ ገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒየን ተቀጥሬ እየሰራሁ ሳለ ያለምንም ጥፋት በሕግ ወጥ መንገድ ከሥራ ስላሰናበተኝ ወደ ኪራዩ እንዲመልሰኝ ካልሆነ ከሕግ ውጭ ከስራዬ ያሰናበተኝ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ሊከፈለኝ የሚገባ ክፍያዎች እንዲከፍለን በማለት አቅርቧል፡፡ ተከሳሽም/ የአሁን አመልካች/ በሰጠው መልስ ከሳሽ የሥራ ድርሻውን የጥበቃ ስራ ባግባቡ ባለመወጣቱ በ29-11-2005 ዓ.ም የተሸከርካሪ ሞተርም ስለተወሰደና በተከሳሽ መ/ቤት ላይ ጉዳቱ ስላደረሰ ከስራ ተሰናብቶአልና የስራ ውሉ የተቋረጠው ህጋዊ ነውና ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በማለት ተከራክሏል፡፡

የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤትም በመ.ቁ. 35655 አከራክሮ በቀን 7-5-2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ይርጋን በተመለከተ ጥፋት መፈፀሙ ከታወቀበት ከቀን 29-11-2005 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሉ መቋረጡን ደብዳቤ እስከተፃፈበት ቀን 8-1-2006 ዓ.ም ድረስ ሲቆጠር 31 የስራ ቀናት /ሆኗል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ መሠረት በይርጋ የታገደ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም ጥፋት ተፈፅሞ ከሥራ ማሰናበት ከሚገባበት ጊዜ ካለፈ በኃላ ተከሳሽ ከሳሽን ከሥራ ያለማስጠንቀቂያ ያሰናበተው በመሆኑ ህገ ወጥ ነው ብሎ ከሳሽ ወደ ስራ እንዲመለስና የደሞዝ መክፈያ ከተቋረጠበት ጊዜ ደምሮ ውዝፍ እንዲከፈለው በማለት ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የምዕ/ሸዋ ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 02963 በቀን 4-6 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 183802 በቀን 22-8-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት አጣርቶ እንዲወሰን በውሳኔ የመለሰለት መሆኑን ገልፃ የሰጠው ፍርድ ግራና ቀኝ ተከራካሪዎች ይግባኝ ባይ /ከሳሽ/ ወደ ስራ ይመለስ በሚለው ውሳኔ ላይ ክርክር ወይም ተቋውሞ የላቸውም ሊከፍለው የሚገባ ውዝፍ ደሞዝና የአመት እረፍት ክፍያን በተመለከተ ውዝፍ ደሞዝ በማስላት የ12 ወራት ብር 22,080 የ76 ቀን የዓመት ዕረፍት ብር 4657.50 በአጠቃላይ ብር 26737.50 ለከሳሽ ይከፈለው ከሳሽ ወደ ሥራ ይመለስ ብሎ ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች አቤቱታ አቅርቦ በመ.ቁጥር 202963 አከራክሮ በቀን 29-10-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ አመልካች ለክርክሩ ተጠሪ የዓመት ዕረፍት እንደሌለው አልተከራከረም፡፡ በመሆኑም የዓመት ዕረፍትን በተመለከተ ሕጉ አዋጅ 377/96 የዓመት ዕረፍት ከሁለት ቀጣይ ዓመታት በላይ ማስተላለፍ አይችልም ይላል ይህ ማለት ተጠሪ ከ2006 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም የዓመት ዕረፍት ተደምሮ ሊከፈለው ይገባል በመሆኑም የተጠሪ 76 የዓመት እረፍት ቀናት ከህጉ ጋር የሚጋጭ አይደለም፡፡ ውዝፍ ደሞዝ በተመለከተ ወደ ስራ ይመለስ የተባለ ሠራተኛ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተከራክሮ ከተወሰነ የ12 ወር ውዝፍ ደሞዝ ስለሚከፈለው የስር የምዕ/ሸዋ/ከፍ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ፀንቷል፡፡ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር ምክንያት የሆነው የክርክር ጭብጥ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 183802 በቀን 22-3-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የመከራከሪያ ጭብጥ በመያዝ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ የመለሰውና እንዲጣራ ጭብጥ ተይዞ የተመለሰውም የአሁን ተጠሪ ወደ ሥራ ይመለስ ወይስ አይመለስ በሚለውና አይመለስ ከተባለ ስለሚከፈለው ክፍያ በተመለከተ ነው፡፡ በመሆኑም ስለ ከሥራ ማሰናበት ሕጋዊነት ወይም ሕገወጥነት እና የይርጋ ጉዳይ የጭብጡ አካል አይደሉም፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍርድ የታለፈን ጉዳይና ለከፍተኛው ፍ/ቤት ጭብጥ ያልሆነውን የይርጋ ጉዳይ አሁን በአቤቱታ ሊያንሱ የሚችሉበት የህግ መሠረት የለም፡፡ የአሁን ተጠሪ ወደ ስራ ይመለስ ወይስ አይመለስ የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የተጠሪን ወደ ሥራ መመለስ የተስማማ መሆኑን አረጋግጦ የወሰነ መሆኑን ከተሰጠው ፍርድ ላየ መገንዘብ የሚቻል ነው የስር ፍ/ቤት ውሳኔዎችን ከህግ ወጪ ከስራ የተሰናበተ ሠራተኛ ወደ ስራ ሲመለስ ሊከፍሉት የሚገቡ ክፍያዎች የዓመት እረፍትና ያልተከፈለ ውዝፍ ደሞዝን በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ እና አንቀጽ 79/5/ መሠረት ተሰልቶ የተወሰነው ክፍያ ስህተት ያለበት አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ የሚደነግገው የአሁን አመልካች እንደሚከራከረው ውዝፍ ያልተከፈለ ደሞዝ ከሥራ ስለተሰናበተ ሰራተኛ የሚከፈል ሳይሆን ወደ ሥራ እንዲመለስ ለተወሰነበት ሰራተኛ ነው፡፡ ውሳኔውም ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ወደ ስራው ይመለስ ውሳኔ ከፀና እስከ አንድ አመት ውዝፍ ደሞዝ እንደሚከፈል ይገልፃል፡፡ የአመት ፍቃድ ክፍያንም በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንድ 79/5/ የዓመት እረፍት ከሁለት ቀጣይ ዓመት በላይ እንጅ እስከ ቀጣይ ሁለት ዓመት ማስተላፍን የሚከለክል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከህግ ወጪ ከስራ የተሰናበተ መሆኑን አረጋግጦና የተጠሪ"ን ወደ ሥራ መመለስ የአሁን አመልካች የተስማማበት መሆኑን በማየት መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ እና 79/5/ መሠረት ወደ ሥራ ለሚመለስ ሠራተኛ የሚከፈለውን ያልተከፈለ ውዝፍ ደሞዝና የዓመት ዕረፍት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35655 በቀን 7-5 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 02963 በቀን 4-6-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 202963 በቀን 29-10-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ውጪና ኪሳራ ተቻችሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.117076

ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፉ አህመድ

ተፈሪ ተብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት የቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ ነ/ፍጅ ብሩክ ታፈነ ቀረቡ ወክልና አያያዝ

ተጠሪ፡- አቶ ዮሐንስ ብዙነህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብት ክፍያ ጥያቄን አስመልክቶ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ከሳሽ በ14/02/2007 ዓ.ም. ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከ17/08/2005 ዓ.ም. ጀምሮ በወር ብር 4,699 እየተከፈላቸው በሳይት መሀንዲስነት በመስራት ላይ እያሉ ተከሳሽ ድርጅት የስራ ውላቸውን ከሕግ አግባብ ውጪ ያቋጠባቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸው እና ተዛማጅ ክፍያዎች አግባብነት ባላቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች መሰረት በድምሩ ብር 77,219 (ሰባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ሺህ) እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ08/03/2007 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ከሳሽ የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት ሊስተናገድ የሚገባው አይደለም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካስቀደመ በኃላ በፍሬ ጉዳዩ ረገድም የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ እና በየሶስት ወሩ የሚታደስ መሆኑን፣እያንዳንዱ ወገን የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል በውሉ የተመለከተ መሆኑን፣ውሉ የተቋረጠውም ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሱ በርካታ ጥፋቶችን መፈጸማቸውን ተከሳሽ ገምጋሚ ቡድን ወደ ቦታው በመላክ በማረጋገጡ መሆኑን በመግለጽ ክሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የመቃወሚያ ነጥቡን በብይን አልፎ እና በፍሬ ጉዳዩ ላይ ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የስራ ውሉ የኮንትራት ውል መሆኑን፣የስራው ባህርይም የሚያልቅ መሆኑን እና ከሳሽ ስራቸውን በአግባቡ እንደማያከናውኑ የተከሳሽ ምስክሮች ያስረዱ መሆኑን ገልጾ የስራ ውሉ በሕግ አግባብ የተቋረጠ በመሆኑ ተከሳሽ ድርጅት ለከሳሽ የሚከፍለው ክፍያ የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ ያሰናበተው ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ከሳሽ የስራ መሪ ስለመሆናቸው ተከሳሽ ድርጅት በማስረጃነት ያቀረበው የስራ መዘርዝርም ሆነ የስራ ውል የሚያረጋግጡ ባለመሆኑ በተከሳሽ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በስር ፍርድ ውድቅ የተደረገው በአግባቡ መሆኑን፣የስራ ውሉ የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ስለመሆኑ ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 10 (1) ድንጋጌ መሰረት ያላስረዳ መሆኑን እና በከሳሽ ተፈጽመዋል የተባሉት ጥፋቶች በአዋጁ አንቀጽ 28 (1) ስር የሚሸፈኑ ካለመሆኑም በላይ ተከሳሽ ድርጅት ለእነዚህ ጥፋቶች እርምጃ ሲወስድ የነበረ ስለመሆኑ የተገለጸ ነገር አለመኖሩን ገልጾ ተከሳሽ ድርጅት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት የወሰደው የስንብት እርምጃ ሕገወጥ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ በስር ከሳሽ የተጠየቀውን የክፍያ ዓይነት እና መጠን አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመመለስ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው የስራ መሪ ናቸው በማለት አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የማጣቱን አግባብነት ከተጠሪው የስራ መዘርዝር አንጻር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. ተጠሪው የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት የተስተናገደው አላግባብ ነው በማለት አመልካች ያቀረበው እና ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው የክርክር ነጥብ በዚህ ችሎት ሊስተናገድ የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም በማለት ተጠሪው ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. ተጠሪው የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት ሊስተናገድ የሚገባው አይደለም በሚል አመልካች ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ተደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪው የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት የተስተናገደው አላግባብ ነው በማለት አመልካች ያቀረበው እና ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው የክርክር ነጥብ በዚህ ችሎት ሊስተናገድ የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም በማለት ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ተከራክረዋል፡፡በመሰረቱ አመልካቹ ይህንን የክርክር ነጥብ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊያቀርብ የቻለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በጭብጥነት ይዞ ውሳኔ ያሳረፈው በዚህ የክርክር ነጥብ ላይ ጭምር በመሆኑ ነው፡፡ተጠሪው የስራ መሪ አይደሉም ተብሎ በወረዳ ፍርድ ቤት በተሰጠው ብይን ላይ አመልካች በወቅቱ ያቀረበው ይግባኝ ሳይኖር ተጠሪው ባቀረቡት አቤቱታ ሳቢያ አመልካች ይህንን የክርክር ነጥብ በክልል ሰበር ደረጃ ማንሳቱ ስነ ስርዓታዊ አይደለም የሚሉ ከሆነ ተጠሪው የዚህ ዓይነት መከራከሪያ ማቅረብ የነበረባቸው በክልሉ ሰበር ችሎት እንጂ በዚህ የሰበር ደረጃ አይደለም፡፡የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር መልስ አቅርቦ የተከራከረ አንድ ተከሳሽ ወገን መቃወሚያው ውድቅ ተደርጎበት ነገር ግን ክርክሩን በሚሰማው ፍርድ ቤት በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ተጠቃሚ ከሆነ አቅርቦት የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ ብቻ ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችልበት አግባብ ካለመኖሩም በተጨማሪ ከሳሽ ወገን ለበላይ ፍርድ ቤት በሚያቀርበው ይግባኝ እና አቤቱታ ላይ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውድቅ የተደረገበትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተጨማሪ መከራከሪያነት ከማቅረብ የሚከለክለው ነገር ባለመኖሩ ተጠሪው የስራ መሪ ናቸው የሚለውን የመከራከሪያ ነጥብ አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ አንስቶ ሊከራከር የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም በማለት ተጠሪው ያቀረቡት መከራከሪያ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈጻሚነት የሚኖረው በአዋጁ አንቀጽ 2 ስር የተመለከቱትን ሳይጨምር በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሰረተ የስራ ግንኙነት ላይ ስለመሆኑ በአንቀጽ 3 (1) ስር የተደነገገ ሲሆን የአዋጁ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚደረጉበት የስራ ውል ተቋቁሟ የሚባለውም ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአሰሪው ለመስራት በተስማማ ጊዜ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 2 (3) እና 4 (1) ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡

በሌላ በኩል የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈጻሚ ከማይሆንባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የስራ መሪን አስመልክቶ በሚደረግ የስራ ውል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 (በአዋጅ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

494/1998 እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 3 (2) (ሐ) ስር የተመለከተ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ በተሰጠው ትርጉም መሰረትም የስራ መሪ ማለት በሕግ ወይም እንደ ድርጅቱ የስራ ፀባይ በአሰሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሰረት የስራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣት እና የማስፈጸም ከነዚሁ በተጨማሪ ወይም እነዚህኑ ሳይጨምር ሰራተኞን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ የማገድ፣የማሰናበት፣የመመደብ ወይም የስነ ስርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውን እና የሚወስን ግለሰብን የሚመለከት እና እንዲሁም እነዚህን የስራ አመራር ጉዳዮች አስመልክቶ የአሰሪውን ጥቅም ለመጠበቅ አሰሪው ሊወስድ ስለሚገባው እርምጃ በራሱ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ የሕግ አገልግሎት ኃላፊንም የሚጨምር ነው።ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ተጠሪው የስራ መሪ ስለሆኑ ጉዳያቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 እና በስራ ክርክር ችሎት የሚታይ አይደለም በማለት አመልክች ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ ያልገለጸ ቢሆንም የክልሉ ሰበር ችሎት ግን በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ ሳይቀበል የቀረው የተጠሪው የስራ መዘርዝር እና የግራ ቀኙ የስራ ውል ይዘት ተጠሪው የስራ መሪ ናቸው የሚያሰኝ የስራ ኃላፊነት የተሰጣቸው መሆኑን አያመለክትም በማለት ነው።

ተጠሪ በመሰረቱት ክስ ላይ የስራ መደባቸው ሳይት መሀንዲስ እንደሆነ አድርገው የገለጹ ቢሆንም በቀጣይ የክርክር ሂደት ሳይት መሀንዲስ ሳይሆኑ አመልካች ድርጅት በሆሳዕና ከተማ የሚያከናውናቸውን አራት ፕረጀክቶች በበላይነት የመምራት የስራ ኃላፊነት ያላቸው የፕሮጀክት መሀንዲስ መሆናቸው ተረጋግጦአል።ተጠሪነታቸውም ለአመልካች ድርጅት የኮንስትራክሽን መምሪያ መሆኑን የስራ መዘርዝራቸው ያመለክታል። የተጠሪው የስራ መዘርዝር በስሪ መሪ የሚከናወኑ ተግባራትን የማከናወን የስራ ኃላፊነት እንዳላቸው የሚያመለክት አይደለም የሚባል ካለመሆኑም በተጨማሪ በድርጅቱ የስራ መመሪያ መሰረት ተጠሪው የፕሮጀክቶቹ ማኔጅመንት ኮሚቴ የበላይ ኃላፊ በመሆን የሰው ኃይል፣የፋይናንስ፣የንብረት ግዢ እና አስተዳደር ጉዳዮችን በበላይነት የማስተዳደር እና የመምራት፣የባንክ ሂሳብ የማንቀሳቀስ፣ ለፕሮጀክቶቹ አስፈላጊ የሆነውን የሰው ኃይል የመቅጠር፣ማገድ እና የማሰናበት ስራዎችን ጨምሮ በስራ መሪ የሚከናወኑ ናቸው የተባሉትን ተግባራት የማከናወን ኃላፊነት የነበራቸው ስለመሆኑ አመልካች በሰበር አቤቱታው ላይ በዝርዝር ላቀረበው ክርክር ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ያቀረቡት ግልጽ የማስተባበያ ክርክር አለመኖሩን ተገንዝበናል።አንድ ሰራተኛ የስራ መሪ ሆኖ የሚቆጠረውም የሚያከናውናቸው ተግባራት እንደየድርጅቱ የስራ ፀባይ እየታየ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 (በአዋጅ ቁጥር 494/1998 እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 3 (2) (ሐ) ስር ተመልክቷል።ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት በማከናወን ተጠሪነታቸው ለአመልካች ድርጅት የኮንስትራክሽን መምሪያ ሆኖ ድርጅቱ በሆሳዕና ከተማ የሚያከናውናቸውን አራት ፕሮጀክቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በበላይነት የሚመሩ መሆኑ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ ደግሞ ተጠሪው ክላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት የስራ መሪ ናቸው ሊባሉ የማይችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡የስራ መሪ ከሆኑ ደግሞ ተጠሪው ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት ሊስተናገድ የሚገባው አይሆንም፡፡

ሲጠቃለል በአመልካቹ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርገው ተጠሪው ያቀረቡትን ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት በማስተናገድ በስር ፍርድ ቤቶች በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 29077 በ02/07/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ፣በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17538 በ30/07/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 65144 በ01/12/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በሙሉ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪው የስራ መሪ በመሆናቸው ክሱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት የተስተናገደው በአግባቡ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117517

ቀን ጥር 30/2008ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ሬድ ፎክስ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረበም

ተጠሪ፡- ወ/ት ጀላኔ ጌታቸው - ከጠበቃ መስታውት አሸናፊ ጋር - ቀርበዋል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ የተነሳውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ሲጀመር ከሳሽ የነበረችው ተጠሪ ናት፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው የስራ ውል ከሕግ ውጪ አቋርጠዋል በማለትነው፡፡ በዚህ መሰረትም ልዩ ልዩ ክፍያዎችን እንዲከፈላት ጠይቃለች፡፡

በአመልካች ድርጅት ተመድቤ የምሰራበት ሥራ ከኬሚካል ንኪኪ ያለው በመሆኑ ለሰራተኛው በየጊዜው ምርመራ ይደረጋል፡፡ በመጀመሪያ የተወሰደው የደም ናሙና ውጤቱ የደም ጥራት መጠን በታች በመሆኑ ለሶስት ወር ከኬሚካል ጋር ግንኙነት በሌለበት ሥራ እንዲያዛውር በባለሙያ የተሰጠው አሰተያየት ከአንድ ወር በላይ በመደበቅ ውጤቱ አውቄ ራሴን እንዲጠናቀቅ አልቻልኩም፡፡ ወደ ሌላ ስራ አላዘወረችኝም፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የደም ናሙና ተወስዶ ውጤቱ እንዲያሰውቀኝ ብጠይቅም ምላሽ አልሰጠኝም፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 32/1/ለ/ መሰረት ከመስከረም 5 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ ስራዬን ለማቋረጥ ተገድጃሎህ፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ሕገ ወጥ ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እና ማስረጃዎች እንዲሰጣት እንዲወሰንላት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡

የአሁኑ አመልካች መከላከያ መልሱን እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ በገዛ ፍቃድዋ ሥራውን ያቋረጠች እንጂ በአመልካች ምክንያት ወይም በህገ ወጥ መንገድ አይደለም፡፡ የመጀመሪያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምርመራ ውጤት መሰረት ወደ ሌላ ስራ ተዛውራ እንድትሰራ ተደርገዋል፡፡ በሁለተኛ የደም ናሙና ውጤቱ ወደ ኖርማል የተመለሰ በመሆኑ ወደ ቀድምዋ ስራ ተመልሳለች፡፡ ከተሰናበተች በኋላ የ3ኛው የደም ናሙና ምርመራ ውጤት ከጤነኛ ደም ሬንጅ ውስጥ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ የ30 ቀን ማስጠንቀቅያ ሳትሰጥ የለቀቀች ስለሆነ የ30 ቀን ደመወዝ በመቀነስ እንድትሰናበት የተደረገው፡፡ ስለሆነም የቀረበው ክስ የህግ መሰረት የለውም ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መልሳቸውን አቅረበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማና ከመረመረ በኋላ የስራ ወሉ የተቋረጠው ከሕጉ ውጭ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎችን በድምሩ ብር 59,103 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት ስላላገኘ ይግባኙን ሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ነሀሴ 21 ቀን 2007 ዓ/ም በዓፈው ማመልከቻ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟአል የሚልበትን ምክንያት በመግለፅ አቤቱታውን አቅርበዋል፡፡ አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪ እንዲቀርብ በማድረግ ክርክራቸውን በዕሁፍ አቅርቧል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስሕተት ነው የሚልበት የስራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ እንጂ በአመልካች አይደለም፡፡ በመጀመሪያው በተደረገው ምርመራ ውጤት ዝቅተኛ የነበረ ቢሆንም ከዚያ በኋላ የተደረጉት ምርመራ ውጤት ጤነኛ መሆኑን በመረጋገጡ አመልካች ለተጠሪ አደጋ የሚጥል ሁኔታ እንዲትሰራ አላደረገም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 12 ግዴታው አልተወጣም የሚያሰኝ ሁኔታ ሳይኖር ሕገ ወጥ መባሉ አግባብነት የለውም የሚል ነው፡፡ በተጠሪ በኩል ደግሞ ስራውን ለመቋረጥ የተገደድኩት ለጤነንቱ ስል ነው፡፡ የምርመራ ውጤት ከአንድ ወር በላይ በመደበቅ፤ ከኬሚካል ነፃ የሆነ ሰራ ለሶስት ወር እንድሰራ በባለሙያ የተገለፀው ባለመፈፀሙ፤ ሁለተኛው ምርመራ ውጤት በዕሑፍ ብጠይቅም ምላሽ አልሰጠኝም፡፡ ይህ ደግሞ አመልካች ግዴታውን አልተወጣም በማለት የተሰጠ ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡

በአመልካችና ተጠሪ የተደረገው የስራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት መብትና ግዴታ ያቋቁማል፡፡ በሕጉ አንቀጽ 12 የአሰሪው ግዴታ በአንቀጽ 13 ደግሞ የሰራተኛው በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ሕገ ወጥ ድርጊት የተባሉት የአሰሪና ሰራተኛ በቅደም ተከተል በአንቀጽ 14 /1/ እና 14/2/ በዝርዝር ሰፍሮ ይገኛል፡፡ የአሰሪው ግዴታ ከተገለፁት 12/4/ ከስራው ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያያዘ ሰራተኛውን ደኅንነትና ጤንነት ለመጠበቅና ከአደጋ ለመከላከል የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች ሁሉ የመውሰድና እነዚሁንም እርምጃዎችን በሚመለከት ረገድ አግባብ ባላቸው ባለስልጣኖች የሚሰጡትን ደረጃዎችን መመሪያዎች የመከተል በአሰሪው ግዴታ ላይ የጣለ ነው፡፡ በሌላ በኩል አሰሪውና ሰራተኛው ሕገ ወጥ ድርጊት ተብለው ከተገለፁት ውስጥ በሕጉ አንቀጽ 14/1/ሠ/ በአሰሪው ሰራተኛውን በሕይወቱ ላይ አደጋ ሊያደርስበት በሚችል አኳኋን እንዲሰራ ማድረግ ሕገወጥ ድርጊት መሆኑን የተመለከተ ነው፡፡አሰሪው ግዴታውን ካልፈፀመና ሕገ ወጥ ድርጊት መፈፀሙ ከተረጋገጠ ሰራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉ ማቋረጥ በቂ ምክንያት ይሆናል በማለት በአንቀጽ 32/1/ለ ይደነግጋል፡፡ ይህን ከተረጋገጠ ደግሞ ሰራተኛው በአዋጁ መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን ከአሰሪው የማግኘት መብት አለው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች ክርክር በአንቀጽ 32/1/ለ የተመለከቱትን ሳይሟላ የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ ሊሻር ይገባል ሲል፤ በተጠሪ ደግሞ በማስረጃ የተረጋገጠና በአግባቡ የተወሰነ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ እንደሚያመለክተው አመልካች ለሰራተኞቹ በየሶስት ወር ምርመራ እንደሚያደርግ ግልፅ ነው፡፡ እዚህ ላይ አከራካሪ የሆነው ውጤቱ ከሚመለከተው አካል በወቅቱ ማምጣት፤ እንደመጣም በጊዜ መግለፅ እና በውጤቱ መሰረት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ በፍሬ ጉዳይ የማጣራትና የየመመዘን ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት የተጠሪ የምርመራ ውጤት እንድታውቅ የተደረገው ዘግይቶ መሆኑ፤ ከኬሚካል ንኪኪ ነፃ በሆነ ስራ ለሶስት ወር እንዲሰሩ አለማድረጉ እና ውጤት በወቅቱ ሂዶ አለማምጣት የተደጋገመ ድርጊት መሆኑን የአመልካች ክሊኒክ ሓላፊ የሰጡት የምስክርነት ቃል ውጤት ሂዶ በወቅቱ የማይመጣው ትራንስፖርት የለም እየተባሉ እንደሆነ፤ የተጠሪ የምርመራ ውጤት መሰረት በሌላ ስራ እንዲመደቡ የሰጡት ምክር ተቀባይነት እንደለገኘ፤ የነርቭ ችግር እንደሚያስከትል፡፡ የተጠሪ የደም ናሙና ሶስት ተወስዶ ዝቅተኛ ስለሆነ ወደ ጤነኛ ተመልሰዋል ለማለት የሚቻለው ሶስት ጊዜ ምርመራ ከተደረገ በኋላ የሚረጋገጥ እንጂ በአንድ በሁለት የተደረገ ምርመራ ውጤት ጤነኛ ነው ለማለት እንደማይቻል ሙያዊ ምስክርነታቸው ሰጥተዋል፡፡

አመልካች ምርመራ እንዲደረግ ማድረጉ ብቻ በቂ ነው ግዴታውን ወጥቷል የሚያሰኝ አይደለም፡፡ ከምርመራ በኋላ በተገኘው ውጤት መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ ከመውሰድ ላይ ነው፡፡ በትራንስፖርት ምክንያት በወቅቱ አለማምጣት፤ ከመጣም በኋላ በባለሙያ የተሰጠ ምክር ተግባራዊ አለማድረጉ ግዴታው አለመወጣቱና ለጉዳዩ ትኩረት ያለሰጠው መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስሕተት ያለበት ሆኖ ተገኝተዋል፡፡ በዚሁ መሰረትም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 15958 በቀን 11/09/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሰጠ ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 168399 በቀን 29/11/2007 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ከዚህ በፊት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስተዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 119734

የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ተብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- ይርጋ ትራዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ብዙነህ መኮንን
2. አቶ ሻምበል አሰፋ } ጠበቃ እስጢፋኖስ ተስፋ ቀረቡ
3. አቶ ረድኤት መሐመድ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብት እርምጃን በመቃወም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርጎ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በአዳማ ልዩ ዞን በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሾች የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾቹ በ16/10/2007 ዓ.ም. ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ከሳሾቹ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከተለያየ ጊዜ ጀምሮ በተለያየ የስራ መደብ የተለያየ መጠን ያለው ደመወዝ እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እያሉ የድርጅቱ ባለቤት ተከሳሽ ድርጅትን ሸጠው ተከሳሽ ድርጅት ለከሳሾቹ ሌላ ስራ ሳይሰጥ ወይም ተገቢ ክፍያዎችን ሳይከፍል አላግባብ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ የስንብት እርምጃው ሕገወጥ ነው ተብሎ ሕገወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸው እና ተያያዥ ክፍያዎች በአዋጁ መሰረት ተሰልቶ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ02/11/2007 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ከሳሾቹ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው ድርጅቱ በመሸጡ እና የሚመደቡበት ሌላ የስራ ቦታ ባለመገኘቱ መሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ከሳሾቹ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው ድርጅቱ በመሸጡ ምክንያት ቢሆንም ተከሳሽ ደርጅት ይህንኑ በመግለጽ ለከሳሾቹ አስቀደሞ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ከዛሬ ጀምሮ ስራ የለም በማለት ከሳሾቹን በቀጥታ ማሰናበቱ ሕገወጥ መሆኑን ገልጾ ተከሳሽ ድርጅት ለእያንዳንዱ ከሳሽ በውሳኔው ላይ ተለይቶ በተገለጸው መጠን ሕገ ወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸው እና ተያያዥ ክፍያዎችን ከአስር በመቶ የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይዘቱ ከላይ የተመለከተውን የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በትዕዛዝ በማጽናታቸው የሶስቱም ስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ድርጅት ተሸጦ ንብረትነቱ ለዘለቄታው ወደ ሌላ ሰው መተላፉ እና ተጠሪዎቹን ወደ ሌላ ስፍራ አዛውሮ ለማሰራት የሚችል መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪዎቹ የማስጠንቀቂያ እና የስንብት ክፍያ የሚያገኙ ከሚሆን በቀር ለተሸጠ ድርጅት ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ የካሳ ክፍያ እንዲከፈላቸው የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ ጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቹ ከስር ጀምሮ የሚከራከረው ተጠሪዎቹ ይሰሩበት የነበረው ድርጅት የተሸጠ እና ለሶስተኛ ወገን የተላለፈ በመሆኑ ምክንያት የስራ መደባቸው የተሰረዘ በመሆኑ ተጠሪዎቹ የተሰናበቱት በሕግ አግባብ መሰረት ነው በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡በመሰረቱ ተከሳሽ ድርጅት “ይርጋ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር” በሚል የሚታወቅ ሲሆን የተሸጠውም ይኸው ማህበር በባለቤትነት ከሚያስተዳድራቸው ንብረቶች መካከል አንዱ የሆነው እና ተጠሪዎቹ ሲሰሩበት የነበረው በአዳማ ከተማ የሚገኝ መጋዘን ነው፡፡

በመሆኑም የተሸጠው ተከሳሽ ድርጅት በአጠቃላይ ወይም በሙሉ አይደለም፡፡በመሰረቱ የስራ ውል የሚቋረጠው በአሰሪው ወይም በሰራተኛው አነሳሽነት ወይም በሕግ በተደነገገው መሰረት ወይም በሕብረት ስምምነት ወይም በተዋዋይ ወገኖች በሚደረግ ስምምነት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 23 (1) ስር የተደነገገ ሲሆን የአንድ ድርጅት ከሌላ ጋር መቀላቀል ወይም መከፋፈል ወይም የባለቤትነት መብት ወደ ሌላ መተላፍ የስራ ውልን የማቋረጥ ውጤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይኖረው ስለመሆኑም በዚሁ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር (2) ስር ተመልክቷል፡፡አመልካች የድርጅቱ አካል የሆነውን መጋዘን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ በሚያስተላልፍበት ጊዜ የሰራተኞቹ የቅጥር ውል ከገዥው አካል ጋር የሚቀጥልበትን አግባብ ማመቻቸት ወይም ለሰራተኞቹ በሕጉ የተመለከተውን ተገቢ ክፍያዎች ከፍሎ ማሰናበት ሲገባው ድርጅቱ የተሸጠ በመሆኑ ምክንያት የስራ መደባቸው ተሰርዞአል የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪዎቹን ማሰናበቱ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡የመጋዘኑን መሸጥም ከስራ መደብ ስረዛ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡ከመሰረቱ የመጋዘኑ በሽያጭ መተላለፍ የስራ ውሉን በማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ባለመሆኑ የመጋዘኑ መሸጥ ሰራተኞቹን በማስጠንቀቂያ ለማሰናበት እንደሚያስችል አድርጎ አመልካች ያቀረበው ክርክርም ሆነ በዚህ ረገድ በሰበር አጣሪ ችሎት ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ከላይ የተጠቀሱትን የአዋጁን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረጉ ናቸው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡አመልካቹ የወሰደው የስንብት እርምጃ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 23 (2) ድንጋጌን በቀጥታ የሚቃረን ከሆነ ደግሞ የስንብት እርምጃው ሕገ ወጥ የማይሆንበት ምክንያት አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል በአመልካቹ የተወሰደውን የስራ ስንብት እርምጃ ሕገ ወጥነት በማረጋገጥ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች አመልካች ለተጠሪዎቹ እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ ስሕተት ተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 90108 በ27/01/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 21815 በ23/02/2008 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 231434 በ02/03/2008 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
3. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 91780 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዙህ መዝገብ በ09/03/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትሐ ብሔር

ሥነ - ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 102056

ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ሳምሶን ካሳዬ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ መሰረት ግርማ - ተወካይ ኃይሉ ቦሰት ቀረቡ

2. አቶ ሳሙኤል ካሳዬ
3. አቶ ኢሳያስ ካሳዬ } ቀረቡ
4. ወ/ሮ ሜላት ካሳዬ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ይለቀቅልኝ ጋር ተያይዞ የተሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበውን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ በ17/04/2006 ዓ/ም የተሻፈ ሁኖ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ፣ የአሁኑ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተራ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረው በመ/ቁጥር 24515 በ16/10/2002 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ከእናቱ ከወ/ሮ ፀሐይ ንብሬ በውርስ ሊተላለፍልኝ በሚገባ ንብረት ላይ የተሰጠና መብቱን የነካ ነው በሚል ምክንያት ውሳኔ ተነስቶ የክርክሩ ተካፋይ ልሆን ይገባል የሚል ሲሆን የአሁኑ ሥር ፍርድ ቤትም ለፍርዱ መሰረት የሆነው ንብረት ላይ የተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ ነው በሚል ድምዳሜ የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ በመዝገቡ ሊስተናገድ እንደማይችል፣ ሆኖም አመልካች መብታቸውን ቀጥታ ክስ አቅርበው ማስጠበቅ የሚችሉ መሆኑን ጠቅሶ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎባቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸው ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ ከተራ ቁጥር 2 እስከ 4 ያሉት ተጠሪዎች በአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ላይ የውርስ ንብረት ይለቀቅልን ክስ አቅርበው የወረዳው ፍርድ ቤት ክርክር ያስነሳው ይዞታና ንብረት ለከሳሾች እንዲለቀቅላቸው መወሰኑን፣ ይህ ውሳኔ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቶ የነበረ ቢሆንም የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም በመ/ቁጥር 11115 በ03/03/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለበት ነው በሚል ምክንያት ሙሉ በሙሉ በመሻር ክርክር የተነሳበት ይዞታና ንብረት የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት የወሰነ መሆኑን፣ ይህ ውሳኔ በመሰጠቱ ምክንያትም 1ኛ ተጠሪ የተወሰደባቸው ንብረት እንዲመለስላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349(1) ድንጋጌ መሰረት አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ባሉት ተጠሪዎች የ1ኛ ተጠሪ ቤት ፈርሶ ስለነበር በአሁኗ 2ኛ ተጠሪ ስም ያለው ቤት ተሸጦ ለ1ኛ ተጠሪ ግምቱ እንዲከፈል ጨረታ እንዲወጣ አድርጎ በሂደት እንደሚገኝ፣ የወረዳው ፍርድ ቤት በዚህ አግባብ አፈጻጸሙን እየመራ ያለው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 11115 የሰጠውን ውሳኔ መነሻ አድርጎ ስለመሆኑና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ሊቀርብ የሚገባው ደግሞ ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት መሆኑን ጠቅሶ የአሁኑ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አቀራረብ ስርዓት ስርዓቱን የተከተለ አይደለም በሚል ድምዳሜ የሥር ፍርድ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉን ተገቢ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የወረዳው ፍርድ ቤት እያስፈጸመ ያለው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 11115 የሰጠውን ውሳኔ ሁኖ እያለና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ሆነ በበታች ፍርድ ቤቶች ክርክሩ መኖሩን አመልካች ባላወቁበት ሁኔታ እንዲሁም የ1ኛ ተጠሪ አፈጻጸም ሂደት ላይ ስለመኖሩ ክርክሩ እያሳየ ፍርዱ ተፈጽሟል ተብሎ የፍርድ መቃወሚያው በወረዳው ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉም ሆነ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ በወረዳ ፍርድ ቤት የፍርድ መቃወሚያ ሊቀርብበት የሚችል አይደለም በማለት መወሰኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ አላማ ውጪ የሆነ እና የአመልካችን የውርስ መብት የጎዳ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች እና የአሁኑ ተጠሪ ከተራ ቁጥር 2 እስከ 4 የተጠቀሱት ተጠሪዎች የወ/ሮ ጸሐይ ገብሬ ወራሽ መሆናቸውን፣ የአሁኑ አመልካች ከተራ ቁጥር 2 እስከ 4 የተጠቀሱት ተጠሪዎች ከወ/ሮ ጸሐይ ገብሬ በውርስ የሚተላለፍልን ቤትና ይዞታ በ1ኛ ተጠሪ ከሕግ ውጪ ተይዞ ይገኛል በሚል በተጠሪዋ ላይ ክስ መስርተው በወረዳው ፍርድ ቤት ንብረቱ እንዲለቀቅላቸው ተወስኖላቸው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ፀንቶ የነበረ ቢሆንም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ አከራካሪው ቤትና ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ነው ተብሎ መወሰኑን፣ በዚህ ሂደት ግን የስር ከሳሾች በ1ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ቤት ላይ ጉዳት አድርሰው/አፍርሰው/ ስለነበር ተጠሪዋ የፈረሰው ቤታቸው ግምቱ እንዲከፍላቸው አፈጻጸሙን በወረዳው ፍርድ ቤት ቀጥለው ባሉበት ሁኔታ የአሁኑ አመልካች በዋናው ጉዳይ የተሰጠው ፍርድ የውርስ መብቴን የነካ ነው በሚል የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡና ተቀባይነት ያጡ መሆኑን ነው፡፡

የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልፅ የሚያሳየው አመልካች የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡበት ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 11115 የተሰጠና ፍርዱ ከተፈፀመ በኃላ የቀረበ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች መቃወሚያው የቀረበበት ፍርድ አልተፈፀመም፤ በሂደት ላይ ያለ ነው የሚሉት 1ኛ ተጠሪ ቤታቸው በሌሎች ተጠሪዎች የፈረሰባቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349(1) መሰረት የቤቱን ግምት ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ አድርጎ የስር ፍርድ ቤት ይህንኑ አቤቱታ ለማስፈፀም በ28/04/2006 ዓ/ም የሰጠውን ትዕዛዝ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ከወረዳው ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ ተመልክተናል፡፡

በእግርጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት የሚቀርበው አቤቱታ የሚስተናገደው ለመቃወሚያው መነሻ የሆነውን ውሳኔ ለሰጠው ፍ/ቤት ነው፡፡ አቤቱታው የሚጣራው ወይም የሚስተናገደው ማንኛውም ክስ በሚስተናገድበት ሥርዓት በመሆኑ እና ይህም ማስረጃ መስማትንና ማስረጃውን መዝኖ ውሳኔ መስጠትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለሆነም ታህሳስ 17 ቀን 2006 ዓ/ም ለወረዳው ፍርድ ቤት የቀረበው የተቃዋሚ ማመልከቻ ወይም ክርክር በማስረጃ ተጣርቶ የሚወሰን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የፍርድ መቃወሚያ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነው፡ የሰበር ችሎቱ ፍሬ ነገሮችን በማስረጃ የማጣራትም ሆነ ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን የለውም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ፍሬ ነገርን የሚያጣራበት ወይም የማስረጃ ምዘናን ክርክርና ቅሬታ የሚመለከትበት ሥልጣን የሌለው መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ለ))፣ ከክልሉ ሕገ መንግስት አንቀፅ 64 (2(ሐ)) እና የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 31 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም በሕግ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመውን ስህተት ለማረም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ለ)) ከክልሉ ሕገ መንግስት አንቀፅ 64(2(ሐ)) እና የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 31 ድንጋጌዎች መሰረት ስልጣን በተሰጠው በክልሉ ሰበር ችሎት የሚታይ አይሆንም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ክርክሩ የተጀመረው በወረዳው ፍርድ ቤት እንደሆነ መቃወሚያው መቅረብ ያለበት ለዚሁ ፍ/ቤት ነው ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ የተሻረው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነው፡፡ በመሆኑም የወረዳው ፍርድ ቤት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍርድ መቃወሚያ መነሻ አይቶ እንዲሽር ማድረግ ከፍርድ ቤቶች የስልጣን ተዋረድ አንጻር ሲታይ ያልተፈለገ ውጤትን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት የፍርድ መቃወሚያውን እንዲመለከትና ዳኝነት እንዲሰጥ ማድረግ የሚመረጥ አይሆንም፡፡ በሌላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኩል ግን ተቃዋሚው መብታቸውን የሚያስከብሩበትን መድረክ ሊያገኙ የሚገባ መሆኑ ሲታይም ይኸው ሊታይላቸው የሚገባው በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አይደለም፡፡ የክርክሩ ሂደት እንደሚያሳየው ከወረዳው ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተቃዋሚ የክርክሩ ተካፋይ አልነበሩም፡፡ ከዚህ የተነሳም በክልሉ ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ተቃዋሚውን የሚያስገድድ አይሆንም፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው ተቃዋሚ አለኝ የሚሉትን መብት ለማስከበር ይችሉ ዘንድ መብቴን የሚነካ ውሳኔ ሰጥቷል በሚሉት ፍርድ ቤት አቤቱታቸውን ከሚያቀርቡ ወይም መብቴን ተጋፍቶአል በሚለው ሰው ላይ በስሙ ቀጥታ ክስ መመስረት መብታቸውን ከሚያስከብሩ በስተቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ለወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ስርዓቱን የጠበቀ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በሌሎች ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349(1) መሰረት ያቀረቡት አፈጻጸም በሂደት ላይ መሆኑም የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካችን የፍርድ መቃወሚያ እንዲያስተናገድ የሚያስችለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም በዋናው ክርክር ላይ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 11115 የተሠጠው ውሳኔ የ1ኛ ተጠሪን በይዞታውና በቤቱ ላይ ሙሉ መብት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ እስከሆነ ድረስ ይሄው መብታቸው የሚለወጥ መሆኑን አመልካች በቅድሚያ በቀጥታ ክስ ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው ከክርክሩ ሂደት እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር የሚነቀፍ ሁኖ ስላልተገኘ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 24515 በ10/04/2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.036604 በ19/09/2006 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 185034 በ4/10/2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች አለኝ የሚሉትን መብት በሌላ አግባብ ከማስከበር ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በ24/10/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡ **መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 107838

ቀን 19/4/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲ.ር.ጋ.ጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- 1. አቶ ታከለ አርአያ - አልቀረቡም

2. አቶ አብርሃ ተክሉ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ደጀን ገ/እግዚአብሔር - ቀርበዋል

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች 1.አቶ ታከለ አረአያ 2.አቶ አብረሃ ተክሉ በቀን 23/3/2007 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 05504 አከራክሮ በቀን 11/2/2007 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ቅሬታቸውም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት መጀመሪያ የቀረበው ክስ መጥሪያ ደርሶን ከቀረብን በኃላ በፍ/ቤቱ ክሱ እንዲሻሻል ታዞ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ክሱ ተሻሽሎ መዝገቡ ሲንቀሳቀስ ግን የአሁን ተጠሪ (ከሳሽ) አድራሻችንን እያወቀ የሁመራ ቤት ሲታገድ መጥሪያ ሊሰጠን ሲችል በቤታችን ላይ መለጠፍ ሲቻል ፍ/ቤት ግቢ ውስጥ መጥሪያውን በመለጠፍና በጋዜጣ ጥሪ ማስደረጉ ሆን ብሎና ተገቢ አለመሆኑን መገንዘብ ሲቻል የስር ፍ/ቤት በሌለንበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልን ብለን ያቀረብነውን ማመልከቻ ውድቅ ማድረጉ ስህተት በመሆኑ ይታረምል የሚል ነው፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካቾች መጀመሪያ ክስ ሲቀርብባቸው ቀርበው መልስ የሰጡ ሲሆን በሌሉበት ይታይ የሚል ትዕዛዝ የተሰጠው ተጠሪ ክስ አሻሽሉ ተብለው መዝገቡ ከተዘጋባቸው በኃላ ባቀረቡት የተሻሻለ ክስ ጊዜ አመልካቾች ከአካባቢው አልተገኙም ተብለው በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ እና በጋዜጣ ተጠርተው አልቀረቡም በማለት ክርክሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌሉበት ተካሂዶ ውሳኔ የተሰጠውና አመልካቾች ይህንኑ ገልፀው ሲያመለክቱ ማመልከቻቸውን ውድቅ ማድረጉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አን. 94-110 ጋር ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡

ተጠሪ በቀን 25/7/2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች በአሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.37304 የተወሰነልኝን ውሳኔ በመ.ቁ.08505 የአፈፃፀም መዝገብ ከፍቼ መጥሪያ ላለመቀበል ከተሰወሩ በኃላ ንብረታቸው ከታገደ ከ2 ወር በኃላ ቀርበው ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርጉ ሲጠየቁ በሌለንበት የተወሰነ ውሳኔ ነው በማለት በአፈፃፀም መዝገብ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አን. 78 መሠረት አመልክተዋል እኔም ይህንኑ አንስቼ ተከራክሬያለሁ፡፡ መጀመሪያ መዝገቡ ክስ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ አዞ መዝገቡን ዘጋው ይበሉ እንጅ የተዘጋ መዝገብ የለም፡፡ አመልካቾች በሚኖሩበት ሁሉ ፊልጌ በማጣቱ ለፍ/ቤቱ አመልክቼ መጥሪያው ተሰጥፏል በጋዜጣም ጥሪ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ አቤቱታቸው ውድቅ ይሁንልን ብለው ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በቀን 16/8/2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

በዚሁ መሠረት መዝገቡን እንደመረመርነው ክርክሩ የጀመረው ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት አሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች (የከፍ/ፍ/ቤት ተከሣሾች) ለአሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ከሳሽ አቶ ደጀን ገ/እግዛብሄር በተከሳሾች (የአሁን አመልካቾች) ላይ በቀን 7/3/2005 ዓ.ም በተፃፈ ክስ አቅርቦብን እኛም ቀርበን ክርክር ከተጀመረ በኃላ ፍ/ቤቱ ከሳሽ ክስህን አሻሽል ተብሎ መዝገቡ ተዘጋ ከዚህ በኃላ መዝገቡ ሲንቀሳቀስ እኛ ያልሰማንና ከሳሽ የኛን አድራሻ እያወቀ ሆን ብሎ ላገኛቸው አልቻልኩም በማለት በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በመለጠፍና በጋዜጣ ጥሪ በማስደረግ ሲሆን ባለመስማታችን በሌለንበት ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ በሌለንበት መወሰኑን የሰማነው በቀን 6/8/2006 ዓ.ም በመሆኑና እንደሰማንም ቀርበን ያመለከትን ስለሆነ በሌለንበት የተሰጠው ውሳኔ እንድነሣልን በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም (የከፍ/ፍ/ቤት ከሳሽ) የሰጠው መልስ የተከሳሾች ማመልከቻ የቀረበው ለፍርድ ቤቱ በመሆኑ እኔ መልስ እንድሰጥ አይጠበቅብኝም፡፡ ፍ/ቤቱ ከሳሽ ክሱን ያሻሽል ብሎ መዝገቡን ቢዘጋም በተለዋጭ ቀጠሮ ክሱ ተሻሽሎ የሚቀርብ እንጂ መዝገብ እንድዘጋ የሚያዝ ሥነ ሥርዓትም የለም፡፡ ተከሳሾቹ መጥሪያ እንዳይደርሳቸው ሆን ብለው ከአካባቢው በመሰወራቸው ተፈልገው በአድራሻቸው ስላልተገኙ መጥሪያውን ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ ተለጥፏል ስለዚህ ማመልከቻቸው ውድቅ ይሁንልኝ ብሏል፡፡

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 08505 በቀን 21/9/2006 ዓ.ም በቀረበው ማመልከቻ ላይ የሰጠው ብይን ተከሳሾች ያቀረቡት ማመልከቻ ክርክሩ ተጀምሮ ክሱ እንዲሻሻል ከተደረገ በኃላ ከአካባቢው ቢሰወሩም ይኖራሉ በሚባልበት ቦታና ህዝብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚሰበስብበት ቦታ ሁሉ በፍ/ቤት አጥር ግቢ እና በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው አልቀረቡም ተከሣሾች (አመልካቾች) ክሱ እንዲሻሻል የታዘዘ ቢሆንም በቀጣዩ የሚቀጥል ጉዳይ መሆኑን አያውቅም ተብሎ አይታሰብም፡፡ ስለዚህ ያቀረቡት ምክንያት በቂ አይደለም በማለት ማመልከታቸውን አልተቀበልነውም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 05445 በቀን 10/10/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አን. 337 መሠረት የሚያስቀርብ ሆኖ አልተገኘም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ.ቁ. 05504 አከራክሮ በቀን 11/2/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ አመልካቾች የተሻሻለው ክስ ከመጥሪያ ጋር እንዲደርሳቸው በተደጋጋሚ ጊዜ ታዞ ከአካባቢው በመሰወራቸው ሌሎች የመጥሪያ አደራረስ ምርጫዎችን በመጠቀም አመልካቾች ሊመለከቱት ይችላሉ በተባሉ ግልፅ ቦታዎች እና በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ በመለጠፍና በጋዜጣ ቢጠሩም ስላልቀረቡ በሌሉበት መወሰኑ እና የስር ፍ/ቤት ማመልከቻቸውን በዚህ ሁኔታ ውድቅ ማድረጉ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም በማለት የስር ፍ/ቤትን ትዕዛዝና ብይን በማፅናት ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት የተያዘው ጭብጥ አመልካቾች በመጀመሪያ ክስ ሲቀርብባቸው መጥሪያ ደርሷቸው ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ ክስ ያሻሽል ተብሎ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ክሱ ተሻሽሎ መዝገቡ ከተከፈተ በኃላ አመልካቾች በአካባቢው አልተገኙም በማለት መጥሪያ በፍ/ቤት ግቢ በመለጠፍና በጋዜጣ ጥሪ በማድረግ አልቀረቡም በማለት በሌሉበት የተወሰነው ተጠሪና አመልካቾች ጎን ለጎን በእርሻ እንቨስትመንት የተሠማሩ መሆኑ እየታወቀ በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ መለጠፉና በጋዜጣ ጥሪ የተደረገላቸው እየታወቀ በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ መለጠፉና በጋዜጣ ጥሪ የተደረገላቸው መሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አን 94-110 ካለው የመጥሪያ አሰጣጥ ድንጋጌና ከመጥሪያ አሠጣጥ አላማ ጋር ለመመርመር ነው፡፡ በተያዘው ጭብጥ መሠረት አመልካቾች መጀመሪያ በአሁን ተጠሪ ክስ ሲቀርብባቸው መጥሪያ አድርሷቸው ቀርበዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ (የሥር ፍ/ቤት ከሣሽ) ክሱን ያሻሽል ብሎ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ክሱ ተሻሽሎ መዝገቡ ሲከፈት ለአመልካቾች መጥሪያ ሊደርሣቸው ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካቾች አቤቱታ መጥሪያ ሣይደርሰን በሌለንበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሣልን ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት ምክንያት አመልካቾች መጥሪያ እንዳይደርሳቸው ተሸሽገዋል በሚልና መዝገቡ ተዘግቶ በሚቀጥለው ቀጠሮ ክርክሩ እንዲቀጥል ማወቅ ይችላሉ ሲል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተከሣሾች (የአሁን አመልካቾች) በሚቀጥለው ቀጠሮ ክርክሩ ይቀጥላል ለማለት የሚችሉት መዝገቡ ባይዘጋና ቀጠሮ ቢሰጥ እንጂ መዝገቡ ተዘግቶ ቀጠሮ ባልተሰጠበት የሚቀጥለውን ቀጠሮ ሊያውቁ የሚችሉበት መንገድ የለም፡፡ አመልካቾች መጀመሪያ መጥሪያ ደርሷቸው ቀርበው እያለ መጥሪያ እንዳይደርሳቸው የተሸሸጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም መሰናክል ያደረጉ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ተረድቻለሁ የሚለው ተጠሪ ከገለፀላቸው ውጪ በሌላ መንገድ የተረጋገጠ ስለመሆኑ የተገለፀው ነገር የለም፡፡ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር ጎን ለጎን የእርሻ ኢንቨስትመንት ሥራ ይሰራሉ በዚህ የሥራ ቦታቸው መጥሪያ እንዲደርሳቸው የተደረገ መሆኑ ወይም የተለጠፈ መሆኑ የተገለፀ ነገር የለም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ.አንቀጽ 100 ይገልፃል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 105 በተደነገገው መሠረት በመኖሪያ ቤታቸው ወይም በመጨረሻ ጊዜ ይኖሩበት በነበረ ሥፍራ መጥሪያ የተለጠፈ መሆኑ የተገለፀ የለም፡፡ ይህ በቅድሚያ የሚወሰድ የመጥሪያ አደራረስ ዘዴ እያለ የሥር ፍ/ቤት የመጨረሻ አማራጭ በጋዜጣ ጥሪ መጥሪያ ማድረግ ዘዴ ተጠቅሞ እና ተከሳሾች (የአሁን አመልካቾች) መጥሪያ ሣይደርሰን ሳንሰማ በሌለንበት የተሰጠ ውሳኔ ይነሳልን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አልታየንም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ተዘግቶ የነበረው መዝገብ ተከፍቶ ክርክር የጀመረ መሆኑን ባልሰሙበት የሥር ፍ/ቤት የመጥሪያ አስፈላጊነት ተከራካሪዎች ቀርበው እንዲከራከሩ ያላቸውን ህጋዊ መብት ለማክበር ፍ/ቤቱም እውነቱን እንዲደርስበት ለማስቻል በመሆኑ መጥሪያ ለአመልካቾች ሲያደርሳቸው በቅድሚያ ሊጠቀም የሚገባውን የመጥሪያ አደራረስ መንገድ በመተው የመጨረሻ አማራጭ በጋዜጣ ጥሪ በመጠቀሙና አመልካቾች ይህንኑ ገልፀው መጥሪያውን ያልሰሙና በሌለንበት የተሰጠው ውሳኔ ይንሣልን ብለው ሲያመለክቱ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአሳሳ ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08505 ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የቤ/ጉ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05454 ሰኔ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የቤ/ጉ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 05504 ጥቅምት 11 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካቾች ክስ እንዲሻሻል ተብሎ የተዘጋ መ.ቁጥር 07304 ተከፍቶ ክርክር የጀመሩ መሆኑን ሳያውቁ መጥሪያ በአግባቡ ሳይደርሳቸው የተሰጠ ውሳኔ እንዲነሳላቸው ያቀረቡት ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀጽ 78(2) መሠረት ውሳኔውን ለማንሳት በቂ በመሆኑ በመ.ቁጥር 07304 የተሰጠው ውሳኔ ተነስቷል የቤ/ጉ/ክ/መ/የአሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት የተሻሻለውን ክስ ለአመልካቾች አድርሶ ካከራከረ በኃላ ውሳኔ እንዲሰጥበት መልሰናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሣራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
4. በ17/6/2007 ዓ.ም የተሰጠ እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 100475

ታህሳስ 20 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ሳምሶን አበራ ጠበቃ ክፍሌ አማረ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀሐይ አበራ ጠበቃ አሸናፊ ወጂ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን እንደቅደም ተከተላቸው አመልካች እና ተጠሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩም ፍቺን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው መሠረታዊ ጭብጥም የአሁኑ አመልካች የንብረት ክፍፍል በጠየቀበት ጊዜ ለአሁን ክርክር መነሻ የሆነችውን የሰሌዳ ቁጥር 3-15556 መኪና በተመለከተ መኪናው የተፈራችው በጋብቻ ውስጥ ሳይሆን እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የተፈራች ስለመሆኑ ለማሳየት አመልካች የክስ ማሻሻያ ጥያቄ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ፈቅዶ ክሱ ከተሻሻለ በኃላ ጋብቻ ከመመሰረቱ በፊት ከጥቅምት 1998 እስከ ህዳር 2001 ዓ.ም አብሮው ይኖሩ እንደነበር ግምት ተወስዶ መኪናው የጋራ ንብረት ነች ተብሎ ተወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91 አቤቱታ የሚሻሻልበት ሥርዓትና ዓላማው ዳኝነት ከተጠየቀበት ጉዳይ ፈፅሞ የተለየ ጥያቄ ለማቅረብ እንደማይፈቀድ፤ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብረን ኖረን ነበር በዚህ ጊዜ የተፈሩ ንብረቶች እንዲከፈል በሚል ማስረጃዎች ጭምር በመጥቀስ የቀረበው ጥያቄ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.256 ድንጋጌን ያላገናዘበ ስለመሆኑ፤ የፍቺ ውጤት በተጠየቀበት መዝገብ እንደባልና ሚስት አብረው ኑረዋል ወይስ አልኖሩም? የሚለው ጥያቄ በክስ ማሻሻል ምክንያት ተቀብሎ መታየቱ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም፡፡ እንደባልና ሚስት አብረው ሳያቋርጡ ኖረዋል ወይስ አልነበረም? የሚለው ነጥብም ማየት ባያስፈልገውም እንደተመለከተው ከጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም እስከ ነሃሴ 19 /1998 ዓ.ም ድረስ አብረው ቆይተው ከዛ በኃላ ግንኙነታቸው እንደተቋረጠ እንደገና አብረው መኖር የጀመሩት ጋብቻ ከተመሰረተበት ህዳር 2001 ዓ.ም ጀምሮ ስለመሆኑ የአሁን ተጠሪ ምስክሮች የአመልካች ምስክሮች ከሰጡት ቃለ ሚዛን በሚደፋ አግባብ አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም የሰሌዳ ቁጥር 3-15556 የሆነውን መኪና የግለ ንብረት ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ባንክ ላይ ነበር በተባለው ገንዘብ በተመለከተ ግን የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በማየት እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 /1/ መልሶታል፡፡የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርቡም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የአመልካች ቅሬታ መሠረታዊ ይዘትም ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብረው ይኖሩ እንደነበር የፍቺ ጥያቄ የቀረበበት መዝግቦ ለመግለጽ እንደማይገደዱ፤ በአመለካች የቀረቡ ምስክሮችም በተጠሪ ከቀረቡ ምስክሮች በተሻለ አግባብ ያስረዱ በመሆኑ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት በመሆን አብረው ይኖሩ እንደነበር የሕግ ግምት እንዲወሰድላቸው ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ከ1998 እስከ ተጋቡበት 2001 ዓ.ም ያልተቋረጠ ግንኙነት መኖሩን አመልካች አላስረዱም፡፡ በግል የተፈራ ንብረት የግል ነው መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉይዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከሥር የክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ቤት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-15556 የሆነውን መኪና የአመልካች እና ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በመሻር መኪናው የተጠሪ የግል ሀብት ነው በማለት ወስነዋል፡፡ አመልካች ከሥር ፍ/ቤት አንስቶ አጥብቆ የሚከራከረው የፍቺ ጥያቄ በቀረበበት መዝገብ ላይ እንደባልና ሚስት አብረው ይኖሩ ነበር የሚል ክርክር የማቅረብ ግዴታ እንደሌላቸው ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት የክስ ማሻሻል ጥያቄው የተለየ ውጤት የሚያመጣ መሆን የለበትም እንዲሁም አመልካችና እና ተጠሪ እንደባልና ሚስት አብረው ስለመኖራቸው አላስረዱም በማለት ውሳኔ መስጠቱ መዝገቡ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ አቤቱታ የሚሻሻልበት ዓላማና ማሻሻያው የሚቀርብበት ስርዓት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91 ሥራ ተመልክቷል፡፡ የክስ ማሻሻያ ጥያቄ መሠረታዊ ዓላማም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ የሚረዳ መሆኑ በፍርድ ቤቱ የታመነ ከሆነ ነው፡፡ አመልካች የፍቺ ጥያቄ በቀረበበት መዝገብ ላየ እንደባልና ሚስት ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ሲኖሩ ቆይተው በ2001 ዓ.ም ስለመጋባታቸው ያቀረቡት ክርክር የነበረ ስለመሆኑ መዝገቡ አያሳይም፡፡ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት እንኖር ነበር የሚለው አከራካሪ ጥያቄ የተነሳው የጋራና የግል ንብረት ለመለየት የተደረገው ክርክር ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በሥር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፍቺን ተከትሎ የቀረበው የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የቀረበው በአመልካች ነው፡፡ አመልካች የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲያነሱ ለክርክሩ መሠረት የሆኑ መሠረታዊ ጉዳዮች በዝርዝር መገለጽ ያለባቸው ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 222/1/ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የምንረዳው የጋራ ንብረት የተፈጠረበት /የተገኘበት/ አግባብ እና ሁኔታ በቀረበው ክስ በግልጽ ማመላከት ይጠበቅ ነበር፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-15556 በክስ ማሻሻያ እንደገለጹት እንደባልና ሚስት ሲኖሩ በነበሩበት ጊዜ ከሆነ መጀመሪያ ክስ ሲያቀርቡ ዳኝነት ያልጠየቁበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ አንድ የመብት ጥያቄ የሚያቀርብ ተከራካሪ ወገን ለክርክሩ መነሻ የሆነ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 222(1)(2) በሚያዘው አግባብ "ምክንያት የሆኑ ነገሮች እና የተፈጠሩበት ሁኔታ" በግልጽ ዳኝነተ መጠየቅ እየተገባው የፍቺ ውጤት ክርክር ሲደረግ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብረን ኖረናል የሚለው አዲስ የተለየ ክርክር ማቅረብ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91 ያላገናዘበ ነው የሚለው የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የአቤቱታ ማሻሻያ ጥያቄ የቀረበበት አግባብ ብቻ ሲሆን በእርግጥም በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ከ1998 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም ያልተቋረጠ ግንኙነት ነበር ወይስ አልነበረም የሚለውን ጭብጥ መርምሮ በፍሬ ነገር ደረጃ ግንኙነት አልነበረም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዎል፡፡ አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገቡ ላይ በሰፈረው ማስረጃ መሠረት ተገቢ ሁኖ ሲያገኘው ጭብጥን በማሻሻል ወይም በመለወጥ ተገቢ የመሰለውን የመጨረሻ ፍርድ መስጠት የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 ሥር ተደንግጓል፡፡ የተያዘው ጉዳይ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመረመረው አቤቱታው የተሻሻለበት አግባብ ብቻ ሳይሆን በእርግጥም አመልካች እና ተጠሪ እንደባልና ሚስት አብረው ኖረዋል ወይስ አልኖሩም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀኙ ማስረጃ መርምሮ ግንኙነት አልነበረም፡፡ መኪናው የግል ሀብት ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘናና ድምዳሜ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚለወጥበት አግባብ የለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ሥልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸም ያለመፈፀሙን በማረጋገጥ ፍርድ መሰጡት ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ /ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ በነዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-15556 በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ በመሻር መኪናው የተጠሪ የግል ንብረት ነው ማለቱና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱ በጉዳዩ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን ስለማያሳይ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 135453 በ21/04/2006 ዓ.ም የሰጠው፣ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 89470 በ15/08/2005 ዓ.ም የሰሌዳ ቁጥር 3-15556 በተመለከተ የሰጠው ፍርድ መሻሩ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 97972 በ30/07/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. የሰሌዳ ቁጥር 3-15556 የተጠሪ የግል ሀብት ነው መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ችሎት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

የተሰጠ የዕግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡

መዝገብ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 109383
የካቲት 2 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
መስጠፉ አህመድ
ተፈሪ ገብሩ
ሽምሱ ሲርጋጋ
አብርሃ መሰለ

አመልካች - ሳሊሆም ከፍተኛ ክሊኒክ - ተሾመ ጉታ ቀረቡ
ተጠሪ - ዶ/ር ዘመኑ ዮሃንስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ሲሆን አላግባብ ከስራ መሰናበታቸው ህገወጥ ነው ተብሎ ልዩ ልዩ ክፍያ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ድርጅቱ የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል ሰበታ ከተማ ቀበሌ 02 በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ እና በፍሬ ገዳዩም ስንብቱ ህጋዊ ነው እንዲባል የበኩላቸውን መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራቀኙ ተከራካሪዎች በተለያየ ክልል ነዋሪዎች ስለሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው በማለት መቃወሚያውን በብይን አልፎ በፍሬ ጉዳዩ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የስራ ዉሉ በአመልካች የተቋረጠው ከህጉ ውጭ ነው፤ ስለሆነም ለተጠሪ የካሳ፤ የስንብት እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በድምሩ ብር 104,730.00 (አንድ መቶ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ) እንዲሁም በክርክሩ ምክንያት በተጠሪ ላይ ለደረሰው ወጪ እና መጉላላት በቁርጥ ብር 500.00 (አምስት መቶ) እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይህን ውሳኔ በመቃወም አመልካች በይግባኝ ተጠሪ ደግሞ በመስቀለኛ ይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ክርክራቸውን ሰምቶ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለኝ ማለቱና ስንብቱ ህገወጥ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ በአግባቡ መሆኑን፤ ወጭና ኪሳራን በተመለከተ ተጠሪ ዝርዝር የማቅረብ መብታቸው ሊጠበቅ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥር 20 ቀን 2007 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ተጠሪ በስር ክሳቸው በአመልካች ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበር ገልፀው ክስ ማቅረባቸው ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት ግራቀኙ በተለያየ ክልል ነዋሪዎች ስለሆኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው? አይደለም? የሚለው ነጥብ እንዲጣራ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ክርክሩን ቅሬታ ካስነሳው ውሳኔ እና ተገቢነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምረናል ፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ ተጠሪ ተቀጥረዉ ሲሰሩ የነበረበት ድርጅት የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል ሰበታ ከተማ ቀበሌ 02 በመሆኑ፤ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 138(1) እና በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 22(1) መሰረት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ድርጅቱ በሚገኝበት ቦታ ያለው የክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት (ሰበታ ሀዋስ ወረዳ ፍርድ ቤት) በመሆኑ፤ በአዲስ አበባ እና ድሬድዋ ያሉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስራ ክርክርን ለማየት ስልጣኑ የተሰጣቸው ቢሆንም በሁለት ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ ተከራካሪዎች በመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(2) መሰረት ጉዳዩን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የማየት ስልጣን አላቸው ተብሎ የክስ መቃወሚያው ውድቅ መደረጉ የስራ ክርክርን አስመልክቶ የተከራካሪ ወገን ማንነት ወይም የሚኖርበት ክልል ከግምት ውስጥ ሳይገባ የክልል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲኖራቸው ታስቦ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በግልፅ የተደነገገውን የሚቃረን በመሆኑ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኮልፌ ምድብ የስራ ክርክር ችሎት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም ተብሎ ውሳኔው እንዲሻር ፤ እንዲሁም በፍሬ ነገሩ የስራ ውሉ እንዲቋረጥ የተደረገው የአመልካች የስራ እንቅስቃሴ እየቀዘቀዘና ትርፋም እየቀነሰ በመሄዱ ምክንያት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው በመሆኑ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተሸሮ ለጠሪ የሚከፈል ክፍያ የለም ተብሎ በነዛ እንዲሰናበቱ ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ክሊኒኩ ህጋዊ ሰውነት የሌለው በመሆኑና ክሱም የቀረበው ስራ አስኪያጅ እና ባለቤት አቶ ተሾመ ጉታ ተብሎ በመሆኑ፤ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(2) መሰረት ክሳሽና ተከሳሽ መደበኛ መኖሪያችን በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል ጎንደር ከተማ መሆኑ መነሻ ተደርጎ ክሱ መቅረብ ያለበት በፌዴራል ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ብይን መሰጠቱ የሚነቀፍ ባለመሆኑ፤ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የስራ ክርክርን አስመልክቶ የፌዴራል እና የክልል በማለት ለይቶ ያላስቀመጠ በመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 20 እና 23 መሰረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስራ ክርክሮችንም እንደሚመለከቱ ስለሚደነግግ የተሰጠው ብይን የሚነቀፍ አይደለም ተብሎ የአመልካች ቅሬታ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመር ነው በክርክሩ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ የስር ፍርድ ቤት ስልጣን (የግዛት ክልል) የለውም ተብሎ በሚቀርብለት መቃወሚያ ላይ በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ (የሰበር አቤቱታ) መቅረቡ ህጉን መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? በፍሬ ጉዳዩ ስንብቱ ህገወጥ ነው ተብሎ ልዩ ልዩ ክፍያ እነዲከፈል በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለ ወይስ የለም? የሚሉት ናቸው በዚሁ ቅደም ተከተል መሰረት መርምረናል፡፡

ቀዳሚውን ጭብጥ በተመለከተ ከክርክሩ እንደተረዳነው አመልካች ያቀረቡት የስልጣን መቃወሚያ ስረ ነገርን የተመለከተ ሳይሆን የግዛት ክልል ስልጣንን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ግራ ቀኙ እንደገለፁት በአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ያሉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስራ ክርክርን ለማየት የስረ ነገር ስልጣኑ በህግ ተሰጥቷቸዋል፡፡ አመልካች እየተከራከሩበት ያለው የግዛት የዳኝነት ስልጣን በዋነኛነት መሰረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረበትን ቦታ፤ለተከራካሪ ወገኖች የሚኖረውን አመቺነት እና መሰል ሁኔታዎችን ሲሆን የስረ ነገር ስልጣን መሰረት የሚያደርገው ግን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ይዘት፣የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ጥቅም ክብደት እናመጠን፤የጉዳዩን የውስብስበነት ደረጃ እና መሰል ነጥቦችን በመሆኑ በጉዳዮች አመራር ስርዓት ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ለስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ነው፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9 እና 10 ድንጋጌዎች ተገናዝበው ሲታዩም ሕጉ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ከግዛት ስልጣን ይልቅ ለስረ ነገር ስልጣን መሆኑን መገንዘብ የሚያስችሉናቸው፡፡ በተለይ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 10(2) ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው ፍርድ ቤቱ የግዛት ክልል ስልጣን የለውም በማለት ለሚቀርብለት መቃወሚያ የሚሰጠው ውሳኔ ፍትህን የሚያጓድል ካልሆነ በቀር ይግባኝ ሊቀርብበት እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካቾች ቅሬታ በስር ፍርድ ቤት የተላለፈው ውሳኔ ፍትህን የሚያጓድል ነው በማለት የቀረበ አይደለም፡፡ ፍትህን የሚያጓድል ውሳኔ ስለመተላለፉ የቀረበ ክርክር በሌለበት ደግሞ የስር ፍርድ ቤት የግዛት ክልል ስልጣን የለውም ተብሎ በቀረበው መቃወሚያ ላይ ባሳለፈው ብይን ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ መቅረቡ ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች በሆኑ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚነሳ ክርክርን የማየት ስልጣን የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑበአዋጁ 25/1988 አንቀጽ 5(2) ስርመደንገጉ የግዛት ክልል ስልጣንን ሳይሆን የስረነገር ስልጣንን የሚመለከት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ይህን ምክንያት በመጥቀስ የስልጣን ክርክሩን መወሰናቸው ተገቢ ሆኖ ባናገኘውም በግዛት ክልል ስልጣን ረገድ በተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ (የሰበር አቤቱታ) መቅረቡ የስነ ስርአት ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ክርክርና ማስረጃውን ተመልክተው የስራ ውሉን ለማቋረጥ አመልካች እንደሚሉት ባጋጠማቸው የገቢ ማሽቆልቆል የተነሳ ሰራተኛን ለመቀነስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያስችል አስገዳጅ ሁኔታ ስለመፈጠሩ ያላረጋገጡ በመሆኑ፤ ቅነሳውም በህጉ የተዘረጋውን ስርዓት የተከተለ ስለመሆኑ የቀረበ መከራከሪያና ማስረጃ አለመኖሩን በማረጋገጥ የስራ ስንብቱ ህገወጥ ነው በማለት መወሰኑ እና በሕጉ የተመለከቱ ክፍያዎች ይከፈሉ ማለታቸው የሚነቀፍ አይደለም ። በዚህ ረገድ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም ብለናል ።

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 32414 ታህሳስ 11/2006 ዓ.ም ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በከ/መ/ቁ 139491 ህዳር 25/2007 ዓ.ም የተሻሻለው ውሳኔ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 348(1) መሰረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል ።
2. በስር ፍርድ ቤት የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል ። ይፃፍ
3. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ እልባት ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት።

የልዩነት ሐሳብ

በዚህ መዝገብ ለክርክር በቀረበው ጉዳይ ተጠሪው ሲሰሩበት የነበረው ተቋም የሚገኝ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን በሰበታ ሃዋስ ወረዳ ውስጥ መሆኑ፣ የስራ ውሉ የተደረገውም ሆነ ሲፈጸም የነበረው በዚያው ወረዳ ውስጥ መሆኑ አላከራከረም። በክልል ውስጥ የሚነሳ የግል የስራ ክርክር ጉዳይን አይቶ የመወሰን ስልጣን ደግሞ በአዋጅ ቁ. 377/1996 አንቀጽ 138(1) ስር የተሰጠው ለክልል ወረዳ ፍ/ቤት ነው። የግዛት ስልጣን የሌለው አንድ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ፍትሕን የሚያጓድል ካልሆነ በቀር ተቀባይነት እንደማያጣ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አንቀጽ 10(2) ስር የተመለከተ ቢሆንም በመሰረቱ ቀደም ሲል አሃዳዊ የመንግስት አወቃቀርን መሰረት አድርገው የወጡት እና አሁን ድረስ በስራ ላይ ያሉት ሕጎች መተርጎም እና ተግባራዊ መደረግ የሚገባቸው በአሁኑ ጊዜ ያለው ፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀር ስርዓት ካስከተላቸው ለውጦች ጋር ተጣጥመው ነው። በአሁኑ የመንግስት አወቃቀር ስርዓት መሰረት የፍርድ ቤቶችን የስረ ነገር ስልጣን ለመወሰን እንደመስፈርት ከሚወሰዱት ነጥቦች አንዱ ደግሞ ጉዳዩ የተነሳበት ስፍራ ወይም ግዛት በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ክሱ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎት ተስተናግዶ ውሳኔ ማግኘቱ የሚያስነሳው የስረ ነገርን ሳይሆን በስነ ስርዓት ሕጉ አንቀጽ 10(2) ድንጋጌ መሰረት የግዛት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጣን ጥያቄን ብቻ ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ የስነ ስርዓት ሕጉ አንቀጽ 10(2) ድንጋጌን በዚህ አግባብ መተርጎም በአንድ ክልል ወረዳ ፍ/ቤት ቀርቦ መታየት ያለበት ጉዳይ ትይዩ ስልጣን ባለው በማንኛውም የሌላ ክልል ወረዳ ፍ/ቤት ታይቶ ቢወሰን ጉዳዩ የሚያስነሳው የስረ ነገር ሳይሆን የግዛት ስልጣን ጉዳይን ነው እንደማለት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የፍርድ ቤቶች ስልጣን በአሁኑ ጊዜ በፌዴራል እና በተለያዩ ክልሎች በተደለደለበት ሁኔታ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ጉዳዩ የሚያስነሳው የስረ ነገር ሳይሆን የግዛት ስልጣንን ጥያቄ ነው ሊባል ይችል የነበረው ክሱ ተስተናግዶ ውሳኔ ያገኘው በዚያው ክልል በሚገኝ ሌላ ወረዳ ፍ/ቤት ቢሆን ኖሮ ነው፡፡ በክልል ወረዳ ፍ/ቤት ቀርበው መስተናገድ የሚገባቸውን የግል የስራ ክርክር ጉዳዮች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎት ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁ. 100950 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን የስራ ክርክር ጉዳዮችን አስመልክቶ በመዝገብ ቁ. 113339 እና 113675 የተሰጡ ገዥ ውሳኔዎችም ቢሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስረ ነገር ስልጣንን አስመልክቶ በተከሳሽ ወገን የቀረበለት መቃወሚያ ባይኖር ኖሮ እንኳ የቀረበለትን ጉዳይ አስተናግዶ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረነገር ስልጣን ያለው መሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት ሲሆን ስልጣን የሌለው በሆነ ጊዜም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁ. 9(1) እና 231 (1) (ለ) መሰረት ጉዳዩን ዘግቶ ማሰናበት ይጠበቅበታል፡፡

በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በስልጣን ምክንያት ሊሻር ይገባው ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁ. ሁለት የተመለከተው ዳኛ የልዩነት ሃሳቤን አስፍሬአለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 109206

የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዲኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
መስጠፉ አህመድ
ተፈሪ ገብሩ
ሽምሱ ሲርጋጋ
አብርሃ መሰለ

አመልካች - አቶ ፍስሃ እርቅ ይሁን
ተጠሪ - አቶ ኪሮስ ስዩም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገንዘብ ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በጋምቤላ ክልል ማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው ፡፡ የክሱ ይዘት ግራቀኙ በነበረን የንግድ ግንኙነት ጀንፈል ቡና በጋራ ገዝተን አስበጥረን ለማእከላዊ ገበያ አቅርበን በመሸጥ ትርፉን ለመከፋፈል ባደረግነው ስምምነት መሰረት ለጀንፈል ቡና መግዣ ብር 122,000.00 (መቶ ሃያ ሁለት ሺህ) ሰጥቸው ቡናው ተገዝቶ አስበጥረን እና በከሳሽ ፈቃድ ማእከላዊ ገበያ ተልኮ በከሳሽ የቡና ሽያጭ ወኪል በአቶ ዘላለም ጥላሁን አማካኝነት ተሸጦ ገንዘቡ በንግድ ባንክ በኩል የተላከልኝ ሲሆን ይህን ገንዘብ አውጥቼ ትርፉን ተሳስበን እስክንከፋፈል ድረስ ሙሉ ገንዘቡን ለተከሳሽ የሰጠሁት ቢሆንም ሂሳብ ተሳስበን ገንዘባችንን ሳንካፈል በመካከላችን አለመግባባት ስለተፈጠረ በ 10/07/2006 ዓ.ም በሽማግሌ ዋና ገንዘቤንና ትርፉን እንዲሰጠኝ አስጠይቁው ቡና መግዣ ብር 122,000.00 (መቶ ሃያ ሁለት ሺህ) እንደሰጠሁት አምኖ ከዚህ ገንዘብ ብር 41,000.00 (አርባ አንድ ሺህ) የሰጠኝ ሲሆን ቀሪውን ብር 81,000.00 (ሰማንያ አንድ ሺህ) ዛሬ ነገ በማለት ሊሰጠኝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ዋና ገንዘቤንና ትርፉ ታስቦ እንዲከፍለኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማና የሰነድ ማስረጃዉን ከመረመረ በኋላ ተከሳሽ በምስክሮች ለመክፈል ተስማምቷል የተባለውን ቀሪ ገንዘብ ብር 81,000.00 (ሰማንያ አንድ ሺህ) ለከሳሽ እንዲከፍለው ወስኗል፡፡ ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ የይግባኝ ክርክሩን ሰምቶ የባንኩ ሰነድ ገንዘቡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተላከ ለከሳሽ ስለመሆኑ ከሚያስረዳ በቀር ለተከሳሽ ስለመላኩ ስለማያስረዳ፤ ከሳሽ ገንዘቡን ከባንክ አውጥቶ ለተከሳሽ ስለመስጠቱ የሚያስረዳ አንዳች የሰነድ ማስረጃ ስላልቀረበ፤ የተሰሙት ምስክሮችም ገንዘቡን ሲሰጥ አይተናል በማለት ስላልመሰከሩ፤ እንዲሁም ተከሳሹ ገንዘቡ ያለበት መሆኑን በሽማግሌዎች ፊት ተስማምቷል ለተባለውም ስለመስማማቱ የቀረበ የስምምነት ሰነድ ስለሌለ ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም ገንዘቡንም ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ጉዳዩን ለክልሉ ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ቅሬታቸው ተቀባይት ሳያገኝ አያስቀርብም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ 4/አራት/ ገፅ የሰበር ማመልከቻ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ውሣኔና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክሱን በዝርዝር ክደው መልስ ያልሰጡ በመሆኑ በመሸሽ ክሱን እንዳመኑ የሚያስገምት በመሆኑ፤ ገንዘቡ በብድር የተሰጠ ባለመሆኑ በሰው ምስክር ማስረዳት እየተቻለ የሰነድ ማስረጃ አላገኘንም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ፤ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ዳኝነት የተጠየቀበትን ከቡና ሽያጭ የተገኘን ትርፍ ሂሳቡ እንዲጣራ አስደርጎ አለመወሰኑ እና የወለድ ጥያቄውን ማለፉ የህግ ስህተት በመሆኑ እንዲታረም መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ 4 /አራት/ ገፅ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ከብር 500.00 (አምስት መቶ) በላይ በሆነ የገንዘብ ክርክር በፅሁፍ ማረጋገጫ ካልተደገፈ ተቀባይነት የለውም ተብሎ መዝገቡ እንዲዘጋ፤ በሽማግሌዎች ፊት ተጠሪ ገንዘብ ስለመውሰዱ አምኖልኛል የሚለው መከራከሪያም ከእውነት የራቀ ከመሆኑም በላይ የተቆጠሩት ምስክሮች የሰጡት ቃል እርስ በርሱ የሚጋጭና ገንዘቡን ሰጥቶኛል ብሎ ነግሮናል የሚል አመሰካከር በመሆኑና ገንዘቡን አመልካች ለተጠሪ ሲሰጥ አይተናል የሚል ባለመሆኑ የፍታብሄር ስነ ስርዓት ህጉን አንቀፅ 242 እና 128 ድንጋጌዎች አፈጻጸም ያልተከተለ ምስክርነት አሰጣጥ በመሆኑ፤ ያለሰነድ ተሰጠ ለተባለው ገንዘብ ተጠሪ ኃላፊነትም ተጠያቂነትም የለበትም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ስለሆነም ሊጸና ይገባል የሚል ነው ፡፡
አመልካችም ሰኔ 26 ቀን 2007 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገፅ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡
የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ደንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው ተጠሪ በሽማግሌዎች ፊት አምነው ለመክፈል ስለመስማማታቸው የሰነድ ማስረጃ አልቀረበም በማለት ገንዘቡን መክፈል ኃላፊነት

የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

እንደሚታወቀው የፍትሃብሔር ግዴታ ከውል ወይም ከህግ ከሚመነጭ ግንኙነት ላይ የሚመሰረት ሲሆን ክስ አቅራቢው ወገን የግዴታውን ምንጭ በመግለጽ የሚጠይቀውን ዳኝነት በዝርዝር የማቅረብ ግዴታ አበለት፡፡ ተከሳሹም በክሱ የተጠቀሰን ግንኙነት አስመልክቶ ዝርዝር በልሱን እንዲያቀርብ ይጠበቃል፡፡ በዚህ መልኩ ግንኙነቱ ተለይቶ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የህጉን ድንጋጌዎች በመመልከት ግንኙነቱን ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚችለው ማስረጃ አይነት እና የማስረዳት ሸክሙ ስለሚያርፍበት ወገን በህጉ አግባብ ሊወሰን የሚገባ ይሆናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተፈጠረው የንግድ ግንኙነት ጀንፈል ቡና በጋራ ገዝተው አስበጥረው ለማእከላዊ ገበያ በማቅረብ ትርፉን ለመከፋፈል ስለመሆኑና የሚጠይቁትን ዳኝነት ገልፀው አመልካች ክስ ያቀረቡ ሲሆን በማስረጃነትም ጉዳዩን በሽምግልና አይተዋል የተባሉ ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በሰጡት መልስ የተጠቀሰው ግንኙነት መኖሩን ሳይክዱ ከሳሽ ራሱ የቡና ሽያጭ ገንዘቡን ከባንክ የተቀበለ መሆኑን በክሱ ስላመነ ክስ ማቅረብ አይችልም ተብሎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ፤ እንዲሁም ከብር 500.00 በላይ ያለሰነድ ማስረጃ መክሰስ አይችልም የሚሉ መቃወሚያወች እና በአማረጭም ከሳሽ ባቀረበው ሰነድ መሰረት ከባንክ ከተረከበው የድርሻቸውን ገንዘብ እንዲከፍል የሚጠይቅ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከተደረገው ክርክር የግራቀኙ ግንኙነት በፅሁፍ ያልተረጋገጠ የሽርክና የንግድ ግንኙነት ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በእንዲህ አይነቱ ግንኙነት ተቃራኒ ስምምነት ከሌላቸው በቀር ግራ ቀኙ ገቢ ላደረጉት መዋጮ ባለሀብትነቱን እንደያዙ ይቆያሉ፡፡ ተጠሪ በመከላከያ መልሱም ባይሆን በሌላ በማናቸውም መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለፀ እንደሆነ በእምነቱ መሰረት ይገባኛል የሚለው ማናቸውም ዳኝነት እንዲሰጠው አመልካቹ ሊጠይቅ እንደሚችል፤ በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ የታመነውን ለማስረዳት የጽሁፍ የስምምነት ሰነድ ሊያቀርቡ ይገባል በሌላ አይነት ማስረጃ ሊያስረዱ አይችሉም የሚባልበት የህግ ምክንያት እንደሌለ ክርክሩ ከሚመራበት የስነ ስርዓት ህግ ድናጋጌዎች እና ከማስረጃ ፅንሰ ሃሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ክሱን ለማስረዳት ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ተቀባይነት የላቸዉም የሚባልበት የህግ ምክንት ባለመኖሩ፤ ይልቁንም ባቀረቡዋቸው ማስረጃዎች ተጠሪ ገንዘቡ እንዳለበቸውና ለመክፈል መስማማታቸውን ማስረዳታቸውን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ በአንጻሩ የሰነድ ማስረጃ አልቀረበም ተብሎ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም ገንዘቡንም ሊከፍል አይገባም በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔውን መሻሩ እና የሰበር ችሎቱም ይህን ሳያርም ማለፉ ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘንውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች የሳለፉት ውሳኔ እና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በቅሬታቸው የስር ፍርድ ቤት ዳኝነት የተጠየቀበትን ከቡና ሽያጭ የተገኘን ትርፍ ሂሳቡ እንዲጣራ አስደርጎ አለመወሰኑ እና የወለድ ጥያቄውን ማለፉ የህግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረም የጠየቁ ቢሆንም በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የበኩላቸውን ይግባኝ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው በየደረጃው ውሳኔ የተሰጠበት ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የጋምቤላ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 01686/07 ጥቅምት 21 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ፤ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በፍ/ሰ/መ/ቁ 00396/07 ህዳር 8 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 (1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ/ 01978/06 ጳጉሜ 3 ቀን 2006 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 (1) መሠረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ፊት ስለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 109497

የካቲት 3 ቀን 2008ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- አቶ አግማስ ኡመር እና ወ/ሮ ሰብረና ጌታቸው

ጠበቃ ይትባረክ መኮንን ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ኡመር አሳዬ እና ወ/ሮ አስገድ ሃሰን -ጠበቃ መስፍን እሼቱ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካቾች አቶ አግማስ ኡመር እና ወ/ሮ ሰብርና ጌታቸው ጥር 26ቀን 2007ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌ.ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 156998 ታህሳስ 20 ቀን 2007ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት የቀረበ ነው፡፡ ቅሬታቸውም የውል ስምምነት በተዋዋዮች መሀከል ሕግ መሆኑ ተደንግጎ እያለ የውል ስምምነት የህግና የሞራል ጥሰት እንዲሁም ሌሎች ህጋዊ ምክንያቶች የተጓደሉበት ሁታዎች የተካተቱበት ሲሆን እና እነዚህ ምክንያቶች ከተዋዋዩ በአንዱ ወገን ላይ የመብት ሆነ የግዴታ ተጽእኖ የበለጠ የሚያበዛበት ሆኖ የተገኘ ከሆነ ተቀባይነት የለውም ሊባል ካልተቻለ በቀር የስር ፍ/ቤት ካለበቂ ምክንያት ስምምነታችንን ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ባለመሆኑ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የተደረገው ክርክር በአፈጻጸም የፍ/ባለመብቶች (የአሁን አመልካቾች) በፍ/ባለእዳ (የአሁን ተጠሪዎች) ላይ ብር 480,000 እንዲከፍሉን ተወስኖልናል ሲሉ የአፈጻጸም መዝገብ በፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት ይከፍታሉ፡፡ ፍ/ቤቱም የአ.ፍ/ባለእዳዎች በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽሙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያዛል፡፡ የፍርድ ባለመብቶች (የአሁን አመልካቾች) ከፍ/ባለእዳዎች ጋር ሰኔ 13 ቀን2006ዓ.ም በአፈጻጸም ስምምነት አድርገናል፡፡

በዚሁ ስምምነት መሰረት ፍርዱ እንዲፈጸም ስምምነቱን ፍ/ቤቱ አጽድቆ የፍ/ቤት ማህተም አርፎበት እንዲሰጠን ሲሉ ያመለክታሉ፡፡ የፍ/ባለእዳዎችም ተስማምተዋል፡፡

የፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 215541 አከራክሮ ሐምሌ 11ቀን 2006ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ የቀረበው አቤቱታ በተመለከተ ፍ/ቤት የተሰጠ ፍርድ፣ ውሳኔ ያስፈጽማል፡፡ የተሰጠው ውሳኔ ብር 480,000 እንዲከፍል ነው የቀረበው ስምምነት ደግሞ ቤት ለማስረከብ የተዋዋሉ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲፈጸም ከቀረበው ፍርድ የተለየ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 396(1) መሰረት ተስማምተው ፈጽመው ከቀረቡ ተቀብሎ ትእዛዝ ይሰጣል ይሁንና እንደዋና ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277 መሰረት ውል ተመዝግቦ ውሳኔ መስጠት ግን የሚቻል ባለመሆኑ አልተቀበልነውም ሲል አሏል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለፌ.ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 156998 ታህሳስ 20ቀን 2007ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ስህተት የተገኘበት አይደለም ሲል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት ግራቀኙ ስለፍርዱ አፈጻጸም ከፍርድ ውጪም ቢሆን የተስማሙበትን ውል በተመለከተ ተቀብሎ አልመዘገብም ያለበትን አግባብ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277 እና 396 እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731 ድንጋጌዎች አንጻር ተገቢነቱን ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪዎች ሰኔ 5 ቀን 2007ዓ.ም በተጻፈ መልስ የፍ/ባለእዳዎች ከፍ/ባለመብቶች ጋር ተስማምተን ስምምነቱን ለፍ/ቤት አቅርበን እያለ በተጠሪነት መጠራታችን ተገቢ ባመሆኑ በነጻ እንሰናበት ሲል ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካቾችም ሐምሌ 3 ቀን 2007ዓ.ም በተጻፈ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መዝገቡን እንደመረመርነው የአሁን አመልካች ግንቦት 26 ቀን 2006ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸምላቸው ያቀረቡት የአፈጻጸም ክስ ብር 480,000 እንዲከፈላቸው ነው፡፡ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277 መሰረት ተዋዋዮቹ በእርቅ መጨረሳቸውን ገልጸው እንዲጸድቅላቸውና ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ በእርቁ መሰረት እንዲፈጸም ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው የጠየቁት ፍርዱ የባለእዳ (የአሁን ተጠሪ) ቤት ላይ እንዲፈጸም ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277(1) ተከራካሪዎቹ ነገሩን በእርቅ ለመጨረስ ለፍ/ቤቱ ሲያቀርቡ የእርቁ ስምምነት ሕግንና ሞራልን የማይቃረን መሆኑን ፍ/ቤቱ ስረዳው እርቁን ተቀብሎ በማጽደቅ ከመዝገቡ ጋር ማያያዝ እንደሚገባው ይደነግጋል፡፡ የአሁን አመልካችና የተጠሪ የእርቅ ስምምነት በገንዘብ እንዲከፈል የተወሰነን ውሳኔ የአሁን ተጠሪን ቤት ለአመልካች ለማስተላለፍ (ለመፈጸም)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደረገ ስምምነት ነው፡፡ ለአሁን አመልካች የሚፈጸም ቤት የእርቅ ስምነነቱ ህጋዊነት የማረጋገጥ ጉዳይ በተመለከተ ሊነሳበት የሚችል ክርክር ጋር በተያያዘ እራሱን የቻለ ማጣራት የሚፈልግና ውሳኔ የሚያስፈልገው ጉዳይ በመሆኑ ፍ/ቤት በተዋዋዮች መሃል የተደረገ ውል በፍ/ብ/ሕ/አንቀጽ 1731 እንደሚደነግገው ውሎች ባቋቋማቸው ሰዎች ላይ ሕግ በመሆናቸው ብቻ ህጋዊነታቸው ሳይረጋገጥ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277 በሚደነግገው አንጻር የእርቅ ስምምነቱን ተቀብሎ በአፈጻጸም መዝገብ ላይ የሚያጸድቅበት አግባብ የለም፡፡ ለአፈጻጸም ተብሎ የተደነገው ስርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 396 በሚደነግገው መሰረት አመልካችና ተጠሪዎች ከፍ/ቤት ውጭ በተደረገ ስምምነት በውሳኔው መሰረት ለፍ/ባለመብቱ የተከፈለ መሆኑን ለፍ/ቤቱ ካሳወቁት ፍ/ቤቱ ስምምነቱን ተቀብሎ ትእዛዝ የሚሰጥበት አካሄድ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ይህንኑ በማተት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ.ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 156998 ታህሳስ 20ቀን 2007ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 215541 ሐምሌ 8 ቀን 2006ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻችሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 110150

የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀንዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ገ/መድህን ወ/ሚካኤል - ጠበቃ አብይ ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ግርማይ ፍትዊ - ጠበቃ ወርቅነሽ መንግስቱ ቀረቡ

2. የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ፅ/ቤት - ነ/ፈጅ ሙሴ ዳዊት ቀረቡ

3. የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ፅ/ቤት

- ዐቃቤ ሕግ ታደሰ አንዳርጌ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የውጭ አገር ዜጋ በመሆናቸው ተከራክረው በለቱ አንደኛ ተጠሪ ለሚደርስባቸው ኪሳራ ዋስትና የሚሆን ብር 5,500 /አምስት ሺ አምስት መቶ ብር/ እንዲያስይዙ የተሰጠውን ትዕዛዝ አልፈፀመም በሚል የስር ፍርድ ቤት አመልካች በተከሳሾች ላይ ያቀረበውን ክስና መዝገብ መዝጋቱ የሕግ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘትም በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ኤርትራዊያን ከአገር ሲወጡ፣ በቦሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 13 የሚገኘውን ቁጥሩ 3018 የሆነ ቤት ለአንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ አከራይቸው ነበር ሁለተኛ ተከሳሽ ይህንን ቤት በአንደኛ ተከሳሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሸጦለታል፡፡ የከሳሽ ዕዳ ነው በሚል ከቤቱ ዋጋ በመቀነስ ለሶስተኛ ተከሳሽ ከከፈለ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ በብሔራዊ ባንክ በኩል ሲሳብ በስሜ አስቀምጧል፡፡ ከሳሽ ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ በመንግስት ፈቃድ ከተመለስኩ በኋላ ለሶስተኛ ተከሳሽ በድጋሜ ክፍያ ፈፅሜለሁ፡፡ ስለዚህ ከሳሽ ከመንግስት መመሪያ ውጭ አከራይቸው ለሄድኩት አንደኛ ተከሳሽ ቤቴን ለመሸጥ ሁለተኛ ተከሳሽ ያደረገው ውል ፈራሽ እንዲሆንልኝ፡፡ ይህ የማይቻል ከሆነ ከቤቱ ዋጋ አላግባብ ያስቀነሰው ገንዘብና ለሶስተኛ ተከሳሽ በድጋሜ የከፈልኩት ገንዘብ እንዲመለስልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

2. አንደኛ ተጠሪ /አንደኛ ተከሳሽ/ አመልካች በዚህ አገር ዜጋና ኗሪ ባለመሆኑ በክርክሩ ለሚደርስብኝ ኪሳራ ዋስትና ያስብልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ በአንደኛ ተከሳሽ ላይ ለሚያደርሰው ኪሳራ ብር 5,500 /አምስት መቶ ሺ አምስት መቶ ብር/ ዋስትና እንዲያስይዝ፣ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ሰኔ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በዋስትና እንዲያሲዙ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠበትን የዋስትና ገንዘብ ያላስያዙና በሁለተኛ ተከሳሽና በሶስተኛው ተከሳሽ ላይ የቀረበው ክስ በአንደኛ ተከሳሽ ጋር ከቀረበው ክስ ጋር የተያያዘ መሆኑን ገልፆና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 201 ጠቅሶ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

3. አመልካች አንደኛ ተጠሪ ከጠየቀው የዋስትና ገንዘብ በላይ በብሔራዊ ባንክ በስሜ በግል አካውንት የተቀመጠ ገንዘብ እንዳለ በክስ ማመልከቻየ ገልጨ እያለ፣ ከዚህ ገንዘብ ለኪሳራ የሚሆን ገንዘብ እንደታገደ በማድረግ ክርክሩን መቀጠል ስችል የስር ፍርድ ቤት የዋሰትና ገንዘብ እስዲያስይዝ የሰጠው ትዕዛዝና ትዕዛዙን አልፈፀምክም በማለት መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የካቲት 17 ቀን 2007 ዓ.ም የተሣፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች በተናጥል አመልካች የስር ፍርድ ቤት በሕግ በተደነገገው መሰረት እንዲያስይዝ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የዋስትና መዝገብ ያላስያዘው በመሆኑ አመልካች ትዕዛዙን እስኪፈፀም ድረስ የስር ፍርድ ቤት መዝገቡን መዝጋቱ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 201 መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በሚል ይዘት ያለው መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ክስ ያቀረበው ሁለተኛ ተጠሪ ለአንደኛ ተከሳሽ በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል በነበረው ጦርነት ምክንያት እኔ ከአገር ስወጣ፣ ከመመሪያ ውጭ የፈፀመው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ይደረግልኝ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሽያጭ ውሉ አይፈረስም ከተባለ፣ በብሔራዊ ባንክ በከሳሽ ስም በግል አካውንት የተቀመጠ ገንዘብ፣ ከቤቱ ሽያጭ አንደኛ ተከሳሽ ከሳሽ የግብር እዳ ያለብኝ መሆኑን ሣያረጋግጥ ቀንሶ ለሶስተኛ ተከሳሽ የከፈው ክፍያ እና ከሳሽ ለሶስተኛ ተከሳሽ ከቤቱ ዋጋ ተቀንሶ ለሶስተኛ ተከሳሽ የተከፈለ መሆኑን ሣላውቅ በድጋሜ የከፈልኩት ገንዘብ እንዲመለስ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት እንደሆነ ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል፡፡

5. የከሳሽ ክስ በመሰረታዊ ባህሪውን ይዘቱ ከሳሽ በክርክሩ ረች ወይም ተረች ቢሆን አንደኛ ተጠሪ በክርክሩ ምክንያት የሚያደርስበትን ኪሣራ ለመሸፈን የሚያስችል ገንዘብ የሚያሳጣ አይደለም፡፡ ከሳሽ በአንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ መካከል የአመልካች ቤት ለመሸሻጥ የተዋዋሉት ውል ፈራሽ ነው ቢባል፣ አመልካች ለተጠሪዎች ኪሳራ መክፈል እንደማይገደዱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ 463 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ውድቅ ቢሆንበትና አመልካች በክርክሩ ተረቶ ቢሆን፣ በክርክሩ ምክንያት በተጠሪዎች ላይ ያደተሰውን ኪሳራ ለመክፈል የሚችል ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን በአንደኛ ተጠሪ ሽጦ በአመልካች ስም በብሔራዊ ባንክ በግል አካውንት ያስቀመጠው ጥሬ ገንዘብ ያለ መሆኑን አመልካች ካቀረበው ክስ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አንደኛ ተጠሪ አመልካች በክርክሩ ለሚያደርስበት ኪሳራ የዋስትና ገንዘብ እንዲያሲዝ ያቀረበውን ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት በብሔሪዊ ባንክ ከሚገኘውና በአመልካች ስም በዝግ አካውንት ከተቀመጠው ገንዘብ፣ በአንደኛ ተጠሪ በክርክር ምክንያት ለሚደረስበት ኪሳራ መከፈያ እንዲሆን ብር 5,500 /አምስት ሺ አምስት መቶ ብር/ ብሔራዊ ባንክ አግዶ እንዲያቆይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 155 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ትዕዛዝ መስጠት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶና አከራክሮ ውሳኔ ለመስጠት እየቻለ፣ አመልካች የኪሳራ ገንዘብ እንዲያስይዝ የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 200 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መስፈርት የሚያሟላ አይደለም፡፡

6. በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 200 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ለሚደርሰው ኪሳራ ዋስ እንዲያስይዝ የሚጠየቀው፣ ከሳሽ በክሱ ምክንያት በተከሳሽ ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመክፈል የሚችሉ ሁኔታ የሚያጠራጥር ሲሆንና ኪሳራውንም ለመክፈል የሚያስችል ሀብት ወይም ገንዘብ የሌለው በሆነ ጊዜ እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 200 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 ተደግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ በክርክሩ ለሚደርስበት ኪስራ አመልካች ዋስትና እንደሰጠው ያቀረበውን ጥያቄ፣ በአመልካች ስም በዝግ አካውንት በብሔራዊ ባንክ ከተቀመጠው ገንዘብ በአንደኛ ተጠሪ ላይ ሊደረስ ይችላል ተብሎ የገመተውን ኪሳራ ማለትም ብር 5,500 /አምስት ሺ አምስት መቶ ብር/ ባንኩ ይዞ እንዲቆይ በማዘዝ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ ፍትሕ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማግኘት መብት በማያጣብብ ሁኔታ ለማስፈፀም እየቻለ፣ አመልካች የዋስትና ገንዘብ እንዲያሰጥ የሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 200 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 እና የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

7. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሕግ አግባብ ውጭ የዋስትና ገንዘብ እንዲያስይዝ የሰጠውን ትዕዛዝ እንዳልፈፀመ ገለፃ መዝገቡን መዝጋቱ ከላይ የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች፣ የሚጥስ መሆኑን ገልፆ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻር ሲገባው፣ የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 212488 ሰኔ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 157449 ታህሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በብሔራዊ ባንክ በአመልካች ስም በዝግ አካውንት ከተቀመጠው ገንዘብ ብር 5,500 /አምስት ሺ አምስት መቶ ብር/ ወጭ እንዳይሆን የዕግድ ትዕዛዝ በመስጠትና የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 212488 በማንቀሳቀስ የአመልካችን እና የተጠሪዎችን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመርመር ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 112927

ቀን የካቲት 16/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የማርዘነብ ዕቁብ ዳኛ አቶ ባዬ አጥናፉ - ጠበቃ አለጌታ መርሻ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ዋለልኝ ተመስገን - ቀረቡ

2. አቶ አዲሱ ጥሩነህ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ ላልተከፈለ የዕቁብ ገንዘብ የተሰጠ የዋስትና ግዴታ የሚመለከት ነው፡፡ የአመልካች ዕቁብ አባል የሆነ ወርቁ ሚናስ የተባለና የሥር አንደኛ ተከሳሽ የሆነ ሰው የዕቁብ እጣ ደርሶት ብር 465,000 /አራት መቶ ስልሳ አምስት ሺ ብር/ ተቀብሎ ሲወስድ ቀሪውን የዕቁብ እጣ በየጊዜው የሚከፍል ስለመሆኑ፣ አቶ ወርቁ ሚናስ የዕቁብ ገንዘብ መጣሉን ቢያቋርጥ፤ ተጠሪዎች ገንዘቡን የሚከፍሉ ስለመሆኑ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ ገብተው ፈርመዋል፡፡ አቶ ወርቁ ሚናስ መክፈል የነበረበትን ብር 222,000 /ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ሺ ብር/ ሣይከፍል የዕቁብ ገንዘቡን መጣሉን በማቋረጡ አመልካች አንደኛ ተከሳሽ ወርቁ ሚናስና እሱ የዕቁብ ገንዘቡን ሲወስድ ዋስ የሆኑት ተጠሪዎች ገንዘቡን እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ለምሥራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡
2. ተጠሪዎች የዕቁብ አባላትና የዕቁብ ገንዘብ በእጣ ደርሶት የወሰደው አቶ ወርቁ ሚናስ ዋስ እንደሆነ ገልፆም በዕቁብ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የዚህ አይነት የዕቁብ ገንዘብ ለዕቁብተኛ ሲሰጥ የዕቁቡ ኃላፊዎች አራት ዋሶችን አስጠርተው ገንዘቡን መስጠት ነበረባቸው፡፡ የዕቁብ ኃላፊዎች ሁለት ዋሶችን አስጠረተው ገንዘብ መስጠታቸው የዕቁቡን መተዳደሪያ ደንብ ያልተከተለ መሆኑን ስለማያሳይ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተከሳሾች እያንዳንዳችን ክስ የቀረበበትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘብ አንድ አራተኛውን ብቻ ነው የመክፈል ኃላፊነት ያለብን በማለት መልስ የሰጡ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሮታል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት ዕቁብ የደረሰው ሰው የደረሰውን የዕቁብ ገንዘብ ከመውሰዱ በፊት የዕቁብ አባላት የሆኑ ስንት ዋሶችን የመጥራት ኃላፊነት እንዳለበት በጭብጥነት ይዞ ለማጣራት የዕቁቡን መተዳደሪያ ደንብና የምስክሮችን ቃል ከሰማ በኃላ የዕቁቡ ኃላፊዎች የዕቁቡን ገንዘብ የወሰደውን አቶ ወርቁ ሚናስ አራት ዋሶችን የማስጠራት ኃላፊነት የለባቸውም ስለዚህ አንደኛ ተከሳሽ ወርቁ ሚናስ ያልከፈለውን የዕቁብ ገንዘብ ይክፈል፡፡ የዕቁቡን ገንዘብ አንደኛ ተከሳሽ ካልከፈለ፣ ሁለተኛ ተከሳሽና ሶስተኛ ተከሳሾች ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
4. ተጠሪዎች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የተጠሪዎችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኃላ ተጠሪዎች የፈረሙት የዋስትና ውል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1725 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 የተደነገገውን መሰረት የሚያሟላ ባለመሆኑ ዋስትናው ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡ ተጠሪዎች አንደኛ ተከሳሽ የዕቁብ ገንዘብ ሲወስድ በሰጡት ዋስትና አይገደዱም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
5. አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የዕቁብ ገንዘብ ደርሶት ቢወሰድ ዋስ መሆናቸውን በግልፅ ክደው አልተከራከሩም፡፡ በአንዳሩ ተጠሪዎች ዋስ እንደነበሩ አምነው ክስ ከቀረበበት ገንዘብ አንድ አራተኛውን ብቻ እንደሆነ ገልፀው ተከራክረው እያለ የዋስትና ውሉ የህጉን ፎርማት አያሟላም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት የዋስትና ውሉን በመቃወምና በመካድ የተከራከርን በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የዋስትና ውሉ ህጋዊ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን በመመርመር የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡
6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪዎች የፈረሙት የዋስትና ውል የህጉን ፎርም አያሟላም በማለት ተጠሪዎች ክስ ያቀረበበትን የዕቁብ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የለባቸውም በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ተጠሪዎች በሥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንደኛ ተከሳሽ የሆነው አቶ ወርቁ ሚናስ ለደረሰው የዕቁብ ገንዘብ ዋስ መሆናቸው በሥር ፍርድ ቤት አከራካሪ ጭብጥ ሆኗል ወይስ አልሆነም? የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

7. ተጠሪዎች ለሥር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ የአመልካች የዕቁብ አባላት መሆናቸውንና እነርሡም በስማቸው የዕቁብ ገንዘብ የሚጥሉ መሆኑን፣ አቶ ወርቁ ሚናስ የተባለ ዕቁብተኛ የዕቁብ ገንዘብ ሲደርሰው ዋስ ሆነው ያፈረሙ መሆኑን በማመን ለሥር ፍርድ ቤት መልስ የሰጡ መሆኑ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልፅ አስፍሯል፡፡ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት አቶ ወርቁ ሚናስ ለወሰደው የዕቁብ ገንዘብ የዋስትና ግዴታ የገቡ መሆኑን ሣይክዱ፣ አከራካሪ ነጥብ አድርገው ያቀረቡት በገቡት የዋስትና ግዴታ መሠረት ሊከፍሉ የሚገባውን የገንዘብ መጠን እንደሆነና ተጠሪዎች የቁብ ኃላፊዎች በአቶ ወርቁ ሚናስ የዕቁብ ገንዘቡን ከመስጠታቸው በፊት አቶ ወርቁ ሚናስ አራት ዋስ እንዲጠራ ማድረግ ሲገባቸው በእኛ ዋስትና ብቻ የዕቁቡን ገንዘብ የከፈሉት ከዕቁቡ መተዳደሪያ ደንብ ውጭ ስለሆነ እኛ የምንገደደው እያንዳንዳችን አቶ ወርቁ ሚናስ የወሰደውንና ሣይከፍል የቀረውን የዕቁብ ገንዘብ 1/4ኛ ብቻ ነው በማለት እንደሆነ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሯል፡፡

8. የአንድ ጉዳይ አከራካሪ ጭብጥ ከሳሽ በክስ የገለፀውንና ተከሳሽ በመልሱ ክዶ የተከራከረበት ነጥብ እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 ንዑስ አንቀጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተከራካሪዎች ክርክራቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሚገደዱትና ፍርድ ቤቱን በተከራካሪዎች ያቀረበውን ማስረጃ ተዓማኒት ክብደት የሚመዝነው ግራ ቀኙ ተካክደው በሚከራከሩበት ጭብጥ ላይ ብቻ እንደሆነና ከሳሽና ተከሳሽ ያልተካካዱበትና ከሳሽ በክሱ ገልፆ ተከሳሽ ባመነው ነጥብ ላይ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ማስረጃ በመመዘን ሣይሆን በተከሳሹ በሰጠው የዕምነት ቃል ወይም መልስ መሠረት መወሰን እንዳለበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 242 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪዎች አቶ ወርቁ ሚናስ የዕቁብ እጣ ወጥቶለት በቁብ ያደረሰውን ገንዘብ ከዕቁቡ የሥራ ኃላፊዎች ሲወስድ እነርሱ የዋስትና ግዴታ የገቡ መሆኑ ያልተካደና አከራካሪ ጭብጥ ባለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች የታመነውን ወርቁ ሚናስ ላልተከፈለው የዕቁብ ገንዘብ የገቡት የዋስትና ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት አመልካች ያቀረበው የውል ሰነድ የህጉን ፎርም አያሟላም በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የጠቀስናቸውን የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 (1) የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 242 ድንጋጌዎችና አመልካቾች ያለበት የማስረዳት ግዴታ እስከምን ድረስ እንደሆነ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

9. የሥር ፍርድ ቤት የአመልካች የዕቁብ ኃላፊዎች ተጠሪዎችን በሰጡት ዋስትና ብቻ የዕቁቡን ገንዘብ በዕቁቡ ባለዕድል /ባለ እጣ/ አቶ ወርቁ ሚናስ መክፈላቸው ተገቢ ነው ወይስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም? ተጠሪዎች በዋስትናው መክፈል የሚገባቸው ወርቁ ሚናስ የወሰደውን የዕቁብ ገንዘብ ሙሉውን ነው ወይስ እያንዳንዳቸው አንድ አራተኛ (ግማሹን ገንዘብ) የሚለውን አመልካችና ተጠሪዎች የተካከደበትን ጭብጥ በመያዝ የሰውና የዕሑፍ ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪዎች ወርቁ ሚናስ የወሰደውን ሣይከፍል ያቀረበውን የዕቁብ ገንዘብ እያንዳንዳቸው 1/2ኛውን (ሙሉ ገንዘቡን) የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይህም የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበት የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ በይግባኝ ሰሚው ችሎት ፀንቷል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት አከራካሪ የፍሬ ጉዳይ ጭብጥ ያልሆነ ተከራካሪዎች ያልተካካደበት ነጥብ ጭብጥ አድርጎ በመያዝ የዋስትና ውሉ የህጉን ፎርም ስለማያሟላ ተጠሪዎች የዕቁብ ዋስ በመሆን ለገቡት ግዴታ ተጠያቂ አይደሉም በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 44853 መጋቢት 24 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 7630 ጥቅምት 19 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 39054 ታህሣሥ 23 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 104028

የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-1.አልማው ወሌ

2.ዓሊ መሐመድ

3.ተክሊት ይመስል

4. እንዳሻው አዳነ

5.ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ብዙአየሁ ያለው - ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ሲሳይ ካሴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት መብት መሰረት አድርጎ የቀረበውን ይዞታ ይለቀቀልኝ ጥያቄን የሚመለከት የቀረበውን ክርክር በግራ ቀኙ ማስረጃና ከሚመለከተው አካል በቀረበው ማረጋገጫ መሰረት ይዞታው የተጠሪ ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ ለውሳኔው መሰረት የሆነውና ከሚመለከመተው አስተዳደር አካል የተሰጠው የሰነድ ማስረጃ ሐሰተኛነቱ ከውሳኔው በኋላ ማስረጃውን በላከው አካል ተረጋግጧል በሚል የቀረበውን የዳግም ዳኝነት ይታይልን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በላይ ጋይነት ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 02162 ሲሆን ጉዳዩ በመጀመሪያ ሲጀመር የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ አመልካችና አመልካች እና አቱ ብርሃን ደመቀ ደግሞ ተከሰሽ ነበሩ የአሁን ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘትም፡- ቁበላይ ገይንት 01 ቀበሌ አስተዳደር መኮቢያ ገብሬኤል ገብር ውሥት ጥሩ 498/ለ እና 501 የሆኑ ቤቶች ግማሹ የሚች አባታችን የአቶ ገብሬ ድንቅነህ ሲሆኑ ወረሾች ነን፣ ግማሹን ደግሞ ሚች ወ/ሮ ብዙነሽ አደራ በኑዛዜ ሰጥተውናል በማለት ቤቱን ተጠሪዎች ያላግባብ መያዛቸውን ዘርዝረው ቤቱ እንዲለቀቅ ይወሰን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከማቅረባቸውም በተጨማሪ በፍሬ ነገሩም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አድርጎ ጉዳዩን በመመርመር የአመልካቾች ክስ ከሰላሳ ሶስት አመት በኋላ የቀረበ ነው በማለት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ሲል በመ/ቁጥር 75780 የተከፈተውን መዝገብ ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካቾች የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ የሚች ወ/ሮ ብዙነሽ አደራ ወራሽነትን በመጠየቅ የሚቺ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ናቸው ተብሎ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 147267 የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ተቃውመው ፍርድ ቤቱን ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪው የሚቺ ልጅ ሳይሆኑ የወራሽነት ማስረጃ መውሰዳቸውን አመልካቾች አረጋግጠዋል ተብሎ የቀደመው የወራሽነት ማሰረጃ እንዲረዝ ታህሳስ 09 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶአል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልቾች የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75780 የተሰጠውን ብይን በሕገ ወጥ መንገድ በተገኘ የወራሽነት ማስረጃ ምስክር ወረቀት ያሰጡት ብይን ነው በማለት በድጋሚ እንዲታይ ዳኝነት ጠይቀው ፍርድ ቤቱም በይርጋ የተዘጋ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 መሰረት በድጋሚ የሚታይበት አግባብ የለም በማለት ሳይቀባላቸው ቀርቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-3ኛ ተጠሪ ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ ሐሰተኛ ነው ከተባለ ተጠሪዎች ይህንኑ የሚያስተባብል ማስረጃ ባላቀረበቡት ሁኔታ የውርስ ንብረቱን አይለቁም ተብሎ የተሠጠው ብይን በዳግም ዳኝነት የሚታይ አይደለም ተብሎ የአመልካቾች ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካቾች የቀደመው ክስ በይርጋ የታገደ ን በሚል ምክንያት የዳግም ዳኝነት ጥያቄው ሳይታይ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን 1ኛ፣2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ሊቀርቡ ስላልቻሉ በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎአል፡፡ 3ኛ ተጠሪ ግን ቀርበው በሠጡት መልስ፡-የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ስርዓቱን ያልጠበቀ መሆኑን፣ የአመልካቾች የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ በይርጋ ውድቅ የሆነበት መ/ቁጥር 75780 እና የተጠሪን የወራሽነት ማስረጃ ያሰረዙበት መዝገብ ቁጥር 147267 ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ የዳግም ዳኝነት ጥያቄው የሚቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ ዳኝነት የተሰጠው ተገቢው የክርክር አመራር ስርዓት ተፈፅሞና ተገቢው ጭብጥ ተይዞ፣ በሕጉ አግባብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጣራት ተደርጎ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ነጥቦች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ድንጋጌዎች ይዘት መመልከቱ ተገቢ ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁኑ አመልካቾች ለወረዳው ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረቡት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 መሰረት ዳግም ዳኝነት እንዲታይላቸው በመጠየቅ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም አቤቱታውን በጉዳዩ ላይ ቀድሞ ፍርድ ቤት ከተሠጠበት መዝገብ ቁጥር 02162 ውጭ በመቀበል ተጠሪዎችን ያቀረቡት አቤቱታ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6 መሰረት ሊስተናገድ እንደማይችል በማመን የአመልካቾች የቀድሞ ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ብይን የተሰጠበት በመሆኑ በዳግም ዳኝነት ስርዓት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት አቤቱታው ውድቅ አድርጎታል፡፡

ይህ ችሎት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ይዘቱንና መንፈሱን ከሌሎች የፍተሓብሔር ሥነ ስርአት ውስጥ ከተመለከቱት የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች እና የፍርድ መቃወሚያ ስርዓቶች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የድንጋጌው ዓላማ በእውነት ላይ የተመሰረተ ዳኝነት እንዲሠጥ ማድረግ ከመሆኑ አኳያ በመመርመር ለተጠቀሰው ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) ድንጋጌ መሰረት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም በመ/ቁጥር 43821 እና በመ/ቁጥር 32269 ሠጥቶበታል፡፡በሰ/መ/ቁጥር 43821 ላይ በቀረበው ጉዳይም ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 16624 የያዘውን አቋም ማለትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 መሰረት የዳግም ዳኝነት ጥያቄ መቅረብ ያለበት ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት እንጂ በይግባኝ ቀርቦ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ አይደለም በማለት የሠጠው የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት ተለውጧል፡፡ በዚህም መሰረት የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ውሳኔ ከተገኘ በሁዋላም ቢሆን በቁጥር 6 ስር የተመለከቱት መመዘኛዎች ተሟልተው እስከተገኙ ድረስ መቅረብ እንደሚችል ተግለጸ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው የሕግ ነጥብ /ጉዳይ/ የአመልካቾች ጥያቄ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 6(2) ስር የሚወድቅ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ስለሆነ ይህን ድንጋጌ ማየቱ ለጉዳዩ አወሳሰን ይጠቅማል፡ ይህ ድንጋጌ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ የተሰጠው በሃሰት ተዘጋጅቶ በቀረበ ሰነድን ሃሰተኛ የምስክርነት ቃልን፣ ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቅሶ የሆነ ተግባርን መሰረት አድርጎ መሆኑን አቤት ባዩ ሲረዳው ጉዳዩ በይግባኝ ከመታየቱ በፊት ውሳኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ራሱ ዳኝነቱን በድጋሚ እንዲያይ ጥያቄ ለማቅረብ መብት የሚሰጠው ነው፡፡ የድንጋጌው ሙሉ ይዘትና መንፈስ የሚያሳየው የመጨረሻው ፍርድ ከተሰጠ በሁዋላ ሀሰተኛ ሰነድ ወይም ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል ወይም መደለያ እንደተደረገና አቤት ባዮም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጎ ለማወቅ ያለመቻሉን በሚገባ ለማስረዳት የሚችል የሆነ እነደሆነ፣እነዚህ ጉዳዮች መኖራቸው ወይም መፈጸማቸው ታውቆና ተገልጾ ቢሆን ኖሮ ለፍርድ መለወጥ ወይም መሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችል እንደነበር ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፣ የተሰጠ ፍርድ ሊያስለውጥ የሚችል አዲስ ማስረጃ ማግኘቱ ብቻ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደገና እንዲታይ የማያደርግ መሆኑን፣ ማስረጃው ፍርዱን በማሳሳት ውጤቱን ያበላሸና ተገቢ ያልሆነ ድርጊትን የሚያሳይ መሆን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ማስረጃውም በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሰነድን፣ ሀሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ ተግባርን መሰረት ያደረገ መሆንና ማስረጃው ፍርዱ በሚሰጥበት ጊዜ ፍርዱ እንደገና ይታይልኝ የሚለው ተከራካሪ ወገን ማስረጃው መኖሩን ያውቀው የነበረ ያለመሆኑ፣ ይግባኝ ቀርቦበት ከሆነ አዲስ ማስረጃው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ግምት ውስጥ እንዲያስገባ ይግባኙ ለቀረበለት ፍርድ ቤት መቅረብ ያለበት መሆኑ፣ የተገኘው አዲስ ማስረጃ የሀሰት ሰነድን፣ ሀሰተኛ ምስክርነትን፣ መደለያንና የመሳሰሉትን የሚመለከት ለመሆኑ ማረጋገጫ መኖሩን በሚጠቅስ ቃለመሐላ የተደገፈና ማስረጃው አስፈላጊው ትጋት የተደረገበት ቢሆንም ፍርዱ በተሰጠ ጊዜ በአመልካቹ ያልታወቀ መሆኑን የሚገልፅ መሆን ያለበት መሆኑ በቅድመ ሁኔታነት ሊሟሉ የሚገባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ድንጋጌው ያስገነዝባል፡፡ የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ጥብቅ መለኪያዎች ያሉት መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ሲሆን የድንጋጌው ጥብቅ የመሆን አይነተኛ አላማም የተሰጡ ውሳኔዎችን አጣራጣሪነት ለማስወገድ መሆኑ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የዳግም ዳኝነት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት የሆነው ሰነድ ወይም ማስረጃ ሐሰተኛ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በሕጉ የተመለከቱት ሁሉም መመዘኛዎችን አቤቱታ አቅራቢው ማሟላቱን በቅድሚ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የሚከራከሩት 3ኛ ተጠሪ አለኝ የሚሉት የወራሽነት ማስረጃ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰረዝ ተደርጎአል በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤት ይህ የሰነድ ማስረጃ ሐሰተኛ ነው ከተባለ 3ኛ ተጠሪ በመ/ቁጥር 75780 በነበረው ክርክር የክርክሩ ተሳታፊ መሆን ይችል ነበር ወይስ አልነበረም?፣ በአመልካቾች ላይ የይርጋ መቃወሚያውን ሊያነሳ የሚችልበት ሕጋዊ መብትና ጥቅም አለው ወይስ የለውም?፣ ይርጋ ለማንሳት የሚችል ከሆነስ ለግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት የሚኖረው የይርጋ ጊዜ ምን ያህል ነው፣ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ ከተለየ በኋላስ የአመልካች የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትንና ይህ ሁሉ የሚታለፈ እና ወደ ፍሬ ነገሩ የሚገባ ከሆነ ደግሞ አከራካሪ ቤቶች የውርስ ንብረት መሆን ያለመሆናቸውንና ለአመልካቾች የሚለቀቁበት አግባብ መኖር ያለመኖሩ በጭብጥነት ተይዞ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተገቢው ዳኝነት የሚሠጠበት ይሆናል፡፡ ስለሆነም አንድ ክስ በይርጋ መዘጋቱ የዳግም ዳኝነት ጥያቄውን ላለማስተናገድ እንደበቂ ምክንያት የማይወሰድና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ድንጋጌም በመመዘኛነት ያልተቀመጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት ያስቀመጠውን ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡

ሲጠቃለልም የአመልካቾች የዳግም ዳኝነት ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ሰር የተመለከቱትን ጥብቅ መመዘኛዎችን ያማላ መሆን ያለመሆኑ በቅድሚያ ከታዬ በኋላና ጥያቄያቸው በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟላ ነው የሚባል ከሆነም በመልካቾች እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠሪዎች መካከል ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ ተለይቶ ክሱ አግባብነት ባለው የይርጋ ጊዜ ቀሪ የማይሆን ከሆነም ግራ ቀኙ በፍሬ ነገሩ ክርክር አድርገውበትና በተገቢው መንገድ ሁሉ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም በተጨማሪ ማስረጃዎች አጣርቶ እንዲሁም ወደ ክርክሩ ሊገባ የሚገባው አስፈላጊ አካል ካለም ወደ ክርክሩ እንዲገባ አድርጎ ክርክሩን ከመራው በኋላ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ሊወሰንበት የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 75780 ሐምሌ 23 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡
2. የአመልካቾች የዳግም ዳኝነት ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ስር የተመለከቱትን ጥብቅ መመዘኛዎችን ያሟላ መሆን ያለመሆኑ ሳይጣራ ክሱ በይርጋ ውድቅ የሆነ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ተቀባይነት የሚያጣበት አግባብ የለም፣ አቤቱታቸው በሕጉ የተመለከተውን መመዘኛ ያሟላል ከተባለም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ ተለይቶና በስነ ስርዓት ሕጉ አግባብ ክርክሩ ተመርቶ ተገቢው ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል ብለናል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 75780 ቀጥሎ በፍርድ ሐተታው ላይ ስለዳግም ዳኝነት አቀራረብ ስርዓትና መመዘኛዎች እንዲሁም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለውን ይርጋ ጊዜ በመለየት እና የአመልካቾችን ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም የተጠሪዎችን ክርክርና ማስረጃ በመመርመርና እውነታውን ለማወቅ የሚረዱ የሰነድ ማስረጃዎችን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145(1) መሠረት በማስቀረብ፣ የክርክሩ አስፈላጊ ወገን ካለም ወደ ክርክሩ በማስገባት አከራካሪውን ቤት የማን ነው? በሚለው ላይ ተገቢውን ሁሉ በማጣራት ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 116209

የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
መስጠፋ አህመድ
ተፈሪ ገብሩ
ሸምሱ ሲርጋጋ
ፈይሳ ወርቁ

አመልካች - የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን - አልቀረቡም
ተጠሪ - ወ/ሮ ምዕላል አብርሃ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው በግራ ቀኙ መካከል ባለው የንብረት ካሳ ክርክር በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በማዕከላዊ ዞን ማዕከላዊ ፍርድ ቤት የአብይ አዲ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 02634 ግንቦት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈውን ብይን በመቃወም ነው ፡፡ አመልካች ይግባኝ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ብር 791,225.00 (ሰባት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃያ አምስት) በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመወሰን ስልጣን የለውም፤ እንዲሁም በስር በተደረገ ክርክር ተካፋይ አልነበርኩም የሚሉ መቃወሚያዎችን አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም መቃወሚያዎችን ከመረመረ በኋላ ባሳለፈው ብይን ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 455/1997 አንቀጽ 11(4) እንዲሁም የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ በወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 29(4) ስር እንደተደነገገው ካሳን በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ለሚመለከተው የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሌለበት ለሚመለከተው መደበኛ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ እንደሚችል ከሚደነግጉ በቀር የተጠቀሱት አዋጆች በካሳዉ ግምት መጠን ወደተለያየ ፍርድ ቤት ይግባኝ እንደሚቀርብ የሚደነግጉ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ብሏል፡፡ ሁለተኛውን መቃወሚያ በተመለከተም የአሁን አመልካች እየተሰራ ያለው መንገድ ባለቤት በመሆኑ ለመንገድ ስራ ስለተወሰደው መሬት እና በመሬቱ ላይ ስለነበረው ንብረት ካሳ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት

በአዋጁ በግልፅ ስለተደነገገ፤ በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ፊት ተከራካሪ አልነበርኩም የሚል ክርክር ቢያቀርብም በስር የተወሰነውን ካሳ ከፋይ ከሆነ በካሳው መጠን ላይ ለቀረበው ይግባኝ መልስ እንዲሰጥ እና እንዲከራከር መደረጉ በአግባቡ ነው በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህን ተከትሎም የግራ ቀኙን ክርክር ለመስማት ቀጠሮ ለውጧል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ የቀረበው አመልካች ያነሳቸውን መቃወሚያወች ውድቅ በማድረግ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በመቃወም ነው ፡፡ አመልካች ሀምሌ 20 ቀን 2007 ዓ.ም ያቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ መቃወሚያዎቹ ውድቅ ተደርገው ወደ ክርክሩ ለመግባት የተሰጠውን ብይን ስነስርዓታዊነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል ፡፡ በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን በመጀመሪያ በሰበር የተያዘውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበትና በሰበር መታየት የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የሰበር አቤቱታ የቀረበው የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቶ ክርክር ለመስማት ቀጠሮ መያዙን በመቃወም ነው ፡፡ ነገር ግን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በዳኝነት አይቶ ውሣኔ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንኡስ አንቀፅ 3/ሀ/ ተደንግጓል ፡፡ ከዚህም ሌላ ማናቸውም ፍርድ ቤት ክርክሩን በሚሰማበት ጊዜ በመጀመሪያ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ ተገቢ መስሎ የታየውን ብይን ሲሰጥ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ (የሰበር አቤቱታ) ሊቀርብ እንደማይችል ፤ ስለሆነም ለክርክሩ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመቃወሚያው ላይ በተሰጠው ብይን ያለውን ቅሬታ ጨምሮ ከስረ ነገሩ ጋር ይግባኝ (የሰበር አቤቱታ) ለማቅረብ እንደሚቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 320(3) ስር ተደንግጓል

ቅሬታ የቀረበበት ብይን ይዘትና ተገቢነት ያላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ከላይ የተመለከተው በመሆኑ አመልካች በተሰጠው ብይን ላይ ቅሬታ ካለውም በስረ-ነገሩ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ይህንን ቅሬታም ጨምሮ በአንድ ላይ በማጠቃለል ያቀርባል እንጂ ክርክሩ እንዲቀጥል በተደረገበት ሁኔታ በብይኑ ላይ የሰበር አቤቱታ ማቅረቡ ህጉን መሠረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. አመልካች ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ሳያገኝ ለሰበር ችሎት ያቀረበውን አቤቱታ ለማስተናገድ የሚቻልበት የህግ መሠረት የሌለ በመሆኑ አቤቱታውን አልተቀበልነውም፡፡

2. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በማዕከላዊ ዞን ማዕከላዊ ፍርድ ቤት የአብይ አዲ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 02634 ግንቦት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ባሳለፈው ብይን ላይ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት የሚቻል አይደለም ብለናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ በ05/01/2008 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የአፈፃፀም ዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይባፍ፡፡

4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 113973

ቀን 21/04/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጠጅቱ ኡርጋ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ገመዳ ሬባ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ሜታ ሮቢ ወ/ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በዚህ ወረዳ ፍ/ቤት ባለቤታቸው በነበሩት አቶ አሰፋ ገመዳ ላይ ክስ የመሰረቱት ኤደ ከተባለ አከባቢ የሚገኝ ሁለት የበሬ መዋያ መሬት እና ሰምንተኛ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ግማሽ የበሬ መዋያ ይዞታ መሬታችንን እኩል እንደንካፈል ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን ተከሳሽ በበኩላቸው የተጠቀሰው ይዞታ መሬት የጋራ ይዞታችን አይደለም ሊካፈል አይገባም ብለዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው ግራ ቀኙ የሚከረከሩበት መሬት የግል ይዞታዬ ነው በስሜ ተለክቶ የሚገኝ እና በስሜ የምግብርበት ነው ከሳሽና ተከሳሽ በዚህ መሬት ላይ አንዳችም መብት የላቸውም ብለው ተከራካረዋል፡፡

ከሳሽ (የአሁኑ አመልካች) በበኩላቸው ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት በ1994 ዓ/ም ከተከሳሽ ጋር ስንጋባ የተከሳሽ አባት የሆኑት ጣልቃ ገብ ሰጥተውን በጋብቻ ውላችን ላይም ተጠቅሶ ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ በይዞታችን ስር ሆኖ ስንጠቀምበት ቆይተናል፡፡ ሰሞንኛ ተብሎ ከሚታወቀው አካባቢ ባለን ይዞታ ላይ ቤት ያለን ሲሆን በመ/ቁ. 15710 እና 14792 በሆኑ መዝገቦች በዚህ ቤት ውስጥ ሆኜ ልጆችን እንደሳደግ ፍ/ቤት አዞልኛል የጣልቃ ገብ አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ ብለው ተከራከረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙ ምስክሮችን ሰምቶ ክርክራቸው ከቀረበው ማስረጃ ጋር በማገናዘብ መርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት በጋብቻ ውሉ ላይ የተመዘገበ እና ከሳሽና ተከሳሽ ይዘውት ሲጠቀሙበት የቆዩ በመሆኑ ጣልቃ ገብ የመሬቱ ይዞታ በስማቸው የሚገኝና ግብር በስማቸው የሚገብርበት ቢሆንም ከሳሽና ተከሳሽ ይዘው የሚጠቀሙበትን መሬት ጣልቃ ገብ መጠየቅ አይችሉም ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት ከሳሽና ተከሳሽ እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

ጣልቃ ገብ (የአሁኑ ተጠሪ) በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት የስር ከሳሽና ተከሳሽ ሲጋቡ ይ/ባይ (የስር ጣልቃ ገብ) የሰጠው መሆኑን የስር ከሳሽ ምስክሮች ያስረዳ ቢሆንም መሬት የሚሰጠው በቃል ሳይሆን በጽሁፍ ማስረጃ ሆኖ ስልጣን ባለው አካል መመዝገብ እንዳለበት ከገጠር መሬት አዋጅና ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መረዳት ይቻላል፡፡ መሬቱ የጣልቃ ገብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ለይግባኝ መልስ ሰጭ ከባለቤታቸው ጋር በህጋዊ መንገድ የተሰጠ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ የጋብቻ ውሉም ለወደፊቱ ከአባታችን ላይ የምናገኛው መሬት የሚል በመሆኑ እና ከዚያ ወዲህም የተደረገ ስጦታ የሌለ በመሆኑ ክርክር ያስነሳው መሬት የይግባኝ ባይ (የስር ጣልቃ ገብ) ይዞታ ነው በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ ክርክር ያስነሳውን መሬት ይ/ባይ ከስር ተከሳሽ ጋር በሚጋቡበት ጊዜ በጋብቻ ውላቸው ላይ የተገለጸ እና ከዚያ ወዲህ ይ/ባይ ከባለቤታቸው ጋር እየተጠቀሙበት የቆዩ መሆኑ ተመስክሯል የቀበሌው አስተዳደር ለወረዳ ፍ/ቤት በጻፈው ሪፖርት ላይም መሬቱን ተጋቢዎቹ በጋራ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑን ገልጿል፡፡ የመሬት እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ለወ/ፍ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ መሬቱ በመልስ ሰጭ (በስር ጣልቃ ገብ) ስም የተለካ መሆኑን ነገር ግን እየተጠቀሙበት ያሉት ተጋቢዎቹ መሆናቸውን ገልጿል፡፡ መሬቱ በጋብቻ ውል ላይ የተጠቀሰ መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱም ከዚያ ወዲህም ተጋቢዎቹ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ መ/ሰጭ በስሙ በመመዝገቡ ብቻ እስካሁን ያልተጠቀሙበትን መሬት በስሜ ተለክቷል በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡ ቤት የሰሩበትን መሬት ይ/ባይ ቀደም ሲል እንደኖርበት በፍ/ቤት ተውስኖልኛል ብለው ያቀረቡትን መከራካሪያ መ/ሰጭ አላስተባበሉም ክርክር ያስናሳውን መሬት ይ/ባይ ከባለቤታቸው ጋር ሊካፈሉ ይገባል በማለት የከፍ/ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ለማስረም ለኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ሰበር ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማገናዘብ መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ተጠሪዋ ከባለቤቷ አባት (ከአመልካች) ያገኙትና ለ9 ዓመት ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑ በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ የገጠር መሬት አጠቃቀም ደንብ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 መሰረት የገጠር መሬት ስጦታ በጽሁፍ መሆንና መመዝገብ አለበት ተጠሪ መሬቱን በጋብቻ ወቅት በስጦታ ያገኙ ስለመሆኑ አግባብነት ያለው ማስረጃ አቅርበው ያላረጋገጡ በመሆኑ ክርክር ያስነሳው መሬት የአመልካች (የስር ጣ/ገብ) ይዞታ ነው በማለት ወረዳ እና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት ውሳኔን በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ በመዘርዘር እንዲታረምላቸውን አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች አከራካሪውን 2 ጥማድ እርሻ መሬት ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ከስር ተከሳሽ ጋር እስከተፋቱበት ጊዜ 2003 ዓ/ም ድረስ በጋራ ሲጠቀሙ መቆየታቸው ተረጋግጦ እያለ መሬቱን ልትካፈል አይገባም ተብሎ ጥያቄዋ በክልሉ ሰበር ችሎት ተቀባይነት የማጣቱን አግባብነት ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙ በጽሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጋር በማገናዘብ አቤቱታው እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ክርክር ያስነሳውን መሬት አመልካች የስር ተከሳሽ ከነበሩበት ባለቤታቸው ጋር በ1994 ዓ/ም ሲጋቡ የባለቤታቸው አባት የሆኑት ተጠሪ ሰጥተዋቸው በጋብቻ ውላቸው ላይም ተጠቅሶ ጋብቻ ከመሰረቱበት ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ጋብቻው በፍቺ እስከፈረሰበት 2003 ዓ/ም ድረስ ተጋቢዎቹ በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ ፍሬ ነገርን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተረጋግጧል፡፡ ክርክር ያስነሳው መሬት ተመዝግቦ የሚገኘው እና ግብር የሚከፈልበት በተጠሪው ስም ቢሆንም ይህን መሬት ለአመልካቹ እና ለባለቤታቸው ሰጡ ከተባለበት ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2003 ዓ/ም ድረስ ተጠሪ ተጠቅመውበት የማያውቁ መሆኑና ሲጠቀሙበት የቆዩት አመልካች ከባለቤታቸው (የስር ተከሳሽ) ጋር መሆኑ በስር ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ማንኛውም አርሶአደር በመሬት ይዞታው የመጠቀም መብቱን በዚያ መሬት ገቢ ለሚተዳደሩ ወይም ሌላ ገቢ ለሌላቸው የቤተሰብ አባላት ወይም መሬት ለሌላቸው ልጆቹ በስጦታ ማስተላለፍ እንደሚችል በኦሮሚያ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1997 አንቀጽ 9(5) ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በጽሁፍ የተደረጉ የስጦታ ውል ባይኖርም ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት በተጠሪ ስም ተመዝግቦ ያለ መሆኑን ነገር ግን እየተጠቀሙበት ያሉት አመልካች እና ባለቤታቸው መሆኑን ገልጻ ለሜታ ሮቢ ወ/ፍ/ቤት መልስ የሰጠ ሲሆን የቀበሌው አስተዳደርም ለስር ፍ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ ለክርክር ምክንያት በሆነው መሬት አመልካች ከባለቤታቸው ጋር ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑን ገልጿል፡፡ ስር ፍ/ቤት ቀርበው የተሰሙ የአመልካች ምስክሮችም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሬቱን ተጠሪ ሰጥተዋቸው አመልካችና ባለቤታቸው ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ተጠሪ ለክርክር ምክንያት በሆነው መሬት ላይ የነበራቸውን የመጠቀም መብት ልጃቸው የሆነው የአመልካች ባለቤት ከአመልካች ጋር ጋብቻ ሲፈጽሙ በዚህ መሬት እንዲተዳደሩ በአባትነታቸው አስልፈው ሰጥተው ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ አመልካች ከባለቤታቸው ጋር በፍቺ ውሳኔ እስከተለያዩበት 2003 ዓ/ም ድረስ ሲጠቀሙበት የቆዩ በመሆኑ በመሬቱ የነበራቸውን የተጠቃሚነት መብት ካስተላለፉ በኋላ መሬቱ ተመዝግቦ የሚገኘው እና ግብርም የሚከፈለው በተጠሪው ስም ብቻ በመሆኑ መሬቱ ለተጠሪ ሊመለስላቸው ይገባል ማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት እንደቤተሰብ በእኔ ስር ሆነው አመልካች ባለቤቷ ተጠቀሙ እንጂ በግላቸው ስር ሆኖ አንድም ቀን አልተጠቀሙበትም በማለት ተጠሪ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት መልስ የተጠቀሱ ቢሆንም ይህን ስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክራቸው አላስረዳም፡፡ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተረጋገጠው መሬቱን ተጠሪ ለአመልካች ከሰጡ በኃላ ሲጠቀሙበት የቆዩት አመልካች እና ባለቤታቸው መሆናቸውን ነው፡፡ በገጠር መሬት ላይ የሚኖረው መብት የመጠቀም መብት ሲሆን ተጠሪ ይህን መብታቸውን ለአመልካችና ባለቤታቸው አሳልፈው ሰጥተው ለረጅም ጊዜ በዚህ መሬት ላይ ተጠቃሚነታቸው በተቋረጠበት ሁኔታ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በጽሁፍ የተደረገ ስጦታ ውል አለመኖሩን ብቻ መሰረት በማድረግ በክርክሩ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆነ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 55478 በቀን 3/03/2006 ዓ/ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.186326 በቀን 26/08/2007 ዓ/ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ሜታ ሮቤ ወ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.15357 በቀን 10/01/2006 ዓ/ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 170790 በቀን 8/11/2006 ዓ/ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት የአመልካች እና ባለቤታቸው የነበሩተ የስር ተከሳሽ የጋራ ይዘት ነው ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ላደረጉት ክርክር ያወጡትን ወጪ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ዕልባት ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105054

ታህሳስ 22 ቀን 2008ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲ.ጋ.ጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጌጤ እጅጉ -ቀርበዋል

ተጠሪ፡-አቶ ብርሃኑ ተሰማ -ቀርቧል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ነው፡፡ የአቤቱታውን ይዘትም ባጭሩ በመ/ቁ.343/96 በቀን 21/8/1996 ዓ/ም የነበረው ጋብቻ ሲፈርስ ንብረት ክፍፍል በሚመለከት በእርቅ ውል ስምምነት በሽማግሌ የተደረገው እርቅ በፍርድ ቤት ተመዝግቦ ተዘግተዋል፡፡ በዚሁ መሰረትም አንድ ወፍጮ ቤት፤ አንድ የዘይት መጭመቂያ ቤት እና አንድ ፒፒሻ ሽጉጥ የተጠሪው እንደሆነ ፍርድ ቤት በውሳኔው አረጋግጠዋል፡፡ ከውሳኔ በኃላ ታርቀን በባልና ሚስት ሆነን ስንኖር የዲገሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት መ/ቁ.19963 በቀን 9/8/ 2005ዓ/ም እና የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.6054 በቀን 19/10/05ዓ/ም በመ/ቁ. 343/96 በሆነው መዝገብ ላይ የተሰጠ የንብረት ክፍፍል እንዳይነካ ሲል ተወስነዋል፡፡ ስለዚህ የወፍጮ ቤት የነበረው አሁን የእንጨት መሰንጠቂያ የሆነው እና የዘይት መጭመቂያ ቤት ስም ይዛወርልኝ ፒፒሻ ሽጉጥ ታስረክበኝ ወይም ግምቱ 26,000 ብር እንዲከፈለኝ ሲሉ አፈፃፀም መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በሰጡት መልስ በ1996 ዓ/ም ባልና ሚስት መሆናችን የማይካድ እውነት ነው፡፡ ትዳር ሲፈርስ ለኔ የተሰጠኝ የያዝኩት እንጂ የተጠሪ አይደለም፡፡ ያልተወሰነበት የሚፈፅምበት ነገር የለም፡፡ በእጄ የሌለውን ነገር ለመፈፀም አልገደድም፡፡ ጋብቻ ከፈረሰ የሰራሁት በስሜ ካርታ አውጥቼ የሚሰራበት ነው በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ማስረጃ በመመዘን በውላቸው መሰረት መፈፀም አለበት በማለት የዘይት መጨመቂያና የወፍጮ ቤት የነበረ ወደ እንጨት መሰንጠቂያ የተቀየረው ወደ ተጠሪ ስም እንዲዛወር እና ሽጥጥ እንዲያስረክቡ ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡

በዚሁ ትእዛዝ ላይ ከአሁኑ አመልካች ይግባኝ የቀረበለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በሽጥጥ የተሰጠው ትእዛዝ በማሻሻል በሌሎቹ ንብረቶች ላይ የስር ፍርድ ቤት በማፅናት ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡ በመቀጠል ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታ በአመልካች በመቅረቡ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኃላ የዘይት መጭመቂያ በተመለከተ የተሰጠው ትእዛዝ በማፅናት፤ ወፍጮ ቤት የነበረው ወደ እንጨት መሰንጠቂያ ቤቱ የተጠሪ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ እንጨት ድርጅት ሲቀየር ማሽኖቹና መሳሪያዎቹ የተገዙት እንደ ባልና ሚስት በአንድ ቤት በሚኖርበት ጊዜ ስለሆነ ማሽኖቹና ዕቃዎቹ በባለሙያ ተገምቶ ግምቱ ወይም በጨረታ በመሸጥ እኩል እንዲካፈሉ በማለት በመሻሻል ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የለበትም ሲል አቤቱታው ሳይቀበለው በትእዛዝ ዘግቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ የእንጨት ድርጅት የተቋቋመው ወፍጮ ቤት የነበረው በ1996ዓ/ም በስምምነት ከተካፈሉ በኃላ እንደገና እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ መሆኑ ባልተካደበት በተደረገው የንብረት ክፍፍል ስምምነት መሰረት ቤቱ የተጠሪ ነው ተብሏል በሚል መነሻ አመልካች በአፈፃፀም መዝገብ ላይ ለተጠሪ እንድትለቅ የተሰጠው ትእዛዝ ህጋዊ የክርክር አካሄድና አመራርን የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባ ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን በዚህ መሰረትም በጭብጥነት በተያዘው ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፤ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ ጉዳዩ የአፈፃፀም ክስ ስለሆነ በዋናው ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈፀም መደረግ አለበት፡፡ በግራ ቀኙ የተማመኑበት ጉዳይ በመሐከላቸው የነበረው ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የንብረት ክፍፍል በስምምነት በማድረግ በፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቶ የፀደቀ ነው፡፡ ከፍቺ በኃላም እንደባልና ሚስት አብረው እየኖሩ እንደነበር በስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ በ2005ዓ/ም የአሁኑ ተጠሪ የፍቺ ክስ ለፍርድ ቤት አቅርበው ነገር ግን ጋብቻ የለም ግንኙታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደ ባልና ሚስት አብረው እንደሚኖሩ ሰዎች የሚባል ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አብረው ያፈሩት ንብረት የጋራ እንዲሆንና በ1996 ዓ/ም የተደረገው ክፍፍል የተጠበቀ መሆኑን ውሳኔ ተሰጥተዋል፡፡

ውሳኔው ይህ ከሆነ አፈፃፀሙን የዘይት መጭመቂያና የወፍጮ ቤት ለተጠሪ የደረሰው መሆኑን አመልካችም የራስዋ ድርሻ እንደያዘች ከስር መዝገብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከፍቺ በኃላ አብረው መኖር ከጀመሩ ያፈሩት ንብረት መኖር አለመኖሩን ለማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ወፍጮ ቤት የነበረው ወደ የእንጨት ድርጅት ሲቀየር የተለያዩ ማሽኖችና ዕቃዎች አብረው ያፈሯቸው እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም አብረው ያፈሩት ማሽኖችና እቃዎች እኩል አንዲካፈሉ፤ ቤቱ ደግሞ ለተጠሪ እንዲሆን በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚሁ መሰረትም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠ/ ፍ/ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.181913 በቀን 12/10/2006 ዓ/ም የስር

   ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በማሻሻል ሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.185727 በቀን 22/11/2006ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት አጽንተናል፡፡

2. በዚህ ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነሰተዋል ለሚመለከተው አካል ይተላለፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

   መዝገብ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102662

የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ለሼ- ጠበቃ ኤርሚያስ ደስታ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ በቀለ በላቸው- ወኪል ትርፍነሽ በቀለ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ጋብቻ ፈርሷል ሊባል የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደብረብርሃን ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ክሱን ያቀረቡት የአሁኑ አመልካች ናቸው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ከአሁኑ ተጠሪ ጋር በአገር ባህል የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓት ጋብቻ ፈጽመው ለአርባ አመታት ያህል አብረው መኖራቸውን፣ ይሁን እንጂ ከመስከረም 2006 ዓ/ም ጀምሮ ሊስማሙ ባለመቻላቸው በመካከላቸው ሰላም እንደሌለ ገልፅው ጋብቻው ፈርሶ የጋራ ንብረት እንዲካፈሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ከአመልካች ጋር ባልና ሚስት የነበሩ መሆኑን ሳይክዱ አመልካች ከአስራ ዘጠኝ አመታት በፊት ቤቱን ጥለው መሄዳቸውንና ተለያይተው የሚኖሩ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያስቀደሙ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ ከአመልካች ጋር ያፈሩት የጋራ ንብረት የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ ከአስር አመታት በፊት ፈርሷል የሚል ድምዳሜ ደርሶ የአመልካች ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሑፍ አከራክሯል፡፡እንዲሁም የወረዳው ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ እንዲመጣ አድርጓል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በተጠሪና በአመልካች መካከል ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ተገቢነት አለውን? የሚለውነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ በአመልካችናበተጠሪ መካከልየነበረውጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል በማለት በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር አልተቀበለውም፡፡ ፍርድ ቤቱ ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው የጋብቻ ግንኙነታቸው ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ ተቋርጦ ግራ ቀኙ ለየብቻ መኖር መጀመራቸው ተረጋግጧል በሚል አቢይ ምክንያት ነው፡፡ ይህ የወረዳው ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ የሆነ ስልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ አመልካች በዚህ ችሎት አጥብቀው የሚከራከሩት ግራ ቀኙ ሌላ ትዳር መስርተው የራሳቸውን ሕይወት የማይኖሩ መሆኑን፣ አልፎ አልፎ በጤና ምክንያት አመልካች ለፀበል ወደ ሌላ ቦታ ከመሄዳቸው ውጪ አመልካችና ተጠሪ ያልተለያዩና እስከ መስከረም 2006 ዓ/ም ድረስ አንድ ላይ የሚኖሩ መሆኑን ዘርዝረው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው አስገዳጅ ውሳኔ ተጠቅሶ መወሰኑ ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14290፣ 20983፣ 31891፣ 67924 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ከሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ የወረዳው ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገውና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 31891 ሌሎች ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት በሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች በባልና ሚስት መካከል ያለ ጋብቻ በፍ/ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ ፈርሷል ባይባልም የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረጅም ጊዜ መኖር፣ በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መሥርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በሕጋዊ መንገድ ተቋርጧል ሊያስብል ይችላል በማለት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም ውሳኔ ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው የጋብቻ መፍረስ በተጋቢዎች የረዥም ጊዜ መለያየት ሊከናወን የሚችል መሆኑና ፍርድ ቤቱም በዚህ አግባብ የፈረሰውን ጋብቻ እንደገና እንዲፈርስ ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ነው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 67924 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ አግባብ የመተጋገዝና የመተባበር ግዴታቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲወጡና የነበሩና ያልተለያዩ መሆኑ ከተረጋገጠ ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ለማለት የማይቻል መሆኑን በመዝገቡ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች በመነሳት የተወሰነ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካችና ተጠሪ በሕጉ አግባብ ጋብቻ መሰርተው ልጆችን ከወለዱ በኋላ በ1987 ዓ/ም ጀምሮ በአካል ተለያይተው ለአስራ ዘጠኝ አመታት ያህል ሳይገናኙ የኖሩ መሆኑን ከግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል የተረጋገጠ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ደምድመዋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀረበው የወረዳው ፍርድ ቤት ዋና መዝገብም የግራ ቀኙ ምስክሮች የመሰከሩት የፍሬ ነገር ነጥብ በይዘቱ የበታች ፍርድ ቤቶች ከደመደሙት ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ተገንዝቦአል፡፡ በመሆኑም አመልካች ከተጠሪ ጋር እስከ መስከረም 2006 ዓ/ም ድረስ አልተለያየንም በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታ በስር ፍርደ ቤት ዋና መዝገብ ውስጥ በምስክሮች ከተነገረው የምስክርነት ቃል ይዘትና ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ከደረሱበት ድምዳሜ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች አግባብ የተሰጠውን ስልጣንም ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ ጋብቻ በተጋቢዎች መካከል የመተጋገዝ፣ የመከባበርና መደጋገፍ እንዲሁም አብሮ የመኖር ግዴታን የሚጥል መሆኑን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 60 እና 61 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚሁ አኳያ በተጠሪና በአመልካች መካከል የነበረው ጋብቻ ይህ ሰበር ችሎት አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳይ ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ተቋርጧል? ወይንስ አልተቋረጠም? የሚለውን ለመወሰን ከፍ ብሎ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በጋብቻ ውስጥ በግራ ቀኙ የሚጠበቁ ግዴታዎች ባግባቡ ሲተገበሩ ያልነበሩና እነዚህን ግዴታዎችን ለመወጣት ደግሞ በአመልካች በኩል ያጋጠመው ሁኔታ በሕጉ የተጣሉባቸውን ግዴታቸውን ለመወጣት የማያስችል የነበረ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ከተጠሪ ጋር አልተለያየንም፣ በጤና ችግር ምክንያት አልፎ አልፎ ለፀበል ሌላ ቦታ እሄድ ነበር በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በክርክሩ ሂደት በማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን መሰረት አድርጎ ያልቀረበ ሁኖ አግንተነዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተያዘው መዝገብና ይህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸው መዛግብት የያዟቸው መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ከዚህ መዝገብ ከተረጋገጡት እውነታዎች ሙሉ በሙሉ የተመሳሳይነት ያላቸው ሁኖ እያለ አመልካችም ሆነ ተጠሪ ሌላ ትዳር መስርተው ሕይወታቸውን በመምራት ላይ አይገኙም በማለት በሰ/መ/ቁጥር 31891 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመተውና ግንኙነቱ ያልተቋረጠ ተጋቢዎችን መሰረት ተደርጎ በመ/ቁጥር 67924 የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ አመልካች መከራከራቸው ከአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2 (1) አተገባበር ጋር የሚጋጭ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ በሁኔታ የፈረሰ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ እና ለጉዳዩ አግባብነት በላቸው ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት በተሰጠው ትርጉም መሰረት የጋራ ንብረት ጥያቄም በአስር አመት ያልቀረበ በመሆኑ የተጠሪ ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ብይን መሰጠቱ የሚነቀፍበትን የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሁኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0108191/06 በ22/08/2006 ተሠጥቶ በሰሜን ሸዋ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0114418 በ30/08/2006 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 030-5041 ግንቦት 19 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል በአገር ባህል የጋብቻ አፈፃጸም ስርዓት ተመስርቶ የነበረው ጋብቻ ለረዥም ጊዜ ተለያይቶ በመኖር ምክንያት ፈርሷል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

ከደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርደ ቤት የመጣ መዝገብ ቁጥር 0108191/06 በመጣበት አካሂን ይመለስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 116977

የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች ፡- ወ/ሪት ሃና ታምራት ጠበቃ አሰፋ ካሳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍርድ ቤት ውድቅ በማድረጉና በየደረጃው ያሉ የከተማው አስተዳደር የበላይ ፍርድ ቤቶችም የመ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናታቸው ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 08 ቀን 2007 ዓ/ም ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ቃሉ፡- ቀድም ሲል ጸሐይ ብርሃኔ እና ሀና ታምራት እየተባልኩ በሁለት ስም ስለምጠራ ጸሐይ ብርሃኔ መባሌ ቀርቶ ሃና ታምራት ብቻ እየተባልኩ እንድጠራ ውሳኔ ይሰጠኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም አመልካች የአቶ ታምራት አመዴ ልጅ ለመሆናቸው ከሚመለከተው ፍርድ ቤት የልጅነት ውሳኔ ይዘው ሲቀርቡ መዝገቡ ይቅረብ በማለት መዝገቡን የዘጋው ሲሆን በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ የሰበር አቤቱታቸው ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ሁለት ስም የነበረኝ በመሆኑ የግል ስሜና የወላጅ አባቴ ስም ተቀይሮ በአንዱ የግል ስም እና በአሳዳጊዬ የቤተዘመድ ስም እንድጠራ ያቀረብኩት አቤቱታ ውድቅ መደረጉ ከሕግ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን አመልካች በወላጅ አባቱ ስም እንዲጠራ ይወሰንልኝ ሲሉ ያቀረቡትን አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመርህ ደረጃ አንድ ሰው የቤተዘመድ ስም(family name)፣አንድ ወይም ከዚያ በላይ የግል ስሞች(first names) እና የአባት ስም(patronymic) እንደሚኖረው በፍ/ህ/ቁ/32(1) የተደነገገ ሲሆን ለልጁ የአባት ስም የሚሆነው ደግሞ የአባቱ የግል ስም እንደሆነ በቁጥር 36 ተመልክቷል፡፡

በመሰረቱ እያንዳንዱ ሰው አንድ የቤተዘመድ ስምና አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞች እና የአባት ስም እንደሚኖረው፣እንዲሁም ለልጁ የአባት ስም የሚሆነው የአባቱ የግል ስም እንደሆነ በፍ.ሕ.ቁ.32(1) እና 36(1) ድንጋጌዎች ተመልክቶአል፡፡አንድ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች በአባቱ ብቻ ሳይሆን በአሳዳጊው ስም ጭምር ሊጠራ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው የሚታወቅ ሲሆን እንዲህ ዓይነቱ ሰው ተገቢ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በአሳዳጊው ስም ጭምር መጠራቱ ቀሪ ሆኖ ከላይ በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ መሰረት በአባቱ ስም ብቻ እንዲጠራ የመወሰን መብት ያለው በመሆኑ ይህንኑ መብቱን በፍርድ ለማረጋገጥ የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ አመልካች ክሱን ያቀረቡት ከሚጠሩበት ሁለት የግልና የቤተዘመድ ስሞች መካከል ባንዱ እንዲጠሩ ሲጠሩበት ከነበረው የቤተዘበመድ ስሞች መካከል ደግሞ አሁን ለመጠራት የፈለጉት ወላጅ አባቱ በሚሉት ሰው ስም ሳይሆን የአሳዳጊያቸው ስም በመምረጥ መሆኑን ከዳኝነት ጥያቄአቸው ይዘት ለመንገዘብ ችለናል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በአሳዳጊያቸው ስም እንዲጠሩ በፍርድ ቤት ዳኝነት የሚያገኙበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ ከግል ስሞቻቸው መካከል ደግሞ ሃና ተብዬ ልጠራ፣ ፀሐይ መባሌ ይቅርልኝ ብለው በአማራጭ የጠየቁት የሰበር የዳኝነት ጥያቄ የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ወላጅ አባቴ ናቸው በማይሏቸው ሰው የቤተዘመድ ስም ልጠራ ይገባል በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በሕጉ ስለስም ለውጥ ጥያቄ ማቅረብ ስለሚቻልባቸውና የዳኝነት አካሉም ለመቀበል መሟላት ከሚገባቸው ሕጋዊ መስፈርቶች ይዘትና ሕጋዊ ውጤት ጋር አብሮ የማይሄድ በመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 87420 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የቤተዘመድ ስሙ አሳዳጊ በሆኑ ሰው ሲጠሩ የነበሩት አመልካች በትክክለኛ ስጋ ወላጆቻቸው ስም ለመጠራት ባቀረቡት ጥያቄ የተሰጠ ሲሆን በሰ/መ/ቁጥር 95995 የቀረበው ጉዳይም አመልካች ክሱን ያቀረቡት በሚጠሩበት የአሳዳጊያቸው ስም የተሰጡ ሰነዶችን ወደሚጠሩበት አባታቸው ስም በሕግ አግባብ ለማስቀየር እና እነዚሁ ሰነዶች በሚሰጡት መብት ለመገልገል ጭምር ስለመሆኑ ታይቶ ዳኝነት የተሰጠበት በመሆኑ ከአሁኑ ጉዳይ ጋር በመሰረታዊ የፍሬ ነገርና የሕግ ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይነተ የሌለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ ይህ ችሎት በእነዚህ መዛግብት የተሠጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ክርክርና የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘው ጭብጥ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 117/08 በቀን 13/11/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/23938 በቀን 17/11/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የከተማው አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/24066 በቀን 6/12/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ወላጅ አባታቸው ባልሁኑት አቶ ታምራት አመዴ ስም እንዲጠሩ የጠየቁት የዳኝነት ጥያቄ ስለልጅነታቸው ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ሲያቀርቡ የሚታይ ነው ተብሎ ውድቅ በመደረጉ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 103721

የካቲት 03 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፉ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሰሚራ ጀማል ከጠበቃ ሰለሞን ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. አቶ ጀማል እንዲሪስ ከጠበቃ መሰረት ስዩም ጋር ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ሉላ አረፈ አልቀረቡም

3ኛ.አቶ ሀጎስ አብዱራህማን በመዝገብ ቤት በኩል እንዲሰሙ ተናግሯል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ለየካቲት 01 ቀን 2008 ዓ/ም ቀጠሮ የያዘ ሲሆን በዚህም መሰረት መዝገቡን መርምረን በአዳሪ በዚሁ እለት የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በአሁን አመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔ መሰረት መፍረሱን ተከትሉ በአሁን አመልካች የጋራ ንብረት ድርሻ ጥያቄ መነሻ የስር ፍ/ቤቶች የጋብቻ ውጤት በሆነው የንብረት ክርክር ላይ የሰጡትን ዳኝነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ካስነሳው የውሳኔ ክፍል አንፃር ተመልክቶ የውሳኔውን አግባብነት ከግራ ቀኙና ክርክሩ የሚመለከተው ሆኖ የተገኘው 3ኛ ተጠሪም ካቀረቡት ክርክር ጋር በማገናዘብ አስፈላጊውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም አመጣጥ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው በአሁን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል ሚያዚያ 21 ቀን 1987 ዓ/ም ተደርጎ የነበረው ጋብቻ ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ/ም በፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተክትሎ የአሁን ተጠሪ ሀምሌ 27 ቀን 2003 ዓ/ም ተሻሽሎ ባቀረቡ ማመልከቻ የጋራ ንብረት ናቸው ያሏቸውን ናቸው የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረቶች በመዘርዘር ድርሻቸው ተለይቶ ይወሰንላቸው ዘንድ ተገቢ የነበሩትን የአሁን 1ኛ ተጠሪን እና የ1ኛ ተጠሪ ሌላ ሚስት የሆነችን የአሁን 2ኛ ተጠሪን በተከሳሽነት ላይ ደመወዝ በዚሁ የጋብቻ ውጤት በሆነው የንብረት ድርሻ ጥያቄ ላይ፣ እንደዚህም 1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረትን ሲያስተዳድር የደረሰው፣ ጉዳት ሲታወቅ በኃላ ተገቢውን የካሳ ለአመልካች እንዳይከፍል ይወሰንልኝ በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ እንደክርክራቸው ያስረዳልናል ያሏቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃም አያይዘው አቀርበናል፡፡

የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የጋራ ንብረት ናቸው በሚል በአሁን አመልካች የክስ ማመልከቻ ላይ ከተዘረዘሩት ንብረቶች የጋራ ንብረት የሆኑትን በማመን፣ በጋራ ሀብትነት የማይታወቁትን፤ የሚያገኙትን ደግሞ በመካድ በአመልካች ክስ በተዘረዘረው የንብረት ዝርዝር አንፃር መልስ የሰጡ ሲሆን፤ በንብረት አስተዳደር ረገድ ያደረስኩት ጉዳት የሌላ በመሆኑ የሰጠው ጥያቄ አይመለከተኝም በማለት ክርክራቸውን አቅርቧዋል፡፡ ለክርክሩም ድጋፍ ያላቸውን ማስረጃዎች አያይዘው አቅርበዋል፡፡

የአሁን 3ኛ ተጠሪም የጋራ ንብረት ነው በሚል በአሁን አመልካች ከተጠቀሱት ንብረቶችና መካከል በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍል ከተማ ወረዳ 3 ክልል በቤት ቁጥር 2545 የሚታወቀውን ቤት በውል አዋዋዩ ክፍል ዘንድ ጂ. ኤስ. ኤ.ጀኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ከተባለው ድርጅት የገዙት ስለሆነ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ ይወሰንልኝ በማለት በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብተውም ተከራክረዋል፡፡ ለዚህም ክርክራቸው ለማስረጃነት ሰነዶችን እንዳቀረበም የመዝገቡ መልሰን ያስረዳል፡፡

እኚሁ ጣልቃ ገብ ያቀረቡትን ክርክር አስመልክቶ የአሁን አመልካች ጣልቃገብ ፍ/ቤቱ በንብረቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ በሰጠበት ንብረት ላይ ግዥ የፈጸሙ ስለሆነ የሽያጭ ውሉ ከጅምሩ ፈራሽ ስለሆነ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ይህንኑ በቁጥር 2545 ተመዝግቦ የሚታወቀውን ቤት አስመልክቶ ንብረቱ በማናቸውም ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ የጋራ ንብረት ባለመሆኑ እንጂ የጋራ ንብረት ተቆጥሮ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት አመልካች ባቀረቡት ክስ ቀጥተኛ መልስ የሰጡ ከመሆኑም በላይ በጣልቃ ገብ በኩል የቀረበው ክርክር አስመልክቶ ደግሞ ተቃውሞ የሌለባቸው መሆኑን ገልጸናል፡፡

ሁሉም ወገኖች ከላይ ባጭሩ ለይዞታ ደረጃ የተገለጸውን የጽሁፍ ክርክር ካደረጉ በኋላ ለጉዳዩም ላይ የቃል ክርክር እንዳደረጉ መዝገቡ ያስረዳል፡፡

የስር ፍ/ቤትም ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት በአከራካሪነታቸው በጭብጥነት ተይዘው ከማስረጃ አንፃር ለማየት ዳኝነት ያስፈልጋቸዋል፡፡ በማለት ከሙግት ደረጃ ደርሶ ለማስረጃ ሰምቶ ዳኝነት ካሳረፈባቸው ንብረቶች መካከል በአከራካሪያቸው ከዚህ ሰበር ደረጃ ዘልቀው ከደረሱት መካከል አንዱ በቤት ቁጥር 2545 የተመዘገበውን ቤት አስመልክቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች በጋብቻ ዘንድ የተፈራውን ይህንኑ ንብረት ከእኔ ለማሸሽ ሲል ያለ እኔ ፈቃድ ጀ. ኤስ.ኤ አጀኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ወደ ተባለው ድርጅት በመዋጨነት አስገምቶ አሸሽቶ የሰጠ በመሆኑ፤ እንዲሁም ይህን ንብረት የአሁን 3ኛ ተጠሪ ፍ/ቤቱ በንብረቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ ከተሰጠበት በኋላ እንዲገዙት የተደረገ ስለሆነ ንብረቱ የጋራ ሀብት መሆኑ ታውቆ በድርሻዬ ልከፍል ይገባል በማለት የተከራከሩ ቢሆንም በኢፊድሪ የፍትህ ሚንስተር የሰነዶች ማረጋገጫና ከዘገባ ጽ/ቤት በቀን 10/3/2002 ዓ/ም በተፈረመ የጂ ኤስ ኤ ጀነራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር የመመስረቻ ጽሁፍ ይዘው በቤት ቁጥር 2545 ተመዝግቦ የሚታወቀው በ1ኛ ተጠሪ አማካኝነት በመጭነት የተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ሚያዚያ 16 ቀን 2002 ዓ/ም በተካሄደ የጂ ኤስ ኤ.ኤጀኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ለሂሳብ 1ኛ ተጠሪ በማህበሩ የየራሳቸውን አክስዮን በብር 240,000.00 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ ሸጠው የተሰራበት መሆኑ በኢፈደሪ የፍትህ ሚኒስቴር ማስረጃ ማረጋገጫ ምዝገባ ጽ/ቤት ማህተም በተረጋጠ ሰነድ ተረጋግጧል ጂ. ኤስ ጀኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/ የግል ማህበር ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም በተፃፈና በሰነዶች ማረጋገጫና መዝገብ ጽ/ቤት በተመዘገበ የሽያጭ ውል ይህንኑ የቤት ቁጥር 2545 የሆነው በብር 240,000.00 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ ለጣልቃ ገብ ለአሁን 3ኛ ተጠሪ አብዱራህማን አህመድ የተሸጠ ስለመሆኑም በጣልቃ ገብ አማካኝነት በቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧ በመሆኑም ይኸው ቤት ከ1ኛ ተጠሪ እጅ ሙሉ በሙሉ ወጥቶ በጂ ኤስ. ኤ.ተራ ደንብ ኃ/የተ/የግል ማህበር ተጠቃሎ ተላልፏል የተስፋፋውም የአመልካችና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ እንዳይፈርስ የፍቺ ጥያቄ ለመቅረቡ በፊት እና ለፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ በፊት ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

የጋራ የሆነውን ንብረት ያለ ሁለተኛው ተጋቢ ፈቃድ በአንደኛው ተጋቢ አማካኝነት ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 68/ሀ/ እና 69 እንደተደነገገው ፈቅደን ባልሰጠው ተጋቢ ጥያቄ መሰረት ንብረቱ የተላለፈበት ግዴታ እንዲፈርስ ካልተደረገ በቀር በተፈጸፀመው የንብረት ማስተላለፍ ስምምነት ውስጥ ተጋቢዎች እንደታሰበው ግምት እንደሚሰጡ ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች በዚህ በመ/ቁ 2545 የተደረገውን የሽያጭ ስምምነት በመቃወም በፍ/ቤት ጥያቄ አቅርበው ያስወሰኑት የለም፡፡ ስለሆነም ንብረቱን ከእኔ ለማሸሽ ሲል ለኢ.ኤስ.ኤ ትሬድንግ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር በመውጫ ሰጥቷል የፍ/ቤቱን ዕግድ በመጣስ ሸጦታል በማለት ያቀረቡት ክርክር ራሱ ችሎ መቅረብ የነበረበት ክርክር እንጅ በዚህ አሁን በቀረበው ክርክር ሊታይ የማይችል ከመሆኑም በላይ ንብረቱ ወደ ማህበሩ የተዛወረው በአመልካች በኩል የፍቺ ጥያቄ ለመቅረብና የዕግድ ትዕዛዝ ከመተላለፉ በፊት ስለሆነ የመ/ቁጥር 2545 የሚታወቀው ቤት የአመልካችና የተጠሪዎች የጋራ ሀብት ሳይሆን ጣልቃ ገብ በግዥ ያገኙት ንብረት ነው በማለት ወስኗል፡፡ እንዲሁም በዘምዘም ባንክ አ/ማህበር በተጠሪዎች ስም የአክሲዮን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድርሻ የለም፣ በባንክ ስማችን የተቀመጠ ገንዘብ የለም በማለት ተጠሪዎች ቢከራከሩም ፍ/ቤቱ ስላቀረበው ማስረጃ ጭምር የተረጋገጠ ሆኖ ተገኝቷል በማለት ተረጋግጧል ባለው የገንዘብ መጠን መሰረት የአሁን አመልካች ድርሻ እንዳላቸው ገልፆ ዳኝነት ሰጥቶበታል በሌላ በኩል ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ወቅት ንብረት በማስተዳደር በኩል የፈፀሙት ጉድለት ያለመሆኑ ያለ መሆኑ ተጣርቶ ከተረጋገጠ በኋላ ለማ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ይሁን እንጅ ተጋቢዎች በጋብቻቸው ዘመን የጋራ ንብረታቸውን በጋራ እንዲያስተዳድሩ በሕጉ ግምት የሚወስድ ሲሆን ይህን ግምት ማፍረስ የሚቻለው አንደኛው ተጋቢ የሌለውን መብት የሚጎዳ ተግባር ፈፅሞ ስለመገኘቱ የማረጋገጥ ማስረጃ የቀረበ እንደሆነ በሕጉ አንቀፅ 87 ተደንግጓል 1ኛ ተጠሪ ንብረት ሲያስተዳድሩ ፈፀሙ በሚል በማስረጃ የተረጋገጠና ተለይቶ የታወቀ ጉድለት ያልተገኘ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጥያቄውን አልተቀበለውም የሚለውን ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ፍ/ቤቱ ለሰጠው ዳኝነት በምክንያትነት ያሰፈረውን ሐተታ እና የሰጠውን የዳኝነት ዓይነት ከዚህ በላይ ባሰፈረው አኳኋን በሰጠው የፍርድ ክፍል ላይ ከገለፀው በኋላ በፍርድ መሰረት የተረጋገጠውንና ሊረጋገጥ ያልቻለውን ምስክር አስመልክቶ የፍርድ ተከታይ በሆነው የውሳኔ ክፍል ላይ

በቂርቆስ ክ/ከተማ በቀሌ 02/03 ክልል በቤት ቁጥር 297 ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ የሚገኘውን ቤት አመልካችና ተጠሪዎች በጋራ ያፈሩት ንብረቶች ስለሆነ የክፍፍሉንም መንገድና ስልት ከመጥቀስ ጋር ሶስቱም እኩል እንዲከፈሉ በን/ስ/ላፍ/ክፍለ ከተማ በመ/ቁጥር 2545 የግልግል ሀብት ነው፤

1ኛ ተጠሪ በቴክኖሎጅ ሲስተም ኃ/የተ/የግ/ማህበር ያላቸውን ሸር፣ በፒስ ደልለን ኃ/የተ/የማህበር ውስጥ ያለው ሸር 2ኛ ተጠሪ በዘምዘም ባንክ አ/ማህበር ያላቸው በሁለተኛ ተጠሪ ስም በዳሸን ባንክ ስለ አካባቢ ቅርንጫፍ በ1ኛ ተጠሪ ስም በወጋገን ባንክ ተ/ኃይማኖት ቅርንጫፍ በ1ኛ ተጠሪ ስም በዳሸን ባንክ ስለ አካባቢ ያስቀመጠውን ገንዘብ ከእነ መጠኑ በመግለፅ ሶስቱም እኩል እንዲካፈሉ በማለት በከ/መ/ቁ 61875 በቀን 13/10/2004 ዓ.ም ወስኖ ግራ ቀኙን አሰናብቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት በከ/መ/ቁ 125893 ሁሉንም ወገኖች ከክርክር በኋላ

የቤት ቁጥር 2545 አስመልክቶ የቀረበውን ጉዳይ በሚመለከት በዚሁ ቤት ላይ የስር ፍ/ቤት የካቲት 16/2003 ዓ.ም የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ቤቱ በ1ኛ አማካኝነት በመውጫነት ወደ ጅ.ኤስ.ኤ ጀኔራል ትሬድግግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ገብቶ የነበረ እና 1ኛ ተጠሪ በማህበሩ ውስጥ የነበራቸውን 4127/4/ለ/2002 በቀን 12/9/2002 መተላለፉን የሰነዶች ማረጋገጫ ፅ/ቤት ለስር ፍ/ቤት በቀን 20/4/2004 ዓ.ም ከላከው ማስረጃ አረጋግጧል፡፡ እንዲሁም የዚሁ ቤት ስመ-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሀብትነት ወደ ጆኤስኤ ጀኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በቀን 04/8/2002 በቁጥር ን/ስ/ቀ/05/83/3805/02 የተላለፈ ስለመሆኑ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት አስተዳደርና ግንባታ ፅ/ቤት የካቲት 14 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈና ለስር ፍ/ቤት ክላከው ሰነድ ተረጋግጧል፡፡

ቤቱ ወደ ሶስተኛ ወገን በተላለፈበት ጊዜ ግንቦት 1/2002 ዓ.ም ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ የነበሩ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው የፍቺ ውሳኔ ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም ይኸው ንብረት በጋብቻ ጊዜ ወደ ሶስተኛ ወገን ሲተላለፍ መተላለፉን አላወቀም ነበር የሚሉ ሲሆን አሁን ለዚህ ችሎት ውሉ እንዲፈርስ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ጥያቄ አቅርበው እየተከራከሩ እንደሚገኙ በገለፁት መልኩ ይኸው ውል በማስፈረስ መብታቸውን ከሚያስከብሩ በቀር በጠየቁት ዳኝነት አኳኋን ሊስተናገድ የሚችል አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሲያፀናው በ1ኛ ተጠሪ እና በ2ኛ ተጠሪ ስም የሚገኘውን የሼር ሀብት መጠንን በሚመለከት ማህበሮቹ ለስራ ተሰማርተው ያገኙትን ትርፍ ሁሉ አጠቃሎ መወሰን ሲገባው ማህበሮች በተቋቋሙበት ጊዜ በተደረገው መነሻ ይካተታል መጠን ላይ መወሰኑ አግባብ አለመሆኑን እንዲሁም በልዩ ልዩ በባንኮች በእነዚሁ ተጠሪዎች ስም አንፃር ይገኛል የተባለውን ሀብት መጠን አስመልክቶ ፍ/ቤቱ ገንዘብ ስለመኖሩ በጠየቀበት ጊዜ በባንኮች ተቀምጦ ተገኝቷል የተባለውን የገንዘብ መጠን ሳይሆን በትዳር በነበሩበት ጊዜ አንደኛዉ ወገን ብቻ በማውጣት ለግል ጥቅም ተጠቅሞበታል ከሚያሰኝ በቀር ለጋራ ጥቅም እንደዋለ አያስቀጥርም በማለት መነሻ ሊሆን ከሚችለው ጊዜ ጋር በማስተያየት በባንኮች ካላቸው ሂሳብ እንቅስቃሴ በመነሳት መሠረት የሚገባዉ መሆኑን ጠቅሰን በዚሁ መሠረት እራሱ ይግባኝ በከካሽ ፍርድ ቤት ጉዳዮን ተመልክቶ የገንዘቡን መጠን በፍርዱ የውሣኔ ክፍፍል በተገለፀው አኳኋን ከፍ አድርጎ በሚሻሻል መወሰን ፤

በሸር ድርሻ ላይ የተወሰነውን የድርሻ መጠንን ክላይ በተመለከተው መሠረት ከውሳነ በኃላ የክፍፍል ማስረጃን በሚመለከት 1ኛ መልሰ ሰጭ በሀብቱም ማህበሮች የተወሰነላቸውን የአክስዮን ድርሻ ለተቻለ እና ተጠሪዎች የሚስማሙ ከሆነ በአባልነት እንዲቀጥሉ ይህ ካልተቻለ ተሸጦ የሸያጩን ድርሻ ይከፈላቸው የአክስዮኖች አሻሻጭም በንግድ ህግ አንቀጽ 523 እና ተከታዮች ድንጋጌዎች እንደዚሁም የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.57288 በሰጠው የህግ ትርጉም መሠረት ሆኖ ድርሻቸው እንዲሰጣቸውና እንዲሁም በቤት ቁጥር 2545 ውስጥ/ የተሰጠውን ዕቃ በሚመለከት ቀርቧል በተባለው የወንጀል ክስ ምርመራ ውጤት መሠረት የአሁኑ አመልካች ጥያቄ የማቅርብ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን ከዚህ በላይ ከተገለፁት በቀር ሥማቸው በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የፀና መሆኑን ለመግለፅ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል የወሰነ መሆኑን ከፍርዱ ግልባጭ ተረድተናል ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረም ይገባል በማለት ለቅሬታቸው መሠረት ያደረጉት የቤት ቁጥር 2545 የሆነው ቤት የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው ወይስ የአሁን 3ኛ ተጠሪ የሚለውን ለይቶ በመወሰን ረገድ፤እንዲሁም በሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ የተረጋገጠባቸውን የአክስዮን ድርሻዎ የክፍፍሉን መንገድ በሚመለከት የአክስዮን ድርሻዎች በሚገኙበት ማህበር በአባልነት እንድቀጥል በማድረግ መወሰን ስገባው ማህበሩ ለተስማማ በሚል ተገልፆ የህግ መሠረት የለውም ለሚሉት መወሰኑ ነጥቦች ላይ ።።

ተጠሪዎችም በበኩላቸው ክርክር በሚመለከታቸው ክርክር አንፃር በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም የሚሉበትን ምክንያት በመጥቀስ ተከራክረዋል።።

እንግዲህ የጉዳዮ አነሳስ፤የክርክሩ ይዘትና የሥር ፍ/ቤቶች በየደረጃው የሰጡት ዳኝነት ፤የዚህን ዳኝነት አግባብነት በሚመለከት ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር በይዘት ደረጃ ከላይ ከፍ ሲል ባጭር ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን ፤እኛም ጉዳዮን እንደሚከተለው መርምረናል ።። ተመልክተናል ።።

ጉዳዮን እንደመረመርነውም በቤት ቁጥር 2545 የተመለከተውን ቤት አስመልክቶ የአሁን አመልካች ከሥር ፍ/ቤት ጀምሮ ለክርክራቸው መሠረት ያደረጉት ንብረቱ በሽያጭ ወደ አሁን 3ኛ ተጠሪ የተላለፈው ፍ/ቤቱ በዚሁ ንብረት ላይ ዕግድ ከሰጡበት በኃላ የፍ/ቤቱ ዕግድ ተጥሶ ስለሆነ የሽያጭ ተግባሩ ዋጋ አልባ ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል የሚለውን አንደኛው የክርክር ነጥብ ሲሆን የዚህኑ ክርክር አግባብነት ለዚሁ ጉዳዮ በሥር ፍ/ቤቶች በነበረው የክርክር ሂደት በማስረጃ ከተረጋገጠው የፍሬ ነገር ጉዳይ በመነሳት ተመልክተናል ።።

የአሁን አመልካች ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን ክስ ከቀረቡ በኃላ የክርክሩ ውጤት እስክታወቅ በሚል ይኸው ቤት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የዕግድ ትእዛዝ የሰጡት የካቲት 16 ቀን 2003 ዓ.ም መሆኑና ይኸው ቤት በአሁን 1ኛ ተጠሪ አማካኝነት በዓይነት በመወጫነት ወደ ጂ.ኤስ.ኤ ጀኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የገባውና ስመ ሀብትነቱም ወደ ዚሁ ማህበር ስም የተላለፈው ይኸው የወሰነበት የዕግድ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው።። የአንድ ንብረት ባለሀብት ማን ነው የሚለው የሚወሰነው ደግሞ ንብረት ከአንዱ ወደ ሌላው ለማስተላለፍ የሚያስችለው እንደ ሽያጭ ስጦታ ወዘተ የመሳሰሉት ህጋዊ ተግባሮች በህግ ፊት በሚፀና አኳኋን ተፈፅመው እንደሆነ እና በዚሁ አኳኋን በተፈፀመው ህጋዊ ተግባር የተነሣ በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብት ያገኘ ሰው ንብረቱን ካስተላለፈዉ ተፈጥሯዊም ሆነ የህግ ሰው ባሻገር ማናቸውንም 3ኛ ወገን ለመመለስ የሚያስችለውን የስመ ሀብት ዝውውር ሥርዓት ሁሉ ታከናውኖ እንደሆነ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1678 ፣1731፣1184፣1195 ተደንግጓል፡፡ አሁን የተያዘውን ጉዳይ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንፃር ስነየው ክርክር ያስነሰው ንብረት በ1ኛ ተጠሪ እና ጀ አስ ኤ ጀኔራል ትሬዲንግ መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት ይኽው ንብረት በዓይነት በመወሰኑ ወደ ከማህበሩ ገብቶ፤ ማህበሩ በዚሁ ንብነት ላይ መብትና ግዴታ ያቋቋመ ሲሆን ከዚሁ ንብረት ወደ ማህበሩ መግበት የተነሰ ለአስተላለፈውም ግዴታ ፈጥሮለታል ይህ በህግ የተፈቀደ ንብረት ሊተላለፍ የሚችለበት አንዱ ህጋዊ ተግበር ሲሆን ማህበሩ በዚሁ ንብረት ላይ የእኔ በይ በመጣ ለመመለስ ዋስትና የሆነውን የስመ ሀብት ዝውውር ሥርዓት ሁሉ ፈፅሟ፡፡ በዚህም መሠረት የዚሁ ንብረት የበላቤትነት መብት ያለው ይኽው ማህበር እንጂ ሌላ ማናቸውም ወገን ሊሆን አይችልም ይህን በንብረት ላይ ያለን የበለሀብትነት መብት ማህበሩ ያቋቋመው ፍ/ቤቱ በንብረቱ ላይ የፅግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ነው ከዚህ በንብረቱ ላይ የበለቤትነት መብት ከቋቋመ በኃላ በዚህ በህግ ከቋቋመው ላይ የበለቤትናት መብቱ ተጠብቆም በንብረቱ ላይ የማዘዝ ወደ ሌላ 3ኛ ወገን የመስተልለፍ መብት ያለው ሲሆን ሌላ ማየናቸውም 3ኛ ወገን ይህንኑ ንብረት ለሚመለከት ከመህበሩ ጋር በሚያደረገው ህጋዊ ተግበር ወደ እራሱ ያዛወረው ከሆነ ንብረቱን ለማዘወር መብትና ስልጣን ከለው ወገን ያገኘ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለመለየት ማህበር ንብረቱን በሸጠበት ጊዜ በንብረቱ ላይ የተመለከተውን ስመ ሀብትነት ምዝገባ የሚከተል እንጂ 3ኛ ወገን ከማህበሩ ጋር ግብይት የፈፀመበት ጊዜ ሊሆን አይችልም ከዚህ በላይ ንብረት ከንደኛው ወገን ወደ ሌላው ሊተላለፍ የሚችልበትን መንገድ በሚመለከት በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተቀመጡት ሁለት ቋሚ መሚያዎች ማናቸውም በንብረት ላይ ሊኖር የሚችለው ግብዓት በህግ ዋስትና ተሰጥቶት በህ/ሰብ ደረጃ ያለስጋት የሠለጠ ኢኮኒሚያዊ ግንኙት ለመፍጠር እንዲያስችል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአሁን አመልካች የፍ/ቤቱ የፅግድ ትዕዛዝ ከተለለፈ በኃላ 3ኛው ተጠሪ ከማህበሩ ጋር የሽያጭ ውል ያደረገበትን ጊዜ ተንተርሰው የሚያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

ከዚህም በቀር የማይንቀሳቀስ ንብረት በዓይነት ለመውጫ ወደ አክሲሆን ማህበር ወይም ወደ ኩባንያ ስለመዘወሩ በመመስረቻ ፅሑፍ ሰፍሮና በዚህ መስረጃ መዝገብ ጽ/ቤት ተመዝግቦ በማንቀሰቀስ ንብረት በመዝገብ ውስጥ መመዝገቡ ከተረጋገጠ የ3ኛ ወገኖችን ላይ ለመመለስ የሚያስችለው ሥርዓት መሚለቱን እንደሚያመለክት ይህ ለሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀርቦ ተመሰሰይ በሆነው በሰበር መ/ቁ.. 27869 ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ በመሆኑም ጭምር ከፅግድ ትዕዛዝ ጋር በተያየዘ የአሁን አመልካች የሚያቀርብበት ክርክር በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረተዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን የሚያመለክት ህጋዊ መሰረት የለው ክርክር አይደለም ሌላውና ይህንኑ በቤት ቁጥር 2545 የተመለከተውን ቤት አስመልክቶ የአሁን አመልካች ያቀረቡት ክርክር በዋጅ ቁጥር 2/3/92 ስለጋራ የበልና ሚስት ሀብት አስተዳደርና ጥበቃ በህጉ የተቀመጠውን የተጋቢዎች የጋራ ስምምነትን አስፈላጊነት በመጥቀስ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጋራ ሃብት የሆነን ንብረት አንደኛው ተጋቢ ያለ ሌላኛው ተጋቢ ስምምነት ለሌላ ሶስተኛ ወገን በሽያጭ ማስተላለፍ እንደማይችል በዚሁ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 68 የተደነገገ ሲሆን፤ ይህ ድንጋጌ በይዘቱ የጋራ በሆነ ንብረት ላይ ተጋቢዎች እኩል መብት ያላቸው መሆኑን በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 34(1) የተመለከተውን ህገ-መግስታዊ ድንጋጌ ተከትሎ የተደነገገ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በአገር በማህበረሰብ ውስጥ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረገው ግብይት ያለማነቆ በሰለጠ አካኋን እንዲፈጸም ካልተደረገ በአገር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን እንቅፋት በማየት ይህ ከላይ የተመከተው የጋራ ስምምነት አስፈላጊነት በሁኔታ ላይ እንዲመረኮዝ በማስፈለጉ ተከታይ በሆነው አንቀጽ 69 እንደተመለከተው አንደኛው ተጋቢ ያለፈቃዱ ንብረቱ በአንደኛው ተጋቢ ብቻ መሸጡን በተረዳ ጊዜ ይህ የሽያጭ ተግባር በህጉ የተሰጠውን መብት የጣሰ መሆኑን መነሻ አድርጎ በክስ አማካኝነት ማስፈረስ እንደሚቻል፤ ይህንኑ የማስፈረስ ተግባሩን ካልተጠቀመ፤ ወይም በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የማስፈረስ ጥያቄው ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ካልቀረበ ግን አንደኛው ተጋቢ ብቻውን የፈጸመው ህጋዊ ተግባር እንደጸና እንደሚቀር እንጂ የጋራ ስምምነት ባለመኖሩ ምክንያት ብቻ ንብረቱ የተላለፈበትን ግብይት ወይም የሽያጭ ውል በዘፈቀደ በማናቸውም ጊዜ መቃወም እንደማይቻል ተደንግጓል። ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ዳኝነት የህጉን ትክክለኛ አፈጻጸም የተከተለ እንጂ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመ አይደለም።

የአሁን አመልካችም ይህንኑ ተገንዝበው ክርክራቸው በይግባኝ ደረጃ ለደረሰበት ጊዜ በዚሁ ስርዓት መሰረት በንብረት ላይ ያላቸውን መብታቸውን ለማስከበር ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ክስ አቅርበው በክርክር ላይ የሚገኙ መሆኑን የገለጹ በመሆኑና ይህ ችሎም ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ ይህንኑ የተባለውን በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበውን የኮ/መ/ቁ. 194776 የሆነውን መዝገብም አስቀርበን እንደተመከትነው ጥያቄውን በዚያው አግባብ ማቅረባቸውን ተገንዝበናል። ይኸው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ለጊዜው የዘጋው የፌዴራል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 125895 የቀረበለትን የይግባኝ ጉዳይ መርምሮ የመጨረሻ ዳኝነት እስኪሰጥበት ጊዜ ድረስ በማገዱ ምክንያት በመሆኑና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዳኝነት የሰጠበት ጉዳይ ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች በፍርዳቸው ላይ እንደገለጹት መብታቸውን ከሚያስከብሩ በቀር በዚህ የጋራ ንብረት መሆኑ ተረጋግጦ የጋራ ሃብትን ለማከፋፈል እንዲቻል በቀረበው መዝገብ ላይ ወደ ሶስተኛ ወገን በሽያጭ አማካኝነት ተላልፎ የባልና ሚስት የጋራ ሃብት መሆኑ ያልተረጋገጠውን የቤት ቁጥር 2545 እንደጋራ ሃብት ሊቆጠር ይገባል በማለት የሚያቀ ርቡት ክርክር ተቀባይነት ያለውም አይደለም።

ሌላውና ለዚህ የሰበር ጉዳይ የክርክር ምክንያት የሆነው ለአሁን አመልካች ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛው ፍ/ቤት አሻሽሎ በወሰነላቸው የአክሲዮን ሼር ድርሻ ላይ ያላቸውን ሀብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያገኙበትን ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሚስማማ ከሆነ በአባልነት እንዲቀጥሉ ይህ ካልሆነም ተሽጦ የሸያጭ ድርሻ እንዲያገኙ በማለት በንግድ ህግ ቁጥር 523 እና ተከታዮቹ የተመለከተውን መሠረት በማድረግና በሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መ/ቁ.57288 የተሰጠውን ትዕዛዝ በመከተል የሰጠውን ዳኝነት አግባብነቱን አስመልክቶ ግራ ቀኙ ክርክር ያደረጉበት ጉዳይ ነው፡፡

ይህንንም ጉዳይ እንደተመለከትነው በማናቸውም ምክንያት በፍ/ቤት በሚሰጥ ፍርድ የሚረጋገጠው መብት ከተብ ወይም ከውል የመነጨውን መብት መኖርና አለመኖር አስመልክቶ እንዲህኑ አነጋገር ለማስረዳት የቀረበውን ክርክርና ክርክሩን አነጋገር ለማስረዳት የቀረበውን ክርክርና ክርክርን ለማስረዳት የቀረበውን መብት ወደ ተግባር ይህንኑ ከህግ እንዲያስችል ለመብት ምንጭ የሆነውን ህግ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ከዚህም አንፃር ጉዳዩን አግባብነት ካለው ህግ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

አግባብነት ካላቸው ህጎች አንዱ ይኸው የአክቢዮን ድርሻ ግራ ቀኙ በጋብቻ ዘን በነበሩበት ጊዜ የተፈራ የጋራ ሀብት እንደመሆኑ መጠን በሀብቱ የባለእኩልነት ድርሻቸውን የሚቃረጋግጠው አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62 አንዱ ሲሆን እንዲሁም ከዚሁ የጋራ ሀብት ነው፡፡ ከተባለው የሀብት ዓይነት አንፃር ሊታይ ደግሞ የዚህ የጋራ ሀብት የክፍፍል ሁኔታ የሀብቱን ጉዳይ ምክንያት በማድረግ በሚደነግገው በንግድ ህጉ አንቀጽ 523 የተመለከተው ድንጋጌ ደግሞ ሌላው ነው፡፡ ስለሆነም የዚህኑ ክፍፍል ሥርዓት የሚደረግበትን መንገድ በሚመለከት የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በንግድ ህጉ አንቀጽ 523 ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት ማድረግ የሚያነቀፍ አይደለም፡፡ ሆኖም ይህንኑ ድንጋጌ እንደሙሉ ይዘቱ አይነት ተፈፃሚ በማድረግ ስለሆነም የአሁኑ አመልካች በፍርድ በተረጋገጠላቸው የአክሲዮን ድርሻ ባት መብት ላይ ከንግድ ህጉ አንቀጽ 523 አንፃር አየቶ መብቱን ለማረጋገጥ መነሻ ለሆኑ ከሚገባቸው የህጉ ክልሎች መካከል በንግድ ህጉ አንቀጽ 523/2/ እንደተመለከተው የአክሲዮን ማህበር መመሥረቻ ፅሑፍ የይዙቱ የአሁን አመልካች በማህበሩ አባልነት ተካተው በአባልነት ይህንኑ ለፍርድ በተረጋገጡባቸው የአክሲዮን ድርሻ ሀብት መገልገል የሚቻሉ መሆኑንና አለመሆኑን አስመልክቶ ምን እንደሚል ከመመስረቻ ፅሑፍ ጋር አገናዝቦ ከታየ በኋላ ሊታይ የሚገባው እንጂ ሆና እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ዳኝነት በዚህ ረገድ የተባለ ሆኖ አላገኘነውም ስለሆነም በዚሁ የነግድ ህግ ቁጥር 523/2/ ድንጋጌ ተትክክለኛ አፈፃፀሙን ተከትሎ ፍርድ በመስጠት ረገድ የታየው ጉድለት ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.61875በቀን 13/10/2004 ዓ5ም የሰጠውን ፍርድ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ12559 ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 325/1/ መሠረት አሻሽለን ወስነናል፡፡
2. በን/ስ/ላ/ከተማ ወረዳ 03 ክልል ውስጥ በመ/ቁጥር 2545 ተመዝግቦ የሚታወቀው ቤት ላይ የባለቤትነት መብት ያለው የአሁን 3ኛ ተጠሪ አቶ ሐገስ አብዱራህማን ናቸው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለአሁን አመልካች በፍርድ በተረጋገጡላቸው የአክሲዮን ድርሻና መጠን ላይ ባላገሯው የሀብት መብት ላይ መገልገል የሚቻልበት ማበህበሩ አባልነት ተካተው በአባልነት ነው ወይስ በአባልነት መገልገሉ የሚቻሉበት ህጋዊ ምክንያት ታይቶ በሐራጁ ተሸጦ ይህንኑ ሀብት እንደያገኙት ነው?የሚባለው ጭብጥ ከማህበሩ መመስረቻ ፅሑፍ ይዘት እና ከንግድ ህጉ አንቀጽ 523/2/ አንፃር ታይቶ ይወሰልን ዘንድ ብቻ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ.343/1/ መሠረት ወደ ሥር ፈ/ቤት መልሰናል፡፡
4. የዚህ ክርክር ውጤት እስኪታወቅ ድረስ በሚል በዚህ የስር መዝገብ ቁጥር 103721 ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
5. የዚህ የሰበር ክርክር ጉዳይ ስላስከተው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መቁ.103151

መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ብሩ አየለ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መርዕድ ብስራት - ጠበቃ አበበ ማስረሻ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- የሥር ከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የወላጅ አባቱ እና የ2ኛ ተከሳሽ የጋራ ንብረት የሆነውን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር አዲስ ካረታ ቁ.3329 የሆነውን ቤት 2ኛ ተከሳሽ ከሞግዚትነት ስልጣን ተቃራኒ ሚያዝያ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገ ሽያጭ ውል ለ1ኛ ተከሳሽ በብር 350,000 የሸጠች ስለሆነ 1ኛ ተከሳሽም /የአሁኑ አመልካች/ የከሳሽና የሌሎች ሰዎች የጋራ ንብረት መሆኑን እያወቀ ለቅን ልቡና ተቃራኒ በሆነ መንገድ ስለገዛ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስልኝ፣ 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን እንዲያስረክበኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ ተከሳሾች መልስ እንዲሰጡበት የታዘዘ ሲሆን የሥር 1ኛ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/መጥሪያ ደርሶት የጽሑፍ መልስ ስላልሰጠ ታልፏል፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽ በሰጠችው መልስ ባለቤቴ ከሞተ በኋላ ልጆች ለማሳደግ የተቸገርኩ በመሆኑ የቤት ሽያጭ ውል ፈጽሜአለሁ፡፡ 1ኛ ተከሳሽም የቤቱን ሽያጭ ገንዘብ እንደውሉ አልከፈለኝም፤ እኔ ቤቱን የሸጥኩኝ ለከሳሽና ለሁለት ወንድሞቹ ጥቅም እንጂ ለግሌ ጥቅም አይደለም፤ ፍ/ቤቱ የመሰለውን ውሳኔ ቢሰጥ አልቃወምም በማለት ተከራክራለች፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ክርክር በሚሰማበት ቀን ቀርቦ ሲከራከር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥ ትችላለች፣ እኔ በቤቱ ላይ ሰፊ ለውጥ ያደረኩ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር፣ የከሳሽን የሰው ምስክር በመስማት በሰጠው ውሳኔ በተከሳሾች መካከል ሚያዝያ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የልጆችን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ስለተፈጸመ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ይመለሱ፣ 2ኛ ተከሳሽ ብር 60,000 ለ1ኛ ተከሳሽ ትመልስ፣ 1ኛ ተከሳሽ በገዙት ይዞታ ሲገለገሉበት በነበረው ቤት ላይ ያወጡት ወጪ ካለ ክስ አቅርቦ መጠየቅ ይችላል በማለት ወስኗል፡፡ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ማመልከቻውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ፣ የቤቱ ሽያጭ ዋጋ በአብዛኛው ስላልተከፈለ 2ኛ ተከሳሽ ለግል ጥቅም አውላለች፣ የልጆች ቅጥም ላይ ጉዳት ድርሷል የሚያስብል ስላልሆነ፣የሽያጭ ውሉን ለማፍረስ በቂና አሳማኝ ምክንያት ስለሌለ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሥር ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሽ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ማመልከቻውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ፣ የቤት ሽያጭ ውሉ የከሳሽን ጥቅም የሚጎዳ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የፌዴራል የመጀመያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታም ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ የቀረበ ነው፡፡

የአሁን አመልካች ሐምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የተጠሪ ሞግዚትና አስተዳዳሪ የነበሩት ወ/ሮ ክብካብ አስፋው የቤት ሽያጭ ውሉን ያደረጉት ለተጠሪ እና ለሌሎች ሁለት ወንድሞቻቸው መልካም አስተዳደር ስለሆነ ውሉን የተደረገው ለልጆቹ ቅጥም መዋሉ በተጠሪም ሞግዚት በጽሑፍ እና በምስክሮች በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ ውሉ ሊፈረስ ይገባል በማለት የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የተጠሪ ሞግዚት ከተቀበለችው የቤት ሽያጭ ውሉ ገንዘብ የተጠሪ ድርሻ ብር 10,000 ብቻ ስለሆነ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም፡፡ አመልካች ቤቱን ከገዛሁ በኋላ ሌላ አዲስ ሰርቪስ ቤት ክፍሎች ብር 450,000 በላይ ወጪ በማድረግ በቤቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ የይዘት ለውጥ አድረጎበታል፡፡ ስለዚህ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሉ ፈርሶ ወደ ነበራችሁበት ተመለሱ በማለት የወሰኑት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለው ስለሆነ እንዲሻርልኝ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎትም መዝገቡን በመመርመር "በአመልካች እና በተጠሪ ሞግዚት መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስ ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከመዝገብ ቁ.46490 አንጻር ለመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በታዘዘው መሰረት መስከረም 7 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱ ይዘትም፡- የተጠሪ ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥ አትችልም። እኔ ከቤቱ ድርሻ እያለኝ ያለ እኔ ፈቃድ ሸጣለች። የተጠሪ መብት መጣስ እና መጎዳት የሚጀምረው ከዚህ መሰረታዊ ከሆነው የባለቤትነት መብቶች አኳያ ስንነሳ ነው። እኔ በቤቱ ሽያጭ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰብኝ አስረድቼአለሁ፣ አመልካች ግን ከሽያጩ ጥቅም ያገኘሁት መሆኑን አላስረዳም። አመልካች ከቤቱ ሽያጭ ገንዘብ የከፈለው ብር 60,000 ብቻ ሲሆን ቤቱን ተረክቦ እያኖረበት ነው፣ ከጉዳት በቀር ጥቅም ሊኖር አይችልም። ተጠሪው በሽያጩ ጉዳት እንጂ ያገኘሁት ጥቅም ስለሌለ ለሰበር መዝገብ ቁ.46490 ከሰጠው ውሳኔ ጋር የማይቃረን ስለሆነ ውሳኔው እንዲፀናልኝ፣ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልኝ። አመልካች ከቤቱ ድርሻ የተጠሪ ድርሻ 10,000 ብር ብቻ ስለሆነ ሊፈርስ አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር የባለቤትነት መብትን የጣሰ እና ሕጉ ተቃራኒ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም። አመልካቹ በቤቱ ላይ ግንባታ ስለመካሄዱ ያቀረበው ማስረጃም የለም፣ በቤቱም ላይ የይዘትም ሆነ የቅርጽ ለውጥ አላደረገም፣ የተጠሪ ሞግዚት የቤት ሽያጩን ገንዘብ ማባከናቸውን እንጂ ለልጆች ጥቅም ያወሉት መሆኑን ያረጋገጠ ማስረጃ የለም። ስለዚህ አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀናልኝ፣ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል። አመልካች ጥቅምት 04 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተ ሲሆን፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል። መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ባቀረበው ክስ የሸያጭ ውል የተፈጸመበት ቤት ላይ ድረሻ እያለኝ የእኔን ጥቅም በሚጎዳ መልክ ሞግዚት የሆነችው ወ/ሮ ክብካብ ሣህሉ ወልደማርያም በሽጨጭ ውል ለአመልካች የሸጠች ስለሆነ ውሉ እንዲፈርስልኝ በማለት አልክቷል። የተጠሪ ሞግዚት /የሥር 2ኛ ተከሳሽ/ በጽሑፍ ባቀረበችው መልስ ቤቱን የሸጥኩት ለተጠሪ እና ለሌሎች ወንድሞቹ ቅጥም ነው በማለት የተከራከረች ቢሆንም እንደምስክር ሆነ በሰጠችው ቃል ደግሞ ከቤቱ ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ ብር 60,000 ብቻ የተቀበለች እንደሆነና ለራሷ ትምህርት ክፍያ እንደከፈለችና ቀሪውን ለወንድሟ እንዳበደረች ገልጻለች። አመልካች በበኩሉ መጥሪያ ደርሶት የፍሑፍ መልስ ባለመስጠቱ የታለፈ ስለሆነ የጽሑፍ መልስ እና ማስረጃ በማቅረብ በማስረዳት መከራከር የነበረበትን ክርክር በተመለከተ መብት አጥቷል። ስለዚህ አልካች በጽሑፍ መከራከር የነበረበትና ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት የነበረበትን ፍሬ ነገር በተመለከተ አሁን ለማንሳት የሚችልበት የሕግ መሰረት የለውም። ተጠሪ ባቀረበው ክርክር አመልካች ከተጠሪ ሞግዚት ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቤት ሽያጭ ውሉን ሲፈጽም በቤቱ ላይ ልጆች ድርሻ ያላቸው መሆኑን ውሉ እያመለከተ ነው ቤቱን የገዛው የሚለውን፣ አመልካች ይህን ፍሬ ነገር ክዶ እየተከራከረ አይደለም፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው በሞግዚቱ በኩል የተደረገው የቤቱ ሽያጭ ለልጆች ጥቅም ነው እንጂ ጥቅማቸውን የሚጎዳ አይደለም የሚል ነው፡፡ የተጠሪ እናት የሆነችው የሥር 2ኛ ተከሳሽ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.213/1992 አንቀጽ 220/1/ መሰረት ሕጋዊ የሞግዚትነት ስልጣን እንደተሰጣቸው ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት የሥር 2ኛ ተከሳሽ ተጠሪን በመወከል ሕጋዊ ተግባሮችን ለተጠሪ ጥቅም ለመፈጸም ስልጣን የተሰጣቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚሁ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 277 የሞግዚት ስልጣን በተመለከተ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከመሸጥ ጋር ተያይዞ የሚለው ነገር የለውም፡፡ ነገር ግን ሕጉ ሞግዚት መሸጥ የሚችላቸውን የንብረት ዓይነቶች በመዘርዘር በማስቀመጡ፣ ከዚህ ዝርዝር ወጭ ያሉትን ንብርቶች በተመለከተ ሞግዚት መሸጥ አይችልም ቢባል እንኳን ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ፈጽሞ ከተገኘ ግን ምላሽ ለማግኘት ሌላ ሕግ መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ ይታያል፡፡ ከዚህ አንጻር የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.213/1992 አንቀጽ 306 እንደሚደነግገው "የሕግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች፤ ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሠራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ" የሚል ነው ፡፡ በዚህ መሰረት ተወካዩ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ በመውጣት የሰራውን ስራ በተመለከተ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2207/1/ እንደሚያመለክተው "ተወካዩ ከስልጣኑ ውጭ የሠራው ስራ በቅን ልቡና ሆኖ ሲገኝ ሥራውን ወካዩ እንዲያጸድቅለት ይገደዳል" የሚል ነው፡፡ በዚህ አግባብ የሞግዚቱ "ቅን ልቡና" መታየት ያለበት የተሰራ ስራ የልጁን ጥቅም የሚጎዳ ነው ወይስ አይደለም? ከሚል አንጻር መሆን እንዳለበት ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁ.46490 መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት ለልጆች መልካም አስተዳደግና ጥቅም የሸጠ መሆኑ ከተረጋገጠ የሽያጭ ውል ለማፍረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ማለት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭን በተመለከተ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚል ጭብጥ መታየት ያለበት ለልጆች ቅጥም መሆን አለመሆኑን በማጣራት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በተጠሪ ሞግዚት እና በአልመካች መካከል የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል ለተጠሪ እና ለሌሎች ወንድሞቹ ጥቅም የዋለ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ሲታይ ለተጠሪ ጥቅም መዋሉን የሚያመለክት ምንም ነገር የለም፡፡ የተጠሪ ሞግዚት ከቤቱ ሽያጭ አመልካች የከፈላት ገንዘብ ብር 60,000 እንደሆነ ከዚህ ውስጥ ብር 10,000 ለትምህርት እንደከፈለች፣ ቀሪውን ለወንድሟ እንዳበደረች አረጋግጣለች፡፡ ይህ ማለት ከቤት ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ ለተጠሪም ሆነ ለሌሎች ልጆች አለመዋሉን ያመለክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሁም ከቤቱ ሽያጭ የተገኘ ገንዘብ ለልጆቹ ጥቅም መዋሉን የሚያመለክት ማስረጃ መቅረቡን የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ነገር የለም፡፡ አመልካች ራሱ ከቤቱ ሽያጭ ብር 350,000 ውስጥ እስካሁን የከፈለው ብር 60,000 ብቻ ሲሆን ቀሪውን ገንዘብ ያለመክፈሉ ግራ ቀኙ የሚካሰዱት ጉዳይ ስላልሆነ፣ የቤቱ ሽያጭ ውል ለተጠሪ እና ለሌሎች ልጆች ጥቅም የዋለ ነው ለማለት የሚያችል አንድም ነገር የለም፡፡ አመልካች ቤቱ የተሸጠበትን ገንዘብ አብዛኛውን ሳይከፍል እንዲያውም አነስተኛ ገንዘብ ብቻ ከፍሎ በዚህ ሽያጭ የልጆቹ ጥቅም ተጠብቆላቸዋል፣ የሽያጭ ውሉም ለልጆች ጥቅም የተደረገ ነው፤ ለተጠሪና ለሌሎች ወንድሞቹ መልካም አስተዳደግ ውሏል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አይታይም፡፡ ስለዚህ የሚያዝያ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተጠሪ ሞግዚትና በመአልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ለተጠሪና ለሌሎች ወንድሞቹ ማለትም ለልጆች ጥቅም እና መልካም አስተዳደግ ያልዋለ መሆኑ ስለተረጋገጠ፣ የሽያጭ ውሉ ሌፈርስ አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር በየትኛውም የሕግ መመዘኛ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካች ባቀረበው ክርክር ተጠሪ ከቤቱ ያለው ድርሻ አነስተኛ መሆኑን በመግለጽ ለውሉ መፍረስ መክንያት ሊሆን አይችልም የሚለው ሲታይ ተጠሪ ከቤቱ ድርሻ እስካለው ድረስ የጋራ ንብረቱ ከሱ ፈቃድ ውጭ መሸጥ የሌለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከልጆች መብት አንጻር የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ቤቱን ከገዘሁ በኋላ በቤቱ ላይ ግንባታ አካሄጃለሁ ያለውን በተመለከተ ተጠሪ ምንም ዓይነት ግንባታ አልተደረገም በማለት ክዶ የተከራከረ ሲሆን፣ አመልካች ደግሞ የጽሑፍ ክርክር በማቅረብ በማስረጃ ስላላስረዳ፣ በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ ያላስረዳውን ክርክር ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅሬታ ነጥብ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329/1/ መሰረት ተቀባይነት የለውም፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤቶች የሽያጭ ውሉ የልጆችን ጥቅም የሚጎዳ ስለሆነ ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል፣ አመልካች በቤቱ ላይ ያወጣ ወጪ ካለ ከሶ መጠየቅ ይችላል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተተ የሌለው በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.201566 በ07/08/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.137501 ታህሳስ 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለው በመሆኑ በመሻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.98101 በ22/09/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ በውሳኔ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 103049

ቀን 28/01/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

. ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሊዕማ ሓዲሽ

ተጠሪ፡- አቶ አንዋር ሓዲሽ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳዩ የውርስ ንብረትን በተመለከተ የተሰጠን ውሳኔ አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡ የአፈጻጸም ክሳሽ የተባሉት የአሁን አመልካች በአፈ/ ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ላይ በወረዳው ፍ/ቤት ንብረቱን ለመከፋፈል የአፈጻጸም ክስ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የመቐለ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት አስቀድሞ ሌላ የአፈጻጸም ክስ ተከፍቶ እንደነበር ፤ በቀደመው መዝገብ ንብረቱ በባለሙያ እንዲገመት ተደርጎ ብር 163,349.50 መገመቱን ፤ በዚህ ላይ ከግራ ቀኙ ወገኖች የቀረበ ተቃወሞ አለመኖሩን ፤ ነገር ግን ከወራሾች መካከል አካለ መጠን ያላደረሱ በመኖራቸው እድሜያቸው ደርሶ ቤቱን በጋራ ተስማምተን እንሸጠው መዝገቡ ተዘግቶ ይቆይ የሚል ሃሳብ በማቅረባቸው መዝገቡ ተዘግቶ እንደነበር ፤ ለአፈጻጸሙ ምክንያት የሆነው በፍ/መ/ቁ.03151 ታህሳስ 22/2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ለአፈ/ከሳሽዋ “በድርሻዋ ይሰጣት” የሚል በመሆኑና ከውሳኔው ውጭ ወደ ሽያጭ የሚኬድበት ህጋዊ አግባብ ባለመኖሩ እና ለአንድ ልጅ ሲባል በቤቱ የሚኖሩ አራት ልጆችን በማስወጣት ቤቱ ይሸጥ ማለት ፍትሃዊነት የለውም በማለት የባለሙያው ግምት ለአምስቱ ወራሾች ተካፍሎ የከሳሽ ድርሻ የሆነው ብር 32,669.09 እንዲከፈላቸው ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ “አመልካች ያላቸውን ድርሻ በገበያ ዋጋ ሊያገኙ ይገባል ወይስ ባለሙያ በገመተው” በሚለው ነጥብ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አከራክሮ በመጨረሻ ባሳለፈው ውሳኔ አመልካች ንብረቱ በሃራጅ ተሸጦ ወራሾች እንዲከፋፈሉ የሚያቀርቡትን ክርክር በተመለከተ እንዲፈጸም በቀረበው ውሳኔ አመልካች ድርሻቸውን እንዲያገኙ እንጅ ንብረቱ በሃረጅ እንዲሸጥ ስላልተወሰነ ተቀባይነት የለውም ፤ በሰበር ለማጣራት የተያዘውን ጭብጥ በተመለከተም ንብረቱ እንዲሸጥ እስካልታዘዘ ድረስ የገበያ ግምቱ ይህን ያህል ይሆናል ተብሎ መገመት የሚቻል ባለመሆኑ ባለሙያ ከገመተው ውጭ የገበያ ዋጋው የሚረጋገጥበት ዘዴ የለም በማለት የስር ፍ/ቤቶች ያሳለፉትን ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበ ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች በውርስ የጋራ የሆነው ቤትና ቦታ በአይነት መካፈል እስካልተቻለ ድረስ በሓራጅ ተሸጦ እንጅ በመሃንዲስ መነሻ ግምት ብቻ ድርሻ ይሰጥሽ በሚል የተሳለፈው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረም ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታቸው ተመርምሮ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ህጉ የውርስ ሃብት የመከፋፈልን አሰራር በተመለከተ ከተደነገገው አንጻር ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በሰጡት መልስ የአሁን አመልካች ከስር ክሳቸው ጀምሮ ጥያቄያቸው የወላጆች ድርሻ ይሰጠኝ የሚል እንጅ ቤቱ በሃራጅ ተሸጦ ድርሻዬ ይሰጠኝ የሚል ክስ ስላልነበር ፍ/ቤቱ ይህን ታሳቢ በማድረግ ድርሻዋ እንዲሰጣት የወሰነ በመሆኑ ፤ ጉዳዩ በአፈጻጸም ደረጃ ከደረስ በኃላ በሃራጅ ተሸጦ ሊከፈለኝ ይገባል የሚሉት ክርክርም ከውሳኔው ውጭ የቀረበ በመሆኑና የህግ መሰረት ስለሌለው አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጎ በቀረበው ግምት መሰረት ሊወሰዱ ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካቹም ክርክራቸውን በማጠናከር የመ/መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ ለመግለጽ የሞከረነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ፍርዱን ለማስፈጸም በተሰጠው ትዕዛዝ እና ውሳኔ የተፈጸመ የህግ ስህተት ቢኖር መርምረናል፡፡

ከላይ ለመግልጽ እንደተሞከረው አከራካሪው ጉዳይ የውርስ ንብረት ክፍፍልን የተመለከተ ቢሆንም የተመራው በፍርድ አፈጻጸም ስርዓት ነው፡፡ የፍርድ አፈጻጸም በፍርድ የተገኘ መብት ውጤት እንዲሰጥ እና በፍርድ ባለመብት የተባለው ወገን ፍርዱን እንዲያጣጥም የሚደረግብት ስርዓት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በፍርድ አስፈጻሚው ፍ/ቤት የሚፈጸመው እንደ ፍርዱ ነው፡፡ ነገር ግን ፍርድ አስፈጻሚው ፍ/ቤት በሚያስፈጽምበት ጊዜ ፍርዱ ውጤት እንዲያገኝ አመች የሚሆነውን በህጉ የተፈቀደ ስርዓት ሊከተል ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በአፈጻጸም ወቅት ከፍርዱ ውጭ እንዲየስፈጽም የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቹ ከፍርዱ ውጭ እንዲፈጸም የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ንብረቱ እንዲሸጥ እስካልታዘዘ ድረስ የገበያ ግምቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህን ያህል ይሆናል ተብሎ መገመት የሚቻልበት ስርዓት የለም በመሆኑም ባለሙያ ለገመተው ዋጋ አመልካች የድርሻቸውን እንዲወስዱ የደረስበት መደምደሚያ በህጉ የተደነገገውን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1083 በግልጽ እንደተደነገገው የወራሾች ድርሻ በክፍያ ጊዜ እንደሚገመት ፤ የንብረቱን ግምት የሚያደርጉት ራሳቸው ወራሾች መሆናቸው ፤ እንዲሁም ወራሾቹ በግምቱ የማይስማሙ ከሆነ ግምቱ እነሱ በመረጧቸው የሽምግልና ዳኞች ፣ በመምረጥ ባይሰማሙ ዳኞች በመረጧቸው የሽምግልና ዳኞች ግምቱ እንዲሚደረግ ተመልክቷል፡፡ አመልካች “የድርሻቸው እንዲሰጣቸው” የተላለፈው የስር ፍርድ በዚህ የህግ ስርዓት መሰረት መፈጸሙ ህጉን መሰረት ያደረገ ከመሆኑም በላይ ፍርዱ ውጤት እንዲያገኝ የሚያደርግ ነው፡፡

ስለሆነም ይህን የህግ ስርዓት መከተል ሲቻል ንብረቱን እንዲሸጥ እስካልታዘዘ ድረስ የገበያ ግምቱን ማወቅ አይቻልም ባለሙያ ከገመተው ውጭ ዋጋው የሚረጋገጥበት ዘዴ የለም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ህጉን መሰረት ያላደረገ እና ፍርዱ በህጉ አግባብ ውጤት እንዲያገኝ የሚያደርግ ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩም ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1ኛ. የመቐለ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የዓደር ምድብ ችሎት በመ/ቁ.04388 ግንቦት 6/2006 ዓ/ም ያሳለፈው ትዕዛዝ ፤ የመቐለ ከተማ ማእከላይ (ከፍተኛ) ፍ/ቤት በመ/ቁ.15262 ግንቦት 18/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 66999 ሰኔ 20/2006 ዓ/ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. የወረዳው ፍ/ቤት የአፈጻጸም መዝገቡን በማንቀሳቀስ ንብረቱን ራሳቸው ወራሾች እንዲገምቱ በማድረግ ፣ ወራሾቹ በግምቱ የማይስማሙ ከሆነ ግምቱ እነሱ በመረጧቸው የሽምግልና ዳኞች ፣ በመምረጥ ካልተስማሙ ፍ/ቤቱ በሚመረጣቸው የሽምግልና ዳኞች እንዲገመት በማድረግ ተገቢውን እንዲወሰን ብለናል፡፡

3ኛ. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላላፍ፡፡

4ኛ. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ.ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 100931

ታህሳስ 18 ቀን 2008ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀንዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ጥላሁን ዓለሙ ጠበቃ አቶ ተስፋሁን ጸጋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ደረጀ ማሞ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ወላጅ እናቴ ሟች ወ/ሮ ዘውዴ በየነ የአእምሮ በሽተኛ በነበሩበት ጊዜ የፈጸሙት የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ይደረግልኝ በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ የበታች ፍ/ቤቶች ውድቅ ያደረጉት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች በከሳሽነት ቀርቦ ሟች እናቴ ወ/ሮ ዘውዴ በየነ በአእምሮ ህመም ምክንያት በአማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ሲታከሙ ቆይተው፣ ጤናማ አእምሮ ሙሉ ፈቃዳቸውን ለመስጠት በማይችሉበት ሁኔታ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ቁጥሩ 1020 የሆነውንና በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም በብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ለተከሳሽ ሸጠውላቸዋል፡፡ ሟች እናቴ በአእምሮ ህመም ሲሰቃዩ ቆይተው ከዚህ ዓለም በ2003 ዓ.ም በሞት ተለይተዋል፡፡ ስለዚህ እናቴ የአእምሮ ህመምተኛ በሆኑበትና ፈቃዳቸውን ለመስጠት በማይችሉበት ሁኔታ በእርካሽ ዋጋ ቤታቸውን ለተከሳሽ (ተጠሪ) ለመሸጥ የተዋዋሉት ውል እንዲፈርስ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያና የመከላከያ መልስ አቅርቧል፡፡ ተከሳሽ የከሳሽ እናት የአእምሮ ህመም በግልጽ የታወቀ የአእምሮ ህመም አይደለም፡፡ ተከሳሽ ቤቱን ከከሳሽ እናት የገዛሁት እናቱ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው ጤናማ አእምሮ እንዳላቸውና ቤታቸውን ለመሸጥ ፈቃደኛ መሆናቸው ተረጋግጦ ነው፡፡ የከሳሽ እናት የሸያጭ ውሉን ከተከሳሽ ጋር በተዋዋሉበት ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም ድብርት ውስጥ አልነበሩም፡፡ ተከሳሽ ቤቱን የገዛሁበት ትክክለኛ ዋጋ ብር 1,350,000 /አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃምሳ ሺ ብር/ ሲሆን የከሳሽ እናት ይህንን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ተቀብለዋል፡፡ ተከሳሽ ቤቱን ከገዛሁ በኋላ ከፍተኛ ወጭ በማውጣት የተለያዩ የእድሳት ስራዎችን የሰራሁ በመሆኑ ውሉ ፈርሶ ተዋዋዮች ወደ ነበርንበት ለመመለስ የማይቻል በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡

3. የስር ፍ/ቤት የከሳሽ /የአመልካች/ እናት ወ/ሮ ዘውዴ በየነ የቤት ሽያጭ ውል ከተጠሪ /ከተከሳሽ/ ጋር ሲዋዋሉ የታወቁ የአእምሮ ህመምተኛ ነበሩ? ወይስ አልነበሩም? የቤት ሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? ውሉ ሊፈርስ ይገባል ከተባለ ተዋዋዮች ወደነበሩበት መመለስ አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚሉትን ጭብጦች መስርቶ፣ የከሳሽ እናት በድብርት ምክንያት በአማኑኤል ሆስፒታል በየቀጠሮ እየተመላለሱ የህክምና አገልግሎት ሲያገኙ የነበሩ መሆናቸው የህክምና ማስረጃው ያሳያል፡፡ የከሳሽ እናት ተመላላሽ ታካሚ በመሆናቸው በግልጽ የታወቀ የአእምሮ ህመም የነበረባቸው ሴት ነበሩ ብሎ ለመደምደም በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት አያሟሉም፤ ተከሳሽ የከሳሽ እናት የአእምሮ ህመም /ችግር/ ያለባቸው መሆኑን እያወቀ ውሉን የተዋዋለ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የከሳሽ እናት በመጨረሻ ጊዜ በአማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተገኝተው የሕክምና አገልግሎት ያገኙት ጥር 21 ቀን 2001 መሆኑን የቀረበው የሕክምና ማስረጃ ያሳያል፡፡ ይህም ውሉ በተደረገበት ሰኔ 18 ቀን 2001 ህክምናቸውን ጨርሰው በጤናማ የአእምሮ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተከሳሽ የከሳሽ እናት በጤናም አእምሮ የቤት ሽያጭ ውል የተዋዋሉ ስለመሆኑ የመከላከያ ማስረጃ በማቅረብ አስረድቷል፡፡ ስለዚህ የቤት ሽያጭ ውሉ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

4. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ መስቀለኛ ይግባኝ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ተጠሪ የስር ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ይታገዳል፤ አመልካች የመክሰስ መብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለውም በማለት ያቀረብኩትን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አላግባብ ውድቅ አድርጎብኛል በማለት ያቀረበውን መስቀለኛ ይግባኝ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

5. አመልካች ግንቦት 12 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ፤ ሟች ወላጅ እናቴ 1996 የአእምሮ ህመም ምክንያት ወደ አማኑኤል ሆስፒታል በመሄድ ስትታከም የቆየች መሆኑንና ህመሙ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረ መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 256 መሰረት ለማቅረብ ጠይቀው የነበረው ሆስፒታሉ ጥር 3 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ማስረጃ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወላጅ እናቴን በሰኔ ወር 2001 ዓ.ም ከሌላ ገዥ ጋር አገናኝታት የነበረ ደላላ እናቴ እራሷን መቆጣጠር የማትችል እንደነበረች መስክሯል፡፡ እናቴ ቤት ተዘግቶባት የምትኖር ነበረች፡፡ ቤቱንም የሸጠችው በእርካሽ ዋጋ ነው፡፡ እንደዚሁም ውሉ የሟች ጣት አሻራ የሌለው መሆኑ ዋናውን ቅጅ ለማረጋገጥ ፈልጎ ሊያገኘው እንዳልቻለ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ገልጾ እያለ፤ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

6. ተጠሪ መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የአመልካች እናት እብደታቸው በግልጽ የተወቀ ወይም የተዘጋባቸው እብድ አልነበሩም፡፡ የአመልካች እናት እብደታቸው በግልጽ ያልታወቁ ናቸው፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ወላጅ እናቴ የተዋዋሉትን ውል ፈራሽ ይሁንልኝ በማለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው መብት በህግ አልተሰጠውም፡፡ ተጠሪ ቤቱን የገዛሁት የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በአዋጅ ቁ. 334/95 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚያጣራቸውን ነገሮች አጣርቶና አረጋግጦ፤ የአመልካች እናትም ውል ለመዋዋል ችሎታ ያላቸው መሆኑንና በነጻ ፈቃዳቸው ውሉን የተፈራረሙ መሆኑ ተረጋግጦ ነው፡፡ አመልካች ውል መዋዋል አይችሉም ነበር በማለት አንድ ሃኪም የሰጠው ማስረጃ የግል አስተያየቱና ከሙያ ስነ ምግባሩ በወጣ ሁኔታ የተሰጠ ነው፡፡ በሆስፒታሉ ህክምና ቦርድ በኩል ተረጋግጦ የቀረበ ማስረጃ አይደለም፡፡ አመልካች እናታቸው የአእምሮ ህመምተኛ መሆናቸውን ካወቁ በህግ በተደነገገው መሰረት እናታቸው ውል እንዳይዋዋሉ በፍርድ ማስከልከል ሲገባቸው ይህንን ሳያደርጉ ውሉ ይፍረስ በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡ የአመልካች እናት፤ ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተደረገው ውል ከተገለጸው በላይ የሆነ ገንዘብ ከተጠሪ መቀበላቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ እንዲሰናበት በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2007ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

7. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ተጠሪ ከሟች ወ/ሮ ዘውዴ በየነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጋር አድርጎት የነበረው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ይሁንልኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

8. መዝገቡን እንደመረመርነው የአመልካች እናት ወ/ሮ ዘውዴ በየነ የፍተሐ ብሔር ህግ ቁ. 341 እና የፍተሐ ብሔር ህግ ቁ. 342 በሚደነግገው መሰረት የነበረባቸው የአአምሮ ጉድለት፤ በግልጽ የሚታወቅ የአእምሮ ጉድለት ስለመሆኑ አመልካች የማስረዳት ግዴታውን /Burdon or proof/ ያልተወጣ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች በወላጅ እናቱ ላይ ነበረ የሚለው የአእምሮ ጉድለት በፍተሐ ብሔር ህጉ በግልጽ ያልታወቀ የአእምሮ ጉድለት በሚል መንገድ የሚገልጸው የአእምሮ ጉድለት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
9. የእብደቱ ሁኔታ በግልጽ ያልታወቀ ሰው የፈጸማቸው የህግ ስራዎች በዚሁ ሰው የአእምሮ ጉድለት ምክንያት ሊሻሩ የማይችሉ ስለመሆኑ በመርህ ደረጃ የፍተሐ ብሔር ህግ ቁ. 347 ንዑስ አንቀጽ 1 ደንግጓል፡፡ ከዚህ ጠቅላላ መርህ በልዩ ሁኔታ የተፈቀደው በፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 347 ንዑስ አንቀጽ 2 እብደቱ በግልጽ ያልታወቀ ሰው ውሉ እንዲፈርስለት የሚጠይቅበት ሁኔታና በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 349 እና በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 350 የተደነገጉት ልዩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ሟች ወ/ሮ ዘውዴ በየነ ቤታቸውን ለተጠሪ የሸጡት በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በተደረገ ውል ሲሆን፤ አመልካች የሚከራከረው የቤቱ ዋጋ ዝቅተኛ መሆኑ ሟች እናቱ የአእምሮ ህመም ምክንያት ንብረቱን በበቂ ዋጋ ያልሸጠች እና የአእምሮ ህመም ምክንያት ውል የተዋዋለች መሆኑን ያሳያል በማለት ነው፡፡
10. ተጠሪ አከራካሪውን ቤት በምን ያህል ገንዘብ ነው የገዛው የሚለው ነጥብ፤ በመጀመሪያ ሟች ወ/ሮ ዘውዴ በየነ ከተጠሪ ጋር በውሉና በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ያደረጉት ውል ፈራሽ ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጭብጥ ምላሽ ካገኘ በኋላ የሚታይ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ ስለቤቱ ዋጋ ያደረጉትን ክርክርና ክርክሩን ለማስረዳት ለበታች ፍ/ቤቶች ያቀረቧቸውን የተለያዩ ማስረጃዎች ይዘት መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ ደረጃ አመልካች የቤቱ ዋጋ ማነሱን ለውል ማፍረሻነት ምክንያት አድርገው ያቀረቡት ክርክር የህግ ድጋፍ አለው ወይስ የለውም የሚለውን ነጥብ መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህ አመልካች ያነሳው መከራከሪያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ለማፍረስ በቂ ምክንያትና መከራከሪያ ሆኖ ሊቀርብ የማይችል መሆኑ በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 2887 የተደነገገ በመሆኑ፤ አመልካች ቤቱ በዝቅተኛ ዋጋ የተሸጠ መሆኑ፤ ሻጭ የአእምሮ ጉድለት ያለባቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ስለሚያሳይ ውሉ ይፍረስልኝ በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት ያለው ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

11. በአጠቃላይ ሲታይ የፍተሐ ብሔር ህጉ እብደቱ በግልጽ ያልተወቀ ሰው ወራሾች ወይም ባለገንዘቦች ይህ ሰው የፈጸመው ውል ጉድለት የሌለበት ፈቃድ አልሰጠበትምና ውሉ ሊፈርስ ይገባል ሲሉ እብደቱን ምክንያት በማድረግ የውሉን መፍረስ መጠየቅ እንደማይችሉ በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 348 ተደንግጓል፡፡ ህጉ ይህንን የደነገገው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ባለቤቱ በግልጽ ያልታወቀ የአእምሮ ህመም ምክንያት የእለት በእለት እንቅስቃሴው በራሱ መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስ የህግ ተግባር ሊፈጽም የሚችል መሆኑን በቅርበት የሚያውቁት ይህ እብደቱ በግልጽ ያልታወቀው ሰው ወራሾች፣ ወይም አበዳሪዎች፣ እብደቱ በግልጽ ያልታወቀ ሰው /ሌት/ ህጋዊ ተግባራትን የመፈጸም ችሎታው በፍርድ ክልከላ እንዲደረግበት ስልጣን ላለው ፍ/ቤት በማመልከትና በፍርድ በማስከልከል መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚችሉበት እድል በትጋት በመጠቀም፣ እብደቱ በግልጽ ያልታወቀውን ሰው፣ የራሳቸው እና በሶስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሚከላከል ግዴታ ጥሎባቸዋል፡፡ አመልካች የሚች እናቱ የአእምሮ ህመም በስር ፍ/ቤትና ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ደረጃ የሚያውቅበት ጊዜ፣ የእናቱ ችሎታ በፍርድ ክልከላ እንዲደረግበት መጠየቅና ማስወሰን ሲገባው ይህንን ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም፡፡

12. ተጠሪ ከወ/ሮ ዘውዴ በየነ ጋር ቤት ገዥ ውል ሲዋዋል፣ ወ/ሮ ዘውዴ በየነ የአእምሮ ህመም ያለባቸው መሆኑን የማያውቅና በቅን ልቦና የሸያጭ ውሉን የተዋዋለ መሆኑን የበታች ፍ/ቤት አረጋግጠዋል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች የሸያጭ ውሉ እንዲፈርስለት ያቀረበው ጥያቄ ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገና የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ፣ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበውን የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው፣ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት፣ ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 75175 ህዳር 2 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 142657 ሚያዚያ 9 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ነሐሴ 5 ቀን 2006ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ የእግድ ትእዛዙ የተነሳ መሆኑ ለሚመለከተው ክፍል ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ የማይበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተራ ቁ. ሶስት የተመዘገብኩት ዳኛ የስራ ባልደረቦቼ በአብላጫ ድምጽ በሰጡት ውሳኔ ላይ ባለመስማማት የልዩነት ሐሳቤ እንደሚከተለው አስፍራለሁ፡፡

በዚህ መዝገብ አከራካሪው ጉዳይ የአመልካች አውራሽ ወ/ሮ ዘውዴ በየነ ከተጠሪ ጋር አደረጉት የተባለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ በሕግ ፊት የሚጸና መሆን ያለመሆን ነው፡፡ አመልካች ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩት ወላጅ እናታቸው በከፍተኛ የአእምሮ ህመም እየተሰቃዩ በነበሩበት ጊዜ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት በርካሽ ዋጋ ለተጠሪ መሸጣቸውን ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ከአመልካች አውራሽ ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል በውልና ማስረጃ የተደረገ መሆኑን በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን የመረመረው የስር ፍ/ቤትም የአመልካች አውራሽ በግልጽ ያልታወቀ የአእምሮ ጉድለት የነበራቸው ስለመሆኑ በመግለጽ የቤት ሽያጭ ውሉ ፈራሽ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አፅንቷል፡፡

በመሰረቱ አንድ ውል በተዋዋይ ወገኖች በሕጉ አግባብ ተደረገ የሚባለው በፍ/ሕ/ቁ. 1678 የተመለከቱት መሰረታዊ መስፈርቶች ሲሟሉ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ እንደመሰረታዊነት ከተመለከቱት ነጥቦች አንዱ ፈቃድ /consent/ የሚሰጥበት አግባብ ነው፡፡ አንድ ተዋዋይ ጉድለት የሌለበት ፈቃድ ሰጥቷል ለማለትም ያከናወነው ሕጋዊ ተግባር /juridical act/ በምክንያታዊ ሰው አእምሮ ተቀባይነት ያለው ድርጊት ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው መሰረታዊ ጭብጥ አመልካች አውራሽ በህመም ላይ እንደነበሩ ቤቱም የተሸጠው ከገበያ ዋጋ በታች ስለመሆኑ ክርክር መቅረቡን መዝገቡን ያሳያል፡፡ የአመልካች አውራሽ ሃኪም ቤት እየተመላለሱ የድብርት ህመም ህክምና እንደተደረገላቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ በስር ፍ/ቤት መዝገቡ እንደተገለጸው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ለሌላ ሰው ለመሸጥ በተደረገ ጥረት የአእምሮ ችግር የነበራቸው በመሆኑ ቤቱ ሊሸጥ አለመቻሉን በአመልካች የቀረቡ ምስክር አስረድተዋል፡፡

የስር ፍርድ የአመልካች አውራሽ የሕመም ሁኔታ ያልታወቀ የአእምሮ ጉድለት ነው ለማለት እንደመነሻ የወሰደው ሆስፒታል ውስጥ አልጋ ይዘው እየታከሙ አለመሆኑን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ የታወቀ የአእምሮ ጉደለት ታማሚው የተዘጋበት መሆን እንደመነሻ የተወሰደ ስራ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 341 ተመልክቷል፡፡ ይሁንና ይህ ድንጋጌ መተርጎም ያለበት አገሪቷ አሁን ከደረሰችበት የእድገት ደረጃ እና የሆስፒታሎች የማስተናገድ አቅም ተገናዝቦ ነው፡፡ የአእምሮ ህመም ያላቸው ታካሚዎች ለማስተናገድ የሚያስችል በቂ የጤና ተቋም በሌለበት ሁኔታ ሆስፒታል ወይም ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀው መኖሪያ ያልተዘጋበት ግለሰብ እንደ የታወቀ የአእምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉድለት ያለበት ሰው አይወሰድም የሚለው ክርክር ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ ነው፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበ የሃኪም ማስረጃ ሟች እናታቸው በከፍተኛ የአእምሮ ሕመም ይሰቃዩ እንደነበር ከአማኑኤል ሆስፒታል የቀረበ ማስረጃ ስለመኖሩ በተጠሪ ሳይካድ ሙያዊ አስተያየቱ ዋጋ የሌለው ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች ሌላ ያቀረቡት ክርክር ተደረገ የተባለው ውል የጣት አሻራ የለውም፤ ውሉ ከውልና ማስረጃ ቀርቦ ይጣራ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በተመለከተም ተጠሪ ውሉ በውልና ማስረጃ የተደረገ ነው ከማለት ውጭ በእርግጥም በስር ፍ/ቤት የቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄ በሕጉ አግባብ ስለመስተናገዱ የቀረበ ክርክር የለም፡፡

የአመልካች አውራሽ ሽያጩ ሲፈጸሙ ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም የአእምሮ ጤናቸው ምን ደረጃ ላይ ነበር የሚለው ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ ማጣራት የተደረገበት አይደለም፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ ሟች ወ/ሮ ዘውዴ በየነ የጤና ሁኔታቸው በጥሩ ሁኔታ እንዳልነበረ ለማጣራት መነሻ የሆነውን የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ከአማኑኤል ሆስፒታል የተገኘ ማስረጃ ይሁን በአመልካች የቀረበው የሰው ምስክር የሟች የጤና ሁኔታ ሕጋዊ ተግባር ለማከናወን በሚችሉበት ሁኔታ እንዳልነበሩ መነሻ ክርክር ከቀረበ ፍ/ቤቱ እውነት የማፈላለግ (truth finding) ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ግራቀኙ የሚያቀርቡት ማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት በሕጉ አግባብ ተጣርቶ የሟች የጤና ሁኔታ ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ በዚህ ጉዳይ ሙያ ያላቸው (expert opinion) ሳይከትሪስት ትንታኔ ሊሰጥበት ይገባ ነበር፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካች አውራሽ የአእምሮ ሁኔታ በግልጽ ያልታወቀ እብደት ነው ከሚል ድምዳሜ ለመድረስ መሰረት ያደረገው አልተዘጋጀባቸውም በሚል ምክንያት እንጂ የአእምሮ ጉድለቱ ያልታወቀ እብደት ስለመሆኑ ሳይንሳዊ ትንታኔ የተሰጠበት ጉዳይ አይደለም፡፡ የህመሙ ደረጃ በግልጽ አልተለየም፡፡

በአመልካች አውራሽ እና የተጠሪ የተደረገው ሽያጭ ጉድለት የሌለበት ስለመሆኑ ለመለየት ግራቀኙ ያደረጉት የውል ማቅረብ (offer) እና መቀበል (acceptance)፤ እንዴት እንደተገናኙ፤ ቤቱ በምን ያህል ገንዘብ እንደተሸጠ፤ የሽያጭ ገንዘቡ የተከፈለበት አግባብ በዝርዝር መጣራት የነበረበት ጉዳይ ነው፡፡ የሽያጭ ውሉ በውልና ማስረጃ የተደረገ ነው ከተባለም የሟች ወ/ሮ ዘውዴ በየነ የጤና ሁኔታ አከራካሪ እስከሆነ ድረስ ሂደቱን ሊመረመር ይገባ ነበር፡፡ ሕጉ ጥበቃ የሚያደርገው የቅን ልቦና ገዥ ነኝ ለሚል ሰው ብቻ ሳይሆን የአእምሮ ጉድለት ያለባቸው ግለሰቦችም ሕጋዊ መብታቸው እንዳይጣስ የወራሾችም መብትና ጥቅም ጭምር ለማስከበር በፍ/ሕ/ቁ. 339 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም የአመልካች አውራሽ የሽያጭ ውል አደረጉ በተባሉበት ጊዜ የነበራቸው የአእምሮ ሁኔታ እብደቱ በግልጽ የሚታወቅ ነው ወይስ የማይታወቅ ? የሚለው መሰረታዊ ጭብጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በባለሙያ በተደገፈ ሳይንሳዊ ትንታኔ ተደርጎበት በአግባቡ አለመጣራቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሊሆን ይገባው ነበር፡፡ የአመልካች አውራሽ እና ተጠሪ የቤት ሽያጭ ግንኙነት እንዴት እንደተመሰረተ? ተከፈለ የተባለው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ እና ገንዘቡ ማን እንደተቀበለው? በመንደር ውል የተጻፈው የገንዘብ መጠን እና በውልና ማስረጃ ተከፈለ የተባለው ገንዘብ ልዩነት ካለው ለምን ሊሆን እንደቻለ በዝርዝር ቢጣራ በእርግጥም የአመልካች አውራሽ የጤንነት ሁኔታ የሚጠቁም እውነት ላይ ለመድረስ የሚያችል ነገር ይገኝ ነበር የሚል እምነት አለኝ፡፡

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ፍ/ቤቶች የአመልካች አውራሽ እና ተጠሪ አደረጉት የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ከጉድለት የጸዳ ስለመሆኑ ከላይ በተገለጹ ዝርዝር ምክንያቶች ሳይጣሩ የሽያጭ ውሉ በሕግ ፊት የጸና ነው በማለት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ አይደለም፡፡ ጉዳዩ በሕጉ አግባብ ተመርምሮ በእርግጥም በሕግ ፊት የሚጸና የቤት ሽያጭ ውል ነበረ ወይስ አልነበረም? የሚለው አከራካሪ ነጥብ በስር ፍ/ቤት በድጋሚ ከተጣራ በኋላ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባ ነበር፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በስር ፍ/ቤት የተፈጸሙ ግድፎቶች ሳይጣሩ ውሳኔውን ማጽናቱ ተገቢ አይደለም በማለት በሐሳብ ተለይቻሎህ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 106856

ጥር 16/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ እየሩሳሌም ገመቹ ወኪል ሀቢብ መሐመድ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ሮማን ገመቹ ጠበቃ እንዳርጋቸው ዳኘው ጋር - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሀብት ነው የተባለው ንብረት ለይቶ ከመወሰን ጋር የተያያዘ የቀረበ ክርክር ሲሆን የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባቀረቡት የውርስ ሀብት ይጣራልኝ ጥያቄ መሰረት የውርስ አጣሪ ተሾሞ ጉዳዩን አጣርቶ ለፍርድ ቤት ባቀረበው ሪፖርት መነሻነት ነው፡፡ የውርስ አጣሪው በ29/03/2005 እና ግንቦት 08 ቀን 2005 አሻሽሎ ያቀረበው ሪፖርት ላይ የውርስ ሀብት ንብረት የሆኑና ያልሆኑ ለይቷል፡፡ የውርስ ሀብት ንብረት አይደለም ተብሎ የተለየው እና ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነውን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 በቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር 3215 የሆነውን መኖሪያ ቤት ሲሆን የአሁኗ ተጠሪ ቤቱ የውርስ ሀብት ነው በማለት ሲከራከሩ፤ አመልካች በበኩላቸው አውራሻቸው (ገመቹ ውለታ) በሕይወት እያሉ ቤቱን ለአመልካች የገዙት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የውርስ አጣሪው ባደረገው ማጣራት ቤቱ በ18/05/1994 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል በቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 15 የኑሮ በህብረት የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ያለው በ160 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈው ጅምር ቤት በብር 27,000.00 /ሀያ ሰባት ሺህ ብር/ ከወ/ሮ ከድጃ ሀሰን በአመልካች ስም መገዛቱን አረጋግጠዋል፡፡ በማጠቃለያ አስተያየቱም ቤቱ በሚች ገንዘብ እንደተገዛ ማስረጃ አልቀረበም በሚል ምክንያት የውርስ ሀብት ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም ሲል ደምድመዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውርስ አጣሪው ሪፖርት የመረመረው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ አስተያየት ያዳመጠ ሲሆን በሌሎች ጉዳዮች ተስማምተው በዚሁ ለክርክሩ መነሻ የሆነው በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ በወረዳ 4 የቤት ቁጥር 3215 የሆነው መኖሪያ ቤት በሟች አቶ ገመቹ ውለታ ገንዘብ በአመልካች ስም የተገዛ በመሆኑ የውርስ ሀብቱ ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል አቤቱታ እና ሟች በአመልካች ስም ወደው የገዙት ቤት በመሆኑ የውርስ ሀብት ሆኖ መመዝገብ የለበትም የሚል ክርክር መቅረቡ ፍ/ቤቱ መዝግቦዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ አስተያየት ከመረመረ በኃላ ምንም እንኳ ጅምር ቤቱ በተጠሪ ስም የተገዛ ቢሆንም ጅምር ቤቱ የተገዛበት ገንዘብ ግን በአመልካችና ተጠሪ ወላጅ አባት የሟች አቶ ገመቹ ውለታ መሆኑን አመልካች አልካዱም፡፡ ስለሆነ ጅምር ቤቱ መገኛ ምንጩ የተገዛበትን ገንዘብ የሟች አቶ ገመቹ ውለታ ስለሆነ ተጠሪ እስካልካዱ መኖሪያ ቤቱ የውርስ ሀብት ንብረት ነው በማለት የውርስ አጣሪው ሪፖርት በማሻሻል በማፅደቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኗ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ቤቱ በአመልካች ስም የተገዛ ቢሆንም ቤቱ የተገዛው በአውራሻቸው ገንዘብ መሆኑ ታምነዋል፡፡ የሽያጭ ውልና የማህበሩ አባልነት መታወቂያ ቢያቀርቡም እንደ ፍ/ሕ/ቁ. 1195 (1) አነጋገር የቀረበ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት ያልቀረበ መሆኑን እና የቤቱ መግዣ ምንጭ ሟች አባታቸው ስለመሆናቸው እየተከራከሩ ቤቱ የውርስ ሀብት ንብረት የማይሆንበት ምክንያት የለም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ በሰበር ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ቤቱ በስማቸው የተገዛ በመሆኑ የውርስ ሀብት ንብረት ሊሆን አይገባም፤ ባለቤትነት ለማረጋገጥ በፍ/ሕ/ቁ. 1195 (1) የሚቀርበው የይዞታ ማረጋገጫ ብቸኛ ማስረጃ አይደለም፤ በማህበራት የተደራጀ የመኖሪያ ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ በሂደት እንደሚሰጥ እየታወቀ መታለፍ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ቤቱ የተገዛው በአውራሽ ገንዘብ በመሆኑ ቤቱ የውርስ ሀብት ንብረት ነው መባሉ በአግባቡ ነው በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ አከራካሪ የሆነውን ቤት ሟች በሕይወት እያሉ በአመልካች ስም የተገዛና በስማቸው የተመዘገበ መሆኑን ባለተካደበት፤ ቤቱ የተገዛው በሟች ገንዘብ ነው በሚል ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውርስ ሀብት ንብረት ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች መወሰኑ በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በአመልካች ስም የተገዛና የተመዘገበ ቢሆንም ቤቱ የተገዛው በአውራሽ ገንዘብ ስለመሆኑን ነው፡፡ አመልካች ቤቱ በስማቸው የተገዛው የውርስ ሀብት መሆን እንደማይገባው ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩላቸው ቤቱ የተገዛበት ገንዘብ ምንጩ የአውራሽ በመሆኑ ቤቱ ከውርስ ሀብት ውጭ የሚሆንበት አግባብ እንደሌለ መከራከራቸውን ተረድተናል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት በአመልካች ስም የተገዛና የተመዘገበ ስለመሆኑ ግራ ቀኙ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ቤቱ ለመግዛት ምንጭ የሆነውን ገንዘብ የአውራሻቸው በመሆኑ ቤቱ የውርስ ሀብት ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም? የሚል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ቤቱ የውርስ ሀብት ነው ለማለት መነሻ ያደረጉት ቤቱ በአውራሽ ወይም በሚች ገንዘብ የተገዛ በመሆኑ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወራሽ የሚች ውርስ የተቀበለ ከሆነ አስቀድሞ የወሰደው ንብረት ተመላሽ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁ. 1065 ሥር ተደንግጓአል፡፡ ይሁንና አውራሽ አስቀድሞ ንብረት የወሰደ ወራሽ ንብረቱ ተመላሽ እንዳይደረግ ነፃ ሊያደርገው እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቤቱን በስማቸው የተገዛና የተመዘገበ ቢሆንም አስቀድሞ የተወሰደው ንብረት ተመላሽ እንዳይደርጉ በሚፈቅድ አግባብ ቤቱ የተሰጣቸው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ቤቱ በሚች ገንዘብ ስለተገዛ ቤቱ የውርስ ሀብት ነው ያሉ ቢሆንም ቤቱ ለአመልካች ሚች ከመሞታቸው በፊት የተገዛ ከመሆኑ አንፃር ጉዳዩ መታየት የነበረበት የፍ/ሕ/ቁ.1065 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የሚች ወራሾች ተመላሽ የሚያደርጉት ንብረት የሚመለስበት ሥርዓት ከፍ/ሕ/ቁ.1074 እና 1076 አንፃር መታየት አለበት፡፡ የሚች ሀብት ወራሹ ከወሰደውና ከሚደርሰው ገንዘብ በላይ ከሆነ አስቀድሞ የወሰደው የንብረት መጠን /ግምት/ ተቀንሶ በቀሪ የጋራ ወራሾች ሀብት ላይ ድርሻውን ማግኘት ያለበት ስለመሆኑ ከፍ/ሕ/ቁ.1074 (2) እና 1076 (1) ድጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ በሌላ በኩል ወራሽ አስቀድሞ የወሰደው ንብረት ግምት ወራሾች በጋራ ከሚወርሱት ሀብት የበለጠ ከሆነ ድርሻው ተሰልቶ እስከ ድርሻውን መጠን ታስቦ የውርስ ሀብት እንደሆነ ግምት የሚወሰድ ቢሆንም ከግምት በላይ የተወሰደውን ለመመለስ ግዴታ እንደሌለው በፍ/ሕ/ቁ. 1076(2) ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ቤቱ የተገዛው በብር 27,000.00 /ሀያ ሰባት ሺህ ብር/ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የታመነ ፍሬ ነገር ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ከአውራሻቸው ሀብት አስቀድመው ብር 27,000.00 ግምት ያለው ንብረት መውሰዳቸው የሕግ ግምት ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም የሚች ሀብት አመልካች አስቀድመው ከወሰዱት ግምት በላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ድርሻቸው ይህ የገንዘብ መጠን ከተቀነሰ በኃላ ከቀረው ገንዘብ የሚወሰዱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሆን የአውራሻቸው ሀብት አመልካች አስቀድመው ከወሰዱት ብር 27,000.00 በታች ከሆነ ግን ይህንን ገንዘብ ለመመለስ የሚገደዱበት የሕግ ሥርዓት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ቤቱ የተገዛው በአመልካች እና ተጠሪ አውራሽ ገንዘብ ነው በሚል መነሻ ቤቱ የውርስ ሀብቱ ንብረት ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች ከአውራሻቸው ከሚያገኙት ሀብት የብር 27,000.00 ግምት አስቀድመው እንዲወሰዱ ከሚቆጠር በስተቀር በአመልካች ስም የተገዛና የተመዘገበ ቤት የውርስ ሀብት አካል ተደርጎ ክፍፍል የሚደረግበት አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች አስቀድሞ በስማቸው የተገዛውና የተመዘገበው ቤት ተመላሽ ለማድረግ የማይገደዱ ሲሆን የአውራሻቸው ሀብት ከዚህ ቤት መግዣ ገንዘብ በላይ ከሆነ፤ ይህ ገንዘብ ተቀንሶ ድርሻቸው እንዲወሰዱ፤ የአውራሽ ሀብት ከወሰዱት ቤት ተመጣጣኝ ከሆነ በዚህ መጠን ተወስነው እንዲቀሩ፤ የአውራሽ ሀብት በክሱ ከተጠቀሰው የቤቱ ዋጋ በታች ከሆነ ግን አመልካች ገንዘቡን ወይም ቤቱን የውርስ ሀብት አካል ለማድረግ የሕግ ግዴታ እንደሌለባቸው ከፍ/ሕ/ቁ. 1074(2) እና 1076(2) ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች አንዱ ወራሽ አውራሹ ከመሞቱ በፊት ያገኘው ንብረት ተመላሽ የሚያደርግበት ሥርዓት /Collation by heirs/ በሕጉ አግባብ ሳያገናዝቡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የውርስ ሀብት ነው ማለታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26419 ሐምሌ 4/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 140321 መስከረም 20 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነው በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር 3215 በአውራሽ ገንዘብ የተገዛ በመሆኑ ብቻ የውርስ ሀብት ሊሆን አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ከአውራሻቸው የሚያገኙት ንብረት በክሱ ከተጠቀሰው ቤቱ የተገዛበት ብር 27,000.0 በላይ ከሆነ፤ ይህንን ገንዘብ ከድርሻቸው ተቀንሶ ከቀረው ገንዘብ ድርሻቸው እንዲገኙ፤ ከአውራሻቸው የሚያገኙት ገንዘብ እኩል ከሆነ ባሉበት እንዲፀኑ፤ የቤቱ ዋጋ በውርስ ከሚያገኙት ገንዘብ በላይ ከሆነም በፍ/ሕ/ቁ. 1076(2) መሰረት ለመመለስ አይገደዱም ብለናል፡፡
4. የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. በዚህ ችሎት ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.111216

ቀን የከተተ 15/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተክሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ
ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኤልሳቤት አህመድ ተወካይ ፀሃይነሽ አህመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ማፈኛ አባዩ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፈርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ አከራከሪ የሆነው ጭብጥ የውርስ እና የሚስት ግማሽ ድርሻ ንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ሟች ከተቀበሩበት ቀን ጀምሮ እስከ 80 ቀን ድረስ ያለውን ውጪ በእኩል ለመካፈል የተደረገው ስምምነት መሠረት ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች የአሁኗ አመልከች የብር 153,040.00 ግማሽ ይክፈሉ በማለት የሰጡት ትእዛዝ በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

አመልካች ውሉን እንዳልተስማሙበት የተከራከሩ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት የቀረበው ውል ሪፖርት እንደተቀበለ፤ በቀረበው ውል መሠረት ሟቹ ከተቀበሩበት ቀን ጀምሮ እስከ 80 ድረስ ያለው ወጪ ብር 153,540.00 እንደሆነ፤ በፍ/ህ/ቁ. 1014 መሠረት ወጪ ከውርስ ንብረት ክፍፍል በፊት የሚከፈል ስለመሆኑ በደንገጉን የግራ ቀኙ የውል ስምምነትም በዋናው መዝገብ ቁጥር 08093 ላይ ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ ቤቶቹ የሚከፋፈሉት ከማንኛውም እዳ ነፃ ከሆኑ በኃላ ስለ ሚል፤ ወጪውም ሁለቱም ተከራከሪ ወገኖች እንደሚመለከት፤ የአፈፃፀም ክሳሽ (አመልካች) የወጪውን ግማሽ ብር 76,520.00 ከፍለው እንዲሁም እንደውላቸው የሴንተናል ሆቴል ቤት ግምት አንድ መቶ ሺህ ብር ከፍለው የቤት ቁጥር 1345 የሆነውን እንዲራከቡ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የዲጋ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 08412 በ21/08/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በመቃወም ሰምስረቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ከተመረመረ በኃላ በአመልካች በኩል እዳው ከሆቴሉ ገቢ ተከፍሏል የሚል ክርክር እንደቀረበ ይሁንና ለክርክሩ መነሻ የሆነውን እዳ ብር 153,040.00 ከሆቴል ገቢ መከፈሉን እንዳልተረጋገጠ፣ ግራ ቀኙ ባደረጉት የውል ስምምነትም አውራሹ ከሞቱ በኃላ ከሞቱበት ቀን ጀምሮ እስከ 80 ቀናት ድረስ የወጣው ውጪ ሊካፈሉ መስማማታቸው እንደሚያሳይ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡

የአሁኗ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ተደርጓአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ /ትእዛዝ/ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርመሮ በሰበር እንዲታይ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ዕዳ ከሟ የጋራ ሀብት የተከፈለ ወይም ሊከፈል የሚገባው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ብር 76,520.00 እንዲከፍሉ መወሰናቸው በአግባቡ አይደለም የሚል ክርክር ሲያቀርቡ፤ ተጠሪ በሰጡት መልስ ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት የሟች ዕዳዎች ተለይተው አመልካችም በግልጽ የተስማሙበት ስለመሆኑ፣ ወጪ የተደረገውም ለቀብር ብቻ ሳይሆን ሟች በህይወት በነበሩበት ጊዜ የነበረባቸው የብድር ዕዳዎች የሚመለከት በአመልከችም የታመነ ነው የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ የሚነቀፍ አይደለም የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ዕልበት የሚያስፈለገው ጭብጥ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች እና ተጠሪ ሟች ከተቀበሩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 80 ቀን ተደረጉ የተባሉትን ወጪዎች እኩል ይክፈሉ በማለት ትዕዛዝ የመስጠታቸው አግባብነት በግራ ቀኙ ያደረጉት ስምምነት መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

ከስር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ሟች ከተቀመሩበት ቀን ጀምሮ እስከ 80 ቀን ድረስ ያለውን ወጪ ብር 153,040 መሆኑን በ15/08/2004 ዓ/ም በተጻፈው ውል ቃለ ጉባኤ እንደተገለጸ፣ የህም ሁለቱን ወገኖች የሚመለከት ስለመሆኑ ነው፡፡ አመልካች ዕዳው ለሴንትራል ሆቴል ገቢ የተከፈለ ነው የሚል ክርክር ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ በደረገው ማጣራት ዕዳው ከሆቴሉ ገቢ ስለ መከፈሉ የሚያረጋግጥ ነገር አለመቅረቡን በትዕዛዙ አስፍሯል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ሚያዝያ 15 ቀን 2008 ዓ/ም በሽማግሌዎች ፊት የፈረሙት ውል ላይ እንደተመለከተው የሟች ዕዳ ከግብአት ቀብር እስከ 80 ቀን በአጠቃላይ የሚመለከት እንዲሆነ፤ ሟች ከግለሰቦች የወሰዱት ዕዳም እንደሚያከቲት እና አጠቃላይ ወጪው 153,040.00 /አንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቶ ሀምሳ ሦስት ከአርባ ብር/ እደሆነ ተገልጸዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአሁኑ አመልካች እንዲጋሩት የተጠየቁት ዕዳ ለቀብር ስነ ስርዓት ማስፈጸሚያ የወጣውን ወጪ ብቻ ይሆን የሚች ዕዳዎች የሚያጠቃልል ስለመሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው /ትዕዛዙ/ እንደገለጸው በአመልካች እና ተጠሪ የተፈረመው ውል በመዝገብ ቁጥር 08093 ውሳኔ የተሰጠበት ለፍርድ አፈፃፀም መነሻ እንደሆነ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ውል ስለማደረጋቸውን በህግ የተደገፈ ክርክር አላቀረቡም፡፡ ይህ ከሆነ ግራ ቀኙ ባደረጉት ግልጽ ስምምነት የውርስ ሀብት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የሚች ዕዳዎች ቅድሚያ እንደሚከፈሉ የተስማሙ መሆኑን መስራት በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ግማሹን ዕዳ አንዲከፍሉ መወሰናቸው በህጉ አግባብ ነው ከሚበል በቀር በጉዳዩ መሰረታዊ የህግ ስህተት በፈጸማቸውን አያሰይም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ከአውራሻቸው ያገኙት ሀብት ወደ ስማቸው ሲተላለፍ የሚችለው በቅድሚያ የሚች ዕዳ የሆነውን ግማሹ ማለትም 153,040.00 ሲካፈል ለሁለት 76,520.00 የመክፈል ግዴታቸው ከተወጡ በኃላ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶችም አመልካች ከተጠሪ ጋሪ በገቡት ውል መሠረት የሚች ዕዳ መሆኑን የተረጋገጠው ግማሹን ይክፈሉ በማለት መወሰናቸው በህጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የዲጋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08412 በ29/08/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 34524 በ10/11/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 186415 በ18/5/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. አመልካች የሚች ዕዳ መሆኑን በገቡት ውል መሰረት ያረጋገጡት የብር 153,040.00 ግማሹን 76,520 /ሰባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሀያ/ እንዲከፍሉ መወሰኑ በህጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ 110040

የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ እሴተማርያም አክሎግ

2. ወ/ሪት ወይንሸት አክሎግ } የቀረበ የለም

3. አቶ መክብብ አክሎግ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ውርስ ጥያቄ የመመልከት ነው፡፡ አመልካቾች ለአ.አ.ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የአያታቸው ወ/ሮ ደብረወርቅ ሀ/ሚካኤል ወራሽነት ይረጋገጥልን በማለት አቅርበዋ፡፡ የአባታቸው ሻለቃ አክሎግ አድማሱ ወራሽነት ያረጋገጡ ሲሆን የወላጅ አባታቸው እናት ወራሽነት ለማረጋጥ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡ወላጅ አባታቸው በ1981 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ሲሆን አያታቸው ወ/ሮ ደብረወርቅ ሀብተ ሚካኤል የሞቱት ደግሞ በ1978 ዓ/ም ነው፡፡ በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም አያታቹህ ከአባታቹሁ ቀድመው የሞቱ ስለሆነ ተተኪ ወራሽ ልትሆኑ አትችልም በማለት ብይን ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ብይን ባለመስማማት አቤቱታቸውን ለአ.አ.ከተማ ይግባኝ ሰሚና ለሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት ሳያገኝ በትእዛዝ ሰርዞውታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች ተወካይ የካቲት 10 ቀን 2007 ዓ/ም በፃፉት የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ብይን ተእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ወላጅ አባታችን እናቱ ከሞቱ ጀምሮ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ በህመም ላይ እንደነበረ ለስር ፍርድ ቤቶች አስረድተን እያለን የአያታችን ወራሽነት አታረጋግጡም መባሉ ከፍተኛ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ወላጅ አባታችን ለ3 አመት የአልጋ ቁራኛ ሆኖ የእናቱ ወራሽነት ሳያረጋግጥ ቢቀርም አመልካቾች ተተኪ ወራሾች የአያታችን ወራሽነት የሚከለክለን አንዳችም ህግ የሌለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ በመሻር የአያታችን ወራሽነት እንዲረጋገጥላቸው አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተተኪ ወራሾች ሊሆኑ አይችሉም በማለት የተሰጠ ብይን ከፍ/ብ/ህ/ቁ/ 830፣831/3/844 እና 839 አንፃር ለመመርመር በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ሊቀርብ የቻለው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ካቀረበበት ብይን እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካቾ ጥያቄ ወላጅ አባታቸው ተከተው የአያታቸው ወራሽነት እንዲረጋጥላቸው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ደግሞ ተተኪ ወራሾች ልትሆኑ አትችሉም በማለት ብይን ተሰጥተዋል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 842/3/ ስር እንደተመለከተው የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሲሆኑ ልጆች ቀድመው ከሞቱና ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ትተው ከሆነ ተወላጆቹ ወላጃቻውን ተተክተው ሟችን እንደሚወርሱ ያመላክታል፡፡ የተተኪ ወራሽነት የተፈፃሚነት ወሰን ወደ ታች የሚቆጥሩ ተወላጆች እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ወላጅ አባታቸው የእናታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ናቸው፡፡ አመልካቾችም የወላጅ አባታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች እንደሆኑ ህጉ ከመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተተኪ ወራሽ ለመሆን ከፍ/ብ/ህ/ቁ/ 842/3/ አንፃር ሲታይ የአመልካቾ ጥያቄ የሚያሟላ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ወላጅ አባታቸው የእናታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ በመሆን የወረሱ ስለሆነ የምትክ ጉዳይ ሊነሳ አይችልም፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካቾች አባታቸው ተክተው አያታቸውን መውረስ የሚችሉት አባታቸው ከአያታቸው በፊት የሞቱ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ስሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች የሟች አባታቸውን ወራሽነት ስለማረጋገጣቸው ከክርክሩ ስለተረዳን አባታቸው የወረሱትን ንብረት ለመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡ በዚሁ መሰረትም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 1118/07 ጥር 6 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን፤ የአ/አ፤ የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ/23073 ጥር 21 ቀን 2007 ዓ/ም እና የአ/አ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 23140 የካቲት 2 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 348/1/መሰረት በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገብ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>የልዩነት ሀሳብ</u>

የአመልካቾቹ መሰረታዊ የአቤቱታ ነጥብ ወላጅ አባታችን ሻለቃ አክሎግ አድማሱ ከወላጅ እናታቸው ከወ/ሮ ደብረወርቅ ሀብተ ሚካኤል በኃላ የሞቱ በመሆኑ አባታችን የነበራቸው እናታቸውን የመውረስ መብት ለእኛ ለሻለቃ አክሎግ አድማሱ ልጆች እና ወራሾች የሚተላለፍ መሆኑ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠን የሚል መሆኑን ከስር ጀምሮ ከሚያቀርቡት ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሰረቱ ለአንድ ውርስ ወራሽ የሆነ አንድ ሰው ውርሱ ከተከፈተ በኃላ የሞተ እንደሆነ የወራሽነቱ መብቶች ለርሱ ወራሾች የሚተላለፉ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 833 ተመልክቶአል፡፡ ከአውራሹ አስቀድሞ የሞተን ወራሽ ተክቶ መውረስ (ቁጥር 844 (2) እና ከአውራሹ በኃላ የሞተን ወራሽ ተክቶ መውረስ (ቁጥር 833) የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆም ለአቤቱታው አግባብነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ ቁጥር 844 (2) ሳይሆን 833 ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በቁጥር 833 ድንጋጌ መሰረት ከአውራሹ በኃላ የሞተ ወራሽ ተተኪ ወራሾች መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው አመልካቾቹ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ተሽሮ በአመልካቾቹ አቤቱታ መሰረት ሊወሰን ይገባው ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁጥር ሁለት የተመለከተው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬአለሁ፡፡

መ/ተ የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95922

መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

አመልካች፡- 1.አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ - ነ/ፈጅ ብሩክ ዘረሁን - ቀረቡ

2. አቶተፈራ ታርቄ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1.ሃምሳ አለቃ ለገሰ ክፍለይ } ጠበቃ አወግቸው መኮንን ቀረቡ

2. ወ/ሮ አክበረት አማረ }

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአጓዥ ተጓዥ ውልን መሰረት ያደረገን የጉዳት ካሳ ይከፈለን ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ 2ኛአመልካች ላይ በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትግንቦት 28 ቀን 2005 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ንብረትነቱ የአሁኑ 2ኛአመልካች የሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 3-10457 ፣ የሳን ቁጥሩ 1320 የሆነ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የተጠሪዎች ልጅ የሆነውን አለም ለገሰ ከአዲስ አበባ ተሳፍሮ ወደ መቐሌ በመጓዝ ላይ እያለ ደብረ ብርሃን ከተማ ቀበሌ 09 ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ ሲደርስ መኪናው ተገልብጦ በዚህ ምክንያት የልጃቸው ህይወት ማለፉንና በህይወትእያለም በግብርና ስራ ላይ ተሰማርቶ ይረዳቸው የነበረ መሆኑን ገልጸው በጠቅላላው ብር 484,000.00(አራት መቶ ሰማንያ አራት ሺ ብር) ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ 2ኛ አመልካችም ሟች በመኪናቸው ተሳፍረው ሲሄድ መሞቱን ሳይክዱ ግንኙነቱ የመጓጓዣ ውልን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ክሱ ከውል ውጪ ሊቀርብ እንደማይገባ፣ በአጓዥ ግንኙነትም ክሱ መቅረብ የነበረበት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሁኖ እያለ ከአራት ዓመታት በላይ ቆይቶ መቅረቡ ያላግባብ መሆኑን፣ በተሳፋሪዎች ለሚደርስ ጉዳትም ከአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ የመድን ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የገባ መሆኑን ጠቅሶ ይኼው አካል ወደ ክርክሩ እንዲገባለት ጠይቆአል፡፡ የአሁኑ 1ኛ አመልካችም ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብቶ የተጠሪዎች ክስ ከውል ውጪ ሕግን መሰረት አድርጎ መቅረቡ ያላግባብ መሆኑን፣ ክሱም በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም የተጠሪዎች የካሳ ስሌት ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግና በእርግጥም ያጡትን ጥቅም ያህል በማስረጃ አስደግፎ ያልቀረበ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የይርጋ መቃወሚያውን ያለፈው ሲሆን ፍሬ ነገሩን በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ግንኙነቱ በንግድ ሕጉ የሚገዛ መሆኑንና አደጋው የደረሰውም በንግድ ሕጉ አንቀፅ 599 አግባብ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ደምድሞ ተጠሪዎች ብር 40,000.00 የጉዳት ካሳ፣ ብር 1000.00 የሕሊና ጉዳት ካሳ፣ ለአስክሬን ማንጓጓዣ የአወጡት ብር 11,000.00 በድምሩ ብር 52,000.00 (ሃምሳ ሁለት ሺህ ብር) እንዲከፈላቸው፣ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ የአሁኑ 1ኛ አመልካች በሰጠው የመድን ሽፋን መጠን ብር 10,000.00 (አስር ሺህ)፣የአሁኑ 2ኛ አመልካች ደግሞ ቀሪውን ብር 42,000.00 (አርባ ሁለት ሺህ) ለተጠሪዎች እንዲተኩ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የተጠሪዎች ልጅ በ2ኛ አመልካች ንብረት በሆነው የሕዝብ ተሸከርካሪ ተሳፍረው በመሄድ ላይ በደረሰው የመገልበጥ አደጋ ሕይወቱ ያለፈ ሁኖ እያለ ክሱ ከሁለት አመት በላይ ቆይቶ ቀርቦ የይርጋው መቃወሚያ ታልፎ ለተጠሪዎች ከብር 40,000.00 (አርባ ሺህ) በላይ የጉዳት ካሳ እንዲከፈል መወሰኑ በን/ሕ/ቁጥር 587 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በተለይም የን/ሕ/ቁ/ጥር 603 እና 597 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው አመልካቾች ያቀረቡት የይርጋ ተቃውሞ ታልፎ አመልካቾች ለክሱ ኃላፊ የመባላቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጹሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክርለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎችጋርበማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ጭብጦች፡-

1. ጉዳዩ መዳኘት ያለበት ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዙት ድንጋጌዎች ነው? ወይስ በንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ነው? እና
2. ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚሉትን ሁኖ አግኝቷል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በግብርና እርሻ ስራ ተሰማርቶ ይኖር የነበረው የተጠሪዎች ልጅ የህዝብ ማመላለሻ ሁኖ ለንግድ በሚሰራው ንብረትነቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ2ኛ አመልካች ተሽከርካሪ ላይ ተሳፍሮ ከአዲስ አበባ ወደ መቐሌ ሲሄድ ተሽከርካሪው በመገልበጡ ምክንያት ለሕልፈተ ህይወት የተዳረገ መሆኑን ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪዎችን የካሳ ጥያቄ በመመልከት ተገቢ ነው ያሉትን ዳኝነት ሲሰጡ የአመልካቾችን ኃላፊነት የወሰኑት የንግድ ሕጉን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑም ከውሳኔው ግልባጭ ተመልክተናል፡፡ በ2ኛ አመልካችና በሟች መካከል የንግድ ህግ ቁጥር አንቀጽ 587 በሚደነግገው መሠረት የአጓዥና የመንገደኛ ግንኙነት መኖሩን አመልካቾችና ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ባቀረቡት ክርክር የሚተማመኑበት ጉዳይ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በአመልካቾችና በሟች መካከል ሰው ለማጓጓዝ የተደረገ ውል መኖሩን አመልካቾችና ተጠሪዎች የሚስማሙበት ከሆነ 2ኛ አመልካች ሟች ዋጋ ከፍለው ሲጓዝበት የነበረው የትራንስፖርት ተሽከርካሪ ባለሀብት ሲሆኑ 1ኛ አመልካች ደግሞ በመኪናው ተሳፋሪ ለሚደርሰው ጉዳት የመድን ሽፋን የሰጠ ነው፡፡ በን/ሕ/ቁጥር 588 ድንጋጌ ይዘት ሲታይ አጓዡ መንገደኛውን በመልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ስለ ምቾቱና ስለ ጉዞው በውሉ የተወሰነውን ጊዜ አክብሮ እንደተወሰነው እመድረሻ ስፍራ የማድረስ ግዴታ እንዳለበት በሐይለ ቃል አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የአጓዡን የትራንስፖርት መኪና በኃላፊነት ተረክቦ የመኪናውን ደህንነትና ብቃት አረጋግጦ የትራፊክን ደንብና ሥርዓትን አክብሮ የማሽከርከር ኃላፊነት ያለበት አሽከርካሪ /ሹፌር/ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች መንገደኛውን መልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ምቾት በመጠበቅ በሰላም ወደሚፈለግበት ቦታ የማድረስ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማስቻል ሲሆን ይህንኑ በሕግ የተጣላባቸውን ግዴታ ካልተወጡ ደግሞ መንገደኛው በጉዞው ላይ ስለሚደርስበት መዘግየትና በጉዞው ጊዜ ወይም በሚሣፈርበት ወይም በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል ማጉደል ወይም የህይወት ማለፍ አጓዡ ኃላፊ እንደሚሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 595 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ አጓዡ መንገደኛው በጉዞ ጊዜ በሚሣፈርበትና በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል መጉደል ወይም ህይወት ማለፍ አጓዡ በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን በመሠረታዊ መርህነት የሚያስቀምጥ ሲሆን ፣ አጓዡ ከኃላፊነት ነጻ የሚሆንባቸዉን ልዩ ሁኔታዎች የህላፊነቱን መጠንና አጓዡ በህግ ከተደነገገው መጠን በላይ በህላፊነት ሊጠየቅ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎች አካቶ ይዟል፡፡ በንግድ ህግ አንቀጽ 595 ከተደነገገው ኃላፊነት አጓዡ ነጻ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚደነግገው የንግድ ህጉ አንቀጽ 596 ሲሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 596 አጓዡ በመንገደኛው ላይ የአካል መጐዳት ወይም የሞት አደጋ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ከፍተኛ ህይል መሆኑን ፣ ወይም ጉዳቱ የደረሰው በሶስተኛ ሰው ጥፋት መሆኑን ወይም በመንገደኛው ጥፋት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ አጓዡ ከኃላፊነት ነጻ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ የካሳ መጠኑን በተመለከተ የቀረበውን ቅሬታ ስንመለከተውም አጉዡ በንግድ ህግ ቁጥር 596 መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ በመንገደኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 597 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የኃላፊነት መጠን በተመለከተ ደግሞ ለአንድ መንገደኛ ከብር 40,000 /አርባ ሺ ብር/ እንደማይበልጥ የንግድ ህግ አንቀጽ 597 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በንግድ ህግ አንቀጽ 597 የተደነገገው የኃላፊነት መጠን አጓዡ በንግድ ህግ አንቀጽ 596 የተደነገጉትና ከኃላፊነት ነጻ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታና መንገደኛው በንግድ ህግ አንቀጽ 599 በሚደነገገው መሠረት አጓዡ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑን እያወቀ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ባልቻለበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግን የ2ኛ አመልካች ንብረት የሆነውን የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ያሽከረክር የነበረው የ2ኛ አመልካች ሰራተኛና የመኪናው ሹፌር የሆነው ለአደጋው ምክንያት ስለመሆኑ ያለመረጋገጡንና በወንጀልም ክስ ተመስርቶበት በሂደት ላይ ያለ ወይም በሕጉ አግባብ የተቋረጠ ወይም የተቀጣ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት አልተረጋገጠም፡፡ በንግድ ህግ ቁጥር 588 በሚደነግገው መሠረት የመንገደኛውን መልካም ይዞታ ደህንነትና ምቾት በመጠበቅ መንገደኛውን የማጓጓዝ ኃላፊነቱን ሊወጡ የሚገባቸውን ወገኖች የመኪና ባለቤት፣ ሹፌር፣ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ መኖሩን፣ በንግድ ህግ አንቀጽ 599 “አጓዡ የተፈፀመው ተግባር ወይም ጉድለት” የሚለው ሀረግ አጓዡ በግሉ የፈጸመውን ተግባር ወይም ጉድለት የሚመለከት ሣይሆን የአጓዡ ሰራተኞች አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጠር እንደሚችል እያወቁ የፈጸሙትን ተግባር ወይም ጉድለት የሚያካትት ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 67973 በሆነው መዝገብ ላይ በቀረበው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በማናቸውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያሰገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት የተያዘው ጉዳዩ ሲታይም አደጋው የደረሰው የ2ኛ አመልካች መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር ባጠፋው ጥፋት ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የክርክር ሂደት ያልተረጋገጠ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የን/ሕ/ቁጥር 599 የሚሆንበት አግባብ የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ 2ኛ አመልካች በተጠሪዎች ልጅ ላይ ለደረሰው የሞት ጉዳት በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው በላይ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አይኖርባቸውም፡፡ በመሆኑም አመልካች በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው የኃላፊነት መጠን በላይ ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት እንደሌለባቸው የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ድንጋጌ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በን/ሕ/ቁ ህግ ቁጥር 599 ድንጋጌ መሠረት ለመንገደኛው ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት አጓዥ ለመንገደኛው የሚከፍለው የካሣ መጠን ለመወሰን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2092 የተደነገጉት የካሳ አከፋፈል መርሆች አግባብነት ያላቸው ስለመሆናቸውም ይህ ችሎት ከላይ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ጉዳዩ ሲታይም ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን፣ መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣ 2091፣ 2092፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ለሚጠየቅ የአንዥር ተንዥር ግንኙነት ተፈፃሚነት የሚኖረው የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143 ድንጋጌ ስር ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ክሱ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚገዙትን ድንጋጌዎችን መሰረት አድርገው ማቅረባቸውም ሆነ የስር ፍርድ ቤት ይርጋውን በተመለከተ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143 ድንጋጌን መሰረት አድርጎ መመልከቱ በ2ኛ አመልካችና በሚቹ መካከል ያለውን ግንኙነት ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ የካሳውን መጠን በን/ሕ/ቁጥር 597 ድንጋጌ ማስላቱ ተገቢነት የነበረው ሁኖ አግኝተናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>አንገቡ በንግድ ህግ ቁጥር 596 መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ በመንገደኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 597 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ሟች የሞቱት ንብረትነቱ በ2ኛ አመልካች በሆነ የሰው መንገጥር አገልግሎት ይሰጥ በነበረ የህዝብ ማመላለሻ ላይ በደረሰው የመገልበጥ አደጋ መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ሲሆን በመካካላቸው ካለው የትራንስፖርት ውል ግንኙነት አኳያ ሲታይ አመልካቾች ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆኑበት ሁኔታ በንግድ ህጉ ወይም በዚሁ ሕጉ በልዩ ሁኔታ በአንቀፅ 599 በተመለከተው አግባብ ነው፡፡ ስለሆነም በንግድ ሕጉ ስለ ይርጋም ሆነ ለካሳ የተደገጉትን ድንጋጌዎች ወይም በንግድ ህጉ አንቀፅ 599 በተመለተከው ሁኔታ ጉዳዩን ለመዳኘት ይቻል ዘንድ አስቀድሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን መለየት የግድ የሚል ነው፡፡ ምክንያቱም የመንገጥር ውልን መሰረት አድርጎ የሚቀርበው ክስ የሚታገድበት የይርጋ ጊዜና የካሳ መጠኑ የሚሰላበት አግባብ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 599 አግባብ በልዩ ሁኔታ ጉዳዩ ሲታይ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ሊኖረው ከሚገባው የይርጋ ድንጋጌ እና የካሳ አሰላል የተለየ መሆኑን በንግድ ሕጉ አንቀፅ 587፣ 603 እና 597 ድንጋጌዎችን በአንድ በኩል፣ የንግድ ሕጉ አንቀፅ 599 እና ከውል ውጪ ኃላፊነትነት በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143፣ 2090 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተቀመጡትን ሁኔታዎች በሌላ በኩል በመመርመር የምንረዳው ጉዳይ ነውና ስለሆነም የመንገጥር ውልን መሰረት ያደረገ የካሳ ጥያቄ ሲቀርብ ጉዳዩ በየትኛው የህግ ማዕቀፍ እንደሚገዛ መለየት የይርጋውንም ሆነ የካሳ ስሌቱን በአግባቡ ለመዳኘት የሚያስችል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚገዙ ድንጋጌዎችን ጠቅሰው ሲሆን የአሁኑ አመልካቾች የክሱ አመሰራረት ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሰረት ማድረጉ ያላግባብ መሆኑን በመጥቀስ ግንኙነቱ የመንገጥር ውል መሆኑንና በንግድ ሕጉ ሲታይም ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ገልፀው ተከራክረው የስር ፍርድ ቤት የይርጋውን መቃወሚያ በሟች ላይ የደረሰው የሞት አደጋ በወንጀል ተጠቂነትን የሚያስከትል መሆኑን ጠቅሶና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(2) ድንጋጌን ዋቢ በማድረግ ከአለፈው በኃላ የካሳውን መጠን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲወስን ግን አደጋው የደረሰው በጥፋት ስለመሆኑ ያለመረጋገጡንና የን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ካሳው ሊሰላ የሚችልበት ምክንያት ያለመኖሩን ገልጾ ካሳውን በን/ሕ/ቁጥር 597 አግባብ መወሰኑን የውሳኔው ግልባጭ በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ለይርጋ ጉዳይ ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ መሰረት ማድረጉ በካሳው ስሌት ጊዜ ከደረሰበት ምክንያት ጋር የሚጋጭ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ጉዳዩ በን/ህ/ቁጥር 599 አግባብ በተቀመጠው ልዩ ሁኔታ አግባብ ወደ ውል ውጪ ድንጋጌዎች የሚያስኬድ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ ለይርጋ አፈጻጸም ወደ ፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143 ድንጋጌ ለመሄድ የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ተጠሪዎች ጉዳቱ በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ በተቀመጠው ጥፋት የደረሰ ስለመሆኑ ያላስረዱ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያሳይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ ከሕግ እና ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ ነው የሚሉ ከሆነም በስርዓቱ መሰረት ያቀረቡት ይግባኝ ወይም የሰበር ክርክር ስለመኖሩ ተጠሪዎች ገልጸው ያለመከራከራቸውን ተገንዝበናል፡፡ እንዲሁም የ2ኛ ተጠሪን ተሸከርካሪ ያሽከረክር የነበረው አሽከርካሪ በወንጀል ተከሶ ነበር የሚል ክርክር ተጠሪዎች ከማቅረባቸው ውጪ ይህንኑ የሚያሳይ ማስረጃ ያለማቅረባቸውንና የወንጀል ክርክሩ ተጀምሮ ከነበረም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሰነድ እንዲያቀርቡ በቂ ጊዜ ተሰጥቶአቸው ማስረጃው ያለመቅረቡ የይርጋው ጉዳይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(2) ድንጋጌ አግባብ የሚታይ ነው ለማለት የሚያስችል አግባብ ያለመኖሩን የሚያስገነዝብ ሁኖ አግኝተናል፡፡

እንግዲህ በ2ኛ አመልካች በተጠሪዎች ልጅ መካከል የተመሰረተው የመንገጭ ውል ነው ከተባለና ግንኙነቱ በንግድ ሕጉ የሚገዛ ነው ከተባለ ይርጋውን አስመልክቶም ይኼው ልዩ ሕግ በአንቀፅ 603 ስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት አጓዥ ተጓዥ መሰረት ተደርገው የሚቀርቡት ክሶች በንግድ ሕጉ 603 በተደነገገው አግባብ መሰረት በሁለት ዓመት ጊዜ መቅረብ እንደአለባቸውና በዚህ አግባብ ካልቀረቡ ግን የአጓዥ ተጓዥ ግንኙነትን መሰረት በማድረግ ማቅረብ እንደማይቻል የድንጋጌው ይዘት ያሳያል፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት ልጃቸው ሰኔ 07 ቀን 2001 ዓ/ም በመኪና መገልበጥ አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በኋላ ግንቦት 28 ቀን 2005 ዓ/ም መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሲሆን ይህ ጊዜ የን/ሕ/ቁጥር 603 መሰረት ተደርጎ ሲታይ ሶስት አመት ከ11 ወራት ከ21 ቀናት በኋላ ክስ መቅረቡን የሚያስገነዝብ በመሆኑና ይርጋውን ሊያቋርጥ የሚያስችል የሕግ ምክንያትም የሌለ ሁኖ ስለአገኘነው የበታች ፍርደ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143 ድንጋጌን መሰረት አድርገው የይርጋ ክርክሩን ማለፋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0111646 ህዳር 13 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01-14794 ታህሳስ 01 ቀን 2006 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ካሳ እንዲከፈላቸው የመሰረቱት ክስ የሚገዛው በን/ሕ/ቁጥር 587፣ በን/ሕ/ቁጥር 595 597 እና 603 ድንጋጌዎች አንፃር በመሆኑ ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ የታገደ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.98961

መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

መስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሣለኝ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ኡመር መሐመድ ┐ ከጠበቃ ገናነው ተሾመ

2. ወ/ሮ ነፍሳ ሲራጅ ┘ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሻ/ባሻ ከድር ቬህ አብዱላሂ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ከውክልና /እንደራሴነት/ ህግ አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ ተጠሪ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ለስር ፍ/ቤት ያቀረበው የክሱ ይዘት ባጭሩ፡- ተጠሪ በጊኒር ከተማ 02 ቀበሌ ውስጥ በስማቸው የተመዘገበ ቤት ያላቸው መሆኑን፣ ይህንኑ ቤትና ቦታ 1ኛ አመልካች በአደራ እንዲጠብቁና እንዲያስተዳድሩ የሚል በ4/9/1985 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተመዘገበ የውክልና ስልጣን ተሰጥቷቸው የነበረ መሆኑን፣ ሆኖም ግን አንደኛ አመልካች ከተሰጠው ውክልና ስልጣን ውጭ በመውጣት ባለቤታቸው ለሆኑት ለሁለተኛ አመልካች በዝቅተኛ ዋጋ በብር 2500 የሸጡ መሆኑን፣ በዚሁ መነሻነት ለ1ኛ አመልካች ተሰጥቶ የነበረው የውክልና ስልጣን በተጠሪ መሻሩን፣ ይህንኑን ተከትሎም አንደኛ አመልካች ቤቱን ለማስረከብ ፍላጎት ስላልነበረው በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ-05861 በሆነው ላይ ክስ ቀርቦ እንደነበረና ፍ/ቤቱም በበኩሉ አንደኛ አመልካች በቤቱ ላይ የፈፀመው የሽያጭ ውል የተጠሪን መብት የሚጋፋ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ-2187 መሠረት ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብቱን ጠብቆ ወስኖ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው ይህ በአመልካቾች መካከል የተፈፀመው የሽያጭ ውል አንደኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከራሱ ጋር እንደፈፀመ የሚቆጠር በመሆኑና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ-2187 መሠረት የጥቅም ግጭት መፈጠሩን የሚያሳይ ስለሆነ በዚሁ የህግ ድንጋጌ መሠረት ውሉ ፈርሶ አመልካቾች ቤቱን እንዲያስረክቡና እንዲሁም ከ5/3/1998 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን ያለአግባብ ለተጠቀሙበት የቤቱ ኪራይ ገቢ በወር ብር 500 ታስቦ በድምሩ ብር 33,000 አመልካቾች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ጭምር ይወሰንባቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ሲሆን አንደኛ አመልካችም በበኩሉ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው የመከላከያ መልስ፡- ይህንኑ ቤት በተመለከተ ከዚህ በፊት ክስ ቀርቦ ውድቀ የተደረገ ስለሆነ ክሱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ-5 መሠረት በድጋሚ ሊቀርብ የማይገባ መሆኑንና ክሱም በ2 ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን በመቃወም የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም የውክልና ስልጣኑ ቤቱን እንዲያስተዳድር ብቻ የሚል ሳይሆን ቤቱን የመሸጥና የመለወጥ ስልጣን ጭምር ያካተተ ስለሆነ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በ19/5/1986 ዓ.ም የተደረገው የአነድ ክፍል አሮጌ ቤት ሽያጭ ውል ከወቅቱ የቤቱ ዋጋ ጋርም ተገናዝቦ ሲታይ ህጋዊና የተጠሪን መብት የነካ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ አመልካችም በበኩሏ ከ1ኛ አመልካች ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው መቃወሚያ አቅርበው የተከራከሩ መሆኑን ከስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም የቤቱ ሽያጭ ውል ህጋዊ በመሆኑ ሊሰረዝ የማይገባ መሆኑንና እንዲሁም ሽያጭ ውሉን ተከትሎ የቤቱ ስመ ሀብት ወደ ስማቸው እንዲዞር ከተደረገ በኋላ በ1987 ዓ.ም ቤቱን አፍርሰው በአዲስ መልክ ትልቅ ቤት ገንብተው እየተገለገሉበት ያለ የግል ንብረታቸው መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ይወሰንላቸው ዘንድ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቶ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ፡- 1. ጉዳዩ ከዚህ በፊት በፍ/ቤቱ መ.ቁ 05861 ውሳኔ አግኝቷል? ወይስ አላገኘም? 2. አመልካችስ ቤቱን ለመሸጥና ለመለወጥ የሚያስችለው የውክልና ስልጣን ነበረው? ወይስ አልነበረውም? 3. ነበረው ከተባለስ ተጠሪ ሽያጭ ውሉን መቃወም ይችላል? ወይስ አይችልም? 4. ይችላል ከተባለስ ይሄንን ጥያቄ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ማቅረብ አለበት? የሚሉትን ነጥቦች በጭብጥነት ይዞ 1ኛ አመልካች ከተጠሪ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት ቤቱን ስለመሸጡና የውክልና ሰነዱም ይሄንን ለማድረግ ለ1ኛ አመልካች ስልጣን የሚሰጠው ስለመሆኑ በመ.ቁ.05861 ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ መሆኑን ጠቅሶ በዚህ ነጥብ ላይ በድጋሚ ውሳኔ መስጠቱ አላስፈላጊ ነው በማለት አልፏል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በክሱ እንደገለፀው 1ኛ አመልካች በእንደራሴነት ስልጣኑ ቤቱን ባለቤታቸው ለሆኑት ሁለተኛ አመልካች መሸጡን የውክልና ስልጣኑን በ1/3/1998 ዓ.ም በሚያነሳበት ጊዜ ያውቅ የነበረ መሆኑን ስለገለፀና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ያለው ጊዜ ደግሞ ሲቆጠር 5 ዓመት ከ6 ወር በላይ መሆኑን በማስፈር ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ-2187/2/ መሠረት በ2 ዓመት ይርጋ ይታገዳል ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢቀርቡም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ሆኖም ግን በተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪና አንደኛ አመልካች በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ-05861 ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ክርክር ላይ የቆዩ መሆናቸውን ጠቅሶ እና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ-1851 መሠረት የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠር የሚያቋርጥ ሆኖ ሳለ የበታች ፍ/ቤቶች ክሱ በ2 ዓመት ይርጋ ይታገዳል ሲሉ መወሰናቸው ህጋዊ አይደለም በማለት ሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍሬ ነገሩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን ይወሰን ዘንድ ክርክሩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ-341/1/ መሠረት መልሶ ልኮለታል፡፡ አመልካቾችም ይህንኑ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ ሲሆን አቤቱታውም ተመርምሮ በሰበር ሰሚ ችሎቱ እንዲታይ በመታዘዙ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ ይዘት ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክሱ በይርጋ አይታገድም ሲል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪ ክሱን በስር ፍ/ቤት ሲያቀርብ አንደኛ አመልካች ቤቱን ለማስተዳደር እንጅ ለመሸጥና ለመለወጥ የውክልና ስልጣን አልተሰጠውም በማለት ቢከራከሩም ለአንደኛ አመልካች ተሰጥቶ የነበረው የውክልና ስልጣን ቤቱን ለመሸጥና ለመለወጥ የሚያስችላቸው ስልጣንም ጭምር የሚያካትት ስለመሆኑ ከዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ይዘት መገንዘብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ቢሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበትን መደምደሚያ ሃሳብ በውሳኔው ጠቅሶ አልለወጠውም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ይህ ክርክር የቀረበበት የውክልና ስልጣን አድማሱ ቤቱንም የመሸጥና የመለወጥ ተግባርንም ያካትታል ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች ድምዳሜ የተያዘበት ጉዳይ እኛም ልንቀበለው የሚገባው ነው፡፡

በሌላ በኩል የሰበር አመልካቾች ባልና ሚስት መሆናቸው አልተካደም፡፡ እንዲሁም 1ኛ አመልካችም የውክልና ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ቤቱን በ19/5/1986 ዓ.ም በተደረገው ሽያጭ ውል ስምምነት መሠረት የሸጡት ሚስታቸው ለሆኑት ሁለተኛ አመልካች ስለመሆኑ አከራካሪ ጉዳይ ካለመሆኑም በላይ በማስረጃም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ውክልና ስልጣኑን መሰረት ተደርጐ ከተፈጸመው ሽያጭ ውል ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ሕ/ቁ-2187/1/ ስር እንደተመለከተው የጥቅም ግጭት ስለመኖሩ የሚያከራክር ጉዳይ ባለመሆኑ ተጠሪ የሽያጭ ውሉን በዚሁ በተጠቃሹ ድንጋጌ መሠረት ለማስፈረስ ለመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ቤቱ ለ2ኛ አመልካች መሸጡን ተጠሪ የውክልና ስልጣኑን በሻሩበት ጊዜ /በ1/3/1998 ዓ.ም/ ያውቅ የነበረ ስለመሆኑና ይህንኑም በክሱ አቤቱታ ጭምር እራሱ ገልጾ የነበረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሽያጭ ውሉ ይፍረስልኝ የሚለው ጥያቄ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ-2187/2/ መሠረት በ 2ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ ከተጠቀሰው የህጉ ድንጋጌ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ ቀርቶ ተጠሪ በቀድሞው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መ.ቁ-05861 በሆነው እራሱ ክሱን ያአቀረበው በ22/9/2000 ዓ.ም ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለ ሲሆን ይህም ከ1/3/1998 ዓ.ም ጀምሮ ጊዜው ሲቆጠር ከ2 ዓመት በኋላ የቀረበ ሆኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መ.ቁ-05861 የቀረበው ጉዳይ ለክርክሩ አግባብነት ያለውንና በፍ/ብ/ህ/ቁ-2187/2/ ስር የተመለከተውን የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ ስለሚያቋርጥ ክሱ በይርጋ አይታገድም የሚል የመደምደሚያ ሀሳብ ላይ ደርሶ የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ-1851 እና 2187 ድንጋጌዎች ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያገናዘበ ባለመሆኑ ውሳኔው የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.158348 በ21/4/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ-348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የባሌ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ-11926 በ19/11/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ-144852 በ9/4/05 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ-348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የተጠሪ ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ-2187/2/ መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳል ብለናል፤ በዞኑ ከ/ፍ/ቤት መ.ቁ.05861 በተጠሪ ቀርቦ የነበረው ክስም ተጠሪ ሽያጭ ውሉ መደረጉን ካወቁበት ጊዜ አንስቶ ከ2 ዓመት ጊዜ በኋላ የቀረበ በመሆኑ የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠር የሚያቋርጥ አይደለም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ የሰበር ወጪና ክሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.104061

መስከረም 25ቀን 2008ዓ.ም

ዳኞች:-አልማዉ ወሌ

ረታ ቶሎሣ

መስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሣለኝ

አመልካቾች፦ አቶ ፍቅሬ ግርማ ቀረቡ

ተጠሪ፦ አቶ ደስታ ጫምሶ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከዋስትና ውል ጋር ተያይዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የጀመረው ያለሁኑ አመልካች በኦሮሚያ ክልል አርሲ ነገሌ ወረዳ ፍ/ቤት የሰበር ክርክሩ ተከፋይ ያልሆነው አቶ አበበ ኤርጊቾ እና ሰበር ተጠሪ ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው።የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ÷ግምቱ 20,000 ብር የሆነውን የኢጣሊያን ስሪት እህል ሚዛን 1ኛተከሳሽ በ 24/2/2001 ዓም በተደረገ ኪራይ ውል ወስዶ በኋላ ላይ እንዲመልስ ሲጠየቅ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነም፣2ኛ ተከሳሽም በበኩሉ ሚዛኑን ለመመለስ ወይም መተካት የዋስትና ግዴታ ገብቷል፣ስለዚህ ተከሳሾቹ ተጠይቀው ሚዛኑን የማይመልሱ ከሆነ በገቡት ግዴታ መሠረት ግምቱን ይክፈሉኝ በሚል ዳኝነት የተጠየቀበት መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ክሱ ስነ-ስርዓቱን ጠብቆና ተሟልቶ አልቀረበም በሚል ምክንያት ተከሳሹ በወረዳ ፍ/ቤቱ ከክሱ ወጭ መደረጉን ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለ ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ ግን ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ የገባው የዋስትና ግዴታ የሌለ መሆኑን፣የዋስትና ውል ነውተብሎ በቀረበው ሰነድ ላይ ያለውም ፊርማ የራሱ ያለመሆኑንና የዋስትና ውሉም ራሱ ለምን ያህል ገንዘብ ግዴታ እንደተገባ ስለማያሳይ በፍ/ብ/ህ/ቁ-1922(3) መሠረት ውሉ ፎርማሊቲን አያሟላም ተብሎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ወረዳ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና በዋስትና ውሉ ላይ የተጠቀሱትን ምስክሮች ቃል ሰምቶ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ተጠሪ የዋስትና ዉሉን መፈረሙ በምስክሮች ቃል መረጋገጡን መገንዘቡን ካሰፈረ በኋላ ተጠሪ በዉሉ የተጠቀሰውን ሚዛን አይነት አዲስ ለአመልካች ይተካ ሲል ወስኗል። ባለሁኑ ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በዋስትና ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ መሆን ያለመሆኑን ለማጣራት ሲባል ፊርማው በፎረንሲክ ተመርምሮ ውጤቱ እንዲቀርብ የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የዋስትና ውሉ ፎቶ ኮፒ በመሆኑ ምርመራውን በዚህ ምክንያት ማካሄድ አልተቻለም የሚል ምላሽ ከተሰጠው በኋላ ጉዳዩን ባለበት ሁኔታ መርምሮ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ-348(1) መሠረት መልሶ አፅንቶታል። ተጠሪ አሁንም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርቦና ችሎቱም በበኩሉ ግራ ቀኙ ቀርበው እንዲከራከሩ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የዋስትና ውሉ ዋሱ (ተጠሪ) ለምን ያህል ገንዘብ ግዴታ እንደገባ የማይገልፅ መሆኑን ጠቅሶና እንዲህ ከሆነ ደግሞ ውሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ-1922(3) ስር የተመለከተውን የህግ መስፈርት ስለማያሟላ በዋሱ ላይ ግዴታ ሊጥል አይችልም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሽሯል።

አመልካችም ይሄንኑ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም ባጭሩ፣ለዋስትና ውሉ መነሻ የሆነው ግዴታ ዓይነትም የእቃ ኪራይ እንጅ ብድር ውልን የሚመለከት ካለመሆኑ በላይ ተጠሪም እራሱ በዋስትና ውሉ መሠረት የገባው ግዴታ በፍ/ብ/ህ/ቁ-2727 እና 2738 ስር እንደተመለከተው ሚዛኑን እራሱን በአይነት ለመተካት ወይም ለመመለስ ከመሆኑ አንፃር በውሉ ላይ የገንዘብ መጠን መጥቀስ የግድ አይደለም የሚል ይዘት ያለው ሲሆን አቤቱታውም ተመርምሮ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት በመመራቱ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን መርምረናል። መዝገቡን እንደመረመርነውም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ሚዛን ከአመልካች የተከራየሁ ግለሰብ (ዋና ባለእዳ) በውሉ መሠረት መልሶ ለአመልካች አለማስረከቡ ክርክር የቀረበበት ጉዳይ አይደለም።ተጠሪም በበኩሉ በዋስትና ውሉ ላይ ተመሳሳዩን ሚዛን በዓይነት ለመተካት በሚል የዋስትና ግዴታ እንደገባ ተደርጎ በውሉ ላይ መስፈሩን የክርክሩ ሂደት ያሳያል።ሆኖም ግን የዋስትና ውሉ አፃፃፍ ወይም ይዘት ምንም ይሁን ምን ዋሱ ግዴታ የገባበትን የጎላፊነት መጠን ወይም ልኩ ምን ያህል እንደሆነ በዋስትና ውሉ ላይ በገንዘብ ካልተገለፀ በስተቀር ዋስትናው ፈራሽ እንደሚሆን ከፍ/ብ/ህ/ቁ-1922(3) ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ ተመሳሳዩን ሚዛን በዓይነት ለመተካት በሚል የዋስትና ውሉን የፈረመ ቢሆንም የግዴታው መጠን ግን እስከ ምን ያህል እንደሆነ በገንዘብ ተገልፆ በውሉ ላይ አልተመለከተም። ይህ የዋስትና ግዴታ አድማስ ደግሞ ለምን ያህል እንደሆነ በውሉ ላይ በገንዘብ ካልተገለፀ የዋስትና ውሉ ዋጋ ስለማይኖረው ወይም ፈራሽ ስለሚሆን አመልካች የገንዘቡ መጠን መገለፅ የግድ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት ስለሌለው አልተቀበልነውም።

በሌላ በኩል ለዋስትና ግዴታው መሠረት የሆነው ጉዳይ የእቃ ኪራይን የሚመለከት ግዴታ ይሁን ወይም ሌላ ዋናው ቁም ነገር በዚህ ጉዳይ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የዋናው ግዴታ ውል (የእቃ ኪራይ ውል) እራሱ ሳይሆን የእሱ ተቀፅላ (accessory) የሆነው የዋስትና ውል ነው።አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ጉዳይ የዋስትና ውሉ ከሆነ ደግሞ በተለይ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የህጉ ክፍል የፍ/ብ/ህ/ቁ- 1920ና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ናቸዉ እንጂ አመልካች በሰበር አቤቱታዉ የጠቀሳቸዉ የፍ/ብ/ህ/ቁ2727 እና 2738 ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም። ሲጠቃለል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተፈፀመው የዋስትና ውል ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ህ/ቁ-1922(3) ድንጋጌን መስፈርት ስለማያሟላና ፈራሽ ስለሆነ ተጠሪ ላይ ግዴታ ሊጥል አይችልም በማለት ከኃላፊነት ነፃ በማድረግ መወሰኑ ህጉን በትክክል መሠረት ያደረገነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ሊባል የሚቻል ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመቁ-175321 በ 23/10/2006 ዓ.ም የሰጠዉ ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ-348(1) መሠረት ፀንቷል።
2. የአመልካች ሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል።
3. የሰበር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.98583

መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካቾች፡- 1ኛ/ ወ/ሮ ኤደን ሲሳይ ጠበቃ አቶ በላይነህ ማሞ ቀረበ

2ኛ/ ወ/ሮ አስቱር ደምሴ

ተጠሪ፡- አቶ ሰይፈ ዓለሙ - የህፃን ናትናኤል ሰይፉ እና የህፃን ዮናታን ሰይፉ ሞግዚት ጠበቃ አለማየሁ አበበ

መዝገቡን መርምረን ተከታዮን ወስነናል ፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳዩ የውል ይፍረስልኝ የዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው ፡፡ የአሁን ተጠሪ ከሳሽ ፤የአሁን አመልካቾች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ከሥር ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጮች መረዳት እንደሚቻለው ከሳሽ ባቀረቡት የክስ አቤቱታ የሚች ወ/ሮ ፈትለወርቅ ተረፈ በህይወት በነበሩበት ወቅት በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ቀበሌ 09/14 የቤት ቁጥር 750 የሆነ የድርጅት ቤት የነበራቸው ሲሆን ይህን ቤት 1ኛ ተከሳሽ ከሚች ውክልና ተሠጥቶኛል በሚል ሚች በከፍተኛ ህመም በነበሩበት ጥቅምት 25/2002 ዓ.ም ተደረገ በተባለ ውል ለ 2ኛ ተከሳሽ የሸጡ በመሆኑና ውሉንም አደረግን የሚሉት በውል አዋዋይ ፊት ሚች ከሞቱ ከዘጠኝ ቀን በኃላ በመሆኑ ፤ውክልናው በሞት ምክንያት ቀሪ ከተደረገ በኃላ የተደረገ በመሆኑና ፤ቤቱም በሚሊዮን የሚቆጠር ዋጋ የሚያወጣ ሆኖ እያለ ሞግዚት የሆንኩላቸውን ተተኪ ወራሾች ለመጉዳት በብር 250,000.00 ተሸጠ መባሉ ተገቢ ባለመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰን በማለት ጠይቀዋል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሾችም በየራሳቸው በሠጡት መልስ ሟች ቤቱን ሚያዝያ 1/2001 ዓ.ም በተደረገ የመንደር ውል የሸጡ መሆኑን፤በዚህ ውል ቤቱን ከዕዳ ነፃ ሲያደርጉ በአዋዋይ ፊት ለመፈረም በተስማሙት መሠረት ይህን ለማክበር ጥቅምት 25/2002 ዓ.ም የሽያጭ ውል መደረጉን ፤በዕለቱም በሠነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ለመፈራረም ውሉንና ምስክሮች ይዘው በአካል ቀርበው ወደ እገዳ ማጣሪያ ክፍል ተመርቶ ግብሩ ላይ እንዲታረም የተነገራቸው ታርሞ ከተጠናቀቀ በኃላ ውሉ በ 27/2/2002 ዓ.ም የተፈረመ መሆኑንና፤ ህዳር 7/2002 ዓ.ም የግዥ አገልግሎት ክፍያ የተፈፀመበት እንጂ ውሉ የተፈረመበት አለመሆኑን ፤ውሉ ከተፈፀመ በኃላ ሟች ወ/ሮ ፈትለወርቅ ተረፈ ጥቅምት 28/2002 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዮ መሆኑን ነገር ግን በ1/08/2001 ዓ.ም ከሽያጩ ገንዘብ ብር 200,000.00 መከፈሉን በመጥቀስ ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዮን በቅድሚያ የተመለከተዉ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ተመልክቶ በመጨረሻ በሰጠው ውሳኔ ሟች ለ 1ኛ ተከሳሽ ውክልና የሠጡትና በሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በ27/02/2002 ዓ.ም በወኪሉ 1ኛ ተከሳሽ እና በገዥ 2ኛ ተከሳሽ መካከል ውል ሲፈረምና ከሽያጩ የቀረው ገንዘብ ብር 5000.00 ሲከፈል በህይወት የነበሩ በመሆኑ ፤በፍ/ብ/ህ/ቁ.2232/1/ መሠረት ወካዮ ከሞተ የውክልናው ስልጣን ወዲያውኑ ቀሪ የሚሆን ቢሆንም በንዑስ ቁጥር 2 ሥር በእንዲህ አይነት ሁኔታ ተወካይ ሥራውን ቢያቋርጥ በጉዳዩ ላይ አደጋ የሚደርስበት እንደሆነና በዉክልናው ሥልጣን መሠረት ሥራውን ጀምሮ እንደሆነ የዋናው ወካይ ወራሾች ወይም ህጋዊ እንደራሲዎች አስፈላጊውን እስኪያደርጉና ራሳቸውም ሊያስቡበት እስኪችሉ ድረስ ስራውን መቀጠል አለበት በማለት የሚደነግግ በመሆኑ፤በተያዘውም ጉዳዮ 1ኛ ተከሳሽ ተወካዮ መሆናቸው ያልተካደና ውሉም ቀደም ብሎ በመንደር የተደረገውን ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ለማድረግ መሆኑን መገመት የማያዳግት በመሆኑ ፤ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2232/2/ መሠረት ተወካዮ (1ኛ ተከሳሽ)ሥራውን ጀምሮት ስለ ነበር መቀጠል እንዳለበት የተደነገገውን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ከሳሽ ውክልናው ቀሪ ከሆነ በኃላ የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኃላ ባሳለፈው ውሳኔ ሚያዝያ 1/2001 ዓ.ም ተደረገ ስለተባለው የገንዘብ አከፋፈል በተመለከተ የአሁን 1ኛ አመልካች የሽያጭ ገንዘቡን እኔ እራሴ ቆጥሬ ተቀብያለሁ ሲሉ 2ኛ አመልካች ደግሞ ለሟች ወ/ሮ ፈትለወርቅ ገንዘቡን ቆጥሬ በእጃቸው ሰጥቻለሁ በማለት የሚቃረን መልስ ማቅረባቸው የሽያጭ ውሉ ሚያዝያ 1/2001 ዓ.ም የተጀመረ ነው በማለት የሚያቀርቡትን ክርክር አሳማኝ የማያደርገዉ በመሆኑ፤ጥቅምት 25/2002 ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል ሟች ከመሞታቸው ከ3 ቀናት በፊት መሆኑና በሠነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተመዘገበው ደግሞ ህዳር 7/2002 ዓ.ም ሟች ከሞቱ ከዘጠኝ ቀን በኃላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑ የታመነ ጉዳይ በመሆኑ፤የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2232(2) አግባብነት የሚኖረዉ በወኪሉ ቀድሞ የተጀመረው ሥራ ወራሾችን በሚጠቅም መልኩ እንዲቀጥል የተደረገ እንደሆነ ብቻ ሲሆን በተያዘው ጉዳዮ ግን ወኪሉ ወካያቸው ከሞቱ በኃላ በሟች ንብረት ላይ የሽያጭ ውል መፈራረማቸው ወራሾችን የሚጠቅም ሳይሆን ንብረቱን ለሌላ አሳልፎ በመስጠት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግና በእጅጉ የሚጐዳቸው በመሆኑ፤ የቤት ሽያጭ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረው ሟች ከሞቱ በኃላ ህዳር 7/2002 ዓ.ም ነው እንጅ እንደ መ/ሰጭዎች /የአሁን አመልካቾች / አባባል ሟች ከመሞታቸው ከ 3 ቀን በፊት ተጀምሮ ነበር ቢባል አንኳን ሟች በጠና ታመው ኮማ ውስጥ ነበሩ በተባለበት ሰዓት ላይ በመሆኑ በጅምር የቤት ሽያጭ ውሉ ላይ የሟች ፈቃድ ነበረበት ለማለት አያስደፍርም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር በአመልካቾች መካከል ጠቅምት 25/2002 ዓ.ም የተጀመረውና ህዳር 7 ቀን 2002 ዓ.ም የተመዘገበው የሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባል በማለት ወስኗል ።

የአሁን አመልካቾች ይህን ውሣኔ በመቃወም ይግባኙን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ውሳኔው ጉድለት የለበትም ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሠረት ይግባኙ ተሠርዟል ። የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበው በዚህ ነው አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ መልስ እንዲሠጡበት ጥሪ የተደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅሑፍ አቅርበዋል ። ይህ ችሎትም የሠበር አቤቱታውን ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

ከላይ እንደተገለፀው አመልካቾች የሽያጭ ውሉ የተደረገው ሟች በህይወት ሳሉ በመሆኑ ወራሾች ሟች በህይወት ሳሉ የፈፀሟቸውን ህጋዊ ተግባራት መቃወም መብት ስለሌላቸው ውሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት እንዳይኖረው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ውክልናው በወካዮ ሞት ምክንያት ቀሪ ከሆነ በኃላ የተደረገ ውል በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ እንደሚገባ ተከራክረዋል ። ስለሆነም የሽያጭ ውሉ ተደረገ የሚባለው መቼ ነው የሚለውን አግባብ ካለው ህግ ጋር በማያያዝ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል።

የሽያጭ ውሉ የሚመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረትን በመሆኑ ውሉ በጽሑፍ ከመደረጉ በተጨማሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በዳኛ ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1723/1/ ሥር ተደንግጓል ። የቤት ሽያጭ ውሉ ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው በዚህ የህግ ስርዓት /ፎርም/ መደረግ ይኖርበታል። የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት እንዲደረግ የሚያስፈልገው የተዋዋዮችን ማንነት፣ያላቸውን ችሎታና መብት እንዲሁም ነፃ ፈቃዳቸውን መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ውሉ የተደረገበትን ቀንም ለማረጋገጥ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይ እንደ አመልካቾች ክርክር ቤቱን የተመለከተ ዕዳና እገዳ ለማጣራትና ክፍያ ለማስፈፀም የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተወሰኑ ቀናት መውሰዱ የተመለከተ ቢሆንም በውሉ ላይ ማህተሙ የተደረገውና የኘሮቶኮል ቁጥር ተሠጥቶት የተረጋገጠው ህዳር 7/2002 ዓ.ም መሆኑ እና በዚህ ቀን ውክልና ስልጣን ሰጭ በህይወት እንዳልነበሩ አላከራከረም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2015/ሀ/ መሠረት ሠነዱ የተፃፈበት እርግጠኛ ቀን ነው የሚባለው ሠነዱን የፃፈው ወይም የተቀበለው እንደ ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤትን በመሠለ የመንግስት መ/ቤት ሲሆን የፃፈበት /የተቀበለበት/ ቀን መሆኑም ተደንግጓል፡፡ ፍሬ ነገሩን ለማጣራት በህጉ ሥልጣን የተሰጣቸው ፍ/ቤቶች የአመልካቾችን ክርክር ተቀብለው የሽያጭ ረቂቅ ሰነዱን ጽ/ቤቱ የተቀበለበትን ቀን እስካላረጋገጡ ድረስ በሰነዱ ላይ የተፃፈበት ቀን ተደርጐ የሚወሰደው በባለሥልጣኑ የተጻፈው ቀን ነው፡፡

ስለሆነም የቤት ሽያጭ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገው ህዳር 7/2002 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ጊዜ በሟሚው ሞት ምክንያት ለሻጭ /1ኛ አመልካች/ የተሰጠው ውክልና ቀሪ በሆነበትና ንብረቱን በሽያጭ ማስተላለፍ የሚያስችል ሥልጣን በሌለበት የተደረገ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ በመወሠኑ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል የተባለበትን ነጥብ በሥር ፍ/ቤቶች ያልተረጋገጠን ፍሬ ነገር የያዘና ለጉዳዮ አወሳሰን ተገቢነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2232/2/ መሠረት ያደረገ በመሆኑ መመርመር አላስፈለገንም ፡፡ በመሆኑም ተከታዮ ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ.131733 ታህሳስ 10/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.96979 የካቲት 12/2006 ዓ.ም ያሳለፈው ተእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ፡፡
3. የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል ይባፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 99667

መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ለሊሴ ደሳለኝ

አመልካች፡- ቻኮ ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር -- የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ናሽናል ሞተርስ ኮርፖሬሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር -ጠበቃ ነስቡ ሜኮ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የሽያጭ ውል አፈጻጸምን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ በ26/07/2004 ዓ.ም. አዘጋጅቶ ያቀረበው ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ከሳሽ እና ተከሳሽ በ06/04/1998 ዓ.ም. ባደረጉት የሽያጭ ውል ከሳሽ ብዛታቸው 13 የሆነ ሬኖ ክራክስ ተሽርካሪዎችን/ሻሲዎችን/ የተጨማሪ እሴት እና የስም ማዛወሪያ ወጪዎችን ጨምሮ እያንዳንዳቸውን በብር 1,051,346 በጠቅላላው ደግሞ በብር 13,667,498 ለመሸጥ በመስማማት ተሽከርካሪዎቹን ከ29/02/2000 ዓ.ም. በፊት ለተከሳሽ ያስረከበ መሆኑን፣ተከሳሽ ከሸያጩ ገንዘብ ውስጥ ብር 9,434,248.80 በባንክ በኩል የከፈለ መሆኑን፣ከቀሪው ብር 4,233,249.80 ውስጥ ከሳሽ ብር 2,183,125 በውሉ አንቀጽ 4.2 መሰረት መክፈል የነበረበት ተሽርካሪዎቹን ከመረከቡ በፊት ቢሆንም ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 545,781.27 ያልከፈለ መሆኑን፣የመጨረሻውን ክፍያ ብር 2,050,124.70 በውሉ አንቀጽ 4.3 መሰረት ተከሳሽ ተሽርካሪዎቹን ከተረከበ የአንድ ወር የችሮታ ጊዜ ካለፈ በኃላ ባለው 12 ወር ጊዜ ውስጥ ከ9.5% ወለድ ጋር ከፍሎ ለማጠናቀቅ የተስማማ ቢሆንም ክፍያውን ያልፈጸመ መሆኑን፣የሚፈለግበትን ገንዘብ እንዲከፍል ከሳሽ በ23/07/2003 ዓ.ም. ለተከሳሽ ማስጠንቀቂያ የሰጠ ቢሆንም ለመክፈል ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሽ የሚፈለግበትን ገንዘብ ብር 2,595,905.97 መክፈል ከነበረበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከ20/05/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በውሉ አንቀጽ 5 መሰረት በዚሁ ገንዘብ ላይ ከሚታሰበው 9.5% ወለድ ጋር እንዲከፍል ከሳሽ በክሱ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ በ18/10/2004 ዓ.ም. በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጠው መልስ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1803 መሰረት የገንዘብ ዕዳ ያለበት ሰው ወለድ ለመክፈል የሚገደደው ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ ከሳሽ ማስጠንቀቂያ ከሰጠበት ከ10/08/2003 ዓ.ም. በፊት ወለዱ እንዲታሰብ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ይህ የሚታለፍ ከሆነ ከሳሽ ተሽከርካሪዎቹን አስረክቤለሁ ካለበት ከ29/02/2000 ዓ.ም. ጀምሮ የአንድ ወር የችሮታ ጊዜውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ወለዱ መታሰብ መጀመር የሚገባው ተከሳሽ ገንዘቡን አልከፈለም ሊባል ከሚችልበት ከ29/03/2001 ዓ.ም. ጀምሮ በመሆኑ ከሳሽ ከዚህ ቀን በፊት ወለዱ መታሰብ እንዲጀምር ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ከሳሽ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1757 ድንጋጌን እና በመዝገብ ቁጥር 38568 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሚቃረን ሁኔታ የበኩሉን ግዴታ ሳይወጣ ክስ ማቅረቡ ተገቢነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ተከሳሽ የመቻቻል ጥያቄ ያቀረበ በመሆኑ ገንዘቡን በማቻቻል ከሳሽ ተራፊውን ገንዘብ ለተከሳሽ እንዲከፍል እንዲወሰን በመጠየቅ ተከራክሮአል፡፡

ተከሳሽ በ18/10/2004 ዓ.ም. ባቀረበው የመቻቻል ጥያቄ ከሳሽ ለተከሳሽ በሰጠው ፕሮፎርማ ተሽከርካሪዎቹን ለማስረከብ የተስማማው በስምንት ወራት ውስጥ ሆኖ እያለ ያስረከበው ግን ለ15 ወራት አዘግይቶ በመሆኑ እና ለመኪናው የአካል ግንባታ የሚያስፈልገው ሶስት ወር ሲቀነስ ተከሳሽ በ12 ወራት ከተሽከርካሪዎቹ ስምሪት ማግኘት ይችል የነበረውን ገንዘብ ብር 6,240,000 ያጣ በመሆኑ ከዚሁ ገንዘብ እና በዚሁ ገንዘብ ከሚታሰበው ወለድ ላይ ከሳሽ የሚፈልገው ገንዘብ ተቀናሽ ተደርጎ ቀሪውን ገንዘብ ከሳሽ ከነወለዱ ለተከሳሽ እንዲከፍል እንዲወሰንለት የጠየቀ ሲሆን ከከሳሽ በመቻቻል ጥያቄው ላይ በ12/11/2004 ዓ.ም. በሰጠው መልስ በውሉ አንቀጽ 4.2 መሰረት ተከሳሽ ከርክክቡ በፊት መክፈል ከሚገባው ገንዘብ ብር 2,183,125 ውስጥ ብር 545,781.27 ያልከፈለ እና የውል ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ ምክንያት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1757፣2278 (1) እና በመዝገብ ቁጥር 39568 በተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት የበኩሉን የውል ግዴታ ሳይወጣ የኪሳራ ጥያቄ ሊያነሳ የማይችል መሆኑን፣ተከሳሽ የርክክቡን የጊዜ ስምምነት ያስረዳልኛል በማለት በማስረጃነት ያቀረበው ፕሮፎርማ የተሰጠው ለተከሳሽ ሳይሆን ለ3ኛ ወገን በመሆኑ እና ለተከሳሽ ነው ቢባል እንኳ የውሉ አካል ያልተደረገ በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ውሉ የተደረገው በተሽከርካሪዎቹ ሞዴል እና የመጫን አቅም እንጂ በሻንሲ ርዝመት ላይ አለመሆኑን፣ይሁን እንጂ ተከሳሽ እና ሌሎች ገዥዎች በጠየቁት መሰረት ከሳሽ የውል ግዴታ ባይኖርበትም ለመልካም ስሙ በማሰብ እና በቅን ልቦና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በርካታ ወጪ በማውጣት እና አስፈላጊ ዕቃዎችን የተሸከርካሪዎቹ የስሪት አገር ከሆነው ከፈረንሳይ አገር አስመጥቶ በመስፍን ኢንጂነሪንግ አማካይነት የማስተካከያ ስራ እንዲከናወን በማድረግ ርክክቡን የፈጸመ በመሆኑ ተከሳሽ በአስረጂነት የጠቀሰው እና የገዙትን ዕቃ ከጉድለቱ የተረከቡትን ገዥዎች የሚመለከተው የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2299 (2) ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ከሳሽ ተሽከርካሪዎቹን ማስረከብ የነበረበት በዘጠኝ ወር ጊዜ ውስጥ ነው ቢባል እንኳ ተከሳሽ ተገቢነት የሌለውን የካሳ ጥያቄ በማንሳት ማስተካከያ የሚደረግባቸው ከሆነ የሚረከባቸው መሆኑን ወይም አለመሆኑን በወቅቱ ባለመግለጹ እና በኃላ ላይ ግን በከሳሽ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት የሚረከባቸው መሆኑን የገለጸ ቢሆንም ማስተካከያ ተደርጎባቸው እንዲረከብ በተገለጸለት ጊዜም ባለመረከቡ በአጠቃላይ ርክክቡ ሰባት ወር ከአስራ አምስት ቀን የዘገየው በተከሳሹ ጥፋት መሆኑን፣ተቋረጠብኝ የሚለው ጥቅምም ተከሳሽ የገለጸውን ያህል አለመሆኑን በመግለጽ የመቻቻል ጥያቄው ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሮአል፡፡

ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን በ09/04/2005 ዓ.ም. በብይን በማለፍ በ22/06/2005 ዓ.ም. ክሱን ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ከሳሽ ክስ ባቀረበበት የገንዘብ መጠን ላይ ተከሳሽ ያቀረበው የማስተባበያ ክርክር ባለመኖሩ እንደታመነ የሚቆጠር መሆኑን፣ተከሳሽ ወለዱ መቆጠር መጀመር ያለበት ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ወይም ክርክክቡ ቀን ጀምሮ የአንድ ወር የችሮታ ጊዜን ሳይጨምር ገንዘቡ ተከፍሎ መጠናቀቅ ከሚገባው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ አለመሆኑ በውሉ አንቀጽ 5.2 የተመለከተ በመሆኑ እና ተከሳሽ የጠቀሰው የፍተሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1803 ድንጋጌም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ወለዱ መታሰብ የሚገባው ከርክክቡ ቀን ጀምሮ የአንድ ወር የችሮታ ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ መሆኑን፣የመቻቻል ጥያቄውን በተመለከተ ፕሮፎርማው በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1685 መሰረት የውሉ አካል ነው በማለት ተከሳሽ የተከራከረ ቢሆንም የተጠቀሰው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው አስቀድሞ የውል ግንኙነት ባላቸው ተዋዋዮች መካከል በመሆኑ ምክንያት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑን፣በቁጥር 1687 ድንጋጌ መሰረት ፕሮፎርማ የሀሳብ መግለጫ እንጂ ውል ባለመሆኑ የውሉ አካል አለመሆኑን፣በመሆኑም በውሉ መሰረት የርክክቡ አፈጻጸም መሰረት ያደረገው ጊዜን ሳይሆን የክፍያ ሁኔታን መሆኑን፣ከሳሽ ተሽከርካሪዎቹን ማስረከብ ያለበትን ጊዜ ውሉ የማይገልጽ በመሆኑ ምክንያት ሻጭ ማስረከብ የሚገባው በቁጥር 2276 እና 1756 (3) መሰረት ገዥው ሲጠይቀው መሆኑን፣ነገር ግን ተከሳሽ ከርክክቡ በፊት መክፈል ከነበረበት ገንዘብ ውስጥ ብር 545,781.27 ያልከፈለ በመሆኑ እና በባንኩ በኩል የተከፈለው ክፍያም የተከፈለው ከርክክቡ በኃላ ዘግይቶ መሆኑን፣ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1757፣2278 (1) እና በመዝገብ ቁጥር 39568 በተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ተከሳሽ የበኩሉን የውል ግዴታ ሳይወጣ ርክክብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲፈጸምለት ከሳሽን የመጠየቅ መብት የማይኖረው በመሆኑ ርክክቡ የዘገየው በከሳሽ ምክንያት ነው ለማለት የማይቻል መሆኑን፣ተከሳሽ በአስረጂነት የጠቀሰው ቁጥር 2299 (2) ደንጋጌ ተፈጸሚነት የሚኖረው የዕቃው ርክክብ የተፈጸመው ጉድለት እንዳለበት ሳይታወቅ በሆነ ጊዜ እንጂ ዕቃው አለበት የተባለው ጉደለት እየታወቀ ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎበት ርክክብ በተፈጸመበት ጊዜ ጭምር አለመሆኑን፣ተከሳሽ እንደሚለው ሻሲዎቹ ችግር አለባቸው ቢባል እንኳ ተከሳሽ ውሉን ማፍረስ ወይም የበኩሉን ግዴታ በመፈጸም ርክክብ በመጠየቅ ከተረከበ በኃላ ለደረሰበት ጉዳት ካሳ መጠየቅ የሚችል ሆኖ ሳለ ግዴታውን ሳይወጣ ርክክቡ በመዘግየቱ ምክንያት ለደረሰብኝ ጉዳት ከሳሽ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበው ጥያቄ የውልም ሆነ የሕግ አግባብ የሌለው መሆኑን ገልጾ የመቻቻል ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ተከሳሽ የሚፈለግበትን ቀሪ ክፍያ ብር 2,595,905.97 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አምስት ከዘጠና ሰባት) ከ26/04/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ 9.5% ወለድ ለከሳሽ እንዲከፍል የወጪን ኪሳራ መብት በመጠበቅ ጭምር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተከሳሽ ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ወለዱ መታሰብ የሚጀምርበትን ጊዜ በተመለከተ ብቻ ውሳኔውን በማሻሻል ወለዱ መታሰብ የሚገባው ከሳሽ በክሱ ከጠየቀበት ከ20/05/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው የመቻቻል ጥያቄ ከፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2299 ድንጋጌ አንጻር መታለፉ አላግባብ ነው የሚለውን እና ርክክብ የተፈጸመው በ29/02/2000 ዓ.ም. በመሆኑ ክፍያው መጠናቀቅ ያለበት ከ29/03/2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 29/03/2001 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑ በውሉ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች ገንዘቡን ከፍሎ አላጠናቀቀም ተብሎ በዕዳው ላይ ወለድ መታሰብ መጀመር የሚገባው ክፍያው ከሚጠናቀቅበት የመጨረሻ ቀን ማለትም ከ29/03/2001 ዓ.ም. ጀምሮ እንጂ መከፈል ከሚጀምርበት ከ20/05/2000 ዓ.ም. ጀምሮ መሆን የለበትም የሚለውን የአመልካች የአቤቱታ ነጥቦች ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብም በ09/03/2007 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ቀርቦ ተያይዞአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዙት ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም መሰረት ከፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2299 ድንጋጌ አንጻር የአመልካች የመቻቻል ጥያቄ የታሰፈው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? በሚል የተያዘውን የክርክር ነጥብ በተመለከለተ አመልካች በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመቻቻል ጥያቄ ያቀረበው በፍትበሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1685 ድንጋጌ አነጋገር መሰረት ፕሮፎርማው የውሉ አካል መሆኑን በመጥቀስ እና በፕሮፎርማው ላይ የተመለከተውን የርክክብ ጊዜ መሰረት በማድረግ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በፕሮፎርማው ላይ የርክክብ ጊዜ የተመለከተ መሆኑን ሳይክድ ነገር ግን ፕሮፎርማው የውሉ አካል ባለመሆኑ የርክክብ ጊዜውን ለመወሰን መሰረት ሊሆን አይችልም በማለት መከራከሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበውን የክርክር ነጥብ ሳይቀበል የቀረው የፍትበሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1685 ድንጋጌ ተፈጸሚነት የሚኖረው ተዋዋዮቹ አስቀድሞ የተቋቋመ የውል ግንኙነት ሲኖራቸው በመሆኑ እና አስቀድሞ የውል ግንኙነት ያላቸው ስለመሆኑ ደግሞ አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡በመሰረቱ የግራ ቀኙ የውል ግንኙነት የተመሰረተው ፕሮፎርማውን ብቻ በቂ አድርጎ በመቀበል ሳይሆን ፕሮፎርማው ከተሰጠ በኃላ ስለ ሽያጩ ዝርዝር አፈጻጸም ራሱን ችሎ በጽሁፍ በተደረገ የሽያጭ ውል ላይ ነው፡፡በፕሮፎርማው ላይ የተጠቀሱት የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የሽያጭ ዋጋ፣የክፍያ ሁኔታ እና የተሽከርካሪው ሞዴል በቀጣይ በጽሁፍ በተደረገው ውል ውስጥ የተካተቱ ቢሆንም የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የሽያጭ ዋጋ እና የክፍያ ሁኔታ በሽያጭ ውሉ የተካተተው በፕሮፎርማው ከተገለጸው በተለየ መጠን እና ሁኔታ ነው፡፡ በፕሮፎርማው ላይ የተመለከተውን የርክክብ ጊዜ ግን ግራ ቀኙ የውሉ አካል አላደረጉትም፡፡በውሉ ውስጥ የተመለከቱት ዝርዝር የውል አፈጻጸም ሁኔታዎችም በፕሮፎርማው አልተጠቀሱም፡፡ፕሮፎርማ በባህርይው የዚህ ዓይነት ዝርዝር የውል አፈጻጸም ሁኔታዎችን እንዲያካትትም አይጠበቅም፡፡የተዋዋዮች የውል ግንኙነት መሰረት ያደረገው ፕሮፎርማን ሳይሆን ፕሮፎርማውን ተከትሎ በጽሁፍ የተደረገን ውል በሆነ ጊዜ ደግሞ በፕሮፎርማው ላይ ተጠቅሶ ነገር ግን ተዋዋዮቹ የውላቸው አካል አድርገው ያልተስማሙበት ጉዳይ በፕሮፎርማው ላይ የተጠቀሰ በመሆኑ ብቻ እንደ ውሉ አካል ተቆጥሮ በተዋዋዮቹ ወይም ከተዋዋዮቹ በአንዱ ላይ አስገዳጅነት እንዳለው አድርጎ መውሰዱ የሕግ ጥበቃ ካለው ፈቅዶ የመዋዋል ነጻነት እና መብት አንጻር ሕጋዊ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚገባው አይደለም፡፡ በመሆኑም በፕሮፎርማው ላይ የተመለከተውን የርክክብ ጊዜ በአስረጂነት ጠቅሶ ተጠሪው ርክክቡን ለ12 ወራት ያዘገየው በመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከተሽከርካሪዎቹ ስምሪት ማግኘት እችል የነበረውን ገቢ ተጠሪው ሊተካልኝ ይገባል በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ የሚነቀፍበትን ሕግዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡አመልካች ከርክክቡ በፊት ማጠናቀቅ ከነበረበት ክፍያ ውስጥ የተወሰነውን ያህል እንዳልከፈለ ያልተካደ ከመሆኑም በላይ ሻሲዎቹ ጉድለት ያሉባቸው ናቸው በሚል መነሻ የዋጋ ቅናሽ ካልተደረገለት በስተቀር ለመረከብ ፈቃደኛ አለመሆኑን ለተጠሪው አስታውቆ የነበረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን፣ተጠሪውም ለዚሁ ማስታወቂያ በሰጠው ምላሽ በውሉ ምክንያት የተቀበለውን ቅድመ ክፍያ ከሕጋዊ ወለድ ጋር መልሶ ውሉን ለማስቀረት ፈቃደኛ መሆኑን ለአመልካች የገለጸ መሆኑን እና አመልካች ሀሳቡን በመቀየር ተሸከርካሪዎቹን እንደሚረከብ ሀሳቡን የገለጸው ከዚህ በኃላ መሆኑን ቀርቦ ከተያያዘው የከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ተገንዝበናል፡፡ይህም ተጠሪው ርክክቡን አዘግይቶአል በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው መሆኑን ለውሉ አፈጻጸም መዘግየት አመልካቹ ጭምር አስተዋጽኦ እንደነበረው መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ከቁጥር 2287 እስከ 2300 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደገለጸው በዕቃው ላይ ተገኘ የተባለው ጉድለት መኖሩ በገዥው የታወቀው ከርክክብ በኃላ በሆነ ጊዜ እንጂ ጉድለቱ ከርክክቡ በፊት ታውቆ በሻጩ እንዲስተካከል ከተደረገ በኃላ ርክክብ በሚደረግበት ጊዜ ጭምር እንዳልሆነ ከድንጋጌዎቹ አነጋገር እና ይዘት በግልጽ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ ቁጥር 2299 ድንጋጌን ጠቅሶ አመልካች ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉም ቢሆን የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ለተጠሪው በተወሰነው ገንዘብ ላይ ወለድ መታሰብ የሚጀምርበትን ቀን በተመለከተ ርክክብ መፈጸሙን ተከትሎ የአንድ ወር የችሮታ ጊዜ ካበቃ በኃላ አመልካች ከራሱ የሚከፈለውን የመጨረሻ ክፍያ ብር 2,050,124.70 በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ከፍሎ እንዲያጠናቅቅ ግራ ቀኙ የተስማሙት ዋናውን ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ከ9.5% ወለድ ጋር ስለመሆኑ በውላቸው አንቀጽ 4.3 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡በዚህ የውል ቃል አነጋገር ትርጉም ረገድ ወይም በውል ቃሉ ሕጋዊነት ረገድ አመልካች ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ አመልካች እንደሚከራከረው ወለዱ የ12 ወራት ጊዜ ካበቃ በኃላ መታሰብ መጀመር ይችል የነበረው በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ ግራ ቀኙ የተስማሙት ወለድ ሳይታሰብበት ዋናው ገንዘብ ብር 2,050,124.70 ብቻ ቢሆን ኖሮ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ግን ገንዘቡ በ12 ወራት ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ ግራ ቀኙ የተስማሙት ከነወለዱ ነው፡፡ይህም በገንዘቡ ላይ ወለዱ መታሰብ የሚጀምረው የአንድ ወር የእፎይታ ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ገንዘቡን በየወሩ እየከፈለ በ12 ወራት ቢያጠናቅቅም ሆነ በ12ኛው ወር መጨረሻ ላይ ገንዘቡን አጠቃሎ በአንድ ጊዜ ቢከፍል በዋናው ገንዘብ ብር 2,050,124.70 ላይ በግራ ቀኙ ስምምነት መሰረት 9.5% ወለድ የእፎይታ ጊዜው ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ መታሰቡ የሚቀጥል በመሆኑ ገንዘቡ በየወሩ መከፈሉ ወይም በዓመቱ መጨረሻ በአንድ ጊዜ ተጠቃሎ መከፈሉ በአመልካቹ የግዴታ አፈጻጸም ረገድ የሚያስከትለው ልዩነት የለም፡፡ ውሳኔ ካረፈበት ገንዘብ ውስጥ ብር 545,781.27 መከፈል የነበረበት ከርክክቡ በፊት በመሆኑ በዚህኛው ገንዘብ ላይ ወለዱ ከ20/05/2000 ዓ.ም. ጀምሮ እንዲታሰብ መደረጉ አመልካችን ተጎጂ ሳይሆን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 117102 በ11/10/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 92783 በ30/05/2006 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሳኔ በፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡ የስር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.97797

መስከረም 28/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስለሴ

ብርሃኑ አመነው

ሸምሱ ሲ.ርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- ናሽናል ስሚንቶ አ/ማህበር አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ብርሃኑ ግደይ ጠበቃ አቶ በላቸው ዘመድኩን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሽያጭ ውል አፈፃፀም የተመለከተ ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ከአመልካች ጋር መጋቢት 30 ቀን 2003 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ስምንት ሺህ ኩንታል (8000) ስሚንቶ የአንዱ ኩንታል ብር 255.41 ሂሣብ ቫት እና ታርንአቫር ታክስ ጨምሮ ነው 2,360,000 (ሁለት ሚሊዮን ሦስት መቶ ስልሣ ሺህ) መክፈሉን እና አመልካች (ሸጭ) 7272 ኩንታል ሲምንቶ ካሰረከበ በኃላ 723 ኩንታል ስሚንቶ ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ይህንኑ ቀሪ ስሚንቶ ተገዶ እንዲያሰረክብ አለያም ዋጋውን ብር 214. 760 እንዲከፍል እንዲወሰን ጠይቋል በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር የዋጋ ለውጥ ሊደረግ እንደሚቻል አስቀድሞ መስማማታቸው በዚሁም መሠረት በየጊዜው የዋጋ ለውጥ ሲደረግ እንደነበርና ተጠሪም ይህንኑ አውቆ ሲረከብ እንደነበረ ገልጾ አጠቃላይ እስከ አሁን የተረከበው በየጊዜው ከነበረው ዋጋ ለውጥ አንፃር ተሰልቶ ቀሪ ብር 120 (አንድ መቶ ሃያ ብር) ብቻ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ እንድደረግ ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን ያከራከረው የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የስሚንቶ ዋጋ ለውጥ ወይም ጭማሪ መደረጉን የተጠሪ (የከሳሽ) ወኪል ያውቃል እንዲሁም ለተጠሪም አሳውቋል ዋጋ ጭማሪ የተደረገውም በስምምነታቸው መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው በማለት ተጠሪ የተረከበው ሲምንቶ ሲሳላ የተከፈው ዋጋ ጋር ተቻችሏል ቀሪ ብር 120 (አንድ መቶ ሃያ ብቻ) ነው ሲል ክሱ ውድቅ አድርጓል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል የእጅ በእጅ የሽያጭ ውል ነው በሚል ምክንያት የፍ/ብ/ሕጉን አንቀጽ 2278(1) በመጥቀስ የዋጋ ጭማሪ የማድረግ መብት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ቀሪውን ስሚንቶ ያስረክብ ወይም ዋጋውን ይመልስ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አለገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን የሰበር አመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ውል ከተደረገበት ንብረት መጠን አኳያ የሽያጭ ውሉ የእጅ በእጅ የሽያጭ ውል ነው ማለት ይቻላል ወይስ አይችልም? የዋጋ ጭማሪ አስመልክቶ ተጠሪ ስምምነት አልሰጠም የሚልውን አግበብነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የለውም በአግባቡ ነው በማለት ተከረክሯል፡፡ የጉዳዩ አመጠጥና የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከህጉ ጋር አገናዝበናል፡፡ ከመዝገቡ መገንዘብ እንደተቻለው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተነሳው ክርክር መሠረቱ መጋቢት 30 ቀን 2003 ዓ/ም የተደረገ ውል ነው፡፡ በዚህ የሽያጭ ውል ላይ የ8000 ኩንታል ስሚንቶ ዋጋ ተጠሪ ብር 2,360,000 መክፈሉም ተረጋግጧል፡፡ የስሚንቶ ርክክብ አፈፃፀም በተለያየ መጠን በተለያዩ ጊዜያት የተፈፀመ ሲሆን በጥቅሉ ከ6 ወራት ያላነሰ ጊዜ ወስዷል፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገ ውል ክፍያ የተፈፀመበት ደርሰኝ (ሰነድ) የእጅ በእጅ ሽያጭ የሚል ሲሆን በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 2278(1) በሚደነግገው አግባብ ይህ ውል የእጅ በእጅ ሽያጭ ውል ይሰኛል ወይ የሚለው ነጥብ ምለሽ የሚያሻው ሆኖ አግኝተናል፡፡ ምክንያቱም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው ይህንኑ ድንጋጌ በመሆኑ ነው፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ አንቀጽ 2278(1) በውሉ የተነገረ ተቃራኒ ነገር ከሌላ በቀር የተሸጠውን ማስረከብ ከዋጋው መክፈል ጋር በአንድ ጊዜ መሆን አለበት በማለት ይገልፃል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መንፈስ መረዳት የሚቻለው የዋጋ ክፍያ እና የተሸጠው ነገር ርክክብ በአንድ ጊዜ የተፈፀመ እንደሆነ በእርግጥም የእጅ በእጅ ሽያጭ ተደርጓል ለማለት የሚቻል መሆኑን ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የ8000 ኩንታል ሲሚንቶ ዋጋ ውሉ ሲፈፀም የከፈለ ቢሆንም እቃውን የተረከበው ግን በተለያየ መጠን በተለየየ ጊዜና ዋጋ ልክ ስለመሆኑ በስር ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ እንደ ሕጉ ሀሳቤ የእጅ በእጅ ሽያጭ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል ሆኖ አላገኘንም፡፡

ከዚህም ባሻገር ተጠሪ ሲሚንቶ የተረከበው ውል ከተደረገ በኃላ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ በተለየየ ጊዜና መጠን ከመሆኑም በተጨማሪ የዋጋ ለውጥ ሊደረግ እንደሚችል አመልክች አስቀድሞ በሰጠው ፕሮፎርማ ላይ ከማስታወቁም አልፎ ስሚንቶ ርክክብ ሲደረግ በየጊዜው የነበረውን የዋጋ ለውጥ ተጠሪ ለወከለው ተረካቢ ማስታወቁን በዚሁ አግባብም የመረካከቢያ ሰነድ ላይ ይፈርም እንደነበር በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ማስረዳቱን የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ወደ ጎን በመተው ሽያጩ የእጅ በጅ ሽያጭ ነው በሚል ምክንያት ብቻ አልፎታል፡፡

ስለሆነም በአመልካች እና በተጠሪ መከከል የተደረገው የስሚንቶ ሽያጭ ውል 8000 (ስምንት ሺህ) ኩንታል ስሚንቶ በአንድ ጊዜ ተጠሪ የተረከበው ካለመሆኑም በላይ አመልካች የዋጋ ጭማሪ ሊደረግ እንደሚችል አስቀድሞ አሰውቆ በዚሁ አግባብ መዋዋላቸው አልፎም አመልካች የዋጋ ጭማሪ ስለማድረጉ በመረካከቢያ ሰነድ እያረገገጠ ተጠሪም ይህንን ሳይቃወም ተረክቦ እያለ አሁን የዋጋ ጭማሪ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚልውን ክርክር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀብሎ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ የሕጉን ይዘት የግራ ቀኙን ውል እና በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህታት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128323 ጥቅምት 4 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ እና ይህንኑ ፍርድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 94351 ታህሳስ 30 ቀን 2006 ዓ/ም በማፅናት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል
2. የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03910 በ05/03/05 የሰጠው ፍርድ ፀንቷል
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 103910

ቀን 28/01/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ሀብታሙ ተመስገን - ጠበቃ አቶ ሙሉ ገ/ስላሴ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ለስልጠና የወጣ ወጪ በውሉ መሰረት ይመለሰልኝ በማለት አመልካች በተጠሪ ላይ ላቀረበው ክስ የተሰጠው ውሳኔ ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በግራ ቀኙ መካከል በቅድሚያ ህዳር 9/2002 ዓ/ም በተደረገ ውል በአመልካች የስልጠና ት/ቤት ውስጥ የሚሰጠውን የቢ 737 አውሮፕላን አካላት ስልጠና ተጠሪ በመውሰድ ለ24 ወራት ለማገልገል ይህን ግዴታውን ባይወጣ ግን የስልጠናውን ወጪ ብር 50,000.00 ለአመልካች ለመክፈል ተስማምቶ ለ 9 ወራት ቀሪ አገልግሎት ሳይሰጥ ስላቋረጠ ብር 16,664.00 እንዲመልስ ፣ በሌላም በኩል ህምሌ 24 ቀን 2002 ዓ/ም በተደረገ ውል ተጠሪ በአሜሪካን ሀገር ቢሲያትል በሚገኘው የቦይንግ ስልጠና ማዕከል የሚሰጠውን የቢ 777 አውሮፕላን አካላት ስርዓተ ትምህርት ለመውሰድ የሚያስፈልገውን ወጪ ብር 389,059.23 አመልካች ለመሸፈን ተጠሪ ደግሞ ስልጠናውን ወስዶ ለ36 ወራት ለማገልገል ይህን ግዴታውን ባይወጣ ግን የስልጠናውን ወጪ ለመክፈል የተሰማማ ቢሆንም ስራውን ጥሎ ስልጠፉ የሁለተኛውን ውል የስልጠና ወጪ ብር 389,059.23 በአጠቃላይ ብር 407,806.23 ከነወለዱ እንዲከፈላቸው እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክሱ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ የሰጡትን መልስ ፤ ውሎቹ የተደረጉበትን ጊዜና የውሎችን ይዘት በመመርመር ተጠሪ በቀደመው ውል መሰረት ግዴታውን በመፈጸም ላይ እያለ ለ2ኛው ስልጠና የተላከ በመሆኑ ፤ ሀምሌ 24 ቀን 2002 ዓ/ም የተፈረመው ውል አንቀጽ 7 ደግሞ ሰልጣኙ የቀድሞ ግዴታውን በመፈጸም ላይ እያለ ለሌላ ስልጠና ቢጠራ (ቢመደብ) ሰልጣኙ ለዚሁ ስልጠና አዲስ ውል እንደሚፈርምና የአገልግሎት ጊዜውም በዚሁ ጊዜ የሁለቱንም ስምምነት ለመሸፈን እንደሚጠቃለል የሚደነግግ በመሆኑ ፤ ይህም በቀደመው ግዴታ መሰረት ሳይፈጽም የቀረውን ጊዜ ቀሪ የሚያደርገው በመሆኑ ከቀደመው ውል ሳይፈጸም ቀርቷል ተብሎ የተጠየቀውን የ9 ወራት የክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ፤ በ2ኛው ዙር በተደረገው ስምምነት መሰረት ስልጠናውን ወስዶ በውሉ ለተመለከተው ጊዜ ያላገለገለ በመሆኑ ለስልጠና የወጣውን ወጪ ብር 389,059.23 ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች የሁለቱም ውሎች ግዴታዎች በ2ኛ ውል እንደተጠቃለለ ተደርጎ ውሉ መተርጎሙን በመቃወም ይግባኝ ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በመጨረሻ ውሉ የተተረጎመበት መንገድ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት የስር ፍ/ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አጸንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች ውሉን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ እንዲሻርና ህዳር 9/2002 ዓ/ም በተደረገው ውል መሰረት ተጠሪ ላላገለገለበት ጊዜ የሚፈለግበትን ብር 16,664.00 ለአመልካች መክፈል አለበት ተብሎ በዚህ ነጥብ ላይ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሻሽሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

ቅሬታቸው ተመርምሮ ውሉ የተተረጎመበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል ተጠሪ ቀርበው መልስ እንደሰጡበት ተደርጓል፡፡

በበኩላችን የተያዘውን ጭብጥ ግራ ቀኝ ወገኖች ካደረጉት ክርክር ፤ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንዲሚቻለው ለክሱ መነሻ የሆኑት ውሎች ስለመደረጋቸው ፤ ተጠሪም በሁለቱም ውሎች መሰረት ስልጠና መውሰዱ ፤ ሁለተኛው ስልጠና የጀመረው ተጠሪ የቀደመውን ስልጠና አጠናቆ ግዴታውን በመወጣት ላይ እያለ ነገር ግን የቀደመውን ግዴታ ከማጠናቀቁ በፊት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከቀደመው ውል የሚጠበቀው የ9 ወራት የአገልግሎት ቀሪ ዋጋ ብር 16,664.00 ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተወሰነው ሁለተኛው የስልጠና እና የአገልግሎት ውል የቀረውን የቀደመ ግዴታ የሚጠቀልል እና ቀሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያደርግ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ የተቃወሙት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ውል እና ህጉን መሰረት ያደረገ አይደለም በማለት ነው፡፡

ክርክሩ ሊወሰን የሚገባው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረጉትን ውሎችና ለጉዳዩ አግባብነት የሚኖረውን ህግ መሰረት በማደረግ ሲሆን አከራካሪ የሆነውን የውሉን አንቀጽ 7 ይዘት እና ተገቢነቱ ያለውን የህጉን ድንጋጌ ተመልክተናል፡፡

አመልካች ክሱን ለማስረዳት ባቀረበው ውል አንቀጽ 7 እንደተመለከተው ሰልጣኙ (ተጠሪ) በቀዳሚው ውል የነበረበትን የአገልግሎት ግዴታ ሳይጨርስ ለሌላ ስልጠና ሊመደብ እንደሚችል ፤ በዚህ ሁኔታ አዲስ ውል እንደሚፈረምና የአገልግሎት ጊዜውም በዚሁ ጊዜ የሁለቱም ስምምነት ለመሸፈን እንደሚጠቃለል ተደንግጓል፡፡

አመልካች ይህ የውሉ አንቀጽ ግልጽ እና ተጠሪ የሁለቱም ውሎች የአገልግሎተ ጊዜ አጠቃሎ አገልግሎት መስጠት እንዳለበት የሚያመለክት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ሁለተኛው የስልጠና የአገልግሎት ጊዜ የሁለቱም ስምምነቶች የሚሸፍን (የሚያጠቃልል) መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት የተጠሪን መከራከሪያ ተቀበሎ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የውሉ ስምምነት በስር ፍ/ቤት የተተረጎመበት መንገድ ስህተት ሆኖ እንዳላገኘው በውሳኔው አመልክቷል፡፡

ከላይ እንዲተመለከተው የውሉ አንቀጽ 7 ተጠሪ የሚኖርበትን የአገልግሎት ጊዜ ግዴታ በተመለከተ አጠራጣሪ ይዘት ያለው ነው፡፡ እንዲህ አይነት አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም የውሉ ድንጋጌ መተርጎም ያለበት በውሉ አስገዳጅ የሆነው ወገን በሚጠቀምበት ሁኔታ ሳይሆን በውሉ ተገዳጅ ለሆነው ሰው ምቹ በሚሆንበት አኳኋን ነው፡፡ ይኸው የትርጉም መርህ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1738(1) ስር ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ በቀዳሚው ውል የነበረበትን የአገልግሎት ግዴታ ሳይጨርስ ለሌላ ስልጠና ሲመደብ እና አዲስ ውል ሲያገ የአገልግሎት ጊዜ ግዴታን በተመለከተ የሚደነገገው የውሉ አንቀጽ 7 መተርጎም ያለበት አመልካችን በሚጠቅም መንገድ ሳይሆን በአንቀጹ ተገዳጅ የሆነውን ተጠሪን በሚጠቅም መንገድ ነው፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ከውል ድንጋጌዎች አተረጓጎም አንጻር አይተው አለመወሰናቸው የሚነቀፍ ቢሆንም በውጤት ደረጃ ተጠሪ ከቀዳሚው ስምምነት ሳይፈጸም ቀረውን የአገልግሎት ጊዜ ግዴታ በገንዘብ ተሰልቶ የቀረበውን ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1ኛ. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 73094 የካቲት 19/2005 ዓ/ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ.135184 ግንቦት 13/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በውጤቱ ጸንቷል፡፡

2ኛ. የሰበር ክርክሩ ስላስከተለው ወጪ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

3ኛ. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105919

ቀን ጥቅምት 4/2008ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲ.ር.ጋ.ጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ መኪያ አብደላ -ጠበቃ ቶማስ ወ/ሰንበት ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጣሰው ሽምሱ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ ውል መሰረት ያደረገ ክርክር ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን ክሱም ከአመልካች ጋር ባደረግነው የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ ውል መሰረት ቤቱን ታስረክበኝ የሚል ሲሆን አመልካች ክሱ ከደረሳቸው በኋላ ውሉ በተንኮልና በማሳሳት የተደረገ ነው በሚል እንዲፈርስ እንዲወሰን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያከራከረው የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የለም አመልካች በዚህ የልውውጥ ውል መነሻም ተጨማሪ ብር 9000 (ዘጠኝ ሺ.) መቀበላቸው ስለተረጋገጠ በውሉ መሰረት ይፈጸም በማለት ወስነ፡፡

አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ሲሆን የሰበር ችሎቱም ኮንኮሚኒየም ቤት የደረሰው ሰው እስከ አምስት አመት ድረስ ቤቱን ለሌላ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ይችላል ወይ? የሚለውን ጭብጥ ከአዋጅ ቁጥር 19/1997 አንቀጽ 14(2) አንጻር ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪም በግራቀኙ መካከል የተደረገው የቤት ልውውጥ ውል ያልተሻረ እና ጸንቶ ያለ ስለሆነ ሊፈጸም ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ እንደተቻለው መጋቢት 14ቀን 2001ዓ.ም በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው የኮንዶሚኒየም ቤት ቅይይር ውል በአመልካች ስም በጀሞ 1ሳይት ብሎክ ቁጥር 1 የሕንጻ ቁጥር 93 የወለል ቁጥር 1 የቤት ቁጥር JG - B 93/9 የሆነው ቤት በተጠሪ ስም ያለው ጀሞ 1ሳይት ቁጥር - 163 ወለል ቁጥር 1 የቤት ቁጥር JC - B — 163/11 በሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት በመለዋወጥ መስማማታቸውን ይገልጻል፡፡ የቤቶቹ ይዘት በተመለከተ በተጠሪ ስም ያለው ስቱዲዮ ሲሆን በአመልካች ስም ባለ አንድ መኝታ በመሆኑ ይህንኑ በገንዘብ ለማስተካከል ተስማምተው ብር 9000 (ዘጠኝ ሺህ) ተጠሪ ለአመልካች ለመጨመር መስማማታቸውም ተገልጿል፡፡በክርክሩ ሂደትም አመልካች ብር 9000 መቀበላቸው ተረጋጧል፡፡

እንግዲህ ይህ የኮንኮሚኒየም ቤት ልውውጥ በአዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ 14/2/ መሰረት የተከለከለ ነው ወይ? የሚለው ጭብጥ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 14(2) ገዢው ጠቅላላው ዋጋውን ከፍሎ ቢያጠናቅቅም ቤቱን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለው ቤቱን ከገዛ 5(አምስት) አመት ሲሞላው ብቻ ይሆናል በማለት ደንግጓል፡፡

ድንጋጌው በግልጽ ቃል የጠቀሰው ቤቱን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የከለከለ መሆኑን ሲሆን አመልካች በማንኛውም መልክ ማስተላፍን ይከለክላል በሚል ህሳቤ ይከራከራሉ፡፡ የተያዘው ጉዳይ የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ እንጂ በሽያጭ ወይም በስጦታማስተላለፍ የተመለከተ ባለመሆኑ ሕግ አውጭው ይህንንም ለመከልከል ፈልጎ ቢሆን ኖሮ "በማናቸውም አኳኋን" ማስተላለፍ አይቻልም የሚል አጠቃላይ የሆነ ቋንቋ መጠቀም ይችል እንደነበር መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በመሰረቱ እዚህ መነሳት ያለበት መሰረታዊ ጥያቄ በአንድ በኩል አንድ ዜጋ ባፈራው ንብረት የመጠቀም ሙሉ መብት ያለው መሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ በተያዘው የኮንዶሚንየም ቤት አጠቃቀም መብት ላይ በጊዜ ገደብ በተወሰነ ሁኔታ ገደብ ማድረጉን አስፈላጊነትና አላማ በማመዛዘን የሕጉን አላማ በሚያሳካ መልኩ ማስተግበር መቻሉን ማረጋገጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም በእጣ የደረሰው ሰው ቤቱን በሽያጭም ሆነ በስጦታ ለሶስተኛ ወገን እስከአምስት አመት ጊዜ ድረስ ማስተላለፍ አይችልም ተብሎ በሕገ መብቱ ሲገደብ ታሳቢ የተደረገው ጥቅም የራሱ የመብቱ ተጠቃሚ የሆነው ባለእጣ መሆኑን ግልጽ ነው፡፡ ይኸውም የአዋጅ መግቢያ እንደሚያመላክተው በከተማ ውስጥ ያለውን አነስተኛ የመጠለያ ችግር መቅረፍ እና በሂደትም ነዋሪው የቤት ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ የደረሰው የከተማው ነዋሪ በተለያዩ ጊዜያዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች ተገፋፍቶ ቤቱን በሽያጭ ወይም በስጦታ የሚያስተላልፍ ከሆነ ነዋሪው የቤት ባለቤት እንዲሆን በሕጉ ታስቦ የተሰራው ስራ መክኖ ይቀራል የሚል ህሳቤ በመያዝ ምናልባት ችግሮች እንኳን ቢኖሩበት ወይም ሌላ ማህበራዊ ምክንያቶች ቢያስገድዱት በ5አመት ቆይታ ጊዜ ስለጥቅምና ጉዳት የማሰላሰያ ጊዜ አግኝቶ አመዛዝኖ ከውሳኔ ይደርሳል ተብሎ ተገምቶ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ስለሆነም ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ውል የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ እስከሆነ ድረስ አንዳቸውም ያለቤት ቀርቷል የሚያሰኝ ባለመሆኑ የህጉን ሃሳብና አላማ ይጥሳል ወይም ሕገ-ወጥ ውል ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

ይህ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 65140 አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ 14(2) ጠቅሶ ውሉ ሕገወጥ ነው በማለት የሰጠው ፍርድ ለተያዘውም ክርክር ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል በማለት በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር መሰረት አድርገን በመ/ቁጥር 65140 የተሰጠውን ፍርድ ይዘት ስንመረምር ተጠቃሹ መዝገብ ላይ የቀረበው ክርክር የኮንዶሚኒየም ቤት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ውል የሚመለከት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም በዚህ መዝገብ ከተያዘው ኮንዶሚኒየም ቤት በልውውጥ ማስተላለፍ ጋር ተመሳሳይ ባለመሆኑ አግባብነት የለውም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ 14(2) ድንጋጌ የተላለፈ ሕገ-ወጥ ውል ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በስር ፍ/ቤት ለቀረበባቸው መልስ ሲሰጡ ልውውጥ ከተደረገ በኋላ የቤቱን ማጠናቀቂያ ስራዎች ለመስራት ብር 12,000 (አስራ ሁለት ሺህ) ወጪ ማድረጋቸውን ጠቅሰዋል፡፡ ለዚህም ማስረጃ አለኝ ሲሉ ዘርዝረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲያቀርቡ ተጠሪ ይህንን ገንዘብ እንዲተካላቸው በተለዋዋጭ (በአማራጭ) ዳኝነት የጠየቁ ስለመሆኑ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ይዘት አያመለክትም፡፡

ስለሆነም ውሉ የጸና ነው የሚለው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በዚህ ሰበር ችሎት የሚሻርበት ህጋዊ ምክንያት ባለመገኘቱ አመልካች ከውሉ በኋላ አወጣሁ ያሉት ብር 12,000 አስመልክቶ ወደፊት የሚጠይቁት ዳኝነት ካለ ይህ ፍርድ አያግዳቸውም ብለናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 60424 በ22/5/2005 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 132260 በ4/02/2007ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ
3. በዚህ መዝገብ ታህሳስ 15 ቀን 2007ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡ የስር ፍ/ቤት መዝገብ በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/98348

ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተሽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካቾች፡.1ኛ አቶ ዘሪሁን የኔነህ ቀረቡ

2ኛ የአቶ የኔነህ ጨርቆሴ ህጋዊ ወረሾች

1. አቶ ታረቀኝ የኔነህ
2. ,, የኃላሸት የኔነህ አልቀረቡም
3. ,, ዘሪሁን የኔነህ

ተጠሪ፡- ሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ ነገረ ፈጅ እንግዳወርቅ ጌታቸው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመልከም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልከቾች ባሁኑ ተጠሪ እና በዚህ መዝገብ የክርክሩ ተከፋይ ባልሆኑ 1ኛ ወ/ት ንሰሐ ወርቅህ 2ኛ ዳሽን ባንክ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በዚህ መዝገብ የክርክሩ ተከፋይ ያልሆነችው ወ/ሪት ንሰሐ ወርቅነህ ከአሁኑ ተጠሪ ሀዋሣ ዩኒቨርሰቲ ጋር በተፈራረሙት የበሰለ ምግም አቅርቦት ውል 1ኛ ተከሳሽ የነበረቸው ወ/ት ንሰሐ ቀርቅነህ ለመልከም አፈፃፀም ዋስትና 3ኛ ተከሳሽ ከነበረው የዳሽን ባንክ እንዲሰጣት ጠይቃ፤ 3ኛ ተከሳሽም ለዋሰትና የሚበቃ ንብራት እንድታቀርብ በመጠየቁ የአሁኑ 1ኛ አመልከች በስሙ ተመዝግቦ የሚገኝ የመኖሪያ ቤትና የሰሌዳ ቁጥር 3-42314 አይሱዙ የጭነት መኪና እንዲሁም 2ኛ አመልከች የመኖሪያ ቤት በመያዣ እንዲያዝ በመፍቀዳቸው ሦስቱም ንብረቶች በብር 658,568.00 ተገምተው ህዳር 15 ቀን 2007 ዓ/ም እ/ኤ/አ/ በተፈረመ የመያዣ ውል ለ3ኛ ተከሳሽ ሰጥቷል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ (የአሁኑ ተጠሪ) አቅርቦቱ የጥራት ደረጃውን አልጠበቀም በሚል የአቅርቦት ውሉን ከታህሳስ 13 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ ሙሉ በሙሉ አቋርጧል፡፡ ውሉ በተቋረጠ በ4ኛ ቀን 2ኛ ተከሳሽ ቀደም ሲል በጨረታው 2ኛ የወጣውን ተወዳዳሪ በ1ኛ ተከሳሽ ምትክ በመተካት ውል መፈጸሙ አቅርቦቱ በግለሰቡ አማካኝነት እየተከናወነ ይገኛል፡፡ የ1ኛ ተከሳሽ የአቅርቦት ውል በመቋረጡ በ2ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ላይ የደረሰ ኪሳራ ወይም ተጨማሪ ወጪ ከለ ለ1ኛ ተከሳሽ ተከፋይ ከሚሆን የአቅርቦት ሂሳብ ተቀናሽ ሆኖ ወጪው ከተካካ በኃላ 3ኛ ተከሳሽ ለሰጠው የብር 658,568 .00 ዋስትና በመያዣነት የተያዙ ንብረቶች እንዲለቀቅላቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄ አቅርበው ኪሳራው አስልቶ ከአንደኛ ተከሳሽ ተከፋይ ሂሳብ ተቀነሽ በማድረግ ለራሱ ገቢ ካደረገ በኃላ ንብረቶችን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ የአቅርቦት ውሉ በ2ኛው ተጫራች አማከይነት ወዲያውኑ በመቀጠሉ ንብረቶቹ በመያዣነት እንደተያዙ ሊቀጥሉ ወይም የዋስትናውን ገንዘብ ሊወረስ የሚችልበት አግባብ ባለመኖሩ ዋስትናው ቀሪ ሆኖ ንብረቶቹ እንዲለቀቁ በ3ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኙት የበለቤትነት ሰነዶች ተመለሽ እንደሆኑ እንዲወስንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች የነበሩ የአሁኑ ተጠሪ ጨምሮ መልስ አቅርቦዋል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው የሚትከሰስበት ምክንያት እንደሌላ፤ ውሉ በ2ኛ ተከሳሽ ፍላጎትና ውሳኔ ተቋርጠዋል፤ በጨረታው አሸናፊ የሆነውን 2ኛ ተጫራች የነበረው ተተክቶ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር የውል ግዴታ ገብቶ ሥራን ቀጥሏል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ የሚጠይቀው ዕዳ የለውም መያዣው ሊለቀቅ ይገባል የሚል ይዘት ያለው መልስ ያቀረበች ሲሆን፤ 2ኛ ተከሳሽ (የአሁኑ ተጠሪ) ደግሞ ከአመልካች ጋር የውል ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ተጣምሮ መከሰስ እንዳልነበረበት ክሱን ንብረቱን በያዘው አካል ላይ ብቻ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ በፍሬ ጉዳዩም የምግብ አቅርቦት ውሉ የተቋረጠው በ1ኛ ተከሳሽ ግዴታ ያለመወጣት ምክንያት በመሆኑ ተጠሪ ለተጨማሪ ኪሳራ ተደርጓል፡፡ መያዣው ሊመሰስ አይገባም የሚል ክርክር አቅርቦዋል 3ኛ ተከሳሽ የነበረው የዳሽን ባንክ 1ኛ ተከሳሽ የውል ግዴታቸው ባለመወጣታቸውን በገባው ውል መሠረት የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ብር 658,568.00 ለሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ገቢ አደርገዋል፡፡ መያዣው ሊለቅ አይችልም፡፡ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገበል የሚል ይዘት ያለው መልስ አቅርበዋል፡፡

የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረቡ መቃወሚያዎች ውድቅ አድርጓል፡፡ በፍሬ ጉዳዩም 2ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) 1ኛ ተከሳሽ በውሉ መሠረት ግዴታዋን አልተወጣችም በሚል ያፈረሰው በመሆኑ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ሁኔታ መመለስ የሚገበቸው ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ውሉን ለመፈጸም የተሰራው ሁሉ ቀሪ ሆኖ ውጤት ስለማይኖረው በፍ/ሕ/ቁ. 1815 መሠረት አመልከቾች የገቡት ዋስትና ቀሪ ይሆናል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ውሉን እስከ ፈረሰ ድረስ ከ1ኛ ተከሳሽ አለኝ የሚለው ቀሪ ሂሣብ ከለው በህግ ከመጠየቅ ውጭ ለዋስትና ግዴታ የተገባው ንብረት ለ3ኛ ተከሳሽ ሊከለከል አይገበም፡፡ የምግብ አቅርቦት ውሉ ሲቋረጥ መያዣው ይቋረጣል፡፡ 3ኛ ተከሳሽ ገንዘቡን መክፈል አልነበረበትም፡፡ 3ኛ ተከሳሽ ለመልካም አፈፃፀም የከፈለው ገንዘብ የማስመለስ መብቱ ተጠብቆ ከአመልካቾች የተያዙ መኖሪያ ቤቶችና መኪና የባለቤትናት ማረጋገጫ ሰነዶች ጭምር ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ እና በስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተከሳሽ የነበረው ዳሽን ባንክ እንደቅደም ተከተላቸው በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 63309 እና 63860 ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ እና በስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተከሳሽ የነበረው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳሽን ባንክ በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀበይነት በማግኘቱ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር የሃዋሳ ዩኒቨርሰቲ በራሱ አነሰሽነት ውሉን ለማቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ በሕግ መብት ያለው ቢሆንም እንደ ውሉ ያልፈጸመው ወገን ማን ነው? የሚለውን ክርክር ባስነሳ ጊዜ እና እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰው የጉዳት ኪሣራ ምን ያህል ነው? የሚለው ሁሉ የመረጋገጥ ግዴታ ስላለበት በዚህ ጭብጥ መሰረት 1ኛ ተከሳሽ ባለችበት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ተሰምቶ ሊወሰን እንደሚገባ፤ በዚህ ክርክር ውጤት መሠረት በማድረግ የዳሽን ባንክ ለዩኒቨርሲቲው የከፈለው የክፍያ መጠን አግባብ መሆኑና አለመሆኑን ታይቶ አሰፈላጊው ዳኝነት እንዲሰጥበት በጭብጥ የተያዙ ነጥቦች በክርክር እና በማስረጃ መሠረት ተለይቶ ከመታወቁ በፊት በመያዣ የተያዙ ንብረቶች ሊለቀቁ አይገበም በማለት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343 (1) መሠረት ተጠርቶ እንዲወሰን ለሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የከ/መ/ቁ. 67820 በማንቀሳቀስ ጉዳዩ በድጋሚ የተመለከተው ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ ባለመቅረቧ ክርክሩ በሌለችበት እንዲቀጥል አደርጓል፤ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ 1ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ጋሪ በፈፀመችው የምግብ አቅርቦት ውል ከ11/2/2000 እስከ 11/12/2000 ዓ/ም ለ10 ወር ጊዜ ለማቅረብ የተስማማች ቢሆንም 2 ወር አቅርቦት ከፈጸመች በኃላ በማቋረጧ ተጠሪ ውሉን በ14/04/2000 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ማቋረጡን፤ ለውሉ ማቋረጥ ምክንያትም በጥራትና በጊዜ መቅረብ ባለመቻሉ ስለመሆኑ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ያሰያል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ቀርባ አልተከራከረችም በመሆኑም 1ኛ ተከሳሽ ለውሉ መቋረጥ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ማረጋገጥ ተችሎአል፡፡ ሁለተኛ ጭብጥ በተመለከተ የጉዳት ክሳ ከደረሰው ጉዳት አንፃር መታየት ያለበት ስለመሆኑ ተጠሪ የገባው ሁለተኛ ውል በመጀመሪያ ውል ከተቀመጠው ዋጋ በልዩነት 1,347,403.02 ተጨማሪ ወጭ የሚጠይቀው መሆኑ መከራከሩን፤ አቅርቦት በመጠን ሲያንስ ሂሳቡ ሲቀነስ እንደነበር ውሉ ከመቋረጡ በፊት የደረሰው ኪሳር ዝርዝር አለመያዙን ውሉ በመቋረጡ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ሲመዘንም ከ14/4/2000 እስከ 17/4/2000 ዓ/ም በለው ጊዜ የደረሰ ኪሳራ መሆኑን እንደሚያሳይ ለ8 ሺህ ተማሪዎች ለዳቦ ግዥ ለ3 ቀናት ያወጣው የኪሳራ ልክ 96,000 ብር መሆኑ እንዳረጋገጠ፤ 3ኛ ጭብጥ በተመለከተ 2ኛ ተከሳሽ የደረሰበት የጉደት መጠን አስልቶ ክስ ከሚያቀርብ በቀር አጠቃላይ ለውሉ አፈፃፀም የተያዘው መብት እንደሌለው፤ 3ኛ ተከሳሽ (ዳሽን ባንክ) የሚፈጸመው ክፍያም ውል ባለመፈፀሙ የደረሰ ጉዳት ታሳቢ የሚያደረግ እንጂ ጉዳት ቢደርስም በይደርስም ለመክፈል ይገደዳል ማለት አለመሆኑን፤ በዚሁም በሁለተኛ ጭብጥ በተረጋገጠው መሰረት 3ኛ ተከሳሽ ለ2ኛ ተከሳሽ ሊከፈል የሚገባው ብር 658,568 ሳይሆን ብር 96,000 መሆኑን፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አራተኛው ጭብጥ መያዣው ከላይ በተመለከተው የካሣ ልክ ያረፈበት በመሆኑ ይህ ክፍያ ሳይፈፀም መያዣ ሊለቀቅ የሚችልበት አግባብ የለም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ክፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ በመጀመሪያ እና ሁለተኛ አቅረቢ የዋጋ ልዩነት መኖሩን አልተከደም፡፡ በስር 1ኛ ተከሳሽ የነበሩ አቅረቢ ለ8 ወራት ቢያቀርቡ ችግሩ አይከሰትም ነበር፡፡ 2ኛ ተጫራች የነበረው ሌላ ውድድር ሳይደረግ የአቅረቦት ውል እንዲቀጥል የተፈቀደው የ8,000 ተማሪዎች የምግብ አቅርቦት ማሟላት ፋታ የማይሰጥ ነው፡፡ የፌዴራል መንግስት የግዥ አዋጅ መመሪያ ይዘት መረዳት የሚችለው በአቅራቢ ችግር ምክንያት ውሉ በመቋረጡ ሊከሰት የሚችለው ተጨማሪ ውጭ /ጉዳት/ መሸፈን የሚገበው አቅረቢ መሆኑንና ለዚህም ለውሉ መልከም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለደረሰው ጉዳት መተኪያ ሊውል የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በውሉ መቋረጥ ምክንያት ደረሰብኝ የሚለው ጉዳት ብር 1,453,429.20 ነው፡፡ ይሁን እንጂ ክርክሩ ሲጀመረም ይሁን አሁን በይግባኝ ደረጃ ይህ ገንዘብ ሊከፈልኝ ይገበል የሚል ግልጽ ጥያቄ አላቀረበም፤ በግልጽ የጠየቀው ለመልከም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው ብር 658,568.00 ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ስለሆነ በይግባኝ ባይ (ተጠሪ) ለደረሰው ጉዳት ሊከፈል የሚገበው ብር 96,000 ሳይሆን ለውሉ መልካም አፈፃፀም የተያዘ ጠቅላላ ገንዘብ ብር 658,568 ነው፡፡ አመልከቾች ይህንን ገንዘብ ለሥር 3ኛ ተከሳሽ (ዳሸን ባንክ) ሲተኩ የዋስትና መያዝው ይለቀቅላቸው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልከቾች በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በመቃወም ጉዳዩን በሰበር ታይቶ እንዲመረመር እና እንዲለወጥ የሚጠይቅ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ ክርክር አደርጓል፡፡ የአመልካቾች ቅሬታ መሠረታዊ ይዘትም ውሉ የተቋረጠው በዩኒቨርሲቲው ድብቅ ምክንያት ነው፡፡ አቅርቦቱ የተቋረጠው ለ3 ቀን ብቻ በመሆኑ የጉዳት ክሳ ልክ መታየት ያለበት ከዚህ አንፃር መሆኑን እርግጠኛ ጉዳት መድረሱ ሳይረጋገጥ የጉዳት ክሳው ለመልከም አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው በሙሉ እንዲከፈል መውሰኑ በአግባቡ አይደለም፡፡ የግዥ አዋጅና መመሪያ አፈፃፀም በአግባቡ አልታየም፡፡ ጉዳዩ ሰበር በመለሰው መሰረት አልተጣራም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የአቅርቦት ውሉ የተቋረጠው በስር 1ኛ ተከሳሽ በነበረችው ምክንያት መሆኑን መረጋገጡን በመጀመሪያ እና ሁለተኛ አቅራቢ የዋጋ ልዩነት መኖሩን በተጠሪ ተቋም ላይ ጉዳት ማድረስን ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ከለው ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካቾች እና ተጠሪ እያከራከራ ያለው መሰረታዊ ነጥብ ለመልካም አፈጻጸም የተሰጠ ዋስትና ሙሉ በሙሉ ገቢ ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ መኖር ያለመኖሩን ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዳጣራው የምግብ አቅረቦቱ ለ3 ቀን ብቻ ተቋረጦ የነበረ መሆኑን እየታወቀ የ8 ወር አቅርቦት መሰረት ተደርጎ የጉዳት ክሳው ሊሰላ አይገባም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የመጀመሪያ አቅርቢ በውሉ በሠረት ባለ መፈፀምዋ ውሉን እንደተቋረጠ 2ኛ አቅረቢ ሲመረጥ ያቀረበው ዋጋ ከመጀመሪያው የአቅርቦት ዋጋ በግልጽ ጭማሪ ያለው በመሆኑ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን በማጣራት ለመልከም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው ገንዘብ ገቢ እንዲሆን መወሰኑ በአግባቡ ነው የሚል ክርክር ማቅረቡን ተመልክተናል፡፡

በስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው ወ/ት ንሰሐ ወርቅነህ በገባችው ውል መሰረት የምግብ አቅርቦቱ በመጠን በጊዜ እና በጥራት ባለማከናወንዋ ተጠሪ ማስጠንቀቅያ በመስጠት ውሉን አቋርጦታል፡፡ በስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው ለውሉ መቋረጥ መነሻ አለመሆናን ያቀረበችው ክርክር ይሁን ማስተባበያ የለም ፡፡ በስር 3ኛ ተከሳሽ የነበረው ዳሽን ባንክ የመልከም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ሊሰጥ የተቻለው ምናልባት በስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው በውሉ ይዘትና መንፈስ አቅርቦቱን ከለከናወነች ተጠሪ ለሚደርስባት ጉዳት ለማከሻ እንዲሆን ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው ለሁለት ወር ያህል ስታቀርብ በነበረችበት ጊዜ የነበረው ዋጋ እና ውሉ ከፈረሰ /ከተቋረጠ/ በኃላ በ2ኛ አቅራቢ የተጠየቀው ዋጋ ለወንዶ ገነት ዳን ኮሌጅ የ0.28 ሳንቲም ለሌሎች ከምፓሶች ደግሞ 0.39 ሳንቲም የዋጋ ልዩነት እንዳለው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ የዋጋ ልዩነቱ በ8 ወራት ሂሣብ ስሌቱ ሲሰራ በድምሩ ብር 1,453,429.20 ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው መጀመሪያ ከነበረው የአቅርቦት ውል 2ኛ አቅራቢ ዋጋ በመጨመሩ በተጠሪ ላይ ተጨማሪ ገንዘብ ወጭ ለማድረግ የሚገደድ ስለመሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡ አመልካቾች አቅርቦቱ የተቋረጠው ለ3 ቀን ብቻ ነው የሚል ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ለ8 ወራት የሚዘልቅ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡ ምክንያቱም የአሁኑ ተጠሪ ከ2ኛ አቅራቢ ጋር ያደረገው ውል ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ ወጭ የጠየቀው በመሆኑ በስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው በውሉ መሰረት በጊዜ መጠን እና ጥራት የምግብ አቅረቦቱ ቢቀጥል ሌላ 2ኛ አቅራቢ በላሰፈለገ ነበር፡፡ በመሆኑም በተጠሪ ላይ ጉዳት አልደረሰም የሚለውን ክርክር በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠው አንጻር የህግ መሰረት ያለው ክርክር ሁኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ ለመልካም ስራ አፈፃፀም የሚሰጥ ዋስትና ዓይነተኛ ዓለማው በተሰራው ነገር ጉዳት የደረሰበት ተዋዋይ ወገን በገንዘብ ረገድ ለመካስ ነው፡፡ ከስር ፍ/ቤት የክርክር ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው አቅራቢ በውሉ መሠረት ማቅረብ ባለመቻሏ ውሉ ፈርሷል፡፡ ተጠሪ ከሌላ ተዋዋይ የአቅርቦት ውል የፈፀመ መሆኑ ባይካድም በመጀመሪያ እና ሁለተኛ አቅርቦት ላይ በዋጋ ረገድ ከፍተኛ ልዩነት መኖሩን ግልጽ ነው፡፡ በአሁኑ ተጠሪ እና በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው ግለሰብ ተፈፀሞ የነበረው የምግብ አቅርቦት ውሉ ለ10 ወራት የሚቆይ እንደነበር፤ ይሁንና በ1ኛ ተከሳሽ ውል አለመፈፀም ምክንያት በ2ኛ ወር ተቋርጧል፡፡ በአሁኑ ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ የነበራችው እንደውሉ ባለመፈፀምዋ ከ2ኛ ተዋዋይ የአቅርቦት ውል ለማድረግ የተገደደ በመሆኑ ተጨማሪ ወጭ የጠየቀው ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተከሳሽ ከነበረው ዳሽን ባንክ የውል ማስከበሪያ ገንዘብ ገቢ እንዲሆንለት መጠየቁ ውሉን መሰረት ያደረገ በደረሰው ጉዳት ልክ ሳይሆን በተሰጠው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ብር 658,568,00 የተገደደ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል መልካም የስራ አፈፃፀም ዋስትና ላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ማለትም ብር 658,568.00 ገቢ እንዲሆን መወሰኑ ውሉን በህጉ አግባብ ተፈፃሚ አደረጓአል ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን አያሳይም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረሰ በተባለው ጉዳት ሊከፈል ይገባል በማለት የወሰነው 96,000 ብር በማሻሻል ለመልከም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው ብር 658,568.00 ገቢ እንዲሆን መወሰኑ በህጉ አግባብ ሆኖ በመገኘቱ የሚታረም የህግ ስህተት የለውም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 89493 በ30/03/2006 ዓ/ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 67820 በ 09/07/2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. በተጠሪ ላይ ለደረሰ ጉዳት ሊከፈል የሚገባው ብር 96,000 ሳይሆን ለውሉ መልከም ስራ አፈፃፀም የተያዘው ጠቅላላ ገንዘብ ብር 658,568 /ስድስት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ስምንት/ ተብሎ መወሰኑ በአግባብ ነው ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካቾች ይህንን ገንዘብ በስር 3ኛ ተከሳሽ ለነበረው ደሽን ባንክ ሲተኩ የዋስትና መያዣው ይለቀቅለቸው ብለናል፡፡
4. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር በጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት የመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101053

ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ጌታቸው መንትስኖት

ተጠሪ፡- አቶ የምሩ ነጋ - ጠበቃ አሳምነው አረጋ

መዝገቡን መርምረን ተከታን ወስነናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በኪራይ የተያዘን ቤት ጥገና መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ታህሳስ 10 ቀን 2004 ዓ/ም ባቀረበው ክስ መነሻ ነው፡፡

የክሱ ይዘትም ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች የሆነ በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 20 የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 695 የሆነ ቤት ተከራይቼ እንዳድሰውና ለዕድሳት የማወጣው ወጭ ከቤቱ ኪራይ እንዲታሰብልኝ ለመ/ቤቱ የቦርድ አመራር አመልክቼ ቦርዱ ህዳር 29/1998 ዓ/ም በፈቀደልኝ መሰረት የቤቱን ጥገና ለማካሄድ ከንኮማድ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/ግል ማህበር ጋር ተዋውዬ ለቤቱ ጥገና ብር 1,415,604.80 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አስራ አምስት ሺህ ስድስት መቶ አራት ከ80/100) ወጪ አድርጌ ሳስጠግን የቆየሁ ቢሆንም ተከሳሽ ሀምሌ 18/2000 ዓ/ም በጻፈው ደብዳቤ ዋናውን የቤቱን አካል በማፍረስ በህገ-ወጥ መንገድ ግንባታ እያደረጉ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት በአዋጅ ቁጥር 555/2000 የተሰጠውን ስልጣን ያላግባብ ተጠቅሞ ሀምሌ 23/2000 ዓ.ም በፖሊስ ኃይል አስለቅቆ ቤቱን የወሰደው ስለሆነ ያላግባብ የወሰደውን ቤት መልሶ እንዲስረክበኝ፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ለቤቱ ጥገና ያወጣሁትን ወጪ እና በቤቱ ሳልጠቀም ጥገና ሲካሄድ ለነበረበት ጊዜ የከፈልኩት የኪራይ ገንዘብ ብር 232,891.50 ከወለድና ወጪና ኪሳራ ጋር እንደመልስልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በክስ መቃወሚያነት ከሳሽ ከውል ውጭ ህገ ወጥ ግንባታ ስለገነቡና ህገ ወጥ ግንባታ የማስፈረስ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 555/2000 የተሰጠው በመሆኑና በዚሁ መሰረት ተከሳሽ ቤቱን የተረከበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም ብሏል፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ በሰጠው መልስ ቤቱን ከሳሽ እንዲጠግኑ ፈቃድ ያልተሰጠ በመሆኑ የጥገና ወጪ ይከፈልኝ፤ በጥገና ለቆየበት ጊዜ የከፈልኩት የቤት ኪራይ ይመለስልኝ በማለት ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡ ከሳሽ ቦርዱ ቤቱን እንድጠግን ወስኖልኛል ካሉበት ከህዳር 29/1998 ዓ/ም በኃላ የኮንስትራክሽንና ዲዛይን አ/ማ የካቲት 22 ቀን 1998 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ቤቱን ለማደስ በጣም አስቸጋሪና ወጪውም ከፍተኛ በመሆኑ በጠቅላላው ቤቱ ፈርሶ በአዲስ መልክ ቢሰራ የተሻለ መሆኑን ገልጿል፡፡ በዚሁ መነሻነት የተከሳሽ የማኔጅመንት ስራ አመራር ጥር 7/1999 ዓ/ም ባካሄደው ሰብሰባ ከሳሽ ቀደም ብሎ ባቀረቡት የማሻሻያ ስራ ጥያቄ ላይ ነባሩ የቤቱን ፕላን ተጠብቆ ስራው እንዲሰራ ይህንንም የቴክኒክና ምህንድስና መምሪያ በበላይነት እየተቆጣጠረ እንዲያሰራ የተወሰነ መሆኑን በማስታወስ የአሁን ከሳሽ ባቀረበው ጥናት መሰረት ቢሰራ የባለቤትነት ጥያቄ ሊያስነሳና የተከሳሽንም መብት ሊያሳጣ እንደሚችል በመረጋገጡ ከሳሽ ባቀረበው ጥናት መሰረት መፍቀድ ስለማይቻል ቤቱን እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ የተከሳሽ ስራ አመራር ቦርድ በወሰነው መሰረት ጥናት አካሂደ በኤጀንሲው ተቀባይነት ሳያገኙና ቤቱን እንዴት ማደስ እንዳለባቸው ሳይዋዋሉ በተከሳሽ ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6(3) መሰረት ከውል ውጭ ህገወጥ ግንባታ በሚያካሄድ ተከራይ ላይ ማስጠንቀቂያ በመሰጠት ቤቱን እንዲረከብ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተረከባቸው በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም፡፡ ቤቱ እንደ አዲስ ፈርሶ እንዲሰራ አልፈቀደም ፤ የስራ አፈጻጸም ውልም አልገባም፡፡ ከሳሽ ከተከሳሽ እውቅና ውጭ ያወጡትን የጥገናና እድሳት ወጭ እንዲመለስላቸው መጠየቃቸውም የህግ መሰረት የለውም፤ ተከሳሽ የመንግስት መ/ቤት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3250-3253 ድንጋጌዎች መሰረት የስራ ውል ከፈጸመ በኃላ በበላይነት የስራውን አካሄድ እንዲቆጣጠር ሊደረግ ይገባ ነበር፤ ከሳሽ ከንኮማድ ከተባለው የራሳቸው የኮንስትራክሽን ድርጅት ጋር ያደረጉት የስራ ውል ተቀባይነት የለውም፤ በአጠቃላይ ከሳሽ ምንም ዓይነት የጥገና ዕድሳት ውል ሳይደረግ በማን አለብኝነት አፍርሰው በመሰራታቸው ለግንባታ አወጣሁ የሚሉትንም ሆነ በጥገና ለቆየበት ጊዜ የከፈልኩት ኪራይ ይመለስልኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ክርክርና ማስረጃውን ተመልክቶ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ተከሳሽ መልሶ መውሰዱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የኪራይ ውሉ ሊቀጥል ይገባል? የሚሉትን ነጥቦች በተመለከተ በኪራይ ውሉ አንቀጽ 7(2) ተከራይ የአከራዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ የቤቱን ጣሪያ፤ ግድግዳ፣ ወለል አያፈርስም አይሰራም፤ በቤቱ ውስጥም ሆነ በቤቱ አጥር ክልል ውስጥ የኮንስትራክሽን ስራ አይሰራም ተብሎ የተከራዩ ግዴታ በግልጽ የተመለከት በመሆኑ፤ እንዲሁም በውሉ አንቀጽ 11(3) የቤት ኪራይ ውሉ ከሚፈርስባቸው መንገዶች መካከል አንደኛው አንዱ ወገን በውሉ ውስጥ የተመለከተውን ግዴታውን በትክክል ሳይወጣ መቅረቱ መሆኑ ስለተመለከተ፤ የተከሳሹ ድርጅት ስራ አመራር ቦርድ ቤቱን አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ ቢኖርም እድሳቱና ግንባታው በምን ያህል ወጪና ደረጃ እንደሚከናውን ከሳሽ ለተከሳሽ አሳውቆ ፈቃድ ሳያገኝ ግንባታውን ማከናወኑ በውል የተመለከተውን ግዴታ መጣስ ነው፤ ተከሳሹም በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6(3) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ቤቱን ከከሳሽ መረከቡ በህጉ አግባብ ነው፤ በውሉ መሰረት ከሳሽ ቤቱን እንዲጠቀመበት ለመመለስ የሚገደድበት ምክንያት የለም ብሏል፡፡

ከሳሽ ቤቱን ለማደስ ያወጡትን ወጪና የከፈሉት የኪራይ ገንዘብ እንዲመለስ የተጠየቀውን ዳኝነት በተመለከተም ስለግንባታው የተደረገ ዝርዝር ስምምነት በሌለበት፤ ስለአፈጻጸሙም ሆነ ስለሚያስከትለው ወጪ ተከሳሽ እንዲያውቁትና በዚሁ መሰረት እንዲከታተሉ ሳይደረግ የቦርዱን መነሻ ውሳኔ በቻ መሰረት በማድረግ ግንባታ ማካሄዳቸው ተገቢ ባለመሆኑ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2912 አከራይ ሳይፈቅድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁኔታን መለወጥ እንደማቻል ስለሚደንግግ፤ የማደሻ ወጪን የሚችለው ተከራይ ባልሆነ ጊዜ ተከራዩ ይህን ሁኔታ ማሳወቅ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ3/ቁ.2917 የተደነገገ በመሆኑ፤ እንዲሁም ተከራይ ያላከራይ ፈቃድ በቤቱ ላይ ስላደረገው ማሻሻያ አንዳች ወጭ መጠየቅ መብት እንደሌለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2973(1) ስር የተደነገገ በመሆኑ፤ የቤቱን ዕድሳትና ጥገና ሁኔታ እና የሚያስከትለውን ወጪ ተከሳሽ አውቆ ስምምነቱን የሰጠና የፈቀደ ለመሆኑ ከሳሽ ባላስረዱበት ሁኔታ ቤቱን ለማደስና ለመገንባት ያወጡትን ወጪ ተከሳሽ ይክፈሉኝ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፤ የኪራዩን ገንዘብ በተመለከተም ከተከራዩበት ጊዜ ጀምሮ የከፈሉትን ገንዘብም ተከሳሽ ሊመልስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁን ተጠሪ ቅር ተሰኝተው ይግባኙን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በመጨረሻ በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ጥገናው ወዲያው እንደተጀመረ ተከታትሎ ማስቆምና ተጠሪን ከቤቱ ማስወጣት ሲገባው የቤቱ ዕድሳት ሲሰራ ዝም በማለት ለወጪ ከዳረጋቸው በኃላ እድሳቱን አቋርጠው እንዲወጡ ማድረጉ ቅንልቦናን የተከተለ ባለመሆኑ፤ የስር ፍ/ቤትም ጉዳይን ከግራ ቀኙ የቤት ኪራይ ውል እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2912፣ 2917፣ 2973(1) ድንጋጌዎች አንጻር ብቻ በመመልከት የአመልካች መ/ቤት ስራ አመራር ቦርድ ቤቱን እንዲጠግኑ ፈቃድ የሰጠበትን በተገቢው ሳያገናዝብ የቤቱ ዕድሳት ገንዘብ መክፈል የለበትም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም፤ ነገር ግን የቤቱን ኪራይ በተመለከተ በቤቱ እንዳልተገለገሉ የሚያሳይ ማስረጃ ስላላቀረቡ ወይም ቤቱ እስኪጠገንና አገልግሎት እስኪሰጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኪራይ እንዳይታሰብ የተደረገ ስምምነት ስለመኖሩ ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ የኪራይ ገንዘብ ሊመለስ አይገባም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የቤቱን ጥገና ወጭ በተመለከተ ክርክር ተደርጎ እንዲወሰን ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት መልሷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበ በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 18/2006 ዓ/ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ አመልካች ሳልፈቅድለት በአከራየሁት የመኖሪያ ቤት ላይ ያካሄደው ግንባታ ከውል ስምምነታችን ውጭ በህገ ወጥ መንገድ የሰራው በመሆኑ ያወጣው ወጭ የመተካት ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ታይቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት የተጠሪ ጥያቄ በውሉም ሆነ በፍ/ብሔር ህጉ ድጋፍ የለውም ተብሎ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ተጠሪ ከአመልካች የተከራየውን ቤት ለማደስ ባያስፈቅድም ተጠሪ ግንባታ ሲያካሁድ እያወቀ ዝም ብሎ ቆይቶ እኔ ሳልፈቅድ ያወጣውን ወጭ አይከፍልም በማለት የስር ፍ/ቤት መወሰኑ የአመልካች ስራ አመራር ቦርድ ቤቱን ተጠሪ እንዲጠግኑ የሰጠውን ውሳኔ ያላገናዘበ ነው በማለት ሽሮ አመልካች ተጠሪ ለቤቱ ጥገና ያወጣውን ወጪ የመሸፈን ኃላፊነት አለበት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ በጽሁፍ ክርክራቸውን ተለዋወጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ካስነሳው የውሳኔ ክፍል እና አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ለእድሳት ያወጣው ገንዘብ እንዲተካለት ዳኝነት የጠየቀው የተከራየውን ቤት እንዲያድሰውና ለዕድሳት ያወጣው ወጭ ከቤቱ ኪራይ እንዲታሰብለት ለመ/ቤቱ የቦርድ አመራር አመልክቶ ተፈቅዶለት እያለ የቤቱን አካል በማፍረስ ህገ ወጥ ግንባታ እያደረጉ ነው በሚል አመልካች ቤቱን መልሶ ወስዷል በማለት ነው፡፡ አመልካች የኪራዩን ቤት ከተጠሪ መልሰው መውሰዳቸውን ሳይክዱ ከውሉ ወጭ ህገ ወጥ ግንባታ መደረጉን ከሳሽ ባቀረበው ጥናት መሰረት ቤቱን ለማደስ አስቸጋሪና ወጪውም ከፍተኛ በመሆኑ በጠቅላላ ቤቱ ፈርሶ በአዲስ መልክ ቢሰራ የተሻለ መሆኑ ስለተገለጸ በጥናቱ መሰረት መፍቀድ እንደማይቻልና ቤቱን እንዲያስረክቡ ከማድረጉ ውጭ የሰጠው ፈቃድ ስለሌለ ወጪውን ለመክፈል ኃላፊነት እንደማይኖርበት ተከራክሯል፡፡

በኪራይ ውሉ ተጠሪ በቤቱ ላይ የሚያከናውኑትን ግንባታ ለአመልካች በቅድሚያ የማሳወቅ እና ከአመልካቹ የጽሁፍ ፈቃድ ካላገኙ በቀር ግንባታ ያላመካሄድ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከህጉም አንጻር ሲታይ የማደሻውን ወጪ የሚችለው ተከራዩ ካልሆነ ይህን ሁኔታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላካራዩ ማስታወቅ ግዴታ ሲሆነ ተከራዩ ያላከራዩ ፈቃድ በተከራየው ቤት ላይ ስላደረገው ማሻሻያ አንዳች ወጭ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት እንደማይኖረው፤ ነገር ግን ማሻሻያውን ያደረገው በአከራዩ ፈቃድ እንደ ሆነ ተከራዩ ያደረጋቸውን ወጭዎች ሁሉ እንዲከፍለው አከራዩን ከሶ ሊጠይቀው እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2973 እና 2917 እንዲሁም ስለማይንቀሳቀስ ንብረት ኪራይ ከተደነገጉ የፍ/ብ/ህጉ ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

በኪራይ ውሉም ሆነ በህጉ ተጠሪ በኪራይ ቤቱ ላይ የሚያከናውነውን ግንባታ ለአመልካች ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን ለማሻሻያው ያወጣው ወጪ የሚተካለት ማሻሻያው በግልጽ በአከራዩ ተፈቅደ የተከናወነ ሲሆን ስለመሆኑ አከራካሪ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አከራካሪ ሆነ የዘለቀው ለማሻሻያው የተደረገው ወጪን በተመለከ የሚሰጠው “ፈቃድ” ነው፡፡

ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍ/ቤቶች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር መረዳት እንዲሚቻለው የአመልካች ድርጅት የስራ አመራር ቦርድ ህዳር 29/1998 ዓ/ም ባደረገው መደበኛ ሰብሰባ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ውይይት አድርጎ ኤጀንሲው ቤቱን ባለበት ሁኔታ ለጠያቂው (ለተጠሪ) በኪራይ እንዲሰጣቸውና ለጥገና የሚያወጡት ወጭም በኪራይ እንዲተካላቸው ወስኗል፡፡ ከቦርዱ ውሳኔ በኃላ የኮንስትራክሽንና ዲዛይን አ/ማ ቤቱ ባለበት ሁኔታ ሊጠገን እንማይችል ባቀረበው አስተያየት መነሻነት ጥር 07 ቀን 1999 ዓ/ም በመ/ቤቱ የማኔጅመንት ስራ አመራር አካላት ዕድሳት ሊፈቀድ እንደማይችልና ተጠሪ ቤቱን ማስረከብ እንደሚገባቸው ተወስኗል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ቤቱ ፈርሶ መስራት ቢኖርበት እንኳ ስለሚደረገው መሻሻል እና ስለሚያስወጣው ወጭ የተደረገ ስምምነት እና የተሰጠ ፈቃድ በሌለበት ግንባታ በማድረጋቸው አመልካች ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ሀምሌ 23/2000 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 555/2000 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ቤቱን መልሶ ተረክቧል፡፡ ይህ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር አመልካች በውሉና በህግ ከተመለከተው ውጭ ሰርቷል የሚያሰኝ ካለመሆኑም በላይ ተጠሪ በኪራይ ቤቱ ላይ ጥገና (ማሻሻያ) ያደረጉት የሚጠበቀውን ፈቃድ ከአመልካች አግኝተው ነው የሚያሰኝ አይደለም፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ ለቤቱ ጥገና (ዕድሳት) ያወጡትን ወጪ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የወሰነው አመልካች ጥገናው እንደተጀመረ ተከታትሎ ማስቆምና ተጠሪን ከቤቱ ማስወጣት ነበረበት፤ ለወጭ ከዳረጋቸው በኃላ እድሳቱ አቋተጠው እንዲወጡ ማደረጉ ቀንልቦናን የተከተለ አይደለም እንዲሁም ጉዳዩ ከውሉ እና ከህጉ ድንጋጌዎች ብቻ ሳይሆን የአመልካች ስራ አመራር ቦርድ አስቀድሞ ካሳለፈው ውሳኔ አንጻር መታየት ነበረበት በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ከቀደመው የቦርድ ውሳኔ በኃላ የኮንስትራክሽንና ዲዛይን አ/ማ ቤቱ ሊጠገን እንደማይችል ያቀረበውን አስተያየት ተከትሎ የአመልካች መ/ቤት ማኔጅመንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እድሳት ሊፈቀድ እንደማይችል መወሰኑን እንደማያውቁ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ይልቁንም ጉዳዩን በቅርበት እንደመከታተላቸው የቀደመውን የቦርድ ውሳኔ ሲያውቁ የኃለኛውን አያውቁም ለማለትም አይቻልም፡፡ ተከራይ የኪራይ ቤት ለማደስ ያወጣው ወጪ አከራዩ ሳይፈቀድ የተደረገ ከሆነ በህጉ መጠየቅ እንደማይቻል ከላይ ከተመለከተነው ድንጋጌ መረዳት እየተቻለ ከቅን ልቦና ውጭ የተሰራ ስለመሆኑ እንኳ ሳይረጋገጥ ይህን ምክንያት በማድረግ ተጠሪ ጥገናውን ወጭ የመክፈል ኃላፊነት አለበት መባሉ ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ክርክሩም የግራ ቀኙ ካደረጉት የኪራይ ውል እና ስለማይንቀሳቀስ ንብረት ኪራይ በጠቅላላውና የቤትን ኪራይ በተለይ ከሚመለከቱ የህጉ ልዩ ደንቦች አንጻር ታይቶ የማይወሰንበት የህግ ምክንያትም የለም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ለተጠሪ ባከራየው ቤት ላይ ስለተደረገው ጥገና (ማሻሻያ) የሰጠው ፈቃድ ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ለጥገና አወጣሁ ያሉትን ወጪ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1ኛ. በፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 91172 የካቲት 24/2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ. በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 111615 ሚያዝያ 21/2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

3ኛ. አመልካች ለጥገና የወጣውን ወጪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ተወስኗል፡፡

4ኛ. በዚህ ፍ/ቤት ፊት ስለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 111778

ጥር 16 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሪት ገንዘብ ስጦታው ቀረቡ

ተጠሪ፡- የራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት የክ/ዐ/ህግ ዘላለም ተስፋዬ ቀረቡ፡፡

መዝገቡንመርምረንተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለመንግስት መስሪያ ቤት ለሚፈጸም ቅጥር የተገባውን የዋስትና ውልን መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞንራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤትየአሁን ተጠሪ ባሁኑ አመልካችና በአቶ ዘመኑ ይላቅ (የሥር 1ኛ ተከሳሽ) ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ በመሰረተው ክስ አቶ ዘመኑ ይላቅ በራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በግዥና በፋይናንስ የሥራ ሂደት ተቀጥሮ እየሰራ እያለ በተሰጠው ውክልና መሰረት ከልዩ ልዩ ገቢ ደረሰኝ 2617.00 ብርና ከሞዴል 85 ብር 10,070.00 አጠቃላይ ብር 12,687 (አስራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ሰባት ብር) ያንደለ ሲሆን አመልካች በሲቪል ሰርቪስ ሐምሌ 2002 ዓ/ም በወጣው መመሪያ መሰረት ለስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ዘመኑ ይላቅ ዋስትና ስለገቡ የጎደለውን ብር 12,687.00 ከወለድ ጋር በዋስትና ግዴታቸው መሰረት ይክፈሉ ሲል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ የፍርድ ቤቱን የሥረ ነገር ስልጣን መሰረት አድርገው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የስር 1ኛ ተከሳሽ የተቀጠሩት በግዥ ኦፊሰርነት ሁኖ አመልካች ዋስ የሆኑትም ለዚሁ የስራ መደብ መሆኑን፣ ለክሱ መሰረት የሆነው ገንዘብ ሊጎድል የቻለው የሥር 1ኛ ተከሳሽ በእለት ገንዘብ ተቀባይነት የስራ መደብ ተጠሪ መድቦ ሲያሰራውና አመልካችም ስምምነት ሳይሰጡበት መሆኑን ጠቅሰው ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም 1ኛ ተከሳሽ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳውን ክርክር መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን አመልካች እስከ ብር 60,000.00 የዋስትና ግዴታ የገቡ በመሆኑ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ በገቡት ዋስትና መሰረት ከህጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር አመልካች ለስር 1ኛ ተከሳሽ ዋስ የሆኑት ሰራተኛው በግዥ ኦፊሰርነት የሥራ መደብ ተቀጥረው ለሚከሰት ጉዳት መሆኑን፣ ለክሱ መሰረት የሆነው ጉድለት የተከሰተው ደግሞ ሰራተኛው በውክልና በእለት ገንዘብ ያዥነት ተመድበው ሲሰሩና ተጠሪ ደግሞ ይህንኑ እንዲያውቁ ሳይደረግ መሆኑን፣ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ሐምሌ 2002 ዓ/ም የወጣው መመሪያም የሥራ መደብ ለውጥ ሲደረግ ዋሱ እንዲያውቅ መደረግ እንደአለበት የሚደነግግ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አመልካች ዋስትና የገቡበትን የስራ መደብና ለክሱ መሰረት የሆነው ጉድለት የተከሰተው አመልካች በማያውቀት የስራ መደብ ላይ ሰራተኛው ተወክሎ ሲሰራ መሆኑን አግባብነት ያላቸውንየመመሪያ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነው በማለት ሽሮታል።

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ተቀባይነት ያጣ ቢሆንም የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን ግራ ቀኙን አከራክሮ አንድን የመንግስት ሰራተኛ ከተቀጠረበት የስራ መደብ ውጪ በሌላ የስራ መደብ ወክሎ ማስራት በክልሉ የመንግስት ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 171/2002 የተፈቀደ መሆኑን፣ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ወጣ የተባለው መመሪያም ተፈፃሚነት ያለው የስራ መደቡ ሲቀየር እንጂ በውክልና ለሚሰራ ስራ አለመሆኑን በምክንያነት ይዞ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሳኔ ሽሮ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት አመልካችን ለጉድለቱ ኃላፊ አድርጎአል። የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካችን ለጉድለቱ ኃላፊ ያደረገው አመልካች ከገቡት የዋስትና አድማስ ውጪና በክልሉ ሲቭል ሰርቪስ ቢሮ የወጣውን መመሪያ እንዲሁም የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1928 ድንጋጌን ሳያገናዝብ መሆኑን ዘርዝው ውሳኔው ሊስተካከል ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል። እንደመረመረውም አመልካች የገቡት የመንግስት ስራ ቅጥር ዋስትና ውል ተቀጣሪው በመንግስት መስሪያ ቤት ባለበት ጊዜ ከተቀጠረበት የስራ መደብ በተጨማሪ በውክልና እንዲሰራ ቢደረግና በዚሁ በውክልና ደርቦ እንዲሰራ በተደረገበት የስራ መደብ ላይ ሁኖ ለሚያጠፋው ጥፋት ሁሉ ለዋናው የሥራ መደብ ዋስ በሆነው ሰው ላይ ኃላፊነትን የሚያስከትል ነው? ወይስ አይደለም?፣ የኃላፊነት መጠኑስ ምን ያህል ይሆናል? የሚሉትን ጭብጦች ምላሽ መስጠቱ ተገቢ ሁኖ አግኝቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካችን ለክሱ ገንዘብ ኃላፊ ያደረገው አሰሪው የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጣሪውን ሰራተኛ ከተቀጠረበት የስራ መደብ በተጨማሪ በውክልና በሌላ የሥራ መደብ ላይ መድቦ ማስራት በህግ የተፈቀደ ነው በሚል አቢይ ምክንያት ሲሆን የስራ መደብ ለውጥ ሳይደረግ በውክልና ይሰራ በነበረው የሥራ መደብ ሰራተኛው ተመድቦ ሲሰራ ለሰራተኛው ዋስ ለሆኑት ለአመልካች እንዲያውቁት ማድረግን የሚያስገድድ ሕግ የለም በማለት ነው፡፡ በመሆኑምአመልካች የዋስትና ግዴታቸውን የገቡት ሰራተኛው ለግዥ ኦፊሰርነት ስራ ሲቀጠሩ መሆኑና አሁን ክርክር ያስነሳው ደግሞ ይኼው ሰራተኛ በዚሁ አመልካች ግዴታ በገቡበት መስሪያ ቤት ውስጥ የስራ መደብ ለውጥ ሳይደረግ በውክልና ደርበው እንዲሰሩ በተደረገበት የእለት ገንዘብ ተቀባይ የሥራ መደብ ላይ በመስራት ላይ እያሉ በፈጸሙበት የእምነት ማጉደል ድርጊት የጎደለ ገንዘብ መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረና ሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶችም የተቀበሉት የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡ስለዚህ የሕግ ጥያቄው የሚሆነውና የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት የተቀጠረ ሰራተኛ በውክልና ሲሰራላጎደለውገንዘብ ሰራተኛው ሲቀጠር ዋስ የሆነ ሰው የዋስትና ግዴታ አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ የዋስትና ግዴታ በሕጉ ጥበቃ የሚያገኘው በፍ/ሕ/ቁጥር 1922 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ዋስትና ግልፅ መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ ከተደረገው ውል ወሰን ለማለፍ የማይችል እና ለግዴታው ዋስ የሆነበት የገንዘቡ ልክ በዋስትናው ውል መገለፅ አለበት፡፡ ዋስትና ይህን ፎርማሊቲ ከማሟላቱም በተጨማሪ ለዋስትናው መሰረት የሆነው ዋናው ጉዳይም ሕጋዊና ግራ ቀኙ የተስማሙበትና የሚታወቅ መሆን አለበት፡፡

አመልካች አቶ ዘመኑ ይላቅ በግዥ ኦፊሰርነት የሥራ መደብ ሲቀጠሩ የዋስትና ውል ግዴታ መፈረማቸው እና የውሉ አይነት ዋስትና እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1922 እንደተመለከተው የዋስትና ግዴታውን በግልፅ ጠቅሶ አመልካቿ እስከ ብር 60,000.00 ግዴታ መግባታቸውም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ውሉ የዋስትና መጠኑን በግልፅ ከገለፀ አመልካች ሊገደዱ የሚገባው በዚሁ በውሉ በተገለፀው የገንዘብ መጠን ልክ ነው፡፡ አመልካች አቶ ዘመን ይላቅ የተቀጠሩት በመንግስት መስሪያ ቤት መሆኑን አውቀው እስከፈረሙ ድረስ ሰራተኛው በዚያው መስሪያ ቤት በተለያዩ ምክንያቶች ከተቀጠሩበት የስራ መደብ በተጨማሪ ሌላ የስራ መደብ ላይ ተወክለውየመንግስትን ስራ ሊሰሩ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን እንደሚያውቁ የሚታወቅ ነው፡፡ ሰራተኛው የሰራበት የስራ መደብ ባህርይ ለዋስትና ግዴታ ወሳኝነት ያለው መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን አመልካች መጀመሪያ ግዴታ የገቡበትየግዥ ኦፊሰርነት የሥራ መደብም ከመስሪያ ቤቱ አጠቃላይ ገንዘብና ንብረት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከእለት ገንዘብ ተቀባይነት የስራ መደብ የሥራ ባህርይ ያነሰ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ሰራተኛው ሲቀጥር የዋስትና ግዴታውን መግባታቸው ከተረጋገጠና ሰራተኛው በስራ መደቡ ላይ ተጨማሪ የሥራ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሰጣቸውም ተከታትለው ግዴታቻውን እንዲወርድ ሳያደርጉ ሰራተኛው በዚያው በተቀጠረበት መስሪያ ቤት ክፍት በሆነው የሥራ መደብ ላይ በሕጉ አግባብ በውክልና እንዲሰሩ ተደርጎ ስራውን ሲሰራ ለተከሰተው ጉድለት የዋስትና ግዴታ ያልገባሁበትና ሰራተኛው ስራውን በውክልና እንዲሰራ ሲደረግ እንዳውቅ ያልተደረገ የስራ መደብ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም የሚሉት ክርክር የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731(1) ፣1922 እና 1928 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ሰራተኛው ከተቀጠረበት የስራ ባህርይ ጋር ያልተገናዘበ በመሆኑ የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ተጠሪ ሰራተኛውን ከተመደበበት የስራ መደብ ውጪ በውክልና ማሰራቱ የዋሱን ግዴታ የሚያባብስ/የሚያከብድ/ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1928(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ተቀባይነት የለውም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1928(2) ስር የተመለከተው ድንጋጌ አይነተኛ አላማ ከዋስትና ውል መፈጸም በኋላ በባለገንዘቡና ባለእዳው መካከል የዋሱን ግዴታዎች የሚያባብሱ አዲስ ስምምነቶች እንዳይደረጉና ዋሱን ለተጨማሪ ጉዳት እንዳይዳርጉት ለመጠበቅ ስለመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17077 በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከትምአመልካች ስራተኛውን ተጨማሪ የስራ መደብ ላይ በውክልና ማስራቱ በክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 አንቀጽ 61(3) የተሰጠው ኃላፊነትና ተግባር በመሆኑ ይህ ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ለጉዳዩ አግባብነት አለው የሚሉት የክልሉ የመንግስት ሰራተኞች ዋስትና አፈፃጸም መመሪያም የስራ መደብ ለውጥ ሲደረግ ዋስ ይህንኑ እንዲያውቅ የሚደረግበትን አግባብ የሚመለከት እንጂ በውክልና ሰራተኛው ከተቀጠረበት ስራ ሌላ የሥራ መደብ ደርቦ እንዲሰራ ሲደረግ አሰሪው መስሪያ ቤት ይህንኑ ለዋስ እንዲያሳውቅ ግዴታ የሚጥል ድንጋጌን ያልያዘ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክርም ከመመሪያው ድንጋጌዎችና ከክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 አንቀጽ 61(3) ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ አንፃር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01017692 ጥር 26 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-08884 የካቲት 25 ቀን 2007 ዓ/ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በገቡት የዋስትና ግዴታ ውል መሠረት ለተጠሪ ኃላፊ ነው ተብለው ለክርክሩ ምክንያት እንዲከፍሉ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.106535

ቀን 17/05/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ረዲ ተፈራ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ አቶ አብሹ በቀለ } የቀረበ የለም

2ኛ አቶ ዳመሳ ኤርጳዛ }

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል አዳሚ ቱሉ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪዎች በመ/ቁ. 21265 በቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በራ ሳይወሰደበት ዳለቻ በራ ወሰደሃል በሚል ጥቁር ጋራ የሆነ በራ ግምቱ 8000 (ስምንት ሺህ) የሚያወጣ እንደወሰደበት የራሱ በራ ከሌላ ሰው ጋር አግኝቶ የወሰደ ቢሆንም በራውን አልመለሰም በሽማግሌዎች አማካይነት በራው ለመመለስ በ26/12/2005 በተፃፈ ውል በ03/13/2006 ዓ/ም በራውን ለማቅረብ ተስማምተው እንደፈረሙ፤ 2ኛ ተጠሪም 1ኛ ተጠሪ በራው የማይመለስ ከሆነ ዋስ እንደሆነ፣ በተጨማሪነትም 1ኛ ተጠሪ 27/08/2006 ዓ/ም በተፃፈው ውል ብር 6000.00 /ስድስት ሺህ/ ለመክፈል ፈርሞ የተቀበለ ቢሆንም ገንዘቡን ባለመክፈሉ ለመክሰስ እንደተገደደ በመሆኑም የበራው ግምት 8,000.00 ብር ብድር 6,000.00 ከኪሰራና ወጪ ጭምር እንዲከፈለው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በቀረቡት የመከላከያ መልስ 1ኛ ተጠሪ በራውን አለማግኘቱን በሽማግሌዎች ፊት ተስማምተናል በማለት ያቀረበው ውል በሕግ ተሟልቶ የቀረበ አይደለም፤ 03/13/2006 ዓ/ም የተባለው ቀን ስላልደረሰ አመልካች መክሰስ አይችሉም፤ የብድር ውሉ የተባለው በሐሰት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተዘጋጀ ሰነድ ነው፤ በ2006 ዓ/ም ይበል እንጅ በየትኛው ቀን እንደሚከፈል ስለማይገልጽ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ይዘት ያለው መልስ አቅርበዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ክሱ የመክፍያ ጊዜ የተባለው ቀን ከመድረሱ በፊት እንደቀረበ ዋስ ተጠያቂ የሚሆነው ዋና ተበዳሪ አልከፈልም የሚል ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የገንዘብ ብድር ውል ስምምነት አለ ወይስ የለም? ተጠሪዎች የበሬውን ግምት መክፈል አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ በአመልካች የቀረበው የውል ሰነድ ሰርዝ ድልዝ ስላለው አመልካች ኦርጅናሉ እንዲያቀርብ የታዘዘ ሲሆን በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት አመልካች ኦርጅናል ነው ያለውን ውል ያቀረበ ሲሆን አመልካች መጀመሪያ ክስ ሲያቀርብ በ26/12/2005 ዓ/ም በተጻፈ ውል በማለት የተገለጸ ሲሆን እንደማስረጃ በቀረበው ውል ላይ ደግሞ በ2006 ዓ/ም የሚለውን በመሰረዝ 2005 ዓ/ም እንዳደረገ በችሎቱ ትዕዛዝ ከቀረበው ኦርጅናል ውል መረዳት እንደተቻለ፤ 2ኛ ተጠሪ በተመለከተውም 1ኛ ተጠሪ በራው ስለ አገኘ የራሴ በሬ እንዲመስል ፈርሞልኛል የሚለው ከመነሻው የሰው ንብረት የወሰደ ሰው በሸማግሌ ታምኖበት ሳይገደድ ወሰደ የተባለው ንብረት ከከፈለ በኃላ እንዲመልስልኝ በማለት መስማማት የህግ መሠረት ያለው አለመሆኑን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ውል እንደኛው በምስክሮች የተፈረመ አለመሆኑን ውሉ ነው የተባለው በአመልካች ተሰርዞ የቀረበ ስለ መሆኑ በመረጋገጡ አመልካች በቀረበው ክስ ማስረጃ መስማት ሳያስልግ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች በነጻ አሰናብተዋል (ወስነዋል)፡፡

የአሁኑ አመልካች በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከከራከረ በኃላ ኦርጅናል ውሉ የተሰረዘ ነገር እንዳለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማረጋገጡ ውሉ የተፃፈበትና የሚጠናቀቅበት ቀን ወደ ኃላ የሚቆጥር መሆኑ ሲታይ ውሉ የእውነት እንደልሆነ የሚያሳይ እና የህግ መሰረት የሌለው ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉ ስህተት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ አመልካች በጉዳዩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፀመዋል በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተቀበይነት አለገኘም፡፡ የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፀመ ያለውን ስህተት በመዘርዘር ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም በክሱ የጠቀሰቸው ምስክሮች ሳይሰሙ ክሱ ውድቅ መደረጉ በሕጉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ጥሪ የተደረገላቸው ቢሆንም ባለመቅረበቸው መጋቢት 09 ቀን 2007 ዓ/ም መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ ለክርክሩ መነሻ በሆኑ ውሎች ላይ ስማቸው የተጠቀሱ እማኞች ቀርበው ስለ ውሎቹ መፈፀም አለመፈጸም መኖር ያለመኖር ምስክርነታቸው ሳይሰጡ ውሉ ስርዝ ድልዝ አለበት ተብሎ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፤፤

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች የተወሰደባቸው በሬ እንዲመለስላቸው በብሄረሰቡ ሽማግሌዎች የተደረገ ስምምነት ስለመኖሩ እና 1ኛ በብድር መልክ የወሰደው ገንዘብ እንዲከፍል፤ 2ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ በሬ ከመመለስ ጋር በተያያዘ የተገበው ግዴታ ላይ ዋስ ስለመሆኑን ነው፡፡ ተጠሪዎች የቀረበባቸው ክስ ክደው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በአመልካች እና ተጠሪዎች ተደረገ የተበለው ውል ስርዝ ድልዝ አለበት በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች ክሱን ለማስረዳት የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በመዘርዘር ያቀረበ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት ውሳኔው ላይ እንዳስፈረው ውሉ የተሰረዘ በመሆኑ በምስክሮች ማረጋገጥ ወይም ማጣራት አይቻልም ከሚል ድምዳሜ ላይ መደረሱን መረዳት ይቻላል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሰው ምስክሮች ለመስማት አልገደድም ለማለት እንደመነሻ የወሰደው የፍ/ሕ/ቁ. 2005 በጽሑፍ ውስጥ ያሉ ቃላት በሰው ምስክር ለማስረዳት አይቻልም የሚል ይዘት ያለው ድንጋጌ ነው ከሚል እሰቤ ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡ ይሁንና አመልካች እንዲሰሙለት እየጠየቀ ያለው በሁለቱም ውሎች ላይ እማኞች ናቸው ተብለው የፈረሙ ምስክሮች እንጅ በውሉ ላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች ምስክሮች አይደሉም፡፡ በመሆኑም ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ክልከላ የሚያደርገው አከራከሪ በሆነው ውል ላይ ይዘቱ ላይ ምስክሮች እንደይሰሙ እንጅ በጉዳዩ ላይ እማኞች በመሆን የፈረሙ ምስክሮች ካሉ ስለ ውሉ መኖር አለመኖር እንዳያስረዱ ክልከላ ስለማደረጉ ህጉ አያሳይም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ውል ላይ አልተማመኑም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ክሱን ለማስረዳት የጠቀሳቸው የሰው ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃ ሊመረመርሉት ይገባል፡፡ ፍርድ ቤቱ በአመልካች የቀረቡ ምስክሮች ከሰማ በኃላ የሰጡት ቃል በህጉ አግባብ መዝኖ ምክንያት በመስጠት ሊቀበለው ወይም ላይቀበለው ይችላል፡፡ ነገር ግን የአመልካች ምስክሮች አከራካሪ በሆነው የውል ጉዳይ ምን ዓይነት ምስክርነት እንደሚሰጡት ሳይታወቅ ከወዲሁ ሳይሰሙ በጽሁፍ ሰነድ ላይ ብቻ ተመስርቶ የአመልካች ክስ ውድቅ ማድረጉ በህጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የአመልካች ምስክሮች እንዲሰሙ ካልተደረገ ያቀረበው ክስ ለማስረዳት የሚችገር ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች እና ተጠሪዎች የሚከራከሩበት መሰረታዊ የውል ይፈጸምልኝ ክስ በተጠሪዎች የተከደ በመሆኑ ግራ ቀኙ በተካካዱበት ነጥብ ላይ አመልካች ማስረጃ የማቅረብ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል፡፡ በአመልካች የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ የሚችለው ያቀረበቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች በሕጉ አግባብ ተስምተው የሰጡት ቃል ይዘት ተመዝኖ በምክንያት የተደገፈ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ወረዳ ፍርድ ቤት እና ጉዳዩን በየደረጃው በይግባኝ እና በሰበር የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክሱን የማስረዳት ማስረጃ የማስማት መብቱ አልፈው ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 238 (1) 255፣ 257፣259 እና 261 መሰረታዊ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያላገነዘበ ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ የአመልካች የመደመጥና ክሱን የማሳረዳት መብቱ ያለከበረ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በዚሁም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዳሚ ቱሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 21265 በ11/10/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/ቁ. 38245 በ14/01/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 187691 በ02/03/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የአዳሚቱሉ ወረዳ ፍርድ ቤት የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 21265 በመክፈት በፍርድ ይዘቱ በተገለጸው መንፈስ አመልካች በክሱ የጠቀሳቸው እና ለክርክሩ ምክንያት በሆኑ ውሎቹ ላይ እማኞች የነበሩ ግለሰቦች ቀርበው ግራ ቀኙ እያከራከራ ያለው ውል መፈጸም ያለመፈጸሙን ውሉ መኖር ያለመኖሩን ምስክርነታቸው እንዲሰጡ ከተደረገ በኃላ የሰጡት ቃል በህጉ አግባብ ተመዝኖ ጉዳዩ ተገቢ ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 343 (1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 112328

የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመለካች፡- ሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይ - ኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ግርማ ዘለቀ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኤፍሬም አሸቱ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመኪና ሽያጭ ውልን መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2003 ዓ/ም ባወጣው የመኪና ሽያጭ ጨረታ ላይ ተሳትፈው የታርጋ ቁጥር 3-18353 ኢት የሆነውን መኪና በብር 127,915.55 (አንድ መቶ ሃያ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ አምስት ብር ከሃምሳ አምስት ሳንቲም) የገዙ ቢሆንም ለስም ዝውውሩ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተሸከርካሪውን ማጣሪያ ክሊራንስ እንዲመጣ መጠየቃቸውንና ተጠሪ አመልካችን በዚህ አግባብ እንዲፈፀም ማስጠንቀቂያ ቢሰጥም አመልካች ለማስጠንቀቂያው በሰጠው ምላሽ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስም ዝውውሩ እንዲፈጸም ቃል የገባ ቢሆንም አለመፈጸሙን፣ በዚህ መሰረት አመልካች መኪናውን ለገዛው ተጠሪ ስም ለማዛወር የሚረዱ ሰነዶችን ለተጠሪ የማስረከብ ግዴታውን ያልፈፀመ እና የመኪናው የኪራይ ገቢ ዋጋ በቀን ገቢ ተሰልቶ ብር 205,000.00(ሁለት መቶ አምስት ሺህ) ጥቅም የቀረባቸው መሆኑን ዘርዝረው አመልካች ለተጠሪ መኪናው ከግብርና ታክስ እዳ ነፃ የሆነበትን የክሊራንስ ሰነዶች እንዲያስረክብ፣ በቀን የታጣ ገቢ ብር 205,000.00 እንዲከፍል፣ ሰነዶቹን እስከሚያስረክብ ድረስ ያለውን ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅላቸው ይወሰን ዘንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም፡- ተጠሪ አከራካሪውን መኪና ከአመልካች በጨረታ መግዛታቸውን ሳይክድ በመኪናው ላይ ምንም አይነት እዳና እገዳ የሌለበት መሆኑን፣ መኪናው ሲሸጥም የመኪናውን የባለቤትነት ደብተር/ሊብሬ/፣ ሌሎች ማስረጃዎችን በሙሉ ከነመለያው ለተጠሪ ማስረከቡን፣ ለሚመለከተው አካልም ስመ ሃብቱ እንዲዞርላቸው ነሀሴ 03 ቀን 2003 ዓ/ም ደብዳቤ የፃፈላቸውና ተጠሪም ግልባጩን ተረክበው የወሰዱና ለፕሮክጀት ስራ ተቋራጭ ነፃ በገቡ ማስረጃዎች ጋር በተያያዘ ከኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በተፈጠረ ችግር ኃላፊነትት የለብንም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ አመልካች ለተጠሪ መኪናው ከግብርና ታክስ እዳ ነፃ የሆነበትን የክሊራንስ ሰነዶች እንዲያስረክብ፣ በቀን የታጣ ገቢ ብር 205,000.00 እንዲከፍል፣ ሰነዶቹ እስከሚያስረክብ ድረስ ያለውን ኪሳራ ደግሞ ተጠሪ የመጠየቅ መብት የተጠበቀ መሆኑን ገልፆ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት፡- ለክሱ መነሻ የሆነውን መኪና አመልካች በግልጽ ጨረታ ሽጦ የስም ዝውውር በተመለከተም በጨረታው መመሪያው መሰረት በሕግ የሚፈለገውን ተግባር ሁሉ አመልካች ድርጅት ፈጽሞ እያለ ንብረቱ ለስም ዝውውር ምንም አይነት እዳና እገዳ ሳይኖርበት የሕግና የፍሬ ነገር መሰረት በሌለበት አግባብ አመልካች ለክሱ ኃላፊ ተደርጎ የቀን ገቢ ብር 205,000.00 እና የጠበቃ አበል እንዲከፍል መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች አከራካሪውን መኪና ስም ለማዛወር የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ለተጠሪው አስረክቢያለሁ ብሎ ተከራክሮ ባለበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት ስም ለማዛወር የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ያላስረከበ መሆኑን አመልካች አልካደም በሚል ምክንያት አመልካች ግዴታውን አልፈፀመም በማለት የተሠጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ባወጣው የመኪና ሽያጭ ጨረታ ላይ ተጠሪ ተወዳድረው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ተሸከርካሪ መግዛታቸው ግራ ቀኙን ያላከራከረ ነጥብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን፣ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት ለስም ዝውውሩ አስፈላጊ ከሆኑት ሰነዶች መካከል መኪናው እዳና አገዳ የሌለበት መሆኑን የሚገለፅ የክሊራስን ሰነድ ለተጠሪ የመስጠት ግዴታ አመልካች ያለው መሆን ያለመሆኑን ላይ ስለመሆኑ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የተጠሪ ዋነኛ የዳኝነት ጥያቄ በውል ገዝቼዋለሁ የሚሉትን መኪና ስመሃብት በስማቸው እንዲመዘገብ መኪናው እዳና እገዳ የሌለበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድ በአመልካች ይሰጠኝ ሲሆን በስሜ እንዲመዘገብ ለማድረግ አስፈላጊ ሰነዶች ከአመልካች አልተሰጠኝም የሚሉት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ስለ መኪናው ከእዳና እገዳ ነፃ መሆን የሚያሳይ የክሊራንስ ሰነድን ነው፡፡ አመልካች የመኪናውን የባለቤትነት ደብተር/ሊበሬ/ እና ሌሎች ማስረጃዎችን በሙሉ ከእነመለያው ለተጠሪ ማስረከቡን ገልፆ ለአቀረበው ክርክር ተጠሪ ማስተባበያ ክርክርና ማስረጃ ያቀረበ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ አሳያስም፡፡ አንድን ንብረት የሸጠ ሰው በፍትብሐር ሕግ ቁጥር 2273 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሸጠውን ንብረት ባለሀብትነት ለገዥው የማዛወር ግዴታ ያለበት ሲሆን ይኸም የሻጭ የንብረቱን ባቤትነት ለገዥ የማዛወር ግዴታ በምን መልኩ መፈፀም እንደሚገባው ህግ አውጭው ‹‹ሻጩ የሸጠውን ነገር የማያስነካ መብት ለገዥው ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ለመፈፀም ግዴታ አለበት›› በማለት በፍትብሐር ህግ ቁጥር 2281 በግልጽ ከደነገገው የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ የመኪናን ሽያጭ በውሉ መሠረት እንዲፈጽሙና ስመንብረቱን ለተጠሪ ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን መፈጸን የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም የስም ሃብት ዝውውሩን ለማድረግ አስፈላጊ ተግባራት አልተከናወኑም የሚለው ገዥ እነዚህን በሻጭ ያልተከናወኑትንና የስመ ሃብት ዝውውሩን የሚያከናውን አካል ኃላፊነቱንና ተግባር ለመፈፀም የማያስችለው አስፈላጊ ተግባር ምን እንደሆነ እና አስፈላጊነቱን ማስረዳት መቻል አለበት፡፡

ከዚህ ውጪ ተገቢው ሰነድና ለሽያጩ መሰረት የሆነው ንብረት ርክክብ ተፈጽሞ እያለ ስመ ሃብቱ አልተዛወረልኝም በሚል ምክንያት ብቻ በሻጩ ላይ ክስ ማቅረብ እና ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ የለም፡፡

ከተዋዋዮቹ አንዱ ወገን የውል ግዴታውን ያልፈጸመ እንደሆነ ሌላው ወገን እንደነገሩ አጋጣሚ ሁኔታ ውሉ እንዲፈጸምለት የመጠየቅ መብት እንዳለው፣ ካልሆነም ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ እንደሚችል ወይም ውሉ መፍረሱን ለሌላው ወገን ሊገልጽ የሚችል መሆኑን የፍ/ህ/ቁ/1771(1) የሚደነግግ ሲሆን በውሉ አለመፈጸም የተነሳ ጉዳት የደረሰበት ከሆነም ኪሳራ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 2 ያመለክታል፡፡ ውሉ ተዋዋዮቹ በአንድነት የሚፈጽሙትን ግዴታ (simultaneous performance) የሚጥል ሆኖ ከተገኘም ተዋዋዩ የተዋዋለበትን ግዴታ በውሉ እንደተመለከተው እንዲፈጸምለት የሚጠይቀው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገን ከውሉ ስምምነት የተነሳ እሱም በበኩሉ ያለውን ግዴታ ወዲያውኑ መፈጸም ወይም ለመፈጸም የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባው መሆኑን የፍ/ህ/ቁ/1757 ያስገነዝባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ አመልካችን ሊከሱ የቻሉት የስመ ሃብቱን ዝውውር በሚያደርጉት እለት በመኪናው ላይ የእዳና እገዳ ነፃ መሆኑን የሚያሳይ የክሊራንስ ሰነድ ከገቢዎችና ጉምሩክ ተጠይቀው ይኼው ሰነድ በአመልካች ሊቀርብላቸው ባለመቻሉ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን የክሊራንስ ሰነድ ማቅረብ የአመልካች ግዴታ ስለመሆኑ የሚያሳይ የውል ግዴታ የሌለ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ሰነዱን ራሳቸው ለመውሰድ ያላስቻላቸው ምክንያት ስለመኖሩ ወይም የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን ክሊራንስ የከለከላቸው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ተጠሪ አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ ስመ ሃብቱን ለማዛወር የሚያስችለው አስፈላጊ ተግባር በአመልካች መከናወን ያለበት ስለመሆኑ ባላስረዱበት ሁኔታና አመልካች ደግሞ መኪናውንና አስፈላጊ ሰነዶችን ለተጠሪ ማስረከቡን ገልፆ በተከራከረበት አግባብ የስር ፍርድ ቤት አመልካች አስፈላጊ ሰነዶችን ያላስረከበ መሆኑን አልካደም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ለጉዳዩ የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር ይዘት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 235 እና 83 ድንጋጌዎች ይዘት ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ እንዲሁም ተጠሪ አመልካች ነሐሴ 03 ቀን 2003 ዓ/ም በፃፈለት ደብዳቤ መነሻ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሂደው መኪናው ከእዳና እገዳ ነጻ ስለመሆኑ የሚያሳይ የክሊራንስ ሰነድ ማግኘት ያልቻሉ መሆኑን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2001፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 258 እና 259 ድንጋጌዎች ይዘት መሰረት ባላስረዱበት ሁኔታ አመልካች ለክሱ ኃላፊ መደረጉ ከማስረዳት ሸክም አንፃር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የሸጠውን መኪና ስመንብረት (ባለሀብትነት) ለተጠሪ ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ግዴታና ሀላፊነት ስላለመወጣቱ ተጠሪ ባለስረዱበት ሁኔታ አመልካች ስም ለማዛወር የሚያስፈልጉ ሰነዶች ያላስረከበ መሆኑን አልካደም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 197988 በ19/09/2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 137860 በ06/08/2007 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ከአመልካች ለገዛው ተሽከርካሪ ስመ ሃብት ዝውውር ያልፈፀመው አስፈላጊ ተግባር ስለመኖሩ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2273 እና 2281 ድንጋጌዎች አግባብ ተጠሪ ስላላስረዱ አመልካች ለክሱ ኃላፊ የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ለክርክሩ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 112168

የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የሺ ትራንስፖርት /የሺ ትራንስፖርት የጭነት ማመላለሺያ ባለንብረቶች ማህበር/ ደምሴ ገበየሁ

ተጠሪ፡- አቶ እስክንድር ዘርፉ - ዳዊት አባተ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 205919 በቀን 13/02/07 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 162749 በቀን 09/07/0227 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጉዳት መድረስን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁን ተጠሪ ሲሆን አመልካች 2ኛ ተከሳሽ እንዲሁም የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ትራንዚት ሎጀስቲክ አገልግሎት 1ኛ ተከሳሽ ሲሆኑ ጣልቃ ገብ የነበሩት ደግሞ ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በተከሳሾች ላይ አቅርቦት የነበረው ክስ ቶዮታ ያሪስ 998 ሲሲ.. የሻንሲ ቁጥር VNKKG96320A001372 የ2005 ምርት ዋጋ ብር 3000 ዩሮ የሆነ ከቤልጂየም ኢንትዊፕ ወደብ ኢትዮጵያ ሞጆ ደረቅ ወደብ ለሚጓጓዝ እና ለማስረከብ በሰነድ ቁጥር LAU538 ከ1ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽ ጋር ውል የገባ ቢሆንም 1ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ጋር የማንገዣ ውል የሌለው ንብረትነቱ የ2ኛ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ የሆነ የሠሌዳ ቁጥር 3-51671 ኢት/3-17327 ኢት ተሳቢ በሆነ ተሽከርካሪ ከጅቡቲ ወደ ሞጆ ደረቅ ወደብ ሲንገዝ በደረሰ የእሳት ቃጠሎ ሙሉ ለሙሉ ወድማል ስለዚህ በመኪናው የጉዞ ሰነድ ላይ የተቀነሰውን ብር 87148.50 /3000ዩሮ/፣ ለጭነት ብር 23546/1272.76 ዩ.ኤስ.ዲ/ እና ብር 3862.08፤ ለኢንሹራንስ ብር 235.60 እንዲሁም የተቀረጠ ጥቅም ብር 50000 በድምሩ ብር 164792.24 እንዲከፍሉኝ የሚል ነው፡፡ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው የኢትዮጵያ ባህር ትራንዚት ሎጀስቲክ አገልግሎት በሰጠው መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መኪና ከቤልጂየም ኢንትዋፕ ጅቡቲ ወደብ ለማድረስ በተሰማማው መሠረት ያደረሰ እና ከተጠሪ ጋር በነበረው ውል አንገዥ ሁሉንም ወይም ከፊሉን የሚንገዝ ሥራ በውለታ ለሌላ ማስተላለፍ የምንችል መሆኑ ስለተገለፀ ለ2ተኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ያስተላለፈ መሆኑን አመልካች ተረክቦ በሚንገዝ ላይ እያለ በደረሰ ቃጠሎ መኪናዋ ሙሉ ለሙሉ መውደሟን መኪናው የተገዘው በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል በመሆኑ በአዋጅ 348/44 መሠረት ኃላፊነት ያለበት አመልካች ነው ስለዚህ ክስ ሊያቀርብብን የሚያስችል መብት የለውም ኃላፊ ነው ከተባልንም ልንጠየቅ የሚገባው በዕቃው ክብደት ልክ በኤስ.ዲ.አር ወይም በጥቅል ሲሆን ይህም ብር 63900 ነው የሚሆነው እንዲሁም ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ የመድን ሽፋን የሰጡ በመሆኑ ወደ ክርክሩ ይግቡልኝ ብሏል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከከሳሽ ጋር ውል የገባው 1ኛ ተከሳሽ በመሆኑ ኃላፊነት የለብንም በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት አልደረሰም፣ መኪናው ጉዳት የደረሰበት በአመልካች መኪና ሳይሆን በደረሰ ቃጠሎ ምክንያት ነው ይህ ደግሞ ከአቅም በላይ የደረሰ ጉዳት ነው፡፡ የመኪናው ዋጋ የመድን ውል ሲገባ የተገለፀው ብር 76868.88 እያለ ተጠሪ ያቀረበው ያለአግባብ ነው፡፡ በማንገዝ የከፈለው ምንዛሬ መሠራት ያለበት መኪናውን ለመጫን በተከፈለ ቀን ነው ተጠሪ አጣሁ ያለውን ጥቅም በተመለከተም የቀረበ ማስረጃ የለም አለ ቢባልም መተካት ያለበት መድን ሠጪው ነው ብሏል፡፡ ፍርድ ቤቱም ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ አዞ መልሳቸውን በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ ጉዳት ደረሰበት ለተባለው መኪናም የመድን ሽፋን ያልሠጡ መሆናቸውን የገለጹ መሆኑን መዝግቧል፡፡ እንዲሁም የአሁን አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 256 መረት እንዲቀርብ ጠይቆ መኪናው የተቃጠለበትን ሁኔታ የሚገልፅ የፌደራል ፖሊስ የምርመራ ዘርፍ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት ለቃጠሎው መፈጠር ምክንያት የሆነው የተሽከርካሪው ተሳቢ የፊት የግራ ጐማዎች የውስጥ ጐማ በመፈንዳቱ ምክንያት ቸርኬው ከመሬት ጋር በመጋጨቱ የተፈጠረ እሳት ከተቀጣጣይ ነገሮች ጋር መያያዙ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ቀርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በአዋጅ 547/99 አንቀጽ 36 አጋዥ የማንገዝን ሥራ በአንድ ውል የሚገዛ ሆኖ በተለያዩ አንገዦች በመቀባበል የሚፈጽሙ ከሆነ የመጀመሪያው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጓጓዥ በገባው የመጓጓዣ ውል መሠረት 2ኛ አጓጓዥና ተከታዮች የመጓጓዥያ ሰነዱንና ውሉ የሚያስከትለውን ግዴታ በመቀበላቸው የተነሳ የማጓጓዥያ ውሉ ተዋዋይ ወገን ተደርገው በመቆጠሩ እያንዳንዱ አጓጓዥ በተናጠል ስለአጠቃላዩ የማጓጓዝ ስራ ኃላፊነት የሚኖርበት መሆኑ የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የነበረው የማጓጓዥያ ውል ስምምነት መሠረት ከጅቡቲ ወደብ ሞጆ ደረቅ ወደብ ድረስ የማጓጓዝ ሥራ ለአመልካች መስጠቱን በግራ ቀኙ ወይም ውልም ሆነ በህጉ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ 1ኛ ተከሳሽ መኪናውን ለአመልካች ካስረከበ በኋላ የተፈጠረ አደጋ በመሆኑ የመጨረሻ ኃላፊነት የሚወድቀው በ2ኛ ተከሳሽ ነው፡፡ አመልካች የማጓጓዝ ሥራውን በሚረከብ ጊዜ እንደውሉ አካል የሚቆጠር እና ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ከተረከበ በኋላ ለተፈጠረው አደጋ አመልካች ኃላፊ ነው በማለት የኋላፊነት መጠን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 547/99 አንቀጽ 27/3/ እና 29 መሠረት መኪናው የተገዛበት ብር 87148.5፣ የመኪናውን ማስጫኛ እና የኢንሹራንስ ክፍያ በውላቸው አንቀጽ 5/2/ መሠረት ለጭነት ብር 23546 ለኢንሹራንስ ብር 235.60 በድምሩ ብር 107930.10 እንዲሁም መኪናው የተገዛበትን ዋጋ ክስ ከቀረበበት 12/04/2005 ዓ.ም ጀምሮ 9% ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል 1ኛ ተከሳሽ እና ጣልቃ ገቦች ከክሱ በነፃ ተሰናብተዋል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለመቀበል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም መሠረታዊ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን ይዘቱም በክሱ ላይ የተገለፀሙ መኪና ጉዳት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 547/1999 አንቀጽ 10 እና 22 መሠረት ኃላፊነት የለብንም ጉዳት የደረሰበት መኪና ሙሉ በሙሉ ከነወለዱ የምንከፍል ከሆነ ጉዳት የደረሰበትን መኪና /ሰልባጁን/ እንዲመለስልን ሊወሰን ይገባ ነበር የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ እሳቱ የተፈጠረው የመኪናው የውስጥ ጉማ /ከመነዳሪ/ ፈንድቶ ቸርኬው ከመሬቱ ጋር በመጋጨቱ ምክንያት መሆኑ በባለሙያ ከመረጋገጡ አንጻር ክስተቱ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሥር የሚሸፈን መሆን አለመሆን እና ጉዳት የደረሰበትን መኪና ሙሉ ዋጋ አከፋፈል የመኪናውን ቅሪት አካል /ሰልባጅ/ ተመላሽ እንዲሆን በቃል ክርክር ወቅት ጠይቀው መታለፉን ለመመርመር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ለሰጠው መልስ አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማስረጃ የለም ከፍ/ህ/ቁ 1793 ከተዘረዘረው ምክንያት ውስጥም የሚካተት አይደለም፡፡ የደረሰው ጉዳት ለጉዞ ከመሠማራት በፊትም ሆነ በጉዞ ላይ እያለ ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ የደረሰ ጉዳት ነው፡፡ በተለይም የእሳት መከላከያና ማጥፊያ ቁሳቁስ በአጓጓዥ ተሽከርካሪ ውስጥ አለመኖር ወዲያውኑ እንዲጠፋ አላደረገም፡፡ ጉማው ሲፈነዳም በጥንቃቄ አቁሞ መቀየር ሲገባው መሄዱ ቸልተኝነቱን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተሸከርካሪ አካልን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት አልተነሳም ዳኝነትም አልተከፈለበት፣ አመልካች ይህንን ቅሪትም አላስረከበኝም ስለዚህ የስር ፍ/ቤት ይጽናልኝ ብሏል። አመልካችም የመልስ መልስ አቅርቧል።

የክርክሩ አጠቃላይ ሂደት ከለይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ፍርድ እና ያስቀርባል ከተባለው ነጥብ አንፃር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረነዋል።

የክርክሩ አጠቃላይ ሂደትም የሚያስገነዝበው ተጠሪ አንድ ቶዮታ ያሪስ 998 ሲሲ የሻንሲ ቁጥር VNKKG96320a001372 የ2005 ምርት የሆነች መኪና ከቤልጅየም ኢንትዊፕ ወደብ እስከ ኢትዮጵያ ሞጆ ደረቅ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝና ለመረከብ በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ ከነበረው ከኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ትራንዚት ሎጅስቲክ አገልግሎት ጋር ውል ገብተዋል። ይህ 1ኛ ተከሳሽ በውላቸው ላይ ሁሉንም ወይም ከፊሉን የማጓጓዝ ሥራ በውል ለሌላ ማስተላለፍ የሚችል መሆኑን በተስማሙት መሠረት ከጅቡቲ ወደብ እስከ ኢትዮጵያ ሞጆ ደረቅ ወደብ እንዲያጓጉዝ ለአሁን አመልካች ጅቡቲ ወደብ አስረክቧል። አመልካች በዚሁ መሠረት ሲያጓጉዝ የአጓዥ ተሽከርካሪ ተሳቢ የፊት የግራ ጐማዎች የውስጥ ጐማ በመፈንዳቱ ምክንያት ቸርኬው ከመሬት ጋር በመጋጨቱ በተፈጠረ እሳት መኪናው መቃጠሉ ሲሆን ይህም በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ናቸው። አመልካች አጥብቀው እየተከራከሩ ያሉት በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 547/1999 አንቀጽ 10 እና 22 ኃላፊነት የለብኝም የሚል ነው። በየብስ የዕቃ ማጋዝ ስራን ለመደንገግ ተሻሽሎ በወጣው በአዋጅ ቁጥር 547/1999 ዓ.ም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ "በማለት ምን ማለት እንደሆነ የተመለከተ ነገር ስለሌለ ትርጉሙን ለማወቅ ወደ ጠቅላላ ህጉ በተለይም ደግሞ ስለውሎች በጠቅላላ ስለሚመለከቱ ድንጋጌዎች መምራት የግድ ይሆናል። በዚህም መሠረት በፍ/ህ/ቁ 1792 ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ለማለት የሚቻለው መቼ እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን ይህም ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ኃይል ደርሷል የሚባለው ባለዕዳው ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍፁም መሰናክል በሆነበት አይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመው ጊዜ እንደሆነ ተመልክቷል። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለዕዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈጻጸም ከባድ የሆነ ወጪ በባለዕዳው የሚደርስ ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት ተልክቷል።

ስለሆነም በእነዚህ የህጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው በባለዕዳው በምንም መልኩ በቅድሚያ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የሚያስችል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስተት ሊፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለዕዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገምት ወይም ሊያስብና ጥንቃቄ ሊያደርግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገት ደራሽ ቢሆንም እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይም የሥር ፍርድ ቤቱ አመልካችን ኃላፊ ያደረገው የክሱ ምክንያት የሆነው መኪና በእሳት ቃጠሎ ምክንያት ሊወድም የቻለው የመኪናው የውስጥ ጐማ /ከመነዳሪ/ በመፈንዳቱ እና ቸርኬው ከመሬቱ ጋር ሲጋጭ ለተፈጠረ እሳት ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ይህ አጓዡ ሊገምተውና ሊያስቀረው የማይችል በመሆኑ ሁኔታው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የተፈጠረ ነው የሚል ነው፡፡ ይሁንና የተሸከርካሪው አጓዥ የሆነው አመልካች ተሸከርካሪውን በዚህ አይነት ሥራ በሚያሠማራበት ወቅት ምንም አይነት ቴክኒካዊ ችግሮች እንዳያጋጥሙ ተሸከርካሪው የሚጓዘውን ርቀት የአየር ሁኔታ ሌሎች በሚያረጋግጥበት ጊዜ ጐማውን ማየት እና ደረጃውን መገመት የሚቻለው ሲሆን በጉዞ ላይም ችግሩ በድንገት ደርሷል ቢባል እንኳን ሊቆጣጠረው የሚችል እና ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ነው ተብሎ ሊገመት የሚችል መሆኑ የፖሊስ ቴክኒካል ማስረጃን የስር ፍርድ ቤት የመዘነበት አግባብ ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት አደጋው የደረሰው የአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም የማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ ስህተት ያለበት አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ጉዳት የደረሰበትን መኪና ሙሉ ለሙሉ ከነወለዱ የምከፍል ከሆነ ጉዳት የደረሰበትን መኪና /ሰልባጁን/ እንዲመልስልኝ ሊወሰን ይገባ ነበር በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አመልካች ይህንን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤት አንስተው የተከራከሩበት ሁኔታ እንደሌለ ተጠሪ የገለፀ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት መዝገብም እንደሚያስገነዝበው አመልካች በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ ከነበረው የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ትራንዚት ሎጀስቲክ የተጠሪ ንብረት የሆነውንና ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነውን ቶዮታ ያሪስ መኪና ጅቡቲ ወደብ መረከባቸውንና ወደ ኢትዮጵያ ሞጆ ደረቅ ወደብ ሲያጓጉዙ በእሳት ሙሉ ለሙሉ መውደሙን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጉዳት ደረሰበት የተባለው መኪና በእሳት መውደሙን አሊያም በአመልካች እጅ መሆኑን የሚያመለክት ከመሆኑም ባሻገር በስር ፍ/ቤትም አልተነሳም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በህጉ በተቀመጡት ሁኔታዎች መሠረት ሊያነሳቸው የሚገቡ እና ያላነሳቸውን መከራከሪያዎች በራሱ ምክንያት ሳያቀርብ እና ተጠሪም ባልተከራከረበትና ባልተነሳ ሁኔታ በይግባኝ ወይም በዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 329/1/ እና 182/2 ድንጋጌዎች ዓላማ ጋር የማይጣጣም ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ ያቀረቡት አቤቱታ ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድ እና ትእዛዝ መሠረታዊ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 205919 በቀን 13/02/07 የሰጠው ፍርድ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 162749 በቀን 04/07/2007 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1 መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ጉዳት የደረሰበትን መኪና ለተጠሪ ስለማስረከባቸው እና የመኪናውን ቅሪት /ሰልባጅ/ አስመልክቶ ክስ ለማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ት እ ዛ ዝ

ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሰጠ ትእዛዝ የስር ፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 225335 የተጀመረው አፈጻጸም እንዲታገድ የተሠጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.99447

.ጥቅምት 26 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች:- አቶ ተፈራ ጣሰው - የቀረበ የለም

ተጠሪ:- ወ/ሮ ፈንታዬ በንቲ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በተሸከርካሪ መገልበጥ ምክንያት ከደረሰ የሞት አደጋ ጋር ተያይዞ የተነሳ የጉዳት ካሳ ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት የምዕራብ ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት ከሳሽ በመሆን ክሱን የመሰረቱት ተጠሪ ናቸው፡፡ ተጠሪ ክስ የመሰረቱት በአሁኑ አመልካችና አቶ አስማማው ደረጀ በተባሉ ግለሰብ ሲሆን ክሱም በ15/03/2003 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት ነው፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ፡- ንብረትነቱ የተከሳሾች የሆነና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-30038 አ.አ. የሆነ አይሱዚ ተሽከርካሪ በ04/05/2002 ዓ.ም. በደረሰ አደጋ በመገልበጡ ከጌዶ ወደ አዲስ አበባ ተሳፍረው ሲጓዙ በነበሩት የከሳሽ ባለቤት አቶ እንዳሉ ባይሳ ላይ የሞት አደጋ እንደደረሰ፣ ባለቤታቸው በንግድ ስራ ያገኙት ከነበረው ገቢ ከሳሽን እንዲሁም የ 4 እና የ 2 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ሁለት ልጆቹን ያስተዳድር እንደነበረ እና በሞቱ ምክንያት በመተዳደሪያ ረገድ ጉዳት እንደደረሰባቸውና በጉዳቱ ጊዜ ደግሞ ወጪ ያወጡ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ በድምሩ ብር 349,192.61(ሶስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከስልሳ አንድ ሳንቲም)፣ የጠበቃ አበል 10% እና ለክሱ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ተከሳሾች እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ 2ኛ ከሳሽ የነበረውን ግለሰብ ከተጠሪ ጋር በእርቅ በመጨረሳቸው ምክንያት ከክሱ ውጪ የሆኑ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ግን ወደ ክርክሩ ተጠርተው በሰጡት መልስ ጉዳዩ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ከነበሩት የመኪናው የጋራ ባለሃብት ጋር በእርቅ በማለቁ ክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊቀርብበት እንደማይገባ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ከአስቀደሙ በኋላ በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ሟቹ ተሸከርካሪውን ባለው ግንኙነት ለምኖ በነጻ የተሳፈረና የሄደ በመሆኑ ለጉዳቱ ኃላፊነት እንደሌለባቸው፣ የሟቹ ገቢ መጠንም ተቀባይነት እንደሌለውና የተቋረጠ ገቢ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአሁኑ አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገሩ ላይ ግራ ቀኙንና ማስረጃዎቻቸውን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን የኃላፊነቱን መጠን በተመለከተም በትክክል ሟቹ ያስገኙ የነበረው የቀን ገቢ በተጠሪ ምስክሮች እንደተገለፀው ያለመሆኑን ደምድሞ መካከለኛ ያለውን የቀን ገቢ በብር 20.00 ፍርድ ቤቱ ይዞ እና ሟች ለ15 አመታት ሊሰሩ ይችሉ ነበር በማለት በድምሩ 100,800.00(አንድ መቶ ሺህ ስምንት መቶ ብር) ለተቋረጠ ገቢ ወስዶና በአደጋው ምክንያት የወጣውን ወጪ ደግሞ ብር 6000.00(ስድስት ሺህ)፣የሞራል ካሳ ብር 1000.00 በመያዝ በድምሩ ብር 107,800.00(አንድ መቶ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ብር) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካች ለክሱ ኃላፊ መባላቸው በአግባቡ መሆኑን፣የኃላፊነት መጠንን በተመለከተ ግን በተጨባጭ ይገኝ የነበረው ገቢ የሚያስችገር መሆኑንና ተጠሪ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ከነበሩት የመኪናው የጋራ ባለሃብት ጋር ባደረጉት የእርቅ ስምምነትም ብር 14,000.00 የተከፈላቸው መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባትና በርትዕ መወሰን ተገቢ መሆኑን ገልጾ ብር 56,000.00 (ሃምሳ ስድስት ሺህ) እንዲከፈላቸው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ግንኙነት የትራንስፖርት ግንኙነት መሆኑን፣ ግንኙነቱ የትራንስፖርት ቢሆንም በዚህ ረገድ ያለው ሕግ ስለ ካሳ የሚደነግገው ሁኔታ ያለመኖሩን ጠቅሶ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095 ድንጋጌ መሰረት ካሳው መሰላት እንደአለበት፣ በዚህ አግባብ ሲሰላም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የካሳ መጠን ውሳኔ መኪናው የጋራ ባለሃብትነት የተቋቋመበት መሆኑን ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተሰጠ መሆኑን መገንዘቡን ዘርዝሮ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የተጠሪ ባለቤት የሆኑት ሟች ከአመልካች ጋር የጥቅም ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ለሞት አደጋው ኃላፊ መደረጋቸው ያላግባብ መሆኑን፣የትራንስፖርት ግንኙነት ነበር ከተባለም የካሳ መጠን በንግድ ሕጉ መወሰን ሲገባ ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሰረት አድርጎ መወሰኑ ያላግባብ መሆኑን፣ እና አደጋውን አደረሰ የተባለን መኪና አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በጋራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያፈሩት መሆኑና ይኼው የጋራ ባለሃብት ደግሞ ከተጠሪ ጋር በአደረጉት እርቅ መሰረት ብር 14,000.00 ከፍለው እያለ ክሱ መቀጠሉ ያላግባብ መሆኑን፣ ክሱ መቀጠሉ ተገቢ ነው ከተባለም አመልካች ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉት በድርሻቸው መጠን መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ውሳኔ እንዲታረምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባው ጭብጥ የስር ፍ/ቤቶች የአመልካቹን ኃላፊነት እና የኃላፊነት መጠን ለመወሰን ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካችና የስር 2ኛ ተከሳሽ የጋራ ንብረት የሆነው አይሱዙ ተሽከርካሪ ተገልብጦ በስር በተጠሪ ባለቤት ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ ምክንያት የሆነው ተሽከርካሪ የጭነት ማመላለሻ መሆኑ እና ሟችም የእህል ነጋዴ ሁነው በተሽከርካሪው ሲጓዝ የነበሩት ከመኪናው የጋራ ባለሃብቶች ጋር የጥቅም ግንኙነት ሳይኖር ስለመሆኑ በአመልካች በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የተሽከርካሪው የጋራ ባለሃብት የሆኑት የአሁኑ አመልካች ሟቹ ከእህል ንግድ ጋር ተያይዞ በነበራቸው የመጓጓዣ ውል መግባታቸውን የሚያመለክት ሲሆን የማጓጓዝ ውል ማለት አጓዥ ዋጋ በመቀበል ሰውን፣ ጓዝን እና ዕቃዎችን ከተወሰነ ስፍራ ለማድረስ ግዴታ የገባበት ስምምነት ማለት መሆኑ በን.ሕ.ቁ. 561 ተመልክቷል፡፡ የዚህ ዓይነቱን ውል የገባ አጓዥ መንገደኛው በመንገድ ላይ ስለሚደርስበት መዘግየት፣ እንዲሁም በጉዞው ጊዜ ወይም በሚሳፈርበትና ወይም በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል መጉደል ወይም የሕይወት ማለፍ ኃላፊ መሆኑ በን.ሕ.ቁ.595 የተመለከተ ሲሆን በን.ሕ.ቁ. 599 በተመለከተው መሰረት ጉዳቱ የደረሰው አጓዡ በፈጸመው ተግባር ወይም ባደረገው ጉድለትና እንዲሁም ይህ ተግባርና አደጋ ጉዳት ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑን እያወቀ በጥንቃቄ ጉድለት መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር የተጎዳው ማንኛውም ዓይነት መንገደኛ ቢሆን አጓዡ በኃላፊነት ለአንድ መንገደኛ የሚከፍለው የካሳ መጠን ከብር 40,000 እንደማይበልጥ በዚሁ ሕግ በቁጥር 597(1) ተደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ተሽከርካሪው ተገልብጦ በባለቤታቸውን እና በልጆቻቸው አባት ላይ የሞት አደጋ ማድረሱን ከመግለጽ በስተቀር ለመገልበጡ በምክንያትነት የሚጠቀስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአሽከርካሪው ወይም በተሽከርካሪው ባለቤት የተከሰተ ጥፋት፣ ቸልተኝነት ወይም የጥንቃቄ ጉድለት ስለመኖሩ የገለጹት ነገር ያለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በመሰረቱ ለደረሰው አደጋ ካሳው በንግድ ሕጉ ከተመለከተው ጣሪያ ከፍ ብሎ ሊወሰንልኝ ይገባል የሚል ከሳሽ አደጋው የደረሰው በአንገፍ ወይም የአንዙ ሰራተኛ በሆነ ሰው ጥፋት ወይም የጥንቃቄ ጉድለት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ግን አደጋው የደረሰው በአንገፍ ወይም በሰራተኛው ጥፋት ወይም ጉድለት ምክንያት ስለመሆኑ የተጠሪ የክስ ማመልከቻ አይገልጽም፡፡ ስለሆነም የአመልካችና የተጠሪ ባለቤት ግንኙነት የመንገገጥ ውልን መሰረት ያደረገ ነው ከተባለና በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ አደጋው መድረሱ እስካልተረጋገጠ ድረስ በዚህ አይነት ግንኙነት ለሚደደርሰው የሞት አደጋ የካሳ መጠን ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዛው የህግ ክፍል የተመለከቱት የካሳ አተማመን ድንጋጌዎች መሰረት ሊሆኑ የሚችሉበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡፡

የካሳው መጠን መወሰን የሚገባው በንግድ ህጉ በተመለከተው ጣሪያ ነው፡፡ቀደም ሲል በውሳኔው ላይ እንደተገለጸው በንግድ ሕጉ በቁጥር 597 ድንጋጌ መሰረት የአመልካች የኃላፊነት ጣሪያ በብር 40,000 የተገደበ ሲሆን በስር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ የነበረው ግለሰብ የመኪናው የጋራ ባለሃብት ነው፡፡ አመልካችና እኚህ ግለሰብ በመኪናው ላይ ያላቸው ድርሻ የሚበላለጥ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ በመሆኑ ሃላፊነቱ እኩል ሊካፈሉት የሚገባ ነው፡፡ የስር 2ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ጋር ያደረጉት እርቅ አመልካች ስምምነታቸውን የሰጡ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለአመልካችም ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብም የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው የካሳ መጠን ብር 20,000.00(ሃያ ሺህ) ነው፡፡

ይሁን እንጂ ተጠሪ ከአደጋው ጋር ተያይዞ ያወጡት ወጪ በማስረጃ የተረጋገጠውን ገንዘብ ብር 6000.00 ግማሹን ብር 3000.00(ሶስት ሺህ) አመልካች ለተጠሪ ሊተኩላቸው የሚገባ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለልም በአመልካች በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የመንገገጥ ውል ተብሎ ከተደመደመ በኋላ የካሳው መጠን ሊሰላ የሚገባው በንግድ ሕጉ መሰረት ሳይሆን ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ነው በማለት እና ከሳውንም በዚሁ መሰረት በማስላት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትና ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 140813 በ13/03/05 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 158714 በ26/05/2006 ዓ.ም ምክንያቱ ተለውጦ የፀናው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተሸከርካሪው የጭነት ማመላለሻ ቢሆንም ሟች ከነበራቸው የንግድ ስራ ጋር በተያያዘ የመጓጓዣ ውል ግንኙነት ከአመልካች ጋር የነበራቸው በመሆኑና የመገልበጥ አደጋ የደረሰበትም በአጓዡ ወይም በሰራተኛው ጥፋት ወይም የጥንቃቄ ጉድለት ስለመሆኑ ከሳሽ ወገን ክርክርም ሆነ ማስረጃ ያላቀረበበት በመሆኑ ለካሳ መጠን አወሳሰኑ አግባብነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ ሳይሆን የንግድ ሕጉ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በተጠሪ ባለቤት እና የልጆች አባት ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ በጉዳት ካሳ ረገድ የአመልካቹና የስር 2ኛ ተከሳሽ የኃላፊነት መጠን ጣሪያ በንግድ ሕግ በቁጥር 597(1)ድንጋጌ መሰረት ብር 40,000 ነው በማለት ወስነናል፡፡በዚህም መሰረት አመልካች ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ግማሹን ብር 20,000.00(ሃያ ሺህ ብር) ለሞት አደጋው ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ በአደጋው ምክንያት ተጠሪ ከአወጡት ወጪ ደግሞ ብር 3000.00 እንዲሁም ለሞራል ካሳ ብር 500.00 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 99124

የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካቾች ፡- 1ኛ ወ/ሮ ስብለ ማሞ } ጠበቃ እሌኒ አስራት ቀረቡ

2ኛ አቶ ዳዊት ግርማ }

ተጠሪዎች፡- 1ኛ የ፲ አለቃ ተስፋየ በዛብህ ወራሾች

1. ወ/ሮ ትግስት ተስፋየ - ቀርቧል

2. ወ/ሮ አስራት ተስፋየ -ቀርቧል

2ኛ ወ/ሮ ጥሩነሽ ሀይሉ -ወኪል ወ/ሮ ትግስት ተስፋዬ ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካቾች ከሰሾች፤ የአሁኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የስር ከሳሾች የካቲት 22 ቀን 2005ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘቱ በግራ ቀኙ ጥቅምት 30/2005ዓ/ም በተደረገው የሽያጭ ውል በኮ/ቀ/ክ/ከ/ወ/07 በተከሳሾች ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የቦታው የስፋት መጠን 105ካ/ሜ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/154/12199/00 የሆነውን ቤት በ800,000/ስምንት መቶ ሺ ብር /ሊሸጡልን የተዋዋልን ሲሆን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሰነዶች ማረጋገጫ እና መዝገብ ጽ/ቤት እስከሚረጋገጥ ድረስ በቅድሚያ 50,000/ሀምሳ ሺ ብር/ በምስክር ፊት ቆጥረን ሰጠናል፡፡ ሆኖም ተከሳሾች ከዛሬ ነገ ሲሉ እስከ ሶስት ወር ውል ያልፈፀሙ ሲሆን እንዲያውም አንደኛ ተከሳሽ የአእምሮ በሽተኛ እንደሆነ እና ውሉን በምናደርግበት ሰዓት ሁለተኛ ተከሳሽ ይህኑን ያልነገሩን ሲሆን በዚሁም ምክንያት ውሉ ተፈፃሚ መሆን እንደማይችል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለተረዳን ውሉን ማፍረሳችን እና የሰጠውን ብር 50,000/ አምሳ ሺ ብር/ ቀብድ የሰጠናቸውን እንዲመልሱልን በቀን 11/06/2005 ዓ/ም በፅሁፍ ብንጠይቃቸው ፍቃደኛ ስላልሆኑ ፍ/ቤቱ አንደኛ ተከሳሽ የአእምሮ በሽተኛ ስለሆኑ ውሉ እንዲፈርስልን እንዲሁም ቀብድ የወሰዱትን 50,000 ብር እንዲመልሱልን እና በውሉ መሰረት ስላልፈፀሙ መቀጮ 20,000 ብር እንዲከፍሉ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ እንዲተካላቸው ዳንኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በ29/08/2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰጡት መልስ በፍ/በብስ/ስ/ህ/ቁ.1810 መሰረት ውሉን የማፍረስ ስልጣን የላቸውም፡፡ 1ኛ ተከሳሽ የአእምሮ በሽተኛ አይደሉም እንጂ በሆኑ እንኳ እሳቸው ነበሩ ውሉ ይፍረስልን ብለው መጠየቅ የነበረባቸው፡፡ ከሳሾች ውሉን በፍቃዳቸው ካፈረሱት በውሉ ያስያዙት ቀብድና መቀጮ የጠየቁት ሕግን የተከተለ አይደለም፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከበቂ ወጪና ኪሳራ ጋር ክሱን ውድቅ እንዲደረግ፡፡ ይህ የሚታለፍ ከሆነ ግን በፍሬ ነገሩ ላይ የተሰጠ መልስ 1ኛ ተከሳሽ ውሉን ከተዋዋልን በኋላ ውልና ማስረጃ ሂደን ልናስመዘግብ ስንል በእድሜው የገፋ ሰው ስለሆኑ ፍ/ቤት ሄዳችሁ አጽድቁ እንዲህ አይነት ዕድሜ የገፋ ሰው ፍ/ቤት ነው የሚያፀድቀው በማለት እንዲመለስ አድርጎናል፡፡ ነገር ግን ከሳሽ የባንክ ብድር ስለሚያመልጠኝ እና ቅናሽ ቤትም ስላገኘን ቀብዱን መልሱ ብለው ጠየቁን እኛ ግን ፍ/ቤት ሄደናል፡፡ አላፈረስንም እነሱ ናቸው ያፈረሱት ስለሆነም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1885/1/2/ መሰረት ከሳሾች በውሉ መሰረት 20,000 ብር ለተከሳሾች እና 20,000 ብር ለመንግስት በአጠቃላይ 40,000 ብር መቀጮ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ በማስከፈል ክሱ ውድቅ ተብሎ እንዲወሰንላቸው በማለት መከላከያ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካከሄደ በኋላ ውሉ ያልተፈፀመው ተከሳሾች በውሉ መሰረት ለመፈፀም ጥረት እያደረጉ እያለ በከሳሽ የባንክ ብድር ያመልጠናል በሚል እና ሌላ ቤት በማግኘት ውሉን በራሳቸው ፍቃድ ሰርዘው ሌላ ቤት የገዙ መሆናቸው ነው፡፡ ውሉ ያልተፈፀመው በከሳሾች ምክንያት ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1885/1/ መሰረት ቀብድ የከፈለው ሰው በራሱ ፍቃድ ውል ከሰረዘ ቀብድውን መጠየቅ ስለማይችል ከሳሾች የከፈሉት ቀብድ ብር ተከሻሾች መክፈል የለባቸውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተፈፀመ ስሕተት የለበትም በማለት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 19 ቀን 2006 ዓ/ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ከተጠሪዎች ያደረግነው ውል በ1ኛ ተከሳሽ ፍቃድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉድለት ምክንያት ሊፈፀም አለመቻሉ በተጠሪዎች የታመነ ሁኖ እያለ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላችሁም በማለት ውሳኔ መስጠቱ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33 እና 244 ድንጋጌ የሚቃረን ውሳኔ በመሆኑ፤ 1ኛ መልስ ሰጪ የሰነዶች መረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በተደጋጋሚ ቀረበው ስለሚዋዋሉት ጉዳይ አውቀው ፍቃዳቸውን ለመስጠት ባለመቻላቸው ምክንያት የሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 በሚደነግገው መሰረት ሊመዘገብና ሊፈፀም ያልቻለ መሆኑ፤ ጥቅማችን የጎዳ በመሆኑ ውሉ እንዲሰረዝ የመጠቅ መብት ያለን ሆኖ እያለ አትጠይቁም በማለት የተሰጠ ውሳኔ በመሻር በክሳቸው መሰረት እንዲወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ግንቦት 8 ቀን 2006 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 መሰረት በፍርድ ቤት ወይም በአዋዋይ ፊት ይላል እንጂ በአንዱ ብቻ እንዲደረግ አይልም፤ ውሉ ለመፈፀም ፍቃደኛ ሳይሆኑ ውሉ አፍርሰናል የከፈልነው ቀብድ ይመለስልን ለማለት አይችሉም፤1ኛ ተዋዋይ የ፲ አለቃ ተስፋየ በዛብህ የእእምሮ በሽተኛ አይደሉም እንጂ ቢሆኑ እንኳን በእሳቸው የችሎታ አለመኖር አመልካቾች የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም፤የስር ፍርድ ቤት ቀብድ አይመለስም ሲል የሰጠው ውሳኔ ህጉን መሰረት ያደረገ ስለሆነ የሚነቀፍበት ምክንያት ስሌለ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በማጽናት እንዲሰናበቱ በመጠየቅ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረቶች ባለቤትነት ወይም ባንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የአላባ ጥቅም መብት ወይም የመያዣ ወይም የሌላ አገልግሎት መብት ለመቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉት ውሎች ሁሉ በጽሁፍና በሚገባ አካኋን በፍርድ ቤት መዘገብ ወይም ውል የመዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት መሆን እንዳለባቸው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723(1) ተደንግጓል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግ ውል በተለየ ፎርም እንዲፈፀም ግድ ከሚሆነባቸው ሁኔታዎች አንዱ የሽያጭ ውል ነው፡፡ በአመልካቾችና ተጠሪዎች መካከል የሽያጭ ውል ለማድረግ ያሰቡት ይህንኑ የህግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ውሉ ለመዋዋል ስልጣን ባለው አካል ቀረበው ለመፈፀም መሆኑን በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን በመከተል ወደ ውልና ማስረጃ ማረጋገጫና ምዝገባ ሰነዶች ተመላልሰው 1ኛ ተከሳሽ ስለሚዋዋሉት ጉዳይ ሀሰባቸውን ለመግለፅ በላመቻለቸው ውሉ ለማድረግ ያለተቻለ መሆኑን ይህም የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠሪዎች በፍርድ ቤት ሊነዋወል እየተቻለ አመልካቾች ፍቃደኛ አልሆኑም፤ፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 በአዋዋይ ፊት ብቻ አይልም በፍርድ ቤትም ሊደረግ የምችል ነው ከሁለቱ በአንዱ ሊደረግ ይችላል በማለት ያቀረቡት ተቀባይነት የለውም ምክንያቱ ህጉ ያሰቀመጠው በአመራጭ ነው፡፡ በፍርድ ቤት ወይም በአዋዋይ ፊት ሊደረግ እንደሚቻል ሲገልፅ ከሁለቱ አንዱን የመምረጥ ለተዋዋዮች የተተወ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የተመረጠው በአዋዋይ ስልጣን በላው አካል እንዲደረግ ነው፡፡ ስለዚህ በተስማሙት መሰረት ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል በመቅረብ በታሰበው መሰረት ሊፈፀም በለመቻሉ ረቂቅ ውል ከመሆን አልፎ ውል ነበረ ለማለት አይቻልም፡፡ ረቂቅ ከሆነ ደግሞ በማናቸው ሁኔታ ያሰቡትን ለመተውና የተከፈለ ገንዘብ ካለ ለማስመለስ ከመጠየቅ የሚከለክሉበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ከመሰረቱ ውል ከሌለ ከውል ጋር ተያይዥነት ያላቸው ውል እንዲሰረዝ የመጠየቅ መብት ያለው ማነው? የሚል እና ፍ/ብ/ህ/ቁ.1808 /1/2/፤1810፤1885/1/ የተመለከቱት ተያያዥ ጉዳች ሊነሱ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በረቂቅ ደረጃ በቀረ ጉደይ ላይ አግባብነት የሌላቸው የህግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ የአመልካቾች ክስ ውድቅ በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሰረትም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.30711 ሐምሌ 2 ቀን 2005ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.140449 ታህሳስ 24 ቀን 2006ዓ/ም የተሰጠ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ለአመልካቾች ብር 50,000 /አምሳ ሺ ብር/ በዚህ ችሎት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ አስከሚያልቅ ድረስ ከ9% ወለድ ጋር ይክፈሉ፡፡
3. በፍርዱ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔው ቅጂ ለፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ይላክ፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
5. መዝገብ ተዘግተዋል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጭ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 100651

መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ መንበረ ሰፈርህ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ብርሃኔ ጌቴ የኤርሚያስ ምህረት እና የትዕግስተ ምህረት ሞግዚት

2ኛ. ወ/ሮ ባንቻየሁ አዝመራ የሊዲያ ምህረት እና የውባለም ምህረት ሞግዚት

3ኛ. ወ/ሪት አዜብ ምህረት - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርምራ የተቀጠረ ሲሆን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ፍ ር ድ

ከግራ ቀኙ የቀደመ ክርክር እና በሰበር መ/ቁ.78774 ጥር 29/2005 ዓ/ም ከተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ከሚች አቶ ምህረት ታዬ ጋር በተደረገ የጋብቻ ውል የክርክሩን ንብረት የጋራ አድርገናል ቢሉም የጋብቻ ውሉ በፍርድ ቤት ያልጸደቀ በመሆኑ ምክንያት ንብረቶቹ የውርስ ሀብቶች ናቸው በሚል ለወራሾች /ለተጠሪዎች/ እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ አመልካች ከሚች ባለቤታቸው ጋር በጋብቻ አብረው ሲኖሩበት የነበረውን የመኖሪያ ቤት ተጠሪዎች የኪራይ ግምት አውጥተው ሚች ከሞቱበት ሚያዝያ 30/2000 ዓ/ም ጀምሮ እስካስረከቡበት ጊዜ ድረስ የሚታሰብ ኪራይ እንዲከፍሉ እና ንብረቱንም እንዲያስረክቡ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች ኪራይ አልከፍልም በማለት የሚከራከሩት ሚስት ነኝ በሚል ቢሆንም ሚስት የሆኑት እስከ ሚች እለተሞት ብቻ ነው ፤ ሚች ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ በንብረቱ ምንም መብትና ጥቅም ሳይኖራቸው በቤቱ መቀመጣቸው የህግ ድጋፍ የለውም ፤ በቤቱ ኪራይ መጠን ላይ ያቀረቡት ክርክርም የለም፡፡ በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2162 መሰረት ያላግባብ በቤቱ ለተጠቀሙበት በወር 600 ብር ሂሳብ ለ 4

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመት ብር 28,800 (ሃያ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ) አንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው አመልካች ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ኪራይ ሊታሰብ የሚገባ ተጠሪዎች ቤቱን ለመረከብ ከጠየቁበት ጊዜ ጀምሮ ነው ፤ ሟች ምህረት ታዬ ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ አመት ተጠሪዎች ቤቱን ለመረከብ አልጠየቁም ፤ ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ባልጠየቁበት ሁኔታ ደግሞ አመልካች በቤቱ ለተጠቀሙበት ክፈሉ ሊባሉ የሚችሉበት ሁኔታ የለም በማለት የአንድ ዓመት ጊዜ ኪራይ ብር 7,200.00 ቀንሶ ብር 21,600 (ሃያ አንድ ሺ ስድስት መቶ) እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 5/2006 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ከሟች ባለቤቴ ጋር በመሰረትነው ጋብቻ ምክንያት በጋራ ልንኖርበት በተሰማማነው መሰረት የኖርኩበተን ቤት ፤ ቤቱን ለሌላ ሰው በማከረየት ያገኘሁት ጥቅም ስለመኖሩ ማረጋገጫ ሳይቀርብ መብቴን ለማስከበር በክርክር የቆየሁበት ጊዜ ተሰልቶ ኪራይ እንድከፍል መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2162 ድንጋጌ በአግባቡ ሳይተረጎም በመሆኑና በቤቱም የኖርኩት በአሳማኝና በቂ ምክንያት በመሆኑ ኪራይ እንድከፍል የቀረበው ጥያቄ እና በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብለዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ ቤቱን እንዲያስረክቡና ለተገለገሉበት ኪራይ እንዲከፍሉ ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ክስ ማቅረባቸው የሚነቀፍ ባለመሆኑ ፤ በሟችና በአመልካች መካከል የነበረው ጋብቻ በሞት ምክንያት የፈረሰ በመሆኑ ሟች ከሞቱበት ከሚያዝያ 30/2000 ዓ/ም ጀምሮ ቤቱን ማስረከብ ሲኖርባቸው ክርክር በማቅረብ በተጠሪዎች የውርስ ሃብት ያላግባብ መጠቀም የሚገባቸው ባለመሆኑ ፤ ተገቢ ያልሆነ ክርክር በማቅረብ ፍርድ እስኪሰጥ ድረስ በውርስ ሃብት ያላግባብ መገልገል አለብኝ የሚለው ክርክርም የህግም ሆነ የፍትህ መሰረት የሌለው በመሆኑ የተገለገሉበትን ኪራይ እንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረከቡ መወሰኑ ትክክል ነው ተብሎ የሰበር አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመ/መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ የተገለጸው የጉዳዩን አመጣጥ ለማመልከት ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር እና የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ከህጉ ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ለተገለገሉበት ጊዜ ኪራይ እንዲከፍሉ በተወሰነባቸው ቤት ውስጥ ከሟች ባለቤታቸው ምህረት ታዬ ጋር ተጋብተው ይኖሩበት እንደነበር ግራ ቀኙ አላከራከረም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን ተጠሪዎች የውርስ ሃብት ነው የተባለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት አመልካች በጋብቻ ውል የጋራ የተደረገ ነው የሚል ክርክር አቅርበውበት የነበረ ሲሆን ክርክሩን በቅድሚያ የተመለከተው የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የጋራ ሃብት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ በይግባኝ እና በሰበር ሲያከራክር ቆይቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥር 29/2005 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ የጋብቻ ውሉ በፍ/ቤት ያልጸደቀ በመሆኑ ምክንያት ንብረቱ የውርስ ሃብት ነው በሚል ተወስኗል፡፡

ግራ ቀኙ በክርክር መቆየታቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ከባለቤታቸው ሞት በኋላ በቤቱ ለተጠቀሙበት ጊዜ አላግባብ ጥቅመ አግኝተዋል ተብሎ በንብረቱ በተገለገሉበት ልክ ኪራይ እንዲከፍሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2162 ተጠቅሶ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2162 እንደተደነገገው በሌላ ሰው ሀብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሃብቱ የመመለስና የመካስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከባለቤታቸው ሞት በኃላ በቀደመው መልኩ በቤቱ መገልገል መቀጠላቸው እና ቤቱ የጋብቻ የጋራ ሃብት ነው በማለት ክርክር አቅርበው በክርክራቸው መሰረት ተወስኖላቸው የነበረ መሆኑ ሁሉ ሲታይ በቤቱ የተገለገሉት በቂ ምክንያት በሌለበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በህጉ መንፈስ አላግባብ ጥቅም አገኙ የሚሰኝ ሆኖ አይታይም፡፡ ከዚህም ሌላ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2178 ይዘት መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ንብረቱ ሊያፈራ የሚችለውን የገንዘብ ግምት እንዲመልሱ ሊወሰን የሚችለው በንብረቱ ላይ አንዳች መብት እንደሌላቸው እያወቁ በእጃቸው አድርገው እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የተረጋገጡው ከላይ የተመለከተው ፍሬ ነገሮችን ይህን የሚያሳይ አይደለም፡፡ በመሆም አመልካች ያላግባብ በልጽገዋል ተብሎ ገንዘብ እንዲመልሱ እና ተጠሪዎችን እንደ ክሱ የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1ኛ. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤተ በኮ/መ/ቁ. 135467 የካቲት 7/2006 ዓ/ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የፊ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.25610 ሚያዝያ 7/2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ. አመልካች በቤቱ ለተገለገሉበት እንዲከፍሉ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

3ኛ. የስር ፍ/ቤቶች ያሳለፉት ቀሪው ፍርድ እና ውሳኔ የጸና ነው ብለናል፡፡

4ኛ. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96548

መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

አመልካች፡- የሐያት ሆስፒታል ባለቤት አቶ ኢብራሂም ናውድ ጠበቃ ፍቅሬ ሞያ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን /የህፃን ሐምራዊ ቀለሙ ሞግዚት - ጠበቃ አሰፋ አሊ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በወሊድ ወቅት በተጠሪ ሕፃን ላይ የደረሰውን የአካል ጉዳት በተመለከተ የጉዳት ካሳ ለማስከፈል የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- የስር ከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበችው ክስ ከሳሽ በ1ኛ ተከሳሽ ሆስፒታል የነፍሰጡር ምርመራ ክትትል ሳደርግ ቆይቼ፣ መጋቢት 4 ቀን 1992 ዓ/ም በ2ኛ ተከሳሽ ዶ/ር ይልማ አስረስ/ አዋላጅ ሀኪም አማካኝነት የወለድኩ ሲሆን የህፃን ሐምራዊ ቀለሙ እናት ከወሊድ በፊት በጥሩ ጤንነት ላይ የነበርኩኝ፤ በወሊድ ወቅት አዋላጅ ሐኪም በትክክለኛ የማዋለድ ሥርዓት የሙያ ግዴታቸውን መፈጸም ሲገባቸው ባለማድረጋቸው በቸልተኝነት ጉዳት የደረሰባት ልጅ እንድትወለድ አድርገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ የጡንቻዎች መስነፍ፣ የብራካ መስለል፣ የቀኝ እጅ መስነፍ እና መዘርጋት ችግር አጋጥሟታል፣ ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ላይ በወሊድ ወቅት የደረሰባት ከፍተኛ የጤና ጉዳት ችግር ለወደፊት የትምህርት እና እንቅስቃሴ ቀጣይ ሕይወቷ ላይ ቋሚ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት እና ተፅዕኖ የሚያሳድር ነው፡፡ ስለዚህ ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ወደ ውጭ አገር ሄዳ ቀዶ ጥገና ሕክምና ማድረግ እንዳለባት በባለሙያ ስለተረጋገጠ ለውጭ አገር ሕክምና እና ለልዩ ልዩ ወጪ የሚያስፈልገው ብር 410,050 ለረዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰራተኛ ለወደ ፊት ለ60 ዓመት የሚያስፈልገው በወር ብር 171.00 ለ60 ዓመት ሲደመር 5 ፐርሰንት ጭማሪ 799,923 ፀጉሯን ለማሰራት 406,511 ለተሸከርካሪ ሾፌር ደመወዝ ብር 811,391 ለወደ ፊት ለምትወልዳቸው ሶስት ልጆች ተንከባካቢ ሰራተኛ ብር 72,000 ጂምና ለፊዚዮቴራፒ እንቅስቃሴ ብር 1,611,811 በጠቅላለው ብር 4,111,686.00 /አራት ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ስድስት/ ስለሆነ እና በርትእ የሚወሰን የሞራል ካሳ እና ከሕጋዊ ወለድ ጋር ተከሳሾች በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉኝ፣ የወጪ ዝርዝር መብት እንዲጠበቅልኝ በማለት ከሳለች፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ የሥር 1ኛ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ በሰጠው መልስ፡- ከሳሽ የጉዳት ካሳ ክስ ለማቅረብ የሚችሉት ጉዳቱ በደረሰ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለሆነ የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የ1ኛ ተከሳሽ ሆስፒታል በቂ መሣሪያዎች እና አስፔሻሊስት ሀኪም በማቅረብ አገልግሎት የሚሰጥ ስለሆነ የራሱ ጥፋት የለበትም፡፡ 2ኛ ተከሳሽ በስፔሻልስት ደረጃ የተመረቁ በሙያ ስነ ምግባራቸውና ጠንቃቀነታቸው መልካም ስም ያተረፉ ናቸው፣ ከሳሽ ቅድመ ውሊድ ክትትል ተከሳሹ ጋር ነው ያደረጉት፡፡ የከሳሽ እናት ለወሊድ ስትመጣና ከወሊድ በኃላ የጤና ችግር ነበረባት፡፡ ከሳሽ ሐኪሙ ቸልተኛ ነው ከማለት ውጭ ትክክለኛ የማዋለድ ስርዓት ምን እንደሆነ አልገለፀም፡፡ የሐኪሙ የኃላፊነት መስፈርት ምን እንደሆነ በመግለጽ አላስረዱም፡፡ የሕፀኗ ችግር ወይም ጉዳት ከሳሽን ተጠያቂ ሊያደርግ አይችልም፡፡ ካሳውን ለመጠየቅ የሕክምና ቦርድ ውሳኔ አልቀረበም፡፡ ልጅቷ ሁሉንም ስራዎች መስራት የምትችል መሆኑን የከሳሽ ማስረጃ ያሳያል፡፡ የተጠየቀው ካሳም የተጋነነ እና ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ ነው፡፡ ሕፃኗ ወደ ውጭ ሄዳ የቀዶ ሕክምና ማድረግ አለባት የተባለው አይመለከተንም ከሆነም ደግሞ ህክምናውን በሕንድ አገር በአነስተኛ ወጪ ማግኘት ይቻላል በማለት ዘርዝሮ የካሳው ጥያቄ እንደማይመለከተው በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ /ዶ/ር ይልማ አስረስ መጥሪያ በጋዜጣ ተድርጎለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ እሱ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር፣ የከሳሽን የሰው ምስክሮች ቃል በመስማት፣ የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመመዘን በሰጠው ውሳኔ፣ የከሳሽ ህፃን በ1ኛ ተከሳሽ ሆስፒታል እና በ2ኛ ተከሳሽ አዋላጅነት ስትወለድ በወሊድ ወቅት የ"ፎርሲፕስ" መሳሪያ በመጠቀም እንዲወልዱ በማድረጉ በህፃኗ የቀኝ እጅ ጡንቻ ስንፈት እንደተከሰተ በሽታውም የብራቪያስ ነርቭ መጎዳት ሲሆን ይህ በሽታ ሊከሰት የቻለው በወሊድ ጊዜ በደረሰ ጉዳት እንደሆነ የቀረበው ማስረጃ ያስገነዝባል፡፡ ተከሳሽ ይህን ማስረጃ በማስተባበል በገባው የወሊድ ውል መሠረት ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን አላስረዳም፡፡ 2ኛ ተከሳሽም ያለውን የሙያ ብቃት ተጠቅሞ ከሳሽ ያለ ምንም እንከን የማወለድ ስራቸውን የሰሩ መሆኑን አያመለክትም፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ የገባውን የማዋለድ ግዴታውን ሊወጣ ባለመቻሉ በከሳሽ ላይ ለደረሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳት በፍ/ብ/ህ/ቁ.1790 /1/ መሰረት ኃላፊነት አለበት፡፡ 2ኛ ተከሳሽም ሥራቸውን ሲሰሩ የወሰዱትን እርምጃ የተከተሉትን ፕሮሲጀር ያልማዘገበ ሲሆን ከሕፃኗ ትልቅነት የተነሳ 2ኛ ተከሳሽ ከፎርሲፕስ የማዋለጃ መሳሪያ ይልቅ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም እንደነበረበት እንደሚያስገድዱ ያመለክታል፡፡ ይህን መሳሪያ ለመጠቀም የታካሚዋን ፍላጎች መጠየቅ ሲገባው የህን አላደረገም፡፡ ስለዚህ 2ኛ ተከሳሽ በሙያቸው ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄ ማድረግ ባለመቻላቸው የደረሰ ጉዳት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2028 እና 2031 መሰረት ኃላፊነት አለባቸው በማለት ወስኗል፡፡ የካሳውን መጠን በተመለከተ የጥቁር አንበሳ እስፔሻሊሽት ሆስፒታል በሰጠው ማስረጃ ከጠቅላለ የሰውነት ክፍሉ 55 ፐርሰንት አከባቢ መሆኑን ስላራጋገጠ የመዕከላዊ ስታትስቲክስ በጻፈው ዳብዳቤ በአዲስ አበባ የተወለደች የአንድ ሴት ልጅ አማካይ ዕድሜ 68.9 ዓመት እንደሆነ ገልጿል፡፡ ሕፃኑ ለወደ ፊት የመኖር ዕድሜዋ 59.1 ዓመት ነው፡፡ ከሳሽ በሁለት እጅ የሚሰሩትን ስራዎች መሥራት እንደማትችል ተረጋግጧል፡፡ በርካታ ሥራዎች ራሷን ችላ መስራት አትችልም፡፡ ስለዚህ ተከሳሾች በአንድነትና በነጣለ ከሳሽ ረዳት ሰራተኛ ለመቅጠር የሚያስፈልገውን ብር 689,049.32 ከሳሽ ውጭ አገር ሄዳ ለመታከም የሚያስፈልጋት ወጪ ብር 346,250፣ ከሳሽ ለጅምና ለፊዚዮትራፒ እና ለሰውነት እንቅስቃሴ የሚያስልጋት ወጪ ብር 1,453,035.17 የሞራል ካሳ ብር 1000 በአጠቃላይ 2,489,334.49 የጉዳት ካሳ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ከታህሳስ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9 ፐርሰንት ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሏት በማለት ወስኗል፡፡ ወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብትም ጠብቋል፡፡ ከሳሽ ለፀጉር ማስሪያ ለሾፌር ደመወዝ ለወደፊት እወልዳለሁ ላለቻቸው ልጆች ለእንክብካቤ ያስፈልጋል በማለት የጠየቀችውን ወጪ በተመለከተ ፍ/ቤቱ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ምክንያቱን በመግለጽ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን የሚያስለውጥ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት አላገኘንም በማለት አጽንቷል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በ06/05/2006 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ተጠሪ ሐኪሙ የፈፀመውን ቸልተኝነት የማስረዳት ኃላፊነት እያለባት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጉዳቱ የመጣው በተፈጥሮ መሆኑን ሐኪሙ ስህተት አለመፈጸሙን አመልካችም ሆነ ሐኪሙ አላስረዳም በማለት የማስረዳት ሸክሙን ማዞሩ የህግ አግባብ የለውም ። የሕክምና ታሪክ አለመመዝገብ ለተጠሪ ወሊዱ ችግር ያለበት መሆኑን አለማስረዳት በፎርሲፕርስ ለመውለድ የተጠሪን ፈቃደኝነት አለመጠየቅ በሕይወት ማዳን ጥድፊያ ጊዜ ሊታለፍ የሚችሉ ሲሆን ስህተት የሚሆኑት ጥድፊያ የሌለ መሆኑን ማስረዳት ሲቻል ነው ። በአሁኑ ሁኔታ ተጠሪ የመውለድ ሁኔታ ጥድፊያ ውስጥ ስለገባች ሐኪሙ ተገቢውን ወስኖ የሙያ ግዴታውን መወጣቱ በቸልተኝነት /ስህተት/ መኖሩን አያመለክትም፡፡ አመልካች በበኩሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጠራቸውን ሐኪሞች ምስክርነት የተወው የባለሙያ ምስክር በየትኛውም ወገን ቢቀርብ የሚመዘነው በመዕከላዊነት እና የባለሙያ ምስክር ለማስተባበል ሌላ የባለሙያ ምስክር አይቀርብም በሚል መርህ ነው፡፤ አመልካች ግን ተጨማሪ የባለሙያ ምስክር ከኢትዮጵያ የማህጸንና ፅንስ ባለሙያዎች ማህበር እንዲቀርብለት የጠየቀው ማስረጃ አለመቅረቡ አለአግባብ ስለሆነ ሊቀርብልን ይገባል ። ተጠሪ በእንግሊዝ ሀገር በግል ሆስፒታል ውስጥ ከሚሰሩት የሕክምና ባለሙያ የተገኘ የሕክምና ዋጋ ተመን የእንግሊዝ ፓውንድ 9625 ከኢንተርኔት የተወሰደ የላኪው ማንነት የማይታወቅ ስለሆነ እንደማስረጃ ሊወሰድ አይገባም በማለት አመልካች ቢከራከርም ተቀባይነት አላገኘም። ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ሰነድ የሰነድ ማስረጃ ከሚታወቅ ተቋም መቅረብ አለበት። በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ገብቶ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት መመዝገብ አለበት። ይህ ሰበር ችሎትም በመዝ.ቁ .32282 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል። ስለሆነም ይህን የማይታወቅ የጉዳት ተመን እንደማስረጃ አድርጎ ወስዶ ውሳኔ መስጠት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት አመልክቷል።

ይህ ሰበር ችሎት መዝገቡን በመመርመር ህፃን ሐምራዊ ቀለሙ በወሊድ ጊዜ የደረሰባት ጉዳት በቸልተኝነት ለመፈጸሙ የቀረበ ሙያዊ ማስረጃ ሳይኖር የኃላፊነት ውሳኔ በስር ፍ/ቤቶች ተሰጥቷል። ይህ ቢታለፍ የካሳ መጠኑን በተመለከተ የቀረበ ተጨማሪ ማስረጃ ሳይኖር በኢንተርኔት የተገኘን መረጃ መሰረት በማድረግ ወሳኔ የመሰጠቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት የካቲት 03 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ቀርቧል ። የመልሱም ይዘት ፡- የቀረበው ክርክር የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ጉዳይ ስለሆነ የዚህ ችሎት ስልጣን ስላልሆነ ሊስተናገድ አይገባም። የተጠሪን የማስረዳት ሸክምን በተመለከተ 1ኛ በሀኪሙ በኩል ግዴታ የነበረ መሆኑን፣ 2ኛ ሐኪሙ በውል ግንኙነት ሊፈጽም የሚገባውን ታካሚዋን የማዋለድ አገልግሎት ወይም እናት እና የልጅን በሰላምና በጤንነት የማለያየት ስራ አለመፈፀሙን 3ኛ የውል ግዴታውን ሙያው በሚጠይቀው ክህሎት ጥንቃቄና በተገቢው ሁኔታ ባለመፈፀሙ በህፃኗ ላይ የብራክያስ ነርቭ መጎዳት/የቀኝ ጡንቻ ሰንፈት /ጉዳት የደረሰባት መሆኑ ይህም በወሊድ ጊዜ ከውጭ በኃይል ጉተታ በደረሰ ጉዳት መሆኑን በተጠሪ በኩል በ12 ስፔሻሊስት ዶክተሮች ምስክርነት ፣በራሱ በአመልካች የተሰጡ የሰነድ ማስረጃዎች ፣ በአለርት ሆስፒታል፣ በቤተል ቲቺንግ ሆስፒታል በድንበሯ ሆስፒታል ፣ በኢንተርሜዲካል ዲያግኖስቲክ እና ኢሜጂንግ ማዕከል፣ በጥቁር አንበሳ የሐኪሞች ቦርድ፣ የተጎጂዋ የምስክርነት ቃል ጉዳቱንም ቀርባ ለፍ/ቤት አሳይታ በእናቷ እና በአባቷ የምስክርነት ቃል ያስረዳች ሲሆን በአመልካች በኩል አንዳችም የማስተባበያ መከላከያ ማስረጃ አልቀረበም። ከውጭ አገር የመጣውን አስፈላጊ የሆነውን የሕክምና ወጪን የሚያስረዳውን የሰነድ ማስረጃ በተመለከተ አመልካች በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት አልተመዘገበም፣በማስረጃነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊታይ አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር በስር ፍ/ቤት ፊዕሞ ያልተነሳ ጉዳይ ስለ ሆነ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊነሳ አይችልም። ታካሚዋ በወሊድ ወቅት ችግር ያለበት ወሊድ ምልክቶች/ Risk factors/ መኖራቸው ከታወቀ ባለሙያ ሐኪሙ በፎርሴፕስ /የብረት መጎተቻ መሣሪያ/ ተጠቅሞ ፅንሱን በኃይል ከመጎተት ሌሎች ጥንቃቄ የሚፈልጉ የሙያ ወሳኔዎችን መስጠት ነበረባቸው ፣ በነበረው ሁኔታ ግፊ ማለት አልነበረባቸውም ፣ በፎርሲፕስ መጎተት አልነበረባቸውም። ፎርሴፕስና ምጥ የሚያፋፍም መድኃኒት መጠቀም አልነበረባቸውም ። የሥር 2ኛ ተከሳሽ ይህን ሁኔታ በመገንዘብ ሌሎች አማራጭ ዘዴዎችን መጠቀም ነበረበት። ይህ ደግሞ የሐኪሙ ጥፋት መሆኑን ያመለክታል። የተጠሪ የባሙያ ምስክሮች ሁሉም እንዳስረዱት ሐኪሙ የታካሚዋ ካርድ ሪኮርድ አልተሞላም ፣ የተመዘገበ ነገር አልተገኘም። ይህ ደግሞ ስህተት መሆኑን መስክሯል። ስለዚህ ተጠሪ አመልካችን ጨምሮ የስር ተከሳሾች ህፃኗ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት እንዳለባቸው በበቂ ማስረጃ ያረጋገጠች ስለሆነ አመልካች በማስረጃ ያስተባበለው ነገር ስለሌለ የሥር ፍ/ቤቶች የጉዳት ካሳውን እንዲከፍሉ የሰጡት ውሳኔ የማስረጃ ስህተትም ሆነ የሕግ መሰረት ስለሌለ የቀረበው አቤቱታ ፍሬ ነገር እና የማስረጃ ክርክር ስለሆነ ውድቅ ተደርጎ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍል እንዲወሰንበት በማለት ተከራክረዋል። አመልካች መጋቢት 01 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተ ሲሆን ፣ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል። መዝገቡን እንደመረመርነው ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን ከወሊድ በፊት የቅድመ ወሊድ ክትትል አመልካች ሆስፒታል ዘንድ ስታደርግ እንደነበር ግራ ቀኙ አልተካካዱም ።ይህ ማለት ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን የተሻለ የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ሲባል አመልካች ዘንድ ቅድመ ወሊድ ክትትል ስታደርግ እንደነበር እና በወሊድ ወቅት ተገቢውን ሕክምና በማግኘት በሰላም ፣ጤናማ ልጅ ለመውለድ ሲባል እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም። አመልካች ደግሞ በሚያቀርበው ባለሙያዎች እና የሕክምና መሳሪያዎችን ተጠቅሞ በገባው ውል መሠረት ግዴታውን በሚገባ መወጣት ይጠበቅበታል። ከዚህ አንፃር የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2639፣2641፣2642 መመልከት ይቻላል። አመልካች ያለውን የሕክምና መሳሪያዎች እና ባለሙያዎችን አቀናጅቶ በወሊድ ወቅት እናትና ልጅን የመለያየት ስራ የሙያው ግዴታ በመወጣት እናትና ልጅን በሰላም እና በሙሉ ጤንነት ማለያየት አለበት። አመልካች ለሕክምና አገልገሎት የሚያስፈልገውን መሳሪያዎች ማቅረቡ ብቻ በቂ አይደለም ነገር ግን እንዚህን መሳሪያዎችን በመጠቀም ባለሙያው ያለውን እውቀትና ክህሎት ተጠቅሞ የማዋለድ ውሉ የሚጥልበትን ግዴታ መፈፀም አለበት። አመልካች ለሕክምናው የሚያስፈልገውን መሳሪያዎች ቢያቀርብም እንኳን የሥር 2ኛ ተከሳሽ እነዚህ መሳሪያዎችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጠቀም የሕክምና ሙያው የሚጠይቀውን ሄደት በመጠበቅ ተጠሪን በሙሉ ጤንነት ካላዋለደ ከተጠያቂነት የሚያመልጥበት ሁኔታ የለም የአመልካች ተቀጣሪ ሰራተኛ የሆነው የሥር 2ኛ ተከሳሽ የሙያ ሰነ-ምግባሩ የሚጠይቀውን ሁሉ በመፈፀም እውቀቱን እና ክህሎቱን በመጠቀም ከአንድ አዋላጅ ሐኪም የሚጠበቀውን ሁሉ ያደረገ እንደሆነ እና ከዚህ ውጭ በሆነ ሰምሳሌ በተፈጥሮ ችግር ምክንያት በእናትም ሆነ በተወለደች ሕፃን ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ አመልካችንም ሆነ የሥር 2ኛ ተከሳሽን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል ። አመልካችም ሆነ የሥር 2ኛ ተከሳሽ ከተጠያቂነት ነፃ ለለመሆን 2ኛ ተከሳሽ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ሙያው በሚጠይቀው መሰረት የፈፀመ መሆኑን አግባብነት ባለው ማስረጃ ያስረዱ እንደሆነ ብቻ ነው። አመልካች የሕክምና አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት ሐኪሙ የሚጠበቅበትን ግዴታ መወጣቱን በቅድሚያ የማስረዳት ግዴታ/ሸክም የእርሱ ነው። አመልካች የሱ ተቀጣሪ ባለሙያ የሕክምና ሙያው በሚጠይቀው መሠረት ምንም ስህተት ፣ጥፋት፣ ቸልተኝነት ሳይኖር ስራውን መስራቱን በቅድሚያ የማስረዳት ግዴታ አለበት። ምክንያቱም የሕክምና አገልግሎት ውሉን በገባ ጊዜ በወሊድ ወቅት እናትና ልጅን በሰላምና በሙሉ ጤንነት ለመለያየት ግዴታ ስለገባ ነው ታካሚዋ በሕክምና ወቅት ጉዳት የደረሰባት እንደሆነ የሕክምና አገልግሎት ሰጭውን ተቋም እና ሐኪሙ ለደረሰባት ጉዳት ተጠያቂ ናቸው በማለት በኃላፊነት የመጠየቅ መብት አላት። ይህን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2647 /2/ እና 2651 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል አመልካችም ሆነ ሐኪሙ ደግሞ በወሊድ ወቅት ምንም አይነት ስህተትም ሆነ ቸልተኝነት አለመፈፀሙን በተሻለ ማስረጃ የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው ። ከዚህ በኋላ ታካሚዋ የአመልካች ሐኪም ጥፋት የፈፀመ መሆኑን በማስረጃ የማስተባበል፣ በማስረጃ የማስረዳት ሸክም አለባት።

በዚህ አግባብ አሁን የተያዘው ጉዳይ ሲታይ ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን ተጠሪን በወለደች ወቅት ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ጉዳት እንደደረሰባት አመልካችም አልካደም። ከዚህም በላይ አመልካች የሰጠው ማስረጃን ጨምሮ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ በወሊድ ወቅት አካላዊ ጉዳት የደረሰባት መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው ።አመልካች በካርድ ው.12058 በ22/03/2000 ዓ.ም በፃፈው ሰነድ ሐምራዊ ቀለሙ ስትወለድ ክብደቷ 4.3 ኪ.ግ እንደሆነች፣የቀኝ እጅ ክንድ መስነፍ፣ የብራኪ መስለል የነበረባት እንደሆነ፣ የብራሺ.ጋያል ፓልሲ የሚባል የነርቭ በሽታ እንዳለባት እና ይህ በሽታ በወሊድ ጊዜ በደረሰ ጉዳት የተከሰተ መሆኑን ፣ሕፃኗ የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳለባት ያመለክታል ። ሌላው ከአለርት አገር አቀፍ ሪፈራል ማዕከል ፣ ኦፕሬሽናል ቴራፒ ምርመራ አገልግሎት ማስረጃ ድንበሯ የእናቶችን ሕፃናት ሆስፒታል ፣ኢንተርሜዲካ ዲያግኖስቲክ እና ኢሜጂንግ ማዕከል ፣ቤተል ቲቺንግ አጠቃላይ ሆስፒታል ፣ከፕሪንሰስ ግሬስ ሆስፒታል የቀረቡ ማስረጃዎች ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ በወሊድ ወቅት በደረሰባት ጉዳት በክሱ ላይ የተጠቀሰው የአካል ጉዳት የደረሰባት መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሚያረጋግጥ የሥር ፍ/ቤቶች አመለክቷል፡፡ የተጠሪ የሰው ምስክሮችም በሰጡት የምስክርነት ቃል ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ የተባለው ጉዳት የደረሰባት እንደሆነ መመስከራቸውን የሥር ፍ/ቤቶች መዝገብ ያመለክታል፡፡

የሰው ምስክሮች እንዳመለከቱት 2ኛ ተከሳሽ ዶ/ር ይልማ አስረስ ወ/ሮ አስቴርን ሲያዋልዱ የተከተሉትን ፕሮሲጀር እና የወሰዱትን እርምጃዎችና አማራጮችን አለመመዝገቡን መመስከራቸው የሥር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ ይህም በመንግስት ሆስፒታል ለምሳሌ እንደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል እንኳን ሙሉ ለሙሉ እንደማይተገበር ምስክሮች ገልፀው፣ይህ ማለት ግን ይህን አለመመዝገብ ትክክል ነው ማለት እንዳሆነ አስረድተዋል ፡፡ ይህ ደግሞ የአመልካች ባለሙያ የነበረው አዋላጅ ሐኪም /የሥር 2ኛ ተከሳሽ / ሙያው በሚጠይቀው መሰረት ተጠሪን ሲያክም ለምን የተወሰደውን አማራጭ ሊወሰድ እንደቻለ አለመመዝገቡ በራሱ ጥፋት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሐኪሙ ይህን ባለመመዝገቡ የወሰዳቸው እርምጃዎች/ አማራጮች ልክ ነበሩ ለማለት የሚያስችል ነገር የለም ሐኪሙ /የሥር 2ኛ ተከሳሽ/ ለምን ምጥ የሚያፋፍም መድኃኒት እና ፎርሲፕስ መሳሪያ ተጠቅሞ ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙን በመጎተት እንድትወለድ እንዳደረገ ምንም የሚያመላክት ነገር የለም ፡፡ የአመልካች ባለሙያ ይህን የታካሚዋን ታርክ በአግባቡ ባለመመዝገቡ አመልካች አሁን ላይ ቆሞ ባለሙያው ያን ጊዜ የወሰደውን እርምጃ ልክ ነው በማለት በማስረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ የክርክሩ ሄደት አያሳይም ይህ በእንዲህ እንዳለ አመልካች በበኩሉ 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙን በምትወልድበት ወቅት የወሰደው እርምጃ ትክክል እንደነበረ ህፃኗ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ከሐኪሙ ጥፋት ጋር የማይገናኝ እና ምንም አይነት ቸልተኝነት እንደሌለበት ለማስረዳት ምንም አይነት ማስረጃ አለመቀረቡን እሱም አይክድም የስር ፍ/ቤቶችም ይህንን በሚገባ አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች የሥር 2ኛ ተከሳሽ እናትና ልጅን በሙሉ ጤንነት እንዳለያየ ምንም አይነት ማስረጃ ባለቀረበበት በውሉ መሰረት ግዴታውን እንደተወጣ አስመሰሉ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ አመልካች ተቀጣሪ ሐኪሙ /የሥር 2ኛ ተከሳሽ/ ሙያው በሚያዘው መሰረት ታካሚዋን በሚያዋልድበት ወቅት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ሳይመዘግብ ሲቀር ተከታትሎ ማስተካከል ሲገባው አሁን ባለሙያው ይህን አለማድረጉ እንደጥፋት አይቆጠርም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው መልስ የሰው ማስረጃ ዝርዝር ስር የኢትዮጵያ የማህጸንና የፅንስ ባለሙያዎች ማህበር እንደማስረጃ የጠቀሰ ሲሆን፣ የሰው ማስረጃ ማሰማት አልፈልግም በማለት የሥር ፍ/ቤት እንዲያልፍ ካደረገ በኋላ ፣ይህ ማስረጃ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክርም የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል መርህን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች እና ሐኪሙ ዶ/ር ይልማ አስረስ የሚጠበቅባቸውን የውል ግዴታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለመወጣታቸው በሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ኃላፊነት ስላለበት የጉዳትካሳም ለመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1790፣2028፣2031፣2647 /2/ እና 2651/ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

የካሳውን መጠን አወሳሰን ስንመለከተም ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ሁለት እጆቿን በመጠቀም ሁሉንም ስራ መስራት እንደማትችል የተጠሪ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ማረጋገጣቸውን የሥር ፍ/ቤቶች መዝግቧል፡፡ በዚህ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች ለሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ አጋዥ ሰው እንደሚያስፈልጋት በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጠል ፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ በተለያዩ ስራዎች ሕፃኗን የሚያግዝ ሰው በነጻ ያለ ክፍያ ማግኘት ይቻላል ተብሎ ስለማይገመት ክፍያ እንደሚያስፈልግ የሚያከራክር አይሆንም ፡፡ ነገር ግን ሕፃኗ ለመስራት ለማትችላቸው ስራዎች ስራተኛ ቀጥሮ ለማሰራት ለወደ ፊቱ በየወሩ እና በየአመቱ ይህን ያህል ገንዘብ ይከፈላል ለማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2102 መሰረት ዳኞች በርትዕ የካሳን መጠን የመወሰን ስለጣን እንዳለቸው ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ ይህ ችሎት እንደተገነዘበው ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ለወደ ፊቱ ሕይወቷን ምቹ ለማድረግ መሥራት የማትችላቸውን ሥራዎች የሚያግዛትን ሰራተኛ ለመቅጠር ለረዳት ሰራተኛ በርትዕ ብር 300,000 /ስስት መቶ ሺህ ብር /ያስፈልጋታል ብለናል፡፡ ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ በደረሰባት ጉዳት ምክንያት ጤንነቷን በመልካም ሁኔታ ለመጠበቅ የአካ እንቅስቃሴ፣ ጂምና ፊዚዮትራፒ እንደሚያስፈልጋት በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህም ደግሞ ለወደፊቱ በሳምንት ፣በወር ይህን ያህል ገንዘብ ያስፈልጋል ለማለት የሚያስችግር ስለሆነ በርትዕ ግን ለመወሰን እንደሚቻል ሕጉ ይፈቅዳል፡፡ በዚህም መሠረት ሕፃኗ ለወደ ፊት ጂምና ፊዚዮትራፒ የሰውነት እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስፈልጋት ወጪ በርትዕ ብር 500,000/አምስት መቶ ሺህ/ ሊከፈላት ይገባል ብለናል፡፡

ሌላው ሕፃን ሐምዊ ቀለሙ ለደረሰባት የአካል ጉዳት ወደ ውጭ አገር ሄዳ ጥገና ሕክምና ማድረግ እንዳለባት እና ለዚህም ወደ እንግሊዝ አገር ሄዳ ለመታከም በአጠቃላይ ብር 346,250 /ሶስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ / ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጡትን ውሳኔ በተመለከተ አመልካች ባቀረበው ተቃውሞ ፣ይህ ማስረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ገብቶ በውልና ማስረጃ ስላልተመዘገበ እንደማስረጃ መወሰድ አልነበረበትም የሚል ነው፡፡ ነገር ግን አመልካች ሚያዝያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው መልስ ይህን ማስረጃ በተመለከተ ያቀረበው ክርክር ቢኖር ሕንድ አገር ተመሳሳይ አገልግሎት በአፖሎ ሆስፒታል በጣም አነስተኛ በሆነ ወጪ ለማግኘት እንደሚቻል ለመጠቆም እንወዳለን የሚል ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ከዚህ ውጭ የአቀረበው ማሰረጃ ተቀባይነት የለውም በማለት አሁን የሚያነሳውን ክርክር በሥር ፍ/ቤት በማንሳት የተከራከረው ነገር ባመኖሩ በዚህ ሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት ይህን ማስረጃ በተመለከተ ያቀረበው አዲስ ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329 /1/ መሰረት ተቀባይነት የለውም ። ይህ በመሆኑ የሥ/ፍ/ቤቶች ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ወደ ውጭ አገር ሄዳ ለመታከም የሚያስፈልጋት ወጪ የወሰኑት ገንዘብ በምንም መልኩ የተጋነነ አይደለም ብለናል፤ ስለዚህ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤቶች የካሳ መጠን በተመለከተ የሰጡትን ውሳኔ ብቻ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መሰረት በማሻሻል በአብላጫ ድምፅ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.90681 መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.89303 በ30/03/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የካሳ መጠንን በተመለከተ ብቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት በድምፅ ብልጫ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች እና የሥር 2ኛ ተከሳሽ በሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ላይ በወሊድ ወቅት ለደረሰባት የአካል ጉዳት ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፣ በአንድነትና በነጠላ በፍርድ ሐተታው ውስጥ በዝርዝር እንደተመለከተው በአጠቃለይ ብር 1,147,250.00/አንድ ሚሊዬን አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር/ የጉዳት ካሳ ለተጠሪ ሊከፍላት ይገባል ብለናል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ለደረሰባቸው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ ዕግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
6. የሥር ፍ/ቤት መዝገብ እንደመጣ ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የልዩነት ሀሳብ</u>

ህጻኗ የቀኝ እጅ የነርቭ መስነፍ ጉዳት የደረሰባት መሆኑ፤ ጉዳቱም የደረሰው በወሊድ ጊዜ መሆኑ እና የደረሰውም የስር 2ኛ ተከሳሽ ፎርሴፕስ (forceps) በተባለ የማወለጃ መሳሪያ ተጠቅመው የህፃኗን እናት ባዋለዱበት ጊዜ መሆኑ የልተካዱ እና የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ ተጠሪዋ ካሰሟቸው ምስክሮች መካከል ከፊሎቹ በማወለድ የህክምና ሙያ ልዩ ዕውቀት ያላቸው የህክምና ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ሆስፒታል ውስጥ ይሰሩ የነበሩት የስር 2ኛ ተከሳሽ የማዋለድ ተግባሩን ባከናወኑበት ጊዜ ሆን ብለው ወይም በቸልተኝነት የሙያ ግድፈት ወይም ጥፋት በመፈጸማቸው ምክንያት ስለመሆኑ ከእነዚህ ባለሙያዎች መካከል አንዳቸውም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አረጋግጠው ያልመሰከሩ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ በግልጽ ያመለክታል። የባለሙያዎች የምስክርነት ቃል ይዘት የማዋለድ ተግባሩ በፎርሴፕስ መሳሪያ በሚከናወንበት ጊዜ በሚወለዱት ህጻናት ላይ አሁን መከሰቱ የተረጋገጠው ዓይነት ጉዳት ሊደርስ የሚችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ከመሆኑ በቀር የስር 2ኛ ተከሳሽ የማዋለድ ተግባሩን በፎርሴፕስ ባከናወኑበት ጊዜ አሁን የተከሰተው ጉዳት እንዳይከሰት ማድረግ ይችሉ የነበረ ስለመሆኑ ወይም በሌላ አነጋገር ጉዳቱ የተከሰተው በሙያ ግድፈት ምክንያት ስለመሆኑ የሚያመለክት አይደለም። በፎርሴፕስ መሳሪያ ማዋለድ ያልተፈቀደ ተግባር ስለመሆኑም አልተገለጸም።

በባለሙያዎች የተሰጠው ምስክርነት የማዋለጃ ስርዓቱን ወይም መሳሪያውን የመምረጥ እና የመወሰን ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ለአዋላጅ ሐኪሙ የተተወ መሆኑን እና የስር 2ኛ ተከሳሽ የተመሰከረላቸው ብቁ ባለሙያ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። በርግጥ ምስክሮቹ አዋላጅ ሐኪሙ በዘርፉ ከሚታወቁት የማዋለድ ስርዓቶች ወይም ዘዴዎች መካከል አንዱን ወይም ሌላኛውን የመረጠበትን ምክንያት በሕክምና ካርዱ ላይ ከተቻለ በማዋለዱ ሂደት የሁኔታዎች አጣዳፊነት ካላስቻለውም የማዋለዱ ተግባር ከተጠናቀቀ በኃላ መመዝገብ እንደሚገባው የሙያው ስነ ምግባር የሚያዝ መሆኑን ሐኪሙ እንደኛውን ወይም ሌላኛውን የማዋለድ ዘዴ የተጠቀመባቸውን ነባራዊ ሁኔታዎች መገንዘብ እና ተገቢ ስለመሆን አለመሆኑ ሙያዊ አስያየት መስጠት የሚቻለው ከዚህ ዓይነቱ ምዝገባ መሆኑን እና በተያዘው ጉዳይ ግን ሐኪሙ ምዝገባውን ስላላከናወኑ በፎርሴፕስ የማዋለጃ መሳሪያ መጠቀማቸው ስህተት ነበር ወይስ አልነበረም የሚል አስተያየት ለመስጠት የማይችሉ መሆናቸውን ገልጸው መስክረዋል። የስር 2ኛ ተከሳሽ ምዘገባውን አላከናወኑም መባሉ በህጻኗ ላይ መድረሱ ከተረጋገጠው ጉዳት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ ዓይነቱ የመመዝገብ ሁኔታ የመንግስት ትላልቅ ሆስፒታሎችን ጨምሮ በአገሪቱ ውስጥ ያልተለመደ እና የማይተገበር መሆኑን እና እራሳቸውም ቢሆኑ በሙያው ላይ በቆዩባቸው በበርካታ ዓመታት የሙያው ስነ ምግባር የሚጠይቀው ነው ያሉትን መረጃዎችን መዝግቦ የመያዝ ሁኔታ ተግባራዊ አድርገው የማያውቁ መሆኑን ጭምር እነዚሁ የተጠሪ ምስክሮች ገልጸዋል። በመሠረቱ የአንድን ሙያ ስነ ምግባር በሙያው ላይ የተሰማራ አንድ ሰው ሙያውን በቀሰመበት ቆይታ ሊያገኘው ይችላል። ይህ በትምህርት ቆይታ የተገኘ ነው የሚባለው የሙያ ስነ ምግባር የፍትሐብሔር ኃላፊነትን ለማስከተል በሚያስችል ሁኔታ ተጥሶአል ለማለት የሚቻለው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2031 (1) አነጋገር መሰረት **የሙያ ስራው የሚመራበት ደንብ** ወይም በፍትሕብሔር ሕግ ቁጥር 2647 (1) አነጋገር መሠረት **የሙያው የኪነ ጥበብ ደንብ** መሆኑ ሲረጋገጥ መሆን ይኖርበታል። በተያዘው ጉዳይ የመመዝገቡ ሁኔታ በአገሪቱ ውስጥ ያልተለመደ እና የማይተገበር መሆኑ በተጠሪዋ ምስክሮች የተገለጸ እስከሆነ ድረስ የምዝገባው ሁኔታ የሙያ ስራው የሚመራበት ደንብ ወይም የሙያው የኪነ ጥበብ ደንብ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻል ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በመሆኑም ውሳኔው ተሸሮ አንድ አዋላጅ ሐኪም በዘርፉ ከተፈቀዱት የማዋለድ ስርዓቶች ወይም ዘዴዎች መካከል አንዱን ወይም ሌላኛውን የመረጠበትን እና የተጠቀመበትን ምክንያት መዝገቦ የማስቀመጡ ጉዳይ በሚመለከተው የመንግስት አካል ታውቆ እና ተረጋግጦ የሙያ ስራው የሚመራበት ደንብ ነው በሚያሰኝ ሁኔታ በአገሪቱ ውስጥ ዕውቅና እና ተቀባይነትን አግኝቶ በዘርፉ ባሉ ባለሙያዎች እየተተገበረ መሆን አለመሆኑ ወደ ስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመልሶ ተጨማሪ ማጣራት ሊደረግበት ይገባ ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁጥር ሶስት የተመለከተውን ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬአለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 96041

ጥቅምት 26 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተሽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ፖሊስ አገልግሎት ድርጅት የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ግዛው ተወካይ ትዝታ አቡሌ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል

<u>ፍ ር ድ</u>

የጉዳዩ መነሻ በፖሊስ ቤት በኩል ወደ ኖርዌይ አገር እንዲላክ አመልከች የተረከበው እቃ አደራረስ ላይ በተነሳው ክርክር የግራቀኙ መብትና ግዴታ ምን እንደነበር ከመወሰን እንፃር የቀረበ ነው ። በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል ። ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች መከራከሪያ ነጥቦች ውድቅ በማድረግ የዕቃውን ዋጋ እንዲከፍል በመወሰናቸው ምክንያት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልከች ያቀረበው አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው።

የክሱ ይዘትም፡- አመልካች ወደ ኖርዌይ አገር ዕቃውን ለማድረስ ውል የገባ ቢሆንም ዕቃውን በውሉ መሰረት ወደ ተባለው አገር ባለማድረሱ ነው የዕቃው ግምትና የማጓጓ ክፍያ በድምር ብር 9374.38 /ዘጠኝ ሺህሦስት መቶ ሰባ አራት 38/100) እንዲከፍላት ተጠሪ ዳኝነት መጠየቋን የሚያሳይ ነው ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አመልካች በሰጠው መልስም በግራቀኙ ስምምነት መስረት ዕቃው ወደ ኖርዌይ ተልኮ ተቀባይ ካላገኘ እንደሚመጣ መፈረማቸው ዕቃው ወደ ተባለው አገር ተልኮ ተቀባይ ያጣ በመሆኑ ወደ ሀገር ቤት እንደተመለሰ ፤የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ አመልካች ዕቃው ወደ ኖርዌይ አገር ልኮት ተቀባይነት ካጣ መመለስ አልነበረበትም ከስምምነታቸው ውጭ እንዲመለስ ዕቃው ወደ ኖርዌይ አገር ስለመላኩ እና ዕቃውን የሚቀበል ሰው ስለመጥፋቱ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ አመልካች ካሳ እንዲከፈል የካሳ መጠኑም ብር 5300 እንዲሁም ውጪና ኪሳራ ብር 750 እንዲሆን ፍርድ ሰጥቷል ፡፡ የአሁኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቤቱታው የቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ ዕቃውን ወደ ኖርዌይ አገር መላኩ አልተረጋገጠም በሥር ፍ/ቤት የተወሰነው የካሳ መጠን በማሻሻል ብር 5000 እና ወጪና ኪሳራ ብር 750 በድምር ብር 5750.00 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል ፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪም ጥሪ ተደርጎላት ቀርባ ግራ ቀኙ የጽሐፍ ክርክር አድርጓል ፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ዕቃ ወደ ኖርዌይ አገር አድርሶ ተቀባይ በማጣቱ ንብረቱ ወደ ኢትዮጵያ እንደ ተመለሰ ስለ ድርጅቱ አሠራር ለማስረዳት የቆጠራቸው ምስክሮች ሳይደመጡ ጉዳዩ መወሰኑ የመደመጥ መብቱ እንደሚጋፋ በመግለጽ ውሳኔ እንዲሻር ጠይቋል ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን አጣርተው የወሰኑት በመሆኑ የሚነቀፍ ነገር የለውም የሚል ክርክር አቅርበዋል ፡፡ አመልካች የመልስ መልስም አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ፤ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነ ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዝብ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል ፡፡

ከሥር የክርክር ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች እና ተጠሪ ዕቃን በፖስታ ቤት በኩል የመላክ ውል የተፈራረሙ ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

ግራቀኙ እያከራከረ ያለው መሠረታዊ ጭብጥ ለክርክር መነሻ የሆነውን ዕቃ በግራ ቀኙ ስምምነት መሠረት ወደ ኖርዌይ አገር ተልከዋል ወይስ አልተላከም ከተላከ በኃላ ተቀባይ በመጥፋቱ በእርግጥ ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል ወይስ አልተመለሰም?የሚለው ነው፡፡ አመልካች በገባው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል መሰረት ዕቃውን ወደ ኖርዌይ አገር እንደላከው እና ዕቃውን የሚቀበል ሰው በመታጣቱ የተላከው ንብረት ወደ አገር ቤት እንደተመለሰ ለዚህም የሰነድና የሰው ምስክሮች የቆጠረ ስለመሆኑ በአንድነት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በአንፃሩ ንብረቱ ወደ ኖርዌይ አገር አልተላከም ንብረቱ የተላከ ቢሆን አንኳ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ እንዳልነበረበት የበኩላቸውን ክርክር ማቅረባቸውን ተመልክተናል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ ዕቃውን ወደ ኖርዌይ አገር ስለመላኩ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት አመልካች ካሣ አንዲከፍል ወስነዋል፡፡

በመሰረቱ አንድ ግዴታ በአግባቡ መፈጸም ያለመፈጸሙን ለማጣራት የግራቀኙ ተዋዋይ ወገኖች የገቡት ግዴታ እና ያላቸውን መብት የሚገልጽ የሰነድና የሰው ምስክር እንዲሁም የግዴታው ልዩ ባሕሪ መሠረት በማድረግ አለም አቀፍ ልምዱ ጭምር መዳሰስ የሚጠይቅ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች ዕቃውን ወደ ኖርዌይ አገር ለመላክ እንደተቀበለ የተካደ ባይሆንም ዕቃውን በእርግጥ ወደ ኖርዌይ አገር መላክ ያለመላኩን የሚያረጋግጠው በሚያቀርበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ እንዲሁም የድርጅቱ አሠራር አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከት ነው ፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ዕቃ ወደ ኖርዌይ አገር ስለመላኩ ከዌብ ሳይት (ድሕረ ገጽ) የተገኘው መረጃ አያያይዞ እንደቀረበ የሰው ምስክሮች እንደቆጠረ በሚከራከርበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤቶች የቀረበው ሰነድ በዓለም አቀፍ የፖስታ አገልግሎት አሰጣጥ ልምድ ያለው ተቀባይነት እና ምስክሮች የሚሰጡት ቃል ይዘት ምን እንደሆነ ሳይቀበል ቀረበ በተባለው የሰነድ ማስረጃ ብቻ ተመርኩዞ ከድምዳሜ ላይ መድረሱ ጉዳዩን በአግባቡ በማጣራት ውሳኔ አለመስጠቱን የሚያሳይ ነው ፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ዕቃውን ለፖስታ ቤት (አመልካች)ካስረከቡ በኃላ ዕቃውን በስምምነቱ መስረት አለመላኩን እቃው ተቀባይ አለማጣቱን የሚያስረዳ ነገር ስለማቅረበቀቸውም በሥር ፍ/ቤት የተመዘገበ ነገር የለም፡፡ ተጠሪ ዕቃውን በውላቸው መሠረት አለመላኩን መነሻ በማድረግ ክስ ማቅረባቸው ሲታይ የቀረበው ክስ በማስረጃ አስደግፈው የማስረዳት ግዴታቸው ሳይወጡ ወይም ፍ/ቤቱ ዕቃው መላኩን የማስረዳት ግዴታው የአመልካች ነው ለማለት የሚያስችለው ሕጋዊ ምክንያት መኖሩን በውሳኔው ሳይገልጽ በደፈናው ዕቃውን በግራቀኙ ውል መሰረት አልተላከም ከሚል ድምዳሜ ላይ መደረሱ በሕጉ የተዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት የተከተለ ሆኖ አላገኘውም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ግራቀኙ እያከራከረ ያለው የውል አፈፃፀም ክርክር በተገቢ ሁኔታ ለመወሰን በሕጉ አግባብ የሚያከራክረው ጭብጥ ተለይቶ የግራቀኙ ማስረጃ ተመዝኖ መሆን ሲገባው የአመልካች የሰው ምስክሮች ቃል ሲያዳምጥ ቀረበ የተባለው የሰነድ ማስረጃም ከዓለም አቀፍ ልምድ ያለው ተያያዥነት በባለሙያ አስተያየት ተደግፎ ማብራሪያ ሳይሰጥበት ፍ/ቤቱ በራሱ ጊዜ ውድቅ ማድረጉ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 ፣247፣248 እና 249 የተመለከቱት መሠረታዊ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 136 እና 264(1) እና (2) ድንጋጌዎች በሚያዙት አግባብ ተገቢ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው ማስረጃ በማስቀረብ እና ጉዳዩን በማጣራት መወሰን እየቻለ ከዚህ በተቃራኒ ቀረበ የተባለው የሰነድ ማስረጃ ብቻ መሰረት በማድረግ አመልካች ግዴታውን አልተወጣም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በሕጉ አግባብ አይደለም ብለናል ። በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በአግባቡ ሳያጣሩ ውሳኔ ላይ መድሳቸውን የተረዳን በመሆኑ ውሳኔውን ተሽሮ በድጋሚ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ነው ። በመሆኑም የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የፈጸመውን ስህተት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳያርም ውሳኔው ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን የሚያሳይ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. የባሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ16237 በ 23/11/2005 የሰጠው ፍርድ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 168408 በ 15/04/2006 የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል።
2. የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ ይዘቱ እንደተገለፀው ግራቀኙ የሚከራከሩበት ዕቃ ወደ ኖርዌይ አገር ተልኳል ወይስ አልተላከም ? ወደ ኖርዌይ አገር መላኩ ከተረጋገጠ ወደ ኢትዮጲያ የተመለሰው ተቀባይ በመጥፋቱ ነው ወይስ አይደለም ? በአመልካች የቀረበውና ከዓለም አቀፍ ዌብይት ተገኘ የተባለው የሰነድ ማስረጃ ይዘት እና በዓለም አቀፍ ስለፖስታ አላላክ ያለው ልምድ ምን ይመስላል ?በግራቀኙ የውል ስምምነት ዓለም አቀፍ ልምድ ዕቃው የሚላክበት ሥርዓትና አፈፃፀሙ ምን ይመስላል?የሚሉና ተያያዥ ነጥቦች አመልካች የቆጠራቸው ምስክሮች እና በተጠሪ በኩል የሚቀርብ ማስረጃም ካለ አንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ የሚጠቅም ከሆነ በፍ/ቤቱ አነሳሽነት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ተገቢ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል። ይፃፍ።
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ላስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል።

ት ዕ ዛ ዝ

- ዕግድ ተነስቷል። ይፃፍ።
- መዝገቡ ወደ መዝብ ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 108251

ቀን ጥር 5/2008ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን የጎዴ ደናን መንገድ ፕሮጀክት

-ነ/ፊ አብርሃም አሰፋ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አመካክ ከሊፋ -አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሸበሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. M/S/Sh — 60/2006 ግንቦት 26 ቀን 2007ዓ.ም እንዲሁም የኢትዮጵያ ሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05-1-185/06 ህዳር 5ቀን 2007ዓ.ም ያሳለፉትን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ድርጅት በቆፈረው የውሃ መሄጃ ጉድጓድ ልጃቸው መሃመድ አመካክ ከሊፋ ህዳር 12/2006ዓ.ም ጉድጓዱ ውሃ ሞልቶ በቸልተኝነት ሳይሸፈን በመቅረቱ ምክንያት ገብቶ ስለሞተ ለደረሰባቸው ጉዳት አመልካች ሃላፊ እንዲባልና ልጁ የ4ኛ ክፍል ተማሪ የነበረ ከትምህርት ሰዓት በኋላ በአህያ ውሃ እየቀዳ ለሰፈር ነዋሪዎች በበርሚል 25ብር በመሸጥ በቀን የስምንት በርሚል ብር 200.00 በወር ብር 6000.00 ለቤተሰቡ ገቢ በማስገባት ደረጃ ስለነበር ትምህርቱን እስኪያጠናቅቅ ድረስ ታስቦ በጠቅላላ ብር 564,000.00፤ እንዲሁም የሞራል ካሳ ብር 1,000.00 እና የቀብር ማስፈጸሚያ ብር 25,000.00 እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አመልካች ለክሱ መቃወሚያ እና በሃላፊነት ሆነ በጉዳቱ መጠን ላይ የበኩሉን ክርክር አቅርበዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት ክርክሩን እና ማስጃዎችን ሰምቶ አመልካች ለጉዳቱ ሀላፊነት አለበት በማለት ካሳውን በርትዕ አስተያየት በመወሰን ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ/ እንዲከፈል ፈርዷል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ለማከራከር ስልጣን የለውም በማለት የሚያቀርቡትን መከራከሪያ በተመለከተ አስቀድሞ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ክሱን የስር ፍ/ቤት ተመልክቶ እንዲወስን በመለሰለት መሰረት ታይቶ የተወሰነ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው፣ ለጉዳቱ ሃላፊ መደረጉ በአግባቡ መሆኑን፣ እንዲሁም የካሳውን መጠን በተመለከተ የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ /የጎደ አካባቢ/ በሙሉ ልጆቹን ውሃ በአህያ እያስቀዳ የሚያሰራቸውና የኑሮ መሰረታቸው ስለመሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ ፍርዱ እንዲጸና ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 21,2007ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ሚች የ8 ዓመት ልጅ የነበረ ከመሆኑ አኳያ ውሃ በመሸጥ በየወሩ ያለማቋረጥ ብር 6000 ያስገኝ ነበር ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች በእርግጠኝነት ተቀባይነት ማግኘቱ ከህግም ሆነ ከልማዳዊ አሰራር አንጻር ተገናዝቦ የተሰጠ መሆን አለሞኑን ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ግራቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ እንዲለዋወጡ ትእዛዝ የተሰጠ ቢሆንም ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው እንዳልቀረቡ አመልካች በቃለ መሃላ የተደገፈ አቤቱታ ስላቀረቡ በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎ መዝገቡ ለምርመራ ቀጠሮ ይዟል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ቅሬታ ያስነሳውን ውሳኔ ከተያዘው ጭብጥ እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

አመልካች የስር ፍ/ቤት በህግ ከተሰጠው በገንዘብ መጠን የተወሰነ የዳኝነት ስልጣን በላይ ተመልክቶ የሰጠው ውሳኔ በመሆኑ ስልጣን በሌለው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ እንዳልተሰጠ እንዲቆጠር በሰበር ቅሬታቸው ያመለከቱ ቢሆንም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ እንደተመለከተው ይኸው መከራከሪያቸው ታልፎ ጉዳዩ በስር ፍ/ቤት ታይቶ እንዲወሰን ሲመለስ በወቅቱ ጉዳዩን በሰበር አቅርበው እንዲታረም ያላደረጉ በመሆኑ ቅሬታው ክርክሩ አሁን በደረሰበት ደረጃ የሚቀርብ አይደለም ብለናል፡፡

ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት የካሳውን መጠን በርትዕ የወሰነ ሲሆን አመልካች የካሳው መጠን እጅግ የተጋነነ እና ካሳው ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት በህጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተደነገገው ውጭ የተወሰነ መሆኑን በመጥቀስ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው እንዲባል ጠይቀዋል፡፡

በመሰረቱ ጉዳት መድረሱ ምክንያታዊ የሆነ እርግጠኝነት ሲኖር እና የካሳውን መጠን ለመወሰን አስቸጋሪ ሲሆን ዳኞች በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 መሰረት የካሳውን መጠን በርትዕ እንዲወስኑ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጎጂው የ4ኛ ክፍል ተማሪ የነበረና እንደ አካባቢው ህጻናት ውሃ በአሕያ በመቅዳት ቤተሰቡን ይረዳ እንደነበር ቢታወቅም በህጻኑ ሞት ምክንያት የቀረው ጥቅም መጠን በትክክል ለማስላት ስለሚያዳግት በርትዕ መወሰን ተገቢ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የካሳ መጠኑ ያላግባብ እንዳይጋነንም ሆነ ያላግባብ እንዳይቀንስ በተቻለ መጠን የጉዳት ካሳው መጠን ከደረሰው ወይም ወደፊት ሊደርስ ከሚችለው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግና ሃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ውሳኔ መስጠት ይገባል፡፡ ስለሆነም በርትዕ በሚወሰንበት ጊዜም ቢሆን የጉዳት ካሳው መጠን ከጉዳቱ ተመጣጣኝ ይሆን ዘንድ ሚዛን ላይ ሊቀመጡ የሚገባቸው መለኪያዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2153 እንደተደነገገው ዳኞች ሊገምቱት የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ በአግባቡ በመያዝ፣ ሊገምቱ የሚገባቸውን ትክክለኛውን መንገድ በመያዝ፤ ከአእምሮ ግምት ውጭ ያልሆነ፤ ከዝንባሌ የጸዳ ውሳኔ እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡

የካሳውን መጠን በርትዕ ለመወሰን የሚያስገድድ ሁኔታ በገጠመ ጊዜ መጠኑን ለመወሰን ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ሁኔታዎች ወይም መለኪያዎች ካልተመለከቱ የሚሰጠው ውሳኔ ስሜትን መሰረት የሚያደርግ እና የሕጉን አላማ የሚስት በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በተያዘውም ጉዳይ የካሳው መጠን የተሰላበት ሁኔታ እና ለስሌቱ ግምት ውስጥ የገቡ ሁኔታዎች (መለኪያዎች) በግልጽ ሳይመለከቱ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1ኛ. የሸበሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. m/s/sh/60/2006 ግንቦት 26/2006ዓ.ም ያሳለፈው እና በሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05-1-185/06 ህዳር 5/2007ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ. አመልካች ለጉዳቱ ሃላፊ ነው መባሉ በአግባቡ በመሆኑ ይኸው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3ኛ. የካሳውን መጠን በተመለከተ በርትዕ መወሰኑ የሚነቀፍ ባይሆንም መጠኑን ለመወሰን ያስቻለው ሁኔታ ወይም መለኪያዎች ባልተመለከቱበት እና ይህ ነው የሚባል መነሻ ምክንያት ሳይሰጥ አመልካች ለተጠሪ ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ/ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ተሽሯል፡፡

4ኛ. የከፍተኛው ፍ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ የካሳውን መጠን በህጉ አግባብ እንዲወሰን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡

5ኛ. ጉዳዩ በሰበር ሲታይ ስላስከተለው ወጪ አመልካች የራሱን ይቻል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 117383

ቀን 6/03/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፍ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽመሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሠለ

አመልካች፡- አቶ አዲስ ዋለልኝ በላይ

ተጠሪ፡- የፌ/ሥ/ዐ/መ/ኮ/ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዮ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በወንጀል የዋስትና ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች አብረዋቸው ከተከሰሱ ሌሎች ተከሳሽ ጋር በመሆን ተከሰንበት የነበረው የወ/ህ/ቁ. 676/1/ በአዲሱ የመስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁ. 881/2007 የተሻረ በመሆኑ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ዋስትና መብት ስለማይከላከል የዋስትና መብት ይፈቀድልን ብለው ያመለከቱ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በአዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 37 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ስር ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተያዘው የመስና ወንጀሎች የሚታዮት በወንጀል ሕጉ ድንጋጌ መሠረት ይሆናል ስለሊልና የወ/ህ/አ/676/1/ የዋስትና መብት ስለማያሰጥ ዋስትና ሊፈቀድ አይገባም፡፡ የሚሰጥ ከሆነም የዐ/ሕግ ምስክሮች ከተሰሙ በኃላ ማስረጃ ተመዝኖ መሆን አለበት በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካለው ህግ ጋር መርምሮ የወንጀል ህግ አንቀጽ 6 እና የህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 መሠረት ቅጣት ሲወሰን ለተከሳሽ ጠቀሜታ ካለው ሕግ አኳያ ሊታይ ይገባል፡፡ የተከሰሱበት የወ/ህ/ቁ. 676/1/ በአዲሱ አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 31/1/ ስለሚወድቅ እና ቅጣቱ ከ10 ዓመት በታች በሆነ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ በፌ/ሥ/ዐ/መስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ አዋጅ ቁ.434/97 መሠረት በብር 10,000 ዋስትና ከእስር ሊፈቱ ይገባል በማለት ብይን የሰጠ መሆኑን ከስር መዝገብ ለመረዳት ተችሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ብይን ቅሬታውን ለማሳረም ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ካከራከረ በኃላ መልስ ሰጪዎች የተከሰሱበት የወ/ህ/ቁ. 676/1/ ከ 5 ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ቅጣት እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ የሚያስቀጣ ነው፡፡ ተከሳሽ (መ/ሰጪዎች) የተከሰሱበት የወ/ህ/ቁ. 676/1/ በአዲሱ አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 31 የተካተተ ቢሆንም፡፡ ቀደም ሲል በመ/ሰጪዎች ላይ የቀረበው የክባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ክስ ባለበት የቀጠለ እንጂ እንደገና ተሻሽሎ በአዲስ መልክ የቀረበ አይደለም፡፡ መሸጋገሪያ ድንጋጌው ቀደም ሲል የተፈፀሙ ወንጀሎች ባሉበት ሁኔታ መታየታቸው እንደሚቀጥል የሚጠቁም ነው አዲሱ አዋጅ ቁጥር 881/2007 መውጣቱ አስቀድሞ የተከላከሉትን የዋስትና መብት በአዲስ መልክ ለማቅረብ የሚያስችላቸው አይደለም፡፡ መ/ሰጪዎች የተከሰሱበት የወ/ህ/ቁ. 676/1/ በአዲሱ አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 31/1/ ሥር የማሸፍን መሆን አለመሆኑ ማስረጃ ተሰምቶ ከሚረጋግጠው ፍሬ ነገር አንፃር ታይቶ የሚወሰን እንጂ ማስረጃ ተሰምቶ ባልተጠናቀቅበት ጉዳዩና የተረጋገጠውም ፍሬ ነገር ምን እንደሆነ ባልታወቀበት ሁኔታ እንደገና በቀረበ የዋስትና ጥያቄ መነሻ ከወዲሁ ወደ ፍሬ ነገር ምዘና በመግባት ከአስር ዓመት በታች በሚያስቀጣው በአዋጅ አንቀጽ 31/1/ ሥር የሚሸፍን ነው የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የህጉን ስርዓት የሚንድ ነው አደሱ አዋጅ መውጣቱ እና መ/ሰጪዎች የተከሰሱበት ወንጀል የአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 31 መተካቱ እንደገና የዋስትና ጥያቄ ለማቅረብም ሆነ በዋስትና መልቀቅን ለመፍቀድ የሚያስችል ባለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት መልስ ሰጭዎች በዋስትና ይፈቱ በማለት የሰጠው ብይን ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ በመዘርዘር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት ያስቀርባል የተባለው በአመልካች ላይ ተጠሪ ጠቅሶ ያቀረበው የወ/ህ/አ/676/1/ በተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርዓት እና ማስረጃ ህግ አ. 434/97 አንቀጽ 4 መሠረት ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ በመሆኑ የዋስ መብት የተከላከለ ሲሆን የሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 31/1/ ስር የወ/ህ/ቁ. 676/1/ የሚወድቅ በመሆኑ የዋስትና መብት አይከላከልም በማለት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ለብር 10,000 ለሚበቃ ዋስትና የፈቀደውን በይግባኝ ደረጃ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት አመልካች ዋስትና የተከለከለበት ጉዳይ የወ/ህግ አንቀጽ 676/1/ በአዋጅ ቁ 881/2007 አንቀጽ 31/1/ ስር የሚወድቅ መሆን ያለመሆኑ ወደ ፊት ማስረጃ ተሰምቶ የሚረጋገጥ እንጂ ከወዲሁ መተበይ የማይቻል ስለሆነ የዋስትና ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤትን ብይን የሻረበትን አግባብነት ለማጣራት ተብሎ ነው፡፡

ግራ ቀኙ በፅሑፍ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ሰበር ችሎት የአመልካችና የተጠሪን ክርክር ለሰበር አቤቱታው ምክንያት ከሆነው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና አግባብነት አለው የህግ ድንጋጌ ጋር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት የተከሰሰበት ወንጀል የወ/ህግ አንቀጽ 27፣32/1/ሀ/ እና 676/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የእምነት መጉደል ወንጀል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ የወ/ህ/ቁ. 676/1/ ላይ የተመለከተው የቅጣት መጠን ከ5 ዓመት እስከ 25 ዓመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ እስራት እና ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት እንደሚያስቀጣ የተመለከተ ሲሆን የሙስና ወንጀሎቹን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 እምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ተክቷል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 ሥር 4 ንዕስ አንቀጽ ያሉ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው የቅጣት መጠን ከ3 ዓመት እስከ 7 ዓመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ የተመለከተ ሲሆን በንዑስ ቁጥር 2 የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት የጥፍተኛው የስልጣን ወይም የኃላፊነት ደረጃ ወይም በመንግስት በህዝብ ወይም በግለሰብ ጥቅም ላይ ያደረሰ ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተፈፀመውን ወንጀል ከባድ አድራጐት እንደሆነ ቅጣቱ ከ7 ዓመት እስከ 25 ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራትና ከሀምሳ ሺህ እስከ መቶ ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በፈ/ከፍ/ቤት የተከሰሰበት ወንጀል የሙስና ወጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 በአንቀጽ 31 የተደነገገ ሲሆን፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር 4 ንዑስ አንቀጾች ተመልክተዋል በንዕስ ቁጥር 1 የተመለከተው የቅጣት መጠን ከ3 ዓመት እስከ 7 ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል በንዑስ ቁ. 2 የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት የጥፋተኛው የሥልጣን ወይም የኃላፊነት ደረጃ ወይም በመንግስት፣ በሕዝባዊ ድርጅት በሕዝብ ወይም በግለሰብ ጥቅም ላይ ያደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተፈፀመውን ወንጀል ከባድ አድራጐት እንደሆነና ቅጣቱ ከ7 ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከሃምሳ ሺህ እስከ መቶ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል፡፡

አመልካች የተከሰሱበት ወንጀል ክስ ማመልከቻ ላይ የተመለከተውን የወንጀል ዝርዝር ከሚቀርበው የዐ/ሕግ /የተጠሪ/ ማስረጃ ጋር መዝኖ አመልካች የተከሰሱበት ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 ስር በየትኛም ንዑስ አንቀጽ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል ክሱ እየታየ ባለበት ለፈ/ከፍ/ፍ/ቤት ብይን የሚሰጥበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአመልካች ላይ በተመሰረተው ወንጀል ክስ በወንጀሉ ዝርዝር ከተመለከተው አንፃር የአመልካች በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ በስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ተቀባይነት ማጣቱ ወይም የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት አመልካች በዋስትና ይፈቱ በማለት የሰጠውን ብይን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት መሻሩ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሐምሌ 24 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለ ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ. 113580 የሰጠውን ውሳኔ አፅንተናል፡፡

መዝገቡ እልባት ያገኘ በመሆኑ መ/ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 107166

ቀን ጥቅምት 4/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብራሃ መለሰ

አመልካች ፡- መኪንንት ማሞ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- የኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(1) ተላልፎ እድሜዋ 8 ዓመት የሆናት የግል ተበዳይ ሕፃን ያብስራ አብይ ላይ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈፅሟል ተብሎ የቀረበበት ክስ የሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የ16 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ወስኖበት በየደረጃው ያሉት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ስለፀኑበት ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልኝ ሲል አመልካች ስለጠየቀ ነው፡፡

የአመልካች የቅሬታ ነጥብ የግል ተበዳይ ክብረ ንፅህና ያልተገረሰሰ ስለሆነ በሙከራ ደረጃ የቀረ ስለሆነ የጥፋተኝነት ውሳኔም ሆነ ቅጣቱ እንዲሻሻል የሚል ነው፡፡

ይህንኑ ጉዳይ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ዐቃቤ ሕግ መልስ ሰጥቷል ፡፡ ዐቃቤ ሕግም የአመልካች ድርጊት በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተበዳይን ጨምሮ የተረጋገጠ መሆኑን ጠቅሶ በሥር ፍርድ ቤት የተላለፈው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ በአግባቡ ነው ተብሎ አንዲፀና ተከራክሯል ፡፡በእኛ መኩል ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል አመልካች የሚከራከረው የሕፃኗ ክብረ ንፅህና አለመገርሰሱ በህክምና ማስረጃ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት

ድርጊቱ በሙከራ ቀርቷል በማለት ነው፡፡ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ተግባር (ድርጊት) ስለመፈፀሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ ፍሬ ነገር የመመርመርና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋጡት ጉዳይ ነው ። የድርጊቱ አፈፃፀም ሲታይ አመልካች የወንድ ብልቱን በሕፃኗ የሴት ብልት ውስጥ ማስገባቱ በግል ተበዳይ የተመሰከረ ሲሆን በዚህም ምክንያት ማህፀኗ ላይ የመቅላት ምልክት የታዬ ስለመሆኑ በህክምና ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ክብረንፅህና አለመገርሰሱ ድርጊቱን በሙከራ የቀረ ነው የሚያሰኝ ባለመሆኑ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም ። የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 627(1) ድንጋጌም ክብረ ንፅህና መኖር አለመኖር ወይም መገርሰስ አለመገርሰስ እንደ መስፈርት ያስቀመጠው ጉዳይ ባለመሆኑ ክርክሩ የሕግ መሠረት የለውም ብለናል፡፡

በቅጣት ረገድ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት አንቀጽ 627(1) ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት (15-25) በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማድረግ በሕግ ተቀባይነት ያለው እና በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ተቀብሎ የድንጋጌው መነሻ የሆነ ቅጣት አሥራ ስድስት ዓመት (16) ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው የሚያስኝ የሕግ ምክንያት አልተገኘም ።

በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 186777 በ 20/01/07 የሰጠው ትዕዛዝ ፣የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 122177 በ 22/11/06 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11654 በ 08/09/06 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2-.ለ-.2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 112725

ቀን 22/02/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፉ መሐመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ስርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ሀሰን አብዳል ጠበቃ ገበዮህ ይርደው ቀርበዋል

ተጠሪ፡- የፌዴራል ማዕከል ዐቃቤ ህግ የቀረ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከተዩ ፍርድ ተሰትቷል

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ አመልካች የፀና ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ስራ ሰርቷል በሚል በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 2(3) 31(1) እና 60(1) የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በሚል የወንጀል ክስ የቀረበበት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ እየተመለከተ የነበረው ፍርድ ቤትም የአመልካቾችን ዋስትና መብት በብር 50,000 ወይም ለዚሁ ብቁ የሆነ ዋስትና ከቀረበ በኃላ ከእስር እንዲለቀቅ በሚል የዋስትና መብቱን ጠብቆለታል፡፡ ተጠሪ ቅሬታ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቅረቡ ግራ ቀኙን አስቀርቦ በዋስትና ጉዳይ ላይ እነዲከረክሩ ከዳረገ በኃላ የስር ፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ በመሻር የአመልካችን ዋስትና መብት ጥያቄ ከወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 67(ሀ) አንፃር በመካልከል አመልካች ማረሚያ ቤት ሆኖ ጉዳዩን ይከታተል ስል ወስነዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስላወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በዋስትና መፍቀድ ላይ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ ለማለት ስልጣን አለው የሚል አንቀጽ በወ/መ/ስ/ስ/ህጉ ላይም ሳይኖር ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ተቀብሎ አከራክሮ ዋስትናውን መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል፤ ዐቃቤ ህግ አመልካች በዋስትና ቢወጣ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ አይመጣም ለማለት የቀረበው ምክንያት አድራሻ የለውም ቢፈረድበት ብዙ ዓመት ስለሚቀጣ የሚል ሲሆን አድራሻ የለውም የሚለው አመልካች አድራሻ እንዳለው የተረጋገጠና ሊረጋገጥ የሚችል በመሆኑ የዋስትና መብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያስከለክል ሁኔታ ስለሌላ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበት በመሆኑ ነው ተብሎ ተሽሮ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ፀንቶ አመልካች በዋስ ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል የሚል ትዕዛዝ እንደሰጠው የመለከተው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ መልሱን በፅሑፍ ሰጥቶአል፡፡

ይህ ችሎትም አመልካችና አቃቤ ህግ ያቀረቡትን የፅሑፍ ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ ተመልክቶታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀረብ እንዲታይ የተደረገው ጭብጥ ተጠሪ በአመልካች በዋስትና መለቀቅ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችል መሆኑ ያለመሆኑን ይህ ቢታለፍ ከሆነም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝን መሻሩ ከወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 67(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 686 (2002 አንቀጽ 60(1) ድንጋጌ አንፃር በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

አቃቤ ህግ በዋስትና መለቀቅ ውሳኔ ላይ አቃቤ ህግ ይግባኝ ለመጠየቅ የሚችል መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ፡- በመሠረቱ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 75 ርዕሱ ሲታይ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ያልተፈቀዳ ሲሆን ለይግባኝ ፍርድ ቤት ማመልካቻ ስለማቅረብ በሚል የተቀመጠ ሆኖ ዝርዝር ይዘቱ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ያልተፈቀደለት ተካሳሽ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማመልካቸውን ማቅረብ የሚችል መሆኑንና የጊዜ ገደቡን የሚያስቀምጥ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ድንጋጌው አቃቤ ህግ የዋስትና መብት ሲፈቀድ ይግባኝ ማቅረብ የማይችል መሆኑን አይደነግግም፡፡ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ በስነ ስርዓት ህጉ ስለ ይግባኝ አቅራረብ ከተመለከቱት ድንጋጌዎችና ከወንጀል ሕጉ መሰረታዊ አላማ ሲታይ የዋስትና መብት ጠይቆ ሊከለከል የሚችለው ተከሳሽ በመሆኑ ተከሳሹ በህጉ ሊኖረው የሚችለውን የመብት ማስከበሪያ መንጋድ ለመጠቆም ተብሎ የተቀመጠ ከመሆኑ ውጭ ህጉ በማይፈቅደው አግባብ የዋስትና መብት የተከበረለት ተካሳሽ ሁሉ ዋስትና መብቱ ተከብሮለት በዋስትና ወረቀት ሲለቀቅ የወንጀል ሕጉን የሚያስፈፅመው አቃቤ ህግ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ለማለት አይችልም በሚል ሊተረጎም የማይገባው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው የአቀቤ ሕግን ይግባኝ የማቅረብ መብት የማይከለክል በመሆኑ በዚህ ረገድ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የፈፀመው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡

አመልካች ወደ ፊት ቀጠሮ አክብረው ሊቀርቡ አይችሉም ተብሎ ግምት መወሰዱን በተመለከተ፡- የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካች ላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ በረሱ ዋስትና የሚከለክል አለመሆኑን የተቀባሉት ጉዳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ለዋስትና መከለካል ምክንያት ያደረገው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ ቁጥር 67(ሀ) ሲሆን ፍረድ ቤቱ ይህንኑ ድንጋጌ ተግባራዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲያደርግ ግምትን መነሻ ለማድረግ የሚችለው ሕጋዊ ስልጣን ያለው መሆኑን ነው፡፡ የዋስትና መብት መሠረታዊ የሆነ ህግ መንግስታዊ መብት ቢሆንም ፍፁም መብት ሳይሆን በሕጉ አግባብ ሊከለከል የሚችል ነው፡፡ ፍርድ ቤት አግባብነት የለውን ልዩ ህግ መሠረት አድርጎ ጉዳዩን ሊመዝነውና ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ጉዳዩ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾች የዋስትና ጥያቄ ያልተቀበለው በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 67(ሀ) መሠረት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በዋስትና ወረቀት የመልቀቅ ማመልካቻ ለመቀበል የማይቻልባቸውን ሁኔታዎችን አስቀምጧል፡፡ ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ለመከለከል ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች በተጠቀሰው ድንጋጌ በግልፅ አልተመለከቱም እንዲህ ከሆነ አንድ ተካሳሽ የዋስትና መብት ቢከባርስት ግዴታውን የሚፈፅም፣ የማይመስል ነው ተብሎ ግምት የሚወስዳው በቂና እና ህጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆኑ ይግባል ተብሎ የሚታመን ሲሆን ምክንያቶቹ በቂና ህጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳዩ ከተለያዩ ከባባዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህሪይ አንፃር እየተየ በፍርድ ቤቱ ግንዘቤ ሊወስድባቸው የሚችላቸው ነጥቦች ናቸው ተብሎ የሚታሰብ እንጂ ቁርጥ ያለ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ ለማለት የማይችልበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 67 በጠቅላላው ሲታይ ፍርድ ቤት የወስትና መብትን የሚከለከልበቻው ሁኔታዎች የሚያሰይ ሲሆን ምክንያቶችን ፍርድ ቤቱ ከተለየዩ ሁኔታዎች በመመልከት ሊመዝናቸው የሚገባቸው ሲሆን የድንጋጌው ቅርፅ ይዘትና መንፋስ ሲታይ በሁኔታዎቹ ግምት የመውሰድ የለመውሰድ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ስልጣን (Discretion) መሆኑን ያሰያል በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 59304 በቀረበው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ቢወጣ የዋስትናውን ግዴታ አክብሮ ይገኛል ለማለት የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡

ይህ ግምት መሠረቱ በአመልካች ቋሚ አድራሻ አለመኖር ሳይሆን ትኩረት የተሰጠው በአመልካች ላይ የተመሰረተው ክስ ሊያስከትል ከሚችለው የእስራት ቅጣት ከፍተኛነትና ከወንጀሉ ልዩ ባህሪይ መሆኑ መገመቱን ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ ገልፀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በእነዚህ ምክንያቶች ላይ በመመስረት ዋስትናውን ከልክለዋል፡፡ እነዚህን ምክንያቶች ለግምቱ መነሻ እንዲያደርግ ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው በህጉ የተከለከለ ካለመሆኑንም በላይ ግምት የመውሰድ ጉዳይ በህጉ ለፍርድ ቤቱ ስልጣን የተሰጠው ነው፡፡ ግምቱ በቂ ነው ወይም አይደለም የሚለው ክርክር ደግሞ የጠቅላላ ሁኔታዎች ምዘና ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት ደግሞ በኢፌ/ዲ/ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3) ሀ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለበትን ማንኛውንም የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ የማስረጃና የሌሎች ክባቢያዊ ነገሮችን ምዘና ጉዳይ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን አይደለም፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግን ፍሬ ነገሩን የማጠረትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ስላለው ይህ ችሎት የክርክር አጠቃላይ በህሪይ መሰረት በማድረግ የሚዘው ድምዳሜ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ይጋባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ ህገ መንግስት አንቀጽ 19(6) እና የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 67(ሀ) መሠረት የሰጠው መሳኔ ሕጉ የተሰጠውን ስልጣን መሰረት ያደረገ እና በሕጉ አተረጋጎም አተገባበር ረገድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 110478 መጋቢት 21 ቀን 2007 ዓ/ም መተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 75(2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሆኖው እንዲከታተሉ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 109441

ቀን 17/05/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀንዓ ቂጢታ

አመልካች፡- ፈይሳ ማም ማሩ የቀረበ የለም ከተበለ በኃላ አዲስ መሀመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ህግ - የቀረበ የለም**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥተናል፡፡**

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ሚች ቁምቢ በዳሳን የመግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በህግ አግባብ የተሰጠነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የተያው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም ሰዓቱ በውል ተለይቶ በውል ባልታወቀ ጊዜ በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20/21 ሃያት ኮንደሚኒያም ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ አብሮት ከኦሮሚያ ክልል ሰንደፈ ወረዳ ቀርሳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ወደ አዲስ አበባ የመጣውን ሚች ቁንቢ በዳሳ ምንነቱ ባልታወቀ ነገር ጭንቅላቱን በመምታት በደርሰበት ጉዳት ህክምና ሲከታተል ቅይቶ ሀምሌ 18 ቀን 2003 ዓ/ም ህወይቱ እንደያልፍ በማድረጉ ተራ የሰው መግደል ወንጅ ፈጽሟል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ወንጀሉን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ክሱን ያስረዳልኛል በማለት የሰውና የጽሁፍ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የተጠሪ የሰው ምስክሮች ቃል በተመለከተ ፤ አንደኛ የተጠሪ ምስክር ሚች አጎቷ መሆኑን ገልጻ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም ከቀኑ 6፡00 ሰዓት አከባቢ ሚች እና ተከሳሽ ከሰንደፋ ወደ አዲስ አበባ ስሄዱ አግኝቻቸው የት ልትሄድ ብየ ሚችን ስጠየቀው ልጄን ለመጠየቅ ወደ አዲስ አበባ እሄዳለሁ አለኝ፡፡ ሚች አዲስ አበባ ከተከሳሽ ጋር ከሄደ በኃላ በዚያው ሳያመለስ ቀረ፡፡ ከዚያ ሚች ወድቂል ተብሎ እንደተነገራቸውና ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል ሄደን ስናየው ጭንቅላቱ ቅስሎና ተፈንክቶ ነበር፡፡ በመጨረሻም ወደ ቤት የመጣና ያስታመመችው መሆኑን ሚች ወደ ቤት በመጣ ጊዜ መናገር ማይችል እንደነበር፣ ይህንን የፈጸመብህ ተከሳሽ ነወይ ብየ ሰጠይቀው በሚች በምልክት በአዎት መልስ ሰጥትኛል ምስክር ተከሳሹን የጠረጠረችው በመጀመሪያ ከሚች ጋር አዲስ አበባ አብሮ በመሄደና ተከሳሽም ሲሞት ለቀበር ያልመጣ በመሆኑ ምክንያት መሆኑን፤ ሚች በምልክት ለምስክር ምላሽ ከሰጠ ከአምስት ቀን በኃላ ህይወቱ ያለፈ መሆኑን የመሰከረች መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

3. ሁለተኛ የተጠሪ ምስክር የሚች እህት መሆኗን ገልጻ፣ ተከሳሽ ሚችን አዲስ አበባ ልጅህንና ሚስትህን ያሉበት ቦታ አሳይለሁ ብሎ ከቤት ይዞት እንደወጣ አብረው እንደሄዱ የሰማች መሆኑን፤ ሚች ከቤት ከወጣ በኃላ ሳይመለስ እንደቀረና ከሁለት ሳንምንት በኃላ ዳግማዊ ሚኒሊክ የተኛ መሆኑ አንደወቁ ሚች እግሩ፣ አንገቱና ጭንቅላቱ ተጎድቶ እንደነበር፤ ሚች ወደ ቤት ከመጣ በኃላ መልስ መስጠትና ከሰው ጋር መግባባት የማይችል መሆኑንና የሚገባባውም በምልክት እነደነበርና ሚች እሺ የሚል መልስ ብቻ ይሰጥ እንደነበር ተከሳሽን የጠረጠሩት አብርው ከቤት ወጥተው የት ጣለው በሚልና ሚች ከጠፋና ከታመመ ጊዜ ጀምሮ ተከሳሽ ፍለጋ አለማድረጉ ሚችንም አለመጠየቁን ሚችና ተከሳሽ ጠብ የሌላቸው መሆኑንና አንደኛ ምስክር ሚችን ድርጊቱ የፈጸመብህ ተከሳሽ ነዎይ ብያ ስጠይቀው በምልክት አዎ ብሎ መልሶልኛል ብላ እንደነገራቻትና ነግራኛለች፣ እኔ ሚች በምልክት ተከሳሽ ነው ብሎ መልስ ሲሰጥ አልሰማሁም፡፡ ሚች ብር 5000 (አምስት ሺ ብር) ይዞ ስለነበር ለብሩ ስል ገድሎታል ብላ እንደምታስብ የመሰከረች መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

4. ሶስተኛው የተጠሪ ምስክር ሀምሌ 23 ቀን 2003 ዓ/ም ተከሳሽን ሲይዘው ተከሳሽ ለማምለጥ መከራ ያለማድረጉን እንደመሰከር በስር ፍርድ ቤት በውሳኔው አስፍሯል፡፡ በችሎት ያልቀረበው የተጠሪ ምስክር በበኩሉ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል አከባቢ በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ አያት ኮንደሚኒየም አከባቢ ሰው ተሰብስቦና ሚችን ውድቆ እንዳየና ከሚች አጠገብ ሁለት ዱላዎች እንደነበሩና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚችን ወደ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የተወሰደ መሆኑን ገልጻ ለፖሊስ ቃሉን ያስመዘገበ መሆኑን እንደተረዳ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ገልጿል። ተጠሪ ስለ ሟች አሞሞት የሚገልጽ የአስክሬን ምርምራ ውጤት የቀረበ መሆኑና ማስረጃው ሟች የሞተው በድብደባ ምክንያት ሁለቱም ሳንባዎቹና ጭንቅላቱ ላይ በደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት ምክንያት መሆኑን የሚገልጽ እንደሆነ ተረድተናል።

5. የስር ፍርድ ቤት አመልካች መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብይን ሰጥቶ ሟች በምልክት ፈይሳ ነው ብሏል በተባለው መሰረት ሌለ ፈይሳ የተባለ ሰው ተይዞ እንደነበርና ግንቦት 3 ቀን ስራ ስሰራ ወየ ማታ አስራ አንድ ሰዓት አከባቢ ባለቤቴ ስራ ቦታ መጥታ ተያይዘን ከአበልጃችን ጋር ሄደን እዚያ አድርን ግንቦት 4 ቀን 2030 ዓ/ም ወደ ቤታችን መመለሳችን ያስረደልናል በማለት ጭብጥ አስይዞ አራት መከላከያ ምስክሮችን ቃል አስምቷል። የስር ፍርድ ቤት የተከሳሽ መከላከያ ምስክሮች የሰጡት ቃል ተከሳሽ በጉዳዩ ተጠርጥሮ ሲያዝ ጳግሜ 3 ቀን 2003 ዓ/ም ለፖሊስ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም ከሟቸው ጋር ቀርስ ምላስ ሰንበር በልተን ማወራረጃ አንድ አንድ ብርሌ ጠጅ ጠጥተው እንደተለያዩና ፤ ከሟች ጋር ከተለያዩ በኃላ ተከሳሽ በኮንትራት ጭቃ የመለጠፍ ስራ ሲስራበት ወደ ነበረው ጠጅቱ ቤት በመሄድ ጭቃ ሲለጥፍ ወሎ፣ ስራው ስላለቀለት ወ/ሮ ጠጅቱ ቤት አድሮ በማግስቱ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም አምስት ሰዓት አከባቢ ወደ ቤቱ እንደተመለሰ በመግልጽ ከሰጠው ተከሳሽነት ቃል ጋር የሚቃረንና ታዓማኒነት የሌለው መሆኑን ገልጻ የአመልካችን የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ አድርጎታል።

6. የስር ፍርድ ቤት የተጠሪ ማስረጃ አመልካች በወንጀል ክሱ የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌ መተላለፍ ሟችን የገደለ መሆኑን ያረጋግጣል። ተጠሪ ያቀረባቸው የመከላከያ ምስክሮች ቃል ተዓማኒነት የሌለውና የዐ/ህግን ማስረጃ የሚያስተባብል አይደለም በማለት አመልካች (ተከሳሽ) በወንጀል ህግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ሟችን በመደብደብ ህይወቱ እንደያልፍ ያደረገና ተራ የሰው መግደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው ብሎ ፤ አመልካች በአሰር አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል። አመልካች የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም፤ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል። ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት አጽንቶታል።

7. አመልካች ጥር 20 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን የፈጸምኩ ስለመሆኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት አቅርቦ የሰማቸው ምስክሮች አላስርዱም። የተጠሪ ምስክሮች የሰጡት ቃልም ሰፊ ልዩነት ያለበት የተጠሪ ምስክሮች በአከባቢው ከእኔ ሌላ ፈይሳ ቡሻ የሚባል ሰው እንዳለና ሟች ከሟች ፈይሳ ቡሻና ከአንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልጅ ጋር ቁማር ስጫወት እንደነበር መስክረዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ወንጀሉን የፈጸምኩ ስለመሆኑ የቀረበብኝ በቂ ማስረጃ ሳይኖር፣ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽመሀል ተብሎዬ የ ተወሰነብኝ የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ መልስ አመልካችና ሚች አንድ ላይ ወደ አዲስ አበባ የመጡ መሆኑንና ሚች ወደ ቤቱ ሳይመለስ መቅረቱና ሚች ህይወቱ ያለፈው በደብደባ በደረሰበት ጉዳት መሆኑ የተጠሪ ማስረጃ ተደጋጋፊ በሆነ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ታህሳስ 1 ቀን 2008 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

8. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ አመልካች ሚችን ሆነ ብሎ ባደረሰበት ድብደባ ህይወቱ እንዲያልገፍ ያደረግ መሆኑን የማስረዳት ግደታውን (Burdon of proof) የተወጣ መሆኑን መርምረናል፡፡ አመልካች የተከሰሰበትን ተራ የሰው መግደል ወንጀል እንዳለፈጸመ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ የሚገመት በመሆኑ አመልካች በህገ መንግስቱ የፀና ነው ተብሎ የመገመተ መብት ጠቃሚ ከማስረጃ የማፍረስና አመልካች ወንጀል የፈጸመ መሆኑን የማስረዳት ህጋዊ ግደታ (Legal Burdon of proof) ያለበት አመልካችን በወንጀል የከሰሰው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ ይህንን የተጠሪን ጥፋተኝነት ማለትም ተጠሪ ወንጀል የፈጸመ መሆኑን የማስረዳት በህግ የተጣለበትን የማስረዳት ግደታውን የሚወጣው፣ አመልካች ወንጀሉን የፈጸመ መሆኑን በምን ደረጃ ማስረጃ በማቅርብ (Standard of proof) ሲያስረዳ እንደሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 141 እና በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 149 ተደንግጓል፡፡

9. ከላይ ከተጠቀሱት የህገ መንግስቱና የወንጀል መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት የሚቻለው፣ አመልካች ሚችን ሆነ ብሎ የገደል ስለመሆኑ ተጠሪ በበቂና አሳማኝ ማስረጃ የማስረዳትና የማረጋገጥ ግደታ አለበት፡፡ ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ግደታውን በአግባቡ ካልተወጣ፣ መልካች የተጠሪን ማስረጃ የመከለካልም ሆነ የማስተባበል ግደታ አንደሌለበት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ አላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ፣ ተጠሪ ሚች ቁንቢ በዳሳ፣ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ልዩ ቦታው አያት ኮንደሚኒየም አካባቢ፣ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ከጧቱ አንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን ለጊዜው ማንነቱ ባልታወቀ ሰው ጭንቅላቱንና ሌሎች የሰውነት ክፍሎች ተደብደቦ ወድቆ መገኘቱ፣ ሚችን ወድቆ ያገኙት ሰዎች የህክምና እርዳታ እንደያገኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የወሰዱት መሆኑን፣ ሟች ከሆስፒታል እርዳታ ስደርግለት ከቆየ በኃላ ወጥቶ ወደ ቤቱ መሄዱን፣ ሟች ቤቱ ውስጥ በህመም ላይ ቆይቶ፣ ሀምሌ 18 ቀን 2003 ዓ/ም ከዚህ አለም ህይወቱ ያለፈ መሆኑን፤ ሟች የሞተው በድብደባው ምክንያት በጭንቅላቱና በሁለት ሳንባዎቹ ላይ በደረሰበት ጉዳት መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው የሰውና የጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

10. ይህም ሟች ቁንቢ በዳሳ ህይወት ማለፍ ምክንያት የሆነው ማንነቱ ባልታወቀ ወይም ባልታወቁ ሰዎች ትክክለኛ ሰዓቱ ተለይቶ ባልታወቀበት ሰዓት በተፈጸመበት ደብዳብ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት መሆኑን የወንጀል ህግ አንቀጽ ት 24 በሚደነግገው መሰረት ተጠሪ የማስረዳት ግደታውን የተወጣ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተርድተናል፡፡ ተጠሪ በህግ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታ የተወጣ መሆኑ አከራካሪ የሚሆነው ሟችን ደብዱቦ በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ አያት ኮንደሚኒየም ከሚባለው ልዩ ቦታ የጠለው ተከሳሽ (አመልካች) መሆኑን፣ በበቂ ሁኔታ አረጋግጧል ወይስ አላረጋገጠም? የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ነው፡፡

11. ተጠሪ አመልካች ሟችን ስደበድብ አይቻለሁ የሚል ቁጥተኛ ማስረጃ (direct evidence) አላቀረበም፡፡ ተጠሪ ሟችን የገደለው አመልካች ነው በማለት ያቀረበውን የወንጀል ክስ ለማስረዳት የሞከረው ሟች ተደብድቦ ወድቆ ከመገኘቱ በፊትና ሟች ተደበድቦ ወድቆ ከተገኘ በኋላ የነበሩትን የአካባቢ ሁኔታ ነገሮች በማስረዳት፣ ፍርድ ቤቱ ሟችን የገደለው ተከሳሽ (አመልካች) ነው ወይም አይደለም ከሚለው ሎጅካል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃዎችን ከማቅረብ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው አንደኛ የተጠሪ ምስክር አመልካችና ሟች ግንቦትን 3 ቀን 2003 ዓ/ም አንድላይ ወደ አዲስ አበባ ስሄዱ ማየቷን፣ አመልካች ሟች ጠፍቶ ስፈለግም ሆነ ታሞ እቤት በነበረበት ሰዓት ያልጠየቁ መሆኑን፣ አንደኛ ተጠሪ ሟች በምልክት የደበደበህ ተከሳሽ ነወይ? ብየ ስጠይቀው ተከሳሹ መሆኑን በምልክት መልስ ሰጥቶኛል በማለት የሰጠችውን የምስክርነት ቃል እና የስር ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት ባስቀርበው የፖሊስ መርመራ መዝገብ ውስጥ አመልካች በወንጀለኛ መቀጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 27 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለፖሊስ 3-13-2003 በሰጠው የተከሳሽነት ቃል "ተከሳሽ ከሟች ጋር ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ አብረው መጥተው አዲስ አበባ ከደርሱ በኃላ ቁርሳቸውን ምላስ ሰንበር በልተው ማወራረጃ አንድ አንድ ብርሌ ጠጅ ጠጥተው የተለያዩ መሆኑን ተከሳሽ ከሟች ጋር ከተለያየ በኃላ ኮንትራት ጭቃ የመለጠፍ ስራ ይሰራበት ወደነበረው ወ/ሮ ጠጅቱ ቤት የሄደ መሆኑንና ከሳሽ የጭቃ ልጠፋው ስራ ያላለቀለት በመሆኑ ከወ/ሮ ጠጅቱ ቤት አድሮ በማግስቱ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ከቀኑ አምስት ሰዓት ወደ ቤቱ የተመለስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን በመግለጽ የሰጠውን የተከሳሽነት ቃል፤ እንድዚሁም የሚች እህት የሆነቸው ሁለተኛ ተጠሪ ምስክር ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም አመልካች ከሚች ጋር ወደ አዲስ አበባ መሄዱን ሰዎች እንደነገሯት፣ ሚች ተከሳሽ ነው የደበደበኝ ብሎ በምልክት ነግሮኛል ብላ አንደኛ ተጠሪ የነገረቻት መሆኑን ሚች በምልክት ይህንን ሲናገር እንዳላየች የሰጠችውን የምስክርነት ቃልና አንደኛ ሁለተኛ የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪዎችን ታሞ በነበረበት ጊዜ ያልጠየቀው መሆኑንና በሚች ቀብር ስነ ስርዓት ላይ አመልካች ያልተገኛ መሆኑን በመግልጽ የሰጡት የምስክርነት ቃል አመልካች ሚችን የገደለ መሆኑን የሚያረጋግጡ የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃዎች ናቸው በማለት እንደሆነ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

12. የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃ ወንጀሉን የፈጸመው ተከሳሽ መሆኑንና ከተከሳሽ ውጭ ሌላ ሰው ወንጀሉን ሊፈጽመው አይችልም በሚል መደምደሚያ ላይ ለማድረስ በቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ የሚያስርዳ ሆኖ ሲገኝ የአስረጅነት ብቃት ያለው ማስረጃ ተደርጎ እንደሚወስድ የማስረጃ ብቃት መስፈርትና የማስረጃ አመዛዘን መርሆች ያሳያሉ፡፡ የአከባቢ ሁኔታ አንድን የተፈጸመ ወንጀል ለማስረዳት የአስረጅነት ብቃት ያለው ማስረጃ የሚሆነው ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት ወንጀሉ ከተፈጸመ በኃላ ስላላው ሁኔታ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች (የአከባቢ ሁኔታዎች) ተከሳሽ ወንጀሉን ፈጽሞታል ከሚል እርግጠኛ መደምደሚያ ለመድረስ የሚያስችል ይዘትና ባህሪ ያላቸው ሲሆን፣ የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃዎቹ ተያያዥነት ያላቸውና ክፍተት የሌለባቸው ሲሆኑ፤ የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃዎቹ የተከሳሹ ጥፋተኝነት ወንጀል መምራት የሚያረጋግጡ አንጅ በተቃራኒው ተከሳሹ ንጸህ ነው ወንጀሉን አልፈጸመም ወደሚለው ሎጅካል መደምደሚያ የማይወስደ ሲሆኑና የቀረቡት የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃዎች በማናቸውም የሞራልና የህሊና መመዘኛ ወንጀሉ በተከሳሹ ሳይሆን በሌላ ሰው የመፈጸም እድልና አግጣሚ የሌለ መሆኑን በበቂ ሁኔታ ለማስረዳት የሚችሉ ሆነው ሲገኙ እንደሆነ ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ህግ መርሆች ያሳያሉ፡፡

13. ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ሚች አዲስ አበባ አብረው ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም የወጡ መሆኑን፣ አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ወደ ቤቱ መመለሱና ሚች ሳይመለስ መቅረቱ፣ ሚች በአዲስ አበባ የካ ክተማ አያት ኮንደሚኒየም ከተባለው አከባቢ ደብደባ ተፈጽሞበት ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም አንድ ሰዓት ተኩል አከባቢ ውድቆ መገኘቱ ሚች ላይ የሞት ጉዳት የደረሰበትን ድበዳቤ የፈጸመው አመልካች ስለመሆኑና ከአመልካች ውጭ ሚችን ሌላ ማን ሰው ሊደበድበው የማይችል ስለመሆኑ ሎጅካል መደምደሚያ ላይ የሚያድረሱ፣ ተያያዥነት ያላቸውና ክፍተቶ የማይፈጥሩ የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃዎች ናቸው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

14. ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት ዕወነትነት ያለው ማስረጃ እንደሆነ በመውሰድ የአመልካችን የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ ለማድረግ አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 27 ንዑስ አንቀጽ 2 የሰጠው የተከሳሽነት ቃል፣ አመልካችና ሟች ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም አዱስ አበባ አብረው ከመጡ በኃላ ከሟች ጋር ምላስ ሰንበር ቀርሳቸውን በልተውና ማወራረጃ አንድ አንድ ብርሌ ጠጅ ጠጥተው የተለያዩ መሆኑን፣ አመልካች ከሟች ጋር ቀርስ በልተው ከተለያዩ በኃላ ኮንትራት ሲሰራው ጭቃ የመልጠፍ ስራ ሲሰራበት ወ/ሮ ጠጁቱ ቤት መሄዱን ከዚያ በኃላ ጭቃ የመለጥፈ ስራው ስላልተጠናቀቀለት ከወ/ሮ ጠጅቱ ቤት አድሮ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ብቻውን ወደ ቤት መመለሱን የሚገለጽ ማስረጃ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት የቀር በትዕዛዝ ያስቀረበው ይህ አመልካች ለፖሊስ የሰጠው የተከሳሽነት ቃል፣ የአስርጅነት ብቃት እና ተዓማኒነት ያለው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት በማረጋገጥ ለፍርድ ግበዕት አድርጎ ተጠቀሞበታል፡፡ ይህ ከሆነ የስር ፍርድ ቤት ለፖሊስ ከሰጠው የተከሳሽነት ቃል ውስጥ አመልካቹን የሚግዳውን ማለትም ከሟች ጋር ወደ አዲስ አበባ አብረው መምጣታቸውንና ቁርስ አብረው መብላታቸውን የሚገልጸውን የማስረጃነት ክፍል ለማስረጃነት ከያዘ በኃላ አመልካች ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም አዲስ አበባ ከደርስንና ቁርስ ከባለን በኃላ እኔና ሟች ተለያይተናል፡፡ ከዚያ በኃላ እኔ በኮንትራት ጭቃ ወደምለጥፍበት ወ/ሮ ጠጅቱ ቤት ሄጀ፣ ወ/ሮ ጠጅቱ አድራ በማግስቱ ብቻየን ወደ ቤት ተመልሻለሁ በማለት አመልካችን የሚጠቅመውን የማስረጃ ክፍል በማስረጃነት አልያዘለትም፡፡ ይህም የስር ፍርድ ቤት በትዕዛዝ ባስቀርበው የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ውስጥ ተይይዞ ያገኘውንና አመልካች በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 27(2) የሰጠውን የተከሳሽነት ቃል ከነሙሉ ይዘቱ ሳይሆን አመልካች ጥፋተኛነው ለማለት የሚጠቅመውን የማስረጃውን ክፍል ብቻ ለፍርድ ግብዓት ያዋለና መሰረታዊ የማስረጃ አመዛዘን መርህ በመጣስ መሰረታዊ የህግ ስህተት የፈጸመ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

15. እንደዚሁም ከላይ በተገለጸው በተጨማሪ አንደኛ ተጠሪ ሟች በምልክት ተከሳሽ እንደደበደበው ገልጾልኛል በማለት የምስክርነት ቃል የሰጠች ቢሆንም ሟች በምልክት ይህንን ሲገልጽ ከምስክር ውጭ ሌሎች ሰዎች ያላዩ መሆኑና የሟች የምልክት ቋንቋ ትክክለኛ መልዕክት ለመረዳት አስቸጋሪ በመሆኑ፣ የተጠሪ አንደኛ ምስክር ሟች በምልክት ቋንቋው ስለገለጸው ትክክለኛ መልዕክት ሳይሆን እሷ ይህንን ማለቱ ነው ብላ የገመተችውን የመሰከረች መሆኑን ስለሚያሳይ፣ አመልካች በቁጥጥር ሲወል ለማምለጥ አለመምከሩና ሌሎች ባህሪያቶችን አለማሳያቱን የተጠሪ ሶስተኛ ምስክር የመሰከር በመሆኑና ሁለተኛ ተጠሪ የሰጠችው የምስክርነት ቃል የሰሚ ሰሚ ማስረጃ በመሆኑ ማስረጃው በወ/መ/ስ/ህግ ቁጥር 137 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተቀባይነት ያለው ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቢሆንም አመልካች ሚችን ስለመግደሉ ለማረጋገጥ የሚያስችል ይዘት የሌለው በመሆኑ፣ የተጠሪ የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃም ሚች ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም ከአመልካች ጋር ወደ አዲስ አበባ መጥቶ፣ አዲስ አበባ ከአመልካች ጋር ቁርስ ከበሉ በኃላ አመልካችና ተጠሪ ወደ ተለያየ አቅጣጫ ሄደዋል ወይስ አብረው አንድ ላይ ዉለዋል፣ አመልካች ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም አዲስ አበባ ከደረሰ በኃላ ወደየት ቦታ እንደ ሄደ፣ ምን ሲሰራና እነ ማን ጋር እንደዋል፣ የማያስረዳና ክፍተት ያለበት በመሆኑ፣ ሌላው ቀርቶ ሚች ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ወድቆ ከተገኘበት የካ ክፍለ ከተማ አያት ኮንደሚኒየም ከተባለው ቦታ ላይ ሚች ከወደቀበት ጎን ወድቀው ከተገኙት ሁለት ብትሮች አንደኛው የአመልካች ስለመሆኑ ተጠሪ በሰው ምስክር ወይም በሳይንስ ምርመራ ያላረጋገጠ በመሆኑ፣ ተጠሪ ሚች ሰዓቱ በውል ባልተወቀበት ጊዜ ማንነቱ ወይም ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ተደብድቦ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም አዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ አያት ኮንደሚኒየም ከተባለው ቦታ ወድቆ መገኘቱንና በድበደባው በደረሰበትን ጉዳት ህይወቱ ያለፈ መሆኑን ከማስረዳት ውጭ ሚችን የደበደብ አመልካች ስለመሆኑ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 141 በሚደነግገው መሰረት በቂና አሳማኝ የሆነ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ግደታውን አልተወጣም፡፡ ተጠሪ የማስረዳት ግደታውን ባልተወጣበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን በወ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 141 መሰረት በነጻ ማሰናበት ሲገባው ተጠሪ መከላከያ ማስረጃ እንደያቀርብ የሰጠው ብይንና በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና የማስረጃ ህግ መርሆች የሚጥስ ነው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ስህተት ሳያርም ፍርዱን ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ሽረነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 113102 የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101772 የሰጠውን ፍርድ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ-1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል በነጻ የተሰናበት በመሆኑ ከእስር እንዲለቅቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 113464

ህዳር 22 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- 1. እናት ሁናቸው
2. ባለው እንደወቅቱ
3. ሃብታሙ ሁነኛው
4. በልስቲ ሁነኛው

የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች እና ስንሻው አለሙ በተባለው ግለሰብ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱም ይዘት፡- ተከሳሾች በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ወንጀል አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና 671(2) ስር የተደነገገውን መተላለፍ የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት አስበው ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ/ም ከምሽቱ በግምት 4፡00 እስከ 6፡00 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ጎዛመን ወረዳ ማይ አንገታም ቀበሌ ከአሁኗ 1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ውስጥ አቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውላለም ግዛቸው ይባል የነበረውን በአሰቃቂ ሁኔታ ደብድበው ገለው እሬሳውን ከሻይ ቤት ራቅ አድርገው ጥለውት ይዞት የነበደርን ባለስደፍ ክላሽ ጠመንጃ የወሰዱበት መሆኑን ዘርዝሮ ተከሳሾች ከባድ የውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም ሆነ የሥር 1ኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ስንሻው አለሙ ፍርድ ቤት ቀርበው የአቃቤ ሕግ የክስ ቻርጅ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በሁዋላ እምነት ክህደት ቃላቸውን ሲጠየቁ የወንጀል ድርጊቱን አለመፈፀማቸውን ክደው በመከራከራቸው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን አራት ምስክሮች ቆጥሮ ሶስቱን ፍርድ ቤት አስቀርቦ አስምቷል፡፡ ከዚህም በሁዋላ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የማጣሪያ ምስክሮችን መስማት አስፈላጊ ነው ብሎ ትዕዛዝ ሰጥቶ የ1ኛ አመልካች ጎረቤት ናቸው የተባሉትን ግለሰብ የምስክርነት ቃል በመቀበልና የፖሊስ የምርምራ መዝገብ ሁሉ አስቀርቦ አይቶ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃዎች ቀርበው ተሰምተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃዎች መርምሮ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ስንሻው አለሙ በመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ሕግን ማስረጃዎችን አስተባብሎአል በማለት ክሱ በነጻ ያሰናበተ ሲሆን የአሁኑን አመልካቾች ግን በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው የአቃቤ ሕግ ማስጃዎችን አላስተባበሉም በማለት በአቃቤ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማድረግ እና የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል የቅጣት አወሳሰኑን ከተሻሻለው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንፃር በማየት የወንጀሉ ደረጃ በእርከን 38 ስር እንደሚወድቅ ከለየና ለሁሉም አመልካቾች ሁለት ሁለት የቅጣት ማቅለያ በመያዝ ወደ እርከን 36 አውርዶ በዚሁ እርከን ስር አመልካቾች እያንዳንዳቸውን በ18 አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ በመወሰን በስር 1ኛ ተከሳሽ እጅ ተያዘ ተብሎ በኢግዚቢትነት የተያዘው የጦር መሳሪያም የዚሁ ሰው መሆኑ ተረጋግጦ እንዲመለስላቸው በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህም በኋላ የሰበር ኤቱታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ በአመልካቾች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝት ውሳኔ አፅንቶ የቅጣት ውሳኔውን ብቻ ከመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንጻር መታየት እንደነበረበት በምክንያትነት ይዞ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተያዘላቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በእያንዳንዱ ሶስት ሶስት እርከን መቀነስ እንዳለበትና በዚህም ስሌት መሰረት ቅጣቱ ወደ እርከን 32 እንደሚወርድ ገልፆ በዚሁ እርከን ለፍርድ ቤቱ በተተወው ፍቅድ ስልጣን መሰረት እያንዳንዳቸው በአስራ አራት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች ሚያዚያ 29 ቀን 2007 ዓ/ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካቾች ጥፋተኛ ተብለን እንድንቀጣ የተወሰነው አቃቤ ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምስክሮች በአይን ባላዩትና የስሚ ስሚ ምስክርነት ነው፣ በመከለካከያ ማስረጃዎችም የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ቃል አሰተባብለናል በማለት ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪ ቀርቦ በቁጥር ወየሣ/4173/መ/ቁ95/908 በቀን 21/01/2008 ዓ/ም በተፃፈ አራት ገፅ ማመልከቻ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የተሰጠው በሚታመን የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል መሆኑን ዘርዝሮና ውሳኔው ተገቢነት ያለው መሆኑን በመግልፅ ውሳኔው ሊጸና የሚገባው መሆኑን ጠቅሶ የጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ ፣ ከድርጊቱ አፈፃጸም ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካቾች ጥፋተኛ ተብለው በስር ፍርድ ቤቶች የመቀጣታቸውን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡

አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና 671 (2) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል፣ ውባለም ግዛች ይባል የነበርን ግለሰብ ደብድበው ገድለው ሬሳውን ከሻይ ቤት ራቅ አድርገው ጥለው ይዞት የነበረውን ባለሰደፍ ክላሽ ጠመንጃ ወስደዋል በሚል ምክንያት ሲሆን አመልካቾች ድርጊቱን መፈጸማቸውን ክደው ተከራክረውም አቃቤ ሕግ ሶስት የሰው ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ለትክክለኛ ፍትህ ሲል ማጣሪያ ምስክሮችን ከመስማቱም በላይ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ሁሉ አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ እነዚህ የሕግ ማስረጃዎች ታይተውም አቃቤ ሕግ እንደክሱ አስረድቷል የሚል እምነት የበታች ፍርድ ቤቶች ደርሰዋል፡፡ ለጉዳዩ በማስረጃነት የተሰሙት ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘትም የሚከለተው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ ያሳያል፡፡

አቶ ታዬ ብርሃን የተባል የአቃቤ 1ኛ ምስክር በሰጠው የምስክርነት ቃል በክሱ በተገለፀው ቀንና ቦታ ማታ ተከሳሾችና ሟች ሻይ ቤት ከምስክሩ ጋር ገብተው እንደነበር፣ ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት እንተኛ ተባብለው ይኼው ምስክርና አሊ የተባለው የአቃቤ ሕግ ምስክር ለሽንት ወጥተው ወደ አሁኗ 1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ሲመለሱ የኩራዝ መብራት ጠብቶ የሽመልና የብርጭቆ ኳኳታ ድምጽ ሰምተው አሊ የተባለው ምስክር ምንድን ነው ሲል ምን ሰማህ ብሎ የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ስንሻው አመራ መሳሪያ ሲያቀባብል ደንግጠው በመሮጥ ይኼው ምስክሩና አሊ የተባለው ምስክር ተበታትነው ከውጭ አድረው ከዚያ በኋጋታው ውባለም ሞተ ተብለው ምስክሩ ከሟች ጋር የጋብቻ ዝድምና እንዳለው፣ ከበረሃው በእዛው እለት ድርጊቱ ተፈጸመ ወደ ተባለበት ሐመሲት ከተማ ምስክሩ ሊሄድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቻለውም ሚች ዱቄት ይሰጣችኃል ተብሎ መሆኑንና በዚህ ምክንያት ድርጊቱ ሲፈፀም ማየቱን እንዲሁም ከ1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ የገቡ መሆኑን ገልጸ መስክሯል፡፡

አቶ አሊ መኮንን የተባለው የአቃቤ ሕግ ምስክር በበኩሉ እንደ አቶ ታዬ ብርሃን በተመሳሳይ መመስከሩን ፍርድ ቤቱ ገልፆ የምስክርነቱን ቃል ዝርዝሩን በውሳኔው ላይ አላሰፈረውም፡፡ ቂስ ማማሩ ደመወዝ የተባለው የአቃቤ ሕግ ሶስተኛ ምስክር ደግሞ በክሱ በተገለጸው ቀን በነጋታው ጥዋት ከአገራቸው ወደ ሃሙሲት ከተማ ሞባይል ካርድ ሊሞሉ መጥተው ሳለ ሚች ሞተ ተብሎ ፖሊስ እንደአሰጠራቸው፣ የሚች አስክሬን ከወደቀበት ቦታ ሂደው ሲመለከቱም የሚችን መታወቂያ፣ዱላ፣ ሽመልም ያገኙ መሆኑን፣ ከአሁኗ 1ኛ አመልካች ቤት እስከ ሚች አስክሬን የደም ነጠብጣብ መመልከታቸውን እንዲሁም አልኮል የተቀባ የቁስል ማሸጊያ/ፋሻ/ ማግኘታቸውን፣ የአሁኑ 4ኛ አመልካች በስለት ተቆርጦ ታሸጎ ማየቱንና የሚችን አስክሬን ወደ አገሩ መውሰዳቸውን እንዲሁም ምስክሩም ራሱ ተጠርጥሮ ታስሮ እንደነበር፣ ነገር ግን ድርጊቱን እንዳልፈፀሙ፣ ድርጊቱን የፈጸመው ማን ነው የሚለውን ያጣራ መሆኑንና ከሚች ጋር በገንዘብ ተጣልተው በሽማግሌ የታረቁ መሆኑን፣ የሙሉ ቢተው ሚስት አቃቤ ሕግ በክሱ በገለፀው እለት አህያ ከውጭ ታስሮ ነበር፣ ድምፅ የአህያው ሳይሆን ሰው ሲያጓጉርና ሲንፈራገጥ ሰማሁ በማለት ለአለኽን ሚስት ተናግራ አለኽኝ ደግሞ ለምስክሩ የነገራቸው መሆኑን፣ አቃቤ ሕግ በክሱ በገለጸው እለት ሚች መሳሪያ ይዞ ከሚች አበጀ መንግስቱ ያስፈጨውን ዱቄት ከፋንታ ምስጋናው ማስቀመጡን መስማቱን፣ ሚች ልደር ብሏት ወንድ የለም ብዬ መልሼዋለሁ ብላ የነገረቻቸው መሆኑንና የሚችን አስክሬን መጀመሪያ ያገኘው ልጃለም ስንታየሁ ነው በማለት መስክሯል፡፡ ከዚኅም በኃላ ፍርድ ቤቱ የአሁኗ አመልካች ጎረቤት ሰው ሲያጓጉር ሰምቻለሁ ብላ ተናግራለች ተብሎ በሶስተኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር በመገለፁ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ያመች ዘንድ ምስክሯ ቀርባ እንድትሰማ ትዕዛዝ ሰጥቶ ምስክሯ ቀርባ የተሰማች ሲሆነን ምስክሯ በሰጠችው የምስክርነት ቃልም የአሁኗ 1ኛ አመልካች ጎረቤታቸው መሆናቸውን ገልፀው ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ/ም ምሽት የሰሙት ድምጽ የለም፣ አህያም ከውጭ አልታሰረም በማለት የመሰከረችና ምስክርነቱ በዚሁ ያበቃ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት የፖሊስ የምርመራ መዝገብ በማየት ድምጽ መሰማቱን፣ አህያ መስሎኝ ነው እንጂ በማለት መገለጹን አገንዝቦ አልፎታል፡፡ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ መዝገቡን በመመርመር ዱቄት 1ኛ እና 2ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እንዲያመጡ ላካቸው የተባለውን ስንሻው ጎሹ የተባለውን ግለሰብ ቀርቦ እንዲሰማ ትዕዛዝ ሰጥቶ የክፍሉ ፖሊስ ሰንሻው ጎሹ የተባለ ግለሰብ እንደሌለና ሊያገኘው ያለመቻሉን ለፍርድ ቤቱ በመግለፁ ምክንያት ይኼው ግለሰብ በተጨማሪ ማስረጃነት ሳይሰማ ታልፎአል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገ ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወ.ሕ.አ. 23 (1)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑም በወ.ሕ.አ. 32(1) ስር ተደንግጎአል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወ.ሕ.አ. 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል መማቂቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቶአል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 142 መሰረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ስለመሆኑ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ከአንድ በላይ ሰዎች በተከሰሱበት የወንጀል ጉዳይም የእያንዳንዱ ተከሳሽ ሚና እና የተሳትፎ ደረጃው በቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ በከሳሽ ወገን በኩል በሚቀርበው ማስረጃ ነጥሮ ሊወጣ የሚገባ መሆኑን ስለመወንጀል አፈፃጸም ተካፋይ መሆን የሚመለከቱ የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች በተለይም አንቀፅ 32 እና 40 እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ጉዳይን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በዐ/ሕግ በኩል በቀረበው የአካባቢ ማስረጃ የተረጋገጡት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ሟች ከ1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ገብተው እንደነበርና በሻይ ቤቱ ከሟች ጋር ነበርን ያሉት 1ኛ እና 2ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ከሻይ ቤቱ ለሽንት ወጥተው ሲመለሱ በቤቱ የነበረው የኩራዝ መብራት ጠፍቶ የሽመልና የብርጭቆ ኳኳታ ሰምተው ምንድነው የሚለውን ጥያቄ 2ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ሲያቀርብ በስር 1ኛ ተከሳሽ ተከሳሽ የነበረውና በመከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ቃል አስተባብሎአል ተብሎ በነጻ የተሰናበተው አቶ ስንሻው አመራ የጦር መሳሪያ ሲያቀባብሉ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ደንግጠው የራሳቸውን ሕይወት ለማትረፍ ተበታትነው ሸሽተው አድረው በበነጋው ሟች ሞተ ተብሎ እንደተነገራቸውና የሟች አስክሬንም ከአሁኗ 1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ራቅ ብሎ ተጥሎ መገኘቱን ነው፡፡

በመሰረቱ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ደግሞ ብቻቸውን በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 ስር በግልጽ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ዐ/ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርግ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማለት የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ ዐ/ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ሚቹ በአመልካቾቹ ተገድሏል ለማለት የማያስደፍር ስለመሆኑ የምስክሮች ዝርዝር የምስክርነት ቃሉ አያሳይም፡ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በተለይ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ሚችን ከአነማን ጋር እንደነበር ከማየታቸው ውጪ አመልካቾቹ በወንጀሉ ድርጊት የነበራቸውን ሚና፣ ተሳትፎና ደረጃውን ገልጸው የመሰከሩ አይደሉም፡፡ አመልካቾች በጊዜና በቦታው ነበሩ ስለተባለ ብቻ ግን ጥፋተኛ ለማድረግ የሚያስችል የወንጀል ጉዳይ ማስረጃ ምዘና መርህ የለም፡፡ እያንዳንዱ አመልካች በወንጀሉ የነበረው ተሳትፎና ደረጃው በቂ በሆነ ሁኔታ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን ይህ ካልሆን ግንሞ ፍ/ቤቱ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 መሰረት ተከሳሽን ማሰናበት የግድ የሚል እንጂ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ መስጠት የሕግ መሰረት አይኖረውም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች በሚች ሕይወት ማለፍ የነበራቸው ተሳትፎ ተለይቶ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ከሚቹ ጋር ነበሩ ስለተባሉ ብቻ ድርጊቱን እንደፈጸሙ በአቃቤ ሕግ ምስክሮች ተረጋግጦባቸዋል ተብሎና በመጨረሻም የዐ/ሕግን ማስረጃ አላስተባበለም በማለት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መስጠታቸው ከላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ የሆኑ የወንጀል ሕግ እና የወንጀል ስነስርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን የጣሰ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች በወቅቱ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ /circumstantial Evidence/ የሠጡ ናቸው ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተገለጸው የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ስለ አከባቢ ማስረጃ ምዘና መርህ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ አይደለም፡፡ ለአንድ የአከባቢ ማስረጃ ክብደት ለመስጠት ማስረጃው ጠንከራ መሆንን ይጠይቃል፡፡ የአከባቢ ማስረጃ ስለጉዳዩ በቀጥታ የማይነግረን በመሆኑ የተወሰኑ ፍሬ ነገሮች መኖራቸው ወይም ያለመኖራቸው ሲረጋገጥ ወደ አንድ ድምዳሜ የምንደርስበት የማስረጃ አይነት ነው፡፡ ስለመሆኑም ፍሬ ጉዳዮቹ ተያያዥነት ያላቸውና ጠንከራ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከዚህ ውጪ ተያያዥነት የሌላቸው ፍሬ ነገሮች መሰረት ተደርጎና የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ያለመኖር ሳይረጋገጥ ለአከባቢ ማስረጃ ክብደት መስጠት የማስረጃው አይነት የምዘና መርህን መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በአገራችን የህግ ሥርዓት ምስክሩ ስለአጠቃላይ ሁኔታዎች በአይኑ የታዘበውን በጆሮው የሰማውንና የሚያውቀውን ፍሬ ጉዳይ ሊስመሰክር እንደሚችልና የምስክሩም ቃል ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 137 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ቃል የአከባቢ ማስረጃ ከሚመዝንበት እና የስሚ ስሚ ማስረጃውም ለጉዳዩ በማስረጃነት ከሚሰድበት አግባብ ወጪ የመሰከሩ ናቸው ከሚባል በስተቀር በቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ የአመልካቾችን የወንጀሉን ተሳታፊነት ያረጋገጡ ናቸው ተብሎ የሚወሰዱ ሁነው አልተገኘም፡፡ በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረው ግለሰብ በ1ኛ እና 2ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ሚች ሞተ በተባለበት ሻይ ቤት በመሳሪያ ያስፈራራቸው ስለመሆኑ የተነገረ ቢሆንም ይህ ግለሰብ ከወንጀሉ ነፃ ከመውጣቱም በላይ ከሚች ተወሰደ የተባለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሳሪያም በኢግዚቪትነት የተያዘ ስለመሆኑ ያለመረጋገጡም የአመልካቾችን የወንጀል ተሳታፊነት ጥርጣሬ ውስጥ የሚከተው ሁኖ አግኝተናል፡፡ አቃቤ ሕግ በዚህ ሰበር ችሎት አመልካቾች ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ ቢወሰን በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተዕጽኖ ገልፆ መከራከሩ አመልካቾች በወንጀሉ የነበራቸውን ተሳትፎና በወንጀል ጉዳይ ማስረጃ የሚመዘንበትን መርህ መሰረት ያላደረገና የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሲጠቃለል ከሳሽ ዐ/ሕግ በአመልካቹ ላይ ባቀረበው የግፍ ግድያ የወንጀል ክስ መሰረት ለማስረዳት በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ባልወጣበት ሁኔታ ክሱን የተመለከተው የዞን አንድ ከ/ፍ/ቤት ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሰጠው ትዕዛዝም ሆነ በመጨረሻ የሰጠውና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ በአብላጫ ድምጽ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 0206782 ጥር 26 እና የካቲት 06 ቀን 2006 ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ./ቁጥር 09870 መጋቢት 23 ቀን 2006 ዓ/ም የፀናውና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 39613 በ12/06/2007 ዓ.ም. የተሻሻለው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 195(2)(ለ)(1) መሰረት በድምጽ ብልጫ ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ አመልካቾች ወንጀሉን ማድረጋቸውን ያላስረዳ እና በሕግ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታ ያልተወጣ በመሆኑ አመልካቾች ከተከሰሱበት የከባድ ውንብድና የወንጀል ክስ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. በአመልካቾች ላይ ተጥሎ የነበረው የአስራ አራት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት የተሻረ በመሆኑ የሚፈለጉበት ሌላ ጉዳይ አለመኖሩን አረጋግጦ አመልካቾችን ዛሬውኑ ከእስር እንዲለቃቸው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ትዕዛዝ ይተላለፍ፡፡ ይፃፍ፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች እና ለአውሲረሱ ማረሚያ ቤት ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የልዩነት ሐሳብ

ሰሜ በ5ኛ ላይ የተጠቀሰው ዳኛ የአብላጫ ድምጽ ከሰጠው ውሳኔ እንደሚከተለው በመለየት ሐሳቤን አስቀምጣለሁ፡፡ ከዚህ መዝገብ ውስጥ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ያቀረበው ክስ የስር 1ኛ ተከሳሽ እና የአሁን አመልካቾች የወ/ህ/ቁ.32/1፣ሀ/ እና 671(2) በመተላለፍ ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ/ም በግምት ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት እስከ 6፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ የግል ተበዳይ ዉላለም ግዛቸው የሚባለውን በአሰቃቂ ሁኔታ ደብድበው ገድለው እሬሳውን ጥለው ይዞት የነበረውን ጠመንጃ የወሰዱ በመሆኑ ከባድ የውንበድና ወንጀል ፈጽመዋል ተከሷል፡፡ አመልካቾች ፍ/ቤት ቀርበው በሰጡት የእምነት ክህደት ቃላቸው ወንጀሉን አልፈጸምንም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቶች የግራ ቀኝ የሰው ምስክሮች በመስማት ተጨማሪ የሰው ማስረጃ መስማት፣ የፖሊስ ማስረጃ በማስቀረብ በማየት በሰጡት ውሳኔ የስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ስንሻው አለሙ ከክሱ በነጻ በማሰናበት፣ የአሁን አመልካቾችን በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው በማለት የእስራት ቅጣት የወሰኑ መወሰናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካቾችን ወንጀሉን አልፈጸምንም፣ በመከላከያ ምስክሮቻችን ተከላክለናል፣ የስር ፍ/ቤት የጥፋተኝነትም ሆነ የእስራት ውሳኔ ተሸሮ በነጻ እንዲንሰናበት የሚል አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች የተከሰሱበተን ወንጀል ስለመፈጸማቸው የዐ/ህግ ምስክሮች በሚገባ ስላረጋገጡ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸናልን በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር የስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ካረጋገጡት ነገሮች አንጻር ማይት አስፈላጊ ነው፡፡ የዐ/ህግ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች የወንጀል ድረጊቱ ተፈጸመ በተባለ ቀን ምሽት በሚች ጋር 1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ጀምሮ እንደነበሩ፣ ሚችን እዛው ትተው ለሽንት ወጥተው ስመለሱ የሻይ ቤቱ መብራት ጠፍቶ የሻይ ብርጭቆና የአረቄ መለኪስ ኳኳ የሚል ድምጽ እንደሰሙ፣ ዓለ የተባለው ምስክር ምንደነው ብሎ ሲጠይቅ የስር 1ኛ ተከሳሽ ምን ሰማህ በማለት መሳሪያ ሲያቀባብል ለህይወታቸው ፈርተው ሸሽተው እንደሄዱ መስክሯል፡፡ 3ኛ ምስክር ደግሞ በሰጠው ቃል ጠዋት ወደ ሌላ ቦታ ሲሄድ ሚች ወድቆ ሞቶ እንደገኘ ሚች ከወደቀበት እስከ ከ1ኛ አመልካች ቤት የደም ነጠብጣብ መኖሩን መስክሯል፡፡

ስለዚህ እነዚህ የዐ/ህግ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሲታይ የአከባቢ ማስረጃ ይሁኑ እንጂ ከሚች ጋር የ1ኛ አመልካች ሻይ ቤት እንደነበሩ እና ሌሎች አመልካቾች እዛው እንደነበሩ ሚችን ሻይ ቤቱ ውስጥ ትተው ለሽንት ወጥቶ ስመለሱ የሻይ ቤቱ መብራት ጠፍቶ የሻይ ብርጨቆ እና የአርቂ መለኪያ ኳኳታ ድምጽ እንደሰሙ እና 1ኛ ተከሳሽ ወደ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳይገቡ አድርጓቸው ለሕይወታቸው ሲሉ ሸሽቶ ከቦታው መሄዳቸው ሲታይ ሚች ከዚህ ሻይ ቤት እንደነበር ያመለክታል፡፡ ሚች በዚህ ሻይ ቤት ውስጥ ከምስክሮች ጋር እንደነበረ በመረጋገጡ፣ ሚች ከምስክሮቹ ጋር አብሮ ወጥቶ መሄዱ እስካልተረጋገጠ ድረስ፣ ምስክሮቹ ከሄዱ በኋላ እንኳን ወጥቶ መሄዱ እስካልተረጋገጠ ድረስ፣ ሚች በ1ኛ አመልካች ሻይ ቤት እያለ የተገደለ መሆኑን ያመልክታል፡፡ በዚህ ሻይ ቤት ውስጥ በዛን ሰዓት ከአመልካቾች በቀር ሌላ ሰው መኖሩን የሚያረጋግጥ ነገር የለም፡፡ አመልካቾች በ1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ውስጥ እያሉ ሚችም እዚያው ሻይ ቤት ውሳጥ እያለ የግዱያ ወንጀል የተፈጸመበት በመሆኑ አመልካቾች ውጭ ሌላ ሰው ይህን የግድያ ወንጀል ፈጸሟል ለማለት የሚያስችል ነገር የለም፡፡ ከዚህም በላይ የስር ፍ/ቤቶች የፖ/ሊስ ምርምራ መዝገብ ማስቀረበ ያዩ መሆናቸውን መዝገቡን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ እነዚህ የዐ/ህግ ምስክሮች የአከባቢ ምስክሮች ቢሆኑም አመልካቾቹ ሚች ዉባለም ግዛቸው የሚባለውን ሰው ገድለው ይዞ የነበረውን ጠመንጃ መውሰዳቸውን ለማስረዳት በቂ ማስረጃ (sufficient evidence) ሊሆን የማይችሉበት ምንም ተጨባጭ ምክንያት የለም፡፡ ይህ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት አመልካቾች በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.142(1) መሰረት መከላከያ ምስክሮቻቸውን አቅርበው እንዲከላከሉ ብይን መስጠታቸውን በአግባቡ ነው፡፡

በመቀጠል መታየት ያለበት ጉዳይ አመልካቾች ባቀረቡት የሰው ምስክሮች የዐ/ህግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ጥርጣሬ ላይ እንዲወድቅ አድርገዋል ወይ? የሚለውን ነጥብ መልስ ማግኘት ያለበት ነገር ነው፡፡ አመልካቾች መከላከያ ምስክሮቻቸው ቃል ሲታይ 1ኛ አመልካች ቤት መጥተው ቆይተው የሄዱ ጊዜ፣ እሮንድ መጠበቃቸው፣ ሌሎች ተከሳሾች 1ኛ አመልካች ቤት ስለመግባታቸው ጋር ተያይዞ የሰጡት ቃል የዐ/ህግ ምስክሮችን ጥርጣሪ ውስጥ አስገብቷል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ የመከላከያ ምስክሮች በተጠቀሰው ምሽት 1ኛ አመልካች ቤት ሻይ ወይም አረቄ ለመጠጣት ሚች እና የዐ/ህግ ምስክሮች በእርግጠኝነት አለመምጣታቸውን ያመለከቱት ነገር የለም፡፡ እነዚህ ምስክሮች በእርግጠኝነት ሚች እና የዐ/ህግ ምስክሮች አለማምጣታቸውን ካላረጋገጡ ደግሞ የዐ/ህግ ምስክሮች የሰጡትን ቃል ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱበት አቅም አይኖራቸውም፡፡ ይህ በመሆኑን የስር ፍ/ቤቶች አመልካቾች የዐ/ህግ ምስክሮችን የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች ጥርጣሬ ላይ በመጣል አመልካቾች ተከላክለዋል የሚያስብላቸው ነገር ባለመኖሩ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠታቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ በአዋጅ 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ሲታይ የስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጡትን እውነታ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት መቀበል ይገበዋል፡፡ በመሆኑም የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና አማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም እላለ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅጣትን በተመለከተ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የጽኑ እስራት ቅጣት ሊጸና ይገባል፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል እንጂ አመልካቾች ነጻ እንዲሰናበቱ የሚያበቃቸው ምክንያት የለም በማለት የልዩነት ሐሰቤን አስቀምጣለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 118252

ቀን 24/05/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀንዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ሀብታሙ አያሌው - ጠበቃ አመሃ መኮንን - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ህግ - ዐ/ህግ ብርሃኑ ወንድምአገኘሁ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ በሽብር ወንጀል የተከሰሰ ሰው ክሱ ምንም መከላከል ሳያስፈልገው በነጻ ሲሰነበት በዚሁ ብይን አቃቤ ህግ ይግባኝ ለበላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የስር ፍርድ ቤት የነጻ መለቀቅ ብይን እንዲታገድለት ሲያመልክት ተቀባይነት የሚያገኝበትን የህግ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሌሎች ዘጠኝ ግልሰቦች ጋር የተከሰሱበት የጸረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ከሽብር ቡድን ጋር የተለያዩ ግንኙነቶች በመፍጥር የሽብር ቡድኑ በኢትዮጵያ ሊያደርግ ያሰበውን የሽብር እንቅስቃሴ በመምራት በስሩም አባላትን በመመልመል፣ ከሽብር ድርጅቱ አባልና አመራሮች ጋር ግንኙነት በማድረግ፣ የሽብር ቡድኑን ዓላማ፣ ተግባር እና ተልእኮ ለመፈጸም በመንቀሳቀሳቸው በፈጸሙት የሽብርተኝነት ድርጊት ማቀድ፣ መዘጋጀት፣ ማሴር፣ ማነሳሳት እና መክራ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ነው፡፡ አመልካቹ የወንጀል ድርጊቱን ክደው በመከራከራቸው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸው ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቶአል፡፡ ከዚህም በኃላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አቃቤ ሕግ አመልካቹ የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ስለመፈፀማቸው እንደ ክሱ አላስረዳም በማለት አመልካቹን ምንም መከላከል ሳያስፈልጋቸው ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱና ማረሚያ ቤቱም ከእስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወዲያውኑ እንዲፈታቸው በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ብይን የአሁን ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑን አመልካች እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ሳይሰጥ አመልካቹ በነፃ እንዲሰናበቱ በተሰጠው ብይን መሰረት ከእስር እንዲለቀቁ የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲታገድ የአሁኑ ተጠሪ አመልክቶ ፍርድ ቤቱም የተጠሪን ጥያቄ መነሻ በማድረግ የአመልካችን የነፃ መለቀቅ ትዕዛዝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 188(5) ድንጋጌ መሰረት ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤተታ የቀረበውም ይህንኑ የእግድ ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በስር ፍርድ ቤት አመልካች በነጻ እንዲሰናበቱ የተሰጠው ትዕዛዝ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የታገደው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ድንጋጌ ተጠቅሶ መሆኑን የሚዘረዝር ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ትዕዛዝ እና ከግራ ቀኙ ክርክር አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ችሎት እንዲታይ በሰበር አጣሪ የተያዘው ጭብጥ አመልካች በነጻ እንዲሰናበቱ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 188(5) ተጠቅሶ መታገዱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ፍርድ ቤት በአንድ ጉዳይ ላይ ዳኝነት መስጠት የሚገባው በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት አድርጎ ዳኝነት በመስጠት ሂደት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ መለየትና ተፈጻሚ ማድረግ የግድ ይላል፡፡ የፀረ ሽብር አዋጅ ተጠቅሶ ክስ የቀረበበት ሰው ክርክሩ የሚመራበት አግባብ በአዋጁ አንቀጽ 36 የተመለከተ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት የጸረ ሽብር አዋጁን መሰረት አድርገው የሚቀርቡ ክርክሮች በአዋጁ በራሱ በተጠቀሱት የስነ ስርዓት ደንቦች እንዲሁም ከአዋጁ ጋር ተቃርኖ ከሌለ ደግሞ በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዴ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግና በ1954ቱ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ የሚመሩ መሆኑን ተጠቃሹ የአዋጁ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የጸረ ሽብር አዋጅ መሰረት ክስ ቀርቦበት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ከተሰሙ በኋላ አንድ ሰው በነፃ ቢሰናበት አቃቤ ሕግ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ብሎ የስር ፍርድ ቤት የነፃ መለቀቅ ብይንን ማሳገድ የሚችልበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን የአዋጅ ቁጥር 652/2001 ድንጋጌዎች አያሳዩም፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 36 መሰረት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 188/5/ ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄ ሲነሳም ይህ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ አርዕስቱ ፍርድ እንዳይፈፀም ስለማገድ የሚል ያለው ሁኖ ዘርዝሮ ይዘቱ በተለይም የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አምስት ሲታይ ይግባኙ ከመሰማቱ በፊት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማንኛውም ጊዜ ወይም ይግባኙ በሚሰማበት በማንኛውም ጊዜ ፍርዱ እንዲታገድ ለይግባኝ ፍርድ ቤት ማመልከት እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ የዚህ ንዑስ ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ በአንቀፁ ንዑስ አንድ ድንጋጌ ስር ያለውን ድንጋጌ ዉጤታማ ለማድረግ ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን የወንጀል ጉዳይ ከሰው ልጅ ነፃነት፣ ሕይወትና ክብር ጋር እጅጉን የተቆራኘ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ፍርድ ቢፈፀም በእነዚህ መብቶች ላይ ሊመለስ የማይችል ጉዳት ሊደርስ ስለሚችል ከወዲሁ ለመከላከል ነው ተብሎ መሆኑ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ፍርዱ በተከሳሹ ከተሰጠ ተከሳሹ ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብሎ ሲቀርብ የበታች ፍርድ ቤትን ውሳኔ የበላይ ፍርድ ቤቱ ማገድ የሚችልበትን አግባብ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 188/5/ ድንጋጌ የሚያስገነዝብ ከመሆኑ ውጪ ከሳሽ ወገን በነፃ መለቀቅ ላይ ይግባኝ ብሎ ሲሄድ ፍርዱ እንዳይፈፀም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመስጠት መነሻ የሚያደርገው ድንጋጌ ነው ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሆኖም አንድ ተከሳሽ በነፃ ሲሰናበት አቃቤ ሕግ ይግባኝ ብሎ ፍርዱን ለማሳገድ የሚችልበት የሕግ መሰረት የለም ማለት ግን አይደለም፡፡ የፀረ ሙስና ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጎችና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 63 እና 67 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌወችን መሰረት በማደረግ በነፃ የተለቀቀ ተከሳሽ በማረሚያ ቤት ሁኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ማድረግ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው ግን ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በነፃ እንዲሰናበቱ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤትን ብይን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 188/5/ መሰረት ያገደው ድንጋጌው ለጉዳዩ አግባብነት ሳይኖረው ሁኖ አግኝተናል፡፡

በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው የፍርድ ቤቶች መደበኛ የስራ ጊዜ በተዘጋበት ተረኛ ችሎት በተመደበበት አግባብ ሲሆን ዋናውን ጉዳይ ሳይመረምር የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ እንደሚመጣ ብሎ ከአዘዘ በኃላ የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ከመቅረቡ በፊት ስለመሆኑ ከትዕዛዙ ግልባጭ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ቀርቦ መ/ሰጪን የሚያስቀርብ የህግና የፍሬ ነገር ነጥብ ስለመኖሩ የሚያሳይ ትዕዛዙ በተረኛው ችሎት አልተሰጠም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ከቀረበ በኋላ በዋናው ጉዳይ ላይ ግራ ቀኙን ለማከራከር የሚያስችል የህግና የፍሬ ነገር ነጥብ መኖሩ ላይ ተገቢውን ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው መደበናው ችሎት መሆኑን ተረኛው ችሎት በ15/12/2007 ዓ/ም ከሰጠው ትዕዛዝ በኃላ ያሉት ጊዜያትና የክርክር ሂደቶች የሚያስገነዝቡት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ዋናውን ጉዳይ ማየት የቀጠለው መደበኛ ችሎት አመልካች ጉዳዩን በውጪ ሁነው የማይከታተሉበት ህጋዊ አግባብ መኖር ያለመኖሩ ላይ አግባብነት ያለውን ህግና ድንጋጌ በመለየት ብይን ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ15/12/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 117340 በ15/12/2007 ዓ/መ የተሰጠው እግድ የህግ መሰረት የለውም በማለት በድምጽ ብልጫ ሽረናል፡፡ በሌላ በኩል መደበኛው ችሎት በዋናው ጉዳይ ክርክር ቀጥሎ ከሆነ አመልካች ከእስር ውጪ ሁነው ጉዳዩን መከታተል የማይችሉበት የህግ መሰረት መኖር ያለመኖሩን ተመልክቶ ተገቢውን ትዕዛዝ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተራ ቁጥር ሶስት የተመዘገብኩት ዳኛ የስራ ባልደረቦቼ በሰጡት ፍርድ ባለመስማማት የልዩነት ሐሳቤዩን እንደሚከተለው አስፍሬአለሁ፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረኛ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 117340 ነሀሴ 15 ቀን 2007 ዓ/ም ችሎቱ የሰጠው ትዕዛዝ ሲሆን በትዕዛዝ ክፍሉም የቀረበውን ይግባኝ ቅሬታ መርምሮ ተገቢ ትዕዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 158194 በ14/12/2007 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ ከመፈጸም ታግዶ እንዲቆይ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 188(5) መሰረት ትዕዛዝ መስጠቱን ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ የውሳኔ ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡

የአሁኑ አመልካች አቶ ሀብታሙ አያሌው ከሌሎች ዘጠኝ ግለሰቦች ጋር ከተከሰሱበት የፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4 የተመለከተውን በመተላለፍ የሽብር ወንጀል በማቀድ፣ በመዘጋጀት፣ ማሴር እና መነሳሳት ወንጀል ዐቃቤ ህግ እንደክሱ አላስረዳም ተብሎ ከክሱ በነጻ እንዲሰናበቱና ማረሚያ ቤቱም ከእስር ወዲያውኑ እንዲፈታቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመወሰኑ ምክንያት የአሁኑ ተጠሪ በጉዳዩ ይግባኝ በመጠየቅ ፍርዱ እንዳይፈጸም ዕግድ አሰጥቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት መሰረታዊ የክርክር ነጥብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረኛ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ የሰበር አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስችል ህጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ አንድ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ብቁ ሁኖ ሊታይ የሚችለው ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ስለመሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ነው። በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10(2) በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ብቁ የሚሆነው አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ (Final court decision) ያገኘ መሆን ያለመሆኑን በቅድሚያ መረጋገጥ ያለበት መሰረታዊ ነጥብ ስለመሆኑ የድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝቡናል። በመሆኑም ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ፍርድ ባለገኙ ጉዳዮች ውሳኔ የመስጠት ስልጣንና ኃላፊነት ያልተሰጠው መሆኑን መረዳት ይቻላል። በሌላ አገላለጽ ለሰበር ብቁ ያልሆኑ የመጨረሻ ፍርድ ያላገኙ ጉዳዮች በሰበር ሰሚ ችሎት ሊስተናገዱ የሚችሉበት ስርዓት አይኖርም።

አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ መሆን ያለመሆኑን ለመለየት በመመዘኛነት መታየት ያለባቸው መሰረታዊ ነጥቦች ምን ምን ናቸው? የሚለው አንኳር ነጥብ አገርቷ ከምትከተለው የህግ ስርዓት ጋር ተገናዝቦ መታየት ይኖርበታል። አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው አከራካሪ ጭብጥ ለመፍታት እንደመነሻ ከሚወሰዱ ነገሮች በፍርድ ቤቶቻችን የዳበረው አሰራር፤ የምንከተለው የህግ ስርዓት እና ሰበር ሰሚ ችሎቱ የራሱ የሆነ የስነ ስርዓት ህግ ያልተቀረጸለት በመሆኑ በህገ መንግስቱ የተጠቀሰው "የመጨረሻ ውሳኔ" የሚለው ቃል ይዘት ከህግ አወጭው ሐሳብ በተጣጣመ መልኩ በመተርጎም እና በመደበኛ እንደሁም ከስነ ስርዓት ህጎቻችን መሰረታዊ ድንጋጌዎች አንጻር መመልከቱ ተገቢ ይሆናል። ከዚህ በተያያዘ በስነ ህግ (jurisprudence) የዳበረው የአተራጓጎም ስርዓት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ሲባል መሰረታዊ ህጋዊ መስፈረቱ ምንድነው? የሚለው እንደአግባብነቱ ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚ የሚሆንበት ስርዓት ይኖራል።

ከላይ እንደተመለከትነው አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው መሰረታዊ ነጥብ ሊመዘን የሚችለው በተያዘው ጉዳይ ምንም የተንጠለጠለ ነገር የሌለው፤ የይግባኝ ሂደቱ አማጦ የጨረሸ፣ በጉዳዩ በተያዙ አከራካሪ ነጥቦች መልሶ ማየት በማያስችል መንገድ ዕልባት የተሰጠበት መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። በስነ ህግ በዳበረው የአተረጓጎም ስርዓትም አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘነው የሚለው ሲታይ፡- final decision generally is one which ends the litigation on the merit and leaves nothing for the court to do but execute the judgment በማለት ትርጉም የተሰጠው ሲሆን ይህ ትርጎም በግርድፍ ወደ አማርኛ ስንመለስው አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ አገኘቷል ለማለት የሚቻለው በሚያከራክረው ጭብጥ ላይ የመጨረሻ መቋጫ ያገኘ ሲሆን እና ጉዳዩ እንደ ፍርዱ ከመፈጸም ወጭ ሌላ አማራጭ የሌለው የውሳኔ ዓይነት መሆኑን ሲርጋገጥ ብቻ ነው። ከዚህ በተያየዘ በመጀመሪያ መቃወሚያ ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትዕዛዝ ላይ የሰበር አቤቱታ መቅረብ እንደማይችል በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ረገድ የዳበረው የሰነ ህግ ትርጉም ያመልክታል። (preliminary ruling and temporary injunctions may not qualify a case to be reviewed by way of cassation) ከዚህ የምንገነዘበው ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ትዕዛዙን በሰጠው ችሎት በራሱ ጊዜ መልሶ ሊያስተካክለው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው የሚችል ነው። የመጀመሪያ መቃወሚያ ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸው ትዕዛዞች በተከራካሪ ወገን መብት እና ነፃነት ላይ ለጊዜው ገደብ አይጥሉም ባይባልም በዚህ አግባብ የሚሰጥ ትዕዛዝ ግን የመጨረሻ ውሳኔ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም።

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከእስር እንዲፈቱ የተሰጠው ትዕዛዝ ለጊዜው መታገዱን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረኛ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዕግድ የሰጠበት የህግ ድንጋጌ ተገቢ ባይሆንም የትዕዛዙ ይዘት ሲታይ ግን አመልካች ከእስር እንዲፈቱ ገደብ የተደረገው ጉዳዩ በይግባኝ እስከሚታይ እንጂ ሊታረም የማይችል በፍሬ ጉዳዩ (merit of the case) የመጨረሻ ውሳኔ መስጠቱን አያሳይም። ከላይ እንደተመለከተው አንድ ጉዳይ ለሰበር ብቁ የሚሆነው የተሰጠው ትዕዛዝ (ውሳኔ) ፍርድ ይዘትና መንፈስ ሲታይ የመጨረሻ እና ጉዳዩ በያዘው ፍ/ቤት መልሶ የማይታርም ሲሆን ብቻ ነው። በያዝነው ጉዳይ በአመልካች ላይ የቀረበው የዐቃቤ ህግ ይግባኝ ፍርድ ቤቱ ሊቀበለው ወይም ላይቀበለው ይችላል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች በእስር ይቆይ ጥያቄ የአሁኑ ተጠሪ ያቀረበው ይግባኝ አቤቱታ በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ካገኘ እና የዐቃቤ ህግ ክስና ማስረጃ እንዲከላከል የሚታዘዝ ከሆነ አመልካች የተጠረጠሩበት ወንጀል ዓይነትና ክብደት መሰረት ተደርጎ የዋስትና ጉዳይ የሚታይ ይሆናል። ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን የሚያጸና ከሆነም ስርዓቱን ጠብቆ ለሰበር የሚቀርብ አቤቱታ ቢኖርም ባይኖርም ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ የሚገኝ በመሆኑ የአመልካች በእስር ይቆይ ትዕዛዝ ህጋዊ ውጤት በተሰጠው ውሳኔ ምክንያት የሚያበቃ ነው። ከዚህ አንጻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረኛ ችሎት አመልካች ከእስር እንዳይለቀቁ የሰጠው ትዕዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም። ከላይ እንደተመለከተው በአመልካች ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ ይዘት እና ባህሪ ችሎቱ በራሱ ጊዜ መልሶ የሚያርመው ነው። በመሆኑም የአመልካች የሰበር አቤቱታ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ያልቀረበ ጊዜያዊ ዕገዳ (temporary injuction) መሆኑ እየታወቀ ለሰበር ብቁ ነው መባሉ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ (3) (ሀ) እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ እንደተሻሻለ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ የተከተለ ሆኖ አልተገኘም።

የሰበር ስርዓት የተዘረጋበት አይነተኛ ዓላማ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለ በማረም የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ስለመሆኑ ከአጠቃላይ የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጽንስ ሐሳብና ዓላማ የምንረዳው ነው፡፡ የሰበር ስርዓት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው ውሳኔዎች በማረም በአንድ አገር በተቻለ መጠን ወጥ የሆነ የህግ አተርጓጎም እና አፈጻጸም (in order to attain uniform application and interpretation of laws throughout the nation) እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር አንድ ጉዳይ በሰበር እንዲታይ እንደመሰረታዊ ቅድመ ሁኔታ የሚወሰድ አስገዳጅ ህጋዊ መስፈርት ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ መሆን ያለመሆኑን ህገ መንግስቱና ተከታይ አዋጆች መሰረት በማድረግ መመዘን ነው፡፡ ህግ አወጪው የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ የሚፈጸም መስረታዊ የህግ ስህተት ካለ እና ይህ ስህተት ሳይታረም እንደረጋ ወይም እንደጸና የሚቆይ ከሆነ በአንድ አገር ህዝብ፤ መንግስት እና ዜጎች መብትና ጥቅም ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ የህግ የበላይነትን (rule of law) ከማረጋገጥ አንጻር ያለው ዓይነተኛ ትርጉም እና ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ታሳቢ በማደረጉ ስለመሆኑ ከህገ መንግስቱ እና ተከታይ ድንጋጌዎች (አዋጆች) የምንገነዘበው ነው፡፡ በሌላ በኩል ሰበር ሰሚ ችሎቱ መሰረታዊ ያልሆኑ የህግ ስህተቶች የማረም ስልጣን ይሁን ኃላፊነት አልተሰጠውም፡፡ የፍሬ ነገር ክርክር እና የማስረጃ ምዘና ስርዓትም ከሰበር ስልጣን ውጭ መሆኖቸው ልብ ይሏል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አከራካሪ ሁኖ የቀረበው የፍርዱ ለጊዜው እንዳይፈጸም የማገድ ጉዳይ በአመልካች ላይ ለጊዜው በእርስር መቆየትን ማስከተሉ ግልጽ ቢሆንም የተረኛ ችሎቱ ትዕዛዝ የማይታረም የመጨረሻ ውሳኔ (ትዕዛዝ) ነው ለማለት የሚያስችል አንዳችም የህግ መሰረት የለውም፡፡

አከራካሪው ትዕዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በክርክር ጊዜ ሊያረመው የሚችል ወይም የይግባኝ ሂደቱ ካበቃ በኃላ ህጋዊ ውጤቱ የሚያበቃ ትዕዛዝ መሆኑ እየታወቀ እንደ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ መወሰዱ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእነዚህ ሁሉም ምክንያቶች የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረኛ ችሎት የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙ እስከሚታይ (እስከሚሰማ) ማገዱ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዘዝ ሰጥቷል ከሚባል በስተቀር የመጨረሻ ውሳኔ እንደሰጠ መቆጠሩ በህጉ አግባብ አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ በጊዜያዊ ዕግድ ላይ የተመሰረት እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት መሆኑን ግንዘቤ በመወሰድ ጉዳዩ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት መዝገቡ መዘጋት ሲገባው በፍሬ ጉዳዩ ውሳኔ እንደተሰጠ ግምት በመወሰድ ውሳኔ መስጠቱ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3) (ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተመለከተው “የመጨረሻ ውሳኔ” (Final decision) መስፈርት የማያሟላ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት በልዩነት ሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 111498

የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አቃቤ ሕግ

- የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ሃብታሙ ካርሎ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በሀድያ ዞን የሆሳእና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱም ይዘትም፡- ተጠሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2)(ሐ) ስር በመተላለፍ ተጠሪ በሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ ጉዳት ለማድረስ አስቦ በቀን 14/05/2006 ዓ/ም ከቀኑ በግምት 6፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በሆሳዕና ከተማ ሜእእል አምባ ቀበሌ ልዩ ስሙ ውሃዋና ፊት ለፊት ባሉ መጋዘኖች አከባቢ ወ/ሮ ነፃነት አለሙ የተባለችውን ሚስቱን አንገቱን አንቆ በመያዝ አንድ ጊዜ በቀኝ እጁ በጥፊ ፊቷን ሲመታት በአፏና በጥርሷ ላይ ደም ከመፍሰሱም በላይ በግንባሯ ላይ በቦክስ አንድ ጊዜ ሲደግማት ወዲያውኑ መሬት ላይ እንደወደቀች ፖሊሶች ደርሰው ያስጣሉት በመሆኑ በሰው አካል ላይ ቀላል የአካል ጉዳት አድርሷል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ክሱ ድርሶት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ሲጠየቅ ወንጀሉን አልፈጸምኩም፤ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ሁለት የሰው ምስክሮችን ከሰማና ማስረጃዎቹ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ከመረመረ በኃላ በግል ተበዳይ ላይ ተጠሪ በክሱ የተገለፀውን ተግባር ስለመፈፀሙ የተመለከተ ምስክር የሌለ መሆኑ መረጋገጡን ገልጾ ተጠሪን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክሱ ምንም መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ ያሰናበተው ሲሆን አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን፣ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም ተጠሪ ሳይጠራ ቅሬታው ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በግል ተበዳይ ላይ በተጠሪ የአካል ጉዳት ስለመድረሱ በተረጋገጠበትና ማን እንደአደረሰው ደግሞ ለፍርድ ቤት ቀርበው የምስክርነት ቃል የሰጡት ፖሊሶች በምርመራ ጊዜ መስክረው ፍርድ ቤት ሲቀርቡ መቀየራቸው እየታወቀ የሥር ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል ሲቀበል ተገቢውን ጥያቄ ሳይጠይቅና የግል ተበዳይ ቀርባ እንድትመሰክር ያለማድረጉና፣ ፖሊሶች በምርመራ ጊዜ የሰጡትን ቃል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 145(1) አስርቀቦ ሳይመለከት ተጠሪን በነፃ ማሰናበቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

ከሥር የክርክሩ አምጣጥና ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ አልተመሰከረበትም በሚል ምክንያት በነፃ እንዲሰናበት ማድረጋቸው ህግን መሰረት ያደረገ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የአካል ጉዳት አድርሷል ተብሎ የተከሰሰው በሚስቱ ላይ ሲሆን ይህ አድራጎት ሲፈፀም በጊዜውና በቦታው ደርሰው የግል ተበዳይን ከድብደባው ተግባር ያስቀሯት ሁለት ፖሊሶች መሆናቸው በአመልካች ክስ ተጠቅሶ እነዚህ ፖሊሶች ለምስክርነት ተቆጥረው ፍርድ ቤት ቀርበው የመሰከሩ መሆኑን፣ ፖሊሶቹ ፍርድ ቤት ቀርበው በተመሳሳይ የሰጡት ምስክርነት ቃል ደግሞ በጊዜው በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በጥበቃ ስራ ላይ የነበሩ መሆኑን፣ ተጠሪ ቀደም ሲል ፖሊስ ጣቢያ ገብቶ እንደነበር፣ የግል ተበዳይ ከቀኑ 6፡00 ላይ መጥታ ከተጠሪ ጋር ጭቅጭቅ ስትፈጥር ጊዜ በዚያ ግቢ ውስጥ እንዲህ አይነት ጭቅጭቅ መፍጠር አግባብ ያለመሆኑን አስረድተዋት የግል ተበዳይን ያረጋጉ መሆኑን፣ ሆኖም የግል ተበዳይ በግንባር ላይ እብጠት ይታይባት እንደነበርና አፏ ላይም ደም ይታይባት የነበረ ቢሆንም ማን እንደመታትና እንዳቆሰላት የማያውቁ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን፣ ፖሊሶቹ በጥበቃ ስራ ላይ የነበሩና የግል ተበዳይ ጉዳት ደረሰባት የተባለው በሜዕላባ ቀበሌ ልዩ ስሙ ውሃ ዋና ፊት ለፊት ሁኖ በዚህ ቦታ ላይ የነበረውን ክስተት ምስክሮቹ እንደማያውቁና በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ስለነበረው ሂደት የመሰከሩ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎቹን መዝኖ በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጣቸው ነጥቦች መሆናቸውንና በዚህ ረገድ ተመሳሳይ ስልጣን ያለው የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተመሳሳይ ድምዳሜ ላይ የደረሰ መሆኑን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በዚህ የክርክር ደረጃ አጥብቆ የሚከራከረው የስር ፍርድ ቤት ምስክሮቹ መጠየቅ ይገባቸው የነበራቸውን ማጣሪያ ጥያቄዎችን አልጠየቀም፣ ፖሊሶቹ በምርመራ ጊዜ የሰጡት የምስክርነት ቃል ፍርድ ቤት በቀረቡ ጊዜ ለውጠው በወንጀልም የተቀጡ በመሆኑ በምርመራ ጊዜ የሰጡት የምስክርነት ቃላቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 145(1) ቀርቦ መታየት ነበረበት፣ የግል ተበዳይም ለምስክርነት የተቆጠረች በመሆኑ መሰማት ነበረባት በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ክርክር ሂደት ምስክሮች ሲጠየቁ በተከራካሪ ወገኖችም ሆነ በፍርድ ቤት የሚጠየቁ ጥያቄዎች አይነታቸው የትኞቹ እንደሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር ጥር 137፣ 138 እና 140 ስር የተመለከተ ሲሆን የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ስርዓትም በዚሁ ሕግ ተመልክቶአል፡፡ አቃቤ ሕግ ክሱን ያስረዱልኛል ብሎ የቆጣራቸው ምስክሮችን ሲያሰማ በዋና ጥያቄ ስር ተገቢ ጥያቄዎችን የመጠየቅ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ ሊጠየቅ የሚችለውም ያልተብራራለት የምስክርነት ቃል ሲኖር መሆኑን ስለፍርድ ቤቱ ሚና የሚያመላክተው የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 136 (4) እና 143 (1) ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው በመሰረቱ ማስረጃ ማቅረብና ምስክሮችን መመርመር የዓቃቤ ህግና የተከሳሹ ኃላፊነት ቢሆንም ፍርድ ቤቱም ውስን ሚናዎች የአሉት መሆኑን ነው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎችና በሌሎች ድንጋጌዎች መሰረት ምስክሮችን መመርመር የባለ ጉዳዮች ሚና ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ትክክኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ ምስክሮቹን የማብራሪያ ጥያቄ መጠየቅ እንደሚችል በወ/መ/ህ/ቁ 136/4/ የተመለከተ ሲሆን በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 143/1/ መሰረት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ምስክርነቱ አስፈላጊ ከመሰለው ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማንኛውንም ምስክር /አስቀድሞ ቃሉን የሰጠም ሆነ ያልሰጠ/ መጥራት የሚችል ሲሆን እንዲሁም አቃቤ ህጉ ወይም ተከሳሹ በምስክር ዝርዝር ላይ ያልተጠቀሱ ምስክሮች እንዲቀርቡላቸው በጠየቁ ጊዜም ምስክሮቹ ነገሩን ለማዘግየት ሳይሆን ለትክክለኛ ፍትህ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሮቹ እንዲጠሩ ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተጨማሪ ማስረጃ ሊሰማ የሚችለው ተጨማሪ መስማት የሚያስፈልግ መስሎ ሲታየው ስለመሆኑ በወ/መ/ህ/ቁጥር 194/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ በማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ሂደቶች ፍርድ ቤቱ ስለሚኖረው ሚና ከሚደነግጉት ሕጋዊ ስርዓቶች መረዳት የሚቻለው በሕጉ ተለይቶ የተሰጠውን ሚና ፍርድ ቤቱ ሊያከናውን የሚችለው የፍርድ ቤቱን ገለልተኛነቱን በማይነካ መልኩ በጥንቃቄ መሆን የአለበት መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 136/4/ እና 143 እንዲሁም 194/1/ ድንጋጋዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ ፍርድ ቤት ወይም ዳኛው የቀረበለትን ጉዳይ በተመለከተ ማስረጃ ለመፈለግ የግሉን ምርመራና የምርመራ ስራ ለማድረግ የሚችልበት የዳኝነት አሰጣጥ ስርአት የለም፡፡ እንዲሁም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 145 ላይ አንድ ምስክር በፖሊስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምርመራ ወቅት የሰጠው ቃል ዓቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሹ ባመለከተ ጊዜ የተሰጠውን ምስክርነት ፍርድ ቤቱ ሊመለከተው እንደሚችል የተደነገገ ቢሆንም የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ አላማም በምርምራ ጊዜ ተሰጠ የተባለውን የምስክርነት ቃል በፍርድ ቤት ምስክሩ ቀርቦ ቢለውጠው ይኼው ምስክርነት እንዲቃናና ፍርድ ቤት ለያዘው ክስ ሁልጊዜ ከብደት እንዲሰጠው ለማድረግ ነው ተብሎ አይታሰብም፡፡

ከላይ ከተመለከቱት በወንጀል ጉዳይ የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ስርዓቶች አንጻር የተያዘውን ጉዳይን ስንመለከትም አመልካች ድርጊቱ ሲፈጸም በቦታው ተገኝተው ተመልክተዋል የተባሉት ፖሊሶች ቃላቸውን ስለቀየሩና በወንጀል ስለተቀጡ በምርመራ ጊዜ የሰጡት የምስክርነት ቃል ለማስረጃነት መቅረብ ነበረበት፣ ፍርድ ቤቱም ማጣሪያ ጥያቄዎችን መጠየቅ ነበረበት በማለት የሚያቀርበው የሰበር ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ እንዲሁም የግል ተበዳይ የሆኑት ወ/ሮ ነጻነት አለሙ በስር ፍርድ ቤት መሰማት ነበረባቸው የሚለው ቅሬታውም ምስክሯ በጉዳዩ ምስክር ሁነው እስከተቆጠሩ ድረስ በስር ፍርድ ቤት እንዲሰሙ ማድረግ የአቃቤ ሕግ ግዴታ ሁኖ እያለና ምስክሯ ሳይሰሙ የታለፈበት ሂደት በፍርድ ቤቱ ግድፈት ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት አግባብ በሰበር ቅሬታነት ሊነሳ የሚችልና ተቀባይነት የሚያገኝ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ አቃቤ በሕጉ የተጣለበትን የማስረጃ ማቅረብና ጉዳዩን በበቂና በአሳማኝ የማስረዳት ግዴታውን ባልተወጣበት ሁኔታ በማስረጃ አቀራረብናና አቀባበል ረገድ ለፍርድ ቤቱ በሕጉ በግልጽ ተለይተው የተሰጡት ሚናዎችን ባላገናዘበ መልኩ ፍርድ ቤቱ የምርመራና የምርመር ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል በሚል ይዘትና መንፈስ የቀረበው የአቃቤ ሕግ የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ደግሞ ፍሬ ነገሩን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን ተጠሪ በግል ተበዳይ ላይ በክሱ ላይ የተገለፀውን አድራጎት ስለመፈጸሙ እንደክሱ አልተነገረበትም በማለት በነፃ እንዲሰናበት የሰጡት ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በሆሳእና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15/99 በ06/06/2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13598 ታህሳስ 09 ቀን 2007 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 63871 በ29/05/2007 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡ ፡፡
2. ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ አልተረጋገጠም ተብሎ በነፃ እንዲሰናበት በተሠጠው ብይን የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/120762

የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡-የፌደራል ዐቃቤ ሕግ - ሮዛ በላቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ዱባይ አውቶ ጋለሪ-ኤል.ኤል.ሲ ጠበቃ አበበ አስማረ

2. ወርልድ ኢንተርናሽናል ፍሪዞን ካምፓኒ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 155568 ታህሳስ 28 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 111863 ጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት መዝገቡን በመዝጋቱ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ክስ በቀረበበት ጊዜ በጠበቃ የመወከል ላይ የተሰጠ ትእዛዝ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚገባ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ አመልካች ሲሆን ተከሳሾች እነአሸረፋ አወል አብዩ /17 ሰዎች/ ሲሆን ተጠሪዎች 12ኛ እና 13ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች በተከሳሾች ላይ 6 የተለያዩ ክሶችን ያቀረበ ሲሆን በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ 3ኛ ክስ የወ/ህ/ቁ 32/1/ /ለ/፣ 34/1/ እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 96 የተመለከተውን በመተላለፍ የንግድ ትርፍ ግብር ባለመክፈል፣ 4ኛ ክስ የወ/ህ/ቁ 32/1/ /ለ/፣ 34/1/ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 በመተላለፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግብይት ባካሄዱባቸው ሥራዎች ተጨማሪ እሴት ታክስ አሳውቆ ባለመክፈል፣ 5ኛ ክስ የወ/ህ ቁጥር 32/1/ /ለ/34/1/ እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 37/1/ /ሀ/፣/ለ/ እና 3/ለ/ በመተላለፍ ለባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት መካተት የሚገባውን ነጥብ በማስቀረትና ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ማስረጃ በማቅረብ 6ኛ ክስ የወ/ህ/ቁ 32/1/ /ሀ/ /ለ/፣ 34/1/ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 50/1/1ሀ/ /ለ/ እና /3/ በመተላለፍ ለግብር ሰብሳቢ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት መካተት የሚገባውን ነጥብ በማስቀረት እና ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ማስረጃ በማቅረብ የሚሉ ሲሆኑ 12ኛ ተከሳሽ የነበረው 1ኛ ተጠሪ በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት 13ኛ ተከሳሽ የነበረው 2ኛ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ መሠረት ጠበቃው ቀርበው የክሱ ማመልከቻ የደረሳቸው ሲሆን ፍርድ ቤቱ በጋዜጣ ተጠርተው ባልቀረቡት ላይ በሌሉበት ክርክሩ እንዲቀጥል አዞ በክሱ ላይ የተጠሪዎች ጠበቃን መቃወሚያ መቀበል ሲጀምር አመልካች የተጠሪዎች ሥ/አስኪያጅ እና ባለቤት የሆኑት በክሱ በተራ ቁጥር 14፣15 እና 16 የተጠቀሱት ከህግ ተሰውረዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህን የወከሉ ጠበቃ ለድርድቶቹም መከራከር አይችሉም፡፡ ድርጅቶቹ የሚከሰሱት ሥ/አስኪያጅ ወይም ሠራተኞች በፈፀሙት ድርጊት ነው፡፡ ሥ/አስኪያጅ በሌለበት እንዲታይ ከታዘዘ የድርጅቶቹም ጉዳይ በሌሉበት መታየት አለበት በማለት ያቀረበው ከአቤቱታ በመመርመር አመልካች ያቀረበው ክስ የድርጅቶቹ ከሥራ አስኪያጆች የተለያየ ነው፡፡ በጠበቃ የመወከል መብት ደግሞ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል መብት ነው፡፡ አንድ ድርጅት በወንጀል ህግ ድንጋጌ ተከሳሽ ለመሆን የሚያበቃ ሁኔታ አለ ተብሎ ክስ ከቀረበ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20/5/ መሠረት በጠበቃ የመወከል መብት አለው ይህንን የሚጻረር አሠራርም ሆነ ሌላ ህግ ተፈጻሚነትየሌለው መሆኑን ይደነግጋል ስለዚህ የአሁን ተጠሪዎች በጠበቃ መወከል ይችላሉ አለ፡፡

አመልካች ይህንን ትእዛዝ በመቃወም ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በሰጠው ውሳኔ ዳኝነቱት የሚታየው በህጉ በተመለከተው መሠረት ነው፡፡ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 184 እና 185 በግል ይግባኝ የሚባልባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር የተቀመጠ በመሆኑ አሁን ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ ወደፊት በክርክር መጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ተጠቃልሎ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል እንጂ አሁን በዚህ ደረጃ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት ዘግቶታል፡፡ የአመልካች 8 ገጽ የሰበር አቤቱታ መሠረት ያደረገውም በዚሁ ውሳኔ ሲሆን ይዘቱም የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 184 ይግባኝ የማይባልባቸውን ትእዛዞች የሚዘረዝረው ሆኖ በስር ፍ/ቤት ይህንኑ በመጥቀስ ውድቅ ማድረጉ መሠታዊ ስህተት ነው፡፡ የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 185 የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ላይ የሚቀርብ እንጂ ከዚህ ውጭ በሆኑ ጉዳዮች ይግባኝ ማለት ይቻላል አይልም፡፡ ከቁጥር 184 ጋር ተጣጥሞ ሊተረጐም የሚገባና ከሰበር መ/ቁ 93234 ከተሰጠው ትርጉም ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 127/1/ በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ጠበቃ ብቻውን ሊቀርብ እንደማይችል የሚያሳይ ነው፡፡ የተከሳሽ በጠበቃ የመወከል መብት የተቀመጠው ተከሳሹ በቀረበ ጊዜ ተፈጻሚነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው እንጂ ለመቅረብ ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ አይደለም፡፡ የወ/ህ/ አንቀጽ 34/1/ እንደተመለከተው ድርጅት በወንጀል የሚጠየቀው የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በሰራው ወንጀል በመሆኑና ለጠበቃው ውክልና የሰጠው 15ኛ ተከሳሽ የሆነው የ12ኛ እና 13ኛ ተከሳሽ ድርጅቶች ባለቤትና ሥራ መሪ ከቀረበባቸው ክስ ተሰውረው በሌሉበት እየታየ በጠበቃ ተወክለው መከራከር የህግ መሠረት የለውም፣ በወንጀል ጉዳይ ህጋዊ ሠውነት ያላቸው ድርጅቶት ከድርጅቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጆችና ሠራተኞች ተነጥለው የሚታይ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች በ15ኛ ተከሳሽ በተሰጠ ውክልና እንዲከራከሩ መፍቀድ በሌሉበት እንዲታይ ብይን የተሰጣቸውን ተከሳሾች በጠበቃ እንዲከራከሩ የመፍቀድ ውጤት አለው፡፡ ስለዚህ በወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ ላይም ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቱም የስር የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ከወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 184 እና 185 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች በጠበቃ መወከል አይችሉም በማለት አመልካች ያቀረበው ተቃውሞ የመሰረታዊ ህግም ሆነ የስነ-ሥርዓት ህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ፍ/ቤቱ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 184 ውጭ በመሆኑ ሊያልፈው ይገባ ነበር፣ በጠበቃ የመወከል መብት ሕገ-መንግስታዊ ሆኖ በአንቀጽ 20/5/ የተደነገገ ሲሆን አመልካችም በውጤት ደረጃ በወንጀል ፍትህ ሥርህቱ የሚያስገኘው አሉታዊ ተጽዕኖ አንጻር አክብሮ ሊቀበለው የሚገባ ነው፣ ሰበር መ/ቁ 93234 የሰጠው ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 185 /2/ የይግባኝ መብቱ የተገደበውን አመልካችን የሚመለከት አይደለም፡፡ ከአመልካችና ከተጠሪ ክርክር ጋር ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፣ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በመልስ ሰጪዎችላይ የወንጀል ዳኝነት ሥልጣን የላቸውም፣ የወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 127/1/ እና 197 ተፈጻሚ የሚሆነው ለተፈጥሮ ሠዎች እንጂ የህግ የሰውነት ባላቸው ሰዎች አይደለም፣ አንድ ሠው በግሉ የተከሰሰበት ጉዳይ በሥ/አስኪያጅነት ከሚመራው የህግ ሠውነት ካለው ድርጅት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፣ ውክልና ለመስጠት መብት ያለው የተፈጥሮ ሠው ስለድርጅቱ በመሆን ጠበቃ መወከል የተፈቀደ ተግባር ነው፡፡ ተጠሪዎች ከ14፣15 እና 16ኛ ተከሳሾች ጋር ፈፀሙ ያለው ተግባር ምንም ግንኙነት የለውም ተጣምረው ወይም በግብረ አበርነት የቀረበባቸው ክስ የለም፣ የወ/ህ/ቁ 34/1/ ተፈጻሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ ለተመዘገቡ ድርጅቶች ሲሆን ተጠሪዎች ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገቡ ዓለምዓቀፋ የንግድ ድርጅቶች ናቸው ስለዚህ በተጠሪዎች ላይ ተፈጻሚነት የለውም፣ የድርጅት የወንጀል ኃላፊነት የሥ/አስኪያጅ የወንጀል ኃላፊነት አያስከትልም 15ኛ ተከሳሽ የተከሰሰው በራሱ በግሉ ሲሆን ከተጠሪዎች ጋር ክስ አልቀረበበትም፣ ሌሎች በአመልካች ተነስተዋል ባሉት ነጥብም በዝርዝር መልስ ሠጥተዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክርክሩ አጠቃላይ ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የተነሱትን ክርክሮች ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

አመልካች በእነ አሸረፍ አወል /17 ሰዎች/ ላይ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ የአሁን ተጠሪዎች 12ኛ እና 13ኛ ተከሳሾች በመሆን በጠበቃቸው አማካኝነት በችሎት የተገኙ ቢሆንም አመልካች ተከሳሾች ያልቀረቡና ሥራ አስኪያጆችም በሌሉበት ክርክሩ እንዲሰማ ትእዛዝ ተሰጥቶ ባለበት እነዚህ ተከሳሾች በጠበቃ ተወክለው መከራከር አይችሉም በማለት የቀረበውን ተቃውሞ ፍርድ ቤቱ ውድቅ በማድረግ ትእዛዝ የሠጠ ሲሆን በዚህ ትእዛዝ ላይ የቀረበውን ይግባኝ ሠሚው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደፊት በክርክሩ መጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥበት ይግባኝ ሊባልበት የሚችል እንጂ በዚህ ደረጃ ይግባኝ የሚቀርብበት አይደለም በማለት በወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 184 እና 185 መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ስለሆነም በዚህ ሰበር ችሎት በቅድሚያ መታየት ያለበት ተጠሪዎች በጠበቃ ሊወከሉ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጭብጥ እና አመልካችና ተጠሪ በሰፊው ያደረጋቸውን ክርክሮች ሳይሆን ተጠሪዎች በጠበቃ ሊወከሉ ይገባል በማለት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ አይገባም በማለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ መሠታዊ ስህተት መኖር አለመኖሩን ነው፡፡

የፌደራሉ ጠቅላይ ፍድ ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 የትእዛዝ ይግባኝ ስላለመኖሩ እና የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 185 የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት ወይም በቅጣቱ ይግባኝ ስለማለት የሚደነግገውን ነው፡፡

ይግባኝን በተመለከተ መሠረቱ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ-መንግስት ሲሆን የተከሰሱ ሰዎችን መብት በሚደነግገው አንቀጽ 20/6/ ላይ ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም ፍርድ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት ያላቸው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ አንድ የበታች ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ ወይም በፍርዱ ቅር የተሰኘና ፍትህ ተዛባብኝ የሚል ተከራካሪ ወገን ቅሬታውን ለበላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርዱ እንዲመረመር እና ተፈፀመ ያለው ሥህተት እንዲታረምለት ይግባኝ የማለት መብት ተሠጥቶታል፡፡

የሥነ-ሥርዓት ህጐች ዋናው ዓላማ ፍትሐዊ ኢኮኖሚያዊና አፋጣኝ በሆነ መንገድ ክርክሮች እንዲያልቁ ማስቻል በመሆኑ ፍርድ ቤቶች የሥነ-ሥርዓት ህጉን አስመልክቶ ክርክሮች ሲቀርቡ ከተከራካሪ ወገኖች መብት አልፎም የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅና የተፋጠነ ፍትህ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ መተርጐም ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም አንጻር በወንጀል ክስ ጉዳይ ይግባኝ የሚባልባቸውን የፍርድ ቤት ውሳኔዎች የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181 ስለ ይግባኝ መሠረቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊዘረዘር የሥረ-ነገር ክርክሩን የሚያቋርጡ መሆናቸውን የሚያመለክት ሲሆን ይኸውም የጥፋተኝነት ውሳኔ፣ የቅጣት ውሳኔ፣ ለጊዜው የመለቀቅ /Discharge/ እና በነፃ የመለቀቅ ውሳኔ /aquittal/ መሆናቸውን ያመለክታል። ነገር ግን የሥረ-ነገር ክርክር የሚያቋርጡ እንደቀጠሮ መስጠት አለመስጠት እንደማስረጃ መቀበል አለመቀበል የመሳሰሉት የብይን /ትእዛዝ/ ሁኔታዎች ወዲያውኑ ይግባኝ የማይባልባቸው ናቸው ሆኖም ግን በእነዚህ ብይን/ትእዛዞች ላይ ወዲያውኑ ይግባኝ ለማለት ባይቻልም ፍርድ ቤቱ ነገሩን ሰምቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ፍርዱን በመቃወም ይግባኝ ሲቀርብ እነዚህን በክርክሩ ሂደት የተሰጡ እትዛዞች የቅሬታው ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 መደንገጉ የተፋጠነ ፍትህ የማይገኝት ህገ-መንግስትዊ መብት ያለውን ተከራካሪ ተጠቃለው መታየት በሚችሉ ሁኔታዎች ምክንያት ክርክሩ እንዳይዘገይ የማድረግ ዓላማ ያለው መሆኑን የማያስገነዝብ ነው።

በዚህ በያዝነው ጉዳይም የስር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊባልበት የሚገባ አይደለም ያለው በወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 181 እንደተመለከተው የሥረ-ነገር ክርክሩን የማያቋርጥ እና ፍርድ ቤቱ ነገሩን ሰምቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት የቅሬታ ምክንያት ሆነ ተጠቃሎ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል መሆኑን መሠረት በማድረግ ነው። አመልካች የሰበር መ/ቁ 93234 የተሰጠን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት በማድረግ ያቀረቡት መከራከሪያም ቢሆን ጉዳዩ የክስ ማሻሻልን የሚመለከት ሆኖ የተሰጠው ትእዛዝ በቀጣይ የወንጀል ክርክር ሂደት ጋር የሚያስተሳስረው ነገር ባለመኖሩ ድጋሚ ክርክር የሚቀርብበት ዕድል የሌለ በመሆኑ ትእዛዙ የመጨረሻ በመሆኑ ከዋናው ክርክር ጋር ተጠቃልሎ ይግባኝ ሊባልበት የማይችል መሆኑን መሠረት በማድረግ የተሰጠ በመሆኑ ጠበቃ በመወከል ላይ በተሰጠው ትእዛዝ ጋር ተመሳሳይነት የላቸውም።

በአጠቃላይ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ በጠበቃ መወከልን አስመልክቶ በተሰጠው ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚገባ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ከወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181, 184 እና 185 አንጻር መሠረታዊ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 155568 በቀን ታህሳስ 28/2004 በሰጠው ትእዛዝ ላይ የቀረበው ይግባኝ ላይ የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ 111863 በቀን ጥቅምት 1/2008 የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

ት እ ዛ ዝ

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 155568 የቀጠለው ክርክር ለጊዜው እንዲታገድ በ 12/05/08 የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 103940

ቀን 24/05/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

.እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ አመለወርቅ ጌታነህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የአሁኗ አመልካች ጨምሮ በ17 ተከሳሾች ላይ ክስ ማቅረቡን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት 9ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኗ አመልካች ያቀረበው ክስ ባጭሩ፡- በንፋስ ስልክ ከተማ ቀበሌ 12/13 የቤት ቁጥር የማይታወቅ ንግድ ቤት ውስጥ ስልክ የማስደወል ፈቃድ ሳይኖራት ከቴሌ ኮሚንኬሽን ሲስተም በመደበቅ ስልክ ማስደወል የሚያስችል ራስ አዲስ ፒሲቶከር እና ራስ ዳሽን የተባሉ ሶፍትዌሮችና የካርድ ቁጥሮች (Accounts numbers) ከ3ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች በመግዛት እንዲሁም ለጊዜው ማን እንዳስመጣው የማይታወቅ ኔት 2ፎን ዲያለር የተባለ ሶፍትዌር በመጠቀም 3ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጋር በስውር በመመሳጠር ባዘጋጁት ህገወጥ ተግባር በመታገዝ ወደ ወጭ አገር ስልክ በማስደወል እ.ኤ.አ ከ01/11/2004 እስከ 06/10/2010 ለ5 አመታት ከ339 ቀናት 779,040 ደቂቃዎች ወደ ተለያየ አገራት ከኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ሲስተም መደበቅ የሚያስችል ቴክኖሎጂ በመጠቀም በህገወጥ መንገድ በማስደወል ብር 7,70,400 (ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ሺህ አራት መቶ ብር)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደረስ በማደርገና በህገወጥ መንገድ ብር 3895200.00 (ሶስት ሚሊዮን ዘጠና አምስት ሺህ ሁለት መቶ ብር) ተጠቃሚ በመሆኗ እንዲሁም በሽያጭ የተዘጋጁ ግምታቸው USD 17500 የሚያወጡ የካርድ ቁጥሮች በህገ ወጥ ሱቋ ውስጥ በመገኘታቸው የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1) (ሀ)፤ 33፣ 411(1) ሐ የተመለከተው በመተላለፍ በህዝብና በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሳለች የሚል ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ የቀረበባት ክስ ክዳ በመከራከሯ የስር ፍርድ ቤት የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ካደመጠ በኃላ እንድትከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡ የአሁኗ አመልካች የበኩሏን የመከላከያ ማስረጃ በማስቀረብ አስምታለች፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የአሁኗ አመልካች እና ሌሎች ተከሳሾች በክሱ በተገለጸው አግባብ ከቴሌኮሚኒኬሽን እውቅናና ፈቃድ ውጭ ሶፍትዌሮችን በመገልግል በኢንተርኔት ስልኮች በማስደወል ከፍተኛ ገንዘብ መሰብሰባቸውንና መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ የቴሌኮሙኒኬሽንን መስርያቤት ማስጣታቸውን ተረጋግጦባቸው አልተከላከሉም፡፡ በክሱ ላይ የተገለጹት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች መከላከላቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ጉዳዩ የሙስና ወንጀል መሆኑ ይቀራል ይህ በመሆኑም በ1ኛ ክስ የቀረበባቸው ዘጠኝ ተከሳሾች (3ኛ፣ 5ኛ፣ 6ኛ፣ 7ኛ፣ 9ኛ፣ 11ኛ፣ 12ኛ እና 13ኛ ተከሳሾች) በህገወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል ስልክ ለማስደወል ሶፍትዌሮች ማስደወያ ካርድ ቁጥሮችን በማከፋፈል ለአገኙት ህገወጥ ጥቅምና ለአሳጡት ጥቅም ተጠያቂና ጥፋተኛ የሚሆኑት በሙስና ወንጀል መሆኑ ቀርቶ ተከሳሾች ሊጠየቁ የሚገባቸው በኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 11(4) ድንጋጌ ኢንተርኔት በመጠቀም የድምጽ መልእክትን ማስተላለፍ ወይም የማስተላለፍ አገልግሎት መስጠት ድንጋጌ ተላልፎ መገኘት በመሆኑ የተከሰሱበትን የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1) (ሀ)፣ 33፣ 411(1) (ሐ) እና (2) ድንጋጌዎች በወ/መ/ስ/ስ/ቁ. 113(2) በመለወጥ ከላይ በተጠቀሰው የአዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 13 ድንጋጌ ጥፋተኛ ናቸው በማለት በአብላጫ ድምጽ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር የመረመረ ሲሆን ወንጀሉ በከፍተኛ ደረጃ መድቦ ቅጣቱ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማስላት ወስኗል፡፡ ድንጋጌው ከ3 እስከ ከ5 አመት የሚያስቀጣ በመሆኑ ለከባድ ወንጀል የቅጣት መነሻና መድረሻ ከ4 ዓመት አስከ 4 ዓመት ከ6 ወር የሚያስቀጣ በመሆኑ በእርከን 18 የሚውድቅ ነው፡፡ በአሁኗ አመልካች የቀረበው አንድ የቅጣት ማቅለያ ተቀብሎ በእርከን 17 ስር በ3 አመት እንዲትቀጣ፤ የገንዘብ መቀጮ በተመለከተ ከኢፌዴሪ የኢንፎርመሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በ11/04/2003 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት በአሁኗ አመልካች ተሰበሰበ የተባለው የገንዘብ መጠን 3,895,200 (ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሁለት መቶ) ያለፈቃድ በሰሩበት ጊዜ ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግኝተውታል ተብሎ የቀረበባቸውንና በመከላከያቸው ያላስተባበሉት ገንዘብ እጥፍ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያደረጉ ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የአሁኗ አመልካች የስር ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበገውም የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የወንጀል ድርጊቱ እንዳልፈጸመ፤ በማስደወል አገኙት የተበለው ገንዘብም ሆነ በመንግስት ላይ ደረሰ የተባለው ጉዳት አልተረጋገጠም፤ የተወሰነው የእስራት ቅጣት ይሁን የገንዘብም መቀጮ የግህ መሰረት የለውም በማለት መከራከራቸውን ያሳያል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት ያገናዘበ ስለመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርባዋል፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆነ እኛም ግራ ቀኝ በጽሁፍ ያደርጉት ክርክር ፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩን ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንዲሚከተለው መርምረናል፡፡ ጉዳዩን ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነትና የእስራት ቅጣት በአግባቡ ሆኖ በወንጀል ስራ ምክንያት አመልካች አግኝታለች የተባለው የገንዘብ መጠን የተወሰነበት ስርዓት በህጉ አግባብ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ነው፡፡

ጉዳዩ እንደመረመረነውም አመልካች ፈቃድ ሳያወጡ ወይም የፀና ፈቃድ ሳይኖራቸው ስልክ በማስደወላቸው ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ባደረገው ማጣራት የአሁኗ አመልካች ምንም ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው ስልክ በማስደወል ብር 3895200.00 እንደሰበሰቡ ቴሌኮሚንኬሽን ደግሞ ብር 7790400.00 ማጣቱን ከኢፌዴሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ማስረጃ መቅረቡን በውሳኔው አስፍሯል፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጉቱን አልፈጸምኩም፣ ስልክ በማስደወል ገንዘብ አላገኘሁም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት በውሳኔው እንደገለጸው የቀረበው ማስረጃ የሚያስተባብል ነገር አለማቅረባቸውን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ረገድ የሚደርስበት ድምዳሜ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳለ የሚቀበለው እንጂ በድጋሚ የሚያጣራበት ስርዓት የሌለ ስለመሆኑ ከኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው የአሁኗ አመልካች (የስር 9ኛ ተከሳሽ የነበሩ) ያለ ፈቃድ ስልክ በማስደወል ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሁለት መቶ ብር ጥቅም እንዳገኙ ነው፡፡ ይህ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ይዘን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአዋጅ ቁጥር 49/1989 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 13 ስር የተመለከተው መቀጮ ዓይነትና ባህሪ መርምረናል፡፡

በዚህ አዋጅ ክልከላ የተደረገባቸው ድርጊቶች ፈጸሞ ጥፋተኛ የተበለው ግለሰብ በእስራትና በመቀጮ እንደሚቀጣ ተመልክቷል፡፡ የድንጋጌው የአማራኛ እንግልዝኛ ይዘት፡- “በዚህ አዋጅ ወይም በሌሎች አግባብ ባለቸው ህጎች መሰረት ፈቃድ ሳያወጣ ወይም የጸና ፈቃድ ሳይኖረው አገልግሎት የሰጠ ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ በሰራበት ጊዜ ውስጥ ሊገኝ ይችላል ተብሎ የሚወሰነውን ገቢ እጥፍ የገንዘብ መቀጮና ከ3 አመት እስከ አምስት አመት በሚደረስ እስራት ይቀጣል በማለት የተደነገገ ሲሆን የእንግልዝኛው ትርጉም “any person who engages in tele communication service without having license or a valid license as per this proclamation or any other relevant laws shall be punished with fine equal to double the revenue estimated to have been earned by the person during the period of time he operated the service and with imprison mint from 3 up to 5 years” በማለት ተደንግጓአል፡፡ በዚህ ድንጋገ የመቀጮው መሰረት ወንጀል ፈጻሚው ካገኘው ጥቅም ወይም ሊያገኘው ይችላል ተብሎ የሚገመት የገንዘብ መጠን መሰረት የሚያደረግ ስለመሆኑ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በህገ ወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል ያገኙት የገንዘብ መጠንና መንግስት ያጣው ገቢ በሚመለከተው አካል ተጣርቶ እና ተረጋግጦ መቅረቡን የስር ፍ/ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 13 ላይ እንደተገለጸው የመቀጮው መጠን እጥፍ እንደሚሆን ነው፡፡ ድንጋጌው ተቀጪው እጥፍ እንደሚከፈል በግልጽ ካስቀመጠ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በህገ ወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል ያገኙው ጥቅም እጥፍ እንዲከፍሉ መወሰናቸው ሲታይ በህጉ አተረጓጉም ረገድ የፈጸሙት ስህተት መኖሩን አያሳይም፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው በአዋጅ ቁጥር 281/94 አንቀጽ 13 ድንጋጌዎች መሰረታዊ የመቀጮ አወሳሰን ስርዓት ተቀጪው ወንጀል በመስራቱ ያገኘው ጥቅም ታሳቢ ያደረጉ በመሆኑ ወንጀል በመስራቱ ብቻ ጥቅም ሲያገኝ የሚወሰንበት ስርዓት መሆኑን ተረደተናል፡፡ ከዚህ አንጻር በአመልካች ላይ የተወሰነው መቀጮ ተገኘ የተባለው ጥቅም በማስረጃ መረጋገጡን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 281/94 አንቀጽ 13 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ብለናል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
2. አመልካች በህገወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል አገኙት የተባለው የገንዘብ መጠን እጥፍ እንዲከፍሉ መወሰኑ በህጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.94913

ህዳር 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት - ዓ/ሕግ አቤል ገ/እግዚአብሔር - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ጆሳምቢን ትራዲንግ ኃ/የግ/ማህበር
2. አቶ ዮሴፍ ተስፋዬ አርጋዉ
} ከጠበቃ አለማየሁ ታደሰ ጋር - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለዉን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ከጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ጋር በተያያዘ ተፈጸመ የተባለዉን የማጭበርበር ወንጀል የሚመለከት ክርክር መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- የሥር ከሳሽ /የአሁን አመልካች/ በምስራቅ ሻዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ ተከሳሾች የጉምሩክ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 93 /1/ (ሀ) እና 93 /2/ በመፈተላለፍ ቻይና አገር የተመረቱን ዕቃዎች ከዉጭ አገር ለማስገባት የንግድ ፈቃድ አዉጥቶ፣ ዕቃዎቹ ሞጆ ደረቅ ወደብ ገብቶ ሲፈተሽ በዲክላራስዮን ቁጥር C-10951 በ20/12/2012 እ.አ.አ. እና ይህን በሚደግፍ ሰነድ ላይ ያልተሞለዉን መለያ ያለዉ ቬትናም አገር የተመረተ እና የጫማ ሳጥን በማስገባት ቀረጥ እና ታክስ ብር 3,328,524.38 መክፈል ያለበትን ብር 931,799.33 በመክፈል በልዩነት ብር 2,396,725.05 ሳይከፍል ዝቅተኛ ቀረጥና ታክስ በመክፈል ዕቃዉ ወደ አገር ወስጥ እንዲገባ ስላደረገ በማጭበርበር ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

የሥር 2ኛ ተከሳሽ /የአሁን 2ኛ ተጠሪ/ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት በሰጠዉ ቃል በዚህ የወንጀል ድርጊት ምንም ዓይነት ተሰትፎ የለኝም ምክንያቱ በዲክላራስዮኑ ሰነድ ላይ ከተጠቀሱት ዕቃዎች ዉጭ የላከዉ ከዉጭ አገር ዕቃዎቹን የላከዉ ካመፓኒ የፈጸመዉ ስህተት ነዉ እንጂ የተከሳሽ ተሳትፎ የለም በማለት ገልጸል፡፡

ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ ምስክሮችን በመስማት፣ 2ኛ ተከሳሽ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.142 /3/ መሰረት የሰጠዉን ቃል በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ከዉጭ የመጠዉን ዕቃዎች ያወቀዉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሞጆ ደረቅ ጣቢያ ሲፈተሽ እንደሆነ የዐ/ሕግ ምስክሮች ገልጸዋል፤ ዕቃዉ የመጣዉ ከተከሳሽ ጥያቄ ዉጭ በመሆኑ፣ ላኪዉ ካመፓኒ የራሱ ስህተት እንደሆነ እና ተከሳሹ በሰጠዉ ቃል የላኪዉ ካምፓኒ ስህተት እና ከእርሱ እዉቅና ዉጭ እንደሆነ በመግለጹ በወ/ሕ/ቁ.23 /2/ መሰረት ወንጀል ለመፈጸም የሐሰብ ክፍል ስላልተሟላ፣ ተከሳሽ ሊጠየቅ አይገባም በማለት በወ/ሕ/ቁ.149 /2/ መሰረት ነጻ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምስራቅ ችሎት በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሾች ይህን ለመፈጸም የሀሳብ ክፍል የለም በማለት ክሱ ነጻ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፣ በዕቃዎቹ ላይ መከፈል ያለበትን ቀረጥና ታክስን በተመለከተ ዕቃዎቹ ላይ መከፈል ባለበት ላይ በተከፈለዉ መካከል በቅናሽ የሚፈለግ ክፍያ ካለ ተከሳሾች በመመሪያዉ መሰረት አስፈላጊዉን ክፍያ ከከፈሉ በኃላ ዕቃዎቹ እንዲለቀቁ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች በ07/03/2006 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 93 /1/ (ሀ) የተጠቀሱ የወንጀል ድርጊቶችን መፈጸሙ በአዋጁ አንቀጽ 93 /2/ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን፣ ተጠሪ ድርጅት በመሆኑ የሐሳብ ክፍል እንዲያሟላ የሚጠበቅ ሳይሆን ተጠሪዉ በከፈለዉ ታክስ እና ቀረጥ መካከል በልዩነት ብር 2,396,725.05 ሳይከፍልበት ወደ አገር ዉስጥ አስገብቶ መገኘቱ ነዉ፡፡ ይህን የወንጀል ድርጊት መፈጸሙ ተረጋግጧል፡፡ በዲክላራሲዮን ቁጥር C-10951 በቻይና አገር የተመረተዉን ዕቃ አቅራቢ ከሆነዉ ከSHEZHENE XINGCHEN በአደራ ተቀብሎ ተጠሪዎችን ወክሎ ተረክቦ የላካ ሆኖ ኢንተርናሽናል /HOPE INTERNATIONAL/ በአዋጁ አንቀጽ 2/23/ መሰረት ወኪልንም ስለሚጨምር አቅራቢ ያልሆነዉ ሆኖ ኢንተርናሽናል የጻፈዉን ደብድቤ በመውሰድ ተጠሪዎችን ነጻ መልቀቁ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ሆኖ ኢንተርናሽናል ድርጅት የጻፈዉ ደብዳቤ በአዋጅ ቁ.334/1995 አንቀጽ 26 /1/ እና 27 /1/ መሰረት ስላልተረጋገጠ፣ የደብዳቤዉም ይዘት ሲታይ በልዩነት የታየዉን ገንዘብ ትተንልሃል የሚል ስለሆነ ከዘመናዊ ግብይት አንጽር ከንግድ መርህ ዉጭ ነዉ፤ ደብዳቤዉም የተጻፈዉ ተጠሪዎች ከተከሰሱ በኃላ ነዉ፡፡ ስለዚህ የስር ፍ/ቤቶች በሕግ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ያልሆነን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን ከክስ ነጻ ማድረጋቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለዉ በመሆኑ ተጠሪዎቹ ላይ የጥፋተኝነት ዉሳኔ እንዲሰጥ በማለት ተከራከረዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቡን በመመርመር ፣ተጠሪዎች ይህን የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም የሐሳብ ክፍል እንደአስፈላጊ ሁኔታ ተቆጥሮ የተሰጠዉን ዳኝነት አግባብነት፣ ለማየት ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ በታዘዙት መሰረት መጋቢት 3 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ቀርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት፡ 1ኛ ተጠሪ ሆኖ ኢንተርናሽናል ቻይና አገር ከሚገኝ ዕቃዎችን ለመግዛት ይህ ድርጅት የዕቃዎቹን ከዋጋ ዝርዝር ጋር በላከዉ መሰረት የዉጭ ምንዛሬ እንዲፈቀድለት ጠይቆ ሲፈቀድለት በዳሻን ባንክ በኩል አል.ሲ /letter of credit/ ክፍቶ ግዥዉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አከናውኗል፡፡ ይህ ኩባንያ የዕቃዉን ዝርዝር እና የዋጋዉን መጠን በኮሚርሻል ኢንቮይስ በባንክ በኩል ለተጠሪዎች ልኮ ክፍያም በዳሽን ባንክ በኩል በኤል.ሲ አድቫይዝ ተፈጽሟል፡፡ ዕቃዎቹ በኢትዮጵያ መርከብ ተልከዉ ሞጆ ደረቅ ወደብ የደረሱ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ኤልሲ፣ ኮሚርሻል ኢንቮይስ፣ የዕቃዎች ዝርዝር ፓክንግ ሊስት፣ ቢል ኦፍ ሎድንግ፣ እና ሌሎች አስፈላጊ ዶክመንቶችን በአግባቡ ተልከዉለት በሰጠዉ ትዕዛዝና በከፈለዉ ዋጋ መጠን መሆናቸዉን አረጋግጦ ሰነዶቹ በሙሉ ትክክል ስለሆኑ ሰነዶቹን ከባንክ አዉጥቶ ለትራዚተር አስተላልፏል፡፡ በዚህ መሰረት ዲክላራሲዮን ተሞልቶ ተገቢዉ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ ዕቃዎቹ በፍተሻ ሲታይ ቻይና አገር የሚገኘዉ አቅራቢ የአላላክ ስህተት በመፈጸሙ ዕቃዎቹ ጫማ መሆናቸዉ እና ብዛታቸዉ በሠነዱ በተገለጸዉ ልክ ቢሆንም ስሪታቸዉና አዲዳስ የሚል ቢራንድ ስም ስለተለጠፈባቸዉ በመሆኑ በቀረጥና ታክስ አከፋፈል ላይ ለብራንድ የሚከፈለዉ ቀረጥና ታክስ ልዩነት አምጥቷል፡፡ ይህ ደግሞ የአቅራቢዉ ስህተት መሆኑን ኩባንያዉ ገልጸል፡፡ በተጠሪዎች በኩል የተፈጸመ ሕገ ወጥ ድርጊት የለም፤ በተጠሪዎች እዉቅና ወይም ቸልተኝነት የተፈጸመ ነገር የለም፡፡ በጉምሩክ አዋጅ ቁ.622/2001 መሰረት የፈጸምነው የወንጀል ድርጊት የለም፡፡ ወንጀል ለመፈጸማችን የሐሳብ ከፍል የተሟላ ነገር የለም፡፡ የሥር ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በልዩነት የታየዉን ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ስላደረገ የመንግስት ጥቅም ያስጠበቀ ዉሳኔ ነዉ፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስላልሆነ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ክርክራቸዉን አቅርበዋል፡፡ አመልካች በ23/07/2006 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተ ሲሆን፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እና መዝገቡ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነዉ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ተጠሪዎች ከዉጭ አገር ለማስገባት ፈቃድ ከወሰዱት ዕቃዎች ዉጭ ሌላ አገር የተመረተ ዕቃዎች በማስገባት ሊከፈል ከሚገባ ቀረጥ እና ታክስ አናስተኛ በመክፈል የማጭበርበር ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ሲሆን፣ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ የፈጸምናዉ የወንጀል ድርጊት የለም፣ ዕቃዎቹን ከዉጭ አገር የላከዉ ኩባንያ የፈጸመዉ ስህተት ስለሆነ ሊንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ከግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለዉ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ሥራ አስኪያጅነት በቻይና አገር የተመረተ የእስፖርት ጫማዎችን ወይም ዕቃዎችን ወደ አገር ዉስጥ ለማስገባት ፈቃድ የወሰዳ ሲሆን፣ እነዚህ ዕቃዎች ከዉጭ አገር ወደ አገር ዉስጥ ገብቶ ሞጆ ደረቀ ወደብ ከደረሳ በኃላ በተደረገ ፍተሻ ቻይና አገር የተመረተ ሳይሆን መለያ ያለዉ ቬትናም አገር የተመረቱ ዕቃዎች እንደሆኑ፣ በዚህ ምክንያት ለመንግስት መከፈል ካለበት ቀረጥና ታክስ ዉስጥ በልዩነት ብር 2,396,725.05

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይከፍልበት ወደ አገር ዉስጥ እንደገቡ ግራ ቀኙ ያልተካካዱ ከመሆኑም በላይ በማስረጃም ተረጋግጧል፡፡ የአመልካች ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ይህ ድርጊት መደረጉን በዲክላራሲዮን ላይ ከተገለጹት ዕቃዎች ዉጭ ወደ አገር ዉስጥ መግባታቸዉን አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች ያቀረባቸዉ የሰነድም ሆነ የሰዉ ምስክሮች 1ኛ ተጠሪ ወደ አገር ዉስጥ እንዲያስገባ ከተፈቀደለት ዕቃዎች ዉጭ ሌሎች ዕቃዎችን ወደ አገር ዉስጥ በእሱ ምክንያት እንደገባ አስረድተዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች በተጠሪዎች ምክንያት ወደ አገር እንዲገባ ከተፈቀዱ ዕቃዎች ዉጭ ወደ አገር ዉስጥ ገብቶ መገኘታቸዉ እና በዚህ ምክንያት መከፈል ከነበረበት ቀረጥና ታክስ በክሱ ላይ የተጠቀሰዉ ገንዘብ በልዩነት መገኘቱን የማስረዳት ሸክሙን መወጣቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ነገር ግን የሥር ፍ/ቤቶች እንዳረጋገጡት በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ ማስረጃ ዕቃዎቹን ከዉጭ አገር የላከዉ ሆፕ ኢንተርናሽናል ኩባንያ በኩል የተፈጠረ ስህተት መሆኑን የሚያመለክት እንደሆነ ገልጸዋል፤ 2ኛ ተጠሪም በሰጠዉ ቃል ዲክላራሲዮን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ ሰነዶች በአግባቡ ተሞልቶ በባንክ በኩል ተገቢዉ ክፍያ ተፈጽሞ የተላካ ሲሆን፣ ከዉጭ አገር ዕቃዎቹን ወደ አገር ዉስጥ የላካዉ ኩባንያ በፈጠረዉ ስህተት በሰነዱ ላይ ያልተጠቀሱ ዕቃዎች ወደ አገር ዉስጥ ገብቶ ሞጆ ደረቅ ወደብ ሲፈተሽ እንዳወቀ እና አነስተኛ ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ተብሎ ምንም ነገር እንዳላደረገ እና በዚህ ድርጊት ዉስጥ ምንም ዓይነት ተሳትፎ እንደሌለዉ ገልጻል፡፡ በጉምሩክ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 93 (1)(ሀ) እና 93 /2/ በመፈተላለፍ የማጭበርበር የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም እያወቁ የተፈጸመ ድርጊት መሆን እንዳለበት የሚያከራክር አይደለም፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 /2/ መሰረት አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለዉ ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሞልተዉ ሲገኙ ብቻ ነዉ በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ አግባብ ሲታይ 2ኛ ተጠሪ ይህን የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም ምንም ዓይነት ሚና እንዳልነበረዉ እና ድርጊቱን ለመፈጸም ሐሳብ እንዳልነበረዉ የቀረበዉ ማስረጃ እንደሚያረጋግጥ የሥር ፍ/ቤቶች አረጋግጧል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ይህን የወንጀል ድርጊት አዉቆ መፈጸም ይቅርና ያልተጠየቁ ዕቃዎች ወደ አገር ዉስጥ መግባታቸዉን ያወቀዉ ሞጆ ደረቅ ወደብ እንደሆነ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ 2ኛ ተጠሪ በዚህ ድርጊት ምክንያት የወንጀል ተጠያቂነት አለበት ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (3) የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በዚህ ሕግ በአንቀጽ 34 በተደነገጉ ሁኔታዎች መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል፡፡ በአንቀጽ 34 (1) መሰረት አንድ ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣዉም ከኃላፊዎቹ ወይም ከሠራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የድርጅቱን ጥቅም በሕገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ፣ ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ፣ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ ነዉ በማለት ደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ 1ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ ማስረጃ የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ድርጅቱን ተገን በማድረግ ወንጀሉን ያልፈጸመ መሆኑን ባቀረበዉ ማስረጃ ያረጋገጠ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ድንጋጌ አግባብ 1ኛ ተጠሪ የተጠቀሰዉን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸሙን በማረጋገጡ፣ የሥር ፍ/ቤቶች 1ኛ ተጠሪን ከክሱ ነፃ እንዲወጣ የሰጡት ዉሳኔ የህግና የማስረጃ ድጋፍ ያለዉ ነዉ፡፡ ስለዚህ ተጠሪዎች በዚህ የወንጀል ድርጊት ዉስጥ ምንም ተሳትፎ እንደሌላቸዉ በመከላከያ ማሰረጃ በማረጋገጥ እና በመከላከላቸዉ ከክሱ ነጻ እንዲወጡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.33613 በ02/08/2005 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የምስራቅ ችሎት በመ.ቁ.161271 በ16/12/2005 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.195 /2/ /ለ/፣/ 2/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይድረስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101618

ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/መ/ፀረ- ሙስና ኮሚሽን - ዐ/ህግ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- መስከረም ፋንታዬ የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ መንግስታዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀትና ወደ ሐሰት መለወጥ የሙስና ወንጀል ድርጊትን የሚመለከት ክርክር ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- የሥር ከሳሽ /የአሁን አመልካች / ለጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ ቁ. 379/1/ሀ በመተላለፍ ተከሳሽ በ26/03/2001 ዓ.ም የንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር የተጠቀሰ የንግድና ኢንዲስትሪ ቢሮ የንግድ ምዝገባ ፈቃድ ክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ የሥራ ሂደት በሚል የሚጀምር እና በሀሮ ወላቦ ክ/ከተማ ንግድ ምዝገባና ፍቃድ ክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ የስራ ሂደት የተዘጋጀ በማስመሰል በስሙ የተዘጋጀ የቡና አቅራቢነት ሀሰተኛ ንግድ ፈቃድ በሀሰተኛ ክብ ማህተም፣ ሀሰተኛ ስምና ስልጣን ቲተሮች የተዘጋጀውን ሰነድ በመያዝ በቀን 18/08/2005 ዓ.ም 9፡30 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ከሀሮ ወላቡ ክ/ከተማ ንግድ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት ወደ ጌድኦ ዞን ንግድ ማስፋፊያ ይዛወርልኝ በማለት ሲገለገል ሊያዝ ችሏል ፡፡ በመሆኑም ተከሳሹ የሕዝብ ጥቅም የሚሰራበት ሰነድ ላይ በሀሰት የተዘጋጀ ስለመሆኑ እያወቀ በመገልገሉ በፈጸመው መንግስታዊ ወይም ወታደራዊ ሰነዶችን አስመስሎ በማዘጋጀት ወይም ወደ ሀሰት መለወጥ የሙስና ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ተከሳሽ/ የአሁን ተጠሪ/ ፍ/ቤት ቀርቦ ይህ ክስ ተነቦለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ሳይቀበለው በመቅረቱ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል ፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ ምስክሮችን በመስማት ተከሳሽ እንዲከላከል ባዘዘው መሰረት ተከሳሽ ራሱ ቃሉን በመስጠት የመከላከያ ምስክር አንድ ሰው ያቀረበውን ሰምቷል ፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ተከሳሽ የተከሰሰበት ሐሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት የሚል ሲሆን ተከሳሹ የፈጸመው ድርጊት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 379/1ሀ/ ሥር የሚሸፈን አይሆንም ፣ ተከሳሽ የፈጸመው ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 378 ሥር የሚሸፈን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የዐ/ሕግ ምስክሮችም በሰጡት የምስክርነት ቃል ይህ የሀሰት ሰነድ በተከሳሹ መዘጋጀቱን አናውቅም በማለት መስክሯል ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በሐሰት የተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት በወ/ሕ/ቁ. 375 መሰረት ቅጣት ይጣልበታል፡፡ ነገር ግን የዐ/ሕግ ምስክሮች ተከሳሹ ይህ የሐሰት ሰነድ ይዞ ከመገኘት ውጭ በሰነዱ መገልገሉን አልመሰከሩም፡፡ የተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮች ተከሳሽ የሐሰት ሰነዱን አለማዘጋጀቱንና አለመገልግሉን፣ ይህንንም የሀሰት ሰነድ አምጥቶ ለሚስቱ የተሰጠው ተከሳሽ ለትምህርት ወደ ጎንደር ዩኒቨርስቲ በሄደበት ወቅት ጉዳይ አስፈጻሚ እንደሆነ የመሰከሩ ሲሆን እና በተባለ ጊዜ ተከሳሹ ዩኒቨርስቲ እንደነበር በዩኒቨርስቲ የተጻፈ ደብዳቤ ያመለክታል፡፡ ተከሳሹ በተጠቀሰው የሐሰት ሰነድ ምንም አይነት የቡና ንግድ ያላካሄደ መሆኑን የዲላ ዙሪያ ወረዳ ግብይትና ኃ/ሥራ ማህበር ጽ/ቤት መግለጹ እንዲሁም የሚፈለገው ምንም እዳ የሌለ መሆኑን ከገቢዎች ጽ/ቤት የተጻፉ ደብዳቤዎች ያስረዳሉ፡፡ ተከሳሹ በሀሰት ሰነድ አለመገልገሉ የግራ ቀኙ ማስረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ ተከሳሹ ይህ ሰነድ ይዞ መገኘቱ እንደወንጀል ሊቆጠር ስለማይገባ ተከሳሹ ከተከሰሰበት የወንጀል ክስ በነጻ እንዲለቀቅ ወስኗል ፡፡ የሥር ከሳሽ ይህን ውሳኔ በመቃወም ቅሬታውን ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቶች ቅሬታውን ባለመቀበል ውድቅ በማድረግ የሥር ውሳኔ በማጽናት ወስኗል ፡፡ የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በ27/09/2006 ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ የሥር ፍ/ቤት ለወ/ሕ/ቁ. 379/1፣ሀ/ የሰጠው የሕግ ትርጉም አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የዐ/ህግ ምስክሮች ተጠሪው በሐሰተኛ የንግድ ፈቃዱ እያወቀ መገልገሉን አስረድተዋል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ እንዲታረምልን ተጠሪ ላይ ተገቢው የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ እንዲወሰንበት በማለት አመልክተዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣ ተጠሪ ሐሰተኛ የንግድ ፈቃድ ተጠቅሞ ማህደሩ ከአንዱ የመንግስት መ/ቤት ወደ ሌላ እንዲዛወርለት ጠይቆ ይህንኑ ሂደት በማስፈጸም ላይ እያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደረሰበት ሆኖ ሳለ ድርጊቱ የወንጀል ሃላፊነትን አያስከትልም ተብሎ በነጻ የመሰናበቱ፣ አግባብነት ለመመርመር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ታህሳስ 06 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልሱም ይዘት ተጠሪ ሀሰተኛ ሰነድ መሆኑን እያወቅሁ ማህደር ከአንዱ የመንግስት መ/ቤት ወደ ሌላ የመንግስት መ/ቤት እንዲዛወር ያላደረግኩ ስለመሆኑ በማስረጃ አረጋግጠዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ለወ/ሕ/ቁ. 379/1ሀ/ የሰጡት ትርጉም አግባብነት ያለው ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ሰነዱ ሀሰተኛ የንግድ ፈቃድ መሆኑን እያወቅኩ ስለመገልገሌ በማስረጃ ያላረጋገጠ ስለሆነ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበው ወንጀል ክስ በማስረጃ ባለመረጋገጡ ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ ውሳኔው እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በ04/05/2007 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እና መዝገቡ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምሯል ፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ባቀረበው ክስ መሰረት የቀረቡት ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል መንግስታዊ ወይም ወታደራዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት ወይም ወደ ሀሰት መለወጥ ያረጋገጡት ነገር እንደሌለ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ያመለክታል፡፡

እንዲያውም የዐ/ሕግ ምስክሮች እንደገለጹት ተጠሪን ከየት አመጥተህ ነው ብሎ ሲጠይቁት እሱ ለትምህርት በሄደ ጊዜ የተወከለ ሰው እንዳወጣለት እና ተጠሪው ሰነዱን ማዘጋጀቱን እና መገልገል አመለገልገሉን እንደማያውቁ መስክረዋል ፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ ከምስክሮች ቃል አንጻር ሲታይ ተጠሪ የፈጸመው ድርጊት የተባለውን ድርጊት እንደማይሸፍን በመግለጽ ወደ ወ/ሕ/ቁ. 378 መለወጡ በአግባቡ ነው እንጂ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል የሚያስብል ነገር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ እንዳረጋገጡት ዐ/ሕግ ያቀረባቸው ማስረጃዎች ተጠሪው ይህን ሀሰተኛ የንግድ ፈቃድ አዘጋጅቶ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ የሚያረጋግጡት አይደለም፡፡ በወ/ሕ/ቁ. 378 መሰረት የወንጀል ሃላፊነት ሊያስከትል የሚችለው በሀሰት የተዘጋጀ ወይም የተለወጠ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ተጠሪ እና ያቀረበው መከላከያ ምስክር በሰጡት ቃል ተጠሪ ይህን ሀሰተኛ የንግድ ፈቃድ እንዳላዘጋጀ እና ሐሰተኛ መሆኑን አውቆ እንዳልተገለገለበት ገልጿል፡፡ በሌላ በኩል በስር ፍ/ቤት የቀረበው የሠነድ ማስረጃ ተጠሪ በዚህ ሀሰተኛ የንግድ ፈቃድ በመገልገል ያካሄደው የቡና ንግድ እንደሌለ አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪው ይህ ሀሰተኛ የንግድ ፈቃድ በማዘጋጀት እያወቀ የተገለገለበት መሆኑን በማስረጃ አላረጋገጠም በማለት ተጠሪ ከተከሰሰበት ወንጀል በነጻ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሰናበት የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጿሚል በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለው የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ . 09459 በ30/05/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61255 በ26/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 61563 በ14/08/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/2፣ለ፣2 መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉምሩክ/ታክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 95941

ታህሳስ 7 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፉ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ሒስ ትራቭል ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ ረታ አለማየሁ - ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዓ/ህግ ኃይለመለኮት አበበ - ቀርበዋል

2. የኢትዮጵያ ግዮን ሆቴሎች ድርጅት - ነ/ፈ መላት ማሞ - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡ ተከታዩን

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች ሒስ ትራቭል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ታህሣስ 15 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 92474፣ ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ቅሬታውም የአሁን 1ኛ ተጠሪ ሲከራከር የነበረው ለአመልካች የገበሩት ታክስ ቅናሽ እንዲደረግለት ግብሩን ሲያሳውቅ አብሮ ሕጋዊ ደረሰኝ (የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ) ማቅረብ አለበት፡፡ አመልካች ግን ደረሰኝ ብያቀርብም ህጋዊ አይደለም የሚል ሲሆን፤ ከአሁን በፊት የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በጣልቃ ገቢነት የኢትዮጲያ ግዮን ሆቴሎች ድርጅት ገብቶ እንዲከራከር ወስኖ ወደ ፌ/ከ/ፍ/ቤት በመለሰው መሠረት የኢት.ግዮን ሆቴሎች ድርጅት በጣልቃ ገቢነት የሰጠው መልስ በግብር ዘመኑ ገቢ ያደረገ መሆኑን ከአሁን አመልካች ብር 533,951.97 የሰበሰበና የተ.እ.ታ. ብር 80,089.97 ብቻ እንደሆነ ገልጿል፡፡ ይህ የጣልቃ ገቢ (የኢትዮ.ግዮን ሆቴሎች ድርጅት) የሰበሰው የተ.እ.ታ. ብር 80,089.97 ብቻ ያለው ስህተት መሆኑና ብር 408,619.47 እንደሆነ ይጣራልኝ ብዬ ፍ/ቤቱን ብጠይቅም አልተቀበለኝም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም የኢት.ግዮን ሆቴሎች ድርጅት የተ.እ.ታ ሲሰበሰብ የነበረው በአንደኛ ተጠሪ የታወቁ ደረሰኞች እንደሆኑና 2ኛ ተጠሪ (የኢት.ግዮን ሆቴሎች ድርጅት) ታክሱን አልከፈሉም ሳይባል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሰኔ የሥር ፍ/ቤት መሻሩ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ ይላል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ ክርክር የተነሳበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ በሥር ጣልቃ ገብ የሆነው የአሁን 2ኛ ተጠሪ መክፈሉ ተረጋግጦ እያለና የሂሳብ ስሌት ስህተት ካለም በሂሳብ አጣሪ እንዲታይ ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤት ይህን ባለማገናዘብ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ነው የሚለውን የአመልካች ቅሬታ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡

1ኛ ተጠሪ መጋቢት 25 ቀን 2006 ዓ.ም በተሻሻለ መልስ አመልካች በትክክል የዚህን ዘመን የተ.እ.ታ በስሙ የከፈለ ለመሆኑ የሚያስረዳ ተጨባጭ ደረሰኝ ማቅረብ ሲገባው ያላቀረበ በመሆኑና 2ኛ ተጠሪ በስሙ ለተጠሪ ገቢ ያደረገው ታክስ በስሜ እንደተከፈለ ተቆጥሮ ይቀነስልኝ በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑና የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይሁንልኝ በማለት ተከላክሏል 2ኛ ተጠሪም የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በተ.እ.ታ. አዋጅና በደንቡ ላይ ተመስርቶ ህጉን ተከትሎ በመሆኑ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ያፅናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሚያዚያ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በተሻሻለ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

በዚሁ መሠረት መዝገቡን እንደመረመርነው ከፌ/ከ/ፍ/ቤት ሲሆን የፌ/ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ ውሳኔ የሰጠበት በመጀመሪያ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 115 መሠረት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የካቲት 3 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው መሠረት በቀረበው ላይ ነው፡፡ የአሁን አመልካች (ይግባኝ ባይ) ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረበው ይግባኝ የግብር ዓላማ በሕጎቹና በደንቦቹ ላይ እንደተጠቀሰው ከሚሰጡ አገልግሎች ላይ ግብሩ ተሰብስቦ በጊዜው ለግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ገቢ መደረጉ ሲሆን፤ ይሄውም ገቢ መደረጉ ግብሩን የሰበሰበው በጊዜው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከከፈሉት ድርጅቶች ማረጋገጫ ለተገኘበት ሂሳብ በእኛ በኩል እንዳልተከፈለ ተደርጎ ተቀባይነት ማጣቱ ተገቢ ባለመሆኑ የቀረቡትን ማስረጃ በተገቢው ሁኔታ ዝርዝሩ ታይቶ ይስተካከልልኝ የሚል ሲሆን መልስ ሰጪ የኢት/ገ/ጉ/ባለሥልጣንም የሰጠው መልስ በተጨማሪ እሴት ታክስ አ.ቁ 285/94 አንቀጽ 21 የተ.እ.ታ ክፋይነት ታክስ ተመዝጋቢ ሰው ክሻት በተቀበለው የተ.እ.ታ ደረሰኝ መሆን አለበት፡፡ ይግባኝ ባይ ታክስ የከፈለበትን የተ.እ.ታ ደረሰኝ ሳያቀርብ ታክሱ እንዲቀነስለት መጠየቁ ተቀባይነት የለውም ይግባኝ ባይ ከ1995 ዓ.ም እስከ 1997 ዓ.ም የግብአት ታክስ ከፍያለሁ ቢልም የተ.እ.ታ የከፈለበትን ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ይግባኛቸው ውድቅ ይሁንልኝ በማለት ተከላክሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤውም የካቲት 3 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ባይ ለተጠየቁት ግብር ከ1995 ዓ.ም እስከ 1997 ዓ.ም የግብር ዘመን የተ.እ.ታ የግዮን ሆቴሎች ድርጅት በጊዜው በትክክለኛ ፎርማት መሠረት ደረሰኞቹን እንዳላሳተመና በኢንቮይስ እንዲጠቀም የፈቀደለት መሆኑን ገልፆ የግዮን ሆቴሎች ድርጅት በይግባኝ ባይ ስም የተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል ለመልስ ሰጪ ገቢ ያደረገበት ማስረጃ እና ይህንኑ የሚያስረዳ ባለሙያ ቀርበው ገቢ ማድረጋቸውን አስረድተዋል፡፡ ይግባኝ ባይ በመልስ ሰጪ መሥሪያ ቤት የተጠየቀውን የተ.እ.ታ.መክፈሉን የጊዮን ሆቴሎች ያረጋገጠ ሲሆን መልስ ሰጪ ገቢው በትክክል አልደረሰም የሚል ከሆነ የጊዮን ሆቴሎች ድርጅት መጠየቅ እንጂ በይግባኝ ባይ ላይ የወሰነው ግብር አለአግባብ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ይህን ውሳኔ መልስ ሰጪ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ብሎ የፌ/ከፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ብሎ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በጣልቃ ገቢነት የኢትዮ. ግዮን ሆቴሎች ድርጅት አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ወደ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመመለሱ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤ በመ.ቁጥር 94730 ይግባኝ ባይ የኢት.ገ/ጉ ባለሥልጣን መልስ ሰጪ ሐኤስ ትራቭል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጣልቃ ገቢ የኢት.ግዮን ሆቴሎች ድርጅትን አከራክሮ ሐምሌ 3 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ይግባኝ ባይ አጥብቆ የሚከራከረው መልስ ሰጭ (ሐኤስ ትራቭል ኃ/ተ/የግ/ማ) የግብአት ታክስ እንዲቀነስለት ግብር ሲያስታውቅ አብሮ የተጨማሪ እሴት ደረሰኞችን ማቅረብ አለበት፡፡ መልስ ሰጪ ደግሞ ግብሩን የከፈለው መሆኑን ህጋዊ ደረሰኝ ያልቀረበና በጣልቃ ገቢ በኩል ያልተከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ መልስ ሰጭ ግብሩን በጣልቃ ገቢ በኩል ከፍያለው ቢልም በስሙ የተከፈለ መሆኑን ማስረጃ አላቀረበም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪን የግብር ክፍያ የጠየቀው ጣልቃ ገቢ በግብር ዘመኑም የሰበሰበው ታክስ እንደከፈለ ግን በመልስ ሰጪ ስም ለይቶ ያልከፈለ መሆኑን የገለፀ ስለሆነ በመልስ ሰጪ ላይ የሚፈለገው ታክስ በራሱ ስም ገቢ ሆኗል ለማለት አይቻልም በማለት የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመ.ቁ. 625/1/02 የሰጠውን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የአሁን አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢልም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 92474 ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ..337 መሠረት የስር ፍ/ቤት ፍርድ ጉድለት የሌለበት ሆኖ አግኝተናል ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ (የኢት/ገ/ጉ/ባለሥልጣን) በሥር ፍ/ቤት ሲከራከር የነበረው ለአመልካች የግብአት ታክስ ቅናሽ እንዲደረግለት ግብሩን ሲያሣውቅ አብሮ ሕጋዊ ደረሰኝ አያይዞ ማቅረብ አለበት፤ አመልካች ግን ደረሰኝ ቢያቀርቡም ህጋዊ አይደለም በሚል ሲሆን 2ኛ ተጠሪ የኢት.ግዮን ሆቴሎች ድርጅት የወቅቱን የግብር ታክስ አልከፈለም ሣይባል በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠው ውሳኔ መሻሩ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጣራ የተያዘው ጭብጥ ክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተነሣበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ በሥር ጣልቃ ገቢ የሆነው 2ኛ ተጠሪ የወቅቱ ግብር መክፈሉ ተረጋግጦ እያለና የሂሣብ ስሌት ስህተት ካለም በሂሣብ አጣሪ እንዲታይ ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤት በማለፍ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ነው የሚለውን የአመልካች ቅሬታ ለማጣራት ነው፡፡ በዚሁ በተያዘው ጭብጥ መሠረት እንደመረመርነው የአሁን አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ለ2ኛ ተጠሪ የከፈልኩት ተቀናሽ ያደረግልኝ ሲል ለ1ኛ ተጠሪ ያቀረባቸው ደረሰኞች አሉ፡፡ 1ኛ ተጠሪ እነዚህን ደረሰኞች ህጋዊ ደረሰኞች ባለመሆናቸው ተቀናሽ ማድረግ አልችልም በማለት ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ያቀረባቸው ደረሰኞች ህጋዊነትን ለመለየት 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ተወስኖ 2ኛ ተጠሪም ጣልቃ ገብቶ ሲከራከር በወቅቱ የሰበሰባቸውን ግብር ለ1ኛ ተጠሪ ገቢ ያደረጋቸው መሆኑን፣ ከአሁን አመልካች የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 80,089.97 በስሙ ገቢ ያደረገ መሆኑን ገልጿል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በዘመኑ ግብር ሲሰበስብ የነበረው በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሣይሆን 1ኛ ተጠሪ በፈቀደለት ደረሰኝ በመሆኑ የአሁን አመልካች ተቀናሽ እንዲደረግለት ለ1ኛ ተጠሪ ያቀረባቸው ደረሰኞች ሁሉም ከ2ኛ ተጠሪ የተሰጡ ለመሆኑ ሊረጋገጥ የሚችለው በ2ኛ ተጠሪ (ደረሰኙን በሰጠውና) በ1ኛ ተጠሪ የደረሰኙን በፈቀደው ስለሆነ ከ2ኛ ተጠሪ የተሰጡ ደረሰኞች ስለመኖራቸው 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች የሰበሰበውን ግብር ከራሱ ሰነዶች እና ደረሰኞች ላይ በማመሣከር የተገኘውን የግብር መጠን አሳውቋል፡፡ የ2ኛ ተጠሪ የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል አለመክፈል ለመመርመር ሥልጣኑ የተሰጠው ለ1ኛ ተጠሪ ነው፡፡ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት 2ኛ ተጠሪን ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ካደረገ በኃላ የአሁን አመልካች ተቀናሽ እንዲደረግለት 1ኛ ተጠሪ ያቀረባቸው ደረሰኞች ህጋዊ ደረሰኝ ያለመሆናቸውን፣ 2ኛ ተጠሪም በጣልቃ ገብ የሰጠው መልስ ይህንኑ የሚያረጋግጥ መሆኑን በማረጋገጥ የግብር ይግባኝ ጉባኤን ውሳኔ የሻረውና፣ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤትም የከፍ/ፍ/ቤትን ውሳኔ ያፀናው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 94730 ሐምሌ 3 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 92474 ጥቅምት 2 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሣራ ተቻችሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.114043

የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አቃቤ ሕግ ዐ/ህግ መብት አየሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አባዲ ሞገስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ እና በአቶ ንጉሴ ገ/ሕይወት ላይ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ) እና(ለ) እንዲሁም የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 166 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ሆነ ብለው ሕገ ወጥ ጥቅም ለማስገኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ንብረትነቱ የ2ኛ ተከሳሽ(ንጉሴ ገ/ሕይወት) የሰሌዳ ቁጥር 2-A01474 አ.አ የሆነች የቤት መኪና የቀረጥና ታክስ ስሌቱ ብር 170,958.10(አንድ መቶ ሰባ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ስምንት ብር ከአስር ሳንቲም) የሚያወጣ የኮንትሮባንድ እቃ በ2ኛ ተከሳሽ እና በሌሎች ግብረአበሮች አማካኝነት ጭኖ በመያዟ እና 2ኛ ተከሳሽም የመኪናው ባለቤት በመሆኑ እና የኮንትሮባንድ ወንጀል ክስ ተመስርቶበት ጉዳዩ በፍርድ ቤት እየታዬ ባለበት ሁኔታ እና ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያስገኝ ድረስ ተከሳሽ በዋስ ሁኖ ጉዳዩን እንዲከታተል የተሰጠውን መብት በመጠቀም ልትወርስ የምትችለውን መኪና በቀን 27/04/07 ዓ/ም የመኪና ሽያጭ ውል በመፈራረም ሽያጩን ከቅን ልቦና ውጪ ከመደበኛ የገበያ ዋጋ በታች በ35,000.00(ሰላሳ አምስት ሺህ) በመሸጥ እና መኪናዋንም በጉምሩክ ወንጀል መተላለፍ ምክንያት በጉምሩክ ቁጥጥር ስር መሆኗን እያወቁ የባለቤትነት መብት /ሊብሬ/ 2ኛ ተከሳሽ ለ1ኛ ተከሰሽ (አባዲ ሞገስ) ስም ንብረቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲተላለፍ በማድረግ በቁጥጥር ስር የነበረችውን መኪና በ1ኛ ተከሳሽ አማካኝነት በቀን 01/05/07 ዓ/ም ሚሌ ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ መኪናዋን ለማውጣት ሲሞክር በቁጥጥር ስር በመዋሉ የጉምሩክ ቁጥጥር በማሰናከል ወንጀል ተከሶአል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃልም ስለወንጀሉ የሚያውቁት ነገር የሌለ መሆኑን፣ መኪናውን በቅን ልቦና የገዙት መሆኑን ጠቅሰው መብታቸውን ጠብቀው የተከራከሩ ሲሆን የስር 2ኛ ተከሳሽ ግን ሊቀርብ ባለመቻሉ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ ትእዛዝ ተሰጥቶአል፡፡ በአመልካችና በአሁኑ ተጠሪ መካከል ያለው ጉዳይ ግን ክርክሩ ለብቻው እንዲቀጥል ተደርጎ አመልካች አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን ተጠሪም የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ከተደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ መኪናውን የገዙት የፍርድ ቤት እግድ በሌለበት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ መኪናው እንዲለቀቅለት ጉምሩክ ቀርቦ መኪናው ኮንትሮባንድ በመጫኑ ምክንያት ለመንግስት ሊከፈል የሚገባውን ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ) መክፈሉ ግዥውን የፈፀመው በቅን ልቦና መሆኑን የሚያሳይ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ተጠሪን ከወንጀሉ ክስ ነፃ ያሰናበታቸው ሲሆን የተያዘውም ንብረት ተገቢውን የአስተዳደር ቅጣት መክፍሉ ተረጋግጦ እንዲለቀቅ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-ተጠሪ ከቅን ልቦና ውጭ በመንቀሳቀስ በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 198(1) በወቅቱ የመኪናው ባለቤት የነበረው ግለሰብ በመተላለፍ በሕግ ጥላ ስር ውላ እና የውርስ ውሳኔ ተላለፎባት የምትገኘውን መኪና በሕገ ወጥ መልኩ በመግዛት እና ባለቤት ነኝ በማለት የጉምሩክ ቁጥጥር ስራን ሆነ ብሎ ለማሰናከል ጥረት ያደረገ እና በእጅ በማስገባት ሲል እጅ ከፍንጅ የተያዘ መሆኑ መረጋገጡን ገልፆ ተጠሪ በዚሁ አድራጎታቸው ጥፋተኛ ሊባሉ እንደሚገባ፣ የሥር ፍርድ ቤቶች ከስልጣናቸው ውጪ መኪናው እንዲለቀቅ የሰጡት ውሳኔም ተገቢነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው ሊታረም ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መኪና ለተጠሪ እንዲለቀቅ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማጋዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መኪና በስር 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት ግለሰብ ስም የሚታወቅ ሁኖ የኮንትሮባንድ ወንጀል ተፈጽሞበታል ተብሎ በ09/04/2007 ዓ/ም በአመልካች ቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ በ13/08/2007 ዓ/ም በውልና ማስረጃ በተደረገ የሽያጭ ውል ከስር 2ኛ ተከሳሽ በብር 35,000.00 የገዙ መሆኑን፣ግዥው ሲፈጸም በመኪናው ላይ የተላለፈ እገዳ የሌለ መሆኑ የተረጋገጠና ተጠሪ መኪናው መያዙን አውቀው ለማስለቀቅ በሄዱበት ጊዜም ብር 40,000.00(አርባ ሺህ) እንዲከፍሉ ሲጠየቁ ይህንኑ ክፍያ ከፈፀሙ በኃላ የጉምሩክ ቁጥጥር ስራ በማሰናከል ወንጀል የተከሰሱ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ የጠቀሰባቸው አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 166 ሙሉ ይዘቱ ሲታይ የጉምሩክ ቁጥጥርን ስለማሰናከል የሚል አርእስት ያለው ሁኖ ዝርዝሩ ማንኛውም ሰው የጉምሩክ ሹም ሰነዶችን እንዳይመረምር ወይም ማጓጓዣዎችን ወይም ዕቃዎችን እንዳይፈትሽ ወይም ወደ መጋዘን፣ የንግድ መደብር ወይም መኖሪያ ቤት እንዳይገባ ያደረገ ወይም ሁከት የፈጠረ ወይም ለሚጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ያልሰጠ ወይም ለምርመራ ያልተባበረ ወይም በማናቸውም መንገድ ሥራውን ለማደናቀፍ ጣልቃ የገባ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ እንደሚቀጣ በንኡስ ቁጥር አንድ ስር ያሰፈረ ሲሆን በንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ኃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የእስራት ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ከፍ ይደረጋል በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ ከድንጋጌው ለተጠሪ አድራጎት አግባብነት ያለው የወንጀሉ ማቋቋሚያ "በማናቸውም መንገድ ስራውን ለማደናቀፍ ጣልቃ የገባ" የሚለው ሐረግ ሲሆን አድራጎቱ ሆነ ተብሎ የሚፈጸም መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የጉምሩክ ቁጥጥርን የማሰናከል ተግባር ሆነ ተብሎ የሚፈፀም ስለመሆኑ የተጠቃሹ አዋጅ ድንጋጌ ይዘቱን መንፈሱ የሚያሳይ ሲሆን አመልካች ተጠሪ አድራጎቱን ሆነ ብለው ስለመፈፀማቸው የሚያስገነዝቡትን የድርጊት አፈፃጸም ተግባር የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4)፣ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረባቸው ማስረጃዎች ተጠሪ አከራካሪው መኪና የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ ከተያዘ በኋላ መግዛታቸውን ያስረዱ ቢሆንም ተጠሪ በመኪናው ላይ የእግድ ትዕዛዝ ባለመሰጠቱ ምክንያት ተገቢው ማጣራት ተደርጎ በውልና ማስረጃ ቀርበው ግዥውን ፈጽመው መኪናው በጉምሩክ ቁጥጥር ስር የዋለ መሆኑን ከአወቁ በኋላም በመኪናው ላይ የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ ሲጠየቁ ብር 40,000.00 ለአመልካች ገቢ ከአደረጉ በኋላ በወንጀል የተከሰሱ መሆኑን በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አረጋግጠው አመልካች ይህንኑ ማስረጃ ሊያፈርስ የሚያስችል ማስረጃ ሊያቀርብ ያለመቻሉን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የግዥ ተግባር በቅን ልቦና የተፈጸመ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት በመሆኑ በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ደግሞ ከአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 166 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ሲታይ በዚህ ችሎት ሊሻወጥ የሚችል ሁኖ አልተኘም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የፈፀሙት ተግባር በቅን ልቦና የተከናወነ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ ይህ ችሎት የሚቀበልበት አግባብ የሌለ ሁኖ ተገኝቶአል፡፡ እንዲሁም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ባቀረበው የወንጀል ክስ መነሻ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው መኪና አስተዳደራዊ ቅጣት ተከፍሎ እንዲለቀቅ ያሰፈሩት ምክንያት ክፍልም በውጤቱ ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ለአመልካች መስሪያ ቤት የተሰጠውን አስተዳደራዊ ስልጣን የገደበ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ምክንያቱም የበታች ፍርድ ቤቶቹ የአመልካችን አስተዳደራዊ ስልጣን ተፈጻሚ እንዲሆን በሚያስገነዝብ መልኩ በውሳኔአቸው ላይ ከማስፈራቸው ውጪ ይህንኑ ስልጣኑን ተግባራዊ እንዳያደርግ በግልጽ አልገለፁምና፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በጉዳዩ ለይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 3867 ግንቦት 06 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 3997 ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 192(2(ሀ)) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪ የቅን ልቦና ገዥ ነው ተብሎ ከወንጀሉ በነፃ እንዲሰናበት በመደረጉ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ሆኖም አመልካች በሕጉ በተሰጠው ስልጣን አግባብ በመኪናው ላይ የሚወስደውን አስተዳደራዊ ውሳኔ ይህ ውሳኔ አያስቀረውም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 111086

የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተሾሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጠታ

አመልካች፡- የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ህግ ማትሪያሲን

ተጠሪ፡- አሚኮ/ሸማቾች የህብረት ስራ ማህበር የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን ፍርድ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በአፋር ክልል የገቢርሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ አመልካች ያቀረበው ክስ አጭር ይዘትም የአሁኑ ተጠሪ የኢፌደሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 98/1/ሀ/ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ለሱማሌ ክልል ህዝብ የሚያገለግል የምግብ ሸቀጥ የለውም ምንዛሪ /ፊራኮ ቫሎታ/ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ እንዲገባ የተደረገው 400 ኩንታል ስኳር የመመሪያ ቁጥር 25/2002 አንቀጽ 6 እና 7/2/ የተመለከተውን በመተላለፍ ተጠሪ ሆነ ብሎ ህገወጥ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ መመሪያው መሰረት ባለስልጣኑ ባዘዘው መሰረትና ቀን ማጓጓዝ ሲገባው ከተመለከት አላማው ውጭ በመገልገል መብቱን ሽፋን በማድረግ በሌላ ሰው ይዞታ ስር ለማዋዋል በህገ ወጥ መንገድ ሲዘዋወር በአዋሽ ጉምሩክ ኬላ በመያዙ በፈጸመው ከቀረጥ ነፃ በገባ እቃ አላግባብ መገልገል ወንጀል መክሰሱን የሚያሳይ ነው፡፡

የተጠሪ ድርጅት ወኪል ቀርቦ በሰጠው መልስ ድርጅቱ ወንጀል አለመፈጸሙን፤ በንብረቱ አጓጓዥ ላይ አመልካች ያቀረበው ክስ በብይን ውድቅ ተደርጓል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ አመልካች ባቀረበው ክስ ስኳሩን ጭነው ሲሄዱ የተያዙ ሹፌሮች በፍ/መ/ቁ/ 03544 ተከሰው በነፃ እንደተሰናበቱ፤ የአሁኑ ተጠሪ አብሮ ተከሰው የወጣ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባይሆንም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ አንቀጽ በመሆኑ ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት የዓቃቤ ህግ /አመልቾች ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁን አመልች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይቅባኝ ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር እንዲታይ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አድርጓል፡፡ ዐቃቤ ህግ በሰበር አቤቱታው የአሁኑ ተጠሪ ከአሁን በፊት ተከሶ በነፃ ለመሰናበቱን፣ በሹፌሮች ላይ የቀረበው ክስ የኮንትሮ ባንድ ወንጀል ስለመሆኑ በመዘርዘር የስ ር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሻር የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና አመልክቷል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

ይህ መዝገብ ከሰ/መ/ቁ/111087 አንፃር እንዲታይ የቀረበ ሲሆን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈጽመዋል የተባሉት ሹፌሮች በአመልካች የቀረበባቸው ክስና ማስረጃ እንዲከላከሉ ትእዛዝ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡ በዚህም ክርክሩ በስር በገቢርሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲቀጥል መደረጉን የውሳኔው ግልባጭ ያመላክታል፡፡

የአሁኑ አመልች መዝገቡ በቀጠሮ ላይ በነበረበት ጊዜ ነሀሴ 22 ቀን 2007 ዓ/ም በፃፈው አቤቱታ በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር በቀድሞ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 98/1/ሀ/ለ/ እንደወንጀል ድርጊት የሚቆጠር ቢሆንም በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163 መሰረት ድርጊቱ አስተዳደራዊ ጥፋት ሆኖ ወንጀልነቱ ቀሪ የተደረገ በመሆኑ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5፣3 መሰረት በሰ/መ/ቁ/ 111086 የተጀመረው የወንጀል ክርክር ተቋርጦ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163 መሰረት ጉዳዩ በባለስልጣኑ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት እንዲፈቀድለት ጠይቋል፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁኑ ተጠሪ የተከሰሰበት አዋጅ ቁ/ 622/2001 አንቀጽ 98/1/ሀ/ እና /ለ/ በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163 መሰረት ወንጀልነቱ ቀሪ ሆነዋል ወይስ አል ሆነም? አመልካች በጉዳዩ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥ ያቀረበው ጥያቄ በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉ ጭብጦች ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ሁነው አግኝተናቸዋል፡፡

የመጀመሪያ ጭብጥ በተመለከተ፡- በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 98/1/ሀ/ እና /ለ/ ስር እንደተመለከተው ከቀረጥ ነፃ በገባ እቃ አላአግባብ መገልገል የወንጀል ተጠያቂነት እንደሚያስከትል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠበት ሰው የእቃው መወረስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደተጠበቀ ሆኖ እቃው በገባ ጊዜ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር የሚመጣጠን የገንዘብ መቀጮና ከሶስት አመት እስከ አምስት አመት በሚደርስ እስራት እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል፡፡ በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163/1/ሀ/ እና /ለ/ ከቀረጥ ነፃ በገባ እቃ ያለአግባብ መገልገል ያለው ተጠያቂነት ቀረጥና ታክስ መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱ በመቶ /50%/ የገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ተደርጓል፡፡ በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ክፍል ሰባት የጉምሩክ ጥፋቶች እና ቅጣቶች በሚል በምእራፍ አንድ "የጉምሩክ ጥፋቶች እና አስተዳደራዊ ቅጣቶች" በሚል ከአንቀጽ 156 እስከ 165 የተዘረዘሩትን ድርጊቶች በአስተዳደራዊ ቅጣት የሚታዩ ስለመሆናቸው ከድንጋጌዎቹ ይዞት መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በአቤቱታው እንዳስረዳው ተጠሪ የተከሰሰበት ጉዳይ አስተዳደራዊ ጥፋት ሆኖ ወንጀልነቱ ቀሪ መሆኑ ተረድተናል፡፡ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5/3/ መሰረት በቀደሞ ህግ እንደወንጀል የሚቆጠር ድርጊት በአዲሱ ህግ የወንጀል ድርጊት መሆኑ ቀሪ ከሆነ ጉዳይ በሚታይበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በዚህም ተጠሪ የተከሰሰበት ጉዳይ በአስተዳደራዊ ውሳኔ የሚታይ እንጂ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል አይደለም ብለናል፡፡

ሁለተኛ ጭብጥ በተመለከተ፡- በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163 መሰረት የተያዘው ጉዳይ በአስተዳደራዊ ውሳኔ የሚታይ ስለመሆኑና የአሁኑ አመልካችም አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የማስተላለፍ ስልጣን በዚህ አዋጅ የተሰጠው በመሆኑ የመወሰን ስልጣኑ የተጠበቀ ነው፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአፋር ክልል የገቢረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 03559 በ30/03/2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ/ 3106 ጥር 28 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ በተለወጠ ምክንያት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ ወንጀልነቱ ቀሪ የተደረገ፤ በአስተዳደራዊ ቅጣት የሚታይ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች በተጠሪ ላይ ህጉ በዘረጋው ስርዓት አስተዳደራዊ ቅጣት የመወሰን ስልጣኑ የተጠበቀ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117065

የካቲት 30 ቀን 2008ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሹ ሺርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓቃቤ ህግ ምህረቱ ቀምላቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሚፍታ ካሚል ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለክርክር መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ክሱ የኮንትሮባንድ ወንጀል ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት አሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ ከስር ክስ ሶስት ተከሳሾች ከነበሩት ጋር የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ የተደነገገውን በመተላለፍ በቀን 10/10/2006 ዓ.ም ከቀኑ 7፡15 አከባቢ ምንም ዓይነት የጉምሩክ ስነስርአት ያልተፈፀባቸው እና ጠቅላላ ቀረጥና ታክሳቸው ብር 15,425.23 /አስራ አምስት ሺህ አራት መቶ ሃያ አምስት ብር ከሃያ ሶስት ሳንቲም/ ለመንግስት ያልተከፈለባቸው መሆናቸውን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው የተለያዩ ንብረቶች በ1ኛው ተከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ረዳትነትና የመኪናው ባለቤትነት እና 2ኛ ተከሳሽ አሽከርካሪነት ከጊዘን ወደ አሶሳ ለመሄድ በኮድ3-00277 ቤጉ በሆነ ሚኒባስ ጭነው በመንገዝ ላይ እያሉ ሽርቆሌ ፌዴራል ፖሊስ ካምፕ አካባቢ በፌዴራል ፖሊስ አባላት በቁጥጥር ስር በማዋላቸው የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ክስ ቀርበውበታል፡፡ ከ2ኛ-4ኛ ተከሳሾች ባለመቅረባቸው በሌሉበት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን ከስር መዝገብ መረዳት ይቻላል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የቀረበውን የወንጀል ክስ በመካዱ ፍርድ ቤቱም የዐ/ህግ ምስክሮች በመስማት ከመረመረ በኋላ ተጠሪ እንዲከላከል ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ መከላከያ ምስክር ያቀረበ ቢሆንም ባለመከላከሉ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛ ካለ በኋላ ቅጣት በተመለከተም በሁለት ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 50,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣና የእስራት ቅጣት በሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ ገደብ እና በተከሳሾች እጅ የተያዘው የኮንትሮባንድ ወንጀል ንብረቶች ለመንግስት ገቢ እንዲደረጉ፡፡ በተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስም የተመዘገበውን ንብረት ኮድ 3-00277 ቤጉ ሚኒባስ መኪና ለባለ ንብረቱ እንዲመለስ በማለት ወስኗል ።

አመልካች በዚሁ የእስራት ቅጣቱ በገደብ መለቀቁና መኪናው ይመለስ በማለት የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታው ቢያቀርብም በውሳኔ ተቀባይነት አላገኘም። የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የስር ፍርድ ቤቶች ቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ እንዲታረም በማለት የቀረበ ነው። የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ፡- የአሁኑ ተጠሪ የተሸከርካሪው ባለቤት እና በወቅቱ በተሸከርካሪው ላይ በረዳትነት ሲሰራ የኮንትሮባንድ እቃዎች ጭኖ በመያዙ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ የተከሰሰ እና በዚሁ አዋጅ ስር ጥፋተኛ የተባለ እንደመሆኑ በወንጀል የተፈፀመበትን ማንንጣ መወረስ እንዳለበት ህጉ በግልፅ ደንግጎ ይገኛል። የስር ፍርድ ቤት ይህን የህግ ድንጋጌ በጥልቀጥት ሳይመለከት እና ከዚህ ተቀራኒ በሆነ መልኩ ማንንጣውን በተመለከተ ያለምንም ምክንያት ለባለንብረቱ ይመለስ በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው።

በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የተጠሪ ማንንጣ ላይ የተሰጠውን ትእዛዝ አግባብነት ከጉምሩክ ህግ አንፃር በጥልቀት መመርመር ሲገባው ተጠሪ በወቅቱ በመኪናው ላይ በረዳትነት ሲሰራ እንደነበረ የስር ፍርድ ቤት በማረጋገጥ የሰጠው ጥፋተኝነት ውሳኔ ባልተሸረበት እና የመከራከሪያ ነጥብ ያለሆነውን የአሁን ተጠሪ መኪናው ኮንትሮባንድ እቃ ሲጫን በቦታው አልነበረም በማለት የወ/መ/ስ/ስ/ህግን እና የሙግት ስነስረአት በሚቃረን መልኩ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ማፅናቱ የህግ ስህተት የተፈፀመ መሆኑን፤ እንዲሁም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 192፤196 እና 197 የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት የቅጣቱን አፈፃፀም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 196/2/ መሰረት መገደቡ መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ተጠሪ ላይ የተጣለውን የቅጣት አፈፃፀም ገደብ እንዲያነሳልን እና የአሁኑ ተጠሪ የሆነውን ኮድ 3-00277 ቤጉ ተሸከርካሪ እንዲመለስ የተሰጠው ትእዛዝ ተሽሮ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ መሰረት ለመንግስት ውርስ እንዲሆን ትእዛዝ እንድሰጥላቸው አቤቱታቸውን አቅርቧል።

የቀረበው የሰበር አቤቱታ በመመርመር ንብረትነቱ የተጠሪ ከሆነ ኮድ 3-00277 ቤጉ ሚኒባስ የኮንትሮባንድ ዕቃ ተጭኖ በመገኘቱ በአዋጅ ቁ.622/2001/ አንቀጽ 91/2/ መሰረት ተጠሪ ጥፋተኛ መባሉ ተረጋግጦ እያለ ዕቃው የተጫነበት መኪና ለተጠሪ ይመለስ የመባሉን አግባብነት ከአዋጅ ቁ. 622/2001/ አንቀጽ 91/2/ እና 104 ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል። በዚሁ መሰረትም ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በታዘዘው መሰረት በቀን 21/01/2008ዓ/ም የተፃፈ 2 ገጽ መልስ አቅርቧል። ይዘቱም ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የገደበው ህጉ በሚፈቅደው አግባብ ስለሆነ የህግ ስህተት የሚያነሳና ለክርክር የሚቀርብ አይደለም፡፡ በወቅቱ ነዳጅ አልቆብናል አምጣልን ብለውን ከአሶሳ ይገቦላቸው በሄድኩበት የእርዳታ ዘይቱ ጫነ መሆኑን በመገንዘብና ከፍተኛው የገንዘብ ቅጣት 50,000 የተቀጣሁ በመሆኑ በኢግዚቢትነት የተያዘው ተሽከርካሪ ለተከሳሽ ይመለስለት መባሉአግባብነት ያለውነው፡፡ ስለዚ የስር ፍርድ ቤቶች ወሳኔ በማፅናት የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ በነፃ እንዲያሰናብተኝ በማለት መልሱን አቅርበዋል፡፡

አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2008ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል ተጠሪ በጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ምንም ቅሬታ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አላቀረበም:: የስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሳይሻር መኪናው ሲያዛ በቦታው አልነበርኩም የመከራከሪያ ነጥብ ተቀባይነት የለውም:: በሌላ በኩል 50,000 ብር ከፈልኩ በማለት ያቀረበው ጥፋተኛ በተባለበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ስር በተነገገው መሰረት የተጣለበት የገንዘብ መቀጮ እንጂ የተያዘው መኪና ላማስለቀቅ የተከፈለ አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ እንዲገነዘብልን በማለት አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም ታክስና ቀረጥ ሳይከፈለበት የኮንትሮባንድ ዕቃ ስታጓጉዝ የተያዘችው የተጠሪ መኪና ይመለስ በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከግምሩክ አዋጅ ህጉ አግባብነት ያለው መሆኑንና አለመሆኑን የሚለውን ጭብጥ መልስ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት የኮንትሮባንድ ዕቃ ለመንግስት ሊከፈል የሚገባው ታክስ እና ቀረጥ ብር 15,425.23/አስራአምስት ሺህ አራት መቶ ሃያ አምስት ብር ከሃያ ሶስት ሳንቲም/ያልተከፈለበት ሲያጓጉዝ በተያዘበት ወቅት ተጠሪ የመኪነው በረዳትነት እንደነበረ እንዲሁም የመኪናው ባለቤት መሆኑን በማረጋገጥ በተከሰሰበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ የጥፋተኝነት ውሳኔ በመስጠት የፅኑ እስራትና የገንዘብ መቀጮ ቅጣት የተወሰነበት መሆኑን ተረጋግጠዋል፡፡ በተጠሪ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ በይግባኝ ቀርቦ የተለወጠ አይደለም፡፡ ተጠሪ ጥፋተኛ ከተባለና ለኮንትሮባንድ ዕቃ መጓጓዣ የዋለው የተጠሪ መኪና መሆኑን ከተረጋገጠ መኪናው የማይወረስበት ሁኔታ አለ ወይ የሚለውን ከሕጉ አንፃር መታየት አለበት፡፡

አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ/1/ ላይ በተመለከተው ሕገወጥ መንገድ የተገኙ እቃዎች መሆናቸውን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው እቃዎቹ ያጓጓዘ፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያከማች፤ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ ማንኛውም ሰው በቅን ልቦና ለወንወጀሉ ባዕድ የሆኑት ሰዎች መብት ሳይነካ ወንጀሉ የተፈፀመበት ዕቃና መሳሪያ እና የወንጀሉ ፍሬ እንደሚወረሱ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ የኮንትሮባንድ ዕቃ መሆኑን እያወቀ ያንዝዘ በመሆኑ በመረጋገጥ ጥፋተኛ ስለተባለ በቅንልቦና ወይም ለወንጀሉ ባዕድ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ እንዲሁ በሆነበት ከጉምሩክ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 104/1/ ማንኛውንም እቃ ወይም ማንጓጓዣ ሊወረስ በሚችል ወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ ተጨማሪ ትእዛዝ መስጠት ሳይስፈልግ እቃው ወይም ማንጓጓው እንዲወረስ ይደረጋል ሲል ተደንግጓል፡፡

የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ለማፅናት እንደምክንያት ያደረገው ተጠሪ ዕቃው ሲያዝ በቦታው አልነበረም ዕቃው ሲጫን አያውቅም የሚለውን በማሰረጃ የተረጋገጠው ረዳት ሆኖ ዕቃው የመኪናው ሽፌር የነበረው 2ኛ ተከሳሽ የኮንትሮባንድ ነው እንዳይጫን እየተባለ የጫነ መሆኑን በአመልካች ምስክሮችበመረጋገጥ በተጠሪ ላይ የጥፋተኝነት ከተሰጠበት ውሳኔ በሚቃረን እና የሰ/መ/ቁ.76976 ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመጥቀስ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

ለዚህ ጉዳይ ተመሳሳይ በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 64819 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥተቦታል፡፡ በመሆኑ ይህ የህጉ መንፈስ መሰረት በማድረግ ተጠሪ የመኪናው ባለቤት ሆኖ በወንጀሉ ተሳተፊነት በማረጋገጥ የጥፋተኝነት ከተሰጠ ሌላ ተጨማሪ ትእዛዝ ሳያስፈልግ የኮንትሮባንድ ዕቃ ለመንጓጓዣ የዋለው መኪና ምንም ህጋዊ ምክንያት በሌለው ለተጠሪ ይመለስ በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ከጉምሩክ አዋጁ አንቀጽ 91/2/ እና 104/1/ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝተዋል ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የቤ/ጉ/ክ/መ/ ጠ/ፍ/ቤትበመ/ቁ.06590ሐምሌ 23 ቀን 2007ዓ/ም፤ የተሰጠ ውሳኔ እና የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.09092ግንቦት 28 ቀን 2007ዓ/ም የተጠሪ መኪና ይመለስለት በማለት የተሰጠ ቅጣት ውሳኔ ክፍል ብቻ በወ/መ/ስ/ስ/ቁ.195/2/መ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በተጠሪ ላይ የሁለት ዓመት የፅኑ እስራት በመገደብ የተወሰነ ቅጣትና የገንዘብ መቀጮ ፀንተዋል፡፡
3. በተጠሪ ስመንብረቱ ተመዝግቦ የሚገኘው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-00277 ቤጉ የህዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ ለመንግስት በውርስ ገቢ እንዲደረግ በማለት ታዟል፡፡

መዘገቡ ተዘግተዋል፤ ወደ መዘገብ ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዕምሯዊ ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 99082

ጥቅምት 23 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፍሬ ህይወት ደመቀ (የመካኒኩ ፊልም ኘሬዲውሰር)- ጠበቃ ሙሉጌታ ዘመነ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ት ቤሩት ዳዊት - ጠበቃ መንግስቱ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቅጅና ተዛማጅ መብት ጥያቄ ጋር የተያያዘ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኗ አመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡

የተጠሪ የክስ ይዘትም፡- ዕውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ጊዜያቸውን በመሰዋት በነጠላ ዜማ የለቀቁትን “በትዝታ አቅርቤ” የተሰኘውን የዘፈን ሥራቸውን ያለፈቃዳቸውና ያለ ስምምነታቸው የአሁኗ አመልካች ኘሮዲውስ ላደረጉት "መካኒኩ" ለተባለው ፊልም በማጀቢያነት (ሳውንድትራክ) በመጠቀም ያለአግባብ ቁሳዊ ጥቅም ያገኙበት መሆኑን፣በአመልካች አድራጎትም 164,000.00 የሚገመት የኢኮኖሚ ጥቅም ማጣታቸውንና የብር 100,000.00 የሞራል ጉዳት እንደደረሰባቸው ጠቅሰው በድምሩ ብር 264,000.00 (ሁለት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ብር) ከነወለድ ወጪና ኪሣራ ጨምረው እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጡት መልስም፡- የተጠሪ የሙዚቃ ሥራ ለመካኒኩ ፊልም ማጀቢያነት የተጠቀሙት መሆኑን ሳይክዱ የሙዚቃው ሥራ ለፊልሙ መጠቀም ይችሉ እንደሆነ በአቶ ዮናስ ብርሃነ መዋ በኩል ተጠሪን ጠይቀውና ተገናኝተንው የተጠሪን ስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲያስተዋውቁላቸው ተነጋግረው ሰኔ 8 ቀን 2003 ዓ.ም በአቀነባባሪያቸው የእጅ ጽሑፍ የተፃፈ ሲዲ ተጠሪ አምጥተው የሠጧቸው መሆኑን፣ በዚህም ተጠሪ ወደውና ፈቅደው በማጀብያነት አመልካች እንዲጠቀሙበት ሰጥተዋቸው እያለ ያለፍቃዴ ነው ማለታቸው ሐሰት መሆኑን ጠቅሰው ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው ምክንያት የለም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲደረግላቸው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭም እንደተጠሪ ያለ ጀማሪ ዘፋኝ የዘፈነው ዘፈን ከብር 3000.00(ሶስት ሺህ) ባለይ እንደማይሸጥ እየታወቀ ተጠሪ ብር 164,000.00 የኢኮኖሚ ጉዳት ደርሶብኛል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸው ያላግባብ መሆኑንና በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪን ግምት እንደሚቃወሙ፣አዲስ ዘፈን እንደመሆኑ መጠን ለዘፈኑ ገንዘብ ከሚከፈላቸው ክሊፕ እንዲሰራላትና ዘፈኑ የፊልም ማጀቢያ እንዲሆን የምረቃ ቀን ቀርበው ምስጋናና ሰርቲፊኬት እንዲሰጣት፣ዘፈኑ በተለያዩ ሚዲያዎች ተሰራጭቶ እንዲተዋወቅላት በዝርዝር ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ ሰኔ 08 ቀን 2003 ዓ/ም ተፈራርመው ከስምምነቱ በኋላ ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ/ም በአቀናባሪያቸው የእጅ ፅሑፍ የተፃፈ ሲዲ እራሷ አምጥታ የሰጠቻቸው መሆኑን፣በዚህም መሰረት የሙዚቃ ሲዲዋን በላይ ላይ ድምፃዊት እራሷ መሆኗን አቀናባሪያቸው ሮቤል ዳኜ መሆኑን፣ ስራቸው በቅርብ ቀን በአልበም እንደሚወጣ፣ሲዲውም ላይ በመግለፅ የተለያዩ ሚዲያዎች በፕሮግራማቸው በማስተላለፍ እንዲያስተዋወቁላቸው ያደረጉ መሆኑን፣ፊልሙ በሚመረቅበት ጊዜም ለፊልሙ ማጀቢያነት የተጠቀሙት ሙዚቃ የተጠሪ መሆኑን በማስተዋወቅ በመድረክ ላይ ተጠርተው ሰርቲፊኬት እንዲሰጣቸው ማድረጋቸውንና በስምምነቱ መሰረት በአመልካች በኩል ሳይፈፀም የቀረው የዘፈኑን ክሊፕ ማዘጋጀት ብቻ ሲሆን ይህን በተመለከተም ስራው ያልተሰራው ተጠሪ የዘፈኑን ታሪክ አዘጋጅተው ባለማቅረብና ለክሊፑ የሚሆነውን አልባሳትና ቦታ አዘጋጅተው ባለመቅረባቸው ጥፋት መሆኑን፣ ክሊፑ የሚሰራበት ዋጋ ከብር 4000.00 እንደማይበልጥና ተጠሪ ዜማቸውን በመሸጥ ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አመልካች ያለማስቀረታቸውንና በፈቃዳቸው መሰረት ለተከናወነ ተግባርም የሞራል ካሳ የሚከፈልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና የአመልካችን የሰው ምስክሮችን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ከተጠሪ ዕውቅና ውጭ ማጀቢያ ዘፈኑን ለፊልሙ ያለመጠቀማቸውን ያስረዱ ስለሆነ ከሳሽ የደረሰባቸው ኢኮኖሚያዊም ሆነ የሞራል ጉዳት የለም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊልሙ ማጀቢያነት የተጠቀሙት በተጠሪ ሙሉ ፍቃድ ስለመሆኑ ተረጋግጦአል ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መወሰኑ ባግባቡ ነው በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቀበለው ሲሆን ተጠሪ ዘፈናቸውን ለአመልካች ፊልም ማጀቢያ በፍቃዳቸው ሲሰጡ ተጠሪ በአመልካች በኩል የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራላቸው፣በገንዘብ መልክ ከሚሰጣቸው ይልቅ የዘፈኑ ክሊፕ እንዲሰራላቸው አመልካች መዋዋላቸውን አልካዱም፣አመልካች እንደውሉ ያልፈጸምኩት ተጠሪ የዘፈኑ ታሪክ፣ አልባሳት እና ክሊፑ የሚሰራበት ቦታ ባለመምረጣቸው ነው ቢሉም አመልካች ክሊፑን ለመስራት የጠቀሷቸው ነገሮች ተጠሪ ሚሚላት እንደሚገባቸው የሚያመላክት ስምምነት ስለመኖሩ አላስረዱም በሚል ድምዳሜ ተጠሪ እነዚህ ነገሮች ባይሟሉ፣ በክሊፑ ፈንታ ገንዘብ ሊከፈላቸው ይችል እንደነበረ፣ አመልካች በክሊፑ ፋንታ ለተጠሪ ክፍያ ሊፈጽሙ እንደሚገባ ፍርድ ቤቱ አምኖበታል በማለት የካሳውን መጠንም በርትዕ ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ) አድርጎ ይህንኑ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም፡- ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊልሙ ማጀቢያነት የተጠቀሙት በተጠሪ እውቅና እና ፈቃድ ስለመሆኑ ከአረጋገጠ በኋላ በክሊፑ ፋንታ ተጠሪ ገንዘብ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ባልተወጡበት አግባብ ከመሆኑም በላይ የካሳው መጠንም ማስረጃ ቀርቦ እያለ በርትዕ መወሰኑ ከሕጉ ይዘትና መንፈስ ውጪ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም

1. አመልካች ለተጠሪ በክሊፑ ፈንታ ገንዘብ እንዲከፍሉ መወሰኑ የግራ ቀኙን ተነፃፃሪ ግዴታ ያገናዘበ ነው? ወይስ አይደለም?
2. የካሳው መጠን በርትዕ መወሰኑን ሕጋዊ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ነጥቦች በጭብጥነት ሊታይ የሚገባ ሁነው አግኝተናል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በተጠሪ ውል መኖሩን በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን ተጠሪ አመልካች በጽሑፍ የተደረገው ውል ጠፍቶአል በማለት በሰው ምስክሮች ማረጋገጥ እንደሚችሉ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢነት የሌለውና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2003 ድንጋጌን የሚቃረን ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ለዚህ ችሎት በጽሑፍ ከአቀረቡት መልሳቸው የተገነዘብን ቢሆንም ይህ የተጠሪ ክርክር በዚህ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባስከፈቱት የሰበር መዝገብ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ረገድ ራሱን የቻለ የሠበር አቤቱታ ያቀረቡ መሆኑን የጠቀሱ ሲሆን በዚህ ረገድ አለ የተባለውን የሰ/መ/ቁጥር 100338 አስቀርበውን ስንመለከተውም መዝገቡ በሰበር አጣሪ ችሎት በ03/10/2006 ዓ/ም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ መዘጋቱን መረዳትን ችለናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በግራ ቀኙ መካከል በፅሑፍ የተደረገ ውል የለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አልተኘም፡፡ በግራ ቀኙ መካከል ሕጋዊ ውል መኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ የግራ ቀኙ ተነፃፃሪ

ግዴታ የሚለየው በዚሁ ውል በመሆኑ እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን የሚቀርበው ክርክር በዚሁ የውል ሰነድ ይዘት መደገፍ ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2001 እና 2005 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡

በመሠረቱ ውል ሕጋዊ ውጤት ያለው ተግባር እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን በውሉ የተጣለበትን ግዴታ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ተዋዋዮች በውሉ በተገለጸው ስምምነት መሰረት ግዴታቸውን ከተወጡ ውለታው በታሰበው ዓላማ መሰረት ተፈፅሟል ለማለት የሚቻል ሲሆን ይህም ማለት የውሉ ግዴታ ያለበት ሰው በውሉ ላይ የተገለጸውን የመስጠት፣ የማድረግ ወይም ያለማድረግ ተግባር በተገቢው መንገድና በብቃት ማከናወኑን ማረጋገጥ መሆኑ ይታመናል፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በምን አይነት አኳኋን፣ ጊዜና ቦታ የውል ግዴታቸውን መፈጸም እንዳለባቸው በፍትሓ ብሔር ሕጉ ከቁጥር 1740 እስከ 1762 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ አንድ ተዋዋይ ወገን በውሉ የገባውን ግዴታ በውላቸውና በሕጉ ውስጥ በተደነገገው አኳኋን ያልፈፀመ እንደሆነ የውል ግዴታውን እንደጣሰ የሚቆጥር ሲሆን የውሉ ተጠቃሚ የሆነ ተዋዋይ ወገን ደግሞ እንደውሉ እንዲፈጸምለት ወይም ውሉ እንዲፈርስለት የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1771(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1757 ድንጋጌ እንደሚየሳየው ውሉ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ወገን ጥያቄውን ማቅረብ ያለበትና ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው በውሉ መሠረት አስቀድሞ ሊወጣው የሚገባ ግዴታ የተወጣ ስለመሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክሊፕ ለማሰራት ግዴታ መግባቸውን ሳይክዱ የክሊፑ ስራ እንደውሉ ያልተፈፀመው በተጠሪ ጥፋት ነው፣ተጠሪ የዘፈኑን ታሪክ፣አልባሳት ባላማቅረባቸውና ክሊፑ የሚሰራበትን ቦታ ባለመምረጣቸው ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በዚህ ረገድ ስልጣን ያለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ውሉ መኖሩን አምነው የተጠሪ ግዴታ ነው እስካሉ ድረስ ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ መወጣት የነበረባቸው መሆኑን ከክርክራቸው አቀራረብ መረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በውሉ የገቡትን ግዴታ ያልተወጡበት መንገድ ስለመኖሩ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 258 እና 259፣ እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1757፣ 2001 እና 2005 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ዘፈኑ ለፊልም ማጀብያ እንዲውል ፈቅደው ከሰጡ የሞራል ጉዳት ደርሶብኛል፣ የሞራል ጉዳት ካሣ ይከፈል ሊሉ አይችሉም በማለት መወሰናቸውን፣ግራ ቀኙን እስከዚህ ችሎት የሚያከራክራቸው ነጥብ ግን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በክሊፑ ፈንታ አመልካች ለተጠሪ ገንዘብ ሊከፍሉ የሚገባ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አምኖአል በማለት አመልካችን ኃላፊ አድርጎ የኃላፊነቱን መጠንም በርትዕ ብር 100,000.00 ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል መሆኑን ነው፡፡

የተጠሪ ስራ በአዋጅ ቁጥር 410/96 አግባብ ጥበቃ የሚደረግለት መሆኑና አመልካች ለፊልማቸው ማጀቢያነት የተጠቀሙበት መሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊማቸው ማጀቢያነት ሲጠቀሙ ግን ለተጠሪ የከፈሉት ገንዘብ ስለመኖሩ በፍሬ ነገር ደረጃ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም ለተጠሪ ገንዘብ ከሚከፈላቸው የክሊፑን ወጪ አመልካች ሸፍነው ክሊፑን ሊሰሩላቸው መስማማቸውን፣ ሆኖም ይህ ስምምነት ተፈፃሚነት ሳያገኝ የቀረው ተጠሪ በራሳቸው በኩል የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ባለመወጣታቸው ነው በማለት አመልካች ተከራክረው ይህ የአመልካች ክርክር በማስረጃ ያለመደገፉን ይግባኝ ሰሚው ችሎት ማረጋገጡን ይህ ችሎት ተገንዝቦአል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 410/96 ጥበቃ ያገኘውን የተጠሪን ዘፈን አመልካች መጠቀማቸው እስከተረጋገጠ ድረስ አንድ ዘፈን ለፊልም ማጀቢያነት ሲውል ለዘፈኑ ባለቤት ሊከፈል የሚገባውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያህል ተጠሪ የማያገኙበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አመልካችን ኃላፊ ማድረጉ ከአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 7፣ 8 እና 34 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንጻር የሚነቀፍ ሁኖ ስላልተገኘ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ረገድ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻው አቢይ ነጥብ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካሳውን የወሰነበት አግባብ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ በቅጅ ወይም በተዛማጅ መብቶች መጣስ ምክንያት ለፍ/ቤት የቀረቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮች የካሣ አከፋፈል ባለመብቱ የደረሠበት የገንዘብ ጉዳት እና በመብቱ መጣስ ምክንያት የተገኘ ትርፍን መሰረት ያደረገ መሆን እንደአለበት የሕጉ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ የካሳ አከፋፈሉ ባለመብቱ መብቱ ለተጣሰበት ሥራ ያወጣውን ወጪና ተከሣሹ ያገኘው ትርፍን ኢኮኖሚያዊ መብቱን ለማስከበርና የሞራል ካሣ የመክፈል ኃላፊነትን የሚያጠቃልል መሆኑ ይታወቃል፡፡ አዋጁ ለሞራል ጉዳት የሚከፈል ካሣ በጣም አነሰ ቢባል ከ100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የማያንስ ሆኖ እንደ ጉዳቱ መጠን ከ100 ሺህ ብር በላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊወሠን እንደሚችል የአንቀፅ 34(4) ድንጋጌ በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን የቅጂና ተዛማጅ መብቶችን በመጣስ የሚኖር የፍትሐብሔር ኃላፊነት የጉዳት ካሣና የሞራል ካሣ ከመክፈል በተጨማሪ ለካሣ አከፋፈሉ ምክንያት የሆነው ሥራ በባለመብቱ ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ ከንግዱ እንቅስቃሴ ውጭ እንዲሆኑ ወይም እንዲወገዱ ወይም በሌላ ተገቢ አኳኋን እንዲጣሉ ለማዘዝ እንደሚቻልም ሕጉ ይደነግጋል፡፡ ፍርድ ቤት በዚህ አግባብ ውሳኔ ሲሰጥ የተከራካሪ ወገኖችን የማስረዳት ግዴታ ግንዛቤ ባስገባ መልኩ ማስረጃን መሰረት ማድረግ እንዳለበት የሚታወቅ ሲሆን በጉዳዩ ላይ ማስረጃ ቀርቦ በማስረጃው መወሰን አስቸጋሪ ሁኔታ ካለም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 በተመለከተው አግባብ ካሳውን መወሰን እንደሚቻል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1790(2) ድንጋጌን በምንመለከትበት ጊዜ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ካሳ በርትዕ ከሚወሰንባቸው ምክንያቶች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ስር የተመለከቱት ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ የነገሮች ተራ ሁኔታዎች የሚለው ሐረግ ይገኝበታል፡፡ ይህ የድንጋጌው ይዘት ነባራዊ አለምን መሰረት በማድረግ የነገሮች ተራ ሁኔታዎች ተመዛዝነው የካሳ መጠኑ ሊወሰን እንደሚችል የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊልሙ ማጀቢያ በመጠቀማቸው ምክንያት በተጠሪ የደረሰ የኢኮኖሚ ጉዳት አልያም አመልች የተጠሪን ዘፈን በፊልም ማጅብያ ሲጠቀሙበት በገንዘብ ምን ያህል ይከፈላቸዋል ለሚለው ጥያቄ ተጠሪ 164,000.00 (አንድ መቶ ስድሳ አራት ሺህ ብር) የኢኮኖሚ ጉዳት ደርሶብኛል ከማለታቸው በቀር ይህንኑ የኢኮኖሚ ጉዳት የደረሰባቸው ለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳላቀረቡ፣ አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊልም ማጀብያ ሲያውሉ ሊከፍላቸው ያሰቡት አልያም ለዘፈኑ ክሊኝ ምን ያህል እንደሚያወጡ ተዋውለናል ከማለታቸው ውጪ በጽሑፍ ውስጥ አስፍረው የነበረ ስለመሆኑ ያስረዱት ነገር የለም የሚሉትን ምክንያቶችን ጠቅሶ በተጠሪ ላይ የደረሰው ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ወይም የቀረ ጥቅም ለመገመት አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱን መደምደሙን በዚህም ምክንያት አመልካች በርትዕ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት መወሰኑን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በውል ሰነዱ ላይ የሰፈረውን ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ባያስረዱም ለአንድ ፊልም ማጀቢያነት የሚውል ዘፈን ሊከፈልበት የሚገባው ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ገበያውን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ዘፋኞች ለተያዩ ፊልሞች የተከፈላቸውን ዋጋ ለይተው በመግለፅ፣ በዚህ ረገድም የሰነድ ማስረጃ ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው የተከራከሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪም አመልካች የጠቀሷቸው ዘፈኖችና ዋጋቸው በስር ፍርድ ቤት በክርክር ደረጃ አልተነሱም ሳይሉ አመልካች ሊከፈል ይገባል የሚሉት ዋጋ የወቅቱን የፊልም ማጀቢያ ዘፈን ዋጋ ያላገናዘበ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ለዚህ ችሎት ከሰጡት የፅሑፍ መልስ ተመልክተናል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ማስረጃ ቆጥረው እያሉና ማስረጃዎቹ ለጉዳዩ ያላቸውን አግባብነት ሳይመረምር በውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰነዱ ላይ ሰፍሮ የተገኘ ዋጋ አልተገኘም በሚል ምክንያት ብቻ ወደ ርትዕ መሄዱ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም የተከራካሪ ወገኖችን ማስረጃ የመስማት መብት እና ፍርድ ቤቱ እውነትን መሰረት ያደረገ ዳኝነት ለመስጠት ይቻለው ዘንድ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 ድንጋጌን ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባበትን አግባብ ያላገናዘበ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

አንድ ዘፈን ለአንድ ፊልም ማጀቢያ ሲውል ዋጋው በተዋዋይ ወገኖች ሊቆረጥለት የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም ዋጋው በውሉ መታወቅ ካልተቻለ ግን ተከራካሪ ወገኞች በሚያቀርቧቸው አግባብነት ባላቸው ሌሎች ማስረጃዎች ወይም ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 መሰረት መድቦ በሚያጣራው ባለሙያ ሊታወቅ የሚችል መሆኑን የነገሮች ተራ ሁኔታዎች የሚያስረዱ መሆኑን ነባራዊው አለም ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠሪ ዘፈን ለፊልም ማጀቢያነት ሲውል ሊከፈል ይችል የነበረውን ዋጋ አመልካች በዚህ ረገድ ማስረጃዎቹ ናቸው በማለት ከአቀረቧቸው የሠነድ ማስረጃዎች ወይም ከሚመለከተው የሙያ ማህበር አግባብነት ያለውን ባለሙያ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 መሰረት እንዲመደብ አድርጎ ትክክለኛውን የወቅቱን ዋጋ አጣርቶ መወሰን ሲገባ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ውጪ በርትዕ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 117093 ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 93456 ጥር 30 ቀን 2006 ዓ/ም በከፊል የተሻረው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊልሙ ማጀቢያ በመጠቀማቸው ዋጋውን ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ሆኖም አመልካች ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሉ በርትዕ መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ትክክለኛ አፈፃጸም ያላገናዘበ በመሆኑ ተሽሯል፡፡በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ኃላፊ የተባሉ መሆኑን በመገንዘብ የኃላፊነት መጠኑን ግን በፍርድ ሀተታው ላይ በተገለጸው አግባብ አግባብነት ባላቸው የአመልካች ማስረጃዎች እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 መሰረት ከሚመለከተው የሙያ ማህበር ተጣርቶ በሚቀርበው ማስረጃ መሰረት በመመርመር ሊወሰን ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡ **መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡** የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105211

ጥቅምት 1/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲ.ር.ጋ.ጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካቾች፡- 1. አቶ እንዳለ ደንቦባ
2. አቶ ንጉሴ ደንቦባ
3. ወ/ሪት ውቢት ደንቦባ
4. ወ/ሮ ሽቶ ደንቦባ

ጠበቃ አብዮት አበበ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አልማዝ ደንቦባ
2. ወ/ሮ ዘውዲቱ ደንቦባ
3. ወ/ሮ እታፈራሁ ደንቦባ
4. አቶ ጌታቸው ደንቦባ
5. ወ/ሮ ወይንሐረግ ደንቦባ

ጠበቃ ሰለሞን ስዩም ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ ተቀብሎ የቀደመ ውሳኔውን በመሻሩ እና ይግባኝ ሰሚውና የሰበር ችሎቱም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የቀረበላቸውን አቤቱታ ባለመቀበል መዝገቡ በመዝጋታቸው የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ባላንባራስ ደንቦባ ውፍዬ ህዳር 1996 ዓ.ም ኑዛዜ አድርገዋል ተብሎ ለፍ/ቤቱ ቀርቦ ፍ/ቤቱ ኑዛዜውን በማፅደቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን በኑዛዜው ላይ የተጠቀሱት ምስክሮች ኑዛዜው በተደረገበት ዕለት በቦታው ያልነበሩ ኑዛዜው ላይ የፈረሙት ኑዛዜው ከተደረገ በኋላ ቢሮዋቸው ድረስ በሄደላቸው መሰረት በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 881/3/ የተመለከተውን የሚያሟላ አይደለም፤ በኑዛዜው ተራ ቁጥር 5 የተመለከተው የንግድ ድርጅት ሟች ከባለቤታቸው ጋር ያፈሩት በመሆኑ የራሳቸው ብቻ ባልሆነ ንብረት ላይ ኑዛዜ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም፤ ለመቃወም አመልካቾች የተናዘዙትም ሊደርሳቸው ከሚገባው ድርሻ በታች ነው፤ ስለሆነም ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለት የመቃወም አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአሁን አመልካቾች ለአቤቱታው በሰጡት መልስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት የሚቀርብ አቤቱታን ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ጉዳይም ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት የተደረገ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 881 እና 882 የተመለከተውን የተከተለ ነው፤ ሟች በኑዛዜው የገለፁት ድርሻዬን በማለት ነው፤ ሊደርሰን ከሚገባው ድርሻ በታች ነው ለሚሉትም በህይወት የሌሉትን ወ/ሮ አለምፀሐይ ደንቦባን በመቀላቀል የንብረቱን ግምት በማካፈል በመሆኑ መቃወሚያው የሕግ መሰረት የለውም ብለዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በተመለከተ የኑዛዜውን ሰነድ መርምሮ የኑዛዜ ወራሽነት ውሳኔ የሰጠ ራሱ ፍ/ቤቱ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት በውሳኔው ላይ በዚያው መዝገብ ላይ የሚቀርበውን መቃወሚያ ተቀብሎ ለማየት ስልጣን አለው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በፍሬ ጉዳዩም የግራ ቀኙን ክርክር እና በኑዛዜው ላይ የተመለከቱ ምስክሮችን ቃል ከሰማ በኋላ ከአራቱ ምስክሮች መካከል ሁለቱ ኑዛዜው በማን እንደተፃፈ የት እንደተፃፈ አለማወቃቸውን ገልፀው ኑዛዜው ላይም የፈረሙት ሁሉም ምስክሮች በሌሉበት መሆኑን ተናዛዡ ሲፈርም ያላዩ መሆኑን ገለፀዋል፤ የቀሩት ሁለቱ ምስክሮች ደግሞ ኑዛዜው የት እንደተፃፈና ማን እንደፃፈው ያላዩ መሆኑን ገልፀው ነገር ግን ተፅፎ የቀረበው ኑዛዜ በአራቱ ምስክሮች ፊት ተነቦ ተፈርሞ ነበር በማለት መስክረዋል፡፡ ስለሆነም ኑዛዜው የፍ/ብ/ህ/ቁ 881 ስር የሰፈረው ያሟላ ካለመሆኑም በላይ የምስክሮች ቃል ተመሳሳይ አይደለም በማለት ቀሪዎችን መከራከሪያዎች መመልከት ሳያስፈልግ አስቀድሞ የተሰጠው የኑዛዜ ወራሽነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 360/2/ መሰረት በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኙ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሰረት የሰረዘ ሲሆን የከተማው የሰበር ችሎትም ውሳኔው መሰረታዊ ሊባል የሚችል የሕግ ስህተት ስላልተገኘበት ለሰበር አያስቀርብም ብሏል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ፍ/ቤት መስከረም 13/2007 ዓ.ም የተፃፈ 4 ገፅ ዝርዝር የሰበር ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ይኸው ተመርመሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሰረት የቀረበለትን የመቃወም አቤቱታ አከራክሮ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና ከአዋጅ ቁጥር 408/1996 እንዲሁም በሰበር መ/ቁ 75560 ከተሰጠው የሕግ ትርጉም አንፃር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙም በፅሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41/1//ሸ/ በአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀፅ 2/1/ እንደተሻሻለው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት በሚቀርብ አቤቱታ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡ ተቃውሞ የቀረበበት ውሳኔ የተሰጠውም በሕጉ በተደረገው የዳኝነት ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በሌላም በኩል የተቃውሞ አቤቱታው ያስከተለው የሕግ እና የፍሬ ነገር ክርክር ይዘት ሲታይ ከኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀቱ የዘለለ እንድምታ የለውም፡፡

ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች አስቀድመው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት በቀረበ አቤቱታ ላይ ባሳለፉት ውሳኔ የሚነሳን የተቃውሞ አቤቱታ ተቀብለው ለማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን የላቸውም ተብሎ የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም፡፡

የሰ/መ/ቁ/ 75560 ሐምሌ 26/2004 ዓ.ም በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የባልና ሚስትነትን ማስረጃን የሚመለከት ሲሆን በእጃችን ካለው የወራሽነት ማስረጃ ጥያቄ ጋር አንድ ናቸው ወይም ተመሳሳይነት አላቸው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የስረ ነገር ስልጣን ጥያቄን ለመወሰን መርህ የሆነው የክሱን ምክንያት ይዘት መመልከት ነው፡፡ ከይዘቱ ውጭ የሆኑ ሌሎች የማያመሳስሉ ሁኔታዎች መኖር ጉዳዮች በተመሳሳይ የስረ ነገር ስልጣን ስር ያርፋሉ የሚል መደምደሚያ ላይ አይደርስም፡፡ የባል ወይም የሚስትነት ማስረጃ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በቀረበ አቤቱታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት ተቃውሞ ሲቀርብበት ተቃውሞውን ተከትሎ ፍ/ቤቶች የምስክር ወቀረቱን ትክክለኛነት ከማረጋገጥ ባለፈ ስለ ጋብቻ መኖር አለመኖር እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጋብቻ ውጤት ላይ ሁሉ እንድምታ ያለው ሌሎችን ሕጎች የሚነካ የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ይመለከታሉ፡፡ በአንዣሩ የወራሽነት የምስክር ወረቀትን በተመለከተ የሚቀርብ የተቃውሞ አቤቱታ የማስረጃውን ትክክለኛነት እና ህጋዊነት ከማረጋገጥ ያለፈ እንድምታ የለውም፡፡

በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሚሰጠው ትርጉም አስገዳጅነት የሚኖረው ተመሳሳይ የሕግ ክርክር በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2/1/ ድንጋጌ እና ከአስገዳጅ ውሳኔዎች ፅንስ ሃሳብ መረዳት የሚቻል ሲሆን በሰ/መ/ቁ. 75560 በተሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበው የሕግ ክርክር በእኛችን ካለው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተው በስር ፍ/ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መረዳት እንደሚቻለው ኑዛዜው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 የተመለከተውን ፎርም ተከትሎ የተደረገ ባለመሆኑ አስቀድሞ የተሰጠው የኑዛዜ የወራሽነት ምስክር ወረቀት በመሻሩ የተፈፀሙ የሕግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 1038/2005 ግንቦት 28/2006 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የአ/አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22371 ሐምሌ 22 ቀን 2006 ዓ.ም እና የአ/አበባ ከተማ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 22404 ነሐሴ 8/2006 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 92991

ጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ተፈራ ተሰማ አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- የአርሲ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኢንቨስትመንት ውልን መሠረት አድርጐ ለአመልካች ተሠጥቶ የነበረ የገጠር መሬትን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ ውሉን አፍርሶ መሬቱ እንዲለቀቅ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ለክሱ ምክንያት በማድረግ አመልካች ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀጥታ ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በተጠሪ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል ጉዳዩ የኢንቨስትመንት ጉዳዮችን አይቶ ውሳኔ ለመስጠት የተቋቋመው የኢንቨስትመንት ኮሚቴ ስልጣን መሆኑን በመጥቀስ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ የቀረበላቸው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶችም ውሳኔው ጉድለት የለበትም እንዲሁም የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም በማለት አሰናብተዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች በሊዝ የወሰደውን መሬት በማልማት የተለያዩ አትክልት አይነቶች እያመረተ መሆኑን በሚከራከርበት ሁኔታና የአርሲ ዞን አስተዳደር የኢንቨስትመንት ኮሚቴ ከአዋጅ ውጭ መሬቱን የነጠቀው መሆኑን እየተከራከረ የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በዳኝነት አካል የሚታዮ አይደለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ የማድረጋቸው አግባብነት የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት አስተዳደር እንደገና ለመወሰን ከወጣው አዋጅ ቁጥር 115/1998 አንፃር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በበኩላቸን ቅሬታ ያነሳውን ውሳኔ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ከህጉ ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው ጉዳዩ በፍርድ ሊታይ የሚችል መሆን አለመሆኑ እና የሥር ፍ/ቤት የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም ማለቱ ህጉን የተከተለ መሆኑን መመልከት ይጠይቃል፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37/1/ ማንኛውንም ሰው በፍ/ቤት ወይም የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል ጉዳዮን አቅርቦ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 4 ሥር እንደተመለከተውም ፍርድ ቤቶች በሌላ ህግ በግልፅ ለሌላ አካል ከተሰጡ ጉዳዮች ውጭ አከከራክሮ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው ስለሆነም ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ተቀብለው በማከራከር ውሳኔ መሰጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በግለፅ ህግ ለሌላ አካል እስካልተወጣ ድረስ ነው፡፡ በህግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉት ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት የስረ ነገር ሥልጣን ስለሌለው በህጉ መሠረት ሥልጣን ለተሰጠው የአስተዳደር አካል ቀርቦ በየደረጀው አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥበትን ጉዳይ ፍ/ቤት አስተናግዶ ውሳኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡

በተያዘው ጉዳይ የኢንቨስትመንት ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ላይ እንዲሁም ኢንቨስትመንትን በሚመለከት በኮሚሽኑና በኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ ድርሻ ባላቸው አካላት የሚወሰኑትን ጉዳዮች አስመልክቶ በሚቀርቡ ይግባኞች ላይ ውሳኔ የሚሰጠው የኢንቨስትመንት ቦርዱ ስለመሆኑ እና ብርዱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ኢንቨስትመንት አስተዳደርን እንደገና ለመወሰን የመጣውን አዋጅ ቁጥር 115/1998 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 138/2000 አንቀጽ 6/5/ ይደነግጋል፡፡ የተሻሻለው አዋጅ አንቀጽ 9/4/ ላይ እንደተመለከተውም ካሳ አነሠኝ ወይም ካሳ ተከሰከስኩ ወይም መሠረታዊ የህግ ሥህተት ተፈፀመብኝ በሚሉ ክርክሮች ላይ ካልሆነ በቀር በኢንቨስትመንት የሚቀርቡ የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር ይግባኞች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሠጠው ቦርዱ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም የቀጥታ ክስ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሥረ ነገር ሥልጣንን አስመልክቶ የቀረበውን መቃወሚያ ተቀብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244/2/ሀ/ እና 245/2/ መሠረት ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት መወሰኑ እና ይግባኝ መባሉም ሆነ የሰበር ችሎቱ አቤቱታውን በመሰረዛቸው የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1ኛ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 38932 ህዳር 14/2005 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 152805 ታህሳስ 23/2005 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.158804 ሰኔ 18/2005 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2ኛ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 107805

ጥቅምት 04 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ጅዳው አማካሪ አርክተክቶችና መሐንዲሶች ባለቤት አቶ ዳንኤል አሰፋ ጠበቃ

አለሙ ገበየህ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ነገረ ፈጅ አቶ ፋሲል ተሰማ - ቀረቡ

2ኛ. የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በአስተዳደር አካል የተወሰነ ጉዳይ በመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችልበትን የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓትና ቅሬታውን ተቀብሎ የማየትና የመወሰን ሥልጣን ያለው በየትኛው ደረጃ የተዋቀረው ፍ/ቤት ነው? የሚለውን አስመልክቶ ግራ ቀኙ ከተከራከሩበት ጉዳይና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ ለይቶ ለመወሰን በሚል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን አመልካች በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀጥታ ያቀረበው ክስ ሲሆን የክሱም ይዘት ተከሳሹ ለብሔራዊ ስታድየም ግንባታ የሚሆን የዲዛይን ሥራ ፈልጎ ባወጣው የጨረታ ውድድር መሠረት ተወዳዳሪ አሸናፊ ሆኖለሁ በጨረታ ሰነዱ (በገዘክር ተግባሩ) መሠረት ሥራው ለ2ኛው ዕጩ ተወዳዳሪ ሊሰጥ የሚችለው አሸናፊው በእርሱ ምክንያት ሥራውን ለማከናወን አለመቻሉ የተረጋገጠ እንደሆነ ብቻ መሆኑ ተገልፆ እያለ ተከሳሹ በህገ-ወጥ መንገድ ጨረታ እንደገና እንዲደረግ የሚያስችል ተግባር በሚከናወን በሁለተኛ ደረጃ ለተሰየመው ተወዳዳሪ ሰጥቶ በዚሁ መሠረት እያከናወነ ስለሚገኝ ይህንኑ ተግባሩን አቁሞ በአሸናፊነቱ ቴክኒካል ፕሮፖዛል እንዲቀርብ እና የቴክኒካል ፕሮፖዛል ድርድር እንዲያደርግ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽ የነበረውም የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ በጨረታው የአሸናፊነት ደረጃ አልደረሰም የሚልበትን ዝርዝር የክርክር ነጥብ በመጥቀስ በውድድሩ ሂደት ከሳሽ ለዲዛይን ሥራው ብቁ የሚያደርገውን መስፈርት አላሟላም፤

እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 75(1) መሠረት የመንግሥት ግዥን በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎች ሥልጣን ባለው የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ ቀርበው እንዲታዩ በማድረግ ሥልጣኑን የቦርዱ እንጂ የፍ/ቤቱ አይደለም ስለሆነም ክሱ ሊዘጋ ይገባል የሚለውንም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር አቅርቧል፡፡

ከሳሽም ጉዳዩን ለዚሁ ቦርድ አቅርቦ ማስወሰኑን ይህ ቦርድ የሚሰጠውም ውሳኔ የመጨረሻና አስገዳጅ ነው ተብሎ በአዋጅ አልተደነገገም ይልቁንም አዋጁን ተከትሎ በወጣው መመሪያ አንቀደጽ 49 (1) መሠረት በቦርዱ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው አቤቱታውን አግባብ ባለው ፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚቻል ስለተደነገገ ፍ/ቤቱ የቀረበለት ክስ ተቀብሎ ለማየት ሥልጣን አለው በማለት ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ በቀጥታ ተቀብሎ በማስተናገድ ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በሚመለከት አግባብነት ያለወን የአዋጁንና የመመሪያውን ድንጋጌዎች በመጥቀስ የጉዳዩ አቀራረብ ሥርዓቱን ጠብቆ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት የቀረበ ነው የሚል ዳኝነት የሰጠበት ሲሆን፤

ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ጉዳዩ በይግባኝ ደረጃ የይግባኙን ጉዳዩ ለማየት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ከማቅረብ በቀር የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ተቀብሎ ለማየትና ለመወሰን የሚያስችል የህግ የመነጨ ሥልጣን የለውም ሲል ሽሮ ወስኗል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ይግባኝ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በየደረጃው የተሰጡትን ውሳኔዎች ተመልክቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ መሆኑን አትቶ በመወሰን የአሁን አመልካችን አሰናብቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ ትርጉም የሚያስፈልገው ሆኖ ከተያዘው አከራካሪ ነጥብ አንፃር ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ ግራ ቀኙ የተከራከሩበትን ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 649 /2001 አንቀጽ 75 (1) መሠረት አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጠው ለመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ እንጂ በመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችል አይደለም በሚል ያቀረበው ክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህንኑ አዋጅ ለማስፈፀም በሠጠው መመሪያ አንቀጽ 49 (1) ድንጋጌ ሥር በግልፅ እንደተመለከተው ይኸው ቅሬታ ሰሚ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ያለው ወገን አግባብ ላለው ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ የሚቻል በመሆኑ ጉዳዩ በማናቸውም ምክንያት ለመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችል አይደለም የሚለው ክርክሩ ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

አከራካሪ ሆኖ የተገኘው በዚሁ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታውን "አግባብ ባለው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላሉ ተብሎ ከተደነገገው ይህ አግባብ ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው? የመጀመሪያ ደረጃ ክስን በጉዳዩ ዓይነት ወይም በገንዘቡ መጠን መሠረት ተቀብሎ ጉዳዩን በቀጥታ የክስ ደረጃ የሚያየው ፍ/ቤት ወይስ የቦርዱን ውሳኔ አግባብነት እንደገና ተመልክቶና ክስ በይግባኝ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ላለው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት? የሚለው ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 79 የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው በሚል የተደነገገውን በዚሁ ህገ-መንግስት የፍ/ቤቶችን የሥልጣን ወሰን ለሚያመለክተው ከአንቀጽ 37 ጋር አጣቅሶ ማየት እንደሚቻለው ማንኛውም ጉዳይ ያለገደብ በመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ የማይችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይልቁንም በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 የተቀመጠው የሥልጣን ክፍፍል ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል እና ጉዳዩንም አይቶ ለመወሰን ከመደበኛ ፍ/ቤት ውጭ በሌላ የዳኝነት ሰጭ አካል ያልተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህንኑ በፍርድ ሊያልቅ የሚችለውን ጉዳይ ለማየትና ለመወሰን ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው (exclusive Jurisdiction jurisdiction) ያላቸው ፍ/ቤቶች መሆናቸውን ለማስገንዘብ ሲባል በአንቀጽ 79 መደንገጉን መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም መደበኛ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል መሆኑን በማረጋገጥ ላይ ብቻ ላይወሰኑ በህገ- መንግስቱ አንቀጽ 37 መሠረት ይኸው ጉዳይ ከመደበኛ ፍ/ቤት ውጭ ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ቀርቦ የሚታይ መሆኑንና አለመሆኑን በቀጥታ የመመርመር ግዴታ አለባቸው፡፡

ከዚህ አንፃር አሁን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት በፍሬ ነገር ደረጃ እንደተረጋገጠውና ግራ ቀኙም እንደተማመነበት ሁለቱም ወገኖች ያለያያቸው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 75(1) መሠረት ጉዳዩ ለመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ከመታየቱ በፊት በመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ መቅረብ እንዳለበትና በዚሁ የቅሬታ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ማግኘት አለበት በዚህም መሠረት ጉዳዩ በዚሁ አካል ቀርቦ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ነው በዚህም አኳኃን በዚሁ የአስተዳደር አካልም (ከፊል የዳኝነት ሰጭ አካል) ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ሆኖ የሚቀር ሳይሆን በውሳኔው ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን አግባብ ላለው ፍ/ቤት አቅርቦ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታውን ማቅረብ እንደሚችል አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ አንቀጽ 49(1) ተደንግጓል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 75(1) በህገ-መንግስት አንቀጽ 37 እንደተደነገገው ይህንኑ ጉዳይ በቀዳሚ ተቀብሎ ለማስተናገድ ሥልጣን ያለውን የዳኝነት አካል (ከፊል የዳኝነት አካል) ለይቶ ካስቀመጠ በኃላ እንደገና ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ለማቅረብ የጉዳዩን አሰማምሮ አወሳሰን በሚመለከት በአስተዳደራዊ ክፍል የዳኝነት ሰጭ አካል እና በመደበኛ ፍ/ቤት መካከል ያለውን ቁርኝት በሚመለከት ይህንኑ በአዋጅ አንቀጽ 75(1) የተቀመጠውን ድንጋጌ ለማስፈፀም በሠጠው መሠረት አንቀጽ 49(1) በግልፅ ተመልክቷል፡፡ እንግዲህ በከፊል የዳኝነት ሰጭው አካልና በመደበኛው ፍ/ቤት መካከል ያለውን ቁርኝነት በተገለፀበት መመሪያ አንቀጽ 49(1) “በቦርዱ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው አግባብ ላለው ፍ/ቤት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡” በሚል ከተገለፀው ቅሬታው አስቀድሞ በተሰጡ የቦርድ ውሳኔ ላይ የተመሠረተ ከመሆኑ፤ ቅሬታ የሚለውም ቀጥተኛ ትርጉም በአንድ አካል በተሰጠ ውሳኔ ላይ ያልተስማማ ወገን አለመስማማቱን የሚገልፅበት ቃል መሆኑን በዚህም ድንጋጌ የእግሊዘኛ ቅጂ “Review of complaint by the coyrt” በሚል ከተገለጸው “Review” የሚለው አስቀድሞ በተወሰነ ውሳኔ ላይ ተመርኩዞ በዚሁ ውሳኔ ላይ ቅር ተሰኝቶ ከቀረበው ቅሬታ ጋር በማዛመድ ጉዳዩን እንደገና በዳኝነት ሰጭ አካል የሚታይ መሆኑን የሚያመለክት በመሆኑ በህገ - መንግስቱ አንቀጽ 37 ሆነ በአዋጅ አንቀጽ 75(1) የመደበኛ ፍ/ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ወሰን ካስቀመጠ በኃላ በማስፈፀሚያው መመሪያ አንቀጽ 49(1) የተቀመጠው ከመደበኛ ፍ/ቤቶች ጋር ያለው ቁርኝት መገለጫው በይግባኝ ሥርዓቱ አማካኝነት ውሳኔውን በይግባኝ ሰሚነቱ ሥልጣን መሠረት በቦርዱ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ካለው ህግና መመሪያ አንፃር በማየት መመርመር እንዲቻል እንጂ ጉዳዩን እንደ አዲስ በመቀጠር ተከራካሪ ወገኖች በጉዳዩ ላይ ክርክር በአዲስ መልክ የሚያከናውኑበትን ሥርዓት የሚመለክት አይደለም፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አግባብ ያለው ፍ/ቤት ጉዳዩን ከህግ አንፃር ብቻ መመልከት እንዲቻል ሆኖ አልተቀረፀም ይባል እንጂ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የተሰጠበትና በዚህም ውሳኔ ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንደሚቻል በመመሪያ የተፈቀደ በመሆኑ ጉዳዩን በክለሳ “Review” መልክ የሚያየው ፍ/ቤት የህግም ጥያቄ ሁሉ መመልከት የሚችል መሆኑ በውስጠ ታዋቂነት ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባ ነበር እንጂ ጉዳዩ በቀጥታ ክስ አማካኝነት ሊቀርብ ይገባል የሚለው ወደሚለው በቂ የውሳኔ መነሻ ትችትና ሊያደገውም አይገባም ነበር፡፡

በሀገራችን የህግ ሥርዓቱ በልዩ ልዩ ህጎች እንደተመለከተው በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 በአስተዳደርና፣ በከፊል የዳኝነት ሰጭ አካል እንጂ በመደበኛ ፍ/ቤቱ አስቀድመው ሊታዩ የማይችሉን ጉዳዮች ከተመለከቱ በኃላ ፍትህ የማግኘት መብትን ይበልጥ ለማረጋገጥ ሲባል ከፍ/ቤቱ ጋር ቁርኝት ሊኖራቸው እንደሚገባና ቁርኝቱም ለይግባኝ ሥርዓቱ አማካኝነት ጉዳዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አማካኝነት እንዲታዩ በማድረግ የተደነገጉ እንጂ እንደገና እንደ አዲስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ (of first instance) አቅርቦ አዲስ ክርክርን በሚጋብዝ ደረጃ የተቀረፀ አይደለም፡፡

በዚሁ ሁሉ ምክንያት በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነቱ ሥልጣን ላይ መ/ቁ 103961 ህዳር 17/2007 ዓ.ም በአብላጫ ድምፅ በትዕዛዝ የሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን በይግባኝ አቤቱታ አቀራረብ ደንብን ሥርዓት መሠረት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው አግባብ ላለው ፍ/ቤት ከሚያቀርብ በቀር በቀጥታ ክስ አቀራረብ ሥርዓት የጉዳዩን ዓይነትም ሆነ የገንዘብ መጠኑን መሠረት በማድረግ ጉዳዮች በቀጥታ ደረጃ በሚታዩበት ሥርዓተ መሠረት ማቅረቡ ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ደረጃ ግራቀኙ ባደረጉት ክርክር ሳቢያ ለወጣው ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.117390

ታህሳስ 21 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ አለማየሁ መኮነን ጠበቃ ሞላ ዘገየ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የምስራቅ አፍሪካ የበርሃ አንበጣ መከላከያ ድርጅት ጠበቃ አድምጠው በለጠ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ላይ ያቀረብኩትን ክስ የማየትና አጣርተው የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ገልፆ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች የተጠሪ ሰራተኛ የነበሩ መሆናቸውን ገልፀው ተከሳሽ ሊከፍለኝ ይገባል የሚሏቸውን ክፍያዎች ዘርዝረው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ አለም አቀፍ ድርጅት መሆኑን ገልፆ፣ የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በኢትዮጵያ አቆጣጠር ግንቦት 30 ቀን 1969 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ሰኔ 7 ቀን 1977 ዓ.ም በተዋዋለው ውል መሰረት በፍትሐብሔር ጉዳይ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ያለመክሰስ መብት ያለኝ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪ ዋና መስሪያ ቤት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ያደረገው ስምምነት ያለመሆኑንና ስምምነቱም እስካሁን ድረስ የፀናና ያልተሻረ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በፅሁፍ ያረጋገጠለት መሆኑን ገልፆ፣ ስምምነቱ በይዘቱ የኢትዮጵያ መንግስት በድርጅቱ ላይ ክስ እንዳያቀርብ የሚገደብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንጅ ዜጎች በድርጅቱ ላይ ክስ እንዳያቀርቡ የሚከለክል አይደለም በማለት አመልካች በክሱ የጠቀሰውን ገንዘብ ተጠሪ ክዶ የቀረበው ክርክር ስለሌለ እንዳመነ ይቆጠራል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ስምምነቱ በተጠሪ /ይግባኝ ባይ/ ላይ የማቀረብ የፍትሐብሔር ክስ የኢትዮጵያ መንግስት የመዳኘት ስልጣን የሌለው መሆኑን የሚገልፀ ስለሆነ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የዳኝነት ስልጣን የለም በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

3. አመልካች ስምምነቱ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠውን ፍትህ የማግኘት መብት በማያጣብብ ሁኔታ መተርጎም ይገባዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና የሕገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አገሪቱ የገባችውን አለም አቀፍ ግዴታና ስምምነት መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
4. እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት ከተጠሪ ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነትን ውል አለን፡፡ አሰሪው በስር ውሉ መሰረት ለመወጣት የሚገባውን ግዴታ ያልተወጣና መክፈል የሚገባውን ክፍያ ያልከፈለኝ ስለሆነ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ አለም አቀፍ ድርጅት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 በኢትዮጵያ ግዛት ክልል ባሉ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ለማስተዳደር የወጣ ልዩ የሕግ ክፍል ቢሆንም ይኽ አዋጅ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ልዩ ሁኔታዎች በአዋጅ ተደንግጓል፡፡ አዋጅ ተፈፃሚ የማይሆንበት ልዩ ሁኔታ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ስራቸውን የሚያከናውኑ አለማቀፍ ድርጅቶች ከኢትዮጵያዊን ጋር በሚመሰርቱት የስራ ግንኙነት ላየ ተፈፃሚ እንዳይሆን በአለም አቀፍ ስምምነት የተወሰነ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በአዋጅ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ ተደንግጓል፡፡ ይኽ ድንጋጌ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተደረገና ፀንተው የቆዩ አለም አቀፍ ስምምነቶችንም የሚያካትት ድንጋጌ ነው፡፡
5. የኢትዮጵያ መንግስትና የተጠሪ ዋና መሰሪያ ቤት ያደረጉት ስምምነት አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 1 በተፃፈበት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ቃል በቃል ሲነበብ “The organization shall, enjoy immunity from the criminal junsdiction of the government. If shall also enjoy immunity from its civil and administrative Jurisdiction except in so far as the counsel of the organization has unvalued the immunity”

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ይኽ ስምምነት እስካሁን ድረስ የፀናና ሕጋዊ ውጤት ያለው ስምምነት መሆኑን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለስር ፍ/ቤት በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡

6. ይኽ የስምምነቱ ሃይለ ቃል፣ የኢትዮጵያ መንግስት ተጠሪ ከሚቀጥራቸው ሰራተኞች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚወስን ሕግ የማውጣት፣ በዳኝነት አይቶ የመወሰንና ውሳኔውን በፍርድ ቤትም ሆነ በአስተዳደራዊ መንገድ የማሰፈፀም ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ ከተጠሪ ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ያላቸው ኢትዮጵያውያንም ሆነ የሌሎች አገሮች ዜጎች መብታቸውንና ጥቅማቸውን በተጠሪ መተዳደሪያ ደንብና አግባብነት ባላቸው አለማቀፍ ስምምነቶች አለም አቀፍ ልምዶችና ሕግጋት መሰረት ጉዳዩን አይተው ውሳኔ ለሚሰጡ አካላት በማቅረብ እንዲወሰንላቸው ከሚጠይቁ ውጭ በኢትዮጵያ ሕግና መሰረት በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ለማቅረብ የማይችሉና የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም የዚህ አይነት ጉዳይ በዳኝነት አይተው የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ግልፅ የሚያደርግ ነው፡፡ የስምምነቱ አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 2 ይዘትም ከላይ የተጠቀሰውን ድንጋጌ መልዕክት የሚያጠናክር ይዘት ያለው ነው፡፡

7. የአንድ አለም አቀፍ ድርጅት በግዛት ክልል ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ወይም ዋና ፅ/ቤት እንዲከፍት የፈቀደች ወይም አለም አቀፍ ድርጅቱ በግዛት ክልል እያንቀሳቀሰ የተቋቋመበትን መሰረታዊ ዓላማና ተግባር እንዲፈፅም የፈቀደች አገር፣ ከአለም አቀፍ ድርጅቱ ጋር ያደረገችውን ስምምነት የማክበር ግዴታ ያለበት መሆኑን ኮቬና የአለም አቀፍ ስምምነቶች ሕግ እና በልምድ ከዳበረው የግል ማዕቀፍ ሕግ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም መሆኑ አገሪቱ ለተጠሪ ድርጅት የሰጠችው በፍትሐብሔር ያለመከሰስ ጥበቃ እስካሁን ድረስ የፀናና አገሪቱ ልታከብረው የሚገባው ቃል ኪዳን በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን የሌለ መሆኑን ገልፆ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ያቀረበውን ክስ አይቶ የመወሰን ስልጣን የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 104858

ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲ.ር.ጋ.ጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ታደሰ ካሣ - ጠበቃ እንዳልካቸው ይሳቅ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 አስተዳደር
2ኛ. ቦሌ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር } አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት ከከተማ ቦታ ማስለቀቅ እና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ምትክ ቦታን በተመለከተ በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ አቤቱታን ተቀብሎ ለመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የለኝም በማለት ያሳለፈውን ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ነሀሴ 27/2006 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ የአዲስ አበባ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ ከአዋጅ ቁጥር 721/2003 አንቀጽ 29 እና 30 ድንጋጌዎች አንፃር ተገቢ መሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸውና መልስ ለመስጠትም ቀጠሮ እንዲሰወጥላቸው ጠይቀው ነገር ግን መልስ ስላላቀረቡ በፅሑፍ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፎ መዝገቡ ለምርምራ ተቀጥሯል፡፡ በበኩላችን የከተማው ሰበር ችሎት ያሳለፈውን ትዕዛዝ አመልካች ካቀረቡት ቅሬታ እና ተገቢነት ካላቸው ህጎች ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 አስተዳደር ውስጥ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ በ200 ካ.ሜ ቦታ ላይ ቤት ገንብተው እየኖሩ ከተጠሪዎች ቦታው ለልማት ይፈለጋል በሚል እንዲለቁ ማስጠንቀቂያ በፅሑፍ ስለተሠጣቸው የቤት ካሣ እና ምትክ ቦታ እንዲሠጣቸው ጠይቀው አስተዳደሩ በህግ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎብኛል በሚል ይግባኙን ለመስማት ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጠሪዎችን መልስ ተቀብሎ ጉዳዩን ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሠን ከወጣው አዋጅ ቁጥር 455/1997፤ ስለ ካሣው አወሳሰን ከወጣው የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/1999 እንዲሁም አዋጅና ደንቡን ለማስፈፀም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ከወጣው መመሪያ ቁጥር 3/2002 አንፃር በመመርመር በህጎቹ እንዲቀርብ የሚጠበቀው የንብረት ካሣ እና ምትክ ቦታ ለማግኘት የሚያበቁ ማስረጃዎ አልቀረቡም ስለሆነም ይግባኙ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የምትክ ቦታ ጥያቄውን በተመለከተ የጉባኤው ውሳኔ የመጨረሻ ነው በማለት የሰበር አቤቱታ ለከተማው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሚኖረው የአ/አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ነው፤ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም ሥልጣን ያለው የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት ነው በመሆኑም ጉዳዩ በከተማው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ የማይችል ነው በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

እንደመረመርነው የከተማው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ምትክ ቦታን በሚመለከት በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ በሰበር አይቶ ለመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለው የህግ ጭብጥ ውሳኔ የሚሻ ነው፡፡

የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ በወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 29(3) መሠረት በካሣ ክርክር ላይ ካልሆነ በቀር ምትክ ቦታን ጨምሮ በሌሎች በህግም ሆነ በፍሬ ነገር ላይ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው፡፡ በሌላ በኩል በካሳው ላይ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ሊቀርብ እንደሚችል በአንቀጽ 29 (4) ሥር ተመልክቷል፡፡ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ደግሞ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ በከተማው ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 43(5) እና አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 29(6) ድንጋጌዎች መሠረት የመጨረሻ በመሆኑ በዚህ ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በሰበር ስርዓት ለከተማው ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ስለመሆኑ በቻርተሩ አንቀጽ 42(2) ተመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከተማ ቦታ ማስለቀቅ እና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤም በቻርተሩ አንቀጽ 40 ከተዘረዘሩ በህግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት የሚመደብ ነው፡፡

በመሆኑም ጉባኤው ምትክ ቦታን በተመለከተ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑና ጉባኤውም በህግ የመዳኘት ስልጣን ተሰጥቶት የተቋቋመ የአስተዳደሩ አካል መሆኑ እየታወቀ በዚህ ውሳኔ ላይ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ የከተማው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የመመለስ ሥልጣን የለውም ተብሎ የተሰጠው ትዕዛዝ ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰ/መ/ቁ. 104857 ህዳር 24/2008 ዓ.ም በዋለ ችሎት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በምትክ ቦታ ይሰጠኝ ጥያቄ ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ፍርድ የሠበር አቤቱታ ለከተማው ፍ/ቤት ሳይቀርብ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት የህግ አግባብ እንደሌለም ተወስኗል፡፡ ይኸው ውሳኔም በተያዘው ጉዳይ በተመሳሳይ ተፈፃሚ ነው፡፡

በመሆኑም የከተማው ሰበር ችሎት ያሳለፈው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1ኛ. የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22374 ነሀሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን ያለው በመሆኑ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሰናል ይባፍ፡፡

3ኛ. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.112575

30/06/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሠለ

አመልካች፡- አቶ አፈወርቅ መኩሪያ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ማዳሊና ፍራንሲኔቲ ጠበቃ ኤልያና ጥላሁን

መዝገቡን መርምረን ተከታዮን ፍርድ ሰጥተናል ።

ፍ ር ድ

ጉዳዮ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪ ቀደም ሲል ከዚህ ፍ/ቤት የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ አመልካች ያቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ይዘት የመቃ/ተጠሪ/የአሁኗ ተጠሪ/ የሟች ወ/ሮ ፈንታዮ መተኪያ ልጅ ሳይሆኑ በተፈጥሮ ሟች እንደወለዱዋቸው ልጅ ነኝ ብለው የወሰድት የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ባቀረቡት የመጀ/ደ/መቃወሚያ ፍ/ቤቱ የልጅነትን ክርክር ጭብጥ ይዞ ለማየት ስልጣን የለውም፣የመቃ/አመልካች የሟች ልጅ /ተወላጅ/ ሳይሆኑ ያቀረቡት መቃወሚያ አቤቱታ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም ፣የመቃ/አመልካች ወላጅ እናት ወ/ሮ አፀደ ንዋይ የሞቱት ከ 30 ዓመት በፊት ስለሆነ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መቃወሚያ እና በአማራጭም መልስ ማቅረባቸው ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተመልክቷል፡፡

ፍ/ቤቱ የቀረበውን የመጀመሪያ መቃወሚያ መርምሮ የመቃ/አመልካች እንደሚሉት እና በመቃ/ተጠሪም የግራ ቀኙን የልጅነት ክርክርን ፍ/ቤቱ ጭብጥ ይዞ ሲመረምረው በተገቢው ፍ/ቤት አጠናቀው እና ማስረጃ ይዘው እስከ ቀረቡ የወራሽነት ክርክሩ መዝገብ ለጊዜው ተዘግቶ ይቆይ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ሌሎች መቃወሚያዎች ላይ መቃወሚያዎቹን ባለመቀበል በብይን አልፋል፡፡ ተጠሪ በዚህ ብይን ላይ ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 መሠረት ይግባኙ የተሰረዘ ሲሆን የሰበር አቤቱታ ለይ/ሰሚው ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤትን ብይን በመሻር አመልካች /የስር የመቃ/ተጠሪ/ የሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፍቻ ልጅ መሆን አለመሆኑን የቀረበውን ማስረጃ እና እንዲቀርብ የተጠየቀውን ማስረጃ በማስቀረብ መርምሮ የመሰለውን እንዲወሰን ለስር ፍ/ቤት በመመለስ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ቅሬታቸውን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤት ተጠሪ የሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፈቻ ልጅ መሆን አለመሆናቸውን የማጣራት የሥር ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው ሲል ጉዳዮ ተጣርቶ እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.343/1/ መሠረት የመለሰበትን አግባብ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁ.361/1996 አንቀፅ 41 መሠረት ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ ከዚህ በላይ አጠር ተደርጐ የተመዘገበዉ ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤት ውሣኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ከስር ፍ/ቤት ጀምረው የሚከራከሩት ተጠሪ የሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፈቻ ልጅ አይደለም በማለት ሳይሆን ተጠሪ ከሚች በተፈጥሮ የተወለዱ ልጅ ሳይሆኑ የተፈጥሮ ልጅነኝ ብለው የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ነው ተጠሪ በበኩላቸው የሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፈቻ ልጅ መሆናቸውንና ለዚህም ማስረጃ ያላቸው መሆኑን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዮን በመጀመሪያ የተመለተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ከግራ ቀኙ ክርክር አንፃር ተጠሪ ከሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ በተፈጥሮ የተወለዱ መሆኑን ገልፀው ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት የወራሽነት ማስረጃ ወስደዋል ወይስ አልወለዱም የሚለውን ጭብጥ ለማጣራት ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ወስደዋል የተባለበትን መዝገብ አሰቀርቦ አልተመለከተምደ ግራ ቀኙንም በዚህ ነጥብ ላይ አላከራከረም ፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 በአንቀጽ 182 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቀው ሆነው የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ የሚቆጠር መሆኑን ደንግጓል፡፡ የጉዲፈቻ ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሳዳሪ መካከል የሚደረግ መሆኑ በዚሁ ሕግ አንቀፅ 190 የተመለከተ ሲሆን የጉዲፈቻ ስምምነትን አስመልክቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለ ፍ/ቤት ስልጣን በአንቀጽ 194 ተደንግጓል፡፡ የጉዲፈቻ ስምምነትን በተመለከተ የፍ/ቤት ሚና ስምመነቱን ከማፅደቁ በፊት በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ 2 እስከ 4 የተመለከቱ መመዘኛዎችን የማጣራትና የማረጋገጥ መሆኑን ከድንጋጌው መረዳት ይቻላል፡፡ የጉዲፈቻ ስምምነቱ የሚሰረዝበትን የሕግ አግባብ በተመለከተም በአንቀፅ 196 ተመልክቷል ፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪ አጥብቀው የሚከራከሩት የሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፈቻ ልጅ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያላቸው መሆኑ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.145 መሠት በፍ/ቤቱ ትህዛዙ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት እና እንዲቀርብ የጠየቁ ማስረጃ እንዲቀርብ አድርጐ የሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፈቻ ልጅ መሆን አለመሆናቸውን ማስረጃን በመመርመር ወራሽ ናቸው ወይም ወራሽ አይደሉም ብሎ ውሣኔ መስጠት፣የተፈጥሮ ልጅነት ከሚረጋገጥበት በህጉ ከተመለከተው ስርዓት የተለየ ነው ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣንን የደነገገው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ.361/1995 አንቀጽ 41/ሸ/ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን ለማየት የዳኝነት ሥለጣን ያላቸው መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የቤተሰብ ሕግ በተመለከተው መሠረት የተደረገ የጉዲፈቻ ስምምነት ማስረጃን ተመልክቶ ወራሽነት ማስረጃን በስተት የአ/ከተማ ፍ/ቤት ስልጣን ሆኖ እያለ ክርክሩ የጀመረበት የአ.አ.ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የክርክር ይዘት በውል ባለማጤን የልጅነት ክርክርን ለማየት ስልጣን የለኝም በተገቢው ፍ/ቤት ተጣርቶ ይቅረብ ብሎ የሰጠው ብይን ተገቢ አለመሆኑን እና የተጠሪን የጉዲፈቻ ልጅ ማስረጃን ተመልክቶ የመሰለውን እንዲወሰን የአ.አ.ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአ.አ. ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.22960 በቀን 30/07/2007 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348/1/ መሠረት ፀንቷል ፡፡
2. በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ላደረጉት ክርክር ያወጡትን ወጭ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል ፡፡
3. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.ጥር 108335
የካቲት 4 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፉ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካቾች፡-

1. አቶ ዓለሙ ስሜ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ ታደሱ ስሜ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ ብዙነሽ ስሜ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ ፀዳሉ ስሜ - ቀረቡ
3. አቶ ተሾመ ሽሜ
4. ወ/ሮ ሰላማዊት ስሜ } ወኪል 1ኛ ተጠሪ ቀረቡ
5. ወ/ሮ ወርቅነሽ ስሜ
6. አቶ ብርሃኑ ስሜ } የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በገጠር የእርሻ ይዞታ ላይ የተነሳ የውርስ ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሾች የነበሩት የአሁኖቹ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች በደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ 1ኛ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡የአሁኗ 2ኛ አመልካች በዋናው ክርክር ጊዜ በጉዳዩ በጣልቃ ገብነት የተከራከሩ ሲሆኑ የአሁኖቹ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ደግሞ በጉዳዩ ላይ የወረዳ ፍርድ ቤቱ በ27/07/2006 ዓ.ም. ውሳኔ ከሰጠ በኃላ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ መሰረት ወደ ጉዳዩ የገቡ ናቸው፡፡

ፍርድ ቤቱ በከሳሾች እና በተከሳሽ፣እንደሁም በጣልቃ ገቧ የአሁኗ 2ኛ አመልካች መካከል የነበረውን ክርክር መርምሮ ክርክር ያስነሳውን የእርሻ መሬት፣ እንዲሁም የእንስሳት ግምት ብር 7,000 (ሰባት ሺህ) ከሳሾች እና ተከሳሽ እኩል ይካፈሉ በማለት በመዝገብ ቁጥር 12083 በ27/07/2006 ዓ.ም. ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ከዚህ በኃላ የእርሻ ይዞታው እና የከብቶቹ ግምት በውርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊተላለፍ የሚገባው ለከሳሾች እና ለተከሳሹ ብቻ ሳይሆን ለእኛም ጭምር በመሆኑ ውሳኔው ሊሻሻል ይገባል በማለት የአሁኖቹ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ መሰረት በ24/10/2006 ዓ.ም. የተጻፈ የመቃወም አቤቱታ በማቅረባቸው መዝገቡ ተንቀሳቅሶ የስር ከሳሾች ውሳኔው መቃወሚያ አቅራቢዎቹ በጠየቁት አግባብ ቢሻሻል ተቃውሞ እንደሌላቸው በመግለጽ መልስ የሰጡ ሲሆን የስር ተከሳሽ በበኩላቸው በሰጡት መልስ መቃወሚያ አቅራቢዎቹ ከሚች ስሜ ደገፋ የሚወለዱ ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ እና በደመወዝ የሚተዳደሩ በመሆናቸው እና የሚች የቤተሰብ አባል ከሳሽ ብቻ በመሆናቸው ጥያቄአቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የተከራከሩ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርመሮ መቃወሚ አቅራቢዎቹ የሚች ስሜ ደገፋ ልጆች እና ወራሾች መሆናቸው አልተካደም በማለት የቀድሞውን ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 360 (2) መሰረት አሻሽሎ ክርክር ያስነሳውን የእርሻ መሬት፣እንዲሁም የእንስሳት ግምት ብር 7,000 (ሰባት ሺህ) ከሳሾች፣ተከሳሽ እና መቃወሚያ አቅራቢዎቹ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት በ09/11/2006 ዓ.ም.ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኖቹ አመልካቾች ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የክልሉ ሰበር ችሎት የቀረበለትን አቤቱታ ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን ለዚህ ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ የአሁኖቹ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ እና በደመወዝ የሚተዳደሩ በመሆናቸው የገጠር የእርሻ ይዞታን የመውረስ መብት የላቸውም በማለት የአሁኑ 1ኛ አመልካች ያቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. 2ኛ ተጠሪ በዚህ መዝገብ በአመልካችነት የመከራከር መብት አላቸው ወይስ የላቸውም?
2. 1ኛ አመልካች በ27/07/2006 ዓ.ም. በወረዳው ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ መዝገብ ያቀረቡት የክርክር ነጥብ በዚህ መዝገብ ሊስተናገድ የሚችል ነው ወይስ አይደለም?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የቀድሞውን ውሳኔ በማሻሻል በወረዳው ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ የተሰጠው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ፍሬ ነገሮች በአግባቡ እንዲጣሩ ከተደረገ በኃላ ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ 2ኛ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት በጣልቃ ገብነት የክርክሩ ተካፋይ የነበሩት የመቃወም አቤቱታ ከመቅረቡ በፊት በነበረው ሂደት ነው፡፡የመቃወም አቤቱታው ከቀረበ በኃላ 2ኛ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የነበሩ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው የመቃወም አቤቱታው ከመቅረቡ በፊት ውሳኔ የተሰጠው በ27/07/2006 ዓ.ም. ሲሆን የመቃወም አቤቱታ ከቀረበ በኃላ ውሳኔ የተሰጠው ደግሞ በ09/11/2006 ዓ.ም. ነው፡፡2ኛ አመልካች በ27/07/2006 ዓ.ም. በተሰጠባቸው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸው በውሳኔው ላይ ያላቸውን ይግባኝ እና አቤቱታ ስርዓቱን ጠብቀው ማቅረብ ይችሉ የነበረ ከመሆኑ ውጪ ተካፋይ ባልተደረጉበት ክርክር በ09/11/2006 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ እና አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ በዚህ መዝገብ በአመልካችነት የመከራከር መብት አላቸው ማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የመቃወም አቤቱታ ከቀረበ በኃላ በ09/11/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በመሆኑ 1ኛ አመልካች ይግባኝ እና አቤቱታ ማቅረብ የሚገባቸው ይህንኑ በ09/11/2006 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ከሚሆን በቀር የኃለኛውን ውሳኔ አስታከው የመቃወም አቤቱታ ከመቅረቡ አስቀድሞ በ27/07/2006 ዓ.ም.በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ እና አቤቱታ ሊያቀርቡ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡በመሆኑም 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጭምር የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በመሆናቸው የእርሻ መሬት የመውረስ መብት የላቸውም፣በ3ኛ ተጠሪ እጅ የሚገኝ የውርስ ንብረት ጭምር መኖሩን በመጥቀስ ያቀረበኩት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የታለፈብኝ አላግባብ ነው በማለት 1ኛ አመልካች ያቀረቡት ክርክር በዚህ መዝገብ ሊስተናገድ የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሶስተኛውን ነጥብ በተመለከተ 1ኛ አመልካችም ሆኑ ተጠሪዎቹ የሟች ስሜ ደገፋ ልጆች እና ወራሾች መሆናቸው በግራ ቀኙ ያልተካደ ሲሆን የአንድ አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት በውርስ የሚተላለፈው በውርስ ሕግ መሰረት በይዞታው የመጠቀም መብቱን የመውረስ መብት ላለው የቤተሰብ አባል ስለመሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 9 (1) ስር የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅድሚያ የውርስ መብት የሚሰጠው ከመሬቱ በሚያገኙት ገቢ ለሚተዳደሩ ወይም ሌላ መተዳደሪያ ገቢ ለሌላቸው ወራሾች እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 9 (2) ስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመልክቶአል፡፡አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 10 (1) ስር ያለው ድንጋጌም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው፡፡ የአሁኖቹ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ እና በደመወዝ የሚተዳደሩ በመሆናቸው የገጠር የእርሻ ይዞታን የመውረስ ቀዳሚ መብት ያላቸው የሚች ቤተሰብ አባል ሆነው ከእርሻ መሬቱ በሚገኘው ገቢ የሚተዳደሩ የአሁኑ 1ኛ አመልካች መሆናቸውን በመግለጽ የአሁኑ 1ኛ አመልካች መከራከራቸውን እና 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሳይሆኑ የእርሻ መሬቱ የሚገኝበት ቀበሌ ነዋሪዎች መሆናቸውን በመግለጽ የተከራከሩ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንን መከራከሪያ ሳይቀበሉ የቀሩት ሁሉም ወራሾች በእርሻ መሬት አወራረስ ላይ እኩል መብት እንዳላቸው በመቁጠር እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡በመሆኑም በአንድ በኩል በ1ኛ አመልካች እና በሌላ በኩል ደግሞ በ5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች መካከል የተነሳውን ክርክር በማስረጃ ሳያጣራ ሁሉም ወራሾች በእርሻ መሬት ላይ እኩል መብት እንዳላቸው በመቁጠር መሬቱን እኩል እንዲካፈሉ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡ከእርሻ ይዞታው ውርስ ጋር ተያይዞ በተነሳው ክርክር ከሚች የተላለፉት እንስሳት ውርስ ጉዳይ የሚገዛው ውርስን በሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረት በመሆኑ የእንስሳቱን ግምት ብር 7,000 (ሰባት ሺህ) ከሳሾች፣ተከሳሽ እና መቃወሚያ አቅራቢዎቹ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

ው ሳ ኔ

1. 2ኛ አመልካች ተከራካሪ ወገን ባልነበሩበት በ09/11/2006 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ እና አቤቱታ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡
2. በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12083 በ09/11/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 47817 በ28/12/2006 ዓ.ም. በፍርድ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 187287 በ09/04/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
3. የእንስሳቱን ግምት ብር 7,000 (ሰባት ሺህ) ከሳሾች፣ተከሳሽ እና መቃወሚያ አቅራቢዎቹ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. ክርክር ያስነሳውን የእርሻ ይዞታ ከሳሾች፣ተከሳሽ እና መቃወሚያ አቅራቢዎቹ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
5. የአሁኖቹ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች የመኖሪያ አድራሻ እንደ 1ኛ አመልካች አባባል በአዲስ አበባ ከተማ ነው ወይስ እንደ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች አባባል ክርክር የተነሳበት የእርሻ መሬት በሚገኝበት ወረዳ እና ቀበሌ ነው? 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ከደመወዝ በሚገኝ የሚተዳደሩ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚሉትን እና ተያያዥ ነጥቦችን በግራ ቀኙ ማስረጃ፣እንደሁም ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ሁሉ በፍርድ ቤት በትዕዛዝ በሚቀርብ የማጣሪያ ማስረጃ እንዲጣራ ካደረገ በኃላ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 9 (2) እና በደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 10 (1) ድንጋጌዎች አነጋገር መሰረት ክርክር የተነሳበትን የእርሻ ይዞታ ውርስ የመካፈል መብት ያላቸው መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ለደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
6. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቁት ደግሞ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 110549

የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተሽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ደመቀች ንርአ ጠበቃ ኪሮስ አቢዲ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጋለመ ረብሶ ተወካይ አለ ረብሶ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት የሚመለከት ሆኖ በአሁኑ ተጠሪ ክሳሽነት የተጀመረው በአላማጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ፡- አዋሳኙ በክስ ማመልከቻቸው የጠቀሱትና በአላማጣ ወረዳ፣ ኩልግዘ ለምለም ጣብያ፣ በጆሃን ጎጥ ውስጥ የሚገኘውንና ስፋቱ 33ሜትር በ50 ሜትር የሆነውን የእርሻ መሬት በሕግ አግባብ ከአያታቸው ከሚች ወ/ሮ ሙሽራ አራርሶ ወርሰው የይዞታ ማረጋገጫ ያወጡበት መሆኑን፣ ይዞታውን ለአመልካች በኪራይ እያከራዩ የነበሩ መሆኑን፣ ቦታው ወደ አላማጣ ከተማ ሲገባ ግን ተጠሪ የታመሙበትን አጋጣሚ በመጠቀም የጎጆ መውጫ የነበረ ቦታ በማስመሰል አመልካች ይዞታውን በስማቸው እንዲሆን ማድረጋቸውን ዘርዝረው አመልካች ቦታውን እንዲያስረክቡ ወይም የአስር አመት አላባ፤ የመሬቱን ቋሚ ማሻሻያ ብር 126,500.00(አንድ መቶ ሃያ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም በይዞታቸው ስር ያለው በተጠሪ ክስ ውስጥ አዋሳኙ የተጠቀሰው ይዞታ ያለመሆኑን፣ በይዞታቸው ስር ያለው መሬት የሚታረስ ሳይሆን የጎጆ መውጫ ሁኖ ባለቤታች ሟች አቶ አድሃና አስፋው በቀን 10/10/1994 ዓ/ም ከወ/ሮ ሙሽራ ልጆች ከሆኑት ወ/ሮ ቡልቡላ ብርዋን በሽማግሌ ፊት በብር 1500.00 የገዙት መሆኑን፣ ይህ መሬት ታራሽ መሬት ነው፣ ይገባኛል በማለት ወ/ሮ ቡልቡላ ብርዋን በተወካያቸው አቶ መሃመድ ጎሳ በ2000 ዓ/ም ክስ መስርተውባቸው ቦታው ጎጆ መውጫ ነው በኩሉግዘ ለምለም ቀበሌ የመሬት ዳኝነት በ12/5/2000 ዓ/ም የተወሰነ መሆኑንና በፍርድ ያለቀ ጉዳይ መሆኑን፣ ጎጆ መውጫ ሁኖ ባለቤታቸው በ1994

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓ/ም የገዙት ከመሆኑም በላይ በ2001 ዓ/ም ወደ ስማቸው ዙሮ የሚጠቀሙበትና ቦታው ታራሽ ነው በሚል የአላባ ጥያቄ መቅረቡ ያላግባብ ነው የሚሉ ነጥቦችን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ከሚመለከተው አካል ተጣርቶ እንዲቀርብለት ያደረገውን ማስረጃ በመመርመር የአሁኑ ተጠሪ በውርስ ያገኙት ታራሽ መሬት መሆኑን፣ክርክሩ በመታየት ላይ ባለበት ጊዜ ግን ይዞታው ወደ አላማጣ ከተማ ስለገባ በስም የተጠሪ ሁኖ እንዲመዘገብ፣ የአንድ አመት አላባ ብር 5238.65 ደግሞ ለተጠሪ እንዲከፈላቸው፣ በአመልካች ባለቤት ስም ያለው ሳይት ፕላንም እንዲሰረዝ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለአላማጣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት እስከ 2005 ዓ/ም ድረስ ከከተማ ውጪ ሁኖ በገጠር መሬት አስተዳደር ቁጥጥር የነበረ ሁኖ አመልካች ከ12 አመታት በላይ ይዘው በቁጥጥራቸው ስር አድርገው ቤት ስርተውና የተለያዩ ተክሎችን ተክለው የሚኖሩበት የነበረ ጎጆ መውጫ በ2001 ዓ/ም ወራሽነት ማስረጃ አውጥቼአለሁ በሚሉ ተጠሪ በ2006 ዓ/ም ክስ ሊመሰርትባቸው አይገባም እንደማይገባ፣ የሽያጭ ውሉም የይርፍረስልኝ ጥያቄ ሳይቀርብበት ክርክር ሊነሳበት የማይገባ መሆኑን እና በክፍሉ ማዘጋጃ ቤት አመልካች የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር ያገኙ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊመክን የማይችል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር አመልካች ለተጠሪ የሚያስረክቡት መሬትና የሚከፍሉት አላባ ግምት የለም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ይዞታው ወደ ከተማ ክልል ከመግባቱ በፊት የሚታረስ የነበረ መሆኑ መረጋገጡን፣ አመልካች ይዞታውን አገኘሁ የሚሉት ደግሞ በሽያጭ በመሆኑና የገጠር እርሻ መሬት የሚሸጥበት ወይም የሚለወጥበት አግባብ በሕግ የተከለከለ ተግባር መሆኑን፣ ከሕግ ውጪ የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ደግሞ በፍርድ ቤት ውሳኔ የማይመክንበት ምክንያት የሌለ መሆኑን በምክንያት ይዞ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ይዞታው በተጠሪ ስም እንዲመዘገብ፣በአድሃና አስፋው ስም የተመዘገበው ሳይት ፕላን ሕገ ወጥ በመሆኑ እንዲሰረዝ፣ አላባውን ግን ያልተጠየቀ ዳኝነት በመሆኑ ለተጠሪ ሊከፈላቸው የማይገባ መሆኑን ገልጾ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ይዞታው የጎጆ መውጫ ሁኖ በሽያጭ ለአመልካች ባለቤት በ1994 ዓ/ም ተላልፎ ቆይቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይዞታው ወደ አላማጣ ከተማ ክልል ከገባ በኋላም በ2001 ዓ/ም በአመልካች ስም የይዞታ ማረጋገጫ ከአላማጣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ተሰጥቶአቸው ይዞታው ላይ ቤት ሰርተውና የተለያዩ ተክሎችን አልምተው የሚገኙ መሆኑን ዘርዝረው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አከራካሪው ይዞታ ወደ አመልካች የተላለፈው በሽያጭ ውል ነው ተብሎ ሽያጩ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ አመልካች አከራካሪውን ይዞታ ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የመወሰኑን አግባብነትና ተያያዥ ነጥቦችን በጭብጥነት መያዙ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች ባለቤት የነበሩት ሟች አቶ አድሃና አስፋው 10/10/1994 ዓ/ም ከወ/ሮ ሙሽራ ልጆች ከሆኑት ወ/ሮ ቡልቡላ ብርዋን በሽማግሌ ፊት በብር 1500.00 የገዙት መሆኑና አከራካሪው መሬት ወደ አላማጣ ከተማ አስተዳደር ከመግባቱ በፊት ታራሽ መሬት እንጂ ጎጆ መውጫ ያልነበረ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጧቸው ነጥቦች መሆናቸውን ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ግዥው ሲደረግ ይዞታው ላይ የጎጆ መውጫ ነው፣ ቤት ተሰርቶና ተክሎችን በመትከል ይዞታውን አልምተን ለብዙ አመታት በመጠቀም ላይ ቆይተን ይዞታ ወደ ከተማ ክልል ገብቶ ከሚመለከት አስተዳደር አካል የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያገኘሁበት ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊነት ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ እና ስለጠቅላላ ውል በፍትሓብሔር ሕጋችን የተመለከቱትን የውል አመሰራረት መርሆች ጋር ተዛምዶ መታየት ያለበት መሆኑን ተረድተናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ውል በሕግ ጥበቃ እንዲደረግለት ወይም እንዲጸና በሕጉ ተለይተው የተቀመጡት ሁኔታዎችን አሟልቶ ሊገኝ ይገባል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎችም ውሉ ውል ለመዋዋል ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር፣በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ መሆንና የውሉ አጻጻፍ ፎርም በህግ በታዘዘ ጊዜ ይህኑ ልዩ ፎርም አሟልቶ መገኘት የሚሉትን ሶስት መሰረታዊ የሆኑ ሁኔታዎች ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1678 ድንጋጌው- ከሀ-ሐ ፊደላት ስር በዝርዝር አስቀምጧቸዋል፡፡ የአንቀጹ ፊደል "ለ" ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ውሉ በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ ላይ መደረግ እንደሚገባው የሚያስገነዝበው ሲሆን በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ፣የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ደግሞ ህገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወጥ ውል (unlawful contract)ይሆናል፡፡ አንድ ውል የተደረገበት መሰረታዊ ጉዳይ (object of contract) በህግ ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜም ውሉ በህግ ፊት ምንም ዓይነት ህጋዊ ውጤት የማያስከትል (void contract) መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አከራካሪው ይዞታ ወደ አመልካች እጅ ሊገባ የቻለው ሟች ባለቤታቸው አቶ አድሃና አስፋው በ10/10/1994 ዓ/ም አደረጉ በተባለው የገጠር እርሻ መሬት ይዞታ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና ህዝብ እንደሆነና መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ሀብት መሆኑ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የክልሉ ሕገ መንግስትም በዚህ ረገድ ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ድንጋጌ አስቀምጦአል፡፡ በሌሎች ዝርዝር ህጎችም ማለትም፡- በአዋጅ ቁጥር 456/97"ም" ቢሆን ባለይዞታ አርሶ አደር የመሬት ይዞታውን ለመሸጥ መብት አልተሰጠውም፡፡ አሁን በስራ ላይ ባለው የክልሉ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006ም ሆነ በ1994 ዓ/ም ስራ ላይ በነበረው አዋጅ ቁጥር 55/1994 የገጠር መሬትን በሽያጭ ማስተላለፍ በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ተግባር አይደለም፡፡ በመሆኑም በአመልካች ባለቤት በ1994 ዓ/ም ተደረገ የተባለው ውል በገጠር መሬት ላይ በግልጽ በሕግ ክልከላ ተደርጎ እያለ የተደረገ በመሆኑ ሕገወጥ ነው ተብሎ የሚወሰድ ነው፡፡ ህገ ወጥ ውል ደግሞ በፍ/ህ/ቁ/1716 መሰረት በህግ ፊት ውጤት የማይኖረው ፈራሽ ውል ነው፡፡

ይህ ብቻም ሳይሆን ሕገ ወጥ ውል በማናቸውም ጊዜ ሊፈርስ የሚችል እንጂ የይርጋ ገደብ የሌለው መሆኑን ይህ ችሎት የፍ/ህ/ቁ/1678፣1716 እና 1718 ድንጋጌዎችን በጣምራ በመመርመር በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁጥር 43226፣79394 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ወስኗል፡፡ በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት የውሉ መሰረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነውን ውል (unlawful contract) በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈጻሚነት የለውም በማለት ለመወሰን እንደሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገው የይርጋ ጊዜ ገደብም መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል ችሎቱ በግልጽ አስፍሯል፡፡

ስለሆነም አመልካች ለብዙ አመታት ይዞታውን ይዘው መጠቀማቸውን ጠቅሰውና እና ተክል አልምተው ይዞታው ወደ ከተማ ሲከለል ከማዘጋጃ ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አግኝቼአለሁ የሚለውን ምክንያት መሰረት አድርገው የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ የተጠሪን አውራሽ ልጆች የሆኑት ከአመልካች ባለቤት ጋር የገጠር እርሻ መሬት ሲሸጡ ሙሉ ፍላጎትና እውቅና የነበራቸው መሆኑም በሕግ በግልጽ የተደረገውን የገጠር እርሻ መሬት ሽያጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል ካለመሆኑም በላይ የሕገ መንግስቱንና ይህንኑ ተከትሎ የወጡትን የክልሉን የገጠር እርሻ መሬት አስተዳደር ሕግጋትን መሰረት ያላደረገ ነው፡፡

አመልካች ይዞታው ወደ ከተማ ክልል ከገባ በኋላ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የይዞታ ማረጋጋጫ ደብተር መውሰዳቸው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም ይዞታው ወደ አመልካች የገባበት መንገድ ከመነሻው ሕጋዊ ባለመሆኑና በሕግ አግባብ ባልተገኘ የይዞታ መብት ላይ የሚሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ስልጣን ባለው አካል በመሰጠቱ ብቻ ሕጋዊ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከፍ//ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እንዲሁም ሕገ መንግስቱ ስለንብረት መብት ከሚሠጠው ጥበቃና የመሬት ሽያጭ ውል ሕገ ወጥ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ውድቅ በማድረግ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎች በተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሰረት የሽያጭ ውሉ ህገ ወጥ ነው በሚል ይዞታውን አመልካች ለተጠሪ እንዲለቁ፣ በአመልካች ባለቤት ስም የተሰራው ሳይት ፕላን እንዲሰረዝ በማለት መወሰናቸው ስለገጠር መሬት ይዞታ በፌዴራሉም ሆነ በክልሉ ሕግጋት-መንግስታት፣ሽያጩ ተደረገ በተባለው ጊዜ ስራ ላይ በነበረው የክልሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 55/94፣ እንዲሁም ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ተፈጻሚነት ባለው አዋጅ ቁጥር 236/2006 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ባገናዘበ መልኩ የሰጡት ውሳኔ ሁኖ ስለአገኘን በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 682220 በ11/02/2007 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 70901 በ18/05/2007 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ ፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አከራካሪው ይዞታ የሚታረስ መሬት ነው ሁኖ በሽያጭ ወደ አመልካች በሕገ ወጥ መንገድ ዙሮአል ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ሆኖም በይዞታው ላይ በአመልካች የተፈሩትን ንብረቶችን አመልካች በሕግ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

<u>ት እ ዛ ዝ</u>

በ25/06/2007 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 112906

ቀን የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ማንአህሎህ አንተነህ ተወካይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የማቻካል ወረዳ አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ተወካይ የክልሉ ዓ/ሕግ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመሬት ይዞታ እና የሰብል ግምት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው በአብኪመ የማቻኮል ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በዓቃቤ ህግ በኩል በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ባጭሩ ፡- አመልካች ከማንም ሕጋዊ መብት ካለው አካል ሳይሰጠው በመቻኮል ወረዳ በሸይ ቀበሌ ልዩ ስሙ ገለቦ በተባለው ቦታ በምስራቅ መንገድ በምዕራብ ተምጫ ወንዝ፣ በሰሜን የኔወርቅ ለቀው በደቡብ አሚጋ የሚያዋስነው የህዝብ ግጦሽ መሬት በወርድ 50 ሜትር በቁመት 80 ሜትር የሆነውን የመስኖ መሬት በመያዝ በ2004፣2005 እና 2006 እህል በመዝራት፤ አትክልት በማፍራት ገቢ በማግኘቱ የሰብል ግምት በመክፈል የህዝብና የመንግስት ይዘት ለቆ እንዲያሰረክብ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሰይ ነው፡፤

የአሁኑ አመልካች የመከለከያ መልስ ያቀረበ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩ የሰብል ግምት መቅረብ ያለበት በመሬት ይዞታው ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ መሆን እንዳለበት፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት በ1994 ኣ/ም የቀበሌ አመራር ኮሚቴዎች ለወፍጮ መትከያ የተሰጠው ስለመሆኑ በመግለጽ መልስ አቅርበዋል፡፤

የስር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የአሁን አመልካች መሬቱ ከ1994 ዓ/ም የያዝኩት ስለሆነ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ያቀረበው ክርክር በተመለከተ በዚህ ጉዳይ በ1999 ዓ/ም በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ የተበለ በመሆኑ በይርጋ የሚቋረጥ አይደለም ፡፡ አመልካች መሬቱን በቀበሌ የአመራር አካላት የተሰጠኝ ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም መሬት የማስተዳደር ስልጣን የወረዳው መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ጽ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንጅ የቀበሌ አመራር አይደለም፡፡ አመልካች በመሬቱ ላይ የዘራው ሰብል ግምት በድምሩ 11,474/ አስራ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ብር ይክፈል ይዞታውም ይልቀቅ በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች የስር ወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙ ከከራከረ በኃላ አመልከች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት ለወፍጮ ተጠቃሚ ህብረተሰብ አህያ እንዲያስርበት በቀበሌ አስተዳደር የተሰጠው መሆኑ በወቅቱ የቀበሌ አስተዳደር ኃላፍዎች የነበሩ ቀርበው የመስከሩ ቢሆንም መሬት የመስጠት ስልጣን የወረዳ አስተዳደር መሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 133/98 ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች መሬቱን ያገኘው ህጋዊ ሥልጣን ከሌለው የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት በመሆኑ ይልቀቅ መባሉ በአግባብ ነው፡፡ የሰብል ግምት በተመለከተ አመልካች መሬቱን ያረሰው መብት ያለው መስሎት በመሆኑ በፍ/ህ/ቁ/1173 (2) መስራት ሊሻሽል እንደሚገባው የጠፍ ሰብል ግምት ዳኝነት ያልተጠየቀበት በመሆኑ የዚህን ግምት መጠን ተቀንሶ ብር 7,726.5 ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል የአሁን ሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር አደርጓል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት መሬቱ በ1994 ዓ/ም የተሰጠው በመሆኑ በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ እንንደሚሆን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት የሰጡት የቀበሌ አስተዳደር በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር መጠየቁን የሚያሰይ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የህዝብና የመንግስት ንብረት በህገወጥ የያዘ በመሆኑ ጉዳዩ በይርጋ ህግ ቀሪ የሚሆን አይደለም መሬቱም ሥልጣን በሌለው የቀበሌ አስተዳደር የተሰጠው በመሆኑ ይልቀቅ መባሉ በህጉ አግባብ ነው የሚል መልስ አቅርበዋል፡፤ አመልካች የሰበር አቤቱታው የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ የጉዳዩ አመጠጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸም ያለመፈፀሙን መርምረዋል፡፡ እንደመረመርናውም የአሁኑ አመልካች አጥብቆ የሚከራከራው የመሬት ይዞታው በቀበሌ አስተዳደር እንደተሰጠው እና ለረጅም ዓመት ሲጠቀምበት እንደነበር ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የቀበሌ አስተዳደር መሬት የመስጠት ስልጣን እንደሌለው እና ሰብል በማምረት ያገኘው ህገወጥ ጥቅም ገቢ እንዲያደርግ መወሰኑ በአግባቡ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው አመልካች ከዚህ መሬት ጋር በተያየዘ በ1999 ዓ/ም በወንጀል ተከሶ እንደተቀጣ መሬት የመስጠት ስልጣን በሌለው የቀበሌ አስተዳደር የተመራው ስለመሆኑ ነው፡፡ አመልካች የመሬት ይዞታው በቀበሌ አስተዳደር ተሰጠኝ ይበል እንጂ የቀበሌ አስተዳደር መሬት የመስጠት ኃላፊነት እንደነበራቸው በህግ የተደገፈ ክርክር አላቀረበም፡፤ በህጉ አግባብ ሥልጣን ባለው አካል የመሬት ይዞታው ማግኘቱ ካልተረጋገጠ ደግሞ የህዝብና የመንግስት ይዞታ ሊለቅ ይገባል መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ያቀረበው የይርጋ ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም ብለናል፡፡

አመልካች በህገ ወጥ መንገድ በያዘው መሬት ላይ ሰብል ዘርቶ ገዚ በማግኘቱ ምክንያት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ በማሻሸል 7,726 ብር የሰብል ግምት እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች ሰብሉን የዘራበት አግባብ ሲታይ የመሬት ይዞታው በቀበሌ አስተዳደር የተሰጠው ስለመሆኑ እምነት በመያዝ ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ቀርበው የተሰሙ የቀበሌ የስራ ኃላፊዎች የነበሩ ግለሰቦች መሬት ሰጥተው እንደነበረ አስረድቷል፡፡ ይህ ሲታይ አመልካች መሬቱ ስልጣን ባለው አካል ተሰጥቶኛል ከሚል እምነት በመነጨ በቅን ልቦና ሰብል ያመረተ መሆኑን መረዳት ይቻላል ተጠሪም መሬቱ ሥልጣን ባለው አካል አልተሰጠውም በማለት ተከራከረ እንጅ የቀበሌ አስተዳደር ያልሰጠው ስለመሆኑ ክዶ አልተከራከረም፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ሰብል በመዝራት አገኘው የተበለው ግምት 7,726 ብር ይክፈል መባሉ በህጉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም አመልካች መሬቱ እንዲለቅ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሆኖ የሰብል ግምት ይክፈል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ግን ሊሻሻል የሚገባው ነው፡፤ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፤

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የምስራቅ ስደሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 011806 በ 24/06/2007 ዓ/ም የመቻከል ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11475 በ2/08/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በማሻሸል የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፤
2. አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን መሬቶች እንዲያስረክብ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች የሰብል ግምት 7726 /ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ሰድስት ብር 50/100 የሆነውን ለመልስ ሰጭው ሊከፍል ይገባል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል
4. የወጪና ኪሰራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንግድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 99900

መስከረም 25 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

መስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሣለኝ

አመልካች፡- አቶ ኃይሉ መንግስቱ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሬገን መሐመድ - አልቀረቡም

2. አቶ ጌታሁን ገሰሰ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሽርክና ማህበር በማቋቋም የተዋጣው ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የጀመረው የአሁኑ አመልካች በአፋር ክልል ገቢረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም በአጭሩ ከተጠሪዎች ጋር በነበራቸው የሽርክና ውል መሰረት የእርሻ ስራ መጀመራቸውን ገልፆ በመካከሉ ግን አመልካች ከማህበሩ መውጣት መፈለጉን ተከትሎ ያዋጣው ገንዘብ ብር 38,900 አመልካች እንዲመለስለት በጠየቀው መሰረት ተጠሪዎች ገንዘቡን በሁለት ዙር ክፍያ ሊከፍሉ ከተስማሙ በኃላ ያለመከፈላቸውን ጠቅሶ በውሉ መሰረት ሊከፍሉ የተስማሙበትን ብር 38,900ና ብሩ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም በውሉ መሰረት ባለመፈፀማቸው ቅጣት/ ገደብ ብር 5000 እና ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፈልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ሲሆን የስር 1ኛ ተከሳሽ የሆነው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪም በበኩሉ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ ፡- ከአመልካች ጋር በሽርክና በጋራ ስራ ለመስራት ገንዘብ ማዋጣቸውን አምኖ ሆኖም ግን አመልካች የዋጣውን ገንዘብ ለመመለስ አለመስማማቱን ወይም ውል አለመፈረሙንና አመልካች የውል ስምምነት ነው ብሎ ያቀረበው ሰነድም 2ኛ ተጠሪን ብቻ በሽማግሌዎች አማካኝነት በመደለልና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አታሎ ያስፈረመው ውል እንጂ እኔን ጭምር ያካተተ ባለመሆኑ ውሉ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ ይልቁንም በሽርክና ውላችን መሰረት የከዚህ ቀደሙን ኪሳራ አመልካች ከእኛ ጋር ከተጋራ በኃላ በቀጣዩም አብረን እንድንሰራ ተብሎ ይወሰንልን በማለት ተከራክሯል። ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም በበኩሉ የግራ ቀኙን ቃል ክርክር ካአዳመጠ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች አስቀድሞ ያዋጣው የገንዘብ ይመለስለት በሚለው ሰነድ ላይ 1ኛ ተከሳሽ (የስር 1ኛ ተጠሪ) ባይፈርምም በሁለቱ ተከሳሾች መካከል የወካይና ተወካይ ግንኙነት መኖሩንና እንዲሁም የስር 1ኛ ተከሳሽም በራሱ በውሉ ላይ ባይፈርምም በውሉ መስማማቱን ግን ከቀረበው ክርክር ለመረዳት መቻሉን ካሰፈረ በኃላ ተከሳሾች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1675 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት በገቡት ውል መሰረት ዋናውን ገንዘብ ብር 38,900 ክስ ከተመሰረተበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ 9%ወለድ ጋርና እንዲሁም ብር 5000 ገደብ ጭምር በአንድነትና በነጠላ ለስር ከሳሽ ይከፈሉ ሲል ወስኗል ። በአሁኑ ተጠሪዎች የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን ተከራክሪ ወገኖች አስቀርቦ እንዲከራከሩ ካደረገ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የሽርክና ውል መኖሩን መረጋገጡን ከገለፀ በኃላ ከዚኅ ውል ለመውጣትም ሆነ የሽርክና ውሉን ለማፍረስ የፈለገ አባል ካለ ጥያቄውን ማቅረብ ያለበትም ሆነ ጉዳዩ ታይቶ ተገቢው ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ጉዳዩን በተለይ በሚገዛው ንግድ ህጉ መሰረት መሆን አለበት እንጂ ስለ ውሎች በጠቅላላው የሚመለከተው የፍ/ብ/ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት ባለመሆኑ የህንኑን ተከትሎ ተፈጸሚል የተባለው የውል ሰነድም በዚሁ ምክንያት ተፈፃሚነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ከተቸ በኃላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ሽሮታል ።አሁን የቀረበው በሰበር አቤቱታም ይህንኑ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን ይህ ሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል መዝገቡን እንደተመለከትነውም በአመልካችና ተጠሪዎች መካከል አስቀድሞ የተቋቋመ የሽርክና ማህበር ውል መኖሩን ፣በዚህ ውል መነሻነትም አመልካች የበኩላቸውን ድርሻ ብር 38,900 ገንዘብ ማዋጣቱን በሽርክና ውሉ መሠረትም የእርሻ ስራ በጋራ መስራት መጀመራቸውም ፣ይህ በእንዲህ እንዳለ 2ኛ ተጠሪ በ23/11/2004 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት መሰረት አመልካች በማህበር አባልነቱ አስቀድሞ ያዋጣውን ገንዘብ በሁለት ዙር የክፍያ አፈጻጸም ጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለመክፈል በራሱና 1ኛ ተጠሪን በመወከል ውል መፈረሙን አመልካችም ይሄው ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ በተጠሪዎች እንዲከፈለው የጠየቀው ይህንኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል መሰረት በማድረግ መሆኑን ፣ነገር ግን 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠው ውክልና ስልጣን አለመኖሩን ፣1ኛ ተጠሪም በዚሁ መሰረት በአመልካች ጥያቄ አለመስማማቱንና እንዲሁም ካለ 1ኛ ተጠሪ ፈቃድ ውጭ ሁለቱ አባላት ብቻቸውን ይህንኑ አመልካች አስቀድሞ ያዋጣውን መዋጮ ይዞ ከማህበሩ ይውጣ በማለት መወሰንም የማይችሉ መሆኑን ገልፆ የሚከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

እንግዲህ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች መካከል በውል መሰረት የተቋቋመ የሽርክና ማህበር አለ ከተባለ ከዚህ ማህበር ለመውጣት የፈለገ አባል እንዴት እና በምን አግባብ መውጣት እንደሚችል በንግድ ህጉ አንቀጽ 227 እና ተከታዮቹ ጠቅላላ ድንጋጌዎች በሚመለከተው መሰረት ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል ፡፡ በእርግጥ አመልካች የራሱን መዋጮ ይዞ ከማህበሩ ይውጣ በሚለው ሀሳብ ላይ ሁሉም የማህበሩ አባላት ቢስማሙበት ኖሮ አመልካች ይህንኑ በውሉ መሰረት እንዲሰጠው መጠየቅ እንደሚችል ከንግድ ህጉ አንቀጽ 233(1) ድንጋጌ ይዘትና ሌሎችም ተከታይ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል ፡፡ይሁንና ከማህበሩ አባላት አንዱ የሆነው 1ኛ ተጠሪ በዚህ ነጥብ ላይ መስማማቱን አመልካች አላስረዳም ፡፡ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪም ቢሆን ከ1ኛ ተጠሪ የተሰጠውን ውክልና ስልጣን መሠረት በማድረግ ለአመልካች መዋጮው እንዲመለስለት የሚለውንና በ 23/11/2004 ዓ.ም ተደርጓል የተባለውን የውል ስምምነቱ ስለመፈረሙም በፍሬ ነገር ደረጃ በማስረጃ አልተረጋገጠም እንዲህ ከሆነ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ረገድ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠው የውክልና ስልጣን ከሌለና 1ኛ ተጠሪም በራሱ በ 23/11/2004 ዓ.ም ተደርጓል በተባለው ስምምነት ሰነድ ላይ አለመፈረሙ ከተረጋገጠ አመልካች ይህንን ውል በሰነድ መሠረት በማድረግ አስቀድሞ የዋጣው መዋጮ እንዲከፈለው /እንዲመለስለት /መጠየቅ የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም ፡፡ ስለሆነም አመልካች ሁሉም የማህበሩ አባላት ያልተስማሙበትን የውል ስምምነት ሰነድ(በ23/11/2004 ዓ.ም ተደርጓል የተባለውን) መሠረት በማድረግ አስቀድሞ ለማህበሩ አዋጥቶ የነበረውን መዋጮ ብር 38,900 እንዲመለስለት መጠየቁ ለጉዳዩ በተለይ አግባብነት ያለው የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች መሠረት ያላደረገ በመሆኑ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን መሻሩ በውጤት ደረጃ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአፋር ብ/ክ/መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁጥር 2752 በ 14/5/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሠረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች ሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም
3. አመልካች በንግድ ህጉ መሰረት መብቱን ከማስከበር ይህ ውሳኔ አይከለከለውም ፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.97760

ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ንግስቲ አትክልቲ -ጠበቃ ሙሉዓለም ፈጠነ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አበባው ሽፈራው -የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአካል ጉዳት ካሳ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኗ አመልካች እና አቶ በረከት ተስፋዬ ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡ ንብረትነቱ የአመልካች በሆነውና በስር 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት በአቶ በረከት ተስፋዬ ይሽከረከር በነበረው ኮድ 3-58098 አ.አ ተሸከርካሪ ከአለታ ወንዶ ከተማ ወደ ሐዋሳ ከተማ ብር 22.00 ከፍለው በመንገዝ ላይ እንዳሉ መኪናው በከፍተኛ ፍጥነት ይሽከረከርና ሹፌሩም ሞይባል ያናገር ስለነበር ከተራራው ጋር ተጋጭተው በአካላቸው ላይ 50% የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን፣በዚህም ምክንያት ገቢ ያጡና ለሕክምና ወጪ ያወጡ መሆኑንና ሹፌሩም በወንጀል የተቀጡ መሆኑን ዘርዝረው በድምሩ ብር 497,105.97(አራት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ አንድ መቶ አምስት ብር ከዘጠና ሳንቲም) ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የመኪናው ባለቤትና ሹፌሩ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ጉዳቱ የጥቅም ግንኙነት በሌለው ሁኔታ ስለመሆኑ፣ ተጠሪ በጉዳቱ ምክንያት የተቋረጠባቸው ገቢ ወይም ጥቅም የሌለ መሆኑንና የጉዳት ካሳ መጠኑም የተጋነነ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት ግለሰብ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጎአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ አመልካችን ኃላፊ በማድረግ ብር 376,226.00 (ሶስት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ስድስት ብር) በአንድነትና በነጣላ እንዲከፈላቸው ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን እንዲከራከሩ እና አማካይ እድሜን በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ እንዲቀርብ ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ላይ የተሰጠውን የኃላፊነት ውሳኔ ተቀብሎ የጉዳት ክሳ መጠኑን ግን ከአማካይ እድሜ ጋር በማመጣጣን አስልቶ በድምሩ ብር 284,280.00(ሁለት መቶ ሰማንያ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ብር) አመልካችና የስር 2ኛ ተከሳሽ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚኅም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 04 ቀን 2006 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2081፣2086(2) እና 2089 ድንጋጌዎች ጋር እና የጥቅም ግንኙነት በሌለበት ሁኔታ የተሸከርካሪው ባለቤት ተጠያቂነት የለበትም ተብሎ ከተወሰነው የዚህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ ውሳኔ ጋር ያልተጣጣመ መሆኑን፣ ተጠሪ ክሱን ከውል ውጪ ሃላፊነትን በሚገዙ ድንጋጌዎች መሰረት ማቅረባቸው ተገቢነት የሌለው መሆኑንና የካሳ መጠኑንም በጉዳቱ ምክንያት የተቋረጠ የተጠሪ ጥቅም በሌለበትና የተጠሪ ገቢ በአግባቡ ባልተጣራበት ሁኔታ በተጋነነና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090 ይዘትና መንፈስ ውጪ የተወሰኑ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ የፁሑፍ ክርክር አድርገዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ከተያዙት ጭብጦች አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የተያዙት ጭብጦች፡-

1. በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2089 ድንጋጌ እና ከሰ/መ/ቁጥር 38457 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን፣
2. የአጓዥ ተጓዥ ውል መኖሩ ሳይካድ ከውል ውጪ ሃላፊነት ተብሎ የቀረበው ክስ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ተጠሪ በጉዳቱ ምክንያት ያጡት ጥቅም እንደተቋረጠባቸው ባላስረዱበት ለተጠሪ ካሳ እንዲከፈላቸው የተወሰነው የካሳ መጠን ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች ከተጠሪ ጋር የጥቅም ግንኙነት የለኝም በማለት የሚከራከሩት ጉዳት አደረሰ የተባለውን ተሽከርካሪ በወቅቱ Populationa Service International(PSI) ለተባለ ድርጅት አከራይቼ ከመኪናው ጥቅም ሲያገኝ የነበረው ይኼው ድርጅት ነው በሚል አቢይ ምክንያት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ማስረጃ እንዲቀርብ አድርጎ የኪራይ ውል ሊቀርብ ባለመቻሉ መኪናው ተከራይቶ የነበረ ነው ለማለት እንዳልቻለ ግልጾ ያለፈው ስለመሆኑ ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች መኪናውን አከራይተው ያልነበሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን በመመዘን ረገድ ተመሳሳይ የሆነ ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ ፍሬ ነገር የተቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ስናው ይህ ችሎት አመልካች መኪናውን አከራይተው ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለውን የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ነጥብ የሚመረምርበት አግባብ የለም፡፡ ምክንቱም ለዚህ ችሎት በአ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን ለማጣራት ወይም ማስረጃን ለመመዘን ሳይሆን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም ብቻ ነውና፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ በአመልካች በኩል የቀረበው ቅሬታም ሆነ በሰበር አጣሪ ችሎቱ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገርና የዚህን ችሎት ስልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> ተጠሪ በአመልካች መኪና ክፍያ ፈጽመው ሲጓዙ የነበሩ መሆኑ ያልተካደና በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ግንኙነቱ ውልን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ውልን መሰረት ያደረገ የመጓጓዣ ግንኙነት በን/ሕ/ቁጥር 588 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብ ሊታይ የሚገባ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በን/ሕ/ቁጥር 588 ድንጋጌ ይዘት ሲታይ አጓዡ መንገደኛውን በመልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ስለ ምቾቱና ስለ ጉዞው በውሉ የተወሰነውን ጊዜ አክብሮ እንደተወሰነው እመድረሻ ስፍራ የማድረስ ግዴታ እንዳለበት በሓይለ ቃል አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የአጓዡን የትራንስፖርት መኪና በሀላፊነት ተረክቦ መኪናውን ደህንነትና ብቃት አረጋግጦ የትራፊክ ደንብና ሥርዓትን አክብሮ የማሽከርከር ሀላፊነት ያለበት አሽከርካሪ /ሹፌር/ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች መንገደኛውን መልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ምቾት በመጠበቅ በሰላም ወደሚፈለግበት ቦታ የማድረስ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ማስቻል ሲሆን ይህንኑ በሕግ የተጣላባቸውን ግዴታ ካልተወጡ ደግሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መንገደኛው በጉዞው ላይ ስለሚደርስበት መዘግየትና በጉዞው ጊዜ ወይም በሚሣፈርበት ወይም በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል ማጉደል ወይም የህይወት ማለፍ አጓዡ ሀላፊ እንደሚሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 595 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡የዚህ ድንጋጌ አጓዡ መንገደኛው በጉዞ ጊዜ በሚሣፈርበትና በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል መጉደል ወይም ህይወት ማለፍ አጓዡ በሀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን በመሠረታዊ መርህነት የሚያስቀምጥ ሲሆን ፣ አጓዡ ከሀላፊነት ነጻ የሚሆንባቸዉን ልዩ ሁኔታዎች የሀላፊነቱን መጠንና አጓዡ በህግ ከተደነገገው መጠን በላይ በሀላፊነት ሊጠይቅ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎች አካቶ ይዟል፡፡ በንግድ ህግ አንቀጽ 595 ከተደነገገው ሀላፊነት አጓዡ ነጻ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚደነግገው የንግድ ህጉ አንቀጽ 596 ሲሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 596 አጓዡ በመንገደኛው ላይ የአካል መጐዳት ወይም የሞት አደጋ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ከፍተኛ ሀይል መሆኑን ፣ ወይም ጉዳቱ የደረሰው በሶስተኛ ሰው ጥፋት መሆኑን ወይም በመንገደኛው ጥፋት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ አጓዡ ከሀላፊነት ነጻ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ የካሳ መጠኑን በተመለከተ የቀረበውን ቅሬታ ስንመለከተውም አጓዡ በንግድ ህግ ቁጥር 596 መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ በመንገደኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት በሀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 597 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የሀላፊነት መጠን በተመለከተ ደግሞ ለአንድ መንገደኛ ከብር 40,000 /አርባ ሺ ብር/ እንደማይበልጥ የንግድ ህግ አንቀጽ 597 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በንግድ ህግ አንቀጽ 597 የተደነገገው የሀላፊነት መጠን አጓዡ በንግድ ህግ አንቀጽ 596 የተደነገጉትና ከሀላፊነት ነጻ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታና መንገደኛው በንግድ ህግ አንቀጽ 599 በሚደነገገው መሠረት አጓዡ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑን እያወቀ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ባልቻለበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግን የአመልካች ንብረት የሆነውን ተሽከርካሪ ያሽከረክር የነበረው የአመልካች ሰራተኛና የመኪናው ሹፌር የሆነው ለአደጋው ምክንያት ስለመሆኑ ተረጋግጦ በወንጀልም ክስ ተመስርቶበት ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ግልጽ የሆነ ክርክርና ማስተባበያም የለም፡፡ በንግድ ህግ ቁጥር 588 በሚደነግገው መሠረት የመንገደኛውን መልካም ይዞታ ደህንነትና ምቾት በመጠበቅ መንገደኛውን የማንገዝ ሀላፊነቱን ሊወጡ የሚገባቸውን ወገኖች የመኪና ባለቤት፣ ሹፌር፣ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ መኖሩን፣ በንግድ ህግ አንቀጽ 599 “አጓዡ የተፈፀመው ተግባር ወይም ጉድለት” የሚለው ሀረግ አጓዡ በግሉ የፈጸመውን ተግባር ወይም ጉድለት የሚመለከት ሣይሆን የአጓዡ ሰራተኞች አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጠር እንደሚችል እያወቁ የፈጸሙትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተግባር ወይም ጉድለት የሚያካትት ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 67973 በሆነው መዝገብ ላይ በቀረበው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በማናቸውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያሰገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተያዘው ጉዳዩ ሲታይም አደጋው የደረሰው የ2ኛ አመልካች መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር ባጠፋው ጥፋት ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የክርክር ሂደት የተረጋገጠ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የን/ሕ/ቁጥር 599 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች በተጠሪው ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት በግንድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው በላይ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው የሀላፊነት መጠን በላይ ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት እንደአለባቸው የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ድንጋጌ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በን/ሕ/ቁ 599 ድንጋጌ መሠረት ለመገደኛው ካሣ የመክፈለ ሀላፊነት ያለበት አጓዥ ለመንገደኛው የሚከፍለው የካሣ መጠን ለመወሰን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2092 የተደነገጉት የካሳ አከፋፈል መርሆች አግባብነት ያላቸው ስለመሆናቸውም ይህ ችሎት ከላይ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ጉዳዩ ሲታይም ክሱ መቅረብ ያለበት ከውል ውጪ ሃላፊነትን በሚገዙ ድንጋጌዎች በመሆኑ ተጠሪ በዚህ አግባብ ክስ ማቅረባቸውና የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ክስ ተቀብለው ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዙ ድንጋጌዎች መሰረት መወሰናቸው የሚንቀፍበትን ሕጋዊ ምክንየት አላገኘንም፡፡

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ተጠሪ በመኪናው ግጭት ምክንያት በአካላቸው ላይ 50% ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ፣ ከጉዳቱ የተነሳ ለተለያዩ ወጪዎች የተዳረጉ መሆኑንና ከጉዳቱ በፊት በሲዳማ ቡና አብቃይ ገብሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን ይሰሩ እንደነበርና በጉዳቱ ምክንያትም የስራ ብቃታቸው እና ሲያገኙ የነበረው የገቢ መጠንን ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳቱ ምክንያት ወደፊት ተጠሪ የሚቀርባቸውን ገቢና ከጉዳቱ ጋር ተያይዘው የወጡትን ወጪዎች በመለየት የካሣ መጠኑን ወስነዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተለይ ካሳውን ሊወሰን የቻለው የተጠሪን እድሜና በአከባቢው በጊዜው የታወቀውን አማካይ እድሜ ስንት እንደሆነ በመለየት ስለመሆኑ ውሳኔው በግልጽ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን ፣መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣2091፣2092 ፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የካሳ መጠን ላይ ይግባኝ የሌለው መሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁር 2152 ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኙ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታዎች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 ስር ተገልጸዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች በኩል የቀረበውን ቅሬታ መሰረት ስናደረግ በካሳ አተማመኑ ላይ በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ሳይገቡ በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ስለመሠጠቱ የሚያሳይ ነገር ያለ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ አካላቸው በሕገ መንግስቱም ጥበቃ የተደረገላቸው ሲሆን ካሳው ሲወሰንም ይህንኑና ጉዳቱ በአመልካች የወደፊት ኑሮ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው አጠቃላይ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ሊወሰን የሚችል ነው፡፡ ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ የሚገዙት የፍትሓብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች መንፈስ የጉዳትን ጠቅላላ ባህርይና የካሣ ልክ አተማመን ሁኔታዎችን ያስገነዝቡናል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ ችግር የሚያደርስ መሆኑን፣ ይህም ጥቅም ማቴሪያሊዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራሊዊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጎዳ ሰው ደግሞ መካስ እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ የካሣውን አተማመን በተመለከተም መጠኑ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሁኖ መመዘን ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትን/future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት የጉዳት ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን ሕጉ በግልጽ ከማስቀመጡም በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብነት ሊለያይ የሚችል መሆኑን የሕጉ መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን የካሣ አከፋፈሉን ልክ በሚደነግገው የሕጉ ክፍል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡ በሌላ በኩል የካሣ አተማመን ሥርዓት ጠቅላላ የመሥራት አቅም /General utility/ ሣይሆን ልዩ ጠቀሜታ/specific utility/ መርህን ቢከተል ፍትሓዊነት ያለው አሠራር መሆኑ ይታመናል፡፡ ይህም አሠራር በተጨባጭ የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የካሣውን ልክ ያላግባብ ከማጋነንና ከመቀነስ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ጉዳት መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠና ጉዳቱም በተጎጂው የወደፊት ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ካሣ መወሰን ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ አኳያ አግባብነት ያለው ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተ በሕጉ ለዳኞች በተሰጠው ሥልጣን ወይም በጉዳዩ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት በመተመን ለተጎጂው መፍርድ የሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መኖሩን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎችና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2101 እና 2102 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ ውጪ ጉዳቱ መድረሱ እየታወቀ የአሁንና የወደፊት ቁሣዊ ጉዳት /material damage/ ስለመኖሩ ተጎጂው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አላስረዳም ተብሎ የመካስ መብት ማጣት ከአጠቃላይ ከውል ውጪ ኃላፊነትን ከሚገዛው ሕግ አላማ ጋር አንድ ላይ የሚሄድ አይሆንም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በአመልካች መኪና ተሳፍረው ሲሄዱ በደረሰው ከተራራ ጋር የመጋጨት አደጋ በአካላቸው ላይ ጉዳት መድረሱ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳቱ ወደፊት ሊጠፋ የሚችል ስለመሆኑም የተገለፀ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበው ቅሬታም ሆነ በአጣሪ ችሎቱ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነጥብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣2141 እና 2153 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ስላለገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1656 ሚያዚያ 03 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 594440 በ10/01/2006 ዓ/ም የተሻሻለውና ይህንኑ የተሻሻለውን ውሳኔ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ያፀናው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 94784 በ30/04/2006 የሠጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105628

ጥቅምት 24/2008 ዓ.ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡..... ዩኒቨርሳል ሜታልስና ሚኒራል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጠበቃ ማርሻል ፍ/ማርቆስ ቀረቡ

ተጠሪ፡..... ባሰፋ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር- የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይሄ ጉዳይ የሕንጻ ኪራይ ውል ካለቀ በኋላ ያልተከፈለውን ከሕንጻው የታጣ ገቢን ለማስከፈል የቀረበ ክስን መሰረት ያደረገ ክርክር ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የሥር ከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የባለ ሁለት ፎቅ ህንጻ ተከሳሽ ህዳር 15 ቀን 2003 ዓ.ም በተሻሻለው የኪራይ ውል ስምምነት የኪራይ እና የተለያዩ ክፍያዎችን ጨምሮ በየወሩ በብር 51,750.00 ተከራይቶ ከህዳር 9 ቀን 2003 ዓ.ም እስከ ህዳር 8 ቀን 2005 ዓ.ም ሲገለገልበት ቆይቶ የውሉ ዘመን እስከሚያልቅ በዚህ አልገደድም በማለት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡ ተከሳሽ ያለበትን የቤቱን ኪራይ ከፍሎ ቤቱን እንዲያስረክበን ከሰን በ20/03/2005 ዓ.ም ፍርድ ተፈርዶበት ፣ በአፈጻጸም በ30/08/2005 ዓ.ም ሕንጻውን ሊያስረክበን ችሏል ፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ በአዲስ የኪራይ ታሪፍ መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ በቀን በብር 3,333.33 ወይም በወር ብር 100,000.00 ሂሳብ የ172 ቀናት ጊዜ ማግኘት የነበረብንን ገቢ በድምሩ ብር 573,333.28 ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍለን በማለት ጠይቋል፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ የሥር ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ ባቀረበው መልስ ተከሳሽ ቤቱን ለቆ የወጣው ታህሳስ 25 ቀን 2005 ዓ.ም ቢሆንም ከሳሽ ቤቱን ለመረከብ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ከሳሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውሳኔው መሰረት ቤቱን ያስረክበኝ በማለት አፈጻጸም ቢያቀርብም ተከሳሽ ቤቱን አስተካክሎ ሊያስረክበኝ ይገባል በሚል ምክንያት ሳይረከብ ቀርቶ በተከሳሽ ተደጋጋሚ ልመና በ30/08/2005 ዓ.ም የቤቱ ርክክብ ሊፈጸም ችሏል ። ከሳሽ ቤቱን ተረክቦ የጎደለ ነገር መጠየቅ ይገባው ነበር እንጂ በዚህ ምክንያት አልረከብም ማለቱ ተገቢ አይደለም ለጨመረው ኪሳራ ሃላፊ እሱ ነው። የቤቱ ርክክብ የዘገየውን በተመለከተ ከታህሳስ 25 ቀን 2005 ዓ.ም በኋላ ያለው የኪራይ ገንዘብ ተከሳሽን አይመለከትም። የኪራይ መጠን መታሰብ ያለበት በብር 51,750.00 እንጂ በብር 100,000.00 ሊሆን አይችልም። ስለዚህ የከሳሽ ክስ ተሰርዞ ከ9/03/2005 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ1 ወር ከ16 ቀን ብቻ ብር 79,350.00 ብቻ ተብሎ እንዲወሰን በማለት ተከራክሯል ።

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ የቤት የኪራይ ውል እንደነበር የተረጋገጠ ሲሆን ተከሳሽ በ20/03/2005 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ መሰረት ህንጻውን ያስረክበው ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በኪራይ ውሉ አንቀጽ 5 መሰረት የኪራይ ውሉ ዘመን ሳያልቅ ቤቱን አስተካክሎ በነበረበት ሁኔታ ለከሳሽ ማስረከብ እንዳለበት ያሳያል። ከሳሽ በ03/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ ማስጠንቀቂያ የቤቱ የኪራይ ዋጋ ብር 100,000.00 ሆኖ መወሰኑን ለተከሳሽ አሳውቆ ተከሳሽም በሰጠው መልስ ይህን እንደማይቀበል ገልጿል። ይህ ማለት ተከሳሽ የቤቱ የኪራይ ዋጋ ተመን ብር 100,0000.00 እንደሚሆን አውቋል ። ስለዚህ ተከሳሽ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ብር 573,333.28 የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ከግንቦት 5 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍለው በማለት ወስኗል። የሥር ተከሳሽ ይህን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻውን ለፌደራል ጠቅላጠይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ምክንያቱን በመጥቀስ የሥር ውሳኔን በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች መስከረም 03 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ የተስማሙት የኪራይ ዋጋ ብር 51,750.00 ሲሆን ይህ የኪራይ ዋጋ በስምምነት ካላሻሻሉት አከራይ የሆነው ወገን ብቻ በራሱ ዋጋ ሊተመን የሚችልበት የሕግ ስርዓት የለም። ተጠሪ የውሉ ዘመን ከመጠናቀቁ በፊት ኪራዩን ብር 100,000.00 አድርጌያለሁ በማለት የሰጠው ማስታወቂያ በወቅቱ በአመልካች ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ቀሪ ሆኗል። ይህ ሆኖ ሳለ የኪራይ ዋጋ ብር 100,000.00 /መቶ ሺህ/ ሂሳብ እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው። ተጠሪ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ቤቱን እንዲያስረክበኝ በማለት ክስ ሲመሰርት እስኪያስረክበኝ ድረስ የቤቱን ኪራይ በወር 51,750.00 ይክፈለኝ በማለት ጠይቋል። ይህ ማለት የኪራይ ጭማሪ ተቀባይነት እንደሌለው ተረድቶ የተወ መሆኑን ነው። ስለዚህ አመልካች የሚጠይቀው ዳኝነት የሥር ፍ/ቤቶች ኪራዩ በብር 100,000.00 ይክፈል በማለት የተሰጠበት ውሳኔ ተሽሮ ስምምነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተደረገበት በብር 51,750.00 እንዲወሰንና የደረሰውን ወጪና ኪሳራ ተጠሪ እንዲተካ እንዲወሰን በማለት አመልክቷል ።

> ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቡን በመመርመር የሚጣራ ጉዳይ ስላለ አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የካቲት 05 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት ፡- ይህ ክስ የጉዳት ካሳና ኪሳራ ይከፈለን የሚል ነው እንጂ የቤት ኪራይ ይከፈለን የሚል አይደለም። አመልካች የሕንጻው የኪራይ ውሉ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ዓመት በፊት ጀምሮ የቤቱ ኪራይ ታሪፍ ከነታክስ ብር 51,750.00 ወደ ብር 100,000.00 ማደጉን በጽሑፍ የተገለጸለትና የአወቀው ሆኖ ሳለ ቤቱን እንዲለቅ ተወስኖበት የውሉ ዘመን ካበቃም በኋላ ከተጠሪ እውቅናና ፈቃድ ውጭ ለ172 ቀናት ከህግ ውጭ ቤቱን ይዞ እየተገለገለበት ማግኘት የነበረብንን እና የቀረብንን ገቢ አመልካች በአዲሱ የኪራይ ታሪፍ የጉዳት ካሳና ኪሳራ እንዲከፍለን ጠይቀን ተፈረደበት እንጂ የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍል አልተፈረደበትም። አመልካች የኪራይ ውሉ ካበቃ በኋላ ቤቱን እንዲያስረክበን በተደጋጋሚ ጊዜ በጽሁፍ እየጠየቅነውና ማስጠንቀቂያ እየተሰጠው ከተጠሪ እውቅና ፈቃድ ውጭ ቤታችንን ከ6 ወራት በላይ ያለአግባብ ተገልግሎበታል። ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የኪራይ ውሉ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ዓመት በፊት የኪራይ ታሪፉን ተጠሪ ባሳወቀው መሰረት የጉዳት ካሳ እንዲከፍለን መወሰናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ውድቅ እንዲሆንልን ወጪና ኪሳራ አመልካች እንዲተካልን በማለት ተከራክሯል። አመልካች በ09/07/2007 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አመልካች የሕንጻው ኪራይ ዘመን ካለቀ በኋላ ሕንጻውን በፍርድ እስካስረከበበት ጊዜ ተጠሪ ያጣውን ገቢ በምን ልክ መክፈል አለበት? የሚለውን እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለው መርምሮታል። መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ እና አመልካች መካከል በነበረው በተሻሻለው የሕንጻ ኪራይ ውል መሰረት የኪራይ ዋጋ እና የተለያዩ ወጪዎችን ጨምሮ በብር 51,750.00 ከህዳር 9 ቀን 2003 ዓ.ም እስከ ህዳር 8 ቀን 2005 ዓ.ም አመልካች ተከራይቶ ሲገለገልበት እንደነበር ተረጋግጧል። በግራ ቀኙ መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ተጠሪ ባቀረበው ክስ አመልካች ያለበትን የኪራይ ገንዘብ ከፍሎ ሕንጻውን እንዲያስረክበው ክስ አቅርቦ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 196631 በ20/03/2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች ያለበትን የሕንጻውን ኪራይ ዋጋ ከፍሎ ሕንጻውን ለተጠሪ እንዲያስረክብ በማለት ወስኗል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ግን በዚህ ውሳኔ መሰረት የሕንጻው ኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኋላ በፍርድ አፈጻጸም መምሪያ በኩል ሲካሄድ በነበረው የፍርድ አፈጻጸም ሂደት ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም ሕንጻውን ለተጠሪ ያስረከበው መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ፍሬ ነገር በማስረጃ አጣርቶ በደረሱበት መደምደሚያ በኪራይ ውሉ መሰረት የኪራይ ዘመኑ ከማለቁ በፊት በሕንጻው ላይ የተገኙትን ጉድለቶች አስተካክሎ ሕንጻውን በነበረ ሁኔታ ነው የመለሰ በሚያስብል መልኩ ለተጠሪ ማስረከብ እንዳለበት አረጋግጧል፡፡ አመልካች የሕንጻው ኪራይ ዘመኑ ከማለቁ በፊት መስተካከል ያለበትን አስተካክሎ በህዳር 8 ቀን 2005 ዓ.ም ሕንጻውን ለተጠሪ ማስረከብ አለበት እንጂ የኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኋላ ሕንጻውን ለማደስ መነሳቱ አግባብነት የለውም፡፡ የሕንጻው የኪራይ ውል ዘመን ካለቀ በኋላ አመልካች በጊዜ ሕንጻውን ማስተካከል ያለበትን ነገር አስተካክሎ ባለማስረከቡ የሕንጻው ርክክብ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም የዘገየ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ የሕንጻው ርክክብ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም የዘገየ መሆኑን የስር ፍ/ቤት ያረጋገጡት ጉዳይ ነው ስለዚህ የህንጻው ርክክብ የዘገየው በተጠሪ ምክንያት መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች የቀረበውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር ይህን በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከመቀበል በቀር ተመልሶ የሚያጣራበት የሕግ አግባብ የለውም፡፡

ይህ በመሆኑ አመልካች የሕንጻው የኪራይ ዘመን ካለቀ በኋላ ያለአግባብ ሕንጻውን ይዞ ለቆየበት ጊዜ ተጠሪው ያጣውን ገቢ በምን ስሌት መክፈል አለበት የሚለው ጭብጥ እልባት ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ሲታይ በ03/04/2004 ዓ.ም ለአመልካች በተሰጠው ማስጠንቀቂያ የሕንጻው ኪራይ ዋጋ ብር 100,000.00 መሆኑን ያሳወቅን በመሆኑ፣ አመልካች ሕንጻውን ያለአግባብ ይዞ በቆየባቸው ጊዜያት በዚህ ገንዘብ ልክ ኪራዩን ሊከፍለን ይገባል በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ ባቀረበው ክርክር የኪራዩን ዋጋ በስምምነት እስካላሻሻልነው ድረስ ተጠሪው ብቻውን ሊወስን አይችልም፣ የተሰጠውም ማስጠንቀቂያ ቀሪ ስለሆነ በብር 100,000.00 የኪራይ ዋጋ ተመን አልገደድም በማለት ተከራክሯል ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የተጠሪን ክርክር በመቀበል ከሕንጻው አጥቷል ያሉትን ገቢ አስልቶ መወሰናቸውን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ በ03/04/2004 ዓ.ም የሕንጻው ኪራይ ዋጋ ብር 100,000.00 እንዲሆን ተወስኗል በማለት ለአመልካች ማስጠንቀቂያ በሰጠ ጊዜ የኪራይ ውሉ ዘመን እንዳላለቀ ያመለክታል፡፡ ከዛ በኋላ ተጠሪ አመልካች በኪራይ ውሉ ላይ በተጠቀሰው የኪራይ ዋጋ ታሪፍ ብር 51,750.00 መሰረት ያልከፈለውን ክፍያ ፈጽሞ ሕንጻውን እንዲያስረክበው የተወሰነ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ የኪራይ ዘመኑ ከማለቁ በፊት ማስጠንቀቂያ የሰጠ ቢሆንም በክርክር ሂደት ውስጥ ይህ ማስጠንቀቂያ ታልፎ እስከ ኪራይ ዘመኑ ያለውን በነበረው የኪራይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዋጋ ፍ/ቤቶቹ ያሰሉት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ስለሆነም ተጠሪ የኪራይ ውሉ ዘመን ሳያልቅ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ መሰረት በማድረግ ዳኝነት የጠየቀው እና የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን መሰረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ሲታይ አግባብነት የሌለው ውሳኔ ነው፡፡ ተጠሪ የኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኋላ የአካባቢውን የሕንጻ ኪራይ ዋጋ ተመን ከግምት ውስጥ በማስገባት ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ የሆነ የኪራይ ዋጋ በማስቀመጥ ለአመልካች ማስጠንቀቂያ የሰጠ መሆን አለመሆኑ ሳይጣራ እንዳለ መውሰድ የሚቻል ሆኖ አይታይም ። ነገር ግን የአካባቢው የሕንጻ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ሚዛነዘዊነቱ፣ ተመጣጣኝነቱ እና ፍትሐዊነቱ ባልተጣራበት ሁኔታ ተጠሪ የቀድሞውን የኪራይ ዋጋ በዕጥፍ በመጨመር በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት ያጣሁት ገቢ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበውን፣ የሥር ፍ/ቤቶች ምንም ማጣሪያ ሳያደርጉ በመቀበል የሰጠበት ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የኪራይ ውል ዘመን ካለቀ በኋላ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ውልን መሰረት ያደረገ የኪራይ ዋጋ ተመን እንደሌለ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ተጠሪ ከሕንጻው ያጣውን ገቢ ለመተመን የኪራይ ልክ መወሰን ያለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2950/2/ መሰረት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት “የኪራይ ልክ በሚያጠራጥር ጊዜ የማዘጋጃ ቤት ባለስጣኖች በወሰኑት ታሪፍ መሰረት ወይም የተወሰነ ታሪፍ የሌለ እንደሆነ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል ይወሰናል” በማለት ደንግጓል፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት እንደሚቻለው የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ ድንጋጌ አግባብ ተጣርቶ የተወሰነ መሆኑን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ለክርክር ምክንያት የሆነው ሕንጻ ያለበት አካባቢ የዚህ ሕንጻ ኪራይ ዋጋ ልክ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ተጣርቶ መወሰን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሕንጻ የሚገኝበት አካባቢ ባለው የገበያ ዋጋ ልማድ መሰረት ሚዛናዊነት እና ፍትሐዊነትን በጠበቀ መልኩ የኪራይ ልክ ተተምኖ መወሰን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የተጠሪን ሕንጻ በፍርድ ተገዶ እስካስረከበ ጊዜ ድረስ ሊከፍል የሚገባው ተጠሪ ያጣውን ገቢ በሚመለከተው ባለሙያ ሳያጣሩ አመልካች እንዲከፍል የወሰኑት የገንዘብ ልክ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የሚከተለከው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 138322 በጥር 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 99152 በሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች የሕንጻው የከራይ ውል ዘመን ካለቀ በኋላ በፍርድ ሕንጻውን እስካስረከበ ጊዜ ድረስ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም ተጠሪ ያገኝ የነበረውን ግን ያሳጣውን ገቢ ለተጠሪ የመክፈል ሃላፊነት አለበት ብለናል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ሕንጻውን ሳያስረክብ ለዘገየበት ጊዜ ተጠሪ ሰጠ በተባለ ማስጠንቀቂያ ላይ የተጠቀሰውን የገንዘብ ልክ ብር 100000.00/መቶ ሺህ/ መሰረት በማድረግ የኪራይ ልክ በመተመን ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህ ጉዳይ በድጋሚ በማየት በፍርድ ሐተታው ውስጥ በተጠቀሰው መሰረት ተጠሪ ለአመልካች አከራይቶት የነበረው ሕንጻ ባለበት አካባቢ የገበያ ዋጋና ልማድ መሰረት ይህ ሕንጻ ከህዳር 9 ቀን 2005 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ በቀን ወይም ወር የኪራይ ልክ ምን ያህል እንደሆነ ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ ተመልሶለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ለደረሰባቸው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
6. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ የሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101631

ጥቅምት 2 ቀን 2008ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ በየነ አሸናፊ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የአማራ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ያሳለፈው የአፈጻጸም ትእዛዝ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በስር የአፈጻጸም ተከሳሽ እንዲሁም የአሁኑ ተጠሪ የአፈጻጸም ከሳሽ ነበሩ፡፡

ግራ ቀኙ በአፈጻጸም ያደረጉት ክርክር ታይቶ በመጨረሻ በተሰጠው ትእዛዝ ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ በሐምሌ 2002 ዓ.ም በወጣው በኃላፊነት የሚነሱ የመንግስት ተሿሚዎች ምደባ አሰጣጥ እና ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ምደባ እንዲደረግ እና በመመሪያው ቁጥር 2.1 አግባብ እንዲፈጸም የተወሰነ በመሆኑ፤ በዚህ መመሪያ መሰረትም ከ3 ዓመት በላይ በሹመት አገልግሎት ከኃላፊነት የተነሳ ከሆነ ይዞት የነበረው ደመወዝ ይዞ ሊቀጥል እንደሚገባ የተደነገገ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፤ በመሆኑም የአፈ/ከሳሽ ይዞት የነበረውን 3348.00 ውሳኔ ከተሰጠበት የካቲት 26/2005 ዓ.ም ጀምሮ ሊከፈለው ይገባል በማለት የአፈጻጸም ተከሳሽ እንዲከፍል ታዟል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ትእዛዝ ላይ አቤቱታ የቀረበበት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር አፈፃፀም ችሎት የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም በማለት አቤቱታውን ሰርዟል፡፡

አመልካች ለዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በዋናው ፍርድ እና በመመሪያው መሰረት የተፈጸመ በመሆኑ፤ የስር ፍ/ቤት ያሳለፈው የአፈጻጸም ትእዛዝ ዋናውን ውሳኔ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ እና ትእዛዙ የመመሪያውን አንቀጽ 2.1 እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 375(1) ሥር የተደነገገውን የስልጣን ወሰን የተላለፈ በመሆኑ እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ተደርጎ በሰጡት መልስ በአፈጻጸም የተላለፈው ትእዛዝ ውሳኔውን እና መመሪያውን መሰረት ያደረገና ተገቢነት ያለው በመሆኑ ቅሬታው ውድቅ ተደርጎ የሥር ፍ/ቤት ትእዛዝ እንዲጸና ጠይቀዋል፡፡ አመልካቹም ክርክራቸውን በማጠናከር የመ/መልስ ሰጥተዋል፡፡

በበኩላችን እንደፍርዱ አልተፈጸመም ተብሎ አመልካች እንዲፈጽም በተሰጠው ትእዛዝ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ከህጉ ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ለአፈጻጸሙ ምክንያት በሆነው ፍርድ እና ውሳኔ የክልሉ የአቅም ግንባታ እና ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ በሐምሌ 2002 ዓ.ም ባወጣው መመሪያ ክፍል ሁለት በቁጥር 2.1 በተመለከተው መሰረት ለአሁን ተጠሪ ባላቸው የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ በሚመጥናቸው መደብ ሊመደቡ እንደሚገባ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞም ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊያገኙ የሚገባው ጥቅማ ጥቅም ሊያገኙ እንደሚገባ ተወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች መ/ቤት የሰው ሀይል ስራ አመራር ደጋፊ የስራ ሂደት የምደባ እና መረጣ ክፍል የፍርድ ውሳኔውን በተመለከተ መጋቢት 18/2005ዓ.ም በተያዘ ቃለ ጉባኤ ተጠሪን በጽ/ቤቱም ሆነ በወረዳው በሚገኙ ጽ/ቤቶች ለመመደብ በትምህርት ዝግጅታቸው የስራ መደብ የጠፋ መሆኑን፤ የሚያሟሉት የስራ ደረጃ በማይገኝበት ጊዜ በመመሪያው ቁጥር 2-2-1 መሰረት ከሚያሟሉት የስራ ደረጃ አንድ ደረጃ ያነሰውን ደመወዝ እየተከፈላቸው በተገኘው ክፍት የስራ ደረጃ እንዲመደቡ እንደሚደረግ፤ በዚህም መሰረት ለተጠሪ የምደባ ቦታ ባለመኖሩ መመደብ እና ጥቅማ ጥቅም ለመስጠት አስቸጋሪ በመሆኑ ከዚህ በፊት በተመደቡበት የስራ መደብ ተመድበው እንዲሰሩ ብሏል፡፡

ይህን ተከትሎ ተጠሪ እንደፍርዱ አልተፈጸመም በማለት አመልካች ደግሞ ተፈጽሟል በማለት ተከራክረው ከላይ የተገለጸው ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው የአፈጻጸም ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

በመሰረቱ አፈጻጸምን ከሚመሩት የስነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው በውሳኔ ባለመብት የሆነ ሰው ፍርዱ ባስገኘለት መብት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ስለሚገባ ሊፈጸም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚችል ውሳኔ እስከቀረበ ድረስ በውሳኔው መሰረት እንዲፈጸም ተገቢው ትእዛዝ መሰጠት ይኖርበታል፡፡ በተለይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392(1) እንደተደነገገው ፍርዱ የማይፈጸምበት ምክንያት ያለመኖሩ ሲረጋገጥ ለአፈጻጸሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ አፈጻጸሙ መመራት ያለበት በዚህ ስርዓት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለስር ፍርዱ መሰረት የሆነው የመመሪያው ቁጥር 2.1 በተከታታይ ሶስት ዓመት እና በላይ በሹመት ላይ ቆይተው በተለያየ ምክንያት ከኃላፊነት የሚነሱ ተሿሚዎች ምደባ የሚደረግላቸው ያላቸው የት/ዝግጅት እና የስራ ልምድ ከግምት ውስጥ ገብቶ በሚያሟሉበት የስራ ደረጃ ላይ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ፍርዱም የተሰጠ በዚህ መሰረት ነው፡፡ ከዚህ በቀር ቅሬታ ባስነሳው የስር ፍ/ቤት ባሳለፈው ትእዛዝ እንደተገለጸው ከ 3 ዓመት በላይ በሹመት አገልግሎት ከኃላፊነት የተነሳ ከሆነ ይዞት የነበረውን ደመወዝ ይዞ ሊቀጥል እንደሚገባ በመመሪያው አልተደነገገም፡፡ ስለሆነም በአፈጻጸም የተሰጠው ትእዛዝ የሥር ፍርዱንም ሆነ ፍርዱ የተመሰረተበትን የመመሪያውን ድንጋጌ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ትእዛዙ ከላይ የተመለከተውን አፈጻጸምን የሚመሩትን የስነ-ሥርዓት ህጉን ድንጋጌዎች የተከተለ ባለመሆኑም የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1ኛ. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 35184 ሚያዚያ 3 ቀን 2006 ዓ.ም ያሳለፈው ትእዛዝ፤ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/አ/መ/ቁ. 39465 ግንቦት 4/2006 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የፍርዱን አፈጻጸም በተመለከተ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ከስር ፍርዱ፤ ለፍርዱ መሰረት ከሆነው መመሪያ፤ አፈጻጸሙ ከሚመራበት ስነ-ሥርዓት እና ተገቢነት ካላቸው ህጎች ጋር በመመርመር ተገቢውን ይወስን ብለናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

3ኛ. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.95537

ጥቅምት 3 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ለሊሴ ደሳለኝ

አመልካች፡- ክራውን ቴክስታይል ዊቪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ቸርነት

ወርደፍ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. ሚድሮክ ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ መክተ ዳኘው ቀረቡ
2. ሠመራ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ የሽጥላ አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር ክርክር መነሻ የሆኑትም የፍርድ ባለመብት በነበረው የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ፣የፍርድ ባለዕዳ በነበረው የአሁኑ አመልካች እና በአፈጻጸም መዝገቡ ላይ “ተጠሪ” ተብሎ በተሰየመው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረውን የፍርድ አፈጻጸም ክርክር የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 107477 በ10/09/2003 ዓ.ም.እና በ29/11/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጣቸው ትዕዛዞች፣እንዲሁም በትዕዛዞቹ ቅር በመሰኘት የስር የፍርድ ባለዕዳ ያቀረበው ይግባኝ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁኖቹን ተጠሪዎች ተቃውሞ በመቀበል በመዝገብ ቁጥር 71612 በ30/03/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን ናቸው፡፡

በ10/09/2003ዓ.ም. የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ፡-

1. የፍርድ ባለዕዳ ለተጠሪ አክሲዮን ድርሻውን /ለሚድሮክ / በውልና ማስረጃ አቅርበው በስምምነቱ መሰረት ፈጽመው እንዲቀርቡ ታዟል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የፍርድ ባለዕዳ መጋቢት 20/2002 በተደረገው የመግባቢያ ስምምነት መሰረት የአክሲዮን ማህበሩን እንዲያሰረክቡ ታዟል፡፡
3. የአክሲዮን እና የኩባንያው ርክክብ እንደተፈጸመ ተጠሪ በስምምነቱ የተገለጸውን 12 ሚሊዮን ብር ለፍርድ ባለመብቱ እንዲከፍሉ ታዟል፡፡ቀጠሮ ውጤት ለመጠባበቅ ቀጠሮ 29/09/2003 በ3፡00 ሰዓት ተቀጠረ፡፡
4. ዳኛ እንዲነሳ በ10/09/2003 በአቶ ምኒልክ ሙሉዓለም በቀረበው አቤቱታ ላይ ብይን ለመስጠት ቀጠሮ 12/09/2003 በ8፡00 ሰዓት ተቀጠረ፡፡

የሚል ሲሆን በ29/11/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው ትዕዛዝ ይዘት ደግሞ ጉዳዩ በዚህ ቀን ለተሰየመው ችሎት የተመራው ቀደም ሲል በ10/09/2003 ዓ.ም. የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሰጡት ዳኛ ከችሎት እንዲነሱ በመደረጉ መሆኑን፣ቀደም ሲል በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ላይ የፍርድ ባለዕዳው ቅሬታ ካለው ለበላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ማሳረም የነበረበት ከመሆኑ በቀር ጉዳዩ የተመራለት በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኝ ችሎት የቀድሞውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ለመቀየር የሚያስችል ስልጣን የሌለው መሆኑን የሚገልጽ እና ቀደም ሲል በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰረት እንዲፈጸም ጉዳዩ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት እንዲተላለፍ መደረጉን የሚያመለክት ነው፡፡

የስር የፍርድ ባለዕዳ ያቀረበው ይግባኝ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁኖቹን ተጠሪዎች ተቃውሞ በመቀበል በመዝገብ ቁጥር 71612 በ30/03/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን መዝገቡን የዘጋው ይግባኙ ያስቀርባል ተብሎ የነበረው በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተገቢነት ለማጣራት ተብሎ መሆኑን፣የፍርድ ባለዕዳው በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠበት የአፈጻጸም ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የጠየቀው በ29/11/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠበትን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በማስታከክ መሆኑን፣ይሁን እና በ29/11/2003 ዓ.ም. የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ቀደም ሲል በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰረት እንዲፈጸም የሚል እንጂ ከቀድሞው ትዕዛዝ የተለየ ባለመሆኑ ምክንያት በ29/11/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ራሱን ችሎ የይግባኝ ምክንያት ሊሆን የማይችል መሆኑን፣ይግባኝ ባዩ ያቀረበው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አለመኖሩን እና የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ሊስተናገድ የሚችልበት የሕግ አግበብ አለመኖሩን በምክንያትነት በመጥቀስ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ10/09/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ዳኝነት ከመስጠቱ በፊት ዳኛው ከችሎት ይነሱልኝ የሚል አቤቱታ የአሁን አመልካች አቅርቦ እንደነበረ በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያስገነዝብ ሆኖ እያለ ዳኛው ከችሎት ሊነሱ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ጉዳይ ላይ ትእዛዝ ከመሰጠቱ በፊት ዳኛው በዋናው ጉዳይ ላይ ትዕዛዝ መስጠታቸው እስከታወቀ ድረስ ለይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው መነሻ ተደርጎ መያዝ የሚገባው ጉዳዩን ቀደም ሲል ባዩት ዳኛ በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠውን ትዕዛዝ ለመለወጥ የሚያስችል ስልጣን የለኝም በማለት በኃላ ላይ ጉዳዩ የቀረበለት ችሎት በ29/11/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ትዕዛዝ የሰጠበት ቀን ሳይሆን የመጀመሪያው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሰጠበት ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም. ነው በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በ30/03/2006 ዓ.ም. የተሰጠውን ዳኝነት አግባብነት ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 207 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አንጻር ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ ከመሆኑም በላይ በ02/10/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የቃል ክርክር አድርገዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ይግባኙ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ካለፈ በኃላ የቀረበ በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን ሕጋዊ መሰረት ያለው መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልች አጥብቆ የሚከራከረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ10/09/2003 ዓ.ም. የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሰጠው ትዕዛዙን የሰጡት ዳኛ ከችሎት እንዲነሱ ጥያቄ ካቀረብን በኃላ አመልካች የትዕዛዙን መሰጠት ማወቅ በማይችልበት ሁኔታ በመሆኑ የትዕዛዙን መሰጠት ያወቅነው በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ፈጽመን እንድንቀርብ በ14/11/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ከደረሰን በኃላ ነው፣በ10/09/2003 ዓ.ም. ትዕዛዝ የተሰጠው የፍርድ ባለዕዳው እንደፍርዱ የማይፈጽምበትን ምክንያት በወከላቸው የሕግ ባለሙያዎች አማካይነት ቀርቦ ተገቢውን መከራከሪያ እንዲያቀርብ ሳይደረግ ከስረ ነገሩ ስምምነት ይዘት ውጪ በመሆኑ ይኸው የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲታረምልን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 207 ድንጋጌ መሰረት ያቀረብነው ጥያቄ በ29/11/2003 ዓ.ም. ተቀባይነት ያጣውም አላግባብ ነው፣ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የይግባኝ ጊዜው አልፎበታል በማለት የያዘው አቋምም የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 207 እና 320 (2) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነው በማለት ሲሆን ተጠሪዎቹ በበኩላቸው በ10/09/2003 ዓ.ም. የአፈጻጸም ትዕዛዙ የተሰጠው የፍርድ ባለዕዳው ተወካዮች ጭምር ባሉበት እና ክርክራቸውንም ካሰሙ በኃላ ነው፣ ዳኛው ከችሎት እንዲነሱ የፍርድ ባለዕዳው በ10/09/2003 ዓ.ም. ጥያቄ ያቀረበውም በዕለቱ የተሰጠበትን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ዳኛው በችሎት ከገለጹ በኃላ ነው፣ትዕዛዙም ሊለወጥ ወይም ሊታረም የሚገባው በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንጂ በዚያው ትዕዛዙን በሰጠው ፍርድ ቤት ባለመሆኑ የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ አልፎአል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚል በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን ሊነቀፍ አይገባውም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ዳኛው ክችሎት እንዲነሱ በ10/09/2003 ዓ.ም. አቤቱታ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ እስከ 14/11/2003 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ በመዝገቡ ላይ የተለያዩ ትዕዛዞች ሲሰጡ የቆዩት ዳኛው ክችሎት እንዲነሱ ከቀረበው ጥያቄ ጋር በተያያዘ ጉዳይ መሆኑን የከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡አመልካች በ10/09/2003 ዓ.ም. የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሰጠብኝ መሆኑን ያወቅሁት በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ፈጽሜ እንድንቀርብ በ14/11/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ከደረሰኝ በኃላ ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም አመልካቹ ጉዳዩን በማየት ላይ የነበሩት ዳኛ ክችሎት እንዲነሱ በ10/09/2003 ዓ.ም. ጥያቄ ያቀረበው ዳኛው የአፈጻጸም ትዕዛዙን ከሰጡ በኃላ እና የትዕዛዙን መሰጠትም እያወቀ ስለመሆኑ ዳኛው ክችሎት እንዲነሱ በ10/09/2003 ዓ.ም. አዘጋጅቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 8ኛ የፍትሐብሔር ቀጥታ ክስ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ በግልጽ እና በማያሻማ ሁኔታ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ዳኛው ክችሎት እንዲነሱ ጥያቄ ያቀረብኩት የአፈጻጸም ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት እና የትዕዛዙን መሰጠት ሳላውቅ ነው በማለት አመልካቹ ያቀረበው የክርክር ነጥብ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተደረገውን የክርክር ሂደት መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል የፍርድ ባለዕዳው እንደ ዕርቅ ስምምነቱ የማይፈጽምበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ተጠርቶ በቀረበበት ቀን የፍርድ ባለዕዳውን ወክለው የቀረቡት ስራ አስኪያጅ ናቸው የተባሉት አቶ ምኒልክ ሙሉዓለም እና ሁለት ጠበቆች መሆናቸው አላከራከረም፡፡በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው የቃል ክርክር እንደ ስምምነቱ የማይፈጽምበትን ምክንያት እንዲያስረዳ የፍርድ ባለዕዳው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠርቶ ምክንያቱን በጠበቆቹ አማካይነት እያስረዳ በነበረበት ሂደት ከፍርድ ባለዕዳው ጠበቆች አንዱ ከችሎት እንዲወጡ በችሎቱ ታዘው መውጣታቸውን እና ሌላኛው ጠበቃም እንዲቀመጡ ታዘው መቀመጣቸውን በመግለጽ የአመልካቹ ጠበቆች እና ተወካዮች የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎቹ በበኩላቸው አንዱ ጠበቃ ከችሎት የወጡት በራሳቸው አነሳሽነት እንጂ በችሎቱ ትዕዛዝ እንዳልሆነ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡የፍርድ ባለዕዳው ሁለቱ ጠበቆች ረዥም ንግግር በማድረግ ንግግር ሊያቆሙ ባለመቻላቸው እንዲቀመጡ እና ስራ አስኪያጁ አቶ ምኒልክ ሙሉዓለም ባለዕዳው እንደፍርዱ የማይፈጽምበትን ምክንያት እንዲያስረዱ የተደረገ ስለመሆኑ ዳኛው ክችሎት የሚያስነሳቸው በቂ ምክንያት አለመኖሩን ገልጸው በ12/09/2002 ዓ.ም. በሰጡት ትዕዛዝ ላይ ገልጸዋል፡፡

በመሰረቱ የአፈጻጸም ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለአፈጻጸሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርድ እንዲፈጸም ትዕዛዝ የሚሰጠው የፍርድ ባለዕዳውን ጠርቶ ከመረመረው በኃላ እንደፍርዱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይፈጸምበት ምክንያት አለመኖሩን ካረጋገጠ በኃላ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 392 (1) ላይ ተመልክቶአል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ለሚደረግ ምርመራ የሚሰጠው ምላሽ ደግሞ የፍሬ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሕግ ጭምር ሊሆን እንደሚችል የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሁኔታዎች ተገናዝበው ሲታዩ በሕግ ጠበቆቹ ሳልወከል በቁጥር 392 (1) የተደረገው ምርመራ መሰረት ተደርጎ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠብኝ ትዕዛዝ ከስነ ስርዓት ውጪ በመሆኑ በቁጥር 320 (2) ድንጋጌዎች 207 ድንጋጌ መሰረት ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት በዚያው ፍርድ ቤት ሊታረም የሚገባው ነው የሚል በፍርድ ባለዕዳው ላይ እምነት ሊያሳድሩቡት የሚችሉ አይደሉም ከሚል የተረጋገጠ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ ሆነው አልተገኙም፡፡ጉዳዩም የስረ ነገር ሳይሆን የአፈጻጸም ክርክር ነው፡፡አመልካቹ በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲታረምለት የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 207 ድንጋጌን ጠቅሶ በጽሁፍ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው አቤቱታ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክተው ነገር ባይኖርም በ28/11/2003 ዓ.ም. ግራ ቀኙ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ያስመዘገቡት ክርክር ይዘት ሲታይ አመልካች በዚህ ረገድ በቃል ክርክሩም ቢሆን ጥያቄ አቅርቦ የነበረ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ፍርድ ቤቱ በ29/11/2003 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ ላይ በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ሊታረም የሚችለው በበላይ ፍርድ ቤት እንጂ በራሱ በዚህ ፍርድ ቤት አይደለም የሚል ይዘት ያለው ትችት ማስፈሩም አመልካቹ የእርማት ጥያቄ ማቅረቡን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦ የነበረ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው መቆጠር መጀመር የሚገባው ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በዚያው ፍርድ ቤት ሊታረም የማይችል መሆኑን ገልጾ በቀድሞው ትዕዛዝ መሰረት እንዲፈጸም ትዕዛዝ ከሰጠበት ከ29/11/2003 ዓ.ም. ነው፡፡ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ይግባኙ የቀረበው በሕግ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ነው፡፡

ሲጠቃለል ይግባኙ የቀረበው የይግባኝ ማቅረቢያው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኃላ በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. ይግባኙ የቀረበው የይግባኝ ማቅረቢያው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኃላ በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 71612 በ30/03/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ከላይ በውሳኔው ዝርዝር ውስጥ በተገለጸው መሰረት የይግባኝ ጊዜው ያላለፈ መሆኑን በመገንዘብ የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 (1) መሰረት ጉዳዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
3. ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይላክ፡፡
4. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 110681

ቀን 08/04/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሀዋ ጀሬ ተወካይ ታጁ ጀሬ

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ ቀንጨራ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን ቀደም ሲል በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረውን የባልና ሚስት ክርክር ተከትሎ የተሰጠውን የፍቺ እና የንብረት ክፍፍል ውሳኔ መሰረት በማድረግ ተጠሪ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ሞያሌ ወ/ፍ/ቤት የንብረት ክፍፍል ውሳኔን ለማስፈጸም የአፈጻጸም አቤቱታ አቅርበው የአፈጻጸም መዝገብ አስከፈተዋለው፡፡ የአፈጻጸም ችሎቱ የቤቱን ደርሻ ክፍፍል በተመለከተ ግራ ቀኙ ስላልተሰማሙ ቤቱ በግልጽ ጨረታ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ በሚፈቅድው መሰረት ተገቢው ማስታወቂያ ተደርጎ በጨረታ ተሸጦ እኩል እንዲካፈሉ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የጨረታውን ውጤት ለመጠባበቅ በተያዘው ቀጠሮ በቀን 21/01/2007 ዓ/ም ጨረታውን እንዲያስፈጽም የታዘዘው የከተማው አስተዳደር መሐንዲስ ፍ/ቤት በአካል ቀርቦ ለጨረታ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ብዙ ተወዳዳሪዎች ስላልቀረቡ እና በስህተት የጨረታ መነሻ ዋጋ ስላላወጣን ሌላ ቀጠሮ ይሰጠን በማለት ለአፈጻጸም ችሎቱ ሲያመለክት ችሎቱ የቤቱን የጨረታ መነሻ ዋጋ ብር 140,500 (አንድ መቶ አርባ አምስት መቶ ብር) ሆኖ ግልጽ ጨረታ በማወጣት ለ10 ቀን ማስታወቂያ አየር ላይ አቆይቶ ቤቱን በጨረታ በመሸጥ ውጤቱ በቀን 21/01/2007 ዓ/ም እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ቤቱ በጨረታ በብር 210,000 (ሁለት መቶ አስር ሺህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብር) አሸናፊ ለሆኑት አቶ መሐመድ ጀሎ መሸጡን የጨረታ ኮሚቴም በቀን 16/3/07 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ ጉባኤ ለፍ/ቤቱ አስታወቋል፡፡ በቃለ ጉባኤው ላይ የአሁኑ አመልካችን ጨምሮ 3 ተወዳዳሪዎች ቀርበው አቶ መሐመድ ጀሎ በብር 210,000 ያሸነፉ መሆኑ የተመለከት ሲሆን ተጠሪ ደርሻቸውን ብር 105,000 በማመልከቻ ላይ ፈርሞ መወሰዱን እና የአሁኑ አመልካች ድርሻ ገንዘባቸው ሌሎች እኩል ተከፈሉ የተባሉ ዕቃዎች ግምት እስከከፈለኝ ድረስ ይህን ገንዘብ አልወሰደም ማለታቸው ስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ ቤቱን በጨረታ በአሸናፊው አቶ መሐመድ ጀሎ ስም እንዲዛወር ችሎቱ ተዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች (የስር የአፈጻጸም ከሳሽ) በዚህ አፈጻጸም ላይ ያላቸውን ቅሬታ ለማሳረም ለቦረና ዞን ከፍ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በማለት አቤቱታውን አልተቀበለውም፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን በመዘርዘር አቤቱታ አቅርበዋል የአቤቱታው ይዘት በጨረታው ለማስተፍ ለስር ፍ/ቤት አመልካች ፍ/ቤቱ ፈቅደልኝ ተሳትፈያላው የሞያሌ ወ/ፍ/ቤት የጨረታ ማስታወቂያ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ወር ድረስ ቆይቶ የጨረታው ሽያጭ እንዲካሄድ ማዘዝ ሲገባው ለ10 ቀን ብቻ አየር ላይ ማሲታወቂያው እንዲቆይ የሰጠው ትእዛዝ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.426 ውሳኔ ነው አመልካች ከጨረታ መነሻ ዋጋ ላይ በመጨመር 300,000 ብር ግምት የተጠሪን ድርሻ ብር 150,000 ካፍዬ ቤቱን እንዳሰቀር ለሐራጀ ሻጩ የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ ከማወጣቱ በፊት አስቀደሜ አስወቂው እያለ ያለ ምንም የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ በጨረታ ተወዳዳሮ ለአሸነፈው ሰው በብር 210,000 መሸጡ የጨረታ ሽያጭ ሂደቱ ስነ ስርዓቱን ያልተከተለ እና የተጭበረበረ በመሆኑ መብቴን የሚጎዳ ነው፡፡ የተጠሪን ድርሻ ብር 150,000 ከፍዬ ብር 300,000 ግምት ቤቱን ለማስቀርት ጨረታው ይፍረስልኝ ብዬ ያቀረብኩትን መቃወሚያ ያለበቂ ምክንያት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የማይነቀሳቀስ ንብረት የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ ለ30 ቀናት አየር ላይ እንዲቆ መደረግ እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.426 አስገዳጅ ደንጋጌ እያለ የስር ፍ/ቤት ማስታወቂያው ለ 10 ቀን አየር ላይ እንዲቆይ ማደረጉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት የቤቱ የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ ከአንድ ወር በላይ አየር ላይ ቆይቷል፡፡ አመልካች በጨረታው ለመወዳደር ያቀረበችው ብር 150,000 ብቻ ነው የሚል ሲሆን አመልካች በመልስ መልሳቸው አመልካች ብር 150,000 በጨረታው ላይ የጠቀሰኩት የተጠሪን ድርሻ እንጂ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሙሉውን የጨረታ ዋጋ አይደለም፡፡ የመጀመሪያው ጨረታ ማስታወቂያ የቆየው ለ15 ቀን ሲሆን የሞያሌ ከተማ መሀንዲስ ተለዋጭ ትእዛዝ እንዲሰጠው ለስር ፍ/ቤት በጠየቀው መሰረት የጨረታ ማስታወቂያው ለ10 ቀን አየር ላይ እንደወል ትእዛዝ የሰጠ መሆኑን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የሰር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ ጋር በማገናዘብ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ እንዲጣራ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለክርክር ምክንያት በሆነው የቤት ሽያጭ ጨረታ ላይ አመልካች ፍ/ቤቱን አስፈቅደው በጨረታው የተሳተፉ ሲሆን በጨረታው ከተሳተፉ ተጨርቶች መካከል አቶ መሐመድ ጅሎ የተባሉ ተጨራች በብር 210,000 ጨረታውን ያሸነፉ መሆኑን እና አመልካቿ በጨረታው ሲሰተፉ ቤቱን በጨረታ ለመግዛት የገለጹት ዋጋ ብር 300,000 ሳይሆን ብር 150,000 ብር ነው ብር 150,000 የጠቀሱት የተጠረን ድርሻ እንደሆነ በመልስ መልሳቸው የገለጹ ቢሆንም በእርግጥም ቤቱን በ300,000 ብር በጨረታ አሸንፈው የተጠሪን ድርሻ ብር 150,000 ለመክፈል አሰበው ቢሆን በጨረታው ለመወዳደር መጥቀስ የነበረባቸው ብር እንጂ 150,000 ባለመሆኑ በዚህ ረገድ ያነሱት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ የአፈጻጸም ሂደቱ በተካሄደበት የስር ፍ/ቤት ከጨረታው ውጤት በኋላ አመልካች ከቤቱ ሽያጭ ድርሻቸውም ብር 105,000 ለመወሰድ ፈቃደኛ ያልሆኑ በሰበር አቤቱታቸው ላይ እንደገለጹት ሳይሆን ሌሎች ከተጠሪ ጋር እንዲከፍሉ ውሳኔ የተሰጠባቸው ዕቃዎች ግምት እንዲከፍላቸው ድርስ ገንዘቡን አልቀበልም ማለታቸው በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል አመልካች ለቦረና ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ የጨረታ ማስታወቂያ ለአንድ ወር አየር ላይ ሳይቆይ መሸጡን በመቃወም ሳይሆነ በጨረታው እና ብር 300,000 አቅርቤ እያለ በብር 210,000 መሸጡ ተገቢ አይደለም የተጠሪን (የመልስ ሰጪን) ድርሻ ብር 150,000 ካፍዬ ቤቱን እንድወሰድ የወሰንልኝ የሚል መሆኑን ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ተመልክቷል፡፡

አመልካች አፈጻጸሙ በተጀመረበት ቦረና ዞን የሞያሌ ወረዳ ፍ/ቤት የጨረታ ማስታወቂያው ለአንደ ወር አየር ላይ አልቆየም በማለት የተቃወመ መሆኑን በይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍ/ፍ/ቤት ይህን መቃወመያ ያነሱ መሆኑ በውሳኔው ላይ አልተመለከተም፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት በጨረታው እንዲሳተፉ ተፈቀደላቸው በጨረታው በብር 150,000 ተወዳደረው ከአመልካች ጋር ተወዳደርው አሸናፊ ለሆነው ተጨራች በብር 210,000 መሸጡን አረጋግጠናል አመልካች በስር ፍ/ቤቶች በነበራቸው ክርክር የጨረታ ማስታወቂያ ለአንድ ወር አየር ላይ አልቆየም በማለት ያነሱት መቃወሚያ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተመለከተ ባይሆንም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንስተወት እንኳ ቢሆን በአመልካቿ መብት ላይ ቀጥታ ጉዳት ያደረሰ ወይም የሚያደርስ መሆኑ አልተረጋገጠም በመሆኑም በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.445 መሰረት ጨረታ ሽያጩ ሊፈርስ አይገባም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን የሞያሌ ወ/ፍ/ቤት በፋ/ቁ. 04295 ከፍ/ፍ/ቤት በፋ/ቁ.10915 በቀን 25/04/2007 ዓ/ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በፋ/ቁጥር 199719 በቀን 17/06/07 በዋለ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ላደረጉት ክርክር ያወጡትን ወጪ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገብ ዕልባት ያገኘ በመሆኑ በቀን 8/07/2007 ዓ/ም በዋለ ችሎት የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል ይጻፍ ብለናል መዝገቡ ዕልባት ያገኘ በመሆኑ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 103787

ቀን ታህሳስ 21/2008ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- የኢት/ያ ገ/ጉ/ባለስልጣን ሚሌ ቅ/ጽ/ቤት -ዓ/ሕግ መለስ ማእከል

ተጠሪ፡- ፉአድ ደኑር ሁሴን -ወኪል ጠይብ አህመድ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በግራቀኙ መካከል በፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ ምክንያት ያቀረቡትን ክርክር የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ አመራርም ሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ዳኝነት አፈጻጸም ፍርድን መሰረት ሊያደርግ እንደሚገባ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ያቀረበው የአፈጻጸም ክስ በአፋር ብ/ክ/መንግስት የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 4043 ታህሳስ 28ቀን 2006ዓ.ም የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም እንደሆነ ግራቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

በዚህም ውሳኔ የአሁን ተጠሪን ባለመብት፤ የአሁን አመልካችን ባለዕዳ ለማድረግ የሚያስችለው በዚሁ በፍ/መ/ቁ. 4043 ታህሳስ 28ቀን 2006ዓ.ም የተሰጠው የፍርድ ክፍል የአሁን ተጠሪ ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገባቸው ፈቃድ አግኝቶ በዲክላራሲዮን ለተዘረዘሩት 9አይነት እቃዎች 5አይነት እቃዎች ካርታ ከተፈቀደ እቃዎች ውጭ በመሆናቸው ወደ ሃገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ አይደለም፡፡ ስለሆነም አሁን አመልካች በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተጠቅሞ ተገቢ የሆነውን አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥ ይህንን የማይፈጽም ከሆነ ደግሞ ቀደም ሲል ለእቃዎቹ ከተከፈለው ቀረጥና ታክስ 5% ተቀጥቶ እቃዎች ወደ መጡበት ሃገር እንዲመለሱ የአሁን ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዲክላራሲዮኑ መሰረት ያስገባቸው በዲክላራሲዮኑ የተዘረዘሩት ህጋዊ እቃዎች ደግሞ ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡ በሚል የተሰጠው ውሳኔ ነው፡፡

ይህ ውሳኔ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ያልተለወጠ ስለመሆኑም ግራቀኙ የተማመኑበት ጉዳይ ነው፡፡

እንግዲህ ለዚህ ሰበር መነሻ ለሆነው በአፈጻጸም መ/ቁ. 4043 ለሆነው የአፈጻጸም ጉዳይ ምክንያት የሆነው ይህንኑ ከላይ የተመለከተውን ፍርድ ለማፈጸም እስከሆነ ድረስ በዚሁ ፍርድ የፍርድ ባለመብት የሆነው የአሁን ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ ሆኖ በተሰየመው በአሁን አመልካች ላይ ሊያቀርብ የሚገባው የፍርድ ማስፈጸሚያ አቤቱታ ይዘት ይህንኑ ከላይ የተጠቀሰውን ፍርድ ለማስፈጸም የፍርዱን ይዘት በአፈጻጸም ማመልከቻው ላይ በመግለጽና የፍርዱንም ግልባጭ በማስረጃነት በማያያዝ ሊሆን እንደሚገባው የአፈጻጸም ክስ አዘጋጀጀት እና የአፈጻጸም ክስ ጉዳይ አጀማመርን አስመልቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 የተመለከተው ድንጋጌ አስረጂ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በአፈጻ/መ/ቁ. 4043 ተሰይሞ ለቀረበው የአፈጻጸም ጉዳይ መነሻ ይሆን ዘንድ የአሁን ተጠሪ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 በሚያዘው መሰረት ታህሳስ 04ቀን 2006ዓ.ም በተጻፈ የአፈጻጸም ክስ ማመልከቻ ያቀረበው የአፈጻጸም ክስ አቤቱታ ይዘት ወይም ፍሬ ቃሉ በአፈጻጸም ክሱ ምክንያት የሆነውን ፍርድ ይዘት የሚጠቅስ፤ በማስረጃነትም ይህንኑ የፍርድ ግልባጭ አባሪ በማድረግ መሆን ሲገባው በዚሁ ታህሳስ 04ቀን 2006ዓ.ም በተጻፈው የአፈጻጸም የክስ ማመልከቻ የተገለጸው ከፍርዱ ውጭ በፍርድ ያልተካተተውን ሁሉ በመጨመር <<በስህተት ወደ አገር ውስጥ ለገቡት እቃዎች የተከፈለው 5% ቀረጥና ታክስ የፍርድ ባለመብት ተቀጥቶ እቃዎቹ ወደመጡበት አገር እንዲመለሱ እንዲሁም የአሁን አመልካች በሰጠው ፈቃድ (declaration) መሰረት ቀሪ ህጋዊ እቃዎችን ወደ ሃገር ውስጥ እንዲያስገባ የተወሰነልን ቢሆንም በስህተት ወደ ሃገር ውስጥ የገቡት እቃዎች በተከሳሽ እምቢተኛነት በአፋጣኝ ወደ መጡበት ሃገር ባለመመለሳቸው፡፡ በፍርድ ባለዕዳ እጅ የሚገኙት እቃዎች የተበላሹ በመሆኑ የወቅቱ የእቃዎች ዋጋ ተገምቶ ገንዘቡን እንዲከፍል ይታዘዝልኝ>> በማለት የቀረበ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በፍርድ ባለመብት አማካኝነት የተፈረደን ፍርድ ለማስፈጸም የቀረበው የአፈጻጸም የክስ ማመልከቻ ይፈጸም የተባለውን ፍርድ መሰረት ሊያደርግ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ይኸው ፍርዱን መሰረት ያላደረገ የአፈጻጸም ማመልከቻ መቅረቡን እንደተረዳ የአፈጻጸም ችሎቱ የፍርድ ባለእዳን ከመጥራቱ በፊት ይህንኑ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ የአፈጻጸም ማመልከቻ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ማድረግ ይገባው ነበር፡፡

ይህም ታልፎ የአሁን አመልካች በፍርድ ባለእዳነቱ መልስ እንዲሰጥ እንደተጣራ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 386 እንደተመለከተው እቃዎቹ ያልተበላሹ፣ እንዲሁም እቃዎች ወደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጡበት ሃገር አንዲመልሱ እንጂ በፍርድ ባለመብት እንዲወሰዱ በሚል ባልተወሰነበት ሁኔታ የእቃዎችን ግምት መጠየቃቸው ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ማሰባቸውን የሚያመለክት ነው የሚለውን ሁሉ ጨምሮ መልሱን በይዘቱ የአፈጻጸም ማመልከቻው ፍርዱን መሰረት ያደረገ ስላልሆነ እንደጥያቄው እንዲፈጸም አልገደድም በማለት መልሱን የሰጠ መሆኑንም የስር ፍ/ቤቱ እንደተረዳ የአፈጻጸም ማመልከቻውን፤ ለማመልከቻው በፍርድ ባለእዳው የተሰጠውን መልስ፣ በአፈጻጸሙ ጉዳይ ምክንያት ከሆነው በመ/ቁ. 4043 ታህሳስ 28ቀን 2006ዓ.ም ከተሰጠው የፍርድ ይዘት ጋር በማገናዘብ ክርክሩ በደረሰበት ደረጃም ቢሆን የፍርድ ባለመብት በአፈጻጸም ችሎቱ እገዛ እንዲፈጸምላቸው በክስ ማመልከቻው ያቀረቡት ዝርዝር እና የጠየቁት ዳኝነት ለፍርዱ አፈጻጸም መነሻ የሆነውን ፍርድ ምርኩዝ ያላደረገ መሆኑን ገልጾ ዳኝነት መስጠት ሲገባው ከፍርዱ አድማስ ውጭ በመውጣት እቃዎች ተበላሽተው የተገኙ ከሆነ የፍርድ ባለእዳ በምትኩ የእቃዎችን ግምት ዋጋ ሊከፍል ይገባል በሚል በአማራጭ ፍርድ ያረፈበት በማስመሰል አሁን የአሁን አመልካች የእቃዎችን ግምት ዋጋ ብር 4,732,278.64 /አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ስምንት ከ64%/ እና በዚሁ የገንዘብ ግምት ልክ 10% የጠበቃ አበል የአሁን አመልካች ለአሁን ተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ስለፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ አመራር ከተዘረጉት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378,386,391 አንጻር ሲታይ ህጋዊ መሰረት ያለው ዳኝነት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ምናልባት የአሁን ተጠሪ በመ/ቁ. 4043 ታህሳስ 28ቀን 2006ዓ.ም በተወሰነበት ውሳኔ መሰረት እቃዎችን ወደመጡበት ሃገር ለማስመለስ በፍርድ አፈጻጸም ችሎት እገዛ ጥያቄ አቅርቦ እንደፍርዱ ለማስፈጸም ጥረት ሲደረግ ወደ መጡበት ሃገር ይመለሱ የተባሉት እቃዎች ተበላሽተዋል ካለ፤ የፍርድ ባለእዳም ለአፈጻጸም ክሱ በሰጠው መልስ ላይ አልተበላሹም በማለቱ እቃዎች ተበላሽተዋል ወይስ አልተበላሹም? የሚለውን ጭብጥ የስር ፍ/ቤት በአፈጻጸም ጉዳዩ እንደሰጠው ዳኝነት እቃዎችን በማስፈተሽ እምቢተኛ እስከሆነ ድረስ እቃዎቹ እንደተበላሹ ይቆጠራሉ እንኳ ቢባል እቃዎቹ ተበላሽተው የተገኙ እንደሆነ የሚለውን ታሳቢ በማድረግ አማራጭ ክስ ያልቀረበበት፤ በዋናው ፍርድም እቃዎቹ ተበላሽተው የተገኙ እንደሆነ የአሁን አመልካች የእቃዎችን ዋጋ ግምት እንዲከፍል ይገደዳል በሚል ፍርድ ያላረፈበት በመሆኑ ፍርድ ያላረፈበትን ጉዳይ በአፈጻጸም ክስ አስታኮ በአፈጻጸም ጉዳይ ላይ እንደአዲስ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፡፡

ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ለአሁን አመልካች እንደፍርዱ እቃዎችን ወደ መጣበት ሃገር እንዲመለሱ ለማድረግ እምቢተኛ በመሆኑ የተነሳ እቃዎቹ ተበላሽተው ከሆነ ይኸው ስህተት የአሁን አመልካች ከህግ ወይም ከውል በመነጨ ለመክሰስ የሚያስችል ግዴታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለበት ከሆነ እራሱን ከቻለ ክስ የክስ ምክንያት ሊሆን ከሚቻል በቀር ከቶውንም ቢሆን እንደአሁን ተጠሪ አቀራረብ በፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ ለመወሰን የሚቻል አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የአሁን ተጠሪ ታህሳስ 04 ቀን 2006ዓ.ም አዘጋጅቶ በቀረበው የአፈጻጸም የክስ ማመልከቻ መሰረት የስር ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈጻጸምን የጉዳይ ሂደት ለፍርድ አፈጻጸም አንኳር እና መሰረት የሆነውን አፈጻጸም እንደፍርዱ ሊፈጸም እንደሚገባ በፍርድ አፈጻጸም ስርዓት የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ጥሰው ለአፈጻጸም ክሱ መነሻ ከሆነው ፍርድ ይዘት በመውጣት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአፋር ብ/ክ/መንግስት የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአፈ/መ/ቁ. 4043 መጋቢት 12ቀን 2007ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በአፈጻጸሙ 4,732,278.64 /አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ሰላሳ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ከሰባ ስምንት ከ64%/ ሳንቲም እና በዚሁ ልክ የጠበቃ አበል 10% ጨምሮ በድምሩ ብር 5,205,504.00 /አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምስት ሺህ አምስት መቶ አራት ብር/ የመክፈል ግዴታ ስለመሆኑ ለተጠሪ እንዲከፍል አይገደድም ብለናል፡፡
2. ወደ መጡበት ሃገር ይመለሱ የተባሉት እቃዎች በመበላሸታቸው ምክንያት እንደፍርዱ ለመፈጸም የሚቻል አይደለም ከሚል መነሻ የአሁን ተጠሪ መብቱን በማረጋገጥ ረገድ ወደ ፊት ክስ የሚያቀርብ ቢሆን ይህ ፍርድ የሚያግደው አይሆንም ብለናል፡፡
3. በዚሁ የሰበር ጉዳይ ምክንያት ግራቀኙ ባደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 103826

ቀን 25/01/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

አመልካች፡- አንዋር አህመድ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የቤ/ጉ/ክ/መ/ፍትህ ቢሮ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአፈፃፀም ክስ ሂደትን የተመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ከፓዊ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የፓዊ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት የፍርድ ባለመብት በመሆን በአመልካች ላይ ያቀረበው የአፈፃፀም ክስ ሲሆን ዝርዝሩም አመልካች ያለፈቃድ በማሽከርከር በቀን 12/6/2005 - 13/06/2005 ዓ.ም የትራፊክ ደንብ በመጣስ 5000 ብር የተቀጣ ስለሆነ በቅጣቱ መሰረት ይፈጽምልኝ በማለት አቅርቧል፡፡ አመልካችም ያለአግባብ ስለተቀጣሁ ልፈፅም አይገባም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የፓዊ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች በውሳኔው መሰረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ስለአልሆነ በስድስት /6/ ወር/ እስራት እንዲቀጣ ገንዘቡን የሚከፍል ከሆነ ደግሞ ከእስራት እንዲፈታ በማለት ይወስናል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርቡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የሕዝብ የመንገድ ትራንስፖርት የስነ ስርዓት መቆጣጠሪያ መመሪያ ስራ ጥፋት ሪኮርድ አያያዝና ስለቅጣት ደረጃ በዝርዝር የሚገልፅ እንጅ ይህ ቅጣት ባልተፈፀመ ጊዜ ምን መደረግ እንዳለበት በሕጉ የተገለጸ ነገር ስለሌለ በፍ/ቤት የተሰጠ ምንም ውሳኔ ሳይኖር አመልካች እንዲፈፅም መደረጉ ትክክል አይደለም በማለት ወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለክልሉ /የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱም በሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 377 መሰረት ይግባኙን በመሰረዝ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ ሲቀርብ ሰበር ችሎቱም የፓዊ ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የመንገድ ትራንስፖርት መመሪያን ደንብን በመተላለፍ የቀረበበትን የአፈፃፀም ክስ ማስፈፀሙ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፓዊ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ወስኖአል፡፡

አመልካችም ለዚህ ሰበር ችሎት በቀረቡት የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለአለበት ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ በትራፊክ ደንብ መተላለፍ ምክንያት በአመልካች ላይ የተጣለውን ቅጣት በፍርድ ቤት የአፈፃፀም ክስ ሊቀርብበት ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጎአል አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርመረናል፡፡ አመልካች ላይ የቀረበው የአፈፃፀም መዝገብ በትራፊክ ደንብ መተላለፍ ምክንያት ስራን የትራፊክ ደንብን መተላለፍ የሚገዛው ትራፊክን ለመቆጣጠር የወጣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 ነው፡፡

በዚህ ደንብ አንቀፅ 85 ስለ ቅጣቱ እና አፈፃፀሙን የደነገገ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 85/2/ መሰረት የትራፊክ ተቆጣጣሪ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ ያገኘው አሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን እንዲሰጠው በመጠየቅ ቅጣት እንዲፈፅም በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት በማለት ደንግጎአል፡፡ በዚህ ደንብ መሰረት ይህን አዋጅ የተላለፈ አሽከርካሪ ቅጣት ከተጣለበት አፈፃፀሙ የትራፊክ ተቆጣጣሪው በፅሁፍ በማሳወቅ የተቀጣው አሽከርካሪ እንዲፈፅም ማድረግ ነው እንጅ ለአፈፃፀም ፍ/ቤት የሚቀርብ ስለመሆኑ በደንቡ አልተቀመጠም፡፡ ከደንቡ እንደምንረዳው በትራፊክ ተቆጣጣሪው በዛ ሂደት እንዲቀጥል እንጂ ፍ/ቤት ለአፈፃፀም እንዲቀርብ አይደለም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378/1/ የተደነገገው በፍ/ቤት አፈፃፀም የሚፈፀመው ውሳኔው በፍ/ቤት የተወሰነ መሆኑን ታሳቢ የደረገ ነው፡፡ በመሆኑም የትራፊክ ፍሰትን ለመቆጣጠር ሲባል በደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 85 መሰረት የሚጣስ ቅጣት አፈፃፀሙ በፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችል መሆኑን የሚደነግግ ሕግ የለም፡፡ ይህ ሆኖ እያለ በተጠሪ በኩል የቀረበውን የአፈፃፀም ማመልከቻ ውሳኔው በፍ/ቤት ባልተሰጠበት ሁኔታ እንዲሁም በደንብ ቁጥር 208/2003 አፈፃፀሙ ለፍ/ቤት መቅረብ እንደአለበት ሳይደነግግ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ሰበር ችሎት በትራፊክ ተቆጣጣሪ የተጣለው ቅጣት በፍ/ቤት ሊፈፀም ይገባል በማለት የወሰነው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብለን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 05033 ሚያዝያ 27/2006 በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የፓዊ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06041 በቀን 22/09/2005 በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በማፅናት የወሰነውን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የመከተል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09 በቀን 28/10/2005 በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ /በአብላጫ ድምፅ/ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
3. እዚህ ፍ/ቤት ለተካሄደው ክርክር ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊረማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 103458

ቀን 27/01/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ተፈሪ ገብሩ

ሹምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ጋረድ ለበሰ

ተጠሪ፡- የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጡረታ መብትን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በተለያዩ መ/ቤቶች ለ17 ዓመት እና በአ/ብ/ክ/መንግስት ዋና አዲተር መ/ቤት ኃላፊ ሆነው ለ10 አመት አገልግለው በራሳቸው ጥያቄ ከሹመት የተነሱ መሆኑን በአዋጅ ቁ 714/2003 አንቀፅ 19/5/ መሰረት ከአንድ የምርጫ ዘመን ያገለገሉና ዕድሜያቸው ከ50 አመት በላይ በመሆኑ የጡረታ መብታቸው እንዲከበርላቸው አሰሪ መ/ቤታቸውን ጠይቀው የተሰጣቸው ምላሽ ፍትሐዊ አለመሆኑን ገልፀው ቅሬታቸውን ለሰሜን/ምዕ/ሪጅን ማ/ዋ/ኤጀንሲ አቅርበው ኤጀንሲው አመልካች ስራቸውን የለቀቁት በራስ ፈቃድ በመሆኑ በአ/ቁ 714/2003 አንቀፅ 19/3/ መሰረት ዕድሜያቸው 55 አመት ሲሞላ ከየካቲት 1/2010 ጀምሮ የጡረታ አበል የሚወሰንላቸው መሆኑን ኮሚቴው የወሰነ ሲሆን፡-

በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅሬታቸውን ለማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የይግባኝ አቤቱታ አቀርበው የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው በማለት ያፀናው መሆኑን ከቀረበው የአመልካች አቤቱታ እና ውሳኔዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ አቀርበው ይግባኝ የተባለበት ውሳኔ ጉድለት የለበትም ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁጥር 337 የዘጋው ሲሆን አመልካች በዚህ ውሳኔ ተፈፀመ ያሉትን ስህተት በመዘርዘር በዚህ ሰበር ችሎት እንዲታረምላቸው አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለው ከአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 172/2002 አንቀፅ 3/1//ሀ/ አንፃር አመልካች የጡረታ ይከበርልኝ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በሰበር ለመመርመር ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ይዘት የስር ፍ/ቤቶች ለውሳኔያቸው መሰረት ያደረጉት አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀፅ 19/3/ ለመንግስት ተሿሚዎች የሚያገለግል ሣይሆን ከሹመት ውጭ በመንግስት ሰራተኞች ሲያገለግሉ ለነበሩ ሰራተኞች ነው የተጠቀሰው አንቀፅ በፌዴራል ልዩ የተሿሚዎች አዋጅ ቁጥር 653/2001 እና በአማራ ክልል ዝክረ ሕግ አዋጅ ቁጥር 172/2002 በተለየ ሁኔታ መብት የተሰጣቸውን የመንግስት ኃላፊዎች የማይመለከት በመሆኑ ይህ ድንጋጌ ከዝክረ ሕግ አዋጅ ቁጥር 172/2 አንቀፅ 3/1//ሀ/ ጋር ተጣምሮ ሊተረጎም የማይገባው ሆኖ ሣለ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የሕግ ትርጉም መሰረታዊ ስህተት ስላለበት ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 172/2002 አንቀፅ 3/1//ሀ/ ከመንግስት ሰራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁ. 714/2003 አንቀፅ 62/2/ መሰረት የሚቃረን ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ በአዋጅ ቁ. 714/2003 አንቀፅ 2/1/ የመንግስት ሰራተኛ ማለት የመንግስት ተሿሚዎችንም የሚያካትት መሆኑ ተመልክቷል የጡረታ መብትና ጥቅምን በተመለከተ የክልሉ አዋጅ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁ. 714/2003 ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የመንግስት ሰራተኞች ጡረታን በተመለከተ ስራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 714/2003 ሲሆን በዚህ አዋጅ ትርጓሜ አንቀፅ 2/1/ ላይ የመንግስት ሰራተኛ በመንግስት መ/ቤት በቋሚነት በመቀጠር ደመወዝ እየተከፈለው የሚሰራ ሰው ሲሆን የመንግስት ተሿሚዎች፣ የምክር ቤት አባላትንና የመከላከያ ሰራዊት አባላትን እንደሚጨምር ተመልክቷል፡፡ በአንቀፅ 2/2/ “ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ” ማለት ሚኒስቴር፣ሚኒስቴር ዳኤታ ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ያለው የመንግስት ኃላፊ ነው በሚል የተመለከተ ሲሆን በአንቀፅ 2/6/ “መንግስት” ማለት በኢፌዴሪ መንግስት እና የክልል መንግስታትን እንደሚያጠቃልል በአንቀፅ 2/7/ ደግሞ “ክልል” ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብትና ጥቅም ለመጠበቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀፅ 12 እና 21 የጡረታ መብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በአዋጅ 714/2003 አንቀፅ 62/1//ሐ/ የተሻሩ መሆኑ የተመለከተ ሲሆን በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች ወይም የአሰራር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልምዶች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም በማለት ተመልክቷል፡፡ የአ/ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁጥር 172/2002 ቀደም ብሎ የወጣ ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች የጡረታ መብት ጥያቄ መታየት ያለበት የጡረታ መብትን አስመልክቶ በወጣው ልዩ ሕግ በመንግስት ሰራተኞች የጡረታ ሕግ አዋጅ ቁ. 714/2003 እንጅ በአ/ብ/ክ/መ/በወጣው ዝክረ ሕግ አዋጅ ቁጥር 172/2002 አይደለም፡፡

በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀፅ 19/5/ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊን ወይም የምክር ቤት አባልን የሚመለከት ሲሆን ለከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በአዋጅ ትርጓሜ ክፍል ከተሰጠው ትርጉም አንፃር አመልካች ይህን የሚያሟሉ ባለመሆኑ በአዋጅ አንቀፅ 19/3/ መሰረት በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ የሰበር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈፅሟል የሚባል አይደለም ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሰሜን ምዕ/ሪጅን ማ/ዋ/ኤጀንሲ በቀን 8/6/2005፣ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በቁጥር ጡ/ይ/1/1/92/2006 በቀን 17/08/2006 የሰጡት ውሳኔ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 100266 በቀን 11/09/2006 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ላደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/104512

መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

መስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

አመልካች፡- አቶ አባስ ኢብራሂም ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- የሐረር ቢራ አ/ማህበር አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንብረት ጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የጀመረው ያሁን አመልካች በሀረሪ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በሰበር ተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ፡- ተጠሪ ኮስቲክ ሶዳና ሃይድሮሊክ አሲድ የተባለ መርዛማነት ያለው ተረፈ ምርት በእርሻ ማሳዬ ላይ አፍስሶ የተለያዩ ቋሚ ተክሎችና ሰብሎቹን በማድረቅ ስላወደመብኝ በዚህ ምክንያት ለደረሰብኝ ጉዳት በድምሩ ብር 1,526,700 ካሳ ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ፡- በክሱ የተጠቀሰውን መርዛማ ኬሚካል በአመልካች ማሳ ላይ አለማፍሰሱን፣ ያም ሆኖ ግን የድርጅቱን ፍሳሽ ወይም ተረፈ ምርት የክልሉ አርሶ አደሮች ለእርሻ ማሳቸው በማዳባሪያነት ጠቃሚነቱን ተረድተው እንዲደፋላቸው በጠየቁት መሰረት የተደፋላቸው መሆኑን፣ ተረፈ ምርቱም ለእርሻ ማሳ ማዳበሪያነት ጠቃሚ መሆኑን፣ በጉዳዩ ላይ በሐሮሚያ ዩኒቨርስቲ እየተካሄደ ያለው ጥናትም ይህንኑ የሚያረጋግጥ መሆኑንና የጉዳት ካሳ መጠኑም የተጋነነ ነው የሚልና የመሳሰሉትን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ቃል ከሰማ በኃላ በተጨማሪነትም ከክልሉ አካባቢና ጥበቃ ባለስልጣን ጽ/ቤትም ባለሙያ አስቀርቦ በጉዳዩ ላይ ሙያዊ አስተያየቱን ከተቀበለ በኃላ ጉዳዩን መርምሮና ማስረጃውንም ከመዘነ በኃላ የተጠሪ ተረፈ ምርት በአመልካች ማሳ ላይ መፍሰሱን፣ይህንን ተከትሎም ተክሎችና ሰብሎቹ በመድረቅ ጉዳት የደረሰባቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን፣ ለዚህም ጉዳት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 300/95 አንቀጽ 4 /1/ ና ፍ/ብ/ህግ/ቁ/2035 መሰረት ኃላፊነት ያለበት መሆኑንና የደረሰውን ጉዳት መጠንም ብር 145,840 መሆኑን መረጋገጡን ከገለጸ በኃላ በሌላ በኩል ደግሞ ተረፈ ምርቱንም አመልካች እራሱ እንዲደፋለት በጠየቀው ጥያቄ መሰረት በማሳው ላይ እንዲደፋ መደረጉንና እንዲሁም አመልካችም ሌሎች አርሶ አደሮች እንደሚያደርጉት ተረፈ ምርቱ የሚያመጣውን ጉዳት ለማስቀረት ፍሳሹን በየጊዜው በመጥረግ የበኩሉን አስተዋፅዖ ማድረግ ሲገባው ይሄንን አለማድረጉም በምስክሮች ቃል መረጋገጡን ገልፆና ይህም በአንድ ላይ ተገናዝቦ ሲታይ ክፊሉ ጉዳት ራሱ በአመልካች ጥፋት መድረሱን መገንዘቡን በውሳኔው በማስፈርና ይህንኑም በካሳ ክፋያ አሰላሉ ሂደት ከግምት ውስጥ ማስገባቱን ጭምር ከገለጸ በኋላ ተጠሪ ከብር 145,845 ውስጥ የበኩሉን የኃላፊነት ድርሻ 100,00፣ የጠበቃ አበል10% /10,000/ እና የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ብር 3,350 ጋር ለአመልካች ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አሁን ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች የተጠሪ ተረፈ ምርት በእርሻው ማሳው ላይ እንዲደፋ መፍቀዱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለደረሰው ጉዳት እሱም አስተዋፆ አለበት ተብሎ ሊከፈለው ከሚገባው የጉዳት ካሳ መጠን ውስጥ ብር 45,840 ተቀንሶ እንዲከፈለው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎና ለተጠሪም በህጉ መሰረት መጥሪያ እንዲደርሰው ቢደረግም ባለማቅረቡ በፅሁፍ መልስ የመስጠት መብቱ እንዲታለፍ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሰረቱ ጉዳዩ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ፈቃድ ሳይገዝ ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን ማመንጨት፣ ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ማምከን ወይም ማስወገድ የተከለከለ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 300/95 አንቀጽ 4/1/ ስር በግልጽ ተደንግጎ እናገኛለን ፡፡ ከዚህም መገንዘብ እንደሚቻለው አስቀድሞ የአካባቢው ጥበቃ መስሪያ ቤት ሳያስፈቅዱ የፋብሪካ ውጤት የሆነውን መርዛማነት ያለው ተረፈ ምርት ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ማጓጓዝ ወይም ማስወገድ በህጉ የተከለከለ ተግባር መሆኑን ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ቆሻሻ ውሃ የተቀላቀለበትና መርዛማነት ያለው ተረፈ ምርት በአመልካች ማሳ ላይ ማፍሰሱና ይህንንም ያደረገው ያለ አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ፍቃድ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ፍሳሹም በአመልካች ሰብሎችና አትክልቶች ላይ ጉዳት በማድረሱ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 300/95

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 4/1/ እና ፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2035 መሰረት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት እንዳለበት በስር ፍ/ቤት ተወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ግን የስር ፍ/ቤት ተረፈ ምርቱ እንዲደፋ አመልካችም በመፈቀዱና እንዲሁም ተረፈ ምርቱ በእርሻ ውጤቶች ምርት ላይ የሚያመጣውን ጉዳት ለማስቀረት አመልካችም ያደረገው ጥረት ባለመኖሩ እሱም ከዚህ አንፃር ላደረሰው ጉዳት አስተዋዕፆ አድርጓል በሚል ምክንያት ሊከፈለው የሚገባውን የካሳ መጠን በፍ/ብ/ህ/ቁ/2098 መሰረት ቀንሶበታል፡፡ ይሁንና ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የፋብሪካ ተረፈ ምርት የሚደፋበትን ቦታ ለመፍቀድ በህግ ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው ለአካባቢው ጥበቃ መስሪያ ቤት እንጂ ለግለሰቦች አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ተረፈ ምርቱን በማሳ ላይ የደፋሁት አመልካችን ጨምሮ ሌሎች የክልሉ አርሶ አደሮች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ከዚህ አንፃር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፋብሪካው ተረፈ ምርት በሰብል ምርቱ ላይም ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ጉዳትም አመልካች እንደ አርሶ አደርነቱ ያውቃል ወይም ሊያውቅ ይገባ ነበር በሚል ደምዳሚ ግምት መውሰድም የሚችል አይሆንም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የጉዳቱን ውጤት እንዴት እንዲቀንስ ማድረግ ይችል እንደነበርም በዚህ ረገድ ክርክሩ በግልጽ በተጠሪ ቀርቦና በማስረጃም ባልተረጋገጠበትና እንዲሁም አመልካችም በዚህ ረገድ ከቅን ልቦና ውጪ እንቅስቃሴ ማድረጉም ተጠሪ ባላስረዳበት ሁኔታ በፍ/ብ/ህ/ቁ/2098/1/ ድንጋጌ መሰረት እሱም ለጉዳቱ አስተዋዕፆ አድረርጓል ተብሎ በዚህ ምክንያት ሊከፈለው ከሚገባው የካሳ ክፍያ መቀነሱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ከዚህ አንፃር የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሐ/ሕ/ክ/መንግስት ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 02554 በ 6-8-2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማጽናት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በኮ/መ/ቁ/101454 በ17/10/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ሙሉ ሐላፊነት አለበት ብለናል፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤቶች ከተወሰነው በተጨማሪ ብር 45,840 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ተብሏል፡፡
3. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.109535

የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ሳልቫቶሪ ዴበታኮምፕሌክስ ጠበቃ ንጉሽ በልሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሀብታሙ አባዲ ጠበቃ ታየ ወጂ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰትተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የደለላ አበል ክፍያ የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኮልፌ ቀራንዮ ምድብ ችሎት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም የአሁነ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በነበረው የቆየ የኮሚሽን ስራ ግንኙነት በቃል በደረጉት ስምምነት የአመልካች ንብረት የሆነው አንድ ቪላ መኖርያ ቤት ተከራይ ፈልገው እንዲያካራዩላቸው በተለመደው የኮሚሽን ክፍያ አሰራር መሰረት የአንድ ወር የኪራይ ገቢ በኮሚሽን መልክ ለተጠሪ እንደሚከፈሉ በዚህም በተደጋጋሚ በተደረገው ጥራት ቤቱ ጳጉሜ 02 ቀን 2005 ዓ/ም የሮያል ኖረዊጂን ኤምበሲ ቤቱን ለጽ/ቤቱ አገልግሎት በወር 20,000 ዶላር ሂሳብ ኪራይ በመስማማት መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ/ም የ10 ዓመት ኪራይ ውል ስምምነት በመፈራረም ተከራዩ የአንደኛ ኣመት ቅደመ ክፍያ 4,540,800 ብር ለአመልካች የከፈለ ሲሆን አመልካች ግን በስምምነቱ መሰረት መክፈል የሚጠበቅባቸው የአንድ ወር ኪራይ ሒሳብ ለመክፈል ፈቃደኛ በለመሆኑ የኮሚሽን ክፍያ 378,400.00 ብር ከመስከረም 2006 ዓ/ም ከሚተሰብ 9% ህጋዊ ወለድ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍላቸው ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሰይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚ እና በፍሬ ነገሩ መልስ አቅርበዋል፡፡ የመጀመሪያ መቃወሚያ በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የግዘት ስልጣን እንደሌለው ቤቱም የራሰቸው ለመሆኑን የሚገልጽ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ከኖርዋይ ኤምበሲ በተደረገው የኪራይ ውል ስምምነት ተጠሪ ሳይሆን እንግልዝኛው ዴቪድ ዊልስ የተበሉ የረዱዋቸው ስለ መሆኑ የቆየ ግንኙነት እንደልነበራቸው በመካከላቸው ውል የለም እንጅ ውል አለ ከተባለ መክፈል ያላበቸው በመቶ ሁለት ፐርሰንት (2%) ስለመሆኑ የሚገልጽ መልስ አቅርቦዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩ ለመመልከት ሥልጣን እንደለው ቤቱም በአመልካች የሚታወቅ የራሳቸው ስለመሆኑ በሰነድ የተረጋገጠ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ጭብጥ ከያዘ በኃላ የተጠሪ ምስክሮች በአመልከች እና ተጠሪ መካከል የድለላ ስራ ግንኙነት መኖሩን ማረጋገጣቸው የአመልከች ምስክሮች በአንዣፋ የራሱ ልጆች በመሆናቸው በተሸለ አግባብ አስረድቷል ለማለት እንደማይቻል የተጠሪ 2ኛ ምስክር የኖርዋ ኤምባሲ ሰራተኛ በመሆኑ ወገንተኝነት እንደሌለው እና ኤምባሲው እና አመልካች ያገናኛቸው ተጠሪ ስለመሆኑ ማስረዳቱን ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 በ20/02/2006 ዓ/ም የታደሰ የድላለ ስራ ፈቃድ ያለቸው መሆኑ መረጋገጡ ክፍያ በተመለከተም በቃል ባደረጉት ስምምነት የአንድ ወር የቤት ኪራይ ክፍያ እንደሆነ ቤቱም በወር 20,000 ዶላር በመስማማት ለ20 ዓመት እንደተከራየ ኤምባሲው በበኩሉ 57,000 ብር መክፈሉ ሲታይ ከአመልከች ጋር ያገናኙዋቸው ተጠሪ መሆናቸውን እንደሚያሳይ በመግለጽ በግራ ቀኙ የቃል ውል ስምምነት መሰረት የአንድ ወር ኪራይ ሂሳብ በኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር 378,400 ብር ይህ ክስ ከተመሰረተበት ከታህሳስ 16 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ከ9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልከች በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አለገኘም፡፡ የህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር አደርጓአል፡፡ አመልካች ሰፊ የሰበር ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን እንኳን ይዘቱ ከተጠሪ ጋር የድለላ ስምምነት እንዳልነበረ ይከፈል የተበለው የገንዘብ መጠንም ከፍተኛ በመሆኑ ሊቀንስ እንደሚገባ የሚጠይቅ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩለቸው በአመልካች ጋር ስምምነት የነበራቸው ስለ መሆኑ ማስረዳታቸው የክፍያ መጠኑም አመልካች በ20 ዓመት ያገኙታል ተብሎ ከሚጠበቀው የኪራይ ገቢ አንጻር እና ተጠሪ ከሰጡት የድለላ አገልግሎት ሲታይ ተመጣጠኝ ነው በዝቷል ሊባል አይገባም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸ ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የደላለ አበል ክፍያ መጠን በተመለከተ በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 59(3) አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ነው የሚል ነው፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው የስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የድለላ ስራ ግንኙነት መኖሩን ማረጋገጣቸው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልከች እና ተጠሪ ምስክሮች ቃል የሰነድ ማስረጃ መርምሮ የተጠሪ ምስክሮች ክሱን በተሸለ አግባብ ማስረዳታቸውን ከድምዳሜ ላይ መደረሱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ባደረጉት ጥራት አመልካች አንድ ቪላ ቤት ለኖርዌይ ኤምባሲ ለ20 ዓመት ማከራየታቸው እና ክፍያም በወር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

20,000 ዶላር ስለመሆኑ የከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአሁኑ አመልካች ከተጠሪ ጋር የድለላ ስራ ግንኙነት የለንም በሚል በአጽንኦት የተከራከሩ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ግንኙነት መኖሩን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ማጠራት እና ማስረጃ ምዘና እና ድምዳሜ በዚህ ችሎት በድጋሚ የሚመዘን ሆኖ አልተገኘም፡፡ ምክንያቱም የሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ሥልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም ስለመሆኑ ከኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረታዊ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም አመልከች በፍሬ ነገር ክርክር እና ማስረጃ ምዘና ላይ ያቀረቡት ክርክር በአጠሪ ችሎት በጭብጥ ከለመያዙ በተጨማሪ ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ውጪ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት የለውም ብለናል፡፡

አመልካች ለተጠሪ እንዲከፈል የተወሰነው የአንድ ወር የቤት ኪራይ ሒሣብ ብር 378,400.00 ከ9% ወለድ ጋር በዝቷል የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች አከራከሪው ቤት ለ20 ዓመት በወር 20,000 ዶለር ለኖርዌይ ኤምባሲ ማከራየታቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የድለላ ኣባል ክፍያ መጠን በግራ ቀኙ ስምምነት የሚወሰን ሲሆን ፍርድ ቤቱ የድለላ አበል በዝቷል የሚል እምነት ከያዘ ሊቀንስ እንደሚችል በንግድ ህግ አንቀጽ 59 (3) ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሰረቱ የድለላ አበል ክፍያ መጠን ከተሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጠጣኝ ሊሆን እንደሚገባ የሚታመን ቢሆንም ግራ ቀኙ የአበል ክፍያ መጠን ሲወሰኑ ታሰቢ ያደርጓቸው ነገሮች ግምት ውስጥ መግባት አለበቸው፡፡ በተያዛው ጉዳዩ አከራካሪ የሆነው ጭብጥ ለተጠሪ የሚከፈለው የደለላ አበል ክፍያ መጠን በዝቷል? ወይስ አልበዛም? የሚል ነው፡፡ ከላይ እንተመለከተው ግራ ቀኙ ፈቅደው ያደረጉት ስምምነት ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧዋል፡፡ አመልከች የድለላ አበል መጠን 2% መሆን አለበት በማለት የተከራከሩ ቢሆንከም የዚህ ክርክር ሕጋዊ መሰረት ማሳየት አልቻሉም፡፡ የቤት ኪራይ ውሉ ለ20 ዓመት የሚቆይ መሆኑ ሲታይ የስር ፍርድ ቤት ለተጠሪ በስምምነታቸው መሰረት የአንድ ወር ኪራይ ሒሳብ እንዲከፈል መወሰኑ የግራ ቀኑ ስምምነትና አጠቃላይ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የወሰነው መሆኑን ከመቀበል ውጭ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለመሆኑ የሚያሰይ ነገር አልቀረበም፡፡ የቤት ኪራይ ውል ለ20 ዓመት መደረጉን በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ በአመልከች እና ተጠሪም የድላለ ስራ ስምምነት መኖሩን የስር ፍ/ቤት በተቀበለበት ሁኔታ የድለላ አበል ክፍያ መጠን በዝቷል ወይም አንሰዋል በሚል በመጠኑ ላይ የሚደረገው ክርክር አጠቃላይ ሁኔታዎች መመልከት የሚጠይቅ እንጂ አንድ ወጥ መስፈርት መሰረት ተደረጎ የሚወሰን ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በድለላ አበል መጠን ላይ በሚደረገው ክርክር እንደጉዳዩ ዓይነት እና የተሰጠው አገልግሎት እየተገናዘበ የሚወሰን ከመሆኑ አንፃር የስር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት የድለላ ስምምነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መኖሩን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጦ ተጠሪ ለሰጡት አገልግሎት የአንድ ወር ኪራይ ሒሰብ 378,4000.00 ከ9% ወለድ ጋር እንዲከፈለቸው መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን አያስይም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በክ/መ/ቁ. 35650 በ21/02/2007 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክ/መ/ቁ. 162863 በ15/05/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. በአመልካች እና ተጠሪ የድለላ ስራ ስምምነት መኖሩን ተረጋግጦ የቤቱ የአንድ ወር ኪራይ ብር 378,400.00 ከ9% ወለድ ጋር እንዲከፈል መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ፍ/ቤት መጋቢት 23 ቀን 2007 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ድረ-ገጽ፡- www.fsc.gov.et
ስልክ፡- +251 111 55 34 00
ፋክስ፡- +251 111 56 55 83
የመ.ሣ.ቁ.፡- 6166
ነጻ የስልክ ጥሪ፡- 992

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች ቅጽ-20

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



ቅጽ-20

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ-20

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ግንቦት 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

በተሻሻለው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሠበር ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙ የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል ተብሎ መደንገጉ ፍርድ ቤቶች የሠበር ችሎቱ የሰጠውን የህግ ትርጉም ተከትለው በመስራት ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተመሳሳይ ውሳኔዎች እንዲሰጡ ለማስቻል ነው። በሀገሪቱ ያሉ ፍርድ ቤቶች ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተመሳሳይ ውሳኔዎችን መስጠት መቻላቸው የዳኝነት አገልግሎቱ ተገማች እንዲሆን ከማስቻሉም በላይ ባለጉዳዮችን ካልተገባ ወጭና ከእንግልት ሊያድናቸው እንደሚችልም ይታመናል። ይህን እውን ለማድረግ በተቻለ መጠን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች በአግባቡ ታትመው በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶችና ለተለያዩ አካላት እንዲሁም ለህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሰራጩ ይደረጋል።

በሌላ በኩል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች በጥራዝ መልኩ መዘጋጀታቸው ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ የህግ ተመራማሪዎች፣ ለህግ ባለሙያዎች ለጠበቆች፣ ለምሁራንና በጠቅላላው ለህብረተሰቡ ውሳኔዎችን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑም ስለ ታመነበት ጭምር ነው።

ዳኜ መላኩ

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ /ቅፅ 20/

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
አሠሪና ሠራተኛ					1
1.	የአሰሪውን ትእዛዝ አልፈፀመም ተብሎ የስራ ስንብት ያደረገ አሰሪ ትእዛዙ ያለመፈጸሙን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ *አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13*	119639	የደብረዘይት ሄልሜክስ ቁራዎች ድርጅት እና እነ አየለ ዲባባ /ሦስት ሰዎች/	30/5/2008 ዓ.ም	2
2.	በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ በግልጽ በተቀመጡ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር አንዲት ሰፍሰጡር ሴት ከወሊድ በኋላ አራት ወራት ውስጥ ከስራ ያለመባረር መብት ያላት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 25፣27፣29/3/ እና 87/5//6/	121063	መ/ርት ሙሉነሽ መለሰ እና ዋሊያ አጠቃላይ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት	24/06/2008 ዓ/ም	5
3.	የግል አሰሪና ሠራተኛ (ስራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ) እና በሰራተኛ የሚነሳ ማንኛውም የስራ ክርክር የሚፈታው በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀጽ 4*	98771	እነ አቶ ታረቀኝ መኮንን እና አሊ ሚፍታህ ኤጀንሲ	24/8/2008 ዓ.ም	9
4.	አንድን ሰራተኛ በስራ ላይ አልተገኘም ማለት የሚቻለው የስራ	117862	ጎል ኢትዮጵያ	20/10/2008 ዓ.ም	13

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ውሉ ፀንቶ እስከቆየበት ጊዜ ድረስ ብቻ ስለመሆኑ፡- *አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27 (1) (ለ)*		እና አቶ ዲዲሞ አጋቶ		
5.	የገዘውውር ውሳኔን ተከትሎ ሰራተኛው ለአምስት የሰራ ቀናት የሰራ ቦታ ላይ አልተገኘም በማለት የማሰናበት እርምጃ ተገቢነት ለማጣራት ፤ ከነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም ሰራተኛው የሰራ ቦታ ላይ መገኘት ከሚችልበት ሁኔታ አንፃር እንዲሁም ከቀረበው ማስረጃ አንፃር በመመዘን የሚወሰን ስለመሆኑ ፤	125004	አዲስ ፋና ጠቅላላ ሸቀጣ ሸቀጥ እና ሆቴሎች ንግድ አ.ማ እና አቶ ሊቁ ብርሃነ	22/10/2008 ዓ.ም	17
6.	አሰሪ የተጠየቀን የስራ ስንብት ክፍያን በተመለከተ አጠቃላይ ተቃውሞ አቀርቦበት እያለ ፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ሰሌቱን በተመለከተ አልተቃወመም በሚል በመተርጎም በሰራተኛው የተጠየቀን የስንብት ክፍያ ዳኝነት ሙሉ በሙሉ በመወሰን የሚሰጥ ዳኝነት ተገቢ ስላለመሆኑ ፤ፍ/ቤቱ በሕጉ አግባብ አስልቶ መጠኑን ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ ፤ *አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 40 (1 እና 2)*	119694	ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና አቶ አለማየሁ ሁሉቃ	27/11/ 2008ዓ.ም	22
7.	ለጡረታ አፈፃፀም ተብሎ የመንግስት ሰራተኛን የግል ማህደር በኤጀንሲው እንዲላክ ተጠይቆ፤ሰራተኛው የመንግስት	127154	ኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት	23/1/ 2009 ዓ.ም	28

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ንብረት አልመለሰም በማለት ማህደር አልክም ማለት ህጋዊ ሰላለመሆኑ ፤ የጡረታ አበል የማግኘት መብት የዕዳ መያዣ ሊደረግ ወይም በውርስ ወይም በማናቸውም መንገድ ሊተላለፍ የማይችል ስለመሆኑ *አዋጅ ቁጥር 345 /97 አንቀፅ 47 (2) ፣ 44 እና 55 (2)*		እና አቶ ካሳሁን በዛብህ		
8.	አሰሪ ሰራተኞችን ከማሰናበቱ በፊት በትክክል አጣርቶ እርምጃ መውሰድ ሲገባው ፤ክርክር ከተጀመረ በኃላ ከስንብት ደብዳቤ ሌላ ደብዳቤ መፃፉ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁን ዓላማ እና መንፈስ የማያሟላ ስለመሆኑ ፤ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 91 (1) (3)* *አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 (1) (ሸ) (ቀ)*	125778	ሲው ኢንፍራስትራክቸር እና እነ አቶ መሳይ ወ/ገብርኤል (አራት ሰዎች)	23/1/ 2009 ዓ.ም	32
9.	አንድን ሰራተኛ የሥራ መሪ ነው ሊባልበት ስለሚቻልበት አግባብ፡- የሥራ መሪን በተመለከተ ክርክር ሲነሳ ተግባራዊ ሊሆኑ ስለሚገባቸው ህጎች፡- የስራ መሪ የሚያቀርባቸው የመብት ጥያቄዎች ቀሪ ስለሚደረጉበት የይርጋ ጊዜ	116038	ፍራውን ኮ/ህንፃ ተቋራጭ እና እነ አቶ ካህሳይ ገ/እግዚአብሄር (ሁለት ሰዎች)	21/2 /2009 ዓ.ም	37

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2(!)፣ 3(2(ሐ) *የፍ/ሕ/ቁ.1677(1)፣1845፣2512፣2593*				
10.	ተዋዋይ ወገኖች በስራ ውል ስምምነታቸው በግልፅ ኮሚሽንን የደሞዝ አካል አድርገው እስከተዋዋሉ ድረስ ቅራኔ በተነሳ ሰዓት ኮሚሽንን እንደ ደመወዝ አይደለም በማለት መውሰድ ተገቢ ስላለመሆኑ *አዋጅ ቁ.377/1996 አንቀፅ 53(2(መ)*	117070	ወ/ሮ ወይንሸት በቀለ እና ኦሎምፒያኮስ ሄኔኒክ አትሌቲክስ ማህበር (ግሪክ ክለብ)	22/2/ 2009 ዓ.ም	46
የፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት					49
11.	ቼክን በተመለከተ በአጭር ስነ ስርዓት /Summary proceding/ ዳኝነት ታይቶ እንዲወሰን ክስ በቀረበበት ወቅት ተከሳሽ መከላከያውን እንዲያቀርብ ጥያቄ አቅርቦ ተፈቅዶለት መልስ እንዲያቀርብ ተደርጎ መልስና በሕግ አግባብ ምስክር ቆጥሮ እያለ ምስክሮች ሳይሰሙ ይኼው ታልፎ የቼክ ባሕርይን ብቻ መሰረት ተደርጎ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ ትክክል ስላለመሆኑ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 285/1/ 286 እና 291* *የ3/ሕ/ቁ. አንቀጽ 717*	103478	አቶ ኤልያስ ተፈራ እና አንዋር ሁሴን	18/4/ 2008 ዓ.ም	50
12.	አንድ ከሳሽ ክሱን የመሰረተው በብዙ ጉዳዮች ወይም በተለያዩ	109054	አቶ ነገሠ ግዛው	27/7/2008 ዓ.ም	55

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ነገሮች ላይ የሆነ እንደሆነ በተለይ በእያንዳንዱ ጉዳይ እንዲታይ የሚጠይቀውን ዳኝነት መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 224(2)		እና አቶ ሐረጳ ቤኛ		
13.	አንድ በፍርድ ቤት የተወከለን ሰው በችሎት ተገቢ ያልሆነ ስነ ምግባር አሳይቷል በማለት ፍ/ቤት የውክልና ስልጣንን መሻር የማይቻል ስለመሆኑ፣ *ፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 58*	102141	አቶ አደን የሱፍታረ እና አቶአህመድ አብዱላሂ ተረቢ	29/7/2008 ዓ.ም	59
14.	ተከሳሽ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ አምኖ ነገር ግን ሕግ ወይም ሌላ ፍሬ ነገር በመጥቀስ የቀረበብኝ ክስ ዋጋ የለዉም ብሎ የሚከራከር ከሆነ ሙግቱን የሚጀምረው ተከሳሽ ስለመሆኑ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 258/1/*	114816	ዳዊት በለጠ የጠጠር አምራች ድርጅት እና አብዱልራዛቅ	26/10/2008 ዓ.ም	63
15.	የይግባኝ መዝገብ በድሀ ደንብ እንዲከፈት የሚቀርብ ጥያቄን ለመወሰን አመልካች ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት (ንብረት በመታገዱ ፣ገንዘብ ማንቀሳቀስ የማይችል እና የሚከፍለው ገንዘብ የሌለ እንደሆነ) ለዳኝነት የሚከፈለው ገንዘብ ያለው ወይም የሌለው መሆኑ መጣራት እና መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፤ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 567 ፣ፍ/ሕ/ቁ 1793/ለ/ እና ሕገመንግስት*	117754	አክሰስ ሪል እስቴት እና ጋቢኢንቨስትመንት/የተ/የ ግ/ማ	8/10/ 2008 ዓ.ም	66

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	37(1)				
16.	መብቱን የሚነካ ፍርድ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ የፍርድ መቃወሚያን ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይቅርብ በማለት የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢ ሰላለመሆኑ፤ መቃወሚያ መቅረብ ያለበት ክርክሩን ሰምቶ ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት ሰለመሆኑ *ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418*	115892	ወ/ሮ መሰረት አንዳርጌ እና እነ አቶ ይበልጣል ስመኝ (ሦስት ሰዎች)	11/11/2008 ዓ.ም	70
17.	በክርክር ሂደት ላይ ፤ የቀረቡት የባለሙያ አሰተያየቶች ተቃራኒ ይዘት ካላቸው ፤ ግልፅ መሰፈረት እና ምክንያት በሌለበት አንደኛውን ተቀብሎ ሌላውን ውድቅ ማደረግ ተገቢ ሰላለመሆኑ፤ *ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 250 እና 136(1)*	115963	አቶ ኤልያስታምራት እና እነ ወ/ሮ አሰቴር መከተ (ሁለት ሰዎች)	8/11/ 2008 ዓ.ም	75
18.	የሰበር አቤቱታ በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሳይቀርብ ጊዜው ካለፈ የሰበር አቤቱታ ከመቅረቡ በፊት የይግባኝ ማስፈቅጃ ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ሰለመሆኑ፤ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 22(4) ፣ ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 324	101277	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና ሚ/ር አቤንቻንድ ፓፓትላል	23/1/ 2009 ዓ.ም	81
19.	በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ	121387	አፍሮ ፅዩን	26/1 /2009 ዓ.ም	84

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ይቆጠራል የሚለው ድንጋጌ በልዩ ስርዓት(በአጭር ሁኔታ) ለሚመሩ ክርክሮች ላይ ጭምር ለቀረበ መልስ ላይም ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ፤ *ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 284 (ሀ)*		ክ/ኃ/የተ/የግ/ማህ እና እነ አቶ ያሬድ ተሾመ (ሦስት ሰዎች)		
20.	ከሳሽ ያቀረበው ክስ እና የክሱ ዝርዝር ይዘት የተለያየ ሆኖ የተገኘ ከሆነ ፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በማዘዝ ፤የክርክሩን ሂደት መምራት ያለበት ስለመሆኑ፤ *ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 90(1)*	122249	አቶ በላይ አየለ እና በአ/አ/ከ/አ/ከ/ፅ/ቤት አዲስ ዙ ፓርክ ማዕከል	26/1 /2009 ዓ.ም	87
21.	አንድ የዳኝነት አካል የሥረ - ነገር ስልጣን ባይኖረውም እንኳን የሰጠው ውሳኔ ሥርዓቱን ተከትሎ እስካልተሻረ ድረስ የፀናና የመጨረሻ በመሆኑ አዲስ ክስ በተመሳሳይ ጉዳይ ማቅረብ ተገቢ ስላለመሆኑ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5/1/ እና 212	105677	እነ ወ/ሮ ጥሩነሽ ገ/ወልድ /ስድስት ሰዎች/ እና እነ አቶ መኮንን ገ/ወልድ/ ሶስት ሰዎች/	30/1/2009 ዓ.ም	90
22.	በክርክር ወቅት ጣልቃ እንዲገባ የተፈቀደለት ተከራካሪ በመጀመሪያ ሊያቀርብ የሚፈልገውን መቃወሚያ እንዳያቀርብ የሚከለክለው ህግ የሌለ ስለመሆኑ፣ (የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 ፣234/1/	108647	ወ/ሮ ወርቂቱ ገመዳ እና ወ/ሮ ደመቀች ብርሃኑ	15/3/2009 ዓ.ም	96

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
23.	ሒሳብ አስተሣሣቢ የመመደብ ሥልጣን ያለው ዋናው ጉዳይ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለውና የግራ ቀኙን ክርክር የሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ፣ አንድን ጉዳይ ለመወሰን የቀረቡት /የተሰጡት/ የሙያ አስተያየቶች ተቃራኒ ይዘት ባለበት ሁኔታ የአንድን ባለሙያ አስተያየት ብቻ በመቀበል መወሰን ተገቢ ስላለመሆኑ፣ (የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 136፣145/1/፣246፣248 እና 264	105956	አምሣሉ ወርቁ ኮንስትራክሽን እና ትድሃር ኤክስካቬሽን ARዝ ሙቪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	19/3/2009 ዓ.ም	101
24.	ፍ/ቤቶች እውነትን ለማውጣት ማስረጃ አስቀርበው መስማት አለባቸው ሲባል በቀረበው ማስረጃ እውነት እስከተረጋገጠ ድረስ የግድ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሚገደድበት ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ፣ የፍትሐብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገር እንዲጣራ የሚደረገው በማስረጃ የሚገኘው ፍሬ ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ፣	109563	እነ አሰፋ መንግስቱ ኮንስትራክሽን ኪራይ /ሁለት ሰዎች/ እና ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር	26/3/2009 ዓ.ም	112
25.	ማናቸውም ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልሱ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለጸ እንደሆነ ወይም በሚደረግ ምርመራ የእምነት ቃሉን የሰጠ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በታመነው	107217	የዳንግላ ወረዳ ውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና አቶ ሙሉጌታ ገበየሁ	29/3/2009 ዓ.ም	119

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ነገር ላይ ብቻ ፍርድ መሰጠት ያለበት ስለመሆኑ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 83 ፣234/1/ /ሠ/ ፣ 241 እና 242				
26.	ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት የሚከራከሩበትን ጉዳይ በእርቅ መጨረስ የሚችሉና የእርቅ ውሉን ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት አቅርበው ማፀደቅ እንደሚችሉ ፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀ የእርቅ ውል ሥምምነት በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ያህል አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው ከመሆኑ ባሻገር በዚህ እርቅ ውል ተካፋይ ያልሆነ መብቱ ተነክቷል የሚል ወገን የፍርድ መቃወሚያ ሊያቀርብ የሚችል ሥለመሆኑ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.276፣277(1) እና 358*	114623	እነ ሃጂ አባመጫ (ሁለት ሰዎች) እና የኦሮሚያ ክልል ደንና ዱር አራዊት ድርጅት (ሁለት ሰዎች)	22/06/2009 ዓ.ም	124
ንብረት					128
27.	በመንግስት የተወረሰን ቤት የባለቤትነት መብት ከሌለው ሰው/አካል/ መግዛት የማይንቀሳቀስ ንብረትን በቅን ልቦና ባለሀብትነትን የሚያጎናጽፍ ስላለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁጥር 47/67*	112190	አይከል ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና ሼክ ሸምሱ መሀመድ	28/7/ 2008 ዓ.ም	129
28.	ማንኛውም የቀበሌ መኖሪያ ቤት የተከራየ ሰው የራሱ ቤት	123056	ወ/ሮ ትሁኔ አዳነ	24/10/2008 ዓ.ም	133

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ከገነባ ወይም የጋራ ሕንጻ ቤት ከገዛ ወይም የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲን ቤት ካገኘ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ቤቱን የለቀቁ ከሆነ ቤቱን ባለበት ሁኔታ ለአስተዳደሩ ማስረከብ ያለበት ስለመሆኑ፣ *የአ.አ.ከ.አስተዳደር ባወጣው የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁ. 3/2007 አንቀጽ 42/ሀ*		እና በጉ/ክ/ከ/ወ/7/ኮ/ቤ/አ/ል/ፅ/ቤት		
29.	ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ በህጋዊነት ከያዘው ይዞታ ጎን ያለን የከተማ ቦታ አስፋፍቶ መከለልና መጠቀም የማይቻል ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 5(2)*	111311	ን/ስ/ስ/ላ/ክ/ከ/ወ ወረዳ 03 እና አቶ ሲሳይ ተስፋዬ	23/7/2008 ዓ.ም	136
30.	የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ በሚቋረጥበት ወቅት /ሲቋረጥ / ባለይዞታው እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በቦታው ላይ ያሰረፈውን ንብረት በማንሳት ቦታውን አግባብ ላለው አካል መልሶ ማስረከብ ያለበት ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 26(5) እና (6)*	107777	የሱ-ልታ ክ/አስተዳደር እና አቶ ደባልቄ ደምሴ	28/7/2008 ዓ.ም	140
31.	በትግራይ ክልል በገጠር መሬት ላይ የሚደረግ ልውውጥ	106436	አቶ ተክሌ ይይ ተስፋይ	25/8/2008 ዓ.ም	145

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሕጋዊ ነው የሚባለው በውልና ማስረጃ ፀድቆ የወረዳው የመሬት ዴስክ አውቆ በቅጽ ተሞልቶ የተለዋወጡ ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ *የትግራይ የመሬት አዋጅ ቁጥር 239/06 እና ደንብ ቁጥር 48/2000*		እና ወ/ሮ ንግስቲ ገ/መድህን		
32.	የመሬት የይዞታ መብት ያለው ሰው ፤በይዞታው ላይ የአላባ የመጠቀም መበት መስጠቱ በሌላ ጊዜ ይዞታውን በስጦታ የማስተላለፍ መብቱን የማይገድብ ስለመሆኑ ፤ *የአ/ብ/ክ/መ/መሬት አጠቃቀም አዋጅ 133/98 አንቀፅ 1፣7*	119557	አቶ ማናለው ተካ እና ወ/ሮ እቴነሽ ተካ	19/11/2008 ዓ.ም	148
33.	የገጠር መሬት የይዞታ ባለመብት የሆነ በሙሉ ፍቃድ የሰጦታ ውል አድርጎ እንዲሁም ውሉ በሚመለከተው አካል ከተመዘገበ በኃላ ፤በውሉ ላይ ያልተመዘገበ ቅድመ ሁኔታ በመዘርዘር ውሉ ፈራሽ እንዲሆን በማለት የሚቀርብ ጥያቄ ውልንም ህግንም የሚቃረን መሆኑ *የአ/ብ/ክ/መ አዋጅ 133/98 አንቀፅ 15 እና 17 ፤ የአ/ብ/ክ/መ ደንብ ቁጥር 51/99 እና የፍ/ሕ/ቁ 2436 ፣2437 ፣2438 ፣2439*	118191	አቶ ድጋፌ ክፍሌ እና አቶ ጎሣ ገድል	24/1/ 2009 ዓ.ም	152
34.	የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ንብረቱን ከሌሎች ሰዎች	100395	ወ/ሮ አማረች ማሬ	29/3/2009 ዓ.ም	157

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ቁጥጥር ይዞታ ሥር ነዛ አድርጎ ፣የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሀብትነት ለማስተላለፍ የሚያስችሉ አስፈላጊ ሰነዶች ለገዢ የማስረከብና የማይንቀሳቀሰዉን ንብረት የማይነካ የባለሀብትነት መብት ለገዥ ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆነ ተግባራትን የመፈጸም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875፣ 2879(1)፣2281		እና እነ ወ/ሮ ሜሪ ታደሰ (ሦስት ሰዎች)		
የዳኝነት ስልጣን					164
35.	የከተማ ቦታን በሊዝ በመጫረት ጨረታውን በማሸነፍ የሊዝ ውል የተፈጸመ እንደሆነ ይህን የውል ግንኙነት ለመዳኘት የሚችለው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ፣ *የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004* *የፍ/ሔር/ሕ/ቁ. 1731፣1808/2/*	117819	የወላይታ ዞን የቦሌ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ዐ/ሕግ እና ወ/ሮ ታደለች ዲባራ	15/7/2008 ዓ.ም	165
36.	በኦሮሚያ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚነሱ የከተማ ቦታን ከማስለቀቅና ምትክ ቦታ እና ካሣን ከመክፈል አንጻር የሚነሱ የመብት ጥያቄዎችን በመጀመሪያ ደረጃ የማየት ስልጣኑ በከተማው አስተዳደር የተዋቀረው አካል ስለመሆኑ፣ *የኦሮሚያ ክልል የመሬት ሊዝ አዋጅ ቁ. 721/2004 አንቀጽ*	114622	አቶ አወል አማን (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ አሳለፈች እንዳግቤ /ሦስት ሰዎች/	9/9/2008 ዓ.ም	169

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ቁ. 26፣27፣28፣29 እና 30 አዋጁን ለማሰፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 155/2005 አንቀጽ 26፣55 እና 56				
37.	የአዲስ አበባ ከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የቤት ባለቤትነት ክርክርን አጣርቶ የመወሰን ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፣	110901	አቶ ተክለስላሴ ገላን እና ልደታ/ክ/ከ/የመ/ል/ከተማ ልማት ጽ/ቤት	25/9/2008 ዓ.ም	174
38.	ከፊል የዳኝነት ሰልጣን ላለው አካል በፍሬ ነገር ደረጃ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑ በግልፅ ተቀምጦ እያለ፤ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሕግ አተረጓጎም ረገድ ብቻ የተሰጠውን ስልጣን በማለፍ ማሰረጃን በመመዘን በፍሬ ነገር ላይ የሚሰጠው ድምዳሜ ሰርዓቱን የተከተለ ስላለመሆኑ ፤ *የአ/ብ/ክ/መ/ መገናኛ ብዙሀን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ 200/2005 አንቀፅ 13(2)*	119704	አማራ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት እና አቶ ዳንኤል ከፈለ	22/11/ 2008ዓ.ም	178
39.	የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደራጅባቸውና ባልተደራጅባቸው	116154	እነ አቶ ሚሪንዳ ዋሲሁን	13/03/2009 ዓ/ም	181

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ክልሎች ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚነሱ ይግባኞች መቅረብ ያለባቸው ከፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጋር አቻ ስልጣን ላላቸው በየክልሉ ላሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 154 የፌ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/2/ አዋጅ ቁ. 322/95		(አሥር ሰዎች) እና ኢትዩ ቴሌኮም		
ጉሙሩክ					185
40.	ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣው ህግ ስለመሆኑ፣ በአዲሱ የጉሙሩክ አዋጅ ቁ. 859/2006 አንቀጽ 182 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ክርክር ካላስነሳው ጉዳይ በሌሎች ህጎች የተመለከቱት ድንጋጌዎች በማይነካ ሁኔታ ስለመሆኑ፣ *የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22/2/ የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ጠቅላላ ክፍል በአንቀጽ 6*	101462	አቶ ነጂብ አዳም አቡባክር እና የኢትዮ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	20/11/2009 ዓ.ም	186

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
41.	የተሻረው ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከስስም ሆነ ሊያስቀጣ አይችልም ፣ ክሱም ተጀምሮ እንደሆነ የሚቋረጥ ስለመሆኑ፣ *የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 5/3/* *አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 99፣ አዋጅ ቁ. 859/2006*	111960	ወ/ሮ አባይነሽ ፈቀደ /ሁለት ሰዎች/ እና የሺ ኃይሌ	06/3/2009 ዓ.ም	192
ውል					196
42.	የዋስትና ውል ግዴታ ሰራተኛው ተቀጥሮ በሚያገለግልበት ወቅት ለሚደርሰው የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል ተጠያቂ የሚያደረግ ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሔር/ሕ/ቁ. 1933/1/ 1897*	109392	አቶ ሶፎኒያስ ኃ/ማርያም እና ካልዲስ ኮፊ ኃ/የተ/የግ/ማ	28/7/2008 ዓ.ም	197
43.	በተሸጠ ነገር ላይ የተገኘው ጉድለት ለውል ማፍረሻ ምክንያት ሊሆን ስለማይችልበት ምክንያት *የፍ/ሕ/ቁ.2344(2) ፣2289(1)*	107542	አሻምትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ኖንግፋን ሞተርስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	14/8/2008 ዓ.ም	201

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
44.	የስጦታ ዉል ውስጥ ተቃራኒ የሚሆን ቃል ከሌለ በቀር ስጦታ ከተደረገ በኋላ ልጅ መወለዱ ስጦታውን ለመሻር ምክንያት የማይሆን ስለመሆኑ፣ *ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2450*	115981	እነ ሕጻን መይሙና ሀሰን /አምስት ሰዎች/ እና የሕጻን ሃሊሃ ሀሰን ሞግዚት	26/09/2008 ዓ.ም	207
45.	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ በይዞታው ስር የሚገኙትን የመንግስት ቤቶች ለማከራየት የሚያደርጋቸው ውሎች ያልተጠበቁ ምክንያቶች ካልተከሰቱ እና በተለይም ደግሞ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል በተከራይ ወገን በኩል ጥፋት ተፈጽሟል ካልተባለ በቀር በድርጅቱና በተከራዮች መካከል የሚደረጉ ውሎች በየዓመቱ እየታደሱ የሚቆዩ ስለመሆኑ፣ *የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6/1/*	108638	አቶ መህቡክ ከድር እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ	22/09/2008 ዓ.ም	212
46.	በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2472 ላይ ገንዘብ ስለመከፈሉ ማስረጃን በተመለከተ የተደነገገው ፤ ከብድር ውጭ ለሆነ ግንኙነት ከተከፈለ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ ፤	116961	ወ/ሮ አስቱር አርአያ እና ወ/ሮ አወጣሽ መሐሪ	19/11/ 2008ዓ.ም	216

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
47.	በአንድ ሰነድ ላይ ያለን ፊርማ በቴክኒክ ምርመራ የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ ባልተቻለ ጊዜ ፊርማው ሲፈረም የነበሩ ምስክሮችን ቃል በመስማትና በሌሎች ማስረጃዎች ፊርማው የማን እንደሆነ በመመዘን ማረጋገጥ የሚቻል ስለመሆኑ *የፍ/ሕ/ቁ. 2472(1)*	114553	አቶ ኤልያስ ስሜ ተሰማ እና ወ/ሮ ዘነበች ተመስገን ጫካ	29/11/2008 ዓ.ም	221
48.	አንድ ዕቃ ለመሸጥ /በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ/ የተዋዋለ ወገን ከዕርሱ አቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ውሉን መፈጸም ባልቻለ ጊዜ በቅድሚያ ለዚሁ ስራ የተቀበለውን ገንዘብ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ከመመለስ ውጭ ውሉን ባለመፈጸሙ ምክንያት ለደረሰው ኪሳራ እንዲከፍል የማይገደድ ስለመሆኑ፣ ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2356/1/	117036	ፀጉ ብርሃን ትራዲንግ ሀ/የተ/የግ/ማህበር እና ኮሎኔል ይትባረክ አማረ	12/3/2009 ዓ.ም	225
49.	የደረሰው ጉዳት አንሿር በፈጸመው ተግባር ወይም ባደረገው ጉድለት እንዲሁም ይህ ተግባር አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑ እየታወቀ ሲሆን የኃላፊነት መጠኑ በህጉ ከተቀመጠው ውጪ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ፣ በልጅ ቀለብ አወሳሰን ረገድ ልንከተላቸው ስለሚገቡ መሰረታዊ መርሆች	109061	ወ/ሮ ነጋሪነት ሰለሞን የህጻን የአብስራ ቴዎድሮስ እና ስካይ ባስ ትራንስፖርት ሲስተም	19/3/2009 ዓ.ም	235

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	(የን/ሕ/ቁ. 597፣ 599) *(የፍ/ሕ/ቁ. 2091፣ 2092* *የኢ.ፌ.ድ.ሪ የቤተሰብ ህግ ቁ.. 213/92 አንቀጽ 197*				
50.	በአንድ ውል ውስጥ ውልን የሚያፈርሱ የስምምነት ቃሎች ተገልጸ ከተጻፈና የዚህም ስምምነት አፈጻጸም ጉዳይ ተሟልቶ ከተገኘ አንደኛው ተዋዋይ ውል ፈርሷል ሊል መግለጽ የሚችል ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሕ/ቁ. 1786*	105752	አቶ አዲሱ ግርማሁን የኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ እና ጉዞ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ	26/3/2009 ዓ.ም	246
ከውል ውጭ ኃላፊነት					251
51.	በአንድ ሰው ላይ ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነትን በሚጥሉ የተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች ምክንያት ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ለጉዳቱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ በሚሆኑበት ጊዜ ኃላፊ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ብቻ ጥፋት የሰራ እንደሆነ በመጨረሻ የተወሰነውን ዕዳ እርሱ እራሱ ብቻ የመቻል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፣ *ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2157*	117506	የመ/ፈ/አቅርቦት ኤጀንሲ እና አቶ አዲሱ ገዛኽኝ	8/9/2008 ዓ.ም	252

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
52.	በመሬት ይዞታዬ ላይ ጉዳት ደርሶብኛል በማለት የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ *ፍ/ሕ/ቁ 2143*	119563	ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት እና አቶ ሐጂ ነገዋ	26/1/ 2009 ዓ.ም	255
ቤተሰብ					258
53.	እድሜው ያልደረሰ ልጅ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ የሚያስችል የሞግዚት ስልጣን ይሰጠኝ ጥያቄ ፍ/ቤቶች የህፃንን መብትና ድህንነት ቅድሚያ እንዲሰጠው በማደረግ ሲወሰኑ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቀረበውን መሰረታዊ ጥያቄ እና አማራጭ መፍትሔ መኖሩን አለመኖሩን በማጣራት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ *የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሰት 36 (2) ፣ ፍ/ብ/ሕ/ቁ 280 እና 289(1)* *የቤተሰብ ህግ አዋጅ 213/1992 አንቀፅ 43*	116950	ወ/ሮ አስቴር በቀለ ጭጭ አይበሉ እና ተጠሪ የለም (ተጠሪ የሌለበት)	23/7/ 2008 ዓ.ም	259

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
54.	የጋብቻ የምስክር ወረቀት ተገቢውን ስርዓት ተከትሎ የተሰጠ አይደለም ተብሎ መሰረዝ ጋብቻ አልነበረም ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ፣	105694	አቶ ተሾመ ዘርፌ እና ወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኝ	27/7/2008 ዓ.ም	264
55.	የገጠር መሬት እንደሌላው ንብረት በመቁጠር ከቤተሰብ ህጉ አንጻር የሚታይ ስላለመሆኑ ፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በአንድ ተጋቢ ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ ቢፈፀምና ተጋቢዎቹ መሬቱን የጋራ ለማድረግ ሊስማሙ የሚችሉ ስለመሆኑ፣ *የአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 133/1999 አንቀጽ 24/3/ ደንብ ቁ. 151/1999 አንቀጽ 20/6/*	114279	ወ/ሮ ደስታ ታከለ እና አቶ ፀጋ ታዲያስ	30/7/2008 ዓ.ም	268
56.	ባል ወይም ሚስት የጡረታ አበል ተጠቃሚ ሆነው ባሉበት ፍቺ ቢከሰት የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነው ባል ወይም ሚስት የጡረታ አበል ለባል ወይም ለሚስት ሊያካፍል የሚገባ ስላለመሆኑ ፣ *የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 35*	113002	አቶ ባልቻ አበባ እና ወ/ሪ አልማዝ አሊ	28/8/2008 ዓ.ም	272

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
57.	በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የልጁ አባት ነው ተብሎ በህግ ግምት የሚሰጠው ሰው እሱ የሞተ ወይም ችሎታ ያጣ እንደሆነ ከተወላጆቹ አንዱ የመካድ ክስ በማቅረብ መቃወም የሚችል ስለመሆኑ፤ *የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/1992/አንቀጽ 167፣174 እና 179*	116119	ወ/ሮ ሙሉ በዳዳ እና እነ ወ/ሮ ኩሪ በዳዳ	22/9/2008 ዓ.ም	276
58.	የመጀመሪያ ሚስት በንብረትዋ ላይ ስምምነት ባላደረገችበት ፤ባል ሁለተኛ ሚስት ሲያገባ መቃወሚያ አላቀረበችም በማለት በንብረትዋ ላይም ስምምነት አድርጋለች በማለት በመደምደም ፤ሁለተኛ ሚስት እኩል እንድትካፈል በማለት የሚሰጥ ውሳኔ ህጋዊ ስላለመሆኑ	120844	አቶ ሃንደግባ ሸኩር እና ወ/ሮ አለምቱ ኢብራሒም	27/8/ 2008 ዓ.ም	279
59.	አንድ ሰው ህጋዊ ባለይዞታው ሳይቃወም በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ቤት ወይም ንብረት ያፈራ እንደሆነ የዚሁ ቤት/ ንብረት/ ባለመብት የሚሆን ስለመሆኑ፤ የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1179(1)(2) ከኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 አኳያ ሊታይ ስለሚችልበት አግባብ	105125	አቶ አህመድ ዑመር እና እነ አቶ ተስፋዬ አብርሃ /ሁለት ሰዎች/	05/3/2009 ዓ.ም	284

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ውርስ					291
60.	በፍ/ብ/ህ/ቁ. 842/3/ መሰረት የተተኪ ወራሽነት ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሊሟሉ ስለሚገባቸው ጉዳዮች፣	110040	እነወ/ሮእሴተማርያምአክሉ ግ (ሶስት ሰዎች) እና የለም	3/06/2008ዓ/ም	292
61.	ለአንድ ውርስ ወራሽ የሆነ አንድ ሰው ውርስ ከተከፈተ በኋላ የሞተ እንደሆነ የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባያወጣም ለውርሱ አይገባም እስካልተባለ ድረስ የወራሽነት መብቶች ለእርሱ ወራሾች የሚተላለፍ ስለመሆኑ	113529	ወ/ሮ እቴቱ ከንባው (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ሮ ቀለሟ ዓለማየሁ	28/6/ 2008 ዓ.ም	295
62.	አንድ ፍ/ቤት የውርስ ክርክርን አስመልክቶ የሚቀርብለትን የውርስ አጣሪዎች ቃለ- ጉባኤ ከማስጽደቁ በፊት በእርግጥ የውርስ ሀብት የማጣራት ሕጋዊ ሂደት ተከትሎ የተካሄደ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሕ/ቁ. 946፣950፣1062፣1079፣1080*	108328	ወ/ሮ ጫልቱ ዋቀዬ እና አቶ ፍቃዱ ዋቀዬ	13/7/2008 ዓ.ም	299
63.	ሟች በተወው ኑዛዜ መሰረት ውርሱ ሲጣራ እንዲሁም ኑዛዜው በፍ/ቤት ሲፀድቅ ተቃውሞ ሳያቀርብ ፣ ኑዛዜው ከፀደቀ በኃላ ኑዛዜው ይሻርልኝ በማለት የሚቀርብ ቅሬታ	118105	አቶ ተስፋዬ በቀለ እና እነ ወ/ሮ እሸቷ ጎሸዬ	23/1/ 2009 ዓ.ም	304

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ ፤ በሥር ፍ/ቤት ያልቀረበን ክርክር በይግባኝ ደረጃ ላይ ማቅረብ ተቀባይት የሌለው ስለመሆኑ፤ *ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 329 (1)*		(3 ሰዎች)		
64.	አንድ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወራሽነት መብቱን ለአካላ መጠን ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 15 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የውርሱን ንብረት ለመጠየቅ በይርጋ የማይታገድበት ስለመሆኑ ፤ *ፍ/ብ/ሕ/ቁ 198 ፣ 1000(2)*	120841	ወ/ሮ ካባ ተካ እና አቶ ድሪባ ዳዲ	23/1/ 2009 ዓ.ም	308
65.	የተሰጠ ወራሽነት ማረጋገጫ የተሰረዘ ከሆነ ፤በይግባኝ ካልተሻረ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተሰጠ የውርስ ባለቤትነት ውሳኔ የሰረዝልኝ ጥያቄን ክርክር ስምቶ መወሰን ያለበት እንጂ በቀድሞ ያልተነሳ የይርጋ ተቃውሞ በመቀበል ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ ፤	117435	አቶ ተስፋዬ መኮንን እና እነ ወ/ሮ ሰብለ ለማ (ሁለት ሰዎች)	24/1/2009 ዓ.ም	311
66.	የአንድ ሰው መብትና ግዴታ ለተወላጆቹ በውርስ ሊተላለፍ የሚችለው በሚቹ ምክንያት የሚቋረጡ ካልሆነ በቀር ሚቹ በሞተበት ቀን የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች ስለመሆናቸው፤	110680	ወ/ሮ ፅጌዳ በቀለ እና ወ/ሮ ፍቅርተ በቀለ	30/2/2009 ዓ.ም	314

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍ/ሕ/ቁ. 826/2/ ሚች የድርሻ መልቀቅ ውል ፈጽሞ ከዚያም ኑዛዜ ቢያደርግና ይኸው ኑዛዜ የድርሻ መልቀቁን ውል እስካልኑካ ድረስ የውሉን ተፈጻሚነት ሊያስቀር የማይችል ወይም በአዲሱ ኑዛዜ ተተክቷል ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፤ *የፍ/ሕ/ቁ. 900 እና 901*				
ባንክና ኢንሹራንስ					319
67.	የመድን ሥራ የሚሰሩ የመድን ኩባንያዎች በመድን ፖሊሲ ውስጥ ፖሊሲውን ተጠያቂነትን አያስከትልም ወይም በፖሊሲው መሰረት የካሳ ክፍያ ጥያቄ መነሻ የሆነው ክስተት ከደረሰ በኃላ የተወሰነ ድርጊት ከተፈፀመ ወይም ሳይፈፅም ከቀረ ኃላፊነቱ ቀሪ ይሆናል የሚል የውል ሁኔታ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ *አዋጅ ቁጥር 559/2000 በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1*	88135	ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ (አ.ማ) እና ወ/ሮ ነፃነት ሀቤቤ	16/11/ 2005ዓ.ም	320
68.	የመድን ውል ሽፋን ተጠቃሚ ለተገለገለበት ጊዜ በውሉ መሰረት የአርቦን ክፍያ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ ፤ የአርቦን ክፍያ በአንድ ወር ጊዜ ባለመጠየቁ ውሉ እንደተቋረጠ ስለሚቆጠር ክፍያውን የመጠየቅ መብት፤	117608	ኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና የኖሌ ካባ ወረዳ ጤና ጥበቃ ፅ/ቤት	23/1/2008 ዓ.ም	323

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ጉዳት ከደረሰም ኃላፊነት ለመውሰድ አይገደድም ከሚል መደምደሚያ ለብድር (ዱቤ) ላይ ለተመሰረተ ግንኙነት ተፈፃሚ ሰላለመሆኑ ፤ *የን/ሕ/ቁ 666 (4)*				
69.	ከአንድ በላይ የሆኑ ከሳሾች በጋራ በመሆን የህብረት ክስ ሊያቀርቡ ስለሚችልበት ሁኔታ የመድን ሰጪውና የመድን ተቀባዩ ባደረጉት የመድን ሽፋን ውል ላይ የማግለያ ድንጋጌ በስምምነታቸው እስካሰፈሩ ድረስ ይኸው ሊጠበቅ የሚገባ ስለመሆኑ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.35*	104544	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ፀጋብ ገብሩ	25/9/2008 ዓ.ም	328
70.	ለአንድ ንብረት የሚከፈለው የኢንሹራንስ ገንዘብ ***የመያዣ መብት ሳላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ይሰጣል*** የሚለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንሹራንስ ሰጪው ላልተከፈለ የአርቦን ክፍያ ኢንሹራንስ ገቢውን ከመጠየቅ ውጪ የመያዣ መብት ያለውን አካል መጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ የን/ሕ/ቁ.684(1)	115763	ብሔራዊ የኢትዮጲያ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ እና የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ	9/02/2009 ዓ.ም	334

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ወንጀል					337
71.	ፍ/ቤቶች የገንዘብ መቀጫን ሲወስኑ ከግምት እና ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገቡዋቸው የሚገቡ የተከሳሽ ግላዊና የወንጀሉን ሁኔታዎችን በማገናዘብና ፤ በወንጅል ህጉ እና በቅጣት መመሪያው ላይ የተቀመጡ መሰፈርቶችን መሰረት በማድረግ መወሰን ያለባቸው እንጂ በደፈናው የገንዘብ መቀጮ መወሰን ተገቢ ሰላለመሆኑ ፤ *የወ/ሕ/ቁ 88 /2/ እ 90 90 (2)፤ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2000*	88542	አቶ ቢሆነኝ ደምሴ እና የት/ብ/ክ/መ/ዓቃቤ ሕግ	17/11/ 2005ዓ.ም	338
72.	በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ሥርዓት ህግ መሰረት ክስ እንዲሻሻል መፍቀድ የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብትን የሚያጣብብ ነው የሚባል ስላለመሆኑ *የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 188፣119 ኢፌዴሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 20(1)*	116405	የኦ/ሥ/ፀ/ኮሚሽን ዐቃቢ ሕግ እና አቶ ቴዎድሮስ አብርሃ ቀለቲ	2/7/2008 ዓ.ም	342
73.	የወንጀል ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ ይሁን በይግባኝ ደረጃ የሚመለከት ፍ/ቤት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ የማስረጃውን አጭር መግለጫ፣ ማስረጃውን የተቀበለበትን እና	113143	የአ/ብ/ክ/መ/ፍትህ ቢሮ እና እነ አቶ ሕሊና ሀይሌ	30/7/2008 ዓ.ም	346

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ያልተቀበለበትን ምክንያቶች በፍርድ ላይ ማስፈር የሚገባው ስለመሆኑ፤ *የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 149/1/*		(ሦስት ሰዎች)		
74.	ከአንድ የወንጀል ድርጊት በኃላ ተከታትሎ የተፈፀመ ድርጊት ፤አንድን ወንጀል ከግብ ለማድረስ ሲል ተከታትሎ የተደረገ ድርጊት ከቀድሞ አሳቡና ሊደርስበት ከቀደው ግብ ጋር የተያያዘ በዋናው ወንጀል የሚጠቃለል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ የሚጣራበት አግባብ፤ ዓ/ሕግ ባስከፈተው የይግባኝ መዝገብ ላይ መ/ሰጭ ሕግን መሰረት አድርጎ የሚቀርበው ክርክር ተቀባይት ሊያጣ የማይገባው ስለመሆኑ፤ ወ/ሕ/ቁ 88(3)	119159	አቶ ደጀኔ መኮንን እና ፌ/ዓ/ሕግ	20/11/2008 ዓ.ም	353
75.	በእምነት ማጉደል ወንጀል ላይ የተቀመጠው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሓሳብ መርሕ ፤ ለከባድ እምነት ማጉደል ወንጀልም ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ፤ *ወ/ሕ/ቁ 675(3) እና 676 (2) (ሀ)*	118084	አቶ ንጉሴ አሊ እና ፌ/ዓ/ሕግ	21/11/2008 ዓ.ም	359

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
76.	የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የቅጣት ውሳኔ መመሪያ መሰረት በማድረግ በማረም የሚጠው ውሳኔ ከተጠየቀ ዳኝነት ውጭ ተሰጥቷል የሚያስብል ስላለመሆኑ *የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2002 አንቀፅ 21(1) (ሀ) ፣ ወ/ሕ/ቁ 184(!0 (ለ) እና 194 (1) (ለ)*	117877	አቶ ማሰረሻ ገሰሱ እና የፌ/ዓ/ሕግ	22/11/ 2008ዓ.ም	363
77.	በመከራ ደረጃ ለተፈፀመ ወንጀል ቅጣት እንደሚቀንስ በግልፅ በመመሪያ ቁ.2/2006 ላይ ባይደነገገም ነገር ግን በወንጀል ህጉ ቅጣትን በመለለው እንዲያቀል ለፍ/ቤቱ በተፈቀደበት ሁኔታ መሰረት ቅጣትን አቅሎ ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ ፤ *የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 አንቀፅ 24 ፣ የወ/ሕ/ቁ 31 እና 180*	119500	ወ/ሮ ፀሀይ ውብዬ እና ፌ/ዓ/ሕግ	22/11/ 2008ዓ.ም	367

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
78.	ለሽብር ተግባር የሚያገለግል ንብረት ይዞ መገኘት ወንጀል ተፈፅሟል የሚባልበት አግባብ፤ በልዩ ሁኔታ በህግ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሽ ከዞረባቸው ወንጀሎች ውጭ ፤ ዓ/ህግ የሚያቀርበውን ክስ የወንጀል ደንጋጌውን የሚያቋቁሙት የህጋዊ ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን የማሰረዳት ሸክም የመወጣት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፤ *የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 ፣ የወ/ሕ/ቁ 23(2) ፣ የፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥ 652*	102982	ት/ብ/ክ/መ/ዓ/ሕግ እና አቶ ቡሽራ ያህያ	26/11/ 2009ዓ.ም	371
79.	የጉምሩክ ወንጀል ጋር በተያያዘ ፤ተከሳሽ በወንጀሉ ጥፋተኛ ባይባልም ንብረቱ የሚወረሰው ስለድርጊቱ አፈፃፀም ሁኔታ የሚያሰረዳ አጥጋቢ ማስረጃ መቅረቡን ፍ/ቤቱ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው ስለመሆኑ ፤ *አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 104 እና አዋጅ ቁጥር 859/2006*	108550	ኢ.ገ.ጉ.ም.ባለስልጣን እና አቶ ልዑል ገዳሙ	26/11/ 2009ዓ.ም	375
80.	በአንድ የወንጀል ድርጊት በዋና ወንጀል አድራጊነት ወይም ግብረ አበርነት የተሳትፉ ተከሳሾች በግል ሁኔታዎች ሊኖር ከሚችለው ልዩነት በስተቀር ለተመሳሳይ የወንጀል አፈፃፀምና	101003	መክብብ ሞገስ እና የፌደራል ሥነ ምግባርና	2/3/2009 ዓ.ም	380

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የወንጀል ተሳትፎ ተመጣጣኝና ተመሳሳይ ቅጣት ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ቁጥር 196(1) ለሰበር ስርዓትም ተፈፃሚነት ያለውና ከተከሳሾች አንደኛው ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ የሆነበትና አያስቀርብም የተባለን ተከሳሽ ጭምር ሊያካትት የሚገባ ስለመሆኑ፡- *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25፣22* *የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፣4፣6* *የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ 2/2006 አንቀፅ.3(2)*		ፀረ ሙስና ኮምሽን		
81.	በወንጀል ተጠርጥሮ በህግ ከለላ ስር የሚገኝን ተጠርጣሪ በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ ባነሳ ጊዜ ተጠርጣሪው በከተማው ውስጥ ቋሚ የመኖሪያ /የመታወቂያ/ አድራሻ የለውም በማለት የዋስትና መብቱን መከልከል ህገ መንግስታዊ ስላለመሆኑ፣ *አንቀጽ 19/6/፣ 25 እና የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 69/ሀ/*	131863	መሐመድ እንድሪስ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ህዳር 8 ቀን 2009 ዓ.ም	386
82.	ወንጀል ፈጽሞ የተከሰሰን ህፃን ደህንነት ሊጠበቅበት ሥለሚችልበት አግባብ ለአዋቂ ጥፋተኞች የተደነገጉት መደበኛ ቅጣቶች ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ስለመሆኑ፡-	118130	ህጻን አይማሲ አገዘ እና የአማራ ክልል ዐ/ህግ	30/3/2009 ዓ.ም	391

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህግ መንግሥት አንቀጽ 36 (2)፣ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1)፣ የአፍሪካ የህፃናት መብቶች ደኅንነት ቻርተር በአንቀጽ 4 (1) *የወንጀል ህግ አንቀጽ 53 (1)፣ 157፣ 168* *የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ 171፣180*				
83.	የዋስትና መብት የሚነፈግባቸው ምክንያቶች ፍርድ ቤቶች ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር እየተመለከቱ ሊመዝኗቸው የሚገባቸው ስለመሆኑ አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም የማይመስል ነው ተብሎ ግምት የሚወሰደው በቂና ህጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆን እንደሚገባ፤ እንዲሁም ምክንያቶቹ በቂና ህጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከተለያዩ ከባባዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ስለመሆኑ *የወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67(ሀ)*	134228	አቶ ስማቸው ከበደ እና የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ	08/6/2009 ዓ.ም.	398

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
አፈፃፀም					417
84.	የጋራ ወራሾች ሀብት በሆነ ንብረት ላይ ከእንዳንዱ የጋራ ባለሀብቶች ላይ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያላቸው ሰዎች የባለድርሻውን ድርሻ ለመያዝ የሚችሉ ስለመሆኑ፣ በውርስ ሀብት እና የጋራ ወራሾች ያልተከፋፈሉ የውርስ ንብረት መካከል ስላለው ልዩነት *የፍ/ሕ/ቁ. 943፣1052፣1053፣1060 እና 1260*	117735	ህጻን ሣራ ማርቆስ እና እነ አቶ ስዩም አሰፋ(አምስት ሰዎች)	28/07/2008 ዓ.ም.	418
85.	አንድ ለፍርድ ማስፈጸሚያ በሐራጅ ይሸጥ የተባለን ንብረት በባለሙያው የተቀመጠውን የሐራጁ መነሻ ዋጋ አነሰ በማለት የሐራጅ ሽያጩ ተከናውኖ ውጤቱ ባልታወቀበት ሁኔታ የተጀመረው አፈጻጸም ቀሪ ይሁን ማለት ተገቢ ስላለመሆኑ፣	104943	አቶ ይልማ ፈለቀ እና አቶ ጥበቡ ፈለቀ	30/7/2008 ዓ.ም	424
ልዩ ልዩ					428
86.	አንድ ጠበቃ በገባው ውል መሰረት እስከ መጨረሻው ድረስ ጉዳዩን ከተከታተለና ከሙያው አንጻር እውቀትና ጥረቱን ተጠቅሞ አገልግሎት ከሰጠ የተፈለገው ውጤት ባለመምጣቱ ብቻ የተሟላ አገልግሎት አልሰጠም ሊሰኝ የማይችል ስለመሆኑ እና በውሉ መሰረት የተስማሙበትን የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ቀሪ ሊያደርገው የማይችል ስለመሆኑ	117907	እነ ወ/ሮ ዘውዱ ፍቅሬ እና አቶ አበራ ጌታነህ	22/9/2008 ዓ.ም	429

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
87.	አንድ ጠበቃ ሕግን የማስከበር ፣ፍትህን የማስገኘትና ለፍትህ አስተዳደሩ የማገዝ ኃላፊነቱን በመተው ተቃራኒ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየ መሆኑ ከተረጋገጠ የጥብቅና ፍቃዱ ሊሰረዝ የሚችል ስለመሆኑ *የአማራ ክልል የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ ምዝገባና የጠበቆች ሥነምግባር ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁ. 75/1994*	114888	አቶ አትሁነኝ አልማው እና የአ/ብ/ክ/ ፍትህ ቢሮ አቃቤ ህግ	20/3/2008 ዓ.ም	431
88.	በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ተይዞ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁለት /ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በህብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት በሆነ ጊዜ ከተከፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ እንደሆነ የፍርድ ባለእዳው እንደቀረበ ተቆጥሮ የተቀዳሚነት መብት የሚሰጠው ስለመሆኑ፣ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 443፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 126/1/፣ 1386-1409*	124618	እነ ወ/ሮ ደብካ መሰለ እና ሣጅን ሀይሉ ሞገስ	22/3/2009 ዓ.ም	440

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሥሪና ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 119639

ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
መስጠፋ አህመድ
ተፈሪ ገብሩ
ሽምሱ ሲርጋጋ
አብርሃ መሰለ

አመልካች -የደብረዘይት ሄልሜክስ ቄራ ድርጅት- ተወካይ ፀጋ መርጋ ቀረቡ

ተጠሪዎች - 1.አየለ ዲባባ
2. ግርማ ፍቃዱ } ጠበቃ አቦነሽ በላቸው ቀረቡ
3. መኮንን ሳህለ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪዎች በአድአ ወረዳ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ በድርጅቱ ውስጥ በቆዳ መግፈፍ እርድ ሥራ መደብ ተቀጥረው ሲሰሩ ቆይተው ተከሳሽ ድርጅት በቀን 14/06/2007 እና በ16/06/2007 በተጻፈ ደብዳቤ የስራ ዉሉን አቋርጦ ያላግባብ ከስራ ያሰናበታቸው በመሆኑ እና በደብዳቤ የተገለፁት ምክንያቶች የስራ አስኪያጅ ትዕዛዝን አለመቀበል፤ ስራን በመሰልቸት ማጓተት፤ በቀን 8 ሰዓት አለመስራት፤ እንዲሁም ከስጋ መጫን ጋር የተያያዘ ሲሆን አንቀበልም ያልንዉ የስራ አስኪያጅ ትዕዛዝ ባለመኖሩ፤ ስራን ያላጓተትን በመሆኑ፤ እንደ ህጉ ሙሉ የስራ ሰዓት አንሰራም ያላልን በመሆኑ እና የተቀጠርንበት የስጋ መግፈፍ ቢሆንም በተጨማሪ ስንታዘዝ ለስጋ መጫን የተቀጠሩትን አግዘን ስንጭን የነበረ በመሆኑ የተጠቀሱት ምክንያቶች በሙሉ ሆነ ተብለው ከስራ ለማሰናበት በተከሳሽ ድርጅት የተፈጠሩ በመሆኑ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ ልዩ ልዩ ክፍያ ይከፈለን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሹ ለክሱ በሰጠው መልስ በቆዳ መግፈፍ ሥራ ላይ የተሰማሩ ቢሆንም እነሱ ስራ በሌላቸው ጊዜ ተከሳሽ ሌላ ስራ ማሰራት እንደሚችል በህጉ የተፈቀደ በመሆኑ፤ ሰራተኛው ምን አይነት ስራ ቢሰራ ትርፍ ያስገኛል የሚለውን ከግምት በማስገባት ሰራተኛውን ከተቀጠረበት ስራ ዉጪ ማሰራቱ ከስራ ስምሪት ስልጣን የመነጨ መብት በመሆኑ፤ ከሳሾች ታዘው ስራ አንሰራም ስላሉ ስጋ በጊዜ ሳይጫን ቀርቶ በምን አገባኝነት የተከሳሽ ንብረት እንዲጠፋ ስላደረጉ ተከሳሽ በአዋጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 377/1996 መሰረት ያለማስጠንቀቂያ አሰናብቷል። ነገር ግን ከሳሾች በ17/06/2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ወደ ስራ ለመመለስ ጠይቀዉ ተከሳሽ ወደ ስራ የመለሳቸው ቢሆንም በገዛ ፈቃዳቸው ስራውን ትተው ክሱን ያቀረቡ በመሆኑ መሰናበታቸው ህጋዊ ነው ይባል፤ ከዓመት ዕረፍት በቀር ሌሎች ክፍያዎችም ሊከፈሏቸው አይገባም በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሳሽ ያቀረበው መከራከሪያ በራሱ ምስክሮች ጭምር አለመረጋገጡን በመጥቀስ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ብሎ ተከሳሽ በአዋጁ መሰረት ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ለከሳሾች እንዲከፍል ወስኗል። ይግባኙ የቀረበለት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔዉን በማሻሻል በአንቀፅ 38 መሰረት ክፍያ ለዘገየበት የተወሰነውን ቅጣት በመሻር ሌላው የውሳኔ ክፍል እንዲፀና ወስኗል። አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል።

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው። አመልካች ህዳር 2/2008 ዓ.ም ያቀረቡት ማመልከቻ ተመርምሮ ለተጠሪዎች የተሰጠው ስራ ቀድሞ ሲሰሩት ከነበረው ስራ ጋር ተያያዥነት (ተመሳሳይነት) ያለው መሆን አለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ተጣርቶ የመወሰን አለመወሰኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል። ተጠሪዎችም ቀርበው ታህሳስ 14/2007 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የተቀጠሩበት የቆዳ ገፋፊነት ስራ ከጭነት የስራ መደብ የተለየ መሆኑን እና ለሽክም ስራውም አልታዘዙም የተባለው ከእውነት የራቀ መሆኑን በመጥቀስ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቀዋል። አመልካቹ ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል።

ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የሰበር አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል።

እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ለማሰናበት ምክንያት ያደረገው የስራ ሰዓትን ተከትሎ በትጋት አለመስራትንና ከስራ መደባቸው ዉጭ የጭነት ስራ እንዲሰሩ ሲታዘዙ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ አክብረው አለመስራታቸውን ሲሆን ተጠሪዎች የተጠቀሱት ምክንያቶች ሆነ ተብሎ ለስንብት የተዘጋጁ ናቸው በማለት በመካድ ተከራክረዋል። በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (7) እንደተመለከተው ማንኛውም ሠራተኛ በስራ ዉሉ እና በስራ ደንቡ መሰረት በአሰሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ የመፈፀም እንዲሁም የአዋጁን ድንጋጌዎች፤ የህብረት ስምምነትን፤ የስራ ደንብንና በህግ መሰረት የሚተላለፉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን የማክበር ግዴታ አለበት። አመልካች በዚህ የህጉ አግባብ ስራውን በመምራት ለስራው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውጤታማነትና ቅልጥፍና የሚረዱ የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሰራተኞችን ለስራ የማሰማራት ተግባር እንዲያከናውን የተፈቀደለት ቢሆንም ለስንብቱ የተጠቀሱት ምክንያቶች መኖራቸውን፤የሰጠው ትዕዛዝም አለመከበሩን የማስረዳት ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የተካደውን ፍሬ ነገር በማስረጃ ለማጣራትና ማስረጃንም ለመመዘን ስልጣኑ የተሰጠው የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎች ሰምቶ ተጠሪዎች ለስንብቱ የተጠቀሱትን ምክንያቶች አለመፈፀማቸውን አረጋግጫለሁ በማለት የስንብቱን ህገ ወጥነት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች የስራ ግዴታቸውን አለመወጣታቸዉን በማንሳት አመልካች ያቀረበውን ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ ስላላስረዳ የስራ ውሉን ማቋረጡ ህገወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ የአሰሪና ሰራተኛ የአዋጁን ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ያገናዘበ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘንውም፡፡ ስለሆነም በውሳኔው የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስላላገኘን ተከታዩን ውስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 41726 በ23/10/2007ዓ.ም. ተሻሽሎ የተሰጠው ፍርድ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 229654 በ04/02/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 6/2008 ዓ.ም በዋለ ችሎት የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ 121063

የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች ፡- መ/ርት ሙሉነሽ መለሰ ወኪል ገ/አምላክ አበጋዝ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዋሊያ አጠቃላይ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በአ/ብ/ክ/መንግስት ጎንደር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በመምህርነት የስራ መደብ ላይ ከ2004 ዓ/ም እስከ 2007 ተቀጥረው ስራቸውን ሲሰሩ እንደነበር፣ በስራቸው ላይ እያሉ ነፍሰጡር የነበሩ ቢሆንም የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሳይወስዱ በመውለዳቸው በህጉ የተጠበቀላቸውን የድህረ ወሊድ ፈቃድ በመጠቀም ላይ እያሉ ያልተጠቀሙበትን የቅድመ ወሊድ ጊዜ በድህረ ወሊድ በመጠቀም ወደ ስራቸው ሲመለሱ ተጠሪ አመልካች ከስራ ተሰናብተሻል ያላቸው መሆኑንና ይህም ከህጉ ይዘትና መንፈስ ውጭ መሆኑን ጠቅሰው የተጠሪ እርምጃ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ አመልካች በራሳቸው ጊዜ ያልተጠቀሙበትን የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ለድህረ ወሊድ መጠቀማቸው ህጋዊ ያለመሆኑና ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖር ከስራ ገበታቸው በመቅረታቸው መሰናበታቸው ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሳይጠቀሙ በድህረ ወሊድ ጊዜ መጠቀማቸውና ከስራ መቅረታቸው ህጋዊ አይደለም በማለት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት በዚህ ረገድ የተጠየቁትን የአመልካች ክፍያዎችን ውድቅ አድርጎ ከህዳር 01 ቀን እስከ ህዳር 12 ቀን 2007 ዓ/ም ድረስ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ ብቻ ይክፈላት ሲል ወስኗል፡፡ አመልካችም በውሳኔው ቅር በመሰኘት ቅሬታውን ለሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ፍ/ቤትና ቀጥሎም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም በሁለቱም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ከፍ ሲል በተገለጸው መልኩ የተሰጡትን ውሳኔዎች በመቃወም ለማስቀየር ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በቅድመ ወሊድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጊዜ ያልተጠቀመችበት የአንድ ወር የእረፍት ጊዜ በድህረ ወሊድ ጊዜ ከሚሰጠው ሁለት ወር የእረፍት ጊዜ ጋር መጠቀም አትችልም በማለት የሰጡት ውሳኔ የህጉን መንፈስና ይዘት ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ አንድ ሴት ከወለደች በኋላ ከአራት ወራት በፊት ከስራ መሰናበት የለባትም ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 87/4/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ እንዲሁም በሌሎች የመንግስት ሰራተኞች ህግጋት የተመለከተውን የመብት ጥበቃና የህግ አተረጓጎም ያልተከተለ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት የህግ ትርጉም ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪም ቀርበው መልስ ሊሰጡ ስላልቻሉ መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሰረቱ የአሰሪና ሰራተኛ ህጉ በአንድ በኩል ሰራኛው ያለአግባብ ከስራ እንዳይፈናቀል ጥበቃ የሚያደርግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የኢንዱስትሪ ሰላምን በመፍጠር የምርትና ምርታማነት እድገቱ እንዲጨምር ዋስትና ሲጪም እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡ ይሄንኑ መሰረታዊ ሐሳብ መነሻ ባደረገ መልኩ ብሎም የኢንዱስትሪ ሰላሙን ከመጠበቅ አኳያ አንድ ሰራተኛ በአዋጅ ቁ/ 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል “ሀ” እስከ “በ” ባሉት ስር የተዘረዘሩትን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ አሰሪው ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል መደንገጉን ከህጉ አጠቃላይ ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 87/6/ ድንጋጌ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

እንዲሁም ህጉ ለተለዩ የሰራተኛ ክፍሎች የተለዩ ጥበቃ የሚያደርግባቸው ምክንያቶች መኖራቸውን ህጉ ያሳያል፡፡ ህጉ በአዋጅ አንቀጽ 14፣ ከአንቀጽ 87 እስከ 88 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች በተለየ መልኩ ድንጋጌዎችን ከአስቀመጠላቸው ሰራተኞች መካከል ሴት ሰራተኞች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች በአንድ በኩል ሁሉንም ሴት ሰራተኞችን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተለየ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሴት ሰራኞችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ እርግዝናና ወሊድ ደግሞ ሴቶችን በተለያየ ሁኔታ ውስጥ እንዲገኙ የሚያደርጉ ሁኔታዎች በመሆናቸው በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ሴቶች ህጉ ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ ወሊድን በተመለከተ ህጉ ለሴቶች የሚያደርገው ልዩ ጥበቃ የቅድመ ወሊድና የድህረ ወሊድ ፈቃድ ከክፍያ ጋር የማግኘት መብትና እንዲሁም በሌላ ጊዜም ሀኪም እንድታርፍ ካዘዘ ከክፍያ ጋር እረፍት የማግኘት መብት ስለመሆናቸው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 88 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ እንዲሁም አሰሪው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰራተኛዋ ነፍሰ ጡር ከሆነችበትና ከወለደችበት ቀን ጀምሮ በአራት ወራት ውስጥ ከስራ እንዲያሰናብታት ህጉ ጥበቃ የሚያደርግ መሆኑን ከአዋጅ አንቀጽ 87/5/ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ባልወሰዱበት ሁኔታ የወለዱ ሲሆን በአዋጅ አንቀጽ 88/3/ የተጠበቀላቸውን የስልሳ ቀን የድህረ ወሊድ ፈቃድ ከክፍያ ጋር አግኝተው በቅድመ ወሊድ ጊዜ ሊጠቀሙ ይችሉ የነበረውን የሰላሳ ቀን የወሊድ ፈቃድ በህጉ የተጠበቀላቸው የድህረ ወሊድ ጊዜ ሲያልቅ አንድ ላይ በመጠቀም ላይ እያሉ ተጠሪ በህጉ የተጠበቀላቸው የድህረ ወሊድ ጊዜ በማለቁ አመልካች ስራ ላይ አልተገኘም በሚል የስራ ውልን ያቋረጠባቸው መሆኑን ክርክሩ ያሳያል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አንዲት ሴት በእርግዝና ምክንያት በህጉ የተጠበቀላት የቅድመ ወሊድና የድህረ ወሊድ ፈቃድ ጊዜ የሚታወቅ መሆኑን ህጉ ቢያስቀምጥም በቅድመ ወሊድ ጊዜ በህጉ የተጠበቀላትን የፈቃድ ጊዜ ሳትጠቀም ብትወልድ በቅድመ ወሊድ ጊዜ ይሰጥ የነበረው ፈቃድ ያልተጠቀመች ሴት ሰራተኛ ይህንኑ ጊዜ በድህረ ወሊድ ጊዜ መጠቀም የምትችል መሆኑን ያለመሆኑን ግን ህጉ በግልጽ አያስቀምጥም፡፡ ይሁን እንጂ ህጉ ከወሊድ በኋላ አንድ ሴት ሰራተኛ አራት ወር ሳይሞላት ከስራ ልትሰናበት እንደማትችል በአዋጅ አንቀጽ 87/5/ ስር የተመለከተው ድንጋጌ በህጉ ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የህግ አተረጓጎም ደንቦች ያስገነዝባሉ፡፡ አንድ ልዩ ህግ አግባብነት ባለው ድንጋጌ ውስጥ ግልጽ የሆነ መፍትሔ ካላስቀመጠ ይኸው ድንጋጌ ባለበት ክፍልና ምእራፍ ስር ያሉትን ድንጋጌዎች አስተሳስሮ በማየት ተገቢውን ትርጉም መስጠት የህግ ትርጉም ደንቦች የሚፈቅዱት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች በአዋጅ አንቀጽ 25፣ 27 እና 29/3/ ድንጋጌዎች አግባብ ካልሆነ በስተቀር ከወሊድ በኋላ አራት ወራት ውስጥ ከስራ ያለመባረር መብት ያላቸው መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 87 /5/ እና /6/ የሚያስቀምጥ በመሆኑና ተጠሪ ደግሞ ለስንብቱ ህጋዊ ምክንያት ነው በማለት የሚያቀርበው ክርክር በአዋጅ አንቀጽ 27 /1/ለ// ድንጋጌ ስር የተመለከተውንና ህግ አውጪው ከወሊድ ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ ተቀባይነት ያለውን ድንጋጌ በመጥቀስ በመሆኑና የአመልካች ከስራ መባረር ከዲሲፕሊን ወይም ከቅነሳ ስርዓት ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ ባላስረዳበት ክርክሩ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች በህጉ ያለውን ክፍተት በማየት ተገቢውን የህግ አተረጓጎም በመከተል ለጉዳዩ በአዋጅ አንቀጽ 87/5/ የተመለከተውን ጥበቃ ተግባራዊ ማድረግ ሲገባቸው ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት የሌለውን የአዋጅን አንቀጽ 88 /4/ ድንጋጌን መሰረት በማድረግ መወሰናቸው ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው የህግ ትርጉም አተገባበር ሆኖ አልተገኘም፡፡ ቀጥሎ መታየት ያለበት ውጤቱ ነው፡፡ የስራ ውል የተቋረጠበት አግባብ ከሕግ ውጭ ነው ከተባለ ውጤቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 42 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የጠየቁት የተለያዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 35/1/ለ/ መሠረት የሁለት ወር ደመወዝ፣ ክፍያ ለዘገየበት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 38 መሠረት የሁለት ወር ደመወዝ፣ በአዋጅ አንቀጽ 43/4/ሀ/ ደግሞ ካሳ በህጉ በተቀመጡት ስሌቶች መሠረት አመልካች ሊከፍላቸው ይገባል ብለናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የዓመት እረፍት የጠየቁ በመሆኑና ተጠሪ ደግሞ አመልካች የወሰዱ ስለመሆኑ ገልጾ የሚከራከር በመሆኑ አመልካች የአመት እረፍት ያልተጠቀሙ መሆን ያለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተጣርቶ እንዲወሰን ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሌላው አመልካች የጠየቁት የዳኝነት ጥያቄ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ክፍያ ከድህረ ወሊድ ፍቃድ መጠናቀቅ በኃላ ለነበረው ጊዜ ስራ ስላልሰሩ በአዋጅ አንቀጽ 377/96 አንቀጽ 54 መሠረት እንዲከፈላቸው ማድረግ ሕጋዊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተጠየቀው ክፍያ ህጋዊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0122481 በ16/06/2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0123818 በ30/06/2007 ዓ.ም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 46890 በ18/02/2008 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው ከሕግ ውጪ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለአመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 35/1/ለ/ መሠረት የሁለት ወር ደመወዝ፣ ክፍያ ለዘገየበት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 38 መሠረት የሁለት ወር ደመወዝ፣ በአዋጁ አንቀጽ 43/4/ሀ/ ደግሞ ካሳ እና በአንቀጽ 39 እና 40 መሠረት ደግሞ የአገልግሎት ክፍያ በህጉ በተቀመጡት ስሌቶች መሠረት ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡ የአመት እረፍትን በተመለከተ ግን አመልካች የወሰዱ መሆን ያለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተጣርቶ እንዲወሰን ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ በዚህ ረገድ የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ከድህረ ወሊድ ፈቃድ በኃላ ላለው ጊዜ አመልካች የሚከፈላቸው ደመወዝ የለም ብለናል፡፡
4. የሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራን ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 98771

ሚያዝያ 24 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ታረቀኝ መኮንን } ጠበቃ - አቶ ጥጉ ደመመ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፋንታነሽ አረጋ }

ተጠሪ፡- አቢ ሚፍታህ ኤጀንሲ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው የአሁን አመልካቾች በስር ፍርድ ቤቶች የቀረበው ክስ እልባት ማግኘት የሚገባው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 632/2004 የሚደነግግ በመሆኑ ጉዳዩ ልዩ ችሎት የተቋቋመለት ስለሆነ በመደበኛው ፍትሐ ብሔር ችሎት አይታይም በማለት መዝጋቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የአመልካቾች ልጅ ኩየት የቤት ሰራተኛነት ተቀጥራ ሄዳ አሰሪዎቿ ተገቢውን ጥንቃቄ ለድህንነትዋ ተገቢው እንክብካቤ ሳይደረግላት መቅረቱ በካርቦን ጭስ መርዝ ታፍና በሞት ተለይታለች፡፡ አመልካቾች በልጃቸው ሞት ምክንያት ኩየት ሆና በገንዘብ ትረዳቸው ስለነበር የተቋረጠባቸው ጥቅም ለማግኘት በኃላፊነት ወደ ኩየት አገር ለላካት በተጠሪ ላይ በፌ/የመ/ደ/ፍ/በት አራዳ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት ከውል ውጭ ኃላፊነት ክስ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት የሚታይ ስለሆነ ለስራ ክርክር ችሎት የሚቀርብ ነው በማለት እንዲዘጋ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም አመልካቾች ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚሸፈን አይደለም፡፡ ይህ ጉዳይ ከውል ውጭ ኃላፊነት በተደነገገው በፍ/ብ/ህ/ቁ.2035፤2090፤2091 ነው መታየት ያለበት ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲታረም በማለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ በመመርመር ስህተት የለውም በማለት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትእዛዝ ላይ የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባ ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን በዚህ መሰረትም ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፤ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

አመልካቾች ጉዳዩ መታየት ያለበት ከውል ውጭ ኃላፊነት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(1)(2)(መ) በቤት ሰራተኛነት በትርፍ ላልተመሰረተ የአግልግሎት ቅጥር የማይሸፍን መሆኑ ህጉ በግልፅ ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይም የፌዴራል ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 74111 ከውል ውጭ ኃላፊነት እንደሚታይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በሌላ በኩል በመ/ቁ. 419560 ፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት ክስ አቅረበን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 መሰረት አይሸፈንም በሚል መዝገቡ ተዘግቶብናል፡፡ በይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.130500 ጉድለት የለበትም በማለት ዘግቶታል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የህግ ክርክሮች ሳያዩትና ሳይመለከቱ ሳይመረምሩ መዝገብ በመዝጋት የሰጡት ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ጥሰት ነው ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤቶች ትእዛዝ በመሻር ጉዳዩ በመመሪያ ወደ ታች ፍርድ ቤት ተመልሶ ከውል ውጭ ኃላፊነት ታይቶ እንዲወሰን አመልክተዋል፡፡

በተጠሪ በኩል ደግሞ ግንኙነቱ የስራ ውል ነው፡፡ በስራ ላይ እንዳለች በደረሰባት ጉዳት መሞቷን የተገለፀ ስለሆነ አዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀጽ 4፤20 ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3፤110 መሰረት የሚስተናገድ ነው፡፡ የአመልካቾች ልጅ ከተጠሪ ጋር የሥራ ውል ስምምነት በማድረግ በውጭ ሀገር ለስራ ለሶስተኛ ሰው አገልግሎት እንድትሰጥ በህጋዊ መንገድ የሄደች በመሆኑ አመልካቾችም በስራ እንዳለች በደረሰባት ጉዳት መሞቷን የገለፁ ስለሆነ በመካከላችን የሚኖረው ክርክር አፈታት አዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀጽ 4 በግልፅ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ይታያል በማለት በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 632/2001 እና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መታየት አለበት ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 /2/መ/ መሰረት ለትርፍ በሚካሄድ ስራ ላይ ያልተመሰረተ የግል አገልግሎት ቅጥር ላይ ህጉ ተፈፃሚነት እንደሌለው በግልፅ የተደነገገ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀጽ 3/2/ መሰረት ደግሞ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 /2/መ/ ቢኖርም ለትርፍ በሚካሄድ ስራ ላይ ላልተመሰረተ የግል አገልግሎት ስራ ላይ ለመቀጠር ወደ ውጭ አገር በሚሄድ ኢትዮጵያዊ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ሲል ተደንግጓል።

ስለዚህ የቤት ሰራተኛ ወደ ውጭ የተላከ ከሆነ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ በዚህ ረገድ በአመልካቾች የቀረበው ተቀባይነት የለውም። በአዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀጽ 4 መሰረት የግል ስራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ እና በሰራተኛ የሚነሳ ማንኛውም የስራ ክርክር የሚፈታው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ እንደሚታይ ተመልክቷል። አዲስ በወጣው የኢትዮጵያ የውጭ አገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 አንቀጽ 71 በሰራተኛ መሰረት እና በአሰሪው ወይም በኤጀንሲው መካከል ካለው የስራ ግንኙነት በመነጨ ማንኛውም የመብትና የጥቅም ክርክር ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት በተቋቋመ የስራ ክርክር ችሎት ይታያል በማለት ተደንግጎ ይገኛል።

በአጠቃላይ የአመልካቾች ጉዳይ በውል የስራ ግንኙነት የተመሰረተ በልጃቸው የደረሰው ጉዳት መስተናገድ ያለበት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሆኑን በዝርዝር ከላይ እንደተመለከተው ነው። ስለሆነም በአመልካቾች የሚቀርበው ጉዳዩ መታየት ያለበት ከውል ውጭ ኃላፊነት ነው የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም። በሌላ በኩል አመልካቾች በመጀመሪያ ጉዳያቸው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት አቅርበው ፍርድ ቤቱም በእንደዚህ አይነት የስራ ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 337/1996 አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት ሊሸፈን የማይችል እና የክርክር መንፈስም ፍርድ ቤቱ የማየት ሥረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት የተዘጋ መሆኑን ከመ/ቁ.41956 ጥር 15 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከተሰጠው ትእዛዝ መገንዘብ ይቻላል። ይህ የሚያመለክተው ደግሞ አመልካቾች ጉዳያቸውን በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጣቸውና መብታቸውን ለማስጠበቅ በተለያየ ጊዜ ከመጠየቅ ያልተቆጠቡና ጥረት ያደረጉ መሆናቸውን ነው።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ትእዛዝ በህጉ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው የምንልበት ምክንያት አልተገኘም። ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁ.147425 የካቲት 13 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ እና የፌ/መ/ደ/ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.111396 ታህሳስ 11 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾች ክሱን ማቅረብ የሚገባቸው ለስራ ክርክር ችሎት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117862

ሰኔ 20 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች - መስፍን አህመድ
ተፈሪ ገብሩ
ሽምሱ ሲርጋጋ
አብርሃ መሰለ
ፈይሳ ወርቁ

አመልካች - ጎል ኢትዮጵያ ነ/ፈ መስሐረድ ደሳለኝ ቀረቡ

ተጠሪ - አቶ ዲዲሞ አጋቶ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በጋምቤላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአመልካች ድርጅት ውስጥ በመዛኝ የስራ መደብ ተቀጥሬ እያገለገልኩ እያለ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1)(ለ) ከተደነገገው ውጭ የስራ ውሉን ያቋረጠ በመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 43(2) መሰረት ወደ ስራዬ እንዲመልሰኝ ወይም ጥቅማ ጥቅም ተከፍሎኝ እንዲያሰናብተኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ለቅርብ አለቃቸው ሆነ ለሌላ ለሚመለከተው አካል ሳያሳውቁ ለቀሩባቸው ሰባት ቀናት በቂና ህጋዊ ምክንያት ባለማቅረባቸው ከስራ መባረራቸው በአዋጁ አንቀጽ 27(1) መሰረት ህጋዊ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ማስረጃውን መርምሮ ከሳሽ በአያቱ ሞት ምክንያት ሃዘን ላይ እንደነበር የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረቡ በሃዘን ምክንያት በአዋጁ አንቀፅ 81(1)(ለ) መሰረት የሚሰጠው ፈቃድ እና የሳምንት የእረፍት ፈቃድ ተካቶ ሲሰላ ከስራ ያለምክንያት ቀርቷል ሊባል የሚችለው ለሁለት የስራ ቀናት ብቻ በመሆኑ ስንብቱ ህገወጥ ነው፤ ስለሆነም ድርጅቱ ሰራተኛውን ወደ ስራው እንዲመልስ ወደ ስራው መመለስ ካልፈለገም ክፍያ እንዲፈፅም ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ቅሬታቸውን ለጋምቤላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ጳጉሜ 2/2007 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ተጠሪ 5 (አምስት) ቀናት በመደዳው ያለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረቱ በተረጋገጠበት ስንብቱ ህገወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁን ዓላማ እና ይዘት በአግባቡ ያገናዘበ መሆኑን ለማጣራት ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጥሪያውን ተረክበው መልስ በሚሰጥበት ቀን ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

ከላይ ባጭሩ ለመግለፅ የሞከርነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ቅሬታ በቀረበበት ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ቢኖር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው አመልካች በሰበር ቅሬታቸው ተጠሪ ለድርጅቱ ሳያሳውቁ ከየካቲት 23 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ መቅረታቸውንና፤ በዚህም መነሻ ድርጅቱ ከየካቲት 27 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከተጠሪ ጋር የነበረው የቅጥር ውል መቋረጡን የሚገልፅ ደብዳቤ መፃፉን በመካድ አልተከራከሩም፡፡ የስንብት ደብዳቤውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ከስራ ከቀሩ በአስራ ሁለተኛው ቀን ማለትም መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ.ም ወደ ድርጅቱ መመለሳቸውን እና ባቀረቡት የሀዘን ማስረጃ የሚሰጠው ሶስት የረፍት ቀናት እንዲሁም የበዓል እና እሁድ ቅዳሜ የረፍት ቀናት ቢቀነሱ በአዋጁ አንቀፅ 27(1)(ለ) ከተመለከተው ጊዜ በላይ ያለምክንያት ከስራ መቅረታቸውን ስለሚያሳይ ስንብቱ ህጋዊ ነው እንዲባል ተከራክረዋል፡፡

በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27(1)(ለ) እንደተደነገገው በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ያለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረት አሰሪው የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ ያስችለዋል፡፡ ከድንጋጌው መረዳት እንደሚቻለው ሰራተኛው ከስራ የቀረበት ቀን የሚቆጠረው እና የቀረበትም ምክንያት በቂ መሆን አለመሆኑ የሚመዘነው የስራ ዉሉ ፀንቶ እስከቆየበት ጊዜ ድረስ ነው፡፡ ከዚህ በቀር የስራ ውሉ ከተቋረጠ በኋላ ላሉ ቀናት ሰራተኛው በስራው እንዲገኝ ስለማይጠበቅ የቀረበትን ጊዜ መቁጠር እና የቀረበትን ምክንያት በቂነት መመዘን አያስፈልግም፡፡

በመሆኑም በተያዘው ጉዳይ አመልካች ሠራተኛው ለድርጅቱ ሳያሳውቅ ከየካቲት 23 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ መቅረቱንና፤ በዚህ ምክንያት ድርጅቱ ከየካቲት 27 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከተጠሪ ጋር የነበረው የቅጥር ውል መቋረጡን የሚገልፅ ደብዳቤ መፃፉን ሳይክዱ ሰራተኛው መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ.ም ወደ ድርጅቱ መመለሱን መሰረት በማድረግ ከየካቲት 23 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ሲታሰብ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ያለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረቱን ያሳያል ስለሆነም ስንብቱ ህጋዊ ሊባል ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ መሠረት ያላደረገ፤ ድንጋጌውን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያበቁ ሁኔታዎችን ያላሟላ ክርክር በመሆኑ የምንቀበለው አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት በሕጉ ከተደነገገው ውጭ እንዲሰናበት ተደርጓል ስለሆነም ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት ወደ ስራው እንዲመለስ ወይም ለዚህ ዓይነት ሕገ-ወጥ ስንብት ሊከፈል የሚገባው ክፍያ እንዲከፈል ያሳለፉት ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላላገኘነው በአብላጫ ድምፅ ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የጋምቤላ ከተማ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00700/07 በቀን 8/10/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የጋምቤላ ክፍ/ፍ/ቤት በ14/11/2007 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በፍ/ሰ/መ/ቁ 00431/07 በ26/12/2007 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ፍርድ ቤት መስከረም 12/2008 ዓ.ም አፈፃፀሙ እንዲታገድ ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የልዩነት ሐሳብ

ተጠሪው ከ23/06/2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 03/07/2007 ዓ.ም በስራ ላይ ያልነበሩ መሆኑ እና ወደ ስራ ቦታው የመጡት በ04/07/2007 ዓ.ም መሆኑ የተረጋገጠ እና ክርክር ያልቀረበበት ጉዳይ ነው ። ተጠሪው ከስራ ከቀሩባቸው ቀናት መካከል የሀዘን ፈቃድ ነው ተብሎ በአመልካቹ ተቀባይነት ያገኘው ሶስት ቀን ሲቀነስ ተጠሪው ከስራ የቀሩት በመደዳው ከአምስት የስራ ቀናት በላይ ነው። ተጠሪው ከስራ የቀሩበትን ቀን በማስላት ከስራ የተሰናበቱት ከ23/06/2007 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ አመልካች በስንብት ደብዳቤው የገለጸ ቢሆንም ደብዳቤው የተጻፈው በ09/07/2007 ዓ.ም ነው። አመልካቹ የሥንብት ደብዳቤውን ከ24/06/2007 ዓ.ም ጀምሮ መጻፍ ሲችል እስከ 09/07/2007 ዓ.ም ድረስ ያዘገየው ተጠሪው የቀሩበትን በቂ ምክንያት ያቀርቡ ቢሆን ለመጠባበቅ እና እድል ለመስጠት ነው ከሚባል በቀር በሌላ አግባብ ሊተረጎም የሚገባው ሆኖ አላገኘሁትም። የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ለ/ ድንጋጌ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት ወይም በአንድ ወር ውስጥ በጠቅላላው ለአስር የስራ ቀናት ወይም በአንድ ዓመት ውስጥ ለሰላሳ የስራ ቀናት ያለበቂ ምክንያት ከስራ መቅረት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችል መሆኑን ከመደንገግ አልፎ አሰሪው በዚህ ድንጋጌ መሰረት ውሉን ስለማቋረጡ በደብዳቤው ካልገለጸ በቀር ከስራ መቅረቱ በራሱ የሥራ ውሉን አያቋርጥም የሚል ይዘት የለውም። በመሆኑም ሰራተኛው ያለበቂ ምክንያት በመደዳው ለአምስት የሥራ ቀናት ከስራ መቅረቱ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት የስራ ውሉ ያለማስጠንቀቂያ የሚቋረጥ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባው ነበር በማለት ስማችን በተራ ቁጥር አንድ እና አራት የተመለከቱት ዳኞች የልዩነት ሀሳባችንን አስፍረናል ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 125004

ሰኔ 22 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- አዲስ ፋና ጠቅላላ ሸቀጣ ሸቀጥ እና ሆቴሎች ንግድ አ.ማ.

- ነ/ፈጅ ወንድሜነህ ተገኘ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሊቁ ብርሃኑ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ተጠሪው በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በ27/11/2007 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አመልካች ተጠሪን ይሰሩበት ከነበረው የባህርዳር ቅርንጫፍ ከ13/08/2007 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ጅማ ቅርንጫፍ ያዛወራቸው መሆኑን፣ የዝውውር ደብዳቤው በ07/08/2007 ዓ.ም. የተጻፈ ሆኖ ለተጠሪው የደረሰው በ09/08/2007 ዓ.ም. መሆኑን፣ ተጠሪው ወደ ተዛወሩበት ቦታ ሳይሄዱ በባህርዳር ቅርንጫፍ ሲሰሩበት የነበረው የስራ መደብ ሳይሰረዝ ወደ ጅማ ቅርንጫፍ እንዲዛወሩ የተደረገው አለአግባብ መሆኑን ገልጸው ዝውውሩን በመቃወም ለምዕራብ አማራ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በ16/08/2007 ዓ.ም. ክስ አቅርበው መጥሪያውን በ17/08/2007 ዓ.ም. ለአመልካች ማድረሳቸውን፣ተጠሪው ከ13/08/2007 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 17/08/2007 ዓ.ም. ድረስ በመደዳው ለአምስት ቀናት በተዛወሩበት ጅማ ቅርንጫፍ በስራ ላይ አልተገኙም በሚል የስራ ውላቸውን ስለማቋረጡ አመልካች 19/08/2007 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ለተጠሪው ያሳወቀ መሆኑን፣አመልካቹ በቦርድ ለቀረበበት ክስ ተጠሪውን ያሰናበታቸው በመሆኑ ከስራ የተሰናበተን ሰራተኛ ጉዳይ ቦርዱ የማየት ስልጣን የለውም የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቃወሚያ ማቅረቡን፣ቦርዱም የአመልካቹን የስንብት እርምጃ በ20/08/2007 ዓ.ም. በተሰጠ ትዕዛዝ ካገደው በኃላ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለኝ በማለት በ04/09/2007 ዓ.ም. ብይን መስጠቱን፣አመልካቹ በዕግድ ትዕዛዙ መሰረት ተጠሪውን እስከ 29/09/2007 ዓ.ም. ድረስ ሲያሰራው ቆይቶ በቃል ትዕዛዝ ያሰናበተው መሆኑን፣በሌላ በኩል የቦርዱን ብይን በመቃወም አመልካች ለአማራ ብሔራዊ ክላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ቦርዱ ከስራ የተሰናበተን ሰራተኛ ጉዳይ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በሚል ብይኑን በመዝገብ ቁጥር 40770 በ03/11/2007 ዓ.ም. የሻረው መሆኑን፣ ተጠሪው ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡትም ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች በዝርዝር ገልጸው ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራቸው እንዲመለሱ በመጠየቅ መሆኑን፣በፍርድ ቤት በቀረበበት ክስ አመልካቹ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጠው መልስ የአዲስ አደረጃጀት እና ደመወዝ ስኬል ጥናት በማድረግ ከ01/11/2006 ዓ.ም. ጀምሮ አዲስ ምደባ እንዳካሄደ፣ ተጠሪውም እንዲዛወሩ የተደረገው በዚሁ መሰረት እንደሆነ፣ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው ደግሞ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት በተዛወሩበት ቦታ በስራ ላይ ባለመገኘታቸው እንደሆነ እና በተዛወርኩበት ቦታ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት በስራ ላይ ያልተገኘሁት ዝውውሩን በመቃወም አቤቱታ እና ክስ በማቅረቤ ነው በሚል በሰራተኛው የሚቀርበው ምክንያት ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ስላለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት የስንብት እርምጃው የተወሰደው በአግባቡ እንደሆነ ገልጾ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ የተከራከረ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤትም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የስራ መደቡ ባልተሰረዘበት ሁኔታ አመልካች ለ30 ዓመታት ያገለገሉትን ሰራተኛ ወደ ሌላ ቦታ ማዛወሩ ተገቢ አለመሆኑን፣ዝውውሩ ተገቢ ነው ቢባል እንኳ ተጠሪው በነበሩበት ባህርዳር ቅርንጫፍ ርክክብ የጨረሱት በ12/08/2007 ዓ.ም. ስለመሆኑ በተጠሪው ምስክሮች መረጋገጡን፣ ይህም ጉዞው ከሚፈጀው ጊዜ አንጻር ተጠሪው በ13/08/2007 ዓ.ም. በጅማ ቅርንጫፍ በስራ ላይ ሊገኙ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳልነበረ የሚያመለክት መሆኑን፣ የቦርዱ የዕግድ ጊዜ ካበቃ በኃላም ተጠሪው ወደ ተዛወሩበት ቦታ እንዲሄዱ አመልካች ዕድል ያልሰጣቸው መሆኑን ገልጾ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት አመልካች የአራት ወር ደመወዝ ከፍሎ ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመልሳቸው በመዝገብ ቁጥር 39453 በ18/06/2008 ዓ.ም. ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው የባህርዳር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የቀረበላቸውን ይግባኝ እና አቤቱታ እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 0305653 በ05/07/2008 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 56209 በ07/07/2008 ዓ.ም. በትዕዛዝ ዘግተው በማሰናበታቸው ሲሆን የሰበር አቤቱታው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው ለአምስት ተከታታይ ቀናት ከስራ በመቅረታቸው ተሰናብተዋል በማለት የቀረበው የፊርማ መቆጣጠሪያ ሰነድ በስር ፍርድ ቤቶች ሳይታይ የመታለፉን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. የስራ መደቡ ባልተሰረዘበት ሁኔታ አመልካች ለ30 ዓመታት ያገለገሉትን ሰራተኛ ወደ ሌላ ቦታ ማዛወሩ ተገቢ አይደለም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ ተጠሪው ወደስራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?
3. አመልካች የአራት ወራት ውዝፍ ደመወዝ ለተጠሪው እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያው ነጥብ በተመለከተ በመሰረቱ ተጠሪው ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት ዝውውሩን ሳይሆን የስራ ስንብት እርምጃውን በመቃወም ነው፡፡ ዝውውሩ እና ስንብቱ ተያያዥነት ያላቸው መሆኑን ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የዝውውሩን አግባብነት እንደ አንድ የክርክር ጭብጥ አድርጎ ውሳኔ ማሳረፉ ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለስራው አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን አንድ ሰራተኛ ከአንድ የስራ መደብ ተመሳሳይ ደረጃ ወዳለው ሌላ የስራ መደብ ወይም ከአንድ ቅርንጫፍ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ የማዛወር መብት በመሰረቱ የአሰሪው ነው፡፡ የሰራተኛው የአገልግሎት ዘመን መጠን እና የስራ መደቡ አለመሰረዝ በራሱ ሰራተኛውን ከአንድ ቅርንጫፍ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ አዛውሮ ከማሰራት የሚከለክል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የወረዳው ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የወረዳው ፍርድ ቤት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ለማለት ከቻለባቸው ዓበይት ምክንያቶች አንዱ ተጠሪው ርክክብ የጨረሱት በ12/08/2007 ዓ.ም. እንደሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ጉዞው ከሚፈጀው ጊዜ አንጻር ሰራተኛው በ13/08/2007 ዓ.ም. በተዛወሩበት ጅማ ቅርንጫፍ ለመገኘት የሚችሉበት ሁኔታ አልነበረም የሚል ነው፡፡ በግራ ቀኙ በኩል ከተሰሙት ምስክሮች መካከል የተጠሪው 1ኛ ምስክር ተጠሪው ርክክብ የጨረሱት በ12/08/2007 ዓ.ም. እንደሆነ በመግለጽ የመሰከሩ ሲሆን የተጠሪው የቅርብ አለቃ መሆናቸውን የገለጹት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካቹ 2ኛ ምስክር በበኩላቸው ተጠሪው ርክክብ ያጠናቀቁት በ09/08/2007 ዓ.ም. እንደሆነ ገልጸው መመስከራቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ከዚህ ምስክርነት መካከል የወረዳው ፍርድ ቤት ተገቢ አድርጎ የተቀበለው በተጠሪው 1ኛ ምስክር የተሰጠውን ምስክርነት ነው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው ላይ ርክክቡ የተፈጸመው በ09/08/2007 ዓ.ም. መሆኑን አስረድተን እያለ ተቀባይነት ያጣው አለአግባብ ነው ከማለት በቀር ተጠሪው ርክክቡን የፈጸሙት በ12/08/2007 ዓ.ም. ስለመሆኑ በተጠሪው ምስክር የተሰጠው ምስክርነት ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ርክክቡ የተፈጸመበትን ሰነድ በማስረጃነት አቅርቦ የነበረ ስለመሆኑም የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታው ላይ ከስንብቱ ጋር የተያያዙትን ሰነዶች ፍርድ ቤት በማስረጃነት አቅርበን ነበር ከማለት በቀር ካቀረቧቸው ሰነዶች መካከል የርክክቡን ቀን የሚያመለክት ሰነድ ስለመኖሩ አልገለጸም፡፡ በሰበር አጣሪ ችሎት አቅርቦ ከመዝገቡ ካያያዛቸው ሰነዶች መካከልም ይህ ሰነድ የለም፡፡ ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት ከ13/08/2007 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 17/08/2007 ዓ.ም. ድረስ በመደዳው ለአምስት የስራ ቀናት በስራ ላይ አልተገኙም በሚል ሲሆን ርክክቡን ያጠናቀቁት በ12/08/2007 ዓ.ም. ከሆነ ደግሞ ከባህርዳር ወደ ጅማ የሚደረግ ጉዞ የሚፈጀው ጊዜ የሚታወቅ በመሆኑ ተጠሪው በ12/08/2007 ዓ.ም. በስራ ላይ አልተገኙም ሊባሉ የሚችሉበት አግባብ አይኖርም፡፡ ተጠሪው ርክክቡን ባህርዳር ላይ በ12/08/2008 ዓ.ም. አጠናቀው በ13/08/2007 ጅማ ቅርንጫፍ በስራ ላይ ለመገኘት የሚያስችላቸው ሁኔታ የነበረ ስለመሆኑም በአመልካቹ በኩል የቀረበ ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ ተጠሪው ወደስራ እንዲመለሱ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የወሰደው የዝውውር እርምጃ ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ እና ተጠሪውም ወደ ስራ መመለስ የሚገባቸው በጅማ ቅርንጫፍ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪው ወደ ስራ የሚመለሱበትን ቅርንጫፍ ሳይለይ በደፈናው ወደስራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ውሳኔው በዚህ አግባብ ብቻ ሊታረም የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሶስተኛውን ነጥብ በተመለከተ ወደ ስራው እንዲመለስ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት የተወሰነለት ሰራተኛ ከስድስት ወራት የማይበልጥ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው ፍርድ ቤቱ የሚወስን ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43 (5) የተመለከተ በመሆኑ ለተጠሪው የአራት ወራት ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል መወሰኑ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሰራተኛው ወደስራ የመመለስ ውሳኔ ከፀና ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ውዝፍ ደመወዝ ፍርድ ቤቱ ለሰራተኛው የሚወስን ስለመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በዚህ ችሎት ከቆየበት ጊዜ አንጻር ለተጠሪው በተጨማሪ የሁለት ወራት ደመወዝ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 39453 በ18/06/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በባህርዳር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 0305653 በ05/07/2008 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 56209 በ07/07/2008 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የስራ ስንብት እርምጃው ሕገወጥ በመሆኑ ተጠሪው የአራት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራ ሊመለሱ ይገባል በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. በስር ፍርድ ቤቶች ከተወሰነው በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43 (5) በተመለከተው መሰረት አመልካች የሁለት ወር ውዝፍ ደመወዝ ለተጠሪው ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. ወደስራ የሚመለሱበት ቅርንጫፍ ሳይለይ ተጠሪው ወደስራቸው ሊመለሱ ይገባል በሚል በደፈናው የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
5. ተጠሪው ወደ ስራ ሊመለሱ እና ውዝፍ ደመወዝም ሊከፈላቸው በተዛወሩበት ጅማ ቅርንጫፍ ነው በማለት ወስነናል፡፡
6. በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 39453 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ09/07/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
7. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
8. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
9. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ተኽሊት ይመስል
እንዳሻዉ አዳነ
ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች.....ንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ. -የቀረበ የለም
ተጠሪ.....አቶ አለማየሁ ሁሉቃ -ቀርበዋል
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የሥራ ስንብትን የሚመለከት ክስን መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡--በሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች /የሥር ተከሳሽ/፣ የአሁን ተጠሪ /የሥር ከሳሽ/ ሆኖ ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የሥር ከሳሽ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ በተከሳሽ ኩባንያ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥራ አስኪያጅነት ተቀጥሬ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ሲስተም ፕሮጀክት ማናጀርነት በአጠቃላይ ብር 11,327.00 እየተከፈለኝ እየሰራሁ እያለ ምንም ዓይነት የሥራ ብቃት ማነስ ሳይኖርብኝ እና ከሥራ ገበታዬም የቀረሁበት ቀን ሳይኖር ተከሳሽ መጋቢት 17 ቀን 2005 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ከሕግ ዉጭ ከሥራ ስላሰናበተኝ ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ፣ ይህ ካልሆነ በአጠቃላይ ብር 219,439.56 እንዲከፍለኝ በማለት ክሷል፡፡ የሥር ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ ከሥራዉ ሊባረር የቻለዉ በሥራዉ ላይ ባሳየዉ በብቃትና በጥራት ለመስራት ያለመቻል የብቃት ማነስ በመሆኑ ከሥራ የተሰናበተዉ በሕጉ አግባብ ስለሆነ ያቀረበዉ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፣ ፍ/ቤቱ የሥራ ዉሉ የተቋረጠዉ ከሕግ ዉጭ ነዉ የሚል ከሆነ የተከሳሽ ኃላፊነት የ3 ወር ደመወዝ ብቻ ነዉ፣ ወደ ሥራ መመለስ የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን የሰዉ ምስክሮች በመስማት፣ የቀረበዉ የሰነድ ማስረጃዎች በማየት በመመዘን በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ከሳሽን ከሥራዉ ያሰናበተዉ የሥራ ጥራት እና አቅም ማነስ እንዲሁም አለቃን ሳያሳዉቁ በሥራ ገበታ ላይ አለመገኘትን ሲሆን ይህን በማስረጃ ያስረዳዉ ነገር ስለሌለ ተከሳሽ ከሳሽን ያለ በቂ ምክንያት ከሥራዉ ያሰናበተዉ በመሆኑ፣ ከሳሽ ወደ ሥራ ሊመለስ አይገባም በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፣ ተከሳሽ በአጠቃላይ ብር 106,431.89 ዉሳኔዉ ከተሰጠ ቀን ጀምሮ ከ9% ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍለዉ በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፣ የሥር ከሳሽም የመስቀለኛ ይግባኝ ያቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት የሥራ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ መባሉን አግባብ እንደሆነ በማረጋገጥ፣ ክፍያዎችን በተመለከተ የስንብት ክፍያ ብር 35,146.23፣ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ብር 21,400.66፣ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 /4/ /ሀ/ መሰረት ብር 59,862 ብር ዉሳኔዉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ከ9% ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍለዉ በማለት በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ህዳር 3 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ስድስት ገጽ አቤቱታ የአሁን ተጠሪ የሥራ ብቃትና ችሎታ የመመዘን ስልጣን የኩባንያዉ ዋና ስራ አስኪያጅ በመሆኑ በዚህ አግባብ የብቃት ማነስ ያለባቸዉ መሆኑ ከተገመገመ በኋላ ለሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦም ከተጣራ በኋላ ከሥራ የተሰናበት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪን እንደሰራተኛ በመቁጠር በአዋጅ ቁጥር 377/96 /አዋጅ ቁጥር 494/98 እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 39 /1/ /መ/ መሰረት የስንብት ክፍያ እንዲከፈለዉ መወሰናቸዉ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ የስንብት ክፍያዉ ይከፈል ቢባል እንኳን ብር 15,796.92 ብቻ ሆኖ ሳለ ብር 35,146.23 ብር እንዲከፈለዉ መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተዉ በአግባቡ ሆኖ ሳለ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 /4/ /ሀ/ መሰረት ብር 59,862.00 እንዲከፈለዉ መወሰኑ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ የተሰናበተዉ በችሎታ ማነስ ምክንያት በመሆኑ የፕሮቪደንት ፈንድ ብር 21,400 የተወሰነዉ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የሥራ ዉል የተቋረጠዉ ከሕግ ዉጭ ነዉ የሚል አቋም የሚይዝ ከሆነም የአመልካች ኃላፊነት የሶስት ወር ደመወዝ ብቻ የማያልፍ ሆኖ እያለ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት በማድረግ የወሰኑት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ በቂ ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣ተጠሪ በሥራ መሪነቱ ከ3 ወር በላይ ደመወዝ በላይ ሊከፈለዉ አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘዉ መሰረት ጥር 6 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት፡--የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ተጠሪ ከሕግ ዉጭ ከሥራ ያሳናበተዉ መሆኑን በማረጋገጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና በድርጅቱ የሰዉ ሃይል አስተዳደር፣ ግዢና ሎጂስቲክ ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር ማኑዋል መሰረት ዉሳኔዎችን የሰጡ በመሆኑ ዉሳኔዎቹ እንዲጸኑልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች መልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበተዉ ተጠሪዉ በሥራዉ የብቃት ወይም የችሎታ ማነስ በማሳየቱ እና ከ19/3/2013--23/3/2013 እ.ኤ.አ. ያለ ፈቃድ ከሥራ ገበታዉ በመቅረቱ በሚል ምክንያት እንደሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች ያመለክታል፡፡ የአሁን ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክስ ምንም ዓይነት የሥራ ብቃት ማነስ እንደሌለበት እና ከሥራዉም ያለፈቃድ ቀርቶ እንደማያዉቅ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ከዚህ አንጻር የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪን ከሥራዉ ያሰናበተበት ምክንያቶች መኖራቸዉን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ በዚህ አግባብ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረባቸዉ የሰዉ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል የአሁን ተጠሪ በሥሩ ለነበረችዉ አንድ ሠራተኛ በሰጠዉ ዝቅተኛ የሥራ ግምገማ ዉጤት ምክንያት በአመልካች ዋና ሥራ አስኪያጅ እና በሠራተኛዉ መካከል አለመግባባት መፈጠሩን ከመግለጽ ዉጭ ተጠሪ በሥራዉ ላይ የብቃት ማነስ ሁኔታ ያሳየ መሆኑን ያላረጋገጡ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ያመለክታል፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረቡት የሰዉ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ተጠሪ ላለፉት ሁለት አመታት በተደረገ የሥራ ግምገማ ከአጥጋቢ በላይ የሥራ አፈጻጸም እንደነበረዉ፣ በሥራዉ ዕዉቀት እና ችሎታ እንዳለዉ ማረጋገጣቸዉ ማስረዳታቸዉ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡ በሶስተኛ ዓመት የሥራ ግምገማ ወቅት ከዋና ሥራ አስኪያጁ ጋር በተፈጠረዉ አለመግባባት ምክንያት ዋና ሥራ አስኪያጁ ዝቅተኛ የስራ አፈጻጸም ዉጤት የሰጡት መሆኑን መስክሯል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሥራዉ ያሰናበተበት ምክንያት የአሁን ተጠሪ ያለ ፈቃድ ከ19/3/2013--23/3/2013 እ.ኤ.አ. ከሥራ ገበታቸዉ ቀርተዋል የሚል ሲሆን አመልካች ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዳላቀረበ ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ማየት ይቻላል፡፡ የአሁን ተጠሪ ግን ያለ ፈቃድ ከሥራዉ እንዳልቀረ የህክምና ሠርትፍኬት እንዲሁም ለቅርብ አለቃዉ በማሳወቅ ሆስፒታል ሄዶ እንዲታከም ከአመልካች ኩባንያ ወደ ሆስፒታል መላኪያ ቅጽ እንደተሰጠዉ ባቀረበዉ ማስረጃ ያረጋገጠ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ፍሬ ነገርን በማስረጃ አጣርቶ ለመወሰን በተሰጣቸዉ ሥልጣን መሰረት ይህን ጉዳይ በማጣራት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘን በሰጡት ዉሳኔ የአሁን አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል ያቋረጠዉ ያለበቂ ምክንያት ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ እና ከኩባንያዉ ማንዋል ዉጭ መሆኑን በማረጋገጥ የሥራ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ከማለት ዉጭ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚያስችል በቂ ምክንያት የለም፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራዉ የተሰናበተበት ሁኔታ ከሕግ ዉጭ በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ የዚህን ዉጤት በሕጉ አግባብ ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 /2/ መሰረት መገንዘብ እንደሚቻለዉ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት ዉጤት ሠራተኛዉን ወደ ሥራ መመለስ ወይም ተገቢ ክፍያዎች ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ እንደሆነ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ የአሁን ተጠሪ ወደ ሥራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመለስ የለበትም በማለት የወሰኑትን በተመለከተ የአሁን ተጠሪ በየደረጃዉ ላሉት ፍ/ቤቶች ቅሬታዉን በማቅረብ ያስለወጠዉ ነገር ስለሌለ ይህን ነጥብ ማየቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ስለሆነም መታየት ያለበት የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሕግ ዉጭ ከሥራ በማሰናበቱ ለተጠሪዉ ሊከፍለዉ የሚገባዉ ክፍያዎች ምን እንደሆኑ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ የሥራ መሪ ቢሆንም የአመልካች የሰዉ ሃይል አስተዳደር፣ ግገርና ሎጂስቲክ ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር ማንዋል በሚደነግገዉ አግባብ ተጠሪዉ የስራ ዉል የተቋረጠ እንደሆነ ከፍትሐብሔር ሕግ ከተደነገገዉ ይልቅ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ተጠቃሚ እንደሚሆን ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ለተጠሪ ሊከፈል የሚገቡት ክፍያዎች መታየት ያለባቸዉ ይህን ማንዋል እና የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን ባማከለ መልኩ መሆን እንዳለበት የሚያከራክር አይደለም፡፡ የአሁን አመልካች በድርጅቱ ማንዋል መሰረት የሠራተኛዉን መብት ከፍትሐብሔር ሕጉ እና ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ በተሻለ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚያደርገዉ እስከሆነ ድረስ ተፈጻሚ መሆን ያለበት ይህ ማንዋል እንደሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ በዚህ አግባብ የአሁን አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰኑትን ክፍያዎች ማየቱ ተገቢ ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት መጀመሪያ መታየት ያለበት የስራ ስንብት ክፍያ ሲሆን የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር በኩባንያዉ ማንዋል ክፍል 1-ሀ ተራ ቁጥር 13.4 መሰረት የአሁን ተጠሪ የስንብት ክፍያ ተጠቃሚ እንደሆነ ሳይክድ ፣ ተጠሪዉ ለአምስት አመት በኩባንያዉ ዉስጥ ስላላገለገለ የስንብት ክፍያ አይገባዉም የሚል ነዉ፡፡ ነገር ግን የአሁን ተጠሪ ከሥራዉ የተሰናበተዉ በራሱ ፈቃድ ሳይሆን በአመልካች አነሳሽነት ከሕግ ዉጭ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 /አዋጅ ቁጥር 494/98 እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 39 /1/ /ሸ/ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች ተጠሪዉን ከሥራ ያሰናበተዉ ከሕግ ዉጭ በመሆኑ የኩባንያዉ ማንዋል በሚያመለክተዉ አግባብ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሰረት የስንብት ክፍያ ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ለተጠሪ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አግባብ የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍለዉ ይገባል በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን የአሁን አመልካች የሥራ ስንብት ክፍያ ስንት ብር ለተጠሪዉ መክፈል አለበት የሚለዉ ስሌቱ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ብር 35,146.23 የጠየቀ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር በአጠቃላይ የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብንም የሚል ነዉ፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ተጠሪዉ የጠየቀዉን ገንዘብ በሙሉ እንዲከፍለዉ ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበዉ ይግባኝ ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብንም ፣ መክፈል ካለብን ደግሞ ተጠሪዉ የጠየቀዉን ገንዘብ በሙሉ ሳይሆን ብር 15,796.92 ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በተመለከተ በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካች የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብንም ከማለት ዉጭ ስሌቱን በተመለከተ በሥር ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያቀረበዉ ተቃዉሞ ባለመኖሩ በዚህ ፍ/ቤት ደረጃ ማቅረብ አይችልም በማለት ወስኗል፡፡ ነገር ግን የአሁን አመልካች ለተጠሪዉ ሊከፍለዉ የሚገባዉ የሥራ ስንብት ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 አግባብ መሆን አለበት እንጂ የአሁን ተጠሪ ዳኝነት ስለጠየቀ ብቻ እሱ የጠየቀዉ ገንዘብ በሙሉ ሊወሰንለት ይገባል ማለት አይደለም፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ለተጠሪዉ የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብንም በማለት አጠቃላዩን እየተቃወመ በመሆኑ ስሌቱን በተመለከተ ያቀረበዉ መቃወሚያ የለም ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች ለተጠሪዉ መክፈል ያለበት የሥራ ስንብት ክፍያ በሕጉ አግባብ ተሰልቶ ሊከፈለዉ ይገባል እንጂ ተጠሪ የጠየቀዉ ገንዘብ በሙሉ ሊወሰንለት የሚገባበት አግባብ የለም፡፡ የአሁን ተጠሪ ደመወዝ በወር ብር 9,977 /ዘጠኝ ሺህ ዘጠን መቶ ሰባ ሰባት/ እና ተጠሪዉ በአመልካች ኩባንያ ሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ያገለገለ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 /1፣ 2/ መሰረት ሲሰላ የአሁን አመልካች ለተጠሪዉ መክፈል ያለበት የሥራ ስንብት ክፍያ ብር 15,796.91 /አስራ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከዘጠና አንድ ሳንትም/ ነው፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ገንዘብ መወሰን ሲገባቸዉ ተጠሪዉ የጠየቀዉን ገንዘብ በሙሉ አመልካች እንዲከፍል መወሰናቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች የሥራ ስንብት ክፍያ ብር 15,796.91 /አስራ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከዘጠና አንድ ሳንትም/ ለተጠሪ መክፈል አለበት ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የካሳ ክፍያን በተመለከተ የአመልካች ኩባንያ ማንዋል ክፍል 1-ሀ በተራ ቁጥር 13.4 መሰረት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 /4/ /ሀ/ መሰረት የካሳ ክፍያ ሊከፈለዉ እንደሚገባ ስለሚደነግግ፣ የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2574 /2/ መሰረት የሶስት ወር ደመወዝ ብቻ ነዉ መክፈል ያለበት በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ሕግ ድንጋጌ አግባብ የካሳ ክፍያዉን በማስላት የአሁን አመልካች ብር 59,862 /አምሳ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ሁለት/ ዉሳኔዉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠዉ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡

ሌላዉ መታየት ያለበት ፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች ኩባንያ ደንብ ተራ ቁጥር 1.4.3.2 መሰረት በማስላት የአሁን አመልካች ብር 21,400.66 /ሀያ አንድ ሺህ አራት መቶ ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት የሰጡት ዉሳኔዎች በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥራ ስንብት ክፍያ የገንዘብ ስሌትን በተመለከተ ብቻ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.147858 በ09/02/2008 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ የሥራ ስንብት ክፍያን በተመለከተ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአሁን አመልካች የሥራ ስንብት ክፍያን በተመለከተ ብር 15,796.91 /አስራ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከዘጠና አንድ ሳንትም ብቻ ለተጠሪ ሊከፍለዉ ይገባል ብለናል፡፡
3. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሌሎች ክፍያዎችን በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
5. ህዳር 23 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
6. ግራቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 127154

መስከረም 23 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነአ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካቾች ፡- የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት -ወኪል ነ/ፈጅ ይግረም ነጋሽ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ካሳሁን በዛብህ -ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን የሚመለከትና ጡረታ ለመውጣት ከመጠየቅ ጋር የተያያዘ ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የስር ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ደሴ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም በአጭሩ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ለ31 ዓመታት ሳገለግል ቆይቼ እድሜዬ 55 ሲሞላ ጡረታ ለመውጣት ማህበራዊ ዋስትና ብጠይቅም ማህበራዊ ዋስትና ለአመልካች ድርጅት የግል ማህደሬን እንዲልክ በደብዳቤ ብጠይቅም አመልካች ድርጅት ለመላክ ፍቃደኛ አይደለምና የግል ማህደሬን እንዲልክ ይታዘዝልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው የአሁን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ በስራ አጋጣሚ በእጁ የገባ የአመልካች ንብረት ሳያስረክብ የግል ማህደሩን ለመላክ አልችልም ስለሆነም የተጠሪ ክስ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ ጉዳዩን በመመርመር ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ንብረት አልተረከብኩም አላሉም አስረክቤያለሁ ቢሉም ያቀረቡት ማስረጃ ካለመኖሩም በተጨማሪ ያቀረባቸው ምስክሮች ተጠሪ ሊያስረክቡ ሲሄዱ ቢሯቸው ክፍት ሆኖ ስላገኙት ተመለሱ ከማለት ውጪ ንብረት ስለማስረከባቸው አላስረዱም ብሎ ተጠሪ የአመልካችን ድርጅት ንብረት ሳያስረክቡ የግል ማህደሬ ለማህበራዊ ዋስትና ይላክልኝ ዘንድ ይታዘዝልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ቅሬታው መ/ሰጪን መልስ እንዲያቀርብ በማድረግ አከራክረዋል ። ቀጥሎም ተጠሪ ከአመልካች የተረከበውን ንብረት እንዲያስረክብ የስር ፍ/ቤት መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም ንብረት ባለማስረከቡ ብቻ ግን ለጡረታው አፈጻጸም ከማህበራዊ ዋስትና እንዲላክ የታዘዘውን የግል ማህደር አለመላክ የመንግስት ሰራተኛ ጡረታ አዋጅ ቁጥር. 345/95 አንቀጽ 47/2/ን የሚቃረን ነው በማለት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር አመልካች የተጠሪን የግል ማህደር ለማህበራዊ ዋስትና ይላክ በማለት ወሰነ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኑ አመልካች ለአማራ ክልል፤ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታውን ቢያቀርብም የዞኑ ከ/ፍ/ቤትን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲያርም ጉዳዩ የቀረበለት የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ የሚጣራ መሰረታዊ የህግ ጭብጥ የለውም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 /1/ን በመጥቀስ ሰርዞታል ።

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህን በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም እንዲታረም ሲሆን አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ የአመልካችን ንብረት ሳያስረክብ አመልካች የተጠሪን የግል ማህደር የማስረከብ ግዴታ ከመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95 አንጻር ተጠሪ ባለበት ለመመርመር ቅሬታው ተጠሪን ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸውን አድርገዋል።

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን አቤቱታው ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል።

በመሰረቱ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ሲሰሩ በስራው አጋጣሚ በእጃቸው የገባውን የአመልካች ማንኛውም ንብረት የማስረከብ ግዴታ አለባቸው ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ተቀጥረው ሲሰሩ በስራ አጋጣሚ የገባ የአመልካች ንብረት እንዳለ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪ አስረክቤያለሁ ሲሉ አመልካች አላስረከቡም ብለዋል።

ዋናው ጉዳይ ንብረት ማስረከብ ያለማስረከብ ጉዳይ ለተጠሪ ጡረታ መውጫ ፎርማሊቲ ከማህበራዊ ዋስትና የተጠየቀን የግል ማህደር አመልካች አልሰጥም ማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው አመልካች በህ/ስምምነታችን አንቀጽ 9/7/ መሰረት ሰራተኛ ያለበትን ንብረት ሳያስረክብ ከማህበራዊ ዋስትና የታዘዘው የተጠሪን የግል ማህደር መላክ ይከለክላል ሲል ተጠሪ በበኩላቸው የህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 9/7/ የሚከለክለው መሸኛና የስራ ልምድ ነው እንጂ በማህበራዊ ዋስትና የተጠየቀን የግል ማህደር አይደለም ብለዋል በመሆኑም ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሰው የህብረት ስምምነት በተዋዋዮች መሀከል ህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ ለማየት የሚቻል ቢሆንም ባለመቅረቡ አልታየም፡፡የህብረት ስምምነት አመልካች ክርክር የሚደግፍ ቢሆንም የህብረት ስምምነት በህግ ለሰራተኞች የሚሰጠው መብት የበለጠ የሚጠቅሞ ሆኖ ካልተገኘ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 134/2/ ተፈጻሚ እንደማይሆን ይደነግጋል፡፡

ሌላው ግን የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95ን ስንመለከት በአንቀጽ 47/2 ላይ ማንኛውንም አሰሪ /ግለሰብ/ ቀርቦ አስተያየትና መረጃ ወይም የጽሁፍ ማስረጃ እንዲሰጥ በማህበራዊ ዋስትና /በባለስልጣኑ/ ሲታዘዝ የመስጠት ግዴታ አለበት ይልና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 44 ላይ እንደተመለከተው የጡረታ አበል የማግኘት መብት የዕዳ መያዣ ሊደረግ ወይም በውርስ ወይም በማናቸውም መንገድ ሊተላለፍ አይችልም ብሎ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 55/2/ ላይም ይህንን አዋጅ የሚቃረኑ ህጎችና ማሟያዎች ይህንን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም ይላል፡፡

ይህንን ህግ መነሻ ስናደርግ ተጠሪ እንዳቀረቡት ዝርዝር የህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 9/7/ ሰራተኛው ንብረት ባላስረከበ ጊዜ አሰሪ ለመያዝ የሚችለው የስራ ልምድና መሸኛ ካልሆነ በስተቀር በማህበራዊ ዋስትና የሚታዘዘውን ማንኛውንም ለጡረታ መውጫ የሚያስፈልግ ማስረጃ የመስጠት ግዴታ በመንግስት ሰራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 ላይ የተጣለበት ስለሆነ ይህንን ላለመስጠት መስማማት የማይችልና የጡረታ መብትን የማግኘት መብት በእዳ መያዣ ሊደረግ እንደማይገባ ከመደንገጉም በተጨማሪ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 55/2 ላይም ይህንን ድንጋጌ የሚቃረን ህ/ስምምነት ተፈጻሚ እንደማይሆን የደነገገ በመሆኑ ተጠሪ የአመልካችን ንብረት ያልመለሰ ስለሆነ ሳይመልስ የተጠሪን የግል ማህደር ለማህበራዊ ዋስትና ሊልክ አይገባም በማለት የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ዉሳኔ በመሻር የስር ክ/ፍ/ቤት አመልካች የተጠሪን ማህደር ለማህበራዊ ዋስትና እንዲልክ መወሰኑንና የክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ጥሰት አለበት የሚያሰኝ ጉድለት ያላገኘን በመሆኑ ውሳኔው የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም

በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቀ 23359/ ታህሳስ 10 2008 ዓ.ም የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 03-13048 በቀን ሚያዚያ6 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ይህ ውሳኔ አመልካች በተጠሪ ላይ አለኝ የሚሉት ንብረት ካለ ከመጠየቅ አያግዳቸውም
3. በየደረጃ ለሚገኙ ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍ
4. በዚህ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል ይጻፍ
5. ግራ ቀኙ የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል ተመላሽ ይደረግ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.125778

መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ
ተክሊት ይመሰል
ቀነዓ ቂጣታ
ክፍለጽዮን ማሞ
ሰናይት አድነዉ

አመልካች.....ሲዉ ኢንፍራስትራክቸር

ተጠሪዎች..... 1. አቶ መሳይ ወ/ገብርኤል
2. አቶ አሉላ አበጋዘእ
3. አቶ በፍርድ ጥላሁን
4. አቶ ዘሪሁን ከድር

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅን መነሻ ያደረገ የሥራ ስንብትን የሚመለከት ክርክር ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡--በሥር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች የሥር ከሳሾች፣ የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የሥር ከሳሾች በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከሳሾች በተከሳሽ ድርጅት በዳም ትራክ ኦፕሬተር ተቀጥረን ሥራችንን በቅንነትና በታማኝነት እየሠራን እያለ እኛ ደንብ በመጣስ የድርጅቱ ተሽከርካሪ ታንከር ነዳጅ እንዳይሰረቅ የሚያደርገዉን የተሻለ የነዳጅ መያዣ ታንከር መቆጣጠሪያ መሳሪያ /የደህንነት መጠበቂያ/ ላይ ሆን ብለን ያደረሰን ጉዳት ሳይኖር ጉዳት አድርሳችኋል በማለት የሥራ ዉላችንን በሕገ ወጥ መንገድ በማቋረጥ ስላሰናበተን ተከሳሽ ተገቢዉን ክፍያዎች እንዲከፍለን፣ የሥራ ልምድ እንዲሰጠን እንዲወሰንልን በማለት ክሷል፡፡ የሥር ተከሳሽ አሻሽሎ ባቀረበዉ መልስ 1ኛ ከሳሽ በ9/08/2007 ዓ.ም፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ከሳሾች በ10/08/2007 ዓ.ም እያንዳንዳቸዉ ለሥራ በተረከቡት ተሽከርካሪ ላይ የነዳጅ ስርቆትን ለመከላከል በታንከሩ ላይ የተሰራዉን መሳሪያ ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉ በድርጅቱ የቴክኒክ ክፍል ተጣርቶ የተረጋገጠ ሲሆን ከሳሾች ጉዳቱ የደረሰዉ በሌላ ሰዉ መሆኑን ባለማረጋገጣቸዉ፣ በድርጅቱ ንብረት ላይ ጉዳት በማድረሳቸዉ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/ /ሸ፣ ቀ/ እና በድርጅቱ ዉስጠ ደንብ መሰረት ከሥራ የተሰናበቱ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ ከሳሾች የጠየቁትን ክፍያዎች ለመክፈል ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን የሰዉ ምስክሮች በመስማት፣ የሰነድ ማስረጃም በመመዘን፣ በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ የከሳሾችን የሥራ ዉል ያቋረጠዉ ከሕግ ዉጭ በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ በማለት ለከሳሾች በሕጉ አግባብ ክፍያዎችን እንዲከፍላቸዉ ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የሰበር አቤቱታ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ቅሬታዉ ተቀባይነት ሳይገኝ ዉድቅ ተደርጎ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ24/07/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት፡-- የሥር ፍ/ቤት አመልካች መልሱን እንዲያሻሽል በፈቀደለት መሰረት በ22/12/2007 ዓ.ም የተጻፈዉን መልስ ያቀረበ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ግን መልሱን ከመሻሻሉ በፊት የተያያዘዉን የሰነድ ማስረጃ ከተሻሻለዉ የመከላከያ መልስ ማስረጃ ጋር እያነጻጸረ የሰነድ ማስረጃዎቹ እምነት የማይጣልባቸዉ ናቸዉ በማለት የአመልካችን ክርክር ዉድቅ ማድረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 /1/ ያላገናዘበ ዉሳኔ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በመመሳጠር ለነዳጅ ስርቆት እንዲያመቻቸዉ የድርጅቱን አራት መኪኖች የነዳጅ ታንከር በተከታታይ ቀናት በ9/8/2007 ዓ.ም እና በ10/8/2007 ዓ.ም ሰብረዉት እና ቀደዉት ጉዳት ማድረሳቸዉን በሰነድ ማስረጃ እና በሰዉ ምስክሮች አረጋግጠዉ እያለ የሥር ፍ/ቤት እነዚህን የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ አስፈላጊም ከሆነ ገለልተኛ ባለሙያዎችን በተጨማሪ ማስረጃነት አስቀርቦ ምርመራ ማድረግ እየቻለ ማስረጃዉን በማለፍ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ መብት ማለፋቸዉ በመሆኑ እንዲሻርልን፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች ተጠሪዎች በድርጅቱ መኪኖች የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት እና ጥፋት በማድረሳቸዉ ስንብቱ ሕጋዊ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/ /ሸ፣ ቀ/ መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን፣ ክፍያንም በተመለከተ ቅሬታዉን በማቅረብ አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣ተጠሪዎች ጥፋት ለመፈጸማቸዉ አልተረጋገጠም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ በሚል የመወሰኑን አግባብነት ከሰበር መ.ቁ.112733 አንጻር፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት የአሁን ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ በታዘዘዉ መሰረት ግንቦት 12 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት፡--የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች መኪኖች የነዳጅ መያዣ ክፍል ላይ ጉዳት ያላደረስን ሲሆን የአሁን አመልካች ያለጥፋታችን የሥራ ዉላችንን ማቋረጡ ያለአግባብ በመሆኑ የቀረበዉ ቅሬታዉ ዉድቅ እንዲደረግልን እና የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካችም የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች የተጠሪዎችን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበታቸዉ ተጠሪዎች ከድርጅቱ መኪኖች ታንከር ላይ ነዳጅ እንዳይሰረቅ የሚከላከለዉን መቆጣጠሪያ መሳሪያ ላይ ጉዳት በማድረሳቸዉ በአመልካች ንብረት ላይ ሆን ብለዉ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ባደረሱት ጉዳት ምክንያት እንደሆነ ከሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች የተለያዩ ምክንያቶችን በመዘርዘር በመኪኖቹ የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት አለማድረሳቸዉን እና ስንብቱ ሕገ ወጥ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረበዉን መልስ ለማሻሻል ጥያቄ አቅርበዉ ሲፈቀድለት፣ በተሻሻለዉ መልስ የአሁን ተጠሪዎች በመኪኖቹ የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት አደረሱ በማለት መጀመሪያ ባቀረበዉ ክስ ላይ የጠቀሰዉን ቀን እና መጀመሪያ የተጻፈዉን የስራ የስንብት ደብዳቤ በመቀየር ሌላ የስራ የስንብት ደብዳቤ አያይዞ ያቀረበ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡

በዚህ ረገድ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 /1፣ 3/ እንደሚደነግገዉ የክሱ ወይም የመከላከያ መልሱ ማሻሻል አስቀድመዉ የቀረበዉን ሁኔታ የሚያብራራ ወይም የቀረበዉን ክርክር በተሻሻለ ዓይነት ገልጾ የሚያስረዳ ወይም ትክክለኛ ፍትሕን ለመስጠት የሚረዳ መሆኑን ፍ/ቤቱ ከገመተ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት የቀረበዉን ክስ ወይም መልስ እንዲሻሻል እንደሚፈቅድ ያመለክታል፡፡ በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች መልስ ለማሻሻል አቤቱታ አቅርቦ የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ የፈቀደለት ሲሆን፣ አመልካችም በ22/12/2007 ዓ.ም የተጻፈ የተሻሻለ መልስ ያቀረበ መሆኑን ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የአሁን አመልካች ባቀረበዉ መልስ አስቀድመዉ የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች መኪኖች የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት አድርሰዋል በማለት ተጠሪዎችን ከሥራ ያሰናበተባቸዉን የስንበት ደብደቤ ሙሉ በሙሉ በመቀየር ሌላ የስንብት ደብዳቤ /ሌላ አዲስ ማስረጃ ፈጥሮ/ እንዳቀረበ ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የአሁን አመልካች አስቀድመዉ ለተጠሪዎች የሰጣቸዉን የስንብት ደብዳቤ በመቀየር፣ ተጠሪዎች በመኪኖቹ የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት አድርሷል ያለዉን ቀን በመቀየር ያቀረበ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች ክሳቸዉን ሲመሰርቱ የአሁን አመልካች የጻፈላቸዉን የስንብት ደብዳቤ እና በስንብት ደብዳቤዉ ላይ በድርጅቱ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሳችኋል የተባለዉን ቀን እና ሁኔታ መሰረት በማድረግ እንደሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች አሻሽሎ ባቀረበዉ መልስ ይህን ሁሉ ቀይሮ መልሱን አሻሽሎ አቀረበ ማለት ተጠሪዎችን ከሥራ ከማሰናበቱ በፊት በትክክል አጣርቶ እርምጃ መዉሰድ ሲገባዉ አሁን ክርክር ከተጀመረ በኋላ አስቀድመዉ ተጠሪዎችን ካሰናበታቸዉ ደብዳቤ ሌላ ደብዳቤ መጻፉ ከላይ የተመለከተዉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 /1፣ 3/ አላማ እና መንፈስ የሚያሟላ ሁኖ አይታይም፡፡ አመልካች ራሱ በጻፈዉ የስንብት ደብዳቤ መሰረት በማድረግ የአመልካችን እርምጃ በመቃወም ተጠሪዎች ክስ ከመሰረቱ በኋላ አመልካች ሌላ የስንብት ደብዳቤ በማዘጋጀት መልሱን አሻሽሎ ማቅረቡ በቀድሞ መልስ የቀረበዉን ሁኔታ የሚያብራራ ወይም የቀረበዉን ክርክር በተሻሻለ ዓይነት ገልጾ የሚያስረዳ ወይም ትክክለኛ ፍትሕን ለመስጠት የሚረዳ ሳይሆን አዲስ ክርክር እንደማቅረብ የሚገመት ነዉ፡፡ እንዲያዉም ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር ተገቢ መከላከያ መልስ ማቅረብ ሳይሆን ሌላ የማይገናኝ አዲስ ክርክር እንደማቅረብ የሚቆጠር ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ይህን ጉዳይ ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች መኪኖች የነዳጅ ታንከር ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም አለማድረሳቸዉ በተመለከተ የግራ ቀኙን የሰዉ ምስክሮችን በመስማት የሰነድ ማስረጃ በመመዘን ዉሳኔ የሰጠ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ተጠሪዎች በድርጅቱ መኪኖች የነዳጅ ታንክር ላይ ጉዳት አድርሷል በማለት ከሥራ ያሰናብታቸዉ እንጂ የቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ እና የሰዉ ምስክሮች እምነት የሚጣልባቸዉ እንዳልሆኑ በማረጋገጥ፣ የሥራ ስንበቱ ሕገ ወጥ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ማስረጃን በመመዘን ዉሳኔ መስጠቱን ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ተጠሪዎችን በሕጉ አግባብ በጥፋታቸዉ የሥራ ዉላቸዉን በማቋረጥ ያሰናበታቸዉ እና ስንብቱ ህጋዊ መሆኑን የማስረዳት ሸክሙን ያልተወጣ መሆኑን ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ማየት ይቻላል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር መሰረት ተጠሪዎች በድርጅቱ መኪኖች የነዳጅ ታንከር መቆጣጠሪያ መሳሪያ ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉን ባላረጋገጠበት የተጠሪዎች የሥራ ስንብት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/ /ሸ፣ ቀ/ መሰረት ሕጋዊ ነዉ በማለት ያቀረበዉ ክርክር የድንጋጌዉን መንፈስና ይዘት ያላገናዘበ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል በተያዘዉ ጭብጥ ጉዳዩን በሰበር መ.ቁ.112733 ላይ ከተሰጠዉ ዉሳኔ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ በሰበር መ.ቁ.112733 ላይ አመልካች ሲዉ ኢንፍራስትራክቸር ሲሆን፣ ተጠሪ አቶ ጴጥሮስ ስዩም በመሆን፣ ችሎቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በ4/6/2008 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን ተጠሪ ከአመልካች መኪና ነዳጅ እንዳይሰረቅ ለመከላከል የሚያገለግለዉን መቆጣጠሪያ መሳሪያ ላይ ጉዳት ማድረሱ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች የሥራ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በመሻር የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተዉ በሕጋዊ መንገድ ነዉ፣ የሥራ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ በሰበር መ.ቁ.112733 እና አሁን በተያዘዉ መዝገብ ላይ ያለዉ ክርክር ሲታይ በዚህ መዝገብ የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች መኪኖች ነዳጅ እንዳይሰረቅ የሚያገለግለዉን መሳሪያ ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉ በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥር 112733 ውሳኔ ካገኘው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ጭብጥ ነዉ ለማለት ስለማይቻል በዚህ ጉዳይ ላይ አስገዳጅነት ያለዉ የሕግ ትርጉም አይደለም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪዎችን ከድርጅቱ መኪኖች ታንከር ነዳጅ እንዳይሰረቅ ለመቆጣጠር የሚያገለግለዉን መሳሪያ ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉ በማስረጃ ባልተረጋገጠበት የሥራ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ በማለት አመልካች ለተጠሪዎች በሕጉ አግባብ ተገቢዉን ክፍያዎች እንዲከፍላቸዉ የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት ስለማይቻል የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.07323 በ15/04/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.19019 በ13/05/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.66951 በ20/7/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. ሚያዝያ 5 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.116038

ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ፍራውን ኮንስትራክሽን ህንጻ ተቋራጭ -የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. አቶ ካህሳይ ገ/ሄር } የቀረበ የለም

2. አቶ ተመስገን ዘነበ }

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች ላይ በመቐሌ ሰሜን ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- 1ኛው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በፎርማን ስራ መደብ ላይ ማናጀር ሁነው ተቀጥረው ከጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም እስከ ሕዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ በወር ብር 2,500.00(ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) እየተከፈላቸው ሰርተው የአስራ ሶስት ወራት ደመወዝ ብር 32,500.00(ሰላሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) ያልተከፈላቸው መሆኑንና በዚህ ድርጅት ውስጥ ከፎርማን የስራ መደብ ማናጀር ሁነው ከመቀጠራቸው በፊት በነበራቸው የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ሞያ ስራ የአመልካቹ በሆነውና በአጉላዕ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ግንባታ የኤሌክትሪክ ስራውን ለመስራት በቃል በአደረጉት ስምምነት መሰረት ስራውን ሰርተው አስረክበው እያለ አመልካች ብር 3000.00 ብቻ ከፍሏቸው ቀሪውን ብር 5260.00(አምስት ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ ብር) በስምምነቱ መሰረት ያልከፈላቸው መሆኑን ጠቅሰው በድምሩ ብር 37,760.0 (ሰላሳ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ብር) እንዲከፍላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ባላቸው የብረታ ብረት ንግድ ድርጅት መነሻ ከአመልካች ድርጅት ጋር ሁለት መዝጊያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በር በብር 7700.00(ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ብር) ለመስራት ስምምነት አድርገው ቀብድ ብር 300.00(ሶስት መቶ ብር) ተቀብለው ስራውን ሰርተው ሰኔ 26 ቀን 2005 ዓ/ም ያስረከቡ ቢሆንም ቀሪውን ገንዘብ ብር 7400.00(ሰባት ሺህ አራት መቶ ብር) አመልካች ያልከፈላቸው መሆኑን ጠቅሰው ይህንኑ ገንዘብ አመልካች እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስም ይርጋን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወያነት ያነሳ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ረገድ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ ጋር ምንም አይነት የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የሌለው መሆኑን፣ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ስራ ሰርቼአለሁ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄም ስራውን ለመስራት የሚያስችላቸው የንግድ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ሳይቀርብ የቀረበ መሆኑን፣የ2ኛ ተጠሪ ክስም የውል ግንኙነት ሳይኖር ተጠሪው የአመልካቹ ድርጅት ሰራተኛ ሁነው ለሰሩት ስራ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አልፎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ጉዳዩን መርምሮ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ውስጥ የስራ መሪ ሁነው መስራታቸው መረጋገጡን፣ የስራ መሪ ሁነው ከመቀጠራቸው በፊት ደግሞ አመልካቹ ሲሰራ ከነበረው ግንባታ ንዑስ ስራ ተቋራጭ ሁነው ኤሌክትሪክ ኢንስቶል የማድረግ ስራ የሰሩና ለሰሩት ስራም አመልካችም መከፈል ያለበትን ክፍያ ያልከፈላቸው መሆኑ መረጋገጡን፣ የ2ኛ ተጠሪ ክስም በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ዘርዝሮና የአመልካች ድርጅት የ1ኛ ተጠሪን ደመወዝ ስድስት ወር ስላለፈው እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት ያቀረበው ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ሐ) ስር የተመለከውን የሁለት አመት ጊዜ ያላገናዘበ መሆኑን፣ የ2ኛ ተጠሪን የክፍያ ጥያቄ በተመለከተም አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2472(3) ድንጋጌ መሰረት ስለመክፈሉ የሚያሳይ የጽሑፍ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን ጠቅሶ ውድቅ በማድረግ አመልካችን ለተጠሪዎች ክስ ኃላፊ አድርጎ በተጠየቀው ዳኝነት መሰረት ገንዘቡን ለተጠሪዎች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለመቐሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የወረዳው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ አጣሪ ችሎቱ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት በመዝጋቱ ይህንኑ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ጋር የነበራቸው ግንኙነት የአሰሪና ሰራተኛ ሁኖ እያለ ተጠሪው የስራ መሪ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ መሆኑን፣ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄው በይርጋ ይታገዳል እንዲሁም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስድስት ወር ያለፈበት በመሆኑ እንደተከፈለ ይቆጠራል ተብሎ የቀረበው የአመልካች ክርክር በበታች ፍርድ ቤቶች መታለፉ ያላግባብ መሆኑንና 2ኛው ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሁነው ክሱን በአንድ ላይ ለማቅረብ የሚያስችላቸው ህጋዊ ምክንያት ሳይኖር ክሱን አንድ ላይ ማቅረባቸውም ሆነ የተጠሪውንና የአመልካቹ ግንኙነት የአሰሪና ሰራተኛ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው መሆኑን ዘርዝሮ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲለወጥ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ጭብጦች፡-

1. አንደኛ ተጠሪ የስራ መሪ ናቸው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?፣
2. 1ኛ ተጠሪ የስራ መሪ ከተባሉ የጠየቁት የአስራ ሶስት ወራት ደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ወይም በክፍያ ግምት ቀሪ የሚሆንበት አግባብ አለ? ወይስ የለም?
3. ተጠሪዎች ክሱን በአንድ ላይ ማቅረባቸው ስነ ስርዓታዊ ነው ወይስ አይደለም የሚሉትን ነጥቦችን የሚመለከቱ ሁነው አግኝተናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርቱ ከአመልካች ድርጅት ከጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም እስከ ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም የስራ መሪ የነበሩ መሆኑንና በዚህ የስራ መደብ ከመቀጠራቸው በፊት ደግሞ በነበራቸው ሙያ መሰረት ከአመልካች ድርጅት ጋር የንዑስ ስራ ተቋራጭነት ውል አድርገው የኤሌክትሪክ "ኢንስታሌሽን" ስራ የሰሩ መሆኑን ገልፀው ሲሆን ይህ የተጠሪው የክስ ይዘት በግልጽ የሚያሳየውም ተጠሪው ከአመልካች ጋር በተለያዩ ጊዚያት የተለያዩ የግንኙነት አይነቶች የነበራቸው መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ይህንኑ የተጠሪን የክስ ፍሬ ነገር በመካድ ከተጠሪው ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ካልሆነ በስተቀር ሌላ አይነት ግንኙነት ያልነበረው መሆኑን ጠቅሶ የተከራከረ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት አድርጎ ተገቢ ነው ያለውን ጭብጥ ይዞ ተጠሪው በአመልካች ድርጅት በሚከናወነው ግንባታ ላይ ንዑስ ስራ ተቋራጭ ሁነው የኤሌክትሪክ "ኢንስቶሌሽን" ስራ ከጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም በፊት በነሐሴ ወር 2004 እና በመስከረም ወር 2005 ዓ/ም የሰሩ መሆኑንና ከጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም እስከ ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ በአመልካች ድርጅት የስራ መሪ ሁነው የሰሩ መሆኑን ተጠሪው በማስረጃዎቹ ያስረዱ መሆኑን፣ አመልካች ድርጅት ግን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ለማስተባበል ያልቻለ መሆኑን በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሮአል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተጠሪውን የስራ መሪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰውም ተጠሪው በአመልካች ድርጅት በነበራቸው የፎርማን ስራ መደብ ሰራተኞን የማሰናበት፣ የመቅጠር እንዲሁም አስተዳደራዊ ስራዎችን ያካሂዱ የነበሩ መሆኑ በምስክሮች ቃል መረጋገጡን መሰረት አድርጎና የአዋጅ ቁጥር 377/96 ማሻሻያ በሆነው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2(ሐ) ስር የሰፈውን ድንጋጌ ይዘት በመመልከት መሆኑን ውሳኔው ያሳያል፡፡ ይኼው የሥር ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ በስራ መደቡ ሲያከናውኗቸው የነበሯቸው ተግባራት፤ ሰራተኞን የማሰናበት፣ የመቅጠርና እንዲሁም ሌሎች አስተዳደራዊ ስራዎችን የመስራት ጉዳዮች የፍሬ ነገር ማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያገኙ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያስገነዝባል፡፡

ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጧቸው እነኚህ ነጥቦች በዚህ ችሎት ሊለወጡ የማይችሉ መሆኑን ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ከተሰጠው ስልጣን አድማስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በፎርማንነት ሲሰሩ ሰራተኞን የማሰናበት፣ የመቅጠርና እንዲሁም ሌሎች አስተዳደራዊ ስራዎችን የሚመለከቱ ተግባራትን ሲያከናወኑ ነበር ተብሎ ከተረጋገጠ ደግሞ ቀጥሎ መታየት ያለበት የሕግ ጥያቄ እነዚህ ተግባራትን ማከናወን አንድን ተቀጣሪ የስራ መሪ ነው ለማለት ያስችላል? ወይስ አያስችልም? የሚለው ይሆናል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከት ምላሽ ማግኘት የሚቻለው በሕጉ የተቀመጡትን መለኪያዎችን በመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ የአዋጅ ቁጥር 377/96 በአዋጅ ቁጥር ቁጥር 494/98 እንደተሻሻለው ሲሆን የአዋጁ አንቀጽ 3(2(ሐ) ሲታይም የሥራ መሪ ማለት በሕግ ወይም እንደ ድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሠሪው በተሰጠ የውክልና ሥልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈጸም፣ ከእነዚሁ በተጨማሪ ወይም እነዚህኑ ሳይጨምር ሠራተኞን የመቅጠር፣ የማዘዋወር፣ የማገድ፣ የማሰናበት፣ የመመደብ ወይም የሥነ ሥርዓት ዕርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውንና የሚወስን ግለሰብን የሚመለከቱ ሲሆን፤ እንዲሁም እነዚህን የሥራ አመራር ጉዳዮች አስመልክቶ የአሠሪውን ጥቅም ለመጠበቅ አሠሪው ሊወስደው ስለሚገባው ዕርምጃ በራሱ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ባለሙያ የሥራ ኃላፊንም ይጨምራል፤ በማለት ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከዚሁ የሕጉ ድንጋጌና ከማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2(1) ድንጋጌ ይዘት መረዳት የሚቻለው አንድ ሠራተኛ የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የሚያወጣና የሚያስፈጽም፣ ሠራተኞን የሚቀጥርና የሚያሰናብት፣ የሠራተኞችን የሥራ ዕድገት የሚወስን ከደረጃ ዝቅ የሚያደርግ፣ በሠራተኞች ላይ የሥነ ሥርዓት ዕርምጃ የመውሰድ ተግባራትን የሚያከናውን ከሆነ ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥራ አመራር ጉዳዮች አስመልክቶ ለአሠሪው የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ከሆነ የሥራ መሪ ሊባል የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ሠራተኛው ከእነዚህ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ሥራዎችን የሚሠራ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን በሕጉ አግባብ ማስረጃ ቀርቦ በሕጉ የተመለከቱት መስፈርቶች መኖራቸው ከተረጋገጠ ደግሞ በአሰሪውና በተቀጣሪው መካከል ያለው ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/96 የሚገዛበት አግባብ አይኖርም፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከመተው የበታች ፍርድ ቤቶች 1ኛ ተጠሪ በፎርማንነት ሲሰሩ ሰራተኛን የማሰናበት፣ የመቅጠርና እንዲሁም ሌሎች አስተዳደራዊ ስራዎችን የሚመለከቱ ተግባራትን ሲያከናወኑ የነበሩ መሆኑን በሚገባ አረጋግጠው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አግባብ አይገዛም በማለት መደምደማቸው የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላለገኘን በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- እንደሚታወቀው በአገራችን የሥራ መሪና የአሠሪ ግንኙነትን በአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች አግባብ የማይገዛ ስለመሆኑ ከመደንገጉ ውጪ ይህንኑ ግንኙነት እንዲገዛ ተብሎ ተለይቶ የተቀረፀ ሕግ የለም፡፡

የሥራ መሪን የሚመለከት ሕግ ከሌለ ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉትና በተግባር እየተሰራባቸው ያሉት ደንቦች የሥራ ውል፣ የሥራ ደንብና የፍትሐ ብሔር ሕጉ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ የሥራ ውል አሠሪውና የሥራ መሪው በጽሑፍ በሚያርጉት ስምምነት የሚፈጸም ሁኖ ግራ ቀኙ በነፃ ፈቃዳቸው መብትና ግዴታቸውን የሚዘረዝሩበት ሰነድ በመሆኑ የሥራ መሪውን መሠረታዊ የሥራ መብቶች የሚያስጠብቅ እስከሆነ ድረስ ቀዳሚ ተፈጻሚነት ሊያገኝ የሚገባው ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ስምምነቶች የስራ መሪውን መብት ለማስጠበቅ የሚችሉትን ድንጋጌዎች ለይተው የሚያስቀምጡበትና በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ የተቀመጡ የሰራተኛ መብትና ጥቅሞችም ለስራ መሪው ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚያደርጉበት አግባብ መኖሩን በተግባር ይታያል፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 84661 የተሰጠው የዚህ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም ይህንኑ የሚያሳይ ነው፡፡ የሥራ ደንብ ደግሞ የአሠሪውንና የሥራ መሪውን ግንኙነት የሚመለከት ራሱን የቻለ የውስጥ ደንብ ካለ ተፈጻሚ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት ሁኖ ደንቡ በድርጅቱ የሥራ ፀባይ የሥራ መሪዎች የሆኑትን ሠራተኞች ገልጾ በመደንገግ ያላቸውን መብት፣ ግዴታና ልዩ ጥቅም በስፋት እንዲገዛ አድርጎ የሚዘጋጅ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሌላውና የመጨረሻው የአሠሪና የሥራ መሪ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው የህግ ማዕቀፍ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ከአንቀጽ 2512 እስከ 2593 ያሉት "ስለ ሥራ ውል በጠቅላላው" የተመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዘው ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የፍትሐ ብሔር ሕጉ በወጣበት ጊዜ ያሉትን የሥራ ግንኙነቶች ለማስተዳደር የወጡ ሲሆኑ፣ በይዘታቸው የሥራ መሪ እንዳይገዛባቸው የሚከለክል ድንጋጌ ስላልያዙና ስላልተሻሩ የሥራ መሪን ግንኙነት እንደሚገዙ ይታመናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 21329 ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም.፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 27704 ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም.፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 15531 የካቲት 6 ቀን 1999 ዓ.ም.፣በሰበር መዝገብ ቁጥር 15815 ታኅሣሥ 10 ቀን 1998 ዓ.ም. የተሰጡ አስዳጅ የሕግ ትርጉሞችን ሰጥቷል፡፡

የፍትሐ ብሔር ሕጉ የአሠሪና የሥራ መሪን ግንኙነት የሚገዛ ነው ከተባለ ደግሞ በሕጉ አግባብ የሚቀርቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክሮች እልባት ማግኘት ያለባቸው በዚሁ ሕግ አግባብ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ አመልካች የ1ኛውን ተጠሪ ክፍያ በተመለከተ ያቀረበው የይርጋና የክፍያ ግምት ክርክር ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት አመልካች 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ ያነሳውን ይርጋን የሚመለከት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ማለፉን ውሳኔው የሚያሳይ ቢሆንም ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግ ስለመለየቱ ግን የክርክሩ ሂደት አሳይም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ሰበር ደረጃ አጥብቀው የሚከራከሩትም አመልካች የተጠሪውን የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሚከራከረው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162(3) እና (4) ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ነው በማለት ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካች ይርጋ የሚለውን ቃል በስር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ አግባብነት አለው በማለት የጠቀሰው ግን አዋጅ ቁጥር 377/96 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በሕጉ በተጠቀሰው አግባብ ተከራካሪ ወገን የይርጋ መከራከሪያ ካነሳ ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ብይን መስጠት ያለበት ሲሆን ተከራካሪ ወገን ክሱ በይርጋ እንደሚቋረጥ ጠቅሶ ከመከራከር ውጪ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግና ድንጋጌን ለይቶ እንዲከራከር በሕጉ ግዴታ ያልተጣለበት መሆኑን በስነ ስርዓት ሕጉ ስለ አቤቱታ አጻጻፍ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ድርጅት የ1ኛ ተጠሪ ለተሰራ ስራ ያልተከፈለ ደመወዝ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መከራከሩ እስከታወቀ ድረስ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግ መለየት የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት በመሆኑ በዚህ ረገድ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች በዚህ ረገድ የይርጋ ክርክሩን በሕጉ አግባብ ማንሳቱ ከተረጋገጠ ቀጥሎ መታየት ያለበት የይርጋ ክርክሩ ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም የሚለው ጥያቄ ሲሆን ይህንኑ ጥያቄ ለመመለስ ደግሞ አስቀድሞ ለጉዳዩ ገዥነት ያለውን የሕግ ማእቀፍ መለየትን ይጠይቃል፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩን ስንመለከተው ከላይ እንደተገለፀው የስራ መሪዎችን በተመለከተ የተለዩ ሕግ የሌለ ሲሆን በተግባር እየተሰራ ያለው በስራ ውል፣ በስራ ደንብ ወይም በፍትሃ ብሔር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጉ አግባብ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ያለውን ግንኙት የሚገዛ በመካካላቸው የተደረገ የስራ ውል ስምምነት ወይም እየተሰራበት ያለ የስራ ደንብ ስለመኖሩ በግራ ቀኙ ክርክር አልተገለፀም፣ በበታች ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ መገዛት ያለበት በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 2512 እስከ 2593 ድረስ በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ሲታዩ ደግሞ የይርጋ ጊዜን በተመለከተ አስፍረው አይገኙም፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሕግ የይርጋ ጊዜውን ለይቶ ያስቀመጠ ሁኖ አይታይም፡፡ ሆኖም አንድን መብትና ግዴታ የሚጠብቅ ልዩ ሕግ በይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ ለይቶ እስካላመለከተ ድረስ መብቱ ወይም ግዴታው የሚጠይቅበት የጊዜ ገደብ በልዩ ሕጉ ያለመመልከቱ ለጉዳዩ ገደብ የለሽ የይርጋ ጊዜ ተቀምጦአል ብሎ ለማለፍ የሚያስችል ያለመሆኑን ከይርጋ ሕግ ፅንሰ ሃሳብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም የተያዘው ጉዳይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2512 እስከ 2593 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ይገዛል ከተባለ በእነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ የስራ መሪ የሚያቀርባቸው የመብት ጥያቄዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ድንጋጌዎች አግባብ በአስር አመት ጊዜ ሊታገድ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ይህንኑ ይዘን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከትም የአስር አመት ጊዜ ያላለፈበት በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከጥቅምት 01 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ ያልተከፈላቸው የአስራ ሶስት ወራት ደመወዝ ብር 32,500.00 በይርጋ የሚታገድ ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች የ1ኛ ተጠሪ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 ድንጋጌ አግባብ በስድስት ወር ጊዜ እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው በማለት ይህንኑ ድንጋጌ ለጉዳዩ እንደ ይርጋ ሕግና እንደ ክፍያ ግምት ማስወሰኛ አድርጎ ክርክር አቅርቧል፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 እና 2024 ስር የተመለተከቱት ድንጋጌዎች የማስረጃ እንጂ የይርጋ ደንቦች ያለመሆናቸውን ይህ ሠበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 15493 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2024(ሐ) ድንጋጌ ለጉዳዩ መጥቀሱም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ይልቁንም አንድ የሥራ መሪ ለሰራው ስራ ደመወዝ መከፈሉን ማስረጃ ሁኖ ሊቀርብ የሚገባው ማስረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2593(1) በተመለከተው አግባብ የሚቀርበው ደረሰኝ ነው፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ያቀረበው የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ አስር አመት ሳያልፈበት የቀረበ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድበት አግባብ የሌለ ሲሆን አመልካች ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ባለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2593(1) ድንጋጌ አግባብም 1ኛ ተጠሪ የፈረሙበት የቀሪ ሂሳብ የመጨረሻ ደረሰኝ በማቅረብ ደመወዙ ለተጠሪው ስለመከፈሉ ያስረዳበት አግባብ የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለተጠሪ ብር 32,500.00 ያልተከፈለ ደመወዝ እንዲከፍል መወሰኑ በውጤት ደረጃ የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጨረሻውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በአንድ ላይ ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት 1ኛ ተጠሪ በሙያው ለስራው የኤሌክትሪክ ኢንስቶሌሽን ስራና በስራ መሪነቱ ስራ ሰርቶ ያልተከፈለውን ደመወዝ አመልካች እንዲከፈለው ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በውል መነሻ ለአመልካች ድርጅት የገጠሙላቸውን ሁለት በር መሰረት አድርገው መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ያደረገው ከአመልካች ጋር በተናጠል ያደረጓቸውን የተለያዩ ውሎችን መሆኑ ግልፅ ሲሆን አመልካች ከተጠሪዎች ከነበረው ግንኙነት አንጻር ክሱ በአንድ ላይ መቅረቡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 35 (1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ መሰረታዊ አላማ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለለም የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪዎችን ክስ አንድ ላይ በመቀበል አመልካችን እንደተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ ለይተው መወሰናቸው በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በመቐሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10912 በ30/04/2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በመቐሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16742 በ14/07/2007 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 74550 በ14/08/2007 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. 1ኛ ተጠሪ ከጥቅምት 01 ቀን 2005 እስከ ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም የስራ መሪ ነበሩ ተብሎ የተወሰነው ፍሬ ነገሩ በሕጉ አግባብ ተጣርቶና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3(2(ሐ) ስር የተመለከቱት መመዘኛዎች መሰረት ተደርጎ ነው ብለናል፡፡
3. የስራ መሪን በሚመለከት የተለዩ የሕግ ማእቀፍ ስለሌለ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካለው የፍትሃ ብሔር ሕጉ ስንነሳ የስራ መሪ የመብት ጥያቄ ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677(1) እና 1845 ድንጋጌዎች አግባብ የአስር አመት የይርጋ ጊዜ ነው ብለናል፡፡
4. የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2023 እና 2024 ያሉት ድንጋጌዎች የይርጋ ድንጋጌዎች ሳይሆኑ የክፍያ ግምት የሚወሰድባቸው በመሆኑና ለስራ መሪ ደመወዝ ጥያቄም አግባብነት የሌላቸው በመሆኑ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት የላቸውም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. ተጠሪዎች ክሳቸውን በአንድ ላይ ማቅረባቸው ተገቢ ነው፣ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል የተወሰነው የገንዘብ መጠንም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መሰረት ያደረገ ነው ብለናል፡፡
6. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117070

ጥቅምት 22 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሰሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ወይንሸት በቀለ ከጠበቃ ወይንሸት ከበደ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ኦሎምፒያኮስ ሄሌኒክ አትሌቲክስ ማህበር /ግሪክ ክለብ / የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ፤በተጠሪ ድርጅት ከጥር 16/1990 ዓ.ም ጀምሮ እየሰሩ እንደሚገኙ ይሰሩት ከነበረው ተጨማሪ ስራ ደርበው እንዲሰሩ በተደረገ ጊዜ የደመወዝ ማሻሻያ እንዲደረግላቸው ጠይቀው በዚሁ መሰረት ከነሐሴ 1 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዛቸው ተሻሽሎ ያገኙት ከነበረው በተጨማሪ በየወሩ ከሚገኘው አጠቃላይ የመጠጥና የምግብ ሽያጭ ገቢ ላይ 3% /ሶስት በመቶ/ የደመወዝ አካል ሆኖ እንዲከፈል ወስኗል፡፡ በዚሁ ውሳኔ መሰረት ከነሐሴ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሐሴ 2006 ዓ.ም ለ11 ዓመታት እየተከፈላቸው ሲሆን ምክንያቱ ባልተወቀ ከ3% /ሶስት በመቶ/ ቀንሶ 1% /አንድ በመቶ/ ብቻ እንዲከፈል በውሳኔ ያሳወቃቸው ስለሆነ ከነሐሴ 1 ቀን 2006 ዓ.ም እስከ ህዳር 2007 ዓ.ም በጠቅላላ 95,445.95 /ዘጠና አምስት ሺ አራት መቶ አርባ አምስት ከዘጠና አምስት ሳንቲም እንዲሁም ከታህሳስ 2007 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዛቸውን 2% ኮሚሽን ክፍያውን አካቶ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በከተከሳሽነት ቀርበው አመልካች የመጠጥና ምግብ ሰራተኞችን የሚቆጣጠሩ ኃላፊ ስለሆኑ የስራ መሪ ናቸው ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ነገር ላይም በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አንቀጽ 53 መሰረት ኮሚሽን ደመወዝ አይደለም ስለሆነም ተጠሪ ከመጠጥና ከምግብ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ 3% /ሶስት በመቶ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍቃደኝነት ቢወስንም እንደ አስፈላጊነቱ ደግሞ 1% /አንድ በመቶ/ እንዲከፈላቸው መወሰኑ እንደ ጥፋት ተቆጥሮ ኮሚሽን እንደ ደመወዝ ይቆጠርልኝ በማለት የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም መቃወሚያውን በብይን ወድቅ በማድረግ አመልካች የኮሚሽን ክፍያን እንደ ደመወዝ በመቁጠር ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ከደመወዛቸው በተጨማሪ 3% /ሶስት በመቶ/ ከጠቅላላው የምግብና የመጠጥ ሽያጭ እንደሚከፈላቸው በውላቸው የተቀመጠውን ተጠሪው ይህንን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከተጠሪው ነሐሴ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ለአመልካች የተፃፈ ደብዳቤ ይዘት መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ስለ ደመወዝ ማሻሻያ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ስለ ስራዎት ሁኔታ የክለቡ ኮሚቴ አባላት ተወያይተን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡ ታታሪ ሰራተኛ መሆንዎ እና በሙሉ ፍላጎት ስራዎትን የሚያከብሩ መሆኑን በመገንዘብ ከመስከረም 1995 ጀምሮ የክለቡ ተቆጣጣሪ እና ዋና ገንዘብ ያዥ መሆኖትን እና እንዲሁም ከአጠቃላይ የምግብና የመጠጥ ሽያጭ ላይ ኮሚሽን የደመወዝዎ አካል ሆኖ እንዲከፈሎት ወስነናል የሚል ነው፡፡ አመልካች የጠየቁት የደመወዝ ጭማሪ ነው፡፡ ተጠሪም ጥያቄቸው መሰረት በማድረግ ከምግብና የመጠጥ ሽያጭ 3% /ሶስት በመቶ/ ከሚሸን የደመወዝ አካል እንደሆነ በሚገልፅ ነው የፃፈላቸው፡፡ አመልካችም ያቀረቡት የደመወዝ ጭማሪ ምላሽ በማገኘቱ ተስማምተው ለ11 አመታት በዚሁ ስምምነት እየተከፈላቸው እንደነበረና መጠኑም በግራ ቀኙ ያልተካዱ ፍሬ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ከጅምሩ የአመልካች ጥያቄ የደመወዝ ጭማሪ እንጂ ኮሚሽን እንዲከፈላቸው ያልነበረ መሆኑን የደብዳቤው ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከምግብና መጠጥ ሽያጭ ከሚገኝ ገቢ 3% /ሶስት በመቶ/ የደመወዛቸው አካል መሆኑ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ ኮሚሽን ስለሆነ በፍቃድኝነት ያደረኩትን በፈለጉሁት ጊዜ ሁኔታዎች እየታየ የሚሰጥ እንጂ እንደ ደመወዝ በመቁጠር ሊጠየቅ አይገባም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ ምክንያቱ ለአመልካች የተደረገው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጭማሪ በተጠሪ ተነሳሽነት ሳይሆን አመልካች ባቀረቡት የደመወዝ ማሻሻያ ጥያቄ መሆኑ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተረጋገጠ ነው፡፡ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ተስማምተውበት ለ11 ዓመታት የደመወዝ አካል አድርገው ተግባራዊ ያደረጉትን ኮሚሽን ነው የደመወዝ አካል አይደለም በማለት በተጠሪ የሚቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በግልፅ የደመወዝ አካል አድርጎ ለአመልካች ከምግብና ከመጠጥ ሽያጭ ገቢ 3% /ሶስት በመቶ/ እየከፈላቸው የነበረው ኮሚሽን ስለሆነ ወደ 1% /አንድ በመቶ/ መቀነሱ ከስምምነታቸው ውጪ ሆኖ እያለ፤የስር ፍርድ ቤቶች የሚከፈለው መደበኛ ደመወዝ አለ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 53/2/መ/ ኮሚሽን እንደ ደመወዝ አይቆጠርም፤ደመወዝ የሚያስብል መደምደሚያ ላይ አያደርስም ሲል መወሰኑ በበቂ የህግ ምክንያት ያልተደገፈ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 17578 ጥር 26 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 156579 ሰኔ 4 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ከተጠሪ ድርጅት ከምግብና ከመጠጥ ሽያጭ ከሚገኘው ገቢ 3% /ሶስት በመቶ/ ኮሚሽን በስምምነታቸው መሰረት የአመልካች ደመወዝ አካል በመሆኑ ተጠሪ ብቻውን ሊቀንስ አይገባም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከነሐሴ ወር 2006 ዓ.ም ብር 23,907.19፤ ከመስከረም 2007 ዓ.ም 25,762.38፤ከጥቅምት 2007 ዓ.ም ብር 25,612.60፤ከህዳር 2007 ዓ.ም ብር 20,165.73 በጠቅላላ 95,445.95 /ዘጠን አራት ሺ አራት መቶ አርባ አምስት ከ0.95/100 /እንዲከፈላቸው እንዲሁም ከታህሳስ 2007 ዓ.ም ጀምሮ ወደፊት የተቀነሰውን 2% /ሁለት በመቶ/ ኮሚሽን ክፍያውን ከደመወዛቸው አካቶ ለአመልካች እንዲከፍል ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 103478

ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ኤልያስ ተፈራ - ጠበቃ ዳንኤል ፀጋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አንዋር ሁሴን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የተጀመረው በተጠሪ ከሣሽነት አመልካች ለተጠሪ ፈርመው የሰጡትን ቼክ ተጠሪ ቼኩን እንዲከፍላቸው ባንክ ሲያቀርቡ ቼኩ ሳይከፈል በመመለሱ ምክንያት ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ) ከነ ሕጋዊ ወለዱ እና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎች ጋር በአመልካች እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ተጠሪ በተፋጠነ ስነ ስርዓት በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡

አመልካች በመቃወሚያነት በቼኩ የተመለከተው ገንዘብ ለተጠሪ የተሰጠው ከተጠሪ ጋር በነበራቸው የኪራይ ውል ግንኙነት የተነሳ በሕገ ወጥ መንገድ ተጠሪ ጫና ፈጥረው ቼኩን የወሰዱ በመሆኑ ቼኩ እንዳይከፈል አመልካች ያሳገዱ መሆኑን ገልፀውና ይህንኑ ግንኙነት ለማስረዳት እንደሚችሉ ገልጸው በን/ሕ/ቁጥር 717 መሰረት ለመቃወም የሚያስችል የመከላከያ ማስረጃ ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው የቀረበውን ክስ ለመከላከል እንዲፈቀድላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአመልካችን የማስፈቀጃ ጥያቄ መርምሮ አመልካች የሚያቀርቡትን የመከላከያ ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሆኖ ማግኘቱን ገልጾ የአመልካችን የመከላከያ መልስ እንዲቀርብ የፈቀደ ሲሆን በዚህም መሰረት አመልካች መከላከያ መልሳቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ በመልሳቸውም የተጠሪ እናት የሆኑት ወ/ሮ ከድጃ ሠዒድ ከመንግስት የተከራዩትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ለአመልካች ከ1997 ዓ/ም ጀምሮ አከራይተው አመልካች የንግድ ስራ ሲሰሩበት የቆየ መሆኑን፣ በኋላም በመንግስት መመሪያ መሰረት ነጋዴዎች የንግድ ፈቃዳቸውን ለማሳደስ ዳግም ምዝገባ እንዲያደርጉ በሚደረግበት ጊዜ የሚሰሩበት የንግድ ቤት ከሌላ ሰው የተከራዩት ከሆነና አከራዩ በበኩሉ ቤቱን ከመንግስት የተከራየው እንደሆነ ከመንግስት ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል እንዲያቀርቡ በተጠየቁት መሰረት ተጠሪ ከመንግስት ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል እንዲያቀርቡ በተጠየቁት መሰረት አመልካች ተጠሪን ከመንግስት ጋር ያደረጉትን የኪራይ ውል እንዲሰጡና ዳግም ምዝገባውን እንዲያካሂዱ በሚጠይቅበት ወቅት ተጠሪ የእናታቸው ወኪል ሆነው ቤቱን ለአመልካች አከራይተው የነበሩ በመሆኑ ተጠሪ በማያውቁት መንገድ አመልካች ቤቱን በስማቸው ለማዛወር የሚያደርጉት ጥረት ነው በሚል ምክንያት የኪራይ ውሉን አመልካች እንዲሰጣቸው ከፈለጉ አመልካች ቼክ ፈርመው ለተጠሪ እንዲሰጡ፣ያለዚያ የኪራይ ውሉን እንደማይሰጧቸውና ቤቱንም ታስረክባለህ ወይም ለቀህ ትወጣለህ በማለታቸው ምክንያት አመልካች ቼኩን ፈርመው ለተጠሪ የሰጡ መሆኑን በመዘርዘር ተጠሪ በሕገ ወጥ መልኩ የራሳቸው ባልሆነ የመንግስት ቤት የማይገባቸውን ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ሌላ ከቤት ኪራይ ውል ውጪ ምንም ግንኙነት ከአመልካች ጋር ሳይኖራቸው አጋጣሚውን በመጠቀምና ጫና በማሳደር በአመልካች የተፈረመ ቼክ ነው በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ተከራክረዋል፡፡ ይህንኑ ለማስረዳትም አሉኝ ያሏቸውን የሰው ምስክሮች ቆጥረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በአመልካች የተቆጠሩት የሠው ምስክሮች ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም በሚል ምክንያት አልፎ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ብር 500,000.00(አምስት መቶ ሺህ ብር) ቼኩ ለክፍያ ከቀረበበት ከመጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ከመቶ ሕጋዊ ወለድ(9%)፣ ከመቶ 1/3ኛ እንዲከፍሉና ተጠሪ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር ማቅረብ መብታቸውን በመጠበቅ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተስርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ነው፡፡ የአመልከች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የመከላከያ ማስፈቀጃ ጥያቄውን ከተቀበለ በኋላ ሕጋዊ ባልሆኑ ምክንያቶችና የን/ሕ/ቁጥር 717 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ አስገዳጅነት ካላው የሰበሩ ውሳኔ ጋር ባግባቡ ሳያገናዝብ በአመልካች የተቆጠሩትን የሠው ምስክሮችን ሳይሰማ ምንም ግንኙነት ሳይኖር ለተጠሪ አከራካሪው ገንዘብ እንዲከፈል በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ባለመሆኑ ተሸሮ የአመልካች ማስረጃዎች ተሰምተው በጉዳዩ ላይ ተገቢው ዳኝነት እንዲሰጥ የሥር ፍርድ ቤት ይታዘዝ ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የበታች ፍርድ ቤቶች ለን/ሕ/ቁጥር 717 አፈጻጸም የሰጡትን ትርጓሜ አግባብነት ለማየት ጉዳዩ ለዚህ ሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አንፃርና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 284 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት በአጭር ሁኔታ በሚወሰኑ ክርክሮች ላይ ስለሚፈፀም ሥነ ሥርዓት በሕጉ የተመለከቱ ሥርዓቶችን መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ በአጭር ሥነ ሥርዓት ዳኝነት ታይቶ እንዲወሰን ክስ የሚቀርብበት ጊዜ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 285/1/ እንደተመለከተው ከሕጉ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ቁጥር 2 መሠረት ተከሣሽ የሆነው ሰው መጥሪያ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በአሥር ቀናት ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ክሱን ለመከላከል እንዲፈቀድለት ፍ/ቤቱን ፈቃድ እንዲጠይቅ መደረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ አመልካች ቼክ ለተጠሪ የተሰጠበት ምክንያት በኪራይ ውል ግንኙነት መሆኑንና ይኼው የኪራይ ውል በመንግስት በወጣው መመሪያ የተነሳ በአመልካችና በተጠሪ ያለመግባባት ፈጥሮ በዚሁ ምክንያት ቼኩን ባልተገባ መንገድና ሁኔታ ለተጠሪ ፈርመው የሰጡ መሆኑን በመጥቀስ ለመከላከል እንዲፈቀድላቸው በቃለ መሐላ የጠየቁ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህንኑ የአመልካችን ምክንያት በመቀበልም የስር ፍርድ ቤት አመልካች የመከላከያ መልስ እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸው አመልካች ሙሉ የሆነ መከላከያ መልስና አሉኝ የሚሏቸውን የሰው ምስክሮችን ቆጥረው የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ያቀረቡ መሆኑን የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘው የስር ፍርድ ዋና መዝገብ በግልጽ ያሳያል፡፡

የተጠሪ ዋና ክርክር በቼኩ ላይ ሐተታ ወይም ገደብ የለበትም የሚል ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለቼኩ መሰጠት መሰረቱ አመልካች ከተጠሪ እናት ጋር ያላቸው የመንግስት ቤት ላይ የተደረገ የኪራይ ውል የሚል ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ እናት መካከል የኪራይ ውል መኖሩ አልተካደም፡፡ ከአመልካች ጋር የተጠሪ እናት ያደረጉትን የኪራይ ግንኙነትን የሚያስተዳድሩት ደግሞ ወኪላቸው የሆኑት የአሁኑ ተጠሪ መሆኑን አመልካች ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ እንዲሁም በአመልካች በመከላከያ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ላይም ይህ ግንኙነት መኖሩ ተገልጿል፡፡ ይህንኑ ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶም የስር ፍርድ ቤት አመልካች መከላከያ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን ቼክ እንደ ገንዘብ ለተለያዩ ሰዎች በቀላሉ ሊተላለፍ የሚችል ባሕርይ ያለው የገንዘብ ሰነድ በመሆኑ ቼክ አስፋፊል ላይ ማንኛውም መቃወሚያ ሊቀርብበት እንደማይችል በንግድ ሕጉ የተደነገገ በመሆኑ ሕጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር የቼክ ክፍያ በማናቸውም ምክንያት ሊቆምና ሊታገድ የማይችል መሆኑ አከራካሪ ያለመሆኑን የን/ሕ/ቁጥር 717 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በምንመለከትበት የምንረዳው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን በባለጉዳዮቹ መካከል ግልጽ የሆኑ ሁኔታዎች ወይም ግንኙነቶች በተፈጠሩ ጊዜ ብቻ ይህን መቃወሚያ ለማድረግ እንደሚቻል በን/ሕ/ቁ. 717/1/ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ይህን መሠረት በማድረግ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ የተቀበለው ሲሆን በኋላ ግን በአመልካች የተቆጠሩትን የሠው ምስክሮች ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው ናቸው በማለት ሳይሰማ አልፎ የቼክ ክርክር በመሆኑ ብቻ የቼክን ባህርይ መሠረት በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም በዚህ የፈቃድ ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ አመልካች መከላከያ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጎ መልስና በሕግ አግባብ ምስክር ቆጥረው እያለ ምስክሮች ሳይሰሙ ይኼው ታልፎ የቼክ ባሕርይ ብቻ መሰረት ተደርጎ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 286፣ 291 እና 717 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ በአንድ ላይ በማንበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ምክንያት ፈቃድ የሚያሰጥ መሆኑ እስከታመነ ድረስ የቼክ ባህርይ መሰረት ተደርጎ ምስክሮችን የማሰማት መብታቸው ሊታለፍ የሚችልበት ምክንያት መኖሩን ከክርክሩ ሂደት ማግኘት አልተቻለም፡፡ ከፈቃድ በኋላ ያለው የፍሬ ነገር ክርክር ማስረጃ ተሰምቶ ሊነጥር የሚገባውና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የማስረጃ ምዘና መርህ በመከተል የሚታይ ይሆናል እንጂ የተከሳሽን የመከላከል መብት ወደ ኃላ በመመለስ መብቱን ለማጥበብ የሚያስችል አይሆንም፡፡ ከዚህ አኳያ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል ግንኙነት መሠረት በማድረግ ለመከላከል እንዲፈቀድ ፍ/ቤቱን ጠይቆ ተቀባይነት ያገኘው ጉዳይ ማስረጃ ሳይሰማ ውድቅ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም በጉዳዩ የስር ፍ/ቤቱ በአጭር ሥነ ሥርዓት እንዲታይ የሚቀርቡ ክሶች አመራር ሥርዓትን ሳይሆን የቼክ ባሕርይን መሠረት በማድረግ ውሣኔ መደምደሚያ ላይ መድረሱ አግባብ ሆኖ አላገኘንም፡፡ ምክንያቱም አመልካች ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት በፍ/ቤቱ አግኝቶ የተጠየቀውን ገንዘብ ላለመክፈል በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑ የሚታወቀው ፍ/ቤቱ ከአጭር ሥነ ሥርዓት ወደ መደበኛ የክርክር ሥነ ሥርዓት ውስጥ በመግባት ግራ ቀኙን በአግባቡ በማስረጃ ካከራከረ በኋላ ነው፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 125412 ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 99239 ግንቦት 09 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 125412 ቀጥሎ ግራ ቀኙን በመደበኛ የክርክር ሥርዓት አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውንውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሰናል።ይጻፍ።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።

መዝገቡን ዘግተናል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.109054

መጋቢት 26 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- አቶ ነገሰ ግዛው -ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ሒርጳ ቤኛ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች አቶ ነገሰ ግዛው ጥር 15 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 187309 ጥር 14 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጡት ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የቀረበ ነው፡፡ ቅሬታውም በዋናው መዝገብ ቁጥር 21302 በቀን 9-4-2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሰጠው ውሳኔ አዋሳኙ ተጠቅሶ 1 ቀርጥ የመሬት ይዞታ እንደሆነ በግልጽ ተጠቅሶ የቀረበ ሲሆን ሁለት ተኩል ቀርጥ መሬት እንድፈጽም መታዘዙ ተገቢ ባለመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 21780 የአሁን ተጠሪ ሂርጳ ቤኛ የአፈጻጸም ክስ አቅርቦ ፍ/ቤቱ የቀበሌው መስተዳድር የአፈጻጸም ተከሳሽ አቶ ነገሰ ግዛው ከመሬቱ ላይ ባህር ዛፎቹን ለማንሳት ፍቃደኛ ስላልሆነ ከባህርዛፎቹ ጋር ለአፈጻጸም ከሳሽ አስረክበናል፡፡ ባህርዛፎቹ 1 ዓመት የሞላቸው ሆኖ በሁለት ቀርጥ ተኩል መሬት ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልጿል፡፡ የአፈጻጸም ተከሳሽ ለአ/ከሳሽ የተወሰነለት መሬት አንድ ጥማድ ብቻ በመሆኑ ሌላውን መፈጸም አይገባኝም ሲል የአ/ከሳሽ ደግሞ ክስ ያቀረብኩትና የተወሰነልኝ የመሬት አዋሳኝ ይሄው የተፈጸመልኝ መሬት በመሆኑ ባግባቡ የተፈጸመ ነው በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተከራከሩትን መዝግቦ የካቲት 6 ቀን 2006 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የተሰጠው ውሳኔ የመሬቱን አዋሳኝና ስፋቱ በክሱ ውስጥ የተቀመጠው ነው በማለት ስለተወሰነ ለአፈጻጸም ከሳሽ የተፈጸመለት መሬት የተወሰነለትን ነው በማለት ወስደን ውሳኔው ፍጻሜ ስላገኘ መዝገቡን ዘግተነዋል ሲል አሏል፡፡ የአፈጻጸም/ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 00164 ነሐሴ 22/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድ ቤት በዋናው ውሳኔ በመ.ቁጥር 21302 ታህሳስ 9/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የመሬቱ አዋሳኝ በምስራቅ አቶ ጣፋ ሀይሉ እና አበራ ሃይሉ በምዕራብ እና በሰሜን በአፈጻጸም ተከሳሽ እና በደቡብ የመኪና መንገድ ሲሆን አንድ ቀርጥ መሬት ነው፡፡ ቀበሌው በውሳኔ ውስጥ የተጠቀሰውን አዋሳኝ መሬት 2 ቀርጥ ተኩል ያስፈጸመ መሆኑን በሪፖርቱ ጠቅሷል፡፡ የመሬቱ አዋሳኝ በውሳኔ በተጠቀሰው አዋሳኝ ውስጥ ያለው መሬት ሁሉ በመሆኑ ይግባኝ ባይ ቅሬታ ካለው በይግባኝ ማስተካከል ነበረበት እንጂ እንደውሳኔው በመፈጸሙ ቅር የሚያሰኝ አይደለም ሲል የወረዳ ፍ/ቤትን ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡ አ/ተከሳሽ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁ. 187309 ጥር 14/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ የቀረበው አቤቱታ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ አቤቱታ አያስቀርብም ሲል ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካች በዋናው ፍርድ ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተወሰነባቸው አንድ ቀርጥ መሬት መሆኑን የስር ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ ገልጾ አመልካች ለተጠሪ ያስረከቡት ግን ሁለት ቀርጥ ተኩል መሆኑን የቀረበው ሪፖርት የሚያሳይ ሆኖ እያለ ከፍርዱ ውጪ አንድ ቀርጥ ተኩል መሬት በተጨማሪ ማስረከብ የለብኝም ሲል አመልካች ያቀረበውን ቅሬታ የስር ፍ/ቤት ሳይቀበለው የመቅረቱን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 26/2007 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ የወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች መብቱ ያልሆነውን እና በአዋሳኝ የማንገናኝ ይዞታየን ይዞ ባህር ዛፍ መትከሉ ተረጋግጦ ባህርዛፉን አንስቶ ይዞታዬን እንዲለቅልኝ በውሳኔው መሰረት የተፈፀመ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይሁንልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሰኔ 18/2007 ዓ.ም. በተፃፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡ በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው ፡ በዋናው መዝገብ ቁጥር 21302 የተሰጠው ውሳኔ አንድ ቀርጥ መሬት አዋሳኙ ተጠቅሶ የአሁን አመልካች ለተጠሪ እንዲለቅለት የተወሰነ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ውሳኔ የተሰጠበት መሬት ስፋቱ አንድ ቀርጥ መሬት ሆኖ እያለ ሁለት ቀርጥ ተኩል መሬት ለአሁን ተጠሪ መፈጸሙን በተመለከተ የሥር ፍ/ቤት በዋናው መዝገብ ውሳኔ ሲሰጥ አዋሳኙ ተጠቅሶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተወሰነ በመሆኑና አሁንም ለተጠሪ (የአፈጻጸም ከሳሽ) የተፈጸመው በዚሁ አዋሳኙ በተጠቀሰው ክልል ውስጥ የሚገኘው መሬት በመሆኑ አፈጻጸሙ ተገቢ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ለዚህ ውሳኔያቸው ድምዳሜ ምክንያት ያደረጉት የዋናው መዝገብ ቁጥር 21302 ውሳኔ የመሬት አዋሳኝን መሰረት በማድረግ ብቻ እንደሆነ ከተደረገው ክርክር መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ይሁንና በዋናው መዝገብ አንድ ቀርጥ የመሬት ይዞታ ውሳኔ ተሰጥቶበት ከእጥፍ በላይ ሁለት ቀርጥ ተኩል መፈጸሙ የመሬቱ አዋሳኝ በአንድ በኩል በደቡብ አቅጣጫ የአፈጻጸም ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) የሚያዋስነው ሆኖ እያለና በዚሁ አቅጣጫ ወደ አመልካች የመሬት ይዞታ ሊታለፍ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል የስር ፍ/ቤት በሚከተሉት 1. ክርክር ስላስነሳው የእርሻ መሬት አዋሳኝ እና መጠን ጉዳይ ተጠሪዋ ክሳቸውን ባቀረቡበት ጊዜ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 224(2) መሰረት የሰጡት መግለጫ ይዘት ምን እንደሆነ 2. በአመልካቹ መልስ ላይ የተሰጡት ትችት ምን እንደ ሆነ፡ 3. ክርክር ስላስነሳው የእርሻ መሬት አዋሳኝ እና መጠን ጉዳይ በስረ ነገሩ ፍርድ ላይ የተገለጸው የውሳኔ ክፍል የተሟላ ይዘት ምን እንደሆነ 4. ተጠሪዋ ክስ ያቀረቡበት እና የስረነገሩ ፍርድ ያረፈበት የእርሻ መሬት ይታወቅ የነበረው በቀርጥ በምን ያክል መጠን እንደ ሆነ፡ ከተጠቀሱት ነጥቦች በመነሳት በስረነገሩ ፍርድ ላይ በተገለጸው መጠን እና በአፈጻጸም ጊዜ በተሰላው መጠን መካከል ልዩነት ሊከሰት የቻለበት አጠቃላይ ምክንያት ምን እንደሆነ ተጣርቶና ተለይቶ ከታወቀ በኃላ መፈጸም ነበረበት፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በዋናው መዝገብ ውሳኔ የተሰጠበት መሬት አንድ ቀርጥ ሆኖ እያለ ሁለት ቀርጥ ተኩል የሆነበት ምክንያት ሳይጣራ አዋሳኙን ብቻ መሰረት በማድረግ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ እና ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁ. 187309 ጥር 14/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ፣ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ. ቁ. 00164 ነሐሴ 22/2006

   ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ የሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት በመ. ቁ. 21780 የካቲት 6/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት በዋናው መዝገብ ቁ. 21302 የተሰጠው ውሳኔ አንድ ቀርጥ መሬት አዋሳኙ ተጠቅሶ ለአሁን ተጠሪ አመልካች እንዲለቅለት ተወስኖ እያለ የተፈጸመው መሬት ሁለት ቀርጥ ተኩል የሆነበት ምክንያት ከላይ በፍርዱ ክፍል ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ተራ ቁጥር አራት የተጠቀሱትን እና ተያያዥ ነጥቦችን ከስረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነገሩ ፍርድ ይዘት እና ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጭምር በማጣራት ውሳኔውን እንዲያስፈጽም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡

3. የውሳኔው ቅጂ በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲከወን ለሜታ ሮቢ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲያውቁት ደግሞ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ይላክ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻችሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102141

. መጋቢት 29 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ አደን ዩሱፍ ታኒ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አህመድ አብዱላሂ ተረቢ - ጠበቃ ሽፈራው በላይ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክሱ በቀረበበት የዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የተጠሪው አባት መሆኑ በተረጋገጠው ይዞታ ላይ ለገነቡት ቤት የቤቱን የዋጋ ግምት ብር 346,292 (ሶስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት) ወስደው ቤቱን ከነይዞታው ከሳሽ ለነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ለቀው እንዲያስረክቡ በዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር M/13/06 በ06/05/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 05-33/06 በ03/08/2006 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 05-1-91/06 በ14/09/2006 ዓ.ም. የፀናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ አመልካች የተጠሪ አባት ይዞታ በሆነው ቦታ ላይ አላግባብ ቤት መስራታቸውን የሚገልጽ ሆኖ ይህንኑ ይዞታና ቤት ለቀው እንዲያስረክቡ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይዘቱ ከላይ የተገለፀውን ውሳኔ የሰጠው የአመልካቹን መልስ የመስጠት መብት አልፎ የተጠሪውን ምስክሮች በመስማት እና ቀጥሎም ክሱን ከሰማ እና አመልካቹ በይዞታው ላይ የገነቡት ቤት በባለሙያዎች ተገምቶ እንዲቀርብ ካደረገ በኃላ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው ባዶ መሬት በብር 100,000 ገምተው ክስ ማቅረባቸውን፣የአመልካች ተወካይ ከክርክሩ እንዲሰናበቱ ተደርጎ አመልካች መልስ ለማቅረብ በቂ ጊዜ ሳይሰጣቸው መልስ አላቀረቡም በሚል መልስ የመስጠት መብታቸው የመታለፉን፣በኋላም ቀርበው የቃል ክርክር አድርገዋል ተብሎ ማስረጃ የማቅረብ ዕድል ሳይሰጣቸው የተጠሪ ምስክሮች ብቻ ተሰምተው አመልካች ከ35 ዓመት በላይ ሰርተው የሚኖሩበትን ቤት ለተጠሪው እንዲለቁ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመወሰኑን እና ውሳኔው በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የመፅናቱን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቹን መልስ የመስጠት መብት አልፎ የተጠሪውን ክርክር እና ማስረጃ ብቻ መሰረት አድርጎ ውሳኔ መስጠቱ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ነጥብ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው የዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለቀረበባቸው ክስ መልስ ይዘው እንዲቀርቡ በተሰጣቸው የ19/03/2006 ዓ.ም. ቀጠሮ አልቀረቡም በሚል በ30/03/2006 ዓ.ም. በተጻፈ መጥሪያ መልሳቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ለ02/04/2006 ዓ.ም. ተለዋጭ ቀጠሮ የተሰጣቸው መሆኑን፣በዚህ ቀነ ቀጠሮ የአመልካቿ ልጅ እና ተወካይ የጽሁፍ መልሳቸውን ይዘው የቀረቡ መሆኑን፣ይሁን እንጂ መልሱ ስህተት አለበት በሚል አስተካክለው እንዲያቀርቡ በተነገራቸው መሰረት ለመፈጸም ተወካይዋ ፈቃደኛ ስላልሆኑ እና ችሎቱንም ስለሰደቡ በአመልካች የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ተሰርዟል በሚል አመልካች ራሳቸው መልሳቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ለ04/04/2006 ዓ.ም. ተለዋጭ ቀጠሮ የተሰጣቸው መሆኑን፣የአመልካቹ የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብት የታለፈውም አመልካች በዚህ ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርቡ በመቅረታቸው መሆኑን፣ከዚህ በኃላ ፍርድ ቤቱ በ05/04/2006 ዓ.ም. ክርክር ያስነሳውን ቤት እና ይዞታ በአካል ሄዶ የተመለከተ መሆኑን፣በ07/04/2006 ዓ.ም. የተጠሪውን ምስክሮች የሰማ መሆኑን እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 ድንጋጌ መሰረት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል የተባለውም ከላይ የተመለከተው ሂደት ሁሉ ከተከናወነ በኃላ በመጨረሻ ላይ በ15/04/2006 ዓ.ም. መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በመሰረቱ ተገቢው የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው እስከሆነ ድረስ የዋናው ባለጉዳይ ባለቤት፣ወንድም፣እህት፣ልጅ፣አባት፣አያት ስለዋናው ባለጉዳይ ሆነው በወኪልነት ለመከራከር፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመሚጋትና ነገሩን ለመከታተል የሚችሉ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 58 (ሀ) ስር የተመለከተ ሲሆን የአመልካች ልጅም በዚሁ ስርዓት መሰረት ከአባታቸው በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሰረት በ02/04/2006 ዓ.ም. ቀነ ቀጠሮ የጽሁፍ መልስ ይዘው ቀርበው እንደነበረ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ ገልጿል፡፡መልሱ ስህተት አለበት ከመባሉ በቀር ስህተቱ ምን እንደሆነ እና ስርዓቱን ጠብቆ የተሰጠ የመልስ ይሻሻል ትዕዛዝ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡የአመልካች ልጅ ከክርክሩ እንድትሰናበት የተደረገው አባቷን ወክላ ለመከራከር የሚያስችል ተገቢ የውክልና ስልጣን ስላልነበራት ነው በማለት ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ያቀረቡት ክርክር የመዘገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ከላይ እንደተገለጸው ፍርድ ቤቱ ከክርክሩ ያሰናበታትም ለችሎቱ ያልተገባ ሥነ ምግባር አሳይታለች በሚል እንጂ ይዛው የቀረበችው የውክልና ስልጣን ማስረጃ ጉድለት አለበት በማለት አይደለም፡፡

በመሰረቱ የአመልካቹ ተወካይ ለችሎቱ ተገቢ ያልሆነ ስነ ምግባር አሳይተዋል የሚባል ከሆነ የችሎቱን ክብር ለማስጠበቅ ፍርድ ቤቱ በሕግ አግባብ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይችል የነበረ ከመሆኑ ውጪ አመልካች ለልጃቸው የሰጡትን የውክልና ስልጣን ለመሰረዝ ወይም ለመሻር የሚያስችል ስልጣን የለውም፡፡በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ ተገቢ ምክንያቶች ሲያጋጥሙት ምክንያቱን በማስፈር ዋናው ባለጉዳይ እራሱ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት የሚችል ስለመሆኑ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተ ቢሆንም በተያዘው ጉዳይ አመልካች ራሳቸው መልሳቸውን አዘጋጅተው እንዲቀርቡ የተሰጣቸው የሁለት ቀናት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ይህ ጊዜ ደግሞ ከተለያዩ ሁኔታዎች አንጻር ሲታይ በቂ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡በመሆኑም የአመልካች ወኪል ያቀረቡት የጽሁፍ መልስ ተቀባይነት ያጣበት በቂ እና ሕጋዊ ምክንያት መኖሩ ባልተገለጸበት እና ስርዓቱን ጠብቆ የተሰጠ የመልስ ይሻሻል ትዕዛዝ በሌለበት ሁኔታ፣ እንዲሁም አመልካች እራሳቸው መልሳቸውን አዘጋጅተው ማቅረብ እንዲችሉ በቂ የሆነ ጊዜ እንዲሰጣቸው ባልተደረገበት ሁኔታ የአመልካቹ የጽሁፍ መልስ የመስጠት እና ማስረጃ የማሰማት መብት ታልፎ የተጠሪውን ክርክር እና ማስረጃ ብቻ መሰረት አድርጎ አመልካቹን ለክሱ ኃላፊ የሚያደርግ ውሳኔ መሰጠቱ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር M/13/06 በ06/05/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 05-33/06 በ03/08/2006 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 05-1-91/06 በ14/09/2006 ዓ.ም. የፀናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቹ ለደረሳቸው ክስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 334 (1) ድንጋጌ መሰረት ተገቢ ነው የሚሉትን የጽሁፍ መልስ እንዲያቀርቡ ካደረገ በኃላ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት አድርጎ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ጭምር መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ለዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለዶሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
4. በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05-1-91/06 የተሰጠው ፍርድ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ04/13/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 114816

ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች ፡- ዳዊት በለጠ የጠጠር አምራች ድርጅት -ጠበቃ እሸቱ አሰፋ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አብዱራዛቅ መሳ ኡስማን -አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ህግ ከደነገገው ውጭ አመልካች የስራ ውሌን አቋርጧል፤ ስለሆነም ለህገውጥ ስንበት በህጉ የተፈቀደው ልዩ ልዩ ክፍያዎች ይከፈለኝ በማለት የክፍያ አይነቶችን ዘርዝሮ ዳኝነት ሲጠይቅ፤ የአሁን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ከነሀሴ 30 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በመደዳ ከስራ የቀረ በመሆኑ የስራ ውሉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ለ/ ስር በተመለከተው መሰረት እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህጋዊ ስለሆነ ክፍያ ልንጠየቅ አይገባም፡፡ የ25 ቀን የዓመት እረፍት እንከፍላለን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ምስክሮቹን ለማቅረብ በተያዘው ቀጠሮ ቀን ያላቀረበ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 199/1/ መብቱ የታለፈ መሆኑን በመግለፅ፤ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ ስለሌለ ስንብቱ ህገወጥ ነው በማለት ልዩ ልዩ ክፍያዎችን በማስላት በድምሩ ብር 23,000 ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት ስላለገኘ በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 17 ቀን 2007 ዓ.ም በዓፋት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ማስረጃ የማሰማት መብት የታለፈው በግልፅ የተካደ ፍሬ ነገር በማስረጃ ሳይነጥር አምነዋል ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተብሎ እንዲሻርልን ወጪና ኪሳራ እንዲተካልን የሚል አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አብቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል ፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች ጥያቄ የማስረዳት መብት በማለፍ በማስረጃ ሳይረጋገጥ ውሳኔ መሰጠቱ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ደግሞ አመልካች አዲስ ነገር በማቀረቡ ክሱ የሚከፍተው ተከሳሽ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተከሳሽ የማስረዳት ኃለፊነቱ ነው ማለቱ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት የአሁኑ አመልካች ምስክሮቹ እንዲያቀርብ በተያዘው ቀጠሮ አለመቅረቡን ነው፡፡
ክስን መክፈትና ሙግትን የመጀመር መብት የከሳሽ ነው፡፡ ነገር ግን ተከሳሹ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ አምኖ ነገር ግን ሕግ ወይም ሌላ ፍሬ ነገር በመጥቀስ የቀረበብኝ ክስ ዋጋ የለውም ብሎ የሚከራከር ከሆነ ሙግቱን የሚጀምረው ተከሳሹ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 258/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ከሳሽ በማስረጃ አቀራረብ ረገድ ጀማሪ የሚሆነው ሁል ጊዜ እንዳልሆነ የስነ ስርዓት ህጉ በግልፅ ይደነግጋል፡፡
ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በተጠሪ የቀረበው ክስ የስራ ስንብቱ ህገወጥ ነው የሚል ሲሆን አመልካች ደግሞ ከስራ ያሰናበተው መሆኑን በማመን ነገር ግን በተከታታይ የስራ ቀናት በመቅረቱ ስንብቱ ህገወጥ ሊባል አይችልም የሚል ነው፡፡ እዚህ ላይ አመልካች ተጠሪን ከስራ ማሰናበቱን ከተቀበለ ፤ ለሰንብቱ ምክንያት የሆነው የተጠሪ ጥፋት መሆኑን የማሰረዳት ሸክሙ የስር ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ ተጠሪ በተከታታይ የስራ ቀናት መቅረቱን ማረጋገጥ ያለበት አመልካች እንጂ ተጠሪ እንዲያስረዳ አይጠበቅም፡፡ አመልካች ምስክሮቹን እንዲያቀርብ በተያዘው ቀጠሮ ባለማቅረቡ የታለፈበት መሆኑ ከስር መዝገብ ተመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ከህግ ውጭ ከስራ ስላሰናበተኝ ተገቢውን ክፍያ ይከፈለኝ የሚል ክስ ያቀረበው አመልካች ያሰናበተው መሆኑን አምኖ የተሰናበተው በተጠሪ ጥፋት መሆኑን ገልፆ ስለተከራከረ መጀመሪያ ማስረዳት ያለበት አመልካች ነው፡፡ ነገር ግን በአመልካች ጉድለት ምክንያት ምስክሮቹን በማቅረብ ማስረዳት አልቻለም፡፡ በማስረጃ ያልተደገፈ የፍሬ ነገር ክርክር ረቺ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ ከላይ በተዘረዘሩ ምክንያቶች አመልካች ማስረጃ ሳይሰሙ መወሰኑ አግባብ አይደለም ሲል ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚሁ መሰረትም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.54094 ሚያዝያ 28 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ /ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10627 ሰኔ 4 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/በ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በፌ/መ/ደ/ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 57878 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117754

ሐምሌ 8 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አክሰስ ሪል ስቴት (አ.ማ)

ተጠሪ፡- ጋቢ ኢንቨስትመንት ኃ/የተ/የግል ማህበር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የይግባኝ መዝገብ በድሀ ደንብ እንዲከፈትለት ያቀረበውን ማመልከቻ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውድቅ ያደረገው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በሰበር አይቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 5 ቀን 2007 ዓ.ም በተሻረ የቃለ መሃላ ማመልከቻ፡-
   - በድርጅቱ ሠራተኞች፣ ቤት ገዥዎችና ሌሎች ባለመብቶች በፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት የፍርድ ባለዕዳ በመሆኑ፣
   - ድርጅቱ ማናቸውም የባንክ ሒሳብ እንዳይከፍትና እንዳያንቀሳቅስ ብሔራዊ ባንክ በሰጠው መመሪያ የታገደ በመሆኑ፣
   - ድርጅቱ በሊዝና በሌላ መንገድ የያዛቸውና ያለማቸው መሬቶች ላይ ማናቸውንም እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ በሰጠው መመሪያ የታገደ በመሆኑ
   - ድርጅቱ በስሙ ያሉትን ንብረቶች እንዳይሸጥ እንዳያከራይና በዕዳ እንዳያሲዝ የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በሰጠው መመሪያ የታገደ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ድርጅቱ ባለበት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ለዳኝነት የሚከፍለው ገንዘብ ስለሌለ የድርጅቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታ ሲሻሻል የዳኝነቱን ገንዘብ የሚከፍል ሆኖ ለጊዜው የይግባኝ መዝገቡ በድሃ ደንብ ተከፍቶ እንዲታይ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ የሚል ጥያቄ አቅርቧል፡፡

2. ተጠሪ በበኩሉ ድርጅቱ በውጭ አዲተር ተመርምሮ ካለው ካፒታል 3/4ኛው የጠፋ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ አክሲዮን ማህበሩ በፍርድ ቤት የኪሣራ ውሳኔ አልተሰጠበትም፡፡ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በስሙ የሌለው መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ በአንዳሩ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ድርጅቱ በቂ የገንዘብ አቅም ያለው መሆኑንና ለቤት ገዥዎች ቤታቸውን አጠናቅቆ ሊያስረክባቸው እንዲችል የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸው የሚጠይቁ የቤቱ ገዥዎች ገንዘባቸው የሚመለስላቸው መሆኑን ግልፅ የሆነ መግለጫ ሰጥተዋል ስለዚህ አክሲዮን ማህበሩ ደሃ ነው ለማለት ስለማይችል ይግባኙ በድሃ ደንብ ሊከፈትለት አይገባም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

3. ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ አመልካች ይግባኝ ባይ /አመልካች/ ካለው ካፒታል 3/4ኛው የጠፋ ስለመሆኑ በገለልተኛ ባለሙያ ተጣርቶ ያልቀረበ በመሆኑ በድሃ ደንብ ይግባኙ እንዲከፈትለት ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ያለኝን ንብረት ሽጬ ወይም አከራይቼ ለዳኝነት እንዳልከፍል በተለያዩ አካላት በተሰጠ የዕግድ ትዕዛዝ ምክንያት የማልችል መሆኔን በገለፅኩበት ሁኔታ ፍትህ የማግኘት መብቴን የሚያሳጣ ብይን መሰጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚል የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው መሆኑን በመዘርዘርና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያቀረባቸውን መከራከሪያ ነጥቦች በማጠናከር መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የፍተሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 467 የዳኝነት የሚከፍለው ገንዘብ የሌለውና ለማግኘት የማይችል ሰው በነፃ ፋይል ማስከፈት እንደሚችል በንዑስ አንቀጽ 1 ደንግጓል፡፡ አመልካች የይግባኝ መዝገብ በነፃ እንዲከፈትለት ጥያቄ ያቀረበው ያለውን ንብረት እንዳይሸጥ፣ እንዳይለውጥና እንዳያከራይ በተለያዩ የመንግስት አካላት ለጊዜው የተላለፉ የዕግድ ትዕዛዞች ስላሉ ያለኝን ሀብት ሸጬ የባንክ ሒሳቤን አንቀሳቅሼ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መክፈል የሚገባኝን የዳኝነት ገንዘብ ለጊዜው ላገኝ አልቻልኩም በማለት ነው፡፡ ይህም በመንግስት አካላት በተሰጠ ትዕዛዝ አመልካች ያሉትን የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዳይሸጥ፣ እንዳይለውጥ የባንክ ሒሳብ እንዳይከፍትና እንዳያንቀሳቅስ ተደርጎ ከሆነ አመልካች በንግድ ህጉ መሠረት ¾ የነበረውን ካፒታል የተጠቀመ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የከሰረ መሆኑ ባይረጋገጥም በፍተሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1793 (ለ) መሠረት አመልካች ከአቅሙ በላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሆነ የመንግስት አካላት ንብረቱን እንዳያንቀሳቅስ በሰጡት ዕግድና ጊዜያዊ ክልከላ ምክንያት ለጊዜው ይግባኙን ለማሳየት የዳኝነት የሚከፍለው ገንዘብ የሌለ መሆኑ ከተረጋገጠ ንብረቱን መሸጥ መለወጥ ሲፈቀድለት በቅድሚያ የዳኝነት ክፍያውን የሚከፍል ሆኖ ለጊዜው ይግባኙ በነፃ እንዲከፈትለት ከመጠየቅ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 467 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እና የህገ መንግስቱ አንቀጽ 37(1) ድንጋጌ ይዘት፡- አመልካች አለኝ የሚለውን ንብረት እንዳላንቀሳቅስ ታግዶብኛል ከሚለው ክርክር ጋር በማገናዘብ ለመረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ አንፃር ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ከነበረው ካፒታል ¾ኛ መጠቀሙ ስላልተረጋገጠ በነፃ ዳኝነት ሊከፈትለት አይገባም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

5. በሌላ በኩል አመልካች ለጊዜው ይግባኙን ለማሳየት የሚከፍለው የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል የማያስችለው በተለያዩ ንብረቶች ላይ የተለያዩ የመንግስት አካላት የሰጡት ዕግድ ያለመሆኑን የገለፀውን ፍሬ ነገር ይግባኝ ሰሚው ችሎት ዕውነትነት ያለው መሆኑን በጭብጥነት በመያዝ ያላጣራው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ አንፃር ይግባኝ ሰሚው ችሎት፡-

   ሀ) የድርጅቱ ሠራተኞች ገቨርዎች የፍርድ ባለመብት በመሆናቸው በፍርድ ቤት የታገደ የአመልካች ገንዘብና የሚንቀሳቀስንና የማይንቀሳቀስ ንብረት፣

   ለ) አክስዮን ማህበሩ የባንክ ሒሳብ እንዳያንቀሳቅስና እንዳይከፍት ከብሔራዊ ባንክ ለሌሎች ባንኮች የተሰጠ መመሪያና ዕግድ ያለ መሆኑን፣

   ሐ) ድርጅቱ በሒሳብና በሌላ መንገድ የያዛቸውና ያለማቸው መሬቶች ላይ ማናቸውንም እንቅስቃሴ እንዳያደርግ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ለሌሎች አካላት የተሰጠ መመሪያና ዕግድ ያለ መሆኑንና

   መ) ድርጅቱ በስሙ ያሉትን የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዳይሸጥ፣ እንዳይለውጥ፣ እንዳያከራይ፣ በዕዳ እንዳያሲዝ ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንስ የተላለፈ መመሪያና የተሰጠ ዕግድ ያለ ስለመሆኑ አመልካች ማስረጃውን እንዲያቀርብ በማድርግና ተጠሪም የአመልካችን ማስረጃ የሚያስተባብሉ ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ በማድረግ አመልካች በፍተሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 1793 (ለ) በንብረቶች ላይ ባስተላለፈው ዕግድና ጊዛዊ ክልከላ መሠረት ይግባኙን በማሳየት መክፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ ለጊዜው መክፈል የማይችልበት ሁኔታ አለ ወይስ የለም የሚለው ጭብጥ ላይ ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343 (1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 112204 ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዚህ ፍርድ የተገለፁትን ነጥቦች በማጣራት የይግባኝ መዝገቡ በነፃ ሊከፈት ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 115892

ሐምሌ 4 ቀን 2008ዓ.ም

ዳኞች፡ አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ መሰረት አንዳርጌ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ይበልጣል ስመኝ
2. ወ/ሮ ትርንጎ ስመኝ
3. አቶ ታደሰ ስመኝ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

1. ጉዳዩ የቀረበው የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ያቀረበችውን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ለመቀበልና ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ ለመወሰን የሚያስችለኝ የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ብይን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማጽናቱ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካችና ሌሎች የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅራቢዎች፣ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ያቀረቡት የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 13904 አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ከሳሽ ሶስተኛው ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረው መጋቢት 16 ቀን 2001ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንን በማሻሻል የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በመዝገብ ቁ. 13904 አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ቀርበው ተከሳሽ (3ኛ ተጠሪ) የወላጅ አባታችን አቶ ስመኝ ባይህ የውርስ ንብረት የሆነ ንብረት በመያዝ ጠቅላላ ግምቱ ብር 2,856.000 /ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ስድስት ሺ ብር/ የወሰደ በመሆኑ፣ ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ ድርሻችንን እንዲያካፍለን ይወሰንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተከሳሽ ያቀረቡትን ክስ በመቃወምና በመከላከል መልስ አቅርቧል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሳሹ (ሶስተኛ ተጠሪ) ግምቱ ብር 1,867,728 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር/ የሚችን የውርስ ንብረት የያዙ በመሆኑ የከሳሾችን /አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪን/ ድርሻ ከነወለዱ እንዲከፍል በማለት መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
3. ሶስተኛ ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 13904 መጋቢት 16 ቀን 2001ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሶስተኛ ተጠሪንና የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪን የይግባኝ ክርክር በይግባኝ መዝገብ ቁ. 24731 ከሰማ በኋላ፣ የከሳሾች (የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ) የውርስ ንብረት ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ሚያዚያ 11 ቀን 2002 ዓ.ም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 11 ቀን 2002ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ የሰበር አመልካች ሶስተኛ ተጠሪ የሠበር ተጠሪ በመሆን ያቀረቡትን ክርክር በሰበር መዝገብ ቁ. 09914 ከሰማ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች የውርስ ንብረት ለመካፈል ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ሽሮ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ወደ ፍሬ ጉዳዩ ገብቶ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ ይስጥበት በማለት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት መልሶለታል፡፡
4. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል ዘግቶት የነበረውን የይግባኝ መዝገብ ቁ. 24731 ካንቀሳቀሰ በኋላ (የይግባኝ ባዩን/ ሶስተኛ ተጠሪንና) የመልስ ሰጭዎችን /አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች/ ክርክር ከሰማ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ባዩ /ሶስተኛ ተጠሪ/ ለመልስ ሰጭዎች (አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ) ግምቱ ብር 1,867,728 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር/ ከሆነው የውርስ ንብረት ድርሻቸውን ያካፍላቸው በማለት የሠጠውን የውሳኔ ክፍል አፅንቶ፣ ሶስተኛ ተጠሪ ወለድ ሊከፍል ይገባል በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውሳኔ ክፍል ብቻ በመሻር ሶስተኛ ተጠሪ የውርስ ንብረት ወለድ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት በይግባኝ መዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 17 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. ሶስተኛ ተጠሪ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 14 ቀን 2005 ዓ.ም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ወለድን በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት አቅርቦ፣ የክልሉ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሶስተኛ ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት አቅርቦ፣ ይኽ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁ. 96715 የሶስተኛ ተጠሪንና /የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች/ ክርክር ከሰማ በኋላ የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 13904 መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 14 ቀን 2005 ዓ.ም እንደተሻሻለ አፅንቶታል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 14 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለቱ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይህ ሰበር ችሎት በአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች አመልካችነት መነሻ በሰበር መዝገብ ቁ. 98329 ከሰማ በኋላ የአንደኛና የሁለተኛ ተጠሪ የሰበር አቤቱታ በሰበር ለመታየት ብቁ አይደለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

6. አመልካችና በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆኑት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅራቢዎች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ከሳሽ ሶስተኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው በተከራከሩበት በመዝገብ ቁ. 13904 መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም ውሳኔ የሰጠበት የውርስ ንብረት ላይ እኛም ድርሻ ያለን በመሆኑ ወደ ክርክሩ ገብተን ድርሻችን ተረጋግጦ እንዲወሰንልን በማለት ያመለከቱ ሲሆን አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች የመቃወም አመልካችዎች የውርስ ንብረት ድርሻ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚልና ሌሎች መከራከሪያዎችን አቅርበዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 14 ቀን 2005 ዓ.ም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ የሰጠበት በመሆኑ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻው መቅረብ ያለበት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው በማለት የአመልካችንና የሌሎቹን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ይህንን ብይን በመቃወም ያቀረበችውን የይግባኝ ቅሬታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገብ ቁ. 40822 ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም አይቶ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

7. አመልካች የሚች አቶ ስመኝ ባይህን የውርስ ንብረት በተመለከተ የሚች ተተኪ ወራሽ የሆንኩት አመልካች በክርክሩ ተሳታፊ ሳልሆን፣ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ከሳሽ ሶስተኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረው የውርሱን ንብረት እንዲካፈሉ ውሳኔ የሰጠበት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ወለድን በተመለከተ ብቻ ከማሻሻል ውጭ የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ ስለዚህ የፍርድ መቃወሚያው መታየት የሚገባው የውርስ ንብረቱን በተመለከተ አከራክሮ ውሳኔ ለሰጠው ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆን ሲገባው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን ስህተት አለበት በማለት ያመለከቱች ሲሆን ተጠሪዎች ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ድረስ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን ገልጸው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ የፍርድ መቃወሚያ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

8. ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው፣ አመልካች መብቱና ጥቅሜ በክርክሩ ተካፋይ ሳልሆን ውሳኔ ተሰጥቶበታል የምትለውን የሚች ስመኝ ባይህን የውርስ ንብረት በተመለከተ የአንደኛና የሁለተኛ ተጠሪን ክስና ማስረጃ የሶስተኛ ተጠሪን የመከላከያ መልስና ማስረጃ ሰምቶና የሚች ውርስ ብር 1,867,728 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር/ እንደሆነ በመግለጽ፣ ይንን ገንዘብ ከነ ወለዱ ሶስተኛ ተጠሪ ለአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ድርሻቸውን እንዲያካፍል በማለት ውሳኔ የሰጠው የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 13904 መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ የወለድ ክፍያን በተመለከተ ካልሆነ በስተቀር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 24731 ሚያዚያ 14 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔም ሆነ ይህ የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁ. 96715 እና በሰበር መዝገብ ቁ. 98329 በሰጠው ውሳኔ አልተለወጠም፡፡

9. ይህም የሚያሳየው አመልካች አጠቃላይ ግምቱ ብር 2,801,592 /ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ አንድ ሺ አምስት መቶ ዘጠና ስምንት ብር/ በሆነው የሚች ስመኝ ባይህ የውርስ ንብረት ላይ ድርሻ እያለኝ የክርክሩ ተሳታፊ ሳልሆን መብትና ጥቅሜን የሚጎዳ ውሳኔ ተሰጥቶብኛል በማለት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ላይ መሰረታዊ የሆነ ውሳኔ የሰጠበት የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህንን ፍርድ በመቃወም አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት የምታቀርበውን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ተቀብሎና የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360(2) መሰረት የማፅናት፣ የማሻሻል፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመሰረዝ ወይም የመሻር ስልጣን ያለው አመልካች በውሳኔው መብትና ጥቅሜ ተነክቷል የምትለው የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የፍርድ መቃወሚያዋን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ታቅርብ በማለት የሰጠው ውሳኔ በጉዳዩ በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ይዘትና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን ይዘትና ተግባራዊ አፈጻጸም ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በትእዛዝ ማፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 13904 ግንቦት 13 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 40822 ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ተቀብሎና የግራቀኙን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡
3. የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበችውን የፍርድ መቃወሚያና ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 115963

ሐምሌ 8 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አለማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ኤሊያስ ታምራት - ጠበቃ መኮንን ኪዳነ ጋር - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ አስቴር መከተ - ቀረቡ

2. የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች አጥር አስደግፎ የገነባውን ግንባታ እንዲያፈርስና የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ በማለት የሰጡት ውሣኔ በህግ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርባ ከአንደኛ ተከሳሽ /አመልካች/ ጋር ወሰንተኞች ነን፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ባለሁለት ፎቅ ህንፃ ለመገንባት ከክፍሉ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ሲወስዱ እኔም ስምምነቴን ተጠይቄ ከድንበሩ 0.70 ሣንቲ ሜትር በመራቅ ህንፃውን እንዲገነባ ተስማምቸ ፊርሜያለሁ፡፡ ሆኖም አንደኛ ተከሳሽ የከሳሽን የአጥር ግንብ ግድግዳ በማድረግ የቤቱን ፍሳሽ ወደ ከሳሽ እንዲፈስ በማድረግ ግንባታ በመገንባት ጉዳት እያደረሰብኝ ይገኛል፡፡ ስለዚህ አንደኛ ተከሳሽ በከሳሽ አጥር ግንብ ላይ የገነባውን ግንባታ እንዲያፈርስና የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ውሣኔ ይስጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡
2. አመልካች በበኩሉ በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ በመሆን ቀርቦ ህንፃውን የገነባሁት በራሴ ይዞታና በተሰጠኝ የግንባታ ፈቃድ መሠረት ነው፡፡ ከከሳሽ አጥር ላይ የሰራሁት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንባታ የለም፡፡ የከሳሽን ይዞታ አልገፋሁም በከሳሽ ላይ የፈጠርኩት ሁከት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችና አንደኛ ተጠሪ ክርክራችንን ይደግፉልናል በማለት በተለያየ ጊዜ በቀድሞው አሰራር ቀበሌ 01/09 አስተዳደር የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የሚመለከተው ክፍል የፃፋቸውን የተለያየ ይዘት ያላቸውን ደብዳቤዎች በማስረጃነት የያዙ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሮታል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ውጭ ህንፃ በመሥራት በከሳሽ ይዞታ ላይ ሁከት የፈጠረ መሆኑ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ሰጥቶ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የይዞታና አስተዳደር የሽግግር ጊዜ ፕሮግራም ጽ/ቤት ሀምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የባለሙያዎች ቡድን ከቦታው ድረስ በመላክ ባደረገው ማጣራት አንደኛ ተከሳሽ /አመልካች/ በከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ ይዞታ ውስጥ አልገቡም፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ከመንግስት ይዞታ 26 ካሬ ሜትር የገቡ መሆኑ ተረጋግጧል የሚል መግለጫ ለሥር ፍርድ ቤት በመላኩ አንደኛ ተከሳሽ በከሳሽ ይዞታ ላይ የፈጠረው ሁከት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡
4. በዚህ ውሣኔ አንደኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት አጣርቶ ውጤቱን እንዲልክ ትዕዛዝ ሰጥቶ ጥር 20 ቀን 2006 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የክፍለ ከተማው ግንባታና ፈቃድ ቁጥጥር ጽ/ቤት ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው መልስ አመልካች ከዋናው ቤት በስተጀርባ የገነባው ሰርቪስ ኳርተር በስተቀኝ ያለው ግድግዳ ገፅ በይግባኝ ባይና በመልስ ሰጭ መካከል ባለው አጥር ላይ የተገነባ መሆኑን አይተናል የሚል የፅሑፍ መግለጫ ልኳል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ማስረጃ መሠረት በማድረግ አመልካች በአጥሩ ላይ የገነባውን ኳርተር ሰርቪስ ግንባታ ይፍረስ በአንደኛ ተጠሪ ይዞታ ላይ የፈጠረው ሁከት ይወገድ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኃላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በድምፅ ብልጫ አጽንቶታል፡፡
5. አመልካችና ተጠሪ የተስማሙበት ሰነድ ዋናው ህንፃ የሚገነባበትንና ከዋናው መንገድ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን አጥር እንጂ ሰርቪስ ክፍሉ ተደግፎ የተሰራበትን አጥር የሚመለከት አይደለም፡፡ ሰርቪስ ክፍሉ ተደግፎ የተሰራበትን አጥር ያጠርኩት አመልካች 1984 ዓ.ም ሲሆን የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር አስቀምጨበት እኖር ነበር፡፡ የውሃ ታንከሩን በማውረድ ግንባታ አካሄጀበታለሁ፡፡ ይህንን በተመለከተ አንደኛ ተጠሪ ያቀረበችው ክስ ሳይኖርና የአጥሩን ባለቤት በተመለከተ በጭብጥነት ተይዞ የግራ ቀኙችን ማስረጃ ተሰምቶ ውሣኔ አልተሰጠም ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ክስ ካቀረበበት ጭብጥ ውጭ በመውጣት የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329 (1) በሚቃረን ሁኔታ የሰጠው ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልክቷል፡፡

6. አንደኛ ተጠሪ ጥር 23 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በአጥሬ ላይ ግንባታ የገነባ መሆኑን በመግለፅ ክስ አቅርቤያለሁ፡፡ አመልካች ይህንን ክስ በግልፅ ክዶ ካለመከራከሩም በላይ የክፍለ ከተማው የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የባለሙያ ቡድን በመመደብ አመልካች አንደኛ ተጠሪ አጥር ላይ ግንባታ የፈጸመ መሆኑን ማረጋገጫ አቅርበዋል፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሰበትም፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያላነሳውን የአጥር ባለሀብትነት ክርክር አቅርቧል፡፡ ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ በሥር ፍርድ ቤትና ጉዳዩ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት የታየው ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች ከተሰጣቸው የግንባታ ፈቃድ ውጭ የገነባ በመሆኑ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው በማለት ጥር 23 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መጋቢት 12 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

7. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የክፍለ ከተማው ባለሙያዎች በተለያየ ጊዜ እቦታው ድረስ በመሄድ አንድ ጊዜ አመልካች ግንባታውን የገነባው ተሻሽሎ በተሰጠው የግንባታ ፈቃድ መሠረት ነው የሚል መግለጫ የሰጡ መሆኑንና በሌላ ጊዜ ደግሞ አመልካች ከግንባታ ፈቃድ ውጭ ህንፃውን በመሥራት ከአንደኛ ተጠሪን መብት እንደተጋፋ የሚገልጽ መግለጫ ያቀረቡ መሆኑን አመልካችና አንደኛ ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቧቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ይዘትና ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የይዞታ አስተዳደርና የሽግግር ፕሮግራም ጽ/ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በባለሙያ አጣርቶ እንዲልክለት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የባለሙያ ቡድን መድቤ አድርጌዋለሁ ባለው ማጣራት አመልካች የተጠሪን ይዞታ ያልተጋፋ መሆኑን በመግለጽ ሀምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የፅሁፍ መግለጫ ሰጥቷል፡፡ በአንፃሩ ጉዳዩ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥር 20 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የባለሙያ ቡድን መድቤ ጉዳዩን አጣርቻለሁ በማለት ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም የፅሑፍ መግለጫ የሰጠው የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት አመልካች የሰርቪስ ኳርተር የአንደኛ ተጠሪን አጥር አስደግፎ ገንብቷል የሚል መግለጫ ያቀረበ መሆኑን ተረድተናል፡፡

8. ከዚህ አንፃር ሲታይ የክፍለ ከተማው የተለያዩ አካላት የአንደኛ ተጠሪና የአመልካችን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ባለሙያ መድበው ባደረጉት ማጣራት የደረሱበት መደምደሚያና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጧቸው ደብዳቤዎች ዕርስበርሳቸው የሚቃረን ይዘት ያላቸው መሆናቸውን ከበታች ፍርድ ቤቶች ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የክፍለ ከተማው የአስተዳደር አካላት ለፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት ለሰጠው ትዕዛዝ የባለሙያ ቡድን መድበውና አጣርተው ሀምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው መግለጫና በተመሣሣይ ጭብጥ ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መነሻ ከቦታው ድረስ ሄደው አጣርተዋል የተባሉ ባለሙያዎች ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ያቀረቡት መግለጫ ዕርስ በርሱ የሚቃረን ይዘት ያለው መሆኑ ሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሣኔ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

9. የክፍለ ከተማው የተለያዩ አካላት በተለያዩ ጊዜ የመደቧቸው ባለሙያዎች የተለያየ ውጤት ያለው ሙያዊ መግለጫ የሚያቀርቡት በመጀመሪያ ደረጃ የሥር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በጭብጥነት ሊያዙና ሊጣሩ የሚገቡ የፍሬ ጉዳይና የህግ ጭብጦች ሣይመሰርቱና የባለሙያዎች ቡድን አጣርቶ መግለጫ ሊያቀርብባቸው የሚገቡትን አከራካሪ ፍሬ ነገሮች ማለትም፡-

   (ሀ) አመልካች ከአንደኛ ተጠሪ ይዞታ 70 ሣንቲ ሜትር ርቆ ለመገንባት የተስማማው ባለሁለት ፎቅ ህንፃውን ብቻ ነው ወይስ ሰርቪስ ቤቱን ከአጥሩ 70 ሣንቲ ሜትር ርቆ ለመገንባት ተስማምቷል? ወይስ አልተስማማም?

   (ለ) ለአመልካች የተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ህጋዊ ሥልጣን ባለው አካል ተጠንቶ ተሻሽሏል ወይስ አልተሻሻለም?

   (ሐ) አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ከተገነባው አጥር ላይ አስደግፎ ሰርቪስ ቤት የማይሠራ መሆኑን ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ተስማምቷል ቢባል አመልካች ሰርቪስ ኳርተር አሰጠግቶ የገነባበትን የአጥር ክፍል የገነባችው አንደኛ ተጠሪ ናት ወይስ አመልካች?

   (መ) አመልካች ሰርቪስ ኳርተሩ የተገነባበትን የአጥር ክፍል አመልካች የገነባው መሆኑ ሲረጋገጥ አንደኛ ተጠሪ አመልካች አጥሩን አስደግፎ የገነባውን ሰርቪስ ኳርተር እንዲያፈርስ ለመጠየቅ የሚያስችላት የህግ መሠረት አለ ወይስ የለም?

   (ሠ) አመልካች ሰርቪስ ኳርተሩን የገነባበትን የአጥር ክፍል የሠራችው አንደኛ ተጠሪ መሆኗ ቢረጋገጥ አመልካች አጥሩን አስደግፎ የሠራውን ሰርቪስ ኳርተር እንዲያፈርስ አንደኛ ተጠሪ ለመጠየቅ የሚያስችላት የህግ መሠረት አለ ወይስ የለም?

   (ረ) አመልካች ባከናወነው ግንባታ የአንደኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ህገ ወጥ ተግባር በመፈፀም በአንደኛ ተጠሪ ላይ ጉዳት በማድረስ የሁከት ድርጊት ፈፅሟል ወይስ አልፈፀመም?

   (ሰ) በአጠቃላይ አመልካች ህጋዊ ሥልጣን ባለው አካል ከተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ውጭ ፈፅሟል ወይስ አልፈፀመም? አመልካች ከግንባታ ፈቃድ ውጭ ገንብቷል ቢባል በዚህ ግንባታ አንደኛ ተጠሪ መብትና ጥቅሟ ተነክቷል፡፡ ከግንባታ ፈቃድ ውጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተሠራው ግንባታ የአንደኛ ተጠሪ መብትና ጥቅም አልተነካም ቢባል ውጤቱ ምን ይሆናል? ከግንባታ ፈቃድ ውጭ በተሠራው ግንባታ የአንደኛ ተጠሪ መብትና ጥቅም ተነክቷል ቢባል ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚሉትን ጭብጦች በግልፅ በመያዝ ባለሙያዎች ቦታው ሄደው በማጣራት በተለያየ ጊዜ ለአመልካችና ለአንደኛ ተጠሪ በተለያዩ የክፍለ ከተማው የተለያዩ አካላት የተሰጣቸውን ሰነድ ማስረጃዎች ይዘት፡- አግባብነት ካለው የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በማድረግ አጣርተው እንዲያቀርቡ ግልፅ ትዕዛዝ ባለመስጠታቸው ልዩነት የተፈጠረ መሆኑን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለክፍለ ከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ ፕሮግራም ጽ/ቤት ሀምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም በባለሙያ አጣርቶ የሰጠውን መግለጫና ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክፍለ ከተማው የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ጽ/ቤት ባለሙያ ቡድን አጣርቶ ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም በጽሁፍ የሰጠውን መግለጫ ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

10. ይህም የሥር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በባለሙያ ተጣርተው ሊቀርቡ የሚገባቸው አከራካሪ የፍሬ ጉዳይ ጭብጦች በግልጽ ሣይመሰርቱና መጣራት የሚገባቸውን ፍሬ ጉዳዮች በውል ሣይለዩና በግልጽ ሣይዘረዝሩ ባለሙያዎች አጣርተው ያቅርቡ የሚል ጥልቅ ትዕዛዝ በመስጠታቸው ተቃራኒ ይዘት ያላቸው ማስረጃዎች (Contradictory Evidence) ከክፍለ ከተማው የተለያዩ አካላት በተለያየ ጊዜ ቦታው ድረስ ሄደው አይተው የሰጡ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 246፣ አንቀጽ 247 እና አንቀጽ 248 መሠረት አከራካሪ ጉዳዮችንና ጭብጦችን በአግባቡ ሣይመሰርቱና ሣያጣሩ ውሣኔ በመስጠት መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀሙ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

11. ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የክፍለ ከተማው ባለሙያዎች በተለያየ ጊዜ ከቦታው ድረስ በመሄድና የሥር ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለሰጡት ትዕዛዝ ተቃራኒ ይዘት ያለው አስተያየት ካቀረቡ ተቃራኒ ይዘት ካላቸው አስተያየቶች አንደኛውን ተቀብሎ ሌላውን ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ግልፅ መሰፈርትና ምክንያት ሊኖር ይገባል፡፡ በተመሣሣይ የሙያ ብቃትና ልምድ ትይዩ የሆነ ሥልጣን ያላቸው የክፍለ ከተማው የተለያዩ አካላትና ባለሙያዎች አንድ መሠረታዊ ፍሬ ጉዳይ ላይ ያቀረቡት መግለጫ ዕርስ በርሱ የሚቃረን ሆኖ ዕውነታውን ለመለየት የማያስችል በሚሆንበት ጊዜ ተቃራኒ መግለጫውን ያየው ፍርድ ቤት ጉዳዩ በክፍለ ከተማው ካለ ባለሙያዎች የተሻለ ዕውቀትና የሥራ ልምድ ባላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚመለከተው ቢሮ ባለሙያዎች ተጣርቶ እንዲቀርብና ዕውነታው እንዲረጋገጥ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 250 እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136 (1) መሠረት ትዕዛዝ ሣይሰጥ አንደኛውን መግለጫ ተቀብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌላውን ዕውነት ነው ብሎ ውሣኔ ለመስጠት የሚቻልበት የህግ መሠረት የለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ፍርድ ተራ ቁጥር 8 የተገለፁት ጭብጦች በግልጽ ሣይዙና እንዲጣሩ ሣያደርጉና የክፍለ ከተማው ባለሙያዎች ከሰጡት ዕርስበርሱ የሚቃረን ሙያዊ ምስክርነትና መግለጫ ዕውነታው የትኛው እንደሆነ የተሻለ ሙያ ዕውቀትና ልምድ ባላቸው የአዲስ አበባ አስተዳደር ባለሙያዎች ተጣርቶ እንዲቀርብላቸው ሣያደርጉ የሰጡት ውሣኔ ከላይ የገለፅናቸውን የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 246፣ አንቀጽ 247፣ አንቀጽ 248 አንቀጽ 250 እና አንቀጽ 136 (1) ድንጋጌዎች ያልተከተለ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57471 ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142629 ጥቅምት 20 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 108027 ሚያዝያ 22 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 9 የተገለፁትን ጭብጦች በመያዝና እነዚህ አከራካሪ የፍሬ ነገር ጭብጦች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚመለከተው አካል የካበተ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች መድቦ አጣርቶ ውጤቱን እንዲያሳውቀው በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136 (1) መሠረት በማድረግና ዕውነታውን ለማረጋገጥ ይጠቅማሉ ያላቸውን ሰነዶች በማስቀረብና የምስክሮችን ቃል በመስማት ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343 (1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ.101277

መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓለ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ክፍለጽዬን ማሞ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ ተወካይ አልቀረበም

ተጠሪ፡- ሚ/ር አቤቻንድ ፖፖትላል ሜታ ወራሽ ጠበቃ አቶ ታደሰ መንገሻ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በፕራይቬታዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ያቀረቡት አቤቱታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቀድሞ ወረዳ 2 ቀበሌ 11 በአሁኑ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 271 የሆነ የቡና ማጠቢያና ማከማቻ መጋዘን ከነቢሮዎቹ ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰደብን ይመለስልን የሚል ነው፡፡ ኤጀንሲውም ጉዳዩን አጣርቶ በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀጽ2(3) ድንጋጌ መሰረት ከአዋጅ ውጭ በቀላጤ የተወሰደ ንብረት በሚለው ትርጓሜ ስለሚሸፈን አቤቱታ የቀረበበት መጋዘን ከነቢሮዎቹ በመርህ ደረጃ እንዲመለስላቸው ሲወስን ንብረቱን ግን ተጠሪ የሚረከበው በተጨማሪነት ለተሰሩት ክፍሎች የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ በሚያቀርበው ወጪ መሰረት ክፍያውን ሲፈጽም ነው በማለት መጋቢት 20 ቀን 2004 ዓ/ም ወስኗል፡፡ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተርም መጋቢት 28 ቀን 2004 ዓ/ም የውሳኔውን ትክክለኛነት አረጋግጦ ለመንግሥት ቤቶች አጀንሲ ጽፏል፡፡ የመንግሥት ቤቶች አጀንሲ ይግባኝ ለፕራይቤታይዜሽን ቦርድ አቅርቦ ቦርዱም የአጀንሲውን ውሳኔ የሚያስለውጥ ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም በማለት ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ/ም አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤት ቁጥር 271 የቡና ማጠቢያና ማከማቻ መጋዘን ከነቢሮዎቹ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሰው ከጥቅምት 1 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1972 ዓ/ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት /ጅንአድ/በማከራየት አመልካች እያስተዳደረ የሚገኘውን ለተጠሪ ይመለስ በማለት የተወሰነው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ከተመረመረ በኋላ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲም ሆነ ቦርዱ አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ እንዲመልስ የወሰኑት አመልካች በከርክሩ ተጠርቶ በአግባቡ ተከራክሮ መሆን ያለመሆኑን እና በቤቶች ኤጀንሲ ስር ሆኖ የቆዬው የድርጅት ቤትና መጋዘን ለተጠሪ ይመለስ ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 193/92 አንቀጽ 7 አንጻር ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ታህሳስ 24 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ ተቃውሞና መልስ ያቀረበ ሲሆን ተቃውሞውም የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ በመሆኑ ክርክሩ ሊቀጥል አይገባም የሚል ነው፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለውን የውሳኔ ይዘት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ከመመርመሩ በፊት የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፏል ወይስ አላለፈም? የሚለውን በቅድሚያ ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፕራይቤታይዜሽን ቦርድ ውሳኔ የሰጠው ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ/ም ነው፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በ8/9/2006 ዓ.ም ነው፡፡ ይህም የይግባኝ ውሳኔ ከተሰጠ ከአንድ ዓመት ከአስራ አንድ ወር ከሰባት ቀን በኋላ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡ አመልካች ግን የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንስ ለፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ውክልና ታግዶ እንዲቆይ ካደረገ በኋላ የካቲት 25 ቀን 2006 ዓ/ም እግዱን ያነሳ በመሆኑ የይግባኝ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው ከዚህ ቀን ጀምሮ ነው በማለት ተከራክሯል፡ ይህ ችሎት የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አፈጻጸሙን አግዷል የተባለውን ለማጣራት ማጎደሩን በትዕዛዝ አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ ኤጀንሲው ነሐሴ 11 ቀን 2004 ዓ/ም ለአራዳ ክፍለ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጻፈው ደብዳቤ በኤጀንሲው ውሳኔ የተጠቀሰውን ቁጥር 271 የሆነውን መጋዘንና ቢሮዎች በአፈጻጸሙ መሰረት እንዲረከቡ በማድረግ ጅንአድ ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነባቸውን ቁጥር 006፣008/1 እና 008/2 የሆኑትን መጋዘኖች በሚመለከት በተለዋጭ ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ እስከምናሳውቅ ድረስ አፈጻጸሙ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ የሚል ነው፡፡በዚህ ደብዳቤ መሰረት መጀመሪያ ውሳኔ ያረፈበት ቤት አፈጻጸም አልታገደም፡፡ ይልቁንም ደብዳቤው ውሳኔ የተሰጠውን ቤት የፍርድ ባለመብት እንዲረከብ ፍርድ ቤቱ እንዲያደርግ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የአመልካች የይግባኝ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው ከ8/9/2006 ዓ/ም ጀምሮ ነው የሚለው ክርክር ከዚህ አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 22(4) እንደተደነገገው ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርበው አቤቱታ ውሳኔ በተሰጠ 90 ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የሰበር አቤቱታውን ለማቅረብ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካጋጠመ የሰበር አቤቱታው ከመቅረቡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፊት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 324 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻ ቀርቦ ሊወሰን ይገባል፡፡ ይህ ባልተደረገበት ሁኔታ አመልካች ጊዜ ያለፈበትን የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ጭብጥ ተይዞ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የመልስ ልውውጥ ያደረጉ ቢሆንም የሰበር አቤቱታው የስነ ሥርዓት ግድፈት የተፈጸመበት በመሆኑ የክርክሩን ይዘት መመርመር ሳያስፈልግ የሰበር አቤቱታውን ሰርዘናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. አመልካች በህግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሰበር አቤቱታውን ያላቀረበ በመሆኑ የሰበር አቤቱታውን ውድቅ አድርገነዋል፡፡
2. የሰበር አቤቱታው መሰረዙን እንዲያውቅ የፍርዱ ግልባጭ ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ይላክ፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ በተመለከተ የግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ጥር 28 ቀን 2007 የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡ የአከራካሪው ንብረት ማህደር በመጣበት አኳኋን ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 121387

መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች - አልማው ወሌ
ተፈሪ ገብሩ
አብርሃ መሰለ
አብዬ ካሳሁን
እትመት አሰፋ

አመልካች - አፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ነ/ፈ ዘላለም ብሩክ ቀረቡ

ተጠሪዎች - 1ኛ. አቶ ያሬድ ተሾመ
2ኛ. አቶ አድማሱ መርሻ } አልቀረቡም
3ኛ. አቶ ገረመው አሰፋ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የተጀመረው የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአጭር ሁኔታ የሚወሰኑ ክርክሮች በሚታዩበት ስርዓት ታይቶ እንዲወሰን ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡

የተጠሪዎች ክስ ይዘት ባጭሩ ተከሳሹ ከ1ኛ ተጠሪ ላይ የውሃ ቦቴ ተሸከርካሪ ፤ ከ2ኛ ተጠሪ ሎደር ተሸከርካሪ እና ከ3ኛ ተጠሪ ግሪደር እና ሎደር ተሸከርካሪ በመከራየት የኪራይ ዋጋ እንደ ቅደም ተከተላቸው ብር 34,757.21 (ሰላሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ሰባት ከ21/100) ፤ ብር 21,555.00 (ሃያ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ አምስት) እና ብር 302,201.42 (ሶስት መቶ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አንድ ከ42/100) ስላልከፈላቸው ይህን ገንዘብ ከነወለዱ ወጪና ኪሳራ ጨምሮ እንዲከፍል እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ቀርቦ ክሱን ለመከላከል እንዲፈቀድለት በ09/02/2008 ዓ.ም በተፃፈ ጠይቆ ተፈቅዶለት መልስ አቅርቧል፡፡ ነገር ግን አመልካች በ22/03/2008 ዓ.ም በተፃፈ ባቀረበው መልስ የተከሰሰበት ገንዘብ ያለበት መሆኑን አምኖ መልስ ሰጥቷል ተብሎ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተከሰሰበትን ገንዘብ ከነወለዱ፤ ወጪና ኪሳራ ጨምሮ ለተጠሪዎች እንዲከፍል ተወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስ ባላስረዱበት አግባብ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ፤ እንዲሁም የአመልካች ጠበቃ ከቅን ልቦና ውጭ ክሱን ማመኑን ተከትሎ በተጨማሪ ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊረጋገጥ ሲገባው በማመን ብቻ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻርልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ታዞ በሰጡት መልስ በኪራይ ውሉ መሰረት በሚመለከታቸው የድርጅቱ ኃላፊዎች ድርጅቱ ባዘጋጀው የክፍያ ማዘዣ ፎርም ላይ ተፈርሞ በተሰጣቸው የገንዘብ አለብኝ መተማመኛ ሰነድ ተደግፎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 284(ሀ) መሰረት የቀረበ ክስ በመሆኑ፤ እንዲሁም ጠበቃው የሰጠውን መልስ ከመድገም ውጭ የአሁኑ የአመልካች ጠበቃ ለቀረበው ክስ መከላከያ መልሱ በእንዲህ አይነት መልኩ መሰጠት ይገባው ነበር ባላሉበት ሁኔታ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሚዛን የሚደፋ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም ተብሎ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጠው የመልስ መልስ በተጠሪዎች የክፍያ ማዘዣ ላይ የገንዘብ መጠኑን በመጥቀስ ሰነድ የሰጣቸው መሆኑን እና ይህንኑም ሰነድ ለክሱ በማስረጃነት አያይዘው ማቅረባቸውን በመግለፅ ሆኖም ግን የስር ፍርድ ቤት ክሱን ከማስረጃው አንፃር ትክክለኛነቱን እና ተገቢነቱን ሳይመረምር የአመልካች ጠበቃ አላግባብ በማመኑ ብቻ ተቀብሎ ውሳኔ ማስተላለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው የሚለውን ክርክር በማጠናከር አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ እና ግራ ቀኙ በሰበር ያደረጉትን ክርክር ሲሆን በበኩላችን ክርክሩን ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ለተጠቀመባቸው የተጠሪዎች ማሽነሪዎች የሚጠበቅበትን ክፍያ አልከፈለም በሚል የገንዘቡን መጠን በመጥቀስ እንዲከፈላቸው ተጠሪዎች ክስ አቅርበዋል፡፡ ክሱም ውልን እና የገንዘብ አለብኝ ሰነድን መሰረት በማድረግ በአጭር ሁኔታ እንዲወሰን የቀረበ ነው፡፡ የአመልካች (ሥር ተከሳሽ) ጠበቃ በተወካይነቱ ቀርቦ ለመከላከል ፈቃድ ጠይቆ ቢፈቀድለትም በሰጠው መልስ '.... ከሳሾች በክሳቸው ላይ ከተከሳሽ ጋር የስራ ውል በመዋዋል ስራ መስራታቸው የሚካድ አለመሆኑን፤ ከሳሾች ክፍያው እንዲከፈላቸው ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄ አዲስ አበባ የሚገኘው የበላይ አካል መልስ እስኪሰጥ ድረስ እንዲጠብቁ ተነግሯቸው ትዕግስት በማጣት ክስ አቀረቡ እንጂ ተከሳሽ ክፍያውን ለመፈፀም ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ አይደለም፤ ስለዚህ ተከሳሽ ድርጅት አሁንም ለከሳሾቹ ክፍያ ለመክፈል አዲስ አበባ ከሚገኘው ዋና መስሪያ ቤት ምላሽ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፤ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ይገንዘብልን .....' በማለት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት እንደተጠሪዎች ጥያቄ ገንዘቡ እንዲከፈል የወሰነው ተከሳሽ የሰጠው መልስ ገንዘቡ የሌለበት መሆኑን አልካደም፤ እንዲያውም አምኖ መከራከሩን ያሳያል በሚል ነው፡፡

የአመልካች መሰረታዊ ቅሬታ ክርክሩ የተመራበትን እና ውሳኔ የተሰጠበትን አግባብ በተመለከተ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ክርክሩን የመራበት እና ውሳኔ ላይ የደረሰበት አካሄድ የህግ ስህተት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ የፍትሃብሄር ሥነ ሥርዓት ህጉ በቁ 235 እና 83 ስር የሚደነግገው በግልፅ ያልተካደ ፍሬ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል በሚል ሲሆን ይህ ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌ እንደተያዘው ጉዳይ በልዩ ስርዓት የሚመሩና ማስፈቀጃ ተጠይቆበት በፈቃድ ለቀረበ መልስም ተፈፃሚ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ተከሳሽ ካመነ በአመነው መሰረት ውሳኔ ለመስጠት የሚከለክል በቂ የህግ ምክንያት እስከሌለ ድረስ ውሳኔ መስጠት የሚገባ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የጠየቁት ልኩ የታወቀ ገንዘብ መሆኑንና ክሱም የተመሰረተው በውል እንዲሁም በገንዘብ አለብኝ ደረሰኝ ምክንያት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ጉዳዩ በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት እንዲቀርብ መፍቀዱ፤ አመልካች ቀርቦ ለመከላከል ያቀረበውን ማመልከቻ መቀበሉ እና በቀረበው መልስ መሰረት ውሳኔ መስጠቱን ከተደረገው ክርክር መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ከሥነ ሥርዓት ህጉ የሙግት አመራር መርህ አኳያ ጉድለት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ እና ትዕዛዝ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የአመልካችን ቅሬታ ባለመቀበል ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 21704 በ24/03/08 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 233716 በ13/04/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ፤ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በፋ/ቁጥር 232726 በ15/04/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ በመ/ቁ 22293 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ከዚህ ፍርድ ቤት ታህሳስ 22/2008 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

ሩ/ለ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 122249

መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-. አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ በላይ አየለ - ከጠበቃ ዮሴፍ አስምሮ ጋር - ቀረቡ

ተጠሪ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት አዲስ ዙ ፓርክ ማዕከል - ኃ.ፊ.ጅ አብይ አስናቀ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሁከት እንዲወገድ እና በሁከት ምክንያት የተቋረጠ ጥቅም ይከፈለኝ በማለት የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ክስ ይዘት በአንበሳ ግቢ ውስጥ የሚገኘውን ቦታ ገንዘብ እና ንብረት በማፍሰስ የተለያየ የልጆች መጫወቻ የተከሉበት መሆኑን፤ ስራውን ሲሰሩ የነበረው ብር 3300 /ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ብር/ በመክፈል መሆኑን፤ ተከሳሹ በጨረታ አከራያለሁ በማለት ጨረታውን ያሸነፉ ግለሰቦች ባሸነፉበት ዋጋ መቀጠል ስላልቻሉ አመልካች በሰጡት የጨረታ ዋጋ በብር 10921 /አሥር ሺህ ዘጠኝ መቶ ሐያ አንድ ብር/ እየከፈሉ እንዲቀጥሉ እና የውል ቆይታ ጊዜውም በ6 ኪሎ የሚገኘው ጽ/ቤት አዲስ እያስራ ወዳለው የፒኮክ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እስከሚዛወር ድረስ መሆኑን በመግለጽ ተከሳሹ የጻፈላቸው መሆኑን፤ ሆኖም ተከሳሹ የውለታው ጊዜ ሳያልቅ ግቢ ለቀህ ውጣ በማለት የጻፈላቸው መሆኑን፤ በመግለጽ ተከሳሽ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ እና በሁከቱ ምክንያት የተቋረጠባቸው ጥቅም እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ አስቀድሞ ለአመልካች የተጻፈው ደብዳቤ በሚመለከተው አካል የተጻፈ አይደለም፡፡ ተጻፈ የተባለው ደብዳቤም በሌላ ደብዳቤ ተሸሯል፡፡ አመልካች ቀርበው ውል እንዲያድሱ ጥሪ ቢደረግላቸውም ቀርበው ውል አላደሱም፡፡ እንደውል ያቀረቡት ደብዳቤም የውል ሰነድ ተደርጎ ሊቆጠር አይችልም፡፡ ንብረቱን በተሻለ ገንዘብ ለማከራየት ለአመልካች ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉ እንዲቋረጥ መደረጉ የሁከት ተግባር አይደለም፡፡ የተቋረጠ ጥቅም በማለት የቀረበው ጥያቄም በማስረጃ የተደገፈ ስላልሆነ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም ለአመልካች የጻፈው ደብዳቤ እንደውል ማሻሻያ የሚታይ እንጂ ተራ ደብዳቤ አይደለም፡፡ ደብዳቤው የኪራይ ማሻሻያን የሚመለከት እና የውል ቆይታ ጊዜውም በስድስት ኪሎ የሚገኘው የአዲስ ዙ ፕሮጀክት በመሠራት ላይ ወዳለው ፒኮክ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እስኪዛወር የሚገልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የውል ጊዜው ሳይጠናቀቅ አመልካች እንዲለቅ መደረጉ የሁከት ተግባር ነው በማለት ተጠሪ ሁከቱን አስወግዶ አመልካች ሥራውን እስኪጀምር ድረስ ከጥቅምት ወር 2007 ዓ.ም ጀምሮ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ አንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤትም ለአመልካች መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ በአንድ ወገን የቀረበ ጥያቄ እንጂ አስቀድሞ የነበረውን ውል ያራዘመ አይደለም፡፡ ተጠሪው ጥር 9 2006 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤም አስቀድሞ የጻፈውን ደብዳቤ ሽሮታል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በተሠጠው ስልጣን መሠረት አመልካች ለቀው እንዲወጡ ማድረጉ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሠጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው የነበረ ቢሆንም አቤቱታቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ተሰርዟል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች በአዲስ አበባ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት መጋቢት 9 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈው የውል ማሻሻያ ሰነድ ተቀብዬ በሰነዱ ላይ የተገለጸውን የዋጋ ማሻሻያ ስከፍል ቆይቻለሁ፤ በሰነዱ ላይ የኪራይ ውሉ ቆይታ ጊዜ በስድስት ኪሎ የሚገኘው የአዲስ ዙ ፕሮጀክት ጽ/ቤት አዲስ እያሰራ ወዳለው ፒኮክ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እስኪዛወር ድረስ የሚቆይ መሆኑ ተመልክቷል፤ በድጋሚ ተጽፏል የተባለው ደብዳቤም የጸና ውል እያለኝ ድጋሚ የኪራይ ውል ለማድረግ የሚያስገድደኝ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይህን በማለፍ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ በመሆኑ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በሰበር የተያዘው ጭብጥ ከመወሰኑ በፊት ከመነሻውም ቢሆን የሥር ፍ/ቤቶች ክርክሩን ሁከት ይወገድልኝ በማለት በተጠየቀው ዳኝነት መምራት ነበረባቸው? ወይስ አልነበረባቸውም? የሚለውን ጭብጥ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ርዕስ ሁከት እንዲወገድ እና በሁከቱ ምክንያት የተቋረጠ ጥቅም ለማስከፈል በሚል የቀረበ ቢሆንም ዝርዝር ይዘቱ ሲታይ ከኪራይ ውል አፈፃፀም ጋር የተገናኘ ነው፡፡ በግራ ቀኝ ወገኖች የሚቀርብ የክርክር ይዘት ፍ/ቤቱ ለሚይዘው ጭብጥ መሠረት ነው፡፡ በአግባቡ ያልቀረበን ክስ መነሻ በማድረግ በፍ/ቤቶች የሚሠጥ ፍርድም ፍትሐዊ ሊሆን አይችልም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡትን ክስ በመቀበል የተጠሪ ተግባር ሁከት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ ከመስጠቱ ውጪ የክሱን ዝርዝር ይዘት በማየት ክርክሩ ከኪራይ ውል አፈጻጸም ጋር የተገናኘ መሆኑን ተገንዝቦ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91/1 በሚፈቅደው መሠረት ክሱ እንዲሻሻል አላደረገም፡፡

የፍ/ቤቶች ዋነኛ ሚና ክርክሮች በተገቢው የሕግ ሥርዓት እንዲመሩ ማድረግ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት በክርክሩ ላይ ባለው የመሪነት ሚና ክሱ እንዲሻሻል ማድረግ ሲገባው የቀረበውን ክስ አከራክሮ ውሳኔ መስጠቱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182/2 በሚደነግገው መሰረት ጉዳዩ የሚመራበትን ሂደት ማረም ሲገባው ይህንኑ ሳያርም ተጠሪ የፈጠረው ሁከት የለም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 46548 ጥር 6 ቀን 2007 ዓ.ም የሠጠው ውሳኔ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 166197 ጥቅምት 25 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 120477 ታህሳስ 05 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡት ክስ በሁከት ይወገድልኝ የሚታይ ሳይሆን ከውል አፈጻጸም ጋር የተገናኘ መሆኑን አውቆ አመልካች ክሱን እንዲያሻሽሉ እና ተገቢውን ዳኝነት እንዲከፍሉ በማድረግ ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1 መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ. 46548 የሆነው መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

??/? /?.105677

? ???? 30 ?? 2009 ?.?

???? ??? ? ??

??? ???

???? ? ??

??? ??? ?

?? ????? 1. ?/? ?? ?? ?? ??

2. ?/? ??? ?? ?? ??

3. ?/? ???? ?? ?? ??

4. ?/? ? ?? ?? ?? ??

5. ?/? ???? ?? ?? ??

6. ?? ? ? ? ? ???

?? ?? ?? 1. ?? ? ??? ?? ?? ??

2. ?/? ?? ??? ?? ?? ??

3. ?/? ? ??? ?? ??

? ??? ? ?? ?? ?? ?? ?? ? ??? ?? ? ?? ??

? ?? ??? ? ?? ? ??? ???

? ?? ? ??? ? ??? ???

? ? ?

??? ????? ?? ? ? ? ???? ??? ?? ?? ??? ??? 137372 ? ? ? 11 ?? 2006 ?.? ???? ??? ??? ? ???? ? ? ?? ? ??? ???? ??? ?? ?? ??? ? ????

https://t.me/ethiopianlegalbrief

? ? ? ? ? ?? ? ? ? ??? ?? ?? ?? ? ??? ? ???? 30 ?? 2007 ?.? ?? ?? 03 ?? ???? ???? ?? ? ???? ? ?? ??

???? ?? ?? ?? ? ???? ? ? ? ?? ? ???? ? ? ? ???? ??? ??? ?? ? ? ? ?? ?? ?? ??? ??? ?? ??? ? ?? ? ??? ? ???? ? ???? ? ? ? 1?? 2? ? ? ?? ? ? ??? ???? ??? ? ? 3? ? ? ? ? ? ? ?? ??? ?? ? ? ? ?? ???? ?? ???? ? ?? ? ???? ?? ?? ??? ? 1?? 2? ? ? ?? ? ? ???? 28 ?? 2003 ?.? ?? ?? ?? ??? ? ? ? ?? ? ?? ?? ? ?? ? ???? ? ? ? ??? ??? ? ?? ??? ? ??? ? ?? ?? ? ? ? ?? ??? ??? ??? ? ? ? ?? ?? ?? ? ? ??? ? ? ? ?? ?? ? ??? ?? ? ??? ?? ?? ?? ???? ??? ??? ?? ? ? ??? ? ? ? ?? ?? ?? ?? ? ???? ? ? ? ? ???? ?1? ??? 5? ?? ?? ? ??? ?? 1?? 2? ? ? ?? ? ? ? ?? ? ?6?? ?? ? ?? ? ? ? ??? ?? ?? ? ? ? ??? 6?? ?? ? ??? 1?? 2? ? ? ?? ? ? ????? ?? ? ???? ?? ? ??? ???? ? ? ? ??? ?? ? ??? ? ????? ??? ? ?? ? ??? ?? ? ? ? ? ? ?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

??? ??? ?? ?????? ???? ???? ?? ? ????? ?? ? ?? ? ? ? ??? ?? ? ? ???? ???? ?? ?? ????⁇

? ? ?? ? ??? ? ?? ?? ?? ??? ?? ? ? ? ???? ???? ??? ?? ???? ?????? ??? ?? ????? ?????⁇ ??? ? ?? ?? ????? ? ???? ⁇ ???? ????? ????? ???? ???? ?? ???? ?? ⁇

??? ? ?? ???? ???? ????? ??? ?/??? ???? ? ???? ??? ???? ???? ?? ? ??? ????? ??? ? ?? ? ??? ??? ????? ???? ?????? ?? ? ?? ? ?? ??? ??? ?? ???? ?? ?? ?? ? ????? ? ???? ??? ???? ????? ?? ?? ?? ?? ??? ?????? ?? ???? ???????

??? ?? ?? ? ?? ? ??? ? ??? ? ?? ? ??? ??? ?? ? ??? ??? ?? ??????? ??? ???? ??? ??? ?? ?? ??? ??? ?? ? ? ??? ??? ?? ?? ????? ???? ??? ? ? ? ? ??? ??? ?? ??? ?? ??? ??? ?? ?? ???? ??? ??? ?? ???? ?? ?? ? ? ??? ? ?? ? ??? ?? ??? ?? ? ?? ? ??? ?? ? ? ???? ? ?? ?? ? ???? ? ??????⁇

???? ??? ??⁇ ? ?? ? ? ???⁇ ??? ????? ???? ?????? ?? ???? ⁇ ? ???? ???? ???? ???? ? ?? ???⁇ ???? ?? ?? ? ? ?? ? ??? ?? ??? ⁇ ? ?? ???? ??? ?? ???? ???? ⁇ ??? ? ?? ?? ? ? ?? ? ??? ?? ? ? ? ??? ??? ??? ?? ? ? ? ? ? ? ??? ??? ?? ? ? ? ? ? ?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

? ??? ??? 63360 ?????? ???? ????? ? ??? ? ???? ??? ?? ??? ???? ? ? ? ??? ? ?? ? ?? ??? ?? ?? ???? ? ??? ? ??? ?? ? ??? ??? ? ?? ? ??? ? ?? ? ??? ??? ?? ? ??? ??? ?? ?? ??? ??? 30 ?? 2002 ?.? ??? ?? ? ??? ??? ?? ?? ??? ??? 01984 ??? ? ?? ? ??? ?? ????? ?? ????? ? ???? ??? ?? ??? ???? ?? ?? ???? ??? ??? ? ? ??? 65,000 ? ?? ???? ? ? ???? ? ??? ?? ?? ????? ??? ??? ??? ?? ? ? 24 ?? 2002 ?.? ???? ??? ? ? ???? ???? ??? ? ?? ??? ? ? ?? ??? ? ??? ? ??? ??? ?? ? ?? ?? ?? ??? ???? ??? ?? ???? ? ??? ??? ?? ??? ??? ? ??? ??? ?? ??? ?? ? ? ??? ??? ??? ?? ? ??? ??? ?? ? ??? ??? ?? ? ?? ?? ?? ??? ???? ??? ??? ??? ?? ? ??? ??? ??? ?? ????? ?? ??? ??? 17810 ??? ? 12 ?? 2002 ?.? ???? ??? ? ???? ? ??? ? ?????? ?? ???? ??? ?? ??? ? ???? ???? ????? ???? ??? ? ? ??? ?? ? ??? ?? ???? ??? ? ?? ? ?? ??? ??? ? ?? ?? ??? ?? ? ??? ??? ?? ? ??? ??? ?? ? ??? ??? ?? ? ?? ?? ??? ??? ? ??? ??? ?? ? ??? ??? ? ?? ?? ???? ?? ? ??? ? ?? ? ?? ??? ??? ? ?? ? ??? ??? ? ??? ??? ?? ? ??? ??? ? ??? ??? ?? ? ??? ??? ? ??? ??

https://t.me/ethiopianlegalbrief

??? ??? ?? ? ??? ??? ?? ?? ?? ? ?? ?? ??? ??? ??? ? ? ?? ?? ? ?? ? ?? ?? ? ? ?? ????? ?? ??? ?? ?? ?? ? ?? ?? ? ?? ??? ??? ?? ???? ??? ? ??? ??? ??? ??? ??? ??? ??? ??? ??? ?? ??? ? ??? ? ????? ? ?? ?? ? ??? ?? ?? ? ??? ? ??? ??? 25/88 ???? 5(2) ? ?????? ??? ? ??? ??? ??? ??? ?? ??? ?? ? ?? ??? ? ??? ? ? ??? ???? ? ? ? ?? ? ? ? ?? ? ???? ???? 80 ??? ? ???? ? ??? ?? ?? ? ? ? ?? ? ?? ??? ?? ? ???? ??? ?? ? ??? ? ? ? ? ?? ??? ??? ??? ??? ?? ?? ? ??? ? ? ? ? ?? ??? ? ??? ??? ?? ? ??? ? ??? ??? 85718 ?? ??? ? ?? ??? ??? ?? ? ??? ? ?? ?? ???? ?? ? ? ? ??? ? ??? ??? ? ??? ? ??? ??? 454/1997 ? ? ?? ????? ? ??? ? ?? ? ? ?? ??? ?? ?? ? ? ?? ??? ??? ?? ?? ? ?? ??? 01984 ?? ? ? ? ? ? ??? ??? ??? ? ? ? ?? ?? ? ? ?? ? ? ? ? ?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

? ? ?

1. ?? ? ? ? ?? ?? ?? ??? ? ?? ?? ?? ?? ? ? ? 176201 ? ? ? ? 02 ?? 2005 ?.? ?? ?? ? ? ? ??? ? ? ?? ??? ? ? ?? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ?? ?? ? ?? ? ? ? 137372 ? ? ? 11 ?? 2006 ?.? ?? ?? ? ? ? ??? ? ? ??? ?? /? /? /?/? 348(1) ? ??? ? ?? ? ??

2. ???? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 108647

ሕዳር 15 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሀ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ወርቂቱ ገመዳ -አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ደመቀች ብርሃኑ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ውርስ እንዲጣራ በማለት የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ አመልካች በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉ አቶ ሳህሉ ብርሀኑ እና ወ/ት አባይነሽ ብርሃኑ እንደ ቅደም ተከተላቸው ተጠሪዎች፤ የአሁን አመልካች ደግሞ ጣልቃገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካቾች ክስ ይዘት በአጭሩ ከሟች አባታቸው መቶ አለቃ ብርሃኑ አያኖ በውርስ የተላለፈላቸው በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ቤ.ቁ 389 የሆነው ቤት ከሥር ተጠሪዎች ጋር በጋራ ይዘው በአላባው እየተጠቀሙበት መሆኑን፤ ድርሻቸው ሳይለይ ቢቀጥል ችግር ሊገጥማቸው የሚችል መሆኑን በመጥቀስ ውርስ አጣሪ ተሹሞ ውርሱ እንዲጣራ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የሥር 1ኛ ተጠሪ ድርሻቸውን በስምምነት ይዘው እየተጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽ ውርሱ ሊጣራ አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሥር 2ኛ ተጠሪም የይርጋ መቃወሚያ በማንሳት ውርሱ ሊጣራ አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የአሁን አመልካች ተጠቃሹን ቤት ይዘው የሚያስተዳድሩት እና ተጠሪ በንብረቱ የማይጠቀሙ መሆኑን በመጥቀስ የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ የገቡት ፈልገው ነው፤ በውርስ ማጣራቱ ሂደት የሚስትነት ድርሻ ካላቸው ለአጣሪው ማስረጃቸውን ከሚያቀርቡ በቀር የውርስ ሀብቱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም፤ ያነሱት የይርጋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄም ከውርስ ማጣራት ጋር የሚገናኝ አይደለም በማለት አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ በብይን ውድቅ በማድረግ የሟች መቶ አለቃ ብርሃኑ አያኖን የውርስ ሀብት የሚያጣራ ውርስ አጣሪ እንዲሾም አድርጓል፤ ውርስ አጣሪው ያቀረበውን ሪፖርት ከመረመረም በኃላ አመልካች የሟች ሚስት በመሆናቸው አከራካሪው ቤት የሟች እና የአመልካች የጋራ ሀብት እንደሆነ ይገመታል፤ የተጠሪ ምስክሮች ቤቱ የተሰራበትን ትክክለኛ ጊዜ አላስረዱም፤ ቤቱ በውርስ ወይም በሌላ መንገድ ለሟች የተላለፈ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፤ የስጦታ ውል ነው በማለት የቀረበው ሰነድም ቦታ እንጂ ቤቱ ለሟች የተላለፈ መሆኑን አያሳይም፤ የሟች አባት አቶ አያኖ አደራ ለሟች አቶ ብርሃኑ አያኖ ቤት መስራታቸውን ያሳያል የተባለው ሰነድም አዋሳኙን ያልገለጸ እና አከራካሪውን ቤት የሚመለከት ነው ሊባል የማይችል በመሆኑ ክርክር የቀረበበት በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ቤ.ቁ 389 የሆነው ቤት የሟች መቶ አለቃ ብርሃኑ አያኖ እና የአመልካች የጋራ ሀብት ነው፤ ቤቱን ተከፋፍለው በመኖሪያ ቤትነት እና በማከራየት ሲጠቀሙበት የነበረ በመሆኑ የቤት ኪራይን በተመለከተ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ተሰርዘዋል፤ ለበር ማሠሪያ ተጠሪ ያወጡትን ወጪ ድርሻቸው ተቀንሶ አመልካች እና የሥር ተጠሪዎች ሊከፍሏቸው ይገባል በማለት ውርስ አጣሪው ያቀረበውን ሪፖርት በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በተጠሪ በኩል ቀርበው የተሰሙት ምስክሮች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ሟች መቶ አለቃ ብርሃኑ አያኖ አመልካችን ከማግባታቸው በፊት በአባታቸው አቶ አያኖ አደራ ተሰርቶ የገቡበት እና እየኖሩበት የነበረ መሆኑን ያስረዱ በመሆኑ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 389 የሆነው ቤት ሟች አቶ ብርሃኑ አያኖ አመልካችን ከማግባታቸው በፊት በግላቸው የነበራቸው ቤት ነው በማለት ተጠቃሹ ቤት የሟች አቶ ብርሃኑ አያኖ የውርስ ሀብት ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በፍ/ቤት የተፈቀደለት ወገን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስቶ እንዳይከራከር የሚከለክል ሕግ በሌለበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረብኩትን የይርጋ መቃወሚያ በብይን ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፤ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ሟች አባታቸው ከወላጅ እናታቸው በውርስ የተላለፈላቸው ይዞታ ላይ ቤት ሰርተው በስጦታ የተላለፈላቸው ነው በማለት ከሚከራከሩ በቀር አቶ አያኖ አደራ ቤቱን ሰርተው ለሟች አባታቸው የሰጡ መሆኑን በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር በሌለበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ካቀረቡት ክርክር ውጪ በመውጣት የሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉን እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ካቀረቡት የክርክር መሥመር ውጪ በመውጣት አከራካሪው ቤት የአመልካች እና የሟች የጋራ ሀብት ነው በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ የመሻሩን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎ የጽሑፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ በብይን ውድቅ ካደረገው በኋላ በብይኑ ላይ በይግባኝም ሆነ በመስቀለኛ ይግባኝ አቤቱታ ቀርቦበት ይርጋውን በተመለከተ የተወሰነ ነገር ስለሌለ ይህ ችሎት በይርጋው ላይ የተያዘውን ጭብጥ የመመርመር ስልጣን የለውም፤አመልካች እና ተጠሪ በአከራካሪው ቤት ውስጥ የራሳችንን ክፍል ይዘን የምንኖርበት በመሆኑ ቤቱ በአመልካች እጅ ብቻ አይደለም፤ አመልካች መብታቸው በማይነካበት ሁኔታ የራሳቸውን መብት ለማስከበር ጣልቃ በገቡበት ክርክር የይርጋ መቃወሚያን ሊያነሱ አይችሉም፤ሟች የውርስ ሀብቱን ያገኙት ከማነው የሚለው ነጥብ የፍሬነገር ክርክር እና የማስረጃ ምዘና በመሆኑ ችሎቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ወደ ዋናው ጉዳይ ከመገባቱ በፊት ጉደዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ የገቡት ፈልገው በመሆኑ በውርስ ማጣራቱ ሂደት የሚስትነት ድርሻ ካላቸው ለአጣሪው ማስረጃቸውን ከሚያቀርቡ በስተቀር የውርስ ሀብቱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በአግባቡ ነው?ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ውርሱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው አመልካች ወደ ክርክሩ የገቡት ፈልገው ነው፤ በውርስ ማጣራቱ ሂደት የሚስትነት ድርሻ ካላቸው ለአጣሪው ማስረጃቸውን ከሚያቀርቡ በስተቀር የውርስ ሀብቱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም በሚል መሆኑን ከሰጠው ብይን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሥር ፍ/ቤቱ የደረሰበት ይህ ድምዳሜ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ይዘት ጋር በማገናዘብ ሊመረመር ይገባል፡፡በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን አስመልክቶ ከተደነገጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ድንጋጌዎች ውስጥ ሦስተኛ ወገኖች በጣልቃ ገብነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክርክር ተካፋይ መሆን ስለሚችሉበት ሥርዓት የተደነገገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 ድንጋጌ ተጠቃሽ ነው፡፡

ይህ ድንጋጌ በአንድ ክርክር ያገባኛል የሚል ማናቸውም ሦስተኛ ወገን ከፍርድ ውሳኔ በፊት ጣልቃገብ ሆኖ ለመከራከር እንዲችል እንዲፈቀድለት ማመልከት ስለሚችልበት እና በክርክሩ ተካፋይ ለመሆን ሊፈቀድለት ስለሚችልበት ሥርዓት የሚደነግግ ነው፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ዓላማ ክርክርን በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ በመምራት ፍትሀዊ ውሳኔ መስጠት ነው፡፡ ተጠቃሹ ድንጋጌም ይህን ዓላማ የማሳካት ዓይነተኛ ሚና ያለው በመሆኑ የድንጋጌው አተገባበርም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ዓላማ ጋር በማገናዘብ ሊሆን ይገባል፡፡ የሥነሥርዓት ሕጉ ዓላማም ሊሳካ የሚችለው በድንጋጌው መሠረት ጣልቃ እንዲገባ የተፈቀደለት ተከራካሪ ወገን አለኝ የሚለውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያም ሆነ የፍሬነገር ክርክር ማቅረብ ሲችል ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በዚህ ድንጋጌ መሠረት ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ ጠይቀው ተፈቅዶላቸው የክርክሩ ተካፋይ እንደሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ያሳያል፡፡ አመልካች በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ከተፈቀደላቸው በኋላ ያላቸው መብት ለጉዳዩ ይጠቅመኛል ያሉትን መከራከሪያ ማቅረብ እንደሆነ ከድንጋጌው ይዘት እና ዓላማ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ አመልካች ጣልቃገብ ተከራካሪ ወገን በመሆናቸው በሚያቀርቡት መከራከሪያ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ማቅረብ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚለው ነው፡፡

አንድ ተከራካሪ ወገን አለኝ የሚለውን መከራከሪያ ሳያቀርብ የሚሰጠው ውሳኔ ፍትሐዊ ሊሆን አይችልም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 234/1/ሐ ተከሳሽ በሚያቀርበው መከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካለው በመከላከያ መልሱ መግለጽ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ እስከተፈቀደላቸው ድረስ ይህ ድንጋጌ በሚፈቅደው መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካላቸው ዘርዝረው የማቅረብ መብት ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ጣልቃገብ ተከራካሪ ወገን ስለሆኑ ውርሱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ወደ ዋናው ጉዳይ በመግባት ውሳኔ መስጠቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 ድንጋጌን ትክክለኛ አተገባበር ያልተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ የሥር ፍ/ቤት የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ በሰጠው ብይን ላይ በይግባኝ ወይም በመስቀለኛ ይግባኝ ቅሬታ ቀርቦበት ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ይህ ችሎት በይርጋው ላይ የተያዘውን ጭብጥ የመመርመር ሥልጣን የለውም በማለት መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት ከመነሻውም ቢሆን አመልካች ውርሱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት የአመልካችን መቃወሚያ ያልተቀበለው እና ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል? ወይስ አይታገድም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብይን ያልሰጠበት በመሆኑ አመልካች የይርጋ መቃወሚያውን መሠረት በማድረግ ይግባኝ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ ማቅረብ ነበረባቸው የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ ተጠሪ በዚህ አግባብ ያቀረቡትን መከራከሪያ አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ውርሱ እንዳይጣራ ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ብይን መስጠቱ፤ በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ሳያርሙ ማለፋቸው መሰረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ147733 ጥቅምት 03 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 107370 ታሕሳስ 15 ቀን 2007 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በውርስ ማጣራቱ ሂደት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 መሠረት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር የተፈቀደለት ተከራካሪ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሠረት አለኝ የሚለውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስቶ መከራከር ይችላል ብለናል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ላይ በጉዳዩ ተከራካሪ የነበሩት ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር በመስማት እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ ተገቢ የሆነ ብይን እንዲሰጥበት፤ የሚሰጠው ብይን የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ ከሆነ በዋናው ጉዳይ ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1 መሠረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ትዕዛዝ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ.ቁ 147733 የሆነው መዝገብ ወደመጣበት ይመለስ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.105956

ህዳር 19 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ዓሊ መሀመድ

ተሻሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሠናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡-አምሣሉ ወርቁ ኮንስትራክሽን ድርጅት

ተጠሪ፡- ትድሃር ኤስካቬሽንና ኤርዝ ሙቪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

1.ጉዳዩ የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍትብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 188 መሠረት በመዝገብ ቁጥር 32664 ያጣራውን የገንዘብ መጠን ውድቅ በማድረግ፣ በራሱ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና ተገቢውን ማጣሪያ በማድረግ፣ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ብር 1,500,144/አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ አንድ መቶ አርባ አራት ብር/ ብቻ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ ይግባኝ ሰሚል ችሎት ማፅናቱ በህግ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

2. ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው በክልሉ ጠቅለይ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ መነሻ ከሳሽ/አመልካች/ ያቀረበው የክስ ማመልቻ ነው፡፡ ከሳሽ ከተከሳሽ ድርጅት ጋር ጥር 6 ቀን 2006 ዓ.ም በተዋዋልኩት የግንባታ ሥራ ውል 1,00,000 ሜትር ኪዩብ ድንጋይ ለማውጣት ተስማምቻለሁ በውሉ መሠረት በሰኔ 8 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ስራውን ቀጥዬ በቀን 1500 ሜትር ኪዩብ ድንጋይ ለማንሳት ተስማምቻለሁ፡፡ ተከሳሽ ሰኔ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኛል፡፡ ነሐሴ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ተቆጣጣሪ መሃንዲሱ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ጥሎኝ ሄዲል እኔም ካለተቆጣጣሪ መሃንዲሱ መሥራት ስለማልችል 10 ቀናት ያህል ማሽነሪዎችን ያቆምኩ ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሹን ስጠይቀው ከዋናው ኮንተራክተር ጋር ያደረገው ንዑስ የሥራ ውል የተቋረጠ መሆኑን ገልጿል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ ከሳሽ ለ30 ቀናት ሠርቼ 54,000 ሜትር ኪዩብ ያነሳሁበትንና ለአስር ቀናት ማሽኖች የቆሙበት በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጣራው መሠረት ብር 5,800,000 ማሽኖች ከቆሙበትና ከቫት ጋር የነዳጅ ወጪ በመቀነስ ተከሳሽ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

3. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ ብር 300,000የ/ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ቅድሚያ ክፍያ ወስዶ 100,000 ሜትር ኪዩብ በስልሳ ቀናት ውስጥ አንስቶ እንዲጨርስ ከተከሳሽ ጋር ተስማምቷል፡፡ በውላችን መሠረት ከሳሽ በቂ ማሽነሪ በማሠማራት በቀን 5,500 ኪዩብ ድንጋይና አፈር ለማንሳት ተስማምቷል፡፡ ሆኖም ከሳሽ በውሉ የተገለፀውን ስልሣ ቀን ለማጠናቀቅ ስድስት ቀናት ሲቀረው የውል ግዴታውን ለመፈፅም ባለመቻሉ ውሉ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ከሳሽ በክሱ የገለፀውን 54,000 ሜትር ኪዩብ አፈርና ድንጋይ አላነሳም፡፡ ዋናው ኮንትራክተር ሲ.ሲ.ሲ. ከተከሳሽ ጋር የነበረውን የሥራ ውል አቋርጦ ከሳሽ የሠራውን ሥራ ሲረከብ የተሠራው ጠቅላላ የእስካቬሽን ሥራ 8997 ሜትር ኪዩብ መሆኑንና ከዚህ ውስጥ ከሳሽ የሠራው 2416.79 ሜትር ኪዩብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ከሳሽ ይህንን ሥራ ለመምራት የወሰደው 5021 ሊተር ነዳጅ ሲሆን ከሳሽ ከሠራው ሥራ የወሰደው የነዳጅ ዋጋ ሲቀነስ ቀሪው ብር 195,660.50/አንድ መቶ ዘጠና አምስት ሽህ ስድስት መቶ ስልሳ ብር ከሃምሣ ሣንቲም/ ነው፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ያቀረቡት ገንዘብ የሌለ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

4. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር በገባው የሥራ ውል መሠረት ለሥራ ያሰማራቸው ማሽነሪዎች በቀን ሥምንት ሠዓት ሠርተው ምን ያህል መጠን ያለው የኢስካቬሽን ሥራ መሥራት እንደሚችሉ ከሙያ አንፃር መርመረው አስተያየት እንዲሰጡበት ለአራት የተለያዩ ድርጅቶች ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ከደረሳቸው መካከል የኦሮሚያ ክልል ከተማና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ለመገመት እንደማይችል ገልፆ መልስ የሰጠ ሲሆን፣ ሳፍኮን ኮንስትራክሽን የተባለው ድርጅት በቀን ከ320 ሜትር ኪዩብ እስከ 384 ሜትር ኪዩብ ይሆናል በማለት በፅሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ አረጋ አባተ ኮንስትራክሽን የተበለ ድርጅት በቀን 1400 ሜትር ኪዩብ ሊያነሱ ይችላሉ በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን የምስራቅ ሸዋ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጽ/ቤት በቀን 1120 ሜትር ኪዩብ ማንሳት ይችላሉ በማለት በጽሑፍ መልስ የሰጠ መሆኑን የክልል ጠቅለይ ፍ/ቤት በውሣኔው በግልፅ አስፍሮታል፡፡

5. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳፍኮን የተባለው ድርጅት ማሽነሪዎች በቀን 320 ሜትር ኪዩብ ያነሳሉ በማለት የሰጠውን መግለጫ በመወሰድ አመልካች በአርባ ስድስት ቀናት 14720 ሜትር ኪዩብ ድንጋይና አፈር ለማንሳት የሚችል በመሆኑ የአንድ ሜትር በብር 102 /አንድ መቶ ሁለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብር/ ሒሳብ ተከሳሽ ለከሳሽ ብር 1,500,144/አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ አንድ መቶ አርባ አራት ብር/ ተከሳሽ ለከሳሽ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቷል፡፡ አመልካች በይግባኝ ሰሚው ችሎት በመልስ ሰጭነት ቀርቦ ለይግባኝ ባይ /ተጠሪ/ ይግባኝ ቅሬታ መልስ ከመስጠቱ በተጨማሪ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 340 መሠረት መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን መስቀለኛ ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚው ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በመቀበልና ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር በመመርመር ይግባኝ ባይ /ተጠሪ/ ለመልስ ሰጭ የምከፍለው ብር 195,660.05 /አንድ መቶ ዘጠና አምስት ሺ ስድስት መቶ ስልሣ ብር ከዜሮ አምስት ሣንቲም / ብቻ ከዚህ ውስጥ መልስ ሰጪ /አመልካች /ከይግባኝ ባይ /ተጠሪ/ የወሰደው ብር 300000 /ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ቅድመ ክፍያ ያለ በመሆኑ መልስ ሰጪ /አመልካች/ ከይግባኝ ባይ ከሰራው ስራ በላይ ገንዘብ የወሰደ በመሆኑ ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጪ የሚከፍለው ገንዘብ የለም በማለት ሰጥቷል፡፡

6. አመልካች መስከረም 10 ቀን 2007 ዓ.ም ፅፎ ባቀረባቸው የሰበር አቤቱታ የምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኦዲተሮች መድቦ፣ አመልካች ከተጠሪ የሚጠይቀው ብር 5,828,590/አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ብር/ ያለው መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክሰ ያቀረብኩት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 188 መሠረት ሒሳብ አስተሳስቦ የተሰጠውን ውሣኔ በማስረጀነት በማያያዝ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን ማስረጃ ውድቅ በማድረግ ሌላ የባለሙያ አስተያየት መጠየቅና ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ የሰጠው የቻይና መንገድ ሥራ ኩባንያ /CCCC/ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፃፈውን ደብዳቤ ነው፡፡ ሆኖም የቻይና መንገድ ሥራ ኩባንያ ደብዳቤውን የፃፈው ከተጠሪ ያገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ መሆኑን በደብዳቤ የገለፀውን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሣያገናዝብ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሮ የምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባፀደቀውና ተጠሪ በይግባኝ ያላሻረው ብር 5,828,509.76 /አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠኝ ብር ከሰባ ስድስት ሣንቲም/ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

7. ተጠሪ የካቲት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ባቀረበው መልስ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፍሬ ጉዳይና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማስረጃ ምዘና ስህተት የፈፀመበት መሆኑን በሰፊው በመግለፅ ነው፡፡ የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ስህተት በዚህ ሰበር ችሎት የሚታይና የማይታረም በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ያሰናብተን፣ አመልካች የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሒሳብ ባለሙያዎችን በመመደብ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ተጠሪ የመክፈል ሃላፊነት ያለበት መሆኑ ተረጋግጧል በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ በመሠረቱ አመልካችና ተጠሪ የምንከራከርበት ጉዳይ የፌዴራል ጉዳይ ነው፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መጠኑ በአመልካች ክስ ማመልከቻ የተገለፀውን የፌዴራል ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን የለውም፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዳኝነት የማየት ስልጣን በሌለው ጉዳይ ሒሳብ ታስቦ እንዲቀርብ ለኦዲተሮች የሰጠው ትአዛዝም ሆነ ኦዲተሮች ያቀረቡለትን ሪፖርት በማፅደቅ የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ ምንም አይነት የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ፡፡ አመልካች ይግባኝ ሰሚው ችሎት የቻይና መንገድ ሥራ ድርጅት የፃፈውን ደብዳቤ በአግባቡ ያልመዘነ መሆኑን በመግለፅ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የማስረጃ ምዘና ስህተት ክርክር ነው ይህም የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊደረግልኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካች መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

8. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ይዘት ከላይ በአጭሩ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ጉዳይ ለመወሰን፣ የሚከተሉትን የህግ ጭብጦች በዝርዝር ማየትና መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዝርዝር መታየት ያለባቸው ጭብጦችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/የአሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የሒሳብ ማስተሳሰብ ጥያቄ ተቀብሎ ኦዲተሮች በመመደብና ኦዲተሮች አጣርተው ያቀረቡለትን ሪፖርት በመዝገብ ቁጥር 32664 ታህሳስ 24 ቀን 2005 ዓ.ም በማፅደቅ የሰጠውን ውሣኔ እንደማናቸውም የሰነድ ማስረጃ መዝነው ውድቅ ማድረጋቸው ህጋዊ አሠራርን የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ሪፖርቱን በማፅደቅ የሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ያልተሻረ በመሆን ሙሉ በሙሉ ክሱን ለማስረዳት ተቀበይነት ያለው ማስረጃ ተደርጐ መወሰድ አለበት በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት አለው ወይስ የለውም?

ለ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቻይና መንገድ ሥራ ኩባንያ CCCC የፃፈውን ደብዳቤ ተቀበይነትና የአስረጅነት ብቃት ያለው ማስረጃ ነው በማለት ለውሣኔው መሠረት ማድረግ የማስረጃ አመዛዘን መርሆዎችን የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? ይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰሚው ችሎት ደብዳቤውን የማስረጃ አቀባበልና አመዛዘን ሥርዓትና መርህ ተከትሎ አልመዘነም ቢባል ውጤቱ ምን ይሆናል?

ሐ/የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትና የፌራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስገዳጅ የሆኑ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ድንጋጌዎችን በመከተል መጣራት የሚገባቸው አከራካሪ ጭብጦች በአግባቡ እንዲጣሩ በማድረግ ውሣኔ ሰጥተዋል ወይስ አልሰጡም?የሚሉትን ጭብጦች አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር የሚጠይቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

9. <u>የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32664 ኦዲተሮች ያቀረቡትን ሪፖርት በማፅናት የሰጠውን ውሣኔ በተመለከተ፡-</u>

አመልካች ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32664 ያቀረበው ጥያቄ፤ ተጠሪ የሚፈለግበት ገንዘብ ተጣርቶ ቀርቦ እንዲከፈል ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች ያቀረበው ጥያቄ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኦዲተሮች በመመደብ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 188 መሠረት ሒሳብ ያስተሳስበኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ይህም አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ጥያቄ ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 300 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 306 በተደነገገው ሥርዓት ወይም ከፍትሐበሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 307 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 314 በተደነገጉት ልዩ ሁኔታዎች የማይሸፈንና በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት /Accelerated procedures/ ታይቶ ውሣኔ የሚሰጥበት ጉዳይ እንዳልሆነ ከህጉ ድንጋጌዎች ዝርዝር ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

10.የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪን ሒሳብ የሚያስተሳስቡ ኦዲተሮች የመደበውና የኦዲተሮች ሪፖርት ያፀደቀው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 188 መሠረት እንደሆነ በመዝገብ ቁጥር 32664 ታህሳስ 24 ቀን 2005 ዓ.ም የኦዲተሮችን ሪፖርት ባፀደቀበት ውሣኔ ጠቅሷል፡፡ ይህም በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 188 ሒሳብ አስተሳሳቢ የመመደብ ሥልጣን ያለው ዋናው ጉዳይ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለውና የግራ ቀኙን ክርክር የሰማው ፍርድ ቤት ነው ወይስ ዋናው ጉዳይ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የሌለው ጥያቄ የቀረበለት ማናቸውም ፍርድ ቤት የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 188 በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በምዕራፍ ስድስት ስለ ፍርድና ስለ ትእዛዝ በሚለው ርዕስ ውስጥ የተደነገገ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለ ፍርድና ስለ ትእዛዝ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በክፍል አንድና በክፍል ሁለት የተከፈሉ ሲሆን በክፍል አንድ ሥር አጠቃላይ ድንጋጌዎች ከፍትሐበሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 180 እስከ ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ 184 የተደነጉትን ድንጋጌዎች የሚያካተት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የምዕራፍ ስድስት ክፍል 2 በአንድ አንድ ውሣኔ ስለሚሰጥ የተለየ መመሪያ የሚደነገግበት ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 188 እስከ ፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር191 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የያዘ ነው፡

11.ከላይ የገለፅነው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ምዕራፍ ስድስት በክፍል አንድና በክፍል ሁለት ሥር የተደነገጉት ድንጋጌዎች፣ ጉዳዩ በዳኝነት አይቶ፣ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ፍርድ ሲሰጥ ሊከተላቸው የሚገቡ ሥነ ሥርዓቶችንና በዋናው አከራካሪ ጭብጥ ላይ ፍርድ ከሰጠ በኋላ በቀጣይነት ሊሰጣቸው የሚገቡ የተለያዩ ትእዛዞችን የሚያሳዩ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ከዚህ አንፃር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ምዕራፍ ስድስት በጠቅላላውና ተከራከሪዎቹ ሒሳብ ተሰርቶ እንዲቀርብ በፍትሐብሔር ሥነ ሥዓርዓት ሕግ ቁጥር 188 መሠረት ልዩ ተፈፃሚነት ያለው ትእዛዝ ለመስጠት ፍርድ ቤቱ ከሳሽና ተከሳሽ ያቀረቡትን የተሟላ ክርክር ለማሰማትና ማስረጃ በመቀበልና በመመዘን ከሳሽና ተከሳሽ በሚከራከሩበት ጉዳይ ላይ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 3 መሠረት ፍርድ ለሚለው ቃልና ትእዛዝ ለሚለው ቃል በተሰጠው ትርጉምና ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 280 እስከ ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 291 የተደነገጉትን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ ፍርድ እና ልዩ ተፈፃሚነት ያለው ትእዛዝ የመስጠት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የሚመለከት ሥርዓት ነው፡፡

12 ከዚህ አንፃር የፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 188 አንድ ሰው ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ለሌለው ማናቸውም ፍርድ ቤት ከተከሳሽ ጋር ሒሳብ እንድተሳሰብ ትእዛዝ ይሰጥልኝ የሚለውን ጥያቄ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያገለግል የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ አይደለም፡፡የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 188 ድንጋጌ ይዘትም ሆነ መሠረታዊ ዓላማ አንድ ሰው ከሌላ ሰው አለኝ የሚለውን ሒሳብ በባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀብር ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ለሌለው ለማናቸውም ፍርድ ቤት ጥያቄ እንዲያቀርብ ለመፍቀድ የተደነገገ የስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ በአንጻሩ ጉዳዩን በዳኝነት የማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ፍርድ ከሰጠ በኃላ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ገንዘብ መተሳሰብን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሒሳቡ ተሰልቶ እንዲቀርብ ቀጣይ ትዕዛዝ ሊሰጥ ስለሚችልበት ሁኔታ የሚደነግግ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን ጉዳዩ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ስልጣን የሌለው መሆኑ ህገ መንግስቱን አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 4 እና የአዋጅ ቁጥር 25/1988 ድንጋጌ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት አይቶ ለመወሰን በማይችለው ጉዳይ ላይ የሒሳብ ባለሙያዎች የአመልካችንና የተጠሪን ሒሳብ ሰርተው ሪፖርት እንዲያቀርቡለት የሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትዕዛዝና ሪፖርት ከቀረበለት በኋላ ሪፖርቱን በማጽደቅ የሰጠው ውሳኔ የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 188 ደንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ ውጭ የሰጠውና በፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር "ፍርድ" "ውሳኔ" እና ትዕዛዝ ለሚሉት ቃላት የተሰጠውን ህጋዊ ትርጉም የማያሟላ መሆኑን ተረድተናል።

13. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32664 አዲተሮችን መድቦ፣ አዲተሮች አጣርተው ያመጡለትን ሪፖርት በማጽደቅ የሰጠው ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ፣ ህጋዊ አስገዳጅነትና ተፈጻሚነት እንዳለው የፍርድ ቤት ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ለማየት የሚያስችል ባህሪም ሆነ ይዘት የለውም። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜ ህጋዊ ስርዓትን የተከተለ አይደለም። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜ የሚነጻጸረው ጉዳዩን የማየት ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ከሰጠው ፍርድ፣ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ጋር ሳይሆን፣ ከፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 132 እስከ ፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 135 በተዘረጋው ስርዓት መሰረት አከራካሪ ፍሬ ጉዳይ በምትክ ዳኛ ተጣርቶ እንዲቀርብ በተሰጠ ትዕዛዝ መሰረት ምትክ ዳኞች በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 134 መሰረት ከሚያቀርቡት የሒሳብ ምርመራ ውጤት ጋር ነው።

14. በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሒሳብ አጣርተው እንዲቀርቡ የተመደቡ አዲተሮች በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተመደቡ ምትክ ዳኞች ወይም ባለሙያዎች አይደሉም። አመልካችንና ተጠሪን የሚያከራክራቸው መሰረታዊ ጭብጥ አመልካች ከተጠሪ ጋር በገባው የኮንስትራክሽን ስራ ውል መሰረት፣ መንገድ ከሚሰራበት ስፍራ ቆፍሮ ያነሳው ድንጋይና አፈር ምን ያህል ኪዩብክ ሜትር ነው የሚለው የምህንድስና ሙያ የሚጠይቅ ሆኖ እያለ በሒሳብ ባለሙያዎች የአዲት ምርመራ ውጤት የቀረበበት በመሆኑ፣ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ የማየት ስልጣን ያላቸው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሌለው የዳኝነት ስልጣንና በህግ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ አዲተሮች (ምትክ ዳኞች) መድቦ ያጸደቀውን ሪፖርት እንደማኛውም የሰነድ ማስረጃ ህጋዊ ተቀባይነት (legal admissibility) ያለውና ተዓማኒነት ያለው መሆኑን መዝነው ውድቅ በማድረግ ጉዳዩን በሌላ መንገድ የማጣራትና ሌላ ማስረጃን መሰረት በማድረግ ለመወሰን የተከተሉት ስርዓት የፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 135 እና ሌሎች የማስረጃ አቀባበልና አመዛዘን መርሆችን የተከተለ ምንም አይነት የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

15. የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) የተጻፈው ደብዳቤ በተመለከተ፣ አመልካችና ተጠሪ አመልካች በሰራው ስራና ጨርሶ ባነሳው ድንጋይና አፈር መጠንና ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል በሚገባው የገንዘብ መጠን ላይ ሰፊ ልዩነት ያላቸው በመሆኑ ግራ ቀኙ የሚካካዱበትን ጭብጥ ለመወሰን በጉዳዩ ገለልተኛ ሆኖ ትክክለኛ ማስረጃ ሊሰጥ ይችላል ተብሎ የተሰጠው የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ፣ አከራካሪውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች የሰራው የኢስካቬሽን ስራ መጠን አጣርቶ እንዲያሳውቀው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የደረሰው የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) በቁጥር CCCC(E) AA/2013/56 እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ህዳር 11 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መልስ ሰጥቷል።

16. የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ ከላይ ቁጥሩ በተገለጸው ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ በሰጠው ምላሽ ተጠሪ 241647 ሜትር ኩዩብ ትልቅ ደንጋይና 283 ሜትር ኩዩብ ቀላል ድንጋይ አነስቶ ገንዘቡ ተከፍሎት እንደተሰናበት ከገለጸ በኃላ በደብዳቤው መደምደሚያ ላይ "በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት ከኢትዮጵያ መንገዶች ስራ ጋር ኩባንያችን CCCC አንድ ላይ በመሆን እንዳንለካ ቦታው በሰብቤዝና በአስፓልት ተሸፍኗል። ስለሆነም የመርመርነው ከመልስ ሰጭው በተገኘው የጽሁፍ ማስረጃ ነው" በማለት ግልጽ አድርጓል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቻይና መንገድ ስራ ካንፓኒ በደብዳቤው የገለጻቸውን ፍሬ ነገሮች የራሱን የሰነድ ማስረጃዎች መነሻ በማድረግ ሳይሆን የስር ተከሳሽ (ተጠሪ) የቀረበለትን የሰነድ ማስረጃ መሰረት በማድረግ የሰጠው መረጃ መሆኑን በመገንዘብ ውድቅ አድርጎታል።

17. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግን፣ የደብዳቤውን ሙሉ ይዘት ሳይመረምር በተለይም CCCC በደብዳቤው የገለጻቸውን ፍሬ ነገሮች ያገኘው የስር ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ የቀረበለትን የሰነድ ማስረጃ በመመልከት እንደሆነ የገለጸው መደምደሚያ ህጋዊ ውጤት ሳያገናዝብ ደብዳቤው የአሰረጅነት ብቃት ያለው የሰነድ ማስረጃ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። ይህ የይግባኝ ሰሚው ችሎት አሰራር አንድ ማስረጃ ሊመዘን የሚገባው ከማስረጃው ውስጥ ከሳሽን ወይም ተከሳሽን የሚጠቅመውን ክፍል ነጥሎ በመወሰድ ሳይሆን የማስረጃውን ሙሉ ይዘት በመመርመርና በመመዘን መሆን ይኖርበታል የሚለውን መሰረታዊ የማስረጃ አመዛዘን መርህ የሚጥስ ነው። የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) በደብዳቤው የገለጻቸውና ፍሬ ነገሮች ያገኛቸው ተከሳሽ (ተጠሪ) ከቀረበለት የሰነድ ማስረጃ መሆኑን እንደገለጸ ሳያገናዝብና CCCC የሰጠው መረጃ የተከሳሽን (ተጠሪን) የቀረበበት ሰነድ ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆኑ በራሱ የተከሳሽን ማስረጃ በቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) በኩል ተጽፎ ቁጥር ተሰጥቶና ደብዳቤው የተጻፈበት ቀን ተገልጾና በማህተም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተረጋግጦ እንዲቀርብ ከማድረግ ውጭ የተለየ ህጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን ሳያገናዝብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደብዳቤውን ለውሳኔው መሰረት አድርጎ መጠቀሙ ከላይ የገለጸነውን የማስረጃ አመዛዘን መርህ ያልተከተለ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

18. ከዚህ አንጻር ሲታይ የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) የጻፈው ደብዳቤ ተጠሪ በመከራከሪያነት ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች በሌላ መንገድ የሚገልጽና የሚደግም ሰነድ እንጅ ስለአከራካሪው ጭብጥ በቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) ወይም በሌላ ሶስተኛ ወገን (ኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን) እጅ ያሉትን፣ ሰነዶች መሰረት በማድረግ የተጻፈ ደብዳቤ ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ይህንን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

19. **<u>መጣራት የሚገባቸው ፍሬ ጉዳዩች ስለመጣራቸው፣</u>**

ከላይ እንደተገለጸው የቻይና መንገድ ስራ ድርጅት (CCCC) ተጠሪ የቀረበለትን ሰነድ መሰረት በማድረግ የጻፈውን ደብዳቤ ሙሉ ይዘት ሳይመዘን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ የማስረጃ አመዛዘን መሰረታዊ መርህ ያልተከተለ ነው፡፡ ይህም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው መጣራት የሚገባቸውን አከረካሪ ፍሬ ጉዳዩች በአግባቡ በማጣራት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ እንድንመረምር የሚያስገደድ ነው፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሒሳብ ባለሙያዎች መድቦ ያገኘውን የኦዲት ሪፖርትም ሆነ የቻይና የመንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) የጻፈውን ደብዳቤ አከራካሪውን ጭብጥ ለማስረዳት ተቀባይነትና የአስረጅነት ብቃት ያላቸው ማስረጃዎች አይደሉም በማለት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አከራካሪውን ጭብጥ ሌሎች ባለሙያዎች የመንግስትና የግል ድርጅቶች በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብለት የሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 250 እና የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 136(1) ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

20. አከራካሪው የህግ ጭብጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው ውል መሰረት የሰራው የኢስካቬሽን ስራ መጠንና ለዚህ ስራው ሊከፈለው የሚገባው ገንዘብ ምን ያህል ነው የሚለውን አጣርተው መግለጫ እንዲያቀርቡለት ያዘዛቸው አራት ድርጅቶች የተለያየና ተቃራኒ ይዘት ያለው አስተያየት አቅርበውለት እያለ የአንደኛውን “ሳፍኮን” የተባለው ድርጅት የሰጠውን የሙያ አስተያየት ተቀብሎና የሌሎቹን የሙያ አስተያየት ውድቅ አድርጎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ የሰጠበት ህጋዊ ምክንያት ምንድን ነው የሚለው ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለጉዳዩ አጥንተው የሙያ አስተያየት እንዲሰጥ ትዕዛዝ ከሰጣቸው ድርጅቶች አንደኛው ማለትም የኦሮሚያ ከተማና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ፣ ለመገመት እንደማይቻል የገለጸለት ሲሆን ሳፍኮን ኮንስትራክሽን የተባለው አመልካች በቀን 320 ኩዩቢክ ሜትር ያነሳል በማለት የገልጸ ሲሆን አርጋ አባተ ኮንስትራክሽን የተባለ ድርጅት አመልካች በቀን 1400 ኪዩብክ ሜትር አፈርና ድንጋይ ያነሳል በማለት ገልጿል፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ኢንዲስትና ከተማ ጽ/ቤት በበኩል አመልካች በቀን 1120 ኩዩቢክ ሜትር ያነሳል በማለት ጽፋል፡፡

21. ከላይ የገለጽነው ተቃራኒ ይዘትና የተለያየ የሙያ አስተያየት በተሰጠበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያለምንም ህጋዊ ምክንያትና መነሻ ሳፍኮን የተባለው ድርጅት የሰጠውን የሙያ አስተያየት በመቀበል አመልካች በቀን 320 ኩብቢክ ሜትር ስራ ይሰራል በማለት የሰጠውን አስተያየት በመቀበልና በሌሎች ድርጅቶች የሰጡትን የሙያ አስተያየቶች ውድቅ በማድረግ መወሰኑ ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ አንጻር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከተለያዩ የመንግስትና የግል ተቋማት የሚሰሩ በጉዳዩ ላይ በቂ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 136(1) መሰረት በመመደብ የተመደቡት ባለሙያዎች፡-

ሀ. አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው ውል መሰረት የኤስካቬሽን ስራ ሲሰራ የተጠሪ አማካሪ ማህንዲስ ስራውን ሲቆጣጠርበት የነበረውን ሳይት ቡክ፣

ለ. አመልካችና ተጠሪ ማሽነሪዎች በየቀኑ ለምን ያህል ሰዓት እንደሰሩ የመዘገቡበትን ሰነድ፣

ሐ. አመልካች የተጠቀመው ነዳጅ 5021 (አምስት ሺ ሃያ አንድ ሊትር) ነዳጅ አመልካች ለስራ ባሰማራቸው ማሽነሪዎች ምን ያህል የኢስካቬሽን ስራ ሊያሰራ እንደሚችል በመገመት፣

መ. ተጠሪ ከቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) በአመልካችና በራሱ አቅም ለሰራው የኢስካቬሽን ስራ ምን ያህል ክፍያ እንደተከፈል በማጣራትና፣

ሠ. የተጠሪ አማካሪ መሀንዲስ፣ ስራው ከሚሰራበት ቦታ ለቅቆ ከመሄዱ በፊት፣ አመልካች ምን ያህል ኩዩብክ ሜትር አፈርና ድንጋይ እንዳነሳ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ይዞ በመቅረብ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 246(1) መሰረት ትዕዛዝ በመሰጠትና ሌሎች አከራካሪውን ፍሬ ጉዳይ ለመወሰን የሚጠቅሙ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን በትዕዛዝ በማቅረብና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ አንቀጽ 246፣ አንቀጽ 247፣ አንቀጽ 248፣ አንቀጽ 145(1) አንቀጽ 136(1) እና አንቀጽ 264(1) መሰረት አጣርቶ መወሰን ሲገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በገለጽነው ሁኔታ ጉዳዩን በማጣራት ሳይሆን ተቃራኒ ይዘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካላቸው ሙያዊ አስተያየቶች የአንደኛውን ድርጅት አስተያየት መርጦ በመውሰድ መወሰኑ ከላይ የጠቀሰናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ያልተከተለና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፈጸመውን ስህተት ሳያርም አመልካች ያቀረበውን መስቀልኛ ይግባኝ ውድቅ ማድረጉና የቻይና መንገድ ስራ ኩባንያ (CCCC) የጻፈውን ደብዳቤ ብቻ መሰረት በማድረግ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 160114 ሚያዝያ 9 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 100383 ሀምሌ 28 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሙያው በቂ ዕወቀትና ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 136(1) መሰረት መመደብና በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 20 ከ “ሀ እስከ ሠ” የተዘረዘሩ መሰረታዊ ጉዳዮች መነሻ በማድረግ አጣርተው እንዲያቀርቡለት በማደረግ ትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ የሰነድ ማስረጃዎች በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 145(1) መሰረት በትዕዛዝ በማሰቀረብና ተጠሪን በመወከል ስራውን ሲያሰራ የነበረውን አማካሪ መሃንድስና ሌሎች ጠቃሚ የምስክርነት ቃል ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎች በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 264(1) መሰረት በምስክርነት ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ በማድረግ፣ አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው ውል መሰረት የሰራው የኢስካቬሽን ስራ መጠኑ ምን ያህል ነው? ተጠሪ ለአመልካች መክፈል የሚገባው ክፍያ (ገንዘብ) ምን ያህል ሊሆን ይገባል የሚሉትን ጭብጦች አጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 343(1) መሰረት መልስን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 109563

ሕዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዩ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1. አሰፋ መንግስቱ ኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ኪራይ - የቀረበ የለም

2. ኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክስዮን ማህበር (በሰበር መዝገብ ቁጥር 109563 አመልካች) ጠበቃ ጌታቸው ጎንፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አክስዮን ማህበር የቀረበ የለም

ይህንን መዝገብ ከሰበር መዝብ ቁጥር 109563 ጋር አጣምረን በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ተመልክቶ ይግባኙ ተቀባይነት የለውም በማለት መሰረዙ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልን ይገባል በማለት 1ኛ አመልካች ጥር 29 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ፤ 2ኛው አመልካች ደግሞ ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የየራሳቸውን የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ክርክሩ በመኪና አደጋ ለደረሰ ጉዳት ካሳን ለማስከፈል በመዳረግ የቀረበ ክስን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በጀመረበት በፌደራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ 1ኛ አመልካች ተከሳሽ 2ኛ አመልካች ደግሞ ጣልቃ ገብ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ጥቅምት 27 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ ክስ በ1ኛው አመልካች ላይ በማቅረባቸው ሲሆን የክሱም ይዘት በአጭሩ፡-ንብረትነቱ የ1ኛ አመልካች የሆነው የሰሌዳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥሩ 3-31175 ኢት. መኪና ንብረትነቱ የተጠሪ ደንበኛ አቶ ሙላት ሳጃ የሆነውን የሰሌዳ ቁጥሩ 3-14981 የሆነ መኪና በመግጨት ላደረሰው ጉዳት ተጠሪው ለደንበኛቸው የከፈሉትን ብር 159,626.68 /አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከስልሳ ስምንት ሳንቲም/ የጉዳት አድራሹ መኪና ባለቤት የሆኑት 1ኛ አመልካች ለክርክሩ ከሚወጣ ወጭና ኪሳራ ጋር እንዲተኩላቸው ለማስወሰን የቀረበ ነበር፡፡

1ኛ አመልካችም ክሱ ደርሷቸው ህዳር 18 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ሰሌዳ ቁጥሩ 3-31175 ኢት. የሆነው መኪና የ1ኛ አመልካች ንብረት ስለመሆኑ አምነው አደጋው የደረሰው በ1ኛ አመልካች መኪና ጥፋት ሳይሆን በተጠሪ ደንበኛ መኪና ጥፋት መሆኑን፤ከፖሊስ የቀረበው ማስረጃ የሚታመን አለመሆኑን፤ በ1ኛ አመልካች መኪና ላይ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ከገለፁ በኋላ ተጠሪ ጥፋተኛውን በአግባቡ ሳይለዩ ለደንበኛቸው የከፈሉትን ገንዘብ 1ኛ አመልካች የመተካት ኃላፊነት የሌለባቸው መሆናቸውን በመከራከሪያነት ካቀረቡ በኋላ ለጉዳቱ ኃላፊ የሚባሉበት ምክንያት ካለም ለ1ኛ አመልካች መኪና የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠው የአሁን 2ኛ አመልካች ኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክስዮን ማህበር ወደ ክርክሩ ገብቶ እንዲከራከር እንዲታዘዝላቸው አመልክተዋል፡፡

የአሁን 2ኛ አመልካች የሆነው ኒያላ ኢንሹራንስ አክስዮን ማህበር ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ በሰጠው መልስ በማስረጃነት የቀረበው የፖሊስ ሪፖርት ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም የ1ኛ አመልካች መኪና የቀኝ መስመሩን ይዞ አሽዋ ሲጭን የተጠሪ ደንበኛ መኪና ከሌላ አቅጣጫ በፍጥነት መጥቶ የ1ኛ አመልካችን መኪና በመግጨቱ የደረሰ ጉዳት ነው፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የፖሊስ ሪፖርቱ በመርማሪው ባለሙያ ሳይዘጋጅ ያላግባብ የቀረበ ነው፡፡ በምርመራ ሂደቱ ላይ የተሳተፈው የፖሊስ አባል ቀርቦ ምስክርነት እንዲሰጥ ይደረግልን ካለ በኋላ የኢንሹራንስ ሽፋን መጠኑም ብር 100,000/አንድ መቶ ሺህ ብር/ መሆኑን በመግለፅ ክርክር አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራቀኙን ወገኖች የቃል ክርክር እና ማስረጃዎች በመስማት፤በጉዳዩ ላይ ቅሬታ ቀርቦበት ድጋሚ ምርመራ ተደርጓል የተባለ በመሆኑ ይኸው የፖሊስ የምርመራ መዝገብ እንዲቀርብ፤እንዲሁም ስለ ሁኔታው ያውቃሉ የተባሉት የፖሊስ አባል ቀርበው ምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ በማድረግ ካጣራ በኋላ አደጋው የደረሰው በ1ኛ አመልካች መኪና ጥፋት ለመሆኑ በቀረበው ምስክሮች ቃል ከፖሊስ መምሪያ በተጻፈ ደብዳቤ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ያመች ዘንድ አስቀርቦ ከሰማው ምስክር ቃል መገንዘብ መቻሉን ገልፆ የመኪናው ባለቤት የሆኑት 1ኛ አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፤ 2ኛው አመልካች በበኩላቸው ለ1ኛው አመልካች ተሽከርካሪ በሰጡት የኢንሹራንስ ሽፋን መሻሻት ኃላፊ ሆነው በመገኘታቸው ሁለቱም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት ብር 159,626.68/አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስደስት ብር ከስልሳ ስምንት ሳንቲም/ ጉዳዩ ውሳኔ ካገኘበት ከጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ክፍያው ተፈፅሞ እስኪጠናቀቅ ከሚታሰብ 9% ወለድ እና ከክርክር ወጭ ብር 1,000/አንድ ሺህ ብር/ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካቾች ቅር በመሰኘት የየራሳቸውን የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ይግባኙን ሠርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የስር ፍ/ቤቶች ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን 1ኛ አመልካች በዚህ የሰበር መዝገብ እንዲሁም 2ኛ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 109563 ላይ የየራሳቸውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የ1ኛው አመልካች የሰበር አቤቱታ በአጭሩ፡- የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ማስረጃን መሠረት ያደረገ አለመሆኑን፤ለውሳኔው መሰረት የሆነው የፖሊስ ሪፖርትም በሀሰት የተዘጋጀ መሆኑን፤ለደረሰው አደጋ ጥፋተኛው የተጠሪ ደንበኛ መኪና ስለመሆኑ የተረጋገጠ ማስረጃ አቅረበው በበቂ ሁኔታ ክሱን ማስተባበላቸውን፤ በድጋሚ የተሰራው የትራፊክ ምርምራ ለውሳኔው መሰረት መደረጉ ተገቢ አለመሆኑን፤የ1ኛ አመልካች ማስረጃዎች የታለፉበት ምክንያት በግልፅ አለመጠቀሱን፤ ኒያላ ኢንሹራንስ ወደ ክርክሩ ገብቶ እስከ ብር 100,000 ለ1ኛ አመልካች የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሮ እያለ የ1ኛ አመልካች ኃላፊነት እስከ ብር 159,626.68 በአንድነትና በነጠላ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን በመግለፅ እንዲታረምላቸው ያቀረቡት ነው፡፡ 2ኛው አመልካች በመዝገብ ቁጥር 109563 ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ደግሞ በይዘቱ ከ1ኛው አመልካች ቅሬታ ጋር የሚመሳሰል ሆኖ በአጭሩ፡- የሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ አለመወሰኑን፤የአመልካቾች ማስረጃ ውድቅ የተደረገው በተገቢው ምክንያት ላይ ተመስርቶ አለመሆኑን፤ተጨማሪ ማስረጃ ለማቅረብ የጠየቁበት የማስፈቀጃ ጥያቄ ያላግባብ ውድቅ መደረጉን የሚመለከት ነው፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎቱም ሁለቱንም መዝገቦች መርምሮ በዚህ ጉዳይ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች አንፃር አመልካቾች የደረሰውን ጉዳት የመተካት ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ይህ የሚታለፍ ከሆነ የኃላፊነት መጠኑን አስመልክቶ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ የተባለበትን አግባብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ መልሳቸውን አመልካቾችም የመልስ መልሳቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንፃር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካቾች የሚከራከሩት ጉዳት መድረሱን ሳይክዱ ጉዳቱ በተጠሪ ደንበኛ መኪና አሽከርካሪ ጥፋት የደረሰ በመሆኑ 1ኛው አመልካችም ሆነ ለእርሱ የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠው 2ኛው አመልካች ጉዳቱን ለመካስ ኃፊነት የለብንም፤ በዚህ ረገድ በማስረጃ ያረጋገጥነው ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ባግባቡ ታይቶ የተወሰነ አይደለም የሚል የጋራ ክርክር ያቀረቡ ሲሆን 1ኛው አመልካች ኃላፊነት አለብህ የምባል ቢሆን እንኳን ብር 100,000 በ2ኛው አመልካች ተሸፍኖ ቀሪውን 2ኛው አመልካች እንዲከፍል ሊወሰን ይገባል እንጂ ሁለቱ አመልካቾች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ሙሉን ጉዳት እንድንክስ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በሚል አቅርበዋል፡፡ 2ኛው አመልካችም ተጨማሪ ማስረጃ እንድናቀርብ ጠይቀን ሳይፈቀድ ቀርቷል የሚል ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ከግራቀኙ ወገኖች ክርክር አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤት ኃላፊነት ያለበትን ወገን በመለየት ረገድ የፈፀመው መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራርና በማስረጃ የማጣራት ስህተት አለ ወይስ የለም? 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ሙሉውን የካሳ መጠን ለተጠሪ እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? በአጠቃላይ የሥር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የፈፀሙት መሠረታዊ የህግ ስህተት አለ ወይስ የለም? የሚሉት ነጥቦች ምላሽ ማግኘት ያለባቸው መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ ስንመለከት ከመዝገቡ እንደተረዳነው ንብረትነቱ የ1ኛው አመልካች የሆነው ሰሌዳ ቁጥሩ 3-31175 እና ንብረትነቱ የተጠሪ ደንበኛ አቶ ሙላት ሳኛ በሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-14981 በሆነው ተሽከርካሪ መካከል በተፈጠረ የግጭት አደጋ በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ ሲሆን በአመልካቾች በኩልም ቢሆን የቀረበው ክርክር የተጠሪ ደንበኛ መኪና አልተጎዳም የሚል ሳይሆን የ1ኛ አመልካች ተሽከርካሪ ጥፋት የሌለበት በመሆኑ ካሳውን ለመክፈል ኃላፊነት የለብንም በማለት መከራከራቸውን ተገንዝበናል፡፡ ከሁለቱም አመልካቾች ክርክር መረዳት እንደተቻለው የተጠሪ ደንበኛ መኪና በፍጥነት መጥቶ ቆሞ አሽዋ ሲጭን የነበረውን የ1ኛ አመልካች መኪና በመግጨት የደረሰ ጉዳት ለመሆኑ ይከራከራሉ፡፡ በጉዳዩ ላይ በወቅቱ ፕላን የማንሳትና የምርመራ ሥራ ተከናውኖ እንደነበርና ይህ የትራፊክ ፕላን አነሳስ እና የምርመራ ተግባር ችግር እንዳለበት ለሚመለከተው የኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን አቤቱታ ቀርቦ ሌላ ጉዳዩን በድጋሚ የሚያጣራ አምስት አባላት ያሉት ቡድን ተቋቁሞ ምርመራ ተደርጎ እንደነበር አመልካቾች ሳይክዱ አቅርበን ያሰማናቸው የመጀመሪውን ምርመራ ያከናወኑ አባላትን በማስረጃነት አቅርበን አሰምተን እያለን ማስረጃችን ያለ ምክንያት ተቀባይነት አጥቷል በሚል ይከራከራሉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አስቀድሞ የተደረገው ምርመራ ችግር እንዳለበት ታምኖበት እንደገና እንዲጣራ በመደረጉ ምክንያት የኋለኛው መርማሪ ቡድን ያገኛቸውን ማስረጃዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት አድርገው የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት ይከራከራሉ፡፡

በመሠረቱ ፍርድ ቤቶች ተገቢውን የክርክር አመራር መከተል እንዳለባቸው፤ጉዳዩን ባግባቡ በማጣራት የግራቀኙን ወገኖች ማስረጃ በማስማትና ለፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ በሆነም ጊዜ ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርበው በመስማትና በማጣራት ውሳኔ ሊሰጡ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ስ/ህ/ቁ 145፤264፤266፤267፤345 እና በሌሎችም በግልፅ ተመልክቶ የሚገኝ ቢሆንም በፍትሐብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገሩ እንዲነጥር የሚደረገውም በማስረጃ የሚነጥረው ፍሬ ነገር ለዳኝነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ፍርድ ቤቶች እውነትን ለማውጣት ማስረጃ አስቀርበው መስማት አለባቸው ሲባል በቀረበው ማስረጃ እውነቱ እስከተረጋገጠ ድረስ የግድ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያስቀረቡ የሚገደዱበት ምክንያት ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጨማሪ ማስረጃ ለማቅረብ ማስፈቀጃ አቅርበን መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው በሚል 2ኛው አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካቾች ያቀረብነው ማስረጃ በምክንያት ውድቅ አልተደረገም በሚል የሚያቀርቡትን ክርክር በተመለከተ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት የሚያመለክተው በአመልካቾች በኩል የቀረበው ክርክርና ማስረጃ ከተጠሪ ክርክርና ማስረጃ በተሻለ ሁኔታ ሊታመን የማይችል መሆኑ ግምት ውስጥ ገብቶ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ ማስረጃን የማጣራት የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ያለው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተገቢውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በማስረጃ ለማጣራት የግራቀኙን ወገኖች ማስረጃ ሰምቷል፡፡ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትንና ሰነድና የሰው ምስክርም አስቀርቦ ሰምቷል፡፡ በአስፈላጊነቱ ላይ ያላመነበትን ማስረጃ ሳያስቀርብ ቀርቷል፡፡ ከዚህ በመነሳትም ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበትን ወገን ለመለየት በግራቀኙ ወገኖች የቀረቡትንና ለፍትህ አስጣጥ አመችነት ፍርድ ቤቱ ያስቀረባቸውን ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ እንዲሁም የራሱን ምክንያት በመሰጠት አደጋው ለመድረሱ ከማረጋገጡም በላይ አደጋውንም ያደረሰው የ1ኛ አመልካች መኪና የሆነው አሸዋ ሲጭን የነበረው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-31175 ኢት. የሆነው መኪና ለመሆኑ አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በመነሳትም በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2081(1) መሰረት የመኪናው ባለቤት የሆነው 1ኛው አመልካች ካሳውን ለመክፈል ኃላፊ መሆናቸውን ሲወስን 2ኛው አመልካች ከ1ኛው አመልካች ጋር የኢንሹራንስ ውል ያላቸው ለመሆኑ ስላልተካደ ኃላፊነት ያለባቸው ለመሆኑ ወስኗል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት ተገቢውን ጭብጥ በመመስረት በግራቀኙ ወገኖች የቀረቡትን ማስረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ማስረጃ አስቀርቦ በመስማትና በመመርመር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መወሰኑን መዝገቡ ስለሚያስረዳ በሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካቾች ኃላፊ መሆናቸው ከተረጋገጠ የኃላፊነት መጠናቸውን መመልከቱ ተገቢነት ያለው ይሆናል፡፡ ተጠሪ ለደንበኛቸው የከፈሉትን ብር 159,626.68/አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከስልሳ ስምንት ሳንቲም/ 1ኛ አመልካች እንዲተኩላቸው ዳኝነት ጠይቀው ላቀረቡት ክስ በ1ኛው አመልካች በኩል የቀረበ የካሳ መጠንን የሚመለከት ክርክር የለም፡፡ 2ኛው አመልካች በሰጡት መልስ ለ1ኛው አመልካች መኪና የሰጡት የኢንሹራንስ ሽፋን እስከ ብር 100,000/አንድ መቶ ሺህ ብር/ እንደሆነ ገልፀው መልስ አቅርበዋል፡፡ የ2ኛው አመልካች ኃላፊነት ለ1ኛው አመልካች ከሰጡት የኢንሹራንስ ውል የሚመነጭ ከመሆኑም በላይ መጠኑም በውሉ ልክ የሚወሰን ነው፡፡ ይህ ከሆነ የሁለቱ አመልካቾች ኃላፊነት መጠን የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር 2ኛው አመልካች ለተጠሪ እስከ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠ መሆኑ እስካልካደ ድረስ ከተወሰነው የካሳ መጠን በዚሁ ገንዘብ ልክ ሊከፍሉ የሚገባቸው ይሆናል፡፡ 1ኛው አመልካች ደግሞ ቀሪውን የውሳኔ መጠን ሊከፍሉ ይገባል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠን ብር 159,626.68/አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከስልሳ ሳንቲም/ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ሁለቱም አመልካቾች በአንድነትና በነጠላ ይህንኑ ገንዘብ ከጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድና ከብር 1,000 /አንድ ሺህ ብር/ የክርክር ወጭ ጋር ይክፈሉ የተባለበት አግባብ የ1ኛ አመልካችንና የ2ኛ አመልካችን የኢንሹራንስ ውል ግንኙነትና 1ኛ አመልካች 2ኛውን አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገቡላቸው የጠየቁበትን ዓላማ ያላገናዘበ በመሆኑ በመጠኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ ማስረጃ የመመርመር፤ የማጣራትና መመዘን ሥልጣን የተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች በኩል የቀረቡ ክርክሮችን መሠረት በማድረግ ተገቢውን ጭብጥ ይዘውና አጣርተው ከፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ማስረጃ ምዘና አንፃር በመመልከት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ የሚያሳምን አለመሆኑን ጠቅሰው ውድቅ በማድረግ የተጠሪን ማስረጃ በመቀበል አመልካቾች የደረሰውን ጉዳት የመክስ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ላይ የደረሱበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ምክንያት አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል 2ኛው አመልካች ለ1ኛው አመልካች እስከ ብር 100,000 ኢንሹራን ሽፋን የሰጡ ለመሆናቸው በመልሳቸው አምነው አቅርበው እያለ ከተወሰነው የካሳ መጠን ውስጥ ብር 100,000 ከነወለዱ በ2ኛው አመልካች እንዲሸፈን ሆኖ ቀሪውን 1ኛው አመልካች እንዲከፍሉ መወሰን ሲገባው ሁለቱም አመልካቾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሙሉውን ካሳ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 188781 ጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 147566 ሕዳር 01 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካቾች በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው መባሉና በዚህ ጉዳት ምክንያት የመጣ ካሳ ብር 159,626.68 ከጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ የሚታሰብ በዓመት 9% ህጋዊ ወለድና ብር 1,000 /አንድ ሺህ ብር/ የክርክር ወጭ ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል መባሉ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡

3. አከፋፈሉን በተመለከተ ከዚሁ የካሳ መጠን ውስጥ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ከጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፋሎ እስኪያልቅ ድረስ ከሚታሰብ በአመት 9% ወለድ ጨምሮ በ2ኛው አመልካች የሚሸፈን ሆኖ ቀሪው የካሳ መጠን ከነወለዱና የክርክር ወጭ በ1ኛው አመልካች እንዲከፈል ወስነናል፡፡

4. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈፅም ተወስኗል፤ ይጻፍ፡፡

5. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣ ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

6. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ የሰበር መዝገብ ቁጥር 109563 አካል ይሁን ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.107217

ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተሽሊትይመስል

ቀነዓ ቀጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የዳንግላ ወረዳ ውሃ ሃብት ልማት ፅ/ቤት ወኪል የፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሙሉጌታ ገበየሁ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግንባታ ሥራ ውል የሚመለከት ሲሆን የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ ሲሆን በአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ ፅ/ቤት ላይ ለአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ ፅ/ቤት ባለ አራት መቀመጫ ሽታ አልባ መፀዳጃ ቤት ለመስራት ባወጣው ጨረታ ተወዳድሬ በማሸነፍ ተከሳሽ ጋር በገባው ውል መሠረት አምስት ሳይቶችን ሰርቼ በማስረከብ ክፍያ እንዲፈፅሙልኝ ብጠይቅና በፅ/ቤቱ መሀንዲስ ቢታዘዝም የአራት ሳይት ክፍያ ከፍለውኝ የአምስተኛውን ሳይት /የኳንች ኳኩርታን/ ሣይት ብር 68,776.71/ስልሳ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ብር ከሰባ አንድ ሣንቲም/ ያልከፍሉኝ ስለሆነ ይህንኑ ክፍያ እንዲከፍለኝ ይኸው ክፍያ በመሀንዲስ ከታዘዘበት ቀን ጀምሮ 379 ቀን ስለሆነ የብር 68,776.71 / ስልሣ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ስደስት ከ ሰባ አንድ ሣንቲም/1% x379 ቀን =ብር 260,663.93/ሁለት መቶ ስልሳ ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከዘጠና ሦስት ሣንቲም/ መቀጫ ግንባታውን አጠናቅቄ ካስረከብኩኝ አንድ ዓመት ስለሞላ ለዋስትና የተያዘ ብር 3,725.38/ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ አምስት ብር ከሰላሳ ስምንት ሣንቲም/ የዳኝነት የጠበቃ አበል 10% እና ኪሣራ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽ ፅ/ቤትም በወኪሉ አማካኝነት የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ ቢያቀርብም የታለፈበት ሲሆን በአማራጭ ባቀረበው መልስ ከሳሽ በውሉ እና በተሰጣቸው የመሀንዲስ የስራ ዝርዝር መሠረት ግንባታውን ሰርተው ያስረከቡና በፅ/ቤት መሀንዲስ ሂሳቡ በትክክል ተሠርቶ በመስሪያ ቤቱ ፀድቆ ለወረዳው ፋ/ኢ/ል/ማ/ ፅ/ቤት ክፍያ እንዲፈፀም በደብዳቤ ብጠይቅም ክፍያ ሊፈፀም አልቻለም እንጂ ተከሳሽ ጽ/ቤት ክፍያ አልከለከላቸውም ካለ በኋላ መልሴን ላሻሽል ብሎ አሻሽሎ የሠጠው መልስ ከሳሽ በውሉ መሠረት ሽንት ቤቶቹ ሠርተው አስከርበው ክፍያ ያልወሰዱ ቢሆንም ክፍያ ያልወሰዱት ከሳሽ ከውል ዉጪ በተቆጣጣሪው መሀንዲስ ትእዛዝ የብር 17,358.46 /አስራ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሃምሣ ስምንት ከ አርባ ስድስት ሣንቲም/ሠርቻለሁ እና ይህንን ሂሳብ ካልረከፈለኝ ሌላውን አልበቀልም በማለታቸው ነው፡፡ የተጨማሪ ሥራ ክፍያ የሚፈፀመው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤቱ በግዢ አፈፃፀም መመሪያው ተጨማሪ ስራውን ሲያውቀው ነው፡፡ ባላወቀው ስራ ክፍያ ሊጠይቅ አይገባም፡፡ ለዋስትና ጉዳይ የተያዘውን ገንዘብ አልተከለከሉም ስለሆነም የወሰዱት ገንዘብ ተቀንሶ ቀሪ ካላቸው እንዲወስዱ ይወሰንልኝ ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ካዳመጠ በኋላ በግራ ቀኙ ክርክር የሚጠነጥነውን ለተጨማሪ ሥራ ክፍያ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በግራ ቀኙ ውል ገጽ 3 ተራ ቁጥር 5/3/ ሥር እንደተመለከተው በተመደበ ተቆጣጣሪ ወይም አማካሪ መሀንዲስ ሲደገፍ ተጨማሪ ሥራ ሊሰራ እንደሚችልና ተጨማሪ ክፍያ ሊፈፀም እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ስራው ተሠርቶ መረከቡን ተከሳሽ ፅ/ቤት አምኗል ስለሆነም ለተጨማሪ ሥራ ክፍያ አልፈፅምም መባሉ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ክፍያ ለዘገየበት መቀጫን በተመለከተ ፅ/ቤት ክፍያው እንዲፈፀምለት ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ያስተላለፈ ቢሆንም ክፍያውን ፈፃሚው ፅ/ቤት ከተሰራው ስራ ላይ በላይ ከውል ውጪ የሚታየውን ብር 17,358.46/አስራ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሃምሣ ስምንት ብር ከ አርባ ስድስት ሣንቲም/በስተቀር ሌሎች ክፍያዎችን አልቀበልም ያሉት ከሳሽ መሆናቸው ሲገልፅ ከሳሽ እነዚህ ክፍያዎች በተከሳሽ ፅ/ቤት ምክንያት የዘገዩ ስለመሆናቸው አላስረዱም በማለት ከሳሽ የጠየቁትን ክፍያ ለዘገየበት ለ379 ቀን 1 ፐርሰንት ብር 260,663.93/ሁለት መቶ ስልሣ ሺህ ስድስት መቶ ስልሣ ሦስት ከ ዘጠና ሦስት ሣንቲም/ መቀጫ ተከሳሽ ፅ/ቤት ሊከፍል አይገባም በማለት የተቀሩትን ዋናውን ገንዘብ ብር 68,776.71/ስልሳ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ብር ከሰባአንድ ሣንቲም/ ለዋስትና የተያዘ ብር 3,725.38/ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ አምስት ብር ከሰላሳ ስምንት ሣንቲም/ በጠቅላላው ብር 72,502.09/ሰባ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ብር ከ ዜሮ ዘጠኝ ሣንቲም/ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ዳኝነት እና የጠበቃ አበል10% ተከሳሽ ለከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን የቅሬታው ይዘትም በአጭሩ ክፍያ ለዘገየበት ለ379 ቀን መቀጮ ሊከፍል አይገባም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ ቅሬታው የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሥራው ተሰርቶ የተጠናቀቀ መሆኑንና ክፍያው ያለመፈፀሙ በተከሳሽ የታመነ ጉዳይ ነው ስለሆነም የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ ባቀቡት ክስ መሰረት አላስረዱም ማለቱ ተገቢ አይደለም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁ. 348/1/ መሰረት ውሣኔውን በመሻር ክፍያ ለዘገየበት ብር 260,663.73 /ሁለት መቶ ስልሣ ሺህ ስድስት መቶ ስልሣ ሦስት ብር ከ ሰባ ሦስት ሣንቲም /ተከሳሽ ጽ/ቤት ሊከፍል ይገባል በማለት ሲወሰን በአሁን አመልካች በበኩል የሠበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት ቅሬታው ተጠሪን አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሠረት አቤቱታውን ሠርዞታል፡፡

ለፊደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሠበር አቤቱታውን ያቀረበው አመልካች ፅ/ቤት ሲሆን አቤቱታው ክፍያ አዘግይተናል ብለን በእምነት የሰጠነው ቃል የለም፡፡ ከተጨማሪ ሥራ በስተቀር የተቀሩትን አልወስድም ያሉት ተጠሪ ናቸው ስለሆነም ክፍያው ለዘገየበት ልንከፍል አይገባም፤ ክፍያ ለዘገየበት የምንከፍል ቢሆን እንኳን ክፍያ የዘገየበት የገንዘብ መጠን 1 ፐርሰንት ሳይሆን 0.1 ፐርሰንት ከመሆኑም በተጨማሪ በአማራ ክልል የግር መመሪያ መሠረት ክፍያው ከዋናዋ ገንዘብ 10% በላይ ሊሆን አይገባም የሚል ነው፡፡

አጣሪው ችሎትም የቀረበውን አቤቱታና የሥር መዝገብ መርምሮ የመቀጮ ክፍያ ከዋናው ገንዘብ 10%በላይ በስር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ያመች ዘንድ ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በፅሑፍ በሰጡት መልስ የመቀጮ መብዛትንም ይሁን ማነስ የፍሬ ነገር ክርክር ባልሆነበት እና ይህን አስመልክቶ አመልካች ፅ/ቤት ያነሳው መከላከያ ነጥብ በሌለበት የሠበር አጣሪው ችሎት የያዘው ጭብጥ በሥር ያልተነሳ ክርክር ነውና የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ይፅናልኝ ብለዋል፡፡ እኛም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርና ማስረጃ አንፃር የሠበር አቤቱታው የቀረበበትን ውሣኔ የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎት የሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን ያለመሆኑን ከተገቢው ህግ አንፃር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የአሁን ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ፅ/ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር በነበረን የግንባታ ውል ግንባታውን ከተጨማሪ የመሀንዲስ ትእዛዝ ጋር ሠርቼ ለፅ/ቤቱ ያስረከብኩኝ ቢሆንም አመልካች ፅ/ቤት ክፍያውን አጠናቆ አልከፈለኝምና ያልተከፈለኝ ገንዘብ ከነቅጣቱና ተያያዥ ያላቸውን ክፍያዎች እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን፣ የአሁን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ፅ/ቤት በወኪሉ አማካኝነት በሰጠው መልስ ጽህፈት ቤቱ አልከፍልም አላለም የተጨማሪ ስራ ገንዘብ ካልተከፈለ አልቀበልም በማለት ዋናውን ገንዘብ ያልወሰዱት ተጠሪ ናቸው ስለሆነም ክፍያ ለዘገየበት ልጠየቅ አይገባም ብለዋል፡፡ ምንም እንኳን በሰበር አጣሪው ችሎት አቤቱታው ያስቀርባል የተባለበት ምክንያት ክፍያ ለዘገየበት መቀጫ ከዋናው ገንዘብ ከ10%በላይ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ቢሆንም ይህ ነጥብ ከታየቱ በፊት ክፍያ ለዘገየበት መቀጮ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተዋል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 242 ስር እንደተደነገገው ማናቸውም ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልሱ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለፀው እንደሆነ ወይም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241 መሠረት በሚደረግ ምርመራ የእምነት ቃሉን የሰጠን እንደሆነ ፍ/ቤቱ በታመነው ነገር ላይ ብቻ ፍርድ መስጠት እንዳለበት ይገልፅና በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 83 እና 234/1/ሠ ሥር እንደተደነገው በግልፅና በዝርዝር ያልተካዱ ነገሮች ሁሉ እንደታመኑ እንደሚቆጠር ደንግጓል፡፡

በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ፅ/ቤት በነበረው የግንባታ ውሉ ግንባታውን ጨርሼ ያስረከብኩኝ ቢሆንም አመልካች ፅ/ቤት ሊከፍለኝ ከሚገባው ገንዘብ ውስጥ ብር 68,776.71 /ስልሣ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ብር ከሰባ አንድ ሳንቲም/ያልከፈለኝ ስለሆነ ይኸው ዋናው ገንዘብና ተያያዥነት ያላቸው ክፍያዎች እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት መጠየቃቸውን የአሁኑ አመልካች ጽ/ቤት በግራ ቀኙ መሀከል ውል መኖሩን ተጠሪ በውሉ መሠረት ግንባታውን አጠናቀው በተጨማሪም በመሃንዲስ ትእዛዝ ፅ/ቤቱ የማያውቀው የብር 17,358.43 /አስራ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሃምሣ ስምንት ብር ከአርባ ሦስት ሣንቲም/ ተጨማሪ ሥራ መሥራታቸውንና በዚህም ምክንያት አመልካች ጽህፈት ቤት የተጨማሪ ሥራውን ክፍያ አልከፍልም በማለቱ ተጠሪ ሁሉንም ክፍያ አልወስድም በማለታቸው ክፍያ መዘግየቱን መልስ በመስጠት መከራከሩን በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከተደረገ የግራ ቀኙ ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡

በዚህም ክርክር የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ፅ/ቤት በእርግጥም ተጠሪ ዳኝነት የጠየቁበት ገንዘብ ያልተከፈለው መሆኑን አምኗል ነገር ግን ያልተከፈለው በኔ ምክንያት አይደለም እስካለ ድረስ ታምኗል የሚያሰኝ አይደለም፤በተጨማሪም ተጠሪ ክፍያው የዘገየው በአመልካች ምክንያት ስለመሆኑ አላስረዱም ስለሆነም ክፍያ ለዘገየበት አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት ሲወስን፤ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ጽህፈት ቤት ተጠሪ ስራውን ሰርተው ማስረከባቸውንና ጽ/ቤቱ ክፍያ ያለመፈፀሙን እስካመነ ድረስ ክፍያ የዘገየው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአመልካች ጽ/ቤት ምክንያት መሆኑ ታምኗል በማለት አመልካች ጽ/ቤት ክፍያ ለዘገየበት ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔን በመሻር መወሰኑንና የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት መወሰኑ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

ነገር ግን ተጠሪ ክፍያ የዘገየው በአመልካች ጽ/ቤት ምክንያት ነው ሲሉ አመልካች ጽ/ቤት ክፍያ የዘገየው በተጠሪ ምክነያት ነው እስካለ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.242 መሠረት የታመነ ጉዳይ ነው ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.234/1/ ሥር እንደተመለከተው ጉዳዩ በግልፅ ያልተካደ ጉዳይ ነው ሊባል የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ክፍያ የዘገየው በማን ምክንያት ነው የሚለው ነገር አከራካሪው ነው፡፡ በፍትሐብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ የአሁን ተጠሪ ክፍያው የዘገየው በአመልካች ፅ/ቤት ምክንያት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ያላስረዱ መሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ ሁሉ ስንነሳ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክፍያው የዘገየበት በአመልካች ፅ/ቤት ምክንያት ስለመሆኑ ተጠሪ አላስረዳም በማለት ክፍያ የዘገየበት የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ሲወስን የስር ጠቅላይ ፍ/ቤት ክፍያ የዘገየው አመልካች ጽ/ቤት መሆኑ ታምኗል በሚል የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አንችተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 37313 ሰኔ 10 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41544 ጥቅምት 29 ቀን 2007 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.07181 የካቲት 6 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 338/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙን ለዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ትእዛዝ

1. በዚህ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረው የአፈፃፀም እግድ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
2. የውሣኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ/ሰ/መ/ቁ. 114623

ቀን 22/06/2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

አይሸሹም መለሰ

ፀሃይ መንክር

አመልካችዎች፡- 1. ሀጅ ቢያ አባመጫ
2. አቶ ከሊፋ አባ ቆያስ } ጠበቃ ከድር መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. የኦሮሚያ ክልል ደንና ዱር አራዊት ድርጅት አልቀረበም

2. መራዋ አርሶ አደሮች የህብረት ሥራ ማህበር ጠበቃ በላይ እሸቱ ቀረቡ

<u>ፍ ር ድ</u>

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካችዎች ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር የእርቅ ሥምምነት በማድረግ በፍርድ ቤት እንዲመዘገብና እንዲፀድቅ ካደረጉ በኃላ አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን የፍርድ መቃወሚያ በመቀበል የእርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ውሳኔ የሰጠው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም ?የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው ጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡
2. አመልካችዎችና ሁለተኛው ተጠሪ በፈረንጅ ፅድ ሽያጭ ውል በተመለከተ ባለመስማማታቸው አመልካቾች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ከሳሽ፣ሁለተኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመከራከር ላይ እያሉ ጥር 5 ቀን 2001ዓ.ም ባደረጉት ዕርቅ ውል አመልካችዎች 1,200,000 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ብር) ለሁለተኛ ተጠሪ ሊከፍሉ ሁለተኛ ተጠሪም የክርክሩ መነሻ የሆነውን የፈረንጅ ፅድ ለአመልካችዎች ሊያስረክቡ ሥምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ አመልካችዎችና ሁለተኛ ተጠሪ የዕርቅ ሥምምነታቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14220 ህዳር 25 ቀን 2002ዓ.ም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277(1) መሠረት የዕርቅ ውላቸውን በመቀበል ግራቀኝ በዕርቅ ውሉ መሠረት እንደፈፅሙ ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡን ዘግቶታል ፡፡

3. አንደኛ ተጠሪ አመልካችዎችና ሁለተኛው ተጠሪ ጥር 5 ቀን 2001ዓ.ም አድርገነዋል በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ህዳር 25 ቀን 2002ዓ/ም ያፀደቁት የዕርቅ ውል የፈፀሙበት የፈረንጅ ፅድ የመንግስት ደን መሆኑን ገልፆ የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው እንዲባልለት ጥር 27 ቀን 2005ዓ/ም የተፃፈ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳያቸውን በዕርቅ ያዘጉት አመልካችዎችና ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ አንደኛ ተጠሪ ፍርዱን ለመቃወም የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የዕርቅ ስምምነቱ የፍርድ መቃወሚያ አመልካችን መብት የሚነካ በመሆኑ የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. አመልካችዎች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የፍርድ መቃወሚያ አቅርበው የዕርቅ ስምምነት በተደረገበት የፈረንጅ ፅድ ላይ መብት የሌለው መሆኑ በወቅቱ በተያዘው ቃለጉባኤ የተረጋገጠ ስለሆነ ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የዕርቅ ውል የተደረገበት የፈረንጅ ፅድ የመንግስት ደን በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

5. አመልካችዎች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ እኛ የገዛነው የመንግስት ደን ሣይሆን የሁለተኛ ተጠሪ ንብረት የሆነ የፈረንጅ ፅድ ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ከሻጭ ጋር ያለንን ልዩነት በዕርቅ ጨርሰን የዕርቅ ውሉ በፍርድ ቤት ከፀደቀ በኃላ ማስረጃ እንዲፃፍ በማድረግ የዕርቅ ውሉ እንዲፈርስ ማድረጉ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር ታይቶ እንደታረምልኝ በማለት አመልክተዋል ፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ንብረቴን ነው የሸጥኩት ከአመልካችዎች ጋር የዕርቅ ውል የፈፀምኩት በንብረቴ ላይ በመሆኑ የሁለተኛ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የአመልካችዎችን የሰበር አቤቱታ በመደገፍ መልስ ሰጥቷል ፡፡ አንደኛ ተጠሪ ግራቀኙ ዕርቅ የፈፀሙበት የመንግስት ደን በመሆኑ የአመልካችዎች የሰበር አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቀባይነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል ። አመልካችዎች የመልስ መልስ አቅርበዋል።

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል ። ጉዳዩን እንደመረመርነው ሁለት ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት የሚከራከሩበትን ጉዳይ በዕርቅ መጨረስ እንደሚችሉና የእርቅ ውሉን ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት አቅርበው ማፅደቅ እንደሚችሉ ፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀ የዕርቅ ውል ሥምምነት በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ያህል አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 276 እና አንቀፅ 277(1) ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል።

7. አመልካችዎችና ሁለተኛው ተጠሪ የፈረንጅ ዕድ ሽያጭ ውል በተመለከተ ጥር 5 ቀን 2001ዓ.ም ያደረጉትና ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277(1) መሠረት ያፀደቁት የዕርቅ ውል የፍርድ ያህል አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ በዚህ ዕርቅ ውል ተካፋይ ያልሆነ መብቱ ተነክቷል የሚለው አንደኛ ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉን በማፅደቅ የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ፤የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ማቅረቡና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአንደኛ ተጠሪን የፍርድ መቃወሚያና ማመልከቻን ማስረጃ በመቀበል የዕርቅ ውሉ የመንግስት ደን የሚያስተዳድረውን የአንደኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሥነ ሥርዓት ሕግ ግድፈት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም ።

8. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አንደኛ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ ለማቅረብ መሠረትና ማስረጃ የሆነውንና አመልካችዎች ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር የዕርቅ ሥምምነት የፈፀሙበት የፈረንጅ ዕድ ጫካ የመንግስት ደን መሆኑን የሚያረጋግጠውን የቴክኒክ ኮሚቴ ሪፓርትና ማስረጃ ያለበቂ ምክንያት ውድቅ በማድረግ አከራካሪው የፈረንጅ ዕድ ዛፍ ጫካ በጨረታ ለአመልካችዎች ከመሸጡ በፊት የተያዘውን ቃለ ጉባኤ ነው መያዝ ያለበት በማለት አከራካሪው የዕድ ዛፍ የሁለተኛ ተጠሪ ሀብት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ አመዛዘን መርህን ያልተከተለና መሠረታዊ የማስረጃ ህግ ድንጋጌዎችን የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 250 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136(1) ያልተከተለና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም ። በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችዎች እና አንደኛ ተጠሪ የዕርቅ ሥምምነት ያደረጉት የአንደኛ ተጠሪ መብትና ጥቅም ባለበት የመንግስት ደን ላይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቦለት እያለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንደኛ ተጠሪ የዕርቅ ሥምምነቱን መቃወምና ፈራሽ ለማስደረግ የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለውም በማለት የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 184867 መጋቢት 14 ቀን 2007ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 112190

መጋቢት 28 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች ፡--አይከል ከተማ አገልግሎት ፅ/ቤት ዐ/ህ ዮሃኒስ ተገኘ ቀርበዋል

ተጠሪ፡ -ሼክ ሸምሱ መሀመድ ተ/ይ አሚናት ሸምሱ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች አይከል ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ የአማራ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 41846 ታህሳስ 7 ቀን 2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የቀረበ ሲሆን ቅሬታውም የሥር ፍ/ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት በቅን ልቦና ባለሀብትነት ሊገኝ የማይችል ሆኖ እያለ የአይከል ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የተወረሰ ቤት በተመለከተ የመወሰን ስልጣን የሌለው ሆኖ እያለ የተወረሰን ቤት መብትና ጥቅም የሌለው አካል መሸጥ የማይችል በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የቤት ቁጥር 140 የተወረሰ መሆኑን አረጋግጦ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) በቅን ልቦና ገዝተውታል ሲል የሰጠው ውሳኔ ስህተት በመሆኑ፣ ያከራከረውን ቤት ከ36 ዓመት በላይ ቀበሌው ሲያስተዳድር የቆየ ሆኖ እያለ ከሳሽ ገዛሁት የሚሉትን ቤት ካርታና ፕላን ያላወጡበትና ገዛሁ ካሉት ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ቀበሌው እንዲያስረክባቸው ጠይቀው በማያውቁበት ሁኔታ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ሼክ ሸምሱ መሀመድ በአማራ ብ/ክ/መ/ ጭልጋ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ተከሳሽ እሙሃይ ማናለብሽ ጌታሁን ከሳሽ በአይከል 01

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በካርታ ቁጥር 89911-92316 የሚታወቅ አዋሳኙን በመጥቀስ 4 ክፍል ቤት ያላቸው ሲሆን ተከሳሽ ባልታወቀ ምክንያት ቤቱ ውስጥ ገብተው የሚኖሩበት ሲሆን ጉዳዩ ለአይከል ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት ቤትና ቦታ አስለቃቂ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀርቦ ጉባኤው በቁጥር ደስ/26/2001 በቀን 27-5-2001 ዓ.ም. በተጻፈ ውሳኔ ቤቱ የተወሰነልኝ ቢሆንም ተከሳሽ ለመልቀቅ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ቤቱን ይልቀቁልኝ ሲሉ ከሰዋል፡፡ ተከሳሽም በሰጡት መልስ ቤቱን ለ35 ዓመት ያህል ለቀበሌ ኪራይ እየከፈልኩበት የኖርኩበት በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ በቅጽ ተሞልቶ ከቀበሌ ተከራይቼ ለ35 ዓመት የኖርኩበት በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ ብለዋል፡፡ ጣልቃ ገቢ የአይከል ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በአ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተወስኖ በመመለሱ ጣልቃ ገብቶ የሰጠው መልስ ከሳሽ ከ1988 ዓ.ም. እስከ 2003 ዓ.ም.ከፍያለሁ የሚሉት ግብር በ2003 ዓ.ም.የከፈሉትና ከመመርያ ቁጥር 4/2000 ጋር የሚጻረር ነው፡፡ ከሳሽ በዚህ ግብር ብቻ የቤቱ ባለቤት ሊሆን አይችልም፡፡ ቤቱ ከአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶ ለተከሳሽ የተከራየና ተከሳሽ ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1983 ኪራይ ከፍለው የአይከል አውራጃ አስተዳደር በጻፈው ደብዳቤ ተከሳሽ የኪራይ ክፍያ አቋርጠዋል፡፡ ቤቱ የከሳሽ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ ብለዋል፡፡

በአማራ ብ/ክ/መ/ ጭልጋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 02912 አከራክሮ ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ካሁን በፊት በዚህ ጉዳይ ውሳኔ ተሰጥቶ የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ ጉዳዩን ከአዋጅ ቁጥር 47/67 ከቅጽ 001፣004 እና 003 ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥ በመለሰው መሰረት አይተነዋል፡፡ከሳሽ ያቀረቧቸው የተለያዩ የአስተዳደር ክፍል ሀላፊዎች የጻፏቸው የሰነድ ማስረጃዎችና የግብር ካሪኒዎች ይህ ክርክር የተነሳበት ቤት በመንግስት ያልተወረሰና የከሳሽ ህጋዊ ቦታ እና ቤት መሆኑን እጅግ ሚዛን በደፋ ከፍ ባለ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ተከሳሽ ቤቱን ለከሳሽ ይልቀቁለት ሲል ወስኗል፡፡ ጣልቃ ገብ የአይከል ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ለሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 01-17437 አከራክሮ ግንቦት 16 ቀን 2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከሳሽ የገዙት ቤት አራት ክፍል ሲሆን የተገዛው ቤት ለወፍጮ ቤት የሚውል ነበረ፡፡

የጎንደር አስተዳደር አካባቢ ኢንዱስትሪና እደጥበብ ለአይከል ልዩ ከፍተኛ አንድ ጽ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ ቤቱ በባንክ ዕዳ ታግዶ የነበረና ቤቱ ተሸጦ ከባንክ ዕዳ ነጻ መሆናቸውን ገልጾ የጻፈው ደብዳቤ ማዘጋጃ ቤቱም ሽያጩን በማይንቀሳቀስ ንብረት ማስተላለፍያ ሰነድ ቅጽ 13(1) መገማቢያ፡፡ የቦታ እና የይዞታ የምስክር ወረቀት 8991 መዘገብ የያዘው መሆኑ የሚያስረዳ 1 ገጽ ጽሁፍ ቀርቧል፡፡ ከሳሽ የተወረሰ ቤት መሆኑን ሳያውቁ ከአራቱ ክፍል አንድ ክፍል ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቅን ልቦና የተወረሰ መሆኑን ሳያውቁ የገዙት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ከሳሽ የአራቱም ቤቶች ባለሀብት እንደሆነ የሚገመትና ይህን ግምት ሊያስተባብል የሚችል ነገር የሌለ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ ከሳሽ ያከራከረውን አንድ ክፍል ቤት የቅን ልቦና ባለሀብት ሊሆኑ እንደሚገባ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንተነዋል ሲል ወስኗል፡፡ ጣልቃ ገብ (የአሁን አመልካች) ለአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 41846 ታህሳስ 7 ቀን 2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ለቀረበው አቤቱታ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አላገኘንበትም አቤቱታውን አያስቀርብም ሲል ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ከ36 ዓመት በላይ እያስተዳደረው እንዳለ በተረጋገጠበት ቤቱ ለተጠሪ በሌሎች ግለሰቦች የተሸጠ ነው ተብሎ እንዲያስረክብ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ.ም.በጻፈ መልስ ያከራከረውን ቤት ጥር 3 ቀን 1983 ዓ.ም. 4 ደጃፍ ቤት በሽያጭ ውል ህጋዊነቱ ተረጋግጦ ስመ ንብረቱ ወደ ተጠሪ እንዲዛወር ተወስኖ በአይከል ከተማ ማ/ቤት በኩል ተላልፎልኛል፡፡ በአመልካች በኩል የቀረቡት ሰነዶች አከራካሪ የሆነው የወፍጮ ድርጅት 1 ክፍል ቤት በአመልካች ይዞታ ስር ሆኖ ለ36 ዓመት በይዞታው አድርጎ እያከራየው የነበረ ስለመሆኑ ሰነዶቹ በእርግጠኝነት ስለማያስረዱ የበታች ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ባለመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይሁንልኝ ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ነሐሴ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው፡ በከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ክስ የቀረበበት ያከራከረው ቤት የስር ፍ/ቤት ተከሳሽ እሙሃይ ማናለብሽ ጌታሁን ከቀበሌ መስተዳድር ተከራይተው ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ ሲኖሩበት እንደነበር፣ ቤቱ በቀበሌ መስተዳድር ስር ሆኖ የቀበሌው መስተዳድር ሲያስተዳድረው የነበረ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠና የተወረሰ ቤት ስለመሆኑ በሥር የአማራ ብ/ክ/መ. ሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍ/ፍ/ቤት አረጋግጦ የአሁን ተጠሪ ቤቱን የገዛው የተወረሰ መሆኑን ሳያውቅ በመሆኑ በቅን ልቦና የቤቱ ባለሀብት ይሆናል በሚል የወሰነ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ያከራከረው ቤት ባለሀብት ነኝ ብለው የሚከራከሩት ደግሞ በግዥ ተላልፎልኛል በማለት ነው፡፡ ቤቱን ለአሁን ተጠሪ የሸጠለት አካል የቤቱ ባለሀብት አለመሆናቸውና የተወረሰ ቤት መሆኑ፣ ቤቱ በቀበሌው መስተዳድር ስር ገብቶ ቀበሌው ማስተዳደር ከጀመረና ለስር ተከሳሽ እሙሃይ ማንአለብሽ ጌታሁን ከተከራየ በኋላ የተመለሰለት ስለመሆኑ የሚያሳይ ነገር የሌለና የአሁን ተጠሪም ለሸጡለት ግለሰብ ከተመለሰ በኋላ የገዛሁት ነው ብሎ አይከራከርም፡፡ በመሆኑም ያከራከረውን ቤት የሸጠው ሰው የራሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያልሆነውን እና የባለቤትነት መብት ሳይኖረው የተወረሰ ቤት ሽጦ ተጠሪም በመንግስት የተወረሰ ቤት ገዝቶት የቤቱ ባለቤት የሚሆንበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪ ቤቱ መወረሱን ሳያውቅ በቅን ልቦና ንብረቱ ካልሆነው ሰው ላይ ገዝቶም ከሆነ ካለአግባብ የሸጡለትን ሰዎች ከመጠየቅ ውጪ በመንግስት የተወረሰ ቤት መሆኑን ሳያውቅ መግዛቱ የቤቱ ባለቤት የሚያደርገው አይደለም፡፡ በመሆኑም የአሁን ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሰ ቤት መብቱ ከሌለውና ባለቤት ካልሆነው ሰው ገዝቻለሁ በማለት ቤቱ እንዲለቀቅለት ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የሌለውና የስር ፍ/ቤትም በመንግስት የተወረሰ ቤት መሆኑን መብቱ ከሌለው ግለሰብ ላይ የአሁን ተጠሪ የገዛ መሆኑ አረጋግጠው እያለ በቅን ልቦና ባለቤት የሚሆንበት የህግ መሰረት ሳይኖር የአሁን ተጠሪ ያከራከረው ቤት ባለቤት ስለሆነ ይለቀቅለት ብለው መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁ. 41846 ታህሳስ 7/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ. ቁ. 01-17437 ግንቦት 18/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔና የአ/ብ/ክ/መ. ጭልጋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 02912 ሐምሌ 11/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡ የአሁን ተጠሪ ክስ ውድቅ በማድረግ ወስነናል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻችሉ ብለናል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች እንዲያውቁት ይድረሳቸው፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 123056

ሰኔ 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ወ/ሮ ትሁኔ አዳነ ጠበቃ አቶ መሉጌታ ዱላ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ኮንስትራክሽንና ቤቶች አስተዳደር ልማት ፅ/ቤት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው የአሁን አመልካች አ/አ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ሲሆን የክሱ ይዘት ጉለሌ ክ/ከ/ወረዳ 7 ቤ.ቁ 673 በሆነው የመንግስት መኖሪያ ቤት ውስጥ ከሟች ባለቤቴ አቶ አረጋ ካሳ ጋር ስንኖርበት ነበር፡፡ ባለቤቴ በሞት የተለየኝ በመሆኑ ተከሳሽ የቤቱን ኪራይ ውል ሊያዛውርልኝ ሲገባ ፈቃደኛ ባለመሆን ቤቱን ለቃችሁ እንድታስረክቡኝ በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኛል ተከሳሽ የቤቱን ኪራይ ውል በስሜ እንዲያዋውለኝ የተሰጠኝ ማስጠንቀቂያም ይነሳልኝ የሚል ነው፡፡፡

ተከሳሽ ለክሱ በሰጠው መልስ በመጀ/ደ/መቃወሚያ ከሳሽ ክስ በቀረበበት ቤት ላይ መብት የላትም ክስ ማቅረብ አትችልም የሚል እና በፍሬ ጉዳይ መልሱ የከሳሽ ባለቤት የቤ.ቁ 734 የሆነ ሕጋዊ የግል መኖሪያ ቤታቸውን በግልፅ ኑዛዜ ከእነ ሙሉ ዕቃው የወረሷቸው በመሆኑ በመመሪያ ቁ. 3/07 መሰረት የመንግስት ቤት ከሳሽ ማስረከብ አለባቸው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን በብይን በማለፉ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃን መርምሮ ከሳሽ ከሌሎች ወራሾች ጋር በጋራ የወረሱት የግል ቤት እንዳላቸው የቀረበው ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ በመመሪያ ቁ. 3/07 የግል ቤት ያለው ግለሰብ በመንግስት መኖሪያ ቤት ላይ የኪራይ ውል ለመዋዋል አይቻልም በማለት ደንግጓል፡፡ የቀረበውን ክስ አልተቀበልነውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሳሽ በዚህ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለአ/አ/ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ የፀና ሲሆን ከሳሽ ለሰበር ሰሚው ችሎትም አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የስር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች ከሚች ባለቤታቸው ጋር የመንግስት ቤ.ቁ 763 ተከራይተው ሲኖሩ በባለቤታቸው ሞት ምክንያት የግል ቤት ቁ. 734 ላይ ከሌሎች ወራሾች ጋር የኑዛዜ ወራሽ በመሆን ተጠቃሹን የመንግስት ቤት ሊለቁ ይገባል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ አቤቱታው እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሰረቱ የመንግስት መኖሪያ ቤት ለኪራይ የሚገባው የመኖሪያ ቤት ለሌላቸው ነዋሪዎች ነው፡፡ ማንኛውም የቀበሌ መኖሪያ ቤት የተከራየ ሰው የራሱ ቤት ከገነባ ወይም የጋራ ሕንፃ ቤት ከገዙ ወይም የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ቤት ካገኘ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ቤቱን የለቀቁ ከሆነ ቤቱን ባለበት ሁኔታ ለአስተዳደሩ ማስረከብ ያለበት ስለመሆኑ የአ/አ/ከተማ አስተዳደር በወጣው የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁ. 3/2007 አንቀፅ 42/ሀ/ ተመልክቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ለክርክር ምክንያት በሆነው መኖሪያ ቤት አመልካች ከባለቤታቸው ጋር ሲኖሩበት የነበረ መሆኑ አልተካደም አመልካች ከሌሎች ወራሾች ጋር በጋራ ሚች ባለቤታቸው ባደረጉት ኑዛዜ የግል ቤት የወረሱ መሆኑ ስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ አመልካች በክሱ መሰማት ወቅት ባለቤታቸው ቁጥሩ 734 የሆነ የግል ቤታቸውን የራሱን ድርሻ ከሌሎች 4 ልጆች ጋር እንዲወርሱ እንደተናዘዙላቸው ያመኑ መሆኑ ስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ በሰበር አቤቱታቸውም ሚች ባደረጉት ኑዛዜ የራሳቸውን ግማሽ ድርሻ አመልካች ከአራት ወራሾች ጋር በመሆን 1/5 ኛ ለአመልካች እንዲሰጥ የተናዘዙ መሆኑን እና የሚች የውርስ ንብረት ተጣርቶ ድርሻዬ አልተለየም፡፡ የውርስ ድርሻ አለኝ ማለት ለመኖር የሚያስችለኝ ቤት አለኝ ማለት አይደለም፡፡ በኑዛዜው መሰረት ገንዘብ ወይም ቤት ይድረሰኝ አልታወቀም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች ባለቤት በኑዛዜ የራሳቸውን ድርሻ እና ሙሉ የቤት ዕቃ በቀጥታ ሰጥተዋቸዋል፡፡ ቤቱ ከ10 በላይ ሰርቪስ ቤት ያለው 720 ካ.ሜ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለአራት ሰዎች የተላለፈ በመሆኑ አመልካች ከዚህ የመኖሪያ ቤት አይደርሳቸውም ብሎ ማለት የሚቻል አይደለም ስር ፍ/ቤት ይህን በማጣራት ወስኗል፡፡ በማለት ተከራክሯል፡፡

በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ አመልካች ከሌሎች ወራሾች ጋር በኑዛዜ የወረሱትን ቤት ይዘት እና ከዚህ ቤት ለአመልካች ለመኖሪያ የሚሆን ቤት የሚደርሳቸው ስለመሆኑ መጣራቱን ውሳኔው አያመለክትም፡፡ የአመልካች ባለቤት ባደረጉት ኑዛዜ አመልካች ከሌሎች 4 ወራሾች ጋር የቤ.ቁ 734 የሆነውን የግል መኖሪያ ቤት በጋራ እንዲወርሱ ያሉ ቢሆንም ቤቱ ለወራሾች በዓይነት ተካፍሎ ለአመልካች ለመኖሪያ የሚሆን ቤት በክፍፍሉ ሊደርሳቸው የሚችል መሆን አለመሆኑን ስር ፍ/ቤት ሳያጣራ አመልካች ከሌሎች ወራሾች ጋር የግል ቤት በኑዛዜ አግኝተዋል በሚል ብቻ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን መመሪያ ቁ. 3/2007 ዓላማና መንፈስ የተከተለ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ፈፅሟል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአ/አ/ከ/አስ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 04308 በቀን 10/03/08 በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ፣ የአ/አ/ከ/አ/ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 24398 በቀን 1/4/08 እና ሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ 24659 በቀን 20/5/08 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአ/አ/ከ/አስ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት የተዘጋውን መ/ቁ. 04308 የሆነውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የአመልካች ባለቤት የነበሩት ሟች አቶ አረጋ ካሳ ቤ.ቁ 734 ላይ ባደረጉት ኑዛዜ መሰረት በኑዛዜ ወራሾች መካከል ክፍፍል ቢደረግ ለአመልካች መኖሪያ ቤት የሚደርሳቸው መሆን አለመሆኑን ተገቢውን ማጣራት በማድረግ እንዲወሰን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ላስከተለው ወጭ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 111311

መጋቢት 23 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- በን/ስ/ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የግንባታ ፈቃድ ቁጥጥር ጽ/ቤት - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ ሲሳይ ተስፋዬ -አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 65367 በቀን 7/11/06 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ላይ ያቀረቡትን ይግባኝ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22512 በቀን 7/02/07 እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሠሚ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 22762 በቀን 02/06/07 ዓ.ም በማጽናታቸው መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ የሠጠው የአሁን ተጠሪ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 3 ክልል ውስጥ ከሚገኘው የቤት ቁጥር 1/17 የሆነ ቤታቸው ጋር በተያያዘ ከጐረቤት ጋር የወሰን ምልክት ይሆን ዘንድ አጥር ያጠሩበት ይዞታ መኖሩን በይዞታው ላይ ለ10 ዓመት ግብር የገበሩበት መሆኑን፣ አጥሩ በሊዝ ወደ ህጋዊ ይዞታቸው እንዲጠቃለል አመልካችን ጠይቀው ተከሳሽም ካርታ እንዲዘጋጅ በ7/10/2001 ዓ.ም የተጻፈ ደብዳቤ ለክ/ከተማ ፅፎ የነበረ ቢሆንም በ2004 ዓ.ም ካወጣው የሊዝ አዋጅ ሥርዓት ጋር በተገናኘ ጥያቄው መቆሙን፣ ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሁን አመልካች በ20/02/2006 በተፃፈ ደብዳቤ አጥሩ በ3 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲፈርስ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሁከት የፈጠረብኝ በመሆኑ ሁከት እንዲነሳ ይወሰንልኝ በማለት በ20/03/2006 ዓ.ም ያቀረቡትን ክስ መነሻ በማድረግ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ ክርክር ያስነሳው አጥር ተጠሪ አስፋፍተው የያዙት ትርፍ ቦታ ላይ የሚገኝ መሆኑን፣ አጥሩን ለመስራት የግንባታ ፈቃድ አለማውጣታቸውን ማስጠንቀቂያው የተጣለብኝን ኃላፊነት የምወጣበት እንጂ ሁከት አለመሆኑን በመገለጽ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ ከክ/ከተማው የመጡት ምላሾች የአሁን ተጠሪ ያጠሩት ቦታ መንገድ መሆኑንና መንገድ ሆኖ አጐራባቾች ሲገለገሉበት ቆይተው በመሀል የተጠሪ መሆኑን የሚያስረዱ አይደሉም፡፡ መንገድ በከሳሽ ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም የአሁን አመልካች በሌላ አካሄድ መጠየቅ ከሚችል በቀር በማስጠንቀቂያ መጠየቅ አይችልም፡፡ የከተማ ልማት ጥናቱ /LDP/ ወደ ተግባር ያልተሸጋገረ በመሆኑ እሱን መሠረት በማድረግ ለባለይዞታው ሳይነግሩ ይዞታው እንዲፈርስ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፡፡ ይህም ሁከት በመሆኑ ይወገድ በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡ ይህንኑ ውሳኔ የከተማዋ አስተደደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመደበኛ ይግባኝ እና በሰበር ችሎት ተመልክቶ አፅንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአቤቱታው ይዘትም ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት መመስረት የነበረበትን ጭብጥ ሳይመሰርት፣ የአሁን ተጠሪ በግልፅ አከራካሪው ይዞታ ወደ ይዞታቸው እንዲጠቃለልላቸው የጠየቁ መሆኑን በማለፉ ከከተማው የአስተዳደር አካላት የመጣውን ምላሽ ያለአግባብ በመረዳት፣ በአሁን አመልካች የቀረቡትን ምስክሮች ሳይሰማ በዝምታ በማለፉ፣ በስራ ላይ የዋለውን የኤልዲ.ፒ ጥናት ስራ ላይ ያልዋለ ነው በማለት የመንግስት መሬት አያያዝ አዋጅና መመሪያዎችን ሳይመረምር ወደ ጐን በመተው የአሁን አመልካች ህጐችን ለማስከበር የሠጠውን ግዴታ የሁከት ተግባር ነው በማለት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ እንዲታረም የጠየቁ መሆኑን ያሳያል፡፡

ተጠሪም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ደርሷቸው በሰጡት መልስ ክርክር ባስነሳው ይዞታ መሬት ይዞታን አስመልክቶ በወጡ ህጐች መብት ያገኙ መሆናቸውን የስር ፍ/ቤት ከከተማው አስተዳደር አካላት የመጡትን ምላሾች በትክክል ተረድቶ የተገበረ መሆኑንና የኤል.ዲ ፒ ጥናት ከ20 ዓመት በፊት ለተገነባ አጥር ተመልሶ ተግባራዊ መሆን የሌለበት መሆኑን በመግለፅ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ፀንቶ አመልካች የተጠሪን ወጪና ኪሳራ እንዲሸፍን ይታዘዝልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ችሎት ዕልባት ማግኘት ያለበት የአሁን አመልካች ድርጊት የሁከት ተግባር ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሁከት ተፈጥሮብኛል ይወገድልኝ የሚል ተከራካሪ ወገን ሁከት ተፈጠረበት በተባለው ንብረት ላይ የተሻለ መብት ያለው መሆኑን የመለየት ግዴታ ያለበት መሆኑን ከፍ/ህ/ቁ 1149 ድንጋጌ መረዳት እንችላለን፡፡

በዚህ በያዝነው ጉዳይ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ አከራካሪ የሆነው አጥር የሚገኝበት ቦታ በሊዝ ሥሪት መሠረትም ወደ ይዞታቸው እንዲገባላቸው የጠየቁ መሆኑን፣ ቦታውን አጥር በማጠር የያዙት በራሳቸው የወሰን ምልክት ይሆነኛል በማለት እንደሆነ ነው፡፡

በመሠረቱ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ በህጋዊነት ከያዘው ይዞታ ጐን ያለን የከተማ ቦታ አስፋፍቶ መከለልና መጠቀምም ሆነ በሊዝ አዋጁ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ የከተማ ቦታ መያዝ እንደማይችል የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 5/2/ እና /4/ ተቀምጧል፡፡

የአሁን ተጠሪ አከራካሪ የሆነውን ቦታ በሊዝ ወደ ይዞታቸው ለመቀላቀል አቅርበውት የነበረው ጥያቄም ተቀባይነት አግኝቶ ያልተፈፀመ መሆኑን ገልፀው ቦታውን የያዝኩት ከሊዝ አዋጁ መውጣት በፊት ሲሆን ነባር ይዞታን ወደ ሊዝ ስሪት በመቀየር ከቀድሞ ይዞታቸው ጋር እንዲካተትላቸው እየጠየቁ በሂደት ላይ ያለ ሁኔታ መኖሩን፣ የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡

የሚመለከታቸው የከተማዋ አስተዳደር አካላትም የሰጡት መልስ እንደሚያስረዳው በተጠሪ ካርታ ላይ በተጠናው የኤል.ዲ.ፒ ጥናት መሠረት በቦታው ላይ መንገድ ያለ መሆኑን ይገልጻል፡፡ የከተማ ቦታ አሰጣጥ ስርዓት ደግሞ የህዝቡንና የከተሞችን ጥቅም በቀዳሚነት በማስከበር የከተማ ልማትን በማፋጠንና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የዜጐችን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የሀገሪቱን ልማት ቀጣይነት የሚያረጋጋጥ መሆን እንዳለበት የሊዝ አዋጁ አንቀጽ 4/4/ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በቦታው ላይ የሊዝ ጥያቄ አቅርቤ በመጠየቅ ላይ እገኛለሁ ቢሉ እንኳን ቦታው የከተማዋ ልማት እንቅስቃሴ አካል የሆነው መንገድ የሚሠራበት መሆኑን መሠረት በማድረግ አመልካች ለተጠሪ አጥሩን እንዲያፈርሱ የሰጠው ትዕዛዝ በህግ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የወሰደው እርምጃ ሆኖ እያለ በስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ አጥሩን እንዲያነሱ የፃፈው ደብዳቤ የአመልካችን ድርጊት የሁከት ተግባር ነው ያለው ያለአግባብ ስለሆነ ውሳኔውን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህ መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05367 በቀን 7/11/06 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማዋ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22512 በቀን 7/02/07 ዓ.ም እና በከተማዋ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 22762 በቀን 02/06/07 ዓ.ም ያፀናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ከህጋዊ ይዞታ ውጭ ያለፈቃድ ያጠረውን አጥር እንዲያነሳ አመልካች የፃፈው ደብዳቤ የሁከት ተግባር አይደለም፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 107777

መጋቢት 28/2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- የሱሉልታ ከተማ አስተዳደር -አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ደባልቄ ደምሴ -ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች የሱሉልታ ከተማ አስተዳደር ታህሳስ 10/2007 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) በመሬቱ ላይ የነበረውን የከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ንብረት በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(5 እና 6) መሰረት ያለምንም ክፍያ ሊወሰድ እንደሚችል ደንግጎ እያለ የስር ፍ/ቤት ንብረቱ ይመለስ ብሎ መወሰኑ ካለአግባብ ነው፡፡ ከሳሽ የንብረቶቹን ትክክለኛ ግምትና አይነት የሚያስረዳ ማስረጃ ባልቀረበበት ንብረቱ ይመለስ መባሉ አግባብነት የለውም፡፡ ተከሳሽ በጽሁፍ በሰጠው ማስጠንቀቅያ ከሳሽን ያሳወቀው በመሆኑ ለንብረቱ መጥፋትና መበላሸት ሃለፊነት የለበትም፡፡ ተከሳሽ ንብረቶቹን ለማፍረስ ለተጠቀመው የሰው ሀይል ወጪ ታሳቢ ሳይደረግ የትኞቹ ንብረቶች መመለስ እንዳለባቸው ሳይለይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) አቶ ደባልቄ ደምሴ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍ/ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ የሱሉልታ ከተማ አስተዳደር የከሳሽ ጋራዥ የሆነውን በሱሉልታ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኝ ስፋቱ 1500 ካ/ሜ በካርታ ቁጥር 05-ስ-01/90 አዋሳኙን ጠቅሶ የካቲት 7/2001 ዓ.ም.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስላፈረሰብኝ በሁከት ከስሼ ሁከት የለም ተብሎ ቢወሰንም አፍርሶ የወሰደብኝን ንብረት ግምት ለመጠየቅ ስለምችል ግርግዳው በቆርቆሮ እና በእንጨት የተሰራ 2 ቤቶች፣ የተከልኳቸው ባህር ዛፎች፣ 120 ቢያጆ ድንጋይ፣ በቆርቆሮ የተሰራ አጥር፣ የአየር ኮምፕሬሰር ከነ ዕቃው፣ አንድ የብረት መበየጃ፣ አንድ ግራይንደር፣ ትራንስፎርመር ጨምሮ የተለያዩ መፍቻዎች ሁለት የብረት ሳጥኖች በአጠቃላይ ብር 1,330,100 እንዲከፍለኝ ሲል ከሷል፡፡ ተከሳሽም በሰጠው መልስ ከሳሽ በተጠቀሰው መሬት ላይ ለ3 ዓመት ከ1990 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም. ድረስ ለመጠቀም ከተከሳሽ ላይ በሊዝ ውል ወስዶ እያለ ለ7 ዓመት ለመልቀቅ ፍቃደኛ ስላልሆነ በአዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 25(5 እና 6) እና አንቀጽ 16(1እና2) እንዲሁም በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(5 እና 8) መሰረት ንብረቱን የማንሳት ስልጣን ስላለን ቦታውን ለህዝብ አገልግሎት እንዲውል ማድረጋችን ህጋዊ በመሆኑ ከሳሽ የጠየቀውን ንብረት ግምት የመክፈል ግዴታ የለብንም፡፡ ሃላፊነት አለባቸው ቢባል እንኳ ከመሬቱ ላይ የተወረሰው ንብረት ከጭቃ እና እንጨት የተሰራ 2 ቤት እና 2 ቢያጆ ድንጋይ በአጠቃላይ ግምቱ 50000 ብር የማይበልጥ ሆኖ ሳለ በከሳሽ የቀረበው ግምት የተጋነነ በመሆኑ ውድቅ ይሁንልኝ ብሏል፡፡ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ፌንፊኔ ዙርያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 09981 አከራክሮ ነሐሴ 15/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከሳሽ ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት ከ1990 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም. ድረስ ተከራይቶ የክራዩ ዘመን ያበቃ ቢሆንም ለ7 ዓመት ይዞ ለመልቀቅ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ተከሳሽ ከመሬቱ ላይ ንብረቱን ስላነሳ በሁከት ከሶት ሁከት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡ በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(5) መሰረት የኪራይ ውል ከተጠናቀቀ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ንብረቱን ካላነሳ የሚመለከተው አካል መሬቱን በላዩ ላይ ካለው ንብረት ጋር ካለክፍያ መውሰድ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 25(6) በመደንገጉ የከሳሽ የሊዝ ውል ኪራይ በ1993 ዓ.ም. ካለቀ በኋላ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ንብረቱን አንስቶ መሬቱን ማስረከብ ሲገባው እስከ 7 ዓመት ይዞ በመቆየቱ ተከሳሽ ያለ አንዳች ክፍያ ንብረቱን አንስቶ መሬቱን መውሰድ ስለሚችል ተከሳሽ ለተጠየቀው ክፍያ ሃላፊነት የለበትም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 170402 ታህሳስ 1/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ለቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጉድለት ያለበት ሆኖ አልተገኘም ሲል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁን ተጠሪ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 183036 አከራክሮ መስከረም 19/2007 በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ከሳሽ ከ1990 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም. በሊዝ ኪራይ የያዘውን መሬት ጊዜው ተጠናቆ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውሉ ዘመን የሚታደስ ካልሆነ ንብረቱን አንስቶ ይዞታውን ለተከሳሽ መመለስ እንደሚገባው አያከራክርም፡፡ ከሳሽ ውሉ ሳይታደስ እስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ መቆየቱ ታውቋል ተከሳሽ ታህሳስ 3/2001 ዓ.ም. እስከ የካቲት 26/2001 ዓ.ም. ድረስ ለከሳሽ የማስጠንቀቅያ ደብዳቤ መፃፉ ተረጋግጧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 15(5) እና 16(1 እና 2) እንዲሁም በመሬት ሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25 (5 እና 6) ከመሬቱ ላይ የነበረውን ንብረት ከሳሽ ለማንሳት ፍቃደኛ ባለመሆኑና ተከሳሽ በማንሳቱ ካሳ ለመክፈል የሚገደድ አይደለም፡፡ ይሁንና ተከሳሽ በመሬቱ ላይ የነበረውን ንብረት ለመውሰድ የሚፈቅድለት ህግ ባለመኖሩ የወሰደውን ንብረት ለአመልካች መመለስ አለበት ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አሻሽሎ ተከሳሽ የወሰደውን ንብረት ይመልስ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካች ለተጠሪ በኪራይ የሰጠውን ቦታ የኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኋላ ተጠሪ መሬቱን ለአመልካች ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ አመልካች በቦታው ላይ የነበረውን ቤት አፍርሶ መውሰዱ አያስጠይቀውም በማለት በክልሉ የስር ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሽሮ አመልካች የወሰደውን ንብረት ይመልስ በማለት የሰጠውን ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 272/1994 አንቀጽ 25(5) ድንጋጌ አንጻር ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሚያዚያ 15/2007 ዓ.ም. በተጻፈ መልስ የአመልካች አቤቱታ በተሻረ አዋጅ ቁጥር 272/94 ን በመጥቀስ ከአዋጅ ቁጥር 721/2004 ጋር በመጻረር የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ይሁንልኝ፡፡ አመልካች ከአዋጁ ድንጋጌ ውጪ ንብረቴን የወሰደብኝ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ይህንኑ በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ ተገቢና ቅር የማያሰኝ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ግንቦት 9/2007 ዓ.ም. በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው፡ የአሁን ተጠሪ የ3 ዓመት የሊዝ ኪራይ ውል ማብቃቱ እና በቦታው ላይ ያከናወነውን ግንባታ በህግ በተቀመጠው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያላነሳና ከዚያም በላይ እስከ 7 ዓመት የቆየ መሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ የአሁን አመልካች በአዋጅ ቁጥር 721/2004 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ቦታውን ከነንብረቱ ያለምንም ክፍያ ሊወስድ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(6) ስር ተደንግጓል፡፡ የአሁን ተጠሪ በአዋጁ አንቀጽ 25(5) መሰረት ቦታውን የሊዝ ጊዜው እንዳለቀ በአንድ ዓመት ውስጥ ንብረቱን አንስቶ ቦታውን ለሚመለከተው አካል ያላስረከበ መሆኑ በመረጋገጡ አመልካች በቦታው ላይ የነበሩትን ግንባታ አፍርሶ መውሰዱ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(6) መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሃላፊነት የሚያስከትልበት አይደለም፡፡ በአዋጁ ቁ. 721/2004 አንቀጽ 25(5 እና 6) መሰረት ተጠሪ በሊዝ የያዘውን መሬት ጊዜው አልቆና ባለመታደሱ በቦታው ላይ ያሰፈረውን ንብረት አንስቶ ቦታውን ለሚመለከተው አካል ባለማስረከቡ አመልካች በቦታው ላይ የሰፈረውን ንብረት አንስቶ መውሰድ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ ይሁንና በቦታው ላይ የሰፈረ ንብረት ሲባል ግን ቦታውን ለተፈለገው ሥራ ጉዳይ እንዳያስችግሩ ምቹ ለማድረግ በቦታው ላይ የተሰሩ ግንባታዎችንና ከዚሁ ጋር የሚያያዙ የመሳሰሉትን ንብረቶች ለማንሳት እንጂ በቀላሉ የሚነሱ የሥራ መገልገያዎችን ጨምሮ የሚወረስ መሆኑን አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች በቦታው ላይ በተጠሪ የተገነቡ ግንባታዎች ቤቶች፣ ድንጋዮች፣ ባህር ዛፎች እና አጥር አንስቶ መውሰዱ በአዋጁ መሰረት ሃላፊነት ያለበት አይደለም፡፡ ከዚህ ውጪ ያሉትን ግን ተጠሪ በአመልካች ተወስደውብኛል ሲል የከሰሰውና አመልካች በመልሱ መውሰዱን ያላመነውን የሥራ መገልገያ ንብረቶችን በተመለከተ ለመውረስ በአዋጁ የሚሸፈን ባለመሆኑ ተጣርቶ ለተጠሪ ሊመለስ የሚገባ ነው፡፡ የስር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ንብረቱን ከቦታው ላይ ማንሳቱ ተገቢነቱን ተቀብሎ ንብረቱን ግን ለመውረስ የሚፈቅድለት ህግ የለም የወሰደውን ንብረት ይመልስ ሲል መወሰኑ በአዋጁ በግልጽ ተቀምጦ ባለና የሚመለሱ ንብረቶችንም ሳይለይ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ነው፡፡ በአዋጅ ቁ. 721/2004 አንቀጽ 25(6) አመልካች ከቦታው ላይ የሰፈሩ ንብረቶችን አንስቶ መውሰድ እንደሚችል ደንግጎ እያለ ተጠሪ ተወስደውብኛል ሲል የከሰሰውና የአሁን አመልካችም ወስጃለሁ ያላላቸውን ንብረት በማስረጃ ሳይጣራና ሣይለይ በደፈናው አመልካች የወሰደውን ንብረት ይመልስ ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁ. 193036 መስከረም 19/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ. ቁ. 170402 ታህሳስ 1/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ በፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ. ቁ. 09981 ነሐሴ 13/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች(ተከሳሽ) ተወስደውብኛል ሲል በክሱ እንዲመለሱለት ከጠየቀው ንብረቶች ውስጥ ቤቶቹን፣ ድንጋዮች፣ ባህርዛፎች እና አጥርን ሳይጨምር የተጠሪ ስራ መገልገያ ንብረቶች የማይወረሱ ያልናቸው እንደ የአየር ኮምፕሬሰር፣ የብረት መበየጃ፣ ግራይንደር ትራንስፎርመርን ጨምሮ፣ የተለያዩ መፍቻዎች እና የብረት ሳጥኖች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላቸውን እና በአመልካች መወሰዳቸው ያልታመኑ በመሆኑ በአመልካች መወሰድ አለመወሰዳቸው በማስረጃ በማጣራት ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻችሉ ብለናል፡፡
4. ለኦ/ብ/ክ/መ/ ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲከወን የዚህ ውሳኔ ቅጂ ይድረሰው ለሌሎች የስር ፍ/ቤቶች ደግሞ እንዲያውቁት ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 106436

ሚያዚያ 25 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች - አቶ ተክኤ ፀጋይ ተስፋይ -ቀርበዋል

ተጠሪ - ወ/ሮ ንግስቲ ገ/መድህን - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች አቶ ተክኤ ፀጋይ ተስፋይ ጥቅምት 11/2007 ዓ/ም. በተጻፈ አቤቱታ ከተጠሪ ጋር ያደረግነው የመሬት ይዞታ ልውጫ በፍላጎታችን ተስማምተን ያደረግነውና ለ3 ዓመት ቆይቶ የሚፈርስበት ምክንያት ሳይኖር መሬቱን ይመላለሱ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ የመሬት ለውጥ ውል መኖሩን እያመነች በሥር ፍ/ቤት ወደነበሩበት ይመለሱ መባሉ አለአግባብ በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ወ/ሮ ንግስቲ ገ/መድህን በትግራይ ብ/ክ/መንግስት በዕምብላ ወረዳ አስተዳደር በደብረአባይ ቀበሌ መሬት አስተዳደር ዳኝነት አካል ባቀረቡት ክስ ከሳሽና ተከሳሽ አቶ ተክኤ ፀጋይ መሬት ተለዋውጠን በኔ የመሬት ይዞታ ላይ ቤት ሰርቶበት የራሱን ግን ያላስረከበኝ በመሆኑ መሬቴን ይመልስልኝ ስትል ከሳለች ተከሳሽም በሰጠው መልስ መሬት ተለዋውጠናል ከተለዋወጥን ከ3 ዓመት በኋላ እና ቤት ሰርቼበት ካለማሁ በኋላ ይመልስልኝ ማለቷ ተገቢ ባለመሆኑ ክሷ ውድቅ ይሁንልኝ ብሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የደብረ አባይ ቀበሌ መሬት አስተዳደር የዳኝነት አካል አከራክሮ ጥር 14/2006 ዓ/ም. በሰጠው ውሳኔ ከሳሽና ተከሳሽ መሬት እንዲለዋወጡ የቀበሌው የመሬት አስተዳደር ድጋፍ ሰጥታቸው እና በመሬት አስተዳደር ዴስክ እንድትጨርሱ ተብሎ የነበረ ቢሆንም ሳይጨርሱ ቀርተዋል፡፡ የከሳሽ መሬት በተከሳሽ እጅ ያለው ወሰኑን በመጥቀስ ለከሳሽ ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡ ተከሳሽ ለፅምብላ ወረዳ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የፅምብላ ወረዳ ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 04232/06 አከራክሮ ሚያዚያ 15/2006 ዓ/ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የግራ ቀኙ ምስክር ተሰምቶ ከሳሽና ተከሳሽ የተለዋወጡት መሬት ተከሳሽ ሁለት ቤት የሰራበት ቢሆንም የመሬት ለውጡ በሚመለከተው አካል አልፀደቀም፡፡ በመሆኑም ልውጫው ህጋዊነት የሌለው በመሆኑ ወደየራሳቸው ይመለሱ ተከሳሽ የሰራውን ቤት በተመለከተ የቤቱን ዋጋ ተስማምተው ለተከሳሽ ይከፈለው፡፡ ካልሆነ ¼(አንድ አራተኛ) ከሳሽ ለተከሳሽ ትክፈለው ሲል ወስኗል፡፡ተከሳሽ ለሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 18282/06 አከራክሮ ግንቦት 29/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ መሬት መለዋወጣቸውን አይካካዱም እየተከራከሩ ያለው የመሬት ልውጫው በሚመለከተው አካል አልፀደቀም በሚል ነው፡፡ የመሬት መለዋወጡ ከህግ ጋር እስካልተቃረነ ድረስ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህም በላይ ውል ይፍረስ ቢባል እንኳ ወደ ነበሩበት መመለስ የሚችሉ አይደለም ተከሳሽ በመሬቱ ላይ በብር 70000 የሚገመት ቤት ሰርቶበታል፡፡ በመሆኑም የተለዋወጡትን መሬት ይዘው ይቆዩ ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ለትግራይ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርባ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 68037 አከራክሮ ጳጉሜ 3/2006 ዓ/ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ በተከራካሪዎቹ መሀከል የመሬት ልውጫ የተባለው ህጉ በሚያዘው በአዋጅ ቁ. 239/06 እና ደንብ ቁ. 48/2000 መሰረት በውልና ማስረጃ ፀድቆ የወረዳው የመሬት ዴስክ አውቆ በቅፅ ተሞልቶ የተለዋወጡ ካልሆነ ህጋዊ ልውጫ አይደለም፡፡ ይህ ሆኖ እያለ ከፍ/ፍ/ቤት የወረዳውን ውሳኔ እና የቀበሌውን ውሳኔ መሻሩ ስህተት ነው በማለት የከፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ የወረዳውንና የቀበሌውን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ግራ ቀኙ ይዞታቸውን ተለዋውጠው ከቆዩ በኋላ ልውውጡ በሚመለከተው አካል አልፀደቀም በሚል ብቻ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ የካቲት 25/2007 ዓ/ም. በተፃፈ መልስ በኔና አመልካች ተደርጎ የነበረውን የመሬት ለውጥ የመሬት ውል አፅዳቂው አካል አመልካች የመሬት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሌለው ስለሆነ አላጸደቀውም፡፡ በመሬቱ ላይ የሰራቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስራዎች እየተቃወምኩት የሰራው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር የሚያሰኝ ባለመሆኑ ይጽናልኝ ብለዋል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ባለመቅረቡ ታልፏል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው፡ በትግራይ ብ/ክ/መ. የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/06 የተመለከተውን አሟልቶ የመሬት ይዞታ መለዋወጥ አልተከለከለም፡፡ ይሁንና አመልካች ከተጠሪ ጋር ተለዋወጥን የሚሉት የመሬት ይዞታ በአዋጅ ቁ. 239/06 መሰረት በውልና ማስረጃ ጸድቆ የወረዳው የመሬት ዴስክ ያልመዘገበው በመሆኑ የክልሉ የመሬት አስተዳደርና እና አጠቃቀም አዋጅና ደንቡ በሚደነግገው መሰረት ያላሟላ በመሆኑ የመሬት ይዞታ ልውጫ በአመልካችና ተጠሪ መሀከል ተፈጽሟል ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የትግራይ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ. ቁጥር 68037 ጳጉሜ 3/2006 ዓ/ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የዕምብላ ወረዳ ፍ/ቤት በመ. ቁጥር 04232/06 ሚያዚያ 15/2006 ዓ/ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻችሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ መጋቢት 23/2007 ዓ/ም. በዋለው ችሎት የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 119557

ሐምሌ 19 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲ.ር.ጋ.ጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች ፡- አቶ ማናለው ተካ - ተወካይ ታደ ተካ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እቴነሽ ተካ - ተወካይ አቶ ተስፋው ከቤ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳዩ የተጀመረው በምስራቅ ጎጃም ዞን እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ወላጅ አባቴ አቶ ተካ አንተነህ በስጦታ ያስተላለፉልኝን መሬት አመልካች በጉልበት በመያዝ እየተጠቀመበት ስለሚገኝ እንዲለቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የሰጠው መልስ ክስ የቀረበበት መሬት ላይ ለተጠሪ የስጦታ አስተላላፊ ከሆኑት ከአቶ ተካ አንተነህ ጋር አስቀድሞ የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የእርቅ ስምምነት ያለቀ በመሆኑ የተጠሪ ስጦታ አድራጊ በስጦታ ለማስተላለፍ የማይችሉ ከመሆኑም በላይ መሬቱ ለአመልካች እናት ጭምር የተሰጠ ስለሆነ የተጠሪ ክስ የአመልካችን መብት የሚነካ ስለሆነ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አቶ ተካ አንተነህ አስቀድሞ ያደረጉት የእርቅ ስምምነት መሬቱን በስጦታ ከማስተላለፍ የሚከለክል ባለመሆኑ አመልካች መሬቱን ለተጠሪ ሊለቅ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም አቶ ተካ አንተነህ መሬቱን በተመለከተ አስቀድመው በእርቅ የጨረሱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነ መሬቱን ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት የላቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

ተጠሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲሁም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው የክልሉ ሰበር ችሎት አባ ተካ አንተነህና አመልካች ያደረጉትን ስምምነት ይዘት የአባ ተካ አንተነህ የይዞታ መሬት አመልካች ይዞ እያረሰ ሰብል እንዲሰጥ የተስማሙበት እንጂ የአባ ተካን መሬት ወደ አመልካች የማስተላለፍ ህጋዊ ውጤት ያለው ስምምነት አይደለም፤ የክፍሉ መሬት አስተዳዳርም አስቀድሞ የአባ ተካ መሬት ለአመልካች ያለማስተላለፉን በመገንዘብ ለተጠሪ የተሰጠውን ስጦታ መዝግቦታል በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 30 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በክልሉ ሰበር ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- በአባ ተካ አንተነህ እና በአመልካች መካከል የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገው እርቅና በፍርድ ቤት የፀደቀው ስምምነት ባለበት ሁኔታ እንዲሁም በዚሁ ስምምነት መሰረት እንዲፈፀም የአፈፃፀም ትእዛዝ ባለበት ሁኔታ ያደረጉት ስምምነት መሬቱን ወደ አመልካች የማስተላለፍ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይህ ውሳኔ ተሽሮ የካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገው ስምምነት እንዲፈፀም ለተጠሪ የተደረገው ስጦታ እንዲሻር በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት የካቲት 2 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች ጥያቄ ለክርክር መነሻ የሆነው መሬት በእርቅ ስምምነት ያገኘሁት ለተጠሪ ልለቅ አይገባም የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ በስጦታ ያገኘሁትና በአግባቡ በማስረጃ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ ሊፀና ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ለክርክሩ መነሻ የሆነው የመሬት ይዞታ አመልካች ከስጦታ አድራጊ አባ ተካ የእርቅ ስምምነት የነበራቸው መሆኑ እና ተጠሪም በስጦታ የተሰጣቸው መሆኑ አከራካሪ ነጥብ አይደለም፡፡ የሚያከራክረው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአመልካችና በአባ ተካ መካከል የተደረገው የእርቅ ስምምነት ይዘት ላይ ነው፡፡ ስለሆነም የእርቁ ስምምነት አመጣጥ መመርመሩ ተገቢ ነው የሚሆነው፡፡

አመልካች ለአባ ተካ የመሬት ይዞታ እያረሰ በአላባ እንዲጠቀም በነበራቸው ስምምነት አለመግባባት በመፈጠሩ ጉዳያቸው ወደ ፍርድ ቤት ደርሶ ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ባደረጉት የእርቅ ስምምነት ሊቋጭ እንደቻለ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ አባ ተካ የአማራ/ብ/ክ/መ/ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ አንቀጽ 15/1/፣17 ማንኛውም ሰው የይዞታ መብቱን በስጦታ ለማስተላለፍ በሚፈቅደው መሰረት በሚመለከተው አካል ቀርበው ለአሁን ተጠሪ በስጦታ መስጠታቸውን በክፍሉ ተመዝግቦ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑ የፍሬ ነገር የማጣራትና የማስረጃ የመመዘን ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋጋጠ ነው፡፡

የእርቁ ስምምነት ይዘት አባ ተካ የመሬት ባለይዞታ በመሆን አመልካች ደግሞ በጉልበቱ እያረሰ የአላባ የመጠቀም መብት የሚሰጥ ነው፡፡ ይህ የእርቅ ስምምነት ለአባ ተካ የመሬት ይዞታቸው በስጦታ ለፈለጉት ሰው የማስተላለፍ መብታቸውን የሚገድብ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ስምምነቱ አመልካች የአባ ተካ ይዞታ እስካለ ድረስ የአላባ የመጠቀም መብት የሰጠ ነው፡፡ ይዞታው ለሌላ ሰው ከተላለፈ ተጠሪ በአላባ የመጠቀም መብቱም የማቋረጥ ውጤት ነው ያለው፡፡ አመልካች ሌላ መከራከሪያ ነጥብ አባ ተካ ለተጠሪ ያደረጉት ስጦታ የእናቴ ይዞታ ጭምር ነው በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የመሬት ይዞታው ለአባ ተካ ተለክቶ የተሰጣቸው መሆኑን ባደረጉት ማጣራት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ችሎትም በፍሬ ነገር የማጣራትና የመመዘን ስልጣን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80/3/ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ስልጣን ያልተሰጠው ስለሆነ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲጠቃለል በተያዘው ጉዳይ ላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአ/ብ/ክ/መ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.03-40156 ጥቅምት 9 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0116362 ታህሳስ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.37155 ሚያዝያ 2 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ በመሻር የእነብሴ ሳርምድር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.01-012499 ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ከዚህ ፍርድ ቤት የእነብሴ ሳርምድር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0112499 የተጀመረው አፈፃፀም ተላልፎ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስተዋል። የሚመለከው አካል ይፃፍ።
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ።

መዝገብ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 118191

መስከረም 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነአ ቁጣታ

ክፍለፅዮን ማሞ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- አቶ ድጋፌ ክፍሌ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ጎሣ ገድል - የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ስጦታ ውል ክርክር የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መ/ሰሜን ሸዋ ዞን የምንጃር ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በ22/03/2007 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 011010715/07 ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- አመልካች ካላቸው የመሬት ይዞታ ለተጠሪ አዋሳኙ በምስራቅ ወንድአፈራሽ ፣በምዕራብ ገደል፣ በደቡብ ጎደና በሰሜን ወንዝ የሚያዋስነው 3 ጥማድ መሬት በሽተኛ በመሆናቸው ተጠሪ መሬቱን፣ በመሬቱ ላይ ያለ ዛፍ እና ድንጋዮች እንዲቆጠርላቸው የመሬት ግብር በየዓመቱ ተከታትሎ እንዲገብር በቀን 18/07/2005 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል አድርገው በስጦታ ይዞታ መሬቱን አስተላልፈውለት ተጠሪው የመሬት ግብር እንኳ ሳይገብር ለከፍተኛ ጉዳት መዳረጉን፣ በመሬቱ ላይ ያሉ ዛፎችም ያልተንከባከባቸው የተቆራረጡ እንዲሁም የመሬቱ አጥርም መፍረሱን፤ አመልካችን ሊጠይቃቸውና ሊያስታምማቸው አለመቻሉን በመግለጽ የመሬት ስጦታ ውሉ ፈራሽ እንዲሆንላቸውና ወደነበሩበት እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጠው መልስም ከአመልካች ጋር የስጋ ዝምድና እንዳላቸው አመልካችን ለረጅም ዓመታት ያለጥቅም እያረሰ ምርት ሲሰጣቸው እንደነበር ውለታውም ማንም ሳያስገድዳቸው በጤናማ አዕምሮ በራሳቸው ፍላጎት የአካባቢ ሰዎች ሰብስበው በ03/07/2005 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል መስጠታቸው፤ የስጦታ ውሉ በሚመለከተው አካል ከመመዝገቡ በፊት ለአካለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጠን ያልደረሱ ሕፃናት ወይም የቤተሰብ አባል እንዳሉ፣ መሬቱ ለ3ኛ ወገን ተላልፎ ወይም በኮንትራት የተሰጠ ከሆነ ከክትቻ ቀበሌ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እንዲጣራ ተደርጎ መጋቢት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በወረዳው የመሬት አስተዳደር አጠቃቀም ፀድቆ ማስረጃ እንደተሰጠው የስጦታ ውሉ ከህግም ከሞራልም ተቃራኒ አለመሆኑን ስጦታው በሚመለከተው አካል ፊት የተደረገና በስጦታ በተላለፈለት መሬት በስሙ መገበሩን በይዞታ መ/ቁ. A/I/83/17/850 በሆነ ቋሚ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንደወጣለት በመግለፅ አመልካች ያቀረቡት የስጦታ ውል ይፍረስልኝ ክስ ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክራል፡፡

የሥር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ የሆነው የስጦታ ውል በማስቀረብ ከመረመረ በኋላ ውሉ የመሬት አዋጅ በሚያዘው አግባብ ስለመደረጉ፤ ተጠሪ በስጦታ ባገኘው መሬት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማውጣቱን፣ አመልካች ውሉን ለማፍረስ እንደመከራከሪያ ያቀረቡት ምክንያት በማስረጃ ያልተደገፈ፣ ውሉ በክልሉ የመሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 17 አግባብ ተደርጎ በሚመለከተው አካል የፀደቀ እና ሕጋዊ እውቅና ያለው በመሆኑ የሚፈርስበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የአ/ብ/ክ/መ/ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/98 ሆነ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣው የደንብ ቁጥር 51/99 የእርሻ መሬት ስጦታ የሚፈርስበት ምክንያት ያልደነገገ በመሆኑ አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2436 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ መመልከቱ ተገቢ እንደሆነ፣ በእነዚህ ድንጋጌዎች የስጦታ ውል የሚጸናው ስጦታ አድራጊው ወዶና ፈቅዶ ስጦታ በአደረገበትና የስጦታ ተቀባዩም ውሉን በተቀበለበት ቅጽበት መሆኑን የፍ/ህ/ቁ. 2436(1) በግልጽ የሚያስነብብ ስለመሆኑ ውሉ ሊፈርስ የሚችለው ስጦታ አድራጊው ስጦታው ያደረገው ጤነኛ ባልሆነ አእምሮ ያደረገው መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ወይም ስጦታው የተደረገው በህግ ከተፈቀደው ውጭ የሆነ እንደሆነ ወይም ስጦታ የተደረገበት ነገር ግብረገብ ካልሆነ ወይም ስጦታ አድራጊው የመንፈስ መጫን ደርሶበት እንደሆነ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2437፣ 2438፣ 2439 ድንጋጌዎች እንደሚያመለክቱ፣ በተያዘው ጉዳይ እነዚህ ተግባራት መከናወናቸው አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም ስጦታ አድራጊው በጤነኛ አዕምሯቸው ስጦታው ያደረጉ መሆኑን ስልጣን በአለው አካል ህጋዊነት ተረጋግጦ የስጦታ ውሉ በጽሑፍ ከተደረገ በኋላ የጸደቀ የተመዘገበ ስለመሆኑ፣ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በአንድ ግቢ ጋር የሚኖሩ መሆኑንና የአመልካች መሬት በነፃ እያረሰ የቆየ መሆኑን የምንጃር ሸንኮራ ወረዳ አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር አጣርቶ ስጦታውን ያጸደቀ ከመሆኑም በላይ በስር ፍ/ቤትም ይህንኑ በሰው ማስረጃ የአረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የስጦታ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በማጽናት ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም የአሁኑ ተጠሪ አመልካችን እየጦረና እየተንከባከበ ስለመሆኑ አላስረዳም፣ የመሬት ይዞታ ስጦታ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መታየት የለበትም፤ አመልካች አቅመ ደካማና በሽተኛ በመሆናቸው ውሉ ፈርሶ ወደነበሩበት እንዲመለሱ መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስም አመልካች ካላቸው 20 ጥማድ መሬቱ 3 ብቻ እንደሰጡት፤ ስጦታው ተጠሪ ለረጅም ጊዜ ባበረከተው አገልግሎት የተሰጠው ስለመሆኑ ውሉም ገደብ እንደሌለበት፣ በሚመለከተው አካል ተጣርቶ የተመዘገበ በመሆኑ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህ ችሎትም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ ግራ ቀኙ አደረጉት የተባለው የስጦታ ውል በማስቀረብ ተመልክቶታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ “በዚህ ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ለመጦር የሰጡት የመሬት ስጦታ ውሉ ይፍረስልኝ ሲሉ ያቀረቡት ክስ ውሉ አይፈርስም የመባሉን አግባብነት ከክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አንፃር” ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር የሚል ሆኖ አገኝቶታል፡፡

ከሥር የክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የስጦታ ውል ማድረጋቸው ሳይክዱ የአሁኑ ተጠሪ መሬቱ እንዳልተንከባከበ ሊያስታምማቸው አለመቻሉን በመግለጽ የስጦታ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን መጠየቃቸውን ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የስጦታ ውሉ በሕጉ አግባብ የተደረገ በመሆኑ የሚፈርስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የመሬት ስጦታው ፈራሽ የሚሆንበት ምክንያት አልተገኘም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርገውታል፡፡ አመልካች የስጦታ ውሉ ለማፍረስ እንደምክንያት የጠቀሱዋቸው ነጥቦች በስጦታ ውሉ ላይ የተመዘገቡ ቅድመሁኔታዎች /Conditions/ ስለመሆናቸው የግራ ቀኙ ያደረጉት የውል ስምምነት አያሳይም፡፡ አመልካች ያደረጉት ስጦታ የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 15 እና 17 መሰረት መደረጉ በትዕዛዝ ከቀረበው ሰነድ መመልከት ይቻላል፡፡ አመልካች እንደውል ማፍረሻ የዘረዘሩዋቸው ምክንያቶች በስጦታ ውሉ ላይ ያልተመዘገቡ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሬት ስጦታ ውል ክርክር በቀረበበት ሁኔታ ፈራሽ መሆን ያለመሆኑን ለመወሰን የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 ሆነ አዋጁን ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 ግልጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌ እንደሌላቸው በውሳኔው አስፍሯል፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክርክር ጉዳዩ ከፍትሐብሔር ሕግ አንፃር መታየት የለበትም ያሉ ቢሆንም የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው እንዳሰፈረው የስጦታ ውል የሚፈርስበት ሁኔታ ካለ አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች አስተሳስሮ ማየቱ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእርግጥ የገጠር መሬት የክርክር ይዘትና ባሕሪ እንዲሁም ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ በመለየት ረገድ ተገቢ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ ይሁንና አመልካች ያነሱዋቸው የስጦታ ውሉ ያፈርሳሉ የተባሉ ምክንያቶች የሕግና የውል መሰረት ያላቸው መሆን ያለመሆኑን መርምሮ መወሰን ተገቢ ነው፡፡

አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት ስጦታ በነፃ ፍላጎት እና በትክክለኛ የአእምሮ ሁኔታ እንደነበር እንዲሁም ውሉ አግባብ ባለው አካል መመዝገቡን የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የስጦታ ውሉ ሕገወጥ በሆነ ምክንያት ወይም የመንፈስ መጫን እንደነበረ አመልካች አላስረዱም፡፡ አመልካች የስጦታ ውሉ በገደብ የማድረግ መብት የነበራቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2455(1) ያስገነዝበናል፡፡ ይሁንና አመልካች በስጦታ ውሉ ላይ ያስቀመጡት ቅድመሁኔታ ስለመኖሩ ውሉ አያሳይም፣ ያቀረቡዋቸው ምስክሮችም ስጦታ ውሉ በገደብ /ግዴታ/ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን ፍሬ ነገር በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ከድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በአንፃሩ የአሁኑ ተጠሪ ለረጅም ጊዜ ያገለገላቸው ስለመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ ግንዛቤ መወሰዱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በመሆኑም አመልካች በገፃ ፈቃዳቸው 3 ጥማድ መሬት መስጠታቸው እና ውሉም ሥልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ መመዝገቡን ባለተካደበት አመልካች በውሉ ላይ ያልተመዘገበ ቅድመ ሁኔታዎች በመዘርዘር ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ያቀረቡት ክርክር የሕግም ሆነ የውል መሰረት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት የእርሻ መሬት ስጦታ ለማፍረስ የሚያስችል የሕግ ድጋፍ ያለው ክርክር አለማቅረባቸው ተረድተናል፡፡

አመልካች ለተጠሪ ከሰጡት 3 ጥማድ መሬት ውጭ ሌላ የመሬት ይዞታ ያላቸው ስለመሆኑ በትዕዛዝ ቀርቦ ከታየው የአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በእርግጥ አመልካች ስጦታ ከሰጡት መሬት ውጭ ሌላ መሬት እንደሌላቸው ወይም ራሳቸው መቀለብ በማይችሉበት ደረጃ የሚኖሩ ከሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2458(1) በሚያዘው አግባብ ቀለብ የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ተጠሪም ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለው በመሆኑ መብታቸውን በሕጉ አግባብ ማስከበር የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ችሎቱ ይገነዘባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ውሉን ለማፍረስ እንደምክንያት የጠቀሱዋቸው ቀለብ ከመጠየቅ ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ከመሬቱ እንክብካቤና ግብር መክፈል የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን 3 ጥማድ መሬት በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የወጣበት በመሆኑ የሚመለከተው አካል ከሚጠይቀው በስተቀር አመልካች ስለግብር መክፈልና መሬቱ ላይ መደረግ ያለበት እንክብካቤ የሚጠይቁበት ሥርዓትና የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በእነዚህ ሁሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት የስጦታ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ ማድረጋቸው ሕጉን በአግባቡ ተፈፃሚ አድርጓአል ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸማቸውን የማያሳይ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የምንጃር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 01010775/07 በ15/05/2007፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0116800 በ13/08/2007 የሰጡት ፍርድ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 030-6216 በ22/10/2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት የ3 ጥማድ መሬት ስጦታ ውል በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/98 ይዘትና መንፈስ የተደረገ በመሆኑ የሚፈርስበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.100395

ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሠናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አማረች ማሬ ..... ጠበቃ ማስታወል ሀብታሙ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሜሪ ታደሰ
2. ወ/ሪት ፈጣኑ ታደሰ } ጠበቃ ሀይሉ ዓይናለም ቀረቡ
3. ወ/ሪት ሮማን ነስሩ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪዎች እየኖሩበት ያለውንና በ 300 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ቤት ለቀው እንዲያስረክቧት የመጠየቅ መብት የላትም ንብረቱን የሸጠችላትን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ከሳ ትጠይቅ በማለት የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል ፡፡
2. ከሳሽ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የመፈላም ክስ ነው ከሳሽ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 287 የግል ሀብቱ ስለመሆኑ በክፍሉ አስተዳደር የባለሀብትነትና ባለይዞታነት ማረጋገጫ ማስረጃ (ካርታ) በእጁ ይገኛል፡፡ ተከሳሾች ከቤቱ ውስጥ በጥገኝነት እንዲኖሩ ፈቅጀላቸው ሲኖሩ ቆይተዋል ፡፡ አሁን ግን ቤቱን እንዲለቁ ብጠይቃቸው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ፍርድ ቤቱ ተከሳሾች ቤቱን እንዲለቁና እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ተጠሪዎች በተከሳሽነት ቀርበው እኛ በከሳሽ ቤት በከሳሽ ፈቃድ በጥገኝነት የምንኖር ሰዎች አይደለም ። ተከሳሾች በእጃችን አድርገን ይዘን እየኖርንበት ያለው ቤትና ይዞታ አያታችንና እናታችን ከዛሬ አርባ ዘጠኝ ዓመት ጀምሮ ይዘውት ሲኖሩበት የነበረ ቤት ነው።ተከሳሾች ከአያታችንና ከእናታችን ጋር ክስ ያቀረበበትን ቤት ይዘን ስንኖር ፣ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በአያታችን ባዶ የይዞታ ቦታ ላይ በአንድ በኩል ቤት ሠርታ ስትጠቀም ቆይታ ፣ቤቱን ለአሁን ከሳሽ ሸጣለታለች ሆኖም እኛ የምንኖርበት ቤት ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ በእጇ አድርጋ ይዛው የማታውቅና የራሱ የሆነ ይዞታና የወሰን አጥር ያለው በመሆኑ ከሳሽ ቤቱን ለከሳሽ የሸጠችውም ሆነ ከሳሽ የእኛን ቤትና ይዞታ በማጠቃለል እንዴት ካርታና ፕላን እንዳወጡ የክፍሉ አስተዳደር እንዴት የእኛን ቤትና ይዞታ በማጠቃለል እንዴት ካርታና ፕላን እንደሰጠ ይጠየቅልን በማለት መልስ ሰጥተዋል። የስር ፍርድ ቤት የክፍሉ አስተዳደር ተገቢውን ማጣሪያ በማድረግ መግለጫ እንዲሰጥ ትዕዛዝ የቤቱ ስመ ሀብትና ከወ/ሮ እህተ ገብረማርያም ሂሩት አበራሽ ስም ሂሩት ስም የተዛወረዉ በስር ትዕዛዝ ፋይል ቁጥር 139/84 መስከረም 25 ቀን 1985 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንደሆነና ከዚያ በኃላ ሂሩት አበራሽ በውልና ማስረጃ ከከሳሽ ጋር በተዋዋለችው የቤት ሽያጭ ውል 1189 ሜትር ካሬ ላይ ያረፈው ቤትና ይዞታ በከሳሽ ስም እንዲዘዋወር ተደርጎ ከሳሽ የባለሀብትነት ማስረጃ የሰጠ መሆኑን ተረጋግጧል ።

4. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ወ/ሮ እህተ ገብረማሪያም ጋር ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የገዙት ዋናውን ቤት የቤት ቁጥር 287 እንደሆነ የሚገልፅ ቢሆንም ገዥ ይህንን ዋናውን ቤት ተረክበውና በእጃቸው አድርገውት አያውቁም ። ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ ገብተውና ከሻጭም ተረክበው ይኖሩ የነበሩት ሰርቪስ ቤትና በባዶ ይዞታ ላይ ራሳቸው የሠሩትን ቤት ነው ። ገዥ ገዝቻለሁ የሚሉትን የቤት ቁጥር 287 በ 300 ካሬ ሜትር ላይ 1984 ዓ.ም ጀምሮ ተረክበውና በእጃቸው አድርገውት አያውቁም ነገር ግን የሻጭን መሞት ምክንያት በማድረግ ይህንን 1984 ዓ.ም ተረክበውና ይዘው የማያውቁትን ቤት ጨምሮ በሽያጭ ውሉ መሠረት ተረክበው የሚኖሩበትን ይዞታ ላይ ያለው ቤት ስመሀብት እንዲዛወርላቸው በማድረግ የባለሀብትነት ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል ። ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በፍርድ ቤት ውሣኔ መነሻ የተሰጣቸውን የባለሀብትነት ሰነድ በማየት ፣ከሚች እህተ ገ/ማሪያም ቤቱን ከገነባች ጀምራ ተረክባና በእጇ አድርጋ የማታውቀውን የቤት ቁጥር 287 ዋናውን ቤት በ 300 ካሬ ሜትር እንዳረፈ ፣በእጇ አድርጋ ስታካብት ከኖረችው ቤት ጋር አንድ ላይ ለከሳሽ ሸጣ ቤቱና ይዞታው በተከሳሾች እጅ ባለበት ከሳሽ በሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እጅ ባልነበረና ሆኖ በማያውቅ ቤትና ይዞታ ላይ ጭምር የባለሀብትነት ማስረጃ አውጥታለች ። ይህም ለከሳሽ ቤቱን የሸጠችው ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ ተከሳሾች ይዘው የሚኖሩበትን ቤትና የይዞታ ቦታ በሽያጭ ውሉ መሠረት ያላስረከበቻትና ቤቱና ይዞታው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተከሳሽ እጅ ባለበት የሰነድ ርክክብ ብቻ ያደረገች መሆኑን ስለሚያሳይ ከሳሽ ሻጭዋን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እንጂ ተከሳሾች ቤቱን እንዲያስረክቧት መክሰስ አትችልም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል ። ይህንን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲያየው አመልካች ጠይቃ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል።

5. አመልካች ሚያዝያ 27 ቀን 2008 ዓ.ም አመልካች አከራካሪውን ቤት በውል ገዝታ የንብረት ባለሀብት መሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላት ይህ ከሆነ ንብረቷ እንዲለቀቅ የመክሰስ መብት የላትም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው። የበታች ፍርድ ቤቶች ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ጭብጦችን አልመሰረቱም ተጠሪዎች ቤቱን በጥገኝነት ስለመያዛቸው ለቀበሌ ለአስተዳደር አመልክተዋል በሻጭና በከሳሽ መካከል የተደረገው ውል ተጠሪዎችን የሚመለከት አይደለም ። አመልካች የቤቱ ሻጭ በዋቢነት እንድትቀርብላት ማትጠራ ፣ንብረቱ ላይ ያገኛቸው የባለሀብትነት መብት ለማስከበርና ለመፋለም የሚከለክላት ህግ በሌለበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልክታለች ።

6. ተጠሪዎች በመጀመሪያም ሂሩት አበራሽ ከሚች አያታችን እህተ ገ/ማሪያም ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል አስመልክቶ ለአውራጃው ፍርድ ቤት ክስ ስታቀርብ ሚች የሸጠችላትን ቤት እጇ አድርጋና ተረክባ እየኖረችበት መሆኑን ገልፃለች። ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እኛ የምንኖርበትን ቤትና በአዋሳኝ አጥር ታይቶ ያለውን 300 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ተረክባም ሆነ ይዛው አታውቅም ። እኛ በማናውቀው ሁኔታ የእኛን ቤትና ይዞታ ካርታና ፕላን ማውጣቷና ለከሳሽ መሸጧ ከሳሽን የቤቱ ባለመብት አያደርጋትም ። የባለሀብትነት ካርታና ማስረጃውም በክፍሉ አስተዳደር የታገደ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል ። አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል ። ግራቀኙ የሚያከራክራቸውን ጭብጥ ለመረዳት ችሎቱ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቶ የቃል ክርክሩ ከትራንስክራይበር ማሽን ተገልብጦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል ። የክፍሉ አስተዳደር በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የፃፈውን መግለጫ ለማየት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 135280 እንዲቀርብ በታዘዘው መሠረት መዝገቡ ቀርቦ ተያይዟል ።

7. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩ እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ቤቱና ይዞታው እንዲለቀቅላቸው ክስ ያቀረቡት ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታ ከሻጭ ተረክበው የያዙትን ቤትና ይዞታ በድምሩ 1139 ካሬ ሜትር ላይ ያሉትን ቤቶችና ይዞታ በብር 120,000 የካቲት 3 ቀን 1997 ገዝቼ የቤቱ ስመሀብት የተዛወረልኝ በመሆኑ ተከሳሾች (ተጠሪዎች) የግል ሀብቴና ንብረቴ የሆነውን ቤትና ይዞታ ይለቀቁልኝ በማለት ነው። ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ከሳሽ የቤትና ይዞታውን ባለቤትነት መብት በሽያጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስተላልፋልኛለች የሚሉት አበራሽ ሂሩት እኛ የያዝነውን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ለከሳሽ በሽያጭ ለማስተላለፍ መብት የላትም ። ከሳሽ እኛን ከመጠየቋ በፊት በሽያጭ ውሉ መሠረት እኛ የምንኖርበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ሻጭ ነፃ አድርጋ እንድታስረክባትና የሽያጭ ውሉን እንድትፈፅምላት ከምትጠይቅ በስተቀር ከሳሽ የሽያጭ ውሉ ሙሉ በሙሉ እንደተፈጸመላትና ንብረቱንም ከሻጭ እንደተረከበች አድርጋ በመቁጠር በቀጥታ እኛን ከቤት እንድንወጣ የመጠየቅና ክስ የማቅረብ መብት የላትም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተረድተናል።

8. ግራቀኙ በሥር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር አመልካችና ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት የካቲት 3 ቀን 1997 ዓ.ም የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል ሻጭ ሙሉ ለሙሉ ፈፅማለች ወይስ አልፈፀመችም ሻጭ በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታዋን ሙሉ በሙሉ ካልፈፀመችና ውሉን በከፊል የፈፀመች መሆኑ ቢረጋገጥ ገዥዋ ሻጭ ቀሪውን ግዴታዋን እንድትፈፅምላት በሻጭ ላይ ክስ ማቅረብ ወይም በተከሳሽነት አጣምራ ሳትከስ የውሉ ተዋዋይ ያልሆኑ ሶስተኛ ወገኖች ላይ በቀጥታ ክስ ለማቅረብ ትችላለች ወይስ አትችልም ?የሚሉት ነጥቦች መታየት ያለባቸው ናቸው።

9. ከላይ ከተገለፁት ነጥቦች አንፃር ስንመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል የገባውን ግዴታ የሚፈፅምባቸው ሁለት መሠረታዊ ኃላፊነቶች አሉ። የመጀመሪያው ሻጭ በሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ በስፍራው የሚገኙ ሰዎች የተሸጠውን የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲለቁ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ይዞታ ከሌሎች ሶስተኛ ወገኖችና ከሻጭ ቁጥጥርና ይዞታ ነፃ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለገዥ ማስረከብ እንደሆነ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና ከፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2274 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ለመረዳት ይቻላል ሻጭ ከዚህ በተለየ ሁኔታ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ርዕስ መዝገብ ላይ የተመዘገበና ገዢውንም ሊያስገድዱ የሚችሉ የሶስተኛ ወገኖች መብት በሰጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ካሉ ይህንኑ የሶስተኛ ወገኖች መብት ካለ ሻጭ ለገዥ ማስታወቅ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2880 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2881 ተደንግጓል ።

10. የሻጭ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ከሶስተኛ ወገን ይዞታና ቁጥጥር ነፃ በማድረግ የማስረከብ ግዴታ ገዥ ለሻጭ ከሚሰጠው የመነቀል ዋስትና ግዴታ የተለየ ነው ። ሻጭ በንብረቱ ላይ ያሰፈሩና በንብረቱ መዝገብ የተመዘገበ መብት የሌላቸውን ሰዎች የማይንቀሳቀሰውን ንብረት እንዲለቁ በማድረግ ለሻጭ የማስረከብ ግዴታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ውል በመፈፀም ሂደት ገዥ ሻጭ ሊያከናውነው የሚገባ የመጀመሪያ ግዴታ ሲሆን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2882 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ሻጭ ለገዥ የሸጠለት የማይንቀሳቀስ ንብረት የማይነቀል ስለመሆኑ የሚሰጠው ዋስትና ገዥ የገዛውን የተረከበውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሌሎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰዎች ቁጥጥር ነፃ ሆኖ ከተረከበ በኃላ ንብረቱ የእኔ ነው ባይ ቢመጣ ሻጭ በዋቢነት ሊቆምለት የሚገባ መሆኑን የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

11. የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ንብረቱን ከሌሎች ሰዎች ቁጥጥር ይዞታ ሥር ነፃ አድርጎ ለገዢ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2274 መሠረት የማስረከብ ግዴታ ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሀብትነት ለማስተላለፍ የሚችሉ አስፈላጊ ሰነዶች ለገዢ የማስረከብና የማይንቀሳቀሰዉን ንብረት የማይነካ የባለሀብትነት መብት ለገዥ ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆነ ተግባራትን የመፈጸም ግዴታ መሆኑ በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 2875 በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2879 ንሁስ አንቀጽ 1 እና የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2281 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

12. ከላይ በዝርዝር ካየናቸው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ 1139 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ ያረፈውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሙሉ በሙሉ ለአመልካች የሸጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት፣በሽያጭ ውሉ መሰረት የማይንቀሳቀስውን ንብረትና ይዞታውን ከሌሎች ሰዎች ቁጥጥርና ይዞታ ስር በማስለቀቅ የማይንቀሳቀስ ንብረትና ይዞታውን በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2875 በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2274 እና በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2888 መሰረት ለገዥ(ለአመልካች)የመፈጸም ግዴታውን የተወጣችው ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በከፊል ነው፡፡ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ከተጠሪዎች አውራሽ ንብረቱን ገዛሁ ከምትልበት 1984 ዓ.ም ጀምሮ ተረክባውና በእጇ አድርጋው የማይታወቅ መሆኑና፣ቤቱን ለአመልካች ከሸጠችላት በኋላ ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታ፣ ተጠሪዎች በህግ አግባብ እንዲለቁ በማድረግ ለአመልካች ያላስረከበችበት አመልካችም በሽያጭ ውሉ የተገለጸውን ቤትና ይዞታ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን፣ሻጭ(አበራሽ ሂሩት)ይዛው የነበረውን ቤትና ይዞታ ብቻ ከሻጭ የተረከበች መሆኑን ተረድተናል፡፡

13. ገዥ ሻጭ በሽያጭ ውሉ የገለጸችውን የማይንቀሳቀስ ንብረትና ይዞታ፣ ተጠሪዎች የሚኖሩበት ቤትና ይዞታ ሳይጨምር በሻጭ እጅና ይዞታ ስር ያለውን ቤትና ይዞታ የተረከበች ቢሆንም፣ሻጭ የሰጠቻትን ሰነድ በመጠቀም በሽያጭ ውሉ ላይ የተመለከተውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለመብት መሆኗን የሚሳይ ማስረጃ ከክፍሉ አስተዳደር ተሰጥቷታል፡፡ይህም ገዥዋ(አመልካች)ከሌሎች ሰዎች ይዞታና ቁጥጥር እንደዚሁም የመብት ጥያቄ ነጻ ሆኖ ከሽያጭ ያልተረከበችውን ተጠሪዎች የሚኖሩበት ቤትና ይዞታ ባለመብት መሆኗን የሚያረጋግጥ የባለሀብትነት ማስረጃ የተሰጣት መሆኑን ያሳያል፡፡አመልካች የቤቱ ባለሃብትነት መብት በሽያጭ ውል ከወ/ሮ አበራሽ ሂሩት የተላለፈላት መሆኑን የሚያሳይ የሽያጭ ውል ሰነድና በሽያጭ ውሉ መሰረት በማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለሀብትነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተሣወረላት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በማያያዝ በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1206 መሰረት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም አላት፡፡ነገር ግን አመልካች ባቀረበችው የክስ መነሻ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ጭብጥ፤(ሀ) ቤቱን ንብረቱ ነው ካለች ለአመልካች የሸጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት አከራካሪውንና ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታ ባለሃብትነት መብት ለአመልካች የማስተላለፍ እርግጠኛ የሆነ የባለሀብትነት መብት በንብረቱ ላይ አላት ወይስ የላትም?

(ለ)ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ተጠሪዎች የሚኖርበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ጨምራ የባለሀብትነትን ማስረጃና ካርታ ያሰራችው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?አመልካችስ 1139 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትና ባለይዞታ መሆኗን የሚያረጋግጥ የባለሀብትነት ማስረጃና ካርታ የተሰጣት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?(ሐ)ተጠሪዎች እየኖሩበት ያለውን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ቦታ ለአመልካች የመልቀቅና የማስረከብ ግዴታ አለባቸው ወይስ የለባቸውም?የሚሉት ለአመልካች 1139 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ውል አስተላልፋለች የተባለችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በክርክሩ ተሳታፊ ሳትሆን ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ጭብጦች አይደሉም፡፡

14. የስር ፍርድ ቤት አመልካች የቤቱ ሻጭ የሆነችውን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ከሚከሱ በስተቀር በቀጥታ ተጠሪዎች ቤቱን እንዲለቁላት ክስ ማቅረብ አትችልም በማለት የሰጠው ውሳኔ ሻጭ በሽያጭ ያስተላለፈው ንብረት ላይ ያለውን መብትና ጥቅም ለማስከበር ገዥው ከውል የመነጨ መብት ያለው መሆኑን ያላገናዘበና የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1195 የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1206 እና የፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 33(2) ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ ስህተት ያለበት ነው፡፡ነገር ግን የበታች ፍርድ ቤቶች ቤቱን ለአመልካች የሸጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በክርክሩ ተከሳሽ መሆን አለባት በማለት የደረሱበት ድምዳሜ የፍትሃብሄር ህግ አንቀጽ 2875፣ አንቀጽ 2274፣አንቀጽ 2888 እና የፍትሃብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በጉዳዩ ተከሳሽ መሆን አለባት በማለት የደረሱበት መደምደሚያ በውጤት ደረጃ የሚነቅፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

15. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የቤቱን ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት መክሰስ አለባት ካሉ በኋላ፣ይህ ውሳኔአቸው የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት ሳይመዝኑ ተጠሪዎችን ከክስ ማሰናበታቸው አግባብነት ያላቸውን የስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም አመልካች ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በሽያጭ ውሉ መሰረት ተጠሪዎች የያዙትን ቤት አስለቅቃ ታስረክበኝ የሚል ክስ ስታቀርብ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ በማናቸውም ሁኔታ የሚገኙ ሰዎችን በተከሳሽነት አጣምራ መክሰስ እንዳለባት የፍትሃብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 36

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንዑስ አንቀጽ 4 አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ይደነግጋል፡፡ይህም አመልካች ሻጭዋን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩትን በምትከስበት ጉዳይ ተጠሪዎች የግድ በተከሳሽነት እንዲሳተፉ ማድረግ የሚገባ መሆኑ በህግ የተደነገገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ዳኝነት ከፍላ ያቀረበችውን ክስ የቤቱ ሻጭ በጉዳዩ የመጀመሪያ ተከሳሽ መሆን አለባት በሚል ምክንያት ዘግቶ አመልካችን ከሚያሰናብት፣በጉዳዩ የቤቱ ሻጭ በክርክሩ በተከሳሽነት ተሳታፊ እንድትሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ትዕዛዝ መስጠት በዚህ ፍርድ አንቀጽ ተራ ቁጥር 13 በተመለከቱና በሌሎች ጭብጦች ላይ አመልካች (የቤቱ ገዥ)፣ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ሻጭና በአከራካሪው ቤትና ይዞታ ይዘው የሚኖሩት ተጠሪዎች የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ መወሰን ሲገባው፣አመልካች ተጠሪዎችን የመክሰስ መብት የላትም በማለት መዝገቡን መዝጋቱና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ማጽናቱ ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና የዳኝነት አካሄድ ስርዓት ያልተከተለና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66605 የካቲት 29 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 135280 መጋቢት 2 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በተከሳሽነት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በመጨመር፣በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 13 የተመለከቱትንና ሌሎች አከራካሪ ጭብጦች ላይ ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በማሰማትና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117819

መጋቢት 15 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- በወላይታ ዞን የበሌ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ዓ/ሕግ ኤርገና ቆልቻ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ታደለች ዳባራ - ተወካይ ታደለ ወ/ሚካኤል - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በዉል ያገኘሁትን የከተማ ይዞታ እንዲያስረክበኝ በማለት የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡ የአሁን አመልካች የሥር 1ኛ ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ በመሆን ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የአሁን ተጠሪ በኪንዶ ኮይሻ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ በበሌ ቀበሌ 02 በግብርና ሰፈር በኮድ ቁ.0443፣ 300 ካ.ሜ ይዞታ ለጨረታ አዉጥቶ እኔ ተወዳድሬ አሸንፌ ተገቢዉን ክፍያ ሁሉ ፈጽሜ ዉል ተዋዉዬ እያለሁን፣ 2ኛ ተከሳሽ ተወዳድሮ ያሸነፈዉ ኮድ 0024፣ 200 ካ.ሜ ይዞታ ሁኖ እያለ የመጀመሪያዉን ዉል አስቀርድዶ በቦታዉ ላይ የተለጠፈዉን ታፔላ በመቀያየር ሌላ ክፍያ በመፈጸም ለ2ኛ ተከሳሽ አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ፣ 1ኛ ተከሳሽ ይህን ይዞታ ከ2ኛ ተከሳሽ አስለቅቆ ለከሳሽ እንዲያስረክበኝ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ በተወዳደረችበት ቦታ ላይ ያቀረበችዉን የጨረታ ሰነድ በሰም ያልታሸገ በመሆኑና ሕጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ አሰጣጥን ያልተከለተለ ስለመሆኑ በመረጋገጡ በ1ኛ ተከሳሽ ማኔጅመንት በሕግ አግባብ የከሳሽ ዉል እንዲመክን ተደርጓል፤ ከሳሽ ይህን ክስ ያቀረበችዉ ከቅን ልቦና በመሆኑ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽ /አቶ ማቴዎስ ማያ/ ባቀረበዉ መልስ ይህን ይዞታ በሕጋዊ መንገድ ተወዳድሬ ያገኘሁት በመሆኑ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ክርክሩን በማጣራት በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካችን ክርክር በመቀበል የአሁን ተጠሪን ክስ ዉድቅ በማድረግ፣ የአሁን ተጠሪ ከጨረታዉ ጋር በተያያዘ የከፈሉት ገንዘብ ብር 3600 /ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ብር/ የአሁን አመልካች እንዲከፍላቸዉ ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በሰጠዉ ዉሳኔ መደበኛዉ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለዉም በማለት የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ጉዳዩ በአስተዳደር በኩል ታይቶ እልባት እንዲሰጣት አቤቱታዋን በየደረጃዉ ላሉት የመንግስት መዋቅር አቅርበዉ ምላሽ በማጣታቸዉ ይህን ክስ ለፍ/ቤት ያቀረቡ በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለዉ፤ የሥር 2ኛ ተከሳሽ ተወዳድረዉ ያሸነፉት በ200 ካ.ሜ ሲሆን፣ ከሳሽ በ300 ካ.ሜ ላይ በጨረታ ተወዳድረዉ አሸነፊዉ ዉልም ተዋዉለዉ ክፍያ ከፈጸሙ በኋላ የአሁን አመልካች በሰም የታሸገ ኤንቨሎፕ አላቀረብሽም በሚል ምክንያት ዉሉን ዉድቅ ማድረጉ አግባብነት የለዉም፣ በዉሉ በተጠቀሰዉ መሰረት በጨረታ ያሸነፈችዉን ይዞታ 300 ካ.ሜ ለከሳሽ እንዲያስረክባት በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች አሁንም ይህን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታዉን ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለዉም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ነሐሴ 20 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ ተጠሪዋ ያሰነፈችበትን ዉጤት እንዲሰረዝ ዉሳኔ የሰጠዉ የወረዳዉ ማኔጅመንት ኮሚቴ በመሆኑ የሊዝ አዋጁን ለማስፈጸም በወጣዉ መመሪያ መሰረት ቅሬታዋን ለሚመለከተዉ አስተዳደር ማቅረብ ነበራባት እንጂ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም፡፡ የአሁን ተጠሪ በጨረታ ሂደት አለአግባብ መብቴ ተነክቷል የምትል ከሆነ የሊዝ ኮሚቴ ወይም የመሬት ማኔጅመንት ኮሚቴ ቅሬታዋን አቅርባ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ካልተስማሙ ይግባኝ ለዞን ይግባኝ ሰሚ ወይም ለክልሉ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ እንዳለባቸዉ በሊዝ አዋጅ ቁ.721/2004 መሰረት ክልሉ ባወጠዉ መመሪያ ቁ/01/2005 አንቀጽ 74 መሰረት መሆን አለበት፡፡ የሥር ፍ/ቤት በዚህ መቃወሚያ መሰረት የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የተጠሪዋን መሬት ለሌላ ግለሰብ አሣልፎ ለመስጠት ነዉ ዉጤቱን የሰረዘዉ፣ የተወዳደሩበትን ታፔላ ቀያይሯል የሚል ሲሆን ይህ ስለመሆኑ በተጨባጭ ማስረጃ ያጣራዉ ነገር የለም ወይም ወደ ስር ፍ/ቤት መልሶት እንዲጣራ ያደረገዉ ነገር በሌለበት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ስለዚህ ይህን ጉዳይ የመደበኛዉ ፍ/ቤት ለማየት ስልጣን ስለሌለዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሻርልን፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማየት የሚጣራ ጉዳይ አለ በማለት አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ10/02/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልሱም ይዘት፡ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብት እንዲጠበቅልኝ ወይም በቁርጥ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ፣ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን ጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች በበሌ ቀበሌ 02 በግብርና ሰፈር በኮድ ቁ.0443፣ 300 ካ.ሜ ይዞታ ለጨረታ ባቀረበዉ መሰረት የአሁን ተጠሪ ተወዳድረዉ አሸንፈዉ ተገቢዉን ክፍያ ፈጽመዉ ዉል ያደረጉ መሆኑን ግራ ቀኙ የሚካካዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ በሌላ በኩልም የአመልካች መ/ቤት በዚህ አግባብ ተጠሪ ጨረታዉን አሸንፈዉ ተገቢዉን ሁሉ ፈጽመዉ ዉል ከተዋዋሉ በኋላ ለጨረታዉ ሲወዳደሩ በሰም የታሸገ ኤንቨሎፕ አላቀረቡም የሚል ምክንያት በማንሳት በኮሚቴ በማየት ዉሉን የሰረዘ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረቡት ክስ አመልካች ይህን ዉል ያለአግባብ የሰረዘ በመሆኑ በዉሉ ላይ በተመለከተዉ መሰረት ይዞታዉን እንዲያስረክበኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁን አመልካች ይህ ጉዳይ በአስተዳደር አካል መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ እንጂ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚህ አግባብ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማየት መደበኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም የሚለዉን ጭብጥ መመልከቱ ተገቢ ነዉ፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ የአሁን አመልካች የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 እንዲሁም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ መሰረት ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ይዞታ ለጨረታ አቅርቦ፣ የአሁን ተጠሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 /1-6/ መሰረት ተወዳድረዉ የጨረታ ሂደቱን አልፈዉ አሸንፈዉ በአንቀጽ 16 መሰረት የሊዝ ዉል የፈጸሙ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የአሁን ተጠሪ በሕጉ የተመለከተዉን ሂደት ሁሉ አልፈዉ ዉል ከፈጸሙ በኋላ አመልካች ወደ ኋላ በመመለስ ለዉድድር ሲቀርቡ ተጠሪ በሰም የታሸገ ፖስታ ወይም ኤንቨሎፕ ባለማቅረባቸዉ የጨረታዉን ዉጤት የሆነዉን ዉል መሰረዙን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን የአመልካች መ/ቤት ተጠሪዋ በጨረታዉ ለመሳተፍ የሚያስፈልገዉን መስፈርቶች ሁሉ ያሟሉ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ በጨረታዉ እንዲሳተፉ ያደረጋቸዉ መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም፡፡ የአሁን ተጠሪ አስፈላጊዉን መስፈርት ባያሟሉ ኖሩ በጨረታዉ ላይ እንዲሳተፉ ያደረጋል ተብሎ አይገመትም፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች ተጠሪዋ በአግባቡ የጨረታ ሂደቱን አልፈዉ ዉል ከተዋዋሉ በኋላ በሰም የታሸገ ኤንቨሎፕ አላቀረቡም በማለት ይህን ዉል መሰረዙ ከጨረታ ሂደት አልፎ አስገዳጅ የዉል ግዴታ በተገባበት ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ መታየት ያለበት ከላይ የተመለከተዉ የሕግ ድንጋጌ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የዉል ሕግ ድንጋጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደአግባብነቱ ተፈጻሚነት የሚኖረዉ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በግራ ቀኙ መካከል በሕግ ፊት የሚጸና መብት ግዴታ የሚፈጥር ዉል እስከተደረገ ድረስ ይህን ዉል የማፍረሱ ጉዳይ በአመልካች መ/ቤት ብቻ የሚተዉ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ማለት በግራ ቀኙ መካከል ይህ ዉል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 መሰረት እንደሕግ የሚቆጠር ነዉ፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ ዉል መሰረት መብትና ግዴታቸዉን መወጣት እንደሚጠበቅባቸዉ ግልጽ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ይህ ዉል የሚፈርስባቸዉ ሕጋዊ ምክንቶች አሉ ወይስ የሉም የሚለዉን አይቶ ለመወሰን ለተዋዋይ ወገኖች ብቻ የሚተዉ ጉዳይ ሳይሆን ገለልተኛ በሆነ ፍ/ቤት ታይቶ መዳኘት ያለበት ጉዳይ ሁኖ ይታያል፡፡ ይህን ዉል ለማፍረስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1808 ሥር የተመለከቱት ዉልን ለማፍረስ ተገቢ የሆኑ ምክንያቶች መሟላት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ በመሆኑ እነዚህ ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች መሟላታቸዉን አለማሟላታቸዉን በመደበኛ ፍ/ቤት ታይቶ እልባት ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ ጉዳይ በህጋዊ መንገድ የተቋቋመዉን ዉል ከማፍረስ ጋር የሚመለከት በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ የማያይበት ምክንያት የለም፡፡ የአሁን አመልካች መ/ቤት ማናቸዉንም ምክንያት በመፈለግ በፈለገ ጊዜ እያነሳ ይህን በሕግ አግባብ የተቋቋመዉን ዉል ለመሰረዝ የሚያስችለዉ የሕግ አግባብ የለም፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ዉል ለመሰረዝ የጠቀሰዉ ምክንያት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1808 /2/ ሥር የሚወድቅ ሁኖ ስለማይታይ ዉሉን ለመሰረዝ በቂ ምክንያት ነዉ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች መደበኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን አላቸዉ በማለት የአሁን አመልካች ያለ በቂ ምክንያት ዉሉን መሰረዙ ተቀባይነት የለዉም አመልካች በዉሉ ላይ የተጠቀሰዉን ይዞታ ለአሁን ተጠሪ እንዲያስረክብ በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.06872 በ13/09/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 07874 በ29/11/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. በ29/12/2007 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.114622

ግንቦት 9 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማዉ ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ተኽሊት ይመሰል
እንዳሻዉ አዳነ
ቀነዓ ቂጣታ

አመልካቾች፡- 1. አቶ አወል አማን } ተወካይ ሙስጠፋ አዋል
2. ወ/ሮ ሩቅያ ሙሳ } ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አሳለፈች አንዳግቤ } ተወካይ አቶ ግርማ ጥላሁን ቀርበዋል
2. አቶ አስራት ግርማ
3. የአዳማ ከተማ የመሬት ልማት እና ማናጅመንት ኤጀንሲ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ክስ መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡ የአሁን አመልካቾች /የሥር ጣልቃ ገቦች/፣ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች /የሥር ከሳሾች/፣ የአሁን 3ኛ ተጠሪ /የሥር ተከሳሽ/ ሆኖ ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ለእያንዳንዳችን 200 ካ.ሜ ቦታ እንዲሰጠን ተወስኖ በዚሁ መሰረት ካርታ የተሰጠን ቢሆንም 1ኛ ከሳሽ በእጁ የደረሰዉ ቦታ 90 ካ.ሜ ሲሆን፣ 2ኛ ከሳሽ ደግሞ በእጁ የገባዉ 110 ካ.ሜ ብቻ በመሆኑ ተከሳሽ እና ማዘጋጃ ቤት የተቀነሰዉን ቀሪ ቦታ አሟልቶ እንዲያስረክበን በማለት ከሷል፡፡ የሥር ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሾች ለእያንዳንዳቸዉ 200 ካ.ሜ እንዲሰጣቸዉ ተወስኖ ካርታ ተሰጥቷቸዉ መሬት ቢሰጣቸዉም በካርታ ላይ የተጠቀሰዉ ሙሉ ይዞታ በእጃቸዉ ስላልገባ ተከሳሽ እና ማዘጋጃ ቤት የተቀነሰዉን ቀሪ ቦታ አሟልቶ እንዲያስረክባቸዉ በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት ባቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ከሳሾች እና ተከሳሽ የተስማሙበት ይዞታ ጣልቃ ገቦች ከኃ/ስላሴ ጊዜ ጀምሮ በገጠር መሬት ይዘን የቤት ቁጥር 188

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና ግምቱ 500,000.00 የሚያወጣ ቤት ሰርተንበት እየተጠቀምን ያለን በመሆኑ፣ ተከሳሽ ንብረታችንን ለከሳሾች እንዳያስክረብብን፣ ካልሆነ ካሳ የመጠየቅ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት አመልክተዋል። የሥር ከሳሾች እና የሥር ተከሳሽ ለየብቻ ባቀረቡት መልስ ከሳሾች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም በማለት ወስኗል።

የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የሰዉ ምስክሮች በመስማት በሰጠዉ ዉሳኔ የከተማዉ አስተዳደር በጣልቃ ገቦች ይዞታ ላይ ለከሳሾች ካርታ ሰርቶላቸዉ እንደሆነ ወይም መሬቱን በሕጋዊ መንገድ ወስዶ እንደሆነ ከመሬት ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 26፣ 29፣ 30 በደንብ ቁጥር 155/2005 እና የኦሮሚያ ከተማ በሊዝ ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 9/2005 መሰረት በአስተዳደራዊ መንገድ እዛዉ የሚታይ እንጂ በፍ/ቤት የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም፣ የካሳ ጥያቄም ከሆነ መጠኑን ለይተዉ ለብቻ ክስ ማቅረብ ስለሚቻል፣ ጣልቃ ገቦች ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት የለዉም በማለት የቀረበዉን የመቃወሚያ አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የቀድሞዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን አመልካቾች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ከሳሾች የተጓደለዉ ይዞታ ተሟልቶ እንዲሰጣቸዉ በማለት ያቀረቡት ክስም ሆነ የሥር ጣልቃ ገቦች ያቀረቡት አቤቱታ ፍ/ቤት የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ለሥር ፍ/ቤት ቀድሞ እና በኋላ የተሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል። የሥር ከሳሾች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ፍ/ቤት የሥር ከሳሾች ያቀረቡትን ጥያቄ ለማየት ስልጣን የለዉም የሚያስብል ነገር የለም፣ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ጸንቷል፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል። የሥር ጣልቃ ገቦች ይህን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸዉ ተቀባይነት ሳያገኝ ዉድቅ ተደርጎ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጸንቷል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካቾች በ11/10/2007 ዓ.ም በተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የጎደለዉን መሬት አሟልቶ 3ኛ ተጠሪ እንዲሰጣቸዉ ያቀረቡት ዳኝነት ፍ/ቤቶች በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና የኦሮሚያ ክልል የከተማ መሬትን አስተዳደር ያወጣ ሊዝ አዋጅ ቁጥር 55/2006 ለመወሰን ያልተፈቀደላቸዉ ሆኖ ሳለ ያለስልጣን የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ። የአሁን አመልካቾች በዋናነት ያቀረብነዉ የዳኝነት ጥያቄ ለረጅም ዓመታት በእጃችን የቆየዉን ይዞታንና ንብረትን 3ኛ ተጠሪ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ማስረከብ አይገባዉም እንዲሁም በአማራጭ ማስረከብ አለበት የሚባል ከሆነ ካሣ የመጠየቅ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት አመልክተን እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥያቄያችን የመሬት ካሳ ጥያቄ ስለሆነ በፍ/ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈጸመበት ነዉ። ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ተሸሮልን፣ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል።

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማየት የሚጣራ ነጥብ አለ በማለት አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ በታዘዘዉ መሰረት የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሐምሌ 16 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ እና የአሁን 3ኛ ተጠሪ በ15/01/2007 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ሶስት ገጽ አቅርበዉ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል። የመልሱም ይዘት፡ የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ ትክክለኛ ዉሳኔ ስለሆነ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካቾችም የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ያላቸዉን የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ፣ እንዲሁም መደበኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምሮታል። መዝገቡን እንደመረመርነዉ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ሲሆን፣ የዳኝነት ጥያቄአቸዉም በካርታ ላይ ተጠቅሶ ለእያንዳንዳችን የተሰጠዉ ቦታ 200 ካ.ሜ ቢሆንም በእጃችን የገባዉ የቦታ መጠን ከዚህ የሚያንስ በመሆኑ የጎደለዉ ይዞታ ተሟልቶ እንዲሰጠን በማለት 3ኛ ተጠሪን የከሰሱ ሲሆን፣ የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን የዳኝነት ጥያቄ መሰረት በማድረግ ዉሳኔ የሰጠ በመሆኑ፣ የአሁን አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይዞታችን ማስረከብ የለበትም ካልሆነ ካሳ ሊሰጥን ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርቧል። የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት ጥየቄ የጎደለዉ ይዞታ ተሟልቶ እንዲሰጥን የሚል ሲሆን፣ የአሁን አመልካቾች ደግሞ ያለምንም ምትክ ቦታ ወይም ካሳ ይዞታችን ሊወሰድብን አይገባም የሚል መቃወሚያ ማቅረባቸዉን ማየት ይቻላል። የግራ ቀኙ ክርክር የሚያተኩረዉ በአዳማ ከተማ አስተዳደር ሥር ያለውን የከተማ ቦታን የሚመለከት ነዉ። የአዳማ ከተማ አስተዳደር በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ዉስጥ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን ይህን የከተማ ቦታ የሚያስተዳድረዉ የከተማ መሬት የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004፣ ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ ክልሉ ያወጠዉ የከተማ መሬትን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣ ደንብ ቁጥር 155/2005 እና የከተማ መሬትን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 9/2005 በተመለከቱ መርሆዎች መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል። ከከተማ ቦታ ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጥያቄዎች እንዲሁም ቦታን ከማስለቀቅ እና ተያያዥነት ያላቸዉ ጥያቄዎች የሚስተናገዱት በዚህ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሆን ይገባል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አግባብነት ያላቸዉ የአዋጁ ድንጋጌዎች አንቀጽ 26፣ 27፣ 28፣ 29፣ እና 30 ሲሆን፣ የከተማ ቦታን ከማስለቀቅና ምትክ ቦታ እና ካሳን ከመክፈል አንጻር ጉዳዩ የሚታይ መጀመሪያ በሕግ አግባብ በከተማዉ አስተዳደር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተዋቀረዉ አካል እንደሆነ ያመለክታል፡፡ የደንብ 155/2005 አንቀጽ 26፣ 55 እና 56 እንዲሁም የመመሪያ አንቀጽ 33 እና 36 ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንዳለዉ ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ አግባብ ስልጣን የተሰጠዉ የአስተዳደር አካል የከተማ ቦታ ጋር በተያያዘ ለሚነሱ የመብት ጥያቄዎች፣ ይዞታን ለማስለቀቅ ትዕዛዝ ከመስጠት፣ ምትክ ቦታ እና የካሳ መጠን ወስኖ ከማሳወቅ አንጻር ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚህ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ አካል አቤቱታዉን እዛዉ በሕግ አግባብ በተዋቀረዉ አካል ዘንድ ማቅረብ እንዳለበት ነዉ፡፡ ይህ አካል በአቤቱታዉ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ አካል ይግባኙን በከተማ አስተዳደር ደረጃ በተዋቀረዉ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ መብት እንዳለዉ ከአዋጁ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አካሄድ ጉባኤዉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ካሳን በተመለከተ ካልሆነ በስተቀር ሌሎች ምትክ ቦታን ጨምሮ በሌሎች በሕግም ሆነ በፍሬ ነገር ክርክሮች ላይ ጉባኤዉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ የካሳ ጥያቄም ቢሆን በይግባኝ ለመደበኛ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ እንደሚገባ እንጂ ቀጥታ ክስ ሊቀርብ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ ይህ የሚሆነዉ ግን እነዚህ አካላት በሕጉ አግባብ ተዋቅረዉ ከከተማ መሬት ጋር በተያያዘ የሚነሱትን ክርክሮች የሚያስተናግዱበት ሥርዓት የተዘረጋ እንደሆነ ነዉ፡፡ የአሁን አመልካቾችም ሆኑ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ይህ አስተዳደራዊ አካል በህጉ አግባብ ስላልተዋቀረ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ማቅረባቸዉን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ አስደግፈዉ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ስለዚህ ከዚህ አንጻር ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል ያለዉን የጎደለዉ ይዞታ እንዲሟላልን የሚል የዳኝነት ጥያቄ፣ ምትክ ቦታ እና ካሳ ሳይከፈለን ከይዞታችን ልንነቀል እና ማስረከብ የለብንም የሚለዉ የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ በቀጥታ ክስ ለመደበኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ስልጣን ላለዉ የአስተዳደር አካል የሚቀርብ ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ አግባብ በማየት ከግራ ቀኙ የቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄዎች ለመወሰን ስልጣን ስለሌላቸዉ የቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 /2፣ ሀ/ እና 245 /2/ መሰረት ዉድቅ ማድረግ ሲገባቸዉ፣ ጥያቄዉን በመቀበል የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለዉ በመሆኑ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.68317 በ06/12/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.200569 በ13/08/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.204835 በ25/09/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የአዳማ ልዮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.19245 በ04/03/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. መደበኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በቀጥታ ክስ ተቀብሎ አከራክሮ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን የለዉም ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 110901

ግንቦት 24 ቀን 2008ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ንብሩ

ሸምሹ ሺርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ድጋፌ ታደሰ - ጠበቃ ሞገስ ናደው ቀርቧል

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ፍቅርተ ታደሰ ጠበቃ ክፍ አማከለው ቀርቧል

2. አቶ ወንድዬ ታደሰ - ቀርቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለክርክር መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች የውርስ ሃብት ይጠራልኝ ሲሉ ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ፡- አባታቸው አቶ ታደሰ አበበ ሐምሌ 11 ቀን 1974 ዓ.ም ከዚህ አለም የተለዩ ሲሆን ወራሽነታቸው የካቲት 11 ቀን 1975 ዓ.ም በመ/ቁ. 830/75 ያረጋገጡ መሆናቸው፤ ተጠሪዎች የወላጅ አባታቸው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ የሚገኘውን የቤት ቁጥር 092 የሆነውን መኖሪያ ቤት ይዘው ስለሚገኙ የውርስ ሃብት ይጣራልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የቀረበውን አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የውርስ ሃብት ይጣራልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/2/ መሰረት የውርስ ሃብቱ በተጠሪዎች መያዙን ካወቁ ሶስት አመት ካለፈ በኋላ የቀረበ ስለሆነ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በፍሬ ጉዳዩ ላይም የውርስ ሐብቱ ተመዝግቦ የሚገኘው በተጠሪዎች ስም እንጂ በአባታችን አይደለም፡፡ በዚህ ንብረት ላይ ከፍተኛ ንብረት አፍሰውበት ይዘው እንደሚገኙ በመግለፅ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግላቸው መከላከያ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአሁን 2ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ በመፍቀድ ክርክር ካከሄደ በኋላ አመልካች አባታቸው ከሞቱ በኋላ በ1975 ዓ.ም ወራሽነታቸው ያረጋገጡት በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/ የተጠቀሰው የ3 ዓመት ይርጋ ጊዜ ሳያልፍ ስለሆነ የቀረበው መቃወሚያ በብይን ውድቅ በማድረግ፤ የውርስ አጣሪ በመሾም ከዚያም በውርስ አጣሪው የቀረበውን ሪፖርቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ስላልሆነ በማለት ተቀብሎ መዝግቦታል፡፡

ይህ ውሳኔ በመቃወም የአሁኑ ተጠሪዎች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/ መሰረት በ3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይንና ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታው ቢያቀርብም በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ እንዲታረም በማለት የቀረበ ነው፡፡ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ያቀረብኩት አቤቱታ ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ በማናቸውም ጊዜ ውርስ ሀብቱን ለመካፈል የፍ/ብ/ህ/ቁ.1060 አስከ 1113 ባለው ህግ ስር የተሸፈነ ስለሆነ በይርጋ የማይተገድ እያለ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠ ውሳኔ የተፈፀመው መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናት እንዲወሰንለት አቤቱታውን አቅርበዋል፡፡

የቀረበው የሰበር አቤቱታ በመመርመር አመልካች በወቅቱ ወራሽነቱን ማረጋገጡ አልተካደም ተጠሪዎችም የውርስ ንብረቱን በስማቸው በማዞር ካርታ ያሰሩት በ2004 ዓ.ም ከመሆኑ አንፃር የአመልካችን የውርስ ንብረት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነትና የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ተጠሪዎች ንብረቱን በሰማቸው አድርገው ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ ነው ወይስ ሟች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ነው የሚለውን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረትም ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ 2 ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ ጥር 26 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች ያቀረብኩት አቤቱታ ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማናቸውም ጊዜ የውርስ ሀብቱን ለመካፈል የፍ/ብ/ህ/ቁ.1060 አስከ 1113 ባለው ህግ ስር የተሸፈነ ስለሆነ በይርጋ አይታገድም የሚል ነው፡፡ በተጠሪዎች በኩል ደግሞ አመልካች በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1060 ተጠቃሚ የሚሆነው በወቅቱ ውርስ አጣርተው የወርሱ ንብረት በወራሾች የጋራ ስም ተመዝግቦ ወይም ታውቆ የተቀመጠ የውርስ ሀብቱን እንከፋፈል ብሎ ለሚጠይቅ እንጂ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ለሚያቀርብ አይደለም፡፡ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የውርስ ሃብት ይጣራልኝ ስለሆነ አቤቱታና ሪፖርት በይርጋ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተጠሪዎች የውርስ ሀብት ስለያዙ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ የሚል መሆኑ በስር መዝገብ ተመልክቷል፡፡ ከቀረበው አቤቱታ በመነሳት ነው በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የውርስ ሀብት የሚያጣራ በመሾም ሪፖርት ሊቀበል የቻለው፡፡ ስለሆነም አመልካች የውርስ ይጣራልኝ ሳይሆን የውርስ ሀብት ክፍፍል ስለሆነ በይርጋ የሚታገድ አይደለም የሚል ክርክር፤ በስር ያልተነሳና ክርክር ያልተካሄደበት በዚህ ደረጃ መነሳቱ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 83 እና 329/1/ መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

በሌላ በኩል የአመልካች አቤቱታ ይዘት ሲመረመር ለአቤቱታ መነሻ የሆነው የውርስ ሀብት ነው የተባለው ቤት ይዘው የሚኖርበት ወይም በኪራይ በሌላ አግባብ ተጠቃሚ መሆናቸው የሚያመለክት ክርክር የለም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄ የወራሽነት እንጂ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/ መሰረት በሶስት ዓመት ዋጋ የሚታገድ ነው፡፡ ወራሾች ተለይተው የውርስ ሀብቱ ድርሻ ታውቆ ግን ደግሞ ክፍፍል ሳይደረግ የቆየውን የውርስ ሀብት በማናቸውም ጊዜ መጠየቅና በይርጋ የሚታገድ እንዳልሆነ ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1060 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ውርስ ማጣራት በመሆኑ ወራሾች መለየት፤ኑዛዜ መኖሩን አለመኖሩን፤ ዕዳ ጠያቂዎች መኖራቸው አለመኖራቸው፤ የእያንዳንዱ ወራሽ ድርሻ የሚታወቅበትና የሚጣራበት ነው፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ጥያቄ አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሀብት በያዘው ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ተፈፃሚነት ባላው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1000/1/ ድንጋጌ ስር በተመለከተው በሶስት አመት ይርጋ የሚገደብ በመሆኑ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ የፈጸሙት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.107852 ጥር 15 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.151632 ህዳር 18 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለ ችሎት የፌ/የመ/ደ/ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የተሰጠ ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 119704

ሀምሌ 22 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች ፡- የአማራ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት - ነ/ፈ አብርሃም ጌቱ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ዳንኤል ከፋለ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል ፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ተጠሪ በስራ ገበታቸው ባለመገኘታቸው የዲሲፕሊን ቅጣት ተቀጥተው እያለ በዚህ ሳይታረሙ ሃሰተኛ የህክምና ፈቃድ ማስረጃ በማቅረብ ከባድ የድሲፕሊን ጥፋት ፈፅመዋል ተብሎ ከስራ እንዲሰናበቱ በአመልካች ድርጅት የበላይ አካል የተሰጠው ውሳኔ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ታይቶ ውሳኔው መሻሩን በመቃወም አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ይመለከታል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ እንደማንኛውም ታካሚ ካርድ አውጥቼ የታከምኩ በመሆኑና ማስረጃውን ከፈለገ ህይወት ሆስፒታል መቀበሌ ባልተካደበት ሁኔታ በካርዱ ላይ የበሽታው አይነት አልተጠቀሰም በሚል ምክንያት የህክምናው ማስረጃ በሃሰት የቀረበ ነው ተብሎ ጥፋተኛ ተብየ መቀጣቴ አግባብ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በሰጡት መልስ የይ/ባይ ቅሬታ የፍሬ ነገር እንጅ የህግ ስህተት ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፤ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም ይ/ባይ በሃሰት የተዘጋጀ የህክምና ፈቃድ ማስረጃ ያቀረበ ለመሆኑ ማስረጃውን ሰጠ የተባለው ሆስፒታል ያረጋገጠና ጥፋቱ ከባድ ከመሆኑም በላይ ከዚህ በፊትም በዲሲፕሊን የተቀጣ በመሆኑ ከስራው እንዲሰናበት መወሰኑ ተገቢ ነው ተብሎ ውሳኔው እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡

የይግባኝ ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሻሻለው የክልሉ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 200/2005 አንቀፅ 13(2) መሰረት ቦርዱ በፍሬ ነገር ረገድ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ሲሆን ውሳኔው የህግ ስህተት ያለበት ከሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ለማየት ስልጣን እንዳለው መደንገጉን፤ ከዲሲፕሊን መመሪያው አንፃር ከስራ ሊያሰናብተው የሚችል ጥፋት ፈፅሟል/አልፈፀመም የሚለው ጭብጥ የህግ ክርክር በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንዳለው፤ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም በድርጅቱ የሥነ ምግባር እና የድስፕሊን መመሪያ ቁጥር 002/2006 አንቀፅ 24(3) መሰረት ሃሰተኛ ማስረጃ ማቅረብ ከባድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዲሲፕሊን ጥፋት መሆኑ መደንገጉን፤ ማስረጃውን ሰጠ የተባለው ሆስፒታል የማስረጃውን ትክክለኛነት እንዲያረጋግጥ ተጠይቆ የህክምና ካርዱን አውጥቶ በመመልከት ህመሙን የሚያስረዳ ነገር ካርዱ ላይ ያልተገለፀ በመሆኑ የህክምና ማስረጃው ህጋዊ አይደለም የሚል ምላሽ መሰጡን፤ ነገር ግን የህክምና ፈቃድ ማስረጃው ከሆስፒታሉ የተሰጠ ለመሆኑ ባልተካደበት ሁኔታ በካርዱ ላይ የበሽታው አይነት አልተገለፀም በሚል ምክንያት ተጠሪ ሀሰተኛ ማስረጃ አቅርቧል ተብሎ ጥፋተኛ መባሉ አግባብ አይደለም በማለት የዲሲፕሊን ኮሚቴው እና ዋና ስራ አስኪያጁ እንዲሁም ቦርዱ የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ያልተከፈለው ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው እንዲመለስ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት ቅሬታውን ሳይቀበል ቀርቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይህን በመቃወም ነው፡፡ ህዳር 3/2008 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ የፈለገ ህይወት ሆስፒታል ተጠሪ ያቀረበው የሐኪም ማስረጃ ህጋዊ አይደለም በማለት እያረጋገጠ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ሐሰተኛ ሰነድ አላቀረበም በማለት ወደ ስራው እንዲመለስ የመወሰኑን አግባብ ለማጣራት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅሁፍ እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከፍ ሲል በተጠቀሰው የድርጅቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃውን ለመመዘን ስልጣን የተሰጠው የድርጅቱ የበላይ አካል ተጠሪ በተደጋጋሚ በስራ ገበታው የማይገኝ፤ በምክር እና በቅጣትም ሊመለስና ሊማር ያለመቻሉን፤ እንዲሁም ከስምሪትና ከተቋሙ ፈቃድ ውጪ ሰቆጣ መሄዱ እና እዚያ የታየ ስለሆነ ለዚሁ እንዲረዳው ከፈለገ ህይወት ሆስፒታል የ10 (አስር) ቀን የህክምና ማስረጃ ማምጣቱን፤ ሆስፒታሉም ስለማስረጃው ትክክለኛነት ተጠይቆ የተሰጠው የሀኪም ማስረጃ ትክክለኛ አለመሆኑን ገልጾ መሰጡን ፤ ይህም በተቋሙ የዲሲፕሊን መመሪያ አንቀፅ 23 መሰረት ከስራ የሚያሰናብት ከባድ ጥፋት መሆኑን በማረጋገጥ ከ19/05/2007 ዓ.ም ጀምሮ ከተቋሙ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን ውሳኔ የሻረው የህክምና ፈቃድ ማስረጃው ከሆስፒታሉ የተሰጠ ለመሆኑ አልተካደም፤ በካርዱ ላይ የበሽታው አይነት ሳይገለፅ መገኘቱም ተጠሪ ሀሰተኛ ማስረጃ አቅርቧል አያሰኝም በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ስልጣን ያለው አካል በፍሬ ነገር ረገድ ያረጋገጠውን ሳይቀበል ማለፉና ማስረጃውን በመመዘን የራሱ መደምደሚያ ላይ መድረሱ በህጉ የተሰጠውን ስልጣን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን ይመዝን ቢባል እንኳ የህክምና ማስረጃው ወጣ የተባለበት የፈለገ ህይወት ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር በቁጥር 959/2687/06 በ26/12/06 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከሆስፒታሉ ተወሰደ የተባለው የሀኪም ዕረፍት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ በተመለከተ አጣርቶ ህጋዊ አለመሆኑን እያረጋገጠ ፍርድ ቤቱ ማስረጃው ከሆስፒታሉ የተሰጠ ለመሆኑ እስካልተካደ ሀሰተኛ ሊባል አይችልም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ አይደለም፡፡ መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ሲባል አንድን ፍሬ ነገር ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በማስረጃነት የሚቀርቡ ዕሁፎችን (ሰነዶችን) በሃሰት መፍጠርም ሆነ በእነዚህና መሰል ዕሁፎች መገልገል የድሲፕሊን እና የወንጀል ጥፋተኝነትን የሚያስከትል በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ውሳኔ በህጉ የተደነገገውን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን በተመለከተ የሰጠው ትርጉምና የደረሰበት መደምደሚያ እንዲሁም ይህን ተከትሎ ያሳለፈው ውሳኔ ህጋዊ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች ድርጅት የበላይ አካል (ቦርዱ) በፍሬ ነገር ረገድ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ ይኸው አካል በፍሬ ነገር ረገድ በደረሰበት መደምደሚያ ላይ ተመስርቶ ያሳለፈውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተመልክቶ ውሳኔው የህግ ስህተት ያለበት ከሆነ ማረም ሲገባው ከዚህ አልፎ ፍሬ ጉዳዩን ለማጣራት ማስረጃውን መመዘኑ ህጉን የተከተለ ካለመሆኑም በላይ ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን በመመዘን የደረሰበት መደምደሚያም የተሻሻለውን የክልሉ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 200/2005 አንቀፅ 13(2) እና አመልካች ያወጣውን የሥነ ምግባር እና የዲስፕሊን መመሪያ ቁጥር 002/2006 አንቀፅ 24(3) ድንጋጌዎች እንዲሁም በሃሰተኛ ማስረጃ ስለመገልገል በህጉ የተደነገገውን የጣሰና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ሰላገኘነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያሳለፈው ውሳኔ እና የሰበር ችሎቱ የሰጠው ትዕዛዝ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 40498 ጥቅምት 02 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/አ/መ/ቁ 51812 ጥቅምት 18 ቀን 2008 ዓ/ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአማራ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ በ7/5/2007 ዓ.ም፤ እንዲሁም ቦርዱ በ22/7/2007 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
መስጠፉ አህመድ
አብርሃ መሰለ
አብዬ ካሣሁን
እትመት አሰፋ

አመልካች፡-1. አቶ ሚሪንዳ ዋሲሁን
2. አቶ መንግስቱ በለጠ
3. አቶ ፍቃዱ
4. አቶ ሰይፉ ለማ
5. አቶ ውድነህ ዘለቀ
6. ወ/ሮ አመለወርቅ ባቾሌ
7. ወ/ሮ ገነት አድነው
8. አቶ አብነት ዩሐንስ
9. ወ/ሮ ብርቁ መሻሸ
10. አቶ ሱልጣን ኡስማን

የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ኢትዩ ቴሌኮም - ነ/ፈጅ አደመ አየለ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የተጀመረ ነው፡፡ ክርክሩ የበርሃ አበል ከደመወዝ ጋር ተደምሮ የገቢ ግብር እንዲከፈልበት መደረጉ ያላግባብ ነው በሚለው የአመልካቾች ክስ መነሻ የተጀመረ ነው፡፡

አመልካቾች ለስራ ወደ ጉጂ ዞን ሊበን ወረዳ ነገሌ ከተማ አስተዳደር በነገሌ ቦረና ሾፕ ስር ተጠሪ መድቧቸው በመስራት ላይ እያሉ በዚሁ አካባቢ ለሚሰሩ ሰራኞች 30% የበረሃ አበል ምክንያት እስከ ግንቦት ወር 2004 ዓ/ም ድረስ ሲከፈላቸው መቆየቱንና ከግንቦት ወር 2004 ዓ/ም በኋላ ግን ባልታወቀ ምክንያት ይከፈላቸው የነበረው የ30% የበርሃ አበል ላይ በወር ከሚያገኙት ደመወዝ ጋር በመደመር ያላግባብ ግብር እየተቆረጠባቸው ከፍተኛ የመብት ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑን ገልፀው ይኼው የተጠሪ እርምጃ ተገቢ ያለመሆኑ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው የመከላከያ መልስ ክርክርም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደረጃ መቃወሚያት ያነሳውም ጉዳዩ በቦርዱ ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም የሚል ሲሆን መቃወሚያው የቀረበለት ቦርድም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 147(1(ሀ)) ስር ስልጣኑ በግልጽ መደንገጉንና የአመልካቾች ጥያቄ ደግሞ በዚህ ድንጋጌ ስር የማይወድቅ መሆኑን ገልጾ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ አመልካቾች ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን ስር እንደሚወድቅ አምነው በቦርዱ ላይ ክስ ከአቀረቡና ተጠሪም ይህንኑ በመቃወሙ በተሰጠው ብይን ላይ ይግባኙ መቅረብ ያለበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 139 (ለ) መሰረት በክልሉ ላለው የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይሆን በአዋጁ አንቀፅ 154 በተደነገገው መሰረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት ይግባኛቸውን ሰርዞታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካቾች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበውም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ጉዳዩ የወል የሥራ ክርክር ሁኖ እያለ ቦርዱ በስልጣኔ ስር አይወድቅም ማለቱም ሆነ የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙ የሚቀርበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት ብይን ሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መፅናቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ የጹሑፍ መልስ የሰጠ ሲሆን በመልሱ ላይም ጉዳዩ በቋሚ ቦርድ ስልጣን ስር እንደማይወድቅና ጉዳዩን ለማየት የሚችል አካልም በአዋጅ ቁጥር 466/97 አግባብ በክልሉ ያለ ቋሚ ቦርድ ያለመሆኑን፣ ተጠሪ እጅግ አስፈላጊ ከሚባሉት መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች መካከል አንዱ በመሆኑ የአመልካቾች ጥያቄው በክስ ሊታይ የማይችል መሆኑን ዘርዝሮ በአመልካቾች የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይህም ችሎት በቅድሚያ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው አቢይ የህግ ነጥብ ላይ ብቻ በማተኮር መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዋነኛነት ሊፈታ የሚገባው የነገሩ ጭብጥ፡- አንድ ጉዳይ የወል የስራ ክርክር ነው በሚል እምነት በቋሚ ቦርዱ ከቀረበ በኋላ ቋሚ ቦርዱ በስልጣኑ ስር የማይወድቅ መሆኑን ገልፆ መዝገቡን ሲዘጋው ይግባኙ መቅረብ ያለበት ለየትኛው ፍርድ ቤት ነው? የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ የማግኘቱ ጉዳይ ስለ ስራ ክርክር፣ ስለ ቦርድና ስለ ፍርድ ቤት ሥልጣን የሚገልጹትን የአዋጅ ቁ. 377/96 ድንጋጌዎችን ተመስርቶ ጭብጡን መመርመርን ይጠይቃል፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 በኋላ የወጣ ሲሆን በአንቀጽ 136(3) ስለ ስራ ክርክር ምንነት ትርጓሜ የሚሰጥ ድንጋጌ ከመያዙም በላይ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 137 ደግሞ የስራ ክርክር ችሎት መቋቋማቸውን በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ በዚህም መሰረት የአዋጁ አንቀጽ 147

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለቦርድ ሥልጣን የሚደነግገው ሲሆን የፍ/ቤት ስልጣን ደግሞ የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 138/2/ ነው። በአዋጁ አንቀጽ 138/1/ የተዘረዘሩትንና መሰል የግል የሥራ ክርክሮችን የመዳኘት ሥልጣን ለፍርድ ቤት መስጠቱን ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። አዋጁ የስራ ክርክርን የክልልና የፌዴራል ጉዳይ ነው የሚል መለኪያ በመስጠት የስነ-ነገር የዳኝነት ስልጣን መከፋፈሉን በግልፅ አያሳይም። በአዋጅ ቁጥር 322/95"ም" ሆነ በሕገ መንግስቱ መሰረት የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስራ ክርክርን አስመልክቶ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በውክልና ሊመለከት ይችላል የሚባልበት አግባብም የለም። በአዋጁ አንቀፅ 138(1) ድንጋጌ መሰረት ለፍርድ ቤት የተሰጡትን የስራ ክርክሮችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት(የወረዳ ፍርድ ቤት) መሆኑ በግልፅ ተቀምጧል። የአዋጁ አንቀጽ 139(1(ሀ)) ደግሞ በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በስራ ክርክር ችሎት የተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት የይግባኝ ስልጣን እንዳለው ያሳያል። በመሆኑም የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 138 መሰረት በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚታዩት ጉዳዮች ላይ የይግባኝ ስልጣን ያለው መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 139(1(ሀ)) በግልፅ ያሳያል።

በሌላ በኩል በክልል በተቋቋሙ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶች በሚሰጡ ብይኖች እና ውሳኔዎች ይግባኙ የሚቀርበው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 154 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 466/97 ድንጋጌዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መሆኑ ይታወቃል። በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 154 እንደተመለከተው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በተሰጠ ብይን ወይም ውሳኔ ላይ ይግባኝ መቅረብ ያለበት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ተደንግጓል። በአዋጅ ቁጥር 322/95 ከተደነገገው ውጪ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመደበኛነት የተዋቀሩት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች መሆኑ ይታወቃል። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ- መንግሥት አንቀጽ 78/2/ እንደተደነገገው ክርክር የተነሣበትን ክልል ጨምሮ በአፋር፣ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል፣ በሱማሌና በደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመደራጀቱ በአዋጅ ቁጥር 322/95 አንቀጽ 2 ስር በግልጽ ተደንግጓል። ይህ ማለት ግን በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተዘረጋውን የይግባኝ ስርዓት ቀሪ የሚያደርግ አይደለም። በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 113675 ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል። ስለሆነም ሰራተኞች ተጠሪን ከሚመስሉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጋር በክልሎች የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶች በሚያቀርቧቸው ክሶች የሚነሱ የይግባኝ ቅሬታዎች ላይ ይግባኝ ማቅረብ ያለባቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 154(1) ስር የተቀመጠውን መሰረት በማድረግ በአዋጅ ቁጥር 322/95 የተደነገገውን ስርዓትና በሕገ መንግስቱ በተሰጠው የውክልና ስልጣን አግባብ ሳይሆንን በአዋጅ ቁጥር 377/96 በተዘረጋው የይግባኝ አቀራረብ ስርዓት ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንጻር ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 322/95 አግባብ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተደራጀባቸውና ባልተደራጀባቸው ክልሎች ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚነሱ ይግባኞች መቅረብ ያለባቸው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(2) ድንጋጌ መሰረት ከፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጋር አቻ ስልጣን ላላቸው ለክልሉ ላሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 154 መገንዘብ የሚቻል ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም አመልካቾች ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር ነው የሚል የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ባደረገ መልኩ ክስ ያቀረቡ ስለመሆናቸው የክርክሩ ሂደት ስለሚያሳይ እና ይኼው ጥያቄ የቀረበት ቦርድ ደግሞ ተገቢ ነው ያለውን ብይን ከሰጠ በዚሁ ብይን ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ማቅረብ ያለበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 154(1) እና ለዚህ ድንጋጌ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 113675 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው፡፡ የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የተነሳ መሆኑን የተገነዘበና ራሱ ይግባኙን አላይም በማለት ብይን መስጠቱ ተገቢ ቢሆንም ጉዳዩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት በማለት ብይን መስጠቱ ግን ከላይ የተዘረዘረውን የሕግ ማዕቀፍና ስለሕግ ማዕቀፉ ትክክለኛ አተገባበር ይህ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ የተፈጸመውን የሕግ ስህተት ሳያርም ብይኑን ማፅናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈጸሙን የሚያሳይ ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 64715 ሰኔ 01 ቀን 2007 ዓ/ም የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ጉዳዩ በይግባኝ ስልጣን ደረጃ ሊታይ የሚገባው በክልሉ በተደራጀው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይሆን በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው ብለናል፡፡ አመልካቾች አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉምሩክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 101462

ሐምሌ 20 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፉ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ነጂብ አደም አቡበክር - ጠበቃ ጌቱ ሶራሳ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ሕግ - ነስሪያ ሡልጣን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን ሁለት የወንጀል ክሶች የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ በማለት በመዝገብ ቁጥር 179576 በ14/02/2006 ዓ.ም. እና በ22/02/2006 ዓ.ም. የሰጠባቸው እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 143236 በ08/07/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት በአሁኑ አመልካች እና የተጠሪ ተቋም ሰራተኛ በነበሩት የስር 2ኛ ተከሳሽ አቶ ስዩም በላቸው ላይ በ15/03/2004 ዓ.ም. አሻሽሎ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- በአንደኛ ክስ ተከሳሾቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 95 (1) (ሐ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ 1ኛ ተከሳሽ ረዳት የጉምሩክ አስተላላፊ፣2ኛ ተከሳሽ ደግሞ የጉምሩክ መጋዘን ሰራተኛ ሆነው ሲሰሩ በ17/08/2003 ዓ.ም. ተለይቶ ባልታወቀ ሰዓት 1ኛ ተከሳሽ ቁጥሩ C-5446/2011 የሆነ ሀሰተኛ ዲክላራሲዮን እና ሀሰተኛ የናሙና መጠየቂያ ፎርም ይዞ ወደ መጋዘን ቁጥር 8 በመቅረብ እና የዚሁ መጋዘን ሰራተኛ የነበረው 2ኛ ተከሳሽም በዚሁ ድርጊት በመተባበር በግል ተበዳይ ለትውልድ ምስክር አስመጪነት በመጋዘኑ ውስጥ የነበረውን ኮንቴይነር ቁልፍ ገንጥለው ቀረጥና ታክስን ጨምሮ የዋጋ ግምታቸው ብር 54,733.07 የሆነ ሁለት ቴሌቪዥኖችን የወሰዱ በመሆኑ አግባብ ካለው የባለስልጣኑ ሹም ፈቃድ ሳያገኙ እሽጎችን የመፍታት እና ምልቶችን የማንሳት ወንጀል አድርገዋል፤በሁለተኛ ክስ ተከሳሾቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 94 (1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የባለስልጣኑን ሰነዶች እና መለያዎች ወደ ሀሰት የመለወጥ ወንጀል አድርገዋል የሚል ነው።

አመልካቹ ያቀረቡት መቃወሚያ ውደቅ ተደርጎ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ወንጀሉን አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ የግል ተበዳይን ጨምሮ በተጠሪው በኩል የተቆጠሩትን ስምንት ምስክሮች ከሰማ እና የተጠሪውን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቹ እንዲከላከሉ በሰጠው ብይን መሰረት ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ ሰነዶችንም በመከላከያ ማስረጃነት አቅርበዋል።ፍርድ ቤቱም አመልካቹ ባሰሟቸው ምስክሮች እና ባቀረቧቸው ሰነዶች በተጠሪ ማስረጃ የተመሰከረባቸውን ማስረጃ ማስተባበል አለመቻላቸውን ገልጾ በሁለቱም ክሶች በተጠቀሱባቸው ድንጋጌዎች ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ ወንጀሎቹ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ደረጃ ያልወጣላቸው መሆኑን ገልጾ በሁለቱም ክሶች ወንጀሉን በዝቅተኛ ደረጃ መድቦ ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ የሆነውን እንደቅደም ተከተሉ ሰባት ዓመት እና አምስት ዓመት ደምሮ የ12 ዓመት ጽኑ እስራት መነሻ አድርጎ በመያዝ፣ይህ የቅጣት መጠን የሚወድቀው በአባሪ አንድ በእርከን 29 ስር መሆኑን በመግለጽ፣ወንጀሉ የተደረገው በግብረአበርነት መሆኑን በምክንያትነት ይዞ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 84 (1) (መ) መሰረት ቅጣቱን በአንድ ማክበጃ ወደ እርከን 30 ከፍ በማድረግ እና ቀጥሎም የቀድሞ ጸባይ መልካምነትን እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነትን በሁለት የማቅለያ ምክንያትነት ተቀብሎ ቅጣቱን ወደ እርከን 28 ዝቅ በማድረግ እና ለሁለቱ ወንጀሎች የተቀመጠውን መነሻ መቀጮ እንደቅደም ተከተላቸው ብር 5,000 እና ብር 10,000 ደምሮ ተከሳሾቹ እያንዳንዳቸው በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 15,000 (አስራ አምስት ሺህ) መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሁለቱ ተከሳሾች በተለያዩ መዝገቦች ያቀረቡትን ይግባኝ አጣምሮ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ በ2ኛ ክስ ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር እና በ1ኛ ክስ ስር የተሰጠበትን የቅጣት መጠን በማሻሻል በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር ሁለት ሺህ መቀጮ እንዲቀጡ ሲወስን የአሁኑን አመልካች ይግባኝ ግን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል።የስር 2ኛ ተከሳሽ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ያቀረቡት አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101241 በ25/10/2006 ዓ.ም. በተሰጠ ትዕዛዝ ውድቅ የተደረገ መሆኑንም መዝገቡን አስቀርበን ተመልክተናል፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በ1ኛው ክስ ስር ጥፋተኛ መባላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ 2ኛውን ክስ በተመለከተ ግን ድርጊቱን መፈጸሙ ግምት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያስወስድ ነው የመባሉን አግባብነት ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

1. አመልካቹ በሁለቱም የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ የተባሉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?
2. ቅጣቱ ሊሻሻል ይገባል ወይስ አይገባም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቹ ወንጀሎቹን አላደረግሁም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ተጠሪው ያቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ አጠቃላይ ይዘት ሲታይ አመልካቹ ረዳት የጉምሩክ አስተላላፊ ሆነው ይሰሩ የነበረ መሆኑን፣በስራው ደንብ መሰረት እሽጎች ተከፍተው ናሙና ሊወሰድ የሚችለው ባለዕቃውን፣የጉምሩክ ሹምን እና የመጋዘን ኃላፊውን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው አካላት በተገኙበት መሆኑን፣አመልካች ሀሰተኛ የናሙና መጠየቂያ ቅጽ ይዘው በመቅረብ እና ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በመተባበር ለናሙና ነው በሚል እሽጉን ከፍተው ሁለት ቴሌቪዥኖችን የወሰዱት ከእርሳቸው እና ከመጋዘን ጠባቂው ውጪ ሌላ ሰው ባልተገኘበት መሆኑን፣በግል ተበዳይ አስመጪነት ከመጣው ዕቃ ውስጥ ናሙና እንዲወሰድ በባለስልጣኑ የተሰጠ ትዕዛዝ አለመኖሩን፣ ቴሌቪዥኖቹ ከተወሰዱ በኃላ አመልካች ሞባይል ስልካቸውን አጥፍተው ከግል ተበዳይ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ያቋረጡ መሆኑን እና መሰል ፍሬ ነገሮችን የሚያረጋግጥ ሲሆን ከተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች መካከል በተጠሪ ተቋም መጋዘን የገቢ እና የወጪ ዕቃዎች መዝጋቢ መሆናቸውን የገለጹት 8ኛው ምስክር አመልካቹ ሰነዱን በማቅረብ የስር 2ኛ ተከሳሽ ከሚጠብቁት መጋዘን ቴሌቪዥኖቹን ይዘው ሲወጡ ማየታቸውን በማረጋገጥ የመሰከሩ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካቹ ወንጀሎቹን አለማድረጌን ያስረዱልኛል በማለት ያቀረቡት የሰው እና የሰነድ ማስረጃ የተጠሪን ማስረጃ ሊያስተባብል ያልቻለ ስለመሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው ሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች የተስማሙበት ጉዳይ ሲሆን በ1ኛ ክስ የተሰጠባቸውን የጥፋተኝነት ውሳኔ አስመልክቶ አመልካቹ ያቀረቡት የአቤቱታ ነጥብ በአጣሪው ችሎትም ቢሆን ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን ከማስቀረቢያ ጭብጡ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡2ኛውን ክስ በተመለከተ አመልካች ድርጊቱን መፈጸሙ ግምት የሚያስወስድ ነው የመባሉን አግባብነት ለማጣራት በሚል በአጣሪው ችሎት የተያዘውን ነጥብ በተመለከተ በመሰረቱ ይህ አነጋገር የተገለጸው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ሲሆን የተገለጸውም የአሁኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በሚመለከት ሳይሆን የስር 2ኛ ተከሳሽን በሚመለከት ሆኖ ከድርጊቱ አጠቃላይ አፈጻጸም አንጻር 2ኛ ተከሳሽ በ1ኛው ክስ በተመለከተው ወንጀል ከአሁኑ አመልካች ጋር ወንጀሉን በመተባበር ያደረገው ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድበት ነው ተብሎ ነው፡፡በሌላ በኩል አመልካች ቴሌቪዥኖቹን ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር መሆኑን እሸጉን ከፍቶ የወሰደው ሀሰተኛ የሆነ የናሙና መጠየቂያ ፎርም ለተጠሪ 8ኛ ምስክር በማቅረብ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ይህ በሁለተኛ ክስ የተመለከተው የባለስልጣኑ ሰነዶችን ወደ ሀሰት የመለወጥ ተግባር ራሱን ችሎ በአዋጁ በወንጀልነት የተደነገገ በመሆኑ በማስረጃ በተረጋገጠው መሰረት አመልካቹ በ2ኛው ክስ ጭምር ጥፋተኛ መባሉን የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው የስር 2ኛ ተከሳሽ ከ2ኛው ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ የተደረገው የሰነዱን ሀሰተኛነት ያውቁ የነበረ ወይም ማወቅ ይገባቸው የነበረ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል እንጂ የሰነዱ ሀሰተኛነት ጉዳይ ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካቹን በሁለቱም ወንጀሎች ጥፋተኛ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አላገኝንም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ድንጋጌዎች ሲሆን ጉዳዩ በስር የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ካገኘ በኃላ በዚህ የሰበር ደረጃ በክርክር ላይ ባለበት ሂደት አመልካቹ ጥፋተኛ ተብለውበት የነበረው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ከ30/03/2007 ዓ.ም. ጀምሮ ተሽሮ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ተተክቷል፡፡ አመልካች የተከሰሱባቸው ድርጊቶች በአዲሱ አዋጅም ቢሆን እንደቅደም ተከተላቸው በአንቀጽ 170 (1) እና በአንቀጽ 167 (1) ስር በወንጀልነት ተደንግገዋል፡፡ለ2ኛው ክስ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ ሕግ የተደነገገው የእስራት ቅጣት መጠን ተመሳሳይ ሲሆን በ1ኛው ክስ በቀድሞው ሕግ በአንቀጽ 95 (1) (ሐ) ስር ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት ጽኑ እስራት ሊደርስ ይችል የነበረው የቅጣት መጠን ግን በአዲሱ ሕግ ከአምስት ዓመት ወደማያንስ እና ከአስር ዓመት ወደማይበልጥ ጽኑ እስራት ዝቅ የተደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በአንድ በኩል አዲሱ የወንጀል ሕግ እንዲጸና ከተደረገ በኃላ አድራጊው ሕጉ ከመጽናቱ በፊት ላደረገው ወንጀል ሲፈረድበት ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው ሕግ ይልቅ አዲሱ ሕግ ቅጣትን የሚያቃልለት በሆነ ጊዜ ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተመለከተው ቅጣት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ጠቅላላ ክፍል በአንቀጽ 6 ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ከጸናበት ቀን በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች ፍጻሜ የሚያገኙት በነበረው ሕግ መሰረት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 182 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሰረቱ ደርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣው ሕግ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 (2) ስር የተደነገገ ከመሆኑም በላይ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ከጸናበት ቀን በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች ፍጻሜ የሚያገኙት በነበረው ሕግ መሰረት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 182 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ክርክር ስላስነሳው ጉዳይ በሌሎች ሕጎች የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በማይነካ ሁኔታ ስለመሆኑ ከላይ ከተጠቀሰው የአዋጁ አንቀጽ 182 ድንጋጌ አነጋገር መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ በአዋጁ አንቀጽ 182 የተመለከተው ድንጋጌ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ጠቅላላ ክፍል በአንቀጽ 6 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተፈጻሚነት የማያስቀር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም በ1ኛው ክስ በአመልካቹ ላይ ለሚጣለው ቅጣት መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በአንቀጽ 170 (1) ስር የተመለከተው የቅጣት መጠን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቹ ወንጀሎቹን ያደረጉት በ17/08/2003 ዓ.ም. ሲሆን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው ደግሞ እንደቅደም ተከተሉ በ14/02/2006 ዓ.ም. እና በ22/02/2006 ዓ.ም. ነው፡፡ይህንኑ ጊዜ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች ቅጣቱ የተሰላውም ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ በዋለው የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ ነው፡፡የጥፋተኝት እና የቅጣት ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ይልቅ ለተከሳሽ ወገን ቅጣቱን የሚያቀለው ወንጀሉ በተደረገበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ከሆነ ለቅጣቱ አወሳሰን መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው ይኸው መመሪያ ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 95440 እና በሌሎችም መዝገቦች በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ለቅጣቱ አወሳሰን መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው የቀድሞው መመሪያ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ከላይ በተገለጸው ሁኔታ በሁለቱ ወንጀሎች በአመልካቹ ላይ ሊጣል የሚገባው መነሻ ቅጣት የአስር ዓመት ጽኑ እስራት ሲሆን ይህም በአባሪ አንድ በእርከን 27 ስር የሚወድቅ ነው፡፡ይህ የቅጣት መጠን በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኘው አንድ የማክበጃ ምክንያት ወደ እርከን 28 ከፍ ከተደረገ በኃላ በተመሳሳይ ሁኔታ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኙት ሁለት የማቅለያ ምክንያቶች ወደ እርከን 24 ዝቅ የሚደረግ በመሆኑ በአመልካቹ ላይ ለሚጣለው ቅጣት መነሻ ተደርጎ መያዝ የሚገባው በእርከን 24 ስር የተመለከተው የቅጣት ፍቅድ ስልጣን ነው፡፡በተመሳሳይ ምክንያት በመቀጮው መጠን ላይም ተገቢው ማሻሻያ ሊደረግበት የሚገባ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል በአመልካቹ ላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ባይሆንም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በአመልካቹ ላይ ተጥሎ የነበረው የቅጣት መጠን ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በአመልካቹ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሁለቱም ክሶች በመዝገብ ቁጥር 179576 በ14/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 143236 በ08/07/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሁለቱ ክሶች በመዝገብ ቁጥር 179576 በ22/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 143236 በ08/07/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናውን የዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት የብር አስራ አምስት ሺህ መቀጮ የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት በማሻሻል አመልካቹ በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ሁሉ ታስቦላቸው በሰባት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር ስምንት ሺህ መቀጮ እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
3. በተሻሻለው የጽኑ እስራት ቅጣት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመሸኛ ትዕዛዝ ጋር አመልካቹ ለሚገኙበት የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ፡፡
4. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 111960

ህዳር 06 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዐ/ህግ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- ሰይፈ አበበ ንጉሴ - በሌለበት ታይቶ የተወሰነ በመሆኑ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ተከሳሽ (ተጠሪ) አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 በመተላለፍ የኮንትሮባንድ እቃ የጉምሩክ ስርዓት ያልተፈጸመበት መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ እያለበት 21 ጆሪካን ዘይት ቀረጥና ታክስ መጠኑ በአጠቃላይ ብር 6025.45 (ስድስት ሺህ ሃያ አምስት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም) የሆነ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ሸንት ቤት ክፍል ውስጥ ተከማችቶ እጅ ከፍንጅ ስለተያዘ የኮንትሮባንድ እቃ ይዞ በመገኘት ወንጀል ፈጽሞ ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ፍቃድ እያለኝ ከእኔ ላይ የተያዘው ስለሆነ ህጋዊ ነኝ ጥፋት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ከሳሽ የአሁኑ አመልካች የሆነው ዐቃቤ ህግ ሁለት ምስክሮችን ያሰማ ሲሆን ተከሳሽም ሁለት መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አስመስክሯል፡፡ የጽሁፍ መከላከያ ማስረጃ በቀን 30/01/2004 ዓ/ም የተሰጠ እስከ 2007 ዓ/ም የታደሰ የምግብ ዘይት የንግድ ፈቃድ ተከሳሽ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን የተመለከተው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽን (የአሁኑ ተጠሪን) ተከላክሏል በማለት በወንጀል ስነስርዓት ህግ ቁጥር 149(2) መሰረት በነጻ እንዲሰናበት በማለት የአሁኑ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ በወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 195(1) መሰረት በመ/ቁ.200935 በቀን 01/07/2007 ዓ/ም ዘግቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡-

1. የስር ፍርድ ቤቶች በጅምላ ተጠሪው የታደሰ የንግድ ፍቃድ መኖሩን በማረጋገጡ ብቻ ከኮንትሮ ባንድ ወንጀል ሃላፊነት ያድናል ማለት መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ነው፣
2. የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 መሰረት ማንኛውም ስሪት ሃገሩ የውጪ የሆነ እቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በነጻ ዝውውር እንደማይለቀቅ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪው ከኮንትሮ ባንድ ወንጀል ሃላፊነት ነጻ ለመሆን ለእቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የእቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) የማቅረብ ህጋዊ ግዴታ እያለበት የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ታክስ ከፍሎ ንግድ ፍቃድ አውጥቷል በማለት በነጻ ማሰናበታቸው የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትዕዛዝ ተሰጥቶ አመልካች ተጠሪን ፈልጎ ያለማግኘቱን ገልጾ ጥሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ በዚሁ መሰረት ሀምሌ 6 ቀን 2007 ዓ/ም በታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ ስላልቀረበ በሌለበት ታይቶ እንዲወሰን ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

የክርክሩ ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ጉዳዩን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፤አመልካች ካቀረበው አቤቱታ እንዲሁም አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም በተጠሪ መኖሪያ ቤት ውስጥ በሚገኘው ሸንተ ቤት ውስጥ በክሱ የተጠቀሰው 21 ጆሪካን ዘይት ተይዟል፡፡ በክሱ ውስጥ የተጠቀሰ መጋዘን እየታደሰ ዘይቱ አዲስ ሸንተ ቤት ውስጥ ከሌሎች የሱቅ እቃዎች ጋር መገኘቱን የከሳሽም ሆነ የተከሳሽ ምስክሮች በተመሳሳይ ሁኔታ መስክረዋል፡፡ ተከሳሽ (ተጠሪ) በ2004 ዓ/ም የተሰጠ የዘይት ንግድ ፍቃድ እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ የታደሰውን ማቅረቡ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጧል፡፡ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ተከላክሏል በማለት በነጻ አሰናብቷል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 መሰረት ተጠሪው ከተከሰሰበት ወንጀል ሃላፊነት ነጻ ለመሆን ለእቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የዕቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) የማቅረብ ህጋዊ ግዴታ እንዳለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመልክቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪው የዘይት ንግድ ፈቃድ አለው ከመባሉ በስተቀር ዘይቱን ከማንና ከየት እንደገዛ እንዲሁም ለገዛበት ዘይት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የእቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) ተጠሪ አቅርቦ አላረጋገጠም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ተጠሪ ተከላክሏል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሆኖም ግን አከራካሪ ሆኖ የታየው ተጠሪ በተከሰሰበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 “ህገ ወጥ እቃዎች ይዞ ስለመገኘት” ተብሎ የተደነገገው ድንጋጌ ይህን አዋጅ በተካው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ ወንጀል ሆኖ ተደንግጓል ወይስ አልተደነገገም? የሚለውነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ አልተደነገገም፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 168 የተደነገገው “የኮንትሮ ባንድ ወንጀል” በሚል ነው፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የተደነገገነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 የተደነገገው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ካልተደነገገ ህጋዊ መፍትሔ (legal remedy) ምንድነው? የሚለው ምላሽ ሊያገኝ ይገባል፡፡ ይህ አዋጅ ግን ይህንን ጥያቄ የሚመልስ የህግ መርህ አይደነግግም፡፡ በዚህ ጊዜ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት የተደነገገው መሰረታዊ መርህ እንዲሁም በወንጀል ህጉ በመርህነት የተደነገገው ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በሌላ አነጋገር በኢፌዲሪ ህገ መንግስትና በወንጀል ህግ ከተደነገገው መሰረታዊ መርህ አንጻር ታይቶ መተርጎም ይኖርበታል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22 የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 5 በተመሳሳይ መልኩ ደንግጎታል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22(2) ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኃላ የወጣ ህግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል በማለት ተደንግጓል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 5(3) የተሻረው ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከሰሰም ሆነ ሊያስቀጣ አይችልም፤ ክሱም ተጀምሮ እንደሆነ ይቋረጣል ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የፈጸመው ድርጊት ምንም እንኳን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 ላይ ወንጀል ሆኖ የተደነገገ ቢሆንም በዚህ አዋጅ ምትክ በተተካው አዋጅ ቁጥር 859/2006 ወንጀል ሆኖ አልተደነገገም፡፡ ስለዚህ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት እና በወንጀል ህጉ በተደነገገው መሰረታዊ መርህ አንጻር ሲደመደም ተጠሪ ጥፋተኛ ተደርጎ ቅጣት የሚወሰንበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 44610 በቀን 22/04/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 200935 በቀን 01/07/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ከላይ በፍርድ ሀተታው የተገለጸውን የኢፌዲሪ ህገ መንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ መሰረት ያደረገ ባይሆንም በውጤት ደረጃ ግን ልዩነት ስለሌለው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 195(2) (ለ) (2) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤትይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 109392

ቀን 28/7/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- አቶ ሶፎኒያስ ሀብተማርያም ጠበቃ ሀ/ማርያም መልካ

ተጠሪ፡- ካልዲስ ኮፊ ኃላ/የተ/የግ/ማ- ጠበቃ አሰፋ መኮንን - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች አቶ ሶፊኒያስ ሀብተማሪያም ጥር 9/2007 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፊ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 104228 ጥቅምት 2/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የቀረበ ሲሆን የአሁን አመልካች የዋስትና ስምምነት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ቢኒያም አሰፋ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በእስቶር ኪፐር ወይም ዕቃ ግምጃ ቤት ሰራተኛ የሥራ ቅጥር መደብ ተመድቦ ሲሰራ ለሚደርሰው የንብረት ጉድለት ዋስ መሆኔ እየታወቀ 1ኛ ተከሳሽ የገንዘብ ያዥነት ስራ እንዲያከናውን ከተመደበበት ስራ ውጪ ከ100000 ብር በላይ በመስጠት በተላላኪነት ተጠሪ እራሱ አሰማርቶት በደረሰው የገንዘብ ጉድለት አመልካች ተጠያቂ ነው ተብሎ መወሰኑ አለአግባብ በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ካልዲስ ኮፊ የኃ/የተ/የግ/ማ በፊ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ በከሳሽ ድርጅት በቦሌ ቅርንጫፍ ለንብረት ክፍል ሲቀጠሩ 2ኛ ተከሳሽ አቶ ሶፊኒያስ ሀብተማሪያም እስከ ብር 50000 የዋስትና ግዴታ ነሐሴ 8/2004 ዓ.ም በተጻፈ የዋስትና ግዴታ ውል ገብቷል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ በንብረት ክፍል ተቀጥረው በሚሰሩበት ጊዜ መስከረም 2/2005 ዓ.ም ወደ ባንክ እንዲያስገባ ከሳሽ የሰጠውን ብር 111552 ይዘው በመሰወራቸው 2ኛ ተከሳሽ በተገኙበት የንብረት ቆጠራ ተደርጎ የብር 5643.49

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት ጎሏል፡፡ ተከሳሽ በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ሆነው የ1 ዓመት ከ7 ወር ቅጣት ተወስኖባቸዋል፡፡ ስለዚህ 1ኛ ተከሳሽ እና 2ኛ ተከሳሽ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1995 መሰረት በገቡት የዋስትና ውል ግዴታ ብር 117195.49 ከህዳር 2/2005 ዓ.ም በሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ ሲል ከሷል፡፡ የተከሳሾች መልስ የ1ኛ ተከሳሽ መልስ የስራ ኃላፊነቱ የንብረት ክፍል ተቆጣጣሪ እንጂ ገንዘብ የማንቀሳቀስ ኃላፊነት የለብኝም፡፡ ስለዚህ ለብር 111552 በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1928(1) መሰረት ተጠያቂ ልሆን አይገባም፡፡ የብር 5643.49 የንብረት ጉድለት ለተባለው ተጠያቂ ነኝ ሲል 2ኛ ተከሳሽም በሰጠው መልስ የብር 5643.49 ንብረት ጉድለት ለተባለው ብቻ በገባሁት የዋስትና ውል ግዴታ መሰረት ተጠያቂ እሆናለሁ፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ከተቀጠረበት ስራ ውጪ አሰማርተውት ለደረሰው ጥፋት ሀላፊነት የለብኝም ብለዋል፡፡

የፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 07408 ግንቦት 27/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ ብር 111552 በሰነድ ተረክበው ለባንክ ገቢ ያላደረጉና የብር 5643.49 ንብረት ያጎደሉ መሆኑን በቀረበው የሰነድ ማስረጃና 1ኛ ተከሳሽም በጽሁፍና በቃል ክርክር ያመኑ በመሆኑ ተጠያቂ ናቸው፡፡ 2ኛ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታቸው 1ኛ ተከሳሽ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆነው ሲቀጠሩ ለንብረት ጉድለት ኃላፊነት እንጂ ከጥሬ ገንዘብ ብር ጋር በተገናኜ እንዳልሆነ የቀረበው የዋስትና ግዴታ ውል ያስረዳል፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተከሳሽ ለብር 5643.49 ንብረት ለጎደለው ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1933(1) እና 1897 መሰረት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ነው 1ኛ ተከሳሽ ለብር 111552 ከህዳር 2/2005 ዓ.ም ጀምሮ በሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ ይክፈለው፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ ለብር 5643.49 ከግንቦት 27/2005 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጨምሮ ለከሳሽ ይክፈሉት ሲል ወስኗል፡፡ ለፌ.ከፍ/ፍ/ቤት ከሳሽ ይግባኝ አቅርቦ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 140236 አከራክሮ ሰኔ 16/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ ተቀጥረው በሚያገለግሉበት ወቅት ለደረሰው የንብረት መጉደል ብቻ ሳይሆን ለገንዘብ መጥፋትና የንብረት መጉደል 2ኛ ተከሳሽ (የአሁን መልስ ሰጪ) በገቡት የዋስትና ግዴታ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት የመልስ ሰጪን (2ኛ ተከሳሽን) የዋስትና ግዴታ ወሰን በግልጽ ከተጻፈው የግዴታ ዝርዝር አንጻር ተመልክቶ መወሰን ሲገባው 1ኛ ተከሳሽ የስራ መደብ ባልተቀየረበት እና የዋስትና ውሉን ከሰራተኛው የስራ መደብ ብቻ በማያያዝ አለአግባብ መተርጎሙ የዋስትናውን ግዴታ ወሰን አላማ ያላገናዘበ በመሆኑ የደረሰበት የውሳኔ መደምደሚያ ስህተት ያለበት ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አሻሽሎ 2ኛ ተከሳሽ (መልስ ሰጪ) 1ኛ ተከሳሽ ብር 111552 ለጎደለው እና በስር ፍ/ቤት የተወሰነውን ብር 5643.49 ጨምሮ እስከ ብር 50000 ብቻ ተጠያቂ ነው ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች (2ኛ ተከሳሽ) ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 104228 ጥቅምት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

24/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ይግባኝ የተባለበት ውሳኔ ጉድለት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካች ዋስ የሆነለት አቶ ቢኒያም አሰፋ ሲቀጠር በዋስትና ውሉ ላይ የንብረት ክፍል ሰራተኛ መሆኑ በተገለጸበት ከስራ መደቡ ውጪ ባንክ እንዲያስገባ በተጠሪ የተሰጠውን ገንዘብ ይዞ በመጥፋቱ አመልካች ሃላፊነት አለበት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 28/2007 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ነሐሴ 8/2004 ዓ.ም በተደረገው የዋስትና ውል የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ በተጠሪ ድርጅት ተቀጥረው በሚያገለግሉበት ወቅት ለሚያደርሱት የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል እስከ ብር 50000 በጋራ እና በተናጥል የዋስትና ግዴታ ውል ገብተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ቅር የሚያሰኝ ባለመሆኑ ይጽናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን አጠንክረው ተከራክረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው የአሁን አመልካች (የስር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ) አጥብቀው የሚከራከሩት የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ በተጠሪ ድርጅት ሲቀጠሩ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆነው ሲሆን የዋስትና ግዴታዬም የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ በንብረት ክፍል ሰራተኛነት ለሚያጎድሉት ንብረት እና ገንዘብ እንጂ ከተቀጠሩበት ስራ ውጪ እንዲሰራ ተደርጎ ለደረሰው ጉድለት ሃላፊነት ሊኖርብኝ አይገባም በሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ አጉድለዋል የተባለውን በአጠቃላይ ብር 117193.49 ያጎደሉት የስራ መደባቸው ሳይቀየር የንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆነው እየሰሩ በነበሩበት ወቅት ነው፡፡ የአመልካች የዋስትና ውል ግዴታ ሰራተኛው ተቀጥረው በሚያገለግሉበት ወቅት ለሚደርሰው የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል ተጠያቂ ለመሆን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የገቡት የዋስትና ግዴታ ሰራተኛው በስራቸው ወቅት ለሚያደርሱት የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል እንጂ ለሚከራከሩበት የንብረት መጉደል ብቻ ተብሎ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ ያጎደሉትን ገንዘብ የድርጅቱ ሰራተኛ ሆነው በሚሰሩበት ወቅት በእጃቸው የገባ ገንዘብ መጉደሉ አመልካች ከገቡት የዋስትና ግዴታ ውል ውጪ የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት አመልካችን በገቡት የዋስትና ግዴታ ውል መሰረት ሃላፊነት አለባቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 104228 ጥቅምት 24/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 140236 ሰኔ 16/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻችሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ሐምሌ 29/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው እግድ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ቅጂ የስር ፍ/ቤቶች እንዲያውቁት ይድረሳቸው፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 107542

ቀን 14/08/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አሻም ትሬዲንግ ኤንድ ኢንደስትሪ ስራ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ስራ አስኪያጅ አሸበር ውንድሠስሽ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የንግሩን ሞተርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ ደባስ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ተጠሪ የሸጠልኝ ሊፋን መኪና ከአዲስ መኪና የማይጠበቅ በተደጋጋሚ ብልሽት ምክንያት ወደ ተከሳሽ ጋራዥ የምትገባና መሰረታዊ ጉድለት ያለባት በመሆኑ ተከሳሽ (ተጠሪ) በሌላ አዲስ መኪና እንዲተካ ወይም መኪናዋን ለመግዛት የከፈለኩትን ገንዘብ እንዲመልስ ውሳኔ ይስጥልኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ የበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የተያው በፊዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡
2. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሆኖ ቀርቦ ከተከሳሽ LF7132 የሞተር ጉልበት 1300 cc የሆነ አዲስ መኪና ጥር 4 ቀን 2002 ዓ/ም በተዋዋልነው ውል ሽጦልኛል፡፡ ተከሳሽ መኪናዋን የሸጠልኝ በብር 189,800 (አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ብር) ሲሆን ተከሳሽ ብር 94,900 (ዘጠና አራት ሺ ዘጠኝ መቶ ብር) በቅድመ ክፍያ፣ ቀሪውን መኪናዋን ስረከብ ከፍያለሁ፡፡ ተከሳሽ ለከሳሽ የሸጠልኝ መኪና በሃያ አራት ወራት ውስጥ 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ ጉድለት ቢገኝበት በራሱ ወጭ ለማስተካከል ወይም ለመቀየር የውል ግዴታ ገብቷል፡፡ ሆኖም መኪናዋን ከተረከብኩበት ጊዜ ጀምሮ ባለበት መሰረታዊ ጉደለት በተደጋጋሚ ወደ ተከሳሽ ጋራዥ የገባች ሲሆን ጉድለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከአዲስ መኪና የማይጠበቅ በመሆኑ በሌላ አዲስ መኪና እንዲቀይርልኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ መኪናዋ ፍርድ በተሰጠበት ቀን ከምታወጣው ዋጋ ለከሳሽ ከወጭና ኪሳራ ጋር እንዲመልስ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

3. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ መኪናዋ የነበረባት አነስተኛ ጉደለቶች በተከሳሽ ጋራዥና ወጭ ተስተካክላ በአዲስ ሁኔታ ላይ ትገኛለች፡፡ ከሳሽ መኪናዋን ተረክቦ ወስዶ አገልግሎት ላይ ለማዋል የሚችል በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ይሁን በማለት ያቀረበው ክስ የህግ መሰረት የለውም፡፡ ከሳሽ መኪናዋን በጋራዣችን ትቶ የሄደ በመሆኑ መኪናዋ በጋራዥ ለቆየችበትና ወደፊት ለምትቆይበት ኪራይ የመጠየቅ መብታችን ይጠበቅልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመር በኃላ መኪናዋ መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ባለሙያዎች ተመርምራ መግለጫ እንዲቀርብለት ካደረገ በኃላ መኪናዋ መሰረታዊ ችግር ያለበት መሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ የከሳሽ ክስ የህግ መሰረት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ በፊዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፊዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

4. አመልካች ህዳር 30 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የሸጠልን መኪና ሶስት ሺ ኪ.ሜትር ሳይነዳ ለአምስት ጊዜ ያህል ሞተሩ ጭምር በድንገትና ሳይታሰብ እየቆመ ለከፍተኛ አደጋ ጭምር ያጋለጠን መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃና ተጠሪ መኪናዋን በተደጋጋሚ በራሱ ጋራዥ ቢጠግናትም መኪናዋ የአመራረትና የጥራት ጉድለት ያለባት በመሆኑ ሊስተካከል አለመቻሉን ለስር ፍርድ ቤት በማስረጃ አስርድተን እያለ የስር ፍርድ ቤት መኪናዋ መሰረታዊ ጉድለት የለባትም በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

5. ተጠሪ ሚያዝያ 12 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ መልስ፤ መኪናዋ መሰረታዊ ጉደለት የሌለበት መሆኑን የባለሙያ ማስረጃ በማቅረብ ጥያቄ አቅርበን ነበር በመኪናዋ ላይ የተከሰተው ችግር መሰረታዊና የማይጠገን ችግር አይደለም ተጠሪ መኪናዋን አስተካክሎ ለመስጠት በውል የገባውን ግዴታ ሲፈጽም ቆይቷል፡፡ አመልካች ለተጠሪ መኪናዋን ማስተካከል ከአቅሙ በላይ መሆኑን ሳይገልጽላት መኪናዋን ከተጠሪ ጋራዥ ጥሎ ጠፍቷል፡፡ መኪናዋ የአመራረት ጉድለት የለባትም ስለዚህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሚያዝያ 26 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

6. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ጽሑፍ ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ለአመልካች በክሱ አይነት የተገለጸቸውን መኪና በብር 189,800 (አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሺ ብር) የሸጠ መሆኑንና በመኪናዋ ላይ ለሚታይ ጉድለትም ዋስትና የሰጠ መሆኑ አከራካሪ ጭብጥ አይደለም፡፡ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት አመልካች መኪናዋ ሶስት ኪሎ ሜትር ሳትነዳ የሞተርና ሌሎች ጉድለቶች ተከስተው ለአምስት ጊዜ ከሻጭ ጋራዥ ገብታ፣ ሻጭ(ተጠሪ) የመኪናዋን ጉድለት ለማስተካከል አልቻለም፡፡ አመልካች በገዛት መኪና በአዲስ መኪና ሊያገኝ የሚገባውን አገልግሎት ያላገኘ በመሆኑ መኪናዋ መሰረታዊ ችግር ያለበት ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ነው ይባልልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በተቃራኒው በመኪናዋ ላይ የተከሰቱ ብልሽቶች በማንኛውም አዲስ መኪና ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ቀላል ብልሽቶች ናቸው፡፡ አመልካች በመኪናዋ ላይ አሉ የሚላቸውን ጉድለቶች ሙሉ በሙሉ ያስተካከልኩ በመሆኔ አመልካች መኪናዋን ወሰዶ ከመጠቀም በስተቀር የሸያጭ ውሉ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

7. ከላይ ከተገለጸውና ግራ ቀኙ ከተካካዱባቸው ነጥቦች ለመረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ለአመልካች በሸጣት መኪና ላይ የታዩ ብልሽቶችና መኪናዋ ወደ ሊፋን ጋራዥ እየገባች ጥገና ያገኘችበት ሁኔታ ከአዲስ መኪና የሚጠበቅ ነው ወይም አይደለም? ብልሽቱ ከአዲስ መኪና የሚጠበቅ አይደለም ከተባለ ውሉን ፈራሽ ለማድረግ በቂ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ነጥቦች መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከላይ የተገለጹትን ነጥቦች፣ ላይ ውሳኔ ለመስጠት እንዲመቸው የስር ፍርድ ቤት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.136 ንዑስ አንቀጽ 1 በሚደነግገው መሰረት ለጉዳዩ ገለልተኛ በሆኑ በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ጉዳዩ ተጣርቶ የሙያ አስተያያት እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ሰጥቶ፣ የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ዕወቀትና ክህሎት አላቸው የሚላቸውን ሶስት ባለሙያዎች መድቦ ባለሙያዎቹ መኪናዋን በአካል ከፈተሸና ከመርመሩ በኃላ ጥር 25 ቀን 2004 ዓ/ም ሪፖርት ያቀረቡ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

8. የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ባለሙያዎች መኪናዋን በአካል በፈተሸበትና በመረመሩበት ወቅት አመልካች መኪናዋን ሊፋን ጋራዥ እንዲያስገባት ምክንያት የሆኑ ጉድለቶች ሊፋን ጋራዥ ያስተካከላቸው መሆኑን ከሪፖርታቸው የገለጸ ሲሆን፣ ባለሙያዎች የመኪናዋን ፋይል በማስቀረብ የተመለከቱ መሆኑንና መኪናዋ 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ ከአምስት ጊዜ በላይ ወደ ሊፋን ጋራዥ እየገባች የተለያዩ የጥገና አገልግሎት የተሰጣት መሆኑን እንዳረጋገጡ ገልጸው አንድ አዲስ መኪና 3000 ኪሎ ሜትር ሳይነዳ እንዲህ አይነት የበዛ ችግሮች ማጋጠም ስለሌለበት ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ከአዲስ መኪና የሚጠበቁ ችግሮች አይደሉም በማለት ሙያዊ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

9. ተጠሪ ለአመልካች በሸጣትና በአገር ውስጥ ተጠሪ ባቋቋመው የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ በተገጣጠመችው አዲስ መኪና ላይ በተደጋጋሚ የተከሰተው ብልሽት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2344 መሰረት የሸያጭ ውሉ ፈራሽ ለማድረግ በቂ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚልውን ተመልክተናል፡፡ “የተሸጠው ነገር ጉድለት” የሚል ርዕስ ያለው የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 “የተሸጠው ነገር ሻጩ ለገዥው ዋቢ ሊሆንለት የሚገባው ጉድለት የተገኘበት እንደሆነ ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል በንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ደነግጋል፡፡ አንድ ሻጭ የሸጠው ነገር ለደንበኛው አገልግሎት ወይም ንግድ ረገድ ለመጠቀሚያነት ጥሩነት የሌለው ሲሆንና የሸጠው ነገር በውሉ ውስጥ በግልጽ ወይም በውስጣዊ ሀሳብ ለተነገረው ልዩ አገልግሎት የሚሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ጥሩነት የሌለው በሆነ ጊዜ ሻጭ ለገዥው ዋቢ እንደሚሆን በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2289 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡

10. ከዚህ አንጻር ተጠሪ በሸጠው አዲስ መኪና ላይ እስከ 3000 ኪሎ ሜትር ለሚደርስ ብልሽት ዋቢ በመሆን ዋስትና የሰጠ ሲሆን፣ መኪናዋ 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ የተለያየ ብልሽት እያጋጠማት ከአምስት ጊዜ በላይ ሊፋን ጋራዥ እየገባች ተጠግና መውጣቷ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ገዥው አዲስ ከፋብሪካ የወጣ መኪና በመግዛትና በመረከብ ከገዥው የአጠቃቀም ጉድለት ካልፈጸመ ወይም አደጋ ካላጋጠማት በስተቀር ቀላልና መለስተኛ የሆኑ ጥገና ለትንሽ ቀናት ብቻ እያቆመች መኪናዋን ለትራንስፖርት እገለገልባታለሁ በሚል ሀሳብ የገዛ መሆኑንና ተጠሪ ለአመልካች የሸጣት መኪና ግን ለአመልካች መስጠት የሚገባትን መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ሳትሰጥ በየወቅቱ የተለያዩ ክፍሎቿ እየተበላሹ ሊፋን ጋራዥ ለጥገና ስትገባ የቆየች መሆኑን በገለልተኛ ባለሙያዎች የቀረበው ሪፖርት ያሳያል፡፡

11. በተሸጠው ነገር ላይ የተገኘው ጉድለት ለውል ማፍረሻ ምክንያት የማይሆነው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ሁኔታ ሲሟላ ነው፡፡ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 2 የአማርኛ ቅጅ ቃል በቃል ሲነበብ “እንዲህም በሆነ ጊዜ ጉድለቱ እጅግም የማይጎዳ እንደሆነና ገዥው ጉደለቱን አውቆ ኖሮም ቢሆን ጉደለት የተገኘበትን ነገር ሳይገዛው የማይቀር እንደነበር ሲታይ ውሉን ለማፍርስ አይችልም” የሚል ይዘት ያለው ሲሆን የዚህ ድንጋጌ የእንግሊኛው ቅጅ፣ “the contract may however not be cancelled where the defect is of small importance and it oppears that buyer would have bougut the thing had he known the defect” የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

12. በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ለአመልካች በሸጠለት መኪና ላይ በየወቅቱ የታዩ ብልሽቶች ከሞተር አሰራር ጀምሮ የፍሪስዮንና ሌሎች ችግሮች እየጋጠሙ መኪናዋ 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ ከአምስት ጊዜ በላይ ለጥገና ወደ ሊፋን ጋራዥ የገባች መሆኑ ግራ ቀኙ ካደርጉት ክርክርና ከስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ካስፈራቸው ነገሮች ተረድተናል፡፡ ተጠሪ የሚያከራክረው ከዚህ በፊት በመኪናዋ ላይ የታዩ ጉድለቶችና ብልሽቶች ቀላል በመሆናቸው በተጠሪ በቀላሉ ተስተካክለዋል በማለት ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ ለአመልካች የሸጠው ያገለገለ መኪና ሳይሆን ከፋብሪካ ተገጣጥሞ የወጣ አዲስ መኪና ከመሆኑ አንጻር መኪናው ትንሽ ኪሎ ሜትር እየተነዳ በሚያጋጥመው ብልሽት ምክንያት አመልካች በመኪናው ሊያገኝ የሚገባውን መደበኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የትራንስፖርት አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉና በየወቅቱ መኪናዋን ወደ ሊፋን ጋራዥ እየወሰደ ጉድለቶችን በመዘርዘርና የስራ ትዕዛዝ በመስጠት፣ መኪናዋ በጥገና ለመስተካከል የምትችል መሆኗን ምክሮ ያልተሳካ በመሆኑ ውሉ እንደፈርስ የጠየቀ መሆኑን፣ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

13. ይህም ተጠሪ ለአመልካች የሸጣት መኪና ከአዲስ መኪና የማይጠበቅ ተደጋጋሚ ብልሽት የጋጠማትና ተጠሪ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2289 ንዑስ አንቀጽ 1 በዋቢነት ሊያልፍበት የሚገባውን ለመደበኛው ትራንስፖርት አገልግሎት ጥሩነት የሌላት መሆኑን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ አመልካች መኪናዋ 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ ከአምስት ጊዜ በላይ ጋራዥ እየገባች ለጥገና የምትቆም መሆኑን መኪናዋን ከመግዛቱ በፊት ቢያወቅ ኖሮ መኪናዋን ይገዛታል ተብሎ የማይገመትን በመኪናዋ ላይ የታዩት ብልሽቶች ቀላል ሊባሉ የማይችሉ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

14. ከዚህ አንጻር አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገውን የመኪና ግዥ ውል እንዲፈርስለት ለመጠየቅ የሚያስችለውና ውለንም ፈራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2289 ንዑስ አንቀጽ 1 በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጹት ጉደለቶች ተጠሪ በሸጣት መኪና ላይ የታዩ መሆኑን፣ የስር ፍርድ ቤት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 136 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በመደባቸው የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ባለሙያዎች ተጠሪ በሸጣት መኪና 3000 ኪሎ ሜትር ሳትነዳ ያጋጠሙ ብልሽቶችና ችግሮች በአዲስ መኪና ሊታዩ የሚገቡ ችግሮች አይደሉም በማለት የሙያ አስተያያት የሰጡበት ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት መኪናዋ በተደጋጋሚ ጋራዥ መግባቷ ውሉን ለማፍረስ በቂ ምክንያት አይደለም በማለት መወሰኑን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 1 የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2289 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ ሳያገናዝብ የተሰጠና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

15. ተጠሪ አመልካች ጋር ያደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ከተባለ ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለውን በማስከተል መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ መኪናዋ ሊፋን ጋራዥ የቆመችና ተጠሪ የተረከባት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች መኪናዋን ለመግዛት የከፈለው ብር 189,800 (አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ብር) ተጠሪ ለአመልካች የመመለስ ግዴታ አለበት አመልካች ተጠሪ በአሁኑ ወቅት መኪናዋ የምታወጣውን ዋጋ እንዲከፍለው ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም፣ ይህ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአንጻሩ ተጠሪ አመልካች የከፈለውን ብር 189,800 (አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ሰምንት መቶ ብር) አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ክስ ካቀረበበት መጋቢት 14 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2003 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ሊመልስ ይገባል በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1815 እና በፍታብሔር ቁጥር 1751 መሰረት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176453 ግንቦት 14 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137600 ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. በተጠሪና በአመልካች መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2289 ንዑስ አንቀጽ 1፣ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2344 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ ሊፋን ጋራዥ ገብታ የቆመችውን መኪና ተረክቦ ለሚፈልገው አገልግሎት ሊውል ይችላል ብለናል፡፡
4. ተጠሪ አመልካች መኪናዋን ሲገዛ የከፈለውን ብር 189,800 (አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ብር) ከመጋቢት 14 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይክፈል በማለት ወሰነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 115981

ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተክሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካቾች፡- 1ኛ. ሕፃን መይሙና ሀሰን
2ኛ. ሕፃን መሳይ ሀሰን
3ኛ. ሕፃን ረሂማ ሀሰን
ጠበቃቸው ጌታቸው አለሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የሕፃን ሳሊሃ ሀሰን ሞግዚት ወ/ሮ ፀሃይ አድማሱ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልል ዲላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡በስር ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኗ ተጠሪ አመልካች፤አመልካቾች ፤ተጠሪዎች፤ የአመልካቾች ሞግዚት ወ/ሮ ዙልፋ ከማል ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የተጠሪ ሞግዚት ወ/ሮ ፀሐይ አድማሱ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ባጭሩ፡- ሟች ሀሰን አዲል የህፃን ሳሊሃ ሀሰን ወላጅ አባት ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውንና ህፃን ሳሊህ ሀሰን ወራሽ መሆኗ የተረጋገጠበትን ማስረጃ አያይዘው በማቅረብ ሟች በህይወት እያሉ ያፈሯቸውን ንብረቶች ዝርዝር አቅርበው የውርስ አጣሪ ተሾሞ ተጠርተው የህጻን ሳሊህ ሀሰን ድርሻ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት በሰጡት መልስም ጉዳዩ ከአሁን በፊት በፍርድ ያለቀ ስለመሆኑ፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትም የግላቸው መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍርድ ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ ለክርክሩም ምክንያት የሆነው ቤት በጣልቃ ገብ ስም የሚታወቅ ነው።ተጠሪ የሚች ንብረት ስለመሆኑ አላስረዳችም።ንብረት በአመልካቾች ሞግዚት ስለመኖሩ ተጠሪ አላረጋገጠችም።ሌሎች የቤት ቁሳቁሶች በአመልካቾች ሞግዚት ስለመኖሩ ተጠሪ በሰው ይሁን በሰነድ ማስረጃ አላስረዳችም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል።የአሁኗ ተጠሪ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙ ከአከራካሪ እና ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ከአደረገ በኋላ ሚች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የቤት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር 1303 የተሰጠው በ1988 ዓ.ም ለአሁኗ የአመልካቾች ሞግዚት ተሰጠ ከተባለ በኋላ በ1992 ዓ.ም የእድሳት ፍቃድ ጠይቆ ማሳደሱን፤ስጦታ ተሰጠ የተባለው ቤትም መኖሪያ ቤቴ ነው በሚል ሲገብርበት እንደነበረ ማስረጃ በመቅረቡ የስጦታ ውሉን በዝምታ በመሻር ቦታውንና ቤቱን በባለቤትነት ስር አድርጎ ሲጠቀምበትና ሲገለገልበት የነበረ መሆኑን ያሳያል፤፤የስር ፍርድ ቤት በአግባቡ ሳያጣራና ሳይመረምር የደረሰበት መደምደሚያና የሰጠው ውሳኔ የሕግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለው ነው በማለት ውሳኔውን ሽሮ በይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር 1303 ላይ ያለውን ይዞታና ቤት ሚች አቶ አዝጊ (ሀሰን) አዲል እና የአመልካቾች ሞግዚት ወ/ሮ ዙልፋ ከማል የጋራ ንብረት በመሆኑ ሚች አቶ አዝጊ አዲል ድርሻ የውርስ ሀብት ነው።የሚች ልጆች የአባታቸው የውርስ ድርሻ ይክፈሉ በማለት ወስኗል።የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት የጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 የተሰረዘ ሲሆን በሰበር ስልጣኑ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የሚያከራክረውን ንብረት ላይ ድርሻ የላቸውም ያለ አለመሆኑን የአመልካቾች ሞግዚት ባለቤቷን በፍቺ ስለተለያዩ የደረሰኝ ነው ትበል እንጂ ፍቺና የንብረት ክፍፍል መኖሩን አላስረዳችም።በይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቁጥር 1303 የሆነውን የአመልካቾች ሞግዚት ድርሻ ከተለየ በኋላ የሚች ልጆች ይክፈሉ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል።የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም የስር ከፍተኛ እና በየደረጃውን ጉዳዩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤትና ይዞታ የግላቸው ስለመሆኑ፤የስጦታ ውሉም እንዳልተሻረ፤የተጠሪ ሞግዚት ከአሁን በፊት ክስ አቅርበው ውድቅ የተደረገባቸው ስለመሆኑ፤ተጠሪ በማይመለከታት ንብረት አጣርታ እንደቀረበች በመግለጽ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው።የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ የፁሁፍ ክርክር አድርጓል።ተጠሪ በሰጠችው መልስም ሚች ልጅን መሻር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደማይችል፤የተወለደቺው ከስጦታ በኋላ ስለመሆኑ ፤ስጦታውን በዝምታ የተሻረ መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና አመልክቷል፡፡የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጹሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ "በዚህ ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን ንብረት ከሟች ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ወቅት በስጦታ ያገኙት እና ጋብቻቸው ሲፈርስ የንብረት ክፍፍል አድርገው መለያየታቸው እየገለጹ ተጠሪ /ህጻን/ ሳሊህ ሀሰን ድርሻ አለው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከሰ/መ/ቁ 77735 አንጻር ለመመርመር" የሚል ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከስር ፍርድ ቤት አንስቶ አጥብቀው የሚከራከሩት ከሟች አቶ ሀሰን አዲል የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍል መደረጉን፤በይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት 1303 የሚታወቀው ቤትና ይዞታ በ1988 ዓ/ም ከሟች በስጦታ ያገኙትና የግላቸው ቤትና ይዞታ ስለመሆኑን ነው፡፡የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት በበኩላቸው ከአሁን በፊት የተደረገው ክርክር ሚስት መሆናቸውን መሰረት ያደረገ እንጂ ተጠሪ ወራሽ በመሆኗ ምክንያት የቀረበ ክስ አለመሆኑን ክርክር የተደረገበት በቁጥር 1303 የሚታወቀው ቤት የአመልካቾች ሞግዚት የግል ቤት አለመሆኑን መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህን ጉዳይ በይግባኝ እና ሰበር የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች ቤቱ በመጀመሪያ የአሁን ተጠሪዎች ሞግዚት በስጦታ ያገኙት መሆኑን ገልጸው፤ነገር ግን ሟች ከስጦታ በኋላ በአከናወኗቸው ድርጊቶች ስጦታቸው በዝምታ ተሸሯል ከሚል መደምደሚያ ደርሰዋል፡፡

ከመዝገቡ ጋር ከተያያዙ ሰነዶች መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት 1303/83 የሚታወቀው የሟች ንብረት ስለመሆኑ ሐምሌ 17 ቀን 1988 ዓ.ም በተደረገው ስጦታ ለወ/ሮ ዙልፋ ከማል መስጠታቸውን፤ስጦታውም በስረ ፋይል መዝገብ ቁጥር 156/88 ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቁን ነው፡፡በሌላ በኩል የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት በጌዴኦ ዞን ወናጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 00726 ክስ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ጥር 30/05/2003 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይዘትም የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት በይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር 1303/83 በሚታወቀው ቤት ላይ ድርሻ እንዳላቸው የጠየቁ ቢሆንም የአሁን አመልካቾች ሞግዚት በስጦታ ያገኙት ነው በማለት የተጠሪ ሞግዚት ክስ ውድቅ ማድረጉን የሚያሳይ ነው፡፡ይህ ውሳኔም ጉዳዩን በየደረጃው ባዩት ፍርድ ቤቶች የጸና ሲሆን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰመ/ቁ 77735 በ12/08/2004 ዓ.ም መሰረታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት ድርሻ አለኝ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ከመደረጉ በተጨማሪ የአሁን አመልካቾች ሞግዚት ቤትና ይዞታውን ያገኙት በስጦታ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ከክርክሩ ይዘት መገንዘብ የተቻለው የስጦታ ውሉ የጸና ስለመሆኑ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት መወሰኑን ነው፡፡የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት በ2003 ዓ.ም በአመልካቾች ሞግዚት ላይ ክስ አቅርበው ውድቅ ከተደረገ በኋላ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪን ወክለው በ2005 ዓ.ም ክስ ማቅረባቸው መዝገቡ ያሳያል፡፡የስር ፍርድ ቤቶች ሟች የስጦታ ውሉን በዝምታ ሽሮታል ከሚል ድምዳሜ የደረሱ ቢሆንም በ2003 ዓ.ም አስቀድሞ በተሰጠው ውሳኔ የስጦታ ውሉ የጸና ስለመሆኑ በየትኛውም ፍርድ ቤት ያልተሻረ ውሳኔ መስጠቱን ካቀረቡት የውሳኔ ግልባጮች መገንዘብ ተችሏል፡፡

የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት በስር ፍርድ ቤት ይሁን በሰበር ደረጃ ባደረጉት ክርክር ወላጅ ልጅን ከስጦታ መሻር አይችልም የሚል ነው፡፡ስጦታው የአሁኗ ተጠሪ ከመወለዷ በፊት የተሰጠ ስለመሆኑ አልተካደም፡፡ስጦታው በፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቁም ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ሟች ባደረጉት ስጦታ በምስክር ወረቀት ቁጥር 1303/83 በስማቸው ተመዝግቦ የሚታወቀውን 27x12፡ 324 ካሬ ሜትር ላይ የተሰራውን አንድ ክፍል ቆርቆሮ ክዳን ቤት ከነቦታው ለወ/ሮ ዙልፋ ከማል መስጠታቸው አረጋግጠዋል፡፡በመሰረቱ የስጦታ ውል በፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 2427 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የሚመራ ሲሆን ሟች ያደረጉት ስጦታ በህጋዊነቱ ይሁን ፎረማሊቲ የተነሳ ክርክር የለም፡፡ የተጠሪ ሞግዚት ስጦታው ውድቅ ለማድረግ እንደ ምክንያት ያቀረቡት ከስጦታ መደረግ በኋላ የተጠሪ መወለድን ነው፡፡የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት ክርክር ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2450 አንጻር እንደተመለከተው ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡የድንጋጌው ሙሉ ይዘት "በተደረገው የስጦታ ውል ውስጥ ተቃራኒ የሚሆን ቃል ከሌለ በቀር ስጦታ ከተደረገ በኋላ ልጅ በመውለዱ ምክንያት ስጦታውን ለመሻር አይቻልም"፡፡በማለት የተደነገገ ሲሆን የእንግሊዝኛው አቻ ትርጉም " unless otherwise provided in the contract of donation, a donation may not be revoked where a child is born to the donor" በሚል ተቀምጧል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት እንደተመለከተው የስጦታ ውል ተቃራኒ ቃል ከሌለው በቀር የልጅ መውለድ የስጦታ ውሉን ለመሻር በቂ ምክንያት አለመሆኑን በግልጽ ተደንግጓል ሟች ሐምሌ 17 ቀን 1988 ዓ/ም ያደረጉት የስጦታ ውልም ለወ/ሮ ዙልፋ ከሚል ከመስጠት ውጭ ሌላ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠበት ስለመሆኑ ከመዝገቡ ጋር የተያያዘው የስጦታ ውል አያሳይም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የአሁኗ ተጠሪ በመውለዷ ምክንያት የስጦታ ውሉ የሚሻርበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የስጦታ ውሉ የጸና ስለመሆኑ የፍርድ ቤት የጸና ውሳኔ በቀረበበት /ባለበት/ እና ልጅ መውለድ ስጦታ ለመሻር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት እንደማይሆን በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2450 በግልጽ በተደነገገበት ሁኔታ የሚች ስጦታ በዝምታ ተሸሯል ከሚል ድምዳሜ የደረሰው የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻራቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸማቸውን የሚያሳይ ነው ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የጌዶኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 09588 በህምሌ 17 ቀን 2006 በዋለው ችሎት የዲላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሐሮ ወለቡ ምድብ ችሎት በመ/ቁ/ 00670 በ18/02/2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በመሻር የሰጠው ፍርድ፤ የደ/ብ/ብ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/63836 በ20/06/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 64413 በ18/09/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሮአል፡፡
2. በይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር 1303 ላይ ያለውን ይዞታና ቤት የአመልካቾች ሞግዚት ወ/ሮ ዙልፋ ከማል የግል ቤትና ይዞታ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዲላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 00670 በ18/02/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.108638

ግንቦት 22 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡-አቶ መህቡብ ከድር -ጠበቃ ሂሩት ሂላይ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ -ነ/ፈጅ መብራቱ ግርማይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ክሳቸውን ውድቅ በማድረግ ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 209236 በ12/07/2006 ዓ.ም. የሰጠው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150986 በ05/02/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

አመልካች በ02/01/2006 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት በአራዳ ክፍለ ከተማ በወረዳ 2 የሚገኝ ቁጥሩ 507 የሆነውን የንግድ ቤት ከ18/12/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ከተጠሪ ተከራይተው ሲገለገሉበት ከቆዩ በኃላ የውሉ ዘመን ሲጠናቀቅ ውሉን ለማደስ አመልካች በ17/12/2005 ዓ.ም. ብር 246.00 የቴምብር ቀረጥ፣እንዲሁም እስከ ጥቅምት ወር 2006 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የሁለት ወር ኪራይ የከፈሉ መሆኑን፣በዚህ ሁኔታ ተጠሪ ውሉን አራዝሞ ኪራይ ከተቀበላቸው በኃላ በ28/12/2005 ዓ.ም.በተጻፈ ደብዳቤ ውሉን ከ30/12/2005 ዓ.ም. ጀምሮ እንዳቋረጠ የገለጸላቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ተጠሪ የውል ማደሻ እና የወደፊቱን ኪራይ ከተቀበለ በኃላ የፈጸመው የውል ማቋረጥ ተግባር ተገቢ አይደለም ተብሎ ውል እንዲቀጥል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተጠሪው በበኩሉ በ18/03/2006 ዓ.ም. በሰጠው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መልስ በ18/12/2004 ዓ.ም. የተደረገው የኪራይ ውል የሚቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ መሆኑን፣ውሉ ከዚህ በኃላ ላለው ጊዜ የታደሰ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን፣ የውሉ ዘመን ሲጠናቀቅ ተጠሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ለማቋረጥ የሚችል መሆኑን፣የቴምብር ቀረጥ የተከፈለውም ውሉን ለማራዘም ታስቦ ነው የሚያሰኝ አለመሆኑን እና አመልካች የቤቱን ኪራይ የከፈሉት በራሳቸው አነሳሽነት በመሆኑ የኪራዩ መክፈል የውሉን መታደስ የሚያረጋግጥ አለመሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የመጀመሪያው ውል የጊዜ ቆይታ የተጠናቀቀ መሆኑን፣ውሉ የታደሰ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን፣የውሉ ዘመን ካበቃ በኃላ የሁለት ወር ኪራይ ተከፍሎ መገኘቱም ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚያስቆጥር መሆኑን እና ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገን ውል ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2966 በተመለከተው መሰረት አከራዩ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ የሚችል መሆኑን ገልጾ የኪራይ ውሉ እንዲቀጥል እንዲወሰን የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ የኪራይ ውል ማደሻ ቅጽ ተሞልቶ የቴምብር ቀረጥ ክፍያ ከተፈጸመ በኃላ ጥፋት ተፈጽሟል ሳይባል ቀደም ብሎ የነበረው የኪራይ ውል እንዲታደስ አመልካች ካቀረቡት ክስ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በአግባቡ ያስተናገዱ መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ክርክሩ የተስተናገደበትን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ጭምር አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርመረናል፡፡

በዚህም መሰረት በ18/12/2004 ዓ.ም. ለአንድ ዓመት ተደርጎ የነበረው የኪራይ ውል የቆይታ ጊዜ ያለቀ መሆኑ ያላከራከረ ሲሆን አመልካች ውሉ ለተጨማሪ አንድ ዓመት ታድሷል በማለት ቢከራከሩም ውሉ በዚህ አግባብ የታደሰ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ተጠሪው በ28/12/2005 ዓ.ም. ለአመልካች በጻፈው የውል ማቋረጫ ደብዳቤ ላይ ውሉን ማቋረጡን ከመግለጽ በቀር ውሉን ያቋረጠበትን ምክንያት አልገለጸም፡፡ተጠሪው በስር ፍርድ ቤት በሰጠው የጽሁፍ መልስ የውሉ ዘመን ሲያልቅ ውሉን የማቋረጥ መብት አለን በማለት የተከራከረ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው የውሉ ዘመን ካበቃ በኃላ የሁለት ወር ኪራይ ተከፍሎ መገኘቱ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚያስቆጥር መሆኑን እና ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገን ውል ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2966 መሰረት አከራዩ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ የሚቻል መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ተጠሪው በሰበር ደረጃ በሰጠው መልስ የውሉን አንቀጽ 10 (2) እና (4) ድንጋጌዎች ጠቅሶ የተከራከረ ሲሆን እነዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎችም የውሉ ዘመን ሲያልቅ ውሉ የሚቋረጥ መሆኑን እና የውሉ ዘመን ያላለቀ በሆነ ጊዜ ደግሞ አንደኛው ወገን በሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ውሉ ሊቋረጥ የሚችል መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው።

በመሰረቱ ቤቱ በኪራይ የተሰጠው ለንግድ ዓላማ ሲሆን ከተጠሪ ድርጅት ስልጣንና ተግባር መካከል አንዱ በይዞታው ስር የሚገኙትን የመንግስት ቤቶች ማከራየት እና ኪራይ መሰብሰብ ስለመሆኑ ኤጀንሲውን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6 (1) ስር ተመልክቷል።ይህም ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችሉ ያልተጠበቁ ምክንያቶች ካልተከሰቱ እና በተለይ ደግሞ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል በተከራይ ወገን በኩል ጥፋት ተፈጽሟል ካልተባለ በቀር በተጠሪው ድርጅት እና በተከራዮች መካከል የሚደረጉ ውሎች በየዓመቱ እየታደሱ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው።በመሆኑም በውሉ ውስጥ የተመለከቱት ከላይ የተጠቀሱት የውል ማቋረጫ ድንጋጌዎች፣እንዲሁም ተጠሪው በሕግ ያለው የመዋዋል መብትና ነጻነት ለኤጀንሲው በሕግ ከተሰጠው ስልጣን እና ተግባር አንጻር በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የውሉ ዘመን ሲያልቅ ያለማስጠንቀቂያ፣እንዲሁም የውሉ ዘመን ያላለቀ በሆነ ጊዜ ደግሞ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለተጠሪው ያለተገቢ እና ሕጋዊ ምክንያት የኪራይ ውሎችን ለማቋረጥ መብት እንደሚሰጡት ተደርገው ሊተረጎሙ የሚገባቸው አይደሉም።በመሆኑም ተጠሪው በዚህ ረገድ ያቀረበው መከራከሪያ በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው በአግባቡ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

በሌላ በኩል ተጠሪው ለዚህ ሰበር ችሎት በሰጠው መልስ ላይ አመልካች የንግድ ድርጅቱን የገዙት አቶ ድራር ገዛኢ ከተባሉ ኤርትራዊ ዜጋ መሆኑን እና ውሉም እንዲቋረጥ የተደረገው አመልካች የንግድ ድርጅቱን ካልተፈቀደለት ግለሰብ የገዙት በመሆኑ ነው በማለት ተከራክሯል።ይሁን እንጂ ተጠሪው ይህንን የክርክር ነጥብ በስር የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በጽሁፍ መልሱም ሆነ ክሱ በተሰማበት ጊዜ አንስቶ ያልተከራከረበት መሆኑን ቀርቦ ከተያያዘው የስር መዝገብ ተገንዝበናል።በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ እና ለውሳኔው መሰረት ያልተደረገ ክርክር ደግሞ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 329 (1) መሰረት አሁን በሰበር ደረጃ ሊስተናገድ የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪው ውሉን ስላቋረጠበት ምክንያት በውል ማቋረጫ ደብዳቤው ላይ የገለጸው ነገር ባይኖርም በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሉን ያቋረጠው ቤቱን ስለፈለገው እንደሆነ በመግለጽ የተከራከረ መሆኑን የስር መዝገብ ያመለክታል።ይሁን እንጂ ተጠሪው በመደበኛ ሁኔታ የንግድ ቤቶችን የሚያስተዳድረው ለሶስተኛ ወገን በኪራይ እየሰጠ እንደመሆኑ መጠን ውሉን ያቋረጠው በርግጥም ቤቱን ለሌላ ተገቢ እና ሕጋዊ ምክንያት ፈልጎት ከሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህንኑ ምክንያት ጠቅሶ መከራከር የሚጠበቅበት ሆኖ ሳለ በደፈናው ውሉን ያቋረጥኩት ቤቱን ስለፈለግሁት ነው ከማለት በቀር የፈለገው ለምን ዓላማ እንደሆነ በግልጽ ያቀረበው ክርክር የለም።ውሉን ያቋረጥኩት ቤቱን ስለፈለግሁት ነው የሚለውን የክርክር ነጥብ በዚህ ሰበር ደረጃ በሰጠው መልስ ውስጥም አላካተተም።በመሆኑም ተጠሪው ውሉን ያቋረጠው ቤቱን ለማስለቀቅ የሚያስችል ተገቢ እና ሕጋዊ ምክንያት ኖሮት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 209236 በ12/07/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150986 በ05/02/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. ተጠሪው ከአመልካቹ ጋር የነበረውን የኪራይ ውል ያቋረጠው በአግባቡ አይደለም በማለት ወስነናል።
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይላክ።
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶ ቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 116961

ሐምሌ 19 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
መስጠፋ አህመድ
ተፈሪ ገብሩ
ሽምሱ ሲር.ጋ.ጋ
አብርሃ መሰለ

አመልካች - ወ/ሮ አስቱር አርአያ

ተጠሪ - ወ/ሮ አወጣሽ መሐሪ - ጠበቃ ሐየሎም በቀለ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው የአሁን አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2006 ዓ.ም በተባለ አቤቱታ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- ባላቸው የጥብቅና ሙያ ተከሳሽ ከባለቤታቸው ከአቶ ወርቁ ወ/ማርቆስ ጋር የነበረባቸውን የፍች ክርክር እና የንብረት ክፍፍል ጉዳይ እንዲከታተሉላቸው በመፈለግ ታህሳስ 19 ቀን 1999 ዓ.ም በተደረገ የጥብቅና አገልግሎት ውል በንብረት ክፍፍሉ ተከሳሽ ከሚደርሳቸው ድርሻ 10% (አስር በመቶ) ለመክፈል ተስማምተው ስራውን በመጀመር የፍች ውሳኔ በማሰጠት፤ የንብረት ክፍፍል አቤቱታ በማቅርብ እና በአፈፃፀም ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሁለት ጊዜ ደርሶ ሲመለስ ተከታትለው የተከሳሽን መብት ለማስከበር ከ8 ዓመት በላይ ስራውን በአግባቡ በመስራት ግዴታቸውን እንደተወጡ፤ ተከሳሽ መጋቢት 25/2006 ዓ.ም ባደረጉት የዕርቅ ስምምነት ድርሻቸውን ብር 11,000,000.00 (አስራ አንድ ሚሊዮን) በመቀበል ክርክሮችን በሙሉ እንዳቋረጡ፤ ከዚህ በኋላ ግራ ቀኙ ባላቸው የአገልግሎት ውል ስምምነት መሰረት ክፍያ እንዲፈፅሙ እና መዝገቦችን እንዲረከቡ ቢጠየቁም ፈቃደኛ ስላልሆኑ በውሉ መሰረት ካገኙት ገንዘብ አስር በመቶ ብር 1,100,000.00 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ) ከነወለዱ እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ ከከሳሽ ጋር የጥብቅና አገልግሎት ውል እንደነበራቸው፤ በውሉ እንደተመለከተውና በክሱም እንዳልካዱት ብር 65,000.00 (ስድሳ አምስት ሺህ) የወሰዱ በመሆኑ ይህን ሳይቀንሱ የጠየቁት ክፍያ አግባብነት እንደሌለው፤ እንዲሁም ከሳሽ በገቡት ግዴታ መሰረት ባለመወጣታቸው ጉዳዩ ረጅም ጊዜ ስለተንተረተና በአግባቡ እንዲከታተሉ ሲጠየቁም ግዴታዬን ተወጥቻለሁ በማለት ዶክመንቶችን ጥለው በመሄዳቸው ሌላ ጠበቃ በመቅጠር ክርክር የቀጠሉ መሆኑን፤ ከዚያ በኋላ ብር 11,000,000.00 (አስራ አንድ ሚሊዮን) በመውሰድ ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዕርቅ እንደጨረሱት፤ ተከሳሽም ከሳሽ በውሉ መሰረት ጉዳዩን ሳይጨርሱ ቢያቋርጡም እስከሰሩበት ጊዜ ሊከፈላቸው የሚገባ መሆኑን በማመን ከሳሽ ብር 800,000.00 (ስምንት መቶ ሺህ) ጠይቀው በመጨረሻ ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ) ለመክፈል በመስማማት ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ልደታ ቅርንጫፍ በመሄድ ተከሳሽ ቁጥሩ 1000043340011 ከሆነ የቁጠባ ሂሳባቸው ሚያዝያ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሃምስ ሺህ) ወጪ አድርገው ከሳሽ በዚያው ባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ ተደርጎ ብር 600,000.00 (ስድስት መቶ ሺህ) ወደ ሂሳባቸው እንዲተላለፈላቸው የተደረገ ሲሆን ቀሪውን ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) በእጃቸው እንደተሰጡ፤ በዚህ መልኩ ተከፍሏቸው እያለ ከሳሽ አልተከፈለኝም በማለት የጠየቁት አግባብነት እንደሌለው፤ በውሉ መሰረት ከተከሳሽ ድርሻ 10% (አስር በመቶ) ለከሳሽ ሊከፈል የሚገባው ጉዳዩን ተከታትለው አስጨርሰው ንብረት ሲያስረክቡ ብቻ እንደሆነ በመግለፅ ከሳሽ በአጠቃላይ ብር 815,000.00 (ስምንት መቶ አስራ አምስት ሺህ) የተቀበሉ በመሆኑ እና ቀሪውም ሊከፈላቸው የማይገባ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሳሽ ብር 65,000.00 (ስድሳ አምስት ሺህ) አስቀድመው የከፈሉ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረቧቸው ምስክር ተከሳሽ ገንዘቡን ለከሳሽ ከፍያለሁ በማለት በስልክ ሲነጋገሩ መስማታቸውን ከሚገልፁ በቀር ስለመክፈላቸው ሌላ ማስረጃ ስላላቀረቡ ተከሳሽ ከሚጠበቅባቸው ክፍያ ውስጥ ብር 65,000.00 (ስድሳ አምስት ሺህ) እንዲከፍሉ፤ በባንክ ቀርበው ክፍያ መፈፀሙን በተመለከተ የቀረበውን ክርክር ለማጣራት ፍርድ ቤቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ልደታ ቅርንጫፍ ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠይቆ ባንኩ በቁጥር ልደ/ዳአ/026/1/15 በቀን 18/5/2007 ዓ.ም በሠጠው ምላሽ ተከሳሽ ሚያዝያ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ) ከሂሳባቸው እዳወጡ እና በዕለቱም በከሳሽ ስም ሂሳብ ተከፍቶ ብር 600,000.00 (ስድስት መቶ ሺህ) ወደ ሂሳባቸው ገቢ እንደተደረገ መግለፁን፤ ይህም የተከሳሽን ክርክር የሚያጠናክር አስረጅ ሆኖ መገኘቱን፤ ከዚህም ሌላ ገንዘቡ በከሳሽ ሂሳብ ገቢ መደረጉን እና ቀሪው ገንዘብ በእጃቸው የተሰጣቸው መሆኑን ያውቃሉ ተብለው በእለቱ የገንዘብ ልውውጡን የሰሩት የባንክ ባለሙያ አቶ ደረጀ ካሳ ቀርበው በሚያዝያ ወር 2006 ዓ.ም ተከሳሽ በባንኩ ቀርበው ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ) ከሂሳባቸው አውጥተው ብር 600,000.00 (ስድስት መቶ ሺህ) በዕለቱ ወደተከፈተው የከሳሽ ሂሳብ ገቢ እንደተደረገና ብር 150,000.00 (መቶ ሃምሳ ሺህ) በጥሬ ገንዘብ ለከሳሽ የተሠጠ መሆኑን እንደሚያውቁ መመስከራቸውን፤ ስለሆነም ባንኩ በሰጠው መግለጫ እና ሂሳቡን የሰሩት ባለሙያ ከሰጡት የምስክርነት ቃል ተከሳሽ በአጠቃላይ ብር 750,000.00 (ሰባት መቶ ሃምስ ሺህ) የከፈሉ መሆኑ በመረጋገጡ ይኸው ገንዘብ ከሳሽ ከጠየቁት ክፍያ ሊቀነስ እንደሚገባ፤ በሌላ በኩል ከሳሽ ጉዳዩን ተከታትለው ያላስጨረሱ በመሆኑ ቀሪው ክፍያ ሊከፈላቸው እንደማይገባ ተከሳሽ ቢከራከሩም ፍርድ ቤቱ ክርክር የተደረገባቸውን መዝገቦች በትዕዛዝ አስቀርቦ እንደተመለከተው ከሳሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በየቀጠሮው ይከራከሩ እንደነበር እና ክሳሽ ውሉን ከፈረሙበት 1999ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ ለ 7 ዓመታት ተከሳሽን በመወከል የተከራከሩ መሆኑ ስለተረጋገጠ ተከሳሽ በውሉ መሰረት አገልግሎት አልሰጡኝም በማለት የሚያቀርቡት መከራከሪያ ተቀባይነት እንደሌለው፤ ስለሆነም ቀሪውን ክፍያ ብር 285,000.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ) ሊከፍሉ ይገባል ብሏል፡፡ በአጠቃላይ ተከሳሽ ብር 285,000.00 + ብር 65,000.00 = ብር 350,000.00 (ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ) ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሉ፤ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን እንዲቻቻሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ለአመልካች ብር 750.000.00 (ሰባት መቶ ሃምስ ሺህ) ስለመክፈላቸው በፍ/ብ/ህ/ቁ/2472(2) እና (3) በተደነገገው መሰረት ሊቀርብ በሚገባው ማስረጃ ማለትም ደረሰኝ ወይም የሰነድ ማስረጃ አቅርበው ሳያረጋገጡ ይኸው ገንዘብ መከፈሉ ተረጋግጧል ተብሎ መወሰኑ ስህተት በመሆኑ ታርሞ ገንዘቡን ከነወለዱ እንዲከፍሉ እንዲወሰን፤ እንዲሁም የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብቱ ሊጠበቅ ሲገባ ይቻቻሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ ዝርዝር የማቅረብ መብቱ ተጠብቆ ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ቀደም ሲል የተከፈላቸውን ብር 750.000.00 (ሰባት መቶ ሃምስ ሺህ) ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ወደ ጎን በመተው ለሁለተኛ ጊዜ እንዲከፈላቸው ክስ ማቅረባቸው የሚያሳዝን እና የሙያውን ክብር የሚያዋርድ በመሆኑ፤ ወጪና ኪሳራን በተመለከተ ያቀረቡት ጥያቄም እንደነገሩ ሁኔታ ለመወሰን ፍርድ ቤቱ ሙሉ ስልጣን ያለው በመሆኑና በጉዳዩም ረችና ተረቺ ባለመኖሩ ይኸው ግምት ውስጥ ገብቶ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ተብሎ መወሰኑ ምንም ስህተት ስላልተፈፀመበት ቅሬታው ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ እና በሰበር የተደረገውን ክርክር ሲሆን ክርክሩን ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌ ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የአመልካች መሰረታዊ ክርክር ብር 750.000.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ) ስለመከፈሉ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባልቀረበበት መከፈሉ ተረጋግጧል ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መወሰኑን የሚመለከት ነው፡፡ በመሰረቱ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንዳለው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እንዲሁም በፌዴራሉ ፍርድ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ሥር ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን የሰበር ችሎቱ የግራ ቀኝ ማስረጃዎችን ጥንካሬ በመመዘንና በመመርመር ውሣኔ እንዲሰጥ የቀረበው አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረታዊ የህግ ስህተት ለማረም ከላይ በተጠቀሱት ህጎች ለችሎቱ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት የተከተለ ባለመሆኑ የምንቀበለው አይሆንም፡፡

በሌላም በኩል አመልካች ገንዘቡ ስለመከፈሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ/2472(2) እና (3) በተደነገገው መሰረት ሊረጋገጥ እንደሚገባ የተከራከሩ ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የጥብቅና አገልግሎት ውል እንጂ የብድር ውል ባለመሆኑና የፍ/ብ/ህ/ቁ 2472 ከብድር ውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ከተከፈለ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ የሚሆንበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 64397 እና ሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት የሠጠው አስገዳጅ ትርጉም ለተያዘውም ጉዳይ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2 ድንጋጌ መረዳት ስለሚቻል በዚህም ረገድ የቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ ስልጣኑ የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ከተጠየቀበት ገንዘብ ውስጥ ብር 750.000.00 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ) ለአመልካች አስቀድሞ ስለመከፈሉ በማስረጃ በማረጋገጥ ውሳኔ ላይ መድረሳቸውን ተገንዝበናል፡፡ አግባብነት እና ተቀባይነት ባለው ማስረጃ የተረጋገጠው ገንዘቡ አስቀድሞ መከፈሉ ከሆነ ደግሞ ይኸው ገንዘብ አመልካች ከጠየቁት ክፍያ ሊቀነስ እንደሚገባ በመወሰኑ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚያሰኝ አይሆንም፡፡

የስር ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ በማለት ያሳለፈው ውሳኔም የስነ ስርዓት ህጉን የተከተለ አይደለም በሚል ውሳኔው እንዲታረም ቅሬታ ቀርቧል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 462 እንደተደነገገው በክርክር ምክንያት የወጣን ወጭና ኪሣራ ማን እንደሚከፍልና ምን ያህል እንደሚከፍል ፍ/ቤቱ በመሰለው ሊወስን እንዲችል ፍቅድ ስልጣን ተሰጥቶታል ፡፡ ፍርድ ቤቱ በህጉ የተሰጠውን ፍቅድ ስልጣን ተጠቅሞ ሊወስን ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ጉዳዩች ሁሉ ተመልክቶና አረጋግጦ ሊወስን እንደሚገባ በህጉ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እንዲከፈላቸው ከጠየቁት ገንዘብ ከፊሉን አስቀድመው ስለወሰዱ በሙሉ ሊከፈላቸው እንደማይገባ፤ በአንፃሩ ተጠሪ ብር 350,000.00 (ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ) ከነወለዱ እንዲከፍሉ በመወሰኑ ባለዕዳ መሆናቸውን፤ አመልካች በራሳቸው ተጠሪ ደግሞ በጠበቃ ተወክለው መከራከራቸውን እና የነገሩን አጠቃላይ ሁኔታ በማየት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ እና ትዕዛዝ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/ 153169 ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 116173 ሐምሌ 27/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በተጠሪ ቤት ላይ በዚህ ፍርድ ቤት የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም የተላለፈው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው ሁሉ ይፃፍ፡፡

3. በዚህ ፍርድ ቤት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 114553

ሐምሌ 29ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ኤልያስ ስሜ ተሰማ ..... አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘነበች ተመስገን ጫካ..... አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 198148 በቀን 08/09/2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረብኩትን የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 140263 በቀን መጋቢት 15/2007 ዓ.ም ያፀናው በመሆኑ መሠታዊ ስህተት ያለበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የብድር ውልን የሚመለከት ነው በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት ተጠሪ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘት ጥቅምት 28/2004 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል አመልካች ነሐሴ 30/2004 ዓ.ም ለመመለስ ብር 200,000 ተበድረው ወስደው ሊመልሱ አልቻሉም ስለዚህ ዋናውን ገንዘብ፣ ወለድ፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉኝ የሚል ሲሆን አመልካች በሰጡት መልስ ከተጠሪ ጋር ገንዘብ ሊያስበድር የሚችል ትውውቅ የለንም አመልካች በመ/ቁ 198149 በተጠሪ ባለቤት ክስ የቀረበባት ወ/ሮ መስከረም አሰግድ ሰፊ ቦታ ገዝተን አርት ጋለሪ መስራት በመፈለጋችን በኮሚሽን ሠራተኞች አማካኝነት በተጠሪ ባለቤት አቶ ደጁ አበራ ስም የተመዘገበውን በብር 700000 ለመግዛት ተስማምተን በተፈራረምነው የቤት ሽያጭ ውል ላይ ግን ብር 400000 በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት የተገዛው ብር 500000 ቢሆንም በውልና ማስረጃ በተደረገው የሽያጭ ውል የተጻፈው ብር 300000 ሲሆን ከዚህ በኋላ የከረረ ፀብ ውስጥ ነን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሎቹ በአንድ ኮምፒውተር መጻፋቸው ሙሉ ፊርማዬ በሰነድ ላይ ያለው አይደለም፡ ብፈርም ኖሮ ሙሉ ስሜን ከጉን እጽፍ ነበር አጭር ፊርማዬን ለማስመሰል የተሞከረ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ማጣራት ይችላል ስለሆነም ክሱ በሀሰት የቀረበብኝ በመሆኑ ኪሳራ ተከፍሎ በነፃ ልሰናበት ብለዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የአመልካች ፊርማ በፌደራል ፖሊስ ፎረንሲክ ምርመራ መምሪያ እንዲጣራ ተደርጐ ምስክሮችን ሠምቷል፡፡ በአመልካች በብድር ውሉ ሊገደዱ የሚችሉት የብድር ውሉን ከፈፀሙ ነው፡፡ በጽሁፍ የተደረገውን የብድር ውል በሰው ማስረጃ ማስተባበል አይቻልም፡፡ አመልካች የብድር ውሉን አልፈፀምኩም የሚሉት ፊርማውን በመካድ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ፊርማው እንዲመረመር አዞ በአመልካች የተፈረመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በተጠሪና በአመልካች መካከል የብድር ውል መደረጉን የሚያረጋግጥ ሲሆን በውሉ ላይ ያሉ ምስክሮቹም የብድር ውሉ መደረጉን አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም ክስ የቀረበበትን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ብር 200000 ከነሐሴ 30 ቀን 2004 ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ ብር 4850 ለቴምብርና ቀረጥ ብር 10 ለጥብቅና አገልግሎት ብር 15,000 እንዲከፍል ብሏል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን በመቃወም መሠረታዊ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን ይዘቱም ሙሉ ፊርማዬ በሰነዱ ላይ ያለው አይደለም፡፡ አጭር ፊርማ ስፈርም ስሜን ከጉን አልጽፍም ስለዚህ አጭር ፊርማዬን ለማስመሰል የተደረገ ጥረት መኖሩን ሠነዱ ያስረዳል በፍ/ሕ/ቁ 1728/1/ ፊርማ በውሉ ተገዳጅ የሆነ ሰው እጅ መጻፍ እንዳለበት የተደነገገ በመሆኑና የሠነድ ምርመራ ውጤትም የመጨረሻ ማስረጃ ባለመሆኑ ባልተሟላ ፊርማ የተወሰነ በመሆኑ መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በሠነዱ ተዓማኒነት ላይ የተነሱትን ክርክሮች የስር ፍርድ ቤት ሳይመረምር ማለፉ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182/2/ መሠረት የውል ስምምነቱ አጠራጣሪ በሚሆንበት ጊዜ ተገዳጅ የሆነውን በሚጠቅም መልኩ መታየት እንዳለበት ከተደነገገው አኳያ ሳይታይ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ የቀረቡት ምስክሮች አመልካችና ተጠሪ የብድር ውሉን አለመፈፀማቸውን፣ አመልካችም ከተጠሪ ገንዘብ መበደር ደረጃ የሚያደርስ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ይግባኙን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ ውጭ ስለጭብጥ አመሠራረት የተደነገገውን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የአመልከች ፊርማ የለም እየተባለ በግራ ቀኙ መካከል የብድር ውል አለ መባሉንና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በሰጡት መልስ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የብድር ውል እና የሽያጭ ውል በተመሳሳይ ቀን ተደርጓል ምስክሮቹም አንድ ናቸው፡፡ፍርድ ቤቱም እነዚህኑ አስቀርቦ ሰምቷል፡፡ አመልካች እኔ ስፈርም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሦኑ ስሜን እጽፋለሁ ብለው ክደው ቢከራከሩም ፊርማው በፎረንሲክ ተመርምሮ ፊርማቸው መሆኑ ተረጋግጧል ፍርድ ቤቱ በተጨማሪ በውሉ ላይ የተመለከቱትን ምስክሮችንም ሠምቶ አረጋግጧል። ይህንን አላስተባበሉም አመልካች ከተጠሪ የተሻለ እውቀት ያላቸው ባለሙያ ናቸው የውል ክፍሉ ሳያነቡላቸው እና ሳያረጋግጡ የሚፈርሙ አይደሉም ፊርማው የአመልካች መሆኑ እስከተረጋገጠ ሙሉ ፊርማ እና አጭር ፊርማዬ በማለት ከኃላፊነት ማምለጥ አይችሉም ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ይጽናልኝ ብለዋል። አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘበ የሚቻለው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጥቅምት 28 ቀን 2004 ዓ.ም ተደርጓል የተባለውን የብር 200000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ብድር ውል ላይ አመልካች ከተጠሪ ገንዘብ ለማስበደር የሚያደርስ ትውውቅ የለንም በውሉ ላይ የተመለከተው ፊርማ የኔ አይደለም ልገደድ አይገባም ሲሉ ተጠሪ በመካከላችን በነበረው መኖርያ ቤት ሽያጭ ውል ከአጠቃላይ ገንዘቡ 100000 /አንድ መቶ ሺ ብር ከፍለውኝ/ ቀሪውን ብር 200000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ በብድር ውል ለነሐሴ 30/2004 ዓ.ም ለመመለስ ተስማምተናል የሚል ነው። በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ውል አለ ለማለት ከሚያስችሉት ነጥቦች አንዱ ደግሞ በፍ/ሕ/ቁ 1728 እንደተመለከተው በውሉ ተገዳጅ የሆነው ሠው እጅ የተጻፈ ፊርማ መኖር ነው። በዚህ ጉዳይ ደግሞ ፊርማው የተካደ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። እዚህ ላይ ተበዳሪው በፍትሐብሔር ህግ ቁ. 2472/1/ መሠረት የብድር ውሉን ለማስረዳት በቀረበው የሰነድ ማስረጃ ላይ ያለው ፊርማ የእኔ አይደለም በማለት የካደ በሆነ ጊዜ ፊርማው የተበዳሪ መሆኑን ለማረጋገጥ ምን ዓይነት ማስረጃ ተቀባይነት አለው የሚለው በሰነድ ላይ ያሉ ፊርማዎችን ለማረጋገጥ /Authenticate/ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች መመልከቱ አስፈላጊ ነው።

በሰነድ ላይ ያለ ፊርማ በተካደ ጊዜ ፊርማውን የማረጋገጫው የመጀመሪያው መንገድ የቴክኒክ ምርመራ እንዲደረግ ማድረግ ነው። ሆኖም ፊርማው በቴክኒክ ምርመራ የማን እንደሆነ ለማረጋገጥ ባልተቻለ ጊዜ ፊርማው ሲፈረም የነበሩ ምስክሮችን ቃል በመስማትና በሌሎች ማስረጃዎች ፊርማው የማን እንደሆነ በመመዘን ማረጋገጥ እንደሚቻል ከማስረጃ ምዘና ጠቅላላ መርሆዎች ለመረዳት ይቻላል። የስር ፍርድ ቤት አመልካች ፊርማውን በመካዳቸው ምክንያት ለፌደራል ፖሊስ ፎረንሲክ ምርመራ መምሪያ በኩል የቴክኒክ ምርመራ እንዲደረግ አዞ የአመልካች ፊርማ ስለመሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን ገልጿል ፍርድ ቤቱ በአመልካች የተፈረመ መሆኑ በቴክኒክ ምርመራ መረጋገጡ ሳያበቃ ሁለተኛውን አማራጭም በመከተልም በውሉ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያሉትን ምስክሮች በመስማት ፌርማው በአመልካች የተፈረመ ስለመሆኑ ፍሬ ነገርንና ማስረጃን በሚመዝንበት ወቅት አረጋግጧል፡፡ አመልካች ፌርማው አጭር እና ረጅም ሲሆን የሚፈጥሯቸውን ልዩነቶች በመግለጽ ከመከራከር ውጭ ፌርማውን የፈረመው በሌላ ህጋዊ ተጽዕኖ ወይም ግዴታ ምክንያቶች መሆኑን መሠረት በማድረግ አልተከራከረም፡፡ ፌርማ ሀሳብን ወይም ፈቃድ መስጠትን የሚረጋገጥበት በመሆኑ በአመልካች የተፈረመ መሆኑ ከተረጋገጠ አጭር እና ረጅም መሆኑ ደግሞ በውጤቱ ላይ ልዩነት አያመጣም፡፡ በሌላው በብድር ውሉ ስምምነት ላይ የመክፈያ ጊዜው ተወስኖ የተቀመጠ በመሆኑ አመልካች በፍ/ሕ/ቁ 2482/2/ /3/ መሠረት የመመለሻ ጊዜው ከማለፉ በፊት የመክፈል ግዴታ ያለበት በመሆኑ አለመክፈሉ እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ የብድሩን ገንዘብ ህጋዊ ወለድ ጋር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የብድር ውል አለ በማለት በውሉ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ከነወለዱ አመልካች እንዲከፍል በማለት የደረሱበት ድምዳሜ መሠረታዊ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወሰነ፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 198148 በቀን 08/09/2005 እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 140263 መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

የስር ፍርድ ቤት በአፈ/መ/ቁ 23365 የጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በ17/02/2008 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ሩ/ለ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117036

ህዳር 12 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተሽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ፀጉብርሃን ትራዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ኮሎኔል ይትባረክ አማረ - ከጠበቃ ኃይለስላሴ ገ/መድህን ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የሽያጭ ውሉን በወቅቱ ባለመፈፀሙ በኃላፊነት ይጠየቃል በማለት አመልካች የመኪና ሽያጭ ውሉን ባለመፈፀሙ ተጠሪ ላይ የደረሰበት ጉዳት ተጣርቶ እንዲቀርብ በማለት የሰጡት ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ /ከሳሽ/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡
2. ከሳሽ ለሰር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል፣ ከተከሳሽ ሁለት ተሽከርካሪዎችን ለመግዛት ተዋውሎ፣ የሁለቱን መኪኖች ዋጋ ብር 2,300,000 /ሁለት ሚሊዬን ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ገቢ አድርጌለሁ፡፡ ተከሳሽ መኪኖቹን ውሉን ከተፈራረምንበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ማለትም እስከ ነሐሴ 27 ቀን 2006 ዓ.ም ሊያስረክበኝ የውል ግዴታ ገብቷል፡፡ ከሳሽም መኪኖቹ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሰጥቶኛል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ በውሉ መሠረት መኪኖቹን ያላስረከበኝ በመሆኑ፣ ከሳሽ የከፈልኩትን ገንዘብ እንዲከፍል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይወሰንልኝ፡፡ ከሳሽ ከነሐሴ 27 ቀን 2006 ዓ.ም መኪኖቹን እረከባለው በሚል እምነት አንድ ተሽከርካሪ በወር ብር 3000 /ሶስት ሺህ ብር/ ሁለቱን በብር 6000 /ስድስት ሺህ ብር/ አከራይቼ አገኝ የነበረውን ጥቅም ስለቀረብኝና በዚህ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ብር 354,000 /ሶስት መቶ ሀምሳ አራት ሺህ ብር/ እንዲከፍልና ዕዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ በወር ብር 6000 /ስድስት ሺህ ብር/ እየተሰላ ካሣ እንዲከፍል፤ የወሰደውን ገንዘብ ወለድ እንዲከፍልና፣ የገደብ መቀጮ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

3. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ለከሳሽ ሁለት መኪኖች ለመሸጥና የመኪኖችን ዋጋ ከሳሽ መክፈሉ የሚካድ አይደለም፡፡ ተከሳሽ ለከሳሽ መኪኖችን ለማስረከብ የተለያዩ ተግባራትን ከከሳሽ ሰራተኞች ጋር በመተባበር ሲፈጽም ቆይቷል፡፡ መኪኖችንም በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ ፈቃደኛ ነበር፣ ነገር ግን በመዝገብ ቁጥር 24172 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ.ም በመኪኖቹ ላይ የዕግድ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙን በመቃወም ተከሳሽ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቤ በመዝገብ ቁጥር 157145 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡ በመሆኑም በሽያጭ ውሉ መሠረት ያልተፈፀመው ተከሳሽ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ በመሆኑ ከሳሽ ለውሉ አለመፈፀም ተከሳሽ ኃላፊ እንዲሆንና ካሣ እንዲከፍል ለማለት ያቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ በሽያጭ ውሉ አለመፈፀም ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ የሚያስቀጣ መሆኑ ከሳሽ ካሣ ይክፈለኝ በማለት የጠየቀው ተገቢ አይደለም የሚሉና ሌሎች መከራከሪያዎችን በማንሳት መልስ ሰጥቷል፡፡

4. የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተከሳሽ ለከሳሽ ከሰጣቸው ሁለት መኪኖች መካከል የአንደኛው መኪና የሳንሲ ቁጥር lzz5ewd77n847969 እና የሞተር ቁጥር 131107038497 መሆኑ ከሳሽ ባቀረበው የሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ከከሳሽ ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በመሸጥ ሙሉ ዋጋውን የተቀበለበት የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተጠቀሰውን መኪና ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ ውል ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መኪና መሆኑ ተረጋግጣል፡፡ ይህም ተከሳሽ ለከሳሽ የሸጠውን አንደኛው መኪና የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ ተለይቶ የታወቀውን መኪና ለከሳሽ በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚያስችል መብት ሳይኖረው የፈፀመው የሽያጭ ውል በመሆኑ ለውሉ አለመፈፀምም ሆነ በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተከሳሽ ኃላፊነት አለበት፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሽ ብር 3000,000 /ሶስት ሚሊዬን ብር/ አስይዞ ዕግዱን በማስነሳት መኪኖቹን ለከሳሽ ማስረከብ እየቻለ ይህንን ያላደረገ በመሆኑ ለሽያጭ ውሉ ኃላፊ ነው በማለት ከሳሽ የከፈለውን የመኪኖቹን ዋጋ ከዘጠኝ ፐርሰንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወለድ ጋር እንዲመልስ በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍልና በውሉ አለመፈፀም ምክንያት በከሳሽ ላይ የደረሰበት ኪሣራና /ጉዳት ተጣርቶ/ እንዲቀርብ በማለት በመዝገብ ቁጥር 153576 ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ክፊል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአመልካችን ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

5. አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ከሸጣቸው ሁለት መኪኖች አንደኛው ቀደም ሲል ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መሆኑን በመግለጽ ውሳኔ የሰጠው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪም ጋር ሆነ ከአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ ጋር በተዋዋለው የመኪና ሽያጭ ውል ላይ የመኪና የሻንሲ ቁጥርና የሞተር ቁጥር አልጠቀሰም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 223፤አንቀጽ 137/1 እና አንቀጽ 256 መሠረት ያላቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመቀበል አመልካች አንደኛውን መኪና ለተጠሪ ያላስረከበው ቀደም ብሎ መኪናውን በሽያጭ ለሌላ ሰው ስለሸጠው ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የማስረጃ አቀራረብ ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ የሰጣቸውን ሁለት መኪኖች ለተጠሪ ሳያስረክብ የቀረው በባልና ሚስት ክርክር መነሻ መኪኖቹ እንዳይሸጡ እንዳይለወጡና ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፅሁድ ትዕዛዝ በመስጠቱና የፅሁድ ትዕዛዙን ለማስነሳት አመልካች ጥረት ቢያደርግም ጥረቱ ውጤት አልባ በመሆኑ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ስለገጠመው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የከፈለውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ውሣኔ ከሰጠ በኃላ የሸያጭ ውሉ ያለመፈፀሙ ተጠሪ ላይ ያደረሰውን ኪሳራ አመልካች የመሸፈን ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ተጠሪ ወሉን ያልፈፀመ ወገን ምንያህል ገንዘብ መክፈል እንዳለበት ውል ተዋውለዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በውሉ የተረጋገጠውን የገደብ መቀጫ ማስከፈል ሲገባው ከገደብ መቀጫው አልፎ ለተጠሪ አመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

6. ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠ መልስ አመልካች ለተጠሪ ነሀሴ 7 ቀን 206 ዓ.ም በተደረገው የሽያጭ ውል ከሸጣቸው መኪናዎች ውስጥ የአንደኛውን የሻንሲና የሞተር ቁጥር በመግለጽ ለገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ያሳወቀ በመሆኑ ተጠሪ ከገዛቸው መኪናዎች ውስጥ የአንደኛው መኪና የሻንሲ እና የሞተር ቁጥር ተለይቶ የታወቀ ነው፡፡ ሆኖም አመልካች በተጠሪ ከሰጣቸው መኪናዎች ውስጥ ይህንን የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን ለይቶ ያሳወቀውን መኪና ቀደም ሲም ሲል ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተደረገ ውል ለአቶ ግደይ ገ/ፃድቅ የሸጠውና ይህንኑ መኪና ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ ለማስረከብ የሚችል መሆኑን ገልጾ የፃፈው ደብዳቤ የአመልካች ስራ አስኪያጅ በፈፀመው የማታለል ወንጀል ክስ የቀረበበት መሆኑንና አቶግደይ ገ/ፃዲቅ አመልካች የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀውን መኪና እንዲያሰረክባቸው ከፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153390 ክስ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ጳጉሜ 5 ቀን 2006 ዓ.ም እና መስከረም 12 ቀን 2007 ዓ.ም የዕግድ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች መኖራቸውን ያወቅነው ክሱንና የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ለፍርድ ቤቱ ካቀረብን በኃላ በመሆኑ ማስረጃዎቹን የስር ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 መሠረት እንድናቀርብ ፈቃድ ጠይቀን በፍርድ ቤቱ ፍቃድ መሠረት ያቀረብናቸው የሰነድ ማስረጃዎች በመሆናቸው አመልካች የስር ፍርድ ቤት ከሥነ-ሥርዓት ሕግ ውጭ ማስረጃ እንደተቀበለ በመግለጽ ያቀረበው አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ሌላውን መኪና በተመለከተ አመልካች ብር 3000,000 /ሶስት ሚሊዬን ብር/ በማስያዝ ዕግዱን ማስነሳትና የውል ግደታውን መወጣት እየቻለ ይህንን አላደረገም አመልካች ውሉን ያልፈፀመው በፍርድ ቤቱ ዕግድ ምክንያት አይደለም ስለሆነም ውሉን ያልፈፀምኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የወሰደውን ገንዘብ ወለድ ተጠሪ በውሉ አለመፈፀም የደረሰበትን ኪሳራና በውሉ ላይ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ እንዲከፍል የተወሰነው በአግባቡ ነው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሰ አቅርቧል፡፡

7. ይኸ ሰበር ችሎት አመልካችና ተጠሪ በቃል ሊከራከሩባቸው የሚገቡ ነጥቦችን ሰኔ 22 ቀን 2008 ዓ.ም ለይቶ ለግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲደርሳቸው ካደረገና በተለያየ ምክንያት የቃል ክርክር ለማስማት የሰጠውን ቀነ ቀጠሮ ከተለወጠ በኃላ የቃል ክርክሩን የመጨረሻ ቀነ ቀጠሮ በሰጠበት ጥቅምት 24 ቀን 2009 ዓ.ም አመልካች ወኪል ወይም ጠበቃ ባለመቅረቡ የተጠሪን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ አመልካች ስለ ማስረጃ አቀራረብ ሥርዓትና ሌሎች ነጥቦች የቀረበውን የሰበር ክርክር ለማረጋገጥና ለማገናዘብ እንዲቻል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 153516 እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ መዝገቡን በትዕዛዙ መሠረት በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

8. ከስር የክርክር አመጣጥና ግራቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው ሁለት ገልባጭ መኪኖች ሽያጭ መሠረት ለተጠሪ የሚያስረክበው መሆኑን ገልጾ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በፃፈው ደብዳቤ የገለፀውና ያሳወቀው የሻንሲ ቁጥር lzz5ewd77n847969 የሆነውና የሞተር ቁጥሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

131107038497 የሆነውን መኪና ቀደም ብሎ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለአቶ ግደይ ገ/ዓዲቅ የሸጠውና ይህንኑ መኪና ለአቶ ግደይ ገ/ዓዲቅ ለማስረከብ እንደሚችል ገልጾ ደብዳቤ የፃፈበት መሆኑን በአጠቃላይ መኪናውን ለሁለት ሰው በመሸጥ ዋጋ የተቀበለበት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡

9. አመልካች ተጠሪ የሻንሲ ቁጥሩና የሞተር ቁጥሩ ተለይቶ የተገለፀው መኪና ለሌላ ሰው የተሸጠ መሆኑን ተጠሪ የፍትሐብሔር ሥን-ሥርዓት ሕግ በሚደነግገው መሠረት የሰነድ ማስረጃዎቹን አላቀረበም በማለት ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታና ክርክር ተገቢነት መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እኛም የስር ፍርድ ቤቶች መዝገብ በትዕዛዝ በማስቀረብ የስር ከሳሽ /ተጠሪ/ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የገለፀውን መኪና ቀደም ሲል ለአቶ ግደይ ገ/ዓዲቅ ይሸጠው መሆኑንና ይህንኑ መኪና ለአቶ ግደይ ገ/ዓዲቅ ለማስረከብ የሚችል መሆኑን ገልጾ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ደብዳቤ ጽፎ እንደነበር የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃዎች ተጠሪ ክሱን ሲያቀርብ የማያውቃቸውና ያላገኛቸው መሆኑን በመግለጽ ፍርድ ቤቱ ሰነዶቹን በተጨማሪ ማስረጃነት ለማቅረብ እንዲፈቅድለት የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ /ተጠሪ/ ባቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ የማቅረብ ጥያቄ ላይ ተከሳሹ /አመልካች/ አስተያየቱን እንዲያቀርብ የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝና አባሪውን የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም የደረሰው መሆኑ በድርጅቱ ማህተም ካረጋገጠ በኃላ ተከሳሽ /አመልካች/ ከሳሽ /ተጠሪ/ ባቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ የማቅረብ ጥያቄ ላይ አስተያየቱን ባለማቅረቡ የሰነድ ማስረጃዎች የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 መሰፈርት የሚያሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ ማስረጃዎቹ እንደቀረቡና ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዙ ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ብይን ከሰጠ በኃላ የሰነድ ማስረጃዎችን በመቀበል ለፍርድ በግብዓትነት የተጠቀመባቸው መሆኑን ተረድተናል፡፡

10. ይኸ ሰበር ችሎት በትዕዛዝ ካስቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 153516 እንደተረዳነው የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን ተጨማሪ ማስረጃዎች በተጨማሪ ማስረጃነት ከመቀበሉ በፊት አመልካች አስተያየት የመስጠትና የመከራከር መብቱን ጠብቆ አመልካች ዕድሉን ተጠቅሞ አስተያየቱን ባለማቅረቡ ይህንኑ ምክንያቱን በግልጽ በመዝገብ ላይ በማስፈር ትዕዛዝ ሰጥቶ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ሰነዶቹ በተጨማሪ ማስረጃነት ሊቀርቡ አይገባም የሚልበትን ምክንያት ለሥር ፍርድ ቤት ያላቀረበውን ክርክርና አስተያየት ለዚህ ሰበር ችሎት ማቅረቡ ተገቢ ሆኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ የማቅረብ ጥያቄው ላይ አመልካች አስተያየትና ክርክር የማቅረብ መብቱን መጠበቁ ብቻ ሳይሆን ከሳሽ /ተጠሪ/ በተጨማሪ ማስረጃነት ለማቅረብ ጥያቄ ያቀረበባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 256 የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን ነጥብ በአግባቡ በመመርመር ማስረጃዎቹን ለመቀበል ብይን የሰጠ መሆኑን ተረድተናል፡፡

11. ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ሲያቀርብ ተገቢውን ትጋት በማድረግ ሊያውቃቸውና ሊያገኛቸው የማይችላቸው ማለትም አመልካች ለተጠሪ የሸጠው መሆኑን ገልጾ ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቁጥር TB.TP116/48/14 ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀውን መኪና ቀደም ሲል አመልካች ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርጫፍ ጽ/ቤት ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መሆኑን ቁጥሩ TB.TB1606/14 ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን የተገለፀውን መኪና መሆኑን ይህንን መኪና ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም አመልካች ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠ መሆኑ ገልፀው አቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153390 ክስ ማቅረባቸውን በመጀመሪያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጳጉሜ 4 ቀን 2006 እስከ መስከረም 9 ቀን 2007 የሚቆይ የዕግድ ትዕዛዝ መስጠቱንና መስከረም 9 ቀን 2007 ዓ.ም መኪናው ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የዕግድ ትዕዛዝ የሰጠመሆኑን የሚያሳዩ የሰነድ ማስረጃዎች እንደሆኑ ተረድተናል፡፡ እነዚህ በአመልካችና በሌላ ሶስተኛ ወገን እጅ የነበሩ ማስረጃዎች ተጠሪ ክስ ሲያቀርብ የማያውቃቸውና ሊያገኛቸው የማይችል ማስረጃዎች በመሆናቸው በስር ፍርድ ቤት የሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርቡ በማድረግ መርምሮና መዝኖ ውሳኔ የሰጠው የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት በመሆኑ በዚህ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታና ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

12. አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ባደረገው የመኪና ሽያጭ ውል በአመልካች የሸጠው የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀው አንደኛው መኪና አመልካች ቀደም ብሎ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሰጠው መሆኑንና አመልካች መኪናውን ለአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ የሰጠ መሆኑን ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን ጠቅሶ ለኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያሳወቀ መሆኑ የሕጉን ሥርዓት በመከተል ተጠሪ ባቀረባቸው ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ ተመልክተናል፡፡ ከላይ በዝርዝር እንደተገለፀው አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተደረገ የሁለት መኪናዎች ሽያጭ ውል መሠረት ሙሉ ዋጋውን የተቀበለበትና እስከ ነሐሴ 25 ቀን 2006 ዓ.ም ለተጠሪ ለማስረከብ የውል ግዴታ የገባበት የሞተር ቁጥሩ 131107038497 እና የሻንሲ ቁጥሩ lzz5ewd77n847969 የሆነው መኪና አመልካች ቀደም ብሎ ለሌላ ሰው የሸጠው መሆኑንም ለገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ያረጋገጠው የመኪናውን ባለሀብትነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2273 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2281 በተደነገገው መሠረት ለማስተላለፍ የማይችል መሆኑን እያወቀ የተዋዋለው የሽያጭ ውል ነው።

13. ከዚህ አንፃር ሲታይ ከላይ ከሞተረኛ የሻንሲ ቁጥር የተገለፀውን መኪና በተመለከተ አመልካች በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በባልና ሚስት ክርክር ምክንያት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም የዕግድ ትዕዛዝ በመስጠቱ ምክንያት ነው በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር በማስረጃ የተረጋገጡትን ኩነቶች /ፍሬ ነገሮች/ መሰረት ያደረገ አይደለም አመልካች ለተጠሪ ከሸጣቸው መኪናዎች ውስጥ ሲታይ የሞተር ቁጥር የሻንሲ ቁጥር የተጠቀሰውን መኪና ሙሉ የባለሃብትነት መብት ለተጠሪ ለማስተላለፍ የማይቻልበት የሶስተኛ ወገን መብትና ጥያቄ በመኪናው ላይ ያለ መሆኑን ተረጋግጧል። የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ባይኖር ወይም የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቶ ቢሆንም አመልካች በሽያጭ ውሉ መሰረት የመኪናውን ውል ባለመብትነት ሊያስተላልፍ እንደማይችልና መኪናውን በቀዳሚነት ገዝቸ ዋጋ ከፍየበታለሁ የሚለው አቶ ግደይ ገ/ዓዲቅ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ያሳገደው መሆኑን ፣የአመልካች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ መኪናውን ለሌላ ሻጭ ከሸጠ በኃላ ያንኑ መኪና ለተጠሪ መሸጥ የማታለል ተግባር የፈፀመ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመወሰን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል ።

14 .ይህም አመልካች የተጠሪን መብት በሚነካ ጉድለት ምክንያት የሞተርና የሻንሲ ቁጥር የተገለፀልን መኪና መኪናውን ከአመልካች ቀድሞ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ/ም በተደረገው ውል ከገዛው አቶ ግደይ ገ/ዓዲቅ መብትና ጥያቄ ነፃ አድርጎ ለተጠሪ ሊያስረክበው እንደማይችል እያወቀ የሸያጭ ውሉን ከተጠሪ ጋር በመዋዋሉ ምክንያት ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል ተጠሪ ውሉን የተዋዋለው መኪናውን ለሌላ ሰው አመልካች የሸጠው መሆኑን ሳያውቅ በመሆኑና አመልካች የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣና ሊወጣ እንደማይችል እያወቀ የፈፀመው የሸያጭ ውል በመሆኑ ተጠሪ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ፣ ተጠሪ የተቀበለውን የመኪናውን ዋጋ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲመለስለትና አመልካች መኪናውን በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያደረሰበት ኪሣራ እንዲከፍል ያቀረበው ጥያቄ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝቶታል ።

15 ከዚህ አንፃር አመልካች የሞተርና የሻንሲ ቁጥር የተገለፀውን መኪና ሙሉ ባለሀብትነት ለተጠሪ ሊያስተላልፍ እንደማይችልና መኪናውን ለሌላ ሰው አስቀድሞ የሸጠው መሆኑን እያወቀ ከተጠሪ ጋር የመኪና ሽያጭ ውል በመዋዋል የመኪናውን ሙሉ ዋጋ ከተቀበለ በኃላ የመኪናውን ሙሉ ባለሀብትነት ለተጠሪ ለማስተላለፍ የማይችል በመሆኑ ምክንያት የሽያጭ ውል ያፈረሰው በተጠሪ ጥፋት ምክንያት መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ከተጠሪ የወሰደውን ብር 1,150,000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር) ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ፣ ውሉን ባለመፈፀሙ በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) እና ውሉ ባለመፈፀሙ በተጠሪ ላይ የደረሰበት ኪሣራ ተጣርቶ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከላይ የገለፅናቸውን ስለ ሽያጭ ዉሉ የተደነገጉትን ልዩ ድንጋጌዎች ማለትም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀጽ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

16 አመልካች ከተጠሪ ጋር ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ/ም በተዋዋለው ውል የሸጠለት ሌላውን አንድ መኪና በተመለከተ በባልና ሚስት ክርክር መነሻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 25 ቀን 2006 ዓ/ም የዕግድ ትዕዛዝ ባይሰጥና የዕግድ ትዕዛዙን ለማስነሳት አመልካች በይግባኝ አቅርቦ የዕግድ ትዕዛዝ ባይፀናበት በወሉ መሰረት ለመፈፀም የማያስችለው ሌላ ምክንያት የሌለው መሆኑ የስር ፍ/ቤትና በውሳኔው ካሰፈራቸው ፍሬ ነገሮች ለመረዳት ይቻላል የሥር ፍርድ ቤት አመልካች መኪናውን ለተጠሪ ባለማስረከቡ ሃላፊነት አለበት ያለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ አመልካች ብር 3,000.000 (ሶስት ሚሊዮን ብር) በማሲያዝ አስነስቶ መኪናውን ለተጠሪ ለማስረከብ የሚችልበት ሁኔታ ነበር በማለት ነው ሆኖም የስር ፍርድ ቤት በወቅቱ የባንክ ሂሳቡን በነፃነት ለማንቀሳቀስና ብር 3,000.000 (ሶስት ሚሊዮን ብር) የባልና የሚስት ክርክር ሲያይ የነበረውና የዕግድ ትዕዛዙን በሰጠው ፍርድ ማስያዝ አቅም እና ችሎታ የነበረው ለመሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረቡለት ማስረጃ ስለመኖሩና ስለመረጋገጡ በውሳኔው አላሰፈረም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

17 ይህም አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን ሌላውን አንድ መኪናን በተመለከተ በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በአመልካች ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ሳይሆን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ለ/ መሰረት አመልካች በገባው የውል ግዴታ መሰረት መኪናውን ለተጠሪ ሆነ ለሌላ ሶስተኛ ወገን እንዲያስተላልፍ ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክልከላ የተደረገበት ወይም የፅግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት በመሆኑ ምክንያት ለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በተጠሪ የሸጠውን አንድ መኪና ያላስረከበውና እንደ ውሉ ያልፈፀመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም በማለት የሰጠውን ውሳኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ለ/ ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

18 አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን አንድ መኪና ያላስረከበውና እንደ ውሉ ያልፈፀመው ከእሱ አቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት በመሆኑ አመልካች የወሰደውን የመኪናውን ዋጋ ብር 1,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከመመለስ ውጭ ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሰውን ኪሣራ /ጉዳት/ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት እንዲከፍል የሚገደድበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን አንደኛውን መኪና በተመለከተ በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ተጠሪ የደረሰበት ጉዳት የመክፈል ኃላፊነት አመልካች አለበት በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል ፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153516 ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ከፊል ፍርድና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 115897 ሐምሌ 23 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የሞተር ቁጥር 131207038497 የሆነውና የሻንሲ ቁጥር LZZ5 ELND77NB 847969 የሆነውን መኪና ለተጠሪ ለመሸጥ ውል የተዋዋለውና የመኪናውን ሙሉ ዋጋ የተቀበለው የመኪናውን ሙሉ ባለሀብትነት መብት ለተጠሪ ሊያስተላልፍለት እንደማይችልና መኪናውን ለሌላ ሰው አስቀድሞ የሸጠው መሆንን እያወቀ በመሆኑ የመኪናውን ዋጋ ብር 1,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሺ. ብር) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ከሚወልደው ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) እና አመልካች የሸያጭ ውሉን ባለመፈፀሙ ተጠሪ የደረሰበት ኪሳራ / ጉዳት / ካሳ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተጣርቶ ቀርቦ ሊከፍል ይገባል በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን ሌላውን አንድ መኪና በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793 /ለ/ በተደነገገው መሰረት በፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ በመከልከሉ ምክንያት በመሆኑ የመኪናውን ዋጋ ብር 1,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር የመመለስ ግዴታ አለበት በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793 /ለ / እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ወስነናል፡፡ ይህንን መኪና ለተጠሪ ባለማስረከቡ አመልካች ለተጠሪ ኪሳራ /ካሣ/ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ጥቅምት 3 ቀን 2008 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.109061

ሕዳር 19 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ነጋሪት ሰለሞን ሞግዚት ለሆኑለት ሕፃን የአብስራ ቴዎድሮስ-

ጠበቃ ሙለታ ደበል ቀርቡ

ተጠሪ፡- ስካይ ባስ ትራንስፖርት ሲስተም አ.ማ - ጠበቃ በላይ ከተማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ግንኙነቱ የመንገዣ ውልን መሰረት ያደረገ ቢሆንም የጉዳት ካሳ ክፍያው ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሰረት አድርጎ ሊከፈለን ይገባል የሚለውን የአመልካችን ጥያቄ መነሻ አድርጎ የታየውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ንብረትነቱ የአሁኑ ተጠሪ የሆነና የታርጋ ቁጥር 3-40411ኢት በሚል የሚታወቀው የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የአመልካች ባለቤትና ሞግዚትና አስተዳዳሪ ለሆኑለት ህጻን ደግሞ ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው ተሳፍረውበት ጥር 08 ቀን 2004 ዓ/ም ከአዲስ አበባ ወደ ጎንደር እየተጓዙበት እያለ አባይ በርሃ ላይ ከአሽከርካሪው ጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ ለሕልፈት የተዳረጉ መሆኑን፣ ሟች በሕይወት እያሉ በወር ብር 3136.00 ገቢ በሚያስገኙ ስራ ላይ ተሰማርተው በሚያገኙት ገቢ አመልካችን ያስተዳድሯቸው እንደነበር፣የህጻኑንና የሟች እድሜ በመግለጽ እንዲሁም የሕሊና ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን በመጥቀስና የተቋረጠባቸውን ጥቅም በመዘርዝር በድምሩ ብር 395,816.00(ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ስምንት መቶ አስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስድስት ብር) ለክሱ ከአወጡት ወጪና ኪሳራ ጋር ተጠሪ ኃላፊ ተብሎ እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሰጠው መከላከያ መልስም፡-ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የግዛት ስልጣን የሌለው መሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ከአስቀደመ በኋላ በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ ተጠሪ ጉዳቱን አምኖ መረጃዎችን በማሰባሰብ ወደ መድን ድርጅት በማስተላለፍ የሚጠበቅበትን ማድረጉን፣ አመልካች የሚፈለግባቸውን አሟልተው ከመድን ሰጪው ጋር ከመነጋገር ውጪ ተጠሪው ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን፣ ካሳው በአሰሪውና በሰራተኛው አዋጅ መሰረት በኢንሹራንስ ወይም በመጠባበቂያ ጡረታ ገንዘብ የሚሸፈን መሆኑን፣ መጠኑ ከጉዳቱ ጋር ተመጣጣኝ መሆን ያለበት መሆኑን፣ ለወደፊቱ ሊደርስ ይችላል ተብሎ በሚገመተው ጉዳት የተረጋገጠ መሆን ያለበት መሆኑን፣ ሟች በሕይወት ሳለ ለሕጻኑ ይህን ያህል ወጪ ያወጣ ነበር ተብሎ በማስረጃ ተደግፎ ያለመቅረቡን፣ በመተዳደሪያ በኩል የተቋረጠ ገቢ ሳይኖር የቀረበ ክስ መሆኑን፣ የቀረበው መጠን በማስረጃ ያለመረጋገጡን ዘርዝሮና በአጠቃላይ የአስራ ሰባት አመት የተጠየቀው የሕግ መሰረት የለውም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ለመኪናው መድን ሽፋን የሠጠው አካል ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባለትም ለፍርድ ቤቱ አመልክቷል፡፡

የኢትዩጵያ መድን ድርጅት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎም የሃላፊነት መጠኑ እስከ ብር 40,000.00(አርባ ሺህ) መሆኑን፣አመልካች የህጻኑ እናት ስለመሆናቸውና ከሟቹ ጋር የነበራቸው ምን እንደሆነ እንደማይታወቅ፣ሕጻኑ ሲወለድ ሟች በሕይወት ስለሌሉ ህጻኑ ሊያገኘው የሚገባው ጥቅም ተቋርጧል የተባለው ከእውነት የራቀ ምክንያታዊነት የሌለው መሆኑን፣ የሟች ደመወዝ ብር 3,136.00 የተባለው ተጣርቶ የሚደርሳቸውን ያለመሆኑን፣ የተቋረጠው የጥቅም መቋረጥ የተጋነነ እና ከሟች ችሎታ እንዲሁም ከመሰረታዊ ፍላጎት ውጪ የሆኑትን ያካተተ መሆኑን ዘርዝሮ ኃላፊነት የለብንም፣ አለ ቢባል እንኳን ያላግባብ የቀረበ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ተደርጎ ልንሰናበት ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የአሁኗ አመልካች በራሳቸው በኩል ያቀረቡት የካሣ ጥያቄ የሌለ መሆኑን ገልፆና ህጻኑ ግን ወራሽነቱ ተረጋግጦ በሞግዚቱ በኩል ክስ የአቀረበ በመሆኑ ክስ ለማቅረብ መብት እንዳለው ገልፆ በዚህ ረገድ ተጠሪና ጣልቃ ገቡ ያቀረቡትን ክርክር በማለፍ በፍሬ ነገሩ ደግሞ ሟች ከተጠሪ ጋር የመጓጓዣ ውል ግንኙነት የነበረው መሆኑ መረጋገጡን፣ በዚህ ምክንያትም ለደረሰው የሞት አደጋ ተጠሪ በን/ሕ/ቁጥር 596 መሰረት ኃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የካሣ መጠኑን በተመለከተ ደግሞ አደጋው በመደበኛ የመኪና ክስተት የደረሰ በመሆኑ በን/ሕ/ቁጥር 597 ከተመለከተው የካሳ መጠን በላይ ሊያልፍ የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሶና ሟች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በየወሩ ያገኙ ከነበረው ደመወዝ ውስጥ ለህጻኑ ብር 500.00(አምስት መቶ ብር) ወጪ ሊያደርጉ ይችሉ እንደነበር፣ ህፃኑ በወቅቱ የነበረው ዕድሜ አንድ አመት ሁኖ ቀሰቡ ለምግብ፣ ለልብስ፣ ለትምህርት፣ ለጤና እና ለሌሎች ለመልካም አስተዳደግ የሚበጁ ፍላጎቶች ለቀጣይ አስራ ሰባት አመት ድረስ የሚያስፈልገው መሆኑን ጠቅሶ በድምሩ ብር 102,000.00(አንድ መቶ ሁለት ሺህ ብር) ሊደርስ እንደሚችል ከገለፀ በኋላ በን/ሕ/ቁጥር 597 ድንጋጌ መሰረት የጉዳት ካሳ መጠኑ ከብር 40,000.00(አርባ ሺህ) ሊበልጥ አይችልም በማለት ይህንኑ ብር ተጠሪና ጣልቃ ገብ ባልተነጣጠለ ሁኔታ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ኃላፊነት በተመለከተ አደጋው በተለመደው የማሽከርከር ሂደት የተከሰተ ነው የሚለውን ድምዳሜ ያላግባብ ማስፈሩንና መረዳቱን፣ መኪናው መንገዱን ስቶ መግባቱ በን/ሕ/ቁጥር 599 ድንጋጌን መሰረት ተጠያቂነትን የሚያስከትል አይደለም በማለት ለህጻኑ በቀለብ ረገድ እንዲከፈል ካሳው ሲወሰን መጠኑ ከብር 40,000.00 ሊበልጥ አይችልም መባሉ የአመልካችን ክስና ማስረጃ እንዲሁም የተጠሪን ክርክር ይዘት ያላገናዘበ ነው በማለት የተጠሪ ኃላፊነት በን/ሕ/ቁጥር 599 ታይቶ የካሳው መጠንም በተጠየቀው አግባብ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዙት ጭብጦች መገንዘብ የተቻለው፡-

1. የአመልካችን ኃላፊነት አስመልክቶ ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 599 አንጻር የሚታይ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?፣እና
2. የካሳ መጠን አወሳሰኑ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉ ነጥቦች በጭብጥነት ሊታዩ የሚገባቸው መሆኑን ነው፡፡፡ በመሆኑም እነዚህን ጭብጦችን መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ዳኝነት የተሰጠበትን አግባብ ከንግድ ሕጉና ስለካሳ ክፍያ ከተደነገጉት ሌሎች ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንዲሚከተለው አይተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሚች የሕዝብ ማመላለሻ በሆነው የአመልካች መኪና በመንገዝ ላይ እንዳሉ መኪናው አባይ በርሃ ተብሎ በሚታወቀው አከባቢ ተገልብጦ ለሕልፈተ-ሕይወት የተዳረጉ መሆኑ መረጋገጡን፣ አመልካች አሁን አጥብቀው የሚከራከሩት የተሸከርካሪው አሽከርካሪ መንገድ ስቶ መግባቱ ተረጋግጦ እያለ አመልካች አሽከርካሪው የፊፀመው ጥፋት ስለመኖሩ የሚያሳይ ክርክርና ማስረጃ በአመልካች አልቀረቡም ተብሎ በተጠሪና እና በሚች መካከል ያለው ግንኙነት የመንገገር ውልን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የካሳ መጠኑ ከብር 40,000.00 ሊበልጥ አይችልም በሚል መወሰኑ ያላግባብ ነው በሚል መሆኑን ነው።

በሚች ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገው የአመልካች መኪና የሕዝብ መንገገር የሚሰጥ መሆኑን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርቱ ከመግለጻቸውም በላይ አደጋው የደረሰበትን ሁኔታ ለማስረዳትም የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ዘርዝረው ማቅረባቸውን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ በገጽ ሁለት በግልጽ ያሳያል። አመልካች በሕጉ አግባብ የቆጠሩአቸው ምስክሮች ያልተሰሙት በምን ምክንያት እንደሆነ የስር ፍርድ ቤትም ሆነ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጮች የሚያሳዩት ነገር የሌለ ሲሆን ለጉዳዩ ቀረበ የተባለው የሰነድ ማስረጃ ግን ተሸከርካሪው መንገዱን ስቶ በመግባቱ አደጋው መድረሱን እንደሚገልጽ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት ጉዳይ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሁኖ ተገኝቷል። የበታች ፍርድ ቤቶች ተሸከርካሪው መንገዱን ስቶ ገድል መግባቱ መረጋገጡን ተቀብለው ይህ ክስተት በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ተጠያቂነት አያስከትልም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት እንዲዚህ አይነት አደጋ በመደበኛ የመኪና ክስተት የደረሰ መሆኑን የሚያስረዳ ነው በሚል ምክንያት ነው። ይሁን እንጂ አንድ አሽከርካሪ የመኪናውን መንገድ ስቶ የሚገባው በመደበኛው የማሽከርከር ሂደት ነው ተብሎ ድምዳሜ የሚያዝበት አግባብ የሌለ ሲሆን በማሽከርከር ሂደት መንገድ መሳት ሊከሰት የሚችለው በመኪናው ላይ በሚያጋጥመው የቴክኒክ ችግር ወይም በሹፌሩ የአነዳድ ችግር ወይም ሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ትክክለኛውን መስመር ይዞ ለማሽከርከር የማያስችል ሁኔታ ሲያጋጥም መሆኑ የሚታወቅ ነው። የአሁኑ ተጠሪ አደጋው መደረሱን አምኖ መኪናው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በሌላ ሕጋዊና አሳማኝ ምክንያት አደጋው የደረሰ ስለመሆኑ ገልፆ ያቀረበው ክርክር የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል። ከዚህ አንጻር ጉዳዩ ሲታይ መኪናው መንገዱን ስቶ ገደል የገባው በሹፌሩ በተፈፀመው የጥንቃቄ ጉድለት መሆኑን የሚያስረዳ እንጂ በተለመደበው የመኪና ክስተት ነው ሊባል የሚችል ሁኖ አልተገኘም። የተጠሪ መኪና አሽከርካሪ ጥፋት የነበረበት ስለመሆኑ በዚህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 130972፣ 115724፣ እና 122676 በቀረቡት ጉዳዮች ላይም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። በመሆኑም መኪናው መንገድ ስቶ ገድል መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ አመልካች ከማቅረባቸውና ተጠሪ ደግሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለአመልካች ክስ በሰጠው መልስ መኪናው መንገድ ስቶ ገደል የገባው ከአሽከርካሪው ጥንቃቄ ጉድለት ስለመሆኑ ገልጾ ያልተከራከረ የመሆኑ ጉዳይ አደጋው በአሽከርካሪው ጥፋት የደረሰ ስለመሆኑ ተመሳሳይ በሆኑ መዝገቦች ተረጋግጧል ተብሎ ድምዳሜ ከመያዙ ጋር ተዳምሮ ሲታይ በዚህ ጉዳይም የአመልካች ኃላፊነት መጠን በን/ሕ/ቁጥር 597 የሚገደብበትን አግባብ አላገኘንም፡፡

ሟቹን ለሕልፈት የዳረገው ተሽከርካሪ ሟቹ የመጓጓዣ ውል የመሰረቱበትና በጉዞ ላይ እንዳሉ ተገልብጦ ጉዳቱ መድረሱ ከተረጋገጠ ጉዳዩ መገዛት ያለበት በንግድ ሕጉ ስለሰዎች መጓጓዣ በሚደነግጉት ድንጋጌዎች አግባብ ስለመሆኑ በመርህ ደረጃ በንግድ ሕጉ የተደነገገ ጉዳይ ነው፡፡ የመንገደኛውን ግዴታ በሚደነግገው በን/ሕ/ቁጥር 687 ስር መንገደኛው በውሉ ላይ የተወሰነውን ዋጋ መክፈል፣ ጉዞውን በሚጀምርበትን ስፍራ በተወሰነው ሰዓት መድረስና እንዲሁም በጉዞው ጊዜ ሁሉ አጓዡ የሚሰጠውን ትዕዛዝና በሕግ የታዘዘውን ማክበር እንደሚገባው በአስገዳጅ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ አጓዡ ደግሞ መንገደኛውን በመልካም ይዞታና ጥበቃ እንዲሁም ስለ ምቾቱና ስለጉዞው በውሉ በተወሰነው ጊዜ አክብሮ እንደተወሰነው መድረሻው ስፍራ የማድረስ ግዴታ ያለበት መሆኑን የን/ሕ/ቁጥር 588 በግልጽ ያሳያል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የመንገደኛውን እና የአጓዡን ተነፃፃሪ ግዴታዎችን የሚደነግጉ ሲሆን አጓዡን ኃላፊነት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 547/1999 የተሻሻሉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሁነው ከቁጥር 589 እና ተከታይ ድንግጌዎች ስር አስፍሯል፡፡ በመንገደኛው አካል እና ሕይወት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የአጓዡን የኃላፊነት መጠን በን/ሕ/ቁጥር 597 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ስር ያሉት የአላፊነት አይነቶች የሚከሰቱት በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመጓጓዣ ውል መኖሩ ሲረጋገጥ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 547/1999 ያልተሻረውን የሰው መጓጓዝን መሰረት አድርገን ስናየው የመጓጓዣ ውል የሚባለው አጓጓዥ ዋጋ በመቀበል ሰውን የተወሰነ ስፍራ ለማድረስ ግዴታ የገባበት ስምምነት ስለመሆኑ በን/ሕ/ቁጥር 561 ስር የተደነገገ ሲሆን የን/ሕ/ቁጥር 567(1) ድንጋጌ ሲታይም ሰውን ለማጓጓዝ የሚደረግ ውል በሁለቱ ወገኖች ስምምነት መሰረት ስለመሆኑና አጓዡ መንገደኛው የማጓጓዣ ሰነድ ትኬት ወይም የደንበኛነት ቲኬት እንዲቀርብና ጉዞውን እስኪፈጽም ድረስ ጠብቆ መያዝ የሚገባው መሆኑን ሊያስታውቀው እንደሚችል ደንግጓል፡፡ የን/ሕ/ቁጥር 567(2) ድንጋጌ ደግሞ የመጓጓዣ ሰነድ ሳይኖረው የሚጓዝ መንገደኛ ከዋጋው በላይ ተጨማሪ ገንዘብ ይከፈላል የሚል ማስታወቂያ ሊደረግ እንደሚችል ሲደነግግ ለመንገደኛው በሚሰጠው ቲኬት ላይ የሚከፈለው ዋጋና የሰዓቱ መነሻና መድረሻ የተመለከተ መሆን እንዳለበትም የተጠቃሹ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሶስት ስር በግልጽ አስፍሯል፡፡ ጉዳዩን የሚገዛው ልዩ ሕግ የንግድ ሕጉ ነው ከተባለ ደግሞ የጉዳት ካሳ የሚሰላውም በዚሁ ሕግ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ነው፡፡

በመሰረቱ በንግድ ህግ ቁጥር 596 መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ በመንገደኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት በሀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 597 ድንጋጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያሳያል፡፡ የሀላፊነት መጠንን በተመለከተ ደግሞ ለአንድ መንገደኛ ከብር 40,000 /አርባ ሺ ብር/ እንደማይበልጥ የንግድ ህግ አንቀጽ 597 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በንግድ ህግ አንቀጽ 597 የተደነገገው የሀላፊነት መጠን አጓዡ በንግድ ህግ አንቀጽ 596 የተደነገጉትና ከሀላፊነት ነጻ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታና መንገደኛው በንግድ ህግ አንቀጽ 599 በሚደነገገው መሠረት አጓዡ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑን እያወቀ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ባልቻለበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡

በንግድ ህግ ቁጥር 588 በሚደነግገው መሠረት የመንገደኛውን መልካም ይዞታ ደህንነትና ምቾት በመጠበቅ መንገደኛውን የማጓጓዝ ሀላፊነቱን ሊወጡ የሚገባቸውን ወገኖች የመኪና ባለቤት፣ ሹፌር፣ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ መኖሩን፣ በንግድ ህግ አንቀጽ 599 “አጓዡ የተፈፀመው ተግባር ወይም ጉድለት” የሚለው ሀረግ አጓዡ በግሉ የፈጸመውን ተግባር ወይም ጉድለት የሚመለከት ሣይሆን የአጓዡ ሰራተኞች አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጠር እንደሚችል እያወቁ የፈጸሙትን ተግባር ወይም ጉድለት የሚያካትት ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 67973 በሆነው መዝገብ ላይ በቀረበው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በማናቸውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያሰገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተያዘው ጉዳዩ ሲታይም አደጋው የደረሰው የአመልካች መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር ባጠፋው ጥፋት ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የክርክር ሂደት የተረጋገጠ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የን/ሕ/ቁጥር 599 ሁኖ አግኝተናል፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው በላይ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት የለብንም በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት ያለው አደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው የሀላፊነት መጠን በላይ ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት እንዳለባቸው የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ድንጋጌ የሚያስገነዝበን በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የካሳው መጠን ብር 40,000.00 ሊሆን ይገባል ሲሉ የደረጉት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ምክንያቱም የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ድንጋጌ በን/ሕ/ቁጥር 597 ስር የጉዳት ካሳ ከብር 40,000.00 እንደማይበልጥ በመርህ ደረጃ የተቀመጠውን የሀላፊነቱን መጠን በልዩ ሁኔታ የደነገገ፣ መንገደኛው ከአጓዡ ከብር 40,000 በላይ ካሣ ለመጠየቅና ለማግኘት የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ የሚደነግግ ድንጋጌ ነውና፡፡ በን/ሕ/ቁ. 599 ድንጋጌ መሠረት ለመንገደኛው ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት አጓዥ ለመንገደኛው የሚከፍለው የካሣ መጠን ለመወሰን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2092 የተደነገጉት የካሳ አከፋፈል መርሆች አግባብነት ያላቸው ስለመሆናቸውም ይህ ችሎት ከላይ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይ ግን የተጠሪ ንብረት የሆነውን የህዝብ ማመላለሻ ያሽከረክር የነበረው የተጠሪ ሰራተኛና የመኪናው ሹፌር በፈጸመው ከባድ ጥፋት ምክንያት አደጋው መድረሱ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ተጠሪ በዚህ ሰበር ደረጃ አጥብቆ የሚከራከረው የተጠሪ ንብረት የሆነውን የህዝብ ማመላለሻ መኪናን ያሽከረክር የነበረው የተጠሪ ሰራተኛና የመኪናው ሹፌር የሆነው ከባድ ጥፋት የነበረበት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው ፖሊስ አልቀረበም፣ ተሽከርካሪው ፍጥነት የነበረው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፣ አመልካች ባቀረቡት የሰነድ ማስረጃ መኪናው መንገድ ስቶ ገደል ገብቷል ተብሎ መጠቀሱ የአሽከርካሪውን ጥፋት የሚያሳይ አይደለም በማለት ስለመሆኑም ተገንዝበናል፡፡

ይሁን እንጂ የክፍሉ ፖሊሲ በሰ/መ/ቁጥር 130972፣ 122676፣115724 በቀረቡት ጉዳዮች ለስር ፍርድ ቤቶች በቁጥር 01514 በቀን 26/06/2007 ዓ/ም በላከው ማስረጃ ስለአደጋው በወቅቱ የተደራጀ የምርመራ መዝገብ እንደሌለ፣ በተሽከርካሪው ላይ የቴክኒክ ምርመራ ባለመደረጉ እና ፕላን ባለመነሳቱ በወቅቱ የነበረውን የተሽከርካሪውን ፍጥነት ለማወቅ ያለመቻሉን በመግለፁ የሥር ፍርድ ቤቶች በእነዚህ መዛግብት በከሳሾች የተቆጠሩትን ምስክሮች መስማታቸውን የክርክሩ ሂደት በግልጽ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ የስር ከሳሾች በዚህ ረገድ ለይተው ያሰሟቸው ምስክሮች በወቅቱ ተሳፋሪ የነበሩና መኪናው የነበረውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በጊዜውና በቦታው ሁነው በስሜት ሕዋሳቶቻቸው በአዩት እና በተገነዘቡት መጠን የመሰከሩ መሆናቸውን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ስለአደጋው የተደራጀ የትራፊክ ማስረጃ የሌለ መሆኑና በአሁኗ አመልካች በኩል ቀረበ የተባለው የሠነድ ማስረጃም መኪናው መንገድ ስቶ ገድል መግባቱን የሚያሳይ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የተደራጀ የትራፊክ ማስረጃ ቢቀርብ እንኳን ማስረጃው የባለሙያ ማስረጃ እንደመሆኑ መጠን ባለሙያው መጨረሻ ላይ የሚደርስበት መደምደሚያ /ግኝት/ ሙያዊ አስተያየት /opinion/ ከመሆን አልፎ ፍሬ ነገር /fact/ መሆን እንደማይችል፣ ኤክስፐርቱ የሚደርስበት የመጨረሻ አስተያየት ከሚኖረው ሙያዊ ዕውቀት አድማስ ከሚታገዘበት መሣሪያና ከመሳሰሉት ጋር የተሟላና ሙሉ ዕምነት የሚጣልበት ማስረጃ /conclusive evidence/ ሊሆን ስለማይችል በዓይን ምስክሮች የተነገረን ፍሬ ነገር ለማስተባበል የሚያበቃ አቅም ሊኖረው አይችልም፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም ቀደም ሲል በሰበር መ.ቁ. 14981 የኤክስፐርት ማስረጃ ሙሉ ዕምነት ሊጣልበት የሚችል ማስረጃ እንዳልሆነ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡ ከዚህም ሌላ የኤክስፐርት ማስረጃ በማስረጃነት በቀረበ ጊዜ ይበልጥ ተቀባይነት የሚኖረው ከቀጥተኛ ማስረጃ ጋር በተጣጣመ ጊዜ እንጂ ቀጥተኛ ማስረጃውን በሚፃረር ጊዜ የበለጠ ክብደት የሚሰጠው ለቀጥተኛ ማስረጃው ስለሆነ የኤክስፐርት ማስረጃው ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል መገንዘብ ስለሚቻል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን በቀጥተኛው ማስረጃ በማጣራት የተጠሪን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕዝብ ማመላለሻ መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር በማሽከርከር ሂደቱ ከመጠን በላይ ፍጥነት ጨምሮ ሲያሽከረክር የነበረ በመሆኑ ጥፋት መፈፀሙን ተረጋግጦ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ከማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን መሠረታዊ መርህ ውጪ በሆነ ሁኔታ አመልካች ካሳው በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ የሚታይበትን ሁኔታ አላስረዱም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር ባለመበቀል ተጠሪ በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ለጉዳዩ ኃላፊ አለበት ብለናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>ከላይ እንደተገለጸው የተጠሪ ሃላፊነት መታየት ያለበት በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ነው ከተባለ ይህ ድንጋጌ የካሳ መጠኑ በብር 40,000.00 የማይገደብ መሆኑንና ካሳው ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዛው የሕግ ክፍል ስር ባሉት ድንጋጌዎች አግባብ መሰላት እንደለአበት ያስገነዝባል፡፡እንዲህ ከሆነ ተጠሪ በሚች ላይ ለደረሰው ጉዳት በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው በላይ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት የለብንም በማለት የሚያቀርበው ክርክርም ሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ የተጠሪን ክርክር በመቀበል የሰጡት ዳኝነት የህግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ስለዚህ በን/ሕ/ቁ ህግ ቁጥር 599 ድንጋጌ መሠረት ለመንገደኛው ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት አጓዥ ለመንገደኛው የሚከፍለው የካሣ መጠን ለመወሰን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2092 የተደነገጉት የካሳ አከፋፈል መርሆች አግባብነት አላቸው፡፡

በመሰረቱ ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን ፣መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣2091፣2092 ፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው፡፡

ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ የሚገዙት የፍትሓብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች መንፈስ የጉዳትን ጠቅላላ ባህርይና የካሣ ልክ አተማመን ሁኔታዎችን ያስገነዝቡናል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ ችግር የሚያደርስ መሆኑን፣ ይህም ጥቅም ማቴሪያላዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራሊዊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጎዳ ሰው ደግሞ መካስ እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ የካሣውን አተማመን በተመለከተም መጠኑ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደ ፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትን/future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ በእነዚህ ድንዳጌዎች የጉዳት ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን ሕጉ በግልጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከማስቀመጡም በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብነት ሊለያይ የሚችል መሆኑን የሕጉ መንፈስ ያስገነዝባል፡ ፡በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን የካሣ አከፋፈሉን ልክ በሚደነግገው የሕጉ ክፍል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

በመሆኑም ጉዳት መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠና ጉዳቱ እርግጠኝነት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ካሣ መወሰን ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ አኳያ አግባብነት ያለው ነው፡፡ጉዳቱ መድረሱና የጉዳቱ መጠን ከታወቀ ተጎጂው በጉዳቱ ልክ ሊካስ የሚገባው መሆኑን በአጠቃላይ ከውል ውጪ ኃላፊነትን ከሚገዛው ሕግ አላማ ጋር አንድ ላይ የሚሄድ ነው፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች የህፃን የአብስራ ወላጅ አባት የሆኑት ቴዎድሮስ ጌታቸው ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው ሕፃኑ ለወደፊቱ የተቋረጠበትንና ሊቋረጥበት የሚችል ጥቅም ያለው መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም ህፃኑ ለወደፊቱ የተቋረጠበት ጥቅም ምን ያህል እንደሆነ ከወዲሁ በትክክል ማስቀመጥ የማይቻል መሆኑ የክርክሩ ሂደትና ባህርይ ያስገነዝባል፡፡ ሚች በወቅቱ የብር 3136.00 ወርሃዊ ደመወዝተኛ የነበሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከዚህ ገቢ ውስጥ ለህጻኑ ቀለብ ሊውል ይችላል ያለው መጠን ብር 500.00(አምስት መቶ) ነው፡፡ ይህንኑ መጠን ሲይዝም የቀለብ ወጪ ሲታሰብ ግንዛቤ ውስጥ የሚገቡ የልብስ፣ ምግብ፣ትምህርት፣ ጤና እና ሌሎች ለመልካም አስተዳደግ የሚበጁ ፍላጎቶች ወጪዎችን ሊያካትት እንደሚገባ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ በእርግጥ በልጅ ቀለብ አወሳሰን ጊዜ ሊታዩ የሚገባቸው መሰረታዊ ጉዳዩች በህጉ በግልጽ ባይመለከቱም የልጆችን ጥቅም ቀዳሚ ማድረግ፣መሰረታዊ የሆኑ ነገሮችን ታሳቢ ማድረግንና መሠረታዊ ፍላጎቶችና ልዩ ወጪዎች ታሳቢ ማድረግን የሚጠይቁ መሆኑን ከቀለብ ባህርይና ከህጉ መሰረታዊ አላማ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ወላጆች ለራሳቸው መሰረታዊ ፍላጎቶች ሊያሟሉ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባትም የግድ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከትም የስር ፍርድ ቤት ሚች አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው በወቅቱ ያገኙ ይችሉ የነበረውን ወርሃዊ ደመወዝ ለሚቹ ፍላጎቶች ሊወጣ ከሚችለው ወጪና ከሕጻኑ መሰረታዊ ፍላጎቶችና ልዩ ወጪዎች ጋር ለማገናዘብ የሞከረ ቢሆንም ሚቹ በሕይወት ቢኖሩ ኑሮ ለወደፊቱ አቅማቸውን ገንብተውና ተገቢውን ጥረት በማድረግ የተሻሻለ ደመወዝ ላይ ሊደርሱ የሚችሉበትን ሁኔታንና ለመሰረታዊ ፍላጎቶች የሚወጣው ወጪ መጠን በየጊዜው ከፍ እያለ የሚሄድበት አጋጣሚ የሚከሰት ስለመሆኑ ማገናዘቡን ግን የውሳኔው ግልባጭ አያሳይም፡፡ ይህም ለህጻኑ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት መልካም አስተዳደግን በተቻለ መጠንና አቅም በሚፈቅደው ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የወጪ መጠን ለመወሰን ግንዛቤ ውስጥ መገባት ያለባቸው አጠቃላይ ከባባዊ ሁኔታዎች ያለመያዛቸውን የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንጻር ሲታይ ለሕጻን የአብስራ ቴዎድሮስ በወር ሊወጣ የሚችለው የቀለብ ገንዘብ መጠን ብር 500.00(አምስት መቶ) ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት ተይዞ የነበረው መነሻ በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ስለቀለብ መጠን አወሳሰን የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ ሁኖ አግኝቶናል፡፡ ሚች በሕይወት ቢኖሩ ኑሮ ከፍ ወደ አለ ደረጃ በመድረስ የተሻለ ደመወዝ ሊያገኙ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩና ለህጻኑ የወደፊት ኑሮ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ፍላጎቶች ሊያስወጡ የሚችሉት የወጪ መጠን ወደፊት ሊኖር ከሚችለው አጠቃላይ የህብረተሰቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኑሮ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ቢገባ እንኳ በእርግጠኝነት የቀለቡን መጠን ከወዲሁ ለመወሰን የሚያስችል ነው ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ለህፃኑ የቀለብ መጠኑን ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታ ያለ መሆኑ ተገንዝበን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ድንጋጌ መሰረት በርትዕ መወሰኑ ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ለህጻኑ በወር ለወደፊቱ የሚያስፈልገው ወጪ ብር 1000.00(አንድ ሺህ) ነው በማለት ህጻኑ አባቱ በመኪናው አደጋ በሞተበት ጊዜ የአንድ አመት እድሜ የነበረው መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በተረጋገጠው መሰረት አስራ ስምንት አመት እስኪሞላው የቀረበት የቀለብ ጥቅም ታስቦ የሚመጣው ውጤት ማለትም ብር1000.00x12x17= 204,000.00(ሁለት መቶ አራት ሺህ) ለአመልካች ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ የቀለቡን አከፋፈል በተመለከተም አመልካች የህጻኑ ወላጅ እናትና ሞግዚት በመሆናቸው ተገቢውን ግዴታቸውን እንደሚወጡና ለተሻለ ጥቅምም ገንዘቡን ሊያወሉ የሚችሉበት ነባራዊ ሁኔታዎች መኖራቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2154 ድንጋጌ ለፍርድ ቤቶች የሚሰጠውን ስልጣን በማገናዘብ በአንድ ጊዜ ተጠቃልሎ እንዲከፈል ማድረጉ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪን በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ተጠቂነት የለበትም በማለት የካሳ መጠኑን ብር 40,000.00(አርባ ሺህ ብር) አድርገው የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወሰነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09275 ጥቅምት 08 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 142838 ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ/ም የፀናው፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
   የአመልካች ሞግዚት የሆኑት ህጻን የአብስራ ቴዎድሮስ በደረሰው የሞት ጉዳት ምክንያት የጉዳት ክሳ በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ሊከፈለው ይገባል ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ለህፃኑ ሊከፈለው የሚገባው የጉዳት ክሳ መጠን ብር 204,000.00(ሁለት መቶ አራት ሺህ) ሁኖ አካፋፈሉም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2154 ድንጋጌ አግባብ በአንድ ጊዜ ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡
3. አመልካች በህጻኑ ስም የባንክ ሂሳብ ከፍተው ገንዘቡን የሞግዚትነት ስልጣን በሚፈቅደው አካሄድ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውሉም ብለናል፡፡
4. የኢትዩጵያ መድን ድርጅት በሰጠው የመድን ሽፋን እስከ ብር 40,000.00(አርባ ሺህ) ለመሸፈን የተስማማ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ብር 40,000.00(አርባ ሺህ ብር) ተጠሪና የኢትዩጵያ መድን ድርጅት ባልተነጣጣለ ሃላፊነት ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡ ቀሪውን ብር 164,000.00(አንድ መቶ ስልሳ አራት ሺህ) ደግሞ ተጠሪ ብቻውን ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ኪሳራና የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 105752

ህዳር 26/2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አዲሱ ግርማሁን የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች አከራይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጉዝ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ስራ አስኪያጅ አቶ ተስፋዬ ታደሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ፡- የኪራይ ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን የአሁን ተጠሪ የሆነው የስር ከሳሽ በአሁን አመልካች የስር ተከሳሽ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን በሺርካ ወረዳ ለሶሎ ዳጋሎና ጎልቤሳ ሴሩ መንገድ ስራ አገልግሎት የሚውል ሞዴሉ D7H CAT ዶዘር በሰዓት በብር 2,127.50 /ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ሂሳብ ለ 200 ሰዓት ሊያቀርብልኝ ተዋውለን ህዳር 28/2005 ዓ.ም ብር 422,500.00 /አራት መቶ ሃያ ሁለት ሺኅ አምስት መቶ ብር/ ከፍየዋለሁ፡፡ ተከሳሽም ዶዘሩን አቅርቦ ከታሕሳስ 4/2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 6/2005 ድረስ ለ 13 ሰዓት ያህል ከሰራ በኋላ ተበላሽቶ በመቆሙ ምክንያት ከተከሳሽ ጋር ውላችንን አሻሽለን ታህሳስ 17/2005 ዓ.ም CAT 322L ኤክስካቫተር በሰዓት 1,322.50 /አንድ ሺኅ ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ በጠቅላላ ለ 301 ሰዓት በብር 398,072.50 /ሶስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺኅ ሰባ ሁለት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ሊያቀርብልኝ ተዋውለናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከሳሽ ኤክስካቫተሩን አቅርቦ ታህሳስ 23/2005 ዓ.ም ለ 3፡45 የሰራና ታህሳስ 26/2005 ለ 4፡45 በድምሩ 8፡30 ሰዓት ብቻ ሰርቶ በብልሽት ቆሟል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽ በዶዘሩ ማሽን ለ 13 ሰዓት ብቻ ያገለገለ በመሆኑ የ 13 ሰዓት ክፍያ 13X 2,127.50= 27657.50 /ሃያ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ሲሆን በኤክሳካቫተሩ ለ 8፡30 ያገለገለ በመሆኑ 8፡50 X በ 1,322.50= 11,241.25 በድምሩ ብር 38,898.75 /ሰላሳ ስምንት ሺኅ ስምንት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም/ ተቀንሶ ቀሪው ብር 386,601.30 /ሶስት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺኅ ስድስት መቶ አንድ ብር ከሰላሳ ሳንቲም/ እንዲመልስልኝ ብጠይቀው ፍቃደኛ አይደለምና ዋናውን ገንዘብ ከነህጋዊ ወለዱ ይክፈለኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተከሳሽ ኢንተርፕራይዝም በሰጠው መልስ ከከሳሽ ጋር ውል መኖሩን አምኖ መጀመሪያ ለዶዘሩ የተዋዋልነውን ውል በስምምነት ታህሳስ 17/2005 ዓ.ም በተጻፈ ውል ወደ ኤክስካቫተር ለውጠነዋል ኤክስካቫተሩ እስከ ታህሳስ 26/2005 ዓ.ም ሰርቶ ተበላሽቶ ለመቆሙ የማውቀው ነገር የለም ከሳሽም በብልሽት ለመቆሙ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ቢበላሽ እኳን በውላችን አንቀጽ 5 ላይ ማሽኑ ለአስር ተከታታይ ቀናት ካልሰራ የተከፈለው ገንዘብ እንደሚመለስ እየታወቀና በ 26/4/2005 ዓ.ም ማሽኑ አገልግሎት መስጠቱን በከሳሽ እየታወቀ አስር ቀን ሳይሞላው በ 2/5/2005 ዓ.ም ከሳሽ ውለታ አቋርጠናል ማለቱ አግባብ አይደለም፤ በተጨማሪም ከተከሳሽ ብር 422,500.00 /አራት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ የተቀበልኩ ቢሆንም አስራ አምስት ፐርሰንት ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት የከፈልኩ ስለሆነ የከሳሽ ትክክለኛ ገንዘብ 370,000.00 /ሶስት መቶ ሰባ ሺኅ ብር/ ብቻ ነው ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሳሽ የመጀመሪያው ውል በሁለተኛው ውል የተተካው በዶዘሩ ብልሽት ሳይሆን በግራ ቀኙ ስምምነት ነው ቢልም የግራ ቀኙ ስምምነት የተደረገው በዶዘሩ መበላሸት ምክንያት መሆኑን ከማሻሻያው ውል መረዳት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ተከሳሽ ማሽኖቹን በራሴ ወጪ አንጉገፎ ለማምጣት ወጪ አውጥቻለሁ ቢልም በውላቸው ላይ ተከሳሽ በራሱ ወጪ አንጉዞ ለማስገባት እና ማሽኑ በቀን ስምንት ሰዓት በሳምንት ስድስት ቀን ሊሰራና ማሽኑ ሳይበላሽ ስራ ካልሰራ ሃላፊ ከሳሽ መሆኑን፤ መስማታቸውንና፤ ማሽኑ ለተከታታይ አስር ቀናት በብልሽት ቢቆም የሰራበት ታስቦ ያልሰራበትን ተከሳሽ ሊመልስ የተስማሙ ቢሆንም ሁለተኛው ማሽንም በብልሽት ምክንያት ከ 23/4/2005 ዓ.ም ጀምሮ በየቀኑ አስር ሰዓት ሊሰራ አለመቻሉ በሰዓት መመዝገቢያ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የከሳሽ ምስክሮች በወቅቱ በማሽኑ መበላሸት ስራ ያለመስራታቸውን ሲገልጹ የተከሳሽ ምስክሮች ማሽኑ ስራውን ያልሰራው በመበላሸት ምክንያት ሳይሆን በገና በዓል ምክንያት ኦፕሬተሩና ረዳቱ ወደ ቤተሰብ በመሄዳቸው ነው ብለዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጨማሪም ማሽኑ ባለመስራቱ ከሳሽ ለተከሳሽ በ 2/5/2005 ዓ.ም በጻፈው ማስጠንቀቂያ ከጥር 3/2005 ዓ.ም ጀምሮ ውሉ መቋረጡን መግለጹን በተከሳሽም ታምኗል በማለት አትቶ ተከሳሽ ከተከፈለው ገንዘብ ውስጥ ማሽኑ የሰራበት ብር 38,818.70 ሳ ተቀንሶ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያን ጨምሮ ብር 386,601.30 ከሚታሰብ ወለድ እና ተያያዥ ከሆኑ ክፍያዎች ጋር ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ቅሬታው የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅሬታው መልስ ሰጭን አያስጠራም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታልና ሊታረም ይገባል በሚል አመልካች በመጠየቃቸው ነው፡፡ የሰበር አጣሪው ችሎትም በግራቀኙ መካከል ያለው ውል በአንቀጽ 5 ላይ ኤክስካቫተሩ ለአስር ተከታታይ ቀናት በብልሽት ምክንያት ካልሰራ ውሉ እንደሚቋረጥና የተከፈለው ገንዘብ እንደሚመለስ የተስማሙና ማሽኑ እስከ ታህሳስ 26/2005 ዓ.ም ድረስ የሰራ መሆኑ እየታወቀ አመልካች የከፈለውን ገንዘብ በተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያን ጨምሮ ሊከፍል ይገባል በማለት የተወሰነበትን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ያስችል ዘንድ ተጠሪን ያስቀርባል ብሏል፡፡

ተጠሪም በወኪሉ አማካኝነት በጽሑፍ በሰጠው መልስ ተጠሪ በውለታችን መሰረት መጀመሪያ ያቀረበው ማሽን በብልሽት ምክንያት ባለመስራቱ ውለታችንን አሻሽለን ሌላ ማሽን እንዲያስገባ ብንስማማም 2ኛው ማሽንም በውላችን መሰረት በቀን 8 ሰዓት በሳምንት 6 ቀን ሊሰራልኝ አልቻለም፡፡ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለም ቢሆን በማሽኑ ብልሽት ምክንያት ስራ ላልተሰራበት ያልተከፈለ መሆኑን በማሳወቅ ተጠሪ ገንዘቡን ማስመለስ ይችላል በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተገቢ ነውና ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡

አመልካችም የጽሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ችሎት ግራቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነውም ተጠሪ በገባው ውል መሰረት በቀን ለስምንት ሰዓት በሳምንት ለስድስት ቀናት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ማሽን ማቅረብ ሲገባው ያቀረበው ማሽን በብልሽት ምክንያት ሊሰራ አልቻለም በሚል የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለአመልካች የከፈለውን ገንዘብና ተያያዥ ክፍያዎችን እንዲመልስ መወሰናቸው አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ አመልካችና ተጠሪ የማሽን ኪራይ ውል ያላቸው መሆኑን በዚህም መነሻ ተጠሪ ብር 422,500 ለአመልካች የከፈለ መሆኑን አመልካችም በውለታው መሰረት ማሽን ማቅረቡንና ማሽኑ ለ 3 ቀንና ለ 13 ሰዓት መስራቱ በግራቀኙ የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር በስምምነት ውለታውን ወደ ኤክስካቫተር ቀይረናል ሲል ተጠሪ ውሉን ልንቀይር የቻልነው በማሽኑ ብልሽት ምክንያት ነው ብሏል፡፡ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሳኔ ላይ እንዳተተውም ውለታቸው የተሻሻለው በዶዘሩ መበላሸት ምክንያት መሆኑን ውለታቸው የሚገልጽ መሆኑን ነው፡፡ በመቀጠልም አመልካች በተሻሻለው ውለታ መሰረት ኤክስካቫተሩን ያቀረበ ቢሆንም ይህም ማሽን ለሁለት ቀን በድምሩ ለ 8፡30 አገልግሎት መስጠቱን በግራቀኙ የታመነ ጉዳይ ሲሆን ስራው የቆመው ግን አመልካች የገና በዓል ስለነበረ የማሽኑ ኦፕሬተርና ረዳቱ ለበዓል ወደ ቤተሰብ እንዲሄዱ ከተጠሪ ጋር በተነጋገርነው መሰረት ነው ሲል ተጠሪ በብልሽት ምክንያት መሆኑን ገልጾ በዚሁ ምክንያት መሆኑን በሰውና በሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርና ማስረጃ መረዳት ተችሏል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ዋናው ምክንያት በውለታችን አንቀጽ 5 ላይ ማሽኑ በቀን ለስምንት ሰዓት በሳምንት ለስድስት ቀን አገልግሎት መስጠት እንዳለበት ተዋውለን እያለ ማሽኑ ታህሳስ ታህሳስ 23/2005 ዓ.ም ለ 3፡45 ታህሳስ 26/2005 ዓ.ም ለ 4፡45 ሰዓት የሰራ ሆኖ እያለ ማሽኑ መስራት ካቆመ አስር ቀን ሳይሞላ ጥር 2/2005 ዓ.ም ተጠሪ ለአመልካች የውል ማቋረጫ ማስጠንቀቂያ በመላክ በቀን 3/5/2005 ዓ.ም ውሉ መቋረጡ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ እኛም ይህን ጭብጥ አስመልክቶ እንደመረመርነው በግራቀኙ ውል አንቀጽ 5 ስር እንደተመለከተው ማሽኑ በቀን ለስምንት ሰዓት በሳምንት ለስድስት ቀን ሊሰራ እንደሚገባና በዚህ በተቀመጠው መለኪያ /አስታንዳርድ/ መሰረት ለአስር ተከታታይ ቀናት አገልግሎት ካልሰጠ ውሉ ፈርሶ አመልካች በውሉ ምክንያት የተቀበለውን ገንዘብ እንዲመልስ መስማማታቸውን ከግራቀኙ ክርክር በመታመኑ ከመረጋገጡም በተጨማሪ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ መሆኑን ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ ተጠሪ የውለታውን ገንዘብ መክፈሉ ግልጽ እስከሆነ ድረስ አመልካች በውለታው መሰረት ማሽን አቅርቦ አገልግሎቱን የመስጠቱን ጉዳይ ሲታይ በውላቸው የተስማሙት ማሽኑ በቀን 8 ሰዓት በሳምንት 6 ቀን አገልግሎት ሊሰጥ የነበረ ቢሆንም ማሽኑ በውሉ መሰረት አገልግሎት ያለመስጠቱን በግራቀኙ የታመነ ሆኖ አመልካች በበአል ምክንያት ነው ቢልም በዚህ መልኩ ያለማስረዳቱ ከስር ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1786 ስር እንደተመለከተው በአንድ ውል ውስጥ ውልን የሚያፈርሱ የስምምነቶች ቃል ተገልጾ ከተጻፈበትና የዚህም ስምምነት አፈጻጸም ጉዳይ ተሟልቶ ከተገኘ አንደኛው ተዋዋይ ውል ፈርሷል ሲል ለመግለጽ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ስንነሳ አመልካች በገባው የውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግዴታ መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ ተጠሪ ውሉን ያቋረጠ መሆኑን መግለጹ ከውለታቸውም ሆነ ከሕጉ የወጣ አሰራር አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ በጠየቀው ዳኝነት መሰረት ውሉ ስለፈረሰ ለአመልካች ከተከፈለው ክፍያ ውስጥ አገልግሎት የሰጠበት ሰዓት ክፍያ ብር 38,818.70 /ሰላሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከሰባ ሳንቲም/ ተቀንሶ የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ አመልካች ከፍሎ ከሆነ በሚያቀርበው ማስረጃ ለከፈለው አካል ከሚጠይቅ በስተቀር ተጠሪ ላላገኘው አገልግሎት ሊከፍል አይገባም በማለት ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ ክፍያን ጨምሮ ብር 386,601.30 /ሶስት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺኅ ስድስት መቶ አንድ ብር ከሰላሳ ሳንቲም/ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9 ፐርሰንት ህጋዊ ወለድ ጋር፤ ውሳኔ ያገኘበት የገንዘብ መጠን 8 ፐርሰንት የጠበቃ አበል ብር 30,934.50 /ሰላሳ ሺኅ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ለዳኝነት የተከፈለ ብር 6716.05 /ስድስት ሺኅ ሰባት መቶ አስራ ስድስት ብር ከዜሮ አምስት/ አመልካች ለተጠሪ ይመልስ፤ በማለት ሲወሰን የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ውሳኔ በማጽናት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የስር የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 10332 የካቲት 20 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 150808 በቀን ሐምሌ 23 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ለዚህ ፍ/ቤት ክርክር ግራቀኙ ያወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

- በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
- የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጪ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117506

ግንቦት 8 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች ፡- የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ነገረ ፈጅ ኦስኒ በከር ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- አቶ አዲሱ ገዛኽኝ በሌሉበት ታይቷል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው የዳርጎት ክስ ተጠሪ ኃላፊ የሚሆነው ለግማሹ ብቻ ነው? በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አይቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ተጠሪ የአመልካች ሠራተኛ ሆኖ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነውንና የመለያ ቁጥር 4-01647 ኢት የሆነ መኪና እያሽከረከረ እያለ አቶ ሚልኬሣ ደበላ የተባሉ ሰው ገጭቶ የሞት አደጋ በማድረሱ የአቶ ሚልኬሣ ደበላ ወራሾች በአመልካች ላይ የጉዳት ካሳ ክስ አቅርበው አመልካች ለክሱ ኃላፊ መሆኑ በፍርድ ተረጋግጧል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከወሰነው የካሣ ክፍያ ውስጥ ብር 38,704 (ሰላሣ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ አራት ብር) የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለአቶ ሚልኬሣ ደበላ ቤተሰቦች የከፈለ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ወጭና ኪሳራን ጨምሮ ብር 11234 /አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሣ አራት ብር) ለሟች ወራሾች በፍርድ አፈፃፀም ተገዶ ከፍሏል፡፡ አመልካች ሟች ላይ የደረሰው አደጋ በሹፌሩ (በተጠሪ) ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት መሆኑ ተረጋግጦ ተጠሪ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 08383 በከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ገልፆ አመልካች የመኪናው ባለ ሀብት በመሆኑ ምክንያት ለሟች ቤተሰቦች የከፈለውን ብር 11234 /አስራ አንድ ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ አራት ብር) ሙሉ በሙሉ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ተከሳሽ (ተጠሪ) በመሆኑ ገንዘቡን እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል። ተጠሪ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ከታየ በኃላ ተከሳሽ መክፈል ያለበት የራሱን ድርሻ ብር 5617 /አምስት ሺህ ስድስት መቶ አስራ ሰባት ብር) ብቻ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሰጥቷል።

3. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል። አመልካች አደጋው የደረሰው በተጠሪ ጥፋት መሆኑ ተረጋግጦ ፤ ተጠሪ በወንጀል የተቀጣ በመሆኑ ጉዳዩን ሙሉ በሙሉ የመካስ ኃላፊነት ያለበት ተጠሪ ነው። ሆኖም የበታች ፍርድ ቤቶች አግባብነት የሌለውን የህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ተጠሪ አመልካች የከፈለውን ቀሪ ገንዘብ ግማሹን ብቻ ነው የሚሸፍነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካቷል። ተጠሪ ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ/ም ታትሞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ተጠርቶ ያልቀረበ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ እንዲታለፍ ይህ ሰበር ችሎት ጥር 18 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቷል።
4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል። መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነውን ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲያሽከረክር አቶ ሚልኬሣ ደበላን ገጭቶ የሞት አደጋ ያደረሰበት መሆኑ በፍታብሔር መዝገብ ቁጥር 45630 ህዳር 9 ቀን 2006 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ ተረጋግጧል። አመልካች በሟች ላይ የሞት አደጋ ያደረሰው ተሽከርካሪ ባለሀብት የተጠሪ አሰሪ በመሆኑ በሟች ላይ ለደረሰው ጉዳት በእሱ በኩል የተፈፀመ ድርጊት ወይም ጥፋት ባይኖርም በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2081 (1) እና በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2130 መሠረት በኃላፊነት ተጠያቂ ሆኗል። በሌላ በኩል ተጠሪ የአመልካችን መኪና ሲያሽከረክር በፈፀመው ጥፋት የሆነ ቸልተኝነት በሟች ላይ የሞት አደጋ በማድረሱ ለጉዳቱ በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2029 (1) እና በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2035 መሠረት ኃላፊነት አለበት። በአጠቃላይ ሲታይ አመልካችና ተጠሪ ለጉዳቱ በአንድነትና በነጠላ በኃላፊነት የሚጠየቁ መሆኑን ከፍተብሔር ህግ ቁጥር 2155 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል።
5. በአንድ ሰው ላይ ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነትን በሚጥሉ የተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች ምክንያት ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ለጉዳቱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ በሚሆኑበት ጊዜ ኃላፊ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ብቻ ጥፋት የሠራ እንደሆነ በመጨረሻ የተወሰነውን ዕዳ ዕርሱ እራሱ ብቻ የመቻል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የፍተብሔር ህግ ቁጥር 2157 በግልጽ ይደነግጋል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በያዘነው ጉዳይ በሟች ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ አይነተኛው ምክንያት የተጠሪ ቸልተኝነት መሆኑ ተረጋግጦ ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 08383 ህዳር 11 ቀን 2005 ዓ/ም በሰጠው የወንጀል ፍርድ ተረጋግጧል፡፡ ይህም አመልካች የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤትና የተጠሪ አሠሪ በመሆኑ በሟች ሚልኬሣ ደበላ ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ ከተጠሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ነው ተብሎ በፍተብሔር የተወሰነበት ቢሆንም አደጋው የደረሰው በተጠሪ ጥፋት የሆነ ቸልተኛነት ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በጉዳት ምክንያት አመልካች የከፈለውን ወጭ ሙሉ በሙሉ የመሸፈን ህጋዊ ግዴታ ያለበት ተጠሪ መሆኑን ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2157 ድንጋጌ ይዘት መሠረታዊ ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡

6. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ተጠሪ በፈጸመው ጥፋት ምክንያት ለሟች ቤተሰቦች የከፈለውን ብር 11234 /አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሣ አራት ብር) ተጠሪ ሙሉ በሙሉ እንዲተካለት አመልካች በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2161 መሠረት ያቀረበውን ክስ የስር ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2157 ድንጋጌዎች ይዘትና ህጋዊ ውጤት በአግባቡ ሣያገናዝብ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍተብሔር ህግ ቁጥር 2083 በመጥቀስ ተጠሪ የመሸፈን ግዴታ አለበት አመልካች ለሟች ወራሾች የከፈለውን ገንዘብ ግማሹን ብር 5617 /አምስት ሺ ስድስት መቶ አስራ ሰባት ብር ነው) በማለት የሰጠው ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማፅናቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 08383 ህዳር 11 ቀን 2005 በተጠሪ ላይ ያሰተላለፈው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2157 መሰረት የሚያስከትለውን ውጤት ያላገናዘበ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 51830 ጥር 29 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10501 ሀምሌ 9 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ አመልካች ለሟች ሚልኬሳ ደበላ ቤተሰቦች የከፈለውን ብር 11234 /አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሣ አራት ብር) ሙሉ በሙሉ ለአመልካች የመክፈልና የመተካት ኃላፊነት አለበት በማለት በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2157 እና በፍተብሔር ህግ ቁጥር 2161 ድጋጌዎች መሠረት ወስነናል፡፡
3. አመልካች በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭ ለራሱ ይቻል

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 119563

መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል አገልግሎት የአሉቶ ላንጋኖ ጂኦተርማል

አሉቶ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ -- ነ/ፈጅ ቦንቱ ቢራቱ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሐጂ ነገሥ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በእርሻ መሬት ይዞታ ላይ ለደረሰ ጉዳት በኃላፊነት ስለመጠየቅና የካሳ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡

የተጠሪ ክስ አመልካች በ2001 ዓ.ም መንገድ ሲሰራ ለውሃ መውረጃ ቦይ ሳያወጣ በመቅረቱ ውሃው 4 ቀረጥ የእርሻ መሬትን ስላበላሸ የ7 አመት የእርሻ ገቢ በመቋረጡ የ7 ዓመት ምርት 178 ኩንታል ስንዴ በ900 ብር ሒሳብ 151,200 / አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ሁለት መቶ ብር / ያጣሁ ስለሆነ አመልካች በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1254፤ 2027 እና 2092 መሰረት እንዲከፍለኝ ሲሉ ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ጉዳቱ ከደረሰ 7 ዓመት ስለሞላው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.2143 መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ በፍሬ ነገሩም የመከላከያ መልሱን አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም ክርክሩ የአላባ ስለሆነ በማለት በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ በአመልካች ጥፋት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት የ6 ዓመት ምርት ብር 151,200 / አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ሁለት መቶ ብር / እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ምድብ ችሎት አቅርበዋል፡፡ በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 ካሳ የሚመለከት ሲሆን ካሳ ለመጠየቅ ደግሞ በሁለት አመት ውስጥ የሚል ስለሆነ በሁለት አመት አልጠየቀም፡፡ የሰባት ዓመት ሊጠይቅ አይችልም ስለሆነም የሁለት አመት ብቻ ነው መጠየቅ የሚችለው በማለት የሶስት አመት እንዲከፈለው ይኸውም የ151,200 ብር ግማሽ አመልካች እንዲከፍል ሲል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካች ጥያቄ በ2001 ዓ.ም ይህን መንገድ በከፍተኛ ወጪ ሲሰራ የቀበሌውም ነዋሪዎች ከሳሽን ጨምሮ የወረዳውና የቀበሌው መስተዳድር አንድ ላይ በመሆን ከአዳሚ ቱሉ አስከ አለታ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ድረስ የሚሰራው መንገድ ለአከባቢው ህብረተሰብ ጠቃሚ መሆኑን አምኖበት በደስታ ተቀብለው መንገዱን እየተገለገሉበት ለ7 ዓመት ያህል ምንም አይነት ቅሬታ ለአመልካች ሆነ ለሌሎች ጉዳዩን ስልጣን ላላቸው የመንግስት አካል ሳያቀርቡ ዛሬ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የሌለው፤ በሁለት አመት ይርጋ ጊዜ የታገደ ነው በሚል የቀረበው ክርክር ውድቅ በማድረግ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበውን ግምት ሙሉ በሙሉ ይከፈል ብሎ ሲወሰን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም የ3 ዓመት ይከፈለው ሲል በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ደግሞ የቀረበው የይርጋ ጥያቄ ከጉዳዩ ጋር ስለማይገናኝ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ትክክለኛና ህገ መንግስታዊ መብቴን ያረጋገጠልኝ ስለሆነ ምንም የህግ ስህተት የለበትም ይህ የሚታለፍ ከሆነ በአማራጭ የጠቅላይ ፍርድ ቤትን ውሳኔ እንዲያፀናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ቅድሚያ መታየት ያለበት ለክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳት ደርሷል የተባለው በ2001 ዓ.ም ከመሆኑ አኳያ አመልካች ያነሳው የይርጋ ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች በትክክል የመታየት ያለመታየቱን ይህ ቢታለፍ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት ያለው የሁለት አመት ይርጋ ነው ካለ በኋላ ተመልሶ የ3 አመት የታጣ ጥቅም የመወሰኑን አግባብነት ነው፡፡ አመልካች ለሚያሰራው የአሉቶ ላንጋኖ ጂኦተርማል አሉቶ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የሚወስድ መንገድ ስራ ምክንያት በተጠሪ መሬት ይዞታ ላይ ጉዳት መድረሱ ፍሬ ነገሩን የማጣራት ስልጣን ባለቸው በስር ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች የተረጋገጠ ነው፡፡ በተጠሪ ክስ እንደተመለከተው በይዞታቸው ጉዳት የደረሰው ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑና እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ሳገኝ የነበረውን ጥቅም ማጣታቸውን ገልፀዋል፡፡ የተጠሪ ጥያቄ በቀጥታ ከውል ውጭ ኃላፊነት ጋር የሚገናኝ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በዚሁ መሰረትም ክስር ፍርድ ቤት ጀምሮ በአመልካች እየተነሳ ያለው ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል መቃወሚያ ነው፡፡ ከውል ውጭ ኃላፊነት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ክስ ማቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143 ተመልክቷል፡፡ ይህ ማለት ከሁለት አመት በኋላ የሚቀርብ ክስ በይርጋ የሚታገድ ይሆናል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በተጠሪ ሀብት ወይም ጥቅም ጉዳት የደረሰው ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑ አከራካሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ በአመልካች ተግባር ምክንያት ለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ የሰባት ዓመት ማግኘት የነበረባቸውን የምርት ዘመን ገምተው ክስ የመሰረቱት መጋቢት 23 ቀን 2007 ዓ.ም ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ከስድስት ዓመት በኋላ መሆኑ ነው፡፡ ተጠሪ በመሬት ይዞታቸው ላይ ጉዳት መድረሱን ከማወቅና በወቅቱ ከመጠየቅ ያገዳቸውን ምክንያት አቅርበው የተከራከሩበት ሁኔታ የለም፡፡ በመሬት ይዞታቸው በየአመቱ ምርት የሚያገኙበት ላይ ጉዳት ለመድረሱ ወይም የቀረባቸውን ጥቅም ለማወቅ አንድ የምርት ዘመን ጊዜ በቂ ነው፡፡ በተጠሪ በኩል ያቀረበው ክርክር ጉዳቱ በየአመቱ እየጨመረ የሄደ እንጂ በአንድ ጊዜ የተከሰተ አይደለም በማለት ላቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም የጉዳቱ መጠን ሊጨምር እንደሆነ እንጂ ጉዳት ስለመድረሱ ላለማወቅ በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ክሱ ከውል ውጭ ኃላፊነት ለሚደርስ ጉዳት ካሳ ክስ መቅረብ ያለበት በህጉ በግለፅ የተቀመጠውን በማለፍ ከስድስት አመት በኋላ የቀረበ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ ይህንኑ በማለፍ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁ መሰረትም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.40951 ግንቦት 11 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ በመ/ቁ.225865 መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ ክስ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2143 መሰረት ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በሁለት አመት ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ስለሆነ አመልካች ሊጠየቅ አይገባም ብለናል፡፡ በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዘገብ ቤት ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.116950

መጋቢት 23 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስቱር በቀለ ጭጭ አይበሉ ሞግዚት አድራጊ ህፃን ማህደር የማነህ በሸህ

ተጠሪ ፡- የለም ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረት (ቤት) ለመሸጥ የሚያስችል የሞግዚትነት ስልጣን ይሰጠኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በመ/ቁ 562/07 ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ባጭሩ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር 1590 የሆነው መኖሪያ ቤት ከሌሎች ወራሾች ጋር የሚካፈል ድርሻ ያላቸው በመሆኑ አመልካች ቤቱን መሸጥ መለወጥ እንዲችሉ ተጨማሪ የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሰጣቸው መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤትም ምስክሮች አስቀርቦ እንደሰማ አመልካች ቤቱን በማከራየት በሚያገኙት ገቢ እንደሚተዳደሩ ቤቱን የሚወርሱ ሌሎች ልጆችም እንዳሉ ከእነዚህ የተወሰኑት ራሳቸውን ችለው እንደሚኖሩ አመልካች ሞግዚት የሆኑላት ዕድሜዋ 15 ዓመት እንደሆነ ከዚህ ቤት ውጪ ሌላ መኖሪያ ቤት እንደሌላቸው በመግለጽ መመስከራቸውን ፍ/ቤቱ መመዝገቡን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ፍርድ ቤቱም አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ ህፃን ማህደር የማነ ከሞግዚት ለመውጣት የተቃረበች ሲሆን ሌላ መኖርያ ቤት ስለሌላቸው እንዲሁም በዚሁ ቤት ኪራይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እየተማረች እንደምትገኝ አስቀድሞ ቤቱ ቢሸጥ አካለመጠን ስላላደረሰኝ ድርሻዬ ሊጠፋብት እንደሚችል ፍ/ቤቱ ግምት በመውሰድ እንዲሁም ቢሸጥ ሌላ መኖሪያ ቤት እንደሌላቸው ፍ/ቤቱ የተገነዘበ ስለሆነ የአመልካችን አቤቱታ ፍ/ቤቱ ባለመቀበል መዝገቡን በብይን ዘግቶታል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንዲሁም ለሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶችን ብይን ትዕዛዝና ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የጤና ችግር ያለበቸው በመሆኑ የህፃን ማህደር የማነን መሠረታዊ የኑሮ ወጪ ማሟላት እንዳልቻሉ ቤቱ ተሸጦ የቀለብ የልብስ የትምህርት ወጪ ካልተሸፈነ በቀር ቤቱን በማከራየት በሚያገኙት ገቢ ማሟላት አለመቻላቸውን ሌሎች ወራሾችም ቤቱ ቢሸጥ እንደማይቃወሙ በተገለጸበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው በሕጉ አግባብ አይደለም የሚል ክርክር ማቅረባቸውን የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 562/07 በ12/02/2007 ዓ/ም የማህደር የማነ በሻህ ሞገዚትና አስተዳዳሪ መሆናቸውን ፍ/ቤቱ እውቅና መስጠቱን በኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ነሐሴ 01 ቀን 2007 ዓ/ም የውክልና ስልጣን መውሰዳቸውን የሚያሰይ ማስረጃ ከመዝገቡ ጋር አያይዟል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት መጋቢት 16/2008 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝም ህፃን ማህደር የማነ በሻህ በችሎት ቀርባ እንድታሰረዳ ያደረገ ሲሆን መጋቢት 19 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠችው ቃል ወላጅ እናቷ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ማሟላት ከማይችሉበት ደረጃ የደረሱ በመሆኑ ቤቱ ተሸጦ ከዚህ የሚገኘው ገንዘብ ለቀለብ፤ ለትምህርት፤ ልብስ እና ሌሎች ወጪዎች እንዲሸፈኑላት ተቃውሞ እንደሌላት አስረድታለች፡፡ የአሁኑ አመልካችም ከቤቱ የሚያገኙት ገቢ ሌሎች ወራሾችም የሚካፈሉት እንደሆነ የጤና ሁኔታቸውም በጥሩ ሁኔታ የሌለ በመሆኑ ቤቱ እንዲሸጥ አመልክተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለው ሲሆን ይህ ችሎትም አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ በአመልካች የቀረበው ተጨማሪ የሞግዚትነት ስልጣን ይሰጠኝ ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከህፃኗ የተሻለ ጥቅም /Best interest of the child/ አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን መመርመር መሆኑን ተረድተናል፡፡

አመልካች ከስር ፍርድ ቤት አንስቶ አጥብቀው የሚከራከሩት የሞግዚት አድራጊያቸውን መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ባለመቻላቸው ከአባቷ በውርስ የምታገኘው የማይንቀሳቀስ ቤት ተሸጦ ለቀለብ ፣ትምህርት፣ ልብስና ተያያዥ ወጪዎች መሸፈኛ እንዲሆን ጠይቀው የስር ፍርድ ቤት ተማሪ (ህፃን) ማህደር የማነ ከሞግዚት ነፃ ለመውጣት ጥቂት ዓመት የቀራት መሆኑ ሌላ ቤትም የሌላቸው መሆኑ በመረጋገጡ ቤቱ ሊሸጥ አይገባም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ አመልካች አሁን ያላቸው ህመም ቤተሰቡን ማስተዳደር የሚችል ገቢ ለማመንጨት የሚያስችላቸው እንዳልሆነና ቤቱ ካልተሸጠ በቀር የህፃን ማህደር የማነን የኑሮ ወጪ መሸፈን እንደማይችሉ ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ ባቀረቡት ክርክር የገለጹ ሲሆን አሁን ለአከለ መጠን ያልደረሰችውን ልጅ ጨምሮ ሁሉም ልጆቻቸው ቤት ቢሸጥ ተቃውሞ እንደሌላቸው የሚያሳይ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያነጋገራት ተማሪ ማህደር የማነም እናቷ ቤተሰቡ የሚያስፈልገውን መሠረታዊ ነገሮች ለማሟላት በማይችሉበት ደረጃ በመድረሳቸው ቤቱ ቢሸጥ እንደማትቃወም አስረድታለች፡፡

በመሰረቱ አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ሀብት በህጉ አግባብ ሊተዳደር እንደሚገባ ከፍ/ህ/ቁ. 280 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት ያስገነዝቡናል፡፡ አካለ መጠን ያልደረሰው ሀብት ሊሸጥ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 289 (1) የተመለከተ ሲሆን መቃወሚያ የሚቀርብበት ስርዓትም በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 2 ተመልክቷል፤፤ ፍርድ ቤቶች ስለህፃናት መብትና ጥቅም ሲወስኑ የጉዳዩ ዓይነት ይዘትና ባህሪ ያገናዘበ መሆን እንዳለበት በየትኛውም መልኩ መብትና ደሕንነታቸው ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 36 (2) ሥር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ፍቺ በሚወሰንበት ጉዳይም የህፃናቱ አያያዝና የቀለብ ጉዳይ ትኩረት ከሚሹ ነጥቦች እንዱ ስለመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213 /1992 አንቀጽ 113 ስር ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ መሸፈን አለመቻላቸውን በዝርዝር ምክንያት አሰደግፈው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ህፃን ማህደር የማነ ለአካለ መጠን እየደረሰች እንደሆነና ቤቱ ከተሸጠ ለወደ ፊቱ ችግር ሊያጋጥም ይችላል በሚል እሳቤ ስለመሆኑ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች ቤቱን በማከራየት የሚያገኙት 2000 ብር ለሌሎች ወራሾችም ድርሻ ድርሻቸው እንደሚያከፋፍሉ ገልጸው ይህ ቤት ከማከራየት የሚያገኙት ገቢ በየትኛውም መልኩ አሁን ያለውን ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት የማያሟላ ስለመሆኑ መከረከራቸውን ተረድተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች መሰረታዊ ጥያቄ ሞግዚት የሆኑለት ልጅ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ቤቱን በማከራየት ከሚገኘው ገቢ የማይሸፈን ከሆነ ሌላ ህጋዊ መፍትሔ መስጠቱ የህፃን ማህደር የማን ቀጣይ ሕይወት በተደለደለ መሠረት ለማኖር ወሳኝ ነው። ህፃን ማህደር የማነ የ10ኛ ክፍል ተማሪ እንደሆነች በችሎቱ ቀርባ አስረድታለች። ከዚህ መገንዘብ የምንችለው እስከ ኮሌጅ መግቢያ ድረስ ያለው ጊዜ ረጅም መሆኑን ነው። ወላጅ እናቷም ካላቸው የጤና እክል የህፃን ማህዳር የማን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት በማይችሉበት ደረጃ መድረሳቸውን ችሎቱ ገልጿል የስር ፍ/ቤት የተማሪ ማህደር የማነ ከሚግዚት አስተዳደር ነፃ ለመውጣት የቀራት ጊዜ አጭር መሆንና ለወደ ፊቱ ያለው ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገበ ቢሆንም ህፃን ማህደር የማን አሁን ያለው ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ መሸፈን የሚችል አስተማማኝ የገቢ ምንጭ ያላት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም። የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት የማሟት ጉደይ የማይታለፍ መሰረታዊ ጥያቄ ከሆነ ቤቱን በመሸጥ ኑሮ እንድትደጉም ከማድረግ ውጭ ሌላ ህጋዊ መፍትሔ ያለውም። ህፃን ማህደር የማነ ትምህርቷን ሳይስተጓጎል መቀጠል የምትችለው መሰረታዊ የሆነውን ምግብ፣ ልብስ ፣ህክምና የተለያዩ የትምህርት መረጃ መፃሕፍት ማግኘት ስትችል ብቻ ነው። ህፃኗ ለወደፊቱ ራሷን መቻል የምትችለው አሁን በሚሰራው ስራ ነው። ህፃን ማህደር የማነ ትምህርቷን ሳታቋርጥ እስከ ዩኒቨርስቲ መዝለቅ የምትችለው ከወዲሁ በሚደረግ ድጋፍ ክትትልና እንክብካቤ ነው። በመሆኑም አመልካች ህፃን ማህደር የማነ እና ሌሎች ወራሾች የሚጋሩት ቤት ሁሉም ባለመብቶች በተሳተፉበት አግባብ ሊሸጥ የሚገባው ነው። የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች የቀረበው ቤቱን በመሸጥ የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት ላሟላ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ያለበቂ ምክንያት ውድቅ መደረጉ በጉዳዩ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን የሚያሳይ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው።

አመልካች ህፃን ማህደር የማነ እና ሌሎች ወራሾች የሚጋሩት ቤት እንዲሸጥ መወሰኑ ተገቢ መሆኑ ከታመነ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ የህፃን ማህደር የማነ ድርሻ ገንዘብ በምን ሁኔታ ሊቀመጥ ይገባል የሚል ነው። ቤቱ ከተሸጠ በኃላ የህፃን ማህደር የማነ ድርሻ የሚታወቅ ሲሆን ገንዘቡ ለረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አግባብ እንድትጠቀምበት ሞግዚት አድራጊዋ በህፃኗ ስም የሚሣብ ቁጥር ከፍተው ገንዘቡን ሊያስቀምጡ ይገባል። በዚህም መሰረት የአሁኗ አመልካች በህፃን ማህደር የማነ የባንክ ሂሣብ ደብተር ከፍተው ቤቱ ከተሸጠ በኃላ ገንዘቡን በሙሉ ገቢ ካደረጉ በኃላ ለልጆቷ ተፈጥሮአዊና ሰብአዊ ፍላጎቷ ለቀለብ፤ ለትምህርት፤ለመኖሪያ ቤት ለጤና አጠበበቅ እና ለልዩ ልዩ ወጪዎች በየወሩ 1,000 (አንድ ሺህ/ ብር ወጪ እያደረጉ ሊጠቀሙ ይገባል ብለናል። በየወሩ ወጪ የሚደረገው 1,000 ብር የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት የማያሟላ ከሆነና ይኽውም በበቂ ምክንያት ተደግፎ ከቀረበ የስር ፍ/ቤቶች ተገቢ ህጋዊ ትዕዛዝ የሚሰጡበት ሁኔታ በዚህ ውሳኔ የሚገደብ አይሆንም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡት ቤት ለመሸጥ ይፈቀድልኝ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት ያላገናዘበ በመሆኑ ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡ ቤቱም በንብረቱ መብት ያላቸው ወገኖች በተሳተፉበት ይሸጥ በማለት ወስነናል፡፡ ቤቱ ከተሸጠ በኃላ የህጻን ማህደር የማነ ድርሻ በስሟ በተከፈተ የሂሣብ ቁጥር ገቢ ሆኖ በየወሩ አንድ ሺህ ብር ወጪ ይደረግ ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.562/07 በ19/09/2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23752 በ8/10/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ የአስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት በወ/ቁ. 23834 በ14/11/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የህፃን ማህደር የማነ ወቅታዊ የኑሮ ወጪ ፍላጎት ማሟላት ባለመቻላቸው አመልካች እና ሌሎች ወራሾች የሚጋሩት በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር 1590 የሆነውን መኖሪያ ቤት ሁሉም ባለመብቶች ባሳተፈ መልኩ ይሸጥ ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ከተሸጠ በኃላ የአመልካች ህፃን ማህደር የማነ ድርሻ በስሟ በተከፈተ የሂሣብ ቁጥር ገቢ ይሁን ብለናል፡፡ ህፃኗ በየወሩ ለሚያስፈልጋት መሠረታዊ የኑሮ ወጪ 1,000 (አንድ ሺህ /ብር በሞግዚቷ በኩል ወጪ እየተደረገ ይከፈል በማለት ወስነናል፡፡ በየወሩ ወጪ እንዲሆን የታዘዘው መጠን ገንዘብ የህፃኗ መሰረታዊ የኑሮ ወጪ የማይሸፍን መሆኑ ከተረጋገጠ ለመሻሻል የሚቀርበውን ጥያቄ ይህን ውሳኔ አያግድም ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.105694

መጋቢት 27 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ተሾመ ጎርፌ - ወራሽ ወ/ሮ መቅደስ ተሾመ - ጠበቃ አብርሃም ሀዲስ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኘሁ - ወራሽ አቶ ጣሰው ተሾመ - ጠበቃ ሃልማ አቻሜ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታን አስመልክቶ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአመልካች ባለቤት የነበሩት ልጃቸው ወ/ሮ ተናኘ ተሾመ በሞት መለየታቸውን እና በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት ንብረት በአመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑን ገልጸው ውርስ እንዲጣራላቸው ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ08/08/2004 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ሲሆን አመልካቹም በ02/02/2005 ዓ.ም. በሰጡት መልስ በአመልካች እጅ ይገኛል የተባለው ንብረት የሚች ወ/ሮ ተናኘ ተሾመ የጋራ ንብረት ሳይሆን የአመልካቹ የግል ሀብት በመሆኑ ውርሱ ሊጣራ አይገባም ተብሎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ፍርድ ቤቱም ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብ አጣሪ የመደበ ሲሆን አጣሪውም በተመራለት መሰረት ውርሱን አጣርቶ በ14/05/2005 ዓ.ም. የተጻፈ ሪፖርት አቅርቧል፡፡ የሪፖርቱም ይዘት በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 7 የሚገኘው ቁጥሩ 1177 የሆነው ቤት የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት መሆኑ ስለተረጋገጠ የቤቱ አጋማሽ እና ከኪራዩ የተገኘው ገንዘብ ብር 35,400 ውስጥ አጋማሹ ብር 17,700 የውርስ ሀብት ነው፣ለቤቱ ዕድሳት ወጣ የተባለው ብር 4,400 አጋማሽ የውርሱ ዕዳ አይደለም የሚል መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቱም በሪፖርቱ ላይ የግራ ቀኙን አስተያየት ከተቀበለ በኃላ የአሁኑ አመልካች ቤቱ የአመልካቹ የግል ሀብት በመሆኑ ሪፖርቱ ሊመዘገብ አይገባም በማለት ያቀረቡትን የመቃወሚያ አስተያየት ውድቅ በማድረግ ሪፖርቱን ተቀብሎ በመመዝገብ በመዝገብ ቁጥር 78124 በ26/09/2005 ዓ.ም. ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይግባኙን የተመለከተው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከቤቱ ኪራይ የተገኘውን ገቢ ወደ ብር 29,400 ዝቅ አድርጎ የውርስ ሀብት ሊሆን የሚገባውን የኪራይ ገንዘብ ወደ ብር 14,700 ዝቅ በማድረግ እና ለቤቱ ዕድሳት የወጣ ነው ከተባለው ብር 4,400 ውስጥ አጋማሹ ብር 2,200 የውርሱ ዕዳ መሆን ይገባዋል በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በዚህ አግባብ በማሻሻሉ የሁለቱም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ በተጠሪ አውራሽ እና በአመልካች መካከል በ1975 ዓ.ም. ባህላዊ ጋብቻ ስለመፈጸሙ የተረጋገጠ ነገር እንደሌለ ከመንግስት ተቋም ተገናዝቦ የተሰጠ ማስረጃ ስላለመኖሩ ከመንግስት ተቋም ለስር ፍርድ ቤት ከተሰጠው ምላሽ እና በባህል ጋብቻ ውሉ ላይ በእማኝነት የፈረሙት ግለሰቦች በ1975 ዓ.ም. ከፊሎቹ ያልተወለዱ እና ከፊሎቹም በወቅቱ ለአካለመጠን ያልደረሱ በመሆናቸው በግራ ቀኙ መካከል በ1975 ዓ.ም. ጋብቻ መፈጸሙ አልተረጋጠም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገውን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በምስክሮች ተረጋግጧል የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ የመሻሩን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት እና ለሰበር ክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ በስር ፍርድ ቤቶች የተደረገውን የክርክር ጭብጥ መሰረት ያደረጉ ናቸው ወይስ አይደሉም?
2. የአከራካሪው ቤት አጋማሽ እና የኪራይ ገቢው አጋማሽ የውርስ ሀብት ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 78124 በ26/09/2005 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ በከፊል በማሻሻል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 137902 በ28/11/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ይህንንም አመልካቹ በ12/12/2006 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መግቢያ ላይ በትክክል አስፍረዋል፡፡አመልካቹ ይህንን በትክክል ካሰፈሩ በኃላ ግን ዝርዝር አቤቱታቸውን ያቀረቡት በሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች ከላይ በተጠቀሱት መዝገቦች በተሰጡት ውሳኔ ላይ ሳይሆን ይልቁንም የአመልካች እና የተጠሪዋ አውራሽ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ተገቢውን ስርዓት አሟልቶ የተሰጠ ባለመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05087 በ02/04/2006 ዓ.ም. ከሰጠው ውሳኔ ጋር አያይዘው ነው፡፡

በመሰረቱ ይህ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ አመልካቹን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን በይግባኝ የተለወጠ ስለመሆኑም የመዝገቡ ግልባጭ የሚጠቁመው ነገር የለም፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05087 በ02/04/2006 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ የተሰማው ወገን ካለ ጉዳዩ ስርዓቱን ጠብቆ ሲቀርብ ከሚታይ በቀር በስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ከነበረው ክርክር ጋር ግንኙነት የሌለውን ውሳኔ መሰረት አድርገው አመልካች የሰበር ክርክር ሊያቀርቡ የሚችሉበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም፡፡ በውርስ ማጣራቱ ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ቤቱን ያፈራሁት ከጋብቻው በፊት ነው ከማለት በቀር የተጠሪዋ አውራሽ ባለቤታቸው የነበሩ ስለመሆኑ አመልካች ክደው ያቀረቡት ክርክር ባለመኖሩ ምክንያት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በውርስ ማጣራቱ ጉዳይ በስር ፍርድ ቤቶች ከነበረው የክርክር ጭብጥ እና ከተሰጠው ውሳኔ ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑ እና ውሳኔው ተጠቃሚ የሚያደርገውም አመልካቹን መሆኑ እየታወቀ፣እንዲሁም በይግባኝ የተለወጠ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ የሚጠቁመው ነገር ሳይኖር ውሳኔው የሰበር ክርክሩ መነሻ እንደሆነ እና በበላይ ፍርድ ቤትም እንደተሻረ ተወስዶ በአጣሪው ችሎት የተያዘው ጭብጥ የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት እና ለሰበር ክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ በስር ፍርድ ቤቶች የተደረገውን የክርክር ጭብጥ መሰረት ያደረጉ ናቸው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከላይ እንደተገለጸው በውርስ ማጣራቱ ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ቤቱን ያፈራሁት ከጋብቻው በፊት ነው ከማለት በቀር የተጠሪዋ አውራሽ ባለቤታቸው የነበሩ ስለመሆኑ አመልካች ክደው ያቀረቡት ክርክር አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ በግልጽ ያመለክታል፡፡ ይህንን ክርክር በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርቤ ነበር በማለት አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃም ቢሆን ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ አከራካሪው ቤት በአመልካች እና በተጠሪዋ አውራሽ በጋራ የተሰራ ስለመሆኑ በተጠሪዋ ብቻ ሳይሆን አመልካች ራሳቸው ካሰሟቸው ምስክሮች መካከል በከፊሎቹ ጭምር የተረጋገጠ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያመለክታል፡፡አመልካች ከስርዓት ውጪ የተሰጠ ነው የሚለትን የጋብቻ የምስክር ወረቀት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲሰረዝ ካደረጉ በኃላ ይኸው ውሳኔ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲታይላቸው በይግባኝ ለሚው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ጠይቀው የነበረ መሆኑን ከመዝገቡ ግልባጭ ማረጋገጥ የተቻለ ቢሆንም በመሰረቱ በስር ፍርድ ቤት ክደው ያልተከራከሩበትን ነጥብ በይግባኝ ደረጃ ክደው እና ክርክራቸውንም ለውጠው የሚከራከሩበት አግባብ በስነ ስርዓት ሕጉ በአንቀጽ 329 (1) ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄያቸውን አልፎ የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት ካለመኖሩም በላይ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጡት መልስ ይዘት እና በግራ ቀኙ ምስክሮች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንጻር የጋብቻ የምስክር ወረቀቱ ተገቢውን ስርዓት ተከትሎ የተሰጠ አይደለም ተብሎ መሰረዙ በአመልካች እና በተጠሪዋ አውራሽ መካከል ጋብቻ አልነበረም ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ባለመሆኑ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05087 በ02/04/2006 ዓ.ም. ከሰጠው ውሳኔ ጋር አያይዘው የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 78124 በ26/09/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137902 በ28/11/2006 ዓ.ም. ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
3. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 225588 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ19/09/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ፣እንዲሁም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 207228 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ26/09/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 114279

መጋቢት 30 ቀን 2008ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ደስታ ታከለ - ወኪል አቶ ታከለ በቀለ ቀርቧል /VC/

ተጠሪ፡- አቶ ፀጋ ታዲየስ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በባልና ሚስት በገጠር የእርሻ ይዞታ ላይ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበረችው የአሁኗ አመልካች በአንከሻ ጓግሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረበችው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ በ6/10/2006 ዓ.ም አዘጋጅታ ያቀረበችው ክስ ይዘትም ባጭሩ ከተጠሪ ጋር በባልና ሚስትነት ስንኖር ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ ሲሆን የጋራ የሆነ 8 ቃዳ መሬት በድርሻዬ እንዲያካፍለኝ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡

ተከሳሽ በበኩሉ በ13/10/2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ማመልከቻ በስሜ የተመዘገበ የግሌ እንጂ አመልካችን የሚመለከታት አይደለም ልትካፈል አትችልም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ሲል ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ 4 ቃዳ መሬት መኖሩን በማረጋገጥ ግራ ቀኙ በጊዚያዊ የይዞታ መረጋገጫ ደብተርና በጋብቻ ውል ያደረጉ ስለመሆኑ ተረጋግጠዋል፡፡ የአ/ብ/ክ/መ ቤተሰብ ህግ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 53/1/ የመሬት ይዞታ በአንዱ ስም ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ ሲፈፀም ተጋቢዎች መሬትን የጋራ ለማድረግ ሊሰማሙ አንደሚችሉ አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 24/3/ ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ 4 ቃዳ ግማሹ ይሰጥ ወይም ያካፍል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይኸው ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ተቀባይነት በማግኘቱ የግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይህ ጋብቻ ሲመሰረት የጋራ የማድረግ ስምምነት የለም፡፡ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት በአዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 58 መሰረት ጋብቻ የማደስ ሁኔታ መኖሩን ይደነግጋል፡፡ ይህ ውል ፍርድ ቤት ቀርቦ መፅደቅ አለበት ካልፀደቀ ግን ፈራሽ ይሆናል፡፡ ግራ ቀኙ ያደረጉት ጋብቻ የማደስ ውል በፍርድ ቤት አልፀደቀም ስለሆነም ፈራሽ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች አመልካች 4 ቃዳ ግማሽ ልትካፈል ይገባል በማለት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ክስ የቀረበባቸውን መሬቶች ሊያካፍል አይገባም ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 11 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የምትልበትን ምክንያቶች ዘርዝራ አቅርባለች፡፡

የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በመመርመር በዚህ ጉዳይ ግራ ቀኙ ተጠቃሹን የመሬት ይዞታ በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ ባልተካደበት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጋብቻ ውሉ ለፍርድ ቤት ቀርቦ አልተመዘገበም በማለት የእርሻ መሬቱ የተጠሪ የግሉ ነው ሲሉ የመወሰናቸውን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ጥሪ የተደረገለት ቢሆንም ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት አመልካችና ተጠሪ 18 ዓመት በጋራ ሲጠቀሙበት ከዚያም ጋብቻቸው ጥር 23 ቀን 2005 ዓ.ም በተደረገው የማደስ ስምምነት የጋራ እንደሆን ያደረጉ መሆናቸው በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠና በተጠሪም የተካደ አይደለም፡፡ ከስምምነት በኋላ በይዞታ ማረጋገጫ ላይ በጋራ በስማቸው የተቆጠረ መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ትዳር ፀንቶ ባለበት የትዳር ውል በፍርድ ቤት ያልተመዘገበ ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያለውና የሌለው መሆኑን መመርመር ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የተሻሻለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 24/3/ መሰረት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንዱ ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ ከተፈፀመ ተጋቢዎቹ መሬቱን የጋራ ለማድረግ ሊስማሙ እንደሚችሉ በግልፅ ተመለክቷል፡፡ ይህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 20/6/ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንዱ ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ የተፈፀመ እንደሆነ ተጋቢዎች ይህንኑ ፍሬ ነገር አግባብ ላለው የቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃመም ኮሚቴ በወቅቱ ገልፀው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ ተሻሽሎና በሁለቱም ስም ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው ማመልከት እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ህጉን ተከትለው በተጠሪ ሰም የነበረውን የጋራ ማድረግ በመሰማማት ለሚመለከተው አካል ጥያቄ አቅርበው በሁለቱ ተጋቢዎች ስም የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆኑን ፍሬ ነገር የማጣራትና መመዘን ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን በተመለከተ ባለው ልዩ ባህሪ ራሱን ችሎ ሕግ የወጣለት ሲሆን የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንዱ ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ ከተፈፀመ ተጋቢዎቹ መሬቱን የጋራ ለማድረግ ሲፈልጉ እንዴት ሊለወጥ እንደሚችል ስርዓት የተዘረጋለት መሆኑን ከህጉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የገጠር መሬትን በሚመለከት በሚነሱ ጉዳዮች ህጉ ግልፅ እስከሆነ ድረስ ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላል፡፡ የገጠር መሬትን እንደ ሌላው ንብረት በመቁጠር በቤተሰብ ህጉ አንፃር የሚታይ አይደለም፡፡ መታየት ያለበት የግራ ቀኙ ተጋቢዎች በገጠር መሬት አዋጁ መሰረት በአንድ ተጋቢ ሰም ብቻ የነበረውን የጋራ ለማድረግ ስምምነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ነው፡፡

ስለዚህ አመልካችና ተጠሪ የገጠር መሬት አዋጅና ደንብ ተከትለው በመስማማት የጋራ ያደረጉትን በሁለቱ ስም የይዞታ መረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸውን በፍርድ ቤት ያልፀደቀ ነው በማለት አግባብነት የሌለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 58 በመጥቀስ ውሉ ፈራሽ ነው ሲል የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.38441 ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአንከሻ ጓግሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.2743/05 የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ እና በአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁ. 01-08191 መጋቢት 5 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ 4 ቃዳ መሬት ግማሹን ለአመልካች ያካፍል ብለናል፡፡
4. የአንከሻ ጓግሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈፅም የውሳኔው ቅጂ ይላክለት፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.113002

ሚያዚያ 28 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ባልቻ አበበ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ዓሊ - ቀርበዋል

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የሎሜ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 44429 በ12/12/2006 የሰጠውን ብይን የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 38920 በቀን 09/04/2007 ዓ.ም የሻረው ቢሆንም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ችሎት በመ/ቁ 200327 በቀን 01/07/2007 የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ የሻረ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 204019 በ17/07/2002 ዓ.ም መሠረታዊ ስህተት አልተፈፀመም በማለቱ በዚህ ሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበው የጡረታ አበልን አስመልክቶ ከፍቺ በኋላ ስለሚኖረው ውጤት ነው በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት ተጠሪ ሲሆኑ አመልካች ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከተጠናቀቀ በኋላ የንብረት ክፍፍል አድርገዋል ፣አመልካች በተጠሪ ኪራይ ቤት ላይ የተደገፈውን ቤትና ሱቅ አፍርሶ ያንሳልኝ የጡረታ አበልም እንድንካፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡፡ አመልካችም በሰጠው መልስ ሱቁን አስመልክቶ በ5/11/2006 የተጻፈ የስምምነት ደብዳቤ አለ በዚሁ መሠረት ቀበሌው አካፍሎን ተለያይተናል፡፡ የጡረታ አበልን አስመልክቶ የማግኘት መብት የላትም ብሏል፡፡ ፍርድ ቤቱም መርምሮ የሞጆ ከተማ ቀበሌ 02

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስተዳደር በቁጥር 602/930/2006 በ7/11/2006 በተጻፈ ደብዳቤ በ5/11/2006 ዓ.ም የተሰማሙ መሆኑን የገለፀ በመሆኑ ቤቱን አፍርሶ እንዲያነሳ በማለት የቀረበውን አልተቀበልኩም የጡረታ አበል አመልካችና ተጠሪ አብረው በቆዩ ወቅት ከደመወዝ ላይ ተቆርጦ ሲከማች የኖረ በመሆኑ እንደጋራ ሀብት የሚወሰድ ነው ስለዚህ እኩል ይካፈሉ በማለት ሲወስን አመልካች በዚህ ውሳኔ ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በጡረታ የሚኖር በመሆኑ በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 78/1/ መሠረት አብረው ሠርተው የሚያገኙትን እንጂ የጡረታ አበልን አይጨምርም በአዋጅ ቁ 45/95 አንቀጽ 44 የጡረታ አበልን እኩል ይካፈሉ የሚል መሠረታዊ ህግ ያለው ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም የቀበሌ ቤት በስምምነት በኪራይ የሚገኝ ነው የግል ንብረት አይደለም ተጠሪ የግል ቤት እንዳላት ከሞጆ ከተማ ቀበሌ 02 የተጻፈ ደብዳቤ ያለ በመሆኑ የቀበሌውን ኪራይ ቤት እንድትለቅ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ምድብ ችሎት ያቀረቡትን ይግባኝ ፍርድ ቤቱ ተመልክቶ የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ 83/96 አንቀጽ 78/1/ ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ እያሉ የግልም ሆነ የጋራ ንብረት ከጋራ ንብረት ላይ የሚገኝ ገቢ ሁሉ የጋራ ንብረት እንደሆነ አስቀምጧል፡፡ በግል ጥረት የሚገኘው ደመወዝ ላይ የሚቆረጠው የጋራ ንብረት እንዲሆን ነው ጡረታ አዋጅ 345/1995 አንቀጽ 7 የጡረታ ገንዘብ ከደመወዝ የሚቆረጥ ነው ሠራተኛው የሞተ እንደሆነ ሚስት የሚከፈላት ጡረታ ገንዘብ ግማሹን እንደሆነ አንቀጽ 35 ደንግጓል ስለዚህ ከ1960 ጀምሮ ባልና ሚስት ሆነው ከጋራ ደመወዝ ሲቆረጥ የቆየው ገንዘብ ጡረታ በሚወጣ ጊዜ የሚከፈለው ገንዘብ ስለሆነ የጋራ ነው እኩል ይካፈሉ የመንግስት ቤትን በተመለከተ ደሀ ለሆኑ የግል ቤት መስራት ለማይችሉ አቅመ ደካማ ተከራይተው እንዲኖሩ ነው ተጠሪ የግል ቤት እንዳላት አላስተባበለችም ስለዚህ ቤቱ ለአሁን አመልካች ሊሆን ይገባል በማለት የቀበሌ ቤት እንድታስረክብ ብሏል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም መሠረታዊ ስህተት የለውም በማለት አፅድቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን በመቃወም ሲሆን የሰበር አቤቱታው በአጭሩ አመልካች የመንግስት ሠራተኛ ሆኜ የተቀጠርኩት ተጠሪን ከማግባቴ 2 ዓመት በፊት ሲሆን ተጋብተን ብዙ ልጆች ወልደን ጋብቻችን በፍቺ ከተቋረጠበት 2006 ዓ.ም በፊት በጡረታ ተገልዬ ኖረናል፡፡ አብረን በመኖር ላይ ሳለን እኔ ቀድሜ ብሞት ግማሽ ጡረታ የማግኘት መብት እንዳላት የማይካድ ቢሆንም ከፍቺ በኋላ በእኔ ድካም የተገኘውን የጡረታ አበል እንድትካፈል የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህንን አቤቱታ መርምሮ ባልና ሚስት ጋብቻቸው ከፈረሰ በኋላ ለአንደኛው ወገን ይከፈል የነበረ ጡረታ ለሌላኛው ወገን ሊከፈል የሚገባ መሆን አለመሆኑን ከአዋጅ ቁ 345/95 አንቀጽ 7

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና ከቤተሰብ ህጉ ዓላማ አንጻር ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በሰጠችው መልስ ስለቀበሌ ቤት እና ውርስ ቤት በተመለከተ የተነሳው ክርክር በሌላ ፍርድ ቤት እየታየ መሆኑን በመግለጽ ያስቀርባል ከተባለው ነጥብ አንጻር ሲመረመር አመልካች የ9 ወር ደመወዝ ከወሰደ በኋላ ነው ጋብቻ የመሰረትነው፣ በአመልካች መ/ቤት በጡረታ ተመዝግቦ የጡረታ አበሉን 7 ዓመት ሙሉ አብረን ተጠቅመናል ስለዚህ የጋራ በመሆኑ ልንካፈል የሚገባ ሲሆን በህይወት መኖርና ከዚህ ከጡረታ አበል ድርሻዬን ብቻ እንጂ የአመልካችን የሚመለከት አይደለም፡፡ የሚል ነው አመልካችም የመልስ መልስ አቅረበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ያስቀርባል ከተባለው ነጥብ አንጻር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች እና ተጠሪ በባልና ሚስትነት ተጋብተው አብረው በሞጆ ከተማ ውስጥ ከ40 ዓመት ላላነሰ ጊዜ የኖሩ ቢሆንም ጋብቻቸው በፍቺ በመጠናቀቁ የፍቺ ውጤት በሆነው የንብረት ክፍፍል ክርክር አድርገዋል፡፡ ተጠሪ እና አመልካች በዚሁ የንብረት ክፍፍል ላይ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እያገኘ በመጣው የቀበሌ የኪራይ ቤት ባለ ይዞታነት አስመልክቶ በሌላ ፍርድ ቤት ክርክር ላይ በመሆናቸው በዚህ መዝገብ አልተመረመረም ሆኖም የአመልካችን የጡረታ ክፍያ አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤት የጋራ በመሆኑ ሊከፈል ይገባል በማለት የሰጡትን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ተመርምሯል፡፡ አመልካችና ተጠሪ አመልካች ከጋብቻ በፊት በመንግስት ሥራ ላይ የጡረታ መዋጮ እየከፈሉ የቆዩበትን ጊዜ በተመለከተ 2 ዓመት እና 9 ወር በማለት ከመለያየታቸው ውጭ በጋብቻ የቆዩበትን ጊዜ እና በጋብቻ ውስጥ እያሉ አመልካች በጡረታ ከሥራው መገለሉን አስመልክቶ ልዩነት የላቸውም፡፡ ስለሆነም በዚህ ላይ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ከተጋቢዎቹ አንዱ በጡረታ የሚተዳደር በሆነ ጊዜ ጋብቻው በፍቺ ቢጠናቀቅ የጡረታ አበል ክፍያው በጋብቻ ወቅት በተደረገ መዋጮ ወደፊት የሚከፈል በመሆኑ የጋራ ሆኖ ለተጋቢዎች የመከፈል ውጤት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም የሚለው ነው፡፡

የጡረታ ገንዘብ ምንጩ ምን እንደሆነ በወቅቱ ተፈፃሚነት በነበረው በመንግስት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 5 እንደተመለከተው ከአሰሪው ስድስት በመቶ /6%/ ከመንግስት ሠራተኛው አራት በመቶ /4%/ ነው፡፡ እዚህ ላይ የአሁን ተጠሪ መከራከሪያ በጋብቻ ውስጥ በነበርን ጊዜ ከአመልካች ደመወዝ እየተቀነሰ የሚከፈለው 4% በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 83/96 አንቀጽ 78/1/ መሠረት የጋራ ከሆነው ደመወዝ በመሆኑ የጡረታ አበሉ የጋራ ሊባል ይገባል በሚል ሲሆን አመልካች ደግሞ የሚከራከረው የጡረታ አበል የሚከፈለው ለአመልካች ነው ተጠሪ ልትካፈል የምትችለው በጋብቻ ውስጥ ሳለን ብሞት ብቻ ነው ከፍቺ በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግን ልትካፈል የሚያስችል መብት የላትም በማለት ነው፡ በመሠረቱ ለጡረታ ተብሎ ከህግ በመነጨ ቅድመ ሁኔታ የሚከማች ገንዘብ ባል ወይም ሚስት ካከማቹት ተጠራቅሞ እራሱን ችሎ ለክፍያ ይውላል ወይም ይሸፍናል ተብሎ መደምደሚያ ሊያሰጥ የሚችል አይደለም፡፡የጡረታ አበል ለአንድ ሠራተኛ የሚከፈለው ዕድሜው በገፋበት እና ጉልበቱ በደከመ ጊዜ መጦሪያ የሚሆነው ለመኖር የሚያስፈልገውን ወጪ በከፊልም ቢሆን በመሸፈንና ማህበራዊ ደህንነቱን ዋስትና ለመስጠት መንግስት ካለው የማህበራዊ ደህንነት ዋስትና ፖሊሲ የመነጨ በመሆኑ እንደማንኛውም ገቢ የጋራ ንብረት ነው የሚባል እንዳልሆነ የሰበር ችሎት በመ/ቁ 34384 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ በነበሩ ጊዜ አመልካች ጡረታ አበል ማግኘት መጀመሩን 7 ዓመት መኖራቸውን ከዚህ በኋላ ፍቺ የተፈፀመ መሆኑ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ የሚገኝ ፍሬ ነገር ነው፡፡ አመልካች በጡረታ ከተገለሉ በኋላ ፍቺ መፈፀሙን ምክንያት በማድረግም የጡረታ አበል ሊካፈል አይገባም የሚለውን መከራከሪያ ያነሳሉ በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ 345/95 አንቀጽ 35 ለሚች ሚስት ወይም ባል የሚከፈለውን የጡረታ አበል ሲደነግግ ሟች ያገኝ የነበረውን የጡረታ አበል 50% /ሃምሳ በመቶ/ የሚሆን እና ሆኖም ይህንን በመቀበል ላይ እያለ ካገባ በመከፈል ላይ ያለ አበል እንደሚቋረጥ ያመለክታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ ሳሉ የጡረታ ባለመብት የሆነው ባል ወይም ሚስት ከሞቱ ስለሚኖር የጡረታ አበል ክፍያ ነው ስለሆነም ባል ወይም ሚስት የጡረታ አበል ተጠቃሚ ሆነው ባሉበት ፍቺ ቢከሰት የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነው ባልና ወይም ሚስት የጡረታ አበል ለባል ወይም ለሚስት ሊያካፍል የሚገባ ስለመሆኑ አይደለም፡፡ስለሆነም የአመልካች የጡረታ አበል ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበትን ድምዳሜ መሠረታዊ ስህተት ያለበት በመሆኑ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሎሜ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 44429 በ12/12/2006 የኦሮምያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ችሎት በመ/ቁ 200327 በቀን 01/07/2007 ዓ.ም እና የኦሮምያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 204019 በቀን 17/07/2002 የሰጡት ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 38920 በቀን 04/04/2007 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች የሚያገኘው የጡረታ አበል የጋራ ንብረት ተደርጐ ለተጠሪ ሊካፈል አይገባም ብለናል፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 116119

ቀን 22/09/08ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉ በዳዳ -አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ ኩሪ በዳዳ -ቀረቡ
2. ወ/ሪት መስከረም በዳዳ } አልቀረቡም
3. ወ/ሪት ውድነሽ በዳዳ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ለአ/አ/ክ/አስ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበውት በነበረው አቤቱታ መሰረት አመልካች የሚች አቶ በዳዳ ባቱ ህጋዊ ወራሽ ናቸው፡፡ በማለት የወሰነ ሲሆን ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት ባቀረቡት መቃወሚያ የመቃ/ተጠሪ የሚች አቶ በዳዳ ባቱ ልጅ አይደሉም፡፡ የተሰጣቸው የወራሽነት ውሳኔ ይሻርልን ብለዋል፡፡ የመቃ/ተጠሪ በበኩላቸው ሚች አባቴ ናቸው የተወለድኩት ሚች ከእናቴ ጋር በትዳር አብረው ሲኖሩ በነበሩበት ጊዜ ነው፡፡ የወራሽነት ውሳኔው ሊሻር አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ክርክር ከቀረቡት ማስረጃ ጋር በመመርመር ለመቃ/ተጠሪ ቀደም ሲል የሰጠው የወራሽነት ውሳኔ እንዳይፈጸም በማገድ የመቃ/ተጠሪ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ልጅነታቸውን አረጋግጠው በመጡ ጊዜ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብታቸው ተጠብቋል ብሎ መዝገቡን ዘጋው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመቃ/ተጠሪ (የአሁን አመልካች) በዚህ ትእዛዝ ላይ ቅሬታቸውን በየደረጃው ለይግባኝ ሰሚ ችሎቱ እና ለሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የስር ፍ/ቤትን ትእዛዝ ለማሳረም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች አቶ በዳዳ ባቱ ልጅ መሆናቸው ተረጋግጦ የወራሽነት ማስረጃ ካገኙ በኋላ ተጠሪዎች በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 167 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት የመካድ ክስ ባላቀረቡበት ሁኔታ በሌላ የመቃወም ዘዴ ተጠቅመው የአመልካችን የወራሽት ማስረጃ ውድቅ እንዲሆን ያደረገበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከዚህ በላይ የተመዘገበው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ የሰበር አቤቱታው እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም፡- በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የልጁ አባት ነው ተብሎ በህግ ግምት የሚሰጠው ሰው፤ እሱ የሞተ ወይም ችሎታ ያጣ እንደሆነ ከተወላጆቹ አንዱ የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ስለመሆኑ ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 213/1992 አንቀጽ 167፣174 እና 179 ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች ስር ፍ/ቤት የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት የአሁን አመልካች የሚች አቶ በዳዳ ንጋቱ ልጅ ሳይሆኑ የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልን በሚል ሲሆን የአሁን አመልካች የተወለድኩት በጋብቻ ውስጥ ነው፡፡ ይህን መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት ክርክር ያደረጉ መሆኑን ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ የአሁን አመልካች ስር ፍ/ቤት በነበረ ክርክር እና በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት ክርክር በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑን ጠቅሰው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች ይህን በማስተባበል በሰበር መልሳቸው በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ አመልካች በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑ ካልተካደ ደግሞ ልጅነታቸውን እንዲያረጋግጡ አይጠበቅም፡፡ የአሁን ተጠሪዎች የአመልካችን ተወላጅነት ለመካድ ክስ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ የሚገባቸው ሲሆን የስር ፍ/ቤት ከዚህ በላይ በተጠቀሱ የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎች መሰረት ጉዳዩን ለማየት በህግ ስልጣን በተሰጠው ፌ/ፍ/ቤት የመካድ ክስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቶ የመቃወም አቤቱታውን ውድቅ ማድረግ ሲገባው የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ተመልክቶ ለአሁን አመልካች የተሰጠውን የወራሽነት ውሳኔ እንዳይፈጸም በማገድ የአሁን አመልካች ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ልጅነታቸውን አረጋግጠው ባቀረቡ ጊዜ መዝገቡን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማንቀሳቀስ መብታቸው ተጠብቋል በማለት የሰጠው ትእዛዝ ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር አቤቱታ የተመለከተው የአ/አ/ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ይህን ሳያርም ማለፉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአ/አ/ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 893/07 በቀን 19/09/07 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣ የአ/አ/ከ/አስ/ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 23748 ሰኔ 16 ቀን 2007ዓ.ም እና ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰ/መ/ቁ. 23837 በቀን 26/10/2007ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች የአመልካችን ተወላጅነት መካድ የሚችሉት የመካድ ክስ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት በማቅረብ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ግራቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 120844

መስከረም 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
ተፈሪ ገብሩ
አብርሃ መሰለ
አብዬ ካሳሁን
እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ሃንደግባ ሽኩር - ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አለምቱ ኢብራሂም - ወኪል ለይላ ሃንዳግባ - ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 66280 ህዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ በተመሳሳይ ጥያቄ በሰ/መ/ቁ.120843 አመልካች የሆኑት ወ/ሮ መኪያ ሐጂ ማመጫ ያለው ክርክር ጭብጥ ተመሳሳይና አንድ አይነት በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.11/1/ መሰረት እንዲጣመሩ ተደርገዋል፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ በትዳር የቆዩ ሲሆን ለዚህ ክርክር መነሻው ጋብቻው በፍቺ በመፍረሱ የተጀመረው የጋራ ንብረት ከፍፍል ጉዳይ ነው፡፡ በአመልካች እና ተጠሪ የነበረው ጋብቻ በመፍረሱ የአሁኗ ተጠሪ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በማቀርቧ ወ/ሮ ሚኪያ ሐጂ ሁለተኛ ሚስት ጣልቃ መግባቷን በስር መዝገብ ተመልክቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ተጠሪ በክስዋ ከተራ ቁጥር 1ኛ-4ኛ ድረስ አዋሳኝ ተጠቅሶ በአራት ቦታዎች የሚገኙ መሬቶች በአጠቃላይ 0.85 ሄ/ር ይካፈሉ፡፡ ጣልቃ ገብ/2ኛ ሚስት/ለአሁን አመልካች በሚደርሰው የመሬት እርሻ መጠን ላይ ግማሽ መብት አላት፡፡ እልፍኝ እና የሳር ክዳን ቤት የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት በመሆኑ ቢቻል በአይነት አሊያም በገንዘብ ተገምቶ እኩል ይካፈሉ፡፡ በጓሮው የሚገኘውን ጫትና ቡና ሌሎች አትክልቶች ከብቶች እና እንስሳቶችን አመልካች እና ተጠሪ እኩል ይካፈሉ እንዲሁም በ2004 ዓ.ም ለመንገድ ስራ ምክንያት የተከፈለ ብር 20,000 /ሃያ ሺ ብር/ የንብረት ካሳን በተመለከተ 1ኛ አመልካች እና ተጠሪ እኩል እኩል ከተካፈሉ በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጣልቃ ገብ ከአመልካች ድርሻ ላይ ግማሽ ወይም ከአጠቃላዩ የካሳ ብር ላይ 1/4ኛ ሊደርሳት ይገባል በማለት ውሳኔ ስጥተዋል፡፡

ይህን ውሳኔ በመቃወም የአሁኗ አመልካችና ጣልቃ ገብ የየራሳቸውን ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ሁለቱንም ይግባኝ መዝገቦች አጣምሮ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ አድረጎ ከመረመረ በኋላ በስር ፍርድ ቤት በተገቢው ዳኝነት ሳይከፈልበት የቀረቡትን ቅሬታዎች ዳኝነት ከፍለው የመጠየቅ መብታቸው ከጠበቀ በኋላ በተቀሩት ላይ በመንገድ ስራ ምክንያት ንብረት ካሳ የተከፈለ ሙሉ በሙሉ ለጋራ ጥቅም አለመዋሉን በበቂ ሁኔታ በተጠሪ ማረጋገጥ ሳይቻል የተሰጠ ውሳኔ ነው በማለት ሽሮታል፡፡ በ2006 ዓ.ም የተገኘ መሬት ላይ ተጠሪ 2.5 ኩንታል ስንዴ ይድረሳት ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተወሰነውን አጽንቶታል፡፡ እንዲሁም እልፍኝ ቤት የስር ፍርድ ቤት ለሶስት እኩል ይካፈሉ የተባለው ውሳኔ የሚነቀፍበት ነጥብ የሌለው ሆኖ ለአፈፃፀም እንዲመች የእልፍኝ ቤቱን 1/3ኛ ግምት ለተጠሪ እንዲከፈል በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ሁለቱ ሚስቶች በየጓሯቸው ያለውን አንድ ጥማድ እንሰት፤ጫት እንዲሁም አቡካዶ ያላቸው መሆኑን በወረዳ ፍ/ቤት በሰው ምስክር ያረጋገጡ ቢሆንም እንዲሁም ጣልቃ ገብ ከ21 አመታት በላይ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ስትፈጽም ተጠሪ ሳትቃወም እና በጋራ ስትኖር መቆየቷ እየታወቀ በጋራ የሚጠቀሙበትን አጠቃላይ መሬት 1/4ኛ ብቻ ይገባታል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የወረዳው ውሳኔ ተሽሯል ካለ በኋላ እያንዳንዳቸው ሚስቶች በይዞታቸው በስተጀርባ ያለውን እንሰትና አትክልት ከአመልካች ጋር እኩል ይካፈሉ፤ ቀሪውን ሁለት መሬት እና መሬቱ ላይ የሚገኙ ዛፎች ደግሞ ሶስቱም እያንዳንዳቸው 1/3ኛ መጠን ይካፈሉ፡፡ በሬና ፈረስ እንዲሁም እልፍኝ የሳር ቤቱን በተመለከተ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔውን በማጽናት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ አፈፃፀሙ ግን እያንዳንዳቸው 1/3ኛ ይካፈሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደ/ብ/ብ/ህ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ብታቀርብም የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ላይ ጉድለት የሌለው መሆኑን ገልፆ የተጠሪን ይግባኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

በተጠሪ አመልካችነት ቀጥሎ በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ አስቀርቦ ከሰማቸው በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቤት ጓሮ ያለው የእርሻ ይዞታ ብቻ ከስር ተከሳሽ ጋር ይካፈሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በሌሎች ይዞታዎች ላይ ያላትን መብት ያላገናዘበ በመሆኑ በመሻር የምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በአራቱ የተለያዩ አዋሳኞቸው የተጠቀሱት ስፋታቸው 0.85 ሄ/ር ከሳሽና ተከሳሽ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ እልፍኝ የሳር ክዳን ቤት የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ለሶስት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይካፈሉ ለአፈፃፀም ያመች ዘንድ ተጠሪ ግምት ትውሰድ በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪና የስር አመልካች እኩል እንዲካፈሉ የሚለውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች ታህሳስ 6 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት በመግለፅ ስህተቱ እንዲታረምላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪም ሳትቃወም ጣልቃ ገብ ከስር ተከሳሽ ጋር ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሳስረው ንብረት ሁሉ በጋራ ማፍራታቸው እየታወቀ አሁን በተጠሪና ተከሳሽ መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሶ የጋራ ንብረት ሲደረግ አመልካች በጋብቻ ላይ ጋብቻ የፈፀመች ስለሆነ ድርሻዋን ከስር ተከሳሽ ግማሹን ታግኝ በማለት በክልሉ ሰበር ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ አመልካቾችና ተጠሪ ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን በዚህ መሰረትም አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ አመልካቾች በጣልቃ ገብና ተከሳሽ ስም የተመዘገበ በደማላ ደስይበር ቀበሌ ስፋቱ 0.486 ሄ/ር ይዞታ መኖሩ ተረጋግጦ ከግብርና ለፍርድ ቤት ተልኳል፡፡ ከተከሳሽ እናት ለወ/ሮ ሚኪያ ሓጂ ጎጆ መውጫ መቋቋሚያ ይሆን ዘንድ ከ21 አመት በፊት የሰጠችን ይዞታ ላይ ከወ/ሮ ሚኪያ ሓጂ ጋር የሰራነው ቤት እና በጓሮው በቆጮና በሌሎች ቋሚ ሰብሎች በማልማት የቆየንበት የአሁኗ ተጠሪም ይዞታዋና ልማቷን የማይነካ በመሆኑ ጋብቻችንን ሳትቃወም 21 አመት የቆየች ስትሆን የወ/ሮ መኪያ ሓጂ የራሷን ይዞታ እና መሬት በስሟ ግብር እየገበረች ቆይታ በ1997 ዓ.ም በስሟ ቁጥር 0316623 የሆነ የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርቲፍኬት የሁለታችን ፎቶ ያለበት አውጥታበተለች፡፡ ይህን ማስረጃ ስታወጣ ተጠሪ ተቃውሞ አልነበራትም እስከ ዛሬ ድረስ ተቃውሞ አቅርባ ደብተሩን አላሰረዘችም፡፡ በስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሕጉን ተከትሎ አጣርቶ የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ሰበር ችሎት በቂና አሳማኝ ምክንያት ሳይሰጥ መሻሩ እንዲሁም ከወ/ሮ መኪያ ጋር ያለ ጋብቻ ሳይፈርስ ሁላችንም እንድንከፋፈል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የቤተሰብ ህግ መርህ የጣሰ በመሆኑ የክልሉ ሰበር የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተሽሮ እንዲወሰልን የሚል ነው፡፡

በተጠሪ በኩል ደግሞ ከአመልካች ጋር በ1970 ዓ.ም ጋብቻ ከፈፅምን ጀምሮ መጠኑ 0.85 ሄ/ር በጋራ ማፍረታችን በማስረጃ ተረጋግጦ ከዚሁ ግማሽ ድርሻ እንድታገኝ የሰጠው ውሳኔ ስህተት የለውም፡፡ አመልካች ከወላጅ እናቱ ለማቋቋሚያ የተሰጠው አስመስሎ ያቀረበው በስር ወረዳ ፍ/ቤት ክርክር ያልተነሳና በጭብጥነት ያልተያዘ ከስነ-ስርዓት ህጉ ውጭ አዲስ የቀረበ ክርክር ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ፡፡ አመልካችና ተጠሪ እኩል ድርሻ እንድናገኝ የሰጠው ውሳኔ ጣልቃ ገብ አመልካች በደረሰው ድርሻ ላይ መብት እንዳላት በመግለፅ የቤተሰብ ህግ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር በመ/ቁ. 45548 የሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሰረት አድርጎ የተሰጠ ትክክለኛና ፍትሓዊ ነው፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ የተገኘበት መንገድ የህግን አግባብ ያልተከተለ መሆኑ በማረጋገጥ ሰነዱን ውድቅ በማድረግ የስር ተከሳሽና የተጠሪ ንብረት መሆኑን ማስረጃ የመስማትና የመመዘን ስልጣን በተሰጠው የስር ፍርድ ቤት ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡ ጋብቻ ሲፈርስ የንብረት ክፍፍል ሲደረግ የሁለተኛ ሚስት ጋብቻ በፀናበት በንብረቶቹ ላይ ያለን ድርሻ መወሰኑ የቤተሰብ ህግ መርህ የሚጥስ አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአመልካችና ተጠሪ የተመሰረተው ጋብቻና አከራካሪው የእርሻ መሬት ይዞታዎች በምሪት የተሰጣቸው አመልካችና ጣልቃ ገብ ከመጋባታቸው በፊት መሆኑ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የተካደ አይደለም፡፡ አመልካች እና በስር ጣልቃ ገብ በመሬት ይዞታቸው ይገባናል የሚሉት በስጦታ የተሰጠን በሌላ በኩል ደግሞ በስማችን ተመዝግቧል፤መቃወሚያ በማቅረብ አልተሰረዘም የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ መከራከሪያ ነጥቦች በስር ክርክር ሂደት ያልነበሩና ያልተረጋገጡ ናቸው፡፡ በክርክር አመራር ስርአት አንድ ተከራከሪ ወገን ማንሳት የሚገባው በመጀመሪያ በሚሰጠው የመከላከያ መልስ በግልፅ ማቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.234 ስር ተመልክቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃ የመመዘንና የማጣራት ስልጣን ባለቸው ቀርቦ ውሳኔ ያልተሰጠበት ነጥብ በዚህ ደረጃ ማንሳቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.329 እንዲሁም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 አንፃር ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የተሰጣቸው የእርሻ መሬት ይዞታ ከአመታት በኋላ ወ/ሮ መኪያ ሐጂ በሁለተኛ ሚስትነት ጋብቻ መመስረት የነበረው የመሬት ይዞታ ላይ ተጠሪ ስምምነት ባላደረገችበት በቀጥታ እኩል የምታገኝበት የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ ተጠሪ አመልካች ሁለተኛ ሚስት ሲያገባ መቃወሚያ ባለማቅረብዋ በንብረቶችዋ ላይም ተስማምታለች ለማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም በክልሉ ሰበር ችሎት በእርሻ መሬት ይዞታዎችና እልፍኝ የሳር ክዳን ቤት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 66280 ህዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም በክስ ተራ ቁጥር 1-4 የተዘረዘሩት የመሬት ይዞታዎች 0.85 ሄክታር እና እልፍኝ የሳር ክዳን ቤት በተመለከተ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.11537መስከረም 7 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሌሎች ጉዳዮች የተሰጠ ውሳኔ አልተነካም፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመ/ቁ.120843 ጋር እንዲያያዝ ይደረግ፡፡
4. ከዚህ ፍርድ ቤት በቀን 19/04/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት በምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ በመ/ቁ. 03867የተጀመረው አፈፃፀም ላይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 105125

ሕዳር 05 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ክፍለፅዮን ማሞ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አህመድ ዑመር

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ተስፋዬ አብራሃ

2ኛ. አቶ ኃይለ ማሪያም አብራሃ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነውን ጭብጥ የመሬት ባለይዞታ ሳይቃወም የተሰራ ቤት የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት፣ የፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 1179/1/ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔዎች አንፃር አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞን ዓዲግራት ወረዳ ፍርድ ቤቶች የአሰበሰበያ ምድብ ችሎት የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፍ/መ/ቁ 020212 ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰው 490 ካሬ ሜትር የመሬት ይዞታ ያላቸው ሲሆን ተጠሪዎች በጉልበታቸው በሕጋዊነት ሳይሰጣቸው በኃይል በ1998 አንዳንድ ሰርቪስ ሁለት ክፍል ቤት እንደሰሩ፣ እንዲሁም በ2006 ዓ.ም በቀበሌ በታገደበት ሁኔታ ፊት ለፊት ባለው ይዞታ ላይ በክብ ድንጋይ ቆርቆሮ ተክለው በሕጋዊ መንገድ ከተሰጣቸው ይዞታ ላይ ከሕግ ውጭ ስለወሰዱባቸው ተጠሪዎች የሰሩቷ ቤት በራሳቸው ወጪ አፍርሰው ይዞታውን እንዲመልሱ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪዎች በሰጡት መልስም በ1998 ዓ.ም ቤቱን መስራታቸውን ሳይክዱ ከዛ በኋላ ግን ምንም እንዳልሰሩና የሰሩት ቤትም አስተዳደር በሰጣቸው ቦታ ስለመሆኑ ተከራክረዋል፡፡

የስር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ አጠቃላይ ይዘት በመዝገቡ ካሰፈረ በኋላ የአሁኑ ተጠሪዎች የሰሩት ሰርቪስ ቤት በ1998 ዓ.ም መሆኑ እንዳልተካደ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40/6/ እና የፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 1179/1/ መሰረት በማድረግ አመልካች ሳይቃወሙ የተሰሩት ሁለት ሰርቪስ ሆነ አጥር ግቢው ለመቃወም የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት የላቸውም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በስር የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ ያቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አከራካሪው ይዞታ ለቆዳና ሌጦ ድርጅት እንደተሰጣቸው የተጠሪዎች ሕገ ወጥ ተግባር ይቃወሙ እንደነበር በመግለፅ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ እንዲሻር ማመልከታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ይዞታ የአሁኑ የሰበር አመልካች መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ከመሆኑ አንፃር የሰበር አመልካች ተጠሪዎች ቤቱን ሲሰሩ ሳይቃወም ነው ቤቱ የተጠሪ ነው በሚል አግባብ ተጠሪዎች ቤት የሰሩበትን ይዞታ መልቀቅ የለባቸውም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1179/2/ እና /3/ እና ፍ/ብ/ሕ/ቁ 1180 ድንጋጌዎች አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎችን ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪዎች የካቲት 06 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡ ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በፅሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ተገቢ ከሆነው ድንጋጌ በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች በሚመለከተለው የአስተዳደር ክፍል 490 ካሬ ሜትር የተሰጣቸው ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች አከራካሪ በሆነው ይዞታ ላይ ቤት እንዲሰሩ በሚመለከተው አስተዳደር የተፈቀደላቸው መሆኑን በመግለፅ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ባያገኝም ለክርክሩ መነሻ የሆኑ ቤቶች በ1998 ዓ.ም ስለመስራታቸው ግን በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በአከራካሪው ይዞታ ላይ ቤት ሲሰሩ አመልካች ያቀረቡት ተቃውሞ እንደነበረ ቢከራከሩም በስር ፍርድ ቤት በተደረገው የማጣራት ሂደት ግን መቃወሚያ ስለማቅረባቸው አልተረጋገጠም፡፡ አንድባለይዞታ ሳይቃወም የተሰራ ቤት ቤቱን የሰራው ሰው ባለመብት እንደሚሆን በፍ/ሕ/ቁ 1179/1/ ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ አመልካች እየተከራከሩ ያሉት የይዞታ ባለቤት በማንኛውም ጊዜ ተጠሪዎችን የማስለቀቅ መብት አለው በሚል እሳቤ ነው፡፡ በእርግጥ የይዞታ ባለመብት በይዞታው የተሰራው ቤት እንዲነሳለት ወይም ከ ¼ ኛ የማይበልጥ ካሳ ከፍሎ ቤቱን የማስቀረት መብት እንዳለው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1179/2/ እና 1180 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ይሁንና የፍትሐብሔር ሕግ በታወጀበት ዘመን መሬት በግል ባለሀብትነት የሚያዝ በመሆኑ በየትኛውም መልኩ በመሬቱ ላይ ከሁሉም የሰፋ መብት ያለው በመሆኑ በባለቤቱ መቃወሚያ ሳይቀርብ የተሰራ ቤት ጭምር እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት እንዳለው ተደንግጎ ነበር፡፡ ከላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች የሕዝብና የመንግስት መሆኑን ከደነገገው አንቀፅ 40/3/ ጋር በተጣጣመ መልኩ ነው፡፡ በዚሕም መሰረት የመሬት ባለይዞታ በፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 1179/2/ እና 1180 በተደነገገው አግባብ በይዞታ ላይ ምንም ተቃውሞ ሳያቀርብ የተሰሩ ቤቶች ላይ የፈለገው እርምጃ የመውሰድ መብት የለውም፡፡ መሬት የሕዝብና የመንግስት ከመሆኑ አንፃር በባዶ መሬት ላይ የተሰራው ቤት ላይ የመሬት ይዞታ መብት አለኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚለው ወገን ቤቱን ከሰሩ ሰዎች የተሻለ መብት ሊኖረው አይችልም፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በ490 ካሬ ሜትር ላይ የይዞታ ባለመብት ሁኖ የነበረ ቢሆንም አመልካች ሳይቃወም ተጠሪዎች በባዶ መሬት ላይ ቤት ገንብተዋል፡፡ ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ አልተሰጣቸውም ቢባል እንኳ የሚመለከተውን አስተዳደር ከሚጠይቅ በቀር በባዶ የመሬት ይዞታ ላይ ጉልበትና ገንዘባቸውን በማፍሰስ የሰሩበት ቤት ላይ ከአመልካች የተሻለ መብት እንዳላቸው ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40/7/ እንደተመለከተው ተጠሪዎች በአከራካሪው ይዞታ ላይ የገነቡት ቤት ባለይዞታ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

አመልካች በአከራካሪው ይዞታ አለኝ የሚሉትን መብት ለማስከበር ተገቢ ጥረት ባለማድረጋቸው ተጠሪዎች ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ቤት ሰርተው እየኖሩ እንደሚገኙ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1179/2/ እና 1180 የተመለከቱትን መሬት በግል መያዝ በተፈቀደበት ስርዓት በነበረው አካሄድ በማንኛውም ጊዜ ተጠሪዎችን ከሰሩት ቤት ማፈናቀል እንደሚችሉ በመግለፅ ያቀረቡት ክርክር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40/2/ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 30101፣ 36638 እና በሌሎች መዝገቦች የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካች ሳይቃወሙ የሰሩት ሁለት ሰርቨስ ቤት ሆነ አጥር ግቢው ባለይዞታ መሆናቸውን በማረጋገጥ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40/3/ እና /7/ እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 30101 እና 36638 የሰጣቸው ገዥ ውሳኔዎች መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር በጉዳዩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አያሳይም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካች ሳይቃወሙ የተሰሩ ቤቶች እንዲፈርሱ የመጠየቅ መብት የላቸውም ብለናል፡፡ ተጠሪዎች አመልካች ሳይቃወሙ የሰሯቸው ቤቶች ባለመብት ናቸው ብለናል፡፡

በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዓዲግራት ወረዳ ፍርድ ቤቶች የአሰበሰበያ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02012 በቀን 8/07/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 17820 በቀን 13/09/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 66911 በ23/10/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በድምፅ ብልጫ ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪዎች አመልካች ሳይቃወሙ የሰሩት ሁለት ሰርቨስ ቤት እና አጥር /ግቢው/ ባለመብት ናቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የልዩነት ሐሳብ

እኛ ስማችን በ2ኛ እና 4ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰዉ ዳኞች አብላጫዉ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በመለየት የሚከተለዉን የልዩነት ሐሳባችንን እናስቀምጣለን፡፡

በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት አሁን በአገራችን ባለዉ ሥርዓት እና የሕግ ማዕቀፍ ግለሰቦች ወይም ዜጎች የመሬት ነክ ንብረት ጋር በተያያዘ ያላቸዉ መብት ነዉ፡፡ የኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት የመሬት ነክ ንብረት በግለሰብ ደረጃ በግል መያዝ እንደሚቻል በወቅቱ በሥራ ላይ የነበሩት የሕግ ማዕቀፍ የሚያመለክት ጉዳይ ነዉ፡፡ የኃይለ ስላሴ መንግስት ከወቀደ በኋላ የመሬት ነክ ንብረት በግለሰብ በግል የመያዝ ሁኔታ በደርግ መንግስት ቀሪ መደረጉ ይታወቃል፡፡ በአገራችን ከደርግ መንግስት ዉድቀት በኋላ እና የኢህአዴግ መንግስት ስልጣን ከያዘ ወዲህ የመሬት ነክ ንብረት ባለቤትነት የኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝብ ሀብት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በዚህ መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት በ1987 ዓ.ም ከመዉጣቱ በፊት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የመንግስትና የሕዝብ ሀብት መሆኑን ባረጋገጠ መልክ የሕግ መዕቀፍ ወጥቶ ሲሰራበት እንደነበር ይታወቃል፡፡ በዛን ወቅት የከተማ መሬትን በተመለከተ የከተማ ቦታ በኪራይ ስለመያዝ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 80/1986 ዓ.ም መሰረት የሚመራ ነበር፡፡ በመቀጠል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 /3/ መሰረት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነዉ፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ፡፡ በማለት ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት ባለቤትነት የመንግስትና የሕዝብ እስከሆነ ድረስ ግለሰቦች በመሬቱ ላይ ሊኖራቸዉ የሚችለዉ የባለይዞታነት መብት እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡

ይህን በሕገ መንግስቱ የተመለከተዉን መርህ ተከትሎ የመንግስትና የሕዝብ የመሬት ባለቤትነትን ባረጋገጠ መልኩ እና ግለሰቦች ደግሞ የመሬት ባለይዞታነት መብት የሚያገኙበት ሥርዓት እና ይህ መብት የሚከበርበት የሕግ ሥርዓት ተዘርግቶ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ የከተማ መሬትን በተመለከት የከተማ ቦታን በሊዝ መያዝን እንደገና ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 272/1994 ዓ.ም በሚደነግገዉ አግባብ ሲመራ የነበረ ሲሆን፣ ይህ አዋጅ ከተሻረ በኋላ በአሁኑ ወቅት የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ዓ.ም እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በወጣዉ ደንብ መሰረት እየተሰራበት መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ ግለሰቦች ወይም ዜጎች የመሬት ነክ ንብረትን በተመለከተ የባለይዞታነት መብት ለማግኘት የሚችሉት እነዚህ ሕገ መንግስቱን ተከትሎ በወጡት ዝርዝር ሕጎች መሰረት ስልጣን ባለዉ የመንግስት አካል መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ዉጭ ግን የከተማ መሬት መያዝ እንደማይቻል እና ከዚህ ሕግ አግባብ ዉጭ ማንም ግለሰብ የከተማ መሬትን በመያዝ ሕጋዊ የባለይዞታነት መብት ሊያገኝ አይችልም፡፡ በዚህ ሕግ አግባብ አንድ ግለሰብ የከተማ መሬት ስልጣን ባለዉ የመንግስት አካል የተሰጠዉ እንደሆነ ይህ መብት ሊከበርለት ይገባል፤ ከሕግ ዉጭ የባለይዞታነት መብቱን በመንግስትም ሆነ በሌላ አካል ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግለሰብ ሊነጠቅ አይገባም፡፡ ይህ ማለት በዚህ አግባብ ባገኘዉ የከተማ መሬት ላይ የግል ንብረት የማፍራት መብት አለዉ፡፡ አንድ ሰዉ በሕጉ አግባብ ባገኘዉ የከተማ መሬት ላይ በጉልበቱ፣ በእዉቀቱ ወይም በገንዘቡ ንብረትን ያፈራ እንደሆነ የንብረቱ ባለሀብት እንደሆነ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 /2/ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አንድ ግለሰብ የከተማ መሬት መያዝ የሚችለዉ በሕጉ አግባብ ሲሆን፣ በዚህ አግባብ ባገኘዉ የመሬት ይዞታ ላይ የግል ሀብት ማፍራት ይችላል፡፡ ከዚህ ዉጭ የከተማ መሬትን በሕገ ወጥ መንገድ በመያዝ በመሬቱ ላይ ንብረት ስላፈራ ብቻ የባለይዞታነት መብት ሊሰጠዉ የሚችል አይሆንም፡፡ ሕግ የዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ የተገኘዉን የባለይዞታነት መብት በዚህ ይዞታ ላይ ከተፈራ ንብረት መብት አንጻር በአግባቡ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ የመሬት ባለይዞታነት መብት ትልቅ መብት በመሆኑ በሕገ ወጥ መንገድ ተይዞ ንብረት ስለተፈራ ብቻ ከባለይዞታነት መብት ይልቅ ለንብረት መብት የበለጠ ክብደት በመስጠት ያነሰ ዋጋ ሊሰጠዉ አይገባም፡፡ ይህ ደግሞ የመሬት ባለይዞታነት መብትን ተገቢ ክብደት የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ ሕገ ወጥ የሆነ የከተማ መሬት ወረራን ለመከላከልም የሚያግዝ ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነዉን 490 ካ.ሜ የከተማ መሬት በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለዉ የመንግስት አስተዳደር አካል የተሰጠዉ እና የባለይዞታነት መብት ያገኘ መሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ይህ በመሆኑ የአሁን አመልካች በዚህ መሰረት ያገኘዉን የባለይዞታነት መብት የሕግ አግባብ ተከትሎ ስልጣን ባለዉ አካል ከሚወሰነዉ ዉሳኔ ዉጭ ይህን የባለይዞታነት መብቱን ሊያጣ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ይዞታ ለታለመለት ዓላማ ያላዋለ እንደሆነ የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል በሕግ አግባብ በሚወስደዉ እርምጃ ይህን የባለይዞታነት መብቱን ከሚያጣ በስተቀር ማንም ግለሰብ ይህን ይዞታ ከሕግ ዉጭ ይዞበት ንብረት ስላፈራ አመልካች መብቱን የሚያጣበት አግባብ የለም፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ይዞታ ላይ ሁለት ሰርቪስ ቤቶችን መስራታቸዉ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ነገር ግን የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ይዞታ ላይ ሰርቪስ ቤቶች ይስሩ እንጂ በይዞታዉ ላይ የባለይዞታነት መብት በሚመለከተዉ የመንግስት አስተዳደር አካል ማግኘታቸዉን በሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ነገር የለም፡፡ በመሆኑም የአሁን ተጠሪዎች ይህን የከተማ መሬት የባለይዞታነት መብት የሕጉን አግባብ ተከትለዉ ባላገኙበት ሁኔታ በዚህ ይዞታ ላይ ቤት በመሥራታቸዉ ብቻ የባለይዞታነት መብት የሚያጎናጽፋቸዉ ነገር የለም፡፡ ከላይ የተመለከቱትን የከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ እና ደንብ ሲታይ በሕግ አግባብ ባልተገኙ ይዞታ ንብረት ማፍራት የባለይዞታነት መብት የሚያጎናጽፍ መሆኑን የሚያመለክተዉ ነገር የለም፡፡

ከዚህ አንጻር በ1952 ዓ.ም በኃይለ ስላሴ መንግስት የታወጀዉን የፍትሐብሔር ሕግ አሁን ያለዉ የመሬት ነክ ንብረት ተፈጻሚነት አለዉ ወይ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕግ የታወጀበት ወቅት መሬት እንደግል ሀብት የሚታይ እና በግል መያዝ እና እንደግል ሀብት እንደሚቆጠር የሚያመለክት ነዉ። በመሆኑም በዚህ ሕግ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ሲታዩ መሬት በግል ሀብትነት የሚያዝ መሆኑን በሚያመለክት መልኩ ‹‹ባለመሬቱ›› በማለት ይደነግጋል። በዚህ ረገድ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1178፣ 1179 እና 1180 ማየት ይቻላል። የእነዚህ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ሲታይ መሬት በግለሰብ እንደግል ሀብት መያዝ በሚችልበት ሥርዓት ዉስጥ እንደሆነ ግልጽ ነዉ። ይህ ከሆነ ደግሞ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት እና ሕገ መንግስቱን ተከትሎ ከወጡት ዝርዝር ሕጎች አንጻር ሲታይ እነዚህ የፍትሓ ብሔር ድንጋጌዎች የከተማ መሬት ነክ ንብረትን በተመለከተ ተፈጻሚነት የላቸዉም። ሆኖም ግን በአሁኑ ወቅት የከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ለመቆጣጠር የወጡት ሕጎች አንድ ሰዉ ሕጋዊ ባለይዞታ መብት ሳይኖረዉ ሕጋዊ ባለይዞታዉ ሳይቃወም በሌላ ሰዉ ይዞታ ላይ ቤት ወይም ንብረት ያሳረፈ ወይም ያፈራ እንደሆነ ይህ ጉዳይ በምን አግባብ ይታያል? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ።

በዚህ ረገድ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስትን ተከትለዉ የከተማ መሬት ነክ ንብረትን ለማስተዳደር የወጡት ሕጎች የሚሉት ነገር ባለመኖሩ በግለሰቦች መካከል የተፈጠረዉን አለመግባባት ለመፍታት የፍትሓ ብሔር ሕግ እንደአግባብነቱ ተፈጻሚነት ሊኖረዉ ይገባል የሚባል ከሆነ የግራ ቀኙን መብት ፍትሓዊና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በሚያስጠብቅ ሁኔታ ተፈጻሚ መደረግ አለበት እንጂ የአንዱን ወገን ተጠቃሚነት ብቻ በሚያረጋግጥ መንገድ ተፈጻሚ መደረግ የለበትም። ይህ ማለት የባለይዞታዉን መብት ብቻ ወይም በይዞታዉ ላይ ንብረት ያፈራዉን ወገን መብት ብቻ ባስጠበቀ መልኩ ተፈጻሚ መሆን የለበትም። የሁለቱንም ወገኖች መብት ፍትሓዊና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ባስጠበቀ ሁኔታ ተፈጻሚ ማድረጉ ተገቢ ነዉ። በዚህ መሰረት የአሁን አመልካች በይዞታዉ ላይ ተጠሪዎች የሰርቪስ ቤቶችን ሲሰሩ ባለመቃወሙ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179 /1/ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል የሚባል ከሆነ፣ የአንቀጹ ሌሎች ንዑስ አንቀጾችም ተፈጻሚነት ሊኖራቸዉ ይገባቸዋል። የድንጋጌዉ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደሚደነግገዉ ‹‹ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰዉ መሬት ሕንጻ የሠራ ሰዉ የዚሁ ሕንጻ ባለሀብት ነዉ›› የሚል ነዉ። አሁን ለተያዘዉ ጉዳይ ይህን ድንጋጌ ብቻ ተፈጻሚ አድርጎ መተዉ፣ የተጠሪዎችን የንብረት መብት ብቻ ባስጠበቀ መንገድ ተፈጻሚ መደረጉን እንጂ የአመልካችን የባለይዞታነት መብት ከግምት ያስገባ ሆኖ አይታይም። ይህን ድንጋጌ ፍትሓዊ በሆነ ሁኔታ ተፈጻሚ ማድረግ ካስፈለገ ለንብረት መብት ብቻ ሳይሆን ለባለይዞታ መብትም ተገቢዉ ክብደት ሊሰጠዉ ይገባል። ይህ ደግሞ ሊረጋገጥ የሚችለዉ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1179 ሥር የተመለከቱትን ንዑስ አንቀጾች በአጠቃላይ ተፈጻሚ በማድረግ ነዉ። ይህ ማለት የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1179 እና 1180 እንደሚደነግገዉ ባለይዞታዉ በሕጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት ሕንጻዉን ለገነባዉ ሰዉ ተገቢዉን የካሳ ግምት በመክፈል ይዞታዉን የማስለቀቅ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች በዚህ ድንጋጌ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት ለአመልካቾች ተገቢዉን የንብረት ካሳ ግምት በመክፈል ይዞታዉን የማስለቀቅ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባዉ ነበር፡፡ ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶችም የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት በሆነዉ ይዞታዉ ላይ ተጠሪዎች የሰሩት ቤቶች ግምት ምን ያህል እንደሆነ በባለሙያ አስገምተዉ አመልካች ተገቢዉን ካሳ ከፍሎ ይዞታዉን እንዲያስለቅቅ ማድረግ ሲገባቸዉ የተጠሪዎችን መብት ብቻ በሚያስጠብቅ መልክ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179 /1/ ተርጉመዉ ተፈጻሚ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሯል፡፡ እንዲሁም የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ድጋሚ በማየት በባለሙያ ቤቱን በማስገመት አመልካች ይህን ግምት ለተጠሪዎች እንዲከፍል በማድረግ ይዞታዉ ለአመልካች እንዲለቀቅ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 /1/ መሰረት ሊመለስለት ይገባ ነበር በማለት ወስነናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ 110040

የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ እሴተማርያም አክሎግ

2. ወ/ሪት ወይንሸት አክሎግ } የቀረበ የለም

3. አቶ መክብብ አክሎግ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ውርስ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካቾች ለአ.አ.ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የአያታቸው ወ/ሮ ደብረወርቅ ሀ/ሚካኤል ወራሽነት ይረጋገጥልን በማለት አቅርበዋል፡፡የአባታቸው ሻለቃ አክሎግ አድማሱ ወራሽነት ያረጋገጡ ሲሆን የወላጅ አባታቸውን እናት ወራሽነት ለማረጋጥ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡ወላጅ አባታቸው በ1981 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ሲሆን አያታቸው ወ/ሮ ደብረወርቅ ሀብተ ሚካኤል የሞቱት ደግሞ በ1978 ዓ/ም ነው፡፡ በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም አያታችህ ከአባታችሁ ቀድመው የሞቱ ስለሆነ ተተኪ ወራሽ ልትሆኑ አትችሉም በማለት ብይን ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ብይን ባለመስማማት አቤቱታቸውን ለአ.አ.ከተማ ይግባኝ ሰሚና ለሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኝ በትእዛዝ ሰርዞውታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች ተወካይ የካቲት 10 ቀን 2007 ዓ/ም በፃፉት የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ብይን ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ወላጅ አባታችን እናቱ ከሞቱ ጀምሮ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ በህመም ላይ እንደነበር ለስር ፍርድ ቤቶች አስረድተን እያለን የአያታች ወራሽነት አታረጋግጡም መባሉ ከፍተኛ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ወላጅ አባታችን ለ3 አመት የአልጋ ቁራኛ ሆኖ የእናቱን ወራሽነት ሳያረጋግጥ ቢቀርም አመልካቾች ተተኪ ወራሾች የአያታችንን ወራሽነት የሚከለክለን አንዳችም ህግ የሌለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ብይንና ትእዛዝ በመሻር የአያታቸውን ወራሽነት እንዲረጋገጥላቸው አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተተኪ ወራሾች ሊሆኑ አይችሉም በማለት የተሰጠ ብይን ከፍ/ብ/ህ/ቁ/ 830፣831/3/844 እና 839 አንፃር ለመመርመር በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ሊቀርብ የቻለው የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካቾች ጥያቄ ወላጅ አባታቸውን ተክተው የአያታቸው ወራሽነት እንዲረጋጥላቸው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ደግሞ ተተኪ ወራሾች ልትሆኑ አትችሉም በማለት ብይን ሰጥተዋል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 842/3/ ስር እንደተመለከተው የሟች ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሲሆኑ ልጆች ቀድመው ከሞቱና ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ትተው ከሆነ ተወላጆቹ ወላጃቻውን ተክተው ሟችን እንደሚወርሱ ያመላክታል፡፡ የተተኪ ወራሽነት የተፈፃሚነት ወሰን ወደ ታች የሚቆጥሩ ተወላጆች እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ወላጅ አባታቸው የእናታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ናቸው፡፡ አመልካቾችም የወላጅ አባታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች እንደሆኑ የህጉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተተኪ ወራሽ ለመሆን ከፍ/ብ/ህ/ቁ/ 842/3/ አንፃር ሲታይ የአመልካቾች ጥያቄ የሚያሚላ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ወላጅ አባታቸው የእናታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ በመሆን የወረሱ ስለሆነ የምትክ ጉዳይ ሊነሳ አይችልም፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካቾች አባታቸውን ተክተው አያታቸውን መውረስ የሚችሉት አባታቸው ከአያታቸው በፊት የሞቱ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች የሟች አባታቸውን ወራሽነት ስለማረጋገጣቸው ከክርክሩ ስለተረዳን አባታቸው የወረሱትን ንብረት ለመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡ በዚሁ መሰረትም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 1118/07 ጥር 6 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን፤ የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ/23073 ጥር 21 ቀን 2007 ዓ/ም እና የአ/አ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 23140 የካቲት 2 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 348/1/መሰረት በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የልዩነት ሀሳብ

የአመልካቾቹ መሰረታዊ የአቤቱታ ነጥብ ወላጅ አባታችን ሻለቃ አክሎግ አድማሱ ከወላጅ እናታቸው ከወ/ሮ ደብረወርቅ ሀብተ ሚካኤል በኃላ የሞቱ በመሆኑ አባታችን የነበራቸው እናታቸውን የመውረስ መብት ለእኛ ለሻለቃ አክሎግ አድማሱ ልጆች እና ወራሾች የሚተላለፍ መሆኑ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠን የሚል መሆኑን ከስር ጀምሮ ከሚያቀርቡት ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሰረቱ ለአንድ ውርስ ወራሽ የሆነ አንድ ሰው ውርሱ ከተከፈተ በኃላ የሞተ እንደሆነ የወራሽነቱ መብቶች ለርሱ ወራሾች የሚተላለፉ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 833 ተመልክቷል፡፡ ከአውራሹ አስቀድሞ የሞተን ወራሽ ተክቶ መውረስ (ቁጥር 844 (2) እና ከአውራሹ በኃላ የሞተን ወራሽ ተክቶ መውረስ (ቁጥር 833) የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆም ለአቤቱታው አግባብነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ ቁጥር 844 (2) ሳይሆን 833 ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በቁጥር 833 ድንጋጌ መሰረት ከአውራሹ በኃላ የሞተ ወራሽ ተተኪ ወራሾች መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው አመልካቾቹ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ተሽሮ በአመልካቾቹ አቤቱታ መሰረት ሊወሰን ይገባው ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁጥር ሁለት የተመለከተው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬአለሁ፡፡

መ/ተ የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 113529

የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካቾች፡

1. ወ/ሮ እቴቱ ከንባው
2. አቶ ኃይሉ ከንባው

} ከጠበቃ ወንደሰን ሽዋረጋ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ቀለሚ ዓለማየሁ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁኖቹ አመልካቾች የአባታቸው እናት ማለትም የሴት አያታቸው የሚች ወ/ሮ ላቀች ቸርነት ታፋይ ውርስ እንዲጣራላቸው በአሁኗ ተጠሪ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተጠሪዋን መልስ ከተቀበለ በኃላ ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ በ19/07/2006 ዓ.ም. የተዘጋጀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ የሪፖርቱ ይዘትም የአመልካቾቹ አባት አቶ ከንባው ወርቅነህ ሚች እናታቸው (የአመልካቾች አያት) ወ/ሮ ላቀች ቸርነት በሞቱበት ጊዜ በሕይወት የነበሩ ሆኖ ነገር ግን የእናታቸው ወራሽ መሆናቸውን ሳያረጋግጡ ቆይተው የሞቱ በመሆኑ አመልካቾቹ በአባታቸው እግር ተተክተው አያታቸውን ሊወርሱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ ውርሱን ከእናታቸው ወ/ሮ ላቀች ቸርነት በኃላ ነገር ግን የእናታቸው ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው በሞቱት ሚች የሸዋመብራት ወርቅነህ እግር ተተክተው የእኒሁ የሸዋመብራት ወርቅነህ ልጅ እና ወራሽ የሆኑት ተጠሪ፣እንዲሁም የወ/ሮ ላቀች ቸርነት ሌላ ወራሽ ካለ እንዲቀርብ አጣሪው ባወጣው ማስታወቂያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠርተው የቀረቡት ወ/ሮ የማርያምወርቅ ወርቅነህ በጋራ ይወርሳሉ የሚል ነው፡፡በሪፖርቱ ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአሁኖቹን አመልካቾች አስተያየት ውድቅ አድርጎ የአጣሪውን ሪፖርት በማጽደቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ የተደረገ ቢሆንም ተጠሪዋ በምስክሮች ፊት መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸው በመሀላ ቃል በመረጋገጡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎ ጉዳዩ ለምርመራ እንዲቀጠር የተደረገ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የአመልካቾቹ ወላጅ አባት አቶ ከንባው ወርቅነህ ከሟች እናታቸው ወ/ሮ ላቀች ቸርነት የሚያገኙት ውርስ ለአመልካቾቹ ሊተላለፍ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካቾቹ አባት እናት (የአመልካቾቹ አያት) የሆኑት ወ/ሮ ላቀች ቸርነት ታፋይ በሞት የተለዩት በ14/02/1979 ዓ.ም. መሆኑን፣የአመልካቾቹ አባት አቶ ከንባው ወርቅነህ የሞቱበትን ጊዜ የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት ባይሆንም የሞቱት ከእናታቸው ሞት በኃላ ረዥም ጊዜ ቆይተው መሆኑን፣የተጠሪዋ እናትም የሞቱት በተመሳሳይ ሁኔታ ከእናታቸው ከወ/ሮ ላቀች ቸርነት ሞት ከ24 ዓመታት በኃላ በ2003 ዓ.ም. መሆኑን፣ የአመልካቾቹ አባት የሞቱት የእናታቸው ላቀች ቸርነት ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይወስዱ መሆኑን፣በአንጻሩ የተጠሪዋ እናት የሞቱት የእናታቸው ወ/ሮ ላቀች ቸርነት ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በ1997 ዓ.ም. ከወሰዱ በኃላ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡እናታቸው በሞቱበት ጊዜ የአመልካቾቹ አባት በሕይወት የነበሩ እና ለወራሽነት አይገቡም ያልተባሉ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 ድንጋጌ መሰረት እናታቸውን የመውረስ መብት አላቸው፡፡አንድ ሰው የሞተ እንደሆነ በሞተበት ጊዜ ዋናው መኖሪያው ስፍራ በሆነበት ቦታ የሟቹ ውርስ የሚከፈት ስለመሆኑ እና በሟቹ ሞት ምክንያት የሚቋረጡ ካልሆኑ በቀር በውርሱ ውስጥ የሚገኙት የሟቹ መብቶች እና ግዴታዎች ለወራሾቹ እና የኑዛዜ ባለስጦታዎች የሚተላለፉ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 826 የተመለከተ ሲሆን ለአንድ ውርስ ወራሽ የሆነ አንድ ሰው ውርሱ ከተከፈተ በኃላ የሞተ እንደሆነ የወራሽነቱ መብቶች ለእርሱ ወራሾች የሚተላለፍ ስለመሆኑም በቁጥር 833 ተደንግጎ ይገኛል፡፡በመሆኑም ከላይ በተጠቀሰው ቁጥር 833 ድንጋጌ መሰረት የወ/ሮ የሸዋመብራት ወርቅነህ ድርሻ ወራሻቸው ለሆኑት የአሁኗ ተጠሪ እንደተላለፈው ሁሉ የአመልካቾቹ አባት አቶ ከንባው ወርቅነህ ከእናታቸው ከሟች ላቀች ቸርነት የሚያገኙት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የውርስ ድርሻ ለሚች ከንባው ወርቅነህ ወራሾች የሚተላለፍ ከሚሆን በቀር አቶ ከንባው ወርቅነህ በሕይወት እያሉ የእናታቸው ላቀች ቸርነት ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ባለመውሰዳቸው ብቻ የአቶ ከንባው ወርቅነህ የውርስ ድርሻ ለሌሎች የሚች ላቀች ቸርነት ወራሾች እንዲተላለፍ ሊደረግ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የአመልካቾቹ አባት ከእናታቸው የሚያገኙት የውርስ ድርሻ ወደ አሁኖቹ አመልካቾች ሊተላለፍ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከላይ የተጠቀሱትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከላይ የሰፈረው ትችት እንደተጠበቀ ሆኖ በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ተጠሪዋ በአመልካቾቹ ላይ የይርጋ መቃወሚያ አላነሱም፡፡ከመዝገቡ መገንዘብ እንደሚቻለው ወ/ሮ ላቀች ቸርነት ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ የአመልካቾቹ አባት በዚሁ የውርስ ቤት ውስጥ ሲኖሩ የነበረ በመሆኑ እና አመልካቾቹም እየኖሩ የሚገኙት በዚሁ ቤት በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያ ሊነሳ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ውርሱ እንዲጣራላቸው አመልካቾቹ ላቀረቡት አቤቱታ ተጠሪዋ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾቹ ከቤቱ የውርስ ድርሻ እንዳላቸው በማመን ውርሱ ቢጣራ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ መልስ የሰጡ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ በመሰረቱ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ መስጠት የማይችል ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 182 (2) በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም የአመልካቾቹ አባት ከእናታቸው የሚያገኙት የውርስ ድርሻ ወደ አሁኖቹ አመልካቾች ሊተላለፍ አይገባም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተሰጠው ከተጠሪዋም ሆነ ከሌላኛዋ ወራሽ ምንም ዓይነት ተቃውሞ ባልቀረበበት እና ይልቁንም የአመልካቾቹ የመውረስ መብት በግልጽ በታመነበት ሁኔታ ጭምር በመሆኑ አመልካቾቹን ከውርሱ በማግለል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት አድርጎ የተሰጠ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43731 በ03/01/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 162716 በ30/06/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የውርስ አጣሪው በ19/07/2006 ዓ.ም. ባቀረበው ሪፖርት ላይ ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎ የሟች ወ/ሮ ላቀች ቸርነት ውርስ ከሆነው በጉለሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 5 ከሚገኘው ቁጥሩ 147 ከሆነው ቤት ውስጥ የአሁኗ ተጠሪ ወ/ሮ ቀለሟ ዓለማየሁ አንድ ሶስተኛ፣ወ/ሮ የማርያምወርቅ ወርቅነህ አንድ ሶስተኛ፣የአሁኖቹ ሁለቱ አመልካቾች ደግሞ በጋራ አንድ ሶስተኛ ድርሻ አላቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. በዚህ መዝገብ በ24/02/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 108328

መጋቢት 13 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጫልቱ ዋቀዬ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ፈቃዱ ዋቀዬ - ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በኦሮሚያ ክልል የወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ የሟች አባታቸው አቶ ዋቀዬ ነገአ እና ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ እሼቱ አባላቱ እንደነበረ፤ ወላጅ እናታቸው በ2001 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኃላ የቤተሰብ አባላት የውርስ ንብረት የማጣራት ሥራውን በስምምነት ማከናወን ባለመቻላቸው በፍ/ቤት በኩል በመ/ቁ.20782 ጠይቀው ወራሾች እንዲቀርቡ በሚኖርበት አካባቢ በማስታወቂያ ጥሪ ቢደረግም የቀረበ ሰው እንዳልነበረ፤ የውርስ አጣሪዎች የውርስ ንብረቱን ለይተው የየድርሻቸውን እንዳስረከቡዋቸው፤ በዚሁም አመልካች የድርሻቸውን 2262 ካሬ ሜትር ይዞታ ሳይረሱት አክርመውት የአሁኑ ተጠሪ ያለ አመልካች ፈቃድ በ2004/2005 ዓ.ም መሬቱን በማረስ ገብስ የዘራ በመሆኑ መሬቱን ለቆ የሰብል ግምት የ4 ኩንታል ብር 4,000 እንዲከፍል እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በፍሬ ጉዳዩም መልስ አቅርበዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ መሬቱን ለ5 ዓመታት የተጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1000/1/ መሠረት የይርጋ መቃወሚያ እንዲሁም ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው የሚል ክርክር ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ያቀረቡት የውርስ ንብረትና ወራሾችን በግልጽ ያላስቀመጠ እንደሆነ ይዞታው ከተጠሪ እጅ በመውጣት በአመልካች ይዞታ ሥር አለመግባቱን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የይርጋ እና ጉዳዩን ውሳኔ ያገኘነው የሚል ክርክር ሳይቀበል በፍሬ ጉዳዩ ለክርክር ምክንያት የሆነውን የመሬት ይዞታ በተጠሪ እጅ ያለ ስለመሆኑ አልተካደም፤ የተጠሪ ምስክሮች ይህ የውርስ ንብረት አለመክፈሉን አላየሁም ይበሉ እንጅ በአመልካች የቀረቡ ምስክሮች በሚያሳምን መልኩ አሁን ክርክር ያስነሳው ይዞታ የአቶ ዋቀዬ ነገአ ወራሾች ሃብት ሲከፋፈል ለአመልካች ድርሻቸው የተሰጣቸው ስለመሆኑ ያረጋገጡ በመሆኑ ተጠሪ አመልካች በውርስ ያገኙትን 2666 ካሬ ሜትር በእጃቸው የሚገኘውን እንዲለቁ አመልካች በ2004 ዓ.ም ያጡት የ2004 ዓ.ም ምርት 4,000 እንዲከፍሉ ወስነዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፍንፍኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ በውርስ አጣሪዎች ቀረበ የተባለው ሪፖርት የውርስ ንብረት እና ወራሾች በአግባቡ የለየ አለመሆኑን የእያንዳንዱ ወራሽ ድርሻ ተለይቶ ባልተወሰነበት፤ ፍርድ ቤትም የቀረበለትን ሪፖርት አጣሪው በሥልጣኑ መሠረት አጣርቶ ያቀረበው ስለመሆኑ በማረጋገጥ ያፀደቀው የአሁኑ ተጠሪ ይዞታ እንዲለቅ እና የሰብል ግምት እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ አለመሆኑን፤ አመልካች አቤቱታቸው የይርጋ ጊዜ ሳያልፈው ያቀረቡት በመሆኑ የእናታቸውን የውርስ ድርሻ የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው ሲል የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርመሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ አንኳር ነጥቦች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የመሬት ይዞታ በእጃቸው ገብቶ የነበረ ስለመሆኑ የወራሾች ድርሻ የተከፋፈለ ነው፣ ለአመልካች ከሚደርሳቸው በላይ እንዳልተሰጣቸው በመግለጽ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የማጣራት ሥራው ወራሾች ባልተሳተፉበት ሁኔታ እንደተከናወነ፤ አጣሪዎች በሕግ ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ በይዞታው እየተጠቀሙ ያሉት ተጠሪ ስለመሆናቸው በመግለጽ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና አመልክተዋል፡፡ የመልስ መልስም አቅርበናል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የውርስ አጣሪዎች ሪፖርት ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20782 ቀርቦ የተመዘገበው ቃለ-ጉባኤ የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህ ችሎት ዕልባት የሚያሻው ዓብይ ነጥብ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የውርስ ንብረት በአግባቡ ተጣርቶ የተወሰነ አይደለም በማለት የሥር ወረዳ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔንና ትዕዛዝ መሻሩ በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት ክስ በውርስ አጣሪዎች ድርሻቸው ተለይቶ ከታወቀ በኃላ የአሁኑ ተጠሪ ከሕግ ውጪ በመያዝ እየተጠቀመበት መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ይዞታውን እንዲለቁ እንዲሁም የሰብል ግምት አራት ሺህ ብር እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን ነው፡፡ ተጠሪ ጉዳዩ በይርጋ እንደሚታገድ፤ ከአሁን በፊትም በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ስለመሆኑ እንዲሁም የወራሾች ድርሻ በሕጉ አግባብ አለመወሰኑን መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡ አመልካች የውርስ ሃብት ለወራሾች በአግባቡ ተከፋፍሏል ይበሉ እንጂ በሥር ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 20782 ተመዘገበ የተባለው የውርስ አጣሪዎች ሪፖርት ወራሾች እነማን እንደሆኑ፤ የአውራሾቻቸው የሚንቀሳቀስና የማይቀሳቀስ ንብረት ምን እንደሆነ፤ እያንዳንዱ ወራሽ የሚደርሰው የሃብት መጠን ምን ያህል እንደሆነ? በግልጽና በማያሻማ መልኩ ያስቀመጠ ስለመሆኑ ሰነዱ አያሳይም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የውርሰ አጣሪዎች የተባሉ ሸማግሌዎችም ወራሾች በማጣራት ሂደት እንዲሳተፉ በማስታወቂያ ጥሪ አድርገን ነበር ያሉ ቢሆንም በእርግጥ ከአመልካች ውጭ ያሉ ወራሾች በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጐላቸው ውርስ እንደሚጣራ አውቀው በዳታኝነት የቀሩ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡

በመሰረቱ ውርስ የሚጣራው በወራሾች ሲሆን ስምምነት ከሌለ ወይም ሌላ ሕጋዊ ምክንያት ካለ አጣሪዎች በፍ/ቤት እንደሚሰየሙ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 946 እና 950 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡ የውርስ ሃብት ማጣራት በሕጉ አግባብ ከተከናወነም ወራሾች ድርሻቸውን የመጠየቅ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1062 ተመልክቷል፡፡ የክፍፍል ሥርዓቱም በወራሾች ስምምነት ሊሆን እንደሚችል፤ በውርስ ክፍፍል ጊዜ ያልተወከለ ወራሽ ካለም በፍ/ቤት እንደሚፀድቅ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1079 እና 1080 ተደንግጓል፣ የውርስ ሀብት የክፍፍል መርህም በዓይነት እንደሚሆን፤ ንብረቱን በዓይነት ለማከፋፈል ባልተቻለበት ሁኔታ በማቻቻል ሕጋዊ መፍትሄ እንደሚያገኝ የፍ/ሕ/ቁ. 1086 እና 1087 ድንጋጌዎች ያስገነዝቡናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ቀረበ ያለውን የውርስ አጣሪዎች ቃለ ጉባኤ ከማፅደቁ በፊት በእርግጥ የውርስ ሃብት የማጣራት ሕጋዊ ሂደት ተከትሎ ወራሾች እና የውርስ ሀብት በአግባብ የተካሄደ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ነበረበት፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት የሚቾች የውርስ ሀብት ምን ምን እንደሆነ፤ ወራሾች እነማን እንደሆኑ እና ድርሻቸውን በሕጉ አግባብ በመለየት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለመወሰኑ መዝገቡ አያሳይም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የውርስ ሀብት በሕጉ አግባብ ተጣርቶ የተወሰነ አይደለም በማለት የወረዳውን ውሳኔ እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ውድቅ ማድረጉ በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡ ምክንያቱም የወረዳው ፍርድ ቤት ወራሾችና የውርስ ሀብት በአግባቡ በመለየት ውሳኔ አልሰጠም፡፡ በዚህ ረገድ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የውርስ ሃብት ድርሻቸውን ከሰው የመጠየቅ መብታቸውን የጠበቀ ስለመሆኑ የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ይሁንና አመልካች የውርስ ሃብት ድርሻቸውን ለመጠየቅ ክስ እንዳቀረቡ መዝገቡ ስለሚያሳይ አመልካች ሌላ ክስ ማቅረብ ሳይጠበቅባቸው አለኝ የሚሉትን ድርሻ በሕጉ አግባብ ክሳቸውን እንዳያሻሽሉ በማድረግ እና ተገቢ ዳኝነት በመክፈል በሥር መ/ቁ. 46789 ክርክራቸውን የመቀጠል መብታቸው ሊነፈግ አይገባም፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ በሚጋብዝ አግባብ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ዓላማ አንፃር ሲታይ ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ወረዳ ፍ/ቤት ወራሾችና የውርስ ሀብት በመለየት ውሳኔ አልሰጠም በማለት የውርስ አጣሪ ሪፖርት ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ሆኖ አመልካች አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ በመፍቀድ የሰጠው የውሳኔ ክፍል ግን ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኤሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 185583 በ26/01/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46789 በ14/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የአዲስ አበባ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 72261 በ6/09/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በመሻር የሰጠው ፍርድ ተሻሽሏል፡፡
2. የውርስ አጣሪዎች ሪፖርት ወራሾች እና የውርሰ ሀብት በአግባቡ ለይቶ ያላስቀመጠ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ሌላ ክስ ማቅረብ ሳይጠበቅባቸው ድርሻ አለኝ ካሉ በሕጉ አግባብ ክሳቸውን አሻሽለውና ተገቢ ዳኝነት ከፍለው ክርክሩን የመቀጠል መብታቸው የተጠበቀ ነው ብለን ወስነናል፡፡ የወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤትም የመ/ቁ. 46789 በመክፈት የውርስ ሀብት ክርክር ከቀረበ በሕጉ አግባብ ለማጣራት ተገቢ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማየነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 118105

መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ዓሊ መሐመድ
ተኽሊት ይመሰል
ቀነዓ ቂጣታ
ሰናይት አድነው
ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ በቀለ .....ቀርበዋል

ተጠሪዎ ፡- 1. ወ/ሮ እሸቷ ጎሽዬ.....ቀርበዋል

2. አቶ ሀብታሙ በቀለ.....ቀርበዋል

3. ወ/ሮ መብራት በቀለ.....ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ኑዛዜን መነሻ ያደረገ የዉርስ ክርክርን የሚመለከት ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- በሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች /የሥር ተጠሪ/፣ የአሁን ተጠሪዎች /የሥር አመልካቾች/ ሁኖው ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የሥር አመልካቾች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሟች ሻምበል በቀለ ደምሴ ጥር 13 ቀን 1988 ዓ.ም የሞተ ሲሆን፣ ሟች በሕይወት በነበረ ጊዜ በ22/11/1982 ዓ.ም የተጻፈ ኑዛዜ ያደረገ ስለሆነ የዉርስ አጣሪ ተሹሞ እንዲያጣራልን በማለት አመልክተዋል፡፡ የሥር ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ አመልካቾች የዉርስ ንብረቱን ሙሉ ለሙሉ ይዘዉ እያሉ ተጠሪን ተከሳሽ ማድረጋቸዉ አግባብነት የለዉም፣ እኔም ወራሽ ስለሆንኩኝ የዉርስ ንብረቱ ቢጣራ አልቃወምም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የዉርስ አጣሪ በማሾም የዉርስ አጣሪዉ የዉርስ ሀብቱን በማጣራት በ28/02/2006 ዓ.ም የተጻፈ ሪፖርት ያቀረበ ሲሆን ግራ ቀኙ በሪፖርቱ ላይ አስተያየት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ሪፖርት እና አስተያየት በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ግራ ቀኙ ሟች ያደረገዉን ኑዛዜ በጋራ ፍ/ቤት አቅርበዉ የፀደቁ በመሆኑ የዉርስ ማጣራት ሥራዉ እና ክፍፍሉም መካሄድ ያለበት በዚህ አግባብ ነዉ፡፡ ይህ ኑዛዜ ገደብ ያለበት በመሆኑ 1ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ወ/ሮ እሸቷ ጎሽዬ በሕይወት እስካሉ ድረስ በዚህ ቤት የመጠቀም መብት ስላላቸዉ ወራሾች የመኖሪያ ቤት፣ የቤት ኪራይ እንዲሁም የቤት ዉስጥ ቁሳቁስ ለመጠየቅ መብት አይኖራቸዉም ። ነገር ግን ከ1ኛ አመልካች ህልፈተ ሕይወት በኋላ ከጠቅላላ ንብረት 50% የ2ኛ አመልካች አቶ ሀብታሙ በቀለ በመሆኑ፣ ቀሪዉ 50% የተጠሪ አቶ ተስፋዬ በቀለ እና 3ኛ አመልካች ወ/ሮ መብራት በቀለ ድርሻ እያንዳንዳቸዉ 25% ድርሻ ይኖራቸዋል፣ ስለዚህ በኑዛዜዉ መሰረት ሪፖርቱ በዚህ አግባብ ተሻሽሏል በማለት ወስኗል። የሥር ተጠሪ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሰረት ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔን በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች መስከረም 6 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ሁለት ገጽ አቤቱታ ሟች አባታችን በ22/11/1982 ዓ.ም ያደረገዉ ኑዛዜ በግል ሀብት ላይ ሳይሆን በአጠቃላይ በዉርስ ሀብት ላይ የተደረገ ኑዛዜ በመሆኑ ኑዛዜዉ ተሽሮ የዉርስ ሀብት ሳይናዘዝ እንደሞተ ሰዉ ተቆጥሮ የዉርስን ሀብት በሕግ አግባብ እንድንካፈል። 1ኛ ተጠሪ ኑዛዜዉን ወደጎን በመተዉ የዉርስ ሀብት እንዲጣራላቸዉ በሥር ፍ/ቤት ባመለከቱት መሰረት ኑዛዜዉ የማይሰራ በመሆኑ የዉርስ ሀብቱን ድርሻዬን 25% እንዳገኝ እንዲወሰንልኝ። ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች 1ኛ ተጠሪ በሕይወት እስካሉ ድረስ ምንም ዓይነት የዉርስ ድርሻ መጠየቅ አትችልም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልኝ እንዲሁም ኑዛዜዉ ተሽሮ የዉርስ ሀብቱን ሳይናዘዝ እንደሞተ ሰዉ የዉርስ ሀብት ድርሻ በሕግ አግባብ እንዲካፈል እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በመመርመር ፣የዉርስ ይጣራ ጥያቄ የቀረበዉ በኑዛዜዉ ተጠቃሚዎች ከመሆኑ አንጻር የግራ ቀኙ የዉርስ ድርሻ ጭምር እንዲጣራ ያለመደረጉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ በታዘዘዉ መሰረት የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት፡-የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ እንዲጸናልን፣ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ እንዲደረግልን፣ በዚህ ምክንያት የደረሰዉን ወጪና የጠበቃ አበል እንዲወሰንልን በማለት ተከራክሯል። አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለአቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። መዝገቡን እንደመረመርነዉ ሟች ሻምበል በቀለ ደምሴ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕይወት በነበሩ ጊዜ በ22/11/1982 ዓ.ም የተጻፈ ኑዛዜ ማድረጋቸዉ ግራ ቀኙ የሚካካዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንደሚያመለክተው የአሁን አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የሚች አባታቸዉ ወራሽ፣ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ የሚች ሚስት እንደሆኑ እና 3ኛ ተጠሪ የኑዛዜ ወራሽ እንደሆነች ተመልክቷል፡፡ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ሚች ይህን ኑዛዜ ያደረገዉ ጠቅላላዉን ንብረት በሚመለከት ሲሆን የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሕይወት እስካሉ ድረስ ሀብቱን የመጠቀም መብት እንዳላቸዉ እና ማንም ተወላጅ የአባቱ ዉርስ ይገባኛል በማለት መጠየቅ እንደማይችል እና ከ1ኛ ተጠሪ ህልፈተ ሕይወት በኋላ ከጠቅላላ ሀብቱ 2ኛ ተጠሪ 50% እንዲካፈል፣ አመልካች እና 3ኛ ተጠሪ ቀሪዉን ሀብት 50% ለሁለት እንዲካፈሉ (እያንዳንዳቸዉ 25%) እንዲካፈሉ በማለት የተናዘዘ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ግራ ቀኙ ይህን ኑዛዜ በመቀበል እንዲጸድቅላቸዉ በጋራ ለፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዉ በፍ/ቤት ዉሳኔ የጸደቀ መሆኑን ተማምነዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረበዉ ክርክር ሲታይ ሚች ያደረገዉ ኑዛዜ በፍ/ቤት ቀርቦ ሲጸድቅ ያልተቃወመ መሆኑን፣ የዉርስ ማጣራትም ሆነ ክፍፍሉ መሆን ያለበት በኑዛዜዉ አግባብ መሆን እንዳለበት ተከራክሯል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር የኑዛዜዉ ይዘት ላይ የተለያየ ክርክር ቢያቀርቡም የዉርስ ማጣራት ሂደትም ሆነ ክፍፍሉ በዚሁ አግባብ መሆን እንዳለበት ገልጸዉ ተከራክረዋል፡፡ እንዲሁም የሥር ፍ/ቤት የዉርስ አጣሪዉን ሪፖርት በማሻሻል ክፍፍሉ በኑዛዜዉ አግባብ መሆን እንዳለበት ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረቡት ቅሬታ የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ኑዛዜዉ ገደብ ያለበት መሆኑን በመገንዘብ 1ኛ ተጠሪ በሕይወት እስካሉ ድረስ ተጠሪዎች የዉርስ ሀብት መጠየቅ እንደማይችሉ እና ከ1ኛ ተጠሪ ህልፈተ ሕይወት በኋላ ከጠቅላላ ሀብቱ 2ኛ ተጠሪ 50% እንዲካፈል፣ አመልካች እና 3ኛ ተጠሪ ቀሪዉን ሀብት 50% ለሁለት እንዲካፈሉ እያንዳንዳቸዉ 25% እንዲካፈሉ በማለት የወሰነ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ፍ/ቤት የኑዛዜዉን ይዘት በማየት ተርጉሞ የሰጠዉን ዉሳኔ በተመለከተ ሚች ኑዛዜዉን የሰጠዉ በአጠቃላይ ሀብት ላይ ሳይሆን በንብረቱ ግማሽ የግል ሀብታቸዉ ላይ ነዉ ተብሎ እንዲወሰን ያቀረቡት ክርክር የሥነ ሥርዓት ሕጉን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የአሁን አመልካች ሚች በሰጠዉ ኑዛዜ መሰረት ዉርስ ቢጣራ እና ክፍፍል ቢደረግ እንደማይቃወም እንዲሁም ኑዛዜዉ መጀመሪያ በፍ/ቤት ሲጸድቅ እንዳልተቃወመ በመግለጽ ሲከራከር እንደነበር የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡ እነዚህ ሁሉ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሆናቸዉ ግልጽ ነዉ፡፡ እነዚህ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች በኑዛዜዉ አግባብ የዉርስ መጣራት ሂደቱም ሆነ ክፍፍል ቢደረግ እንደማይቃወም እየገለጸ፣ ይህ ኑዛዜ በፍ/ቤት እንዲጸድቅ ከተጠሪዎች ጋር ለፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዉ ኑዛዜዉ በማጽደቅ ከጨረሰ በኋላ አሁን በኑዛዜዉ አግባብ የተሰጠዉን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ኑዛዜዉን እንዲሻርልኝ በማለት ያቀረበዉ ክርክር በሥር ፍ/ቤት ያልቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበዉ ቅሬታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329 /1/ መሰረት ተቀባይነት የለዉም ። ሌላዉ የአሁን አመልካች የሀብቱ 25% ድርሻ እንዲሰጠኝ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ሲታይ የአሁን አመልካች ከጠቅላላ ሀብት 25% እንደሚገባዉ የሥር ፍ/ቤት በዉሳኔዉ ያረጋገጠ ሲሆን የአሁን አመልካች ኑዛዜዉ ገደብ ያለበት ነዉ በማለት እየተከራከረ እያለ አሁን ደግሞ ድርሻዬ አሁን እንዲሰጠኝ በማለት ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤት ሚች የሰጠዉን ኑዛዜ እና በግራ ቀኙ ተቀባይነት ያገኘዉን ኑዛዜ መሰረት በማድረግ ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን አመልካች በሥር ፍ/ቤት አሁን እንደቅሬታ ያቀረባቸዉን ነጥቦች ያላቀረበ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች በሕጉ አግባብ የተሰጡ ናቸዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ነዉ ለማለት ስለማይቻል የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.42390 በ17/06/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.167257 ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ለደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 120841

መስከረም 23 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ
ተክሊት ይመሰል
ክፍለጽዮን ማሞ
ሰናይት አድነው
ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ካባ ተካ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ድሪባ ዳዲ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለዉ ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአሁን አመልካች አባቷን ተክታ ሚች አያቷን ወራሽ መሆኗን መሰረት በማድረግ ያቀረበችው የውርስ ንብረት የመካፈል ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ውድቅ በመደረጉ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት መናገሻ ችሎት ሲሆን ፍ/ቤቱ ከተጠሪ የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 የተቀመጠውን የ10 ዓመት የጊዜ ወሰን መሰረት በማድረግ ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፊኒፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ብታቀርብም ፍ/ቤቱ የይግባኙ ቅሬታ መ/ሰጪን ያስቀርባል በማለት አከራክሮ ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1000/1/ መሰረት በ 3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የስር መጀመሪያ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታው የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታው መልስ ሰጪን አያስጠራም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337ን ጠቅሶ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች ታህሳስ 5/2008 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ አቤቱታ ባቀረበችበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የምትልበትን ምክንያት ገልጻ ስህተቱን የሚያርም ውሳኔ ይሰጥላት ዘንድ ጠይቃለች፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፤ ክርክሩ የተሰማው የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ የሆነው በአግባቡ ነው አይደለም የሚለው ጭብጥ መሰረት ተደርጎ ነው፡፡ በዚሁ መሰረትም ግራ ቀኙ ወገኖች ጭብጡን በማስመልከት ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ክስ የመሰረተችው የወራሽነት መብትን መነሻ በማድረግ ነው ለክስ ምክንያት የሆነው ንብረት ባለሀብት የነበሩ የአመልካች አያት የሞቱት ነሐሴ 10/1997 ዓ.ም ሆኖ አመልካች የውርስ ንብረቱ እንዲሰጣት ክስ የመሰረተችው ደግሞ መስከረም 23 ቀን 2007 ዓ.ም እንደሆነ ከመዝገቡ ተረድተናል ተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ ያቀረበው ከዚህ በመነሳት ሲሆን ስር ፍ/ቤቶችም ተመሳሳይ ምክንያት በመስጠት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ወስነዋል፡፡ አመልካች ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ትክክል አይደለም በሚል ክርክሩን በመግፋት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች በዚህ ረገድ የሰጠችው ምክንያት ሟች አያቴ የሞተችው በ1997 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ወቅት እኔ የ9 ዓመት ልጅ ነበርኩ የሚል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በወቅቱ ክስ ለማቅረብ እድሜዬ አልደረሰም ነበር ብላለች፡፡ ተጠሪም የአመልካች አያት የእኔ እናት የሞቱት በ1997 ዓ.ም ሳይሆን በ1992 ነው ከማለት በስተቀር ሟቹ ሲሞቱ አመልካች 9 አመቷ አልነበረም በሚል የቀረበው መከራከሪያ የለም፡፡

በተጨማሪም አመልካች ሟች የሞቱት በ1997 ዓ.ም ነው ስትል ተጠሪ ሟች የሞቱት በ1992 ዓ.ም ነው ቢሉም አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ከማቅረቧ በፊት መስከረም 8/2007 ዓ.ም ወራሽነቷን በፍ/ቤት ውሳኔ ስታረጋግጥ ሟች የሞቱት በ1997 መሆኑን ጭምር ማረጋገጧን ያሳያል፡፡ ከዚህ መነሻ ሲደረግ ሟች የሞቱት በ1997 ዓ.ም ሆኖ አመልካች በወቅቱ 9 አመቷ እንደነበር አመልካች ስትገልጽ ተጠሪ ያልተቃወሙ በመሆኑ ሟች በ1997 ዓ.ም መሞታቸውንና አመልካች 9 አመቷ የነበረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ስለሆነም በ2007 ዓ.ም አመልካች ወራሽነቷን ባረጋገጠችበት ጊዜና አመልካች መብቷ ላይ ክስ ባቀረበችበት ጊዜ የ19 ዓመት ልጅ መሆኗን ተረድተናል፡፡ አመልካች የወራሽነት መብቷን ለመጠየቅም ሆነ ለመጠቀም ወይም ማናቸውንም ህጋዊው ተግባራት ለማድረግ ችሎታ የሚኖራት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.198 በተገለጸው መሰረት 18 ዓመት ሲሞላት ነው፡፡ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወራሽነት መብቱን አላለ መጠን ካደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/2/ መሰረት በአሥራ አምስት ዓመት ውስጥ በፍ/ቤት ካረጋገጠ ንብረቱን ለመጠየቅ በይርጋ እንደማይታገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 57114 እና በሌሎች መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በ19 አመቷ አቤቱታ ማቅረቧ ግልጽ ሲሆን ከዚህ መነሻ ሲደረግ አመልካች በመብቷ መጠቀም ከጀመረችበት ጊዜ አሥራ አምስት ዓመት ሳያልፍ ወራሽነቷን ያረጋገጠች ስለሆነ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ሊታገድ የማይገባ ሆኖ ሳለ ስር ፍ/ቤቶችም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ እና 1845ን በመጥቀስ የአመልካች አቤቱታ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ማረም ሲገባው ሳያርም ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ብለናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉ ሳ ኔ

1. የወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት መናገሻ ችሎት በመ/ቁ. 54576 ታህሳስ 27/2007 ዓ.ም የፊኒፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24039 ሰኔ 8 ቀን 2007 ዓ.ም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 229962 ጥቅምት 8 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡
3. የወልመራ ወረዳ ፍ/ቤት መናገሻ ችሎት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ፍሬ ክርክሩን ሰምቶ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/3/ መሰረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በየደረጃው ላሉ ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ተመላሽ ይደረግ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 117435

መስከረም 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓለ. መሐመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ክፍለጽዮን ማሞ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች ፡- አቶ ተስፋዬ መኮንን …….. ጠበቃ አቶ ጥባቡ ምህረቱ ቀረበ

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሰብለ ለማ…… ቀረበ

2ኛ. ወ/ሮ ፀሐይ ለገሰ ….. አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ በፌደራል የመ/ደ/ፍ/ቤትና በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው:: የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ሆኖ ይዘቱም እናቴ ወ/ሮ አየለች ገ/ማርያም በ1989 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩና እኔ ብቸኛ ወራሽ ስሆን ተጠሪዎች የሚች የእህት ልጆች ሆነው ሳለ ሚች እናቴ ልጅ የላትም በማለት እራሳቸውን ምትክ ወራሽ በማድረግ የምትክ ወራሽነት ማስረጃ ከፍርድ ቤት ከመውሰዳቸውም በተጨማሪ የሚች እናቴ ውርስ እንዲጣራ በማድረግ የውርሱ ባለሀብት ሆነዋል፡፡ እኔም ይህንኑ እንዳወኩኝ የፍርድ መቃወሚያ የተጠሪዎችን ምትክ ወራሽነት ተቃውሜ ማስረጃቸው ተሰርዞ ለእኔ ህጋዊ ወራሽነቴ ተረጋግጦ ማስረጃ ተሰጥቶኛል ስለሆነም በዚሁ መዝገብ የፍርድ መቃወሚያ ተጠሪዎች የጸደቀላቸው የውርስ አጣሪ ሪፖርት እንዲሻርና የሚች እናቴ የውርስ ሃብት እንደ አዲስ እንዲጣራልኝ ወጪና ኪሳራም የመጠየቅ መብቴ እንዲጠበቅልኝ የሚል ነው ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎችም በሰጡት መልስ አመልካች የሚች ወ/ሮ አየለች ገ/ማርያም ልጅ መሆኑን አምነው አመልካች የሚች እናቱ ውርስ ሲጣራ የሚያውቅና በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.39542 ውርሱ ሲጣራ መቃወሚያ አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት ስለሆነ 2 ጊዜ መቃወም አይችልም በተጨማሪም ወላጅ እናቱ ከሞቱ 21 ዓመት ያለፋቸው ስለሆነ መቃወሚያው በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌደ/መጀ/ደረጃ /ፍ/ቤት የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም የሚለውን ጭብጥ መስርቶ ከመረመረ በኃላ የአመልካች እናት የሞቱት ህዳር 29 ቀን 1989 ዓ.ም ሲሆን አመልካች ወራሽነታቸውን ያረጋገጡት ጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም በመሆኑ 15 ዓመት ካለፈ በኃላ ከመሆኑም በተጨማሪ ሚች በሞቱ በ3 ዓመት ውስጥ ወራሽነታቸውን ያላረጋገጡ ስለሆነ የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታው በይርጋ ይታገዳል በማለት ሲወስን ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ እንዲያርም የይግባኝ ቅሬታ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታው መ/ሰጪን ያስጠራል በማለት ያከራከረ ቢሆንም በውሳኔ ረገድ የስር የመ/ደ/ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን በቡኩላችንም አመልካች ነሐሴ 18 ቀን 2007 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበዉን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አቅርበን ክርክሩን ሰምተናል በመቀጠልም ከግራ ቀኙ ወገኖች የቀረበውን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ሰበር ችሎት የሚመረመረው ጭብጥ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ወራሽ የሆኑበት ውሳኔ እንዲሰረዝ ሲያስደርግና የሱን ወራሽነት ሲያረጋግጥ የይርጋ መቃወሚያ ሳይነሳ ታልፎ የተጠሪዎችን ወራሽነት አሰርዞና የሱን ወራሽነት አረጋግጦ የውርስ ማጣራት ሂደቱ ላይ በይርጋ ይታገዳል የተባለበትን አግባብነት ለማጣራት ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበው የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካች አቤቱታ በይርጋ ይታገዳል ማለታቸው ተገቢ ነው ሲሉ አመልካችም በበኩላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ በመልስ መልሳቸው አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ መረዳት የተቻለው የአመልካች እናትና የተጠሪዎች አክስት ወ/ሮ አየለች ገ/ማርያም ህዳር 29 ቀን 1989 ዓ.ም ህይወታቸው ያለፈ መሆኑን የአሁን አመልካች የእናቱን ወራሽነት ጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም ያሳወጀ መሆኑን ተጠሪዎች ሚያዚያ 15 ቀን 2005 ዓ.ም ሚች ልጅ የላቸውም በማለትና የእናታቸው ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን ማስወሰናቸውንና መጋቢት 9 2005 ዓ.ም የሚች ወ/ሮ አየለች ውርስ ይጣራልን ብለው ባቀረቡት አቤቱታ ፍርድ ቤቱ በ2/9/2005 ዓ.ም የውርስ አጣሪው ያቀረበውን ሪፖርት በማጽደቅ መወሰኑን ነው፡፡ በመቀጠልም የአሁን አመልካች በሐምሌ 22 ቀን 2005 ዓ.ም ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪዎች የወራሽነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታ ሲያቀርቡ ሚች ልጅ የላትም ያሉት በሐሰት ነውና እኔም ልጅና ወራሽ ስለሆንኩኝ ለእነሱ የተሰጠው የወራሽነት ማረጋገጫ ይሰረዝልኝ በማለቱ ፍ/ቤቱ አጣርቶ ጥቅምት 4 ቀን 2006 ዓ.ም የተጠሪዎችን የወራሽነት ማስረጃ በመሰረዝ መወሰኑን ነው፡፡

በመቀጠልም የአሁን አመልካች ተጠሪዎችን አቅርበው ያስወሰኑት የውርስ ሀብት ባለቤትነት ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ማቅረቡንና ተጠሪዎች የአመልካች አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ ነው ማለታቸውን የስር ፍርድ ቤቶችም ክርክሩ በይርጋ ይታገዳል ማለታቸውን ነው፡፡

ይህንን መነሻ ስናደርግ የተጠሪዎች ወራሽነት ማረጋገጫ የተሰረዘ መሆኑና በይግባኝ ያለመሻሩ ግልጽ እስከሆነ ድረስ ከወራሽነት ውሳኔው ጋር ተያይዞ የቀረበው የተሰጠ ውሳኔ ይሰረዝልኝና የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ በይርጋ ይታገዳል በማለት የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲወስን የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ብለናል በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 42445 በቀን 9/1/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 163312 ግንቦት 27 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች የቀረበው የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ በይርጋ አይታገድም ባልነው መሰረት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን አቅርቦ የግራ ቀኙን የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1/ መሰረት ይመለስ ብለናል ይጻፍ፡፡
3. ለዚህ ውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊነት ከፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጣው መ/ቁ.42445 የሆነ መዝገብ ይመለስ፡፡
4. ለዚህ ፍ/ቤት ክርክር ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ወጪ ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዝግቷል ተመላሽ ይደረግ ::

ሩ/ለ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.110680

ጥቅምት 30 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-ወ/ሮ ጽጌረዳ በቀለ

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ፍቅርተ በቀለ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ውርስን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረውም የሟች አቶ በቀለ ካሣ ውርስ ይጣራልኝ ሲሉ የአሁኗ አመልካች በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡የአሁኗ ተጠሪም በጉዳዩ በጣልቃ ገብነት ተከራክረዋል፡፡ግራ ቀኙ ከተለያዩ እናቶች የተወለዱ የአንድ አባት ልጆች መሆናቸውን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ፍርድ ቤቱም በጣልቃ ገቧ አቤቱታ ላይ የአመልካቿን አስተያየት ከተቀበለ በኃላ ጉዳዩን ወደ ውርስ አጣሪ የመራው ሲሆን አጣሪዋም ውርሱን ካጣሩ በኃላ አከራካሪ ሆኖ የቀረበውን በጉለሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 3 የሚገኝ በቤት ቁጥር 460 የሚታወቀውን ቤት ሟች አቶ በቀለ ካሣ ግማሹ የጣልቃ ገቧ እናት የወ/ሮ በቀለች ጎሽሜ ሆኖ ግማሹ ግን የእርሳቸው መሆኑን ገልጸው የራሳቸውን ድርሻ በ19/11/1997 ዓ.ም. በአዋዋይ ፊት በተደረገ የድርሻ መልቀቅ ውል ለጣልቃ ገቧ እንደለቀቁ ከቀረቡት ማስረጃዎች አጣሪዋ መገንዘብ መቻላቸውን፣ይሁን እንጂ የቤቱን አጋማሽ ከእናታቸው በውርስ ያገኙት ሆኖ ቀሪው ግማሽ ደግሞ በሟች አባታቸው በተደረገላቸው የድርሻ መልቀቅ ውል መሰረት የቤቱን ስመ ሀብት ወደ ራሳቸው አዛውረው እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ በአንድ በኩል የአሁኗ ተጠሪ መከራከራቸውን፣በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች የድርሻ መልቀቅ ውሉ ተደረገ የተባለው አመልካችን ሆነ ብሎ ከውርስ ለመንቀል በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው እና ሟች የድርሻ መልቀቅ ውሉን አደረጉ ከተባለ በኃላም ቤቱን በስማቸው አድርገው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቀሙበት እንደቆዩ በመግለጽ የድርሻ መልቀቅ ውሉ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ መከራከራቸውን ገልጸው በጉዳዩ ላይ ፍርድ እንዲያርፍበት በሚል፣ እንዲሁም ከቤቱ ኪራይ የተገኘው ገንዘብ የውርስ ሀብት ነው የሚል እና ሌሎችም ፍሬ ነገሮች የተገለጹበትን በ18/09/2005 ዓ.ም. የተዘጋጀ ሪፖርት አቅርበዋል።

ፍርድ ቤቱም በሪፖርቱ ላይ የግራ ቀኙን አስተያየት ተቀብሎ ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ የቤቱ አጋማሽ በእናታቸው በኩል ለተጠሪዋ በውርስ የተላለፈ ሆኖ ቀሪውን ግማሽ ደግሞ ሟች በድርሻ መልቀቅ ውሉ መሰረት ለተጠሪዋ ማስተላለፋቸው የተረጋገጠ በመሆኑ ቤቱ የውርስ ሀብት አካል አይደለም፣ቤቱ የውርስ ሀብት አይደለም ከተባለ ደግሞ ከቤቱ የተገኘው የኪራይ ገንዘብም የውርስ ሀብት ሊሆን ስለማይችል አጣሪዋ ከዚሁ ቤት የተገኘው የኪራይ ገንዘብ የውርስ ሀብት ነው በማለት ሪፖርት ማቅረባቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ ሪፖርቱን በዚህ አግባብ በማሻሻል በመዝገብ ቁጥር 40838 በ29/09/2006 ዓ.ም. ውሳኔ የሰጠ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።

አመልካቿ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በመዝገብ ቁጥር 154581 በ06/04/2007 ዓ.ም. ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመሮምሮ በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ቤት የውርስ ሀብት ሳይሆን የተጠሪዋ የግል ሀብት ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች ተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ሟች በ19/11/1997 ዓ.ም. ለተጠሪ ጥቅም አድርገውት የነበረውን ስጦታ በ26/12/1997 ዓ.ም. ባደረጉት ኑዛዜ የተኩት እና ኑዛዜው ደግሞ አመልካችን ከውርስ የነቀለ ነው ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 88358 በ30/11/2007 ዓ.ም. ከተሰጠው ገዥ ውሳኔ አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል።

በዚህም መሰረት የአንድ ሰው መብትና ግዴታ ለተወላጆቹ በውርስ ሊተላለፍ የሚችለው በሟቹ ሞት ምክንያት የሚቋረጡ ካልሆነ በቀር ሟቹ በሞተበት ቀን የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች ስለመሆናቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 (2) ድንጋጌ ይዘት ያመለክታል።በተያዘው ጉዳይ ሟች የአከራካሪው ቤት አጋማሽ ድርሻ የሟች ባለቤታቸው ማለትም የአሁኗ ተጠሪ እናት መሆኑን በማረጋገጥ በቤቱ ላይ ያላቸውን ግማሽ ድርሻ በ19/11/1997 ዓ.ም. በአዋዋይ ፊት በተደረገ የድርሻ መልቀቅ ውል ለአሁኗ ተጠሪ ያስተላለፉ ስለመሆኑ እና በሞት የተለዩትም በ28/08/2004 ዓ.ም. ስለመሆኑ በአመልካቿም ያልተካደ እና በክርክሩም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው።ሚች በአከራካሪው ቤት ላይ የነበራቸውን ግማሽ ድርሻ አስቀድመው በ1997 ዓ.ም. ለተጠሪዋ በውል ማስተላለፋቸው ከተረጋገጠ ደግሞ ይህ ቤት በሞቱበት 2004 ዓ.ም. የእርሳቸው ንብረት ነበር ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም።

አመልካቿ አጥብቀው የሚከራከሩት ሟች አድርገውት የነበረው የድርሻ መልቀቅ ውል ከአንድ ወር በኃላ አካባቢ በ26/12/1997 ዓ.ም. በተደረገ ኑዛዜ የተተካ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 900 እና 901 ድንጋጌዎች መሰረት የድርሻ መልቀቅ ውሉ ውጤት እንደሌለው መቆጠር አለበት በማለት መሆኑን የሰበር አቤቱታቸው ይዘት ያመለክታል።በቁጥር 900 የተመለከተው ድንጋጌ በኑዛዜ የተሰጠን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ተናዛዡ ፈቅዶ ለሌላ ሰው ያስተላለፈ በሆነ ጊዜ አስቀድሞ ተደርጎ የነበረው ኑዛዜ ፈራሽ እንደሚሆን የሚደነግግ ሲሆን በቁጥር 901 የተመለከተው ድንጋጌ ደግሞ አንድ ተናዛዥ አስቀድሞ አንድ ኑዛዜ ካደረገ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ ሌላ ኑዛዜ አድርጎ መገኘቱ የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤት የሚመለከት ነው።በተያዘው ጉዳይ ኑዛዜው የተደረገው ከድርሻ መልቀቅ ውሉ በኃላ እንጂ በፊት ባለመሆኑ እና ሟች ኑዛዜ አድርገዋል የተባለውም አንድ ጊዜ ብቻ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ በቁጥር 900 እና 901 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው አይደሉም።ሟች በ26/12/1997 ዓ.ም. ባደረጉት ኑዛዜም ቀደም ሲል አድርገውት የነበረው የድርሻ መልቀቅ ውል እንደተጠበቀ መሆኑ ከመገለጹ ውጪ ሟች የድርሻ መልቀቅ ውሉን በኑዛዜው የመተካት ሀሳብ የነበራቸው መሆኑን የሚጠቁም እንዳልሆነ በዚሁ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 88358 ውስጥ ተያይዘው ከሚገኙት የድርሻ መልቀቅ ውል እና የኑዛዜ ሰነዶች ይዘት ተገንዝበናል። በመሆኑም ሟች ቀደም ሲል አድርገውት የነበረውን የድርሻ መልቀቅ ውል በኑዛዜው እንደተኩት ተደርጎ በማስቀረቢያ ትዕዛዙ ላይ የሰፈረው ፍሬ ነገር የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

የኑዛዜ ይሰረዝልኝ ጉዳይን አስመልክቶ በግራ ቀኙ መካከል በመዝገብ ቁጥር 88358 በነበረው ክርክር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በ30/11/2007 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ ግራ ቀኙ ሲከራከሩ የነበረው የኑዛዜ ሰነዱን ብቻ መሰረት በማድረግ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ከሕጉ አንጻር መርምሮ በኑዛዜው ለአሁኗ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ቤት በተሰጠበት ሁኔታ ለአመልካቿ ብር አንድ ሺህ ብቻ መሰጠቱ ከውርስ እንደተነቀሉ የሚያስቆጥር በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 938 እና 939 ድንጋጌዎች መሰረት ግራ ቀኙ የአከራካሪው ቤት እኩል ወራሽ ናቸው በሚል በስር ሁለቱ የበላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል።በመዝገብ ቁጥር 88358 በነበረው ክርክር የአሁኗ አመልካች መቃወሚያ ያቀረቡትም ሆነ በየእርከኑ ባሉ ፍርድ ቤቶች አከራካሪ ጭብጥ ሆኖ ቀርቦ የነበረው የኑዛዜው ዋጋ እና ሕጋዊ ውጤት እንጂ የድርሻ መልቀቅ ውሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጋዊነት ጉዳይ ጭምር አይደለም።በክርክሩ አመልካች የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ "...በሕግ አግባብ የተደረገ ስጦታ አለ የሚሉ ከሆነ በዚህ ረገድ የሚያቀርቡትን ክርክር ይህ ውሳኔ አያግደውም.."በሚል ተፈጻሚነት ባለው የውሳኔው ክፍል በተራ ቁጥር ሁለት ስር በግልጽ የሰፈረውም በዚሁ ምክንያት ነው።በመሆኑም በመዝገብ ቁጥር 88358 የተሰጠው ውሳኔ በስጦታ /በድርሻ መልቀቅ/ ውል ላይ በቀጣይ ሊነሳ የሚችለውን ክርክር ታሳቢ አድርጎ የተሰጠ እንጂ የድርሻ መልቀቅ ውሉ በኑዛዜ ስለተተካ ሕጋዊ ውጤት የለውም ከሚል ድምዳሜ ላይ የተደረሰበት አይደለም።አመልካቿ በሕጉ አግባብ ያላፈሩት እስከሆነ ድረስ ደግሞ የድርሻ መልቀቅ ውሉ ዋጋ የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቶች የቤቱ አጋማሽ በእናት መስመር በውርስ ለተጠሪዋ የተላለፈ ሆኖ ቀሪውን ግማሽ ደግሞ የግራ ቀኙ አባት በ19/11/1997 ዓ.ም. በአዋዋይ ፊት በተደረገ የድርሻ መልቀቅ ውል ለአሁኗ ተጠሪ ያስተላለፉ በመሆኑ ቤቱ የሟች አቶ በቀለ ካሣ የውርስ ሀብት አይደለም በሚል የደረሱበት ድምዳሜ እና ይህንኑ ድምዳሜ መሰረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም።አከራካሪውን ቤት የግራ ቀኙ አባት የአሁኗን ተጠሪ እናት ከማግባታቸው በፊት ያፈሩት ነው ከማለት በቀር በእናት መስመር ከቤቱ የውርስ ድርሻ አለኝ በማለት አመልካቿ በስር ፍርድ ቤቶችም ሆነ በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡት ክርክር አለመኖሩን ተገንዝበናል።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪዋን ሪፖርት በማሻሻል በመዝገብ ቁጥር 40838 በ29/09/2006 ዓ.ም. የሰጠው እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 154581 በ06/04/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል።
2. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
4. ውሳኔ ያገኘ ሰለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

<u>የሐሳብ ልዩነት</u>

አብላጫው ድምጽ የቤቱ አጋማሽ በእናት መስመር በውርስ ለተጠሪ የተላለፈ ሆኖ ቀሪውን ግማሽ የግራቀኙ አባት ሐምሌ 19 ቀን 1997 ዓ.ም በአዋዋይ ፊት በተደረገ የድርሻ መልቀቅ ውል ለአሁን ተጠሪ ያስተላለፉ በመሆኑ ቤቱ የሟች አቶ በቀለ ካሳ የውርስ ሀብት አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ሆኖም ሟች ሐምሌ 19 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገ የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት አከራካሪውን ቤት ከሟች ባለቤታቸው ወ/ሮ በላይነሽ ጎሽሜ ጋር በጋራ ያፈሩት መሆኑን በመጥቀስ ድርሻቸውን ለተጠሪ የለቀቁ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም ሟች ይህንኑ ቤት በተመለከተ ነሐሴ 26 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረጉት ግልጽ ኑዛዜ ድርሻቸውን ለተጠሪ የተናዘዙላት መሆኑን የኑዛዜው ሰነድ ያሳያል፡፡ በዚህ የኑዛዜ ሰነድ ላይ ክርክር ተደርጎበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 88358 ሐምሌ 30 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ አመልካችን በተዘዋዋሪ መንገድ በዝምታ ከውርስ የነቀለ በመሆኑ አመልካች ከጠቅላላ ኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ በመሆን የውርስ ንብረቱን ሊከፋፈሉት ይገባል በማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆኑን ጠቅሶ ውሳኔውን በማጽናት ተጠሪ በሕግ አግባብ የተደረገ ስጦታ አለ የሚሉ ከሆነ በዚህ ረገድ የሚያቀርቡትን ክርክር ውሳኔው አያግደውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ሟች ነሐሴ 26 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ሐምሌ 19 ቀን 1997 ዓ.ም ያደረጉት የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት የተጠበቀ ነው በማለት የገለጹ ቢሆንም የሟች ኑዛዜ አመልካችን ከውርስ የነቀለ ነው በማለት አመልካች ከጠቅላላ የኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል ወራሽ እንድትሆን በዚሁ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ ሟች በቤቱ ላይ አስቀድሞ ያደረጉት የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት ውጤት ያበቃለት ነው፤ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች እና ተጠሪ እኩል ወራሽ ናቸው በማለት በሰጠው ውሳኔ መሰረት የሟች ድርሻ ሊከፋፈል ይገባል በማለት ስማችን በተ.ቁ. 3 እና 5 ላይ የተጠቀሰው ዳኞች አብላጫው ድምጽ ከደረሰበት ድምዳሜ በሃሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባንክና ኢንሹራንስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 88135

ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አምልካች፡- ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ (አ.ማ) - ነ/ፊጅ ወርቅነህ ዘውዱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ነፃነት ሀቤቤ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፤

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ተሽከርካሪ የሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የተሰጠ የመድን ሽፋን ኃላፊነትን የሚመለከት ነው፡፡ ከስር ፍርድ ቤት በዚህ ክርክር ወ/ሮ አለምነሽ ገብረ ማርያም በራሷና ሞግዚት በሆነችላቸው እነ ህፃን አዲስ ብርሃኑ(አራት ሕፃናት) ስም ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ አመልካች ደግሞ ሶስተኛ ወገን ተከራካሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ወ/ሮ አለምነሽ ገብረማርያም በተጠሪ ላይ ያስቀረበችው ክስ ነው ወ/ሮ አለምነሽ ገብረማርያም የተጠሪ ንብረት ቁጥር 3-178887 የሆነ መኪና የልጆች አባት የሆነውን አቶ ብርሃኑ ጥላሁንን የግጭት ጉዳት አድርሶበታል ባለቤቱና የልጆቹ አባት በአደጋው በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ስለሞተ በእኔና ልጆቹ በመተዳደሪያ እረገድ ለደረሰብን ጉዳት ብር 541,538 (አምስት መቶ አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር) ካሳ እንዲከፈል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርባ የተጠየቀውን የካሳ መጠን በመቃወም ክርክር ያቀረበች ሲሆን አመልካች የመድን ሽፋን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠ በመሆኑ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ እንዲሰጥላት ጠይቃለች አመልካች በክርክሩ ገብቶ የተጠሪ መኪና በሶስተኛ ወገን ላይ ስሚያደርሰው ጉዳት ለአንድ ሰው እስከ ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑን ከገለፀ በኃላ ተጠሪ በመድን ታሳቢ መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን የማሳወቅ ግዴታዋን አልተወጣችም፡፡ ስለዚህ በመድን ውሉ መሰረት ሽፋን እንድሰጥ አልገደድም፡፡ በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ ለወ/ሮ አለምነሽ ገብረማርያና ልጆቻቸው ብር 222,538 ወይም /ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ስምንት እንድትከፍል ወስኗል፡፡ ከዚህ የካሳ ገንዘብ አመልካች ብር 40.000 (አርባ ሺህ) እንዲከፍል ወስኗል፡፡

2. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አደጋው የደረሰ መሆኑን በአስር ቀን ውስጥ ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ በመድን ውሉ ገብታለች፡፡ ተጠሪ በ10 ቀን ውስጥ አደጋ የደረሰ መሆኑን ያላሳወቀች በመሆኑ አመልካች በመድን ውል መሠረት ብር 40.00 የመክፍል ግዴታ የለበትም የበታች ፍርድ ቤቶች በግልፅ የተቀመጠውን የውል ቃል በመተላለፍ አመልካች በመድን ውል መሠረት ኪሳራውን እንዲጋራ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡
3. ተጠሪ ሚያዝያ 21 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈው መልስ ተጠሪ በአስር ቀን ውስጥ አደጋው የደረሰ መሆኑን ለአመልካች አለማሳወቁ አመልካች በመድን ውል መሰረት ለሶስተኛ ወገኖች የመድን ሽፋን የሰጠበትን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነቱን አያስቀርም፡፡ ስለሆነም የአመልካች ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክራለች አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፤
4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆነ እኛም አመልካች የመድን ሽፋን የሰጣት የመለያ ቁጥር 3-17887 የሆነችው መኪና በሚች ብርሃን ጥላሁን ላይ ባደረሰው የሞት እደጋ ተጠሪ ከተወሰነባት የካሳ ገንዘብ ውስጥ አመልካች ብር 40,000 (አርባ ሺህ) ለሚች አቶ ብርሃን ጥላሁን ሚስትና ልጆች እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተጠሪ መኪና በሌላ ሰው አካል ወይም ህይወት ላይ ስሚያደርሰው አደጋ እስከ ብር 40,000 (አርባ ሺህ) ኃላፊነቱን ለመጋራት የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጣት መኪና በሚች ብርሃን ጥላሁን ላይ የሞት አደጋ ማስከተሏና ተጠሪ ለጉዳቷ ኃላፊ መሆኗ በፍርድ ቤት ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የሚከራከረው በሰጠሁት የመድን ሽፋን መሰረት ገንዘቡን ለከሳሾች የምከፍለው ተጠሪ በመድን ውሉ መሰረት በአስር ቀን ውስጥ አደጋው የደረሰ መሆኑን ብታሳውቀኝና ግዴታዋን ብትወጣ ነበር፡፡ ተጠሪ የውል ግዴታዋን ያልተወጣችና በአስር ቀን ውስጥ አደጋው መድረሱን ያላሳወቀችው በመሆኑ የመድን ሽፋን የሰጠሁበትን ገንዘብ ለከሳሾች የመክፈል ግዴታ የለብኝም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ አደጋው የደረሰ መሆኑን በአስር ቀን ውስጥ ለአመልካች ለማሳወቅ የውል ግዴታ የገባች መሆኑን በመካድ ያቀረበችው ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ የምትከራከረው እኔና አመልካች በቅድመ ሁኔታነት በመድን ውል የተዋዋልነው ሃይለ ቃል በህግ ያልተፈቀደ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ነው፡፡

6. ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር ተዋዋዮች ሁሉ የሚዋዋሉበትን ጉዳይ የመወሰን መብት ያላቸው መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1711 ተደንግጓል፡፡ የመድን ሥራ የሚሰሩ የመድን ኩባንያዎች በመድን ፖሊሲ ውስጥ ፖሊሲውን ተጠያቂነትን አያስከትልም ወይም በፖሊሲው መሰረት የካሳ ክፍያ ጥያቄ መነሻ የሆነው ክስተት ከደረሰ በኃላ የተወሰነ ድርጊት ከተፈፀመ ወይም ሳይፈጸም ከቀረ ኃላፊነቱ ቀሪ ይሆናል የሚል የውል ሁኔታ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑ ስለተሸከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ዋስትና የወጣው አዋጅ ቁጥር 559/2000 በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ የህግ ድንጋጌ አንፃር ሲታይ አመልካች ተጠሪ አደጋው ከደረሰ በኃላ በአስር ቀን ውስጥ ካላሳወቀችኝ በመድን ፖሊሲው መሰረት ገንዘቡን ለተጎጂዋ (ለከሳሾች) የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር ከላይ ይዘቱ የተገለፀውን የህግ ድንጋጌ የሚጥስና የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች በመድን ፖሊሲው መሠረት ብር 40,000 (አርባ ሺህ) ብር ለከሳሾች እንዲከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 16 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው የፅሁፍ ትዕዛዝ ተነስቷል ይባፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 117608

መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተክሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሠናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነገረ ፈጅ ጀሲያክን ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኖሌ ካባ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ተወካይ ተስፋዬ ተሾመ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመድን ዋስትና ክፍያ የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 29030 በአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ንብረትነቱ የተጠሪ ለሆነው ሰሌዳ ቁጥር 4-02912 ኦሮ በውል ቁጥር 5041112020046113 ተጠሪ ባቀረበው ጥያቄ የኢንሹራንስ ዋስትና የብር 38,431.80 መስጠቱን የመድን ዋስትናውም በንግድ ህጉ መሠረት ተሟልቶ ተፈርሞ ከየካቲት 9 ቀን 2005 ዓ.ም እስከ የካቲት የ9 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ የሚቆይ የአንድ ዓመት ዋስትና ተጠሪ የገዛ ቢሆንም የሚፈለግበትን ክፍያ እንዲከፍል ሲጠየቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ አመልካች ክስ ለማቅረብ እንደተገደደ በመግለጽ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 24704 ከዚህ ጉዳይ ጋር ተመሳሰይነት ባለው ጉዳይ አስገዳጅ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ተጠሪ የሚፈለግበትን ክፍያ እንዲፈጽም እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ የመድን ዋስትና ከአመልካች ጋር የገባ መሆኑን ሳይክድ ንብረትነቱ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የሆነ መኪና በኦሮሚያ ኢንሹራንስ ኩባንያ ስር ውሉ እንዲገባ ከኦሮሚያ ምክር ቤት በቀን 29/11/2005 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ውሳኔ ስለተላለፈ ውሉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊቀጥልበት አይገባም፣ ተጠሪም አያስገድድም። በዚህ ውል ግዴታም የተፈፀመልኝ ነገር የለም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆንለት ተከራክሯል።

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ. 24704 የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ከተያዘው ጉዳይ ተመሳሳይነት እንደሌለው፣ በንግድ ሕግ አንቀጽ 664 መሠረት ክፍያ ለኢንሹራንስ ከተከፈለ በኋላ ቀጥሎ ቢሆንም ኖሮ ውል ተቀባይ ጉዳት በንብረቱ ላይ የሚደርስ ከሆነ ውሉ እንደ አዲስ መቀጠል እንዳለበት የውሉን ቀጣይነት ለማረጋገጥ እንጂ አመልካች በፈለገበት ጊዜ ከሶ ክፍያ ማስፈጸም ወይም ውል እንዲያቋርጥ ገደብ የሌለው መብት ለማጎናፀፍ አይደለም። አመልካች በዚህ ውል የሚኖሩት መብቶች ካሉ ክፍያ ፈፀሞ አንድ ወር ካለፈ ውሉ እንደተቋጠ ስለሚቆጠር የሚመጣው ኃላፊነት ለመውሰድ አይገደድም። በዚህ ክርክር ውስጥ ደግሞ ተጠሪም ክፍያ ያቋረጠው ከዓመት በላይ ከመሆኑም በላይ የመድን ውል ጊዜ ገደቡም በቀን 09/06/2006 ዓ/ም የተጠናቀቀ ስለሆነ ተጠሪ የመድን ዋስትና ውል ገንዘብ እንዲከፍል የሚገደድበት ሁኔታ ስለሌለ የቀረበውን ክስ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 33/2/ መሠረት ውድቅ በማድረግ ተጠሪ በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል።

አመልካች በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ሠረታዊ ይዘትም የተጠሪ ንብረት የሆነውን የሰሌዳ ቁጥር 4-02912 ኦሮ አምቡላንስ ተሽከርካሪ ለአንድ ዓመት የሚቆይ በዱቤ ማስታወሻ የመድን ሽፋን የሰጠ ስለመሆኑ የአርቦን ክፍያ ጊዜው በስምምነት ያልተገለጸ ስለሆነ መድን ሰጪ መብቱን ያለ ምንም ቅደመ ሁኔታ በ2 ዓመት ውስጥ ከሶ መጠየቅ እንደሚችል የውል ግዴታውም ተጠሪ ሽፋን ለተሰጠበት ጊዜ የ11 ወር ከ11 ቀን አርበን ተሰልቶ ሊከፈል እንደሚገባ የሚያስገደድ ስለመሆኑ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ተሽሮ ተጠሪ የመድን ሽፋኑ ለተገለገለበት ጊዜያት አርበን ተሰልቶ እንዲከፈለው እንዲወሰን የሚጠይቅ ነው። አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።

ይህ ችሎትም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ግራ ቀኙን ሐምሌ 27/2008 ዓ/ም በቃል ከማነጋገሩ በተጨማሪ በተጠሪ ተፃፉ የተባሉትን የኢንሹራንስ ውል ማቋረጫ ደብዳቤዎች ወደ አመልካች መቼ ገቢ እንደተደረጉ ለመለየት ደብዳቤዎቹን በማስቀረብ ተመልክቷል።

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ከላቸው ድንጋጌዎች ጋር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያሻው ዓብይ ነጥብ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ለአመልካች የመድን ውሉ ሽፋን ለመክፈል አይገደድም በማለት የሰጡት ውሳኔ በሕጉ አግባብነት ወይስ አይደለም? የሚል ሆኖ አገኝቶታል፡፡

ከስር የክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች እና ተጠሪ ለአንድ ዓመት ጸንቶ የሚቆይ የመድን ዋስትና ውል ስምምነት ያደረጉ ስለመሆናቸው ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የመድን ዋስትና ከአመልካች ጋር መግባቱን ላይክድ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውሳኔ መሠረት በክልሉ ያሉ የመንግስት መኪናዎች ከኦሮሚያ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር ውል እንዲገቡ በመወሰኑ ከአመልካች ጋር የነበረውን ግንኙነት ማቋረጡን በስር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ካቀረበው ክርክር ተረድተናል፡፡ አመልካች በበኩሉ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የንግድ ህግ ቁጥር 666 የተረጎመበት አግባብ ተገቢ አለመሆኑን፤ የኢንሹራንስ ውል ማቋረጫ ደብዳቤ ሁለት ጊዜ ቢፅፉም በአንድ ቀን ጥር 22/2006 ዓ/ም የደረሰው ስለመሆኑ፤ የአርቦን ክፍያውም በዱቤ ማስታወሻ የተሰጠ እንጂ ከመጀመሪያውኑ የመክፈያ ቀን ያልተቆረጠለት ስለመሆኑ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ተገቢነት እንደሌለው መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አመልካች የአርቦን ክፍያው በአንድ ወር ጊዜ ባለመጠየቁ ውሉ እንደተቋረጠ ስለሚቆጠር ክፍያውን መጠየቅም ሆነ ጉዳት ከደረሰም ኃላፊነት ለመውሰድ አይገደድም ከሚል ድምዳሜ ላይ መደረሱን የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ አደረጉት የተባለው የመድን ውል ቆይታው አንድ ዓመት እንደነበር አላከራከረም ተጠሪ አመልካች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የአርቦን ክፍያውን መጠየቅ ነበረበት የሚል ክርክር ያቀረበ ቢሆንም የግራቀኙ ስምምነት ክፍያው በአንድ ወር ካልተጠየቀ ቀሪ እንደሚሆን ስለመስማማታቸው በህግ የተደገፈ ክርክር አላቀረበም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገው የመድን ውል ስምምነት በዱቤ ማስታወሻ የተሰጠ ስለመሆኑ ካቀረበው ክርክር ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ በግራ ቀኙ የነበረው የመድን ውል ስምምነት በዱቤ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን በመካድ ያቀረበው ህጋዊ ክርክር የለም፡፡ የግራ ቀኙ ግንኙነት በብድር /ዱቤ/ ላይ የተመሰረተ ከሆነ ደግሞ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የታወቀ ጊዜ የተቆረጠለት የአርቦን ክፍያ እንደሆነ በመውሰድ የንግድ ህግ ቁጥር 666 (4) መሰረት በማድረግ ከአንድ ወር በኋላ ክፍያ መጠየቅ እንደማይቻል ደምድሞ የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጉ በሕጉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ሌላ የክርክር ነጥብ እና በሥር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘው ውል የተቋረጠበት ጊዜ የተመለከተ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የክልሉ መንግስት በሰጠው ውሳኔ መሠረት የክልሉ መኪናዎች ከክልሉ እንሹራንስ ኩባንያ ጋር የመድን ውል እንዲገቡ ያዘዘ በመሆኑ የውል ማቋረጫ ደብዳቤ በቀን 12/11/2005

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና በ20/05/2006 ዓ/ም ለአመልካች ጽፈናል የሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ከተጠሪ የተባሉ ደብዳቤዎች ገቢ የሆኑት ጥር 22/2006 ዓ/ም መሆናቸውን አጥብቆ ተከራክሯል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀርቦ የተመለከታቸው ሁሉቱም ደብዳቤዎች ለአመልካች ጽ/ቤት ገቢ የሆኑት ጥር 22 ቀን 2006 ዓ/ም መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች ተላኩ የተባሉ ደብዳቤዎች በ12/11/2005 እና በ20/5/2006 የተባሉ ስለመሆናቸው ግልጽ ቢሆንም ለአመልካች በተባሉበት ቀን ገቢ ስለመሆናቸው በተጠሪ በኩል የቀረበ ማረጋገጫ የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ ውሉ እንዲቋረጥ በወቅቱ ጠይቀናል በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በአመልካች የተጠየቀው የአርቦን ክፍያ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ የግራ ቀኙ ስምምነት የንግድ ሕጉ መሠረታዊ ይዘትና ዓለማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

ተጠሪ በዱቤ ሽፋን ለተሰጠው ተሽከርካሪ መክፈል ያለበት አርቦን መኖሩ ከተረጋገጠ ቀጥሎ መታየት ያለበት የአርቦን መጠኑ ነው፡፡ በግራ ቀኙ ስምምነት መሰረት በአመት መከፈል ያለበት የገንዘብ መጠን 38,431.80 መሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪ ውል ማቋረጡን ያሳወቀው የውል ዘመኑ ከመጀረ ከ11 ወር ከ11 ቀን በኃላ ስለመሆኑ አመልካች ካቀረበው የሰበር አቤቱታ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ በሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው መልስ በአመልካች የተጠቀሰው ጊዜ ተገቢ አለመሆኑን በመካድ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ተጠሪ የተገለገለበት የ11 ወር ከ11 ቀናት የአርቦን ክፍያ መጠን 36,403.45/ ሰላሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ ሶስት ከአርባ አምስት ሳንቲም /መሆኑን አመልካች በሰበር አቤቱታ አመልክቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በሰበር ችሎት በሰጠው መልስ ከላይ የተገለፀውን መጠን ገንዘብ አለመሆኑን በግልጽ ያቀረበው ክርክር የለም በተጠሪ በኩል በግልጽ ያልተካዳ ፍሬ ጉዳይ እንደታመነ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 83 እና 235 ያስገነዘቡናል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ ውሉን እስከ ተቋረጠበት ጊዜ ድረስ ለተገለገለበት የኢንሹራንስ ጊዜያት አርቦን ተሰልቶ የ11 ወር ከ11 ቀናት ብር 36,403.45 የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብለናል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የመድን ውል ሽፋን ተጠሪ ለተገለገለበት የኢንሹራንስ ጊዜያት በውሉ መሰረት ተገቢ የአርቦን ክፍያ መክፈል እያለበት ተጠያቂ ሊሆን አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሽረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 29030 በ19/06/2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 205391 በ25/9/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል ። ይፃፍ።
2. ተጠሪ ለተገለገለበት የኢንሹራንስ ጊዜያት አርቦን የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል። ተጠሪ ለአመልካች ብር 36,403.45 (ሰላሳ ስድስት ሺ አራት መቶ ሶስት ከአርባ አምስት ሳንቲም) ይክፈል ብለናል። ይፃፍ።
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 104544

ግንቦት 25 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ዕጋብ ገብሩ
2. ቄስ ካህሳይ ገ/ማርያም
3. ወ/ሮ ገርገስ ገ/አናንያ
4. ወ/ሮ አማረች ወላይ

} የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ በተጀመረበት የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሽሬ እንዳስላሴ ምድብ ችሎት ተከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በሰጠው የመድን ሽፋን መሰረት ለክሱ ኃላፊ መሆኑ በመረጋገጡ ከሳሾች ለነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች በድምሩ ብር 350,760.31 (ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ከሰላሳ አንድ ሳንቲም) ካሳ እንዲከፍል በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 16952 በ25/03/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63314 በ26/09/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎቹ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት ንብረትነቱ የ1ኛ ተጠሪ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኢት-312179 ማርቸዲስ የጭነት መኪና የ4ኛ ተጠሪ ልጅ በሆነው አቶ ተከስተ ካህሳይ ሲሸከረክር በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ ሾፌሩ እና በጋቢናው ውስጥ ተሳፍሮ የነበረ አቶ ኃይለማርያም ካህሳይ የሚባል የ2ኛ እና የ3ኛ ተጠሪዎች ልጅ መሞታቸውን እና በተሸከርካሪው ላይም ከፍተኛ ጉዳት የደረሰ መሆኑን፣ተከሳሽ ድርጅት በተሸከርካሪው ላይ ለሚደርስ ጉዳትም ሆነ በተሳፋሪ እና በአሽከርካሪው ላይ ለሚደርስ የሞት አደጋ የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑን፣ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከሟች ልጆቻቸው ያገኙት የነበረው ድጎማ የቀረባቸው መሆኑን እና ተከሳሽ ድርጅት ተሽከርካሪውን ከወደቀበት ያነሳ ቢሆንም ለማስጠገንም ሆነ የማስጠገኛ ወጪ ለመክፈል እንዲሁም ካሳ ለመክፈል ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን እና በዚህም ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪውን በራሳቸው ወጪ ያስጠገኑ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ፡-

1. 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ ለተሽከርካሪው ማስጠገኛ የወጣውን ብር 220,760.31 እና ተሽከርካሪው ለጥገና በቆመበት ጊዜ ለተቋረጠ ጥቅም ብር 120,000 በድምሩ ብር 340,760.31፣
2. 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ በልጃቸው ሞት ምክንያት የተቋረጠውን ገቢ በመድን ሽፋኑ መጠን ብር 40,000፣
3. 4ኛ ተጠሪን በተመለከተ በአሽከርካሪው ሞት ምክንያት ለተቋረጠ ጥቅም በመድን ሽፋኑ መጠን ብር 90,000፣

በድምሩ ብር 470,760.31 ተከሳሽ ድርጅት ለከሳሾች እንዲከፍል ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ ከሌሎች የክርክር ነጥቦች በተጨማሪ ተሽከርካሪው ሕጋዊ መንጃ ፈቃድ በሌለው ሰው ሲሽከረክር ለሚደርስ ጉዳት መድን ሰጪው ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ በ1ኛ ተጠሪ እና በአመልካች መካከል በተደረገው የመድን ውል በአንቀጽ 3 የተመለከተ መሆኑን፣አቶ ተከስተ ካህሳይ ይዘውት የነበረው ቁጥሩ 04-465219 የሆነው መንጃ ፈቃድ የተሰጠው ለአቶ ተከስተ ካህሳይ ሳይሆን ለአቶ ቅዱስ ሙሉጌታ መሆኑን መንጃ ፈቃዱን የሰጠው አካል ያረጋገጠ በመሆኑ ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ በያዘ ሰው ሲሽከረክር ለደረሰው አደጋ አመልካች ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የ1ኛ ተጠሪን ምስክሮች ከሰማ በኋላ በመድን ውሉ አንቀጽ 3 አነጋገር አመልካች ድርጅት ኃላፊነት የማይኖርበት አደጋው በደረሰበት ጊዜ ተሽከርካሪው ሲሽከረክር የነበረው መንጃ ፈቃድ በሌለው ሰው በሆነ ጊዜ እንጂ ሕጋዊ መንጃ ፈቃድ በሌለው ሰው በሆነ ጊዜ ጭምር ተደርጎ መተርጎም የሚገባው አለመሆኑን፣1ኛ ተጠሪም አሽከርካሪውን የቀጠሩት ግለሰቡ የያዘውን መንጃ ፈቃድ አይተው ስለመሆኑ በምስክሮች ያስረዱ መሆኑን፣መንጃ ፈቃዱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከማየት በቀር ሕጋዊነቱን ከሚመለከተው አካል የማረጋገጥ ግዴታ የመድን ውሉ የማይጥልባቸው መሆኑን፣ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎችም በሚቾቹ ይረዱ የነበረ ስለመሆኑ እና ወራሽነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ያቀረቡ መሆኑን፣1ኛ ተጠሪ ለተሸከርካሪው ማስጠገኛ ያወጡት ወጪ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን እና የተሸከርካሪው የተቋረጠ ጥቅም ግን የመድን ሽፋን ያልተሰጠው መሆኑን ገልጾ አመልካቹን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ የተሸከርካሪውን የተቋረጠ ጥቅም አስመልክቶ ከተጠየቀው ገንዘብ ውጪ ያለውን በክሱ የተመለከተውን የካሳ መጠን አመልካች ለተጠሪዎቹ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አደጋው በደረሰበት ጊዜ ተሸከርካሪውን ሲያሽከረክር የነበረው ግለሰብ ይዞት የነበረው መንጃ ፈቃድ ተገቢ ወይም ሕጋዊ ያልሆነ መንጃ ፈቃድ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአመልካች ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች ታልፎ አመልካች በንግድ ሕጉ እና በመድን ውሉ መሰረት የመካስ ኃላፊነት አለበት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች፡-

1. ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን በቀጥታ በአመልካች ላይ ክስ ማቅረባቸው ስነ ስርዓታዊ ነው ወይስ አይደለም?
2. አመልካቹን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በክርክሩ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ከአንድ በላይ የሆኑ ከሳሾች የህብረት ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን ሁኔታ በተመለከተ ብዙ ሰዎች በአንድ ምክንያት ወይም ዓይነታቸው አንድ በሆኑ በብዙ ምክንያቶች የተመሰረተ ክስ ሲያቀርቡና ምክንያቱም እያንዳንዱን ከሳሽ የሚመለከት ሲሆን ከሳሾቹም ተነጣጥለው በየራሳቸው ስም ክስ ለማቅረብ የሚችሉ ሲሆኑ ለክሱ መነሻ የሆነው ሀብት ወይም መብት የጋራ ወይም የየራሳቸው ቢሆንም እንኳ በሚቀርበው ክስ ሊወሰን የሚችለው የሕግ እና የስረ ነገር ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ ከሳሾቹ በሕብረት ሆነው አንድ ክስ ብቻ ለማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 35 ይደነግጋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ የተሸከርካሪው ባለቤት ሲሆኑ ክሱን ያቀረቡትም ከአመልካች ጋር ያላቸውን የመድን ውል መነሻ በማድረግ የመድን ሽፋን የተሰጠውን እና የመገልበጥ አደጋ የደረሰበትን ተሸከርካሪ ጠግኖ ወደ ነበረበት ለመመለስ ተጠሪው ያወጡትን ወጪ ለማስተካት እና የተቋረጠ ጥቅም ለማስከፈል በመሆኑ በተናጠልም ቢሆን በአመልካቹ ላይ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም ያላቸው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። ቀሪዎቹ ተጠሪዎቹ ክስ ያቀረቡት በተሸከርካሪው ተሳፍረው የነበሩት ሰው እና የተሸከርካሪው ሾፌር በመሞታቸው ከሚኞቹ ስናገኘው የነበረው ጥቅም ቀርቶብናል በሚል ተገቢውን ካሳ ለማስወሰን ነው። በመሰረቱ ጉዳቱን አደረሰ የተባለው ተሸከርካሪ ባለንብረት 1ኛ ተጠሪ ናቸው። ስለዚህ 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ተቋርጦብናል ለሚሉት ጉዳት የካሳ ክፍያ ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉት አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት በተሸከርካሪው ባለቤት ላይ እንጂ በአመልካች ላይ ሊሆን አይችልም። 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በተናጠል በአመልካቹ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚችሉበት አግባብ ከሌለ ደግሞ በጋራም በመሆን በአመልካቹ ላይ ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ አይኖርም።ተሸከርካሪው ለሚያደርሰው አደጋ እና ጉዳት ከአመልካች የተሰጠ የመድን ሽፋን መኖሩም ቢሆን 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችን በቀጥታ በአመልካቹ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው አይሆንም። 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ከአመልካቹ ጋር ሊከራከሩ የሚችሉት በ1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው በ1ኛ ተጠሪ ጠያቂነት አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 43 ድንጋጌ መሰረት ወደ ጉዳዩ እንዲገባ የተደረገ በሆነ ጊዜ ነው። በመሆኑም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን በቀጥታ በአመልካች ላይ ክስ ማቅረባቸው ስነ ስርዓታዊ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም። ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ይህንኑ ተገንዝቦ በክሱ አቀራረብ ስነ ስርዓታዊነት ረገድ ተገቢውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ መስጠት ሲገባው ከስነ ስርዓት ውጪ በሆነ አግባብ የቀረበለትን ክስ መርቶ ውሳኔ መስጠቱ እና ውሳኔውም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የመድን ውል በአንቀጽ 3 ስር የመድን ሽፋን የተሰጠው ተሸከርካሪ ለመንዳት ተገቢ የሆነውን መንጃ ፈቃድ ባልያዘ ወይም ይህን መንጃ ፈቃድ እንዳይዝ በተከለከለ ግለሰብ ሲነዳ ለደረሰ አደጋ መድን ሰጪው ኃላፊነት የማይኖርበት መሆኑን የሚደነግግ የማግለያ ድንጋጌ መኖሩ አላከራከረም። የስር ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ በአመልካቹ የቀረበውን ክርክር ሳይቀበሉ የቀሩት የማግለያ ድንጋጌው ተገቢውን መንጃ ፈቃድ ባልያዘ ወይም እንዳይዝ በተከለከለ ግለሰብ የሚል እንጂ ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ በያዘ የሚል አነጋገር የሌለው መሆኑን፣እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ አሽከርካሪውን የቀጠሩት መንጃ ፈቃዱን በማየት በመሆኑ እና የመድን ውሉም በተሸከርካሪው ባለቤት ላይ የመንጃ ፈቃዱን እውነተኛነት የማረጋገጥ ግዴታ የማይጥል መሆኑን በመግለጽ ነው። በመሰረቱ መንጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፈቃድ ማለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ለመንዳት የሚያስችል አግባብነት ባለው አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሰረት የሚሰጥ የመንጃ ፈቃድ ስለመሆኑ በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 በአንቀጽ 2 (8) ስር ትርጉም የተሰጠው ሲሆን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 600/2000 በአንቀጽ 2 (3) የተመለከተው የመንጃ ፈቃድ ትርጉምም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው።የ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ የነበሩት የተሽከርካሪው ሾፌር በተጠቀሱት አዋጆች ድንጋጌዎች መሰረት የተሰጠ መንጃ ፈቃድ ያልነበራቸው እና ይዘውት የነበረው መንጃ ፈቃድም የተሰጠው ለእርሳቸው ሳይሆን ለሌላ ግለሰብ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ግለሰቡ ይዘውት የነበረው መንጃ ፈቃድ ሀሰተኛ ነው ከሚባል በቀር ተገቢ መንጃ ፈቃድ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም።

የማግለያ ድንጋጌው መሰረታዊ ዓላማ ተሽከርካሪው ተገቢውን ትምህርት እና ስልጠና ባልወሰደ እና ስልጣን ካለው አካል አግባብነት ባለው ሕግ እና ደንብ መሰረት ተገቢው መንጃ ፈቃድ ባልተሰጠው ግለሰብ ሲነዳ ለሚደርሰው ጉዳት የመድን ሰጪውን ኃላፊነት ለማስወገድ እንደሆነ የሚታወቅ በመሆኑ የተሽከርካሪው የመገልበጥ አደጋ የደረሰው አሽከርካሪው አግባብነት ባለው ሕግና ደንብ መሰረት በባለስልጣኑ ያልተሰጠውን ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ ይዞ ሲያሽከረክር በነበረበት ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ በማግለያ ድንጋጌ መሰረት መድን ሰጪው በኃላፊነት የሚጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም። በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች ላይ የተጠቀሱት የንግድ ሕግ ቁጥር 654፣664 እና 668 ድንጋጌዎችም በመድን ውሉ አንቀጽ 3 ላይ የተቀመጠውን የማግለያ ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚያስቀሩ አይደሉም። በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ የማግለያ ድንጋጌው የመንጃ ፈቃዱን ሕጋዊነት የማረጋገጥ ግዴታ የሚጥልብኝ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል አይደለም።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. ሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሽሬ እንዳስላሴ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 16952 በ25/03/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63314 በ26/09/2006 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን በአመልካቹ ላይ በጋራ ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ሥነ - ስርዓታዊ አግባብ የለም በማለት ወስነናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ንብረትነቱ የ1ኛ ተጠሪ በሆነው ተሽከርካሪ ላይ የመገልበጥ አደጋ የደረሰው ተገቢውን መንጃ ፈቃድ ባልያዘ ወይም ሀሰተኛ መንጃ ፈቃድ በያዘ ግለሰብ ሲሽከረከር በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ላቀረቡት ክስ በመድን ውሉ አንቀጽ 3 በተመለከተው የማግለያ ድንጋጌ መሰረት አመልካች ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል።
4. ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች መብታቸውን መጠየቅ የሚችሉት የተሽከርካሪው ባለንብረት ከሆኑት 1ኛ ተጠሪ ነው በማለት ወስነናል።
5. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ።
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 115763

ቀን 09/02/2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ክፍለጽዮን ማሞ

ጳውሎስ ኦርሲሾ

አመልካች፡- ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንሽ ኩባንያ አ.ማ ጌታቸው ገዳሙ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ትዕግስት ገ/እግዚአብሔር ነገረ ፈጅ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የተጀመረው አመልካች የስር ክሳሽ በመሆን በአሁን ተጠሪ (1ኛ ተከሳሽ) እና በዛሬ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግል ማህበር (2ኛ ተከሳሽ) ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በቀን 19/02/2006 ዓ/ም በመሰረተው ክስ ነው፡፡

2ኛ ተከሳሽ ልዩ ልዩ ተሽከርካሪዎችን በዋስትና በማስያዝ ከ1ኛው ተከሳሽ ብድር የወሰደ ሲሆን አመልካች ለተሸከርካሪዎቹ የመድን ሽፋን ሰጥቷል ክሱንም ሊመሠርት የቻለው በሰጠሁት የመድን ሽፋን መሠረት ያልተከፈለኝ ቀሪ የኦርቦን ክፍያ ስላለ ሁለቱም (የስር) ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ ባለ ዕዳ ናቸው በሚል ነው፡፡

2ኛ ተከሳሽ የወሰደውን የባንክ ዕዳ እንደውሉ አጠናቆ ሊከፍል ባለመቻሉ 1ኛው ተከሳሽ በመያዣ ውሉ መሠረት ንብረቶቹን ካስቆጠረ በኋላ በሐራጅ በመሸጥ በብድር የሰጠውን ገንዘብ ሰብስቧል ቀጥሎ ለአመልካች በላከው ማስታወሻ የመድን ውሉ እንዲቋረጥ አሳስቧል፡፡

2ኛ ተከሳሽ በመክሰሩ ምክንያት ከ1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ጋር የነበረው ውል በመቋረጡና የመድን ፖሊሲውም እንዲሰረዝ በመደረጉ አመልካች ገቢ ያላደረገው ብር 42,037.15 እንዲከፈለው በሁለቱ ተከሳሾች ላይ ክስ መስርቷል የክሱ አመሠራረት ተጠሪን 1ኛ ተከሳሽ በማድረግ ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይዘቱም በመድን ፖሊሲው ላይ ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሳሽ እንደጣምራ መድን ገቢዎች ሆነው የተጻፉ ኦርቦኑንም እንደ 2ኛ ተከሳሽ በመሆን 1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ሲከፍል የነበረ ፖሊሲው እንዲታይለም ተጠሪ ሲፈቅድም ሲስማማ የነበረ የመድን ሽፋን የነበራቸው ተሸከርካሪዎች በመሸጥ ተጠሪ እዳውን የሰበሰበና በዚህም ተጠቃሚ የሆነ በመሆኑ 2ኛ ተከሳሽ መክሰሩን ተከትሎ ተጠሪ የማረውን ኦርቦን ልከፍል አይገባም ማለቱ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው።

አመልካች በበኩሉ በሰጠው መልስ ከአመልካች ጋር ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግንኙነት አለመመስረቱን አመልካች የመድን ውሉን የፈረመው ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር እንጂ ከተጠሪ (1ኛ ተከሳሽ) ጋር አለመሆኑን ተጠሪ የመድን ግዴታ ውል ፈጽሞ አለመግባቱን እንዲሁም የመድን ውሉ እንዲታደስ መስማማቱ የውሉ ተጠቃሚ በመሆኑ እንጂ ባለእዳ ጌዴታ ያለበት መሆኑን አያመለክትም ብሏል።

2ኛ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ በመቅረቱ ፍ/ቤቱ የአመልካች (ከሳሽ) እና ተጠሪ (1ኛ ተከሳሽ) ክርክሮችንና ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ ጉዳዩን መርመሯል እንደመረመረውም 1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ኦርቦኑን ሲከፍል እንደነበረ በመድን ውሉ ላይም ሁለቱም ተከሳሾች መድን ገቢዎች ለመሆናቸው "እና " በሚል ቃል የተጠቀሱ መሆኑ መድን ውሉ እንዳይቋረጥ ሲከታተል ና እንዲታደስ ሲፈቅድ የነበረው 1ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) በመሆኑ የሰጠውን ብድር ከሰበሰቡ በኋላ የተጠራቀመውን ኦረቦን አልከፍልም የሚልበት አግባብ ባለመኖሩ 1ኛው ተከሳሽ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነትና በነጠላ ሃላፊነት አለባቸው ሲል ስር ፍ/ቤት ወስኗል። ፣

ተጠሪ የስር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅሬታውን አቅርቧል ተጠሪ ቅሬታውን ሲያቀርብ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተመሰረቱ የውል ግንኙነት ሳይኖር በአመልካችና በ2ኛው ተከሳሽ መካከል የመድን ውሉ ከተመሠረተ በኋላ በተደረጉ በአመልካችና በተበዳሪው በ2ኛ ተከሳሽ መካከል ከነበሩ የብድር ውል ግዴታዎች አፈፃፀም ላይ ተመስርቶ አመልካችን እንደመድን ገቢ በመቁጠር የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊሻር ይገባዋል ብሏል። አመልካችም በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸውን የክርክር ነጥቦች አጠናክሮ አቅርቧል።

ጉዳዩን የያዘው ከፍተኛ ፍ/ቤት በንግድ ህግ ቁ. 675 (1) ላይ በመመስረት መልስ ሰጭ የአሁን አመልካች ያቀረባቸውን መከራከሪያዎች ከመዘነ በኋላ በይግባኝ ባይ (ተጠሪ) እና በመልስ ሰጭ መካከል የመድን ሰጭና መድን ተቀባይ ውል አለ ለማለት የማያስችሉ በመሆኑ አረቦኑን መክፈል ያለበት የስር 2ኛ ተከሳሽ ብቻ ነው በማለት ወስኗል ።

ፍ/ቤቱ በተጨማሪም የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ በአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መካከል በነበረው ክርክር በሰበር መዝገብ ቁ. 43886 በቀን 22

https://t.me/ethiopianlegalbrief

/4/2002 ዓ/ም የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ የይግባኝ ባይን (የአሁን ተጠሪን) ክርክር የሚደግፍ በመሆኑ የይግባኝ ባይ (አመልካች) ማመልከቻን አልተቀበልነውም ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው በከፍተኛው ፍ/ቤት ተፈጸመ የተባለው የህግ ስህተት እንዲታረም ነው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው ተጠሪ ተሸከርክሪዎችን ተረክቦ ከ5 ዓመት በላይ ካስተዳደረና ዋስትናው እንዲታደስ እየጠየቀ አርቦን በየአመቱ እየከፈለ ከቆየ በኃላ ንብረቶቹን ሸጦ ከብር 27 ሚሊዮን በላይ ከሰበሰበ በኋላ ውሉን በማቋረጥ አርቦንን አልከፍልም ያለበትን ክርክር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ መወሰኑ አግባብ አይደለም ይታረምልኝ ብሏል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የስር ክርክሩን በማጠናከር የከፍተኛው ፍ/ቤት አስገዳጅነት ያለውን የሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 43886 መሠረት ያደረገ ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡ እኛም መዝገቡን መርምረናል እንደመረመርነውም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔውን መሠረት ያደረገው በውል ፖሊሲው ላይ ተጠሪና 2ኛ ተከሳሽ “እና” በሚል በመጣመራቸው ሲሆን ተጠሪ ከውል የመነጨ ግዴታ ያለበት ለመሆኑ ግን አግባብ ያለውን ህግ ወይም የሰበር ውሳኔ ጠቅሶ አላብራራም፡፡

በሌላ በኩል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዚህ ቀደም ሰበር ችሎቱ በተመሳሳይ ጉዳይ በመዝገብ ቁ. 43886 የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ በመጥቀስ እና የንግድ ህግ ቁጥሮች 654 እና 657 -659 ን በአግባቡ በመተርጎም የሰጠው ውሳኔ ምንም ስህተት አልተገኘበትም፡፡ በዚህ መሠረት የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 147374 በታህሳስ 13 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠውን በጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 110005 በሚያዝያ 14 ቀን 2007 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348 (1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የስር 2ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ጋር በገባው የመድን ውል መሠረት ያልከፈለውን የአርቦን ክፍያና ወለድ ተጠሪ በአንድነትም ሆነ በነጠላ የመክፈል አላፊነት የለበትም ፡፡
3. የስር 2ኛ ተከሳሽ በገባው የመድን ውል መሰረት የተጠየቀውን አርቦን ክፍያና ወለድ ሙሉ በሙሉ የመክፈል አላፊነት አላበት
4. ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ይጻፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 88542

ሐምሌ 17 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ቢሆነኝ ደምሌ - ጉዳይ ተከታታይ መንበሩ ተስፋው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የት/ብ/ክ/መንግስት ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ሥራን በህገ ወጥ መንገድ ማከናወን ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በት/ብ/ክ/መንግስት አላማጣ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ አመልካች ላይ ባቀረበው የወንጀል ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው በ17/11/2004 ዓ.ም ከጥዋቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ በአላማጣ ከተማ 02 ቀበሌ ልዩ ቦታው ወደ ዋጃ መውጫ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ አንድ ኩንታል ስኳር በመኪና ላይ ጭኖ ወደ ቆቦ ወረዳ ሲጓዝ ስለተያዘ አዋጅ ቁ 686/2002 አንቀፅ 60/1/ ተላልፎ በፈፀመው ሕጋዊ ያልሆነ ንግድ ሥራ በማካሄድ ተከሷል የሚል ሲሆን ተከሳሹም ቀርቦ ስኳሩን ወደ ቆቦ ከተማ ወስዶ ለመሸጥ በመኪና እየተጓዘ ሳለ መያዙን ጠቅሶ ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው ይዤንን የንግድ ሥራ መፈፀሙ ጥፋት መሆኑን በማመን የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ወረዳ ፍ/ቤትም ተከሳሹ የሰጠውን የእምነት ክህደት መነሻ በማድረግ ተከሳሹን በተከሰሰበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ካደረገ በኃላ በሁለት ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) ገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወሙ ቅሬታውን ለዞኑ ከፍ/ፍ/ቤትና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃውን ጠብቆ ቢያቀርብም በሁለቱም ደረጃ ተቀባይነት አላገኘም አሁን የቀረበው የሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም አንዱን ኩንታል ስኳር ገዝቼ ወደ ቆቦ ከተማ ስንጓዝ የነበረው ለንግድ ወይም ለሽያጭ ሳይሆን ወላጅ አባቴና ሴት አያቴ በሞት በመለየታቸው ምክንያት ለሃዘን ለሚመጡ ሰዎች ሻይና ቡና ማስተናገጃ ሆኖ ሳለ ጥፋተኛ መባሌ አላግባብ መሆኑን ለንግድ ነው ቢባል እንኳ የቀረበብኝን ክስ ሙሉ በሙሉ በማመን የእምነት ክህደት ቃልን መስጠቴ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኔን የወንጀል ሪከርድ የሌለብኝ መሆኔ የግል ሁኔታዬና የገቢ ምንጭ በወንጀል ህግ ቁ 88/2/፤ 90/2/ እና እንዲሁም በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በአግባቡ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ቅጣቱ መጣል ሲገባ ያላግባብ በሁለት ዓመት ፀኑ እስራትና 150,000 ብር የገንዘብ መቀጮ እንድቀጣ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ተሻሽሎ የጥፋተኝነት ደረጃዬን ባገናዘበና የገንዘብ መቀጮውንም በተመለከተ የመክፈል አቅሜን ባገናዘበ መልኩ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል መባሉ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠበት ሲሆን አመልካችም የመልስ መልሱን ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር አቤቱታ በቀረበበት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል::

እንደመረመርነውም የጥፋተኝነት ውሳኔን በተመለከተ አመልካቹ የቀረበበትን የወንጀል ክስ መፈፀሙን በዝርዝርና ሙሉ በሙሉ በማመን የእምነት ክደት ቃሉን መስጠቱና ፍ/ቤቱም ይህንኑ የአመልካችን የእምነት ቃል መነሻ በማድረግ የጥፋተኝነት ውሣኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.134 /1/ ድንጋጌ አንፃር መሰጠቱን መገንዘብ ተችሏል ሆኖም ግን አንድ ሰው በተሰጠበት የጥፋተኝነት የቅጣት ውሳኔ ላይ ደረጃውን ጠብቆ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት የሚችል ቢሆንም የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠው በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ134/1/ ስር እንደተመለከተው የተከሳሹን የእምነት ቃል መነሻ በማድረግ ከሆነ በቅጣቱ ላይ ካልሆነ በጥፋተኝነቱ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ እንደማይቻል በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 185/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል አመልካች ወንጀሉን በህጉ አግባብ ሙሉ በሙሉ መፈፀሙን አምኖ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቶና የጥፋተኝነት ውሳኔም ይህንኑ መነሻ በማድርግ ተሰጥቶ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ በበታች ፍ/ቤት ከሰጠው እምነት ቃል በተቃራኒ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ እርስ በራሱ የሚጋጭ በመሆኑ ተቀባይት ያለው አይደለም ብለናል፡፡

የቅጣት ውሳኔን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የህጉ ድንጋጌ ከብር 150,000-300,000 የገንዘብ መቀጮና እንዲሁም ከ7-15 ዓመት ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ የደነገገ ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አኳያ የእስራት ቅጣቱን በተመለከተ የበታች ፍ/ቤቶች የወንጀሉን ክብደት የአመልካቹን የግል ሁኔታና ሌሎች የቅጣት ማቅለያዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በድንጋጌው ስር ከተመለከተው መነሻ የእስራት ቅጣት (7 ዓመት ፅኑ እስራት) በመውረድ አመልካቹ በሁለት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሲሆን ይህ ደግሞ ሊነቀፍ የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታም አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ በወ/ህ/ቁ 90/2/ ስር እንደተመለከተው ፍ/ቤቶች ይህንን የገንዘብ መቀጮ ሲወስኑ የወንጀሉ ክብደት የአጥፊውን አደገኛነት መጠን የሀብቱን ሁኔታ የገቢ ምንጩን ዕድሜውንና የጤንነቱን ሁኔታ ከቤተሰብ አስተዳዳሪነት አኳያ ያለንበትን ሸክም የሙያ ስራውንና ከስራው የሚያገኘውን ገቢ መጠን ከግምትና ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ ሁኔታ መቀጮው ሊጣል እንደሚገባ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ላይ የተጣለው የብር 150,000 የገንዘብ መቀጮ እነዚህ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የህጉን መስፈርቶች ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ አግባብ መሆን አለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አያሳይም የመቀጮ ቅጣቱ እነዚህ መስፈርቶችን ባላገናዘበ ሁኔታ የሚጣል ሆኖ ከተገኘም የወንጀል ህጉ ካሰበው ዓላማ ውጭም በመውጣት አጥፊውንና ሌሎቹን ከማስተማር እና ከማስጠንቀቅ አልፎ አላስፈላጊ ጫናና ችግር በተከሳሹና በቤተሰቡ ላይ እንዳይፈጥር ጭምር ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል በተለይም አመልካቹ አርሶ አደርና የቤተሰብ አስተዳዳሪ ከመሆኑ አኳያ የሀብቱ ሁኔታ የገቢ ምንጩ አደገኛነቱና የወንጀሉ ክብደትም በተገቢ ሁኔታ ተመዝኖ መታየት ከነበረበት ባጠቃላይ በህጉ እስካልተከለከለ ድረስ በህጉ ከተመለከተው መነሻ መቀጮውም በመውረድ (አጠቃላይ የገንዘብ መቀጮው መነሻ እንደተጠበቀ ሆኖ) መቀጮው በወንጀል ህጉ አግባብና በተለይም በወ/ህ/ቁ88/2/ ፤ 90/2/ እና በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ 1/2002 አኳያ መጣል ሲገባ በደፈናው አመልካቹ በብር 150,000 እንዲቀጣ መወሰኑና ይኼውም በዞኑ ከፍ/ፍ/ቤት እና ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መታረም ሲገባ መፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፤

ው ሳ ኔ

1. በአላማጣ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት መ.ቁ 03421 በ15/2/2005 ዓ.ም ተወስኖ በከፍተኛ ፍ/ቤቱና ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፀናው የጥፋተኝነትና የእስራት ቅጣቱ ውሳኔ ክፍል በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ.195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፤
2. ሆኖም ግን አመልካች በብር 150,000 (መቶ ሃምሳ ሺህ) ገንዘብ መቀጮ ይቀጣ በማለት የተሰጠው የቅጣቱ ውሳኔ ክፍል ብቻ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 195/2/ /ለ/ /2/ መሰረት ተሽሯል፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የአላማጣ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የራሱን መዝገብ በማንቀሳቀስና ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ከዚህ በላይ በፍርዱ ሐተታ ክፍል በተገለፀው አኳኋን የገንዘብ መቀጮውን ከወንጀል ህጉ ቁ 90/2/፤ 88 /2/ እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው ሌሎች ድንጋጌዎችና እንዲሁም በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ 1/2002 አኳያ የገንዘብ ቅጣቱን በማገናዘብ ከመረመረ በኃላ ተገቢውን አስልቶ እንዲወስን ዘንድ ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፤

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 116405

መጋቢት 2 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- የኦሮሚያ የስነ ምግባርና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ህግ - ጉዳኔ ፈቃዱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ቴዎድሮስ አብርሃ ቀለቲ - ጠበቃ አማላዩ ፀጋዬ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የወንጀል ክስ ማሻሻልን የሚመለከት ነው፡፡ በስር 1ኛ ተከሳሽ ደርበው ሻንቆ እና 2ኛ ተከሳሽ በሆነው የአሁን ተጠሪ ላይ አመልካች የመሰረተውን ክስ ለማሻሻል ያቀረበው አቤቱታ ጉዳዩን ሲመለከት በነበረው የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 11311 በ23/4/2007 በዋለው ችሎት በትእዛዝ ውድቅ የተደረገ ሲሆን ትእዛዝ ላይ አመልካች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ/192830 በ3/6/2007 በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ትእዛዝ በመሻር ክሱ እንዲሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ ክስ እንዲሻሻል መፈቀዱን በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበው ችሎቱ በመ/ቁ/ 203090 በ1/10/2007 የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የክስ ማሻሻል ጥያቄ የቀረበው መዝገቡ ለምርመራ ከተቀጠረ በኋላ በመሆኑ፣ በዚህ ሁኔታ ክሱ ይሻሻል ቢባል ክርክሩ እንደ አዲስ የሚጀምር በመሆኑ፣ይህ ደግሞ በኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 20/1/ የተጠበቀውን አፋጣኝ ውሳኔ የማግኘት መብት የሚጻረር በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ሽሮ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ትእዛዝ አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ አመልካች ምክንያቶችን በመዘርዘር በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ላሻሽል ጥያቄ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20 /1/ የሚጥስ ነው ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብ ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ቅሬታ ያስነሳውን ውሳኔ እና የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች መስርቶት በነበረው ክስ የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ድርጅት የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ኃላፊ የነበረው 1ኛ ተከሳሽ ከመንግስት የግዥ ወይም የጨረታ አወጣጥ ደንብና ከድርጅቱ መመሪያ ውጭ ስልጣኑን ያላግባብ በመገልገል ንብረትነቱ የመንግስት የሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-07074 ገልባጭ መኪና ያለምንም ጨረታና የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ለአሁን ተጠሪ በጥገና ሰበብ በ21/07/2007 ዓ/ም እንዲሰጥ በማድረግ መንግስት ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ እንዲያጣ በማድረጋቸው ክስ ቀርቦባቸው የዓቃቤ ህግ ማስረጃዎች ተሰምተው እንዲከላከሉ ተፈቅዶላቸው መከላከያ ተሰምቶ መዝገቡ ለምርመራ ተቀጥሮ ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነው መኪና ለሌላ 3ኛ ወገን የተሸጠ መሆኑን፤ የገዛው ሰውም የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ የሰሌዳ ቁጥር በዚህ መኪና ላይ በመለጠፍ ከአዲስ አበባ መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ሰራተኞች ጋር በመመሳጠር በህገ ወጥ መንገድ የሻንሲ፤ የሞተር ቁጥርና ሌሎች መረጃዎችን ከላዩ በመፋቅ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ በማስመሰል ከትራንስፖርት ባለስልጣን እውቅና ሌሎች መረጃዎችን ከላዩ በመፋቅ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ በማስመሰል ከትራንስፖርት ባለስልጣን እውቅና ደንብና መመሪያ ውጭ በላዩ ላይ እንዲመታ በማድረግ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ/ በመውሰድ በሽያጭ ለሌላ ግለሰብ አስተላልፎ መኪናው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በመስራት ላይ እንዳለ ከ6 ዓመታት ፍለጋ በኋላ ያላግባብ በተጠሪ ተወስዶ የተሰወረ መኪና እና በወንጀሉ ውስጥ ተካፋይ የሆኑ ሰዎች የተያዙና የስር ተከሳሾች የሙስና ወንጀል ድርጊት አፈፃጸምና የተገኘው ጥቅም በአግባቡ በግልጽ በመታወቁ፤ እንዲሁም በወንጀሉ ተካፋይ የሆኑ ሰዎች ላይ እንደተሳትፏቸው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 118 እና 119/1/ መሰረት ክስ አሻሽለን ብናቀርብ ፍርድ ቤቱ ትክክለኛ እና ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት ይረዳዋል በማለት ክሱን አሻሽለው ለማቅረብ እንዲፈቀድ ጠይቀዋል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ በበኩላቸው ጉዳዩ 1 አመት ከ6 ወር የቆየ መሆኑን፤ መዝገቡም ክርክሩ ተጠናቆ ለምርመራ መቀጠሩን ፤ ምንአልባት ዓቃቤ ህግ ሌሎች ሰዎች ላይ ክስ መመስረት ከፈለገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚገድበው ነገር አለመኖሩንና የተጠቀሰው ምክንያት ክሱን አሻሽሎ ለማቅረብ የህግ ድጋፍ ያለው አለመሆኑን በማንሳት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ከፍ ሲል የተመለከቱትን ውሳኔዎች ሰጥተዋል፡፡ በተለይ የክልሉ ሰበር ችሎት ትክክለኛ እና ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት ሲባል ክሱ ሊሻሻል ይችላል በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ቢቀበለውም የክሱ መሻሻል አስቀድሞ በእስር ሆነው ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩ ተከሳሾች አፋጣኝ ውሳኔ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት የሚያጣብብ በመሆኑ የክስ ላሻሽል ጥያቄው ተቀባይነት እንደሌለው ወስኗል፡፡

በመሰረቱ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ክሱ እንዲሻሻል ፍርድ ቤቱ ሊፈቅድ የሚችል ሲሆን በዚህ መልኩ ክሱ እንዲሻሻል ፈቃድ ሲሰጥ ወይም የክሱ መሻሻል ሲከለከል ፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ያለው ህጋዊ ምክንያት እንዲሰጥ ይጠበቃል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ሰበር ችሎት ክሱ እንዲሻሻል በመፈቀዱ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው ጉዳዩ ለምርመራ ያደረ በመሆኑ እና ክሱ ተሻሽሎ እንደ አዲስ ቢጀመር አፋጣኝ ውሳኔ የማግኘት መብትን ይጋፋል በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው የክሱ መሻሻል ፍርድ ቤቱ ትክክለኛ እና ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለው መሆኑ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ፤ ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ክሱ እንዲሻሻል መፍቀድ እንደሚቻል በህጉ የተመለከተ በመሆኑ፤ እንዲሁም የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት የሚረጋገጠው በህግ የተዘረጋን ስነ ስርዓት ተከትሎ ጉዳዩን ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ በመምራት እንጂ በህግ የተዘረጋን ስነ-ስርዓት ወደጎን በማለት ባለመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት የክሱ መሻሻል ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ተገቢ መሆኑን ተቀብሎ ነገር ግን ክርክሩ የደረሰበትን ደረጃ ብቻ ግምት ውስጥ በማስገባትና አፋጣኝ ፍትህ የማግኘት መብትን ህጋዊ አፈፃጸም ባልተከተለ መልኩ ክሱ እንዲሻሻል ሊፈቀድ አይገባም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ እና ያሳለፈው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የተፋጠነ ፍትህ የሚገኘው ጉዳዩ የወንጀል ክርክር በሚመራበት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ድንጋጌዎች አግባብ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ በመምራት በመሆኑ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 118 እና 119 እንዲሁም ተያያዥ ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት ባለው ምክንያት ክስ እንዲሻሻል መፈቀዱ የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብትን የሚያጣብብ ነው የሚባል አይሆንም ብለናል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት ክሱ እንዲሻሻል ሊፈቀድ አይገባም በማለት የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተከታዩም ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ልዩ ዞን ፍንፍኔ ዙሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 11311 በ23/4/2007 በዋለው ችሎት ያሳለፈው ትእዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 203090 በ1/10/2007 የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ/ 195/2/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 192830 በ3/6/2007 ያሳለፈው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 11311 እየተካሄደ የነበረው ክርክር ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ፍርድ ቤት ጥቅምት 15/2008 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
4. አመልካች የተሻሻለውን ክስ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ፤ የስር ፍርድ ቤትም የተሻሻለውን ክስ ተቀብሎ አከራክሮ እንዲወሰን ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.113143

መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ሕሊና ኃይሌ
2. አቶ ፋሲካ አዕምሮ } የቀረበ የለም
3. አቶ መላኩ ደምሴ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የሐረሪ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሶስቱም ተጠሪዎች ላይ በወንጀል ሕግ ቁጥር 555 (ሐ) ስር በመዝገብ ቁጥር 40031 እንደቅደም ተከተሉ በ24/11/2006 ዓ.ም. እና በ29/11/2006 ዓ.ም. የሰጠባቸውን የጥፋተኝነት እና የእስራት ቅጣት ውሳኔ በከፊል ሽሮ እና በከፊል ደግሞ አሻሽሎ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በነጻ በማሰናበት እና 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ ደግሞ ድንጋጌውን ወደ 557 (1) (ሐ) ለውጦ በብር 2,000 እንዲቀጡ በማለት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12394 በ13/05/2007 ዓ.ም የሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03061 በ24/08/2007 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎቹ ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ተከሳሾቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) እና 555 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በሰው አካል ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው በ19/03/2006 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ላይ በሐረር ከተማ ቀበሌ 10 ክልል ልዩ ስሙ ሥላሴ ሐይቱክ ትምህርት ቤት አካባቢ ገ/መስቀል ገ/ሥላሴ የተባለውን የግል ተበዳይ ተባብረው ፊቱን እና አፍንጫውን በቦክስ በመምታት፣መላ ሰውነቱን በመደብደብ፣በአፍንጫው ላይ የአጥንት ስብራት ጉዳት፣በግራና በቀኝ ፊቱ ላይ የእብጠት፣በቀኝ አይኑ እና በቀኝ ጆሮው መካከል እብጠትና የመላላጥ ጉዳት እንዲደርስ በማድረጋቸው በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት የማድረስ ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን ተጠሪዎቹ ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ተደርጎ የእምነት ክደት ቃል ሲጠየቁ ወንጀሉን አላደረግንም በማለታቸው አመልካች እንደክሱ ያስረዱልኛል በማለት ከቆጠራቸው ሰባት ምስክሮች መካከል የግል ተበዳይን ጨምሮ ስድስቱን አቅርቦ ያሰማ መሆኑን እና አንዱ ምስክር በአድራሻቸው አልተገኙም በመባሉ በምርመራ ጊዜ ለፖ/ሊስ የሰጡት ምስክርነት ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ የተደረገ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ፍርድ ቤቱ የምስክሮቹን ቃል እና አመልካቹ በሰነድ ማስረጃነት ያቀረበውን የሀኪም ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በተጠሪዎቹ ላይ አመልካች በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎቹ ከቆጠሯቸው 11 የመከላከያ ምስክሮች መካከል እራሳቸውን ጨምሮ በድምሩ ሰባት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡

ከዚህ በኃላ ፍርድ ቤቱ በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪዎቹ ባሰሟቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረተባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት በሶስቱም ተጠሪዎች ላይ በክሱ በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ በማስተላለፍ ግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየታቸውን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡ በመቀጠልም በአመልካቹ በኩል የቀረበ የማክበጃ ምክንያት አለመኖሩን፣በተጠሪዎቹ በኩል የቀረቡት የማቅለያ ምክንያቶች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን፣ወንጀሉ ደረጃ የወጣለትና የሚመደበውም በደረጃ አንድ መሆኑን እና በድንጋጌው ስር በደረጃ አንድ ለተመደበ ወንጀል በመመሪያው የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን በአባሪ አንድ በእርከን 16 የተመለከተው መሆኑን ገልጾ በመመሪያው በእርከን 16 በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን መሰረት 1ኛ ተጠሪ በሶስት ዓመት ከአራት ወር ጽኑ እስራት፣2ኛ ተጠሪ በሶስት ዓመት ከሁለት ወር ጽኑ እስራት፣ሶስተኛ ተጠሪ በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በመወሰን እና ተጠሪዎቹ ያቀረቡትን የቅጣት ገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በከፊል ለመሻር እና በከፊል ደግሞ ለማሻሻል የሰጠው ምክንያት የግራ ቀኙ ማስረጃ በማገናዘብ ሲመረመር በግል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተበዳይ ላይ ለደረሰው ጉዳት መንስኤ የሆነው እራሱ የግል ተበዳይ መሆኑን እና ጉዳቱም የደረሰበት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተያይዘው በኮብልስቶን ድንጋይ ላይ በመውደቃቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔውን የሰጠው የግራ ቀኙን ማስረጃ በአግባቡ መዝኖ ነው ለማለት አልተቻለም የሚል መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያመለክታል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተመርመሮ የአመልካች የዓይን ምስክሮች ቃል በሁለቱ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመከለተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪዎቹ ተጠይቀው ወንጀሉን አላደረግንም በማለታቸው አመልካች አቅርቦ ካሰማቸው ስድስት ምስክሮች መካከል፡-

- የግል ተበዳይ የሆኑት 1ኛ ምስክር በክሱ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በመንገድ ላይ በመሄድ ላይ እያለ 2ኛ ተጠሪ የግል ተበዳይን “ይህም የአጽብሃ ወንድም ነው” ብሎ አንቆ ከያዘው በኃላ ትፈለጋለህ በማለት በቦክስ ከፊቱ ላይ እንደመታው፣ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በአካባቢው ከነበረ መኪና ውስጥ ወርደው ወደ ግል ተበዳይ በማምራት 1ኛ ተጠሪ በእጁ ይዞት በነበረው ጠፍጣፋ ነገር አፍንጫው ላይ ሲመታው 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በጠረባ መቶት ከመሬት ላይ እንደጣለው እና በወደቀበትም ሶስቱም ተጠሪዎች እየረገጡ እንደደበደቡት፣በደረሰበት ድብደባ ምክንያትም የመስማት ችግር እንዳጋጠመው እና በአፍንጫው ስብራት እና ቁስል ምክንያት ማሽተት እንደሚችግረው በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤
- 3ኛ እና 4ኛ ምስክሮች በአካባቢው ከሚገኝ ግቢ ውስጥ የአናጺነት ስራ በመስራት ላይ እያሉ “ገደለው” የሚል ጩኸት ሰምተው ሲወጡ ተጠሪዎቹ የግል ተበዳይን አሸባሪ ነው አያሉ ሲናገሩ እንደሰሙ፣ተበዳይ ደምቶ እንደነበረ እና ተጠሪዎቹ ቀበቶውን አውልቀው ሲፈትሹት እንደነበረ እና ጠቡን ግን ከጅምሩ እንዳላዩ በመግለጽ ምስክርነት መስጠታቸውን፤
- 5ኛ ምስክር በቦታው በደረሰበት ሰዓት ተበዳይ አፍንጫው ላይ ደምቶ ማየቱን፣የግል ተበዳይ ሽጉጥ ጥሏል በማለት 1ኛ ተጠሪ ቆርቆሮ ስር ሲፈልግ እንደነበረ እና 3ኛ ተጠሪን ከቦታው እንዳላየው በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤
- 6ኛ ምስክር በቦታው በደረሰበት ሰዓት ተበዳይን 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እጁን ግራና ቀን ይዘው ማየቱን፣የተበዳይ ፊት ደም በደም ሆኖ እንደነበረ፣ምስክሩ ሲጠይቃቸው አሸባሪ ነው በማለት እንደመለሱለት፣ሽጉጥ ይሏል በማለት ሲፈትሹት እንደነበረ፣ምስክሩ የአካባቢው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰዎች ውሃ እንዲያመጡ አድርጎ ፊቱን ሲያጥቡለት 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ያዙኝ ልቀቁኝ ይል እንደነበረ በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤

- የግል ተበዳይ ወንድም መሆኑን የገለጸው 7ኛ ምስክር ከ1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር የቆየ ቂም እንደነበረው፣በዚሁ ዕለት ከምሽቱ 12፡30 ላይ ሁለት የፖሊስ አባላትን ይዘው በመምጣት ምስክሩን ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንደወሰዱት፣እዚያ እያለ የግል ተበዳይ አፉና አፍንጫው ደምቶ እንዳየውና ተጠሪዎቹ የደበደቡት መሆኑን እንደነገረው በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤በመግለጽ የመሰከሩ መሆኑን እና የሀኪም ማስረጃውም በግል ተበዳይ የግራ እና የቀኝ ፊት ላይ እብጠትና የሰንበር ምልክት መታየቱን፣በአፍንጫው ላይ እብጠት፣በቀኝ አይኑና በቀኝ ጆሮው መካከል እብጠትና የመላላጥ ምልክት መታየቱን እና በተደረገለት የራጅ ምርመራም የአፍንጫ አጥንት ስብራት መታየቱን የሚያረጋግጥ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ሶስቱን ተጠሪዎች ጨምሮ በተጠሪዎቹ በኩል የተሰሙት ሰባት የመከላከያ ምስክሮች አመሰካከር ተጠቃሎ ሲታይ በዕለቱ የግል ተበዳይ ሽጉጥ ይዞ ማንነቱ ከማይታወቅ ሰው ጋር በመሆን በ2ኛ ተጠሪ ላይ ጸብ ማንሳታቸውን፣በዚህ ጸብም የግል ተበዳይና 2ኛ ተጠሪ ተያይዘው ከኮብልስቶን ድንጋይ ላይ መውደቃቸውን፣በግል ተበዳይ ላይ ጉዳቱ የደረሰውም በኮብልስቶን ድንጋይ ላይ በመውደቁ መሆኑን፣1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በቦታው የነበሩ ቢሆንም በግል ተበዳይ ላይ የፈጸሙት ነገር አለመኖሩን የሚያመለክት ነው፡፡ተጠሪዎቹ በጠበቃቸው አማካይነት በሰጡት የሰበር መልስ ላይ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የግራ ቀኙን ማስረጃ የመመዘን ጉዳይን የሚመለከት እንጂ የመሰረታዊ የሕግ ስህተት ጥያቄን የሚያስነሳ ባለመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀት 10 ድንጋጌ አንጻር ሰበር ችሎቱ ጉዳዩን የመመርመር ስልጣን የለውም በማለት መከራከራቸውን ተገንዝበናል፡፡ እንደተባለው የዚህ ሰበር ችሎት ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ መርምሮ በማረም የተገደበ በመሆኑ በሕግ ስልጣን የተሰጣቸው የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገርን በማጣራት እና ማስረጃን በመመዘን ረገድ የደረሱበትን ድምዳሜ አግባብነት የመመርመር እና የማቃናት ስልጣን የለውም፡፡ይህ ማለት ግን የማስረጃ ምዘናው በሕግ ተቀባይነት ያላቸውን መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆዎች በጣሰ መልኩ በተከናወነ ጊዜ ጭምር ጉዳዩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ጥያቄን አያስነሳም ወደሚል ድምዳሜ ለማምራት የሚያስችል አይደለም፡፡በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ እና በውሳኔው ላይ የቀረበው የሰበር አቤቱታ የማስረጃ ምዘና ጉዳይን የሚመለከት እንጂ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ጥያቄን የሚያስነሳ ስላልሆነ ሰበር ችሎቱ አቤቱታውን የማስተናገድ ስልጣን የለውም በማለት ተጠሪዎቹ ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- በመሰረቱ የወንጀል ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከት ፍርድ ቤት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ የማስረጃውን አጭር መግለጫ፣ማስረጃውን የተቀበለበትን እና ያልተቀበለበትን ምክንያቶች በፍርዱ ላይ ማስፈር እንደሚገባው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ በቁጥር 149 (1) ስር ተመልክቷል፡፡በሌላ በኩል የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የማጽናት፣የማሻሻል ወይም የመሻር ስልጣን እንዳለው በዚሁ ሕግ ቁጥር 195 ስር የተደነገገ ቢሆንም በተለይ ውሳኔውን የሚሽረው ከሆነ እና የሚሽረውም በማስረጃ ምዘና ምክንያት ከሆነ በጉዳዩ ከቀረበው እያንዳንዱ ማስረጃ አንፃር በስር ፍርድ ቤት የተከናወነው የማስረጃ ምዘና ተቀባይነት የለውም የሚልበትን ምክንያት እና በስር ፍርድ ቤት የቀረበውን እያንዳንዱን ማስረጃ የተቀበለበትን እና ያልተቀበለበትን ምክንያቶች በፍርዱ ላይ ማስፈር የሚጠበቅበት በመሆኑ የማስረጃ ምዘናን አስመልክቶ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 149 (1) ስር የተመለከተው መስፈርት ተፈጻሚነት የሚኖረው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጭምር መሆኑን ከሁለቱ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ አያዳግትም፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎቹ ጸብ በማንሳት የደበደቡት እና ጉዳት ያደረሱበት መሆኑን የግል ተበዳይ የሆነው ግለሰብ ቀርቦ ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡የግል ተበዳይ ሽጉጥ ይዞ እንደነበረ በተጠሪዎቹ መከላከያ የተነገረ ቢሆንም ይህ የተባለው ሽጉጥ አልተያዘም፡፡ድርጊቱ የተፈጸመው ቀን ላይ በመሆኑ የግል ተበዳይ ሽጉጥ ይዞ ነበር የሚሉ ከሆነ ተጠሪዎቹ የግል ተበዳይን ከደበደቡት በኃላ ወደ ፖሊስ ጽ/ቤት እንደወሰዱት ሁሉ የግል ተበዳይ ይዞት ነበር የተባለውን ሽጉጥ ወይም የግል ተበዳይ ሽጉጡን አቀብሎታል የተባለውን እና ማንነቱ አልታወቀም የተባለውን ግለሰብ ጭምር ይዘው ለፖሊስ ማድረስ ያልቻሉበት ምክንያት ስለመኖሩ በመከላከያ ምስክሮች የተገለጸ ነገር የለም፡፡ይህም የግል ተበዳይ ሽጉጥ ይዞ እንደነበረ እና ጠብ ቀስቃሽም እንደነበረ በማስመሰል ተጠሪዎቹ እንደዋነኛ የመከላከያ ጭብጥ አድርገው በመከላከያ ምስክሮቻቸው ያስነገሩት ፍሬ ነገር የሌለ እና በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን በግልጽ መገንዘብ የሚያስችል ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪዎቹ የአመልካችን ማስረጃ አስተባብለዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰውም ይህንን በማስረጃ ያልተረጋገጠ ፍሬ ነገር እንደዋነኛ የመከላከያ ማስረጃ በመውሰድ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተከተለው የማሰረጃ ምዘና መርህ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በግል ተበዳይ ሰውነት ላይ መድረሱ በሕክምና ማስረጃ የተረጋገጠው የጉዳት ዓይነትም ቢሆን የሚያረጋግጠው እና የሚደግፈው በአመልካች ምስክሮች ከተመሰከረው ፍሬ ነገር ጋር እንጂ በተጠሪዎቹ የመከላከያ ምስክሮች ከተነገረው ፍሬ ነገር ጋር እንዳልሆነ ከግራ ቀኙ ምስክሮች ቃልና ከህክምና ማስረጃው ይዘት በግልጽ መገንዘብ የሚቻል ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በግል ተበዳይ ላይ በህክምና ማስረጃው ላይ የተመለከተው ጉዳት ሊደርስ የቻለው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተያይዞ በወደቀበት ጊዜ በኮብልስቶን ድንጋይ ጠርዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመመታቱ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ በግል ተበዳይ ላይ ስለደረሰው የጉዳት ዓይነት በህክምና ማስረጃው የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

- ሲጠቃለል ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በከፊል በመሻር እና በከፊል ደግሞ በማሻሻል የሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ በሕግ ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ምዘና መርህን የጣሰ በመሆኑ ምክንያት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡በሌላ በኩል ተጠሪዎቹ በማቅለያ ምክንያትነት እንዲያዙላቸው የተለያዩ ምክንቶችን በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ውድቅ የተደረጉባቸው ቢሆንም የቀደመ የወንጀል ሪከርድ ያለባቸው ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክር ባለመኖሩ እና የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች ሳላለመሆናቸውም በአመልካች በኩል የቀረበ ተቃራኒ ክርክር እና ማስረጃ ባለመኖሩ የቀደመ የዘወትር ጸባያቸው መልካምነት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው በሁለት የማቅለያ ምክንያቶች ተይዘው የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለቅጣቱ መነሻ አድርጎ ከያዘው እርከን 16 በሁለት እርከኖች ዝቅ ተደርጎ በእርከን 14 በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን መሰረት በቅጣቱ ረገድ ተገቢው መሻሻል ሊደረግበት የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሐረሪ ብ/ክ/መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12394 በ13/05/2007 ዓ.ም. የሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03061 በ24/08/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195 (2) (ሀ) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በተራ ቁጥር አንድ የተመለከተው ውሳኔ በሕግ ተቀባይነት ያለውን የማስረጃ ምዘና መርህ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስነናል፡፡
3. የሐረሪ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 40031 የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
4. በተራ ቁጥር ሶስት ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በሶስቱም ተጠሪዎች ላይ በወንጀል ሕግ ቁጥር 555 (ሐ) ስር በ24/11/2006 ዓ.ም. የተሰጠው የጥፋተኝነት የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
5. በተራ ቁጥር ሶስት ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በሶስቱም ተጠሪዎች ላይ በ29/11/2006 ዓ.ም. የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ በዚህ ጉዳይ ከአሁን በፊት የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሆኖ 1ኛ ተጠሪ አቶ ሕሊና ኃይሌ በሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት፣2ኛ ተጠሪ አቶ ፋሲካ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዕምሮ በሁለት ዓመት ከሰባት ወር ጽኑ እስራት፣3ኛ ተጠሪ አቶ መላኩ ደምሴ በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡

6. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመሆን ተጠሪዎቹን ተከታትሎ በመያዝ ለክልሉ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክባቸው እና ማረሚያ ቤቱም ተጠሪዎቹ ተይዘው ሲቀርቡለት ተረክቦ በቅጣት ውሳኔው መሰረት እንዲያስፈጽም ለሶስቱም አካላት ትዕዛዝ ይተላለፍ፡፡
7. በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት 2ኛ ተጠሪ የተወሰነባቸውን መቀጮ ብር 2,000 (ሁለት ሺህ) ከፍለው ከሆነ በሚያቀርቡት ደረሰኝ መሰረት እንዲመለስላቸው ተጠሪው ለሚጠይቁት አካል ይጻፍ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 119159
ሐምሌ 20 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተሻገር ገ/ሥላሴ
መ·ስጠፋ አህመድ
ተፈሪ ገብሩ
ሽምሱ ሲርጋጋ
አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ደጀኔ መኮንን ሀብተማርያም - ጠበቃ በራሳ በየነ - ቀረቡ
ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከሰሱት ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመሆን በ1ኛ ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና 453 (1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ሀሰተኛ ምስክርነት የመስጠት ወንጀል አድርገዋል፤በ2ኛ ክስ ደግሞ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና 375 (ሀ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ሀሰተኛ ሰነድ የመፍጠር ወንጀል አድርገዋል ተብለው ነው፡፡

የወንጀሎቹ አፈጻጸምም በ1ኛ ክስ ሚች አቶ ተፈሪ በቀለ ምንም ዓይነት ኑዛዜ ሳያደርጉ አመልካቹ በ16/04/1999 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርበው ሚች ለስር 1ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ዕፀገነት ተፈራ ጥቅም በ27/11/1998 ዓ.ም. ኑዛዜ አድርገዋል፣ኑዛዜው ሚች እየተናገሩ በሌላ ሰው የተጻፈ ነው፣ለሚችም ሆነ ለምስክሮች ተነቧል፣ኑዛዜ ሲያደርጉ አንደበታቸውም ሆነ ሕሊናቸው ትክክል ነበር በማለት ሀሰተኛ ምስክርነት ሰጥተዋል የሚል ሲሆን በ2ኛ ክስ ደግሞ ሚች ያደረጉት ኑዛዜ ሳይኖር ያለ አስመስለው ሌሎች ተከሳሾች ባዘጋጁት የኑዛዜ ሰነድ ላይ በምስክርነት በመፈረማቸው ሀሰተኛ ሰነድ ፈጥረዋል የሚል መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካቹ ያቀረቡት መቃወሚያ በብይን ታልፎ የእምነት ክደት ቃል ሲጠየቁ ድርጊቶቹን መፈጸማቸውን፣ይሁን እንጂ የፈጸሙት ሀሰተኛ ምስክርነት ለመስጠት አስበው ሳይሆን የኑዛዜው ተጠቃሚ ናቸው ከተባሉት የስር 1ኛ ተከሳሽ ባለቤት ጋር በአንድ መስሪያ ቤት ስለሚሰሩ በእኒሁ የስራ ባልደረባቸው የተነገራቸውን ነገር እውነት እንደሆነ አድርገው በመቀበል ነው የሚል ቃል በማስመዝገባቸው ፍርድ ቤቱ አመልካቹ ክደው እንደተከራከሩ መዝገቦ የዐቃቤ ሕግን አንድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምስክር ከሰማ እና የሰነድ ማስረጃ ከተቀበለ በኃላ ተጠሪው በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 142 (1) መሰረት መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ ብይን የሰጠ ቢሆንም የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ እንደማይችሉ በመግለጻቸው በስር 1ኛ ተከሳሽ በኩል የቀረበውን የሰው እና የሰነድ የመከላከያ ማስረጃ ከተቀበለ በኃላ በተከሳሾቹ ላይ በሁሉቱም ክሶች በክሱ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች ስር በመዝገብ ቁጥር 113071 በ17/08/2006 ዓ.ም. የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ቀጥሎም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መዝግቦ ቅጣቱን በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማስላት የጥፋተኝነት ውሳኔው በተመሰረተባቸው ድንጋጌዎች ስር ከተመለከተው የቀላል እና የጽኑ እስራት ቅጣት አማራጭ መካከል ተገቢ ሆኖ የተገኘው የጽኑ እስራት ቅጣቱ መሆኑን፣የወንጀሎቹ ደረጃ በዝቅተኛ ደረጃ የተመደበ መሆኑን፣በ1ኛ ክስ ለተመለከተው ወንጀል መነሻ ተደርጎ የተያዘው አንድ ዓመት ከስድስት ወር መሆኑን፣በ2ኛ ክስ ለተመለከተው ወንጀል መነሻ ተደርጎ የተያዘው ሁለት ዓመት መሆኑን፣ይህ የቅጣት መጠን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 (1) (ለ) መሰረት ሲደመር ሶስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት ሆኖ በእርከን 16 ስር የሚወድቅ መሆኑን፣ወንጀሉ ተደራራቢ በመሆኑ በመመሪያው አንቀጽ 22 (1) (ሀ) መሰረት በአንድ ማክበጃ ወደ እርከን 17 ከፍ የሚል መሆኑን፣ወንጀሉ የተደረገው በግብረአበርነት በመሆኑ ቅጣቱ በአንቀጽ 84 (1) (መ) መሰረት እንዲከብድ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣የአመልካቹ የዘወትር ፀባይ መልካምነት፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት እና በመንግስት እና በማህበራዊ ተቋማት የሰጡት ረዥም አገልግሎት እንደቅደም ተከተላቸው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 82 (1) (ሀ)፣82 (1) (ሠ) እና 86 ድንጋጌዎች መሰረት በሶስት የማቅለያ ምክንያትነት ሲያዙ እርከኑ ወደ 14 ዝቅ የሚል መሆኑን ገልጾ አመልካቹ በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሆኖ ነገር ግን የቤተሰብ ኃላፊ እና የልጆች አባት መሆናቸውን፣በርካታ አገልግሎት ፈጽመው በጡረታ ላይ የሚገኙ እና ዕድሜአቸውም ከ70 ዓመት በላይ መሆኑን በምክንያትነት በማስፈር የተወሰነባቸው የእስራት ቅጣት በአንቀጽ 192 ድንጋጌ መሰረት በሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ ከመፈጸም ታግዶ እንዲቆይ በ15/09/2006 ዓ.ም የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በስር 1ኛ ተከሳሽ እና በአመልካች ላይ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ከክብደቱ እና ከአፈጻጸሙ አንጻር የወንጀሉ ደረጃ ሊመደብ የሚገባው በመካከለኛ ደረጃ ሆኖ ሳለ በስር ፍርድ ቤት በዝቅተኛ ደረጃ የተመደበው አላግባብ መሆኑን፣በ1ኛ ክስ ለተመለከተው ወንጀል መነሻ ተደርጎ የተያዘው ሁለት ዓመት ከሁለት ወር መሆኑን፣በ2ኛ ክስ ለተመለከተው ወንጀል መነሻ ተደርጎ የተያዘው አራት ዓመት መሆኑን፣ይህ የቅጣት መጠን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 (1) (ለ) መሰረት ሲደመር ስድስት ዓመት ከሁለት ወር ጽኑ እስራት ሆኖ በእርከን 22 ስር የሚወድቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን፣ወንጀሉ ተደራራቢ ነው በሚል የስር ፍርድ ቤት የመመሪያውን አንቀጽ 22 (1) (ሀ) ጠቅሶ ቅጣቱን ማክበዱ ሕጋዊ መሰረት የሌለው መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤት አንድ የማቅለያ ምክንያት የሚያስቀንሰው አንድ እርከን ብቻ እንደሆነ አድርጎ የወሰነ በመሆኑ ምክንያት አመልካች ለእያንዳንዱ የማቅለያ ምክንያት ሁለት እርከን እንዲቀነስላቸው በዐቃቤ ሕግ ይግባኝ ላይ ያቀረቡት ጥያቄ ስነ ስርዓታዊ አለመሆኑን፣በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኙት ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች ቅጣቱ ከእርከን 22 ወደ እርከን 19 ዝቅ የሚል መሆኑን እና የቅጣት ገደብን አስመልክቶ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 197 (1) ከተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መካከል ለግል ተበዳይ ከፍለዋል የተባለ ካሳ ባለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው የገደብ ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ አለመሆኑን ገልጾ ውሳኔውን በማሻሻል አመልካች በአራት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ እና ቅጣቱንም በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲፈጽሙ በመዝገብ ቁጥር 111560 በ01/02/2008 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በሁለቱ ክሶች ጥፋተኛ የመባላቸውን አግባብነት ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61 (3) ድንጋጌ አንጻር፣እንዲሁም ለቅጣቱ አወሳሰን መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው ወይስ ቁጥር 2/2006 ነው? የሚሉትን ነጥቦች ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

1. አመልካቹ በሁለቱም የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ የተባሉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?
2. ቅጣቱ ሊሻሻል ይገባል ወይስ አይገባም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቹ ወንጀሎቹን ማድረጋቸውን ያልካዱ ከመሆኑም በላይ ሟች አቶ ተፈሪ በቀለ ከመሞታቸው በፊት በነበረባቸው ሕመም ምክንያት መናገርም ሆነ መጻፍ የማይችሉ የነበረ መሆኑ፣ሟች ያደረጉት ነው በተባለው ኑዛዜ ላይ ከስማቸው ትይዩ የተመለከተው ፊርማም የእርሳቸው አለመሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ የተረጋገጠ መሆኑ፣የስር 1ኛ ተከሳሽ ይህንኑ ኑዛዜ ለፍርድ ቤት አቅርበው በአመልካች ምስክርነት ጭምር በሀሰት ተናዛዡ አባታቸው እንደሆኑ በመግለጽ የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ከወሰዱ በኃላ የሟች ንብረት የነበረውን ቤት የሸጡ መሆኑ፣የግል ተበዳይ ናቸው በተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር አቤቱታ አቅራቢነት ኑዛዜውም ሆነ የኑዛዜ የወራሽነት ማስረጃው በፍርድ ቤት እንዲሰረዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደረገ መሆኑ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን እና ይህንኑ ማስረጃ ለማስተባበል አመልካቹ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻሉ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61 (3) ድንጋጌ ተጠቅሶ የተያዘውን ጭብጥ በተመለከተ ድንጋጌው ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መሆኑን የሚደነግግ ሆኖ የንዑስ ቁጥር (3) ድንጋጌም አድራጊው የተወሰነ ወንጀል ለማድረግ አሳብ አለው ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ በተለይም የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት በንብረት ላይ ወንጀል አድርጎ እንደሆነ ወይም የሐሰት ገንዘብ ሰርቶ እንደሆነ ወይም ይህንኑ ገንዘብ እንዲዘዋወር አድርጎ እንደሆነ ወይም ሀሰተኛ ሰነድ ሰርቶ ተጠቅሞበት እንደሆነ የመጀመሪያውን የጥፋት ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ሲል መሰረታዊ ከሆነው ወንጀል በኃላ አከታትሎ ያደረገው ድርጊት ከቀድሞ ሃሳቡና ሊደርስበት ካቀደው ግቡ ጋር የተያያዘ ሆኖ በዋናው ወንጀል እንደሚጠቃለል የሚደነግግ ነው።የዚህ ንዑስ ቁጥር ድንጋጌ ዓላማ እና ይዘት የሀሰት ገንዘብ የሰራ አንድ ሰው ገንዘቡ እንዲዘዋወር ካላደረገ በቀር ወይም ሀሰተኛ ሰነድ የሰራ ሰው ካልተጠቀመበት በቀር በወንጀሉ ያቀደውን ዓላማ ከግቡ ሊያደርስ የማይችል በመሆኑ ምክንያት ተከታትለው የተፈጸሙት አድራጎቶች በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ እንደተፈጸሙ ተቆጥረው በዋናው ወንጀል እንደሚጠቃለሉ እና አድራጊው የሚጠየቀው በአንድ ወንጀል መሆኑን የሚያመለክት ነው።በተያዘው ጉዳይ ሐሰተኛ ሰነድ የመፍጠሩ ወንጀል አስቀድሞ ከተጠናቀቀ እና ፍጻሜ ካገኘ በኃላ አመልካች በፍርድ ቤት ቀርበው ሟች ኑዛዜ ሲያደርጉ በምስክርነት ተገኝተው ማየታቸውን እና መስማታቸውን በማረጋገጥ የሀሰት ምስክርነት መስጠታቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 63 ድንጋጌ አነጋገር መሰረት በሁለቱ ወንጀሎች ተጠያቂነትን የሚያስከትል ከሚሆን በስተቀር በአንቀጽ 61 (3) ድንጋጌ አነጋገር መሰረት በአንድ ወንጀል የሚጠቃለል ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም አመልካቹን በሁለቱም የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም።

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቹ ወንጀሎቹን ያደረጉት በ16/04/1999 ዓ.ም. ሲሆን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው ደግሞ እንደቅደም ተከተሉ በ17/08/2006 ዓ.ም. እና በ15/09/2006 ዓ.ም. ነው።ይህንኑ ጊዜ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች ቅጣቱ የተሰላውም ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ የዋለውን የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ ነው።የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ይልቅ ለተከሳሽ ወገን ቅጣቱን የሚያቀለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ከሆነ ለቅጣቱ አወሳሰን መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው ይኸው መመሪያ ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 95440 እና በሌሎችም መዝገቦች በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ለቅጣቱ አወሳሰን መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው የቀድሞው መመሪያ መሆኑን ተገንዝበናል።ይግባኙን የተመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን ክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይቀበል የቀረው አመልካቹ የዚህ ዓይነት ክርክር ዐቃቤ ሕግ ባስከፈተው መዝገብ ላይ ማቅረብ አይችሉም በማለት ነው። በመሰረቱ አመልካች በስር የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው የጥፋተኝነት፣የቅጣት እና የገደብ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካልነበራቸው ይግባኝ የሚሉበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖራቸውም። ክርክሩ የወንጀል እንደመሆኑ መጠን ዐቃቤ ሕግ ባስከፈተው የይግባኝ መዝገብ ላይ ሕጉ የሚሰጣቸውን መብት መሰረት አድርገው የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት የለም። ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን በወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 88 (3) የተመለከተው ድንጋጌም ሆነ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው በቅጣት አወሳሰን መመሪያ የተካተቱት ድንጋጌዎች ይህንኑ የሚያመለክቱ ናቸው።በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ ባስከፈተው የይግባኝ መዝገብ ላይ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አስመልክቶ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ስነ ስርዓታዊ አይደለም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተያዘው አቋም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ለሁለቱ ወንጀሎች መነሻ ተደርጎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተያዘው ቅጣት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 (1) (ለ) መሰረት ሲደመር ስድስት ዓመት ከሁለት ወር ጽኑ እስራት ሆኖ በእርከን 22 ስር የሚወድቅ ሲሆን ይህ የቅጣት መጠን በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኙት ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች በቀድሞው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በእያንዳንዱ የማቅለያ ምክንያት በሁለት እርከን ዝቅ ሲደረግ ከእርከን 22 ወደ እርከን 16 ዝቅ የሚል በመሆኑ በአመልካቹ ላይ ለሚጣለው ቅጣት መነሻ ተደርጎ መያዝ የሚገባው በእርከን 16 ስር የተመለከተው የቅጣት ፍቅድ ስልጣን ነው።

ሲጠቃለል በአመልካቹ ላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ያልተቻለ በመሆኑ እና ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በአመልካቹ ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጥሎ የነበረው የቅጣት መጠን ግን ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአመልካቹ ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሁለቱም ክሶች በመዝገብ ቁጥር 113071 በ17/08/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111560 በ01/02/2008 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ፀንቷል።
2. በአመልካቹ ላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 111560 በ01/02/2008 ዓ.ም. የተሰጠውን የአራት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማሻሻል አመልካቹ በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ሁሉ ታስቦላቸው በሶስት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡

3. በተሻሻለው የጽኑ እስራት ቅጣት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመሸኛ ትዕዛዝ ጋር አመልካቹ ለሚገኙበት የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ፡፡
4. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይላክ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.118084

ሐምሌ 21 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

መ·ስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡-አቶ ንጉሴ አለ. አስፋው -ጠበቃ አወል ሰይድ ቀረቡ

ተጠሪ፡-የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ -ሰላማዊት ወንድሙ· ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተከሰሱት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 676 (2) (ሀ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል አድርገዋል ተብለው ነው፡፡የወንጀሉ አፈጻጸምም አመልካቹ በን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ በቀበሌ 15 የላፍቶ ቁጥር 1 ኮንዶሚኒየም ባለቤቶች ኃላፊነቱ የተወሰነ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ በዋና ገንዘብ ያዥነት በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጠው ሲሰሩ ከአባላቱ ከተሰበሰበው ገንዘብ ብር 823,617.00 ውስጥ ብር 749,997.00 ብቻ በማህበሩ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ገቢ አድርገው ልዩነቱን ብር 73,620.00 ገቢ ሳያደርጉ አጉድለው ተገኝተዋል ተብለው ሲሆን ያቀረቡት መቃወሚያ በብይን ታልፎ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ወንጀሉን አላደረኩም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ ሶስት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ከሰማ እና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቹ መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 142 (1) በሰጠው ብይን መሰረት ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አሰምተዋል፡፡ የተለያዩ ሰነዶችን በማስረጃነት አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በተጠሪ ማስረጃ የተመሰከረባቸውን ፍሬ ነገር በመከላከያቸው አላስተባበሉም በማለት በተከሰሱበት ድንጋጌ ስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመዝገብ ቁጥር 71523 በ24/06/2007 ዓ.ም. የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል።ቀጥሎም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መዝግቦ ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት በማስላት የጥፋተኛነት ውሳኔው በተመሰረተበት ድንጋጌ ስር ከተመለከተው የቀላል እና የጽኑ እስራት ቅጣት አማራጭ መካከል ተገቢ ሆኖ የተገኘው የጽኑ እስራት ቅጣት መሆኑን፣ወንጀሉ በመካከለኛ ደረጃ የተመደበ መሆኑን፣መነሻ ተደርጎ የተያዘው አራት ዓመት ሆኖ ይህ የቅጣት መጠን የሚወድቀው በአባሪ አንድ በእርከን 19 ስር መሆኑን፣የአመልካቹ የቀድሞ የዘወትር ፀባይ መልካምነት፣የቤተሰብ አስተዳዳሪነት እና የጤና ችግር በሶስት የማቅለያ ምክንያትነት ሲያዙ ቅጣቱ በስድስት እርከን ዝቅ ብሎ በእርከን 13 ስር የሚሸፈን መሆኑን ገልጾ አመልካቹ በሁለት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በ01/07/2007 ዓ.ም. ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በመዝገብ ቁጥር 145422 በ16/10/2007 ዓ.ም. ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ዐቃቤ ሕግ ተፈጻሚነት ያለው አዋጅ የህብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ስለሆነ በወንጀል ሕጉ ክስ መቅረብ የለበትም፣ክሴን አንስቻለሁ እያለ ፍርድ ቤቱ በክርክሩ ቀጥሎ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፣ይህ ቢታለፍ የእምነት ማጉደል ወንጀል ስለማድረጌ አንድም ኦዲተር ቀርቦ አላረጋገጠም በማለት በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል።

በዚህም መሰረት የስር ፍርድ ቤት አቤቱታ የቀረበበትን የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠው አመልካች ወንጀሉን አላደረኩም ቢሉም ከአባላት የሰበሰቡት እና ባንክ ያስገቡት የገንዘብ መጠን ሲቀናነስ መጠኑ በክሱ የተጠቀሰው ገንዘብ በጉድለት የተገኘባቸው መሆኑ በተጠሪው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ አመልካቹ ያቀረቡት መከላከያ የተጠሪውን ማስረጃ ለማስተባበል ያልቻለ መሆኑን በመግለጽ ሲሆን ፍሬ ነገርን በማጣራት እና ማስረጃን በመመዘን ረገድ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተደረሰበት ድምዳሜ ተመሳሳይ ስልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል።አመልካች በሰበር አቤቱታቸውም ቢሆን የህብረት ስራ ማህበራት የሂሳብ ምርመራ አዋጅ ቁጥር 147/1991 “ን” በሚያስፈጽመው አካል ካልሆነ በቀር በማህበሩ በራሱም ሆነ በሌላ አካል ኦዲት ሊደረግ አይችልም ከማለት በቀር የተገኘባቸው ጉድለት ስላለመኖሩ ያቀረቡት ክርክር የለም።አዋጁ አመልካቹ የሚሉት ዓይነት ትርጉም ያለው ስለመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ጠቅሰው የሚከራከሩባቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች አያመለክቱም።በማህበሩ የውስጥ ኦዲተርም ሆነ ሂሳቡን እንደገና ባጣራው ገለልተኛ ኦዲተር የተገኘው ጉድለት ተመሳሳይ ስለመሆኑም የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።

ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሃሳብ እንዳለው የሚቆጠር ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675 (3) የተመለከተው መርህ አመልካቹ ጥፋተኛ ለተባሉበት ድንጋጌም ተፈጻሚነት ያለው ነው።አመልካች በእጃቸው እንደገባ በተጠሪ ማስረጃ የተረጋገጠውን ገንዘብ በዚህ ድንጋጌ አነጋገር መሰረት ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋሉ መሆኑን ለማስረዳት እንዳልቻሉ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ በተከሰሱበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መባላቸው የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም።

በሌላ በኩል ተጠሪ ክሱን አንስቶ እያለ ፍርድ ቤቱ በራሱ ክርክሩን ቀጥሎ ውሳኔ ሰጥቶብኛል በማለት አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የተከራከሩ ቢሆንም ይህ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም።ይልቁንም መዝገቡ የሚያረጋግጠው ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ የቅጣት ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የክርክሩ አካል የነበረ መሆኑን ነው።በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ክሴን አንስቻለሁ በማለት የገለጸበት ጊዜ እንዳልነበረም ተጠሪው አሁን በሰበር መልሱ አረጋግጧል። በመሆኑም ተጠሪው በስር ፍርድ ቤት ክሱ ቢነሳ አልቃወምም ብሏል በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።አመልካች በጥፋተኝነት ውሳኔው ላይ ካልሆነ በቀር በቅጣት ውሳኔው ላይ ያቀረቡት የቅሬታ ነጥብ ካለመኖሩም በላይ የቅጣት ውሳኔውም የተሰላው አና የተወሰነው ሕጉን እና አግባብነት ያለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ በመሆኑ የቅጣት ውሳኔው የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 71523 በ24/06/2007 ዓ.ም. እና በ01/07/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 145422 በ16/10/2007 ዓ.ም. የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ፀንቷል።
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች እና አመልካቹ ለሚገኙበት አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ይላክ።ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ።
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።።

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117877

ሐምሌ 22 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ማስረሻ ገሰሱ

ተጠሪ፡- የፌ/ዐ/ሕግ ወይን ገ/እግዚአብሔር

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ አመልካች ላይ በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በክስ 1. ተከሳሽ የወ/ህ/አ 543(3) የተመለከተውን በመተላለፍ ሲያሽከረክሩት የነበረው ሲኖትራክ ገልባጭ መኪና የመጫን አቅሙ 132 ኩንታል ሆኖ እያለ 200 ኩንታል ሲሚንቶ ጭኖበት ከአዲሱ ገበያ ወደ ሰሜን ሆቴል አቅጣጫ ያለጥንቃቄ በቂ ርቀት ሳይጠበቅ ሲያሽከረክር ከፊት ለፊቱ በተመሳሳይ አቅጣጫ ሲሽከረከር የነበረውን ኤፍ ኤስ አር መኪና በሃይል ከፊት ለፊት አካሉ በመግጨት ወደ ቀኝ ከመንገድ ውጪ እንዲወጣ ካደረገ በኋላ አልፎ በመሄድ ሚኒባስ መኪና ገጭቶ መንገድ ዳር ላይ ቆመው ከነበሩ ላዳዎች ጋር በማጋጨት ሟች ጥሩ ደምሴ፣ ገነት ጽጌን እና ቁስ በቀለ ደምሴ ሕይወታቸው እንዲያልፍ በማድረጉ በፈጸመው በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሷል፡፡

በክስ 2. የወ/ሕ/ቁ. 559(2) የተመለከተውን በመተላለፍ በክስ 1. በተጠቀሰው አካኋን ተከሳሽ መኪኖችን ገጭቶ በማገጫጨት በእግረኛ መንገድ ላይ የነበረችውን ወ/ሪት ሄለን አበባን በፊት ለፊት አካሉ በመግጨት ከላይኛው መንጋጋዋ ላይ 2 ጥርሶችንና ከታችኛው መንጋጋዋ አንድ ጥርስ እንዲወልቅ በማድረጉ፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በክስ 3. የወ/ሕ/ቁ. 559(2) የተመለከተውን በመተላለፍ በክስ 1. በተጠቀሰው አካኋን ተከሳሽ መኪኖችን ገጭቶ በመገጫጨት የሰ/ቁ. 3-12333 ኦሮ ሚኒባስ መኪና ውስጥ ተሳፋሪ የነበረችውን ወ/ሪት አስቴር ከፊት የዳሌ አጥንት ስብራት እንዲደርስባት ያደረገ በመሆኑ በፈጸመው በቸልተኝነት የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል፡፡

በክስ 4. የወ/ሕ/ቁ. 572(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በክስ 1. በተጠቀሰው አካኋን ኤፍ.ኤስ.አር መኪና ገጭቶ ከመንገድ ወጥቶ ከሌላ መኪና እና ሱቅ ጋር በማጋጨት ብር 45,000 የሚገመት ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ በመሆኑ በፈጸመው የትራፊክ ደንብ በመጣስ በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) በአራቱም ክሶች ላይ የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶችን መፈጸማቸውንና ጥፋተኛ መሆናቸውን በማመናቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 134(1) መሰረት ፍ/ቤቱ በተከሳሽ ላይ በአራቱም ክሶች የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መዝገብ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 መሰረት በማስላት በየክሶቹ አራት የማቅለያ ምክንያቶችን ወስዶ በክስ 1. ተከሳሽ በ 3 አመት ከ 3 ወር እስራት እና በብር 2000 የገንዘብ ቅጣት በክስ 2 ተከሳሽ በ 2 ወር እስራት እና በብር 1000 የገንዘብ ቅጣት በክስ 3 ተከሳሽ በ 3 ወር እስራት እና በብር 1000 የገንዘብ ቅጣት በክስ 4 አፈጻጸሙን ዝቅተኛ በማድረግ በ 3 አመት ከ 10 ወር እስራት አና በብር 500 የገንዘብ መቀጮ በድምሩ በ 3 አመት ከ 10 ወር እስራት እና በብር 5000 የገንዘብ ቅጣት ተከሳሽ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ቅጣቱም በገደብ እንዲቆይ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ የቅጣት ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራቀኙን አከራክሮ የተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184(1)(ለ) ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈጸመ ወንጀል ተገቢ ቅጣት ተወስኖ እንደሚደመር ያስረዳል፡፡ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 22 (1(ሀ) እና 23(5) የተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 184(1)(ለ) የተከተለ ሆኖ ወደ ቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያዎች ከመግባቱ በፊት የእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ተደምሮ ድምሩ የሚያርፍበት ዝቅተኛው የእስራት ቅጣት እርከን ተለይቶ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የስር ፍ/ቤት በዚህ አግባብ ሳይሆን በእያንዳንዱ ወንጀል የእስራት ቅጣት እርከን ላይ የቅጣት ማቅለያዎችን በመጠቀም በተናጠል በየክሱ ቅጣቱን በማቅለል የወሰነው ከህጉ ውጭና መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ክስ 1. ደረጃ 2 እርከን 21 የገንዘብ መቀጮ ደግሞ እርከን 6 ይሆናል፡፡ መ/ሰጪ የ 3 ሰዎች ሕይወት እንዲጠፋ ስላደረገ መነሻ ቅጣት 6 ዓመት ጽኑ እስራት በክስ 2 በወንጀሉ ድርጊት የግል ተበዳይ 3 ጥርሶች የወለቁ በመሆኑ ወንጀሉ ደረጃ 3 እርከን 9 የገንዘብ መቀጫ እርከን 3 ይሆናል፡፡ 1 አመት ከ 6 ወር እስራት ወደ ጽኑ እስራት ሲለወጥ በ 9 ወር ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት በክስ 3 መነሻ ቅጣት ደረጃ 1 እርከን 7 ላይ የእስራት ቅጣቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደ ጽኑ እስራት በመለወጥ በ 7 ወር ጽኑ እስራት በክስ 4 የእስራት ቅጣቱን ወደ ጽኑ እስራት በመለወጥ በ 3 ወር ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት በመወሰን የአራቱንም ተደራራቢ ወንጀሎችን መነሻ ቅጣት በመደመር 7 አመት ከ 7 ወር ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት ይዞ በአራት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መነሻ ቅጣቱ ካረፈበት እርከን 24 ወደ እርከን 20 ዝቅ በማድረግ መ/ሰጪ (የስር ተከሳሽ) ለፈጸመው ወንጀል በ 5 አመት ከ 4 ወር ጽኑ እስራት እና በብር 7,000 የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ በመወሰን የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ገደብ ውሳኔ በማንሳት መ/ሰጪ የጽኑ እስራት ቅጣቱን እንዲፈጽም የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ ውሳኔ ላይ ተፈጸመ ያሉትን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ለማሳረም ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ የጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ገደብን አስመልክቶ ይግባኝ ባልተባለበት ቅጣት ማቅለያዎችን ከተቀበለ በኋላ የመጨረሻውን 5 አመት ከ 4 ወር በማሳደግ መወሰኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194(2)(ሐ) እና ከቅጣት አወሳሰን መርህ አንጻር ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ አቤቱታው እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ አመልካች ላይ በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት አራት የወንጀል ክሶችን ያቀረበ ሲሆን አመልካች የተከሰሱባቸውን አራቱም ክሶች ላይ የተመለከተውን ወንጀል መፈጸማቸውን በማመናቸው ፍ/ቤቱ በአራቱም ክሶች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ቅጣት ሲወሰን በወ/ሕ/አንቀጽ 184(1(ለ) እና በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 21(1)(ሀ) መሰረት ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት በመወሰን እና መነሻ ቅጣቶቹን በመደመር ድምሩ የቅጣት መጠን የሚያርፍበትን ዝቅተኛ የቅጣት እርከን በመምረጥ ለይቶ በመቀጠል ወደ ቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶችን በማገናዘብ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ተገቢ ነው የሚለው ቅጣት መወሰን ሲገባው አመልካች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠባቸው አራት ወንጀሎች በእያንዳንዱ ወንጀል በተናጠል አራት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመውሰድ ቅጣት ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ የስር ፍ/ቤት ቅጣት አወሳሰን ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ የስር ከፍ/ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን የወንጀል ሕጉን እና የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን የተከተለ ባለመሆኑ በማረም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 መሰረት ለአራቱ ወንጀሎች በተናጠል መነሻ ቅጣት ወስኖ በመደመር ድምሩ የሚያርፍበትን ዝቅተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እርከን ከለየ በኋላ ለአመልካች ለስር ፍ/ቤት የተያዘላቸውን 4 ማቅለያ ምክንያቶች ወስዶ በእርከን 20 ከተመለከተው የቅጣት ፍቅድ ስልጣን በ 5 አመት ከ 4 ወር ጽኑ እስራት እና በብር 7,000 የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጡ እና የተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ ከ 5 አመት በላይ ጽኑ እስራት በመሆኑ አመልካች የቅጣት ውሳኔውን በማ/ቤት ሆነው እንዲከታተሉ የሰጠው ውሳኔ የወ/ሕጉን አንቀጽ 184(1(ለ) ፣ 194(1)ለ) እና የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 21 (1(ሀ) እና 23(5) መሰረት ያደረገ ነው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው ይግባኝ የስር ፍ/ቤት ቅጣት አሰላል ላይ የተፈጸመው ግድፈት ይታረምልኝ አለ እንጂ ቅጣቱ ከፍ ተደርጎ ይወሰንልኝ አላለም ያሉ ቢሆንም ተጠሪ ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት 4 ማቅለያ ምክንያቶችን ከወንጀል ሕጉ እና ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው ውጭ በመደጋገም ለእያንዳንዱ ወንጀል በመጠቀም ቅጣት መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ በክስ 2 ደረጃ እና እርከን አለአግባብ ተይሟል በአራቱም ክሶች ላይ የተፈጸመው የቅጣት አሰላል ግድፈት ይስተካከልን በማለት ያቀረበውን ቅሬታ ተከትሎ ከፍ ሲል እንደተገለጸው በወንጀል ህጉ እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤትን የቅጣት ውሳኔ በማረም መወሰኑ በይግባኝ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጭ ወስኗል የሚያስብል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ አቤቱታ ግራቀኙን አከራክሮ የስር ፌ/ከፍ/ፍ/ቤትን የቅጣት አወሳሰን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184(1)(ለ) እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 21(1) (ሀ) እና 23(5) መሰረት በማረም መወሰኑ እና አመልካች ላይ የተወሰነው ቅጣት ከ 5 አመት ጽኑ እስራት በላይ በመሆኑ በወ/ሕጉ አንቀጽ 194(1)(ለ) መሰረት የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ገደብ ውሳኔ በማንሳት አመልካች የተወሰነባቸውን 5 አመት ከ 4 ወር ጽኑ እስራት በማ/ቤት ሆነው እንዲፈጽሙ የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 107679 በቀን 19/10/2007 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195(2)(መ) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 119500

ሐምሌ 22 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፀሀይ ውብዬ } አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የፌደራል/ዓ/ህግ }

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግስት ማህተምን ያለአግባብ መገልገል መከራ ወንጀል የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች እና አብረዋቸው በተከሰሱ ተከሳሾች ላይ ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ላይ የቀረበው ክስ ይዘት ተከሳሽ ለመንግስት ስራ የሚውል ማህተምን ያላግባብ ለመገልገል አስባ በዐ/ህግ 3ኛ ምስክር አማካኝነት ለወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል (1ኛ ተከሳሽ) 1000 ብር ከፍላ የኢት/ንግድ ባንክን ማህተም ከባንኩ ሰርቃ እንድታመጣላት ካደረገች በኃላ በምስክሯ ጥቆማ የተያዘች በመሆኑ የወ/ህ/አ 27(1) እና 363 (1) (ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ የመንግስት ማህተም ያለአግባብ መገልገል መከራ ወንጀል ተከሰላች የሚል ነው፡፡

አመልካች (የስር ተከሳሽ) በክሱ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት በመካዳቸው ዐ/ህግ ማህተመ የጠፋበት የኢት/ን/ባንክ ሱማሌ ተራ ቅርንጫፍ ሠራተኞችን ጨምሮ 3 ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱ ከዐ/ህግ ምስክሮች 1ኛ ተከሳሽ የሆኑት ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል በተጨማሪ ምስክርነት ሰምቶ አመልካች ክሱ የቀረበበትን የወንጀል ድርጊት ለመፈፀማቸው የተመለከረባቸው በመሆኑ እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ሲሆን አመልካች የሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መከላከያ ማስረጃ የለኝም በሚሮን ሚካኤል የግል ስልክ በወቅቱ ስለመደወሌ ከኢት/ቴሌኮም ዝርዝር ቀርቦ ይታይልኝ ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱ ከሰኔ ወር መጀመሪያ እስከ ሐምሌ ወር መጨረሻ 2006 ዓ/ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል በግል ስልካቸው የተደወለ የስልክ ቁጥር ዝርዝር እንዲቀርብ ባዘዘው መሠረት ከኢት/ቴሌኮም በቀረበው ዝርዝር ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል በሚጠቀሙበት ስልክ ቁጥር አመልካች በሚሰሩበት የመከላከያ ሚ/ር የቢሮ ስልክ ቁጥር ላይ ተደውሎ የነበረ መሆን አለመሆኑን ባያሳይም ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል ስልክ ላይ ተከሳሽ አልደወለችም ብሎ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያዳግት ነው በማለት አመልካች (ተከሰሽ) በተከሰሱበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ናቸው ብሎ በመወሰን የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያያት በማገናዘብ በቅጣት አወሰሰን መመሪያው ቅጣቱን በማስላት በ3 ዓመት ከ3 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን ለፌ/ክልል ፍ/ቤት በይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር አመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔን በማፅናት ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ የቀረ እና በመንግስትና በህዝብ ላይ የደረሰ ጉዳት ባለመኖሩ ስር ፍ/ቤት የወንጀሉን ደረጃ በቀላል ደረጃ መመደብ ሲገባው መካከለኛ ደረጃ መመደቡ ተገቢ አይደለም ብሎ የወንጀሉን ደረጃ በቀላል ደረጃ በመመደብ መነሻ ቅጣት 3 ዓመት ወስኖ በ2 ማቅለያ ምክንያቶች ቅጣቱ ወደ 2 ዓመት ፅኑ እስራት በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተፈፀመ ያሉትን መሠረታዊ የህግ ስህተት በመጥቀስ እንዲታረምላቸው የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት የተወሰነባቸው በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የህግ አንቀጽ የሚያቋቁም ድርጊት መፈፀማቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ መሆን አለመሆኑን እና በዚህ ጉዳይ በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩትና ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤልን በአመልካች ክስ በማጣሪያ ምስክርነት ጠርቶ የመስማቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ ምክንያት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉት የወ/ህጉን አንቀጽ 27(1) እና 363 (1) “ለ” የተመለከተውን ተላልፈው ለመንግስት ስራ በተዘጋጀ ማህተም ያለ አግባብ መገልገል ሙከራ ወንጀል ሲሆን የድንጋጌው ይዘት ለመንግስት ስራ ጉዳይ ብቻ የሚታተምበትን የመንግስትን ወይም የመንግስታዊ አካላት የአንዱን ማህተም ያለአግባብ የተገለገለ እንደሆነ ከ3 ዓመት እስከ 10 ዓመት ሊደርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚችል ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡ አመልካች ለኢት/ንግድ ባንክ ሱማሌ ተራ ቅርንጫፍ መገልገያነት የተዘጋጀውን የመንግስት ማህተም በተጠሪ 3ኛ ምስክር እና በስር 1ኛ ተከሳሽ በሆኑት የባንኩ ተላላኪ ሠራተኛ አማካኝነት ማህተሙን ተቀብለው የባንኩ ተላላኪ ሠራተኛ ለሆኑት የስር 1ኛ ተከሳሽ ብር 1000 መላካቸው ስር ፍ/ቤት በቀረበው ማስረጃ በማረጋጋጥ አመልካች ላይ ያሳለፈው የጥፋተኝነት ውሳኔ በህጉ አግባብ በመሆኑ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም በሌላ በኩል አመልካች የተከሰሱት እና የጥፋተኝነት ውሳኔ የተላለፈባቸው በሙከራ ደረጃ በቀረ ወንጀል በመሆኑ በወ/ሕ/አንቀጽ 31 እንደተመለከተው ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት የሙከራ ወንጀል ድርጊት የደረሰ ጉዳት ከሌላ በወ/ህ/ቁ. 180 በተመለከተው መሠረት ቅጣቱን በመሰለው እንደሚያቀል የተደነገገ በመሆኑ እና በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ቀደም ሲል እንደነበረው የቅጣት አወሳሰን በሙከራ ደረጃ ለተፈጸመ ወንጀል ቅጣት እንደሚቀንስ በግልጽ ባይመለከትም በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 24 ስር በወንጀል ህጉ ቅጣትን በመሰለው እንዲያቀል በፈቀደ ጊዜ ፍ/ቤቱ በመመሪያው ሳይወሰን ቅጣትን በማቅለል እንደሚወሰን የተመለከተ በመሆኑ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በተመሳሳይ በሰ/መ/ቁ. 104937 አስገዳጅነት ያለው የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ የቀረ መሆኑን መሠረት በማድረግ የስር ፍ/ቤት ቅጣቱን በመሰለው ማቅለል ሲገባው ይህን በማለፍ በቀረቡለት 2 ማቅለያ ምክንያቶች ላይ ብቻ በመወሰን የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ሊታረም የሚገባው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 121682 በቀን 6/11/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 001102 በቀን 18/2/2008 ዓ/ም የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 195(2) (ለ) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ያሳለፈው የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
3. አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል በሙከራ ደረጃ የቀረ እና በመንግስት ላይ የደረሰ ጉዳት ባለመኖሩ የወ/ህጉን አንቀጽ 27(1)፣31፣ 180፣ እና 363(1) (ለ) እንዲሁም የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 24 መሠረት በማድረግ ለአመልካች ስር ፍ/ቤት የተያዘላቸውን ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችንም ከግምት በማስገባት አመልካች ለፈፀሙት ጥፋት ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የታሰሩበት የሚታሰብላቸው ሆኖ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ውሳኔ በመሻሻል ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. አመልካች ታስረው የሚገኙበት ማ/ቤት በዚህ በተሸሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ይፃፍ ብለናል መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102982

መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዩ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የትግራይ ብሔራዊ ክልል ዓ/ህግ -- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ቡሽራ ያህያ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይ/ሠ/ችሎት በመዝገብ ቁጥር 99191 ሰኔ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች በቁጥር 1043/45/06 ሐምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ክርክሩ የወንጀል ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በጀመረበት በትግራይ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው አመልካች በቁጥር 18162/05 ህዳር 06 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ የወንጀል ክስ በአሁኑ ተጠሪና በሌሎች ሁለት ግለሰቦች ላይ በማቅረባቸው ሲሆን በ1ኛ ክስ የተጠቀሰውና ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ክስ ይዘት በአጭሩ ሲታይ ተጠሪው የፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 በአንቀጽ 8 ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ሲሆን ውቅሮ ከተማ በሚገኝ መኖሪያ ቤቱ ውስጥ ለሽብር ተግባር ለማዋል በማሰብ የኢህአዴግ መንግስት የአሜሪካንና የአይሁዶች መንግስታት ጥቅም ለማስጠበቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፀረ እስላም እንቅስቃሴ የሚያደርግና የእስላም አንድነት ለማጥፋት የሚሠራ መንግስት መሆኑን የሚገልፁ፤ አህባሽ የሳውዲና የምዕራባዊን ተልዕኮ የሚያስፈፅም በእስልምና ሐይማኖት ላይም ክህደት የሚፈፅም ቡድን በመሆኑ ለመንግስትና ለመጅሊስ እውቅና መስጠት የለብንም የሚልና ሁሉም የእስልምና ሐይማኖት ተከታይ በኢህአዴግ መንግስት በፀሎት ተቃውሞውን ያቅርብ የሚል ይዘት ያላቸው ለሽብር ተግባር የሚያነሳሱ ሲዲዎችን ይዞ የተገኘ በመሆኑ ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈፀሚያነት ንብረት መያዝ ወይም መጠቀም ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነበር፡፡

ተጠሪም ፍርድ ቤት ቀርበው ክሱን ክደው የተከራከሩ ሲሆን አመልካች የሰው ምስክሮችንና ሌሎች ጠቃሚ ናቸው ያሏቸውን ማስረጃዎች አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የትግራይ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የአመልካችን ክስና ማስረጃ በመመርመር ተጠሪ እንዲከላከል ትዕዛዝ ሰጥቶ መከላከያ ምስክሮችን ሰምቷል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ በአመልካች ማስረጃ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጁን አንቀፅ 8 ድንጋጌ በመተላለፍ ለሽብር ተግባር የሚያገለግሉ ንብረቶችን ይዞ የመገኘት ወንጀል ስለመፈፀሙ የተነገረባቸውን በመከላከያ ማስረጃቸው ማስተባበል አልቻሉም በማለት በተከሰሱበት ድንጋጌ የጥፋተኝነት ፍርድ ሰጥቶ ቅጣቱን በመመሪያው መሠረት በማስላት ተጠሪው በስድስት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ፍርድ ቤቱ ቅሬታው መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሮ ሲያበቃ ከተጠሪ ቤት ውስጥ የተገኙት ሲዲዎች የያዙት ንግግር በቴፕ ተደርጎ ሲደመጥ የኢህአዴግ መንግስት ሙስሊሞችን እንደሚጨቁን፤አልሀባሽ የሚባለው የመንግስት ካድሬ እንዳልሆነ፤ነባሩ የእስልምና ሐይማኖት ፈርሶ በአዲስ እንዲተካ እንደሚጠይቅ፤ ውሃብያ ሐይማኖት እንዲስፋፋ እንደሚፈልግ፤መንግስት በሀይማኖት ጣልቃ እንደሚገባ እና የመጅሊስ ነባር አባላት የመንግስት ፈፃሚዎች ስለመሆናቸው የሚገልፅ መልዕክት የያዘ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ገልፆ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የሚያቋቁሙት ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈጸሚያ እንዲውሉ ተጠሪው ንብረት መያዝን ሳይሆን በወንጀል ህጉ አንቀጽ 486(ለ) ስር የሚሸፈን የሐይማኖት ሁከት የመቀስቀስ ወንጀልን ነው በማለት በዚሁ አግባብ የጥፋተኝነት ፍርድ በመስጠት ቅጣቱን አስልቶ ተጠሪ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይ/ሠ/ችሎት ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታው በአጭሩ ተጠሪ የፈጸመው ድርጊት አመልካች ጠቅሶ ያቀረበውን የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 8 ሥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁም ሆኖ እያለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያላግባብ ህጉንና ድንጋጌውን በመለወጥ ወስኗል የሚል ነው።

ሰበር አጣሪው ችሎትም መዝገቡን መርምሮ ተጠሪው ጥፋተኛ መባል ያለበት በፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 8 ነው ወይስ በወንጀል ህግ አንቀጽ 486(ለ) ነው? የሚለውን ነጥብ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካች የመልስ መልሳቸውን ሊያቀርቡ ባለመቻላቸው መብታቸው መታለፉን ከመዝገቡ ተረድተናል።

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል። እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል። እንደመረመርነውም ከተጠሪው ቤት የተገኙት ሲዲዎች ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈፀሚያነት እንዲውሉ ታስበው የተያዙ ለመሆናቸው በፍሬ ነገር ደረጃ አመልካች አረጋግጧል ወይ? የሚለው ጭብጥ ምላሽ ማግኘት ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል።

ኢትዮጵያ በ2001 ዓ.ም ያወጀችው የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ለሽብር ድርጊት በቂ የህግ ማዕቀፍ ለመስጠት ታስቦ ከመደበኛው የወንጀል ህግ በተሻለ ሁኔታ ከሽብር ጋር የሚገናኙ ድርጊቶች ወንጀል በማድረግ የሽብር ወንጀልን መከላከልና መቆጣጠር ለማስቻል ታስቦ የወጣ አዋጅ ነው። ስለሆነም አመልካች ለክርክራቸው መሠረት ያደረጉት የፀረ ሽብርተኝት አዋጅ አንቀጽ 8 ድንጋጌ ለሽብርተኝነት ድርጊት መፈፀሚያነት እንዲውል ንብረት መያዝ ወይም መጠቀምን ወንጀል አድርጎ ደንግጎታል። የድንጋጌውን ሙሉ ይዘት ስንመለከት ማንኛውም ሰው የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ወይም እንዲፈፀም ለማመቻቸት እንደሚውል እያወቀ ወይም እንዲውል በማሰብ ማናቸውንም ንብረት የያዘ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአምስት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል በማለት ደንግጓል።

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ማስረጃ አቅርቦ ያረጋገጣቸው ፍሬ ነገሮች የተጠሪው ቤት ብርበራ ተደርጎ ሲዲዎች መገኘታቸው፤ እነዚህ ሲዲዎች የያዙት መልዕክትም ሲደመጥ የኢህአዴግ መንግስት ሙስሊሞችን እንደሚጨቁን፤አልሀባሽ የሚባለው የመንግስት ካድሬ እንደሆነ፣ ነባሩ የእስልምና ሐይማኖት ፈርሶ በአዲስ እንዲተካ እንደሚጠይቅ፤ ውሃብያ ሐይማኖት እንዲስፋፋ እንደሚፈልግ፤መንግስት በሀይማኖት ጣልቃ እንደሚገባ እና የመጅሊስ ነባር አባላት የመንግስት ተልዕኮ ፈፃሚዎች ስለመሆናቸው የሚገልፅ መልዕክት የያዙ ለመሆናቸው የሚያስረዱ ሲሆኑ ተጠሪው እነዚህን ሲዲዎች የያዟቸውን መልዕክቶችና ሲዲዎችን የሽብርተኝነት ተግባር እንዲፈፀም ለማመቻቸት አስቦ የያዘ ለመሆኑ የሚያረጋግጡ ፍሬ ነገሮች ለመኖራቸው አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ የመስማትና የማጣራት ሥልጣን ላላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ባቀረቡት ማስረጃ አላረጋገጡም፡፡

ወንጀልና አፈፃጸሙን በተመለከተ በሚደነግገው የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 23(2) ሥር እንደተደነገገው የሚያስቀጣ ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፤ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ በልዩ ሁኔታ በህግ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሽ ከዞረባቸው ጥቂት ወንጀሎች ውጭ በወንጀል የክርክር ሂደት በበቂና አሳማኝ ሁኔታ ፍሬ ነገርን የማስረዳት ሸክም በዐ/ህጉ ላይ የተጣለ ኃላፊነት ለመሆኑ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 141 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ አንቀጽ 8 ሥር የሚገኙ ፍሬ ነገሮች የማስረዳት ሸክም በልዩ ሁኔታ ወደ ተከሳሹ የዞረ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፤ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የማስረዳት ሸክሙን የመወጣት ግዴታ እንዳለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም አመልካች በተጠሪው እጅ ከላይ የተገለፀውን መልዕክት የያዙ ሲዲዎች መገኘታቸውንና በሲዲዎች ያለው መልዕክት ሲደመጥ ከላይ የተገለፀው መሆኑን በማስረዳቱ ብቻ አመልካች የያዛቸው ሲዲዎችም ሆኑ በውስጣቸው የነበሩት መልዕክቶች ለሽብረተኝነት ተግባር ለማመቻቸት የታሰቡ ነበሩ ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የትግራይ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪው ስለመፈጸሙ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች በፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 8 ሥር የሚሸፈን ወንጀልን ያቋቁማሉ በማለት መወሰኑ አመልካች የማስረዳት ሸክሙን ባልተወጣበት ሁኔታ የተወሰነ ስለነበር የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ተጠሪው የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀም ወይም እንዲፈፀም ለማመቻቸት እንደሚውል እያወቀ ወይም እንዲውል በማሰብ ማናቸውንም ንብረት የያዘ ወይም የተጠቀመ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ በውጤት ደረጃ የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 99191 ሰኔ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195(2)(ለ)(2) በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 108550

መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች - አልማው ወሌ
ተፈሪ ገብሩ
አብርሃ መሰለ
አብዬ ካሳሁን
እትመት አሰፋ

አመልካች - የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን - ዓቃቤ ህግ አልቀረቡም

ተጠሪ - አቶ ልዑል አዳሙ ብዙነህ --ጠበቃ መአሪፍ ሰዒድ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪው የኮንትሮባንድ ዕቃ የጫነው መኪና ሾፌር እና ባለቤት ከመሆኑም በላይ ወንጀሉ በታወቀበት ጊዜም መኪናውን ያሽከረክር የነበረው እሱ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በነፃ ይሰናበት መባሉ እና፤ መኪናውም የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ ሲንቀሳቀስ የተገኘ ሆኖ እያለ ይለቀቅ መባሉ ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 እና 104 አንፃር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

እንደመረመርነው የክሱ መነሻ ንብረትነቱ የስር 1ኛ ተከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) በሆነውና እራሱ በሚያሽከረክረው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-93060 አ/አ በሆነ FSR መኪና ላይ ሆን ብሎ ህገወጥ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ከ2ኛ ተከሳሽ አቶ ጉሌ እንዳለ (ረዳቱ) ጋር በመተባበር የ3ኛ ተከሳሽ አቶ ወገኔ ወርቅነህ ንብረት የሆኑትን 5 ካርቶን ጥፍር መቁረጫ፤ 3 ብርድ ልብስ እና ሁለት ጎማ ጭኖ መስከረም 4 ቀን 2007 ዓ.ም ከምሽቱ 6፡00 ሰዓት ከሃረር ወደ መሃል አገር ሲጓዝ አዋሽ ጉምሩክ ኬላ በፍተሻ ተይዟል በሚል በሶስቱም ተከሳሾች ላይ የወንጀል ህግ ቁጥር 32(1)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ተጠቅሶ ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

ተጠሪ ድርጊቱ መፈፀሙን ገልፆ ነገር ግን እኔ አልፈፀምኩትም ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ክዶ የተከራከረ ሲሆን፤ 2ኛ ተከሳሽ (ረዳቱ) በበኩሉ ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ እቃዉን ጭኛለሁ ኮንትሮባንድ መሆኑን አላወኩም አይቼ ባለመጫኔ ጥፋተኛ ነኝ 1ኛ ተከሳሽ አያውቅም ነበር ብሏል፡፡ 3ኛ ተከሳሽ በበኩሉ ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ ንብረቱ የእኔ ነው ጥፍር መቁረጫ ኮንትሮባንድ መሆኑን ባለማወቅ ፈፅሜያለሁ ማወቅ ነበረብኝ ጥፋተኛ ነኝ በማለት አምኗል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የገቢ ረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችን እንደ ክሱ ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው አምነዋል በማለት ባመኑት መሰረት ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወስኗል፡፡ 1ኛ ተከሳሽን በተመለከተ የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች በወቅቱ ፍተሻ ሲደረግ ተጠሪ የሚያሽከረክረው መኪና ላይ ዕቃውን ማግኘታቸውን ከመመስከራቸው ውጭ እንደ ክሱ አቀራረብ ሆነ ብሎ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት ብሎ የፈፀመው ለመሆኑ አለማረጋገጣቸውን፤ ተከሳሹም ዕቃው መገኘቱን ሳይክድ በእኔ እውቅና አልተጫነም በማለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ማሰማቱን፤ የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች በእለቱ ከተከሳሽ ጋር የራሳቸውን መኪና ይዘው የሽንኩርት ጭነት ጭነው ሳይለያዩ ተከታትለው መንዛቸውን አሰበ ተፈሪ ላይ ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት ሲሆን አንድ ላይ እራት ሲበሉ ረዳቱ (2ኛ ተከሳሽ) አለመኖሩን እና 3ኛ ተከሳሽ አሰበ ተፈሪ ከተማ ላይ የተሳፈረ መሆኑን፤ 1ኛ ተከሳሽ ዕቃው በፍተሻ ሲገኝበት ጉድ ሰራኝ አሰበ ላይ ተማሪ ነው ብሎ ያሳፈረው ሰው ብሎ ሲናገር እንደነበርና በማያውቀው ሁኔታ እራት በሚበሉበት ሰዓት 2ኛ ተከሳሽ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ድርጊቱን መፈፀሙን ማስረዳታቸውን፤ እንዲሁም 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ዕቃውን የጫኑት 1ኛ ተከሳሽ ሳያውቅ እንደነበር የሰጡት የዕምነት ቃል የመከላከያ ማስረጃውን እንደሚያጠናክር፤ ተጭኖ ለነበረው ጎማ የዕጅ በዕጅ ሽያጭ ደረሰኝ መቅረቡን በመጥቀስ ተጠሪ ድርጊቱን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ያልፈፀመው ስለመሆኑ፤ ይልቁንም ሊጠረጥር ወይም ሊገምት በማይችልበት ሁኔታ ከእውቅናው ውጭ የተፈፀመ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አረጋግጧል በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 149(2) መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በነፃ የተሰናበተ በመሆኑም የተያዘውን መኪና በተመለከተ በአዋሽ ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ በአስተዳደር የገንዘብ ቅጣት ተቀጥቶ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ እና ትዕዛዝ በመቃወም ለአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ በወንጀሉ ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው በመላ ሃሳቡ እና እውቀቱ ለፈፀመው ተግባር እንጂ ከእሱ እውቅና ውጭ ሌሎች ሰዎች በፈፀሙት ተግባር አብሮ ስለነበር ብቻ ኃላፊ እና ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም፤ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ስለተሰጠ ብቻ በድርጊቱ ምንም አይነት ተሳትፎ ያልነበረውን ባለንብረት በማያውቀውና ባልተመሰከረበት ነገር ጥፋተኛ ማድረግ ስለማይገባና የዓቃቤ ህግን ክስና ማስረጃ በሚገባ ስለተከላከለ ከክሱ በነፃ እንዲሰናበት መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ከፍ ሲል በመግቢያው የተጠቀሰው ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት ውሳኔዎችና አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ተጠሪ ተከላክሏል ተብሎ በነፃ እንዲሰናበት በመወሰኑ፤ እንዲሁም ተሸከርካሪውን በተመለከተ ተጠሪ አስተዳደራዊ ቅጣት ተቀጥቶ እንዲለቀቅለት በተሰጠው ትዕዛዝ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በስር ፍርድ ቤት በማስረጃዎች ከተረጋገጡት ፍሬ ጉዳዮች እና አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

አመልካች በቅሬታቸው ክሱን አስረድተው እያለ እና ተጠሪም የቀረበበትን ክስ በአግባቡ ባልተከላከለበት ሁኔታ በነፃ መሰናበቱ እንዲሁም ተሸከርካሪው በተጠሪ ሲሸከረከር የነበረ ከመሆኑም ሌላ የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጥፋተኛ መባላቸው በመኪናው የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙን ስለሚያረጋግጥ በአዋጁ አንቀፅ 104 መሰረት የውርስ ትዕዛዝ ለመስጠት ከበቂ በላይ ምክንያት እያለ ተሸከርካሪው እንዲለቀቅ ትዕዛዝ መሰጠቱ የህግ ስህተት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው የመኪናው ሹፌር እና ባለቤት ብሆንም ተዋዉዬ በህጋዊ መንገድ የጫንኩት ሽንኩርት ብቻ መሆኑን አጣርቼ ከተጓዝኩ በኋላ የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የእኔን አለመኖር ሽፋን በማድረግ ደብቀው እና እንዳይታይ በማድረግ የኮንትሮባንድ ዕቃውን መጫናቸውን የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃዎች እና 2ኛና 3ኛ ተከሰሳሾ በዕምነት ከሰጡት ቃል አረጋግጠው ያሳለፉት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ ውሳኔው ሊፀና ይገባል ብለዋል፡፡

በመሰረቱ የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖረው በወንጀል ህጉ አንቀፅ 23(2) ሥር የተመለከቱት ህጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ሲሆን በተያዘው ጉዳይም ሞራላዊ ፍሬ ነገሩ የተሟላ መሆን ያለመሆኑን በመመልከት ውሳኔ መስጠት የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 57 እንደተመለከተው ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ የማይሆን ሲሆን፤ የፈፀመው ድርጊት በህግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ያላደረገ ሆኖ ሲገኝ ሊፈረድበት አይገባም፡፡ ከዚህም ሌላ በቸልተኝነት ወንጀል ማድረግን በተመለከተ ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለው ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም በሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን፤ ወይም ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ ከወ/ህጉ አንቀፅ 59(1) ግልፅ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከፍ ሲል እንደተገለፀው በአመልካች ምስክሮች የተረጋገጠው ተጠሪ በሚያሽከረክረው መኪና ላይ ዕቃው በፍተሻ መገኘቱ ብቻ ስለመሆኑ፤ ከዚህ ውጭ እንደ ክሱ አቀራረብ ሆነ ብሎ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት ብሎ የፈፀመው ለመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በማስረጃ አለማረጋገጡን፤ በአንጻሩ ተጠሪ በመከላከያዎቹ በእለቱ የሽንኩርት ጭነት ጭነው ከሌሎች አሽከርካሪዎች ጋር ሳይለያዩ ተከታትለው ይጓዙ እንደነበር፤ አሰበ ተፈሪ ላይ ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት ሲሆን አንድ ላይ እራት ሲበሉ ረዳቱ (2ኛ ተከሳሽ) ተጠሪ ያለመኖሩን አጋጣሚ ተጠቅሞ ተማሪ ነው በማለት 3ኛ ተከሳሽን ያሳፈረ መሆኑን፤ 1ኛ ተከሳሽ ዕቃው በፍተሻ ሲገኝበት ጉድ ሰራኝ አሰበ ተፈሪ ላይ ተማሪ ነው ብሎ ያሳፈረው ሰው ብሎ ሲናገር እንደነበር፤ በአጠቃላይ ዕቃው ተጠሪ በማያውቀው ሁኔታ በጉዞ መሃል ተደብቆ መጫኑን የስር ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

ከዚህ የክርክር ሂደት መገንዘብ የሚቻለው ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህጉ ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ድርጊቱን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ያልፈፀመው ስለመሆኑ፤ በአንፃሩ ከነበረው ሁኔታ እና ከተጠሪ የሹፌርነት ኃላፊነት አንፃር ሊጠረጥር ወይም ሊገምት በማይችልበት ሁኔታ ከእውቅናው ውጭ የተፈፀመ መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ መስጠታቸውን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተጠሪ አስቦ ወይም በቸልተኝነት ሊባል በሚችል መልኩ ጥፋት መፈፀሙን የሚያሳይ አይደለም፡፡

በመሆኑም ተጠሪ አስቦ ወይም በቸልተኝነት የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት ማድረጉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ሊባል ይገባ ነበር በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር የወንጀል ህጉን አንቀጽ 23(2)፤ 57፤ 58 እና 59 ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሌላው የክርክር ነጥብ ተሽከርካሪውን በተመለከተ በተሰጠው ትዕዛዝ ተፈፀመ የተባለውን የህግ ስህተት የሚመለከት ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪ ከቀረበባቸው የኮንትሮባንድ ወንጀል ክስ በነፃ ተሰናብተዋል፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነውና በተጠሪ ሲሸከረክር የነበረው መኪና የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ መገኘቱ ተረጋግጦ 2ኛ ተከሳሽ (ረዳቱ) እና 3ኛ ተከሳሽ (ባለንብረቱ) ጥፋተኞች ተብለው የተቀጡ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104 መሠረት መኪናው መወረስ ነበረበት በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ ተከሳሽ በነፃ የተሰናበተ እንደሆነ ተሽከርካሪው ሊወረስ የሚቻልበት ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 104/3/ሀ/ ስር በተለየ ሁኔታነቱ (exceptional situation) ተመልክቷል፡፡ የተለየ ሁኔታነቱ መሰረታዊ ምክንያት ደግሞ የንብረት ውርስ ከወንጀል ቅጣቶች አንዱ መሆኑ እና ቅጣት የሚመጣው የወንጀል ጥፋተኝነትን ተከትሎ መሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ነው ጥፋተኛ ባይባልም ንብረቱ የሚወረሰው ‘ስለድርጊቱ አፈፃፀም ሁኔታ የሚያስረዳ አጥጋቢ ማስረጃ መቅረቡንና ፍ/ቤቱ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው’ የሚወሰን ስለመሆኑ በድንጋጌው ይዘት የተመለከተው አዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ያሻሻላቸው እና አዲስ ያካተታቸው ድንጋጌዎች ይዘትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ በዚህ መሰረት የማንገሥ ባለቤቶች ጥፋት ሳይፈፅሙ በመንገሥ ወንጀል በመፈፀሙ ብቻ ተጥሎ የነበረው የገንዘብ ቅጣት ሁሉ እንዲቀር ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አንፃር በዚህ መዝገብ የቀረበውን ክርክር ስንመለከት የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጥፋተኛ ሆነው የተቀጡት በመኪናው የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭነው በመገኘታቸው ሲሆን በስር ፍ/ቤት በቀረበው እና በተረጋገጠው ፍሬ ነገር ተጠሪ በወንጀሉ አፈፃፀም ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሃሳብ ወይም ቸልተኝነት ነበረው ሊያሰኝ የሚችል ሁኔታ እንዳልነበር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንፃር በህጉ አነጋገር የተጠሪ ንብረት የሆነው መኪና እንዲወረስ ለማድረግ ፍ/ቤቱን ሊያሳምን የሚችል ማስረጃ በአመልካች በኩል ያልቀረበ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የተጠሪ መኪና እንዲወረስ በአመልካች የቀረበው ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ባለማግኘቱ በህጉ ረገድ መሠረታዊ የሆነ ስህተት ተፈፅሟል ማለት አልተቻለም፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአፋር ብ/ክ/መንግስት የገቢረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03484 በ16/03/2007ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ 3079 በ27/04/2007 ዓ.ም የተላለፈው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195(2) (ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ጥር 12 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.101003

ህዳር 02 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- መክብብ ሞገስ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነውን መሰረታዊ ጭብጥ አመልካች በልዩ ወንጀል ተካፋይነት በግብረአበርነት ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ከሱ ጋር በግብረአበርነት ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉ ተከሳሾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የተጣለባቸው ቅጣት ከተሻሻለ እና በግብረአበርነት ጥፋተኛ የተባለው አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ግን በአጣሪ ችሎት አያስቀርብም ተብሎ በመዘጋቱ ምክንያት ለግብረአበሮቹ የተደረገው የቅጣት ማሻሻያ አመልካችን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን ያለመሆኑን ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.196፣አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎች አንፃር አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክስ የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ አመልካችን ጨምሮ በሰባት ግለሰቦች ያቀረበው ክስ ነው ፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ 6ኛ ተከሳሽ ሲሆን በፈፀመው የወንጀል ድርጊትም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና(ለ) ፣33 እና 407(1)(ሐ) (2) ሥር በአንድ ክስ በልዩ ወንጀል መፈፀሙን ተካፋይነት በግብረአበርነት ሥልጣንን ያለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦ ከ2ኛ ፣3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ጋር ጥፋተኛ ነው ተብሏል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቅጣት ለመወሰን ተፈፃሚነት ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሆኑን ግንዛቤ በመውሰድ ቅጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያሰላ ሲሆን አመልካች በአንድ የወንጀል ድርጊት (ክስ) ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ መነሻ ቅጣቱ 8 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራትና ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) በመያዝ የእስራት መነሻ ቅጣቱ በእርከን 27 መቀጮ ደግሞ በእርከን 9 ፍቅድ ሥልጣን የሚወድቅ ነው በማለት በአመልካች በኩል ከቀረቡ የቅጣት ማቅለያዎች አራቱ ተቀባይነት ያገኙ ስለመሆኑ ፤በዚህም በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ አንድ እርከን ዝቅ የሚል በመሆኑ በእርከን 23 የሚወድቅ መሆኑን በመግለጽ በፍቅድ ሥልጣኑ ከተቀመጠው 6 ዓመት እስከ 7 ዓመት ከ2 ወር ፣መቀጮውም የወ/ሕ/ቁ.90(2) መሰረት በማድረግ በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 25,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡

አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ቁ.97541 ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ የተደረገ ሲሆን በመቀጠል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.101003 ያቀረበው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የለበትም ተብሎ ሰኔ 27 ቀን 2006 ዓ.ም መዝገቡ ለሰበር ችሎት አይቀርብም በማለት ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል ። አመልካች ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ለዚህ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ ከሱ ጋር በግብረ አበርነት ጥፋተኛ የተባሉ ግለሰቦች ጉዳያቸው በሰበር ሰሚ ችሎት ከታየ በኃላ በሰ/መ/ቁ.101225፣102826 እና 112435 በተሰጠው ውሳኔ ቅጣቱ መሰላት ያለበት በአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ሳይሆን በቀድሞው መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው ተብሎ ቅጣት ተሻሽሎላቸው የተወሰነ በመሆኑ እሱም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.196(1) መሰረት ተጠቃሚ እንዲሆን አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የተዘጋው በራሱ ስሕተት ሳይሆን ከእርሱ ውጭ በሆነ ጉዳይ በመሆኑ በድጋሚ እንዲታይለት ጠይቋል ። ይህ ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ ከመረመረ በኃላ ጉዳዩን ለአጣሪ ችሎት ከሚያቀርብ በስተቀር በችሎቱ እንደማይስተናገድ ሰኔ 24 ቀን 2007 ዓ.ም ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ አመልካች አቤቱታውን ለአጣሪ ችሎት በድጋሚ በማቅረቡ ሐምሌ 09 ቀን 2007ዓ.ም ትዕዛዝ ተሰጥቷል አጣሪ ችሎትም አመልካች ከሌሎች ግብረአበሮቹ ጋር ተከሶ እንደነበር በመግለጽ “በአመልካችና በወንጀል ግብረ አበሮች ላይ የቀረበባቸው ክስ የተጠቀሰባቸው የሕግ አንቀጽና የተላለፈባቸው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በሥር ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ሲጓዝ ቆይቶ በሰበር ደረጃ የግብረ አበሮቹ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ተመርምሮ ቅጣቱ መሠላት የነበረበት ወንጀሉ በተፈጸመበትና ክስ በቀረበበት ወቅት ሥራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ እንጂ በአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሆን አልነበረበትም ተብሎ ቅጣት ሲቀነስላቸው የአመልካች አቤቱታ ወደ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ባለመደረጉ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነበትን ቅጣት እንዲፈጽም እየተደረገ ያለበት ሁኔታ አመልካቹ በሕገ መንግስቱ የተቀመጠው በሕግ ፊት እኩል የመታየት መብቱ ተጥሷል በማለት ከጠቀሰው የሕገ መንግስቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 25 እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.196 አንፃር ሊታይ ስለሚገባው እና በተመሳሳይ መንገድ በሰበር መ/ቁ 101056 ቀርቦ በመመርመር ላይ ካለው ጉዳይ ጋር እና ከዚህ ቀደም ቀርበው ተመርምረው በሰበር መዝገብ ቁጥር 101225 እና 102826 ላይ የተሰጠው ውሳኔ አመልካችን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን አለመሆኑን "ተጠሪን ያስቀርባል ተብሏል። ተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በ 05/12/2007 ዓ.ም መልስ ያቀረበ ሲሆን ዋናው ይዘቱ ፡- የአመልካች አቤቱታ አስቀድሞ በሰበር አጣሪ ችሎት ውድቅ እንደተደረገ ፣የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ.156 ለአመልካች ይጠቅማል የተባለው ውሳኔ ይግባኝ ያልጠየቀ ከሆነ እንጂ ይግባኝ የጠየቀ ከሆነ ተጠቃሚ እንደማይሆን ፣ውሳኔው ከእኩልነት መርህ ጋር እንደማይያያዝ ፣አጣሪ ችሎቱ የራሱን ብይን መልሶ መሻር እንደማይችል በሰ/መ/ቁ.101225 እና 102826 ላይ የተሰጡ ውሳኔዎች ለአመልካች ተፈፃሚ የሚሆንበት የሕግ አግባብ እንደሌለ በመግለጽ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል። አመልካች አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ መስከረም 21 ቀን 2008 ዓ.ም አቅርበዋል።

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰ/መ/ቁ.101225 እና የሰ/መ/ቁ102826 በማስቀረብ የተመለከተ ሲሆን ፤በመጀመሪያው መዝገብ ከአመልካች ጋር ግብረአበር ሆኖ የተከሰሰው አቶ ገዛኻኝ አድገህ(የሥር 5ኛ ተከሳሽ) ፤በሁለተኛው መዝገብ አቶ ያረጋል አይሸሹም (የሥር 1ኛ ተከሳሽ) ያቀረቡዋቸው የሰበር መዝገቦች ሲሆኑ ጉዳዩን የመረመረው ይህ ችሎትም ሁለቱም ተከሳሾች ያቀረቡት ጥፋተኛ አይደለንም የሚለውን ክርክር ውድቅ በማድረግ በቅጣት ረገድ ግን ተፈፃሚነት ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ወንጀሉ ሲፈጸም ወይም ክስ ሲቀርብ ሥራ ላይ የነበረው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002 ስለመሆኑ፣የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.95438 በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት በማድረግ የቅጣት ማቅለያ ዋጋ አሰጣጥ ላይ ተመርኩዞ አቶ ገዛኽኝ አድገህ የስድስት አመት ጽኑ እስራት በማሻሻል በሦስት ዓመት ጽኑ እስራት ፣አቶ ያረጋል አይሸሹም የሰባት ዓመት ጽኑ እስራት በማሻሻል በሦስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የገንዘብ መቀጮ ግን ሳይነካ ማጽናቱን የውሳኔ ግልባጮቹ ያሳያሉ።

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ እንደሚከተለው መርምሮታል።

እንደመረመረውም አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር እና ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ አመልካች እና ግብረአበሮቹ ጥፋተኛ ተብለው ለጉዳዩ ቅጣት ሲወሰን ተፈፃሚነት የነበረው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አግባብነት እንዳለው ተጠቅሶ ቅጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተወሰነባቸው ስለመሆኑ የሚያከራክር ሆኖ አልተገኘም ። የከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች እና ሌሎች ግብረአበሮቹ ተገቢነው ያለውን ቅጣት ከወሰነ በኃላ በተናጠል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ተቀባይነት ባለማግኘቱ ቀጥሎ በተናጠል ለሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች የነበሩት ለሰበር ችሎት የቀረበላቸው ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ግን አያስቀርብም ተብሎ መዘጋቱ በመዝገቡ የተያያዘው ትዕዛዝ አረጋጋጭ ነው። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁ101225 እና 102826 የቀረቡለትን የሰበር አቤቱታዎች ከመረመረ በኃላ የጥፋተኝነት ውሳኔውን በማፅናት በቅጣት ረገድ ግን ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የቀደሞ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ነው በማለት ቅጣቱን አሻሽሎ ወስኗል። የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ውድቅ በመደረጉ ምክንያት ግብረአበሮቹ ያገኙትን የቅጣት ማሻሻያ ማግኘትና መጠቀም አለመቻሉን መዝገቡ ያሳያል።

በመሰረቱ ቅጣት ሲወሰን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 1፣4፣41፣88 እና የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረታዊ ድጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የተከተለ ሊሆን ይገባል። በአንድ የወንጀል ድርጊት በዋና ወንጀል አድራጊነት ወይም ግብረ አበርነት የተሳትፎ ተከሳሾች በግል ሁኔታዎች ማለትም የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ካለ ሊኖር የሚችለው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ ለተመሳሳይ የወንጀል አፈፃፀምና የወንጀል ተሳትፎ ተመጣጣኝና ተመሳሳይ ቅጣት ሊወሰን እንደሚገባ ከኢፌዲሬ ህገ መንግስት አንቀጽ 25 የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 4 እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ 2/2006 አንቀፅ.3.2 ሥር ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው ። በተያዘው ጉዳይ አመልካች እና ሌሎች ግብረ አበሮቹ የተጠየቁበት የወንጀሉ ሕግ አንቀጽ ልዩነት የሌለው ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ከአመልካች ጋር በጋራ ተከሰው ጉዳያቸው በዚህ ችሎት ከታየ በኃላ በሰ/መ/ቁ101225 እና 102826 በተሰጠው ውሳኔ ተፈፃሚነት ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የቀድሞ መሆኑን በመለየት ቅጣት አሻሽሏል ። በአመልካች እና በሌሎች ግብረ አበሮቹ የተፈጠረ ልዩነት በወንጀል አፈፃፀም የተፈጠረ ሳይሆን በቅጣት ማቅለያዎች ብዛትና ዋጋ ብቻ ነው ። የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ውድቅ በመደረጉ በነባሩ /የቀድሞ/የቅጣት መመሪያ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም ። ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ነባሩ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ለተከሳሹ የሚጠቅም ከሆነ የቀደም የቅጣት መመሪያ ሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ የተፈፀመ ወንጀል ወይም የቀረበ ክስ ከሆነ ቅጣቱ የሚወሰነው አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ተፈፃሚ በሆነበት ጊዜ ቢሆንም የቀድሞ የቅጣት መመሪያ ለተከሳሹ በሚጠቅም አግባብ መተርጉም እንዳለበት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 ደንጋጌዎችን በመጥቀስ በሰ/መ/ቁ.95438 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል። ይህ ገዥ ውሳኔ በየትኛውም እርከን ባሉ ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚነት እንዳለው በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) ሥር ተደንግጓል ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች አራት ማቅለያዎች ያሉት በመሆኑ ቅጣቱ በነባሩ የቅጣት መመሪያ ቢሰላ ትርጉም ያለው የቅጣት ለውጥ እንደሚያመጣ መገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጂ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በአጣሪ ችሎቱ አያስቀርብም የተባለ በመሆኑ አመልካች በነባሩ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቅጣቱ ቢሰላ ሊያገኝ የሚችለው የእስራት ማሻሻያ ማግኘት አልቻለም።

የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ በ 1954 የታወጀ ከመሆኑ አንፃር ጉዳዮች በይግባኝ ከታዩ በኃላ ለሰበር ቀርበው የሚታዩበት ሥርዓት ያልተዘረጋ ቢሆንም የሥነ ሥርዓት ሕጉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ(80(3)(ሀ) የተመለከተው የሰበር ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማና ግብ በሚያሳካ መንገድ ሊተረጎም የሚገባው ነው። ከተያዘው ጉዳይ ተመሳሳይነት ያለው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.101056 ሐምሌ 30ቀን 2007ዓ/ም በሰጠው ገዥ ውሳኔ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.196 ድንጋጌ አሁን ላለው የሰበር ሥርዓት ለመጠቀም ካለው የሰበር ችሎት አደረጃጀትና አሰራር ጋር በሚጣጣምና የሰበርን መሰረታዊ ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መንገድ መተርጎምና ስራ ላይ ማዋል እንደሚጠይቅ ገልጾ አድርጓል። የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ196 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የተፈረደባቸው ብዙ ሰዎች ሆነው አንዱ ብቻ ይግባኝ ጠይቆ ቅጣቱ ቢሻሻልና የተሻሻለው ቅጣት ይግባኝ ላልጠየቁ ጥፋተኞችም የሚጠቅም ከሆነ ይግባኝ ላልጠየቁ ጥፋተኞችም ተፈፃሚነት እንዳለው የሚያመለክት ነው። በተያዘው ጉዳይ አመልካች በነባሩ የቅጣት መመሪያ መሰረት ቅጣት ሊቀነስለት እንደሚችል ግልጽ ነው። ምክንያቱም ከአመልካች ጋር በግብረአበርነት የተከሰሱ ግለሰቦች ለሰበር ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ቅጣት ተቀንሶላቸዋል። በመሆኑም አመልካች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.101056 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ጉዳዩ በድጋሚ ታይቶ ቅጣቱን በቀደም የቅጣት መመሪያ ተሰልቶ ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚገባ ተረድተናል።

አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ከተባለ በኃላ መነሻ ቅጣቱ 8 ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራት ሁኖ ተይዟል ። ይህ መነሻ ቅጣት በእርከን 27 የሚወድቅ ነው ። በአዲሱ የቅጣት መመሪያ እያንዳንዱ ማቅለያ 1 እርከን ብቻ እንደሚቀንስ በመመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 23/1 እና 4 ስር ተመልክቷል።ቅጣቱ በቀድሞ መመሪያ ቁጥር 1/2002 ቢሰላ በእያንዳንዱ ማቅለያ 3 እርከን እንደሚቀነስ ከዚህ መመሪያ አንቀጽ 16(7) የምንገነዘበው ነው። አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ካቀረባቸው ማቅለያዎች አራቱ ተቀባይነት አገኝቷል። ቅጣቱ አመልካች ካቀረባቸው እና በሥር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ካገኙ ማቅለያዎች አንፃር ቅጣቱ ሲሰላ ከእርከን 27 ወደ እርከን 15 ዝቅ የሚል ሲሆን በዚህ እርከን ያለው የፍርድ ቤት ፍቅድ ሥልጣን ከ 2 ዓመት ከ 9 ወር እስከ 3 ዓመት ከ3 ወር ነው። ይህ ችሎትም አመልካችን ሊያርምና ሊያስተምር ይችላል ብሎ ያመነበት በዚህ ፍቃድ ስልጣን ከተቀመጠዉ ቅጣት በሶስት አመት ጽኑ እስራት ሊቀጣ ይገባል ብለናል መቀጫ በተመለከተ የስር ፍ/ቤት የግራቀኙን አስተያየት መሰረት አድርጎ ተገቢ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለውን መወሰኑን ስለተገነዘብን የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አመልካች ከእሱ ጋር ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅጣት እንደ ተሻሻለላቸው ተከሳሾች ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22፣25፣የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 4 እና 6 እንዲሁም የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ይዘትና መንፈስ በአግባቡ ተፈፃሚ የሚያደርግ መሆኑን ስለ ተገነዘብን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 196(1) መሰረት በአመልካች ላይ የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አሻሽለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 112435 በቀን 02/05/2006 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ይግባኝ ችሎት በወ/መ/ቁ.97541 በቀን 8/7/2006 የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 196 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ተሻሽሏል ፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት ሰኔ 27 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በዚህ ፍርድ ተለውጧል፡፡
3. አመልካች በዚህ ጉዳይ ተጠርጥሮ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በሦስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል ፡፡ ገንዘብ መቀጮ አልተነካም ፡፡
4. የቅጣት ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንደያስፈጽም ለክፍሉ ማረሚያ ቤትና ለአመልካች ይድረሳቸው ብለናል፡፡ ይፃፍ ፡፡ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 131863

ህዳር 8 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጠታ

ክፍለጽዮን ማሞ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- መሐመድ እንድሪስ

ተጠሪ፡- የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ ቅርንጫፍ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በዋስ ቢለቀቅ ቀነ ቀጠሮውን አክብሮ ሊቀርብ፣ስለማይችል በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ መብቱ ተነፍጎ በማረሚያ ቤት እንዲቆይ በማለት የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ብይን አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም /የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የጉዳዩ መነሻ ተጠሪ አመልካች አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/2/ በመተላለፍ ንብረትነቱ የደርባን ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሆነ የሰሌዳ ቁጥር 430 Volvo መኪና የቀረጥና ታክስ መጠናቸው ብር 88,613.33 /ሰማንያ ስምንት ሺ ስድስት መቶ አስራ ሶስት ብር ከሰላሳ ሶስት ሳንቲም/ የሆኑ እቃዎቹን በመጫን ከዲላ ወደ ሀዋሳ መስመር ሰኔ 14 ቀን 2008 ዓ/ም ይዞ ሲጓዝ የተያዘ በመሆኑ የኮንትሮ ባንድ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡
2. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ እኔ ረመዳን ፆም ጾሜ እያፈጠርኩ እያለሁ፣ ረዳቱ ሳላየው የጫናቸው እቃዎች ስለሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም፡፡ የዋስ መብቴ ይከበርልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የአመልካችን በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ እቃወማለሁ፡፡ ዋስትናውን የምቃወመው ተከሳሹ /አመልካች/ በመታወቂያው ላይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኮልፌ ቀራንዮ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር 2654 እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን በመንጃ ፈቃድ ላይ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የቤት ቁጥር 352 እንደሆነ የተገለጸ በመሆኑ ተከሳሹ ሆነ ብሎ አድራሻውን የሚለዋውጥ በመሆኑ በቀጠሮ ቀን ላይ ሊቀርብ ይችላል ብለን ስለማናምን የዋስትና ጥያቄው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዐቃቤ ህግን መቃወሚያ በመቀበል አመልካች የተለያየ አድራሻ ያለው በመሆኑ ላይቀርብ ይችላል በማለት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡

3. አመልካች ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን አጽንቶታል፡፡ አመልካች የመንጃ ፈቃድ ያወጣሁት በ1992 ዓ/ም ነው፡፡ በዚያ ጊዜ የምኖርበት የነበረው ቤት ለቅቄዋለሁ፡፡ ደርባን ትራንስፖር ኃ/የተ/የግል ማህበር ስቀጠር የምኖርበት የነበረው አድራሻ ደግሞ ከስድስት አመት በፊት ስኖርበት የነበረው ነው፡፡ አሁን የምኖረው በሌላ ቦታ ሲሆን ይህንን አድራሻዬን ለመርማሪ ፖሊስ አስመዝግቢያለሁ፡፡ ስለዚህ በተለያየ ጊዜ ከተለያየ ቦታ መኖሬ በቀጠሮው ቀን ሊቀርብ አይችልም ከሚል መደምደሚያ ላይ የማያደርስ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን ሊሻርልኝ ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ አመልካች ሶስት የተለያዩ አድራሻዎች ያሉት በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካቹን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በወንጀል የተከሰሰው በዋስትና ወረቀት ተለቅቆ ጉዳዩን የመከታተል መብት ያለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 16 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ የምንገነዘበው በወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው በዋስ መለቀቅ መሰረታዊ መብት ሲሆን ህግ አውጭም በልዩ ሁኔታ በህግ በደነገጋቸው ምክንያቶችና ፍርድ ቤቶች የሚቀርብላቸው ክርክር መረጃና ማስረጃ በሚሰጡት ብይን የተከሰሰ ሰው በዋስ የመለቀቅ መብቱ የሚነፈግበት ሁኔታ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል፡፡

5. አመልካች የተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ በዋስ የመለቀቅ መብቱን የሚገድብ አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በዋስ ለመለቀቅ ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 67/ሀ/ በመጥቀስ ነው፡፡ ድንጋጌው ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን በማክበር በቀነ ቀጠሮው ሊቀርብ የማይችል መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካመነ፣ የዋስትና ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ የሚችል መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ከሚለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መደምደሚያ ላይ የሚደርሰው በዘፈቀድ አይደለም፡፡ ዐቃቤ ህግ ተከሳሹ ቀጠሮውን አክብሮ ሊመጣና የዋስትናውን ግዴታ ሊያከብር አይችልም ከሚል መደምደሚያ ላይ ፍርድ ቤቱ ሊደርስባቸው የሚችሉ በቂ ምክንያትና መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

6. በያዝነው ጉዳይ አመልካች የመንጃ ፈቃድ ያወጣው 1992 ዓ/ም መሆኑን በዚያን ወቅት ይኖርበት የነበረውን አድራሻ የለቀቀ በመሆኑ አሁን ከሚሰራበት ድርጅት ሲቀጠር ይኖርበት የነበረው አድራሻ ከበፊቱ የተለየ መሆኑን፣ የአመልካችን መንጃ ፈቃድና የመስሪያ ቤት መታወቂያ ካርድ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በ2008 ዓ/ም በተሰጠው የቀበሌ ኗሪነት መታወቂያ ካርድ ላይ የተገለጸው አድራሻ ከስድስት አመት በፊት ደርባን ትራንስፖርት ሲቀጠር ይኖርበት ከነበረው አድራሻ የተለያየ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር ተገንዝበናል፡፡ አመልካች የመንጃ ፈቃድ ሲያወጣ፣ ደርባን ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲቀጠርና አሁን የሚኖረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለያየ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳና የቤት ቁጥር መሆኑ አመልካች ቋሚ አድራሻ የለውም ከሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡

7. የመኖሪያ ቤት ከግለሰብ ተከራይተው የሚኖሩ ሰዎች፣ በአመታት ውስጥ ሳይሆን በወራት ወይም በቀናት ልዩነት የተከራዩትን ቤት በተለያየ ምክንያት ለቀው በሌላ ክፍለ ከተማ፣ ሌላ ወረዳ ሌላ ቤት ተከራይተው የሚኖሩ መሆኑንና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የመኖሪያ ቤት እጥረት መኖሩ፣መንግስት በፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎች በግልፅ ያመነውና የአዲስ አበባ የቤቶች ኮንስትራክሽን ልማት ኤጀንሲ በአዋጅ በመቋቋም የጋራ መኖሪያ ቤቶች መምሪያ ቤቶች በመገንባት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት እያደረገ መሆኑ በግልጽ የሚታወቅና ማስረጃ እንዲቀርብለት የማያስፈልግ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች መንጃ ፈቃድ ሲያወጣ የዛሬ አስራ አምስት አመት ይኖርበት የነበረውን አድራሻ አስመዝግቧል፡፡ ይህንን መኖሪያ አድራሻው ከስድስት አመት በፊት ደርባን ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲቀጠር፣ የለቀቀው መሆኑን በመግለጽና አዲሱን አድራሻውን ለመስሪያ ቤቱ አሳውቋል፡፡ ባሁኑ ወቅት የሚኖርበት አድራሻ በመ/ቤት ሲቀጠር ካስመዘገበው አድራሻ የተለየ መሆኑን የሚያረጋግጥ የቀበሌ መታወቂያ ማቅረቡ፣ አመልካች በአድራሻው ተፈልጎ እንዳይገኝ ሆነ ብሎ የፈጠረው ዘዴ ሳይሆን፣ አመልካች የራሱ የሆነ ቋሚ መኖሪያ ቤት ስለሌለው በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወሩና ቤት እየተከራየ የኖረ መሆኑን እውነታ /ፍሬ ነገር/ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

8. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተለያየ ክፍለ ከተማዎች፣ ወረዳዎች በተለያዩ ጊዜ እየተዘዋወረ ቤት እየተከራዩ የሚኖሩ ሰዎች፣ በዋስ ቢለቀቁ ፣የዋስትና ጉዳያቸውን አክብረው በቀነ ቀጠሮው ቀን ሊቀርቡ አይችሉም የሚለውን መቃወሚያና መከራከሪያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

፣ሰዎች አዲስ አበባ ውስጥ የራሳቸው የሆነ የመኖሪያ ቤት ስለሌላቸው ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ቤት እየተከራዩ የሚኖሩ በመሆናቸው ምክንያት ብቻ የዋስትና መብታቸው እንዳይፈቀድ የሚጠይቅ፣ የሰዎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በአዲስ አበባ ከተማ አንድ ቋሚ የሆነ አድራሻና መኖሪያ ቤት ስለሌላቸው ብቻ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 6 የተረጋገጠላቸው በዋስ የመለቀቅ መብት እንዲነፈግ የሚጠይቅ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 25 የተደነገገውን በሕግ ፊት እኩል የመሆንና እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብትን የሚጥስ መቃወሚያና መከራከሪያ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው መቃወሚያ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በተለያየ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች፣ ወረዳዎችና ቤቶች ውስጥ የኖረ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ማለትም የመንጃ ፈቃድ፣ የሚሰራበት መስሪያ ቤትና የመታወቂያ ካርድና የቀበሌ ኗሪዎች መታወቂያ ይዞ መገኘቱ አመልካች በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ በቀነ ቀጠሮው ሊቀርብ አይችልም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 69/ሀ/ ድንጋጌዎች ቋሚ የመኖሪያ ቤት ባለመኖሩ ምክንያት በተለያየ ጊዜ የተለያየ ቦታ እየተዘዋወረ ቤት እየተከራየ መኖሩን መነሻ በማድረግ ብቻ ተከሳሹን የዋስትና መብቱን ለመንፈግ ታስቦ የተደነገገ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በዋስትና ለመለቀቅ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 6 እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 69/ሀ/ ከተደነገገው ውጭ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነዉ በማለት ወስነናል፡፡

9. አመልካች የተከሰሰበት የሕግ ድንጋጌ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ መብትን የማያስከለክል በመሆኑና ተጠሪ አመልካች በዋስትና እንዳይለቀቅ ያቀረበው መቃወሚያና መረጃ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 69/ሀ/ መሰረታዊ ይዘትና አላማ ውጭ በመሆኑ፣ አመልካች ለብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ የሚበቃ ዋስ አቅርቦ ወይም ገንዘብን አስይዞ በዋስ ተለቅቆ ሊከራከር ይገባል በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 75 መሰረት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 39554 ሰኔ 28 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 68379 ሐምሌ 12 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች ብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ በማስያዝ ወይም ለዚህ ገንዘብ የሚበቃ ዋስ በማቅረብ የተከሰሰበትን ወንጀል በዋስ እያቀረበ ይከራከር በማለት ወስነናል፡፡ ውሳኔው ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ቁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.118130

ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-ዓሊ መሐመድ

ተሻሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ህፃን አድማሱ አገዘ--ከወልዲያ ማረሚያ ቤት ጉዳይ የምትከታተል እህቱ እየሩሳሌም አገዘ ቀርባለች

ተጠሪ፡-የአማራ ክልል ዓቃቤ ህግ አቶ ታራቀኝ አረጋ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በተከሰሰበት የግብረ ሥጋ ድፍረት ወንጀል በመፈጸም ጥፋተኛ ተደርጎ በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍርድ ቤት የተወሰነበትን የሰሜን ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማጽናቱ እንዲሁም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ5 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ቅጣቱን አሻሽሎ የወሰነበትን በመቃወም አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች እድሜው 11 (አስራ አንድ) ዓመት ሲሆን በጉባላፍቱ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0200915 እድሜዋ 13 ዓመት ያልሞላትን የአራት ዓመት ህፃን ልጅ አፀደ ምስጌን አስገድዶ ክብረ ንጽህናዋን የደፈራት በመሆኑ በፈጸመው የህፃናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል ወንጀል ተከሷል በማለት በወንጀል ህግ ቁጥር 627(1) መሠረት ክስ ቀርቦበት በዚሁ ጥፋተኛ ተብሎ በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት የተወሰነበትን በመቃወም ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የወረዳ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ያሰናበተው በመሆኑ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ሰበር ሰሚ ችሎቱም ጥፋተኝነቱን በማጽናት አልፎ ቅጣቱ በምን መልክ ይፈጸም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚለውን በአብላጫ ድምፅ ወደ 5(አምስት) ዓመት ጽኑ እስራት ዝቅ በማድረግ አሻሽሎ እንዲቀጣ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

የአሁኑ አመልካች እድሜው የ11 (አስራ አንድ) አመት ህፃን መሆኑን ጠቅሶ ምንም ዓይነት ቀጥተኛ ማስረጃ እንዳልቀረበበት እና ጥፋተኛ ሊባል እንደማይገባው እንዲሁም ጥፋተኛ ቢባል እንኳን ቅጣቱን በማረሚያ ቤት ከሌሎች አዋቂ ታራሚዎች ጋር መታሠር እንደሌለበትና በቤተሰቦቹ ሥር ሆኖ ክትትል ሊደረግበት እንደሚገባ ገልጾ ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

የሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች እድሜ 11 ዓመት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ቅጣቱ በወንጀል ሕግ ቁጥር 157 እስከ 168 ባሉት ድንጋጌዎች ለምን መፈጸም እንደሌለበት የሥር ፍርድ ቤቶች ሳይገልጹ በመደበኛ የቅጣት ድንጋጌዎች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት የክልሉ ዓቃቤ ህግ መልስ እንዲሰጥበት ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪም አመልካች ቅጣቱን ከአዋቂ ታራሚዎች ጋር ይፈጸም ቢባል በአመልካች ላይ ሊያስከትል ከሚችለው ጉዳት አንጻር ዕድሜውን መሠረት ያደረገ የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ ተፈጻሚ ቢሆን እንደማይቃወም ገልጾ በቁጥር ወየሃ-424/08 በቀን 9/05/2008 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡

የክርክሩ ሂደት አጠር ባለመልኩ ከላይ እንደተመዘገበው ሲሆን ጉዳዩን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፣በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክር፣ አጣሪው ከያዘው ጭብጥ እንዲሁም አግባብነት ካለው ህግ አንጻር መርምረናል፡፡ አካለ መጠን ያላደረሱ ወጣቶች ወንጀል ፈጽመው በተገኙ ጊዜ የሚደረገው የክስ ሥነ ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 171 እና ተከታዩቹ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት የምርመራውም ሆነ የክስ ሥነ ሥርዓት የሚመራው በፍርድ ቤት ክትትልና ቁጥጥር ነው፡፡ የቀረበው ክስ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ አቃቤ ህግ የክስ ማመልከቻውን አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሚሰጥ በተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 172 (3) ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም አካለ መጠን ያልደረሰው ወጣት ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ወይም በሞት በሚያስቀጣ ወንጀል በተከሰሰ ጊዜ ፍርድ ቤቱ አካለ መጠን ያልደረሰውን ወጣት የሚረዳው ጠበቃ ያዝለታል በማለት በዚሁ የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 174 (ለ) ላይ ተደንግጓል፡፡ አካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት የተከሰሰበትን የሚሰማው ችሎት በሌላ ነገር ተሰይሞ ከሚያነጋግረው አካኋኑና ሁኔታ የተለየ እንደሆነ የሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 176 (2) ደንግጓል፡፡እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡት አካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት በተከሰሰ ጊዜ የወጣቱን እድሜ ባገናዘበ መልኩ ያለውን የአእምሮ ብስለት፣ስለ ጉዳዩ ያለውን አረዳድ፣የሞራል ሁኔታ፣ስለተከሰሰው ህፃን ደህንነት ህግ አውጪው ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ አሚጋች ፍርድ ቤት ስለ ጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት ክርክሩን እንዲመራ ለማድረግ ታስቦ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያደርሳል፡፡ ይህም ስለ ህፃናት መብት ከተደነገገው ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 36 (2) ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደኅንነት በቀዳምትነት መታሰብ አለበት በማለት ከተደነገገው ድንጋጌ ጋር የሚጣጣም እንደሆነ ለመመልከት ይቻላል፡፡ በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1) ላይ የሰፈረው ይህ መርህ የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት በሚወስዷቸው እርምጃዎች ለህጻናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት ያለባቸው መሆኑን ያሳስባል፡፡ የአፍሪካ የህፃናት መብቶች ደህንነት ቻርተር በአንቀጽ 4 (1) ላይ በተመሳሳይ መልኩ ደንግጓል፡፡ ወንጀል ፈጽሞ የተከሰሰ ህፃን ደህንነት የሚጠበቀው የህፃኑን ሥነ ልቦና በመጠበቅ፤በክርክር ሂደት የሚደርስበትን መሸማቀቅ በመከላከል፤ እንዳይጨናነቅ በማድረግ፣ አዋቂዎችን በሚያስችሉበት ችሎት አብሮ እንዳይሆን በማድረግ፤ የሚረዳው ጠበቃ እንዲኖር በማድረግ ነው፡፡

በዚህ መሠረት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህጉም ሆነ የወንጀል ህጉ ለህፃናት ወንጀል ፈጻሚዎች ከአዋቂዎች የተለየ የምርመራ፣ የክስ፤ የፍርድ እና የቅጣት ሁኔታን ማስቀመጥ ያስፈለገው ህገ መንግሥቱ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች ላይ ከተደነገጉ የህፃናት መብቶች በእጅጉ ለማያያዝ ታስቦ ነው፡፡ የዚህም አስፈላጊነት መደበኛ የክርክር ሥርዓት ለመዘርጋት ያለመ ሳይሆን በህፃናት ላይ ለጥፋተኝነት የሚወሰን ቅጣት ማስተማርና ማረም እንጂ መበቀል እንዳይሆን ታሳቢ አድርጎ ህፃናት በአከባቢያቸው አብሮዎቸው የሚውለው፣ የሚያዩት፣የሚማሩበት በተለይም በምርመራ፣ ክስ፣ ፍርድ እና የቅጣት አፈጻጸም ላይ ጥንቃቄ ካልተደረገ እነርሱን ከመጉዳት አልፎ የመጡበትን ማኅበረሰብ፣አካባቢና ሀገር የሚጎዳ ማንነት እንዳይከሰት ነው፡፡በተጨማሪም ህፃናት እራሳቸውን የሚጠብቁና የሚቆጣጠሩ ባለመሆናቸው ያጠፉት ጥፋት ቢኖር እንኳ እኩል ከአዋቂዎች ዓይነት የቅጣት አፈጻጸም ከመከተል ይልቅ ስለወደፊት መልካም አስተዳደግ እና ደኅንነታቸው ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ ነው፡፡

ይህን ዓላማ ለማሳካትም ሲባል ከህገ መንግሥት አንቀጽ 36 (2) እና (3)፣ ከአህጉሩና ዓለም አቀፍ ስምምነት ሰነዶች በተጨማሪ በዝርዝር የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 157 እስከ 168 እና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ 171 እስከ 180 ላይ ዝርዝር የምርመራ፣ የክስ፣ የፍርድ እና የቅጣት አፈጻጸም ድንጋጌዎችም ሥራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ የተጣለው በፍርድ ቤት ላይ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በወንጀል ለተከሰሱ ህፃናት ምቹ የሆነ የክርክር መሰማት ሥርዓትን ማስጠበቅና ማስከበር በዓለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን፣ በአፍሪካ የህፃናት መብቶች ቻርተር፣ በኢፌዴሪ ህግ መንግሥት፣በወንጀል ህግ እና በወንጀለኛ መቅጫ ህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥነ ሥርዓት በተደነገገው መሠረት የፍርድ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡ የተያዘውን ጉዳይ የተመለከተው የጉባላፍቶ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚያመለክተው ከላይ የተገለጹትን ሥነ ሥርዓታዊ ድንጋጌዎች ተከትሎ የተደረገ ክርክር አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የሥነ ሥርዓት ግድፈት እንደፈጸመ መገንዘብ ተችሏል፡፡

የጥፋተኝነት ውሳኔን በተመለከተ አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት የፈጸመ መሆኑ በሥር ወረዳ ፍርድ ቤት በማስረጃ ተረጋገጦ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ቅጣትን በተመለከተ እድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ አስራ አምስት ዓመት የሞላቸው ወንጀል ያደረጉ ወጣቶች የሚወሰንባቸው ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ከአንቀጽ 157 እስከ 168 የተደነገጉ ብቻ ናቸው፡፡ ለአዋቂ ጥፋተኞች የተደነገጉት መደበኛ ቅጣቶች ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፤ ከአዋቂዎችም ጋር አይታሰሩም በማለት የወንጀል ህግ አንቀጽ 53 (1) ይደነግጋል፡፡ በወንጅል ህግ አንቀጽ 168 (2) ወጣቱ የፈጸመውን ወንጀል ከባድነትና ጥፋቱንም በፈጸመበት ጊዜ የነበረውን የዕድሜ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ታስሮ የሚቆይበትን የጊዜ ልክ ፍርድ ቤቱ ይወስናል፡፡ ጊዜውም ከአንድ ዓመት ሳያንስ እስከ አስር ዓመት ሊደርስ ይችላል በማለት ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሚወሰነው ቅጣት ከአንድ ዓመት እስከ አስር ዓመት ሲሆን የሥር አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን የቅጣት ውሳኔን በማሻሻል አመልካች በአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ ቅጣቱንም የወልዳያ ማረሚያ ቤት እንዲያስፈጽም በአብላጫ ድምፅ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አነስተኛው ድምፅ የአመልካችን አቆያየት በተመለከተ የወንጀል ህግ ቁጥር 168 (1) ሀ) ላይ ከወንጀሉ ከባድነት አንጻር ወንጀለኛው ወደ ፀባይ ማረሚያ ተቋም ሊላክ እንደሚችል ቢገልጽም ይህ ዓይነት የማረሚያ ተቋም በአሁኑ ጊዜ የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የወንጀል ህግ ቁጥር 53 (1) ደግሞ በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ወንጀለኞች ከአዋቂዎች ጋር አይታሠሩም በማለት ግልጽ የሆነ ክልከላ አስቀምጧል፡፡ ይህ ከመሆኑ አንጻር አመልካች ወደ ማጎበረሰቡ እንዲቀላቀል ተደርጎ ፀባዩ በፖሊስ ክትትል ሊደረግበት ሲገባ ግልጽ የሆነውን የህግ ክልከላ በመተላለፍ አብላጫው ደምፅ አመልካች ከአዋቂዎች ጋር እንዲታሠር መወሠኑ ተገቢነት የለውም በማለት ከአብላጫው ድምፅ ተለይቷል፡፡

የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጣሪ አቤቱታውን ሲያስቀርብ የአመልካች እድሜ 11 ዓመት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ቅጣቱ በወንጀል ሕግ ቁጥር 157 እስከ 168 ባሉት ድንጋጌዎች ለምን መፈጸም እንደሌለበት የሥር ፍርድ ቤቶች ሳይገልጹ በመደበኛ የቅጣት ድንጋጌዎች የመወሰኑን አግባብነት መመርመር ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ጭብጥ የያዘውም የአነስተኛውን ድምፅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩነት ሀሳብ ህጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን ተመልክቶ ነው ወደ ሚል ድምዳሜ ያደርሰናል፡፡ እኛም የስር ፍርድ ቤት ሁለት ዳኞች በልዩነት ያነሱትን እንዲሁም አጣሪው የያዘውን ጭብጥ የምንስማማበት ነው፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ ይህ ችሎት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ህፃናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተገቢውን ባለሙያ በመመደብ ስለ አመልካቹ ህፃን ጠባይ፣ ስለአስተዳደጉ፣ ስለኑሮውና ስለህይወቱ እንዲሁም የአካልና የአእምሮ ሁኔታውን አስጠንቶ ውጤቱን እንዲያቀርብ ሚያዝያ 6 ቀን 2008 ዓ/ም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ መሠረት የህፃናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ በመመደብ በወልዲያ ማረሚያ ቤት ስለሚገኘው ህፃን አድማሱ አገዘ ሁኔታ ያጠናውን ጥናት በቁጥር ሃ/4-9-3/17920 ሐምሌ 19 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ መሸኛ ደብዳቤ ልኳል፡፡ ጥናቱም ከአመልካቹ፣ ከቤተሰቦቹ፣ ከጓደኛው፣ ከጎራቤቶቹ እና ከማረሚያ ቤቱ ሙያተኞች የተገኘ መረጃ እንደሆነ ሲገልጽ የሚከተሉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች ለመውሰድ የሚረዱ ሃሳቦች ለማግኘት እንዳስቻለ ያመለክታል፡፡ እነዚህም፡-

1. አመልካች ወንጀሉን መፈጸሙን ባያምንም ከዚህ በኃላ ፀባዩን ለማሻሻልና ትምህርቱ ላይ ብቻ ሙሉ ትኩረቱን ለማድረግ ማቀዱ፣
2. ህፃኑ ከቤተሰቡ እና ከጓደኞቹ ተለይቶ ማረሚያ ቤት መግባቱ ከባድ እንደሆነ በመረዳቱ እና ለወደፊት ከወንጀል ነክ ነገሮች ለመራቅ ማቀዱ፣
3. ህፃኑ ወደ ወላጅ እናቱ ጋር ለመኖር ከተመለሰባቸው ምክንያቶች አንዱ በሥራ ጫና ምክንያት ትምህርቱን ላለማቋረጥ ባደረገው ትግል ከወላጅ አባቱ እና ከእንጀራ እናቱ ጋር አለመስማማት ተፈጥሮ መሆኑ፣
4. ከማረሚያ ቤቱ ሙያተኞች ለመረዳት እንደተቻለው ህፃን አድማሱ/አመልካቹ/ ታዛዥ እና ምክርም የሚሰማ መሆኑ፤
5. ከቤተሰቦቹ፣ ከጓደኛው እና ከመኖሪያ አካባቢው የተገኘውም መረጃ አመልካች በባህሪይው ጨዋ እና ምስጉን እንደሆነ እና ከዚህ በፊት በወንጀል ድርጊት ተከሶም ሆነ ጥፋተኛ ተብሎ እንደማያውቅ የሚያሳይ በመሆኑ፣
6. የአመልካች ወላጅ እናትም ህጻኑ ወደ ወንጀል ድርጊት ሊገባ የቻለው በተለያየ ቦታ በማደጉ ከአስተዳደግ ክፍተት እና ከቤተሰብ ክትትል እና ቁጥጥር ማነስ ሊሆን እንደሚችል በማመን ወደፊት ኃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት እንዳቀዱ የገለጹ መሆኑ እና የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ ቤተሰቡ ተበዳይን ለመካስ ጥረት ማድረጋቸው በጥናቱ የተካተቱ ነጥቦች ናቸው፡፡ እነዚህ የጥናት ውጤቶች በአመልካች ላይ ሊወሰድ የሚገባው ቅጣት ምን ሊሆን እንደሚገባ ግንዛቤ የሚሰጡ ሆነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገኝተዋል፡፡የወንጀል ህግ ቁጥር 157 አስከ 168 ላይ የተመለከቱት የቅጣት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች ተፈጻሚ ሲሆኑም የወጣቱን ፀባይ እና የቀድሞ ባህሪው ምን እንደሚመስል መገንዘብ እንደሚያስፈልግ የደነገገ ሲሆን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 177 (2) ድንጋጌም ይህንን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች የፈጸመው የወንጀል ድርጊት ከእሱ ዕድሜ በታች ላይ የምትገኘው ህፃን ልጅ ላይ ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸሙ ወንጀሉ ከባድ የሚባል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት እርምጃ መወሰዱ ተገቢነት ቢኖረውም የቅጣት አፈጻጸም ሲታይ በምን መልኩ ተፈጻሚ መሆን አለበት የሚለው ጉዳይ ከአመልካቹ እድሜ እና ስለ ነበረው ባህሪ እና መልካም ፀባይ በመነሳት ከወንጀል ህግ ቁጥር 157 እስከ 168 አኳያ የተለያዩ እርምጃዎች ተፈጻሚ መሆን እንደሚገባቸው ህጉ ያስቀመጠ በመሆኑ የተወሰነበትን የእስራት ቅጣት ከአዋቂ የህግ ታራሚዎች ጋር ይፈጽም ቢባል ወደፊት በአመልካች ላይ ሊያስከትልበት ከሚችለው የሞራል እና የተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች አኳያ ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የክስና የክርክር ሂደት የመሩበት አካሄድ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት፣ የወንጀል ህጉን መሠረታዊ ድንጋጌዎች እና በህገ መንግሥቱ ስለህፃናት የተቀመጡ መርሆችን የተከተለ ካለመሆኑም ባሻገር ፍርድ ቤቶቹ ቅጣቱን ሲወስኑ እንዲሁም ቅጣቱ ከአዋቂ ታራሚዎች ጋር እንዲፈጸም ትዕዛዝ መስጠታቸው ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0200915 በቀን 04/06/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0205865 በቀን 10/06/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ፣የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቁጥር 03-10537 ሐምሌ 28 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የወንጀል ህግ ቁጥር 168/1/ሀ/ ከወንጀሉ ከባድነት አንጻር አካለ መጠን ያልደረሰ ወንጀል አድራጊ ወደ ፀባይ ማረሚያ ተቋም ሊላክ እንደሚችል ቢደነግግም ይህ ዓይነት ማረሚያ ተቋም በአሁኑ ጊዜ ያልተሟላ ሲሆን የወንጀል ህግ ቁጥር 53/1/ ደግሞ በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ወንጀል አድራጊዎች ከአዋቂዎች ጋር አይታሰሩም በማለት ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንጻር አመልካች ወደ ማኅበረሰቡ እንዲቀላቀል ተደርጎ በፖሊስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡ በመሆኑም በሥር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው የቅጣት ውሳኔ በወንጀል ህግ ቁጥር 171 እና 192 መሠረት ታግዶ እንዲቆይ ተወስኗል፡፡

3. ስለ አመልካቹ መልካም አስተዳደግና ባህርይ ክትትል እንዲያደርጉ ለአመልካቹ እናትና አባት እንዲገለጽ ታዟል፤ ይጸፍ፡፡
4. አመልካች ከማረሚያ ቤት ወጥቶ በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ ለፈተና በተሰጠው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚያሳየውን ባህርይ እንደከታተል ለሚገኝበት ወረዳ ፖሊስ በጽሁፍ እንዲገለጽ ታዟል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለወልድያ ማረሚያ ቤት በመሸኛ እንዲደርሰውና አመልካቹንም እንዲፈታው የመፍቻ ዋራንት እንዲጻፍ ታዟል፡፡
6. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡
7. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.134228

የካቲት 08 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሃመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

አይሸሹም መለሰ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ስማቸው ከበደ

- ጠበቆች ታምሩ ወ/አገኝ፤ ሲሳይ ለምለም ፍስሃ አለማየሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ - ያለምወርቅ አስታጥቄ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል ባለው የወንጀል ክስ ክርክር የቀረበን የዋስትና ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ክሱን እየተመለከተ ለሚገኘው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ከ2ኛው ክስ ነጻ ስለወጣሁና ተከላከል የተባልኩባቸው ክሶች ላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ዋስትና የማያስከለክሉ በመሆኑ የዋስትና መብት ይፈቀድልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስ ተከሳሽ የተከሰሰበት ወንጀል ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ መሆኑን፤ እንዲሁም ነፃ በወጡበት ጉዳይ ይግባኝ የጠየቁበት መሆኑን በማንሳት የዋስትና መብታቸው እንዲነፈግ ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአመልካች እና 19ኛ ተከሳሽ በሆነው ድርጅታቸው ላይ የቀረቡት 37ኛ፤ 38ኛ፤ 40ኛ፤ 41ኛ፤ 42ኛ፤ 43ኛ፤ 44ኛ፤ እና 45ኛ ክሶች የግብር ዓዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 96 እና 97፤ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49፤ 50፤ 102 እና 56 መሰረት ያደረጉ እና በእነዚህ 8 (ስምንት) ክሶች በድምሩ ብር 50,374,960.00 የሚጠጋ የመንግስት የገቢ ግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ እዳ እንዳለባቸው የሚያሳዩ ግብር አሳውቆ አለመክፈልን እና አሳንሶ ማሳወቅን የሚመለከቱ የወንጀል ክሶች በመሆናቸው፤ በድርጅቱ ላይ የቀረቡትም ክሶች አመልካችን የሚመለከቱ እና በተደራቢነት የሚታዩ በመሆናቸው፤ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በመርህ ደረጃ ዋስትና የሚከለክሉ ባይሆንም ተደራራቢ ቅጣትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ተደራራቢ ወንጀሎች በመሆናቸው አመልካች ሊከተል የሚችለውን ከፍተኛ ቅጣት በመሸሽ በዋስ ቢወጡ ሊቀርቡ ይችላሉ ተብሎ መገመት አለመቻሉን፤ የክሱ የገንዘብ መጠን ከፍተኛ መሆኑና በሃገር ኢኮኖሚ የሚያሳድረው ተፅእኖ ከፍተኛነት ሲታይ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኛነት እና የወንጀሉን ከባድነት ስለሚያስገነዝብ አመልካች በዋስትና ቢወጡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይቀርባሉ ተብሎ ለመገመት የማያስችል በመሆኑ፤ አመልካች ያላቸውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅመው ከሃገር አይወጡም የሚለውን ግምት የሚያስተባብል አሳማኝ ምክንያት ያላቀረቡ በመሆኑ፤ በአጠቃላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች አመልካች የዋስትና መብት ቢፈቀድላቸው የዋስትና ግዴታን አክብረው ፍርድ ቤት በየቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ የለም ብሎ ፍርድ ቤቱ ስላመነ የዋስትና ጥያቄውን አልተቀበልኩም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ብይን በመቃወም ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ብይኑን ለመለወጥ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ ምክንያት አልተገኘም ተብሎ የይግባኝ ማመልከቻው ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ህዳር 10 ቀን 2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የተከሰሱባቸው የወንጀል ክሶች በመርህ ደረጃ የአመልካችን የዋስትና መብት የሚያስነፍጉ ስላለመሆናቸው የሥር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ነገር ግን ክርክሩ ከተጠናቀቀ በኋላ አመልካች ጥፋተኛ ቢባሉ ሊያስከትልባቸው ከሚችለው ቅጣት አንፃር አመልካች ከሃገር ሊሸሹ ይችላሉ የሚለውን ግምት መነሻ በማድረግ የዋስትና መብት የመከልከሉን አግባብነት፤ እንዲሁም ከሃገር ሊሸሹ ይችሉ ይሆናል የሚል ግምት ቢወሰድም እንኳ ከሀገር ለመሸሽ የማይችሉበትን ሥርዓት ማስፈፀም እየተቻለ መሰረታዊ የሆነውን የዋስትና መብት ለመንፈግ የተሰጠው ምክንያት እንደህጉ አነጋገር በቂ ምክንያትን የተመረኮዘ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በሰበር መ/ቁ 31734 ከሰጠው ትርጉም አንፃር ማየት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ ተብሏል፡፡ በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት መርምረናል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(6) በግልፅ እንደተመለከተው የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት ያላቸው ሲሆን ዋስትና ሊከለከል የሚችለው በህግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ነው፡፡ በህጉ ከተደነገጉት ልዩ ሁኔታዎች መካከል በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67(ሀ) ሥር የተደነገገው ተጠቃሽ ነው፡፡ በድንጋጌው ሥር እንደተመለከተው ተከሣሹ የዋስትና ግዴታውን ሊፈጽም አይችልም ተብሎ ሲገመት ዋስትና መከልከል ይቻላል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ በዋስ ቢለቀቁ ተመልሰው ሊቀርቡ አይችሉም የሚል ግምት ለመውሰድ እና ዋስትና ለመከልከል የሚያስችል ማስረጃም ሆነ ምክንያት ሳይኖር፤ ይልቁንም ከፍተኛ ባለሃብት በመሆናቸው በቢሊዮን የሚቆጠር ሃብት የሚያንቀሳቅሱ እና አንደኛ ደረጃ ግብር ከፋይ ተብለው መሸለማቸውን፤ እንዲሁም ከፍተኛ የሥራ ዕድል መፍጠራቸውን ሁሉ ለፍርድ ቤቱ ተገልፆ በገሃድ ቀርቦ እያለ ምንም ማፍረሻ ማስረጃ ሳይቀርብ በደፈናው አይቀርቡም የሚለውን ግምት ሊያስተባብሉ አልቻሉም በማለት መደምደሙ፤ እንዲሁም ጉልህ ግምት ቢኖር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያንን እንዳፈርስ ወይም እንዳስረዳ እንኳ እድል ሳይሰጥ የተወሰነ ውሳኔ በመሆኑ በዚህ መልኩ የተሰጠው ብይን ተሽሮ ዋስትና ሊፈቀድ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ነገር ግን ተከሣሹ የዋስትና ግዴታውን ሊፈጽም አይችልም ለማለት የሚያስችል በበቂ ምክንያት የተደገፈ ግምት ካለ ይህ በመኖሩ ብቻ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67/ሀ/ መሠረት ዋስትና መከልከል የሚቻል ሲሆን በተያዘው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት አመልካች የዋስትና መብት የተከለከሉት የዋስትና ግዴታን አክብረው ፍርድ ቤት በየቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ በመቀበሉ ነው። ፍርድ ቤቱ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው በአመልካች እና በድርጅታቸው ላይ የቀረቡትን ተደራራቢ ክሶች፤ ክሶቹ የያዙትን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን እና ወንጀሉም ግብር አሳውቆ ካለመክፈል እና አሳንሶ ከማሳወቅ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች መሆናቸውን፤ እነዚህ ከፍተኛ ቅጣትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ተደራራቢ ወንጀሎች በመሆናቸው፤ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኛነት እና የወንጀሉ ከባድነት ሁሉ ሲታይ አመልካች በዋስትና ቢወጡ ይቀርባሉ ተብሎ ለመገመት የማያስችል መሆኑን፤ እንዲሁም አመልካች ያላቸውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅመው ከሃገር አይወጡም የሚለውን ግምት የሚያስተባብል አሳማኝ ምክንያት ያላቀረቡ መሆኑን በማንሳት ነው።

የወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67(ሀ) በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች አመልካች የሚፈጽሙ የማይመስል እንደሆነ በዋስትና የመለቀቅ ማመልከቻውን መቀበል የማይቻል ስለመሆኑ ቢደነግግም ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ለመከልከል ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች በግልጽ አልተመለከቱም። በመሆኑም አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም የማይመስል ነው ተብሎ ግምት የሚወሰደው በቂና ህጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆን እንደሚገባ፤ እንዲሁም ምክንያቶቹ በቂና ህጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከተለያዩ ከባባዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚገባ ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59304 እና ሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት ውሳኔ ሰጥቷል። ስለሆነም በወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67 መሰረት የዋስትና መብት የሚነፈግባቸው ምክንያቶች ፍርድ ቤቶች ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር እየተመለከቱ ሊመዝኗቸው የሚገባቸው ናቸው።

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ያልተቀበለው የዋስትና መብት ቢፈቀድላቸው የዋስትና ግዴታውን አክብረው ፍርድ ቤት በቀነ ቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን ነው። ለዚህ በምክንያትነት የተጠቀሰው ከፍ ሲል እንደገለፅነው የቀረቡት ክሶች ተደራራቢነት፤ ክሶቹ የያዙትን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን፤ የወንጀሉ አይነት እና የድርጊቱ አፈፃፀም፤ ሊያስከትል የሚችለው ከፍተኛ ቅጣት፤ እንዲሁም አመልካች ያላቸውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅመው ከሃገር አይወጡም የማያሰኝ ሁኔታ አለመኖሩን ነው። እነዚህ ምክንያቶች ለግምቱ መነሻ እንዳይደረጉ በህጉ ክልከላ ካለመኖሩም በላይ በምክንያትነት ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም የሚባልበት ሁኔታ ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤት በተጠቀሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት እና ግምት ላይ ተመስርቶ በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻውን ባለመቀበል በመወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡

በሌላም በኩል ቅሬታው ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በሰበር መ/ቁ 31734 ከሰጠው ትርጉም አንፃር ለማየትም እንዲቻል ተብሎ ቢሆንም በተጠቀሰው መዝገብ ተከሳሹ የብዙ ሃገር ፓስፖርትና ቪዛ በእጁ ስለሚገኝ ብቻ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ለማለት የሚያስችል በቂ መንደርደሪያ ምክንያት ስላለመሆኑ፤ እንዲሁም የዋስትና ግዴታውን አክብሮ እንዲቀርብ የሚያደርግ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚቻል የተወሰነበት ከመሆኑ ውጭ በሁለቱ መዛግብት የቀረበው ክርክር እና ዋስትና ለመከልከል መንደርደሪያ የተደረጉት ምክንያቶች ተመሳሳይ ናቸው የሚባሉ ሆነው አላገኘናቸውም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት በህጉ ተቀባይነት የላቸውም የማይባሉ ምክንያቶች ላይ በመመስረት አመልካች የዋስትና መብት ቢፈቀድላቸው የዋስትና ግዴታውን አክብረው ፍርድ ቤት በየቀጠሮው ይቀርባሉ የሚል ዕምነት ሊጣልበት የሚያስችል ሁኔታ የለም በማለት በዋስትና ወረቀት የመለቀቅ ማመልከቻውን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 67/ሀ/ መሰረት ባለመቀበል በመወሰኑ፤ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የይግባኝ ማመልከቻውን ባለመቀበል በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/መ/ቁጥር 141352 ጥቅምት 1 ቀን 2009 ዓ.ም. የተሰጠው ብይን፤ እንዲሁም በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ 133103 ጥቅምት 15 ቀን 2009 ዓ.ም የተላለፈው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 75/2/ መሠረት በአብላጫ ድምፅ ፀንቷል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>**የልዩነት ሃሳብ**</u>

እኔ በተራ ቁጥር አንድ ስሜ የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በደረሰበት ድምዳሜና ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡ በሀሳብ የተለየሁባቸውን ምክንያቶች ግልፅ ለማድረግ በመጀመሪያ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸውን የወንጀል ክሶች ይዘት፣ የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን ማስረጃ ከተሰማ በኋላ አመልካች መከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲሰናበት የሰጠውን ብይንና ብይኑን በማስተካከል አመልካች በዋስ ልለቀቅ ይገባል በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የስር ፍርድ ቤት የሰጣቸውን ምክንያቶች በአጭሩና በዝርዝር መግለፁ አስፈላጊ ነው ብየ ስለማስብ ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ አስፍራለሁ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 141352 ባቀረበው የወንጀል ክስ

   - አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 33፣ አንቀፅ 32 እና አንቀፅ 411 ንዑስ አንቀፅ 1/ሐ/ እና ንዑስ አንቀፅ 2 በመተላለፍ ከላይ ቁጥሩ በተገለፀው የወንጀል መዝገብ አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሽ ሆነው ከተከሰሱት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣኖች ጋር በመሆን የመንግስት ስራ በማያመች ሁኔታ የመምራት ከባድ የሙስና ወንጀል ፈፅሟል በማለት በሁለተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ አመልካች በስር ፍርድ ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የሆነው ጄ ኤች ሴሚክስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ እንደሆነ ገልፆ፤
   - አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 49 በመተላለፍ ከ1998 ዓ.ም እስከ 2004 የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 20,111,328.94 አሳውቆ ያለመክፈል ወንጀል ፈፅሟል በማለት በሰላሳ ሰባተኛው ወንጀል ክስ ላይ የገለፀ ሲሆን፣ አመልካች የ19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 56 እና አንቀፅ 49 በመተላለፍ በሰላሳ ሰባተኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በሰላሳ ስምንተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡
   - አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ አሳውቆ መክፈል ሲገባው 1998 ዓ.ም እስከ 2004 የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 20,111,328.94 የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ በመደበቅና የተጭበረበረ መረጃ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የመስጠት ወንጀል ፈፅሟል በማለት በሰላሳ ዘጠነኛው የወንጀል ክስ ላይ የገለፀ ሲሆን፣ አመልካች የ19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 56/1/ እና አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ በሰላሳ ዘጠነኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በአርባኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡
   - አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 96 የተመለከተውን በመተላለፍ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 29, 433, 214.24 ያገኘውን ትክክለኛ ገቢ አሳውቆ መክፈል የሚገባውን ገቢ ግብር ያለመክፈል ወንጀል ፈፅሟል በማለት በአርባ አንደኛው ወንጀል ክስ ላይ የገለፀ ሲሆን፣ አመልካች 19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 102/1/ እና አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ በአርባ አንደኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በአርባ ሁለተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም ብር 29,433,214.24 ያገኘውን ትክክለኛ ገቢ አሳውቆ መክፈል የሚገባው ገቢ ግብር በመደበቅና ያለመክፈል ወንጀል ፈፅሟል በማለት በአርባ ሶስተኛው ወንጀል ክስ ላይ የገለፀ ሲሆን፣ አመልካች 19ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 102/1/ እና አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ በመተላለፍ በአርባ ሶስተኛው ክስ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በማለት በአርባ አራተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡
- አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 98 የተመለከተውን በመተላለፍ ከቀረጥ ነፃ ያስገባቸውን የቀረጥ መጠናቸው 197556.61 የሆኑ መሳሪያዎች ከተፈቀደለት ተግባር ወጭ ተጠቅሟል በማለት በአርባ አምስተኛው የወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡

2. አመልካች በሁለተኛው የወንጀል ክስ የተከሰሰበትን ወንጀል ማለትም አመልካች ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 33 እና አንቀፅ 411 ንዑስ አንቀፅ 1/ሐ/ እና ንዑስ አንቀፅ 2 በመተላለፍ ፈፅሞታል የተባለው ከባድ የሙስና ወንጀል ከአስር አመት በላይ የሚያስቀጣ የሙስና ወንጀል በመሆኑ፣ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 4/1/ መሰረት አመልካች በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ የሕጉ ድንጋጌ ስለማይፈቀድለት አመልካች በማረሚያ ቤት ሆኖ ሲከራከር ቆይቷል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሐምሌ 26 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በሁለተኛው የወንጀል ክስ የተከሰሰበትን ከባድ የሙስና ወንጀል የፈፀመ ስለመሆኑ ተጠሪ በበቂ ሁኔታ ያላስረዳ በመሆኑ፣ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲሰናበት በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በመተላለፍ በበኩላቸው የወንጀል ክሶች ከሳሽ /ተጠሪ/ በበቂ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ተከሳሽ /አመልካች/ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የስር ፍርድ ቤት ብይን ሰጥቷል፡፡

3. የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ከሰማ በኋላ አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ፣ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 4/1/ መሰረት በዋስትና ወረቀት እንዳይለቀቅ ከማያስከለክለው ከባድ ሙስና የወንጀል ክስ ፍርድ ቤቱ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ብይን የተሰጠ መሆኑንና ተከላከል የተባለባቸው ሌሎች ወንጀሎች በዋስትና የመለቀቅ መብትን የሚያስከለክሉ መሆኑን ገልፆ፣ በዋስ የመለቀቅ መብቱ ይከበርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች ላቀረበው የዋስትና ጥያቄ ተጠሪ ነሐሴ 2 ቀን 2008 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም መልስ የሰጠ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ብይን ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ በዋስትናው ጥያቄ ላይ ያደረጉትን ክርክር ከመረመረ በኋላ፤

- ተከሳሽ በተደራራቢ ወንጀል ማለትም በ37ኛ ፣ 38፣ 40፣ 41፣ 42፣43፣44፣ እና በ45ኛ በድምሩ በስምንት ክሶች ብር 50,374,960 ተጨማሪ እሴት ታክስና ገቢ ግብር አሳውቆ ያለመክፈል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሰና ክሶቹ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ በመሆናቸው፣
- ተከሳሽ የተከሰሰባቸው ተጨማሪ እሴት ታክስና ገቢ አሳውቆ ያለመክፈል ተደራራቢ ወንጀሎች ሳይከፍል ቀርቷል የተባለው ታክስና ግብር ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያለው (ብር 50,374,960) በመሆኑና ወንጀሉ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍተኛነት ሲታይ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኝነትና የወንጀሉ ከባድነት ተከሳሹ በዋስትና ቢወጣ ይቀርባል ብሎ መገመት የማያስችል ምክንያት በመሆኑና፣
- ተከሳሹ ያለውን ኢኮኖሚ አቅም ተጠቅሞ ከአገር አይወጣም የሚለውን ግምት ሊያስተባብል የሚችል አሳማኝ ምክንያት በከሳሽ በኩል ስላልቀረበ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 (ሀ) እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሠረት ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚል እምነት ያለን በመሆኑ ተከሳሹ በማረሚያ ቤት ሆኖ ይከራከር በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ዋስትና መብት ለመገደብ የሰጡት ምክንያት የህገ መንግስቱንና የሌሎች ህግ ድንጋጌዎችን የተከተለ አይደለም በማለት ሲሆን ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

4. በእኔ በኩል የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ በብይኑ ላይ ያሰፈራቸው ምክንያቶች ህጋዊ ተቀባይነት ያላቸው ስለመሆናቸው የስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ያለውን ከፍተኛ የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅሞ ከአገር የማይወጣ ስለመሆኑ የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም በማለት የሰጠው ትርጉምና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በዋቢነት የጠቀሰበት ሁኔታ በሰበር ሊታረም የሚገባው መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

በመርህ ደረጃ የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀፅ 6 የመጀመሪያው ሐረግ “የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው” በማለት ቃል በቃል የተደነገገ ሲሆን በህግ በተደነገጉ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት የተከሳሹን በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተከሳሹ በዋስትና የመለቀቅ መብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገድቦ ሊቆይ እንደሚችል በህግ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 ተከታዩ ሐረግ ይደነግል። በአገራችን የተከሳሽን በዋስትና የመለቀቅ መብት ሕግ አውጭው በሕግ የገደበባቸው ሁኔታዎች አሉ። ሕግ አውጭው የዋስትና መብትን አስገዳጅ በሆኑ የህግ ድንጋጌዎች በከለከለባቸው ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን ዳኞች በዋስ የመፍታት ፈቃደ ስልጣን የላቸውም። ሕግ አውጭው የተከሳሽን በዋስትና የመለቀቅ መብት አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ የገደበው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 63 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በተሻሻለው ልዩ የሙስና የስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ1 በተመለከቱ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን የሚመለከት ነው።

5. ሕግ አውጭው የተከሳሽን በዋስትና የመለቀቅ መብት በህግ ከገደበባቸው ከላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ በሆኑ ሌሎች ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎች በመርህ ደረጃ የቀረበባቸው የወንጀል ክስ ሊያስከትል የሚችለው ከፍተኛ የወንጀል ቅጣትና በተከሳሹ ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ ብዛት ግምት ውስጥ ሳይገባ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት በዋስ የመለቀቅ መብት አላቸው። በህግ በዋስትና የመለቀቅ መብታቸውን በማያስገድቡ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት የሚገደበው መንግስትና ሕዝብን ወክሎ የሚከራከረው ዐቃቤ ህግ የተከሳሹን በዋስ መለቀቅ በመቃወም ክርክር ሲያነሳና ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ በዋስትናው ላይ ያቀረቡትን ክርክር ማስረጃ መርምሮ የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት የሚገድብ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ሲሰጥ ነው። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ዳኞች በህግ የተሰጣቸውን ፈቃደ ስልጣን በመጠቀም ተከሳሹ በዋስ እንዲለቀቅ ወይም የተከሳሽ በዋስ የመለቀቅ መብት ተገድቦ እንዲቆይ ትዕዛዝ የሚሰጡት ምን ምን ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ነው? የሚለው ነጥብ ሲሆን ይህም በዝርዝር ሲታይ፡-

- ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 የተረጋገጠው በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት የሚገድብ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚሰጡት ምን አይነት ልዩ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ነው?
- ተከሳሹ በዋስ ለመልቀቅ የማያስችሉና የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በልዩ ሁኔታ ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ማን ነው?
- ተከሳሹን በዋስ ለመልቀቅ የማያስችሉና የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት በፍርድ ቤት ውሳኔ (ትዕዛዝ በልዩ ሁኔታ ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ወገን፣ የማስረዳት ግዴታውን የሚወጣው በምን ደረጃ (standard of proof) እስከምን ድረስ ነው? የሚሉትን ነጥቦች በዝርዝር ማየት የሚጠይቅ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

6. ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 የተረጋገጠውን በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት የሚገድብ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚሰጡባቸውን ጥቅል ሁኔታዎች ህግ አውጭው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 ለማመለከትና ለመደንገግ ሞክሯል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 መሠረት አንድ ተከሳሽ በዋስትና የመለቀቅ መብቱን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚገደበው፡-

   ሀ/ ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን የማይፈጽም የሚመስል የሆነ እንደሆነ

   ለ/ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ተብሎ ሲገመት ወይም

   ሐ/ ምስክሮችን በመግዛት (በማባበል) ወይም አስረጅ የሚሆኑበትን ያጠፋል ተብሎ የሚገመት ሲሆን እንደሆነ ቃል በቃል ተደንግጓል፡፡

   ከላይ ዝርዝር ይዘታቸው የተገለጸው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ዓላማ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ በተጀመረው የወንጀል ምርመራ ወይም በፍርድ ቤት በተጀመረው የወንጀል ፍርድ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ተግባሮችን ሊፈጽም ይችላል ብሎ ፍርድ ቤቱ የሚገምተውን ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በማረሚያ ቤት ሆኖ ክርክሩን እንዲከታተል በማዘዝ፣ ወንጀል ምርመራው ወይም የፍርድ ሂደቱ ተከሳሹ በዋስ ተለቅቆ ሊፈጽማቸው ይችላል ተብለው ከሚገመቱ አሉታዊ ተግባራት ነፃ በሆነ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ለማስቻል መሆኑን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 ድንጋጌዎች ባህሪ ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

7. ከላይ የተገለጸውን መሠረታዊ ዓላማ ለማሳካት የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ መብት እንዲገድብ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ በህገ መንግስት አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 ዕውቅናና ጥበቃ የተሰጠውን መብት የመገደብ ውጤት ያለው በመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት የገደበው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ክርክር የሚያስነሳ ነው፤ ከሁሉም በላይ ፍርድ ቤቱ የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የጠቀሳቸው ምክንያቶችና ያስቀመጣቸው ሁኔታዎች ህገ መንግስታዊና ህጋዊ መሰረት ያላቸው ናቸው ወይስ አይደለም? የሚለውን ክርክር የሚያስነሱ ናቸው፡፡
8. ለዚህም መሠረት የሚሆነው የህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘትና ትርጓሜ፣ ድንጋጌው በመንግስት ላይ የሚጥለው ግዴታና ኃላፊነት በወንጀል ፍርድ ሂደት ላይ የሚኖረው ተግባራዊ ተፈፃሚነትና የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት ነው፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 “የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ ሁሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው" በማለት የሚደነግግ ሲሆን፣ የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዘኛ ቅጅ "During proceedings accused persons have the right to be presumed innocent until proved guilty according to the law and not to be compelled to testify against themselves" ተብሎ ተደንግጓል።

9. ተከሳሹ ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት ህገ መንግስታዊ መብት ያለው በመሆኑ፣ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ ለወደፊት ይዘታቸው ከላይ የተገለጹት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 67 የተደነገጉ አሉታዊ ውጤት ከሚያስከትሉ ተግባራት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ይፈጽማል ብሎ ፍርድ ቤቱ ከጅምሩ ግምት እዳይገበት ዋስትናና ጥበቃ ይሰጠዋል። ይህም ማለት ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ከቀረበበት የወንጀል ክስ ውጭ የሆኑ በቂ ምክንያትና ማስረጃ ሳይቀርብበት ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 67 ከተዘረዘሩት የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብትን ሊያስገድቡ ከሚችሉ ተግባራት አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ሊፈጽም ይችላል ብሎ ግምት ለመያዝና የተከሳሽን ዋስትና ጥያቄ እንዲሰርዝ ከላይ ይዘቱን የገለጽነው ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ የሚፈቅድ አይደለም በዚህ ምክንያት ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወ/መ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 67 ከተዘረዘሩት በዋስ የመለቀቅ መብትን ሊያስገድቡ ከሚችሉ ተግባራት አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ሊፈጽም ይችላል ብሎ ፍርድ ቤቱ ምክንያታዊ ግምትና መደሚደሚያ ላይ ሊደርስ የሚችልባቸውን ፍሬ ነገሮች የማቅረብና የማስረዳት ግዴታ (burdon of proof) ያለበት ዐቃቤ ህግ ነው።

10. በእርግጥ የዐቃቤ ህግ የማስረዳት ሸክም ደረጃና መጠን (standard of proof) ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 67 ከተዘረዘሩት በዋስ የመለቀቅ መብትን ሊያስገድቡ ከሚችሉ ተግባራት አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን በእርግጠኝነት የሚፈፅም መሆኑን በበቂ ሁኔታ የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ መሆን አይጠበቅበትም። የዐቃቤ ህግ የማስረዳት ሸክም ደረጃና መጠን (stanedard of proof) ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ፣ የዋስትና ግዴታውን ላይፈጽምና ቀጠሮውን አክብሮ ላይመጣ ይችላል፣ ወይም ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ወይም ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ ምስክሮችን በመግዛት (በማባበል) ወይም አስረጅ የሚሆኑበትን ያጠፉል ብለው ዳኞች የህሊና ግምት ለመውሰድ የሚያስችሉ ህጋዊ ተቀባይነት ያላቸውና ታዓማኒነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች ከማቅረብ ያለፈ አይደለም። ይህም ዳኞች የተከሳሹን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የሚያደርግ ትዕዛዝ የሚሰጡት በመጀመሪያ ዐቃቤ ህግ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ ከተከሰሰበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ወደ ፊት የሚኖረው ባህሪ ሊፈጽም የሚችላቸው ተግባራትና ስነ ምግባሩ ጥሩ አይሆንም ከሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያታዊ ጥርጣሬና ግምት ላይ እንዲደርሱ የሚያስችል ማስረጃ ወይም ፍሬ ነገር ሲያቀርብና ሲያስረዳ መሆኑን ያሳያል፡፡

11. ከላይ የተገለጸውን መሠረታዊ ሀሳብ ይገፍ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የሰጣቸውን ምክንያቶች አንድ በአንድ ተመልክቻለሁ፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የሰጠው የመጀመሪያው ምክንያት ተከሳሽ የተጨማሪ እሴት ታክስና የገቢ ግብር አሳውቆ ባለመክፈሉ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ቀርበውበታል፡፡ አመልካች በስምንት የወንጀል ክሶች መጠኑ ብር 50,374-960 ግብርና ታክስ ያለመክፈል ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በተደራራቢ ወንጀሎች ተከሷል፡፡ ተከሳሽ የተከሰሰባቸው ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ተደደራቢና ከባድ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ በመሆናቸው በወንጀሉ ያልተከፈለው የግብር የገንዘቡ መጠን ከፍተኛ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው አስተዋፅኦ የድርጊቱ አፈፃፀም አደገኛነት ያለው በመሆኑ አመልካች በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ አይቀርብም የሚል ነው፡፡

12. ከላይ እንደተገለጸው" የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ ሁሉ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው" በማለት የህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 መደንገጉ፣ የአመልካችን በዋስትና የመለቀቅ መብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለማስገደብ ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ይዘት፣ ብዛትና ወንጀሉ ሊያስቀጣ የሚችለው ቅጣት ክብደት መከራከሪያ አድርጎ ሊያቀርብ እንደማይችል እና ዐቃቤ ህግ መከራከሪያ አድርጎ ቢያቀርበው እንኳ ይህ ምክንያት የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት ለመገደብ የሚያስችል ህጋዊ መሠረትና ተቀባይነት ያለው ምክንያት ተደርጎ በፍርድ ቤት መወሰድ የሌለበት መሆኑን ነው፡፡ በአንድ ሰው ላይ ዐቃቤ ህግ ብዙ የወንጀል ክሶች ማቅረቡ ብቻውን ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ከሚለው ምክንያታዊ ጥርጣሬና ግምት ለማድረስ የሚያስችል ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ፍሬ ነገር (ማስረጃ) ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም አንድ ተከሳሽ የተከሰሰው በአንድ የወንጀል ክስ ወይም በብዙ የወንጀል ክሶች መሆኑ፣ተከሳሹ በተከሰሰባቸው ሁሉም የወንጀል ክሶች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብቱን የሚያሳጣው አይደለም፡፡ የተከሳሽ ከፍርድ በፊት ንፁህ ነው ተብሎ የመገመት ህገ መንግስታዊ መብት በአንፃራዊነት መብቱን የማክበርና ማስከበር ግዴታ ባለበት መንግስት ላይ በጠቅላላውና አግባብነት ባላቸው የመንግስት አካላት ላይ በልዩ ሁኔታ የሚያስከትለው ኃላፊነት አለ፡፡

13. የተከሳሽ በተከሰሰበት (በተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት ህገ መንግስታዊ መብት በተከሳሹ ላይ የቀረበውን የወንጀል ክስ በሚያየው የዳኝነት አካል(ፍርድ ቤት) እንደ አንድ የመንግስት አካልና ጉዳዩን በሚያዩ ዳኞች ላይ የሚጥለው ግዴታና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኃላፊነት አለ። ይኽውም ህገ መንግስታዊ ኃላፊነትና ግዴታ ተከሳሽ በተከሰሰበት (በተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንደሆነ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ 3 እና የህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ይዘት ተግባራዊ ተፈፃሚነትና ህጋዊ ውጤት በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል። የዳኝነት አካሉ እንደተቋምና የወንጀል ጉዳዩን የሚያዩት ዳኞች የተከሳሽን በተከሰሰበት (በተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ከፍርድ በፊት ንፁህ ነው ተብሎ የመገመት መብት የማክበር ኃላፊነታቸውን የሚወጡት የተከሳሹ ጉዳይ መታየት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በሚሰጡት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ከህግ አግባብ ውጭ ሳይሸራረፉ ለተከሳሹ መብት ዕውቅናና ከበሬታ መስጠታቸውን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ጉዳዩን አይተው እልባት ሲሰጡ መሆኑን የህገ መንግስቱን አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ያሳያሉ።

14. ይህም ዐቃቤ ህግ የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት ለማስገደብ የሚያቀርበው ምክንያት ፍሬ ጉዳይና ማስረጃ ተከሳሹ ከተከሰሰበት (ከተከሰሰባቸው) ወንጀሎች ይዘት ብዛትና ክብደት ውጭ የሆኑ ሌሎች ምክንያቶች መሆን ያለበት መሆኑን ያሳያል። የወንጀል ጉዳዩን የሚያዩት ዳኞች የተከሳሽን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚሰጡት በተከሳሽ ላይ የቀረበበትን የወንጀል ክስ ወይም ክሶች ይዘት ብዛትና ክብደት ተከሳሽ በዋስትና ወረቀት እንዳይለቀቅ ለመወሰን የሚያስችል በቂና ህጋዊ ምክንያት አድርገው በመቀበል መሆን አይገባም። ምክንያቱም የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ ሁሉ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው" በማለት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ድንጋጌ ዳኞች የፍርድ ሂደቱ ሳይጠናቀቅና በተከሳሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ ብዙ የወንጀል ክስ ስለቀረበበትና ተከሳሹ በቀረበበት የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችል ተከሳሹ ወደ ፊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ የሚጣልበትን ተደራራቢ ቅጣት በመፍራት የዋስትና ግዴታውን አክብሮ በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት ላይቀርብ ይችላል የሚል ግምትና መደምደሚያ እንዲይዙ የሚፈቅድ አይደለም። ዐቃቤ ህግ በተከሳሹ ላይ ያቀረባቸውን ወንጀል ክሶች ብዛትና ክብደት መነሻ በማድረግ የተከሳሽን ዋስትና መብት ለመገደብ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ከጅምሩ የተከሳሽን ከፍርድ በፊት ንፁህ ነው ተብሎ የመገመት መብት የሚጥስ ነው።

15. በአንጻሩ ዐቃቤ ህግ በተከሳሽ ላይ ብዙ የወንጀል ክስ ስላቀረበበትና ተከሳሹ በቀረቡበት ወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ተደራራቢ የወንጀል ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችል ተከሳሹ ወደፊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ የሚጣልበትን ተደራራቢ ቅጣት በመፍራት የዋስትና ግዴታውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አክብሮ በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት ላይቀርብ ይችላል የሚል ግምትና መደምደሚያ በመያዝ ዳኞች ተከሳሽ በእስር እንዲቆይ የሚሰጡት ትዕዛዝ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ የተከሳሹን ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ መገመት መብት ከህግ አግባብ ውጭ የተሸራረፈና ያልተከበረ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ በይዘቱም ሆነ በውጤቱ፣ ተከሳሽ በዐቃቤ ህግ ክቀረቡበት የወንጀል ክሶች በተወሰኑት የወንጀል ክሶች ወይም በሁሉም የወንጀል ክሶች ጥፋተኛ ሊባልና ሊቀጣ ስለሚችል፣ ተከሳሽ ወደ ፊት ጥፋተኛ ቢባል በፍርድ የሚወሰንበትን የወንጀል ቅጣት ለማምለጥ በዋስ ቢለቀቅ ከአገር ሊጠፋ ይችላል የሚል ዕምነትና ግምት ዳኞች ያላቸው መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት ዳኞች የተከሳሽን ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ መገመት መብት ባከበረና በሚያስከብር ሁኔታ ጉዳዩን አይተው እልባት የመስጠት ግዴታና ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጡ መሆናቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የተከሳሽን ዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የተጠቀመበት ከላይ የተገለፀው ምክንያት ዳኞች አስቀድመው ተከሳሹ የተከሰሰባቸውን ወንጀሎች ፈጽሟቸዋል የሚል ግምትና አቋም ሳይዙ ገለልተኛ ሆነው ጉዳዩን አይተዋል ወይም አላዩም የሚል ክርክር የሚያስነሳ የህግ አተረጓጎም ነው፡፡

16. በእኔ እምነት ዐቃቤ ህግ የተከሳሽን በዋስ የመለቀቅ መብት በመቃወም ካቀረበው ክርክር አንፃር፣ ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 76 (ሀ) በተደነገገው መሠረት ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን የማይፈጽም ይመስላል ወይም አይመስልም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን ፍርድ ቤቱ መመልከትና መመዘን ያለበት በተከሳሹ ላይ ዓቃቤ ህግ ያቀረበው ወንጀል ክስ ብዛትና ክብደት ሳይሆን የተከሳሽ ግላዊ ሁኔታ ባህሪውን፣ ስብዕናውን እና ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን በማክበር የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተል ሊያደርጉት የሚያስችሉ ግላዊ፣ ቤተሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችና ሌሎች ተጨባጭ ኩነቶች መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን በመመዘን መሆን እንዳለበት የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3፣ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ- ስርዓት ሕግ ቁጥር 67/ሀ/ ድንጋጌዎች የጣምራ ንባብ ይዘት፣ ዓላማና ተግባራዊ ተፈጻሚነት ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፍ/ቤቱ ጭብጡን መወሰን ያለበት ተከሳሹ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ፣ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ የሚያስችሉና ተከሳሹን በእስር ከማቆየት የተሻሉ ሌሎች አማራጮች፣ ለምሳሌ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ ከአገር እንዳይወጣ ወይም ከሚኖርበት ከተማ ውጭ እንዳይንቀሳቀስ በመገደብና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ትእዛዞች በመስጠት ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ የሚቻል መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም አለመሆኑን በማገናዘብና በማጣራት መሆን ይገባዋል። በማጣራቱ ሂደት ፍ/ቤቱ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ የሚያስችሉና ተከሳሹን በእስር ከማቆየት የተሻሉ ሌሎች አማራጮች መኖራቸውን ከተረዳ ተከሳሽ በዋስ እንዲለቀቅ የሚሰጠውን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች /የመብት ማዕቀቦች/ ጋር ተጣምረው እንዲፈጸሙ ትእዛዝ በመስጠት ፣ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3፣ እና አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1፣ እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 /ሀ/ ድንጋጌዎች የጣምራ ንባብ ይዘትና ዓላማ ማሳካት ይገባዋል ብዬ አስባለሁ።

17. በእኔ እምነት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67/ሀ/ በተደነገገው መሰረት ተከሳሹ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን የማይፈጽም ይመስላል ወይም አይመስልም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በተከሳሹ ላይ ዓቃቤ ሕግ ካቀረበው የወንጀል ክስ ክብደትና ብዛት በበለጠ፣

- ተከሳሽ በአገር ውስጥ ተለይቶ የሚታወቅ ቋሚ አድራሻ ያለው መሆኑ ወይም አለመሆኑ ፣
- ተከሳሹ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ወይም አለመሆኑና ተከሳሽ ከቤተሰቦቹ ጋር በአገር ውስጥ የሚኖር መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣
- ተከሳሹ በአገር ውስጥ የሚተዳደርበት ቋሚ ስራ፣ የገቢ ምንጭ ወይም ንግድ ወይም ኢንቨስትመንት ያለው መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣
- ተከሳሹ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት በቀጠሮው ቀን ፍርድ ቤት ባይቀርብ ፍ/ቤቱ በሕግ አግባብ በቀጣይ በሚሰጠው ትእዛዝ ሊያጣው የሚችለው መብትና ጥቅም ያለ መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣
- ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ በነጻነቱ ላይ ሌሎች ገደቦችን በመጣል ለምሳሌ ከአገር እንዳይወጣ በመገደብ፣ እንደግለሰቡ ሁኔታ ተከሳሽ በሚኖርበት ከተማ ወይም ቀበሌ በየቀኑ ወይም በየሳምንቱ ለክፍሉ ፖሊስ በአካል እየሄደ ሪፖርት የሚያደርግበትንና ፖሊስም ተከሳሹ በፍርድ ቤት የታዘዘውን ገደብና ሁኔታ እያከበረ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርግና ፍ/ቤቱ ያስቀመጣቸውን ገደቦችና ሁኔታዎች ተከሳሹ ጥሶ ባገኘው ጊዜ፣ ተከሳሹን በቁጥጥር ስር አውሎ በዋስ እንዲለቀቅ ትእዛዝ ለሰጠው ፍ/ቤት የሚያቀርብበትን አሰራር በመከተል ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ እንዲቀርብ ለማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣
- በተከሳሹ ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ ሊወሰን የሚችል መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን ባለማክበሩ ጉዳዩ በሌለበት ቢታይና ተከሳሽ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ፣ ፍ/ቤቱ ሊወስን የሚችለውን የወንጀል ፍርድና ቅጣት፣ መንግስት ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠውን የወንጀል ፍርድና ቅጣት ተከትሎ በሕግ መሰረት በተከሳሽ ንብረት ላይ የሚሰጠው የመወረስ ውሳኔ ተከሳሹ ሊያጣ የሚችለው ገንዘብና ሃብት፣ ተከሳሹ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ የፍርድ ሂደቱን ጥሎ እንዲፈረጥጥ የሚገፋፉ ናቸው ወይስ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኋላ የቀጠሮውን ቀን አክብሮ የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተል የሚያስገድዱ ተጨባጭ ምክንያቶች የሚለውን በማነጻጸር፣ ከእያንዳንዱ ተከሳሽ ሁኔታ ጋር በማየትና በመመዘን ፍ/ቤቱ ምክንያታዊ ግምትና ሎጂካል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ይገባዋል የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

18. ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤት ዓቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ ተደራራቢ የወንጀል ክስ ማቅረቡንና ተከሳሽ ሊጣልበት የሚችለውን ተደራራቢ ቅጣት ለመሸሽ በዋስ ቢለቀቅ ቀነ - ቀጠሮውን አክብሮ ፍ/ቤት ሊቀርብ አይችልም በማለት የሰጠው ምክንያት ከላይ በተራ ቁጥር 15 እና 16 የገለጽኳቸውን መሰረታዊ ሁኔታዎች ያላገናዘበና ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ ያላገኘሁት በመሆኑ አመልካች በዋስ ሊለቀቅ ይገባል በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

19. ከላይ በዝርዝር የገለጽኩት እንዳለ ሆኖ፣ የስር ፍ/ቤት አመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ አመልካች በስምንት ተደራራቢ የወንጀል ክሶች ማለትም ተጠሪ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 141352 ባቀረባቸው በ 37ኛ ፣ 38ኛ፣ 40ኛ፣ 41ኛ፣ 42ኛ፣ 43ኛ፣ 44ኛ እና በ 45ኛ በድምሩ በስምንት ክሶች ብር 50,374,960 ግብርና ታክስ እንዳይከፈል በማድረግ ወንጀል እንደተከሰሰና መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብይን እንደተሰጠበት አድርጎ በብይኑ ውስጥ ያሰፈረው ፍሬ ሃሳብ ሊታረምና ተገቢ የሕግ ትርጉም ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የዋስትና መብት ለመገደብ ተደራራቢ ናቸው ብሎ የጠቀሳቸው ስምንት ክሶች፣ አመልካች ላይ የቀረቡትን የወንጀል ክሶች ብቻ የሚመለከቱ ሳይሆኑ አመልካቹ በስራ አስኪያጅነት ሲያስተዳድረው የነበረውና በስር ፍ/ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የሆነው ጄ ኤች ሴሚክስ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የተከሰሰባቸውን የወንጀል ክሶች ጨምሮ በመቁጠር የአመልካችን ዋስትና መብት መገደቢያ ምክንያት አድርጎ የስር ፍ/ቤት ብይን የሰጠ በመሆኑ ነው፡፡

20. ከላይ ይዘታቸውን በተራ ቁጥር 1 የገለጽኳቸውና ተጠሪ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 141352 በ 37ኛ፣ 41ኛ እና በ 43ኛ ያቀረባቸው ወንጀል ክሶች አመልካች በስራ አስኪያጅነት ሲያስተዳድረው የነበረው በስር ፍ/ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ ሆነው ጄ ኤች ሴሚክስ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የከሰሰባቸው የወንጀል ክሶች ናቸው፡፡ የንግድ ድርጅቱ የተከሰሰባቸው የወንጀል ክሶች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 ፣ በአዋጅ ቁጥር 285/94 እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 ልዩ ድንጋጌዎች መሰረት የንግድ ድርጅቱ ለተከሰሰበት ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ፣ አመልካች ሳይሆን ራሱ የንግድ ድርጅቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የሚወሰንበት የእስራትና የጽኑ እስራት ቅጣት ወደ ገንዘብ ተለውጦ የሚቀጣባቸውና ቅጣቱን እንዲፈጽም የሚደረግባቸው የወንጀል ክሶች ናቸው፡፡ አስራ ዘጠነኛው ተከሳሽ ሕግ ወለድ ሰው በመሆኑ በፍርድ ሂደቱ በእስር ላይ አይገኝም፡፡ በዚህ ምክንያት አስራ ዘጠነኛው ተከሳሽ ያቀረበውና ሊያቀርበው የሚችለው የዋስትና መብት ጥያቄ የለም፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ፣ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸውን የወንጀል ክሶች ብቻ ሳይሆን፣ በስር ፍ/ቤት አስራ ዘጠነኛ ተከሳሽ የሆነው የንግድ ኩባንያ የከሰሰባቸውን የወንጀል ክሶች ጨምሮ በመቁጠር አመልካች ስምንት ተደራራቢ ወንጀል ክሶች እንደቀረቡበት አድርጎ ብይን መስጠቱ በሰበር ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

21. የስር ፍ/ቤት የተከሳሹ የዋስትና መብት ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት ሌላው ምክንያት ተከሳሹ ያለውን የኢኮኖሚ አቅም ተጠቅሞ ከአገር ሊወጣ ይችላል የሚለውን ግምት ሊያስተባብል የሚችል አሳማኝ ምክንያት በተከሳሽ በኩል አልቀረበም በማለት ነው፡፡ ሲጀመር ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ያለው በወንጀል የተከሰሰ ባለሃብት ያለውን የገንዘብ አቅም ከቀረበበት የወንጀል ክስ ለማምለጥ ሊጠቀምበት ይችላል የሚል ግምትና መደምደሚያ ዳኞች ከፍርድ በፊት እንዲይዙ፣ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የተከሳሽ ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ መገመት መብት የሚፈቅድ አይደለም፡፡

22. በሁለተኛ ደረጃ ተከሳሽ በዋስ ቢፈታ ያለውን የገንዘብ አቅም ከቀረበበት የወንጀል ክስ ለማምለጥ ሊጠቀምበት ይችላል የሚለውን ፍሬ ጉዳይ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ዓቃቤ ሕግ እንጅ ተከሳሹ አይደለም፡፡ ዓቃቤ ሕግ በህግ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታ የሚወጣው ተከሳሹ ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ያለው መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማሳየት ብቻ አይደለም፡፡ በአንጻሩ ተከሳሹ በአገሪቱ ውስጥ ያጠራቀመው ሃብት ወይም ተከሳሹ ኢንቨስት ያደረገበት የንግድ ዘርፍ በባህሪው፣ ተከሳሽ በዚህ አገር ያለውን እሴትና ገንዘብ በቀላል ሰብስቦ ወደ ሌላ አገር ለማሻገር ውጣ ውረድን የማያስከትል መሆኑን፣ ተከሳሹ በዚህ አገር የሚሳሳለትና ወደ ኋላ የሚቀር በቀላሉ ሊያጓጉዘው የማይችል ቋሚ ሃብት የሌለው መሆኑን ተከሳሹ ከአገር ሊጠፋ ይችላል የሚልባቸውን፣ ሌሎች ተጨባጭ ምክንያቶች በማቅረብ መሆን አለበት፡፡

23. በያዝነው ጉዳይ ተከሳሽ በተከሰሰበት ወንጀል ሳይከፍለው የቀረ ነው ተብሎ በወንጀል ክሱ ከተጠቀሰው የግብርና ታክስ ገንዘብ ብር 50,374,960 በብዙ እጥፍ የሚበልጥ ካፒታል አውጥቶ በረኸርም ጊዜ ኢንቨስትመንት ካፒታሉን በሚመልስ ሆቴል ግንባታ ስራ ያዋለ መሆኑን ተጠሪ አይክድም፡፡ ይህም ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ በዚህ አገር ኢንቨስት ያደረገውን ሃብትና ገንዘብ በቀላሉ ሊያንቀሳቅሰው በማይችለው የኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ ያፈሰሰው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ተከሳሹ በዚህ አገር የሚሳሳለትና ወደ ኋላ የሚቀር በቀላሉ ሊያንገዳግዘው የማይችል ቋሚ ሀብት ያለው መሆኑና ተከሳሹ ያለው ቋሚ ሃብት በወንጀል ስራው አግኝቶታል ከሚባለው የግብር ገንዘብ በብዙ እጥፍ የሚበልጥ መሆኑ ካላከራከረ፣ ይኸ ምክንያት ተከሳሹ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ የፍርድ ሂደቱን እስከመጨረሻው እንዲከታተል የሚያደርገው የንብረት መብትና ጥቅም ያለው መሆኑን ለመደምደምና ተከሳሽን በዋስ ለመልቀቅ የሚያስችል ምክንያት ከሚሆን በስተቀር ተከሳሽን የዋስትና መብት ለመንፈግ የሚያስችል አይሆንም፡፡

24. ተከሳሽ ከፍተኛ ኢኮኖሚ አቅም ያለው መሆኑን ፍ/ቤቶች የተከሳሽን የዋስትና መብት ለመገደብ በቂ ምክንያት አድርገው መቀበላቸው፣ ኢንቨስተሮችን ወደ አገራችን ለመሳብ በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል የዋስትና ሕግ ድንጋጌ አተረጓጎም ነው፡፡ መንግስት የተጀመረውን ፈጣን ልማትና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠንና ለማስቀጠል ኢንቨስትመንት ይፈልጋል፡፡ መንግስት የአገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስተሮች መዋዕለ ነዋይ፣ ገንዘብና ካፒታል ፍሰት ለማሳደግና ለመሳብ ከሌሎች ኢንቨስትመንት ከሚቀበሉ አገሮች ጋር በሕግ ፣ በአስተዳደርና በፍትህ ዘርፍ ተወዳዳሪና ተመራጭ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡ መንግስት ኢንቨስተሮችን ለመሳብ የኢንዱስትሪ ፓርክ በመገንባት፣ ከሊዝ ነጻ መሬት በመስጠት፣ የታክስ፣ የግብርና ሌሎች ማበረታቻዎችን በሕግ ከመደንገግና ተፈጻሚ ከማድረግ አልፎ፣ ለውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስተሮች ዓለማቀፍ የመድን ዋስትና እየሰጠ መሆኑን በዚህ ዙሪያ የወጡ የሕግ ማእቀፎችን፣ የተደረጉ ዓለማቀፍ ስምምነቶችን ይዘትና ተግባራዊ አፈጻጸም በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

25. በአገር ደረጃ የተለያየ ማበረታቻ ተሰጥቷቸው፣ መዋዕለ ነዋያችንን በዚህ አገር ኢንቨስት ማድረግ ይሻለናል ብለው አገራችንን መርጠው የመጡ ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ያላቸው ባለሃብቶች በወንጀል ተጠርጥረው ወይም ተከሰው በቁጥጥር ስር የሚውሉበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት በግልጽ በብይኑ ባሰፈረው መንገድ፣ ተጠርጣሪዎቹ ወይም ተከሳሾቹ ባለሃብቶችና ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ስላላቸው ከአገር ሊጠፉ ይችላሉ የሚል ግምትና መደምደሚያ ፍ/ቤቶች እየያዙ የዋስ መብታቸውን የማያከብሩላቸው መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህንን ግምትና የዋስትና ሕግ ድንጋጌ አተረጓጎም ይህ ሰበር ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ ፣ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን ሳያርመው ማለፉ ተገቢ አይደለም ብዬ አስባለው፡፡ ይህ የሕግ አተረጓጎም አገሪቱን መርጠው ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሃብቶች በወንጀል በተጠረጠሩ ወይም በተከሰሱ ጊዜ ይዘውት የመጡት ሃብት ከፍርድ በፊት እነርሱን አስሮ ለማቆየትና የዋስትና መብት ለመንፈግ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የሚያረጋግጥ፣ ለባለሃብቶቹ ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመገመትና የነጻነት መብት ዋስትናና ጥበቃ የማይሰጥ አስፈሪና ባለሃብቶቹን በሩቁ እንዲሸሹ የሚያደርግ የሕግ አተረጓጎም ይሆናል፡፡

26. የሕግ አተረጓጎማችን የኢንቨስተሮች /ባለሃብቶች/ በወንጀል ተጠርጥረው በተያዙ ጊዜ ወይም በወንጀል በተከሰሱ ጊዜ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 የተረጋገጠላቸውን ከፍርድ በፊት ንጹህ ነው ተብሎ የመገመት መብት፣ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6 የተረጋገጠላቸውን በዋስ የመለቀቅ መብትና በአንቀጽ 25 የተረጋገጠውን እኩል የሕግ ጥበቃና የዋስትና ማግኘት መብት የሚጥስና በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ፣ ፈርጀ ብዙ የሆኑ ችግሮችን የሚያስከትል የሕግ አተረጓጎምና ውሳኔ ነው የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤት አመልካች በዋስ ቢለቀቅ ያለውን ኢኮኖሚ አቅሙን ተጠቅሞ ከአገር የማይወጣ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱን የሚያሳምን ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ የዋስትና ጥያቄውን አልተቀበልነውም በሚል መንገድ የተሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል እምነት ስላለኝ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

27. የስር ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ከዚህ በፊት፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም የአመልካችን ዋስትና መብት ለመንፈግ በዋቢነት ሲጠቅስ በዚህ መዝገብ የተከሳሽ የዋስትና ጥያቄ ሲታይ የነበሩ ፍሬ ጉዳዮች፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ከተሰጠባቸው ፍሬ ጉዳዮች የሚለያዩበትና የተለየ የሕግ ትርጉም ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን በአግባቡ አላገናዘበም፡፡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 የዋስትና ክርክሩ የተነሳው ተከሳሾች የወንጀል ክስ እንደቀረበባቸው ወዲያውኑ ክሱ በቀረበባቸው በሳምንታት ጊዜ ውስጥ ነው፤ በዚህ መዝገብ የአመልካች የዋስትና ጥያቄ አከራካሪ የሆነው አመልካች በቀረበበት የወንጀል ክስ ምክንያት ሶስት አመት ከስድስት ወር በላይ በእስር ከቆየ በኋላ ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ ከፍርድ በፊት ታስሮ የቆየበት ጊዜ ተከሳሹ በዋስ እንዲለቀቅ ወይም በእስር እንዲቆይ በመወሰን ሂደት የራሱ የሆነ ትርጉምና ፋይዳ እንደዚሁም ህጋዊ ውጤት አለው፡፡ ረዥም ጊዜ በወሰደ የፍርድ ሂደት ምክንያት፣ አመልካች ከፍርድ በፊት ረዥም ጊዜ በእስር የቆየ መሆኑ በራሱ፣ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም ከሚለው ሎጅካል መደምደሚያና ግምት ላይ ለመድረስ የማያስችልና አመልካቹን የዋስትና ጥያቄ ለመቀበልና በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመውጣት የአመልካች የዋስትና ጥያቄ በልዩ ሁኔታ አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ምክንያት ነው፡፡

28. ከዚህ በተጨማሪ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠውና የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 286/1994 የወንጀል ድንጋጌዎች ይዘትና ቅጣት ላይ መሰረታዊ የሕግ ማሻሻያና ለውጥ በሕግ አውጭው ከመደረጉ በፊት ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሶበት የነበረው የወንጀል ድንጋጌ፣ የተከሳሹ ጉዳይ በመታየት ላይ እያለ፣ ተከሳሽ የተከሰሰበትን የሕግ ማዕቀፍ በሂደት በህግ አውጭው ተከሳሹን የሚጠቅም ይዘት ባለውና ቀላል ቅጣት በሚደነግግ ሌላ ሕግ የተሻሻለና የተለወጠ መሆኑ የተከሳሹን የዋስትና ጥያቄና ከተሻሻለው ህግ አንጻር አይቶ ለመወሰን የሚጠቅም መሆኑ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 67 ድንጋጌዎች ፣ ከሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 ፣የወንጀል አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 አስገዳጅ ድንጋጌ ጋር በማጣመር ለመተርጎምና ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካችን በተደራራቢ የወንጀል ክስ የተከሰሰባቸው የአዋጅ ቁጥር 285/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 286/1994 ወንጀል ድንጋጌዎች፣ ሕግ አውጭው ባወጣው የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ተሻሽሏል፡፡ የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ድንጋጌዎች አመልካችን የሚጠቅም ይዘትና ቅጣት መጠን ያላቸው መሆኑን ድንጋጌዎቹን በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሲሰጥ በወቅቱ ባመለከቱት ተከሳሾች ላይ ተፈጻሚነት ነበራቸው የአዋጅ ቁጥር 285/1994 እና የአዋጅ ቁጥር 286/1994 ወንጀል ድንጋጌዎች፣ አመልካችን የሚጠቅም ይዘት ባለው አዋጅ ቁጥር 983/2008 ድንጋጌዎች የተለወጡና የተሻሻሉ መሆኑን ሳያገናዝብ የስር ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአሁኑ ወቅት የተሻረ የሕግ ማዕቀፍ መሰረት በማድረግ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59304 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አላግባብ በዋቢነት በመጥቀስ የአመልካችን ዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

29. ከላይ በዝርዝር በገለጽኳቸው የሕግ አተረጓጎም ልዩነቶችና ዝርዝር ምክንያቶች የስር ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በዋስ ሊለቀቅ ይገባል የሚል አቋም ስላለኝ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117735

መጋቢት 28 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፦ ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ህጻን ሣራ ማርቆስ - ሞግዚት ብርነሽ ሁንዴ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ስዩም አሰፋ
2. አቶ ዮሐንስ አሰፋ
3. ወ/ት አብነት አሰፋ
4. አቶ ብሩክ ግርማ

} 3ኛ ተጠሪ የ4ቱም ተጠሪዎች ጠበቃ አቶ አያሌው አለማየሁ ቀረቡ

5. አቶ ማርቆስ አሰፋበሆኑት - መብታቸው ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 157255 በ17/07/2007 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 111970 በ15/10/2007 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የክርክሩን አመጣጥ በተመለከተ፡-በስረ ነገሩ ጉዳይ የህጻን ልጃቸውን ቀለብ የአሁኑ 5ኛ ተጠሪ በየወሩ ብር 5,000 (አምስት ሺህ) እንዲከፍሉ የአመልካች ሞግዚት ውሳኔ ማሰጠታቸውን፣ በዚሁ ፍርድ መሰረት ለማስፈጸም እንዲቻል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቁጥሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

213611 የሆነ የአፈጻጸም መዝገብ አስከፍተው የፍርድ ባለዕዳው በአገር ውስጥ የሌሉ መሆኑን ጠቅሰው ፍርዱ የፍርድ ባለዕዳው ከአሁኖቹ 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር ከወላጆቻቸው በጋራ በውርስ ያገኙት በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 5 የሚገኘው ቁጥሩ 327 የሆነው ቤት በሐራጅ ተሸጦ ከሽያጩ ገንዘብ የፍርድ ባለዕዳው ድርሻ በፍርዱ መጠን እንዲከፈላቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን፣ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ጥያቄ ተቀብሎ ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ከሽያጩ ገንዘብ ከአንድ አራተኛው ውስጥ ውዝፍ ቀለቡ ታስቦ ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል፣ከውዝፍ ቀለቡ የተረፈው ደግሞ በህጻኗ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተቀምጦ ዕድሜዋ 18 ዓመት እስኪሞላት ድረስ በየወሩ ብር 5,000 ወጪ እየተደረገ እንዲከፈላት በመዝገብ ቁጥር 213611 በ29/11/2006 ዓ.ም. ትዕዛዝ መስጠቱን፣አፈጻጸሙ በዚህ ሂደት ላይ እያለ የአሁኖቹ 1ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ውርሱ ተጣርቶ የወራሾቹ ድርሻ ባልተለየበት ሁኔታ በውርስ ሀብቱ ላይ የሐራጅ ሽያጭ ትዕዛዝ የተሰጠው አላግባብ ነው በማለት በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 418 ድንጋጌ መሰረት መቃወሚያ ማቅረባቸውን፣የአፈጻጸም ችሎቱም የአመልካቿን ሞግዚት አስተያየት ከተቀበለ በኃላ የመቃወሚያ አቅራቢዎቹን ክርክር ተገቢ አድርጎ በመቀበል የሐራጅ ሽያጭ ትዕዛዙ እንዲቋረጥ በመዝገብ ቁጥር 213611 በ23/01/2007 ዓ.ም. ብይን መስጠቱን፣በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት የህጻኗ ሞግዚት ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የአሁኖቹ 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የፍርድ ባለዕዳ ከሆኑት 5ኛ ተጠሪ ጋር የወላጆቻቸው ወራሾች መሆናቸውን በጋራ በማረጋገጥ የተሰጣቸውን የወራሽነት ማረጋገጫ ማስረጃ ጉዳዩ በሚመለከተው ክፍለ ከተማ አስተዳደር አቅርበው ከቤቱ ማህደር ጋር እንዲያያዝ ማድረጋቸው መረጋገጡን፣መቃወሚያ አቅራቢዎቹ ሌላ ወራሽ ወይም የውርሱ ዕዳ ወይም የሚኞቹ ኑዛዜ መኖር አለመኖሩ አልተረጋገጠም ከማለት በቀር ሌላ ወራሽ ወይም የውርሱ ዕዳ ወይም የሚኞቹ ኑዛዜ ስለመኖሩ ያቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ አለመኖሩን እና የወራሽነት ማስረጃ አቅርበው ከቤቱ ማህደር ጋር ካያያዙ ከሁለት ዓመት በኃላም ቢሆን መቃወሚያ አቅራቢዎቹ ውርሱ እንዲጣራ ያቀረቡት ጥያቄ አለመኖሩ ውርሱን የማጣራት ፍላጎት እንደሌላቸው የሚያመለክት መሆኑን ገልጾ ብይኑን በመሻር አፈጻጸሙ በስር ፍርድ ቤት በ29/11/2006 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት እንዲቀጥል በመዝገብ ቁጥር 157255 በ17/07/2007 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኖቹ 1ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች በተራቸው ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ወራሾቹ በስምምነት ውርሱን የማያጣሩ ከሆነ ውርስ አጣሪ ሾሞ ውርሱ እንዲጣራ ካደረገ በኃላ በፍርድ ባለዕዳው ድርሻ ላይ ተገቢውን ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመመለስ በመዝገብ ቁጥር 111970 በ15/10/2007 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ውርሱ ስላልተጣራ በውርስ ሀብት ላይ ፍርዱን ማስፈጸም አይቻልም በሚል በተለይም የህጻን የመብት ጥያቄ ወደ ጎን ተትቶ ውርሱ በቅድሚያ ይጣራ ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በመዝገብ ቁጥር 34703 እና በመዝገብ ቁጥር 35710 ከተሰጠው ገዥ የሕግ ትርጉም አንጻር ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ በጋዜጣ ማስታወቂያ ተጠርተው መልስ ባለመስጠታቸው ምክንያት መብታቸው ከታለፈው 5ኛ ተጠሪ በስተቀር አመልካች እና ቀሪዎቹ ተጠሪዎች የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 418 ድንጋጌ መሰረት መቃወሚያ ያቀረቡት እና ከስር ጀምረው የሚከራከሩት የውርስ ማጣራት ሂደት ተከናውኖ ውጤቱ ባልታወቀበት ሁኔታ ፍርዱ ከውርስ ሀብቱ ውስጥ የ5ኛ ተጠሪ ነው በተባለው ድርሻ ላይ ሊፈጸም አይገባም በማለት መሆኑን የክርክራቸው ይዘት ያመለክታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው በዋናነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 943 (3) ድንጋጌን አነጋገር መሰረት አድርጎ በመያዝ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያመለክታል፡፡በመሰረቱ በውርስ ማጣራት ሂደት በአጣሪው የሚከናወኑት ተግባራት የውርስ ሀብቱ ምን እንደሆነ እና የውርሱ ተቀባዮች እነማን እንደሆኑ መወሰን፣ዕዳዎችን መክፈልና መቀበል፣ሟቹ ኑዛዜ ትቶ እንደሆነ መፈለግ፣የኑዛዜ ስጦታዎችን መክፈል፣የውርሱን ሀብት ማስተዳደር ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕጉ በቁጥር 944 እና 956 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡በዳኞች ትዕዛዝ ጊዜው እንዲራዘም ካልተደረገ በቀር የውርሱ የሒሳብ ማጣራት ስራ ሟቹ ከሞተ ከአንድ ዓመት በኃላ የሚዘጋ ስለመሆኑ፣የውርሱ ሒሳብ ማጣራት በተዘጋ ጊዜ ከውርሱ ውስጥ ሆኖ የሚገኘው ንብረት ከወራሹ ሌላው ሀብት ጋር የሚቀላቀል ስለመሆኑ፣የጋራ ወራሾችም እንዳሉ የውርሱ ሆኖ የሚገኘው ንብረት የጋራ ወራሾች ንብረት እንደሚሆን፣የውርሱ አከፋፈል እስኪፈጸም ድረስ በወራሾቹ መካከል ውርሱ ሳይነጣጠል የሚቆይ ስለመሆኑ፣የጋራ ወራሾች የሆኑ ሰዎች ባልተከፋፈሉት የውርስ ንብረት ላይ ያላቸው መብት በፍትሐብሔር ሕጉ ስለጋራ ባለሀብትነት፣ስለሪምና ስለሌሎች ግዙፍ መብቶች በሚለው አንቀጽ በተነገሩት ድንጋጌዎች (ከቁጥር 1257 እስከ 1277) መሰረት የሚወሰን ስለመሆኑ እና ከእያንዳንዶቹ የጋራ ባለሀብቶች ላይ ገንዘብ የመጠየቅ መብት ያላቸው ሰዎች የባለዕዳውን ድርሻ ለመያዝ የሚችሉ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 1052፣1053፣1060 እና 1260 ድንጋጌዎች ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የአከራካሪው ንብረት የጋራ ወራሾች መሆናቸውን ገልጸው ጥያቄያቸውን ለፍርድ ቤት በማቅረብ የወራሽነት ማስረጃ በ2004 ዓ.ም.

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወሰዱ መሆኑ፣ይህንንም የወራሽነት የምስክር ወረቀት የቤቱ ማህደር በሚገኝበት ክፍለ ከተማ አስተዳደር በማቅረብ ከቤቱ ማህደር ጋር እንዲያያዝ ያደረጉ መሆኑ፣የውርስ ሀብቱ የሆነውን ቤትም በይዞታቸው ስር አድርገው እየተገለገሉበት መሆኑ በተጠሪዎቹ ያልተካዱ እና በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክርም የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው።የውርስ ማጣራት ሂደት ተከናውኖ ውጤቱ ባልታወቀበት ሁኔታ ፍርዱ ከውርስ ሀብቱ ውስጥ የ5ኛ ተጠሪ ነው በተባለው ድርሻ ላይ ሊፈጸም አይገባም በማለት በደፈናው ከመከራከር በቀር በአከራካሪው ቤት ላይ መብት ያለው ሌላ የኑዛዜም ሆነ የሕግ ወራሽ ስለመኖሩ እነዚህ ተጠሪዎች በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የለም።እነዚህ ሁኔታዎች ተጠቃለው ሲታዩም 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በሕጉ በተመለከተው የውርስ ማጣራት ሂደት ውስጥ ማለፍ ሳያስፈልጋቸው የውርስ ሀብት መሆኑ በተረጋገጠው ቤት ላይ እያንዳንዳቸው እኩል ድርሻ እንዳላቸው ተስማምተው እና ቤቱንም በቁጥጥራቸው ወይም በይዞታቸው ስር አድርገው በቤቱ ላይ በጋራ ባለሀብትነት መብት በማቋቋም እየተገለገሉበት መሆኑን መገንዘብ የሚያስችሉ ናቸው።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው በዋናነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 943 (3) ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ሲሆን ይህ ድንጋጌ ከወራሾቹ ከራሳቸው ገንዘብ ጠያቂ የሆኑ ሰዎች የውርሱ ሀብት በሚጣራበት ጊዜ በውርስ ሀብቱ ላይ አንዳችም መብት የሌላቸው መሆኑን የሚደነግግ ነው። በመሰረቱ የውርስ ሀብት እና የጋራ ወራሾች ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ከቁጥር 943 እና 1060 ድንጋጌዎች ይዘት በግልጽ መገንዘብ ይቻላል። አንድ ሀብት የውርስ ሀብት ነው የሚባለው ውርሱ በመጣራት ሂደት ላይ ባለበት ጊዜ ስለመሆኑ የቁጥር 942 ድንጋጌ ያመለክታል።በተያዘው ጉዳይ ግን ወራሾቹ በሕጉ በተመለከተው የውርስ ማጣራት ሂደት ውስጥ ማለፍ ሳያስፈልጋቸው ወራሽነታቸውን አረጋግጠው እና የውርስ ሀብቱንም በይዞታቸው ስር አድርገው እና ወደ ራሳቸው ንብረት ቀላቅለው የጋራ ባለሀብትነት መብት በማቋቋም እየተገለገሉበት በመሆኑ አከራካሪው ቤት በቁጥር 1060 ድንጋጌ አነጋገር መሰረት የጋራ ወራሾች ያልተከፋፈለ የጋራ ንብረት እንጂ በቁጥር 942 እና 943 ድንጋጌዎች አነጋገር መሰረት የውርስ ሀብት የሚባል ባለመሆኑ ቁጥር 943 (3) ድንጋጌ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይችልም።ቤቱ የወራሾቹ የጋራ ሀብት መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ በቁጥር 1260 (2) ድንጋጌ መሰረት ከጋራ ባለሀብቶቹ መካከል ከአንደኛው ገንዘብ ጠያቂ የሆነ ሰው የዚህኑ የጋራ ባለሀብት ድርሻ የመያዝ መብት ይኖረዋል።

ሲጠቃለል አከራካሪው ቤት የውርስ ሀብት በመሆኑ የውርስ ማጣራት ሂደት ተጠናቆ ውጤቱ ከመታወቁ በፊት ከወራሾቹ ላይ ገንዘብ ጠያቂ ለሆኑ ሰዎች የፍርድ ማስፈጸሚያ ሊውል አይችልም በማለት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በክርክሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች እና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በሌላ በኩል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአከራካሪው ቤት ውስጥ የ5ኛ ተጠሪ ድርሻ ለአፈጻጸሙ ሊውል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ቢሆንም 4ኛ ተጠሪ በዚህ ቤት ላይ የውርስ ድርሻ ያላቸው መሆን አለመሆኑ በክርክር ላይ እንደሚገኝ የታወቀ ሆኖ እያለ የክርክሩ ውጤት ባልታወቀበት ሁኔታ ከቤቱ የሽያጭ ገንዘብ ውስጥ ለአፈጻጸሙ ሊውል የሚገባው አንድ አራተኛው ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል መታረም ያለበት እና ለአፈጻጸሙ ሊውል የሚገባው ከተጠሪዎቹ ቁጥር አንጻር ከቤቱ የሽያጭ ገንዘብ ውስጥ አንድ አምስተኛ ሆኖ የ4ኛው ተጠሪ አንድ አምስተኛ ድርሻ ለጊዜው በሞዴል 85 ተይዞ እንዲቆይ ከተደረገ በኃላ የወራሽነት ክርክሩ የመጨረሻ ውጤት ከታወቀ በኃላ በዚህ በተቀማጩ ገንዘብ ላይ በአፈጻጸም ችሎቱ እንደአግባብነቱ ተገቢው ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ሊደረግ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ከወላጆቻቸው በጋራ በውርስ ያገኙት በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 5 የሚገኘው ቁጥሩ 327 በሆነው ቤት የውርስ ሀብት በመሆኑ ውርሱ ተጣርቶ ውጤቱ እስካልታወቀ ድረስ ከወራሾቹ መካከል አንዱ ከሆኑት 5ኛ ተጠሪ ላይ ገንዘብ ጠያቂ በሆኑት አመልካች በአፈጻጸም ሊያዝ አይገባም በማለት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 111970 በ15/10/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አከራካሪው ቤት የወራሾች የጋራ ሀብት እንጂ የውርስ ሀብት ባለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1060 (1) እና (2) እንዲሁም በዚሁ ሕግ በቁጥር 1260 (2) ድንጋጌ መሰረት ከወራሾቹ መካከል የአንደኛው ድርሻ ከዚሁ ወራሽ ላይ ገንዘብ ጠያቂ በሆኑ ሰዎች ሊያዝ ይችላል በማለት ወስነናል፡፡
3. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 157255 በ17/07/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
4. በተራ ቁጥር 3 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ አከራካሪ ቤት በሐራጅ ተሸጦ የ5ኛ ተጠሪ ድርሻ ለአፈጻጸሙ ሊውል ይገባል በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
5. በተራ ቁጥር 3 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ የ4ኛ ተጠሪን ክርክር በገዘምታ በማለፍ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
6. 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ከወላጆቻቸው በጋራ በውርስ ያገኙት በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 5 የሚገኘው ቁጥሩ 327 የሆነው ቤት በሐራጅ ከተሸጠ በኃላ ከሽያጩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚገኘው ገንዘብ ውስጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 213611 በ29/11/2006 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ በገለጸው የአፈጻጸም ስርዓት መሰረት የፍርድ ባለዕዳው የ5ኛ ተጠሪ ድርሻ የሆነው አንድ አምስተኛው ለአፈጻጸሙ እንዲውል፣ሶስት አምስተኛው ለ1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው አንድ አምስተኛ ወጪ ተደርጎ እንዲከፈል፣ቀሪው አንድ አምስተኛ በሞዴል 85 ተይዞ እንዲቆይ ከተደረገ በኃላ የ4ኛ ተጠሪ የአቶ ብሩክ ግርማ የወራሽነት ክርክር የመጨረሻ ውጤት ከታወቀ በኃላ እንደአግባብነቱ ተገቢው ትዕዛዝ እንዲሰጥበት በማለት ወስነናል፡፡

7. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቁት ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይላክ፡፡
8. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
9. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 104943

መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ይልማ ፈለቀ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጥበቡ ፈለቀ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው ግራ ቀኙን ያከራከረው የአፈፃፀም ጉዳይ ይፈፀም ከተባለው ፍርድ ይዘት ውጭ እንዲፈፀም የሚገልፅ ዳኝነት ተሰጥቷል ወይስ አልተሰጠም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በክርክር ሂደት ከተረጋገጠው የፍሬ ነገሮች ጉዳዮች እና አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦና ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

በዚህም መሰረት በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙ ከአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባለው ደረጃ በተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ አሁን ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ ሆኖ የተያዘውን እና ለአፈፃፀሙ ክስ ምክንያት የሆነውን ጥቅምት 08 ቀን 2005 ዓ.ም በሽማግሌ ዳኞች አማካኝነት ጉዳዩ በእርቅ እንዲያልቅ ከማድረጋቸው በፊት እርቅ ባደረጉበት ምክንያት ግራ ቀኙ ከነበራቸው የንግድ ሽርክና ውል የመነጨ የሀብት ድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ምክንያት ጉዳያቸው በፍ/ቤት ቀርቦ በመ/ቁ 10208 በሆነው መዝገብ የአሁን ተጠሪ በስሙ ተመዝግበው የሚገኙትን ንብረቶች ለአሁን አመልካች እንዲያካፍል ፍርድ መስጠቱንና በዚህ ፍርድ መሰረት ለማስፈፀም የአፈፃፀም ክስ ቀርቦ በክርክር ላይ እያሉ በአፈፃፀም ደረጃ የደረሰውን ጉዳይ አስመልክቶ ግራ ቀኙ በሽማግሌዎች አማካኝነት በእርቅ እንዲያልቅ ተስማምተው፤ በሽማግሌዎችም ታይቶ አሁን ለዚህ ሰበር ጉዳይ ምክንያት በሆነው ጥቅምት 08 ቀን 2005 ዓ.ም በተደረገው የእርቅ ስምምነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት የአፈፃፀሙ ክስ እንዲዘጋ መደረጉን ገልፆ ለክርክር የአሁን ተጠሪ ይህ በአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10208 በሆነው መዝገብ ላይ አስቀድሞ ፍርድ ያገኘ ጉዳይ ነው በሚል የቀረበው ክስርዓት ውጭ የቀረበ ነው፤ ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለው ጥቅምት 8 ቀን 2005 ዓ.ም የተደረገው የእርቅ ስምምነት ብቻ ነው የሚል ክርክር ከማቅረባቸው በቀር በግልፅ የካዱት ጉዳይ አይደለም፡፡

ከስርዓት ውጭ የቀረበ ክርክር በመሆኑ ምክንያት አንድ ክርክር ውድቅ ሊደረግ የሚችለው ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መነሻና ዋነኛ ዓላማ የሆነውን የተከራካሪ ወገን የመደመጥ መብት ለማስከበር ሲባል ክርክርና ማስረጃ ስርዓቱን ጠብቆ በሚደረግበት ፍ/ቤት እና የክርክር ደረጃ እንዲቀርብ ለማድረግ ነው፡፡ ይህ አሁን በአሁን አመልካች በኩል የጉዳዩን አመጣጥና መነሻ ለማስረዳት ሲባል የቀረበው ክርክር ጉዳይ በፍ/ቤት ቀርቦና ታይቶ በመዝገብ ፍርድ የተቋጨበት ነው የሚል እስከሆነና ይህም አሁን ክርክር ከተነሳበት ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው እስከሆነ ድረስ ፍሬ ነገሩ እንደተባለው አይደለም፤ ሐሰት ነው የሚባል ከሆነ ይህንኑ በቀላል ለመግለፅ እና ለማስረዳት የሚቻል እንጅ ከሕግ ሐሳብ ውጭ በመራቅ የተሟላ የክርክር ሂደትን ጠብቆ በሙግት ደረጃ ነጥሮ እንደማይወጣ ጉዳይ ተቆጥሮ በደፈናው በስርዓት ውጭ ያቀረበ ነው ለማለት የሚያበቃ አይደለም፡፡ በዚህም የተነሳ እና ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለው ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውና በሽማግሌዎች ፊት ጥቅምት 02 ቀን 2005 ዓ.ም ባደረጉት የእርቅ ስምምነት ላይ የካርታ ቁጥር 0442/2001 በሚል የተገለፀው የንግድ ቤት ለግራ ቀኙ የሽርክና ስራ ውል በመነጨ የአሁን ተጠሪ ግማሽ ድርሻ ለአሁን አመልካች ሊያካፍል ይገባል ተብሎ ፍርድ ያረፈበት ይህንኑም ፍርድ በማስፈፀም የአፈፃፀም ክስ ከቀረበ በኋላ አፈፃፀም ደረጃ የቀረበውን ክርክር በዚሁ የእርቅ ስምምነት አቋርጠው የእርቅ ስምምነት እንደተካው ተደርጎ በእርቅ ስምምነት መሰረት እንዲፈፀም የተደረገ ስለመሆኑ እስካልተካደ ድረስ የካርታ ቁጥር 0442/2001 በሚል የተጠቀሰው ስህተት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 2008 እንደተመለከተው በእርቁ አፃፃፍ ጊዜ የተፈፀመ የአፃፃፍ ስህተት ነው ከሚባል የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው አይደለም፡፡ የአሁን ተጠሪም ይኸው ንብረት ክፍፍል የሚደረግበት ከዚህ በፊት ፍርድ ያረፈበት በኋላም በሽምግልና የእርቁ ሰነዱ ላይ የተጠቀሰውና ክፍፍል የሚደረግበት ንብረት መሆኑን ተቀብሎ የንብረቱ ግምት በሽማግሌዎች የእርቅ ሰነድ ከተመለከተው ሊያንስ አይገባም፤ በተከታዩም ቀጠሮ ይህ ክፍፍል የተደረገበት ንብረት በባዶ መሬትነት የሚታወቅ እንጅ ቤት የሌለው መሆኑን የከተማው አስተዳደር አስቀድሞ የሰጠውን ማረጋገጫ ቀይሮ ማስረጃ ሰጥቶኛል ስለዚህ ባዶ መሬት የህዝብና የመንግስት ስለሆነ ላካፍል አይገባም በሚል መከራከራቸውን ከመረጋገጡ በቀር በካርታ ቁጥር 0442/2001 በሚል የተሰየመው ንብረት አከራካሪ ሆኖ ከተገኘው ንብረት የተለየ ነው በሚል ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባለው የክርክር ደረጃ ያቀረበው የማስተባበያ ክርክና ማስረጃ የለም፡፡ አልተገኘም

ስለሆነም ከዚህ በፊት አስቀድሞ በፍርድ ተቋጭቶ ያደረው የግራ ቀኙ ጉዳይ በአፈፃፀም የክስ ደረጃ ደርሶ እያለ በግራ ቀኙ ስምምነት የአፈፃፀሙ ጉዳይ ጥቅምት 08/2005 ዓ.ም በሽማግሌዎች አማካኝነት በተደረገው የእርቅ ስምምነት መሰረት እንዲፈፀም አድርገው መሰማማታቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ለመሆኑና በዚህም የእርቅ ስምምነት መሰረት በእርቅ ሰነዱ ላይ የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች በድርሻነት ሊያካፍል ይገባል በማለት የተገለፀውን ገንዘብ ከእነ መጠኑ የአሁኑ ተጠሪ ስለመክፈሉ ተረጋግጦ ቀሪውን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ ቤት በሽምግልና ዳኞች የእርቅ ስምምነት መሰረት ሽማግሌዎች አሽጠው ድርሻ ድርሻቸውን ለማከፋፈል ባደረጉት ጥረት ያጋጠመውን መጓተት በማሳየት ቀሪው ተግባር በፍርድ ቤት እገዛ እልባት እንዲያገኝ የተደረገበት አስቀድሞ በፍርድ የተቋጨው እና በአፈፃፀም ደረጃ ደርሶ የአፈፃፀሙ ጉዳይ በእርቅ ሰነዱ መሰረት እንዲመራ የተደረገበት የዚያው ተከታይ እና ቅጥያ ነው ከሚባል በቀር እራሱን እንደቻለ ፍርድም ሊቆጠር የሚችል አይደለም፡፡

በመሆኑም የካርታ ቁጥር 0442/2001 በሚል ጥቅምት 08 ቀን 2005 ዓ.ም ለተደረገው የእርቅ ሰነድ ላይ የተደረገው የካርታ ቁጥር አጠቃቀስ በአፃፃፍ ስራ ምክንያት የተከሰተ ግድፈት መሆኑን የስር የአዳማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተገንዝቦ ያው በፊትም ሆነ በኋላ ስለእርቁ ጉዳይ በተደረሰው ስምምነት ላይ የተጠቀሰው ንብረት እንጂ ሌላ የተለየ ንብረት አለመሆኑን በማረጋገጥ የአፃፃፍ ስህተቱ እንዲረታም አድርጓል ከሚባል በቀር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ እንዳሰፈረው ትችት ለአፈፃፀም መነሻ የሆነው የፍርድ ይዘት በአፈፃፀም የክርክር ጉዳይ ላይ እንዲለወጥ ተደርጓል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

የአሁን ተጠሪ በበኩሉ አፈፃፀሙን ከዳር ለማድረስ ሲል ፍ/ቤቱ ባከናወነው የባለሙያ ግምት ስራ ውጤት አስቀድመን በስምምነታቸው ለተገለፀው የንብረቱ ግምት መጠን በታች ሊሆን አይገባም በሚል ያቀረቡትን የመከራከሪያ ነጥብ እንደተመለከትነው በእርግጥም በእርቅ ሰነዱ ላይ የተመለከተው የንብረቱ ግምት ብር 1,000,000.00 /አንድ ሚሊዮን ብር/ ግምት ሽማግሌዎች ሸጠው በሚል ተጠቅሶ እያለ ፍ/ቤቱ ይህንኑ በሽማግሌዎች አማካኝነት የተደረሰውን የንብረት ክፍፍል ስራ ከዳር ለማድረስ ሲል የመሸጫ ዋጋውን እንደገና ሲያስገምት ከዚሁ በሰነዱ ከተገለፀው በታች ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

ይሁን እንጅ የዚህ አነስተኛ ሆኖ የተያዘው የንብረት ግምት ለሐራጅ ሽያጭ ሥራ ሲባል የተያዘ የመሸጫ መነሻ ዋጋ ነው የሚባል እንጂ ንብረቱ በዚሁ በባለሙያ ግምት መሰረት እንዲሸጥ የተደረገ መሆኑን አያመለክትም በዚሁ ግምት መሰረት ሊሸጥ የሚችል ነው የሐራጅ ውጤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመታወቁ በፊት ለመደምደም የሚቻል አይደለም፡፡ ስለሆነም ውጤቱ እንደስጋታቸው ሆኖ ከተገኘ ከውጤቱ በኋላ ስርዓቱን ጠብቀው እንዲታረም ከማድረግ በቀር የተጀመረውን የአፈፃፀም ጉዳይ ግን ቀሪ ለማድረግ የሚያበቃ የክርክር ይዘት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት የፍርድ ሀተታዎች አንፃር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፋ/ቁ 175732 በቀን 19/12/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በፍይል ቁጥር 16457 በቀን 26/02/2006 እና በፋይል ቁጥር 172185 በቀን 11/03/2006 ዓ.ም የሰጡት ዳኝነቶች ፀንተዋል፡፡
2. በስር የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጀመረው የአፈፃፀም ክርክር ጉዳይ ሊቀጥል ይገባል መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለየራሳቸው ይቻሉ
4. የዚህ የክርክር ውጤት እስከሚታወቅ ድረስ በሚል በዚህ የሰበር መዝገብ ላይ ጥቅምት 05 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117907

ግንቦት 22 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ
መስጠፋ አህመድ
ተፈሪ ገብሩ
ሸምሱ ሲርጋጋ
አብርሃ መሰለ

አመልካቾች - 1ኛ- ወ/ሮ ዘውዴ ፍቅሬ -
2ኛ- አቶ ኃ/ሚካኤል ተስፋየ 1ኛ } አመልካች በራሳቸው እና ስለ 2ኛ አመልካች ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ አበራ ጌታነህ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በአማራ ክልል ደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት ሶስት የተለያዩ ጉዳዮችን በመያዝ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ለመከራከር የጥብቅና አገልግሎት ውል አድርገን ተገቢውን አገልግሎት የሰጠሁ ሲሆን በውሉ መሰረት ሊከፍሉኝ የሚገባውን አበል ያልከፈሉኝ በመሆኑ ብር 39,850.00 (ሰላሳ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ) ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስ በጥብቅና ውሉ መሰረት ተገቢውን አገልግሎት አልሰጠም፤ በክርክሩም ያስገኘልን ጥቅም የለም በመሆኑም የጠበቃ አበል ልንከፍል አይገባም፤ በአንዳሩ አገልግሎት ሳይሰጥ በመጀመሪያ ደረጃ ከፍያ የወሰደውን ብር 5,650.00 (አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ) እንዲመልስ እንዲወሰን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ በውሉ መሰረት አገልግሎት ሰጥቻለሁ ይበል እንጂ የቀረቡት ማስረጃዎች በተደረገው የጥብቅና ውል መሰረት እስከመጨረሻው አገልግሎት መስጠቱን የሚያስረዱ ባለመሆኑ የዳኝነት ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ተከሳሾች የቅድሚያ ክፍያ ይመለስልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄም ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ጉዳዩ በይግባኝ በየደረጃው እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ደርሶ የሰበር ችሎቱ በመጨረሻ ባሳለፈው ውሳኔ ተጠሪ ውል በተደረገባቸው በሶስቱም መዛግብቶች እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቅሬታ አቅርቦ የሰበር አቤቱታው አያስቀርብም ተብሎ የተዘጋ ስለመሆኑ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፃፈው ደብዳቤ መረዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይቻላል በማለት ተጠሪ ለሰጠው የጥብቅና አገልግሎት በቁርጥ ብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ) አመልካቾች እንዲከፍሉት ወስኗል፡፡የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካቾች ነሀሴ 27/2007 ዓ.ም ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈለው የተወሰነበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙም የስር ሙግታቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የክልሉ ሰበር ችሎት የጥብቅና አገልግሎት እንዲከፈል ባሳለፈው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ቢኖር በጭብጥነት ይዘን መርምረናል፡፡ በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል የጥብቅና አገልግሎት ውል ስለመደረጉና ስምምነቱም ተጠሪ ባለው የጥብቅና ሙያ ጉዳዩን እስከ መጨረሻ ድረስ ሊከራከርላቸውና በአንዣሩ ለአገልግሎቱ የተጠቀሰውን ዋጋ ሊከፍሉ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካቾች የተሟላ አገልግሎት ባልተሰጠበት ብር 20,000.00 እንዲከፈል የክልሉ ሰበር ችሎት መወሰኑ የህግ ስህተት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በሙያው ደንብና ልማድ መሰረት ህግንና ማስረጃን ተንተርሶ እስከመጨረሻ ጉዳዩን በመከታተል በአፈፃፀም እንዲያገኙ ያደረግሁ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት ማግኘት ከሚገባኝ ባነሰ ርትዕን መሰረት በማድረግ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም ተብሎ ውሳኔው እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ይዘዋቸው በነበሩ ሶስት የአመልካቾች ጉዳዮች እስከ ፌዴራሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበው የነበረ ስለመሆኑና ለሰበር አያስቀርብም በሚል የመ/ቁ 85890፤85891 እና 84464 የተዘጉ ስለመሆኑ ከፍርድ ቤቱ የተፃፈው ደብዳቤ ተጠቅሶ ከተሰጠው ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በገቡት ውል መሰረት እስከ መጨረሻ ድረስ ጉዳዩን ከተከታተሉ እና ከሙያቸው አንፃር እውቀትና ክህሎታቸውን ተጠቅመው አገልግሎት ከሰጡ የተፈለገው ውጤት ባለመምጣቱ ብቻ የተሟላ አገልግሎት አልሰጡም ሊሰኝ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ምንም አይነት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር የውልም ሆነ የህግ መሰረት ስለሌለው የምንቀበለው አይሆንም፡፡ የነገሩ አጠቃላይ ሁኔታ ታይቶ ተጠሪ ለሰጠው የጥብቅና አገልግሎት በቁርጥ ብር 20,000.00 ይከፈል ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሚባል ህግ ስህተት ባለመኖሩም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 45107 ሰኔ 9 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 114888

ህዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ አትሁነኝ አልማው ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ አባይነህ ከበደ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ በክልሉ የተሰጠ የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰረዝ የተሰጠን የዲሲፕሊን ውሳኔ ህጋዊነት የሚመለከት ነው፡፡ የድስፒሊን ክሱ የቀረበው አቶ ጓዙሁን አዘዘው የተባለ የድስፒሊን አቤቱታ አቅራቢ ነው፡፡ አቤቱታ አቅርበው በባህር ዳር ዙርያ ወረዳ ይነሳ 3ቱ ቀበሌ በሚች አቶ ወንደ ተገኘ የገጠር መሬት ይዞታ ምክንያት ከአቶ በሪሁን ወንደ ጋር እየተከራከሩኩ እገኛለሁ፡፡ አቶ በሪሁን ወንደ የባህር ዳር ዙርያ ወረዳ የይነሳ 3ቱ ቀበሌም ሆነ በኢትዮጲያ ውስጥ ኗሪ አይደለም፡፡ አቶ በሪሁን ወንደ ላለፉት ሰላሳ አንድ አመታት በእስራኤል አገር የሚኖር ሰው ነው፡፡ ሆኖም የዲስፒሊን ተከሳሹ ከቀበሌው ስራ አስኪያጅ ጋር በመመሳጠር በአገር ውስጥ ከሌለ ሰው በይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ በማስመሰል የሀሰት መታወቂያ በማውጣት ከጠበቆች ስነ ምግባር ውጭ ተገቢነት የሌለው ስራ በመምራትና ማስረጃ በማቅረብ ፍትህ የሚያጓድል ስራ እያሰራ ስለሆነ ፍትህ ቢሮ ክትትል አድርጎ የእርምት እርምጃ እንዲወስድበት በማለት በጽሁፍ አቤቱታ አቅርቧል፡፡
2. አመልካች የአቶ በሪሁን ወንደ ጠበቃ ሆነው በተለያዩ ፍ/ቤቶች የተለያየ ክርክር እያቀረበ መሆኑን ገልፆ፣ የጥብቅና አገልግሎት በደንበኛዋ እየሰጠሁ ያለሁት በክልሉ ፍትህ ቢሮ የሰነዶችና ጠበቆች ማረጋገጫና ምዝገባዎች የስራ ሂደት ተገኝተው ደንበኛዬ ታህሳስ 22 ቀን 2005 ዓ/ም በህጋዊ መንገድ በሰጡኝ የውክልና ሰነድ መሰረት ነው፡፡ ለአቶ በሪሁን ወንደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀበሌ መታወቂያ አላወጣሁም የውክልና ሰነድም በህገ ወጥ መንገድ አላወጣሁም፡፡ ደንበኛዬ በእስራኤል አገር የሚኖር ቢሆንም ትውልዳቸው ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የይነሳ 3ቱ ቀበሌ ነው፡፡ ለዲስፒሊን ምክንያት የሆነው ጉዳይ በወረዳ ፍርድ ቤትና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እየታየ ይገኛል፡፡ ፍትህ ቢሮ ህጋዊነቱን አረጋግጦ በሰጠኝ የውክልና ማስረጃ ምክንያት ልከስስ አይገባኝም በማለት መልስ የሰጠ መሆኑን ተረድተናል፡፡

3. የክልሉ ፍትህ ቢሮ የጠበቆች ዲስፒሊን ጉባኤ በአመልካች ላይ የቀረበው የዲስፒሊን አቤቱታ እውነትነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚመለከታቸውን የባህር ዳር ወረዳ አስተዳደር አካላትና የይነሳ 3ቱ ቀበሌ አስተዳደር እንደዚሁም የኢሜግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ አግባብነት ያለው ማስረጃ እንዲሰጡት ጠይቋል፡፡ ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን ማጣሪያ ያደረገ መሆኑንና በማጣራቱ ሂደት በ2005 ዓ/ም አቶ በሪሁን ወንዴ ወደ አገር ውስጥ ስለመግባቱም ሆነ ከአገር ስለመውጣቱ መረጃ ያላገኘ መሆኑን የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ በጽሁፉ የገለጹለት መሆኑን አቶ በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የይነሳ 3ቱ ቀበሌ ነዋሪ አለመሆኑን የቀበሌው አስተዳደር በዕሁፍ የገለጽ መሆኑን፣ አቶ በሪሁን ወንዴ በአንድ ወቅት ከእስራኤል አገር በመጣበት ጊዜ የይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የቀበሌ መታወቂያ እንዲሰጠው ጠይቆ የነበረ መሆኑና የቀበሌው ነዋሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ማይሰጠው መሆኑን የባይነሳ ሶስቱ ቀበሌ አስተዳደር ተነገረው መሆኑ፣አቶ በሪሁን ወንዴ የባይነሳ ሶስቱ ቀበሌ ነዋሪ መሆኑን ሚያረጋግጥ መታወቂያ ያለው መሆኑን በመግለፅ ለባህርዳር ዙሪያ ወረዳ የመሬት አስተዳደርና የአካባቢው ጽ/ቤት መታወቂያ ይዞ የአቀረበው አመልካች መሆኑን እንዳረጋገጠ በመግለጽና አመልካች ከዚህ በፊት የጥብቅና ፈቃድ ለማውጣት የሀሰት ማስረጃ /የስራ ልምድ ተጠቅሟል የሚል ክስ ቀርቦበትና ይህም ተረጋግጦ በቢሮ ኃላፊ ውሳኔ ሳይቀጣ የታለፈ መሆኑን ገልፆ የአመልካች የሀሰት መታወቂያ በመጠቀም የተሟጋችነት ውክልና ማስረጃ የወሰደና አርሶ አደሮችን በመከላከል በከፍተኛ እንግልት በመዳረግ ክባድ የድስፒሊን ጥፋት ፈጽሟል በማለት የአመልካች የጥብቅና ፍቃድ እንዲሰረዙና ስሙ ከጠበቆች መዝገብ እንዲሰረዝ የሚል የውሳኔ ሀሳብ አቅርቦ የድስፒሊን ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ የቢሮ ኃላፊ ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡ ውሳኔ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይገባኝ ሰሚ ችሎት ሰበር ችሎት ጸንቷል፡፡

4. አመልካች ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በ2005 ዓ/ም አቶ በሪሁን ወንዴ ወደ አገር ውስጥ መጥቶ የነበረ መሆኑን አቤቱታ አቅርበው ክዶ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ የኢምግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ አመልካች አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 አ/ም ወደ አገር ውስጥ የገባም ሆነ የወጣ ስለመሆኑ መረጃ አላገኘንም ከማለት ውጭ ወደ አገር ውስጥ ያልገባ ስለመሆኑ የሰጠው ማስረጃ የለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በዲስፒሊን የተከሰሱበትን ጥፋት ስለመፈጸሜ በበቂ ሁኔታ ሳይረጋገጥብኝ በክባድ የድስፒሊን ጥፋት ጥፋተኛ መባሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የዲስፒሊን ጉባኤው አመልካች በድስፒሊን ባልተከሰሰኩበትና ያልተከራከርኩበትን ጉዳይ ማለትም ከዚህ በፊት ከጥብቅና ፈቃድ አወጣጥ ላይ የሀሰት ማስረጃ ተጠቅሟል ተብዬ የተከሰሰኩበትንና በቢሮ ኃላፊው ውሳኔ ያለምንም ቅጣት በነፃ የተሰናበትኩበትን ጉዳይ በመጥቀስ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የሰጠብኝ በመሆኑ ውሳኔው የመከራከር መብቴን ያጣበበና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የጥብቅና ፈቃዴን እንዲሰርዝ የተሰጠው ውሳኔ ከህግ አግባብ ውጭ የተሰጠና የድስፒሊን ጥፋት ስለመፈጸሜ በበቂ ሁኔታ ሳይረጋገጥብኝ የተሰጠ ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

5. የክልል ፍትህ ቢሮ በሀምሌ 15 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚልበትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ ቢሮው በአማራጭ ባቀረበው ክርክር አመልካች የውጭ አገር ኗሪ ለሆነ ሰው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅና አዋጅን ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ከሚደነገገው የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በማሰራት በውጭ አገር ኗሪ የሆነ ሰው የባህር ዳር ዙሪያ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ የኗሪነት መታወቂያ በማውጣትና በ2005 ዓ/ም ደንበኛው አቶ በሪሁን ወንዴ ወደ ሀገር ውስጥ ሳይገባ የሀሰት የተሟጋችነት የውክልና ሰነድ በመውሰድ እየተከራከረ በአርሶ አደሮች ላይ ከፍተኛ እንግልት ያደረሰ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ደንበኛውን በ2005 ዓ/ም ወደ አገር ውስጥ የገባ መሆኑን የማያስረዳ ማስረጃ እንዲያቀርብ በጉባኤው ብቻ ሳይሆን በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እድል ተሰጥቶት አላቀረበም፡፡ አመልካች የጥብቅና ፈቃድ ሲያወጣ ፈጽሟል ተብሎ ተከሶበት የነበረው የድስፒሊን ጥፋትና ጉባኤው አጣርቶ የደረሰበት እውነት በጉባኤው ውሳኔ ከመገለጹ ውጭ ውሳኔው የጥፋተኝነትንም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ለመወሰን ጥቅም ላይ አልዋለም ስለሆነም አመልካች ከባድ የድስፒሊን ጥፋት መፈጸሙ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

6. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸውን እኛም የክልሉ ፍትህ ቢሮ አመልካች የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰረዝ በማለት የሰጠው ውሳኔ በህግ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

7. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የተሟጋችነት ውክልና ወስዶ የእርሻ መሬት ይዞታን በተመለከተ የተለያየ ክርክር የሚከራከርለትና አመልካች የጥብቅና አገልግሎት የሚሰጠው አቶ በሪሁን ወንዴ በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ እንዳልሆነ አቶ በሪሁን ወንዴ ከሰላሳ አንድ ዓመት በላይ በቋሚነት የሚኖረው በእስራኤል አገር እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ በእስራኤል አገር የሚኖረው አቶ በሪሁን ወንዴ መተዳደሪያው የእርሻ ስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይሆንና የቀበሌው ኗሪ ባልሆነበት ሁኔታ አቤቱታ አቅራቢው ከሰላሳ አመት በላይ በይዞታው አድርጎ ሲጠቀምበት በኖረው የእርሻ መሬት ባለይዞታ የመሆኑን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አቤቱታ አቅርባው ሳያውቅ ያወጣ መሆኑን ገልጾ በሀሰት ለአቶ በሪሁን ወንደ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲሰረዝለት አቤቱታ አቅርበው ለባህር ዳር ዙሪያ የመሬት አስተዳደርና አካባቢ ጽ/ቤት ማመልከቱንና አቶ በሪሁን ወንደ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የባይነሳ ሶስቱ ቀበሌ ኗሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ የቀበሌ መታወቂያ እንዲያቀርብ ሲጠይቅ አመልካች አቶ በሪሁን ወንደ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ መሆኑን የሚያሳይ መታወቂያ ለወረዳው መሬት አስተዳደርና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ይዞ በመቅረብ የሰጠ መሆኑ የወረዳው የመሬት አስተዳደርና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በሰጠው ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የድስፒሊን ጉባኤው ከሰጠው ውሳኔ ተረድተናል፡፡

8. ከላይ በዝርዝር የተገለጸው ፍሬ ጉዳይ አመልካች ደንበኛው አቶ በሪሁን ወንደ በእስራኤል አገር የሚኖርና የባህር ዳር ዙሪያ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ እንዳልሆነ እያወቀ አቶ በሪሁን ወንደ የባህር ዳር ዙሪያ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ እንደሆነ የሚገልጸውን ሀሰተኛ መታወቂያ ስለ እርሻ መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ለሚሰጠውና ውሳኔ ለሚሰጠው ክፍል ወስደው ያስረከቡ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አቤቱታ አቅርበው አመልካች ከቀበሌው ስራ አስኪያጅ ጋር በመመሳጠር ሀሰተኛ መታወቂያ በበሪሁን ወንደ ስም በማውጣት ሀሰተኛ ማስረጃ በመጠቀም ከጠበቆች ስነ ምግባር ውጭ እየተከራከረው መሆኑን ገልፆ እውነታው እንዲጣራለት ስለጠየቀ ጉባኤው አመልካች ታህሳስ 22 ቀን 2005 ዓ/ም ከአቶ በሪሁን ወንደ ተሰጥቶኛል የሚለው የተሟጋችነት የውክልና ሰነድ ትክክለኛነት የማጣራት ስራ የስራ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በተደረገው የማጣራት ስራ በ2005 ዓ/ም አቶ በሪሁን ወንደ አመልካች ወደ አገር ውስጥ የገባም ሆነ የወጣ ስለመሆኑ መረጃ ያልተገኘ መሆኑ የኢምግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ በጽሁፍ አረጋግጧል፡፡ አመልካች ይህ ማስረጃ ደንበኛው አቶ በሪሁን ወንደ በ2005 ዓ/ም ወደ አገር ውስጥ ያልገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ አይደለም በማለት የሚከራከር መሆኑን አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ካቀረበው የሰበር ክርክርና የሰበር ማጣሪያ ችሎት ከያዘው ጭብጥ ተረድተናል፡፡

9. የአመልካች ደንበኛ አቶ በሪሁን ወንደ ቋሚ የመኖሪያ ቦታው እስራኤል አገር መሆኑን አመልካች ክዶ ያልተከራከረ ከመሆኑም በላይ አቶ በሪሁን ወንደ እስራኤል አገር ኗሪ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የዲስፒሊን አቤቱታ አቅርበው አቶ በሪሁ ወንደ በ2005 ዓ/ም ወደ አገር ቤት የመጣ መሆኑን ክዶ አልተከራከረም የሚል መከራከሪያ ከማቅረቡ ውጭ ደንበኛው በ2005 ዓ/ም ወደ አገር ውስጥ የገባ ወይም ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ለጉባኤውና ለይ/ባይ ሰሚ ችሎት ያላቀረበ መሆኑን የክልሉ ፍትህ ቢሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሳኔ በማገናዘብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተረድተናል፡፡ በመሰረቱ አመልካች የዲስፒሊን አቤቱታ አቅራቢው አቶ ጓድይሁን አዘዘው የአመልካች ደንበኛ በ2005 ዓ/ም ወደ አገር ቤት የመጣ መሆኑን ባቀረበው አቤቱታ ላይ እንዳልካደ በመግለጽ ያቀረበው ክርክር አቤቱታ አቅርበው የካቲት 3 ቀን 2006 ዓ/ም ጽፎ ያቀረበውን ፍሬ ጉዳይና የገለጸውን እምነት የሚሳይ ክርክር ሆኖ አላገኘነውም፡፡

10. የዲስፒሊን አቤቱታ አቅራቢው አቶ በሪሁን ወንደ ወደ አገር ቤት የመጣ ስለመሆኑ በአቤቱታው አልገለጸም፡፡ አቤቱታ አቅራቢው አቶ በሪሁን ወንደ በእስራኤል አገር እንደሚኖርና አንድ ወቅት ወደ አገር ቤት መጥቶ እንደነበር ወደ አገር ቤት በመጣበትም ጊዜ ከህግ ውጭ እሱ በማያውቀው ሁኔታ ከሰላሳ አምስት ዓመት በላይ በእጅ አድርጎ የሚጠቀምበትን የእርሻ መሬት የአቶ በሪሁን ወንደ መሆኑን የማያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያስመጣበት መሆኑን የይዞታ ደብተሩ እንዲሰረዝለት ለሚመለከተው አካል ሲያመለክት አመልካች በእስራኤል አገር የሚኖረው በሪሁን ወንደ የባህር ዳር ዙሪያ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ መሆኑን የሚገለጽ ሀሰተኛ መታወቂያ በማስወጣትና ሀሰተኛ ማስረጃ በመጠቀም እየተከራከረው በመሆኑን በዲስፒሊን ጉዳይ እንዲታይ የሚገልጽ ነው፡፡ አቶ በሪሁን ወንደ አመልካች ሀሰተኛ መታወቂያና ሀሰተኛ የተሟጋችነት ውክልና አምጥቷል ከተባለበት ጊዜ በፊት በአንድ ወቅት ወደ አገር ቤት መጥቶ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ነዋሪ መሆኑን የሚያሳይ መታወቂያ እንዲሰጠው የቀበሌውን አስተዳዳሪ ጠይቆ የነበረ መሆኑንና የቀበሌው አስተዳደርም መታወቂያው አይሰጥህም የሚል ምላሽ እንደሰጠው የዲስፒሊን ጉባኤው ከቀበሌው አስተዳደር ጋር ባደረገው ማጣራት እንዳረጋገጠ በውሣኔው በግልፅ አስፍሯል፡፡ አቤቱታ አቅራቢው አቶ በሪሁን ወንደ በአንድ ወቅት ወደ አገር ቤት መጥቶ የነበረ መሆኑን ባቀረበው አቤቱታ መግለፁ አቶ በሪሁን ወንደ በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ቤት የመጣ መሆኑን በአቤቱታው ያመነና የገለፀ መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አቤቱታ አቅራቢው አቶ በሪሁን ወንደ ለዲስፒሊን ክስ መነሻ የሆኑት ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ወደ አገር ቤት መጥቶ የነበረ መሆኑ በአቤቱታው ላይ የገለፀው ፍሬ ጉዳይ ዕውነትነት ያለው መሆኑን በቀበሌው አስተዳደርም የተረጋገጠ መሆኑ ሲታይ አቤቱታ አቅራቢው በአቤቱታው ላይ ትክክለኛውን ፍሬ ጉዳይ ያሰፈረ መሆኑን ከሚያረጋግጥ ውጭ አቶ በሪሁን ወንደ በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ቤት የመጣ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ መከራከሪያና ሰነድ አይደለም፡፡

11. የዲስፒሊን አቤቱታ አቅራቢው የዲስፒሊን ክስ ዋና ይዘት አመልካች በባህር ዳር ዙሪያ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ነዋሪ ላልሆነው አቶ በሪሁን ወንደ የቀበሌው ነዋሪ መሆኑን የሚያረግጥ መታወቂያ በማውጣት ሀሰተኛ የውክልና ሰነድ በመጠቀም እየተሟገተኝ ነው የሚል ነው፡፡ አመልካች ከአቶ በሪሁን ወንደ የተሟጋችነት የውክልና ሥልጣን ተሰጥቶኛል የሚለው ታህሣሥ 22 ቀን 2005 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች የተሟጋችነት ውክልና ሰጥቶኛል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚለው በሪሁን ወንዴ በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ውስጥ የገባ መሆኑን በጭብጥነት ይዞ ጉባኤው ማጣራቱ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል። አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ውስጥ የገባና ከአገር የወጣ መሆኑ አከራካሪ ጭብጥ ከሆነ ስለ ጉዳዩ መረጃ የመያዝና መረጃ የመስጠት ሥልጣን ያለው አካል መጠየቁ የግድ አስፈላጊ ነው።

12. አንድ ሰው ወደ አገር ውስጥ ስለመግባቱና ከአገር ስለመውጣቱ ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርገውና ወደ አገር ውስጥ የሚገባም ሆነ ከአገር የሚወጣ ሰው ማሟላት የሚገባውን ሥርዓት ያሟላና የጉዞ ሰነዶችን የያዘ መሆኑን የማረጋገጥ ሥልጣን ያለው የደህንነት የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን መሆኑን በኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር 354/95 ተደንግጓል። በአዋጅ ቁጥር 354/95 አንቀፅ 16 ባለሥልጣኑ የኢሚግሬሽን ኦፊሰሮችን በመመደብ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትንም ሆነ ከአገር የሚወጡ ሰዎች መንገደኞች የሚከታተልና መረጃ የሚይዝ ስለመሆኑ በውጭ አገር የሚኖር ሰው ወደ አገር ውስጥ ሲገባም ሆነ ሲወጣ አስፈላጊ የጉዞ ሰነዶች የያዘ መሆኑንና ከአገር ሲወጣ ሊይዘው የሚገባውን ማናቸውንም መረጃ እንደሚይዝ ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ ከውጭ አገር ወደ አገር ቤት አንድ ሰው ተጓጉዞ ሲመጣና ሲወጣ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጡ መንገደኞችን ያሣፈረ ማናቸውም ማጓጓዣ የመንገደኖችን ስም ዝርዝር የያዘ ሰነድ ለሚመለከተው የኢሚግሬሽን ኦፊሰር የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 354/95 አንቀጽ 17 ተደንግጓል።

13. ከዚህ አንፃር ሲታይ የአመልካች ደንበኛ አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 አ.ም ወደ አገር ውስጥ ስለመግባቱም ሆነ ስለመውጣቱ የተገኘ መረጃ የሌለ መሆኑን ገልፆ የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ ለዲስፒሊን ጉባኤው የሰጠው መግለጫ በአዋጅ ቁጥር 354/95 በሚደነግገው መሠረት የአመልካች ደንበኛ በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ውስጥ በህጋዊ መንገድ የገባ ስለመሆኑ ማስረጃ የሌለ መሆኑን የሚሳይ ነው። የአመልካች ደንበኛ በአዋጅ የተደነገጉትን መስፈርቶች በማሟላት በ2005 ዓ.ም ወደ አገር ውስጥ የገባና ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩ በራሱ የአመልካች ደንበኛ ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩ በራሱ የአመልካች ደንበኛ በ2005 ዓ.ም በህጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ አልገባም ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ማስረጃ ነው። ይህ ከሆነ አመልካች ደንበኛው በ2005 ዓ.ም በህጋዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የገባና ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በማቅረብ ወይም አመልካች ደንበኛው ህጋዊ መስፈርቶችን ሣያሟላ በህገ ወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የገባና ከአገር የወጣ መሆኑን የሚሳይ ማስረጃ በማቅረብ ያቀረበበትን ማስረጃ ካላስተባበለ አቶ በሪሁን ወንዴ በ2005 ዓ.ም አገር ውስጥ አልነበረም። አመልካች ታህሣሥ 22 ቀን 2005 ዓ.ም ከፍትህ ቢሮ የወሰደው የተሟጋችነት የውክልና ሰነድ አመልካች አቶ በሪሁን ወንዴ የባህርዳር ከተማ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ ስለመሆኑ የሚገልፀውን ሀሰተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መታወቂያ በመጠቀምና ሌላውን ሰው በሪሁን ወንዴ አስመስሎ በማቅረብ የወሰደው ሀሰተኛ የውክልና ማስረጃ ነው በማለት የዲስፒሊን ጉባኤው የደረሰበትን የማስረጃና የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያ ለመቃወም የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረት የሌለው መሆኑን የሚሳይ ነው።

14. አመልካች ደንበኛው በ2005 ዓ.ም ህጋዊ መስፈርቶችን በማሟላት ወይም ከህግ አግባብ ውጭ ድንበር ጥሶ ወደ አገር ቤት መጥቶ የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም። ከዚህ በተጨማሪ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ደንበኛው በ2005 ዓ.ም ወደ አገር የገባና ከአገር የወጣ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ካለው ማስረጃውን እንዲያቀርብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 345 መሠረት እድል ሰጥቶት አመልካች ማስረጃውን ሊያቀርብ ያልቻለ መሆኑን በውሣኔው በግልፅ አስፍሯል። ከዚህ አንፃር ሲታይ የክልሉ ፍትህ ቢሮ አመልካች ደንበኛው በሪሁን ወንዴ በእስራኤል አገር ኗሪ መሆኑን እያወቀ በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ኗሪ መሆኑን የሚገልፀውን የሀሰት መታወቂያ መጠቀሙንና የሀሰት የተሟጋችነት የውክልና ሰነድ በመያዝ ክርክር እያቀረበ መሆኑን ገልፆ አመልካች በክልሉ የጥብቅና ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ምዝገባና የጠበቆችን ሥነ ምግባር ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 75/1994 የሚጥስ ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት ፈፅሟል በማለት የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰበር ችሎት በማፅናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም።

15. አመልካች የዲስፒሊን ጉባኤው ከዚህ በፊት ተከሳሽ በቢሮ ኃላፊው ውሣኔ በነፃ የተሰናበተበትን ጉዳይ በውሣኔ ውስጥ መግለፁን ምክንያት በማድረግ ባልተከሰሰበት ጉዳይ ጥፋተኛ ተብዬ ተቀጥቻለሁ የሚል የሰበር መከራከሪያ አቅርቧል። በእርግጥ ጉባኤው በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ውሣኔ አመልካች የክልሉ 2ኛ ና 1ኛ ደረጃ የጥብቅና ፈቃድ ሲያወጣ አግባብነት የሌለው የሥራ ልምድ ተጠቅሟል የሚል የዲስፒሊን ክስ ቀርቦበትና ሁኔታው ተጣርቶ አመልካች የጥብቅና ፈቅድ የወሰደው አግባብነት የሌለው የሥራ ልምድ መሆኑን ተረጋግጦበት እንደነበርና የቢሮ ኃላፊው ቀደም ብለው በነበሩት የቢሮው አመራሮች ተምኖበት የተሰጠው መሆኑንና ፈቃዱ ቢሰርዝ ለአመልካች ላይ የሚደርሰው ማህበራዊ እና ቤተሠባዊ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት ሣይወሰንበት የቀረ መሆኑን በውሣኔው ገልፆል። የልዩነት ሀሳብ ይኸ ሀሳብ በዲስፒሊን ውሳኔ ላይ መፃፉ ተገቢ አይደለም በሚል ምክንያት የተፃፈ መሆኑን ተገንዝበናል።

16. የዲስፒሊን ጉባኤው የአመልካች ማህደር ሲመረምር ከማህደሩ ጋር ተያይዞ ያገኘውን ፍሬ ጉዳይ በውሣኔው ውስጥ መግለፅ በክልሉ አዋጅ ቁጥር 75/1994 የተከለከለ ተግባር ሆኖ አላገኘነውም። በአንፃሩ የዲስፒሊን ጉባኤው አመልካች ማህበር ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የሥነ ምግባር ሁኔታ መግለፁ በአዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 5 ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲገኝ በጠበቃው ላይ የሚጣለውን ቅጣት በመወሰን የወንጀል ሪከርድ የጠበቃውን የግል ማህደር ወይም ሌላ ተመሣሣይ ማስረጃ የማስቀረብ የማሰማትና የመመርመር ሥልጣን የተጠቀመ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጉባኤው በአመልካች ማህደር ተያይዞ ያገኘውን ፍሬ ጉዳይ በውሣኔው ከመግለፁ ውጭ ይህን ፍሬ ጉዳይ ቅጣቱን አቅልሎም ሆነ አክብዶ ለመወሰን ያልተጠቀመበት መሆኑን ከውሣኔው ተረድተናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ጉባኤው ማህደሩን ሲመረምር ያገኘውን ግኝት በውሣኔው ውስጥ መግለፁ መሠረታዊ የህግ ስህተት እንደሆነ በመግለፅ ያቀረበው አቤቱታ የአዋጅ ቁጥር 75/94 አንቀጽ 21 ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

17. አመልካች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 4፣ የፌዴራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 456/97 በክልሉ መሬት አስተዳደር አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 እና በደንብ ቁጥር 51/99 መሠረት የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ በስጦታም ሆነ በውርስ የማግኘት መብት የሌለው በእስራኤል አገር ነዋሪ የሆነውን አቶ በሪሁን ወንዴ የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የባይነሳ 3ቱ ቀበሌ ነዋሪ እንደሆነ ተደርጎ በሀሰት ተዘጋጅቶ የተሰጠውን መታወቂያ እያወቀ ለባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የመሬት አስተዳደርና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ያቀረበና ይህንኑ መታወቂያ በመጠቀም አቶ በሪሁን ወንዴ ወደ አገር ውስጥ ባልገባበት በአገር ውስጥ በሌለበት ታህሣሥ 22 ቀን 2005 ዓ.ም የሀሰት የተሟጋችነት ውክልና በማውጣት አቤቱታ አቅራቢውንና ሌሎች አርሶ አደሮችን በመክሰስ ከፍተኛ እንግልት ያስከተለና ዕውነት እንዳይወጣና ፍትህ እንዲዛባ የሚደርግ ጥፋት የፈፀመ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የክልሉ ፍትህ ቢሮ የጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡

18. አመልካች የፈፀመው የዲስፒሊን ጥፋት እጅግ ከባድና በአዋጅ ቁጥር 75/1994 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2(መ) እና በሌሎች አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን ድንጋጌዎች የጣሰ አመልካች ሕግን የማስከበር ፍትህን የማስገኘትና ለፍትህ አስተዳደሩ የማገዝ ኃላፊነቱን ወደ ጎን በመተው ተቃራኒ የሆነ ተግባር የፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ አመልካች ላጠፋው ከባድ የዲስፒሊን ጥፋት የጥብቅና ፈቃዱ እንዲሰረዝ በማለት የክልሉ ፍትህ ቢሮ የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ማፅናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ የጠበቆች የዲስፒሊን ጉባኤና የቢሮ ኃላፊ የሰጠው ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38431 የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 49403 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 124618

ሕዳር 22 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አልማው ወሌ

2. መስጠፋ አህመድ

3. አብርሃ መሰለ

4. አብዬ ካሳሁን

5. እትመት አሰፋ

አመልካች፡-

1. ወ/ሮ ድባካ መሰለ - ቀረቡ
2. ሀብቱ ሞገስ - ሞግዚት ወ/ሮ ድባካ መሰለ - ቀረቡ
3. የሽወርቅ ሞገስ - ሞግዚት ወ/ሮ ድባካ መሰለ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሳጅን ኃይሉ ሞገስ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም ለፍርድ አፈጻጸሙ ምክንያት የሆነው መኖሪያ ቤት ክፍፍል መፈጸም የሚገባው በሀራጅ ተሸጦ ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍርድ በማጽናት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡- የ1ኛ አመልካች ባለቤት የነበሩት አቶ ሞገስ ጌታሁን በሞት መለየታቸውን ተከትሎ በተነሳው የውርስ እና የጋራ ንብረት ክፍያ ክርክር በዋግኽምራ ዞን በሰቆጣ ከተማ በቀበሌ 02 ክልል በሚች ስም ተመዝግቦ ይታወቅ ከነበረው ቤት ውስጥ ግማሹ የአሁኗ 1ኛ አመልካች ድርሻ ሆኖ ቀሪው ግማሽ ደግሞ ከሚች ለሚወለዱት ሰባት ልጆች እንዲከፋፈል ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ ይህንን የስረ ነገር ፍርድ ለማስፈጸም 1ኛ አመልካች በፍርድ ባለመብትነት ተሰይመው ባደረጉት እንቅስቃሴ በከተማው አስተዳደር በቀረበው የዋጋ ግምት መሰረት የቀሪዎቹን ወራሾች ድርሻ 1ኛ አመልካች ከፍለው እና ከወራሾቹ መካከል የአሁኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ቤቱ በጨረታ መሸጥ ከሚገባው በቀር ግምቱን ለመቀበል አልስማማም በማለታቸው ድርሻቸው በሞዴል 85 እንዲያገዝ ተደርጎ የቤቱ ስመሀብት አፈጻጸሙን በያዘው የሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወደ 1ኛ አመልካች የተዛወረ መሆኑን፣ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ትዕዛዝ ባለመስማማት በየደረጃው ያቀረቡት ክርክር በመጨረሻ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍርድ ቤቶችን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሽሮ ቤቱ ከተቻለ በዓይነት፣ ካልተቻለ ግራ ቀኙ እርስ በእርስ በሚያደርጉት ጨረታ፣ ይህም ካልተቻለ ለ3ኛ ወገን በጨረታ እንዲሸጥ በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም. ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፣ የወረዳው ፍርድ ቤትም በዚሁ አግባብ ቤቱ በጨረታ እንዲሸጥ ለማስቻል የጨረታ ማስታወቂያ እንዲወጣ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን፣በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት 1ኛ አመልካች ያቀረቡት ይግባኝ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 010913 በ02/10/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የተዘጋ እና አቤቱታቸውም በክልሉ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. በተሰጠ በፍርድ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾቹ በአከራካሪው ቤት ላይ ያላቸው የጋራ ድርሻ በጣም ብዙ ሆኖ እያለ እና የተጠሪው ድርሻ ግን በድርሻቸው ብቻ የታጠረ ሆኖ እያለ፣ ይህንኑ ከግምት በማስገባትም 1ኛ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ በቀር ለቀሪው እያንዳንዱ ወራሽ ግምቱን ከፍለው ቤቱን በስማቸው አዛውረው እያለ የአሁኑ ተጠሪ ግምቱን ለመቀበል ባለመስማማታቸው ብቻ ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የመታዘዙን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. በስረ ነገሩ ፍርድ መሰረት ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በቤቱ ላይ የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ እንዲወጣ በወረዳው ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
2. አመልካቾቹ ከአከራካሪው ቤት ላይ አለን የሚሉትን አብላጫ ድርሻ መሰረት በማድረግ ቤቱን ማስቀረት የሚችሉበት የሕግ አግባብ አለ ወይስ የለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ 1ኛ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከአከራካሪው ቤት በሚስትነታቸው ያላቸው ድርሻ ግማሽ ሆኖ እያለ እና የሰባት ወራሾች ድርሻ ከሆነው የቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጋማሽ ውስጥ ደግሞ 1ኛ አመልካች ሞግዚት የሆኗቸው 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች እያንዳንዳቸው አንድ ሰባተኛ ድርሻ ያላቸው ሆኖ እያለ እንዲሁም ከተጠሪው ውጪ ላሉት ቀሪ ወራሾች 1ኛ አመልካች ድርሻቸውን ከፍለው እያለ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ አንድ ሰባተኛ ድርሻ ብቻ ላላቸው የአሁኑ ተጠሪ ጥቅም ብቻ ሲባል ወደ 1ኛ አመልካች ስም ተዛውሮ የነበረው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው ትዕዛዝ ፍትሐዊ አይደለም የሚል መሆኑን የአቤቱታቸው ይዘት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ የክልሉ ሰበር ችሎት የአፈጻጸም ሂደቱን አስመልክቶ ቀደም ሲል ቤቱ ከተቻለ በዓይነት፣ ካልተቻለ ግራ ቀኙ በመካከላቸው በሚያደርጉት ጨረታ፣ ይህም ካልተቻለ ደግሞ ለ3ኛ ወገን በጨረታ እንዲሸጥ በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም. ውሳኔ የሰጠው 1ኛ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ውጪ ላሉት ሌሎች ወራሾች ድርሻቸውን ሰጥተው ቤቱን በስማቸው ካዛወሩ በኋላ በመሆኑ የተጠሪው ድርሻ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ አንድ ሰባተኛ ብቻ ሆኖ እያለ ቤቱ በሐራጅ ይሸጥ መባሉ ተገቢ አይደለም የሚሉ ከሆነ የሰበር አቤቱታቸውን በወቅቱ በስርዓቱ መሰረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ተገቢውን ውሳኔ ማሰጠት ይገባቸው የነበረ ከመሆኑ በቀር በክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ ወደ ወረዳው ፍርድ ቤት ተመልሶ የአፈጻጸም ሂደቱ ከቀጠለ በኃላ ወደኋላ ተመልሰው ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ፍትሀዊ አይደለም በማለት አሁን እያቀረቡ ያሉት ክርክር ስነ ስርዓታዊ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አፈጻጸሙን የያዘው የሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል በክልሉ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም. የሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ በስረ ነገሩ ፍርድ መሰረት ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በቤቱ ላይ የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ እንዲወጣ የሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከአከራካሪው ቤት 1ኛ አመልካች ግማሽ ድርሻ፣2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ደግሞ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ እያንዳንዳቸው አንድ ሰባተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑ አላከራከረም፡፡ ይህም 1ኛ አመልካችም ሆኑ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከቀሪዎቹ ወራሾች ጋር የአከራካሪው ቤት የጋራ ባለሀብቶች መሆናቸውን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ተይዞ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በሕብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት በሆነ ጊዜ ከተካፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ እንደሆነ የፍርድ ባለዕዳው እንደቀረበ ተቆጥሮ የተቀዳሚነት መብት የሚሰጠው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443 ይደነግጋል፡፡ ከስነ ስርዓት ሕጉ በተጨማሪም የጋራ ባለሀብቶች የሆኑ ሰዎች ያልተከፋፈለውን የጋራ ንብረት ከማንኛውም ሶስተኛ ወገን በፊት ቀዳሚ ሆነው በግዥ የማስቀረት ሕጋዊ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1) የተደነገገ ሲሆን ይህ መብት ተግባራዊ የሚደረግበት ስርዓትም በዚሁ ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከቁጥር 1386 እስከ 1409 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አመልካቾቹ አከራካሪውን ቤት ለማስቀረት የሚችሉት በቤቱ ላይ በሚከናወነው ጨረታ መሰረት ከፍተኛ ዋጋ በማቅረብ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ጨረታውን ያሸነፈበትን ዋጋ መሰረት በማድረግ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች በተጠበቀላቸው የቀዳሚነት መብት በመገልገል ነው፡፡ በቀጣይ የአፈጻጸሙ ሂደት አመልካቾቹ ከፍተኛ ዋጋ በማቅረብ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ጨረታውን ያሸነፈበትን ዋጋ መሰረት በማድረግ የቀዳሚነት መብታቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉ ከሆነ በሰበር አቤቱታቸው እንደሚከራከሩት ከአሁኑ ተጠሪ ውጪ ላሉት ሌሎች ወራሾች ድርሻቸውን ከፍለው በቤቱ ላይ ያላቸውን ድርሻ ከፍ ያደረጉ መሆን አለመሆኑ፣ ጨረታውን ካሸነፉበት የዋጋ መጠን ውስጥ የራሳቸው ድርሻ ተቀንሶ ገቢ ማድረግ የሚገባቸው የገንዘብ መጠን ምን ያህል እንደሆነ እና መሰል የአፈጻጸም ጉዳዮች ፍርዱን በሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ተስተናግደው ተገቢው ትዕዛዝ የሚሰጥባቸው ይሆናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካቾቹ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443 እንዲሁም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1)፣ 1386 እስከ 1409 በተደነገገው የቀዳሚነት መብታቸው የመገልገል መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ አከራካሪው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በዋግኽምራ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0101913 በ02/10/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍርድ በማጽናት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የስረ ነገሩ ፍርድ ያረፈበት ቤት በሀራጅ ይሸጥ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አከራካሪው ቤት በሀራጅ በሚሸጥበት ጊዜ አመልካቾቹ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443፣ እንዲሁም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1)፣ 1386 እስከ 1409 በተደነገገው የቀዳሚነት መብት የመገልገል መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ ለዋግኽምራ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ06/07/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ድረ-ገጽ፡- www.fsc.gov.et
ስልክ፡- +251 111 55 34 00
ፋክስ፡- +251 111 56 55 83
የመ.ሣ.ቁ፡- 6166
ነፃ የስልክ ጥሪ፡- 992

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች

ቅጽ -21

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



ቅጽ -21

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ-21

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ጥር 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ /ቅፅ 21/

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
አሠሪና ሠራተኛ					**1**
1.	አንድ ሠራተኛ የሥራ መሪ ሆኖ ሥራውን ሲመራ በፈጸማቸው ማናቸውም ክንውኖች ምክንያት በተወሰደበት እርምጃ ሊያነሳቸው የሚችላቸው የመብት ጥያቄዎች የሥራ መሪው በሂደት ወደ ሠራተኛ የሥራ መደብ የተዛወረ ቢሆንም እንኳን በፍትሐብሔሩ ድንጋጌዎች የሚገዙ ስለመሆናቸው *አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3/1፣3/2/ሐ*	130685	ወጋገን ባንክ እና አቶ አናጋው ገበየሁ	ሕዳር 13 ቀን 2009 ዓ.ም	2
2.	አንድ ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ስራ በሚለቅበት ጊዜ የሠላሳ ቀናት የማስጠንቀቂያ ጊዜ አለመስጠቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ለሰራተኛው ከሚከፈለው ክፍያ ከሰላሳ ቀናት ክፍያ ያልበለጠ ካሳ ለአሰሪው ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 31፤አንቀጽ 45*	119448	አዲስ ጋዝና ፕላስቲክ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ሰለሞን ኃይሌ	ታህሳስ 06 ቀን 2009 ዓ.ም	6
3.	በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚፈጸም ጊዜያዊ ቅጥር ውል ሊከተላቸው ስለሚገባ መስፈርቶች	132714	ዶ/ር ደስአለኝ ተመስገን እና	ታህሳስ 28 ቀን 2009	9

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መንግስት መስሪያ ቤት የሚደረግ የጊዜያዊ ሰራተኛ ቅጥር ውል ለፕሮጀክት ስራ ካልሆነ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀጽ 22/3/፣93* *የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሀዳር 18/2005 በቁጥር መ80-893/1/ የተጻፈ ደብዳቤ* *የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰመ30/መ/18/22/459 በ16/04/2005 የተጻፈ ደብዳቤ*		የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ	ዓ.ም	
4.	ከቅጥር ውል በመነጨ ግንኙነት የሚጠየቅ ማንኛውም ክስ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ ፣ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ ለመጠቀም ከሚችልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/1/፣163/1/*	136981	የሐረር ቢራ ፋብሪካ አ.ማህበር እና እነ አቶ አለሙ ነጋሽ (ሰላሳ ዘጠኝ ሰዎች)	ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓ.ም	17
5.	አንድ አሠሪ የቀጠረውን ሠራተኛ በሙከራ ጊዜ አጥጋቢ ውጤት አላሳየህም በማለት የሥራ ውሉን ያለምንም ማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ መብት የሚኖረው በህጉ አግባብ የተደረገ የሙከራ ጊዜ	140781	ታደሰ እንጆሪ ሆቴልና ጠቅላላ ንግድ ስራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና	ሐምሌ 18 ቀን 2009 ዓ.ም	22

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስምምነት መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 11/1/ /2/ እና /3/*		ወ/ሪት ሉላ ዘሪሁን		
6.	ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረን ሠራተኛ የሥራ ውሉ የሚቋረጥበት ጊዜ ሲደርስ አሰሪው ማሰናበት የሚችል ሲሆን ስንብቱ ከህግ ውጪ ነው ሊያሰኝ የማይችል ሲሆን በዚህ አግባብ የተሰናበተን ሰራተኛ የሥራ ሥንብት ክፍያ ሊያገኝ ይገባል የማያስብል ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24/1/፣ አንቀጽ 30/1/*	138054	የላሊበላ ማር መ.ገ.ዘየም እና ወ/ሮ ማሬ በዛ	ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም	26
7.	ማንኛውም ወገን የይርጋው ጊዜ ካለፈ በኋላ የይርጋ ጊዜን እንደመቃወሚያ አድርጎ ለማንሳት ያለውን መብት ሊተው የሚችል ስለመሆኑ፣ ዳኞች በገዛ ስልጣናቸው የይርጋውንም ደንብ መከላከያ ለመጥቀስ የማይችሉ ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 165/5/፣ የፍ/ሕ/ቁ. 1856/2/*	142752	በከልቻ ትራንስፖርት አ/ማህበር እና አቶ ወልደሰንበት ዳዲ	ሐምሌ 27 ቀን 2009 ዓ.ም	30
8.	በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ የተሰጠ አገልግሎት ለጡረታ ተግባር ስለሚያዝበት አግባብ	130944	አቶ ተሞገስ ወ/መላክ እና	ሐምሌ 26 ቀን 2009	34

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አዋጅ ቁጥር 345/1995 ፤በአዋጅ ቁጥር 907/2007		የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	ዓ.ም	
9.	ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ እና በራሱ ፈቃድ ወይም በአዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል ለዘለቄታው ሊከፈለው የሚችል ስለመሆኑ *የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር907/2007 አንቀጽ 5/2/፤በአንቀጽ 18*	132861	እነ አቶ እርጋጤ መድበው እና የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ-	ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም	38
10.	በሥራ ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት ወደ ዘላቂ የአካል ጉዳት ከተሸጋገረ የካሣ ጥያቄው የይርጋ ጊዜ መነሻ መቆጠር ያለበት ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ሳይሆን ዘላቂ የአካል ጉዳት መሆኑ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ *አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162(1)*	134188	አቶ ዊንታ ቦርጄ እና ይርጋለም ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም	42
የፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት					46
11.	ክስን ከማሻሻል ጋር በተያያዘ ፤ፍ/ቤት ክስ እንዲሻሻል ከፈቀደ	104621	ወ/ሮ አዜብ ታምሩ	ህዳር 13	47

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በኃላ የቀረበውን ክስ የሚሻሻልበትን ነጥብ ተገቢነት መመርመር ያለበት ከመፍቀዱ በፊት ስለመሆኑ እና ክሱ የተሻሻለበት ነጥብ ፍቃድ ከተሰጠበት ነጥብ ውጭ ከሆነም በውሳኔው ላይ መግለፅ ያለበት ስለመሆኑ ፤ *ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 91 እና 216 (3)*		እና አቶ ደጀኔ ዘውዴ	ቀን 2009 ዓ.ም	
12.	ያለዋጋ ወይም በደመወዝ የሚሰጥ አደራ ሰጭና አደራ ተቀባይ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር በአደራ የሚቀመጥ ዕቃ ዋጋ የማይከፈልበት ስለመሆኑና አደራ ሰጭው አደራ ተቀባዩ ዕቃውን በመልካም አያያዝ ለማኖር ያወጣውን ወጭ ሁሉ ሊከፍለው የሚገባ ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሕ/ቁ. 2788 እና 2793/2/*	119571	አቶ ባብሶ ቃልቦሬ እና ወ/ሮ ኩዘይማ ሁሴን	ህዳር 14 ቀን 2009 ዓ.ም	50
13.	ከሳሽ ወገን ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በተወው ወይም በሰረዘው ነገር ሌላ ክስ ለማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.፤278፤ 279/1/*	116860	ወ/ሮ አስቱር ሌንጂሳ እና እነ ወ/ሮ ሽታዬ ግርማ /ሁለት ሰዎች/	ታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም	54
14.	በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ተቋማት በድሃ ደንብ ዳኝነት ሳይከፍሉ ለመስተናገድ በማስረጃ ሊያቀርቡት ስለሚገባቸው	121938	የድሬ እንጭኒ ወረዳ መንገዶች ባለስልጣን	ታህሳስ 27 ቀን 2009	58

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ጉዳዮች *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.467-479*		እና አንጭኒ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ	ዓ.ም	
15.	በልዩ አዋቂነት ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት በሒሳብ አጣሪነት የሾመው ባለሙያ ለማጣራቱ ሥራ ይረዳው ዘንድ ሊቀርቡለት የሚገቡ ጠቃሚ ማስረጃዎች ከአንደኛው ተከራካሪ ወገን ወይም በሁለቱም ወገን ተከራካሪዎች ወይም በሌላ ሶስተኛ ሰው ሳያቀርቡለት ቢቀሩ ሊከተላቸው ስለሚገቡ እርምጃዎች *በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 132፣136፣145(1)እና 250*	97023	የአ/አ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ አምባቸው ፈቀደነህ	ታህሳስ 28 ቀን 2009 ዓ.ም	63
16.	አንድ ፍ/ቤት ክስ ቀርቦለት ጉዳዩን የማየት ሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋው እንደሆነ ዋናውን ክርክር እንዳላየ የሚያስቆጥር ሲሆን በመዝገቡ ላይ የሰጣቸው ማናቸውም ትእዛዞች በማናቸውም ወገን ላይ ህጋዊ የሆነ አስገዳጅነት ውጤት የሌለውና በዚሁ ጉዳይ ለሚመለከተው ፍ/ቤት መዝገቡ ቢቀርብ ከዚህ ቀደም በፍርድ ያለቀ ነው ሊያስብል የማይችል ስለመሆኑ	100295	አቶ ደጓለ ገዳሙ እና ላይኩን መሉጌታ (አራት ሰዎች)	ህዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም	70

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5፣9 እና 231				
17.	ተከራካሪ ወገኖች ባላነሱት የመከራከሪያ ነጥብ ወይም የግራ ቀኙ ወገኖች ባልተለያዩበት ጉዳይ እንዲጣራ በማድረግ ውሳኔ መስጠት ተገቢ ስላለመሆኑ፣ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 241፣242*	124669	የሳስኮ ኢንዱስትሪያል ንግድና ት/ት ድርጅት እና የኢ.ፌ.ድ.ሪ ት/ት ሚኒስቴር	ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም	74
18.	አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከተከራካሪ ወገኖች አንዳቸው በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ሲያቀርቡለት በስር ፍ/ቤት የታዩ ሰነዶችን ወይም መታየት የነበረባቸውን ሰነዶች አስቀርቦ ሳይመረምር በይግባኙ ላይ ውሳኔ፣ ፍርድ ወይም ትእዛዝ መስጠት የሌለበት ስለመሆኑ፣ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 145/1/*	99474	እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ ደራሳ እና እነ ወ/ሮ ማሚቱ ጌታቸው	ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም	78
19.	በክርክር ተሳታፊ ያልሆነ ወገን በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ እግድ ትዕዛዝ የዕግድ ትዕዛዙን ለሰጠው ፍ/ቤት የዕግድ ይነሳ አቤቱታ ሳያቀርብ በቀጥታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚያቀርብበት እና የዕግድ ትዕዛዙ ላይ ውሣኔ የሚያሰጥበት ስርዓት የሌለ ስለመሆኑ *በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 154፣158*	123833	አቶ ለሜሳ ደገፉ እና የአዳማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ.ም.	87

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
20.	በክስ አቀራረብ ሥርዓት ላይ ጉድለት ያለበት መሆኑ ተረጋግጦ የተዘጋ መዝገብ ምንም አይነት ክስ እንዳልቀረበ የሚያስቆጥርና የይርጋ ጊዜ የማቋረጥ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278 (2) (ሀ) እና (3)*	123123	አቶ ተክሊት አፈርቂ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም	92
21.	በአጭር ስነ ሥርዓት ክስ ሊቀርብ ስለሚችልበት አግባብ *በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 284*	124552	አቶ ምትኩ አበበ እና የከሰረውሆላንድ ካር ኃ/የተ/የግ/ማሕበር	ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም.	95
22.	የሥር ፍ/ቤት በጭብጥነት ይዞ በአግባቡ ባጣራው ፍሬ ጉዳይ ላይ በይግባኝ ፍርዱን የሚመለከተው ፍ/ቤት ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት የተጣራውን ፍሬ ነገር በድጋሚ እንዲጣራ ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለስ ተገቢ ስላለመሆኑ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.136(1)፣343(1)*	127580	የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን እና ዲኖ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም	100
23.	የክሳሽ ተክሳሽ ክሳሽነት ክስ ሊቀርብ የሚችለው በክሳሽ ወገን ላይ ብቻ ሥለመሆኑ ተክሳሽ የተክሳሽ ክሳሽነት ክስ ሲያቀርብ ሊከተለው ሥለሚገባ	102668	ማክሲመም ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ.ም	105

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሥነ-ሥርዓት *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 30፣36፣224 እና 234(1)(ረ)*		እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/የሆሳህና ከተማ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ፅ/ቤት		
24.	በጠፋው ሰው መሞት ምክንያት መብት የሚያገኙ ሰዎች በመብታቸው መጠቀም የሚችሉት መጥፋቱን የሚወስነው ፍርድ የመጨረሻ ከሆነ በኃላ ስለመሆኑ *የፍ*ሕብሔር ሀግ ቁጥር 165(1)*	132208	ወ/ሮ ጸሀይ አጎናፍር እና አቶ ጌራ ላቀው	ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም	114
25.	• አንዱን የፍ*ሕብሔር ክስ ባንድ ወይም ካንድ በበለጡ ፍርድ ቤቶች ዘንድ ለማቅረብ የሚቻል ሲሆን የክሱ ማመልከቻ በቀደምትነት የቀረበለት ፍርድ ቤት ብቻ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለው ተቆጥሮ ለክርክሩ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል ሥለመሆኑ • አንድን ሰው በመወከል በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመሟገት በህጉ የተቀመጠውን የዝምድና ደረጃ ወይም በህጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ የውክልና ስልጣን	131622	ወ/ሮ አልማዝ እምሩ እና ወ/ሮ አይጠገብ ቀሬ	ሰኔ 20 ቀን 2009 ዓ/ም	119

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የሚያስፈልግ ስለመሆኑ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 7(2)፣32፣57፣58 እና 63*				
26.	ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ክሶች ወይም ይግባኞች መጣመር በነበረባቸው ሰዓት ሣይጣመሩ ቢቀሩና የግራ ቀኙን የተለያየ መብት በሚያጎናፅፍ ሁኔታ ቢወሰን እነዚህን ውሳኔዎች ተጣጥሞ እንዲፈፀሙ ማድረግ ተገቢ ሥለመሆኑ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.11*	113613	በደቡብ ወሎ ዞን የለገሂዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት እና ሰለሞን አባይ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ	ግንቦት 30 ቀን 2009 ዓ.ም	125
27.	በፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ የክስ ምክንያት አለው ብሎ ለመወሰን የሚቻለው በክሱ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሹ የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ሕግ የሚፈቅድለት የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ፡- ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ፡- *የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1)*	136775	ህዳሴ 1ኛ ደረጃ ከፍተኛ አገር አቋራጭ የህዝብ ባለንብረቶች ማህበር እና የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን	ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓ.ም	130

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ንብረት					134
28.	በኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም ህግ መሰረት ግጭትና አለመግባባትን በመጀመሪያ በአስታራቂ ሽማግሌዎች እንዲፈቱ የሚደነገጉት ድንጋጌዎች አርሶ አደር ከአርሶ አደር በሚያደርገው የሚፈጠርን አለመግባባትን ለመፍታት እንጂ በህግ ወለድ እና በአንድ አርሶ አደር ሰዎች መካከል የሚፈጠርን አለመግባባት ጭምር የሚያካትት ሥላለመሆኑ *አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀፅ 16*	102406	የወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ እና አቶ ባጫ አለሙ	ህዳር 9 ቀን 2009 ዓ/ም	135
29.	የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ ሻጭ ንብረቱን ከ3ተኛ ወገን ይዞታና ቁጥጥር ነፃ በማድረግ የማስረከብ ግዴታ እና ገዥ ከተረከበ በኃላ ንብረቱ የእኔ ነው ባይ ቢመጣ ሻጩ በዋቢነት የመቆም ግዴታ የተለያየ ግዴታ ስለመሆኑ፤ *ፍ/ብ/ሕ/ቁ 2875 ፣ 2274 ፣ 2880 ፣ 2881 ፣ 2882 ፣2879፣ 2888 ፣1206 ፣ 1195 ፤ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) 36(4) እና 40 (2)*	100395	ወ/ሮ አማረች ማሬ እና እነ ወ/ሮ ሜሪ ታደሰ (ሦስት ሰዎች)	ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም	138
30.	የእርሻ መሬት ይዞታን ከማስለቀቅ ጋር በተገናኘ የሚቀርብ ክስ ከእርሻ መሬት ልዩ ባህሪ አንጻር ከንብረቱ የሚገኘውን አላባ	120087	አቶ አስራት ኩምሳ እና	ታህሳስ 07 ቀን 2009	146

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ወይም ሌላ ጥቅም ጭምር ከዋናው ክስ ጋር አጣምሮ ይክሰስ ሊባል ስለማይችል፣ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216/3/፣218/ሀ/* *አዋጅ ቁ. 452/1997 አንቀጽ 12* *የአ/ክ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 130/1999 አንቀጽ 16 ደንብ ቁ. 151/2005 አንቀጽ 18*		እነ ጉደታ በዳዳ (ሁለት ሰዎች)	ዓ.ም	
31.	በትግራይ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ መሰረት ወራሽ የሌለው መሬት በቀበሌው የገጠር መሬት አስተዳደር ኮሚቴ መሬት ለሌላቸው ከተሸጋሸገ በኋላ የሚቀርብ አቤቱታ ከመሬት ዳኝነትና ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁ. 239/2006 አንቀጽ 14/8/* *ደንብ ቁ. 85/2006 አንቀጽ 22/1//ሀ/፣21/8/*	121663	አቶ ሀጋዚ ዘውድ እና ወ/ሮ ረዝብ ቸኮል	ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም	152
32.	በአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ መሰረት መሬት በኑዛዜ ተላልፎልኛል የሚል አካል ኑዛዜው ተቀባይነት እንዲያገኝ ሊያደርገው ስለሚገባ እርምጃ *የአ/ክ/የመ/አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 133/98*	115399	እነ አቶ ተስፋዬ ተሾመ (ሁለት ሰዎች) እና ሞላን ወልደ	ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም	156

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ደንብ ቁ. 51/99ን ለማስፈጸም የወጣው መመሪያ አንቀፅ 13/1/2/		(ሁለት ሰዎች)		
33.	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት ስጦታው በተደረገበት የእርሻ መሬት ላይ በቤተሰብነት የተመዘገበ አባልን ያገለለ መሆኑ ከታወቀ ይኸው ሰነድ በህግ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ ህጉን ያልጠበቀ የገጠር መሬት ይዞታ በኑዛዜ ወይም በስጦታ ተላልፏል የሚለው ወገን መብቱን ለማስጠበቅ በሁለት ዓመት መጠየቅ ነበረበት ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ *በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2441፣* *አዋጅ ቁጥር 456/97* *የአ/ብ/ክ/መ/የመ/አስ/አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 133/98 አንቀጽ 16/3፣* *ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/2*	125186	ወ/ሮ አዛል አይናለም እና እነ አቶ ምህረት በላይ (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 26 ቀን 2009 ዓ.ም.	160
34.	በደቡብ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት በወረዳ በተጀመረ ክርክር በክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከፀና ውሳኔው የፀናበት ወገን ለተጨማሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ	114670	እነ አቶ ባንኩ ኢሩስ (ሁለት ሰዎች) እና	ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም	163

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ፣ *የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3//ሀ/* *የደቡብ ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ 75/2/ሐ/* *የክ/ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 43/1994 አንቀጽ 5/3/* *የፌደራል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 456/1997 አንቀጽ 12* *የደ/ክ/የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 110/1999 አንቀጽ 12/4/*		አቶ ሳምሶን ገ/ዮኃንስ		
35.	የገጠር መሬት ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ አግባብ ባለው አካል በስጦታ የተላለፈለት ተጠቃሚ ለረጅም ጊዜ ተጠቃሚ የሆነበት መሬት መሆኑ ከተረጋገጠ መሬቱ በስጦታ ሰጪዉ ስም ተመዝግቦ መገኘቱ እና ግብር በስሙ መከፈሉ ብቻ ይዞታዉ በስጦታ ዉል አልተላለፈም የሚያሰኝ ወይም በመሬቱ ላይ ያለዉን የባለይዞታነቱን መብት የማያስቀር ስላለመሆኑ *የኦሮሚያ ክልል ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 2/3፤9(5)*	122740	አቶ ጤና ጋርደዉ እና ወ/ሮ መደቅሴ ገርቢ	ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም	170
36.	የመንግስት ቤት ተከራይቶ የሚኖሩ ሰዎች የባለቤትነት መብት	115387	እነ አቶ መክብብ ተስፋ	ሚያዚያ 26	175

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	(የመፋለም ክስ) የመጠየቅ ክስ ማቅረብ የሚችሉበት ህጋዊ ምክንያት ስላለመኖሩ *የፍ/ሕ/ቁ. 1205*		(ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ፀሐይ ለገሰ (ሁለት ሰዎች)	ቀን 2009 ዓ.ም	
የዳኝነት ስልጣን					*180*
37.	የአዲስ አበባ ከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀደም ብሎ በሰጠው ፍርድ ላይ የሚቀርብለትን የፍርድ መቃወሚያ ተቀብሎ የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358፣የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37/1/ አዋጅ ቁ. 721/2004*	121660	አቶ ለገሰ ገለታ እና እነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ (ሁለት ሰዎች)	ህዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም	181
38.	በህገወጥ መንገድ ተይዘው በተገኙ የቁም እንስሳት ላይ አግባብ ያለው አካል በሚወስደው እርምጃ ላይ በቀጥታ ክስ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣ *የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 አንቀጽ 15/5/*	129430	የእነማይ ወረዳ ንግድ ትንስፖርት ጽ/ቤት እና አቶ ጉበዜ አሰፋ	ታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም	188

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እና 8 ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀጽ 19/4/ እና 5				
39.	የተጨማሪ እሴት ታክስ የፌዴራል ታክስ በመሆኑና የክልል የገቢዎች ቢሮዎች ታክሱን የሚያስተዳድሩት በወክልና ስልጣናቸዉ በመሆኑ ምንም እንኳ ታክሱ የተወሰነዉ በክልሉ የገቢዎች ቢሮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቢሆንም የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ይግባኝ ማቅረብ የሚገባዉ ስልጣን ላለዉ የፌዴራል ፍ/ቤት ወይም የወክልና ስልጣን ላለዉ የክልል ፍ/ቤት ሥለመሆኑ *አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 28(2) እና አንቀጽ 30፣አንቀጽ 43(3)፣ 112*	123986	አቶ መቻልደጉ ሰሙር እና የሚዛን አማን ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤት	ግንቦት 18 ቀን 2009 ዓ.ም	192
40.	የአንድ ሃገር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ብሔራዊ የዳኝነት(judicial jurisdiction) ስልጣን አለው ለማለት ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ዝርዝር ነጥቦች	183200	እነ ማጂኮን ኮንስትራክሽን ሊትድ(ሁለት ሰዎች) እና አቶ ታትገኝ ፊጣሞ ወሌቦ (አራት ሰዎች)	ሰኔ 27 ቀን 2009 ዓ.ም	197
41.	የሊዝ ውል እንዲሰረዝ የሚቀርብን የዳኝነት ጥያቄን በተመለከተ	119435	አቶ አብዱልቀኒ አብዱራህማን	ሰኔ 27 ቀን	201

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሊያስተናግድ የሚገባ ስለመሆኑ		እና እነ አቶ ዳንኤል ወ/ኃዋሪያት(ሁለት ሰዎች)	2009 ዓ.ም.	
ጉመሩክ					204
42.	የተሻረው ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖርና በአዲሱ ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ድርጊቱ ሊያስከስስም ሆነ ሊያስቀጣ የማይችልና የተጀመረውን ክስም የማቋረጥ ህጋዊ ውጤት ያለው ስለመሆኑ *የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 21(2)፣ የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5/3/* *አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 99፣ አዋጅ ቁ. 859/2006*	111960	ወ/ሮ አባይነሽ ፈቀደ (ሁለት ሰዎች) እና የሺ ኃይሌ	ሕዳር 06 ቀን 2009 ዓ.ም	205
43.	አንድ ግብር ከፋይ የሂሳብ መዝገብ እና ሰነድ ካልያዘ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለስልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላስታወቀ እንደሆነ ግብር አስገቢው ባለስልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወስን የሚችል	133773	አቶ ተክሌ ፈረጃ ጋዲሳ እና የኢ/ያ ገ/ጉ/ ባለስልጣን የመርካቶ ቁ.1	ሐምሌ 14 ቀን 2009 ዓ.ም	209

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑ፡- *የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 69*				
ውል					213
44.	አንድ ዕቃ ለመሸጥ /በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ/ የተዋዋለ ወገን ከዕርሱ አቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ውሉን መፈጸም ባልቻለ ጊዜ በቅድሚያ ለዚሁ ስራ የተቀበለውን ገንዘብ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ከመመለስ ውጭ ውሉን ባለመፈጸሙ ምክንያት ለደረሰው ኪሳራ እንዲከፍል የማይገደድ ስለመሆኑ፣ *ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2356/1/*	117036	ፀጉ ብርሃን ትራዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ኮሎኔል ይትባረክ አማረ	ህዳር 12 ቀን 2009 ዓ.ም	214
45.	በጽሁፍ በተደረገ ውል አንደኛው ወገን ውሉን ለማሻሻል ሲፈለግ ዋናው ውል በፅሁፍ እስከተደረገ ድረስ ማሻሻያውም በዛው አግባብ መሆን ያለበት ሥለመሆኑ በጽሁፍ በተደረገ ውል አንደኛው ወገን የውል ማሻሻያ ጽሁፍ ለሌላኛው ወገን ሲላክልት ሌላኛው ወገን ሊቀበለው እንደሚችል ሲደነግግ ውሉን ለመቀበሉ ግን የተለየ ስርዓት ካለማስቀመጡ በተጨማሪ በምክንያታዊ ጊዜ ውሉን ያለመቀበሉን ካላስታወቀ	120150	እሌ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ሀ/የተ/የግ/ማህበር እና ፋርም አፍሪካ የኢትዮ ፕሮግራም	ታህሳስ 5 ቀን 2009 ዓ.ም	224

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ውሉን እንደተቀበለ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሕ/ቁ. 1722፣2625*				
46.	የሊዝ ውል ሊቋረጥ ወይም ሊፈርስ ስለሚችልባቸው መሰረታዊ ምክንያቶች *የሊዝ አዋጅ ቁ. 272/94 አንቀጽ 15/1/*	109194	የጎንደር ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት እና እስማኤል አህመድ ሃላፊነቱ የተ/የግ/ማህበር	ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም	230
47.	በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተደረገ ውል የፍቃድ ጉድለት ስለመኖሩ ማሳያ ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች ውስጥ ከተዋዋይ ወገኖች በአንዱ ውልን ለማፍረስ የሚያስችል ጉዳይ መኖሩን ማሳየት ሲቻል ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሕ/ቁ. 1696፣1710/2/*	114398	ወ/ሮ ደስታ ኪዳነ እና ወ/ሮ አመቱ ኤርታቦ	ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም	235

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
48.	የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ህገ ወጥ ውል ነው በማለት በውሉ መሰረት ላለመፈፀም የሚቀርብ ክርክር ህጋዊ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ *የፍትሓ ብሔር ህግ ቁጥር 1792 ንዑስ አንቀጽ 1፤1793*	119233	አያት አክሲዮን ማህበር እና ወ/ሪት ክፍለሚካኤል ተክሌ	ሚያዚያ 17 ቀን 2009 ዓ/ም	240
49.	የዕቃ አቅርቦት ውል በአቅራቢው ባለመፈፀሙና ለተወሰደ ቅድሚያ ክፍያ እንዲሆን የቅድሚያ ክፍያ የዋስትና ሰነድ የሰጠ አካል ውል አቅራቢው በውል የገባውን ግዴታ ባለመፈፀሙ ምክንያት በሰጠው የዋስትና ሰነድ መሠረት ከዋናው ባለዕዳ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ	106994	ብሔራዊ የኢትዮጲያ ኢንሹራንስ /አ.ማ/ እና እነ የአብክመ ዘላቂ ግብርና ተሃድሶ ኮሚሽን	ሚያዚያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም	248
50.	የህብረት ሥራ ማህበር ውስጥ ያለ የማህበር አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ሲያስተላልፍ ሊከተለው ስለሚገባ አካሄድ *ለዋጅ ቁ.147/91 አንቀፅ 19*	113013	ወ/ት ማህሌት እንዳለ እና እነ አቶ አህመድ አለም (ሁለት ሰዎች)	ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም	254

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
51.	በህጉ አግባብ በሕግ ፊት የጸና የወለድ አገድ ዉል መደረጉ ባልተረጋገጠበት የወለድ አገድ ዉል ተቋቋሚል ማለት ስላለመቻሉ *የፍ/ሕ ብሔር ሕግ ቁጥር 3052፤ 3053፤3117–3130*	117953	አቶ ሰብስቤ አበበ እና ወ/ሮ ፍቅርተ ካህሳይ	ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም	258
ከውል ውጪ ኃላፊነት					262
52.	በተሸከርካሪዎች ላይ የደረሰን ጉዳት በተመለከተ የገበያ ዋጋ አስልቶ ግምት ለማቅረብ በህግ ለትራፊክ ፖ/ሊስ የተሰጠ ተግባር ስላለመሆኑ የተሸከርካሪ ዋጋ ግምት የመተመን አገልግሎት መስጠት የትራንስፖርት ባለሥልጣን ስለመሆኑ በአንድ ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት ጠቅላላ ጉዳት (total loss) በሚሆንበት ጊዜ በንብረቱ ላይ የደረሰውን አጠቃላይ ግምት ከመጠየቅ ውጪ ይገኛል ተብሎ የሚታሰበውን ገቢ መጠየቅ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ *አዋጅ ቁ.681/2002 አንቀፅ 2(25)፣37(2(ሐ)* *አዋጅ ቁ.468/97 አንቀፅ 7(1(ዘ)) የፍ/ሕ/ቁ.2090(1)፣2092 እና 2119(1)(2)*	127587	ፕሮፌክት ትራንዚትና ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ አህመድ ዳውድ	ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም	263
ቤተሰብ					***269***

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
53.	ባልና ሚስት የጋራ የሆነውን የንግድ ድርጅታቸውን መልካም ስም የማከራየት መብትና በቤቱ ውስጥ የሚገኘውን የንግድ ዕቃ የመከፋፈል መብት ያላቸው ስለመሆኑ፣ *ፆን/ሕ/ቁ. 127*	117164	ወ/ሮ ተክአ ሐጎስ እና አቶ ፀጋዬ ገ/ጻዲቅ	ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም	270
54.	ጋብቻ የተፈጸመው በአንድ ክልል ውስጥ እና በዚያው ክልል ሕግ መሰረት ሆኖ ክስ በቀረበበት ጊዜ ተጋቢዎቹ የሚኖሩት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ከፍቺ እና መሰል ጥያቄዎች ጋር ተይይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የተሰጠው የክልሉ ፍርድ ቤት እንጂ ተጋቢዎቹ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተቆጥሮ ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ስላለመሆኑ *አዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 (2)*	127714	ወ/ሮ ቃልኪዳን ይሽነው እና አቶ ኢብሳ ያደታ	መጋቢት 26 ቀን 2009 ዓ.ም.	275

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
55.	በሌላ አገር ህግ እና በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ መካከል እንደባልና ሚስት አብረው በመኖር ግንኙነት ውስጥ የተፈራ ንብረት የጋራ እንዲሆን ለመወሰን በሁለቱም ህጎች መካከል ግጭት መኖር ያለመኖሩን የሌላኛው አገር ህግ እንዲቀርብ በማድረግ መወሰን የሚገባው ስለመሆኑ በዓለም አቀፍ የግለሰብ ህግ /Private International law/ መሠረት በዘርፉ እውቀት ያለ ወይም ምሁር /Scholar/ የሰጠውን አስተያየት በማስረጃነት ሲቀርብ የቀረበውን አስተያየት እንደማንኛውም ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን አስተያየቱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ስለመሆኑ *የኢ.ፌ.ድ.ሪ ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 5፣102 /1/*	123132	አቶ ክሳሁን ታደሰ እና ወ/ሪ ፀዳለ ሀፍታይ	ሚያዝያ 30 ቀን 2009 ዓ/ም	279
56.	ለህፃን ልጅ ማሳደጊያ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ወላጅ፣ የሚከፍለውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ ለመወሰን ግምት ውስጥ ሊገቡ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች *የተሻሻለው ፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 (2) ፣202*	130931	አቶ በላይ ዘለቀ እና ወ/ሮ ትዕግስት ዳባ /የህፃን ሀሴት በላይ ሞግዚት/	ሰኔ 19 ቀን 2009 ዓ.ም	284

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
57.	በፌደራል የቤተሰብ ህግ መሰረት በአባት በኩል ያለን መወለድ የመካድ ክስ በማቅረብ መቃወም ስለሚችሉ ሰዎች *የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 177/1-3*	129933	አቶ አየለ ወ/አለማው እና እነ ወ/ሮ እመቤት ማሞ (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ/ም	288
ውርስ					***292***
58.	የውርስ ንብረት የመከፋፈል ጥያቄ ንብረቱ በአይነት ተለይቶና ተገምቶ እስከቀረበ ድረስ በቀረበው ግምት መሰረት የፍርድ ቤቶችን የስረ ነገር ስልጣን ሊወሰንበት የሚገባ ስለመሆኑ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 18፣23*	124313	እነ ወ/ሪት ቅድስት ዮሴፍ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ምስራቅ አለማየሁ (ሶስት ሰዎች)	ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም	293
59.	ፍ/ቤት የሚችን ኑዛዜ ፈራሽ መሆን አለመሆን ላይ ተመስርቶ በሚቀርብለት የዳኝነት ጥያቄ ላይ አግባብ ያለው ዳኝነት ከመስጠት አልፎ በኑዛዜ የሚደርሳቸውን ድርሻ በትክክል ለይተው ሳይጠይቁ የውርስ ንብረት መጠን ግምት በመቀመጡ ብቻ ይኼው ግምት መሰረት ተደርጎ ሊፈጸም የሚችል ዳኝነት ስላለመኖሩ *ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1)*	135694	እነ አቶ ይርዳው ሽፈራው (አምስት ሰዎች) እና እነ አቶ መስፍን ሽፈራው (አስር ሰዎች)	ሐምሌ 20 ቀን 2009 ዓ.ም	298
ንግድ					302

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
60.	በአንድ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ አባል የሆነ ሰው በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በአካል ተገኝቶ ድምፅ መሰጠት ያለበት ስለመሆኑ እና ይህ ሁኔታ /አጠቃላይ መርህ/ ሊታለፍ የሚችለው መረጃ ሊቀርብበት የሚችል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁጥር 147/91 /በአዋጅ ቁጥር 402/96 እንደተሻሻለ አንቀጽ 18/2/*	110149	ምድር ሎዛ የጋራ ሕንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ እና አቶ ይህደጎ ኪዳኔ	ታህሳስ 27 ቀን 2009 ዓ.ም	303
61.	ቼክ የብድር ዉልን ተክቶ ብድር መኖሩን ለማስረዳት አግባብነት ያለዉ ሰነድ ነዉ ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ በብድር የተሰጠዉ ገንዘብ 500 /አምስት መቶ/ የኢትዮጵያ ብር በላይ ሲሆን የብድሩ ዉል በጽሑፍ ወይም በፍ/ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሐላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት የማይቻል ሥለመሆኑ *ንግድ ሕጉ ቁጥር 827 /ሀ/ እና 854* *የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2472(1)*	123984	አቶ ጌታቸዉ መሸሻ እና አቶ ተሾመ ወልዴ	ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም	308

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
62.	አንድ የውጪ ዜግነት ያለው ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄደው ኢንቨስትመንት ውስጥ አክሲዮንን በመግዛት ለንግድ ስራ ምቹ የሆነ ህንፃ በማሰራት የሥራ መስክ ሊሳተፍ የሚችል ስለመሆኑ አንድ የባለአክሲዮኖቹ ጉባኤ ሕግን፣ መመስረቻ ፅሑፍንና መተዳደሪያ ደንብን በመከተል የተደረገ እስከሆነ ድረስ በሕጉ ጥበቃ የሚያገኝ ስለመሆኑ *አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 12(1ሀ))፣ 2(6) እና 38* *ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 3* *የንሥሕ/ቁጥር 416(1)*	118246	የሲዳሞ ተራ ህንጻ ስራ አክሲዮን ማህበር እና ወ/ሮ አብረኸት ሀብተእዝጊ ተማኑ ወራሾች (ዘጠኝ ሰዎች)	ሰኔ 23 ቀን 2009 ዓ.ም	312
63.	ቼክ አምጪው በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ባንክ ሣያቀርብ ይህንኑ ጊዜ አሳልፎ አንድ ዓመት ሣያልፍ ባንክ አቅርቦ በቼክ አውጪው ስም በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን ያረጋገጠ ቼክ አምጪ ቼኩን መሰረት አድርጎ የሚያቀርበው ክስ አንድ ዓመት አላለፈም በሚል የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ በንግድ ህግ ቁጥር 881/1/ ስር በተመለከተው የአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ክስ የማቅረብ መብታቸው በህግ ፊት ተቀባይነት	139932	አስማማው በየነ እና አሰፋ ነጋሽ	ሐምሌ 20 ቀን 2009 ዓ.ም	327

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሊኖር የሚችለው በን/ሕ/ቁ. 855 ስር ቼኩን በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለባንክ የማቅረብ ቅድመ ሁኔታ ሲያሟላ ስለመሆኑ፣ *የን/ሕ/ቁ. 855፣881/1*				
ወንጀል					***331***
64.	ወንጀል አድራጊው የመጀመሪያውን የጥፋት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሲል መሰረታዊ ከሆነው ወንጀል በኋላ አከታትሎ ያደረገው ድርጊት ከቀድሞ ሃሳቡና ሊደርስበት ካቀደው ግብ ጋር የተያያዘ ሆኖ ሲገኝ በዋናው ወንጀል ስር መጠቃለል የሚገባው ስለመሆኑ ፣ የወ/ሕ/ቁ. 61/3/	104637	የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ እና መዑዝ ደስታ ገ/እግዚአብሔር	ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም	332
65.	ሰውን ለአደጋ ማጋለጥ ወይም መተው ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች *የወ/ሕ/ቁ. 57*	132266	ወ/ሮ አልማዝ አስፋው እና የኢትዮ ሱማሌ ክልል ዐ/ህግ	ታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም	338
66.	አንድ አሽከርካሪ በአንድ ቸልተኝነት ተግባር በተለያዩ ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ሲያደርስ የወንጀል ሕግ ቅጣቱን ከፍ ከሚያደርግበት በስተቀር በቸልተኝነት ተደራራቢ አካል ማጉደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ ተደራራቢ ወንጀል ክስ ሊቀርብበትና	123046	አቶ አዲሱ ገመቹ እና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዓ/ሕግ	የካቲት 29 ቀን 2009ዓ.ም	345

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በተደራራቢ ወንጀል በመፈፀም ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባ ስላለመሆኑ *የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60(ሐ)፣61፣ 543(3)፣559(2)*				
67.	አንድ ተከሳሽ በወንጀል ተጠርጥሮ የጣት አሻራ ሰጥቷል በመባሉ ብቻ እንደጥፋተኛ ተቆጥሮ የወንጀል ጥፋት ሪከርድ እንዳለበት ተደርጎ ግምት በመውሰድና እንደ ቅጣት ማቅለያ ሳይያዝ የሚሰጥ ውሳኔ መሰረታዊ የህገ መንግስት መርህን የሚጣረስ ስለመሆኑ *የወንጀል ህግ አንቀጽ 82*	131705	እነ አብርሃም ሰለሞን (ሦስት ሰዎች) እና የፌዴራል ዓ/ህግ	ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም	354
68.	በወንጀል ጉዳይ በኤግዚቪትነት የተያዘ ንብረት በፍርድ ውሳኔ የሚያገኘው በወንጀሉ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ለባለንብረቱ ይመለስ ወይም ለመንግስት ገቢ ይሁን ተብሎ ሲወሰን ወይም ተገቢውን የህግ ስርዓት ተከትሎ ሥልጣን ባለው አካል ትዕዛዝ ሲተላለፍ ስለመሆኑ	126017	የአርሲ ነገሌ ከተማ ፖሊስ ጽ/ቤት እና አቶ ተስፋአለም ገ/ሚካኤል	ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም.	358

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
69.	ተከሳሽ በሚያቀርበው ይግባኝ መነሻነት ቅጣትን በማክበድ መወሰን መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ *የወንጀል መ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 196(2*	131088	አቶ ጎይትኦም ግደይ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ሚያዝያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም.	362
70.	ዓቃቤ ህግ በቅድሚያ ያቀረበው ክስ ላይ ማስረጃዎቹን ካሰማና እንዲከላከሉ ታዞ የክሱ መሰማት በቀጠለበት ሂደት ላይ ያቀረበው ክስ ማሻሻል አቤቱታ ተቀባይነት ሲያጣ ይህንን በህጉ አግባብ በይግባኝ ከማሳረም በቀር ክሱን በማንሳት በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ማቅረብ ሥነ-ሥርዓታዊ ሥላለመሆኑ *የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 118/፣119፣38፣40/1/ እና 41፣*	127312	የአ/ብ/ክ/መ/ፍ/ቢሮ ዐቃቤ ህግ እና እነ አቶ እሸቱ ሉሌ ንጉሴ (አራት ሰዎች)	ግንቦት 23 ቀን 2009 ዓ.ም	367
71.	በአንድነት ተጣምረው መታየት የነበረባቸው የወንጀል ክሶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች በተወሰኑ ጊዜ እንደገና በአዲስ መልክ እያንዳንዱ ቅጣት ተሰልቶና የቅጣት ማቅለያዎች ሁሉ ታይተው የሚወሰን ሳይሆን ሕጉ ጥፋተኛው በፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ጊዜ ቢፈረድበት ኖሮ ሊወሰንበት ይችል ከነበረው ከፍተኛ ቅጣት ሳያልፍ መወሰን ያለበት ሥለመሆኑ	110736	አብዲ ኡመር ሰዒድ እና የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ	ሰኔ 23 ቀን 2009 ዓ.ም	372

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3)				
72.	በወንጀል ጉዳይ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ይግባኝ የሚጠይቅ አካል ሊከተላቸው ስለሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች *የወንጀል ሥነ- ሥርዓት ሕግ ቁጥር 187/1*	134834	የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቢ ሕግ እና እነ ሸዋነሽ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች)	ሰኔ 29 ቀን 2009 ዓ.ም	375
73.	ፍርድ ቤቶች በተከሳሽ ላይ የሚጣለው ቅጣት ከወንጀል አፈጻጸሙ ሆነ ባህሪዉ እንዲሁም ከተፈፀመው ወንጀል ክብደት አንፃር ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ መሠረት ለመወሰን የማያስችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ምክንያቱን በማስቀመጥ በመመሪያው ከተቀመጠው በተለየ መልኩ ቅጣት ሊወስኑ የሚችሉ ሥለመሆኑ *የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 21(1)* *የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2)*	122766	አቶ ሄኖክ ብሩክ አረጋ እና ፌዴራል ዓ/ህግ	ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም.	379
አፈፃፀም					393
74.	በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ተይዞ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ	124618	እነ ወ/ሮ ደብኳ መሰለ	ህዳር 22	394

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ንብረት ሁለት /ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በህብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት በሆነ ጊዜ ከተከፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ እንደሆነ የፍርድ ባለእዳው እንደቀረበ ተቆጥሮ የቀዳሚነት መብት የሚሰጠው ስለመሆኑ፣ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ. 443፣ የፍ/ብ/ሀ/ቁ. 126/1/፣ 1386-1409*		እና ሣጅን ሀይሉ ሞገስ	ቀን 2009 ዓ.ም	
75.	የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው የተባለ ንብረትን አፈፃፀምን በተመለከተ የንብረቱ ሕጋዊነት ላይ የሚመለከተው አስተዳደር አካል አግባብ ያለው ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ መሸጥ መለወጥ ባይቻልም ባለበት ሁኔታ የግራ ቀኙን እኩል ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አግባብ በጋራ የሚያስተዳድሩበት ወይም ተከፋፍለው የሚጠቀሙበት ወይም አከራይተው ጥቅሙን እኩል የሚከፋፈሉበት ሁኔታ መመቻቸት ያለበት ስለመሆኑ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 386/2/*	121565	ወ/ሮ ፍረወይኒ አብርሃ እና አቶ ገ/ጊዮርግስ ፀጋይ	ሚያዚያ 20 ቀን 2009 ዓ.ም	399
76.	ሁለት ባለዕዳዎች በአንድነትና በነጠላ አንድን ዕዳ እንዲከፍሉ ከተፈረደባቸዉ ባለገንዘቡ ገንዘቡ እንዲከፈለዉ ሁለቱን ባለዕዳዎች በአንድነት ወይም አንደኛዉን ባለዕዳ ሙሉ ገንዘቡን እንዲከፍል	118808	አቶ ደስታ ንጉሴ እና አቶ ሐየሎም በላይ	ሚያዚያ 30 ቀን 2009ዓ.ም	402

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሊጠይቅ የሚችል ሥለመሆኑ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ከሆኑት የፍርድ ባለእዳዎች አንዱ የፍርድ ባለዕዳ በዋናዉ ፍርድ ይግባኝ ጠይቆ የራሱን ኃላፊነት አስመልክቶ ፍርዱን አሽሮት ከሆነ ሙሉ እዳዉን ለመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ይግባኝ ሳይጠይቅ በመቅረቱ ዋናዉን ፍርድ ባልተሻረለት ወይም ይግባኝ ጠይቆ ፍርዱ በጸናበት ሰዉ ላይ የሚሆን ስለመሆኑ *ክፍ/ብ/ሕ/ቁ 1896፣ 1897*				
77.	በፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ ማናቸውም ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በሚወሰንበት ጊዜ የሚሸጠው ንብረት ከትክክለኛው የዋጋ ግምት አላግባብ ከፍ ወይም ዝቅ ተደርጎል ብሎ የሚያስበው ወገን የጨረታው ቀን ከመድረሱ በፊት የጨረታውን ትዕዛዝ ለሰጠው ፍ/ቤት ግምቱ ተጋኗል በማለት መቃወሚያ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሥለመሆኑ በሁለተኛው የጨረታ ማስታወቂያ በተወሰነው ቀን ተጫራች ያልቀረበ እንደሆነ ለጨረታ የቀረበውን ንብረት የፍርድ ባለገንዘቡ ተረክቦ እንዲይዝ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው የፍርድ ባለገንዘቡ	128776	አቶ ገ/ኢየሱስ ሃይሉ እና ዳዊት ልዑል	ግንቦት 16 ቀን 2009 ዓ.ም	407

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ንብረቱን ለመረከብ ፈቃደኛ ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 423/(1)(2)፣የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2*				
አእምሯዊ ንብረት					412
78.	በንግድ ምልክት መመሳሰል በአንድ ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ የሕዝብ ግንዛቤ ያዛባ ወይም ሊያዛባ የሚችል፤ በሁለት ድርጅቶች መካከል መሳከርን የሚፈጥር ከሆነ ሕብረተሰቡ ሊያገኝ የሚገባው ሕጋዊ ጥበቃና ዋስትና በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ በተመሳሳይ የንግድ ምልክት ላይ ምዝገባ እንዲደረግ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ *አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀፅ 7* አዋጅ ቁጥር 320/1995	104755	ዱራታ ባትሪ ካምፓኒ እና የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት	ህዳር 16 ቀን 2009 ዓ.ም	413
ልዩ ልዩ					417
79.	ፍርድ ቤቶች የሥም ይቀየርልኝ ጥያቄ በሚቀርብላቸው ጊዜ የአመልካችን ስም መለወጥ አስፈላጊ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን በማስረጃ አጣርተውና የሶስተኛ ወገን ጥቅም የማይጎዳ ለመሆኑ ጭምር ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን	120355	ወ/ሪት ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ እና የለም	ህዳር 6 ቀን 2009 ዓ.ም	418

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ *አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41/1/ /1/*				
80.	በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ አንድ ጠበቃ የጥቅም ግጭት ሊፈጥር በሚችልበት ሁኔታ የተለያዩ ተከራካሪዎችን በመወከል መከራከር የማይችልና ይዜንኑ ተግባር ፈፅሞ ሲገኝ እንደ ከባድ የሥነ -ምግባር ጥሰት ሊቆጠር የሚችል ስለመሆኑ *የኦሮሚያ ክልል የጠበቆች እና ሕግ ጉዳይ ፀሃፊዎች እና ፍቃድ አሰጣጥ አዋጅ ቁ. 182/2005 አንቀፅ 36(3)* *ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 10፣11፣12 እና 13*	110507	አቶ ጉታ ጫካ እና የኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ (ሁለት ሰዎች)	ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም	422
81.	አንድ ዳኛ ተግባሩን በሚያከናውንበት ወቅት የፍርድ ስራ ስህተት ተፈጽሟል ከተባለ በይግባኝ ፣ በሰበር ወይም በሌላ በህግ በተዘረጋ ስርዓት ከማሳረም በቀር ስልጣንን አላግባብ ተጠቅሟል በሚል ሊቀጣ የማይችል ስለመሆኑ፣	108692	የትግራይ ክልል ዓቃቤ ህግ እና አቶ ገብረሃርያ አሰፋ	ታህሳስ 4 ቀን 2009 ዓ.ም	428
82.	አንድ ጠበቃ ከጅምሩ የሕግ መሠረት የሌለዉና አዋጭ አለመሆኑ የተረጋገጠን ወይም ተከራክሮ የመርታት ዕድል የሌለዉ መሆኑን	128466	አቶ እንዳልካቸዉ ይላቅ እና	ሰኔ 29 ቀን 2009 ዓ.ም	431

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እያወቀ ደንበኛዉን አላስፈላጊ ለሆነ ክርክርና ወጪ መጋበዝ የሌለበት ስለመሆኑ አንድ ጠበቃ የጥብቅና አገልግሎት ዉል ከመዋዋሉ በፊት ማስረጃ ሰብስቦ ማጠናቀቅ ወይም ምስክሮችን አስቀርቦ መጠየቅና የሚያዉቁትን አስቀድሞ ማወቅ የሚጠበቅበት ሥላለመሆኑ *የደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4*		የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ሕግ		
83.	አንድን ጉዳይ በግልግል እንዲያይ የተቀመጠን የግልግል ዳኛ ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ እንዲነሳ ጥያቄ ሲቀርብ ዳኛው ገለልተኛ ወይም ነፃ ላይሆን የሚችልበት ግምት ለመውሰድ የሚያስችል ወይም ጥርጣሬን የሚፈጥር አከባቢያዊ ምክንያት መኖሩ ብቻ በቂ ሥለመሆኑ *የፍ/ሕ/ቁ. 3340(2)፣3342*	135094	አቶ ዳዊት በላይ እና እነ አቶ ደነቀ አበበ (ሁለት ሰዎች)	ግንቦት 21 ቀን 2009 ዓ.ም	436
84.	በጡረታ አበል ተጠቃሚ ሆኖ በወንጀል ጥፋት ምክንያት ከሦስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እስራት የተፈረደበት የዘለቄታ የጡረታ አበል መብቱን ያጣ ባለመብት የተሻሻለው የጡረታ አዋጅ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ ውዝፍ አበል ሳይጨምር የጡረታ አበል የማግኘት መብት	117151	የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ቸኮለ ሙሉጌታ	ህዳር 21 ቀን 2009 ዓ.ም	440

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የሚኖረው ስለመሆኑ፣ *አዋጅ ቁ. 907/2007 አንቀጽ 11/9*				
85.	በዕዳ አከፋፈል ሂደት የቀደምትነት መብትን ለመወሰን መታየት ያለበት ህጎች ከወጡበት ጊዜ አንፃር ሳይሆን በክርክሩ ለተያዘው ጉዳይ በልዩ ህግ /special law/ የተቋቋመው የቀደምትነት መብት ስለመሆኑ *የአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 11/12/ ፤ 57/(1)፤* *አዋጁ ቁጥር 97/1990*	122258	አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር እና የኤ.ፌ.ድ.ሪ የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የደቡብ ሪጅን ዕ/ቤት	ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም	444

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሥሪና ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 130685

ሕዳር 13 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወጋገን ባንክ -ነ/ፈጅ ቢንያም ትእግስቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አናጋው ገበየሁ -ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡የተጠሪ ክስ ይዘት በአጭሩ ከጥቅምት 02 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ ድርጅት ሥራ አሥኪያጅ ሆነው ሲሰሩ የነበረ እና መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ.ም በክሬዲት ቁጥጥር የሥራ ዘርፍ ተመድበው ሲሰሩ የነበረ መሆኑን፤አመልካች የተለያዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ ከሥራ ያሰናበታቸው ቢሆንም የጠቀሳቸው ምክንያቶች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን በመጥቀስ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪው የተሰናበቱት የብድር መያዣ የሆነውን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ በሚመለከተው አካል ሳይመረመር እና ሳይፈቀድ በመቀየራቸው፤ ከተቀመጠላቸው የብድር ወሰን በላይ በመበደራቸው፤እራሳቸው ተበዳሪ እንዲሁም ባንኩን በመወከል አበዳሪ በመሆን ውል በመዋዋላቸው ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ ጥፋታቸው ያለማስጠንቀቂያ የሚያሰናብታቸው በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው፤ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያም የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤት ተጠሪው ንብረት አጥፍተዋል በማለት አመልካች የተከራከረ ቢሆንም ተጠሪ አመልካቹ የጠቀሰውን የታግ ቁጥሩ WB/BU/CA/10-02-002 የሆነ ሠርቨር ሞኒተር አልተረከቡም በመሆኑም አመልካች ይህን አስመልክቶ የሰጠው ምክንያት ተቀባይነት የለውም፤በሌላ በኩል አመልካች የጠቀሳቸውን ሌሎች ጥፋቶች በተመለከተ አመልካች እነዚህ ጥፋቶች መፈጸማቸውን ያወቀው መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም ሆኖ ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ከ41 የሥራ ቀናት በኋላ ነው፤በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3 መሠረት አሠሪው ጥፋት መፈጸሙን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ በመብቱ ካልተጠቀመ ይርጋ የሚያግደው በመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነው፤ተጠሪው በሥልጣን አለአግባብ መጠቀም ድርጊት የፈጸሙት በተለያየ ጊዜ በመሆኑ እና በድርጅቱ የሰው ሀይል መመሪያ ቁጥር 3.2.2.2 መሠረት ሥልጣንን አለአግባብ መጠቀም ለሁለተኛ ጊዜ ሲፈጸም ከሥራ የሚያሰናብት በመሆኑ የተጠሪ የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ መቋረጡ ተገቢ ነው በመሆኑም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈል አይገባም በማለት አመልካች ለተጠሪው የካሣ ክፍያ ብር 82,572 / ሠማንያ ሁለት ሺህ አምሥት መቶ ሠባ ሁለት ብር /፤የሥራ ስንብት ክፍያ ብር 55,048 / ሀምሳ አምሥት ሺህ አርባ ሥምንት ብር / በድምሩ ብር 137,620 /አንድ መቶ ሠላሳ ሰባት ሺህ ሥድስት መቶ ሀያ ብር / እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታው ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-ተጠሪው የፈጸሟቸው ጥፋቶች የተፈጸሙት የሥራ መሪ በነበሩበት ወቅት ነው፤ይህንኑ በመጥቀስ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት መቃወሚያ ያቀረብን ቢሆንም ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ተጠሪ ከሥራ ሲሰናበት ሲሰራበት የነበረው የስራ መደብ ነው በማለት መቃወሚያችን ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፤የተጠሪን ጥፋት በተመለከተ የኢንስፔክሽን ሥራ የተሰራው መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም ቢሆንም ጉዳዩ ወደ ዲስፕሊን ኮሚቴ ተመርቶ የዲስፕሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ ያቀረበው ሚያዝያ 21 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ ተጠሪን የማሰናበቻ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ ተመልክተው መወሰን ሲገባቸው ይህን በመተላለፍ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪው ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ መልሳቸውን በጽሑፍ ሰጥተዋል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ ለስራ ውሉ መቋረጥ መንስኤ የሆነው ምክንያት የተፈጸመው ተጠሪ የሥራ መሪ በነበርኩበት ጊዜ ቢሆንም መፍትሔ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ተጠሪ ጥፋቱን የፈጸምኩ መሆን አለመሆኑ እና ጥፋቶቹ ከሥራ ለማሰናበት በቂ ናቸው? ወይስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደሉም? የሚለው ነው፤አመልካቹ ተጠሪን ከሥራ የማሰናበት መብቱም በይርጋ ቀሪ የሆነ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡አመልካቹም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ይህ ችሎትም ወደዋናው ጉዳይ ከመገባቱ በፊት ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የተጠሪን አቤቱታ አይቶ የማስተናገድ ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ ስላገኘነው ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች ለስንብቱ ምክንያት ያደረጋቸውን በተጠሪው ተፈጽመዋል የተባሉት ጥፋቶች የተፈጸሙት ተጠሪ የሥራ መሪ በነበሩበት ጊዜ መሆኑን ተጠሪ አልካዱም፤ተጠሪው ለዚህ ችሎት በሰጡት መልስም ይህንኑ አረጋግጠዋል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ለተጠሪ ስንብት ምክንያት የሆኑት ጥፋቶች ተጠሪ የሥራ መሪ በነበሩበት ወቅት የተፈጸሙ ሆኖ የተጠሪ የሥራ ውል ሲቋረጥ ተጠሪ በሠራተኛ የሥራ መደብ ላይ የነበሩ መሆናቸው ጉዳዩን በሥራ ክርክር ችሎት እንዲታይ ያደርገዋል? ወይስ አያደርገውም? የሚለው ነው

የአዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈጻሚነት በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ላይ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 3/2/ሐ በቅጥር ላይ በተመሠረተ ግንኙነትም ቢሆን አዋጁ በሥራ መሪ ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን ይደነግጋል፡፡ ከድንጋጌው ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የሥራ መሪው የሥራ መሪ ሆኖ ሥራውን ሲመራ በፈጸማቸው ማናቸውም ክንውኖች ምክንያት በተወሰደበት እርምጃ ሊያነሳቸው የሚችላቸው የመብት ጥያቄዎች የሥራ መሪው በሂደት ወደ ሠራተኛ የሥራ መደብ የተዛወረ ቢሆንም አዋጁ ተፈጻሚ ሊሆን እንደማይችል ነው፡፡ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ለመስጠት የቻለው ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በሠራተኛ የሥራ መደብ ላይ በነበሩበት ወቅት ነው በማለት እንደሆነ ግራቀኙ ካቀረቡት ክርክር መገንዘብ ችለናል፡፡ለተጠሪ የሥራ ስንብት ምክንያት የሆነው ጥፋት የተፈጸመው ተጠሪ የሥራ መሪ በነበሩበት ጊዜ በመሆኑ ተጠሪ የሥራ መሪ በነበሩበት ጊዜ በፈጸሟቸው ጥፋቶች ምክንያት የተወሰደባቸው እርምጃ ተገቢ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ማንኛውም የመብት ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችለው በፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች እንጂ በአሠሪ እና ሠራተኛ ሕጉ መሠረት አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሚያስችል የሥረ ነገር ሥልጣን ሳይኖረው ውሳኔ መስጠቱ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 23020 መጋቢት 21 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ173531 ሐምሌ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለተጠሪው የሥራ ስንብት ምክንያት የሆኑት ጥፋቶች የተፈጸሙት ተጠሪው የሥራ መሪ በነበሩበት ጊዜ በመሆኑ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕጉን መሠረት በማድረግ በሥራ ክርክር ችሎት ክስ ለማቅረብ አይችሉም፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎትም የተጠሪን አቤቱታ ተቀብሎ የማየት የሥረነገር ሥልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪው ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ክስ የማቅረብ መብታቸውን ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.119448

ታህሳስ 06 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-አዲስ ጋዝና ፕላስቲክ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ነ/ፈጅ ዘገየች ግደይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሰለሞን ኃይሌ የቀረበ የለም ... ከተባለ በኋላ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መቅረብ ምክንያት የሆነው በተጠሪ ክስ አቅራቢነት የተጀመረውን ክርክር ሲመለከት የቆየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከአሁን ተጠሪ ዕዳ አለብህ በማለት የቀነሱትን ብር 2,000/ሁለት ሺህ ብር/ ስርዓቱን ተከትለው የተቀነሰ ባለመሆኑ ለተጠሪ እንዲመልሱላቸው የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ተመልክቶ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች ጥቅምት 25 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ 02 ገጽ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

አቤቱታቸው ከሥር ፍርድ ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ ጋር ተገናዝቦ ከተመረመረ በኋላ ተጠሪው ሥራቸውን በራሳቸው ፈቃድ ሲለቁ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 31 መሠረት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጡ ሥራ በመልቀቃቸው በፈቃዳቸው አንድ ወር ደመወዝ ከከፈሉ በኋላ ከሌሎች ክፍያዎች ጋር ቀላቅለው የአንድ ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያን ጭምር በመጠየቃቸው ገንዘቡ እንዲመለስላቸው የተወሰነበት አግባብ ተጠሪ ባሉበት ሊጣራ የሚገባው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዝዘው መልስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ አግባብ ተጠናቋል እኛም ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ከተወሰነበት ነጥብ አንፃር ጉዳዩን በመመልከት አመልካች ከተጠሪ የቀነሱት ብር 2,000/ሁለት ሺህ ብር/ እንዲመልሱለት የተወሰነበት አግባብ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡ እንደመረመረነውም ለሰበር አቤቱታው መቅረብ ምክንያት የሆነው ብር 2,000/ሁለት ሺህ ብር/ የተጠሪ የወር ደመወዝ ሲሆን አመልካች የሚከራከሩት ተጠሪው በራሳቸው ፈቃድ ሥራ ሲለቁ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ መስጠት ከህግ የመነጨ ግዴታ እያለባቸው ይህንኑ ሳይፈፅሙ ሥራ በመልቀቃቸው የአንድ ወር ደመወዝ ያስከፈሏቸው መሆኑን ጠቅሰው አከፋፈሉም ተጠሪው አምነውበት በፈቃዳቸው ገቢ ያደረጉት ስለመሆኑ ይከራከራሉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በአመልካች ፋብሪካ ሲሰሩት የነበረው ሥራ በፈቃዳቸው የለቀቁት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከመሆኑም በላይ ገንዘቡን ገቢ ያደረጉት ተገደው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀናላቸው ይከራከራሉ፡፡ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክር ወቅት ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪ የአንድ ወር የማስጠንቀቂቂያ ጊዜ ሳይሰጡ ሥራ ስለለቀቁ አመልካች ቀንሰው ያስቀሩ ለመሆናቸው አስመዝግበዋል፡፡

በመሠረቱ አንድ ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ሥራ በሚለቅበት ጊዜ ለአሰሪው የሰላሳ ቀናት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ሊሰጥ እንደሚገባ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 31 ሥር የተደነገገ ሲሆን ሰራተኛው ይህንን ማስጠንቀቂያ ጊዜ ለአለመስጠቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ለሰራተኛው ከሚከፈለው ክፍያ ከሰላሳ ቀናት ክፍያ ያልበለጠ ካሳ ለአሰሪው ሊከፍል እንደሚገባም በአዋጁ አንቀፅ 45 ሥር ተደንግጓል፡፡ የዚህ ካሳ አከፋፈል ሰራተኛው ለአሰሪው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ያለመስጠቱ ሥልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ ካሳው ሲወሰን የሚከፈል መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ከሥር መዝገቡ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በተጠሪው በኩል በህግ የተቀመጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ እንዳልተሰጣቸው ያላረጋገጡ ከመሆኑም በላይ ገንዘቡን ቀንሰው ያስቀሩት ራሳቸው ለመሆናቸው አምነዋል፡፡ አመልካች ክክፍያዎቹ እንዲቀንስባቸው ያቀረቡት ፈቃድ ስለመኖሩም በጽሑፍ በተጠሪው ተፈርሞ የተረጋገጠ ማስረጃ በዚህ ረገድ ሥልጣን ለተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች አልቀረበም፡፡ ይልቁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያስመዘገቡት ተጠሪው የአንድ ወር ጊዜ ማስጠንቀቂያ ባለመስጠታቸው ብር 2,000/ሁለት ሺህ ብር/ ቀንሰን አስቀርተናል የሚል ነው፡፡ አሰሪው ከሰራተኛው ክፍያ ውስጥ የራሱን ጉዳይ ራሱ በመዳኘት ገንዘብ ቀንሶ ለማስቀረት የሚፈቅድ ግልፅ ህግ በሌለበት ሁኔታ አመልካች ለተጠሪው የሚከፈል ክፍያን ቀንሰው ማስቀረታቸው ተገቢነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ተጠሪው ከሚከፈላቸው ገንዘብ ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አከራካሪ የሆነው ገንዘብ እንዲቀነስ መስማማታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ተጠሪ በፊርማቸው ያረጋገጡበት ስነድ ሳይቀርብ ቀንሰው ያስቀሩትን ገንዘብ ለተጠሪው እንዲመልሱ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13531 ሐምሌ 15 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠውና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 155830 መስከረም 20 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፀናው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔው መፅናቱን አውቆ እንደ ፍርዱ እንዲያስፈፅም የዚህ ችሎት ውሳኔ ይተላለፍለት ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.132714

ታህሳስ 28 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ህትመት አሰፋ

አመልካች፡- ዶ/ር ደስአለኝ ተመስገን ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው በኢፌዴሪ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስተር አስተዳደር ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 041/2008 ቀን የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የመንግስት ሰራተኞችን የስራ ክርክር በይግባኝ አይቶ ሊያስተናግድ የሚችለው በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 በተሰጠው ስልጣን በአንቀጽ 2/1/ እና /3/ መሰረት አዋጅ ተፈፃሚ በሚሆንላቸው በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በቋሚነት ተቀጥረው ለሚያገለግሉ የመንግስት ሰራተኞች ብቻ በመሆኑ የአሁኑ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የፈጸሙት የስራ ውል በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አ/ቁ/ 515/99 አንቀጽ 22/3/ መሰረት ህዳር 09 ቀን 2000 ዓ/ም በወጣው የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች /ጊዜያዊ/ ኮንትራት ቅጥር አፈፃጸም መመሪያ አንቀጽ 10 መሰረት በመሆኑ የአመልካች ቅጥር ቋሚ ሳይሆን ኮንትራት ቅጥር ስለሆነ ጊዜያዊ ሰራተኛ ጉዳይ የማየት ስልጣን የለውም በማለት በብይን መዝገቡን ዘግይቶ ይህ ብይን በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 125278 በ22/10/2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት በመዕናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች የሠበር አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ይህንኑ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ጉዳይ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የተጀመረ ሲሆን የአሁን አመልካች ይግባኝ ባይ፣ ተጠሪ ደግሞ መልስ ሰጪ ሁኖ ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ይዘቱ ሲታይም፡- ከተጠሪ መስሪያ ቤት በቁጥር ገወ 3.9/3/53/08 በቀን ጥቅምት 08 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የተላለፈባቸውን የሥራ ስንብት ውሳኔ ያላግባብ የተሰጠ መሆኑን የሚዘርዝር ሁኖ ተጠሪ መስሪያ ቤት የሰጠው ውሳኔ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተሸሮ ወደ መደበኛ ስራቸው እንዲመለሱ፣ ከየካቲት 01 ቀን 2007 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 23 ቀን 2008 ዓ/ም ያልተከፈላቸው የወር ደመወዝ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎም አመልካች በዩኒቨርሲቲው ሴኔት "ሊጂስሌሽን" እንደ ስነ ምግባር ጉድለት የተጠቀሱትንና የፈጸሟቸውን ግድፈቶች ያመኑ በመሆናቸውና ከስነ ምግባር ግድፈት ጋር በተገናኘ ጉዳዩ በተጠሪ አጠቃላይ ቦርድ በጉባኤ ተመርምሮ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44(ኀ) መሰረት በቦርዱ የተሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ የማይችል መሆኑን፣ አመልካች በተጠሪው መስሪያ ቤት ሰራተኛ ቢሆኑም በመስሪያ ቤቱ ቋሚ ሰራተኛ ለመሆን በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 33(1) እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 210/2003 አንቀፅ 6 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተጠሪው መስሪያ ቤት ታህሳስ 16 ቀን 2005 ዓ/ም ባወጣው የቋሚ ቅጥር አፈፃፀም መስፈርቶችን አሟልተው ያልተገኙ መሆናቸውንና በተጨማሪም በየሁለት አመት በሚታደስ የኮንትራት ውል መሰረት የተቀጠሩ ሰራተኛ መሆናቸውን በመዘርዝር ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም በማለት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይም ተገቢ ነው ያለውን ክርክር አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር መርምሮ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የመንግስት ሠራተኞችን የስራ ክርክር በይግባኝ አይቶ ሊያስተናግድ የሚችለው በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 በተሰጠው ስልጣን በአንቀጽ 2/1/ እና /3/ መሰረት አዋጅ ተፈፃሚ በሚሆንባቸው በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በቋሚነት ተቀጥረው ለሚያገለግሉ የመንግስት ሰራተኞች ብቻ በመሆኑ የአሁኑ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የፈጸሙት የስራ ውል በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አ/ቁ/ 515/99 አንቀጽ 22/3/ መሰረት ህዳር 09 ቀን 2000 ዓ/ም በወጣው የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች /ጊዜያዊ/ ኮንትራት ቅጥር አፈፃጸም መመሪያ አንቀጽ 10 መሰረት በመሆኑ የአመልካች ቅጥር ቋሚ ሳይሆን ኮንትራት ቅጥር ስለሆነ ጊዜያዊ ሰራተኛ ጉዳይ የማየት ስልጣን የለውም በማለት በብይን መዝገቡን ዘግቷል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሠጠውን ብይን ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-በተጠሪ መ/ቤት በሚቀጠሩበት ጊዜ ከላይ ርዕሱ ኮንትራት ቅጥር ይባል እንጂ ለብዙ ጊዜ ለተለያዩ መ/ቤቶች ተጠሪው በፃፉቸው ደብዳቤዎች አመልካች ቋሚ የመንግስት ሰራተኛ መሆናቸውን በመግለጽ ተጠሪው ለተለያዩ መስሪያ ቤት ደብዳቤ ሲፃፍ የቆየ መሆኑን፣ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 33(1) ድንጋጌም የዩኒቨርሲቲ መምህራን ቅጥር በኮንትራት የሚፈፀም መሆኑን የሚያስገንዝብ ይዘትና መንፈስ የሌለው መሆኑን፣ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አግባብ ወጣ የተባለው የመንግስት ሰራተኞች የኮንትራት ቅጥር አፈፃፀም መመሪያም በጠቅላይ ሚኒስትሩ በቁጥር መ80-839/1 በተላለፈው መመሪያ መሰረት ቀሪ የሆነ እና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ታህሳስ 16 ቀን 2005 ዓ/ም በቁጥር ሲሰሚ.30/ጠ18/22/459 ባሰራጨው ደብዳቤ መሰረት በመንግስት መስሪያ ቤቶች የጊዚያዊ ቅጥር/ኮንትራት/ ለፕሮጀክቶች ብቻ የሚፈፀም እንጂ አመልካች ለተቀጠሩበት ስራ አይነት ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑን፣ አመልካች የተቀጠሩበት የሥራ ውል በጊዜ የተገደበ ቢሆንም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተላለፈው መመሪያና ከስራው ባህርይ የተነሳ ህጋዊ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን፣ ተጠሪ የአመልካችን የቋሚነት ቅጥር በመቀበል የጡረታ መዋጮ እየቆረጠ እንዲጠራቀምላቸው ሲያደርግ የቆየ መሆኑንና ሌሎች ነጥቦችን በመዘርዝር ቅጥሩ ቋሚ ቅጥር በመሆኑ አስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው ተብሎ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ቋሚ ሰራተኛ አይደሉም ተብሎ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበውን ጉዳይ የማየት ስልጣን የለውም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪ ተቋም የተቀጠሩት ከጥቅምት 12 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ በየ2/ሁለት/ አመት በሚታደስ ኮንትራት በባዮጂካል ኬሚካል ሳይንስና ቴክኖሎጂ ት/ቤት ውስጥ በረዳት ፕሮፌሰር የስራ ማዕረግ በወር ብር 5443.00 እየተከፈላቸው እንዲሰሩ የተቀጠሩ በቁጥር ሰሌዳ 25/6-1/05 ቀን ህዳር 19/2005 ዓ/ም ለአመልካቹ የተፃፈው ደብዳቤ ይዘቱ የሚያስረዳ መሆኑን፣ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ12/02/2005 ዓ/ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተደረገው የቅጥር ውል በአንቀጽ 4 የውሉ ጊዜ ከጥቅምት 12 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ጊዜ ፀንቶ የሚቆይ መሆኑን፣ በአንቀጽ 8 ውሉ የውሉን ጊዜ ማብቂያ ተከትሎ በጽሁፍ የሚታደስ መሆኑን፣ በአንቀጽ 9/1/ ዩኒቨርስቲው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እና ማስጠንቀቂያ ውሉን በማንኛውም በቂ ምክንያት የመሰረዝ መብት ያለው መሆኑን፣ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4/መ/ የውሉ ጊዜ ሲያበቃ ውሉ የሚቋረጥ መሆኑን፣ ለውሉ ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎችና የስልጣን ወሰን በኢትዮጲያ ህግ መሰረት የሚስተናገድ መሆኑን በመካከላቸው አለመግባባት በሚፈጠሩበት ጊዜ የኢትዮጲያ ፍርድ ቤት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በአንቀጽ 11 ስር በግልጽ መደንገጉን ነው፡፡ የአስተደዳር ፍርድ ቤት አመልካች ቋሚ አይደሉም በማለት ይግባኙቸውን ሳይቀበል የቀረውም ሆነ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንኑ የአስተዳደር ፍርድ ቤትን ብይን ያጸናው የቅጥር ውሉ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በተስማሙት መሰረት አስገዳጅነት እንዳለው፣ በዚህም ምክንያት ውሉ ከመነሻውም ቢሆን በተጠሪ መ/ቤት በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታውን መቅረብ ያለበት ለአስተዳደር ፍ/ቤት ሳይሆን ለመደበኛ ፍ/ቤት መሆኑን እንደሚያስረዳ፣ አመልካች ቅጥሩ ጊዜያዊ ሳይሆን ቋሚ ቅጥር ነው ሲሉ ለሚያነሱት ክርክር በማስረጃነት የሚጠቅሷቸውና ተጠሪ መ/ቤት ለተለያዩ ተቋማት የጻፏቸው ደብዳቤዎችም በራሪ ደብዳቤዎች ከመሆናቸው ውጪ በ12/02/2005 ዓ/ም የተፈጸመ ውል ወደ ቋሚነት የተሸጋገረ መሆኑን የሚያስረዳ ውል አመልካች አላቀረቡም የሚሉ ምክንያቶችን በማስፈር መሆኑን እንዲሁም የተጠሪ መስሪያ ቤት አመልካችን ሲያሰናብት በቦርዱ ውሳኔ መሰረት የሆኑት ምክንያቶች ከስነ ምግባር ግድፈቶች ጋር የተያያዙ እንጂ ቅጥሩ በሁለት አመት የጊዜ ገደብ በመወሰኑ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ የቅጥር ውል አለ ወይስ የለም? ከሚለው ነጥብ ጋር በተያያዘ የቅጥር ውል አፈፃፀምንና የቅጥር ውል አሰራረዝን አስመልክቶ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የቅጥር ዓይነት በሁለት ዓመት ጊዜ የተገደበ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ክርክር ያስነሳው የቅጥር ዓይነት በጊዜ የተገደበ እንደመሆኑ መጠን የአዋጅ ቁጥር 515/99 የተፈፃሚነት ወሰንን ለመለየት እንዲረዳ በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር "የመንግስት ሠራተኛ" ማለት በፌደራል መንግስት መ/ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሠራን ሠራተኛ ብቻ የሚመለከት በመሆኑና የአዋጁም ተፈፃሚነት ይኸው ቋሚ የመንግስት ሠራተኛ በዚሁ አንቀጽ 2(3) ሥር ከተመለከተው የመንግስት መ/ቤት ጋር በሚያደርጉት ክርክር ላይ የተወሰነ ነው በሚል የተቀመጠውን የአዋጅ ትርጓሜ መነሻ በማድረግ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትርጉም በዚህ ደረጃ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ሆኖም የሚያከራክራቸውን የቅጥር ሁኔታ በጊዜ መገደቡን ተመልክቶ የአሁን አመልካች የኮንትራት ሠራተኛ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 2(2) "ጊዜያዊ ሠራተኛ" ማለት በመንግስት መ/ቤት ውስጥ የዘላቂነት ባህሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌለው ሥራ ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው የሚል ትርጓሜ በማስቀመጥ አዋጁ በእነዚህ ጊዜያዊ ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ሊሆን እንደማይችል በአንቀጽ 2(1) የተመለከተውን የአዋጁን የተፈፃሚነት ወሰን በሚያጠናክር ሁኔታ ከተደነገገና ይህንኑም ይበልጥ ግልፅ በማድረግ በአንቀጽ 3 ላይ የአዋጁ የተፈፃሚነት ወሰንን በመንግስት መ/ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ በሚሠራ የመንግስት ሠራተኛ ላይ ብቻ እንደሆነ ካስቀመጠ በኋላ ጊዜያዊ ሠራተኞች በዚህ አዋጅ ሊካተቱ የማይችሉ መሆኑን በመደንገግ ሳይገደብ በአዋጁ አንቀጽ 22 ሥር በአዋጅ የሚገዛ የመንግስት መ/ቤት ከቋሚ የመንግስት ሠራተኛ ባሻገር ጊዜያዊ ሠራተኛን መቅጠር የሚችልበትን ሁኔታ በንዑስ ቁጥር 1 ለይቶ ከደነገገ በኋላ በዚህ አካኋን በመንግስት መ/ቤት የሚቀጠሩ ጊዜያዊ ሠራተኞች አቀጣጠር ስለሚኖራቸው መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም ስለሚጠበቅላቸው የሥራ ሁኔታዎች ዝርዝር መመሪያ ሊወጣ የሚችል መሆኑንም ሁሉ አካቷል፡፡ እንደዚሁም ይህን አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን በሚኒስትሮች ም/ቤት እነዚህን ደንቦች ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎች በኤጀንሲው አማካኝነት ሊወጡ እንደሚችሉም በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 93 የተመለከተ በመሆኑ በአንቀጽ 22 እና በአንቀጽ 93 መሠረት ጊዜያዊ ሠራተኞችን የሚመለከት ዝርዝር ደንብና መመሪያ እንደሚወጣ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት በአንቀጽ 2(2) ስለ ጊዜያዊ ሠራተኛ የተሰጠውን ትርጓሜ መነሻ በማድረግ፣ በአንቀጽ 22 እንደ ተመለከተው የመንግስት መ/ቤት ጊዜያዊ ሠራተኛን መቅጠር የሚችልበትን አግባብ አስመልክቶ በአዋጁ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 22 (3) እና አንቀጽ 93 መሠረት በሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በህዳር ወር 2000 የወጣውን የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሠራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ መውጣቱ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መመሪያ በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚፈጸመውን የጊዜያዊ ቅጥር ስርዓቱን ዘርግቶ የነበረ ሲሆን በመመሪያው በጊዜያዊ ቅጥር የተቀጠሩ ሰራተኞች ወደ ቋሚነት እንዲሸጋገሩና ጊዜያዊ ቅጥር ለ"ፕሮጀክት" ስራዎች ብቻ እንዲሆንና በዚሁ አግባብ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕብሊክ የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ/ም በቁጥር መ80-839/1 ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የፃፈ መሆኑን፣ የሲቪል ሲርቪስ ሚኒስቴርም ይህንኑ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት የተላከውን መመሪያ መነሻ በማድረግ በቁጥር ሲሰሚ30/መ/18/22/459 በ16/04/2005 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ በመስሪያ ቤት በጊዜያዊነት የተቀጠሩት ሰራተኞች ወደ ቋሚ ሰራተኝነት የሚመደቡበትን አግባብ በመመዘርዘር ከደብዳቤው በኋላ በማንኛውም የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት እጅግ አስፈላጊ ለሆኑና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር እየቀረበ ተቀባይነት ማግኘቱ መረጋገጥ ያለበት መሆኑን በመግለጽና ከዚህ ውጪ በማንኛውም መልኩ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈፀም ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑን የሚያሳይ መመሪያ አስተላልፏል፡፡ በመሆኑም የፐብሊክ ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤትም ሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ ያስቀመጡት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው በሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በህዳር ወር 2000 የወጣውን የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሠራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሲሆን በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚፈፀም የጊዜያዊ ቅጥር ውል በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሲሰሚ30/መ/18/22/459 በ16/04/2005 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ አግባብ መፈጸሙ ካልተረጋገጠ ሕጋዊ ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡

የአሁን ተጠሪ ዩኒቨርሲቲ አጥብቆ የሚከራከራው በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 33(1) እና በደንብ ቁጥር 210/2003 አንቀጽ 6 አግባብ በዩኒቨርስቲው ሰኔት በወጣው ሌጂስሌሽን መሰረት ቅጥሩ በየሁለት አመት የሚታደስ መሆኑ ሕጋዊ ነው፣ ስንብቱም ጊዜውን ጠብቆ የተደረገ ነው በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በተጠሪው ቦርድ ለአመልካች ስንብት ምክንያት የሆነው የቅጥር ጊዜ ማብቃቱ ሳይሆን በአመልካች በኩል ተፈጸሙ የተባሉ የስነ ምግባር ግድፈቶች ከመሆናቸው በላይ የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀፅ 33 (1) አግባብ ቋሚ ቅጥር የሚፈፀመበት አግባብ በዩኒቨርሲቲው እና አመልካችን ከመሰሉ መምህራን ጋር የሚፈጸመው ቅጥር ጊዚያዊ ቅጥር ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ የአሁን ተጠሪ ዩንቨርሲቲ በማስተማር ሙያ ጊዜን ወስኖ ከመምህራን ጋር የቅጥር ውል የሚፈጸመው የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥና በዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የታነፁ ምሩቃንን ለማፍራት የሚያስችል አቅም ያለውን መምህር መሆኑንና አለመሆኑን ለመፈተሽ እንዲረዳው ሲባል ስለመሆኑ ከራሱ ከዩኒቨርስቲው ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 216/2003፣ ለዩኒቨርስቲው በደንብ ቁጥር 210/2003 አንቀጽ 6 በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በወጣው የዩኒቨርሲቲው "ሌጂስሌሽን"ም ሆነ ከከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 በአዋጅ ቁጥር 861/2006 እንደተሻሻለው፤ የተመለከተውን ግብና አላማ በማገናዘብ መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም ቢሆን በሥር ፍ/ቤት የቅጥሩ ሁኔታ በዩኒቨርሲቲው ሌጂስሌሽን አንቀጽ 61 መሰረት ቋሚ አይደለም፤ ቅጥር በዚሁ ደንብ መሰረት የተፈፀመ አለመሆኑ እስከ ተረጋገጠ ድረስ ሊሰረዝ የሚችል ነው በሚል አዋጁን፣ደንቡንና የዩኒቪርሲቲውን "ሌጂስሌሽ"ን ጠቅሶ መከራከሩና ቅጥሩ በጊዜ ተገድቦ እንዲፈፀም መደረጉ በእራሱ ብቻውን ይህ አመልካች ጊዚያዊ /የኮንትራት/ ሠራተኛ ነው በሚለው አቋም ሥር ሊወድቅ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በዚህ በተያዘው ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው የቅጥር ውል በሁለት ዓመት ጊዜ ተገድቦ የመደረጉ እውነታ ለትምህርት ጥራት ስኬት ሲባል ቅጥሩ ሊቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ታስቦ የተደረገ ነው ካልተባለ በስተቀር የተቆረጠው ጊዜ በእራሱ የቅጥሩ ሁኔታ ጊዜያዊ መሆኑን ጠቋሚ ሆኖ ጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሠራተኞች በሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትርጓሜ ሥር የሚሸፈን ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 515/ 1999 በወጣው የጊያዚያዊ ቅጥር አፈጻጸም መመሪያና ይህንኑ መመሪያ በተመለከተ ቀጥሎ በተዘረጋው ስርዓት አግባብ ሊገዛ የሚችልበት ሁኔታ የሌለ ሁኖ አግኝተናል፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቅጥር ውል ስለጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሠራተኞች ቅጥር አፈፃፀም በወጣው መመሪያ መሠረት ሊሆን ይገባል ብሎ ለመደምደም እንደማያበቃ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አግባብ ህዳር 2000 ዓ/ም በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ወጥቶ የነበረውና በኋላም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚስቴር ጽ/ቤት በቁጥር መ80-839/1 በተላለፈው መመሪያ መነሻ ቀሪ የሆነ እና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ታህሳስ 16 ቀን 2005 ዓ/ም በቁጥር ሲሰሚ.30/ጠ18/22/459 ባሰራጨው ደብዳቤ መሰረት በመንግስት መስሪያ ቤቶች የጊዚያዊ ቅጥር/ኮንትራት/ ለፕሮጀክቶች ብቻ የሚፈፀም እንጂ አመልካች ለተቀጠሩበት ስራ አይነት ተፈጻሚነት የሌለው ስለመሆኑ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ይግባኝ ይህ ችሎት በመ/ቁጥር 98435 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) በየትኛውም ፍርድ ቤት የሚገኝ የዳኝነት አካል የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ከመስጠቱና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ከተመለከተው ፍትህ የማግኘት መብት አንፃር ሁሉ ሲታይ ጉዳዩ በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ አዋጅ ቁጥር 515/99 አግባብ በተዘረጋው የይግባኝ ስርዓት ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ቅጥሩ በጊዜ መገደቡን ብቻ በማየት የአመልካችን ይግባኝ ውድቅ ማድረጋቸው ሕጋዊ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የውሉን ቆይታ ጊዜ በተመለከተ ቅጥሩ ሕጋዊ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጻሚነት አለው ተብሎ የተያዘው የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ከላይ የተዘረዘሩትን ሕጋዊ ምክንያቶችን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 የተቀመጠው በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋይ ወገኖች የአስገዳጅነት ኃይል አላቸው የሚለው ድንጋጌ በቅድሚያ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ)፣1711 እና 1716 ስር ስለህጋዊ ውል አመሰራረት የተቀመጡትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቅጥር ውል ጊዚያዊ/ኮንትራት ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 650/2001 በአዋጅ ቁጥር 861/2006 እንደተሻሻለው ከአንቀፅ 30 እና 33 ጣምራ ንባብና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በመምህራን መካከል የሚደረጉ ውሎች በየሁለት አመት እንዲታደሱ ከሚደረገበት መሰረታዊ ዓላማ፣ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አግባብ ሕዳር 09 ቀን 2000 ዓ/ም ወጥቶ የነበረው የጊዚያዊ ቅጥር ውል አፈጻጸም መመሪያ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚስቴር ጽ/ቤት በቁጥር መ80-839/1 በተላለፈው መመሪያ መነሻ በከፊል ቀሪ ከመሆኑና በሕግ ጥበቃ ሊሰጣቸው የሚገባቸው ውሎች በህጉ አግባብ የተቋቋሙ ናቸው ከሚለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት የተገነዘብን በመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 041/2008 ቀን የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 125278 በቀን 22/10/2008 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙ የተከራከሩበትን የቅጥር ውል አፈፃፀም ሆነ የቅጥር ውል አሰራረዝ በሚመለከት በየፊናቸው ያቀረቡትን ክርክር ማስረጃ ለጉዳዩ ተፈፃሚ መሆን ከሚገባው ህግና ደንብ አንፃር በማየት ተገቢውን ዳኝነት መስጠት ይቻል ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት መልሰናል ፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ውጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.136981

ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፦ አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች ፡- የሀረር ቢራ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር.....አልቀረበም

ተጠሪዎች ፡- 1.አቶ ዓለሙ ነጋሽ

2. አቶ ሙሉቀን ከበደ

3. አቶ ተስፋዬ ማኮ

4. አቶ መለሰ ሸምታጋ

5. ወ/ሮ ጽጌ አክሊሉ

6. አቶ እሸቱ በየነ

7. አቶ አገሳ ዋቅጅራ

8. አቶ ተስፋዬ ደስታ

9. አቶ ፀጋዬ ሚደቅሳ

10. አቶ አበበ አያሌው

11. አቶ አብዲሳ ታደ

12. አቶ ገ/ሥላሴ ገሠሠ

13. አቶ ብርሃኑ ዘፈሩ

14. አቶ መኮንን ጌታሁን

15. አቶ ጌታቸው ለማ

16. አቶ ተሰማ ተማም

17. አቶ ይታገሱ ሳህሌ

18. አቶ ገ/ማርያም በርሄ

19. አቶ ኤልያስ ይሌ

20. አቶ በዜ አባትሁን

21. አቶ አስናቀ ታደሰ

22. ወ/ሮ የሽምነሽ አድነው

23. አቶ መላኩ መር

24. ወ/ሮ አልማዝ ገ/ማርያም

25. አቶ ሰንበቶ ባይሳ

26. አቶ ቡልቱማ ጉታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

27. ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ	28. አቶ አሰፋ መርጊያ
29. አቶ አለነ አሞኘ	30. አቶ ማስረሻ ገ/አምላክ
31. አቶ መስፍን ግርማ	32. አቶ ገበየሁ አዛለ
33. አቶ አስማማው አንተነህ	34. አቶ ገመቹ ዓለሙ
35.አቶ ባቱ ቶሎሳ	36 አቶ መንግስቱ ግርማ
37. አቶ ፍቃዱ ደበሌ	38. አቶ ዘነበ ፍኔ
39. አቶ አበበ መዘምር	40. አቶ ኃይሌ አክሊሉ
41. አቶ ዘውዴ ፍንታዬ	42. አቶ አብደላ ቃሲም
43. አቶ ፍቃደ ኃይሌ	44.አቶ ሲሣይ መኮንን

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ ::

ፍ ር ድ

ጉዳዩ፡- ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ የደመወዝ ጭማሪን መሰረት ያደረገ ክርክር ነው ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪዎች የነበሩት የስር ከሳሾች 1ኛ. በአሁን አመልካች፣ 2ኛ. በሀረር ቢራ አክሲዮን ማህበር መሰረታዊ ሰራተኛ ማህበር እና 3ኛ.በሀረር ቢራ አክሲዮን ማህበር ብድር እና ቁጠባ ላይ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በሀረሪ ክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፍርድ ቤቱም የከሳሾችን ክስ እና የቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ ከሳሾች በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ያቀረቡትን ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ 40 ፐርሰንት ደመወዝ ጭማሪ ተጨማሪ ክፍያ እና የኢንሹራንስ ክፍያ ክሱ የቀረበው የስራ ውላቸው ከተቋረጠ ከ6 ወር በኃላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል፡፡ ሲል በ2ኛ እና በ3ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበውን ክስ አስመልክቶ በግራ ቀኙ መካከል የስራ ውል ግንኙነት የሌለ ስለሆነ ጉዳዩ በግልጽ የፍትሀብሄር ክርክር በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለከፍተኛው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም ቅሬታው መልስ ሰጪን ያስቀርባል በማለት አስቀርቦ ካከራከረ በኃላ በ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ ላይ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት እና በ1ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበውን ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት በፍሬ ነገር አከራክሮ እንዲወስን ለስር መጀመሪያ ደረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት መልሶ ልኮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ህግ አግባብ የተቋቋመ የሰበር ስርአት ስለሌለ ችሎቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች ለዚህ ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታን ያቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ድርጅት ነ/ፈጅ ጥር 3 ቀን 2009 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአጭሩ ክሱ በይርጋ ይታገድ ይገባው እንደነበር እና የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይርጋ ክርክሩን ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት መሠረታዊ የሕግ ትርጉም ስሕተት የተፈፀመበት ስለመሆኑ በማብራራት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡ የሰበር አጣሪው አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ የአመልካች ድርጅት ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ የታለፈበትን አግባብ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ የተጠሪዎች ወኪል ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም የጽሑፍ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካች የመልስ መልስ ለመስጠት ያለመፈለጉን በመግለጽ ያላቀረበ ስለሆነ የመልስ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም የተያዘውን ጭብጥ ከሕጉ አንፃር አገናዝበን መርምረናል፡፡ ከፍ ሲል በዝርዝር እንደተመለከተው በአመልካች እና ተጠሪዎች መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው ግንቦት 3 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑ እና ክስ የቀረበው መጋቢት 17 ቀን 2006 ዓ.ም መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ክስ የሥራ ውላችን ሲቋረጥ በስምምነት ከስራ ለሚለቅ ሰራተኛ ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ጋር የደመወዙን 100 ፐርሰንት ለመክፈል አሰሪው ስምምነት አድርጎ የተከፈለን ቢሆንም የስራ ውላችን ከተቋረጠ በኃላ ታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም ጀምሮ በስምምነት ከስራ ለሚለቅ ሰራተኛ ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ጋር የደመወዙን 140ፐርሰንት ለመክፈል አሰሪው ስምምነት ላይ መድረሱን በመግለጽ ሊከፈለን የሚገባ የደመወዝ ጭማሪ 40 ፐርሰንት እና የኢንሹራንስ ክፍያ እንዲከፈለን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ልዩ ልዩ የመብት ጥያቄዎችን አስመልክቶ ክሱ መቅረብ ያለበትን የጊዜ ገደብ ወስኗል፡፡

የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት የሥራ ውል ከተቋረጠበት ከግንቦት 3 ቀን 2005 ዓ.ም ክስ እስከቀረበበት መጋቢት 17 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ ስድስት ወር ያለፈው መሆኑን በመግለጽ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(4)ን በመጥቀስ ሲሆን የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ክርክሩ በይርጋ አይታገድም በማለት ውሳኔ የሰጠው የደመወዝ 40 ፐርሰንት ጭማሪ እና የኢንሹራንስ ክፍያ የይርጋ ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

162(1) መሰረት በ1 አመት ይርጋ የሚቋረጥ መሆኑን እና የተጠሪዎች ክስም የቀረበው የስራ ውሉ ከተቋረጠ አንድ አመት ሳይሞላው ነው በማለት መሆኑን ከስር መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(4)ን ስንመለከት የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ የስራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የተጠሪዎችን የክስ ይዘት ስንመለከት ደግሞ የስራ ውላችን ግንቦት 3/2005 ከተቋረጠ በኃላ ታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም ጀምሮ ለሚወጡ ሰራተኞች አመልካች ለመክፈል የተስማማው የደመወዝ ጭማሪ ለኛም ሊከፈለን ይገባል የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡበት መብት ተቋቁሟል የሚሉት የስራ ውላቸው ከተቋረጠ ከ7ወር በኃላ አመልካች ከስራ ለሚለቁ ሰራተኞች የደመወዝ ጭማሪ አድርጓል በሚል መሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ መሆኑ ከተረጋገጠ የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት የተቋቋመ የመብት ጥያቄ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪዎች መብት ከስራ ውል መቋረጥ የመነጨ ነው በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሶ የአዋጁን አንቀፅ 162(4)ን በመጥቀስ ክርክሩ በ6 ወር ይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊና ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይልቁንም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀጽ 162(1) መሰረት ከቅጥር ውል በመነጨ ግንኙነት የሚጠየቅ ማንኛውም ክስ በ1 አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በመጥቀስ እና የተጠሪዎች የስራ ውል ከተቋረጠበት ክስ እስከቀረበበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ 1አመት የማይሞላው መሆኑን በመግለጽ የተጠሪዎች ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሶ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ አዋጁ ለይርጋ አቆጣጠር በምክንያትነት የደነገገውን መስፈርት መሰረት ያደረገ በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ነገር ግን አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርገው የሚቀርቡ ክሶችን የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር በተመለከተ በአዋጁ በተለየ አኳኃን ካልተገለጸ በቀር የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው መብትን ለመጠቀም ከሚቻልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 163(1) ስር የተደነገገ ከመሆኑ በተጨማሪ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 51912 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

የስር ሁለቱም ፍርድ ቤቶች ማለትም መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ክርክሩ በይርጋ የሚታገደው ክሱ በ6ወር ጊዜ ውስጥ ባለመቅረቡ ነው በማለት እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ክሱ በይርጋ የማይታገደው በ1 አመት ጊዜ ውስጥ የቀረበ ስለሆነ ነው በማለት የይርጋ ጊዜውን በማስላት መደምደሚያ ላይ የደረሱት የስንበት ደብዳቤው ለተጠሪዎች ተሰጥቷል ከተባለበት ከ03/09/2005 ዓ.ም ጀምሮ በመቁጠር ስለመሆኑ የውሳኔው ይዘት ያመለክታል፡፡ይሁን እንጂ ለተጠሪዎች የስንብት ደብዳቤው በ03/09/2005ዓ.ም የተሰጣቸው ቢሆንም ተጠሪዎች ለክሳቸው መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያደረጉት ታህሳስ ወር 2006ዓ.ም ጀምሮ በስምምነት ከስራ ለሚለቅ ሰራተኛ ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ጋር የደመወዙን 140 ፐርሰንት ለመክፈል አሰሪው ስምምነት ላይ መድረሱን እና በዚህ መሰረት ክፍያ መፈጸሙን በመግለጽ መሆኑን ተጠሪዎች በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክስ ይዘትም ሆነ ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት የተቻለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የስንብት ደብዳቤው ለተጠሪዎች ተሰጥቷል ተብሎ በተጠሪዎች የተገለጸውን ግንቦት 03 ቀን 2005 ዓ.ም ለይርጋ ጊዜው አቆጣጠር የመነሻ ቀን አድርገው መውሰዳቸው ይልቁንም ተጠሪዎች ከስራ የተሰናበቱት በ3/9/2005 ጀምሮ ቢሆንም ተጠሪዎች ሊከፈለን ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡት ታህሳስ 6 ቀን 2006 ዓ.ም የተደረገ የደመወዝ ጭማሪን መሰረት ያደረገ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 163(1) በተመለከተው መሰረት ለይርጋ ጊዜው አቆጣጠር የመነሻ ቀን ተደርጎ መወሰድ የሚገባው በስምምነት ከስራ ለሚለቁ ሰራተኞች ደመወዝ ጭማሪው ክፍያ 140 ፐርሰንት እንዲሆን ከተወሰነበት ከታህሳስ 6 ቀን 2006 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት መጋቢት 17 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ደግሞ አንድ(1)አመት የማይሞላው በመሆኑ ተጠሪዎች ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄ በአዋጁ አንቀጽ 162(1) መሰረት በይርጋ የሚታገድ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የሀረሪ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠውን ውሳኔ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሻር ክርክሩ በይርጋ አይታገድም በማለት እና የፍሬ ነገር ክርክሩን አከራክሮ እና አጣርቶ እንዲወስን ለስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ የሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሀረሪ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 40519 በ9/12/2006ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሀረሪ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12532 በ18/8/2008ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1)መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የተጠሪዎች የክፍያ ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162(4) መሠረት በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የውሳኔው ግልብጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷልወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 140781

ሐምሌ 18 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ታደሰ እንጆሪ ሆቴልና ጠቅላላ ንግድ ስራ ኃ.የተ.የግል ማህበር -ነ/ፈጅ ይሁንልኝ ቡሎ- ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ሉላ ዘሪሁን - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ በሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ ለሪቬኒ ሂሳብ ስራ መደብ በቋሚነት ተቀጥረው ከአርባ አምስት ቀናት በላይ በስራ ላይ ከቆዩ በኋላ አመልካች ድርጅት ከህግ ውጪ የሥራ ውላቸውን ያቋረጠባቸው መሆኑን ገልጸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪን የሙከራ ጊዜ ሲጠናቀቅ ያሰናበታቸው በመሆኑ እርምጃው ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የሐዋሳ ከተማ መ/ደ/ፍ/ቤትም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደረገ በተባለው የስራ ቅጥር ውል ላይ ያለው የተጠሪ ፊርማ የተባለው በተጠሪ በመካዱ ምክንያት በባለሙያ እንዲመረመር አድርጎ ውጤቱ እንዲቀርብ በማድረግና የግራ ቀኙን ምስክሮችን በመስማት ፍሬ ነገሩን ከአጣራ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የቅጥር ውል ያቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል በማለት የክፍያዎችን አይነትና መጠናቸውን ለይቶ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የተቀጠሩት ለመከራ ጊዜ ሁኖ የመከራ ጊዜ ሲጠናቀቅ እንዲሰናበቱ መደረጉ ከሕግ ውጪ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ26/09/2008 ዓ/ም የተደረገው የቅጥር ውል ተጠሪ ለመከራ ጊዜ የተቀጠሩ ስለመሆኑ የሚያሳይ አለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ ለመከራ እንደተቀጠሩ ተቆጥሮ የአርባ አምስት ቀን ጊዜ ሲያልፍ የሥራ ውሉ መቋረጡ ተገቢ ነው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለትና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(3) ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ የአርባ አምስት ቀን ጊዜ ከአለፋቸው በኋላ መሰናበታቸው በሕጉ አግባብ ሁኖ እያለ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በዚህም መሰረት በጉዳዩ ላይ ምላሽ የሚያሻውም የጉዳዩ መሰረታዊ ጭብጥ አመልካች ተጠሪን ከሥራ ማሰናበቱ በሕጉ አግባብ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የቅጥር ውል የተደረገው ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ/ም ስለመሆኑና በዚህ የቅጥር ስምምነት ላይ ቅጥሩ የመከራ ጊዜ ያለው ስለመሆኑ የተስማሙበት አግባብ የሌለ መሆኑን ተጠሪ ጠቅሰው የሚከራከሩ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ቅጥሩ በ01/10/2008 ዓ/ም ተደርጎ ስንብቱ በአርባ ሶስተኛው ቀን በ13/11/2008 ዓ/ም የተደረገ ስለመሆኑና በዚህ ጊዜ ደግሞ አሰሪው ሰራተኛውን በማናቸውም ምክንያት ማሰናበት እንደሚችል ሕጉ መብት የሰጠው መሆኑን ገልጾ ተከራክሮ የሥር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል የቅጥር ውሉ የተደረገበትን ጊዜና በ01/10/2008 ዓ/ም ተደረገ በተባለው ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ መሆን ያለመሆኑ ላይ ክርክር በመነሳቱ ምክንያት ፊርማው እንዲመረመር አድርጎ በሰነዱ ላይ ያለው ፊርማ ከተጠሪ ፊርማ ጋር የማይመሳሰል መሆኑን በባለሙያ ተረጋግጦ ያቀረበለት ከመሆኑም በላይ የግራ ቀኙን ምስክሮችን ሰምቶ የተጠሪ ማስረጃዎች ክብደት ሊሰጣቸው የሚገባ መሆኑን በመግለጽ የአመልካች የሥራ ስንብት እርምጃ ሕገ ወጥ ነው በማለት መወሰኑን፣ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ደግሞ ስንብቱ በሕጉ በተመለከተው የመከራ ጊዜ ውስጥ የተከናወነ በመሆኑ ህጋዊ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት የወሰነ ቢሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የሙከራ ጊዜ እንዲኖር የተደረገ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ አመልካች ተጠሪን ከአርባ አምስተኛው ቀን በፊት አሰናብቼአለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ የለም በማለት የወሰነ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

አንድ ሠራተኛ ሊመደብበት ለታቀደው ቦታ ተስማሚ መሆኑና አለመሆኑን ለመመዘን ለሙከራ ጊዜ ሊቀጥር እንደሚችል፤ይህ የግራ ቀኙ ስምምነትም በጽሑፍ መደረግ እንዳለበት፤ የሙከራ ጊዜውም ከ45 ተከታታይ ቀናት መብለጥ እንደሌለበት ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(1) ፣(2) እና (3) አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ የሙከራ ጊዜ ቅጥር ሲፈፀም ሰራተኛው በግልጽ ሊያውቀው የሚገባው ጉዳይ ሲሆን የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ስምምነት ከተደረሰም ስምምነቱ በጽሑፍ ሁኖ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ የተደረገ የሙከራ ጊዜ ስምምነት መኖሩ ከተረጋገጠ አሰሪው ሰራተኛውን ለተቀጠረበት የሥራ መደብ ተስማሚ አለመሆኑን ካመነበት የቅጥር ውሉን ያለምንም ማስጠንቀቂያ የማቋረጥ መብት ሕጉ የሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አሰሪው ይህንኑ በሕጉ የተቀመጠውን መብቱን ሊጠቀም የሚችለው አሰሪው ሰራተኛውን ለሙከራ ጊዜ ለመቅጠር ወስኖ ሰራተኛውም ይህንኑ በግልጽ አውቆትና ተገንዝቦት በፅሑፍ ያሰፈሩት ስምምነት መኖሩ ከተረጋገጠ ብቻ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች ተጠሪን በ43ኛው ቀን ያሰናበታቸው ስለመሆኑ ቢረጋገጥም ለሙከራ ጊዜ የቀጠራቸው ስለመሆኑና በዚህ ረገድም ተጠሪ የሚያውቁት ውል መኖሩን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች አላረጋገጡም፡፡ ይልቁንም አመልካች አለኝ የሚለውና የተጠሪ ፊርማ ተቀምጦበታል በተባለው ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ በባለሙያ እንዲመረመር ተደርጎ ፊርማው የተጠሪ ያለመሆኑና አመልካች ያቀረበው ይኼው ሰነድ ከሌሎች የተጠሪ ማስረጃዎች ጋር ሲመዘን የማስረጃነት ክብደት ሊሰጠው የማይገባ መሆኑ መረጋገጡን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ ለሙከራ የተቀጠሩ በመሆኑ ያለምንም ማስጠንቀቂያ የማቋረጥ መብት አለኝ በማለት የሚያቀርበው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 11(3) ስር የተቀመጠውን ድንጋጌ ሙሉ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚያስችል ጥፋት የፈፀመ ስለመሆኑ አመልካች ገልጾ የሚያቀርበው ክርክርም ስንብቱ የሙከራ ጊዜ ውስጥ የተከናወነ ነው በማለት ከሚያቀርበውና ሕጋዊ ካልሆነው ክርክሩ ጋር አብሮ የማይሄድና በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የወረዳው ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስንብቱ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(3) ድንጋጌን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላገናዘበ መሆኑን በመጥቀስ የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ማፅናቱ የሚነቀፍበትን የሕግ አግባብ ስለሌለ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 06177 በ29/02/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 09913 በ03/08/2009 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ ነው ተብሎ ብር 16,522.00 (አስራ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሁለት ብር) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ተብሎ በተወሰነው ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በ19/08/2009 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 138054

ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የላሊበላ ማር መዝሃም - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ማሬ በዛ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአማራ ብ/ክ/መ/ የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ የነበረ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበረች፡፡ የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘት በአመልካች ድርጅት ከመስከረም 2004 ዓ.ም ጀምሮ በቀን ብር 45.00 /አርባ አምስት / እየተከፈላት እየሰራች እያለ መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ.ም ያለአግባብ ከስራ ስላሰናበተኝ የስንብት ክፍያ፤ የካሳ ክፍያ፤ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፤ የህዝብ በዓላት፤ የዓመት ዕረፍት፤ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎች በጠቅላላ ብር 24,020.60 /ሃያ አራት ሺህ ሃያ ብር ከስልሳ ሳንቲም/ እንዲከፍለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካችም በተከሳሽነት ቀርቦ በሰጠው መልስ ተጠሪ የቀን ሰራተኛ ስለሆነች በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ልትዳኝ አይገባም፤ የህዝብ በዓላትና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ክስ ከከሰሰችበት ወደኋላ እስከ ስድስት ወር ድረስ ያለውን ብቻ እንጂ መጠየቅ የምትችለው ካሣ በፊት ያለው በይርጋ ቀሪ ስለሚሆን ልትጠይቅ አይገባም፤የዓመት ዕረፍት ከ2 ዓመት በላይ ያለው በይርጋ ይታገዳል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት የመጀመሪያ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ አስመልክቶ የሰጠው መልስ ደግሞ ተጠሪ ከስራ የተሰናበተችው ስራው እየቀነሰ ስለሆነ ተቀንሳ ነው፤ የኮንስትራክሽን ድርጅት የሆነ አሰሪ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 30 እና በሰበር መዝገብ ቁጥር 42075 እና 39042 መሰረት የስራ መጠን በቀነሰ ጊዜ ሰራተኞች ለማሰናበት የማስጠንቀቂያና ሌሎች የቅነሳ ስርዓቶችን እንዲከተል የማይጠበቅበት በመሆኑ ተጠሪ የካሳ ክፍያ፤ ያለማስጠንቀቂያና የአገልግሎት ክፍያ ልታገኝ አይገባም፤የአመት እረፍት ይከፈላታል ከተባለ የሁለት ዓመት ብቻ ነው ሊከፈላት የሚገባው ሲል የመከላከያ መልሱን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ተጠሪ ከስራ የተሰናበተችው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 29 እና 30 በተደነገገው መሰረት በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፤ የካሳ ክፍያ አመልካች ሊከፍል አይገባም፤ የሁለት ዓመት እረፍት ክፍያ ብር 1,485.00 /አንድ ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አምስት ብር/፤ የህዝብ በዓል የአንድ ቀን ብር 90.00 /ዘጠና ብር/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል፤ ስራው ሙሉ በሙሉ ሳያልቅ ስራው እየቀነሰ በመምጣቱ ምክንያት ከስራ የተቀነሰ ሰራተኛ በአዋጁ አንቀጽ 39/1/ሐ/ መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ ማግኘት ያለበት ስለሆነ አመልካች ለተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ ብር 3,000.00 /ሶስት ሺህ ብር/ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሰሜን ወሎ ዞን መስተዳድር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሰረት ይግባኙ በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ በመቀጠል አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት አቤቱታው በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 17 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፈው አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝሮ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ግንቦት 14 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው የስራ ስንብት ክፍያ ይከፈል ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው የአሁን ተጠሪ ከስራ እንዲሰናበት የተደረገው በአመልካች ድርጅት የተያዘው የህንፃ ስራ ፕሮጀክት ስራው እየተጠናቀቀ በመሄዱ ነው፡፡ የስራ ውል ሊቋረጥ የሚችልባቸው መንገዶች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 23 ስር ተመልክቷል፡፡ አንደኛው መንገድ በአሰሪው አነሳሽነት የሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ እንደሁኔታው በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ ሊደረግ የሚችል ሆኖ የምክንያቶቹ ዝርዝር እና አፈፃፀሙ ከአንቀፅ 26 እስከ 30 ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በሕብረት ስምምነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ተደርጎ የተወሰደ ጉዳይም በአሰሪው አነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ሊያቋረጥ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 27/1/ተ/ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለዚህ በአዋጁ በተደነገጉ ምክንያቶችና ሁኔታዎች የሚፈፀም የስራ ውል ማቋረጥ ህጋዊ የስራ ማቋረጥ ሲሆን ከነዚህ ውጭ የሚደረጉ የስራ ውል ማቋረጥ ህገወጥ መሆኑን ከአንቀጽ 42 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለአንድ ኮንስትራክሽን ስራ የተቀጠረ ሰራተኛ የኮንስትራክሽኑ ስራ ሲያልቅ ወይ ሲጠናቀቅ በወሳኝ ደረጃ የሚገኝ ሆኖ እያለ አሰሪ የስራ ውሉ ማቋረጥ እንደሚችል እርምጃው ከህግ ውጭ ነው የሚያሰኝ ህጋዊ ምክንያት የለውም፡፡ በኮንስትራክሽን የሚሰሩ ስራዎች በባህሪያቸው በተወሰነ ጊዜ የሚያልቅ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ተጠሪ የተሰማራችው የግንባታ ፕሮጀክት መሆኑ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የሚያከራክር አይደለም፡፡ በፕሮጀክት የተያዘው ስራ ሲጠናቀቅ አሰሪው ሰራተኞች ይዞ የሚቆይበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም የግንባታ ስራው በሂደት እየተጠናቀቀ ሲሄድ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 30 መሰረት ስንብቱ መፈጸሙ በአጠቃላይ የፕሮጀክት ስራ እንደመሆኑ መጠን ተጠሪ የምትሰራው ስራ እየተጠናቀቀ በመሄዱ አመልካች የወሰደው እርምጃ በህጋዊ መንገድ መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ የአመልካች ጥያቄ በዚህ ሁኔታ ከስራ የተሰናበት ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈለው አይገባም የሚል ነው፡፡ የግንባታ ስራው ባለበት ጊዜ የሚሰሩ ስራው ሲገባደድ ወይም ሲጠናቀቅ የስራ ውላቸው የሚቋረጥ ሰራተኞች ናቸው፡፡ ለእንደዚህ አይነት የስራ ውል የተቀጠሩ ሰራተኞች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 24 ንዑስ 1 መሠረት ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች እንደሆኑ የሰበር ችሎቱ ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁጥር 22956 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኛ የስራ ውሉ የሚቋረጥበት ጊዜ ሲደርስ ከስራ ማሰናበት እንደሚቻል ከአዋጁ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 1 ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 1 እና አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት መሆኑ ከተረጋገጠ ለተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ የሚከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሰ/መ/ቁ 42229፤ 42368 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) መሰረት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው በአግባቡ ነው ካሉ በኋላ አመልካች ለተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ ክፍል መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0107289 ጥቅምት 27 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 18806 ህዳር 8 ቀን 2009 ዓ/ም እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 0316070 በትእዛዝ ያፀኑት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረትተሻሽለዋል፡፡
2. የስራ ስንብት ክፍያ ብር 3,000.00 /ሶስት ሺህ ብር /አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የሁለት ዓመት እረፍት ክፍያ ብር 1,485.00/ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አምስት ብር/ እና የህዝብ በዓል የአንድ ቀን ብር 90.00/ዘጠና ብር/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ. 142752

ሐምሌ 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- በከልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር -የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ወልደሰንበት ዳዲ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርጎ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 102019 በ15/07/2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26172 በ16/09/2009 ዓ.ም የተሻሻለው እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 268330 በ28/09/2009 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ በ28/02/2009 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከ01/02/1974 ዓ.ም ጀምሮ በመካኒክነት የስራ መደብ ላይ በመጨረሻ ብር 5,198 (አምስት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ስምንት) ወርኃዊ ደመወዝ እያገኙ ሲሰሩ ቆይተው ስራቸውን በ09/03/2008 ዓ.ም በራሳቸው ፈቃድ የለቀቁ መሆኑን፣አመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲፈጽም እና የመልቀቂያ /የመሸኛ/ ደብዳቤ እንዲሰጣቸው ተጠሪው በ09/03/2008 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የጠየቁ ቢሆንም አመልካች ዛሬ ነገ እያለ አቆይቶ በ25/08/2008 ዓ.ም የሰጣቸው መሆኑን የሚገልፅ ሆኖ፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ማሻሻያ በሆነው አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 39 እና 40 ድንጋጌዎች መሰረት የ34 ዓመት የአገልግሎት ክፍያ ብር 62,376፣
2. በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 77 (5) መሰረት የ2005፣2007 እና 2008 ዓ.ም. የ63 ቀናት የዓመት ዕረፍት ክፍያ ብር 10,915.80፣
3. በ2007 ዓ.ም. ለሰራተኞች የተከፈለ ቦነስ የአንድ ወር ተኩል ደመወዝ ብር 7,797 እና
4. በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 38 መሰረት ክፍያ የዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ ብር 15,594

በድምሩ ብር 96,682.80 (ዘጠና ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ሁለት ከሰማንያ ሳንቲም) አመልካች ድርጅት ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍላቸው እንዲሁም አስፈላጊውን ፎርማሊቲ በማሟላት የስራ ልምዳቸውን እና የክሊራንስ ደብዳቤ ለጡረታና ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እንዲያስተላልፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ በ22/03/2009 ዓ.ም በሰጠው መልስ ክሱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162 (4) መሰረት በስድስት ወር ይርጋ የሚታገድ ነው የሚል የመጀመሪያ መቃወሚያ ካስቀደመ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ክሱ ግልጽነት የጎደለው መሆኑን፣የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ በተደራቢነት የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው መሆኑን፣የአመልካቹ ንብረት በፅዳ የሚፈለግባቸው መሆኑን፣ፅዳ ካለባቸው ደግሞ የስራ ልምድ ማስረጃ ከመስጠት ውጪ አመልካቹ የመልቀቂያ ደብዳቤ ለመስጠት የማይገደድ መሆኑን፣የዓመት ዕረፍታቸውን በወቅቱ መጠቀም ሲገባቸው ያልተጠቀሙ መሆኑን፣ፅዳ እያለባቸው እና የሚከፈላቸው ክፍያ በሌለበት ሁኔታ ክፍያ የዘገየበት መቀጫ መጠየቃቸው ተገቢ አለመሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሮአል፡፡

ፍርድ ቤቱም የይርጋ መቃወሚያውን በ17/04/2009 ዓ.ም በብይን ካለፈ እና በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ክሱን እና የተጠሪውን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ፡-

1. ተጠሪው ስራቸውን እንደለቀቁ የጡረታ ተጠቃሚ መሆናቸውን አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ የ34 ዓመት የአገልግሎት ክፍያ ብር 62,376፣
2. የ2008 ዓ.ም. የዓመት ዕረፍት ክፍያ ብር 3,811 እና
3. የ2007 ዓ.ም. ቦነስ ብር 7,797

በድምሩ ብር 73,984.86 ከ10% የጠበቃ አበል ጋር አመልካች ለተጠሪው እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንን ውሳኔ ያሻሻለው የቦነስ ክፍያው ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ግንኙነት የሌለው በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው በሚል ምክንያት በዚህ ረገድ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ብቻ በመሻር ሲሆን አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪው የስራ ውላቸውን በፈቃዳቸው ያቋረጡት በ09/03/2008 ዓ.ም. ሆኖ ክስ ያቀረቡት ደግሞ በ28/02/2009 ዓ.ም መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162 እና 164 ድንጋጌዎች አንጻር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት እንዲቻል ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቹ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ያደረጉት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162 (4) የተመለከተው የስድስት ወር የይርጋ ጊዜ መቆጠር መጀመር የሚገባው አመልካች እንደሚከራከረው ተጠሪው ስራቸውን በፈቃዳቸው ከለቀቁበት 09/03/2008 ዓ.ም ጀምሮ ሳይሆን አመልካች የመሸኛ ደብዳቤ ለተጠሪ ከሰጠበት ከ25/08/2008 ዓ.ም ጀምሮ ነው፣ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ክሱ እስከቀረበበት 28/02/2009 ዓ.ም ድረስ ስድስት ወር አላለፈውም በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡በይርጋ ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ይህ ብይን ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? ወደሚለው ጥያቄ ከመገባቱ በፊት በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው የይርጋ ብይን ረገድ አመልካቹ በሰበር አቤቱታው ላይ ያቀረበው የቅሬታ ነጥብ መኖር አለመኖሩን በቅድሚያ ማጤኑ ተገቢ ሆኖ ተገኝቶአል፡፡አመልካች በ01/10/2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የይርጋ መቃወሚያ አቅርቦ እንደነበረ እና ነገር ግን ውድቅ እንደተደረገበት የክርክሩን ሂደት እና የጉዳዩን አመጣጥ ለማሳየት ያህል ከመጥቀሱ ውጪ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ቅሬታውን በገለጸበት እና የዚህን ሰበር ችሎት ዳኝነት በጠየቀበት የሰበር አቤቱታው ክፍል ላይ በስር ፍርድ ቤቶች በይርጋ ረገድ የተሰጠው ብይን እና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለመሆኑ የገለጸው ነገር አለመኖሩን እና የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በይርጋ ምክንያት እንዲሻርለት ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አለመኖሩን የሰበር አቤቱታው በግልጽ ያመለክታል፡፡ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ላይ በዚህ ረገድ ባቀረቡት የክርክር ነጥብ ረገድም አመልካቹ በመልስ መልሱ ላይ የሰጠው ማስተባበያ የለም፡፡ማንኛውም ወገን የይርጋው ጊዜ ካለፈ በኃላ የይርጋ ጊዜን እንደመቃወሚያ አድርጎ ለማንሳት ያለውን መብት ሊተው የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ በአንቀጽ 165 የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር ላይ የተመለከተ ሲሆን ዳኞች በገዛ ስልጣናቸው የይርጋውን ደንብ መከላከያ ለመጥቀስ የማይችሉ ስለመሆኑም ከአዋጁ አንቀጽ 162/5/ እና ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1856 (2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቹ በሰበር አቤቱታው ላይ የቅሬታ ነጥብ አድርጎ ባላቀረበበት ሁኔታ የይርጋ ጉዳይ በክርክር ጭብጥነት መያዙ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቹ የሰበር አቤቱታ ያቀረበበት ዓቢይ ነጥብ ተጠሪው የጡረታ መብት ተጠቃሚ ሆነው ሳለ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት የተወሰነላቸው አላግባብ ነው የሚል ሲሆን ተጠሪው ስራቸውን እንደለቀቁ ወዲያውኑ የጡረታ አበል ተጠቃሚ አለመሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት በመሆኑ በዚህ ረገድ በአመልካቹ የቀረበው ክርክርም የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 102019 በ15/07/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26172 በ16/09/2009 ዓ.ም. የተሻሻለው እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 268330 በ28/09/2009 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
2. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 103396 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ01/10/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡
3. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሱን ይቻል፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.130944

ሐምሌ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ዳኜ መላኩ

አሰግድ ጋሻው

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች ፡- አቶ ሞገስ ወ/መላክ - አልቀረበም

ተጠሪ ፡- የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመ/ቁ ጡ/ይ/1/1/155/2008 በቀን 28/07/2008 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 126913 በቀን 15/09/2008 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው ፡፡

ጉዳዩ የኮንትራት ሥራ አገልግሎት ጊዜ ለጡረታ መብት አያያዝን የሚመለከት ነው ፡፡ አመልካች ለመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አዲስ አበባ ሪጅን /በተጠሪ/ ባቀረቡት አቤቱታ ከ11/06/68 እስከ 25/03/73 በቀድሞ ግብርና ሚኒስቴር ፣ከ12/01/84 እስከ 30/01/92 በአዲስ አበባ መስተዳደር የፕሮጀክት ፅ/ቤት ከ02/02/92 እስከ 07/11/2000 አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጀትና ማስፋፊያ ቢሮ ለ21 ዓመት ከ8 ወር ከ9 ቀን ያገለገሉ በመሆኑ የጡረታ አበል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን ከ02/02/92 እስከ 30/10/92 ያለውን አገልግሎት ውድቅ በማድረግ እንዲሁም ከሰኔ 01/1995 ዓ.ም በፊት ያለው የኮንትራት አገልግሎት ጊዜ አግባብ ባለው አካል ያልተፈቀደ በመሆኑ ለጡረታ አይታሰብም በማለት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የአመልካች አገልግሎት ከ21 ዓመት በላይ ቢሆንም በኮንትራት ተቀጥሮ በሰሩባቸው ጊዜያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጡረታ መዋጮ ተቀንሶ ገቢ ያለመሆኑ በጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 መሠረት በኮንትራት የተፈፀሙት አገልግሎት እንዲያዝ ከሚመለከተው ክፍል የተፈቀደበት ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ኤጀንሲ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው በማለት አጽንቷል ። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም መልስ ሰጪን ሳይጠራ የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ ባለመቀበል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አሰናብቶታል ።

የአመልካች የሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህንን በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 11/4/መ በቋሚነት በተቀጠረበት የመንግስት መ/ቤት በጊዜያዊነት በተከታታይ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ ለጡረታ አገልግሎት የሚቆጠር መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑና በሌላ አግባብ ባለው አካል ማስወሰን የሚጠይቅ አይደለም ፣ ከሆነም የጡረታ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ነው፣ በኮንትራት ተቀጥሮ በስራሁበት ጊዜ የሚከፈለው የጡረታ መዋጮን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 11/6/መ/ ሆነ በአዋጅ ቁጥር714/2003 አንቀጽ 17/5/ መሰረት የኮንትራት ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ለመያዝ እንደቅድመ ሁኔታ ሠራተኛው የራሱንና የአሰሪውን የጡረታ መዋጮ ድርሻ ጨምሮ ራሱ ባቀረበ ጊዜ የሚከፍለው እንጂ በአገልግሎት ጊዜ አይደለም ፣በዚህ መሠረት ለመክፈል አመልክቻለሁ ። ስለሆነም የተፈፀመው ስህተት ታርሞ የኮንስትራት ጊዜው ታስቦ አበል ይወሰንልኝ የሚል ነው ።የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በቋሚነት ከመቀጠራቸው በፊት በመንግስት መ/ቤት በኮንትራት የሰሩበት ጊዜ አገልግሎት ለጡረታ አይታሰብም መባሉን በአዋጅ 714/2003 አንቀፅ 17/3 /ሠ/ መሰረት ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ አመልካች ለጡረታ አገልግሎት ሊያዝልኝ ይገባል ያሉት ከ12/01/1984- 30/01/1992 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕሮጀክት ጽ/ቤት በጊዜያዊነት የፈፀሙት ሲሆን ይህም በአዋጅ 345/05 እና 714/03 ከመውጣታቸው በፊት በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ ተፈጻሚነት የለውም ፣ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የነበረውም 209/55 ሲሆን የኮንትራት አገልግሎት ለጡረታ አይታሰብም፣ አመልካች ተጠሪ በኮንትራት በሰራሁበት ጊዜ የጡረታ መዋጮ ተቀንሶ ገቢ አልተደረገም ያሉትም የጡረታ መዋጮ የሚሰበሰበውም ሆነ የጡረታ ተጠቃሚነት ባለመብት የሚረጋገጠው ቋሚ ለሆነ የመንግስት ሰራተኛ ነው ። ስለሆነም በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመ ባለመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን ብሏል ። የአመልካች የመልስ መልስም ቀርቧል ።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተሰገፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ለሰበር ችሎት መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል ። እንደመረመርነው አመልካች በኮንትራት የፈፀሙት አገልግሎት ለጡረታ አይታሰብም የተባለው ነጥብ ከህጉ ጋር በማገናዘብ በቅድሚያ መታየት ያለበት ነው ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 11/4/ /ሠ/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ አዋጁ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በቋሚነት በተቀጠረበት መ/ቤት በጊዜያዊነት /በኮንትራት/ በተከታታይ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ ለጡረታ ተግባር ይታሰብለታል ሲል በተመሳሳይ መልኩ አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 17/3/ /ሠ/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በቋሚነት በተቀጠረበት መ/ቤት በጊዜያዊነት ሳያቋርጥ በተከታታይ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ ለጡረታ ተግባር እንደሚያዝለት ይደነግጋል ።

አመልካች በኮንትራት አገልግሎት ከሰኔ 1 ቀን 1995 ዓ.ም በፊት የሰጠባቸው ደግሞ ከ12/01/84 እስከ 30/01/92 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና ከ02/02/92 እስከ 30/10/92 ድረስ ያሉት ጊዜያት መሆኑን ከክርክሩ መገንዘብ ይቻላል። አመልካች እነዚህንየኮንትራት /ጊዜያዊ/ ሥራ አገልግሎት የሰጠው በዚያው በቋሚነት ተቀጥሮ በሚሠራበት መ/ቤት አይደለም፣ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር345/1995 አንቀጽ 11/6 /መ/ ሆነ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 17/5/ መሠረት የኮንትራት ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ለመያዝ እንደቅድመ ሁኔታ ሠራተኛው የራሱንና የአሰሪውን የጡረታ መዋጮ ድርሻ ጨምሮ ራሱ ቀርቦ ስለመክፈሉ አልተረጋገጠም። በሌላ በኩልም የአመልካች የኮንትራት /ጊዜያዊ/ የስራ አገልግሎት ጊዜ የተፈፀሙት አዋጅ ቁጥር 345/1995 ሆነ አዋጅ ቁጥር 714/2003 በስራ ላይ በነበሩበት ጊዜ አይደለም ። እንደዚህ በሚሆን ጊዜ ደግሞ ተፈጻሚነት የሚኖረውን አዋጅ በተመለከተ በሰበር መ/ቁ 50590፣50591 እና 80323 በተሰጠው ትርጉም መሠረት አዋጅ ቁጥር 345/1995 ከመውጣቱ በፊት የተፈጠሩ ህጋዊ ሁኔታዎች ተፈጻሚ የሚሆነው አዋጅ ቁጥር 209/55 ነው ። በዚህ አዋጅ መሠረት ደግሞ የኮንትራት አገልግሎት ለጡረታ አይታሰብም ።

በሌላ በኩልም በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 17/5/ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ የተሰጠ አገልግሎት ለጡረታ ተግባር የሚያዘው በአዋጅ ቁጥር 345/1995 በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ቋሚ ሠራተኛ ለሆነና በአዋጅ ቁጥር 907/2007 በፀደቀ ቀን ሥራ ላይ ለሚገኝ ሠራተኛ መሆኑን ያስገነዝባሉ ።

በአጠቃላይ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አመልካች በጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 መሠረት ቀደም ሲል በኮንትራት የፈፀሙት አገልግሎት ለጡረታ ሊያዝ አይገባም በማለት የሠራተኛና ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ውሳኔ ያፀናው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም። በዚህ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በቁጥር ጡ/ይ/1/1/155/2008 በቀን 28/07/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 126913 በ15/09/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል ።
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 132861

ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡- 1. አቶ እርጋጤ መድበው 2. ወ/ሮ አበበች ከተማ

3 አቶ ጋዲሳ ረጋሳ 4. አቶ መኮንን ገ/ማርያም

5 አቶ ኃይሌሚካኤል ሰናይ 6. አቶ ዘውዱ ገ/ጻድቅ

7. አቶ እንዳለ ጎሣዬ 8 . አቶ መኩሪያ ወ/ሥላሤ

9 አቶ አለምሰገድ ወ/አማኑኤል 10. የ፤ አለቃጥላሁን ከበደ

11 አቶ መስፍን በቀለ 12. አቶ አብርሃም ለማ

13. አቶ በረሁን ማሞ 14. አቶ ተምትሜ ዓለሙ

15 ም/መ/አለቃ አባተ መድበው 16. አቶ ደምሴ ንጉሴ

17. አቶ ሽመልስ ዓለሙ 18. አቶ ፍጹም ካህሳይ

19 አቶ ግርማ ተሰማ 20. አቶ አያሌው ፋንታዬ

21 አቶ ወንድሙ ገብሬ 22. አቶ ኃይሉ ቡራዩ

ተጠሪ፡- የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ- ኀ/ፈጅ ሄኖክ መሳይ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

የጉዳዩ አመጣጥ የዘለቄታ ጡረታ አበል እንዲከፈል እንዲወሰን ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ለመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አጀንሲ የዘለቄታ የጡረታ አበል እንዲወሰንላቸው ጥያቄ አቅርበው ኮሚቴው ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 27 እና በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 63 ተራ ቁጥር 3 መሠረት አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የሚወሰንላቸው የአንድ ጊዜ የዳረጎት አበል ወይም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ወይም የዘለቄታ ጡረታ አበል የለም ሲል ወስኗል፡፡፡

ይህን ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኖቹ አመልካቾች ይግባኝ ለማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርበው የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ኮሚቴ ውሳኔ ፀንቶባቸዋል፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ውሳኔውን ለማስለወጥ ይግባኝ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካቾች የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፣ የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጡት ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶች መስከረም 18 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 19 /2/ ላይ ማንኛውም መንግሥት ሠራተኛ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ ጡረታ ያገኛል ሲል በግልጽ ደንግጎ እያለ የአመልካቾች አገልግሎት ከ20 ዓመት በታች ነው በማለት የዘለቄታ የጡረታ አበል አይገባቸውም ተብሎ መወሰኑ ግልጽ የሆነ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው አቤቱታውን መርምሮ የአመልካቾች የጡረታ መብት ጥያቄ ከአዋጅ ቁጥር 907/2007 አንጻር የአገልግሎት ዘመናቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዳረጎት አበልም ሆነ የዘለቄታ የጡረታ አበል ሊወሰንላቸው አይገባም ተብሎ በሥር የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል አዟል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በቀን 6//6/2009 ዓ.ም የተጻፈ መቃወሚያ እና መልስ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን አመልካቾቹም መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ጉዳዩን አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካቾች በመንግሥት ሥራ እያገለገሉ ቆይተው ከ1983 ዓ.ም ወዲህ በጽኑ እስራት ምክንያት አገልግሎት ያቋረጡ መሆናቸውን፣ የጽኑ እስራት ጊዜያቸውን ጨርሰው የወጡ መሆናቸውን፣ አስቀድመው በመንግሥት ሥራ ያገለገሉበት ዝቅተኛው 10 ዓመት ሲሆን ከፍተኛው 18 ዓመት መሆኑን አመልካቾች ያቀረቡት ዝርዝር እንዲሁም ተያይዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ የሥር መንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አጀንሲ ኮሚቴ እንዲሁም የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ለውሳኔያቸው መሰረት ያደረጉት ዋናውና መሠረታዊው ነጥብ የአመልካቾች አገልግሎት ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዘለቄታ የጡረታ አበል አይገባቸውም የሚል ነው፡፡ ይህ ውሳኔ ከተሻሻለው የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5 /2/ አንጻር ሲታይ ተገቢ ነው ወይ? የሚለውን መመልከት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የሚያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሠረቱ ተጠሪ ለዚህ ችሎት ባቀረበው መልስ ላይ በአዋጅ ቁጥር 209/55፣በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 5/67 እና አዋጅ ቁጥር 714/2003 ላይ የተደነገገውን ከ20 ዓመት በላይ አገልግሎት እያነሳ የተከራከረ ሲሆን በእነዚህ አዋጆች ላይ የተደነገገው እና የአሁኑ ተጠሪዎች ስለመብታቸው የሚከራከሩበት የአገልግሎት ዘመን በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 ተተክቷል፡፡ በተሻሻለው አዋጅቁጥር 907 አንቀጽ 5/2/ ላይ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 18 1/ በተደነገገው መሠረት የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልክ ይከፈለዋል ሲል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት ቢያንስ አስር ዓመት ማገልገል ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 18/1/ መሠረት የጡረታ እድሜ መድረስ ነው፡፡ የአመልካቾች የጡረታ እድሜ ከ60 ዓመት በላይ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ ሲከራከር የነበረ አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዘለቄታ ጡረታ አበል አይገባቸውም በማለት ነው፡፡ ይህ ክርክር ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19/2/ ላይ የተደነገገውን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ሲሆን ይህ ደግሞ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5/2/ የተተካ በመሆኑ የተጠሪ የ20 ዓመት አገልግሎት ክርክር ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 63/3/ ድንጋጌም ቢሆን አዋጁን ሊጻረር አይችልም፡፡

ምክንያቱም መመሪያው አዋጁን ማስፈጸሚያ ነው እንጂ በአዋጁ የተደነገገውን ድንጋጌን ሊቃረን የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ ምክንያት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌላው የተጠሪ ክርክር የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5/2/ አዋጁ በሚወጣበት ጊዜ በሥራ ላይ ያሉትንና ከአዋጁ በኃላ የጡረታ እድሜያቸው ሲደርስ ጡረታ የሚወጡትን የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ክርክር የማሻሻያ አዋጁን አንቀጽ 5/2/ 'ን' መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ የአሁኑ አመልካቾች የዘለቄታ የጡረታ አበል እየጠየቁ ያሉት በገዛ ፈቃዳቸው ሥራ ለቀው ሳይሆን ታስረው በመቆየታቸውና እድሜያቸው ለጡረታ የደረሰ በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ከተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 11/9/ አንጻር ሲታይ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊና ህጋዊ ሁኔታዎችን በአግባቡ ሳያጤኑ የሰጡት ውሳኔም ሆነ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ኮሚቴ በቀን 9/6/2008 ዓ/ም ፣ የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በቁጥር ይ/1/1/154/2008 በቀን 28/7/2008 የሰጡት ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 126747 ሰኔ 14 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የጡረታ አበል ክፍያ የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከፀናበት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ለአመልካቾች እንዲከፍላቸው ተወስኗል፡፡
3. የዚህ ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይድረሳቸው፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 134188

ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች ፡- አቶ ዊንታ ቦርጇ -የቀረበ የለም

ተጠሪ ፡- ይርጋለም ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር .....የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31163 በ19/09/08 ዓ/ም ተሰጥቶ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20112 በ24/12/08 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 68973 በ09/02/2009 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ በሥራ ላይ በሚደርስ የአካል ጉዳት የሚከፈል የካሣ ገንዘብ ጥያቄ የይርጋ ጊዜ ገደብን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በ20/08/08 ባቀረቡት ከተጠሪ ድርጅት ጋር በፈፀሙት የቅጥር ውል መሰረት ስራ ላይ እያሉ በ17/06/2006 ዓ/ም በደረሰባቸው ከፊል አካል ጉዳት ምክንያት ህክምና ሲከታተሉ የቆዩ ቢሆንም በጥር ወር 2008 ዓ/ም ከፍተኛ የሆነ የጤና መታወክ ያጋጠማቸው መሆኑን ጠቅሰው በአዋጁ መሰረት ዘላቂ የአካል ጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸውና ተጠሪ ድርጅት ለአመልካች ያላግባብ ደመወዝ እየቀነሰ ሲከፍል የነበረ በመሆኑ ይኼው የተቀነሰው ደመወዝም እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ድርጅትም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገው የስድስት ወር የይርጋ ጊዜ ገደብ አልፏል በማለት መቃወሚያ አቅርቧል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ተጠሪ ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል የአካል ጉዳት ካሳ ክስ በአንድ ዓመት፣የደመወዝ ክፍያ በስድስት ወር ይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ብይን ሰጥቷል ።

አመልካች ይግባኝ ለሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት ያጡ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎትም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ብይን የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል። የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በ17/06/2006 ዓ/ም አመልካች ስራ ላይ እያሉ የደረሰባቸው የአካል ጉዳት በህክምና ሲከታታሉ ቆይተውና ተጠሪ ድርጅትም ይህንኑ አውቆ ሲያሳክማቸው ቆይቶ ጉዳቱ ተባብሶ በአመልካች አካል ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ጉዳት መሆኑ አመልካች ያወቁት ክስ ከመቅረቡ ከሶስት ወር በፊት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳቱ የደረሰበትን የካቲት 17 ቀን 2006 ዓ/ም ለይርጋው መቆጠር መነሻ አድርገው መያዛቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦ በ ሰጠው መልስም ከአመልካች ጋር መጀመሪያ የተመሰረተው የስራ ውል በሕጉ አግባብ የተቋረጠ መሆኑን፣ አመልካች ጉዳት ደረሰብኝ የሚሉት በስራ ቦታ ላይ ስለመሆኑ በተጠሪ በሕጉ አግባብ ያላሳወቁ መሆኑን፣ ተጠሪ አመልካችን በስራ ላይ ጉዳት መድረሱን አምኖ ሲያሳክማቸው የነበረበት አግባብ የሌለ መሆኑንና ሌሎች ነጥቦችን በሰፊው ዘርዝሮ የአመልካች ክስ በይርጋ ውድቅ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሯል። የአሁኑ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይንና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሰጡት ዳኝነት ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል ።

ጉዳዩን እንደመረመርነው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ 1 ስር የተደነገገው የአንድ አመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ነው።አሁን አከራካሪ የሆነው ይህ የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው መቼ ነው? የሚለው ነው። ይህንኑ ለመመለስ አመልካች በክሳቸው ላይ የጠቀሷቸውን መሰረታዊ ፍሬ ነገሮችንና ተጠሪም ለእነዚህ ፍሬ ነገሮች ያቀረባቸውን የክርክር ነጥቦችን መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል። አመልካች በክሳቸው ላይ የጠቀሱት መሰረታዊ ነጥብ ከተጠሪ ጋር በመሰረቱት የስራ ውል አግባብ በስራ ላይ እያሉ የአካል ጉዳት የካቲት 17 ቀን 2006 ዓ.ም ደርሶባቸው ሕክምና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲከታታሉ ቆይተው ጉዳቱ ዘላቂ መሆኑን ጥር ወር 2008 ዓ.ም አካባቢ አውቀው ተጠሪ ላይ ለዚሁ ለዘላቂ የአካል ሚያዚያ 20 ቀን 2008 ዓ.ም ክስ የመሰረቱ መሆኑን ሲሆን ተጠሪ ጉዳት ካሳ እንዲከፍል አጥብቆ የሚከራከረው ደግሞ በ2006 ዓ.ም ከአመልካች ጋር የነበረው የስራ ውል በሕግ አግባብ የተቋረጠ መሆኑ በፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተረጋገጠ መሆኑን፣ በዚህ ጊዜ ደረሰ የተባለው ጉዳትም በተጠሪ በሕጉ አግባብ ያልታወቀና በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ሊባል የማይችል መሆኑንና አመልካች ህክምና እንዲያገኙ ሲያደርግ የቆየውም ድርጅቱ በአመልካች ላይ የደረሰውን የአካል ጉዳት በስራ ላይ የደረሰ መሆኑን በማመን ሳይሆን የድርጅቱ ባለቤት በግላቸው በሰብአዊነት ያደረጉት ተግባር መሆኑን በመዘርዘር ነው።ይሁን እንጂ በ2006 ዓ/ም በአመልካች ላይ ደረሰ የተባለው የአካል ጉዳት በሕጉ አግባብ በስራ ላይ የደረሰ መሆን ያለመሆኑ፣ ተጠሪ ለህክምናው ሲያወጣው የነበረ ወጪ መኖርያ ለመኖሩና ጥር 2008 ዓ.ም በአመልካች የታወቀው የዘላቂ አካል ጉዳት በ2006 ዓ.ም በደረሰባቸው አደጋ የመጣ መሆን ያለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በግራ ቀኙ ማስረጃ የሚታዩ ነጥቦች ከመሆናቸው ውጪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ሊነሱ የሚችሉ ነጥቦች አይደሉም። ስለሆነም የአመልካች ክስ አመሰራረት ከተጠሪ ጋር የፀና የስራ ውል እያለ በ2006 ዓ.ም በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት የመጣው ዘላቂ ያልሆነ የአካል ጉዳት በሕክምና ቢከታተሉም ለውጥ ሳያሳይ ቀርቶ ወደ ዘላቂ የአካል ጉዳት መሸጋገሩን የሚገልጽና ይህ ስለመሆኑ የታወቀው ደግሞ በጥር ወር 2008 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑን የሚያሳይ እና ተጠሪም በዚህ ረገድ ግልጽ ማስተባበያ ክርክር ባለቀረበበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ከ17/06/2006 ዓ.ም ጀምሮ ነው በማለት የያዙት መነሻ የአመልካችን ክስ ይዘት ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል። ለይርጋው ጊዜ መነሻ መሆን ያለበት ጥር ወር 2006 ዓ/ም ነው ከተባለ ደግሞ አመልካቹ ክስ ያቀረቡት በ20/08/2008 ዓ.ም በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162(1) ስር ያለው የአንድ አመት ጊዜ አላለፈም። በዚህም ምክንያት አመልካች ያቀረቡት የአካል ጉዳት ካሳ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31163 በ19/09/08 ዓ.ም ተሰጥቶ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20112 በ24/12/08 ዓ.ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 68973 በ09/02/2009 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች የአካል ጉዳት ካሳን በተመለከተ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡ አመልካች በደመወዝ ላይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ውድቅ መደረጉ አልተነካም፡፡
3. በአመልካች የአካል ጉዳት ካሳ ላይ የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር የሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31163 በመቀጠል ጉዳዩን በሚገባ አጣርቶ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭ ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትሐ ብሔር

ሥነ-ሥርዓት ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 104621

ህዳር 13 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አዜብ ታምሩ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ደጀኔ ዘውዴ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በኮፊሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10991 በ27/06/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበርችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 20374 በ23/07/2006 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 184251 በ05/10/2006ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ግራ ቀኙ በንብረት ክርክር ላይ እያሉ አመልካቿ ክሳቸውን ለማሻሻል እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው በተፈቀደላቸው መሰረት በ07/04/2006 ዓ.ም የተሻሻለ ክስ ማቅረባቸውን፣የተሻሻለው ክስ ይዘትም ቀደም ሲል በቀረበው የንብረት ዝርዝር ውስጥ ግራ ቀኙ በጋብቻቸው ውስጥ ያፈሩት ሆኖ ነገር ግን በህጻን ረድኤት ደጀኔ ስም የሚታወቀው 200 ካ.ሜ ይዞታ ያለው ቤት ያልተካተተ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ክፍፍሉ በዚህ ቤት ላይ ጭምር እንዲካሄድ የሚጠይቅ መሆኑን፣ተጠሪው የተሻሻለው ክስ ቅጂ ደርሶአቸው በ10/04/2006 ዓ.ም. በሰጡት አስተያየት የተሻሻለው የንብረት ዝርዝር ክርክሩን ወደኃላ የሚመልሰው በመሆኑ ውድቅ ተደርጎ በቀድሞው ክስ መሰረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም መጠየቃቸውን፣ፍርድ ቤቱም የተጠሪውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር ተገቢ አድርጎ በመቀበል አመልካች አሁን የክፍፍል ጥያቄ ያቀረቡበትን ቤት በመጀመሪያው ክሳቸው አካተው ማቅረብ ሲችሉ ሌላ ንብረት አካተው ማቅረባቸው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (3) ድንጋጌን የሚቃረን መሆኑን ገልጾ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ክፍፍሉ በቀደመው የንብረት ዝርዝር መሰረት እንዲቀጥል ትዕዛዝ መስጠቱን እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ተቀባይነት ያገኘው ይኸው ውሳኔ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የአመልካቿ የሰበር አቤተታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በፍርድ ቤቱ ፈቃድ ክሱን ካሻሻሉ በኃላ አዲስ ጥያቄን ያካተተ ስለሆነ ጉዳዩን ወደኃላ የሚመልስ ነው በማለት ማሻሻያው ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ተገቢ ሆኖ ካገኘው ተከራካሪ ወገኖች ክሳቸውን እንዲያሻሽሉና ክርክራቸውን እንዲለውጡ ሊፈቅድላቸው እንደሚችል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕገ ቁጥር 91(1) ስር ተመልክቶአል፡፡ፍርድ ቤቱ የዚህ ዓይነቱን ፈቃድ የሚሰጠውም የክሱን መሻሻል ተገቢ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ስለመሆኑም ከዚሁ ድንጋጌው አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህ ሁኔታ ክሱ እንዲሻሻል ከተፈቀደ በኃላ ተሻሽሎ የቀረበው ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ከሰጠበት አግባብ ውጪ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ክሱ ውድቅ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክሱን አሻሽለው ያቀረቡት በፍርድ ቤቱ በተፈቀደላቸው መሰረት መሆኑ አላከራከረም፡፡የክሱ መሻሻል ጉዳይ ክርክሩን ወደ ኋላ የሚመልሰው ነው የሚል ከሆነ ፍርድ ቤቱ መጀመሪያውኑ የማሻሻያ ትዕዛዝ መስጠት አልነበረበትም፡፡ክሱ የሚሻሻልባቸው ነጥቦች ተገቢነት ደግሞ መመርመር ያለበት የማሻሻያ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት እንጂ ክሱ ተሻሽሎ ከቀረበ በኃላ አይደለም፡፡ክሱ ተሻሽሎ የቀረበው ፍርድ ቤቱ ፈቃድ ከሰጠበት ነጥብ ውጪ ስለመሆኑ ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ አልገለጸም፡፡ተጠሪውም የዚህ ዓይነት ክርክር አላቀረቡም፡፡ይህም አመልካች ክሱን የሚያሻሽሉበት ነጥብ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊትም ይታወቅ የነበረ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ክሱ ተሻሽሎ ከቀረበ በኃላ በተሻሻለው ክስ መሰረት ክርክሩን መቀጠል ሲገባው ተጠሪው ያቀረቡትን መቃወሚያ ተቀብሎ በመጀመሪያው ክሳቸው አካተው ማቅረብ ሲችሉ በተሻሻለው ክስ ሌላ ንብረት አካተው ማቅረባቸው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (3) ድንጋጌን የሚቃረን ነው በማለት በተሻሻለው ክስ የተጠየቀውን የተጨማሪ ንብረት ክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 91 ድንጋጌን ትክክለኛ ዓላማ፣ይዘት እና አፈጻጸም መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልተገኘም።የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩን ከዚህ አንጻር ተመልክተው ማረም ሲገባቸው ተቀብለው ማጽናታቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኮፈሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10991 በ27/06/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በምዕራብአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበርችሎት እንደቅደም ተከተሉ በ/መ ቁጥር 20374 በ23/07/2006 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 184251 በ05/10/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል።
2. አመልካች በፍርድ ቤቱ ፈቃድ አሻሽለው ያቀረቡትን ክስ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል።
3. የኮፈሌ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች አሻሽለው ያቀረቡትን ክስ መሰረት አድርጎ ክርክሩን በመቀጠል ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ጉዳዩን መልሰንለታል።
4. የውሳኔው ቅጂ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለኮፈሌ ወረዳ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቁት ደግሞ ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ።
5. ቀሪው የውሳኔ ክፍል አልተነካም።
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 119571

ሕዳር 14 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ባብሶ ቃልቦሬ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ኩዚይማ ሁሴን - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 65573 መስከረም 04 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች ጥቅምት 30 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ 02 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ክርክሩ የገንዘብ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በተጀመረበት የሀላባ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው የአሁን ተጠሪ ከአመልካች /በብር 1000/አንድ ሺህ ብር/ መስከረም ወር 2001 ዓ.ም የገዟትን አንዲት ላም ከአመልካች ዘንድ እንድትቆይ በተስማሙት መሠረት ከአመልካች ጋር ሶስት ጥጆችን ወልዳ በአሁኑ ጊዜ 14,500 ብር ሊገመቱ በሚችሉበት ደረጃ ላይ የደረሱ ቢሆንም አመልካች ከብቶችን ለተጠሪ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከብቶችን በዓይነት እንዲመልስ ወይም ግምታቸውን እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ነበር፡፡

አመልካችም በተከሳሽነት ክሱ ደርሷቸው በሰጡት መልስ የተጠሪን ክስ በመካድ ከአመልካች ዘንድ የተጠሪ ከብቶች የሉም፡፡ ክሱም የሚታመን አይደለም ካሉ በኋላ ከብቶችን እንዲመልሱ ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግምታቸውን እንዲከፍሉ የሚወሰንበት ምክንያት ቢኖር እንኳን ከብቶችን ለመንከባከብ ያወጡትን ብር 12,800 የሚገመት ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍሉ ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሀላባ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ወገኖች የቃል ክርክር እና ማስረጃዎች በመመርመር ተጠሪ ለአመልካች የመጀመሪዋን ላም መስጠታቸው፤ይህችም ላም ጥጆችን ወልዳ በቁጥር አራት መሆናቸው፤ አመልካችም እነዚህን ከብቶች ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ተረጋግጧል በማለት አመልካች ተጠሪ በክሳቸው ዘርዝረው ያቀረቧቸውን ከብቶች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሀላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ቅሬታቸው መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ግራቀኙን አከራክሮ ሲያበቃ አመልካች የተጠሪን ከብቶች ተረክበው ቆይተው ሊመልሱ ባለመቻላቸው በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሰው መቀጣታቸው የተረጋገጠ ቢሆንም የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ከብቶችን እንዲመልስ መወሰኑ ተገቢነት የለውም፡፡ ይልቁንም አመልካች በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ በመሆኑ በፍትሐ ብሔር ህግ አንቀጽ 1751 መሠረት 9% በዓመት ታስቦ አስቀድመው ተጠሪ የሰጡትን ብር አንድ ሺህ ላቆዩት ስድስት ዓመት ብር 1,585/አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ አምስት ብር/ ሊከፍሉ ይገባል እንጂ ከብቶችን እንዲመልሱ አይገደዱም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁን ተጠሪ ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን አቅርበው የሀላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህም ዳኝነት ላይ ባለመስማማታቸው የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ክርክር ሲያደረጉ ከቆዩ በኋላ አመልካች ለተጠሪ ጊደር እንዳልሸጡ፤ እንዲሁም ጊደሯም ከ2001 እስከ 2006 ዓ.ም ሶስት ጥጆች አትወልድም በማለት ቢከራከሩም በአማራጭ ባቀረቡት ክርክር ጊደሯን ለመጠበቅ እና ለእንክብካቤ ያወጡትን ብር 12,800 መጠየቃቸውን ከምስክሮች ቃል ጋር በማገናዘብ ሲታይ ጊደሯ ከተጠሪ ጋር እንደቆየችና አራት ራስ መሆንዋ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የወረዳው ፍርድ ቤት አጣርቶ የወሰነው ውሳኔ ተገቢ ሲሆን የሃላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ የአላባ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ከወሰነ በኋላ በአመልካች በኩል በቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ላይ ምንም ሳይል በዝምታ አልፎታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈፅሟል በሚል ይህንኑ ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የስር ፍ/ቤቶች ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታው በአጭሩ፡-የተጠሪን ጊደር ከ2001 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም በመያዝ ሶስት ጥጆችን አልወለደችም እንጂ ወልዳ ከእኔ ጋር ቆይታለች ቢባል እንኳን ከብቶችን ለመንከባከብ ያወጣሁት ወጭ ሊታሰብ ይገባል በሚል ያቀረብኩት ክርክር በዝምታ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ በጉዳዩ ላይ አከራካሪዎቹ ጊደሮች ከአመልካች ዘንድ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም ቆይተዋል በተባሉበት ሁኔታ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለጊደሮች መኖና ለመሳሰሉት የወጣ ወጭ በሥር ፍርድ ቤቶች አለመታሰቡን አግባብነት ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ መልሳቸውን አመልካችም የመልስ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የተጠሪ ከብቶች ከአመልካች ጋር ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2006 ዓ.ም መቆየታቸው በመረጋገጡ ምክንያት ከብቶችን አመልካች ለተጠሪ እንዲመልሱ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተወስኗል፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ከብቶች እየጠበቀ መቆየቱ አከራካሪ አይሆንም ማለት ነው፡፡ ተጠሪ ለከብቶች ጥበቃ አገልግሎት ለአመልካች የከፈሉት ክፍያ ስለመኖሩም ሆነ አመልካች ከብቶች በነፃ የሚንከባከብበት ስምምነት ለመኖሩ አላረጋገጡም፡፡ አመልካች ለከብቶች እንክብካቤ ብር 12,800 ማውጣታቸውን ገልፀው ክርክር አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ይህንን ነጥብ በጭብጥነት ይዘውና አከራክረው ውሳኔ ከመስጠት ይልቅ በዝምታ ማለፍን መርጠዋል፡፡

በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 2784 ሥር እንደተመለከተው ያለዋጋ ወይም በደመወዝ ስለሚሰጥ አደራ ሲደነግግ አደራ ሰጭና አደራ ተቀባዩ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር በአደራ የሚቀመጥ ዕቃ ዋጋ የማይከፈልበት መሆኑን ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል አደራ ሰጭው አደራ ተቀባዩ ዕቃውን በመልካም አያያዝ ለማኖር ያወጣውን ወጭ ሁሉ ሊከፍለው እንደሚገባ በዚሁ ህግ አንቀጽ 2793(2) ሥር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ለአመልካች በህግ የተሰጠው መብት ለመኖሩ ከተጠቃሹ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ጥያቄ እየቀረበ የሥር ፍርድ ቤቶች ዝምታን መምረጣቸው ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም የአመልካች ጥያቄ ሥነ ሥርዓቱን ተከትሎ የቀረበ መሆኑን በመመልከት ተቀብለው ተጠሪም የበኩላቸውን ክርክር እንዲያቀርቡ ካደረጉ በኋላ ጉዳዩን በማጣራት ተገቢው ዳኝነት ሊሰጡበት የሚገባው የክርክር ነጥብ ነበር፡፡ ስለሆነም የደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ክልል ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን ከብቶች እየጠበቁ የቆዩ ለመሆኑ ወይንም ከብቶቹ በአመልካች ጥበቃ ሥር ለመቆየታቸው ካረጋገጡ በኋላ አመልካች ለከብቶቹ መልካም አያያዝ ያወጡት ወጭ እንዲተካ ያቀረቡትን ዳኝነት አጣርተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለመወሰናቸው፤ የዚህ ዓይነት ወጭ ሊተካ የማይችልበት ምክንያት ቢኖር እንኳን ጉዳዩን ባግባቡ መርምረው ተገቢውን ዳኝነት አለመስጠታቸውን ከመዝገቡ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 65573 መስከረም 04 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. በዚህም መሰረት አመልካች ለአላባ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የተጠሪን ከብቶች በመልካም አያያዝ ለማኖር ያወጡት ወጭ ይከፈለኝ ጥያቄ በአግባቡ ተመርምሮ ተገቢው ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባው በመሆኑ አመልካች የተጠሪን ከብቶች ለመንከባከብ ያወጡት ወጭ ምን ያህል ነው? ይህንን ወጭ ተጠሪ የማይሸፍኑበት ምክንያት አለ ወይስ የለም? የሚሉ ነጥቦች በግራቀኙ ወገኖች ክርክርና ማስረጃ በማጣራት ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ሌላው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

3. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣ ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የእየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

4. በዚህ ችሎት የተሰጠው እግድ ተነስቷል፤ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.116860

ታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስቴር ሌንጂሶ ጠበቃ ገናናው ተሾመ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ሽታዬ ግርማ ቀረቡ

2. አቶ ተስፋዬ ወ/እየሱስ ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278(2) ድንጋጌ መሰረት የተዘጋ ክስ አዲስ ክስ የሚቀርበበት መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀረመው የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በኩዩ ወረዳ ፍርድ ቤት በ09/06/2007 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው ላይ በገብረ ጉራቻ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ በ264 ካ/ሜትር ለመኖሪያ ቦታ ቀርቶላቸው ቁጥሩ 505-02 የሆነውን ሁለት ክፍል ቆርቆሮ ቤት ሰርተው ይዘው እንደሚገኙ፣ በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር በመ/ቁጥር 116321 በሆነው ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አግባብ ሲቃወሙም ፍርዱ ተፈፅሟል በሚል ምክንያት ተቀባይነት ያጡ ቢሆንም አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀላቸው መሆኑን፣ በመ/ቁጥር 32342 በሆነው ላይ ክሱን አቅርበውም በወቅቱ ክርክሩን ለመቀጠል በቂ ማስረጃ ባለማቅረባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278 መሰረት የተዘጋውና አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀላቸው መሆኑን ዘርዝረውና ተጠሪዎች በውሳኔ ቤቱን የያዙባቸው መሆኑን ጠቅሰው ውሳኔው ተነስቶ ቤቱን እንዲለቁላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ለክሱ ምክንያት በሆነው ጉዳይ ላይ አመልካች በመ/ቁጥር 32342 ክስ ከፍተው የተዘጋው አመልካች በመ/ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

30084 በሆነ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 41 መሰረት ጣልቃ ገብተው አቤቱታው ውድቅ የሆነባቸው መሆኑን፣ ይግባኝ ጠይቀው ተቀባይነት ሲያጡም በጉዳዩ ላይ የሰበር አቤቱታ አቅርበው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እየታየ መሆኑን፣ቤቱ በመ/ቁጥር 11631 በሆነ ላይ በተወሰነላቸው ውሳኔ መሰረት በመ/ቁጥር 15736 በሆነ የአፈፃፀም መዝገብ ቤቱን የተረከቡ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጎአል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በመ/ቁጥር 11631 በሆነ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር ቤቱ የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ነው ተብሎ መወሰኑን፣ በዚህ ውሳኔ መሰረት አፈጻጸም ቀጥሎ ውሳኔው መፈጸሙን፣ አመልካች በመ/ቁጥር 11631 የፍርድ መቃወሚያ አቅርበው ፍርዱ ተፈጽሞአል በሚል ምክንያት ተቀባይነት ያጡ መሆኑን፣ በመ/ቁጥር 32342 ክስ አቅርበው መልስ ከተሰጠበት በኋላ አመልካች በ22/10/06 በተጻፈ ማመልከቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278 መሰረት ክሱን ያነሱት ጉዳያቸው በመ/ቁጥር 30084 በሆነ መፍትሔ ሊያገኝ ይችላል በሚል ምክንያት መሆኑንና በዚህ መዝገብ ያቀረቡት ጥያቄም ቤቱ የእኔ ነው የሚል ቢሆንም ክርክሩ ቀጥሎ መብት የላቸውም ተብሎ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት ውደቅ ተደርጎ አመልካች በይግባኝ ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወስደው በመ/ቁጥር 196228 በሆነው ላይ ውድቅ ከሆነባቸው በኋላ ጉዳዩን ወደ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ወስደው በመታየት ላይ የሚገኝ መሆኑን ዘርዝሮ አመልካች በመ/ቁጥር 30084 በሆነ ላይ መፍትሔ ያገኛል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 287(2) በመ/ቁጥር 323412 የቀረበውን ክስ ከአዘጉ በኋላ አዲስ ክስ ማቅረባቸው ስነ ስርዓታዊ አይለም በማለት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህም በኋላ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ብይን የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ አቤቱታቸው ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት በመ/ቁጥር 30084 በተሰጠው ብይን በይግባኝና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እየታየ ያለው ጭብጥ ጉዳዩ መቅረብ የሚችልበት የስነ ስርዓት አግባብን ሲሆን አዲስ የቀረበው ክስ ግን መሰረታዊ መብትን ለማስከበር የቀረበ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በመ/ቁጥር 32342 የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278(2) የተዘጋ ነው በማለት ውድቅ ማድረጋቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278(2) የተዘጋ መዝገብ አዲስ ክስ ሊቀርብበት አይገባም ተብሎ የአመልካች ክስ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት የቀረበ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ቀርበው ከአመልካች ጋር በፅሑፍ ክርክር ያደረጉ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ግን በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ምክንያት በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታልፏል፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 32342 የተሰጠው ትዕዛዝ ግልባጭም እንዲቀርብ ተደርጎ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው አመልካች በመ/ቁጥር 32342 ያቀረቡትን ክስ ያስዘጉት በመ/ቁጥር 30084 ላይ ያቀረቡት የቤቱ ባለቤትነት ጥያቄ ምላሽ ያስገኝልኛል ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278(2) መሰረት በመ/ቁጥር 32342 ያቀረቡት ክስ ሲዘጋውም አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን የትዕዛዙ ግልባጭ የማያሳይ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም የወረዳው ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን እንደተመለከተው አመልካች አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ቤቱ ይለቀቅልኝ በማለት በመ/ቁ 32342 አቅርበውት የነበረውን ክስ በራሳቸው ፈቃድ በመ/ቁጥር 30084 በቀረበው ክስ እልባት ያገኛል በሚል እምነት ክሱን አንስቻለሁ በማለት አቤቱታ አቅርበው መዝገቡን ስለማዘጋታቸው ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን በመመልከት አረጋግጧል፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ በተውት ነገር አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችሉበትን መብት ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 278(2) ድንጋጌ መሰረት የጠበቀላቸው ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክርና ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም በላይ በመ/ቁጥር 32342 የተሰጠው ትዕዛዝ ይዘትም ይህንኑ አያሳይም፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 279(1) ግልፅ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለውም ከላሽ ያለፈቃድ በተውት ወይም በሰረዙት ነገር ሌላ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡ ስለሆነም አከራካሪውን ቤት በተመለከተ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ቤቱ ይለቀቅልኝ በሚል ክስ አቅርበው በራሳቸው ፈቃድ ክሱን ያነሱ መሆኑን ገልፀው ፍ/ቤቱ መዝገቡን የዘጋውና አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀላቸው ስለመሆኑ ክርክርና ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ በተውት ወይም በሰረዙት ነገር ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም ተብሎ የተሰጠው ብይን ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በኩዩ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 34512 በ11/07/2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 49489 በ21/07/2007 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር204171 በ11/09/2007 ዓ/ም የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪዎች ላይ ቤቱ ይለቀቅልኝ በሚል ክስ አቅርበው በራሳቸው ፈቃድ ክሱን ያነሱ መሆኑን ገልፀው ፍ/ቤቱ መዝገቡን የዘጋውና አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀላቸው ስላልሆነ ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ በተውት ወይም በሰረዙት ነገር ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም ተብሎ በተሰጠው ብይን የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስህተት የለም ብለናል፡፡ ሆኖም አመልካች በመ/ቁጥር 30084 ባቀረቡት የባለቤትነት ጥያቄ ላይ ክርክራቸውን በስርዓቱ መሰረት ከማቅረብ ይህ ብይን አያግዳቸውም ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

በ14/07/2008 ዓ/ም የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.121938

ታህሳስ 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነዉ

ጳዉሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የድሬ እንጭኒ ወረዳ መንገዶች ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ወልዴ ዋቆ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- እንጭኒ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የገንዘብ ክፍያን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.202599 በ18/4/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የሥር 1ኛ ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ፣ በዚህ ችሎት ተከራከሪ ያልሆነዉ 2ኛ ተከሳሽ የምዕራብ ሸዋ ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሆኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ የሥር ከሳሽ አምስት ሚሊዮን ብር ተከሳሾች እንዲከፍሉት በድሃ ደንብ መዝገብ በማስከፈት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ ብር 9,307,479 ስለተከፈለዉ ድሃ ነዉ ለማለት ስለማይቻል በድሃ ደንብ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽ በዚህ ጉዳይ ባቀረበዉ መልስ ለከሳሽ በነጻ መዝገብ በነጻ ቢከፈትለት ተቃዉሞ የለንም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ በንግድ ሕጉ አግባብ የከሰረ ስለመሆኑ ዉሳኔ ካልተሰጠዉ በቀር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በድሃ ደንብ ክስ ማቅረብ አይችልም፣ ከሳሽ አስቀድሞ በንግድ ሕጉ አግባብ የከሰረ መሆኑን ዉሳኔ ማሰጠት አለበት በማለት አቤቱታዉን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ክሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ባይ የዳኝነት ክፍያ ለመክፈል አቅም እንደሌለዉ በቂ ማስረጃ አቅርቦ እያለ የሥር ፍ/ቤት አቤቱታዉን ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ዉሳኔ በመሻር ለክሳሽ በድሃ ደንብ ፋይል እንዲከፈትለት በማለት ወስኗል፡፡ የሥር 1ኛ ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን፣ ችሎቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ29/4/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ የአሁን ተጠሪ በድሃ ደንብ መሰረት ክስ ለማቅረብ በቅድሚያ ድሃ ስለመሆኑ በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ ማስረጃ ወይም በፍ/ቤት ከስሯል ተብሎ የተሰጠ ዉሳኔ ባለቀረበበት፣ ተጠሪ ወደ አስር ሚሊዮን ብር ክፍያ ተከፍሎ እያለ ግብር ያልከፈለበት ምክንያት ባልተጣራበት፣ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ በድሃ ደንብ ክስ እንዲያቀርብ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣ተጠሪ በድሃ ደንብ ክስ እንዲያቀርብ የመወሰኑን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘዉ መሰረት በ16/7/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት፡- የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ በሕግ አግባብ ስለሆነ የቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርመሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ በድሃ ድንብ ክስ ለማቅረብ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለዉ ነጥብ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 /1/ እንደተመለከተዉ ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ዉሳኔ የማግኘት መብት አለዉ በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተመለከተዉ ፍትሕ የማግኘት መብት ለተፈጥሮ ሰዉም ሆነ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን አካል የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡ ይህ ፍትሕ የማግኘት መብት አግባብነት በሌላቸዉ ምክንያቶች ሊደናቀፍ አይገባም፡፡ ይህን መብት ተፈጻሚ ለማድረግ በፍ/ቤትም ሆነ በሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል አቤቱታ ወይም ክስ የማቅረብ ሂደት ምቹ ሁኔታ ሊኖር እንደሚገባ የሚያከራክር አይሆንም፡፡ ነገር ግን ፍትሕ የማግኘት መብት ተግባራዊ ሲደረግ በዝርዝር ህጎች የተመለከተዉን የክርክር አቀራረብ ሥርዓትን በአስጠበቀ መልኩ መሆን እንዳለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሰመርበት ይገባል፡፡ አንድ በፍትሐብሔር ጉዳይ ክስ የሚያቀርብ ወገን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የደነገገዉን የክስ ወይም አቤቱታ የማቅረብ ሥርዓትን በጠበቀ መንገድ መሆን አለበት፡፡ በዚህ አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.215 /1/ እንደሚደነግገዉ አቤቱታ ወይም ክስ የሚያቀርብ ሰዉ፣ በድሃ ደንብ መሰረት ያላቀረበ እንደሆነ፣ የዳኝነት ክፍያ እስካልተከፈለ ድረስ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደማይችል ያመለክታል፡፡ እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ በሕጉ በግልጽ ያለ ዳኝነት ክፍያ ሊቀርቡ የሚችሉ አቤቱታዎች ወይም ክሶች ያሉ መሆናቸዉን ነዉ፡፡ ስለዚህ ለዳኝነት ሰጭ አካል አቤቱታ ወይም ክስ የሚያቀርብ አካል የገንዘብ አቅም ያለዉ እንደሆነ በደንቡ መሰረት ተገቢዉ የዳኝነት ክፍያ ሊፈጽም እንደሚገባ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት አቤቱታ ወይም ክስ የሚያቀርብ ሰዉ በዚህ አግባብ ተገቢዉን ሳይፈጽም ፍትሕ የማግኘት መብት ሊጠበቅልኝ ይገባል ለማለት አይችልም፡፡

ከዚህ ዉጭ ደግሞ ማንኛዉም ሰዉ አቤቱታ ወይም ክስ ለማቅረብ የሚፈልግ ሆኖ ሳለ የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል የገንዘብ አቅም የሌለዉ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.467--479 መሰረት ዳኝነት ሳይከፈልበት በነጻ ስለሚቀርብ ክስ መሰረት መብቱ ሊከበርለት ይገባል፡፡ የዳኝነት ገንዘብ በሙሉን ወይም በከፊል የመክፈል ገንዘብ የሌለዉ ወይም ሊያገኝ የማይችል ሰዉ፣ ድሃ መሆኑን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ያረጋገጠ እንደሆነ ነጻ ፋይል ተከፍቶለት መሰረታዊ መብቱን መጠየቅ እንደሚችል ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ በድሃ ደንብ በነጻ ፋይል ለማስከፈት አቤቱታ ወይም ክስ ሲቀርብ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙቸዉን ማስረጃ በማጣራት እንዲሁም አግባብነት ባለዉ ማስረጃ አጣርቶ ክስ አቅራቢዉ የገንዘብ አቅም የሌለዉ ድሃ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባዉ ያሳያል፡፡ አቤቱታ ወይም ክስ አቅራቢዉ ሰዉ በዚህ አግባብ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የዳኝነት ገንዘብ በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመክፈል የገንዘብ አቅም የሌለዉ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚህ ዉጭ ግን የዳኝነት ገንዘብ ላለመክፈል ሲባል የተለያዩ ዘዴዎች ወይም የማጭበርበር ድርጊት የሚፈጽም እንደሆነ በዚህ ደንብ መሰረት መዝገቡ በነጻ ሊከፈትለት አይገባም፡፡ ይህ ማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.470 ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች አለመኖራቸዉ እስካልተረጋገጠ ድረስ በድሃ ደንብ ፋይል ማስከፈት አይቻልም፡፡

በመሆኑም አንድ አቤቱታ ወይም ክስ አቅራቢ ሰዉ የዳኝነት ገንዘብ መክፈል አለበት? ወይስ በድሃ ደንብ መሰረት ፋይል ሊከፈትለት ይገባል? የሚለዉ የፍሬ ነገር ጉዳይ፣ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባ ጉዳይ ነዉ፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን ተጠሪ ላቀረበዉ ክስ የዳኝነት የሚከፍለዉ የገንዘብ አቅም ስለሌለኝ በድሃ ደንብ መዝገብ እንዲከፈትልኝ የሚል ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ደግሞ ተጠሪ ከዚህ ቀደም ወደ አስር ሚሊዮን ብር ክፍያ የተቀበለ ስለሆነ በድሃ ደንብ ፋይል ሊከፈትለት አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ አንጻር የአሁን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ይህን ክስ ባቀረበበት ወቅት የገንዘብ አቅሙ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያረጋግጥ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ የአሁን ተጠሪ ደግሞ የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን የገንዘብ አቋም/ደረጃ ምን ላይ እንዳለ ለማወቅ የድርጅቱ ሂሳብ በንግድ ሕጉ አግባብ በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ወይም በኦዲት ባለሙያ ተጣርቶ የቀረበ ማስረጃ ሊኖር እንደሚገባ ግልጽ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ሲታይ የአሁን ተጠሪ የገንዘብ አቅሙን የሚያረጋግጥ ይህን ዓይነት ማስረጃ ያቀረበ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች የሚያመለክቱት ነገር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዉሳኔዎቻቸዉ ተጠሪ አቀረበ የሚሉት ማስረጃዎች መካከል የሚፈለግበትን የመንግስት ግብር ያለመከፈሉን የሚያሳይ ማስረጃ እንደሆነ ነዉ፡፡ ይህ ማስረጃ ግን አጠቃላይ የተጠሪን የገንዘብ አቋም የሚያረጋግጥ አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ነዉ ብሎ ለመዉሰድ የሚያስችል ሆኖ አይገኝም፡፡ በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.79555 የሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተፈጻሚነት እንዳለዉ ማየት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ ላቀረበዉ ክስ የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል በቂ የገንዘብ አቅም የሌለዉ መሆኑን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በሥር ፍ/ቤት ያረጋገጠዉ ነገር ስለሌለ ተጠሪ በሕገ መንግስቱ የተመለከተዉ ፍትሕ የማግኘት መብት ሊጠበቅልኝ ይገባል የሚል ከሆነ ይህን የዳኝነት ገንዘብ ከፍሎ መዝገብ ተከፍቶለት ክርክሩን የማስቀጠል መብት አለዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ላቀረበዉ ክስ ተገቢዉን የዳኝነት ገንዘብ ከፍሎ ክርክሩን መቀጠል አለበት በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ሆኖ ሳለ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የገንዘብ አቅም የሌለዉ መሆኑን ባላስረዳበት ፋይል በነጻ እንዲከራከሉለት የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.196192 በ24/4/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 202599 በ18/4/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 00057 በ9/11/2006 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ ስለሆነ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የአሁን ተጠሪ ላቀረበዉ ክስ በደንቡ መሰረት ተገቢዉን የዳኝነት ገንዘብ የከፈለ እንደሆነ ፋይል ተከፍቶለት ክርክሩን የማቅረብ መብት አለዉ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት ለደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉ ይቻሉ፡፡
6. በ15/6/2008 ዓ.ም የተሰጠዉ እግድ በዚህ ውሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 97023

ታህሳስ 28 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን - ፋሲል በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አምባቸው ፈቀደነህ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ለተጠሪ ሊከፈለው የሚገባው ክፍያ ምን ያህል እንደሆን ሂሳቡ በአግባቡ ተጣርቶ አልቀረበም በማለት አመልካች የሚያቀርበውን ክርክር በማለፉ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ህጋዊ ስርዓትንና አሰራርን የተከተለ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪን የሚያከራክራቸው አመልካች 1998 ዓ/ም የበጀት አመት ላከናወነው የመንገድ ስራ ፕሮጅት የሚያገለግል ገረጋንቲ፣ ሶቦ ቤዝ የተፈጨ ገረጋንቲ፣ የአስፓልት ጠጠርና ቀይ አሸዋ ለማጓጓዝና አፈር እንዲደፋለት ባወጣው ጨረታ ተወዳድሮ ተጠሪ በማሸነፉ ተጠሪ ለአመልካች የሰጠው የማጓጓዝ ግልጋሎት መጠንና ዋጋ የሚመለከት ሆኖ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፈለው ቀሪ ክፍያ አለ ወይስ የለም? አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው ቀሪ ክፍያ አለ ከተባለ፤ የክፍያው መጠን ምን ያህል ነው? የሚሉት ጭብጦች ናቸው፡፡
2. ተጠሪ አመልካች በውሉ መሰረት ለሰጠው የማቴሪያል ማጓጓዝ ግልጋሎት ሊከፍለው የሚገባ ብር 3,204,391.23 (ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አራት ሺ ሶስት መቶ ዘጠና አንድ ብር ሃያ ሶስት ሳንቲም) ያልከፈለን ስለሆነ ቀሪ ክፍያ እንዲከፈል ይወሰንልኝ በማለት ሀምሌ 2 ቀን 1999 ዓ/ም የተጻፈ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ውል መኖሩን ሳይክድ ተጠሪ በተጭበረበረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰነድ ክፍያ የወሰደ መሆኑን ገልፆና የተጠሪን ክስ ክዶ ተከራክሯል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰይድ ዓሊ የተፈቀደላቸው የሒሳብ አዋቂዎችሒሳቡን አጣርቶ እንዲያቀርብ ካደረገ በኋላ፣ አመልካች ለተጠሪ ብር 3,747,741.44 (ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ ሰባት ሺ ሰባት መቶ አርባ አንድ ብር ከአርባ አራት ሳንቲም)ሊከፍል ይገባል በማለት በመዝገብ ቁጥር 57330 ህዳር 19 ቀን 2001 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡

3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57330 ህዳር 19 ቀን 2001 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ላይ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ካደረገና የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ፡- (ሀ) ተጠሪ የኮንስትራክሽን ማቴሪያሎች ያጓጓዘበት ዕርቀት ቀድሞ ተለክቶ የውሉ አካል ሆኗል ወይስ አልሆነም? (ለ) አመልካችና ተጠሪ አፈር ለማጓጓዝና ሌሎች የኮንስትራክሽን ማቴሪያል ለማጓጓዝ በአንድ ጨረታ ሁለት የተለያዩ ውሎች ተዋውለዋል? በክፍያ ሂደት ተጠሪ አፈር ለማጓጓዝና ሌሎች የኮንስትራክሽን ማቴሪያሎችን ለማጓጓዝ የሰራቸውን ስራዎች ቀላቅሎ የክፍያ ጥያቄ አቅርቦ ክፍያ ወስዷል ወይስ አልወሰደም (ሐ) ተጠሪ ለክፍያ አቅርቦ ክፍያ ከወሰደባቸው ሰነዶች መካከል የተጭበረበሩና በመመሳጠር አግባብ ክፍያ የተፈጸመባቸው ሰነዶች አሉ ወይስ የሉም? (መ) ሒሳቡ በገለልተኛ ባለሙያ እንደያጣራ ማድረግ የሚመለከቱ ጨብጦችን በመያዝ የስር ፍርድ ገለልተኛ ባለሙያ መድቦ ሒሳቡን በማጣራት ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ፣ ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 343(1) በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 42620 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መልሶ ልኮለታል፡፡

4. ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና አጣርቶ እንዲወሰን በመዝገብ ቁጥር42620 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ከመለሰለት በኋላ የመደበው ልዩ አዋቂ ባለሙያ ስራውን ያከናወነበት አግባብናየስር ፍርድ ቤት የልዩ አዋቂውን ባለሙያ በመቀበል የሰጠው ውሳኔ ህጋዊ አግባብነት ያለውን ስርዓት የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ጉዳዩን ከመለሰለት በኋላ የስር ፍርድ ቤት ሒሳቡን አጣርቶ እንዲያቀርብ አቶ በየነ ፈቀደ የተባሉ የሒሳብ ባለሙያ መድቧል፡፡ የሒሳብ ባለሙያ ከተመደቡ በኋላ አመልካች ለባለሙያው ጽ/ቤት የሰጣቸው ቢሆንም ሁለት ቀናት ብቻ የታዩ መሆኑን፤ የአመልካችን ሰነዶች በአግባቡ ተረክቦ ያልወሰደ መሆኑንና የሒሳብ ባለሙያው በገለልተኝነት ሒሳቡን ያጣራል የሚል ዕምነት የሌለው መሆኑን ገልጾ አቤቱታ ያቀረበ መሆኑንናበየነፈቀደ የተፈቀደለት የሒሳብ አዋቂ በበኩሉ አመልካች የሒሳብ ሰነዶቹን በሁለት ቀናት ውስጥ አደራጅቶ ካላቀረበለት በስራው ላይ ለሚፈጠረው ጉድለት አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኃላፊነቱን የሚወስድ መሆኑን ገልጾ ሚያዝያ 28 ቀን 2004 ዓ/ም ለአመልካች በቀጥታ ደብዳቤ መጻፉንና አመልካች በበኩሉ የሒሳብ ባለሙያው ለጻፉት ደብዳቤ ግንቦት 2 ቀን 2004 ዓ/ም ለበየነ ከበደ በቀጥታ በጻፈው ደብዳቤ መልስ የሰጠ መሆኑን፣ የሒሳብ ባለሙያና አመልካች ልዩነት የፈጠሩባቸው ጉዳዮች ላይ የስር ፍርድ ቤት መመሪያ ሳይሰጥ፣ የሒሳብ ባለሙያው በመሰለው ሒሳቡን ሰርቶ ሪፖርት ማቅረቡንና አመልካች የሒሳብ ሪፖርቱን በመቃወም አስተያየት ማቅረቡን፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በየነ ከበደ የተፈቀደለት የሒሳብ ባለሙያ የቀረበውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ አመልካችብር 3,757,077.56 (ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺ ሰባ ሰባት ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም) ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በመዝገብ ቁጥር 57330 ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል።

5. አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57330 ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት በመሰረዝ በመዝገብ ቁጥር 92820 ጥቅምት 25 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቷል። አመልካች ጥር 20 ቀን 2006 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 42620 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔና መመሪያ መሰረት ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው። የስር ፍርድ ቤት የዕርቀት ልኬትን በተመለከተ ለሁሉም ቦታ በ27 ኪሎ ሜትር ሒሳብ ክፍያ እንድንፈጽም መወሰኑ፣ አመልካች በተጭበርበሩና በመመሳጠር ክፍያ የወሰደባቸው ሰነዶች እያሉን ሰነዶች በማስረጃነት ሳያቀርቡና ይህንኑ የሚያስረዱ ምስክሮች ሳይሰሙ መወሰኑ፤ ሂሳቡን እንዲያጣሩ የተመደቡት ባለሙያ ሒሳቡን በአግባቡ ሳይሰሩ ሰነዶቹን ፈርመው ካቀረቡበት ሚያዝያ 8 ቀን 2004 ዓ/ም በፊት ሚያዚያ 3 ቀን 2004 ዓ/ም ሰርተው እንዳጠናቀቁ በመግለጽ ያቀረቡትን ሪፖርት በመቀበል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል።

6. ተጠሪ በበኩሉ መጋቢት 3 ቀን 2006 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የዕርቀት የልኬቱን መጠን አመልካች አስቀድሞ በመወሰን የውሉ አካል አድርጎታል ይህንን ዕውነት የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙችን ከተለዋወጥናቸው ደብዳቤዎች የማስረጃ ይዘት በመገንዘብ በውሳኔው በግልጽ አስፍሮታል። ተጠሪ አመልካች ያሳተማቸውን 20,000 የጭነት ደርሰኞች አቅርበሌለሁ ሒሳቡም በገለልተኛ ባለሙያዎች ተጣርቶ ትክክል እንዲሆን ተረጋግጧል፤ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት መቅረብ የሌለባቸውን የፍሬ ነገር ክርክሮችን በማቅረቡ የህግ መሰረት የሌለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካች መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።

7. ከስር የክርክር አመጣጥና ግራቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛ የስር ፍ/ቤት የአመልካችና የተጠሪን ሒሳብ በገለልተኛነት አጣርቶ እንዲቀርብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 136/1/ መሰረት የመደበው በየነ ፈቀደ የተፈቀደለት የሒሳብ አጣሪ ባለሙያ ሂሳቡን በገለልተኛነት እንዲያጣራ ተገቢውን መመሪያ በመስጠትና የሒሳብ ባለሙያው ግራቀኙ አሉን የሚሏቸውን ሰነዶችና አንደኛቸው ሌላው ባቀረበው ሰነድ ላይ ያቀረቧቸውን ተቋውሞዎች ከሙያ አንጻር በመመርመር ሚዛናዊ የሆነ የሒሳብ ሪፖርት እንዲቀርብና ሃላፊነቱን እንዲወጣ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? የሚለው ጭብጥ ተመልክተናል።

8. ይህንን ጭብጥ ለመወሰን፣ በአገራችን የፍትህ ስርዓት በፍርድ ቤት የሚመደብ የልዩ አዋቂ፣ በሙያው አጣርቶ እንዲያቀርብ በፍርድ ቤት የታዘዘውን ነገር ሲያጣራ ስላለበት ሃላፊነትና ሊከፍለው ስለሚገባው የአሰራር ስርዓትና ሊከተለው ስለሚገባ ስነ ምግባር በጥልቀት ማየት ያስፈልጋል። በአገራችን የሕግ ስርዓት አንደኛው ወገን ከሌላው አካል ሊከፈለኝ ይገባል ስለሚለው ገንዘብ በግሉ ልዩ አዋቂ ቀጥሮ በማስጠናት፣ በግል የቀጠረው ልዩ አዋቂ የቀረበለትን የምርመራ ውጤት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 223 እና በፍታብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 137/1/ መሰረት በማስረጃነት በማያያዝና ልዩ አዋቂውን በምስክርነት በመዘርዘር የዳኝነት ጥያቄውን ወይም ክርክሩን ለማቅረብ የሚችል መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘትና አላማ ለመረዳት ይቻላል። ሆኖም በአንደኛው ወገን ቀጣሪነት በልዩ አዋቂ ተመርምሮ የቀረበው ግኝት ተዓማኒነትና ክብደት ያለው ማስረጃ ተደርጎ በፍርድ ቤት የሚወሰደው የልዩ አዋቂውን የምርመራ ውጤት ሌላኛው ወገን ሳይቃወም ትክክለኛ የምርመራ ውጤት ነው ብሎ የተቀበለው በሆነ ጊዜ ብቻ እንደሆነ የፍታብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አንቀጽ 250 " ተከራካሪዎቹ ወገኖች ወይም አንደኛው ወገን ክስ የቀረበበት ሃብት ግምት ወይም ዋጋ ምክንያት ባለመስማማት ክርክር ያቀረቡ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ጭብጡን ከመመስረቱ በፊት ነገሩ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ወስኖ በዚህ ሕግ ቁጥር 132 ወይም በፍታብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 136 በተነገረው መሰረት የሃብቱን ግምት የሚያሳውቁ ምትክ ዳኞች ይሾማል" በማለት ደንግጓል።

9. ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው በአንደኛው ተከራካሪ ወገን የተቀጠረ ልዩ አዋቂ ባለሙያ በምርመራ ሒደት አግኝቻለው የሚለው ግኝትና ውጤት ሌላው ተከራካሪ ወገን ካልተስማማበት፣ ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት የምትክ ዳኛ ስልጣን ያለው ልዩ አዋቂ ባለሙያ የመመደብ ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ የአመልካችንና የተጠሪን ሒሳብ አጣርቶ እንዲቀርብ በስር ፍ/ቤት በሒሳብ አጣሪነት የተሾመው "በየነ ፈቀደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈቀደለት የሒሳብ አጣሪ ባለሙያ" አመልካችና ተጠሪ በየግላቸው የሒሳብ ባለሙያዎች አሰርተው ባቀረቡት የሒሳብ ምርመራ ውጤት ባለመስማማታቸው ምክንያት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 250 መሰረት የስር ፍ/ቤት የመደበው ልዩ አዋቂና መርማሪ ብቻ ሳይሆን፣ የስር ፍ/ቤት ህዳር 14 ቀን 2001 ዓ.ም ለሰጠው ውሳኔ መሰረት የሆነውን የሒሳብ ሪፖርት ያቀረበው ሰይድ አለ የተፈቀደላቸው የሂሳብ አጣሪ፣ ሒሳቡን ገለልተኛ ሆኖ አላጣራም በሚል ምክንያት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ሂሳቡ በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ እንዲጣራ ለማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 42620 መስከረም 20 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔና መመሪያ መሰረት የተመደበ የሂሳብ አጣሪ ነው፡፡

10. የሂሳብ አጣሪው የስር ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136 መሰረት የመደበው የልዩ አዋቂ /ኤክስፐርት/ ነው፡፡ ሒሳብ አጣሪው በፍ/ቤቱ ሒሳቡን አጣርቶ እንዲቀርብ የተሾመ በመሆኑ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሁሉ ከግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች ጋር ያለው ግንኙነት የሙያውን ስነ-ምግባርና ገለልተኝነትን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ የሒሳብ አጣሪው በስራ ሂደት ሊቀርቡለት የሚገቡ ጠቃሚ ማስረጃዎች ከአንደኛው ተከራካሪ ወገን ወይም በሁለቱም ወገን ተከራካሪዎች ወይም በሌላ ሶስተኛ ሰው ሳያቀርቡለት ቢቀሩ ወይም ቢዘገዩበት ይህንኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136 መሰረት በሂሳብ አጣሪነት ለሾመው ፍርድ ቤት በማሳወቅ ፍ/ቤቱ ስለሰነዶቹ አቀራረብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 132፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 145 /1/ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች መሰረት ትእዛዝ እንዲሰጥበትና የማጣራት ስራው ስለሚከናወንበት ሁኔታ መመሪያ እንዲሰጠው ከመጠየቅ ውጭ፣ አንደኛውን ወገን፣ ማስረጃዎችህን በሁለት ቀን፣ ወይም በአንድ ሳምንት ውስጥ ካላቀረብክ፣ ያንተን ሰነዶች የማልቀበልና በሂሳብ ሪፖርቴም የማላካትተው መሆኑን እንድታውቀው በማለት በቀጥታ ለአንደኛው ወገን ማስጠንቀቂያ መስጠትና የአንደኛውን ወገን ሰነድ ሳይቀበልና ሳያካትት የሒሳብ ሪፖርቱን ሰርቶ የማቅረብ ተልዕኮው የማይፈቅድና ስልጣንም የሌለው መሆኑን፣ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 132 እስከ ፍታብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 136 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘትና መሰረታዊ አላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

11. በያዝነው ጉዳይ የአመልካችና የተጠሪን ሂሳብ የሙያውን ስነ-ምግባርና የፋይናንስና የክፍያ ሕጎችንና ደንቦችን መሰረት በማድረግ፣ የግራቀኙን የሰነድ ማስረጃዎችና አንደኛው በሌላው ሰነድ ላይ የሚያቀርቡትን ተቃውሞ ከሙያ አንጻር መርምሮ ሪፖርቱን እንዲያቀርብለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሾመው "በየነ ፈቀደ የተፈቀደለት የሂሳብ አጣሪ" ለምርመራ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን በማቅረብ ሂደት የተፈጠሩ ችግሮችን በምትክ ዳኝነት ለሾመው ፍ/ቤት በማሳወቅ ፍ/ቤቱ ትእዛዝና መመሪያ እንዲሰጥበት የማድረግ አሰራርን ተከትሎ ሒሳቡን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማጣራት ሪፖርቱን ያላቀረበ መሆኑን የሒሳብ አጣሪው ለአመልካች በቁጥር በከሂአ/014/2004 ሚያዝያ 28 ቀን 2004 ዓ/ም በቀጥታ ከሰጠው ማስጠንቀቅያ ይዘትናማስጠንቀቅያው የሒሳብ አጣሪውን ገለልተኝነትና በተሰጠው የስልጣን ወሰን ስር ሆኖ ሒሳቡን ያከናወነ መሆኑን በመመዘን ሂደት ከሚኖረው ህጋዊ ውጤት ከመረመረው ለመረዳት ይቻላል፡፡

12. የሒሳብ አጣሪው ሒሳቡን በሚመረምርበት ጊዜ የሰነዶች አቀራረብ ሂደት ያጋጠመውን ችግር ለሾመው ፍ/ቤት በማሳወቅ ፍ/ቤቱ ቀጣዩ ትእዛዝ እና የስራ መመሪያ እንዲሰጥበት መጠየቅ ሲገባው ራሱ ውሳኔ ሰጭ በመሆን አመልካች በሁለት ቀናት ውስጥ ሰነዶችን አደራጅቶ ካላቀረበለት የሌላኛውን ወገን /የተጠሪን/ ሰነዶች መሰረት በማድረግ ሪፖርቱን ሰርቶ እንደሚያቀርብና በዚህ ምክንያት ለሚፈጠረው ችግር አመልካች ሀላፍነቱን የሚወስድ መሆኑን የሚገልፅ የማስጠንቀቅያ ደብዳቤ በመፃፍ አመልካችም ለሒሳብ አጣሪው ማስጠንቀቅያ ተገቢነት የሌለው መሆኑን የሚገልፅ ምላሽና ደብዳቤ ለሒሳብ አጣሪው በአድራሻቸው በቀጥታ በቁጥሩ 2132/ዎ/ሥ/አስ/9314 ግንቦት 2 ቀን 2009ዓ/ም ደብዳቤ ፅፎለታል ። ይህም የሚያሳየው በሥራ ሂደት የሒሣብ አጣሪው አንደኛውን ተከራካሪ /አመልካችን/ የሚኮንን አኳኋን አቋምን በቀጥታ ለአመልካች በመግለፅ የሒሳብ አጣሪው ገለልተኝነት ጥርጣሬ ውስጥ የሚጥሉ ተግባራትን በፍርድ ቤት ከተሰጠው የአጣሪነት ሹመት ወሰን በማለፍ የፈፀመ መሆኑን ነው፡፡

13. የሒሳብ አጣሪው አመልካችን ሰነድህን አልቀበልህም በማለት የሰጠው ማስጠንቀቅያ በሒሳብ ሪፖረቱም ላይ የተንፀባረቀ መሆኑን የሚያሳይ መሰረታዊ ነጥቦች አሉ፡፡ በአብነት ለማንሳትም አመልካች ተጠሪ በተጭበረበሩ የሒሳብ ሰነዶችና በመመሳጠር የማጓጓጉያ አገልግሎት ሳይሰጥ ክፍያ ወስዶባቸዋል የሚላቸውን ደረሰኝ ቁጥሮት ፕሮጀክቱን የሚገኝበትን ስፍራ በዝርዝር በመመስረት ለፍ/ቤቱ ያቀረበው መሆኑን በትእዛዝ ካስቀረበ ነው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 57330 ተረድተናል፡፡ በአንፃሩ የሒሳብ አጣሪው ባቀረበው ሪፖርት ውስጥ አመልካች በተጭበረበረ ሰነድና በመመሳጠር ተጠሪ ያልሰጠው አገልግሎት ክፍያ ወስዶባቸዋል በማለት ለይቶ በዝርዝር ስላወጣቸው ሰነዶች የተሰጠው ሙያዊ አስተያየት አለመኖሩ የሒሳብ አጣሪው ሚያዝያ 28 ቀን 2004 ዓ/ም በሰጠው ማስጠንቀቅያ መሰረት የሒሳብ ሪፖርቱን የአመልከችን ሰነዶች ሳይመለከትና በአግባቡ ሳይመረምር ያዘጋጀው ስለመሆኑ በእርግጠኝነት ለመናገር ለመደምደም የማያስችል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡የስር ፍ/ቤት የሒሳብ ምርመራ ሂደት ሒሳብ አጣሪው ያጋጠመውን ችግር ለፍ/ቤቱ እንዲያሳውቅ እና በጎንዮሽ ከአንዳቸው ተከራካሪ ወገኖችጋር ማስጠንቀቅያ የመፃፍ እና የሒሳብ አጣሪውን ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚጥሉ ተግባራትን መመሪያና ትእዛዝ መስጠት ሲገባው የሒሳብ አጣሪው በፍትሐብሔር ስነስርዓት ህግ ቀጥር 136(2) ከተደነገገው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውጪ የአመልካችን የሒሳብ ሰነድና መቃወሚያና አስተያየት ሳያካትት መርምሮ ያቀረበለትን ሪፖርት ተቀብሎ ውሳኔ መስጠቱ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 134 የፍታብሄር የስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 135 እና የፍታሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 136 ድንጋጌዎች ያልተከተለ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

14. ከላይ በዝርዝር የገለፅነው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ አመልካች እንዲከፍለው የጠየቀው ብር 3,204,391.33 መሆኑ ሐምሌ 2 ቀን 1999ዓ/ም ፅፎ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ በግልፅ ሰፍሮ እያለ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በግልፅ ዳኝነት ያልተጠየቀበትን 3,757,077.56 እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182 ንኡስ አንቀፅ (2) የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአጠቃላይ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሒሳብ አጣሪው የተሰጠውን በገለልተኝነት የግራ ቀኙን ሒሳብ አጣርቶ የማቅረብ ሀላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ ተገቢውን መመሪያ ሳይሰጥ የሒሳብ አጣሪው አመልካች የተጭበረበሩና በመመሳጠር ሒሳብ ተከፍሎባቸዋል የሚላቸውን ሰነዶች በአግባቡ ሳይመረምር ያቀረበውን የሒሳብ ሪፖርት ተቀብሎ የሰጠውን ውሳኔ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ አይቶ ማረም ሲገባው በትዕዛዝ ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከ/ፍ/ በመቁ 57330 ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 92820 ጥቅምት 25 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከ/ፍ/ቤት የፌደራል አዲት ኮሚሽን ልምድና ዕውቀት ያላቸው የሒሳብ ባለሞያዎች በመመደብ የአመልካች እና የተጠሪን ሒሳብ አጣርተው እንዲያቀርቡለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 136(1) መሰረት ትእዛዝ በመስጠት በማጣራቱ ሂደት ከባለሙያዎች ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ተገቢውን መመሪያና ትእዛዝ በመስጠት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት ጉዳዩ መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት የወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.100295

ህዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ
ተኽሊት ይመሰል
ቀነዓ ቂጣታ
ሰናይት አድነው
ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች.....አቶ ደጓለ ገዳሙ -ቀርበዋል
ተጠሪዎች.....1. አቶ ላይኩን ሙሉጌታ -ቀርበዋል
2. ወ/ሮ አለምፀሐይ ወርቁ -የቀረበ የለም
3. ወ/ሮ አይችል እጅጉ
4. ወ/ሮ ትዕግስት እጅጉ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ዉል ለማስፈጸም የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ሲሆን፣ በምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ጣልቃ ገብ፣ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከሳሾች እና የአሁን 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የሥር ከሳሾች ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ አይችል እጅጉ በ2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ትዕግስት እጅጉ በተሰጣት የዉክልና ስልጣን መሰረት በብቸና ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኘዉን በ2ኛ ተከሳሽ ስም የሚታወቀዉን የመኖሪያ ቤት ቁጥር 1326 ስለሸጠችልኝ ዉሉ እንዲፈጸምልኝ ቤቱን ከነወጪዉ እንዲያስረክቡኝ በማለት ክሷል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሥር ጣልቃ ገብ አቶ ደጓለ ገዳሙ ባቀረበዉ የጣልቃ ገብ አቤቱታ ጣልቃ ገብ እና 1ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ትዕግስት እጅጉ በባህል ጋብቻ ባልና ሚስት ሆነን ሲንጋባ በፈጸምነዉ የጋብቻ ዉል ይህን መኖሪያ ቤት የጋራ ንብረታችን ያደረግን በመሆኑ እኔ ሳላዉቅ ተከሳሾች ቤቱን ለከሳሾች ስለሸጡ ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር በማለት አመልክቷል፡፡

የሥር ጣልቃ ገብ አቤቱታ ላይ የሥር ከሳሾች ባቀረቡት መልስ ከዚህ ቀደም ጣልቃ ገብ በዚህ ጉዳይ በወረዳዉ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቦ በሁለት መዝገቦች በመ.ቁ.5444 እና 5520 ላይ ዉድቅ የተደረገበት በመሆኑ ጣልቃ ለመግባት የቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ብይን ጣልቃ ገብ ይህን መኖሪያ ቤት በተመለከተ ከዚህ ቀደም ሁለት ጊዜ አቤቱታ አቅርቦ በመ.ቁ.5520 እና 5444 ላይ አቤቱታዉ ዉድቅ ያደረገ በመሆኑ አሁንም ጣልቃ ገብቹ ልከራከር በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሰረት ተቀባይነት የለዉም በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ጣልቃ ገብ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የሰበር አቤቱታዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቶቹ የቀረበዉን ቅሬታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት ብይን በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ28/08/2006 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት፡--የአሁን አመልካች እና 4ኛ ተጠሪ ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ባልና ሚስት ሆነን ስንጋባ ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ቤት በብቸና ከተማ 01 ቀበሌ የቤት ቁጥር 1326 የሆነዉን የጋራ ንብረት ያደረግነዉን እኔ ሳልሰማ እና ሳልፈቅድ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያለ አግባብ በብር 140,000 ገዛን በማለት ዉል እንዲፈጸምላቸዉ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችን በመክሰሳቸዉ ጣልቃ ለመግባት አቤቱታ አቅርቤአለሁ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን አቤቱታዉን መቀበል ሲገባቸዉ ከዚህ ቀደም የወረዳዉ ፍ/ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ ከ100,000 ብር በላይ የሆነ ጉዳይ የመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት በመ.ቁ.05444 እና 5520 የሰጠዉን ብይን እንደመጨረሻ ዉሳኔ በመቁጠር በአዲስ ስልጣን ላለዉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡትን የጣልቃ ገብ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሰረት ዉድቅ ማድረጋቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልኝ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብቹ እንድከራከር እንዲፈቀድልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን የቤት ሽያጭ በተመለከተ የማየት ስልጣን የለኝም ያለበት ሲሆን ጉዳዩ ስልጣን ላለዉ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ሲቀርብ የአሁን አመልካች ጣልቃ ለመግባት ያቀረበዉ አቤቱታ ከዚህ ቀደም በወረዳዉ ፍ/ቤት ዉድቅ ስለሆነ እንደገና የጣልቃ ገብ አቤቱታ ማቅረብ አትችልም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ በታዘዘዉ መሰረት የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ18/10/2006 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ መልስ እና 3ኛ ተጠሪ ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ አንድ ገጽ መልስ እና 4ኛ ተጠሪ በ18/10/2006 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ይዘት ሲታይ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ የቀረበዉ ቅሬታ ዉድቅ ተደርጎ የሥር ፍ/ቤት እንዲጸናልን በቂ ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን 3ኛ ተጠሪ ያቀረበችዉ መልስ ይዘት ሲታይ በተሰጣት ዉክልና መሰረት ቤቱን የሸጠች መሆኑን በመግለጽ በሐሰት ችግር እየፈጠረች ያለችዉ 4ኛ ተጠሪ እንደሆነች በመጥቀስ በሕግ አግባብ ዉሳኔ ቢሰጥ የማትቃወም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኖዋን በመግለጽ ተከራክራለች፡፡ የአሁን 4ኛ ተጠሪ መልስ ይዘት ሲታይ የአመልካችን ቅሬታ በሚደግፍ መልኩ በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነዉ ለክርክር መነሻ የሆነዉ መኖሪያ ቤት የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር በተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል በብር 140,000 /አንድ መቶ አርባ ሺህ/ ስለገዛን በዉሉ መሰረት እንዲፈጸምላቸዉ ክስ በማቅረብ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ የጣልቃ ገብ ጥያቄ ይህ ቤት በጋብቻ ዉል የጋራ ንብረት ስለሆነ ወደ ክርክሩ ገብቼ እንድከራከር እንዲፈቀድልኝ የሚል ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን ጉዳዩን በማየት ከዚህ ቀደም አመልካች ይህን ቤት በተመለከተ አቤቱታ አቅርበዉ ዉድቅ ስለሆነ አሁን ማቅረብ አይችልም በማለት መወሰናቸዉ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች ያመለክታል፡፡

ነገር ግን የየእነማይ ወረዳ ፍ/ቤት የመ.ቁ.5444 እና 5520 የሆኑትን መዝገቦች የዘጋዉ ጉዳዩን ለማየት የሥር ነገር ስልጣን ስለሌለዉ እንደሆነ ከሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአሁን አመልካች አስቀድሞ ያቀረበዉ አቤቱታ በእነዚህ መዝገቦች ላይ በተሰጠዉ ትዕዛዝ ዉድቅ የተደረገ መሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን መኖሪያ ቤት በተመለከተ የቀረበዉን ክርክር ለማየት የሥረ ነገር ስልጣን ስለሌለዉ መዝገቡን የዘጋ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ዋናዉን ክርክር እንዳላየ ስለሚቆጠር መዝገቡን ከመዝጋቱ በፊት የሰጠቸዉ ትዕዛዞች ምንም ዓይነት የአስገዳጅነት ዉጤት የላቸዉም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት መጀመሪያዉኑ ይህን ቤት በተመለከተ የቀረበለትን ክስ ተቀብሎ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት በሕጉ አግባብ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን የክልሉ የፍ/ቤቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 169/2002 ዓ.ም መሰረት በማድረግ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 /1/ እና 231 /1/ /ለ/ በሚደነግገዉ አግባብ ክሱ ተቀባይነት የለዉም በማለት መመለስ ይገባዉ ነበር፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን ሳያደርግ የቀረበዉን ክስ ተቀብሎ ከአከራከረ በኋላ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 /2፣ ሀ/ እና 245 /2/ መሰረት መዝገቡን ዘግቶ ተከራካሪዎቹን ያሰናበታቸዉ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች ያመለክታል፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት በዚህ መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋ እንደሆነ ዋናዉን ክርክር እንዳላየ ስለሚያስቆጥረዉ በመዝገቡ ላይ የሰጣቸዉ ማናቸዉም ትዕዛዞች በማንኛዉም ወገን ላይ ሕጋዊ የሆነ አስገዳጅነት ዉጤት የላቸዉም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋ እንደሆነ፣ ይህ ደግሞ ክርክሩን እንደአዲስ ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት ከማቅረብ የሚከለክል ባለመሆኑ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጣቸዉ ትዕዛዞች አዲስ በቀረበዉ ክርክር ላይ ዉጤት ሊኖራቸዉ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለኝም በማለት የወሰነ እስከሆነ ድረስ አስቀድሞ የሰጣቸዉ ትዕዛዞችን ሕጋዊ ዉጤት ስለሌላቸዉ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ማሻር አስፈላጊ አይደለም፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን እንደአዲስ የሚያይ በመሆኑ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉን ትዕዛዝ ታሳቢ በማድረግ የሚሰራበት አግባብ የለም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 /1/ መሰረት ጉዳዩ ከዚህ ቀደም የመጨረሻ ፍርድ ወይም ዉሳኔ አግኝቷል ሊባል ስለማይችል በዚህ ምክንያት የሥር ከፍተኛዉ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ከዚህ ቀደም የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን ቤት በተመለከተ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋ መሆኑን በመገንዘብ፣ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበዉ አዲስ ክርክር ሆኖ ሳለ የአመልካች ክርክሩ መብቴን ስለሚነካ ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር እንዲፈቀድልኝ በማለት የቀረበዉን አቤቱታ በመቀበል ወደ ክርክሩ ገብቶ እንዲከራከር ማድረግ ሲገባቸዉ፣ ከዚህ ቀደም የወረዳዉ ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ስላደረገ ጣልቃ መግባት አይችልም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ በመሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.108283 በ10/03/2005 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.34629 በ03/03/2006 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህን ፍርድ በማጽናት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.35215 መጋቢት 15 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በድጋሚ በማየት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የጣልቃ ገብ አቤቱታ በመቀበል ግራ ቀኞቸዉ በጉዳዩን ላይ እንዲከራከሩ በማድረግ ጉዳዩን በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 /1/ መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. በዚህ መዝገብ ሰኔ 18 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 124669

ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተሽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የሳስኮ ኢንዱስትሪያል ንግድና ትራንስፖርት ድርጅት፡-

ጠበቃ አቶ አብደላ አሊ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር፡- ነ/ፈጅ አማረች መለስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የስር ክሳሽ የአሁን አመልካች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ያቀረቡት ክስ ከተከሳሽ ጋር ውል የፈፀምን ሲሆን ይኸውም የመስታዋት ማንጓዝ ስምምነት ሆኖ ለሆሳዕና ዩንቨርስቲ 400 ኩንታል መስተዋት የአንዱ ዋጋ 69.00 /ስልሳ ዘጠኝ ብር/ በቀጥላላ 27,600.00 /ሃያ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ብር/ ለደብረታቦር ዩኒቨርስቲ 400 ኩንታል መስተዋት የአንዱ ዋጋ በብር 114.00 /አንድ መቶ አስራ አራት ብር/ በቀጥላላ 45,600 /አርባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ብር/ ለቡራ ሆራ ዩኒቨርስቲ 400 ኩንታል መስተዋት በብር 114.00 /አንድ መቶ አስራ አራት ብር/ በጠቅላላ 45,600 /አርባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ብር/ ከላይ የተጠቀሰው ሰራዎች በጠቅላላው ድምር 118,800.00 /አንድ መቶ አስራ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ብር/ የሚያወጣ ስራ ሰርቼ ተከሳሽ ሊከፍለኝ ሲገባ ያልከፈለኝ ስለሆነ እርክክቡ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ፣ ወጪና ኪሳራ ጋር ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት በመጠየቃቸው ነው፡፡

ተከሳሽ በወኪሉ አማካኝነት በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃመሚያ ክሳሽ ችሎታ የለውም በሚል መከራከሪያ አቅርቦ በተጨማሪም ይህ ቢታለፍ ብለው ተከሳሽ መሰሪያ ቤት አስተዳደር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መ/ቤት በመሆኑ ከከሳሽጋር የሚደረግ ውል በጽሁፍ መሆን ሲገባው በጽሁፍ የተደረገ ውል የለንም ስለሆነም ከሳሽ ክስ ማቅረብ አይችልም ይችላል እንኳን ቢባል ከሳሽ ለአስሩ ዩኒቨርስቲዎች መስተዋቱን ለማቅረብ ጨረታ አሸንፎ ለሶስት ዩኒቨርስቲ ብቻ በማቅረብ ክፍያ መጠየቅ አይችልም ከሳሽ ካንዳዘው መስተዋት ውስጥም በከፊል የተሰበረ በመሆኑ ይኸው ተቀንሶ እንዲከፈለው ሲባል ከሳሽ ያልተስማማ በመሆኑ ውሉን ያፈረሰ በመሆኑ ከክሱ በነፃ ልሰናበት ይገባል ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱም በተከሳሽ በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ ካከራከረ በኃላ በከሳሽና በተከሳሽ በኩል የተፈፀመው ዉል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3131-3132 ድረስ በተገለፀው መሠረት ከአስተዳደር መስሪያ ቤት ጋር የተፈፀመ ውል ሲሆን ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1724 መሠረት በጽሁፍ ሊደረግ ሲገባው ባለመደረጉ ውሉ በህጉ መሠረት የተቀመጠው የአጻጻፍ ስርአትን ያሟላ አይደለም በማለትና ይህ ደግሞ በ1720/1/ መሠረት ከረቂቅ የዘለለ ውጤት የለውም በማለት ክሱን ውደቅ በማድረግ ሲወሰን የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ቅሬታው በይግቦኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገቡን መርምሮ ቅሬታው መልስ ሰጪን እያስጠራም በማለት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

ለሰበር የቀረበው አቤቱታ በአመልካችና በተጠሪ መሀከል የተፈፀመ ውል የጨረታ ሆኖ እያለ የአስተዳደር ውል ነው ተብሎ በጽሁፍ ሊደረግ ሲገባ በጽሁፍ አልተደረገም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ውሉ የአስተዳደር ቢሆን እንኳን በፍ/ብ/ህ/ቁ 3141-3117 ድረስ የተደረገ ህጋዊ ውል ሆኖ እያለ በስር ፍ/ቤቶች ክሱ ውድቅ ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታልና ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

በሰበር አጣሪው ችሎት ተጠሪ ሚኒስቴር መሰሪያ ቤት መስተዋት የማቅረብ ማንዳዝ ጨረታ አውጥቶ አመልካች ተወዳድሮ አሸንፎ ለሶስት ዩኒቨርስቲዎች ያቀረበ መሆኑ ባልተካደበት ያንዳዘበት ዋጋ ሲጠየቅ ውላችን በጽሁፍ አልተደረገምና ሊከሰኝ አይገባም ተብሎ በቀረበ ክርክር መነሻነት ክሱ ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ለማጣራት ተጠሪ ይጠራ በማለቱ ተጠሪ መስሪያ ቤት በሰጠው መልስ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተገቢና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ ሊፀና ይገባል ካለ በኃላ አመልካች ድርጅት በውሉ መሠረት ለአስር ዩኒቨርስትዎች ያላቀረቡ ስለሆነ ልንከፍል አይገባም ብለዋል፡፡

በመሠረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 3132/2/ ስር እንደተመለከተው ውሉ ከህግ አገልግሎት ስራ ጋር የተያያዘና ለስራውም አፈፃፀም የተዋዋዩን ስራ ተካፋይነት ሳያቋርጥ የሚጠይቅ በሆነ ጊዜ ውሉ የአስተዳደር መ/ቤት ውል እንደሆነ ይደነግግና በፍ/ብ/ህ/ቁ 3131/1/ ስር እንደተመለከተው መንግስት ወይም ሌሎች የአስተዳደር ሰራተኞች የሚዋዋሏቸው ውሎች ስለውሎቹ በጠቅላላና ስለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ ውሎች የተሰጡት የዚህ ውል ድንጋጌዎች በጠቅላላው እንደሚፀናላቸው ይደነግጋል፡፡ ስለ ውሎች በጠቅላላው በተፃፈው የፍ/ብ/ህ/ቁ 1724 ስርም እንደተመለከተው ከአስተዳደር መ/ቤት ጋር የሚደረጉ ውሎች በጽሁፍ ሊደረጉ እንደሚገባ ይደነግግና በፍ/ብ/ህ/ቁ 1720 ስር እንደተመለከተው ውልን ለማቋቋም በጽሁፍ እንዲደረጉ የታዘዙ ውሎች በጽሁፍ ካልተደረጉ እንደ ረቂቅ እንደሚቆጠሩ ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 242 ስር እንደተደነገገው ማናቸውም ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልሱ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለፀ እንደሆነ ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 241 መሠረት በሚደረግ ምርመራ የእምነት ቃሉን የሠጠ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በታመነው ነገር ላይ ብቻ ፍርድ መሰጠት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይህ ማለት ለአንድ ለቀረበ ክርክር የተሰጠው መልስ የታመነ እስከሆነ ድረስ ፍ/ቤቱ በታመነው መሠረት ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚገባና ወደ ማስረጃ የሚገባው በክስ አይነት ካልታመነ ብቻ እንደሆነ የተደነገገ ነው፡፡ ስለሆነም ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ውሉ በጽሁፍ ነው ወይስ በቃል የውሉ ይዘት ምን ነበር እየተባለ የሚጣራው በክሱ መሠረት ካልታመነ ነው፡፡ በቀረበው ክርክር የስር ተከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ ለቀረበበት ክስ የሰጠው መልስ የእምነት መሆኑ ከክርክሩ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስ ፍርድ ቤቱ ከቀረበው ክስ እና መልስ አንጻር ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

ከዚህ መነሻ ሲደረግ የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን ከሰማ በኃላ ውሉ ከአስተዳደር መ/ቤት ጋር የተፈፀመ በመሆኑ በጽሁፍ መደረግ ሲገባው አልተደረገም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሲሰጥ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ማረም ሲገባው አልፎ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111159 በቀን 21/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ውሳኔ በማጽናት በመዝገብ ቁጥር 170506 በቀን 26/4/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በስር ክሳቸው ለሶስት ዩኒቨርስቲዎች መስታወቶችን አንጉዳፎአለሁ ሲሉ ተጠሪም ለሶስት ዩኒቨርሰቲዎች አመልካች ያቀረበ ቢሆንም ካቀረባቸው መስታውቶች ዉስጥ የተሰባበሩ መስተዋቶች መኖራቸውን በገለፀው መሠረት አመልካች በሶስት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዩኒቨርስቲዎች ለእያንዳንዱ ዩኒቨርስቲ ምን ያህል ኩንታል መስታወት እንዳንጓዙ የአንዱ ኩንታል ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ አመልካች ካንጓዘው ውስጥ ምን ያህሉ እንደተሰበረ በግራ ቀኙ ውል መሠረት ለተጠሪ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ አለ ወይስ የለም የሚከፈላቸው ከሆነስ ሊከፈላቸው የሚገባው የገንዘብ መጠን ምን ያህል እንደሆነ በማስረጃ ተጣርቶ ይወሰን ዘንድ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341/1/ መሠረት ልከናል፡፡

3. ለዚሁ ፍ/ቤት ክርክር የተደረገ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሰቸውን ይቻሉ፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ በውሳኔ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 99474

ሕዳር 30ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች(ዎች)፡- 1. ወ/ሮ ሙሉነሽ ደሬሳ

2. አቶ ዮሐንስ ይባስ

3. ወ/ሮ ቆንጂት ይባስ

4. ወ/ሮ መቅደስ ይባስ

ጠበቃ መስፍን እሸቱ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ማሚቴ ጌታቸው ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፍርኖ ከበደ ተወካይ ደረጃ አያሌው ቀረቡ

3. የአዲስ አበባ ከተማአስተዳደር ልማትና የቤቶች ጉዳይ ኤጀንሲተተኪ /የቦሌክፍለከተማ ቀበሌ 14/15 የዲዛይንና ግናባታ ልማት አስተዳደር ጽ/ቤትደረጀ ማርቆስ ነ/ፈጅቀ

4. የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 14/15 አስተዳደር ጽ/ቤት ደረጀ ማርቆስ ነ/ፈጅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች በውርስ ያገኘናቸው ሁለት ቤቶች ሽራተን አዲስ ሲገነባ በልማት ምክንያት የፈረሱ በመሆኑ፣ የመንግስት አልታድ ከሚባለውድርጅት ጋር አድርጎት በነበረው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስምምነት መሰረት በፈረሱት ሁለት ቤቶች ምትክ የተሰሩትን የቤት ቁጥር 459 እና የቤት ቁጥር 530 ተከሳሾች /ተጠሪዎች/ እንዲያስረክቡ ውሳኔ ይሰጥልን በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ የበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉትን በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

2. የክርክሩ መነሻ ከሳሾች /አመልካቾች/ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካቾች አንደኛ አመልካች የአቶ አብተስላሴ ወራሽ መሆኗንና ስማቸው ከሁለተኛ እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር የተገለጹት አመልካቾች የሟች ይባስ ሰዳን ወራሽ መሆናቸውን ገልጸው፤ የከሳሾችአውራሽ ሟች ይባስ ሰዳን በህይወት እያለ በወረዳ 14 ቀበሌ 24 ቁጥር 382 እና ቁጥር 379 የሆነ ቤቶች አፍርተዋል፡፡ ሟች ከዚህ አለም በሞት ሲለይ 1964 ዓ/ም የሟች ወራሾች በመሆናችን ከፍርድ ቤት አረጋግጠን ሟች ያፈራቸውን ቤቶች ወርሰናል፡፡ የሟች አባታችን ሀብት የነበሩትና ከሳሾች በውርስ ያገኘናቸው ቤቶች ቦታው ሸራተን አዲስ ሆቴል ለመገንባት በመፈለጉ ምክንያት ስፍራው በአልታድ ኩባንያ በኩል ወረዳ 28 ቀበሌ 04 ክልል በአሁኑ አጠራር በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ14/15 በፈረሰው ቤት ቁጥር 379 ምትክ የቤት ቁጥር 459፣ በፈረሰው የቤት ቁጥር 382 ምትክ የቤት ቁጥር 530 የሆኑት ተገንብተዋል፡፡ ከሳሾች የውርስ ያገኛቸውን ቤቶች ተካፍለው እንዲቀርቡ በሚመለከተው አካል በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት በልማት ምክንያት የፈረሰው የቤት ቁጥር 382 የአንደኛና ሁለተኛ ከሳሾች ድርሻ መሆኑና የቤት ቁጥር 382 የሶስተኛና አራኛ ከሳሾች ድርሻ ተገልፆ የሚመለከተው አካል መዝግቦታል፡፡ በመሆኑም ከሳሾችበውርስ ባገኘናቸው ቤቶች ምትክ የተሰሩትን የቤት ቁጥር 459 እና የቤት ቁጥር 430 አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሾች ከሶስተኛና አራተኛ ተከሳሾችተከራይተው እየኖሩባቸው በመሆኑ አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሾች ቤቶቹን ለቅቀው እንደወጡ፣ ሶስተኛና አራኛ ተከሳሾችከአንደኛና ሁለተኛ ተከሳሾች ጋር ያደረጉትን የክራይ ውል በማቋረጥና ቤቶቹን በማስለቀቅ ለከሳሾች በድርሻችን መሰረት እንዲያስረክቡ ውሳኔ ይሰጥልን የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርበዋል፡፡

3. ተከሳሾች የፈረሱት የቤት ቁጥር 379 እና የቤት ቁጥር 382 በአዋጅ ቁ/47/67 መሰረት የተወራሾችፍርድ ቤቱ ስልጣን የሌለው መሆኑን ገልጸው ተከራክረዋል ፡፡ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንደሌለው ገልፆ መስከረም 1 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ዘግቶታል፡፡ አመልካቾች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን በይግባኝ መዝገብ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

97896 ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በመሻር የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡

4. ጉዳዩን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከመለሰው በኋላ አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ ብቻ ቀርበው ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ 1972 ዓ/ም ጀምሮቤቱን ከመንግስት ተከራይቼ በመኖር ላይ እገኛለሁ፡፡ ተከሳሾች የቤት አበል ይወሰዱ ነበር በማለትየተከራከሩ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ፣ ሶስተኛ ተጠሪና አራተኛ ተጠሪዎች ክርክሩ በሚሰማበት ቀነቀጠሮ ባለማቅረባቸው ጉዳዩ እነርሱ በሌሉበት እንዲታይ የስር ፍ/ቤት ብይን ሰጥቶ፣ ጉዳዩን ሁለተኛና አራተኛ ተጠሪዎች በሌሉበት አይቶ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት የሽግግር መንግስት የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የቤት ቁጥር 379 የሶስተኛና አራተኛ ከሳሽ ድርሻ፣ የቤት ቁጥር 382 የአንደኛ አመልካች ልጅና አውራሽ የሆነው የሀብተስላሴ ይባስና የሁለተኛ ከሳሽ ድርሻ መሆኑን የመግለጽ በወቅቱ ለነበረው የክልል 14 አስተዳደር የፃፈው ደብዳቤ በማስረጃነት ከሳሾች ያቀረቡ መሆኑን ገልፆ፣እነዚህ የሰነድ ማስረጃዎች ከሳሾች ክስ ባቀረቡባቸው ቤቶችላይ መብትና ጥቅም ያላቸው መሆኑን አያረጋግጡም በማለት የስር ከሳሾች /አመልካቾች/ ያቀረቡትን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ከዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

5. አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት መጋቢት 2 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ስማችን ከሁለተኛ እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር የተገለጸው አመልካቾች አቶ ሀብተሰላሲ ይባስ የሚች የአቶ ይባስ ሰዴ ወራሽ መሆናችን በመዝገብ ቁጥር 221/65 በፍርድ ቤት ውሳኔ ተረጋግጧል፡፡ ሀብተስላሴ ይባስ የጠፋና አንደኛ አመልካች የሀብተስላሴ ወራሽ መሆናቸው በፍርድ ቤት አስወሰነናል፡፡ አዋጅ ቁ/ 47/67 ከመውጣቱ በፊት የአባታችን ንብረት የነበሩት ሁለት ቤቶች ባለቤትነት ለወራሾች የተላለፈልን ሲሆን፣ የውርስ ንብረቶቹን በመከፋፈል የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የባለሀብትነት ማስረጃ እንዲሰጠን፣ ቤቶቹ የከሳሾች ድርሻ መሆናቸውን በአዋጅ ቁ/ 47/1967 ስልጣን የተሰጠው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አጣርቶና አረጋግጦ የሰጠንን ማስረጃ የበታች ፍ/ቤቶች ውድቅ ያደረጉት ከህግ አግባብ ውጭ በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

6. ተጠሪዎች በተለያዩ ጊዜ በተናጥል ፅፈው ባቀረቡት መልስ፣ የፈረሱት ቤቶች የአመልካቾች አውራሽ ንብረት ስለመሆናቸው አመልካቾች ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ የሚች ይባስ ሰዴ ወርሶ በውርስ አጣሪ በኩል ተጣርቶ፣ ቤቶች ለአመልካቾች ያደረሱ ስለመሆናቸው አመልካቾች አላስረዱም የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የፃፈው ደብዳቤ አመልካቾች የቤቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለሀብት መሆናቸውን የማስረዳትና የማረጋገጥ የአስረጂነት ብቃት የለውም ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ተወርሰው መንግስት ለረዥም ጊዜ ስያስተዳድራቸውና እያከራየ ሲጠቀምባቸው የኖሩ በመሆኑ፣ ቤቶች ያልተወረሱ መሆናቸውን የማስረዳት ግዴታ ያለባቸው ከሳሾች /አመልካቾች/ በመሆናቸው አመልካቾች የማስረዳት ግዴታቸውን ስላልተወጡ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ቤቶችን ከሶስተኛና አራኛ ተጠሪዎች ተከራይተን እየኖርን ሲሆን፣ ከከሳሾች ጋር የሚያገናኘን ከውል ወይም ከህግ የመነጨ ግንኙነት የለንም በማለት የተከራከሩ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልሳቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

7. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረቡ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን የሰበር ችሎት ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት እንድችል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁ/ 171029 አስቀርቦ መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ መዝገቡ እንዲቀርብ በማድረግ ተመልክቶታል፡፡ በስር ፍ/ቤት በማስረጃነት ተያይዘው ከሚገኙ የፍ/ቤት ውሳኔዎችና ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች፣ አመልካቾች በአከራካሪዎቹ ቤቶች ላይ ያላቸውን መብት ለማረጋገጥ፣ በተለያየ ጊዜ ለተለያዩ ፍርድ ቤቶች፣ ክስ ሲያቀርቡና ሲከራከሩ የቆዩ መሆኑን አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ የገለጽዋቸውና በማስረጃነት ካያያዟቸው የተለያዩ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ለመረዳት ችለናል፡፡

8. አመልካቾች በአከራካሪዎች ቤቶች የአባታቸው የሚች ይባስ ሰዴ መሆናቸውን ለማስረዳት ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁ/ 171029 ከማስከፈታቸው በፊት ክስ አቅርበው በተከራከሩባቸው ሌሎች መዛግብት ላይ በማስረጃነት አቅርበው የያዛቸው ጠቃሚ የሰነድ ማስረጃዎች በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ145/1/ መሰረት አስቀርቦ ማየትና መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ይህም የሚሆነው አመልካቾች በቤቶች ላይ ያላቸውን መብት ለማስከበር ክርክር የጀመሩት ከሁለት አስር ዓመት በፊት መሆኑና በጉዳዩ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ሲከራከሩ ረዥም ዘመን ያስቆጠረ መሆኑን፣ የአመልካቾች የሰነድ ማስረጃዎች በተለያዩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተያይዞ የሚገኝ መሆኑን፣ አመልካቾች በማስረጃ ዝርዝር መግለጫቸው ዘርዝረው በማስረጃነት ካያያዟቸው የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ተገልፀው እያለ፣ እነዚህን ጠቃሚ ሰነዶች ያለባቸውን የፍርድ ቤት መዝገቦች በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 145/1/ መሰረት አስቀርበው ሳያዩ፣ አመልካቾች አከራካሪዎቹ ቤቶች የሚች አባታቸው ይባስ ሰዴ ለመሆናቸው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስተር ከፃፈዉ ደብዳቤ ዉጭ ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች አላቀረቡም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የበታች ፍርድቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ እዉነታዉን የማያንጸባርቅና ከላይ የጠቀሳቸዉን የህግ ድንጋጌዎች ያልተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል ።

9. አመልካቾች ክስ ያቀረቡባቸው የቤት ቁጥር 379 እና የቤት ቁጥር 382 የሚች ይባስ ሰዴ ንብረቶች እንዲሆኑ፣ የአመልካቾች አውራሽ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመታወጁ በፊት መሞታቸውናአመልካቾች የሚች ወራሾች መሆናቸውን በስር ፋይል መዝገብ ቁጥር 221/65 በፍርድ ቤት ውሳኔ ያረጋጡ መሆኑን፣ አመልካቾች ከአባታቸው በውርስ የተላለፉላቸውን ሁለት ቤቶች 1974 ዓ/ም ወራሾቹ ባደረጉት የውርስ ንብረት ክፍያ ስምምነት መሰረት፣ የቤት ቁጥር 379 የአንደኛና የሁለተኛ አመልካቾች ድርሻ መሆኑን የቤት ቁጥር 352 ደግሞ የሶስተኛ አራተኛ አመልካቾች ድርሻ መሆኑ ተረጋግጦ የተላኩለትና ይህንንም በአግባቡ መዝግቦ ያያዘ መሆኑን በመግለጽ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የካቲት 10 ቀን 1987 ዓ/ም እና ጥቅምት 25 ቀን 1990 ዓ/ም በፃፈው ደብዳቤ የረጋገጠ መሆኑን በትዕዛዝ ባስቀረብነው በስር ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥ አመልካቾች ካቀረቡአቸው የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት መረዳት ችለናል።

10. የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የካቲት 10 ቀን 1987 ዓ/ም እና ጥቅምት 25 ቀን 1990 ዓ/ም ለአዲስ አበባ አስተዳደር የጻፋቸው ደብዳቤዎች መሆናቸውን ገልጸው፣አመልካቾች ያቀረባቸው ሰነዶች፣ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ደብዳቤ አፃፃፍ ስርዓት ጠብቆ ለክልሉ 14 መስተዳደር ጽፎና ወጭ አድርጎ የላካቸው ደብዳቤዎች መሆናቸውን ተጠሪዎች በመካድ ያቀረቡት ክርክር የለም። ሰነዶቹ ሀሰተኛ ሰነድ ናቸው በማለት አልተከራከሩም። ይህም ማለት ሰነዶቹ በእርግጠኝነት የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት አሰራርና የጽሁፍ ማረጋገጫ አፃፃፍ ስርዓትን ጠብቆ ለክልሉ 14 መስተዳደር የፃፋቸው፣ ዕውነተኛ ደብዳቤዎች መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ደብዳቤዎችን የፃፈው ባለው አሰራር መሰረት ተገቢውን ማጣራት በማድረግና አከራካሪዎቹ ቤቶች የሚች ይባስ ሰዴ ንብረቶቹ መሆናቸውን፣ የንብረቶቹ ባለቤት አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመታወጁ በፊት ከዚህ አለም በሞት መለየቱንና አመልካቾች የሚች ወራሽ መሆናቸውን አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመታወጁ በፊት መዝገብ ቁ/ 221/65 ማረጋገጣቸውንና አመልካቾች በውርስ ያገኘዋቸውን ቤቶች፣ በወራሾች ስምምነት 1974 ዓ/ም ተከፋፍለው ለስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የውርስ ንብረቶቹን የተከፋፈሉበትን ሰነድ አቅርበው ሰነዱ በአግባቡ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤዎች ናቸው።

11. አዋጅ ቁጥር 47/67 የማስፈጸም ኃላፊነትና ስልጣን የተሰጠው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 15 ተደንግጓል። ይህ በህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጣን የተሰጠው የመንግስት መስሪያ ቤት በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በየደረጃው ያዋቀራቸውን አደረጃጀቶች በመጠቀም ተገቢውን ማጣራት በማድረግ፣ የቤት ቁጥር 379 እና የቤት ቁጥር 382 የአመልካቾች አውራሽ ሟች ይባስ ሰዴ እንደሆኑ በማረጋጥ የፃፈው ደብዳቤ፣ አከራካሪዎቹ ቤቶች የሟች ይባስ ሰዴ ስለመሆናቸው የሚያስረዳ ብቃት ያለው ማስረጃ ሆኖ እያለ ደብዳቤዎቹን የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት አሰራር ስርዓትን ተከትሎ የፕሮቶኮል ቁጥር፣ ቀን፣ የባለስልጣን ፊርማና የሚኒስቴር መስሪያ ቤት የራስጌና የግርጌ ማህተም በማረጋገጥ ውጭ አድርጎ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፃፏቸው መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ፣ ደብዳቤዎቹ ውስጥ በግልጽ የቤት ቁጥር 379 የአንደኛና ሁለተኛ አመልካች ድርሻ፣ የቤት ቁጥር 382 የሶስተኛና የአራኛ አመልካቾች ድርሻ መሆኑን በግልጽ በሰፈራበት ሁኔታ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች በህግ ቤቶቹ በትርፍነት የተወረሱ መሆን አለመሆናቸውን፣ ቤቶቹ በመጀመሪያ የማን ሀብት እንደነበሩ የማጣራትና የንብረቱ ባለሀብት የሆኑት ወራሾች መብት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 አንፃር የማጣራትና ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የፃፈው እውነተኛ ደብዳቤ፣ የአስረጂነት ብቃት፣ ተአማኝነትና ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁ/ 47/67 በተሰጠው ስልጣን የሚወሰናቸው ውሳኔዎች ውጤት አልባ የሚያደርግና ህግን ያልተከተለ የማስረጃ አመዛዘን በመሆኑ የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

12. የስርና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አዋጅ ቁጥር 47/67 የማስፈጸም፣ በአዋጅ መሰረት አንድ ቤት በትርፍነት ሊወረስ የሚገባው መሆኑን ወይም አለመሆኑን የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው ከፍተኛ አስተዳደራዊ አካል ነው፡፡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአዲስ አበባ አስተዳደር /ክልል 14 መስተዳደር/ እና በእሱ ስር የተደራጀ ሌሎች የመንግስት አካላት አዋጅ ቁጥር 47/67 በማስፈጸም ሂደት የሰጡት ውሳኔ አዋጁን መሰረት ያደረገ መሆኑን መርምሮ የማሻሻል፤ የመለወጥ ወይም የመሻር አስተዳደራዊ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተሰጠው የመንግስት አካል ነው፡፡ ሌሎች የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት አጣርቶ ለሚሰጠው ውሳኔ የሚከበርና የማስፈጸም ህጋዊ ግዴታና ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 47/67 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የስራና ከተማ ልማትሚኒስቴር የካቲት 10 ቀን 1987 ዓ/ም እና ጥቅምት 25 ቀን 1990 በፃፈው ደብዳቤ የወሰናቸውን ውሳኔዎች የማክበርና የማስፈጸም ግዴታ በህግ የተጣለባቸው 3ኛ ተጠሪና አራኛ ተጠሪ፣ የሚኒስተሩ ውሳኔ ውድቅ እንዲያረግ ለበታች ፍርድ ቤቶች ጽፈው ያቀረቡት ክርክር፣ በህግ የተጣለባቸውን አስተዳደራዊ ኃላፊነት ያልተወጡ መሆኑን የሚያሳይና የህግ መሰረት የሌለው ክርክር ነው፡፡ በወቅቱ በነበሩ የህግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማዕቀፎች የሚኒስቴር መ/ቤቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የክፍለ ከተማውንና የሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ትርፍ ቤትን በተመለከተ የሰጡትን ውሳኔ የመሻር፣ የመለወጥ ወይም የመሻሻል ከፍተኛ የሆነ የአስፈጻሚነትና አስተዳዳራዊ ስልጣን ያለው ሲሆን፣ የከተማው አስተዳደር፣ ክፍለ ከተማውም ሆነ ለሶስኛና አራተኛ ተጠሪዎች የሚኒስቴር መስሪ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አፈፃጸም የማስተጓጎል፣ የማጓተት፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ ህጋዊ ውጤት እንዳይኖረው የሚያደርጉ ተግባራትን የፈጸም፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ውሳኔ የመሻር ወይም የመለወጥ አስተዳደራዊ ስልጣን አልነበራቸውም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪና አራተኛ ተጠሪ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ ተፈፃሚ መሆን የለበትም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ምንም አይነት የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

13. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት መሆኑን ለማረጋገጥ በክፍሉ አስተዳደር የተመዘገበና ተረጋግጦ የተሰጠ የባለሀብነት ካርታና ፕላንና ማስረጃ የሚያስፈልግ መሆኑ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1195 ተደንግጓል፡፡ መርሀ ይህ ሆኖ አንድ ሰው በጉልበቱ፣ በገንዘቡና በዕውቀቱ ያፈራው የማይንቀሳቀስ ሀብት ባለሀብት ስለመሆኑ በክፍሉ አስተዳደር የተሰጠ የባለሀብትነት ማስረጃ የሌለው ሰው፣ የንብረቱ ባለሀብት መሆኑን ሌሎች የሰነድና የሰው ማስረጃዎችንበማቅረብ ለማስረዳት የሚችል ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36320 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአመልካቾች አባት ሟች ይባስ ሰዴ፣ የአከራካሪዎች ቤቶች ባለሀብት እንደሆነና አመልካቾች የውርስ ድርሻ ስለሆኑ ቤቶች የማያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አመልካቾች ለበታች ፍ/ቤቶች አቅርበው እያለ፣ ቤቶች የአባታችሁ ስለመሆናቸው የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ያላቀረባችሁ በመሆኑ፣ ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም የላችሁም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከላይ የገለጽነውን የሰበር ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያልተከተለና የአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ2/1/ ድንጋጌ የሚጥስ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

14. ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የሰጠው ውሳኔና የፃፈው ደብዳቤ የአዋጅ ቁ/ 47/67 እና የሌሎች አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ መሆኑን መርምረናል፡፡ የአመልካቾች አባት አቶ ይባስ ሰዴ ከዚህ አለም በሞት የተለዩት በ1964 ዓ/ም መሆኑ ተረጋግጧል ይህም ማለት በሟች /የአንድ ሰው/ ሀብት የነበሩት ሁለት ቤቶች ሟች በሞት ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ የሟች ወራሾች ሀብት የባለመብትነት መብታቸው ሊተላለፍላቸው የሚችል መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም የሟች ይባስ ሰዴ ሁለት ቤቶች፣ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመታወጁ በፊት የሟች አምስት ወራሾች ንብረት ሆኖ በኢትዮጲያ የውርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አወራረስ ስርዓት መሰረት ከሟች ወደ ወራሾቹ የሚተላለፍ መሆኑን ያሳያል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሰው ትርፍ ቤትና የከተማ ቦታ ነው፡፡ ሆኖም አዋጅ ቁጥር 47/67 በሚታወጅበት ወቅት አምስት የሚሆኑት የሟች ይባስ ሰዴ ልጆችን ወራሾች የአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 5 በሚደነግገው መሰረት የነበራቸው ትርፍ ቤት ሳይሆን፣ ለአምስቱ ወራሾች ከነቤተሰባቸው ለመኖሪያነት የማይበቁ ከአባታቸው በውርስ ያገኛቸው አከራካሪዎቹ ቤቶች ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ የሟች ሰራተኞች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1079 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በስምምነት ሁለቱን ቤቶች ተካፍለው፣የባለሀብትነት ማስረጃ ለሚሰጠው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ጥያቄያቸውንና ማስረጃዎችን አቅርበው እያለ ቤቶች በልማት ምክንያት የፈረሱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሰጠው ውሳኔና የፃፈው ደብዳቤ አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁጥር 47/67 እና የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች ተጠሪዎች አመልካቾች በውርስ አግኝተዋቸው በነበሩ የቤት ቁጥር 375 እና 382 ምትክ የተሰሩትን የቤት ቁጥር 459 እና የቤት ቁጥር 375 እና 382 ምትክ የተሰሩትን የቤት ቁ/ 459 እና የቤት ቁ/530 ለአመልካቾች እንዲያስረክቡ መወሰን ሲገባቸው፣የአመልካቾቹን ክስ ውድቅ በማድረግ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዯራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 171029 የካቲት 10 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዯራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 135103 ጥር 22 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ክስ ያቀረቡባቸውና በልማት ምክንያት የፈረሱት በወረዳ 14 ቀበሌ 24 ይገኙ የነበሩት የቤት ቁጥር 382 እና የቤት ቁጥር 379 የሆኑት ቤቶች አመልካቾች ከሟች አባታቸው አቶ ይባስ ሰዴ በውርስ ያገኟቸውና በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት በትርፍነት ያልተወረሱ የግል ሀብታቸው ናቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካቾች በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1079/1/ መሰረት በስምምነት ተካፍለው ለስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ባስመዘገቡት መሰረት፣ አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች የውርስ ድርሻ በሆነው የቤት ቁጥር 382 ምትክ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 14/15 አልታድ የተባለውን ድርጅት የሰራውን የቤት ቁር 530 ተጠሪዎች ለአንደኛና ሁለተኛ አመልካቾች ያስረክቡ በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. የሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የውርስ ድርሻ በሆነው በቤት ቁጥር 459 ተጠሪዎች ለሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ያስረክቡ በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ 123833

መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች----ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

አይሸሹም መለሰ

ፀሐይ መንክር

አመልካች----------አቶ ለሜሳ ደገፉ ቀረቡ

ተጠሪ----------የአዳማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነ/ፈጅ ቅድስት ቤክሲላ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የእግድ ትዕዛዝን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በኦሮሚያ ክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሣሽ ሲሆኑ እነ ቡኔ በዳኔ / 4 ሰዎች/ ተከሳሾች ነበሩ፡፡

ለእግዱ መሰጠት ምክንያት የሆነው የቤት ክርክር ሲሆን የስር ወረዳ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 154 መሠረት በቃለ መሐላ ተደግፎ በአሁን አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ በአዳማ ከተማ ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 369 የሆነውን ቤት እንዲታገድ በመጠየቁ ምክንያት በመ/ቁ/ 90352 ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ቤቱ እና በቤቱ ውስጥ ያለው ንብረት ጭምር ሌላ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ለ3ኛ ወገን ተላልፎ እንዳይሰጥ ሲል የእግድ ትዕዛዝ ፍ/ቤቱ ሰጥቷል፡፡

ይህን የእግድ ትዕዛዝ በመቃወም የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ብሎ ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በመ/ቁ/ 21371 ሐምሌ 02 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን እግድ ትዕዛዝ እንዳይፈፀም ሲል እግድ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማለታቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አስቀርቦ መርምሮ በስር ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳው በአመልካች እና ሌሎች 4 ሰዎች መሐከል ሲሆን ተጠሪ የሆነው / አስተዳደሩ/ ግን በክርክር ተካፋይ ያልሆነ፣ ወይም በሕግ መሠረት ወደ ክርክሩ የገባ ሳይሆን ተከሶ መልስ ሳይሰጥ እግድ እንዲነሳ አቤቱታ የማቅረብ መብት ሳይኖረው፣ እንዲሁም የተሰጠው እግድ ጊዜያዊ ሆኖ እያለ የወረዳው ፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ ስህተት የሌለበት ሆኖ እያለ በመሻር እንዳይፈፀም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሻር ያለበት ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ በማፅናት በመ/ቁ/ 226292 ሐምሌ 23 ቀን 2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት በሰበር ታይቶ እንዲታረምለት አቤቱታ በማቅረቡ መነሻነት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 231128 ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ክርክር ያስነሳው የመንግሥት ቤት በአዳማ ከተማ መስተዳድር የሚተዳደር መሆኑን ፣ በከተማ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት ቤቶችን የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር እና የማከራየት የከተማ መስተዳድሩ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ የከተማ መስተዳድር በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 158 መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ ሁኔታ ሳያየው የአዳማ ከተማ መስተዳድር ክርክሩ ውስጥ ሳይኖር የእግድ ይነሳልኝ አቤቱታ ማቅረብ አይችልም ብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለው ሆኖ በመገኘቱ በሙሉ ድምጽ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ፍርድ ቤቱ የሰጡትን ውሣኔ በመሻር የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች የሰበር ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ፍርድ በመቃወም በ15/6/2008 ዓ.ም.የተፃፈ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሲሰጥ የሕግ ስህተት ፈጽሟል የሚሉበትን ነጥቦች በመዘርዘር በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

በአቤቱታው ከዘረዘሩት በአጭሩ፡- በስር ፍርድ ቤት እግድ እንዲሰጥልኝ ጠይቄ ፍ/ቤቱ እግዱን የሰጠልኝ ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ተከሣሽ ያልነበረ፣ ወይም በሕግ አግባብ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ሳይገባ፣ ወይም ለወረዳው ፍርድ ቤት እግዱ እንዲነሳ አቤቱታ ሳያቀርብ የእግድ ትዕዛዙን በከፍተኛ ፍርድ ቤት አሽሯል፡፡

እግዱን ያነሳው ፍርድ ቤት የፍትሕ ስርአቱን ጥያቄ ውስጥ በሚጥል መልኩ አቤቱታ ሲቀርብለት መጥሪያ ሳይልክልኝ በጉዳዩ ላይ ምንም አይነት መልስ ሳልሰጥ ሕገመንግስታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብቱን ተጠቅሜ ክርክር ሳላደርግበት የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ የሻረበት ትዕዛዝ እንዲደርሰኝ አድርጓል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ጊዜያዊ እግዱ እንዲቆይ ማድረጉ የማስተዳደር እና የመቆጣጠር መብቱን በምንም መልኩ የሚነፍግ አይደለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የአዳማ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለተፈፀመበት ይታረምልኝ በማለት ሰፊ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ በስር ተከራካሪ ባልነበረበት በሥር ፍ/ቤት በተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ላይ ያቀረበው ይግባኝ ተቀባይነት አግኝቶ እግድ የተነሳበትን አግባብ የሕግ መሠረት ያለው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት ይቅረብ በማለቱ ሊቀርብ ችሏል፡፡

አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አኳያ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ተልኮለት በ19/1/09 የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ከመልሱም በአጭሩ እንደተመለከትነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሣኔ የተፈፀመ ስህተት የለም፣ ምክንያቱም አንድ አቤቱታ አቅራቢ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 154 የተሰጠውን እግድ እንዲነሳለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 158 መሠረት እግዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ የሚችለው ከሳሽ ወይም ተከሣሽ ነው የሚል የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ የአሁን ተጠሪ በክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን የተሰጠውን እግድ እንዲነሳለት የመጠየቅ የሕግ አግባብ የለውም የሚለው ጥያቄ በሕግ ድንጋጌው ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚነቀፍ ውሣኔ ስላልሰጠ ይፅናልን፡፡ አመልካች ቤቱን ያገኘሁት ከተለያዩ አካላት ድጋፍ ደብዳቤ ተጽፎልኝ ነው ይበል እንጂ ማስረጃ ግን የለውም፣ ተጠሪ ባልተከሰበሰበት እና በማያውቀው ጉዳይ ንብረቱ በግለሰቦች መካከል በተፈጠረ ግጭት መታገዱ አግባብ አይደለም በማለት በመልሱ ከገለፀው ውስጥ ለጉዳዩ አግባብ ነው ያልነውን መዝግበናል፡፡

አመልካችም ለቀረበው መልስ የመልስ መልሳቸውን አቤቱታቸውን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበው ተያይዟል፡፡

እኛም የቀረበውን ጉዳይ በአጣሪው ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ከአመልካች አቤቱታ እና መልስ ፣ የመልስ መልስ እና አግባብነት ካለቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ጉዳዩ በስር ፍርድ ቤት እግድ ከመሰጠት ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክር ሲሆን፣ የስር ፍርድ ቤት ክርክር ያስነሳውን ቤት እግድ የሰጠው በስር ከሳሽ በአሁን አመልካች ጠያቂነት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ተከሣሽ የነበረው ሌላ ሰው እንደነበረ እና ተጠሪ ግን በክርክሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተካፋይ እንዳልሆነ ተጠሪም ያመነው እና በስር ፍርድ ቤቶችም ሲገለፅ የመጣ ነገር በመሆኑ አያከራክርም፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 40፣ 41፣ 42፣ 358፣ 418 በተደነገገው ሥርዓት ተጠሪ ወደ ክርክሩ ውስጥ ተሳታፊ መሆኑም አልተመለከተም፡፡ ክርክር ያስነሳው ቤት ግን የአስተዳደሩ /ተጠሪ የሚያስተዳድረው / ነው የተባለ በመሆኑ ተጠሪው በሚያስተዳድረው ቤት ላይ ሁለት ወገኖች ክርክር አንስተው ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘ በመሆኑ አመልካች እግድ በቤቱ ላይ እንዲሰጥበት ጠይቀው እግዱን የወረዳ ፍርድ ቤቱ ሰጥቷል፡፡

እግድ የተሰጠው በክርክሩ ውስጥ ተሳታፊ ባልሆነው ተጠሪ በሚያስተዳድረው ቤት ላይ በመሆኑ ተጠሪ ይህ ጉዳይ አይመለከተውም ምንም ጥያቄ የማንሳት መብት የለውም ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ ቁም ነገሩ ግን አንድ በንብረቱ ላይ እኔ ሳላውቀው ትዕዛዝ ተሰጥቶብኛል የሚል ወገን ፍርድ ቤቱ እኔን ሳያሳትፍ ያልተገባ ትዕዛዝ ሰጥቶብኛል በማለት አሁን በዚህ መዝገብ የተሰጠው እግድ አይነት ትዕዛዝ በተሰጠ ጊዜ አቤቱታ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 158 በግልጽ ተደንግጓል፡፡

አቤቱታውንም ተቀብሎ የማስተናገድ እና የተሰጠው የማገጃ ትዕዛዝ በቀረበው አቤቱታ መሠረት ሊያሻሽል ፣ሊያነሳ፣ ሊሠርዝ የሚችለውም እግዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የቀረበውን አቤቱታ እግዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ሳይቀበል ውድቅ ያደረገ እንደሆነ ይግባኝ የሚባልበት ከሚሆን በቀር በክርክር ተሳታፊ ያልሆነ ወገን በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ እግድ ትዕዛዝ በቀጥታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚያቀርብበት እና ትዕዛዙ ላይ ውሣኔ የሚያሰጥበት ስርዓት ግን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ ውስጥ የተደነገገ አይደለም፡፡

የእግድ ትዕዛዙ ጠቀሜታው ለጊዜው የተሰጠ በመሆኑም ይህ እግድ ሳይነሳ መቅረቱ በአመልካች ላይ የሚያስከትለው ችግር ካለ እግዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ በስር ፍርድ ቤት ቀርቦ አቤቱታም አቅርቦ የስር ፍርድ ቤቱ በቀረበው አቤቱታ ላይ የሰጠው የተለየ ትዕዛዝ ስለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ አመልካችም እግድ የተሰጠው አላግባብ ነው የሚል አቤቱታውን በስር ፍርድ ቤት አቅርቦ ትዕዛዝ ባላሰጠበት ሁኔታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በክርክር ተሣታፊ ባልሆነበት ጉዳይ በቀጥታ ይግባኝ በማቅረብ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ማሻሩ ፣ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ሥነ ሥርዓታዊ መስመሩን ጠብቆ የቀረበ ይግባኝ መሆን ያለመሆኑን ሳያረጋግጥ እና በስር ፍርድ ቤት ታይቶና ትዕዛዝ የተሰጠበት መሆን ያለመሆኑን ሳይመረምር በመዝገቡ ላይ ከሣሽ ወይም ተከሣሽ ወይም ጣልቃ ገብ ያልሆነ ወገን ይግባኝ ቅሬታ ሲቀርብለት ተቀብሎ የስር ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ መሻሩ ፣ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፈፀመውን ስህተት ማረም ሲገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የይግባኝና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠውን ውሣኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 231128 ታሕሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡ ፡፡
3. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረስ መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

   ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 123123

ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

አይሸሹም መለሰ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ተኽሊት አፈወርቂ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - የመቀሌ ቅርንጫፍ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የአመልካች ክስበ ይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የህግ መሰረት ያለው መሆኑን በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአመልካች መኪና የኮንትሮባንድ ዕቃጭና ተገኝታለች በማለት ተጠሪ በቁጥጥር ስር ካዋላት በኋላ የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተለቅቃለች፡፡

   አመልካች ተጠሪ መኪናዬን አላግባብ ቁጥጥር ስር በማዋል ጉዳት አድርሶብኛል በማለት ግንቦት 29 ቀን 2004 ዓ.ም የተጻፈ ክስ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ፣ በቀረበው ክስ ውስጥ ያሰፈረው ፍሬ ነገር ዕውነት ስለመሆኑ የአመልካች ጠበቃ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሰረት ለማረጋገጥ እንደማይቻልና አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሰረት የክሱን እውነተኛነት ቀርቦ ያረጋግጥልን በማለት በመቃወሙ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከጅምሩ በሬጅስትራር በኩል ቴክኒካል መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑ ተረጋግጦ ያልቀረበ መዝገብ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

2. ከዚህ በኋላ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረብኩት ክስ የተጋነነ ስለሆነ አስተካክዬ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ በማለት ጥቅምት 5 ቀን 2007 ዓ/ም አመልክቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም አመልካች ስልጣን ላለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ እንደሚችሉ በመግለጽ ትዕዛዝ ሰጥቷል። አመልካች ጥር 4 ቀን 2007 ዓ.ም ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ ተጠሪ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ቴክኒካል ሁኔታዎችን ባለማሟላቱ የተዘጋ በመሆኑ ይርጋ ሊያቋርጥ አይችልም። ስለዚህ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማለፉ፣ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የወሰነ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያለ ፍርድ ቤቱ ፈቃድ ክሱን ያቋረጠ በመሆኑ፤ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦት በነበረው ክስ ይርጋ አይቋረጥም። ስለዚህ መኪናዋ ከተለቀቀችበት ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ብይን ሰጥቷል። አመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን በመቃወም ሲሆን ተጠሪም በጽሁፍ መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

3. ከስር የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን፣ በእኛ በኩል እንዳየነው አመልካች ተጠሪ መኪናዬን ከህግ አግባብ ውጭ በመያዝ፣ ጉዳት ስላደረሰብኝ ካሳ ይክፈለኝ በማለት በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 53029 ግንቦት 24 ቀን 2004 ዓ.ም አቅርቦት የነበረው ክስ በፍታሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት ህግ ቁጥር 92 መሰረት ዕውነት መሆኑ ተረጋግጦ ያልቀረበ መሆኑን በመግለጽ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን የዘጋው መሆኑ ተረጋግጧል። አመልካች በህጉ የተገለጸው ቴክኒካል መስፈርት አያሟላም ተብሎ የተዘጋበት መዝገብ እንዲንቀሳቀስለት ያመለከተው ፍርድ ቤቱ አልተሟላም ያለውን መስፈርት ለማሟላት ሳይሆን፣ በቀረበው ክስ የተገለጸው የገንዘብ መጠን የተጋነነ በመሆኑ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክሳችንን እንድናቀርብ በማለት እንደሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት ተረድተናል። ይህም አመልካች በተጠሪ ላይ በመዝገብ ቁጥር 53029 ግንቦት 24 ቀን 2004 ዓ.ም አቅርቦት የነበረው ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 278 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) በተደነገገው መሰረት የአመልካች ክስ በፍ/ስ/ስ/ህግቁጥር በተደነገገው መሰረት ዕውነት ስለመሆኑ ተረጋግጦ በከሳሽ (አመልካች) ባለመቅረቡ ምክንያት ውድቅ ያደረገው መሆኑንና አመልካች ጥቅምት 5 ቀን 2007 ዓ.ም ባቀረበው ማመልከቻ፣ በክሱ ውስጥ ተጠሪ (ተከሳሽ) እንዲከፍል የተጠየቀው ገንዘብ ዕውነትነት የሌለውና የተጋነነ መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ ከሳሽ ክሱን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሰረት ዕውነት መሆኑን በማረጋገጥ ክሱ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለማስቀጠል እንደማይችል መሆኑን በማረጋገጥ ክሱን ስልጣን ላለው ፍርድቤት ለማቅረብ እንዲችል ጥያቄ ያቀረበበት ነው።

4. ይህም አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.C92 መሰረት ዕውነት መሆኑን በማረጋገጥ ያቀረበው ክስ የሌለና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህ ቴክኒካል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታ ካልተሟላ ጉዳዩን ልመለከተው አልችልም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.ር 278 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) መዝገቡ እንዲዘጋ የሰጠውን ትዕዛዝ ለማስለወጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት በማቅረብ ክሱ እንዲቀጥል ያላደረገ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በመዝገብ ቁጥር 53029 ግንቦት 24 ቀን ያቀረበው ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.92 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት የማያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ እንዲዘጋ የሰጠው ትዕዛዝ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምንም አይነት ክስ እንዳላቀረበ የሚያስቆጥርና የይርጋ ጊዜ የማቋረጥ ውጤት የሌለው መሆኑን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.278 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ይዘትና ይህ ሰበር ችሎት ስለድንጋጌዎቹ ዓላማ ተግባራዊ አፈጻጸምና ህጋዊ ውጤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 90361 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመረዳት ይቻላል፡፡

5. ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች መኪናዋ እንድትለቀቅ በፍርድ ከተወሰነበት የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ እስካቀረበበት ጥር 5 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ፡፡ መብቱን ለማስከበር ህጋዊና ቴክኒካዊ መስፈርቶችን ያሟላ ክስ አቅርቦ እንደማያውቅ ተቆጥሮ የይርጋው ጊዜ መሰላት ያለበት በመሆኑ አመልካች የፍታሐ ብሔር ህግ ቁጥር 2143 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ ከአስር ወራት በኋላ ክሱን ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ ከላይ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 76156 መስከረም 5 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 124552

ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች ፡- አቶ ምትኩ አበበ - ከጠበቃ ነቃጥበብ ገ/ሚካኤል ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- የከሰረው ሆላንድ ካር ኃ/የተ/የግ/ማሕበር - ነ/ፍጅ ፍቃዱ አስፋው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 196585 በተሠጠው ውሣኔ እንደታየው በዱቤ የመኪና ሽያጭ ውል ምክንያት መኪና እንዲረከቡ በተወሰነው መሠረት አባይ መኪናን መውሰድ ሲገባቸው ውል ከገቡለት መኪና በዋጋው የብር 66,100.00 ብር ልዩነት ያለውን ተከዜ መኪና በመውሰዳቸው በብልጫ የወሰዱትን የመኪና ዋጋ ብር 66,100.00 እና ቅድሚያ ክፍያ ከፍለው የቀረባቸውን ገንዘብ ተደምሮ በጥቅሉ ብር 192,100.00 ብር እንዲከፍሉ በማለት ነሐሴ 21 ቀን 2007 ዓ.ም. በአጭር ሥነ ሥርዓት ታይቶ እንዲወሰንለት ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ የቀረበውን ክስ እና ማስረጃ ከመጥሪያ ጋር ለአመልካች ተልኮላቸው የመከላከያ ማስፈቀጃ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የስር ተከሣሽ በችሎት ቀርበው እዳቸውን ያመኑ በመሆኑ እና የመከለከያ ማስፈቀጃ ቢያቀርቡም እዳቸውን እያመኑ እና እዳ እንደሌለባቸው ሣይክዱ ወይንም በዋጋ ልዩነት ያለውን መኪና አልወሰደኩም ወይም ደግሞ እዳውን ከፍያለሁ በማለት ሣይገልፁ ወይም በመከላከያ ማስፈቀጃቸው ጽሁፍም ላይ ሣያነሱ መ/ማስፈቀጃ ይፈቀድልኝ በማለት ብቻ ሊፈቀድ የሚገባው ሕግ በሚያዘው መሠረት ሲቀርብ እንጂ መከላከያ ማስፈቀጃ ይፈቀድልኝ በማለት አይደለም ሲል ማስፈቀጃውን ውድቅ አድርጌዋለሁ በማለት አመልካች በሰጡት የእምነት ቃል መሠረት በክሱ የተገለፀውን ገንዘብ እንዲከፍሉ በአጭር ሥነ ሥርዓት የወሰነ መሆኑን ገልጾ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሻርለት፤ አመልካች እና ክርክሩ በአጭር ስነ ሥርዓት ሊታይ ስለማይገባው መከላከያ ማስፈቀጃው ተቀባይነት አግኝቶ ጉዳዩ እንዲታይለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ግድፈት የተፈፀመበት አይደለም በሚል የይግባኝ ቅሬታውን ሰርዞታል፡፡

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውም ይህው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ሲሆን፣ አመልካች ሚያዝያ 7 ቀን 2008 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያለሕጋዊ ምክንያት የመከላከያ ማስፈቀጃውን ውድቅ ያደረገው እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.337 ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት በውሣኔው ላይ ግድፈት አልተገኘም በማለት ይግባኙን የሠረዘው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሞ ነው፡፡ በአጭር ስነ ስርዓት እንዲታይ ክስ የቀረበው በደሀ ደንብ ነው፡፡ ተጠሪ ደሀ ሊባል አይገባም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ የከሰረውን የሆላንድ ካር ከብር 83 ሚሊዩን ብር በላይ ንብረት እንዲያስተዳድር ተረክቧል፡፡ በመሆኑም ዳኝነት ሣይከፍል ክስ ሊያቀርብ አይገባም፡፡

የተጠሪ ክስ ጥያቄ የቀረበው ፍርድ ባረፈበት አፈፃፀም በከፈተበትና በይግባኝ በፀና የሽያጭ ውል ጉዳይ ላይ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 284 መሠረት በአጭር ሥነ ሥርዓት ክስ ሊቀርብበት ስለማይችል የተጠሪን ክስ የስር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ያስተናገደው ከሕግ ውጭ ነው፡፡ በውል መሠረት በነበረ መኪና ዋጋ በተመሣሣይ የተረከበው መኪና ስለሆነ የዋጋ ልዩነት ሊጠየቅበት አይገባም በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ተብሎ ይወሰንልን፣ የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ አመልካች ክሱን እንዲከላከል እንዲፈቀድልኝ ሲሉ አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች በአጭር ስነ ስርዓት ታይቶ እንዲወሰን ለቀረበባቸው ክስ ያቀረቡት ማስፈቀጃ ማመልከቻ በሕጉ መሠረት የቀረበአይደለም በማለት ሳይቀበለው የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው መልሣቸውን እንዲያቀርቡ መዝገቡ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

ተጠሪም ግንቦት 10 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን በመልሱ የገለፀውም ማህበሩ ጥር 07 ቀን 2005 ዓ.ም በመ/ቁ/ 20080 የመክሰር ውሣኔ ተሰጥቶበታል፣ አመልካችም ከማህበሩ ጋር ለተከዜ መኪና የሽያጭ ውል መዋዋላቸውን፣ ተከዜ መኪና እንዲረከቡ አልያም በግማሽ የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስ አመልካች መክሰሳቸውን፣ በዚሁ መሠረት በመ/ቁ/ 196585 በሆነው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ተከዜ መኪና እንዲረከቡ እና ለማህበሩም ቀሪ ገንዘብ ብር 126,000.00 እንዲከፍሉ መወሰኑን፣ ነገር ግን አመልካች በውሣኔው መሠረት ገንዘቡን ያለመክፈላቸውን፣ እንዲሁም አመልካች የተዋዋሉት መኪና ተከዜ ሆኖ ዋጋውም 218,000.00

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሆን አመልካች በአፈፃፀም መዝገብ ቁ. 197933 በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ብሔር ችሎት ዋጋው 285,000.00 የሆነውን እና ከተከዜ መኪና ልዩነት ያለውን አባይ መኪና የወሰዱ ሲሆን ልዩነቱን ብር 66,100.00 ስለመክፈላቸው ያላረጋገጡ መሆኑን በአጠቃላይ ከአመልካች የሚፈለግ ብር 192,100.00/አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ አንድ መቶ ብር/ የሚፈለግባቸው መሆኑን ጠቅሶ ክስ መመስረቱን እና አመልካችም ቀርበው ዋጋው ልዩነት ያለውን መኪና ያለመውሰዳቸውን፣ እዳም የሌለባቸው መሆኑን ሳይሆን የተከራከሩት እዳው መኖሩን አምነው ከተጠሪ የሚፈለግበት ገንዘብ ያለ በመሆኑ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 242 መሠረት የሚፈለግባቸውን እንዲከፍሉ የወሰነ ሲሆን፣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያላነሱትን ክርክር የአባይ መኪና የወቅቱ ዋጋ 285,000.00 አይደለም በማለት መከራከራቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እና ችሎቱም በሕግ መሠረት የፍሬ ጉዳይ ክርክር የማድረግ ሥልጣን የሌለው መሆኑን ገልፆ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ እንዲፀናለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በቀደመው አቤቱታ ያቀረቡትን በመልስ መልስ በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገብ ተያይዟል፡፡

ፍ/ቤቱም የቀረበውን አቤቱታ እና መልስ ከስር ፍርድ ቤት ውሣኔ እና በአጣሪው ከተያዘው ጭብጥ አንፃር አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

አመልካች ከተጠሪ ጋር የመኪና ሽያጭ ውል መኖሩ ያላከራከረ ሲሆን ግራ ቀኙም በመኪናው እርክክብ ላይ ያነሱት የተለየ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ በአጭር ስነ ሥርዓት ያቀረቡት ክስ ደርሷቸው የመከላከያ ማስፈቀጃ ማቅረባቸውን የስር ፍርድ ቤት በውሣኔው ላይ የመዘገበ ሲሆን ያቀረቡት የመከላከያ ማስፈቀጃ ጥያቄን ማቅረባቸውን ጠቅሶ ነገር ግን ያቀረቡት የመከላከያ ማስፈቀጃ ይዘት በክሱ ላይ ያለውን ገንዘብ መልሻለሁ፣ እዳም የለብኝም በማለት ሳይሆን በቃል በችሎትም ሲጠየቁ ገንዘቡ እዳቸው መሆኑን አምነው ነገር ግን ከተጠሪ የምፈልገው ገንዘብ ስላለ ነው በማለት እንዲፈቀድላቸው መጠየቃቸውን ገልጿል፡፡

ተጠሪ ከላይ የተገለፀውን መኪና ያስረከበው በፍርድ አስገዳጅነት ሳይሆን ተከዜ መኪና እንዲያስረክብ ተወስኖ አባይ መኪና ያስረከበው ፍርድ ከተሰጠና በዋናው ጉዳይ አፈፃፀም ላይ እያሉ ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሠረት መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብን አስቀርበን ተመልክተናል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 284 መሠረት በአጭር ስነ ሥርአት የሚቀርብ ክስ ሊቀርብ የሚችለው ምንም አይነት መከራከሪያ በሌላኛው ወገን የማይቀርብ መሆኑ ሲረጋገጥ እና ወዲያው ሊወሰን የሚችል ሲሆን መሆኑን የሕጉ ድንጋጌ ያሳያል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 284/ሀ/ በአጭር ሥነ ሥርዓት ክስ ለማቅረብም በግልጽ ውል ወይም በነገሩ አካባቢ ሁኔታ በሚመሠረት ውል ወይም በሐዋላ ወረቀት ወይም በገንዘብ አለብኝ ሰነድ ወይም በቼክ ወይም ተራ የሆነ ባለዕዳነትን የሚመለከት ውል መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ በቅድሚያ የተገናኙት በውል ቢሆንም ነገር ግን አሁን የሚፈለገውን ገንዘብ ስር ከሳሽ እየጠየቀ ያለው የቀደመውን ውል ለማስፈፀመ በተደረገ ስምምነት ላይ የተጨመረው እንጂ በግልጽ ውል ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ እንዲሁም ስር ከሳሽ ባቀረበው ክስ ስር ተከሣሽ ደግሞ የምጠይቀው ገንዘብ አለኝ እያለ ያለ በመሆኑ በግራ ቀኙ መሐከል ክርክር ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 284 ከሚፈቅደው የአጭር ስነ ሥርዓት ውጭ መሆኑን የሚያሳይና የክርክሩ አመራርም በመደበኛው የሙግት ሥርዓት መመራት የሚገባው መሆኑን ተረድተናል፡፡

በመሆኑም የቀረበውን ክስ ተከሣሽ አልካደም በማለት ብቻ ተከሣሽ የሚያቀርበውን ሌሎች ገንዘቡን ልከፍል አይገባም በማለት የሚያቀርባቸውን መከራከሪያ ነጥቦች በመገደብ እና የመከላከያ ማስፈቀጃውን ውድቅ በማድረግ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 231275 ሕዳር 30 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እና ፍርድ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ጉዳይ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ/ 43315 የሰጠውን አስገዳጅ ውሣኔ ካለማገናዘብ እና የቀረበውን ጉዳይ ካለመመርመር የሰጠው ውሣኔ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሲሆን፣ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ በመ/ቁ 174388 የካቲት 21 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት በስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እና ውሣኔ ላይ የተፈፀመውን የሕግ ስህተት ሳያርም የስር ፍርድ ቤት ፍርድ ጉድለት የሌለበት ነው በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 231275 ሕዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 174388 የካቲት 21 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሕዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም. በውሣኔ የዘጋውን የመ/ቁ/ 231275 በማንቀሳቀስ ጉዳዩ በመደበኛ ስነ ስርዓት እንዲገባ በማድረግ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመልከት ተገቢ ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ከስር ፍርድ ቤት የቀረበው የመ/ቁ/ 231275 የሆነው መዝገብ በመጣበት አኳኋን ተመላሽ ይደረግ፡፡
4. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች እንዲላክ ታዟል፡፡
5. መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 127580

ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተሽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- ዲኖ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ለአመልካች መክፈል የሚገበው የመኪኖች ዋጋ እንደገና ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በሕግአግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም?የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በተጠሪ ሥም፤ በአመልካች ገንዘብ፤ ተጠሪ የሚሠራውን መንገድ ለመቆጣጠር አመልካች ለቀጠራቸውን ተቆጣጣሪ መሀንድሶች አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ የሰሌዳ ቁጥር 3-43969 አ.አ እና የሌዳ ቁጥር 3-43997 አ.አ የሆኑ መኪኖች አመልካች ለመረከብ ያቀረበውን ክስና የዳኝነት ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡
2. ተጠሪ ከላይ ቁጥራቸው የተገለፁትን መኪኖች የሥር ከሳሽ /አመልካች/ብር 1,185,688.16 /አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ሥምንት ብር ከአስራ ስድሰት ሣንቲም/ ለተጠሪ ሰጥቶ፤ የተገዙና መኪኖቹ አመልካች ለመደባቸው ተቆጣጣሪ መሀንዲሶች አገልግሎት ሲሰጡ የቆየ መሆናቸውን ገልፃ፣ ሁለቱም መኪኖች የድርጅቱን ሥራ በመምራት ላይ እያሉ የተገለፀው ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ ሆነዋል፡፡ ይህንን ዕውነታ ተከሳሽ የሚያውቀው ሲሆንአዋሽ ኢንሹራንስ /አ.ማ/ ሊያረጋግጠው የሚችለው ፍሬ ነገር ነው፡፡ ተከሳሽ መኪኖች አገልግሉት የሰጡት ሶስት ዓመት ከሥምንት ወር ዲፕሪሴሽን ዋጋ ተጠቅሶ ቀሪውን ለከሳሽ ለመክፈል በፅሑፍ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ በሌላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኩል የመኪኖቹ ዋጋ በፊት ከተገዙበት ከእጥፍ በላይ ስለጨመረ ልዩነቱን ከሳሽ ሸፍኖ አዲስ መኪኖች ገዝተው እንዳስረክበው ጥያቄ አቅርቤለታለሁ በማለት ተከራክሯል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች የተስማማው መኪኖቹን እንደሆነና መኪኖቹ ተገልብጠው ከጥቅም ውጭ በሆኑ የአገልግሎት ቅናሽ ከዋጋቸው ቅናሽ የሚደረግ ስለመሆኑ አመልካችን ተጠሪ ያልተስማሙ መሆኑን ገልፆ፣ ተጠሪ መክፈል የሚገባው መኪኖቹ በወቅቱ ገበያ የሚያወጡትን ገንዘብ መሆን አለበት፡፡ ተጠሪ የሶስት አመት ከስምንት ወር የአገልግሎት ቅናሽ ከዋጋቸው ላይ ይደረግልኝ በማለት የተከራካሪ ቢሆንም፤ መኪኖቹ በአደጋ ሙሉ በሙሉ በመውደማቸው፣ ለመኪኖቹ የመድን ሽፋን የሰጠው የኢንሹራንስ ድርጅት፤ አመልካች ክስ ካቀረበበት ገንዘብ ያሰ ገንዘብ የከፈለው መሆኑን፤ በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመኪኖቹ ግምት እንዲሰራ ትእዛዝሰጥቶ የሰሌዳ ቁጥር 3-43969 አ.አ ብር 780,000 /ሰባት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር/የሚያወጣ እንደነበርና የሰሌዳ ቁጥር 3-43997 ብር 820,000 / ሥምንት መቶ ሃያ ሺህ ብር/ያወጣ እንደበር ቢርቢስ ገዘሙ የንብረት ጉዳት ገማች ሪፖርት አቅርቦልኛል፡፡ ይህም አመልካች ተጠሪ እንዲከፍለው የጠየቀው ብር 118568348/አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ስድሰት መቶ ሰማኒያ ሶስት በር ከርባ ሥምንት ሣንቲም/ መኪኖቹ በወቅቱ ከሚያወጡት ዋጋ በታች በመሆኑ ይህንን ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ፤ ከዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ፤ በአንድ በኩል መኪኖቹ በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት በመወደማቸው ይግባኝ ባዩ /ተጠሪ/ የመድን ሽፋን ከሰጠው የኢንሹራንስ ድርጅት አመልካች የመለሰ ሰጭ እንዲቀበል ማድረግ ሲገባው ራሱ ተቀብሎ ወስኗል ካለ በኋላ፤ በሌላ በኩል ባለሙያው የመኪኖቹ ዋጋ እየጨመረ እንደሚሄድ ታሳቢ በማድረግና የመኪኖቹን የአገልግሎት እርጅና ቀናሽ ታሳቢ ሣያደርግ ግምቱን ሠርቶ ማቅረቡ ስህተት ያለበት ነው በማለት የመኪኖቹ ዋጋበሌላ ገለልተኛ ባለሙያ ተሠርቶ እንዲቀርብ በማድረግ፣ የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጭ ሊከፍል የሚገባውን የገንዘብ መጠን ውሣኔ ይሰጥበት በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሶልኮለታል፡፡

5. አመልካች ውሣኔ ያረፈበት ገንዘብ ባለሙያ ገምቶ ካቀረበው ያነሰ ሆኖ እያለና፤ የመኪኖች ዋጋ የእርጅና ተቀንሶ ተጠሪ የሚከፍል ስለመሆኑ አመልካችና ተጠሪ በተዋዋሉት ውሉ ላይ ባልተገለፀበትና ባልተስማማንበት ሁኔታ፤ የባለሙያ ግምት ውድቅ ለማድረግ ወደ ምክንያት ሣይኖረው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሻሩና ወደ ሥር ፍርድ ቤት ሌላ የባለሙያ ግምት እንዲያሰራ ጉዳዩ መልሶ መላኩ መሠረታዊ የህግ ስህተት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል። ተጠሪ ተፈልጎ ሊገኝ ያልቻለ መሆኑን አመልካች የቃለመሀላ ማመልከቻ በማቅረቡ ህዳር 15 ቀን 2009 ዓ.ም በታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ፣ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል።

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ መኪኖቹን እንዲመልስለት መኪኖቹን መመለስ የማይችል ከሆነ መኪኖቹን ለመግዛት የሰጠውን ገንዘብ እንዲከፍል የዳኝነት ጥያቄ አቅርቧል። ተጠሪ መኪኖቹ በአደጋ የወደም ለመሆኑ መኪኖቹን በአካል ላስረክበው አልችልም። ተመሣሣይ ይዘት ያላቸው መኪኖች ገዝቸ ለአመልካች ለመተካት፤ የመኪኖቹ ዋጋ ከእጥፍ በላይ ያደገ ስለሆነ፣ ቀሪውን ዋጋ ከሳሽ አመልካች ችሎ ገዝቸ እንድተካለት ጥያቄ አቅርቤያለሁ። የመኪኖቹ የእርጅናና የአገልግሎት ዋጋ ቅናሽ ተደርጎልኝ የመኪኖቹን ዋጋ ልክፈል የሚል መከራከሪያ አቅርቧል። ይህ የተጠሪ ክርክር በጉዳት ካሣ ምክንያት የወደሙት መኪኖች፣በአደጋው ምክንያት ከጥቅምውጭ በሆኑበት ወቅት መኪኖቹ ከተገቡበት ዕጥፍ የሆነ የገበያ ዋጋ የነበራቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ መከራከሪያ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

7. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ መኪኖቹ በአደጋው ሙሉ በሙሉ ወደመው ከአገልግሎት ውጭ በመሆናቸው ምክንያት፣ ተጠሪ ለመኪኖቹ የመድን ሽፋን ከሰጠው የኢንሹራንስ ድርጅት፣ የመኪኖቹ የሚከፈለውን የመድን ገንዘብ የተቀበለ መሆኑተረጋግጧል። ለመኪኖቹ የመድን ሽፋን የሰጠው ድርጅት መኪኖቹ ሶስት ዓመት ከስምንት ወር አገልግሎት ከሰጡ በኋላ በአደጋ ምክንያት ከጥቅም ውጭ በመሆናቸው ምክንያት ለተጠሪ የከፈለው ገንዘብ፣ አመልካች ተጠሪ እንዲከፍለው በክሱ ከጠየቀው ገንዘብ ያነሰ መሆኑን በማንሣት ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የለም። በአንፃሩ ተጠሪ የኢንሹራንስ ድርጅቱ ለመኪኖቹ የከፈለው ምን ያህል እንደሆነ ለሥር ፍርድ ቤትም ሆነ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ባቀረበው ክርክር አልገለፀም። ተጠሪ የኢንሹራንስ ድርጅቱ ለመኪኖቹ የከፈለው አመልካች በክሱ ከጠየቀው ገንዘብ በታች መሆኑን እስካላስረዳና በተቃራኒው ከኢንሹራንስ ድርጅቱ የተከፈለውን ገንዘብ ለመግለፅ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ተጠሪ መኪኖቹ ላይ በደረሰው አደጋ ከኢንሹራንስ ድርጅቱ የተከፈለው ገንዘብ አመልካች በክሱ ከጠየቀው ገንዘብ ያልተናነሰ ወይም ከዚህ በላይ ነው የሚለውን የህሊና ግምት ለመያዝ የሚያስችል ነው።

8. ሶስት ዓመት ከስምንት ወራት ካላገለገሉ በኋላ የመገልበጥ አደጋ ደርሶባቸው ከአገልግሎት ውጭ የሆኑት መኪኖች፣ በወቅቱ የነበራቸው የገበያ ዋጋና፣የቅሪት ዋጋቸው ምን ያህል እንደሆነ የሥር ፍርድ ቤት ገለልተኛ ባለሙያ መድቦ አስርቷል። የተመደበው ባለሙያ የመኪኖቹን ዋጋ የገመተው መኪኖቹ ከፋብሪካ ተመርተው እንደመጡ አዲስ መኪኖች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማድረግ ሣይሆን መኪኖቹ ሶስት ዓመት ከሥምንት ወራትአገልግለው በሚኖራቸው ይዞታ፣ መኪኖቹ ሶስት ዓመት ከሥምንት ወር አገልግሎት ሰጥተው የሚያወጡትን ዋጋመሠረት በማድረግ እንደሆነ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔና አመልካችካቀረበው ክርክር ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ገለልተኛ የንብረት ገማች የሆነው ባለሙያ ያቀረበውን የመኪኖች ዋጋ ግምት ተጠሪ የሌላ የባለሙያ ግምት ወይም የተሻለ ዕውቀትናክህሎት ያለው ባለሙያ የሙያ ምስክርነት እንዲሰጥ በማድረግ አላስተባበለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ባለሙያው መኪኖቹ የሰጡትን አገልግሎት ከግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባ የመኪኖቹን ግምት ሠርቶ እንዳቀረበ አድርጎ በመውሰድ ጉዳዩ እንደና በባለሙያ ይገመት በማለት የሰጠው ውሣኔ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136/1/ እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና የሥር ፍርድ ቤት በጭብጥነት ይዞ ያላጣራው ምንም አይነት ፍሬ ጉዳይ ሣይኖረው ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት የተጣራውን ፍሬ ነገር በድጋሚ እንዲያጣራ የሰጠውና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ውሣኔ ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 120329 የካቲት 22 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 138747 የሰጠው ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተራ ቁጥር ሁለት የተመዘገብኩት ዳኛ የሥራ ባልደረቦቼ በሰጡት ውሣኔ ላይ ሥነ ሥርዓታዊ በሆነ ጉዳይ ባለመስማማት የልዩነት ሐሳቤን እንደሚከተለው አስፍራለሁ፡፡

ከክርክሩሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች እና ተጠሪ በሚከራከሩበ የተሸርካሪዎች ዋጋ ክፍያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊከፍል ይገባል ያለው መጠን ለይቶ የወሰነ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሸከርካሪዎች በገበያ ላይ የሚኖራቸው ዋጋ በገለልተኛ ገማች ተጠንቶና ተገምቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲቀርብ በደድረና ሊከፈል የሚገባው የገንዘብ መጠን ይወሰን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት ለስር ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ፍሬ ነገሩ ከመታየቱ በፊት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ብቁ መሆን አለመሆኑን መታየት ነበረበት፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በነጥብ የመለሰው በመሆኑ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ አግኝቷል ለማለት አይችልም፡፡ በእርግጥ የሰበር ሰሚ ችሎቱ እንደመጨረሻ ውሣኔ በሚታዩ ትእዛዞች ላይ መዝገቦችን እየመረመረ ውሣኔ የሰጠበት ሁኔታ ያለ ስለመሆኑ የሚያከራክር ጉዳይ ቢሆንም በተያዘው ጉዳዩ ግን ሊጣሩ የሚገባቸው ነጥቦች ተለይተው ለሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተመለሰ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች አጣርተው የሚሰጡት ውሣኔ ሳይታወቅ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ብቁ ነው ተብሎ መቅረቡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ /ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10/2/ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መግንስት አንቀጽ 80/3//ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ አንድ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ብቁ የሚሆነው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት የመጨረሻ ውሣኔ /any final court decisions/ መስጠቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የይግባኝ ሂደቱን ያጠናቀቀ ጉዳይ ለሰበር መቅረቡ እንዲሁም ይህ ችሎትም ለሥር ፍርድ ቤት በነጥብ የተመለሰው ጉዳይ ተመልክቶ መወሰኑ ከላይ የተጠቀሱትን የኢፌዲሪ ሕገ መንግስትና አዋጅ ቁጥር 25/88 የላገናዘበ በመሆኑ ጉዳዩ ለሰበር ብቁ አይደለም ተብሎ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት በሐሳብ ተለይቻለው፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.102668

ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓሊ መሃመድ
ተክሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ
ቀነአ ቂጣታ
ፀሃይ መንክር

አመልካች/ዎች/፡- 1. ማክሲመም ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወኪል አንዋር አሊ ቀረቡ

2. አቶ መሊክ ዓሊ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ህዝቦች ክልል የሆሳዕና ከተማ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

አልቀረበም

በዚህ መዝገብ አመልካችዎችና ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር፣ አንደኛ አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 95733 ካቀረቡት ክርክር ጋር በማጣመር በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/11/4/ መሰረት በማጣመር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ በሁለተኛው አመልካች ላይ ያቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በመቀበል አከራክረው ውሳኔ መስጠታቸውና አንደኛ አመልካች ህንፃን በጊዜዊነት ሲያስረክብ፣ የአንደኛ አመልች ወኪል ፣ አንደኛ አመልካች ዕዳ ያለበት መሆኑን በማመን የእዳ መተማመኛ ሰነድ ፈርሟል በማለት አንደኛ አመልካች ተጠሪ በተከሳሽነት ከሳሽነት ክሱ የጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ህጋዊ መሰረት ያለው መሆኑን በስበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በአመልካችዎች ላይ አቅርቦ፣ አንደኛና ሁለተኛ አመልካችዎች ስማቸው በከሳሽ ተከሳሽነት ተመዝግቦ ጉዳያቸው ታይቷል፡፡ ከዚህ መዝገብ ጋር በተጣመረው በስበር መዝገብ ቁጥር 95733፣ ያቀረበው ጉዳይ በመጀመሪያ የታየው በሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትሲሆን፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆነው ህብረት ኢንሹራስ አ.ማ ተከሳሽ አንደኛ አመልካች ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ ክርክር መነሻ የሆነው አንደኛ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ተጠሪ ከሚያሰራቸው ኮንደሚኒየም ቤቶች አምስት ኮንደሚኒየም ቤቶችን በብር 1,862,626.74 /አንደ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ሁለት ሺኅ ስድስት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከሰባ አራት ሳንቲም/ ከሳሽ ለተከሳሽ ሰርቼ ላስረክብ ውል ተዋውያለሁ፡፡ በውላችን መሰረት፣ ከሳሽ ሶስት ኮንደሚኒየም ቤቶችን ስራ ሙሉ በሙሉ አጠናቅቄ አስረክቤአለሁ፡፡ ሁለት የኮንደሚኒየም ቤቶች ተከሳሽ አለባቸው የሚለውን የግንባታ ጉድለት አስተካክዬ ለማስረከብ ከሳሽ ጥያቄ ባቀርብም ተከሳሽ ባለመፈቀዱ፣ በሁለቱ ቤቶች ላይ አለ የተባለውን ጉድለት ለማስተካከል የሚሆን ገንዘብ አስቀርቶ ሌላውን ክፍያ እንዲከፍለኝ ብጠይቀው ተከሳሽ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ የሁለት ህንፃ የጉድለት ማስተካከያ ወጭ በመቀነስ፣ ለሰራሁት ጠቅላላ ስራ ተከሳሽ ብር 1,018,898 /አንድ ሚሊዮን አስራ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ስምንት ብር/ መክፈል ሲገባው ያልከፈለኝ በመሆኑ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

3. ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ፣ ህንፃዎቹ ሲገነቡ ለህንጻዎች ግንባታ የሚያገለግሉት የግንባታ ማቴሪያሎች ያቀረበው ተከሳሽ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከሳሽ ከሰሪው ስራ ላይ ግንባታ ማቴሪያል ዋጋ ተከሳሽ ቀንሶ የማስቀረት መብት አለው፡፡ በዚህ መሰረት የአምስቱ ኮንዶሚኒየም ቤቶች ጠቅላላ ዋጋ ከሳሽ በክስ ማመልከቻው ላይ የገለጸው ሲሆን፣ ከሳሽ በቅድመ ክፍያነት ብር 323934.90 /ሶስት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አራት ብር ከዘጠና ሳንቲም/ ወስዷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሳሽ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ብር 157,109.07 /አንድ መቶ ሃምሳ ሰባ ሺኅ አንድ መቶ ዘጠኝ ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም/ ተከፍሎታል፡፡ ከሳሹ በአጠቃላይ ብር 481,043.97/አራት መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ አርባ ሶስት ብር ከዘጠና ሰባት ሳንቲም/ ተከፍሎታል፡፡ ከሳሽ ከሰራቸው አምስት ህንፃዎች ውስጥ ሁለቱ ለሰው መኖሪያነት ሊያገለግሉ እንደማይችሉ በአማካሪ መሀንዲስና በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የምድህስና የትምህርት ክፍል ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ለተከሳሽ የሚከፈለውና የሚመልሰው ሂሳብ ያለበት መሆኑን በማረጋገጥ መተማመኛ የሰጠ በመሆኑ ተከሳሽ ገንዘብ እንድከፍለው የቀረበው ክስ የህግ ድጋፍ የሌለውና በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

4. የስር ተከሳሽ የሆነው ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ይዘት ከሳሽ ለህንፃዎቹ ግንባታ ከተከሳሽ የተረከበውን በቀድመው ዋጋው ብር 370,666.87 /ሶስት መቶ ሰባ ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ብር ከሰማኒያ ሰባት ሳንቲም/ አሁን ባለው ሆሳዕና ከተማ ውስጥ ባለው የገባያ ዋጋ ብር 1,195,231.55/አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከሃምሳ አምስት ሳንቲም/ ለህንፃ ግንባታ ሳይሆን ለግል ጥቅሙ ያዋለ ለመሆኑ አሁን ባለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የገበያ ዋጋ ሊከፍል ይገባዋል፡፡ በመጀመሪያ ዙር ከተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ሊደርግ የሚገባው ብር 137,147 አንድ መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አርባ ሰባት ብር/ እንዲመለስና በሁለቱ የተበላሹ ህንፃዎች ሊከፍል የሚገባው መቀጫ ብር 75,808.81 /ሰባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር ከሰማኒያ አንድ ሳንቲም በድምሩ ብር 1,590,187.37 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሰላሳ ሰባት ሳንቲም/ ከሳሽና የተከሳሽ ስራ አስኪያጅ አቶ መልክ ዓሊ /ሁለተኛ አመልካች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

5. ሁለተኛ ተጠሪ በተከሳሽ ላይ ያቀረብኩት ክስ ስሌለ እኔን ተከሳሽነት ከሳሽነት ባቀረበው ክስ ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ ያቀረበው ክስ ስነ ስርዓታዊ አይደለም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የተከሳሽ ከሳሽ የከሳሽ ተከሳሽና አቶ መልክ ዓሊ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉት በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ያቀረበው ገንዘብ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ከሳሽ ከተከሳሽ የሚጠይቀው ቀሪ ሒሳብ ያለበት ሆኖ እያለ፣ እንደገና ገንዘብ ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ያቀረበው ክስ የህግ ድጋፍ የሌለውና በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከሳሽ /አንደኛ አመልካችና/ ተከሳሽ /ተጠሪ/ የአምስቱን ህንፃዎች እርክክብ ሲፈጽሙ፣ ከሳሽ በተከሳሽ የሚከፍለው ብር 406,446.49 /አራት መቶ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ስድስት ብር ከአርባ ዘጠኝ ሳንቲም/ ያለበት መሆኑን በመግለጽ የዕዳ መተማመኛ ፈርሞና በመሀተም አረጋግጦ ሰጥቷል፡፡ ይህም ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ስለሚያረጋግጥ፣ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጌዋለሁ፡፡ በአንፃር ተከሳሽ በተከሳሽ ከሳሽነት ከጠየቀው ገንዘብ ውስጥ ብር 406,446.49 /አራት መቶ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ስድስት ብር ከአርባ ዘጠኝ ሳንቲም/ እና የመቀጫ ገንዘብ ብር 257,808.81 /ሁለት መቶ ሀምሳ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር ከሰማኒያ አንድ ሳንቲም በድምሩ ብር 664,255.30 /ስድስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ከሰላሳ ሳንቲም/ ከሳሽና አቶ መለክ ዓሊ በአንድነትና በነጠላ ለተከሳሽ ይክፈሉ በማለት በመዝገብ ቁጥር 111544 ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካችዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101881 ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ የአመልካችዎችን በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

6. በሰበር መዝገብ ቁጥር 95733 መነሻ የሆነውን ክስ ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09656 ባቀረበው ክስ ከአንደኛ አመልካች አምስት የኮንዶሚኒየም ቤቶች ሰርቶ የማስረከብ ከከሳሽ ጋር የህንፃ ስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውል ሲዋዋል ተከሳሽ ህብረት ኢንሹራንስ /አ.ማ/ እስከ ብር 182,262.64 /አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ብር ከስልሳ አራት ሳንቲም/ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ሰጥቷል፡፡ የስራ ተቋራጩ ስራውን በተሟላ ሁኔታ ያላስረከበ በመሆኑ ተከሳሽ ዋስትና የሰጠበትን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተከሳሽ የነበረው ህብረት ኢንሹራንስ /አ.ማ/ ክስ ያቀረበበትን የዋስትና ገንዘብ የማይከፍልበትን ምክንያት ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ አንደኛ አመልካች ጣልቃ ገብቶ፣ በህንጻዎቹ ግንባታ ላይ ጉድለት የሌለ በመሆኑ የከሳሽ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የስራ ተቋራጭ /ጣልቃ ገብ/ ከሰራቸው አምስት ህንጻዎች ውስጥ ሁለቱ ህንጻዎች ጉድለት ያለባቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ዋስትና የሰጠበትን ብር 182,262.24 /አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ብር ከሃያ አራት ሳንቲም / ለከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት በመዝገብ ቁጥር 09656 ሰኔ 7 ቀን 2005 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አንደኛ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 01945 ህዳር 12 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

7. አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 95733 የሆሳዕና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ታህሳስ 8 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ከተጠሪ የምጠይቀው ቀሪ ክፍያ ያለኝ መሆኔን ገልጩ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ አቅርቤአለሁ፡፡ የተሰሩት ቤቶች ጉድለት አለባቸው ወይም የለባቸውም የሚለው ጭብጥ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ታይቶ ከመወሰኑ በፊት፣ የሀዲያ ዞን የሕንጻው ግንባታ ጉድለት ያለበት ነው በማለት ለመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ከሕብረት ኢንሹራንስ /አ.ማ/ የተያዘው ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን የአንደኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር መልስ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አንደኛ አመልካች የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8 በመጥቀስ ያቀረበው መቃወሚያ የማለፋቸው አግባብነት በሰበር አጣርቶ ለመወሰን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ በሰበር መዝገብ ቁጥር 102668 /በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱታ ያስቀርባል የሚባል ቢሆን ለመጠባበቅ በሚል ከመጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ቀነ ቀጠሮ ሲለወጥ ቆይቶ፣ ጥቅምት 2 ቀን 2008 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 95733 ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ግራቀኙ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያደረጉት ክርክር ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ እንዲታይ ትእዛዝ የተሰጠበት በመሆኑ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ ታይቷል።

8. በዚህ መዝገብ ማለትም በሰበር መዝገብ ቁጥር 102668 አመልካችዎች ሐምሌ 2 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ነው። አመልካችዎች በጋራ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ሁለተኛ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ የለም። ተጠሪ ክስ ያላቀረበበት ሁለተኛ አመልካችን በመጨመር ያቀረበውን የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ ከሕግ አግባብ ውጭ ተቀብለው የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል። የህንጻዎቹ ጊዜዊ እርክክብ ሲፈጸም ሁለቱ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ሙሉ ለሙሉ እንዲፈርሱ አንደኛ አመልካች እንደተስማማ፣ አንደኛ አመልካች ለተጠሪ ብር 406,446.59 /አራት መቶ ስድስት ሺ አራት መቶ አርባ ስድስት ብር ከሃምሳ ዘጠኝ ሳንቲም/ እንዳለበት የዕዳ መተማመኛ ፈርሞ ሰጥቷል የተባለው ሰው ይህንን ለማድረግ የውክልና ስልጣን የሌለው መሆኑን ገልጸን ተከራክረን እያለን የስር ፍ/ቤት ፣ ለጉዳዩ የማይመለከተው ሰው የፈረመውን ፊርማ ሰነድ መሰረት በማድረግ የአንደኛ አመልካች ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግና የተጠሪን የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ በመቀበል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው። የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካችዎች የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል።

9. ተጠሪ ታህሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። ተጠሪ 2ኛ አመልካች የአንደኛ አመልካች ስራ አስኪያጅ በመሆኑና አንደኛ አመልካች ለፈጸመው ጉድለትና ጥፋት በንግድ ሕጉ መሰረት ሃላፊነት ስላለበት፣ በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ እንዲሆን መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል። የውክልና ስልጣን በተመለከተ አዲስ ያቀረበ የፍሬ ጉዳይ ክርክር ነው ከዚያም በኋላ አንደኛ አመልካች ያደረጋቸው መጻጻፎች ስላሉ የአመልካችዎች ክርክር ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል። በግራቀኙ በኩል የሁለቱም የሰበር መዛግብት ማለትም በዚህ መዝገብና በሰበር መዝገብ ቁጥር 95733 ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለጸው ሲሆን በትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ ይረዳን ዘንድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 111544 ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል።

10. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሁለቱ የሰበር መዛግብት ግራቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረበው አንደኛው አመልካች ነው። ተጠሪ የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ ሲያቀርብ፣ በተጠሪ ላይ ክስ ያላቀረበውን ሁለተኛውን አመልካች በተከሳሽ ተከሳሽነት በመጨመር ክስ የቀረበ መሆኑን ተገንዝበናል። የከሳሽ ተከሳሽ ክሳሽነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስ ሊያቀርብ የሚችለው በከሳሽ ላይ እንደሆነና፣ ተከሳሽ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሚያቀርብ በፍታብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 224 የተገለጸውን ስርዓት መከተል ያለበት መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 234 ንዑስ አንቀጽ 1/ረ/ ተደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተከሳሹ ሲያቀርብ የፍርድ ቤቱ ስልጣን እንዴት እንደሚወሰን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 30 ተደንግጓል። ተጠሪ በከሳሽነት ያልተሳተፈ ሶስተኛ ወገን /ሁለተኛ አመልካች/ ከአንደኛ አመልካች ጋር አጣምሮ ክስ ለማቅረብ ከፈለገ፣ በፍታብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 36 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት አንደኛ አመልካችንና ሁለተኛ አመልካችን አጣምሮ በአዲስ መዝገብ በመክሰስ መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 11/1/ አንደኛ አመልካች ካቀረበው ክስ ጋር ተጣምሮ እንዲታይለት ከሚያመለክት በስተቀር፣ በተጠሪ ላይ ክስ ያላቀረበውን ሁለተኛ አመልካችን በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውስጥ ስሙን መዝግቦና ጨምሮ ማቅረቡ፣ ከላይ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎች ያልተከተለ ሆኖ እያለ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ በሕግ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ ሁለተኛው አመልካች ላይ ያቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተቀብለው ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል።

11. ሁለተኛ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው መስከረም 21 ቀን 2004 ዓ.ም የተደረገው የጊዜዊ እርክብክብ ቅጽ ላይ አንደኛ አመልካች ለተጠሪ የሚመልሰው ብር 406,446.49 /አራት መቶ ስድስት ሺ አራት መቶ አርባ ስድስት ብር ከዜሮ አርባ ዘጠኝ ሳንቲም/ እዳ ያለበት መሆኑን ያሚገልጽ ሰነድ ነው ። አመልካች ይህ በጊዜዊ እርክብክብ ቅጹ ላይ የተገለጸው የሒሳብ ስሌት ትክክል አለመሆኑን በመግለጽ አንደኛ አመልካች ሙሉ በሙሉ ሰርቶ ለስራ ከባቻው ሶስት ህንጻዎች መክፈል የሚገባውን ክፍያ ያልከፈለ መሆኑን፣ በመግልጽ የተከራከር ሲሆን ይህንኑ በተመለከተ ያስረዱልኛል የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች በማስረጃነት ያቀረበ መሆኑን፣ አንደኛ አመልካችና ተጠሪ በቃል በጽሁፍ ካደረጉት ክርክር ተረድተናል። ይህንንም ክርክር መነሻ በማድረግ የተለያዩ የሙያ አስተያየቶች ከተለያዩ መስራያ ቤቶች የተሰጡ መሆኑን ተረድተናል። የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ/ም በተዋለው ጊዜዊ የእርክብክብ ቅጽ ላይ ያስፈሩትን የሒሳብ ስሌቶ በማስረጃነት የሚጠቀም ከሆነ፣ የጊዜዊ የእርክብክብ ቅጽ ላይ የሰፈሩ ፍሬ ነገሮች አገልግሎት የሚስጡት ሙሉ እርክብክብ እስኪፈጸምና የመጨረሻው ሒሳብ ተሰርቶ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ ብቻ ነው ወይስ አይደለም? ጊዜዊ እርክብክብ ቅጹ ላይ የተገለጸው የሒሳብ ስሌት በስራ ተቋራጩና በአስሪው መካከል የሚፈለገውን ክፍያና ሒሳብ ለማስረዳት የሚችላ ሰነድ ነው ከተባለ፣ የዕዳው መታማመኛ የተፈርመው አመልካችን ወክሎ የዕዳ መተማመኛ የመፈርም ስልጣን ባለው ሰው ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች በጭብጥነት ይዞ ማጣራት ነበረበት። በዚህ ቅጽ ላይ የፈረመው ሰው ማንነቱ ያልተገለጸ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም ስሙን ያልተጻፈ ሲሆን ተጠሪ ጊዜዊ እርክብክብ ቅጹ የተፈርመው በአንደኛ አመልካች ስራ እስኪያጅ ነው የሚል ክርክር በስር ፍርድ ቤትና ለዚህ ሰበር ችሎት በቀረበው ክርክር አላቀረበም፡፡

11. ሰነዱ አመልካች ስራ አስኪያጅ በወከለው ሰው የተፈርመ ነው የሚል ክርክር ቀርቧል፡፡ የአንደኛ አመልካች ስራ አስከያጅ ወርቅነህ አብዩ ህዳር 24 ቀን 2003 የሰጡት የውክልና ሰነድ ተወካዩ በኩንባያው ስም የዕዳ መተማመኛ እንዲፈርም ስልጣን የማይሰጠው መሆኑን በትዕዛዝ ከቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ለመረዳት ችለናል፡፡ ኩባንያውን ወክሎ የዕዳ መተማመኛ ለመፈርም የውክልና ስልጣን በሌለው ሰው የተፈረው የዕዳ መተማመኛ ሰነድ መነሻ የስር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ማድርጉና በተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተቀብሎ ውሳኔ መስጠቱ ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት የፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 136(1) መሰረት ባለሙያዎችን በመመደብ፤

(ሀ) አንደኛ አመልካች በውሉ መሰረት ሰርቶ ላስረከባቸው ሶስት የኮንደሚኒየም ህንጻዎች ግንባታ ተጠሪ መክፈል የሚገባው ጠቅላላ ክፍያና አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች መመለስ የሚገባው የግንባታ የማቴሪያል ዋጋ ምን ያህል ነው፡፡

(ለ) ጉድለት አለባቸው የተባሉት ሁለት ህንጻዎች ላይ ያሉ ሁሉም ኮለኖችና የመሬት ውስጥ ስራዎች ሙሉ በሙሉ ፈራሽ ይሆናሉ አይሆኑም? አንደኛ አመልካች ከመሬት በታችና መሰረቱን ለማውጣት ለሁለቱ ህንጻዎች የሰራው ስራ ግምትና፣ ህንጻዎቹን በመስራት የወሰደው የማቴሪያል ግምት ምን ያህል እንደሆነ ተመዝኖ እንዲመጣ በማድረግና፣ ሁለቱ ህንጻዎች ላይ ለታየው ጉድለት ተጠሪ ሊጠይቅ የሚችለው የጉዳት ካሳ ነው ወይስ የመቀጫ ገንዘብ የሚለውን፣ በማመዛዘን የአንደኛ አመልካችን ክስና የተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መወሰን ሲገባው መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ/ም በተምላው የጊዜዊ ዕርክብክብ ቅጽ ላይ ብቻ በመመስረት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

12. ሶስተኛው በሰበር መዝገብ ቁጥር 95733 የተያዘው ጭብጥ የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበው ለመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና በሰጠው በህብረት ኢንሹራንስ (አ.ማ) ላይ ነው፡፡ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና የሰጠው የኢንሹራንስ ድርጅት አንደኛ አመልካች ሊያነሳቸው የሚችላቸውን መከራከሪያዎች ሁሉ በማንሳት ለመከራከር የሚችል መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1926 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠሪ ለመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና የሰጠውን የኢንሹራንስ ድርጅት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሰጠው የዋስትና ግዴታ መሰረት እንድፈጽምለት በሀዲያ ዞን ክስ ያቀረበው ዋስትና ቦንድ የሰጠውን ድርጅት ዋስትና የገባቢትን ገንዘብ እንዲከፍል ለመጠየቅ በመሆኑ አንደኛ አመልካች የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 8 በመጥቀስ ያቀረበውን መቃወሚያ የበታች ፍርድ ቤቶች ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

13. አንደኛ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ሲያቀርብ ከሰራቸው አምስት ህንጻዎች ውስጥ ሁለቱ ጉድለት ያለባቸው መሆኑንና የሁለቱን ጉድለት ለማስተካከል የሚያስፈልገውን ገንዘብ ገምት አቅርቧል፡፡ የአንደኛ አመልካች የስራ አፈጻጸም ዋስትና የሰጠው ህብረት ኢንሹራንስ (አ.ማ) ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነበት ብር 186,262.62 /አንድ መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ብር ከስልሳ ሁለት ሳንቲም/ የአንደኛ አመልካች የተጠሪ ሒሳብ ተሰርቶ አንደኛ አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው ዕዳ ካለ፣ ከአንደኛ አመልካች ዕዳ ላይ ሊቀነስ የሚገባው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ፍርድ ተራ ቁጥር 11 የተያዙትን ጭብጦች ካጣራ በኋላ ሊከተለው የሚገባ የክርክር አመራር ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች የስራ አፈጻጸም ዋስትና ቦንድ በሰጠው የኢንሹራንስ ድርጅት ላይ ያቀረበውን ክስ ተቀበለው የሰጡት ውሳኔ የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 8 ድንጋጌን የማይጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

14. ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግና የተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በመቀበል የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111544 ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101881 ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 11 የተያዙትን ጭብጦች በገለልተኛ ባለሙያዎች ተጣርተው እንዲቀርቡለት በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 136(1) መሰረት ትዕዛዝ በመስጠትና ዕውነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማስረጃዎችን በማስቀረብ ወይም ምስክሮችን በመስማት የአንደኛ አመልካች ክስና የተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ ላቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት መልስን ልከንለታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ሁለተኛ አመልካች ላይ ተጠሪ ያቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ፣ በህጉ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ የቀረ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስነናል፡፡
4. የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09656 ሰኔ 7 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የደቡብ ብሔርብሔረሰቦችና ህዝቦች ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01945 ህዳር 12 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
5. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአንደኛ አመልካችንና ተጠሪ አከራክሮ ውሳኔ ሲሰጥ፣ ለአንደኛ አመልካች የስራ አፈጻጸም ዋስትና የሰጠው ህብረት ኢንሹራንስ (አ.ማ) ለተጠሪ እንዲከፍል በፍርድ የተወሰነበትን ገንዘብ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሂሳብ ስሌቱ እንዲሰራ በማድረግ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለራሳቸው ይቻሉ፡፡
7. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከሰበር መዝገብ ቁጥር 95733 ጋር ይያያዝ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.132208

ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ጸጋዬ አስማማው

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ጸሀይ አጎናፍር ቀረቡ

ተጠሪ ፡-አቶ ጌራ ላቀው አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሀብት ክርክርን ይመለከታል የአሁን ተጠሪ የስር አመልካች ሆነው ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ወላጅ አባቴ ኮ/ል ላቀው ወ/ሰንበት ከቤት ወጥቶ ሳይመለስ በመቅረቱ ሚያዚያ 21 ቀን 2007ዓ.ም የመጥፋት ውሳኔ አሰጥቼ ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ በመሆኑም የሟች አባቴን የውርስ ሀብት የውርስ አጣሪ ተሹሞ ይጣራልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል ፡፡

ፍ/ቤቱም የውርስ አጣሪ በመሾም የሟች የውርስ ሀብት ተጣርቶ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል ውርስ አጣሪው በትእዛዙ መሰረት ኮ/ል ላቀው ወ/ሰንበት ከ10/7/2007ዓ፣ም ጀምሮ ያሉበት ሁኔታ ባለመታወቁ ከሚያዚያ 20/2007ዓ.ም ጀምሮ የመጥፋት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ ኮ/ል ላቀው አመልካችን ብቻ የወለዱ መሆናቸውን፣ ኮ/ል ላቀው ከስር አመልካች እናት ጋር ከተለያዩ በኋላ የአሁን አመልካች ወ/ሮ ፀሀይ አጎናፍርን አግብተው መኖራቸውንና ልጅ ያለመውለዳቸውን፣ ኮ/ል ላቀው ከአሁን አመልካች ወ/ሮ ፀሀይ ጋር በባልና ሚስትነት ሲኖሩ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 2489 የሆነ ቤት ማፍራታቸውን ቤቱ በአሁን አመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑን ሲያጣራ የስር አመልካች የክርክሩ ቤት በወላጅ አባታቸው እና በአሁን አመልካች በጋራ የተፈራ መሆኑን በመግለጻቸው ውርስ አጣሪው የአሁን አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት የአሁን አመልካች የክርክሩን ቤት ከኮ/ል ላቀው ጋር በጋብቻ እያለን 70% ቢሰራም 30% ግን እሳቸው ከቤት ከወጡ በኋላ የሰራሁት የግል ንበረቴ ነው በማለት ክርክር ያቀረቡ በመሆኑ ውርስ አጣሪው ግራ ቀኙ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ቢሰጥም የስር አመልካች አቅርበው ሲያስሙ የአሁን አመልካች በተደጋጋሚ ምስክሮች እንዲያቀርቡ ታዘው ካለማቅረባቸውም በተጨማሪ ምስክር የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ ምስክሮች ያላቀረቡ ሲሆን የውርስ አጣሪው ከግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር እና የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮ የስር አመልካች የክርክሩ ቤት ወላጅ አባታቸው እና የአሁን አመልካች አብረው ባሉበት ተጠናቆ የተሰራ መሆኑን ሲያስረዱ የአሁን አመልካች ግን ኮ/ል ላቀው ከሄዱ በኃላ ለብቻዬ የቤቱን 30 ፐርሰንት ሰርቻለሁ ቢሉም አላስረዱም በማለት አትቶ የክርክሩ ቤት ኮ/ል ላቀው ወ/ሰንበት እና የአሁን አመልካች ወ/ሮ ፀሀይ አጎናፍር የጋራ ንብረት ነው ስለሆነም የስር አመልካች የአባቱን ድርሻ 50% የአሁን አመልካች ድርሻቸውን 50% እኩል ይካፈሉ በማለት ሪፖርት ሲያቀርብ ቤቱ የተከራየ ለመሆኑ የስር አመልካች ሲያስረዱ የአሁን አመልካች አለመከራየቱን አላስረዱም በማለትና እስከ አሁን የተከራየው ብር 84ሺ ነው በማለት ብር 42ሺ የስር አመልካች ድርሻ ነው በማለት ሪፖርቱ አቅርቧል ።

እዳን በተመለከተ እዳ አለኝ ብሎ የመጣ ስለሌለ ኮ/ል ላቀው አዳ የለባቸውም በማለት ሪፖርቱ ገልጾ ሪፖርቱን ከፈፀሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ለፍ/ቤቱ ቀርቧል። ፍርድ ቤቱም በቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት በሰጠው ትእዛዝ መሰረት የስር አመልካች በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ላይ ያቀረቡት ቅሬታ የሌለ ሲሆን ጣልቃ ገብ በሰጡት አስተያየት የክርክሩን ቤት ከኮ/ል ላቀው ጋር ስንሰራ በየካቲት ወር 1985 ዓ.ም ከባንክ ብድር የወሰድን መሆኑን የሚገልጽ እና ኮ/ል ላቀው ከሄዱ በኃላ ለመክፈል ተቸግሬ ባንኩ ማስጠንቀቂያ የሰጠበትን እና ኮ/ል ላቀውም የጻፉትንም ደብዳቤ አቅርቤያለሁ በተጨማሪም ኮ/ል ላቀው ከሄዱ በኃላ ለቤቱ ጠቅላላ ዋጋ 30 ፐርሰንት የሚሆን ወጪ አድርጌያለሁኝ በማለት ሰነዶች ያያያዝኩኝ ስለሆነ ቤቱን የሰራንበት የጋራ እዳ ያለብን መሆኑ እና በግል የሰራሁት 30 ፐርሰንት የግሌ ሊባል ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከውርስ አጣሪው ሪፖርት ጋር መርምሮ የአሁን አመልካች ያቀረቡትን 2 ቅሬታ መሰረት በማድረግ 1ኛ.ለክርክሩ ቤት ከባንክ ተወሰደ የተባለውን ብድር አስመልክቶ የአሁን አመልካች ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ማለትም አመልካች እና ባለቤታቸው ኮ/ል ላቀው በየካቲት ወር 1983 ዓ.ም ከቤቶች እና ገንዘብ ቁጠባ በጋራ ለቤት መስሪያ በማለት ገንዘብ የወሰዱ መሆኑን፣ ኮ/ል ላቀው በግንቦት ወር 1983 ከሀገር ወጥተው በ1985ዓ.ም ለአሁን አመልካች የጻፉት ደብዳቤ ቤቱ ተሰርቶ ያልተጠናቀቀ መሆኑን ያሳያል። በማለት አትቶ ምንም እንኳን የስር አመልካች ኮ/ል ላቀው ከቤት ሲወጡ ቤቱ ተሰርቶ አልቆ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነበር በማለት ቢከራከሩም የአሁን አመልካች ማስረጃ ኮ/ል ላቀው ከቤት ሲወጡ ቤቱ ተጠናቆ ያላለቀ መሆኑን በተሻለ አስረድተዋል በማለት አትቶ ቤቱ ተሰርቶ የተጠናቀቀው ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ ነው በማለት አመልካች ለቤቱ ማሰሪያ ያወጡትን ወጪ የሚያሳዩ ሰነዶች ያቀረቡ ስለሆነ ይህ ገነዘብ ከነወለዱ የአሁን አመልካች እና የአሁን ተጠሪ የጋራ እዳ ነው በማለት ሲወስን የአሁን አመልካች ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ የተሰራው ቤት የግል ንብረቴ ይባልልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ ምንም እንኳን ኮ/ል ላቀው ከቤት የወጡት በ1983 ዓ.ም ቢሆንም ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ እስከ መጋቢት 22/2002 ዓ.ም ድረስ ከአሁን አመልካች ጋር በደብዳቤ ይገናኙ የነበረ መሆኑን አመልካች ካቀረቧቸው የሰነድ ማስረጃዎች መረጋገጥ መቻሉን ገልጾ አመልካች እና ኮ/ል ላቀው በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ አብረው ባይኖሩም በጋብቻ የነበሩ ባል እና ሚስት ነበሩ በማለት አትቶ በጋብቻ ጊዜ የተፈራ ሀብት በሙሉ የባል እና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው በማለት የክርክሩ ቤት የአመልካች እና የባለቤታቸው የኮ/ል ላቀው ነው፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ የአባታቸውን ድርሻ አመልካች የራሳቸውን ድርሻ የቤቱን ግምት እኩል ይካፈሉ በማለት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች ለስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች ዋና ቅሬታ የተጠሪ አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል እና የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩ በይርጋ አይታገድም በማለት ውሳኔ የሰጠው እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያጸነው የአሁን ተጠሪ ክርክሩን ያቀረቡት በ6/9/2007ዓ.ም ሲሆን የአባታቸውን የመጥፋት ውሳኔ በፍርድ ቤት ያሳወጁት በ21/8/2007 ዓ.ም በመሆኑ ክርክሩ በይርጋ አይታገድም በማለት ነው፡፡

በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 165(1)ላይ በጠፋው ሰው መሞት ምክንያት መብት የሚያገኙ ሰዎች በመብታቸው መጠቀም የሚችሉት መጥፋቱን የሚወስነው ፍርድ የመጨረሻ ከሆነ በኃላ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ የአሁን ተጠሪ ክርክሩን ያቀረቡት በ6/9/2007ዓ.ም ሲሆን የአባታቸውን የመጥፋት ውሳኔ በፍርድ ቤት ያሳወጁት በ21/8/2007 ዓ.ም መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በመብታቸው መጠቀም የሚችሉ መሆኑ በህጉ የተመለከተ ሲሆን የመጥፋት ውሳኔ አሰጥተው የውርስ ሀብት ያቀረቡበት ጊዜ ሲቆጠር በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1000(1)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት ክርክሩ በይርጋ የሚታገድ ባለመሆኑ ይርጋን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላውን ክርክር በተመለከተ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ምክንያት በማሻሻል በውጤት ደረጃ ያጸናው ውሳኔ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ያጸነው ውርስ አጣሪው ኮ/ል ላቀው ከቤት ሲወጡ ቤቱ ተጠናቅቆ የነበረ መሆኑን የስር አመልካች በሰው ማስረጃ አስረድተዋል ስለሆነም የአሁን አመልካች ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ የሰሩት ተጨማሪ ስራ ለመኖሩ ያላስረዱ በመሆኑ የግል የሚባልላቸው መብት የለም በማለት ሲሆን፤ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንን ክርክር አስመልክቶ ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ ቤቱ ያልተጠናቀቀ መሆኑን እራሳቸው በጻፉት ደብዳቤ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡

ነገር ግን ኮ/ል ላቀው ከቤት የወጡት በ1983 መሆኑ ክርክር ያልተነሳበት ጉዳይ ቢሆንም እስከ 2002 መጋቢት ወር ድረስ በደብዳቤ ከአሁን አመልካች ጋር ይገናኙ የነበረ መሆኑን አመልካች ካቀረቧቸው ማስረጃዎች ማረጋገጥ የተቻለ ስለሆነ ምንም እንኳን አመልካች ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ የሰሩት ተጨማሪ ቤት መኖሩን በመግለጽ የግላቸው እንዲባልላቸው የጠየቁ ቢሆንም በዚህ ግንኙነት የተፈራ ንብረት የባል እና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉን በስር ከተደረገው ክርክር እና ማስረጃ መረዳት ተችሏል፡፡

በመሰረቱ በፌደራሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 63(1) ላይ አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን እስካላስረዳ ድረስ የተጋቢዎች ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ ቢመዘገብም የተጋቢዎቹ የጋራ ንብረት እንደሆነ እንደሚገመት ተደንግጓል፡፡ የአመልካች ክርክር በቤቱ ላይ ተጨማሪ ስራ የተሰራው ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ ነው በማለት ቢከራከሩም እስከ 2002 መጋቢት ወር ድረስ ይጻጻፉት የነበረውን ደብዳቤ አመልካች በማቅረብ ያስረዱ መሆናቸውን ከመረጋገጡም በተጨማሪ ኮ/ል ላቀው በ1983 ከቤት ወጥተው የመጥፋት ውሳኔ በፍርድ ቤት የተሰጠው ሚያዚያ 21 ቀን 2008ዓ.ም በመሆኑ የአመልካች እና የኮ/ል/ላቀው ጋብቻ እና ግንኙነት በኮ/ል ላቀው ከቤት መውጣት ያልተቋረጠ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም በጋብቻ ጊዜ የተፈራ ንብረት የባል እና ሚስቱ የጋራ ንብረት ሆኖ እንደሚገመት በህጉ የተደነገገ እና የግል ሊባል የሚችለው የግሌ ነው የሚለው ተጋቢ የግሉ መሆኑን በማስረዳት እንደሆነ በህጉ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የአሁን አመልካች ኮ/ል ላቀው ከሄዱ በኃላ የተሰራ በመሆኑ የግል ንብረቴ ነው ከማለት በስተቀር በግል ገንዘቤ ሰርቻለሁ በማለት ያነሱት መከራከሪያ የሌለ በመሆኑ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ምክንያት በማሻሻል በውጤት ደረጃ ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላም ተሰራ የተባለው ቤት የባል እና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ውሳኔ በማጽናት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መወሰኑ ህግን መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. .የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 100091 በቀን 6/8/2008ዓ.ም የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ እና ይህንን ውሳኔ በማጽናት የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 172889 ሀምሌ 8 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔው ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 131622

ሰኔ 20ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ እምሩ - ተወካይ አቶ ኢማሙ እብራሂም ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አይጠገብ ቀሬ- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዮ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የጉዳዩ መነሻ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ በተወካያቸው በኩል በጋምቤላ ክልል መንግሥት ሥር ለሚገኘው ለማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀን 16/10/2007 ዓ/ም ጽፈው ያቀረቡት ክስ የሚች አቶ ደምሴ ጋሻው የመጀመሪያ ሚስት መሆናቸውን፣ አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ ሁለተኛ ሚስት ነኝ በማለት የእሳቸውን የሚስትነት ድርሻ ንብረት እና የሚች ልጅ የውርስ ድርሻ ንብረቱን ለብቻቸው ይዘው የሚጠቀሙ በመሆኑ የተጠሪ የሚስትነት እንዲሁም የሚች ልጅ የውርስ ንብረት ድርሻ ይገባኛል የሚል ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያቀረቡ ሲሆን ይዘታቸውም፡-

1. ከሳሽ /የአሁኗ ተጠሪ/ በክሳቸው ዘርዝረው ያቀረቡት ጉዳይ በአሁኗ አመልካች /በሥር ተከሳሽ/ በኩል በአሁኗ ተጠሪ/ በሥር ተከሳሽ/ ላይ በሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት ክስ ቀርቦ የክሱ መጥሪያ ቀድሞ ለተጠሪ ደርሶዋቸው መልሳቸውን በጽሁፍ አቅርበው የቃል ክርክር ካደረጉ በኃላ ያቀረቡት ክስ ስለሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 7 መሠረት መጀመሪያ ክሱ በቀረበው በሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት እንዲቀጥል ፋይሉ እንዲዘጋልኝ፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የከሳሽ ተወካይ ክስ ለማቅረብና ለመከራከር የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 58 እና 63 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ያሟላ የውክልና ሥልጣን አይደለም፣
3. ከሳሽ የሚች ባለቤት ነኝ በማለት ክስ ያቀረቡ ቢሆንም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 33 እና 244 /2/ /ሠ/ መሠረት የመክሰስ መብት የሌላቸው በመሆኑ ንብረቶቹን ለመጠየቅ በይርጋ ቀሪ የሆነ ጉዳይ በመሆኑ መብት የላቸውም እንዲባልልኝ የሚል ነው።

የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኗ ተጠሪ በመቃወሚያዎቹ ላይ መልስ እንዲሰጡ ካደረገ በኃላ የአመልካችን መቃወሚያዎችን በብይን ውድቅ አድርጎ በማለፍ የፍሬ ነገር ክርክሩን ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን የሰው ምስክሮችን ቃል ሰምቶ ውሳኔ ሰጥቷል።

ይህን ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ለጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦዋል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ተቀብሎ የግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል። ቀጥሎም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን ተቀብሎ ክርክራቸውን ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አጽንቷል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን በአቤቱታቸውም በመጀመሪያ ደረጃ መሠረት የሚያደርጉት የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአመልካች በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በብይን ያለፈው ያለአግባብ ሆኖ እያለ ቀጥሎ ያሉት ፍርድ ቤቶችም ይህንን ሳያርሙ ማለፋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ካሉ በኃላ በፍሬ ነገርም ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽሞዋል የሚሉዋቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል።

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ያደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ/ም በነበረው ቀጠሮ መልሳቸውን ያላቀረቡት መጥሪያ ስላልደረሳቸው መሆኑን ገልጸው ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሠረት መልስ በተለዋጭ ቀጠሮ ቀን እንዲያቀርቡ ተፈቀደላቸው ሳያቀርቡ በመቅረታቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል።

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ወደ ፍሬ ነገሩ ክርክር መግባት ሳያስፈልግ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ብቻ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል። በዚሁ መሠረት፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. አመልካች አስቀድመው ክስ ለሸካ ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል ወይስ አላቀረቡም? ክስ በቅድሚያ ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ከሆነ መቃወሚያቸው በሥር ፍርድ ቤት መታለፉ ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 7 አንፃር እንዴት ይታያል?
2. የአመልካች ተወካይ በውክልና ክስ ለማቅረብ ይችላሉ ወይስ አይችሉም? የሚሉ ጭብጮች ተይዘዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

የአሁኗ ተጠሪ የሚች ባለቤታቸው ንብረት በአሁኗ አመልካች እጅ ስለሚገኝ የልጃቸውና የእርሳቸው ድርሻ እንዲወሰንላቸው ክስ በጋምቤላ ክልል ሥር በሚገኘው በጎዳሬ ወረዳ ፍርድ ቤት መሥርተው የሥረ ነገር ሥልጣን ክርክር በመነሳቱ ምክንያት ክስ የማቅረብመብት ያለው ወገን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ያቅርብ ተብሎ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት ብይንም በየደረጃ ላሉት ፍርድ ቤቶች ቀርቦ ፀንቷል፡፡

ከዚህ በኃላ የአሁኗ አመልካች ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት በቀን 09/10/2007 ዓ/ም የተጻፈ ክስ በአሁኗ ተጠሪ ላይ አቅርበው የክስ መጥሪያ ደርሶዋቸው በቀን 13/10/2007 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበው የቃል ክርክር እንደተደረገና ከዚህ በኃላ የቀረበ ክስ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች መቃወሚያ አቅርበው ተከራክረዋል፡፡ የአሁኗ ተጠሪም የአመልካችን መቃወሚያ ክደው አልተከራከሩም፡፡

የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ በቀደምትነት የቀረበው ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው? ወይስ በማጃንግ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው? የሚል ጭብጥ ይዞ ቀደም ሲል በጎዳሬ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ሲከራከሩ ቆይተው በ26/6/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት በተሰጠው ውሳኔ የአሁኗ ተከሳሽ /አመልካች/ ቅር በመሰኘት በከፍተኛ ፍርድ ቤት በክርክር ላይ የቆዩ ከመሆኑ ባለፈ ተከሳሽ /የአሁኗ አመልካች/ ያነሱትን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በቀደምትነት ክስ የቀረበው በማጃንግ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ግራ ቀኙ ወደ ፍሬ ነገር ገብተው ክርክራቸውን እንዲቀጥሉ ሲል በፍ/መ/ቁ. 02223 በቀን 27/11/ 2007 ዓ/ም ብይን እና በቀን 4/2/2008 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለ ክስ ቀደምትነት መሠረት ያደረገው በጎዳሬ ወረዳ ፍርድ ቤት የቀረበውን ክስ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የአሁኗ ተጠሪ በዚህ ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ነው ተብሎ በሥረ ነገር ሥልጣን ምክንያት የተዘጋ ነው፡፡ በዚህ ብይን ላይ የመክሰስ መብት ያለው ሰው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት በጋምቤላ ክልል እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል ሥር ባሉት ዞኖች ውስጥ የሚገኝ በመሆኑና የግራ ቀኙም የተለያዩ ክልል ነዋሪዎች ስለሆኑ አመልካች በሚኖሩበት ክልል በሚገኘው ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ ለዚህ ክስ ተጠሪ ቀርበው መልስ ሰጥተዋል፡፡ የቃል ክርክርም አድርገዋል፡፡ ይህ ከሆነ በኃላ ለማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሌላ ክስ የአሁኗ ተጠሪ ማቅረባቸውን ከሥር ፍርድ ቤት ብይን ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ክርክር የሚመራበትን ሥርዓት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ የሥነ ሥርዓት ህጉም ዓላማ ክርክር ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ተገማች እና ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ የተያዘውን ጉዳይ በተመለከተ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ እንዲቀርብ ብይን ከተሰጠ በኃላ በቅድሚያ የቀረበው ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 7 /1/ ሥር አንድ የፍትሐብሔር ክስ መታየት የሚገባው በአንድ የፍትሐብሔር ፍርድ ቤት ብቻ እንደሆነ በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ አንዱን የፍትሐብሔር ክስ ባንድ ወይም ካንድ በበለጡ ፍርድ ቤቶች ዘንድ ለማቅረብ የሚቻል ሲሆን የክሱ ማመልከቻ በቀደምትነት የቀረበለት ፍርድ ቤት ብቻ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለው ተቆጥሮ ለክርክሩ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል በማለት ተቀምጧል፡፡ አሁን ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የተጠቀሰው ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 7/2/ ሲሆን ይህም ከላይ ከተመለከተው ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ዓላማ አንጻር ሲታይ የሚገባ ነው፡፡ የማጀንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ በሥረ ነገር ሥልጣን ምክንያት የተዘጋውን ጉዳዩ በይግባኝ ቀደም ሲል አይቶ የዘጋ ሆኖ እያለ አዲስ ክስ ሲቀርብለት መጀመሪያ በሥልጣን ምክንያት በይግባኝ ታይቶ የታለፈውን ግምት ውስጥ በማስገባት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉ ሲታይ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 7 /2/ ድንጋጌን የጣሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የተሰጠው ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

በክሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የሙጉት ተከፋይ ሆነው ለመከራከር የሚችሉ ሰዎችን በተመለከት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ በሁለተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 32 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ እነዚህን ተከራካሪዎችን ወክለው ለመከራከር የሚችሉ ሰዎችንም በተመለከተ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 57 እና ተከታዮቹ አንቀጾች ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን ደንግጓል፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪን ወክለው በሥር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት የተጠሪ ወኪል አንቀጽ 58 ወይም 63 'ን' ድንጋጌ የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለውን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ አመልካች የተጠሪ ወኪል ከእነዚህ ሁለቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎች አንዱንም የማያሟሉ በመሆናቸው ሊከራከሩ አይችሉም በማለት በሥር ፍርድ ቤት ተቃውሞዋቸውን አሰምተዋል፡፡ የማኛንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለዚህ መቃወሚያ ምንም ብይን ሳይሰጥ በዝምታ እንዳለፈ ከሰጠው ብይን ላይ ተመልክተናል፡፡

አንድ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ለቀረበለት መቃወሚያ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 245 /2/ መሠረት ተገቢውን ብይን መስጠት እንዳለበት በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ሳይሰጥ በማለፍ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ 59294 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን በአግባቡ ሳይመለከተውና ለቀረበለት መቃወሚያ ብይን ሳይሰጥ በዝምታ ማለፉ ሲታይ ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠሪ ተወካይ ክስ አቅርበው ለመከራከር እንዲችሉ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 58 ድንጋጌን የማያሟሉ እንዳልሆነ የተጠሪ ተወካይ ለማኛንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካቀረቡትና በብይኑ ላይ ከሰፈረው ለመመልከት ችለናል፡፡ በተጨማሪ የፍትሐብሔር ሥነ ህግ ቁጥር 63 ድንጋጌንም የሚያሟሉ እንዳልሆነ በሥር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 58 ወይም 63 ድንጋጌን የማያሟሉትን የተጠሪን ወኪል የሥር ፍርድ ቤት እንዲከራከሩ ማድረጉ ድንጋጌዎቹን የጣሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድን ሰው በመወከል በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመሟገት በህጉ የተቀመጠውን የዝምድና ደረጃ ወይም በህጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ የውክልና ስልጣን የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ.91493 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉምን፣እንዲሁም በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር ስለዋናዎቹ ባለጉዳዮች በመሆን ሌሎች ሰዎች በተሟጋችነት ሊቀርቡ ስለሚችሉበት ስርዓት፣ በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ አለመገኘት የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤትን በተመለከተ በሰ/መ/ቁ. 94302 ሥር የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያላገናዘ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ በማንኛውም ደረጃ በሚገኙት ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት እንዳለው አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 /1/ ይደነግጋል፡፡

በአጠቃላይ የማኛንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ነገሮችን በአግባቡ ሳያጤን የሰጠው ብይን እንዲሁም ቀጥሎ ያሉት የበላይ ፍርድ ቤት ችሎቶችም ይህን ሳያርሙ ማለፋቸው ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 02223 በቀን 27/11/2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን እና በቀን 4/2/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.01850/08 በቀን 11/04/2008 ዓ/ም እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ሰ/ቁ. 00500/08 በቀን 16/09/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በቀን 09/10/2007 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ መሠረት የተጀመረውን ክርክር በተጀመረው መዝገብ ላይ በመቀጠል የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን ተመልክቶ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ተብሎ ተወስኗል ፡፡
3. ከላይ በሁለተኛ ጭብጥ በፍርድ ሀተታ ላይ በተገለጸው መሠረት ቀደም ሲል ለተጠሪ ወኪል በመሆን የተከራከሩት አቶ ሞገስ አለምነህ ጉዳዩን ለመከራከር አይችሉም ብለናል፡፡
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይላክላቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.113613

ግንቦት 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ
ተክሊት ይመሰል
ተፈሪ ገብሩ
ቀነዓ ቂጣታ
ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- በደቡብ ወሎ ዞን የለገሂዳ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ዓ/ሕግ አበበ ሙሉ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ሰለሞን አባይ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የግንባታ ዉልን መነሻ ክፍያ ለመጠየቅ የቀረበዉን ክስ የሚመለከት ክርክር ሲሆን፣ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.97192 በ5/9/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳ ዩአመጣጥ ሲታይ በደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ የለገሂዳ ትምህርት ጽ/ቤት በወረዳዉ 012 ቀበሌ የሸክፍ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለማሰራት ያወጣዉን ጨረታ ከሳሽ አሸንፎ በ12/10/2002 ዓ.ም ዉል የተዋዋልን ሲሆን፣ በዚህ ዉል መሰረት ሥራዉን አጠናቅቄ ጊዜያዊ ርክክብ ተደረጓል፤ ነገር ግን ተከሳሽ ቀሪ ክፍያ ብር 86,944.26 ስላልከፈለኝ ይህን ገንዘብ ለዘገየበት ጊዜ መቀጫ 1% ጋር እንዲከፍለን፣ እንዲሁም በዚህ ምክንያት የደረሰብኝ ኪሳራ ብር 52,324 ስለሆነ በአጠቃላይ ብር 380,383.53 እንዲከፍለን በማለት ክሷል፡፡ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ይህን ዉል ማድረጋችን የማይካድ ቢሆንም ከሳሽ የቀረበዉ ክፍያ ብር 63,791.63 ብቻ ነዉ፤ እንዲሁም ከሳሽ የግንባታዉን ሥራ በጥራት ሳይሰራ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን የኦዲት ሪፖርት ያረጋገጠ ስለሆነ ብር 58,659.20 እንዲካካስልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በማጣራት በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ለከሳሽ ያልከፈለዉን ክፍያ ብር 86,949.26 ሊከፍል ይገባል የዚህ ገንዘብ ክፍያ ለዘገየበት 1% መቀጫ እንዲከፍል፣ ከሳሽ ያጣዉን ጥቅም በተመለከተ ተከሳሽ ብር 1,683.00 ለከሳሽ እንዲከፍለዉ፣ ተከሳሽ ከሳሹ ሥራዉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በጥራት ስላልሰራ ብር 58,659.20 እንዲመልስልን በማለት የጠየቀውን በተመለከተ ተቀባይነት የለውም ከሳሽ ይህን ገንዘብ ለተከሳሽ ሊመልስ አይገባም፤ ተከሳሽ የጠበቃ አበል በተወሰነ ገንዘብ ልክ 10% እና ወለድ ዉሳኔ ከተሰጠበት እስከሚከፈልበት በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት በመ.ቁ.9121 ብር 58,659 እንደተወሰነለት በመግለጽ ይግባኙን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ የመቀጫ ክፍያ 1% ክስ እስከቀረበበት እንዲከፈል ጠይቆ እያለ ዉሳኔ እስከተሰጠበት የተባለዉ ያልተጠየቀ ዳኝነት ስለሆነ ተገቢ አይደለም፤ ወለድን በተመለከተ ክስ ከቀረበበት ጀምሮ እስከ ዉሳኔ ድረስ ባለዉ ጊዜ ተከሳሽ በተወሰነዉ ገንዘብ ልክ 9% ተከሳሽ ለከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት የሥር ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ አሁንም ይህን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ5/9/2007 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት በአጭሩ፡--የአሁን ተጠሪ ቀሪ ክፍያ እንዲፈጸምለት በመ.ቁ.5402 ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ አመልካች ደግሞ ተጠሪ የሰራዉ የግንባታ ሥራ ጥራት ጉድለት ስላለበት ለማስተካከል ግንባታዉን ለማስተካከል ብር 58,659.00 ወጪ ያደረገ ስለሆነ ይህን ገንዘብ እንዲከፍለን በመ.ቁ.9121 ክስ አቅርበናል፣ የሥር ፍ/ቤት እንዲጣመር በማድረግ አጣርቶ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ይህን ሳያድርግ ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በመ.ቁ.9121 ተጠሪ ለአመልካች ብር 58,659 እንዲከፍለን ዉሳኔ ተሰጥቶ እያለ ይህ ዉሳኔ ጸንቶ እያለ ለአመልካች ገንዘብ እንድንከፍል ዉሳኔ መስጠቱ ጉዳዩን በአግባቡ አለማጣራቱን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በመ.ቁ.9121 በተሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ የግንባታ ሥራዉን በጥራት ስላልሰራ ብር 58,659.00 ለአመልካች እንዲከፍል ተወስኖ እያለ፣ በመ.ቁ.5402 ደግሞ አመልካች ለተጠሪ ቀሪ ክፍያ ብር 86,944.26 እና ክፍያ ለዘገየበት የመቀጫ እና የወለድ ገንዘብ እንዲከፍለዉ የመወሰኑን እና የሁለቱ ፋይሎች በአንድ ላይ ተጣምሮ ያለመወሰን ያስከተለዉን የሥነ ሥርዓት ጉድለት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.11 አንፃር ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጣሪ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘዉ መሰረት በ4/4/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ በአግባቡ ስለሆነ የቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር ሰቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ የግንባታ ዉልን መነሻ በማድረግ ቀሪ ክፍያ እንዲከፈለዉ አመልካች ላይ ክስ አቅርቦ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በመ.ቁ.5402 ላይ አመልካች ለተጠሪ ብር 86,944.26 እና የዚህን ገንዘብ 1% መቀጫ ተሰልቶ እንዲከፍል፣ ወለድ ዉሳኔ ከተሰጠበት ገንዘቡ እስከሚከፈል ድረስ እና የጠበቃ አበል በተወሰነ ገንዘብ ልክ 10% እንዲከፍል ወስኗል፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሊከፈል የሚገባ የመቀጫ ገንዘብ እና የወለድ መጠን ላይ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፣ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ዉሳኔ ማጽናቱን የቀረበዉ የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የሰራዉ የግንባታ ሥራ ጥራት ስላልነበረዉ ይህን ጉድለት ለማስተካከል ብር 58,659.20 ወጪ ስላደረግን ይህን ገንዘብ እንዲከፍለን በማለት በመ.ቁ.9121 ግንቦት 15 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ የሰራዉ ሥራ ጥራት የሌለዉ መሆኑን በማረጋገጥ ተጠሪ ይህን ጉድለት እንዲያስተካክል ወይም በክሱ የተመለከተዉን ብር 58,659.20 ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር የሥር ፍ/ቤቶች እነዚህ መዝገቦች አጣምረዉ ዉሳኔ መስጠት ሲገባቸዉ ይህን ሳያደርጉ ዉሳኔ መስጠታቸዉ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን ተጠሪም ባቀረበዉ ክርክር እነዚህ ሁለት ዉሳኔዎች መሰጠቱን ክዶ የተከራከረ ነገር የለም፡፡ ይህ ችሎት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንደተመለከተዉ በዚህ ጉዳይ ሁለት መዝገቦች መከፈታቸዉን የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ባያመለክትም፣ አመልካች ይህ ገንዘብ እንዲካካስለት የጠየቀ መሆኑን ያሳያል፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በዚህ ጉዳይ በሁለት መዛግብት ዉሳኔ እንደተሰጠበት ግልጾ የተከራከረ ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ላይ ተገቢ ዉሳኔ ሳይሰጡበት አልፈውታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ግራ ቀኞቸዉ በየፊናቸዉ የየራሳቸዉን ክስ አቅርበዉ መዝገብ አስከፍቶ ዉሳኔ ያገኙ መሆናቸዉን ያመለክታል፡፡

በመሰረቱ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ክሶች ወይም ይግባኞች በሚቀርቡብት ጊዜ በሕጉ የተመለከተዉ መስፈርት ተሟልቶ እንደሆነ ተጣምሮ መታየት እንዳለባቸዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.11 ያስገናዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ክሶች ወይም ይግባኞች በአንድ ፍ/ቤት ቀርበዉ በመሰማት ላይ በሚገኙበት ጊዜና ተከራካሪዎቹም ወገኖች ባንድ ዘንግ የተመደቡ ሲሆኑ የቀረበዉም የሕግ ክርክር ወይም የነገር ጭብጥ ተመሳሳይና አንድ ዓይነት ሲሆን ከባለጉዳዮቹ አንደኛዉ ወገን ባመለከተ ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ተገቢነቱን የገመተ እንደሆነ ክሶቹ ተጣምረዉ በአንድነት እንዲታዩ አስፈላጊዉን ትዕዛዝ ለመስጠት ይቻላል፡፡ በማለት ደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ መገንዘብ እንደሚቻለዉ እነዚህ ክሶች ወይም ይግባኞች መጣመራቸዉ ተከራካሪ ወገኖችን ተገቢ ካልሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወጪ ለማስቀረትና ጊዜያቸዉን ለመቆጠብ ሲባል፣ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ተመሳሳይ እና የማይጣረስ ወይም የማይጋጭ እንዲሆን ለማስቻል መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የግራ ቀኞቸዉ ክርክር አንድ የግንባታ ዉልን መነሻ ያደረገ በመሆኑ፣ ከግንባታ ሥራዉ ጋር በተያያዘ ተጠሪ ቀሪ ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎችን የጠየቀ መሆኑን፣ አመልካች ደግሞ የግንባታዉ ሥራ በጥራት ስላልተሰራ አመልካች ይህን ጉድለት ለማስተካከል ያወጣዉን ወጪ ተጠሪ በማለት የጠየቀ በመሆኑ፣ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ11 በሚደነግገዉ አግባብ መዝገቦቹን በማጣመር ዉሳኔ ቢሰጡ ኖሮ አሁን የተፈጠረዉ ሁለት ዉሳኔዎች ባልተወሰነ ነበር፡፡ አሁን ግን በዚህ ጉዳይ በሁለት መዝገቦች ሁለት ዉሳኔዎች እንዳሉ ችሎቱ ተገንዘቦታል፡፡ በአንድ ጉዳዩ ግራ ቀኞቸዉ ባለመብት የሆኑበት ሁለት ዉሳኔዎች እንዳሉ ያመለክታል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች እነዚህን መዝገቦች አጣምሮ ዉሳኔ ባይሰጡም፣ እነዚህ ዉሳኔዎች ተጣጥሞ እንዲፈጸሙ ካልተደረገ ለአፈጻጸምአስቸጋሪ ሁኔታ የሚፈጥሩ እንደሚሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ ስለሆነም ግራ ቀኞቸዉ የየራሳቸዉን ክስ አቅርበዉ የፍርድ ባለመብት እስከሆኑ ድረስ ዉሳኔዎቹ ተጣጥሞ ሊፈጸሙ ይገባል ብለናል፡፡

በዚህ መሰረት ሲታይ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ብር 86,944.26 ከመቀጫ እና ከወለድ እንዲሁም ከጠበቃ እና ከሌሎች ወጪዎች ጋር እንዲከፍል የተወሰነ ሲሆን፣ ተጠሪ ደግሞ ብር 58,659.20 ለአመልካች እንዲከፍል የተወሰነ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ አሁን ተጠሪ ከአመልካች ጋር ባደረገዉ ክርክር ሥራዉን በጥራት እንዳልሰራ ተረጋግጦ ይህን ለማስተካከል አመልካች ያጣዉን ወጪ እንዲተካ በተወሰነበት ሁኔታ የአሁን አመልካች ለተጠሪ የመቀጫ ገንዘብ፣ የጠበቃ አበል እና ሌሎች ክፍያዎችን የሚከፍልበት አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች የገንዘብ መቀጫ፣ የጠበቃ አበል እና ሌሎች ወጪዎችን ለተጠሪ ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ለተጠሪ ሊከፍለዉ የሚገባዉ የገንዘብ መጠን ተቀንሶለት ብር 27,840.06 /ሀያ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ከዜሮ ስድስት ሳንቲም/ እና የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ከሰጠበት ከ17/6/2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ በዚህ አግባብ አይተዉ ሁለቱን መዝገቦች አጣምረዉ ዉሳኔ መስጠት ሲገባቸዉ የአሁን አመልካች በፍርድ መብት ባገኘበት ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለተጠሪ ገንዘብ እንዲከፍል የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.5402 በ17/6/2006 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማሻሻል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.01-02009 ታህሳስ 8 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመ.ቁ.97192 በ5/9/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ ተሻሽሏል፡፡

2. የአሁን አመልካች ብር 27,840.06 /ሀያ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ከዜሮ ስድስት ሳንቲም/ እና የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ከሰጠበት ከ17/6/2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. የአሁን አመልካች በግንባታ ዉሉ መሰረት የገንዘብ መቀጫ፣ የጠበቃ አበል እና ሌሎች ወጪዎችን ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉ ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 136775

ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ጸጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሠለ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡- ህዳሴ 1ኛ ደረጃ ከፍተኛ አገር አቋራጭ የህዝብ ባለንብረቶች ማህበር

ዳዊት ጌታቸው ነ/ፈጅ

ተጠሪ፡- የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ነ/ፈጁ ብሩክ ሀይሌ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ ይመዝገብልኝ ክርክርን ይመለከታል፡፡ ከሳሽ አመልካች ሆኖ በወኪሉ አማካኝነት በተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ላይ ለፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ከሳሽ ማህበር በህግ አግባብ የተቋቋመ በመሆኑ አላማውን ለማሳካት እንዲችል በጠቅላላ ጉባኤው የጸደቀ መተዳደሪያ ደንቡን አሻሽሎ እንዲመዘግብለት በህግ ግዴታ ለተጣለበት ተከሳሽ ቢያቀርብም ተከሳሽ ፍቃደኛ ባለመሆን ያልመዘገበልኝ ስለሆነ ይህንን በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ እንዲመዘግብ እና ወጪ እና ኪሳራ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳንኝነት ጠይቋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተከሳሽ የመተዳደሪያ ደንቡን የሚመዘግበው ወይም የማይመዘግበው በስራ መመሪያው መሰረት ነው፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤት ይህ መተዳደሪያ ደንብ እንዲመዘገብ የሚወስንበት የህግ አግባብ የለም በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ቅሬታው የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታው መልስ ሰጪን ያስቀርባል በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስቀርቦ ሲያከራክር አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያነሳውን ክርክር ሲያቀርብ መልስ ሰጪ በስር ፍርድ ቤት ባለመጠራቱ መልስ አልሰጠም ነበር እና በዚህ ክርክር ያነሳው የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንቡ ያልተመዘገበው ከሞዴል መተዳደሪያ ደንቡ ጋር የሚቃረን ስለሆነ እና ሞዴል መተዳደሪያደንቡን መሰረት ያላደረገ ማሻሻያ ሊመዘገብ ስለማይገባ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ይህ የመልስ ሰጪ ክርክር በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑተቀባይነት የለውም በማለት አትቶ በውጤት ደረጃ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው በነዚህ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም፡- የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ እንዲመዘግብ ይወሰንልኝ አቤቱታ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መወሰናቸው ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎትም ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክራቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ የአመልካችን በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ የተሻሻለ ስለሆነ እንዲመዘግብ ይወሰንልኝ በማለት የቀረበውን አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣንየለንም በማለት መወሰናቸው ተገቢ መሆን ያለመሆኑን በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡

በመሰረቱ አንድ በፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ የክስ ምክንያት አለው ብሎ ለመወሰንየሚቻለውበክሱ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሹ የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ሕግ ይፈቅድለታል ወይ?የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ፍርድ ቤቱ አሥንታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚችል የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑበዚህ ረገድ የተፃፉት የማብራሪያ ዐሐፎች ያሳያሉ፡፡
ትራንስፖርትን ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 468/1997አንቀጽ 15 (2) ስር በትራንስፖርት የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ማህበሮችበጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ ሲያሻሽሉበተጠሪ እንደሚመዘገብተደንግጎ ይገኛል፡፡ስለሆነም ማንኛውም የትራንስፖርትማህበር የማህበሩን አላማ ለማሳካት በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ወጥቶ የጸደቀውን መተዳደሪያ ደንብ ካሻሻለ በተጠሪ ባለስልጣን መ/ቤት አቅርቦ ማስመዝገብ አለበት፡፡
ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስአመልካች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ በመሻሻሉ በተጠሪ እንዲመዘገብጥያቄ ማቅረቡየሕግ አግባብ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲመዘገብለት ለተጠሪ ቢያቀርብም መ/ቤቱ ለመመዝገብ ፍቃደኛ ያለመሆኑን በመግለጹ በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲመዘገብ ይወሰን ዘንድ የቀረበውን አቤቱታ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣን የፍርድ ቤቶች አይደለም በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሰው አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡

በኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1)ስር እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግግ እና በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ስር ደግሞ ማንኛውም ማህበር የአባላቱን የግል ወይም የጋራ ጥቅም በመወከል የመጠየቅ እና ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለው ደንግጓል፡፡

አመልካች የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ እንዲመዘገብለት ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ተቀባይነት ማጣቱ አስከተረጋገጠ ድረስ መብቱን ያጣው በህግ አግባብ መሆን ያለመሆኑ ሊመረመር የሚገባው በመሆኑ አመልካች ይኸው እንዲመረመርለት ያቀረበውን አቤቱታ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪን አስቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት እንኳን ሳያደርግ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ውሳኔጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀረበለት የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ይህንን የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ማረም ሲገባው ባለማረም የሰጠው ውሳኔ ስለክስ ምክንያት አጠቃላይ መንፈስ እና ይዘት በሕጉ ላይ የተመለከተውን መመዘኛንያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.237969 መጋቢት 23 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 176926 ጥቅምት 30 ቀን 2009 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ስለሆነም ጉዳዩ በፍርድ ቤት የሚታይ ነው ብለናል፡፡
3. የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ተጠሪ መ/ቤት በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በማድረግ አመልካች ማህበር እንዲመዘገብለትያቀረበውን የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ ተጠሪ መ/ቤት አልመዘግብም በማለት የወሰነው በአዋጁ እና በመመሪያው መሰረት መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ የመሰለውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት ይመለስ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
5. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ ሰ/ማቁ. 102406

ሕዳር 9 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጠታ

ክፍለጽዮን ማሞ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- የወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ

ተጠሪ፡- አቶ ባጫ አለሙ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የመሬት ይዞታ ክርክር በተመለከተ በሽማግሌዎች ታይቶ የካቲት 17 ቀን 2005 ዓ/ም ውሳኔ ከሰጡበት በኋላ በአዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ እና /ሠ/ በተደነገገው የሰላሳ ቀናት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ/ም ክስ ያቀረበ በመሆኑ፣ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጡት ብይን አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡
2. የክርክሩ መነሻ አመልካች ለአዳማ ልዩዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ከሳሽ/አመልካች/ ከምስራቅ ሸዋ ዞን ከተማ ልማት ጽ/ቤት በህጋዊ ካርታ ተረክቦና የሸንኮራ አገዳ አልምቶ ከሚጠቀምበት የይዞታ መሬት ተከሳሽ /ተጠሪ/ ስፋቱና መጠኑ እንደዚሁም አዋሳኝ ምልክቱ በክስ ማመልከቻው የተገለጸውን ሸንኮራ አገዳ ተክልና የይዞታ መሬት ከህምሌ 1 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ በመያዝ ሁከት እየፈጠረብኝ ስለሆነ ሁከቱ እንዲወገድ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ጉዳዩ በሽማግሌዎች ታይቶ ውሳኔ ከተሰጠውና ውሳኔው በቀበሌው አስተዳደር ከተመዘገበ በኋላ በህጉ የተመለከተው የሰላሳ ቀናት የይርጋ ጊዜ ካለፈው ያቀረበ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

3. አመልካች በዚህ ሰበር ችሎት ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሽንኮራ ተክልና የመሬት ይዞታ ክርክር በጅምሩ በኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት በወጣው አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 16 መሰረት ለአስማሚ ሸማግሌ የሚቅረብ አይደለም፡፡ ጉዳይ ስለ ዕርቅ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የሚያሟላ አይደለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ አስታራቂ ሽማግሌዎቹ ውሳኔ በሰጡ በሰላሳ ቀናት ክስ ያላቀረብክ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ መስከረም 1 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ፣ አመልካች ጉዳዩ በሽማግሌ እንዲታይለት ከጠየቀ በኋላ የቀበሌው አስተዳደር ሽማግሌዎች መድቦ ጉዳዩ ታይቶ ከተወሰነ በኋላ በስልሳ ቀን ውስጥ ክሱን ያላቀረበ በመሆኑ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው ቅሬታ የህግ መሰረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው፣ የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 16 ግጭትና አለመግባባት በመጀመሪያ በአስታራቂ ሽማግሌዎች እንደፊቱ የሚደነግጉ ድንጋጌዎች መሰረታዊ ዓላማ በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ አርሶ አደሮች መካከል በእርሻ መሬት ይዞታ ምክንያት የሚነሳ አለመግባባት፣ ጉዳዩን በቅርብ አይተውና ተመልክተው፣ወደ ሙግት ሳይገባ በሽማግሌዎች የሚፈቱበትን ስርዓት ለመዘርጋትና አርሶ አደሩ በመሬት ይዞታ ግጭት ምክንያት ለምርት ስራ የሚያውለውን ጊዜ በፍርድ ቤት ክርክር እንዳያሳልፍ ለማድረግ ነው፡፡ የዚህ አዋጅ ድንጋጌ የፌዴራል መንግስት ካወጣው አዋጅ ቁጥር 456/97 ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም ያለባቸው መሆኑ የሚያከራክር ነጥብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

5. የክልሉ ም/ቤት ያወጣው የአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 16 ድንጋጌዎች በፌዴራል ወይም በክልል ደረጃ የተመዘገበና ህጋዊ እውቅና ያገኘ ህግ ወለድ ሰው ከአንድ አርሶ አደር ጋር በመሬት ድንበር ወይም ይዞታ ጥያቄ ምክንያት በሚፈጥር አለመግባባት የሚያገለግል እንዳልሆነ በአዋጅ ድንጋጌዎች መሰረታዊ ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአሁን አመልካች በህጋዊ ካርታ ተረክቦ ለስኳር ምርት ካለማው ልማትና ሽንኮራ አገዳ ተክል ተጠሪ እንዲለቅለት ክስ ለማቅረብ፣ ጉዳዩ በመጀመሪያ በሽማግሌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማሳየት ኃላፊነት ቅድመ ሁኔታ የለበትም፡፡ ይርጋውም ጊዜ የሚቆጠረው በቀበሌ አስተዳደር የተመደቡ አስታራቂ ሽማግሌዎች ውሳኔ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ተጠሪ የሽንኮራ እርሻውን በሀይል ይዟል ከተባለበት ሀምሌ 1 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ክስ ያቀረበው ተጠሪ በይዞታው ላይ ሁከት ከፈጠረበት ጀምሮ በህግ የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ከማለፍ በፊት ማለትም ሀምሌ 25 ቀን 2005 ዓ/ም በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አግባብነት የሌለውን የኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1/1/ ጠቅሰው የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 16577 ጥቅምት 2 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 172112 ሰኔ 11 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ይዞታውን ለማስከበር ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት ወስነናል፡፡
3. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 341/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.100395

ሕዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሠናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች ወ/ሮ አማረች ማሬ ጠበቃ ማስታወል ሀብታሙ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሜሪ ታደሰ
2. ወ/ሪት ፈጣኑ ታደሰ
3. ወ/ሪት ሮማን ነስሩ
} ጠበቃ ሀይሉ ዓይናለም ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪዎች እየኖሩበት ያለውንና በ 300 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ቤት ለቅቀው እንዲያስረክቧት የመጠየቅ መብት የላትም ንብረቱን የሸጠችላትን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ከስሳ ትጠይቅ በማለት የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል ፡፡
2. ከሳሽ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የመፈላም ክስ ነው ከሳሽ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 287 የግል ሀብቴ ስለመሆኑ በክፍሉ አስተዳደር የባለሀብትነትና ባለይዞታነት ማረጋገጫ ማስረጃ (ካርታ) በእጁ ይገኛል፡፡ ተከሳሾች ከቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውስጥ በጥገኝነት እንዲኖሩ ፈቅጂላቸው ሲኖሩ ቆይተዋል ። አሁን ግን ቤቴን እንዲለቁ ብጠይቃቸው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ፍርድ ቤቱ ተከሳሾች ቤቴን እንዲለቁና እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች

3. ተጠሪዎች በተከሳሽነት ቀርበው እኛ በከሳሽ ቤት በከሳሽ ፈቃድ በጥገኝነት የምንኖር ሰዎች አይደለም ። ተከሳሾች በእጃችን አድርገን ይዘን እየኖርንበት ያለው ቤትና ይዞታ አያታችንና እናታችን ከዛሬ አርባ ዘጠኝ ዓመት ጀምሮ ይዘውት ሲኖሩበት የነበረ ቤት ነው።ተከሳሾች ከአያታችንና ከእናታችን ጋር ክስ ያቀረበበትን ቤት ይዘን ስንኖር ፣ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በአያታችን ባዶ የይዞታ ቦታ ላይ በአንድ በኩል ቤት ሠርታ ስትጠቀም ቆይታ ፣ቤቱን ለአሁን ከሳሽ ሸጣለታለች ሆኖም እኛ የምንኖርበት ቤት ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ በእጇ አድርጋ ይዛው የማታውቅና የራሱ የሆነ ይዞታና የወሰን አጥር ያለው በመሆኑ ከሳሽ ቤቱን ለከሳሽ የሸጠችውም ሆነ ከሳሽ የእኛን ቤትና ይዞታ በማጠቃለል እንዴት ካርታና ፕላን እንዳወጡ የክፍሉ አስተዳደር እንዴት የእኛን ቤትና ይዞታ በማጠቃለል እንዴት ካርታና ፕላን እንደሰጠ ይጠየቅልን በማለት መልስ ሰጥተዋል። የስር ፍርድ ቤት የክፍሉ አስተዳደር ተገቢውን ማጣሪያ በማድረግ መግለጫ እንዲሰጥ ትዕዛዝ የቤቱ ስመ ሀብትና ከወ/ሮ እህተ ገብረማርያም ሂሩት አበራሽ ስም ሂሩት ስም የተዛወረዉ በስር ትዕዛዝ ፋይል ቁጥር 139/84 መስከረም 25 ቀን 1985 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንደሆነና ከዚያ በኃላ ሂሩት አበራሽ በውልና ማስረጃ ከከሳሽ ጋር በተዋዋለችው የቤት ሽያጭ ውል 1189 ሜትር ካሬ ላይ ያረፈው ቤትና ይዞታ በከሳሽ ስም እንዲዘዋወር ተደርጎ ከሳሽ የባለሀብትነት ማስረጃ የሰጠ መሆኑን ተረጋግጧል ።

4. የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ወ/ሮ እህተ ገብረማሪያም ጋር ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የገዙት ዋናውን ቤት የቤት ቁጥር 287 እንደሆነ የሚገልፅ ቢሆንም ገዥ ይህንን ዋናውን ቤት ተረክበውና በእጃቸው አድርገውት አያውቁም ። ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ ገብተውና ከሻጭም ተረክበው.ይኖሩ የነበሩት ሰርቪስ ቤትና በባዶ ይዞታ ላይ ራሳቸው የሠሩትን ቤት ነው ። ገዥ ገዥቻለሁ የሚሉትን የቤት ቁጥር 287 በ 300 ካሬ ሜትር ላይ 1984ዓ.ም ጀምሮ ተረክበውና በእጃቸው አድርገውት አያውቁም ነገር ግን የሻጭን መሞት ምክንያት በማድረግ ይህንን 1984ዓ.ም ተረክበውና ይዘው የማያውቁትን ቤት ጨምሮ በሽያጭ ውሉ መሠረት ተረክበው የሚኖሩበትን ይዞታ ላይ ያለው ቤት ስመሀብት እንዲዛወርላቸው በማድረግ የባለሀብትነት ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል ። ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በፍርድ ቤት ውሣኔ መነሻ የተሰጣቸውን የባለሀብትነት ሰነድ በማየት ፣ከሚች እህት ገ/ማሪያም ቤቱን ከገነባች ጀምራ ተረክባና በእጇ አድርጋ የማታውቀውን የቤት ቁጥር 287 ዋናውን ቤት በ 300ካሬ ሜትር እንዳለፈ ፣በእጇ አድርጋ ስታካብት ከኖረችው ቤት ጋር አንድ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለከሳሽ ሽጣ ቤቱና ይዞታው በተከሳሾች እጅ ባለበት ከሳሽ በሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እጅ ባልነበረና ሆኖ በማያውቅ ቤትና ይዞታ ላይ ጭምር የባለሀብትነት ማስረጃ አውጥታለች ። ይህም ለከሳሽ ቤቱን የሸጠችው ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ ተከሳሾች ይዘው የሚኖሩበትን ቤትና የይዞታ ቦታ በሽያጭ ውሉ መሠረት ያላስረከበቻትና ቤቱና ይዞታው በተከሳሽ እጅ ባለበት የሰነድ ርክክብ ብቻ ያደረገች መሆኑን ስለሚያሳይ ከሳሽ ሻጭዋን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እንጂ ተከሳሾች ቤቱን እንዲያስረክቧት መክሰስ አትችልም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል ።

ይህንን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲያየው አመልካች ጠይቃ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል።

5. አመልካች ሚያዝያ 27 ቀን 2008ዓ.ም አመልካች አከራካሪውን ቤት በውል ገዝታ የንብረት ባለሀብት መሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አባት ይህ ከሆነ ንብረቷ እንዲለቀቅ የመክሰስ መብት የላትም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው። የበታች ፍርድ ቤቶች ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ጭብጦችን አልመሰረቱም ተጠሪዎች ቤቱን በጥገኝነት ስለመያዛቸው ለቀበሌ ለአስተዳደር አመልክተዋል በሻጭና በከሳሽ መካከል የተደረገው ውል ተጠሪዎችን የሚመለከት አይደለም ። አመልካች የቤቱ ሻጭ በዋቢነት እንድትቀርብላት ሣትጠራ ፣ንብረቱ ላይ ያገኛቸው የባለሀብትነት መብት ለማስከበርና ለመፋለም የሚከለክላት ህግ በሌለበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ያለበት ነው በማለት አመልክታለች ።
6. ተጠሪዎች በመጀመሪያም ሂሩት አበራሽ ከሚች አያታችን እህተ ገ/ማሪያም ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል አስመልክቶ ለአውራጃው ፍርድ ቤት ክስ ስታቀርብ ሚች የሸጠችላትን ቤት እጇ አድርጋና ተረክባ እየኖረችበት መሆኑን ገልፃለች። ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እኛ የምንኖርበትን ቤትና በአዋሳኝ አጥር ታይቶ ያለውን 300 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ተረክባም ሆነ ይዛው አታውቅም ። እኛ በማናውቀው ሁኔታ የእኛን ቤትና ይዞታ ካርታና ፕላን ማውጣቷና ለከሳሽ መሸጧ ከሳሽን የቤቱ ባለመብት አያደርጋትም ። የባለሀብትነት ካርታና ማስረጃውም በክፍሉ አስተዳደር የታገደ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል ። አመልካችዎች የመልስ መልስ አቅርበዋል ። ግራቀኙ የሚያከራክራቸውን ጭብጥ ለመረዳት ችሎቱ የግራቀኙን የቃል ክርክር ሰምቶ የቃል ክርክሩ ከትራንስክራይበር ማሽን ተገልብጦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል ። የክፍሉ አስተዳደር በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የፃፈውን መግለጫ ለማየት የፌዴራል ከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 135280 እንዲቀርብ በታዘዘው መሠረት መዝገቡ ቀርቦ ተያይዟል ።

7. ከሥር የክርክሩ አመጣጥ በዚህ ሰበር ችሎት ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ቤቱና ይዞታው እንዲለቀቅላቸው ክስ ያቀረቡት ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታና ሸጭ ተረክበው የያዙትን ቤትና ይዞታ በድምሩ 1139 ካሬ ሜትር ላይ ያሉትን ቤቶችና ይዞታ በብር 120,000 የካቲት 3 ቀን 1997 ጋብቻ የቤቱ ስመሀብት የተሰራልኝ በመሆኑ ተከሳሾች (ተጠሪዎች) የግል ሀብቴና ንብረቴ የሆነውን ቤትና ይዞታ ይለቀቅልኝ በማለት ነው። ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ክሳሽ የቤትና ይዞታውን ባለቤትነት መብት በሽያጭ አስተላልፋልኛለች የምትሉት አበራሽ ሂሩት እኛ የያዝነውን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ለክሳሽ በሽያጭ ለማስተላለፍ መብት የላትም ። ክሳሽ እኛን ከመጠየቋ በፊት በሽያጭ ውሉ መሠረት እኛ የምንኖርበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ሻጭ ነፃ አድርገ እንድታስረክባትና የሽያጭ ውሉን እንድትፈፅምላትና ከምትጠይቅ በስተቀር ክሳሽ የሽያጭ ውሉ ሙሉ በሙሉ እንደተፈጸመላትና ንብረቱንም ከሻጭ እንደተረከበች አድርጋ በመቁጠር በቀጥታ እኛን ከቤት እንድንወጣ የመጠየቅና ክስ የማቅረብ መብት የላትም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተረድተናል።

8. ግራቀኙ በሥር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር አመልካችና ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት የካቲት 3 ቀን 1997 ዓ.ም የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል ሻጭ ሙሉ ለሙሉ ፈፅማለች ወይስ አልፈፀመችም ሻጭ በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታዋን ሙሉ በሙሉ ካልፈፀመችና ውሉን በከፊል የፈፀመች መሆኑ ቢረጋገጥ ገዥዋ ሻጭ ቀሪውን ግዴታዋን እንድትፈፅምላት በሻጭ ላይ ክስ ማቅረብ ወይም በተከሳሽነት አጣምራ ሳትከስ የውሉ ተዋዋይ ያልሆኑ ሶስተኛ ወገኖች ላይ በቀጥታ ክስ በማቅረብ ትችላለች ወይስ አትችልም ?የሚሉት ነጥቦች መታየት ያለባቸው ናቸው።

9. ከላይ ከተገለፁት ነጥቦች አንፃር ስንመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል የገባውን ግዴታ የሚፈፅምባቸው ሁለት መሠረታዊ ኃላፊነቶች አሉ። የመጀመሪያው ሻጭ በሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ ስፍራው የሚገኙ ሰዎች የተሸጠውን የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲለቁ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ይዞታ ከሌሎች ሶስተኛ ወገኖችና ከሻጭ ቁጥጥርና ይዞታ ነፃ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለገዥ ማስረከብ እንደሆነ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና ከፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2274 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ለመረዳት ይቻላል ሻጭ ከዚህ በተለየ ሁኔታ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ርዕስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገብ ላይ የተመዘገበና ገዢውንም ሊያስገድዱ የሚችሉ የሶስተኛ ወገኖች መብት በሰጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ካሉ ይህንኑ የሶስተኛ ወገኖች መብት ካለ ሻጭ ለገዥ ማስታወቅ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2880 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2881 ተደንግጓል ።

10. የሻጭ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ከሶስተኛ ወገን ይዞታና ቁጥጥር ነፃ በማድረግ የማስረከብ ግዴታ ገዥ ለሻጭ ከሚሰጠው የመነቀል ዋስትና ግዴታ የተለየ ነው ። ሻጭ በንብረቱ ላይ ያስፈሩና በንብረቱ መዝገብ የተመዘገበ መብት የሌላቸውን ሰዎች የማይንቀሳቀሰውን ንብረት እንዲለቁ በማድረግ ለሻጭ የማስረከብ ግዴታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ውል በመፈፀም ሂደት ገዥ ሻጭ ሊያከናውነው የሚገባ የመጀመሪያ ግዴታ ሲሆን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2882 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ሻጭ ለገዥ የሸጠለት የማይንቀሳቀስ ንብረት የማይነቀል ስለመሆኑ የሚሰጠው ዋስትና ገዥ የገዛውን የተረከበውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሌሎች ሰዎች ቁጥጥር ነፃ ሆኖ ከተረከበ በኃላ ንብረቱ የእኔ ነው ባይ ቢመጣ ሻጭ በዋቢነት ሊቆምለት የሚገባ መሆኑን የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች ናቸው።

11. የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ንብረቱን ከሌሎች ሰዎች ቁጥጥር ይዞታ ሥር ነፃ አድርጎ በማንገዝ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2274 መሠረት የማስረከብ ግዴታ ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሀብትነት ለማስተላለፍ የሚችሉ አስፈላጊ ሰነዶች ለገዢ የማስረከብና የማይንቀሳቀሰ ዉን ንብረት የማይነካ የባለሀብትነት መብት ለገዥ ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆነ ተግባራትን የመፈጸም ግዴታ መሆኑ በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 2875 በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2879 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2281 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል።

12. ከላይ በዝርዝር ካየናቸው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ 1139 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ ያረፈውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሙሉ በሙሉ ለአመልካች የሸጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት፣በሽያጭ ውሉ መሰረት የማይንቀሳቀስውን ንብረትና ይዞታውን ከሌሎች ሰዎች ቁጥጥርና ይዞታ ስር በማስለቀቅ የማይንቀሳቀስ ንብረትና ይዞታውን በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2875 በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2274 እና በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2888 መሰረት ለገዥ(ለአመልካች)የመፈጸም ግዴታውን የተወጣችው ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በከፊል ነው።ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ.ከተጠሪዎች አውራሽ ንብረቱን ገዛሁ ከምትልበት 1984 ዓ.ም ጀምሮ ተረክበውና በእጇ አድርጋው የማይታወቅ መሆኑና፣ቤቱን ለአመልካች ከሸጠችላት በኋላ ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታ፣ ተጠሪዎች በህግ አግባብ እንዲለቁ በማድረግ ለአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላስረከበችበት አመልካችም በሽያጭ ውሉ የተገለጸውን ቤትና ይዞታ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን፣ሻጭ(አበራሽ ሂሩት)ይዛው የነበረውን ቤትና ይዞታ ብቻ ከሻጭ የተረከበች መሆኑን ተረድተናል፡፡

13. ገዥ ሻጭ በሽያጭ ውሉ የገለጸችውን የማይንቀሳቀስ ንብረትና ይዞታ፣ ተጠሪዎች የሚኖሩበት ቤትና ይዞታ ሳይጨምር በሻጭ እጅና ይዞታ ስር ያለውን ቤትና ይዞታ የተረከበች ቢሆንም፣ሻጭ የሰጠቻትን ሰነድ በመጠቀም በሽያጭ ውሉ ላይ የተመለከተውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለመብት መሆኗን የሚሳይ ማስረጃ ከክፍሉ አስተዳደር ተሰጥቷታል፡፡ይህም ገዥዋ(አመልካች)ከሌሎች ሰዎች ይዞታና ቁጥጥር እንደዚሁም የመብት ጥያቄ ነጻ ሆኖ ከሽያጭ ያልተረከበችውን ተጠሪዎች የሚኖሩበት ቤትና ይዞታ ባለመብት መሆኗን የሚያረጋግጥ የባለሀብትነት ማስረጃ የተሰጣት መሆኑን ያሳያል፡፡አመልካች የቤቱ ባለሃብትነት መብት በሽያጭ ውል ከወ/ሮ አበራሽ ሂሩት የተላለፈላት መሆኑን የሚያሳይ የሽያጭ ውል ሰነድና በሽያጭ ውሉ መሰረት በማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለሀብትነት የተዛወረላት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በማያያዝ በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1206 መሰረት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም አላት፡፡ነገር ግን አመልካች ባቀረበችው የክስ መነሻ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ጭብጥ፤(ሀ) ቤቱን ንብረቱ ነው ካለ ለአመልካች የሸጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት አከራካሪውንና ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታ ባለሃብትነት መብት ለአመልካች የማስተላለፍ እርግጠኛ የሆነ የባለሀብትነት መብት በንብረቱ ላይ አላት ወይስ የላትም?

(ለ)ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት የተጠሪዎች የሚኖርበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ጨምራ የባለሀብትነትን ማስረጃና ካርታ የሰራችው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?አመልካችስ 1139 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትና ባለይዞታ መሆኗን የሚያረጋግጥ የባለህብትነት ማስረጃና ካርታ የተሰጣት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?(ሐ)ተጠሪዎች እየኖሩበት ያለውን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ቦታ ለአመልካች የመልቀቅና የማስረከብ ግዴታ አለባቸው ወይስ የለባቸውም?የሚሉት ለአመልካች 1139 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ውል አስተላልፋለች የተባለችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በክርክሩ ተሳታፊ ስትሆን ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ጭብጦች አይደሉም፡፡

14. የስር ፍርድ ቤት አመልካች የቤቱ ሻጭ የሆነችውን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ከሚከሰሱ በስተቀር በቀጥታ ተጠሪዎች ቤቱን እንዲለቁለት ክስ ማቅረብ አትችልም በማለት የሰጠው ውሳኔ ሻጭ በሽያጭ ያስተላለፈው ንብረት ላይ ያለውን መብትና ጥቅም ለማስከበር ገዥው ከውል የመነጨ መብት ያለው መሆኑን ያላገናዘበና የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1195 የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1206 እና የፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 33(2)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ ስህተት ያለበት ነው።ነገር ግን የበታች ፍርድ ቤቶች ቤቱን ለአመልካች የሰጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በክርክሩ ተከሳሽ መሆን አለባት በማለት የደረሱበት ድምዳሜ የፍትሃብሄር ህግ አንቀጽ 2875፣ አንቀጽ 2274፣አንቀጽ 2888 እና የፍትሃብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በጉዳዩ ተከሳሽ መሆን አለባት በማለት የደረሱበት መደምደሚያ በውጤት ደረጃ የሚነቅፍ ሆኖ አላገኘነውም።

15. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የቤቱን ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት መክሰስ አለባት ካሉ በኋላ፣ይህ ውሳኔአቸው የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት ሳይመዝን ተጠሪዎችን ከክስ ማሰናበታቸው አግባብነት ያላቸውን የስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም አመልካች ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በሽያጭ ውሉ መሰረት ተጠሪዎች የያዙትን ቤት አስለቅቀው ታስረክበኝ የሚል ክስ ስታቀርብ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ በማናቸውም ሁኔታ የሚገኙ ሰዎችን በተከሳሽነት አጣምራ መክሰስ እንዳለባት የፍትሃብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 36 ንዑስ አንቀጽ 4 አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ይደነግጋል።ይህም አመልካች ሻጭዋን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩትን በምትከስበት ጉዳይ ተጠሪዎች የግድ በተከሳሽነት እንዲሳተፉ ማድረግ የሚገባ መሆኑ በህግ የተደነገገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ዳኝነት ከፍላ ያቀረበችውን ክስ የቤቱ ሻጭ በጉዳዩ የመጀመሪያ ተከሳሽ መሆን አለባት በሚል ምክንያት ዘግቶ አመልካችን ከሚያሰናብት፣በጉዳዩ የቤቱ ሻጭ በክርክሩ በተከሳሽነት ተሳታፊ እንድትሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ትዕዛዝ መስጠት በዚህ ፍርድ አንቀጽ ተራ ቁጥር 13 በተመለከቱና በሌሎች ጭብጦች ላይ አመልካች (የቤቱ ገዥ)፣ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ሻጭና በአከራካሪውን ቤትና ይዞታ ይዘው የሚኖሩት ተጠሪዎች የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ መወሰን ሲገባው፣አመልካች ተጠሪዎችን የመክሰስ መብት የላትም በማለት መዝገቡን መዘጋቱና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ማጽናቱ ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና የዳኝነት አካሄድ ስርዓት ያልተከተለና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66605 የካቲት 29 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 135280 መጋቢት 2 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል።
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በተከሳሽነት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በመጨመር፣በዚህ ፍርድ በተራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁጥር 13 የተመለከቱትንና ሌሎች አከራካሪ ጭብጦች ላይ ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በማሰማትና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መልሰን ልከንለታል፡፡

3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.120087

ታህሳስ 7 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-አቶ አስራት ኩምሳ - ጠበቃ ረጅብ ኡስማን ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ጉደታ በዳዳ
2. አቶ ገነነ ከበደ } ጠበቃ ባይሳ ዲንሳ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩከገጠር መሬት የተገኘ ነው የተባለን አላባ ለማስከፈል ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 29557 በ04/03/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ታይቶበመዝገብ ቁጥር 170570 በ30/07/2006 በፍርድ የጸናውን ውሳኔ በመሻር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ቀደም ሲል በመሬት ይዞታው ላይ የይገባኛል ክስ ባቀረቡበት ጊዜ አሁን በመዝገብ ቁጥር 29557 ክስ ያቀረቡበትንም የአላባ ጥቅም አካተው መክሰስ ሲችሉ ነጥለው በማስቀረት አሁን አዲስ ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (4) እና 218 ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት የሌለው ሆኖ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ከተጠሪዎቹ የቀረበውን መቃወሚያ ተቀብሎ መዝገቡን መዝጋት ሲገባው ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ገብቶ ውሳኔ መስጠቱ እና ውሳኔው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት ማግኘቱ ተገቢነት የለውም በማለት የክልሉ ጠቅላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 185098 በ22/02/2008 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ሲሆኑ ክሱን ያቀረቡትም በአሁኖቹተጠሪዎች ላይ ነው፡፡በ14/09/2005 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ የቀረበው ክስ አጭር ይዘትም ተጠሪዎቹ የአመልካች ሕጋዊ ይዞታ የሆነውን እና አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን አስር ሄክታር የሳር መሬት ምንም መብት ሳይኖራቸው በ1993 ዓ.ም.በመያዛቸው አመልካች ይዞታውን ለማስለቀቅ በቀርሳና ማሊማ ወረዳ ፍርድ ቤት የመሰረቱት ክስ ውድቅ የተደረገ ቢሆንም በይግባኝ ለደቡብ ምዕራብሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትአቅርበው ተጠሪዎቹ ይዞታውን እንዲለቁ በመዝገብ ቁጥር 24028 በ08/02/2004 ዓ.ም.ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ተጠሪዎቹ በይዞታው ከ1993 ዓ.ም.ጀምሮ እስከ 2005 ዓ.ም. ድረስ ለአስራ ሁለት ዓመታት የተገለገሉበት መሆኑን፣ከይዞታው በዓመት ግምቱ ብር አምስት ሺህ የሆነ ሳር የሚገኝ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ተጠሪዎቹ የ12 ዓመታትን አላባ ብር 60,000 (ስድሳ ሺህ) እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተጠሪዎቹ በ24/10/2005 ዓ.ም.በሰጡት መልስ አመልካች ቀደም ሲል በመሬት ይዞታው ይገባኛል ጉዳይ ክስ ባቀረቡበት ጊዜ አሁን ክስ ያቀረቡበትንም የአላባ ግምት አካተው መክሰስ ሲችሉ ነጥለው በማስቀረት አሁን አዲስ ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (3) ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት የለውም የሚል መቃወሚያ ካስቀደሙ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም በቀድሞው ክስ ፍርድ ያረፈበት ይዞታ አሁን በክሱ ላይየተገለጸውን መጠን የሚያህል ባለመሆኑ ክሱ የተጋነነ ነው፣በመሬቱ ላይ በግጦሽ ተሰማርተው የቆዩትም የተጠሪዎቹ ብቻ ሳይሆኑ የሌሎችም አርሶ አደሮች ከብቶች ጭምር በመሆናቸው መከሰስ የሚገባን በድርሻችን መጠን ብቻ ነው፣በአላባው 12 ዓመት ሙሉ ተጠቅማችኋል የተባልነውም አላግባብ ነው የሚሉ እና መሰል የክርክር ነጥቦችን በማንሳት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አመልካቹ በይዞታው ጉዳይ አስቀድሞ ክስ ባቀረቡበት ጊዜ የሚጠይቁት አላባ የስንት ዓመት እንደሆነ ማወቅ የሚችሉበት ሁኔታ ስላልነበረ ይዞታው እና ከይዞታው ላይ የሚገኘው አላባ ግምት አብሮ ሊጠየቅ የሚችል አይደለም የሚል ምክንያት ሰጥቶ መቃወሚያውን በማለፍ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በቀድሞው መዝገብ የቀረበውን ማስረጃ ከተመለከተ እና የአላባውን መጠን በባለሙያ ካስገመተ በኃላ አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃውን መርምሮ ተጠሪዎቹ በይዞታው ለ12 ዓመታት መጠቀማቸው በመረጋገጡ በባለሙያ በቀረበው ግምት መሰረት የ12 ዓመት አላባ ብር 49,280 (አርባ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ) ከብር 1,551.50 የዳኝነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክፍያ ጋር ከብር 500 ወጪና ኪሳራ ጋር ለአመልካች እንዲከፍሉ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በፍርድ ያጸናው ይህንኑ ውሳኔ ነው፡፡

ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ የሻረው አመልካች ቀደም ሲል በመሬት ይዞታው ላይ የይገባኛል ክስ ባቀረቡበት ጊዜ አሁን ክስ ያቀረቡበትንም የአላባ ጥቅም አካተው መክሰስ ሲችሉ ነጥለው በማስቀረት አላባውን በተመለከተ አዲስ ክስ ማቅረባቸው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (4) እና 218 ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት ስለሌለው የአላባው ክስ ከቀድሞው የይዞታ ክስ ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት ተብሎ ውድቅ መደረግ ነበረበት የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ከመሬት ይለቀቅልኝ ክስ ጋር ከመሬቱ የሚገኝ አላባን አጣምሮ መጠየቅን በተመለከተ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 217 እና 218 ድንጋጌዎች ለከሳሽ ወገን አማራጭ የሚሰጡ እንጂ የሚያስገድዱ አይደሉም በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ከድንጋጌዎቹ ይዘት አንጻር ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ከሚቀርብ ክስ ጋር ከንብረቱ የሚገኝ አላባን ወይም ጥቅምን ጉዳይ አጣምሮ መክሰስን በተመለከተ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 217 እና 218 ድንጋጌዎች ፈቃጆች እንጂ አስገዳጆች አይደሉም በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. አመልካች ቀደም ሲል በመሬት ይዞታው ላይ የይገባኛል ክስ ባቀረቡበት ጊዜ አሁን ክስ ያቀረቡበትንም የአላባ ጥቅም አካተው መክሰስ ሲችሉ ነጥለው በማስቀረት አላባውን በተመለከተ አዲስ ክስ ማቅረባቸው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (4) እና 218 ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት የለውም በማለት የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቹ ይዞታውን ለማስለቀቅቀደም ሲል በተጠሪዎቹ ላይ ክስ አቅርበው የነበረ እና በክርክሩም ተጠሪዎቹ መሬቱን እንዲለቁየተወሰነ መሆኑ አላከራከረም፡፡የክስ አቀራረብ ስርዓትን በተመለከተ በአንድ በኩል በሌላ አካኃን እንዲቀርብ ካልተፈቀደ በቀር ማናቸውም ከሳሽ ለሚያቀርበው ክስ መሰረት ሊሆን የሚችል ከአንድ በላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሆነ ነገር ካለው ሁሉንም በአንድነት አጣምሮ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ተከሳሾች ላይ የተጣመረ ክስ ለማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 217 (1) ስር የተመለከተ ሲሆን በሌላ በኩል ግን የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ክስ የሚያቀርብ ሰው ከዚህ ዓይነቱ ክስ ጋር አጣምሮ ማቅረብ የሚችለው በድንጋጌው ስር ከፊደል "ሀ" እስከ "ሐ" የተመለከቱትን የክስ ምክንያቶች ብቻ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 218 ተደንግጓል፡፡የእነዚህ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብም የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስመለስ ክስ የሚያቀርብ ሰው ከዚሁ ንብረት የሚገኘውን ጥቅም ለማስከፈል የሚቀርበውን ክስ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለማስመለስ ከሚያቀርበው ክስ ጋር አጣምሮ ማቅረብ የሚችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡በሌላ በኩል ከሳሽ ሊከስበት ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረው ሀብት ምክንያት እንደገና ሌላ ክስ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ እና ከሳሽ ያቀረበው ክስ በአንድ ጉዳይ ላይ የተመሰረተ ሆኖ የሚጠይቀው ዳኝነት ግን ከአንድ በላይ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ሳይፈቀድለት ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ዳኝነት ውስጥ በከፊል ራሱ ቀንሶ ባስቀረው መብት እንደገና ሊከስበት የማይችል ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 216 (3) (4) ስር ተመልክቷል፡፡ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብም የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ክስ የሚያቀርብ ሰው ከንብረቱ የሚገኘውን አላባ ወይም ሌላ ጥቅም ጭምር በክሱ አጣምሮ እንዲከስ በቁጥር 218 (ሀ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ የአስገዳጅነት ባህርይ ያለው እንጂ አመልካች እንደሚሉት ፈቃጅ እና ክሱን ነጣጥሎ የማቅረብ አማራጭን ለከሳሽ ወገን የሚተው አይደለም፡፡በመሆኑም የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ከሚቀርብ ክስ ጋር ከንብረቱ የሚገኝ አላባን ወይም ጥቅምን ጉዳይ አጣምሮ መክሰስን በተመለከተ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 217 እና 218 ድንጋጌዎች ፈቃጆች እንጂ አስገዳጆች አይደሉም በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር የድንጋጌዎቹን ይዘት እና ዓላማ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስቀድመው በቀረቡለት ተመሳሳይ ጉዳዮች በመዝገብ ቁጥር 98639 እና በሌሎችም መዝገቦች የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪዎቹ አጥብቀው የሚከራከሩትአመልካቹከይዞታው የሚገኝ ነው ያሉትን የአላባ ጥቅም ጥያቄ ቀደም ሲል ካቀረቡት ይዞታ የማስለቀቅ ክስ ጋር አጣምረው ማቅረብ የሚችሉ ሆኖ ሳለ በዚህ አግባብ ሳያቀርቡ ቀርተው የመጀመሪያው ጉዳይ ውሳኔ ካገኘ በኃላ አላባውን በተመለከተ አዲስ ክስ ማቅረባቸው ከላይ ከተጠቀሱት የስነ ስርዓት ድንጋጌዎች ውጪ በመሆኑ በክልሉ ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት መሆኑን የሰበር መልሳቸው ይዘት ያመለክታል፡፡ተጠሪዎቹ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተመለከተውን የክስ አቀራረብ ስርዓት መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክርክር በመርህ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል ግን ይህ ክርክራቸው ለክሱ ምክንያት ከሆነው ጉዳይ ልዩ ባህርይ ጋር ተገናዝቦ በአግባቡ ሊመረመር የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

አመልካቹ የመጀመሪያውን ክስ ያቀረቡት ይዞታውን ለማስለቀቅ ነው፡፡በገጠር የእርሻ መሬት የይዞታ መብት ላይ የሚነሳው ክርክር ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች በውይይትና በስምምነት እንዲፈታ ጥረት የሚደረግ ስለመሆኑ እና በስምምነት ሊፈታ ካልቻል በተከራካሪ ወገኖች በተመረጠ ሽምግልና ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ በተደነገገው መሰረት የሚወሰን ስለመሆኑ በፌዴራል መንግስት በወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀጽ 12 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡በሌላ በኩል ከእርሻ መሬት ይዞታ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ክርክሮች በወረዳ ፍርድ ቤት ቀርበው ከመታየታቸው በፊት በስምምነት እና ቀጥሎም በሽምግልና መታየት የሚገባቸው ስለመሆኑ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 16 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 18 ተመልክቷል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት አዋጆች እና ደንብ ድንጋጌዎች መሰረት ለፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በስምምነት እና ቀጥሎም በሽምግልና እንዲታይ የሚደረገው ጉዳይ የእርሻ ይዞታ ክርክር እንጂ ከእርሻ ይዞታው የሚገኘው ጥቅም ወይም አላባ ጭምር አይደለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከሳሽ የሆነ ወገን አላባውን የሚመለከተውን ክስ ይዞታውን ለማስለቀቅ ከሚያቀርበው ክስ ጋር አጣምሮ ሊያቀርብ የሚችልበት አግባብ አይኖርም፡፡ከእርሻ መሬት የሚገኘውን ጥቅም አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ጉዳይ ተጠሪዎቹ ጠቅሰው የሚከራከሩባቸው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 218 (ሀ) እና 216 (3) ድንጋጌዎች መተርጎም የሚገባቸው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን አስመልክቶ ከወጡ ሕጎች ዓላማ እና መንፈስ ጋር ተገናዝበው ነው፡፡ቀደም ሲል በቀረበለት ተመሳሳይ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 108060 በ18/07/2007 ዓ.ም. የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2 (1) መሰረት በዚህ መዝገብ ለቀረበው ጉዳይ አስገዳጅነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም አመልካቹ ቀደም ሲል በሳር መሬት ይዞታው ላይ የይገባኛል ክስ ባቀረቡበት ጊዜ አሁን ክስ ያቀረቡበትንም የአላባ ጥቅም አካተው መክሰስ ሲችሉ ነጥለው በማስቀረት አሁን አዲስ ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (4) እና 218 ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት የለውም በማለት የክልሉ ሰበር ችሎት የደረሰበት መደምደሚያ እና ይንንኑ መደምደሚያ መሰረት አድርጎ የሰጠው ውሳኔ የጉዳዩን ልዩ ባህርይ፣ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች እና ቀደም ሲል በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡በሌላ በኩል የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔውን የሰጠው ተጠሪዎቹ ያቀረቡትን መቃወሚያ መሰረት በማድረግ በመሆኑ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ የመጨረሻ ፍርድ ያላሰረፈበት በመሆኑ በዚህ ረገድ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ወደ ክልሉ ሰበር ችሎት ሊመለስ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 185098 በ22/02/2008 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 (1) ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንዲመለስ ወስነናል፡፡ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ አመልካቾቹ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.121663

ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ሀጋዚዘውደ VC በሌሉበት ችሎት ስላስቻለ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ራኽብ ቸኮለ VC በሌሉበት ችሎት ስላስቻለ የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የትግራይ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 79704 ህዳር 23 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ አመልካች በመቃወም ታህሳስ 21 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ 01 ገጽ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥም የአሁን ተጠሪ ክርክሩ በጀመረበት በትግራይ ብሔራዊ ክልል ኦፍላ ወረዳ ዓዲጉሎ ቀበሌ የመሬት ዳኝነት ከሳሽ በመሆን ለሰበር አቤቱታቸው ምክንያት የሆነውን በዓዲጉሎ ቀበሌ ዓዲጉሎ በተባለው ቦታ 1ኛ በምስራቅ ሻረው በርሀ፤በምዕራብ መንገድ፤በሰሜን ጥዑማይ ካህሳይ በደቡብ ሻረው በርሀ በሚያዋስኑት መካከል የሚገኝ እና 2ኛ በምስራቅ ታደገ ግርበቱ፤በምዕራብ ጣሰው አብርሃ፤በሰሜን መንገድ፤ በደቡብ ታደገ ግርበቱ በሚያዋስኑት መካከል የሚገኝ መሬት ተጠሪ በሽግሽግ የደረሳቸውን የእርሻ ይዞታ መሬታቸውን አመልካች በኃይል ተጠቅመው የያዙባቸው በመሆኑ ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲወሰንላቸው ያቀረቡትን ክስ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካችም በተከሳሽነት ቀርበው አከራካሪው መሬት የሚች አባታቸው ይዞታ መሆኑን ገልፀው በህግ አግባብ በውርስ ያገኙት በመሆኑ መሬቱ በሽግሽግ ለተጠሪ ሊሰጥ አይገባም በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዓዲጉሎ ቀበሌ መሬት ዳኝነትም አመልካች በክርክሩ መሬት ወራሽነት ማስረጃ ያወጡት መሬቱ ወራሽ የሌለው ለመሆኑ ተረጋግጦ ለተጠሪ ከተሸጋሸገ በኋላ ነው በማለት አመልካች መሬቱን ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦፍላት ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርበው የነበሩ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም ይግባኙ መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ሲያከራክር ቆይቶ አከራካሪው መሬት በህጋዊ ሽግሽግ ለተጠሪ የተሰጣቸው ጥር 29 ቀን 2007 ዓ.ም መሆኑንና አመልካች በክርክሩ መሬት የወራሽነት ማስረጃ ያወጡት ደግሞ የካቲት 19 ቀን 2007 ዓ.ም ለመሆኑ ካረጋገጠ በኋላ አመልካች አከራካሪውን የይዞታ መሬት በውርስ አግኝቻለሁ የሚሉት መሬቱ በሽግሽግ ከተሰጠ በኋላ በመሆኑ የመሬት ዳኝነት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት አፅንቶታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የነበሩ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም በማለት ሳይቀበል ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡ መዝገቡ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርመሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪ መስከረም 09 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም ጥቅምት 28 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የጽሑፍ ክርክራቸውን አጠናቀዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ አግባብ ተጠናቋል፡፡ እኛም መዝግቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ለክርክር መነሻ የሆነውን መሬት አስመልክቶ ለአሁን ተጠሪ ይገባል ተብሎ የተወሰነው ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ምላሽ ማግኘት ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ክርክሮች ሲነሱ ምላሽ ለመስጠት የግራቀኙን ክርክር መሠረት በማድረግ ባግባቡ በማጣራት ተገቢውን ማስረጃ መርምሮ መወሰን ይገባል፡፡ የሥር የመሬት ዳኝነትም ሆነ ወረዳ ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረጉት ግራቀኙ ወገኖች ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች በመመልከት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከሥር መዝገቡ መገንዘብ እንደቻልነው አከራካሪው መሬት ለተጠሪ በሽግሽግ ከተሰጠ በኋላ አመልካች የወራሽነት ማስረጃ ያወጡ መሆናቸው፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪ አከራካሪው መሬት በተሰጠበት ወቅትም ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ ጥሪ ተደርጎ እንደነበርና አመልካች በወቅቱ ሳይቀርቡ ቆይተው መሬቱ ለተጠሪ ከተሰጠ በኋላ ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው ማስረጃ ማቅረባቸውን በማረጋገጥ የሥር ፍርድ ቤቶች አከራካሪው መሬት ለአመልካች የማይገባ ስለመሆኑ ወስነዋል፡፡

በትግራይ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 14(8) እንዲሁም ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 22(1)(ሀ) ሥር እንደተመለከተው ወራሽ የሌለው መሬት በቀበሌው የገጠር መሬት አስተዳደር ኮሚቴ መሬት ለሌላቸው ይሸጋሸጋል በማለት ደንግጓል፡፡ በዚሁ ደንብ አንቀጽ 21(8) ሥር እንደተመለከተው ከሽግሽግ በኋላ የሚቀርብ አቤቱታ ከመሬት ዳኝነትና ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ ተቀባይነት እንደሌለው ደንግጓል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ የሚያስረዳው አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሞተ እንደሆነ መሬቱ ያለወራሽ ስለመቅረቱ ተገቢ ማጣራት በማድረግ እውነትም ወራሽ የሌለው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ መሬት ለሌላቸው የቀበሌ ነዋሪዎች በሽግሽግ ሊሰጥ የሚገባ መሆኑን፤ መሬቱን ከማሸጋሸጉ በፊት የቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደር ኮሚቴው መሬቱ ወራሽ ያለው እንደሆነ ተገቢ ማጣራት ማድረግ ያለበት ሆኖ በዚህ ሂደት አልፎ የተሸጋሸገ መሬት ይመለስልኝ የሚል አቤቱታ በመርህ ደረጃ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በልዩ ሁኔታ በመሬት ዳኝነት አካል ወይም በፍርድ ቤት ከተወሰነ ተቀባይነት ሊኖረው እንደሚችል የሚያስረዳ ነው፡፡ ስለሆነም አንዱ ወራሽ የለውም ተብሎ በሽግሽግ የተሰጠ መሬት በመሬት ዳኝነት ውሳኔ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ አርፎበት ወራሽ የሆነ ሰው ከመጣ አቤቱታ ቀርቦበት በሽግሽግ ያገኘው ሰው ሊለቅ እንደሚችል የትግራይ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 239/2006ን ለማስፈፀም ከወጣው ደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 22(1)(ሀ) ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ አመልካች አሁን በያዙት የወራሽነት ማስረጃ መነሻነት በመሬት ዳኝነት ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ በአከራካሪው መሬት ላይ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉ ከሆነ መሬቱ አንዱ ለተጠሪ በሽግሽግ ተሰጥቷል ተብሎ መብታቸውን መንፈግ ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ ዓላማና መንፈስም አንፃር ሲታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች በክርክሩ መሬት የወራሽነት ማስረጃ ማውጣታቸውን ግንዛቤ ከወሰዱ በኋላ የወራሽነት ማስረጃ በፍርድ ቤት የተሰጣቸው ቢሆንም መሬቱ ከተሸጋሸገ በኋላ የቀረበ የወራሽነት ማስረጃ ውሳኔ ተቀባይነት የለውም ማለታቸው የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የያዙት የወራሽነት ማስረጃ ለማስረጃነት የሚያገለግል በመሆኑ ተጠሪ ጋር ክርክር ሊደረግበት የሚገባውና ሊስተባበልም የሚችል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በጉዳዩ ላይ ተጠሪ የሚያቀርቡት ክርክርና ማስረጃ አመልካች ካቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ ጋር ተገናዝቦ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በጉዳዩ ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኝነት የሰጡት የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ ተመልክተው ያስተናገዱት ሳይሆን አመልካች የወራሽነት ማስረጃ ያቀረቡት መሬቱ ከተሸጋሸገ በኋላ ነው በሚል ምክንያት ብቻ አመልካች አከራካሪውን መሬት መውረስ የሚገባቸው ወይም የማይገባቸው ስለመሆኑ ሳያጣሩ መሬቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ መወሰናቸውን ከመዝገቡ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በዓዲጉሎ ቀበሌ የመሬት ዳኝነት አካል ተወስኖ በኦፍላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12291/07 መስከረም 06 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንዲሁም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 79704 ህዳር 23 ቀን 2008 ዓ.ም ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በመሆኑም አመልካች የያዙት የወራሽነት ማስረጃ በክርክሩ መሬት ላይ የሚሰጣቸው መብት ምን እንደሆነ ተጠሪው አመልካች ባቀረቡት የውርስ ማስረጃ ላይ ያላቸው ክርክርና ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድርግ ከግራቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንፃር ጉዳዩን ካጣራ በኋላ አከራካሪው መሬት ለአመልካች በውርስ ይገባቸዋል ወይስ አይገባቸውም? በሚለው ጭብጥ ላይ ተገቢውን እንዲወስን የዚህ ችሎት ውሳኔ ቅጅ ለዓዲጉሎ ቀበሌ መሬት ዳኝነት ይተላለፍ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣ ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.115399

ታሕሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አለማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሠለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-1.ተስፋዬ ተሾመ } አልቀረቡም

2. ኤፍሬም መኮንን }

ተጠሪዎች፡- 1.ሞላየ ወልዴ ..... አልቀረበም

2.ይመር ወልዴ .....ቀረበ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍረድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የእርሻ መሬትን በሚመለከት ሁከት ይወገድልኝ በማለት የቀረበን ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ወሎ ጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪዎች ክስ ይዘት በአጭሩ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰውን እና ከሚች አቶ አሠፋ እውነቱ በኑዛዜ ያገኙትን የእርሻ መሬት አመልካቾች አታርሱም በማለት ሁከት የፈጠሩባቸው መሆኑን በመግለጽ አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካቾች መልስ ለመስጠት በተያዘው ቀነቀጠሮ ባለመቅረባቸው ጉዳያቸው በሌሉበት እንዲታይ በማለት ትዕዛዝ ከሰጠ እና ምስክር ለመስማት ቀጠሮ ከያዘ በኋላ አመልካቾችን በመወከል የክልሉ ዐቃቤሕግ የቀረበ በመሆኑ የክልሉ ዐቃቤሕግ አመልካቾችን በመወከል ያቀረበውን መልስ በመቀበል የግራቀኙን ምስክሮች ሰምቷል፡፡ ስለመሬቱም ጉዳዩ ከሚመለከተው የወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በትዕዛዝ እንዲጣራ ካደረገ በኋላ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪዎች ምስክሮች ተጠሪዎች መሬቱ ከአቶ አሠፋ እውነቱ በኑዛዜ የተሠጣቸው መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል፤የአመልካች ምስክሮች አመልካቾች ሁከት ያልፈጠሩ መሆኑን፤በጽ/ቤቱ የኑዛዜ ሰነድ የሌለ መሆኑን፤በጊዜው የነበረው ኮሚቴ መሬቱ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ የወሰነ መሆኑን፤ተጠሪዎች ይዞታችን ነው የሚሉት መሬት በሕግ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አታርሱም የተባሉ መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል፤የጉባላፍቶ ወረዳ አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር በጻፈው ደብዳቤ ሟች አቶ አሠፋ እውነቱ አድርገውታል የተባለው የኑዛዜ ሰነድ ከወረዳው አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ያልገባ መሆኑን አረጋግጧል፤በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አካባቢ ጥበቃ መሬት አሥተዳደር እና አጠቃቀም ቢሮ በወረዳው ጽ/ቤት አስቀድሞ ሳይመዘገብ የሚቀርብ የይዞታ መብት የኑዛዜ ውርስ ይተላለፍልኝ ጥያቄ ጉዳዩ ተቀባይነት የለውም በማለት ወዲያውኑ መመለስ አለበት በሚለው መሠረት በጽ/ቤታችን ያልተገኘን የኑዛዜ ሰነድ አልተቀበልነውም በማለት ማብራሪያ ልኳል፤ተጠሪዎች የያዙት መሬት በመሬት ዴስክ ያልተመዘገበ እና የኑዛዜ ሰነዱም በወረዳው ጽ/ቤት ያልተመዘገበ መሆኑ እና ወደ መሬት ባንክ የገባ መሆኑን በጉዳዩ ባለቤት ተረጋግጧል፤አንድ ተከራካሪ ወገን ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ ማቅረብ የሚችለው ይዞታውን በእውነት ይዞ የሚያገለበት ሆኖ ሲገኝ ነው፤ተጠቃሹ ይዞታ በአቶ አሠፋ እውነቱ ሥም የሚገኝ በመሆኑ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪዎች የኑዛዜውን ሰነድ ለቀበሌው መሬት ዴስክ አቅርበው ያለምንም ምክንያት አይገባችሁም የተባሉ መሆኑን፤መሬቱ የተጠሪዎች አጎት የአቶ አሠፋ እውነቱ መሆኑን እና ኑዛዜው በቀበሌው የመሬት ዴስክ ባለሙያ ፊት የተደረገ እና በአራት ምስክሮች ተፈርሞ እና ተነቦ ተናዛዡ የጣት አሻራውን ያሣረፈበት መሆኑን ተረጋግጧል፤በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 ኑዛዜው በወረዳው መሬት ዴስክ ሳይጸድቅ ቢቀር ውጤቱ ምን እንደሚሆን የሚገልጽ ድንጋጌ የለም፤በልዩ ሕጉ ላይ ስለኑዛዜው አለመመዝገብ ውጤት ሳይገለጽ ከቀረ ጉዳዩ ሊዳኝ የሚገባው በጠቅላላ የኑዛዜ ሕጉ መሠረት ነው፤ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 881 ሥር የተመለከቱትን ሥርዓቶች ያሟላ በመሆኑ እና ተጠሪዎች መሬቱ በዚህ ኑዛዜ መሠረት ተላልፎላቸው የወረሱ በመሆኑ ኑዛዜው በወረዳው የመሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ አልጸደቀም በማለት ተጠሪዎች ሕጋዊ ይዞታ ስለሌላቸው ሁከት የለም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሠጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ በማለት በአብላጫ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታቸው ተሰርሿል፡፡በመቀጠል አመልካቾች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-ተጠሪዎች መሬቱን መያዝ የሚገባቸው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 23/4 እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 24/4 መሠረት ኑዛዜውን በወረዳው ጽ/ቤት አስመዝግበው መሆን አለበት፤የመሬት አስተዳደርን እና አጠቃቀምን በሚመለከት በክልሉ የወጣው መመሪያም በወረዳው ጽ/ቤት ያልተመዘገበ ኑዛዜ የማይጸና መሆኑን ይደነግጋል፤ተጠሪዎች የሚች ኑዛዜ ወራሽነታቸው ያልተመዘገበ እና የማይጸና በመሆኑ መሬቱ በሞተከዳ ወደ መሬት ባንክ የገባ እና አመልካቾችም የመሬት አስተዳደር ኮሚቴ በመሆናችን ተጠሪዎች ወደ መሬት ባንክ የገባውን መሬት እንዳያርሱ መከልከላችን ሁከት ፈጥረዋል የሚያሰኝ ባለመሆኑ አመልካቾች ሁከት ፈጥረዋል በማለት ሁከቱ ሊወገድ ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ሰለተገኘ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ኑዛዜው በወረዳው አስተዳደር ቀርቦ ሳይመዘገብ ቢቀር ውጤቱ ምን እንደሆነ የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅም ሆነ አዋጁን ለማስፈጸም የወጣው ደንብ የማይደነግግ በመሆኑ ጉዳዩ ሊዳኝ የሚገባው በመደበኛው ሕግ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ መሆን አለመሆኑ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርን እና አጠቃቀምን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 23/4 ድንጋጌ ከመሬት ጋር የተያያዘ ማናቸውም መብትና ግዴታን የሚመለከት ተግባር መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ባለው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ በስተቀር በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብ እንደማይችል ይደነግጋል፤ይህንኑ አዋጅ ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 24/4 ድንጋጌ በመሬት መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ መሬቱ ኪራይን፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውርስን ወይም ስጦታን የተመለከተ ግዴታ ያለበት እንደሆነ ይኸው መመዝገብ ያለበት መሆኑ፤ ግዴታው በሚሻሻልበት ወይም በሚያበቃበት ጊዜም መረጃው በዚሁ መሠረት መስተካከል የሚኖርበት መሆኑ ይደነግጋል፤የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 ን እና ደንብ ቁጥር 51/99 ን ለማስፈጸም የወጣው መመሪያ አንቀጽ 13 ንዑስ ቁጥር 1 እና 2 ድንጋጌ ማንኛውም በህግ በኑዛዜ ይዞታውን የማስተላለፍ ስልጣን የተሰጠው አካል ይዞታውን በክልሉ ውስጥ በህግ የገጠር መሬት የማግኘት መብት ለተሰጠው ሰው ከሞተ በኋላ ይዞታው እንዲተላለፍለት በጽሁፍ መናዘዝ የሚችል መሆኑን፤ኑዛዜዉ በፍ/ቤት እንዲጸድቅ ከተደረገ በኋላ በወረዳው አካ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ጽ/ቤት ቅጂውን አስመዝግቦ ተናዛዡ ከሞተ በኋላ የይዞታ ዝውውሩ ተጨማሪ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የሚከናወን መሆኑን ይደነግጋል፡፡ከነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው በኑዛዜ መሬት ተላልፍልኛል የሚል አካል ኑዛዜዉን በፍ/ቤት እንዲጸድቅ ካደረገ በኋላ በወረዳው አካ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ጽ/ቤት ቅጂውን ሊያስመዘግብ የሚገባ መሆኑን እና በዚህ አግባብ ያልተመዘገበ ኑዛዜ ውጤት የሌለው መሆኑን ነው፡፡የገጠር መሬትን አስመልክቶ የወጡት ልዩ ሕጎች በፍ/ቤት ያልጸደቀ እና በወረዳው መሬት አስተዳደር እና አጠባበቅ ጽ/ቤት ቀርቦ ያልተመዘገበ ሰነድ ውጤት የሌለው መሆኑን የሚያስገነዝቡ ሆነው ሳለ የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የገጠር መሬትን አስመልክቶ በክልሉ የወጡት ሕጎች ኑዛዜው በወረዳው አስተዳደር መሬት ጽ/ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ ውጤቱ ምን እንደሚሆን የማይደነግጉ በመሆኑ ጉዳዩ ሊዳኝ የሚገባው በጠቅላላ ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው በማለት የሚች ኑዛዜ ፎርማሊቲውን ያሟላ በመሆኑ አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት ሊወገድ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ የገጠር መሬትን አስመልክቶ በክልሉ የወጡትን የሕግ ማዕቀፎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 13027 ታሕሳስ 24 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ፤በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0102797 የካቲት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በትዕዛዝ፤በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-10933 ግንቦት 26 ቀን 2007 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ወሎ ጉባላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 0104522 ጥቅምት 25 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 125186

ሰኔ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አዛል አይናለም -ተወካይ ጌትነት ተረፈ

ተጠሪ፡- 1ኛ፣ አቶ ምህረት በላይ -ቀረቡ

2ኛ. የቡሬ ዘ/ወ/አከ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ፅ/ቤት -አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መንግስት የቡሬ ወረዳ ፍ/ቤት ነው ፡፡ በዚያ ደረጃ አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ ፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አቤቱታ፡- ከሳሽ የፈፀምኩት የስጦታ ውል መንፈስ ልልነት እና አቅመደካማ በመሆኔ የፈፀምኩት ስለሆነ የስጦታ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ በመሆን ባቀረበው መልስ ከሳሽ ያቀረበው ስጦታ ይፍረስልኝ ጥያቄ ይርጋ ጊዜው ያለፈው ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት የተከራከረ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ከሳሽ የፈፀመው ስጦታ ውል በህግ መሰረት የተደረገ ስለሆነ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም በስር ተከሳሾች የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወምያ መሰረት በማድረግ ስጦታው ተደረገ ከተባለው ጊዜ ጀምሮ በሁለት አመት ውስጥ የይረሰዝልኝ ጥያቄ ስላልቀረበበት ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2441 መሰረት በይርጋ የታገደ ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ እንዲሁም የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር አቅርቦም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ተሰርዞበታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በተጠሪዎች የቀረበው መቃወምያ የፍትሃብሄር ህጉን በመጥቀስ ሲሆን ይህ ክርክር ግን የሚዳኘው በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 ፣እና ደንብና መመሪያ እንጂ በፍትሃብሄር ህጉ መሰረት ባለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው የዕሁፍ ክርክራቸው ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጭብጥ የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱት የፈፀምኩት የስጦታ ውል መንፈስ ልልነት እና አቅመ ደካማ በመሆኔ የፈፀምኩት ስለሆነ ስጦታው ሊሰረዝ ይገባል በማለት መሆኑን፣ ተጠሪ ደግሞ ጉዳዩ በሁለት አመት ይርጋ የሚዘጋ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው የበታች ፍርድ ቤቶችም የተጠሪን የመቃወሚያ ነጥብ በመያዝ ክሱን በይርጋ ውድቅ ያደረጉ መሆኑን ነው፡፡
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 16/3 እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈፀም ባወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/2 እንደተደነገገው የአሁኑ ተጠሪ ዋጋ ያለው የስጦታ ማስረጃ አቅርበናል እንኳ ቢባል ስጦታው በተደረገበት የእርሻ መሬት ላይ በቤተሰብነት የተመዘገበ አባልን ያገለለ መሆኑ ከታወቀ ይኸው ሰነድ በህግ ተቀባይነት የማይኖረው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/2/ በተመለከተው መስፈርት መሰረት መሬት ያገኙ በሞተበት ወቅት የእራሱ የሆነ ቤተሰብ እያለው ባደረገው ስጦታ ቤተሰቡን የሚነቅል ሆኖ በመገኘቱ የተነሣ ስጦታ በህግ ፊት ተቀባይነት የሌለው ሆኖ በተገኘ ጊዜ የእርሻ መሬት ለማን እና እንዴት በውርሱ ሊተላለፍ እንደሚገባ በዚሁ ደንብ አንቀጽ 11/7/ ስር ከፊደል /ሀ/ እስከ /መ/ የተቀመጠውን ቅደምተከተል በመጠበቅ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2441 ድንጋጌ መሰረት በሁለት አመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት ስጦታን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የሚገዛው ልዩ በሆኑት የገጠር መሬት አስተዳደር ሕጎች ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች በፌዴራሉ መንግስት የወጣው አዋጅ ቁጥር 456/97፣በክልሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክር ቤት የወጣው አዋጅ ቁጥር 133/98 እና ደንብ ቁጥር 51/99 እንዲሁም ይህንኑ ተከትሎ በክልሉ የወጣው መመሪያ ናቸው፡፡ እነዚህ ሕጎች አንድ የገጠር እርሻ መሬት የሚተላለፍባቸውን መንገዶች የሚያሳዩ ሲሆን ከእነዚህ መንገዶች መካከል በውርስና በስጦታ ይዞታው የሚተላለፍበትን አግባብ የሚመለከቱ ይገኙበታል፡፡ የገጠር እርሻ መሬት በውርስና በስጦታ ሲተላለፍም በሕጎቹ የተቀመጡ ክልከላዎችና እነዚህ ክልከላዎች ሳይከበሩ የሚደረግ ኑዛዜ መኖሩ ሲረጋገጥ የይዞታ መብቱ የሚተላለፍላቸው ወገኖች ቅደም ተከተል መኖሩን የደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11(2) እና (7) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡

ስለሆነም በሕጉ ክልከላ የተደረገባቸው የይዞታ ማስተላለፍ ሁኔታዎች ያሉ ሲሆን ሕጉን ያልጠበቀ የገጠር መሬት ይዞታ በኑዛዜ ወይም በስጦታ ተላልፏል የሚለው ወገን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2441 አግባብ በሁለት አመት መጠየቅ ነበረበት ሊባል የሚችል ያለመሆኑን ከልዩ ሕጎቹ ድንጋጌዎች ይዘት እና መሰረታዊ አላማ የምንረዳው ሁኖ አግኝተናል፡፡ የሁለት አመት ይርጋ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው ከተባለ ደግሞ ከአመልካቾች እድሜና ሌሎች ሕጋዊ ምክንያቶች ጋር ተያይዞ በመታየት እልባት የሚያገኘው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በእድሜ የገፉ መሆናቸውን የክርክሩ ሂደት ስለሚያሳይ እና ይህም ጉዳዩ በሌላ የይርጋ ዘመን የሚቋረጥ መሆን ያለመሆኑ ላይ ክርክር ሊያስነሳ የማይገባ ሁኖ ስለአገኘው አግባብነት ያለውን የይርጋ ዘመን ከወዲሁ መለየቱ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ክሱ በይርጋ የሚታገድ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የክስ ይዘት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2441 ድንጋጌ ይዘት፣መንፈስና ዓላማ ጋር በአግባቡ ሳያገናዝቡናያለ ቦታው ጠቅሰው የአመልካች ክስ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ብይን ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 23260 ህዳር 20 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-65729 ህዳር 27 ቀን 2008 ዓ/ም እንዲሁም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 53060 ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ አይደለም ብለናል፡፡
3. የቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 23260 በሆነው ቀጥሎና በስነ ስርዓቱ ሕጉ መሰረት በመምራት ተገቢውን ይወሰን በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.114670

ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- 1ኛ አቶ ባንኩ ኢሩስ

2ኛ አቶ ኤሊያስ ታኒ

ተጠሪ፡- አቶሳምሶን ገ/ዩሀንስ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬትን የሚመለከት ሆኖ የግራ ቀኙ ክርክር የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/በበንች ማጂ ዞን የሾኮ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኖቹ አመልካቾች ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የአሁኖቹ አመልካቾች ከሳሽ በመሆን በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ይዘት ባጭሩ፡- ከተከሳሽ ጋር ግንቦት 19 ቀን 2004 ዓ/ም በተባ፩ ውል በጅምርሶ ቀበሌ ልዩ ስሙ ምንካታ ተብሎ በሚጠራው መንደር በምስራቅ የአቶ አዲሱ ገመዳ የእርሻ ማሳ፣በምእራብ የጋችብ ወንዝ፣በስሜን የአቶ ሳሙኤል የቡና ማሳ፣በደቡብ የአቶ አዲሱ ገመዳ ይዞታ መሬት የሚያዋስነው የራሱ የሆነ ለመልማት የሚችል ይዞታ መሬት ተከሳሽ ለለማው የቡና ይዞታ 150,000 (አንድ መቶ አምሳ ሺህ ብር) ተገምቶ ገንዘቡን ለተከሳሽ ከፍለን ያልለማው ቡና ውሉ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ የእኛ እና የተከሳሽ የጋራ የቡና ልማት እንዲሆን ተስማምተናል ። ለተከሳሽ ከከፈልነው ገንዘብ በተጨማሪ የለማውን ቡና ለመንከባከብ አዲስቡናለማስተከል

ብር 50,000(አምሳሺህብር) ወጪ በማድረግ አልምተናል፡፡ለጀምሩስ ቀበሌ ፅ/ቤትበቡናው ይዞታ ውስጥ ከሳሾች እንዳይገቡ በማለት ተከሳሽ ህዳር 21 ቀን 2006 ዓ/ም ፅፎያስገባ በመሆኑ እኛም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ በይዞታው መሄድ አቁመናል፡፡ተከሳሽ የ2006 ዓ/ም የቡና አላባ ለብቻው የተጠቀመ ስለሆነ ድርሻችን 112,666ብር ተከሳሽ እንዲከፍለንና በውሉ መሰረትቡናው የጋራ ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአሁኑ ተጠሪ የስር ተከሳሽ በመሆን ባቀረበው መልስ ከከሳሾች ጋር በጋራ ለመስራት ውል ያደረግን ቢሆንም ይህንን መሰረት አድርገው ይዞታው የጋራ ነው ተብሎ ይወሰንልን ብለው ያቀረቡትጥያቄ ውሉ ህግ የሚጠይቀውን መስፈርት ያላሟላ ስለሆነ የህግ መሰረት የለውም ፡፡ የ2006 ዓ/ም አላባ እንድከፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄም በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመርያ ደረጃ የተመለከተው የሸኮ ወረዳ ፍርድ ቤት ክሱንና የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ አጠቃላይ ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ተከሳሽ 95,962 (ዘጠና አምስት ሺህ ዘጠን መቶ ስልሳ ሁለት ብር) ይክፈል፤ክርክር ያስነሳውበጀምሩስ ቀበሌ ልዩስሙ ሞንኪታየሚባለው ቦታ ያለው የቡና ይዞታየግራቀኙ የጋራ ይዞታ ሆኖ በጋራ እንዲጠቀሙ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበውም የቀረበው ይግባኝ ሰርዞታል፡፡የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት አቤቱታው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱ የቀረበው አቤቱታና የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ አጠቃላይ ክርክሩን ከመረመረ በኋላአመልካቾች በይዞታው ላይ አወጣነው የሚሉትን ገንዘብ አግባብ በሆነ መንገድ ከመጠየቅ ውጪ ህገወጥና ፈራሽ በሆነ ውል መሠረት ያቀረቡት ክስ መነሻነት የስር ፍርድ ቤቶች የቡና ማሳው የጋራእንዲሆን የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮለሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸው ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ፅሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የመጀመሪያው ጭብጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀፅ 12(4) መሰረት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሳይታይ በቀጥታ ተቀብሎ ማየቱ ስነ-ስርአታዊ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ሲሆን ጉዳዩ የመሬት መጠቀም መብት ይገባኛል ጥያቄ ጋር የተያያዘ በመሆኑ መታየት ያለበት በመሬት አዋጁ መሰረት ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የደቡብ ብሄር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 የክርክሮች አወሳሰን አስመልክቶ በአዋጁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀፅ 12(1) እንደተደነገገው የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በተመለከተ ክርክር ሲነሳ አቤቱታ ለቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ቀርቦ በተከራካሪ ወገኖች በፍቃደኝነት በተመረጡ ሽማግሌዎች አማካኝነት ታይቶ በእርቅና በድርድር እንዲፈታይደረጋል፡፡በሽማግሌዎቹ እርቅና ድርድር ያልተስማማወገን ለወረዳው መደበኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳለው በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 12(2) ተመልክቷል፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ የወረዳው መደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተስማማ ወገን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል ፣በዚህ ውሳኔ ያልተስማማ ወገን በተጨማሪ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳለው በአዋጁ አንቀፅ 12(4) ተደንግጎ እናገኛለን ። ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ክርክሩ ይዘት ለመረዳት የተቻለውየሸኮ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት ተጠሪ ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናቱ ተጠሪ በቀጥታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ መሆናቸው መዝገቡ ያመለክታል፡፡

በመሠረቱ በገጠር የእርሻ መሬት የመጠቀም መብት፣መብቱን በዉርስ የማስተላለፍ እና መሰል መብቶች ጥበቃ ያገኙት በፌደራል መንግስት በወጣዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 ሲሆን ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ደግሞ ዝርዝር ሕጎች የሚወጡት በእያንዳንዱ ክልል ምክር ቤት ስለመሆኑ በአዋጅ አንቀፅ 17 ስር በግልፅ ተመልክቷል ። እንዲሁም በገጠር የእርሻ መሬት የይዞታ መብት ላይ የሚነሳው ክርክር ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች በውይይትና በስምምነት እንዲፈታ ጥረት የሚደረግ ስለመሆኑ እና በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በተከራከሪ ወገኖች በተመረጡ ሽምግልና ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ በተደነገገው መሰረት የሚወሰን ስለመሆኑ በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 12 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀፅ 17 ድንጋጌ መሰረትም የደቡብብሔሮች ብሔረሰቦችክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 እና አዋጁን ለማስፈፀም ደንብ አውጥቶ በስራ ላይ ያዋለሲሆን በዚህ አዋጅ እና ደንብ በተዘረጋዉ ስርዓት መሰረት በስምምነት እና በሽምግልና እልባት ያላገኙ ጉዳዩችን በመጀመርያ ደረጃ አይቶ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን አስመልክቶ የክርክሮች አወሳሰን በሚል ርእስ ስር በአዋጁ አንቀፅ 12ስር ተመልክቷል፡፡ ከገጠር የእርሻ መሬት ጋር ተያይዘዉ የሚነሱ አለመግባባቶች እና ክርክሮች በስምምነት እና በሽምግልና መፈታት ካልቻሉ ክልሎች በሚያወጡት ሕግ መሰረት ውሳኔ እንዳያገኙ እንደሚደረግ የሚደነግገዉ አዋጅቁጥር 456/1997 እና የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 በክልሉ ምክር ቤት የወጣው የተሻሻለውየክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋምያ አዋጅ ቁጥር 43/94 ከወጣ በኃላ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 43/94 የወረዳ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመሳሳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ የሰጡ እንደሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑ ከታመነበት አቤቱታውበቀጥታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርብ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡

ሕግ አውጪው የአዋጅ ቁጥር 43/94 ምእራፍ ሶስት "የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን" በሚለው ርእስ ስር የተመለከተው ድንጋጌ መኖሩን እያወቀ ከገጠር የእርሻ መሬት ጋር ተያይዘው የሚነሱት አለመግባባቶች እና ክርክሮች በስምምነት እና በሽምግልና መፈታት ካልቻሉ በሚያወጡት ሕግ መሰረት ውሳኔ እንዲያገኙ በአዋጅ ቁጥር 456/1997 መደንገጉና በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀፅ 12(4) የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወገን ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጨማሪ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል መደንገጉ ከእርሻ መሬት ጋር ተያይዘው የሚነሱት ክርክሮች ካላቸው ልዩ ባህርይ አንጻር ከሌሎች ጉዳዬች በተለየ ሁኔታ ተጨማሪ የይግባኝ መብት መስጠቱ እና ከገጠር መሬት የይዞታ ክርክር አንፃር ቁጥር 456/1997 ልዩ ሕግ መሆኑን ከአጠቃላይ የሕግ አወጣጥ ስርዓት መርህ መገንዘብ ይቻላል ፡፡ይህም ከገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ጋር ተያይዞ ለሚነሳው ክርክር በመሬት አዋጁ መሰረት ሊመራ የሚገባው ነው ብለናል፡፡

ከላይ በዝርዝር በተመለከተው መሰረት አቤቱታው የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀፅ 12(5) መሰረት በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ይኖራል ተብሎ ከታሰበ የማየት ስልጣን እንዳለው ተመልክቷል፡፡በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት መሰረታዊ የክርክር ነጥብ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ የሰበር አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስችል ህጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ብቁ ሁኖ ሊታይ የሚችለው ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ስለመሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ ነው፡፡ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) ፣ በክልሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 75 (2(ሐ)) እና የክልሉ ፍርድ ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 43/1994 አንቀጽ 5(3) ድንጋጌ በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ብቁ የሚሆነው አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ (Final court decision) ያገኘ መሆን ያለመሆኑን በቅድሚያ መረጋገጥ ያለበት መሰረታዊ ነጥብ ስለመሆኑ የድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝቡናል፡፡ በመሆኑም ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ፍርድ ባላገኙ ጉዳዮች ውሳኔ የመስጠት ስልጣንና ኃላፊነት ያልተሰጠው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ አገላለጽ ለሰበር ብቁ ያልሆኑ የመጨረሻ ፍርድ ያላገኙ ጉዳዮች በሰበር ሰሚ ችሎት ሊስተናገዱ የሚችሉበት ስርዓት አይኖርም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀፅ 12(4) የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወገን ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጨማሪ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል እንዲሁም በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 12(5) እንደተደነገገው በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ይኖራል ተብሎ ከታሰበ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የማየት ስልጣን እንዳለው በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያልደረሰና የመጨረሻ ፍርድ ያላገኘ ስለሆነ ፣ ሰበር ሰሚ ችለቱ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት አለመሆኑን ተገንዝቦ ስልጣንን በተመለከተ ከተከራከሪ ወገኖች የቀረበለት ተቃውሞ ባይኖርም በፍትሃብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 9(1)እና 231(1) (ለ) እንደተመለከተው በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርቦ ሊስተናገድ በሚችል ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ለዚህ ችሎት ብቁ አይደለም ስልጣን የለኝም በማለት መመለስ ና ማረም ሲገባው ተቀብሎ በማስተናገዱም ሆነ ውሳኔ መስጠቱየህግ ድጋፍ የለውም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የቀረበው ጉዳይ የገጠር መሬት አዋጅ ልዩ ከመሆኑና ገጠር መሬትን መሰረት በማድረግ ለሚነሱ ክርክሮች አወሳሰን፣ በአዋጁ አንቀፅ 12 የተደነገገውን ድንጋጌመሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም አቤቱታ የቀረበበት ውሰኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02504 ሚያዝያ 13 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት በአብላጫ ድምፅ ተሽሯል፡፡

2. በአመልካች ላይ ክስ የቀረበው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 "ን" መሰረት በማድረግ በመሆኑ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቀርቡ ክርክሮች የሚመሩትም በዚሁ አዋጅ በመሆኑ፤በአዋጁ አንቀፅ 12(4) መሰረት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሳይታይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀብሎ ማስተናገዱ አግባብ አይደለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ጉዳዩን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከማቅረቡ በፊት በሕጉ አግባብለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚችሎት የማቅረብ መብቱን ይህ ውሳኔ ቀሪ አላደረገውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ አራት ዳኞች ፊርማ አለበት።

<u>የልዩነት ሐሳብ</u>

ስሜ በተ.ቁ 5 ላይ የተሰየመው ዳኛ አብላጫው ድምጽ ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊስተናገድ በሚችል ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ሆኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ ማስተናገዱ ተገቢ አይደለም በማለት በደረሰበት መደምደሚያ ስላልተስማማሁ በሐሳብ ተለይቻለሁ።

አብላጫው ድምጽ ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት ክርክርን የሚመለከት በመሆኑ ለጉዳዩ አወሳሰን ተፈጻሚነት ያለው ሕግ የክልሉ የገጠር መሬት አሥተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/99 ነው።በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 (4) መሠረት የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል በማለት የሚደነግግ በመሆኑ እና ተጠሪ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያላቀረቡ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የተመለከተው የመጨረሻ ውሳኔ ባላገኘበት ሁኔታ ነው በማለት ጉዳዩን ተቀብሎ ማስተናገዱ ተገቢ አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል።

የክልሉን ፍ/ቤቶች እንደገና ለማቋቋም ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ ቁጥር 43/94 አንቀጽ 5/2 የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ እንዲሁም የከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የወረዳ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ የሰጠበትን ጉዳይ የማየት ሥልጣን አለው በማለት ይደነግጋል፤የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 5/3 የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበትን እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት ያለበትን ክልላዊ ጉዳይ የማየት ሥልጣን እንዳለው ይደነግጋል።

የክልሉ የገጠር መሬት አሥተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀጽ 12/4 ከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል በማለት የሚደነግግ ቢሆንም ይህ አዋጅ የክልሉን የገጠር መሬት አሥተዳደር እና አጠቃቀም ለመወሰን የወጣ አዋጅ እንጂ የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥርዓትን ለይቶ ለመወሰን የወጣ ባለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት እና ዓላማ የክልሉን ፍ/ቤቶች ለማቋቋም ተሻሽሎ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 43/94 ድንጋጌዎች እና ከይግባኝ መብት ተፈጻሚነት ጋር ተጣጥሞ ሊተረጎም የሚገባው ነው።በመሠረቱ ይግባኝ ማቅረብ ሕገመንግሥታዊ ዋስትና ያለው የተከራካሪዎች መሠረታዊ መብት ነው።ሕግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀጽ 12/4 ላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያስቀመጠው ድንጋጌም ይህን መሠረታዊ መብት ለማስከበር እንጂ ለተከራካሪ ወገኖች ተደጋጋሚ የሆነ የይግባኝ መብት ለመስጠት እንዳልሆነ ከአዋጁ አጠቃላይ ይዘት እና ዓላማ መገንዘብ ይቻላል፡፡ከይግባኝ መብት ተፈጻሚነት አኳያ በአዋጁ አንቀጽ 12/4 ንኡስ 4 የተቀመጠው የይግባኝ መብት ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ለተሻሻለበት ወይም ለተሻረበት ወገን እንጂ የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ለጸናበት ወገን አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የወረዳው ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ ያጸናው በመሆኑ እና የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ታይቶ ባልተሻረበት ወይም ባልተሻሻለበት ሁኔታ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ድጋሚ ይግባኝ የሚያቀርቡበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በመሆኑም ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 75/2(ሐ) እና በአዋጅ ቁጥር 43/94 አንቀጽ 5/3 መሠረት ጉዳዩን የመመልከት ሥልጣን አለው፡፡

በአጠቃላይ ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ ጉዳዩን አይቶ የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ያጸናው በመሆኑ ውሳኔው የመጨረሻ ነው፡፡በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 75/2/ሐ እና በተሻሻለው የክልሉ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 43/94 አንቀጽ 5/3 መሠረት ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ ተገቢ ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት::

ሰ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.122740

ቀን ሚያዚያ 30/2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-አቶ ጤና ጋርደዉ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መደቅሴ ገርቢ - ወኪል ያደታ ጋረደ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የእርሻ መሬት ጉዳይ ሆኖ የተጀመረው በጉደያ ቢላ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁንተጠሪ ከሳሽ የነበሩ ሲሆን አቶ ታከለ ቁያሳ ተከሳሽ እንዲሁም የአሁን የሰበር አመልካች ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ተጠሪ አቅርበዉት የነበረዉ ክስ ይዘት፡-የስር ተከሳሽ የነበረው አቶ ታከለ ቁያስ መጠኑ 1½ ሄክታር የሆነውን ይዞታ በ2006 ዓ.ም እኔ በማላውቀው ሁኔታ ያለ ፈቃዴ ይዞብኛል፡፡ ስለዚህ ተከሳሹ በሕገ-ወጥ መንገድ የያዘብኝን ይዞታዬን እንዲለቅልኝ የሚል ነው፡፡

የስር ተከሳሽ በሰጡት መልስ ይዞታዉን በ01/08/2004 ዓ.ም በተፃፈው ውል አቶ ጤና ጋረደው ላይ ኮንትራት ወስጀ እያረስኩ እገኛለሁ እንጂ ከሳሽ እንደሚሉት አይደለም፣ ከሳሽ እኔ ኮንትራት የወሰድሁት መሬት ላይም ምስክር ሆነው በውላችን ላይ ስለነበሩ ሊጠይቁኝ አይችሉም በማለት ተከራክሯል፡፡የአሁኑ አመልካችም የስር ጣልቃ ገብ ሲሆኑ ከሳሽ ድንበሩን እና ቦታውን ጠቅሳ ክስ የመሰረተችበት ይዞታ መሬት በአከባቢያችን ባህል መሰረት በ1986 ዓ.ም እኔ ጋብቻ ስፈፅም ከሳሽ እና አባቴ አብረው በመሆን ሰጥተውኛል፡፡ ከዚያ ወዲህም ይህንን ንብረት እየተጠቀምኩበት ቆይቼ በ01/08/2004 ዓ.ም በተፃፈው ውል እስከ 2007 ዓ.ም ለ3 /ሶስት/ አመት ለተከሳሹ አከራይቻለሁ፡፡ ስለዚህ ከሳሽ የእሷ ባልሆነ ይዞታ ላይ የእሷ አስመስላ ክስ ማቅረቧ ትክክል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስላልሆነ መዝገቡ እንዲዘጋ በማለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ክርክር ያስነሳው ይዞታ በወቅቱ በአካባቢያችን ባህል መሰረት ጋብቻ ስፈፅም በስጦታ መልክ ተሰጥቶኛል በማለት ያቀረበው አቤቱታ እውነት አይደለም፡፡ እኔም ሆንኩ አባቱ ይህንን ይዞታ ለጣልቃ ገብ አልሰጠንም፡፡ እስካሁን ድረስም በባሌ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለሆነ የጣልቃ ገቡ አቤቱታ ውድቅ ሆኖ ክርክር ውስጥ እንዲወጣ በማለት ተከራክሯል፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎችን ተመልክቶ ክርክር ያስነሳው ይዞታ በፊት የከሳሿ እና የባሏ የነበረ መሆኑ ከቀረበው የሰውና የፅሁፍ ማስረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ተከሳሽ ደግሞ ይዞታውን ከጣልቃ ገብ በኮንትራት ወስዶ ይዞታውን በተከታታይ ለሶስት አመታት ያረሰ መሆኑ፣ ይዞታው ደግሞ በ1986 ዓ.ም ጣልቃ ገቡ በሚያገባበት ወቅት በአካባቢው ባሕል መሰረት “ጎጆ መውጫ” በሚል ስጦታ ተሰጥቶት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይዞታውን በመያዝ እንደአሰፈላጊነቱ ሲፈለግ በራሱ እያረሰ ሌላ ጊዜ ደግሞ እኩል እየሰጠ የሚጠቀምበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከሳሽ ተከሳሹ ክርክር የተነሳበትን መሬት ለሶስት አመት ማረሱን እና ጣልቃ ገቡ ደግሞ ለረጅም አመታት ይዞ መቆየቱን እያወቀች ይህንን ሁሉ ጊዜ ቆይታ በአሁኑ ወቅት በ2006 ዓ.ም ተይዞብኛል በማለት ክስ ማቅረቧ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1149/2/ ድንጋጌ መሰረት የሕግ አግባብነት የሌለው ስለሆነ ክርክር የተነሳበት ይዞታም ለረጅም ጊዜ በተለያየ ምክንያት ከከሳሿ እጅ የወጣ በመሆኑ ያቀረበችው ክስ የሕግ አግብብነት ያለው ስላልሆነ ተከሳሹን አያስጠይቅም በማለት ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ የወረዳው ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ክርክር የተነሳበት ይዞታ የአሁን ተጠሪ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት ይህንን አልፎ ክርክር የተነሳበትን መሬት ይግባኝ ባይዋ በፍ/ሕ/ቁ. 1149/2/ መጠየቅ አትችልም ብሎ ክሷን ውድቅ ማድረጉ ከደንብ ቁጥር 152/32 ጋር የሚቃረን ስለሆነ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነዉ በማለት ዉሳኔዉን በመሻርክርክር ያስነሳዉ ይዞታ ለአሁን ተጠሪ ይገባል ሲል አመልካች እንዲለቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ አያስቀርብም በማለት ይግባኙን ዘግቷል፡፡አመልካች የከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ የግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ውሳኔውን አፅንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ነዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት፡- ከከፍተኛ ፍርድ ቤቱ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአካባቢውን ባህልና ወግ መሰረት ሳያደርጉ በጋብቻ ላይ በጎጆ መውጫነት የሚሰጠው መሬት ሰጪው በሕይወት እያለ ወደ ራሴ ይዙርልኝ ጥያቄ መቅረብ እንደማይገባ፣ አመልካች ግን በዚሁ በተሰጠኝ ቦታ ላይ ቤት ንብረት አፍርቼ የወለድኩበት መሆኑን ሳይረዱ የመሬቱ ስምም ሆነ መታወቂያው በወላጅ አባቴ ስም ስለሚገኝ ብቻ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት እና ይዞታ እንድለቅ መወሰኑ ሕግን የተከተለ አይደለም፡፡ የአሁኗ ተጠሪም ለክርክሩ መነሻ በሆነው ይዞታ ኮንትራት ውል ላይ እንደምስክር ሆና የፈረመችበት ስለመሆኗ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ላይ በግልፅ ተቀምጦ እያለ ከከፍተኛ ፍርድ ቤቱ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ያሉት ችሎቶች ግን ሌላ ማስረጃ ሳያስቀርቡ ከ20 አመት በላይ በእጁ ይገፎ የምጠቀመበት ይዞታ መሆኑ በማስጃዎቹ ተረጋግጦልኝ እያለ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ ሕግ ስህተት ስለሆነ ተሽሮ የጉደያ ቢላ ወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነዉ፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች አከራካሪውን መሬት በ1986 ዓ.ም በስጦታ አግኝቶ እስካሁን እየተጠቀመበት ባለበት ሁኔታ እንዲያስረክብ መወሰኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ መልስ ባለማቅረባቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፎ ጥቅምት 07 ቀን 2009 ዓ.ም ዉሳኔ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም በሌሉበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳላቸዉ ተጠሪ አቤቱታ አቅርበዉ ተቀባይነት በማግኘቱ ዉሳኔዉ ተነስቶ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ለአቤቱታዉ የሰጡት መልስ ይዘት፡- አመልካች ክርክር ያስነሳዉን መሬት አንዴ በሕጋዊ መንገድ ተሰጥቶኛል እያለ፤ አንዴ ደግሞ ስጦታዉ ተፈጻሚ የሚሆነዉ የአካባቢዉን ባሕል መሰረት በማድረግ ነዉ በማለት የሚያነሳዉ ነጥብ የሕግ ድጋፍ የለዉም፡፡ተጠሪ ዉል አለማድረጓን ከሥር ጀምራ የተከራከረች ሲሆን የወረዳዉ መሬት እና የአከባቢዉ ጥበቃ ጽ/ቤት በጻፈዉ ደብዳቤ ይዞታዉ በተጠሪ ባለቤት ስም እንዳለ እንጂ በስጦታ ስለመተላለፉ የቀረበ ማስረጃ የለም የሚል ሆኖ እያለ አመልካች ዉል ለመኖሩ ተረጋግጦልኛል የሚለዉ ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካች በ1986 ዓ.ም ሲያገባ ሁለት ሄክታር መሬት ተሰጥቶት ነበር ቢባል እንኳ አንድም ቀን ተጠቅሞበት እንደማያዉቅ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ መሬቱን ይዛ እስከ አሁን ግብር እየከፈለች ስትጠቀምበት እንደነበረ እና አመልካች ደግሞ የገጠር መሬት ትቶ ቢላቲ ከተማ ይኖር እንደነበረ በመ/ቁ 09086 ላይ በቀረበዉ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ተደርጎ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉም የአሁኑ አመልካች ያቀረባቸው ሁለት የሰው ምስክሮች ክርክር የተነሳበትን ይዞታ እንደሚያውቁ፣ በ1986 ዓ.ም ጣልቃ ገቡ ሲያገባ በአካባቢው ባሕል መሰረት ለጎጆ መውጫ ተጠሪ ከባሏ ጋር ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ለአመልካች መስጠታቸውን እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይዞታዉን አመልካቹ ይዞ አንዳንዴ በራሱ እያረሰ እየተጠቀመ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የእኩል ሰጥቶ የሚጠቀምበት መሆኑን፣ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ለሶስት አመት ኮንትራት ለስር ተከሳሹ መስጠቱን እንደሚያውቁና ይዞታው ከ20 አመት በላይ በአመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑን እንደመሰከሩ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአካባቢው ባህል መሰረትአመልካቹ ክርክር የተነሳበት ይዞታ መስጠቱን የሚገልፅ መጋቢት 12 ቀን 1986 ዓ.ም የተፃፈ የስጦታ ውል ቀርቧል፡፡ ሌላዉ በአመልካች እና በስር ተከሳሽ መካከል በተደረገዉ የኪራይ ዉል ተጠሪ በምስክርነት መፈረሟና በስር ፍ/ቤት በተደረገዉ ክርክር ይህንኑ በግልጽ ክዳ አለመከራከሯ መሬቱ ለአመልካች በስጦታ የተሰጠ መሆኑን በተጨማሪነት የሚያረጋግጥ ነዉ፡፡ የተጠሪ ምስክሮችም ቢሆኑ የስር ተከሳሽ መሬቱን በምን መልክ መያዙን ባያዉቁም ለ3 ተከታታይ ዓመት ይዞ እያረሰ ይጠቀምበት መሆኑን መመስከራቸዉ ሲታይ ተጠሪ በመሬቱ መጠቀም ካቆሙ ረጅም ጊዜ ያለፈዉና የአመልካችን ክርክር የሚያጠናክር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ለመሻር የሰጠዉ ምክንያት የእርሻዉ መሬት እስካሁን በተጠሪ ባለቤት ስም ተመዝግቦ የሚገኝ እና ግብር የሚከፈልበት መሆኑን ነዉ፡፡ ነገር ግን ክርክር ያስነሳዉ መሬት በ1986 ዓ.ም አመልካች ሲያገባ ለጎጆ መዉጫ ተብሎ እስከተሰጠዉና በተግባር በይዞታዉ ስር አድርጎ በራሱም ሆነ እያከራዬ ከ20 ዓመት በላይ እየተጠቀመበት የሚገኝ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በአባቱ ስም መሆኑና ግብር መከፈሉ ብቻ በመሬቱ ላይ ያለዉን የባለይዞታነቱን መብት አያስቀርበትም፡፡

በመሠረቱ የኦሮሚያ ክልል ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 2/3/ ሕጋዊ የመሬት ይዞታ ማለት ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ አግባብ ባለው አካል ለተጠቃሚዎች የተሰጠ መሬት፣ ወይም በውርስ ወይም በስጦታ የተገኘ መሬት ማለት ነው በማለት ሲደነግግ፤ የአዋጁ አንቀጽ 9(5) ደግሞ ባለይዞታዉ በመሬት ይዞታው የመጠቀም መብቱን በዚያ መሬት ገቢ ለሚተዳደሩ ወይም ሌላ ገቢ ለሌላቸው የቤተሰብ አባላት ወይም መሬት ለሌላቸው ልጆቹ በስጦታ ማስተላለፍ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተጠሪና ባለቤታቸው ለአሁኑ አመልካች ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በስጦታ አስተላልፈዉ ተጠቃሚ አድርገዉታል፡፡ አመልካች ከ20 ዓመት በላይ ተጠቃሚ የሆነበት መሬት መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ መሬቱ በስጦታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰጪዉ ስም እስከአሁን ተመዝግቦ መገኘቱ እና ግብር በስሙ መከፈሉ ብቻ ይዞታዉ በስጦታ ዉል አልተላለፈም የሚያሰኝ አይሆንም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ክርክር የተነሳበትን መሬት በሕጋዊ መንገድ አግኝተው ከ20 /ሃያ/ አመት በላይ በእጃቸው ይዘው በራሳቸዉም ሆነ አከራይተዉ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆናቸው በሚገባ ተረጋግጦ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ይዞታውን ለተጠሪ እንዲመልሱ በማለት ዉሳኔ መስጠቱ የአመልካችን ከይዞታዉ ያለመፈናቀል ሕገ-መንግስታዊ መብት የሚጥስ ሆኖ እያለየክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ ሰበር ሰሚ ይህን ተቀብለው በማጽናት የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 35592 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ፤በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 191823 የካቲት 20 ቀን 2007 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔእናበኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 203567 ታሕሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የጉደያ ቢላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 69933 ታሕሳስ 02 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. ክርክር ያስነሳዉ የእርሻ መሬት አመልካች ለተጠሪ ለማስረከብ አይገደድም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. አፈጻጸሙ ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ ታሕሳስ 19 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 115387

ሚያዚያ 26 ቀን2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተሽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካቾች፡- 1ኛ አቶ መክብብ ተስፋ
2ኛ ወይዘሪት እስራኤል ተስፋ
} ጠበቃ ወረቅአገኘሁ ፀጋው

ተጠሪ፡- 1ኛ ወ/ሮ ፀሐይ ለገሰ ቀረቡ

2ኛ ወ/ሮ ጽጌ አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የመንግስት ቤት ከመከራየት መብት ጋር የተያያዘ ሲሆን የጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪዎች ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ሐምሌ 23 ቀን 2006 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 በቀድሞ ወረዳ 01 ቀበሌ 04 ቤት ቁጥር 085 ሦስት ክፍልና ሰርቪስ ያለው ቤት ከመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ንብረት የሆነውን ቤት ተከራይተው እንደሚኖሩ፤እስከ 2006 ዓ.ም ድረስም የመንግስት ኪራይ እንደከፈሉ፤ የአሁኑ ተጠሪዎች መንግስት ባከራያቸው የቤት ቁጥር 085 ገብተው ይኖራሉ፡፡ ተጠሪዎች ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ቢጠይቁም ለቀው ለመውጣት ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1206/2035 መሰረት ቤቱን ያስረክቡ፤ያለአግባብየተጠቀሙበትን የቤት ኪራይ የመጠየቅ ይጠበቅልን እንዲሁም በክርክሩ ያወጣነው ወጪና ኪሣራ እንዲተኩ የመጠየቅ መብታችን ይጠበቅልን ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት የመከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ነገር ጉዳዩ መልስ አቅርበዋል። ተጠሪዎች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በቤቱ መኖር ከመጀመሩ ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን የተከራከሩ ሲሆን በፍር ጉዳዩም 1ኛ ተጠሪ ወላጅ አባታቸው ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ አባቴ ከአቶ ተስፋ አበበ ተከራይቶ ሲኖር ቆይቷል። አመልካቾች የተከራዩት የቤት ቁጥር 085 ብቻ እንጂ 3 ሰርቪስ ቤት ለመሆኑ ማስረጃ የላቸውም። ጉዳዩ በዚህ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 121070 እየታየ በመሆኑ ተጣምሮ እንዲታይ እና ክሱ ውድቅ እንዲደረግ የጠየቁ ሲሆን፤2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካቾች የተከራዩት ፎቁን ብቻ ነው። ቤቱ ከዛሬ 16 ዓመት በፊት ድሀ በመሆኔ በቀበሌ አመራሮች የተሰጠኝ ነው። አመልካቾች ተከራዩት ቤት ውጪ ባለው ይዞታ ላይ ክስ ሊያቀርቡብኝ አይገባም ክሱ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

3. የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በተጠሪዎች የቀረበው የመጀመሪያ መቃወሚያ ክሱ የመፋለም ክስ በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያው ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም። አመልካቾች ያቀረቡት ክስ የመፋለም ክስ የሚመለከት ቢሆንም የቤት ቁጥር 085 የሆነ ቤት ባለቤት አመልካቾች እንዳልሆኑ እና ቤቱ በመንግስት የሚተዳደር ቤት ስለመሆኑ ከሳሾች በኪራይ ከመንግስት የያዙት ስለመሆኑ በቀን 01/13/2004 ዓ.ም በአመልካቾች እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ማዕከል የተደረገው ውል መረዳት የሚቻል ሲሆን ይህ ፍሬ ነገር በግራ ቀኙ ያልተካደ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካቾች በቤቱ ላይ ያላቸው መብት የባለሀብትነት ሳይሆን ቤቱን በመከራየታቸው የባለይዞታነት መብት ብቻ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል። አመልካቾች ያላቸው መብት የባለይዞታነት መብት ቢሆንም ያቀረቡት ክስ የመፋለም ይዘት ያለው ክስ ነው። የመፋለም ክስ ማቅረብ የሚችለው የባለሀብትነት መብት አለኝ የሚል ወገን ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካቾች ያላቸው መብት የተከራይነት ወይም ባለይዞታነት መብት እንደመሆኑ መጠን የባለቤትነት ወይም የመፋለም ክስ ለማቅረብ የሚችሉ አይሆንም። ስለሆነም አመልካቾች የባለመብትነት መብት ሳይኖራቸው ተጠሪዎች የቤት ቁጥር 085 የሆነውን ቤት ለቀው ያስረክቡኝ ሲሉ ያቀረቡት የመፋለም ክስ በሌላቸው መብት ያቀረቡት እና ህጉን ያላገናዘበ ዳኝነት በሆኑ ፍርድ ቤት ጥያቄው እንዳልተቀበለው፤አመልካቾች የማከራየት መብት ያላቸው ስላልተረጋገጠ ከተጠሪዎች ኪራይ ለመጠየቅ የሚችሉበት የህግም ሆነ የውልምክንያት ስላላቀረቡና ስላላስረዱ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጉታል። የአሁኑ አመልካቾች የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡

4. አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የቤት ቁጥር 085 ህጋዊ ተከራይ መሆናቸው በተረጋገጠበት እንዲሁም የመንግስት ቤቶችኤጀንሲ ስለ ሰርቪስ ቤቶች አስተያየት ሳይሰጥ የአመልካቾች ክስ የመፋለም ይዘት ያለው ነው፡፡ ተብሎ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ አይደለም የሚል ክርክር ማቅረባቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ አከራካሪው ቤት ከመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የተከራዩት መሆኑ እየገለፀ እና ተጠሪዎች ሠርቪስ ቤቶች ለቀው እንዲያስረክቡ በመጠየቃቸው እየታየ ክሱ ያመፋለም ይዘት ያለው በመሆኑ የመፋለም ክስ የማቅረብ መበት የላቸውም ተብሎ ውድቅ የመደረጉ አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ይጣራ ዘንድ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪዎችምበተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቀርብው በሰጡት መልስ የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔና ትእዛዝ እንዲፀና አመልክቷል፡፡

   የመልሰ መልስም ቀርበዋል፡፡

5. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔና ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

6. ከክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነው አመልካቾች ንብረትነቱ የመንግስት የሆነው የቤት ቁጥር 085 መከራየታቸውን የተከዳ ጉዳይ የአይደለም፡፡ በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው በተጠሪዎች የተያዙት ሰርቪስ ቤቶች የቤት ቁጥር 085 አካል ቻው ወይስ አይደለም?ሰርቪስቤቶቹ የቤት ቁጥር 085ቢሆኑ ተጠሪዎች ለረጅም ዓመት እንዴት ሊኖሩበት ቻሉ? የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች አጥብቀው የሚከራከሩት ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ 1ኛ አመልካች ከወላጅ አባታቸው አቶ ለገሰ ገመታ በዚህ ቤት ሲኖሩ እንደነበር 2ኛ ተጠሪም ከ16 ዓመት በፊት ደሀ በመሆናቸው ቤቱ በቀበሌ አመራር እንደተሰጣቸው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ያየው ከመፋለስ ክስ ጋር በማያያዝ በመሆኑ በግራ ቀኙ ያለው ክርክር ባህሪና ይዘት ባገናዘበ መልኩ ጉዳዩን ያጣራው አይደለም፡፡

7. አመልካቾች ያቀረቡት ክስ የመፋለም ይዘት አለው እንኳ ቢባል የመንግስት ቤት ተከራይቶ የሚኖሩ መሆኑ በክሳቸው በመግለፅ ባመለከቱበት ሁኔታ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1206 በመጠቀሱ ብቻ ክሱ የባቤትነት መብት የመጠየቅ ክስ ነው የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ የአመልካቾች መብት በተከራዩነት የተገደበ መሆኑ ከተረጋገጠ ያቀረቡትክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 መሰረት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ በሚያግዝ መልኩ እንዲሻሻሉ ማዘዝም ይቻል ነበር፡፡ አመልካቾች የተከራዩት ቤት ቁጥር 085 የአሁኑ ተጠሪዎች የያዙት ክፍል የሚያጠቃልል ከሆነ ክሱ ለማቅረብ አይችሉም የሚባልበት ሁኔታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይኖርም፡፡አንድ ተከራይ የተከራየው ቤት ላይ ያለውን ህጋዊ መብት ለማስከበር የክርክር አድማሱን የይዞታ ክርክር አደርጎ በመገደብ ማጣራት የሚቻልበት ሁኔታ ሕጉ የሚከለክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

8. አከራካሪው ቤት የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ መሆኑ አልተካደም፡፡ የቤቱ አከራይ የሆነውመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ግራ ቀኙ እያከራከረባለው ጉዳይ የበኩሉን አስተያየት እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.39/1/ እና 40/2/ መሰረት የክርክሩ ተከፋይ ሊሆን ይገባ ነበር፡፡ በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ነጥብ የባለቤትነት መብት መፋለም ክስ ሳይሆን ተከራይነት የተገኘው የባለይዞታነት መብት ለማስከበር የቀረበ ክስ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የአሁኑ ተጠሪዎች ለክሱ መነሻ የሆኑ ሰርቪስ ቤቶች መቼ እንደያዙት ?ቤቶቹ ለመያዝ የቻሉበት ህጋዊ ምክንያት መኖሩ አለመኖሩን?በተጠሪዎች የተያዙት ሰርቪስ ቤቶች ላይ የመከራየት መብት ያቋቋሙ መሆን አለመሆናቸው?በአጠቃላይ ተጠሪዎች ሰርቪስ ቤቶቹ ይዘው የሚቀጥሉበት ህጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን?በዝርዝር መጣራት ያለበት ጉዳዩ ነው፡፡ ከዚህ በተያያዘ የመንግስት ቤቶች ኤጀሲ ከአመልካቾች ጋር የቤት ቁጥር 085 አደረገው የተባለው የኪራይ ውል ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ሰርቪስ ቤቶቹን የሚያጠቃልል መሆን አለመሆኑን የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 39/1/ እና 40/2/ መሰረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ጉዳዩ መጣራት ያለበት ስለመሆኑ የክርክር ይዘትና ባሕሪ ያለመክታል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው የተከራይነት መብት ሆኖ ሳለ በአመልካቾች ክስ የፍ/ሕ/ቁ. 1205 በመጥቀስ ብቻ የመፋለም ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው በጉዳዩ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሳይ በመሆኑ ሽረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 120983 በ03/04/2007 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 165941 በ29/08/2007 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋው መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ይዘቱ በተገለፀው አግባብ አመልካቾች እና ተጠሪዎች እያከራከረ ያለው የተከራይነት መብት የመንግስት ቤች ኤጀንሲ ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ሰርቪስቤቶች የቤት ቁጥር 085 አካል ናቸው ወይስ አይደሉም?የአሁኑ ተጠሪዎች በሰርቪስ ቤቶቹ መኖር የጀመሩት ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው? ሰርቪስ ቤቶቹ እንዴት ሊይዙት ቻሉ?ተጠሪዎች ከ10 ዓመት በላይ ቤቱን ይዘው እየኖሩ ከሆነ የሚኖረው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው?የአሁኑ ተጠሪዎች ሰርቪስ ቤቶቹ ይዘው የሚቀጥሉበት ህጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን በግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 በሚያዘው አግባብከሚመለከተው አካል ተገቢ ማስረጃ በማስቀረብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 264/1/ የሰው ምስክሮች ጭምር በመስማት ተገቢ ህጋዊ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡ይፃፍ፡፡

3. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. የዚህ ፍርድ ቤት ውሣኔ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ ብለናል፡፡ መዝገቡን ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ሥልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.121660

ሕዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች(ዎች)፡- አቶ ለገሰ ገለታ ቀርቧል

ተጠሪዎች ፡- 1. የአ/አ/አስ/መሬት ልማትና ማኔጅመንት } ነ/ፈጅ በሀይሉ ክብረት ቀረቡ

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ }

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ተጠሪዎች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ አመልካች ምትክ ቦታ ሊሰጣት ይገባል በማለት፣ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ ሕጋዊ አግባብነት ያለው መሆኑን በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡
2. የጉዳዩ መነሻ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ አመልካችና በዚህ ሰበር ችሎት የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነውና በሥር ሁለተኛ የፍርድ መቃወም ተጠሪ ሆኖ ስሙ በተገለጸው የቀድሞው የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና ባንክ የከተማ ልማት ማደስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት(በአሁኑ አጠራርየቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር መምሪያ) መካከል የነበረውን የካሳና የምትክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቦታ ክርክር ሰምቶ፣ መልስ ሰጭ ለአመልካች ምትክ ቦታ የመስጠት ግዴታ አለበት በማለት በመዝገብ ቁጥር 330/99 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ ተጠሪዎች ይህ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት(ተጠሪዎች) በመልሥ ሰጭነት ሳይጠሩና ክርክራቸውን ሣያቀርቡ የተሰጠና የከተማውን አስተዳደር፣ ሕዝብ መብትና ጥቅም የሚጎዳ በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከተን የከተማው አስተዳደር አካላት(ተጠሪዎች) ባለንበት እንደገና ታይቶ ሊወሰን ይገባል በማለት ሀምሌ 6 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ፣ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 በመጥቀስ ለከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርበዋል፡፡

3. የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጠሪዎችን ፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው የሚላቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ፣ ተጠሪዎች የፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 በመጥቀስ ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ተቀብሎ ለማስተናገድና ቀደም ብሎ የሰጠውን ፍርዱ እንደገና ለማየት የሚያስችለው የህግ መሰረትና ሥልጣን የሌለው መሆኑን ገልጾ፣ ተጠሪዎች ያቀረቡትን መቃወሚያ አይቶ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን የለኝም በማለት የጉ/መዝገብ ቁጥር 330/99 ሀምሌ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

4. ተጠሪዎች የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት፣ ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 358ና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ለመቀበልና የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ውሳኔ መስጠት ስልጣን አለው በማለት የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሰጠውን ብይን በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ይግባኝ ሰሚው ችሎት የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጠሪዎችን የፍርድ መቃወሚያ በመቀበልና የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት መልሶ ልኮለታል፡፡

5. አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የከተማው የሰበር ችሎት የአመልካችን ሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ፣የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጉዳዩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጀመሪያ አይቶ ውሳኔ የሰጠው ተጠሪነቱ ለአንደኛ ተጠሪ ሆነው የቀድሞው የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና ባንክ ከተማ ልማት ማደስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት(በአሁኑ አጠራር የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር መምሪያ) በሁለተኛው ተጠሪ በኩል ተወክሎ ያለውን ክርክርና ማስረጃ ካቀረበ በኋላ ነው። ስለዚህ ተጠሪዎች ጉባኤው ቀደም ብሎ ውሳኔ የሰጠው የሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት(ተጠሪዎች) በመልሥ ሰጭነት ሳይጠሩና ክርክራቸውን ሣያቀርቡ የተሰጠ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢነት የሌለውና የህግ መሰረት የሌለው ነው። ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ተጠሪዎችን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ባለመሆኑና በአጠቃላይ ተጠሪዎች ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ተቀብሎ እንዲያይ የሰጡት ብይን በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አመልክተዋል።

6. ተጠሪዎች በጋራ ባቀረቡት መልስ በጉዳዩ ተከራካሪ መሆን የነበረብን እኛ ነን። ጉባኤው እኛን በመልስ ሰጭነት ሣይጠራ የሰጠው ውሳኔ የከተማው አስተዳደርና ሕዝብ ጥቅም የሚጎዳ ነው። ተጠሪዎች በዚህ አይነት ሁኔታ የተሰጠን ፍርድ በመቃወም የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ማቅረብ እንደምንችል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 37502 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ፣ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል። አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል።

7. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ ቀደም ብሎ በሰጠው ውሳኔ ላይ በፍ/ሥ/ሥ ሕግ ቁጥር 358ና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት የሚቀርብለትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው፣ ቀደም ብሎ የሰጠውን ፍርድ እንደገና እንዲመረምር በሌሎች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ተቀብሎ የማየት፣ ክርክር የመስማትና መርምሮ የመወሰን ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

8. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ በልማት ከይዞታቸው ለሚነሱና ንብረታቸውን ለሚያነሱ ሰዎች የካሣ ክፍያና ምትክ ቦታ ጥያቄና አቤቱታ ላይ አስተዳደራዊ ውሳኔ የመሥጠት ኃላፊነት ያለበትና በከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝ ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 272/1994 እና ይህንን አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 መሰረት ሥልጣን የተሰጠው የከተማው አስተዳደር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

"አግባብ ያለው አካል" ፣ ስለ ምትክ ቦታ ጥያቄውና ስለ ካሳ ክፍያ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኙ ሰዎች የሚቀርቡትን የይግባኝ ቅሬታ ተቀብሎና የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶና አጣርቶ ውሳኔ የመስጠት በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡

9. ከላይ በተጠቀሱት አዋጆች የከተማ ቦታ እንዲለቅ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰውና በአስተዳደራዊ ውሳኔው መብቴን ነክቶብኛል የሚል ሰው ለከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ ቅሬታ ከማቅረቡ በፊት አግባብ ላለው የአስተዳደር አካል በሰባት ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ አለበት፡፡የከተማ ቦታ እንዲለቅ የተሰጠውን ውሳኔ ማስታወቂያ በመቃወም አቤቱታ የቀረበለት አግባብ ያለው አስተዳደሩ አካል በጽሁፍ ውሳኔ መስጠት እንዳለበት በአዋጆቹ ተደንግጓል፡፡ የአስተዳደሩ አካል በአቤቱታው ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በውሳኔው ቅር ያለው ሰው ፣ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የይግባኝ ቅሬታውን ስለሚቀርብበት ሁኔታ፣ የአዋጅ ቁጥር272/1994 በአንቀጽ 16 እና አንቀጽ17 በዝርዝር ባስቀመጣቸው ድንጋጌዎችና በአዋጅ ቁጥር 721/2004 በአንቀጽ 26፣ አንቀጽ 27ና በአንቀጽ 28 ድንጋጌዎች ተደንግጎ ይገኛል ፡፡

10. ከላይ በገለጽናቸውና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የህግ ድንጋጌዎች ለከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት፣የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በከተማ ቦታ ማስለቀቅ፣ሂደት የሚቀርቡ የምትክ ቦታና የካሳ ጥያቄ ጉዳዮች ላይ የሚመለከተው አስተዳደር አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ሰው የሚያቀርበውን የይግባኝ ቅሬታ፣ የመቀበል፣ የይግባኝ ባዩንና የመልስ ሰጭ ክርክር የመቀበል፣ ማስረጃ በትዕዛዝ ማስቀረብና አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ የመሰጠት ሥልጣንን የሚያካትት ነው፡፡ ይህ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሥልጣን፣በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ1፣በአዋጅ ቁጥር 272/1994 እና ይህንን አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 መሰረት የተሠጠ የዳኝነት ሥልጣን ነው፡፡

11. የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ1 ከላይ በገለጽናቸው የህግ ማዕቀፎች የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው አካል መሆኑ የራሱ የሆነ መገለጫ፣ ባህሪና ሕጋዊ ውጤት አለው፡፡የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በህግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው አካል መሆኑ፣ በዳኝነት ሥልጣኑ አይቶ የሚወስናቸው ውሳኔዎች በሕግ አግባብ በሌላ ዳኝነትሥልጣን ባለው አካል ታይተው ካልተሻሩ ወይም ካልተለወጡ በስተቀር አስገዳጅነትና ተፈጻሚነት ያላቸው ውሳኔዎች ናቸው፡፡የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በህግ በተሰጠው የዳኝነት ሥልጣኑ የሚወስናቸው ውሳኔዎች በአስተዳደሩ ክፍል ውሳኔ የሚሻሻሉ፣ የሚለወጡ ወይም የሚሻሩ አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

12. የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በህግ በተሰጠው የዳኝነት ሥልጣኑ የሚወስናቸው ውሳኔዎች በፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድና ውሳኔ ልዩ ባህሪና ሕጋዊ ውጤት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህም ማለት የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በህግ በተሰጠው የዳኝነት ሥልጣኑ የሚወስናቸው ውሳኔዎች የሚሻሻሉት፣ የሚለወጡትወይም የሚሻሩት በሁለት መሰረታዊ መንገድና ሥርዓትና አሰራር ነው፡፡ የመጀመሪያው የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ውሳኔ፣በህግ በተደነገገው ሥርዓት መሰረት ታይቶ የሚጸናበት፣የሚሻሻልበት፣ በሚለወጥበትና የሚሻርበት ሥርዓት የይግባኝ ሰሚ ጉባኤውን ውሳኔ በይግባኝና በሰበር ሥርዓት አይተው ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ታይቶ እንዲወሰን የሚደረግበት አሰራር ነው፡፡ ይህ አሰራር የፍርድ ቤቶችን አደረጃጀትና የይግባኝና የሰበር ሥረ ነገር ስልጣን መሰረት በማድረግ የይግባኝ ጉባኤው ውሳኔ የሚታይበት የሕግ ሥርዓት የተዘረጋለትና፣ በልምድ በዳበረ የዳኝነት አሰራር የሚደገፍ ነው፡፡
13. ሁለተኛው የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንደማንኛውም በህግ የዳኝነት ሥልጣን እንደተሰጠው ፍርድ ሰጭ ተቋም፣ ራሱን ውሳኔ በድጋሜ አይቶና አጣርቶ ሊወስን በሚችልባቸው የህግ ሥርዓቶች ማለትም በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ አንቀጽ 74፣አንቀጽ 78፣አንቀጽ 358ና ተከታይ ድንጋጌዎችና በአንቀጽ 6 በተደነገጉት ሥርዓቶች ጉዳዩ እንደገና በማየት፣ የሚመለከታቸውን ባለጉዳዮች ክርክርና ማስረጃ በመስማት የራሱን ውሳኔ በህግ በተደነገገው ሥርዓት መሰረት እንደገና አይቶ በማጽናት፣ በማሻሻል፣ በመለወጥና በመሻር ውሳኔ የሚሰጥበትን አሰራርና ሥርዓት በመከተልና ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡
14. ይህም የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የዳኝነት ነክ ሥልጣን ነጻነት፣ ተጠያቂነት ማስከበሪያና የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በዳኝነት ሥልጣኑ አከራክሮ ሲወስን የፈጸማቸው የዳኝነት አካሄድ፣ የስነ ሥርዓትና የፍርድ ስህተት በራሱ እንደገና ታይቶ ከሚታረምበት መሰረታዊ የዳኝነት የስራ አካሄድና የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በህግ ከተሰጠው የዳኝነት ስልጣን መሰረታዊ ተቋማዊ ባህሪው የሚመነጭ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በህግ በተደነገገው ሥርዓት መሰረትየከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀደም ብሎ የሰጠው ውሳኔ በድጋሜ አይቶ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚቀርብለትን አቤቱታ በመቀበልና መርምሮ ውሳኔ መስጠት ከተፈጥሯዊ ተቋማዊ የዳኝነት ነክ ሥልጣኑ የሚመነጭ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
15. ከላይ በዝርዝር ከገለጽናቸው ሕገ መንግስቱና ሌሎች የህግ ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማአንጻርበከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀደም ብሎ በሰጠው ፍርድ ላይ በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ አንቀጽ 358ና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚቀርብለትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ተቀብሎ የማየት፤ ተከራካሪ በመሆንየሚቀርቡ ሰዎች የሚያቀርቡትን ክርክር የመስማት አጣርቶ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣኑ የሚመነጨው፣ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ1፣አዋጅ ቁጥር272/1994 እና ይህንን አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር721/2004 መሰረት ከተሰጠው የዳኝነት ነክ ሥልጣኑ የሚመነጭ ነው፡፡

16. ይህም የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የዳኝነት ሥልጣኑ ዋና ባህሪና መገለጫ፣የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ውሳኔ መስጠት ነጻነት፣ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ውሳኔ አስገዳጅነት፣ ተፈጻሚነት ተጠያቂነት ማስከበሪያ መንገድ ነው፡፡ የአሰራር ሥርዓቱ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በዳኝነት ሥልጣኑ አከራክሮ ሲወስን የፈጸማቸው የዳኝነት አካሄድ፣ የስነ ሥርዓትና የፍርድ ስህተት በራሱ እንደገና አይቶ የሚታረምበት አሰራር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ አንቀጽ 358 ና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ የመቀበልና መርምሮ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን፣ ከላይ የተገለጹትን ሕግ ድንጋጌዎች ይዘት፣ መሰረታዊ ዓላማ፣ ተግባራዊ ተፈጻሚነትና ህጋዊ ውጤት ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

17. በመሆኑምየአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የከተማው አስተዳደር የሰበር ችሎት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጠሪዎችን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አይቼ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ብይን በመሻር፣ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ በመቀበል መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ አንቀጽ 341(1) መሰረት መመለሳቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24033 ህዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የከተማው አስተዳደር የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24581 ታህሳስ 05 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. አዲስ አበባ ከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ተቀብሎ የማየትና የመወሰን ሥልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. በዚህ ሰበር ችሎት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጀመረው የይግባኝ ክርክር የዚህ ክርክር ውጤት እስኪታወቅ ታግዶ እንድቆይ ተብሎ የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ተነስቷል ።
4. ዕግዱ የተነሳ ስለመሆኑ ለከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚው ችሎትና ለሚመለከተው አካል ይጻፍ።
5. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለየራሳቸው ይቻሉ።
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 129430

ታኅሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- የእነማይ ወረዳ ንግድ ትራንስፖርት ጽ/ቤት - ዐ/ህግ አቶ ታምሩት ወርቁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጎበዜ አሰፋ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ጉዳይ ከገንዘብ ክፍያ ጋር በተያያዘ የቀረበ የፍትሓብሔር ክስ ሲሆን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በእነማይ ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረበው በተሸከርካሪ ተጭነው የነበሩ ስድስት የቁም እንስሶችን አመልካች የወሰደብኝ በመሆኑ እንስሶቹን እንዲመልስልኝ ወይም ግምታቸው ብር 35000.00/ሰላሳ አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍለኝ በሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 ን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ 341/2007 አንቀጽ 19/4 እና 5/ መሠረት በህገወጥ መንገድ ተይዘው በተገኙ የቁም እንስሳት ላይ አግባብ ያለው አካል በሚወስደው እርምጃ ላይ ሊቀርብ የሚችለው ይግባኝ መሆኑ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነ ለወረዳው ፍርድ ቤት የቀጥታ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ በመሆኑም የወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጠን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤት በተጠቀሰው አዋጅ እና ደንብ መሠረት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለኝም በማለት በመ/ቁ.0119015 በቀን 29/02/2008 ዓ/ም ብይን ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ ብይኑን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በመ/ቁ. 0123900 ህዳር 6 ቀን 2008 ዓ/ም ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም የግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀጽ 19 /4 እና 5/ ን በመተርጎም ጉዳዩ በቀጥታ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል በማለት የሥር ፍርድ ቤቶችን ብይንም ሆነ ትዕዛዝ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 341 መሠረት መልሷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ፡- በቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 አንቀጽ 15 /5 እና 8/ መሠረት እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀጽ 17 እና 19 መሰረት ተጠሪ በህገወጥ መንገድ እያጓጓዛቸው የተገኙ ስድስት የቁም እንስሶች ላይ በሰጠው ውሳኔ ላይ ሊቀርብ የሚችለው ይግባኝ እንጂ ቀጥታ ክስ አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የወረዳ ፍርድ ቤት በመቃወሚያው ላይ የሰጠውን ብይን በመሻር የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የወረዳ ፍርድ ቤት ብይን እንዲፀናልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአስተዳደር አካሉ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የይግባኝ አቤቱታ ሳይሆን ቀጥታ ክስ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል በማለት አዋጅ ቁጥር 819/2006 እና አዋጁን ተከትሎ የወጣ ደንብ ቁጥር 341/2007 ደንጋጌዎችን በመተርጎም የደረሰበት ድምዳሜ የህጉን ዓላማ፣ መንፈስና ይዘት በአግባቡ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች አቤቱታ በቀን 01/11/2008 ዓ/ም የተጻፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደቀረበው ሲሆን ጉዳዩን ከሥር ፍርድ ቤቶች ብይን፣ ትዕዛዝ እና ውሳኔ እንዲሁም በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክርና አጣሪ ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ የግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የስልጣን ጥያቄ መሠረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 819/2006 አንቀጽ 15 /5 እና 8/ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀጽ 19 /4 እና 5/ ነው፡፡ አግባብ ያለው አካል በአዋጁ አንቀጽ 15/5/ ማንኛውም የቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊ የግብይት ሂደቱን የሚያዛባ አሳሳች ድርጊት ፈጽሞ ሲገኝ ተገቢውን አስተዳዳራዊ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን እንዳለው ሲደነግግ፣ የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 8 ደግሞ በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ ወይም ግብይት ሲፈጸምባቸው የተገኙ የቁም እንስሳትን የመያዝ፣ የቁም እንስሳቱን እንደ አግባቡ በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማዕከል አቅርቦ በጨረታ በመሸጥ ገንዘቡን በዝግ የባንክ ሂሳብ እንዲቀመጥ የማድረግ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሠረት እንዲወረስ ሲወሰንም ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን የማድረግ ሥልጣን የተሠጠው እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ ያለው አካል ሊወስድባቸው የሚችልባቸውን አስተዳዳራዊ እርምጃ የሚገልጹ ናቸው፡፡ አግባብ ያለው አካል ማነው? ለሚለው ጥያቄ አዋጁ በአንቀጽ 2 (24) "አግባብ ያለው አካል"እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው በማለት ይተረጉማል፡፡ እርምጃዎቹ ሲወሰዱ ክስ ለማን እንደሚቀርብ ግን አዋጁ አይገልጸም፡፡ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀጽ 19/4/ የአስተዳደር አካሉ እርምጃ ሲወስድ ክስ ለማን እንደሚቀርብ ይደነግጋል፡፡ ይኸውም "ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል" የሚለው ነው፡፡ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የትኛው ነው? የሚለውን ደንቡ በግልጽ ባያስቀምጥም ሥልጣን በሥረ ነገር ወይም በገንዘብ መጠን ሊወሰን ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር ክስ አቅራቢ የሚጠይቀው የዳኝነት ዓይነት ወይም የገንዘብ መጠን የፍርድ ቤቱን ሥልጣን ይወስናል ማለት ነው፡፡ በዚህ በዳኝነቱ መጠን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ይቀርባል ማለት ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ክስ የሚቀርበው ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሳይሆን ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው ፡፡ ይህም ወረዳ ፍርድ ቤት ወይም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊሆን ይችላል፡፡ ክስና ይግባኝ የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የህግ አውጪው ሀሳብ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ቀጥታ ክስ ሊቀርብ እንደሚችል መደንገጉን ነው፡፡ የእንግሊዘኛው ትርጉምም ቢሆን " May institute case in a court of law having jurisdiction within 30 day after the decision is passed or after laps of period specified for decision" የሚለው ከላይ የገለጽነውን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ቢሆንም የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 5 ደግሞ "ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት" በማለት የሚገልጽ ሲሆን ይህ በንዑስ አንጽ 4 ላይ ከተደነገገው ጋር ይቃረናል፡፡ሆኖም ግን ከእንግሊዘኛው ትርጉም ሲታይ የህግ አውጪው ሀሳብ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ እንዲቀርብ መሆኑን ነው፡፡ እነዚህን ሁለቱን ንዑስ አንቀጾች ህግ አውጪው ከሰበው ግብ አንጻር መተርጎም የፍርድ ቤት ድርሻ ነው፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እነዚህን ሁኔታዎችን በማጤን የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 52382 በቀን 17/09/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. በቀን 23/10/2008 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.123986

ግንቦት 18 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ መቻልደጉ ሰሙር ጠበቃ አብዱርሃማን ሰይድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የሚዛን አማን ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤት አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች ተጠሪው ከ2000 እስከ 2005 ዓ.ም ባለዉ የግብር ዘመን በኦዲት ምርመራ ዉጤት ላይ በመመስረት የገቢ ግብር፣ አስተዳደራዊ መቀጫና ወለድን ጨምሮ ብር 2,779,095.30 ሲወስን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ አስተዳደራዊ መቀጫና ወለድ ደግሞ ብር 1,972,184.97 በመወሰን ጥር 30 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፉ የግብር ማስታወቂያ ደብዳቤዎች አሳዉቋል፡፡ አመልካች በዉሳኔዉ ቅር ተሰኝቶ ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ አመልካች ፍሬ ግብር እና ፍሬ ታክስ ሙሉ በሙሉ እንዲከፍል ሆኖ ከወለድ 25% ከፍሎ 75% እንዲነሳለት እንዲሁም አስተዳደራዊ መቀጮ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳለት በመሻሻል ወስኗል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ግራቀኙ ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የቤንች ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ወለድ 75% እና አስተዳደራዊ መቀጮ ሙሉ በሙሉ ይነሳ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ሕግን መሠረት ያላደረገ ነዉ በማለት ሲሽር ፍሬ ግብርና ፍሬ ታክሱን በተመለከተ በአግባቡ ሳይጣራ ሙሉ በሙሉ ይክፈል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮት ግብር ይግባኝ ሰሚዉ ጉባኤ እንደገና አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን በመመለስ ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ የአሁኑ ተጠሪ ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍሬ ግብር እና የፍሬ ታክስ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን ለጉባኤዉ መመለሱም ሆነ ጉባኤዉ አስቀድሞ በሰጠዉ ዉሳኔ ወለድ 75% እና አስተዳደራዊ መቀጮ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳ መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት በመሻር ወስኗል፡፡ ይህን ዉሳኔ በመቃወም የአሁን አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 285/94 መሰረት የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን የለዉም በማለት መዝገቡን በትዕዛዝ ዘግቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉን ትዕዛዝ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ጉዳዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክርክር ያለበት ስለሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 285/94 መሰረት የፌዴራል ጉዳይ ነዉ በማለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ ሕግን መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 3 እና 2(3) ድንጋጌ አንጻር ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች የወል ዳኝነት ስልጣን ሥር ይወድቃል ተብሎ ሊተረጎም አይገባም፡፡ አዋጁ በመላ አገሪቱ ተፈጻሚነት ያለዉ አዋጅ በመሆኑ፣ አዋጁን መሰረት አድርገዉ ክልሎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሕግን የሚያስከብሩና ታክሱን የሚሰበስቡ በመሆኑ በአዋጁ ላይ ለሚነሳ ክርክር በክልል ፍ/ቤቶች የመጨረሻ ዉሳኔ ሰጪ አካል የሆነዉ የሰበር ችሎት ስልጣን የለዉም መባሉ የአዋጁን አላማ ያልተከተለ ነዉ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 43(4) መሰረት የይግባኝ አቀራረብ እና የግብር ይግባኝ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር በተመለከተ የገቢ ግብር አዋጅ ተፈጻሚ እንደሚሆን የተደነገገ በመሆኑና አግባብነት ያለዉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/95 የክልል አዋጅ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለዉ፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን እንዳያይ የሚከለክል ግልጽ ድንጋጌ በሌለበት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝጋቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ጉዳዩን አይቶ እንዲወስን ሊመለስለት ይገባል፡፡

የዞኑ ክፍተኛ ፍ/ቤት ስለ አዳሪ ቡና መረጃ ከዞኑ ግብይት መምሪያ አስቀርቦ ከመረመረ በኃላ ጉባኤዉ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/95 አንቀጽ 116(1/ሐ) ላይ የተመለከተዉን ማስረጃን አስቀርቦ የማጣራት ሥራዉን አለመስራቱን አረጋግጦ ዉሳኔዉን በመሻር እንደገና በማስረጃ አጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥ መልሷል፡፡ ይህን ማድረጉ በሕግ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ዉሳኔ አይደለም የሚያስብል ባለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤትን ዉሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም የከፍተኛዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ ከሻረ በኃላ ጉዳዩን ወደ ጉባኤዉ መመለስ ሲገባዉ በዝምታ በማለፉና በተዘዋዋሪ መንገድ የተጠሪን ዉሳኔ ማጽናቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካች ያቀረብኩት የሂሳብ መዝገብ ዉድቅ መደረጉም ስህተት ነዉ፡፡ ባቀረብኩት ሒሳብ መዝገብ ብቻ ግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ልከፍል ይገባል የሚል ክርክር ባላቀረብኩበት አግባብነት የሌላቸዉ ምክንያቶች አንስቶ በመተቸት እና አከራካሪዉን ጭብጥ ባለመረዳት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ ተሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ገልጾታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የክልሉ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ የማየት ስልጣን አለዉ ወይ? የሚለዉንና ይህን ተከትሎ የሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት መጥሪያዉ ለክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን ተብሎ እንዲቀየር አቤቱታ ቢያቀርብም ተቀባይነት በማጣቱ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመከተዉን የሚመስል ሲሆን አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በመገናዘብ መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነዉ ተጠሪ ከ2002 እስከ 2005 ዓ.ም ያለዉ የንግድ እንቅስቃሴ ኦዲት ከተደረገ በኃላ የገቢ ግብር፣ አስተዳደራዊ መቀጮና ወለድ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደራዊ መቀጮና ወለድ ጨምሮ የወሰነበት ሲሆን አመልካች ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ አቅርቦ ፍሬ ግብሩን፣ ፍሬ ታክስ እና 25% ወለድ እንዲከፍል ሲወስን 75% ወለድ እና አስተዳደራዊ መቀጮ እንዲነሳለት ወስኗል፡፡ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ዉሳኔ ባለመስማማት ግራቀኙ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን በከፊል ወለድ እና አስተዳደራዊ መቀጮ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳ መወሰኑ ስህተት መሆኑን ቢገልጽም ፍሬ ግብሩና ታክሱ በአግባቡ ሳይጣራ የተወሰነ ነዉ በማለት ዉሳኔዉን ሽሮት እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ጉባኤዉ መልሶታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍሬ ነገር ክርክሩ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንደገና እንዲጣራ የሰጠዉ ዉሳኔ የሕግ ስህተትን ከማረም ስልጣን ዉጪ ነዉ ሲል ሽሮት የተጠሪን ዉሳኔ በተዘዋዋሪ መንገድ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 285/94 መሰረት የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የፌዴራል በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም የሚለዉን ጭብጥ ለመመለስ አግባብነት ያላቸዉን የሕግ ድንጋጌዎች እንመልከት፡፡

በመሠረቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የፌዴራል መንግስት የታክስ ስልጣን ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 28(2) እና አንቀጽ 30 መሠረት ታክሱን የመሰብሰብና የማስተዳደር ስልጣን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተሰጠ መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የክልል የገቢዎች ባለስልጣን ቢሮዎች ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰበስቡት ታክሱን የማስተዳደር የራሳቸዉ ስልጣን ኖሯቸዉ ሳይሆን ታክሱን ለማስተዳደር ካለዉ አመቺነት የተነሳ ስልጣን ባለዉ አካል በተሰጣቸዉ ዉክልና ነዉ፡፡ የክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን የተጨማሪ እሴት ታክስን በዉክልና ማስተዳደሩ ብቻ ጉዳዩን የክልል ጉዳይ ሊያደርገዉ አይችልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአዋጁ አንቀጽ 43(3) በግልጽ እንደሚደነግገዉ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ዉሳኔ ላይ የሚቀርበዉ ይግባኝ የሚስተናገደዉ በገቢ ግብር አዋጁ መሰረት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 112 ደግሞ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ዉሳኔ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ወገን ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የተጨማሪ እሴት ታክስ የፌዴራል ታክስ በመሆኑና የክልል የገቢዎች ቢሮዎች ታክሱን የሚያስተዳድሩት በዉክልና ስልጣናቸዉ በመሆኑ ምንም እንኳ ታክሱ የተወሰነዉ በክልሉ የገቢዎች ቢሮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቢሆንም የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ይግባኝ ማቅረብ የሚገባዉ ስልጣን ላለዉ የፌዴራል ፍ/ቤት ወይም የዉክልና ስልጣን ላለዉ የክልል ፍ/ቤት መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱ የሚነቀፍ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል ምንም እንኳ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱ ተገቢ ቢሆንም ቀጥሎ የሚነሳዉ ጥያቄ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተመልክተዉ ዉሳኔ የሰጡበት ስልጣን ኖሯቸዉ ነዉ? ወይስ አይደለም የሚለዉ ነዉ፡፡ ጉዳዩ ከላይ እንደተገለጸዉ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11፣ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 43(4) እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 112 መሠረት ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ወገን ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችለዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ የስር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ዓይተዉ የወሰኑት የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበዉ ባላቸዉ የዉክልና ስልጣን ተጠቅመዉ ሳይሆን የክልል ጉዳይ ነዉ በሚል ነዉ፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸዉ ጉዳዩን ተመልክተዉ መወሰናቸዉን ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤቶች የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸዉ ስልጣን አለን በሚል በተሳሳተ ግንዛቤ የሰጡትን ዉሳኔ የማረም ኃለፊነት እያለበት ዉሳኔውን ሳይሽር በዝምታ ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ጉዳይ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስረ-ነገር ክርክሩን ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን የለኝም ማለቱ ተገቢ ቢሆንም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ የፌዴራል መሆኑን ሳይገነዘቡና ስልጣን ሳይኖራቸዉ የሰጡትን ዉሳኔ መሻር ሲገባዉ በዝምታ ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የቤንች ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14511 ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 03164 መስከረም 21 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸዉ የሰጧቸዉ ዉሳኔዎች በመሆናቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 03334 ጥር 26 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ነዉ ተብሏል፡፡
4. የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸዉ የሰጧቸዉ ዉሳኔዎች የተሻሩ በመሆናቸዉ ይህ ዉሳኔ ግራቀኙን በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ዉሳኔ ላይ ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ከማቅረብ አይከለክልም ተብሎ ተወስኗል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 123200

ሰኔ 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነው

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1ኛ. ማጂኮን ኮንስትራክሽን ሊ.ድ

2ኛ ኢ/ር ሙሉጌታ አሰፋ ኃ/ማርያም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ታትገኝ ፊጣሞ ወሌቦ

2ኛ. አቶ ሃሮን ሰሌ ኡስማን

3ኛ. አቶ እስማኤል መሐመድ ሱሌማን

4ኛ አቶ አደም መሃመድ አደም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ተሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱታ ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን አስመልክቶ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ብይን በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡

ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር አድርገዋል፡፡ ክሱ መሰረት ያደረገው በአመልካቾች እና በተጠሪዎች መካከል በደቡብ ሱዳን የተደረገ ውል ላይ ሲሆን ተጠሪዎች በውለታቸው መሰረት ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን ገልጸው አመልካቾች በውል መሰረት የሚፈልግባቸውን ክፍያ እንዲፈጽሙ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ለክሱ በሰጡት መልስ 1ኛ አመልካች ጋር ውል ማደረጋቸውን አምነው ነገር ግን 1ኛ አመልካች የተቋቋመው በሱዳን ሃገር ሕግ መሆኑን፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው፣ ለክሱ መነሻ የሆነው ውል የተደረገው በሱዳን ሃገር ስለመሆኑና የውል ጉዳይ የተፈጸመው እዚያው በመሆኑ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳዮን በማከራከርና ለመወሰን ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን እንደሌላቸው በመጀመሪያ መቃወሚያነት አቅርቧል፡፡ 2ኛ አመልካችም የ 1ኛ አመልካች ስራ አስኪያጅ ከመሆኑ ውጪ በግል ክስ ሊቀርብበት እንደማይገባም አያይዘው ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለክሱ መነሻ የሆነው ውል በሱዳን ሃገር የተደረገና የሚፈጸም ከመሆኑ የተነሳ ከኢትዮጵያ ጋር ግኑኝነት ያለው መሆኑን ከሳሾች /ተጠሪዎች/ አላስረዱም በማለት የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳዩ ላይ አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችላቸው ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን የላቸውም የሚለውን የአመልካቾች መቃወሚያ ተቀብሎ የክስ ምገቡን በብይን ዘግቷል፡፡

ተጠሪዎች /ስር ከሳሾች/ በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 7 መሰረት የውጭ ሃገር ዜጋ ተከራካሪ በሆነበት ጉዳይ የፌዴራል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው በመግለጽ በአዋጁ አንቀጽ 11/2/ሀ መሰረት ጉዳዩ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ሊታይ ይገባል በማለት መዝገቡን መልሰንለታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በውጪ ሃገር የተቋቋመ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ የሌለው በሆነበት ሁኔታ ክርክሩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሊዳኝ ይገባል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር እንዲቻል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ታዟል፡፡

የተጠሪዎች ጠበቃ የፍርድ ቤቱን መጥሪያ ተቀብለው ነገር ግን መልስ ባለማቅረባቸው በዚሁ ታልፎ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡

እንደመረመርነውም በዚህ ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ነጥብ የቀረበውን ክስ አከራክሮ ለመወሰን የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ስልጣን አላቸውን? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሰረቱ የፍርድ ቤቶች ስልጣን በሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ተከፍሎ የሚታይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይኸውም ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን /judicial jurisdiction/ ፣ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን /material jurisdiction/ እና የግዛት ክልል ስልጣን /local jurisdiction/ ናቸው፡፡ የስረ ነገር እና የግዛት ክልል የዳኝነት ስልጣን የሚወሰነው በሐገራዊ /ብሔራዊ/ ሕጎች /domestic or national lows/ ሲሆን በዋናት በስነ ስርዓት ሕጎች አልፎ አልፎም በመሰረታዊ ሕጎች ተደንግጎ እናገኛለን፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን ምንጭ በዋናነት ዓለም ዓቀፍ የግለሰብ ሕግ /private internal low/ ሲሆን ከዚህ አልፎም በሃገራት መካከል የሚደረጉ የሁለትዮሽ ወይም የሶስትዮሽ ውሎች አልያም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኙ ሕጎች ወይም ልማዶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዘርፍ ኢትዮጵያ ራሱን የቻለ ዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ ባይኖራትም በተለያዩ ሃገሮች የዳበረ ልምድና ተቀባይነት ያገኙ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ለጉዳዮች እልባት ሲሰጥ እንዳለ ይታወቃል፡፡

እስከ አሁን የዳበረ ልምድና በዘርፉ ከተደረጉ ጥናቶችና ጽሑፎች መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ሃገር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን አለው ወይ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መሰረት ተደርጎ የሚወሰደው ከተከሳሹ ጋር ያለው ግንኙነት መለኪያዎችን በመጠቀም ነው፡፡ እነዚህም ከተከሳሽ ሰው /action impersonal/ የሕግ ይሁን የተፈጥሮ ሰው በዜግነት ወይም በመደበኛ መኖሪያው ከፍርድ ቤቱ ጋር ያለው ቁርኝት፣ ለክሱ ምክንያት የሆነው ድርጊት /Act/ ውል ይሁን ከውል ውጪ የተፈጸመበት ሐገር ቁርኝት፣ ለክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት /property/ ተንቀሳቃሽ ይሁን የማይንቀሳቀስ የሚገኝበት አሊያም የተከሳሹ ፈቃደኝነት /consent/ መኖር አለመኖር መለያዎች ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ በጉዳዩ ላይ የሚነሳ ብሔራዊ ጥቅም ወይም በጉዳዩ ላይ የሚነሳ ብሔራዊ ጥቅም ወይም ፖሊሲ /national interest or public policy/ ጉዳይ መኖሩ ሲረጋገጥ ክሱ ከቀረበበት ሃገር ፍ/ቤት ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን አለው ሊባል ይችላል፡፡

ከዚህ አንጻር ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡት በሱዳን ሃገር የተደረገና የተፈጸመው ውልን መሰረት በማደረግ የገንዘብ ክፍያ ውሳኔ እንዲሰጥ ዳኝነት ስለመጠየቃቸው ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ የውል አፈጻጸም ላይ ከኢትዮጵያ ፍ/ቤች ጋር የሚያስተሳስር ምክንያት ስለመኖሩ ተጠሪዎች አላስረዱም፡፡ ከላይ በዝርዝር ከተመለከትናቸው ምክንያቶች አንድም ምክንያት ከኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጋር የሚያስተሳስር ምክንያት መኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን አላቸው የሚባልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን ክርክር ላይ እልባት ሳይሰጥ የስረ ነገር ስልጣን ላይ ተመርኩዞ አዋጅ ቁጥር 25/88 መሰረት አድርጎ መወሰኑ በስር ፍ/ቤት ያከራከረውን ጭብጥ በአግባቡ ባለማገናዘብ የተወሰደ አቋም እንደሆነ ተገንዝበናል ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ብይን በመሻር የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁ አግባብ ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 104120 በ 08/03/08 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 130398 በ 01/11/06 ዓ.ም የሰጠው ብይን ጸንቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.119435

ሰኔ 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች- ዓሊ መሀመድ
ተኽሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ
ቀነአ ቂጣታ
ፀሃይ መንክር

አመልካች - አቶ አብዱልቀኒ አብዱራህማን - ጠበቆች ግርማ አለሙና አሰፋ አሊ ቀረቡ
ተጠሪዎች - 1ኛ. አቶ ዳንኤል ወ/ሃዋሪያት - ጠበቃ ግርማ ከበደ ቀረቡ
2ኛ. የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ የይዞታ አስተዳደር ሽግግር ጊ/አገ/ፕ/ጽ/ቤት -
የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በተጠሪዎች መካከል የተደረገ የሊዝ ውል እንዲፈርስ የቀረበን የዳኝነት ጥያቄ የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- መንግስት በውጭ ሃገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በፈጠረው ዕድል የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ተቋቁሞ በአ/አበባ ከተማ ን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ክልል ለማህበሩ አባላት ቤት መስሪያ ቦታ ተሰጥቷል፤ በዳሸን የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አባል የነበሩት 1ኛ ተጠሪ ከማህበሩ ተሰናብተው በምትካቸው አመልካች በአባልነት ተተክቻለሁ፤ የአሜሪካን ዶላር 5,000.00 (አምስት ሺህ) አሜሪካን ሃገር ለሚገኘው ኤምባሲ ክፍያ ፈፅሜያለሁ፤ አመልካች በማህበሩ ስለመተካቱም ማህበሩ ጥቅምት 3 ቀን 1996 ዓ.ም ለአ/አበባ መስተዳድር የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የሊዝ አፈፃፀም መምሪያ በጻፈው ደብዳቤ አሳውቋል፤ የማህበሩ ሥራ አስፈጻሚ አመልካች በአባልነት ስለመተካቱ በዩ ኤስ አሜሪካ ለኢትዮጵያ ኤምባሲ በማሳወቁና ልዩ ልዩ ቃለጉባኤዎችን በማስተላለፉ ኤምባሲው ጥቅምት 25/1996 ዓ.ም ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጉዳዮች ዳይሬክተር በፃፈው ደብዳቤ ገልጿል፤ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ በማህበሩ ያሉ በማስመሰል ከራሳቸው አንዳችም ገንዘብ ሳይከፍሉ ከሳሽ በከፈሉት የቅድሚያ ክፍያ በመጠቀም ከክፍለከተማው የመሬት ልማትና አስተዳደር መምሪያ ጋር የሊዝ ውል በመዋዋል የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) አላግባብ ወስደዋል፤ ስለሆነም 1ኛ ተከሳሽ ከማህበሩ ያልተሰረዙ እና ቅድሚያ ክፍያ የከፈሉ በማስመሰልና በማሳሳት በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 10(10)፣ 13(2) እና (3)፣ 14 (2)(ሐ)፣ 15(1) ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት መብት ሳይኖራቸው ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ታህሳስ 19 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉት የመኖሪያ ቤት ሥራ ቦታ ሊዝ ውል እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ከሳሽ የማህበሩ አባልም ተተኪም አይደሉም፤ ተከሳሽ የማህበሩ መስራች ስለሆንኩ ማህበሩ ለሊዝ አፈጻፀም መምሪያ በላከው ዝርዝር ውስጥ ስሜ በተ.ቁ 11 ተመዝግቦ ይገኛል፤ በአዋጁ መሰረት 2ኛ ተከሳሽ መሬቱን ከነካርታው አስረክቦኝ የሊዝ ውል ተፈራርመን ሥራ ጀምሬያለሁ፤ ብር 123,238.33 የሊዝ ክፍያም ከፍያለሁ፤ 1ኛ ተከሳሽ በራሱ ፈቃድና የጽሁፍ አቤቱታ ከማህበሩ የለቀቀበት ነው ተብሎ የቀረበው ማስረጃ ጽሁፍም ሆነ ፊርማው የኔ አይደለም፤ እኔ ስለመሰረዜ እና ከሳሽ ተተኪ ስለመሆኑ የተያዘው ቃለ ጉባኤ በተደረገበት ስብሰባ ላይ ስላልተጠራሁ አልተገኘሁም፤ በጽሁፍ ፊርሜ አባልነቴን ለቅቄያለሁ አላልኩም ስለሆነም ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዞ ስላላቀረበ በፅሁፍ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከተማ አስተዳደሩ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ እንዲሁም የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና ሌሎች ሰነዶችን ከማህበሩ አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በ1ኛ ተከሳሽ ምትክ አመልካች አባል እንዲሆኑ የወሰነ መሆኑ ታውቆ አስፈላጊው ፎርማሊቲ እንዲፈፀም ለሊዝ አፈጻፀም መምሪያ ከጻፈው ደብዳቤ ባለፈ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የተሰጠ ውሳኔ እና ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርቦ የፀደቀ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ የለም፤ 1ኛ ተከሳሽ በማህበሩ አልቀጥልም ሲሉ ገልጸዋል ተብሎ በተያዘው ቃለ ጉባኤ ላይ ያለው ፊርማ ስለተካደ በፎረንሲክ ተመርምሮ ፊርማው የ1ኛ ተከሳሽ አለመሆኑ ተረጋግጧል፤ ስለሆነም በተከሳሾች መካከል የተፈፀመው የሊዝ ውል እንዲፈርስ ሲሉ ከሳሽ ያቀረቡት አቤቱታ ወድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሥር ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ ተፈጸመ የሚሉትን የህግ ስህተት በመዘርዘር ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ማመልከቻው ተመርምሮ አመልካች የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንጻር ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ለሰበር ችሎቱ በተያዘው ጭብጥ መሰረት ፍሬ ጉዳዩ ከመታየቱ በፊት አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ የከተማው ፍርድ ቤቶች አከራክረው ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን ያላቸው መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሻሽሎ የወጣው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 የከተማው ፍርድ ቤቶች ስለሚኖራቸው የዳኝነት ሥልጣን የሚደነግግ ሲሆን በተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና (መ) ሥር የከተማውን መሪ ፕላን አፈጻፀም የሚመለከቱ የይዞታ ባለመብትነት፤ የፈቃድ አሰጣጥ ወይም የቦታ አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች፤ እንዲሁም የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት (ተቋማት) የሚገቧቸውን አስተዳደራዊ ውሎች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዩችን በተመለከተ የፍትሃብሄር የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ ከማህበሩ ያልተሰረዙ እና ቅድሚያ ክፍያ የከፈሉ በማስመሰልና በማሳሳት በአዋጅ ቁጥር 147/1991 መሰረት መብት ሳይኖራቸው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የመኖሪያ ቤት ሥራ ቦታ ሊዝ ውል እንዲፈርስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ይህ ክስ ተጠሪዎች ያደረጉትን ውል መሰረት ያደረገ ቢሆንም ክሱ የከተማውን መሪ ፕላን አፈጻፀም የሚመለከት የይዞታ ባለመብትነት፤ ከፈቃድ አሰጣጥ ወይም የቦታ አጠቃቀም ጋር ያልተያያዘ ሲሆን አስተዳደራዊ ውል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በከተማው ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ሥር የሚወድቅ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የሊዝ ውል እንዲሰረዝ የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄን በተመለከተ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባው መሆኑን የሚደነግግ በግልጽ የተመለከተ ህግም የለም፡፡ ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት በሰ/መ/ቁ 77175 ፣ 57435 እና ሌሎችም መዛግብት የሰጠው ውሳኔም ይህን የሚያሳይ ነው፡፡

ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች የማህበራት አዋጅ ከሚሰጠው መብት ጋር በማያያዝ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የተደረገው የሊዝ ውል እንዲፈርስ ያቀረቡትን ክስ ተቀብሎ በማከራከር ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን ተቀብሎ ለመዳኘት በህግ ባልተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በመሆኑ፤ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር የተመለከቱ ፍርድ ቤቶችም ይህን ሳያርሙ ማለፋቸው የህግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05435 ጥር 25 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመ/ቁ 2335 መጋቢት 11/2007 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ፤ እንዲሁም የከተማው ሰበር ችሎት በመ/ቁ 23655 ነሃሴ 8/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉምሩክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ. 111960

ሕዳር 06 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናየት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ዓ/ህግ - አልቀረበም

ተጠሪ፡ ሰይፈ አበበ ንጉሴ - በሌለበት ታይቶ የተወሰነ በመሆኑ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ተከሳሽ (ተጠሪ) አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 በመተላለፍ የኮንትሮባንድ እቃ የጉምሩክ ስርዓት ያልተፈጸመበት መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ እያለበት 21 ጆሪካን ዘይት ቀረጥና ታክስ መጠኑ በአጠቃላይ ብር 6025.45 (ስድስት ሺህ ሃያ አምስት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም) የሆነ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ሸንት ቤት ክፍል ውስጥ ተከማችቶ እጅ ከፍንጅ ስለተያዘ የኮንትሮባንድ እቃ ይዞ በመገኘት ወንጀል ፈጽሞ ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ፍቃድ እያለኝ ከእኔ ላይ የተያዘው ስለሆነ ህጋዊ ነኝጥፋት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ከሳሽ የአሁኑ አመልካች የሆነው ዐቃቤ ህግ ሁለት ምስክሮችን ያሰማ ሲሆን ተከሳሽም ሁለት መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አስመስክሯል፡፡ የጽሁፍ መከላከያ ማስረጃ በቀን 30/01/2004 ዓ/ም የተሰጠ እስከ 2007 ዓ/ም የታደሰ የምግብ ዘይት የንግድ ፈቃድ ተከሳሽ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽን (የአሁኑ ተጠሪን) ተከላክሏል በማለት በወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 149(2) መሰረት በነጻ እንዲሰናበት የአሁኑ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ በወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 195(1) መሰረት በመ/ቁ.200935 በቀን 01/07/2007 ዓ/ም ዘግቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡-

1. የስር ፍርድ ቤቶች በጅምላ ተጠሪው የታደሰ የንግድ ፍቃድ መኖሩን በማረጋገጡ ብቻ የኮንትሮባንድ ወንጀል ሃላፊነት ያድናል ማለት መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ነው፣
2. የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 መሰረት ማንኛውም ስሪት ሃገሩ የውጪ የሆነ እቃ ቀረጥና ታክስሳ ይከፈልበት በነጻ ዝውውር እንደማይለቀቅ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪው ከኮንትሮባንድ ወንጀል ሃላፊነት ነጻ ለመሆን ለእቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የእቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) የማቅረብ ህጋዊ ግዴታ እያለበት የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ታክስ ከፍሎ ንግድ ፍቃድ አወጥቷል በማለት በነጻ ማሰናበታቸው የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትዕዛዝ ተሰጥቶ አመልካች ተጠሪን ፈልጎ ያለማግኘቱን ገልጾ ጥሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ በዚሁ መሰረት ሀምሌ 6 ቀን 2007 ዓ/ም በታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ ስላልቀረበ በሌለበት ታይቶ እንዲወሰን ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

   የክርክሩ ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ጉዳዩን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፤ አመልካች ካቀረበው አቤቱታ እንዲሁም አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም በተጠሪ መኖሪያ ቤት ውስጥ በሚገኘው ሸንት ቤት ውስጥ በክሱ የተጠቀሰው 21 ጆሪካን ዘይት ተይዟል፡፡ በክሱ ውስጥ የተጠቀሰ መጋዘን እየታደሰ ዘይቱ አዲስ ሸንት ቤት ውስጥ ከሌሎች የሱቅ እቃዎች ጋር መገኘቱን የከሳሽም ሆነ የተከሳሽ ምስክሮች በተመሳሳይ ሁኔታ መስክረዋል፡፡ ተከሳሽ (ተጠሪ) በ2004 ዓ/ም የተሰጠ የዘይት ንግድ ፍቃድ እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ የታደሰውን ማቅረቡ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጧል፡፡ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ተከላክሏል በማለት በነጻ አሰናብቷል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 መሰረት ተጠሪው ከተከሰሰበት ወንጀል ሃላፊነት ነጻ ለመሆን ለእቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የዕቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) የማቅረብ ህጋዊ ግዴታ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ለተጠሪው የዘይት ንግድ ፈቃድ አለው ከመባሉ በስተቀር ዘይቱን ከማንና ከየት እንደገዛ እንዲሁም ለገዛበት ዘይት የጉምሩክ ቀረጥና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ታክስ መክፈሉን የሚያስረዳ የእቃው ጉምሩክ ዲክለራሲዮን (ሰነድ) ተጠሪ አቅርቦ አላረጋገጠም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ተጠሪ ተከላክሏል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሆኖም ግን አከራካሪ ሆኖ የታየው ተጠሪ በተከሰሰበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 “ህገ ወጥ እቃዎች ይዞ ስለመገኘት” ተብሎ የተደነገገው ድንጋጌ ይህን አዋጅ በተካው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ ወንጀል ሆኖ ተደንግጓል ወይስ አልተደነገገም? የሚለው ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ አልተደነገገም፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 168 የተደነገገ ነው፡፡ “የኮንትሮባንድ ወንጀል” በሚል ነው፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የተደነገገ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 የተደነገገው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ካልተደነገገ ህጋዊ መፍትሔ (legal remedy) ምንድነው? የሚለው ምላሽ ሊያገኝ ይገባል፡፡ ይህ አዋጅ ግን ይህንን ጥያቄ የሚመልስ የህግ መርህ አይደነግግም፡፡ በዚህ ጊዜ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት የተደነገገው መሰረታዊ መርህ እንዲሁም በወንጀል ህጉ በመርህነት የተደነገገው ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በሌላ አነጋገር በኢፌዲሪ ህገመንግስትና በወንጀል ህግ ከተደነገገው መሰረታዊ መርህ አንጻር ታይቶ መተርጎም ይኖርበታል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22 የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 5 በተመሳሳይ መልኩ ደንግጎታል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22(2) ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኃላ የወጣ ህግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል በማለት ተደንግጓል፡፡ በወንጀልህግአንቀጽ 5(3) የተሻረው ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከሰሰም ሆነ ሊያስቀጣ አይችልም፤ ክሱም ተጀምሮ እንደሆነ ይቋረጣል ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የፈጸመው ድርጊት ምንም እንኳን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 ላይ ወንጀል ሆኖ የተደነገገ ቢሆንም በዚህ አዋጅ ምትክ በተተካው አዋጅ ቁጥር 859/2006 ወንጀል ሆኖ አልተደነገገም፡፡ ስለዚህ በኢፌዲሪ ህገመንግስት እና በወንጀል ህጉ በተደነገገው መሰረታዊ መርህ አንጻር ሲደመደም ተጠሪ ጥፋተኛ ተደርጎ ቅጣት የሚወሰንበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 44610 በቀን 22/04/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 200935 በቀን 01/07/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ከላይ በፍርድ ሀተታው የተገለጸውን የኢፌዲሪ ህገመንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ መሰረት ያደረገ ባይሆንም በውጤት ደረጃ ግን ልዩነት ስለሌለው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 195(2) (ለ) (2) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 133773

ሐምሌ 14 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ተክሌ ፈረጃ ጋዲሳ ጠበቃ ሳሙኤል ኤፍሬም ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢ/ያ ገ/ ጉ/ ባለስልጣን የመርካቶ ቁ.1መካከለኛ ግብር ከፋዬች ቅርንጫፍ ፅ/ቤት አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንግድ ሥራ ግብር ክፍያን በሚመለከት የአሁን አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረቡትን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡አመልካች ለግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ያቀረቡት ቅሬታ ይዘት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በመጋዘን ማከራየት ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ መሆኑን፤በ2006 ዓ/ም ግብር ዘመን ገቢውን በመዝገብ በመያዝ እና በማሳወቅ የሂሳብ መዝገብ አቅርቤ እያለ ሳያጣራ ከግብር/ ታክስ አወሳሰን ስርአት ውጪ ከተያዘብህ ያነሰ አመታዊ ሽያጭ ነው ያሳየኸው በሚል ብቻ ውድቅ በማድረግ የወሰነበትን የቀን ገቢ ግምቱን ሳይገልፅልኝ ታክሱን በግምት በወሰንኩት ልትከፍል ይገባል በማለት ወስኗል ፡፡ ገቢየን የማስበስበው በተጠሪ በታወቀና ራሱ አዞ ባስገዛኝ በሂሳብ መመዝገቢያ ማሽን ሆኖ ባለበት እንዲሁም መብራት ሲጠፋ እና በተለያየ ምክንያት የማይሰራ ቢሆን እንኳን ለተጠሪ በማሳወቅ ራሱ በፈቀደልኝና ባወቀው ደረሰኝ የሰበሰብኩትን ገቢየን መዝገብ በመያዝ አሳውቄ እያለሁ ይህን ሁሉ እወነታ በማለፍ ድርጅቱን በግንባር አይቶ የገመተበትን ጊዜ ሳይገልፅ የወሰነው ከአወሳሰን ስርአት ውጭ ነው ፡፡ በሌላ በኩል የቀን ገቢያቸው ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር) መሆኑ አምነው ፈርመዋል በማለት የገለፀው እኔ በወቅቱ በቦታው አልነበርኩም የነበረው ልጄ አስፈራርተውና ተቆጥተው ያስፈረሙት መሆኑ ገልፃልኛል ፡፡ ስለሆነም የምስራበት መጋዘን እጅግ በጣም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አነስተኛ በመሆኑ ጉባኤው በአካል የስራ እንቅስቃሴውን ተመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሰው ተጠሪው አላግባብ የጠየቃቸውን ክፍያ ጉባኤው ውድቅ እንዲያደርግላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪው ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሰጠው መልስ የአመልካች ለ2006 ዓ/ም የግብር ዘመን ያቀረቡትን የሂሳብ መዝገብ መርካቶ መሃል ካላቸው መጋዘን ማከራየት ስራ ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛና ሊቀራረብ የማይችል ከመሆኑም በላይ ግብር ከፋዩ እራሳቸው ከሰጡት የቀን ገቢ መረጃ እንኳን በጣም የራቀ መረጃ ስላቀረቡ ተጠሪ በህግ መሰረት እና ባለው መረጃ መሰረት በማድረግ መወሰኑ ተገቢ ነው ፡፡ የአመልካች መጋዘን ያለበት የስራ ቦታ ከፍተኛ የገበያ ቦታ መሃል መርካቶ ኪኔዲ ህንፃ አጠገብ ሰፊ እቃ የማስቀመጥ አገልግሎት ፈላጊና ተጠቃሚ ያለበት ላይ በመሆኑ የቦታው ስፋትም 65 ካ.ሜ.የሆነ ትንሽ ሱቅ ተከይተው የሚሰሩ ባለሱቆች ሱቆቻቸውን ለማሳያ ብቻ እየተገለገሉ እቃዎቻቸውን በማስቀመጥ የሚጠቀሙበት ነው እራሳቸው ጥቅምት 25 ቀን 2007 ዓ/ም ለቀን ገቢ ገማቾች በሰጡት መረጃ ላይ በቀን 1,000 (አንድ ሺህ ብር) አገኛለሁ ያሉትን በመውሰድ ቢታይ እንኳን የአመት ሽያጭ ብር 365,000 (ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ብር) ነው፡፡ ምንም ገቢ አላገኘሁም ቢሉ እንኳን ያመኑዋቸው አራት ወራት ቢሰላ የሚመጣው ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ሆኖ ሳለ ባቀረቡት ሂሳብ መዝገብ ላይ አገኘሁ ያሉት ሽያጭ ብር 89,100 (ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ) ሲሆን በዚህም በቀን 244.11(ሁለት መቶ አርባ አራት ብር ከአስራ አንድ ሳንቲም) በመሆኑ የአመልካች የሂሳብ መዝገብ እምነት ስላጣንበት ውድቅ አድርገነዋል ፡፡ የቀን ገቢ ግምቱ የተከናወነው በድብቅ ሳይሆን ገማች ኮሚቴ ድርጅታቸው ድረስ በመሄድ ይግባኝ ባይ በሰጡት መረጃ መሰረት በማድረግ የንግድ ቤቱ አያያዝና የመጋዘኑ ስፋት፣እቃ የመያዝ አቅም ና የአካባቢውን ሁኔታ በዚሁ ተግባር የተሰማሩ ብዙ ነጋዴዎች ውሱን መሆናቸው በማየጥ አመልካች በሰጡት በቀን ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር) ላይ የተወሰነ በመጨመር ብር 1,400 (አንድ ሺህ አራት መቶ ብር) በማድረግ የተገመተ መሆኑን በመጥቀስ አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች ከቀን ገቢ ግምት ግማሽ በታች በሆነ መልኩ በሂሳብ መዝገብ ያቀረቡትና ያሳወቁት ገቢ በበቂ እና አሳማኝ ምክንያቶች የተደገፈ ሆኖ ስላላገኘነው መልስ ሰጪ በ2006 ዓ/ም ግብር ዘመን የቀን ገቢ ግምት ብር 1,400 (አንድ ሺህ አራት መቶ) ብር በመያዝ ግብርና ታክስ የወሰነበት አግባብ የሚነቀፍ አይደለም በማለት አፅንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራቀኙን አከራክሮ ውሳኔውን አጽንቶታል፡፡በመቀጠል አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-አመልካች የ2005 ዓ/ም የግብር ዘመን በተመሳሳይ ባሰራሁት የሂሳብ መዝገብ በባለሞያ ሂሳብ መዝገብ ተሰርቶ የቀረበውን ይህንኑ በህጉ በተጣለበት ግዴታ ሳይመረምር የ2006 ዓ/ም የግብር ዘመን በተመለከተ በባለሞያ ሂሳብ መዝገብ ተሰርቶ የቀረበውን ተጠሪው መስሪያ ቤት በሂሳብ መዝገብ የቀረበውን አመታዊ ሽያጭ ከቀን ገቢ ግምት ያነሰ ነው፣ በሚል ምክንያት አልቀበልም ብሎ በቀን ገቢ ግምት መወሰኑ ከአዋጁ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 69 እና ከ64 ጀምሮ ካሉት ድንጋጌዎች የወጣ በሆነ ሁኔታ በራሱ ግምት እንድከፍል መወሰኑ ያለአግባብ ነው፡፡ በመሆኑም ለግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ያቀረብኩት አቤቱታ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው ፡፡ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል ፡፡ በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነጥብም ተጠሪው ባቀረበው ግምት መሰረት አመልካች እንዲከፍሉ የተወሰነው የግብር መጠን በአግባቡ ነው ?ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 69 ግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ እና ሰነድ ካልያዘ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለስልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላስታወቀ እንደሆነ ግብር አስገቢው ባለስልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወስን እንደሚችል ይደነግጋል፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በአመልካች ላይ የቀን ገቢ ግምትን መሠረት የግብር ማስታወቂያ የሰጣቸው አመልካች የ2006 ዓ/ም የግብር ዘመን በተመለከተ በባለሞያ ሂሳብ መዝገብ ተሰርቶ የቀረበ ቢሆንም ተጠሪው መስሪያ ቤት በሂሳብ መዝገብ የቀረበውን አመታዊ ሽጭ ከቀን ገቢ ግምት ያነሰ ነው በሚል ምክንያት አልተቀበላቸውም፡፡ አመልካች ከዚህ በፊት ራሳቸው ባሳወቁት የቀን ገቢ ግምት ብር1,000 (አንድ ሺህ ብር) ነው በማለት የገለፁ ሲሆን በሂሳብ መዝገባቸው ያሳወቁት አመታዊ ገቢ ብር 89,100 (ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ) መሆኑን በዚሁ መሰረትም በዚህም በቀን 244.11(ሁለት መቶ አርባ አራት ብር ከአስራ አንድ ሳንቲም) በመሆኑ ፣አመልካች የአመት ገቢያቸው ከግማሽ በታች ያሳወቁ በመሆናቸው ተረጋግጦ ያቀረቡት የሂሳብ መዝገብ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ሂሳብ መዝገብ ነበረኝ በባለሞያም አሰርቼ ያቀረብኩት ትክክለኛ ገቢየ ነው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም አመልካች ከሚሰሩበት መጋዘን ስፋት እንዲሁም መጋዘኑ ለእቃ ማከማቻነት በጣም አስፈላጊ በሆነ ቦታ ላይ በመሆኑ ያቀረቡት የቀን ገቢ እምነት የማይጣልበት ስለመሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባለው የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ተረጋግጧል ። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 112 መሰረት ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሕግ ስሕተትን የማረም ሥልጣን እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን የለውም ። ስለሆነም በአመልካች ላይ የተጣለው የግብር መጠን በሕጉ መሰረት መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባለው የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀቡት አቤቱታ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም ። በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመ.ቁጥር 033/08 ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 25576 ሃምሌ 27 ቀን 2008 ዓ/ም እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 25816 መስከረም 10 ቀን 2009 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል።
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው·ል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117036

ሕዳር 12 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተሽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ፀጉብርሃን ትራዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ኮሎኔል ይትባረክ አማረ - ከጠበቃ ኃይለስላሴ ገ/መድህን ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የሽያጭ ውሉን በወቅቱ ባለመፈፀሙ በኃላፊነት ይጠየቃል በማለት አመልካች የመኪና ሽያጭ ውሉን ባለመፈፀሙ ተጠሪ ላይ የደረሰበት ጉዳት ተጣርቶ እንዲቀርብ በማለት የሰጡት ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ /ከሳሽ/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡
2. ከሳሽ ለሰር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል፣ ከተከሳሽ ሁለት ተሽከርካሪዎችን ለመግዛት ተዋውሎ፣ የሁለቱን መኪኖች ዋጋ ብር 2,300,000 /ሁለት ሚሊዬን ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ገቢ አድርጌያለሁ፡፡ ተከሳሽ መኪኖቹን ውሉን ከተፈራረምንበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ማለትም እስከ ነሐሴ 27 ቀን 2006 ዓ.ም ሊያስረክበኝ የውል ግዴታ ገብቷል፡፡ ከሳሽም መኪኖቹ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሰጥቶኛል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ በውሉ መሠረት መኪኖቹን ያላስረከበኝ በመሆኑ፣ ከሳሽ የከፈልኩትን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ከሳሽ ከነሐሴ 27 ቀን 2006 ዓ.ም መኪኖቹን እረከባለው በሚል እምነት አንድ ተሽከርካሪ በወር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብር 3000 /ሶስት ሺህ ብር/ ሁለቱን በብር 6000 /ስድስት ሺህ ብር/ አከራይቼ አገኝ የነበረውን ጥቅም ስለቀረብኝና በዚህ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ብር 354,000 /ሶስት መቶ አምሳ አራት ሺህ ብር/ እንዲከፍልና ዕዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ በወር ብር 6000 /ስድስት ሺህ ብር/ እየተሰላ ካሣ እንዲከፍል፤ የወሰደውን ገንዘብ ወለድ እንዲከፍልና፣ የገደብ መቀጮ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

3. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ለከሳሽ ሁለት መኪኖች ለመሸጥና የመኪኖችን ዋጋ ከሳሽ መክፈሉ የሚካድ አይደለም፡፡ ተከሳሽ ለከሳሽ መኪኖችን ለማስረከብ የተለያዩ ተግባራትን ከከሳሽ ሰራተኞች ጋር በመተባበር ሲፈፀም ቆይቷል፡፡ መኪኖችንም በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ ፈቃደኛ ነበር፣ ነገር ግን በመዝገብ ቁጥር 24172 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ.ም በመኪኖቹ ላይ የዕግድ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙን በመቃወም ተከሳሽ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቤ በመዝገብ ቁጥር 157145 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡ በመሆኑም በሽያጭ ውሉ መሠረት ያልተፈፀመው ተከሳሽ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ በመሆኑ ከሳሽ ለውሉ አለመፈፀም ተከሳሽ ኃላፊ እንዲሆንና ካሣ እንዲከፍል ለማለት ያቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ በሽያጭ ውሉ ውል አለመፈፀም ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ የሚያስቀጣ መሆኑ ከሳሽ ካሣ ይክፈለኝ በማለት የጠየቀው ተገቢ አይደለም የውሉና ሌሎች መከራከሪያዎችን በማንሳት መልስ ሰጥቷል፡፡

4. የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተከሳሽ ለከሳሽ ከሸጣቸው ሁለት መኪኖች መካከል የአንደኛው መኪና የሻንሲ ቁጥር lzz5elnd77n847969 እና የሞተር ቁጥር 131107038497 መሆኑ ከሳሽ ባቀረበው የሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ከከሳሽ ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በመሸጥ ሙሉ ዋጋውን የተቀበለበት የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተጠቀሰውን መኪና ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መኪና መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ተከሳሽ ለከሳሽ የሸጠውን አንደኛው መኪና የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ ተለይቶ የታወቀውን መኪና ለከሳሽ በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚያስችል መብት ሳይኖረው የፈፀመው የሽያጭ ውሉ በመሆኑ ለውሉ አለመፈፀምም ሆነ በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተከሳሽ ኃላፊነት አለበት፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሽ ብር 3000,000 /ሶስት ሚሊዬን ብር/ አስይዞ ዕግዱን በማስነሳት መኪኖቹን ለከሳሽ ማስረከብ እየቻለ ይህንን ያላደረገ በመሆኑ ለሽያጭ ውሉ ኃላፊ ነው በማለት ከሳሽ የከፈለውን የመኪኖቹን ዋጋ ከዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር እንዲመልስ በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍልና በውሉ አለመፈፀም ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በከሳሽ ላይ የደረሰውን ኪሳራ /ጉዳት ተጣርቶ/ እንዲቀርብ በማለት በመዝገብ ቁጥር 153576 ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ከፊል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

5. አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ከሸጣቸው ሁለት መኪኖች አንደኛው ቀደም ሲል ለአቶግደይ ገ/ዓዲቅ የሸጠው መሆኑን በመግለጽ ውሳኔ የሰጠው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ላይ የተመሠረተነው፡፡ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ሆነ ከአቶ ግደይ ገ/ዓዲቅ ጋር በተዋዋለው የመኪና ሽያጭ ውል ላይ የመኪና የሻንሲ ቁጥርና የሞተር ቁጥር አልጠቀሰም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 223፤አንቀጽ 137/1 እና አንቀጽ 256 መሠረት ያላቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመቀበል አመልካች አንደኛውን መኪና ለተጠሪ ያላስረከበው ቀደም ብሎ መኪናውን በሽያጭ ለሌላ ሰው ስለሸጠው ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የማስረጃ አቀራረብ ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ የሸጣቸውን ሁለት መኪኖች ለተጠሪ ሳያስረክብ የቀረው በባልና ሚስት ክርክር መነሻ መኪኖቹ እንዳይሸጡ እንዳይለወጡና ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፅግድ ትዕዛዝ በመስጠቱና የፅግድ ትዕዛዙን ለማስነሳት አመልካች ጥረት ቢያደርግም ጥረቱ ውጤት አልባ በመሆኑ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ስለገጠመው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የከፈለውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ውሣኔ ከሰጠ በኃላ የሽያጭ ውሉ ያለመፈፀሙ ተጠሪ ላይ ያደረሰውን ኪሳራ አመልካች የመሸፈን ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ተጠሪ ወሉን ያልፈፀመ ወገን ምንያህል ገንዘብ መክፈል እንዳለበት ውል ተዋውለዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት በውሉ የተገለጸውን የገደብ መቀጫ ማስከፈል ሲገባው ከገደብ መቀጫው አልፎ ለተጠሪ አመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

6. ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠ መልስ አመልካች ለተጠሪ ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገው የሽያጭ ውል ከሸጣቸው መኪናዎች ውስጥ የአንደኛውን የሻንሲና የሞተር ቁጥር በመግለጽ ለገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ያሳወቀ በመሆኑ ተጠሪ ከገዛቸው መኪናዎች ውስጥ የአንደኛው መኪና የሻንሲ እና የሞተር ቁጥር ተለይቶ የታወቀ ነው፡፡ ሆኖም አመልካች በተጠሪ ከሸጣቸው መኪናዎች ውስጥ ይህንን የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን ለይቶ ያሳለቀውን መኪና ቀደም ሲም ሲል ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ ውል ለአቶግደይ ገ/ዓዲቅ የሸጠውና ይህንኑ መኪና ለአቶግደይ ገ/ዓዲቅ ለማስረከብ የሚቻል መሆኑን ገልጾ የፃፈው ደብዳቤ የአመልካች ስራ አስኪያጅ በፈፀመው የማታለል ወንጀል ክስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበበት መሆኑንና አቶግደይ ገ/ዓዲቅ አመልካች የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀውን መኪና እንዲያስረክባቸው ከፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153390 ክስ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ጳጉሜ 5 ቀን 2006 ዓ.ም እና መስከረም 12 ቀን 2007 ዓ.ም የዕግድ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች መኖራቸውን ያወቅነው ክሱንና የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ለፍርድ ቤቱ ካቀረብን በኃላ በመሆኑ ማስረጃዎቹን የስር ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 መሠረት እንደናቀርብ ፈቃድ ጠይቀን በፍርድ ቤቱ ፍቃድ መሠረት ያቀረብናቸው የሰነድ ማስረጃዎች በመሆናቸው አመልካች የስር ፍርድ ቤት ከሥነ-ሥርዓት ሕግ ውጭ ማስረጃ እንደተቀበለ በመግለጽ ያቀረበው አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ሌላውን መኪና በተመለከተ አመልካች ብር 3000,000 /ሶስት ሚሊዬን ብር/ በማስያዝ ዕግዱን ማስነሳትና የውል ግደታውን መወጣት እየቻለ ይህንን አላደረገም አመልካች ውሉን ያልፈፀመው በፍርድ ቤቱ ዕግድ ምክንያት አይደለም ስለሆነም ውሉን ያልፈፀምኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም አመልካች የወሰደውን ገንዘብ ወለድ ተጠሪ በውሉ አለመፈፀም የደረሰበትን ኪሳራና በውሉ ላይ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ እንዲከፍል የተወሰነው በአገባቡ ነው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሰ አቅርቧል፡፡

7. ይኸ ሰበር ችሎት አመልካችና ተጠሪ በቃል ሊከራከሩባቸው የሚገቡ ነጥቦችን ሰኔ 22 ቀን 2008 ዓ.ም ለይቶ ለግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲደርሳቸው ካደረገና በተለያየ ምክንያት የቃል ክርክር ለማስማት የሰጠውን ቀነ ቀጠሮ ከተለወጠ በኃላ የቃል ክርክሩን የመጨረሻ ቀነ ቀጠሮ በሰጠበት ጥቅምት 24 ቀን 2009 ዓ.ም አመልካች ወኪል ወይም ጠበቃ ባለመቅረቡ የተጠሪን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ አመልካች ስለ ማስረጃ አቀራረብ ሥርዓትና ሌሎች ነጥቦች የቀረበውን የሰበር ክርክር ለማረጋገጥና ለማገናዘብ እንዲቻል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 153516 እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ መዝገቡን በትዕዛዙ መሠረት በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

8. ከስር የክርክር አመጣጥና ግራቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው ሁለት ገልባጭ መኪኖች ሽያጭ መሠረት ለተጠሪ የሚያስረክበው መሆኑን ገልጸየገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በዓፈው ደብዳቤ የገለፀውና ያሳወቀው የሻንሲ ቁጥር lzz5elnd77n847969 የሆነውና የሞተር ቁጥሩ 131107038497 የሆነውን መኪና ቀደም ብሎ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለአቶግደይ ገ/ዓዲቅ የሰጠውና ይህንኑ መኪና ለአቶግደይ ገ/ዓዲቅ ለማስረከብ እንደሚችል ገልጾ ደብዳቤ የፃፈበት መሆኑን በአጠቃላይ መኪናውን ለሁለት ሰው በመሸጥ ዋጋ የተቀበለበት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡

9. አመልካች ተጠሪ የሻንሲ ቁጥሩና የሞተር ቁጥሩ ተለይቶ የተገለፀው መኪና በሌላሰው የተሰጠ መሆኑን ተጠሪ የፍትብሔር ሥን-ሥርዓት ሕግ በሚደነግገው መሠረት የሰነድ ማስረጃዎቹን አላቀረበም በማለት ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታና ክርክር ተገቢነት መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እኛም የስር ፍርድ ቤቱች መዝገብ በትዕዛዝ በማስቀረብ ከሳሽ /ተጠሪ/ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የገለፀውን መኪና ቀደም ሲል ለአቶግደይ ገ/ዓዲቅ ይሸጠው መሆኑንና ይህንኑ መኪና ለአቶግደይ ገ/ዓዲቅ ለማስረከብ የሚችል መሆኑን ገልጾ ለገቢወችና ጉምሩክ ባለስልጣን ደብዳቤ ጽፎ እንደነበር የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃዎች ተጠሪ ክሱን ሲያቀርብ የማያውቃቸውና ያላገኛቸው መሆኑን በመግለጽ ፍርድ ቤቱ ሰነዶቹን በተጨማሪ ማስረጃነት ለማቅረብ እንዲፈቅድለት የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ /ተጠሪ/ ባቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ የማቅረብ ጥያቄ ላይ ተከሳሹ /አመልካች/ አስተያየቱን እንዲያቀርብ የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝና አባሪውን የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም የደረሰው መሆኑ በድርጅቱ ማህተም ካረጋገጠ በኃላ ተከሳሽ /አመልካች/ ከሳሽ /ተጠሪ/ ባቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ የማቅረብ ጥያቄ ላይ አስተያየቱን ባለማቅረቡ የስር ፍ/ቤት ከሳሽ በተጨማሪ ማስረጃነት ለማቅረብ ጥያቄ ያቀረበባቸው የሰነድ ማስረጃዎች የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 መሰፈርት የሚያሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ ማስረጃዎቹ እንዲቀረቡና ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዙ ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ብይን ከሰጠ በኃላ የሰነድ ማስረጃዎችን በመቀበል ለፍርድ በግብዓትነት የተጠቀመባቸው መሆኑን ተረድተናል፡፡

10. ይኸ ሰበር ችሎት በትዕዛዝ ካስቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 153516 እንደተረዳነው የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን ተጨማሪ ማስረጃዎች በተጨማሪ ማስረጃነት ከመቀበሉ በፊት አመልካች አስተያየት የመስጠትና የመከራከር መብቱን ጠብቆ አመልካች ዕድሉን ተጠቅሞ አስተያየቱን ባለማቅረቡ ይህንኑ ምክንያቱን በግልጽ በመዝገብ ላይ በማስፈር ትዕዛዝ ሰጥቶ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ሰነዶቹ በተጨማሪ ማስረጃነት ሊቀረቡ አይገባም የሚልበትን ምክንያት ለሥር ፍርድ ቤት ያላቀረበውን ክርክርና አስተያየት ለዚህ ሰበር ችሎት ማቅረቡ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ የማቅረብ ጥያቄ ውላይ አመልካች አስተያየትና ክርክር የማቅረብ መብቱን መጠበቁ ብቻ ሳይሆን ከሳሽ /ተጠሪ/ በተጨማሪ ማስረጃነት ለማቅረብ ጥያቄ ያቀረበባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 256 የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን ነጥብ በአግባቡ በመመርመር ማስረጃዎቹን ለመቀበል ብይን የሰጠ መሆኑን ተረድተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

11. ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ሲያቀርብ ተገቢውን ትጋት በማድረግ ሊያውቃቸውና ሊያገኛቸው የማይችላቸው ማለትም አመልካች ለተጠሪ የሸጠው መሆኑን ገልጾ ለአዲስ አበባ ቃሊቲጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቁጥር TB.TP11648114 ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀውን መኪና ቀደም ሲል አመልካች ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርጫፍ ጽ/ቤት ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መሆኑን ቁጥሩ TB.TB 1106114 ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን የገለፀውን መኪና መሆኑን ይህንን መኪና ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም አመልካች ለግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠ መሆኑ ገልፀው አቶግደይ ገ/ፃዲቅ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153390 ክስ ማቅረባቸውን በመጀመሪያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤት ጳጉሜ 4 ቀን 2006 እስከ መስከረም 9 ቀን 2007 የሚቆይ የዕግድ ትዕዛዝ መስጠቱንና መስከረም 9 ቀን 2007 ዓ.ም መኪናው ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የዕግድ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን የሚያሳዩ የሰነድ ማስረጃዎች እንደሆኑ ተረድተናል፡፡ እነዚህ በአመልካችና በሌላ ሶስተኛ ወገን እጅ የነበሩ ማስረጃዎች ተጠሪ ክስ ሲያቀርብ የማያውቃቸውና ሊያገኛቸው የማይችል ማስረጃዎች በመሆናቸው በስር ፍርድ ቤት የሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርቡ በማድረግ መርምሮና መዝኖ ውሳኔ የሰጠው የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት በመሆኑ በዚህ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታና ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

12. አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ባደረገው የመኪና ሽያጭ ውል በአመልካች የሸጠው የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀው አንደኛውመኪና አመልካች ቀደም ብሎ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሰጠው መሆኑንና አመልካች መኪናውን ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሰጠ መሆኑን ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን ጠቅሶ ለኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያሳወቀ መሆኑ የሕጉን ሥርዓት በመከተል ተጠሪ ባቀረባቸው ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ ተመልክተናል፡፡ ከላይ በዝርዝር እንደተገለፀው አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ የሁለት መኪናዎች ሽያጭ ውል መሠረት ሙሉ ዋጋውን የተቀበለበትና እስከ ነሐሴ 25 ቀን 2006 ዓ.ም ለተጠሪ ለማስረከብ የውል ግደታ የገባበት የሞተር ቁጥሩ 131107038497 እና የሻንሲ ቁጥሩ lzz5elnd77nb847969 የሆነው መኪና አመልካች ቀደም ብሎ ለሌላ ሰው የሸጠውና ለሌላ ሰው የሸጠውመሆኑንም ለገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ያረጋገጠው የመኪናውን ባለሀብትነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2273 ንዑስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 2 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2281 በተደነገገው መሠረት ለማስተላለፍ የማይችል መሆኑን እያወቀ የተዋዋለው የሽያጭ ውል ነው፡፡

13. ከዚህ አንፃር ሲታይ ከላይ የሞተርና ያሻንሲ ቁጥር የተገለፀውን መኪና በተመለከተ አመልካች በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በባልና ሚስት ክርክር ምክንያት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም የዕግድ ትዕዛዝ በመስጠቱ ምክንያት ነው በማለት አመልካች የማያቀርበው ክርክር በማስረጃ የተረጋገጡትን ኩነቶች /ፍሬነገሮች/ መሰረት ያደረገ አይደለም አመልካች ለተጠሪ ከሸጣቸው መኪናዎች ውስጥ ሲታይ የሞተር ቁጥር የሻንሲ ቁጥር የተጠቀሰውን መኪና ሙሉ የባለሃብትነት መብት ለተጠሪ ለማስተላለፍ የማይቻልበት የሶስተኛ ወገን መብትና ጥያቄ በመኪናው ላይ ያለመሆኑን ተረጋግጧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ባይኖር ወይም የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቶ ቢሆንም አመልካች በሽያጥ ውሉ መሰረት የመኪናውን ሙሉባለሀብትነት ሊያስተላልፍ እንደማይችልና መኪናውን በቀዳሚነት ገዝቼ ዋጋ ከፍየበታለሁ የሚለው አቶ ግደይ ገ/ዓዲቅ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ያሳገደው መሆኑን ፣የአመልካች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ መኪናውን ለሌላ ሰው ከሸጠ በኃላ ያንኑ መኪና ለተጠሪ መሸጥ የማታለል ተግባር የፈፀመ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል ፡፡

14. ይህም አመልካች የተጠሪን መብት በሚነካ ጉድለት ምክንያት የሞተርና የሻንሲ ቁጥር የተገለፀልን መኪና መኪናውን ከአመልካች ቀድሞ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ/ም በተደረገው ውል ከገዛው አቶ ግደይ ገ/ዓዲቅ መብትና ጥያቄ ነፃ አድርጎ ለተጠሪ ሊያስረክበው እንደማይችል ዕያወቀ የሸያጭ ውሉን ከተጠሪ ጋር በመዋዋሉ ምክንያት ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል ተጠሪ ውሉን የተዋዋለው መኪናውን ለሌላ ሰው አመልካች የሸጠው መሆኑን ሳያውቅ በመሆኑና አመልካች የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣና ሊወጣ እንደማይችል እያወቀ የፈፀመው የሽያጭ ውል በመሆኑ ተጠሪ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ፣ ተጠሪ የተቀበለውን የመኪናውን ዋጋ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲመለስለትና አመልካች መኪናውን በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ያደረሰበት ኪሣራ እንዲከፍል ያቀረበው ጥያቄ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝቶታል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

15. ከዚህ አንፃር አመልካች የሞተርና የሻንሲ ቁጥር የተገለፀውን መኪና ሙሉ ባለሀብትነት ለተጠሪ ሊያስተላልፍ እንደማይችልና መኪናውን ለሌላ ሰው አስቀድሞ የሸጠው መሆኑን ፅያወቀ ከተጠሪ ጋር የመኪና ሽያጭ ውል በመዋዋል የመኪናውን ሙሉ ዋጋ ከተቀበለ በኃላ የመኪናውን ሙሉ ባለመብት ለተጠሪ ለማስተላለፍ የማይችል በመሆኑ ምክንያት የሽያጭ ውል ያፈረሰው በተጠሪ ጥፋት ምክንያት መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ከተጠሪ የወሰደውን ብር 1,150,000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር) ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ፣ ውሉን ባለመፈፀሙ በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) እና ውሉ ባለመፈፀሙ በተጠሪ ላይ የደረሰበት ኪሣራ ተጣርቶ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከላይ የገለፅናቸውን ስለ ሽያጭ ዉሉ የተደነገጉትን ልዩ ድንጋጌዎች ማለትም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀጽ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

16. አመልካች ከተጠሪ ጋር ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ/ም በተዋዋለው ውል ያሸጠለት ሌላውን አንድ መኪና በተመለከተ በባልና ሚስት ክርክር መነሻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም የፅግድ ትዕዛዝ ባይሰጥና የፅግድ ትዕዛዙን ለማስነሳት አመልካች በይግባኝ አቅርቦ የፅግድ ትዕዛዝ በይፀናበት በወሉ መሰረት ለመፈፀም የሚያስችለው ሌላ ምክንያት የሌለው መሆኑ የስር ፍ/ቤትና በውሳኔው ካሰፈራቸው ፍሬ ነገሮች ለመረዳት ይቻላል የሥር ፍርድ ቤት አመልካች መኪናውን ለተጠሪ ባለማስረከቡ አላፊነት አለበት ያለው የፌዴራል የመጀሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የፅግድ ትዕዛዝ አመልካች ብር 3,000.000 (ሶስት ሚሊዮን ብር) በሚያሲያዝ አስነስቶ መኪናውን ለተጠሪ ለማሰረከብ የማልችልበት ሁኔታ ነበር በማለት ነው ሆኖም የስር ፍርድ ቤት በወቅቱ የባንክ ሂሳቡን በነፃነት ለማንቀሳቀስና ብር 3,000.000 (ሶስት ሚሊዮን ብር) የባልና የሚስት ክርክር ሲያይ የነበረውና የፅግድ ትዕዛዙን ለሰጠው ፍርድ ማስያዝ አቅም እና ችሎታ የነበረው ለመሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረቡለት ማስረጃ ስለመኖሩና ስለመረጋገጡ በውሳኔው አላሰፈረም፡፡

17. ይህም አመልካች ለተጠሪ የሰጠውን ሌላውን አንድ መኪናን በተመለከተ በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በአመልካች ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ሳይሆን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ለ/ መሰረት አመልካች በገባው የውል ግዴታ መሰረት መኪናውን ለተጠሪ ሆነ ለሌላ ሶስተኛ ወገን እንዲያስተላለፍ ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክልከላ የተደረገበት ወይም የፅግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት በመሆኑ ምክንያት ለመሆኑ የሥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን አንድ መኪና ያላስረከበውን እንደ ውሉ ያልፈፀመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም በማለት የሰጠውን ውሳኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ለ/ ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

18. አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን አንድ መኪና ያላስረከበውና እንደ ውል ያልፈፀመው ከእሱ አቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት በመሆኑ አመልካች የወሰደውን የመኪናውን ዋጋ ብር 1,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ አምሳ ሺ ብር) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከመመለስ ውጭውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የተጠሪ ላይ ያደረሰውን ኪሣራ /ጉዳት/ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት እንዲከፍል የሚገደድበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን አንደኛውን መኪና በተመለከተ በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ተጠሪ የደረሰበት ጉዳት የመክፈል አላፊነት አመልካች አለበት በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል ፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153516 ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ከፊል ፍርድና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 115897 ሐምሌ 23 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የሞተር ቁጥር 131207038497 የሆነውና የሻንሲ ቁጥር LZZ5 ELND77NB 847969 የሆነውን መኪና ለተጠሪ ለመሸጥ ውል የተዋዋለውና የመኪናውን ሙሉ ዋጋ የተቀበለው የመኪናውን ሙሉ ባለሀብትነት መብት ለተጠሪ ሊያስተላልፍለት እንደማይችልና መኪናውን ለሌላ ሰው አስቀድሞ የሸጠው መሆንን እያወቀ በመሆኑ የመኪናውን ዋጋ ብር 1,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ከሚወልደው ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) እና አመልካች የሸያጭ ውሉን ባለመፈፀሙ ተጠሪ የደረሰበት ኪሳራ / ጉዳት / ካሳ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተጣርቶ ቀርቦ ሊከፍል ይገባል በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 21 መሰረት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን ሌላውን አንድ መኪና በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793 /ለ/ በተደነገገው መሰረት በፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ በመከልከሉ ምክንያት በመሆኑ የመኪናውን ዋጋ ብር ,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር የመመለስ ግዴታ አለበት በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793 /ለ / እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ወስነናል፡፡ ይህንን መኪና ለተጠሪ ባለማስረከቡ አመልካች ለተጠሪ ኪሳራ /ካሣ/ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ብት ጥቅምት 3 ቀን 2008 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 120150

ታህሳስ 5 ቀን2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተክሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አሌ ኢንተርናሺናል ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር-

ጠበቃ አቶ ደሱ ጨመዳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ፋርም አፍሪካ የኢትዮጵያ ፕሮግራም - ጠበቃ አቶ ሀይሉ ቡራዩ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ውልን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ ሲሆን በአሁን ተጠሪ የሥርተከሳሽ ላይ ባቀረቡት ክስ ከሳሽ በደቡብ ኦሞ ዞን ሀመር ወረዳ ኩሬ ለመገንባት ተከሳሽ ደግሞ ለሥራው ቫትን ጨምሮ ብር 1,850,798.50 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ለመክፈል ተስማምተን እኔ በውሉ መሰረት ሠርቻለሁ ከጉድጓዱየወጣውንም አፈር በውሉ ላይ በተቀመጠው 30 ሜትር ርቀት ላይ 140 ሜትር በመጨመር 170 ሜትር ርቀት አንጉገፍ ደፍቻለሁ ተከሳሽ ግን በውሉ መሰረት መክፈል ያለበትን ገንዘብና ተጨማሪ የአፈር ማንጓዝ ስራ የተሰራበትን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም በመሆኑም ተከሳሽለውሉ ማስፈጸሚያ በቅድሚያ የተከፈለው ቀብድ ብር 555,239.35 /አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም/ ተቀንሶ ቀሪውን ብር 1,295,558.95 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ስምንት ብር ከዘጠና አምስት ሳንቲም/ መክፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈልና ተጨማሪ የአፈር ማንጓዝና መድፋት ስራ ለሰራሁበት ቫትን ጨምሮ ብር 994,450.00 /ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ሺህ አራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቶ ሃምሳ ብር/በድምሩ ብር 2,290,308.95 /ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ሶስት መቶ ስምንት ብር ከዘጠናአምስት ሳንቲም/እንዲከፍለኝና ወጪና ኪሳራም የመጠየቅ መብቱ ይጠበቅልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል ።

ተከሳሽም በወኪሉ አማካኝነት በሠጠው መልስ ከከሳሽ ጋር የተባለውን ውል ፈፅመናል በውሉም መሠረት ከሣሽከተከሳሽ በሚሰጠው የስራ ዝርዝር መሰረት የኩሬውን ጉድጎድ በ2.29 ሜትር ጥልቀት ለመቆፈር እና የወጣውንም አፈር በ30 ሜትር ርቀት አንጉዞ ለመድፋት ይህንንም ሥራ በ20 ቀን ውስጥ ለማጠናቀቅ ተከሳሽ ደግሞ ብር 1,850,798.50 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከሃምሳ ሳንቲም / ለመክፈል ተስማምተናል ።ከሳሽግን የቆፈረው ኩሬ 2.20 ሜትር ሳይሆን 1.92 ሜትር ነው ስራውንም አጠናቆ ማረጋገጫ አቅርቦ አላስረከበም ከሳይት እንዲወጣም በተከሳሽ ትዕዛዝ አልተሰጠውም ከቁፋሮው የሚወጣውንም አፈር ከሳሽ እንዲደፋ የተስማማነው በ30 ሜትር ውስጥ ብቻ ነው ። ከስምምነታችን ውጪ ለተሠራ ስራ ልከፍል አይገባም ካሳሽ ሥራውን በውሉ ላይ ከተቀመጠው በላይ በማዘግየቱ የሚጣልበት የውል ቅጣት ተቀናሽ መሆን አለበት በአጠቃላይ ክሱ ውድቅ ተደርጎ ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብቱ ይጠበቅልኝ የሚል ነው።

ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የጊዜ መራዘሙን ከሳሽ በአካባቢው የአየር ንብረት ችግር ምክንያት የሥራው መጠናቀቂያ ጊዜ ለ15 ቀን እንዲራዘም ህዳር 4 /2005 ዓ.ም ለተከሳሽ የፃፈው ደብዳቤ ቀርቧል።ሆኖም ግን ተከሳሽ መልስ ያልሰጠ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1684 እና 1722 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላው ወገን በጽሁፍ የሚያቀርበው የውል ማሻሻያ ሀሳብ ሌላኛው ወገን ምክንያታዊ በሆነጊዜ ውስጥ መልስ ያልሰጠ ከሆነ በዝምታ ውሉን መቀበል መሆኑ መረዳት የሚቻል በመሆኑ ከሳሽ በፅሁፍ ላቀረበው የውል ማሻሻያ ተከሳሽ ዝም ማለቱ ውሉ በ15 ቀን መራዘሙን የሚያስከትል በመሆኑ ተከሳሽ የጠየቀውን ሥራው ለዘገየበት የሚከፈል ቅጣት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ነገር ግን ውሉ የቁፋሮ ጉድጎድ ጥልቀት 2.20 ሜትር ሲሆን ከሳሽ የቆፈረው 1.92 ሜትር በመሆኑ 0.28 ሜትር ጉድለት ስላለ የዚህ ጉድለት የገንዘብ መጠን 111,840.90 /አንድ መቶ አስራ አንድ ሺህ ስምንት መቶ አርባ ብር ከዘጠና ሳንቲም/ እና የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ ብር 555,239.35 /አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ከሰላሳ አምስት ሳንቲም/ ተቀንሶ ቀሪው ብር1,054,069.45 /አንድ ሚሊዮን ሃምሳ አራት ሺህ ስልሳ ዘጠኝ ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/ቫትን ጨምሮ ተከሳሽለተከሳሽ ይክፈለው በማለት ሲወስን ወለዱን በተመለከተ ለውሉ በአግባቡ ላለመፈፀምየተከሳሽ በአግባቡ የውል ግዴታውን ያለመወጣት አስተዋፅኦ አድርጓል በማለት የወለድ ይከፈለኝ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ሲወስን የተጨማሪ ስራን ማለትም በግራ ቀኙ ውል ላይ የተቀመጠውን አፈሩን በ30 ሜትር ርቀት አንጉዞ ለመድፋት ሲሆን ከሳሽ በ170

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሜትር ርቀት ነው አንጉገፎ የደፋሁት ለዚህም የውል ማሻሻያ በፅሁፍ አድርጌ ለተከሳሽ ሰጥቻለሁ ሲል ተከሳሽም ይኸው የውል ማሻሻያ በፅሁፍ የደረሰው ለመሆኑ ካለመካዱም በተጨማሪ በ23/5/2005 ዓ.ም ከፃፈው ደብዳቤ መረዳት ተችሏል፡፡በተጨማሪም ይህንን የውል ማሻሻያ ሀሳብ አልቀበልም በማለት መቃወሙን ተከሳሽ አልገለፀም ወይም አላስረዳም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1684,1722,2625 መሠረት የማሻሻያውን ውልተከሳሽ ሳይቃወም ዝም ማለቱ ውሉን መቀበሉን ያሳያል፡፡ዋጋውን በተመለከተ በዋናው ውል ከነበረው ለሜትር ኪዩብ 25 ብር ወደ 75 ብር ከፍ ብሏል ቢልም በውል ማሻሻያው ላይ አልተገለፀም በማለት ውሉ ላይ በተቀመጠው ዋጋ መሠረት የተጨማሪው 140 ሜትር ርቀት ብር 994,450.00 /ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር/ ተከሳሽለከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት በአጠቃላይዋናውን ገንዘብ ብር1,054,069.45 /አንድ ሚሊዮን ሃምሳ አራት ሺህ ስልሳ ዘጠኝ ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ህጋዊ ወለድጋር ተከሳሽለከሳሽእንዲከፍል ሲወሰን የተጨማሪ ስራን በተመለከተ ብር994,450.00 /ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር/ ቫትን ጨምሮ ተከሳሽለከሳሽ ይክፈል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታውን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቅሬታው መልስ ሰጪን ያስጠራል በማለት መልስ ሰጪን አስጠርቶ ካከራከረ በኋላ ዋናው ውል ላይ የተጠየቀው ዳኝነት ላይ በተሰጠው ውሳኔ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ በማድረግ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማፅናት ሲወስን፤ ተሠራ የተባለውን ተጨማሪ ስራን በተመለከተ አፈሩን ወስዶ ለመድፋት ግራ ቀኙ በ30 ሜትር የተስማሙ ሲሆን ይግባኝ ባይ ይህ ውል ቢኖርም በ30 ሜትር ርቀት ለመድፋት ቦታው ምቹ ባለመሆኑ በ170 ሜትር ርቀት ላይ ደፍቻለሁ ይህንንም ለፕሮጀክቱ ስራ አስኪያጅ አሳውቄበዚሁ እንድቀጥል በተሰጠኝ ትእዛዝመሰረት ነው በማለትየገለፀ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በግራ ቀኙ መሀከል የተደረገው ውል የፅሁፍ እስከሆነ ድረስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1722 መሠረት የውል ማሻሻያም ሲደረግ በፅሁፍ መደረግ ነበረበት በጽሁፍ ባለመደረጉ ምክንያት ለማሻሻያ ውል የተጠየቀው የዳኝነት ገንዘብ መጠን ሊከፈል የሚገባ አይደለም በማለት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሠኘት የአሁን የሰበር አቤቱታ አቅራቢ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት የሠበር አቤቱታውን ያቀረበ ሲሆን የሠበር አጣሪ ችሎቱም ቅሬታውን ከስር መዝገብ ጋር መርምሮ ተጨማሪውን ሥራ በተመለከተ በግራቀኙ መሀከል የተደረገ ውል የለም በሚል መነሻነት የተጨማሪ ስራ ክፍያ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል አይገባም በማለት የተወሰነበትን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ያስችል ዘንድ ተጠሪ ቀርቦ መልስ ይስጥበት ብሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪም የሰበር አጣሪው ችሎት ከያዘው ጭብጥ አንፃር የሰጠው መልስ በውሉ ከተመለከተው አፈር መድፊያ ቦታ ማለትም 30 ሜትር ወደ 170 ሜትር በመጨመር መደፋቱ ከተሰጠው የስራ ትእዛዝ ውጪ ነው፡፡በመሆኑም ተጠሪ ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም ፡፡ በተጨማሪም ከውል ውጪ የሆነ ግዴታን ለማካተት አንደኛው ወገን ደብዳቤ መፃፍ ብቻውን ሌላኛው ወገን ተዋዋይ እንደተስማማ አያስቆጥረውም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1682 ሥር ተደንግጓል በመሆኑም የተጨማሪ ስራ ክፍያን አስመልክቶ የሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ይፅናልኝ ብሏል፡፡

እኛም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረነዋል፡፡እንደመረመርነውም ለሠበር ከቀረበው አቤቱታ ውስጥ የተጨማሪ ስራ ክፍያ ሊከፈል ይገባል በማለት በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሠጠው ውሳኔ በሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት መሻሩ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በተመለከተ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊከፍል ይገባል በማለት የወሰነው የማሻሻያው ውል በፅሁፍ ተደርጎ ለተጠሪ እንዲደርስ መደረጉንና ተጠሪም ሳይቃወም ዝም ማለቱን ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተረጋግጧል በሚልና በፅሁፍ በተደረገ ውል ላይ አንደኛው ወገን ውሉን ማሻሻል ሲያስፈልገው በፅሁፍ ሌላኛው ወገን ሊያሳውቀው እንደሚገባ ሌላኛው ወገን የማይስማማበት ከሆነ ተቃውሞውን መግለፅ አለበት ነገር ግን በበቂ ምክንያታዊ ጊዜ የማሻሻያ ውል በፅሁፍ የደረሰው ተዋዋይ መልስ ሳይሰጥ ዝም ቢል በፍ/ብ/ሕ/ቁ1684፣1722 እና 2625ን በመጥቀስ የማሻሻያ ውልን እንደተቀበለ ይቆጠራል በሚል ሲሆን የስር ጠ/ፍ/ቤት ይህንን ውሳኔ የሻረው በግራ ቀኙ መሀከል የተፈፀመው የመጀመሪያ ውል በፅሁፍ እስከተደረገ ጊዜ ድረስ ማሻሻያው ውልም በፅሁፍ መደረግ እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1722 ሥር ተደንግጎ እያለአመልካች ተጨማሪ ስራ ሰርቻለሁ ያለው በፕሮጀክቱ ስራ አሰኪያጅ በተሰጠኝ ትእዛዝ ነው ማለቱ የስራ ትእዛዞቹ በፅሁፍ ባልተሰጠበት ሁኔታ የተሻሻለ ውል አለ ለማለትአይቻልም በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ በፅሁፍ የተደረጉ ውሎች አንደኛው ወገን ውሉን ለማሻሻል ሲፈልግ ዋናው ውል በተፈፀመበት አይነት ማለትም ዋናው ውል በፅሁፍ እስከተደረገ ድረስ በፅሁፍ ሊደረግ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1722 ሥር ተደንግጎ ይገኛል ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የተጨማሪ ስራ ውልን ለማድረግ የፅሁፍ ውል ለተጠሪ መስጠቱን ተጠሪም ያምናል፡፡ነገር ግን የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ የተጨማሪ ስራ ትእዛዝ ለመስጠት ስልጣን የለውም ከሚለው ስንነሳ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2625 ሥር እንደተመለከተው በፅሁፍ በተደረገ ውል ላይ አንደኛው ወገን የውል ማሻሻያ ፅሁፍ ለሌላኛው ወገን ሲልክለት ሌላኛው ወገን ሊቀበለው እንደሚችል ሲደነግግ ውሉን ለመቀበሉ ግን የተለየ ስርአት ካለማስቀመጡ በተጨማሪ በምክንያታዊ ጊዜ ውሉን ያለመቀበሉን ካላስታወቀ ውሉን እንደተቀበለ እንደሚቆጠር ደንግጓል፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ፅ/ቤት በፅሁፍ የተደረገው ውል ማሻሻያ ሲደርሰው በቂ በተባለ ጊዜ አይሆንም የሚልበትን ምክንያት መግለፅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይጠበቅበታል ነገር ግን በቂ በሆነ ጊዜ ውል ሊሻሻል የማይችልበትን ምክንያት ካለመግለፁም በተጨማሪ በፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ በተሻሻለው ውል መሠረት ይፈፅም በማለት የቃል ትዕዛዝ መስጠቱን ተጠሪ ፅ/ቤት ከማመኑም በተጨማሪ ተጨማሪ ስራው አልተሰራም በማለት ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ፕሮጀክት ስራ አስኪያጁ ትእዛዝ መስጠት አይችልም ካለ የማሻሻያው ውል በደረሰው ጊዜ ተቃውሞ ማቅረብ ሲገባው አላቀረበም፡፡ፕሮጀክት ስራ አስኪያጁ ተጨማሪ ትእዛዝ ባይሰጥም እንኳን የተጠሪ የፅሁፍ ማሻሻያ ውል ሲደርሰው ዝም ማለት ተጨማሪ ውሉን እንደተቀበለው ያስቆጥራል፡፡ በአመልካች በኩል ሲታይ ደግሞ ላቀረበው ተጨማሪ ማሻሻያ ውል የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ እንዲቀጥል ካዘዘው ውሉ ለመሻሻሉ ምንም ተጨማሪ ማረጋገጫ አስፈላጊ አይሆንም ከዚህ ሁሉ መነሻ ሲደረግ የተሻሻለ ውል አለ በተሻሻለው ውል መሰረት አመልካች ሊሰራ ይችላልና ስራውን ሰርቶታል መስራቱም ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አመልካች ተጨማሪ ስራውን መስራቱ እስከተረጋገጠና የሰራውም በህግ አግባብ እስከሆነ ድረስ ለሰራው ስራ ክፍያ የማይፈጸምበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡ ከዚህ ሁሉ ስንነሳ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጨማሪ ስራውን ክፍያ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት ሲወስን የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጨማሪ ስራ ክፍያን ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ.109882 በቀን 26/02/2008 ዓ.ም አመልካች ለተጠሪለተጨማሪስራ ክፍያ ብር 994.750.00(ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) ሊከፍል ይገባልበማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ 130572 በቀን 28/4/2007 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ /ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ.130572 በቀን 28/4/2007 ዓ.ም አመልካች ለተጠሪብር 994.750.00(ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር)ለተጨማሪ ስራ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ /ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ.109882 በቀን26/2/2008 ዓ.ም ዋናውን ገንዘብብር 1.054 069.45 (አንድ ሚሊዮን ሀምሳ አራት ሺኅ ስልሳ ዘጠኝ ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም) ፍርድ ካረፈበት ቀን ከሚታሰብ 9 ፐርሰንት ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ.130572 በቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

28/4/2007ዓ.ምየሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ /ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

4. ለዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ት እ ዛ ዝ

የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ በውሳኔ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይተላለፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 109194

ታህሳስ 25 ቀን 2005 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- የጎንደር ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት ዐቃቤ ህግ ወ/ሮአይናዲስ አሰጋህኝ ቀርባለች

ተጠሪ፡- እስማኤል አህመድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር-ጠበቃ አቶ ወንድሜነህ ዳኛው ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00768 በቀን 09/08/2006 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ለጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበውን አከራክሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር በመ/ቁጥር 00943 በቀን 25/10/2006 ዓ/ም ሲወስን፣ የአሁን አመልካች ውሳኔውን ለማስለወጥ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚያስቀርብ ሆኖ አልተገኘም በማለት የሰበር አጣሪ በሰ/አ/መ/ቁ 42200 ታህሳስ 8 ቀን 2007 ዓ/ም መዝገቡን በመዘጋቱ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበረ፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ በጎንደር ከተማ ቀበሌ 06 ክልል የቤት ቁጥር 18፣19፣20 እና 22 ያሉትን የመንግስት ቤቶች ተከራይቶ ለበርካታ ዓመታት ሲገለገል መቆየቱን፣ ቤቶቹን በመንግሥት ፖሊሲ መሰረት በሊዝ ገዝቶ ለማልማት እንደሚፈልግ ለተከሳሽ ጽ/ቤት ጥያቄ ማቅረቡን፣ ጥያቄውን ጽ/ቤቱ ለኪቢአድ አቅርቦ መ/ቤቱም ጥያቄያውን ተቀብሎ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ ማድረጉን፣ግምቱ ለኪቢአድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲከፈል ተከሳሽ ጽ/ቤት በቁጥር 1762/765/2001 በቀን 7/9/2001 ዓ/ም በጻፈለት ደብዳቤ መሠረት ብር 292.235.35 (ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም) ገቢ አድረጎ ቅድመ ክፍያ ብር 89.614.80 (ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ አስራ አራት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም) ለተከሳሽ /ለአመልካች/ ጽ/ቤት ገቢ ማድረጉን፣ የሊዝ ውል ፈርሞ 746.79 /ሰባት መቶ አርባ ስድስት ከሰባ ዘጠኝ/ ካ.ሜትር በካርታ ቁጥር 7339/02 በሆነው የሊዝ ይዞታ ቦታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰጠቱን፣ ወደ ግንባታ ለመግባት የግንባታ ፈቃድ ተጠይቆ ሊሰጠው ስላልቻለ ለሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በቀረበው አቤቱታ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮው በሰጠው የተስተካከለ ሳይት ፕላንና ትዕዛዝ ደብዳቤ መሠረት በህግ አስገዳጅነት የግንባታ ፈቃድ ተሰጥቶት ወደ ግንባታ እንዲገባ እንዲወሰን ሲል ጠይቋል፡፡

አሁን አመልካች (የሥር ተከሳሽ) ክሱ ደርሶት በድርድር እንጨርሳለን ብሎ ከሄደ በኃላ በቀጠሮ ቀን ባለመቅረቡ መልስም ባለመስጠቱ ክርክሩ በሌለበት ቀጥሎ እያለ በመቅረቡ በቀን 4/6/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት ግራ ቀኙ የቃል ክርክር ማድረጋቸውን፣ አመልካች /ተከሳሽ/ በቃል ክርክሩ ወቅት ለከሳሽ /ለተጠሪ/ የተሰጠው ካርታ የተሰረዘ መሆኑን በቀን 18/5/2003 ዓ/ም በተጻፈ ዳብዳቤ ትዕዛዝ የተሰጠ መሆኑን፣ ለከሳሽ /ለተጠሪ/ በቀን 25/5/2003 ዓ/ም ካርታው የተሰረዘ መሆኑን የተገለጸለት ስለሆነ በተሰረዘ ካርታ መብት አለኝ ብሎ ክስ ሊመሰርት አይገባም በማለት በቀረበው መቃወሚያ መሠረት መቃወሚያው ተመርምሮ ብይን ተሰጥቶ ነበር፡፡

የአሁን ተጠሪ /የሥር ከሳሽም/ በብይኑ ላይ ቅር በመሰኘት እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተከራክሮ ስለጸናበት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም የግራ ቀኙን አከራክሮ በሰ/መ/ቁ. 87247 በቀን 22/01/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የሥር ፍርድ ቤት ወደ ክርክሩ በመግባት ጉዳዩን ከሚከተሉት ነጥቦች አንጻር አጣርቶ እንዲወስን ፡-

1. ስለ አስተዳደር መሥሪያ ቤት ውሎች በፍትሐብሔር ህጉ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች፣
2. ከሊዝ አዋጁ፣ ከክልሉ የሊዝ ደንብ፣ በግራ ቀኙ መካከል ከተቋቋመው የሊዝ ውል እና ለተጠሪው በህግ ከተሰጠው ሥልጣን አንጻር ክርክሩን ቀጥሎ በማየት እና በማጣራት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 341/1/ መሰረት መልሷል፡፡

ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሠጠው ትዕዛዝ መሠረት መዝገቡ ተንቀሳቅሶ የግራ ቀኙ በጉዳዩ ላይ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡ የጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የከሳሽ ክርታ የተሰረዘው በአግባቡ ነው ወይስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ፣ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎቻቸውን መርምሮ በውሳኔው ላይ የሚከተሉትን ነጥቦችን ካነሳ በኃላ ፍርዱን የደመደመ ሲሆን እነዚህም ነጥቦች፡-

1. በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረው የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 15 ላይ የተቀመጠው ድንጋጌ የሚያስረዳው የሊዝ ይዞታ መቋረጥና የካሳ አከፋፈል በተመለከተ ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 6/94 አንቀጽ 4 (4) ደግሞ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለ መፍቀድ ሲሆን፣ በማናቸውም አግባብ በሊዝ የሚሰጥ የከተማ ቦታ ለውል ገቢው ለማስረከብ ዝግጁ የሆነ መሆን ይኖርበታል ሲል ይደነግጋል፡፡
2. እንዲሁም የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3180 ላይ የተቀመጠው ተዋዋይ ጥፋት ባይኖርበትም የአስተዳደር መ/ቤት ውሉን ሊያፈርስ ይችላል፡፡ ይህም ውሉ ለህዝባዊ አገልግሎት የሚጠቅም ሳይሆን ሲቀር ወይም ለፍላጎቱ የማይስማማ ሆኖ ሲገኝ ነው በሚል አስቀምጧል፡፡
3. በተጨማሪም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ//ቁ. 22719 በቀን 14/02/2000 ዓ/ም በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1195 መሠረት በአስተዳደር አካሉ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ከተሰረዘ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ባለቤትነት የተረጋገጠ ማስረጃ ሳይኖረው ለክርክር መነሻ በሆኑ ቤቶች ላይ መብት እንዳለው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳያቀርብ ክስ ማቅረብ በህግ ተቀባይነት የለውም ሲል የሰጠው ውሳኔ ያስረዳል፡፡
4. ሌላው ከሳሽ እና ተከሳሹ ያደረጉት የሊዝ ውል ላይ የተገለጸው በሊዝ ውል ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 እና ደንብ ቁጥር 6/94 የተደነገጉትንና በውል ህግ መሠረት ተፈጻሚነት ያለው ነው ሲሉ የተስማሙበት መሆኑን በሊዝ ውል አንቀጽ 8 እና 9 ላይ ተቀምጧል፡፡

ስለዚህ እነዚህ ድንጋጌዎች ሲታዩ በሥር ከሳሽ /በአሁን ተጠሪ/ እና በሥር ተከሳሽ/ በአሁን አመልካች/ መካከል የተደረገው የሊዝ ውል የተሰረዘው በአግባቡ ነው ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በውሳኔው ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ለጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ የግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ በሊዝ ውሉ መሠረት የመጠቀም መብት አለው፣ የሊዝ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም፣ ተጠሪ ዳኝነት የጠየቀውን የግንባታ ፍቃድ አመልካች ይስጥ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ ቅር በመሰኘት አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን የሰበር አጣሪ ቅሬታው ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ሆኖ አልተገኘም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ የሰጠውን ትዕዛዝ ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በቀን 13/05/2007 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር ቅሬታ ነጥቦችን አቅርቧል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ሐምሌ 24 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተመዘገው ሲሆን ጉዳዩን ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፣ በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክር እንዲሁም አጣሪው ያስቀርባል ሲል ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም ይህ ጉዳይ ቀደም ሲል እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቀርቦ የነበረና ድጋሚ ታይቶና ተጣርቶ እንዲወሰን የሚጣሩ ነጥቦች ተይዘው የተመለሰ ነው፡፡ ጉዳዩ ወደ ሥር ፍርድ ቤት ከተመለሰ በኃላ የግራ ቀኙ ክርክር ማድረጋቸውን፣ የጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኙ የቀረቡለትን የሰነድ ማስረጃዎችን የተመለከተ መሆኑን፤ የተነሱትን ፍሬ ነገሮችን ከሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94፣ ከደንብ ቁጥር 6/94፣ አግባብነት ካለው የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌ እና በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገው የሊዝ ውል አንጻር ተመልክቶ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ይህ ውሳኔ ግን የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 15/1/ ድንጋጌን ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ሊጤን ይገባል፡፡

በቀድሞው የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 15/1/ ሥር የሊዝ ውል ሊቋረጥ እና ሊፈርስ የሚችልባቸው ምክንያቶች በሊዝ የተያዘው ቦታ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ ሳያውለው ሲቀር፣ ቦታው ለህዝብ ጥቅም ተብሎ ለሌላ አገልግሎት ሲፈለግ እና የሊዝ ዘመኑ ሲያልቅ እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ሥር የሊዝ ውል እንዲፈርስ ለማድረግ በድንጋጌው ሥር ከተቀመጡት ከሶስቱ መሰረታዊ ነገሮች ውስጥ በውል ተቀባዩ በኩል ሳይፈጸም የቀረ ስለመኖሩ ውሉ እንዲፈርስ የሚጠይቀው ወገን የማስረዳት ሸክም ይኖርበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአሁን አመልካች የሊዝ ውሉ ተሰርዟል ከማለት ውጭ በሊዝ አዋጁ አንቀጽ 15/1/ ከተደነገጉት ውስጥ በተጠሪ በኩል ሊፈጸሙ የሚገባቸው ነገሮች ሳይፈጸሙ ስለመቅረታቸው ወይም ክርክር የተነሳበት ቦታ ለህዝብ ጥቅም ስለመፈለጉ በፍጹም አላስረዳም፡፡ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በዚህ ህግ አግባብ መሠረት በአግባቡ ሳይመረምር የይዞታ ማረጋገጫ ካርታው መሠረዙ እና ግንባታ ፈቃድ መከልከሉ ተገቢ ነው በሚል ውሳኔ መስጠቱ ተገቢነት የለውም፡፡ አመልካችም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል የሚከራከረው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ እንዲሁም አመልካች የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ህግ ስለ አስተዳደር መ/ቤት ውሎች የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን በአግባቡ ሳይመለከት የሊዝ አዋጁን ብቻ መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት የለውም በማለት ለዚህ ችሎት ያቀረበው ቅሬታ ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 እየታየ ላለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ እጅጉን አግባብነት ያለውና ልዩ ህግ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህን አዋጅ አንቀጽ 15/1 እና ደንቡን አያይዞ ከመተርጎሙም ባሻገር የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3181 የተረጎመበትም መንገድ ሲታይ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ የጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ከላቸው ህጎች አንጻር ተመልክቶ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የሊዝ ውሉ ሊፈርስ አይገባም፣ የተጠሪ መብት ሊጠበቅ ይገባል፣አመልካችም የግንባታ ፍቃድ ለተጠሪ እንዲሰጥ ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ህጋዊ ምክንያት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ አጣሪም የአመልካችን የሰበር አቤቱታውን መሠረዙ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ሲጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. ጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00943 በቀን 25/10/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/አ/መ/ቁ. 42200 ታህሳስ 8 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በአዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 15/1/ ሥር የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ተጠሪ ስለመጣሱ ባለማሰረዳቱ እንዲሁም ክርክር የተነሳበት ቦታ ለህዝብ ጥቅም ተፈልጎ ስለመሆኑ ባለማረጋገጡ ምክንያት የሊዝ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካች ተጠሪ ዳኝነት የጠየቀውን የግንባታ ፍቃድ የጎንደር ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በወሰነው መሠረት ሊሰጥ ይገባል ብለናል፡፡
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፤

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 114398

ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች ፡- አሊ መሃመድ

ተክሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ደስታ ኪዳነ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አመቱ ኤርታቦ ጉዳዩ ተከታታይ ልጣንጋ ኤርትቦ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል ክርክር ሲሆን የተጀመርው በደ/ብ/ብ/ሕ/ ሀድያ ዞን ሆሳዕና ከተማ ስተዳደር የመጀመርያ ደረጀ ፍ/ቤት ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በስር የክልል ጥቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰበር ሰሚ ችሎት ተፈፀመ ያሉትን የህግ ስህተት ተጣርቶ እንዲወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች የስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ ከአሁኗ አመልካች ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ህግን ያልተከተለ ውል ለመዋዋል ህጋዊ ችሎታ እንደሌላቸው ዕድሜያቸው 70 አመት እንደሆነ እንዲሁም በልብ እና በነርቭ ህመም እንደሚሰቃዩ በመግለፅ ከአመልካች ጋር የተደረገው ውል መብት እና ጥቅማቸው የጎዳ በመሆኑ እንዲፈርስላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት መልስም ተጠሪ ቤቱን ፈቅደው እንደሸጡት ልጅ አለመኖር ፣በበሽታ የተጠቁ መሆናቸው ውሉ ለማፍረስ ምክንያት እንድማይሆን፣ቤቱ በእማኞች ፊት እንደገዙት አመልካች በገንዘባቸው እንዲጦሩዋቸው ተስማምተዋል የተባለው ውሉ ለማፍረስ ምክንያት እንደማይሆን የስም ዝውውር በማዘጋጃ ቤት ተደርጎ ለተለያዩ ወጪዎች 250000 ከፍለው ቤቱን ማልማት እንደጀመሩ በመግለፅ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ውድቅ እንዲሆን አመልክታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍ/ቤትም የግራቀኙ ክርክርና ማስረጃ አጠቃላይ ይዘት ከመረመረ በኃላ የተጠሪ ምስክሮች ልጅ ይሁን ባል የሌላቸው ስለመሆኑ በአመልካች ቤቱ ሲያፈርሱ ቤቱም ዕቃውም አልሸጥኩም ሲሉ እንደነበር በሸተኛ እንደሆኑም በአንድ እጃቸው የያዙት ነገር የሚረሱ እና ከሚያግዛቸው ሰው የሚጨቃጨቁ መሆናቸውን እንዳስረዱ የአመልካች ምስክሮች በአንፃሩ ተጠሪ ቤት ለመሸጥ ይፈልጉ እንደነበር 1ኛ መከላከያ ምስክር በነባርነት እንደተገኙ የቤቱ ሽያጭም ዋጋ ብር 180000 በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ መደረጉ መግለፃቸውን ጠቅሶ በፍታብሔር ህጉ የዕድሜ ጣርያ ገደብ የሌለ መሆኑ በእድሜ መግፋት/መጃጀት/ ውል የሚፈርስበት ምክንያት መኖሩን፣አመልካች ያደረጉት የተንኮል ተግባር ባይኖርም የተጠሪ ዕድሜ ከ90 አመት በላይ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1710 ንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት የተዋዋይን ዕድሜ መጃጀት እና በንግድ/ሽያጭ/ ግልፅ የሆነ የልምድ እርቀት የሌለ ከሆነ ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል መደንገጉን ፍ/ቤቱ ተጠሪ በማስቀረብ እንደተመለከታቸው ዕድሜያቸው እጅግ የገፋ እና ከእድሜ መግፋት ጋር የተያያዘ የሚታይ ባህርያት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጡ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ እንደሚገባ አመልካች እና ተጠሪ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815(1) መሰረት ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲል በፍርድ ሰጥቷል፡፡

የአመልካች የሥር መጀመሪያ ደረጃ ውሳኔ በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል በህጉ አግባብ እንደተከናወነ ፣ ተጠሪ ቤት ለመሸጥ ሲፈልጉ እንደነበረ በአመልካች ምስክሮች መረጋገጡን፣ ተጠሪ የሸያጭ ውሉ እንዲፈርስ የፈለጉት የቤት ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት እንደሆነ ፣ በተጠሪ ላይ ህመም መኖሩ፣ ልጅ አለመውለዳቸው ከውሉ ጋር ተያያዥነት እንደሌለው ተጠሪ አርጅቷል፣ ጃጅቷል የሚሉ የሥር ፍ/ቤት ትችት አላስፈላጊ ናቸው በማለት ውሳኔውን ሽሮ የሽያጭ ውሉ አይፈርስም ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤትም በስር ፍ/ቤቶች የተደረገው አጠቃላይ የክርክር ይዘት ከመዘገበ በኃላ ተጠሪ ባላቸው አነስተኛ ማህበራዊ ተሳትፎ እና በማርጀታቸው ያወቁት የገበያ ዋጋ የማያውቁ መሆኑን ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በ 15/08/2007 ዓ/ም ተጠሪ አስቀርቦ ቃለ መጠይቅ ያደረግላቸው ሲሆን በተደረገላቸው ቃለመጠይቅም በእድመ መግፋታቸው ምክንያት የሚሰሩት ስራና የሚያደርሰው ውጤት ለመገንዘብ የማይችሉ መሆኑን የከፍተኛ ፍ/ቤት የቤት ዋጋ በመጨመሩ ነው፡፡ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ የቀረበው የሚለው ድምዳሜ ተገቢነት እንደሌለው የአሁኑ ተጠሪ በተሸጠው ቤት ላይ አንድ ክፍል እንዲሰጣቸው፣ለማስታመም የሚሉ ነገሮች ጧሪ እና ዘመድ እንደሌላቸው የሚያሳይ መሆኑን ፣ተጠሪ በድርድር ቤቱን በአግባቡ ይሸጣል ተብሎ ሊወሰድ እንደማይቻል ቤቱ ለመሸጥ ረዳት እና ደጋፊ ያስፈልጋቸው እንደነበር በመግፅ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡በአመልካች በኩል የሰበር አቤቱታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስሕተት የለም በማለት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም በስር ፍ/ቤቶች ተፈፅመ የተባለው ስህተት ለማሳረም ነው፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የሽያጭ ውሉ የማይፈርስበት ምክንያት በማለት ዘርዝረው ያቀረቡ ሲሆን ሲጠቃለል የሽያጭ ውሉ በህጉ አግባብ የተከናወነ በመሆኑ የሚፈርስበት አንዳችም በማስረጃ የተደገፈ ህጋዊ ምክንያት በሌለበት ውል ሊፈርስ ይግባኝ ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ እንዲሽር እና የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ እንደሚፈልጉ የሽያጭ ውሉ በእማኝ ፊት መከናወኑ የቤቱ ስመሀብትም በአመልካች ስም መዛወሩ በፍሬ ነገር ረገድ በተረጋገጠ ቤት ሁኔታ የተጠሪ እድሜ 97 ነው መባሉ እና የልብ ህመም እንዲሁም የነርቭ ህመም አለብኝ በማለታቸው ብቻ ይህ ስለመሆኑ አግባብ ባለው ባለሞያ የተረጋገጠ ነገር ሳይኖር በፍ/ብ/ህ/ቁ 1810(2) ውሉ ይፍረስ መባሉ ተጠሪ ባለበት ይጣራ ዘንድ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጠበቃቸው በኩል በሰጡት መልስ የስር ፍ/ቤት ውሉ ለማፍረስ በህመም ምክንያት አለማድረጉን ውሉ እንዲፈርስ መነሻ የተደረገው በፍ/ህ/ቁ 1710(2) በመሆኑ አጣሪ ችሎቱ የያዘው ጭብጥ ተገቢነት እንደሌለው ቤቱ ለመሸጥ የተገኘው ፍቃድ ከእድሜ መግፋት ጋር የተያያዘ እንደሆነ የእድሜ ምርመራ በስር ፍ/ቤት አለመቅረቡ ቤቱ በአፈፃፀም ተረክበው እየኖሩበት እንደሚገኙ በመግለፅ ውሳኔውን እንዲፀና አመልክቷል፡፡ አመልካች አቤቱታውን የሚያጠነክር የመልስ መልስ አቀርቧል፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለውነው፡፡ይህ ችሎትም ግራቀኙ በፅሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በመገናዘብ የስር የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ መሆን አለመሆኑ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ክርክሩ በሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉ በህጉ አግባብ የተደረገ በመሆኑ የሚፈርስበት አንዳች ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የሽያጭ ውሉ የተደረገው የፍቃድ ጉድለት ባለበት ሁኔታ በመሆኑ በስር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፅናቱ የሚነቀፍ ነጥብ የለውም በማለት መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡ በስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የአሁኑ ተጠሪ እድሜያቸው ከ 90 አመት በላይ እንደሆነ እና ተጠሪን በአካል አስቀርበው ጉዳዩን ያጣሩት የሥር ወረዳ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ በእድሜ መግፋታቸው ምክንያት የሚሰሩት ስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያደርሰው ስሜት ለመገንዘብ የማይችሉ መሆናቸውን ነው፡፡ በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የተደረገው የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በመነሻነት የሥር የወሰደው የተጠሪ ጤና ሁኔታ መልካም አለመሆን ሳይሆን በዕድሜ በመግፋታቸው ምክንያት ቤቱን በአግባቡ ተደራድረው ይሸጣሉ ተብሎ ስለማይገመት ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ውል በህግ ፊት የጸና ህጋዊ ተቀባይነት ወይም (ውጤት) እንዲኖረው ውል ለማቋቋም ከሚያስችሉ መስፈርቶች አንዱ የችሎታ መስፈርት ሲሟላ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1678(ሀ) ስር ተመልክቷል፡፡ አንድ ውል በህጉ አግባብ ተፈፅመዋል ለማለት የሚቻለው ግራቀኙ ፍፁም በሆነ አኳሃን የተስማሙ እና ፍቃዳቸው የሰጡ መሆኑን ሲረጋገጥ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1680(1) ተደንግጓል ፡፡በተዋዋይ ወገኖች የተደረገው ውል የፈቃድ ጉድለት ያለበት መሆኑ ሲረጋገጥ የተደረገውን ውል እንዲፈርስ ዳኝነት መጠየቅ እንደሚቻል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1696 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተደነገገ ጉዳይ ነው፡፡ የፍቃድ ጉድለት ከሚገለፅባቸው ነገሮች አንዱ ከተዋዋይ ወገኖች በአንዱ ውልን ለማፍረስ የሚያስችል ጉዳት መኖሩ ማሳየት ሲቻል ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1710 ንኡስ አንቀፅ 2 እንደተመለከተው“...የተጎጂው ፈቃድ የተገኘው ችግሩን የመንፈስ ቀላልነቱን መጀመቱን በእድሜ መግፋቱን ወይም በንግድ ግልፅ የሆነ የልማድ እውቀት የሌለው መሆኑን በመደገፍ እንደሆነ እና በህሊናም ግፍ መስሎ ሲታይ ውሉን ማፍረስ ይቻላል ፡፡ በማለት የተደነገገው መሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የስር መጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ይሁን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪን በችሎት በማስቀረብ ቃለ መጠይቅ ስለማድረጋቸው እና በተደረገው ማጣራትም ተጠሪ በእድሜ መግፋት /መጃጀት/ ምክንያት የህጋዊ ተግባራት ውጤት (juridical acts) በአግባቡ ማመዛዘን የማይችሉ መሆኑን ማረጋገጫቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

በተዋዋይ ወገኖች የሚደረገው ውል ተወዳዳሪ መብትና ግዴታ የሚያቋቁም በሆነ ጊዜ የግራቀኙ መብት እና ግዴታ በተቻለ መጠን ፍትሐዊ ስምምነት ላይ መድረስ አስፈላጊ መሆኑ ከአጠቃላይ የውል መርሆዎች የምንገነዘበው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በእድሜ በመግፋት ወይም በመጃጀታቸው ሳቢያ ከአመልካች ጋር ያደረጉት ውል የገበያ ሁኔታበአግባቡ አጥንተው ተደራድረው የገበያ ዋጋውንምን ያህል እንደሆነ ለይተው ታዋውሏል ማለት የሚቻል አይደለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ዕድሜያቸው ከ90 አመት በላይ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተደረገው ውል እንዲፈርስ የወሰኑት የተጠሪ የጤና ሁኔታ መሰረት በማድረግ ሳይሆን በእድሜው መግፋት ወይም(በመጃጀት) ምክንያት ማህበራዊ ግንኙነታቸው የተገደበ በንግድ ግልፅ የሆነ ልማድ ወይም እውቀት የሌላቸው ስለመሆኑ በማረጋገጥ ነው፡፡ በህጉ አግባብ የተደረገ ውሎች ህጋዊ ውጤት ሊኖራቸው እንደሚገባ በመርህ ደረጃ ግልፅ ቢሆንም በፍቃድ ጉድለት የተገኘ ውል ግን የተዋዋይ ወገን ጥቅም በሚጎዳ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መልኩ የሚጸናበት የህግ ምክንያት አይኖርም በተያዘው ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ በዕድሜ የገፉ ከመሆናቸው አንፃር አረጋውያን የህግ ጥበቃ ከሚደረግላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አንዱ በመሆናቸው ከአመልካች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ህጋዊ ውጤቱ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ከአመልካች ጋር እኩል የመደራደር አቅም እና ችሎታ የነበራቸው መሆኑን ባልተረጋገጠበት የተደረገው የሽያጭ ውል መብታቸው የነካ አይደለም የሚያስብል አይደለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲሁም የክልሉ የጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ከ/ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ ህጉ በአግባቡ ተፈፃሚ አድርገዋል ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳይ ሆኖ አልተገኘም፡፡በዚህም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርገን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደ/ብ/ብ/ህ/ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 04350 በ29/08/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሀድያ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 13636 በ08/05/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በመሻር የተሰጠውን ውሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 65012 በ28/09/2007 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ የስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ሰኔ 09/2007 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ዘግቶን ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ/ገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 119233

ሚያዚያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓለ. መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አያት አክሲዮን ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ሜሮን ክፍለሚካኤል ተክሌ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

<u>ፍ ር ድ</u>

1. ጉዳዩን የቀረበው የግልግል ዳኞች ጉባኤ አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት የመፈጸም ግዴታ አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ አመልካች በዱቤ የቤት ሽያጭ ውል ስዋዋል የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ከተሰጠበት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር በሰበር አጣርቶ ለመወሰን የሚል ጭብጥ ተይዞ ነው፡፡
2. የክርክሩ መነሻ አመልካችና ተጠሪ ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም የተዋዋሉት የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል በተለይም የክፍያ ስርዓቱ የውሉን ሁኔታዎች ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ ወይም ወሉን ለማፍረስ የሚያበቃ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ በተዋዋሉት የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል አመልካች በአዲስ አባበ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 28 በተለምዶ አያት መንደር እየተባለ ከሚጠራው ስፍራ አመልካች በሚገነባው የጋራ የመኖሪ አፓርታማ ህንጻ በሁለተኛ ፎቅ ቁጥሩ አ-2-2 የሆነ ባለሶስት መኝታ ክፍል ቤት በብር 660,121 (ስድስት መቶ ስልሳ ሺ አንድ መቶ ሃያ አንድ ብር) ለተጠሪ ለመሸጥ ተስማምቷል፡፡ የቤቱን ዋጋ አከፋፈል በተመለከተ ከቤቱ ዋጋ ውስጥ 197,704 (አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ሰባት መቶ አራት ብር) ከሳሽ (ተጠሪ) ቤቱን ከመረከቢ በፊት በስድስት ክፍያዎች እንድትከፍል ቀሪውን ብር 462,417 (አራት መቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልሳ ሁለት ሺ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር) ቤቱን ከተረከበች ጊዜ ጀምሮ በሰላሳ አመት ውስጥ ከነወለዱ በየወሩ ብር 5,133 (አምስት ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) እየከፈለች ልታጠናቅቅ ሻጭና ገዥ (አመልካችና ተጠሪ) የተሰማሙ መሆኑ ግራ ቀኙ የሚካካዱበት ነጥብ አይደለም፡፡

3. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ለተፈጠረው አለመግባበትና ሙግት ምክንያት የሆነው ተጠሪ በዱቤሽያጭ ውሉ መሰረት የመጀመሪያና ሁለተኛውን ክፍያ ከከፈሉ በኋላ ቀጣዮቹን ክፍያዎች ለመክፈል ተጠሪ ጥያቄ ስታቀርብ በዱቤ ቤት በመሸጥ ከዋጋ ጋር የረዥም ጊዜ ወለድ አብሮ ከቤቱ ዋጋ ጋር ጨምሮ መሰብሰብ የወንጀል ድርጊት መሆኑ ተለግጾ አመልካችና የአመልካች ከፍተኛ የስራ አመራሮች በፌዴራል ዐቃቤ ህግ በኩል የወንጀል ክስ የቀረበባቸው መሆኑን ገልጾ የቤቱን ዋጋ በአንድ ጊዜ ካልከፈለች በስተቀር ቀደም ሲል በተዋዋልነው የዱቤ ቤት ሽያጭ ውል መሰረት ለመፈጸምና የቤቱንም ዋጋ ለመቀበል የሚቸገር መሆኑን ገልጾ ክፍያ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑና ለተጠሪ በማሳወቁ ነው፡፡

4. ተጠሪ ለግልግለ ዳኞች ጉባኤ ክስ ያቀረበችው አመልካች በዱቤ ሽያጭ ወሉ መሰረት ቀጣይ ክፍያዎችን እንዲቀበልና በዱቤ ሽያጭ ወሉ መሰረት ቤቱን ለከሳሽ (ተጠሪ) እንዲያስረክብ ውሳኔ ይሰጥልኝ፡፡ አመልካች የዱቤ የቤት ሽያጭ ውሉን በራሱ ስልጣንና ፍላጎት ወደ እጅ በጅ ሽያጭ ለመለወጥ የወሰደው እርምጃ የህግ መሰረትና ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው ተብሎ የዱቤ የሽያጭ ውል የጸናና ህጋዊ ውጤት ያለው ነው ይባልልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለግልግል ዳኞች ጉባኤ በአመልካችና በአመልካች ከፍተኛ የስራ አመራር አባላት ባልተፈቀደ ሁኔታ የባንክ ስራ ሰርተዋል በማለት ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት በማስረጃነት ያቀረባቸው አመልካች ከሃያ ስድስት ደንበኞች ጋር ያደረገውን የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሆኑንና ይህም የወንጀል ድርጊት ነው ተብሎ በአመልካችና በአመልካች ከፍተኛ የስራ አመራር አባላት ላይ የተወሰነባቸው መሆኑን ገልጾ ከሳሽ (ተጠሪ) የቤቱን ዋጋ እጅ በእጅ ከፍላ እንድትረከብ ካልተደረገ በስተቀር ህገ ወጥ ነው የተባለን የዱቤ ሽያጭ ውል መሰረት በማድረግ ከገዥ ቤቱን ዋጋ ለመስብሰብና የዱቤ ሽያጭ ውሉን ለመፈጸም አልችልም በማለት ነው፡፡

5. የግልግል ጉባኤው አመልካች በሰላሳ አመት ውስጥ የቤቱን ዋጋ ከተጠሪ ለመቀበል በማስማማት የተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል እንደ ህገ ወጥ የባንክ ስራ ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 91837 መጋቢት 2 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው የወንጀል ፍርድ ውጤቱ ምንድን ነው? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ አመልካች ከተጠሪ ጋር የተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል እንደ ህገወጥ የባንክ ስራ ወንጀል የማይቆጠር መሆኑንና የወንጀል ፍርዱ የዱቤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሽያጭውን በጠቅላላው ህገ ወጥ የማድረግ ውጤት የሌለው ነው በማለት አመልካችና ተጠሪ የተዋዋሉት የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል የጸናና ህጋዊ ውጤት ያለው ነው፡፡ ተከሳሽ (አመልካች) በዱቤ ሽያጭ ውሉ መሰረት ክፍያ አልቀበልም የሚልበት ምክንያት የለም፡፡ ተከሳሽ (አመልካች) በዱቤ ሽያጭ ወሉ መሰረት ቤቱን ገንብቶ ለከሳሽ (ለተጠሪ) ያስረክብ በማለት ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

6. አመልካች ሚያዝያ 24 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ለተጠሪና ለሌሎች ደንበኞቹ ቤት በዱቤ በመሸጥ ከቤቱ ዋጋ ጋር ወለድ ጨምሮ በረኸቦም ጊዜ ቤቱን ዋጋ ለማስከፈል የተዋዋላቸው ውሎች ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ነው ተብሎ አመልካችና የአመልካች ከፍተኛ የስራ አመራሮች በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ከተቀጡ በኋላ የግልግል ጉባኤው የዱቤ ሽያጭ ውሉና የአከፋፈል ስርዓቱ ህጋዊ ነው፡፡ በዱቤ ሽያጭ ውሉ መሰረት የቤቱ ዋጋ ልትቀበል ይገባል፡፡ ቤቱን ለገኘር አስርክብ በማለት የሰጠው ውሳኔ አንድ ድርጊት በአንድ ስርዓት ውስጥ ህገ ወጥ የሆነ ወንጀል ነው ከተባለ በኋላ እንደገና ህጋዊ ነው የሚባልበት ምክንያት ሳይኖር ህጋዊ ነው የተባለ መሆኑን የሚያሳይና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካች ግንቦት 25 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠችው መልስ አመልካች በዱቤ በመሸጡ ሳይሆን በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ በመስራቱ ነው፡፡ በወንጀል የተሰጠው ፍርድ ከፍታብሔር ህጉ ጋር በሚጣጣም መንገድ መትርጎም አለበት፡፡ አመልካች በራሱ ስልጣን የውሉን መሰረታዊ ሁኔታ የማሻሻልም ሆነ የመለወጥ ስልጣን የለውም፡፡ ስለዚህ የግልግል ጉባኤው የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ስለሆነ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ይደረግልግኝ በማለት ተከራክራለች፡፡ አመልካች ግንቦት 25 ቀን 2008 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

7. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመርመርነው አመልካች በጳግሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል ለተጠሪ በብር 660,121 (ስድስት መቶ ስልሳ ሺ አንድ መቶ ሃያ አንድ ብር) ለተጠሪ ተለይቶ የተገለጸውን አፓርትመንት ቤት ለመሸጥ የተስማማና ተጠሪም ቤቱን ለመግዛት የተስማማች መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው አመልካች ይህንን የቤቱን ዋጋ ከተጠሪ ለመቀበልና ተጠሪም ለአመልካች የቤቱን ዋጋ ለመክፈል የተስማሙበት የቤቱ ዋጋ የአከፋፈል ስርዓት ነው፡፡

8. አመልካችና ተጠሪ በተዋዋሉት የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ገኘዋ (ተጠሪ) ቤቱን ከመረከቧ በፊት በስድስት ክፍያዎች ብር 197,704 (አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ሰባት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቶ አራት ብር)ለመክፈል የተስማማች ሲሆን ቀሪውን ብር 462,417 (አራት መቶ ስልሳ ሁለት ሺ አራት መቶ አስራ ሰባት ብር) ተጠሪ ቤቱን ከተረከበች በኋላ የቤቱ ዋጋ ከሚወልደው ወለድ ጋር በወር 5,133 (አምስት ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) እየከፈለች በሰላሳ አመት ውስጥ ከፍላ ለማጠናቀቅና አመልካችም ቀሪውን ቤቱን ዋጋ በውሉ በተገለጸው መንገድ ለመሰብሰብ ተስማምተው የዱቤ ሽያጭ ውሉን የተፈራረሙ መሆኑን ግራ ቀኙ ለግልግል ጉባኤውና ለዚህ ሰበር ችሎት ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል አይነታዊ ጉዳይ የሆነው የቤቱ ዋጋ አከፋፈል ስርዓት ማለትም ተጠሪ የቤቱን ዋጋ ከነወለዱ በወር የተወሰነ ክፍያ እየከፈለች በሰላሳ አመት ውስጥ ከፍላ እንድታጠናቀቅ የተዋዋልነው የውል ክፍል ያለ ህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ነው ተብሎ አመልካችና የአመልካች ከፍተኛ የስራ ኃላፊ በወንጀል የተከሰሱና በፍርድ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ በመሆኑ አመልካች በፍርድ ወንጀል ነው የተባለ ውል የሚፈጽምበት ምክንያት የለም በማለት ነው፡፡

9. እኛም አመልካች መከራከሪያ ያደረገው የወንጀል ፍርድ፣ ፍርዱ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸና ወይም የተሻረ ስለመሆኑና በጉዳይ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ መሰረታዊ ይዘት ለመረዳት አግባብነት ያላቸውን መዛግብት በማስቀረብ መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባልስልጣን ዐቃቤ ህግ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 91837 ባቀረበው የወንጀል ክስ፣ አመልካች የገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/1986 አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1(ሸ)፣ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና “ሐ” የተደነገገውን በመተላለፍ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ 1999 ዓ/ም በተደራጀ መንገድ ቤት በዱቤ በመሸጥ የዱቤ ብድር በመስጠት ቤት በዱቤ ከገዙት ደንበኞቹ ከፍተኛ መጠን ያለው ወለድ በመሰብሰብ በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ፈጽሟል በማለት በመጀመሪያ (አንድኛው) የወንጀል ክስ የመሰረተበት ሲሆነ በሁለተኛው የወንጀል ክስ የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሰው አመልካች በመጀመሪያው የወንጀል ክስ የተጠቀሰውን ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ የቀረበ መሆኑን ካስቀረብናቸው መዛግብት ተረድተናል፡፡

10. ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ አመልካች አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 1 በመተላለፍ፣ ከብሔራዊ ባንክ የባንክ ስራ ለመስራት የሚያስችለው ፈቃድ ሳያገኝ፣ በ2001 ዓ/ም ለበርካታ ደንበኞቹ ቤት በዱቤ ከሸጠ በኋላ የቤቱን ካርታ በመያዣነት በመያዝ፣ ከዱቤ ከተሸጠው የቤቶቹ ዋጋ ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ወለድ በማስከፈል ለደንበኞቹ የዱቤ የቤት ሽያጭ ብድር በመሰጠት በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ፈጽሟል በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሶስተኛው የወንጀል ክስ፣ ክስ መስርቶበታል። እንዲሁም በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ በነበሩት የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ በሶስተኛው የወንጀል ክስ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በሶስተኛው የወንጀል ክስ የተጠቀሰውን ወንጀል ፈጽመዋል በማለት በአራተኛው የወንጀል ክስ መስርቷል።

11. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 91837፣ ከላይ ይዘታቸው ስለተገለጸው የወንጀል ክሶችና ሌሎች የህግ ማዕቀፎች ተጠቅሰው በቀረቡት የወንጀል ክሶች ላይ የከሳሹንና የተከሳሾችን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ፣ ከመርመርና ከመዘነ በኋላ አመልካች ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በዱቤ ቤት በመሸጥና ወለድ በማስከፈል በአንደኛው የወንጀል ክስና በሶስተኛ የወንጀል ክስ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀሎችን የፈጸመ ጥፋተኛ ነው። የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት ሁለተኛው ተከሳሽም በሁለተኛው የወንጀል ክስና በአራተኛው የወንጀል ክስ የተገለጹትን በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀሎችን ፈጽሟል በማለት በመዝገብ ቁጥር 91837 መጋቢት 2 ቀን 2005 ዓ/ም የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠ መሆኑንና በአመልካችና በአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ በነበሩት ሁለተኛው ተከሳሽ ላይ ግንቦት 14 ቀን 2005 ዓ/ም የቅጣት ውሳኔ የወሰነ መሆኑን ተረድተናል።

12. አመልካች በዱቤ ቤት መሸጥ ህገ ወጥ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ነው ተብሎ የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው በአንደኛው የወንጀል ክስ እና ሶስተኛውን የወንጀል ክስ ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቧል። በስር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ በሁለተኛው የወንጀል ክስና በአራተኛው የወንጀል ክስ የጠቀሳቸውን የህግ ድንጋጌዎች ተላልፈሀል ተብየ የተሰጠብኝ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ሊሻርልኝ ይገባል በማለት የይግባኝ ቅሬታቸውን ማቅረባቸውን ተረድተናል።

13. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችና የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ እና ሌሎች ተከሳሾች እንዲሁም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 90549 የቀረበውን ይግባኝ፣ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 90222 በማጣመር፣ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ከመረመረ በኋላ፣ ቤት በዱቤ በመሸጥ የቤት ዋጋ ከወለድ ጋር መቀበል ህገ ወጥ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ነው ሊባል የማይችልና አመልካችም አዋጅ ቁጥር 83/1986 እና አዋጅ ቁጥር 592/2000 በልዩ ሁኔታ ኮርፖሬሽኖችና ድርጅቶችን ጥፋተኛ የሚያደርግ ልዩ ድንጋጌ ባልያዙበት ሁኔታ በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ መስራት ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ሊከሰስና ጥፋተኛ ሊባል የሚችልበት የህግ ማዕቀፍ የሌለ መሆኑን ገልጻ፣ አመልካች የከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ብሎ የቅጣት ውሳኔ ከሰጠበት አንደኛ እና ሶስተኛው የወንጀል ክሶች በነጻ እንዲሰናበት፣ የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ የነበሩት ሁለተኛው ተከሳሽ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በሁለተኛው ክስና በአራተኛው ክስ ጥፋተኛ ብሎ ከወሰነባቸው የቅጣት ውሳኔ በነጻ እንዲሰናበቱ ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ፍርድ ከገጽ 15 እስከ ገጽ 19 የሰጠውን ፍርድ ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ችለናል፡፡

14. ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ አመልካች በአንደኛው የወንጀል ክስና በሶስተኛው የወንጀል ክስ ከተከሰሰበት ወንጀል በነጻ የተሰናበተ መሆኑን፣ የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ ሁለተኛው ተከሳሽ በሁለተኛው የወንጀል ክስ እና በአራተኛው የወንጀል ክስ ከተከሰሰበት በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል በነጻ እንዲሰናበቱ በግልጽ ውሳኔ የሰጠበት መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 90222 ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ፍርድ፣ በውሳኔው ክፍል በተራ ቁር 1 እና በተራ ቁጥር 2 ካሰፈረው ውሳኔ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 90222 ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መጋቢት 27 ቀን 2008 ዓ/ም የተጻፈ ሃያ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቦ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድና ውሳኔ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚቻል መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለው መሆኑን በመግለጽ፣ የሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 126067 ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ መዝገቡን የዘጋው መሆኑን ተረድተናል፡፡

15. ከላይ ከገለጽናቸው በየደረጃው ከተሰጡ የወንጀል ፍርዶች የምረዳው፣ ምንም እንኳን አመልካች ቤት በዱቤ በመሸጥ፣ ከቤቱ ዋጋ ጋር በመጨመር ወለድ መቀበሉ ያለ ህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 91837 በአመልካችና በአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም፣ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 90222 ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ፍርድና ውሳኔ አመልካችና የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ የአዋጅ ቁጥር 83/1986 እና የአዋጅ ቁጥር 592/2000 የወንጀል ድንጋጌዎች በመተላለፍ ያለ ህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመሻር አመልካችና የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ ከቀረበባቸው ያለ ህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመስራት ወንጀል በነጻ እንዲሰናበቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የወንጀል ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ፍርድና ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 126067 ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ አጽንቶታል፡፡

16. ከዚህ አንጻር ሲታይ በይግባኝ የተሻረውን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 91837 የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በማጣቀስ ከተጠሪ ጋር ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም የተዋዋልኩት የዱቤ የቤ ሽያጭ ውል የወንጀል ተግባር ነው የተባለ ስለሆነ ውሉን እንዲፈጸም አልገደድም በማለት አቅርቦት የነበረው ክርክር ተገቢነት የነበረው ቢሆንም፣ በሂደት የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 91837 የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 90222 ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ፍርድና ውሳኔ የተሻረ መሆኑን እያወቀ፣ ለዚህ ሰበር ችሎት ግንቦት 25 ቀን 2008 ዓ/ም ባቀረበው የመልስ መልስ ከተጠሪ ጋር የተዋዋለውን የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል ላለመፈጸም መከራከሪያ አድርጎ ማቅረቡ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

17. በመሆኑም የግልግል ጉባኤ ዳኞች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ በመዝገብ ቁጥር 91837 የአመልካችና በአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ፣ ያለ ህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ፣ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል ሊፈጽም ይገባል ወይም አይገባም የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን አግባብነት እንደሌለው በመግለጽ የሰጠው የህግ ትርጉምና በሌሎች ነጥቦች ላይ ያስፈራቸው ትችቶች በፍርድ ወንጀል ነው የተባለን ክፍያ፣ የወንጀል ፍርዱ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ ከመሻሩ በፊት አመልካች እንዲቀበል የሚያስገደድና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1792 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1793 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት የነበረበት ውሳኔ እንደሆነ ተረድተናል፡፡

18. ሆኖም የግልግል ጉባኤው ነሐሴ 22 ቀን 2007 ዓ/ም የአመልካችና የተጠሪን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ፣ አመልካች ቤት በዱቤ በመሸጥ የቤቱን ዋጋ ከነወለዱ በረሻቦም ክፍያ ለመሰብሰብ ከደንበኞቹ ጋር በመዋዋል የቤቱን ዋጋ ከውሉ መሰረት ከነወለዱ መቀበሉ፣ ያለህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ መስራት ወንጀል አመልካችንና የአመልካችን የቦርድ ሰብሳቢ ጥፋተኛ የማያስኝና በወንጀል የማያስቀጣ መሆኑን በመግለጽ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 91837 የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 90222 ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ፍርድና ውሳኔ የሻረው በመሆኑና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ፍርድና ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 126061 ታህሳስ 19 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ ያጸናው በመሆኑ፣ አመልካች ከተጠሪ ጋር ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም የተዋዋልኩት የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ በውሉ መሰረት እንድፈጽም ልገደድ አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ህጋዊ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የግልግል ዳኞች ለውሳኔያቸው የሰጡትን ምክንያትና በውሳኔያቸው ላይ የሰጧቸውን ትዕዛዞች በማሻሻል በውጤት ደረጃ አመልካች ከተጠሪ ጋር ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ሊፈጽም ይገባል በማለት የሰጡትን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የግልግል ዳኞች ነሐሴ 22 ቀን 2007 ዓ/ም፣ አመልካች ከተጠሪ ጋር ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ሊፈጽም ይገባል በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል ምክንያት ተለውጦ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት፣ የቤቱን ዋጋ በውሉ ከተገለጸው ወለድ ጋር በውሉ በተቀመጠው የአከፋፈል ስርዓት መሰረት ነው ሊቀበል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ለተጠሪ የሸጠውን ቤት የማስረከብ ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
4. ተጠሪ (ከሳሽ) ጉዳዩን በግልግል ዳኞች ለማሳየት ያወጣቸውን ብር 40,506 (አርባ ሺ አምስት መቶ ስድስት ብር) ተከሳሽ (አመልካች) ሊከፍላት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.106994

ሚያዚያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ብሔራዊ የኢትዮጲያ ኢንሹራንስ /አ.ማ/ አልቀረበም

ተጠሪዎች፡-የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

1. ዘላቂ ግብርና ተሃድሶ ኮሚሽን
2. ትምህርት ቢሮ
3. የገጠር መንገዶች ባለስልጣን
4. ስራና ክተማ ልማት ቢሮ
5. የገንዘብ ቢሮ
6. ፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

ፀ/ህግ ሙሉ ባይለየኝ ቀረቡ

7. ዛምስ ኢንተርናሽናል የንግድ ድርጅት፣ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው የግልግል ዳኞች ጉባኤ፣ የስር ከሳሾች /ተጠሪዎች/ የእቃውን ማቅረቢያ ጊዜ ካለ አመልካች ፈቅዶና ስምምነት ያራዘሙ በመሆኑ በሰጠሁት የዋስትና ሰነድ መሰረት ልገደድ አይገባኝም በማለት ያቀረበውን ክርክር በማለፍ አመልካች ለክስ ኃላፊ ነው ማለታቸውና አመልካች ፅዳው እስከከፈል ድረስ 0.07 መቀጫ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡትን ውሳኔ አግባብነት በሰበር አጣርቶ ለመወሰን የሚል ጭብጥ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመስርቶ ነው፡፡
2. ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው የግልግል ዳኞች ጉባኤ ነው፡፡ የግልግል ዳኞች በወቅቱ አንደኛ ተከሳሽ በነበረው ሰባተኛ ተጠሪና በከሳሾች የሌሎች ተጠሪዎችመካከል ያለውን ክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰምቶ መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቶ ነበር፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ/የአሁን አመልካች/ የግልግል ዳኞች ለእኔ በአግባቡ መጥሪያ እንዲደርሰኝ ሳያደርገው መስጠታቸው ስህተት ያለበት ነው በማለት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ፣የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የግልግል ዳኞች የሰጡትን ውሳኔ በመዝገብ ቁጥር 01-82566 ሀምሌ 11 ቀን 2004 ዓ/ም በመሻር ጉዳዩን ለግልግል ዳኞች መልሶታል፡፡

3. ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የግልግል ጉባኤ ዳኞች ጉዳዩ፣ ወደ ግልግል ዳኞች ከመለሰው በኋላ፣ የግልግል ጉባኤው የስር አንደኛ ተከሳሽ /ሰባተኛው ተጠሪ/ ና ሁለተኛው ተከሳሽ /አመልካች/ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ሀምሌ 7 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ከሳሾችያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾች የተለያዩ የቢሮ ዕቃዎችን ለመግዛት ባወጣው ጨረታ አንደኛ ተከሳሽ/ሰባተኛ ተጠሪ/ አሸናፊ ሆኖ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 468540 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አርባ ብር/ የሆኑ እቃዎችን ለማቅረብ መስከረም 12 ቀን 1991 ዓ/ም ውል የተዋዋለ መሆኑን፣አንደኛ ተከሳሽ የእቃዎቹን ሙሉ ዋጋ ብር 468540/ አራትመቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አርባ ብር/ በቅድሚያ ክፍያነት የተከፈለው መሆኑን፣ አመልካች /ሁለተኛተከሳሽ/ አንደኛ ተከሳሽ እቃዎቹን ባያቀርብ፣ አንደኛ ተከሳሽ ለወሰደው ዋጋ ለመክፈል የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነድ ጥቅምት 19 ቀን 1994 ዓ/ም የሰጠ መሆኑን፣ አንደኛ ተከሳሽ የውል ግዴው ከገባባቸው ዕቃዎች ውስጥ የብር 73,800 /ሰባሶስት ሺህ ስምንት መቶ ብር/ የሚያወጡ እቃዎችን የቀረበና ቀሪዎቹን ዋጋቸው 394740 /ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ብር/ የሆኑ እቃዎች ያላቀረበ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ፣ በውሉ ላይ የተገለጸውን የመቀጫ ገንዘብና ወለድ ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ እንዲወሰንላቸው ከሳሾች የግልግል ዳኞች ጉባኤውን ጠይቀዋል፡፡

4. የስር አንደኛ ተከሳሽ/ሰባተኛ ተጠሪ/ በወቅቱ ያቀረባቸው እቃዎች የጥራት መስፈርት አያሟሉም በማለት ከሳሾች አላግባብ የመለሱ በመሆኑ ለውሉ አለመፈጸም ተጠያቂነት ያለባቸው ከሳሾችእንደሆኑና መቀጫም የመክፈል ኃላፊነት እንደሌለበት በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ /አመልካች/ ዕቃዎች ከሳሾች መረከብ ነበረባቸው፡፡ አላግባብ ባለመረከባቸው ለውሉ አፈፃጸም ላይ ችግር የፈጠሩት ከሳሾች ናቸው፡፡ ከሳሾች ሁለተኛ ተከሳሽ ዋናው ባለዕዳ /አንደኛ ተከሳሽ/ ዕቃዎቹን ያላቀረበ መሆኑን ቢያሳውቁኝ ኖሮ እኔ ራሴ ወይም ሌላ ሰው ወክዬ የውልን ግዴታ እፈጽም ነበር፡፡ ከሳሾች ያለሁለተኛ ተከሳሽ ፈቃድና ስምምነት ሀምሌ 25 ቀን 1993 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ለአንደኛ ተከሳሽ የዕቃውን ማቅረቢያ ጊዜ ያራዘመ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. የግልግል ዳኞች የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፣ የስር አንደኛ ተከሳሽ /ሰባተኛ ተጠሪና/ ሁለተኛ ተከሳሽ አመልካቾች/ ያቀረቧቸውን መከራከሪያዎች ውድቅ በማድረግ፣ ተከሳሾች ከሳሾች ክስ ያቀረቡበትን ብር 394740 /ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺ ሰባት መቶ አርባ ብር/ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ይህንን ገንዘብ ከፍለው ተከሳሾች እስከሚያጠናቅቅ ድረስ፣ በውሉ ላይ የተቀመጠውን በቀን 0.007 መቀጫ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ፡፡ እንዲሁም ተከሳሾች ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በብር 394740 /ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ስባት መቶ አርባ ብር/ ከፍለው እስከጠናቀቁበት ጊዜ ድረስ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ለከሳሾች ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡
6. አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ህዳር 18 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ከሳሾች ለዋሱ ማስጠንቀቂያ አልሰጡም፡፡ ሁለተኛው ተከሳሽ በሰጠው ዋስትና መሰረት ኃላፊ የሚሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ የግልግል ዳኞች መደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ እዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ወለድ እና በቀን 0.007 መቀጫ ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች ጥር 29 ቀን 2007 ዓ/ም የአመልካች ክርክር አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ ሰባተኛ ተጠሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ተጠርቶ ስላልቀረበ መልስ የመስጠቱ መብት ታልፏል፡፡ አመልካች መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
7. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው፣ ጉዳዩ በግልግል ዳኞች ጉባኤ ሲታይ አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ሰባተኛው ተጠሪ የተለያዩ የቢሮ እቃዎችን ለማቅረብ የጨረታ አሸናፊ ሆኖ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 468540 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አርባ ብር/ የሆኑ የቢሮ ዕቃዎች በጨረታ ሰነድ የተገለጸውን የጥራት መስፈርትና /specification/በማሟላት ለማቅረብ ውል መዋዋል አከራካሪ አይደለም፡፡ የእቃው አቅራቢ የሆነው ሰባተኛው ተጠሪ እቃዎችን ሙሉ ዋጋ ብር 468,540 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አርባ ብር/ በቅድመ ክፍያነት የወሰደ መሆኑና፣ ሰባተኛው ተጠሪ ለወሰደው የቅድመ ክፍያ ዋስትና ይሆን ዘንድ አመልካች የቅድመ ክፍያ የዋስትና ሰነድ መሰጠቱ የግልግል ጉባኤ ዳኞች አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ዋስ የሆኑት ሰባተኛው ተጠሪ አቅርባለሁ ብሎ የውል ግዴታ ከገባበትውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብር 73,800/ሰባሶስትሺህ ስምንት መቶ ብር/ የሚያወጡ የቢሮ እቃዎች በውሉ የተገለጸውን የጥራት መስፈርት በማያሚላ ሁኔታ ማቅረቡንና ቀሪዎችን ዋጋቸው ብር 394,740ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ብር) የሚያወጡ ዕቃዎች በውሉ የተገለፀውን የጥራት መስፈርት በሚያሚላ ሁኔታ ያላቀረበና በውል የገባውን ግዴታ ባለመፈፀሙ ለውሉ አለመፈፀም ኃላፊ ሆኖ መገኘቱን የግልግል ጉባኤው ዳኞች በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ በመርመርና በመመዘን ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡

8. አመልካች የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰናድ የሰጠው ሰባተኛው ተጠሪ የዕቃ አቅርቦት ውሉን በአግባቡ ባለመፈፀሙ ለውሉ አለመፈፀምና ውሉ በአግባቡ ባለመፈጸሙ ምክንያት ፈራሽ ለመሆኑ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች የዕቃ አቅርቦት ውሉ በአቅረቢው (ሰባተኛ ተጠሪ) ባለመፈፀሙ ምክንያት በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባኝም በማለት ያቀረበው ክርክር የሰጠው የዋስትና ሰነድ የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ አመልካች ስማቸው ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ተራ ቁጥር የተገለጹት ተጠሪዎች የዕቃው ማቅረቢያ ጊዜ እስከ ሀምሌ 25 ቀን 1993 ዓ/ም ያራዘሙ በመሆኑ ተጠያቂነት ያለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክርም አመልካች ነሐሴ 28 ቀን 1991 ዓ/ም የሰጠውን የዋስትና ሰነድ ለማደስ ጥቅምት 19 ቀን 1994 ዓ/ም የተጻፈ የዋስትና ሰነድ የሰጠ በመሆኑና አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 1994 ዓ/ም የተጻፈ የዋስትና ሰነድ የሰጠው በመጀመሪያው ውል የተገለፀው የዕቃ ማቅረቢያ ጊዜ የተራዘመ መሆኑን እያወቀ በመሆኑ ክርክሩ የህግ ድጋፍ ያሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የዕቃ አቅረቢው (ሰባተኛ ተጠሪ) በውሉ መሠረት ላላቀረበው የቢሮ ዕቃ አመልካች በሰጠው የዋስትና ሰነድ መሠረት በአንድናትና በነጠላ ኃላፊነት አለበት በማለት የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማዕናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

9. በዚህ ሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባውና አከራካሪ የሆነው ጭብጥ የእቃው አቅረቢ የነበረው (ሰባተኛው ተጠሪ) የውል ግዴታውን ባለመፈጸሙ ምክንያት አመልካች ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 6 ለተገለፀው ተጠሪዎች ከዋናው ባለዕዳ ጋር በአንድነትና በነጠላ ለመክፈል የሚገደደው ምን ያህል ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡ የዕቃው አቅረቢ በቅድመ ክፍያነት ከወሰደው ገንዘብ ውስጥ የብር 394740 (ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ብር) ዋጋ ያላቸውን የቢሮ ዕቃዎች ያላቀረበ በመሆኑ አመልካች ከዋናው ባለዕዳ ጋር በአንድናትና በነጠላ ይህንን ገንዘብ እንዲከፍል የግልግል ዳኞች የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

10. የወለድ ክፍያን በተመለከተ በመጀመሪያ የስር ከሳሾች ስልጣን ለሌላው ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ወደ ግልግል ዳኞች ጉዳያቸውን እንዲያቀርቡ የተወሰነ መሆኑን ጉዳዩ ለግልግል ጉባኤ ቀርቦ ላይቶ መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ/ም በግልግል ዳኞች ጉባኤ ውሳኔ አግኝቶ የነበረ መሆኑንና የስር ከሳሾች መጥሪያ ለአመልካች በአግባቡ አለማድረሳቸውን በማረጋገጥ የግልግል ዳኞች መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 01-82566 ሀምሌ 11 ቀን 2004 ዓ/ም የሻረው መሆኑ ተረጋግጧል። ይህ ከሆነ አመልካችን በተመለከተ ወለድ መክፈል የሚገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ከሀምሌ 11 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ የሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ታስቦ መሆን ሲገባው የግልግል ጉባኤው ክሱ መደበኛ ፍርድ ቤት ከቀረበበት ቀን አንስቶ የሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ አመልካች ለዋናው ባለ ዕዳ (ሰባተኛ ተጠሪ) ጋር በአንድናትና በነጠላ ይክፈል በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሀምሌ 11 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ ህጋዊ ውጤት ያላገናዘበና በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

11. መቀጫውን በተመለከተ የስር ከሳሾችና የእቃው አቅራቢ ሀምሌ 12 ቀን 1991 ዓ/ም በተዋዋሉት ውል አንቀጽ 6 መሠረት ውሉ ባለመፈፀሙ 0.07 መቀጫ በቀን ታስቦ የሚከፈለው እስከ ሰባ ቀናት ድረስ ብቻ እንደሆነ በግልፅ ተመልክቷል። ይህ ከሆነ አመልካች ዋናው ባለዕዳ በቅድመ ክፍያነት ወስዶ በውሉ አግባብ ያልፈጸመውን የብር 394,740 (ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ብር) መቀጫ በቀን 0.07% ታስቦ ለሰባ ቀናት ብቻ መቀጫ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል። ከዚህ ውጭ የግልግል ጉባኤ ዳኞች አመልካች 0.07 ፐርሰንት መቀጫ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ዕዳው ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ያውሉን አንቀፅ 6 የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1889 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1924 ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገና በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህታት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

12. ከላይ በገለፀናቸው ምክንያቶች የግልግል ዳኞች ጉባኤ አመልካችን በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ በከፊል በማሻሻል።

(ሀ) አመልካች ዋናው ባለዕዳ (ሰባተኛ ተጠሪ) በቅድመ ክፍያነት ወሰዶ ዕቃውን በውሉ መሠረት ባለመቅረቡ ለከሳሾች መመለስ የሚገባውን ብር 394740 (ሶስት መቶ ዘጠና አረት ሺ ሰባት መቶ አርባ ብር) ከዋናው ባለዕዳ ጋር በአንድነትና በነጠላ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል።

(ለ) አመልካች ከዋናው ባለዕዳ ጋር እንዲከፍል የተወሰነበትን ብር 394,740 (ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺ ሰባት መቶ አርባ ብር) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሀምሌ 11 ቀን 2004 ዓ/ም ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ የሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ በአንድነትና በነጠላ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

(ሐ) አመልካች ዋናው ባለዕዳ መመለስ ያለበትን ብር 394,740 /ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺ ሰባት መቶ አርባ ብር) በቀን 0.07% መቀጫ ታስቦ በሰባ ቀናት ተባዝቶ የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት የግልግል ዳኞች የሰጡትን ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348 (1) መሠረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የግልግል ጉባኤ ዳኞች ሀምሌ 7 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01-38894 ጥቅምት 25 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 12 ከ"ሀ" እስከ "ሐ" የተገለፀውን ገንዘብ ከዋናው ባለዕዳ /ሰባተኛ ተጠሪ/ ጋር በአንድናትና በነጠላ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
3. የግልግል ጉባኤ ዳኞች ዋናው የፍርድ ባለዕዳ (ሰባተኛ ተጠሪ) በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ በዚህ ሰበር ችሎት የልተያ በመሆኑ አልተነካም፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለያረሳቸው ይቻሉ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ጥር 5 ቀን 2007 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዝ የተነሳ መሆኑን እንዲታወቅ ለሚመለከተው ክፍል ይጻፍ፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.113013

ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመካው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- ወ/ት ማሕሌት እንዳለ አልቀረቡም

ተጠሪ፡-1.አቶ አህመድ አለም } አልቀረቡም

2.ወ/ሮ ዘይነባ አብደላ }

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ነው፡፡በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች የመቃወም አመልካች፤ተጠሪዎች ደግሞ እንደ የቅደም ተከተላቸው የፍርድ ባለመብት እና የፍርድ ባለዕዳ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሠጠበት በኮልፌ ቀራንዩ ክ/ከተማ ቀበሌ 05 በደብረአባይ ቁጥር 1 እና 2 ራሥ አገዝ የመኖሪያ ቤቶች ሕብረት ሥራ ማሕበር በ175 ካ.ሜ ላይ የሚገኘውን ቤት ግንቦት 01 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል የገዙት መሆኑን በመግለጽ ተከራካሪ ሳይሆኑ በቤቱ ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መብታቸውን የሚጎዳ በመሆኑ ይሻርላቸው ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ስላልቀረቡ ፍ/ቤቱ አስተያየት የመስጠትመብታቸውን አልፎታል፡፡1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በቂ ምክንያት የሌለው መሆኑን፤አመልካች ቤቱ በዕዳ መያዙን እያወቁ ዘግይተው ያቀረቡት አቤታታ ከቅን ልቦና ውጪ የቀረበ በመሆኑአቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአፈጻጸም ችሎቱ የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች ቤቱን ገዝቸዋለሁ በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ያቀረቡት የሽያጭ ውሉ ሥልጣን ባለው አካል ፊት ያልተመዘገበ በመሆኑ በፍርድ ባለመብት ላይ የመቃወሚያ መሠረት ሊሆን አይችልም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል። ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አከራካሪው ቤት የማሕበር ቤት በመሆኑ ለጉዳዩ አወሳሰን ተፈጻሚነት ያለው ሕግ ሥለ ሕብረት ሥራ ማሕበራት አደረጃጀት እና አሥተዳደር የሚደነግገው አዋጅ ቁጥር 147/91 ነው፤የዚህ ሕግ አንቀጽ 19/1/ለ በማሕበሩ ውስጥ በተሠራ ቤት ላይ መብት ያገኘ ሠው ይህንኑ መብቱን ለሌላ ሠው ለማሥተላለፍ ቢፈልግ ከማሕበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቃድ ማግኘት እንደሚኖርበት ይደነግጋል፤የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ.ቁ 36294 ይህንኑ በመጥቀስ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤አመልካች ያቀረቡት የሽያጭ ውል የማሕበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቅዶ ያስተላለፈው መሆኑን፤የመተካካት ሥርዓቱም በማሕበሩ ዘንድ የተመዘገበ እና አግባብ ባለው አደራጅ መሥሪያ ቤት እንዲመዘገብ የተላለፈ ሥለመሆኑ የሚያስረዳ አይደለም፤በሰነዱ ላይ የማሕበሩ ማሕተም አርፎ መገኘቱ ብቻውን ሕጉ በሚጠይቀው አሠራር የመብት ማስተላለፍ ሒደት መከናወኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፤ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለውም 2ኛ ተጠሪ የቤቱን ሥመሐብት ወደ አመልካች ሣያዞሩ እየኖሩበት የሚገኙ መሆናቸውን በመሆኑ በ2ኛ ተጠሪ ሥም በሚታወቅ ቤት ላይ በመንደር የቤት ሽያጭ ውል መብት አግኝቸበታለሁ በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ ተቀብሎ አጽንቶታል።የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-ማሕበሩ የሽያጭ ውሉን ተቀብሎት አመልካችም በ2ኛ ተጠሪ ምትክ ተተክቼ ማሕበሩ የሚጠይቀውን ተገቢውን ክፍያ እየከፈልኩ የማሕበሩ አባል ሆኘ እንድቀጥል ፈቅዶልኝ ውሉ በማሕበሩ ከገባበት ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በቤቱ እየኖርኩበት እገኛለሁ፤በአሁኑ ሰዓትም ማህበሩ ካርታ በሥሜ እንዲዘጋጅ አድርጎልኝ የፍ/ቤት ክርክር አለበት የተባለ በመሆኑ ተቀምጦ ይገኛል፤ማሕበሩ ይህን እውነታ ያሳወቀኝ የይግባኝ ክርክሩ ከተደረገ በኋላ ነው፤አከራካሪው ቤት በክፍለ-ከተማውም ሆነ በማሕበሩ ተመዝግቦ የሚገኘው በአመልካች ሥም እንጂ በ1ኛ ተጠሪ ሥም አይደለም፤የማሕበሩ ማሕተም አርፎበት ከማሕበሩ የተላከው ውልም የሚያሣየው አመልካች እና ሁለተኛ ተጠሪ ያደረግነው የቤት ሽያጭ ውል የጸና መሆኑን ነው፤በማሕበሩ ትዕዛዝ በሥሜ ካርታ ተሠርቶ እያለ 1ኛ ተጠሪ ካርታው ሊሰጥ አይገባም ብለው በመከራከራቸው እንዳይሰጠኝ የተደረገ መሆኑ እየታወቀ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል በማለት የተሠጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካችን ውል የሕብረት ሥራ አመራሮች ፈቅደው ያልተቀበሉት በመሆኑ አመልካች መቃወሚያ ማቅረብ አትችልም በማለት ውሳኔ የመስጠቱን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡እኛም የግራቀኙን ክርክር እንዲጣራ ከተያዘው ነጥብ እና ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ለዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክርክር አከራካሪው ቤት በክፍለ-ከተማውም ሆነ በማሕበሩ በአመልካች ሥም ተመዝግቦ ይገኛል፤ ከማሕበሩ የተላከው እና የማሕበሩ ማሕተም ያረፈበት ውልም የሚያሣየው ይህንኑ ነው፤በማሕበሩ ትዕዛዝ በሥሜ ካርታ ተሠርቶ 1ኛ ተጠሪ ካርታው ሊሰጥ አይገባም ብለው በመከራከራቸው እንዳይሰጠኝ ተደርጓል በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ይህን ፍሬነገር በመግለጽ በበታች ፍ/ቤቶች የተከራከሩ ለመሆኑ የክርክሩ ሒደት አያሳይም፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 329/1 በበታች ፍ/ቤቶች ያልቀረበን አዲስ ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መቀበል የለበትም በማለት የሚደነግግ በመሆኑ አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡትን አዲስ ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ አመልካች በበታች ፍ/ቤቶች የተከራከሩት የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሠጠበትን ቤት ግንቦት 01 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ ውል ከ2ኛ ተጠሪ የገዙ መሆናቸውን በመግለጽ መሆኑን፤በማስረጃነት ያቀረቡት ውልም ግንቦት 01 ቀን 1998 ዓ.ም ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተፈጽሟል ያሉትን የመንደር ውል መሆኑን፤የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተላለፈበት በኮልፌ ቀራንዩ ክ/ከተማ ቀበሌ 05 በደብረአባይ ቁጥር 1 እና 2 ራሥ አገዝ የመኖሪያ ቤቶች ሕብረት ሥራ ማሕበር በ175 ካ.ሜ የሚገኘው ቤት የማሕበር ቤት መሆኑን፤አመልካች ባቀረቡት የሽያጭ ውል ላይ የማሕበሩ ማሕተም አርፎ መገኘቱ ብቻውን የመብት ማስተላለፉ የማሕበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቅዶ ያስተላለፈው ስለመሆኑ እና የመተካካት ሥርዓቱም በማሕበሩ ዘንድ ተመዝግቦ አግባብ ባለው አደራጅ መሥሪያ ቤት እንዲመዘገብ የተላለፈ ሥለመሆኑ የማያሳይ መሆኑ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 36294 ሰዎች በመደራጀት ያቋቋሟቸው የሕብረት ስራ ማህበራትን በተመለከተ የተደነገገው የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 ስለማሕበራቱ ዓላማ፣ ስለማሕበራቱ አመሠራረት፤ስለሚመሩባቸው መርሆዎች፣ ስለሕግ ሰውነትና ኃላፊነት፤ስለመተዳደሪያ ደንብ፣ ወዘተ በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ያካተተ መሆኑን፤የአዋጁ አንቀጽ 19 የማህበሩ አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ለማስተላለፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚችል፤የማስተላለፉ ሁኔታም የራሱ የሆነ የተለየ ስርዓት እንዳለው፤የማህበሩ አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ለማስተላለፍ ቢፈልግ ከማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቃድ ማግኘት እንደሚኖርበት፤በማህበር ተደራጅቶ የተገኘውን መብት የማስተላለፊያ ስርዓቱ በግል ከተገኘ መብት የተለየ መሆኑን፤መብት የሚተላለፍለት ወገንም በአስተላላፊው መብት መጠቀም የሚችለው በመተካት የማህበሩ አባል መሆን ከቻለ ብቻ መሆኑን፤ይህ የማስተላለፍ ሥርዓት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ከተመለከተው የማይንቀሣቀስ ንብረት መብት ማስተላለፊያ ስርዓት የተለየ መሆኑን፤በማህበር በመደራጀት የተሠራውን ቤት ሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕግ/ቁ 1723 ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር አያይዞ ማየቱ ትክክል እንዳልሆነ እና በማህበሩ ያለውን መብት ማስተላለፍን በተመለከተ ከአዋጅ ቁጥር 147/91 አንፃር መታየት ያለበት መሆኑን በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ላሉ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡

የሰበር ሰሚ ችሎቱ ይህን የሕግ ትርጉም ከሠጠ በኋላ የሕብረት ሥራ ማሕበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 402/96 የወጣ ቢሆንም ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ የአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 19 ድንጋጌን በተመለከተ ያሻሻለው ነገር የለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ገዝቸዋለሁ የሚሉትን የማሕበር ቤት በአዋጅ ቁጥር 147/91 መሠረት ከማሕበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቃድ አግኝተው እና በመተካት የማሕበሩ አባል ሆነው የተላለፈላቸው መሆኑን በመግለጽ በበታች ፍ/ቤቶች ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ ሥለሌለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን በአዋጅ ቁ 147/91 እና ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ ተቀብሎ ማጽናቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 163565 መጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ፤በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 150823 የካቲት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117953

ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ሰብስቤ አበበ ከጠበቃ እንድሪያስ ተፈራ ጋር ቀርበዋል

ተጠሪ፡ ወ/ሮ ፍቅርተ ካህሳይ ጠበቃ ወርቁ ገበየሁ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የኮንዶሚኒያም ቤት ለማስለቀቅ የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.170075 ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣ የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ ከሳሽ ባቀረቡት ክስ ሚች ልጂ ዘዉዱ አስራት በሕይወት በነበረ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ ባልቻ ሜዳ ሳይት ቀበሌ 05/08 የሕንጻ ቁጥር ቢ1 የቤት ቁጥር 11 የወለል ስፋት 48.79 ካ.ሜ ባለ ሁለት መኝታ መኖሪያ ቤት የነበረዉ ስለሆነ ተከሳሽ ሚች ልጂ ከሞተ በኋላ ባዘጋጀዉ ሐሰተኛ እና የሕጉን ፎርም ባልተጠበቀ ዉል ቤቱን ይዘው ስላሉ ቤቱን ለቀዉ እንዲያስረክቡኝ በማለት ከሷል፡፡

የሥር ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ሚች ይህን ቤት በወለድ አግድ ዉል አስይዞ ብር 350000 ተበድረዉ ገንዘቡን መመለስ ካልቻሉ መንግስት ቤቱን ለመሸጥ ያስቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ሲያበቃ ቤቱን ለእዳዉ መክፈያ እንዲሆን እና ባለቤትነቱን ወደ ተከሳሽ ስም ለማዘዋወር ተስማምተናል ዉል ፈርመናል፡፡ በዉሉ ላይ ያለዉ ፊርማ የሚች ስለመሆኑ በፎረንሲክ ተመርምሮ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ ስለዚህ ከሳሽ ቤቱን ለመረከብ ያቀረቡት ክስ ዉድቅ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ይህን ቤት በወለድ አግድ ዉል ይገፍለሀ ይበሉ እንጂ በፍትሐብሐር ሕጉ በተመለከተዉ አግባብ ዉሉን የማይንቀሳቀስ ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገብ ላይ ስለማስመዝገባቸዉ ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ የወለድ አግድ ዉል ተቋቋሚል ለማለት ስለማይቻል ቤቱን ለከሳሽ ሊያስረክብ ግዴታ አለባቸዉ በማለት ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ጳጉሜ 4 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት በአጭሩ ሚች ዘዉዱ አስራት ከአመልካች ገንዘብ ተበድረዉ ቤቱን ማስያዛቸዉን ምስክሮች አስረድተዋል፣ ዉሉም በልደታ ክ/ከተማ የይዞታ አስተዳደር ዉስጥ መያያዙን ለፍ/ቤቱ በተላከዉ ደብዳቤ ተረጋግጧል፣ አመልካች ቤቱን የያዝኩት ያለአግባብ ሳይሆን በወለድ አግድ ዉል በመያዝ ቤቱና ሰነዶቹን ተረክቤ እያለሁ፣ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዳስረክብ የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በአመልካችና በተጠሪዋ አዉራሽ መካከል ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ተደርጓል የተባለዉ የወለድ አግድ ዉሉን አከራካሪዉ ቤት በሚገኝበት ማዘጋጃ ቤት ከሚመለከተዉ ማህደር ጋር በወቅቱ እንዲያያዝ እንደተደረገ መሆኑን ማዘጋጃ ቤቱ ግለጾ እያለ የሥር ፍ/ቤት በዚህ ዉል ሊይዙ አይችሉም በማለት ቤቱን ለተጠሪዋ እንዲያስረክቡ የመባሉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ በታዘዘዉ መሰረት ህዳር 7 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡- የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የሚነቀፍበት ምንም የሕግ ምክንያት ስለሌለ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ ከሳሽን የሚያስገድድ ዉል ሳይኖር በሐሰተኛ ዉል እና የሕጉን ፎርም ባልጠበቀ ዉል የሚች ልጂ ንብረት የሆነዉን የኮንዶሚኒያም ቤት ይዞ ስለሚገኝ ቤቱን ለቀዉ እንዲያስረክበኝ በማለት የከሰሱ ሲሆን፤ የአሁን አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ መልስ ሚች በሕይወት በነበረበት ወቅት ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ወለድ አግድ ዉል ቤቱን አስይዞ ብር 350000 ተበድረዉ ቤቱን እና ሰነዱን ስላስረከበኝ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም የሚል ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር የአሁን አመልካች ከሚች ጋር ይህ ዉል ተዋዉለናል ባሉበት ወቅት በሕግ የተቀመጠ በኮንዶሚኒያም ቤት በተመለከተ ዉል የማድረግ ክልከላ ጊዜ ሳያልቅ መሆኑን አመልካች ራሳቸዉ ባቀረቡት ክርክር ያረጋገጡት ጉዳይ ነዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም በሕግ የተቀመጠ ክልከላ እያለ በዚህ ኮንዶሚኒያም ላይ የተደረገ ዉል ሕግን የሚቃረን እስከሆነ ድረስ ፍ/ቤት ለዚህ ዉል ዋጋ በመስጠት አመልካች በሕግ ፊት ዋጋ ባለዉ ዉል ቤቱን ይዟል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡

ከዚህም በላይ የአሁን አመልካች ቤቱን በወለድ አግድ ይገፎአለሁ እያለ ስለሆነ በሕግ ፊት ዉጤት ያለዉ ዉል አለ ወይስ የለዉም? የሚለዉም ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ ወለድ አግድን በተመለከተ የፍትሐብሐር ሕግ ቁጥር 3117--3130 ሥር ተመልክቷል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3117 እንደሚደነግገዉ ‹‹ወለድ አግድ ማለት አንድ ባለዕዳ ግዴታዉን ለመፈጸም ማረጋገጫ በማድረግ ለገንዘብ ጠያቂዉ የማይንቀሳቀሰዉን ንብረት ለማስረከብ የሚገደድበት ዉል ነዉ›› በማለት ደንግጎታል፡፡ የወለድ አግድ ዉልን ለማቋቋም የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣን መቋቋም የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንዳላቸዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3118 ተመልክቷል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ዉል የሚያቋቁሙት ድንጋጌዎች ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3052 እንደሚያመለክተዉ ይህ ዉል ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በማይንቀሳቀስበት ሀብት መዝገብ ካልተጻፈ ምንም ዓይነት ዉጤት እንደሌለዉ ነዉ፡፡ ይህ የምዝገባ አፈጻጸም ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3053 ሥር ተመልክቷል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን የወለድ አግድ ዉል አደርገናል የሚለዉን ዉል በዚህ አግባብ የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ እንዳልተመዘገበ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ አግባብ ተፈጽሟል እና የሰበር አጣሪ ችሎትም እንደጭብጥ አድርጎ የያዘዉ ይህ ዉል በቤቱ ማህደር ዉስጥ መገኘቱን ነዉ፡፡ ነገር ግን ይህ ዉል መቼ የቤቱ ማህደር ዉስጥ እንደተገኘ እና ይህ በሕጉ የተመለከተዉን የምዝገባ ሥርዓት ያሟላ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

በዚህ ረገድ የልደታ ክ/ከተማ ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ለሥር ፍ/ቤት በጻፈዉ ደብዳቤ ከሳሽ የቤቱ ስመ ሀብት ከሚች ወደ እሳቸዉ እንዲዛወርላቸዉ ጠይቀዉ፣ ነገር ግን ካርታ ጠፋኝ ስላሉ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ በ4/2/2004 ዓ.ም ታዉጆ፣ አመልካች በ25/3/2004 ዓ.ም የስም ዝዉዉር ቢደረግ መብቴን ይነካል በማለት በማመልከቱ በዚህ ምክንያት ከማህደሩ ጋር እንደተያያዘ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን አመልካች ይህን ዉል ከላይ በተመለከተዉ የሕግ ድንጋጌዎች አግባብ ዉሉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ መመዝገቡን የሚያመለክት አይደለም፡፡ ይህ ዉል ለክርክር ምክንያት በሆነዉ ኮንዶሚኒያም ቤት ላይ የተደረገዉ በሕግ የተቀመጠዉ ክልከለ ባለበት ሁኔታ ስለሆነ የልደታ ክ/ከተማ ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ዉሉን ይመዘግባል ተብሎም አይገመትም፡፡ በመሆኑም በሕግ ፊት የሚጸና የወለድ አግድ ዉል በአመልካች እና በሚች ዘዉዱ አስራት መካከል ተደርጓል ለማለት አይቻልም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በአመልካች እና በሟች መካከል በሕግ ፊት የጸና የወለድ አግድ ዉል መደረጉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስለሌለ አመልካች ቤቱን ያለ አግባብ ይዞ ስለሚገኝ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ መወሰናቸዉ በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.191279 በ12/10/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.170075 ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. በ15/2/2007 ዓ.ም የተሰጠ የአፈጻጸም እግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጭ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 127587

ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጸውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ፐርፌክት ትራንዚትና ትራንስፖርት ኃላ/የተ/የግ/ ማኅበር - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ አህመድ ዳውድ (አቶ አህመድ ሁሴን ወኪል) - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የአሁኑ አመልካች ሚያዝያ 28 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ. 4627 ታኅሳስ 27 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁ. 4105 መጋቢት 13 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ዳኝነት በመጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3- 30303 ኢት የተሳቢ ቁጥር 09839 ከባድ ተሸካርካሪ መኪና ከጅቡቲ አዲስ አበባ በመንገዝ ላይ እያለ በአፋር ክልል ዲቾአቶ ተብሎ በሚታወቀው ቦታ በደረሰው ግጭት ንብረትነቱ የተጠሪ በሆነ መኪና ላይ ጉዳት በመድረሱ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በመኪናው ላይ ለደረሰበት ጉዳት ብር 350.000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ/፤ መኪናው የሚንቀሳቀስበት ከፒታል ቢያንስ ከአደጋው በኃላ ሶስት ዙር ሽያጭ ተካሂዶበት ሊገኝ የሚችለው በአንድ ዙር ብር 20.000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ x የ3 ዙር 60.000.00 /ስልሳ ሺህ/ ብር፣ መኪናው አደጋው በደረሰበት ቦታ ከአንድ ወር በላይ አመልካች በ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ አስገምታለሁ ብሎ ሲያጉላላ በዘብ ለማስጠበቅ ብር 5.000.00 /አምስት ሺህ ብር/፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የትራንስፖርት ማስጫኛና ማውረጃ ለሰራተኛ 1000.00 /አንድ ሺህ/ ብር እንዲሁም በዚህ ጉዳይ አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ያወጣሁት የአልጋ፣ የምግብና የትራንስፖርት ወጪና ኪሳራ ብር 20.000.00 /ሃያ ሺህ/ እንደሆነ ገልጾ በድምሩ 441.000.00 /አራት መቶ አርባ አንድ ሺህ/ ብር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካችም በበኩሉ በተጠሪ መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት ለአመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው ሕብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ የጉዳቱን ካሳ ለመክፈል ወይም እንደአስፈላጊነቱ መኪናውን ለማስጠገን ዋስትና ሰጥቶ እያለ ተጠሪ አመልካች ለጉዳቱ ዋስትና አላቀረበም በማለት በተሳሳተ መንገድ የመዳኘት ሥልጣን ለሌለው አፋር ክልል አልዳአር ወረዳ ፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ በማሰጠት የአመልካች መኪና እንዳይንቀሳቀስ ከሶስት ወራት በላይ እንዲቆም በማድረጉ አመልካች በዚህ ምክንያት የተቀቋረጠበትን አንድ ወር ገቢ 50.000.00 /አምሳ ሺህ/ ብር የሶስት ወር 150.000.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ/ ብር እንዲከፍል ሲል የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡

ሁለቱንም ክሶች የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን እና የጣልቃ ገቡን የህብረት ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኅበር ክርክር ፣ የምስክሮችን ቃል እንዲሁም የሰነድ ማስረጃን መርምሮ የአሁኑን አመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ በማድረግ የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ ተጠሪ የመኪናውን ግምት 350.000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ/ ብር፣ የተቋረጠ የሶስት ወር ገቢ 60.000.00 /ስልሳ ሺህ/ ብር፣ ለመኪናው ጥበቃ የተከፈለውን 5.000.00 /አምስት ሺህ/ ብር በድምሩ 415.000.00 /አራት መቶ አስራ አምስት ሺህ/ ብር ከ10% የጠበቃ አበል እንዲሁም ዳኝነት በታርፍ መሠረት እና ሌሎች ወጪዎች ካሉ ዝርዝር የማቅረብ መብት ለረቺ ጠብቀናል በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙን ተቀብሎ የግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታ ይዘቱም በአጭሩ፡-

1. ፍርድ ቤት በገለልተኛ ባለሙያ የተገመተው ግምት እያለ በፖሊስ ግምት ተመስርቶ 350.000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ/ ብር የጉዳት ከሳ መወሰኑ ያለአግባብ ነው፡፡
2. ተጠሪ የተቋረጠበት 60.000.00 /ስልሳ ሺህ/ ብር እንዲሁም ለጥበቃ የወጣ ወጪ ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ እንዲከፈለው የሥር ፍርድ ቤት ከመወሰኑ ወጪ አንዳችም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ ሳይቀርብ የሰጠው ውሳኔ አቤቱታን ሳይሆን ማስረጃን መሠረት አድርጎ የመወሰን መሠረታዊ መርህን የተጻረረ ፍጹም የዳኝነት ግድፈት ነው፡፡

3. ተጠሪ ለጠበቃ ስለመክፈላቸው ያቀረቡት ማስረጃ በሌለበት እና መኪና ወደ ሀገር ቤት እየገባ እያለ በመሆኑ ገቢ ማስገባት ባልጀመረበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤት የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈል መወሰኑ ፍርድ ቤቱ ፍትሓዊ እንዳልሆነ በቂ ማስረጃ ነው፡፡
4. አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ያቀረበውን ክስ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው በህግ አግባብ አይደለም፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ኃላፊነትን በተመለከተ ያቀረቡት ክርክር ባይኖርም የከሳ መጠኑን በተመለከተ ግን ያቀረቡት ክርክር በአግባቡ በሥር ፍርድ ቤቶች ተጣርቶ ውሳኔ የተሰጠበት መሆን ያለመሆኑንና እንዲሁም በአመልካች የቀረበው የተከሳሽ ከሳሽት ክስ ውድቅ ተደርጎ የታለፈበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በቀን 20/01/2009 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን አመልካቹም ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን ጉዳዩን በሶስት ጭብጮች ከፍለን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

1. ፖሊስ በተጠሪ መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት ገምቶ ለማቅረብ በህግ የተሰጠ ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? በዚህ ረገድ የተገመተው ግምት በገለልተኛ ባለሙያ የተገመተ ነው ለማለት ያስችላል ወይስ አያስችልም?
2. አመልካች የተቋረጠበትን ገቢ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? ለመኪና ጥበቃስ የወጣውን ወጪ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም?
3. አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ያቀረበውን ክስ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፤

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በተጠሪ መኪና ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ኃላፊነትን መሠረት አድርጎ የተነሳ ክርክር ባይኖርም ጉዳቱን ተከትሎ ሊካስ የሚገባው የካሳ ግምት በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ያስነሳ ከሆነ ሊጣራ የሚገባው እንዴት ነው? ግምቱን አጣርቶ የሚያቀርበውስ ማነው? የሚሉ ነጥቦች በቅድሚያ ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው፡፡ መኪናው ላይ በደረሰው ጉዳት ከጥቅም ውጪ የሆኑ የመኪና እቃዎች በማንኛውም ምስክር የሚረጋገጡ ሳይሆኑ በዘርፉ እውቀት ባላቸው ባለሙያዎች የሚረጋገጡ እንደሆኑ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደዚህ ያሉ ነገሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ፍርድ ቤት የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 136 ድንጋጌን በመከተል ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) በመሾም እንዲጣራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ያስችል ዘንድ ጉዳዩ በሚመለከው ባለሙያ እንዲጣራ ማድረግ የዳኝነት አካሉ ዋነኛው ተግባር ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ትራፊክ ፖሊስ በመኪናው ላይ የደረሰውን የጉዳት ካሳ ግምት ለማረጋገጥ ሙያው ብቃት መኖር ያለመኖሩን እንዲሁም ለዚህ አካል በህግ የተሰጠውን ሥልጣን ከዋጅ ቁጥር 681/2002 አንጻርመመልከት ተገቢ ነው፡፡ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 /25/ እና 37 /2/ /ሐ/ እንደሚያመለክተውየትራፊክ ተግባርና ኃላፊነት ተሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ አስፈላጊውን ቴክኒካዊ ብቃት እንዳላቸው መመርመር እና በአደጋው ጊዜ የአደጋውን መንሥኤ ማጣራት እንዲሁም ከአደጋው በኃላ ተሽከርካሪው መንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ ቴክኒካዊ ብቃት እንዳለው ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በተሽከርካሪዎች ላይ የደረሰ ጉዳትን በተመለከተ የገበያ ዋጋ አስልቶ ግምት ለማቅረብ በህግ ለትራፊክ ፖሊስ የተሰጠው ተግባርም ሆነ ኃላፊነት የለም፡፡ በሌላ አነጋገር በመኪናው ላይ የደረሰውን ጉዳት ብቻ ሳይሆን ንብረቱ በወቅቱ ለገበያ ቀርቦ ሊያወጣ የሚችለው የገበያ ዋጋ /Market Value/ ገምቶ ለማቅረብ የሚችለው ፖሊስ ሳይሆን በዚህ ዘርፍ በቂ እውቀት፣ ክህሎት እና ሙያ ያለው ሰው ነው፡፤ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ በፖሊስ የቀረበው ግምት መኪናው ላይ የደረሰውን ጉዳት በተመለከተ የገበያ ዋጋን ግምት መጠን በአግባቡ አጣርቶ ለማቅረብ በቂ ሙያዊና ቴክኒካዊ ብቃት ባለው ባለሙያ የቀረበ ግምት ባለመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የተሽከርካሪ ዋጋ ግምት የመተመን አገልግሎት መስጠት በአዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀጽ 7 /1/ዘ/ መሠረት የትራንስፖርት ባለሥልጣን ስለመሆኑ የሚደነግግ ቢሆንም የገበያ ቃጋን መሰረት አድርጎ እስካልቀረበ ድረስ ተቀባይነት የሚሰጠው አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል የአሁኑ አመልካች በግራ ቀኙ በኩል በተደረሰው ስምምነት መሠረት ጉዳት የደረሰበት መኪና ወደ አዳማ ከተማ ተጓጉዞ በገለልተኛ ባለሙያ ከተመረመረ በኃላ የጉዳቱ ካሳ መጠን ብር 108.747.83 /አንድ መቶ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ሰባት ብር ከሰማኒያ ሶስት ሳንቲም/ ተረጋግጦ ያለና ሕብረት ኢንሹራንስ ግምቱን ለመክፈል ፍቃደኛ ሲሆን ተጠሪ ግን የተገመተውንም ግምት ለመቀበል እምቢተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሊወስን የሚገባውም ይህ ግምት ነው ሲል ይከራከራል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ተገምቷል በተባለው አካል መኪናው ላይ የደረሰው የጉዳት መጠን እንዲገመት ያለመስማማቱን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ይህ ክርክር የሚያመለክተው በግራ ቀኙ መካከል የጋራ መስማማት እንዳልነበረ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም የተደረሰበት ስምምነት ስለመኖሩ ለሥር ፍርድ ቤት የቀረበና ያስረዳ ማስረጃ እንደሌለ ውሳኔው ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር በግራ ቀኙ በጋራ በተደረሰ ስምምነት መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግምት የተሠራለት /የወጣለት/ ስለመሆኑ በማስረጃ የተደገፈ ክርክር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት በዘርፉ በቂ እውቀትና ክህሎት ባለው /ባላቸው/ ባለሙያ /ባለሙያዎች/ ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል ብለናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የአሁን ተጠሪ መኪናው ጉዳት ሳይደርስበት ቢሸጥ ኖሮ በሶስት ወር ውስጥ ሊያተርፍ የሚችለውን ብር 60.000.00 /ስልሳ ሺህ/ ገምቶ ያቀረበው በሥር ፍርድ ቤት ተፈርዶለታል፡፡ በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት ጠቅላላ ጉዳት / Total Loss/ እንደሆነ ከተጠሪ ክርክር ተረድተናል፡፡ እንዲህ ዓይነት ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ በንብረቱ ላይ የደረሰውን አጠቃላይ ግምት ከመጠየቅ ውጭ ይገኛል ተብሎ የሚታሰበውን ገቢ መጠየቅ አግባብነት አይኖረውም፡፡ በህጉ መሠረት የጉዳት ክሳ ክፍያ ዓላማው ተጎጂው በደረሰበት ጉዳት ልክ ጉዳት አድራሹ ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ እንዲከፍል በማድረግ ወይም የደረሰውን ጉዳት በማሠራት /በማስጠገን/ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ ማድረግ ነው፡፡ ይህንን ከፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 2090 /1/፣ 2092 እና 2119 /1 እና 2/ መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ የአመልካች ኃላፊነት በተጠሪ መኪና ላይ ለደረሰበት ጉዳት በጉዳቱ ልክ ተመጣጣኝ ካሳ መክፈል ወይም ጉዳቱን በመጠገን መኪናው ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ ወጭ ከደረሰው አደጋ ጋር ግንኙነት የሌለውን ክፍያ አመልካች የሚከፍልበት ህጋዊ ግዴታ ሊኖር አይችልም፡፡

የመኪና ጥበቃ ወጪን በተመለከተ አመልካች መኪናው ፖሊስ ዘንድ ስለቆየ ተጠሪ ለመኪና ጥበቃ የሚከፍልበት ምክንያት አይኖርም ሲል የተከራከረ ቢሆንም ይህን የሚደግፍ ማስረጃ ለሥር እንዳቀረበ የሚያመለክት ነገር ተያይዞ በቀረበልን ውሳኔ ላይ ስለሌለ በዚህ ረገድ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የአመልካች መኪና በወረዳ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታግዶ መቆየቱን የግራ ቀኙ አይካካዱም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚያመለክተው መኪና ለጊዜው ታግዶ የቆየው አመልካች ዋስትና እንዲያስይዝ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 151 እና 152 መሠረት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ፍርድ ቤቱ የተከሰተውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባትና በማጤን የሰጠ ትዕዛዝ በመሆኑ በተጠሪ ክፉ ልቦና ምክንያት የተፈጸመ ድርጊት ሆኖ አይታይም፡፡ አመልካች ተጠሪ ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት መኪናውን አሳግዶ በማቆየቱ የሶስት ወር 150.000.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ/ ብር ኪሳራ አድርሶብኛል በማለት ያቀረበው የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ በሥር ፍርድ ቤት ተቀባይነትን ማጣቱ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመጨረሻም በመኪናው ላይ የደረሰውን የጉዳት ካሳ ግምት ብር 350.000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ/ እንዲሁም ይገኝ የነበረ ገቢ ነው ተብሎ 60.000.00 /ስልሳ ሺህ /ብር አመልካች ለተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ከላይ በዝርዝር ከተገለጹ ህጋዊ ምክንያቶች አንጻር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ. 4627 በቀን 04/05/2008 ዓም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁ. 4105 መጋቢት 13 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ለተጠሪ መኪና ጥበቃ የተከፈለ ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ አመልካች እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተቀባይነት የለውም ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. በተጠሪ መኪና ላይ ለደረሰ ጉዳት የካሳ ግምት ብር 350,000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ እንዲሁም ለተቋረጠበት ገቢ ብር 60,000.00 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ የተወሰነው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. ለተቋረጠ ገቢ አመልካች ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ/ ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

5. በመኪናው ላይ የደረሰውን የጉዳት ካሳ ግምት በተመለከተ ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ በአንደኛ ጭብጥነት ተይዞ በዝርዝር በተገለጸው መሠረት ስለ ጉዳዩ በቂ እውቀትና ክህሎት ባለው ባለሙያ በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት ተጣርቶ እንደገና እንዲወሰን በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት ለአውሲረሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልስናል፡፡
6. ሐምሌ 20 ቀን 2008 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡
7. ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይላክላቸው፡፡ በ20/11/08 ዓ/ም የተሰጠ እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 117164

ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ተክለ ሐጎስ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ፀጋዬ ገ/ዓዲቅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳይ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ወቅት ያፈራናቸው የማይንቀሳቀስ የጋራ ንብረቶች በን/ስ/ላ/ክ/ከ ቀበሌ 09/14 የቤት ቁጥር 889፤890 እና 936 በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቅድስት ማሪያም ከፍተኛ ክሊኒክ የንግድ ድርጅት ከነቤቱ በተጠሪ ስም በአዲግራት ከተማ ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 461 የሆነ መኖሪያ ቤት፤በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ቤት ቁጥር 081 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የጎማና ባሌስትራ የንግድ ድርጅት እና ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የንግድ ድርጅት፤በተጠሪ ስም የተመዘገቡ የተለያዩ መኪኖች፤የአክስዮን ድርሻ በፋርማ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር በአመልካችና ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ደርሻ እናበአሉላ አባነጋ ማህበር ውስጥ በተጠሪ የተከፈለን ገንዘብ፤ ከን/ስ/ላ/ክ/ከተማ፤ቂርቆስና ልደታ የሚገኙ ድርጅቶች የተገኘው ገቢ አመልካች ከቤት ከወጡበት ከየካቲት ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ የተሰበሰቡ ገቢዎች፤በዳሸን እና ህብረት ባንክ የተቀመጠ ገንዘብ እነዚህ የተዘረዘሩት የጋራ ሀብቶችን ተጠሪ እንዲያከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠሪ በኩል የተሰጠ መልስ ከድርጀቶቹ የሚፈለግ እዳ አለ፤እንዲሁም አመልካች ልጆቻችንን ስንድርና ለንግድ ስራ የሚሆን ገንዘብ ተበደር ብላኝ በጠቅላላው ብር 3,880,000/ ሶስት ሚሊየን ስምንት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር/ ተብድሬያለሁ፤በመሆኑም አመልካችና ተጠሪ ለዚህ ገንዘብ ባለእዳዎች ስለሆንን በቅድሚያ ይህ ገንዘብ እንዲከፈል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ህዳር 24 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ በን/ስ/ላ/ክ/ከ ወረዳ 1 በካርታ ቁጥር ሊዝ-እጣ-408-93-24552/01 የሆነው አቶ ተከስተ ጸጋዬ ለአመልካች በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በተፈፀመ ስጦታ ውል በስጦታ የተላለፈላቸው ቤትእና የቤት ቁሳቁሶች የጋራ ሀብት ይባልልኝየሚል ክስ አቅርበዋል፡፡አመልካችም ለተከሳሽ ክሳሽነት ክሱ ታህሳስ 11 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የመከላከያ መልስ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአመልካች ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላአመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ በማለፍ በፍሬ ነገሩም ላይ በን/ስ/ላ/ክ/ከ ቀበሌ 09/14 የቤት ቁጥር 889፤890 እና 936 በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቅድስት ማሪያም ከፍተኛ ክሊኒክ በውስጡ የሚገኙና በቬርቫል ተቆጥሮ በዝርዝር ከተከበሩ እቃዎች ጭምር፤በአዲግራት ከተማ ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 461 የሆነ መኖሪያ ቤት፤በቁርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ቤት ቁጥር081 የጎማና ባሌስትራ የንግድ ድርጅት፤ሶስት መኪኖች መኖራቸው የተረጋገጡትን ኮድ 3-1160 አ/አ የሆነ አንቡላስ፤ኮድ 2-15532 አ.አ እና ኮድ3-11628 ኢ.ት ተሳቢ የጋራ ስለሆኑ ከተስማሙ በአይነት እኩል እንዲካፈሉ ወይም አንዱ ለሌላው ግምቱን በመክፈል እንዲያስቀር ወይም በዚሁ ካልተስማሙ ንብረቱ በሀራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉት ተወስኗል፡፡

ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የንግድ ድርጅት በተመለከተ የመንግስት ወይም ቀበሌ ቤትን በተመለከተ ባካራያቸው ቀበሌ ወይም መንግስት በሚያስተዳድረው የአስተዳደር ደንብ መሰረት አስተዳዳራዊ መፍትሄ እና ምላሽ በዚያው ጠይቆ ከማረጋገጥ ባለፈ ፍርድ ቤቱ ለድርጅት ስራ የተከራዩትን የመንግስት ቤት የጋራ ንብረት ነው ብሎ በትዳር እንደተፈራ ንብረት ይከፋፈሉ በሚል ውሳኔ ውስጥ አይገባም በማለት ባለመቀበል ወስኖ አልፎታል፡፡ ፋርማ ትሬዲንግ ሊንክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የባላና ሚስት የጋራ ድርሻ መኖሩ የታመነ ቢሆንም ክፍፍሉን በተመለከተ በንግድ ህግ መሰረት የሚፈርስና ሂሳብ የሚጣራ ካልሆነ በቀር እንደሌላው የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍሉ የሚወሰንበት የህግ አግባብ አይኖርም ሲል ውሳኔ ሰጥቦታል፡፡ በአሉላ አባነጋ ማህበር ድርሻ እንዲከፈል ያቀረቡት ጥያቄ በማስረጃ ያልደገፈ እና በተጠሪ ስም በራሱ ተክል ማህበር ድርሻ መኖሩ ያልተረጋገጠ ነው በማለት ባለመቀበል አልፎታል፤ህብረት ባንክ አ/ማ ጎፋ ቅርንጫፍ መኖሩን የተረጋገጠው ብር 402.30 እኩል እንዲካፈሉ፤ከአራቱ የንግድ ዘርፍ ክሊኒክ፤ ከጎማ መሸጫ፤ከፔንስዬንና ትራንስፖርት ከተሰበሰበው ገቢ ብር 293,985.60 የዚህ ግማሹ ተጠሪ ለአመልካች ብር 146,992.80 እንዲከፍሏቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተወስኗል፡፡ በሲፒኦ ቁጥር 942560 በሆነው ለገቢዎች እና ጉምሩክ መከፈሉን የተረጋገጠው ብር 206,441.43 አመልካች ለተጠሪ ከተከፈለው ብር 103,220.71 ሊጋሩ እና ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል በተጠሪ ክስ የቀረበበት በሁለት ፎቅ መኖሪያ ቤት አመልካች በስጦታ የተሰጠኝ የግል ንብረት በማለት ያቀረቡት ክርክር ውድቅ በማድረግ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት በመሆኑ እንዲሁምየቤት ቁሳቁሶች በተመለከተ ድሬሲንግ ቴብል፤አልጋ የሸሚዝ ማስቀመጫ፤ኮሚዶኖ፤የጫማ መደራደሪያ፤ሁለት ቁም ሳጥን የሳሎንና የኪችን እቃዎችን፤6 አልጋዎችን ፤2 ትላልቅ ፍሪጆችን፤አንድ ቋሚ ፊሪጅ፤እንድ ቡታ ጋዝ ምድጃ፤የሳሎን የሌዘር ሶፋ እና ትልቅ ቴሌቪዥን የባልና ሚስት የጋራ ንብረታቸው ነው በማለት ከተስማሙ በአይነት እኩል እንዲካፈሉ ወይም አንዱ ለሌላው ግምቱን በመክፈል እንዲያስቀር ወይም በዚሁ ካልተስማሙ ንብረቱ በሀራጅ ተሽጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉት ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በተሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካች ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በሰጠው ማስረጃ ላይ የስር ፍርድ ቤት ሒሳቡን ሲሰራ በፈጸመው ስህተት ላይ የቀረበውን ቅሬታ ላይ የተመለከተውን ነጥብ ብቻ በማሻሻል ሌላው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ክፍል በማፅናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 11ቀን 2007 ዓ.ም በዓፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 7 የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ድርጅት ቤቱ የቀበሌ ስለሆነ የጋራ አይደለም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ በቤት ነው መታየት ያለበት ወይስ በድርጅት በድርጅቱ ውስጥ ያለው ንብረት ሳይወሰን መታለፉ አግባብነት በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበትበታዘዘው መሰረት መጋቢት 1 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም የአመልካች ጥያቄ በልደታ ክ/ከተማ የቤት ቁጥር 1035 የሆነ ንግድ ድርጅት ያለ መሆንና በትዳር ዘመን የተፈራ መሆኑ ያልተካደ በንግድ ህጉ መሰረት የንግድ ድርጅት/መደብር/ ከንግድ ቤቱ ተለይቶ የሚታወቅና ይህ የጋራ ሀብት የሆነው የንግድ ድርጅት ክፍፍል እንዳይፈፀምበት የሚከለክል ህግ ሳይኖር ክፍፍል ሊፈፀምበት አይችልም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠው ውሳኔ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ የንግድ ቤት ቁጥር 1035 የሆነው የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ክፍፍል የሚፈፀምበት ሆኖ ክፍፍል ከመፈፀሙ በፊት ድርጅቱ የግብር ዕዳ ያለበት በመሆኑ ይህ የግብር ዕዳ በቅድሚያ ሊከፈል ይገባል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንግስት በኪራይ የተገኘው ቤት የጋራ ንብረት ነው ብሎ መጠየቁ አግባብነት የለውም፤የንግድ ቤቱ አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደትና በአመልካች ከቀረበው ክስ ይዘት መገንዘብ የተቻለው በልደታ ክ/ከተማ የሚገኘው የንግድ ድርጅት የጋራ ንብረት ተብሎ ክፍፍል እንዲደረግ እንጂ የመንግስት ቤት የሆነው የንግድ ቤቱ አይደለም፡፡ በተጠሪ በኩልም መልስ ሲሰጡ ድርጅቱ መኖሩን አልተካደም፡፡ በንግድ ቤቱ የጋራ ንብረት ተብሎ ክፍፍል እንዲደረግ የቀረበበት ጥያቄ ተደርጎ በተጠሪ በዚህ ችሎት ያቀረቡት መልስ ተቀባይነት የለውም፡፡አመልካች በጋራ ንብረትነት ፍርድ ቤቱ እንዲያካፍላቸው የጠየቁት በልደታ ክ/ከተማ የቤት ቁጥር1035 ያለውን የንግድ ድርጅት ንግድ ህግ ቁጥር 124 በሚደነግገው መሰረት በንግድድርጅትነቱ መጠሪያና በውሰጡ የሚገኘው የንግድ ማካሄጃ ዕቃ የሚመለከት ሆኖ እያለ እንደ ባልና ሚስት የጋራ ንብረት በፍርድ ቤት ውሳኔ የሚሰጠው አይደለም በማለት መወሰኑ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከንግድ ህግ ቁጥር 127 ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የአንድ ንግድ ድርጅት መሰረታዊ አካል የንግድ ድርጅቱ መልካም ዝና፤ ስም፤ በደንበኞች የተለመደ መሆኑ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ነገሮች አካትቶ የሚይዝ ነው፡፡ከዚህ ውስጥ ንግዱ የሚከናወንበትን ክፍል የመከራየት መብት የንግድ ድርጅት አንደኛው ክፍል እንደሆነ ይህ ሰበር ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ የን/ሕ/ቁጥር 127 ድንጋጌ ይዘቱና መንፈሱ ይህ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁጥር 33760፣ 33954 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም የድርጅቱን መልካም ስም፤የመከራየት መብትና በቤቱ ውስጥ የሚገኘው የንግድ ዕቃ የጋራ መሆኑ በተጠሪ ሳይካድ የመንግስት ወይም ቀበሌ ቤትን በተመለከተ ባካራያቸው ቀበሌ ወይም መንግስት በሚያስተዳድረው የአስተዳደር ደንብ መሰረት አስተዳዳራዊ መፍትሄ እና ምላሽ በዚያው ጠይቆ ከማረጋገጥ ባለፈ በፍርድ ቤት ክፍፍል እንዲደረግ ውሳኔ ሊሰጥበት አይቻልም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.76838 ሐምሌ 28ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 157144 ሰኔ24 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔበፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በስር ፍርድ ቤቶች በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የንግድ ድርጅት የመንግስት ንግድ ቤት ስለሆነ በሚያስተዳድረው አካል የሚታይ ነው በማለት የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የንግድ ድርጅትን በንግድ ቤቱ የመከራየት መብት ጭምር የጋራ ሀብት ነው ብለናል፡፡
4. በሌሎች ጉዳዮች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔዎች እንደፀኑ ናቸው፡፡
5. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የንግድ ድርጅት ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎች ተገቢውን ማጣራት ካደረገ በኋላ ዕቃዎቹእንዲሁም የንግድ ድርጅቱ ግምት የመከራየት መብትን ጨምሮ ክፍፍል በተመለከተ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረትተመልሶለታል፡፡
6. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዘገቡ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 127714

መጋቢት 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ቃልኪዳን ይኸነው የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ኢብሳ ያደታ ጠበቃ ዘውዱ እንዳለው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከጋብቻ መኖር አለመኖር ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም በባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤትበመዝገብ ቁጥር 03-01390 በ01/10/2007 ተሰጥቶ በአማራብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41000 በ13/07/2008 ዓ.ም የተሻሻለው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ግራ ቀኙ የተለያዩ ክልሎች ነዋሪዎች ነው በሚል አመልካች ክሱን ያቀረቡት ለባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በ23/04/2007 ዓ.ም ተዘጋጅቶ የቀረበው ክስ አጭር ይዘት፡- ከተጠሪው ጋር በ1999 ዓ.ም ጋብቻ መስርተው ሲኖሩ በ2005 ዓ.ም ያብስራ ኢብሳ የተባለች ልጅ መውለዳቸውን፣ጋብቻውን በመሰረቱበት ጊዜ ተጠሪው ከጋብቻው በፊት ያፈሩት ንብረት የጋራ እንዲሆን መስማማታቸውን፣የውሉ ቅጂም የሚገኘው በተጠሪው እጅ መሆኑን፣በተጠሪው እጅ የሚገኝ የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ግምት ብር 16,960,000 መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ጋብቻው እንዲፈርስ፣ተጠሪው የልጅ ቀለብ እንዲቆርጡ እና የጋራ ንብረቱን አጋማሽ ብር 8,480,000 ለአመልካች እንዲያካፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተጠሪው በበኩላቸው በ05/06/2007 ዓ.ም. በሰጡት መልስ መደበኛ ነዋሪነታቸውም ሆነ ንብረቶቹ የሚገኙት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ በመሆኑ እና የአመልካቿ መኖሪያ አድርሻም እንደዚሁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካስቀደሙ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከአመልካች ጋር ጋብቻ የሌላቸው መሆኑን፣የጋብቻ ጽሁፍ በተጠሪው እጅ ይገኛል የተባለውም ሀሰት መሆኑን፣ልጅም ያልወለዱ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በዝርዝር የተከራከሩ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል።

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የአመልካቿ መደበኛ መኖሪያ ቦታ ባህርዳር ከተማ እንደሆነ በመረጋገጡ በተጠሪው የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ይሁን እንጂ በግራ ቀኙ መካከል ጋብቻ መኖሩን አመልካች ማስረዳት ያልቻሉ መሆኑን፣ጋብቻ ከሌለ ደግሞ አመልካች የልጅ ቀለብ መጠየቅ የሚችሉት በቅድሚያ የልጁን አባትነት በማረጋገጥ በመሆኑ ቀለብ ሊቆረጥ የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን ገልጾ ክሱን ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶአል።ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ውሳኔውን አሻሽሎ ጋብቻ የለም መባሉ ተገቢ ቢሆንም ህጻኗ ልጃቸው መሆኗን ግን ተጠሪው በሽማግሌዎች ፊት ማመናቸው በምስክር የተገለጸ ሆኖ ሳለ መታለፉ ተገቢ ባለመሆኑ ህጻን ያብስራ ኢብሳ የተጠሪው ልጅ ናት፣ተጠሪው በየወሩ ብር 1,000 ቀለብ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል።

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰጡት ጋብቻ ስለመኖሩ በአመልካች በኩል የቀረበውን ማስረጃ መዝነው/አገናዝበው/ መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።በሌላ በኩል ህጻን ያብስራ የተጠሪው ልጅ ናት በሚል በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 127767 በ30/02/2009 ዓ.ምየተሻረ መሆኑን በመግለጽ ውሳኔው ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝላቸው ተጠሪው 29/03/2009 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ ጠይቀዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ለጉዳዩ በጭብጥነት ወደተያዘው የፍሬ ነገር ክርክር ከመገባቱ በፊት የባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አስተናግዶ ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን ኖሮት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ አስቀድሞ እልባት ማግኘት የሚገባው መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ነጥብ አንጻር መርምረናል።

በዚህም መሰረት አመልካች ክሳቸውን ለባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጋብቻው የተፈጸመው እና ግራ ቀኙም አብረው ሲኖሩ የነበረው በአማራ ብሔራዊ ክልል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በባህርዳር ከተማ ውስጥ ሆኖ ክሱ በተመሰረተበት ጊዜ ግን አመልካቿ እዚያው ባህርዳር ከተማ የሚኖሩ ሆኖ ተጠሪው የሚኖሩት ደግሞ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ መሆኑን መሰረት በማድረግ እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።እንደተባለው መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 5 (2) ስር ተመልክቶአል።ከጋብቻ ጉዳይ ጋር ተያይዘው የሚነሱት የክልል ጉዳዮች የሚታዩት በክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት መሆኑ እየታወቀ የባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ለማስተናገድ የቻለውም ይህንኑ አዋጅ መሰረት አድርጎ ጉዳዩ የፌዴራል ነው በማለት ነው።ይሁን እንጂ የተጋቢዎቹ መደበኛ ነዋሪነት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተቆጥሮ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 5 (2) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ከጋብቻ ጋር ተያይዘው በሚነሱ ጉዳዮች ረገድ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ነው።

በጋብቻ የተሳሰሩ አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት በተለያዩ ምክንያቶች ተለያይተው የሚኖሩባቸው ሁኔታዎች በተግባር እንደሚያጋጥሙ ይታወቃል።ተለያይተው የሚኖሩትም በአንድ ክልል ውስጥ ወይም በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንዲሁም በተለያዩ አገሮች ውስጥ ጭምር ሊሆን ይችላል።ይህ ማለት ግን የተጋቢዎቹ መደበኛ መኖሪያ ቦታ የተለያየ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም።ይልቁንም ጋብቻው ከተቋቋመበት መሰረታዊ ዓላማ አንጻር ተጋቢዎቹ በመርህ ደረጃ አንድ መደበኛ መኖሪያ ቦታ እንዳላቸው ግምት የሚወሰድበት ነው።በመሆኑም ጋብቻው እስካልፈረሰ ወይም በተራዘመ የጊዜ ቆይታ ምክንያት በተግባር እንደፈረሰ እስካልተቆጠረ ድረስ የተጋቢዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች ለጊዜው በተለያዩ ቦታዎች መኖር መደበኛ መኖሪያቸውን በተለያዩ ቦታዎች አድርገዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም።

በተያዘው ጉዳይ ጋብቻው የተፈጸመው እና ግራ ቀኙም አብረው ሲኖሩ የነበረው በአማራ ብሔራዊ ክልል በባህርዳር ከተማ ውስጥ መሆኑን አመልካቿ በክስ ማመልከቻቸው ላይ ገልጸዋል። በክሳቸው መሰረት ማስረዳት የሚጠበቅባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጋብቻው የተመሰረተው እና ግራ ቀኙም ከጋብቻው በኃላ ሲኖሩ የነበረው በአማራ ክልል ውስጥ ነው እስከተባለ ድረስ ክሱ መቅረብ የሚገባው በክልሉ ሕግ መሰረት ከጋብቻ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው የሚነሱ የክልል ጉዳዮችን የማየት ስልጣን ላለው የክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሚሆን በቀር ግራ ቀኙ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተደርጎ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 5 (2) ስር በተመለከተው ስርዓት መሰረት አይደለም።ጋብቻው የተፈጸመው በአንድ ክልል ውስጥ እና በዚያው ክልል የቤተሰብ ሕግ መሰረት በሆነ ጊዜ ከፍቺ ጋር ተያይዞ ጥያቄ በተነሳበት ወቅት ተጋቢዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች የሚኖሩት በተለያዩ ክልሎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውስጥ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ከፍቺ እና መሰል ጥያቄዎች ጋር ተይይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የተሰጠው የክልሉ ፍርድ ቤት ከሚሆን በቀር ተጋቢዎቹ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተቆጥሮ ጉዳዩ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 (2) ድንጋጌ አንጻር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ ስላለመኖሩ የፌዴሬራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አስቀድሞ በቀረበለት ተመሳሳይ ጉዳይ በመዝገብ ቁጥር 119582 በ26/04/2009 ዓ.ም. የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል።

ው ሳ ኔ

1. በባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤትበመዝገብ ቁጥር 03-01390 በ01/10/2007 ተሰጥቶ በአማራብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41000 በ13/07/2008 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቶአል።
2. ጋብቻ የተፈጸመው በአንድ ክልል ውስጥ እና በዚያው ክልል ሕግ መሰረት ሆኖ ክስ በቀረበበት ጊዜ ተጋቢዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች የሚኖሩት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ከፍቺ እና መሰል ጥያቄዎች ጋር ተይይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የተሰጠው የክልሉ ፍርድ ቤት ከሚሆን በቀር ተጋቢዎቹ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተቆጥሮ ጉዳዩ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 (2) ድንጋጌ አንጻር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ሊባል የሚችል አይደለም በማለት ወስነናል።
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይላክ።
4. አመልካቿን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረብ ይህ ውሳኔ የሚያግዳቸው አይሆንም።
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
6. በዚህ መዝገብ በ23/01/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ።

ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 123132

ሚያዝያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጸውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ከሳሁን ታደሰ - ጠበቃ አቶ ዘበነ ፍቅሬ ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀዳለ ሀፍታይ- ጠበቃ አቶ ኤልያስ ወርቁ ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የጉዳዩ መንሥኤ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከአሁን አመልካች /ከሥር ተከሳሽ/ ጋር ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት በመሆን አብረው በሚኖሩ ጊዜ ያፈሩዋቸው በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ ቤት እና የሠሌዳ ቁጥሩ ኢት 03-01-52703 የሆነ የጭነት መኪና የጋራ በመሆናቸው ተከሳሽ /አመልካች/ ንብረቶቹን እንዲያካፍሉን ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የሥር ተከሳሽ /የአሁኑ አመልካች/ የግራ ቀኙ በጣልያን ሀገር የሚኖሩ በመሆናቸው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ተፈጻሚነት የለውም፣ የተከሳሽ ነዋሪነት ውጭ አገር በመሆኑ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ጉዳዩ መቅረብ አይችልም፣ የግራ ቀኙ እንደ ባልና ሚስት ለመኖር የተስማሙት ጣልያን አገር በመሆኑ ተጠሪ/ከሳሽ/ በኢትዮጵያ ክስ መመስረት አይችሉም፣ ስለ ንብረት የሚያነሱትም ክርክር በጣልያን አገር ህግ መሠረት ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ሰዎች በሚለያዩበት ጊዜ በአንዱ ስም የተመዘገበውን ሌላኛው መጠየቅ እንደማይችል በጣልያን አገር ከሚያገለግል ጠበቃ የቀረበ የሕግ አስተያየት አስተርጉመን ስላቀረብን እና ከሳሽ /ተጠሪ/ ለክርክሩ መነሻ ያደረጉዋቸው ንብረቶች በተከሳሽ ስም የተመዘገቡ በመሆናቸው ከሳሽ መብት የላቸውም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአሁኗ ተጠሪ በመቃወሚያዎቹ ላይ መልስ እንዲሰጡበት ካደረገ በኃላ የአሁኑን አመልካችን መቃወሚያዎችን ውድቅ በማድረግ በከ/መ/ቁ.138413 ሰኔ 2 ቀን 2006 ዓ/ም ብይን ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ በፍሬ ነገሩ ላይ ክርክር እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ሰጥቶ የአሁኑ አመልካች ንብረቶቹ ስለመኖራቸው ሳይክድ ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአሁኗ ተጠሪ የጠየቁዋቸው ንብረቶች የጋራ ስለሆኑ እኩል እንዲካፈሉ ሲል በኮ/መ/ቁ. 138413 የካቲት 24 ቀን 2007 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ብይን እንዲሁም ውሳኔው ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይግባኙ በመቀበል ክርክራቸውን ከሰማ በኃላ በፍ/ይ/መ/ቁ. 111588 ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታ ይዘቱም በአጭሩ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡትውን መቃወሚያችን በማለፍ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንደተፈጸመበት የሚገልጽ ሲሆን ሌሎች ነጥቦች በፍሬ ነገር ረገድ ተፈጸሙ ያሉዋቸውን ስህተቶች በመዘርዘር የቀረቡ ናቸው፡፡

የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የግራ ቀኙ በጣሊያን አገር ሳሉ የፈጠሩት ግንኙነት የባልና ሚስት ዓይነት ግንኙነት ነበር የመባሉንና ይህ ቢታለፍ ግራ ቀኙ የንብረት ግንኙነት ነበራቸው ወይስ አልነበራቸውም? የሚለው የመጣራት አለመጣራቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል ህዳር 1 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ዝርዝር ነጥቦችን አንስተው ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ጠበቃም ታህሳስ 5 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተው የሚመስል ሲሆን አመልካችና ተጠሪ በጣሊያን ሀገር ህግ መሠረት እንደባልና ሚስት አብረው መኖራቸው በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 5 መሠረት ሊታይ ይገባል ወይስ አይገባም? በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግና በጣሊያን ህግ መካከል የሕግ ግጭት አለ ወይስ የለም? የአመልካችና የተጠሪ ንብረት ክርክር እልባት ሊያገኝ የሚችለው በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ነው ወይስ በጣሊያን ህግ መሠረት ነው? የሚሉት ነጥቦች ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ጣሊያን አገር መኖራቸው፣ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የኖሩ መሆናቸው፣ በዚህ ግንኙነት ልጅ የወለዱ መሆናቸው በግራ ቀኙ መካከል ክህደት የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሠረቱ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 5 ሥር በውጭ አገር የተፈጸመ ጋብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ ለህግና ለሞራል ታቃራኒ እስካልሆነ ድረስ ተቀባይነት አለው የሚለውን በጣሊያን አገር እንደ ባልና ሚስት አብረው የኖሩበትን ሁኔታ አመሳስለው መተርጎም ተገቢ ነው ወይ? የሚለውን ከድንጋጌው ዓላማና መንፈስ ጋር አያይዞ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 5 " በተፈጸመበት አገር የጋብቻ አፈጻጸም ህግ መሠረት ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈጸመ ጋብቻ የህዝቡን ሞራል እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ ህግ ተቀባይነት ይኖረዋል" በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚህ ህግ ድንጋጌ ዓላማ በውጭ አገር ጋብቻ የፈጸሙ ባልና ሚስት የጋብቻ ማስረጃቸው በኢትዮጵያ ህግ ተቀባይነት የሚያገኝበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተጋቢዎች በውጭ አገር ህግ መሠረት ተጋብተው ነገር ግን ጋብቻቸው ከኢትዮጵያ ህዝብ ሞራል ጋር የማይቃረን ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ይህ አንቀጽ ከኢትየጵያ ወጭ ጋብቻው ቢፈጸምም የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቱ ጋብቻን ለመመሥረት የሚያሰችል ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ድንጋጌውም እውቅና የሚሰጠው በውጭ አገር ለተፈጸመ ጋብቻ እንጂ ለሌሎች ግንኙነቶች አይደለም፡፡ በውጭ አገር በአንድ ወንድና ሴት መካከል እንደባልና ሚስት አብረው መኖርን ከዚህ ድንጋጌ ጋር በማመሳሰል መተርጎም የህግ ስህተት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት የደረሰው ድምዳሜ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግና በጣሊያን ህግ መካከል የህግ ግጭት አለ ወይስ የለም? የሚለውን ሁለተኛውን ነጥብ ከክርክሩ እንዲሁም ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አንጻር ተመልክተናል፡፡ ይህን ጭብጥ በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት በሁለቱም አገር ህጎች መካከል ግጭት እንዳለ ተቀብሎ መሆን የሚገባውን በተመለከተ ግን በቂ ምላሽ ሳይሰጥ እንዳለፈ የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሣያል፡፡ አመልካች በጣሊያን አገር ህግ መሠረት ሁለት ግለሰቦች ጋብቻ ሳይመሰርቱ እንደባልና ሚስት ከኖሩ በጋራ የሚያፈሩት ንብረት እንደሌለ፣ ሁለቱም በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኘው ንብረት ባለቤት ተደርገው ስለሚቆጠሩ ሲለያዩም በየግላቸው ያላቸውን ንብረት ይዘው እንደሚቀሩ ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ ተከራክሯል፡፡ አመልካች በዚህ ጉዳይ ላይ የጣሊያን ህግ በተመለከተ ኤሌክሳድሮ ለፒዛ ከሚባል በጣሊያን አገር ህጋዊ ከሆነ ጠበቃ ማብራሪያ በታች ፍርድ ቤት በማስረጃነት አስተርጉመው ጣሊያን አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲ እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል አረጋግጠው ማቅረባቸውን ተያይዞ የቀረበልን የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በዓለም አቀፍ የግለሰብ ህግ /Private International law/ መሠረት በዘርፉ እውቀት ያለ ወይም ምሁር /Scholar/ የሰጠውን አስተያየት በማስረጃነት ማቅረብ እንደሚቻል የተረጋገጠ ነው፡፡ የቀረበውን አስተያየት እንደማንኛውም ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ግን አስተያየቱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 102 /1/ ላይ የንብረት አስተዳደራቸውን አስመልክቶ የሚያደርጉት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ለሶስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነቱ ውስጥ እያሉ ያፈሩዋቸው ንብረቶች የጋራ ሀብታቸው ይሆናሉ በማለት ይደነግጋል። ይህም የኢኮኖሚ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር፣ በመተማመን መንፈስ ሆነው ንብረት እንዲያፈሩ ለማድረግ እና ለዚሁም የህግ ጥበቃና ዋስትና እንዲኖር ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በሌላ አነጋገር እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ከሶስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ የሚያፈሩት ንብረት የጋራ እንደሆነና ለዚህም ህጉ ጥበቃ እንደሚያደርግ ነው።

በዚህ መሠረት አመልካች ካቀረቡት ክርክር አኳያ የጣሊያን ሀገር ህግ እና የኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ የተለያየ ድንጋጌ እንዳላቸው ነው። ይህም በሁለቱ ህጎች መካከል ግጭት እንዳለ ያሳያል። ስለሆነም ይህ በአግባቡ ሳይጣራ የሚሰጥ ውሳኔ የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ይሆናል። በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት የጣሊያን አገር ህግ አመልካች እንደሚሉት መሆን ያለመሆኑን ህጉ እንዲቀርብ በማድረግ አጣርቶ መወሰን ሲገባው ይህንን ሳያደርግ እና የህግ ግጭቱን ለይቶ ሳያረጋግጥ የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አግኝተነዋል።

በሌላ በኩል የአመልካችና የተጠሪ ንብረት ክርክር እልባት ሊያገኝ የሚችለው በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ነው ወይስ በጣሊያን ህግ መሠረት? የሚለው ነጥብ እልባት ሊያገኝ የሚችለው ከላይ በተመለከተው መሠረት የህግ ግጭት መኖር አለመኖሩ ከተረጋገጠ በኃላ ነው። ስለዚህ የህግ ግጭት መኖር አለመኖሩ ሳይረጋገጥ ክርክር የተነሳባቸው ንብረቶች የጋራ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

በመጨረሻም የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ነጥቦችን በአግባቡ ሳያጣሩ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፤ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. የከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 138413 የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ. 111588 ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽሯል።
2. ከላይ በፍርድ ሀተታው በተገለጸው መሠረት በጣሊያን አገር ህግ እና በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ መካከል እንደባልና ሚስት አብረው በመኖር ግንኙነት ውስጥ የተፈራ ንብረት የጋራ አንዲሆን ለመወሰን በሁለቱም ህጎች መካከል ግጭት መኖር ያለመኖሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጣሊያን አገር ህግ እንዲቀርብ ተደርጎ ጉዳዩ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሰናል፡፡

3. ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡

መዝገቡ ስለተወሰነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 130931

ሰኔ 19 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ በላይ ዘለቀ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ትዕግስት ዳባ /የህፃን ሀሴት በላይ ሞግዚት/- ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ ከህፃን ልጅ ማሣደጊያ የሚቆረጥ ገንዘብ መጠን የሚመለከት ክርክር ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ ከግራ ቀኙቸው ሕፃን ሀሴት በላይ በጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም የተወለደች መሆኑንና የአመልካች አባትነትም በፍርድ ቤት ውሳኔ የተረጋገጠ መሆኑን፤ ለልጅቷ ቀለብ ብር 5,750.00 (አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) እንዲከፍሉና አመልካች ነዋሪነታቸው ስዊዘርላንድ በመሆኑ ቀለቡን በየወሩ ሳያቋርጡ የሚከፈሉ ስለመሆኑ በቂ ዋስ ወይም መያዣ እንዲያቀርቡ እንዲታዘዝላቸው፤ ይህ ካልተቻለም የህፃኗ ዕድሜ 18 ዓመት እስኪሞላት ድረስ ያለውን ቀለብ ፍርድ ቤቱ አስልቶ አመልካች በአንድ ጊዜ በህፃኗ ሞግዚት ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርጉላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው ተጠሪ የጠየቀችውን ገንዘብ አመልካች በየወሩ ለህፃኗ ማሳደጊያ ለመክፈል አልችልም፤የምችለው በወር ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) መሆኑን ወርሐዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገቢያቸው በኢትዮጵያ ብር ከ4,000.00 (አራት ሺህ ብር) እንደማይበልጥ፤ለሌላ ልጃቸው ቀለብ እንደሚቆርጡ፤ዕዳ እንደሚከፍሉና ሌላ ትዳርም መስርተው እየኖሩ በመሆኑ ወጪ ያለባቸው መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት አመልካች ተጨባጭ ማስረጃ አላቀረቡም የቀለብ መጠን ሲወሰን ለቀለብ ተቀባዩ የሚያስፈልጉ ተጨባጭ ወጭዎች እንዲሁም የቀለብ ክፍያ አቅም ተገናዝቦ መሆን አለበት፡፡ በዚሁ መሰረትም አመልካች ከነሐሴ ወር 2007 ዓ.ም ጀምሮ ለልጅቷ ቀለብ በየወሩ ብር 4,000.00 (አራት ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ክፍያውንም አመልካች በጠየቁት መሰረት የ6 ወርን በአንድ ጊዜ በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርጉ፤ለዚሁ ክፍያ መፈፀምም ዋስትና የሚሆን ለብር 696,000.00 (ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር) የሚበቃ የሰው ዋስ ወይንም የንብረት ማስያዣ እንዲያሲይዙ ይህንን ማድረግ ካልቻሉ ለቀሪው የ14 ዓመትና 6 ወራት የሚሆን የቀለብ ክፍያ ብር 696,000.00 (ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር) የህፃን ሞግዚት ለዚሁ ጉዳይ በሚከፍቱት የባንክ ሂሳብ በአንድ ጊዜ እንዲያደርጉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በስር ፍርድ ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በውሳኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 20 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ከኢትዮጵያ ውጪ ስለሚኖር የገቢውን መጠን የማስረዳት ሸክም በርሱ ላይ ያርፋል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታቸውን የመልስ መልስ የማቅረብ መብት በመታለፉ የቀረበ የመልስ መልስ የለም፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤቶች ለህፃን ማሳደጊያ አመልካች እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠው በሕግ የተመለከቱትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአመልካች ጥያቄ በወር ብዙ ውጭ ማለትም የባንክ ዕዳ፤የልጅ ቀለብ፤የቤተሰብ ማስተዳደር ሁሉ ወጭዎች ያሉብኝ መሆኑን በማስረጃ አስደግፌ አቅርቤ እያለሁና የምችለውም በወር ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) ብቻ መሆኑን እያስረዳሁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከአቅሜ በላይ የተጋነነ ቀለብ በወር ብር 4,000.00 (አራት ሺህ ብር) እንድከፍልና እና በአንድ ጊዜ በሞግዚት አድራጊዋ በተከፈተ ባንክ ብር 696,000.00 (ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር) ገቢ እንዳደርግ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ልጅ ወልዶ ማሳደግ ከፍተኛ ሀላፊነት የሚጠይቅ እና እንደ አባት እንደ እናት ተንከባክቦ ፍቅርን፤ጊዜን እንዲሁም ገንዘብን ሰውቶ ለቁም ነገር ማብቃትን ይጠይቃል፡፡ ተጠሪም እስከ አሁን ድረስ ይህን ሀላፊነት ለብቻቸው በመወጣት ላይ ይገኛሉ፤ በአንፃሩ አመልካች ከመኖሪያ ቤት ሽያጭ ከፍተኛ ገንዘብ(ከአምስት ሚሊዮን ብር) በላይ ማግኘታቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ልጅነትን ሳይክዱ ከሚጠበቅባቸው የበዛ ሀላፊነት የህፃኗን አስተዳደግ በገንዘብ የመደገፍ ሀላፊነትን ሊወጡ እንደሚገባ በማመን እንዲሁም ኢፌዴሪ ህገመንግስት እና ሀገራችን ባጸደቀቻቸው ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች እንዲሁም የሰበር ችሎቱ በተደጋጋሚ በሰጣቸውን ውሳኔዎች ፍርድ ቤቶች ህፃናትን አስመልክቶ የሚወሰኑ ውሳኔዎች የህጻናቱን ጥቅም ከግምት ሊያስገቡ እንደሚገባ የተመለከተውን ግምት ውስጥ በማስገባት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለወለዳት ህፃን ሀሴት በላይ ለማሣደግ የሚያስፈልገውን ወጪ የመጋራትና የመሸፈን ግዴታ ያለበት መሆኑ አላከራከረም አመልካችንና ተጠሪ የሚያከራከረው አመልካች ለህፃኗ አስተዳዳግ ሊከፍለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ ለህፃን ልጅ ማሳደጊያ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ወላጅ፣ የሚከፍለው የገንዘብ መጠን የሚወስነው እንደባለጉዳዩ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልምድ የሚስማማውን በመከተል በቀለብ ተቀባዩ ምግብ፣ መኖሪያ፣ ልብስ፣ ጤናውን የሚጠብቅበትና እንደ ሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑትን ወጭዎች የሚሸፈን መሆን እንደሚገባው በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች በተወሰነ መልኩ ከኢትዮጵያ ውጭ ገቢ እንዳለቸው ከመታመኑ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥም ከመኖሪያ ቤት ሽያጭ ከ2.5 ሚሊዮን ብር ያገኙ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡አንድ ወላጅ ህፃን ልጁን በጥሩ ሁኔታ ለመመገብ፤ በጥሩ መኖሪያ አካባቢ ለማኖርና ጤናውን ለመጠበቅ እንዲሁም ጥሩ ትምህርት እንዲያገኝ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ወጭ መሠረት በመድረግ ሊወሰን እንደሚገባና ከአመልካች ገቢ አንፃር ሲታይ ከብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ በላይ ለመክፈል አቅም የለኝም በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 197 እና አንቀጽ 202 ድንጋጌዎችን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ አልተበቀልነውም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ለህግኗ አስተዳደግ እንዲከፍሉየሰጡት ውሳኔ የቀለብ ገንዘብ መጠኑ ሆነ የአከፋፈሉ ሁኔታ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

7. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.108713 ነሐሴ 6 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 173752 ሚያዚያ 28 ቀን 2008 ዓ.ም በውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
8. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.129933

ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ አየለ ወ/አለማው -ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.ወ/ሮ እመቤት ማሞ ስለሁለቱም ተጠሪዎች 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ

2.አቶ ሄኖክ ገ/ጻዲቅ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 29 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ በመዝገብ ቁጥር 51387 በቀን 27/12/2007ዓ.ም የሥር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 170917 የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 125536 በ14/8/2008ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ስህተቱ እንዲታረምልኝ በማለት ዳኝነት በመጠየቃቸው ነው፡፡

የክርክሩ መንሥኤ የውርስ ሀብት ክርክር ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በ7/11/ 2007 ዓ/ም በተጻፈ በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ከሚች አቶ ገ/ጻዲቅ ደስታ በኑዛዜ የተላለፈልንን በቀድሞ ወረዳ 23 ቀበሌ 16 የቤት ቁጥር 207 የሆነ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የሚች ሚስት ሳይሆኑ ሚስት ነኝ በማለት እና 2ኛ ተከሳሽም የሚች ልጅ ሳይሆኑ ልጅ ነኝ በማለት በኑዛዜ የተላለፈልኝን ቤት ይዘው ስለሚገኙ 1ኛ ተከሳሽ ሚስት አይደሉም 2ኛ ተከሳሽም ልጅ አይደሉም በማለት ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡትን የውርስ ሀብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ 1ኛ ተከሳሽ የሚች አቶ ገ/ጻዲቅ ደስታ ሚስት 2ኛ ተከሳሽም ልጅ አይደሉም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች 1ኛተጠሪ የሚች ሚስት አይደሉም 2ኛ ተጠሪ የሚች ልጅ አይደሉም በማለት በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሥር ፍርድ ቤት የወሰነውን እና 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት አይደሉም 2ኛ ተጠሪ የሚች ልጅ አይደሉም በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የስር ከሳሽ የስር ተከሳሾችን 1ኛ ተከሳሽ ሚስት አይደሉም 2ኛ ተከሳሽም ልጅ አይደሉም በማለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ይህ ውሳኔ በስር የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ በአመልካች የቀረበውም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጸናውን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ፡- የኑዛዜ ተጠቃሚ የሆንኩበትን ንብረት ተጠሪዎች መብት ሳይኖራቸው መያዛቸውን በመግለጽ መብቴ እንዲከበርልኝ ያቀረብኩት ክርክር ውድቅ ተደርጎ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመጽናት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረም የሚጠይቅ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች 1ኛ ተጠሪ ከሚች ጋር ጋብቻ እንደሌላቸው እና ከሚች ጋር በጋራ ያፈሩት ንብረት የሌለ መሆኑን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አቅርቤያለሁ እያሉ ይህ ታልፎ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት በስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው የካቲት 16 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ክርክር አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡ አመልካቹም መጋቢት 19 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ከቀረበው ክርክር አንጻር በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩ ተመርምሯል፡

የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ተቀብሎ እና የስር ተከሳሾችን ክርክር ውድቅ በማድረግ 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት 2ኛ ተጠሪ የሚች ልጅ አይደሉም በማለት ውሳኔ የሰጠው ሚች ለአመልካች የእህታቸው ልጅ መሆናቸውን በመግለጽ እና የክርክሩ ይዞታ በስተ ግራ ባለው ክፍት ቦታ የተሰራውን ቤት ከሚች ጋር በጋራ የሰሩ መሆናቸውን በመግለጽ ከሞትኩኝ በኃላ አመልካች በስማቸው አዙረው እንዲጠቀሙበት፣ እንዲሸጡ እና እንዲለውጡ ያደረጉት እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጣን ባለው አካል የጸደቀ የቁም ኑዛዜ ማቅረባቸውን እና ሟች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በ23/11/1992ዓ.ም በተጻፈ ከሚያዝያ 12 ቀን 1978ዓ.ም ጀምሮ 1ኛ ተጠሪ እንደ ሚስት በ80 እንደ ሰራተኛ በደመወዝ ልጅ ሳንወልድ አብረን ስንኖር በእድሜ ባለመመጣጠናችን የሰራሁበትን ደመወዝ ብር 3000.00 ተቀብዬ ወደፊት ቀሪ ንብረት እና ሀብት አለኝ በማለት ላልጠይቅ ተስማምቻለሁ በማለት የፈረሙበትን ማስረጃ አቅርበዋል በማለት ሲሆን የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ የሻረው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በመሆኑም ተጠሪዎች ይህንን አስመልክቶ ያቀረቡትን መቃወሚያ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን ተገቢ አይደለም በማለት ሲሆን ይህ ውሳኔ በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የቀረበ ሲሆን እኛም የሰበር አመልካች 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት 2ኛ ተጠሪ የሚች ልጅ አይደሉም ይባልልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ቢያገኝም በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውድቅ በማድረግ መወሰናቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

አመልካች በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት አይደሉም 2ኛ ተጠሪም የሚች ልጅ አይደሉም ይባልልኝ የሚል ሲሆን ለዚህም ምክንያታቸው 1ኛ ተጠሪ ከሚች እንደ ሚስት በ80 እንደ ሰራተኛ በደመወዝ ልጅ ሳይወልዱ አብረው ለመኖር ተስማምተው ሲኖሩ ቆይተው 1ኛ ተጠሪ የነበራቸውን ብር 3000.00 ወስደው ከአመልካች ጋር ወደፊት ምንም የቀረ ንብረት እና መብት አለኝ በማለት ላልጠይቅ ብለው የተስማሙበት የሰነድ ማስረጃ አለኝ በማለት አቅርበው በዚህ ምክንያት 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት 2ኛ ተጠሪም የሚች ልጅ አይደሉም ይባልልኝ በማለት ነው፡፡

ከተጠሪዎች በኩል የቀረበው እና ምላሽ ማግኘት የሚገባው መከራከሪያ አመልካች ይህንን ክስ በማቅረብ የመከራከር ህጋዊ መብት የላቸውም የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 177/1-3/ ያሉ ድንጋጌዎች በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ሲሆን ክሱንም የሚያቀርበው የልጅ አባት ነህ የተባለ ሰው ነው፡፡ ሆኖም በህግ ግምት የልጁ አባት ነህ የሚባለው ሰው የሞት ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አባት ነህ የተባለው ሰው ችሎታ ያጣ እንደሆነ ከተወላጆች አንዱ በእርሱ ፋንታ ሆኖ የመካድ ክስ ማቅረብ እንደሚችል የፌደራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/1/ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ተወላጆች የሌሉ እንደሆነ እናት እና አባት የመካድ ክስ የማቅረብ መብት ያላቸው ሲሆን እነዚህም በሌሉ ጊዜ ደግሞ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች አንዱ መብቱን ሊሰራበት እንደሚችል ከዚህ በላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠቀሰው የህግ አንቀጽ 177/2/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በመጨረሻም ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች የሌሉ እንደሆነ በመካድ ክስ መብት ሊሰራበት የሚችለው ከወንድሞቹ ወይም ከእህቶቹ አንዱ እንደሆነ የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 177/3/ ይደነግጋል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የሟች የእህት ልጅ መሆናቸው በኑዛዜ ሰነዱ ላይ የተመለከተ በመሆኑ ይህንን ክስ ለማቅረብ ህጋዊ መብት የላቸውም ሌላው ሚስትነት በተመለከተ የቀረበው መቃወሚያ እንደመረመርነው አመልካች ሟች አለ የሚሉት ኑዛዜ አመልካች የእህቱ ልጅ ስለሆነ በአዲስ ከተማ ወረዳ 23 ቀበሌ 16 የቤ.ቁ 207 ከሆነው መኖሪያ ቤቱ በስተግራ ባለው ክፍት ቦታ ወጪ በማውጣት አብሮ ስለሰራ ይህንን የተሰራ ቤት ከህልፈተ ህይወቱ በኋላ በስሙ አዙሮ እንዲጠቀም ተናዝኖለሁ የሚል ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ኑዛዜ አለኝ የሚሉት ከዋናው ቤት በስተግራ በኩል ባለው ክፍት ቦታ ላይ የተሰራ ቤትን በተመለከተ በመሆኑ የጠቅላላ ሀብት ነኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ በማለት ያቀረቡት ክርክር በሌለበት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ሚስትነት በመቃወም አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33 መሰረት መብት ወይም ጥቅም የላቸውም፡፡

በመሆኑም የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች በቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት ክሱን ውድቅ በማድረግ ሊወስን ሲገባ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ በአመልካች ክስ መሰረት 1ኛ ተጠሪ የሟች አቶ ገ/ጻዲቅ ደስታ ሚስት አይደሉም 2ኛ ተጠሪም የሟች ልጅ አይደሉም በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 51387 በ27/12/2007 ዓ.ምተሰጥቶ በስር የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 170917 በ30/6/2008ዓ.ም ዓ.ም የተሻረው እና በስር የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 125536 በ14/8/2008ዓ.ም ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ይህ ውሳኔ አመልካችን በኑዛዜው መሰረት የውርስ ሃብት ክርክር ከማቅረብ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ክርክር ምክንያት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው·ር·ስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ.124313

ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡-1ኛ. ወ/ሪት ቅድስት ዮሴፍ

2ኛ. አቶ ኃይለየሱስ ዬሴፍ ጠበቃ ምትክ ኦሉማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ምስራቅ አለማየሁ

2. አቶ አብነት አለማየሁ - የቀረበ የለም

3. ወ/ሮ ስንታየሁ አለማየሁ

በሰ/መ/ቁጥር 125453 የሆነውን መዝገብ ከዚህ መዝገብ ጋር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 11 መሰረት አጣምረን በመመርመር ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልን ክርክርን መሰረት ያደረገ ሲሆን የተጀመረውም በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆን ተጠሪዎችና ሔለን አለማየሁ የተባሉት ግለሰብ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት ክስም ወ/ሮ ምንትዋብ አለማየሁ የተባሉት ግለሰብ ወላጅ እናታቸው መሆናቸውንና ወራሽነታችን ማረጋገጣቸውን፣ ሚች በሕይወት እያሉም ግምቱ ብር 250,000.00 የሆነ ቤት በሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ ያፈሩ መሆኑን፣ ይህንን ቤት ከሕግ ውጪ ተከሳሾች ይዘው እንደሚገኙ ገልጸው ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ይወሰን ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ የሥር ተከሳሾችም ከሳሾች የንብረት ባለቤትነት ክርክርና የውርስ ክርክር አደባልቀው የባለቤትነት መብት ሳይኖራቸው መከራከር ስለማይችሉ ክስ ለማቅረብ እንደማይችሉ፣ ጉዳዩ በመ/ቁጥር 22056 የታዬና በድጋሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስ ሊቀርብበት የማይገባ መሆኑን፣ አውራሻቸው አቶ አለማየሁ በላቸው የውርስ ማስረጃ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 22056 ያገኙትን በማሻር የተሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ብለው ክርክር ላይ መሆናቸውን፣ ክሱ በሶስት አመት ይርጋ የታገደ መሆኑን የሚመለከቱ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አስነተዋል፡፡ በፍሬ ነገሩ ላይም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በተከሳሾች በኩል ከቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦች መካከል ይርጋን የሚመለከተውን መቃወሚያ ብቻ ተቀብሎ ክሱ በሶስት አመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የስር ከሳሾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች የእናታቸው የወ/ሮ ምንትዋብ አለማየሁ ወራሽ ነን በማለት የሚከራከሩና ተከሳሾች ደግሞ የአቶ አለማየሁ በላቸው ወራሽ ነን በማለት የሚከራከሩ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 1000 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የአመልካቾች ክስ በይርጋ የሚታገድ አይደለም፣ ፍሬ ነገሩ ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል በማለት ጉዳዩን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡ በዚህ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ በገንዘብ ሊገመት በማይቻል ርእስ እንጂ ተገምቶ ሊቀርብ አይገባም፣ ስለሆነም በገንዘብ ግምት ሊቀርብ የማይቻል ክርክር የማየት ስልጣን የወረዳ ፍርድ ቤት ሆኖ ንብረቱ ተገምቶ በንብረት ግምቱ መሰረት ጉዳዩ ለስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረቡ ተገቢ በሚል ድምዳሜ ጉዳዩ ከመነሻው የቀረበው የሥረ ነገር ስልጣን በሌላቸው ፍርድ ቤቶች ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ እነ ወ/ት ቅድስት ዬሴፍ፤የስር ከሳሾች፣ በሰ/መ/ቁጥር 124313 የሠበር አቤቱታ ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው ያለስረ ነገር ስልጣኑ ነው መባሉ ያላግባብ ነው በሚል ሲሆን የስር ተከሳሾች ከነበሩት ውስጥ የአሁኑ ተጠሪዎች በሰ/መ/ቁጥር 125453 የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ደግሞ የስር ከሳሾች ክስ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው ነው በሚል ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ በሁለቱም መዝገቦች የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱም ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች፡-

1. ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የየትኛው ፍርድ ቤት ነው?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የስር ተከሳሾች ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በዚህ ችሎት ሊስተናገድ የሚችል ነው ወይስ አይደለም የሚሉ ሁነው ተገኝተዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የሥር ከሳሾች ከወላጅ እናታቸው ሊተላለፍላቸው የሚገባውና ግምቱ ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ) የሆነ መኖሪያ ቤት በስር ተከሳሾች ከሕግ ውጪ መያዙን በክሳቸው ገልጸው ይህ ቤት እንዲለቀቅላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡ የሥር ተከሳሾች በቤቱ ላይ ከአመልካቾች እናት ያገኙት የውርስ መብት አለን የሚል ክርክር የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ቤቱን ለስር ከሳሾች ያስተላለፉት ሟች አቶ አለማየሁ በላቸው ከሕግ ውጪ የሟች ወ/ሮ ምንትዋብ አለማየሁ ወራሽነታቸውን በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 22056 አረጋግጠው የሟች ወ/ሮ ምንትዋብ ሕጋዊ ወራሾች ተቃውሞ አቅርበው የሥር ከሳሾች ወላጅ አባት ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ ከመሰረዙም በላይ ይህንኑ የወራሽነት ማስረጃ የተሰረዘበትን ውሳኔ በሕግ አግባብ ስለማስለወጣቸው የሥር ተከሳሾች የሚያቀርቡት ክርክር የሌለ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተመልክተናል፡፡ የሥር ከሳሾች አጥብቀው የሚከራከሩት አከራካሪውን ቤት አቶ አለማየሁ በላቸው ከአቶ ካሳሁን ጥላሁን የገዙት ነው የሚለውን ነጥብም በማንሳት ነው፡፡ በመሆኑም የስር ከሳሾች ግልፅ የዳኝነት ጥያቄ በውርስ የተላለፈላቸው ቤት ከሕግ ውጪ በስር ተከሳሾች የተያዘ መሆኑን የሚያሳይ የክስ ፍሬ ነገር ተጠቅሶ ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ይወሰን ዘንድ የሚጠይቅ በመሆኑ አከራካሪው ቤት የስር ከሳሾች አውራሽ የወ/ሮ ምንትዋብ በላቸው ነው ወይስ የስር ተካሶሾች ወላጅ አባት የሆኑት የሟች አቶ አለማየሁ በላቸው ነው? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ፍሬ ነገሩን በሚገባ አጣርቶ ተገቢውን ዳኝነት መስጠትን የሚጠይቅ እንጂ የውርስ ማጣራት ሒደትን ተከትሎ በንብረቱ ላይ ወራሾች ያላቸውን የድርሻ መጠን ለይቶ ዳኝነት መስጠትን የሚጠይቅ አይደለም፡፡የሥር ተከሳሾች ቤቱ አንድ መሆኑንና ግምቱ ተለይቶ ክስ መቅረቡን ጠቅሰው ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንጂ የወረዳው ፍርድ ቤት አይደለም በማለት የስር ከሳሾችን የሠበር አቤቱታ ደግፈው መልሳቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡

ከእነዚህ ነጥቦች አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የስር ከሳሾች ክስ በማይገመት የውርስ ሃብት ላይ የቀረበ ያለመሆኑን ነው፡፡ ይልቁንም ከሳሾቹ በውርስ ሊተላለፍልን የሚገባው ቤት ከሕግ ውጪ ተይዞአል ከአሉና ይህ የውርስ ንብረት ተለይቶ የታወቀ እስከሆነ ድረስ ውርስ የሚጣራበት ወይም ሃብቱ የውርስ ስለሆነ ግምቱ ሊታወቅ የሚችል አይደለም ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 34703 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም የውርስ ሃብቱን የመከፋፈል ጥያቄ ንብረቱ በአይነት ተለይቶና ተገምቶ እስከቀረበ ድረስ በቀረበው ግምት መሰረት የፍርድ ቤቶችን የስረ ነገር ስልጣን ሊወሰንበት የሚገባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ገልጾ ወስኖል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ከሳሾች የክፍፍል ጥያቄ ያቀረቡበት ጉዳይ ሳይሆን የውርስ ንብረቱ ይለቀቅልኝ ጥያቄ ያቀረቡበትና ንብረቱም ተለይቶ የታወቀ በመሆኑ በንብረቱ ግምት የፍርድ ቤቱ የሥረ ነገር ስልጣን የማይወሰንበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በተሻሻለው የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 27 (3) መሰረት ግምቱ ከብር 50,000.00 በላይ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እና ግምቱ ከብር 30,000.00 በላይ የሆነ የሚንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚነሳ ክርክርንአይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው መሆኑንም በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 18 እንደተደነገገው የገንዘብ ግምት ሊወሰን የማይችል ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 23 ስር እንደሰፈረው የውርስ ማጣራት ስራ የተጀመረበት ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብም አላገኘንም፡፡

ስለሆነም የሥር ከሳሾች በጠየቁት ግምት መሰረት ጉዳዩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን ማየቱና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የስረ ነገር ስልጣኑን ማለፉ ተገቢ ሁኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩ በወረዳ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የሚውድቅ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ከላይ እንደተገለፀው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበለትን የስር ተከሳሾችን ቅሬታ አልተመለከተውም፡፡ ይህም የሆነው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት ነው በሚል ድምዳሜ ችሎቱ በመያዙ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት እያሳዬ የስር ተከሳሾች ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባል፣ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ይርጋም በውርስ ሕጉ የተመለከተው ነው በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ፍርድ ሳይሰጥበት ነው፡፡ ከክልል ፍርድ ቤቶች የተነሳ ጉዳይ የሰበር ስርዓት በተዘረጋባቸው ክልሎች በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታይ ለዚህ ችሎት የሚቀርብበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 83261 እና በሌሎችም በርካታ መዛግብትበአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) መሰረት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም በአንደኛው ጭብጥ ጉዳዩ በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ ነው ከተባለና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከጸና ወይም ከተለወጠ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑ ተለይቶ ሳይወሰን ለዚህ ችሎት የሠበር አቤቱታ የሚቀርብበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የሌለ በመሆኑ የሥር ተከሳሾች የይርጋ ክርክርን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስመልክቶ ያቀረቡት አቤቱታ በቅድሚያ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ መታየት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 199980 በ04/04/2008 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 199980 ክርክሩ እንዲቀጥል በማድረግ ከስረ ነገር ውጪ ባሉት ሌሎች ክርክሮች እነ ምስራቅ አለማየሁ (ሶስት ሰዎች) ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 171320 በ27/01/2007 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔመሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን መርምሮ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት በሁለቱም መላግብት ለተደረጉት ክርክሮች ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.135694

ሐምሌ 20 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡-

1. አቶ ይርዳው ሽፈራው
2. አቶ መኮንን ሽፈራው
3. አቶ ወርቁ ሽፈራው ቀረቡ
4. አቶ ደምሴ ሽፈራው
5. ወ/ሮ ጽጌሬዳ ሽፈራው

} 1ኛ አመልካች በራሳቸውና በሌሎች ወኪልነታቸው

ተጠሪ

1. አቶ መስፍን ሽፈራው
2. አቶ ተክሌ ሽፈራው
3. አቶ ደረጃ ሽፈራው
4. አቶ ስብሰቤ ሽፈራው
5. ወ/ሪት ሳቢዘር ሽፈራው
6. ወ/ሪት መስከረም ሽፈራው
7. አቶ አማኑኤል ሽፈራው
8. አቶ ዳዊት ሽፈራው
9. አቶ ጥላሁን ሽፈራው
10. ወ/ሪት አበባ ሽፈራው

} 1ኛ ተጠሪ በራሳቸውና በሌሎች ወኪልነታቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ኑዛዜ እንዲፈርስ ከቀረበው ክስ ጋር ተያያዞ የተነሳውን የስልጣን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ሲሆን የክሱ ይዘትም የግራ ቀኙ ወላጅ አባት የሆኑት ሟች አቶ ሽፈራው መብራቱ በ13/02/2002 ዓ/ም ለተጠሪዎች ያደረጉት ኑዛዜ በሕገ ወጥ መንገድ የተደረገ ስለሆነ ፈራሽ ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች ለክሱ በሠጡት መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚየና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው እስከዚህ ችሎት የሚያከራክራቸው ነጥብ አመልካቾች በክሳቸው ላይ የጠቀሱት የውርስ ንብረት ግምት 10,000,000.00(አስር ሚሊዩን ብር) በመሆኑና ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕጉ ባለው የውክልና ስልጣን ክርክሩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበበት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ መቃወሚያ መሰረት አድርጎ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን፣ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት በሕጉ የተሠጠው የውክልና ስልጣን ስር እንደማይወድቅ በምክንያትነት ይዞ ክሱን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ሲያከራክር ከቆየ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካቾች ክስ ሲመስርቱ ግምቱ 10,000,000.00(አስር ሚሊዩን ብር) የሆነ የውርስ ንብረት ለተጠሪዎች በኑዛዜ የተሰጠው በሕገ ወጥ ኑዛዜ ነው፣ ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ይገባልወ በማለት ዳኝነት የጠየቁት ጠቅላላውን የሟች የውርስ ንብረት እንጂ ለአመልካቾች ሊደርስ የሚገባው ነው በማለት ስላለመሆኑ፣ የንብረት ግምትን ንብረቱ ሊጣራ ይገባል በሚል የተዘረዘረው አመልካቾች ከውርስ የተነቀሉ ስለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ሲያጣራ መነሻ እንዲሆን በሚል ሃሳብ እንጂ ለአመልካቾች የሚደርሰውን ንብረት ድርሻ በትክክል በማወቅ ያለመሆኑን ዘርዝረው ጉዳዩ የኑዛዜ ይፍረስልኝ ሁኖ እያለ እንደ ውርስ ንብረት ድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ተደርጎ ስልጣኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለው የፌዴራል የውክልና ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም ተብሎ ብይን መሰጠቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች በመቅረባቸውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከውርስ ሕጉ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ሚች አቶ ሽፈራው መብራቱ በ13/02/2002 ዓ/ም ለተጠሪዎች ያደረጉት ኑዛዜ ሕገ ወጥ በመሆኑ ፈራሽ ሊባል ይገባል በማለት አመልካች ክስ ሲመሰርቱ አጠቃላይ የሚች የውርስ ንብረት ግምቱ ብር 10,000,000.00(አስር ሚሊዩን ብር) እንደሆነ ጠቅሰወ ክስ መመስረታቸውን ነው፡፡ ተጠሪዎች የሚች የማይንቀሳቀስ ንብረት ብቻ አጠቃላይ ግምት 10,060,000.00 መሆኑን የጠቀሱና ከዚህ ውስጥ እኩል እንድንካፈል ባሉት መሰረት ቢወሰንላቸው እንኳን አመልካቾች ድርሻችን ነው የሚሉት ንብረት ግምት ከብር 3.3 ሚሊዩን የበለጠ መሆኑንና አመልካቾች ድርሻቸውን በማስላት ያቀረቡት ክስ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ አደይደም በማለት መወሰናቸው ተገቢ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍርድ ቤት ዳኝነት የሚሰጠው በሕጉ አግባብ በተጠየቀው ጉዳይ ላይ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1) ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ዳኝነት የሚሰጠውም በከሳሽ የቀረበውን ዳኝነትና በተከሳሽ በኩል የቀረበው መከላከያ መልስ መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 247፣248 እና 249 ድንጋጌዎች አግባብ ጭብጥ ተይዞ የፍሬ ነገርና የሕግ ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ መሆኑ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የሚች አባታቸውን የውርስ ንብረት ግምት በክሳቸው ላይ መጥቀሳቸውን ሳይክዱ የጠየቁት ዳኝነት ግን ሚቹ በ13/02/2002 ዓ/ም ለተጠሪዎች ያደረጉት ኑዛዜ ሕገ ወጥ በመሆኑ ፈራሽ ነው ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትምበሚቹ በ13/02/2002 ዓ/ም ተደረገ የተባለው ኑዛዜ ሕገ ወጥ ተብሎ ተብሎ ፈራሽ ነው ሊባል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ይዞ የኑዛዜውን ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን ከውርስ ህግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንጻር በመመርመር በኑዛዜው ሰነድ ፈራሽ መሆን ያለመሆን ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1) አግባብ ዳኝነት ከመስጠት አልፎ አመልካቾች ከሚቹ ውርስ ንብረት ንብረት ላይ በተወላጅነታቸው በሚደርሳቸው የውርስ ንብረት መጠን ላይ ሊፈጸም የሚችል ዳኝነት ሊሰጥ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ አመልካቾች የሚቹን ኑዛዜ ፈራሽ ለማስደረግ ያቀረቡት ዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ከአገኘ በኋላ በሕጉ አግባብ በሚደርሳቸው የውርስ ንብረት ላይ ተገቢውን ዳኝነት አቅርበው ሌላ ዳኝነት የሚያገኙ ከሚሆኑ በስተቀር በኑዛዜ ፈራሽ ይደረግልኝ ክስ ላይ በድርሻቸው መጠን የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፍሉ ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የጠየቁት ዳኝነት ኑዛዜው ይፍረስልኝ ሆኖ እያለ በኑዛዜ የሚደርሳቸውን ድርሻ በትክክል ለይተው ሳይጠይቁ የሚችን የውርስ ንብረት ግምት በማስቀመጣቸው ብቻ ይኼው ግምት መሰረት ተደርጎ ከፍርድ ቤት ስረ ነገር ስልጣን ጋር የተነሳው ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ መዘጋቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በአምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 08187 በ3/13/2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር06881 በ20/03/2009 ዓ/ም የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡት ክስ የኑዛዜ ይፍረስልኝ በመሆኑና ይህ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 14 የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስር ስለሚወድቅ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕጉ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት ጉዳዩን የማየት ስረ ነገር ስልጣን አለው ብለናል፡፡ በዚህም መሰረት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢው ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጸፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንግድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 110149

ታህሳስ 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-ምድረ ሎዛ የጋራ ሕንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበር

-ም/ሊ/መንበር አቶ ኃይሌ ገ/ማርያም ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ይሕደጎ ኪዳኔ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ከማህበር አባልነት ማሰናበትን በመቃወም ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው በኀብረት ስራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 መሰረት በተቋቋመው የሽምግልና ጉባኤ በ01/11/2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 115209 በ16/03/2007 ዓ.ም የተሻሻለው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪው በ28/06/2003 ዓ.ም. አዘጋጅተው ለሽምግልና ጉባኤው ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት የማህበሩ መስራች አባል መሆናቸውን፣ማህበሩ አባላት ባልሆኑ ግለሰቦች የሚመራ መሆኑን፣ ወጪና ገቢውም የማይታወቅ መሆኑን፣የቤቶች ዕደላም በማህበሩ ውስጠ ደንብ መሰረት በዕጣ መሆን ሲገባው ከዚህ ውጪ በሆነ አሰራር የታደለ መሆኑን እና ማህበሩ ሌሎችንም ጥፋቶች እየፈጸመ መሆኑን ገልጸው ተገቢው እርማት እንዲደረግ ለማህበሩ እና ቀጥለውም ማህበሩን ለሚቆጣጠረው የቦሌ ክፍለ ከተማ የህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት በ14/06/2000 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መጠየቃቸውን፣ይህን የመብት ጥያቄ በማቅረባቸውም ምልዓተ ጉባኤው ሳይሟላ እና ምንም ዓይነት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸው ማህበሩ በ07/07/2000

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓ.ም እና በ02/13/2000 ዓ.ም ባደረጋቸው ስብሰባዎች ተጠሪን ከማህበሩ አባልነት ያሰናበተ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ውሳኔው ተሸሮ ወደ ማህበሩ እንዲመለስ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው።

አመልካቹ በ23/07/2003 ዓ.ም በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጠው መልስ ተጠሪው ከማህበሩ እንዲሰናበቱ የተደረገው በማህበሩ ላይ በፈጸሙት በደል መሆኑን፣ከእነዚህም መካከል በፀሀፊነት ተመርጠው አልሰራም ማለታቸው፣በማህበሩ ላይ የማቴርያል ኪሳራ እንዲደርስ ማድረጋቸው/ለምሳሌ በብር 290 የሚገዛን አንድ መኪና ድንጋይ በራሳቸው ፈቃድ በብር 300 መግዛታቸው/፣ክፍያን በወቅቱ አለመፈጸማቸው፣ቤቶቹ ተሰርተው ካለቁ በኃላም ቢሆን እቀያይራቸዋለሁ ብለው መዛታቸው እና ፀሐፊ ሆነው በሰሩበት ጊዜ የያዟቸውን ሰነዶች እንዲያስረክቡ ሲጠየቁ ማዘግየታቸው የሚጠቀሱ መሆኑን እና ከአባልነት የማሰናበት ውሳኔው የተላለፈው በተሟላ ምልዓተ ጉባኤ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሮአል።

ጉባኤውምየግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በ07/07/2000 ዓ.ም ውሳኔ የተላለፈው ባልተሟላ ምልዓተ ጉባኤ እንደሆነ በአመልካቹም መታመኑን፣በ02/13/2000 ዓ.ም በተደረገው ስብሰባም ከማህበሩ 24 መስራች አባላት መካከል በአካል ተገኝተው ድምጽ የሰጡት ዘጠኝ አባላት ብቻ መሆናቸውን፣አራቱ መስራች አባላት ድምጽ ሰጥተዋል የተባለው በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 18 ከተመለከተው ውጪ በውክልና በመሆኑ ድምጻቸው ሊቆጠር የማይገባው መሆኑን፣ተተኪ አባላት ናቸው የተባሉት ስምንት ሰዎች ስለመተካታቸው ለማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት በደብዳቤ የተገለጸ ቢሆንም በማህበሩ ውስጥ የተተኩበትን አግባብ የሚመለከት ሰነድ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ማህበሩ ማናቸውንም ሰነድ ማቅረብ ያልቻለ በመሆኑ ድምጻቸው ሊቆጠር የማይገባው መሆኑን፣በዚህ አግባብ በማህበሩ ውስጠ ደንብ ከተመለከተው ስርዓት ውጪ ቁጥራቸው ከግማሽ በታች በሆነ የማህበሩ አባላት የተሰጠ ውሳኔ አንድን አባል የማሰናበት ውጤት ሊኖረው የማይገባ መሆኑን፣ተጠሪው የፈጸሙት ጥፋት አለ ቢባል እንኳ በማህበሩ ውስጠ ደንብ አንቀጽ 17 እና 23 መሰረት ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ተግሳጽ በጽሁፍ ሳይሰጣቸው በቀጥታ የስንብት እርምጃ መውሰድ የማይቻል መሆኑን ገልጾ ተጠሪው ወደ ማህበሩ አባልነት ተመልሰው ድርሻቸውን በዕጣ የማግኘት መብትን ጨምሮ መብቶቻቸው እንዲከበሩ እና ግዴታዎቻቸውን እንዲወጡ እና የማህበሩ ሂሳብም በውጪ ኦዲተር እንዲመረመር በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቶአል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሽምግልና ጉባኤው በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሰናበት የተደረገን አባል ወደ ማህበሩ እንዲመለስ የመወሰን ስልጣን እንደሌለው እና ክሱም በይርጋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የታገደ እንደሆነ ገልጾ የሽምግልና ጉባኤውን ውሳኔበመዝገብ ቁጥር 115209 በ22/08/2004 ዓ.ም ሽሮት የነበረ ቢሆንም የአሁኑ ተጠሪ በተራቸው ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት በመዝገብ ቁጥር 80395 በ30/07/2005 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ ጉዳዩን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የመለሰው መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በተመለሰለት መሰረት የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ የማህበሩ ሂሳብ እንዲጣራ ውሳኔ የተሰጠው ባልተጠየቀ ዳኝነት መሆኑን ገልጾ በዚህ ረገድ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር እና ተጠሪው ወደ ማህበሩ እንዲመለሱ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ግን በማጽናት የጉባኤውን ውሳኔ አሻሽሎአል።አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪን ከማህበሩ ለማሰናበት በውክልና ድምጽ የሰጡት እና ተተኪ አባላት የሆኑትም ጭምር የማህበሩ አባላት ናቸው ወይም አይደሉም ሳይባል ድምጻቸው አይቆጠርም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጁ እና ከማህበራት መተዳደሪያ ደንብ እንጻር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል።

በዚህም መሰረት ተጠሪውን ከማህበር አባልነት ለማሰናበት በውክልና ድምጽ የሰጡት አባላት ድምጽ ሊቆጠር አይገባውም በሚል የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በተመለከተ ማንኛውም የመሰረታዊ ማህበር አባል በስብሰባ ላይ ተገኝቶ ራሱ ድምጽ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ በኅብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 /በአዋጅ ቁጥር 402/1996 እንደተሻሻለ/ በአንቀጽ18 (2) ስር ተመልክቶአል።ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤ ላይ በአካል ተገኝቶ ድምጽ መስጠት ያለበት ስለመሆኑም የአመልካች ማህበር መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 8 (1) ስር በግልጽ ያመለክታል።ይህ አጠቃላይ መርህ ሊታለፍ የሚችለው መረጃ ሊቀርብበት የሚችል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ስለመሆኑም በዚሁ ደንብ በአንቀጽ 21.1.5 ስር ተመልክቶአል።በተያዘው ጉዳይ ተጠሪውን ከማህበሩ አባልነት ለማሰናበት አራት ሰዎች ድምጽ የሰጡት በውክልና መሆኑ አልተካደም።ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም በውክልና ድምጽ መስጠት እንደሚቻል ገልጾ አመልካች በሰበር አቤቱታው የተከራከረ ቢሆንም አራቱ ሰዎች በውክልና ድምጽ እንዲሰጡ የተደረገው ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ስለመሆኑ በ02/13/2000 ዓ.ም. በተያዘው ቃለ ጉባኤ ላይ የተገለጸ ነገር ስላለመኖሩ እና በዚህ ረገድ አመልካቹ በስር ፍርድ ቤቶች ያቀረበው ማስረጃ ስላለመኖሩ ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ያቀረቡትን የክርክር ነጥብ አመልካቹ በመልስ መልሱ ማስተባበያ አልሰጠበትም።ጉዳዮችን በውክልና የማስፈጸም መብትን አስመልክቶ በአዋጁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በሕገ መንግስቱ፣በቤተሰብ ሕጉ እና በፍትሐብሔር ሕጉ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የሚቃረኑ ናቸው በማለት አመልካች እያቀረበ ያለው ክርክርም የአዋጅ ቁጥር 147/1991 "ን" ዓላማ እና የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8 (1) እና 21.1.5 ግልጽ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም።በመሆኑም ማንኛውም የማህበሩ አባል በጠቅላላ ጉባኤ በሚተላለፉ ውሳኔዎች ላይ ድምጽ መስጠት ያለበት በመርህ ደረጃ በአካል ተገኝቶ ስለመሆኑ በአዋጁ እና በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በግልጽ የተመለከተ እስከሆነ ድረስ እና የዚህን መርህ ተፈጻሚነት የሚያስቀር የተለየ ሁኔታ የነበረ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቹ የቀረበ ክርክር እና ማስረጃ እስከሌለ ድረስ ተጠሪውን ከማህበሩ አባልነት ለማሰናበት በውክልና ድምጽ የሰጡት አባላት ድምጽ ሊቆጠር የሚገባው አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም።

ተተኪ አባላትን በተመለከተ ስምንቱ ተተኪ አባላት በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ተገኝተው ተጠሪውን ከማህበር አባልነት በማሰናበት ውሳኔ ላይ ድምጽ የሰጡት በ02/13/2000 ዓ.ም መሆኑ እና አመልካቹ ማህበር ተጠቃሾቹ ግለሰቦች በሌሎች አባላት ምትክ በማህበሩ የገቡ ስለመሆኑ ለክፍለ ከተማው የማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት የገለጸው ድምጹ ከተሰጠ ከአንድ ወር በኃላ በ27/01/2001 ዓ.ም መሆኑን የሽምግልና ጉባኤው ውሳኔ ያመለክታል።አመልካቹም የእነዚህን ፍሬ ነገሮች ክንውን ቅደም ተከተል አስመልክቶ ያቀረበው የማስተባበያ ክርክር የለም። ስምንቱ ተተኪ አባላት በማህበሩ አባልነት የተተኩበትን አግባብ በሚያመለክት ማህበሩ ማናቸውንም ዓይነት ሰነድ ማለትም የውርስ፣የስጦታ፣የሽያጭ፣ድርሻ የማስተላለፍ፣በተተኪ አባልነት የመቀበል ቃለ ጉባኤ እና መሰል ሰነዶችን እንዲያቀርብ ተጠይቆ ማቅረብ ያልቻለ ስለመሆኑም በጉባኤው ውሳኔ ላይ ሰፍሮ ይገኛል።አመልካቹ እነዚህ ሰነዶች ተሟልተው የነበረ ስለመሆኑ በሰበር አቤቱታው ላይ ያቀረበው ክርክር የለም።እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተተኪ አባላቱ ተጠሪው ከማህበር አባልነት እንዲሰናበቱ ድምጽ በሰጡበት ቀን በርግጥ የማህበሩ አባላት የነበሩ መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻልበት አግባብ አይኖርም።በመሆኑም ተተኪ አባላት ናቸው በተባሉት ሰዎች የተሰጠውንም ድምጽ ባለመቀበል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍልም የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም።

ተጠሪን ከማህበሩ ለማሰናበት በውክልና ድምጽ የሰጡት እና ተተኪ አባላት የሆኑትም ጭምር የማህበሩ አባላት ናቸው ወይም አይደሉም ሳይባል ድምጻቸው አይቆጠርም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት በሚል ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘውን ነጥብ በተመለከተ በመሰረቱ በጉባኤው ዘንድ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው እና ውሳኔ ያረፈበት ጭብጥ ተጠቃሾቹ ግለሰቦች ተጠሪውን ከማህበሩ አባልነት ለማሰናበት በተላለፈው ውሳኔ ላይ የሰጡት ድምጽ ሊቆጠር ይገባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይስ አይገባም? የሚል እንጂ የማህበሩ አባላት ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚል ባለመሆኑ የጉባኤው ውሳኔ የድምጽ አሰጣጥ ስርዓቱን በተመለከተ ካልሆነ በቀር በሌሎች ጉዳዮች ረገድ የተጠቃሾቹን ግለሰቦች መብት የሚነካ አይደለም።በመሆኑም በውክልና ድምጽ የሰጡትም ሆነ ተተኪ አባላት ከማህበሩ ጋር ያላቸውን የግንኙነት ሁኔታ በጭብጥነት መያዙም ሆነ በዚህ ነጥብ ላይ ውሳኔ ማሳረፉ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት አልተገኘም።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአዋጅ ቁጥር 147/1991 መሰረት በተቋቋመው የሸምግልና ጉባኤ በ01/11/2003 ዓ.ም. በአብላጫ ድምጽ ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 115209 በ16/03/2007 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቶአል።
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰመ/ቁ.123984

ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገበሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ጌታቸዉ መሸሻ - ጠበቃ አለማየሁ ብርሀኔ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ተሾመ ወልደ - ጠበቃ ገመዳ ስፋው ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.232927 በ26/04/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ከሳሽ በ16/3/2006 ዓ.ም በቼክ ቁጥር ሲ 926821 በሆነዉ ብር 100000 /አንድ መቶ ሺህ/ ለተከሳሽ አበድሬዉ ስላልመለሰልኝ ይህን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ 9% ጋር እንዲከፍለኝ በማለት ከሷል፡፡ የሥር ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ከከሳሽ ገንዘብ አልተበደርኩም እኔን ለመክሰስ መብቱን አላስረዳም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ በክስ የተጠቀሰዉን ብር 100000 /አንድ መቶ ሺህ/ ለተከሳሽ ስለማበደሩ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2472 በሚደነግገዉ አግባብ ያቀረበዉ ማስረጃ ስለሌለ ከሳሽ በዚህ ገንዘብ ተከሳሽን ለመጠየቅ ሕጋዊ መብት የለዉም፣ ቼኩን የተቀበልኩት ከሳሽ ገንዘብ አበድሮኝ ሳይሆን አስቀድሞ የሰጡሁትን ገንዘብ ከፍሎኝ ነው በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡

የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሽ አሁንም ይህን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ የቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፣ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመመባቸዉ በመሆናቸዉ ተሽረዉ ተጠሪ የተበደረዉን ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍለዉ በዝርዝር ቅሬታቸዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣር ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣አመልካች ለተጠሪ ቼክ ሰጥቷቸዉ ከባንክ ገንዘብ መዉሰዳቸዉ ተረጋግጦ እያለ የብድር ዉል አቅርበዉ አላስረዱም በማለት የተከሰሱበትን ገንዘብ እንዳይከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት ከሰ.መ.ቁ.31737 ከተሰጠዉ ትርጉም አንጻር ለመመርመር ሲባል፣ አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘዉ መሰረት በ1/2/2009 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔዎች የሕግ ስህተት የሌላቸዉ ስለሆነ የቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ ሆኖ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክስና ክርክር ለተጠሪ በቼክ አንድ መቶ ሺህ ብር አበድሬዉ ስላልከፈለኝ እንዲከፍለኝ በማለት ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቼኩን መቀበሉን ሳይክድ ቀደም ሲል የሰጠሁትን ገንዘብ መልሶልኝ ነዉ፣ ገንዘብ አልተበደርኩም፣ ገንዘብ የተበደርኩኝ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2472 መሰረት የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም በማለት ተከራክሯል፡፡ ከግራ ቀኞቸዉ ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ቼኩን ተቀብሎ ገንዘቡን ከባንክ መዉሰዱን ሳይክድ፣ ነገር ግን ገንዘብ ተብድሬዉ አይደለም በማለት የብር 100000 /አንድ መቶ ሺህ/ ብድር መኖሩን ክዶ ተከራክሯል፡፡ ይህ ከሆነ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ይህን ገንዘብ በብድር ስለመስጠቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.259 /1/ በሚደነግገዉ አግባብ የማስረዳቱ ሸክም የእርሱ ነዉ፡፡ አመልካች በዚህ መሰረት አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ብድር መኖሩን ያስረዳ እንደሆነ ተጠሪ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.259 /2/ በሚደነግገዉ መሰረት የመከላከያ ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክም ይኖርበታል ማለት ነዉ፡፡

ይህ ከሆነ የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የብር 100000 /አንድ መቶ ሺህ/ ብድር ገንዘብ ለማስረዳት አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ምንድን ነዉ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀረበዉ ቼክ የብድር ዉሉን ለማስረዳት አግባብነት እንዳለዉ ነዉ፡፡ ነገር ግን በመሰረቱ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትዕዛዝ የያዘና ቼኩም እንደቀረበ የሚከፈል ስለመሆኑ በንግድ ሕጉ ቁጥር 827 /ሀ/ እና 854 ሥር ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለዉ ቼክ ክፍያ የሚፈጸምበት ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክፍያ ሰነድ መሆኑን ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጭ ግን ቼክ የብድር ዉልን ተክቶ ብድር መኖሩን ለማስረዳት አግባብነት ያለዉ ሰነድ ነዉ ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት የለም፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ከክሱ ጋር የቀረበዉ ቼክ የብድር ዉል መኖሩን ያረጋግጣል በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡

የአሁን አመልካች በክሱ የጠቀሰዉ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ ለተጠሪ በብድር ሰጥቼዋለሁ የሚል ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2472 የተመለከተዉን አግባብነት ያለዉን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደሚደነግገዉ ፣በብድር የተሰጠዉ ገንዘብ 500 /አምስት መቶ/ የኢትዮጵያ ብር በላይ ሲሆን የብድሩ ዉል በጽሑፍ ወይም በፍ/ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሐላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት አይቻል፣ በማለት ደንግጓታል፡፡ በዚህ አግባብ ሲታይ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ብር 100,000 ስለማበደሩ ወይም የብድር ዉል ስለመኖሩ በዚህ ድንጋጌ አግባብ በሚቀርብ ማስረጃ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን አመልካች ደግሞ በዚህ መሰረት ያቀረበዉ የብድር ዉል ሰነድ ስለሌለ ለተጠሪ ገንዘቡን ስለማበደሩ የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ የአሁን አመልካች ከጅምሩ በሕጉ አግባብ የብድር ዉል መኖሩን ባላስረዳበት ሁኔታ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ገንዘቡን እንዳልተበደረዉ የሚያስረዳበት የሥነ ሥርዓት ሕግ አካሄድ ስለሌለ በዚህ ረገድ ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የሰበር አጣር ችሎት አቤቱታዉ ያስቀርባል በሚልበት ጊዜ የጠቀሰዉ የሰ.መ.ቁ.31737 /ቅጽ 5/ ላይ የተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሲታይ በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩ የሚመለከተዉ የሐዋላ ወረቀት እንጂ ቼክን ስላልሆነ በዉሳኔዉ የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮችም ተመሳሳይነት ስለሌላቸዉ ተፈጻሚነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ለተጠሪ ብር 100000 /አንድ መቶ ሺህ/ ያበደረ ስለመሆኑ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ስላላስረዳ ክሱ ተቀባይነት ያለዉም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ የተሰጠ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሌለዉ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.20647 በ15/11/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.226770 በ07/04/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.232927 በ26/4/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ግራ ቀኙቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በ27/12/2008 ዓ/ም እና ጥቅምት 16 ቀን 2009 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ውሳኔ ተነስቷል ይባፍ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 118246

ሰኔ 23 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡- የሲዳሞ ተራ ህንጻ ስራ አክሲዮን ማህበር - ጠበቃ ሰላም ተሾመ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አብረኸት ሀብተእዝጊ ተማኑ ወራሾቻች

1. አቶ ሚካኤል አብርሃ
2. አቶ ሳሙኤል አብርሃ
3. አቶ ጴጥሮስ አብርሃ
4. ወ/ሮ ሳባ አብርሃ
5. ወ/ሮ ሄለን አብርሃ
6. ወ/ሮ ፀጉ አብርሃ
7. ወ/ሮ ዘውዲቱ አብርሃ
8. ወ/ሮ አይዳ አብርሃ
9. አቶ ጳውሎስ አብርሃ

ተወካይ በርሄ ፀጋዬ ቀረቡ

በዚህ መዝገቡ የቀረበው የአመልካች የሠበር አቤቱታ እና በሰ/መ/ቁጥር 120709 የቀረበው የተጠሪዎች የሠበር አቤቱታ መነሻቸው በስር ፍርድ ቤትም ሆነ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አንድ ላይ በተካሄዱ የክርክር መዛግብት በመሆኑ መዛግብቱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 11 መሰረት በማጣመር መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአክሲዩን ብዛት ከፍ ብሎ እንዲመዘገብ የቀረበውን ክስ መነሻ አድርጎ የተደረገን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች አውራሽ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 29 ቀን 2005 ዓ/ም በአመልካች ማህበር ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- በጥቅምት 22 ቀን 1993 ዓ/ም ከሌሎች 27 ሰዎች ጋር በመሆን በአመልካች ማህበር ውስጥ በመስራችነት የተደራጁ መሆኑን፣ በመስራች አባልነታቸውም 4 ሼር በመግዛት ለእያንዳንዱ ብር 50,000.00 በጠቅላላው ብር 200,000.00 መክፈላቸውን፣ በተጨማሪም በጥቅምት 22 ቀን 1993 ዓ/ም በተካሄደው ጉባኤ በተወሰነው መሰረት ለህንጻው ግንባታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚውል አባላቱ እንዲያዋጡ በተወሰነው መሰረት ብር 100,000.00 መክፈላቸውን፣ ይህን በተጨማሪ የተከፈለውን ብር 100,000.00 በተመለከተ በቃለ ጉባኤው እንደተገለፀው ላዋጡት አባላት በአክሲዩን ግዥ እንደሚታሰብላቸው መመልከቱን፣ በዚህ መሰረትም ከሳሽ በድምሩ 6 የአክሲዩን፣ ዋጋቸውን ብር 300,000.00 ከፍለው እያለ መብታቸውን በሚጎዳ አኳኃን የአክሲዩን ብዛቱ አራት አክሲዩን ብቻ ሁኖ ተመዝግቦ እንደሚገኝ፣ በሌላ በኩልም የአክሲዩን ድልድልን በተመለከተ ከሳሽ የ6 አክሲዩን ዋጋ ብር 300,000.00 በመክፈል መስራች አባል መሆን የሚገባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ የአክሲዮን ማህበሩ አባላት በሕጉ በሼራቸው መጠን እኩል ድርሻ እንዳላቸው የተመለከተ ቢሆንም መንግስት ለተከሳሽ ማህበር በሰጠው የግንባታ ቦታ ሰፋሪ የነበሩት ሰዎችም በአባልነት እንዲካተቱ በተወሰነው መሰረት 81 አባላት እንዲኖሩት መደረጉን፣ ይሁን እንጂ ነባር መስራች አባላት የሼር መጠን በተጨማሪ አክሲዮን የማግኘት መብት እንዳላቸው በሕጉ ተቀመጦ የተጨማሪ አክሲዩን ድርሻ ድልድል በምን መልኩ እንደተከናወነ ሳይታወቅ ቀደም ሲል አንደ፣ሁለት እና ሶስት የአክሲዩን ድርሻ የነበራቸው በአሁኑ ወቅት ባለ 8 እና 10 ባለአክሲዩን እንዲሆኑ መደረጉን፣ በዚህም መሰረት ወደ 13 የሚሆኑ አባላት ከ8-20 አክሲዩን እንዲኖራቸው መደረጉን፣ ይህም አዲስ ገቢዎችና ነባር አባላትን የሚመለከት መሆኑን፣ በመሆኑም ከሳሽ በመስራች አባልነታቻውና በከፈሉት የ6 አክሲዩን ዋጋ የ6 አክሲዩን ድርሻ ሲገባቸው አራት አክሲዩን ብቻ እንዲኖራቸው በማድረግና ከአዲስ አክሲዮኖች በተጨማሪ አክሲዩን ሊሰጣቸው ሲገባ ባልታወቀና ከመተዳደሪያው ደንቡ ውጪ በተከናወነ የአክሲዩን ድልድል ተከሳሽ ማኅበር የከሳሽን መብት መንፈጉን፣ የተከናወነው የአክሲዩን ድልድል ተገቢ እንዳልሆነ በመግለፅ ከሌሎች አምስት አባላት ጋር በመሆን ለማህበሩ ቦርድ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት በ12/02/2005 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ በተሰጠ መልስም በመስከረም 2004 ዓ/ም በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ለፊርማ የቀረበው ቃለ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ በ13/08/2004 ዓ/ም ተወያይተንበታል በሚል እምነት በቅን ልቦና የተደረገ ሲሆን ቅሬታ ካስከተለ ግን ቀሪ ሆኖ ለጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ እንደሚቀርብ ገልፀው በደብዳቤ መልስ የሰጧቸው ቢሆንም በዚህ ደብዳቤ መሰረት የተወሰደ ማስተካከያ እርምጃ የሌለ መሆኑንና የማህበሩ አባላት በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በመቅረብ የአባልነት ፊርማቸውን እንዲያኖሩ በተነገረው መሰረት ለመፈረም በቦታው ሲሄዱም የአባላቱ ቁጥር በጉባኤው በተነገረው መሰረት 81 አባላት ሳይሆን 89 ተብሎ ተዘርዝሮ መገኘቱን፣ ይህም ተጨማሪ 8 አባላት በምን መልኩ እንደተጨመሩ የማይታወቅ መሆኑን፣ ጉባኤው ያሳለፋቸው ውሳኔዎችና አዲስ አክሲዮን መጨመር እና ድልድሉን በተመለከተ የመተዳደሪያ ደንቡና የመመስረቻ ፅሁፍ አባላት በሚፈርሙበት ቦታ ከፊርማ ወረቀቱ ጋር አብሮ መቀመጥ እንዳለበትና ከፈለጉ ፊርማቸውን የሚያኖሩ አባላት ይህንኑ ፅሑፍ እየተመለከቱ ተረድተው መፈረም እንዳላባቸው በሕጉ ተደንግጎ እያለ እነዚህ ሰነዶችን ለማየት ጥያቄ ቢያቀርቡም ከፈለጋችሁ ፊርማችሁ ውጪ እንጂ አይሰጥም በማለታቸው የተወሰኑት አባላት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይፈርሙ ሊወጡ መቻላቸውንና በዚህ የማህበሩ ድርጊትም የከሳሽ መብት መነፈጉን እንዲሁም ሌሎች አባላት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የፈረሙትን ሰነድ ተከሳሽ ማኅበር ለማፅደቅ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ ዘርዝረው ከሳሽ የተከሳሽ ማህበር መስራች አባል በመሆን የከፈሉት የስድስት አክሲዩን ዋጋ ብር 300,000.00 ታሳቢ ተደርጎ ተጨማሪ የ14 አክሲዩን ዋጋ ከፍለው የ20 አክሲዩን ባለቤት እንዲሆን ይወሰንልኝ፣ የተከሳሽ ማኅበር የመተዳደሪያ ደንብና የመመስረቻ ፅሑፍ በዚህም መሰረት የሆነው የቃለ ጉባኤ ሰነድ የማንበብ መብታቸው እንዲከበርና ሰነዶቹ እንዲሰጧቸው፣ በተጨማሪ እንዲገቡ የተደረጉት 8 አዲስ አባላትም በምን ሁኔታ አባል እንደሆነ ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ/ም በሰጠው መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነትም ክሱ በተፋጠነ ስነ ሰርዓት ለመቅረብ በሕጉ የተመለከቱትን መመዘኛዎችን የማያሟላ መሆኑን፣ የማህበሩ አባላት 81 ሁነው እያለ 89 የተባለው በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን፣ ከሳሽ ከኢትዮጵያ ከወጡ ከ15 አመት በላይ የሆናቸው ከመሆኑም በላይ ኤርትራዊ ዜግነት እንዳላቸው ውክልና የሰጡት ኢትዮጵያ ኢምባሲ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ስም ካለው የአሜሪካን አዋዋይ ዘንድ ሆኖ ከዩ.ኤስ. ውጭ ጉዳይ በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኢምባሲ መረጋገጡ ሁሉንም ነገር በወኪል የሚሰራ በመሆኑ በግለሰቧ ሁኔታ የተጣራ ባለመሆኑ ከሳሽ ራሳቸው እንዲቀርቡ ወይም አሜሪካ አገር ኢትዮጵያ ኢምባሲ በአካል ቀርበው ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት እንዲደረግ የሚሉትን ነጥቦችን አንስቶ ተከራክሯል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የተከሳሽ ማህበርን ሕጋዊ አቋም አስመልክቶ ማህበሩ በ1992 ዓ/ም በሶስት ሰዎች ሲቋቋም የመርካቶ አካባቢ የመልሶ ማልማት ፕሮግራም ያልወጣ ስለመሆኑ ከሳሽ በ1993 ዓ/ም ባለአክሲዩን ሲሆኑም ከሳሽ ተጨማሪ አክሲዩን ያወጣ ስለመሆኑና ከዚህ በኋላ ግን በ18/06/99 ዓ/ም ማህበሩ የሊዝ ውል ተዋውሎ በ28/07/98 9430 ካ/ሜትር ቦታ ሲዳሞ ተራ አከባቢ በሊዝ ቦታ መግዛቱን፣ ይሁን እንጂ ከዚህ ቦታ ውስጥ ሌሎች በማህበርነት የተደራጀ ሶስት ማህበራት ለአዲስ አበባ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት የተወሰነው ቦታ ተቀንሶ ለሌሎች ማህበራት እንደተሠጠና ለእያንዳንዱ ማህበር በተሰጠው ቦታ ላይ የነበሩና በማህበር ያልተካተቱት ተነሺዎች በነበሩበት ቦታ በተደራጁት ማህበራት እንዲካተቱና ይህም ሲረጋገጥ ማህበራቱ የሊዝ ውሉን እንዲዋዋሉ መወሰኑን፣ ከሳሽም በተከሳሽ ማህበር ባለአክሲዩን ቢሆኑም የነበራቸውን ነባር ይዞታና የቤት ቁጥር መሰረት አድርገው በልጃቸው በአቶ ኤፍሬም አብርሃ ወ/ጊዩርጊስ ስም በሲኒማ ራስ ማህበር ውስጥ የተደራጁ መሆኑን፣ ይሁንና ማህበሩ ኃ.የተ.የግል ማህበር በመሆኑ ከሳሽ ሌላ ማኅበር ውስጥ ስለተደራጁ ብቻ ከአባልነት ለማስወጣት ባለመቻሉ በባለአክሲዮንነታቸው እንዲቀጥሉ መደረጉን፣ በሌላ በኩል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሊዝ አፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 1/2002

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀፅ 34.10 ድንጋጌ መሰረት ለሚደራጁ የንግድ ማህበራት የተወሰነው ቦታ ላይ የነበሩና ይዞታቸው የፈረሰባቸው ነጋዴዎች/ሰዎች/ በማህበራቱ በአባልነት እንዲካተቱ መደረጉን፣ በዚህም መሰረት በተከሳሽ ማህበር አባል ከነበሩት 27 ባለአክሲዮኖች በተጨማሪ 54 አዲስ አባላት ባለአክሲዮኖችን ማካተት የግድ መሆኑን፣የማህበሩ አመራር አካላት የነባርና አዲስ የሚገቡ አባላት የአክሲዩን ድልድል ምን መሆን እንደአለበት በሚለው ጉዳይ ላይ ከህግ አንጻር ተወያይተውበት የአባላቱን፣ የነባር ይዞታ መጠንና የነባር ባለአክሲዮኖችን የጎላ አስተዋጽኦ መሰረት በማድረግ ፍትሃዊ የሆነ አጠቃቀም መመዘኛ ተደርጎ ቀድሞ በነበራቸው የይዞታ መጠን/ስፋት/ አክሲዩን ድልድል መከናወኑን፣ በዚህም መሰረት የአንድ አክሲዩን ዋጋ ብር 50,000.00 ሁኖ ትንሽ ይዞታ የነበረው ሰው ዝቅተኛውን አራት አክሲዩን እንዲይዝና ከፍተኛ ይዞታ የነበረው ደግሞ 20 አክሲዩን እንዲይዝ፣ይዞታ ያልነበራቸው ከሳሽን ጨምሮ ባለአክሲዩን የነበሩ ሰዎች ዝቅተኛ የአክሲዩን መጠን እንዲሰጣቸው እንዲሁም በልዩ ሁኔታ ማህበሩ ባልተደራጀበት ወቅት ምንም ክፍያ ሳይሰጣቸው በግል ጥረታቸው ማህበሩን አሁን በሊዝ የያዛቸውን ሶስት ካርታዎች እንዲያገኙ ምክንያት ለሆኑት የተከሳሽ ሊቀመንበር በነበራቸው ስድስት አክሲዩን ላይ አራት አክሲዩን እንዲጨመር መደረጉን፣ ይህ ጥናትም ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ጉባኤውም ተስማምቶበት በ30/08/2005 ዓ/ም ማጽደቁን፣የባለአክሲዮኖቹ ጠቅላላ ጉባኤ በሕግ አግባብ ተጣርቶና ምልዓተ ጉባኤው ተሟልቶ የአክሲዩን ድልድሉን በተመለከተ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ከሳሽም ተስማምተው በቃለ ጉባኤው ላይ ከፈረሙ በኋላ እንደገና የሰረዙት በመሆኑ የ14 ሼር ከፍዬ የ20 ሼር ባለቤት ልሆን ይገባል በማለት ያቀረቡት ጥያቄም የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር አመክንዮ የሌለው መሆኑን፣ ከሳሽ ከአራት አክሲዩን ዋጋ በተጨማሪ ከፍያለሁ ያሉት ብር 100,000.00 ከሳሽ እንዳሉት የተከፈለው በ1993 ዓ/ም ሳይሆን በ2002 ዓ/ም ስለመሆኑ፣ ክፍያውን እንዲፈጽሙ ስለመጠየቃቸውም ማስረጃ ያላቀረቡና የደረሰባቸው ጉዳት ባለመኖሩ ከማህበሩ የአክሲዩን ድልድል መርህ አንፃር በብር 300,000.00 ታስቦ አክሲዮን ይደረግልኝ በማለት የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ከሳሽ መስራች ባለአክሲዩን ያለመሆናቸውንና ባለአክሲዮን የሆኑትም የማህበሩ ካፒታል ባደገበት ጊዜ መሆኑን፣ የአንድ ባለአክሲዩን የአክሲዮን ድርሻ የሚረጋገጠው በአክሲዩን ምስክር ወረቀት ወይም በመመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ ወይም በማሻሻያው ላይ በተገለፀው የአክሲዩንና የገንዘብ መጠን ነው እንጂ በኩባንያው የባንክ ሂሳብ ገንዘቡን ገቢ በማድረግ ብቻ አክሲዩን የማሳደግ መብት የሌለ መሆኑን፣ ብር 100,000.00 የከፈሉቱም ባለአክሲዩን ከሆኑ ከአስር አመት በኋላ ስለመሆኑ፣ የአክሲዩን ድልድል የሚወሰነው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ እንጂ ከጉባኤው እውቅና ውጪ ባለአክሲዮኖቹ በኩባንያ የባንክ ሂሳብ ገንዘብ ገቢ ስለአደረጉ ብቻ ያለመሆኑንና በዚህ ረገድ መብት ሰጪ የሆነ የንግድ ህግ ድንጋጌ የሌለ መሆኑን፣ በመስከረም ወር 2005 ዓ/ም ሲፈረም በነበረው ቃለ ጉባኤ ላይ ከሳሽና ሌሎች አራት ሰዎች ቅሬታ አቅርበው በጥያቄው መሰረት ቀሪ የሆነ ቢሆንም ከዚህ በኋላ ሁለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቃለጉባኤዎች በፍርድ ቤት ትዕዛዝና ለአባላቱ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ በጠቅላላ ጉባኤው በህግ መሰረት የተፈረመ በመሆኑ በ21/02/2005 ተፅፏል የተባለው ደብዳቤ ለክሱ ምንም ፋይዳ የሌለው መሆኑን፣ ተከሳሽ ማህበር በፅሑፍ ከአደረገው ጥሪ በተጨማሪ የካቲት 20 ቀን 2005 ዓ/ም በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ በድጋሚ ባደረገው የባለአክሲዮኖች ጥሪ ላይ የከሳሽ ተወካይ ተገኝተው መፈረማቸውን፣ በስብሰባ ላይም ረቂቅ ቃለጉባኤውና የተሻሻለው የመተዳደሪያ ደንቡና የመመስረቻ ፅሑፍ በንባብ ተሰምቶ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በጠቅላላ ጉባኤው የፀደቀና በዚህ መሰረትም የመግባቢያ ሰነድ ሲፈረም ተወካይዋ ተስማምተው የፈረሙ መሆኑን፣ ሆኖም ከፈረሙ በኃላ በድጋሚ የማየው ነገር አለኝ በማለት ፊርማቸውን የሰረዙ ቢሆንም ተወካይዋ ስብሰባውን አውቀው ሰነዱን አይተውና ተስማምተው የፈረሙና ከስርዓት ውጪ ፊርማቸውን በሰረዙበት ሁኔታ ቃለጉባኤውም 94.12% በላይ በሆኑት የማህበሩ ባለአክሲዮኖች የወሰኑትን ውሳኔ የተቃወሙት ከሕግ ውጪ መሆኑን፣ የፈራሚዎች ጉባኤ አሰራርና ሰነዶችን የማየት መብት ከከሳሽ ክርክር ጋር አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ ከሳሽ የአክሲዮን ድልድሉን በተመለከተ የተዘጋጀው ቃለ ጉባኤ አልጸደቀም ይበሉ እንጂ ሰነዱ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ/ም በ94% የማህበሩ አባላት ፀድቆና ተረጋግጦ የተሰጠ በመሆኑ ክሱ ህግን መሰረት ያላደረገ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሁኖ በቂ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህም በኋላ ማኅበሩ ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ/ም የተጻፈ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡የክሱ ይዘትም፡-ከሳሽ ማኅበር በሶስት ሰዎች በ11/02/92 ዓ/ም ከተቋቋመ በኋላ በ15/03/93 ዓ/ም በቁጥር 332/4ለ/93 በተፈረመ ቃለ ጉባኤ ከሳሽ ብር 200,000.00 ከፍለው የአራት አክሲዩን ባለቤት የሆኑ መሆኑን፣ በዚህ ቃለ ጉባኤ ላይ የከሳሽ ዜግነት ኢትዮጵያዊ በመባሉ ማህበሩ በአከባቢው የንግድ ስራ የነበራቸው መሆኑንና እርሳቸው በግምባር ቀርበው መፈረማቸውን በመገመት ብቻ በአባልነት የተቀበሏቸው መሆኑን፣ ከሳሽ በዚህ ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረባቸው በፊትም እንደኢትዮጵያዊ ስለሚቆጠሩ ወኪላቸው በየስብሰባው ላይ ሲገኙ መቆየታቸውን፣ ይሁንና ከክሱ በኋላ ተከሳሽ ልዩ ልዩ ሰነዶችን በጥንቃቄ ሲመረምር ከሳሽና ባለቤታቸው በ08/01/93 ዓ/ም በጻፉት የውክልና መሻሪያ ሰነድ ላይ የግለሰቧ ዜግነት ኤርትራዊ መሆኑ መረጋገጡን፣ በተጨማሪም ከሳሽ ለወኪላቸው ወ/ሮ ጊዜሽወርቅ ተሰማ ዋሽንግተን ውስጥ ሆነው ውክልና የሰጡት አንድ አንድ ዋሽንግተን ውስጥ ለተመዘገበና ነጋሽ ተስፋዬ በሚባል አዋዋይ ፊት ሆኖ በኋላ ሰነድ ለአሜሪካ ውጭ ጉዳይ በመቀጠልም ዋሽንግተን ለሚገኘው የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይና በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት መደረጉ ከሳሽ ኢትዮጵያ ያለመሆናቸውን አመላካች የሆነ መሆኑን፣ ለዚህም ምክንያት ዋሽንግተን ያሉ የኢትዮጵያዊያ ዜጎች የሚዋዋሉት የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋር በመቅረብ ስለመሆኑና ከሳሽ የውጪ አገር ዜጋ በመሆናቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የንግድ ማህባራት ባለአክሲዩን መሆን የሚችሉበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኢንቨስትመንት አዋጅና በደንቡ ውስጥ የተመለከቱትን ግዴታዎችን ሲያሟሉ ስለመሆኑ፣ በሌላ በኩል የከሳሽ ወኪል ተከሳሽ ማህበር ባለአክሲዮኖች ስብስባ ላይ በመገኘት በመስማማት ስምምነት ላይ ከፈረሙና በዚሁ መሰረት በሰነዶች ምዝገባ ማረጋገጫ ጽ/ቤት በአባላት የተፈረመውን የማህበሩን ቃለ ጉባኤ የተሻሻለ የመመስረቻ ዕሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከፈረሙበት በኃላ ፊርማቸውን መሰረዛቸውን፣ እርሳቸው የተሰረዙ ቃለጉባኤና ማሻሻያዎች አጀንዳ የአክሲዩን ድልድል በማድረግ ማህበሩን ወደ አክሲዩን ማህበርነት የለወጠ መሆኑን፣ ከሳሽ ጠቅላላ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ ላይ የማይስማሙ ከሆነ በንግድ ሕጉ መሰረት ከአባልነት የሚሰረዙ መሆኑን፣ ከሳሽ በማህበሩ በአክሲዩን መዋጮና በሌላ ጊዜ የከፈሉት አክሲዩኑን በመሸጥ ተከሳሽ የሚከፍላቸው መሆኑን ዘርዝሮ ከሳሽ የውጭ አገር ዜጋ በመሆናቸው የኢንቨስትመንት ህግና ደንቡን ሳያሟሉ በተከሳሽ ማኅበር ውስጥ ባለአክሲዩን ሊሆኑ አይገባም ተብሎ እንዲወሰን፣ ይህ የሚታለፍ ከሆነም የተከሳሽ ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ አክሲዩን አደላድሎና አባላት ጨምሮ ማህበሩን ወደ አክሲዩን ማህበርነት የቀየረ ስለሆነና ከሳሽም በዚህ ውሳኔ ያልተስማሙ ስለሆነ አክሲዮናቸው ተሸጦ ከማህበሩ ባለአክሲዮንነት እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የስር ከሳሽ በስር የተከሳሽ ከሳሽ በቀረባበቸው ክስ መከላከያ መልስ ያቀረቡ ሲሆን በመልሳቸው ላይም ከሳሽ ከሌሎች 27 አባላት ጋር በመስራችነት ሲመዘገቡ በአካል መታወቂያቸውን ይዘው በመቅረብ መመዝገባቸውን የተከሳሽ ከሳሽ ያለመካዱን፣ ይህም በቀረበው የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ሊታይ የሚችል መሆኑን፣ ተከሳሽ ከሳሽ የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው ምክንያት ለምን ተነካን በሚል አስተሳሰብ ጥፋት ለመፈገለግ ሰነድ ማፈላለጉ ከቅን ልቦና የጎደለው አካሄድ መሆኑን፣ አስፈላጊ ከሆነውም ከሳሽ ኢትዩጵያዊ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚል ጥያቄ ቢነሳ እንኳን ይህን የማጣራት ስልጣን ያለው ተከሳሽ ሳይሆን የሚመለከተው ራሱን የቻለ አካል እንጂ ተከሳሽ ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ ውክልና በኢትዩጵያ ኢምባሲ በኩል ስላልተሰጠ ከሳሽ ኤርትራዊ ናቸው በማለት ያቀረቡት ክግምት በመነሳት ስለመሆኑ፣ የሰጡት ውክልና ህጋዊ እስከሆነ ድረስ የዜግነቱ ጉዳይ ተከሳሽን የማይመለከተውና ከሳሽ ኤርትራዊ ናቸው ቢባል እንኳን በየትኛው ሕግና አዋጅ ኢትዩጵያዊ ያልሆነ ሰው አክሲዩን ለመግዛት አይችልም በሚል እንደተደነገገ ተከሳሽ በአግባቡ ጠቅሶ ያላቀረበ መሆኑን፣ በወቅቱ የአክሲዩን ድልድሉን የያዘው ቃለ ጉባኤ በተመለከተ ብዙ ሰው ጥያቄ ያነሳና በርካታ ልዩነትና ጭቅጭቅ አስነስቶ እያለ የተቋቋሙትን ሳትፈርሙ ከወጣችሁ ከማህበሩ ትሰረዛላችሁ በማለት በማስፈራራታቸው ብዙ አባላት የፈረሙ መኖራቸውን፣ በዚህ ሁኔታ ከሳሽ የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው ከማህበሩ እንዲወጡ በሚል የቀረበው ክርክር ተገቢነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው ተከሳሽ በተከሳሽ ከሳሽነት የጠየቁባቸው ነጥቦች ከሳሽ ያነሱትን የመብት ጥያቄ ለመቃወም በማሰብ ስለሆነ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቱ ጥያቄዎቹን ውድቅ በማድረግ ተከሳሽ ተገዶ መብታችንን እንዲያስከብርልን ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በቅድሚያ ተከሳሽ በተከሳሽ ከሳሽነት ያቀረበውን ክስ መሰረት አድርጎ የአሁኑ አመልካች ኃላፊነቱ የተወሰነው የግል ማህበር ሁኖ ከተቋቋመ በኃላ ወደ አክሲዩን ማህበርነት መወለጡንና የተደረገውን የአክሲዩን ድልድል የተቃወሙ በመሆኑ እንዲሁም ዜግነታቸው ኤርትራዊና የውጭ አገር ዜጋ በመሆናቸው ከማህበሩ አባልነት ሊወጡ ይገባል በማለት ያቀረበውን ክስ በመመልከት ከሳሽ የውጭ አገር ዜጋ/ኤርትራዊ ናቸው ለመደምደም የሚያስችሉ ማስረጃዎች ካለማቅረባቸውም በላይ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ሰው ባለአክሲዩን ከመሆን በግልጽ የሚከለክል ድንጋጌ በኢንቨስትመንት ህጎች አለመመልከቱን፣ የተከሳሽ ማኅበር ወደ አክሲዩን ማህበር መለወጥና የአክሲዩን ድልድል ባለመስማማት መቃወም ለአባሉ በሕግ የተሰጠው መብት በመሆኑ ይህን ተቃውሞ ያቀረበ የማህበሩ አባል ከማህበሩ በግድ እንዲወጣ የሚደረግበት አግባብ የሌለ መሆኑን እንዲሁም ተጠሪ/የስር ከሳሽ) ባቀረቡት ክስ የማህበሩን ወደ አክሲዩን ማህበርነት የመለወጥ ጉዳይ በተመለከተ ተቃውሞ ያላነሱና ዳኝነት ያልጠየቁበት ነጥብ መሆኑን በምክንያትነት ይዞና የን/ህ/ቁጥር 547/3/ ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ አመልካች ያቀረበውን ክስ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በመቀጠል የተጠሪን ክስ በመመርመር አመልካች ያቀረባቸውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጎ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ደግሞ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ በመመልከት መርምሮ ማህበሩ በ1992 ዓ/ም ሲመሰረት የነበሩት አባላት ብዛት ሶስት ብቻ እንደነበሩ፣ ማህበሩ የተቋቋመበት መሰረታዊ አላማ የማህበሩ አባላት የንግድ ስራዎችን የሚያከናውንባቸው መደብሮችን በዘመናዊ መልክ ደረጃውን ጠብቀው እንዲደራጁና ለንግድ ስራ የተመቻቹ እንዲሆኑ ለማስቻል መደብሮቹ የሚገኙበትን የቦታ ክልሎች ከመንግስት አስፈቅዶ በሊዝ ለመግዛትና በመረከብ እንዲሁም የሕንጻ ስራ ፈቃድ በማውጣት ለንግድና ለቢሮ አገልግሎት የሚወሉ ህንጻዎች ለመስራት እንደአስፈላጊቱም ለአባላቱ ለማከፋፈል በማሰብ የተቋቋመ ስለመሆኑ በመመስረቻ ጽሑፉ በግልጽ መመልከቱንና አንድ ሰው የማህበሩ አባል የሚሆንበት አግባብም በዚሁ በመተዳደሪያ ደንቡ የተገለፀ መሆኑን፣ በ22/02/1993 ዓ/ም በተደረገው ጠቅላላ ጉባኤም ከሳሽና ሌሎች 23 ሰዎች ወደ ማህበሩ ለመግባት አመልክተው እንዲገቡ እንደተወሰነ እንዲሁም ይህን ውሳኔ ተከትሎ የማህበሩ ዋና ገንዘብ እንዲጨምር የማህበሩ የአክሲዩን ዋጋ እና ብዛትም እንዲሁ ከፍ እንዲል የተወሰነና በውሳኔው መሰረትም የአንድ አክሲን ዋጋ ከብር 1000.00 ወደ 50,000.00 ከፍ ያለ እንዲሆን የተወሰነና ከሳሽም በወቅቱ በድምሩ 200,000.00 ለማህበሩ በመክፈል የአራት አክሲዩን ባለቤት የሆኑ መሆኑን፣ ከዚህም በኋላም 32 ሰዎች በፍርድ ቤት ክስ በመመሰረት በአመልካች ማህበር አባል እንዲሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተወሰነ በመሆኑ የማህበሩ አባላት ቀድሞ ከነበረው 27 አባላት ወደ 59 ከፍ ያለ በመሆኑና ኃ.የተ.የግል ማህበር አባላት ቁጥር ከ50 ሊበልጥ እንደማይገባ በንግድ ሕጉ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ማህበር ከነበረበት ኃ.የተ.የግል ማህበርነት ወደ አክሲዩን ማህበርነት እንዲለወጥ ለመወሰን አዲስ የሆኑትን 32 አባላትን በባለአክሲየንነት ለመመዝገብ በሚል አጀንዳ በመያዝ የቦርድ አባላትን ብቻ ስብሰባ በመጥራትና ሌሎች ባለአክሲዮኖችን መጥራት አያስፈልግም በሚል የቦርድ አባላቱ ውይይት ካደረጉ በኋላ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ለማስፈጸም አዲስ ወደ ማህበሩ የሚገቡትን አባላት አክሲዩን ድርሻ ማደላደል የሚያስፈልግ በመሆኑ ድርሻቸውን መደልደሉን፣ አዲስ ባለአክሲዩን ለሆኑት አባላት አክሲዩን የመደልደሉ ጉዳይም በቀጥታ የማህበሩን ዋና ገንዘብ እንዲያደግ የሚያስገድድ በመሆኑ ቦርዱ ቀደም ሲል የነበረውን ብር 3,000,000,.00 የማህበሩና ዋና ገንዘብ ወደ 10,200,000.00 ከፍ እንዲል በማለት መወሰኑን፣ የማህበሩ አክሲዩን ብዛትም ከ60 ወደ 204 ከፍ እንዲል ተደርጎ ቦርዱ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ለመፈፀም ሲል ጠቅላላ ጉባኤው በአጭር ጊዜ ተጠርጥሮ ማህበሩ ወደ አክሲዩን ማህበርነት እንዲለወጥ እንዲወሰን በማለት ውሳኔ መስጠቱን፣ ከዚህ በኋላም በመጋቢት ወር 2005 ዓ/ም የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ የተሰበሰበና ከማህበሩ አጠቃላይ ዋና ገንዘብ እና የአክሲዩን ብዛት ውስጥ 192 የአክሲዩን ድርሻ ወይም 94.12% ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች በተገኙበት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት የአክሲዩን ዝውውር ማድረግ፣ አዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበልና የሚገበቡትን የአክሲዩን ብዛት መወሰን፣ የነባር ባለአክሲዮኖችን የአክሲዩን ድርሻ ማሳደግና በዚህ መብት መጠቀም ያልቻሉትን መብት መጠበቅ፣ ይህን ተከትሎም የማህበሩ ዋና ገንዘብ ማሳደግና በአጠቃላይ የማህበሩን ባለአክሲየኖችን የአክሲዮን ድልድል መወሰንና ሌሎች ነጥቦች ላይ በመወያየት ውሳኔ ተላልፏል በማለት ቃለ ጉባኤው እንደተዘጋጀ መመልከቱን፣ ከዚህ ጋር በተያያዘም በተጠቃሹ ቃለ ጉባኤ እንደተመለከተው በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት የባለአክሲኖችን የአክሲዮን ድርሻ ድልድል ለማድረግ በዋነኛነት መሰረት የተደረገው ማህበሩ በሚያለማው መሬት ላይ ቀደም ሲል የነበራቸውን የይዞታ መጠንና አባላቱ ለማህበሩ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነ መመልከቱን፣ እንዲሁም ነባር አባላት ከነባራች የአክሲዩን ድርሻ ላይ ተጨማሪና የፈለጉትን/አቅማቸው የፈቀደውን/ የአክሲዩን ድርሻ እንዲኖራቸው ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት በጉባኤው እየተፈቀደ የልዩነቱን/የተጨማሪ አክሲዩን ዋጋ እንዲከፍሉ በቃለ ጉባኤ መመልከቱ ፣ በዚህም መሰረትም የአክሲዩን ብዛት ቀድሞ ከነበረው 204 አክሲዮኖች ወደ 495 እንዲሁም የማህበሩ ዋና ገንዘብ ቀድሞ ከተመዘገበው ብር10,200,000.00 ወደ 24,750,000.00 እንዲያድግና የአንድ አክሲዩን ዋጋም በብር 50,000.00 በነበረበት እንዲሆን በሚል መወሰኑ መደንገጉን፣ ከዚህ በመቀጠልም በዚሁ ተጠቃሹ ቃለ ጉባኤ መጨረሻ ላይ ቀድሞ የነበረው ኃ.የተ.የግል ማህበር ወደ አ/ማህበርነት እንዲለወጥ ለጥር 10 ቀን 2005 ዓ/ም በቁጥር ዋ/መ/5872/4ለ/2005 በተላለፈው ውሳኔ መሰረት የነባር ማህበር መመስረቻ ፅሑፍና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መተዳደሪያ ደንብ ተሻሽሎ መፃፍ ያለበት ስለሆነ በሚል ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ተሻሻሎ እንዲዘጋጅ የተደረገና የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፅ/ቤት እንዲቀመጡና አባላት እንዲፈርሙ ተደርጎ 75 ባለአክሲዩኖች የፈረሙ ስለመሆኑ ቃለ ጉባኤው የሚያሳይ መሆኑንና ብር 100,000.00 ተጠሪ ማሰገባታቸው በማስረጃ መረጋገጡን ዘርዝሮና ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን የንግድ ህግ ቁጥር 536(1-2)፣ 544(1-3፣ 547 ለሌሎች አባላት አክሲዩን ቁጥር ለመጨመር መሰረት የሆኑት አባላቱ ቀደም ሲል የነበራቸው የይዞታ ስፋት መጠንና ለማህበሩ መቋቋም ያደረጉት አስተዋጽኦ በመስፈርትነት እንዲያዙ አባላቱ የተስማሙባቸው ስለመሆኑ ተሻሽለው በተዘጋጁት ጽሑፎች ያለመመልከታቸውን ደምድሞ አመልካች ለተጠሪ አስራ አራት አክሲዩን ጨምሮ ሃያ አድርጎ እንዲመዘግባላቸውና ተጠሪም የአስራ አራቱን አክሲኖች ዋጋ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ ኤርትራዊ መሆናቸው በሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ቢሆንም የውጭ አገር ዜጋ አክሲዩን ገዝቶ በኢንቨስትመንት ላይ እንዳይሳተፍ የሚከለክል ሕግ የለም በማለት የስር ፍርድ ቤት የአሁኑን አመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ አድርጎ የከሳሽ የማህበሩ አባልነት እንዲቀጥል ሲል የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ያጸና ሲሆን ከሳሽ በማህበሩ ሊኖራቸው የሚገባውን የአክሲዩን ብዛት በተመለከተ ግን አመልካች ማህበር መጋቢት ወር 2005 ዓ/ም የያዘውና በሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ/ም በፀደቀው ቃለ ጉባኤ የማህበሩ አባላት ቀድሞ የነበራቸው የቦታ ስፋትና ለማህበሩ መመስረት ያደረጉት አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ ገብቶ የአክሲዩን ቁጥር እንዲጨምርላቸው የተደረጉ አባላት መኖሩን እንደሚያሳይ እና ከሳሽ ደግሞ ይዞታ ያልነበራቸውና ለማህበሩም ያደረጉት አስተዋፅኦ የሌለ መሆኑን በማህበሩ ይዞታ ላይ ቦታ ያላቸው አብዛኞቹ ባለአክሲዮኖች የያዙትን የአክሲዩን መጠን በመመልከት ከሳሽ ተጨማሪ አራት አክሲዮኖችን በመግዛት በድምሩ በማህበሩ ውስጥ አስር አክሲዮኖች ባለቤት ሊሆኑ ይገባል ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ በዚሁ በተሻሻለው የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ከሳሽ ቅር በመሰኘት ይግባኞቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በመ/ቁጥር 117601 በ30/02/2008 ዓ/ም ተሰርዞባቸዋል፡፡

ግራ ቀኙ የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ከላይ በተመለከተው አግባብ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን በሰ/መ/ቁጥር 118246 የቀረበው አመልካች በሠበር ነው፡፡ በዚህም የአመልካች ጠበቃ መስከረም 09 ቀን 2008 ዓ/ም የጻፉት 8(ስምንት) ገፅ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘቱም የሥር ከሳሽ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ሳይኖራቸውና በአዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

12(1(ሀ)፣ 2(6) እና 38 ድንጋጌዎች አግባብ በኢትዩጵያ ውስጥ ባለ ኢንቨስትመንት መሳተፍ የሚችሉ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ የውጪ አገር የሆነ የሰው አክሲዩን ለመግዛት የሚከለክል ሕግ የለም በማለት መወሰኑ ያላግባብ መሆኑንና ተጠሪ እንዲሻርላቸው የጠየቁት በ30/08/2005 ዓ/ም በ94.12% ባለአክሲዮኖች የተደረገውን የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በመሆኑ በተወካያቸው በስብሰባው ላይ ተገኝተው ከፈረሙ በኋላ ፊርማቸውን ስለሰርዙ ብቻ የጉባኤው ውሳኔ ተቀባይነት እንደሌለው ተደርጎ የሥር ፍርድ ቤት ወስኖ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመርህ ደረጃ በ30/08/2005 ዓ/ም በተደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የተደረገውን የአክሲዩን ድልድሉን ከተቀበለ በኋላ የጉባኤውን ውሳኔ ለውጦ የሥር ከሳሽ በድምሩ አስር አክሲዩን እንዲኖራቸው በማለት የሠጠው ውሳኔ በሕጉ ለጠቅላላ ጉባኤ የተሰጠውን ስልጣን ያላገናዘበ የሚል እና በእነዚህ ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ዳኝነት እንዲሰጥ መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የተጠሪን ዜግነት መሰረት በማድረግ ያቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በስር ፍርድ ቤት ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን የሥር ከሳሽ ሕጋዊ ወራሾች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

በሰ/መ/ቁጥር 120709 የቀረበው የተጠሪዎች የሰበር አቤቱታ ሲሆን የተጠሪዎች ጠበቃ ህዳር 30 ቀን 2008 ዓ/ም 3 (ሦስት) ገጽ የሰበር አቤቱታ በታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የንግድ ሕጉ ከሚደንግገው ውጪ የስር ከሳሽን አክሲዩን በቀድምትነት የመግዛት መብት በመተው አስር አክሲዮኖችን ብቻ እንዲገዙ በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ባለመሆኑ ተለውጦ የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪዎች እናት ሃያ አክሲዩን ባለቤት ሊሆኑ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በመ/ቁጥር 185768 በተሰጠው ውሳኔ መስራች ባለአክሲዮኖች ያሏቸው መብትና ጥቅም እንዲያገኙ ውሳኔ የተሰጠበት ሆኖ ሳላ ከሌሎች ባለአክሲዮኖች ባነሰ የአስር አክሲዩን ድርሻ ብቻ ሊኖራቸው ይገባል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ የሆነው የስር ተከሳሽም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት መዝገብም እንዲመጣ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክርና በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ይዘት ታይቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ሁለቱም መዝገቦች ያስቀርባል ሲባሉ ከተያዙት ጭብጦች አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. የሥር ክሳሽ ኤትርትራዊ/የውጭ አገር/ዜጋ ናቸው ተብሎ ድምዳሜ በተያዘበት አግባብ በአክሲዩን የማህበር አባል ሁነው መቀጠል ይችላሉ ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተ አለ? ወይም የለም?፣
2. የስር ክሳሽ በአመልካች ማህበር ሊኖራቸው የሚገባው የአክሲዩን ብዛት አስር ነው ተብሎ የተወሰነው በሕጉ አግባብ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ሁነው ተገኝተዋል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> አመልካች የሰበር አቤቱታውን ባቀረበበት የሰበር መዝገብ ቁጥር 118246 በመሰረታዊ ጭብጥነት የተያዘውና በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገው ነጥብ የሥር ተከሳሽ የስር ክሳሽን ዜግነት መሰረት በማድረግ ያቀረበው የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ የማድረጉን አግባብነት የሚመለከት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የሥር ክሳሽ የውጭ አገር ዜጋ ስለመሆናቸው በቂ ማስረጃ አልቀረበም በማለት የያዘውን ድምዳሜ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ ሥልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመዘን የስር ክሳሽን የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸውን ድምዳሜ ይዞአል፡፡ በመሆኑም የስር ክሳሽ የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸው በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተነሳው የሕግ ጥያቄ የውጭ አገር መሆኑ የተረጋገጠበት ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄደው ኢንቨስትመንት አክሲዩን ገዝቶ በንግድ ሕጉ አግባብ በሚቋቋመው ማህበር አባል መሆን የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

የስር ክሳሽ በዚህ ረገድ በግልጽ ጠቅሶ የሚከራከረው በአዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 12(1ሀ))፣ 2(6) እና 38 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ነው፡፡ ተጠቃሹ አዋጅ መስከረም 7 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 12(1(ሀ))ድንጋጌ ሲታይ የውጭ ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ስለመሆኑ የሚገለጽ ሲሆን አንቀጽ 2(6) ደግሞ የውጭ ባለሀብት ማለት የውጭ ካፒኖል ወደኢትዮጵያ በማስገባት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ሙሉ ለሙሉ በውጭ አገር ዜጋ ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ወይም ከሀገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በቅንጅት ኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ ድርጅት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት ሲሆን እንደውጭ ባለሀብት መቀፐጠር ፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊን ይጨምራል በሚል የተቀመጠ ነው፡፡እንዲሁም የአዋጁ አንቀፅ 38 ሲታይም ማንኛውም ባለሃብት የአገሪቱን ሕጎች የማክበር ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚደነግግ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ አዋጁ በአንቀፅ 6 ስር ለመንግስት የተከለሉ ወይም ከመንግስት ጋር በቅንጅት የሚሰሩ የሥራ መስኮች የሚዘርዝር ሲሆን ለአገር ባለሃብቶችና ለውጪ አገር ዜጎች የተከለሉ የስራ መስኮችን ደግሞ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ሊወሰን እንደሚችል በአንቀጽ 7 እና 8 ድንጋጌዎች ስር አስፍሮአል፡፡ በዚህ መሰረት በደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3 ስር ለሀገር ውስጥ ባለሃብቶች የተከለሉ የስራ መስኮች ተዘርዝረው የወጡ ሲሆን በእነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ አክሲዩንን በመግዛት ለንግድ ስራ ምቹ የሆነ ህንፃ በማሰራት የሥራ መስክ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ብቻ የተከለሉ ስለመሆኑ የተጠቃሹ ደንብ ዝርዝር አያሳይም፡፡ በመሆኑም የስር ከሳሽ የአክሲዩን አባል የሆኑት በሕጉ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ወይም በመንግስት በተከለሉ የስራ መስኮች ስር ባልተሸፈነው የስራ መስክ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የስር ተከሳሽ በዚህ ረገድ አጥብቆ የሚከራከረው የሥራ መስኩ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ብቻ የተከለለ ነው በሚል ሳይሆን የውጭ አገር ዜጋ በኢንቨስትመንት ላይ ለመሳተፍ በአዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 12(1(ሀ) ድንጋጌ መሰረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል በሚል ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ድንጋጌ በአዋጁ አንቀጽ 38 አግባብ ሊከበር የሚገባው መሆኑ ይታመናል፡፡ ነገር ግን የሥር ከሳሽ በስር ተከሳሽ ማህበር አባል የሆኑት በ1993 ዓ/ም ሲሆን አዋጅ ቁጥር 769/2004 ስራ ላይ የዋለው ደግሞ መስከረም 07 ቀን 2005 ዓ/ም ሁኖ የሥር ተከሳሽ በዚህ ረገድ ያቀረበውን ክርክር ያነሳው በ29/08/2005 ዓ/ም ክስ ከቀረበበት በኋላ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 769/2004 ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የሥር ከሳሽ የማህበሩ አባል ከሆኑ ሕጉ የሚፈቅደውን ቅድመ ሁኔታዎች ሕጉ ከወጣ በኋላም ቢሆን እንዲያሟሉ አዋጅ ቁጥር 769/2004 እና ይህንኑ ተከትለው የወጡትን ደንቦች እንዲያስፈጽም ስልጣን የተሰጠው አካል ተገቢውን የሚያደርግ ከመሆኑ በቀር የሥር ተከሳሽ የስር ከሳሽ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ባለመያዛቸው ብቻ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ያገኙትን መብት ቀሪ እንዲሆን ክርክር የሚያቀርብበትና ዳኝነት የሚጠይቅበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በመሆኑም በሰ/መ/ቁጥር 118246 አመልካች የሆነው የዲሞ ተራ ህንጻ ስራ አክሲዩን ማህበር የሥር ከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ አብረኸት ሀብተእዝጊ ተማኙ የውጭ አገር ዜጋ ስለሆኑና የኢንቨትመንት ፈቃድ የሌላቸው በመሆኑ በማህበሩ አባል ሁነው ሊቀጥሉ አይችሉም በማለት የሚቀርበው ክርክር ለክርክሩ መሰረት ያደረጋቸው ሕጎች የወጡበትን ጊዜ እና አከራካሪው የማህበር አባልነት የተመሰረተበትን ጊዜ መሰረት ያላደረገ ከመሆኑም በላይ ሕጉ ከመውጣቱ በፊት በሕጉ ባልተከለከሉ የሥራ መስኮች ላይ ተሰማርቶ የተገኘ የውጪ ባለሃብት ሕጎቹ ከወጡ በኋላ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያላያያዘ ከሆነ ከማህበሩ አባልነት እንዲሰረዝ ማህበሩ ወይም የማህበሩ አባላት ዳኝነት ሊጠይቁ የሚችሉበትን አግባብ በህግ አውጪው ያለመቀመጡን ሁሉ ያላገናዘበ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል በዚህ ረገድ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- የሥር ከሳሽ ለክሱ ዳኝነት የጠየቁት ተጨማሪ 14 አክሲዮኖችን እንዲገዙ እንዲወሰንላቸው ሲሆን በ1993 ዓ/ም የማህበሩ አባል ሁነው ብር 200,000.00 ከፍለው የአራት አክሲዩን ባለቤት ከመሆናቸውም በላይ ብር 100,000.00 ገቢ አድርገውም የተጨማሪ ሁለት አክሲዮኖች ባለቤት መሆናቸው በታች ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጣርቶና ማስረጃው ተመዝኖ ድምዳሜ የተያዘበት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች የማህበሩ መስራች አባላት ቁጥር በ1992 ዓ/ም ሶስት የነበረ መሆኑን፣ በ1993 ዓ/ም ደግሞ 27 ደርሶ በፍርድ ቤት ውሳኔና በአስተዳደሩ አካሉ ውሳኔ መነሻ ከሕጉ ጋር ለማጣጣም ሲባል ኃላፊነቱ ከተወሰነው የግል ማህበር ወደ አክሲዩን ማህበርነት ሲለወጥ የማህበሩ አባላት ቁጥርና የማህበሩ ካፒታል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠ መጥቶ የአባላቱ ቁጥር 81 ሲደርስ መጋቢት 2005 ዓ/ም በተያዘውና ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ/ም በጸደቀው ቃለ ጉባኤ መነሻ የአክሲዩን ድልድል መደረጉን፣ በዚህም መሰረት የሥር ተከሳሽ ማህበር የማህበሩን ዋና ገንዘብ ለመጨመር በመወሰን ይህንኑ ለማሳካት ለነባር አባላት የአክሲዩን ማሳደግ እርምጃ መውሰዱን፣ በዚህም 5 አባላት እያንዳንዳቸው ከነበራቸው አንድ አክሲዩን ወደ 8 አክሲዮኖች፣ 3 አባላት እያንዳንዳቸው ከነበራቸው ሁለት አክሲዮኖች ወደ አስር አክሲዩኖች፣ ሁለት አባላት እያንዳንዳቸው ከነበራቸው ሁለት አክሲዮኖች ወደ ስምንት አክሲዮኖች እንዲሁም አንድ አባል ከነበረው ሶስት አክሲዮኖች ወደ 20 አክሲዩን እንዲሁም አንድ አባል ከነበረው አራት አክሲዩን ወደ 20 አክሲዮኖች እንዲያድጉ የተወሰነ መሆኑን ተጠቃሹ ቃለ ጉባኤ የሚያሳይ መሆኑን በሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጡ ነጥቦች መሆናቸውን ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ የውሳኔ ግልባጭና እና ከስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ተመልክተናል፡፡ ይህ ድልድል ህንጻው በነበረው ቦታ ላይ የነበራቸውን የይዞታ መጠንና ለማህበሩ መቋቋምም የነበራቸውን አስተዋጽኦ መሰረት አድርጎ የተደረገ መሆኑንና በጠቅላላ ጉባኤውም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን የሥር ተከሳሽ ገልጾ የሚከራከር ሲሆን የሥር ከሳሽ ግን እነዚህ መስፈርቶች ሕጋዊ አይደሉም፣ በቃለ ጉባኤውም በተጽእኖ ፈርመው ቆይተው ፊርማቸውን የሰረዙ በመሆኑ ሊገደዱበት የማይገባ መሆኑን በመጥቀስ የሚከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

እንግዲህ የሥር ከሳሽ መጋቢት ወር 2005 ዓ/ም የተያዘውንና ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ/ም 94.12% የሆነ የአክሲዮን ድርሻ ባላቸው አባላት በተደረገው የጠቅላላ ጉባኤ የተሰጠው የተደለደለውን የአክሲዩን የሕግ መሰረት በሌላቸው መስፈርቶች የተደረጉ ከመሆናቸውም በላይ መብቴን የጎዳ ውሳኔ ነው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም የጠቅላላ ጉባኤው የጠራውን አካል ስልጣን፣በጠቅላላ ጉባኤ አካሄድ ማለትም በምልዓተ ጉባኤውና ውሳኔው በአብላጫ ስለመሰጠቱ ላይ፣ በጉባኤው ቃለ ጉባኤ አጻጻፍ ላይ በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አንድ የባለአክሲዮኖቹ ጉባኤ በሕጉ ጥበቃ የሚያገኘው በሕጉ የተመለከቱት ሁኔዎች ሲሟሉ ስለመሆኑ ከን/ሕ/ቁጥር 416(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ሕግን፣ መመስረቻ ፅሑፍንና መተዳደሪያ ደንብን በመከተል የተደረገ የጉባኤው ውሳኔዎች በጉባኤው ያልተገኙትን ወይም በሃሳብ ያልተሰማሙትን (ማህበርተኞች) ሁሉ ያስገድዳል በሚል በኃይለ ቃል አስቀምጧል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣም አከራካሪውን የአክሲዩን ድልድል ያደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ሕግን፣ መመስረቻ ጽሑፍንና መተዳደሪያ ደንብን ባለመከተል የተደረገ ነው ለማለት የሚያስችሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍሬ ነገሮች የሌሉ መሆኑን ከማህበሩ አመሰራረት መነሻና አብዛኞቹ አባላት ወደ ማህበሩ እንዲገቡ የተደረጉት ሕንጻው በሚሰራው ቦታ ላይ ነባር ባለይዞታዎች በመሆናቸው ምክንያት ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ የሥር ከሳሽ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የነባር ባለይዞታነትንና የልዩ አስተዋጽኦ መሰፈርቶችን መሰረት አድርጎ አክሲዩን መደልደል አይችልም በማለት ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 13.2.1 ግን የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ማናቸውንም አይነት የማህበሩን ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እንደሚወስን፣ በደንቡ አንቀጽ 13.2.4 ደግሞ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ለማህበሩ ዘላቂ የካፒታል እድገት ተጨማሪ የአክሲዩን መዋጮ መጠን እንደሚወሰን የተደነገገ ከመሆኑም በላይ ይህ የደንቡ ድንጋጌ ከን/ሕ/ቁጥር 536(2) ድንጋጌ ጋር ተዳምሮ ሲታይ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ለክሱ መነሻ የሆነውን ተጨማሪ አክሲዩን መወሰኑ ሕጋዊ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ጠቅላላ ጉባኤው በማናቸውም አይነት የማህበሩ ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እንደሚወሰን በመተዳደሪያ ድንቡ የተቀመጠው ድንጋጌ በይዘቱ ሰፊ መሆኑን ለመረዳት የማያዳግት ሲሆን አሁን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የአክሲዩን ድልድል መሰፈርቶችን መሰረት አድርጎ አክሲዩን እስከመደልደል የሚያደርስ ውሳኔ ማሳለፍን ሊያካትት የማይችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ አከራካሪ መስፈርቶች አብላጫ ድምጽ ባላቸው የማህበሩ አባላት ተቀባይነት ያገኙ ሲሆን አብዛኞቹ የማህበሩ አባላትም ከመነሻው ከነበራቸው የአክሲዩን ብዛት በተወሰነ መልኩ የተጨመረላቸው ከመሆኑ ውጪ ሁሉም እንደአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ሃያ አክሲዩን እንዲኖራቸው የተደረጉ ያለመሆኑን በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የሥር ከሳሽ የማህበሩ መስራች አባል ሳይሆኑ በ1993 ዓ/ም አባል የሆኑና ህንጻው በሚገነባባት ቦታ ላይ ይዞታ የሌላቸው፣ በማህበሩ ምስረታ ላይም የተለየ አስተዋጽኦ ያላደረጉ መሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጧቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ እነዚህ መሰፍርቶችን መሰረት አድርጎ የአክሲዩን ድልድል ማድረግ እንዲቻል አብዛኞቹ የማህበሩ አባላት ፍላጎት ስለመሆኑ በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ውሳኔ ላይ የተገኙት የአባላት ቁጥር ገላጭ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ከሳሽ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 185768 በተሰጠው ውሳኔ መሰረት መስራች ባለአክሲዮኖች ያሏቸው መብትና ጥቅም እንዲያገኙ ውሳኔ በተሰጠበት አግባብ ከሌሎች ባለአክሲዩኖች ባነሰ የአስር አክሲዩን ድርሻ ብቻ ሊኖራቸው ይገባል ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱን በዚህ ሰበር ደረጃ ማንሳታቸውና አጣሪ ችሎቱም በዚህ ረገድ ጭብጥ ለይቶ መያዙ በስር ፍርድ ቤት ያልነበረን የክርክር ነጥብ መሰረት ያደረገና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 32((1) ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ ከመሆኑም በላይ የሥር ከሳሽ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 185768 ተከራካሪ ከነበሩትና ይህ መብት ከተጠበቀላቸው ሰዎች መካከል ያልሆኑና በ1992 ዓ/ም ማህበሩ ሲመሰረት ወይም ከዚህ በኋላ ወደ አክሲዮንነት ሲለወጥም በመስራች አባልነት የሚታወቁ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ በስር ፍርድ ቤቶች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያልቀረበ፣ በመስራችነት ደግሞ የአክሲዮን ቁጥር ከፍ እንዲል ተብሎ በጠቅላላ ጉባኤም የተወሰነ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር የምንቀበልበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡

የሥር ከሳሽ በማህበሩ አባልነታቸው በእኩልነት መርህ መስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ በንግድ ሕጉ ስር ያሉትን ድንጋጌዎች በማየት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን የስር ከሳሾች በእኩልነት መርህ የመስተናገድ አግባብ ተጥሷል ለማለት የሚቻልበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ምክንያቱም በአከራካሪው ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት አክሲዩን የመግዛት የመጨመር መብት የተጠበቀላቸው የማህበሩ አባላት አብዛኞቹ አመልካች የሚጠይቁትን ያህል አክሲዩን እንዲኖራቸው ያልተደረጉ ሲሆን ሁለት አባላት በተለዩ መልኩ አክሲዮኖቹ ሃያ እንዲሆን የተደረገው በቦታው ላይ የነበራቸው የቦታ ስፋትና በማህበሩ ምስረታ ላይ የነበራቸው ተሳትፎ ታይቶ ነውና፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔም የስር ከሳሽ ሕንጻው በተገነባበት ቦታ ላይ ነባር ይዞታ ያልነበራቸው ከመሆኑም በላይ ለማህበሩ ምስረታ ያደረጉት አስተዋጽኦ ያልነበራቸው ቢሆንም ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ የማህበሩ አባላት ከተደረገላቸው የአክሲዮን ጭማሪ አንጻር በማየት የአክሲዩን ቁጥሩ ወደ አስር ከፍ እንዲል መወሰኑም የስር ከሳሽን በእኩል የመስተናገድ መብታቸውን ያስከበረ ነው ከሚባል በስተቀር የሕግ መሰረት የለውም ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር እና የማህበሩ አባላት አክሲዮናቸውን እንዲጨምሩ ከተደረገበት አግባብ አይቶ ለስር ከሳሽ ተጨማሪ አራት አክሲዮኖችን በመግዛት በማህበሩ አባላትነት እንዲቀጥሉ ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ወስናነል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሥር ተከሳሽን በተመለከተ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁጥር 140942 በ23/10/2007 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ፣ የስር ከሳሽን ደግሞ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 140942 በ23/10/2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 117601 በ30/02/2008 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 139932

ሐምሌ 20 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች ፡- አስማማው በየነ -ጠበቃ አዲሱ ወርቁ ቀረቡ

ተጠረ ፡- አሰፋ ነጋሽ -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 26 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-31103 ታህሳስ 21 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 01-00874 የካቲት 28 ቀን 2009 ዓ/ም የጸናው ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ነው፡፡

ክርክሩ ሲጀመር የአሁኑ አመልካች ከሳሽ፣የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስም ጥቅምት 04 ቀን 2009 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ቁጥሩ 5938779 የሆነና በላዩ ላይ ብር 500,000.00(አምስት መቶ ሺህ ብር) የያዘ ቼክ የሰጧቸውና ይህንን ቼክ ይዘው ገንዘቡን ወጪ ለማድረግ መስከረም27 ቀን 2009 ዓ/ም ደባርቅ ከተማ ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ሲሄዱ ባንኩ በተጠሪ ተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ ስለሌለ በቼኩ ላይ የታዘዘው ገንዘብ ሊከፍል እንደማይችል የገለፀላቸው መሆኑን ዘርዝረው ተጠሪው ገንዘቡን ከወለድ፣ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሥር ተከሣሹም መከላከያ መልስ እንዲያቀርቡ ተፈቅዶላቸው ህዳር 08 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጡት መከላከያ መልስ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አነስተዋል፡፡ በዚሁ ነጥብ ላይም ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም በይርጋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቃወሚያ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ አመልካች በንግድ ህግ ቁጥር 855 በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቼኩን ባንክ ያላቀረቡ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን በመያዝና በስድስት ወር ቼክ ለባንክ አቅርቦ ገንዘቡ ያልተከፈለው ቼክ አምጪ በን/ህ/ቁጥር 881 ስር በተመለከተው የይርጋ ጊዜ መብቱን ለማስከበር የሚችለው ከመጀመሪያውኑ በመብቱ ለመጠቀም እንዲችል ቼኩን ማቅረብ ካለበት የስድስት ወር ጊዜ ሳያበቃ ከአቀረበ ነው በሚል ምክንያት የአንድ አመት የይርጋ ጊዜ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን በመገንዘብ አመልካችን ቼኩን መሰረት በማድረግ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ አመልካች ይህንኑ ብይን በመቃወም ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ በን/ሕ/ቁጥር 881 ስር የተመለከተው የአንድ አመት ጊዜ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ቼኩ ባንክ የቀረበው ስድስት ወር ካለፈ በኋላ ነው በማለት ክሱን በይርጋ ውድቅ ማድረጋቸው የን/ሕ/ቁጥር 885 እና 881 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ አድርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ብይንና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች በተጠሪው ላይ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ በመወሰኑ የፈጸመው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ? ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የታቸለው አመልካች ለክሱ መሰረት ያደረጉት ቼክ ቁጥር 5938779 ህዳር 14 ቀን 2008 ዓ/ም የተጻፈ ሁኖ ባንክ መስከረም 27 ቀን 2009 ዓ/ም ቀርቦ ተጠሪ በቂ ስንቅ የላቸውም በሚል ምክንያት አመልካች ገንዘቡ ሳይከፈላቸው ከተመለሰ በኋላ አመልካቹ በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት ጥቅምት 04 ቀን 2009 ዓ/ም ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡ ነጥቦች መሆናቸውን ነው፡፡

በመሰረቱ ቼክ የንግድ ወረቀት ከሚባሉ አንዱ ሲሆን እንደቀረበ የሚከፈል፣በባንክ ተቀማጭ ሂሳብ ያለው ሰው ገንዘቡ ለራሱ ወይም ለሌላ ወገን እንዲከፈል ሐተታ የሌለው ትዕዛዝ የሚሠጥበት፣ገንዘብን ተክቶ ክፍያን የሚያቀላጥፍ የንግድ ወረቀት ወይም ሰነድ ስለመሆኑ ከን/ሕ/ቁጥር 732፣ 827፣828 እና 854 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል የገንዘብ ሰነድ በመሆኑ በቼክ ገንዘብ ለመክፈል አውጭው በባንክ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተቀመጠ የቼኩን ዋጋ አጣርቶ የሚከፍል፣በቂ ስንቅ (ገንዘብ) ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑም እርግጠኛ መሆን እንዳለበት የን/ሕ/ቁጥር 830 (2) ድንጋጌ ያስቀምጣል፡፡ይህንኑ በሕግ የተጣለበትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግዴታ ሳይወጣ የቀረ አውጪ በቼኩ ላይ የተፃፈውን ገንዘብ (እዳ) ለአምጪው እንዲከፍል የሚገደድ ስለመሆኑ የሕጉ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ዕዳ ከፋዩ (አውጪው) ግዴታውን እንዲወጣ የማይገደደው በሕጉ የተቀመጡትን መቃወሚያዎች (መከራከሪያ ነጥቦችን) በአግባቡ ሲያስረዳ ነው፡፡በሕጉ እዳ ከፋዩ በአምጪው ላይ ሊያቀርብ ይችላል ተብለው የተቀመጡት መቃወሚያዎች በን/ሕ/ቁጥር 717 ስር የተመለከቱት ናቸው፡፡ እነዚህም፡-በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ የተመሰረቱ፣በሰነድ አጻጻፍ ፎርምና በሠነዱ ላይ በተጻፉ ቃሎች፣እንዲሁም ፊርማን በማስመሰል የተሠራ፣ ችሎታ ወይም ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ሰልጣን ባለመኖሩ ወይም ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው የሚነሱ መቃወሚያዎችና አምጭው ይህን ሰነድ ባገኘበት ጊዜ እዳ ከፋዩን ለመጉዳት እያወቀ ያደረገው መሆን ስለመሆናቸው የሚያሳዩ እንደሆነ ሕጉ አስቀምጧል፡፡

እንግዲህ ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል እንደመሆኑ መጠን አውጪው ለቼኩ መውጣት ምክንያት የሆነውን ነገር የማስረዳት እና የማስተባበል ሸክም ያለበት ስለመሆኑ ከሕጉ ቅርፅ፣ይዘትና መንፈስ በቀላሉ የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን በቼኩ የተጻፈውን ገንዘብ ለመክፈል አልገደድም የሚለው አውጪው ከላይ በን/ሕ/ቁጥር 717 ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች በበቂ እና አሳማኝ መንገድ ማስረዳት ግዴታውን ሲወጣ ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እነዚህ በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ቼኩን በቼክነቱ መሰረታዊ የሆኑ መብቶችን ማስገኘትና ግዴታዎችን ደግሞ ለማስከተል የሚያስችሉ መሆናቸውን የሚያስገነዝቡ ነው፡፡ በመሆኑም ቼክ በቼክነቱ የሚያስገኘውን መብት ለመጠቀም በህጉ የተመለከቱ ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ ቼክ በቼክነቱ የሚያስገኛቸው መብቶች ቀሪ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንዱ የይርጋ ጉዳይ ነው፡፡

ከይርጋ አንፃር ጉዳዩ ሲታይም አንድ ቼክ ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት 6 ወራት ጊዜያት ውስጥ ወደ ባንክ ለክፍያ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የን/ሕ/ቁጥር 855 አስገዳጅነት ባለው መልኩ የሚደነገግግ ሲሆን በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለባንክ ቀርቦ ክፍያው ካልተፈፀመም ቼክ አምጪው ቼኩ ለባንክ የቀረበበት ጊዜ ካለፈ ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚችል መሆኑን በን/ሕ/ቁጥር 881(1) ስር በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ የን/ሕ/ቁጥር 855 እና 881(1) አንድ ላይ ሲነበቡ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ በቼኩ ላይ ከተፃፈበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር አንድ አመት ጊዜ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጊዜ መያዝ ያለበት ቼኩ በን/ሕ/ቁጥር 855 ስር ሕግ አውጪው በአስገዳጅነት በደነገገው አግባብ ቼኩ ከተፃፈበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ባንክ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም በን/ሕ/ቁጥር 855 ስር በተመለከተው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ባንክ ሳያቀርብ ይህንኑ ጊዜ አሳልፎ አንድ አመት ሳያልፍ ባንክ አቅርቦ በቼክ አውጪው ስም በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን ያረጋገጠ ቼክ አምጪ ቼኩን መሰረት አድርጎ የሚያቀርበው ክስ አንድ አመት አላለፈበትም በሚል ክሱ ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡ አመልካች በን/ሕ/ቁጥር 881(1) ስር በተመለከተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአንድ አመት የጊዜ ገደብ ክስ የማቅረብ መብታቸው በሕግ ፊት ተቀባይነት ሊኖር የሚችለው በን/ሕ/ቁጥር 855 ስር ቼኩን በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለባንክ የማቅረብ ቅድመ ሁኔታ ሲያሟሉ ነው፡፡ ይህ ቅድመ ሁኔታ ሳይሟላ ቼኩን መሰረት አድርገው የሚያቀርቡት ክስ በን/ሕ/ቁጥር 855 እና 881(1) ድንጋጌ አግባብ ይርጋው የሚቆጠርበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በእነዚ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-31103 ታህሳስ 21 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 01-00874 የካቲት 28 ቀን 2009 ዓ/ም የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የቼክ ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ክሱ ውድቅ በመደረጉ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣ ወጪና ኪሳራ ግራ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ዘግቷል፤ ወደ መዝገብ በት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 104637

ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተክሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ራቢያ በድሩ ቀርባለች

ተጠሪ፡- ሙዑዝ ደስታ ገ/እግዚአበሔር ከጠበቃቸዉ አቶ መኮንን በዛብህ ጋር ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 12/12/2006 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/ይ/መ/ ቁጥር 96602 በቀን 29/09/2006 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪን በነፃ መልቀቁን በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ መሠረታዊ ይዘቱ ሲታይ ተጠሪን ሁለት የወንጀል ህግ ድንጋጌዎችን በመጣስ ወንጀል የከሰሰው ሲሆን የመጀመሪያው ክስ ወላጅ እናቱ ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ ሆና እያለ የማይመለከተውንና በሥጋ ዝምድና ግንኙነት የሌላቸውን የአቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ 1,7000.00 (አንድ ሚሊየን ሰባት መቶ ሺህ ብር) የሚገመት ንብረት ያለአግባብ ለመውረስ ሲል ከላይ የተመለከተውን የወላጅ እናቱን ስም በመለወጥ የእናቱ ስም ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ እንደሚባሉና የሟች ግርማ ወ/ጊዮርጊስ እህት እንደሆኑ በማስመሰል የወራሽነት ማስረጃ ከፍርድ ቤት ያወጣ በመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 696 (ሐ) መሠረት በከባድ የማታለል ወንጀል እንደተከሰሰ የሚገልጽ ሲሆን ሁለተኛው ክስ ተጠሪ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ ቁጥር 378 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ላይ እንደተገለጸው ምንም ዓይነት የሥጋ ዝምድና የሌላቸውንና አጎቱ ያልሆኑትን ሟች አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስን የእናቱን ወንድም እና አጎቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሆኑ እና አጎቱ ለማስመሰል ሀሰተኛ የሆነ የአቤቱታና የቃለ መሃላ ሰነድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ችሎት በማቅረቡና እንደዚሁም በድሬዳዋ ማዘጋጃ ቤት በ20/02/2002 ዓ/ም የተሰጠው የጋብቻ ምስክር ወረቀት ላይ የእናቱ ስም የሚለው ቦታ ላይ አወጣሽ አብርሃ ተብሎ የተሰጠውን በተመሳሳይ ማስረጃ ለመውረስ እንዲያመቸው አስቦ ለድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ፅፎ በማቅረብ የጋብቻ ሰርቲፊኬት ላይ የእናቱ አባት ስም ወ/ጊዮርጊስ ሆኖ እያለ በስህተት አብርሃ ተብሏልና ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ መባሉ ቀርቶ ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ ተብሎ ተስተካክሎ ይሰጠኝ ብሎ ለፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም የቀረበውን አቤቱታ እውነተኛ እንደሆነ አድርጎ ቀይሮ የእናቱን አባት ስም አብርሃ መባሉ ቀርቶ ወ/ጊዮርጊስ ይባል ብሎ ውሳኔ በመስጠቱና ፍርድ ቤቱን አታሎ ማስረጃውን ከወሰደ በኃላ ድሬዳዋ ማዘጋጃ ቤት አቅርቦ የጋብቻው ሰርቲፊኬት ላይ ቀደም ሲል የእናቱ ስም ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ ይባል የነበረው ተቀይሮ ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ ተብሎ ሌላ ሀሰተኛ የሆነ የጋብቻ ሰርቲፊኬት አውጥቶ ይህንኑ ሰርቲፊኬት የሚች ንብረትን ለመውረስ በሚደርግ የፍትሐብሔር ክርክር ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ የተጠቀመበት በመሆኑ ተጠሪ በፈጸመው በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ወንጀል ያለመፈጸሙን ክዶ የተከራከረ ሲሆን ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ችሎት የግራ ቀኝ ማስረጃዎችን ተመልክቶ ተጠሪን በተከሰሰባቸው ሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ በ3 ዓመት ከ7 ወር ጽኑ እስራትና በ 1000.00 ብር (አንድ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ተቀብሎ የግራ ቀኙን አከራክሮና ተጨማሪ ማስረጃዎችን ሰምቶ ተጠሪ ወንጀሎቹን ስለመፈጸሙ ስላልተረጋገጠበት በነፃ ሊሰናበት ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪን በነፃ በመልቀቅ የወሰነውን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ፡- ተጠሪ ለፈጸመባቸው ወንጀሎች ከመንግሥታዊ አካል የተሰጡ ሰነዶች እያሉ ይህንን ሳይመለከት ተጠሪ ብቻ ያለውን ሰምቶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መስጠቱ ከማስረጃ አመዛዘንና አቀራረብ አንጻር በአንድ ወገን ያለውን ብቻ በመስማት የተሰጠ ውሳኔ አግባብ አይደለም፣ በተጨማሪ ማስረጃነት የሰማውን የተጠሪን አባት ምስክርነት በተመለከተ በሃሰት መስክረው ከሆነ ክስ የሚመሰረት ሆኖ በማለት የሥር ፍርድ ቤት ጠቅሶ ነገር ግን ለአሁን ጉዳይ የሰጡት ቃል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመኔታ የሚጣልበት ነው ማለቱ አግባብነት የሌለውና እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፣ የተጠሪ እናት ነኝ ብለው የቀረቡት ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ የዲኤንኤ (DNA) ምርመራ እንዲያደርጉ በሥር ፍርድ ቤት ቢጠየቁም ቆራቢ በመሆናቸው በሚል ምርመራውን ለማድረግ አለመፈለጋቸው በተቃራኒው ሊተረጎም ሲገባው ተጠሪን በሚደግፍ ሁኔታ አለመመርመራቸው ጥያቄ ውስጥ ሳይገባና ቆራቢ ናቸው ተብሎ መታለፍ ያለአግባብ ነው፣ በሥር ፍርድ ቤት እንዲመጣ ያልታዘዘ ሰነድ ተጠሪ በራሱ መነሻነት ያቀረበውን በአንድ የፖሊስ አባል የተጻፈን ሰነድ ብቻ ተቀብሎ ታማኝነት ያለው ሰነድ ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለው ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል የቀረበው ማስረጃ በፖሊስ ኮሚሽኑ በምን መነሻነት ሰነዱን ሊሰጥ እንደቻለ ማጣራት ሳያደርግ ተጠሪን በነፃ ማሰናበቱ አግባብነት የሌለውና ምክንያታዊ ያልሆነ በመሆኑ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸናልን የሚል ነው፡፡

አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው ፍርድ ቤት ተጠሪ ያለአግባብ ለመውረስ አስቦ ከዘጠኝ ዓመት በፊት ባስመዘገበው የጋብቻ ሰርቲፊኬት ላይ የትክክለኛ የወላጅ እናቱ ስም ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ ሆኖ እያለ በ2002 ዓ/ም ያረፉት የወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ እናቱ እንደሆኑ አሳስቶ ባገኘው ማስረጃ ስለመገልገሉ በዐቃቤ ህግ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል በማለት የወሰነውን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከፖሊስ ቀደም ብሎ የተጻፈው ዳብዳቤ በኃላ በተጻፈው ተሽሯል በማለት በተለይ የሥር ፍርድ ቤት የቀበሌ ማኅደር ጭምር አስቀርቤያለሁ በማለት በወሰነው ላይ ምንም ሳይል ማለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ተብሎ ታዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለተጠሪ ደርሶት ሚች ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ የተጠሪ እናት ስለመሆናቸው በማያመነታ መንገድ በሰውም ሆነ በጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ የተጠሪ እንጀራ እናት እንጂ ወላጅ እናቱ ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ መሆናቸውን ወላጅ አባቱ ጭምር በምስክርነት ያረጋገጡት ጉዳይ ከመሆኑ በተጨማሪ የአዕቢ ወንበርታ ፖሊስ ጽ/ቤት ሚያዝያ 29 ቀን 2006 ዓ/ም በጻፈው ዳብዳቤ ቀደም ሲል ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ የተጠሪ እናት እንደሆኑ አድርጎ የጻፈው በተጠናከረ ማስረጃ ተመስርቶ አለመሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማረጋገጡ እውነታውን ይበልጥ የሚያሳይ ስለሆነ ተጠሪ ከወንጀል ህግ ቁጥር 23 አኳያ ጥፋተኛ ልባል የሚቻልበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ግንቦት 24 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ቅሬታውን በማጠናከር በቀን 10/10/2007 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክርክሩ ሂደት አጠር ባለ መልኩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ጉዳዩን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፣የግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ካደረጉት ክርክር እንዲሁም ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪን በነፃ መልቀቁ በአግባቡ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራቀኝ ወገኖች ይህን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት አልፈጸምኩም በማለት ተጠሪ ቢከራከርም፤ ክሱን የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በማስረጃ አረጋግጦአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው ፍ/ቤት ግን የራሱን ተጨማሪ ማስረጃ በመስማት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ እንደሚታየው ድርጊቱ ተፈጽሞአል ወይስ አልተፈጸመም የሚለው የፍሬ ነገር ጭበጥ በመሆኑ የሚነጥረው (የሚጣራው) በማስረጃ ነው፡፡ የፍሬ ነገር ጭብጥን በማስረጃ የማጣራት እና የተሰማውን ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክሩን ተመልክተው የተለያየ መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡ በዐቃቤ ህግ ክስ የተመለከተው ድርጊት በተጠሪ መፈጸሙን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በማረጋገጡም ድርጊቱን ከተጠቀሰው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ጋር አገናዝቦ የጥፊተኛነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደግሞ በሰማው ተጨማሪ ማስረጃ ተጠሪ ወንጀል ስላለመፈጸሙ ተረጋግጧል በማለት ተጠሪን በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

በበኩላችንም እንደምናየው ተጠሪ በዐቃቤ ህግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት ፈጽሞአል ወይስ አልፈጸመም የሚለውን የፍሬ ነገር ጭብጥ የማጣራት ሥልጣን ለሰበር ችሎቱ የተሰጠ ባለመሆኑ በዚህ ደረጃ የምንመረምረው አይደለም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ በክሱ በተጠቀሰው ድንጋጌ የተመለከተውን ወንጀል ያቋቁማል ወይ? የሚለው ነጥብ ግን የህግ ጭብጥ በመሆኑ ተመልክተነዋል፡፡

ተጠሪ የተከሰሰው የመጀመሪያው ክስ በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 696 (ሐ) የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፎ ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ድንጋጌው የሚለው "ወንጀሉ የተፈጸመው በህዝብ አስተዳደር ወይም በህዝብ አገልግሎት ላይ እንደሆነ ነው፡፡" በዚህ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ሲባል ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና እስከ ብር ሃምሳ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል፡፡

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የተጠሪ ወላጅ እናቱ ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ ሆና እያለ የማይመለከተውንና በሥጋ ዝምድና ግንኙነት የሌላቸውን የአቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ 1,7000.00 (አንድ ሚሊየን ሰባት መቶ ሺህ ብር) የሚገመት ንብረት ያለአግባብ ለመውረስ ሲል ከላይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተመለከተውን የወላጅ እናቱን ስም በመለወጥ የእናቱ ስም ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ እንደሚባሉና የሚች ግርማ ወ/ጊዮርጊስ እህት እንደሆኑ በማስመሰል የወራሽነት ማስረጃ ከፍርድ ቤት አውጥቷል፡፡ለፍርድ ቤቱ ወራሽ መሆኑ እንዲረጋገጥለት አቤቱታውን በቃለ መኃላ አረጋግጦ አቀርቧል፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 92 እንዲሁም ቁጥር 205 መሠረት አንድን አቤቱታ በቃለ መሃላ እንዲቀርብ ህግ አውጪው የፈለገበት በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያው ሀሰተኛ አቤቱታዎች በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ የሚያስከትሉትን የፍትህን መጓደል ለመከላከል ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ሀሰተኛ አቤቱታ የሚያቀርቡ ተከራካሪዎች በህግ እንዲጠየቁ ለማድረግ ነው፡፡ ተጠሪ ሀሰተኛ አቤቱታ በማቅረብ ፍትህ እንዲዛባ ከማድረጉም ባሻገር በህግ በተቋቋመ የተከራካሪዎችን መብትና ጥቅም በሚያስከበር አካል ፊት እንደዚህ ያለውን ሀሰተኛ የሆነ አቤቱታ አቅርቦ ማስወሰኑ በወንጀል ህግ ቁጥር 696 (ሐ) የተደነገገውን ድንጋጌ የጣሰ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በመሆኑም በተያዘው ጉዳይ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ በክሱ በተጠቀሰው ድንጋጌ የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁም ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንን እውነታ በአግባቡ ሳያጤን አልፎ ተጠሪን በነፃ እንዲሰናበት በማለት መወሰኑ የማስረጃ ህግ መርህን ጭምር የሚጥስ ውሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሁለተኛውን ክስ በተመለከተ በ1ኛው ክስ ሥር ሊጠቃለል የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ከተጠሪ ድርጊት አንጻር መርምረናል፡፡ የተጠሪ ሀሳብና ፍላጎት የሚች ግርማ ወ/ጊዮርጊስን ንብረት ለማግኘት ነው፡፡ ለዚህ ግብ ያስችለው ዘንድ እናቱን የሚች እህት አድረጎ ማስወሰን ስላለበት በ1989 ዓ/ም ጋብቻ ሲመሰርት የእናቱን ስም አወጣሽ አብርሃ በማለት በጋብቻ ሰርቲፊኬት የመዘገበውን ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ ተብሎ እንዲቀየር በድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርቦ ካስወሰነ በኃላ ለማዘጋጃ ቤት በማቅረብ የጋብቻ ሰርቲፊኬቱ እንዲቀየር አድርጓል፡፡ይህንን ማስረጃ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማቅረብ የሚች ወራሽ መሆኑን አስወስኗል፡፡ይህን ሰነድ የተጠቀመውም ዋናው ግብ የሆነውን የሚች ንብረት የማግኘት ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ስለሆነ ሊታይ የሚገባው ከወንጀል ህግ አንቀጽ 61 (3) አንጻር ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 378 ድንጋጌን በመተላለፍ የተከሰሰበት ወንጀል በወንጀል ህግ ቁጥር 61 (3) መሰረት በወንጀል ህግ ቁጥር 696 (ሐ) የሚጠቃለል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በወንጀል ህግ ቁጥር 378 መሠረት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ሊወሰንበት አይገባም ብለናል፡፡

በመጨረሻም ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው ተጠሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 696 (ሐ) በመተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ ስለተገኘ ሊወሰን የሚገባውን ቅጣት ከወንጀል ህግ እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ በሥራ ላይ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንጻር ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪን በወንጀል ህግ ቁጥር 696 (ሐ) መሠረት ጥፋተኛ ነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካለ በኃላ የወንጀል ደረጃውን መካከለኛ ሲል ይሟል፡፡ በእኛም በኩል ይህ ተገቢ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ይህም እርከን 19 ሥር የሚያርፍ በመሆኑ በዚህ እርከን ያለው ፍቅደ ሥልጣን ከ4 ዓመት እስከ 4 ዓመት ከ10 ወር በመሆኑ መነሻ ቅጣት 4 (አራት) ዓመት ተይሟል፡፡ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ለተጠሪ የተያዙለት ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች እያንዳንዳቸው ሁለት እርከን የሚያስቀንሱ በመሆናቸው 4 (አራት) እርከን ተቀንሶ መጨረሻ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው እርከን 15 ሥር በመሆኑ ተጠሪ በ2 ዓመት ከ9 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ብለናል፡፡ ሲጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 96602 በቀን 29/09/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኮ/መ/ቁ 109227 ህዳር 3 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ተሸሽሏል፡፤
3. ተጠሪ ጥፋተኛ በተደረገበት የወንጀል ህግ ቁጥር 696 (ሐ) መሰረት ቀደም ሲል የታሰረው ካለ ታሳቢ ተደርጎ በሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራትና በብር 1000.00 (አንድ ሺህ ብር) መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡
4. በተጠሪ ላይ የተወሰነውን የ2 ዓመት ከ9 ወር ጽኑ እስራትን ቀደም ሲል የታሰረ ካለ ታሳቢ ተደርጎ የተወሰነበትን ቅጣት ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት የመሰሪያ ወራንት ይጻፍ፡፤የብር 1000.00 (አንድ ሺህ) መቀጮ ለመንግሥት ገቢ ይደረግ፤የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር ያስፈጽም፤ይጻፍ፡፡
5. የውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ 132266

ታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ዓሊ መሀመድ

ተሻሊት ይመሰል

ቀነአ ቂጣታ

ሰናይት አድነዉ

ጳዉሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ አሰፋዉ ልጅ መስፍን አስፋዉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጲያ ሱማሌ ክልል የዐቃቤ ህግ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለዉን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበዉ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 574(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽማለች በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ህጋዊ መሰረት ያለዉ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ምላሽ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነዉ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየዉ በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረበዉ የወንጀል ክስ አንደኛ ተከሳሽ የሆነችዉ የአሁን አመልካች የአስራ ሁለት ዓመት ህጻን የሆነችዉ ሟች ኤደን ሃጂ ሸርቅያ ሚያዝያ 3 ቀን 2006 ዓ.ም ከቀኑ አስራ አንድ ሰአት ተኩል ከተከሳሽዋ ሻወር ቤት ዉስጥ በአሰቃቂ ሁኔታ ስትገደል ተከሳሻዋ ግቢ ዉስጥ እያለች ምንም እርዳታ ያላደረገች በመሆኑ ወንጀል ፈጽማለች በማለት ተከሳሽ የወንጀል ህግ ቁጥር 448 በመተላለፍ ለፍትህ እገዛ በማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆን ወንጀል ፈጽማለች በማለት ሁለት የወንጀል ክሶችን አቅርቦባታል፡፡

2.አመልካች በተከሳሽነት ቀርባ የወንጀሉን ድርጊት አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዳ ተከራክራለች ፡፡ ተጠሪ ክሱን ያስረዱልኛል በማለት አምስት ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ አመልካች መከላከያ ማስረጃ እንድታቀርብ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች የሰዉና የሰነድ ማስረጃ በመከላከያ ማስረጃነት አቅርባለች፡፤ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በወንጅል ሕግ አንቀጽ 574(2) እና አንቀጽ 448 የተመለከተዉን በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት የፈጸመች ናት በማለት ወንጀሉ አንደኛ ደረጃ ላይ የሚወድቅ መሆኑን ገልጾ አመልካች በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንድትቀጣ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርባለች፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርባ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የባታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

3. አመልካች ነሐሴ 19 ቀን 2008 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ከሚች ህፃን ኤደን ወላጆች ጋር በአበልጅነት ተሳስረው የቀረበ ወዳጅነት የነበራቸው በመሆኑ ሚችና የእሷ ወንድም በትምህርት ቤታቸው ቅርብ ከሆነው በአመልካች ቤት የምሳ እቃቸውን በማስቀመጥ በምሳ ሰዓት እየመጡ ምሳቸውን ይበሉ ነበር፡፡ ሚያዚያ 1 ቀን 2006 ዓ/ም ሚችና ወንድሟ በተለመደው ሁኔታ ምሳ አስቀምጠው በምሳ ሠዓት በተለመደው ሁኔታ ከአመልካች ቤት መጥተው ምሳቸውን ከበሉ በኃላ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሰው ሄደዋል፡፡ ነገ ግን ህጻን ኤደን የትምህርት ቤት ደንብ ስለጣሰሽ ወላጅ ይዘሽ እንዲትቀርቢ በማለት ትምህርት ቤቱ ይህንን ለወለጆቿ ደውሎ በመናገሩ በዚህ ተደናግጣ፣ ከአመልካች ቤት ውስጥ ተደብቃ በመግባት ከአመልካች ንግድ ቤት ራቅ ብሎ የተሰራው ሻወር ቤት ውስጥ ገብታ ከውስጥ በሩን ቆልፋ ራሷን በጨርቅ አንቀ በጓሮ በኩል ያለው ጎረቤት የጣር ጽምፅ በመስማቱ በሩን ሰብሮ ጨርቁን በመበጠስ ሕይወቷን ለመታደግ ሞክሯል፡፡ ከዚህ በኋላ እኔም ሚችን በባጃጅ ወደ ሀኪም ቤት ስወሰድ ህይወቷ አልፏል፡፡ እውነታው ይህ ሆኖ እያለ ተጠሪ አንድ ጊዜ ሚችን ከሞት ለመታደግ የሞከሩትን ሰዎች በግፍ ገድላችኋታል በማለት ክስ አቅርቦ ሰዎቹን በይግባኝ በነፃ ተሰናብተዋል፡፡ እኔን ደግሞ ከህግ አግባብ ውጭ አግባብነት የሌለው የህግ ድንጋጌ ጠቅሶ ያቀረበውንና ተጠሪ በማስረጃ ያላረጋገጠውን ክስ በመቀበል የበታች ፍረድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በስበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

4. ተጠሪ ጥቅምት 16 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ባቀረበው መልስ እድሜዋ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች በአመልካች ቤት ስታድግና ጤናማ አዕምሮ ያልነበራት ልጅ ለአደጋ ስትጋለጥ ማዳን እያቻለች ለማዳን ያልሞከረች መሆኑ ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ ተረጋግጦ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ጥቅምት 23 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተገቢነት መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ጥፋተኛ የተባለችው የወንጀል ህግ አንቀጽ 574(2) ተላልፋለች ተብሎ ነው፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 574 የወንጀል ህጉ የሰውን ህይወት አካል ወይም ጤንነት ለአደጋ በማጋለጥ የሚፈጸመው ወንጀሎች በማለት በምእራፍ አራት ስር ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 571 እስከ አንቀጽ 579 በዘረዘረቸው ወንጀሎች ውስጥ ተካትቶ የሚገኝ ድንጋጌ ነው፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 57/2/ የተደነጋገውን ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ አንድ ሰው በኃላፊነትን የሚጠየቀው በወንጀል ህግ አንቀጽ 574 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን ወንጀሉን የሚያቋቋሙ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች በአንቀጽ 574 ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱት የማክበጃ ምክንያት መኖራቸው በማስረጃ ሲረጋገጥ ነው፡፡

6. የወንጀል ህግ አንቀጽ 574 "ሰውን ለአደጋ ማጋለጥ ወይም መተው" በእንግሊዘኛው ቅጅ Exposure or Abandonment of Another የሚል ርእስ ያለው ሲሆን የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 1 ቃል በቃል ሲነበብ" በጤናው በእድሜው በሁኔታው ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ራሱን ለመጠበቅ የማይችለውን ሌላ ሰው የማናቸውም ምክንያት ይሁን በጠባቂነት ወይም በኃላፊነት ለማኖር የተቀበለ ማንም ሰው የተባለውን ሰው አስቦ (ሀ) በሕይወቱ ወይም በጤናው ላይ በቅርብ መድረሱ ለማይቀር አደጋ ያገለጠው እንደሆነ ወይም (ለ) ይህን በመሰለ ሁኔታ ላይ በሚገኝበት ጊዜ ጥሎት የሄደ እንደሆነ ወንጀሉን እንደፈጸመ ተቆጥሮ ቅጣት የሚጣልበት መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን የአንቀጽ 574 ንዑስ አንቀጽ 2 ወንጀሉ የተፈጸመው በህጻን ልጅ ላይ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡ በማለት ይደነግጋል፡፡

7. የአንቀጽ 574 የእንግሊዘኛው ቅጅ ይዘት ሲታይም "የአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1" who ever Having the custody or charge, on no matter what grounds of a person in capable of protecting

Himself= whether on account of his health, his age, his situtation any other circumstances intentionally

(a) Exposes him there by putting him imminent danger of life or heath or
(b) Abandons him when in like situation የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ንዑስ አንቀጽ 2 ‹‹where the crime is committed against infant, the punishment shall be rigorous imprisonment not exceeding seven years›› የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

8. ከላይ ከጠቀስነው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 574 ድንጋጌ የምንረዳው፣ በመጀመሪያ ደረጃ ሰውን ለአደጋ የማጋለጥ ወይም የመተው ወንጀል ሆነ ተብሎ የሚፈጸም ወንጀል መሆኑን ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ተጠያቂ የሚሆን ሰው፣ ሰውየውን ለአደጋ ያጋለጠው ወይም ህይወቱ በአደጋ ላይ እንደሚወድቅ እያወቀ የተወው፣ ተጎጅው በአደጋው ህይወቱን እንዲያዳጣ ሆነ ብሎ አስቦበት የፈጸመው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ወንጀሉን የፈጸመው ሰው ከአደጋ ካልጠበቀው በስተቀር የተጎጅውን ህይወት ከአደጋ ውስጥ የሚጥል እርግጠኛና በፍጥነት ሊደርስ የሚችል አደጋ መኖሩን እያወቀ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የሌላውን ህይወት ከአደጋ የመጠበቅ ሃላፊነት ያለበት ሰው፣ ህይወቱ ለአደጋ የተጋለጠውን ሰው በማናቸውም ምክንያት ለመጠበቅና በእሱ ቁጥጥርና ክትትል ስር ለማኖር ሃላፊነቱን የተቀበለ ሰው መሆን ያለበት መሆኑ ሲሆን፣ በአራተኛ ደረጃ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 574 ንዑስ አንቀጽ 2 የአማረኛው ቅጅ “ህጻን” የሚለውን አነጋገር፣ ማናቸውም አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ሰው ማለት እንዳልሆነ ከእንግሊዘኛው ቅጅ “where the crime is committed against infant” በማለት በደነገገው አገላለጽ ግልጽ ያደረገው መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

9. ከላይ የተደነገገውን የሕጉን ይዘት ተጠሪ በአመልካች ላይ ካቀረበው ክስና ማስረጃ ጋር ስናገናዝበው በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪ አመልካች የአስራ ሁለት አመት ህጻን የሆነችው ኤደን፣ በሌሎች ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ስትገደል አመልካች ምንም እርዳታ አላደረገችም በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ የገለጸ ሲሆን፣ ሟች ህጻን ኤደን በሰዎች ያልተገደለች መሆኑና አመልካች መታጠቢያ ክፍል ውስጥ ገብታ ራሷን በጨርቅ በመስቀሏ ምክንያት የሞት አደጋ የደረሰባት መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ሁለተኛው ፓራግራፍ እና በበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይህ የሚያሳየው ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 574 ይዘት በአግባቡ ሳይረዳና የወንጀል ክሱን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 111 እና የወንጀል ሕግ ቁጥር 112 በሚደነግገው መሰረት አዘጋጅቶ ያላቀረበ ፣ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ይዘት ተቃራኒ ይዘት ያለው መሆኑን ነው፡፡

10. ተጠሪ አመልካች የወንጀል ሕግ ቁጥር 574 ንዑስ አንቀጽ 2 በመጣስ ሟች ኤደንን ለአደጋ አጋልጣለች ወይም ትታለች በማለት ባቀረበው የወንጀል ክስ ውስጥ ሟች የሞተችው በአመልካች የገላ መታጠቢያ ክፍል ውስጥ ራሷን በጨርቅ በመስቀል መሆኑን፣ አመልካች በወቅቱ ከዚያው ግቢ ውስጥ ስለነበረች ሟች የታነቀችበትን ጨርቅ በጥሳ ከሞት ልታድናት እየቻለች ይህን ያላደረገች መሆኑን ገልጿል፡፡ ተጠሪ ይህንን ክስ ለማስረዳት ያቀረባቸው ምስክሮች ሚያዚያ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ኤደን የተባለች ልጅ ታንቃ፣ ሰዎች የታነቀችበትን ጨርቅ በጥሰው አመልካችና ሌሎች ሰዎች ወተት ለማጠጣት ሲሞክሩና በኋላም በባጃጅ ሟችን ይዘው ወደ ሃኪም ቤት ሲወስዱ ያዩ መሆናቸውን እንደመሰከሩ ከበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

11. ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ፣ ሟች ህጻን ኤደን ራሷን በራሷ ለማጥፋት እንደምትሞክርና በዚህም ምክንያት የሟች ኤደን ህይወት አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል አመልካች እያወቀች፣ አመልካች ሆንብላና ህጻን ኤደን ራሷን በማነቅ እንድታጠፋ በማሰብ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳታደርግ የተወቻት መሆኑን የሚገልጽ አይደለም፡፡ አመልካች ህጻን ኤደን ህይወቷን በገዛ እጇ ለማጥፋት በሚያስችላት በእርግጠኝነት ሊደርስ በሚችል አደጋ ውስጥ የነበረች መሆኑን እንደምታውቅ የተጠሪ ምስክሮች አላስረዱም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ህጻን ኤደን ትምህርቷን አቋርጣ ወደ እሷ ቤት የመጣች መሆኑን ያየችና የምታውቅ መሆኑን ተጠሪ ያቀረባቸው ማስረጃዎች የሚገልጹ እንዳልሆኑ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ ህጻኗ ከንግድ ቤቱ ራቅ ብሎ ከተሰራው መጸዳጃ ቤት ውስጥ ገብታ በጨርቅ ራሷን ስታንቅ፣ አመልካች በዚያው ግቢ ውስጥ ሆና ሳለ ቀድማ አልደረሰችም በማለት የሚያቀርበው ክርክር በወንጀል ህግ አንቀፅ 574 የተደነገገው ወንጀል የሚፈፀመው ሆን ተብሎ እንደሆነ ከሚገልፀው ጋር አብሮ የሚሄድ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ተጠሪ አመልካች ሆነብላ እና አስባ ህፃን ኤደን ራስዋን በራስዋ እንድታጠፋ ለአደጋ ያጋለጠቻት ወይም ትታት የሄደች መሆኑን የማስረዳት ግዴታውን የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 20 ንኡስ አንቀፅ 3 በሚደነግገው መሰረት አልተወጣም፡፡በሌላ በኩል አንድ ወንጀል ወንጀሉን በቸልተኝነት የሚያስጠይቀው በህጉ በተለየ ክፍል ያስቀጣል ተብሎ በግልፅ በተደነገገ ግዜ እንደሆነ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 59 ንኡስ አንቀፅ 2 የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ሟች ራሷን ባነቀችበት ቤት ግቢ ውስጥ እያለች የሟችን የሲቅና የጣር ድምፅ ባለመስማቷ ምክንያት በወንጀል ህግ ቁጥር 574 ንኡስ አንቀፅ 2 ተጠያቂ የምትሆንበትን የህግ ምክንያት አላገኘንም፡፡

12. ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች ተጠሪ አመልካች የወንጀል ህግ 574 የተዘረዘረውን ወንጀል የፈፀመች ስለመሆኑ በህጉ አነጋገር እና የድርጊቱን አፈጻፀም የሚገልፅ ፡የወንጀል ክስ በወ/መ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 111 እና በወንጀል ህግ ቁጥር 112 መሰረት አላቀረበም፡፡የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ የወንጀል ክሱን በማሻሻል አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 574 (2) የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት የፈጸመች መሆኑን የሚያሳይ የአመልካችን የሀሳብ ክፍል ሆን ብላ ወንጀሉን የፈፀመች በመሆኗ የአመልካችን ግዙፍ ድርጊትና ተሳትፎ ግልፅ አድረጎና ዘርዝሮ እንዲያቀርብ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 119(1) መሰረት ትእዛዝ ሳይሰጡ የወንጀል ክሱን ማየታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ሟች ህፃን ኤደን ከመፃዳጃ ቤት ታንቃ ሌሎች ሰዎች የታነቀችበትን ጨርቅ በጥሳው ከወጣች በኃላ ፈፅማዋለች በማለት በተጣራ ምስክሮች የተዘረዘረው ግዙፍ ተግባር አመልካች የሟችን ሂወት ለመታደግ የቻለችውን ጥረት ማድረጓንና በወንጀል የሚያስጠይቅ የወንጀል ተግባር ያልፈፀመች መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ የበታች ፍ/ቤት አመልካች የወንጀል ሕግ ቁጥር 574(2) በመተላለፍ ወንጀል ፈፅማለች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

13. የስር ፍርድ ቤት አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 448 በመተላለፍ ጥፋት፣ፈጽማለች በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ተጠሪ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 448 የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ስለመፈጸሙ በግልጽና የወ/መ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/111/ እና የወ/መ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 112 በሚደነግግበት መሰረት አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ ያቀረበችው ምስክሮቹም አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 448 የተመለከተውን ወንጀል ስለመፈጸሟ የሰጡት የምስክርነት ቃል የሌለ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ በአግባቡ የወንጀል ክሱን ባላቀረበበትና ክሱን የሚያስረዳ ማስረጃ ባላቀረበበት ሁኔታ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 448 በመተላለፍ ወንጀል ፈጽማለች በማለት የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ማፅናታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

14. በአጠቃላይ ሲታይ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 574/2/ እና አንቀጽ 448 የተደነገጉትን በመተላለፍ የወንጀል ተግባር የፈጸመች መሆኑን በተሟላ ሁኔታ የሚያሳይ የወንጀል ክስ ተጠሪ ያላቀረበበት ሆኖ እያለና ተጠሪ ያቀረበውን የወንጀል ክስ የማስረዳት ግዴታውን በአግባቡ ባልተወጣበት ሁኔታ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 574/2/ እና አንቀጽ 448 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽማለች በማለት በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንድትቀጣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/1 መሰረት በመሻር አመልካች በነፃ ልትሰናበት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኢትዮጲያ ሱማሌ ክልል የፋፋን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 711/06 ሰኔ 10 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና ፍርድ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 05/1/201/06 መጋቢት 1 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 05/01/125/07 ሰኔ 15 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/1/ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 574/2/ እና የወንጀል ህግ 448 በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመች ስለመሆኑ ተጠሪ የማስረዳት ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ አመልካችዋ ከቀረቡቢት ሁለት የወንጀል ክሶች በነፃ እንድትሰናበት በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. በአመልካች ላይ ተወስኖ የነበረው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ አመልካች በነፃ እንድትሰናበት ከዚህ ሰበር ችሎት የተወሰነ መሆኑን አውቆ አመልካችን በዛሬው ዕለት ከእስር እንዲለቃት ለክፍሉ ማ/ቤት የመፍቻ ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.123046

የካቲት 29 ቀን 2009ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

አይሸሽም መለሰ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ አዲሱ ገመቹ ተከታታይ ዘመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዐ/ሕግ ሞገስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

1. ጉዳዩ የቀረበዉ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በቸልተኝነት ሲያሽከረክር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559 ንኡስ አንቀጽ 2 በመተላለፍ ገንዘብ አስከፍሎ አሳፍሯቸዉ በነበሩት በሰባት ሰዎች ላይ ሰባት በቸልተኝነት በሰዉ አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀሎችን የፈጸመ ጥፋተኛ ነዉ በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉም የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ጭብጥ በሰበር አይቶ ለመወሰን ነዉ፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየዉ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ መስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ ሆነዉ ተከራክረዋል፡፡
2. ክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ ነዉ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ሥምንት የወንጀል ክሶችን አቅርቦበታል፡፡ ተጠሪ ባመልካች ላይ ባቀረበዉ የመጀመሪያዉ ወንጀል ክስ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ በመተላለፍ የሰዉን ሕይወትና ጤንነት የመጠበቅ መ.ያዊ ግዴታ እያለበት ሆኖ እያለ ይህንን ግዴታዉን በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመወጣት ነሐሴ 15 ቀን 2006 ዓ.ም ከጠዋቱ በግምት 1፡00 ሰዓት ሲሆን የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-29507 ኦ.ሮ የሆነ የሕዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ እያሽከረከረ ይዞ ከሰንቦ ወደ ሸኖ አቅጣጫ ሲጓዝ ሕግ እንዲጭን ከተፈቀደለት አስራ ሁለት ሰዎች በላይ ሥድስት ሰዎችን በትርፍነት በመጫን በአንለላና ጠራ ወረዳ ፊጦናአላመስኖ ቀበሌ ጨለቅለቃ ከተባለዉ ልዩ ሥፍራ ሲደርስ ከአስፓልት መንገድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

11 ሜትር 40 ሳንቲሜትር ወጥቶ መኪናዉ በመገልበጡ በአደጋዉ ሟች መሰረት በደኑና ሟች ሳህለ ማርያም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዉ፣ በሕክምና ሲረዱ ቆይተዉ ሀምሌ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ሕይወታቸዉ ያለፈ በመሆኑ በከባድ ቸልተኝነት የሰዉ መግደል ወንጀል ፈጽሟል፡፡

3. እንደዚሁም ተጠሪ ከላይ በተገለጸዉ ሥፍራና ጊዜ በመኪናዉ ዉስጥ ተሳፋሪ የነበሩት 1ኛ ሞገስ መገርሳ 2ኛ ደሉ ወልዴ 3ኛ በሻህ ጌታነህ 4ኛ ቤዛ ሞገስ 5ኛ እሸቱ ሉቤን 6ኛ ዘዉድነሽ አለሙና እና 7ኛ አለነሽ ጋሸን በተለያየ የሰዉነት ክፍላቸዉ ላይ ጉዳት የደረሰባቸዉ በመሆኑ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2/ በመተላለፍ ሰባት በሰዉ አካል በቸልተኝት ጉዳት የማድረስ ወንጀሎችን ፈጽሟል በማለት በእያንዳንዱ ተጎጅ ሥም አንድ ወንጀል ክስ በጥቅል ሰባት ወንጀል ክሶችን አቅርቧል፡፡
4. ተከሳሽ በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት ከተረዳ በኃላ በሰጠዉ የእምነት ክህደት ቃል የወንጀል ድርጊት የፈጸመ ቢሆንም እንደ ክሱ አይደለም የሞት አደጋም ሆነ የአካል ጉዳት የደረሰባቸዉ ግለሰቦች ጉዳት የደረሰባቸዉ በድንገት የኃላ ጎማ በመፈንዳቱና ሚዛኑ ወደ አንድ በኩል በማጋደሉ ነዉ፡፡ አደጋ የደረሰዉ በድንገት በመኪናዉ ላይ በደረሰ ችግር ስለሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡
5. ተጠሪ በወቅቱ መኪናዉ ዉስጥ በነበሩ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፣ትራፊክ አደጋ ፕላን መግለጫ ሰነድና ፕላኑን ያነሳዉን ባለሙያ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሥር ፍርድ ቤት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለዉ መሆኑን በጽሁፍ አረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን ተደራራቢ ወንጀል ክስና ማስረጃ ከመረመረ አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543/3/ የተመለከተዉን በመተላለፍ በከባድ ቸልተኝት ሰዉ መግደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነዉ፡፡ እንደዚሁም አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 559/2/ በመተላለፍ ከሳሽ ባቀረባቸዉ ሰባት ወንጀል ክሶች የተገለጹትን ሰባት በቸልተኝት አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነዉ በማለት የጥፋተኝነት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡
6. የቅጣት ዉሳኔዉን በተመለከተ የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኃላ አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543/3/ በመተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘበት አንደኛዉ ክስ የእስራት ቅጣቱ እርከን ሃያ አምስት የገንዘብ መቀጮ እርከን ሰባት ላይ ይወድቃል፡፡ አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 559/2/ በመተላለፍ ጥፋተኛ ለተባለባቸዉ ሰባት ወንጀል ክሶች በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 22 መሰረት ለእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ሁለት እርከን ለሰባት ወንጀሎች አስራ አራት በእርከን ሃያ አምስት ላይ ሲጨመር እርከን 39 ላይ ያርፋል፡፡ ሆኖም በወንጀል ሕግ ቁጥር 187 (ለ) (2) እና በወንጀል ሕግ ቁጥር 66 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) ቅጣቱ በሕግ ልዩ ክፍል ከተደነገገዉ በላይ መብለጥ የሌለበት በመሆኑ የእስራት ቅጣቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እርከን 32 የገንዘብ መቀጮ እርከን ሰባት ሥር ለመመደብ በህግ ተገድደናል፡፡ ተከሳሽ መልካም ፀባይ የነበረዉ መሆኑ ለጎጆዎች ካሳ መክፈሉና ቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆኑ ሶስት ማቅለያ በመያዝ በእርከን 29 ከተቀመጠዉ ቅጣት በአስር ዓመት ፅኑ እስራ እና በብር 5000(አምስት ሺ ብር) ገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡

7. የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ በማጽናት ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ያልተማረ መሀይም መሆኑ አንድ የቅጣት ማቅለያ ሆኖ ሊያገለለት ይገባል በማለት ግን የቅጣት አወሳሰን መመሪያን መሰረት አድርጎ በማስላት ተከሳሽ ከዚህ ቀደም የታሰረዉ ታስቦ በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማሻሻል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ሰጠዉን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

8. አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡ አመልካች ጥር 25 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች በድንገት የመኪናዉ ላይ በደረሰ የቴክኒክ ብልሽት አደጋዉ የደረሰ መሆኑ ገልጸዉ እያለ ጥፋተኛ መባሌ የህግ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካች መጠየቅ አለበት ከተባለ እንኳን በሰባት አካል ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ መባል የለብኝም በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በ 30/04/2008ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ፍርድና ዉሳኔ በማስረጃ ምዘና መርህ እና በሕግ አተረጓጎም ረገድ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ የሕግ ድጋፍ ስለሌለዉ ዉድቅ ተደርጎ የሥር ፍርድና ዉሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

9. የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸውን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔም ሆነ የቅጣት ውሳኔ በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአሁን አመልካች በዐ/ህግ ክስ ላይ በተመለከተው ጊዜ እና ቦታ የሰሌዳ ቁጥሩ የተጠቀሰውን ሚኒባስ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ እያሽከርከረ እያለ፤ መኪናዋ ለመጫን ከተፈቀደላት በላይ ትርፍ ሰው በመጫኑ አደጋው የደረሰና ከመንገድ ወጥታ በመገልበጧ በሁለት ሰዎች ላይ የሞት እና በሌሎች ሰባት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት አደጋ እንደደረሰባቸው የዐ/ህግ ማስረጃ ያረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን የስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ያመለክታል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህን የ0/ህግ ምስክሮች ቃል እና የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመመዘን የአሁን አመልካች ባለው የማሽከርከር ሙያ ተሳፋሪዎች በተሸከርካሪው አሳፍሯቸው ሲጓዝ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ደንብ በመጣስ፣ ከአቅም በላይ ሰው በማሳፈር የሙያውን ግዴታ እና የስራ ልምድ በሚጠይቀው መጠን ላሳፈራቸው የሰዎቹን ህይወት፣ ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ በአግባቡ ባለመወጣቱ አደጋው የደረሰ መሆኑ ፍሬ ጉዳይና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርደ ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ ይህን ተከትሎ ፍ/ቤቱ አመልካች የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል በሰጠው ትዕዛዝ የመከላከያ ምስክሮች የሌለው መሆኑን በመግልጽ ያልተከላከለ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

10. ስለዚህ የስር ፍ/ቤት ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን መዝኖ የመወሰን ስልጣኑን መሰረት በማድረግ የአሁን ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በበቂ ማስረጃ፣ አመልካች ሙያዊ ግዴታውን ባለመወጣት እና በቸልተኛነት በፈጸመው ድርጊት የሁለት ሰዎችን ህይወት እንዳጠፋ እና በሰባት ሰዎች አካል ላይ ጉዳት እንዳደረሰ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) እና 559(2) ስር የጥፋተኝነት በውሳኔ መስጠቱን ከውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይህ ችሎት ደግሞ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር ሲታይ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በህጉ አግባብ የተሰጠ ነው በማለት ከሚቀበል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የማይቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

11. “በእኛ በኩል በዚህ ሰበር ችሎት መታየት ያለበት አመልካች ጥፋተኛ ነው የተባለባቸው ሰባት በቸልተኝነት በሰው የአካል ላይ ጉዳት የማድረስ የወንጀል ድርጊቶቸ በወንጀል ህጉ ከተመለከተው በአንድ የወንጀል ሀሳብና በአንድ የወንጀል ድርጊት በተለያዩ ሰዎች ላይ ከደረሰ ጉዳትና ተደራራቢ ወንጀሎች ተከሳሽ ተጠያቂ ከሚሆንባቸው ሌሎች ሁኔታዎች አንጻር እንዴት ይታያል? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎችን በተመለከተ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60 እና ተከታዮች ድንጋጌዎች ተመለክቶ እናገኛለን፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ሐ) እንደሚያመለክተው “ማንም ሰው ተደራራቢ ወንጀሎችን አድርጓል የሚባለው በአንድ የወንጀል የማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኝነት ያደረገው ወንጀል አንድን የህግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ አንድ ዓይነት ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ነው” በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ቅጅ “In the case of criminal act which, though flowing from the same criminal intention or negligence and violating the same criminal

https://t.me/ethiopianlegalbrief

provision, causes the same harm against the rights or interests of more than one person." በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው የተደራራቢ ወንጀሎች መርህ ከላይ በተገለጸው መንገድ የተቀረጸ መሆኑ የህጉን ድንጋጌ ከሌሎች የህግ ድንጋጌዎች ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ በማድረግና በመተግበር በኩል ግልጽና ከችግር የጸዳ የሚያደርገው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

12. በተለየም ከላይ የተገለጸው የድንጋጌው ይዘትና ተግባራዊ ተፈጻሚነት በወንጀል ህግ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መርህን ከሚደነግገው የወንጀል ህግ አንቀጽ 61 ድንጋጌዎች ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ጥያቄዎችን የሚያስነሳ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በጭብጥነት ከተያዘው ነጥብ አንጻር አንድ ሰው በቸልተኝነት በሚፈጸመው አንድ ድርጊት፣ በአጋጣሚ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ተጎጅዎች ሆነው ቢገኙ፣ ተከሳሹ መከሰስና መቀጣት ያለበት በእያንዳንዱ ተጎጅ ላይ አንድ ራሱን የቻለ የወንጀል ድርጊት እንደፈጸመ ተቆጥሮና ጥፋተኛ ተብሎ ነው ወይስ አንድ ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ ነው የሚለው ነጥብ የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው፡፡ ከላይ የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ በተለይም በአንድ የቸልተኝነት ወንጀል ድርጊት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ተጎጅ ቢሆኑ ውጤቱ ምንድንነው የሚለውን ለመተርጎምና ለመረዳት ህግ አውጭው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ የተደራራቢ ወንጀሎችና ቅጣት መርህ ተፈጻሚ መደረጉ ሕግ አውጭው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ከሚያራምዳቸው ሃሳቦች ጋር የሚሄድና የሕጉን አላማ የሚያሳካ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የቀረፀበትን አግባብና የድንጋጌውን አውደንባብና መሰረታዊ ዓላማ ማገናዘብ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

13. የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዓስ አንቀፅ 3 መሰረቱ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 1 በተመለከተው መሰረት በተከሳሹ ቸልተኝነት የሰው ሕይዎት የሕልፈት የተዳረገ መሆኑ ነው፡፡ በተከሳሹ ቸልተኝነት የሰው ሕይወት ለሕልፈት የተዳረገ መሆኑ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት ማቋቋሚያ አንዱ መሰረታዊ ሁኔታ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 የማክበጃ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ አንድ አሽከርካሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 በመተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት አለበት የሚባለው ጥፋተኛው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ እንደሆነ መሆኑን በግልፅ ተደንግጓል፡፡

14. "ጥፋተኛው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ ወይም ወንጀሉን የፈፀመው ግልፅ የሆነ ደንብ ወይም መመሪያ ተላላፎ ቅጣቱ ከአምስት እስከ አስራ አምስት አመት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፅኑ እስራት እስከ አስራ አምስት ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል" ከሚለው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 አቀራረፅ፣ ይዘትና አውደንባብ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ አሸከርካሪ በአንድ የቸልተኝነት ተግባር ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑትን ሰዎች በሕይወት የመኖር መብት በመጣስ በቸልተኝነት በመግደሉ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ በደነግገው መሰረት እያንዳንዱ ሟች ለመገደል አንድ ራሱን የቻለ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እነደፈፀመ ተቆጥሮ ተደራራቢ የወንጀል ክስና ቅጣት ማይወሰንበት መሆኑና በአንፃሩ አንድ ከባድ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 በመተላለፉ ጥፋተኛ ተብሎ እንደሚቀጣ ከሚለው ድንጋጌው አውደንባብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

15. በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጥፋተኛው በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት አንፃር የሚጠየቅ ባይሆንም ጥፋተኛው ሁለት እና ከዛ በላይ ሰዎችን መግደሉ ሊወሰንበት የሚገባውን ቅጣት ከፍ እንደሚያደርግበት የማያመለክት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ድንጋጌ አግባብ በቸልተኝነት ሰውን መገደል ምንም እንኳን የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ላይ የሞት አደጋ ያስከተለ ቢሆንም ቅጣቱን ከፍ ከሚያደርግበት በስተቀር፣ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ በሚደነግገው መሰረት እያንዳንዱ ሟች ለመገደል አንድ ራሱን የቻለ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፊተኛ የሚያሰኘውና የሚያስቀጣው ሳይሆን በድንጋጌው በተመለከተው ልዩ ማክበጃ ሁኔታ ባለበት አንድ ከባድ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ ጥፋተኛ የሚባልና ቅጣት የሚወሰንበት መሆኑን ሕግ አውጭው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 በመደንገግ በግልፅ አስቀምጧል፡፡

16. እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አሸከርካሪው በፈፀመው በአንድ ቸልተኝነት ተግባር በዚህ መዝገብ አከራካሪ ጭብጥ በሆነው መንገድ ሰባት ሰዎች የአካል ጉዳት ቢደርስባቸው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ ስር በተመለከተው መሰረት ሰባት በቸልተኝነት በሰው አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደፈፀመ ተቆጥሮ ጥፋተኛ ሊባልና ሊቀጣ ይገባዋል ወይስ አንድ ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጠሮ ጥፋተኛ ሊባልና ሊቀጣ ይገባዋል? የሚለው ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው በተሸከርካሪ በቸልተኝነት ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በለይ ሆኑ ሰዎችን የገደለ ጥፋተኛ ሕግ አውጭው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 ቅጣቱን ከፍ የሚያደርግበት በስተቀር፣ ተደራራቢ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀሎችን ፈፅማል ተብሎ ተደራራቢ ወንጀል ክሶች እንደማይቀርቡበትና በተደራራቢ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ እንደማይቀጣ በግልፅ አስቀምጧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

17. ይህ ከሆነ አሸከርካሪው በአንድ ቸልተኝነት ተግባር በተለያዩ ሰዎች አካል ላይ ጉዳት ሲያደርስ በቸልተኝነት ተደራራቢ አካል ማጉደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ ተደራራቢ ወንጀል ክስ ሊቀርብበትና በተደራራቢ ወንጀል በመፈፀም ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ ይገባዋል የሚለው የተጠሪ ክርክርና በታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ሰባት በቸልተኝነት በሰው አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል የፈፀመ ነው በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መርህን ከሚደነግገው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 61 መሰረታዊ መርህ ጋር የማጣረስና የሕጉን ድንጋጌዎች ከፍትሐዊ፣ ወጥነት እና ተገማች የሆነ የሕግ ትርጉም ከመስጠት አንፃር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የአሁኑ አመልካች ምንም እንኳን በክሱ እንደተመለከተው የሰውን አካል ደህንነት ለመጠበቅ ያለበት ግዴታ ወደ ጎን በመተው ከመኪናዋ አቅም በላይ ተርፍ ሰዎች በመጫን መኪናዋ መገልበጥ አደጋ እንድደርባት በማድረግ በሰባት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ቢሆንም፣ በቸልተኝነት በፈፀመው አንድ ተግባር ሰባት ሰዎች አካል ደህንነት መብት በመጣሱ ብቻ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ ተመለከተው የተደራራቢ የወንጀሎችና ቅጣት መርህ ተፈጻሚ መደረጉን ህግ አዉጭዉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 61 እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚያራምዳቸዉን አሳቦች ጋር የሚሄድና የህጉን አላማ የሚያሳካ ሆኖ አላገኘነዉም፡፡

18. የአሁን አመልካች ምንም እንኳን በሰባት ሰዎች ላይ በተሸከርካሪው የአካል ጉዳት ያደረሰ ቢሆንም እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት እንደፈጸመ እንጅ በአንድ ቸልተኝነት ተግባር ምክንያት በደረሰው መኪና መገልበጥ በአደጋ በአጋጣሚ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ቁጥር ሰባት በመሆናቸው ሰባት ተደራራቢ በቸልተኝነት አካል ጉዳት የማድረስ ወንጀሎች እደተፈጸሙ ተደርጎ የወንጀል ክስ ሊቀርብበትም ሆነ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት አይገባም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በሰባት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት በማድረሱ በአንድ ሰው ላይ አካል ማጉደል ካደረሰው አሽከርካሪ ጋር ወንጀሉ ክብደት በእኩል አይን የሚያየው የወንጀሉን ደረጃ በእኩል የሚሳየው አይሆንም፡፡ ከዚህ አንጻር አሁን ስራ ላይ ያለው የቅጣት አወሳሰን *መመሪያ* በተከሳሹ የቸልተኝነት ተግባር የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ቁጥር መሰረት በማድረግ ወንጀሉን ደረጃ እና እርከን የሚደነግግ አለመሆኑ በመመሪያው መሰረት ቅጣት በመወሰን ሂደት በግልጽ የሚታይ ከፍተኛ ያለበት በመሆኑ *መመሪያው* ሲሻሻል በተከሳሹ የቸልተኝነት ተግባር የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ቁጥር መሰረት በማድረግ ወንጀሉን ደረጃ እና እርከን ከፍ ሊያደርግ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

19. ይህ ማለት በተሸከርካሪ በቸልተኝነት ድርጊት በአንድ ሰው አካል ላይ ጉዳት ያደረሰ አሽከርካሪ እና በሁለት እና ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች **የአካል** ላይ ጉዳት ያደረሰ አሽከርካሪ እኩል ሊቀጡ ይገባል ማለት አይቻልም። ስለሆነም የአሁን አመልካች በሚያሽከረክረው ተሽከርካሪ በቸልተኝነት በሶስቱ ሰዎች ላይ ላደረሰባቸው የአካል ጉዳት እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት ተወስዶ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2/ ስር ጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል ብለናል። በዚህ አግባብ የቅጣት ስሌቱ ሲታይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሰረት በመደረግ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ ስር በደረጃ 1 እርከን 25 ስር ስምንት አመት መነሻ ቅጣት ተወስዷል።

20. በቸልተኛነት በሰባት ሰዎች አካል ላይ ጉዳት ማድረስን በተመለከተ እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት በመውሰድ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2/ ስር ጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ አመልካች በሰባት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ያደረሰ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል። በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ይህ ድንጋጌ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 7 ድረስ ተደንግጎ ይገኛል። በዚህ መሰረት ደረጃ 1 ሲታይ ቀላል የአካል ወይም የጤና ጉዳት አድራሹ የሌላ ሰውን አካል ወይም ጤንነት የመጠበቅ ሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ህክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው እንደሆነመ የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 7 የገንዘብ ቅጣት እርከን 1 ስር እንደሚያስቀጣ ያመለክታል። ነገር ግን ከደረጃ 2 እስከ ደረጃ 7 ባሉት ስር በሁለት ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች ቀላል የአካል ጉዳት ያደረሰባቸው እንደሆነ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ በተዘረዘሩት ደረጃዎች የሚሸፈን ሆኖ አይገኝም። ይህ በሆነ ጊዜ ደግሞ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 27/1/ መሰረት ከዚህ ቅጣት መመሪያ ወጥቶ ተገቢ ቅጣት ሊወሰን ይገባል።

21. በዚህ አግባብ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/ቁ. 559/2/ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እስራትና አንድ ሺህ ብር የማያንስ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል። በዚህ መሰረት አመልካች እንደ አንድ አሽከርካሪ ያለበትን ግዴታ መወጣት ሲገባው የሆነው ይሁን በማለት የሚያሽከረክረውን ተሽከርካሪውን ተሽከርካሪ ጥሎ በመውረድ በሰባት ሰዎች ላይ ቀላል የአካል ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ ስር አመልካች ሊቀጣ ይገባል በማለት ችሎት ያመነበት ሁለት /2/ አመት ቀላል እስራት ሲሆን፣ ይህ ደግሞ ወደ ጽኑ እስራት ሲቀየር 1 ዓመት /አንድ አመት/ ጽኑ እስራት ይሆናል። በመሆኑም ከላይ የወ/ሕ/ቁ. 543 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር ከተያዘው መነሻ ቅጣት ጋር ተደምሮ 8 ዓመት ጽኑ እስራት ጋር ተደምሮ ዘጠኝ ዓመት እንደቅጣት መነሻ የሚወሰድ ሲሆን ይህ ደግሞ እርከን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

26 ስር የሚወድቅ ይሆናል፡፡ በስር ፍ/ቤት ሶስት የቅጣት ማቅለያ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አንድ ማቅለያ በድምሩ አራት ማቅለያዎች ይዘውለታል፡፡

22. ይህም ችሎት እነዚህን ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመውሰድ ቅጣቱ ከእርከን 26 ወደ እርከን 22 ዝቅ እንደሚል ተገንዝቧል፡፡ እርከን 22 ስር ከአምስት ዓመት ከስድስት ወር እስከ ስድስት አመት ከሰባት ወር የሚያስቀጣ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ችሎት አመልካችን ያስተምራል፣ ሌሎችን ያስጠነቅቃል በማለት ያመነበት ቅጣት አመልካች በዚህ ጉዳይ ከታሰረበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ በስድስት ዓመት ከሥድስት ወር ጽኑ እስራት በብር 5000(አምስት ሺ ብር ሊቀጣ) ይገባል ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.0235878 የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳ እና ይህንን ዉሳ በማሻሻል የአማራ ክል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችት በመ.ቁ 02-15930 በ 10/09/2007ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.50596 ህዳ 8 ቀን 2008ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአሁን አመልካች በዚህ ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ በበስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራትና በብር 5000(አምስ ሺብር) መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡ የክልሉ ማረሚያ ቤት በዚህ ዉሳ መሰረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. የዚህ ዉሳ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች እና ለአመልካች ይድረስ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 131705

ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሀይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1ኛ.አብርሃም ሰለሞን
2ኛ. የሺመቤት ጓደ
3ኛ. ዳንኤል ሰለሞን
ከማረሚያ ቤት አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የፌዴራል አ/ህግ - ዐ/ህግ መሰረት መላቱ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካቾች በተከሰሱበት ከባድ ስርቆት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በተሰጠ የቅጣት ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል እንዲታረም አቤቱታ ስላቀረበነው፡፡

አመልካቾች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 669/3/ለ ተላልፈው ከግል ተበዳይ ቤት ግምቱ 843,000 ብር የሚያወጣ ልዩ ልዩ ንብረት ሚያዚያ 29 ቀን 2006 ዓ/ም በመውሰዳቸው ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽሟል በሚል ዐ/ህግ ክስ መስርቶባቸው ፍርድ ቤቱም የዐ/ህግ እና የተከሳሾችን መከራከሪያ ከመረመረና ማስረጃ ከሰማ በኃላ በተከሰሱበት አንቀጽ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ አስተላልፎባቸዋል፡፡

አመልካቾች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ቅሬታቸውን ባለመቀበል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲሉ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች በሰበር መ/ቁ/ 131705 ሐምሌወር 2008 ዓ/ም የተፃፈ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን 3ኛ አመልካች በበኩሉ በሰበር መ/ቁ/ 131706 ሐምሌ 30 ቀን 2008 ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

መዝገቦች ከስር በአንድ ክስ የቀረበባቸው መሆኑ ታይቶ ተጣምሮ እንዲመረመር ተደርጓል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች ጥፋተኛ ከተባሉበት አንቀጽ 669/3/ለ/ አንፃር ወንጀሉ በቡድን የተፈጸመ ነው ተብሎ የቅጣት ማክበጃ መወሰዱ የወንጀል ህጉን 84/1/መ/ እና 84/2/ አንፃር አግባብነቱን ለመመርመር ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ዐ/ህግ በሰጠው መልስ በቡድን ወንጀል መስራታቸው መረጋገጡን ጠቅሶ ነገር ግን የአንቀጽ ማቋቋሚያ ከተደረገ በኃላ የቅጣት ማክበጃ ተደርጎ በተጨማሪነት ሊወሰድ እንደማይገባ አስተያየት ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን ይህ ችሎት የቅጣት አወሳሰን በተመለከተ የቀረበውን የክርክር ነጥብ ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ ከመዝገቡ መገንዘብ እንደተቻለው አመልካቾች በግብረአበርነት የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 669/3/ለ/ ተላልፈው ከባድ የስርቆት ወንጀል የፈጸሙ መሆናቸው ማስረጃ የማጣራት ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህ ድንጋጌ ማቋቋሚያ ናቸው ብሎ ዐ/ህግ በክሱ የጠቀሳቸው ፍሬ ነገሮች ሲታዩ የወንጀሉ አፈፃጸም በረቀቀ ዘዴ አደገኛነታቸውን የሚያሳይ መሆኑ፣ 2ኛ አመልካች የቤት ሰራተኛ ሆኖ እንድትገባ ማድረጋቸው እና ይህንን የቅጥር ግንኙነት አጋጣሚ በመጠቀም እንዲሁም በስምምነት በቡድን የተፈጸመ የወንጀል ድርጊት መሆኑ ተመልክቷል፡፡

እንግዲህ ቅጣት አወሳሰን አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የሚሸፍን መሆኑ አከራካሪ ባለመሆኑ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ በተቀመጠው ደረጃ መሰረት ሲታይ ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ከ100,000 /መቶ ሺህ ብር/ በላይ መሆኑና ሶስት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሟላታቸው ጋር ሲዛመድ እርከን 30 ደረጃ 9 ላይ እንደሚመደብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ግን የገንዘብ መጠኑን ታሳቢ አድርጎ ቅጣት ማክበጃ ሁለት እንደተረጋገጠ ግምት አስገብቶ መነሻ ቅጣት ደረጃ 8 እርከን 26 መያዙን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም በቀረበው ክስ ከተረጋገጠው ሶስት በአንቀጽ ማቋቋምያ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ የስር ፍርድ ቤት ሁለቱን ብቻ መውሰዱ ሲታይ በመሰረታዊነት ተከሳሾች /አመልካቾችን/ የጠቀመ ነው ከሚባል በስተቀር የጎዳቸው ነው ሊባል አይችልም፡፡ በእርግጥ የአንቀጽ ማቋቋሚያ የሆነ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ዳግም የቅጣት ማክበጃ ተደርጎ ሊወሰድ እንደማይገባ በወንጀል ህግ አንቀጽ 84/2/ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነ ይህ በጥብቅ ሊከበር እንደሚገባ የምንስማማበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ በውጤቱ ሲታይ አመልካቾች ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ ባለመሆናቸው ከአመልካቾች ጥያቄ አንፃር መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ሆኖ አላገኘንም፡፡ በሌላ በኩል የቀረበው ቅሬታ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት፣ የቀደመ የወንጀል ሪኮርድ ሳይኖር የወንጀል ሪኮርድ አለመኖር እንደቅጣት ማቅለያ አለመያዙ ስህተት ነው በሚል የቀረበውን ክህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በዚህ ረገድ የስር መዝገብ መርምረን እንደተገነዘብነው 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በተደጋጋሚ በወንጀል ተጠርጥረው የጣት አሻራ የሰጡ ስለሆነ የዘውትር ጸባይ መልካም ነው ተብሎ የቅጣት ማቅሊያ በወ/ህግ 82/1/ሀ/ ሳይያዝላቸው ታልፏል፡፡ አመልካቾች ይህንን በጥብቅ ተቃውሞ ተከራክረዋል፡፡ በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 20/3/ እንደተደነገገው በወንጀል ጥፋት እስካልተፈረደ ድረስ እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት የተጠበቀነው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በወንጀል ተጠርጥሮ የጣት አሻራ ሰጥቷል በመባላቸው ብቻ እንደ ጥፋተኛ ተቆጥሮ የወንጀል ጥፋት ሪኮርድ እንዳለባቸው ተደርጎ በስር ፍርድ ቤቶች ግምት መውሰዱ በህገመንግስቱ የተከሰሱ ሰዎች መብት አስመልክቶ ከተደነገገው መሰረት ሀሳብ ጋር የሚጣረስስ ለሆነ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤቶች አቋም መሰረታዊ የህግ መንግስት መርህ የሚጣረስ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁአግባብ 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የመልካም ባህርይ የቅጣት ማቅሊያ ተደርጎ ሊያዝ አይገባም ሲሉ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ሲታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ከዚህ ሌላ በአመልካቾች በኩል የቀረበው የቅጣት ማቅሊያ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተሰጣቸው ቀጠሮ ማስረጃ ማቅረብ እንዳልቻሉ ፍርድ ቤቱ በመዝገቡ መመዝገቡን ማየት ችለናል፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ደግሞ በማስረጃ የሚረጋገጥ ጉዳይ ከመሆኑ አኳያ ማስረጃ የሚረጋገጥ ጉዳይ የመመርመር እና ፍሬ ነገር የማጣራት ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ዘንድ ማስረጃ አቅርቧል ያላረጋገጡትን ፍሬ ነገር መሰረት አድርገው አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 /3/ሀ/ አንፃር የዚህ ሰበር ችሎት ስልጣን ወሰን ወጪ ስለሆነ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ሲጠቃለል በቅጣት አወሳሰን ረገድ አመልካቾች ካቀረቡት የቅሬታ ነጥቦች ተቀባይነት ያገኘው 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የቀደመ የወንጀል ሪኮርድ ስለመኖሩ በፍርድ የተረጋገጠ ባለመቅረቡ በወ/ህግ አንቀጽ 82/1/ሀ መሰረት አንድ የቅጣት ማቅሊያ ምክንያት እንዲያዝላቸው ብለናል፡፡

በዚሁመሰረት 1ኛ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠበት እርከን 27 3ኛ አመልካችም በተመሳሳይ ከእርከን 27 ላይ አንድማቅሊያ ሲያዝላቸው በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 23/4/መሰረት አንድ እርከን ሲቀንስ ቅጣቱ እርከን 26 ላይ ያርፋል፡፡ እርከን 26 ላይ የተመለከተው የእስራት ቅጣት ፍቅደ ስልጣን ከ7 አመት ከ8 ወርእስከ 9 አመት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከ2 ወር ጽኑ እስራት መሆኑ ከአባሪ አንድ ማየት ይቻላል፡፡ ስለሆነም 1ኛእና 3ኛ አመልካቾች በዚህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም የታሰሩት ታሳቢ ተደርጎ በስምንት /8/ አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ተብሎ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ/ 195/2/ለ/2/ መሰረት ቅጣቱ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡

በ2ኛ አመልካች በኩል የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በወ/መ/ቁጥር 120047 በ17/09/07 ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ ቅጣት አስመልክቶ ግን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንኑ ማሻሻል ሲገባው ማለፉ ስህተት መሆኑ ታይቶ 1ኛ እና 3ኛ አመልካች ላይ የተላለፈው የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/195/2/ለ/2/ መሰረት በማሻሻል በዚህ ጉዳይ እጃቸው የተያዘበት ጊዜ ጀምሮ የታሰሩት ታሳቢ ተደርጎ በስምንት /8/ አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡
2. 2ኛ አመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት የተላለፈው የቅጣት ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመ/ቁ/000962 30/09/08 ያጸናው በዚህ ችሎት በቅጣት ረገድ ብቻ የተሻሻለለ መሆኑ እንዲታወቅ ይፃፍ፡፡
4. 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ላይ በስር ፍርድ ቤት የተወሰነው ዘጠኝ አመት ከስድስት ወር /9፡6 ወር /ጽኑ እስራት ወደ ስምንት /8/ዓመት ጽኑ እስራት የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ማረሚያ ቤቱ በዚሁ መሰረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

ይህ መዝገብ ከሰበር መ/ቁ/ 131706 ጋር ተጣምሮ የተወሰነ ስለሆነ የዚህ መዝገብ ውሳኔ ግልባጭ ከመዘገበ ቁጥር 131706 ጋር ይያያዙ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.126017

ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሃመድ
ተኽሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ
ቀነአ ቂጣታ
ፀሃይ መንክር

አመልካች - የአርሲ ነገሌ ከተማ ፖ/ሊስ ጽ/ቤት ተወካይ ገለቶ አኖታ ቀረቡ
ተጠሪ - አቶ ተስፋአለም ገ/ሚካኤል- ቀርቧል
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች የተሰጠው ውሣኔና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ሲሆንጉዳዩ የተጀመረው በምዕራን አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡
የክሱ ይዘት የሰሌዳ ቁጥሩ 03 - 0188468 አ/አ የሆነ ኤፍ ኤስ አር አይሱዚ መኪናዬን በ28/03/2007 ዓ.ም የይለፍና የማንገዝ ፈቃድ ሳይዝ ስኳር ሲያንገዝ ይጥለሁ በሚል ሰበብ የፌደራል የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁር 813/2006 አንቀፅ 27(1) የተደነገገውን በመተላለፍ ስልጣን ሳይኖረው በቁጥጥር ስር በማድረግ ይዞት ስለሚገኝ እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መኪና የያዝኩት ምክንያት ከሳሽ ህጋዊ የይለፍ እና የማንገጥ ፈቃድ ሳይኖረው በራሱ መኪና 100 (መቶ) ኩንታል ስኳር በመጫን እራሱ እያሽከረከረ እያለ በአርሲ ነገሌ ከተማ ውስጥ እጅ ከፍንጅ በመያዙ በተደረገው የፖ/ሊስ ምርመራ የጫነው ስኳርም ህገወጥ ሆኖ ስለተገኘ ሹፈሩም እራሱ የመኪናው ባለቤት በመሆኑ ስኳሩና መኪናው የወንጀል ኤግዚቪት ሆኖ የምርመራ መዝገቡ ለፍትህ ጽ/ቤት ከተላለፈ በኋላ በአቃቤ ህግ ክስ አቅራቢነት ተጠሪ በሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀፅ 43(5) የተደነገገውን በመተላለፍ ህገ ወጥ ስኳር ያጓዝ በመሆኑ የወንጀል ክስ በ07/08/2007 ዓ.ም በፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 27876/07ቀርቦበትመኪናው እንደ ዓቃቤ ህግ ማስረጃ ኤግዚቪት ሆኖ እያለ ይህ የወንጀል ተከሳሽ በዋስትና ምክንያት ወጥቶ ስለታጣ መዝገቡ ለጊዜው ተዘግቷል፡፡ ስለሆነም ከሳሽ በወንጀል ተከሶ መኪናውም እንደ ኤግዚቪት ማስረጃ ሆኖ ውሳኔ ለማግኘት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚጠብቅ እንጂ ከሳሽ እንደሚለው በህገወጥ መንገድ ያለስልጣኔ መኪናውን የያዝኩ ስላልሆነ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተከሳሹ ጽ/ቤት የተመረመረው የወንጀልመዝገብና በፍርድ ቤት የሚገኘው መዝገብ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ በማስቀረብ መርምሮ ከሳሽ በተጠረጠረበት ወንጀል በተጣራበት የምርመራ መዝገብ መኪናው እግዚቢት ሆኖ ተይዞ የሚገኝ መሆኑን እና የፖሊስ መዝገቡ ለፍትህ ጽ/ቤት ተልኮ ክስ ተከፍቶበት በወረዳው ፍርድ ቤት የወንጀል ተከሳሹ (የፍትሃብሔር ክስ የመሰረተው) ባለመቅረቡ የወንጀሉ መዝገብ ለጊዜው መዘጋቱን ማረጋገጡን፤ የፖሊስ ተግባር ወንጀል መከላከልና ወንጀል ከተፈፀመ ደግሞ ጉዳዩን አጣርቶ ለሚመለከተው ስልጣን ላለው የህግ አካል በማቅረብ ፍትሃዊ ውሳኔ ማሰጠት መሆኑን፤ በተያዘው ጉዳይም ተከሳሽ ጽ/ቤት በከሳሽ ላይ መዝገቡን አጣርቶ ይመለከተዋል ለሚለው አካል ጉዳዩን ማቅረቡን፤ ይህ ጉዳይ የቀረበለት ፍትህ ጽ/ቤትም መኪናውን እና የተያዘውን ስኪር እንደ ማስረጃና ኤግዚቪት በማድረግ ክሱን ዓቃቤ ህግ በከሳሽ ላይ መስርቶ ለፍርድ ቤት አቅርቦ ከሳሽ ባለመገኘቱ ምክንያት የመጨረሻ ውሳኔ ሳያገኝ መዝገቡ ለጊዜው መዘጋቱን ማረጋገጡን፤ ስለሆነም ከሳሽ ስለተያዘው መኪና በወንጀሉ መዝገብ ላይ መከራከር የሚችል እና መፍትሄ ሊያገኝበት የሚችል እንጂ ይህ የወንጀል ጉዳይ ውሳኔ ሳያገኝ እግዚቪት ሆኖ እንደማስረጃ ተይዞ ስላለው መኪና ከወንጀሉ ውሳኔ በፊት በፍትሃብሄር መመልከቱ የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ እንዳላገኘው በመግለፅ ተከሳሽ መኪናውን በህገወጥነት የያዘው ስላልሆነና መኪናውን የተመለከተ ዝርዝር ክርክርም በወንጀሉ መዝገብ መፍትሄ የሚያገኝ ስለሆነ በፍትሃብሄር መልክ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ መኪናው ያለመፍትሄ ተይዞ የመቀመጡን ተገቢነት ለማጣራት በሚል የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የወንጀል ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 813/2006 መሰረት የቀረበለትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የሌለው በመሆኑ የተጠሪ መኪና ጉዳይ ስልጣን ባለው አካል ታይቶ ውሳኔ ማግኘት ሲገባው ተይዞ መቆየቱ ህጋዊ ስላልሆነ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት በማለት ውሳኔውን ሽሮ መኪናው ለተጠሪ እንዲለቀቅ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ለክልሉ ሰበር ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች በ28/07/2008 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻተፈፀመ የሚለውን የህግ ስህተት በመዘርዘር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኪና ለተጠሪ እንዲመለስ የሰጡት ውሳኔ ተሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቋል፡፡ተጠሪመልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በ22/09/2008 ዓ.ምበተፃፈ መልስ ውሳኔው ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የክርክሩንአመጣጥ ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በበኩላችን የወንጀል ክሱን ለማየት ሥልጣኑ በሌለው ፍርድ ቤት ክሱ መቅረቡን ምክንያት በማድረግ ከወንጀሉ ክስ ጋር በተያያዘ አግዚቪት ነው የተባለ ንብረት እንዲመለስ የፍትሃብሄር ክስ መቅረቡ እና ንብረቱ እንዲመለስ በፍትሃብሄር ክርክሩ ውሳኔ መሰጠቱ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ወንጀል ተፈፅሟል በሚል በተጠሪ ላይ የወንጀል ምርመራ አድርጎ በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዝ ነበር ያለውን 100 (መቶ) ኩንታል ስኳር እና የተጓጓዘበትን ተሽከርካሪ የወንጀል ኤግዚቪት አድርጎ በመመዝገብ የምርመራ መዝገቡን ለፍትህ ጽ/ቤት አስተላልፎ በአቃቤ ህግ በኩል በተጠሪ ላይ በወረዳው ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ መቅረቡን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቅሬታ የቀረበበትን ውሳኔ ያሳለፈው የወንጀል ክሱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ቀርቧል፤ የተጠሪ መኪና ስልጣን ባለው አካል ታይቶ ውሳኔ ማግኘት ሲገባው ተይዞ መቆየቱ ህጋዊ አይደለም በማለት ነው፡፡ የወንጀል ክሱ ጉዳዩን ለማየት በህግ ስልጣን በተሰጠው ዳኝነት ሰጭ አካል መታየት አለበት መባሉ እንዲሁም የወንጀል ክሱ በአፋጣኝ ታይቶ ውሳኔ ሊያገኝ ይገባል መባሉ ህጉን የተከተለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ምክንያት የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ነገር ግን ክርክሩ የሚመራው በህግ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትሎ በመሆኑ በህግ ከተዘረጋው ስርዓት ውጭ የሚቀርብ ክርክር እና የሚሰጥ ውሳኔ በህጉ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

የወንጀል ጉዳይን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ጉዳዩ ቢቀርብ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን ሳይጠራ ስልጣን የለኝም በማለት መመለስ የሚጠበቅበት ሲሆን ይህ ታልፎ ተከሳሽ እንዲቀርብ ከተደረገምበወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 130 ሥር እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን እንደሌለው በሚቀርብ መቃወሚያ መነሻነት የሥልጣን ክርክሩ እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ በሌላም በኩል በአግዚቢትነት የተመለከተ ከወንጀል ክሱ ጋር የተያያዘ ንብረት በመንግስት ሊወረስ የሚገባ ስለመሆኑ ወይም ለባለንብረቱ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆኑ ውሳኔ የሚሰጠው የወንጀል ክሱን ተፈጥሮ እና ለጉዳዩ ተገቢነት ያላቸውን የወንጀል ህጉን እና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ የወንጀል ክሱን በሚመለከተው አካል ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የወንጀል ክሱን ለማየት ስልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ክስ ቀርቧል በሚል ከወንጀል ክሱ ጋር በተያያዘ በወንጀል ችሎቱ ዳኝነት ታይቶ ውሳኔ ሊያርፍበት የሚገባ ንብረት በፍትሃብሄር ክስ ለማስመለስ የክስ ምክንያት ማድረግ የሚያስችል የህግ አግባብ የለም፡፡ከዚህም በተጨማሪ በወንጀል የሚደረገው ክርክርና በፍትሃብሄር በሚደረገው ክርክር፣ የሚያዘው ጭብጥና የሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደዚሁም የማስረጃ አመዛዘን ሥርዓቱ ሁሉ የተለያየ ነው፡፡

ስለሆነም የክልሉጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ከወንጀል ክስ ጋር በተያያዘ በወንጀል ክርክሩ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባ በኤግዚቢትበት ተመዝግቦ ለፍርድ የቀረበ ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲመለስ ተጠሪ ያቀረቡት የፍትሐብሄር ክስ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ንብረቱ እንዲመለስ ያሳለፉት ውሳኔ የወንጀልና የፍትሃብሄር ክርክሩ የሚመራበትን የሕግ ሥርዓት የሚጥስ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነምተከታዩንወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 237427 በ19/06/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉጠቅላይፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 241263 በ14/07/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 23948 በ03/05/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. በወንጀል ጉዳይ በኤግዚቪትነት የተያዘ ንብረት በፍርድ ውሳኔ የሚያገኘው በወንጀሉ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ለባለንብረቱ ይመለስ ወይም ለመንግስት ገቢ ይሁን ተብሎ ሲወሰን ወይም ተገቢውን የህግ ስርዓት ተከትሎ ሥልጣን ባለው አካል ትዕዛዝ ሲተላለፍ እንጂ በወንጀል ክስ ውሳኔ እየተጠባበቀ ባለው መዝገብ ላይ የተያዘውን እግዚቢት የፍትሐብሄር ክስ እንዲቀርብ ተደርጎ በዚሁ ክስ መነሻነት ንብረቱ ይለቀቅ በማለት ውሳኔ የሚሰጥበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውንይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.131088

ሚያዝያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ጎይትኦም ግደይ - ጠበቃ ወይንሸት ከበደ ቀረቡ
ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - አልቀረቡም
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበዉ አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 212810 የሰጠዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 178772 የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ በማጽናት እና የቅጣት ዉሳኔ በማሻሻል የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡በሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበዉ የወንጀል ክስ ነዉ፡፡የክሱ ዝርዝርም ሲታይ ተከሳሽ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ዓንቀፅ 91(1) በመተላለፍ በግምት ከምሽቱ 3፡00 ሰአት ከማሊ(ባማኮ) በረራ በማድረግ አዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት ሲደርስ በአየር መንገዱ የመንገደኞች ማስተናገጃ ተርሚናል ሁለት ላይ ሲደርስ ይዞት የገባውን ሻንጣ የጓዝና የአካላዊ ፍተሻ ማድረግ ፣ማስደረግ ሲገባው ሳያስፈትሽ መንገድ በመቀየር ጉዞውን በአየር መንገዱ የቀረጥ ነፃ ሱቅ በማድረግ ዋጋ በሚተመንበት በኩል ሊያመልጥ ሲል በቁጥጥር በመዋሉ በያዘው ፎለውሚ ሻንጣ በተደረገበት ፍተሻ ተገቢውን የጉምሩክ ስነስርአት ያልተፈፀመባቸው የቀረጥ ታክስ መጠናቸው 23411.52 (ሃያ ሶስት ሺህ አራት መቶ አስራ አንድ ከ 52/100) የሆኑ መጠናቸው 47600 (አርባ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ) ብር የሆኑ አርቴፊሻል ጥንድ የጀሮ ጌጣጌጦች ይዞ ወደ ሃገር ውስጥ ሲያሥገባ በመያዙ በፈፀመው የኮንትሮባንድ ተግባር ፈጽመዋል በማለት ወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በዓቃቤ ሕግ የቀረበበትን ክስ ክደው በመከራከራቸው ማስረጃዎች ቀርበው ከተሰሙ በኃላ እንዲከላከሉ ታዘው አመልካች መከላከያ ምስክሮቻቸው አስቀርበው አሰምተዋል ። ፍ/ቤቱ ተከሳሽ ባቀረቡዋቸው የመከላከያ ማስረጃ የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ማስተባበል ያልቻሉ በመሆናቸው በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ተብለዋል። በቅጣት ረገድም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ የወንጀሉ ደረጃ እና መነሻ የእስራት እና የገንዘብ ቅጣት እርከን በመለየት ተከሳሽ በሦስት ዓመት ጽኑ እስራት በተጨማሪም 5000(አምስት ሺህ ብር)የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል።

የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የጥፋተኝነት ዉሳኔ በማጽናት ቅጣትን በተመለከተ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ደረጃና እርከን የወጣለት ስለሆነ በስር ፍ/ቤት ከተያዙት የቅጣት ማቅለያዎች በተጨማሪ ሁለት ማቅለያዎች በመያዝ በስር ፍርድ ቤት ካረፈበት እርከን 17 ሁለት ማቅለያ ምክንያት ሲቀነስ የእስራት ቅጣት እርከን 15 የሚያርፍ ይሆናል ።የገንዘብ መቀጮም ከእርከን 7 ሁለት ማቅለያ ሲቀነስ እርከን 5 ላይ ያርፋል ስለሆነም አመልካች ከዚህ በፊት የታሰረበት ካለ የሚታሰብለት ሆኖ በ2 አመት ከዘጠኝ ወር ፅኑ እስራት እና 7000 (ሰባት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል።አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ይግባኝ በጠየቁበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት የተወሰነው የገንዘብ መቀጮ በማሻሻል ከፍ ተደርጎ የመወሰኑ አግባብነት ለመመርመር ሲባል በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸው ተለዋውጠዋል።

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል ከክርክሩ ሂደት ለመረዳት የተቻለው አመልካች በስር ፍ/ቤት የቀረበባቸው ክስ የወንጀል ህግ ድንጋጌ አዋጅ ቁ/ 622/2001 አንቀጽ 91/1/ በመተላለፍ ነው።

ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ሊቀጡ የሚገባው ጥፋተኛ በተባሉባቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ነው። አመልካች በተከሰሱበት የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈፀማቸው በሚገባ ተረጋግጧል። በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91(1) ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው ከአስራ አምስት አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና እስከ ብር ሃምሳ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ነው።

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ “የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የሀሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሰን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም፡፡

በያዝነው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ጥፋተኛ በተባሉበት የህግ ድንጋጌ ቅጣት ሲወስን የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ የወንጀሉ ደረጃ እና መነሻ የእስራት እና የገንዘብ ቅጣት እርከን በመለየት ተከሳሽ በሦስት ዓመት ጽኑ እስራት በተጨማሪም 5000 (አምስት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት አስልቶ ወንጀሎች በዝቅተኛ ደረጃ በመመደብ፣ለወንጀሉ መነሻ ተደርጎ የተያዘው ዝቅተኛው የቅጣት መጠን 5 ዓመት መሆኑን እና ይህም በአባሪ አንድ በእርከን 20 ስር የሚወድቅ መሆኑን በመግለጽ፣በተጠሪ በኩል የቀረበ ማክበጃ ምክንያት ስለሌለ በአመልካች በኩል የቀረቡትን ሦስት የማቅለያ ምክንያቶች ተገቢ አድርጎ በመቀበል እርከኑን ወደ 17 ዝቅ ካደረገ በኃላ በእርከን 17 በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን መሰረት አመልካቹ በሦስት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ መስጠቱን፣አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የህግ ድንጋጌ ከእስራት ቅጣት በተጨማሪ የገንዘብ መቀጮ የሚያስቀጣ በመሆኑ የገንዘብ መቀጮው በተመለከተም የህግ ድንጋጌው የሚያስቀጣው ከ50,000 እስከ 150,000 ብር የገንዘብ መቀጮ ስለሆነ በመመሪያው መሰረት ደረጃ በማውጣት ወንጀሉ ዝቅተኛ የተያዘ በመሆኑ የገንዘብ ቅጣት መነሻ 50,000 በመያዝ በአባሪ ሁለት እርከን 10 መነሻ እርከን በመያዝ ሶስት የቅጣት ማቅለያ መሠረት ወደ እርከን 7 ዝቅ እንዲል ካደረገ በኋላ አመልካች በ5000 ብር እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቅጣት ውሳኔ መሰረት አድርጎ ግራቀኙ ካከራከረ በኋላ በአመልካች ቀርበው በስር ፍርድ ቤት ያልተያዙት ተጨማሪ ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች በመያዝ የእስራት ቅጣት እርከኑ ወደ እርከን 15 ዝቅ በማድረግ በዚሁ እርከን ባለው ፍቅድ ስልጣን ቅጣቱ በማሻሻል አመልካች ሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጡ የወሰነ ሲሆን የገንዘብ መቀጮ በተመለከተ ግን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ላይ ባለው አባሪ ሁለት በተጨማሪነት ለአመልካች ከተያዙለት ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች መሰረት ከእርከን 7 ወደ እርከን 5 ዝቅ ካደረገ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ከወሰነው ቅጣት 5,000 (አምስት ሺህ) የገንዘብ ቅጣት በላይ 7000 (ሰባት ሺህ) ብር እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በሰበር አጣሪ ችሎት ለክርክር የተያዘው ጭብጥም አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የገንዘብ ቅጣቱን የመጨመሩ አግባብነት የሚመለከት ነው፡፡ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 196(2) ስር እንደተደነገገው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቅጣቱን ያፀናል ፣ይጨምራል፣ወይም ይቀንሳል በማለት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ለመረዳት የሚቻለው ተከሳሽ ይግባኝ የሚለው ቅጣቱ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል እንደሆነ አከራካሪ አይሆንም ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የስር ፍርድ ቤት አመልካች (ተከሳሽ)ባቀረቡት ይግባኝ ቅሬታ መነሻነት የገንዘብ ቅጣት መጨመሩ የወንጀል ህጉ አላማ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ባቀረቡት ቅሬታ መነሻነት በስር ፍርድ ቤት ያልተያዘላቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተያዘላቸው ስለሆነ ይህንን ይግባኝ ተብሎ ያልተሻረ ስለሆነ በእርከን 5 ስር ካለው ፍቅድ ስልጣን በወንጀል ህግ ቁጥር 90 መሠረት በማስላት መወሰን ሲገባው አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት የገንዘብ ቅጣት በማክበድ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ጥፋተኛ በተባሉበት የህግ ድንጋጌ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት በማስላት የእስራት ቅጣቱ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሆኖ የገንዘብ ቅጣት በተመለከተ ግን ሊወሰን የሚገባው ቅጣት በእርከን 5 ስር ካለው ፍቅድ ስልጣን በወንጀል ህግ ቁጥር 90 መሠረት መሰላት ስላለበት አመልካች 2000 (ሁለት ሺህ) ብር የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይገባል ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ እና በቅጣት ውሳኔው ላይ ግን ከላይ በተገለጸው ምክንያት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአመልካቹ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 212810 በ03/09/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 178772 በ05/11/2008 ዓ.ም. የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተወሰነው የሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ፅኑ እስራት ቅጣት እንዳለ ተቀብለን ፣ተጥሎ የነበረውን የብር 7,000 (ሰባት ሺህ) መቀጮ የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካቹ ከፅኑ እስራቱ በተጨማሪ 2000 (ሁለት ሺህ) ብር መቀጮ እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
3. ይህንኑ ተገንዝቦ የተሻሻለውን የገንዘብ ቅጣት መሠረት እንዲያስፈጽም ለሚመለከተው አካል የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመሸኛ ትዕዛዝ ጋር ይላክ፡፡
ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ተ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 127312

ግንቦት 23 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-የአ.ብ.ክ.መ. ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ - ዳግማዊ አገኘሁ

ተጠሪዎች፡-1ኛ አቶ እሸቱ ሉሌ ንጉሴ - ቀርበዋል፡፡

2ኛ አቶ ደግዋለ ልክነህ ደርሰህ

3ኛ ወ/ሮ ጥሩዬ ደግዋለ } አልቀረቡም

4ኛ ወ/ሮ ይሳለሙ ደመቀ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የእነማይ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0202415 በቀን 02/04/07 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድና የቅጣት ውሳኔ የምስራቅ ጐጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0213319 በቀን 21/07/2007 ዓ.ም በመሻሩ እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 02-13131 በቀን ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም ይህንኑ በማጽናቱ እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መሠረታዊ የህግ ግድፈት አልተፈፀመም ሲል በሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክስ እንዲሻሻል የተሰጠ ትእዛዝ ውጤትን ይመለከታል፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ /ሀ/ 555 /ለ/ የተመለከተውን ተላልፈው በሌላ ሰው አካል ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው ነሐሴ 9 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2006 ዓ.ም በ12፡00 ሰዓት የግል ተበዳይ ላቃቸው ሞገስን ብቸና ከተማ 01 ቀበሌ ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን 1ኛ ተከሳሽ በጅንፋ ሽመል እየደጋገመ ሲመታው 2ኛ ተከሳሽ በድንጋይ መሐል ራሱን 3ኛ ተከሳሽ ድንጋይ በመወርወር ግንባሩን በመምታታቸው በአካል ላይ ጉዳት አድርሰዋል 4ኛ ተከሳሽ የወ/ህ/ቁ 27/1/ 556/2/ /ሀ/ የተመለከተውን ተላልፈው በተመሳሳይ ቀንና ቦታ ከ1-3 ያሉት ሲመቱት እሷ በድንጋይ ወርውራ የሳተችው በመሆኑ በአካል ላይ ጉዳት ለማድረስ ሞክራለች የሚል ሲሆን ተጠሪዎች በክሱ ላይ በሌላ መዝገብ ታይቶ የተወሰነ ስለመሆኑ መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በ01/03/2007 ብይን ተሰጥቶበታል በማለት አልፎ የግል ተበዳይን ጨምሮ የአመልካችን ሁለት ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ 1ኛ ተጠሪ የወ/ህ/ቁ 556/2//ሀ/፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የወ/ሕ/ቁ. 555/ለ/ እና 4ኛ ተጠሪ በቀረበበት ክስ እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ቢሆንም የተጠሪዎች ጠበቃ ባለመቅረቡ ማስረጃዎቻቸውንም በተከታታይ ቀጠሮዎች አለማቅረባቸውንና ራሳቸውም መሆናቸውን በመግለጽ ጠበቃቸው ሲቀርብ እንዲሰሙ እንዲታዘዝላቸው ተለዋጭ ቀጠሮ የጠየቁ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ህዳር 19፣ ህዳር 29 እና ታህሳስ 1/2007 ተሟልተው አልቀረቡም ጠበቃቸውም አልቀረበም በማለት የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብታቸውን በማለፍ ተከላከሉ በማለት በሰጠው ብይን መሠረት 1ኛ ተጠሪ የወንጀል ህግ ቁጥር 556/2/ /ሀ/ ጥፋተኛ በማለት 4ወር ቀላል እስራት፣ 2ኛ ተጠሪ እና 3ኛ ተጠሪ የወንጀል ህግ ቁጥር 555 /ለ/ ጥፋተኛ በማለት 2 ዓመት ከ4 ወር እና 2ዓመት ከ3ወር እንደቅደም ተከተላቸው እንዲሁም 4ኛ ተጠሪን በ1 ወር ቀላል አስራት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ፍርድ እና የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምስራቅ ጐጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አመልካች የወ/ህ/ቁ 556/2/ /ሀ/ ወደ 555 /ለ/ ለማሻሻል ያቀረበው በብይን ውድቅ ተደርጐ ሳለ በሌላ መዝገብ ክስ ማቅረቡን፣ ይህንኑ መሰረት አድርጎ ተጠሪዎች በቀረበባቸው ክስ ተከላከሉ የተባሉበትን አግባብ እና የመከላከያ ማስረጃ ሳያሰሙ የተሰጠው ፍርድ እንዲሻርልን በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ ፍርድ ቤቱ በመመርመር አስቀድሞ ክስ ቀርቦበት ነበር የተባለውን የእነማይ ወረዳ ፍርድ ቤት መ/ቁ 0202368 እንዲቀርብ በማድረግ መርምሮ አመልካች በተጠሪዎች ላይ አስቀድሞ በመ/ቁ 0202368 በቀላል አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ክስ አቅርቦ ምስክር ከተሰማ እና እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ አመልካች ክሱን በከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ለማቅረብ አሻሽሎ እንዲያቀርብ ጠይቆ ፍርድ ቤቱ ምክንያቱን ባለመቀበል ውድቅ በማድረግ የአመልካቾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲሰማ ያዘዘ ቢሆንም አመልካች ክሱን አንስቶ በሌላ መዝገብ ቁጥር 0202415 አዲስ ክስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን ጭብጥ በመመርመር ክስ ማንሳትና ማሻሻል ለአመልካች በህግ የተሰጠው ቢሆንም ክሱን መቀጠል ያለበት ግን በተዘጋው መዝገብ ላይ እንዲቀጥል እንጂ አዲስ ክስ መዝገብ ተከፍቶበት የሚቀርብ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ተቃውሞ ያለፈበት ምክንያት የህግ መሠረት የለውም፣ የተጠሪዎች የመከላከያ ምስክሮች መጥሪያ ደርሷቸው ያልቀረቡና በፖሊስ አማካኝነት እንዲቀርቡ ታዞም ካለመቅረባቸውም በላይ ጠበቃቸው ባለመቅረቡ ተለዋጭ ቀጠሮ ተጠይቆ ከወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 94 አንፃር ማየት ሲገባው ፍ/ቤቱ የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብታቸውን ማለፉ ተገቢነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮ አመልካች በቀድሞው መዝገብ እንዲቀጥል አዟል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ያቀረበው ይግባኝ የተመለከተው የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናቱ መሠረታዊ ስህተተ ተፈጽሟል በማለት ለአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት የቀረበውም በዚሁ ምክንያት ሲሆን ይዘቱም ዐቃቤ ህግ ከውሳኔ በፊት በማናቸውም ጊዜ ክሱን አሻሽሎ ለማቅረብ የሚከለክለው ህግ ባለመኖሩ ከቀረበው ማስረጃ አንጻር ተመጣጣኝ ድንጋጌ ጠቅሶ ማቅረቡ ተገቢ ነው በሰበር መ/ቁ 57632 ተመላክቷል፡ የወረዳ ዐቃቤ ህግ የህክምና የመጨረሻ ውጤት ሳይጠበቅ ተቀራራቢነት በሌለው አነስተኛ ድንጋጌ ክስ ማቅረቡ ፍትህን ስለሚያዛባ ድንጋጌው ተሻሽሎ ክስ መቅረቡ የተጣሰ ህግ የለም ስለመሆኑም የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ተሽሮ የወረዳው ይጽናልኝ የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሠረት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ መልስ የሰጡ ሲሆን 3ኛ እና 4ኛ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም ዓቃቤ ህግ ክሱን ከውሳኔ በፊት በማንኛውም ጊዜ የማንሳት መብት ቢኖረውም ይህንን መብት ግን ያለአግባብ ሊጠቀምበት አይገባም፣ በሰበር መ/ቁ 57632 በሌለበት የተሰጠ ውሳኔን እንጂ ከዚህ ጉዳት ጋር አይያያዝም፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት ወረዳው የሻረው የወንጀል ህግ አንቀጽ 556 ወደ 555 ለምን ተቀየረ በሚል ሳይሆን በተለየ መዝገብ ክስ መቅረቡን መሰረት በማድረግ ነው ስለሆነም የአመልካች አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ፍርድ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረነዋል እንደመረመርነውም በዋናነት ምላሽ የሚሻው የክርክሩ ጭብጥ ዐቃቤ ህግ አመልካች በተጠሪዎች ላይ አቅርቦት የነበረው ክስ የተጠሪዎች የመከላከያ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ክሱን እንዲያሻሽል የቀረበው አቤቱታ በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት በማጣቱ ክሱን ካነሳ በኋላ በሌላ መዝገብ ለማሻሻል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባቀረበው ምክንያት ውጤት መሠረት አዲስ ክስ ማቅረብ የሚችልበት አግባብ ከወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ዓላማ አንጻር መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0202368 የወ/ህ/ቁ 556 ተላልፈው ቀላል የአካል ጉዳት አድረሰዋል በማለትበቀረበው ክስ ማስረጃዎቹን አሰምቶ እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ አመልካች ክሱን ለማሻሻል ያቀረበውን አቤቱታ ፍርድ ቤቱ ባለመቀበሉ የመከላከያ ምስክሮች ከመሰማቱ በፊት ክሱን በማንሳቱ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች በሌላ መዝገብ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0202415 በተጠሪዎች ላይ የወ/ህ/ቁ555 እና 27/1/ /ሀ/ 556 የተመለከተውን ተላልፈዋል በማለት አዲስ ክስ አቅርባል፡፡ ተጠሪዎቹ መቃወሚያ ቢያቀርቡም ውድቅ ሆኖ ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤት ተሠጥቷል፡፡

በመሠረቱ በተከሳሽ ላይ በቀረበ የወንጀል ክሰ ዋና ስህተት ወይም ያልተጠቀሰ ነገር ሲኖር ይህም ክሱ የቀረበበትን ተከሳሽን የሚያሳስት ወይም ያሳሳተ በመሰለ ጊዜ /የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 118/ በክሱ መሠማት ወቅት ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤቱ በራሱ ጊዜ ወይም ከተከራካሪ ወገኖች በሚነሳ አስተያየት ቀርቦ የነበረው የወንጀል ክስ እንዲለወጥ ወይም እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ለመስጠት እንደሚችል በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 119/1/ ተመልክቷል፣፣ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው ፍርድ ቤቱ በራሱ ወይም ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ በሚያቀርበው ማመልከቻ መሠረት እንደነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ትእዛዝ የሚሰጥ ስለመሆኑ ነው፡፡ ይህ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ትእዛዝ የማሻሻል ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የተሰጠ ከሆነ ደግሞ የመጨረሻ በመሆኑ ይግባኝ ሊባልበት የሚገባ ስለመሆኑ በሰበር መ/ቁ 93234 አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

በዚህ በያዝነው ጉዳይ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በቅድሚያ በመ/ቁ 0202368 በወረዳው ፍርድ ቤት በቀረበው ክስ ላይ ክሱን ለማሻሻል ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሲያጣ አመልካች ይግባኝ በማለት በበላይ ፍርድ ቤት ሊያሳርም አልሞከረም፡፡ በይግባኝ በበላይ ፍርድ ከማሳረም የቀረበውን ክስ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 122/ለ/ መሠረት ክሱን የማንሳት እና ለዚያው ፍርድ ቤት በሌላ መዝገብ በመ/ቁ 0202415 አዲስ ክስ በማቅረብ ለማሻሻል ለፍርድ ቤቱ አቅርቦ ያጣውን መብት ክሱን በማንሳት አዲስ ክስ በማቅረብ ክርክሩ እንዲቀጥል የሆነ መሆኑን ነው መዝገቡ የሚያስረዳው፡፡

የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ ዋነኛ ዓላማ የወንጀል ህጉ በተግባር የሚተረጉምበትን ሥርዓት በመዘርጋት በህጉ ላይ የተመለከቱ ወንጀሎች ተፈጽመው በሚገኙ ጊዜ እውነት በማውጣት ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ፍትሐዊ የወንጀል ፍትህ ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል ነው፡፡ ከሥነ-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥርዓት ሕጉ ውጪ በሆነ አካኋን ተመርምሮና ክርክር ተካሂዶ የሚሰጥ ፍርድ በህገ-መንግስታችን አንቀጽ 20 የተረጋገጠውን በተገቢ አጭር ጊዜ ፍትህ የማግኘት መብት ያጓደለ ነው የሚሆነው፡፡

አመልካች ክሱን ለማሻሻልም ሆነ ለማንሳት ብሎም በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ለመቅረብ ምክንያት የሚያደርገው የወረዳው ዐቃቤ ህግ የህክምና የመጨረሻ ውጤት ሳይቀርብ ክሱን በማቅረቡ በቀላል አካል ጉዳት ክስ የቀረበ ቢሆንም አሁን የህክምና ማስረጃ የደረሰ በመሆኑ ነው ክሴን ላሻሽል የሚል ነው፣ ይህ ሁኔታ አይኖርም ባይባልም መፈጸም ያለበት ግን በሕግ በተዘረጋ ሥርዓት ነው፣ በመሰረታዊነት ያላለቀ ምርመራ ላይ ክስ አይቀርብም.፣ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 40/1/ ዐቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ ክስ ለማቅረብ በቂ ምክንያት መኖሩን ከተረዳ ክስ የሚያቀረብና ከዚህ በፊት ግን ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንዳያጋጥሙ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 38፣ 41 እና ተከታዮቹ መሰረት መፈጸም የሚገባው ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች በቅድሚያ ያቀረበው ክስ ላይ ማስረጃዎቹን ካሰማና እንዲከላከሉ ታዞ የክሱ መሰማት በቀጠለበት ሂደት ላይያቀረበው ክስ ማሻሻል አቤቱታ ተቀባይነት ሲያጣ ይህንን በህጉ አግባብ በይግባኝ ከማሳረም ክሱን በማንሳት በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ማቅረቡ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምንም የሥነ-ሥርዓት ህጉን ዓላማ ያልጠበቀ እና የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ ያላከበረ በመሆኑ ተገቢውን ፍትህ ሊያሰጥ የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የምስራቅ ጉጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና በበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ መሠታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ያላገኘነው በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1/ የእነማይ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0202415 በቀን 02/04/07 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በመሻር የምስራቅ ጉጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0213319 በቀን 21/07/2007 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 02-13131 ህዳር 29 ቀን 2008 ዓ.ም እና አብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መ/ቁ 55406 መጋቢት 5 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጡት ትእዛዝ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ. 110736

ሠኔ 23 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻውአዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-አብዲ ኡመር ሰዒድ

ተጠሪ፡-የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 22 ቀን 2009 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ.ቁ 07770 እና 08155 በመሠረተበት ክስ መነሻነት በድምሩ የ16 ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት የተላለፈበት መሆኑን፤በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 104839 እና 105180 ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም በሁለቱም መዝገቦች ውሳኔው የጸናበት መሆኑን፤በመቀጠልም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትበመ.ቁ 110735 እና 110736 አቤቱታ ያቀረበ መሆኑን፤በመ.ቁ 110735 ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የጸና መሆኑን፤በመ.ቁ 110736 ያቀረቡት አቤቱታ ተመርመሮ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ አመልካች በአምስት ዓመት ከሥድሥት ወር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ እና በበታች ፍ/ቤቶች የተላለፈበት የብር 3,000 / ሦስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ አልተነካም በማለት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን በመግለጽ በመዝገቦቹ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ በአንድ ጊዜ ቢወሰንበት ኖሮ ሊወሰን ይችል ከነበረው ከፍተኛ ቅጣት ሳያልፍ ይጣመርለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ፍ/ቤት አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ላይ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጥበት በፖስታ ቤት መጥሪያ የላከለት ቢሆንም ተጠሪ ቀርቦ የሰጠው አስተያየት የለም፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ.ቁ08155 በተመሰረተበት የካናቢስ ዕጽ ማከማቸት እና ለሽያጭ ማቅረብ ወንጀል ክስ የተላለፈባበት የዘጠኝ ዓመት ጽኑ እሥራት እና የብር 20,000 /ሐያሺ ህ ብር / የገንዘብ መቀጮ ላይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 105180፤በመቀጠልም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 110735 አቤቱታ አቅርቦ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የጸና መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ.ቁ. 07770 በተመሰረተበት የካናቢስ ዕጽ ማከማቸት እና ለሽያጭ ማቅረብ ወንጀል ክስ በሰባት ዓመት ጽኑ እሥራት እና በብር 3,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፤አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ104839 ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔውን ያጸናው መሆኑን፤አመልካች በመቀጠል ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ መዝገብ /የመ.ቁ 110736 / አቤቱታ አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ሕዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካች በአምሥት ዓመት ከሥድስት ውር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ እና በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው የብር 3,000 /ሦስት ሺ ብር / የገንዘብ መቀጮ አልተነካም በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 96505 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) በአንድነት ተጣምረው መታየት የነበረባቸው የወንጀል ክሶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች በተወሰኑ ጊዜ እንደገና በአዲስ መልክ እያንዳንዱ ቅጣት ተሰልቶና የቅጣት ማቅለያዎች ሁሉ ታይተው የሚወሰን ሳይሆን ሕጉ ጥፋተኛው በፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ጊዜ ቢፈረድበት ኖሮ ሊወሰንበት ይችል ከነበረው ከፍተኛ ቅጣት ሳያልፍ እንደሚወሰን የሚያስረዳ መሆኑን፤ ስለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን የሚመለከተው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184(1)(ለ)"ም" ሲታይም ጥፋተኛው ተደራራቢ ወንጀሎች ፈፅሞ በተገኘ ጊዜ በተደራራቢነት ለተፈፀሙ ለእያንዳንዱ ወንጀል በተናጠል ተገቢው የቅጣት መጠን ተወስኖ የሁሉም እንደሚደመር እና ቅጣቶችም ተደምረው ለወንጀሉ አይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት መብለጥ እንደማይችል በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1 መሠረት በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ አመልካች በተለያዩ መዝገቦች ላይ ቅጣት የተላፈለበት በመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት ቅጣቶቹ ተጣምረው ሊወሰኑ የሚገባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠባቸው የመ.ቁ 08155እና 110736 በሆኑት መዝገቦች በሁለቱም የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተደምሮ መወሰን የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም አመልካችየመ.ቁ 08155 በሆነው መዝገብ የተላለፈበት የዘጠኝ ዓመት ጽኑ እሥራት እና የብር 20,000 /ሐያ ሺህ ብር / የገንዘብ መቀጮ እና በዚህ መዝገብ / የመ.ቁ 110736 / በሆነው መዝገብ የተላለፈበት የአምሥት ዓመት ከሥድስት ወር ጽኑ እሥራት እና የብር 3,000 / ሦስት ሺህብር / የገንዘብ መቀጮ ተደምሮ አመልካች በአሥራ አራት ዓመት ከሥድሥት ወር ጽኑ እሥራት እና በብር 23,000 / ሐያ ሦስት ሺህ ብር / ሊቀጣ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

የድሬዳዋ ማረሚያ ቤት በዚህ መዝገብ ተደምሮ በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሠረት የእሥራት ቅጣቱን እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ 134834

ሠኔ 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነው

ሽምሱ ሲርጋጋ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ - ዐ/ሕግ ውብሸት ይመኑ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ሽዋነሽ መንግሥቱ ቀረቡ

2. ወንድአፍራሽ ፍቅሩ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የይግባኝ ማስፈቀጃን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረውን ክስ በሚመለከት ፍ/ቤቱ 1ኛ ተጠሪን ከ2ኛ ክስ፤ 2ኛ ተጠሪን ከ2ኛ እና ከ6ኛ ክስ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነጻ እንዲሰናበቱ በማለት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም ብይን ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል በመዝገቡ ላይ የቀረቡትን ሌሎች ክሶች በተመለከተ ክርክሩ ቀጥሎ ታሕሳስ 13 ቀን 2007 ዓ.ም ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሥር ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ብይን እና በዋናው ጉዳይ ላይ በሰጠው ፍርድ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ስሚ ችሎት ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም ብይን ከሰጠ በኋላ አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ እንዲችል ሐምሌ 25 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ግልባጭ እንዲሰጠው የጠየቀ ሲሆን ለተጠሪዎች የብይኑ ግልባጭ የተሰጣቸው ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች የመዝገብ ግልባጭ የተሰጠን ታሕሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም ነው በማለት ያቀረበው ምክንያት የሚታመን አይደለም፤ አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ጊዜው ሳያልፍ የይግባኝ ቅሬታ ማቅረብ ሲገባው ያለበቂ ምክንያት ዘግይቶ ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኙን ያቀረበ በመሆኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው ይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የሥር ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና በመዝገቡ የተደረገው ሙሉ ክርክር ግልባጭ የተሰጠን ታሕሳስ 22 ቀን 2006 ዓ.ም ነው፤ በዚሁ መሠረት የይግባኝ ቅሬታችንን አዘጋጅተን ጥር 15 ቀን 2007 ዓ.ም ባቀረብንበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የብይኑ ግልባጭ ለተጠሪዎች የደረሰው ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ምክንያት የሚታመን አይደለም በማለት አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜ ያለፈበት ነው በማለት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም የግራቀኙን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 187/1 ድንጋጌ ይግባኝ ማለቱን ለማስታወቅ የሚጽፈውን ማመልከቻ ይግባኝ ባዩ ወይም ጠበቃው ይግባኝ የሚልበት ፍርድ በተሰጠ በአሥራ አምሥት ቀን ውስጥ ማቅረብ አለበት፤ ይግባኝ ማለቱን ለማስታወቅ የጻፈው ማመልከቻ ለፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ሲደርሰው ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ አስገልብጦ ለይግባኝ ባዩ ወይም ለጠበቃው ይሰጣል፤ ይግባኝ ባዩ በእሥር ቤት ያለ እንደሆነ ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ ግልባጭ የፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ለይግባኝ ባይ እንዲሰጥ ለወህኒ ቤቱ ሹም ይልካል፤ ፍርዱ ተገልብጦ ያለቀበትን ቀን እና ኋላም ለይግባኝ ባዩ ወይም ለጠበቃው ወይም ለወህኒ ቤቱ ሹም የደረሰበትን ቀን የፍርድ ቤት መዝገብ ሹም በፊርማው ያረጋግጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ሕግ ንኡስ ቁጥር 2 ድንጋጌ ይግባኝ ማለት የሚፈልገው ወገን ይግባኙን የፍርዱ ግልባጭ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት መዝገብ ቤት ማቅረብ እንዳለበት ይደረግጋል፡፡ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ መጠየቅ የሚፈልገው ወገን ይግባኝ የሚልበት ፍርድ በተሰጠ በአሥራ አምሥት ቀን ውስጥ ይግባኝ የሚጠይቅ መሆኑን በመግለጽ ማመልከቻ ማቅረብ ያለበት መሆኑን፤ የፍርድ ቤቱ መዝገብ ሹም ይግባኝ መጠየቅ የሚፈልገው ወገን ያቀረበው ማመልከቻ ሲደርሰው ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ አስገልብጦ ይግባኝ መጠየቅ ለሚፈልገው ወገን ማድረስ ያለበት መሆኑን፤ ይግባኝ ማለት የሚፈልገው ወገን የፍርዱ ግልባጭ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ይግባኙን ማቅረብ ያለበት መሆኑን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሥር ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግ በመግለጽ በሕጉ የተገለጸው የአሥራ አምሥት ቀን ጊዜ ሳያልፍ ሐምሌ 25 ቀን 2006 ዓ.ም ይግባኝ መጠየቅ እንደሚፈልግ ገልጾ ግልባጭ የጠየቀ ለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ጽ/ቤት መጋቢት 26 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው ብይን ለአመልካች የደረሰው በመዝገቡ ላይ ጠቅላላ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ታሕሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜው ያለፈበት ነው ከሚል መደሚደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው ተጠሪዎች የብይን ግልባጭ የደረሳቸው ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች የብይኑ ግልባጭ የተሰጠኝ ታሕሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የሚታመን አይደለም በማለት ነው፡፡ አመልካች በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ እንደሚፈልግ በመግለጽ ግልባጭ እንዲሰጠው በጠየቀበት ሁኔታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ጽ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው ብይን ለአመልካች የደረሰው በመዝገቡ ላይ ጠቅላላ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ታሕሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም ነው በማለት ባረጋገጠበት ሁኔታ፤ አመልካች የክርክሩን ሙሉ ይዘት የሚያሳይ የመዝገብ ግልባጭ ሳይደርሰው ይግባኝ መጠየቅ በማይችልበት ሁኔታ፤ አመልካች ግልባጭ እንዲሰጠው በጠየቀበት ቀን እና የመዝገቡ ግልባጭ ለአመልካች በደረሰበት ቀን መካከል ያሉት የባከኑ ቀናት በአመልካች ጥፋት ምክንያት ባልባከኑበት ሁኔታ፤ አመልካች የመዝገቡ ግልባጭ ታሕሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም ደርሶት በሕጉ የተቀመጠው የሠላሳ ቀን የጊዜ ገደብ ሳያልፍ ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም ይግባኙን አዘጋጅቶ ባቀረበበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት የብይኑ ግልባጭ ለተጠሪዎች የደረሰው ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ነው በሚል ምክንያት አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜው ያለፈበት ነው በማለት የሰጠው ብይን በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የይግባኝ አቀራረብን አስመልክቶ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡"በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 109183 ሕዳር 05 ቀን 2009 ዓ.ም አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተጠሪዎች ላይ በሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜው ያለፈበት ነው በማለት የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተጠሪዎች ላይ በሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜው ያላላፈበት ነው በማለት በወንጀል ሥነ-ሥርዓት 191/4 መሠረት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜው ያላላፈበት በመሆኑ ይህ ውሳኔ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አሥር ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለሚመለከተው ፍ/ቤት ያቅርብ ብለናል፡፡

መዝገበ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 122766

ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ሄኖክ ብሩክ አረጋ ጠበቃ እንዳለ ክፍሌ

ተጠሪ፡-ፌዴራል ዓ/ህግ መሰረት ሙላቱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ የመሠረተው የወንጀል ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/ህ/አንቀጽ 539(1(ሐ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ የፈፀመው የአስገድዶመድፈር ሙከራ ወንጀል እንዳይገለፅበት ለማድረግ አስቦ ጥር 14 ቀን 2005 ዓ/ም በግምት ከጠዋቱ 2፡50 ሲሆን በን/ላ/ክ/ከ/ቀበሌ 12/13 ልዩ ቦታው ሸገር ማህበር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ከሚገኘው የመኖሪያ ቤት ውስጥ ሟች መዝገበ ክበበው ወይም አባቷ ባወጣላት ስሟ አለምፀሃይ ብሩክ የተባለችው እድሜዋ 13 አመት የሆነችውን ህፃን አስገድዶ መድፈር ሙከራ ወንጀል ከፈፀመባት በኋላ ሟች የፈፀመባትን ድርጊት ለአባትህ እነግርልሃለሁ ስትለው በመጀመሪያ አንገቷን ካነቃት በኋላእጆታው እንጨት በሆነ ቢላዋጨካኝነቱን በሚያሳይ ሁኔታ አንገቷን አርዶ በመግደሉ ክስ የቀረበበት ሲሆን ሁለተኛው ክስየወንጀል ህግ አንቀፅ 27/620(2(ሀ))የተመለከተውን ተላልፎ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ከግል ተበዳይ ጋር የግብረስጋ ግንኙነት ለመፈፀም አስቦየግል ተበዳይ እድሜዋ 13አመት የሆነችውን ህፃን በእጁ አፍኗት ወለል ላይ ወድቃ ራሷን እንድትስት ካደረጋት በኋላ ለብሳው የነበረው ቱታና ፓንት አንድ ላይ በማውለቅ የግብረስጋ ግንኙነት ሊፈፅምባት ሲል ቆሞ የነበረው ብልቱ በመቀዝቀዙ ፣አመልካች በቀኝ እጁ ጣት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብልቷን በመነካካት የግብረስጋ ግንኙነት ለመፈፀም የሞከረ በመሆኑ 18 አመት ባልሞላት ህፃን ላይ አስገድዶ መድፈር ሙከራ ፈፅሟል በሚል ክስ ቀርቦበታል፡፡ ሶስተኛው ክስ የወንጀል ህግ አንቀፅ 654 የተመለከተው በመተላለፍ በአንደኛው ክስ በተገለፀው ጊዜና ስፍራ የአጉቱ ልጅ ለሆነችውየግል ተበዳይ ጋር የግብረስጋ ግንኙነት ለማድረግ መሞከርወንጀል ተከሷል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በዓቃቤ ሕግ የቀረበበትን ሶስት ክሶች በጠበቃው እየታገዘ ተቃውሞ አቅርቦበብይን ከታለፈ በኋላ ስለድርጊቱ ሲጠየቅ ድርጊቱን እንደፈፀመ አምኖ ድርጊቱን ሲፈፅም ራሴን ስቼ ስለነበር ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት በመከራከሩ ማስረጃዎች ቀረበው ከተሰሙ በኋላ ሶስተኛው ክስ በተመለከተአመልካችና የግል ተበዳይ (ሟች) የስጋ ዝምድና ያላቸው ስለመሆኑ ዓ/ህግ አላስረዳም በማለት አመልካች በአንደኛና ሁለተኛው ክሶች ፍርድቤቱ እንዲከላከሉ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡መከለከያ ምስክር አቅርቦም አሰምቷል፡፡ፍ/ቤቱ የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ የዓ/ቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ማስተባበል ያለቻሉ በመሆናቸው አመልካች በተከሰሰበት ሁለቱም የሕግ አንቀፆች ሥር ጥፋተኛ ተብሎዋል፡፡ በቅጣት ረገድም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት በማድረግ የወንጀሉ ደረጃ እና መነሻ ቅጣት እርከን በመለየት ተከሳሹ ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ቀርቦበት፣ሁለት ቅጣት ማቅለያ ምክንያት የተያዙለት በመሆኑ፣ ምክንቶቹ እርስበርሳቸው የሚዋዋጡ በመሆኑ ከተያዘው መነሻ ቅጣት ከፍ ወይም ዝቅ የሚልበት ምክንያት አልተገኘም በማለት አመልካችን በእድሚ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ቅሬታው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ቅሬታው ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው ቅሬታ መሰረታዊ ይዘት ወንጀሉ የተፈፀው በነበረኝ የመንፈስ ጭንቀት በድንገተኛ አጋጣሚ አእምሮየን ስቼ እያለሁ የተፈፀመ እንጂ ቂም በቀልበመያዝ ወይም ወንጀል ለመፈፀም አስቤና ተዘጋጅቼ በጨካኝነት የፈፀምኩት ባለመሆኑ ዓ/ህግ ክስ ሲያቀርብ ተገድጄ በሰጠሁት እምነት ቃል ተመስርቶ እንጂ በሌላ ማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ የተጠቀሰብኝ የህግ አንቀፅና የወንጀል ዝርዝሩ ተጣጥሞ ክሱ በወንጀል ህግ አንቀፅ 540(1)ማቅረብ ነበረበት፡፡ ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ የነበረውእድሜዬ 16 አመት እንጂ 19 አመት አልነበረም፡፡የወንጀል ድርጊቱን ከመፈፀሜ በፊት የመንፈስ ጭንቀት በፈጠረብኝ ምክንያት የአእምሮ ችግር ያለብኝ መሆኑ በስርፍርድ ቤት አመልክቼ ሳይታይ ታልፎየተሰጠው ውሳኔ ነው በማለት እንዲታረምለት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች የአእምሮ በሽተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም ። አመልካች ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ እድሜው 19 አመት ስለመሆኑ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የቀረበው ማስረጃ ተረጋግጧል። ቅጣት በተመለከተ የቅጣት መነሻው እርከን 39 ከተያዘ በኋላ በማንዋሉ መሰረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሶስት እርከን ቢቀነስ ተቃውሞ የለንም በማለት መልስ ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባው፡-

1. በአመልካቹ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

2. በአመልካች ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት? ወይስ የለበትም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንፃር መርምረናል።

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ፡- አመልካች የእምነት ክደት ቃል ሲጠየቅድርጊቱን እንደፈፀመ አምኖ ድርጊቱን ሲፈፅም ራሴን ስቼ ስለነበር ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ቃሉን ያስመዘገበ ቢሆንም በወቅቱ በስር ተከሳሽ የሚያቋቋም ነው ተብሎ ጥፋተኛ የተባለበት በቀረቡት የዓ/ህግ ማስረጃ አመልካች ሚችን በግፍ የገደላት ስለመሆኑ እንዲሁም አስገድዶ ለመድፈር የሞከረ ስለመሆኑ፣የአመልካች እድሜ በሚመለከትምየቀረበው የሃኪም ማስረጃ ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ አመልካች እድሜ 19 አመት የነበረ ስለመሆኑ፣በወቅቱ የአእምሮ ችግርነበረኝ በማለት የተከራከረ ቢሆንም ወንጀሉ ሲፈፅም የአእምሮ ችግር የነበረበት ስለመሆኑ በህግ አግባብ ተደግፎ የቀረበ ምንም አይነት ማስረጃ አለመኖሩ ተረጋግጦና የአመልካች የመከላከያ ማስረጃዎችአመልካች ድርጊቱን ስላለመፈፀሙየምስክሮቹ ቃል ያረጋገጣል ሊያስብል የሚችል አለመሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው።

እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ድርጊቱን ፈፀመ በማለት ድምዳሜ የደረሱትየአመልካች ድርጊቱን ስለመፈፀሙ የአቃቤሕግ ምስክሮች በሚገባ ተረጋግጧል፣አመልካች በመከላከያ ማስረጃው አልተደገፉም በሚል ምክንያት ነው።አመልካች ከሚከራከርባቸው ነጥቦች ውስጥ የአመልካችን የድርጊት ፈጻሚነት በተገቢው መንገድ አቃቤ ሕግ በማስረጃ ያለማስደገፉንና የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አመልካች በመከላከያ ምስክሮች የማስተባበላቸው ሁኔታን የሚመለከቱ ነጥቦች የሚገኙ ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ስር የተመለከተውን የማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምዘና መርህ ተከትለው አመልካችን ጥፋተኛ ያደረጉ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳየን ሁኖ አግኝተነዋል፡፡በመሆኑም ከዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች ጥፋተኛ የተባለው በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ተመዝነው መሆኑን ነው፡፡እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘን ጉዳይ ማረም የሚችለው በውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ተመልክቷል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ይህ ሰበር ችሎት ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡በተያዘው ጉዳይም አመልካች አጥብቆየሚከራከርባቸው ነጥቦች የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን መሰረት ያደረጉ ሳይሆን የፍሬ ነገርንና የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው በዚህ ችሎት ሊታዩ የሚችሉ ሁነው አላገኘናቸውም፡፡

በመሆኑም አመልካች የአቃቤ ሕግማስረጃዎች በመከላከያ ማሰረጃቸው ባላስተባበሉበት ሁኔታ ወንጀል ለመፈፀሜ አልተረጋገጠም በማለት የሚያቀርበው ቅሬታና ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡አመልካች ለድርጊቱ ኃላፊነት አለበት ተብሎ የተወሰነው ወንጀሉ መሰራቱ ወይም መፈጸሙና ተሰራ ወይም ተፈጸመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በአመልካች መፈጸሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በተረጋገጠበት ሁኔታ በመሆኑና ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4)፣27(1(ሀ)፣620(2(ሀ))፣58 እና 539(1(ሐ)) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያሟላ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሁለተኛው ነጥብ፡- ቅጣትን መሰረት አድርጎ ወደቀረበውና በአቢይ ጭብጥነት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካች መሠረታዊ ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ያስተላለፉት የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ቅጣት ውሳኔ የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ያስቀመጣቸውን መርሆዎች ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ቅጣት ሲወስኑ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ሁለት ድንጋጌዎች ውስጥ ለወንጀል ህግ ዓንቀፅ 539(1(ሐ))ከባድ የግፍ መግደል ወንጀል የእድሜልክ ፅኑ እስራት በመውሰድ ፣ ለሁለተኛው ክስ አስገድዶ መድፈር ወንጀል ሙከራ በ15 አመት ፅኑ እስራት የመነሻ ቅጣት እንዲቀጣ ከወሰነ በኋላ በተከሳሽ ላይ ሁለቱም ክሶች የተወሰነበት ቅጣት በወንጀል ህግ አንቀፅ 184(1(ለ)) ሲደመሩ በህጉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት የሚበልጥ ሆኖ ስላገኘው በአንደኛው ክስ የተወሰነው እድሜ ልክ ፅኑ እስራት የሚጠቃለል በመሆኑ ለሁለቱም የህግ ድንጋጌዎች ይህንኑ መነሻ ቅጣት መወሰኑ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ፍርድ ቤቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ቅጣት የወሰነ መሆኑ በመግለፅ የመጨረሻ ቅጣት ሲያስቀምጥም በከሳሽ ዓ/ህግ በኩል የቀረበ ሁለት ቅጣት ማክበጃዎች እንዲሁም በአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኩል የቀረበና ፍርድ ቤቱ የተቀበላቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች እንደተቀበለ በመግለፅ የእድሜ ልክ ፅኑ እስራትአመልካች እንዲቀጣውሳኔ ሰጥቷል፡፡ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበው ይግባኝ ሲያፀና የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱን ከመመሪያው በመውጣት መወሰን የነበረበት መሆኑ በመግለፅ ያፀና መሆኑ ከቀረበው የመዝገብ ግልባጭ ለመረዳት ችለናል፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 187 ድንጋጌ የሚወሰነው ቅጣት ከወንጀል ሕጉ አላማና ግብ ጋር በተጣጣመ መልኩ የጥፋቱን ከባድነት በማመዛዘን በድንጋጌዉ ከተወሰነዉ የቅጣት ጣራ ሳያልፍ ቅጣት ሊወሰን እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡እንዲሁም መመሪያው በወንጀል ሕጉ ስለቅጣት አወሳሰን ከተደገጉት ድንጋጌዎች ጋር ተጣጥሞ መተርጎም እንደሚገባው በአንቀጽ 4(9) ስር ተመልክቷል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ “የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው” በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወሰነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሰን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ከላይ እንደተገለጸው ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ደረጃ ላልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎች ደረጃ የሚወጣበትን አግባብ በመመሪያው በአንቀጽ 13 ከማስቀመጡ በተጨማሪ በ አንቀጽ 21/1/ መሠረት የወንጀል አፈጻጸሙ ሆነ ባህሪዉ በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ መሠረት ለመወሰን የማያስችል ሆኖ ሲገኝ ወይም ቅጣቱ ፍትሕን የሚያዛባ ነዉ ብሎ ፍ/ቤቱ ካመነ መመሪያዉን ተግባራዊ ለማድረግ ያልቻለበትን ምክንያት በዝርዝር በማስቀመጥ በመመሪያዉ ላይ ከተቀመጠዉ በተለየ መልኩ ቅጣት ሊወስን ይችላል በማለት አስቀምጧል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባለበት ሁለት የህግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነሱም የወንጀል ህግ ዓንቀፅ 539(1(ሐ)) ተከሳሽ የራሱ ክፉ ስራ እንዳይገለፅ በማሰብ እድሜዋ 13 አመት የሆነችውን ህፃን አስቃቂ በሆነ ሁኔታ አንገትዋን አርዶ መግደሉ ለዚሁ ወንጀል መነሻ ቅጣቱ እድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም ሞት ቅጣት መሆኑ፣ የወንጀል ህግ ዓንቀፅ 620(2(ሀ))ደግሞ እድሜዋ አስራ ሶስት አመት በሆናት ህፃን ልጅ ላይ የተፈፀመ በመሆኑ ቅጣቱ ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እነዚህ ሁለት የተለያዩ ወንጀሎች የፈፀመው አመልካች ላይ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት ቅጣት ለመወሰን በወንጀል ህግ አንቀፅ 184(1(ለ)) መደመር የግድ ይላል፡፡

የስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ቅጣት ሲወስን አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ሁለት ድንጋጌዎች ለወንጀል ህግ ዓንቀፅ 539(1(ሐ))ከባድ የግፍ መግደል ወንጀል የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት በመውሰድ ለሁለተኛው ክስ አስገድዶ መድፈር ወንጀል ሙከራ በ15 አመት ፅኑ እስራት የመነሻ ቅጣት እንዲቀጣ ከወሰነ በኋላ በተከሳሽ ላይ ሁለቱም ክሶች የተወሰነበት ቅጣት በወንጀል ህግ አንቀፅ 184(1(ለ))ሲደመር በህጉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት የሚበልጥ ሆኖ ስላገኘው በአንደኛው ክስ የተወሰነው እድሜ ልክ ፅኑ እስራት የሚጠቃለል በመሆኑ ለሁለቱም የህግ ድንጋጌዎች ይህንኑ መነሻ ቅጣት ይሏል፡፡በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት የቅጣቱን ለማስላት የተያዘው የመነሻቅጣት በመመሪያው አባሪ አንድ ላይእርከን 38 ላይ የሚያርፍ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በተቀበላቸው ሁለት ማክበጃ ምክንያቶት ሁለት እርከን ሰለሚጨምር እና መመሪያው አባሪ አንድ እስከ እርከን 39 ብቻ እንጂ ከዚህ በላይ እርከን አርባ አልተቀመጠም፡፡

ስለሆነምአመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ሁለት ድንጋጌዎች በወንጀል ህግ አንቀፅ 184(1(ለ)) ሲደመር በህጉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት የሚበልጥ ሆኖ በመገኘቱ ፣ በአንደኛው ክስ የተወሰነው እድሜ ልክ ፅኑ እስራት የተጠቃለለ ከመሆኑ በተጨማሪ ቅጣቱ ሲሰላ በቀረቡት ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በመመሪያው ከተቀመጠው እርከን በላይ ሰለሚሆን ይህንን ጉዳይ የወንጀል አፈጻጸሙ ሆነ ባህሪዉ እንዲሁም ከተፈፀመው ወንጀል ክብደት አንፃር ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ መሠረት ለመወሰን የማያስችል በመሆኑ ከላይ በተገለፁት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያቶች መነሻነት የያዝነው ጉዳይ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ሲወሰን ለተፈፀመው ወንጀል ተመጣጣኝ ቅጣት ለመወሰን ሰለማይቻል፤የሚሠጠው ቅጣትአመልካች የፈፀማቸው ሁለት ከባድ ወንጀሎች በመሆናቸው፣ፍትህን ስለሚያዛባእንዲሁም ስለወንጀል ህጉ ግብና አላማ የማያሳካ ስለሚሆን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 21/1/ መሠረት ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው ውጪ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በተገለፀው ምክንያት መነሻነትየስር ፍርድ ቤት የቀረበለት ጉዳይ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት ሊሰላ የማይቻል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ በመውጣት የቅጣት ውሳኔው መወሰን ሲገባው የሰጠው የቅጣት ውሳኔ በመሆኑ ሊስተካከል የሚገባው ነው ብለናል፡፡ስለሆነም አመልካች ጥፋተኛ ለተባለበትየህግ ድንጋጌዎች፡-የአስገድዶ መድፈር ሙከራ ተግባር የተፈፀመው እድሜዋ አስራ ሶስት አመት በሆናት ህፃን ልጅ ላይ በመሆኑ ፣ እንዲሁም አመልካች የራሱ ክፉ ስራ እንዳይገለፅ በማሰብ እድሜዋ 13 አመት የሆነችውን ህፃን አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ አንገትዋንካነቃት በኋላ እጆታው እንጨት በሆነ ቢላ አንገትዋን አርዶ መግደሉጨካኝነት እና ነውረኝነቱን የሚያሳይ ተግባር ነው፡፡ አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሁኖ ከተገኘ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ያለበት ስለሆነ የሚጣለው ቅጣት የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን የወንጀል ህጉ አላማ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡አመልካች ባቀረባቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 16(8) መሰረት ለእያንዳንዳቸው ሶስት እርከን ጠቅላላ ስድስት እርከን እንዲቀንስለት ቅሬታ አቅርቧል፡፡ይሁን እንጂ የተፈፀሙት ሁለት ወንጀሎች ፤የወንጀል አፈጻጸማቸው ሆነ ባህሪዉ እንዲሁም ከተፈፀመው የወንጀል ክብደት አንፃር ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ መሠረት ለመወሰን የማያስችል በመሆኑ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ ቅጣቱ እንዲወሰን ድምዳሜ ላይ የተደረሰ ስለሆነ የአመልካች አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም በቅጣት ማክበጃነትና ማቅለያነት በማስረጃና በሕግ የተደገፉና በችሎት ተቀባይነት ያገኙትን ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባትና በማመዛዘን ፍትሐዊ ቅጣት ሊወሰን ስለሚገባ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ የወሰነው የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ቅጣት አመልካች እንዲቀጣ መወሰኑን አመልካች ለፈፀማቸው ወንጀሎት ተመጣጣኝ ቅጣት ስለሚሆን ሌላው ህብረተሰብም የሚያስተምር በመሆኑ በአመልካች ላይ የተወሰነው ቅጣት በውጤት ደረጃ የወንጀል ህጉ መሰረታዊ መርሆዎችን ያልተከተለ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች በተከሳሽ ላይ የሚጣለው ቅጣት የወንጀል አፈጻጸሙ ሆነ ባህሪዉ እንዲሁም ከተፈፀመው ወንጀል ክብደት አንፃር ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ መሠረት ለመወሰን የማያስችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ምክንያቱ በማስቀመጥ በመመሪያው ከተቀመጠው በተለየ መልኩ ቅጣት ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለልም በአመልካች ላይ የተሠጠው የጥፋተኝነትና የተጣለው የእድሜልክ ፅኑ እስራት ቅጣት ውሳኔ የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ ግብ እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ከድርጊቱ አፈጻፀም ጋር ያገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 131521 ግንቦት 24 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲሁም ሰኔ05ቀን 2007 ዓ/ምየሰጠውየቅጣት ውሳኔ ፣ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 115002 ታህሳስ 13 ቀን 2008 ዓ.ም የጸናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ-2) መሠረት በአብላጫ ድምፅ ጸንቷል፡፡

2. አመልካች በእድሜ ልክፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

3. የበታች ፍርድ ቤቶች የተሠጠው ውሳኔ የፀና መሆኑን እንዲያውቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

4. ይህ ውሳኔ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 21(1) መሰረት መመሪው ከሚያስቀምጠው በተለየ ከመመርያው በመውጣት የቅጣት ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀፅ 21(2) መሰረት ለሚመለከተው አካል እንዲያውቀው ይደረግ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተ.ቁ 5 የተሰየመው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በአመልካች ላይ የተላለፈውን የቅጣት ውሳኔ አስመልክቶ በሰጠው የሕግ ትርጉም እና በደረሰበት መደምደሚያ ስላልተስማማሁ በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡አብላጫው ድምጽ አመልካች ለፈጸመው የወንጀል ድርጊት ፍትሐዊ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት ለመወሰን የማያስችል በመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅጣቱን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ እንዲወሰን ድምዳሜ ላይ የተደረሰ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው ፍ/ቤቱ ከወንጀል አፈጻጸሙም ሆነ ባሕርይው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት ለመወሰን የማያስችል ሆኖ ሲገኘው ወይም ቅጣቱ ፍትሕን የሚያዛባ ነው ብሎ ካመነ መመሪያውን ተግባራዊ ያላደረገበትን ምክንያት በዝርዝር በማስቀመጥ ከመመሪያው ወጥቶ ቅጣት ሊወስን እንደሚችል የሚደነግግ በመሆኑ፤አመልካች ለፈጸማቸው ሁለት ከባድ ወንጀሎች ቅጣት ለመወሰን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/1/ለ ድንጋጌ መሠረት መደመር የሚያስፈልግ እና የሁለቱም ወንጀሎች መነሻ ቅጣት ሲደመር በሕጉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት የሚበልጥ ሆኖ በመገኘቱ የሥር ፍ/ቤት መነሻ ቅጣቱን በአንደኛው ክስ የተወሰነውን የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የያዘ በመሆኑ፤በአመልካች ላይ ተቀባይነት ያገኙ ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ያሉ ቢሆንም በመመሪያው ላይ እርከን 40 የሌለ በመሆኑ፤ቅጣቱ ሲሰላ በመመሪያው ከተቀመጠው እርከን በላይ የሚሆን በመሆኑ፤አመልካች አሰቃቂ ወንጀል የፈጸመ በመሆኑ እና ድርጊቱም የተፈጸመው ዕድሜዋ 13 ዓመት በሆናት ሕጻን ላይ ነው በማለት ነው።

በመሠረቱ አንድ አቤቱታ አቅራቢ የይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ የሚያቀርበው በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕግን መሠረት በማድረግ ያልተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ ሊታረም ይገባል ከሚል መነሻ እንደሆነ የይግባኝ ወይም የሰበር ሥርዓት ከተዘረጋበት ዓላማ መገንዘብ ይቻላል።በዚሁ አግባብ የቀረበውን አቤቱታ የሚመረምረው የበላይ የሆነው ፍ/ቤት የአቤት ባዩን አቤቱታ ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ በአቤት ባዩ ላይ የተሰጠውን ፍርድ ሊያጸና፤ሊያሻሽል ወይም ሊሽር ከሚችል በቀር አቤት ባዩ ባስከፈተው የይግባኝ ወይም የሰበር መዝገብ ላይ በአቤት ባዩ ላይ የተሰጠውን ፍርድ ሊያከብድ የሚችል የፍርድ ትችት መስጠት አይጠበቅበትም።በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 አመልካችን የሚጠቅም በመሆኑ በዚሁ መመሪያ መሠረት ቅጣቱ ተሰልቷል በማለት በቅጣት ውሳኔው ላይ የገለጸ ቢሆንም አመልካች ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሉኝ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሦስት ሦስት እርከን መቀነስ ሲገባው አንድ አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ የሰጠው ውሳኔ መመሪያውን ያላገናዘበ ነው በማለት የይግባኝ አቤቱታ ባቀረበበት ሁኔታ፤ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሉት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሦስት እርከን ለሁለቱም የቅጣት ማቅለያዎች ሥድሥት እርከን ተቀንሶ ቅጣቱ ቢወሰን ተቃውሞ የለኝም በማለት መልስ በሰጠበት ሁኔታ አብላጫው ድምጽ አመልካች ባስከፈተው የሰበር አቤቱታ / በአመልካች መዝገብ / ላይ በአመልካች የወንጀል አፈጻጸም እና በግል ተበዳይ ዕድሜ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመመሪያው መሠረት ቅጣቱ ቢወሰን ፍትሕ የሚዛባ በመሆኑ ቅጣቱ ከመመሪያው ውጪ ሊወሰን ይገባል በማለት በደረሰበት መደምደሚያ አልተስማማሁም፡፡

አብላጫው ድምጽ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ ቅጣቱ እንዲወሰን ድምዳሜ ላይ ተደርሷል ለማለት አመልካች ድርጊቱን የፈጸመው ዕድሜዋ 13 ዓመት በሆናት ሕጻን ላይ ነው፤የወንጀል አፈጻጸሙ እና ባሕርይው ከባድ ነው በማለት ምክንያት ሰጥቷል፡፡በእርግጥ አመልካች የፈጸመው ወንጀል አሰቃቂ ወንጀል ለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ሆኖም የተበዳይን ዕድሜ መሠረት በማድረግ አመልካች ከመነሻውም ቢሆን በከባድ ወንጀል /aggravated crime/ የተከሰሰ ሆኖ ሳለ አብላጫው ድምጽ በግል ተበዳይ ዕድሜ እና በድርጊት አፈጻጸሙ ምክንያት ቅጣቱ ከመመሪያው ውጪ ሊወሰን ይገባል በማለት በደረሰበት መደምደሚያ አልተስማማሁም፡፡

አብላጫው ድምጽ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ ቅጣቱ እንዲወሰን ድምዳሜ ላይ ተደርሷል ለማለት የሰጠው ሌላ ምክንያት አመልካች ለፈጸማቸው ሁለት ከባድ ወንጀሎች ቅጣት ለመወሰን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/1/ለ ድንጋጌ መሠረት መደመር የሚያስፈልግ እና የሁለቱም ወንጀሎች መነሻ ቅጣት ሲደመር በሕጉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት የሚበልጥ ሆኖ በመገኘቱ በአንደኛው ክስ የተወሰነውን የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት መነሻ ሆኖ የተያዘ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የተቀበላቸውን ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ለማክበድ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ላይ እርከን 40 ስለሌለ አመልካች ከፈጸመው ድርጊት አኳያ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት መወሰን ፍትሕን ያዛባል የሚል ነው፡፡ሆኖም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/1(ሀ)እና(ለ) ድንጋጌ ተደራራቢ ወንጀሎች በአንደኛው ምክንያት የሞት ወይም የዕድሜ ልክ እሥራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሣሣይ ዓይነት የእሥራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተቀመጠው ከፍተኛ ቅጣት ሲወሰን ይህ ውሳኔ ለሌሎቹም ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰነውን ቅጣት ሁሉ አጠቃሎ እንደሚይዝ፤ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ በተደራራቢነት ለተፈጸመው ወንጀል ተገቢ የሆነ ቅጣት ተወስኖ የሚደመር እና ቅጣቱ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተቀመጠው ቅጣት መብለጥ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 ተደራራቢ ወንጀሎችን በተመለከተ የተቀመጠው የቅጣት አሰላል በወንጀል ሕጉ ተደራራቢ ወንጀሎችን አስመልክቶ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት የተቀመጠ ሆኖ ሳለ፤መመሪያው ከባድ የሚባሉትን የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት እና የሞት ቅጣት የያዙ እርከኖች ያሉት ሆኖ ሳለ አብላጫው ድምጽ በመመሪያው መሰረት ቅጣቱ ቢወሰን ቅጣቱ የሚደመር እና በመመሪያው ላይ እርከን 40 ያልተቀመጠ በመሆኑ ቅጣቱ ከመመሪያው ውጪ ሊወሰን ይገባል በማለት በደረሰበት መደምደሚያ አልተስማማሁም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 ተፈጻሚ ሲሆን በአተገባበር ባጋጠሙ ችግሮች ምክንያት መመሪያውን ማሻሻል በማስፈለጉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88/4 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አውጥቷል፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመው በአገሪቱ ውስጥ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር ለማደረግ እንደሆነ ችሎቱ ከሰጣቸው በርካታ ውሳኔዎች እና በተግባር ከሚታየው አሰራር መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚሁ መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቅጣት አወሳሰን መመሪያን በሚመለከት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95438 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 22 እና የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 6 መሠረት በማድረግ ወንጀል ፈጻሚው ድርጊቱን የፈጸመው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ተግባራዊ በነበረበት ጊዜ ከሆነ ቅጣቱ በዚሁ መመሪያ መሠረት ሊወሰን የሚገባ መሆኑን፤አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ቅጣት ሊወሰን የሚችለው አዲሱ መመሪያ ተከሳሽን የሚጠቅም በሆነ ጊዜ ብቻ መሆኑን በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1 መሠረት በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ይህን የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግም ቀላል፤መካከለኛ እና ከባድ በሆኑ የወንጀል አፈጻጸሞች ላይ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ አተገባር ላይ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በበርካታ መዝገቦች ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 አመልካችን የሚጠቅም በመሆኑ ቅጣቱ በዚሁ መመሪያ መሠረት ተሰልቷል በማለት በውሳኔው ላይ የገለጸ ቢሆንም ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ ቅጣቱን ያሰላ በመሆኑ የቅጠት ማቅለያ እርከኖች አሰላል ላይ ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት በማድረግ ውሳኔ እንደሰጠ የሚገመት ነው፡፡አመልካች ድርጊቱን የፈጸመው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ተግባራዊ በነበረበት ጊዜ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የመመሪያውን ሙሉ ይዘት ተፈጻሚ በማድረግ መወሰን የሚገባው ሆኖ ለአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ ውሳኔ መስጠቱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን እና ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ተግባራዊ በነበረበት ጊዜ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የመመሪያው ሙሉ ይዘት ተፈጻሚ በማድረግ መወሰን የሚገባው ሆኖ ለአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ ውሳኔ መስጠቱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን እና ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት በቅጣት አወሳሰን መመሪያ አተገባበር ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚጥስ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ሳለ አብላጫው ድምጽ ከአመልካች የድርጊት አፈጻጸም፤ከወንጀሉ ባሕርይ እና ከተበዳይ ዕድሜ አኳያ በመመሪያው መሠረት ቢወሰን ፍትሕን ያዛባል በማለት በደረሰበት መደምደሚያ አልተስማማሁም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል የአመልካች ግላዊ ሁኔታ በቅጣት ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ታሳቢ ሊደረግ ስለሚችልበት ሁኔታ በተለያዩ ሕጎች ላይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 36/2 ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፤በፍ/ቤቶች በአሥተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪው አካላት የሕጻናት ደህንነት በቀዳሚትነት መታሠብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ኢትዮጲያ የተቀበለችው የሕጻናት መብቶች ሥምምነት አንቀጽ 1 ድንጋጌ ሕጻን ማለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው በማለት ይደነግጋል፤የዚሁ ሥምምነት አንቀጽ 3 በመንግሥት ወይም በግል ማሕበራዊ ደህንነት ተቋሞች በፍርድ ቤቶች በአሥተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት ሕጻናትን የሚመለከት ማንኛውም እርምጃ ሲወሰድ የሕጻናቱ ጥቅም የሚጠበቅበት ሁኔታ ከሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

ሕገመንግሥቱን መሠረት በማድረግ የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በመግቢያው ላይ አዋጁ እንዲወጣ አስፈላጊ ከሆነባቸው ምክንያቶች ውስጥ በአገሪቱ ሥር ነቀል የሆኑ ለውጦች የተካሔዱ በመሆኑ፤ከእነዚህም ውስጥ የህጻናት እና የሴቶች መብቶች ኢትዮጲያ በተቀበለቻቸው ዓለምዓቀፍ ሥምምነቶች እና በሕገመንግስቱ እውቅና ያገኙ በመሆኑ፤ፍርድ ቤቶች በተመሣሣይ ጉዳዮች ላይ ተመሣሣይ ቅጣት የሚወስኑበትን መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤ወንጀል አድራጊዎችን በመቅጣት ወንጀል እንዳይፈጸም በመከላከል ሕብረተሰቡን መጠበቅ እና ወንጀል ለሚፈጽሙ ሰዎች ማሥጠንቀቂያ መሥጠት እና ትክክለኛ የፍትሕ ሥርዓትን ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 176 ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ ፤ከአሥራ ሥምንት ዓመት በታች የሆነ ወጣት ወንጀል አድራጊ ወንጀል በሠራ ጊዜ ፍ/ቤቱ በመደበኛው የሕግ ድንጋጌ መሠረት ሲወስን የነገሩ አካባቢ ሁኔታ በቂ ምክንያት የሚያስገኝ መሆኑን የገመተ እንደሆነ በአንቀጽ 179 በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ቅጣት ሊያቀልለት እንደሚችል፤አሥራ ሥምንት ዓመት ሳይሞላው በፈጸመው ማናቸውም ወንጀል ምክንያት የሞት ቅጣት ሊወሰንበት እንደማይችል ይደነግጋል፡፡የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 87 ዳኞች ቅጣትን ሲወስኑ ሕጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መንፈስ መሠረት መፈጸም ያለባቸው መሆኑን እና ቅጣቶቹ እና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምንጊዜም ሰብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ እንዲሆን ማድረግ ሊከተሉት የሚገባ መርህ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡የዚሁ ሕግ አንቀጽ 88 ድንጋጌም ፍ/ቤቱ ቅጣትን ሲወስን የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኝነት መጠን ያለፈ የሕይወት ታሪኩን፤ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶች እና የአሳቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የትምህርቱን ደረጃ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነት እና የአፈጻጸሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት ሕግ አውጪው ዕድሜው ከአሥራ አምሥት ዓመት በላይ፤ከአሥራ ሥምንት ዓመት በታች የሆነ ወጣት ወንጀል አድራጊ ወንጀል በሠራ ጊዜ በሕጉ የተቀመጡት ከባድ የሚባሉ ቅጣቶች እንዲወሰኑበት ፍላጎት የሌለው መሆኑን እና ፍ/ቤቶች በሚሰጡት የቅጣት ውሳኔ ላይም ጥንቃቄ ሊያደረግ የሚገባቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች እድሜዋ 13 ዓመት በሆናት ሕጻን ላይ ወንጀል የፈጸመ ለመሆኑ፤ ድርጊቱንም የፈጸመው አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ሆኖም በሥር ፍ/ቤት በማስረጃነት የቀረበው አመልካች በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27/2 መሠረት ለፖሊስ የሰጠው ቃል አመልካች ድርጊቱን በፈጸመበት ጊዜ የ16 ዓመት ልጅ እና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ የነበረ መሆኑ ያሳያል፤አመልካች ድርጊቱን ሲፈጽም ዕድሜው 16 ዓመት እንደነበረ የሚያሳይ የልደት ሰርተፍኬት ያቀረበ ሆኖ ሳለ ፤አመልካች ለፖሊስ የሰጠውን ቃል በማስረጃነት የሚወሰደው በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመወሰን ብቻ ሳይሆን ማስረጃው ከነሙሉ ይዘቱ በማስረጃነት የሚወሰድ ሆኖ ሳለ አብላጫው ድምጽ አመልካች ድርጊቱን ሲፈጽም ዕድሜው 19 ዓመት እንደነበረ በራድዮሎጂ ምርመራ ውጤት የተረጋገጠ መሆኑ ተጠቅሶ በበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው በማለት በደረሰበት መደምደሚያ አልተስማማሁም፡፡አመልካች ድርጊቱን ሲፈጽም ዕድሜው 16 ዓመት እንደነበረ ለፖሊስ በሰጠው ቃል ላይ እና ባቀረበው የልደት ሰርተፊኬት የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ድርጊቱን ሲፈጽም ዕድሜው 16 ዓመት ነበር፡፡አመልካች ድርጊቱን ሲፈጽም የ16 ዓመት ልጅ እና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ የነበረ በመሆኑ ድርጊቱ የሚያመጣበትን ውጤት ያመዛዝናል ተብሎ የማይጠበቅ በመሆኑ በአመልካች ላይ የተላለፈው የዕድሜልክ ጽኑ እሥራት አመልካች በሕገመንግሥቱ፤አገሪቱ በተቀበለችው የሕጻናት መብት ሥምምነት እና በወንጀል ሕጉ የተጠበቀለትን መብት መሠረት ያላደረገ ነው በማለት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት ቅጣቱን በመመሪያ ቁጥር 01/2002 መሠረት ያሰላ መሆኑን ገልጾ ተቀባይነት ባገኙ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመመሪያው መሠረት ሦስት ሦስት እርከን በመቀነስ መወሰን ሲገባው ይህን ሳያደርግ በመቅረቱ አመልካች የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲታረም አቤቱታ ባቀረበበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት የቅጣት ማቅለያ አቀናነስ ላይ የፈጸመው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት ሊታረም ሲገባለው አብላጫው ድምጽ በአመልካች መዝገብ ላይ ከወንጀሉ ባሕርይ፤ከድርጊቱ አፈጻጸም እና ከተበዳይ ዕድሜ አኳያ ከላይ ቅጣቱ ከመመሪያ ውጪ ሊወሰን ይገባል በማለት በደረሰበት መደምደሚያ ከላይ በገለጽኳቸው ምክንያቶች ያልተስማማሁበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ተቀባይነት ባገኙ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመመሪያው መሠረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሦስት እርከን ለሁለቱም የቅጣት ማቅለያ ስድሥት እርከን ተቀንሶ ቅጣቱ ሊሰላ ይገባ ነበር በማለት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 124618

ሕዳር 22 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዩ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-

1. ወ/ሮ ድባካ መሰለ - ቀረቡ
2. ሀብቱ ሞገስ - ሞግዚት ወ/ሮ ድባካ መሰለ - ቀረቡ
3. የሸወርቅ ሞገስ - ሞግዚት ወ/ሮ ድባካ መሰለ- ቀረቡ

ተጠሪ፡-ሳጅን ኃይሉ ሞገስ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካቾች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም ለፍርድ አፈጻጸሙ ምክንያት የሆነው መኖሪያ ቤት ክፍፍል መፈጸም የሚገባው በሀራጅ ተሸጦ ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍርድ በማጽናት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡-የ1ኛ አመልካች ባለቤት የነበሩት አቶ ሞገስ ጌታሁን በሞት መለየታቸውን ተከትሎ በተነሳው የውርስ እና የጋራ ንብረት ክፍያ ክርክር በዋግኽምራ ዞን በሰቆጣ ከተማ በቀበሌ 02 ክልል በሚች ስም ተመዝግቦ ይታወቅ ከነበረው ቤት ውስጥ ግማሹ የአሁኗ 1ኛ አመልካች ድርሻ ሆኖ ቀሪው ግማሽ ደግሞ ከሚች ለሚወለዱት ሰባት ልጆች እንዲከፋፈል ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ይህንን የስረ ነገር ፍርድ ለማስፈጸም 1ኛ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍርድ ባለመብትነት ተሰይመው ባደረጉት እንቅስቃሴ በከተማው አስተዳደር በቀረበው የዋጋ ግምት መሰረት የቀሪዎቹን ወራሾች ድርሻ 1ኛ አመልካች ከፍለው እና ከወራሾቹ መካከል የአሁኑ ተጠሪ ቤቱ በጨረታ መሸጥ ከሚገባው በቀር ግምቱን ለመቀበል አልስማማም በማለታቸው ድርሻቸው በሞዴል 85 እንዲያዝ ተደርጎ የቤቱ ስመሀብት አፈጻጸሙን በያዘው የሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወደ 1ኛ አመልካች የተዛወረ መሆኑን፣1ኛ ተጠሪ በዚህ ትዕዛዝ ባለመስማማት በየደረጃው ያቀረቡት ክርክር በመጨረሻ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስርፍርድ ቤቶችን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሽሮቤቱ ከተቻለ በዓይነት፣ካልተቻለ ግራ ቀኙ እርስ በእርስ በሚያደርጉት ጨረታ፣ይህም ካልተቻለ ለ3ኛ ወገን በጨረታ እንዲሸጥ በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፣የወረዳው ፍርድ ቤትም በዚሁ አግባብ ቤቱ በጨረታ እንዲሸጥ ለማስቻል የጨረታ ማስታወቂያ እንዲወጣ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን፣በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት 1ኛ አመልካች ያቀረቡት ይግባኝ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 010913 በ02/10/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የተዘጋ እና አቤቱታቸውም በክልሉ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር0311349 በ16/06/2008 ዓ.ምበተሰጠ በፍርድ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭያመለክታል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾቹ በአከራካሪው ቤት ላይ ያላቸው የጋራ ድርሻ በጣም ብዙ ሆኖ እያለ እና የተጠሪው ድርሻ ግን በድርሻቸው ብቻ የታጠረ ሆኖ እያለ፣ይህንኑ ከግምት በማስገባትም 1ኛ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ በቀር ለቀሪው እያንዳንዱ ወራሽ ግምቱን ከፍለው ቤቱን በስማቸው አዛውረው እያለ የአሁኑ ተጠሪ ግምቱን ለመቀበል ባለመስማማታቸው ብቻቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የመታዘዙን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. በስረ ነገሩ ፍርድ መሰረት ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በቤቱ ላይ የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ እንዲወጣ በወረዳው ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
2. አመልካቾቹ ከአከራካሪው ቤት ላይ አለን የሚሉትን አብላጫ ድርሻ መሰረት በማድረግ ቤቱን ማስቀረት የሚችሉበት የሕግ አግባብ አለ ወይስ የለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ 1ኛ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከአከራካሪው ቤት በሚስትነታቸው ያላቸው ድርሻ ግማሽ ሆኖ እያለ እና የሰባት ወራሾች ድርሻ ከሆነው የቤቱ አጋማሽ ውስጥ ደግሞ 1ኛ አመልካች ሞግዚት የሆኗቸው 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችእያንዳንዳቸው አንድ ሰባተኛ ድርሻ ያላቸው ሆኖ እያለ እንዲሁም ከተጠሪው ውጪ ላሉት ቀሪ ወራሾች 1ኛ አመልካች ድርሻቸውን ከፍለው እያለ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ አንድ ሰባተኛ ድርሻ ብቻ ላላቸው የአሁኑ ተጠሪ ጥቅም ብቻ ሲባል ወደ 1ኛ አመልካች ስም ተዛውሮ የነበረው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው ትዕዛዝ ፍትሐዊ አይደለም የሚል መሆኑን የአቤቱታቸው ይዘት ያመለክታል፡፡ይሁን እንጂ የክልሉ ሰበር ችሎት የአፈጻጸም ሂደቱን አስመልክቶ ቀደም ሲል ቤቱ ከተቻለ በዓይነት፣ካልተቻለ ግራ ቀኙ በመካከላቸው በሚያደርጉት ጨረታ፣ይህም ካልተቻለ ደግሞ ለ3ኛ ወገን በጨረታ እንዲሸጥ በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም. ውሳኔ የሰጠው 1ኛ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ውጪ ላሉት ሌሎች ወራሾች ድርሻቸውን ሰጥተው ቤቱን በስማቸው ካዛወሩ በኃላ በመሆኑ የተጠሪው ድርሻ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ አንድ ሰባተኛ ብቻ ሆኖ እያለ ቤቱ በሐራጅ ይሸጥ መባሉ ተገቢ አይደለም የሚሉ ከሆነ የሰበር አቤቱታቸውን በወቅቱ በስርዓቱ መሰረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ተገቢውን ውሳኔ ማሰጠት ይገባቸው የነበረ ከመሆኑ በቀር በክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ ወደ ወረዳው ፍርድ ቤት ተመልሶ የአፈጻጸም ሂደቱ ከቀጠለ በኃላ ወደኃላ ተመልሰው ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ፍትሀዊ አይደለም በማለት አሁን እያቀረቡ ያሉት ክርክር ስነ ስርዓታዊ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም አፈጻጸሙን የያዘው የሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል በክልሉ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም. የሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ በስረ ነገሩ ፍርድ መሰረት ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በቤቱ ላይ የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ እንዲወጣየሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከአከራካሪው ቤት 1ኛ አመልካች ግማሽ ድርሻ፣2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ደግሞ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ እያንዳንዳቸው አንድ ሰባተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑ አላከራከረም፡፡ይህም 1ኛ አመልካችም ሆኑ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከቀሪዎቹ ወራሾች ጋር የአከራካሪው ቤት የጋራ ባለሀብቶች መሆናቸውን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ተይዞ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በሕብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት በሆነ ጊዜ ከተካፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ እንደሆነ የፍርድ ባለዕዳው እንደቀረበ ተቆጥሮ የተቀዳሚነት መብት የሚሰጠው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443 ይደነግጋል፡፡ከስነ ስርዓት ሕጉ በተጨማሪም የጋራ ባለሀብቶች የሆኑ ሰዎች ያልተከፋፈለውን የጋራ ንብረት ከማንኛውም ሶስተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገን በፊት ቀዳሚ ሆነው በግዥ የማስቀረት ሕጋዊ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1) የተደነገገ ሲሆን ይህ መብት ተግባራዊ የሚደረግበት ስርዓትም በዚሁ ሕግ ከቁጥር 1386 እስከ 1409 ተደንግጎ ይገኛል፡፡በመሆኑም አመልካቾቹ አከራካሪውን ቤት ለማስቀረት የሚችሉት በቤቱ ላይ በሚከናወነው ጨረታ መሰረት ከፍተኛ ዋጋ በማቅረብ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ጨረታውን ያሸነፈበትን ዋጋ መሰረት በማድረግ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች በተጠበቀላቸው የቀዳሚነት መብት በመገልገል ነው፡፡በቀጣይ የአፈጻጸሙ ሂደት አመልካቾቹ ከፍተኛ ዋጋ በማቅረብ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ጨረታውን ያሸነፈበትን ዋጋ መሰረት በማድረግ የቀዳሚነት መብታቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉ ከሆነ በሰበር አቤቱታቸው እንደሚከራከሩት ከአሁኑ ተጠሪ ውጪ ላሉት ሌሎች ወራሾች ድርሻቸውን ከፍለው በቤቱ ላይ ያላቸውን ድርሻ ከፍ ያደረጉ መሆን አለመሆኑ፣ጨረታውን ካሸነፉበት የዋጋ መጠን ውስጥ የራሳቸው ድርሻ ተቀንሶ ገቢ ማድረግ የሚገባቸው የገንዘብ መጠን ምን ያህል እንደሆነ እና መሰል የአፈጻጸም ጉዳዮች ፍርዱን በሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ተስተናግደው ተገቢው ትዕዛዝ የሚሰጥባቸው ይሆናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካቾቹ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443 እንዲሁምበፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1)፣1386 እስከ 1409 በተደነገገው የቀዳሚነት መብታቸው የመገልገል መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ አከራካሪው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በዋግኽምራ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0101913 በ02/10/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍርድ በማጽናት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የስረ ነገሩ ፍርድ ያረፈበት ቤት በሀራጅ ይሸጥ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አከራካሪው ቤት በሀራጅ በሚሸጥበት ጊዜ አመልካቾቹ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443፣እንዲሁም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1)፣1386 እስከ 1409 በተደነገገው የቀዳሚነት መብት የመገልገል መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ለዋግኽምራ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ06/07/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 121565

ሚያዚያ 20 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንደሻው አዳነ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፍረወይኒ አብርሃ

ተጠሪ፡- አቶ ገ/ጊዮርግስ ፀጋይ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀም የተመለከተ ክርክር ነው፡፡ የአመልካች አፈፃፀም ከሳሽ ተጠሪ የአፈፃፀም ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የአፈፃፀም ክርክሩ መነሻ በግራ ቀኙ መካከል የነበረ ጋብቻ ውሣኔ መፍረስን ተከትሎ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ የተሰጠ ውሣኔ ለማስፈፀም ነው፡፡

አሁን አከራካሪ ሆኖ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ምክንያት የሆነው በመቀሌ ከተማ በሐነድነት ክ/ከተማ በደብሪ ቀበሌ የሚገኝ 400 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈ ቤት ክፍፍል ላይ የሥር ፍርድ ቤቶች የተለያየ አቋሞ በመያዛቸው ነው፡፡ ከመዝገቡ መገንዘብ እንደተቻለው የመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህ ቤት የባለቤትነት ማረጋገጫ ስላልወጣለት ወይም ገና ህጋዊ መሆኑ ስላልተረጋገጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ እስኪወጣለት ድረስ የሚፈፀም አይደለም ሲል የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድጓል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ግራቀ ኙን ካከራከር በኋላ ለግራ ቀኙ በአማራጭማስፈፀም የሚቻልበት ሁኔታ የለም በማለት በአብላጫ ድምፅ የሥር ፍርድ ቤት ትእዛዝ አፅንቷል፡፡ አናሳው ድምፅ ቤቱ የጋራ ነው እስከተባለ ድረስ አስተዳደር አካል ተገቢውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ እስኪሰጥበት ድረስ በጋራ የሚጠቀሙበት አማራጭ ሊታይ ይገባል ሲል ልዩነት ሀሳብ አስፍሯል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የቅሬታ ነጥብ በአጭሩ ሲታይ ተጠቃሹ 8 ክፍል ቪላ ቤት አመልካችናተጠሪ በጋራ በትዳር ላይ እያሉ ያፈሩት መሆኑ ተረጋግጦ የሚከፈል ከሆነ በዐይነት እንዲከፋፈሉ ማካፈል ካልተቻለም ደግሞ በጨረታ ወይም በስምምነት ተሸጦ እንዲካፈሉ በመ/ቁጥር 149270 ውሣኔ መስጠቱን፤በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም አቤቱታ ማቅረቧን፤የሐድነት ክ/ከተማ መሬት አስተዳደርም ተጠይቆ ይህ ቦታና ቤት ካርታ ያልወጣለት ስለሆነ መፈፀም እንዳልተቻለ ምላሽ መስጠቱን ይህ የማይቻል ከሆነ ለጊዜው በጋራ እያስተዳደሩ እንዲጠቀሙበት መደረግ ሲገባ ተጠሪ ብቻ እንዲጠቀም መደረጉ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም የሚል ነው፡፡

ይህችሎትም ይህንኑ ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዟል፡፡ የተጠሪ ጠበቃም በሰጡት መልስ ፍርድ ሊፈፀም የሚገባው እንደፍርዱ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 378(1) ጠቅሰው የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙን ክርክር ከላይ ባጭሩ የተመለከተ ሲሆን እኛም አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ እንደተቻለው በሐድነት ክ/ከተማ በ400 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈው ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ ውሣኔ ያረፈበት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በዋናው ውሣኔ ለዚህ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 122453 አቤቱታ አቅርቤያለሁ ቢሉም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ ህዳር 19 ቀን 2009 ዓ.ም መወሰኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ይህ የጋራ ንብረት የተባለው ቤት በፍርድ አፈፃፀም ለጊዜው ሊፈፀም አይችልም የተባለው ይዞታው ህጋዊ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አላገኘውም በሚል ነው፡፡

ስለሆነም የሚመለከተው አስተዳደር አካል ስለህጋዊነቱ ተገቢውን ውሣኔ እስሲጥበት ጊዜ ድረስ በጋራ በማስተዳደር የምንጠቀምበት አግባብ እንዲታዘዝሊሉ አመልካች በአማራጭ ጥያቄ አቅርቧል፡፡

በመሠረቱ በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት ነው እስከተባለ ድረስ በዚህ ንብረት ሕጋዊነት ላይ አስተዳደር አካል አግባብ ያለው ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ መሸጥ መለወጥ ባይችልም ባለበት ሁኔታ ሁለቱም ወገኖች እኩል ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ሊበጅለት ይገባል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ካልሆነ አንደኛው ወገን ብቻ ተጠቃሚ ማድረግ በሕገመንግስቱ እና በሌሎች የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎች የተመለከተውን የእኩልነት መርህ ያላከበረ አካሄድ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ ባሻገር በአፈፃፀም ሂደት እንደ ፍርዱ ለመፈፀም የማይቻልበትህጋዊ ምክንያት ሲገኝ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ተገቢውን አማራጭ ተመርኩዞ አግባብ ያለው ትእዛዝ መስጠት እንደሚቻል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 386/2/ ድንጋጌ ይዘታ ያስገነዝባል፡፡ በተመሣሣይ የሥነ ሥርት ሕጉ አተገባበር ላይ የፌዴራል ጠቅለላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትውሣኔ የሰጠባቸውን መዝገቦች ይዘትም ማየት ይቻላል፡፡ የሰበር መ/ቁጥር 38041፣62804፣101345 እና ሌሎች ተዛማች መዝገቦችን ማየት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ይህ የጋራ ነው የተባለው ቤት በሕጉ አግባብ ለክፍፍል የሚያመች ሕጋዊ ሁኔታእስኪሟላ ጊዜ ድረስ የግራ ቀኙን እኩል ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አግባብ በጋራ የሚያስተዳድሩበት ወይም ተከፋፍለው የሚጠቀሙበት ወይም አከራይተው ጥቅሙን እኩል የሚከፋፈሉት ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ አናሳ ድምፅ ያስቀመጠው አማራጭ ከግራ ቀኙ አስተያየት ተጠይቆ ተገቢ ትእዛዝ ሊሰጥበት እየተገባ ተጠሪ ብቻ ይዞ እንዲጠቀም በሚያደርግ መልኩ መወሰኑየጋራ ባለንብረት የሆነችውን የአመልካችን የእኩልነት መብት ያጣበበ በመሆኑ ውሣኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አከራካሪውን በሐድነት ክ/ከተማ ቀበሌ ደብሪ የሚገኘው ቤት አስመልክቶ የመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አብላጫ ድምፅ እንደቅደም ተከተላቸው በመ/ቁጥር 17034 እና 76406 የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ስለሆነም ይህ ቤት ሕጋዊነቱ በሚመለከተው እኩል ውሣኔ እስኪሰጥበት ጊዜ ድረስ ባለበት ሁኔታ ግራ ቀኙ በጋራ የሚያስተዳድርበት ወይም አከራይተው የሚጠቀሙበት አማራጭ ሁኔታዎች ላይ የግራ ቀኙን አስተያየት ተቀብሎ ተገቢውንና ተስማሚውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 343/1/ መሠረት ለመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ብ/ግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 118808

ሚያዚያ 30 ቀን 2009ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ደስታ ንጉሴ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ሐየሎም በላይ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረዉ የሓድነት ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በአቶ ሕንጻ በላይ እና በአሁኑ ተጠሪ ላይ በአንድነትና በተናጠል እንዲከፍሉ ካስወሰነዉ ገንዘብ ዉስጥ የአሁኑ ተጠሪ ግማሹን መክፈሉን ገልጾ ቀሪዉን ግማሽ ብር 22,165 የመክፈል ግዴታ ያለበት በመሆኑ ተጠሪ እንዲከፍለዉ ሲጠይቅ፤ ተጠሪ በበኩሉ በአንድነትና በተናጠል እንድንከፍል ተወስኖ የነበረዉን አቶ ሕንጻ በላይ ይግባኝ ጠይቀዉ ተጠያቂ ሊሆኑ አይገባም ተብሎ የተወሰነና ከአፈጻጸም ክሱም የተሰናበቱ በመሆነቸዉ በዋናዉ ፍርድ መሠረት ተጠሪ ሙሉ ገንዘቡን ብከፍል በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ነዉ ተብሎ ከነበነረዉ ሰዉ ግማሹን የማስመለስ መብቱ ስለተነካ የአቶ ህንጻ በላይ ድርሻ የምከፍልበት አግባብ የለም ሲል ተከራክሯል፡፡

የወረዳዉ ፍ/ቤት የአፈጻጸም ክርክሩን መርምሮ ተጠሪ ከአቶ ሕንጻ በላይ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ተወስኖ የነበረዉን አቶ ሕንጻ በላይ ይግባኝ ጠይቀዉ ኃላፊነታቸዉን በተመለከተ ዉሳኔዉን አሽረዋል፡፡ ተጠሪ የአቶ ሕንጻ በላይን ድርሻ ለመክፈል ይገደዱ የነበረዉ አቶ ሕንጻ በላይ ባለዕዳ ሆነዉ ለመክፈል ፍቃደኛ ባይሆኑ ነበር፡፡ አሁን ግን አቶ ሕንጻ በላይ የተወሰነባቸዉን ያሻሩ ስለሆነ ተጠሪ ገንዘቡን ጠቅልለዉ ከፍለዉ ከአቶ ሕንጻ በላይ መልሰዉ ድርሻቸዉን የሚያስከፍሉበት የሕግ አግባብ በሌለበት ተጠሪ ድርሻዉ ከሆነዉ ግማሽ ገንዘብ በላይ እንዲከፍል ሊገደድ አይገባም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ይህን ብይን በመቃወም አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተዉ የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙን አሰናብቷል፡፡ እንዲሁም አመልካች የሰበር አቤቱታ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ዋናዉ ፍርድ በግልጽ የሚያመለክተዉ ተጠሪና አቶ ሕንጻ በላይ በአንድነትና በነጠላ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ዋጋ እና ኪራይ እንዲከፍሉኝ ነዉ፡፡ ስለዚህ ዉሳኔዉ ተጠሪና አቶ ሕንጻ በላይ ድርሻ ሳይነጣጠል በጋራ እንዲከፍሉኝ የተወሰነ ነዉ፡፡ በዋናዉ ፍርድ ሁለቱም ለከፍተኛ ፍ/ቤት ለየብቻቸዉ ይግባኝ አቅርበዉ በወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ ቢያሸሩም በተጠሪ መዝገብ በተሰጠዉ ዉሳኔ ስላልተስማማሁ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቤ የከፍተኛዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ተሽሮ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በአፈጻጸም በሰጠዉ ብይን ራሱ የሰጠዉን ዉሳኔ ብቻ ሳይሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ጭምር ሽሯል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህን ብይን ማጽናቱ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተሽሮ ተጠሪ ዕዳዉን በሙሉ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለዚህ አፈጻጸም መሠረት የሆነዉ ፍርድ መነሻ የሆነዉ የክስ ምክንያት ከተጠሪ ጋር ተከሶ የነበረዉን ግለሰብ ጭምር ሳይሆን ተጠሪን ብቻ በግሉ የሚመለከት ነዉ ተብሎ ግለሰቡ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከኃላፊነት ነጻ እስከተባለ ድረስ ተጠሪ ፍርዱን በሙሉ እንዲፈጽም ሊገደድ አይገባም ወይ የሚለዉን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቀባበል እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰበር መልሳቸዉ ያቀረቡት ክርክር ይዘት፡- አቶ ሕንጻ በላይ ተጠያቂ አይደለም የተባለዉ በድርሻዉ ላለዉ ተጠያቂነት ነዉ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ አጽንቻለሁ ማለቱ ሁለቱም በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂዎች መሆናቸዉን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ይህም የአሁኑ ተጠሪ አጠቃላዩን ለመክፈል የሚጠየቅበት አግባብ የለም፡፡ ተጠሪ በዉሳኔዉ መሠረት ግማሽ ድርሻዉን የከፍልኩኝ ሲሆን አቶ ሕንጻ በላይ መክፈል ያለባቸዉን ገንዘብ መክፈል አለብህ የሚለዉ ቅሬታ አቶ ሕንጻ በላይ በነጻ ከመሠናበቱ አንጻር የሕግ መሠረት የለዉም፡፡ ክፈል ተብዬ ተገድጄ ብከፍል መጨረሻ ላይ ከአቶ ሕንጻ ገንዘቡን ማስመለስ አልችልም፡፡ አመልካች በራሳቸዉ ቸልተኝነት በአቶ ሕንጻ በላይ ይግባኝ ሳያቀርቡ ለቀረባቸዉ ግማሽ ክፍያ ተጠያቂ ራሳቸዉ እንጂ ተጠሪ አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ድርሻዉን ግማሹን ገንዘብ ስለከፈልኩ አመልካች ከተጠሪ የሚጠይቁት ተጨማሪ ክፍያ የለም ተብሎ የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግራ ቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ ለአፈጻጸሙ መሠረት የሆነዉን ፍርድ በቅድሚያ የሰጠዉ የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪን እና የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረዉን አቶ ሕንጻ በላይን በአንድነትና በነጣል ዕዳዉን እንዲከፍሉ የወሰነባቸዉ ሲሆን ሁለቱም ባለዕዳዎች በተናጠል ለመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዉ በተለያዩ መዝገብ ዉሳኔዉን አሽረዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ተጠሪን በተመለከተ ብቻ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ ተጠሪ ነጻ የተባለበትን ዉሳኔ በመሻር የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች ፍርዱን ሙሉ በሙሉ ተጠሪ እንዲፈጽምለት የጠየቀ ሲሆን የስር ፍ/ቤቶች በተመሳሳይ ተጠሪ የፍርዱን ግማሽ ገንዘብ በመክፈል ድርሻዉን የተወጣ በመሆኑና በዋናዉ ጉዳይ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቶ ሕንጻ በላይን አስመልክቶ በነጻ እንዲሰናበት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የአሁኑ አመልካች ይግባኝ ጠይቆ ባለማሻሩ ምክንያት የአሁኑ ተጠሪ ሙሉ ገንዘቡን ቢከፍል በድርሻዉ አቶ ሕንጻ በላይን ጠይቆ የማስመለስ መብቱን የሚያሳጣዉ በመሆኑ ተጠሪ ከግማሽ ዕዳ ወይም ከድርሻዉ በላይ እንዲከፍል ሊገደድ አይገባም በማለት ወስነዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ ተጠሪ ለሙሉ ዕዳዉ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ነዉ እስከተባለ ድረስ ተጠሪ ሙሉ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ አለበት በሚል ነዉ፡፡

በመሠረቱ የአንድነትና የነጣላ ኃላፊነት ምን ማለት እንደሆነ በሕጋችን ተካትቶ የምናገኘዉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1896፣ 1897 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ነዉ፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚገኙት ግዴታዎችን በተመለከተዉ የፍትሐብሔር ሕጉ መጽሐፍ በተለይም ስለ ዉሎች በጠቅላለዉ በሚለዉ አንቀጽ 12 ስር ቢሆንም መርሁ ግዴታዉ ከዉል፣ ከሕግም ሆነ ከፍርድ የመነጨ ቢሆንም ይህንኑ የሚመለከት የተለዩ የሕግ ድንጋጌ እስካልኖረ ድረስ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተቀመጠዉ የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት መርህ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1896፣ 1897 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለዉ ሁለት ባለዕዳዎች በአንድነትና በነጠላ አንድን ዕዳ እንዲከፍሉ ከተፈረደባቸዉ ባለገንዘቡ ገንዘቡ እንዲከፈለዉ ሁለቱን ባለዕዳዎች በአንድነት ወይም አንደኛዉ ባለዕዳ ሙሉ ገንዘቡን እንዲከፍል ሊጠይቅ ይችላል፡፡ እንዲሁም አንዱ የፍርድ ባለዕዳ በዋናዉ ፍርድ ይግባኝ ጠይቆ የራሱን ኃላፊነት አስመልክቶ ፍርዱን አሽሮት ከሆነ ሙሉ እዳዉን ለመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ይግባኝ ሳይጠይቅ በመቅረቱ ዋናዉን ፍርድ ባልተሻረለት ወይም ይግባኝ ጠይቆ ፍርዱ በጸናበት ሰዉ ላይ ይሆናል፡፡ ፍርድ ያላሻረዉ ወይም የጸናበት ባለዕዳ ዕዳዉን የምከፍለዉ በድርሻዬ ልክ ወይም ግማሹን ነዉ ለማለት አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሁለት ሰዎች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ናቸዉ ሲባሉ ለእዳዉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አከፋፈል አንዳቸዉ ወይም ሁለቱም በጋራ ለባለገንዘቡ ግዴታ አለባቸዉ ማለት እንጂ ሁለቱ በመካከላቸዉ ዕዳዉን እኩል ለመካፈል ኃላፊነት አለባቸዉ ማለት አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1907 መሠረት የተቀመጠዉ የሕግ ግምት እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለቱ ባለዕዳዎች መካከል ያለዉ የኃላፊነት መጠን የሚወሰነዉ እርስ በርሳቸዉ ሲጠያየቁ በሚኖረዉ ኃላፊነት መሠረት አንዱ ለሙሉ ወይም ለከፊሉ ዕዳ ኃላፊ ነዉ ተብሎ ተለይቶ ሲወሰን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የስር ተከሳሾች በአንድነትና በተናጠል ኃላፊነት የሚያስከትልባቸዉ የሕግ ተጠያቂነት አለባቸዉ ብሎ ቢያምንም ሲፈልግ ሁለቱን ሳይፈልግ አንዱን መርጦ የመክሰስ መብት አለዉ፡፡ እንዲሁም በይግባኝ ደረጃም ቢሆን በአንዱ ላይ ይግባኝ ጠይቆ በሌላኛዉ ላይ ይግባኝ ያለመጠየቅ መብት አለዉ፡፡ ምክንያቱም አንዱን ነጥሎ መክሰሱ ወይም በአንዱ ላይ ብቻ ይግባኝ መጠየቁ ብቻ ገንዘቡን የሚያስከፍለዉ መሆኑን እስካረጋገጠለት ድረስ ሁለቱን በአንድነት የመክሰስ ወይም ይግባኝ የመጠየቅ ግዴታ አይኖርበትም፡፡ አመልካች ያቀረበዉ ክስም ሆነ ይግባኝ የስር ተከሳሾች ለአመልካች የሚኖራቸዉን ግዴታ ወይም ኃላፊነት የሚወስን እንጂ በቀጥታ በሁለቱ ተከሳሾች የዕዳ መከፋፈልን ወይም አንዱ ሙሉ እዳ ከፍሎ ከሌላዉ የሚጠይቅበት ፍርድ ወይም የዳኝነት ጥያቄ አይደለም፡፡ ተጠሪ ለሙሉ እዳዉ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ነዉ ተብሎ የተወሰነበትን በይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ አቅርቦ እስካላሻረ ድረስ ወይም ኃላፊነቱ በድርሻዉ እንዲቀንስ እስካላደረገ ድረስ ሙሉ እዳዉን ለአመልካች ለመክፈል ይገደዳል፡፡ አመልካች የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቶ ሕንጻ በላይን በነጻ ሲያሰናብት ይግባኝ አለመጠየቁ ወይም ይግባኝ ተይቆ የጸናበት መሆኑ ተጠሪ ዕዳዉን በሙሉ ለመክፈል ባለዉ ኃላፊነት ላይ ለዉጥ አያመጣም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች አመልካች የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቶ ሕንጻ በላይን በነጻ ሲያሰናብት ይግባኝ ጠይቆ ባለማሻሩ ተጠሪ ሙሉ ክፍያ ከፍሎ ግማሹን ከአቶ ሕንጻ በላይ የማስመለስ መብቱን የሚነካ በመሆኑ ተጠሪ ድርሻዉን ወይም ግማሹን ፍርድ እንጂ ግማሹን ለመክፈል አይገደድም በማለት የሰጡት የአፈጻጸም ዉሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል በዋናዉ ፍርድ በወረዳዉ ፍ/ቤት ከተጠሪ ጋር በአንድነትና በተናጠል ለሙሉ ዕዳዉ ኃላፊ ተደርጎ የነበረዉ አቶ ሕንጻ በላይ ይግባኝ ጠይቆ ራሱን ከኃላፊነት ነጻ ባደረገበትና በተጠሪ ላይ በወረዳዉ ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ባልተሻሻለለት ወይም ባልተሻረለት ሁኔታ፤ የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ግማሹን እስከከፈለ ድረስ ግማሹን ወይም የአቶ ሕንጻ በላይን ድርሻ ለመክፈል አይገደድም በማለት የሰጡት የአፈጻጸም ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የሓድነት ምድብ ችሎት በመ/ቁ 04593 ሕዳር 22 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 16754 መጋቢት 11 ቀን 2007 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 75025 ነሐሴ 07 ቀን 2007 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ የጸናው የአፈጻጸም ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የተጠሪ ኃላፊነት አስመልክቶ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዋና ፍርድ በይግባኝ የጸና በመሆኑና በይግባኝ የተሻረዉ የአቶ ሕንጻ በላይ ኃላፊነት ብቻ በመሆኑ ተጠሪ የሚከፍለዉን ገንዘብ ግማሽ ከአቶ ሕንጻ ማስመለስ መቻል አለመቻሉ ግምት ዉስጥ ሳይገባ ለአመልካች እንዲከፈል የተወሰነዉን ሙሉ ገንዘብ ተጠሪ የመክፈል ወይም እንደፍርዱ የመፈጸም ኃላፊነት አለበት ተብሎ ተወስኗል፡፡ የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የሓድነት ምድብ ችሎት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ለአመልካች ያልተፈጸመለትን ቀሪ ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍል በማድረግ ፍርዱን እንዲያስፈጽም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት ጉዳዩ ይመለስለት ተብሏል፡፡ ይጸፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ. 128776

ግንቦት 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-አቶ ገ/ኢየሱስ ሃይሉ አልቀረቡም

ተጠሪ፡-ዳዊት ልዑል አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች የአፈጻጸም ክሳሽ ተጠሪ ደግሞ አፈጻጸም ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች ለአፈጻጸም ችሎቱ ባቀረቡት አቤቱታ ተጠሪ በፍርድ ለአመልካች እንዲከፍሉ የተወሰነባቸውን ገንዘብ ለማስከፈል ተጠሪ ከአመልካች የገዟት የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 03-46545 የሆነች መኪና በባለሙያ በተገመተው ብር 731426.05 / ሠባት መቶ ሠላሳ አንድ ሺህ አራት መቶ ሐያ ሥድሥት ብር ከዜሮ አምሥት ሣንቲም / በሐራጅ ተሸጣ የተጠሪ ዕዳ እንዲከፈል በማለት ለሁለት ተከታታይ ጊዜ ጨረታ የወጣ ቢሆንም መኪናዋ በጨረታ ያልተሸጠች መሆኑን፤የመኪናዋ ግምት ከፍ ያለ እና የማይመጥናት ስለሆነ ልትጫረት ያልቻለች መሆኑን፤ተጠሪ በመሠለው ዋጋ መኪናዋን ሸጦ እንዲሰጣቸው የጠየቁት ቢሆንም መኪናዋን ሸጦ ገንዘቡን ሊሰጣቸው ያልቻለ መሆኑን በመግለጽ በውሳኔው መሠረት በብር 430,000 / አራት መቶ ሠላሳ ሺህ / ሒሳብ የመኪናው ሥመሐብት ወደ ሥማቸው እንዲዛወርላቸው ወይም 3ኛ ጨረታ ከታዘዘ በጨረታው እንዲሳተፉ እንዲታዘዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በሰጡት መልስ መኪናዋ እስካሁን የምትታወቀው በአመልካች ሥም መሆኑን፤አመልካች መኪናዋን እንዳትሸጣት በማለት ማስጠንቀቂያ የሰጣቸው መሆኑን ፤መኪናዋ በመንገድ ትራንስፖርት ግምት የወጣላት በመሆኑ አመልካች መኪናውን ወስደው ቀሪ ገንዘቡን እንዲመልሱልኝ ይታዘዝልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክር መርምሮ መኪናዋ ለሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ልትሸጥ አልቻለችም፤የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2 ሁለተኛ ጨረታ ወጥቶ ተጫራች ካልቀረበ የፍርድ ባለመብት ንብረቱን እንዲረከብ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑ ይደነግጋል፤ለአመልካች ሊከፈል የሚገባው ጠቅላላ ገንዘብ ብር 446,098.57 / አራት መቶ አርባ ሥድሥት ሺህ ዘጠና ሥምንት ብር ከሐምሳ ሠባት ሣንቲም / በመሆኑ እና መኪናዋ የተገመተችው ብር 731,426.05 / ሠባት መቶ ሠላሳ አንድ ሺህ አራት መቶ ሐያ ሥድሥት ብር ከዜሮ አምሥት ሣንቲም / በመሆኑ አመልካች ልዩነቱን ብር 285,327.48 /ሁለት መቶ ሠማንያ አምሥት ሺህ ሦስት መቶ ሐያ ሠባት ብር ከአርባ ሥምንት ሣንቲም / ለተጠሪ ከከፈለ በኋላ መኪናዋን ይረከብ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-አንድ ንብረት ለፍርድ አፈጻጸም ተብሎ ለሐራጅ ሲቀርብ መነሻ ዋጋው ወቅታዊ የንብረቱ ዋጋ መሆን ይኖርበታል፤ወቅታዊ የገበያ ግምቱንም በትራንስፖርት ቢሮ በሚገኝ ባለሙያ ማስገመት ይገባል፤የሽሬ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን የባለሙያ ግምት ሳያገኝ መኪናው ወደ ሐገር ውስጥ ሲገባ ለግብር አከፋፈል ተብሎ በኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የተቀመጠውን ግምት በመነሻነት መውሰዱ ተጫራች እንዳይቀርብ ከማድረጉም በተጨማሪ ከአፈጻጸም ሕግ ድንጋጌዎች ጋር የሚጻረር ነው፤ንብረቱ ለሁለተኛ ጨረታ ቀርቦ ገዢ ከታጣ የፍርድ ባለመብት ንብረቱን እንዲረከብ ተደርጎ ፍርዱ በሙሉ ወይም በከፊል እንደተፈጸመ ይቆጠራል እንጂ የፍርድ ባለመብት ገዢ ያጣውን ንብረት ከግምቱ በላይ ለፍርድ ባለዕዳው ገንዘብ በመመለስ የፍርድ ባለዕዳው ያለአግባብ እንዲበለጽግ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም፤በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡እኛም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባበነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. አመልካች ከጨረታው ቀን በኋላ ያቀረቡት የመኪና ግምት መቃወሚያ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?
2. የአፈጻጸም ችሎቱ በሁለተኛው ጨረታ ተጫራች ስላልቀረበ አመልካች በመኪናዋ ግምት እና ለአመልካች ሊከፈል በሚገባው የገንዘብ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት ከፍለው መኪናዋን ሊረከቡ ይገባል በማለት የሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ

አመልካች ለሐራጅ የቀረበችው መኪና ዋጋ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ አይደለም፤መኪናው ሐገር ውስጥ ሲገባ ለግብር አከፋፈል ተብሎ በኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የተቀመጠለትን ግምት በመነሻነት መወሰዱ ተጫራች እንዳይቀርብ ከማድረጉም በተጨማሪ ከአፈጻጸም ሕግ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ነው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም የመኪናውን ግምት በተመለከተ መኪናው ጨረታ ከመውጣቱ በፊት የተቃወሙ ለመሆኑ የክርክሩ ሒደት አያሳይም፡፡

በፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ ማናቸውም ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በሚወሰንበት ጊዜ የሚሸጠው ንብረት ከትክክለኛው የዋጋ ግምት አላግባብ ከፍ ወይም ዝቅ ተደርጎ እንዳይገመት ለማድረግ እና በንብረቱ ግምት ምክንያት በፍርድ ባለገንዘቡም ሆነ በፍርድ ባለዕዳው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መከላከል እንዲቻል ፍርድ ቤቱ የሐራጁን ሥርዓት አፈጻጸም ለሕዝብ ማስታወቅ እንዳለበት፤የሚሸጠው ንብረት ዓይነት እና ግምት በሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያው ውስጥ ከሚገለጹት ነገሮች ውስጥ አንዱ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 423/1እና2 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡አመልካች የመኪናው ግምት ተጋኗል የሚሉ ከሆነ የጨረታው ቀን ከመድረሱ በፊት የጨረታውን ትዕዛዝ ለሰጠው ፍ/ቤት ግምቱ ተጋኗል በማለት መቃወሚያ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

አመልካች የጨረታው ቀን ከመድረሱ በፊት ግምቱ ተጋኗል በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ ሳይኖር በጨረታው ቀን በቀረበው ግምት መሠረት ተጫራች ስላልቀረበ አስቀድሞ የተያዘው ግምት የገበያን ዋጋ መሠረት አላደረገም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢ አይደለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2 በሁለተኛው የጨረታ ማስታወቂያ በተወሰነው ቀን ተጫራች ያልቀረበ እንደሆነ ማናቸውም ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም እንኳን ለጨረታ የቀረበውን ንብረት የፍርድ ባለገንዘቡ ተረክቦ እንዲይዝ ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል፤ይህም በሆነ ጊዜ ፍርዱ በሙሉ ወይም በከፊል እንደተፈጸመ እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የፍርድ ባለገንዘቡ ለጨረታ የቀረበውን ንብረት እንዲረከብ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው የፍርድ ባለገንዘቡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረቱን ለመረከብ ፈቃደኛ ከሆነ እንጂ ከፈቃዱ ውጪ ንብሩቱን እንዲረከብ የማይደረግ መሆኑን ነው።የፍርድ ባለመብት ንብረቱን ለመረከብ ፍቃደኛ ከሆነ ምላሽ ሊሰጠው የሚገበው ቁልፍ ነጥብ ለጨረታ የቀረበው ንብረት ግምት ለፍርድ ባለገንዘቡ ሊከፈለው ከሚገባው የገንዘብ መጠን የሚበልጥ ከሆነ የፍርድ ባለመብት ልዩነቱን የመክፈል ሀላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለው ነው።

በተያዘው ጉዳይ ለጨረታ የቀረበችው መኪና ግምት ብር 731,426.05 / ሠባት መቶ ሠላሳ አንድ ሺህ አራት መቶ ሐያ ሥድስት ብር ከዜሮ አምሥት ሣንቲም / በመሆኑ እና ለአመልካች ሊከፈል የሚገባ አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ብር 446,098.57 / አራት መቶ አርባ ሥድሥት ሺህ ዘጠና ሥምንት ብር ከሐምሳ ሠባት ሣንቲም / በመሆኑ ለጨረታ በቀረበችው መኪና ዋጋ ግምት እና ለአመልካች ሊከፈል በሚገባው የገንዘብ መጠን መካከል የብር 285,327.48 /ሁለት መቶ ሠማንያ አምሥት ሺህ ሦስት መቶ ሐያ ሠባት ብር ከአርባ ሥምንት ሣንቲም / ልዩነት አለ።
ከላይ በአንደኛው ጭብጥ እንደተገለጸው ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በሚወሰንበት ጊዜ የሚሸጠው ንብረት ከትክክለኛው የዋጋ ግምት አላግባብ ከፍ ወይም ዝቅ ተደርጎ እንዳይገመት ለማድረግ እና በንብረቱ ግምት ምክንያት በፍርድ ባለገንዘቡም ሆነ በፍርድ ባለዕዳው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መከላከል እንዲቻል የሚሸጠው ንብረት ዓይነት እና ግምት በሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያው ውስጥ የሚገለጽ በመሆኑ እና አመልካች የጨረታው ቀን ከመድረሱ በፊት ግምቱን በሚመለከት ያቀረቡት መቃወሚያ የሌለ በመሆኑ አስቀድሞ የቀረበውን የዋጋ ግምት እንደተቀበሉት ግምት የሚወሰድበት ነው።
አመልካች ለጨረታ የቀረበውን የመኪናዋን ዋጋ ግምት ከጨረታው ቀን በፊት ባልተቃወሙበት ሁኔታ በሁለተኛው ጨረታ ተጫራች ስላልቀረበ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍለው በሚገባው የገንዘብ መጠን ልክ መኪናዋን ልረከብ ይገባል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 423 እና 428 ድንጋጌዎች ዓላማ ውጪ በመሆኑ በዚህ አግባብ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም።
የክልሉ ፍ/ቤቶች በሁለተኛው ጨረታ ተጫራች ስላልቀረበ በመኪናዋ ዋጋ እና ለአመልካች ሊከፈለው በሚገባ የገንዘብ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት አመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 423 እና 428 ድንጋጌዎች ዓላማ አኳያ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም በሁለተኛው ጨረታ ተጫራች ባለመቅረቡ ምክንያት የፍርድ ባለመብቱ ለጨረታ የቀረበውን ንብረት እንዲረከቡ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው የፍርድ ባለመብቱ ለጨረታ በቀረበው የገንዘብ መጠን መሠረት ንብረቱን ለመረከብ ፈቃደኛ መሆኑ በቅድሚያ ከተረጋገጠ በኋላ ነው።የክልሉ ፍ/ቤቶች አመልካች ንብረቱን ለጨረታ በቀረበው የገንዘብ መጠን መሠረት ለመረከብ ፈቃደኛ መሆናቸውን በቅድሚያ ሳያረጋግጡ አመልካች በመኪናዋ ዋጋ እና ለአመልካች ሊከፈል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚገባው የገንዘብ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት ከፍለው መኪናዋን ይረከቡ በማለት የሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2 ድንጋጌን ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20344 ሕዳር 09 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ፤በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 81864 የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የክልሉ ፍ/ቤቶች አመልካች ለጨረታ በቀረበው የዋጋ መጠን እና ሊከፈላቸው በሚገባው የገንዘብ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት ከፍለው መኪናዋን ለመረከብ ፈቃደኛ መሆናቸውን በቅድሚያ ሳያረጋግጡ አመልካች ልዩነቱን ከፍለው መኪናዋን እንዲረከቡ በማለት የሰጡት ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2 ድንጋጌን ያላገናዘበ ነው ብለናል፡፡
3. በሁለተኛው ጨረታ ተጫራች ባለመቅረቡ ምክንያት አመልካች ለጨረታ በቀረበው የዋጋ መጠን እና ሊከፈላቸው በሚገባው የገንዘብ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት ከፍለው መኪናዋን እንዲረከቡ ሊገደዱ አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
4. የሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በጨረታ መነሻ ዋጋ ተሸከርካሪውን ለመረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አፈጻጸሙ በፍርድ ባለዕዳው ሌላ ንብረት ላይ እንዲቀጥል በማድረግ ወይም ለጨረታ በቀረበው ተሽከርካሪ ላይ አፈጻጸሙ የሚቀጥልበት አግባብ ካለም ተገቢውን በመፈጸም አፈጻጸሙን እንዲቀጥል ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
5. በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
6. ሚያዝያ 19 ቀን 2009 ዓ.ም በመዝገቡ የተሠጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አምሮዊ ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 104755

ሕዳር 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ዱራታ ባትሪ ካምፓኒ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከንግድ ምልክት ምዝገባ ጋር የተያያዘ ክርክር ሲሆን የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ፅ/ቤት ያቀረበው የምዝገባ ጥያቄ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የአመልካች የንግድ ምልክት ይመዝገብልኝ ጥያቄ በተጠሪ ፅ/ቤት ውድቅ ከተደረገ በኋላ ይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም በተጠሪ ፅ/ቤት እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተፈፀመ የተባለውን የሕግ ስህተት አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ አመልካች ለተጠሪ ፅ/ቤት ሚያዝያ 21 ቀን 2005 ዓ.ም ባቀረበው ማመልከቻ “DURA SUN” የሚል የንግድ ምልክት እንዲመዘገብለት የጠየቀ ሲሆን የአመልካች ጥያቄ ያስተናገደው በተጠሪ ፅ/ቤት ስር የተደራጀው ኢንዱስትራዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት አመልካች እንዲመዘገብለት ያቀረበው “DURA SUN” የንግድ ምልክት በፅ/ቤቱ “DURA CELL” በሚል መጥሪያ ስርተፍኬት ቁጥር 1987 ከተመዘገበ የንግድ ምልክት ጋር በአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀፅ 7/1/ መሰረት ተመሳሳይ በመሆኑ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄው ውድቅ ተደርጓአል፡፡

አመልካች በስራ ሂደቱ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በፅ/ቤቱ ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታው አቅርበዋል፡፡ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ምንም እንኳ ሁለቱ የንግድ ምልክቶች “ዱራ” በሚለው ቃል አንድ አይነት ቢሆኑም “DURA SUN” የሚለው የንግድ ምልክት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአነጋገር፣ በትርጉም እና በአቋሙ ጠቅላላ ሲታይ “DURA CELL” ከሚለው የንግድ ምልክትና ምርቶቹን በተመለከተ ጥሩ ስምና እምነት ያገኘበት በመሆኑ የንግድ ምልክቱ እንዲመዘገብለት ጠይቋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው አጠቃላይ የክርክሩን ይዘት ካሰፈረ በኋላ “DURA CELL” ሎጎ ያለበት የንግድ ምልክት እ.ኤ.አ በ1996 ዓ.ም በፅ/ቤቱ የተቀማጭነት የምስክር ወረቀት በማግኘት በንግድ ምልክቱ ላይ የቀዳሚነት መብት /priority Right/ ያገኘ መሆኑን፣ የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚደረግበት ዋነኛ ምክንያት ፅቃ በማምረት፣ በማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን መልካም ስምና ዝና ለመጠበቅ እንዲሁም በተመሳሳይ ፅቃዎችና አገልግሎቶች መካከል መሳከርን ለማሰገድ ስለመሆኑ፣ በፅ/ቤቱ በቀዳሚነት ከተመዘገቡ የንግድ ምልክቶች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው እና መሳከርን የሚያስከትሉ ፅቃዎች ወይም አገልግሎቶች ሊመዘገቡ እንደማይገባ፤ ሁለቱም የንግድ ምልክቶች በፅይታ፣ በንባብ፣ በድምጸት ተመሳሳይነት ያላቸውና በህብረተሰቡ ዘንድ መሳከርን ሊፈጥሩ የሚችሉ መሆናቸውን ኮሚቴ መገንዘቡን፣ በተመሳሳይ ሁለቱ የንግድ ምልክቶችን ለባትሪ ምርት የሚያገለግሉ በመሆኑና ይህንንም ምርት የሚጠቀሙ ሸማቾች ወይም አግባብነት ያላቸው የሕ/ሰቡ ክፍሎች በአንፃራዊነት ከሌሎች ምርቶች አኳያ ሲታይ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው እና የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚጠቀሟቸው ምርቶች በመሆናቸው ሁለቱም የንግድ ምልክቶች በአግባቡ ለይተው ይገዛሉ ብሎ መናገር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አመልካች “DURA SUN” በሚል መጥሪያ እንዲመዘገብለት የጠየቀው የንግድ ምልክት ጋር ከዚህ በፊት በፅ/ቤቱ ከተመዘገበው “DURA CELL” ሎጎ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይና በሕብረተሰቡ ዘንድ መሳከርን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያል ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት የሰጠው ውሳኔ ኮሚቴው ተቀብሎ አፅንቶታል በማለት ወስኗል፡፡

የፅ/ቤቱ የበላይ ኃላፊም በይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የተሰጠው ውሳኔ በማፅደቅ ለአመልካች አሳውቀዋል፡፡ አመልካች በፅ/ቤቱ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም በተጠሪ ፅ/ቤት እና ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ሁለቱም የንግድ ምልክቶች በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ እንደሆኑ፣ የመጀመሪያ ሶስት ፊደሎች ተመሳሳይ በመሆናቸው ብቻ የንግድ ምልክቶቹ መሳከር ይፈጥራሉ ተብሎ መወሰኑ በአዋጅ ከተቀመጠው ትርጉም ውጭ ስለመሆኑ፣ በንባብ፣ በአተረጓጎምና ድምጸት አንድ ናቸው የተባለውም በአግባቡ አለመሆኑን፣ ፅ/ቤቱ አንድ የህብረተሰብ ክፍል ብቻ መሰረት በማድረግ ምዝገባ መከልከሉ የአመልካች መብት በእጅጉ የጣሰ በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ባቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ እንደገለፀው “ዱራታ” የሚለውን ምልክት አስቀድሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያስመዘገበውና በብዙ ሀገሮች አስመዝግቦ እየተገለገለ የሚገኝበት ከሆነ “DURA SUN” የሚለው “DURA CELL” ከሚለው የንግድ ምልክት ጋር የተመሳሰለ ነው ወይስ አይደለም? ለማለት “DURA” የሚለውን ቃል ለምን ተጠቀመ የሚለውን ምክንያት ለፍርድ ሐተታው እና መነሻ ማድረጉና በዚህም የተነሳ ያሳክራል ከሚል መደምደማያ የደረሰበትን አግባብነት ተጠሪን ባለበት ይጣራ ዘንድ ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠ ሲሆን ዋናው ፍሬ ጉዳይ የአመልካች የንግድ ምልክት ይመዝገብልኝ ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በዕ/ቤቱ ቀደም ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ተመሳሳይነት ያለውና መሳከርን የሚፈጥር መሆኑን ተረጋግጦ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

ጉዳዩ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በዕሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተጠሪ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀም አለመፈፀሙን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም፡- አመልካች እንዲመዘገብለት ያቀረበው የንግድ ምልክት /trade mark/ “DURA SUN” የሚል ነው፡፡ ተጠሪ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በዕ/ቤቱ አስቀድሞ የተመዘገበ “DURA CELL” የሚል የንግድ ምልክት እንዳለና አሁን ለምዝገባ የቀረበው “DURASUN” በዕይታ፣ በንባብ እና በድምጸት ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በህብረተሰቡ ዘንድ መሳከርን ይፈጥራል በሚል መነሻ ነው፡፡ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ዕ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 320/1995 አንቀፅ 6 ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት አንዱ የንግድ ምልክት መመዝገብ ስለመሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 የሰጠበት መሰረታዊ ዓላማ “ዕቃ በማምረት እና በማከፋፈል ወይም አግለግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን መልካም ስም እና ዝና ለመጠበቅ እንዲሁም በተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መካከል መሳከርን ለማሰወገድ የንግድ ምልክት ጥበቃ ማድረግ በማስፈለጉ” እንደሆነ በአዋጅ መግቢያ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት ከቀዳሚ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት የሆነ ወይም መሳከርን ሊያስከትል የሚችል ተመሳሳይነት ያለው የንግድ ምልክት መመዝገብ እንደማይቻል በአንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓአል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በተጠሪ ዕ/ቤት እ.ኤ.አ በ1996 ዓ.ም ተመዝግቦ የተቀማጭነት የምስክር ወረቀት ያገኘ፣ “DURA CELL” ተ ሎጎ ያለበት የንግድ ምልክት መኖሩን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች እንዲመዘገብለት ያቀረበው የንግድ ምልክት “DURA SUN” የሚል መሆኑን አልተካደም፡፡ እነዚህ ሁለት ምልክቶች የጋራ የሆነ “ዱራ” የሚል መነሻ ቃል ያላቸው ከመሆኑ በተጨማሪ በዕይታ፣ በንባብ፣ በድምጸት ተመሳሳይነት ያላቸው ስለመሆኑ የተጠሪ ዕ/ቤት ባደረገው ማጣራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አረጋግጧል፡፡ ምዝገባ የተጠየቀበት የንግድ ምልክት አስቀድሞ ከተመዘገበው የንግድ ምልክት በአብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ወይም ተገልጋዮችና ሸማቾች መሳከርን የሚፈጥር መሆኑን ግንዛቤ ከተወሰደበት ሊመዘገብ እንደማይገባ ከአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀፅ 7 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ አመልካች እንዲመዘገብለት ያቀረበው የንግድ ምልክት “DURA SUN” አስቀድሞ ከተመዘገበው “DURA CELL” ባትሪ ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል መሳከርን የሚፈጥር ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ያቀረበው የምዝገባ ጥያቄ በተጠሪ ውድቅ መደረጉ ከላይ የተመለከተውን አዋጅ ዓላማና ግብ በአግባቡ ተፈፃሚ አድርጎአል ከሚባል በስተቀር በጉዳዩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አያሳይም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 57179 የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በንግድ ምልክት መመሳሰል በአንድ ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ የሕዝብ ግንዛቤ ያዛባ ወይም ሊያዛባ የሚችል፤ በሁለት ድርጅቶች መካከል መሳከርን የሚፈጥር ከሆነ ሕ/ሰቡ ሊያገኝ የሚገባው ሕጋዊ ጥበቃና ዋስትና በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ በተመሳሳይ የንግድ ምልክት ላይ ምዝገባ እንዲደረግ የሚቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ይህ ችሎትም የሰጠው ገዥ የሕግ ትርጉም ደግሞ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በሁሉም ደረጃ ባሉ ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2/1/ ስር ተደንግጓአል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የአመልካች የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ በተጠሪ ውድቅ መደረጉ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በአመልካች ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ መሰረዙ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት የሰጠው ውሳኔ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 148038 በ3/10/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልስናል፡፡የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 120355

ሕዳር 06 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዩ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ ጠበቃ ወርቁ መንገሻ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለጉዳዩ መቅረብ ምክንያት የሆነው አዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24125 መስከረም 14 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት ህዳር 13 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአመልካች የሥር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡-ታህሳስ 10 ቀን 1987 ዓ.ም ከአባታቸው ከአቶ እስማኤል አብዱልዋህድና ከእናታቸው ከወ/ሮ ሳባ አልታሰብ አርባ ምንጭ ከተማ ውስጥ ተወልደው ስማቸው ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ በሚል ተፅፎ የምስክር ወረቀት ማግኘታቸውን፤ በኋላም የእናታቸው ወንድም ሚስት የሆኑት ወ/ሮ መአዛ አዳነ አሻሜ ሮሆቦት አካዳሚ በተባለው ት/ቤት ሲያስመዘግቡ ሀና አዳነ አሻሜ በሚል ስም ያስመዘገቧቸውና በሂደትም በዚህ ስም የልደት የምስክር ወረቀት የወጣላቸው መሆኑን፤ ከዚያም ወደ ወላጆቻቸው አካባቢ በመመለስ አስቀድሞ በወጣላቸው ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ በተባለው ስማቸው እየተጠሩ የቀበሌ አስተዳደር መታወቂያ ወጥቶላቸውና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ተመዝግበው እየተማሩ እንደሚገኙ ገልፀው የስማቸው መጠሪያ በተለያየ አጋጣሚ በተለያየ ስም የተመዘገበ በመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችግር ያስከተለባቸው መሆኑን በመጥቀስ ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ ተብለው እንዲጠሩ እንዲወሰንላቸው አቤቱታ አቅርበው ነበር፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በትክክለኛው ወላጅ አባታቸው በአቶ እስማኤል አብዱልዋሂድ ስም ልጠራ ያሉ በመሆናቸው ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ልጅነትን አረጋግጠው ይቅረቡ በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ በኋላም የሰበር አቤቱታ አቅርበው የነበሩ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታቸው በአጭሩ፡ የአመልካች አቤቱታ የማንንም ጥቅምና መብት የማይነካ፤ በአሳማኝ ማስረጃም ተደግፎ የቀረበ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ከውልደቱ ጀምሮ በወጣልኝ ስም ለመጠራት ያቀረብኩትን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉት ያላግባብ በመሆኑ ሊታረምልኝ ይገባል በሚል ያቀረቡት ነው፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ የሥር ፍርድ ቤቶችን ዳኝነት ተገቢነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ በጉዳዩ ላይ ተጠሪ የሆነ ተከራካሪ ባለመኖሩ መዝገቡ ለምርመራ የቀረበ ነው፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመረነው ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ አመልካች በወላጅ አባታቸው እስማኤል አብዱልዋሂድ ስም መጠሪያቸው እንዲሆን የአቀረቡትን አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉበት አግባብ ተገቢ ነውን? የሚለው ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 32(1) ሥር በመርህ ደረጃ እንደተመለከተው አንድ ሰው የቤተዘመድ ስም፤ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የግል ስሞች እና የአባት ስም እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ ለልጁ አባት ስም የሚሆነውም የአባቱ የግል ስም ለመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 36 ሥር ተመልክቷል፡፡ ስለ ልጅ መወለድ መግለጫ ሊሰጥ የሚገባው ሰው ልጁ ከተወለደበት ቀን አንስቶ በዘጠና ቀናት ውስጥ ለልጁ የተሰጠውን የግል ስም ልጁ በተወለደበት ቀበሌ ለሚገኘው የክብር የመዝገብ ጽ/ቤት መግለጫ የማቅረብ ግዴታ የተጣለበት ለመሆኑም ከፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 37 መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ተወልድኩ በሚሉበት በ1987 ዓ.ም በአገራችን ልደት ጋብቻና ሞት የሚመዘገብ የክብር መዝገብ ሹም በህግ አግባብ ተቋቁሞ በተደራጀ መልኩ ሥራ ላይ ያልነበረ በመሆኑ የአንድ ሰው ስምን በተመለከተ ተደራጅቶ የተጻፈ ማስረጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል። በመሆኑም አመልካች በተወለዱበት ወቅት ልደትን፤ሞትንና ጋብቻን ባግባቡ መዝግቦ ለመያዝ የሚችል የተደራጀ አካል ባለመኖሩ በወላጆች የወጣላቸው ስም በአጎታቸው ሚስት አማካኝነት ተለውጦ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ስሞች መጠራታቸውንና የአባታቸውም ስም በተወለዱበት ጊዜ በሆስፒታሉ የምስክር ወረቀት የሰፈረውና በአሁኑ ጊዜ በቀበሌ መታወቂያቸውና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመዝግበው የሚገኘው ለመሆኑ በፍርድ ቤት እንዲነገርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሥር መዝገቡ ያስረዳል።

አመልካች አሳዳጊያቸው የነበሩት የአጎታቸው ሚስት ባስመዘገቧቸው ሀና አዳነ አሻሜ በሚል ስም ሮሆቦት አካዳሚ ተመዝግበው መማራቸው፤ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም የልደት ምስክር ወረቀት ማውጣታቸውን ገልፀዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ተወለዱበት አካባቢ ተመልሰው ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ በሚል ስም የቀበሌ መታወቂያ በማውጣት እስከ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመዝግበው እየተማሩ እንደሚገኙና ይህ ስማቸው አስቀድሞ በተወለዱበት ጊዜ የወጣላቸውና በሆስፒታሉ ምስክር ወረቀት የተመዘገበ ለመሆኑ እየተከራከሩ ይገኛሉ።

አንድ ሰው የቤተዘመድ ስም እንዲለወጥ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን በዚህ ረገድ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ፍርድ ቤቶች በሶስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በጥንቃቄ በመመርመር ስሙን ለመለወጥ በቂ ምክንያት ሲኖር መለወጥ እንደሚችሉ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 42 ሥር የተደነገገ ሲሆን በዚሁ ህግ አንቀጽ 43 ሥር ደግሞ አንድ ሰው የግል ስሙ እንዲለወጥ ወይም ከብዙዎች የግል ስሞች አንዱ እንዲሰረዝ፤ ወይም ሌላ ግል ስም እንዲጨመርለት ባለጥቅሙ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ ሊፈቀድለት እንደሚችል ተደንግጓል። በዚህ ረገድ የሚቀረቡ ጥቄዎችን ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን ስም በማስተካከል ሊወስኑ እንደሚገባቸው የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 87420 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉበት ምክንያት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ልጅነት ሳይረጋገጥ የአባትን ስም መለወጥ አይገባንም በሚል መነሻ ለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል። አመልካች የጠየቁት ዳኝነት ስሜ ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ ለመሆኑ የሚያመለክቱ ማስረጃዎች ያሏቸው መሆኑን በመግለፅ በተወለዱበት ጊዜ በዚህ ስም ተጠርተው እንደነበርና በሂደት የአጎታቸው ሚስት በአሳዳጊነት ዘመናቸው ስማቸውን የለወጡባቸው መሆኑንና በኋላም ሲወለዱ ወደ ወጣላቸው ስም ተለውጦ እየተጠሩበት እንደሚገኝ ይህንን የሚያስረዱ ማስረጃዎች መኖራቸውን በማጣቀስ እየተከራከሩ ይገኛሉ። ስለሆነም ዋናውና መጣራት ያለበት ነጥብ አመልካች በፍሬ ጉዳይነት የሚያነሱት በየጊዜው በተለያዩ ስሞች የመጠራት ወይም ያለመጠራት ጉዳይ ሊሆን ይገባል እንጂ የአመልካች ወላጅ አባት ማን ነው የሚል ጭብጥ ሊሆን አይችልም። ክርክሩ ያስነሳውን ጭብጥ ፍርድ ቤቶች ምላሽ በሚሰጡበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጊዜ የሶስተኛ ወገኖችን ጥቅም እንዳይጎዳ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የሌላን ሰው ስም ያላግባብ የሚጠቀም ወገን ካለም ህጉ ኃላፊነትን የሚያስከትል ለመሆኑ የደነገገው በመሆኑ ስም ይለወጥለኝ በሚል ጥያቄ የሚያቀርብም ወገን ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ጉዳይን ከቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አንፃር በመመልከትና በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሰ) መሠረት በመቀበል የአመልካችን ስም መለወጥ አስፈላጊ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን በማስረጃ አጣርተውና የሶስተኛ ወገን ጥቅም የማይጎዳ ለመሆኑ ጭምር ካረጋገጡ በኋላ ተገቢውን መወሰን ሲገባቸው ጉዳዩን ከልጅነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ አንፃር በመመልከት ውድቅ ማድረጋቸው አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 4332/07 ሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፤የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24075 ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24125 መስከረም 14 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ጥያቄ የሥም ለውጥ ስለሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሰ) መሠረት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለው ብለናል፡፡
3. በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ስማቸው እንዲለወጥላቸው ያቀረቡትን አቤቱታና ማስረጃ አስቀርቦ በመመርመር የአመልካች ስም መለወጥ በሶስተኛ ወገኖች መብት የሚያስከትለው ጉዳት መኖር አለመኖሩን ጭምር ካጣራ በኋላ ተገቢውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሠረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ክርክር የወጣ ወጭና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነብብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 110507

ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሠለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ጉታ ጫካ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1.የኦሮሚያ ፍትሕ ቢሮ አልቀረቡም

2. አቶ አብዱልወሃብ ተካ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጥብቅና አገልግሎት ላይ በተፈጸመ የሥነምግባር ጥሰት ምክንያት የተሰጠ የዲስፕሊን ውሳኔን የሚመለከት ነው፡፡ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠበቆች የሥነምግባር ጉዳይ ጉባኤ የአሁን አመልካች የጥብቅና አገልግሎት ሲሰጡ ፈጽመውታል በተባለው የሥነምግባር ጥሰት ምክንያት የቀረበባቸውን የዲሲፕሊን ክስ ተመልክቶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በአመልካች ላይ የቀረበው የዲስፕሊን ክስ በአጭሩ፡-

1. ሁለተኛ ተጠሪ ንብረትነቱ የወ/ሮ ላቀች ጎሳዬ በሆነ አይሱዙ ተሽከርካሪ እየተጓዙ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-00972 ኢት የሆነ እና አቶ መሐመድ ይመር የተባለ ግለሰብ ሲነዳው ከነበረ ተሽከርካሪ ጋር በመጋጨት እሳቸውን ጨምሮ በአይሱዙ መኪናው ውስጥ በነበሩ ግለሰቦች ላይ ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ ጉዳቱን አድርሷል በተባለው አቶ መሐመድ ይመር ላይ የወንጀል ክስ ቀርቦበት የነበረ ቢሆንም አመልካች ለግለሰቡ ጥብቅና በመቆም ከወንጀል ክሱ በነጻ እንዲሰናበት በማድረጋቸው፤

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ሁለተኛ ተጠሪ ለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸው በማለት ሲጓዙበት የነበረው አይሱዙ ተሽከርካሪ ባለቤት ወ/ሮ ላቀችኃሳዬ ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች ተከሳሽዋን ወክለው የጥብቅና አገልግሎት በመስጠታቸው፤
3. ሁለተኛ ተጠሪ ካሣ እንዲከፈላቸው ባቀረቡት ክስ ላይ ጣልቃ ገብ ሆኖ ለሚከራከረው የመድን ድርጅት አመልካች ጠበቃ በመሆን በመከራከራቸው ምክንያት አመልካች ሁሉንም ወገኖች በመወከል መከራከር አይችሉም የሚል መቃወሚያ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡ መሆኑን፤ክርክሩን ሲመራ የነበረው ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽን እና ጣልቃገብን በመወከል ክርክሩ እንዲቀጥል ቢደረግ የጥቅም ግጭት ሊኖር አይችልም ለማለት ስለማይቻል እና የጥቅም ግጭቱ ካለ ደግሞ የክርክሩን ሂደት የሚያዛባ በመሆኑ አመልካች ተከሳሽ / የጉዳት አድራሹን መኪና ባለቤት / እና ጣልቃ ገብን / መድን ድርጅትን / ወክሎ መከራከር አይችልም ተከሳሽ ሌላ ሰው በመወከል ወይም በራሷ እንድትከራከር በማለት ብይን የሰጠ መሆኑን፤በዚህ ብይን ላይ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ክርክር ተደርጎበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 90540 የተሰጠውን ብይን ያጸናው መሆኑን በመግለጽ አመልካች የጥብቅና ሙያ የሥነ ምግባር ጥሰት የፈጸሙ በመሆናቸው ቅጣት እንዲተላለፍባቸው የሚል ነው፡፡

አመልካች ለቀረበባቸው የዲሲፕሊን ክስ በሰጡት መልስ አመልካች ተከሳሽ እና ጣልቃ ገብን ወክሎ መከራከር አይችልም በማለት ብይን የተሰጠው ግንቦት 23 ቀን 2004 ዓ.ም በመሆኑ ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፤ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዋጅ ቁጥር 86/96 እንጂ በአዋጅ ቁጥር 182/2005 ሊታይ የማይገባ መሆኑን፤ተከሳሽን በመወከል እንዳይከራከሩ የሚያግዳቸው ሕግ የሌለ መሆኑን፤ተከሳሽ በፍትሐብሔር ጉዳይ ጥፋት የሌለባቸው መሆኑን፤ተከሳሽን ወክለው መከራከራቸው በአመልካች ላይ የሚደርስ ጉዳት የሌለ መሆኑን፤ተከሳሽ ለተሸከርካሪዋ መድን ሽፋን ያላቸው በመሆኑ እና ለመድን ድርጅቱ ጠበቃ በመሆናቸው መድን ድርጅቱን ወክለው መልስ መስጠታቸው ጥፋት አለመሆኑን፤በተከራካሪዎች ላይ ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭት የሌለ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የሥነ ምግባር ጉዳይ ጉባኤ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠው ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 182/2005 መሠረት መታየት የለበትም በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ አመልካች ተከሳሽን እና ጣልቃገብን በመወከል ሊከራከር አይገባም በማለት ታሕሳስ 23 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ብይን በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ክርክር ሲደረግበት ቆይቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠው ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ እና የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠውም አዋጅ ቁጥር 182/2005 ከታወጀ በኋላ በመሆኑ ጉዳዩ በቀድሞ አዋጅ መሠረት መታየት አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት የቀረበው ቅሬታ የሕግ መሠረት የለውም፤የይርጋ መቃወሚያውን በተመለከተ የቀረበው ክርክር በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠው ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ እና 2ኛ ተጠሪ ለጉባኤው አቤቱታ ያቀረቡት ነሐሴ 13 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጓል። በዋናው ጉዳይ ላይም አመልካች የአደጋ አድራሹ መኪና አሽከርካሪ በሆነው ግለሰብ ላይ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በጥብቅና በመከራከር በነጻ እንዲሰናበት አድርጓል፤2ኛ ተጠሪ ባቀረበው የፍትሐብሔር ክስ ላይ ተከሳሽ ለሆኑት የመኪናው ባለቤት እና ጣልቃገብቶ ለተከራከረው መድን ድርጅት በጥብቅና በመወከል የጥቅም ግጭት ባለው ጉዳይ ላይ በመከራከሩ በ2ኛ ተጠሪ ተቃውሞ ቀርቦበት ጉዳዩን ሲያይ የነበረው ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽን እና ጠልቃገብን በመወከል ክርክሩ እንዲቀጥል ቢደረግ የጥቅም ግጭት ሊኖር አይችልም ለማለት ስለማይቻል እና የጥቅም ግጭቱ ካለ ደግሞ የክርክሩን ሂደት የሚያዛባ በመሆኑ አመልካች ተከሳሽ እና ጣልቃ ገብን ወክሎ መከራከር አይችልም በማለት ብይን ሰጥቶበታል፤ይህ ብይን እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ክርክር ተደርጎበት ጸንቷል፤አመልካች በተሰጠው ብይን ላይ የሕግ ሥሕተት ተፈጽሟል በማለት በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ቅሬታ በማቅረብ ክርክሩን አሳግዶ የ2ኛ ተጠሪ ጉዳይ በወቅቱ ውሳኔ እንዳይሰጥበት በማድረግ ላልተገባ ወጪ የዳረገው እና ከፍተኛ መጉላላት እንዲደርስበት ያደረገው በመሆኑ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጠበቆች እና ሕግ ጉዳይ ጸሐፊዎች እና የፈቃድ አሠጣጥ አዋጅ ቁጥር 182/2005 አንቀጽ 36/3/15 መሠረት ከባድ የሥነምግባር ጥፋት ፈጽመዋል በማለት አመልካች ብር 10000 / አሥር ሺህ ብር / የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ እና የጥብቅና ፈቃዳቸው ለ6 ወር ታግዶ እንዲቆይ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል። ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የሥነ ምግባር ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል።በመቀጠል አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም።የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-ጉባኤው አመልካች ተከሳሽን እና ጣልቃገብን በመወከል መከራከር አትችልም በማለት ግንቦት 23 ቀን 2004 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ መጠየቅ አልነበረብህም፤ክርክሩንም ማሳገድ አልነበረብህም በማለት ቅጣት የጣለብኝ ቢሆንም ለቅጣቱ መነሻ ያደረገው ምክንያት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 37 ላይ የተደነገገውን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚቃረን ነው፤በጉባኤው እና በበታች ፍ/ቤቶች ያቀረብኩት የይርጋ መቃወሚያ መታለፉም ተገቢ አይደለም፤ጉዳዩ መታየት የነበረበት ቅጣቱን በሚያከብደው አዋጅ ቁጥር 182/2005 ሳይሆን በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 22 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 86/96 መሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነበረበት፤2ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ወገን ጥቅም የሥነ ምግባር ክስ ማቅረብ ይችላል መባሉ የሰዎችን የመዋዋል ነጻነት የሚነካ ነው፤በሥነምግባር ጉባኤውም ሆነ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ጉዳት አድርሷል ተብሎ በወንጀል የተከሰሰውን ግለሰብ በጥብቅና ወክሎ ተከራክሮ በነጻ እንዲሰናበት ካስወሰነ በኋላ በተሸከርካሪው ባለቤት ላይ የጉዳት ካሣን ማስከፈል በቀረበው ክስ ተከሳሽን እና የመድን ድርጅቱን በመወከል መከራከሩ የጥቅም ግጭት ያስነሳል በማለት መወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደሷቸው ባለመቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ይህ ችሎትም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ብቻ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካች ላይ ጉዳት ሊደረስ የቻለው አመልካች ሲጓዙበት የነበረው መኪና እና የወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ መኪና በመጋጨታቸው ምክንያት መሆኑን፤አመልካች የጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው ክስ የመሠረቱት ሲጓዙበት በነበረው መኪና ባለቤት ላይ መሆኑን፤የኢትዬጲያ መድን ድርጅት 1ኛ ጣልቃገብ መሆኑን፤ወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ 2ኛ ጣልቃገብ መሆናቸውን እና አመልካች የወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ መኪናአሽከርካሪ ነው በማለት በወንጀል ተከሶ ለነበረው ግለሰብ፤ለተከሳሽ እና ለ1ኛ ጣልቃገብ ጠበቃ በመሆን መከራከራቸውን ነው፡፡የሥነምግባር ጉባኤው አመልካች የጥብቅና ሙያ ሥነምግባር ጥሰት ፈጽመዋል በማለት የቅጣት ውሳኔ ሊያስተላልፍ የቻለው አመልካች ጉዳት አድርሷል የተባለውን ተሽከርካሪ ሲያሽከረክር በነበረው ግለሰብ ላይ የቀረበውን የወንጀል ክስ ለግለሰቡ ጠበቃ ሆነው በመከራከር በነጻ እንዲሰናበት አድርገዋል፤ተጠሪ ለደረሰባቸው ጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው ተሳፍረው ሲጓዙበት በነበረው ተሽከርካሪ ባለቤት ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች ተከሳሽዋን በመወከል ተከራክረዋል፤በክርክሩ ጣልቃገብ ሆኖ ለሚከራከረው መድን ድርጅትንም በመወከል ተከራክረዋል፤ተጠሪ ጠበቃው ለተከሳሽ እና ለጣልቃገብ በጥብቅና በመወከል መከራከር አይችሉም በማለት ባቀረቡት ተቃውሞ ጉዳዩን ሲመራ የነበረው ፍ/ቤት የጥቅም ግጭት ሊፈጠር ስለሚችል አመልካች ተከሳሽን እና ጣልቃገብን በመወከል መከራከር አይችሉም ተከሳሽ ራሳቸው ወይም ሌላ ጠበቃ በመወከል ይከራከሩ በማለት ብይን ሰጥቷል፤አመልካች በዚህ ብይን ላይ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተከራክረውበት ብይኑ ጸንቷል፤አመልካች ክርክሩን በማሳገድ እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች በተሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ በማቅረብ 2ኛ ተጠሪን ላልተገባ ወጪ ዳርገውታል ከፍተኛ መጉላላትም አድርሰውበታል በሚል ነው፡፡ጉባኤው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ ለመስጠት በዋነኝነት የሰጠው ምክንያት አመልካች የጥቅም ግጭት በሚፈጥር ሁኔታ ጉዳዩን በአግባቡ የሚያውቁ ሆኖ ሳላ በጉዳዩ በወንጀል ተከሳሽ ለነበረ እና የፍ/ብሔር ክስ ለቀረበባቸው ተከራካሪ ወገኖች ጥብቅና በመቆም ተከራክረዋል፡፡ይህም የጥቅም ግጭት የሚፈጥር መሆኑ ተረጋግጦባቸው እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተወስኖባቸዋል የሚል ምክንያት ነው፡፡ጉባኤው አመልካች ለተከሳሽ እና ለጣልቃገብ መከራከር አትችልም በማለት በሰጠው ብይን ላይ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ይግባኝ በመጠየቅ እና ክርክሩን በማሳገድ ጉዳዩ በጊዜ እንዳይወሰን በማድረግ 2ኛ ተጠሪን ለአላስፈላጊ ወጪ ዳርገዋል በማለት የሰጠው ምክንያት በአመልካች ላይ ለተጣለው የዲስፕሊን ቅጣት ብቸኛ ምክንያት ሳይሆን ተጨማሪ ምክንያት በመሆኑ አመልካች ጉባኤው ለውሳኔው መሠረት ያደረገው ምክንያት ለተጣለባቸው የዲስፕሊን ቅጣት ብቸኛ ምክንያት እንደሆነ በመውሰድ በጉባኤው የተሰጠው የዉሳኔ ምክንያት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 37 ላይ የተሰጠውን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚጻረር ነው በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢ አይደለም፡፡

አመልካች በ2ኛ ተጠሪ የጉዳት ካሣን በተመለከተ የፍ/ብሔር ክስ በቀረበባቸው ተከሳሽ እና ጣልቃገብን በመወከል መከራከር አይችሉም፤ተከሳሽ ራሳቸው ወይም ሌላ ጠበቃ በመወከል ይከራከሩ ተብሎ በተሰጠው ብይን ላይ ባቀረቡት ቅሬታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 90540 የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የመድን ውሉን መነሻ በማድረግ በስር ተከሳሿ ላይ ጭምር ክርክር ሊያቀርብ የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ስለሚችል የስር ተከሳሿ እና የኢትዮጵያ መድን ኢንሹራንስ ጥቅም ሊጻረር የሚችልበት አጋጣሚም ሊኖር የሚችል መሆኑን፤በ2ኛ ተጠሪ ላይ ለደረሰው አደጋ ምክንያት የሆኑት 2ኛ ተጠሪ ሲጓዙበት የነበረው መኪና ባለቤት እና ከዚህ መኪና ጋር የተጋጨው መኪና ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ ጉዳቱ በሌላው መኪና አሽከርካሪ ጥፋት ምክንያት የደረሰ ስለሆነ ኃላፊነቱ እኔን አይመለከተኝም በሚል አንዱ የሌላውን ጥቅም በሚፃረር መልኩ አንዳቸው በሌላኛው ላይ ክርክር ሊያቀርቡ የሚችሉበት አጋጣሚም ያለ መሆኑን፤አመልካች ወ/ሮ ዘይነባ መሐመድን መኪና አሽከርካሪ ነው ተብሎ ተከሶ የነበረውን ግለሰብ ወክሎ በወንጀል ሲከራከር በነበረበት ጊዜ በወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ በኩል ሊነሱ የሚችሉትን ክርክሮች እና እንዲሁም ከሙያው ጋር ተያይዞ ሊያገኛቸው የሚችሉትን ሌሎች መረጃዎችንም አጋጣሚውን በመጠቀም ማወቁ ወይም ማግኘቱ የማይቀር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ ጋር ተፃራሪ ጥቅም ሊኖራቸው ከሚችሉት 2ኛ ተጠሪ ተሳፍረው ሲጓዙበት የነበረው መኪና ባለቤት እና ለመኪናዋ የመድን ሽፋን የሰጠውን መድን ድርጅት ወክሎ መከራከሩ እና በተከሳሽዋ እና በመድን ድርጅቱ መካከል የጥቅም ግጭት ሊኖር የሚችልበት አጋጣሚ እያለ ሁለቱን ወክሎ መከራከሩን የሙያውን ስነ-ምግባር መርሆዎችን የሚጥስ ከመሆኑም ባሻገር የጠበቆች ስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

10፣11፣12 እና 13 ድንጋጌዎች ይዘት ፣አላማ እና መንፈስ ጋርም የተጣጣመ አይደለም በማለት አመልካች ተከሳሽን እና ጣልቃገብን ወክሎ መከራከር አይችልም በማለት የተሰጠውን ብይን አጽንቶታል፡፡

የሥነምግባር ጉባኤው ከላይ የተገለጸውን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሠረት በማድረግ አመልካች የጥቅም ግጭት ሊፈጠር በሚችልበት ሁኔታ የተለያዩ ተከራካሪዎችን በመወከል መከራከራቸው በፍ/ቤት ውሳኔ የተረጋገጠባቸው መሆኑን፤ይህ ድርጊታቸውም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጠበቆች እና ሕግ ጉዳይ ጸሐፊዎች እና የፈቃድ አሠጣጥ አዋጅ ቁጥር 182/2005 አንቀጽ 36/3/15 ድንጋጌን የሚጥስ እና ከባድ የሥነምግባር ጥሰት መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ የጉባኤው ውሳኔ አመልካች ባቀረቡት ቅሬታ ላይ ይህ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ መሠረት ያደረገ እና የአመልካች ድርጊትም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት የሥነምግባር ደንብ የሚጥስ በመሆኑ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔም ሆነ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠበቆች የሥነምግባር ጉዳይ ጉባኤ በ16/06/07 ዓ.ም ተሠጥቶ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 201729 ሚያዚያ 01 ቀን 2007 ዓ.ም በውሳኔ፤በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 204457 ሚያዚያ 13 ቀን 2007 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.108692

ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተሽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሠናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የትግራይ ክልል ዐቃቤ ህግ

ተጠሪ፡-አቶ ገብረአርዕያ አሰፋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በሥልጣን አላግባብ የመገልገል የደንብ መተላለፍ ጥፋት አልፈፀመም በማለት የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? ሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የታየው በሐውዜን ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪና ሌሎች በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆኑ ሰዎች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 796 የተመለከተውን በመተላለፍ፤ ሐውዜን ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሆነው ሲሰሩ መጣራት የሚገባውን ነገር ሣያጣሩና አቶ ሃይላይ ገራስና ወ/ደብረብርሃን አረጋዊ እህታቸው እንደፈረሙ በማሰብ ፈርመናል ብለውናል በማለት ግንቦት 7 ቀን 2009 ዓ.ም ዕርቅ በማፅደቅና የአቶ ሃይላይ ገራስ ጋብቻ ፈርሷል የሚል ማስረጃ ለመቀሌ ማዘጋጃ ቤት በመላካቸው በሥልጣን አላግባብ ወንጀልፈፅመዋል የሚል ክስ አቅርቧል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች የቀረበበትን የወንጀል ክስ ክዶ ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሶስት ምስክሮች በማቅረብ፤ ከተጠሪ ፊት ያልቀረቡት አቶ ሀይላ ገራስና ወ/ደብርሃን አረጋዊ ለማህበራዊ ዳኞች ፊት ቀርበው ሣይፈርሙ፤ የፈረሙ በማስመሰልና የዕርቅ ሰነድ በማፅደቅ ለመቀሌ ማዘጋጃ ቤት ማስረጃ ልኳል በማለት የመሰከሩ ሲሆን፤ የፅሑፍ ማስረጃም አመልካች አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ የተጠቀሰበትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወንጀል ህግ አንቀጽ 796 በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ነው በማለት በሁለት ወር እስራት ተጠሪ እንዲቀጣና ቅጣቱ በሁለት ዓመት የመከራ ጊዜ እንዲገደብ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አፅንቶታል፡፡

3. ተጠሪ የበታች ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ችሎት የሰበር አቤተታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪ በህግ የተሰጠውን ሥልጣን አላግባብ ስለመገልገሉ፣ የአመልካች ተጠሪ ፈፅሞታል በማለት የሚዘረዝረው የተረጋገጠው ፍሬ ነገር አያሳይም፡፡ የተጠሪ ተግባር ወንጀል የሚያቋቁም አይደለም በማለት ተጠሪ ከተሰሰበት ወንጀል በነፃ እንዲሰናበት በማለት ውሣኔ ተስቷል፡፡ አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ታህሳስ 21 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበሲሆን፣ ተጠሪ የወ/ሮ ምዕላል ወላጆች ያልፈረሙበትን ሰነድ እንደፈርሙበት በማስመሰልና በችሎት ሣይቀርቡ ቀርበዋል በማለት ማስረጃ መስጠቱ፤ በግል ተበዳይ ላይ ጉዳት ማድረሡ በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም መባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መምህር የማነብርሃን እና ወ/ሮ ምዕላል ሃይላይ የሥጋ ዝምድና ያላቸው መሆኑን በፖሊስ ጣቢያ ከተካሰሱ በኋላ ቤተዘመድ የተራቁ መሆኑን በመግለፅ የሰጠሁት ማስረጃ ስህተት የለበትም በወንጀልም አያስጠይቀኝም በማለት ግንቦት 17 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 796 የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋት ፈፅሟል በማለት ክስ የቀረበበት፣ ተጠሪ ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር ሆኖ የሀውዜን ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ሲሰራ፣ መምህር የማነብርሃን ከወ/ሮ ምዕላል ሃይላይ ጋር ጋብቻ የሚከለክል የሥጋ ዝምድና ያላቸው መሆኑን የሚገልፅ ግንቦት 17 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የዕርቅ ሰነድ በማፅደቅ መጋቢት 2 ቀን 2002 ዓ.ም ከተፃፈ ከመሸኛ ደብዳቤጋር ለመቀሌ ማዘጋጃ ቤት ልከዋል በማለት ነው፡፡

ተጠሪና ሌሎች የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች አፀደቁት የተባለው የዕርቅ ሰነድ መነሻው በሐውዜን ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ያቀረበን የወንጀል ክስ ቀሪ ለማድረግ፤ የወንድና የሴት ቤተዘመዶች ሶስት ሽማግሌዎች ባሉበት የታረቁ መሆኑን የሚገልፅናከአንደኛ እስከ አምስተኛ ስማቸው የተገለፀው ሰዎች የፈረሙ መሆኑን የሚገልፅና 6ኛ ምዕላል ሃይላይ አልፈረመችም የሚልና የአስታረቁትን ሶስት ሰዎች ስም የያዘ መሆኑንና ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሌሎች የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር በመሆን የምስክሮችን ቃል ሰምቶ፤ ማስረጃ የሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

5. አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ ከሌሎች ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር ሆኖ ማጣራት የሚገባውንና ፍሬ ነገር ሣያጣራ በወቅቱ የዕርቅ ሰነዱን ለማፅደቅ በማህበራዊ ፍርድ ቤት ያልቀረቡ የወ/ሮ ምዕላል ሃይላይ ወላጆች፣ ችሎት የቀረቡ መሆኑን በአግባቡ ሣያረጋግጥ፣ በችሎት እንዲቀርቡ በማስመሰል ማስረጃ ሰጥቷል በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ከሌሎች የሀውዜን ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር በመሆን፣ ምስክሮችን በመስማት መምህር የማነብርሃን ወ/ሮ ምዕላል ሀይላይ በትግራይ ክልል የቤተሰብ ህግ መሠረት ጋብቻ እንዳይፈፅሙ የሚከለክል የሥጋ ዝምድና ያላቸው መሆኑን በመግለፅ፣ የዕርቅ ሰነዱን የምስክሮች ቃል ያረጋገጡ መሆኑን ገልፀው ለመቀሌ ማዘጋጀ ቤት ማስረጃ መስጠታቸው ተረጋግጧል፡፡

6. ተጠሪ ማስረጃውን አጣርቶ የሰጠው ከሌሎች የሀውዜን ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር በመሆንና በችሎት በመሰየም እንደሆነ በመከላከያ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የሀውዜን ከተማማህበራዋ ፍርድ ቤት ዳኞች /ተጠሪን ጨምሮ /ይህንን ማስረጃ የሰጡት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ንዑስአንቀጽ 1 1985 በወጣው የትግራይ ክልል ሕገ መንግስት 89 እንደተሻሻለ እና በትግራይ ክልል ምክር ቤት ባወጣው የቤተሰብ ሕግ መሠረት በተሰጣቸው የዳኝነት ነክ ሥልጣን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ይህ ከሆነ፣ ተጠሪ በሕግ የተሰጠውን የዳኝነት ነክ ተግባሩን ከሌሎች ዳኞች ጋር በሚወጣበት ወቅት፤ የፍርድ ሥራ ስህተት በይግባኝ፤ በሰበር ወይም በሌላ በሕግ በተዘረጋ የፍርድ ሥራ ስህተት ማረሚያ መንገዶች የሚመለከታቸው ግለሰቦች አቅርበው እንዲያሳርሙ ከሚደረግ በስተቀር፣ ተጠሪ በተናጠል የወንጀል ህግ አንቀጽ 796 በመተላለፍ በሥልጣን አላግባብ የመገልገል ወንጀል ፈፅሟል በማለት የወንጀል ክስ የሚቀርብበትና ኃላፊ የሚሆንበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር ተጠሪ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 67011 ጥቅምት 14 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ. 128466

ሰኔ 29 ቀን 2009ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ እንዳልካቸዉ ይላቅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ሕግ ሙዕዝ ገ/ሉዑል ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ ተጠሪ መ/ቤት የዲሲፕሊን ኮሚቴ የሰጠው የዲሲፕሊን ውሣኔ ለተጠሪ መ/ቤት የበላይ ሀላፊ ቀርቦ በመጽደቁ አመልካች ይግባኛቸውን በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 29 መሰረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ከፍተኛው ፍ/ቤትም መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዘጋቱ አመልካች የተሠጠዉ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የሰበር አቤቱታቸውን ስላቀረቡ ነው፡፡

ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሣኔ መነሻ ወ/ሮ አበባየሁ አያሌዉ መጋቢት 25 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረቡት አቤቱታ ሲሆን ይዘቱ፡- ከአሁኑ አመልካች ጋር ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ዉል ባላቸዉ የቤት ክርክር ጉዳይ ክስ መስርተዉ እንዲከራከሩ ለጊዜዉ ቅድመ ክፍያ ብር 25,000 እና ለመዝገብ ማስከፈቻ ብር 2,000 ከፍለዉ ወደ ዉጭ አገር መሄዳቸዉን ገልጸዉ ከ3 ዓመት በኃላ ወደ አገር ሲመለሱ አመልካች ክስ ሳይመሰርቱ በመቆየታቸዉ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸዉ መሆኑን ገልጸዉ ተገቢዉ እርምጃ እንዲወሰድላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ከዲስፒሊን ክስ አቅራቢ ጋር የጥብቅና አገልግሎት ዉል ማድረጋቸዉን አምነዉ ብር 25,000 ሳይቀበሉ ዉጪ አገር ከሄዱ በኃላ እንዲልኩ ተስማምተዉ እንደተቀበሉ አድርገዉ የፈረሙ መሆኑን፤ የፋይል ማስከፈቻ ብር 2,000 ያልተቀበሉ መሆኑን፤ ክስ ሳይመሰርቱ የቀሩበት ምክንያት ለክሱ የሚያስፈልጉ ምስክሮችንና መረጃ ደንበኞቸዉ ሳትሰጥ ወደ ዉጭ አገር በመሄዷ እንደ ሕግ ባለሙያ ማስረጃ ሳይያያዝ ክስ መመስረት ስለማይቻል እንጂ በጥፋት ባለመሆኑ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡ የዲስፒሊን ክስ አቅራቢ በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ ለአሁኑ አመልካች አስፈላጊዉን የወራሽነትና ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎችን እንዳስረከቡትና የሰዉ ምስክሮችንም ዝርዝር ሰጥተዉ ወደ ዉጭ አገር እንደሄዱ ከገለጹ በኃላ የግራቀኙን ምስክሮች ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት ግራቀኙ ታሕሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ ስምምነት የአሁኑ አመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ በመክፈል የተፈራረሙትን አያይዘዋል፡፡ የዲስፒሊን ኮሚቴዉ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በጠበቆች የስነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4 መሰረት ዉል ከመፈጸማቸዉ በፊት ስለሚይዙት ጉዳይ ህጋዊነትና በማስረጃ የተደገፈ ስለመሆኑ እና ማስረጃዎችና ምስክሮች ተሟልተዉ የቀረቡ መሆኑን ማረጋገጥ ሲገባቸዉ ዉል ከመፈጸማቸዉ በፊት ምስክሮችና ማስረጃዎች መሟላቱን አለማረጋገጣቸዉ የአመልካች ጉድለት እንጂ የደንበኞቸዉ ችግር አይደለም፤ ደንበኞቸዉ ከአገር ዉስጥ የሌሉ መሆኑን እያወቁ ከ3 ዓመት በላይ ክስ ሳይመሰርቱ በመቆየታቸዉ ጥፋተኛ ናቸዉ በማለት በብር 5,000 እንዲቀጡ የወሳኔ ሀሳብ ለተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አቅርቦ በማስጸደቅ አስወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት፡- የስር አቤቱታ አቅራቢ ታህሳስ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ለጉባኤዉ ያቀረብኩት ክስ ስህተት ነዉ፤ ጠበቃዉ የፈጸመዉ ምንም ዓይነት ጥፋት የለም፤ ክስ ሳይመሰርት የቆየዉ እኔ ማስረጃዎችን ለጠበቃዉ ባለመስጠቴ እና አሟልቼ ባለማስረከቤ ነዉ በማለት የራሷ ጥፋት መሆኑን አረጋግጣለች፡፡ በነጻ እንድሰናበትም አመልክታ እያለ ምንም ዓይነት ጥፋት ሳይኖር ጥፋተኛ ተብዬ ብር 5,000 መቀጣቴ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ሁለቱ የጉባኤ አባላት በዉሳኔ ሀሳቡ ያልፈረሙበት በመሆኑ ባልተሟላ ጉባኤ የተሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት ነዉ፡፡ ክሱ ከቀረበ 1 ዓመት ከ12 ቀን በኃላ የተሰጠ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 119/92 መሰረት በ9 ወር ይርጋ ቀሪ ነዉ፡፡ በመሆኑም ዉሳኔዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ይሻርልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የስር አቤቱታ አቅራቢ ጥፋተኛ እኔ ነኝ፤ አማልካች አይደለም በማለት በጽሁፍ ለጉባኤዉ አመልክተዉ ሳለ እንዲሁም የስር አቤቱታ አቅራቢ የሚኖሩት በዉጭ አገር በመሆኑ ክሱን ለመመስረት የሰዉ ማስረጃ ስም ዝርዝር ባልሰጡበት ሁኔታ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥፋተኛ ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቀባበል ክርክር ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት፡- አመልካች በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4 መሠረት ጉዳዩን ተቀብሎ የጉዳዩን ፍሬ ነገር እና ማስረጃዎች ሳይመረምሩ በጥብቅና አገልግሎት ስም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ማስረጃዎች ሳይሟሉ ዉል ተዋውለዉ ጉዳዩን መያዙ በራሱ የስነ-ምግባር ጥሰት በመሆኑ የግል ተበዳይ ጥፋተኛ እኔ ነኝ በማለት በጽሁፍ ለጉባኤዉ ማመልከታቸዉ የተፈጸመዉን የዲስፒሊን ጉድለት የሚያስቀር አይደለም፡፡ የጉባኤዉ አባላት አብዛኛዎቹ እስከተገኙ ድረስ ጉባኤዉ ዉሳኔ መስጠት ስለሚችል የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 119/92 አንቀጽ 24(8) መሠረት በ6 ወር የወሳኔ ሀሳቡን ማቅረብ ካልቻለ በጽሁፍ ተጨማሪ ጊዜ መጠየቅ ስለሚችል በይርጋ አልታገደም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች ከስር አቤቱታ አቅራቢ ጋር ቤት ክርክርን አስመልክቶ ክስ እንዲመሰርቱ የጥብቅና አገልግሎት ዉል ካደረጉ እና ቅድመ ክፍያ ከተቀበሉ በኃላ አቤቱታ አቅራቢ ዉጭ አገር ከሄዱበት ከ3 ዓመት በኃላ ሲመለሱ ክስ ሳይመሠርቱ ቆይተዋል፡፡ አመልካች ክስ ላለመመስረታቸዉ የሰጡት ምክንያት የስር አቤቱታ አቅራቢ ወይም ደንበኛቸዉ የምስክር ዝርዝር ሳይሰጡ ዉጭ አገር በመሄዳቸዉ ያለማስረጃ ክስ መመስረት ስለማይችሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የስር አቤቱታ አቅራቢ ለጉባኤዉ በሰጡት መልስ የምስክር ዝርዝርና የወራሽነት ማስረጃ ሰጥተዉ እንደሄዱ ቢከራከሩም የግራቀኙን ምስክሮች ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት ግራቀኙ ታርቀዉ አመልካች ቅድመ ክፍያዉን መልሰዉ ደንበኛቸዉ ደግሞ የምስክር ዝርዝር ሳይሰጡ በመሄዳቸዉ ምክንያት ክስ ያለመመስረቱና አሁን በሌላ ጠበቃ በጉዳዩ ክስ ተመስርቶ በክርክር ሂደት ላይ የሚገኝ በመሆኑ አመልካች ጥፋት የሌለባቸዉ መሆኑን ገልጸዉ የተስማሙበትንና የተፈራረሙበትን ታሕሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም የተዘጋጀ ሰነድ አቅርበዋል፡፡ ጉባኤዉ የስር አቤቱታ አቅራቢ የምስክር ዝርዝር ሳይሰጡ መሄዳቸዉ ለክሱ አለመመስረት ምክንያት ሊሆን ቢችል እንኳ ከጅምሩ ምስክሮችና ማስረጃ መሟላቱን ሳያረጋግጥ የጥብቅና አገልግሎት ዉል ፈርመዉና ዉክልና ተቀብለዉ ቅድመ ክፍያ መቀበላቸዉ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4 መሠረት አንድ ጠበቃ የጉዳዩን ፍሬ ነገርና ማስረጃዎች ከመረመረ በኃላ ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት የሌለዉ ከሆነ ጉዳዩን መያዝ የለበትም የሚለዉን ክልከላ ተላልፏል በማለት አመልካችን ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የክርክሩ አብይ ጭብጥ የደንቡ አንቀጽ 4 የምስክርን ዝርዝር ሳይቀበሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጥብቅና አገልግሎት ዉል መዋዋልን ይከለክላል ወይስ አይከለክልም የሚለዉ በመሆኑ የድንጋጌዉን ይዘትና ትርጉም መመልከቱ ተቃሚ ነዉ፡፡

በመሠረቱ የደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4 ማንኛዉም ጠበቃ የሕግ አገልግሎት ለማግኘት የመጣ ደንበኛን ጉዳይ ተቀብሎ የጉዳዩን ፍሬ ነገርና ማስረጃዎች ከመረመረ በኃላ ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት የሌለዉ ከሆነ ጉዳዩን መያዝ የለበትም፡፡ ሆኖም ለሰጠዉ የሕግ ምክር አገልግሎት ተገቢዉን ክፍያ ተቀብሎ ደንበኛዉን ያሰናብታል በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ አንድ ጠበቃ ከጅምሩ የሕግ መሠረት የሌለዉና አዋጭ አለመሆኑ የተረጋገጠን ወይም ተከራክሮ የመርታት ዕድል የሌለዉ መሆኑን እያወቀ ደንበኛዉን አላስፈላጊ ለሆነ ክርክርና ወጪ መጋበዝ የሌለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ጠበቃዉ የጥብቅና አገልግሎት ዉል ከመዋዋሉ በፊት ማስረጃ ሰብስቦ ማጠናቀቅ ይገባዋል ወይም ምስክሮችን አስቀርቦ መጠየቅና የሚያዉቁትን አስቀድሞ ማወቅ አለበት ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ደንበኛዉን ሲቀበል የጉዳዩን ይዘት ደንበኛዉን በማነጋገር መረዳት፣ ደንበኛዉ በእጁ የያዘዉ ሰነድ ካለ ተቀብሎ የማስረጃዉን ይዘት መመልከት እና ክሱ የሕግ መሠረት ያለዉ መሆን አለመሆኑን መገንዘብ ያለበት መሆኑን በቅድመ ሁኔታ የሚያስቀምጥ እንጂ ከጥብቅና አገልግሎቱ በፊት ማስረጃ አሰባስቦ እንዲጨርስ የሚያስገድድ አይደለም፡፡ ክሱን ማዘጋጀትና በደንበኛዉ እንዳሉ የተገለጹ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ እና ማደራጀት የግድ ከዉሉ በፊት አስቀድሞ መጠናቀቅ ያለበት አይደለም፡፡ ጠበቃዉ ዉል ካደረገና በማስረጃ መሰበሰብ ሂደት ላይ ወሳኝ የሆነ ማስረጃ እንደሚያስፈልግ ቢገነዘብ እና ደንበኛዉን በማነጋገር ማስረጃዉን ማግኘት የደንበኛዉን ጥቅም የበለጠ የሚያስጠብቅ ሆኖ ሲያገኘዉ ክስ መመስረቱን አቁሞ ደንበኛዉን ማነጋገርና ማስረጃዉን ማግኘት ከጠበቃዉ የሚጠበቅ ተግባር እንጂ በቅድሚያ መሟላቱን ሳታረጋግጥ ዉል ያገዘክ የሚያስብል አይደለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በአመልካችና በደንበኛቸዉ መካከል ታሕሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገዉ የስምምነት ሰነድ ሰፍሮ እንደሚገኘዉ በአሁኑ ወቅት ጉዳዩ በሌላ ጠበቃ አማካይነት ክስ ተመስርቶ በክርክር ሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑ መገለጹ ከጅምሩ አመልካች የሕግ መሠረት የሌለዉ መሆኑን እያወቀ የጥብቅና አገልግሎት ዉል ገብቷል የሚያስብል አይደለም፡፡ እንዲያዉም አመልካች ከደንበኛዉ የተሰጡትን ሰነዶችን ብቻ መሠረት በማድረግ ደንበኛቸዉ ዉጭ አገር በመሆናቸዉና ሊያገኛቸዉ ስላልቻለ ብቻ የምስክሮችን ዝርዝር ለፍ/ቤት ሳያቀርብ ወይም ዝርዝራቸዉን አቅርቦ ያሉበትን አድራሻ ሳያዉቅና ሳያገኛቸዉ ክስ ቢመሰርት የደንበኛዉን ጥቅም የሚጎዳ ሊሆን ስለሚችል የስነ-ምግባር ጥሰት ሊሆን በቻለ ነበር፡፡ አመልካች ክስ ሳይመሰርቱ ለመቆየታቸዉ ደንበኛቸዉ ዉጭ አገር መገኘታቸዉ እና የምስክሮች ዝርዝር ያለማቅረባቸዉ መሆኑን ምንም እንኳ ክሱ ከቀረበ በኃላ ቢሆንም የስር አቤቱታ አቅራቢ ከላይ በተጠቀሰዉ ሰነድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ ፈርመዉ ባረጋገጡበት፤ ይህ ላለመሆኑና የምስክሮች ዝርዝር ለአመልካች ተሰጥቶት የነበረ ስለመሆኑ በማስረጃ ባልተረጋገጠበት እንዲሁም የስር አቤቱታ አቅራቢ ወጭ አገር የነበሩ በመሆናቸዉ ከአመልካች ጋር የነበራቸዉ ግንኙነት ተቋረጦ የነበረ መሆኑ ክስ ላለመመስርቱ የራሱ አሉታዊ አስተዋጽኦ የነበረዉ መሆኑ መረጋገጡ፤ ደንበኛቸዉ አገር ዉስጥ ቢሆኑ ኖሮ ችግሩ ሊከሰት የማይችል መሆኑን ግምት የሚወሰድበት ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር ጉባኤዉ የስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4ን በተሳሳተ መንገድ በመገንዘብና በመተርጎም አመልካችን የስነ-ምግባር ጥሰት ፈጽሟል በማለት ጥፋተኛ ማድረጉም ሆነ በብር 5,000 መቅጣቱ ተገቢ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች በገባዉ የጥብቅና አገልግሎት ዉል መሠረት ክሱን ሳይመሠርት የቆየዉ ደንበኛቸዉ የምስክሮችን ዝርዝርና አድራሻ ሳይሰጡ ዉጭ አገር በመሄዳቸዉ መሆኑ ታሕሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገዉ የእርቅ ስምምነት ደንበኛቸዉ ባረጋገጡበት፤ ስምምነቱ በተደረገበት ወቅት ክሱ ተሟልቶ ቀርቦ በፍርድ ቤት ክርክር ሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑ በተገለጸበት እና ጉዳዩ የሕግ መሠረት የሌለዉ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጉባኤዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4 መሰረት የጥብቅና አገልግሎት ዉል ከመገባቱ በፊት ማስረጃ ተሰብስቦና ተመርምሮ መጠናቀቅ እንደሚገባዉ ድንጋጌን በተሳሳተ መንገድ በመገንዘብና በመተርጎም አመልካችን ጥፋተኛ በማድረግ በብር 5,000 እንዲቀጣ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባኤ መጋቢት 03 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በፍትህ ሚኒስትሩ መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ/ም ጸድቆ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 173828 የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 52/92 አንቀጽ 4 የተመለከተዉን ተላልፈዋል ተብለዉ በስር ጥፋተኛ መባላቸዉም ሆነ የብር 5,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ሆኖ ባለመገኘቱ ተሽሯል፡፡ አመልካች በነጻ ይሰናበታሉ ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ.135094

ግንቦት 21 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ዳዊት በላይ -- አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ደነቀ አበበ -- ጠበቃ መኮንን ኃ/ስላሴ ጋር ቀረቡ

2. ዶ/ር ዉብሸት ዝቅአለ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግልግል ጉባኤ ዳኛ ሆኖ የተሰየመ ሰዉ ጉዳዩን ከማየት እንዲነሳ የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ አቤቱታ አቅራቢነት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በመካከላቸዉ የተፈጠረዉ አለመግባባት በግልግል ዳኞች ዉሳኔ እንዲሰጥበት ለማድረግ በአመልካች በኩል አቶ ሚካኤል ጉንታ በ1ኛ ተጠሪ በኩል የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በመሰየማቸዉ ሁለቱ የግልግል ዳኞች ሠብሳቢ ዳኛዉን እንዲመርጡ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ሰብሰቢዉ ዳኛ ከመመረጡ በፊት የአሁኑ አመልካች 2ኛ ተጠሪ ጉዳዩን በገለልተኝነት ሊያዩት አይችሉም በሚል ከግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት ይነሱልኝ ሲሉ አቤቱታ ለፍ/ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት፡- 2ኛ ተጠሪ በነጻነትና በገለልተኝነት የመሥራት ኃላፊነት እያለባቸዉ የ1ኛ ተጠሪን ዓላማ ለማሳካት የታሰበ በሚመስል መልኩ የአቶ ሚካኤል ጉንታ ከሳሽ እና በእርሳቸዉ ላይ ያለአግባብ መስካሪ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡ አቶ ሚካኤል እና 2ኛ ተጠሪ ሰብሳቢ ዳኛ ለመምረጥ ሞክረዉ አንዱ ሌላኛዉ ባቀረበዉ ጥቆማ ላይ ባለመስማማታቸዉ 2ኛ ተጠሪ ትልቅ ሥራ ስላገኘሁ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባል ሆኜ አልሠራም፤ ይህንኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመረጠኝ ድርጅት አሳውቂያለሁ ማለታቸዉ እና ሐምሌ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ለአመልካች በጻፉት ደብዳቤ የገለጹት አቋም የገለልተኝነት መርህን የሚቃረን ስለሆነ ከግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት ይነሱልኝ የሚል ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ በበኩላቸዉ የቀረበዉ አቤቱታ 2ኛ ተጠሪ ባላቸዉ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ እንዲሁም በግልግል ድርጅቶች ዉስጥ ስለሚያበርክቱት አስተዋጽኦ ወቀሳ እንደማይገባቸዉና ግምታዊ በሆነ ሀሳብ ከግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት ሊነሱ እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በቀረበባቸዉ መቃወሚያ ላይ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን ተናግረዋል የተባለዉን ነገር እንዳልተናገሩና ባልተጨበጠ ማስረጃ የቀረበባቸዉ ተቃዉሞ የሥራ ብቃትና ሀላፊነታቸዉን የማይለዉጥ መሆኑን በመግለጽ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ የስር ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ሰምቶና መርምሮ 2ኛ ተጠሪ ገለልተኛ አለመሆናቸዉንና የተጠሪን ዓላማ ለማሳካት በሚመስል ሁኔታ አቋማቸዉን አሳይተዋል የተባለዉ በማስረጃ ያልተደገፈና በግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት እንዳይቀጥሉ የሚያደርግ አይደለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች 2ኛ ተጠሪ ገለልተኛ ባለመሆናቸዉ ከግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት ሊነሱ ይገባል ያሉባቸዉን ምክንያቶች በሰበር አቤቱታቸዉ በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች 2ኛ ተጠሪ ከግልግል ዳኝነት እንዲነሱላቸዉ ከገለጽዋቸዉ ምክንያቶች ገለልተኛ አይደሉም የሚያስብል አይደለም በማለት እንዲቀጥሉ መወሰኑ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት በመ/ቁጥር 99679 ከሰጠዉ ዉሳኔ አንጻር አግባብነቱን ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስ እና የመ/መልስ በማቀባበል እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለአቤቱታዉ በሰጡት መልስ የተመረጡት ገላጋይ ዳኛ ወይም 2ኛ ተጠሪ ገለልተኛ አለመሆኑን የሚያሳይ ምክንያትና ማስረጃ በሌለበት ከግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት ሊነሱ አይገባም፡፡ በሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 99679 የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት የለዉም እንዲሁም አመልካች የጠቀሳቸዉ ምክንያቶች የፈጠራ፣ የሀሰትና በማስረጃ ያልተረጋገጡ በመሆናቸዉ 2ኛ ተጠሪ በጉባኤዉ በዳኝነት ሊያገለግሉ ይገባል ተብሎ እንዲወሰን በመጠየቅ በዝርዝር ክርክራቸዉን አቅርበዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ በስር ፍ/ቤት በነበረዉ ክርክር ተከራካሪዎች አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ናቸዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት በመቃወሚያዉ ላይ አስተያየት እንድሰጥበት ብቻ ነዉ ያደረገዉ፡፡ ስለሆነም የክርክሩ ቀጥተኛ ተሳታፊ ባለመሆኔ በሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 99679 በተሰጠዉ ትርጉም መሠረት ከክርክሩ እንድወጣ እንዲደረግ እና ለተከራካሪ ወገኖች ፍትህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማግኘት የወደፊት ጉዞ የተቃና እንዲሆን ተገቢዉ ዉሳኔ ይሰጥበት ብለዋል፡፡ አመልካች አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርባል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች 2ኛ ተጠሪ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ አባልነታቸዉ እንዲነሱ ያቀረቡትን አቤቱታ ዉድቅ ያደረገዉ የአመልካች አቤቱታ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት በርግጥ 2ኛ ተጠሪ አቋማቸዉን አሳይተዉበታል ያለዉን ሐምሌ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ተጻፈ የተባለዉን ደብዳቤ አስቀርቦ እንደተመለከተዉና የደብዳቤዉ ይዘት 2ኛ ተጠሪ የገለልተኝነት መርህን የሚቃረን ሀሳብ ወይም አቋም አንጸባርቋል የሚያስብል አለመሆኑን በፍርዱ ገልፅዋል፡፡ ሆኖም ሌሎች ነጥቦችና አቋማቸዉን አንጸባርቀዋል የተባሉትን ንግግሮች 2ኛ ተጠሪ ተናግረዋል የተባሉት ለአቶ ሚካኤል ጉንታ ከመሆኑ አንጻር ለምን ቀርበዉ እንዳልተሰሙና እንዳልተጣራ ግልጽ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አቤቱታዉ ለሠበር ያስቀርባል ሲባል ወደ ተያዘዉ ጭብጥ ስንመለስ 2ኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ክርክር ከነበረዉ ሚና እና በሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 99679 ከተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም አንጻር በግልግል ጉባኤ አባልነት ይቀጥሉ መባሉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉን እንመልከት፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህን ቀደም በተጠቀሰዉ መዝገብ የሰጠዉ ትርጉም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3342 መሠረት በአንድ የግልግል ዳኛ ላይ መቃወሚያ ሲቀርብበት ተከራካሪ ሆኖ መቅረብ ያለበት ማን እንደሆነ? ከጉባኤዉ እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት ዳኛ ጥያቄዉን ካነሳዉ ተከራካሪ ወገን ጋር መልስ ሰጭ ወይም ተጠሪ ሆኖ ቀርቦ ዝርዝር ክርክር ካቀረበ በኃላ፤ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ሆኖ በቀረበበት ጉዳይና በተከራካሪነት ቀርቦ ሲሞግተዉ የነበረዉን ተከራካሪ ወገን ለግልግል ዳኞች የሚያቀርበዉን ክርክርና ማስረጃ በገለልተኝነት ሰምቶ ሊወስን ይችላል ተብሎ በግልግል ዳኝነት እንዲሰየም ማድረግ በመርህ ደረጃ የግልግል ዳኝነቱን ዓላማ የማያሳካ መሆኑን፤ የግልግል ዳኛዉ ጉዳዩን ለማስረዳት ከሚቀርብ በቀር ዳኛዉን ከዳኝነቱ የሚያስነሳዉ በቂ ምክንያት አለ ወይስ የለም በሚለዉ ጭብጥ ዙሪያ ተከራካሪ ሆኖ መሰለፉንና ዝርዝር ክርክር የሚቀርብበት ሁኔታ መኖር የሌለበት መሆኑን ግልጽና አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ምንም እንኳ 2ኛ ተጠሪ ለሰበር አቤቱታዉ በሰጡት መልስ የክርክሩ አካል ሆኖ መቀጠል ስለማይገባቸዉ ከክርክሩ ዉጭ እንዲደረጉ የጠየቁ ቢሆንም በስር ፍ/ቤቶች የነበራቸዉን ተሳትፎ ምን እንደነበረ መመልከቱ ተገቢ ነዉ፡፡ አመልካች ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ 2ኛ ተጠሪን በተከራካሪነት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ በአቤቱታቸዉ አልጠቀሱም፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት 2ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን 2ኛ ተጠሪም ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡ በርግጥ የዚህ ዓይነት አቤቱታ የቀረበበት የግልግል ዳኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የበኩሉን አጭር አስተያይት እንዲያቀርብ ማድረግ የተለመደ አሠራር ቢሆንም እንደአንድ ተከራካሪ ወገን ተወስዶ በመልስ ሰጭነት ተሰይሞ የክርክሩ ሙሉ ተካፋይ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት በፍርዱ ላይ 2ኛ ተጠሪን በተከራካሪነት ወይም በመልስ ሰጪነት ከመሰየሙም በላይ 2ኛ ተጠሪ ያቀረበዉን አስተያየት በመደበኛ ተከራከሪ እንደቀረበ ክርክር አድርጎ መዝግቦታል፡፡ ይህም በመጀመሪያዉ ክርክር ብቻ ሳይሆን በይግባኝ ሰሚ እና በሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ 2ኛ ተጠሪ በመዝገቦቹ በመልስ ሰጭነት ወይም በተጠሪነት የክርክሩ ተሳታፊ እንዲደረግ ምክንያት ሆኗል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 3340(2) መሠረት እና በሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 99679 ከተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም አንጻር ዳኛዉን ገለልተኛ ወይም ነጻ ላይሆን ይችላል በማለት ከግልግል ዳኝነቱ ለማስነሳት የግድ ዳኛዉ ከአንደኛዉ ተከራካሪ ወገን ጋር ያለዉን ጠንካራ ግንኙነት በጠንካራ ማስረጃ ማረጋገጥ አይጠበቅም፡፡ ዳኛዉ ገለልተኛ ወይም ነጻ ላይሆን የሚችልበት ግምት ለመዉሰድ የሚያስችል ወይም ጥርጣሬን የሚፈጥር አሳማኝ ምክንያት መኖሩ ብቻ በቂ ነዉ፡፡ ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ መ/ሰጪ ወይም ተጠሪ እንዲሆንና ዝርዝር ክርክር እንዲያቀርብ በማድረግ የክርክሩ ተካፋይ በተደረገበት ሁኔታ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ያለዉን ክርክር የግልግል ዳኛ ሆኖ በገለልተኝነትና በነጻነት መመልከት ስለመቻሉ ጥርጣሬ የሚፈጥር በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ከግልግል ጉባኤ አባልነቱ እንዲነሱ ማድረግ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 234067 ሚያዚያ 08 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 180400 ሕዳር 14 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2ኛ ተጠሪ በአመልካች በቀረበዉ አቤቱታ ላይ አስተያየት ከመስጠት ባለፈ ዝርዝር ክርክር እንዲያቀርብና በመ/ሰጪነት ተሰይሞ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን በስር ፍ/ቤት የተደረገ በመሆኑ ከዚህ በኃላ ገለልተኛና ነጻ ሆኖ ጉዳዩን ያየዋል የሚል ግምት ባለመኖሩ ከግልግል ዳኝነት አባልነት እንዲነሳ ተወስኗል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ምትክ ሌላ የግልግል ዳኛ መምረጥ እንዲችል ተገቢዉ ይፈጸም ተብሏል፡፡

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰበር/መ/ቁ 117151

ሕዳር 21 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-የመንግሥት ሠራተኞች ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ...ነ/ፈጅ ሄኖክ መሳው ቀረቡ

ተጠሪ፡-ወ/ር ቸኮል ሙሉጌታ ..... ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 113138 ሐምሌ 27 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ነው።ተጠሪ ከነሐሴ 01 ቀን 1990 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው በእስር ላይ የቆዩ መሆናቸውን በመጥቀስ ተቋርጦ የቆየው የጡረታ አበል ይከፈላቸው ዘንድ ለአመልካች አቤቱታ አቅርበዋል፤አመልካች በጉዳዩ ላይ የሕግ አስተያየት እንዲሰጥበት አድርጓል፤የአመልካች መሥሪያ ቤት የሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተጠሪ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያሉት በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው 12 ዓመት ከተቀጡ በኋላ በመሆኑ እየተከፈላቸው የነበረው የጡረታ አበል አግባብ አይደለም፤ለወደፊትም መቋረጥ አለበት የሚል አስተያየት በመስጠቱ አመልካች የተጠሪን የጡረታ አበል ክፍያ አቋርጧል።

ተጠሪ በአመልካች መሥሪያ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማሕበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ አቅርበዋል።ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው 12 ዓመት ጽኑ እሥራት የተፈረደባቸው በመሆኑ እና የቀድሞ የጡረታ አዋጅ ቁጥር 5/1967 አንቀጽ 34 የመንግሥት ሠራተኛ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆኑ በሕግ በተቋቋመ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤት ከተረጋገጠበት እና ቢያንስ የሦስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ከተወሰነበት የጡረታ መብቱን ያጣል ወይም በመከፈል ላይ ያለው የጡረታ አበል ይቋረጥበታል የሚል በመሆኑ አመልካች የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት አጽንቶታል።

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል።ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች እና የማሕበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጠሪን የጡረታ አበል ለማቋረጥ መሠረት ያደረጉት የአዋጅ ቁጥር 5/1967 አንቀጽ 34 ድንጋጌን ነው።ሆኖም ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 424/97 እና 714/2003 ተሸሯል።አዋጅ ቁጥር 714/2003 በወንጀል የተቀጣ ሰው የጡረታ መብት እንደሚያጣ አይደነግግም።የዚህ አዋጅ አንቀጽ 49/1 ውዝፍ ክፍያ በሦስት ዓመት ይርጋ እንደሚቋረጥ የሚደነግግ በመሆኑ ውዝፍ ክፍያ ለመክፈል አዋጁ ይከለክላል በማለት የተሠጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሆኖም ተጠሪ የጠየቀው ውዝፍ ክፍያ እንዲከፈለው ሆኖ ሳለ አመልካች የተሻረን አዋጅ በመጥቀስ ተጠሪ ባልጠየቀው ዳኝነት ላይ እየተከፈለ ያለው የጡረታ አበል እንዲቋረጥ በማለት መወሰኑ ተገቢ አይለም በማለት አመልካች እና የማሕበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጡትን ውሳኔ በመሻር የተጠሪ የጡረታ አበል ሊቋረጥ አይገባም።የተጠሪ የጡረታ አበል ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ይከፈላቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዋና ይዘት፡-ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካች ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ መስጠት ሲገባው ተጠሪ በጠየቁት የውዝፍ የጡረታ አበል ይከፈለኝ መነሻነት በመከፈል ላይ ያለው የጡረታ አበል እንዲቋረጥ መደረጉ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ መሰጠቱ ተገቢ አይደለም።በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አመልካች መሥሪያ ቤት ተጠየቀም አልተጠየቀም በራሱ ተነሳሽነት ምርመራ ካደረገ በኋላ አላግባብ ሲከፈል የተገኘን የጡረታ አበል ሊያስቆም ይችላል።በጽኑ እሥራት ምክንያት ተከልክሎ የነበረው የጡረታ መብት የተፈቀደው በአዋጅ 907/2007 ነው።ሆኖም ይህ አዋጅ ውዝፍ የጡረታ አበልን ሳይጨምር ለወደፊት የጡረታ አበል የማግኘት መብት ይኖረዋል በሚል የሚደነግግ እንጂ ውዝፍ ክፍያን የሚፈቅድ አይደለም።አመልካች የተጠሪን የጡረታ አበል በማቋረጥ ውሳኔ የሰጠው ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ነው።ተጠሪ የጡረታ አበል መቀበል የሚችሉት አዋጁ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪ የጡረታ አበል ተቋርጦ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፈላቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ነው።በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 345/95 እና አዋጅ ቁጥር 714/2003 አዋጆቹ ከመውጣታቸው በፊት የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ተፈጻሚነታቸው እንደሚቀጥል የሚደነግጉ በመሆኑ አመልካች እና ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጡት ውሳኔ የሕግ መሠረት አለው የሚል ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለተጠሪው እንዲከፈላቸው የተወሰነው የጡረታ አበል ክፍያ ከአዋጅ ቁጥር 907/2007 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ይህ ችሎትም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካችም ሆነ የማሕበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የተጠሪ የጡረታ አበል ሊቋረጥ ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርሱ የቻሉት የጡረታ ሕግን አስመልክቶ በወቅቱ ሥራ ላይ የነበሩትን የሕግ ማእቀፎች መሠረት በማድረግ በመሆኑ ተጠሪ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው ከሦስት ዓመት በላይ ጽኑ እሥራት ቅጣት የተወሰነባቸው በመሆኑ የጡረታ መብታቸው ሊቋረጥ ይገባል በማለት መወሰናቸው ተገቢ ነው፡፡በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከመውጣቱ በፊት አሥቀድመው ሥራ ላይ የነበሩት የጡረታ ሕግ ማዕቀፎች በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ እና ከሦስት ዓመት በላይ ጽኑ እስራት የተፈረደበት ሰው የጡረታ መብቱን እንደሚያጣ የሚደነግጉ ሆነው ሳለ በሥራ ላይ የነበሩት አዋጆች ከሦስት ዓመት በላይ በጽኑ እስራት የተቀጣ ሰው የጡረታ መብቱን እንዲያጣ አይደነግጉም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ ኖኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካች እና የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ውሳኔ ከሰጡ በኋላ አዋጅ ቁጥር 907/2007 ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11/9 የጡረታ አበል ተጠቃሚ ሆኖ በወንጀል ጥፋት ምክንያት ከሦስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ተፈርዶበት የዘለቀታ የጡረታ አበል መብቱን ያጣ ባለመብት ማሻሻያ አዋጁ ከጸናበት ጊዜ ጀምሮ ውዝፍ አበል ሳይጨምር የጡረታ አበል የማግኘት መብት እንደሚኖረው የሚደነግግ በመሆኑ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ለነበሩ የማሕበራዊ ዋስትና ጉዳዮች ተፈጻሚነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረበው ክርክርም አዋጅ ቁጥር 907/2007 ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ መሆኑን አምኖ የተከራከረ በመሆኑ ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ከሦስት ዓመት በላይ ጽኑ እስራት ተፈርዶባቸው የነበረ እና አስቀድመው በሥራ ላይ በነበሩት ሕጎች የጡረታ መብታቸው የተቋረጠ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 907/2007 መሠረት የጡረታ ክፍያ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ሆኖም የአዋጅ አንቀጽ 11/ 9 የጡረታ ባለመብቱ የጡረታ ክፍያ የማግኘት መብት የሚኖረው ማሻሻያ አዋጁ ከጸናበት ጊዜ ጀምሮ ውዝፍ አበል ሳይጨምር እንደሆነ የሚደነግግ በመሆኑ የተጠሪ የጡረታ ክፍያ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፈላቸው በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 113138 ሐምሌ 27 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪ የጡረታ አበል በተጠሪ የቋረጠበት ጊዜ በሥራ ላይ የነበሩት የጡረታ ሕግ ማዕቀፎች በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ከሦስት ዓመት በላይ ጽኑ እስራት የተፈረደበት ሰው የጡረታ መብቱን እንደሚያጣ አይደነግጉም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል እና የተጠሪ የጡረታ አበል ክፍያ ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ እንዲከፈላቸው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የተጠሪ የጡረታ አበል ሊቋረጥ አይገባም በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. ተጠሪ የጡረታ አበል ክፍያ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከጸናበት ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ይከፈላቸው ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.122258

ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓለ መሀመድ

ተሻሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ፀሀይ መንክር

አመልካች፡- አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-የኤ.ፌ.ድ.ሪ የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጅንሲ የደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት - ነገረፈጅ ወንድወሰን ፀጋዬ- ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ በዕዳ አከፋፈል ሂደት አከፋፈል ሂደት የቀደምነት መብት አከባበር ላይ የተመሰረተ ክርክር ሲሆን የጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ተጠሪ ከሳሽአመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ባቀረበው ክስም በአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 9(1)መሰረት ውዙፍ የጡረታ መዋጮ ያላቸው ድርጅቶች ንብረት ከፍርድ ቤት ወጪ በሆነ መንገድ በመሸጥ ገቢ የማስደረግ ስልጣን እንደተሰጠው፤ ብሉናይል የተባለው ሆቴል ንብረትነቱ የአቶ ታምራት ሙሉ ምትኩ የሆነ ድርጅት ህንፃ በአሁኑ አመልካች አማካኝነት በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ከፍርድ ቤት ውጪ በ29/07/2007 ዓ/ም የሽያጭ ጨረታ ተከናውኖበታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ድርጅት ከ 82 ሠራተኞች ተሰብስቦ ያልተከፈለ ብር 443,519.57 የጡረታ መዋጮ ዕዳ አለበት፡፡ በአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀፅ 11(12)የጡረታ ዕዳ ከማንኛውም ዕዳ ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ የድርጅቱ ህንፃ ሽያጭ እንደፀደቀ ተጠሪ ከሽያጭ ገንዘቡ አስቀድሞ የጡረታ ዕዳውን ለአመልካች ገቢ እንዲያደርግ ትዕዛዝ ይሰጥልን ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡
2. የአሁኑ አመልካች በቀረበው የመከላከያ መልስ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የመያዣ ንብረት የመሸጥ መብት እንዳለው፤ የፍ/ሕ/ቁ/3054 የቀድምትነት መብት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚሰጠው፤ አመልካች የመያዝ መብቱ በ2000ዓ.ም ያቋቋመ በመሆኑ እና አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀፅ 57(1) ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ እንደመሆናቸውን ሰለሚያመለክት፤ ገንዘቡም ከህዝብ የተሰበሰበ ከመሆኑ አንፃር የማይመለስ ከሆነ ከፍተኛ ተጽዕኖየሚያሳድር ስለመሆኑ፤ የገንዘብ መጠኑም በገለልተኛ ባለሙያ ያልተጣራ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ክርክር ያቀረበ ሲሆን የድርጅቱ ባለቤት የተባሉት ግለሰብ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት በ20/12/2007 ዓ/ም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/40(2) መሰረት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ አዞ በማረሚያ ቤት በኩልመጥሪያ የደረሣቸው ቢሆንም ወደ ክርክሩ መግባት እንደማይፈልጉ የገለጹ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አልፎታል።

3. የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ የሚጠይቀው የጡረታ መዋጮ ምን ያህል ነው? የሚለው በክሱ 443,519.57 መሆኑን መግለጹን፤ የድርጅቱ ባለቤት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ መጥሪያ የተላከ ቢሆንም ወደ ክርክሩ አልገባም ያሉ በመሆኑ ተጠሪ ያቀረበው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ አልተስተባበለም። የቀደምትነትመብት ያለው ማንነው? የሚለው ነጥብ በተመለከተም የሁለቱም አዋጆች ይዘት እንደመረመረ፤ የጡረታ ዕዳ ከማንኛውም ዕዳ ቅድሚያ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 715/2003 የሚገልጽ ሰለመሆኑ ይህ አዋጅም ከአዋጅ ቁጥር 97/1990 ዓ.ም በኋላ የወጣ ህግ ከመሆኑ አንፃር ተጠሪ በተያዘው ንብረት ላይየቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑ የሚያሳይ በመሆኑ የቀደምትነት መብት አለው ሲል ፍርድ ሰጥቷል። የአሁኑ አመልካች በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘትለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታውን ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም ።

4. የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔበመቃወም ለማሳረም ነው።አመልካች በሰበር አቤቱታው የተጠሪ ክስ ጨረታው ከተካሄደና ገንዘቡ ለዕዳ መክፈያ ከዋለ በኋላ የቀረበ ነው።በአዋጅ ቁጥር 97/1990፣ ፍ/ሕ/ቁ/3059 መሰረት ቀደምትነት መብት እንዳለው፤ የደቡብ ክልል ፍርድ ቤት ውክልና ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 322/2005 እንደተነሳ፣ የጡረታ መዋጮ መጠኑም ሊጣራ ይገባ ነበር የሚል ክርክር አቅርበዋል። የአመልካች አቤቱታ ከተመረመረ በኋላ በዚህ ጉዳይ በግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው የቅድሚያ መብት ጥያቄ ሊታይ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ነው። ወይስ አዋጅ ቁጥር 715/2003? የሚለውን ነጥብ ተጠሪ ባለበት ይጣራ ዘንድ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪም በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ጨረታ ከተካሄደና ለዕዳ መክፈያ ከዋለ በኋላ የቀረበ ክስ ነው የሚለው በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ስለመሆኑ፤ የጡረታ መዋጮ ከማንኛውም ዕዳ ቅድሚያ እንደሚሰጠው፤ዕዳው አልተካደም ተከፍሏል የሚል ማስረጃ ብቻ በማስቀረብ የሚስተባበል ከመሆኑ አንፃር የአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር ተገቢነት እንደሌለው፤ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውክልና ስልጣንም እንዳልተነሳ በመግለጽ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

5. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃርበስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስሕተት መፈጸም አለመፈጸሙን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የቀደምትነት መብት ባደረገው የመያዣ ውል ያረጋገጠ በመሆኑየአሁኑ ተጠሪ የጡረታ መዋጮ ዕዳ የመሰብሰብ የቅድሚያ መብት አለው ተብሎ የተሰጠው ፍርድ ተገቢ አይደለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አዋጅ ቁጥር 715/2003 ዓ.ም የጡረታ ዕዳ ከማንኛውም ዕዳ ቅድሚያ እንደሚሰጠው በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው የተጠሪ ክስ ጨረታው ተከናውኖ ዕዳው ከተከፈለ በኋላ የቀረበ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ተጠሪ በሰጠው መልስ ክርክሩ በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በዋናነት ያቀረበው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 97/1990 የቀደምትነት መብት እንዳለው፤ የአዋጅ ቁጥር 715/2003አንቀጽ 57/(1)ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ተፈፃሚ ናቸው ሰለሚል የተጠሪ የቀደምነት መብት አግባብነት የለውም በሚል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በስር ፍርድ ቤት የክርክር አካል ያላደረገው ጉዳይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዲስ መልክ ሊያነሳ እንደማይችል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/329/1/ በግልጽ ደንግጓል፡፡ የፍርድ ቤት ስልጣንም በተመለከተም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ የሚመለከተው /originaljurisdiction/ ስልጣኑ የተነሳ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመወከል የሚመለከተው ጉዳይ የውክልና ስልጣን ያልተነሳ በመሆኑ ክርክርሩ የህግ መሰረት የለውም ብለናል፡፡

6. አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ ባነሳው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 97/1990 የቀደምነት መብት ያቋቋመ በመሆኑ የተጠሪ ጥያቄ ውድቅ ሊያደርግ ይገባል ብሏል፡፡ ተጠሪም የአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 11/12/ የቀደምትነት መብት እንደሚሰጠው ተከራክሯል፡፡ አመልካች በውል የቀደምትነት መብት ማቋቋሙ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪም ብሉናይል ከተባለው ሆቴል ያልተሰበሰበ የሰራተኞች የጡረታ መዋጮ እዳ እንዳለው አረጋግጧል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ብሉ ናይል በተባለው ሆቴል ላይ የፍርድ ባለመብት መሆናቸው ያከራከረ ነጥብ አይደለም፡፡ አከራካሪ የሆነውን መሰረታዊ ነጥብ የዕዳው አከፋፈል ቅደም ተከተል ነው፡፡ አመልካች ከውል የመነጨ የመያዣ መብት ያለው ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪም በህግ የተረጋገጠ የቀደምትነት መብት አለው፡፡ የስር ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 715/2003 ከአዋጅ ቁጥር 97/1990 በኋላ የወጣ መሆኑን የተጠሪ ቀደምትነት መብት ለመወሰን እንደአንድ መነሻ የወሰደው ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት ህጎች ከወጡበት ጊዜ አንፃር ሳይሆን በክርክሩ ለተያዘው ጉዳይ ልዩ ህግ /special law/ የትኛው ነው? በሚል መሆን ይገባው ነበር፡፡ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ ወደ አከራካሪው ነጥብ ስንመለስ አዋጁ ቁጥር 97/1990 ባንኮች በመያዝ የተያዥ የተያዙ ንብረቶች የሚሸጡበት ስርዓት የሚደነግግ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 715/2003 የግል ድርጅትሰራተኞች ጡረታ አዋጅ የሚመለከት ሲሆን በአዋጅ አንቀጽ 11/12/" የጡረታ መዋጮ ክፍያ ከማንኛዉም እዳ ክፍያ ቅድሚያ ይኖርዋል፡፡ በማለት የደነገገ ሲሆን የእንግሊዘኛ ትርጉም the payment of contribution shall have priority over any debt``በማለት ተገልጸዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የተጠሪ የቀደሞትነት መብት በግልጽ በልዩ ህግ የተመለከተ መሆኑ ነው፡፡ አመልካች የአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 57/1/ በመንቀስ የተከራከረ ቢሆንም አቋቋምኩት የሚለው የቀድምትነት መያዣ መብት የሚደግፍ ድንጋጌ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የአሁኑ ተጠሪ በልዩ ህጉ የጡረታ መዋጮ ክፍያ ከማንኛውም እዳ ቅድሚያ እንደሚሰጠው መሰረት በማድረግ ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት ያለው ነው ብለናል፡፡ የአሁኑ አመልካች በመያዣ ውል አቋቁምኩት ከሚለው የቀደምትነት መብት ይልቅ በልዩ ህግ የተቋቋመው የቀደምትነት መብት ለተጠሪ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች የአሁኑ ተጠሪ ብር 443,519.57 የጡረታ መዋጮ እዳ በቅድሚያ እንዲከፈለው የሰጡት ፍርድ ህጉን በአግባቡ ተፈጻሚነት አድርጓል ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17653 በ11/02/2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ/67034 በ19/04/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት በ16/05/2008 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ድረ-ገጽ፡- www.fsc.gov.et
ስልክ፡- +251 111 55 34 00
ፋክስ፡- +251 111 56 55 83
የመ.ሣ.ቁ፡- 6166
ነፃ የስልክ ጥሪ፡- 992

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች ቁጥር 22

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



ቅጽ -22

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ-22

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

መስከረም 2011 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief



የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሥልጣኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚሰጥባቸውን የሰበር ውሳኔዎች አሳትሞ የማሰራጨት ኃላፊነት እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) ሥር ተመልክቷል፡፡

ይህንን የሕግ ግዴታ ለመወጣት አስገዳጅ የሆኑ የተለያዩ ውሳኔዎችን በቅጽ መልክ በማደራጀትና ለህትመት በማብቃት ለተጠቃሚው ህብረተሰብና ለተለያዩ የፍትህ አካላት እንዲደርስ ለማድረግ በተቋሙ ድህረ ገጽ እንዲሁም በሜጋ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር ባሉት 32 ቅርንጫፎች እንዲሰራጭ በማድረግ የፍትህ ሥርዓቱ ወጥነት እና ተገማችነት እንዲኖረው ለማድረግ የበኩሉን አስተዋፅዖ እያደረገ ይገኛል፡፡

በመሆኑም አገልግሎቱን የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ የምትሰጡን ገንቢ አስተያየቶች ወሳኝ መሆናቸውን እየገለጽኩ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እገልጻለሁ፡፡

ዳኜ መላኩ

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ /ቅፅ 22/

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ውል					**1**
1.	የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ውልን የሚመለከቱ ጉዳዮች በግልግል ዳኝነት (አርቢትሬተር) እንዳይዳኙ የተጣለው ገደብ ወይም ክልከላ ገላጋይ ዳኛ (አድጁዲኬተር) ጋር በተያያዘም ተፈጻሚነት ያላቸው ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 315/2/፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678/ለ፣3131 እና 3132/ለ/	127459	ጣና የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ኢንዱስትሪ ሀ/የተ/የግ/ማህበር	መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም	2
2.	በሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣዉ የትግራይ ክልል ደንብ መሰረት የአምልኮ ቦታዎች በመንግስት የሚሰጡ መሆናቸዉን ቢደነግጉም ከግለሰቦች እንዳይገዛ በግልጽ ክልከላ የማያደርግ ስለመሆኑ፡-	124725	የሸሬ እንደስላሴ አንዋር መስጊድ እና እነ ወ/ሮ ትኑር ፍትዊ /6 ሰዎች/	ጥቅምት 29 ቀን 2010 ዓ.ም	8

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አንድ ውል ህገወጥ ነው በሚል ምክንያት ፈራሽ ሊሆን የሚችለው የውሉ መሰረት የሆነው መብትና ግዴታ በህግ በተከለከለ ነገር ላይ መደረጉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣ ሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ የትግራይ ክልል ደንብ ቁጥር 62/2002 እና የፍትሐብሄር ህግ አንቀጽ 1716				
3.	ከቤት ሽያጭ ውል ጋር በተያያዘ የይርጋው ጊዜ ስለሚታሰብበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1845	131151	እነ አቶ ክፍያለው አየለ እና እነ ወ/ሮ ወርቅነሽ በላይ	ታህሳስ 25 2010 ዓ.ም	15
4.	አንድ የመሬት ሽያጭ ውል ህገ ወጥ ውል መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ገዥ ወገን በመሬቱ ላይ የሰራው ቤት በሻጭ ፈቃድ እንደተሰራ ተደርጎ የህግ ግምት የሚወሰድበት አግባብ የማይኖር ስለመሆኑ የኢፌዴሪ ህ/መ አንቀፅ 40 (3) እና የፍ/ብ/ህ ቁጥር 1678 (ለ) እና 1716	141606	አቶ ማሞ ቱሉ እና አቶ አበበ አበራ	መስከረም 25/2010 ዓ.ም	19

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
5.	የዕቃ ማንጓዝ ውል በማንጓጓ ሰነድ ወይም መሰል ሰነዶች ሊረጋገጥ የሚችል ስለመሆኑ፣ በየብስ የዕቃ ማንጓዝ ስራን ለመደንገግ ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ ቁጥር 547/99 አንቀጽ 4፤8	130676	ጅቡቲ ድንበር ተሻጋሪ ደረጃ 3-ለ የደ/ጭ/ማ/ባ/ማህበር እና አቶ ሞላደርጎ	ጥቅምት 27/2010	22
6.	አንድ ሥራን ለመስራት የመተባበርና የመተጋገዝ ስምምነት ማድረግ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ስምምነት ነው ከሚባል በስተቀር አስገዳጅነት ያለው በሕግ ፊት ግዴታን የሚፈጥር ውል አለ ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678፤1731፤1771	120468	አቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/ክርስቶስ እና አቶ ሐረጎ ገ/እግዚአብሔር	መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም	27
7.	አንድ የሽያጭ ውል ያደረገ ወገን የተደረገው የሽያጭ ውል ያለመመዝገቡን የማይንቀሳቀስ ንብረት በእጁ ባስገባ 3ኛ ወገን ላይ በመቃወሚያነት ለማንሳት የማይችል ስለመሆኑ፣	123761	ወ/ሮ እናኒ ተሰማ እና እነቁስ ገብረማርያም	መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም	33

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የሽያጭ ውል ያደረገ ወገን በውሉ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ የተከናወኑ ተግባራትን ሁሉ ለመቃወም የሚችለው የተደረገው የሽያጭ ውል የተመዘገበ ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878				
8.	አንድ ውል ሳይፈጸም በቀረ ጊዜ እንደውሉ አልተፈጸመልኝም የሚለው ተዋዋይ ወገን ሳይፈጸምልህ ቀርቷል በማለት ክርክር ለማቅረብ በቅድሚያ ውሉን ያልፈጸመው አካል ግዴታውን እንዲፈጸምለት ለማድረግ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑና በዚህ መሰረት ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ወለድ የሚሰላበትን ጊዜ በመወሰን ረገድ ጠቀሜታ ያለው ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 1772	133203	ኢትዮ ቴሌኮም ጋምቤላ ሪጅን እና አዱራ ኮንስትራክሽን አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ	ጥቅምት 29 ቀን 2010 ዓ.ም	39
9.	በመርህ ደረጃ አንድ ውል ለአንደኛው ወገን የበለጠ ጥቅም	138591	ሼህ አደም ፋረስ	የካቲት	44

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ይሰጣል በሚል እንደማይፈርስ ነገር ግን ፈቃድ የተገኘዉ በዕድሜ መግፋት ወይም የንግድ ልምድ ዕዉቀቱ ማነስ ካለና በሕሊና ግፍ መስሎ ከታየ ዉሉ የሚሰርዝበት ሁኔታ ስለመኖሩ፡- አንድ ተዋዋይ የዉል ይሰረዝልኝ ክስ ዉሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ዉስጥ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ ፡- የፍ/ሕ/ቁ. 1710(1)እና(2) ፤ የፍ/ሕ/ቁ.1810(1)		እና ሼህ መሰጠፋ ፍሊ	27/2010 ዓ.ም	
10.	ዉል እንዲፈርስ ጥያቄ የሚያቀርብ ወገን ዉሉ ሊፈርስ የሚችልበት በህግ ተቀባይነት ያለዉ ምክንያት ስለመኖሩ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄ የሚቀርብለት ፍርድ ቤትም ለዉሉ መፍረስ በምክንያትነት የተጠቀሰዉ ሁኔታ ዉሉ እንዲፈርስ ለማድረግ በህግ ተቀባይነት ያለዉ እና በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ የህጉ ድንጋጌዎች ድንጋጌዎች	138386	እነ አቶ ረጋሣ ጉርሙ (2 ሰዎች) እና እነ አቶ ተሾመ አፈወርቅ (2 ሰዎች)	የካቲት 26 ቀን 2010 ዓ.ም	48

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ጋር አገናዝቦ የማጣራት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ ህግ አንቀጽ 347(1)፣ 347(2) እና ፍ/ህ አንቀጽ 1710(2)				
11.	የማይፀናና ህገ ወጥ የሆነ የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ሆኖ ግራ ቀኙ ወገኖች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ውሳኔ ሲሰጥ በህገ ወጥ በመንገድ በተገኘው ባዶ ቦታ ላይ ቤት የገነባው ወገን ቤቱን በራሱ ወጪ በማፍረስ ለባለይዞታው እንዲያስረክብ ከማድረግ ባለፈ ለግንባታው ያወጣውን ወጪ ባለይዞታ የሆነው ወገን እንዲከፍለው ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕ/መ አንቀፅ 40(3) እና የፍ/ብ/ህ ቁ 1815	128650	ወ/ሮ እቴናት አድማሱ እና አቶ ደመቀ ይዘንጋዉ	መስከረም 26 2010 ዓ.ም	54
ፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት					59
12.	ለቀጠሮ ምክንያት የሆነ ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት የሆነ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ ያልተፈፀመ ቢሆንም	138479	ወ/ሮ ሸዋዬ ገ/እግዚአብሔር እና ተጠሪ - ወ/ሮ ብርሃኔ	የካቲት 26 ቀን 2010 ዓ.ም.	60

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንኳ ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ የመሰለውን ውሳኔ መስጠት ስለመቻሉ፡- የፍ/ብ/ስ/ሥ/ህ/ቁ 199(1)		ፀአዱ		
13.	አንድ ወራሽ በሟች የውርስ ንብረት ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲጣራ በግልፅ ተስማምቶና ውክልና ሰጥቶ በሚጣራው የውርስ ፋይል ተሳታፊ ሆኖ እያለ ከሚጣራው ንብረት ላይ የግል ንብረት ያለ በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር እንዲፈቀድልኝ በማለት የሚያቀርበውን ጥያቄ ፍርድ ቤቱ በውርስ አጣሪ ተጣርቶ የቀረበውን ሪፖርት ተቀብሎና መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ከመስጠት ባለፈ የጣልቃ ገብ ክርክሩን ሊቀበለው የማይገባ ስለመሆኑ፡- የፍ/ሕ/ቁ. 947	133708	እነ ወ/ሮ ጣይቱ ደያሳ እና አቶ ጉደታ ደያሳ	ጥቅምት 21 ቀን 2010 ዓ.ም	64
14.	አንድ ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልስ ወይም በማናቸዉም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ	138717	ብርክቲ ግደይ እና	የካቲት 28 ቀን 2010	69

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ሌላኛዉ ተከራካሪ ወገን በዚህ እምነት መሰረት ዉሳኔ እንዲሰጠዉ መጠየቅ እንደሚችል እና ፍ/ቤትም ሌላ በማስረጃ የሚረጋገጥ ነገር ቢኖርም እንኳን በታመነዉና ዉሳኔ እንዲሰጥበት በተጠየቀዉ ጉዳይ ብቻ ፍርድ መስጠት የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242		እነ አቶ ሸምሱ ኑሪ(2 ሰዎች)	ዓ/ም	
15.	በትግራይ ክልል የጎጆ መውጫ ይዞታና ቤት የሚመለከትን ጉዳይ የቀበሌ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ጉዳዩን ተቀብሎ አይቶ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በተሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል በማለት የመቃወሚያ ማመልከቻ ሲቀርብ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻውን ተከትሎ የቀደመዉን ዉሳኔ የማጽደቅ ወይም የማሻሻል ወይም የመለወጥ ወይም የመሰረዝ ስልጣን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የቀበሌ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ስለመሆኑ፡-	131832	ወ/ሮ መረሳ አማረ እና እነ ቂስ ሃይለ ገብረ (2 ሰዎች)	ታህሳስ 23 2010 ዓ.ም	74

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 ፣ 360(2)				
16.	የይዞታ ክርክርን በተመለከተ አንድ ተከራካሪ ወገን ካርታዉ እንደተሰረዘ እና በዚያ ካርታ ይዞታዉን ለመጠየቅ መብት እንደሌለዉ ዉሳኔ ተሰጥቶ እያለ ተከራካሪ ወገን በመቀየር ክስ ስላቀረበ ብቻ የክርክሩ ጭብጥና ተከራካሪ ወገን ስለሚለያይ ከዚህ ቀደም ዉሳኔ ተሰጥቷል የሚያስብል አይደለም በማለት አዲስ ክስ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ፡- የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5(1)	130410	ሱፍያን አቡበከር እና እነ አቶ ክፍሉ ጋሻ (2 ሰዎች)	ታህሳስ 30 2010 ዓ.ም	78
17.	•ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በተለይ ካልፈቀደ በቀር ይግባኝ ባይ በይግባኝ ማመልከቻ ላይ ዘርዝሮ ያልገለጸውን አዲስ ነገር በማንሳት ወይም መሠረት በማድረግ ለመከራከር የማይችል ስለመሆኑ፡- •ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ ማመልከቻ ተዘርዝሮ ከተገለጸ ወይም ክርክር ከተነሳበት ውጭ በሆነ ነገር ፍርድ	137831	ወ/ሮ ለተብርሃን ያይንሸት እና አቶ የማነ በየነ	ህዳር 28 ቀን 2010 ዓ/ም	83

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መስጠት የማይችል ስለመሆኑ፡- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 328 /2/፤328 /3/				
18.	የተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት የክርክር አመራር የሰዎችን የመከላከልና የመሰማት ሕገ መንግስታዊ መብትን በሚነካ መልኩ መተርጎም እና ሥራ ላይ መዋል የማይገባው ስለመሆኑ፡- ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.284-287	131498	አቶ መሳይ ቦጋላ እና ወ/ሮ አይናለም አለሙ	መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም	90
19.	የዕግድ ትእዛዝ በባህሪው ጊዜያዊ በመሆኑ ለዕግዱ ምክንያት የሆነው ክርክር ዕልባት ሲያገኝ የሚነሳ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154	135590	ፋንታሁን ተፈሪ እና አበባ ገ/ማርያም	ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም	96
20.	አንድ ጉዳይ በማንኛውም የክርክር ደረጃ ላይ በሚገኝበት ወቅት ተከራካሪ ወገኞች በእርቅ ወይም በግልግል ስምምነት የመጨረስ መብት ያላቸው ቢሆንም፤ ክሱን በእርቅ ለመጨረስ ቀጠሮ ያስለወጠ ወገን ቀጠሮ	136901	እነ ሐጻን ቤተልሄም ሰለሞን (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ጌታቸዉ	መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም	101

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በተሰጠበት ቀን ፍ/ቤትን ቀርቦ የተደረሰበትን ደረጃ ያለማሳወቅ እና ለረጅም ጊዜ ጉዳዩን ያለመከታተል ኪሳራ እንዲከፈል ሊወሰንበት ከመቻሉ በላይ አዲስ ክስ መመስረት የማይቻል ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 69 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ፣ የፍ/ሥ/ሥ/ቁ. 275 እና 79/1/		ገ/መስቀል(3 ሰዎች)		
21.	በአንድ ክርክር ውስጥ የከሳሾች ወይም የተከሳሾች ብዛት ከአንድ በላይ ሲሆንና ክርክሩም ከሳሾችን ወይም ተከሳሾችን በአንድ ዓይነት መልክ የሚመለከታቸው ሲሆን ከሳሾቹ ወይም ከተከሳሾቹ አንዱ በጠቅላላው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሲጠይቅና ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት ፍርዱን በመለወጥ ያሻሻለው ወይም የለወጠው ወይም ያጸናው ፍርድ ይግባኙን ባላቀረቡት ከሳሾች ወይም ተከሳሾች ላይም በይግባኝ ደረጃም በቀረበው ጉዳዩ ከከሳሾቹ መካከል አንዱ ይግባኝ ጠይቆ የሚሰጠው ውሳኔ ሌሎችንም የሚያካትት	139138	አቶ ኃይሉ ሂንጌ እና አመርቲ ነሼ የፊንጫኣ ሀይል መመንጫ ፕሮጀክት	ህዳር 20 ቀን 2010 ዓ/ም	108

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑ፡- የፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 35 እና 331				
22.	ለአንድ ክርክር መነሻ የሆነ ቤትና ይዞታ በክልል የሚገኝ ሲሆንና የስረ ነገር ስልጣኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት ንብረቱ በሚገኝበት ክልል የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ፡-	139942	ወ/ሮ ዘይባ ሳኒ እና ወ/ሮ ለይላ ዘይኑ	ህዳር 27 ቀን 2010 ዓ/ም	112
23.	በአንድ ክርክር ከሳሽ የሆነው ወገን ጣልቃ በገባ ተከራካሪ ወገን ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ከማንሳት የሚከለከልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.39፤40፤41	135254	አቶ ይስሃቅ ተክለ ፃዲቅ እና እነ ወ/ሮ ሃረገወይን አሸኔ	የካቲት 29 ቀን 2010 ዓ.ም	115
24.	ሰበር ችሎቶች ሥነ ሥርዓታዊ የሆነ የህግ ጥያቄን ብቻ ለማየት ስልጣን እንዳላቸው ግንዛቤ በመውሰድ በአንድ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ውሳኔ ስነ-ስርዓታዊ ሕጎችን መሰረት አድርጎ የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን መመርመር አንጂ	138340	እነ ሶፍያን ከማሎ(6ሰዎች) እና ወ/ሮ ጀሚላ ቃሲም	ህዳር 19 ቀን 2010 ዓ.ም	121

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ከዚህ ውጪ መደበኛ ሕጎችን መሰረት አድርገው በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሊመረምሩ የሚችሉበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፡- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))፣ 80(3(ለ)) እና አዋጅ ቁጥር 53/94 እና አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6				
25.	ሁከት ተወግዶ ይዞታ እንዲለቀቅ ክስ ቀርቦ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በድጋሚ ይዞታ ይለቀቅልኝ በሚል ክስ መመስረት ዳኝነት በተሰጠበት ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5፣ 244(ለ)	138062	የሰቆጣ ከተማ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት እና ወ/ሮአድና ምህረቱ	ህዳር 26 ቀን 2010 ዓ.ም.	125
26.	አንድ ሰው ቀድሞ በቀረበ ክርክር ጣልቃ ገብ በመሆን ክርክር ያቀረበ ወይም በጉዳዩ ተሳታፊ የነበረ መሆኑ በጣልቃ ገብነት በቀረበበት ክርክር ግልጽ ዳኝነት ባልተጠየቀባቸው ጉዳዮች በሌላ ጊዜ ክስ ለማቅረብ የሚችል	137401	ወ/ሮ ጀምላ ጀብር እና አቶ ሶፊያ ጅማ	የካቲት 27 ቀን 2010 ዓ.ም	129

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑና በዚህ አግባብ የሚቀርብን ክስ በቀድሞው ክርክር ተጠቃሎ መቅረብ የነበረበትና ተከፋፍሎ ዳኝነት ሊቀርብበት አይገባም በሚል አቤቱታን ዉድቅ በማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41፣216 እና 218				
27.	አንድ ውል በይዘቱ የአስተዳደር ውል ሲሆን የአስተዳደር አካል ወይም መንግስት ውሉን ለመሰረዝ መብት ያለው ስለመሆኑና ሌላኛው ወገን በውሉ መፍረስ የደረሰበት ጉዳት ካለ ከመጠየቅ በስተቀር ውሉ እንዲሻሻል ሆነ ለስራ ማስኬጃ የተቀበለውን ቅድመ ክፍያ ላለመመለስ የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ ህ/ቁጥር 1815፣3180 እና 3181	129534	የሊቦከምከም ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ እናትነሽ ዘለቀ (2 ሰዎች)	መስከረም 24 ቀን2010 ዓ.ም	134
28.	የአዲት ሪፖርት የሚያሻማና ግልጽነት የሌለው በሆነበትና በሪፖርቱ የቀረበውን ሀሳብ ይዘት እንዲያስረዱ ሪፖርቱን ያዘጋጁ የሂሳብ ባለሙያዎች ቀርበው እንዲያስረዱ	128746	ሻምበል መሐመድ ብርሃን ረዳ እና	መስከረም25 ቀን 2010	138

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ባልተደረገበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች የኦዲት ሪፖርቱን ራሳቸው በተረዱት አግባብ ተርጉመው የሚሰጡት ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 133 (3)		ወ/ሮ ዘምዘም መኮንን	ዓ.ም.	
29.	በቀድሞ ክርክር ጊዜ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት በዝምታ የታለፈ ጉዳይ በሌላ ጊዜ የክስ እና የክርክር ምክንያት ሊሆን አይችልም ማለት እንጂ ፍ/ቤቶች በተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ በዝምታ ማለፍ የማይችሉ ስለመሆኑ የፍ/ስ/ስ/ሕ ቁጥር *5 (3)* ፣182 (1)	131950	ወ/ሮ የሺመቤት ገ/ፃዲቅ እና ወ/ሮ ፋንታዬ ሽጉልቱ	መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም	144
ወንጀል					**149**
30.	በይግባኝ ፍ/ቤቶች አንድ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ውሳኔ ለመስጠት የሚችሉ ቢሆንም የሚሰጠው ውሳኔ የግራ ቀኙን ተከራካሪዎች የይግባኝ መብት የሚያጣብብ ሆኖ ሲገኝ የቀረበው ማስረጃ ተገቢ በሆነ ምክንያት ድጋሚ	127484	አቶ ተስፋዬ በቀለ እና የፌ/ዐ/ህግ	መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም	150

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንዲጣራ እና ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት ለመመለስ የሚችሉ ስለመሆኑ፣ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 143 እና 195/2/ለ//2/				
31.	የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እና የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን የተለያየ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆኑና የሠራዊት አባላት በፋውንዴሽኑ ንብረት ላይ የሚፈጽሟቸው ማንኛውም ወንጀሎች በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ላይ እንደተፈጸሙ ተደርጎ የማይቆጠሩ ስለመሆናቸው፡- የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት በመከላከያ ሰራዊት ፋውንዴሽን ንብረት ላይ የሚፈጽማቸው ወንጀሎችን የማየት ስልጣን የመደበኛ ፍ/ቤቶች ሆኖ የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን የማስተናገድ የመጀመሪያ ደረጃ የፍርድ ስልጣን የሚኖረው ስለመሆኑ፡- የአዋጅ ቁጥር. 434/1997 አንቀጽ 7/1/ እና የአዋጅ ቁጥር.	141663	ሻ/ቃ አለማየሁ ወንጀሉ እና የፌ.ጠ.ዐ/ህግ	መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም	155

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	809/2006 አንቀጽ 28 እና 38 ደንብ ቁ. 179/2002				
32.	"...ማናቸውም የግል አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ይቀጣል.." የሚል አገላለጽ በውስጣቸው የሚገኙ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ በግል አቤቱታ እንዲያቀርብ ከተፈቀደለት ሰው በቀር በሌላ በማንም ሰው የክስ ጉዳይ ሊንቀሳቀስ የማይችል ስለመሆኑና የግል ከሳሽ የሆነው ሰውም የማመልከቻውን አዘገጃጀት በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 150-153 መሰረት መምራት የሚኖርበት ስለመሆኑ፣ የወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2/ እና 575/2/ሀ/ መሰረት ተደርጎ የቀረበ የወንጀል ክስ በግል ተበዳይ ወይም ህጋዊ ወኪሉ አማካይነት የሚቀርብ እና በግል አቤት ባይ የቀረበ ክስ በሚመራበት ስነ-ስርዓት የሚመራ ሳይሆን በዓቃቤ ህግ	141978	የፌ.ጠ.ዓ/ህግ እና እዮኤል ተስፋዬ የሺጥላ	መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም	161

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ወይም በመንግስት የሚቀርቡ የወንጀል ክሶች በሚመሩበት ስርዓት የሚስተናገዱ እና በግል ተበዳይ ፍላጎት መሰረት ሊቋረጡ የማይችሉ ወንጀሎች ስለመሆናቸው፣ የወ/ህ/ስ/ስ/ህ/ቁ 150-153 እና የወ/ህ/ቁ. 559/2/ እና 575/2/ሀ/፣ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 132-135፣ 185፣196፣ 117 94.88 123-131 እና 186-149				
33.	በወንጀል የተከሰሰ ሰው የግል ተበዳይን በመከላከያ ምስክርነት ያቀረበና የግል ተበዳይም ድርጊቱ ያለመፈፀሙን በመግለጽ የምስክርነት ቃል የሰጠ ከሆነ ዓ/ህግ የግል ተበዳይ የምስክርነት ቃል በድለላ ወይም በጥቅም የተገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ እስካልቻለ ድረስ ተከሳሽ ክሱን አላስተባበለም ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ፡- የወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ/ ቁጥር 149 (2)	137545	አቶ አሸብር መለስ እና የፌዴራል ዓቃቤሕግ	መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም	165
34.	አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በመግደል መከራ ወንጀል ጥፋተኛ ሊደረግ የሚገባው የወንጀሉ አፈፃፀም ጠቅላላ	127505	አበራ ዋቅጅራ እና	መስከረም 25/2010	174

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሁኔታ እና በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት አንፃር እውነትም ወንጀሉን ለመፈፀም ሀሳብ የነበረው እና የተፈለገው ውጤት ያልተገኘው ሀሳቡን ለማሳካት የማያስችል ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት መሆኑን ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 555 (1) እና 540፣ 27(1)		የቤ/ን/ክልል ፍትህ ቢሮ		
35.	በአንድ የወንጀል የማድረግ ሃሳብ ወይም ቸልተኝነት የተፈጸመዉ የወንጀል ድርጊት በሕግ በተጠበቀ አንድ መብት ላይ በሚሆንበት ጊዜ እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር መሸፈን ከተቻለ፤ ፈጻሚዉ የሚቀጣዉ ድርጊቶቹ በሚሸፈኑበት በአንድ ድንጋጌ ስር እንጂ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎች ስላለመሆኑ፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 61(1)	134549	አቶ አበበ ተፈራ አለሙ እና የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ	መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም	178
36.	ተሻሽሎ የቀረበ አንድ የወንጀል ክስ የተከሳሹ መሰረታዊ	141677	ያዕቆብ አብዱ	ህዳር 29	184

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መብት ላይ የሚኖረዉ አሉታዊ ተጽእኖ ጋር ተመዛዝኖ በስነስርዓት ህጉ የተጠበቀለት የመሰማት መብቱን በጥብቅ ተግባራዊ በማድረግ ክሱ እንደገና ተሰምቶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ 118፤119/2/ ፤120 እና 121		እና የደቡብ ክልል አቃቤ ህግ	ቀን 2010 ዓ.ም	
37.	የተከሰሰ ሰው የዓቃቤ ህግ ማስረጃ ሲሰማ በመገኘት የዓቃቤ ህግና ምስክሮች የመጠየቅና የመመርመር መብቱን በአግባቡ ከተጠቀመና መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ እንዲከላከል ተፈቅዶለት ቀጠሮውን አክብሮ ያልቀረበ በሆነበት አግባብ ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ አይደለም በማለት የሚሰጡት ውሳኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፡- የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 161 እና 164 እና የህ/መ አንቀጽ 20/4/	127313	የአ/ብ/ክ/መ/ፍ/ቢሮ እና አቶ አንዱአለም ገናናው	መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም	187

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
38.	ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በማከማቸት የሙስና ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ የማስረዳት ግዴታ ዐቃቤ ሕግ በክሱ ከገለፀውና በማስረጃ ካረጋገጠው ውጭ ተከሳሽ ሌላ ገቢ የሚያገኝበት ስራ ወይም የገቢ ምንጭ ያለው መሆኑን ብቻ ለፍርድ ቤቱ በማሳየት የሚወሰን ሳይሆን፣በዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ከተረጋገጠው ገቢ ውጭ በእጁ እንደተገኘ የተረጋገጠው ገንዘብና ሀብት ትክክለኛ ምንጭ ምን አንደሆነ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፡፡- የወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 /1//ሀ/ እና /ለ/	137672	ብርሃነ ሀለፎም ገ/መድህን እና የፌደራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ህግ	ህዳር 25 ቀን 2010 ዓ.ም.	192
39.	ማንኛውም ሰው አግባብነት ካለው አካል ፍቃድ ባላገኘበት ሁኔታ የተሸከርካሪውን የሞተር፣ የሻንሲ ቁጥር እና መሠለ መረጃዎችን የመቀየር ተግባር የፈጸመ ከሆነ አደራጉቱ የተከለከለና በወንጀል ህግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣	122595	የገ/ጉ/ባለስልጣን ዓ/ህግ እና 1ኛ አቶ ፋሲል ጥላሁን 2ኛ አቶ ካሊድ ሳቢት	መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም	197

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አንድ ተሸከርካሪ የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ መግባቱ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ከሆነ የጉምሩክ አዋጅ በሚደነግገዉ አግባብ መኪናዉ በመንግስት ከመወረስ ሊድን የሚችልበት ሁኔታ ስላለመኖሩ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 104/3/ /ሀ/ ፤ ስለተሸከርካሪዎች መለያ፤መመርመሪያ እና መመዝገቢያ የወጣ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 42/5/ እና 48/2/ /ሐ/				
40.	ወንጀል መፈጸሙን ለማጣራትና ምርመራ ለማጠናቀቅ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎች በህግ ጥበቃ የሚደረግላቸው እና ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ለማግኘት የማይቻል በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች የሚቀርብላቸውን ጥያቄ በአግባቡ በማጤን ተገቢውን ትእዛዝ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ የአ.ቁ 592/2000 አንቀጽ 28/4/ /ሠ/ አ.ቁ 720/2004	139107	የጉለሌ ክ/ከ ፖ/ሊስ መምሪያ እና ተጠሪ የለም	መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም	204

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አንቀጽ 6				
41.	ተከሳሽ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ጠይቆ የሥር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት ጠብቆ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት በመጠበቅ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በሰጠው ውሳኔ ላይ ተከሳሽ ይግባኝ ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ፡- የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2	146727	አቶ አክሊሉ አፈወርቅ እና የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕ	ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም	208
42.	በትምህርት ደረጃው ከፍተኛ የሆነና በባህሪው ለህብረተሰብ አርአያ ሊሆን የሚገቡ ሰዎች ፍፁም ነውረኛ በሆነና ጨካኝነት በተሞላበት ሁኔታ የፈፀሙት ከባድ የወንጀል ድርጊት የወንጀል አፈጻጸሙን ከባድነት እና የወንጀለኛውን አደገኛነት የሚያሳይ በሆነ ጊዜ ወንጀለኛው ላይ የቀረበ የቀደመ የወንጀል ሪከርድ ያለመኖር ወንጀለኛው ጥሩ ፀባይ ወይም መልካም ፀባይ ያለው ነው የሚል ግምት	135787	አበባየሁ ሳሙኤል እና የኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ	መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም	211

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ለመውሰድ የማያበቃ ስለመሆኑ፣ -የወ/ህ/ቁ. 184/1/ሀ/ እና ለ ቁ. 539 ቁ. 671/1/0/ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 15 እና የወ/ህ/ቁ. 117				
43.	በወንጀል ህግ አንቀጽ 620/3/ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት በግል ተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአይምሮ ጉዳት ወይም ሞት የደረሰ መሆኑ ሊረጋገጥ የሚገባ ስለመሆኑ እና አንድ የወንጀል ክስ የወ/ህ/አንቀጽ ቁጥር 620/2/መ/ መሰረት በማድረግ በቀረበበት ሁኔታ ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲሰጡ የክስ መሰረት የሆነውን አንቀጽ ወደ አንቀጽ ቁጥር 620/3 በመቀየር ውሳኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆኑ፣ የወንጀል አፈጻጸሙ አፀያፊነት ከወንጀል ፈጻሚው ድርጊት	137262	እነ ሀይላይ ወ/ገብርኤል እና የት/ቤ/ክ/መ/ፍ/ህ ዐ/ህግ	መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም	219

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ከተረጋገጠና በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በወጣው ደረጃ መሰረት ቅጣቱ ቢወሰን የወንጀል ህጉን የቅጣት አላማና ግብ የሚያሳካ የማይሆንበት ሁኔታ ሲኖር ቅጣቱን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ መወሰን የሚቻል ስለመሆኑ፣ የወ/ህ/ቁ. 620/2/ መ፣ 620/3/ እና የወ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 113/2/ የወ/ህ/ቅ/አ/መ/ቁ.2/2006 27/1/ እና 4/9/ የወ/ህ/ቁ. 539/1/2//ሀ/፣ የወ/ህ ቁ. 82				
አሰሪና ሰራተኛ					**226**
44.	አንድ ድርጅት በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው መዘጋት ሠራተኞችን የሥራ ውልን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለማቋረጥ የሚያስችል ሲሆን መረጋገጥ ያለበት መሰረታዊው ነጥብ የአሰሪው ድርጅት ለዘለቄታው መዘጋት ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 24(4)	143334	ዋኢል አብዱጌት አብዱላዚዝ ፕላስቲክ ፋብሪካ እና እነ አበራ አመዩ (8 ኮ ሰዎች)	ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም	227
45.	የሙከራ ጊዜ ቅጥር ሲፈጸም ሰራተኛው በግልጽ	126667	ኤልያስ ባርና ሬስቶራንት	መስከረም	232

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንዲያውቀው ሳይደረግና ስምምነት ሲደረግም በጽሁፍ ተደርጎ በሁለት ምስክሮች ባልተረጋገጠበት አሰሪው ሠራተኛው ለተቀጠረበት የሥራ መደብ ተስማሚ ሆኖ አልተገኘም በሚል የቅጥር ውሉን ያለምንም ማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በህጉ መብት ያልተሰጠው ስለመሆኑ፣ የአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 1/1/ /2/ እና /3/		እና እነወ/ሮ ምርትነሽ አጥናፉ	26 ቀን 2010 ዓ.ም	
46.	አንድ ሠራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የጡረታ መብት ተጠቃሚ ከሆነ አሰሪው የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት የመክፈል ግዴታ የሌለበት ሲሆን በራሱ ፍላጎት እና ፈቃደኝነት የስራ ስንብት ክፍያን በተደራቢነት እንዳይከፍል ክልከላ የሚያደርግ ስላለመሆኑ፡- አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 2 (ሰ)	151474	ቦሰት የሕጻናትና ቤተሰብ በጎ አድራጎት ድርጅት እና ወ/ሮ ዓለም ሽመልስ ቀረቡ	መጋቢት 14 ቀን 2010ዓ.ም.	239
47.	አንድ ሠራተኛ መደበኛ የጡረታ ዕድሜው ደርሶ የመብቱ ተጠቃሚ መሆኑ በተረጋገጠበት አግባብ ለጡረታ መብት ላልተያዘለት ጊዜ የሥራ ስንብት ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል	132280	እነ አቶ አስቻለው አስማማው (2 ሰዎች) እና	መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም	246

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ፡- የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39፤ 43 (4)ፊ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ እና /ሸ/፤		የደቡብ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት		
48.	ሠራተኛ በህይወቱ ላይ አደጋ ሊደርስበት በሚችል አኳኋን እንዲሰራ ማድረግ ህገወጥ ድርጊት ስለመሆኑና ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ ውል እንዲያቋርጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ፣ የአ/ቁ. 14/ሠ/ እና አንቀጽ 32/1/ለ	136571	እድገት ተስፋ ሁለገብ ሀ/የተ/የህ/ ስራ ማህበር እና እነ አቦዬ ለሜሳ	መስከረም 27 ቀን 2010 ዓ.ም	250
49.	ለአንድ ሠራተኛ ማስጠንቀቂያ መባፍ ብቻውን “የስራ መሪ” የማያስብልና ጉዳዩ በስራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይችልም የሚባልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፡- አሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 3/2/ /ሐ/ ስ እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/1/ /ሐ/	140677	አቶ ብርሃኑ ጌቱ እና ብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት አ/ማ ሰራተኛ ማሕበር	ህዳር 22 ቀን 2010 ዓ.ም	256

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
50.	በአዋጅ ቁ 515/1999 መሰረት በህመም ምክንያት ለ8 ወራት ፍቃድ ሊሰጠው የሚገባ ሰራተኛ የ8 ወር ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት በህመም ምክንያት ወደ ስራ ለመመለስ ያልቻለ እንደሆነ የስራ ውሉ ሊቋረጥ የሚገባ ስለመሆኑ፣ አዋጅ/ቁ 515/1999 አንቀጽ 79/1ለ፤/አንቀጽ 42/2/፣/3/ እና/5/	140461	አቶ ንጉሴ ዘርይሁን እና የኢ/መን/ ባለስልጣን	መስከረም 29 ቀን 2010 ዓ.ም	259
51.	ሠራተኞች በሙሉ እውቀታቸውና ብቃታቸው ሰርተው እኩል የምርት ጥራትና መጠን ያመርታሉ ተብሎ የማይገመት ስለመሆኑና የአንደኛው ሠራተኛ ያመረተው ምርት መጠንና ጥራት ብቻ ለሌላው ሠራተኛ ከአቅም በታች ሰርቷል ለማለት በቂ መሰረት ሆኖ ሊወሰድ የማይገባ ስለመሆኑ፡-	150947	ሚሮና ኢንዳስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ እና እነ ጫልቱ ዓለሙ (4 ሰዎች)	መጋቢት12 ቀን 2010 ዓ/ም	264

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
የንግድ ህግ					268
52.	በአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻ ሰነድ ላይ የአክስዮን ማህበሩ ማህተም ማረፉ አልያም ዝውውሩ ፀድቋል ወይም ተመዝግቧል የሚል ምልክት መደረጉ ብቻውን በንግድ ህግ ስር በአዛኝር ሁኔታ የተቀመጠውን በባለአክሲዮኖች መዝገብ የመመዝገብ ግዴታን የማይተካ ወይም ቀሪ የማያደርግ ስለመሆኑ የንግድ ህግ 331 (1) እና 341 (2)	139385	ወ/ሮ መዋዕል ተኩሪ መርሻ እና አንበሳ ኢንተርናሽና ባንክ	መጋቢት 12/2010	269
53.	የአክሲዮን ማህበር ህልውና ከተቀጣሪዎች እና በአጠቃላይ ከሚኖሩ ተያያዥ እንቀውስቃሴዎች ጋር ጭምር በአንድም ሆነ በሌላ አግባብ ግንኙነት የሚኖረው በመሆኑ የማህበር መፍረስ አለመፍረስ አከራካሪ ሆኖ በቀረበ ጊዜ ማህበሩ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚገባው ተከሰተ የተባለው ችግር ማህበሩን እንዲፈርስ በመወሰን ካልሆነ በስተቀር በሌላ የህግ አግባብ መፍታት ወይም ማስወገድ እንደማይቻል	127352	እነ አቶ ታደሰ አይችሉህም /4 ሰዎች/ እና አቶ ዘውዴ ታደሰ	መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም.	275

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣ የማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድም .ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አንድ ማህብር ከተቋቋመ ጀምሮ ተደርጎ አያውቅም በሚል ምክንያት ብቻ አንድ ማህበር እንዲፈርስ ሊወሰን የማይገባ ስለመሆኑና በንግድ ህጉ መሠረት እንደበቂ ምክንያት ሊወሰድ የማይችል ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ 217 እና 218፣ 495/1/ እና /3/				
54.	አንድ ሰው የትራንስፖርት ክፍያ ከፍሎ በመኪና ሲጓዝ በነበረበት ወቅት የአካል ጉዳት ቢደርስበት የንግድ ህጉን መሠረት ያደረገና በውል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት በተጎጂው እና በአጓዡ መካከል ተመስርቷል ማለት ስለሚቻልበት ሁኔታና አጓዡ ለመንገደኛው ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ኃላፊነቱ ሊታይ የሚገባው በንግድ ህጉ ስለ አጓዥ እና ተጓዥ በተደነገገው ድንጋጌ መሠረት መሰረት ስለመሆኑ፡-	136030	ወ/ሮ ምስራ መሐመድ እና እነ አቶ አብደላ አሜ (2 ሰዎች)	ህዳር 20 2010 ዓ.ም	282

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የንግድ ሕግ ቁጥር 561፣ 595 ፣596 ፣ 597 እና 599				
ከውል ውጭ ኃላፊነት					287
55.	በተጎጂ ላይ ከደረሰ የሞት አደጋ የተነሳ በራሳቸው ስም ሆነው በመተዳደሪያ ረገድ ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ የሚችሉት፤ የተጎጂ ባል ወይም ሚስት፤ ወይም ወላጆቹና ልጆቹ ብቻ እንጂ ወንድም ወይም እህት መጠየቅ ስላለመቻላቸው፡- የፍ/ብ/ህ/ቁ.2095/1/	134240	አቶ ፍቃዱ በለጠ እና እነ ወ/ሮ አለሚቱ አድራሮ(4 ሰዎች)	መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም	288
56.	የባንኮችን መልካም ስም፣ የአገልግሎት ብቃት፤ ታማኝነት እና የሥራ እንቅስቃሴን ሌሎች ሰዎች እንዲጠራጠሩ የሚያደርግ ተግባር መፈጸም የፍትሐብሄር ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣ የፍ/ህ/ቁ. 2109 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102	137918	የድሬደዋ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የዳሽን ባንክ አክሲዮን ማህበር	መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም	293

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
57.	የመንግስት ተቋማት ሠራተኞቻቸውን የመቆጣጠር እና የመከታተል ግዴታቸውን ሳይፈጽሙ ቀርተው በተገልጋዮች ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ ጉዳዩ አይመለከተንም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፡- የፍ/ሕ/ብ/ሔር ሕግ ቁጥር 2126 (2) እና 2127 (1)	137589	በደሴ ከተማ የአራዳ ክፍለከተማ ገቢዎች ፅ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ዘይነባ ሰይድ (2ሰዎች)	ህዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም.	298
58.	በግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መኪና በወቅቱ ተጠግኖ ወደ ስራ ቢመለስ በአደጋው ምክንያት የተቋረጠን የገቢ መጠን ለመቀነስ ወይም ለማቅለል በቅን ልቦናና በማስተዋል የተደረገ እንቅስቃሴ ከሌለ በደረሰ ጉዳት መጠን በሙሉ ካሳ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ፡- በፍ/ብ/ህ/ቁ.2098 /1/ ፤2097(2)	132017	እነ አቶ ማቲያስ ወልደየስ (2 ሰዎች) እና አቶ መላኩ መኪ ማዶ	መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም	303

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ቤተሰብ					309
59.	ኑዛዜ ጥብቅ የሆነ፣ የግል ጠባይ ያለው እና በሚች ብቻ የሚፈፀም በመሆኑ ብዙ ሰዎችን አንድ በሆነ ፅሁፍ በጋራ ማናዘዝ የማይቻል እና ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርግ ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ህ/ቁ 857፣858 እና 880	134836	አቶ አባተ ሀይሉ እና አቶ አስረስ ረታ (4 ሰዎች)	መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም	310
60.	ባል እና ሚስት በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረ መሬት ጋብቻው በአንደኛው ተጋቢ ሞት የተቋረጠ ቢሆንም ሌላኛው ተጋቢ በሌላ ህጋዊ ምክንያት መብቱ እስካልተቋረጠ ድረስ ይዞታው በስሙ ተመዝግቦ ደብተር ለማግኘት እና በይዞታው ለመጠቀም የሚችል ስለመሆኑ፣ ሴቶች መሬትን በመጠቀም፣በማስተላለፍ፣በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕ/መ አንቀጽ 35/7/፣ የኦሮሚያ የገጠር	138286	እነ ጫሉሜ ሙለታ እና ጫለሽ ቁልበሻ	መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም	314

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መሬት አዋጅ ቁ. 130/99 አንቀጽ 6/3/ እና ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 15				
61.	በነባር ይዞታ ላይ ያረፈ ንብረት በውርስ የሚተላለፍ እንደሆነ ወደ ሊዝ ስሪት ማስገባት የማይችል እና ለጉዳዩ የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ተፈጻሚነት የሌለው ስለመሆኑ፡-	131677	የወ/ሮ ጌጤ ካሳ ወራሾች እና የኮ/ቀ ክ/ከ መሬትና አስተዳደር ጽ/ቤት	ጥቅምት 28 ቀን 2010 ዓ.ም	318
62.	በጋብቻ በተሳሰሩ ባልና ሚስት መካከል ከአንዱ ጋር የውል ግዴታ የገባ ሰው በዋናው ክርክር ሁለቱን አጣምሮ ሊከስ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ እንዲሁም ተዋዋይ በሆነው ተጋቢ ላይ የተሰጠ ውሳኔ የተጋቢዎች የጋራ እዳ ነው ወይስ የተወሰነበት ተጋቢ የግል እዳ ነው የሚለው ክርክር ሊነሳ የሚችለው በአፈጻጸም ወቅት እንጂ ሌላኛው ተጋቢ ሊከሰስም ሆነ ሊፈረድበት ስላለመቻሉ፡-	132518	እነ ተኽሉ አስፍሃ(6 ሰዎች) እና እነ አቶ ስብሃቱ ገ/መስቀል(2 ሰዎች)	መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም	323

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
63.	የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ለአፈፃፀም የቀረበ አከራካሪ የሆነ ቤት ሊካፈልም ሆነ ሊሸጥ የማይችል ሲሆን ለካፊል የሚችለው በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / ነው በማለት ባለሙያ አስተያየት በተሰጠበት ሁኔታ በዚሁ አግባብ ክፍፍሉ ሲደረግ የበለጠ ይዞታ የደረሰው ወገን ለሌላው ወገን ግምቱን እንዲከፍል በማድረግ መፈፀም የሚገባው እንጂ በፍርዱ በተቀመጠው ሌላ አማራጭ መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም ማድረግ የማይገባ ስለመሆኑ፡- የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 91(1)እና(2)	141527	አቶ እለፋቸው ታምሩ እና ወ/ሮ እመቤት ተሾመ	ሕዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም	329
64.	አንድ የንግድ ቤት በኪራይ የተሰጠው በትዳር ግንኙነት ወይም በጋብቻ ውስጥ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ከትዳር ግንኙነት በፊት መሆኑ ብቻ የንግድ ሱቅ ከጋብቻ በፊት የተገኘ የግል ንብረት ነው ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ፣	136872	ህንጻ እስጢፋኖስ ሀይሉ እና ወ/ሮ ሽቱ ቦንገን	መስከረም 21 ቀን 2010 ዓ.ም	333

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
65.	ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነትን ለማስረዳት የቀረበ ማስረጃ ግንኙነቱን የማሳየት ብቃት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ የግንኙነቱን ያለመኖር በማንሳት የሚከራከረው ሌላኛው ወገን በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ግንኙነት ስላለመኖሩና ንብረቶችም የግል ስለመሆናቸው የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 75/1995 117/4/ እና 114 እና 97 አንቀጽ 109፣110፣113 እና 117	126411	አቶ ተስፋጊዮርጊስ አዳነ እና ወ/ሮ አሰፋ ግርማ	መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም	336
66.	በፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀ ወይም ተቀባይነት ያገኘ የጉዲፈቻ ውልን መሰረት በማድረግ ወራሽነትን ያረጋገጠ ወገን የውርስ ንብረት ድርሻን ለማግኘት ያቀረበው ጥያቄ ቀድሞ በጉዲፈቻ ውል የፀደቀበት ውሳኔ መብቱ ተነካ በሚል ወገን በቀረበ መቃወሚያ መሰረት እንዲፈርስ እንዲሻር ባልተደረገበት የውርስ ድርሻ ክፍያ ጥያቄው ውድቅ ማድረግ ህግን መሰረት ያላደረገ ስለመሆኑ	137853	በለጠ ነጋሽ እና እጅጋየሁ ላቀው	መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም	341

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለ አንቀጽ 202. የፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ. 41፣358				
67.	በውርስ የተላለፈን የመንግስት ንግድ ቤት የማከራየት መብትን ከወራሾች መካከል አንዱ ያለ ከተማ አስተዳደሩ እውቅና ያከራየ እንደሆነ ፤ የተከራይነት መብት የሚቋረጠው ያከራየው ወራሽን በተመለከተ ብቻ እንጂ ሌሎች እሱ በሞግዚትነት የሚያስተዳድራቸው ወራሾች የመከራየት መብታቸው የሚቀጥል ስለመሆኑና ፤አከራዩ ሞግዚታቸው ባከራያቸው ወገኖች ላይ በንግድ ቤት የኪራይ ውል መነሻነት ክስ ለማቅረብ የሚያበቃ መብትና ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ፡-	133736	እነ አቶ መዚድ ተስፋዩ (2 ሰዎች) እና ወ/ሮ ዘይነባ ለካ	ታህሳስ 26 2010 ዓ.ም	345

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
68.	የውርስ ሰርተፊኬት አንድ ሰው የራሱን ወራሽነት ለማስረዳት የሚወስደው ማስረጃ እንጂ ሌሎች ወራሾች አለመኖራቸውን የሚያሳይ ሰነድ ስላለመሆኑ፣ እና በግራ ቀኙ የሚች ወራሾች መሆናቸው በማረጋገጥ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከማስረጃነት በዘለለ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ በሚያዘው መሰረት ከሌሎች ሰዎች ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ ያገኘና በፍርድ ያለቀ መቃወሚያ የማይቀርብበት ተደርጎ ሊወሰድ የማይገባ ስለመሆኑ፡- ፍ/ህ/ቁ. 996/1/ እና ተከታዬቹ	130284	እነ አቶ ክንፈ ሐጎስ /3ሰዎች/ እና ወ/ሮ ሃና ሐጎስ	ጥቅምት 30 ቀን 20010 ዓ.ም	351
69.	በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ ጋብቻ በፍቺም ሆነ በሞት ምክንያት ሲፈርስ ንብረት የሚጣራበት አግባብ በውል ወይም በስምምነት ተለይቶ ባልተቀመጠበት ሁኔታ የባልና ሚስት ሀብት የሚጣራው በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 113 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ስለመሆኑ፡- ኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር	137869	ወ/ሮ ቦንሲቱ ዱፌራ እና ወ/ሮ ታምሪ ረጋሳ	ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ/ም	357

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	83/96 እንደተሻሻለው አንቀጽ 93				
70.	የጉዳት ካሳ ጥያቄ ከጋብቻ ፍቺ ጋር ተያይዞ የቀረበ በሆነበት እና ጉዳቱም የደረሰው ከፍቺው ጋር ተያያዞ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ጥያቄው የባልና ሚስት ፍቺን ተከትሎ ከሚነሳ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ጋር በአንድ ላይ ሊስተናገድ አይችልም በሚል የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፡- የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 84	135902	ወ/ሮ መስከረም ጫካ- እና አቶ አክሊሉ ሽፈራው (2 ሰዎች)	መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም	362
ግብር					367
71.	ከቀረጥ ነጻ መብትን በመጠቀም ወደ ሀገር የገባን እቃ ለመሸጥ ወይም ወደ ሌላ ለማስተላለፍ ከተፈለገ ቀድሞ ቀረጡን በመክፈል ነጻ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ፡- አዋጅ/ቁ 859/2006 አንቀጽ 30(1)	138837	እነ አቶ ብሩክ ገ/ሥላሴ (2 ሰዎች) እና አቶ ዳዊት ተሰማ ቡታ	ጥር 23 ቀን 2010	368

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
72.	አንድ ኩባንያ በደረሰበት ችግር ምክንያት ከገበያ እንዳይወጣ እና ተወዳዳሪ መሆን እንዲችል ተሰጥቶት የነበረው የኪሣራ ማሸጋገር መብት፤ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተለወጠ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ኩባንያው አስቀድሞ ከነበረበት ኪሣራ ወጥቶ በተጨባጭ ያደገ መሆኑ የሚገመት ከሆነ በዚያው የግብር ዘመንም ሆነ ቀደም ባሉት የግብር ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት አስቀድሞ ተሰጥቶት የነበረው ኪሣራ የማካካስ መብት የሚቋረጥ ስለመሆኑ፡-አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28(1)(2)	131900	የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር	ጥቅምት 22/2010 ዓ.ም	374
73.	አንድ ግብር ከፋይ ለንግድ ስራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ እንዲደረግለት ለንግድ ስራው ያወጣውን ወጪ ማስረዳት የሚችለው በሚያቀርበው በስሙ ወጪ በሆነ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው ደረሰኝ ስለመሆኑ፤-	139334	የኢ/ገ/ን/ባለስልጣን እና ሻንዶንግ ሃይወይ ኢንጂነሪንግ	ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም.	380

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 20 የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 22(2) ፤ደረሰኝ አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 28/2001 አንቀፅ 4(1)				
	አፈጻጸም			**384**	
74.	በሀራጅ አካሄድና ሽያጭ ስርዓት ተገቢ ያልሆነ ድርጊት፣ ማጭበርበር ወይም ማታለል መኖሩ በማስረጃ ከተረጋገጠ ጨረታውን ለማፍረስ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ፣ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 445	136092	ሙሉአለም ግዛው ወልዴ እና እነ ዙፋን ዘለቀ /2ሰዎች /	መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም	385
75.	በአፈፃፀም ሂደት ንብረቱ አላግባብ ተሸጠ ወይም መብቱ ተጎዳ የሚል ሰው ፤ አቤቱታውን አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት ወይም አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ስህተት የፈፀመ ነው በማለት በይግባኝ እንዲታረም ማድረግ እንጂ የአፈፃፀሙ መዝገብ ከተዘጋ እና አመታት ካለፉ በኃላ መብቱ ይከበረልኝ በማለት አዲስ ክስ ማቅረብ የማይችል	131084	አቶ ጌታቸው ይርገቡስ እና እነ በላይ ናማጋ (3 ሰዎች)	131084	389

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑ፤ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 404 እና 231(1) (ሀ)				
ልዩ ልዩ					394
76.	በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143(1) የተመለከተው የይርጋ ዘመን አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ላይ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ እና ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው የአስር ዓመት የይርጋ ዘመን ስለመሆኑ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143(1)፤1845	78629	የአቶ ካሣ አበበ ወራሽ አቶ ሰለሞን ካሣ እና ወ/ሮ አያልነሽ ስፍራ	ጥር 14 ቀን 2005 ዓ.ም	395
77.	ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር ተፈጽሟል የሚል ክስ ለፌደራል የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት ማቅረብና አስተዳደራዊ እርምጃና ቅጣት እንዲጣል የማድረግ ስልጣን ያለው የባለስልጣኑ ዓቃቤ ህግ ስለመሆኑ፣	128035	ምስኪ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ቤካስ ኬሚካልስ ሀ/የተ/የግ/ማህበር	ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ.ም	401

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አዋጅ ቁ. 813/2006 አንቀጽ 37/1				
78.	ገንዘብ የተከፈለ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ወይም ደብዳቤ ሰነዱን ባዘጋጀዉ ወይም ደብዳቤዉን በፃፈዉ ሰዉ ላይ ማስረጃ የሚሆን ስለመሆኑ፡- ፍ/ሕ /ቁ 2018(1)	136245	በደሌ ቢራ አ/ማህበር እና አቶ ገብረመድህን ገ/ሕይወት	ጥር 23 ቀን 2010	406
79.	የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማናቸዉም አይነት ሰነድ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ከተጻፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰዉ ንብረት በሚገኝበት ሀገር ባለዉ በማይንቀሳቀስ ርስት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ማንኛውንም አይነት ውጤት የማያስገኝ ስለመሆኑና ፅዳው እንዲከፈል በተወሰነበት ጊዜ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው የመያዣ መብት ያገኝበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይወስዳል የሚል ስምምነት ሁሉ ተቀባይነት የማይኖረዉ ስለመሆኑ፡- ፍ/ሕ/ቁ 3052 እና 3060	135197	አቶ ደለሳ ሌጆሳ እና እነ አቶ ፍቃዱ ጫላ -(2 ሰዎች)	ጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም	410

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
80.	ወጣት ጥፋተኞችን የተመለከቱ የጥንቃቄ እርምጃዎች አፈጻጸም በተቻለ መጠን አጥፊውን በማረም መልካም ውጤት ሊያስገኝ በሚያስችል አግባብ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ፣ ለወጣት ጥፋተኞች የሚያገለግል የጠባይ ማረሚያ ተቋም በሌለበት ፣ በወላጅ ቁጥጥር ስር ሆኖ የሚደረግ የባህሪ ሁኔታ ክትትል የተሻለ ውጤት እንደማይመጣ እና የጥፋተኛው አደገኛነት በተገቢው አግባብ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ቅጣቱ በአዋቂዎች እስር ቤት እንዲፈፀም የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፡- የወንጀል ህግ አንቀጽ 168/2	136262	የወ/ጉ/ክ/ ዐ/ህግ እና መሀሪ ታደሰ	መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም	416
81.	አንድ ቀድሞ በነበረ መመሪያ ዋጋ የወጣለትን ንብረት የተረከበ ወገን የንብረቱን መጥፋት ተከትሎ ክስ ሲመሰረት የንብረቱ ዋጋ በሌላ አዲስ መመርያ የተሻሻለበት ሁኔታ መኖሩ ከተረጋገጠ ንብረቱ የጠፋበት ወገን ተጠያቂ	126529	የሰቆጣ ወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት እና ቂስ መሉጌታ ተፈራ	ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም	421

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የሚሆነው አዲስ በወጣው መመርያ መሠረት በወጣው የዋጋ ተመን አግባብ ስለመሆኑ፣				
82.	በሁለት የህግ ሰውነት በተሰጣቸው አካላት መካከል የኢንቨስትመንት መሬት ያላግባብ ተይዞብኛል በሚል የሚነሳ ክርክርን በተመለከተ ክርክር ባስነሳው መሬት ላይ ግራ ቀኙ ያወጡት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የፌዴራል ከሆነ ጉዳያቸው ሊታይ የሚችለው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሲሆን፣ ፈቃድ ያገኙት ግን በክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ ከሆነ በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታይ ስለመሆኑ፤ እንዲሁም ከሁለቱ አንዱ ወገን የፌዴራል ተመዝጋቢ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6 መሠረት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ የፌደራል ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 ፣የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 138/2000	133667	ብዙአየሁ ሾኔ የቡና ተክል ልማት ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ቢ.ዲ.ኤፍ.ኤስ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ታህሳስ 24 2010 ዓ.ም	425
83.	የድሬድዋ ከተማ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 416/96	134681	ሳዲቅ አብዱሪህማን	ጥቅምት 21	431

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መሰረት የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ለማስፈፀም ሲባል ከይዞታ ባለቤትነት፣ ከፈቃድ አሰጣጥ እና ከቦታ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚነሱ ክርክሮችን ከማየት ባለፈ በእርሻ መሬት ባለይዞታነት ይገባኛል ጥያቄን መሰረት ያደረገ ክርክርን ለማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፡- የአ/ቁ 416/1996 አንቀፅ 31(1)		(ሰዎች) እና የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት	ቀን 2010 ዓ/ም	
84.	በከተማ አስተዳደር ወይም በቀበሌ ያላግባብ የተያዘን የምርጫ ቤት ለማስመለስ የሚቀርብን ክስ የማየት ስልጣን በህግ ለሌላ የመንግስት አካል ባልተሰጠበት ሁኔታ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፡- ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 37	137353	ወ/ሮ አዛለች አጎናፍር እና ገብርኤል አካባቢ ቀበሌ ጽ/ቤት	ጥር 22 ቀን 2010	436
85.	አንድ የመንግስት ቤት ተከራይ የራሱ ቤት ካገኘ የመንግስት ቤትን በተከራይነት ይዞ መቀጠል የማይችል	133309	አቶ ለማ ማሙዬ እና	ጥር 24 ቀን 2010	441

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑ፡- መመሪያ ቁጥር 10/2006 አንቀፅ 15(2)		በአዳማ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 12 ጽ/ቤት		
86.	በኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀም ለረጅም ጊዜ በሌላ ሰው የተያዘና ጥቅም ላይ ሲውል የነበረን የገጠር መሬት የተያዘው ሕገወጥ ውልን መሰረት በማድረግ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ መሬቱ እንዲለቀቅ የሚቀርብ ክስ በአስራ ሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ፣ የኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 32	140538	አቶ ወርቁ ታደሰ እና አቶ ጅራተ አፈልታ	መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም	445
87.	የአ/ብ//ክ/መ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ “በይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል” በሚል ተገልጸው የሚገኙት ድንጋጌዎች በይግባኝ ደረጃ ቀርበው ለመታዬት የማይችሉ የመጨረሻ ውሳኔዎች መሆናቸውን የሚገልጽ	149962	አቶ ስለሽ ዋለልኝ እና የአ/ብ/ክ/መ. ሥ/ምግባርና ፀረ ሙስና ኮምሽን ዐ/ህግ	መጋቢት 25 ቀን 2010 ዓ/ም	449

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንጂ በሰበር ሰሚው ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን ጉዳዮች ለማረም የሚቀርቡ ጉዳዮችን የሚጨምር ስላለመሆኑ፡- የአ/ብ//ክ/መ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር104/2004 አንቀጽ 75(3)				
88.	የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በህጉ አግባብ በሁለት ኢንዱስትሪዊ ንድፎች መካከል ተመሣሣይነት አለ ወይስ የለም የሚለውን ለመለየት የአከራካሪውን ንድፍ አዲስነት ለመወሰን የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ዋና ዋና ባህሪያት በመለየት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ ወይም ተመሳሳይነት ያለው ስለመሆኑ በዘርፉ ያለውን የዳበረ እውቀት እና ልምድ መሰረት በማድረግ ማጣራት አድርጎ ውሳኔ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ	137939	ፍፁም ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት	ጥቅምት 20/2010	454

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የአነስተኛ ፈጠራና ኢንዱስትሪ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(1)፤ 48(1) ፤ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 320/1995				
89.	የአገልግሎት ድርጅት ያከራየ ወገን ያከራየው ድርጅት ተገቢውን አገልግሎት እንዳይሰጥና ታሽጎ እንዲቆይ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረቡን ተከትሎ እግድ የተሰጠ በሆነበት እና ተከራዩም ከድርጅቱ ገቢ ባላገኘበት ሁኔታ ድርጅቱ ታሽጎ ለቆየበት ጊዜ ተከራይ የኪራይ ክፍያ እንዲከፍል የማይገደድ ስለመሆኑ፡-	136024	አቶ ቢልልኝ ጌታነህ እና አቶ ገብራይ ተከስተ	ጥቅምት ቀን 21 2010 ዓ.ም	464

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው·ል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 127459

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ረታ ቶሎሳ

ተክሊት ይመሰል

ቀነአ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- ጣና የውሃ ጉድንድ ቁፋሮና ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር

- ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የድሬዳዋ አስተዳደደር ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን - ዐ/ሕግ አብይ ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 117051 የካቲት 22 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች ሚያዚያ 26 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ 06 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎች በአድጁዲኬሽን የመዳት መፍቻ ዘዴ መዳኘት የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው አመልካች ለተጠሪ 12 ውሃ ጉድንድና 2 የውሃ ጉድንድ መቆጣጠሪያ ለመገንባት፤ ተጠሪ ደግሞ ብር 59,922,705 /ሃምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ አምስት ብር/ ለመክፈል ስምምነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አድርገው እንደነበር በመግለፅ በተጠሪ ጥፋት የተነሳ ሥራው በስምምነቱ መሠረት ሊፈፀም ባለመቻሉ የውል ጊዜው ለተጨማሪ ስድስት ወራት እንዲራዘም፤ የዋጋ ለውጥ እንዲደረግ፤ ካሳና ወለድ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል በመጠየቅ የቀረበ ክስ ነበር፡፡

ተጠሪም በበኩላቸው ጥፋት አለመኖሩን፤ችግሩ የተፈጠረው በአመልካች የቴክኒክ ብቃት ችግር መሆኑን በመጥቀስ የካሳ ክፍያም ሆነ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲሆን መልስ አቅርቧል፡፡

ግራቀኙ ወገኖች አስቀድሞ ባደረጉት ውል አንቀጽ 24 መሠረት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት የተመደበው አድጁዲኬተር ጉዳዩን እንዲዳኝ ተደርጎ በሰጠው ውሳኔ ስለጉዳዩ ተገቢውን ማጣራት ሲያደርግ ቆይቶ አመልካች በጠየቁት መሠረት የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ በስድስት ወራት እንዲራዘም፤ተጠሪ ቅድመ ክፍያ ላዘገየበት ወለድ እንዲከፍሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው ይግባኝ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል መሆኑን ጠቅሶ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎችን በሚመለከቱ አለመግባባቶች የግልግል አካል ዳኝነት መስጠት እንዳይችል በህግ ክልከላ የተደረገ በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ አድጁድኬተር ጉዳዩን ያየው ስልጣን ሳይኖረው ነው የሚልና ሌሎች ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን በማቅረባቸው ፍርድ ቤቱ ቅሬታው መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሮ ሲያበቃ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል የአስተዳደር ውል ነው፡፡ የአስተዳደር ውሎች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የማይገባቸው ለመሆናቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 315(2) ደንግጓል፡፡ ስለሆነም አድጁዲኬተር ጉዳዩን ያየው በህግ በተከለከለ ጉዳይ ላይ በተደረገው ውል መነሻነት በመሆኑ ሥልጣን ሳይኖረው ነው በማለት የአድጁዲኬተሩን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታው በአጭሩ፡- አድጁዲኬሽን በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዓለም አለመግባባቶችን ለመፍታት ጠቃሚ የሆነና ከግልግል ዳኝነት የተለየ የአለመግባባት መፍቻ መንገድ ሆኖ እያለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አድጁዲኬሽንን ከግልግል ዳኝነት ጋር በማመሳሰል የተያዘውን ጉዳይ አድጁዲኬተር ማየት አይችልም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ነው የሚሉና ሌሎችንም የቅሬታ ነጥቦች አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ በግራቀኙ ተከራካሪዎች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት በውላቸው አንቀጽ 24 መሠረት በአድጁዲኬተር መታየቱ ያላግባብ ነው ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አድጁዲኬተር (ገላጋይ ዳኛ) የአስተዳደር ውልን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮችን ለመዳኘት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ጭብጥ ምላሽ ማግኘት ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከመዝገብ ምርመራው መገንዘብ እንደተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል እ.አ.አ ኤፕሪል 06 ቀን 2013 የተደረገ ውል ለመኖሩ በግራቀኙ ወገኖች የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚሁ ውል አንቀጽ 24 ሥር አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አግባብ በተመለከተ አስቀድሞ በአድጁዲኬተር ወይም በገላጋይ ዳኛ ሊታይ እንደሚገባው፤ይህ ገላጋይ ዳኛም በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ሊመደብ የሚገባው መሆኑን እንዲሁም በገላጋይ ዳኛው ውሳኔ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት ምን ሊሆን እንደሚገባ ጭምር ስምምነት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ሲሆን ለክርክሩ መነሻ የሆነው የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮም ለህዝብ ጥቅም ለመስጠጥ የታሰበ በመሆኑ ውሉ ለህዝብ ጥቅም የተደረገ ውል መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3132(ለ) ሥር እንደተመለከተው ከህዝብ አግልግሎት ሥራ ጋር የተያያዙና ለውሉ አፈፃፀምም የተዋዋዩን የድሬዳዋ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ያልተቋረጠ ተካፋይነት የሚጠይቅ በመሆኑ ውሉ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪው ከአመልካች ጋር ያደረጉት ውል አስተዳደር መስሪያ ቤት ውል ነው መባሉ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 315(2) ሥር በግልፅ እንደተመለከተው የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎችን በግልግል ዳኝነት እንዳይታዩ ህግ ክልከላ አድርጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አለመግባባትን ለመዳኘት በውል ሥልጣን የተሰጠው አድኋዲኬተር ወይም ገላጋይ ዳኛ ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 315(2) የአስተዳደር ውልን አስመልክቶ የሚነሳ አለመግባባትን ለመዳኘት የማይችለው የግልግል ዳኝነት አካል ወይም አርቢትሬተር ነው፡፡ እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ዋናው ነጥብ የአድኋዲኬተር እና የአርቢትሬተር አንድነትና ልዩነታቸው ምንድን ነው አርቢትሬተር የአስተዳደር ውሎችን እንዳይዳኝ በህግ ክልከላ ከተደረገበት ዓላማ አንፃር አድኋዲኬተር የአስተዳደር ውሎችን እንዲዳኝ ሊፈቀድለት ይገባል ወይ? ከዚህ አንፃር አመልካችና ተጠሪ ስለአለመግባባት አፈታት በውላቸው አንቀጽ 24 ያደረጉት ስምምነት በህግ ተቀባይነት ያለው ነው ማለት ይቻላል ወይ? የሚሉት ነጥቦች ናቸው፡፡

በመሠረቱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ የሆኑ የተለያዩ አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶች እንዳሉ የሚታወቅ ነው፡፡ ከእነዚህ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስልቶች ውስጥ በአገራችን የሥነ ሥርዓት ህግ ዕውቅና ያገኙት ድርድር፤እርቅ፤ግልግል እና ስምምነት ሲሆኑ አድኋዲኬሽ ወይም ጉዳዩን በገላጋይ ዳኛ የመፍታት አሰራር በብዙ የዓለም ሀገሮች የሚሰራበት ከመሆኑም በላይ በንግዱ ህብረተሰብ መካከል የሚፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በኩል ደንብ ወጥቶለት እየተሰራበት ይገኛል፡፡

አለመግባባት የተፈጠረበትን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ሂደት አድኋዲኬሽን እንደሚባል የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ባወጣው ደንብ አንቀጽ 2 ሥር የተመለከተ ሲሆን ግልግል በግራቀኙ ወገኖች መካከል የሚፈፀም ውል ሲሆን ውሉን መሠረት በማድረግ የግልግል ዳኛ የሚሰጠው ውሳኔ አስገዳጅ ውጤት እንዳለው ከፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 3325 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነው፡፡ ስለ ሁለቱ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶች አንድነት ስንመለከት ውሳኔው አስገዳጅነት ያለው መሆኑ እና ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ በሆነ ሁኔታ አለመግባባት የሚፈታባቸው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀጽ 315(2) ድንጋጌ በግልግል የዳኝነት ሥርዓት የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎች ሊዳኙ እንደማይገባ የደነገገበት አግባብ ፍትህ ከአማራጭ የሙግት መፍቻ የሚገኝ መሆኑን በመዘንጋት ሳይሆን የአስተዳደር ውሎች ጉዳይ የህግ የበላይነትን መርህ በአደረገው መደበኛ ፍርድ ቤት መታየቱ በውሎቹ ሊደረስበት የታሰበውን ዓላማ ለማሳካት እንደሚያስችል ታምኖበት የተወሰደ የመንግስት ፖሊሲ አማራጭ እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ ነው። አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች የራሳቸው የሆነ ጠቀሜታ ያላቸው የመሆኑን ያህል የጎንዮሽ ጉዳትም ሊኖራቸው እንደሚችል መገንዘብ ይገባል። በተለይም በአገራችን ሥርዓት ተበጅቶላቸው በጠነከረ አካኋን የሚመሩ የመንግስትንና ህዝብን ጥቅም ሊያስጠብቁ የሚችሉ የተሟላ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የተሰጣቸው አማራጭ ሙግት መፍቻ ተቋማት ከአለመጠናከራቸው አንፃር የአስተዳደር ውሎች በግልግል ዳኝነት አካል እንዳይታዩ ህግ አውጭው አካል ለመምረጡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀጽ 315 ይዘት መገንዘብ የሚቻል ነው።

የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የማይገቡ ስለመሆኑ በህግ ከተመለከተና ዓላማውም የህግ የበላይነትን ለማስከበር ህግ አውጭው ለአስተዳደር ውሎች ዳኝነት የመረጠው ስለመሆኑ ግንዛቤ ከተወሰደ አድጁዲኬተር ማለትም የአርቢትሬተር ዓይነት አስገዳጅ ውሳኔ የሚሰጥ አካል የአስተዳደር ውሎችን እንዲዳኝ የሚያስችሉ ስምምነቶች የህግ ውጤታቸው ምን ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ ምላሽ መስጠት ይጠይቃል። አርቢትሬተር የአስተዳደር ውሎችን በተመለከተ መዳኘት የማይችል ከሆነ አድጁዲኬተር ከሚሰጠው የዳኝነት ባህሪ አንፃር የአስተዳደር ውሎችን ሊዳኝ የሚችል አይሆንም። ምክንያቱም አድጁዲኬተርም ሆነ አርቢትሬተር አስገዳጅ ውሳኔ የሚሰጡ አማራጭ የሙግት መፍቻ አካላት ስለሆኑ ነው።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አድጁዲኬተር ከአርቢትሬተር የተለየ አማራጭ የሙግት መፍቻ ተቋም ተደርጎ ሊወሰድ ስለማይችል የሥር ፍርድ ቤቱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ ውል የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል በመሆኑ በገላጋይ ዳኛ እንዲታይ ህጉ አይፈቅድም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 315(2)ን፤የፍትሐ ብሔር ህጉን አንቀጽ 1678(ለ) 3131፤3132(ለ) ያገናዘበ በመሆኑ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማጠቃለል ለሰበር አቤቱታው መቅረብ ምክንያት የሆነውን ዳኝነት የሰጠው ገላጋይ ዳኛ በተያዘው ጉዳይ ላይ የመወሰን ስልጣን የሌለው ነው፡፡ ገላጋይ ዳኛ ሥልጣን አልነበረውም የሚል ድምዳሜ ላይ ከተደረሰ በአመልካች በኩል የሚቀርቡ ሌሎች የቅሬታ ነጥቦችን በጭብጥነት ይዞ መወሰን ተገቢ አይሆንም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 117051 የካቲት 22 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡

2. የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎችን አስመልክቶ የሚነሳ አለመግባባትን አይቶ ለመወሰን ገላጋይ ዳኛ (Adjudicator) ሥልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣ ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዲኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ - 124725

ቀን - 29/02/2010

ዳኞች፡-

ዳኜ መላኩ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የሽሬ እንደስላሴ አንዋር መስጊድ-አልቀረበም

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ትኑር ፍትዊ

2. አቶ አደም ዓብደልባቂ

3. አቶ ስራጅ ዓብደልባቂ — አልቀረቡም

4. ወ/ሮ ዘቢባ ዓብደልባቂ

5. ወ/ሮ ሰትኑር ዓብደልባቂ

6. አቶ ኑርሁሴን ዓብደልባቂ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ክርክሩ የተጀመረዉ በትግራይ ክልል ሽሬ እንደስላሴ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ እና የተከሳሽ ከሳሽ እንዲሁም 2ኛ-6ኛ ተጠሪዎች ጣልቃ ገቦች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘትም በአጭሩ፡- ከአመልካች ጋር በ25/08/98 ዓ.ም ሽያጭ እና የልውጫ ውል አመልካች ቤትና ይዞታ በብር 175,000.00 ገዝቶ ብር 20,000.00 ቀብድ ከፍሎ ቀሪውን ገንዘብ ባለመክፈሉ እና ልውጫውንም በውሉ መሠረት ባለመፈጸሙ፣ ቀሪውን ብር 155,000.00 እንዲከፍል እና በልውጫ ውሉ መሠረትም ቤቱን እና ቦታውን የሚመለከቱ ማስረጃዎችን እንዲያስረክቡኝ፤ ውሉ ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ካለም አመልካች ቀብድ ተቀጥተው ግራ ቀኝ ከውሉ በፊት ወደ ነበርንበት እንድንመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

አመልካች በበኩሉ በስሙ ውሉን ያደረጉት ሀጂ ዑስማን ዓብዱልቃዲር አመልካችን ወክለዉ ውሉን ለማድረግ የሚያስችል ዉክልና የሌላቸዉ በመሆኑ በ1998 ዓ.ም ተደረገ በተባለዉ ዉል የማይገደድ መሆኑን፤ በቀን 16/03/2000 ዓ.ም ከተጠሪዎች ጋር ተደርጎ በዞን ፍትሕ መምሪያ በጸደቀዉ ዉል በክሱ የተመለከተዉን ቤትና ቦታ አመልካች በብር 20,000.00 ገዝቶ ቤትና ቦታዉ ተላልፎለት ግብር እየገበረበት በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የ1ኛ ተጠሪ ክስ ዉድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡ በበኩሉ ባቀረበዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ፣ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገ ዉል መሠረት ከተጠሪዎች ገዝቶ ሳይት ፕላን በስሙ ተሰርቶለት ግብር የሚከፍልበትን ቤትና ቦታ ተጠሪዎች እንዲለቁለት ማስጠንቀቂያ የሰጣቸዉ ቢሆንም ለመልቀቅ ፍቃደኛ ባለመሆናቸዉ ቤትና ቦታዉን ለቀዉ እንዲያስረክቡት ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ፤ በ1998 ዓ.ም በተፈረመ ዉል መሠረት የሽያጭ እና የልዉጫ ዉል በብር 175,000.00 ዋጋ ተስማምተዉ ብር 20,000.00 ቀብድ ተከፍሎአቸዉ ቀሪዉ ብር 155,000.00 ሲከፈል የቦታ ርክክብ እንደሚፈጸም ተስማምተዉ እያለ በዉልና ማስረጃ በብር 20,000.00 ብቻ እንደተስማሙ ተደርጎ መገለጹ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በተንኮል የተደረገ መሆኑን፣ የመኖሪያ ቦታን በኃይማኖት ቦታ መለወጥ በህግ የተከለከለ መሆኑን በመግለጽ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ዉድቅ እንዲሆን ጠይቀዋል፡፡ ከ2-6ኛ ያሉት ተጠሪዎችም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በክርክሩ ጣልቃ በመግባት 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር በማንሳት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኝ በዚህ መልኩ ያቀረቡትን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፤ በ25/08/98 ዓ.ም የተደረገዉ ዉል ሐጂ ዑስማን ዓብዱልቃዲር ህጋዊ ዉክልና ሳይኖራቸዉ ያደረጉ በመሆኑ አመልካችን ሊያስገድድ አይችልም፡፡ በቀን 25/08/98 ዓ.ም የተደረገ የሽያጭ እና የልዉጫ ዉል ዋጋዉ ብር 175,000.00 ሆኖ አመልካች ለተጠሪዎች ብር 20,000.00 ሆኖ በዉልና ማስረጃ ስጸድቅ ዋጋዉ ብር 20,000.00 ብቻ እንደሆነ የተገለጸዉ የስመ ሀብት ዝዉዉር በሚፈጸምበት ጊዜ ለመንግስት የሚከፈሉትን የተለያዩ ክፍያዎችን ለመቀነስ ሲባል መሆኑ፣ እንዲሁም አመልካች ቤት እና ቦታዉን የገዛዉ ለማምለኪያ ስፍራ መሆኑ በመረጋገጡ ዉሉ ህጋዊ አይደለም፡፡ በመሆኑም ዉሉ ፈርሶ ተጠሪዎች ብር 20,000.00 የተቀበሉትን ለአመልካች እንዲመልሱ እንዲሁም የቤቱና የይዞታዉ ስመ ሀብት በተጠሪዎች ሆኖ ሳይት ፕላን እንዲሰራላቸዉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለሰ/ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ዉሉ ሊፈርስ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ያመለከተዉን ቤትና ቦታ ተጠሪዎች ለቀዉ እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ ዉሉ ፈራሽ ነዉ በማለት በወረዳዉ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የወሰነ ሲሆን፣ አመልካቾች ይህን ዉሳኔ ለማስለወጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት በቅደም ተከተል የሰጡትን ዉሳኔ እና ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 05/07/08 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በተወካዩ አማካይነት በቀረበ 5 ገጽ የሰበር አቤቱታ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ የሽያጭ እና የልዉጫ ዉል ፈራሽ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ መሠረት የሌለዉ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህን ማረም ሲገባዉ የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል የሰጠዉ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለዉ መሆኑን በመጥቀስ ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡ ተመርምሮ ዉሉ እንዲፈርስ በስር ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አከራክሮ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸዉ 1ኛ ተጠሪ ለብቻ፣ 2ኛ-5ኛ ተጠሪዎች በአንድነት በቀን 04/09/08 ዓ.ም አዘጋጅተዉ ባቀረቡት መልስ፤ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤትና ቦታ በብር 175,000.00 ለመግዛት ተስማምተዉ በቅድሚያ ብር 20,000.00 ከፍሎ ቀሪዉን ብር 155,000.00 ከህዝብ ሰብስቦ እንደሚከፍላቸዉ ተስማምተዉ ግን ስመ ሀብቱን ለማዛወር የሚከፈሉትን ክፍያዎች ለመቀነስ በሚል ሃሳብ ብር 20,000.00 እንዲሆን መደረጉ ዉሉ በተንኮል የተደረገ መሆኑን የሚሳይ ከመሆኑም በላይ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሻጭ ወደ ገዥ ሲተላለፍ የሚከፈሉ ክፍያዎች ጋር በተመለከተ ከወጡ ህጎች እንዲሁም መኖሪያ ቤትን ለመስጊድ መሸጥም ሆነ መለወጥን ከሚከለክለዉ አዋጅ ቁጥር 272/94 እና የክልሉ ደንብ ቁጥር 62/2002ን የሚፃረር በመሆኑ ዉሉ እንዲፈርስ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ መሆኑን ገልጸዉ ፀንቶ እንዲወሰንላቸዉ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ያቀረበዉ የመልስ መልስም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል ሊፈርስ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት አለ? ወይስ የለም? የሚለዉ ጭብጥ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልግ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል በግራ ቀኝ መካከል ስለመደረጉ ግራ ቀኝ አልተካካዱም፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት፣ ለዉሉ መነሻ የሆነዉን ቤት ለአመልካች የሸጡት በብር 175,000.00 ሆኖ ብር 20,000.00 ቀብድ የተሰጣቸዉ መሆኑን ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ቤቱ የተሸጠዉ በብር 175,000.00 ሳይሆን በብር 20,000.00 መሆኑን እና ገንዘቡንም ከፍሎ የቤቱ ስመ ሀብት በስሙ ተመዝግቦ ሳይት ፕላን ተሰጥቶት በስሙ ግብር ሲከፍልበት የነበረ መሆኑን በመግለጽ ይከራከራል፡፡ በግራ ቀኝ መካከል በጽሁፍ ተደርጎ በቁጥር 319/02/2000 በቀን 16/03/2000 በሰ/ምዕራብ ዞን ፍትሕ መምሪያ ጽ/ቤት መጽደቁ የተረጋገጠዉ ዉል ለክርክር መነሻ የሆነዉን ቤት እና ቦታ አመልካች የገዛበት ዋጋ ብር 20,000.00 መሆኑን እንደሚያሳይ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጽሑፍ ሰነድ በላዩ ስለሚገኘዉ የስምምነት ቃል ሙሉ እምነት የሚጣልበት መሆኑን እና የሰዉ ወይም ሌላ የሰነድ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል እንደማይቻል በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2005(1) እና 2006(2) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል። በመሆኑም በግራ ቀኝ መካከል በጽሑፍ ተደርጎ ዉል እና ማስረጃን ለማጽደቅ በህግ ስልጣን በተሰጠዉ በዞኑ ፍትሕ መምሪያ በፀደቀ ዉል ላይ የተመለከተዉ ዋጋ ብር 20000.00 ሆኖ እያለ፣ ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎችን በመስማት ዋጋዉ ብር 175,000.00 ሆኖ ብር 20,000.00 ተብሎ እንዲመዘገብ የተደረገዉ በስመ ሀብት ዝዉዉር ሂደት ሊከፈል የሚችል ክፍያን ለመቀነስ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌ ያገናዘበ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል።

ዉሉ እንዲፈርስ ከመደረጉ ጋር በተያያዘ ወደ ተያዘዉ ጭብጥ ስንመለስ፤ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሉ እንዲፈርስ ለመወሰን በምክንያትነት ከጠቀሷቸዉ ነጥቦች ዉስጥ አንዱ የዉሉ ዋጋ ብር 175000.00 ሆኖ እያለ በዞኑ ፍትሕ መምሪያ በፀደቀዉ የዉል ሰነዱ ላይ ብር 20000.00 ተብሎ የተገለጸዉ በስም ማዛወር ሂደት ሊከፈል የሚገባዉን ገንዘብ ለመቀነስ እና አመልካች ቀሪዉን ገንዘብ ብር 155000.00 ርክክቡ በሚፈጸምበት ወቅት እንደሚከፍላቸዉ አመልካች ቃል በመግባቱ አምኖ እንደፈረመ እና ብር 20000.00 መሆኑን ቢያዉቁ ኖሮ ዉሉን እንደማይፈርሙ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር መሠረት በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ ነዉ። በርግጥ ተንኮል ለዉል መፍረስ ምክንያት ሊሆን የሚችል ሲሆን፣ ይህም የሚሆነዉ ተንኮል ባይደርስበት ኖሮ አንዱ ተዋዋይ ዉሉን እንደማያደርግ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 1704 ስር ተመልክቷል። ይሁንና በግራ ቀኝ መካከል በጽሑፍ ተደርጎ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ቀርቦ የፀደቀዉ ዉል ይዘቱ የሚያሳየዉ ግራ ቀኝ ወደዉ እና ፈቅደዉ የዉሉ ዋጋ ብር 20000.00 በመሆኑ ላይ ተስማምተዉ እንደሆነ የሚያሳየዉ የጽሑፍ ሰነድ እምነት የሚጣልበት ነዉ፤ ከፍ ሲል በተመለከተዉ ምክንያት ይዘቱን በሌላ ማስረጃ ማስተባበል አይቻልም። በመሆኑም ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ዉል በተንኮል የተደረገ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አይሆንም።

የስር ፍርድ ቤቶች በተለይም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሉ ፈራሽ ነዉ ለማለት የቻለበት ሁለተኛዉ ምክንያት ዉሉ ህገ ወጥ እንደሆነ በመግለጽ ነዉ። በርግጥ ህገ ወጥ ዉሎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህጋዊ ውጤት እንደማያስከትሉ እና ፈራሽ መሆናቸዉ በህጉ አንቀጽ 1716 ስር ተደንግጓል፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሉ ህገ ወጥ ነዉ ለማለት የጠቀሰዉ አንዱ ምክንያት፣ አመልካች ለአምልኮ የሚሆን ቦታ ከግለሰቦች መግዛት እንደማይችል በመግለጽ ሲሆን፣ ይህን የሚከለክል ህግ የትኛዉ እንደሆነ ግን አልጠቀሰም፤ የሲዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 እና አዋጁን ለማስፈጸም በክልሉ የወጣዉን ደንብ በመጥቀስ ተጠሪዎች የሚከራከር ቢሆንም እነዚህ ህጎች የአምልኮ ቦታዎች በመንግስት የሚሰጡ መሆናቸዉን ቢደነግጉም አንድ የኃይማኖት ተቋም የማምለኪያ ቦታን ከግለሰቦች እንዳይገዛ በግልጽ ክልከላ አያደርጉም፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሉ ህገ ወጥ ነዉ ለማለት የጠቀሰዉ ሁለተኛ ምክንያት፣ ዉሉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ሀብትን ከገዥዉ ወደ ሻጩ በማስተላለፍ ሂደት ሊከፈሉ ከሚገባቸዉ ክፍያዎች ጋር በተያያዘ ከወጡት አዋጆች ጋር የሚፃረር መሆኑን ነዉ፡፡ ተጠሪዎችም በዚሁ ችሎት ባቀረቡት ክርክር ይህንኑን በማጠናከር ይከራከራሉ፡፡ በሌላ በኩል አንድ ዉል ህገ ወጥ ነዉ በሚል ምክንያት ፈራሽ የሚሆነዉ፣ የዉሉ መሠረት የሆነዉ መብትና ግዴታ (the object of the contract) በህግ በተከለከለ ነገር ላይ መደረጉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከህጉ አንቀጽ 1716 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ስመ ሀብት ለማስተላለፍ ሊከፈሉ የሚገባቸዉን ክፍያዎች በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎች፣ ተዋዋይ ወገኖች በሚያደርጓቸዉ የሽያጭ ዉሎች ላይ ስለሚወስኗቸዉ መብትና ግዴታዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸዉም፡፡ ይህ በመሆኑም፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ ግራ ቀኝ የዉሉ ዋጋ ብር 20000.00 ሊሆን የቻለዉ ስመ ሀብትን ለማዘዋወር የሚከፈለዉን ክፍያ ለመቀነስ ሲባል ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቢረጋገጥ እንኳን በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉን ዉል ፈራሽ የማድረግ ውጤት የሚያስከትል አይደለም፡፡

ለማጠቃለል፣ ከፍ ሲል በዝርዝር ከተመለከቱት ምክንያቶች አንፃር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል ሊፈርስ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ፣ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሉ ፈራሽ ነዉ በማለት በሽሬ እንደስላሴ ወረዳ ተወስኖ የነበረዉን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ ዉል ፈራሽ የሚሆንባቸዉን ምክንያቶች በተመለከተ በህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ፣ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሲሆን፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰሚ ችሎትም ይህን ማረም ሲገባዉ አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል የሰጠዉ ትዕዛዝ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/78476 ላይ የሽሬ እንደስላሴ ወረዳዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ እንዲሁም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/81259 በቀን 20/05/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የሰ/ምዕራብ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/20471 በቀን 06/01/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. በአጣሪ ችሎት በቀን 20/07/08 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.131151

ታህሳስ 25 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች- ተክሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካቾች - 1ኛ. አቶ ከፍያለው አየለ ከጠበቃ ዝውድነሽ ማሞ ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ አሰገደች መኮንን

ተጠሪዎች - 1ኛ. ወ/ሮ ወርቅነሽ በላይ - ተወካይ ጉደታ ቶልቻ ቀረቡ

2ኛ. አቶ ቶልቻ ባልቻ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 103817 መጋቢት 8/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን እንዲሁም ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 172804 ሰኔ 14/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይታረምልን በሚል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

አመልካቾች ጥቅምት 5/2008 ዓ.ም ያቀረቡት የተሻሻለ የክስ ማመልከቻ ይዘት፡- ከተጠሪዎች ጋር ህዳር 22/1997 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር 1352 ከሆነው የተጠሪዎች መኖሪያ ቤት ላይ በ 130 ካ.ሜ ይዞታ ያረፈ ሰርቪስ ቤታቸውን በብር 70.000.00 ሸጠውልን ለዚህ ለተሸጠው ቤት ይዞታ ማረጋገጫውን አስቆርጠው እንዲሰጡን የጠየቅን ቢሆንም ፍቃደኛ ስላልሆኑ በሸጡልን ይዞታ ልክ ካርታውን አስቆርጠው ስም እንዲያዛውሩ እንዲወሰን እና የገደብ መቀጮ በውሉ መሰረት ብር 10000.00 (አስር ሺህ) እንዲከፍሉ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች ለክሱ ባቀረቡት መቃወሚያ ውሉ የተደረገው ህዳር 22 ቀን 1997 ዓ.ም በመሆኑና ውሉን መሰረት በማድረግ ክስ የቀረበው ከ10 ዓመት በኋላ ጥቅምት 5/2008 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ብለዋል፤ በአማራጭም መልስ አቅርበዋል፡፡
የሥር ፍርድ ቤት መቃወሚያውን በተመለከተ የቀረበውን ክርክር ከመረመረ በኋላ ውሉን መሰረት በማድረግ የሚቀርብ ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለበት ሲሆን አመልካቾች ክስ ያቀረቡት 10 ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች ይህን በመቃወም ቅሬታቸውን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ብይኑ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት አልተገኘም ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙ ተሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካቾች ሀምሌ 29 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን አመልካቾች መብታቸውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ነው፤ ይህ ጊዜ ደግሞ ተጠሪዎች ካርታ ያሰሩበት ጊዜ ነው፤ ምክንያቱም አመልካቾች ንብረቱ በእጃችን ስለሚገኝ እና ጥያቄያችንም እንደውሉ ቤት ያስረክቡን ሳይሆን ለይዞታው ማረጋገጫ የሆነውን ካርታ ከራሳቸው ካርታ ጋር ጠቅልለው ስላሰሩት በሽያጭ ስላስተላለፉልን በ130 ካ.ሜ ላይ ያረፈ ሰርቪስ ቤትና ይዞታ እንዲያስቆርጡ የሚል በመሆኑ፤ አመልካቾችም ይህን ለመጠየቅ የምንችለው ተጠሪዎች ካርታውን ካሰሩ በኋላ በመሆኑ እና ውል በፈፀምንበት ጊዜ ይዞታቸው ሰነድ አልባ በመሆኑ ካርታ አስቆርጡልን ብለን መጠየቅ የማንችል በመሆኑ ይርጋው መቆጠር ያለበት ተጠሪዎች ካርታ ካሰሩበት ጥር 4 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ መሆን ሲገባው የሥር ፍርድ ቤቶች ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምረው ቆጥረው ክሱ በይርጋ ይታገዳል ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ይታረምልን ብለዋል፡፡

የሰበር ማመልከቻው ተመርምሮ ውሉ ከተደረገ 10 ዓመት ያለፈ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው የመባሉን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪዎች ሚያዚያ 12 ቀን 2009 ዓ.ም በሰጡት መልስ ጊዜው መቆጠር ያለበት ተጠሪዎች ለይዞታው ካርታ ከወሰዱ ጊዜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጀምሮ ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፤ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ካርታው ከተሰራ ጀምሮ ነው ቢባል እንኳ ካርታ ከተሰራ ጀምሮ ክስ እስከቀረበ ድረስ ያለው ጊዜ 10 ዓመት የሚያልፈው በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ብይን ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም በይርጋው ጉዳይ ላይ መከራከሪያቸውን ከስር ጀምሮ ማቅረባቸውንና የይርጋ ጊዜው እንዳላለፈ በመግለፅ ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል? ወይስ አይገባውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካቾች በሰርቪስ ቤት ሽያጭ ውሉ መሰረት ንብረቱን ተረክበው በእጃቸው እንደሚገኝ ገልፀው ይዞታው ሰነድ አልባ እንደነበርና ተጠሪዎች አጠቃለው ካርታ ያወጡት ጥር 4 ቀን 1998 ዓ.ም በመሆኑ ለተሸጠው ቤት ይዞታ ማረጋገጫውን አስቆርጠው እንዲሰጧቸው ላቀረቡት ክስ ይርጋው መታሰብ ያለበት ተጠሪዎች ካርታ ካሰሩበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ ውሉ ከተደረገበት ህዳር 22/1997 ዓ.ም ጀምሮ ሊሆን አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው ይህ ክርክር በሥር ፍርድ ቤት አለመነሳቱንና ካርታ ከተሰራ ጀምሮ ያለው ጊዜም ቢታሰብ ክስ የቀረበው የይርጋ ጊዜው ካለፈ በኋላ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1846 ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ቀን ጀምሮ ነው፡፡ ለክሱ የይርጋ መቃወሚያ በቀረበ ጊዜም ፍርድ ቤቱ የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምርበትን ቀን በአግባቡ በመለየት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆን አለመሆኑ የመወሰን ኃላፊነት አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ካርታ ያወጡት ጥር 4 ቀን 1998 ዓ.ም መሆኑ እና ውል በተደረገ ጊዜ ይዞታው ሰነድ አልባ እንደነበር ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ደግሞ ካርታው ከመውጣቱ በፊት ለይዞታው ተጠሪዎች አጠቃለው ካርታ አውጥተዋል በተሸጠልን ይዞታ ልክ ካርታውን አስቆርጠው ስም እንዲያዛውሩ ይወሰንልን ብለው ሊከሱ የሚችሉበትና ዳኝነት የሚጠይቁበት ምክንያት አልነበረም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች ካርታ ካወጡበት ጥር 4 ቀን 1998 ዓ.ም በፊት ክሱ ቢቀርብ ኖሮ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ስላለመሆኑ ከክርክሩ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ካርታ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ነሐሴ 18/2007 ዓ.ም እንዲሁም ክሱ ተሻሽሎ እስከቀረበበት ጥቅምት 5/2008 ዓ.ም ድረስ ሲሰላ የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜው አልፏል የሚባል ሆኖም አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች ይርጋው መቆጠር ያለበት ውል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ መሆን አለበት በማለት ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት ያሳለፉት ብይንና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 103817 መጋቢት 8 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 172804 ሰኔ 14/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካቾች የቀረበው ክስ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው የቤት ሽያጭ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ህዳር 22/1997 ዓ.ም ሳይሆን ተጠሪዎች ካርታ ካወጡበት ጥር 4/1998 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑና አመልካቾችም በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱት ነሐሴ 18/2007 ዓ.ም በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት የይርጋው ጊዜ ያለፈበት አይደለም ብለናል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን የኮ/መ/ቁ 103817 በማንቀሳቀስ የግራ ቀኙን ቀሪ ክርክር መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ /ቁ 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ካ/የ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 141606

ቀን 25/01/2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ረታ ቶሎሳ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች ፡- አቶ ማሞ ቱሉ ቀርቡ

ተጠሪ ፡- አቶ አበበ አበራ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

1. ጉዳዩ የቤትና ቦታ ክርክር ሲሆን የጀመረው በኦሮሚያ ክልል የሙሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው ፡፡ በሥር ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በ28/04/2009 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር በቃል ውል የቤትና ቦታ ሽያጭ አድርገው አመልካች ብር 30,000 ለመክፈል የተሰማሙ ቢሆንም ገንዘቡን አልከፈሉም፡፡ በመሆኑም አመልካች የሽያጭ ገንዘቡን እንዲከፍሉ ወይም ቤቱን ለቀው እንዲያስክቧቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

2. የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት የመከላከያ መልስ ከተጠሪ ቤት እንዳልገዙ ነገር ግን በ2002 ዓ.ም ባዶ ቦታ በብር 13,000.00 የገዙ ስለመሆኑ በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡
3. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት የስር ወረዳ ፍርድ ቤት የቤት ሽያጭ ውል በፍ/ሕ/ቁ 1723 መሰረት ካለመደረጉ በተጨማሪ የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች ሽጡት የተባለው ቤት ሳይሆን ቦዶ መሬት በመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) እና በፍ/ህ/ቁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1808(2) መሰረት ውሉ በህግ ፊት ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የሽያጭ ተግባር ከመከናወኑ በፊት ወደ ነበሩበት ይመለሱ፡፡ በዚህም ተጠሪ የተቀበሉት ብር 13,000.00 እንዲመልሱ ፤ አመልካች ደግሞ ገዛሁት ባሉት ይዞታ ላይ ያላቸው ንብረት ሁሉ በማንሳት መሬቱን ለተጠሪ ይልቀቁ በማለት ወስኗል ፡፡

አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡

4. አመልካች በ9/09/2009 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም፡- የከተማ ቦታ መግዛት የሚከላከል ህግ እንደሌለ፤ የተጠሪ ክስ ከሁለት ዓመት በኋላ እንደቀረበ፤ ቤቱን ለመሰራት ወጪ ማውጣታቸውን ገልጸው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ እንዲሻር መጠየቃቸውን ያሳያል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከጠየቀው ዳኝነት አኳያ አመልካች ቤቱን አፍርሰህ ሄድ የመባሉ አግባብነት ከፍ/ህ/ቁ 1178 እና ተከታዮቹ አኳያ ጉዳዩን ተጠሪ ባሉበት ማጣራት ይቻላል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በ16/10/2009 ዓ.ም የጽሑፍ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ዋና ይዘቱም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ የሚነቀፍ ነጥብ የለውም የሚል ክርክር ማቅረቡን ያሳያል፡፡ አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2009 ዓ.ም የመልስ መልስ አቅርቧል፡

5. የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለው መርምረናል ፡፡

6. እንደመረመርነውም፡- በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተደረገው ሽያጭ ውል በባዶ መሬት ላይ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የመከላከያ መልስም ከተጠሪ የገዙት ቤት ሳይሆን ባዶ መሬት ስለመሆኑ በግልጽ አምነው ተከራክሯል፡፡ በአመልካች እና ተጠሪ ተደረገ የተባለው የማይቀሳቀስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት ሽያጭ ውል በቃል ብቻ ስለመደረጉም ግራቀኙ አልተካከዱም፡፡ በመሰረቱ ግራቀኙ ያደረጉት የሽያጭ ውል በባዶ መሬት ላይ ከሆነ ህጋዊ ውጤቱ ምንድነው? የሚለው ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) እና የፍ/ህ/ቁ 1678(ለ) እና 1716(1) ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ስለመሆኑ በግልጽ ተደንግጓአል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ያደረጉት የመሬት ሽያጭ ውል ሕገ መንግስቱን በሚቀረን መልኩ የፈፀሙት በመሆኑ በሕግ ፊት የማይጸና ነው፡፡ አመልካች ባዶ መሬት በመግዛት የሰሩት ቤት ካለም በተጠሪ ፈቃድ እንደተሰራ ተቆጥሮ ህገወጥ የመሬት ሽያጭ ውል በውጤቱ ህጋዊ የሚሆንበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡ አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ከፍ/ሕ/ቁ 1178 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አኳያ እንዲመረመር ያቀረበው ቢሆንም የውለታው መነሻ ህገወጥ የመሬት ሽጭ ከመሆኑ አንፃር አመልካች ቤቱን በተጠሪ ፈቃድ የሰራው ነው ተብሎ የህግ ግምት የሚወሰድበት ሥርዓት አይኖርም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች ውለታው ፈራሽ ነው ግራቀኙ ወደነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል ፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሙሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 07958 በ22/07/2009 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 29090 በ28/07/2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፤የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 262665 በ08/09/2009 ዓ.ም ሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለስ ፡፡

<u>ተጨማሪ ትዕዛዝ</u>

በዚህ ችሎት ሰኔ 14 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.130676

ጥቅምት 27ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች- ዳኜ መላኩ
ተፈሪ ገብሩ
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ፀሃይ መንክር

አመልካች - ጅቡቲ ድንበር ተሻጋሪ ደረጃ 3-ለ የደ/ጭ/ማ/ባ/ማህበር ጠ/ግርማ ስላሴ አርአያ ቀረቡ
ተጠሪ - አቶ ሞላ ደርጎ ከደነው ጠበቃ /ሳሙኤል አስፋው ቀረቡ
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 22591 መጋቢት 6/2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 176735 ሰኔ 23/2008 ዓ.ም የፀናውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር ባደረጉት ውል ንብረትነቱ የአረብ ኮንስትራክሽን የሆነ አንድ ኮንቴነር ከጅቡቲ ወደብ ወደ ይርጋ ጨፌ እንዲያጓጉዝላቸው በተስማሙት መሰረት ከሳሽ አጓጉዞ አስረክቤያለሁ፤ ተከሳሽ ይህን ያዘዘው በ16/04/07 ዓ.ም ሲሆን በቀን 29/05/07 ዓ.ም በርክክብ ሰነዱ ላይ ፈርሞ የክፍያ ቀጠሮ ሰጥቷል፤ ነገር ግን ክፍያ ለመፈፀም ፈቃደኛ ስላልሆነ ጭነቱ ለተጓዝበት ለ300 ኩንታል በብር 150.00 ሂሳብ ብር 450.00.00፣ ኮንቴነር መመለሻ ብር 8.000.00፤ እና ጭነት ለዘገየበት ዲመሬጅ ክፍያ ብር 20.400.00፤ በአጠቃላይ ብር 73,400.00 (ሰባ ሶስት ሺህ አራት መቶ) ከነወለዱ እንዲከፍል እንዲወሰን መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ከሳሽ ዕቃዎቹን ከጂቡቲ ወደብ ለማጓጓዝና የማጓጓዣውን ሰነድ (Way Bill) የተቀበለው ከአረብ ኮንትራክተር ኃ/የተ/የግ/ማህበር መሆኑን ሰነዱ ያስረዳል፤ ከሳሽ እቃዎቹን አጓጉዞ ያስረከበው ለዚሁ ድርጅት ነው፤ ስለሆነም ተከሳሽ የተጓጓዙትን ዕቃዎች ያልተረከበ በመሆኑ በንግድ ህጉ አንቀፅ 581 እና 582 መሰረት ተከሳሽን ለመጓጓዣው ሊጠይቅ አይችልም፤ በተከሳሽ ትዕዛዝ ተሰጥቷል እንዲሁም ርክክቡም መፈፀሙን ያስረዳሉ ተብሎ የቀረቡት ሰነዶችም የማጓጓዣውን ሂሳብ እኔ የምከፍል ስለመሆኑም ሆነ ከከሳሽ ጋር ውል መግባቴን የሚያረጋግጡ አይደሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃውን ከመረመረ በኋላ በከሳሽ በኩል የቀረቡት ምስክር ከሳሽ ከጂቡቲ ዕቃ ጭነው ይርጋጨፌ አጓጉዘው ያስረከቡት ከተከሳሽ ጋር ባላቸው ስምምነት መሆኑን፤ ስለማጓጓዙና ክፍያውን በተመለከተ የተነጋገሩትም ከተከሳሽ ጋር መሆኑን ማስረዳታቸውን እና ይህ ምስክርነት በተከሳሽ በኩል አለመስተባበሉን፤ በሰነድ ማስረጃነት የቀረቡት ሰነዶች ሲታዩም የጭነት ሰነዶችን የተረከበው ተከሳሽ መሆኑን፤ ተከሳሹ ከሳሽ አጓጉዘው ያስረከቡ መሆናቸውን ገልጾ ተከሳሽ ክፍያ ለመክፈል ቀጠሮ መስጠቱን የሚያስረዳ መሆኑን፤ በተለይ ክፍያ ለመክፈል የሰጠው ሰነድ የማጓጓዣ ውልን የሚተካ ደረሰኝ መሰል ነገር ሊባል እንደሚችል፤ በአጠቃላይ ከሳሽ የመጓጓዣ ውል መኖሩን ለማስረዳት ስለቻሉ ፍርድ ቤቱ በግራ ቀኙ መካከል የመጓጓዣ ውል አለ የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱን በመግለፅ ተከሳሽ ገንዘቡን ከነወለዱ ለከሳሽ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በበኩሉ ክርክራቸውን ሰምቶ የቀረቡት ሰነዶች እና የሰው ማስረጃዎች እንዲሁም ክርክሩ የሚያሳየው ተጠሪ የማጓጓዝ ውል ያላቸው ከአመልካች ጋር መሆኑን ነው፤ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በአሰራር አስጫኙ ክፍያ ሲከፍለን ብቻ ነው ለተጠሪ የምንከፍለው በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ ተጠሪ ውል ያላቸው ከአመልካች ጋር በመሆኑ አረብ ኮንትራክተርስ ከፈለም አልከፈለም ተጠሪን የሚመለከት አይደለም፤ እንዲሁም አመልካች ተጠሪን ወክሎ ገንዘብ ለመቀበል ሳይሆን ሰነዱን የተቀበለው እራሱ ለመክፈል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነ ተጠሪ ያጓጓዘበትን ክፍያ ይክፈል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡
የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ሀምሌ 18/2008 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተሰዋውጠዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን ቅሬታ በቀረበበት ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ሥህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር ባደረጉት ስምምነት መሰረት ንብረትነቱ የአረብ ኮንስትራክሽን የሆነ ፅቃ ከጅቡቲ ይርጋ ጨፌ አጓጉዘው ማስረከባቸውንና ተጠሪም በርክክብ ሰነዱ ላይ ፈርሞ ገንዘቡን ለመክፈል የክፍያ ቀጠሮ መስጠቱን ገልፀው ገንዘቡ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ የማጓጓዣ ውል አለማድረጉን፤ ተጠሪ የማጓጓዣውን ሰነድ የተቀበለው ከአረብ ኮንትራክተር መሆኑንና እቃዎቹም ተጓጉዘውለት የተረከበው ይኸው ድርጅት መሆኑን በመግለፅ ሊጠየቅ እንደማይገባ ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙ በተጠቀሰው መልኩ ያቀረቡትን ክርክር በቅድሚያ የመረመረው የሥር ፍርድ ቤት የተለያዩበትን ፍሬ ነገር በማስረጃ በማጣራት የጭነት ሰነዶችን የተረከበው አመልካች መሆኑን፤ አመልካች ተጠሪ አጓጉዘው ያስረከቡ መሆናቸውን ገልጾ ክፍያ ለመክፈል ቀጠሮ መስጠቱ በሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን፤ ክፍያ ለመክፈል የሰጠው ሰነድ የማጓጓዣ ውልን የሚተካ ደረሰኝ ሊባል እንደሚችል፤ በዚህም ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል የመጓጓዣ ውል መኖሩ መረጋገጡን ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም አመልካች አጓጓዥ እንጂ አረብ ኮንስትራክሽንን ወክሎ ስራ የሚሰራ ወይም ትራንዚተር አለመሆኑን በማረጋገጥ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪ ውል ስለመደረጉ በማስረጃነት ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የጭነት ማጓጓዣ ሰነዱን እና አመልካች ክፍያ ለመክፈል ቀጠሮ መስጠቱን ለማስረዳት የቀረበውን ነው፡፡ በየብስ የፅቃ ማጓጓዝ ስራን ለመደንገግ ተሻሽሎ የወጣው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ቁጥር 547/99 በንግድ ሕግ አማካኝነት በ1952 ዓ.ም ወጥቶ በሥራ ላይ ያለውን ሕግ በተለይም የአንገዥችን የኃላፊነት መሠረት፣የኃላፊነት መጠንወሰንና ሌሎች መብቶችና ግዴታዎችን አስመልክቶ ዓለም ዓቀፍ ይዘት ካለውና ወጥ የሆነና የተቀላጠፈ አግልግሎት መስጠት በሚያስችል መልኩ አሻሽሎ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ተሻሽሎ መደንገጉን በአዋጁ መግቢያ ከተመለከተው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ መልኩ ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 547/99 በአንቀጽ 4 ሥር እንደተመለከተው የእቃ ማንገዝ ውል የሚረጋገጠው በማንገዥ ሰነድ መሆኑን፤ ነገር ግን ይህ ሰነድ አለመኖሩን ወይም ያልተሟላ መሆኑ ወይም መጥፋቱ ዕቃዎችን ለማንገዝ የተደረገውን ውል ዋጋ አልባ ሊያደርገው እንደማይችልና ሊያስቀረው እንደማይችል የሚደነግግ ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 8 ሥር እንደተመለከተው ደግሞ ላኪው እና አንገዥ ከተስማሙ የማንገዥው ሰነድ አንገዥ በሚሰጠውና ላኪው ተገቢ የሆኑትን ዕሁፎች በሚያሰፍርበት እንደ ደረሰኝ ባሉ ሰነዶች ሊተካ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም የእቃ ማንገዝ ውል በማንገዥ ሰነድ ወይም መሰል ሰነዶች ሊረጋገጥ እንደሚችል ከተሻሻለው የአዋጁ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ፍሬ ነገሩን የማጣራት ሥልጣን በህጉ የተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃ ተመልክተው ከፍ ሲል እንደተገለፀው የጭነት ሰነዶችን የተረከበው አመልካች መሆኑን፤ አመልካች ተጠሪ አንጉዘው ያስረከቡ መሆናቸውን ገልጾ ክፍያ ለመክፈል ቀጠሮ መስጠቱን፤ እንዲሁም አመልካች አንገዥ እንጂ አረብ ኮንስትራክሽንን ወክሎ ስራ የሚሰራ ወይም ትራንዚተር አለመሆኑ አረጋግጠዋል፡፡ ይህ በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የህጉ ግልፅ ድንጋጌ አንፃር ተገናዝቦ ሲታይ የሥር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል የመንገዥ ውል አለ የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረስ አመልካች ገንዘቡን ከነወለዱ ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰናቸው ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነምተከታዩንወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 22591 መጋቢት 6/2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 176735 ሰኔ 23/2008 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ 120468

መስከረም 23/2010 ዓ.ም

ዳኞች 1. ዳኜ መላኩ

2. ረታ ቶለሳ

3. ተሽሊት ይመስል

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች..... አቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/ክርስቶስ → ከጠበቃ አቶ ዝናቡ ይርጋ ጋር ቀረበዋል፡፡

ተጠሪ ..... አቶ ሐረጎት ገ/እግዚአብሔር → ቀረበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ቤት ለመስራት የወጣውን የጉልበት ዋጋና የገንዘብ ወጪ ለማስከፈል የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 78992 በ11/2/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በናዕዴር ዓዴት ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣ የአሁን አመልካች ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ከሳሽ ባቀረበው ክስ ከሳሽ እና ተከሳሽ በ1995 ዓ.ም በጹሑፍ በተደረገ ውል ተከሳሽ በሰመማ ከተማ በስሙ በተሰጠው ቦታ እኔ እንዳሰራው እና ለእኔም እንደሚሰራ ተስማምተን፣ በዚህ መሰረት አጥር እና ሁለት ክፍል ቤት በብር 80,000.00 /ሰማኒያ ሺህ/ የሚገመት ሰርቼ የእኔን አሰራኝ ስለው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እምቤ ስላለ የጉልበቴን ዋጋ እና ለሰራሁት ግንብ ለሚሆኑት ዕቃዎች ዋጋ ድርሻዬን ብር 40,000 እንዲከፍለኝ በማለት ከሷል። ተከሳሽ የጽሁፍ መልስ ባለማቅረቡ ታልፏል። ግራ ቀኞቸው በቃል ባደረጉት ክርክር ከሳሽ ሁለት ክፍል ቤት እና አጥር የስራሁበትን ገንዘብ እንዲከፍለኝ በማለት ሲጠይቅ፣ ተከሳሽ ደግሞ ከሳሽ የስራው ቤት የለም፣ የ1995 ዓ.ም አሁን ሊጠይቀኝ አይችልም በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የከሳሽን የሰው ምስክሮች በመስማት በሰጠው ውሳኔ ከሳሽ እና ተከሳሽ ተባብረው ለሰሩት ሁለት ክፍል ቤት ተከሳሽ ለከሳሽ ብር 40,000 / አርባ ሺህ/ እንዲከፍለው በማለት ወስኗል። የሥር ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አክሱም ምድብ ችሎት እና የሰበር አቤቱታ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበ ቢሆንም ቅሬታው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጸንቷል። አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

የአሁን አመልካች በ27/3/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል። የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡- የአሁን ተጠሪ በውሉ መሰረት ቤት ተሰርቷል ያለው በ1995 ዓ.ም ሲሆን ገንዘብ እንዲከፈለው የጠየቀው 10 ዓመት ካለፈው በኋለ ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚቋረጥ ነው። በዚህ ጉዳይ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የወረዳ ፍ/ቤት የተዘጋው መዝገብ ይከፈት አይከፈት የሚለውን በተመለከተ ግራ ቀኞቸውን አከራክሮ እንዲወስን መልሶለት እያለ ይህን ሳያደርግ የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረምልኝ፤ ተጠሪ ባቀረበው ክስ በመካከላችን ያለው የመተጋገዝ ውል እንዳለ የገለጸ ሲሆን ይህ ደግሞ ስምምነት እንጂ በሕግ ፊት አሰገዳጅነት ውጤት ያለው ውል አይደለም፣ ተጠሪ የጽሑፍ ውል አለ እያለ ስለሆነ በዚህ አግባብ ማስረዳት ሲገባው የሰው ምስክሮች ብቻ በመስማት የተጠየቀው 40,000 መኖሩን አግባብነት ባለው ማስረጃ ሳያስረዳ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለኝ በማለት አመልክቷል።

ይህ ችሎት አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘው መሰረት ጥር 16 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡- የአሁን አመልካች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ ቢላክላቸውም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እምቢ አልቀበልም ማለታቸው በምስክሮች የተረጋገጠ ስለሆነ ጉዳዩን እንዳመኑበት የሚያስቆጥር ነው። የሥር ፍ/ቤት በአመልካች በኩል የቀረበውን የይርጋ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው። መዝገብ ማስከፈት በተመለከተ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመለሰለት መሰረት የወረዳው ፍ/ቤት እንደገና አጣርቶ የአሁን አመልካች በቀጠሮ ቀን ያልቀረቡት በበቂ ምክንያት እንዳልሆነ አይቶ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያለው ነው። በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው ውል የመተጋገዝ ውል ሳይሆን ሁለታችን በቤቱ ላይ ያለን መብት የሚያስረዳ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አግባብነት ያለው ነው። ተጠሪ ውል ስለመኖሩ በሰው ምስክሮች ያስረዳ ሲሆን አመልካች ውል መኖሩን ስላልካደ፣ ተጠሪ ውል በጽሑፍ አላስረዳም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም የሥር ውሳኔ አግባብነት ያለው ስለሆነ እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል። ይህ ችሎት ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ የሥር መዝገብ የመ.ቁ 02823 አስቀርቦ ከዚህ መዝገብ ጋር ተያይዟል እንዲሁም ግራ ቀኞቸውን በቃል ሰምቷቸዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸውን ክርክር አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመርነው በዚህ ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት በአመልካች እና ተጠሪ መካከል በሕግ ፊት ግዴታን የሚፈጥር ውል አለ ወይስ የለም? የሚለው ነጥብ እንደሆነ ተገንዝበናል። በዚህ መሰረት ተዋዋይ ወገኖች ውልን በሚያደርጉበት ጊዜ በሕጉ የተመለከተውን የውል አመሰራረት ሥርዓት ተከትሎ መሆን እንዳለበት የሚያከራክር አይደለም። የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 ሥር እንደተመለከተው በሕግ ፊት የሚጸና ውል ለማቋቋም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ተዘርዝሮ እናገኛለን። ከእነዚህ መሰረታዊ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ውል መደረግ ያለበት "በቂ የሆነ እርግጠኝነት ያለው የሚቻልና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ" በተመለከተ መሆን እንዳለበት ነው። ተዋዋይ ወገኖች በሕግ የተመለከቱትን አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች በጠበቀ መልክ እና ፈቃጅ የሆኑ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ በመሰላቸው ተነጻጻሪ መብትና ግዴታ በማስቀመጥ መዋዋል እንደሚችሉ ይታመናል። ተዋዋይ ወገኖች በዚህ አግባብ ያቋቋሙት ውል ያንን ጉዳይ በተመለከተ በመካከላቸው ሕግ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1731 ድንጋጌ የሚያስገነዝበው ጉዳይ ነው። ይህ ከሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተዋዋይ ወገኖች በውሉ በተፈጠረው መብት ተጠቃሚ የሚሆኑበት እና በግዴታው ደግሞ የሚገደዱበት ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው፡፡ በዚህ ውል መሻሻትም ግዴታውን የተወጣው ወገን ሌላኛው ወገን ደግሞ ግዴታውን እንዲወጣ የመጠየቅ መብት እንደሚሰጠው ግልጽ ነው፡፡ በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ የአሁን አመልካች ቤቱን አስራኝ የአንተን ደግሞ አሰራአለሁ ብሎ በራሱ ይዞታ ላይ በሰሚኒያ ሺህ ብር ቤት ሰርተን በውሉ መሰረት የእኔን ቤት አሰራኝ ቢለው እምቢ ስላለ የጉልበቴን ዋጋ እና ለስራሁት ግንብ የሚሆነውን ዕቃዎች ዋጋ እንዲከፍለኝ የሚል ነው፡፡ ከዚህ ክስ መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪ እና አመልካች አንዱ የሌላውን ቤት ለመስራት ለመተጋገዝ ያደረጉት ውል እንደሆነ ያሳያል፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አመልካች በዚህ አግባብ ስላልሰራልኝ ገንዘብ እንዲከፍለኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪው የጉልበቱን ዋጋ እና ዕቃዎቹን በምን አግባብ ገምቶ እንዳቀረበ የሚያመለክት ነገር መኖሩን የሥር ውሳኔ የሚያመለክተው ነገር የለም፡፡ በዚህ ረገድ የአሁን አመልካች የቀረበው የጽሁፍ መልስ ባይኖርም በቃል ባቀረበው ክርክር ከሳሽን ያሰራሁት ቤት የለም ያቀረበው ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ማለት አመልካች ውል መኖሩን የካደ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰሙት የሰው ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል 1ኛ ምስክር አመልካች እና ተጠሪ ሚያዚያ ወር 1995 ዓ.ም ሁለት ክፍል ቤት አብረው በአመልካች ይዞታ ለይ እንደሰሩ፣ 2ኛ ምስክር በ1995 ዓ.ም ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ ሁለት ክፍል ቤት እንደሰራ፣ 3ኛ ምስክር በ1995 ዓ.ም በሰመማ ከተማ በአመልካች ቦታ ላይ አመልካች እና ተጠሪ ሁለት ክፍል ቤት እንደሰሩ ተጠሪ ገንዘቤን አካፍለኝ ሲለው እምቢ እንዳለው መመስከራቸውን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ያሳያል፡፡ ከእነዚህ የምስክሮች ቃል መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪ ለሰራው ሥራ የጉልበት ዋጋ በስንት ብር እንደተስማሙ፣ ምን ምን ዕቃዎችን ለቤቱ ግንባታ እንዳቀረበ እና ግምታቸው ምን ያህል እንደሆነ የመሰከሩት ነገር የለም፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የግራ ቀኞቸውን ክርክር እና የምስክሮች ቃል መነሻ በማድረግ በደረሰበት ድምዳሜ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በትብብር ቤት የመስራት ስምምነት እንዳለ ማረጋገጡን አመልክቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ ችሎት በቃል ባቀረበው ክርክር ከአመልካች ጋር ተባብረው ቤት ለመስራት እንደተስማሙ የአመልካች ቤት ከሰሩ በኋላ አመልካች የተጠሪን ለመስራት ፈቃደኛ ባለመሆኑ፣ የጉልበቱን ዋጋ እና ያቀረባቸውን ዕቃዎች ዋጋ እንደጠየቀ ገልጾ ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚለው አብረን ቤት ለመስራት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ያደረግነው ስምምነት የለም፣ ቤቱን በገንዘቤ የሰራሁት እኔ ራሴ ነኝ ተጠሪ በሰራተኝነት ለስራው ሥራ በአካባቢ ዋጋ ተከፍሎታል በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ እንደሚቻለው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል አንዱ ቤት ሲሰራ ሌላው ሊያግዘው እንደዚሁም ሌለው ቤት ሲሰራ መጀመሪያ የተሰራለት ሰው አብረው ሊሰራ እና ሊያግዘው መስማማታቸውን በዚህ ረገድ የመተባባርና የመተጋገዝ ስምምነት ማድረጋቸውን ያመለክታል፡፡ ይህ የመተጋገዝ ወይም የመተባበር ስምምነት በአካባቢው ልማድ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም ከሕግ አንጻር ግን አንዱ ወገን ሌላውን ወገን ግዴታውን አልፈጸመልኝም እና እንዲፈጽምልኝ በማለት ለማስገደድ የሚያስችል አይደለም፡፡ አንዱ ወገን በዚህ በመተባበር ስምምነት መሰረት ሥራው ተሰርቶለት ሌላውን ያለገዘ እንደሆነ ምናልባት በአካባቢው ልማድ የሚያመጣው ትጽእኖ ሊኖር ቢችልም ይህ ስምምነት ከሕግ አንጻር የግራ ቀኞቸዉን ተነጻጻሪ መብትና ግዴታ የፈጠረ ነው እና አንዱ ወገን ሌላውን ወገን እንደውሉ እንዲፈጽምልኝ በማለት የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771 በሚደነግገው አግባብ ለመጠየቅ የሚያስችለው የሕግ መሰረት የለም፡፡ ይህ ማለት በግራ ቀኞቸው መካከል የተደረገው የመተባበር የመተጋገዝ ስምምነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው ከሚባል በስተቀር አስገዳጅነት ያለው በሕግ ፊት ግዴታን የሚፈጥር ውል አለ ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡ ከዚህም በላይ የአሁን ተጠሪ የጉልበት ዋጋ በስንት ብር እንደተስማሙ እና ያቀረባቸው ዕቃዎች ምን እንደሆኑ እና ግምታቸው በማስረጃ ማረጋገጡን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚያመለክተው ነገር የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ የአሁን ተጠሪ እንደውሉ ገንዘብ እንዲከፍለኝ በማለት አመልካችን ለመጠየቅ የሚያስችለው የሕግ አግባብ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በግራ ቀኞቸው መካከል የመተባበርና የመተጋገዝ ስምምነት እንጂ ግዴታን የሚፈጥር ውል በሌለበት ተጠሪ ደግሞ የጉልበት ዋጋ በስንት ብር እንደተስማሙ እና ያቀረባቸው ዕቃዎች ዓይነት እና ግምት በማስረጃ ባላረጋገጠበት ያቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው ክሱን በመቀበል አመልካች ብር 40,000 / አርባ ሺህ/ እንዲከፍል መወሰናቸው ከላይ የተመለከቱትን የውል ሕግ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ

1. የናዕዴር ዓዴት ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 02823 በ1/10/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና ይህን ውሳኔ በማጽናት የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አክሱም ምድብ ችሎት በመ.ቁ. 20724 በ5/12/2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 78992 በ11/2/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በተጠሪ እና በአመልካች መካከል የነበረው ስምምነት በመተጋገዝና በመተባበር ቤት ከመስራት ውጭ በሕግ ፊት መብትና ግዴታን የሚፈጥር ውል ስላልሆነ አመልካች ለተጠሪ ብር 40,000 / አርባ ሺህ/ ለመክፈል የሚገደድበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኞቸው በዚህ ችሎት የደረሰባቸውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የመ.ቁ. 02823 ለናዕዴር ዓዴት ወረዳ ፍ/ቤት ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 123761

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ረታ ቶሎሳ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

አብዩ ካሳሁን

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ እናኒ ተሰማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ቂስ ገብረማርያም ደመቀ

2. ወ/ሮ ሙሉወርቅ ጂዳ } አልቀረቡም

3. አቶ ዬሴፍ ጉታ

4. የቢሾፍቱ ከተማ ልማትና ማናጅመንት ኤጀንሲ ነገረ ፈጅ ሽመልስ ግዛው ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩየቀረበውን የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ. 44309 ሚያዚያ 26 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፤ የምስራቅ ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 41878 ጥር 26 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 240297 የካቲት 09 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት አመልካች የካቲት 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸውነው፡፡

ክርክሩ የቤት ሽያጭ ውልን የሚመለከት ሲሆን በአደአ ወረዳው ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው አመልካች ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ ክስ በአሁን ተጠሪዎች ላይ በማቅረባቸው ሲሆን የክሱ ይዘት በአጭሩ፡-1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ለአሁን አመልካች በብር 32,000/ሰላሳ ሁለት ሺህ ብር/ የሸጡላቸውን በቢሾፍቱ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ኤ/05/026 የተመዘገበ በ105 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተሰራ ቤት በአንድ በኩል ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶችንና ስም ለማዞር የሚያስችል ውክልና ለአሁን አመልካች ከሰጡ በኋላ በሌላ በኩል ከአሁን 3ኛ ተጠሪ ጋር ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የአከራካሪው ቤት ሽያጭ ውል መነሻነት ቤቱን ለ3ኛው ተጠሪ በመሸጥ ስመ ንብረቱ በ3ኛው ተጠሪ እንዲመዘገብ ያደረጉ በመሆናቸው፤ 4ኛው ተጠሪም ስለ ቤቱ በአግባቡ ሳያጣራ ስመ ንበረቱን በአሁኑ 3ኛ ተጠሪ መመዝገቡ ተገቢ ባለመሆኑ በ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎችና በ3ኛው ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ቀሪ ሆኖ በአመልካችና በ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ተፈፃሚነት እንዲኖረው በመጠየቅ ያቀረቡት ክስ ነበር፡፡

1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች በአቀረቡት ክርክር ቤቱን ለአሁን አመልካች መሸጣቸውን አምነው 3ኛው ተጠሪ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ውስጥ የነበሩ በመሆናቸው በወቅቱ ስመ እንዲዞርላቸው የተደረገ መሆኑን ገልፀው ሲከራከሩ 3ኛው ተጠሪ በበኩላቸው አከራካሪውን ቤት አመልካች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ከተለያዩ በኋላ የገዙት ሆኖ እያለ ያላግባብ 3ኛው ተጠሪ ከ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲሁም ከ4ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር በስማቸው በማስመዝገብ የገዙት መሆኑን በመጥቀስ አመልካች ከ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል ተቀባይነት ቢያገኝ እንደማይቃወሙ በመከራከር መልስ አቅርበዋል፡፡ 4ኛውም ተጠሪ በበኩላቸው የአመልካች ክርክር ቅን ልቦና የጎደለውና አከራካሪውን ቤት ከልዩ ልዩ ዕዳ ለማዳን የሚደረግ እንጂ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባልና ሚስት በነበሩበት ወቅት በባላቸው ስም ቤቱን መመዝገቤ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ3ኛው ተጠሪ ሚስት የሆኑት ወ/ሮ ሕይወት አውዴ ጣልቃ ገብተው ከ3ኛው ተጠሪ ጋር ከጥር 19 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ መስርተው ሲኖሩ ቆይተው በፍች የተለያዩ በመሆናቸው አከራካሪው ቤት የጋራ ሀብት ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ተወስኖ ለመካፈል በሂደት ላይ የሚገኝ በመሆኑ የአመልካች ክስ አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡

በጣልቃ ገቢዋ አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጡበት የታዘዙት 1ኛና 2ኛ መልስ ሰጭዎች የአከራካሪው ቤት ስመ ንብረት የተመዘገበው በ3ኛው ተጠሪ ስም በመሆኑ የጣልቃ ገብ አቤቱታ ተቀባይነት ቢያገኝ እንደማይቃወሙ ሲከራከሩ 3ኛው ተጠሪ በበኩላቸው አከራካሪው ቤት አመልካች የገዙት የግል ሀብታቸው ሆኖ እያለ 3ኛው ተጠሪ በማሳሳት በስማቸው ያስመዘገቡት በመሆኑ አከራካሪው ቤት የአመልካች ሀብት ነው ተብሎ ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌላቸው ተከራክረዋል፡፡ 4ኛው ተጠሪ ከጣልቃ ገብ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው አቤቱታቸው ውድቅ እንዲሆን አመልክተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤትምየግራቀኙን ወገኖች የቃልክርክርእናማስረጃዎችበመመርመር አመልካች ከ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር የቤት ሽያጭ ውል አድርጌአለሁ ቢሉም የተመዘገበ የቤት ሽያጭ ውል የሌለ በመሆኑ አቤቱታቸው ተቀባይነት የለውም፤ጣልቃ ገብ ከአከራካሪው ቤት ድርሻ አለኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታም በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የንብረት ክፍፍል ጉዳይ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችንም ሆነ የጣልቃ ገብን ክርክር ባለመቀበል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅርበመሰኘትለምስራቅ ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረባቸውፍርድ ቤቱተጠሪዎችን አስቀርቦ ሲያከራክር ቆይቶ እንዲሁም አከራካሪውን ቤት በ3ኛው ተጠሪ ዕዳ ምክንያት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በወጣ ሀራጅ ገዝቸዋለሁ ያሉትን አቶ ሀይሉ ሳህሌን በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ አስገብቶ ግራቀኙንአከራክሮሲያበቃ አከራካሪው ቤት 1ኛና በ2ኛ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም በአደረጉት የሽያጭ ውል ለአመልካች መሸጣቸው ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አከራካሪው ቤት ለ3ኛ ተጠሪ ተሸጧል፡፡ ይህ ቤት የ3ኛ ተጠሪና የወ/ሮ ሕይወት አውዴ የጋራ ንብረት ለመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤት 3ኛ ተጠሪና ወ/ሮ ሕይወት አውዴ በአደረጉት የጋብቻ ሀብት ክርክር ተረጋግጧል፡፡ ከ3ኛ ተጠሪ ዕዳ ጠያቂ የሆኑ በርካታ ሰዎችም ቤቱን በፍርድ ቤት አስከብረው ክርክር እያደረጉ ቆይተዋል፡፡ የአሁን አመልካችም 3ኛ ተጠሪ ከገንዘብ ጠያቂዎች ጋር ሲከራከሩ የ3ኛው ተጠሪ ሚስት ነኝ፤ ድርሻም በአከራካሪው ቤት ላይ አለኝ በማለት ጣልቃ ገብተው ክርክር ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ስለሆነም አከራካሪው ቤት በ3ኛው ተጠሪ ተመዝግቦ እንደሚገኝ ያውቁ ነበር፡፡ አከራካሪው ቤት በብር 240,000/ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በጨረታ ተሸጦ አቶ ሀይሉ ሳህሌ የተባሉት ገዝተውታል፡፡ ስመ ንብረቱም በአቶ ሀይሉ ሳህሌ ስም ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አመልካች የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገው ውል ፀንቶ ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም የተደረገው ውል እንዲፈርስ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት በውጤት ደረጃ የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘትና መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ለማሳረም ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

አመልካች ይህንን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታቸው በአጭሩ፡- አመልካች ከ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል እያለ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ያላግባብ ያደረጉት ሽያጭ የቤት ውል መነሻ ተደርገው በተከናወኑት ተግባራት የተነሳ አመልካች መብቴን እንዳጣ የተደረገ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ አከራካሪው ቤት ለአመልካች ይገባል ተብሎ ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት ነው፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ አመልካች ከ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር በፈፀሙት የቤት ሽያጭ መነሻነት ውክልናና ሰነዶችን ተረክበው እያለ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ለ3ኛው ተጠሪ እንደገና ቤቱን መሸጣቸው አግባብነቱ ሊጣራ ይገባል በማለት አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪዎች የሥር ክርክራቸውን በማጠናከር መልስአቅርበዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል። እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል። ከመዝገብ ምርመራው መገንዘብ እንደተቻለው አከራካሪውን ቤት በተመለከተ የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሽያጭ ውል ተደርጎ እንደነበር፤ ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም ደግሞ በ3ኛ ተጠሪና በ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች መካከል ሌላ የሽያጭ ውል መደረጉን፤ 3ኛ ተጠሪ ሚስታቸው ከነበሩት ወ/ሮ ሕይወት አውዴ ጋር ፍች ሲፈፅሙ ይኸው ቤት የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው ተብሎ በፍርድ ቤት መወሰኑን፤3ኛው ተጠሪ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ጋር ባደረጉት ክርክር ተፈርዶባቸው አከራካሪው ቤት በጨረታ ተሸጦ አቶ ሀይሉ ሳህሌ የተባሉት ግለሰብ ገዝተው ስመ ንብረቱ በአቶ ሀይሉ ሳህሌ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ የአሁን አመልካች በ3ኛው ተጠሪና በገንዘብ ጠያቂዎቹ መካከል በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር ከ3ኛው ተጠሪ ጋር ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ባልና ሚስት ሆነን እየኖርን በመሆኑ አከራካሪው ቤት የአመልካች ድርሻ ያለበት ነው በሚል በ2004 ዓ.ም ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው መከራከራቸውን የሥር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ከመሆኑም በላይ ይህ ችሎትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 187233 የሆነውን አስቀርቦ ተገንዝቧል።

በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን መሠረት አድርገን እንደመረመርነው 3ኛው ተጠሪ ከአመልካች ጋር ባልና ሚስት ሆነው ባሉበት ጊዜ አከራካሪውን ቤት በባል ስም የተመዘገበ ነው ከሚባል በስተቀር 3ኛው ተጠሪ የአመልካችን ቤት ያላግባብ በስማቸው አስመዝግበዋል ለማለት የሚበቃ ምክንያት የለም። ምክንያቱም አመልካች ራሳቸው በ2004 ዓ.ም አከራካሪው ቤት የአመልካችና የ3ኛው ተጠሪ ንብረት ስለመሆኑ አምነውበዚሁ ቤት ላይ ያላቸውን ድርሻ ከ3ኛው ተጠሪ ገንዘብ ጠያቂዎች ለማስቀረት ሲከራከሩ ለመቆየታቸው በፌዴራል ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥ የሚገኙ ማመልከቻዎች ያስረዳሉ።

በሌላም በኩል ሲታይ አከራካሪው ቤት ወደ ሶስተኛ ወገኖች በመተላለፍና የፍርድ ቤት ውሳኔም አርፎበት በአሁኑ ጊዜ ለአቶ ሀይሉ ሳህሌ በሀራጅ ተሸጦ ስመ ንብረቱ ከ3ኛው ተጠሪ ወደ አቶ ሀይሉ ሳህሌ ተላልፎ የሚገኝ ለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ነው። በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 2878 ሥር እንደተመለከተው አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ በሶስተኛ ወገኖች መቃወሚያ ሆኖ እንዲነሳ ከተፈለገ ውሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማይንቀሳቀስ መዝገብ መፃፍ አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች በወቅቱ ባላስመዘገቡት ሽያጭ መነሻነት ህጉን ተከትሎ ቤቱን ለ3ኛው ወገን ለማስተላላፍ የተከናወኑ ተግባራትን ሁሉ ሊቃወሙ የሚችሉበት አግባብ አይኖርም ፡፡

ለማጠቃለል ከአጠቃላይ የክርክር ይዘት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት ሆነው እስከ 2004 ዓ.ም የቆዩ መሆናቸውን ሲሆን አከራካሪው ቤት በ3ኛው ተጠሪ ስም የተመዘገበውም አመልካች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት ሆነው ባሉበት ጊዜ ነው፡፡ በሌላም በኩል ሲታይ አከራካሪው ቤት ወደ ሶስተኛ ወገን እጅ የገባ በመሆኑ አመልካች የካቲት 01 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት የሽያጭ ውል አለመመዝገቡ አከራካሪውን ቤት በሂደት ወደ እጃቸው በአስገቡት ሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ መነሳት የሚገባው ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የፈፀሙት መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ. 44309 ሚያዚያ 26 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፤ የምስራቅ ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 41878 ጥር 26 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 240297 የካቲት 09 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት አፅንተነዋል፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔያቸው የፀና መሆኑን እንዲያውቁት የዚህ ችሎት ውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍላቸው፡፡

3. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣ ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

4. በዚህ ችሎት የተሰጠው እግድ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.133203
ጥቅምት 29ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች- ዳኜ መላኩ
ተፈሪ ገብሩ
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ፀሃይ መንክር

አመልካች - ኢትዮ ቴሌኮም ጋምቤላ ሪጅን-ነ/ፈ ሰለሞን በንቲ ቀረቡ
ተጠሪ - አዱራ ኮንስትራክሽን አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ-አልቀረቡም
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ቅሬታ በማቅረቡ ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በጋምቤላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት ባጭሩ አመልካች በጋምቤላ ከተማ 04 ቀበሌ ለሚያሰራው የኔትወርክ ታወር ማቆሚያ መሰረት ፎርም ዎርክ (Form work) ለማሰራት የግንባታ ውል ስምምነት ፈፅመን በገባነው ውልና በተሰጠን ትዕዛዝ መሰረት ግንባታውን ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ርክክብ የተደረገ ቢሆንም ተከሳሽ በውላችን ከተስማማነው ክፍያ ውስጥ 70 በመቶ ከፍሎን ቀሪውን 30 በመቶ ክፍያ እንዲከፍለን ጥያቄ ብናቀርብም ለመክፈል ፈቃደኛ አይደለም፡፡ ስለሆነም ሊከፍለን የሚገባውን ብር 284,471.03 ከህጋዊ ወለዱ ጋር እንዲከፈለን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በመላ ጋምቤላ እና አካባቢዋ ለታወር ማቆሚያ ፎርም ወርክ ያስጠናው የዋጋ ተመን ለአንድ ሜትር ስኩዌር ነጠላ ዋጋ ብር 296.95

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን፤ ከውሉ ጋር በተያያዘ ቢል ኦፍ ኳንቲቲ ላይ ለኮንክሪት ሙሊት ሥራ ተመን ለአንድ ሜትር ኩብ ነጠላ ዋጋ ብር 4112.11 የተቀመጠውን ዋጋ በስህተት ለታወር ማቆሚያ ፎርም ወርክ ብር 4112.11 እንዲሆን ተደርጎ በውሉ ላይ በመፃፉ ከተሰራው ስራ ዋጋ ውጪ ተሰልቶ የቀረበ የክፍያ ጥያቄ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ በውሉ መሰረት የመጨረሻ ክፍያ የሚከፈለው አድ ሜጀርመንት (መሬት ላይ የተሰራ ስራ እየተለካ የሚከፈል) ሲሆን ከሳሾች የተሰራውን ሥራ እና ልኬት አስለክተው ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ ቀሪ ክፍያ አልተከፈለንም በማለት ያቀረቡት ክስ ተገቢ አይደለም፤ በውሉም መሰረት ክፍያ የሚፈፀምላቸው ለተሰራው ሥራና ልኬት የሚገልፅ መረካከቢያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለተከሳሽ ሲቀርብ ሲሆን ይህን ሳያቀርቡ ክፍያ እና ወለድ መጠየቃቸው ከውሉ ውጪ ነው፤ በተሰራው ሥራ መያዣ የሚሆን የአንድ አመት ዋስታና እንደሚያዝ በውሉ አንቀጽ 52 ተመልክቶ እያለ በደፈናው ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፤ ከሳሽ የሰራው ሥራም በገለልተኛ ወገን ይታይልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተከሳሽ ድርጅት ራሱ ባወጣው የዋጋ ተመን ብር 4112.11 የተዋዋለ በመሆኑና ውሉ በህግ የተመለከተው ሥርዓት ተጠብቆ የተደረገ በመሆኑ ተከሳሽ ከውሉ ውጪ በብር 296.95 እንዲከፈል ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፤ ስራው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል ወይስ አልጀመረም? የሚለውን በተመለከተም ፍርድ ቤቱ ተጣርቶ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደረገ ሲሆን በሪፖርቱ ሙሉ በሙሉ እንደ ውሉ ሥራው ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ተከሳሽ አልተረከብኩም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ በሌላ በኩል የሥራ ዋስትና መያዣውን በተመለከተ በውሉ አንቀጽ 52 መያዣ ወይም ጋራንቲ መተው እንዳለበት የተመለከተ በመሆኑ በዚህ ረገድ ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ይኖረዋል በማለት በአጠቃላይ ተለክቶ ለቀረበው ዋጋውን ብር 233,498.99 ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል፤ ከዚህ ገንዘብ ላይ የአንድ ዓመት ጋራንቲ ብር 15,792.82 እንዲቀነስ፤ እንዲሁም ቀሪውን ክፍያ መፈፀም ከነበረበት ዕለት አንስቶ የሚታሰብ 9% ወለድ እንዲከፈል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክራቸውን ከሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 15/2009 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ተጠሪ በገባው ውል መሰረት ግንባታውን አጠናቆ ባላስረከበበትና መረካከቢያ ሰነድ ቴክ ኦፍ ሸት (take off sheet) አዘጋጅቶ ባላቀረበበት ሁኔታ ቀሪ ክፍያ እንዲከፈለው መወሰኑ ውሉን ያላገናዘበ ነው፤ የሥር ፍርድ ቤት የባለሙያ ምስክርነት ሪፖርት ብቻ መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የህግ አግባብ የለውም፤ እንዲሁም ርክክብ ባልተደረገበት ሥራ ላይ ወለድ እንዲከፈል መወሰናቸው የህግ አግባብነት የለውም፤ ስለሆነም ውሳኔው ተሸሮ የተሰራው ሥራ ተለክቶና ርክክብ ተደርጎ በሚታወቀው መጠን እና ገለልተኛ ባለሙያ በጥልቀት አጥንቶ በሚያቀርበው መሰረት ተሰልቶ ቀሪ ክፍያ ካለ እንዲከፈል ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ታህሳስ 25/2009 ዓ.ም በሰጠው መልስ አመልካች በውል የተመለከተውን አገልግሎት ማግኘቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ፤ በውሉ ከተወሰነው እና አምኖ ሲከፍል ከቆየው መጠን በላይ ሌላ ክፍያ ሳይጠየቅ በቂ ባልሆነ ምክንያት ላለመክፈል ሞክሮ በፍርድ ኃይል እንዲከፍል መደረጉ ተገቢ በመሆኑ ውሳኔው እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለፅነው የክርክሩን አመጣጥና ግራ ቀኙ በሰበር ያደረጉትን ክርክር ሲሆን በበኩላችን በሥር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ሥህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡
ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤት አከራካሪ የሆነው የግንባታ ስራ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል ወይስ አልጀመረም የሚለውን በተመለከተ በባለሙያ ተጣርቶ ሪፖርት እንዲቀርብለት በማድረግ ሙሉ በሙሉ እንደ ውሉ ሥራው ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው ፍሬ ጉዳዩን ለማጣራትና ማስረጃ ለመመርመርና ለመመዘን በህጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በዚህ መልኩ የተደረሰበትን መደምደሚያ ይህ ፍርድ ቤት የሚቀበለው ይሆናል፡፡ በሌላም በኩል ከውሉ ጋር በተያያዘ ለኮንክሪት ሙሊት ሥራ ተመን ለአንድ ሜትር ኩብ ነጠላ ዋጋ ብር 4112.11 የተቀመጠው ዋጋ በስህተት ለታወር ማቆሚያ ፎርም ወርክ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሆን ተደርጎ በውሉ ላይ የተጻፈ በመሆኑ ዋጋው እንደገና ተሰልቶ ቀሪ ክፍያ ካለ እንዲከፈል እንዲደረግ አመልካች አጥብቆ የተከራከረ ቢሆንም ውሉ ጉድለት የሌለበት መሆኑና አመልካችም ራሱ ባወጣው የዋጋ ተመን የተዋዋለ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ ውሳኔ የተሰጠበት ከመሆኑም በላይ ግራቀኝ የተስማሙበት በውሉ የተመለከተ ዋጋ እያለ እንደገና ዋጋው እንዲተመን የሚደረግበት የህግ ምክንያት ባለመኖሩ በዚህም ረገድ በአመልካች የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በውሉ መሰረት ያልከፈለውን ቀሪ ክፍያ የተሰራው ሥራ ዋጋ 30% ለተጠሪዎች እንዲከፍል በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ወለድን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት ቀሪው ክፍያ መፈፀም ከነበረበት ዕለት አንስቶ የሚታሰብ 9% ወለድ እንዲከፈል የወሰነ ሲሆን አመልካች በሰበር ቅሬታው ርክክብ ባልተደረገበት ሥራ ላይ ወለድ እንዲከፈል መወሰኑ የህግ አግባብነት የለውም እንዲባል ጠይቋል፡፡ ተጠሪም በውሉ መሰረት አገልግሎት በማግኘታቸው እና ለመክፈልም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በህጉ የተቀመጠውን ወለድ የማይከፍሉበት ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡ ባለዕዳው በውል ባይመለከት እንኳ ህጋዊውን 9% ወለድ እንዲከፍል የሚጠበቅ ቢሆንም ወለድ መታሰብ የሚኖርበትን ጊዜ በተመለከተ ቀሪው ክፍያ መፈፀም ከነበረበት ዕለት አንስቶ እንዲታሰብ መወሰኑ ህጉን የተከተለ ስለመሆኑ መርምረናል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1772 ሥር እንደተደነገገው እንደውሉ ሳይፈፀምልኝ ቀርቷል በማለት ክርክር ለማቅረብ የሚፈልገው አንደኛው ወገን ተዋዋይ የተዋዋለው ሌላው አካል ግዴታውን እንዲፈፅምለት ለማድረግ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ ማስጠንቀቂያ መሰጠቱ ወለድ የሚሰላበትን ጊዜ በመወሰን ረገድ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ስለመስጠቱ ወይም ማስጠንቀቂያ መስጠት የማያስፈልግ ስለመሆኑ በመግለፅ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ክፍያ መፈፀም ከነበረበት ዕለት አንስቶወለድ እንዲታሰብ የሚደረግበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በዚህ ረገድ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰኔ 17 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 02034/08 መስከረም 1 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተለክቶ ለቀረበው የግንባታ ዋጋውን ብር 233,498.99 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል፤ ከዚህ ገንዘብ ላይ የአንድ ዓመት ጋራንቲ ብር 15,792.82 እንዲቀነስ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ይህ የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. ወለድ ክስ ከቀረበበት ከግንቦት 10 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ 9% ሊከፈል ይገባል ብለናል፡፡
4. አፈፃፀሙ ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ፍርድ ቤት ጥቅምት 18/2009 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብቤትይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ. 138591

ቀን፡- 27/6/2010ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተሻሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ሼህ አደም ፋረስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሼህ መስጠፋ ፍሊ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

1. ጉዳዩ በጋራ ንብረት ላይ ተደረገ የተባለዉ ስምምነት እንዲፈርስ የቀረበ ክስ የሚመለከት ክርክር ነዉ፡፡ ክርክሩ የጀመረዉ በቤ/ጉ/ክ/መንግስት የአሶሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻ ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስም በአሶሳ ዞን አሶሳ ከተማ 03 ቀበሌ ክልል ዉስጥ በ 1000 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ አንድ ወፍጮ ቤት ህዳር 08 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገዉ ስምምነት በጋራ የያዙት ሲሆን ጥር 16 ቀን 2002 ዓ/ም በተፃፈዉ ዉል ንብረቱ ብር 90,000 ተገኝቶ አንዱ ወገን ንብረቱን እንዲያጠቃልል ስምምነት መደረጉን ከዚህ ገንዘብ ለጥገና ብር 20,000 ዉጪ ሆኖ ቀሪዉ 70,000 ለግራ ቀኙ የተከፋፈለ ሲሆን በግራ ቀኙ ስምምነትም ተጠሪ ለጊዜዉ ብር 15,000 ከፍለዉ ቀሪዉ 20,000 በሁለት ወር እንዲከፍሉ ስምምነት የተደረገ ቢሆንም ክፍያዉ አልተፈፀመም፡፡ የአመልካች ዕድሜ 80 ዓመት ሲሆን ዉሉም በዉልና ማስረጃ ያልተደረገ በመሆኑ ዉሉ ፈርሶ የንብረቱ ግምት አመልካች ከፍለዉ ንብረቱ እንዲያስቀሩ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ተጠሪ በበኩላቸዉ ባቀረቡት የመከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ጉዳዩ መልስ ሰጥቷል። ባቀረቡት የመጀመሪያ መቃወሚያ ስምምነት ከተደረገ 6 ዓመት ያለፈዉ በመሆኑ በይርጋ እንደሚታገድ በፍሬ ጉዳዩ ደግሞ አመልካች የጠየቁት ቀሪ ክፍያ ብር 20,000 ለልጃቸዉ ወ/ሮ ሩቅያ አደም መክፈላቸዉን በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲሆን አመልክቷል።

3. መጀመሪያ ጉዳዩን የተመለከተዉ የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በተጠሪ በኩል የቀረበዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከመረመረ በኃላ ግራ ቀኙ ያደረጉት ዉል ጥር 15 ቀን 2002 ዓ/ም መሆኑን አመልካች የዉል ይሰረዝልኝ ጥያቄ ያቀረቡት በ 2008 ዓ/ም እንደሆነ በመግለጽ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 244/2/ እና የፍ/ሕ/ቁ. 1810(1) መሰረት በማድረግ የአመልካች ዉል ይሰረዝልኝ ጥያቄ የሁለት ዓመት ይርጋ ጊዜ ያለፈበት ነዉ በማለት በብይን ዉድቅ አድርጎታል። አመልካች በስር ፍ/ቤት ብይን ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም የስር ፍ/ቤቶች ብይንና ትእዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነዉ። አመልካች የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የአመልካች ዕድሜ መግፋት ተጠቅሞ ያታለሉ በመሆኑ ዉሉ እንዲሰረዝ የቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ መደረጉ በአግባቡ አለመሆኑን ይህ ቢታለፍ ቀሪ ክፍያ ብር 20,000 የመጠየቅ መብት ሊታለፍ እንደማይገባ በመግለጽ የሥር ፍ/ቤቶች ብይን እንዲሻር ጠይቋል። ጉዳዩ ያጣራዉ ችሎትም የሥር ፍ/ቤት ጭብጥ አመሰራረትና የፍ/ሕ/ቁ. 1810 ለተያዘዉ ጭብጥ ያለዉ አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ለመመርመር ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ብሏል። ተጠሪም በ 10/11/2009ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች ዉል ይሰረዝልኝ ጥያቄ በይርጋ ዉድቅ ማድረጋቸዉ ተገቢ መሆኑን ቀሪ ብር 20,000 በሴት ልጃቸዉ ወይዘሪት ሩቅያ አደም በኩል የተላከላቸዉ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸና ጠይቀዋል። አመልካች አቤቱታቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቧል።

4. የጉዳዩ አመጣጥም አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀዉ ሲሆን እኛም የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. እንደመረመርነውም አመልካች ከተጠሪ ጋር ህዳር 8 ቀን 1998ዓ/ም ባደረጉት ስምምነት 1000 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈዉ ወፍጮ የጋራ ያደረጉ መሆኑን የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች እና ተጠሪ ጥር 16 ቀን 2002ዓ.ም በተፃፈ ዉል ንብረቱ ብር 90,000 ዋጋ እንዳለዉ በመገመት አንዱ ወገን እንዲያጠቃልለዉ ተስማምተዋል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ የአመልካች ድርሻ ብር 35,000 ከፍለዉ እንዲጠቀልሉት ስምምነት መደረጉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነዉ አመልካች በአንድ በኩል ዉሉ እንዲሰረዝ ሲጠይቁ በሌላ በኩል ደግሞ ቀሪዉ ገንዘብ ብር 20,000 ያልተከፈላቸዉ ስለመሆኑ ካደረጉት ክርክር መገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ዉሉ እንዲሰረዝ ለመጠየቅ መነሻ ያደረጉት ዕድሜያቸዉ ከ 80 ዓመት በላይ ከመሆኑም በላይ የንግድ ልምድም የለኝም በሚል ስለመሆኑ መዝገቡ ያሳያል፡፡ በመርህ ደረጃ ዉል ለአንድ ወገን የበለጠ ጥቅም ይሰጣል በሚል እንደማይፈርስ ነገር ግን ፈቃድ የተገኘዉ በዕድሜ መግፋት ወይም የንግድ ልምድ ዕዉቀቱ ማነስ ካለና በሕሊና ግፍ መስሎ ከታየ ዉሉ የሚሰርዝበት ሁኔታ መኖሩን የፍ/ሕ/ቁ. 1710(1) እና (2) ድንጋጌዎች ያስገነዝበናል፡፡ የዉሉ ይሰረዝልኝ ጥያቄ መቅረብ ያለበትም በሕጉ በተደነገገዉ ጊዜ ገደብ ዉስጥ መሆን ያለበት ሲሆን በተያዘዉ ጉዳይ ስምምነት የተደረገዉ ጥር 2002 ዓ/ም ሲሆን የዉል ይሰረዝልኝ ክስ ያቀረበዉ ሚያዝያ 10 ቀን 2008 ዓ.ም መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አንድ ተዋዋይ የዉል ይሰረዝልኝ ክስ ዉሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረቡት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ዉስጥ ማቅረብ ያለበት መሆኑን በፍ/ሕ/ቁ.1810(1) ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች የዉል ይሰረዝልኝ ክስ በሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ አለማቅረባቸዉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተያያዘ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ግልጽነት የሌለዉ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ምክንያቱም አመልካች ብር 20,000 እንዲከፈላቸዉ የጠየቁ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የተጠሪ ድርሻ ብር 35,000 ከፍለዉ ንብረቱ እንዲያስቀሩ ዳኝነት መጠየቃቸዉን ካቀረቡት ክርክር መገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ፊፀምኩት ያሉትን ዉል ችግር ያለበት ከሆነ ዉሉ ይሰረዝ ብለዉ ከሚጠይቁ በቀር በተለየ አግባብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያቀረቡት ክርክር የህግ መሰረት የለዉም፡፡ አመልካች ክሱን መብታቸዉን ለማስከበር በህጉ የተመለከተዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ገደብ ጠብቀዉ ያላቀረቡት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በብይን ዉድቅ ማድጋቸዉ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

6. አመልካች የወፍጮዉ የጥገና ወጪ ብር 20,000 ከተቀነሰ በኃላ ከሚደርሳቸዉ ብር 35,000 ብር 15,000 ብቻ የተከፈላቸዉ መሆኑን በመግለጽ ቀሪ ብር 20,000 እንዲከፈላቸዉ መጠየቃቸዉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ተጠሪ በሰጡት መልስ ብር 20,000 ተከፍሏል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

አመልካች ያቀረቡት የዉል ይሰረዝልኝ ክስ በይርጋ ዉድቅ መደረጉ ተገቢ ቢሆንም አመልካች የጠየቁት ብር 20,000 ያልተከፈላቸዉ ከሆነ ተገቢዉን ዳኝነት ከፍለዉ ክስ የማቅረብ መብታቸዉ ሊጠበቅ ይገባ ነበር፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ዉል ለማሰረዝ ያቀረበ ክስ ዉድቅ ማድረጋቸዉ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ቢሆንም አመልካች አለኝ የሚሉትን ቀሪ ገንዘብ የመጠየቅ መብታቸዉ ግን ሊጠበቅ ይገባል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. በቤ/ን/ክ የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍረድ ቤት በፍ/መ/ቁ 10579 በ25/09/2008 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ብይን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ 07624 በ24/2/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ሰ/መ/ቁ 07939 በ5/05/2009 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በማለት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር አደረጉት ባሉበት የጋራ ሀብት በአንድ ወገን የመጠቅለል ዉል ያልተከፈለኝ ያሉትን ብር 20,000 ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብታቸዉ ይህ ዉሳኔ አያግዳቸዉም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ -138386

ቀን - 26/06/2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካቾች፡- 1. አቶ ረጋሣ ጉርሙ - ጠበቃ አቶ ኃይሉ ቡራዩ

2. አቶ ፀጋዬ ገ/መንፈስ - ጠበቃ አቶ አማሬ ኑሪዬ } ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ተሾመ አፈወርቅ

2. ወ/ሮ ዘነበች ገ/መንፈስ - ጠበቃ ዘነበ ፍቅሬ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄን መሠረት በማድረግ የተሰጠዉን ፍርድ በመቃወም የቀረበን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በቀን 20/08/05 ዓ.ም ጽፈዉ ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ አመልካቾች የማይገባቸዉን ጥቅም ለማግኘት የተጠሪዎችን በዕድሜ መግፋትና ነገሮችን የማመዛዘን አቅማቸዉ እየቀነሰ መሄድን በተለይም 1ኛ ተጠሪ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ፓርኪንሰስ በሚባል የማስታወስ አቅምን በሚያሳጣ በሽታ በመጠቃቱ የአእምሮ እና የነርቭ በሽተኛ መሆኑን በመጠቀም እና 2ኛ ተጠሪን ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ በማሳመን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና በማግባባት በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 2 ዉስጥ የሚገኘዉን የቤ/ቁ/047/26 የሆነዉን ቤት ነሐሴ 06 ቀን 1996 ዓ.ም እራሳቸዉ ባዘጋጁት የሽያጭ ዉል ላይ ተጠሪዎችን አስፈርመዉ ግን በዉሉ ላይ የተጠቀሰዉን ገንዘብ ሳይከፍሉ የቤቱን ካርታ እና ተያያዥ ሰነዶችን መቀበላቸዉን ጠቅሰዉ በተንኮል፣ያልተገባ ተስፋ በመስጠት ዉል ለመዋዋል ችሎታ በሌላቸዉ ሰዎች መካከል የተደረገዉ ዉል ፈራሽ ነዉ ተብሎ ይወሰንልን የሚል ነዉ፡፡

አመልካቾች ለቀረበባቸዉ ክስ በሰጡት መልስ፤ ዉሉ ተደርጎ ከሁለት ዓመት በኋላ የቀረበዉ የዉል ይፍረስልን ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ጠቅሰዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስተዉ የተከራከሩ ሲሆን፣ ፍሬ ነገሩን በተመለከተም ቀደም ሲል በመንደር የተፃፈዉን የሽያጭ ዉል ህጋዊ ለማድረግ በዉልና ሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ጽ/ቤት መመዝገቡን እና ተጠሪዎች ገንዘቡን መቀበላቸዉን እና 1ኛ ተጠሪ የአእምሮ በሽተኛ ነዉ በሚል ዉሉ እንዲፈርስ የቀረበዉም ዳኝነት ተቀባይነት የሌለዉ መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ከግራ ቀኝ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ፤ 1ኛ ተጠሪ ዉሉ በተደረገበት ወቅት ነገሮችን የማገናዘብ እና የማስተዋል ችግር በሚያስከትል ፓርክንሰንስ በሚባል በሽታ መጠቃታቸዉ በሕክምና ማስረጃ መረጋገጡን እና በወቅቱ ዕድሜያቸዉ በ90 ዓመት የሚጠጋ መሆኑ ሲታይ 1ኛ ተጠሪ ዉሉን ያደረጉት ህጋዊ ዉጤቱን ለማወቅ የሚያስችል ጤነኛ የአእምሮ ሁኔታ እና አቅም ሳይኖራቸዉ መሆኑን ጠቅሶ ዉሉ ፈራሽ ነዉ በማለት ተጠሪዎች በዉሉ ምክንያት የተቀበሉትን ብር 700,000.00 ለአመልካቾች እንዲመልሱ፣አመልካቾችም ለዉሉ መነሻ የሆነዉን ቤት ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህኑን አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 21/06/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቆቻቸዉ አማካይነት ባቀረቡት 5 ገጽ የሰበር አቤቱታ፤ 1ኛ ተጠሪ በዕድሜ መጃጃታቸዉ እንዲሁም የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸዉ እና ዉሉም በጫና የተደረገ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ፣ በሌላ በኩል ተጠሪዎች የሽያጭ ዉሉን ያደረጉት ወደዉ እና ፈቅደዉ በሰነዶች ምዝገባ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማረጋገጫ ጽ/ቤት በተረጋገጠ ዉል ሆኖ እያለ ዉሉ ተደርጎ ከሁለት ዓመት በኋላ የቀረበን የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄ በመቀበል ዉሉ እንዲፈርስ በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ በመሆኑ ተሽረዉ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታዉ ተመርምሮ ዉሉ የተደረገዉ ተጠሪዎች በዕድሜ መጃጃት እና አእምሮ መታወክ ላይ በነበሩበት ወቅት ነዉ በሚል ምክንያት ዉሉ ተደርጎ ከሁለት ዓመት በኋላ የቀረበዉን የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄ በመቀበል ዉሉ እንዲፈርስ የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አከራክሮ ለመወሰን ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት የስቀርባል በመባሉ፣ ተጠሪዎች ቀርበዉ በቀን 15/09/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃቸዉ አማካይነት ባቀረቡት 9 ገጽ የጽሑፍ መልስ፤ 1ኛ ተጠሪ የማሰብ እና የማስታወስ አቅም በሚያሳጣ ፓርክንሰስ በሚባል የአእምሮ ህመም ተጠቅቶ ባሉበት ወቅት ዉሉ መደረጉ በመረጋገጡ በፍቃድ ጉድለት ምክንያት ዉሉ እንዲፈርስ መደረጉ እና ክሱም በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ሊሆን የማይገባዉ መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ፀንቶ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች በቀን 12/10/09 ዓ.ም ጽፈዉ ባቀረቡት የመልስ መልስ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ መዝገቡን ለማስቀረብ ከተያዘዉ ጭብጥ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከግራ ቀኝ ክርክር ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ላቀረቡት ክስ መሠረት ያደረጉት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉል የተደረገዉ ተጠሪዎች በዕድሜ ጃጅተዉ ባሉበት ወቅት በተለይም 1ኛ ተጠሪ ፓርክንስንስ በሚባል አእምሮን በሚያጠቃ በሽታ ተጠቅተዉ የዉሉን ህጋዊ ዉጤት ለማወቅ በሚያስችል ጤነኛ የአእምሮ ሁኔታ እና አቅም ሳይኖራቸዉ በመሆኑ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ሲሆን፣ አመልካቾች በበኩላቸዉ ዉሉ በህግ አግባብ የተደረገ በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነዉ፡፡

በመሠረቱ ዉል እንዲፈርስ ጥያቄ የሚያቀርብ ወገን ዉሉ ሊፈርስ የሚችልበት በህግ ተቀባይነት ያለዉ ምክንያት ስለመኖሩ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን የዉል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይፍረስልኝ ጥያቄ የሚቀርብለት ፍርድ ቤትም ለዉሉ መፍረስ በምክንያትነት የተጠቀሰዉ ሁኔታ ዉሉ እንዲፈርስ ለማድረግ በህግ ተቀባይነት ያለዉ እና በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ የፍትሐብሔር ህጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ የማጣራት ግዴታ እንዳለበት ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄ በመቀበል ዉሉ እንዲፈርስ የመወሰኑን አግባብነት መመርመሩ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክሳቸዉ አጠቃላይ ይዘት መረዳት የሚቻለዉ ተጠሪዎች ለዉሉ መፍረስ የጠቀሱት መሠረታዊ ምክንያት ዉሉ በተደረገበት ወቅት ዉል ለማድረግ የሚያስችል ችሎታ የሌላቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ዉሉ እንዲፈርስ ሲል ለደረሰበት ድምዳሜ በመሠረታዊነት የጠቀሰዉ ምክንያት ይህኑን ስለመሆኑ ተመልክተናል፡፡ በርግጥ ህጋዊ ዉልን ለማቋቋም አስፈላጊ ከሆኑት ሁኔታዎች ዉስጥ አንዱ ዉሉ ዉል ለማዋዋል ችሎታ ባላቸዉ ሰዎች መካከል የተደረገ መሆኑ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 1678(ሀ) ተመልክቷል፡፡ አንድ ሰዉ ዉል መዋዋልን ጨምሮ ሌሎች ህጋዉያን ተግባራትን (juridical acts) ለማከናወን ችሎታ የለዉም ማለት ስለሚቻልባቸዉ ሁኔታዎች የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2 ስለ ችሎታ በሚል ርዕስ ከአንቀጽ 192 ጀምሮ ባሉት አንቀፆቹ የሚደነግግ ሲሆን፤ ከአእምሮ ችግር ጋር በተያያዘ በህጉ አንቀጽ 339 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ዉል ከአእምሮ ጉድለት ጋር በተያያዘ ምክንያት ሊፈርስ የሚችለዉ የአእምሮ ጉድለቱ በግልጽ የታወቀ ሲሆን (notorious insanity) ወይም በፍርድ ክልከላ (judicially interdicted) ሲደረግ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 347 (1) እና 372 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ በግልጽ የታወቀ የአእምሮ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለበት መሆኑ ታዉቆ በፍርድ ክልከላ የተደረገ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 339፣ 340 እና 351 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በርግጥ ዉሉ በሚደረግበት ወቅት በነበረበት የአእምሮ ችግር (ህጉ “እብድ” በሚል ይገልፀዋል) የነበረበት በመሆኑ ምክንያት ጉድለት የሌለበትን ፍቃድ ለመስጠት በማይችልበት ሁኔታ ላይ እንደነበረ ለማስረዳት ከቻለ ዉሉን ማስፈረስ የሚችል ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 347(2) ስር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመልክቷል፡፡ ይሁንና ይህ ድንጋጌ፣ የአእምሮ ችግሩ በግልጽ የታወቀ ካልሆነ በስተቀር ወይም በፍርድ ካልተከለከለ በስተቀር የአእምሮ ችግር መኖሩ መረጋገጡ ብቻውን ዉልን ለማፍረስ ምክንያት እንደማይሆን በህጉ አንቀጽ 347(1) ስር ለተመለከተዉ ድንጋጌ ልዩ ሁኔታ (exception) በመሆኑ፣ በጠባቡ መተርጎም እንደሚገባዉ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ተዋዋዩ ዉሉን ያደረገዉ ነፃ ፍቃድ መስጠት በማይችልበት ሁኔታ ላይ መሆኑን በማስረዳት ዉሉ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚቻለዉ ዉሉ በተደረገበት ወቅት ተዋዋዩ እብድ (የአእምሮ ችግር ያለበት) መሆኑን እና ዉሉም የተደረገዉ ተዋዋዩ በዚህ የአእምሮ ሁኔታ ዉስጥ ሆኖ ባለበት ወቅት ስለመሆኑ በማያጠራጥር አኳያ በማስረጃ ማረጋገጥን እንደሚጠይቅ ከፍ ሲል ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አጠቃላይ ዓላማ እና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁንና 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የቀረበ የህክምና ማስረጃ ግለሰቡ አእምሮን ሊያጠቃ በሚችል በሽታ መያዛቸዉን እንጂ በርግጥም ዉሉ በተደረገበት ወቅት በህጉ አጠራር እብድ በመሆን አእምሮአቸዉን መቆጣጠር በማያስችል ደረጃ ላይ የነበሩ መሆናቸዉን አያሳይም፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ተጠሪዎች ዉሉ እንዲፈርስ በምክንያትነት ከጠቀሱት ዉስጥ አንዱ በዕድሜያቸዉ የገፉ ወይም የጃጁ መሆናቸዉን በመግለጽ ነዉ፡፡ በርግጥ መጃጀት ለዉል መፍረስ አንዱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1710(2) ስር ተመልክቷል፡፡ ይሁንና መጃጀት ለዉል መፍረስ ምክንያት ሊሆን የሚችለዉ ዉሉ ለአንደኛዉ ወገን የበለጠ ጥቅም የሚሰጥ ሆኖ ይህም ሊሆን የቻለዉ የአንደኛዉን ወገን (የተጎጂዉን) መጃጀት ወይም በዕድሜ መግፋቱን መሠረት በማድረግ የተደረገ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 1710 (1 እና 2) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዕድሜ መግፋትን ወይም መጃጀትን መሠረት በማድረግ ዉል እንዲፈርስ ጥያቄ የሚያቀርብ ወገን በዕድሜ መግፋቱ ወይም መጃጀቱ መኖሩን ብቻ ሳይሆን ዉሉም ለተከሳሽ የበለጠ ጥቅም በሚሰጥ መልኩ የተደረገ ስለመሆኑ ጭምር የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ተጠሪዎች ዉሉ አመልካቾችን በይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ ስለመሆኑ ለማሳየት ቤቱ 10,000,000.00 እንደሚያወጣ በክሳቸዉ ያመለከቱ ቢሆንም ይህ ግምት መሠረት የሚያደርገዉ ክሱ በተመሰረተበት ወቅት፣ በ2005 ዓ.ም፣ ያለዉን የቤቱን ዋጋ እንጂ ዉሉ በተደረገበት ወቅት በ1996 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የነበረዉን ዋጋ አለመሆኑን ከክሱ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ዉሉ አመልካቾችን በይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ ስለመሆኑ ባላሳዩበት ሁኔታ የተጠሪዎችን መጀመት ወይም በዕድሜ መግፋት ብቻ መሠረት በማድረግ ዉሉ እንዲፈርስ ተጠሪዎች ያቀረቡት ጥያቄም ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ ዉል ሊፈርስ የሚችልበትን እና በህግ ተቀባይነት ያለዉ ተጠሪዎች ምክንያት በማቅረብ ባላስረዱበት ሁኔታ ያዉም ዉሉ ዉልን ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ማለትም በዉል እና ሰነዶች ማረጋገጫ የተደረገ ሆኖ እያለ፣ ዉሉ ተደርጎ ከ9 ዓመት በኋላ እንዲፈርስ ያቀረቡትን ክስ ተቀብሎ ዉሉ እንዲፈርስ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ ዉል ሊፈርስ የሚችልበትን ሁኔታ በተመለከተ ከላይ በፍትሐብሔር ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.128919 በቀን 24/04/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 134268 በቀን 03/08/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰተዉን ዉሳኔ በማጽናት፣ የሰጠዉ ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል ሊፈርስ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. እግድ ተነስቷል፤ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 128650

መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡...1.ረታ ቶለሳ

2. ተክሊት ይመሰል

3. ተፈሪ ገብሩ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች ፡- ወ/ሮ እቴናት አድማሱ - ቀርበዋል ፡፡

ተጠሪ ፡- አቶ ደመቀ ይዘንጋዉ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የመኖሪያ ቤት ክርክርን መነሻ ያደረገ ሲሆን፣ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.45202 በ20/07/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበችዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በቢቡኝ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ክሳሽ፣የአሁን አመልካች ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ በ26/2/1999 ዓ.ም በተደረገዉ ዉል ተከሳሽ 8 ሜትር በ 12 ሜትር የሆነዉ ቦታና ቤት በብር 1,800.00 ሸጠዉልኝ በቦታዉ ላይ 37 ቆርቆሮ ቤት ከሰራሁኝ በኋላ ስመ ሀብቱን አዛዉርልኝ ካርታና ፕላን ላሰራበት ሲላት ፈቃደኛ ካለመሆንዋም በላይ በስሟ ካርታና ፕላን አሰርታ ከይዞታዋ ጋር ስላከተተች ቤቱን የገዛሁበትን ብር 1,800.00 ዉል ላፈረሰችበት ብር 5,000.00፣ 37 ቅጠል ቆርቆሮ ለማሰራት ያወጣሁትን ወጪ በአጠቃላይ ብር 27,198 /ሀያ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ስምነት/ እንዲትከፍለኝ በማለት ከሷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህን ክስ በተመለከተ ተከሳሽ ባቀረበችዉ መልስ በተባለዉ ዉል ቤቱንና ቦታዉን አልሸጥኩም፣ በ26/2/1999 ዓ.ም በተጻፈ ዉል 5 ሜትር በ 5 ሜትር ባዶ ቦታ በብር 1,800.00 ሸጨለት በዉሉ ቀን ብር 50.00 ሰጥቶኝ ቀሪዉን ዉሉ በቀበሌ ሲጸድቅ ሊሰጠኝ ተስማምተን ነገር ግን ባዶ ቦታ አይሸጥም ስለተባለ ብሩን መልሸለታለሁ እኔ ለቅሶ በሄድኩበት በሌለሁበት 32 ቆርቆሮ በጉልበት ባልሸጥኩለት ቦታ ሁሉ ቤት ሰርቷል፣ ባዶ ቦታ አይሸጥም፣ ቤቱን ለመስራት የተባለዉን ወጪ አያወጣም፣ ስለዚህ ቤቱን በራሱ ወጪ አፍርሶ እንዲያነሳ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት በሰጠዉ ዉሳኔ የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ ባዶ ቦታ ላይ ስለሆነ የሚጸና የቤት ሽያጭ ዉል የለም፣ ዉሉ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል፣ ከሳሽ በተከሳሽ ቦታ ላይ 33 ቆርቆሮ የሰራዉ ተከሳሽ እያወቀች ቢሆንም ከሳሽ ቤቱን አፍርሰዉ ከሚያነሳ በቀር ግምቱንም ሆነ ቤቱ የተሰራበትን ወጪ ለመክፈል የሚትገደድበት የሕግ አግባብ የለም፤ ነገር ግን ከሳሽ ቤቱን አፍርሶ ለመዉሰድ የጠየቀዉ ዳኝነት ስለሌለ ታልፏል፣ በዚህ በሕገ ወጥ ዉል ምክንያት ከሳሽ ለተከሳሽ የከፈላት ብር 1,800.0 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ/ ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲትከፍለዉ በማለት ወስኗል፡፡ የምስራቅ ጎጀም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሥር ዉሳኔ አንጽቷል፡፡

የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሽያጭ ዉሉ ሕገ ወጥ ስለሆነ ተጠሪ ለአመልካች ብር 1,800.00 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ/ እንድትመልስ መባሉ በአግባቡ ነዉ፣ የሥር ፍ/ቤት ዉሉ ሕገ ወጥ ቢሆንም መኖሩን እስካመነበት ድረስ አመልካች ቤቱን ለመሥራት ያወጣዉን ወጪ ተጠሪ ልትከፍለዉ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ፣ አመልካች ቤቱን ለመሥራት ያወጣዉን ወጪ ተጠሪ ልትከፍለዉ ይገባል፣ የወጪዉን መጠን ግን የሥር ፍ/ቤት በማስረጃ አጣርቶ እንዲወስን በማለት ወደ ሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች በ16/09/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡--የአሁን አመልካች ከተጠሪ ጋር የፈጸምነው ረቂቅ ውል ሲሆን የሽያጭ ዉሉ ባዶ ቦታ የሚመለከት በመሆኑ በወቅቱም ዉሉን ለማዞር ስንጠይቅ የባዶ ቦታ ሽያጭ ውል አይዞርም በመባላችን ረቂቅ ዉሉ ቀሪ ወይም ፈራሽ ያደረግነው ሆኖ ሳለ ቤቱንም ያለ እኔ ፈቃድ የሰራዉ መሆኑን ምስክሮች ከማረጋገጣቸውም በላይ የቀበሌዉ ዋና አስተዳደሪ በችሎት ቀርቦ ያስረዳ በመሆኑ መክፈል የሚገባዉ ስለረቂቅ ዉሉ የተባልኩትን ገንዘብ ብቻ እንጂ ያለ እኔ ፈቃድ ከሳሽ ስለሰራዉ ቤት ግምት ለመክፈል የምገደድበት ምክንያት የለም፣ ቤቱ የተሰራበትም ተቃዉሜአለሁ ስለዚህ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረምልኝ ይገባል በማስረጃ ተመልሶ እንዲጣራልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ዉሉ ሕገ ወጥ እንደሆነ እና ቤቱ የተሰራዉ በሌለሁበት ነዉ በማለት ያቀረቡት ክርክር ታልፎ ተጠሪ ቤቱን ለመስራት ያወጡት ወጪ አመልካች እንዲከፍሉ የመባሉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ቢታዘዝም ተጠሪ መጥሪያ ተቀብለዉ ባለመቅረባቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች እና ተጠሪ በ26/2/1999 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ዉል ቦታና ቤት እንደሚመለከት ቢገለጽም፣ የሥር ፍ/ቤት ባደረገዉ ማጣራት ግራ ቀኞቸዉ የተሻሻጡት ባዶ ቦታ ብቻ መሆኑን ባቀረበዉ ማስረጃ አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ግራ ቀኞቸዉ የተሻሻጡት ባዶ ቦታ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የሚጸና የቤት ሽያጭ ዉል እንደሌለ እና ዉሉ ሕገ ወጥ መሆኑን ድምዳሜ ላይ በመድረስ ወስኗል፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 /3/ መሰረት ‹‹የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነዉ፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ፡፡ በማለት ደንግጓታል፡፡ ይህን ድንጋጌ ተግባራዊ ለማድረግ ከወጡት ዝርዝር ሕጎች መካከል የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝን እንደገና ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 272/1994 እና ይህን አዋጅ የሻረ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡ እነዚህ እና ሌሎች ዝርዝር ሕጎችን ማየት እንደሚቻለዉ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት በሕጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት ተከትሎ ስልጣን ያለዉን አካል ጠይቆ ከማግኘት ዉጭ በሽያጭ ገዝቶ መያዝ እንደማይቻል ያስገነዝባሉ፡፡ የከተማ ቦታ በሽያጭ ዉል ተሸጦ ከሆነ ዉሉ ሕገ መንግስቱንም ሆነ ዝርዝር ሕጎቹን የሚጥስ ስለሆነ ሕገ ወጥና ፈራሽ ዉል ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን ተጠሪ ባዶ ቦታ ከአመልካች ገዝቶ ቤት የሰራ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዉሳኔዎቻቸዉ እንዳመለከቱት ይህ ዉል ሕገ ወጥ እና ፈረሽ ዉል ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ግራ ቀኛቸዉ ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1815 ማየት ይቻላል፡፡ ግራ ቀኛቸዉ ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል ሲባል ግን የባለይዞታነት መብት ያለዉን ሰዉ/አካል ላይ እዳ በመጫን መሬቱን ሊያጣዉ የሚችል የገንዘብ ክፍያ ሊጣልበት አይገባም፡፡ በመሆኑም ይህ ዉል ሕገ ወጥ በመሆኑ እስከፈረሰ ድረስ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ልትከፍለዉ የሚገባት ብር 1,800 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ/ ብቻ ሊሆን ይገባል እንጂ የአሁን ተጠሪ በሕገ ወጥ ዉል በያዘዉ ቦታ ላይ የሰራዉን ቤት ለማሰራት ያወጣዉን ወጪ አመልካች የምትከፍልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ በአመልካች ቦታ ላይ የሰራዉን ቤት በራሱ ወጪ በማፍረስ ቦታዉን ለተጠሪ ለማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ግራ ቀኛቸዉ ከተስማሙ የአሁን አመልካች የቤቱን ግምት ለተጠሪ ከፍለዉ ቤቱን ለመዉሰድ ይህ ዉሳኔ የሚያግዳቸዉ አይሆንም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኛቸዉ መካከል የተደረገዉ ዉል ሕገ ወጥ ስለሆነ አመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ ብር 1,800.00 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ/ ለተጠሪ እንድትመልስ ያለዉ ተገቢ ቢሆንም ተጠሪ በአመልካች ቦታ ላይ ቤት ለመስራት ያወጣዉን ወጪ እንድትከፍል በማለት የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ በአመልካች ቦታ ላይ ቤት ለመስራት ያወጣውን ወጪ የመክፈል ኃላፊነት አለባት በማለት የሰጠዉ ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ የአሁን ተጠሪ በራሱ ወጪ ቤቱን ከአመልካች ቦታ ላይ አፈርሶ በማንሳት ቦታዉን ለአመልካች ሊለቅ ይገባል፡፡ አመልካች ቤቱን ለመስራት ተጠሪ ያወጣዉን ወጪ ለመክፈል አይገደዱም ብለናል፡፡ ነገር ግን ግራ ቀኞቸዉ ከተስማሙ እና የአሁን አመልካች ከፈለጉ የቤቱን ግምት ለተጠሪ ከፍለዉ ቤቱን ለመዉሰድ ይችላሉ ብለናል፡፡
3. የቢቡኝ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.07213 በ17/3/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ውሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የምስራቅ ጎጆም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.0120127 በ7/4/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
4. የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች በዉል ምክንያት ከተጠሪ የተቀበሉትን ብር 1,800.00 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ/ ለተጠሪ እንዲመልሱ በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
5. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይደረስ፡፡ ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
6. በ8/10/2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.138479
የካቲት 26 ቀን 2010
ዓ.ም.

ዳኞች- ዳኜ መላኩ
ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ፀሃይ መንክር

አመልካች - ወ/ሮ ሸዋዬ ገ/እግዚአብሔር - ጠበቃ ወይንሸት መንግስቱ ቀረቡ
ተጠሪ - ወ/ሮ ብርሃኔ ፀአዱ - ጠበቃ ቅድስት የበቃ- ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

1. አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 20 ቀበሌ 38 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 426 የሆነ ቤት ያላቸው ሲሆን ባለቤቱ ሟች አቶ ኃይለ ስልጣን ፀአዱ በህይወት በነበሩበት ወቅት በራስህ ጉልበትና ገንዘብ ቤት ሰርተህ በመኖሪያነት ተገልገልበት በማለት ውክልና ጭምር ሰጥተውት በቤታቸው ግቢ ውስጥ ተጠሪ ከልለው በሰጡት ቦታ ላይ ግምቱ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ) የሆነ ከእንጨትና ጭቃ የተሰራ አንድ ክፍል ቤት ከነመፀዳጃው ሰርተዋል፤ የሟችን ሞት ተከትሎ ተከሳሽ ቤቱን እየተገለገሉበት ሲሆን በዚሁ ቤት ውስጥ የነበሩ ግምታቸው ብር 11,766.00 (አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ስድስት) የሆኑ የተለያዩ ንብረቶች ይዘው ስለከለከሉኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረቶቹን በአይነት ያስረክቡኝ ወይም ግምቱን እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

2. ተጠሪ በሰጡት መልስ የቤት ቁጥር 426 የሆነው ቤት በተጠሪ እና በባለቤታቸው ሻምበል አረዳ በኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት በ1965 ዓ.ም የተሰራ ሲሆን ከዚያ ወዲህ በግቢው ውስጥ የተሰራ ቤት የለም፤ የአመልካች ባለቤት በተጠሪ ግቢ ቦታ ተሰጥቶት የሰራው ቤት የለም፤ ሟች የተጠሪ ወንድም በመሆኑ በእንግድነት መጥቶ ሲኖር ነበር፤ በመታመሙ ምክንያት ተጠሪ ሳስታምመው ቆይቶ ከዚህ አለም በሞት የተለየ ሲሆን አመልካች ለቅሶ ከመምጣት ውጪ አላስታመሙም፤ የቤት ቁሳቁስ በማለት ዘርዝረው ያቀረቡት አንድም ዕቃ የለም፤ በአጠቃላይ ክሱ አላግባብ ለመበልፀግ የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

3. ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸውን እንዲያቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ከሳሽ ምስክር በቀጠሮ ቀን አቅርበው ባለማሰማታቸው መብታቸው የታለፈ ሲሆን የተከሳሽ ምስክሮች ቀርበው እንደመልሳቸው ማስረዳታቸውን፤ ምስክር ከተሰማ በኋላ የአመልካች ጠበቃ በዕለቱ ሌላ ቦታ ቀጠሮ ስለነበረኝ ምስክሮችን ፍርድ ቤቱ አስቀርቦ ይስማልኝ በማለት ቢጠይቁም በመጀመሪያ ምስክር ለመስማት ሲቀጠር ግራ ቀኙ በተገኙበት መታዘዙን መዝገቡ የሚያሳይ በመሆኑና ከሳሽ ሆነ ጠበቃቸው በቀጠሮው ምስክር እንደሚሰማ እያወቁ ሌላ ቦታ ቀጠሮ ተደርቦ ቢሆን እንኳ ቢያንስ ጠበቃው ከቀጠሮ ቀን በፊት ይህንን ለችሎቱ ማሳወቅ ሲገባቸው ካለማሳወቃቸውም በላይ ለምስክሮች መጥሪያ ስለማድረሳቸው እንኳ አልተረጋገጠም፤ በመሆኑም ከሳሽ በራሳቸው ቸልተኝነት ምስክር አላሰሙም፤ በሰነድ ረገድም ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ ስለሆነም ክሱ በተከሳሽ የተካደ በመሆኑና ከሳሽም በሰነድም ይሁን በሰው ማስረጃ እንደክሱ ያላስረዱ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

4. አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 3/2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ አመልካች ጠበቃቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለመገኘታቸው ብቻ ምስክር የማሰማት መብታቸው ታልፎ ክሱን አላስረዱም ተብሎ የመወሰኑን አግባብ ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል። ተጠሪ መስከረም 23/2010 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ለምስክሮች የተጻፈውን መጥሪያ እንኳን ሳይወስዱ እርሳቸውም ሆነ ጠበቃቸው በቀጠሮው እለት ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በመቅረታቸው በሥነ ሥርዓት ህጉ መሰረት ምስክር የማሰማት መብታቸው የታለፈው በህጉ አግባብ በመሆኑ የሚነቀፍበት አንዳችም ምክንያት ካለመኖሩም በላይ ይህን የታለፈ መብታቸውን ለማስነሳት የሚያበቃ በቂ ምክንያት ያላቀረቡ በመሆኑ ውሳኔው ሊፃና ይገባል በማለት ተከራክረዋል። አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

5. ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ እና በሰበር የተደረገውን ክርክር ሲሆን በበኩላችን በሥር ፍርድ ቤቶች በተላለፈው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል።

6. ክርክሩ በሚመራበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 199(1) ሥር እንደተደነገገው ለቀጠሮ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት ሆኖ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ ያልተፈፀመ ቢሆንም እንኳ ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ የመሰለውን ውሳኔ መስጠት እንደሚችል ተመልክቷል።

7. ከተያዘው ጉዳይ መገንዘብ እንደሚቻለው የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ውደቅ በማድረግ የወሰኑት አመልካች ሆኑ ጠበቃቸው በቀጠሮው ምስክር እንደሚሰማ እያወቁ ባለመቅረባቸውና ጠበቃው ሌላ ቦታ ቀጠሮ ተደርቦባቸው ቢሆን እንኳ ቢያንስ ከቀጠሮ ቀን በፊት ይህን ለፍርድ ቤቱ ካለማሳወቃቸውም በላይ ለምስክሮች መጥሪያ ማድረሳቸው እንኳ አልተረጋገጠም፤ በመሆኑም ከሳሽ በራሳቸው ቸልተኝነት ምስክር አቅርበው ያላስረዱ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል ነው። አመልካች በዚህ መልኩ መብታቸው የታለፈው ከህግ ውጪ ነው ሊባል የሚችልበት በህግ የተደገፈ ምክንያት አላቀረቡም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

8. ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች ክፍ ሲል በተጠቀሰው መልኩ የደረሱበት መደምደሚያ እና ያሳለፉት ውሳኔ ክርክሩ የሚመራበትን የሥነ ሥርዓት ህግ መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የተከተሉት የክርክር አመራር ሥርዓት የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 15286 ጥር 20/2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በከፍተኛው ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 166927 ህዳር 6/2009 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 133708

ጥቅምት 21 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ጣይቱ ደያሳ

2. ወ/ሮ ዘነቡ ደያሳ

3. አቶ አሸናፊ ደያሳ

4. ወ/ሮ ዘር ደያሳ

5. ወ/ሮ ሸዋዬ ለገሰ

6. ወ/ሮ ዲባቤ ለገሰ

7. ወ/ሮ እመቤት ለገሰ

8. አቶ ካሳ ለገሰ

9. አቶ መስፍን ረጋሳ

10. አቶ ደገፋ ረጋሳ

ጠበቃ ጸጋዬ ፈይሳ -ቀረቡ

11. አቶ ሽፈራው ለገሰ

ተጠሪ፡- አቶ ጉደታ ዲያሳ -ጠበቃ በሬሳ በየነ- ቀረቡ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ፌንፌኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በረክ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ የሚች እናታችን የወ/ሮ ሎሚታ ጉደታ በቀን 22/11/2006 ዓም በውርስ አጣሪዎች የተጣራ የውርስ ንብረት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 17 በመዘርዘር በፍ/ብ/ህ/ቁ.996 መሰረት ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው የጠየቁትን ዳኝነት በመቃወም ተጠሪው የጣልቃ ገብነት ማመልከቻ በቀን 24/02/2007 ዓ.ም አቅርበዋል፤ በዚህ ማመልከቻቸውም አመልካቾች በአቤቱታቸው ከተራ ቁጥር 7 እስከ 10 እንዲረጋገጥላቸው የጠየቁት የባህር ዛፍ፤ የሳር እና የእርሻ መሬት የውርስ ሳይሆን የግሌ በመሆኑ ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር እንዲፈቀድልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ የአሁን ተጠሪ የስር ጣልቃ ገብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.43 መሰረት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ሲል ብይን ሰጥተዋል፡፡

የአሁን አመልካቾች የስር ፍርድ ቤት ብይን በመቃወም ለፌንፌኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ብይን በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ሲል በውሳኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች ጥቅምት 29 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ጥር 8 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካቾችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል። የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል።

እንደመረመርነውም የአመልካቾች ጥያቄ ተጠሪ የሚች የውርስ ንብረት ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲጣራ በግልፅ ተስማምቶ ውክልና ሰጥቶ በሚጣራው የውርስ ፋይል ተሳታፊ ሆኖ እያለ ቀድሞ የሰጠው ስምምነት ፀፅቶት ውርሱ ሊጣራ አይገባም በይርጋ ይታገዳል በማለት በጣልቃ ገብነት መቀወሚያ በማንሳትና መከራከሩን ክርክሩ እየታየ ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41፣43 ድንጋጌዎች በመጥቀስ ተጠሪ ጣልቃ ይግባ መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ በወካይና ተወካይ መካከል ያለው ግንኙነት በቅን ልቦና የተመሰረተ መሆን እንዳለበት እና ተወካዩም የወካዩን ጉዳይ ልክ እንደራሱ ጉዳይ የወካዩን ጥቅም በማስቀደም መስራት እንዳለበት የውክልና ህግ ላይ ተደንግጎ ይገኛል። ይሁን እንጂ አመልካቾች ይህንን የውክልና ስልጣን መከታ በማድረግ የተሰጣቸውን የውክልና ስልጣን በመተላለፍ የእናታችን የውርስ ሀብት ብቻ ሳይሆን በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የተጠሪን የግል ንብረት እና ይዞታ ጭምረው ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው ስህተት ነው። የሰጠሁት የውክልና ስልጣን በሌላ ጉዳይ ላይ ሁኖ እያለ ከፍላጎቴና ፍቃዴ ውጭ እንዲሁም በግል ንብረቴ ላይ የቀረበውን ክርክር በተመለከተ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41 ውጭ ጣልቃ ገብቼ ተከራክሬ መብቴን የማስከብርበት ሌላ አመራጭ የለም። ስለዚህ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚሁ ረገድ የሰጠው ውሳኔ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁን ተጠሪ የሚች የውርስ ንብረት ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግ ከአሁን አመልካቾች ውስጥ ለወ/ሮ ዘርፌ ደያሳ እና ለአቶ ደገፋ ረጋሳ የውርስ መብታቸውን ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲታወቅላቸው የውክልና ስልጣን በመስጠት መሰማማታቸው፤በዚሁ መሰረት ውርስ ንብረት አጣርተው ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው፤ የውርስ ማጣራት በሂደት እያለ የአሁን ተጠሪ በስር 3ኛ አመልካች የነበሩት የውርሱ ማጣራት በይርጋ መታገድ አለበት፤ንብረቱ በውርሱ ውስጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጨምሯል የሚሉ ምክንቶች በመዘርዘር በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር መጠየቃቸው ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ የሚች የውርስ ንብረት ለማጣራት አመልካቾችና ተጠሪ ጭምር ተስማምተው አጣርተው ለፍርድ ቤት ማቅረባቸውን ፍሬ ጉዳዩን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ አልተስማማሁም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ የፍትሀብሔር ህጉ የሚች ውርስ የማጣራት ስልጣን ያላቸውን ግለሰቦች በቅደም ተከተል የሚዘረዝር ሲሆን እነርሱም፡-ሚች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ ሆኖ ውርሱን እንዲያጣራ የሾመው ሰው ካለ በመጀመሪያ የውርስ አጣሪ እንደሆነ የፍትሀብሔር ህጉ 948/1/ የሚደነግግ ሲሆን፣ ሚች በውርስ አጣሪነት በኑዛዜ የሾመው ሰው ከሌለ ጠቅላላ የኑዛዜ ተቀባይ የሆነው ሰው የሚችን ውርስ የማጣራት ስልጣን እንዳለው የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር አንቀጽ 948 ንኡስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ሚች በኑዛዜ የመረጠው የውርስ አጣሪ ወይም ጠቅላላ የኑዛዜ ተቀባይ የሌለ በሆነ ጊዜ ሁሉ የሚች ያለኑዛዜ ወራሾች ያላንዳች ፎርማሊቲ የውርስ አጣሪነት ስልጣን እንዳላቸው በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 947 ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሰረት አመልካቾች እና ተጠሪ የሚች ያለ ኑዛዜ ወራሾች በመሆናቸው የውርስ አጣሪነት ስልጣን እንዳለቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት ነጥብ በውርስ አጣሪ ተጣርቶ ለፍርድ ቤት በቀረበው ሪፖርት ላይ ያላቸውን አስተያየት በመቀበል በውርሱ ማጣራት ሂደት በአግባቡ አልተጣራም የሚል መቃወሚያ ካለም ፍርድ ቤቱ በህጉ መሰረት አጣርቶ ሪፖረቱን ሊያሻሽለው ወይም ሊያፀናው ይችላል፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ የውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ በተመለከተ ሪፖርቱን በመደገፍ ወይም በመቃወም የሚቀርበው አስተያየት ተቀብሎና መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ከመስጠት ባለፈ የግድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41 መሰረት ተጠሪ በጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር ያቀረበው ጥያቄ ተገቢነት የለውም፤ፍርድ ቤቱም ሊቀበለው አይገባም፡፡ ምክንያቱም በአንድ ክስ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በክርክር ላይ ባሉበት ጊዜ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም 3ኛ ወገን ከፍርድ ውሣኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ መከራከር እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41/1/ ላይ የተደነገገ በመሆኑ ነው፡፡ ተጠሪ በዚሁ ጉዳይ 3ኛ ወገን አይደለም፡፡ ስለዚህ ለተያዘው ጉዳይ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41፤43 አግባበነት ያላቸው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ ከይርጋ ውጭ በሌሎች ነጥቦች ረገድ የውርስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማጣራቱን ሂደት እና ውጤቱን በተመለከተ አስተያየት መስጠት እና ፍ/ቤቱም ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ሊወስን ይገባል፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ የሚች የውርስ ንብረት ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግ ከአመልካቾች ጋር የተስማማ በመሆኑ የውርስ ማጣራት በይርጋ ይታገዳል በማለት የሚያቀርበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች በገዳዩ የሰጡት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ስጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 240200 መስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 24107 ህዳር 1 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በመሻር የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 227678 ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም እና የበረክ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.12792 ታህሳስ 27 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. ተጠሪ በክርክሩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41/43 መሰረት ጣልቃ ይግባ በማለት የሰጡት ውሳኔ ክፍል በመሻር ፤በውጤት ደረጃ ተጠሪ የሚች ውርስ ንብረት ማጣራት በይርጋ ይታገዳል የሚለውን መቃወሚያ ውጭ ያለውን አስተያየት እንዲያቀርብ መፍቀዳቸው በአግባቡ በመሆኑ አጽንተነዋል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡የ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.138717

የካቲት 28 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡1.ፀጋዬ አስማማው

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራው

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ ብርክቲ ግደይ - ጠበቃ አበባ ዘበነ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1.አቶ ሸምሱ ኑሪ } 1ኛ ተጠሪ ቀርበዋል

2. ወ/ሮ ፈዲላ እስማኤል }

ይህ መዝገብ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የብድር ዉል የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.185781 በ23/05/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ሆነው ሲከራከሩ ነበር፡፡ ከሳሽ ባቀረበችዉ ክስ ተከሳሾች በ16/11/1999 ዓ.ም በተደረገዉ የብድር ዉል ብር 300,000 የተበደሩ ሲሆን በ10/2/2000 ዓ.ም ይህን የብድር ገንዘብ ካልከፈሉ በመያዣነት ያስያዙትን ቤት ስም ሀብት ወደ ከሳሽ ለማስተላለፍ ግዴታ ገብቷል፤ ከሳሽ የቤቱን እዳ ለመንግስት ብር 37,080.40 በተከሳሽ ስም የተከፈለ በመሆኑ፣ የዉስጥ ሁለት በሮችን ለማሰራት ብር 10,000 ያወጣሁ ስለሆነ፣ የቤቱ የመከላከያ ብረት ለማሰራት ብር 2,500 እና ለባለሙያ ብር 1,500 ከፍያለሁ፡፡ ስለዚህ ተከሳሾች ይህን ቤት ስመ ሀብት ወደ ከሳሽ እንዲያዛዉሩልኝ ይህ ካልሆነ ገንዘቡን ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ፣ በዉሉ መሰረት ግዴታቸዉን ባለመፈጸማቸዉ ገደብ ብር 20,000 እንዲከፍሉኝ በማለት ከሷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ክስ ላይ የሥር ተከሳሾች ባቀረቡት መልስ የብድር ዉሉን በተመለከተ ተገቢ ነዉ ያሉትን ክርክር በማቅረብ፣ ከሳሽ ለባንክ ከፍያለዉ በማለት እንዲተካላቸዉ /እንዲከፈላቸዉ/ ያቀረቡትን ጥያቄ በሚመለከት ለባንክ የተከፈለዉን ቀሪ እዳ ብር 37,080.40 ለሁለት በሮች ለመከላከያ ብረት የወጣዉ ወጪ በጊዜዉ የነበረዉን ተመጣጣኝ ዋጋ ብንከፍል ተቃዉሞ የሌለን በመሆኑ በዚህ መሰረት ቢወሰን እንስማማለን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሾች የተበደሩትን ብር 300,000 ለከሳሽ እንዲከፍሉ፤ ከሳሽ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 14 ሚኪሊላንድ ሳይት የሕንጻ የቤት ቁጥር 22 የቤት ቁጥር 843 ለተከሳሾች ሊያስረክቡ ይገባል፣ ለቤቱ አወጣሁ ያሉትን ወጪ በዳኝነት ዉስጥ ስላልጠየቁ ታልፏል በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡
የአሁን አመልካች መጋቢት 4 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች በመያዣነት የተያዘዉን ቤት በተመለከተ የመንግስት እዳ ብር 37,080.40 እና ቤቱም ወጪ ለበር ብር 10,000 ለመከላከያ ብረት ብር 2,500 ለባለሙያ ብር 1,500 ያወጣነዉን ወጪ እንዲከፈለኝ ጠይቄ እያለሁ፣ ተጠሪዎችም ባቀረቡት መልስ ይህን እዳ እና ወጪዎችን ሳይክዱና ታምኖ እያለ፣ ፍ/ቤቱ ይህን የታመነዉን ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242 መሰረት ወዲያዉኑ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ወይም ከዋናዉ ፍርድ ጋር ሊወስንልኝ ሲገባዉ ዳኝነት አልተጠየቀበትም በማለት በማለፍ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ ይህ ገንዘብ ከወለድ ጋር ታስቦ እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የአሁን አመልካች ለባንክ የከፈሉትን እዳ እና ለቤቱ ያወጡትን ወጪዎች ተጠሪዎች የቤቱን ሰነዶች ሲያስረክቡ እንደሚከፍሉ እንደማይቃወሙ፣ ወጪዎችን በተመለከተ ግምቱ የተጋነነ ስለሆነ በነበረዉ የገበያ ዋጋ ተገምቶ ብንከፍል አንቃወምም ብለዉ እያለ በክስ የዳኝነት ክፍል ስላልተጠቀሰ ብቻ ዳኝነት ሳይሰጥበት ዉድቅ የመደረጉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት መስከረም 23 ቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2010 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ እንዲሆንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ባቀረቡት ክስ በብድር ዉል መነሻነት የያዙትን ቤት በተመለከተ ለባንክ የተከፈለ እዳ ብር 37,080.40 እና ለቤቱ ያጣሁት ወጪ 4,000 /አራት ሺህ/ እንደከፈሉ በክሱ ዝርዝር ዉስጥ የገለጹ ቢሆንም በዳኝነት ክፍል ሳይጠቅሱ መቅረታቸዉን መገንዘብ ተችሏል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች ይህን ክስ በተመለከተ ባቀረቡት መልስ ለባንክ ተከፍሏል የተባለዉን ገንዘብ የካዱት ነገር የለም እንዲሁም ቤቱ ላይ ለተሰሩት ስራዎች የወጣዉን ወጪ በተመለከተ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተገምቶ ቢከፍሉ የማይቃወሙ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን ተጠሪዎች ለባንክ የተከፈለዉን ገንዘብ እና ቤቱ ላይ የወጣዉን ወጪ በተመለከተ አምነዉ የተከራከሩ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህን የግራ ቀኞቸዉን ክርክር በሕግ አግባብ ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡

በመሰረቱ ከሳሽ በሚያቀርበዉ የክስ ማመልከቻ ላይ በተለይ ወይም በምትክ ወይም በተለዋዋጭ የሚጠይቀዉን ዳኝነት በግልጽ መጥቀስ እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.224 ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም ከሳሽ የሚጠይቀዉ ዳኝነት ጠቅላላ እንደሆነ የክሱን ጭብጥና የማስረጃዉን አካባቢ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ትክክለኛ መስሎ የታየዉን ፍርድ መስጠት እንደሚችል በዚህ ድንጋጌ ሥር ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልስ ወይም በማናቸዉም በሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ወይም በቃል ክርክር ወቅት የእምነት ቃሉን የሰጠ እንደሆነ፣ ሌላኛዉ ተከራካሪ ወገን በዚህ እምነት መሰረት ዉሳኔ እንዲሰጠዉ መጠየቅ እንደሚችል እና ፍ/ቤትም ሌላ በማስረጃ የሚረጋገጥ ነገር ቢኖርም እንኳን በታመነዉና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉሳኔ እንዲሰጥበት በተጠየቀዉ ጉዳይ ብቻ ፍርድ መስጠት እንደሚገባዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242 ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች በብድር ዉል ምክንያት የያዙትን ቤት በተመለከተ ለባንክ የከፈሉትን ገንዘብ እና ከቤቱ ጋር በተያያዘ ለተሰሩት ሥራዎች ያወጡትን ወጪዎች በክሳቸዉ ዝርዝር ዉስጥ ገልጸዋል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች የሚመልሱበት ሁኔታ መኖሩን እስከተገነዘበ ድረስ አመልካች ከቤቱ ጋር በተያያዘ አዉጥቻለሁ፣ ከፍያለሁ በማለት በክስ ማመልከቻ ላይ እስከጠየቁ ድረስ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ይህ ገንዘብ እንዲከፈላቸዉ በዳኝነት ክፍል ዉስጥ አልጠየቁም የሚል ከሆነ ስለጉዳይ በሕግ አግባብ ግልጽ እንዲያደርጉ ማድረግ የሚከለክለዉ ነገር አልነበረም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስና የቃል ክርክር አመልካች የጠየቀችዉን ይህን ገንዘብ የካዱት ነገር የለም፡፡ የአሁን ተጠሪዎች ከዚህ ቤት ጋር በተያያዘ ለባንክ የተከፈለዉን እዳ እና ለቤቱ የወጣዉን ወጪ አምነዉ እና ለመክፈልም ፈቃደኛ እንደሆኑ ገልጸዉ እስከተከራከሩ ድረስ፣ የሥር ፍ/ቤቶች ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የህግ ድንጋጌ በእምነት ቃላቸዉ አግባብ ዉሳኔ መስጠት ይገባቸዉ ነበር፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች እምነት መሰረት ይህን ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍሉ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ በክሳቸዉ የዳኝነት ክፍል ዉስጥ ይህ ገንዘብ እንዲከፈላቸዉ አልጠየቁም በሚል ምክንያት ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ መስጠቱ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ማረም ሲገባዉ ሳያርመዉ የሥር ዉሳኔ በማጽናት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.61912 በ3/2/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.185781 በ23/5/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የአሁን አመልካች በብድር ዉል ምክንያት የያዙትን ቤት በተመለከተ ለባንክ የከፈሉትን እና ለቤቱ ያወጡትን ወጪ በድምሩ ብር 41,080.40 /አርባ አንድ ሺህ ሰማንያ ከአርባ ሳንቲም/ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ የአሁን ተጠሪዎች ይህን ገንዘብ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡ ነገር ግን የአሁን አመልካች በዚህ ገንዘብ መጠን የዳኝነት ክፍያ ያልከፈሉ እንደሆነ ባለዉ የዳኝነት ክፍያ ታሪፍ ደንብ መሰረት ሊያከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በብድር ዉል ምክንያት የያዙትን ቤት ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ እና ተጠሪዎች ደግሞ በብድር ዉሉ መሰረት የተበደሩትን ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍሏቸዉ በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል አልተነካም፣ ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ.131832

ታህሳስ 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1.ዳኜ መላኩ
2. ተክሊት ይመሰል
3. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
4. ቀነዓ ቂጣታ
5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ መረሳ አማረ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1.ቁስ ሃይለ ገብረ } የቀረበ የለም
2. መቶ አለቃ ካልሃዩ ተስፋይ }

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የጎጆ መዉጫ ይዞታና ቤትን የሚመለከት ሲሆን ለችሎቱ ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.83091 በ19/09/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በተክዓ ቀበሌ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ የአሁን አመልካች የመቃወም አመልካች፣የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ የመቃወም ተጠሪዎች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበዉ ክስ መነሻነት የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የጎጆ መዉጫ ይዞታ ለአሁን 2ኛ ተጠሪ እንዲሆን የአሁን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ የተሰራዉን ቤት ቆርቆሮዉን እና እንጨቱን አፍርሰዉ አንስተዉ እንዲወስዱ በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን፣ የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ጉዳዩን በማየት በሰጠዉ ብይን አመልካች ያቀረቡት የመቃወሚያ ማመልከቻ የብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ/ ግምት ያለዉ የጎጆ መዉጫ ስለሆነ ኮሚቴዉ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በማለት ማመልከቻዉን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለእምባ ኣላጆ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ይህን የጎጆ መዉጫ ክርክር ለማየት ስልጣን አለዉ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 መልሶለታል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች የይግባኝ ማመልከቻ ለማይጨዉ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች አሁንም የሰበር አቤቱታ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ችሎቱ ይህ ጉዳይ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት አቤቱታዉን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አሁን የቀረበዉ አቤቱታ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ የብር 200000 ግምት ያለዉን ንብረት ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን ሳይኖረዉ የተሰጠዉን ዉሳኔ በተመለከተ የሥር የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር ፍ/ቤቶች ተገምተዉ ያልቀረበዉን ንብረት በመጀመሪያ ያየዉ ፍ/ቤት ስልጣን አለዉ በማለት የመወሰናቸዉ አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት ተጠሪዎች የየራሳቸዉን መልስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች ባቀረቡትም መልስ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ዉድቅ እንዲደረግ በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት ያቀረቡት የመቃወሚያ ማመልከቻ በአሁን ተጠሪዎች መካከል ሲካሄድ ቆይቶ የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል በማለት ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ይህን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻን ተቀብሎ የማየት እና የቀደመዉን ዉሳኔ መለወጥ የሚችለዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 ሥር እንደተመለከተዉ ራሱ ፍርዱን የሰጠዉ አካል ነዉ፡፡ በዚህ ጉዳይም የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ ለክርክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት የሆነዉን የጎጆ መዉጫ እና ቤት በተመለከተ ዉሳኔ የሰጠ አካል እስከሆነ ድረስ ይህን የሕግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ፣ አመልካች ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ተከትሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.360 /2/ መሰረት የቀደመዉን ዉሳኔ የማጽደቅ ወይም የማሻሻል ወይም የመለወጥ ወይም የመሰረዝ ስልጣን አለዉ፡፡ የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴዉ በዚህ አግባብ አስቀድሞ የሰጠዉን ዉሳኔ የሚያጸድቀዉ ወይም የሚያሻሽለዉ ወይም የሚለዉጠዉ ወይም የሚያሰርዘዉ የአሁን አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀበሎ ጉዳዩን ያየ እንደሆነ ብቻ ነዉ፡፡ ኮሚቴዉ አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ከጅምሩ ዉድቅ የሚያደርግ እንደሆነ አስቀድሞ የሰጠዉን ዉሳኔ በተመለከተ ምንም ሳይባል እንዳለ ስለሚሆን ከላይ የተመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎችን ዓላማ የሚቃረን ይሆናል፡፡ የቀበሌዉ መሬት ዳኝነት ኮሚቴ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻዉን ተቀብሎ ግራ ቀኞቸዉን ከአከራከራቸዉ በኋላ አስቀድሞ የሰጠዉን ዉሳኔ የሚያጸድቅበት ወይም የሚያሻሽልበት ወይም የሚለዉጥበት በሕግ በተመለከተዉ አግባብ ሲሆን፣ ይህን የሚያደርገዉ በስልጣን ወይም በሌላ ሕጋዊ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ኮሚቴዉ አመልካች ያቀረቡትን የመቃወሚያ ማመልከቻ ተቀብሎ አስቀድሞ የሰጠዉ ዉሳኔ ምን መሆን አለበት በሚለዉ ነጥብ ላይ ዉሳኔ ሊሰጥበት ይገባል እንጂ ከጅምሩ ማመልከቻዉን ለመቀበል ስልጣን የለኝም በማለት አስቀድሞ ስለሰጠዉ ዉሳኔ ምንም ሳይል መተዉ አግባብ አይደለም፡፡ የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን ሁኔታ በመገንዘብ የቀበሌዉን መሬት ዳኝነት ኮሚቴ አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ የማየት ስልጣን አለዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነበር፡፡ በመሆኑም የሥር የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን የወረዳዉ ዉሳኔ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የሥር የሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ በሕግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት ስለማይቻል የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉ ሳ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.83091 በ19/09/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ.130410

ታህሳስ 30 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡...1.ዳኜ መላኩ

2. ተክሊት ይመሰል

3. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-.....አቶ ሱፍያን አቡበከር ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡-.....1.አቶ ክፍሉጋሼ የቀረበ የለም

2. ወ/ሮ ዘዉዴ መኩሪያ

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለችሎቱ ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.233491 22/9/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በአደአ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች 1ኛ የመቃወም ተጠሪ እና የአሁን ተጠሪዎች የመቃወም አመልካቾች፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነዉ የቢሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት አጄንሲ 2ኛ የመቃወም ተጠሪ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች የቢሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት አጄንሲ ላይ ባቀረበዉ ክስ መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ክሳሽ እና ተከሳሽን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን 9936 ካ.ሜ የሆነዉን ቦታ ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲያስረክብ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህን ዉሳኔ ተከትሎ የመቃወም አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት ባቀረቡት አቤቱታ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ የ1ኛ የመቃወም ተጠሪ የአቶ ሱፊያን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቡበከር ሳይሆን የእኛ ነዉ፣ ይዞታዉ ከእጃችን ወጥቶ አያዉቅም፣ በዚህ ጉዳይ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.163687 በ11/2/2006 ዓ.ም ዉሳኔ የሰጠ በመሆኑ 1ኛ የመቃወም ተጠሪ በተሰረዘ ካርታ መክሰስ መብት የለዉም፣ ስለዚህ የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሻርልን በማለት ጠየቁል፡፡

በዚህ የመቃወም ማመልከቻ ላይ 1ኛ የመቃወም ተጠሪ አቶ ሱፊያን አቡበከር ባቀረበዉ መልስ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ በሕግ አግባብ የተሰጠኝ ነዉ፣ ካርታ አልተሰረዘም፣ ይዞታዉ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1996 ዓ.ም ግብር እየከፈልኩኝ ስጠቀምበት ነበር፣ የመቃወም አመልካቾች መብት ሳይኖራቸዉ ነዉ ይህን መሬት ወጥተዉ ያረሱት በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ የመቃወም ተጠሪ የብሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት አጄንሲ ባቀረበዉ መልስ ከዚህ በፊት የ1ኛ ተጠሪ ካርታ መሰረዙ ተረጋግጦ ከይዞታዉ መብት እንደሌለዉ ዉሳኔ የተሰጠ በመሆኑ የ1ኛ ተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የአደአ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ በተመለከተ ለ1ኛ የመቃወም ተጠሪ የተሰጠዉ ካርታ ያልተሰረዘ መሆኑን ማህደሩ ያረጋግጣል፣ የመቃወም አመልካቾች በይዞታዉ ላይ ባለመብት ቢሆኑም መሬታቸዉን ለሌላ ሰዉ አሳልፈዉ የሰጠዉን አካል ከሶ ከሚጠይቁ በስተቀር 1ኛ የመቃወም ተጠሪ በሕገ ወጥ መንገድ ይዟል የሚያስብል ስላልሆነ፣ ከዚህ በፊት የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚያፈርስ ምክንያት ስለሌለ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ.360/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሥር የመቃወም አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ከዚህ በፊት ይህ ችሎት በመ.ቁ.163687 በ11/2/2006 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ለ1ኛ ተጠሪ አቶ ሱፊያን አቡበከር ካርታ ቀሪ ሆኖ የተሰረዘ መሆኑን፣ ይዞታዉ በእጁ ሳይኖር ግብር መክፈሉ ብቻ ባለመብት እንደማያደርገዉ እና አቶ ሱፊያን በዚህ ይዞታ ላይ መብት የለዉም በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ዉሳኔ ሰጥቶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እያለ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ ድጋሚ አጣርተዉ ዉሳኔ መስጠታቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ3/5/2009 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ ብሾፍቱ ከተማ በሕግ አግባብ የተሰጠኝ ካርታም ተሰጥቶኝ እና ከ1983 ዓ.ም ስጠቀምበት የነበረ ሆኖ ሳለ፣ ለአመልካች የተሰጠ ካርታ ያልተሰረዘ መሆኑን ተረጋግጦ እያለ፣ በዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት ዉሳኔ ተሰጥቷል የተባለዉ እና አሁን የቀረበዉ ክርክር የተለያዩ ጭብጦችና ተከራካሪ ወገኖች በመሆኑ አስቀድሞ ዉሳኔ ተሰጥቷል የሚያስብል ነገር በሌለበት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት ዉሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነዉ በማለት ዉሳኔ የመስጠቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ባዘዘዉ መሰረት ተጠሪ በ5/7/2009 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ በዚህ ጉዳይ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ስህተት የሌለዉ በመሆኑ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ከዚህ ቀደም ይህን ይዞታ በተመለከተ የአሁን ተጠሪዎችን ጨምሮ በአራት ሰዎች ላይ ክስ አቅርበዉ ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.163687 በ11/2/2006 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ለአሁን አመልካች የተሰጠዉ ካርታ የተሰረዘ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት የቀረበ ማስረጃ እንደሚያረጋግጥ በማመልከት፣ ይዞታዉም በአመልካች እጅ ሳይገባ እስከ 2004 ዓ.ም ግብር መክፈሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለመብት እንደማያደርገዉ እና አመልካች በተሰረዘ ካርታ ይዞታዉን በተመለከተ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት ዉሳኔ የሰጠ መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የአሁን አመልካች ከዚህ ዉሳኔ በኋላ ባቀረበዉ አዲስ ክስ ካርታዉ እንዳልተሰረዘ እና የብሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ይህን ይዞታ እንዲያስረክበዉ ዳኝነት በመጠየቁ፣ ኤጀንሲዉ የአመልካች ክስ ተቀባይነት እንደሌለዉ በመግለጽ ቢከራከርም፣ የሥር ፍ/ቤት ለአመልካች የተሰጠ ካርታ እንዳልተሰረዘ እና ኤጀንሲዉ መሬቱን እንዲያስረክብ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ይህን ዉሳኔ በመቃወም የመቃወሚያ ማመልከቻ አቅርበዉ ቢከረከሩም፤ የሥር ወረዳ ፍ/ቤት እና ከፍተኛ ፍ/ቤት አስቀድመዉ ካርታዉ እንደተሰረዘ እና ለክርክር ምክንያት በሆነዉ ይዞታ ላይ ዉሳኔ ተሰጥቷል በማለት ያቀረበዉን መቃወሚያ በማለፍ ዉሳኔ መስጠታቸዉን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ሁኔታ በመገንዘብ የአሁን አመልካች ከዚህ ቀደም ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል መወሰኑን የሥር ዉሳኔ ያሳያል፡፡

በዚህ መሰረት ይህ ችሎት ጉዳዩን እንደመረመረዉ የአሁን አመልካች ከዚህ ቀደም የአሁን ተጠሪዎችን ጭምሮ በአራት ሰዎች ላይ ክስ አቅርበዉ ዉሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 /1/ መሰረት ድጋሚ አዲስ ክስ የሚያቀርብበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የአሁን አመልካች ካርታዉ እንደተሰረዘ እና በዚህ ካርታ ይዞታዉን ለመጠየቅ መብት እንደሌለዉ ዉሳኔ ተሰጥቶ እያለ ተከራካሪ ወገን በመቀየር የብሾፍቱ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት አጀንሲ ላይ ክስ ስላቀረበ ብቻ የክርክሩ ጭብጥና ተከራካሪ ወገን ስለሚለያይ የዚህን ድንጋጌ መስፈርት አያሟላም፣ ከዚህ ቀደም ዉሳኔ ተሰጥቷል የሚያስብል አይደለም በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች ያቀረበዉ ክስ ከዚህ ቀደም ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ስለሆነ አዲስ ክስ ለማቅረብ አይችልም፡፡

ሲጠቃለል የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች ያቀረበዉ ክስ ከዚህ በፊት ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በመሻር አመልካች ያቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ በሕግ አግባብ ነዉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስላልሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 233491 22/9/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስላልሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 137831

ህዳር 28 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ለተብርሃን ያይንሸት - የቀረበ የለም ከተባለ በኋላ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ የማነ በየነ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የክርክሩ ምክንያት የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ተጠሪ የነበሩ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ደግሞ አመልካች ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ የግል እና የጋራ ንብረቶች ናቸው ያሉዋቸውን የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን፣ የባንክ ገንዘብ እንዲሁም የኮንደሚኒየም ቤት ቁጠባ በተመለከተ አመልካች ተጠሪን ሳያገቡ የተመዘገቡ በመሆኑ የሥር አመልካች/የአሁን ተጠሪ/ የግል ንብረታቸው መሆኑን ገልጸው ቤቱም ያልደረሳቸው በመሆኑ መካፈል አይችሉም በማለት ውሳኔ እንዲሰጥበት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች /የሥር ተጠሪ/ በሰጡት መልስ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን በተመለከተ የግልና የጋራ ንብረቶች ናቸው ያሉዋቸውን በዝርዝር በማቅረብ እነዚህ ንብረቶች እንዲሁም በወጋገን ባንክ ያለው ገንዘብ እኩል እንዲካፈል፣ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ አመልካች /የአሁን ተጠሪ/ በልጁ ስም በ40/60 የኮንደሚኒየም ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቆጠበውን ገንዘብ ሊካፈል ይገባል፣ ከ1997 ዓ/ም ጀምሮ በአመልካች ስም የተጠራቀመውን ገንዘብ ልንካፈል ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተለያዩ ማስረጃዎችን እንዲቀርቡለት ካደረገ በኃላ የግልና የጋራ ንብረቶች ናቸው ባላቸው የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች፣ ወጋገን ባንክ ያለው ገንዘብ ላይ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የኮንደሚኒየም ቤት በተመለከተ አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ የፈጸሙት ጳጉሜ 2 ቀን 2002 ዓ/ም ሲሆን አመልካች /የአሁን ተጠሪ/ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገንዘብ መቆጠብ የጀመሩት እ.ኤ.አ በ20/6/2013 ነው፡፡ ይህም ጊዜ ሲታይ አመልካች ለኮንደሚኒየም ቤት የቆጠቡት ገንዘብ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ እንዳሉ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦሌ ቡልቡላ ቅርንጫፍ ከቆጠቡት ገንዘብ ከፊሉን ብር 7,227.23 /ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ብር ከሃያ ሶስት ሳንቲም/ ለተጠሪ ይክፈሉ፡፡ የ40/60 ኮንደሚኒየም ቤት በተመለከተ የአሁን አመልካች /የሥር ተጠሪ/ በማስረጃ ስላላስረዱ ታልፏል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪ የግል ንብረቶች ናቸው ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ፣ ከወጋገን ባንክ የአሁን ተጠሪ ጋብቻ ከመፍረሱ በፊት ያወጡትን 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ሳይወስን ያለፈው ያለአግባብ ነው፣ በልጅ ቀለብ ውሳኔ ላይ እንዲሁም የኮንደሚኒየም ቤት ምዝገባ የተደረገውና ቁጠባ የተጀመረው በጋብቻ ውስጥ በመሆኑና የኮንደሚኒየም ቤቱ ከጋብቻ ፍቺ ውሳኔ በኃላ የደረሰ ቢሆንም የንብረት ክፍፍል ጉዳይ በክርክር ላይ እያለ የደረሰ በመሆኑ ቤቱን በጋራ መካፈል ሲገባን የተቆጠበውን ገንዘብ ድርሻ የአሁን ተጠሪ ለአመልካች ይክፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ያለአግባብ ነው በማለት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የቤት ቁሳቁሶች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት፣ ከወጋገን ባንክ የአሁን ተጠሪ ያወጡትን ገንዘብ በተመለከተ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ባለማስረዳታቸው ግማሽ ብር 50,000 /አምሳ ሺህ ብር/ ለአሁን አመልካች እንዲከፍሉ፣ የልጅ ቀለብ ከአንድ ሺህ ብር ወደ ሁለት ሺህ ብር ከፍ በማድረግ እንዲሁም የኮንደሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ምዝገባ የተደረገው ግራ ቀኙ ጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑን፣ ለቤቱ ገንዘብ የተቆጠበውም በትዳር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውስጥ እያሉ በመሆኑ የአሁን ተጠሪ ክፍቺ ውሳኔ በኃላ ለኮንደሚኒየም ቤቱ የከፈሉትን ገንዘብ ግማሽ አመልካች መልሰው /ከፍለው/ ቤቱ የጋራ ሲሆን ይገባል ሲል የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ ከውሳኔዎቹ መካከል በባንክ ገንዘብ እና በኮንደሚኒየም ቤት ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የአሁን ተጠሪ ከባንክ ያወጡትን ገንዘብ ግማሽ ለአሁን አመልካች እንዲከፍሉ የተባለውን የውሳኔ ክፍል አጽንቶ የኮንደሚኒየም ቤቱን በተመለከተ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልስ ሲሰጡ የተጠራቀመው ገንዘብ ድርሻ እንዲሰጠኝ በማለት የጠየቁ በመሆናቸው ከጠየቁት ዳኝነት ውጪ ቤቱን እንዲካፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በኮንደሚኒየም ቤት ላይ የሰጠው ውሳኔ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተፈጽመውብኛል ያሉዋቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን በጠበቃቸው በኩል አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ የኮንደሚኒየም ቤት ላይ ግልጽ የሆነ ክርክር አድርገው እያለ የሥር ፍርድ ቤት ያልተጠየቀ ዳኝነት የማለቱ እና ኮንደሚኒየም ቤቱ ምዝገባ ወቅት ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ የነበሩና ሲቆጥቡ ቆይተው የግራ ቀኙ ጋብቻ ፍቺ ተወስኖ የንብረት ክፍፍል ሳይደረግ የወጣ የኮንደሚኒየም እጣ በተመለከተ የኮንደሚኒየም ቤቱ የተጠሪ የመባሉ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል ግንቦት 15 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን የአመልካች ጠበቃም ሰኔ 5 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን አመልካች የኮንደሚኒየም ቤት ድርሻ እንዲወሰንላቸው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላነሱትን የከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰነው ባልተጠየቀ ዳኝነት ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሻረውን በተመለከተ የአሁን ተጠሪ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር በራሳቸው ይህንን አንስተው ተከራክረውበታል ወይስ ፍርድ ቤቱ በራሱ አንስቶ ነው ውሳኔ የሰጠው ? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ የአሁን ተጠሪ ኮንደሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ከጋብቻ በፊት መመዝገባቸውን፣ ቤቱም ያልደረሳቸው መሆኑን ገልጸው በንብረት ክፍፍል ግን ሊካተት የማይችል የግል ንብረት ነው በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው የዳኝነት ጥያቄያቸው ላይ አንስተዋል፡፡ የአሀኑ አመልካች መልሳቸውን በጽሁፍ የመስጠት መብታቸው በሥር ፍርድ ቤት የታለፈባቸው ቢሆንም በቃል ክርክር ጊዜ የኮንደሚኒየም ቤቱ በጋብቻ ውስጥ በአሁን ተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑንና የቁጠባ ገንዘብ መከፈል የጀመረውም በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑን ገልጸው የተጠራቀመው ገንዘብ ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ለኮንደሚኒየም ቤት ምዝገባ የተመዘገቡት ግራ ቀኙ ከተጋቡ በኃላ በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑን፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦሌ ቡልቡላ ቅርንጫፍ በአሁን ተጠሪ ስም በተከፈተው ሂሳብ ቁጥር መቆጠብ የተጀመረውም ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑን ገልጾ ከተጠራቀመው ብር 14,454.46 /አስራ አራት ሺህ አራት መቶ አምሳ አራት ብር ከአርባ ስድስት ሳንቲም/ ውስጥ ለአሁን አመልካች ብር 7,227.23 /ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ብር ከሃያ ሶስት ሳንቲም/ የአሁን ተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በይግባኝ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሄዱበትም የኮንደሚኒየም ቤት ምዝገባ የተደረገው እና ገንዘብ መቆጠብ የተጀመረው በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑን ገልጸው የኮንደሚኒየም ቤት ለአሁን ተጠሪ የደረሳቸው ምንም እንኳን የፍቺው ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ቢሆንም እጣ የወጣው በንብረት ክርክር ላይ እያሉ በመሆኑ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባል በማለት ነው፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ለውሳኔው መሠረት ያደረገው ይህንን ነጥብ እንደሆነ የውሳኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ለማሻሻል ምክንያት ያደረገው አመልካች የኮንደሚኒየም ቤቱን ሊካፈል ይገባል የሚል ዳኝነት በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስላላነሱ የመከራከሪያ ነጥብ ሆኖ ውሳኔ ያላገኘውን ፍሬ ነገር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ለዚህ ሰበር ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ እንዲሁም በመልስ መልሳቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተጠሪው አመልካች የኮንደኒየም ቤት ያካፍለኝ ብላ በሥር ፍርድ ቤት አልጠየቀችም የሚል በይግባኝ ቅሬታው አላቀረበም፣ የይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዚህ ዓይነት ቅሬታ በጽሁፍም በቃልም ያከራከረው ነገር የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ በተጠሪ /በሥር ይግባኝ ባይ/ በኩል በይግባኝ ቅሬታ ላይ ያልተነሳውን አንስቶ መወሰኑ የሥነ ሥርዓት ህጉን ድንጋጌ የተከተለ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይህን የቅሬታ ነጥብ እውነታ ለማረጋገጥ ይህ ችሎት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍ/ይ/መ/ቁ 130707 የሆነውን አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ /የሥር ይግባኝ ባይ / ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ ከመልስ ሰጪዋ /ከአሁን ተጠሪ / ጋር ከፍቺ በኃላ በተደረገ የንብረት ክፍፍል ከጋብቻ በፊት በይግባኝ ባይ በተደረገ የኮንደሚኒየም ቤት ምዝገባ፣ ከጋብቻ መፍረስ በኃላ በወጣልኝ እጣ በተፈጸመ ክፍያ ምክንያት የተገኘን የኮንደሚኒየም ቤት እንዲሁም ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ከአስተዳደር አካል በተሰጠው ትዕዛዝ ምክንያት መልሶ ምዝገባ መደረግን ብቻ ምክንያት በማድረግ የኮንደሚኒየም ቤት የጋራ ነው ተብሎ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ መወሰኑ አግባብ ስላልሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዳሩ ፀንቶ በነበረበት ወቅት ከተቆጠበው ገንዘብ ላይ ድርሻዋን እንድትወስድ በማለት የወሰነውን የውሳኔ ክፍል በማጽደቅ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አሻሽሎ እንዲወስንልኝ እጠይቃለሁ የሚል እንደሆነ የክርክሩ ሂደት እንዲሁም የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በግልጽ ያሳያል፡፡

የአሁን ተጠሪ በጠቅላይ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር በኮንደሚኒየም ቤቱ ላይ ብቸኛ ባለመብት ያደርገኛል በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያው ነጥብ በ1997 ዓ/ም መመዝገባቸውን ሲሆን ሁለተኛው ሰኔ 4 ቀን 2006 ዓ/ም ጋብቻ ፈርሶ ሚያዚያ ወር 2007 ዓ/ም እጣ ወጥቶላቸው ውል መዋዋላቸውን ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ የተመለከተውን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የነበረውን የአሁን ተጠሪን ክርክር ስንመለከት ክርክር ያስነሳውን የኮንደሚኒየም ቤት የአሁን አመልካች ይገባኛል ወይም ድርሻ ይሰጠኝ የሚል ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያላነሱትን የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል የሚል ቅሬታ በይግባኝ ማመልከቻም ሆነ በቃል ክርክር ወቅት የተነሳ ነገር አልነበረም፡፡ የሥር ይግባኝ ባይ /የአሁን ተጠሪ/ በይግባኛቸው ያላነሱትን አዲስ ነገር የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በራሱ አንስቶ መወሰን ይችላል ወይ? የሚለውን አግባብነት ካለው የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌ አንጻር መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በተለይ ካልፈቀደ በቀር ይግባኝ ባዩ በይግባኝ ማመልከቻው ላይ ዘርዝሮ ያልገለጸውን አዲስ ነገር በማንሳት ወይም መሠረት በማድረግ ለመከራከር አይችልም ሲል የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 328 /2/ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በማመልከቻው ተዘርዝሮ ከተገለጸው ወይም ክርክር ከተነሳበት ውጭ በሆነ ነገር ፍርድ መስጠት እንደማይችል የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 328 /3/ በአስገዳጅነት ደንግጓል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ከላይ እንደተገለጸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በይግባኝ ማመልከቻ ላይ ዘርዝረው ያልገለጹትን መሠረት በማድረግ አመልካች የኮንደሚኒየም ቤት ይገባኛል ሲሉ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልጠየቁትን ዳኝነት መሠረት በማድረግ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም ሲል የደረሰው ድምዳሜ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1.የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.130707 ታኅሳስ 12 ቀን 2009 ዓ/ም ግራ ቀኙን የሚያከራክረውን የኮንደሚኒየም ቤት በተመለከተ የሠጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2.የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ሌላው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 168169 ሚያዚያ 26 ቀን 2008 ዓ/ም ክርክር የተነሳበትን ቤት በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

4.በቱሉ ዲምቱ ቁጥር 2 ሳይት ብሎክ 362 የሚገኘውና ቁጥሩ 36216 የሆነው በተጠሪ ስም የተመዘገበው የኮንደሚኒም ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ ስለሆነም ቤቱን ግራ ቀኙ በዓይነት እኩል እንዲካፈሉ፣ በዓይነት እኩል ለመካፈል የማይቻል ከሆነና ግራ ቀኙ ከተስማሙ የቤቱን ዋጋ አንደኛው ወገን የሌላኛውን ወገን ድርሻ በገንዘብ በመክፈል ቤቱን እንዲያስቀር፣ በዚህ ካልተስማሙ ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ ብለናል፡፡

5.የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

6.የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

7.መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ.131498

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1.ዳኜ መላኩ
2. ረታ ቶለሳ
3. ተሸለት ይመሰል
4. ቀነዓ ቂጣታ
5. አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- አቶ መሳይ ቦጋለ - ተወካይ ወ/ሮ አይናለም በቀለ ቀርበዋል፡፡
ተጠሪ፡- ወ/ሮ አይናለም አለሙ - ጠበቃ ፋሲል ይነሱ ቀርበዋል፡፡
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የብድር ዉልን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.176598 በ14/11/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁን አመልካች ተከሳሽ ሆኖ ተከራክሯል፡፡ ከሳሽ ባቀረበችዉ ክስ በከሳሽ እና ተከሳሽ መካከል በ18/1/2003 ዓ.ም በተደረገ የገንዘብ ብድር ዉል ተከሳሽ ብር 400,000 /አራት መቶ ሺህ/ ከከሳሽ ተበድረዉ በዉሉ መሰረት ስላልከፈለ ይህን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍለኝ በማለት በተፋጠነ ሥነሥርዓት ክስ አቅርቧል፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ ተከሳሽ ቀርበዉ የመከላከያ መልስ እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት ማመልከቻ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ሳይቀበለዉ አልፎታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ በብድር ብር 400,000 /አራት መቶ ሺህ/ ከከሳሽ የወሰደ መሆኑን የቀረበዉ የገንዘብ ብድር ዉል ሰነድ የሚያስረዳ በመሆኑ ተከሳሽ በዉሉ መሰረት የመፈጸም ግዴታ ያለበት ስለሆነ ከሳሽ ደግሞ በዉሉ መሰረት እንዲፈጸምላቸዉ የመጠየቅ መብት ስላላቸዉ ተከሳሽ ይህን በብድር የወሰደዉን ገንዘብ ለከሳሽ እንዲከፍል ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ሐምሌ 9 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- የአሁን ተጠሪ ላቀረቡት ክስ አመልካች ማስፈቀጃ በማቅረብ ወደ ክርክር እንድገባ ያቀረብኳቸዉ ምክንያቶች የብድር ዉሉ በይርጋ የሚታገድ ነዉ፣ ዉሉ ፈራሽ ነዉ፣ ብድሩ ሕገ ወጥ የአራጣ ብድር ዉል ስለሆነ ፈራሽ ነዉ፣ የብድር ዉሉ የኮንዶሚኒያም ቤት ሽያጭ ዉል ተቀጽላ እና ጥገኛ /መተማመኛ/ ዉል ነዉ፣ አመልካች በ1997 ዓ.ም የደረሰኝን ባለ ሁለት ክፍል መኝታ ያለዉ የኮንዶሚኒየም ቤት ለተጠሪ በመሸጥ ዉክልና ሰጥቼ ለዚህ መተማመኛ እንዲሆን የብድር ዉል በማስመሰል የተፈረመ እንደሆነ በመግለጽ ያቀረብኩት ሲሆን የሥር ፍ/ቤት ማስፈቀጃዉን ሳይቀበል እና መልስ እና ማስረጃዬን ሳይሰማኝ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በመመርመር፣በዚህ ጉዳይ አመልካች በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት ለቀረበበት ክስ መከላከያ ለማቅረብ ያቀረበዉ ማስፈቀጃ በሥር ፍ/ቤት ዉድቅ የመደረጉን አግባብነት፣ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘዉ መሰረት መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--አመልካች ለቀረበባቸዉ ክስ ሊያስተባብልላቸዉ የሚችል ማስፈቀጃ በሥር ፍ/ቤት ባላቀረቡበት በሀሰት አቅርቤያለሁ በማለት ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ማመልከቻ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማጽናት በቂ ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ ባቀረቡት ክስ አመልካች በ18/1/2003 ዓ.ም በተደረገ የገንዘብ ብድር ዉል መሰረት ብር 400,000 ተበድረዉ ስላልከፈሉ ገንዘቡን ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ በተፈጠነ ሥነ ሥርዓት ክስ ማቅረባቸዉ ተመልክተናል፡፡ የአሁን አመልካች በበኩሉ ለዚህ ክስ የመከላከያ መልስ ማቅረብ እንዲችል እንዲፈቀድለት የማስፈቀጃ ማመልከቻ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱን የሥር ዉሳኔ ያሳያል፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበዉን የማስፈቀጃ ማመልከቻ ዉድቅ በማድረግ አመልካች በቀረበዉ ክስ መሰረት በብድር ዉሉ መሰረት የወሰደዉን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል የወሰነ መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ከዚህ አንጻር ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት መሰረት የቀረበ ነዉ በሚል ምክንያት የአመልካች ማስፈቀጃ ተቀባይነት ማጣቱ የሕጉን ዓላማ ያገናዘበ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የፍትሐ ብሔር ክርክር የሚመራበት ሂደት በፍትሐ ብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ላይ ተመልክቷል፡፡ የሥነሥርዓት ሕጉ የክርክሮችን ባህር ከግንዛቤ በማስገባት የክስና የመልስ አቀራረብ ሂደቱን በሚያመላክት የተቀረጸ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት የፍትሓ ብሔር ሥነሥርዓት ሕግ በአምስተኛ መጽሐፍ ልዩ ስነሥርዓት ምዕራፍ 1 በአጭር ሁኔታ በሚወሰኑ ክርክሮች ላይ ስለሚፈጸም ሥነ ሥርዓት ከአንቀጽ 284--292 ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚህ ሥርዓት የሚቀርብ ክርክር የሕግ አዉጭዉን ሃሳብ የሚያሳካ ነዉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ነገር ግን የእነዚህን ድንጋጌዎች መስፈርት የማያሟሉ ክሶች በዚህ ሥርዓት የሚቀርቡ ከሆነ እና በተከሳሽ በኩል የሚቀርበዉን የመከራከርና የመከላከል መብቱን የሚያሳጡ ከሆነ በሕገ መንግስቱ የተመለከተዉን የመሰማት መብት የሚነፍግ ይሆናል፡፡ በአጭር ሁኔታ የሚወሰኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሮች መመራት ያለባቸዉ በዚህ ምዕራፍ በተደነገገዉ አግባብ ሊሆን ይገባል። ስለሆነም በአጭር ሁኔታ የሚወሰኑ ክርክሮች ወይም በተፋጠነ ሥነሥርዓት የሚቀርብ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.284 የተመለከተዉን ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟላ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነዉ። በዚህ ድንጋጌ ሥር እንደተመለከተዉ ከሳሽ ከተከሳሽ ላይ የሚጠይቀዉ ሂሳብ ወይም ጥሬ ገንዘብ ከነወለዱ ወይም ያለወለድ ወይም ልኩ ተወስኖ የታወቀ ሲሆን ክሱም የተመሰረተዉ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ምክንያቶች ላይ በሆነ ጊዜ ፡- /ሀ/ በዉል መሰረት በግልጽ በተደረገ ዉል ወይም በሐዋላ ወረቀት ወይም በገንዘብ አለብኝ ሰነድ ወይም በቼክ ወይም ተራ የሆነ የባለዕዳነትን በሚገልጽ ዉል በማለት ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ አግባብ የሚቀርብ ክስ የተፋጠነ ሥነሥርዓት የሚል አርዕስት ተሰጥቶና በቃለ መሓላ ተደግፎ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል። የዚህን ድንጋጌ መስፈርት የሚያሟላ ክስ ሊቀርብ የሚገባዉ በዚህ በአጭር ሁኔታ በሚወሰኑ ክርክሮች ወይም በተፋጠነ ሥነሥርዓት እንደሆነ የሚያከራክር አይሆንም።

በዚህ ድንጋጌ አግባብ የሚቀርብ ክስ ደግሞ የተከሳሽ የመከራከርና የመከላከል መብት ሙሉ ለሙሉ ለመንፈግ ታስቦ የተቀረጸ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.285 ይዘትና ዓላማ እንደሚያመለክተዉ ተከሳሽ ቀርቦ መከላከያ እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት ለፍ/ቤት ማመልከት እንደሚችል ነዉ። በዚህ መልክ የመከላከያ መልስ እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት ማመልከቻ ያላቀረበ እንደሆነ ግን ከሳሽ የጠየቀዉን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል እንደሚወሰንበት ያስገነዝባል። ተከሳሽ ቀርቦ እንዲከላከል እንዲፈቀድለት የሚያመለክተዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.286 ሥር በተመለከተዉ አግባብ ሊሆን እንደሚገባዉ ነዉ። ተከሳሽ ቀርቦ ለመከላከል እንዲፈቀድለት የሚያቀርበዉ ማመልከቻ በቃለ መሓላ ተደግፎ መቅረብ እንዳለበት ነዉ። ፍ/ቤቱ የቀረበዉን መሓላ ቃሉን ተቀብሎ ሊመረምር እንደሚችልና የቀረበዉ የመሐላ ቃልና ማመልከቻዉ ለከሳሽ እንዲደርሰዉ ማድረግ እንደሚገባዉ ይደነግጋል። ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ለመከላከል ማስፈቀጃ ማመልከቻ እና መሐላ ቃል የተቀበለዉ እንደሆነ ተከሳሽ ሙሉ ክርክሩን እንዲያቀርብ የሚደረግ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ማስፈቀጃ ያልተቀበለ እንደሆነ ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.287 መሰረት ወዲያዉኑ ለከሳሽ ፍርድ መስጠት እንደሚገባዉ ማየት ይቻላል። ይህ የተፋጠነ ሥነሥርዓት የክርክር አመራር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰዎችን የመከላከል የመሰማት የመደመጥ ሕገ መንግስታዊ መብትን በሚደፈጥጥ መልኩ መተርጎም እና ሥራ ላይ መዋል እንደማይገባዉ የሚያከራክር አይደለም፡፡
በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር የብድር ዉሉ የተደረገዉ በማስመሰል ነዉ፣ በመካከላችን የኮንዶሚኒያም ቤት ሽያጭ ዉል በሕግ በተከለከለዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ በመደረጉ ለተጠሪ መተማመኛ እንዲሆናቸዉ ይህን የብድር ዉል ፈረምኩኝ እንጂ የተበደርኩት ገንዘብ የለም የሚል ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ለተጠሪ የኮንዶሚኒያም ቤት በመሸጥ ገንዘብ ከመቀበሌ ዉጭ በዚህ የብድር ዉል ምንም ዓይነት ገንዘብ አልተቀበልኩም በማለት በመከራከር ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን አመልካች እና ተጠሪ መካከል የኮንዶሚኒያም ቤት ሽያጭ ዉል ተደርጓል ወይስ አልተደረገም? ይህ የብድር ዉል ከኮንዶሚኒያም ቤት ሽያጭ ዉል ጋር ግንኙነት አለዉ ወይስ የለዉም? ሁለት ዉሎች አሉ ወይስ የሉም? የዉሎቹ ቁርኝት ወይም ግንኙነት ምንድን ነዉ? የሚሉት ነጥቦች ከግራ ቀኞቸዉ በሚቀርበዉ ክርክርና ማስረጃ መመርመር የሚገባቸዉ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የመከላከያ ክርክሩን እንዲያቀርብ ሊፈቅዱለት የሚገባቸዉ የሚያመለክት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ መሰረት አመልካች የመከላከያ መልስ እንዲያቀርብ በመፍቀድ ሙሉ የመከላከያ ክርክሩን እንዲያቀርብ በማድረግ ተገቢዉን ማጣሪያ በማድረግ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ አመልካች ያቀረበዉን የመከላከያ ማስፈቀጃ ማመልከቻ ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.234216 በ28/6/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.176598 በ14/11/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ መደበኛ የክርክር አመራር ሰርዓት ተከትሎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች የመከላከያ መልስ እና ክርክሩን እንዲያቀርብ በማድረግ፣ በሕጉ አግባብ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 /1/ መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. ነሐሴ 11 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 135590

ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ፋንታሁን ተፈሪ - ጠበቃ ብርሃኑ ክፍያለው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አበባ ገ/ማርያም - ጠበቆች ጐሣዬ ጉርሙና አለማየሁ ለገሠ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከኪዚያዊ እግድ ትዕዛዝ ጋር የተያያዘ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡

በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን እየተከራከሩ ሲሆን ለአሁኑ አቤቱታ መነሻ የሆነውን የእግድ ይነሳልኝ ጥያቄ የቀረበው በአሁኑ አመልካች ጠያቂነት ነው፡፡ ዋናው ክርክር የጋብቻ ውጤት የሆነውን ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ሁኖ ግራ ቀኙ አሉን የሚሏቸውን ንብረቶችን አይነታቸውንና ብዛታቸውን ዘርዝረው የክፍፍል ጥያቄውን አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በግራ ቀኙ የንብረት ክፍፍል ላይ ግራ ቀኙ በሕጉ አግባብ እንዲከራከሩ ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የግራ ቀኙን የጋራና የግል ንብረት ስለመሆናቸው ግራ ቀኙ የተማመኑባቸውን ንብረቶች በመለየት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 በሚደነግገው አግባብ በእምነታቸው መሰረት ከፊል ዳኝነት ሰጥቷል፡፡ ግራ ቀኙ በተካካዱባቸው ሌሎች ንብረቶች ላይ ግን ክርክሩ እንዲቀጥል አድርጓል፡፡ በግራ ቀኙ እምነት መሰረት ከፊል ፍርድ ያረፈባቸው ንብረቶችም አንድ G+1 የሆነ መኖሪያ ቤት፣ አንድ ፒካፕ መኪናና አልጋ ሲሆኑ እነዚህ ንብረቶች በሕጉ አግባብ እንዲከፋፈሉም ተብሎ ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሰረት G+1 የሆነ መኖሪያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት በሐራጅ የተሸጠ ሲሆን የአሁኗ ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ጥር 09 ቀን 2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በሌሎች ንብረቶች ላይ በግራ ቀኙ መካከል የሚካሄደው ክርክር ውጤት ለተጠሪ የሚያስገኝላቸው ጥቅምና መብት ያለ መሆኑን ጠቅሰው የአመልካች ድርሻ የሆነው የቤቱ ሽያጭ ገንዘብ ለአመልካች ሳይከፈል ተከብሮ እንዲቆይላቸው ዳኝነት ጠይቀው የአሁኑ አመልካችም ድርሻቸው ሊታገድ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል G+1 የሆነ መኖሪያ ቤት ከተሸጠበት ገንዘብ ውስጥ ለአመልካች የሚደርሳቸው ገንዘብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154 መሰረት ተከብሮ እንዲቆይ የሚደረግበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ በመሻር ገንዘቡ ለጊዜው ተከብሮ እንዲቆይ በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ፍርድ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- G+1 የሆነ መኖሪያ ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሃብት ስለመሆኑ ግራ ቀኙ ተማምነው በሕጉ አግባብ እንዲሸጥ ከተደረገ በኃላ የአመልካች ድርሻ ታግዶ እንዲቆይ የሚደረግበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ትዕዛዝ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ መሰረታዊ ይዘቱ፡- ግራ ቀኙ የጋራ ስለመሆኑ ተማምነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሀራጅ ከተሸጠው ቤት ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ የአመልካች ድርሻ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር የሚል ሆኖ አገኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ የጋብቻ ውጤት በሆነው ንብረት ላይ ክርክር ሲያደርጉ አከራካሪው እግድ የተሰጠበት ገንዘብ የተገኘው የግራ ቀኙ መሆኑ አካራካሪ ያልሆነው ቤት በሐራጅ ተሸጦ መሆኑን፣ ግራ ቀኙ በሌሎች ንብረቶች ላይ ክርክር ሲያደርጉ ቆይተው የሥር ፍርድ ቤት በ5/5/2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውሳኔ በመስጠት መዝገቡን የዘጋው መሆኑን፣ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች ድርሻ የሆነው ገንዘብ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በማለት ዳኝነት የሰጠውም ተጠሪ ከአመልካች የሚፈልጉት ገንዘብ ካለ ለአፈጻጸም እንዲያመቻቸው በሚል ሆኖ እግዱ ተግባራዊ የሚሆነው ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት የገንዘብ ጥያቄ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ መሆኑን በመ/ቁጥር 17440 መጋቢት 01 ቀን 2008 ዓ./ም የሰጠው ውሳኔ የተፈፃሚነት ክፍል በግልጽ የሚያሳይ መሆኑን፣ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች በተጠሪ መካከል የነበረውን የገንዘብ ክርክር ተመልክቶ እልባት መስጠቱን በመ/ቁጥር 198855 ጥር 05 ቀን 2009 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ እንደሚያሳይ አመልካች ገልፀው ለአቀረቡት የሠበር ክርክር በተጠሪ የቀረበ ግልጽ ማስተባበያ የሌለ መሆኑን ተጠሪ ለዚህ ችሎት የሰጡት የመልስ ማመልከቻ የሚያሳይ መሆኑን፣ የሥር ፍርድ ቤት በገንዘብ ክርክሩ ላይ እልባት የሰጠ ከመሆኑም በላይ በዚህ ውሳኔ በባንኮቹ ውስጥ ይገኛል ተብሎ ከተረጋገጠውና ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ ከተገለጸው ከብር 303,401.06(ሶስት መቶ ሶስት ሺህ አራት መቶ አንድ ብር ከዜሮ ስድስት ሳንቲም) ውጪ ተጠሪ ከአመልካች የሚፈልጉት ገንዘብ ስለመኖሩ የማያሳይ መሆኑን፣ ተጠሪም ከአመልካች የሚፈልጉት ገንዘብ በባንኮች ውስጥ ይገኛል ከተባለው ውጪ ስለመሆኑ በሰበር አቤቱታቸው ካለመግለጻቸውም በተጨማሪ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው የገንዘብ ክርክር ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸውና በሕጉ አግባብ ለበላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ መሆኑን ጠቅሰው ያቀረቡት ክርክር የሌለ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ዕግድ የሚሰጠው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ንብረት የሚጠፋ፣ የሚበላሽ፤ ተከሳሹ ለሌላ ሰው አሳልፎ ለመስጠት፣ ለመሸጥ ወይም በሌላ ዘንድ በተሰጠ ውሳኔ ንብረቱን ያለአግባብ አዛውሮ ለመስጠት ወይም ለመሸጥ ያቀደ፣ መሆኑ ወይም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የባለመብቱ ጥቅም ለመጉዳት ለሌላ ሰው አሳልፎ ለመስጠት የሚደረግ እንቅስቃሴ መኖሩን ፍርድ ቤቱ ከተገነዘበ አስፈላጊውን ትዕዛዝ የሚሰጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 154 (1) መረዳት ይቻላል። የድንጋጌው መሰረታዊ ዓላማም ዳኝነት እንዲሰጥለት የጠየቀ ወገን በፍርዱ ሂደት ረቺነቱ ቢረጋገጥለት የተሰጠውን ፍርድ ለማስፈፀም ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርለት ነው ተብሎ ይታሰባል። ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ ከአመልካች ላይ የሚፈልጉት ገንዘብ ክርክር ተደርጎ እልባት ያገኘ ሲሆን የተጠሪ መብት ያለበት ስለመሆኑ የተረጋገጠው ጥሬ ገንዘብም በባንኮች ያለ መሆኑን በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 198855 በ05/05/2009 ዓ/ም የተሰጠው የውሳኔ ይዘት ያሳያል። አከራካሪውን እግድ የሰጠው ፍርድ ቤት እግዱ ተግባራዊ እንዲሆን ትእዛዝ የሰጠውም ይኼው የገንዘብ ክርክር በስር ፍርድ ቤት ታይቶ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል።

በመሆኑም የእግዱ ትዕዛዝ በባህርይው ጊዚያዊ ከመሆኑም በላይ እግዱ እንዲቆይ ምክንያት የሆነው ክርክርም እልባት ያገኘ በመሆኑ G+1 የሆነ መኖሪያ ቤት ተሸጦ የተገኘው የአመልካች ድርሻ ገንዘብ ተከብሮ የሚቆይበት ሕጋዊ ምክንያት ቀሪ የሆነ መሆኑን አሁን ካለው የግራ ቀኙ የክርክር ሂደትና ደረጃ ተገንዝበናል። ሲጠቃለልም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች እግዱን የሰጡበት አግባብ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154 መሰረታዊ አላማ የሚነቀፍበት አግባብ ያልነበረ ቢሆንም አሁን ክርክሩ ከደረሰበት ደረጃና ከእግዱ ባህርይ አንጻር ሲታይ እግዱ የሚቆይበት አግባብ የሌለ በመሆኑ በተለወጠ ምክንያት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ማረም ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም ተከታዩን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 174440 መጋቢት 01 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 126988 ጥቅምት 02 ቀን 2009 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል።
2. G+1 የሆነ መኖሪያ ቤት ተሸጦ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ የአመልካች ድርሻ ታግዶ የሚቆይበት ምክንያት የለም በማለት ወስነናል። ይፃፍ። ሆኖም ተጠሪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ በሠጠው ውሣኔ በስርዓቱ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያቀርቡት ቅሬታ ካለ የእግድ ጥያቄውን ከማቅረቡ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡

3. የዚህ ችሎት ክርክር ያስከተለው ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር---136901

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1ኛ. ሕጻን ቤተልሄም ሰለሞን ሞግዚት ወ/ሮ አዜብ እንግዳ

2ኛ. ሕጻን ቃለአብ ሰለሞን ሞግዚት አዜብ እንግዳ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ጌታቸዉ ገ/መስቀል

2ኛ. ወ/ሮ ንግስት ሃይሉ } ጠበቃ ሀብታም ስብሀቱ ቀረቡ

3ኛ. ወ/ሮ ትርሐስ ሃይሉ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

አመልካቾች በትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በዕርቅ ጉዳዩን ለመጨረስ ጠይቀዉ የተጠሪዎች ወንድም ወደ ዉጭ በመሄዱ ዛሬ ነገ ይመጣል እያሉ ሊሰበሰቡ ስላልቻሉ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት የዘጋዉ መዝገብ ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ ይታይልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ለተጠሪዎች እንዲደርሳቸዉ ተደርጎ በሰጡት መልስ ጉዳዩን በእርቅ እጨርሳለሁ ብለዉ በእርቅ መጨረስ ካልተቻለ ይህንኑ ለፍ/ቤቱ በቀጠሮ እለት ቀርቦ በማስረዳት ጉዳዩ እንዲቀጥል መጠየቅ ሲገባቸዉ የአመልካቾች ጠበቃ ባለመቅረቡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ከተዘጋም ሁለት ዓመት ከ6 ወር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖታል፡፡ መዝገቡ የተዘጋዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69 ሆነ 73 ለዉጥ የሌለዉ በመሆኑ መዝገቡ ሊንቀሳቀስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት ከሳሾች ጉዳዩን በዕርቅ ለመጨረስ ከሄዱ በኃላ ባለመቅረባቸዉ መዝገቡ መዘጋቱ ተገቢ ሲሆን መዝገቡ ከተዘጋ ከ2 ዓመት ከ6 ወር በኃላ የሚከፈትበት አግባብ የለም፤ በቀጠሮ ቀን እርቁን አልጨረስንም ቀጠሮ ይሰጠን ብለዉ መጠየቅ እየተገባቸዉ ይህን አላደረጉም በማለት የአመልካቾችን መዝገብ ይንቀሳቀስልን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተዉ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገቡን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በሰጠዉ ብይን በቀን 06/10/2005 ዓ.ም መዝገቡን የዘጋዉ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በቀን 22/12/2005 ዓ.ም ብይኑን በመሻር ወደ ፍሬ ጉዳዩ ገብቶ እንዲያከራክር ወስኖ መልሶለታል፡፡ ከዚያም መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ጠይቀን በቀን 11/02/2006 ዓ.ም ለቀን 28/02/2006 ዓ.ም ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ሳይቀርቡ በሽማግሌ እንድንጨርስ ጊዜ ይሰጠን ስላሉ እኛም ለፍ/ቤቱ ይህን አሳዉቀን ሂደናል፡፡ ፍ/ቤቱ ራሱ በቀን 23/03/2006 ዓ.ም ቀጠሮ ግራቀኙ ሳንቀርብ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት ዘግቶታል፡፡ ግራቀኛችን ጉዳዩን በእርቅ እንጨርሳለን ብለን ያቀረብነዉ በሌለንበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 69 መሠረት ለጊዜዉ መዝጋት ሲገባዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት መዝጋቱ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት ግራቀኛችን በማናዉቀዉ እኛ ተስማምተን እንመጣለን ብለን የሄድነዉ በማስመሰል 2 ዓመት ከ6 ወር ሆኖታል መዝገቡ ሊንቀሳቀስ አይገባም ማለቱ አግባብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የተጠሪዎች ወንድም ወደ ዉጪ አገር በመሄዱ እየጠበቅን ቆይተን እያለ መዝገቡ የተዘጋዉ በምን ምክንያት መሆኑን ሳናዉቅ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት መዘጋቱ አግባብ ስላልሆነ የስር ፍ/ቤትን ብይን በመሻር መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ይወሰንልን የሚል ነዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩን በእርቅ ለመጨረስ ከፍ/ቤት የሄዱ ቢሆኑም የተከሳሽ ወገን በተለያየ ምክንያት ለእርቁ ዝግጁ ባለመሆናቸዉ የአሁኑ አመልካቾች ጉዳዩ እንዲንቀሳቀስ ሲያመለክቱ ከ1 ወር በላይ ጊዜዉ ያለፈ ስለሆነ የተዘጋዉ መዝገብ ሊንቀሳቀስ አይገባም ተብሎ የተወሰነበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 69-73 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ካላቸዉ ሕጎች መሠረት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በመቀባበል ተከራክረዋል፡፡

የተጠሪዎች መልስ ይዘት፡- የስር ፍ/ቤት አመልካቾች ጉዳዩ በእርቅ ባያልቅም ለ23/03/2006 ዓ.ም በሰጠዉ ቀጠሮ መቅረብ ሲገባቸዉ ባለመቅረባቸዉ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.73 መሠረት መዝጋቱም ሆነ ይንቀሳቀስልን አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74(2) መሰረት በአንድ ወር ዉስጥ የቀረበ ባለመሆኑ ዉድቅ መደረጉ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ ስለሆነም ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጉትን የጽሁፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይን እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡
ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለዉ ጉዳዩ በክርክር ሂደት ላይ እያለ የአሁን አመልካቾች ጉዳዩን በእርቅ ለመጨረስ በተጠሪዎች መጠየቃቸዉን ለፍ/ቤቱ በማስታወቃቸዉ ፍ/ቤቱ ቀጠሮ ለሕዳር 23 ቀን 2006 ዓ.ም ለዉጧል፡፡ በዚህ ቀጠሮ ግራቀኙ ባለመቅረባቸዉ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መዝገቡን መዝጋቱን ገልጾ ተመላሽ አድርጓል፡፡ ከ2 ዓመት ከ6 ወር በኋላ ግንቦት 17 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የተዘጋዉ መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸዉ መጠየቃቸዉን ተገንዝበናል፡፡ አመልካቾች ለሕዳር 23 ቀን 2006 ዓ.ም ቀጠሮ የተያዘዉ ግራቀኛችን በሌለንበት ነዉ የሚለዉ ክርክር ለቀጣይ 2 ዓመት ከ6 ወር ጉዳዩን ያልተከታተሉ በመሆናቸዉ የሚያመጣዉ ለዉጥ የለም፡፡ አመልካቾች መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69 መሠረት ሊዘጋ እየተገባዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሰረት መዘጋቱ ስህተት ነዉ በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ በተመለከተ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት የተዘጋዉ ሐምሌ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠዉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብይን ሳይሆን 2 ዓመት ከ6 ወር በፊት ሕዳር 23 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበዉ ቅሬታ በዚህ መዝገብ ሊታይ አይችልም፡፡

በመሠረቱ አንድ ከሳሽ የሆነ ወገን በአንድ ሰዉ ላይ ክስ ከመሠረተ በኃላ በመጀመሪያዉ ቀጠሮ ይሁን ክርክር ላይ ባለበት ወቅት በተሰጠ ቀጠሮ ቀጠሮን አክብሮ በራሱ ወይም ወክሎት ሊከራከር የሚችል ሰዉ አለመቅረብ ዋጋ እንደሚያስከፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጋችን ስለተከራካሪ ወገኖች መቅረብና አለመቅረብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 69 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች፣ ስለቀጠሮ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.197 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንዲሁም ክስን መተዉ አስመልክቶ ከተደነገጉ ጥብቅ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 275 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት አንድ ጉዳይ በማንኛዉም የክርክር ደረጃ ላይ በሚገኝበት ወቅት ተከራካሪ ወገኖች በእርቅ ወይም በግልግል ስምምነት የመጨረስ መብት ያላቸዉ ቢሆንም ክሱን ከሳሽ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 279(1) መሠረት ፍርድ ቤትን ሳያስፈቅድ ያቀረበዉን ክስ የተወ ከሳሽ ኪሳራ እንዲከፍል ሊወሰንበት ከመቻሉም በላይ በተወዉ ክስ አዲስ ክስ መመስረት እንደማይችል በግልጽ ተመልክቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካቾች በክርክር ላይ ያለዉን ጉዳያቸዉን በእርቅ ለመጨረስ ቀጠሮ እንዲለወጥላቸዉ ጠይቀዉ ተለዉጦላቸዉ በተሰጠዉ ቀጠሮ ቀርበዉ የደረሱበትን ደረጃ ለፍ/ቤቱ አላሳወቁም፡፡ ከዚህ አልፎ ለ2 ዓመት ከ6 ወር ጉዳያቸዉን አልተከታተሉም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ በቀጠሮ ዕለት ላለመቅረባቸዉ ያቀረቡት ምክንያት ምንም ይሁን ከ2 ዓመት ከ6 ወር በኃላ የተዘጋዉን መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸዉ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የተዘጋዉ መዝገብ 2 ዓመት ከ6 ወር በኃላ የሚንቀሳቀስበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት የተዘጋዉ መዝገብ አይንቀሳቀስም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ብይን የስነ ስርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች አላማ የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ በአብላጫ ድምጽ ተወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል በማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1631 ሐምሌ 01 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 88251 ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ባለመቻሉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

<u>የሐሳብ ልዩነት</u>

ስሜ በተ.ቁ 5 ላይ የተገለጸው ዳኛ አብላጫው ድምጽ አመልካቾች በክርክር ላይ ያለውን ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ ቀጠሮ እንዲለወጥላቸው ጠይቀው ተለውጦላቸው በተሰጠው ቀጠሮ ቀርበው የደረሱበትን ደረጃ ለፍ/ቤቱ ያሳወቁ እና ለሁለት ዓመት ከሥድሥት ወር ጉዳያቸውን ያልተከታተሉ በመሆኑ በቀጠሮ ዕለት ላለመቅረባቸው ያቀረቡት ምክንያት ምንም ይሁን ከሁለት ዓመት ከሽድሥት ወር በኋላ የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸው የሚያደርጉበት የሕግ አግባብ የለም በማለት በደረሰበት መደምደሚያ ስላልተሥማማሁ በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡ በሐሳብ ለመለየት ያስቻሉኝን ምክንያቶችም እንደሚከተለው አስፍሬአለሁ፡፡

የሥር ፍ/ቤት አመልካቾች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ ያደረገው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69/2 ግራቀኙ ባለመቅረባቸው የሚዘጋ መዝገብ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 ከሳሽ ባለመቅረቡ በሚዘጋ መዝገብ መካከል ያለው ልዩነት ሁለቱም በሚዘጋበት ጊዜ ስላልነበሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መዘጋቱ ትክክል አይደለም የሚባልበት ምክንያት የለም፤ከሳሽ በቀጠሮው ዕለት ካልተገኘ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት ሊዘጋ ግድ ነው፤ከሳሽ በዕርቅ ለመጨረስ ቀጠሮ ከተሰጠ በኋላ በቀጠሮ ዕለት ቀርቦ ለማስረዳት ስላልቻለ በቀጠሮ አልተገኘም ተብሎ መዘጋቱ ስህተት የለውም፤ጉዳዩ ለሽማግሌ ከተመራ በኋላ ሽማግሌዎች የተከሳሾች ወንድም ወደ ውጪ ስለሄዱ እና ሽማግሌዎች ሊሰበሰቡ ስላልቻሉ ነው በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያቀረቡት ምክንያትም ከዓመታት በኋላ ቆይተው መዝገቡን ለማንቀሳቀስ የሚያስችላቸው ምክንያት አይደለም በማለት ነው፡፡

በእርግጥ የፍትሐብሔር ክርክር በጥብቅ ሥነ-ሥርዓት የሚመራ ስለመሆኑ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከቁጥር 65-78 ስለተከራካሪዎች መቅረብ እና ሳይቀርቡ መቅረት አስመልክቶ ስለሚያስከትለው ውጤት ከተደነገጉት ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ እነኚህ ጥብቅ የሆኑ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚገባውም ጉዳዩን የሚመራው ፍ/ቤት እንደየጉዳዩ አግባብነት ተገቢውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ በማድረግ ጉዳዩን መምራት ሲችል እንደሆነ ድንጋጌዎቹ ራሣቸው አመላካች ናቸው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ የሚከራከሩበትን ጉዳይ በዕርቅ ለመጨረስ አስበው የሥር መዝገብ የግራቀኙን የዕርቅ ሥምምነት ለመጠባበቅ መዝገቡን ቀጥሮት የነበረ እና በዕለቱ ግራቀኙ ባለመቅረባቸው ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት መዝገቡን የዘጋው መሆኑ አላከራከረም፡፡ ፍ/ቤቱ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት ከዘጋው በኋላ አመልካቾች መዝገቡ ተንቀሳቅሶ ጉዳያችን ይታይልን በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ፍ/ቤቱ ውድቅ ማድረግ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ከመታየቱ በፊት ከመነሻውም ቢሆን ፍ/ቤቱ ተገቢውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ በማድረግ መዝገቡን ዘግቷል? ወይስ አልዘጋም? የሚለው ነጥብ ምላሽ ሊያገኝ ይገባል፡፡

ግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍ/ቤቱ መዝገቡን እንደሚዘጋው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69/2/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተዘጋ መዝገብ ውጤትም መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ ከሳሹ ተገቢውን ዳኝነት እና ኪሣራ ከፍሎ መዝገቡን እንደገና ከማስከፈት እንደማያግደው ወይም ከሳሹ በዕለቱ ሳይቀርብ የቀረው በበቂ ምክንያት እንደሆነ ዳኝነት እና ኪሣራ ሳይከፍል መዝገቡ እንዲከፈት ማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ ከዚሁ ሕግ ቁጥር 71 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት አንድ መዝገብ ሊዘጋ የሚችለው ክርክሩ እንዲሰማ በተያዘው ቀነ-ቀጠሮ ከሳሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ እና ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ የካደ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት መዝገብ የተዘጋበት ከሳሽ ለክሱ መነሻ የነበረውን ነገር መሠረት በማድረግ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል በሥነ-ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጉ በቁጥር 74/1 ላይ ተደንግጓል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 279/1/ ከሣሽ ከፍ/ቤቱ ፈቃድ ሳይቀበል ክሱን የተወ እንደሆነ ያለፈቃድ በተወው ክስ ሌላ ክስ ማቅረብ እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 እና 279/1/ መሠረት የሚዘጋው መዝገብ ከሳሹን ለክሱ መነሻ የነበረውን ነገር መሠረት በማድረግ እስከወዲያኛው ክስ እንዳያቀርብ የማድረግ ውጤት ያለው ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 69/2 መሠረት የሚዘጋው መዝገብ ደግሞ ከሳሹ ተገቢውን ዳኝነት እና ኪሣራ ከፍሎ መዝገቡን እንደገና ከማስከፈት የማያግደው በመሆኑ ፍ/ቤቶች የተከራካሪ ወገኖችን አለመቅረብ መሠረት በማድረግ በተከራካሪ ወገኖች ላይ የተለያየ ውጤት የሚያስከትሉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት መዝገብ ሲዘጉ ተገቢውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መዝገቡ ከተዘጋ በኋላም ተከራካሪ ወገኖች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ የሚያቀርቡት አቤቱታም ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ከመነሻውም ቢሆን ፍ/ቤቱ ተገቢውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ በማድረግ መዝገቡን የዘጋው በሆነ ጊዜ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 37 ማንኛውም ሠው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍ/ቤት ወይም በሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከመነሻውም ቢሆን መዝገቡ ለእርቅ በተቀጠረበት ሁኔታ ግራቀኙ አልቀረቡም በማለት ለጉዳዩ አግባብነት በሌለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 73 መሠረት መዝገቡ በተዘጋበት ሁኔታ የበታች ፍ/ቤቶች የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ዜጎች በሕገመንግሥቱ የተረጋገጠላቸውን ፍትሕ የማግኘት መብት የማሳጣት ውጤት ያለው ሆኖ ስላገኘሁት አብላጫው ድምጽ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ከደረሰበት መደምደሚያ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 139138

ህዳር 20 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋዬ አስማማው

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ኃይሉ ሂንጌ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አመርቲ ነሼ የፊንጫኣ ሀይል ማመንጫ ፕሮጀክት ነገረ ፈጅ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የክርክሩ መነሻ በጉዳት ካሳ ክርክር ላይ ተሳታፊ ለመሆን የቀረበ ነው፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የአሁን አመልካችን ጨምሮ አራት ከሳሾች የአሁን ተጠሪ ይዞታቸውን ለኤሌክትሪክ ማመንጫ ስለወሰደባቸው የንብረት ጉዳት ካሳ እንዲከፍል ክስ አቅርበው ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 14442 በቀን 28/6/2006 ዓም የሰጠውን ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሥር ከሳሾች መካከል የአሁኑን አመልካች ጨምሮ ሶስቱ ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ምድብ ችሎት አቅርበው ሲፀናባቸው ከይግባኝ ባዮች መካከል አቶ አመንቱ ደበሎ እና አቶ በላይ በየነ የሰበር አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሲያቀርቡ የአሁን አመልካች ተሳታፊ አልነበሩም፡፡ የተጠቀሱት ሁለቱ አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ በሰበር መዝገብ ቁጥር 111629 የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት ሊጣሩ የሚገባቸውን ነጥቦችን በመለየት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት ለሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ መልሶታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ ከተመለሰ በኃላ የአሁኑ አመልካች በነጥብ የተመለሰው ጉዳይ እሳቸውንም የሚመለከት በመሆኑ ወደ ክርክሩ ለመግባት ጉዳዩን ለያዘው ፍርድ ቤት ሲያመለክቱ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ የተሻረው ሁለቱን ከሳሾች በሚመለከት በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ አመልካችን አይመለከታቸውም ሲል ትዕዛዘ ሰጥቷል፡፡

ይህን ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ምድብ ችሎት አቅርበው ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመውብኛል ያሏቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ የአሁን አመልካች ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን በተጠሪ ላይ የካሳ ጥያቄ አቅርበው እስከ መጨረሻ ድረስ ተከራክረው ክርክራቸው ተቀባይነት በማጣቱ ከነሱ ጋር ተከራካሪ የነበሩ ሰዎች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበው በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት ተገቢው ማጣራት ተደርጎ እንዲወሰን በመመለሱ የአሁን አመልካች በተመለሰው ነጥብ መሠረት ለመከራከር የሚያስችል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለውን ለማጣራት ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብለናል ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ተጠሪን በአድራሻ ለውጥ ምክንያት ለማግኘት ያለመቻላቸውን ገልጸው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ በጠየቁት መሠረት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ባለመቅረቡ ምክንያት መልስ የመስጠት መብቱ እንዲታለፍ ተደርጓል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አስቀድሞ እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ ደርሶ በነጥብ በተመለሰው ጉዳይ የአሁኑን አመልካችን ጨምሮ አራት ሰዎች በአንድ ላይ ሆነው እያንዳንዳቸው የሚገባቸውን የንብረት ጉዳት ካሳ ግምት በማቅረብ በሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.14442 በሆነው ተከራክረዋል፡፡ ክስ ያቀረቡት በአንድ መዝገብ፣በአንድ ዓይነት ጉዳይ፣ በአንድ ላይ ነው፡፡ ይህም የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህግ ቁጥር 35 ድንጋጌን የተከተለ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ በዚህ ሁኔታ ክስ አቅርበው ከተፈረደባቸው ሰዎች መካከል አንዱ ይግባኝ አቅርቦ ውሳኔው ከተሻረ ወይም ከተለወጠ ወይም ከተሻሻለ ይግባኝ ያልጠየቀው ሰው የፍርዱ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 331 በአንድ ክርክር ውስጥ የከሳሾች ወይም የተከሳሾች ብዛት ከአንድ በላይ ሲሆንና ክርክሩም ከሳሾችን ወይም ተከሳሾችን በአንድ ዓይነት መልክ የሚመለከታቸው ሲሆን ከሳሾቹ ወይም ከተከሳሾቹ አንዱ በጠቅላላው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ በዚህ ዓይነት ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደነገሩ አከባቢ ፍርዱን በማሻሻል ወይም በመለወጥ ያሻሻለው ወይም የለወጠው ወይም ያጸናው ፍርድ ይግባኙን ባላቀረቡት ከሳሾች ወይም ተከሳሾች ላይም ይፀናባቸዋል፡፡ ይህ ድንጋጌ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 35 ላይ የተደነገጉትን ዝርዝር ነገሮችን ባሟላ መልኩ በአንድነት ሆነው ክስ ያቀረቡ ከሳሾች ከውሳኔ መልስ በይግባኝ ደረጃም በቀረበው ጉዳዩ ከከሳሾቹ መካከል አንዱ ይግባኝ ጠይቆ የሚሰጠው ውሳኔ ሌሎችንም እንደሚያካትት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለጸው የአሁኑን አመልካች ጨምሮ አራት ከሳሾች ክስ መስርተው በአንድ መዝገብ የተከራከሩ ናቸው፡፡ ጉዳዩ ንብረት ካሳን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እያንዳንዱ ከሳሽ ለራሱ የሚገባውን የካሳ መጠን ገምቶ ማቅረብ ማለት ግን ለየብቻው ክስ አቅርቧል ሊያስብል አይችልም፡፡ የሆሮ ጉድሮ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ሲያደርግ በትዕዛዙ ላይ የገለጸው ምንም እንኳን ከሳሾቹ በአንድ ላይ ክስ ቢያቀርቡም እያንዳንዳቸው የካሳውን መጠን ለይተው ያቀረቡ ስለሆነ ከፊዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በነጥብ በተመለሰው ጉዳይ አመልካች ሊከራከሩ አይችሉም የሚል ሲሆን ይህም የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 35 እና 331 ድንጋጌን መንፈስና ዓላማ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሊጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ

1. የሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.14442 በቀን 07/10/2008 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.209044 በቀን 13/04/2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ወደ ክርክሩ ውስጥ ገብተው ለመከራከር ያቀረቡት አቤቱታ የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 331 ድንጋጌን የተከተለ በመሆኑ ከፊዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 111629 ላይ የሚጣሩ ነጥቦች ተይዘው በተመለሱት መሠረት በመ/ቁ. 14442 በሆነው ላይ የአመልካች ክርክር ቀጥሎ ፍርድ ቤቱ አከራክሮ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. ከፊዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በተመለሰው መሠረት የሁለቱ ከሳሾች ክርክር ውሳኔ አግኝቶ ከሆነም የአመልካች ክርክር በዚያው መዝገብ ታይቶ ውሳኔ ሊያገኝ ይገባል ብለናል፡፡
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይደረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 139942

ቀን 27/03/2010 ዓ/ም

ዳኞች፡-ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘይባ ሳኒ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ለይላ ዘይኑ ተወካይ ዴቻሳ ጉርሙ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ተገቢውን ለመስራት ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቤት ክርክር የሚመለከት ሲሆን የጀመረው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ በኮ/መ/ቁ. 63738 ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የስር ከሳሽ ያቀረቡት ክስ ይዘትም በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ሰበታ ከተማ አስተዳደር ዓለምገና ቀበሌ 02 ውስጥ ስፋቱ 395.7 ካሬ ሜትር በሆነው ይዞታ ላይ ቤት ሰርተው ተጠሪ በነበራቸው ጊዜያዊ ችግር በቤቱ እንዲኖሩ ተፈቅዶላቸው የነበረ ቢሆንም ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ተጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲወሰን መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
2. የአሁኑ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ጉዳዩ የበኩላቸውን መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል ክርክር ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም ቤቱ የራሳቸው እንጂ የአሁኑ ተጠሪ አለመሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡
3. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የተጠሪ ነው ከሚል መደምደሚያ የደረሰ ሲሆን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህም አመልካች ቤቱን ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህ ውሳኔ በመቃወም ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከህግ ውጭ ውድቅ ስለ መደረጉ በፍሬ ጉዳዩም ቤቱ የአመልካች እንጂ የተጠሪ አለመሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ በተረጋገጠበት ሁኔታ በስር ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ በህጉ አግባብ አይደለም በማለት የተከራከሩ ሲሆን በዚህ አግባብ አቤቱታ የቀረበለት አጣሪ ችሎትም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ በአደራ መስጠታቸው ባልተጠረጋገጠበት ሁኔታ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ማጣራት ይቻላል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም የበኩላቸውን መልስ ያቀረቡ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል ፡፡

4. የጉዳዩ አመጠጥ ከላይ የተገለጸው አጭር ይዘት ያለው ሲሆን እኛም ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ከላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመረነው የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያሻው ዓቢይ ነጥብ በፍሬ ጉዳዩ የተሰጠው ፍርድና ትዕዛዝ ተገቢነት ከመመርመራችን በፊት ጉዳዩ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ታይቶ ፍርድ መሰጠቱ ከስረ ነገር ስልጣን አንጻር በህጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን መታየት ያለበት ሆኖ አገኝተነዋል፡፡ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት የሚቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ የሚገኘው ኦሮሚያ ክልል ፈንፊኔ ልዩ ዞን ሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 02 ውስጥ ነው፡፡ አመልካችም ነዋሪነታቸው ኦሮሚያ ክልል ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት መልስ ጉዳዩ የፌደራል ሆኖ በውክልና በኦሮሚያ ክልል ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚታይ ቢሆንም ውክልና ሰጪው በጉዳዩ ላይ ስልጣን የለውም ማለት ስላልሆነ ከዚህ አንጻር የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም የሚል ክርክር ማቅረባቸውን ተመልክተናል፡፡

5. በመሠረቱ የስረ ነገር ስልጣን ጥያቄ በየትኛውም የክርክር ደረጃ የሚነሳ ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 9 እና 231 (1) (ለ) እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዝገቦች በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ጉዳይ በፌደራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ መሆኑ አለመሆኑን ለመለየት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የማይንቀሰቀስ ንብረት በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ ከመሆኑ በተጨማሪ አመልካች እና ተጠሪ የኦሮሚያና አዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ስለመሆናቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በይፋ ባልተቋቋባቸው ክልሎች የፌዴራል ጉዳይ በውክልና የሚታይ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የስረ ነገር ስልጣኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቢሆንም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ በመሆኑ መታየት ያለበት በኦሮሚያ ክልል ንብረቱ የሚገኝበት የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ስለመሆኑ የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80(4) ያስገነዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይሁን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስረ ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ሲገባቸው ይህንን በማለፍ ግራ ቀኙን በማከራከር ፍርድና ትዕዛዝ መስጠታቸው በህጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖራቸው የሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 63738 በ29/11/2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 185671 በ29/06/2009 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ በመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡ ይሁንና የአሁኑ ተጠሪ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብታቸው ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት በ2/08/2009 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 135254

የካቲት 29 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ ይስሃቅ ተክለ ዓዲቅ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ሃረገወይን አሸኔ

2. አቶ ጌጡ አሸኔ

3. ወ/ሮ ወይንሸት ተክሌ

መዝገቡን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 10 ቀን 2009 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታቸው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99270 የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በከ/መ/ቁ 172878 ነሀሴ 30 ቀን 2008 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት የአቀረቡት አቤቱታ በዚህ ችሎት ታይቶ እንዲወሰን በሰበር አጣሪ ችሎቱ ስለተወሰነ ነው፡፡የሕጉ ጥያቄም በአንድ የፍትሃብሔር ክርክር ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ጣልቃ በገባ ተከራካሪ ወገን ላይ በክርክሩ ከሳሽ የሆነው ወገን ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ለማንሳት የሚችልበት የሕግ አግባብ መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ሚያዚያ 19 ቀን 2007 ዓ/ም በፃፉት ማመልከቻ ሲሆን የማመልከቻቸው ይዘትም ወላጅ አባታቸው መምሬ ተክለፃዲቅ ወ/ዳዊት እና ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ ፀዳለ ታደሰ ተሰማ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 190 በሆነ ቤት ውስጥ ሲኖሩ ወላጅ አባታቸው ጥር 22 ቀን 1996 ዓ/ም፣ ወላጅ እናታቸው ደግሞ ግንቦት 21 ቀን 1995 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን ገልፀው የወላጆቻው የውርስ ሃብት በመረጧቸው አጣሪ እንዲጣራላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካች ሌላ ተጠሪ ሰይመው ያልነበሩ ቢሆኑም የአሁኑ ተጠሪዎች ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተዋል፡፡ ውርሱ እንዲጣራ ከተደረገ በኋላም ሪፖርቱ በ28/03/2008 ዓ/ም ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን በዚህ ጊዜም አመልካች ተጠሪዎች ወራሾች ነን በማለት መቅረባቸው በይርጋ የታገደ ነው የሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በዚህ መልኩ የቀረበውን የአመልካችን መቃወሚያ መርምሮ አመልካች በራሳቸው አመልካችነት ውርሱ እንዲጣራ ጠይቀው የውርስ አጣሪው በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ወራሾችን ከለየ በኋላ ይርጋ ማንሳታቸው የህግ አግባብ የሌለው መሆኑን፣ ይርጋውን ማንሳት ይችላሉ ቢባል እንኳን የውርስ አጣሪው ይቋቋም የሚል ጥያቄ ሲቀርብ መሆን አለበት የሚሉ ምክንያቶችን ይዞ የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፤ የሟች ወራሾች እነማን እንደሆኑ በመለየት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት አሻሽሎ አፅድቆታል፡፡

አመልካች የአነሱት የይርጋ ክርክር ውድቅ በመደረጉ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪዎች አውራሾቻቸው ከሞቱ ከአስር አመታት በኋላ አመልካች ባቀረቡት የውርስ ንብረት ክፍፍል መዝገብ ላይ የሚኞች ወራሾች ነን በማለት የአቀረቡት የክፍፍል ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት አመልካች የአቀረቡት መቃወሚያ በበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ የተደረገው ከሕግ ውጪ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታቸው በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጎም ተጠሪዎች ቀርበው ከአመልካች ጋር በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በሚል ምክንያት ውድቅ ማድረጋቸው ሕጋዊ መሰረት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካች የሟች አባታቸው አቶ ተክለጻዲቅ ወ/ዳዊት እና የሟች እናታቸው ወ/ሮ ፀዳለ ታደሰ ወራሽ መሆናቸው የተረጋገጠ መሆኑን፣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የሟች ወ/ሮ ጸዳለ ታደሰ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን፣ 3ኛ ተጠሪ የሟች አቶ ተክለጻዲዲቅ ወ/ዳዊት የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን በአመልካች ያልተካደ ከመሆኑም በላይ የወራሽነት ማስረጃ ቀርቦ መረጋገጡን፣ ተጠሪዎች ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ መብትና ጥቅም ባለው ወገን ተቃውሞ ቀርቦበት ያልተሰረዘ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም የበታች ፍርድ ቤቶች የአሁኑ አመልካች የሟቾች የውርስ ሃብት በፍርድ ቤት ትእዛዝ አጣሪ ተሹሞ የውርስ ሃብቱ ተጣርቶ ብቸኛ የሟቾች ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጦ የውርስ ሃብቱ በስማቸው እንዲዛወር አመልካች በመሆን ክስ ከማቅረባቸው ውጪ ተጠሪዎች የአመልካችን ክስ በመቃወም በተከሳሽነት ጣልቃ ገብተው ለመከራከር አቤቱታ ከማቅረብ ውጪ የሟቾች ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸውም ሆነ የውርስ ሃብት ድርሻቸው እንዲሰጣቸው ክሳሽ በመሆን ክስ ያለማቅረባቸውን በአቢይ ምክንያትነት ይዘው አመልካች የክስ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ የይርጋ መከራከሪያ በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ውድቅ ማድረጋቸውን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና ተካፋይ ያልሆነበት ክርክር የሚሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ወገን አቤቱታውን ለማቅረብ መብት እንደአለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39፣ 40 እና 41 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች የተዘረጋው የጣልቃ ገብነት ስርዓት በአንድ በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር ውስጥ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ያልተሰየሙ ሰዎች ለክሱ ምክንያት በሆነው ነገር ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን በማስረዳት ፍርድ ቤቱ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ገብተው ተካፋይ እንዲሆኑ እንዲፈቀድላቸው ዳኝነት የሚጠይቁበትን አግባብ የሚያሳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስርዓት ነው። ድንጋጌዎቹ ጣልቃ ገብ የሆኑት ወገኖች የሚያቀርቡት አቤቱታ ክስ ከቀረበበት ምክንያት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለው መሆን ያለበት ሲሆን በሚሰጠው ፍርድ ወይም ውሳኔ መብታቸው በቀጥታ የሚነካ መሆኑ መረጋገጥ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ መብት፤ ጥቅማቸውን ወይም ግዴታቸው የሚነካባቸው ወገኖች የግድ ተሳታፊ መሆን እንደሚገባቸው የፍትሃብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 40 (2) ስር ያስቀመጠበት አቢይ ምክንያትም አንድን የክስ ምክንያት የሚመለከቱ የክርክር ነጥቦች ሁሉ በማያዳግም ሁኔታ ዳኝነት እንዲያገኙ ለማድረግ ታስቦ ስለመሆኑ ይታመናል። እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ደግሞ የክሱ ማመልከቻ መሻሻል እንደአለበትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 40(3) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል። እንደዚህ አይነት የክርክር አመራር መከተል ደግሞ የይርጋ ጥያቄውንም ሆነ ሌሎች ክርክሮችን በሕጉ አግባብ በመምራት ተገቢውን ዳኝነት መስጠት የሚያስችልና የፍትሃብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ መሰረታዊ አላማዎችንም የሚያሳካ ነው ተብሎ ይታሰባል።

ከዚህ አንጻር ሲታይ አንድ ክርክር ታይቶ የፍርድ ውሳኔ ቢያርፍ የሚሰጠው ውሳኔ መብቱን፤ጥቅሜን ወይም ግዴታን የሚነካ ነው በማለት ወደ ክርክሩ ለመግባት ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ለመሆን በቂ የክስ ምክንያት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 40(3) አግባብ ክሱ እንዲሻሻል በማድረግ ስርዓቱን ጠብቆ የሚቀርበውን ማናቸውንም ክርክር አግባብነት ካለው መሰረታዊና ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ዳኝነት መስጠት የዳኝነት አካሉ ተግባር ነው። ስለሆነም የጣልቃ ገብነት አቤቱታ አቅራቢዎች በከሳሽነትም ሆነ በተከሳሽነት ሲሰየሙ ይርጋን ለማንሳት የሚችሉበትና የማይችሉበት አግባብ ያለ መሆኑን ከላይ የተመለከቱት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ። እነዚህ ድንጋጌዎች የውርስ ንብረቱን ለብቻው ለመውሰድ ጥያቄ ያቀረበ ወገን በሌሎች መብት አለን በሚሉ ወገኖች የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ቀርቦበት የዳኝነት ጥያቄው ተቀባይነት እንዳያገኝ መፍትሔ ሲጠየቁ ዳኝነት ሰጪው አካል በጣልቃ ገብነት ጊዜ የይርጋ ክርክር ሊነሳ የሚችልበት አግባብን መሰረት በማድረግ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥ እንደሚችል የሚያሳዩ እንጂ ይርጋ ሁሉጊዜ መነሳት የአለበት በተከሳሽነት በተሰየሙ ሰዎች ብቻ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርሱ አይደሉም። እንደየክርክሩ ይዘትና አቀራረብ እንዲሁም የዳኝነት ጥያቄው ውጤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያስከትለውን የመብት አድማስ እየታዬ ከሳሽ የሆነ ወገን ተከሳሽ፣ ተከሳሽ ደግሞ ከሳሽ በሚል ዘንግ ተመድቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባው ነው።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ሊስተናገድ የሚችል አይደለም የተባለው ይርጋ መቃወሚያ የሚነሳው በተከሳሽ በመሆኑና ተጠሪዎችም የጠየቁት ዳኝነት የውርስ ሃብት እንዲሰጣቸው የሚል ይዘት የለውም በሚል ከሳሽ በነበሩት ባሁኑ አመልካች የሚነሳበት አግባብ የለም በሚል ነው። ይሁን እንጂ ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው የፍርድ ውሳኔ መብታቸውን፤ ጥቅማቸውን የሚነካ መሆኑን ጠቅሰው ወደ ክርክሩ ለመግባት የሚያስችላቸው የክስ ምክንያት ያላቸው መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረና በስር ፍርድ ቤቶችም የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን ጥያቄያቸውም አመልካች የሟቾችን የውርስ ንብረት ብቻቸውን ለመጠቀም የሚያስችላቸው መብት የለም በማለት በሕጉ አግባብ አግኝተናል በሚሉት የወራሽነት ማስረጃ መሰረት ድርሻቸው እንዲጠበቅላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ይህ የተጠሪዎች ጥያቄ በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ያልቀረበ መሆኑን አመልካች ገልጸው መከራከራቸው ደግሞ ክርክሩ የውርስ እንደመሆኑ መጠን አመልካችን እንደተከሳሽ ተጠሪዎችን ደግሞ እንደከሳሽ የሚያስቆጥራቸው ነው የሚል ትርጉም ከሚያሰጥ በስተቀር ሌላ የተከራካሪ ወገኖች ዘንግን የሚፈጥር አይደለም። በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ከተጠሪዎች የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ጠቅላላ ይዘት እና መጨረሻ ላይ በፍርድ ቤቱ እንዲረጋገጥላቸው ከጠየቁት የዳኝነት ጥያቄ አንጻር እንዲሁም የክርክሩ ባህርይም የውርስ ንብረት ድርሻ ጋር ተያይዞ የተነሳ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተጠሪዎችና አመልካች የተከራካሪነት ቦታ እንደተለዋወጡ በመቁጠር የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ መሰረት አድርጎ በመሰረታዊ ሕጉ የተደገፈ መሆን ያለመሆኑን በመመርመርና አስፈላጊ ከሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 245 (1) አግባብ በማስረጃ አጣርቶ የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የታገደ መሆን ያለመሆኑ ላይ ብይን መስጠት ሲገባቸው አመልካች በከሳሽነት ዘንግ መቅረባቸውን ብቻ መሰረት በማድረግ የይርጋ መቃወሚያቸውን ሊያነሱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. አመልካች ይርጋን ማንሳት አይችሉም ተብሎ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99270 የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 172878 ነሐሴ 30 ቀን 2008 ዓ/ም የጸናው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪዎች ጣልቃ ሲገቡ ይርጋ ለማንሳት የሚከለክላቸው ሕግ የለም ብለናል፡፡ በዚህም መሰረት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99270 ቀጥሎ በአመልካች የይርጋ ጥያቄ ላይ አስፈላጊ ሲሆን ተገቢውን ማጣራት አድርጎ ተገቢ ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጸፍ፡፡
3. 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የሟች ወ/ሮ ጸዳለ ታደሰ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን፣ 3ኛ ተጠሪ የሟች አቶ ተክለጻዲቅ ወ/ዳዊት የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤቶች የተያዘው ድምዳሜ በዚህ ውሳኔ አልተነካም፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 138340

ህዳር 19 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፦ አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መለሰ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች:- 1. ሶፍያን ከማሎ

2. አማና ከማሎ

3. አሚኖ ከማሎ

4. ጃቢር ከማሎ

5. ሐይቃ ከማሎ

6. ሙስሊም ካመሎ

ወኪል ወ/ሮ ሰዲያ አብድሮ -ቀረቡ

ተጠሪ፦ ወ/ሮ ጀሚላ ቃሲም -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ ::

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ከውርስ ጋር ተያይዞ የቀረበን ክርክርን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህንን የሰበር አቤቱታ አመልካቾች ያቀረቡት በሱዴ ወረዳ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00669 በ28/07/2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00437 በ3/12/2008 ዓ/ም የጸናውን ውሳኔ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 519/2008 በ28/04/2009 ዓ/ም ሽሮ ተጠሪ 2.1589 ሄክታር የገጠር እርሻ መሬት ለአመልካቾች ሊለቁ አይገባም በማለት በመወሰኑና ይኼው የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 255157 በ21/06/2009 ዓ/ም ትእዛዝ በመሰጠቱ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ነው፡፡

የአቤቱታቸው መሰረታዊ ይዘትም፡- የወላጅ አባታቸውን የሚች አቶ ከማሎ ሀምዳ የውርስ ንብረት የሆነውን የገጠር እርሻ መሬትና ባህርዛፍ እንዲካፈሉ ክስ መስርተው የሚቹ ሚስቶች በሆኑት ባሁኗ ተጠሪና የአመልካቾች ወላጅ እናት እጅ ያለው ይዞታ መኖሩ ተረጋግጦ ተጠሪ ያላግባብ የያዙትን ይዞታና ባህርዛፍ እንዲያካፍሉ በወረዳውና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዞኑ የሸሪያ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የተሻረው ተጠሪ ተገቢውን ክርክርና ማስረጃ ባላቀረቡት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ የአመልካቾችን የውርስ ንብረት እንካፈል ጥያቄ በዝምታ ያለፈ ነው የሚል ነው። አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉም ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎል።

በመሰረቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 34(5) እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግት ህገ መንግስት በአንቀጽ 35(5) ስር የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሀይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን በሕገ መንግስቱ ክልከላ እንዳልተደረገበት በግልጽ ከማስቀመጡም በላይ ዝርዝሩ በሕግ እንደሚወሰን ያሳያል። በሸሪዓ ፍርድ ቤት የመዳኘት መብትም ምንጩ ይኼው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ ሲሆን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትም የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 54/1994 መሰረት ተደራጅተዋል። በዚሁ አዋጅም ስልጣናቸው ተለይቶ ተቀምጧል። በአዋጁ የክርክሩን የአመራር ሥርዓት ካልሆነ በስተቀር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሥረ ነገር ሥልጣናቸው ሥር የሆኑ ጉዳዮች የሚቀርብላቸውን አቤቱታና ክርክር የሚወስኑት የሸሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 53/94 በአንቀፅ 6(1) ስር በግልፅ የተደነገገ ሲሆን አንድ ሰው ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ሲያቀርብ ሥነ ሥርዓታዊ ከሆነው ጭብጥና ጥያቄ ውጭ የሆኑት ጉዳዮች በሸሪዓ ህግ ለመዳኘት ፈቃድ የሰጠ መሆኑም ሊረጋገጥ ይገባል።በመሆኑም የሸሪዓ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ዳኝነት ከመስጠቱ በፊት በአዋጅ ቁጥር 53/1994 አግባብ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የተሰጠው መሆኑን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ የሚገባ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 6 ድንጋጌና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231 (1(ለ)) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። ይህ ችሎትም ሆነ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ))፣ 80(3(ለ)) እና አዋጅ ቁጥር 53/94 እና አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 6 ጣምራ ንባብ መሰረት ስነ ስርዓታዊ የሆነ የህግ ጥያቄን ብቻ ለማየት ስልጣን እንዳላቸው ግንዛቤ በመውሰድ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ ሕጎችን መሰረት አድርጎ የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን መመርመር እንጂ ከዚህ ውጪ መደበኛ ሕጎችን መሰረት አድርገው በሸሪዓ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሊመረምሩ የሚችሉበት አግባብ የለም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እኛም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 53/94 ከተዘረጋው ስርዓት አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ስርዓት ህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን መርምረነዋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ተጠሪ 2.1589 ካ/ሜትር ይዘው እንዲቀሩ ውሳኔ የሰጠው አመልካቾች በወላጅ እናታቸው በኩል ተጠሪ ይዞታውንና ባህርዛፉን እንዲለቁላቸው የመሰረቱትን ክስ የበታች የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ተጠሪ ይዞታውን እንዲለቁ መወሰናቸው ተገቢውን የፍሬ ነገር ማጣራትና የሸሪዓ ሕግ መሰረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ስለመሆኑ ከውሳኔው ግልባጭ መረዳት ችለናል፡፡

አመልካቾች በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ለመዳኘት ፍቃደኛ ሳይሆኑ የተሰጠ ውሳኔ ስለመሆኑ ገልጸው ያቀረቡት ቅሬታ የሌለ ሲሆን አጥብቀው የሚከራከሩት ተጠሪ የያዙትን ይዞታ እንድንካፈል አልተወሰነም በሚል ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካቾች ተጠሪ የያዙትን ይዞታ በሟች ከማሎ ሀምዳ ወራሽነታቸው ከተጠሪ ጋር ልንካፈል ይገባል በሚል የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን በራሱ አጣርቶ የአመልካቾች ወላጅ እናት የሆኑት ወ/ሮ ሃዲያ አብድሮ 6.77 ሄክታር ይዘው ያሉ መሆኑን፣ ይህን ይዞታ ይዘውም የአሁኑ አመልካቾችን ወክለው ተጠሪ የያዙትን 2.1589 ሄክታር ጭምር ለመውሰድ ዳኝነት መጠየቃቸው በጉዳዩ ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ከሸሪዓ ሕግ አንጻር ተገቢ ያለመሆኑን በመገንዘብ ተጠሪ የያዙትን ይዞታ ሊለቁ አይገባም በማለት ዳኝነት መስጠቱን የውሳኔ ግልባጭ የሚያሳይ በመሆኑና ይህም ውሳኔ ከሸሪዓ ሕግ አንጻር ታይቶ ከመሰጠቱም በተጨማሪ የአመልካቾች ወላጅ እናትም ከተጠሪ ይዞታ የበለጠ ይዞታ ይዘው እንደሚገኙና አመልካቾችም ከወላጅ እናታቸው ስር ያሉ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በሕግ ተለይቶ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተጠሪ ይዞታውን የሚለቁበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን በማስረጃ አጣርቶና ጉዳዩን በሐይማኖት ስርዓት መዝኖ ይዞታውን ተጠሪ ሊለቁ የሚችሉበት ሐይማኖታዊ ምክንያት የሌለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ድምዳሜ ላይ ደርሷል። ይሔው ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ፍሬ ነገርን በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ስልጣኑ የደረሰበት መደምደሚያ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በድጋሚ የሚመዘንበት አግባብ የሌለ መሆኑን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10፣ እንዲሁም በክልሉ የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 53/94 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው። ከእነዚህ የሕግ ማዕቀፎች አንጸር ስናየው ደግሞ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ክርክሩ ሲመሩ በስነ ስርዓት ሕግ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት የሚያስችል ምክንያት አላገኘንም። ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካቾች የክፍፍል ጥያቄአችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ሆኗል በማለት ያቀረቡት ክርክር የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን አጣርቶና በሐይማኖቱ ስርዓት አግባብ ውድቅ ያደረገውን ያላገናዘበ እና የአመልካቾች ቅሬታ መሰረታዊ ይዘቱ በሐይማኖት ስርዓት ላይ ተመርስቶ የተሠጠውን ውሳኔ በመደበኛው ሕግ እንዲታይ የሚጠይቅ በመሆኑ አልተቀበልነውም።

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ክርክር ውድቅ በማድረግ በሰጠው ውሳኔና ይህንኑ ውሳኔ ባፀናው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህትት አላገኘንም። በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

<u>ውሳኔ</u>

1. በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 519/2008 በ28/4/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 255157 በ21/06/2009 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል።
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.138062

ህዳር 26 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች - ተክሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ፀሃይ መንክር

አመልካች - የሰቆጣ ከተማ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት ዓ/ህ ሙሉ ባዩለኝ ቀረቡ
ተጠሪ - ወ/ሮ አድና ምህረቱ ጠ/ነቀዓጥበብ ገ/ሚካኤል ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ በአማራ ብ/ክ/መንግስት በሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- ተከሳሽ የከሳሽ መ/ቤት የሆነን በሰቆጣ ከተማ 02 ቀበሌ የሚገኝ ኮንደሚኒየም የጋራ መኖሪያ ቤት ቁጥር B 13 R7 ባለሁለት መኝታ ቤት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳያገኙና ሳይሰጣቸው በራሳቸው ከጥር ወር 2008 ዓ.ም ጀምሮ ንብረታቸውን አስገብተው ቤቱን ይዘው ስለሚገኙ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ ባቀረቡት መቃወሚያ በዚሁ ጉዳይ በመ/ቁጥር 0105706 በሁከት ይወገድልኝ ክሶኝ ተከራክረን ፍርድ ቤቱ ሁከት አለመፍጠራንና በህጋዊ መንገድ በቤቱ መቀመጤንና የሚፈለገውን ክፍያ እየከፈልኩ ለመሆኔ አረጋግጦ የፈጠርኩት ሁከት የሌለ ስለመሆኑ ተወስኖልኝ እያለ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ድጋሚ እንደአዲስ ከሳሽ ጭብጡን ሳይቀይር የክሱን ርዕስ ብቻ በመቀየር ይዞታ ይረጋገጥልኝ በሚል ሰበብ ከቤቱ ለማስወጣት ያቀረበው የሃሰት ክስ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 5 እና 244(ለ) መሰረት በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ነው ተብሎ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ግራቀኙን ያከራከረ ሲሆን ከሳሽ በመቃወሚያው ላይ ባቀረበው ክርክር በመጀመሪያው ክስ ተከሳሾች ሁለት የነበሩ መሆኑንና በአሁኑ ክስ ግን ተከሳሽ አንድ ሰው ብቻ መሆናቸውን፤ የክርክሩ ፍሬ ነገርም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጀመሪያው የሁከት ይወገድልኝ ሲሆን የአሁኑ ግን ይዞታ ይለቀቅልኝ የሚል መሆኑን፤ የሚያዙት ጭብጦችም በመጀመሪያው ሁከት አለ የለም የሚል ሲሆን በአሁኑ ደግሞ ተከሳሽ ይዞታውን ይለቃሉ አይለቁም የሚል በመሆኑ የተለያዩ መሆናቸውን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ተከሳሽ በበኩላቸው በመጀመሪያው ክስ ሁለት ተከሳሾች ቢኖሩም ከእሳቸው ውጪ ሌላዋ ተከሳሽ አለመከራከራቸውንና ውሳኔም እንዳልተሰጠባቸው፤ የክርክሩም ይዘት በጭራሽ ልዩነት የሌለውና ዝርዝር ክሱ ተመሳሳይ መሆኑን፤ በመጀመሪያው ክስ ፍርድ ቤቱ አከራክሮ የሰጠው ውሳኔ ሁከት አለ የለም የሚለው ብቻ ሳይሆን የቤት ኪራይ ግንኙነት ስለመኖሩ ጭምር አከራክሮ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን በማንሳት መቃወሚያቸውን አጠናክረዋል፡፡

የመቃወሚያ ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የመጀመሪያው ክስ ላይ ሁለት ተከሳሾች የነበሩ መሆኑና የአሁኑ ክስ ደግሞ በተጠሪ ላይ ብቻ መሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው ከሚለው የመከራከሪያ ሃሳብ ጋር ፍፁም ግንኙነት የሌለው መሆኑን፤ የሥረ ነገር ክርክሩ እና የተያዘው ጭብጥ ሲታይ የከሳሽ የዳኝነት ጥያቄ በፊተኛው ክስም ሆነ በአሁኑ ክስ የቤቱ ይዞታ እንዲለቀቅለት ስለመሆኑ ሁለቱንም የክስ ዝርዝር ይዘቶች አይቶ መረዳት እንደሚቻል፤ በአጠቃላይ በመጀመሪያው ክስ ከሳሽ በሁከት ይወገድልኝ ሽፋን ክስ ያቀረበ ቢሆንም ተከሳሽ የቤት ኪራይ ግንኙነት ያላቸው መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሁከት ሊባል እንደማይገባና በኪራይ ግንኙነት ምክንያት የያዙት ይዞታ ህጋዊ ውጤት ያለው መሆኑ ተረጋግጦ ፍርድ ተሰጥቶበት ያደረ ጉዳይ በመሆኑ በድጋሚ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5፣ 244(ለ) እና 245 መሰረት ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ብይን በመቃወም ቅሬታውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 8/2009 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር ማመልከቻ በሥር ፍርድ ቤቶች የተላለፈው ብይን እና ትዕዛዝ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው እንዲባል እና ተጠሪ በህገወጥ መንገድ የያዙትን ቤት ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ሀምሌ 11/2009 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቱ ውስጥ የገባሁት አመልካች እንደሚለው በህገወጥ መንገድ ሳይሆን እንደማንኛውም የከተማ አስተዳደሩ ሰራተኛ በከተማ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት በነበረው አሰራር መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት እንዲሰጠኝ ወረፋ ከያዝኩ በኋላ መሆኑና በየወሩ የቤቱን ኪራይ እየከፈልኩ መሆኑ አመልካች እራሱ በፍርድ ቤት ያመነውና የማይክደው ከመሆኑ በተጨማሪ በሥር ፍርድ ቤት ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ከዚህ ቀደም ሁከት ይወገድልኝ በማለት ባቀረበው ክስ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ አንድ አይነት ጭብጥ የተያዘበትና አንድ አይነት ክርክር ነው ተብሎ ክሱ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው እንዲባል ጠይቀዋል። አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይን እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል።

የፍትሃብሄር ስነ ስርዓት ህጉ ክርክሮች መቋጫ ይኖራቸው ዘንድ ከዘረጋው ሥርዓት አንዱ በአንቀፅ 5 ሥር የተደነገገው የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮችን የተመለከተው ድንጋጌ ነው። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር እንደተደነገገው አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ያለባቸው ሁኔታዎች ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ይመለከታል። ከሕጉ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ በመጀመሪያው ክርክር ላይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው ፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5፣ 244(2(ለ)) እና 245(2) ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል።

በተያዘው ጉዳይ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች ሁከት ይወገድልኝ በሚል አከራካሪው ቤት እንዲለቀቅለት አስቀድሞ ባቀረበው ክስ መሰረት በግራቀኙ መካከል ክርክር ተደርጎ አመልካች ከተጠሪ ጋር የቤት ኪራይ ግንኙነት ያለው መሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ሁከት ፈጥረዋል ሊባል እንደማይገባና በኪራይ ግንኙነት ምክንያት የያዙት ይዞታ ህጋዊ ውጤት ያለው መሆኑ ተረጋግጦ ፍርድ ተሰጥቶበት ያደረ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ በማረጋገጥ ወስኗል፡፡

ስለሆነም አመልካች ሁከቱ ተወግዶ ቤቱ እንዲለቀቅለት ክስ አቅርቦ የተጠሪ ይዞታ ህጋዊ መሆኑ ዳኝነት ከተሰጠበት በኋላ ይዞታ ይለቀቅልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ዳኝነት በተሰጠበት ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌዎች አንፃር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች በቀደመው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው በየደረጃው በይግባኝ እና በሰበር ስርዓት አቤቱታ ከሚያቀርብ በቀር በዚያው ጉዳይ ድጋሚ ዳኝነት መጠየቁ ህጉን የተከተለ አይደለም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት በድጋሚ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5፣ 244(ለ) እና 245 መሰረት ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ያሳለፈው ብይንና በየደረጃው ቅሬታ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶች ቅሬታውን አለመቀበላቸው ህጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሰቆጣ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 01-05940 ሰኔ 6 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን፤ የዋግኽምራ ብሄረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 01-02548 ሀምሌ 27 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ፤ እንዲሁም የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 03-15514 ታህሳስ 10/2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ሁከት ተወግዶ ይዞታ እንዲለቀቅለት ክስ አቅርቦ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በድጋሚ ይዞታ ይለቀቅልኝ በሚል ክስ የመሰረተበት አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት የለውም መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ.137401

የካቲት 27 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡...1.ዳኜ መላኩ

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-.....ወ/ሮ ጀምላ ጆብር ⟶ ተወካይ ሸፊቃ ሁሴን ቀርበዋል

ተጠሪ፡-.....አቶ ሶፊያ ጅማ ⟶ የቀረበ የለም፡፡

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የንብረት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.253490 በ05/04/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ ፣በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት ሚማ ሚስጠፋ፣ሩማና ጅማ፣አሊማ ጅማ፣መሀመድ ጅማ እና ናስር ሁሴን 2ኛ-6ኛ ተከሳሾች ሆነው ሲከራከሩ ነበር፡፡ ከሳሽ ባቀረበችዉ ክስ በተከሳሾች አክስት ግቢ ዉስጥ በነበረዉ ክፍት መሬት ላይ ሰርቪስ ቤት እና ከ1-22 የተዘረዘሩትን አትክልቶች ያለማሁት ቢሆንም አሁን ይዞታዉን ለወራሾች እንዲተላለፍ ዉሳኔ ስለተሰጠ ግምቱን ብር 908800 እንዲከፍሉኝ በማለት ከሳለች፡፡

በዚህ ክስ ላይ ከ1ኛ-5ኛ ተከሳሾች ባቀረቡት መልስ ይህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኘ በመሆኑ እና አትክልቱን እርሷ ስላልተከለች የንብረት ግምት እንዲከፈለኝ በማለት ያቀረበችዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ 6ኛ ተከሳሽ በበኩሉ ባቀረበዉ መልስ የከሳሽ ክስ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃ በመመዘን በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሾች የቤት እና የአትክልት ግምት በአጠቃላይ ብር 104180 ለከሳሽ እንዲከፍሉ፣ ሰርቪስ ቤቱ እና አትክልቶቹ የዉርስ ንብረት ሆኖ ተከሳሾች እንዲከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

የሥር 1ኛ-5ኛ ተከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ባዮች ከዚህ ቀደም የአክስታቸዉ ይዞታ 800 ካ.ሜ የሆነዉን በዉርስ ለመከፋፈል በፍ/ቤት ክስ ባቀረቡ ጊዜ መልስ ሰጭ /የሥር ከሳሽ/ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብታ ስትከራከር በይዞታዉ ላይ ስለሰራችዉ ቤት ሲሆን በዚህ መሰረት የቤቱ ግምት እንዲከፈላት እና ቤቱ ወደ ዉርስ ተቀላቅሎ እንዲከፋፈሉ የተወሰኑ በመሆኑ፣ መልስ ሰጭ ከዚህ ዉሳኔ በኋላ እንደአዲስ የአትክልቶች ግምት እንዲከፈለኝ በማለት ክስ ያቀረበች በመሆኑ ይህ ደግሞ ዳኝነት በአንድ ቦታ አጠቃላ መጠየቅ ሲገባት ከፋፍላ የጠየቀች በመሆኑ፣ የሥር ፍ/ቤት የሰርቪስ ቤት ግምት ይግባኝ ባዮች እንዲከፍሏት በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ቢሆንም የአትክልቶችን ግምት እንዲከፍሏት የሰጠዉ ዉሳኔ ግን ያለአግባብ ነዉ፣ ይግባኝ ባዮች የአትክልቶችን ግምት ለመልስ ሰጭ መክፈል የለባቸዉም በማለት ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበዉን ቅሬታ ዉድቅ በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ21/5/2009 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ከዚህ ቀደም በነበረዉ ክርክር ወራሾች ከዉርስ ንብረት ቀላቅለዉ የጠየቁት አንድ ትልቅ መኖሪያ ቤት ብቻ ነዉ እንጂ የተለያዩ አትክልቶችን ጨምረዉ ባልጠየቁበት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መኖሪያ ቤቱን በተመለከተ ተጠሪዎች የጠየቁትን መብት ለመቃወም ወደ ክርክሩ የገባሁት ሆኖ እያለ በክርክሩ ዉስጥ ያልነበረዉን የተለያዩ አትክልቶችን በተመለከተ በዛን ጊዜ መጠየቅ ነበረባት አሁን መጠየቅ አትችልም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የአሁን አመልካች በቀድሞ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብተሽ ሲትከራከሪ የአትክልት ግምት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልጠየቅሽም በማለት ክሷ ውድቅ ሲደረግ በቀድሞ ክስ አትክልቶች በተመለከተ ክርክር ስለመኖሩ አለመኖሩን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ4/8/2009 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ ጨምሮ የሥር ተከሳሾች በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት የአክስታቸዉን የወ/ሮ ሀዋ ኡስማን በ800 ካ.ሜ ይዞታ ዉስጥ የሚገኘዉን ንብረት እና ይዞታ ለመከፋፈል ዳኝነት ጠይቀዉ የነበሩ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በበኩሏ በዚህ ይዞታ ዉስጥ የሰራችዉን መኖሪያ ቤት በተመለከተ መብቷን ለማስከበር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብታ እንደተከራከረች የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ጉዳይ ለምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ ፍ/ቤቱ ወራሾች የቤቱን ግምት ለአመልካች ከፍሏት ቤቱን ወደ ዉርስ ንብረት ተቀላቅሎ እንዲከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበችዉ ክርክር በቀደመዉ ክርክር የሥር ተከሳሾች ስለ ቤት እንጂ ስለአትክልት ዳኝነት ስላልጠየቁ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ሲገባ ስለአትክልት የማነሳበት ሁኔታ የለም የሚል ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ጣልቃ ለመግባት አቤቱታ ሲታቀርብ አትክልቶች አለኝ ብላ የጠየቀችዉ ነገር የለም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በ800 ካ.ሜ ይዞታ ዉስጥ የሚገኘዉን የዉርስ ንብረትና ይዞታዉን እንዲትለቅ ዉሳኔ የሰጠ ስለሆነ ለመጠየቅ መብት የላትም የሚል ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጭ የአሁን ተጠሪ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ለመከፋፈል በክሳቸዉ ዝርዝር ስለማቅረባቸዉ የገለጸዉ ነገር የለም፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች በቀደመዉ ክርክር ጣልቃ ገብታ ስትከራከር አትክልቶችን መጠየቅ ነበረባት ከማለት ዉጭ የሥር ተከሳሾች አትክልቶችን ለመከፋፈል ዝርዝር ማቅረባቸዉን በዉሳኔዉ ያመለከታዉ ነገር የለም፡፡ ይህን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር በሕግ አግባብ ማየቱ ተገቢ ነዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ መሰረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 እንደሚደነግገዉ ባንድ ክስ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መካከል ያለዉ ክርክር ያገባኛል ወይም መብቴን ይነካል የሚለዉ ሶስተኛ ወገን ፍርድ ወይም ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ጣልቃ ገብ ሆኖ ለመከራከር እንደሚችል ያመለክታል። ከዚህ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ሶስተኛ ወገን በሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መካከል በሚደረገዉ ክርክር ያገባኛል ወይም መብቴን ይነካል በማለት ወደ ክርክሩ መግባት የሚችለዉ ተከራካሪ ወገኖቹ በግልጽ ዳኝነት ጠይቀዉ የሚከራከሩበት ንብረት፣ ጥቅም፣ ወይም መብት ላይ ነዉ። ባንድ ክስ በሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መካከል በሚደረገዉ ክርክር በግልጽ ዳኝነት ያልተጠየቀበትን ንብረት፣ ጥቅም፣ ወይም መብት በተመለከተ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጣልቃ ገብቶ መብት ማስከበር የሚቻልበት ሁኔታ የለም።

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሥር ከሳሾች የአክስታቸዉን 800 ካ.ሜ የሆነዉን ይዞታና ንብረት ለመከፋፈል ዳኝነት መጠየቃቸዉን እንጂ አሁን ለክርክር ምክንያት የሆኑትን የተለያዩ አትክልቶችን ለመከፋፈል በግልጽ ዳኝነት መጠየቃቸዉን የሚያመለክት ነገር የለም። የሥር ተከሳሾች በቀድሞዉ ክስ እነዚህ አትክልቶች ለመከፋፈል በግልጽ ዳኝነት ካልጠየቁ ደግሞ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብተው ሲትከራከር መብቷን ለማስከበር የሚጠይቀዉ ነገር አይኖርም። አመልካች ጣልቃ ገብ እንጂ ከሳሽ እስካልሆነች በቀድሞ ክርክር እነዚህን አትክልቶች በተመለከተ በግልጽ ዳኝነት እስካልተጠየቀ ድረስ መብቷን ለማስከበር የምትጠይቀዉ ነገር የለም። የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር አመልካች በ800 ካ.ሜ ዉስጥ የሚገኘዉን ንብረትና ይዞታ ላይ መብት የላትም ተብሎ ተወስኗል ይባል እንጂ ክርክሩ የይዞታ ሳይሆን የአትክልት በመሆኑ አመልካች በአትክልቶች ላይ መብት የላትም ተብሎ በግልጽ ዉሳኔ እስካልተሰጠ ድረስ በአትክልቶች ላይ ዉሳኔ ተሰጥቷል ሊባል አይችልም። በደፈናዉ ንብረት ተብሎ ዉሳኔ ተሰጥቶም ከሆነ በትርጉም አትክልቶችን ያጠቃልላል ተብሎ በመተርጎም አመልካች መብት የላትም ለማለት አይቻልም። በመሆኑም የአሁን አመልካች ጣልቃ ገብ ነበረች እንጂ ቀጥታ ክስ ያላቀረበች በመሆንዋ እና ለክርክር ምክንያት በሆኑት አትክልቶች በተመለከተ በግልጽ ዳኝነት ባልተጠየቀበት ከዚህ ቀደም በነበረዉ ክርክር መብቷን አጠቃልላ መጠየቅ ነበረባት አሁን እንደአዲስ ከፋፍላ መጠየቅ የለባትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.216

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና 218 መሰረት ክሷ ተቀባይነት የለውም ማለት ከፍ ሲል የተመለከተውን የሕግ ድንጋጌ የሚቃረን ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የሥር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በቀደመዉ ክርክር ጣልቃ ገብ እንጂ ቀጥታ ክስ ያቀረበች ወገን ባልሆነችበት እና ለክርክር ምክንያት በሆኑት አትክልቶች በተመለከተ በቀደመዉ ክርክር ግልጽ ዳኝነት ባልተጠየቀበት አመልካችዋ ከዚህ በፊት መብቷን አጠቃላይ መጠየቅ ነበረባት አሁን ከፋፍላ ያቀረበችዉ ተቀባይነት የለውም በማለት ክሷን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.207855 በ15/3/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.253490 በ5/4/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ እንደተመለከተዉ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን የተለያዩ አትክልቶችን በተመለከተ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች የቤት ግምት ለአመልካች ተከፍሎ ቤቱ ወደ ዉርስ ንብረት ተቀላቅሎ ወራሾች እንዲከፋፈሉት በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
6. በ29/6/2009 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 129534

ቀን 24/01/2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ረታ ቶሎሳ

ተክሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- የሊቦ ከምከም ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት - ዓ/ህግ አበበ ሙሉ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ ወ/ሮ እናትነሽ ዘለቀ ጠበቃ በላይ መሸሻ ቀረቡ

2ኛ አቶ አበባው ክብረት

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የግንባታ ውል የሚመለከት ክርክር ሲሆን የጀመረው በአ/ብ/ክ/መ የሊቦ ከምከም ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በመዝገብ ቁጥር 6118656 ባቀረበው መነሻ ነው ፡፡ አመልካች ባቀረበው ክስም ከ1ኛ ተጠሪ በተደረገው የግንባታ ውል ስምምነት ጤና ጣቢያ ለመስራት በብር 459,779.81 /አራት መቶ ሀምሳ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ዘጠኝ 81/100 ሚዲታ ገብተው 1ኛ ተጠሪ ለስራ ማስጀመሪያ ቅድመ ክፍያ ብር 137,931.50 የወሰዱ ቢሆንም ሥራውን በ10 ቀን አልጀመሩም ፡፡ 2ኛ ተጠሪም ሥራውን ለመስራት ውክልና የወሰዱ ቢሆንም በ10 ቀን ውስጥ ምንም ዕቃ አላስቀመጡም ፡፡ በመሆኑም ውሉ እንዲሰረዝ በቅድመ ክፍያ የተወሰደውን ገንዘብ እንዲመልሱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው ፡፡
2. የስር ተከሳሾች /ተጠሪዎች/ ባቀረቡት የመከላከያ መልስ 2ኛ ተጠሪ ሊከሰሱ እንደማይገባ የተከራከሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ውሉ የሚሰረዝበት ህጋዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት አይኖርም ፤ውሉ ላይ የተጠቀሰው ሥራ እና ሳይት ፕላኑ ላይ የተቀመጠው ሥራ መሰረታዊ ልዩነት ያለው ስለመሆኑ የሚፈጀው ገንዘብና ጊዜ ልዩነት የሚያመጣ በመሆኑ ውሉ እንዲሻሻል በመጠየቅ በቅድሚያ ክፍያ መልክ የወሰደው ገንዘብ ግን የሚመለስበት አግባብ እንደሌለ በመጥቀስ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል ።

3. በዚህ መልክ ክርክሩ ያቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር ከመረመረ እና ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነው ያለው ጭብጥ ከመሰረተ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ቅድመ ክፍያ የግንባታው አጠቃላይ ዋጋ 30% መቀበሉን የስራ ዝርዝር እና ሳይት ፕላኑ የማይጣጣም ስለመሆኑ ፤የስራ ዝርዝሩ OPd የሚል ሲሆን ፕላኑ ላይ ደግሞ IPd የሚል ስለመሆኑ፤ ይህ ደግሞ የዋጋ ልዩነት እንደሚያስከትል አመልካች ተጠሪዎችን ማስገደድ የሚችለው ፕላኑ በማስተካከል ወይም የሚያስፈልገው ወጪ በባለሙያ አስገምቶ በማስተካከል ብቻ ስለመሆኑ ፤ አመልካች ውሉ በማቋረጡ የሚከፈለው ኪሳራ ካለ ተጠሪዎች የመጠየቅ መብት እንደላቸው በመግለጽ ክሱን ውድቅ በማድረግ ወሰኗል ።የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመቀጠልም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም ። አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም የአሁኑ ሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን የአቤቱታው መሰረታዊ ይዘት ሲታይም ፡- የስር ፍርድ ቤቶች ግራቀኙ ያደረጉት ውል አይፈርስም በማለት የቅድመ ክፍያው እጣ ፋንታ ሳይወሰኑ ማለፋቸው ተገቢ አለመሆኑን ፤1ኛ ተጠሪ ልዩነት እንዳለው እያወቁ ወደ ውል የገቡ በመሆኑ ውሉ ተሻሽሎ መቀጠል አለበት ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው። የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው ግንባታ ሳይጀመር የቀረው በአሁኑ አመልካች ምክንያት ነው የሚባል ቢሆን ተጠሪ በቅድሚያ የወሰዱት የውለታውን ገንዘብ 30% እንዲመልሱ የተጠየቀው ዳኝነት የመታለፋ አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ማጣራት ይቻላል ዘንድ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ይቅረብ ተብሏል ። ተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ባቀረቡት የጽሑፍ መልስ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል ። አመልካች አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቧል ።

4. የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከትነው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበትን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

5. እንደመረመረነውም አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የግንባታ ውል ስምምነት በማድረግ ቅድመ ክፍያ 30% ወይም ብር 137,931.50 የወሰዱ ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም ። አመልካች ባቀረበው ክስ ያደረጉት ውል ተሰረዞ በቅድመ ክፍያ የተወሰደው ገንዘብ እንዲመለሰለት ጠይቋል ። 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ውሉ ተሻሽሎ የፕሮጀክቱ ገንዘብ ተጨምሮ ሥራውን ከሚቀጥል በቀር በቅድመ ክፍያ መልክ የወሰደው ገንዘብ ለመመለስ የሚገደድበት አግባብ አለመኖሩን በመግለጽ ተከራክሯል ። ጉዳዩን ያጣራው የስር ፍርድ ቤት በግንባታ ውሉ ያለው የስራ ዝርዝር እና ሳይት ፕላኑ የማይጣጣም ስለመሆኑ ሥራውን ተጨማሪ ውጪ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ሥራውን መቀጠል የሚችለው ፕላኑ በማስተካከል የሚያስፈልገው ወጪ በባለሙያ አስገምቶ በማስተካከል ብቻ ስለመሆኑ በመግለጽ ክሱን ውድቅ ማድረጉን መዝገቡ ያሳያል ። ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች የቅድመ ክፍያ 30% ከከፈለ በኋላ ከተጠሪዎች ጋር በተነሳው አለመግባባት ሥራውን አለመሰራቱን ነው ። የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ ውድቅ በማድረግ የወሰነ ቢሆንም በቅድመ ክፍያ ተወሰደ የተባለው ገንዘብ በተመለከተ ግን ያለው ነገር የለም ። አመልካች እና ተጠሪዎች ያደረጉት የግንባታ ውል ግራቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሰረት የማይፈጸም ከሆነ ሊኖር የሚችለው ህጋዊ ውጤት ከፍ/ሕ/ቁ 1815 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ማየቱ ተገቢ ይሆናል ። በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ውል የተሰረዘ ወይም የፈረሰ ከሆነ ግራቀኙ ውለታ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ እንደሚገባ በግልጽ ተመልክቷል።

6. አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው ውል ባህሪ ሲታይም አስተዳደራዊ ውል ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል። በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የተደረገው የጤና ጣቢያ ግንባታ ውል ከመሆኑ አንፃር የአስተዳደር አካሉ ውለታ የማፍረስ መብት ያለው ስለመሆኑ ተጠሪም ውሉ በመፍረሱ ምክንያት ጉዳት ያደረሰበት ቢሆን ካሳ የመጠየቅ መብት እንዳለው የፍ/ሕ/ቁ 3180 እና 3181 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት ያስገነዝቡናል ። በመሆኑም የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገው የግንባታ ውል በተፈጠረው አለመግባባት የማይቀጥል ስለመሆኑ ግልጽ በሆነበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት በቅድመ ክፍያ የተወሰደውን ገንዘብ በተመለከተ ምንም ሳይል ማለፉ በሕጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም። በሌላ በኩል አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው ውል አስተዳደራዊ ውል ከመሆኑ አንፃር መንግስት ውሉን የመሰረዝ መብት አለው። የአሁኑ ተጠሪዎች የደረሰባቸው ጉዳት ካለ ካሳ ከሚጠይቁ በቀር መንግስት ውል እንዲያሻሽል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማስገደድ ወይም በቅድመ ክፍያ የተወሰደውን ገንዘብ ያለመመለስ መብት የላቸውም ብለናል ። በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ የቅድሚያ ክፍያ ይመለስልኝ የሚል ሆኖ ሳለ እና ውሉም የሚቀጥልበት የህግ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው የፍ/ሕ/ቁ 1815 ፤ 3180 እና 3181 ያላገናዘበ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል ። በዚህም ተከታዩን ወስነናል ።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በደቡብ ጎንደር መስተዳደር የሊቦ ከምከም ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0118656 በ16/02/2008 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52825 በ01/04/2008 ዓ.ም የሰጠው ብይን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/አ/መ/ቁ 55983 በ08/09/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል ።
2. የአሁኑ ተጠሪዎች ከአመልካች በቅድመ ክፍያ የወሰዱት ከፕሮጀክቱ አጠቃላይ ዋጋ 30% ወይም ብር 137,931.50 /አንድ መቶ ሰላሳ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አንድ ከሀምሳ ሳንቲም / ሊመለሱ ይገባል በማለት ወስነናል ።
3. ተጠሪዎች ከውሉ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የደረሰባቸው ኪሳራ ካለ በሕጉ አግባብ ክስ አቅርበው የመጠየቅ መብታቸው ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል ።
4. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል ።

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 128746

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ፀጋየ አስማማው

አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-ሻምበል መሐመድ ብርሃን ረዳ -የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ዘምዘም መኮንን-ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58200 በ06/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142615 በ06/07/2008 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

በንብረት ክፍያ ክርክሩ ፍርድ ካረፈባቸው ንብረቶች መካከል ለዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነው ራዕይ 2001 ሁለገብ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ግራ ቀኙ በአመልካች ስም ያላቸው ድርሻ ነው፡፡በዚህ ማህበር ውስጥ በአመልካች ስም ያለው ድርሻ ተጣርቶ ክፍፍል እንዲፈጸምላቸው ጥያቄ ያቀረቡት ተጠሪዋ ሲሆኑ አመልካቹም የአባልነት ድርሻው የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት መሆኑን አምነው መልስ በመስጠታቸው ፍርድ ቤቱ አመልካች ያላቸው ድርሻ ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ከሰጠ በኃላ ከማህበሩ በጽሁፍ የተሰጠውን ምላሽ መሰረት አድርጎ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በማህበሩ ውስጥ እንዳላቸው ከተረጋገጠው ብር 174,412.65 (አንድ መቶ ሰባ አራት ሺህ አራት መቶ አስራ ሁለት ከስድሳ አምስት ሳንቲም) ውስጥ ግማሹ የተጠሪዋ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ እና አመልካች በማህበሩ ውስጥ ያላቸው ድርሻ መጠን በድጋሚ ተጣርቶ እንዲቀርብ ሁለት ጊዜ ትዕዛዝ ሰጥቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከተከናወነው ኦዲት ውስጥ በ23/05/2008 ዓ.ም. በተጻፈ መሸኛ የተላከለትን ሁለተኛ የኦዲት ሪፖርት መርምሮ በዚህኛው የኦዲት ሪፖርት ላይ የተገለጸው አመልካች ከማህበሩ ያገኙት ድርሻ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ከተገለጸው መጠን በላይ ሆኖ መገኘቱን በምክንያትነት ይዞ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በተከናወነው ኦዲት መሰረት የቀረበው ሪፖርት ማህበሩ ባለዕዳ መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ ሳለ አመልካች ከማህበሩ ገንዘብ እንዳገኙ ተቆጥሮ ከተጠሪዋ ጋር እኩል ይከፋፈሉ ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ክርክሩ የተስተናገደበትን የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ጭምር አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ በመቀበል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካቹ በማህበሩ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ወይም ከማህበሩ ያገኙትን ትርፍ በተመለከተ ኦዲቱ በድጋሚ ተከናውኖ ሪፖርት እንዲቀርብለት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ኦዲቱ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ተከናውኖ በ16/10/2007 ዓ.ም. በተጻፈ መሸኛ ሰባት ገጽ የኦዲት ሪፖርት የተላከት መሆኑን፣በዚህ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው አመልካች በ02/11/2007ዓ.ም.፣ተጠሪዋ ደግሞ በ29/10/2007 ዓ.ም. የተጻፈ አስተያየት ማቅረባቸውን፣ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን አስተያየት በተለይ ደግሞ በተጠሪዋ የቀረበውን የተቃውሞ አስተያየት መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማድረግ ኦዲቱ አሁንም በድጋሚ ተከናውኖ ሪፖርት እንዲቀርብለት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ኦዲቱ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ተከናውኖ በ23/05/2008 ዓ.ም. በተጻፈ መሸኛ ሶስት ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና ስምንት ገጽ ደጋፊ ሰነድ የተላከት መሆኑን፣በዚህ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው አመልካች በ01/06/2008 ዓ.ም.፣ተጠሪዋም በተመሳሳይ ቀን በ01/06/2008 ዓ.ም. የተጻፈ አስተያየት ማቅረባቸውን፣በተጠሪዋ በኩል የቀረበው አስተያየት ሪፖርቱ ግልጽነት የሌለው በመሆኑ ቢቻል ቀደም ሲል በስር ፍርድ ቤት በቀረበው የኦዲት ሪፖርት መሰረት ውሳኔ እንዲሰጣቸው፣ካልሆነም እንደገና እንዲጣራ እንዲደረግ የሚጠይቅ መሆኑን እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሪፖርቱን እና የግራ ቀኙን አስተያየት ከመረመረ በኃላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ያጸናው በመጨረሻ በቀረበው ሪፖርት መሰረት አመልካች ከማህበሩ ያገኙት ድርሻ በስር ፍርድ ቤት በቀረበው የኦዲት ሪፖርት ላይ ከተገለጸው መጠን በላይ ነው በሚል ምክንያት መሆኑን የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መዝገብ ያመለክታል።

እንደሚታወቀው ማንኛውም ፍርድ ቤት ባለጉዳዮችን ማከራከር የሚገባው የተለያዩበት የሕግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ምን እንደሆነ አረጋግጦ ለጉዳዩ ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ ስለመሆኑ፣የነገር ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ተከራካሪ ወገን ያመነውን የሕግ ወይም የነገር አግባብ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በማስተባበል የካደ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ፣ፍርድ ቤቱ ጭብጥን ለመመስረት የሚችለውም ከግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሰረት በሚደረግ ምርመራ በተከራካሪ ወገኖች የሚሰጠውን መልስ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የጭብጥ አመሰራረትን በሚደነግጉ ከቁጥር 246 እስከ 248 በተመለከቱት የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በክርክሩ የተያዘው ጭብጥ ምን እንደሆነ እና12010 ጭብጡ በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የተወሰነበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ የፍርድ አጻጻፍን በሚመለከተው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 182 (1) ተደንግጎ ይገኛል።

በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ስም በማህበሩ ውስጥ ያለው ድርሻ የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት መሆኑ በአመልካቹ የታመነ ሲሆን እያከራከረ ያለው በማህበሩ ውስጥ አመልካች ያላቸው ድርሻ ምን ያህል ነው? ማህበሩ ለአባላቱ ያስገኘው ትርፍ አለ ወይስ የለም?

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አለ ከተባለ አመልካች ከማህበሩ ያገኙት ወይም ማግኘት የሚገባቸው ወይም የተካፈሉት ድርሻ ምን ያህል ነው? የሚሉ እና ተያያዥ ጥያቄዎች ናቸው።እነዚህ ጥያቄዎች ደግሞ በባህሪያቸው ፍርድ ቤቱ በራሱ ወይም ብቻውን የሚፈታቸው ሳይሆኑ የኦዲት ባለሙያ እገዛ የሚጠይቁ ናቸው።ፍርድ ቤቶች ሂሳብ የማጣራት ስራ በምትክ ዳኞች ወይም በልዩ አዋቂዎች /ኤክስፐርቶች/ ተከናውኖ ውጤቱ እንዲቀርብላቸው ትዕዛዝ መስጠት የሚችሉ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 133 እስከ 136 ድንጋጌዎች የተመለከተ ሲሆን ሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች ኦዲቱን በተመለከተ የተለያየ ትዕዛዝ ሲሰጡ የነበረውም በዚሁ ስርዓት መሰረት ነው።በዚህ አግባብ በጽሁፍ ተዘጋጅተው በቀረቡት የኦዲት ሪፖርቶች ላይ ገልጽ ያልሆኑትን ወይም አሻሚ መስለው የታዩ ነጥቦችን ማጣራቱ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 133 (3) በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት የኦዲት ስራውን አከናውነው ሪፖርቱን ያቀረቡ ልዩ አዋቂዎችን ምስክርነት መስማት ይጠበቅባቸዋል።

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ኦዲቱ በድጋሚ ተከናውኖ ሪፖርት እንዲቀርብለት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ኦዲቱ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ተከናውኖ በ23/05/2008 ዓ.ም. በተጻፈ መሸኛ የተላከው ሶስት ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና ስምንት ገጽ ደጋፊ ሰነድ ማህበሩ በአንድ በኩል በኪሳራ ላይ እንደነበረ እና በሌላ በኩል ደግሞ ትርፋማ እንደነበረ የሚያመላክት አሻሚ ይዘት ያለው መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል።ይህም የኦዲት ሪፖርቱ ግልጽነት የሌለው ነው በማለት ተጠሪዋ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሪፖርቱ ላይ የሰጡት አስተያየት ተገቢነት የነበረው መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 133 (3) ድንጋጌ መሰረት በሪፖርቱ ላይ የሚያሻማ በሚመስል አገላለጽ የሰፈረውን ሀሳብ ይዘት እንዲያስረዱ ፍርድ ቤቱ ስማቸው በሪፖርቱ ላይ የተጠቀሰውን የሂሳብ ባለሙያዎች አስቀርቦ መስማት ይጠበቅበት ነበር። ኦዲቱን ያከናወኑ ኦዲተሮች በሪፖርቱ ላይ የሚያሻማ በሚመስል ሁኔታ የሰፈረውን ሀሳብ ለይተው እንዲያስረዱ ባልተደረገበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች የኦዲት ሪፖርቱን እራሳቸው በተረዱት አግባብ ተርጉመው የሚሰጡት ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ ነው ሊባል የሚችል ካለመሆኑም በላይ በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የሚያስችልም አይደለም።በመሆኑም በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ጉዳዩ ወደ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተመልሶ አዲቱን ያከናወኑት ባለሙያዎች ቀርበው ስለሪፖርቱ አጠቃላይ ይዘት ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ ከተደረገ በኃላ ተገቢው ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 58200 በ06/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142615 በ06/07/2008 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ራዕይ 2001 ሁለገብ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ግራ ቀኙ በአመልካች ስም ያላቸውን ድርሻ በተመለከተ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. ቁጥሩ 142615 የሆነውን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ አስቀርቦ ራዕይ 2001 ሁለገብ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ግራ ቀኙ በአመልካች ስም ያላቸውን ድርሻ በተመለከተ አዲቱ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ተከናውኖ በ23/05/2008 ዓ.ም. በተጻፈ መሸኛ የተላከውን ሶስት ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና ስምንት ገጽ ደጋፊ ሰነድ እንዲሁም በዚሁ የኦዲት ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ የሰጡትን አስተያየት ከመዝገቡ ውስጥ ከተመለከተ በኃላ በሪፖርቱ መጨረሻ ላይ ስማቸው የተጠቀሰውን ሶስት ኦዲተሮች፣እነዚህ ኦዲተሮች በቂ በሆነ ሕጋዊ ምክንያት ሊገኙ እንደማይችሉ የሚረጋገጥ ከሆነም ሰለጉዳዩ ሊያስረዱ የሚችሉ ሌሎች ኦዲተሮችን ከዚያው ተቋም አስቀርቦ ስለሪፖርቱ አጠቃላይ ይዘት ምስክርነታቸውን ከሰማ በኃላ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንደ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት ከተመለከተው ውጪ ያለው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. በዚህ መዝገብ በ14/03/2009 ዓ.ም. እና በ27/07/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም ዕግድ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 131950

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች ፡- ወ/ሮ የሺመቤት ገ/ዓዲቅ - ጠበቃ ተፈሪ ከበደ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ፋንታዬ ሽጉልቱ - ተወካይ ወ/ሮ ንጋቷ ባየህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በፍቺ እና የንብረት ክፍፍል ስምምነት መነሻ አለአግባብ የተወሰደ ነው የተባለን ንብረት ለማስመለስ ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በባሶና ወራና ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 08006 በ27/03/2008 ዓ.ም. የተሰጠው እና በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0119440 በ13/05/2008 ዓ.ም. ተሻሽሎ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 030-7079 02/10/2008 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡-አቶ ደምሴ ባየህ የተባሉ የተጠሪዋ ልጅ እና አመልካቿ ከሃያ ዓመታት በላይ በጋብቻ ተሳስረው ከቆዩ በኃላ በመካከላቸው በተፈጠረው አለመግባባት መነሻ የፍቺ እና የንብረት ክፍፍል ስምምነት አድርገው ይኸው ስምምነት በወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 07651 በ08/09/2007 ዓ.ም.የተመዘገበ እና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረቶቹንም የተከፋፈሉ መሆኑን፣ከዚህ በኃላ የንብረት ክፍፍል ስምምነቱ የተደረገው ተጋቢዎቹ በጋራ ባፈሩት ንብረት ላይ ሳይሆን በእኔ ንብረት ላይ ነው በማለት የአሁኗ ተጠሪ በ24/09/2007 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኗ አመልካች እና 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት የተጠሪዋ ልጅ /የአመልካቿ የቀድሞ ባለቤት/ ላይ የንብረት ያስረክቡኝ ክስ ማቅረባቸውን፣አመልካቿ ለክሱ በሰጡት መልስ ክሱ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው፣ስምምነቱ እንዲፈርስ ባልተደረገበት ሁኔታ አዲስ ክስ ሊቀርብ አይገባውም፣ የንብረት ክፍፍሉ ሲደረግ ተጠሪዋ በቦታው እያሉ ባልተቃወሙበት ሁኔታ አዲስ ክስ ማቅረባቸው ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦችን ካስቀደሙ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ በፍርድ ቤት በጸደቀው ስምምነት መሰረት ክፍፍል የተደረገባቸው ንብረቶች በጋብቻው ውስጥ የተፈሩ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የተከራከሩ መሆኑን፣የስር 2ኛ ተከሳሽን በተመለከተ በእጃቸው የነበረውን 0.5 ጥማድ የእርሻ ይዞታ መልሰውልኛል በማለት ተጠሪዋ ክሱ እንዲቋረጥ ያደረጉ መሆኑን፣ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦችን በብይን አልፎ በተጠሪዋ እና በአመልካቿ መካከል ክሱን እና የግራ ቀኙን እንዲሁም የማጣሪያ ምስክሮችን ከሰማ እና ከወረዳው መሬት እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ተገቢውን ማጣራት ካደረገ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ክርክር ያስነሳው 0.5 ጥማድ የእርሻ መሬት የተጠሪዋ ልጅ እና አመልካቿ በመጋዞ ሲጠቀሙበት እንደነበረ የተገለጸ ቢሆንም የይዞታ ባለመብትነቱ ግን የተጠሪዋ እንደሆነ ከሚመከተው አካል በቀረበ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን እና ክፍፍል የተደረገባቸው ከብቶች እና የተለያዩ እህሎችም የተጠሪዋ እንደሆነ መረጋገጡን ገልጾ አመልካቿ በክፍፍሉ የወሰዷቸውን ከብቶች እና በውሳኔው ላይ መጠናቸው እና ዓይነታቸው በዝርዝር የተገለጸውን የተለያዩ እህሎች ለተጠሪዋ እንዲመልሱ ውሳኔ መስጠቱን፣ይግባኙን የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ክፍፍል የተደረገባቸው ከብቶች እና የተለያዩ እህሎች የተጠሪዋ ስለመሆናቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን አሻሽሎ ከብቶቹን እና እህሎቹን አመልካቿ የመመለስ ግዴታ የለባቸውም በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን እና በክልሉ ሰበር ችሎት በትዕዛዝ የጸናውም ይኸው ውሳኔ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቿ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ለ24 ዓመታት ሲጠቀሙበት የኖሩትን የእርሻ መሬት የስር 2ኛ ተከሳሽ ያገኙት ከእናታቸው ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቿን መብት የማሳጣታቸውን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባው ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ነጥብ አንጻር መርምረናል።

በዚህም መሰረት አመልካቿ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡት ከብቶቹን እና እህሎቹን ይመልሱ መባሉን በመቃወም ብቻ ሳይሆን በ0.5 ጥማድ መሬት ላይ መብት የላቸውም መባሉን በመቃወም ጭምር ስለመሆኑ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ የገለጹ ሲሆን መሬቱ ጭምር የይግባኝ ምክንያት የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪዋም በሰበር መልሳቸው ላይ ገልጸዋል። በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 339 ድንጋጌ መሰረት ይግባኙ በተሰማበት ጊዜም ግራ ቀኙ በመሬት ይገባኛል ጉዳይ ላይ ጭምር የተከራከሩ መሆኑን የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ያመለክታል።ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ክርክሩን የሰማው በመሬት ይገባኛል ጉዳይ ላይ ጭምር ቢሆንም በመጨረሻ ግን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በሌሎች ነጥቦች ረገድ ሲያሻሽል በመሬት ይገባኛል ክርክሩ ረገድ ግን ውሳኔ ሳይሰጥ በዚህ ረገድ በአመልካቿ የቀረበውን ቅሬታ በዝምታ አልፎታል።በመሰረቱ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሚሰጠው የፍርድ ውሳኔ የመጀመሪያውን ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ያሻሻለው ወይም የለወጠው እንደሆነ በትችቱ ላይ ለይግባኝ ባዩ የሚገባውን ዳኝነት ዘርዝሮ መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 182 (1) ድንጋጌ ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኝ በተባለበት ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥ የሰፈረው ማስረጃ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ግምት በቂ ሆኖ ሲገኝ የነገሩን ጭብጥ በማሻሻል ወይም በመለወጥ ተገቢ መስሎ የታየውን የመጨረሻ ፍርድ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ እና ይግባኝ የተባለበት ፍርድ ቤት ፍርዱን የሰጠው በሌላ ምክንያት ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመዝገቡ ላይ በተረዳው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት ጭብጡን ለውጦ ከመፍረድ የማይታገድ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 242 ስር ተመልክቶአል፡፡ በመሆኑም አመልካቿ የይግባኝ ቅሬታ ባቀረቡበት የ0.5 ጥማድ መሬት ክፍያ ጥያቄ ላይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እንደሰማ ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ሊያሳርፍበት ሲገባው በዝምታ ማለፉ ስነ ስርዓታዊ ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በእርግጥ በአንድ ክርክር እና ሙግት ላይ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ጥያቄው ተቀባይነትን ሳያገኝ የታለፈ እንደሆነ የተጠየቀው ዳኝነት እንደተከለከለ የሚቆጠር ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 5 (3) ድንጋጌ ስር ተመልክቶአል፡፡ይህ ማለት ግን በቀድሞ ክርክር ጊዜ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት በዝምታ የታለፈ ጉዳይ በሌላ ጊዜ የክስ እና የክርክር ምክንያት ሊሆን አይችልም ማለት እንጂ በተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ ፍርድ ቤቶች በዝምታ ማለፍ ይችላሉ ማለት አይደለም፡፡ይህ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዝምታ የታለፈው የዳኝነት ጥያቄ ተገቢ ፍሬ ነገሮችን ማጣራትን እና ማስረጃ መመዘንን ጭምር የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩ ወደ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተመልሶ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት ከሚደረግ በቀር በዚህ ሰበር ደረጃ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በባሶና ወራና ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 08006 በ27/03/2008 ዓ.ም. የተሰጠው እና በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0119440 በ13/05/2008 ዓ.ም. ተሻሽሎ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 030-7079 02/10/2008 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካቿ የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡበትን የ0.5 ጥማድ መሬት ክፍያ ጥያቄ ጉዳይ በዝምታ በማለፍ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ችሎት በትዕዛዝ የጸናው የውሳኔ ክፍል ተሽሮአል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት የተጠቀሰውን የይግባኝ ቅሬታ ነጥብ በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቁት ደግሞ ለባሶና ወራና ወረዳ ፍርድ ቤት እና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት ከተጠቀሰው ውጪ ያለው የውሳኔው ክፍል አልተነካም፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 127484

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ በቀለ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤሕግ- ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

የአሁን ተጠሪ አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና 676/1 በመተላለፍ በኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን ማሕበር ሥብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ደብረመድሐኒት መድሐኔዓለም ቤተክርስትያን ሒሳብ ሹም ሆኖ ሲሰራ ከመጋቢት 2004 ዓ.ም እስከ ሕዳር 2005 ዓ.ም ድረስ ሲሰራ ሀላፊነቱን ወደጎን በመተው የሂሳብ አሰራር እና ደንብ ከሚፈቅደው ውጪ ብር 689,688.34 / ሥድሥት መቶ ሠማንያ ዘጠኝ ሺህ ሥድሥት መቶ ሠማንያ ሥምንት ብር ከሠላሣ አራት ሣንቲም / ከሥር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነት በማጉደል ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበበትን ክስ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጠሪን ምስክሮች ከሰማ በኋላ አመልካች ሊከላከል የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675/1 መሠረት ነው በማለት ብይን ከሰጠ በኋላ የአመልካችን መከላከያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምስክሮች ሰምቶ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675/1/ መሠረት ጥፋተኛ ነው በማለት በአንድ አመት ከሥምንት ወር ቀላል እሥራት እንዲቀጣ ወስኗል።

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል። ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች የኦዲት ምርመራው በሚከናወንበት ወቅት በሐገር አቀፍ ምርጫ በምርጫ አስፈጻሚነት ሥራ ላይ የነበሩ መሆኑ፤ የፍትሕ ሚኒስቴርም አመልካች ኦዲቱ በተሰራበት ወቅት በሐገራዊ የምርጫ ማስፈጸም ሥራ ላይ የነበሩ መሆኑን አረጋግጦ አመልካች በተገኙበት የኦዲት ሥራው ተከናውኖ ውጤቱ እንዲገለጽለት ለአዲስአበባ ፖሊስ ኮሚሽን የልዩ ልዩ ወንጀል ምርመር ዲቪዝዮን ማዘዙን እና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ተሰባስበው አመልካች በተገኙበት ድጋሚ ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ እንዲገለጽለት ቤተክርስቲያንዋን ማዘዙን፤የኢትዮጲያ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤትም ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ ምርጫ ጽ/ቤት አመልካች ከሕዳር 27/2005 ዓ.ም እስከ የካቲት 11/2005 ዓ.ም በመራጮች እና እጩዎች ምዝገባ እንዲሁም ከመጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ.ም እስከ ግንቦት 02 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ በወረዳ 06 ምርጫ ጽ/ቤት አስተባባሪነት ቅዳሜ እና እሁድን የበአል ቀናትን ጨምሮ ሲሰሩ ቆይተው ከግንቦት 12/2005 ጀምሮ ወደ መደበኛ ስራቸው መመለሳቸውን ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ከጻፈው ደብዳቤ መገንዘብ ተችሏል፤በኦዲቱ ሥራ ገንዘብ ያዥ፤የሂሳብ ሹም እና የውስጥ ተቆጣጣሪ አስፈላጊዎች መሆናቸው የኦዲት ሪፖርቱ ያስገነዝባል፤አመልካች ሂሳብ ሹም በመሆናቸው ለኦዲት ሥራው አስፈላጊ ቢሆኑም አዲቱ ሲሰራ አልነበሩም፤ሒሳቡን የሠሩት ባለሙያዎች የኦዲት ሥራው አስፈላጊ የሆኑ ገቢ እና ወጪ የሂሳብ ሰነዶች ባልተገኙበት የተከናወነ ስለመሆኑ በሂሳብ ስራው ሂደት ያጋጠሙን ችግሮች ናቸው በማለት ዘርዝረዋል። በመሆኑም አመልካች የተከሰሱበትን የእምነት ማጉዳል ወንጀል ለማረጋገጥ ዓይነተኛ ማስረጃ ሆኖ የቀረበው የኦዲት ሪፖርት ውጤት የአመልካችን ጥፋት ሊያሳይ አይችልም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ለክሱ መነሻ የሆነው የኦዲት ሥራ ግራ ቀኙ በተገኙበት እና በሚያቀርቡት ማስረጃ በገለልተኛ ሂሳብ አዋቂ በድጋሚ ተሰርቶ ሊቀረብ ይገባል፤የሥር ፍ/ቤት የኦዲት ሥራው ድጋሚ ተመርመረሮ የተገኘው ውጤት ከቀረበለት በኋላ የመሰለውን እንዲወስን በማለት ወስኗል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ከሻረ በኋላ አመልካችን በነጻ ማሰናበት ሲገባው ቀደም ሲል ውሳኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ጉዳዩን በድጋሚ እንዲያይ በማለት ጉዳዩን በመመለስ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ አስቀርቦ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ ስለተገኘ ተሽሯል በማለት ከወሰነ በኋላ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2ለ ውጪ በሆነ ሁኔታ ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ የግራቀኙ ማሥረጃ ተሰምቶ እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት የመለሰበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ በግልጽ የሚደነግግ ባይሆንም ከአጠቃላይ የይግባኝ ዓላማ እና ግብ አንጻር ሊታይ የሚገባው ከመሆኑም በላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወስን ትዕዛዝ ከመስጠት የሚያግደው ነገር የለም በማለት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የፍ/ቤቶች ዋነኛ ሚና እውነትን አፈላልጎ ፍትሐዊ ውሳኔ መስጠት እንደሆነ ከወንጀል ህጉ እና ከወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ እውነትን ለማፈላለግ እና እውነቱ ላይ ለመድረስም ፍ/ቤቶች በሕገመንግሥቱ የተሰጣቸውን ሕገመንግሥታዊ ተልዕኮ በአግባቡ በመወጣት ክርክሩን መምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚችለው ወይም ጥፋተኛ አይደለም ተብሎ በነጻ ሊለቀቅ የሚችለው ጥፋተኛ ሊያደርገው ወይም ነጻ ሊያስለቅቀው የሚችል ተገቢ የሆነ ማሥረጃ ሲቀርብበት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የኦዲት ሪፖርቱ ግራቀኙ በተገኙበት ድጋሚ ተሰርቶ ውጤቱ ከቀረበ በኋላ ሊወሰን ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው አመልካች የኦዲት ምርመራው በሚከናወንበት ወቅት በሐገር አቀፍ ምርጫ በምርጫ አስፈጻሚነት ሥራ ላይ የነበሩ በመሆናቸው ነው፤አመልካች ሂሳብ ሹም በመሆናቸው ለኦዲት ሥራው አስፈላጊ ናቸው፤አመልካች ባልተገኙበት የተከናወነው የኦዲት ሥራ የአመልካችን ጥፋት ሊያሳይ አይችልም በማለት እንደሆነ ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ዓቃቤሕግ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚያስችለውን በቂ ማሥረጃ ካላቀረበ ፍ/ቤቱ ተከሳሽን በነጻ ሊያሰናብተው የሚገባ ቢሆንም በአመልካች በኩል የቀረበው የኦዲት ሪፖርት በአመልካች ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችል በቂ ማሥረጃ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የቀረበው የኦዲት ሪፖርት አመልካችን ጥፋተኛ ለማስባል በቂ አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው የኦዲት ሪፖርቱ አመልካች ባልተገኙበት የተሰራ እና አመልካች ሒሳብ ሹም በመሆናቸው ምክንያት ለኦዲት ሥራው አስፈላጊ መሆናቸውን አምኖ ግራቀኙ በተገኙበት እና ግራቀኙ በሚያቀርቡት ማስረጃ የኦዲት ሥራው በገለልተኛ የሒሳብ ባለሙያ ተሰርቶ በሚቀርበው ውጤት መሠረት ሊወሰን ይገባል በማለት ነው፡፡ ይህ መደምደሚያም አመልካች ባልተገኙበት በተሰራው የኦዲት ሪፖርት መሠረት አመልካች ጥፋተኛ እንዳይባሉ በሌላ በኩል ተጠሪ ክስ ለማስረዳት ያቀረበው የኦዲት ሪፖርት አመልካች ባልተገኙበት የተሰራ ነው ስለተባለ ብቻ አመልካችን ከወዲሁ በነጻ እንዳይለቀቁ የሚያደርግ እና እውነትን አፈላልጎ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ እና የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያሻው ዋነኛ ነጥብ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካችን ጥፋተኛ ለማስባል ዓይነተኛ ማስረጃ ሆኖ የቀረበው የኦዲት ሪፖርት አመልካች ባልተገኙበት የተሰራ ስለሆነ አመልካች ባልተገኙበት የተሰራው የኦዲት ሪፖርት አመልካችን ጥፋተኛ ሊያስብል አይችልም ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ በኋላ ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለስ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለው ነው፡፡

የወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 143 ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም ማስረጃ መጥራት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት በአግባቡ ያልተጣሩ ነጥቦች ሲገኙ እና ለትክክለኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍትሕ አሰጣጥ ሲባል መጣራት ያላባቸው ሆነው ሲገኙ ተገቢ የሆነውን ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩ እንዲጣራ ማድረግ የሚችልበትን ሥርዓት የሚደነግግ ነው።

የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጥፋተኛ ነው በተባለበት ውሳኔ እና በቅጣቱ ይግባኝ በተባለ ጊዜ ጥፋተኛ ነው የተባለበትን ውሳኔ እና ቅጣቱን ሰርዞ ተከሳሹን በነጻ ለመልቀቅ ወይም ፍርዱን ለውጦ ወይም ሳይለውጥ ቅጣቱን ያጸናል፤ይጨምራል ወይም ይቀንሳል በማለት ይደነግጋል።ይህ ድንጋጌ ፍርድን መለወጥ፤ቅጣትን ማጽናት፤ መጨመር፤መቀነስ እንዲሁም ፍርድን ሰርዞ ተከሳሹን በነጻ እስከመልቀቅ ድረስ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሥልጣን የሰጠ ድንጋጌ እስከሆነ ድረስ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተከሳሽ ላይ የቀረበው ማሥረጃ ተገቢ በሆነ ምክንየት ድጋሚ ሊጣራ ይገባል ብሎ ሲያምንበት በድጋሚ ተጣርቶ እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት እንዳይመለስ የሚያደርገው ነው ተብሎ ሊተረጎም አይገባም። በእርግጥ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 143 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የኦዲት ሪፖርቱ ግራቀኙ በተገኙበት በገለልተኛ የሒሳብ ባለሙያ ተሰርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ራሡ ለመወሰን የሚችል ቢሆንም ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ቢወሰን የግራቀኙ የይግባኝ መብት የሚጣብብ በመሆኑ ጉዳዩን ለሥር ፍ/ቤት በመመለስ በሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

<u>ውሳኔ</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 001028 መጋቢት 12 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል።

መዝገቡ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡-

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- ሻለቃ አለማየሁ ወንጀሎ ለኮ - ጠበቃ አይረሳም ሽንቁጤ

ተጠሪ፡- የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16522 ጥር 18 ቀን 2008 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ብይን የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 124937 በቀን 22/02/2009 ዓ.ም በመሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የዳኝነት ሥልጣን የሚመለከት ነው፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ ባቀረበው ክስ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 676/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ በኢ.ፌ.ድ.ሪ የሀገር መከላከያ ሚ/ር የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ውስጥ ከግንቦት 8 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በአልባሳት ዋና ግምጃ ቤት ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሠው ለማስገኘት በማሰብ በሥራው ምክንያት ከመስሪያ ቤቱ ከተረከባቸው የ15 ዓመት የሽልማት ሜዳሊያዎች ውስጥ የሰኔ ወር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግምጃ ቤት ቆጠራ ሰኔ 23 ቀን 2006 ዓ.ም ሲካሄድ 300 ሜዳሊያ የአንዱ ዋጋ ብር 2425.49 ጠቅላላ ብር 727647 ለራሱ ያደረገ/ የወሰደ/ ያስወሰደ/ የሰወረ በመሆኑ ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ የቀረበው ክስ ከደረሰው በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለውም ፤አመልካች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የመከላከያ ሚኒስቴር የመከላከያ ሠራዊት አባል ነኝ በአዋጅ 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ መሠረት በሠራዊቱ አባላት መካከል የሚፈፀም የግድያ የድብደባ ወንጀል ወይም የሠራዊቱ አባላት በሚንስትሩ ንብረት ላይ በሚፈጽሟቸው ማናቸውም ወንጀሎች የማየት ሥልጣን የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው፣ ይህ ከታለፈም ጉድለቱ የተከሰተው ተቀጥሬ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ወስጥ በተደረገ ቆጠራ ነው፤ ምስክሮች ሌላ ተጠርጣሪ እንዳለ እያስረዱ ነበር ስለሆነም የሙያ ሥራን በአግባቡ አለመምራት ነው ክሱ ሊቀርብብኝ የሚገባው ። የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በመቃሚያው ላይ በሰጠው መልስ አመልካች የተከሰሰበት ወንጀል በቀጥታ ከውትድርና ሥራቸው ጋር የሚገናኝ ሳይሆን የህዝብና የመንግስት ንብረት አጉድሏል ተብሎ ነው ይህ የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በሌላ ፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ ሌላ ተጠርጣሪ እያለ የቀረበ ነው የተባለው ወደፊት የሚነሳ እንጂ መቃወሚያ የሚሆን አይደለም ብሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም መርምሮ በአዋጅ 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ በተመለከተው መሠረት የሠራዊቱ አባላት በሚኒስቴሩ ንብረቶች ላይ በሚፈጽሟቸው ማናቸውም ወንጀሎችን ስለሚል እና ከሙስና ወንጀሎች በቀር የሚል ሀረግ ስለሌለ፣ የኢ.ፌ.ድ.ሪ የሀገር መከላከያ ሚ/ር የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ከወንጀል ህግ በኋላ የወጣና በቀዳሚነት ተፈጻሚነት ያለው በመሆኑ እና ልዩ ህግ በህጉ ተፈጻሚነት ያለው በመሆኑ፣ እና አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል ከመሆኑም ባሻገር ፋውንዴሽኑ ራሱን በቻለ ደንብ የተቋቋመ ቢሆንም ሠራተኞቹ ወታደሮች መሆናቸው ዓላማውም የሀገር መከላከያ ሚ/ር የመከላከያ ሠራዊት ሥራ በተቀላጠፈ ማስተናገድ ተጠሪነቱም ንብረቱም /ኒሻኑም/ የመከላከያ ሚ/ር በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለውም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ አነስተኛው ድምጽ ፍ/ቤቱ ሥልጣን አለው ብሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ራሱን የቻለ ተቋም ነው አይደለም የሚለው በቅድሚያ መርምሮ በደንብ ቁጥር 179/2002 አንቀጽ 2/3/ መሠረት በህጉ የሰውነት አካል የተሠጠው ራሱን የቻለ ተቋም መሆኑን በአንቀጽ 8 እና ተከታዮቹ በቦርድ የሚተዳደር አባላቱን ከሠራዊቱ አባላት በተጨማሪ ሌሎች ሰዎችን የሚያሳትፍ ራሱን የቻለ በራሱ በጀት የሚተዳደር ተቋም እና በራሱ መክሰስና መከሰስ የሚችል ነው፣ ተጠሪነቱ ለመከላከያ ሚኒስቴር ይሁን እንጂ በሚንስቴር በጀት የሚተዳደር ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1/ለቀደሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ሳይሆን በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታይ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን ሽሯል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ መሠረት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው፤ አመልካች በመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን አገልግሎት የምሰጠው በሠራዊት አባልነት በመመደብ በመሆኑ የተቋሙን ህጋዊ ሠውነት እና የአመልካችን ልዩ መብት ያላገናዘበ ስለሆነ መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ የሚል ሲሆን አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን አግባብነት ከደንብ ቁጥር 179/2002 አንቀጽ 3፣6፣7፣13/ለ/ ጋር ለማገናዘብ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዞ በሰጠው መልሱ አመልካች ተቀጥረው የሚሰሩት በመከላከያ ፋውንዴሽን ሲሆን ይህም ራሱን ችሎ የተቋቋመ የህግ ሠውነት ያለው ተቋም ነው፤ ሠራተኞችም የፋውንዴሽኑ አንጂ የመከላከያ ሚኒስቴር አይደለም፣ ወታደራዊ ፍ/ቤቶች የተቋቋሙት ወታራዊ ይዘት ያላቸው ነው ፡ አመልካች የፈፀሙት ሲቪል ጉዳይ ነው ስለሆነም ጉዳዩ ወታራዊ ይዘት ያለው ባለመሆኑ ስልጣኑ የመደበኛ ፍርድ ቤት ነው ብሏል፡፡ አልካችም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክርክሩ ሂደት የሚያስገነዝበው አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል እና የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን የአልባሳት ዋና ግምጃ ቤት ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ወቅት በሥራው ምክንያት ፈጽሞታል ተብሎ የቀረበበትን የከባድ የእምነት ማጉደል ሙስና ወንጀል ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት የመዳኘነት ሥልጣን መኖር አለመኖርን የሚመለከት ነው።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 79 የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው የሚለውን በዚሁ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 የፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ወሰን ከሚያመለክተው ጋር አገናዝበን ማየት እንደሚቻለው ማንኛውም ጉዳይ ያለ ገደብ በመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊታይ የማይችል መሆኑን ነው። በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 37 የተቀመጠው የሥልጣን ክፍፍል ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል እና ጉዳዩንም አይቶ ለመወሰን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ ለሌላ የዳኝነት ሠጪ አካል ያልተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህንኑ በፍርዱ ሊያልቅ የሚችለውን ጉዳይ ለማየትና ለመወሰን ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው መደበኛ ፍርድ ቤቶች መሆናቸውን ነው። ስለሆነም መደበኛ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል መሆኑ ላይ ብቻ ሳይወሰኑ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 መሠረት ይኸው ጉዳይ ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ቀርቦ የሚታይ መሆን አለመሆኑን በቀጥታ የመመርመር ግዴታ አለባቸው።

አሁን በያዝነው ጉዳይ ክሱ በመደበኛነት የቀረበለት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በወ/ህ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ130/2/ መሠረት በቀረበለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ይህንን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1/ለ/ መሠረት ለቀዳሚ ወታራዊ ፍርድ ቤት የተሰጠ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለውም የሚል መቅረቡን እና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የተለያየ ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ነው። ስለሆነም በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1/ለ/ መሠረት ተሰጥቷል አልተሰጠም የሚለውን መርምረናል፣ የአዋጁ አንቀጽ 38 የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ሥልጣንን የሚዘረዝር ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ በሠራዊቱ አባላት መካከል በሚፈፀም የግድያ ወይም የድብደባ ወንጀል ወይም የሠራዊቱ አባላት በሚኒስቴሩ ንብረት ላይ በሚፈጽማቸው ማናቸውም ወንጀሎች የዳኝነት ሥልጣን ያለው መሆኑን ይደነግጋል በዚሁ ድንጋጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት በስር ፍ/ቤት የክርክርም ምክንያት የሆነው የሠራዊቱ አባላት በሚኒስትር ንብረት ላይ የሚፈጽሟቸው ማናቸውም ወንጀሎች የሚለውን መሠረት በማድረግ ነው። አመልካች የመከላከያ ሠራዊት አባል ሲሆን የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሞበታል የተባለው በመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን በመሆኑ በመከላከያ ሚኒስቴር ንብረት ላይ ተፈጽሟል ለማለት የሁለቱን አካላት አንድነትና ልዩነት ካቋቋማቸው ድንጋጌዎች ተመልክተናል።

የኢ.ፌ.ድ.ሪ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ.316/2008 አንቀጽ 9/1/ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የተቋቋመ እና ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የሆነ የመንግስት አስፈጻሚ አካል ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 38/1//ለ/ላይ ... በሚኒስቴሩ ንብረት ላይ በሚፈፀሙ ማናቸውም ወንጀል ሲል በዚህ የሀገር መከላከያ ሚኒስትር ንብረት ላይ የሚፈፀም ማናቸውም ወንጀሎችን ነው። በሌላ በኩል የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን በመንግስት በጀት ሊሟሉ የማይችሉት የመከላከያ ሠራዊት አባላትን ፍላጐት የሚያረኩና የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽሉ አገልግሎቶች በማቅረብ የተለያዩ ድጋፎችን የማድረግ ዓላማ ይዞ በደንብ ቁጥር 179/2002 የተቋቋመ የህግ ሰውነት ያለው አካል ነው። ከዓላማው አንጻር ተጠሪነቱ ለሀገር መከላከያ የሚኒስቴር መሆኑ፣ በአባልነትም ከተሰናበቱ የሠራዊቱ አባላትና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተጨማሪ የመከላከያ ሠራዊት አባላት መኖር ፋውንዴሽኑን ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚኒስቴሩ ንብረት ላይ የተፈጸመ አያደርገውም። ይህም የሚያስገነዝበው የተለያዩ ህጋዊ ሠውነት ያላቸው አካላት መሆናቸው ነው። ስለሆነም የሠራዊቱ አባላት በፋውንዴሽኑ ንብረት ላይ የሚፈጽማቸው ማናቸውም ወንጀሎች በሚኒስቴር ላይ እንደተፈፀመ ወንጀሎች የሚገመቱ አለመሆናቸውን ነው።

በሌላ በኩልም ወታደራዊ የፍትህ አካላት በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 28 መቋቋም መሠረታዊ ዓላማ ከሥራው ልዩ ባህሪ አንጻር ወታደራዊ የሆነ የወንጀል ድርጊቶችን በተለይም በቁጥር 38 የተመለከቱትን የመከላከል ፣የመመርመር ፣የመክሰስ፣ ውሳኔ የመስጠትና የማስፈፀም ነው። ስለሆነም በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ የሠራዊቱ አባል በሚኒስትሩ ንብረት ላይ የተፈፀመ ተብሎ የሚወሰዱ አይደለም። ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ድርጊቱ ተፈጽሟል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተባለበት ጊዜ በሥራ ላይ በነበረው የተሻሻለው የፀረ-ሙስና የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 7/1/ መሠረት ጉዳዩን የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

በአጠቃላይ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ተጠሪ ያቀረበውን ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ክስ የማየት የዳኝነት ሥልጣን የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት የስር ፍ/ቤት በአብላጫ ድምጽ የሠጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1/ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16555 ጥር 18 ቀን 2008 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠውን ብይን በመሻር የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ/ቁ 124937 በቀን 22/02/2009 ዓ.ም የሰው ፍርድ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 141978

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ - ሙሉተስፋ ከበደ

ተጠሪ፡- እዮኤል ተስፋዬ የሺጥላ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 114261 በቀን 22/02/09 የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 183790 በቀን 13/06/2009 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በዐቃቤ ህግ አማካኝነት የቀረበን ክስ ስለማንሳትና ከክርክር ውጭ ስለመሆን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ሁለት የወንጀል ክስ ያቀረበ ሲሆን ይኸውም የወንጀል ህግ ቁጥር 559/2/ እና 575 /2/ /ሀ/ የተመለከተውን ተላልፎ በዋናው መንገድ ለሚንዝ ተሽከርካሪ ቅድሚያ በመከልከልና ያለጥንቃቄ ሲያሽከረክር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-06155 ኢ.ት የሆነ መኪና የኋላ ግራ ጐን የገጨና አቅጣጫ እንዲስትና ከድንጋይ ጋር ተጋጭቶ በውስጡ የነበሩት የግል ተበዳይ አብነት ጐሹ በመኪናው አካል ተመትቶ የአንገት የቀኝ እግር እና የአካል ጡንቻዎች ላይ የህመም ስሜት እንዲሰማ ያደረገ እና እርዳታ ሳያደርግ በሌላ መኪና ገብቶ ያመለጠ በመሆኑ በቸልተኝነት ቀላል የአካል ጉዳት ያደረሰና በአደጋ ላይ የሚገኝ ሰውን አለመርዳት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ተጠሪ የቀረበው ክስ ደርሶት እምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ ከግል ተበዳይ ጋር የታረቀ መሆኑን የገለፀ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይህንኑ ገልጾ በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ በወንጀል ህግ ሥ/ሥርዓት ቁ 151/2/ መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሳይቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በተጠሪ ላይ የቀረበው የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ በወንጀል ህግ 212 መሠረት በግል አቤቱታ የማይቀርብና በወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት በእርቅ ሊነሳ የማይችል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክሱን ያቋረጠው መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ የቀረበ ክስ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት በእርቅ በመጨረስ የሚቋረጥ መሆኑን ለመመርመር ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ታዞ በሰጠው መልሱ በወቅቱ እኔም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብኝ እራሴን ለማዳን ወደ ህክምና ተቋም ሄጃለሁ ሆነ ብዬ ሰውን ላለመርዳት አልሄድኩም ብሎ ክሱን በመካድ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪም ዕርቁን የማይቃወም መሆኑን እና የሚያቀርቡት ማስረጃ እንደሌለ በመግለጽ ፍ/ቤቱ ክሱን አቋርጧል እንጂ የግል አቤቱታ ነው በማለት አይደለም፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይጽናልኝ ብሏል፡፡ አመልካች በሰጠው የመልስ መልስም ሁለቱም ክሱ የተቋረጠው በእርቅ እንጂ አመልካች ማስረጃ ባለማቅረቡ ወይም እንደክሱ ባለማስረዳቱ አይደለም የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/3/ የተመለከተውን ተቃውሞ አላነሳንም እንጂ በሁለተኛው ክስ ላይ ተቃውሞ ገልፀናል፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ ክሱን ማቋረጡ ተገቢ አይደለም በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነው በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ክሶችንና የሚቀርቡበትን አግባብ የሚመለከት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ ከቀረበው ጭብጥ አንጻር የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ሀ/ በወንጀል ህግ ሥርዓት ቁጥር 151/2/ መሠረት ከተበዳዩ ጋር በዕርቅ በመጨረስ ክሱ የሚቋረጥ ስለመሆኑ አለመሆኑ ምላሽ የሚሰጥ ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የወንጀል ህግ ግብ ስለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የሀገራቱን መንግስት የህዝቦችን የነዋሪዎቹን ሰላም ደህንነት ሥርዓት መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡ መንግስት በህዝብ ስም ሆኖ ለዜጐች ተወክሎ የወንጀል ጉዳይን እንዲከታተልና ክሶ እንዲያስቀጣ ኃላፊነት ሊወድቅበት የቻለውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ሆኖም የጠቅላላውን ህዝብ ሰላምና ፀጥታ የሚያደፈርሱ ከተገዢው ሠው ጥቅም በላይ አልፈው የሌሎችን ጥቅም የማይነኩ አሉ፡፡ በእርግጥ በጠቅላላው ተበዳይ ቢስማማም ባይስማማም የወንጀል ክስን መከታተል የመንግስት ኃላፊነት ቢሆንም በእነደዚህ ባሉ ነገሮች የተጐዳው ሠው ጉዳዩን ክሶ በፍርድ እንዲታይለት ፈቃደኛ መሆኑ በእርግጥ ካላሳየ በቀር መንግስት ይህንን ግዳጁን አያከናውንም፡፡

የወንጀል ህጉ ክስ በቀረበ ጊዜ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች የሚገልጽ የተጠናቀቀ ዝርዝር አይገልጽም ፡፡የወንጀል ህግ አንቀጽ 212 ቢሆንም በጠቅላላው መልክ ነው በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ውስጥም የሚገኙ ድንጋጌዎች “ማናቸውም ... የግል አቤቱታ በቀረበ ጊዜ .... ይቀጣል” ሲል ያዛሉ፡፡ እነዚህን አንቀጾች በመተላለፍ ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ በግል አቤቱታ እንዲያቀርብ ከተፈቀደለት ሰው በቀር በሌላ በማንም ሠው የክስ ጉዳይ ሊንቀሳቀስ አይችልም፡፡ የግል ከሳሹ የክሱን ማመልከቻ ካዘጋጀ በኋላ የክሱ ጉዳይ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 150-153 በተገለፀው መሠረት ይመራል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በአመልካች በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት ክሶች 1ኛ የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/2/ እና 2ኛ የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2/ /ሀ/ በግል ተበዳይ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ አማካኝነት የሚቀርቡ ወይም እንዲቀርቡ የታዘዙ ክሶች አይደሉም፡፡ ክሱም በስር ፍርድ ቤት የቀረበው በአመልካች /በመንግስት/ በዐቃቤ ህግ ነው፡፡ ክሱን የሚመራው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በወ/ህ/ሥ/ሥ /ቁ 132-135 ፣ 185፣196፣117፣ 94-98፣ 123-131 እና 136-149 በተመለከቱት መሠረት ይሆናል፡፡

ስለሆነም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበውን የወንጀል ክስ የግል ተበዳይ ክሱን ትቷል በማለት በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 151/3/ መሠረት በግል አቤት ባይ የቀረበ ክስ በሚመራበት ሥነ ሥርዓት የወንጀል ክሱን ያቋረጠው የወንጀል ህግን ግብ እና በዓቃቤ ህግ ስለሚቀርቡ የወንጀል ክስ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ክስ አመራር ያልተከተለ በመሆኑ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንን ሳያርም ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 114261 በቀን 22/02/09 የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 183750 በቀን 13/06/2009 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ሀ/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች የቀረበውን ክስ ተጠሪን አስቀርቦ የወንጀል ክሱን በመስማት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /መ/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 137545

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ አሸብር መለስ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 626/4/ሀ በመተላለፍ ከእርሱ ጋር ተቃራኒ ጾታ ካላት ዕድሜዋ አሥራ ሥምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም በማሰብ በቀን 10/08/07 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 12፡30 ሲሆን በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16/17 ክልል ልዩ ቦታው ላምበረት አካባቢ የቤት ሠራተኛ የሆነችው እና እድሜዋ ከ15/16 ዓመት የሚገመተውን የግል ተበዳይ ዓይናለም አየነው ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት የፈጸመ በመሆኑ ዕድሜያቸው አሥራ ሦስት ዓመት በሆነ እና አሥራ ሥምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረሥጋ ድፍረት በደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ለአመልካች ክሱ ተነቦለት መቃወሚያ አቅርቦ መቃወሚያው በብይን ውድቅ ከተደረገ በኋላ የእምነት ክሕደት ቃሉን ሲጠየቅ ድርጊቱን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመከራከሩ ፍ/ቤቱ የተጠሪ ምስክሮች እንዲሰሙ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የተጠሪ ምስክሮች ተሰምተዋል፡፡

የተጠሪ 1ኛ ምስክር የሆነችው የግል ተበዳይ ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል በአመልካች ቤት በቤት ሰራተኛነት የተቀጠረች መሆኑን፤አመልካች ጠዋት ሚስቱ ወደ ሥራ ስትወጣ ቀኑን በማታስታውሰው ዕለት አመልካች የግብረሥጋ ግንኙነት የፈጸመባት መሆኑን፤ድርጊቱን የፈጸመችው በፍላጎት መሆኑን፤አመልካች የወርአበባ መምጫ ጊዜዋን የሚያውቅ እና የሚቆጣጠር መሆኑን፤ከአመልካች ቤት ከወጣች በኋላ ሌላ ሰው ቤት የገባች መሆኑን፤ለአመልካች ስልክ ደውላ አርግዣለሁ ስትለው የሰደባት እና አላውቅልሽም ብሎ ስልኩን የዘጋው መሆኑን፤በአመልካች ቤት ያስቀጠረቻት ትዝታ የተባለች ግለሰብ መሆንዋን፤ድርጊቱ እንደተፈጸመ ለማንም ያልተናገረች መሆኑን፤ድርጊቱ ከተፈጸመ ከተወሰነ ቀን በኋላ ከቤቱ የወጣች እና ወደ ትዝታ ቤት የሔደች መሆኑን፤ትዝታ ሰው ቤት ካስቀጠረቻት በኋላ አርግዣለሁ ብላ ለአመልካች ስልክ ስትደውልለት ሲሰድባት ለትዝታ አርግዣለሁ ብላ የነገረቻት መሆኑን፤አርግዣለሁ ያለችው ገንዘቧን ስለከለከላት ተናዳ መሆኑን፤የአመልካች ባለቤት ደውላ የጠየቀቻት እና ሁሉንም ነገር የነገረቻት መሆኑን፤የአመልካች ባለቤት ጋንዲ ሆስፒታል ወስዳ ያስመረመረቻት መሆኑን በመግለጽ መሥክራለች፡፡

የተጠሪ 2ኛ ምስክር ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል የግል ተበዳይ አመልካች ደፍሮኛል ስትላት ማመን ስላቃታት ስልክ ደውይለት ያለቻት መሆኑን፤የግል ተበዳይ ለአመልካች አርግዣለሁ ብላ ስልክ ስትደውልለት የሰደባት መሆኑን፤የአመልካች ባለቤት ስለድርጊቱ ለማወቅ የግል ተበዳይ መመርመር አለባት በማለት ስልክ የደወለችላት መሆኑን፤ከአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን የግል ተበዳይን ሆስፒታል ወስደው ያስመረመሯት መሆኑን በመግለጽ መስክራለች፡፡ የግል ተበዳይ በ25/10/07 ዓ.ም የተመረመረች እና በክብረንጽሕና መገለጫ አካሏ ላይ የቆየ የክብረንጽህና መገርሰስ መኖሩን እና ሌላ አካላዊ ጉዳት ያልተገኘባት መሆኑን የሚያሳይ ከጋንዲ መታሠቢያ ሆስፒታል የቀረበው የሕክምና ማስረጃ እና የግል ተበዳይ ዕድሜ ከ15-16 ዓመት መሆኑን የሚያሳይ ከዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል የተጻፈ የሕክምና ማሥረጃም ቀርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቱ ተጠሪ ባቀረበው የሰው ምስክር እና የሰነድ ማሥረጃ እንደክሱ አስረድቷል በማለት አመልካች እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል። 1ኛ የአመልካች መከላከያ ምስክር ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል አመልካች ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ሰዓት በቤት ውስጥ ያልነበረ መሆኑን፤የግል ተበዳይ ለአመልካች ሥልክ ደውላ አርግጥለሁ ያለች መሆኑን እና እውነት መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ጋንዲ ሆስፒታል ወስደው ያስመረመረቻት መሆኑን በመግለጽ መስክራለች።

2ኛ የአመልካች መከላከያ ምሥክር የግል ተበዳይ ስትሆን ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምሰክርነት ቃል በአመልካች ቤት ተቀጥራ ስትሰራ የነበረ እና ሌላ ሰው ቤት ለመስራት ብላ ከአመልካች ቤት በፍላጎትዋ የለቀቀች መሆኑን፤ከአመልካች ቤት ከለቀቀች በኋላ የተቀጠረችበት ቤት ባለቤት አስቀድሞ ስትሰሪበት የነበረው ቤት አሰሪዎች ገንዘብሽን ከፍለውሻል ወይ ብላ ስትጠይቃት ገንዘቤን አልሰጡኝም ስትላት ገንዘብሽን እንዲሰጡሽ ክሰሽው አስፈራሪያቸው ስላለቻት ክሱን የመሰረተች መሆኑን እንጂ ከአመልካች ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽማ የማታውቅ መሆኑን፤አመልካችን ያለአግባብ በመክሰሷ የጸጸታት መሆኑን፤በዚህም ምክንያት አመልካችንና ባለቤቱን ይቅርታ የጠየቀቻቸው መሆኑን እና ክሱን እንደምታነሳ የነገረቻቸው መሆኑን፤ይቅርታ ጠይቂ ብሎ የነገራት ወይም የመከራት ሰው የሌለ መሆኑን፤በራሷ ተነሳሽነት ይቅርታ የጠየቀች መሆኑን እና በዚህም ምክንያት ከአመልካች ወይም ከባለቤቱ የተከፈላት ገንዘብ የሌለ መሆኑን በመግለጽ መሥክራለች።

የአመልካች 3ኛ መከላከያ ምስክርነት ቃል ለፍ/ቤቱ በሰጠው የምሥክርነት ቃል ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ዕለት አመልካች ቤት ምሳ ተጠርተው ሄደው እንደነበረ እና ተበዳይ በወቅቱ ጤናማ እንደነበረች እና ሰኔ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ልጁን ሲያስመርቅ አመልካችን እና ባለቤቱን ጠርታቸው ተበዳይ ለአመልካች ስልክ ደውላ ደፍሮኛል ብየ እከስሃለሁ ያለችው መሆኑን በመግለጽ መሥክሯል። ፍ/ቤቱ በግራቀኙ የቀረቡትን ማሥረጃዎች ከመረመረ በኋላ አመልካች የግል ተበዳይን በመከላከያ ምሥክርነት አቅርቦ ያሰማ ቢሆንም የግል ተበዳይ የአመልካች መከላከያ ምሥክር ሆና በሰጠችው ቃል አመልካችን እንድከሰው የገፋፋችኝ አመልካችን የማታውቅ እና ከግል ተበዳይ ጋርም ዝምድና የሌላት እና አንድ ሣምንት ብቻ የሠራችባት አሰሪ ነች ያለች በመሆኑ በምንም ሁኔታ ሊሆን የሚችል አይደለም፤ምስክሯ አመልካች አንዱ ደፍሮኛል ሌላ ጊዜ ደግሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አልደፈረችም በማለት የሰጠችው ቃል እምነት የሚጣልበት አይደለም፤የአመልካች ምስክሮች ቃልም እርስ በእርስ የሚደጋገፍ አይደለም በማለት አመልካች በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ነው ብሎ በሦስት ዓመት ከሠባት ወር ቀላል እሥራት እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-የግል ተበዳይ የአመልካች የመከላከያ ምስክር ሆና ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምሥክርነት ቃል አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ድርጊት አልፈጸመብኝም የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽሞብኛል ያልኩት ገንዘቤን ስለከለከለኝ እና አሠሪዬ አመልካች ገንዘብሽን እንዲሰጥሽ ክሰሽው ስላለችኝ ነው በማለት በመሰከረችበት ሁኔታ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የግል ተበዳይ በአመልካች የመከላከያ ምሥክርነት ቀርባ ከአመልካች ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት አልፈጸምንም፤የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽመናል ብዬ የከሰስኩት የሰራሁበትን ደመወዜን እንዲከፍለኝ ነው በማለት በመሰከረችበት ሁኔታ አመልካች ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡ የግል ተበዳይ የተጠሪ ምስክር ሆነ በመቅረብ አመልካች በክሱ በተገለጸው ሁኔታ ድርጊቱን የፈጸመባት ስለመሆኑ የመሰከረች ቢሆንም የአመልካች መከላከያ ምስክር ሆና ስትቀርብ ከአመልካች ቤት በፍላጎትዋ የለቀቀች መሆኑን፤አመልካች በክሱ የተገለጸውን ድርጊት ፈጽሟል ያለችው ከአመልካች ቤት ከለቀቀች በኋላ የተቀጠረችበት ቤት አሰሪ አመልካች ገንዘብሽን እንዲሰጥሽ ክሰሽው አስፈራሪያቸው ስላለቻች እንጂ ከአመልካች ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽማ የማታውቅ መሆኑን፤አመልካችን ያለአግባብ በመክሰሷ የጸጸታት መሆኑን፤አመልካችንና ባለቤቱን ይቅርታ የጠየቀቻቸው መሆኑን እና በዚህም ምክንያት ከአመልካች ወይም ከባለቤቱ የተከፈላት ገንዘብ የሌለ መሆኑን በመግለጽ መሥክራለች፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽ በቀረበበት ማሥረጃ መሠረት የተመሰከረበት እንደሆነ ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል ብይን የሚሰጥ መሆኑ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/1 መሠረት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች በቀረበበት ማስረጃ መሠረት የተመሰከረበት ሆኖ ስላገኘው አመልካች እንዲከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም የግል ተበዳይ የአመልካች መከላከያ ምሥክር ሆና ቀርባ አመልካች ድርጊቱን ያልፈጸመባት መሆኑን፤ድርጊቱ ተፈጽሞብኛል ያለችው ገንዘብዋን ስላልከፈላት ተናዳ እና አሰሪዋ ክሰሽው ስላለቻት መሆኑን፤በዚህም ምክንያት ተጸጽታ አመልካችን እና ባለቤቱን ይቅርታ የጠየቀቻቸው መሆኑን እና ይህንንም በማድረግዋ ከአመልካች ወይም ከባለቤቱ የተከፈላት ገንዘብ የሌለ መሆኑን በማያሻማ ቃል ለፍ/ቤቱ ገልጻለች፡፡ ከዚህም በላይ የግል ተበዳይ የዓቃቤሕግ ቀጥተኛ ምስክር በመሆን ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል አርግጥለሁ ያለችው አመልካች ገንዘቧን ስለከለከላት ተናዳ መሆኑን በመግለጽ የሰጠችው የምስክርነት ቃል የአመልካች መከላከያ ምስክር በመሆን ከሰጠችው የምሰክርነት ቃል ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የግል ተበዳይ ከመነሻውም ቢሆን አመልካች የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽሞብኛል በማለት የሰጠችው የምሰክርነት ቃል ሐሰት እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡

በአጠቃላይ የተጠሪ ቀጥተኛ ምስክር የሆነችው የግል ተበዳይ ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል አመልካች ድርጊቱን አልፈጸመብኝም፤አመልካች የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽሞብኛል ያልኩት ገንዘቤን ስለከለከለኝ ነው፤ ይህንንም በማድረጌ ስለተጸጸትኩ አመልካችን እና ባለቤቱን ይቅርታ ጠይቂያቸዋለሁ፤ይህንንም በማድረጌ የተከፈለኝ ገንዘብ የለም በማለት የመሰከረች በመሆኑ እና ተጠሪ የግል ተበዳይ የአመልካች የመከላከያ ምስክር በመሆን የሰጠችው የምሥክርነት ቃል ተደልላ ወይም ጥቅም አግኝታ የሰጠችው ቃል መሆኑን ያላረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የተጠሪን ማስረጃ የጉዳዩ ባለቤት በሆነችው የግል ተበዳይ በበቂ ሁኔታ አስተባብሏል፡፡ አመልካች የቀረበበትን ክስ እስካስተባበለ ድረስ ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 149/2 መሠረት አመልካችን በነጻ መልቀቅ ይገባዋል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች የጉዳዩ ባለቤት የሆነችውን የግል ተበዳይ በመከላከያ ምስክርነት አቅርቦ የቀረበበትን ክስ በበቂ ሁኔታ ባስተባበለበት ሁኔታ አመልካችን ጥፋተኛ በማለት በሦስት ዓመት ከሰባት ወር ቀላል እሥራት ሊቀጣ ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በአብላጫ ድምጽ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 230341 ሕዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ሕዳር 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 188723 ጥር 23 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ/2 መሠረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ ቀጥተኛ ምስክር የሆነችው የግል ተበዳይ አመልካች ድርጊቱን እንዳልፈጸመ በመግለጽ የአመልካች መከላከያ ምሥክር በመሆን የመሠከረች በመሆኑ አመልካች የቀረበበትን ክስ ተከላክሏል በማለት አመልካች በነጻ እንዲሰናበት በአብላጫ ድምጽ ወስነናል፡፡

ትዕዛዝ

-የሚመለከተው ማረሚያ ቤት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የተሻረ መሆኑ አውቆ አመልካችን ከእሥር እንዲፈታው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክለት፡፡

-የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ 230341 የሆነው መዝገብ ወደመጣበት ይመለስ፡፡

-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የልዩነት ሃሳብ

ስማችን በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተመለከተው ዳኞች በአብላጫው ድምፅ ከሰጠው ውሳኔ በሚከተለው ምክንያት በሃሳብ ተለይተናል፡፡ የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበው ክስ ሲታይ፡- አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 626/4//ሀ/ በመተላለፍ ከእርሱ ጋር ተቃራኒ ጾታ ካላት ዕድሜዋ አሥራ ስምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም በማሰብ በቀን 10/08/07 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 12፡30 ሲሆን በየካ ክፍለከተማ ቀበሌ 16/17 ክልል ልዩ ቦታው ላምበረት አካባቢ የቤት ሠራተኛ የሆነችው እና እድሜዋ ከ15/16 ዓመት የሚገመተውን የግል ተበዳይ ዓይናለም አየነው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመ በመሆኑ ዕድሜአቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሥራ ሦስት ዓመት በሆነ እና አሥራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ ድርጊቱን አለመፈፀሙና ጥፋተኛ አለመሆኑ ገልፆ የተከራከረ ቢሆንም በወቅቱ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በቀረበበት ክስ የወንጀል ህግ አንቀፅ 626/4/ሀ ጥፋተኛ በማለት ድምዳሜ ላይ የደረሰው የቀረቡት የዓ/ህግ ምስክሮች በአመልካች በቤት ሰራተኛነት ተቀጥራ ስትሰራ የነበረችው ተበዳይ አይናለም አየነው አመልካች ጠዋት ሚስቱ ወደ ሥራ ስትወጣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመባት መሆኑን፤ድርጊቱን የፈጸመችው በፍላጎት መሆኑን፤የግል ተበዳይ በሌላ ጊዜ ለአመልካች ስልክ ደውላ አርግጥለሁ ስትለው የሰደባት እና አላውቅልሽም ብሎ ስልኩን የዘጋው መሆኑን፤2ኛ የዓ/ህግ ምስክር ደግሞ ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል የግል ተበዳይ አመልካች ደፍሮኛል በማለት ከነገረቻት በኋላ ስልክ ደውይለት ያለቻት መሆኑን፤የግል ተበዳይ ለአመልካች አርግጥለሁ ብላ ስልክ ስትደውልለት የሰደባት መሆኑን መስክራለች፣ በተጨማሪ የግል ተበዳይ ጋንዲ መታሠቢያ ሆስፒታል በመሄድ የተመረመረች ሲሆን በክብረንጽሕና መገለጫ አካሏ ላይ የቆየ የክብረንጽህና መገርሰስ መኖሩን እና ሌላ አካላዊ ጉዳት ያልተገኘባት መሆኑን ፣እንዲሁም የግል ተበዳይ ዕድሜ ከ15-16 ዓመት መሆኑን የሚያሳይ ከዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል የተጻፈ የሕክምና ማስረጃ በመቅረቡና በቀረበው ማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ስለመሆኑ መዝገቡ ያመለክታል፡፡

አመልካች የተከሰሱት የወንጀል ህግ አንቀፅ 626/4/ሀ በመሆኑ ይኸው የወንጀል ህግ አንቀፅ 626/4/ሀ/ “ ማንም ሰው ተቃራኒ ፆታ ካላት ፣ዕድሜዋ አሥራ ሦስት ዓመት በላይ ሆኖ አሥራ ስምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ይህችው ልጅ እንዲህ አይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንድትፈፅም ያደረገ እንደሆነ ...“ ስለመሆኑ ተደንግጓል:: ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የግል ተበዳይ አካለመጠን ያልደረሰች እድሜዋ ከ16 አመት በታች ሆና በአመልካች ቁጥጥር ስር የቤት ሰራተኛ የነበረች በመሆንዋ ከክርክሩ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ፈፅሞታል የተባለው ወንጀል የግል ተበዳይ ፍቃድ መኖሩ ተበዳይ አካለመጠን ያልደረሰች ስለሆነች ፍቃደኛ ነበረች ተብሎ አመልካች ከጥፋተኝነት ሊድን የሚችልበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕግ ምክንያት ሊኖር ካለመቻሉም በላይ የነበራቸው የአሰሪና የቤት ሠራተኛ ግንኙነት ተበዳይን በተጽዕኖው ስር ያዋላት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው ።

እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤት አመልካች ድርጊቱን ፈፀመ በማለት ድምዳሜ የደረሱት አመልካች ድርጊቱን ስለመፈፀሙ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እና የፅሁፍ ማስረጃዎች በሚገባ ተረጋግጧል ፣አመልካች በመከላከያ ማስረጃው አልተደገፉም በሚል ምክንያት ነው።።አመልካች ከሚከራከርባቸው ነጥቦች ውስጥ የአመልካችን የድርጊት ፈጻሚነት በተገቢው መንገድ አቃቤ ሕግ በማስረጃ ያለማስደገፉንና የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አመልካች በመከላከያ ምስክሮች የማስተባበላቸው ሁኔታን በተለይ የግል ተበዳይ መከላከያ ምስክር ሆና አልተደፈርኩም በማለት መስክራለች በማለት ሲሆን፤ የበታች ፍርድ ቤት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ስር የተመለከተውን የማስረጃ ምዘና መርህ ተከትለው የግል ተበዳይ አካለ መጠን ያልደረሰችና መጀመሪያ የዓ/ህግ ምስክር በመሆን ቀርባ መደፈርዋ በተመለከተ የሰጠችው የምስክርነት ቃል በቀረበው የሃኪም ማስረጃም ጭምር የተረጋገጠ በመሆኑ ተአማኒነት ያለው መጀመሪያ የሰጠችው የምስክርነት ቃል ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ባላቸው ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ተጠቅመው ማስረጃውን መዝነው አመልካችን ጥፋተኛ ያደረጉ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳየን እና በአመልካችና ተበዳይ የነበረው ግንኙነትም የአሰሪና የቤት ሠራተኛ መሆን በራሱ ግምት ውስጥ አስገብቶ ተመዝኖ የተሰጠ በመሆኑ ተገቢና ህጋዊ ሆኖ አግኝተነዋል።። በመሆኑም ከዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለውም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ተመዝነው መሆኑን ነው።። በተያዘው ጉዳይም አብላጫው ድምፅ አመልካች በነፃ እንዲሰናበት እንደ ምክንያትነት የገለፁት የተከሳሽ 2ኛ መከላከያ ምስክር በመሆን የቀረቡት የግል ተበዳይ በዓ/ህግ ምስክር ሆና የሰጠችው ምስክርነት በመቀየር አመልካችን የከሰሰችው የሰራሁበት ገንዘብ ስላልሰጠኝ እንጂ ከአመልካች ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት ፈጽሜ አላውቅም በማለት በመመስከርዋ የዓ/ህግ ምስክር ሆና የሰጠችው ምስክርነት ቃል ተአማኒነት የለውም በማለት መሆኑ ውሳኔው ያመለክታል እዚህ ላይ መታየት ያለበት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘን ጉዳይ ማረም የሚችለው በውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ተመልክቷል።። ከእነዚህ ድንጋጌዎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ይህ ሰበር ችሎት ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው መሆኑን ነው።በተመሳሳይ ጉዳይ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 41526 እና ሌሎች በርካታ መዛግብት የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ እንደሆነ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ በየትኛውም ፍርድ ቤት፤ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትንም ጨምሮ የሚያስገድድ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2 መሰረት አስገዳጅነት ያለው ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው።ስለሆነም የግል ተበዳይ በአመልካች ላይ ክስ መስርታ የከሳሽነት ቃል ከሰጠች በኋላ ፍርድ ቤት ቀርባም መደፈርዋን አረጋግጣ እያለ ፤መጀመሪያ የሰጠችው የምስክርነት ቃል ቀይራለች እና ተአማኒነት ያለው በኋላ የተሰጠው ምስክርነት ነው በማለት በአብላጫው ድምፅ መወሰኑ የግል ተበዳይ አካለመጠን ያልደረሰች ከመሆኑዋና የአመልካች የቤት ሠራተኛ ከመሆኗ ጋር ተያይዞ በሃኪም ማስረጃም ጭምር የተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ፣የዓ/ህግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ መመዘን እንዳለበት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35697 የሰጠው ትርጉም ያላገናዘበና የስር ፍርድ ቤቶች ባላቸው ማስረጃ የመመዘን ስልጣን አመልካች ወንጀል መፈፀሙ በሰውና በሃኪም ማስረጃ ተረጋግጧል አመልካች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች በመከላከያ ማሰረጃው አላስተባበለም በማለት የገለጸዉ ሲታይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁ.25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር ይህን በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር ከመቀበል ዉጭ ድጋሚ ለማጣራት የሚያስችለዉ የህግ አግባብ የለም። ስለሆነም አመልካች ለድርጊቱ ኃላፊነት አለበት ተብሎ የተወሰነው ወንጀሉ መሰራቱ ወይም መፈጸሙና ተሰራ ወይም ተፈጸመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በአመልካች በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በተረጋገጠበት ሁኔታ በመሆኑና ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4) እና 626(4(ሀ)) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያሟላ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ጥፋተኛ በማለት የሰጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት አብላጫው ድምፅ ከሰጠው ውሳኔ በሃሳብ ተለይተናል ።

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ/127505

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች ፡- አበራ ዋቅጅራ

ተጠሪ ፡- የቤ/ጉ/ክልል ፍትህ ቢሮ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የወንጀል ክርክር የሚመለከት ነዉ ፡፡ተጠሪ አመልካች ላይ ያቀረበዉ ክስ ይዘት የወንጀል ህግ አንቀጽ 27/1 እና 539/1/ሀ ተላልፎ በ09/02/07 ዓ.ም ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ላይ በወንበራ ወረዳ ገሳንገሳ ቀበሌ አቶ ፍቃዱ አድማሱ መጠጥ ቤት ዉስጥ ምንም ምክንያት ሳይኖረዉ ከተቀመጠበት ተነስቶ የግል ተበዳይ አቶ በየነ ቡባ መቀመጫዉ ላይ በካራ ሁለት ጊዜ የወጋዉ ስለሆነ ከባድ የግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ሲሆን አመልካች ክዶ በመከራከሩ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኝ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች የዓቃቤ ህግ ማስረጃ ማስተባበል አልቻለም በማለት በተከሰሰበት አንቀጽ ጥፋተኛነትና 16 ዓመት ከ6ወር ጽኑ እስራት ቅጣት ወስኖበታል አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ፍ/ቤቱም አከራክሮ ድርጊቱ የተፈጸመዉ በመጠጥ ቤት በተነሳ ድንገተኛ ፀብ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን መሰረት በማድረግ አንቀጹን ወደ 27/1/ እና 540 በመለወጥ ቅጣቱንም ወደ 10 ዓመት ጽኑ እስራት አሻሽሎ ፍርድ ሰጥቷል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም ።።

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮ የግል ተበዳይ ላይ ደረሰ ከተባለዉ ጉዳት አንጻር አመልካች በወ/ህግ አንቀጽ 27/1/እና 540 ስር ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል ።።ለተጠሪ የፍ/ቤት መጥሪያ በፖስታ ቤት በኩል የተላከለት ቢሆንም መልስ አልሰጠም ።። የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አኳያ ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ።።

ከመዝገቡ መርምረን እንደተገነዘብነዉ ድርጊቱ የተፈጸመዉ በመጠጥ ቤት በተነሳ ድንገተኛ ፀብ ሲሆን ዐቃቤህግ አመልካች በካራ የተበዳይ መቀመጫ ላይ ሁለት ቦታ ወግቶታል ሲል አመልካች ደግሞ በፀቡ ምክንያት ተያይዘዉ ሲወድቁ ተበዳይ አረቄ መጠጫ መለኪያ ሲባሪ ላይ ወድቆ የተወጋ እንጂ አመልካች ስለት ነገር በእጁ እንዳልነበር በመከላከያ ምስክር አስረድቻለሁ በማለት ቢከራከርም የስር ፍ/ቤቶች አልተቀበሉም ስለሆነም አመልካች የግል ተበዳይን በስለት ነገር መቀመጫዉ ላይ ሁለት ጊዜ ወግቶ ጉዳት ማድረሱ ማስረጃ የመመርመርና ፍሬነገር የማጣራት ስልጣን በህግ የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል ።።በዚህ ችሎት እልባት የሚሻዉ ነጥብ የአመልካች ድርጊት የወ/ህጉን አንቀጽ 540 ያቋቁማል መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ላይ ነዉ ።።

በወ/ህግ አንቀጽ 540 ስር አንድ ሰዉ ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ ፈጽሟል ተብሎ የሚቀጣዉ የድርጊቱ አፈጻጸም በወ/ህጉ አንቀጽ 539 ወይም 541 ስር የተመለከተዉን ፍሬነገር የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ ነዉ ።። ስለዚህም የተፈጸመዉ ድርጊት የወ/ህጉን አንቀጽ 539 ሳይሆን 540 ያቋቁማል በማለት ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢነት ሊመረመር የቀረበ ነዉ ።።ድርጊቱ የተፈጸመዉ ሰዉን መግደል ሀሳብ ኖሮት ነገር ግን ዉጤት ሳያገኝ ቢቀርም በመደቡ ጥፋተኛ ተብሎ እንደሚቀጣ የወ/ህጉ አንቀጽ 27/1/እና/3/ ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል ።።በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የፈጸመዉ ድርጊት ተበዳይን መግደል ሀሳብ ኖሮት በሙከራ የቀረ ነዉን የሚለዉን ስንመረምር የግል ተበዳይ የተወጋዉ መቀመጫዉ ላይ መሆኑና የጉዳቱ መጠንም 2 በ2 ሳ.ሜ እና 2 በ5ሳ.ሜ እንደሆነ በማስረጃ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል ።።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ የወንጀል አድራጊዉ የሀሳብ ክፍል የሚታወቀዉ ከወንጀሉ አፈጻጸም ጠቅላላ ሁኔታዎች እንደሆነ ልብ ይለዋል ።አመልካች ስለት ነገር ተጠቅሟል እስከተባለ ድረስ የግል ተበዳይን መግደል አስቦ ቢሆን ኖሮ ስስ ብልቶቹ ላይ እንዳይወጋዉ ያላስቻለዉ ነገር ስለመኖሩ አልተረጋገጠም ። አመልካች በመጠጥ ቤት በተነሳ ፀብ መነሻ ከግል ተበዳይ ጋር ተያይዘዉ በወደቁበት ሁኔታ የግል ተበዳይ መቀመጫ ላይ መዉጋቱና የደረሰዉም የአካል ጉዳት መሆኑ ሲታይ አመልካች ተበዳይን የመግደል ሀሳብ ነበረዉ የሚለዉን የሀሳብ ክፍል ግምት ወይም ድምዳሜ ለመድረስ የሚያስችል ሆኖ አላገኘንም ።ይልቁንም አመልካች ሆነ ብሎ ስለት ነገር ተጠቀሞ የግል ተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬነገር በመሆኑ በወ/ህጉ አንቀጽ 555/1/ የሚያሟላ ድርጊት ሆኖ አግኝተናል ። በዚህ አግባብ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በአንቀጽ 27/1/እና 540 ስር ያሰተላለፈዉን የጥፋተኛነት ዉሳኔ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 113/2/ መሰረት ለዉጠን አመልካች የግል ተበዳይ ላይ ላደረሰዉ ከባድ አካል ጉዳት በወ/ህጉ አንቀጽ 555/1/ስር ጥፋተኛ ነዉ ብለናል ።ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ደንጋጌ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በወጣዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ /2/2006 ደረጃና እርከን የወጣለት ስለሆነ በዚሁ መሰረት በድርጊቱ ከባድ የአካል ጉዳት መድረሱ ስለተረጋገጠ ደረጃ1 እርከን 16 ላይ ይመደባል ። በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስለመኖሩ በፍርዱ አልተመለከተም ። በአመልካች በኩል ተቀባይነት ያገኘዉ 4 የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስለመኖሩ በስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ተገልጸዋል። በዚህ ምክንያት 4 እርከን ሲቀነስ እርከን 12 ላይ ያርፋል ። እርከን 12 ላይ የተመለከተዉ የእስራት ቅጣት ፈቅደ ስልጣን ከ2 አመት እስከ 2 ዓመት ከ6ወር ሲሆን አመልካች በዚህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም የታሰረዉ ታሳቢ ተደርጎ የእርከኑ ጣሪያ 2 አመት ከ6ወር እስራት እንዲቀጣ ፈርደናል ። በዚሁ መሰረት ተከታዩ ተወስኗል ።

ዉ ሳ ኔ

1ኛ/ የቤ/ጉ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/06525 በ22/10/07 ዓ.ም የሰጠዉ የጥፋተኛነትና የቅጣት ዉሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/06674 በ19/02/08 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 195/2/ለ/2 መሰረት ተሻሽሎ ተወስኗል ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2ኛ/ አመልካች ለፈጸመዉ ድርጊት በወ/ህግ አንቀጽ 555/1/ስር ጥፋተኛ ነዉ ብለናል፡፡ቅጣቱም በዚህ ጉዳይ የታሰረዉ ታስቦለት በሁለት አመት ከስድስት ወር /2፡6/ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል ፡፡

3ኛ/ መተከል ዞን ማረሚያ ቤት በዚህ ፍ/ቤት ተሻሽሎ በተወሰነዉ መሰረት እንዲያስፈጽም ዉሳኔ ግልባጭ ይተላለፍለት ብለናል ፡፡ ለአመልካቹም ዉሳኔ ግልባጭ በማ/ቤት በኩል ይድረሰዉ ፡፡ይጻፍ ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መቁ-134549

ቀን-መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ አበበ ተፈራ አለሙ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ አመልካች ላይ ቀርበዉ የነበሩት ሁለት ክሶች ሲሆኑ የ1ኛ ክስ ይዘት፡- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(3) ላይ የተመለከተዉን በመተላለፍ የሙያ ግዴታዉን በመተላለፍ ሚች አያን ገቦቤን ወደ ተከራየበት ቤት በመዉሰድ በባለሙያ ብቻ የሚሰጠዉ ዲያዜፖም እና ትራማ ዶ የሚባሉትን አደንዛዥ መድሃኒቶችን እራሱ በመርፌ በመዉጋት ብልቷን ከሰፋት በኃላ በተወጋችዉ መድሃኒት የተነሳ የመተንፈስ ችግር ተከስቶ የሞተች በመሆኑ በፈጸመዉ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡ የ2ኛ ክስ ይዘት ደግሞ በወንጀል ሕግ ቁጥር 566(1) የተመለከተዉን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ላይ በተገለጸዉ ጊዜና ቦታ የሚች አያን ገቦቤን ብልት የሰፋ በመሆኑ የሴት ልጅ ብልት የመስፋት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በስር ፍ/ቤት አመልካች የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ጥፋተኝነቱን በማረጋገጥ አፈጻጸሙን በዝርዝር ሲያስረዳ ሚያዚያ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ማታ ከሚች ጋር አብረን አድረናል፡፡ ቀን ሥራዬን አጠናቅቄ ለመዉጣት ስል ሚች ቀደሞ የፍቅር ጓደኛዬ ስለነበረች በመማጸን እጮኛዬ ከዉጭ ይመጣል፤ በባህሉ ብልቴን ተሰፍቶ ካላገኘኝ ለቤተሰቤም ለእኔም ዉርደት ይሆንብኛል፤ አግብቶኝ ዉጭ ሀገር የመሄድ አጋጣሚዉ ያመልጠኛል በማለቷ ለድርጊቱ የሚያስፈልጉ ቁሶችን በመያዝ ወደ ቤት ሄጃለሁ፡፡ የአክስቴ ቤት ገብተን ክፍል ተሰጥቶን አድረናል፡፡ ከዚያም ጧት ላይ ብልቷን ሰፍቼ ካጠናቀቅኩ በኃላ ሚች ሕይወቷ አልፏል፡፡ ስለሆነም ጥፋተኛ ነኝ በማለቱ የስር ፍ/ቤት አመልካች በሰጠዉ የእምነት ቃል መሠረት የወንጀል ሕግ ቁጥር 543(3) እና 566(1) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ አመልካች በ10 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዉሳኔዉ ቅር ተሰኝቶ ያቀረበዉን ይግባኝ የተመለከተዉ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህንኑ ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ድርጊቱን ስፈጽም ሁለት የወንጀል ድርጊቶችን ለመፈጸም አቅጄ የፈጸምኩት የወንጀል ድርጊት አይደለም፡፡ ሚችን ብልቷን ስሰፋ የሕመም ስሜት እንዳይሰማት በክሱ ላይ የተገለጹትን መድሃኒቶችን ልሰጣት ችያለሁ፡፡ በወ/ሕ/ቁ 61(1) በአንድ መብት ላይ የሚደረግ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት ሲሆን እና ድርጊቱም በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ ሲሆን አድራጊዉ ተመሳሳይ ባህሪ ባላቸዉ በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች አይቀጣም በማለት ደንግጓል፡፡ ስለሆነም በአንድ የወንጀል ማድረግ ቸልተኝነት የተፈጸመ በመሆኑ ድርጊቶቹም በአንድ የወንጀል ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ያቀረብኩትን መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉም ሆነ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ዉሳኔዉን ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ በአንድ ክስ ተጠቃልሎ ስህተቱ ይታረምልኝ፡፡

የስር ፍ/ቤት የ1ኛ ክስ ደረጃና እርከን ሲያወጣ ደረጃ 2 እርከን 25 ስር ያሳረፈዉ ማደንዘዣ መድሃኒት መስጠት እና ህክምናዉን ለመስጠት ባልተፈቀደ የግል መኖሪያ ቤት በማድረጉ ሁለት የድንጋጌዉ ፍሬ ነገሮች ተሟልተዋል በማለት ነዉ፡፡ እነዚህ ፍሬ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነገሮች እንደሁለት የሚወሰዱ ሳይሆን በድንጋጌው ስር ግልጽ የሆነ ደንብን በመተላለፍ የሚለውን ፍሬ ነገር ብቻ የሚያሟሉ በመሆናቸው እንደ አንድ የሚወሰዱ ናቸው፡፡ ስለሆነም በደረጃ 1 እርከን 21 ስር የሚያርፍ ይሆናል፡፡ 2ኛ ክስ በ1ኛ ክስ የሚጠቃለል ከመሆኑም በላይ ደረጃውን መካከለኛ ማለቱ ተገቢ አይደለም፡፡ በስር ፍ/ቤት ካቀረብኳቸው 6 ማቅለያ ምክንያቶች ውስጥ አንዱን ብቻ በመተው አምስቱን የወሰደ ቢሆንም 4 እርከን ብቻ መቀነሱ ተገቢ ባለመሆኑ 5 እርከን ተቀንሶ ቅጣቱ ሊቀነስልኝ እና ሊገደብልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የአመልካች ሃሳብ በሰጣት የማደንዘዣ መድሃኒት ስትደነዝዝ ብልቷን መስፋት ከሆነ ድርጊቱ ሞት ያስከተለ ቢሆንም በድርጊት እና ሃሳብ አንጻር በሁለቱም የሕግ አንቀጾች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበት አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቀባበል ክርክር ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ያቀረበው መልስ ይዘት፡- በወንጀል ሕግ አንቀጽ 60(ለ) መሠረት በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የሕግ ድንጋጌዎችን ያደረገ እንደሆነ ክሱ በተደራራቢነት መቅረብ እንዳለበት ሕጉ ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ድንጋጌዎችን ወይም በአንድ ድርጊት ልዩ ልዩ ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትሉ ወንጀሎችን ያደረገ በመሆኑ በ1ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 543/3/ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እና በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 566/1/ የሴትን ብልት መስፋት ወንጀል መከሰሱም ሆነ ጥፋተኛ ተብሎ መወሰኑ አግባብና ሕግን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የ10 ዓመት ጽኑ እስራት የተሻሻለውን ቅጣት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካች አቤቱታውን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ከስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ መርምረናል፡፡ በዚህም መሠረት ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ መርምረን እንደተረዳነው አመልካች የሚችን ብልት ለመስፋት የማደንዘዣ መድሃኒት በመስጠት በመስፋት ላይ እያለ በመድሃኒቱ የተነሳ መተንፈስ ተስኗት ሕይወቷ ማለፉ በአመልካች በራሱ የእምነት ቃል የተረጋገጠ በመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ግራቀኙን ያከራከረው እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል በጭብጥነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተያዘዉ አመልካች በወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቸልተኛነት ሰዉ መግደል ወንጀል ጥፋተኛ በተባለበት ሁኔታ በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 566(1) የተመለከተዉን በመተላለፍ የሴት ልጅ ብልት በመስፋት ወንጀል ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በወ/ሕ/አንቀጽ 61(1) በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኝነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ ሲሆን አድራጊዉ ተመሳሳይ ባህሪ ባላቸዉ በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች አይቀጣም በማለት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ የምንገዘበዉ በአንድ የወንጀል የማድረግ ሃሳብ ወይም ቸልተኝነት የተፈጸመዉ የወንጀል ድርጊት በሕግ በተጠበቀ አንድ መብት ላይ በሚሆንበት ጊዜ እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር መሸፈን እስከቻሉ ድረስ ፈጻሚዉ የሚቀጣዉ ድርጊቶቹ በሚሸፈኑበት በአንድ ድንጋጌ ስር እንጂ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎች አለመሆኑን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በአንድ ወንጀል በማድረግ ሃሳብ የፈጸመዉ ወይም በሟች ላይ የፈጸመዉ የሴት ብልት መስፋት የወንጀል ድርጊት ለሟች ሞት ምክንያት ሆኗል፡፡ የሟች ሕይወት ባያልፍ ኖሮ አመልካች የወ/ሕ/አንቀጽ 566(1) የተመለከተዉን በመተላለፍ በሴት ብልት በመስፋት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በተቀጣ ነበር፡፡ ሆኖም ድርጊቱ በሟች አካል ላይ ስቃይና ጉዳት ከማድረስ አልፎ ለሟች ሕይወት ማለፍ ምክንያት ሆኗል፡፡ የሟች ሕይወት ማለፍ ትልቁ ወንጀል በመሆኑ በዉስጡ በሟች አካል ላይ የሚደርሰዉን ስቃይና ጉዳት አጠቃልሎ የሚይዝ በመሆኑ አመልካች የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) ተላልፎ በሟች ላይ በቸልተኝነት ግድያ ፈጽሟል ተብሎ ክስ ቀርቦበት እስከተቀጣ ድረስ በትንሹ ወንጀል የወ/ሕ/አንቀጽ 566(1) የተመለከተዉን ተላልፏል ተብሎ በተደራራቢ ወንጀል የሚቀጣበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡ የዚህ ማጠናከሪያዉ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የሴት ብልት መስፋቱ የጤና ችግር ወይም የአካል ጉዳት አስከትሎ እንደሆነ ቅጣቱ ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ጽኑ እስራት ሊደርስ እንደሚችል ሲደነገግ ነገር ግን የደረሰዉ ጉዳት ወይም ዉጤት ከዚህ በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ተፈጻሚ የሚደረገዉ ትልቁን ወይም ከባዱን ቅጣት የያዘዉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን ያስገነዝበናል እንጂ በተደራራቢ ወንጀል በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎች ይቀጣል አይልም፡፡ በዚሁ መሠረት በ1ኛ ክስ የተጠቀሰዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) ከ5 ዓመት እስከ 15 ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ትልቁን ቅጣት የያዘና በሚች ላይ የተፈጸመዉን ድርጊትና ዉጤት በሙሉ የሚሸፈንበት ከመሆኑም በላይ አመልካች የተከሰሰበትና የተከራከረበት ጭምር በመሆኑ ጥፋተኛ መባል የሚገባዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) ብቻ መሆን ሲገባዉ በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 566(1) የተመለከተዉን ተላልፏል ተብሎ በተደራራቢ ወንጀል መቀጣቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑ በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የተላለፈዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ ተሻሽሎ የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ብቻ ጥፋተኛ ሊባል ይገባል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ በተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) ደረጃ የወጣለት በመሆኑና የወንጀል ማቋቋሚያ ዉስጥ ግልጽ ደንብና መመሪያ በመተላለፍ የተፈጸመ በመሆኑ የተሟላዉ አንድ የአንቀጹ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በዚሁ መሰረት ደረጃ አንድ በእስራት ቅጣት እርከን 21 በገንዘብ መቀጮ እርከን 6 ላይ ያርፋል፡፡ በስር ፍ/ቤት የገንዘብ መቀጮ ያልተወሰነና ቅሬታ ያልቀረበበት በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ የእስራት ቅጣቱን በተመለከተ በስር ፍ/ቤት የተያዙለትን አራት የቅጣት ማቅለያዎችን እንዳለ ወስደን አራት እርከን ሲቀነስለት እርከን 17 ላይ ያርፋል፡፡ እርከን 17 ፍቅድ ስልጣኑ ከ3 ዓመት ከ3 ወር እስከ 3 ዓመት ከ11 ወር የሚያስቀጣ በመሆኑ አመልካች ለፈጸመዉ አድራጎት ይመጥናል ባልነዉ በ3 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት ሊቀጣ ይገባል፡፡

ሲጠቃለል በአመልካች ላይ የተሰጠዉ የጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10692 ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ 126459 ጥቅምት 23

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ የጸናዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. በስር ፍ/ቤት አመልካች የወ/ሕ/ አንቀጽ 543(3) እና 566(1) የተመለከተዉን ተላልፏል ተብሎ የተሰጠዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ እና የ10 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ተሻሽሎ አመልካች የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ ጥፋተኛ ነዉ ተብሎ በ3 (ሦስት) ዓመት ከ6(ስድስት) ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ዉሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም የዉሳኔዉ ግልባጭ አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይተላለፍ፡፡ እንዲሁም ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
4. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ/141677

ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች ፡ያዕቆብ አብዱ -

ተጠሪ ፡የደቡብ ክልል አቃቤ ህግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል ።

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ አመልካች የወ/ህግ አንቀጽ 27/1/ እና 540 ተላልፎ ተራ የሆነ ሰዉ ግድያ መክራ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በ12 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍ/ ቤት የሰጠዉ ፍርድ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ችሎት በማጽናታቸዉ ዉሳኔዉ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል እንዲታረም ስላመለከተ ነዉ ።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በወ/ህግ 541 ተከሶ እያለ በወ/ህግ 540 ጥፋተኛ መባሉና እና ድርጊቱ በመክራ ቀርቶ እያለ በወ/ህጉ አንቀጽ 27/3/ መሰረት ቅጣት ያልቀለለበት አግባብ ለመመርመር እንዲቻል ዓቃቤ ህግ መልስ እንዲሰጥ ታዟል። የፍ/ቤቱ መጥሪያ ለዓቃቤ ህግ በፖስታ ቤት በኩል የተላከለት ቢሆንም ቀርቦ መልስ አልሰጠም ። በዚሁ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎ መዝገቡ ተመርምሯል ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉ አንደኛ ጭብጥ አመልካች በወ/ህግ አንቀጽ 541 ተከሶ እያለ በአንቀጽ 540 ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲሆን በእኛ በኩል መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነዉ ዐቃቤ ህግ መጀመሪያ ክስ ያቀረበዉ በአንቀጽ 541 ቢሆንም በክርክር ሂደት ክሱን በማሻሻል በወ/ህግ አንቀጽ 27/1/ 540 ስር የለወጠ ስለመሆኑ ስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ይዘት ያስረዳል ።ፍ/ቤቱም ተሻሽሎ በቀረበዉ አንቀጽ መሰረት የጥፋተኝነት ዉሳኔ ሰጥቷል ። ስለሆነም አንቀጹን ወደ 540 የለወጠዉ ፍርድ ቤቱ ሳይሆን ከሳሽ ዓቃቤ ህግ ስለሆነ ሰበር አጣሪ ችሎት የስር ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ከአንቀጽ 541 ወደ 540 ማለትም ከቀላል ወደ ከባዱ አንቀጽ የለወጠ መስሎት በዚህ ነጥብ ላይ ጭብጥ መያዙ ፍርዱን ባለማገናዘብ እንደሆነ ማየት ችለናል ። በሌላ በኩል አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ ክሱ ከተሻሻለ በኋላ በከበደዉ አንቀጽ ስር የመከራከር መብቱ ባልተጠበቀበት ሁኔታ የጥፋተኝነት ፍርድ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ በማለት ነዉ ። ስለዚህም ክስ ከተሻሻለ በኋላ ፍ/ቤቱ የተከተለዉ የክርክር አመራር ስርዓት አግባብነት ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ።

በመሰረቱ የወንጀል ክስ ሊሻሻል የሚችልባቸዉ ምክንያቶች በወ/መ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ118 እና 119 ስር የተመለከቱ ሲሆን የክሱ መሻሻል የሚያስከትለዉ ዉጤት በዚሁ ድንጋጌ አንቀጽ 120 እና 121 ላይ ተመልክቷል ።ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ ክስ ተሻሽሎ ከቀረበ በኋላ ለተከሳሹ ተነቦለት የክሱ መሰማት የሚቀጥል መሆኑን እና ምስክሮችም በዚህ አግባብ እንደገና እንዲሰሙ መደረግ የሚችልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ነዉ ።በተያዘዉ ጉዳይ ዓቃቤ ህግ የወ/ህግ አንቀጽ 27/1/ እና 541 ጠቅሶ ክስ አቅርቦ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቃል ከተሰማ በኃላ ዓቃቤ ህግ ክሱን በማሻሻል ወደ አንቀጽ 27/1/ እና 540 ለዉጦ ያቀረበ ሲሆን ጉዳዩን የያዘዉ ፍ/ቤት የተከሳሽን የመሰማት መብት ሳይጠብቅ ቀደም ሲል በተሰማዉ ክርክርና የዓቃቤ ህግ ማስረጃ መሰረት ተከሳሽ /አመልካች / ተሻሽሎ በቀረበበት ክስ ድንጋጌ እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል ።አመልካች ቀደም ሲል የተከሰሰዉ በቀላል ግድያ ሙከራ ወንጀል ሲሆን ተሻሽሎ የቀረበዉ ክስ ደግሞ ተራ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል በመሆኑ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ የሚጣልበት ቅጣት ከባድ ከመሆኑ አንጻር የተከሳሹ መሰረታዊ መብት ላይ የሚኖረዉ አሉታዊ ተጽእኖ ጋር ተመዛዝኖ በስነስርዓት ህጉ የተጠበቀለት የመሰማት መብት በጥብቅ ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ መረዳት አዳጋች አይደለም። ከዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ መብት አንጻር የፍርድ ቤቱ የክርክር አመራር በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/119/2/ ፤120 እና 121 ድንጋጌዎች በአግባቡ ያላገናዘበ እንደሆነ መረዳት ተችሏል ። ስለሆነም ክሱ ተሻሽሎ ለዚያውም ወደ ከባድ አንቀጽ ተለዉጦ ቀርቦ እያለ ክሱ እንደገና እንዲሰማ መደረግ እንዳለበት የተደነገገዉን ስርዓት ሳይጠብቅ ክርክሩን በመምራት የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል ። የበላይ ፍ/ቤቶች ይህንኑ ተገንዝበዉ ሳያርሙ ማጽናታቸዉ ግልጽ ግድፈት ስለሆነ ለታረም ይገባል ብለናል።

ሁለተኛዉ ጭብጥ ድርጊቱ በሙከራ ደረጃ የቀረ ከመሆኑ አኳያ በወ/ህጉ አንቀጽ 27/3/ መሰረት ቅጣት እንዲቀልለት አለመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ነዉ። ነገር ግን ክርክሩ በአንደኛዉ ጭብጥ እልባት ያገኘ ስለሆነ መመርመር አስፈላጊ ባለመሆኑ ታልፏል በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል ።

ዉ ሳ ኔ

1ኛ /የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 5224 በ16/02/09 ዓ.ም አመልካች የወ/ህግ እንቀጽ 27/1/ እና 540 ስር የተመለከተዉን ተላልፎ ተራ የሆነ የሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል በማለት በ12 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/04047 የሰጠዉ ትእዛዝ እና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/04781 የሰጠዉ ትእዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ 195/2/ለ/2 / መሰረት ተሽሯል ።

2ኛ/ዓቃቤ ህግ አሻሽሎ ባቀረበዉ ክስ ላይ የአመልካችን እምነት ክህደት ቃል ከመቀበል ጀምሮ በወ/መ/ ስ/ስ ህግ አንቀጽ 119/2/ ፤120 እና 121 በተደነገገዉ አግባብ ክርክሩን በማየት ተገቢዉን ፍርድ እንዲሰጥ ብለን መዝገቡን በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/ 195/2/ሀ መሰረት ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል ።ይጻፍ ።

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 127313

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የአ/ብ/ክ/መ/ፍ/ቢሮ ዓ/ህግ- አብርሃም በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አንዱአለም ገናነው መላኩ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የጉዳዩን አመጣጥ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች በስር ደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ መነሻ ያደረገ ሲሆን የቀረበው ክስ ይዘት ተከሳሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 555(1(ለ)) በመተላለፍ የሰው አካል ላይ ጉዳት ማደረስ ወንጀል ተከሷል በማለት ክስ ቀርቦበታል፡፡ የሥር ተከሳሽ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ድርጊቱን አልፈፀምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ የሰዉ ምስክሮች በመስማትና በመመርመር ተከሳሽ ስለተመሰከረባቸው እንዲከላከሉ ብይን በሰጠዉ መሰረት ተከሳሽ መከላከያ ምስክሮች አስቀርቦ እንዲያሰማ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ የተከሳሽ መከላከያ ምስክር ለመስማት ተደጋጋሚ ቀጠሮ የተሰጠ ሲሆን ተከሳሽ መከላከያ ምስክሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ መከላከያ ምስክሩን ይዞ ባለመቅረቡ አመልካች ተከሳሽ መከላከያ የማቅረብ መብቱ ታልፎ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይለት ለፍርድ ቤት አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ የተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 161 መሰረት በሌለበት ጉዳዩ ሊታይ የሚቻል አይደለም በማለት ፖሊስ ተከሳሽ ካለበት ቦታ አፈላልጎ እንዲያቀርብ ትእዛዝ በመስጠት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ በዚሁ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው አቅርቦ አቤቱታውን ባለመቀበል ሰርዘውታል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸው እንዲያቀርቡ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበው ቅሬታ የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት እንደተቻለው ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ በመሆን የቀረበበት ክስ የወ/ህ/ቁጥር 555(1(ለ)) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ሲሆን ተጠሪ ችሎት ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉን ሲሰጥ ክዶ የተከራከረ መሆኑ የከሳሽ ዓ/ህግ ምስክሮች ሲሰሙ ችሎት ቀርቦ የተከራከረ እና እንዲከላከል ተነግሮት በተደጋጋሚ ቀጠሮ መከላከያ ማስረጃውን ይዞ ያልቀረበ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ፡፡አሁን ለቀረበው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ እንዲከላከል ትእዛዝ ተሰጥቶና አውቆ መከላከያ ምስክሩን ይዞ ባለመቅረቡ የመከላከል መብቱ ታልፎ ውሳኔ እንዲሰጥ የቀረበው የአመልካች አቤቱታ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ አይደለም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የወንጀል ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ወንጀሉን ያልፈፀመ መሆኑን በመግለፅ የተከራከረ መሆኑ፣ተጠሪ ባለበት አመልካች ማስረጃዎቹን ያሰማ መሆኑንና ተጠሪም የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት እንዲከላከል ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሲሰጥ በችሎት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህም ተጠሪ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት የአመልካችን ምስክሮች ቃል የመመርመርና የመጠየቅ መብቱ ሙሉ በሙሉ በተከበረበት ሁኔታ ተጠሪ በህገ መንግስት የተጠበቀለት የመከላከል መብት ፍርድ ቤት ቀርቦ ማሰማትና መጠቀም ሲገባው በራሱ ፍቃድ የተወው መሆኑ ከክርክሩ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

በመርህ ደረጃ የወንጀል የክርክር ሂደት ተከሳሾች ባሉበት እንደሚደረግ በልዩ ሁኔታ ደግሞ የፈጸሙት ወንጀል ቀርበው መከራከር የማይፈልጉና ከፍትህ ስርዓቱ የሸሹ ግለሰቦች በፍትህ ስርዓቱ መጠየቅ ያለባቸው በመሆኑ በሌሉበት ነገሩ ሊሰማ እንደሚችል ከወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 161(1) እና (2(ሀ) ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት ንባብ የምንረዳው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም አንድን ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ለማየት እንዲችል ተከሳሹ በቀጠሮ ቀን ያለ በቂ ምክንያት መቅረቡ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑ የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ያመለክታል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በሌለበት ነገሩ ለመስማት ትዕዛዝ ከሰጠ ጥሪው ተደራሽ በሆነ አግባብ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል፡፡ በወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162 እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ የሚያስተላለፈው ጥሪ ተከሳሹ ስለተጠረጠረበት ጉዳይ ዝርዝር መግለጫ የያዘ እና ጥሪውም በጋዜጣ እንዲወጣ መታዘዝ እንዳለበት ከድንጋጌው ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ በሌላ በኩል ፍ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘም የመጥሪያ ማስታወቂያው በሌላ መንገድ ማስተላለፍ እንደሚችል የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ያሳያል፡፡በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ክሱ በሚሰማበትና የከሳሽ ዓ/ህግ ምስክሮች በሚሰሙበት ጊዜ ችሎት ቀርቦ የተከራከረ በመሆኑ እና በተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ አውቆ መከላከያ ማስረጃ ለመስማት ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ በያዘበት ቀን ሳይገኝ መቅረቱ ጉዳዩ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (4) በወንጀል የተከሰሰው የዓቃቤ ህግ ማስረጃ ሲሰማ በመገኘት የዓቃቤ ህግን ምስክሮች የመጠየቅና የመመርመር መብቱን በአግባቡ ከተጠቀመና የመከላከያ ምስክሮችንና ማስረጃ እንዲያቀርብ የተሰጠውን መብት በራሱ ፍላጎት ካልተጠቀመ እና የመከላከል መብቱን ካልተጠቀመ ዳኞች የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ በመመዘን ፍርድ ከመስጠት የሚገድባቸው ባለመሆኑ በህጉ ለተከሳሽ ከተሰጠው የመደመጥ መብት አንፃር ተከሳሹ መብቱ በራሱ ፍላጎት ባለመጠቀሙ ጉዳዩ ተከሳሹ በሌለበት እንደሚታይ ጉዳይ ሊታይ የሚችል ባለመሆኑ ፍርድ ቤቶች የቀረበውን ጉዳይ መርምረውና መዝነው ውሳኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመስጠት የሚገድባቸው ጉዳይ አይሆንም፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ (የስር ተከሳሽ) መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ እንዲከላከል ተፈቅዶለት ቀጠሮውን አክብሮ ባልቀረበበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳይ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 161 ጋር በማያያዝ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ አይደለም በማለት ውሳኔ መስጠታቸው፣ አንድ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት በ(default procedure) ታየ የሚባለው መቼ ነው? ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክስ ስለሚታይበት ሁኔታ የሚደነግጉት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነስርዓት ሕግ ቁጥር 161 እስከ 164 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት ትርጉምና ተፈፃሚነትና ውጤት እንደዚሁም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት በሌለበት ታይቶ ከሚሰጥ ፍርድ ለእንዴት አይነት ጉዳይ ነው የሚለውን የህገመንግስቱን አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ ቁጥር 149 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 4 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጡት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ በመሆኑ የክርክሩ ሂደት በአግባቡ የተመራና የተሟላ ሁኖ አልተገኘም፡፡ የክርክሩ ሂደት በአግባቡ ያለመመራትና የተሟላ ፍሬ ነገር እንዲኖር ያለማድረግ የዳኝነት አሰጣጥ ሰርዓት የማይፈቅደው በመሆኑ የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ነው፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብ/ክ/መንግስት የደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁጥር 01362 ታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ./ቁጥር 0215307 ታህሳስ 29 ቀን 2008 ዓ/ም ያፀናው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 54349 መጋቢት 01 ቀን 2008 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 195(2)(ለ)(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የክርክሩ ሙሉ ሂደት ተከታትሎ ለተከሰሰበት ወንጀል እንዲከላከል ትእዛዝ መሰጠቱን አውቆ የጠፋ ስለሆነ ይህ ጉዳይ በሌለበት ሊባል የሚችል ስላልሆነ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቱ ተጠሪ የመከላከል መብቱን ለመጠቀም እንዳልፈለገ ቆጥሮ ተገቢውን እንዲወስን ለክልሉ ደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት ተመልሶለታል፡፡ይባፍ፡፡

3. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 137672

ሕዳር 25 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

አመልካች፡- ብርሃነ ሀለፎም ገ/መድህን-ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ሙናቸው

ተጠሪ፡- የፌደራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐቃቢ ህግ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 164774 በቀን 18/02/2009 ዓ.ም ፍርድ እና በቀን 01/03/2009 ዓ.ም የቅጣት ውሳኔ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 124288 ጥር 10 ቀን 2009 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ገንዘብ ማከማቸት የሙስና ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክሱ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 419/1//ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከመስከረም 1982 ጀምሮ በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች ተቀጥሮ ሲያገለግል በፌደራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ከህዳር 1/1996-ሰኔ 30/1997 በብር 595 ደመወዝ መረጃ አገልግሎት ውስጥ በክለርክነት፣ ከሰኔ 1/1999-ነሐሴ 30/1999 በብር 1145 ደመወዝ በተ.እ.ታ. መምሪያ የግብር ከፋዮች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምዝገባ ውስጥ ሱፐርቫይዘርነት፣ ከሰኔ 1/2006-ሐምሌ 2/2006 በብር 7284 ደመወዝ በኢ/ገ/ጉ/ባለስልጣን የአጠቃላይ ቅሬታ አስተናጋጅ ቡድን አስተባባሪ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ወቅት በመንግስት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ወይም ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ህጋዊ ገቢ ጋር በማይመጣጠን ሁኔታ በባለቤቱ ወ/ሮ አይናለም ጌታቸው ስም የተመዘገበ በአ.አ ኮልፌ ቀ/ክ/ከ ቀበሌ 02/03 የቤት ቁጥር 2244 የካቲት 26/2000 ዓ.ም በብር 275000 የተገዙ፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ቆሬ ኮንደሚኒየም የቤት ቁጥር ቢ51/54003 ሐምሌ 9/2004 ዓ.ም በብር 125000 የተገዛ እና ከ10/03/2005 ጀምሮ የካፍቴሪያ አገልግሎት የሚሰጥ በባለቤቱ ስም የተመዘገበ ንግድ ፈቃድ፣ በአመልካች ስም የዳሸን ባንክ ሂሳብ ቁጥር 5001503553001 እስከ ሐምሌ 13 ቀን 2004 የነበረ ብር 65733.19፣ በባለቤቱ ወ/ሮ አይናለም ጌታቸው ዳሸን ባንክ ሂሳብ ቁጥር 5001503552001 እስከ ሐምሌ 13 ቀን 2004 የነበረ ብር 63294.28 ያለአግባብ ያከማቹ በመሆኑ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ማከማቸት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው።

አመልካች የቀረበበትን ክስ በመካዱ በተጠሪ የቀረውን የሰነድ ማስረጃዎች ፍርድ ቤቱ ከመረመረ በኋላ የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል በሰጠው ብይን በአመልካች 6 የሰው የመከላከያና የጽሁፍ ማስረጃዎች የቀረቡ መሆኑን ገልጾ ፍርድ ቤቱ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ በአመልካች እና በባለቤቱ ስም ተመዝግበው የሚገኙት ንብረት እና ገንዘብ የአመልካች ገቢ ተብሎ ከተገለፁት በላይ መሆኑን የሚያስገነዝብ መሆኑን፤ የአመልካች አንደኛ ምስክር በብድር ለአመልካች ሁለት ጊዜ ሠጥቻለው ያሉትን በተመለከተ የመጀመሪያውን በ1999 ተሰጠ የተባለውን 84000 ውድቅ በማድረግ ሁለተኛው በ2004 ዓ.ም የተሰጠውን ብር 50000 የብድር ውሉ ያረጋግጣል በማለት ተቀብሎታል፡ ሁለት የአመልካች ወንድሞችና መከላከያ ምስክሮች የአባታቸው የውርስ ድርሻ ተሸጦ ብር 80000 ለአመልካች ቤት መግዢያ የሰጡት መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም፡ በሌላ በኩል 4ኛ 5ኛ እና 6ኛ ምስክር በተመለከተም አመልካች በግል ያስተምር የነበረ መሆኑን ገቢው እንደማይታወቅ፤ ዕቁብ ብር 22000 እና 11000 የደረሰው ስለመሆኑ የገለፁ መሆኑን ገልጾ አመልካች የመንግስት ሥራ ከጀመረበት 1982-1999 የነበረው አጠቃላይ የደመወዝ ገቢ ብር 66162 የነበረና በአመልካች ባለቤት ስም ቤት የገዛው በብር 275000 በመሆኑ ይህንን ለመግዛት የሚያስችል ገቢ የለውም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በልዩነት የተገኘው ብር 208838፣ አመልካች ጥቅምት 3/2003 ድረስ ያለው ጥቅል ገቢ ብር 109260 ተሸከርካሪ ከገዛበት በልዩነት የተገኘ ብር 62740 እና ሐምሌ 9/2004 የተገዛውን ቤት ጋር ገቢውና በብድር የተገኘው ሲነፃፀር ንብረቱን ለማፍራት የሚችልበት ነው፣ በባንክ ያለው ገንዘብ በወቅቱ ከነበረው ገቢ ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ ብር 51063.47 አመልካች አላስረዳም በአጠቃላይ አመልካች ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ ተገኝቷል ከተባለው ውስጥ ብር 322641.47 የሆነውን ብቻ ምንጩን ህጋዊ አመጣጡን ያላስረዳ ስለሆነ በቀረበበት ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 419/1//ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው ብሎ በአንድ ዓመት ከሁለት ወር እስራት እና በብር 5000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ እና ብር 322641.47 ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡት ይግባኝ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳይቀበል የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቶታል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የኮንደሚኒየም ቤት የተገዛበትን ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተከፈለው ከቤትና ከባንክ ገንዘብ ሲሆን እንደተለያዩ ንብረት አድርጐ ወስዷል፣ የቀረበውን ክስ በመከላከያ ማስረጃዬ አስተባብያለሁ፣ የመከላከያ ምስክር የሰጠኝ ብድር አንዱን ተቀብሎ ሌላውን ውድቅ ያደረገበት ምክንያት ተገቢ አይደለም፣ የአባቴን የውርስ ድርሻ ወንድሞቼ የሰጡኝ ስለመሆኑ ማረጋገጣቸው መተሳሰብና መፋቀር እንጂ ሀብትን አያመለክትም ፤አመልካች በግል የማስተምር እና የምነግድ መሆኑ ባለቤቴም ከመጋባታችን በፊት ጀምሮ ነጋዴ መሆንዋ መጠኑ ባለመታወቁ መታለፍ የለባትም፣ የደረሰኝ ዕቁብ አልተያዘም፣ ለቤቱ መግዣያ ይሸው መዋሉን ገልጬ አልተያዘም የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት ብር 84000 ሳይዝ ብር 50000 ብቻ የያዘበት እና 2ኛ ምስክር የአመልካች ወንድምን እህት የሰጡትን ፍ/ቤቱ ውድቅ ያደረገበትን አግባብ ለመመርመር ተጠሪ ቀርቦ መልስ አንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት በሰጠው መልሱ የአመልካች አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሳይሆን የማስረጃ ምዘናን የሚጠይቅ ነው፡ ተቀባይነት የለውም፣ የገንዘብ ብድሩን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ተገቢውን ማጣራት አድርጐ የወሰነው ነው፡፡ የመከላከል ምስሮችም የተጠና ሊሆን የሚችል እንጂ አልተከላከለውም፣ ሁለት ጊዜ የታሰበ የለም፣ የሚሉ ዝርዝር መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለዚህ ሰበር ምክንያት ከሆነው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለዚህ ሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች የመንግስት ሠራተኛ በመሆን ያገኘውን ገቢ መሠረት በማድረግ አፍርቶታል የተባለውን ገንዘብ እና ንብረት የብር 322641.47 ልዩነት ያለው በመሆኑ ተመጣጣኝ አይደለም ምንጩንም ማስረዳት አልቻለም በማለት በተሰጠው ውሳኔ ላይ በማስረጃ ምዘና ወቅት በብድር ያገኘው ብር 84000 እና የውርስ ንብረት ከወንድሞቹ የተላለፈለትን ብር 80000 ውድቅ የተረገበትን አግባብ ለመመርመር ያስቀርባል መባሉን ነው፡፡

ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 419 ንዑስ አንቀጽ 1//ሀ/ እና /ለ/ ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻለው ዐቃቤ ሕግ የመንግስት ሠራተኛ የሆነው ወይም የነበረው ሰው ያገኘ የነበረውና የሚያገኘው ገቢ ምን ያህል እንደሆነና የመንግስት ሠራተኛው በራሱ ስምም ሆነ በቤተሰቡ ስም ከሕጋዊ ገቢው ውጪ ይዞት የሚገኘውን የገንዘብና የንብረት ግምት የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግልፅ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል የመንግስት ሠራተኛ የነበረው ሰው ከነበረውና ከሚያገኘው ገቢ በላይ ይዞት የተገኘው ገንዘብ ወይም ሀብት ትክክለኛው ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ሶስተኛው ፓራግራፍ ፣ “... የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት እንደገባ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በስተቀር” ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ በመገኘቱ ጥፋተኛ ተብለው በሕጉ የተደነገገው ቅጣት ሊጣልባቸው እንደሚችል በመግለፅ ይደነግጋሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳው ዐቃቤ ሕግ በግልፅ ከሚታወቀው ሕጋዊ ገቢ በላይ ነው በማለት በክሱ የተገለፀውንና በማስረጃ ያረጋገጠውን ሀብት ትክክለኛ ምንጭ የማስረዳት ግዴታ / Burden of Proof/ በተከሳሾች ላይ የሚወድቅ መሆኑን ነው፡፡ የተከሳሾች የማስረዳት ግዴታም ዐቃቤ ሕግ በክሱ ከገለፀውና በማስረጃ ካረጋገጠው ውጭ ተከሳሽ ሌላ ገቢ የሚያገኝበት ስራ ወይም የገቢ ምንጭ ያለው መሆኑን ብቻ ለፍርድ ቤቱ በማሳየት የሚወሰን ሳይሆን፣ በዐቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ከተረጋገጠው ገቢ ውጭ በእጁ እንደተገኘ የተረጋገጠው ገንዘብና ሀብት ትክክለኛ ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ሶስተኛው ፓራግራፍ ድንጋጌ አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንጻር አመልካች የመንግስት ሠራተኛ ሆነው ካገኙት ህጋዊ ገቢ /ደመወዝ/ በተጨማሪ ያስቀርባል ሲባል የተያዙትን ከመከላከያ ምስክራቸው በብድር አግኝቼዋለሁ ያሉትን ብር 84000 እና እህት እና ወንድማቸው የአባታቸውን ድርሻ ብር 80000 ሰጥተውኛል ያሉት የስር ፍርድ ቤት ቢቀበላቸው በልዩነት ከገቢያቸው በላይ ለሆነው የገንዘቡን ምንጭ አላስረዱም ብሎ ጥፋተኛ ካለበት ብር 322641.47 አንጻር የሚያስተባብል አይደለም፡፡ በዋናነት ግን የስር ፍርድ እነዚህን በብድርና በስጦታ ተገኙ የተባሉትን የገንዘብ ምንጮች ውድቅ ያደረገው በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ መሆኑ ሲሆን ይህ በፍሬ ጉዳይ ላይ የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት ሊታይ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 80/3//ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን በመመዘን በደረሰበት ድምዳሜ ላይ የቀረበው አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

ውሳኔ

የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 164774 በቀን 18/02/2009 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በ01/03/2009 የቅጣት ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 124288 በቀን 10/05/2009 ዓ.ም በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 122595

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የገ/ን/ባለስልጣን ዓ/ህግ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ አቶ ፋሲል ጥላሁን

2ኛ አቶ ካሊድ ሳቢት

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የኮንትሮባንድ ወንጀልን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 10870 በ30/3/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ደግሞ 1ኛ ና 2ኛ ተከሳሽ ሆነው ሲከራከሩ የነበር ሲሆን፣ከሳሽ ባቀረበዉ 1ኛ ክስ፡-በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ የቀረበ ሲሆን ይዘቱም የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን በመተላለፍ ተከሳሾች እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ለራሳቸውም ሆነ ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ለማስገኘት ምንም ዓይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና በሞዴል 270 በቁጥር 876593 ተመዝግቦ ወደ መንግስት መጋዘን የገባው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-020775 ሐረር ሚኒባስ የሆነ ተሽከርካሪ ቀረጥ ተከፍሎበት የገባ መኪና ለማስመሰል የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 እና ሞተር ቁጥሩ 5L21455255 ከሌላ መኪና ተቆርጦ የተለጠፈውን በቀን 10/08/05 ዓ/ም ከቀኑ 8፡00 አከባቢ በፌዴራል ፖሊስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አካላት ክትትል በሃረር ከተማ ቀበሌ 14 በመያዙ 1ኛ ተከሳሽ የህገወጥ መኪና ባለቤት እና 2ኛ ተከሳሽ ለህገወጥ መኪናው የ1ኛ ተከሳሽ ወኪል ሆነው ህገወጥ እቃ ይዘው በመገኘታቸው ተከሷል። 2ኛ ክስ በ2ኛ ና 3ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ሲሆን የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ በመተላለፍ ተከሳሾች እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው የካቲት 30 ቀን 2005 ዓ/ም ምንም አይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና ከላይ በ1ኛ ክስ ላይ የተመለከተው ተሽከርካሪ በ2ኛ ተከሳሽ ወኪልነት ለ3ኛ ተከሳሽ የሸጠለት በመሆኑ ተከሳሾች የኮንትሮባንድ እቃ የተገበያዩ በመሆናቸው በኮንትሮባንድ ወንጀል ተከሷል፣ 3ኛ ክስ 1ኛ ተከሳሽ የተመለከተ ሲሆን የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93 (1(መ))ን በመተላለፍ ተከሳሽ በ1ኛ ክስ ለተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ ካስገባ በኋላ ተገቢዉን ቀረጥና ታክስ ለመንግስት እንዳይከፈል ለማድረግ በማሰብ በፋጢማ መሃመድ ያሲን ስም ተመዝግቦ በህጋዊ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ የገባውን ተሽከርካሪ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 በመጠቀም በራሱ ስም ሊብሬ አውጥቶ ሲገለገልበት በቀን 10/08/05 ዓ/ም በቁጥጥር ስር በመዋሉ ተከሷል የሚል ነዉ።

ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት ቀርበው ክሱ ደርሷቸው ተቃውሞ እንደሌላቸው ገልፀው፣ በሰጡት የእምነት ክህደት ቃል ደርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ክደው ተከራክሯል። ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርመር ተከሳሾች በቀረበባቸው ሁሉም ክሶች እንዲከላከሉ ባዘዘዉ መሰረት ተከሳሾች የፅሁፍ ማስረጃና የሰዉ መከላከያ ምስክሮችንም አቅርበው አሰምቷል። በመቀጠል ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ የሰነድ ማስረጃዎች እና የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃዎችን በሕጉ አግባብ ከመዘነ በኋለ በሰጠዉ ዉሳኔ በክስ የተመለከተዉ ተሽከርካሪ በሕገ ወጥ መንገድ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈጸምበት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ከዉጭ አገር ወደ አገር ዉስጥ መግባቱ እና ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት እንደተከፈለ በማስመሰል ሰነድ የተዘጋጀ መሆኑም አልተረጋገጠም ተከሳሾች በሚገባ ተከላክለዋል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች በ18/05/2008 ዓ.ም በተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ተጠሪዎች በቀረበባቸው ክስ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 እና የሞተር ቁጥር 5L21455255 የሆነ ተሽከርካሪ እነዚህ ቁጥሮች ለተሸከርካሪው በፋብሪካ የተሰጡት ቁጥሮች ሳይሆኑ በህጋዊ መንገድ በዲክለራሲዮን ቁጥር C-1828/2010 በፋጡማ መሃመድ ያሲን ስም ወደ ሃገር ውስጥ የገባው ህጋዊ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 ሲሆን ለሌላ መኪና ተቆርጦ የተመታ መሆኑ ለተያዘው መኪና እንደ ሻንሲ ቁጥር አገልግሏል ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ተሽከርካሪዎች ሻንሲና ሞተር ቁጥር ወደ ሃሰት ተለውጧል የሰሌዳ ቁጥር ከኮድ 3-17811 ኦሮ ወደ ሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-02075 ሐረ. ሲቀየር አካላዊ ሻንሲ ቁጥርና ሞተር ቁጥሩ ከሰነዱ ጋር አልተመሳከረም ይህ ስለመሆኑ በቀረበው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የሥር ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104 /3፣ ሀ/ለ/ መኪናዉ እንዲወረስ ዉሳኔ መስጠት ሲገባቸው ይህንን ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪዎች ቀርበው በፅሁፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው አመልካች የወንጀሉን ድርጊት ተጠሪዎች ፈጽመዋል በሚል ያቀረበው ክስ ዋናው ድርጊት 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠው ውክልናን መሠረት በማድረግ እያወቁ ወይም ማወቅ እየተገባቸው በክሱ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት በመተባበር የፈፀሙ መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዛፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2/ በግልጽ ደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ ማሟላት ያለባቸውን ነጥቦች የሚመለከት ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ አንቀጽ 24፣57 እና 58 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በቀረበው ክስ ላይ የተገለፀው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ተሸከርካሪ በህጋዊ መንገድ በዲክለራሲዮን ቁጥር C-1828/2010 በፋጡማ መሃመድ ያሲን ስም ወደ ሃገር ውስጥ የገባው ህጋዊ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 ሲሆን ይህ አሁን በቁጥጥር ስር ከዋለው መኪና ተቆርጦ የተመታ ነው በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የባለሞያ ማስረጃ እንደተገለፀው በሰሌዳ ቁጥር 3-02075 ሐረ የሆነ ሚኒባስ ተሸከርካሪ ላይ የተገኘው መረጃ በተሸከርካሪው ጋቢና በር ስር (በተሳፋሪ በኩል) የተገኘው የቻንሲ ቁጥር ሆን ተብሎ ለማጭበርበር ተቆርጦ በሌላ የተቀየረ መሆኑ በግልፅ ማረጋገጡ ተለጥፎ የተገኘው የቻንሲ ቁጥር LH172-1039214 መሆኑ እንዲሁም በተሸከርካሪው ሞተር ላይ የተገኘው የሞተር ቁጥር መጀመሪያ በነበረው ቁጥር ላይ በድጋሚ የተመታ መሆኑ በሞተር ላይ የተገኘው ቁጥር 5L-21455255 ስለ ተሸከርካሪው መረጃ የሚሰጥ ፕሌት (ስለ መኪናው ቀለም ፣ሞዴል፣የምርት ዘመን ፣የሞተር ጉልበት) በሌላ መቀየሩን በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የመኪና ሞተር እና የሻንሲ ቁጥር አስመስሎ የተመታ እና መረጃ የሚሰጥ ፕሌትም የተቀየረ ሲሆን አሁን በአካል የተመረመረው ተሸከርካሪ ግን ከላይ የተገለፀው ከሌላ መኪና የተመታ መሆኑ በባለሙያ በመመርመር ተረጋግጧል የሚል በመሆኑ ተጠቃሹ አካል ከጻፋቸው ደብዳቤዎች ይዘት የመኪናው ሞተር እና ሻንሲ ቁጥር ተመሳስሎ የተሰራ እና የተመታ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለሆነም እነዚህ የሻንሲ ቁጥር መለወጥ እና የሞተር ቁጥር መምታት፤ አድራጎቶች ተጠሪዎች ሆነ ብለው ወይም ማወቅ እየተገባቸው ድርጊቱን የፈጸሙትና ውጤቱንም የራሳቸው ያደረጉ መሆኑንን የሚያስገነዝብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለተሸከርካሪዎች መለያ፤መመርመሪያ እና መመዝገቢያ የወጣው አዋጅ ቁጥር 681/2002 ቁጥር 7/1 (ለ) እና (ሐ) የተሸከርካሪን ዝርዝር መግለጫ ለመመዝገብ እና የባለንብረት መታወቂያ ለመስጠት የሞተር ቁጥሩ እና የሻንሲ ቁጥር ሊመዘገብ እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ የአዋጁ ቁጥር 42/5 እና 48/2/ሐ ማንኛውም ሰው አግባብነት ያለው አካል ሳይፈቅድ የተሸከርካሪውን የሞተር ቁጥር የሻንሲ ቁጥር እና መሰል መረጃዎች መቀየር እንደማይቻል እና በወንጀል እንደሚያስጠይቅ ይደነግጋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የተሸከርካሪው ሞተር ቁጥር እና ሻንሲ ቁጥር የተመታ እና ተመሣሥሎ የተሰራ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬነገር ከመሆኑም በላይ ተጠሪ የመኪናው ሞተር ቁጥር እና ሻንሲ ቁጥር የተመታው አግባብነት ያለው አካል ፈቅዶላቸው መሆኑን መኪናው በጨረታ ሲገዙትም አሁን ባለበት ሁኔታ የሚመለከተው አካል አውቆት ስለመሆኑ በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ፈጽመዋቸዋል በማለት በማስረጃ ያረጋገጣቸው ፍሬ ነገሮች ሁለቱም ተጠሪዎች የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን በመተላለፍ እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ለራሳቸውም ሆነ ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ለማስገኘት ምንም ዓይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና በሞዴል 270 በቁጥር 876593 ተመዝግቦ ወደ መንግስት መጋዘን የገባው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-020775 ሐረር ሚኒባስ የሆነ ተሸከርካሪ ቀረጥ ተከፍሎበት የገባ መኪና ለማስመሰል የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214 እና ሞተር ቁጥሩ 5L21455255 ከሌላ መኪና ተቆርጦ የተለጠፈውን በቀን 10/08/05 ዓ/ም ከቀኑ 8፡00 አካባቢ ሲገለገሉ በፊዴራል ፖሊስ አካላት ክትትል በሃረር ከተማ ቀበሌ 14 በመያዙ 1ኛ ተከሳሽ የህገወጥ መኪና ባለቤት እና 2ኛ ተከሳሽ ለህገወጥ መኪናው የ1ኛ ተከሳሽ ወኪል ሆነው ህገወጥ እቃ ይዘው በመገኘታቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን የኮንትሮባንድ ወንጀል የፈፀሙ መሆኑን የተረጋገጠበት በመሆኑ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡ ሁለተኛው ክስም በተመለከተ ፣ 2ኛ ተጠሪ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ በመተላለፍ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ምንም አይነት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትና ከላይ በ1ኛ ክስ ላይ የተመለከተው ተሸከርካሪ ሚያዝያ ወር 2005 ዓ.ም የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-17811 ተሸከርካሪ እንዲያስተዳድር የተሰጠውን ውክልና መሰረት በማድረግ ለ3ኛ ተከሳሽ የሸጠለት በመሆኑ ተከሳሾች የኮንትሮባንድ እቃ የተገበያዩ መሆኑ በኮንትሮባንድ ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጧል ፣ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93 (1(መ))ን በመተላለፍ ተከሳሽ በ1ኛ ክስ ለተጠቀሰዉ ተሸከርካሪ በህገወጥ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ ካስገባ በኋላ ተገቢዉን ቀረጥና ታክስ ለመንግስት እንዳይከፈል ለማድረግ በማሰብ በፋጢማ መሃመድ ያሲን ስም ተመዝግቦ በህጋዊ መንገድ ወደ ሃገር ውስጥ የገባውን ተሸከርካሪ የሻንሲ ቁጥር LH172-1039214

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጠቀም በራሱ ስም ሊብራ አውጥቶ ሲገለገልበት በቀን 10/08/05 ዓ/ም በቁጥጥር ስር በመዋሉ በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ በመገንዘብ መወሰን ሲገባቸው ይህንን ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ፡፡ሌላው መታየት ያለበት በዐ/ሕግ ክስ የተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 104/3/ /ሀ/ በሚደነግገዉ አግባብ መኪናዉ በመንግስት ከመወረስ ሊድን የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ የተያዘ መኪና ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ መኪናዉ ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰዉ ሊመለስ የሚችለዉ መኪናዉ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ አጥጋቢ ማስረጃ ያልቀረበ እንደሆነ ነዉ፡፡ አሁን አከራካሪ የሆነው መኪና የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ በበቂና አጥጋቢ ማስረጃ እስከተረጋገጠ ድረስ መኪናዉ እንዲወረስ ከሚደረግ በስተቀር ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰዉ የሚመለስበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ለክርክር የሆነዉ ተሽከርካሪ የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት መሆኑን እስከተረጋገጠ ድረስ መኪናዉ ሊወረስ ይገባል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ተሽከርካሪ የተጭበርበረ ስለመሆኑ በባለሞያ የቀረበው ማስረጃ ሳይመለከቱ ተሽከርካሪው ሕጋዊ መሆኑ ተከላክለዋል በማለት ተጠሪዎች ነፃ እንዲለቀቁ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1 .የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 48692 በቀን 28/04/2007 ዓ.ም.እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10870 በቀን 30/03/2008 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ሀ/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2 .1ኛ ተጠሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) / ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93 (1(መ))ን በመተላለፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

፣እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) / ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99ን እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 /2/ የተመለከተውን በመተላለፉ ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡

3 .የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈጸመበትን ከላይ የተገለጸውን በኤግዚቢትነት የተያዘው ተሸከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-02075 ሐረ. በሚል የሚታወቀው ተጠሪዎች ጥፋተኛ የተባሉ በመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104/1/ መሠረት ለመንግስት እንዲወረስ ታዟል፡፡ አመልካች ተከታትሎ ያስፈጸም፡፡

4/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ የቅጣት ሀሳብ ከተቀበለና ከአከራከረ በኋላ ከሕጉ እና ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንጻር በመመርመር በተጠሪዎች ላይ የቅጣት ውሳኔ እንዲሰጥ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ /ሀ/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

ት እ ዛ ዝ

1/ የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪዎች፡-1ኛ አቶ ፋሲል ጥላሁን እና 2ኛ አቶ ካሊድ ሳቢት ከተገኙበት ቦታ ይዞ ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት እንዲያቀርበው ታዟል፡፡ይጻፍ ፡፡

2/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት መ/ቁ 48692 በመጣበት አካኋን በፍ/ቤቱ ሬጅስትራር አማካኝነት ተመላሽ ይሁን ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች አለበት፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 139107

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመካዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የጉለሌ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ - ኢንስፔክተር የትምወርቅ ጋሻው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ምርመራ ሂደት የተጠረጠሪን የባንክ ሂሳብ መረጃ የማግኘት ፈቃድን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ አመልካች በተጠርጣሪ አቶ መኮንን በላይ ላይ ለጀመረዉ የቼክ ማጭበርበር ወንጀል ምርመራ ሥራ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተጠርጣሪዉን የባንክ ሂሳብ መረጃ እንዲሰጠዉ እንዲታዘዝለት ለስር ፍ/ቤት ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ጥያቄዉን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 3(3) መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ በወንጀል ምርመራ ወቅት ባንክ ማዘዝ የሚችል ስለሆነና ስልጣኑም የጠቅላይ ዐ/ሕግ በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ በዐ/ሕግ በኩል ሊስተናገድ ስለሚችል ጥያቄዉን አልተቀበልኩም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም አመልካች ያቀረበዉን ይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ የአዋጅ ቁጥር 943 አንቀጽ 6(3/ሀ) ለፖሊስ የተሰጠ ወንጀል የመመርመር ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሚል ቃል ያለዉና ለፖሊስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ራሱን በቻለ አዋጅ ስልጣኑ ተለይቶ ተሰጥቶ ባለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ ተገቢ አይደለም በማለት ትዕዛዙን በመሻር ሲወስን፤ ፖ/ሊስ እንዲሰጠዉ የጠየቀዉን ትዕዛዝ አስፈላጊነት በተመለከተ ፖ/ሊስ ስንቅ የሌለዉ ቼክ ቀርቦለት፤ ባንኩ የቼኩ ባለቤት ቼኩ ተሰርቆብኛል በማለት ያስታወቀዉ መሆኑን በገለጸበት ሁኔታ ፖ/ሊስ ባንክ የሚገኝ ማስረጃ የሚፈልግበት ምክንያት ግልጽ አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበል ቀርቷል፡፡ አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- በፌዴራል ፖ/ሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 720/04 መሠረት ወንጀል የመመርመር ስልጣን ለፖ/ሊስ የተሰጠ ሲሆን እንደሚደርሰን ጥቆማ እና የወንጀሉ ክብደት በብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 እና በአዋጅ ቁጥር 592/2000 መሰረት የግለሰቦች የባንክ መረጃ በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንደሚገኝ ተመልክቷል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ቤት ትዕዛዝ ማስረጃ የማግኘት ያለን መሆኑን ቢያረጋግጥም የወንጀል ምርመራዉ ተጠርጣሪዉ ለባንኩ ጠፍቶብኛል ብሎ ካስታወቀዉ ቼክ ጋር የተያያዘ በመሆኑ እየታወቀ የማስረጃዉ አስፈላጊነት ግልጽ አይደለም በማለት አቤቱታችን ዉድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ስለሆነም የተጀመረዉን ምርመራ ማጠናቀቅ እንዲቻል ቼኩ በወጣበትና ለባንክ ለክፍያ በቀረበበት ጊዜ በተጠርጣሪዉ የባንክ ሂሳብ በቂ ስንቅ ወይም ገንዘብ መኖር አለመኖሩ እንዲረጋገጥ እንዲታዘዝልን፤ በተጠርጣሪዉ ፊርማ ላይ የፎረንሲክ ምርመራ ማድረግ በማስፈለጉ ከዚህን ቀደም ተጠርጣሪዉ የፈረመባቸዉ ከ5 እስከ 7 የሚሆኑ ቼኮች እንዲሰጡ እንዲታዘዝ እና ተጠርጣሪዉ ፊርማ የሌለዉ ቼክ ጠፍቶብኛል ብሎ ያመለከተበት ደብዳቤ እንዲሰጠን ትዕዛዝ ይሰጥልን የሚል ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማዉጣት ወንጀል ተፈጽሟል በሚል በግል ተበዳይ በኩል አቤቱታ ቀርቦ ፖ/ሊስ ለምርመራ ይጠቀምኛል ያላቸዉን ሰነዶች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲሰጠዉ ማዘዣ ከፍ/ቤት ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤት ማስረጃዉ የሚፈለግበት አግባብ ግልጽ አይደለም በሚል የአመልካች ማዘዣ ጥያቄ ዉድቅ ያደረገበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 22(2-ሠ)፣ ከአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 28(4-ሠ)፣ ከአዋጅ ቁጥር 720/04 አንቀጽ 6 እና አግባብነት ካላቸዉ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ድንጋጌዎች መሠረት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ነዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች በፌዴራል ፖ/ሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 6 ወንጀልን የመርመር ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑና ለምርመራ የሚያስፈልገዉን የግለሰብ የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴ መረጃ ማግኘት የሚችለዉ ስለባንክ ስራ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 28(4/ሠ) መሠረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሆኑ በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ ፖ/ሊስ ለምርመራዉ አስፈላጊ የሆነ የተጠርጣሪ የባንክ መረጃ ሲኖር ጥያቄዉን ለፍ/ቤት አቅርቦ አስፈላጊነቱ ሲታመን ፍ/ቤት ለባንክ መረጃ እንዲሰጥ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የተጠርጣሪዉን የባንክ መረጃዉን የሚመለከተዉ ባንክ እንዲሰጠዉ የፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ያቀረበዉ ምክንያት በቂ አይደለም በማለት ጥያቄዉን ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ስንቅ ሳይኖር ቼክ የማዉጣት ወንጀል በተጠረጠረዉ አቶ መኮንን በላይ በጀመረዉ ምርመራ ምክንያት ምንም እንኳ ቼኩ ለባንክ ቀርቦ ክፍያ ሳይፈጸም ተመላሽ የተደረገ መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም ተጠርጣሪዉ አስቀድሞ ቼኩ የተሰረቀ በመሆኑ ክፍያ እንዳይፈጸምበት ለባንኩ ማስታወቁን ባንኩ በመግለጹ ቼኩ የተሰረቀ ነዉ ወይስ በተጠርጣሪዉ ተፈርሞ የተሰጠ ነዉ የሚለዉን እዉነታ ለማጣራትና ምርመራዉን ለማጠናቀቅ የተጠርጣሪን የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴ፣ ቀድሞ የፈረማቸዉን የፊርማ ናሙናዎች ማግኘቱ ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች ያለፍ/ቤት ትዕዛዝና ለተፈቀደላቸዉ ሰዎች ካልሆነ በቀር ለማንም ሰዉ ተላልፎ የማይሰጡ በሕግ ጥበቃ የሚደረግላቸዉ መረጃዎች በመሆናቸዉ ፖ/ሊስ በፍ/ቤት ትዕዛዝ መረጃዎችን ካላገኘ በስተቀር በተጠርጣሪዉ ላይ የጀመረዉን ምርመራ ሊያጠናቅቅ አይችልም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የተጠርጣሪዉን የባንክ መረጃ የሚፈልግበት አግባብ ግልጽ አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበል መቅረቱ የወንጀል ምርመራዉን ልዩ ባህሪ፣ በአዋጅ ቁጥር 720/04 አንቀጽ 6 ለአመልካች የተሰጠዉን ወንጀል የመመርመር ስልጣንና በአዋጅ ቁጥር 592/00 አንቀጽ 28(4/ሠ) መሠረት የተጠርጣሪዉ የባንክ ሂሳብ መረጃ የሚገኝበትን አግባብ ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሌላዉ ይህ ሰበር ችሎት ለባንክ ትዕዛዝ ይስጥልን የሚለዉን የአመልካች ጥያቄን በተመለከተ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት ለዚህ ችሎት የተሰጠዉ ስልጣን የመጨረሻ በሆነ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ በቀጥታ ለባንክ ትዕዛዝ በመስጠትና መረጃዉ መሰጠቱን በመከታተል የሚያስፈጽምበት አግባብ ባለመኖሩ የተፈጸመዉን የሕግ ስህተት በማረም ትዕዛዙ በስር ፍ/ቤት በኩል እንዲሰጥና አፈጻጸሙን አስመልክቶ ክትትል እንዲደረግበት ለስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መመለሱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ 003839 የካቲት 03 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 57579 የሰጠዉን ትዕዛዝ መሻሩ በአግባቡ ነዉ ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. አመልካች በተጠርጣሪዉ ላይ የጀመረውን ምርመራ ለማጠናቀቅ ቼኩ በወጣበት የባንክ ሂሳብ ጋር የተያያዙና በአመልካች የተጠየቁ መረጃዎችን ማግኘት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ አመልካች መረጃዎችን ማግኘት እንዲችል በስር ፍ/ቤት ተገቢዉ ትዕዛዝ ሊሰጥበት ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ አመልካች በተጠርጣሪ ላይ እያካሄደ ላለዉ በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ የማዉጣት ወንጀል ምርመራ የጠየቃቸዉን መረጃዎች ማግኘት እንዲችል ትዕዛዝ ለሚመለከተዉ ባንክ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ይመለስለት ተብሎ ተወስኗል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 146727
ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው
በዕውቀት በላይ
እንዳሻው አዳነ
ሃይሉ ነጋሽ
እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ አክሊሉ አፈወርቅ ጠበቃ ናትናኤል ተክሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 08 ቀን 2009 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎት በመ.ቁ 144037 ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሠበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡ የአሁን አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ሥድሥት ተከሳሾችን ክስ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጠሪን ማሥረጃዎች ከሰማ በኋላ ተከሳሾች በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ፈቅዷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ለአመልካች እና ለሥር ተከሳሾች የሰጠውን የዋስትና መብት በመሻር ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከታተሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 በዋስትና ጉዳይ ላይ ከአንድ ጊዜ በላይ ይግባኝ እንደማይኖር የተደነገገ በመሆኑ አመልካች አቤቱታውን ለሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ከማሳረም ውጪ ሁለተኛ ይግባኝ ሊያቀርብ አይችልም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች ከመነሻውም ቢሆን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዋስትና መብቱ ያልተከለከለ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 ሁለተኛ ይግባኝ አይፈቅድም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን የዋስትና መብት የሻረው ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ሆኖ ሳለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዋስትና ጉዳይ ላይ ሁለት ጊዜ ይግባኝ ማለት አይቻልም በማለት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ወድቅ ማድረጉ የሰጠው ውሳኔ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 እና ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ጥቅምት 02 ቀን 2010 ዓ/ም በሰጠው መልስ በሥር ፍ/ቤት የአመልካች የይግባኝ መብት መታለፉ ተገቢ አይደለም በማለት ሥሕተቱ ቢታረም ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ገልጿል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9/2 የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ የይግባኝ ሥልጣን እንዳለው ይደነግጋል፡፡

የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75 (1)እና(2) በዋስትና ወረቀት ለመለቀቅ የቀረበውን ማመልከቻ ፍ/ቤቱ ያልተቀበለው እንደሆነ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታውን ማቅረብ እንደሚቻል እና በዚህ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የሌለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በድንጋጌው ርዕስ ላይ እንደተገለጸው የዚህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ጠይቆ ባልተፈቀደ ጊዜ እንጂ የሥር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት ጠብቆ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት የተከሳሽን የዋስትና መብት በመጠበቅ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በሰጠው ውሳኔ ላይ ተከሳሽ ይግባኝ እንዳያቀርብ ተፈጻሚ የሚሆን አይደለም፡፡ በወንጀል ሥነ ስርዓት ሕጉ ቁጥር 75 (2) ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለውም በማለት የተደነገገው ድንጋጌ ተከሳሹ በበታች ፍ/ቤት የተፈቀደለት የዋስትና መብት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተሻረበት ጊዜም የተከሳሹ ይግባኝ የማቅረብ መብት እንደሚከለክል አድርጎ መተርጎም የዜጎችን ይግባኝ የማቅረብ መሠረታዊ መብት የማጣበብ ውጤት ያለው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን የዋስትና መብት የሻረው ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት በመሆኑ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 9/2 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 75/2 ሁለተኛ ይግባኝ አይፈቅድም በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕገመንግሥቱ ዕውቅና ያገኘውን የአመልካችን ይግባኝ የማለት መብት ያጣበበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 144037 ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 194317 ሠኔ 05 ቀን 2009 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው ብለናል፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ድጋሚ ይግባኝ የማቅረብ መብት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

-መዝገበ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 135787

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-አበባየሁ ሳሙኤል -ጠበቃ ዮሴፍ ኪሮስ

ተጠሪ፡-የኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ -አልቀረበም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 23604 በቀን 01/06/2008፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 237785 በቀን 17/09/2008 እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 249149 በቀን 8/02/2009 በሰጠው ትእዛዝ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ውንብድናና ከባድ ሰው መግደል ወንጀል የቅጣት ውሳኔ የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካችና ሌሎች 5 ሰዎች ላይ ሁለት የተሻሻለ የወንጀል ክሶችን ያቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ /ሀ/ እና 671/1/ /ሀ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ካልተያዘው አቡሽ ተከተል ጋር በመሆን አመልካች የግል ተበዳይ ሚች ዶ/ር ቢንያም ማሞ መጽሀፍ ለማዘጋጀት ያዘጋጀውን ጽሁፍ ለመውሰድ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር በመምከርና 2ኛ ተከሳሽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘብ ከተከፈለው ጽሁፉን በእጁ እንደሚያስገባለትና አመልካች የሚከፍል መሆኑን ተስማምተው 2ኛ ተከሳሽም ይህንኑ ከ3ኛ-5ኛ እና ካልተያዘው አቡሽ ተከተል ጋር ተመካክረው 5ኛ ተከሳሽ ሜሮን አየለ ከሚች ጋር ተቀራርባ በሚፈልጉት ጊዜ እንድትጠራው ተስማምተው በ20/12/2006 ሚችን ጠርታ እስከ ሌሊት 6፡00 ሰዓት አብረው ቆይተው ከ2ኛ-4ኛ ያሉ ተከሳሾችና አቡሽ ተከተል በጉልበት ይዘውት ባንተ ላይ የምንፈጽመውን ለፖሊስ ከተናገርክ እንገድልሃለን በማለት የሞት አደጋ የሚያደርሱ መሆኑን በማስጠንቀቅ ሞባይል፣ ጃኬት፣ ጫማ፣ ፍላሽ ሚች መድሐፍ ለማሳተም በእጁ የያዘው ጽሁፍ ሶፍት ኮፒ የወሰዱ በመሆኑ ከባድ የውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል እና 2ኛው ክስ ደግሞ ከ1ኛ -6ኛ ተከሳሾች የወንጀል ህግን አንቀጽ 32/1/ /ሀ// /ለ/ እና 539 /1/ /ሀ/ /ለ/ /ሐ/ በመተላለፍ ከላይ በ1ኛው ክሱ የገለፀውን ከፈፀሙ በኋላ ሚችን ለመግደል አስበው ከአቡሽ ተከተል ጋር በመሆን ሚች ለማሳተም ያዘጋጀውን ጽሁፍ ሶፍት ኮፒ 2ኛ ተከሳሽ ለአመልካች /1ኛ ተከሳሽ/ ከሰጠ በኋላ አመልካች ሚች በህይወት ሳለ በዚህ ጽሁፍ መጠቀም ስለማይቻል ሚችን መግደል አለባችሁ ብሎ ሲገልጽ ገንዘብ እንደሚጨምር ከተስማሙ በኋላ ለ2ኛ ተከሳሽ ብር 30000/ሰላሳ ሺህ/ ለ4ኛ ተከሳሽ ብር 15000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ ለ5ኛ ተከሳሽ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ 3ኛ ተከሳሽ እና አቡሽ ተከተል የወሰዱት ገንዘብ የማይታወቅ ከወሰዱ በኋላ 5ኛ ተከሳሽ ሚችን ሻሸመኔ ከተማ ቀበሌ 03 ልዩ ቦታው ሻሌት ከተባለ ሆቴል በስልክ ቀጥራው ሲመጣ ሌሊት ከ2፡00-3፡00 ሰዓት ከ2-4ኛ ያልተያዘው አቡሽ ተከተል ወደ ሆቴል ሲገባ አፍነው መኪናው ውስጥ በመወርወር ከወሰዱት በኋላ ለስድስት ቀን ሌሊት ሌሊት ሻሸመኔ ከተማ መልካ አዳ አና ለገጮቴ በተባለ ቦታ በመውሰድ በፕላስቲክ አፉን በማሸግ እግርና እጁን በማሰር በዘግናኝ ሁኔታ የተያዩ ጉዳቶች ካደረሱበት በኋላ የጮን አጥንት መሰበር፣ የግራ ሳንባ እና ኩላሊት መሰንጠቅ በአሰቃቂ ሁኔታ በ30/12/2006 ከገደሉት በኋላ እሬሳውን በመኪና ጭነው አርሲ ነገሬ ወረዳ ዳኮ ሆራ ቀሎ በተባለ ቀበሌ ውስጥ ሌሊት 5፡00-8፡00 ሰዓት የጣሉት በመሆኑ በአሰቃቂ ሁኔታ የግድያ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች የቀረበበትን የወንጀል ክስ አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ የተከራከረ ቢሆንም አምስተኛ ተከሳሽ የነበረችው የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሟን አምና በሰጠችው ቃል መሠረት በቀረበው ክስ መሠረት ጥፋተኛ በማለት የእድሜ ልክ ጽኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እስራት የቅጣት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በተቀሩት ተከሳሾች ላይ 5 የተጠሪ ምስክሮችን፣ የ5ኛ ተከሳሽ የሰጠችው የእምነት ቃል፣ ሐናን ጌታቸው በቀዳሚ ምርመራ አድራጊ ፍ/ቤት የሰጠችው የምስክርነት ቃል፣ ሚች የተጣለበትን ቦታ የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ አንድ የቪዲዮ ሲዲ፣ የሚች ሲም ካርድ ከ5ኛ ተከሳሽ የተወሰደ፤ከዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የተጻፈ የሚች የህክምና ምስክር ወረቀት የቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ እንዲከላከሉ አመልካችን ጨምሮ በሰጠው ብይን መሠረት አመልካች የተከሳሽነት ቃሉንና የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ ያሰማ እና በፖሊስ ምርመራ የተጣራ መዝገብ እና 5ኛ ተከሳሽ በፍ/ቤት ቀርባ የሰጠችው ቃል፣ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር የስልክ ልውውጥ ስለማድረጌ ከኢትዮ ቴሌኮም ማስረጃ ማቅረብ እና ከአድማስ ገጽ ስነጽሁፍ ማህበር የተጻፈ ማስረጃ አቅርቧል ፍርድ ቤቱም በአመልካች ላይ የቀረበውን ክስ እና በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ የቀረበበትን ሁለቱንም ክስ አልተከላከለም በማለት ጥፋተኛ ነው በማለት ቅጣትን በተመለከተ የአመልካች የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ሁኔታ የወ/ህ/አንቀጽ 539/1/ የሚፈልገውን ሁሉ በመተላለፍ ከዚህ በፊት ጥሩ ሥነ ምግባር የሌላቸው ተከሳሾች ጋር በመሆን ትእዛዝ በመስጠት እና በመፈፀም ተቀራራቢ በሆኑ ጊዜያት ከባድ ዝርፊያ እና ከባድ ግድያ ወንጀል መፈፀሙ ያለፈ የህይወት ታሪኩ መልካም ነው ተብሎ በማቅለያነት ታሳቢ የሚደረግ አይደለም ፤ቤተሰብ አለው በማለት የቀረበው በህጉ በግልጽ ያልተቀመጠና ማስረጃ ያልቀረበበት በመሆኑ ተቀበይነት የለውም በማለት በሞት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አጽንተዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህንን በመቃወም መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን ይዘቱም ጥፋተኛ የተባለባቸው ሁለት ድርጊቶች በአንድ የወንጀል ህግ ድንጋጌ የሚጠቃለሉ ናቸው፣ የመከላከያ ምስክሮች በሚገባ ቀርበው ሳይመረመሩ የተሰጠ ውሳኔ ነው ፤የማስረጃ ምዘና መሠረታዊ መርሆዎች አልተከተሉም ቅጣትን በተመለከተም የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ ቅጣት ሊቀልልኝ ይገባ ነበር የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ በአመልካች የቀድሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወንጀል ሪከርድ በሌለበት እና ከቅጣት አወሳሰን መመሪያም የቅጣት ውሳኔ ያልተሰጠ መሆኑን መሠረት በማድረግ ከወ/ህ/አንቀጽ 117 አንጻር ለመመርመር ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት በሰጠው መልስ የወ/ህ/ አንቀጽ 82/1/ /ሀ/ መሠረት የወንጀል ድርጊቱ በዕውቀት ማነስ ባለማወቅ በየዋህነት ከተፈፀመ የወንጀል ሪከርድ ባልቀረበ ጊዜ በማቅለያነት የሚያዝ እንጂ እንደአመልካች የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመው በዕውቀት ማነስ ሳይሆን የዕውቀት ሥራን ለራስ ለማድረግ ለማሳተም ዕውቅና ለማግኘት በማሰብ እና የተማረ በመሆኑ ቅጣቱ ሊቀልለት አይገባም፣ አመልካች ሁለት የወንጀል ድርጊቶችን አከታትሎ የፈፀመ በመሆን ግምት ውስጥ ገብቶ የተሰጠ የቅጣት ውሳኔ በመሆኑ የተፈፀመ መሠረታዊ ስህተት የለም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይጽናልኝ ብሏል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው ምክንያት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ /ሀ/ እና 671/1//ሀ/ በግብረአበርነት ከባድ የውንብድና የተመለከተውን በመተላለፍ እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ እና 539/1/ /ሀ//ለ//ሐ/ በግብረአበርነት ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከባድ የውንብድና ወንጀል ካስፈፀመ በኋላ ከባድ የግድያ ወንጀል እንዲፈጽም ትእዛዝ አስተላልፎ በማስፈፀም የአመልካች ጠበቃ ያቀረበው የወንጀል ሪከርድ የሌለበት መሆን ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች ያልተቀበለው መሆኑን እና የቤተሰብ አስተዳደሪነት በተመለከተ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑና ለፍርድ ቤቱ የተተወ ነው በማለት ውድቅ በማድረግ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ 2/2006 መሠረት ምንም ማቅለያ ሳይገ በሞት እንዲቀጣ መወሰኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቀቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችን የአሳቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን ነው፡፡ በዚህም አፈጻጸም አወሳሰን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የወጣ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በቅጣት መመሪያ ውስጥ የተቀመጠው የቅጣት አወሳሰን ሥርዓትም ስለቅጣት አወሳሰን በህጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሲታዩ የሚያስገነዝቡን ዓቢይ ነጥብ ቅጣቶችን በመጣልና እርምጃዎችን በመውሠድ ረገድ ዳኞች አመዛዝነው የመወሠን ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ዳኞች አጥፊውን በተመለከተ ከግምት ውስጥ ሊያስገቧቸው የሚገባቸው በርካታ የአጥፊ ሁኔታዎች ቢኖሩም የቅጣት አወሳሰናቸው መሠረት የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን /degree of individual guilt/ ስለመሆኑ የአንቀጽ 88/2/ ድንጋጌ ይዘትና አቀራረፅ ያስረዳል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በሁለት ግዘፍነት ባላቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ሲሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1//ሀ/ እና 671/1/ /ሀ/ እና /ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የውንብድና ወንጀል በመፈፀም ሲሆን ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1//ሀ/ 539 /ሀ/ /ለ/ /ሐ/ የተመለከተውን ተላልፎ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል በመፈፀም ደግሞ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጡ ወንጀሎች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ናቸው፡፡ ሁለቱም የወንጀል ድርጊቶች በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ደረጃ እና እርከን የወጣላቸው ናቸው፤ የመጀመሪያውን ክስ በተመለከተ አመልካች በ2ኛው ክስ የተመለከተውን የውንብድና ወንጀል ከፈፀመ በኋላ በዚሁ የወንጀል ድርጊት ምክንያት ከሚች ዶ/ር ቢኒያም ማሞ የወሰደው ጽሁፍ ለማሳተም የግሉን ስብዕና ለማሳደግ ጥቅም ለማግኘት የሚች መገደል አስፈላጊ ነው በሚል አስነዋሪ የአፍቅሮተ ንዋይ ስሜት ከ2ኛ-5ኛ ተከሳሾች የነበሩትን የውንብድና ቡድን በመጠቀም ከሚች የዕውቀት ብርሃን የተገኘውን ጥበብ /ጽሁፍ/ በውንብድና ተግባር የወሰደውን የአዕምሮ የፈጠራ ውጤት እንዳይገለጽ ለማድረግ የፈፀመው መሆኑ የወንጀሉ ደረጃ 2 እርከን 39 ላይ የሚያርፍ ሲሆን ሁለተኛው ክስ በተመለከተ የወንጀል ድርጊቱ ከባድነት እና አፈጻጸሙ ከላይ የተመለከተው በመሆኑና በመጀመሪያ ክስ ዕድሜ ልክ ወይም ሞት የሚያስቀጣ በመሆኑ ሁለተኛው ክስ ላይ የተመለከተው አጠቃሎ የሚይዝ ስለመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 184/1/ /ሀ/ /ለ/ በተመለከተው መሠረት መነሻ ቅጣት እርከን 39 ላይ የሚያርፍ ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም ሆኖም አመልካች ላይ የቀደመ የወንጀል ሪከርድ የሌለው መሆኑን በቅጣት ማቅለያነት ቀርቦ ፍርድ ቤቱ አመልካች ተቀራራቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ከባድ የዝርፊያ ወንጀል እና ከባድ ግድያ እንዲፈጽም በማድረግ ጥሩ ፀባይ ያለው ነው ብሎ ለመገመት የሚያስችል አይደለም ብሎ አመልካችን በሞት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

በመሰረቱ ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ በተደነገገው ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይገባ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 15 ስር በጎይለ ቃል የደነገገው ጉዳይ ነው፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ ከባድ ወንጀል መፈጽሙ በተረጋገጠበት ሰው ላይ የሞት ቅጣት ማስተላለፍ የሚፈቀድ መሆኑን ሕገ መንግስቱ አስቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል የሞት ቅጣት ሊተላለፍ የሚገባበት አግባብ የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 117 ስር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር አንደ ድንጋጌ መሰረት የሞት ቅጣት የሚወሰነው ወንጀሉ ፍጻሜ ያገኘ ሆኖ እጅግ በጣም ከባድ በመሆኑና ወንጀለኛውም በተለይ አደገኛ በመሆኑ ለወንጀሉ ቅጣት እንዲሆን በሕጉ በግልጽ ተደንግጎ በተገኘ ጊዜ እንዲሁም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወንጀለኛው ቅጣትን የሚያቀልለት ምክንያት በታጣ ጊዜ እድሜው ቢያንስ አስራ ስምንት አመት የሞላው ሆኖ ሲገኝ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባለባቸው የወንጀል ድርጊቶች የተፈፀሙት የአሁን አመልካች የሆነው የስር 1ኛ ተከሳሽ የሚችን ዶ/ር ቢኒያም ማሞን መጽሃፍ ለማዘጋጀት ያዘጋጀውን ጽሁፍ በከባድ የውንብድና ቡድን ተግባር ለመውሰድ እና የዚህን ጹሁፍ ባለቤት ለመሆን የእውቀቱን አመንጪ መግደል ለሌላኛው ወንጀል ከለላ እንዲሆን ታስቦ የተፈፀመ በመሆኑ በዚህ አይነት ሁኔታ በወንጀል ህግ አክብዶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመበት ሚች ሆነ አመልካች የሀገሪቱ ሀብት እና በዩኒቨርስቲ መምህራን የሚቀርፁ ባለሙያዎች ሆነው በመልካም ባህሪያቸው ለህብረተሰቡ አርአያ ተደርገው የሚወሰዱ ሆነው ፍፁም ወራዳ በሆነ ተግባር መፈፀሙ የአመልካችን አደገኛ ባህሪይ የሚያመለክት ሲሆን በአመልካች የቀረበው የቀደመ የወንጀል ሪከርድ አለመኖር በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያላገኘ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መሆኑን ከውሳኔ ይዘት እና ከወንጀል ህግ አንቀፅ 117 አንጻር የወንጀል ድርጊቶቹ አፈጻጸም ከባድነት በተለይም የአመልካችን አደገኛነት መሠረት ያደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በአጠቃላይ በአመልካች ላይ የተወሰነው የሞት ቅጣት የወንጀል ሕጉን መሠረታዊ ግብና ዓላማ እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችን ከአመልካች የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ጋር የተገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1/ በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 23604 በቀን 01/06/2008፣ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 237785 በቀን 17/09/2008 እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 249149 በቀን 08/02/2009 የሰጠው ትእዛዝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2/ አመልካች በሞት እንዲቀጡ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል። የሞት ቅጣቱ ተፈጻሚነት የሚኖረው በወንጀል ህግ አንቀጽ 117/2/ መሠረት በሀገሪቱ ርዕሰ ብሔር ከፀና በኋላ ይሆናል ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 137262

መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካቾች፡- 1. ወጣት ሀይላይ ወ/ገብርኤል

2. ወጣት ወ/ገርግስ ሐጎስ

የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ጉዳይ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከፍተኛ ፍ/ቤት በአክሱም ምድብ ችሎት ነው፡፡ ተጠሪ በአሁን አመልካቾች ላይ በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው የተሻሻለ ክስ ይዘት አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 ድንጋጌን በመተላለፍ ሚያዝያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት አባሪ ተባባሪ በመሆን በአክሱም ከተማ በማዕበል ቀበሌ ቀጠና 4 በተባለ ቦታ የግል ተበዳይ ወ/ት ሐጎሳ ሀይሉን በመምታት በተለያየ የሰውነት አካሏ ላይ 1 × 1 ሳ.ሜ፤ በጭንቅላትዋ ላይ 2 × 1 ሳ.ሜ፤በምላሷ ላይ 2 × 2 ሳ.ሜ ጉዳት ካደረሱባት እና ራሷን እንድትስት ካደረጉ በኋላ ለብሳው የነበረውን ልብስ በመቅደድ አውልቀው እርቃንዋን በማድረግ 1ኛ አመልካች ክብረንጽህናዋን በመድፈሩ፤2ኛ አመልካችም ተባብሮ ክብረንጽሕናዋን በመድፈር ቀጥቅጠው ራሷን እንድትስት በማድረግ አስገድዶ የመድፈር ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካቾች ክሱ ተነቦላቸው መቃወሚያ የሌላቸው መሆኑን ከገለጹ በኋላ የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ሲጠየቁ ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ክደው የተከራከሩ በመሆኑ የተጠሪ ማስረጃዎች ተሰምተዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1ኛ የተጠሪ ምስክር የግል ተበዳይ ለፍ/ቤቱ በሰጠችው የምስክርነት ቃል አመልካቾች በዕለቱ በሐሙስ ገበያ በኩል ወደ ቤታቸው አብረው እንሂድ ያልዋት መሆኑን፤ምሽት ነው አልሔድም ስትላቸው ሞባይል እናበራለን ያልዋት መሆኑን፤2ኛ አመልካች ወደኋላ ቀርቶ ስለነበር 1ኛ አመልካች እንጠብቀው ያላት መሆኑን፤ብርሃን ያለበት ቦታ እንጠብቀው ብትለውም ልብስሽን አውልቂ ያላት መሆኑን፤እንደማትፈልግ በመግለጽ ተው ብትለውም ደጋግሞ አፍንጫዋን በመምታት እያንዳንዱ የለበሰችውን ልብስ ቀዶ የጣለው ፓንት ሳይቀር የወረወረ መሆኑን፤ለሕይወትሽ ሳሳሽላት ሲላት የመጣ ይምጣ ለሕይወቴ አልሳሳም ያለችው መሆኑን፤እንዳልገልሽ ሲላት ግደለኝ ስትለው እንዳታይ በማለት በድንጋይ ዓይኗን ጭንቅላትዋን አንገትዋን እጇን የመታት መሆኑን፤ድንግልናዋን የደፈረ እና ማሕጸኗ የተሰነጠቀ መሆኑን፤ሁለተኛ አመልካችም መጥቶ የደፈራት መሆኑን፤በምላጭ፤በሚስማር ወይም በቢላዋ መሆኑን ባልለየችው ሁኔታ እንደእባብ ሲቀጠቅጧት ያደሩ መሆኑን፤ባሕር ውስጥ እንከትሻለን ያልዋት መሆኑን፤በጀርባዋ ወድቃ እያለ በእግራቸው ሆድዋን ረግጠው ከእግርዋ እስከ ጸጉርዋ ድርስ የሸኑባት መሆኑን፤ምራቃቸውን ከተፉባት በኋላ ሞታለች አልሞተችም እያሉ ሹራብ ሸፍነዋት የሄዱ መሆኑን፤በረሃ ላይ ራቁትዋን ያደረች መሆኑን፤ከፍላጎትዋ ውጪ አስገድደው የእርቅ ውል ያስፈረሟት መሆኑን፤ በደረሰባት አደጋ ምክንያት ሆድዋን የሚቆርጣት፤ የሚነፋት ፤የሚያቃጥላት ፤የሚያዞራት፤ የሚሞቃት እና የሚያሰቃያት መሆኑን በመግለጽ መስክራለች ።።

ሁለተኛ የተጠሪ ምስክር ለፍ/ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃል ሚያዝያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም ከሌሊቱ በ 6፡00 ሰዓት በራቸው የተንኳኳ መሆኑን፤ማነው ሲሉ የግል ተበዳይ ክፈችልኝ ያለቻቸው እና ፈርተው ያልከፈቱላት መሆኑን፤ጠዋት በሩን ሲከፍቱ የግል ተበዳይ ራቁትዋን በር ሥር ቁጭ ብላ ያገኟት መሆኑን፤ሰውነትዋ ተመትቶ የነበረ እና 1ኛ አመልካች መትቶኝ ነው ያለቻቸው መሆኑን፤ልብሶቿ ተቀዳድው ሜዳ ላይ ተጥለው የተገኙ መሆኑን እና ለቤተሰቦቿ ስልክ የደወሉ መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል።።

3ኛ የተጠሪ ምስክር ለፍ/ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃል በእለቱ ስልክ ተደውሎላቸው መጥተው የግል ተበዳይን ሕክምና ቦታ የወሰዷት መሆኑን፤የተመታችበትን አካባቢ ያዩ እና ልብሶቿ ተቀዳደው ተጥለው ከባድ ጉዳት ደርሶባት የነበረ እና አመልካቾች መቱኝ ብላ የነገረቻቸው መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል።። 4ኛ ምስክር በሰጡት የምስክርነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቃል አመልካቾች በእለቱ ከግል ተበዳይ ጋር የግል ተበዳይ ተመታሁ ባለችበት አካባቢ ሲሄዱ ያይዋቸው መሆኑን በመግለጽ መስክሯል። 5ኛ ምስክርም በሰጡት የምሥክርነት ቃል በእለቱ አመልካቾችን ያዩ እና የግል ተበዳይ መቱኝ ብላ የነገረቻቸው መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል። በግል ተበዳይ ላይ አዲስ የሆነ የክብረንጽሕና መገርሰስ እንደደረሰባት፤ማሕጸንዋ እንደተሰነጠቀ እና እንደተሰፋ ፤በተለያየ አካሏ ላይ ጉዳት እንደደረሰ የሚያሳይ የተለያየ የሰነድ ማስረጃም ቀርቧል።

ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት በተጠሪ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ተጠሪ እንደክሱ አስረድቷል በማለት አመልካቾች በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ እንዲከላከሉ በማለት በሰጠው ብይን መሠረት አመልካቾች ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ቦታ ላይ እንዳልነበሩ የሚያስረዱ መከላከያ ምሥክሮችን በማቅረብ አሰምተዋል፤የሰነድ ማሥረጃዎችም አቅርበዋል።

ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ድርጊቱን የፈጸሙ ለመሆኑ በሚገባ ስለተመሰከረባቸው እና ባቀረቡት መከላከያ ማሥረጃ ክሱን ስላላስተባበሉ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል። የቅጣት ውሳኔን በተመለከተም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ቅጣቱን በማስላት የወንጀሉን ደረጃ ደረጃ ሐ እርከን የቅጣት መነሻ እርከን 38 በመያዝ ፤ተጠሪ ድርጊቱ በጭካኔ ስለተፈጸመ በማክበጃነት ይያዝልን በማለት ያቀረበውን የቅጣት ማክበጃ ባለመቀበል፤ተጠሪ ድርጊቱ በጨለማ የተፈጸመ ስለሆነ በማክበጃነት ይያዝ በማለት ያቀረበውን ማክበጃ በመቀበል ወደ እርከን 39 በማሳረፍ፤አመልካቾች ድርጊቱን በሥምምነት የፈጸሙት ስለሆነ በቅጣት ማክበጃነት ሊያዝ የሚገባው ቢሆንም ከእርከን 39 በላይ የሚወጣ በመሆኑ ማክበድ አይቻልም በማለት፤አመልካቾች የወንጀል ሪከርድ የለባቸውም የሚለውን በቅጣት ማቅለያነት በመያዝ፤አመልካቾች የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነን ከተበዳይ ጋር ታርቀናል በማለት ያቀረቡትን የቅጣት ማቅለያ ባለመቀበል አመልካቾች በዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል። አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም።የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- በግል ተበዳይ ላይ ከባድ የሆነ የአካል እና የአእምሮ ጉዳት ወይም ሞት ባልደረሰበት ሁኔታ የተከሰሰንበት የሕግ አንቀጽ መቀየሩ፤የተጠሪ ማሥረጃዎች በአግባቡ ባላስረዱበት ሁኔታ እና አመልካቾች ክሱን በተከላከልንበት ሁኔታ የበታች ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠታቸው እና የወንጀል ሪከርድ የሌለን እና ወጣቶች ሆነን ሳለ በቅጣት ማቅለያነት ሳይያዝ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች የተከሰሱት የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 620/2/መ የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል በሚል ሆኖ የሥር ፍ/ቤት ወደ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 በመለወጥ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱ፤ተፈጸመ ከተባለው የወንጀል ድርጊት በሁለቱ ድንጋጌዎች ላይ ከተመለከተው የቅጣት መጠን እንዲሁም ከወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡ በሰበር አጣሪው እንዲጣራ የተያዘው ነጥብ አመልካቾች የተከሰሱት የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 620/2/መ የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል በሚል ሆኖ የሥር ፍ/ቤት ወደ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 በመለወጥ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱ፤ተፈጸመ ከተባለው የወንጀል ድርጊት በሁለቱ ድንጋጌዎች ላይ ከተመለከተው የቅጣት መጠን እንዲሁም ከወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል የሚል ቢሆንም ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው ክስ አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 ድንጋጌን ተላልፈው ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ ያቀረበባቸው በመሆኑ የሰበር አጣሪው አመልካቾች የተከሰሱት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620/2/መ መሠረት ሆኖ ሳለ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620/3 ጥፋተኛ መባላቸው ከወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር በማለት የያዘውን ማጣሪያ ነጥብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በሌላ በኩል የበታች ፍ/ቤቶች አመልካቾችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620/3 መሠረት ጥፋተኛ የማለታቸውን አግባብነት እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 ድንጋጌ አስገድዶ መድፈሩ ከባድ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት ወይም ሞትን ያስከተለ ሲሆን ቅጣቱ የዕድሜ ልክ እሥራት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ በበታች ፍ/ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬነገር የግል ተበዳይ የተደበደበች ቢሆንም በዚሁ ድንጋጌ በተጠቀሰው ሁኔታ በግል ተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት ወይም ሞት የደረሰባት መሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠው ፍሬነገር አያሳይም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች በግል ተበዳይ ላይ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620/3 በተመለከተው መሠረት ጉዳት እንደደረሰባት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካቾችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620/3 መሠረት ጥፋተኛ ናቸው በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች ድርጊቱን የፈጸሙት ሁለት ሆነው በጭካኔ እና የግል ተበዳይን በማሰቃየት መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማሥረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2/መ አስገድዶ መድፈሩ የተፈጸመው በጭካኔ ወይም በማሰቃየት ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ወንዶች ሕብረት ሲሆን ወንጀል ፈጻሚው ቅጣቱ ከአምስት አመት እስከ ሀያ አመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት እንደሚቀጣ ይደነግጋል፡፡ አመልካቾች ድርጊቱን የፈጸሙት ሁለት ሆነው በጭካኔ እና የግል ተበዳይን በማሰቃየት መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካቾች የተከሰሱበትን የሕግ አንቀጽ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113/2 መሠረት በመቀየር አመልካቾች ጥፋተኛ መባል ያለባቸው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2/መ መሠረት ነው ብለናል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 1 የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዚሁ ሕግ አንቀጽ 87 እና 88 ድንጋጌም ቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች ሕጉ ሊደርስበት ያሰበበትን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መንፈስ መሠረት መፈጸም እንዳለባቸው እና ሰብአዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈጸም እንደሚኖርባቸው፤ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የሀሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን ይደነግጋል። የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 4/9 መመሪያው በወንጀል ሕጉ ስለቅጣት አወሳሰን ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ጋር ተጣጥሞ መተርጎም እንደሚገባው ይደነግጋል።

አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2/መ ድንጋጌ ከአምስት ዓመት እስከ ሀያ ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣ ሲሆን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ደረጃ እና እርከን የወጣለት ነው። አመልካቾች ድርጊቱን የፈጸሙት የግል ተበዳይን አልባሳት በሙሉ በመቀዳደድ፤በድንጋይ የተለያዩ አካላትዋን ደጋግመው በመምታት፤ድርጊቱን እንዳታይ በድንጋይ ዓይኗን ጭንቅላትዋን አንገትዋን እጇን በመታት በመሆኑ እና ድንግልናዋን ከደፈሩ በኋላም እንደእባብ ሲቀጠቀጧት ያደሩ እና በጀርባዋ ወድቃ እያለ በእግራቸው ሆድዋን ረግጠው ከእግርዋ እስከ ጸጉርዋ ድርስ የሸኑባት፤ምራቃቸውን የተፉባት በመሆኑ የአመልካቾች ድርጊት አፈጻጸም አጸያፊ እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ለወንጀሉ በወጣው ደረጃ መሠረት ሊወከል የማይችል እና ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት ቢወሰን የወንጀል ሕጉን የቅጣት ዓላማ እና ግብ የማያሳካ ሆኖ አግኝተነዋል። በመሆኑም ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 27/1 መሠረት ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ ሊወሰን ይገባል ብለናል። አመልካቾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጸያፊ በሆነ ሁኔታ የግል ተበዳይን አልባሳት በመቀዳደድ እና የተለያዩ የሰውነት ክፍሏን በድንጋይ በመምታት አካላትዋን በመርገጥ ድርጊቱን የፈጸሙ እና ድርጊቱን ከፈጸሙ በኋላም በግል ተበዳይ ላይ ምራቃቸውን በመትፋት እና ሽንታቸውን በመሸናት ጥለዋት የሔዱ በመሆኑ አመልካቾች በሀያ ዓመት ጽኑ እሥራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከፍተኛ ፍ/ቤት በአክሱም ምድብ ችሎት በመ.ቁ 20654 ግንቦት 17 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ፤የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 86242 ሐምሌ 28 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 88489 ታሕሣሥ 19 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2/መ መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. የበታች ፍ/ቤቶች በአመልካቾች ላይ ያስተላለፉትን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካቾች በሀያ ዓመት ጽኑ እሥራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

ትዕዛዝ

-የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡

-በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት እንዲደርሰው ታዟል፡፡

-በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 27/2 መሠረት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ ታዟል፡፡

-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሠሪ ሠራተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 143334

ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ዋኢል አብዱጌት አብዱላዚዝ ፕላስቲክ ፋብሪካ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-

1. አበራ አመዩ
2. ስሜነሽ ወርቁ
3. ብርሃኑ ዳበሳ
4. በቀለ መገርሳ

ቀረቡ

5. ዘሜ አባራያ- ወኪል አያደር መሃመድቀረቡ
6. ጥሩ በሬቻ - ወኪል ደጅኔ መርጋ ቀረቡ
7. እቴነሽ ዳኜ - ወኪል አስናቁ ዳኜ ቀረቡ
8. አበበች በቀለ - አልቀረቡም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪዎች ከሌሎች ሶስት ግለሰቦች ጋር በመሆን በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ሰበታ አዋስ ወረዳ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው በመሆኑ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ መልስ ሲሰጥ የተጠሪዎች የስራ ውል የተቋረጠው ድርጅቱ ከውጪ አገር የሚመጣ ጥሬ እቃ በውጭ ምንዛሬ ጋር ተያይዞ ማቅረብ ባለመቻሉ ፋብሪካው ለዘለቄታው ስራ በማቆሙ ስለሆነ የተጠየቀው ክፍያ ሊከፈል እንደማይገባና ለተጠሪዎችም መከፈል የሚገባውን ክፍያ ከፍሎ ያሰናበታቸው በመሆኑ የቀረበው ጥያቄ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ተገቢ ነው ያለውን ዳኝነት ሰጥቶ የነበረ ሲሆን ጉዳዩ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን በይግባኝ ከታየ በኋላ የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ ዳግም እንዲሰማ በማለት በመለሰለት አግባብ ማስረጃዎችን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን ተጠሪዎች ከስራ የተሰናበቱት ድርጅቱ ከስሮ ለዘለቄታው በመዘጋቱ ምክንያት ስለመሆኑ አመልካች ድርጅት አላስረዳም በማለት ደምድሞ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት አመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን ለተጠሪዎች እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኃላ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ተጠሪዎችን ያሰናበታቸው በመክሰሩ ምክንያት በመሆኑ ስንብቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 24(4) አግባብ ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች መክሰሩን በማናቸውም ማስረጃ የሚያረጋግጥ ቢሆን እንኳን በመክሰር ምክንያት ስራውን የሚዘጋ መሆኑን ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ስንብቱን ማከናወኑ ሕጋዊ ሊያደርገው አይችልም በማለት ስንብቱን ህገ ወጥ ነው በማለት የደመደመ ሲሆን ክፍያዎችን በተመለከተ ግን አመልካች ለተጠሪዎች የከፈላቸው የክፍያ አይነቶችና መጠናቸው በስር ፍርድ ቤት ተጣርተው እንዲወሰኑ በማለት በዚህ ረገድ ያለውን ነጥብ ብቻ ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ በቅሬታውም አመልካች ድርጅት የተዘጋው በጥሬ እቃ አቅርቦት እጥረት ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለና ማስጠንቀቂያም በቃል የሰጠ ሆኖ እያለ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተወሰነው ያላግባብ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮም የተጠሪዎች የስራ ስንብት ህገ ወጥ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎችም ክርክራቸውን በፁሁፍ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ስንብቱ ህገ ወጥ የተባለበትን አግባብ እንደሚከለተው መርምሮታል፡፡

አመልካች ድርጅት ከውጭ ምንዛሬ ጋር ተያይዞ በተከሰተው የጥሬ እቃ አቅርቦት እጥረትና በኪሳራ ምክንያት ለዘለቄታው ስለመዘጋቱ አመልካች ጠቅሶ የሚከራከር ቢሆን ተጠሪዎች ይህ የአመልካች ክርክር በሕጋዊ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ድርጅቱ ሙሉ በሙሉ የተዘጋው በጥሬ ዕቃ አቅርቦትና በኪሳራ ስለመሆኑ ማስረዳት የሚቻለው በሰነድ ማስረጃ መሆን ያለመሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግልፅና በሕግ የተደገፈ ምክንያት ሳይጠቅስ ስንብቱን ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው አመልካች ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ መስጠት ሕጋዊ ግዴታ እያለበት ይህንኑ ግዴታ ያለመወጣቱ ስንብቱን ህገ ወጥ ያደረገዋል በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም የመክሰር ወይም የውጭ ምንዛሬ እጥረት በማጋጠሙ ከውጭ አገር የሚገባ የፋብሪካ ጥሬ ዕቃ እጥረት መኖር በማናቸውም የማስረጃ አይነት ሊረጋገጡ የሚችሉ ናቸው ብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ የማይቻል ሲሆን በዚህ ረገድ ለሚቀርቡ ክርክሮች መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች በሕጉ አግባብ ስልጣን በተሰጣቸው አካላት የሚሰጡና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው መሆን ያለባቸው መሆኑን ከማስረጃ አቀራረብና አመዛዘን መርሆዎች እንዲሁም ስለመክሰርም ሆነ ስለ ውጭ ምንዛሬ አግባብነት ባላቸው በሌሎች ሕጎች የተዘረጉትን ስርዓቶች በመመርመር የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ ያሰፈረው የምክንያት ክፍልና አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው የሰበር ክርክር ሕጋዊ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ ማስጠንቀቅያ የሚያስፈልገው መሆን ያለመሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 28(2(ሀ)) ድንጋጌ ከአለው አንድነትና ልዩነት አንፃር ተመልክተናል። በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/2/ሀ/ ሰራተኞች የተሰማሩባቸውን ስራዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቀጥታና ለዘለቂታው የሚያስቆም የሰራተኛ ቅነሳ የሚያስከትል ሁኔታ በአሰሪው ወይም አሰሪውን በሚመለከቱ ምክንያቶች ሲከሰት የስራ ውሉ በማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ እንደሚችል ይገልፃል። ድንጋጌው ምክንያቶች ከአሰሪው ጋር የተያያዙ መሆናቸውንና የድርጅቱ ስራ በከፊል ብቻ ሳይሆን በሙሉ ለዘለቂታው ሲቆም ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ እንደሚገባው የሚያስገነዘብ መሆኑን የድንጋጌውን ይዘትና መንፈስ ከአዋጁ አንቀፅ 24(4) ድንጋጌ አቀራረጽ፣ ይዘትና መንፈስ ጋር አዳምረን በምንመለከትበት ጊዜ የምንረዳው ጉዳይ ነው። አንድ ድርጅት በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቂታው መዘጋት የሥራ ውልን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለማቋረጥ የሚያስችል ሲሆን ለዚህም መረጋገጥ ያለበት መሰረታዊው ነጥብ የአሰሪው ድርጅት ለዘለቂታው መዘጋት ነው። ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24(4) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት ለዘለቂታው መዘጋቱ አልተረጋገጠም። በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪዎች የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ያለመስጠቱን አምኖ ማስጠንቀቂያው በቃል መሰጠቱ ስንብቱን ሕጋዊ ያደርጋል በማለት ያቀረበው ክርክር ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 34 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም። በመሆኑም አመልካች ድርጅቱ በዘለቂታው ስለመዘጋቱ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ማስረጃ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ባላቀረበበት ሁኔታ እርምጃው ሕጋዊ ነው በማለት ከአዋጅ ቁጥር 24(4) ድንጋጌ አንጻር የሚያቀርበው ክርክር የድንጋጌውን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ሆኖ ስለአገኘን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ ከውጤት አኳያ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 253316 ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል።
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትዕዛዝ

ሰኔ 20 ቀን2009 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡ ይጻፍ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.126667

መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ኤልያስ ባርና ሬስቶራንት - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ምርትነሽ አጥናፉ - የቀረበ የለም

2. ወ/ሪት ፌቨን ተክሌ- ተሰርዘዋል፡፡

3. ወ/ሪት ራሄል ገ/ሚካኤል -ታልፏል

4. ወ/ሪት ቆንጂት ብርሃኑ - ታልፏል

5. ወ/ሪት ዓይናለም አገዘው -ታልፏል

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪ እና ሰራተኛ የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሆኖ በአሁኑ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች እና ባሁኑ አመልካች መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ከተባለ በኋላ ክፍያ ለዘገዱበት የሁለት ወር ደመወዝ ለእነዚህ ተጠሪዎች እንዲከፍል፣ 4ኛ ተጠሪ ደግሞ ከሕግ ውጪ ተሰናብተዋል ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ የጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሽ በመሆን ነው፡፡ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ዋና ይዘቱ፡-በአመልካች ድርጅት በተለያዩ ጊዜያትና የተለያዩ የሥራ መደብ ለመስራት ተቀጥረው በመስራት ላይ እያሉ ወደ አልሆነ ሱስና ተግባር ተጠሪዎች እንዲገቡ፤ ከአመልካች ደንበኞች ጋር ተገቢ ያልሆነ ደርጊት እንዲፈፅሙ አመልካች ድርጅት ትዕዛዝ አሰተላልፎ ተጠሪዎች ሊቀበሉና ድርጊቶችን ሊፈፅሙ ፈቃደኛ ሊሆኑ ባለመቻላቸው ምክንያት ያለምንም ጥፋትና ማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ጠቅሰው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ተጠሪዎች ለህግና ለሞራል ተቃራኒ የሆኑና ያልተገቡ ድርጊቶችን ተጠሪዎች ከአመልካች ደንበኞች ጋር እንዲፈፅሙ ያለማድረጉንና ይልቁንም 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች እንዲሰናበቱ የተደረጉት የደረሠኝ ማጭበርበርና ደንበኞችን የማታለል እንዲሁም በሚሰሩት ስራ የገንዘብ ጉድለት ያሳዩ በመሆናቸው ምክንያት ስለመሆኑ፣ 4ኛ ተጠሪ ከማጭበርበርና ከማታለል ተግባራት በተጨማሪ ያልሆነ ምክንያት በማቅረብና በመስጠት በተደጋጋሚ ከስራ የሚቀሩና ማስረጃ የማያቀርቡ በመሆኑ ምክንያት ስለመሆኑ፣ 5ኛ ተጠሪ ደግሞ ከአምስት ተከተታይ የሥራ ቀናት በላይ ቀርተው በቂ ምክንያት ሊያቀርቡ ባለመቻላቸው ምክንያት ስለመሆኑ አመልካች በማረጋገጥ ከስራ እንዲወጡ ማድረጉን ዘርዝሮ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች አመልካች ድርጅት ተጠሪዎችን ወደ አልሆነ ሱስና ተግባር ሲገፋፉቸውና ተጠሪዎች ለመፈጸም ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ሲገልፁ እንደአሰናበታቸው የገለፁ ቢሆንም አመልካች ድርጅት ይህንን ስለማድረጉ ተጠሪዎች በማስረጃዎቻቸው ያላስረዱ መሆኑን፣ ይልቁንም 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በስራ ላይ የማጭበርበርና የማታለል ተግባር መፈፀማቸውን አመልካች ድርጅት በማስረጃዎቹ ማስረዳቱን፣ 5ኛ ተጠሪ ደግሞ ያለበቂ ምክንያት ከአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት በላይ ከስራ መቅረታቸውን አመልካች ማስረዳቱን ገልጾ አመልካች ድርጅት ከ1ኛ፣ 2ኛ፣3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ጋር የነበረውን የስራ ውል ያቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው በማለት የደመደመ ሲሆን 4ኛ ተጠሪን ግን ከሕግ ውጪ ስራ ላይ መቅረታቸውን ወይም በስራ ላይ የማጭበርበርና የማታለል ተግባር የፈጸሙ ስለመሆኑ አመልካች ያላስረዳ መሆኑን ጠቅሶ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ዶርሷል፡፡ ውጤቱን በተመለከተ ለ4ኛ ተጠሪ ስራ ሰርተው ያልተከፈላቸው ብር 800.00 የሚያዚያ ወር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2007 ደመወዝ፣ የሁለት ቀን ደመወዝ ለአመት እረፍት፣ የአንድ ወር ደመወዝ ለማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ 67.00(ስልሳ ሰባት ብር) የአገልግሎት ክፍያ፣የስድስት ወር ደመወዝ ካሳ እንዲከፈላቸውና የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው፣ ለ1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም ለእያንዳንዳቸው ብር 800.00(ስምንት መቶ ብር) የሚያዚያ ወር ደመወዝ፣ ለ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች የሁለት ቀን ደመወዝ ለአመት እረፍት፣ ለ3ኛ ተጠሪ የአምስት ቀን ደመወዝ ለአመት እረፍት፣ለ5ኛ ተጠሪ ደግሞ የአስር ቀን ደመወዝ ለአመት እረፍት እንዲከፈላቸውና የሥራ ልምድ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች ስራ ሰርተው ያልተከፈላቸው የሚያዚያ ወር 2007 ደመወዝ በመዘገዬቱ ምክንያትም አመልካች ለእያንዳንዳቸው ተጠሪዎች የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፍላቸው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የደመወዝ ክፍያ ለዘየበት የሁለት ወር ደመወዝ ለተጠሪዎች እንዲከፈል፣ 4ኛ ተጠሪን በተመለከተ ደግሞ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ተሰርሟል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ረገድ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ክሊራንስ ባላስጨረሱበት ሁኔታ የዘገየ ክፍያ አለ ተብሎ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ያለግባብ መሆኑን፣ 4ኛ ተጠሪም ለመከራ የተቀጠሩ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚቻል ሆኖ እያለ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው፣ 5ኛ ተጠሪም ከስራ በመቅረታቸው ምክንያት የተቆረጠባቸው ደመወዝ ዘግይቷል ተብሎ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎቸው ክሊራንስ ሳይጨርሱ የዘገየ ክፍያ አለ ተብሎ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የመወሰኑን አግባብነት እና የ4ኛ ተጠሪ ስንብትም የመከራ ጊዜአቸውን ያልጨረሱ ሆኖ እያለ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የመወሰኑን፣ 5ኛ ተጠሪም ከስራ በመቅረታቸው ምክንያት የተቆረጠባቸው ደመወዝ ዘገይቶአል በሚል ምክንያት የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የመወሰኑን ተገቢነት ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን 1ኛ፣3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ቀርበው ከአመልካች ጋር የጽሑፍ ልውውጥ ያጠናቀቀ ሲሆን 2ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪን በተመለከተ ግን አመልካች መጥሪያውን ስለማድረሱ ለማረጋገጥ ባለመቻሉ ምክንያት በእኚህ ተጠሪ ላይ አመልካች ያቀረበው የሠበር አቤቱታ በ14/11/2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚጠይቁ አበይት ነጥቦች፡-

1. የአሁኑ አመልካች ለ1ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የሚያዚያ ወር 2007 ዓ/ም ደመወዝ ዘግይቷል በማለት የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው በማለት መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?፣
2. የ4ኛ ተጠሪ ስንብት ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተያያዥ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው በተወሰነው የውሳኔ ክፍል የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ? ወይስ የለም? የሚሉት ሆነው ተገኝተዋል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>በአመልካችና በ1ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች መካከል የተመሰረተው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ሲሆን ይህ የውሳኔ ክፍል በሕጉ አግባብ ስለመለወጡ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ በአመልካችና በ1ኛ፣ 3ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች መካከል እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እያከራከረ ያለው ጉዳይ የሚያዚያ ወር 2007 ዓ/ም ደመወዝ በወቅቱ አልተከፈለም ተብሎ አመልካች ለተጠሪዎች የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈል የመወሰኑ አግባብነት ነው፡፡ አመልካች ለእነዚህ ተጠሪዎች የሚያዚያ ወር ደመወዝ በወቅቱ ያለመክፈሉን አምኖ ይህ ክፍያ ለመዘገየቱ ምክንያት ነው በማለት ክፍያው ለዘገየበት ክፍያ የሚከፈል ክፍያ የለም በማለት መከላከያ የሚያቀርበው ተጠሪዎቹ የተረከቡትን የሆቴሉን ሂሳብ አወራርደውና ያለባቸውን እዳ ከፍለው ደመወዛቸውን እንዲወስዱ ተፈቅዶላቸው ግዴታቸውን አልፈጸሙም የሚል ምክንያት ነው፡፡ተጠሪዎች በዚህ ሰበር ደረጃ ባቀረቡት ክርክር አመልካች ድርጅት ከስራ ሲያሰናብታቸው የግል ልብሳቸውን እንኳን ለመውሰድ ያልቻሉና በጥበቃም እንዳይገቡ የተደረጉ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 መሰረት የስራ ውል ሲቋረጥ የሰራተኛው ደመወዝና ከደመወዙ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት ቀናት ውስጥ መከፈል እንዳለባቸው የተመለከተ ሲሆን፣ የክፍያው ጊዜ ሊዘገይ የሚችለው ሰራተኛው ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት ለማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ሂሳብ ለማወራረድ የራሱ ጥፋት በሆነ ምክንያት ካዘገየ እንደሆነ በሕጉ ተደንግጓል። ሰራተኛው ስለጠየቀው ክፍያ አለመግባባት የተፈጠረ እንደሆነ አሰሪው በአንቀጽ 36 በተመለከተው ሰባት ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ ያመነውን ያህል ሊከፍለው እንደሚገባ በአዋጁ አንቀጽ 37 ሥር ተመልክቷል። ክፍያው ከአሰሪው ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር በአዋጁ አንቀጽ 36 ከተመለከተው የመክፈያ የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተፈፀመ አሰሪው ክፍያውን ላዘገየበት ጊዜ እስከ ሶስት ወር ለመድረስ የሚችል ደመወዙን ለሰራተኛው እንዲከፍለው ዳኞች ሊወስኑ እንደሚችሉ በአዋጁ አንቀጽ 38 ስር በግልጽ ተመልክቷል። ይህ ችሎትም በመዝገብ ቁጥር 44405 ግንቦት 19 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ አሰሪው ሰራተኛውን ያላስረከበው ንብረት አለ ወይም አጉድሏል በሚል ምክንያት ሰራተኛው በሚጠይቃቸው ክፍያዎች ሊጠይቅ አይችልም የሚል የአሰሪው ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲል ወስኗል። ከላይ በሕጉ የተመለከተው የስራ ውል ሲቋረጥ ከደመወዙ የተያያዙ ክፍያዎች በሰባት ቀናት መከፈል ያለባቸው ስለመሆኑ ነው። ክፍያው ሊዘገይ የሚችለው ሰራተኛው ያላስረከበው ንብረት ካለ ወይም ሂሳብ በማወራረድ ላይ ሰራተኛው በራሱ ጥፋት ካዘገየው ለመሆኑ ተመልክቷል። 1ኛ፣3ኛ እና5ኛ ተጠሪዎች ለአመልካች የምንከፍለው ዕዳም ሆነ የሚመልሱት ንብረት የለብኝም የሚል መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካች 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በስራ ላይ እያሉ የማጭበርበርና የማታለል ተግባር በመፈፀማቸው ከስራ መሰናበታቸውን አስረድቷል ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች ደምዳሜ ከመያዙ ውጪ ከእነዚህ ተጠሪዎችም ሆነ ከ5ኛ ተጠሪ የሚፈልገው ዕዳ ያለው ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ከሶ ያስፈረደባቸውና መጠኑንም በትክክል የተለየ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ማስረጃዎች ያለመረጋገጡን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተመልክተናል። 5ኛ ተጠሪ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በመቅረታቸው ከስራ ስለመባረራቸው ከመረጋገጡ ውጪ የሚያዚያ ወር 2007 አስራ ሶስት ቀናት ደመወዝ በሕጉ አግባብ ከስራ በመቅረታቸው የተቆረጠ እና ዘግይቷል ሊባል የማይችል መሆኑን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ተጠሪዋ ደመወዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቀጥተው እያለ ከስራም ተሰናብተዋል የሚለው ክርክርም አንድ ላይ የማይሄድ በመሆኑ ለእኚህ ተጠሪ የዘገየ ደመወዝ ስለሌለ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈል ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የለም ብሎ ለመደምደም የሚቻልበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡ በአጠቃላይ የዘገየ ክፍያ አለ ተብሎ አመልካች የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፍል በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> አንድ ሠራተኛ ሊመደብበት ለታቀደው ቦታ ተስማሚ መሆኑና አለመሆኑን ለመመዘን ለሙከራ ጊዜ ሊቀጥር እንደሚችል፤ይህ የግራ ቀኙ ስምምነትም በጽሑፍ መደረግ እንዳለበት፤ የሙከራ ጊዜውም ከ45 ተከታታይ ቀናት መብለጥ እንደሌለበት ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(1) ፣(2) እና (3) አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ የሙከራ ጊዜ ቅጥር ሲፈፀም ሰራተኛው በግልጽ ሊያውቀው የሚገባው ጉዳይ ሲሆን የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ስምምነት ከተደረሰም ስምምነቱ በጽሑፍ ሁኖ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ የተደረገ የሙከራ ጊዜ ስምምነት መኖሩ ከተረጋገጠ አሰሪው ሰራተኛውን ለተቀጠረበት የሥራ መደብ ተስማሚ አለመሆኑን ካላመነበት የቅጥር ውሉን ያለምንም ማስጠንቀቂያ የማቋረጥ መብት ሕጉ የሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አሰሪው ይህንኑ በሕጉ የተቀመጠውን መብቱን ሊጠቀም የሚችለው አሰሪው ሰራተኛውን ለሙከራ ጊዜ ለመቅጠር ወስኖ ሰራተኛውም ይህንኑ በግልጽ አውቆትና ተገንዝቦት በፅሑፍ ያሰፈሩት ስምምነት መኖሩ ከተረጋገጠ ብቻ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች 4ኛ ተጠሪን የሙከራ ጊዜ ከማለቁ በፊት ስለማባረሩ ገልጾ ቢከራከረም ለሙከራ ጊዜ የቀረጠራቸው ስለመሆኑና በዚህ ረገድም ተጠሪ የሚያውቁት ውል መኖሩን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች አላረጋገጡም፡፡ ስለሆነም አመልካች 4ኛ ተጠሪ ለሙከራ የተቀጠሩ በመሆኑ ያለምንም ማስጠንቀቂያ የማቋረጥ መብት አለኝ በማለት የሚያቀርበው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 11(3) ስር የተቀመጠውን ድንጋጌ ሙሉ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ 4ኛ ተጠሪ ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚያስችል ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆኑ አመልካች ገልጾ ያቀረበው ክርክርም በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የሥር ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ክፍያ ለዘገዬት የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈልም ሆነ ስለ 4ኛ ተጠሪ ስንብት ሕገ ወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36፣ 38 እንዲሁም አንቀፅ 11(3) ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ከክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡበት ፍሬ ነገሮች ጋር ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበትን የሕግ አግባብ ስለሌለ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈጸም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 99812 በ10/05/2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.172555 በ20/07/2008 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. የዚህ ችሎት ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ት እ ዛ ዝ

በ24/08/08 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጸፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 151474

መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-ቦሰት የሕጻናትና ቤተሰብ በጎ አድራጎት ድርጅት ጠበቃ ዩሬሳ በዳዳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዓለም ሽመልስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 377/1996 “ን” መሰረት አድርጎ የተነሳ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምስራቅ ኦሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የቅነሳ እርምጃው የተወሰደው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 28፣29 (3) እና 42 የተመለከተውን ስርዓት ተከትሎ አለመሆኑ እና ድርጅቱ በ2002 ዓ.ም. ባወጣው የሰው ኃይል መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የመስሪያ ቤቱ ቦርድ ሳያጸድቀው መሆኑ ስለተረጋገጠ እርምጃው ሕገወጥ ነው፣ ሕገወጥ ስንብት የሚያስከትላቸውን እና ተያያዥ ክፍያዎችን አመልካች ለተጠሪዋ ሊከፍል ይገባል በማለት በመዝገብ ቁጥር 867/01/2008 በ29/07/2009 ዓ.ም.የሰጠው እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 258827 በ21/02/2010 ዓ.ም.እና በመዝገብ ቁጥር 273765 በ16/04/2010 ዓ.ም. በተመሳሳይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታ በፍርድ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው።

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የመታየቱን አግባብነት፣ቅነሳው የተከናወነው ሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም መሰረት በማድረግ ሆኖ ሳለ ስንብቱ ሕገወጥ ነው የመባሉን አግባነት፣የህክምና ወጪ ከኢንሹራንስ ድርጅት ለተጠሪዋ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት እና ተጠሪዋ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሆነው እያለ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት እንዲከፈል የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 29 (3) እንዲሁም የዚሁ አዋጅ ማሻሻያ ከሆነው አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ (2) (ሰ) እና በመዝገብ ቁጥር 98676 ከተሰጠው የሰበር ችሎት ገዥ ውሳኔ አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት እንዲቻል ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. የቅነሳ እርምጃው የተከናወነው አግባብነት ባላቸው የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት አድርጎ አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
3. ያልተከፈለው የሕክምና ወጪ ታስቦ አመልካች ለተጠሪዋ ሊከፍል ይገባል በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
4. ተጠሪዋ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሆነው እያለ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ (2) (ሰ) ድንጋጌን እና በዚህ ረገድ የተሰጠውን የሰበር ገዥ ውሳኔ የሚጻረር ነው በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር በመዝገቡ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 377 1996 "ን" መሰረት አድርገው የሚነሱ የስራ ክርክር ጉዳዮች የሚታዩት እንደየጉዳዩ ዓይነት በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታዩት በአዋጁ አንቀጽ 138 (1) ስር ከፊደል (ሀ) እስከ (ረ) የተዘረዘሩት እና ሌሎች ተመሳሳይ የግል የስራ ክርክር ጉዳዮች መሆናቸውን እና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ የሚታዩት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 142 (1) ከፊደል (ለ) እስከ (ሸ) የተዘረዘሩት እና ሌሎች ተመሳሳይ የወል የስራ ክርክር ጉዳዮች መሆናቸውን የተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች እንዲሁም የአዋጁ አንቀጽ 147 (1) (ሀ) ድንጋጌ ያመለክታሉ።በሁለቱ ድንጋጌዎች ስር ከተመለከቱት የግል እና የወል የስራ ክርክር ዓይነቶች አንዳንዶቹ በስያሜም ሆነ በይዘት የመመሳሰል ባህርይ ያላቸው በመሆኑ የትኛው ክርክር በግል፣የትኛው ደግሞ በወል የስራ ክርክር ስር እንደሚወድቅ መለየቱ በተግባር ሲያስቸግር ይታያል።ከዚህም በመነሳት እና አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የግል የስራ ክርክርን ከወል የስራ ክርክር ለመለየት ስለሚያስችሉ መስፈርቶች በመዘርዘር የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ.18180 በ29/11/1997 ዓ.ም. እና በሌሎችም በርካታ መዝገቦች አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ መሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው።በዚህ አስገዳጅ የህግ ትርጉምም ሕጉ የስራ ክርክር ጉዳዮችን የወል ወይም የግል ብሎ ለመለየት የተከራካሪ ሰራተኞችን ቁጥር እንደመስፈርት መወሰድ እንዳለበት የማያመለክት መሆኑ፣አንድ የስራ ክርክር የወል ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑ፣አንድን የስራ ክርክር ጉዳይ የግል የስራ ክርክር የሚያደርገው ደግሞ ጉዳዩ ከግል አልፎ በጋራ መብት ላይ የሚያስከትለው ውጤት የሌለ በሆነ ጊዜ መሆኑ እና መሰል ጉዳዮች በዝርዝር ተመልክተዋል።

በሌላ በኩል በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ የስረ ነገር ስልጣን ስር ከሚወድቁ ጉዳዮች አንዱ የሰራተኞች ቅነሳ ጉዳይ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 142 (1) (ሸ) እና አንቀጽ 147 (1) (ሀ) ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል።ይህ ማለት ግን ከቅነሳ ጋር የተያያዘ ማናቸውም ጉዳይ በቦርዱ የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም።በቦርዱ የስረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው ለማለት የሚቻለው ከላይ በተጠቀሰው የሰበር ገ/ኛ ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ የወል ባህርይ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዋ ለክሳቸው ምክንያት ካደረጓቸው ነጥቦች አንዱ ተጠሪዋ በሕመም ፈቃድ እና ቀጥሎም በወሊድ ፈቃድ ምክንያት በስራ ላይ ላልነበሩበት ጊዜ የስራ አፈጻጸማቸውን ሞልቶ ለቅነሳው መሰረት በማድረግ አመልካች ድርጅት የዘረጋው የቅነሳ ስርዓት ተገቢነት የለውም የሚል መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።ይህ ደግሞ የድርጅቱ ሰራተኞች በተለያዩ ምክንያቶች በስራ ገበታ ላይ ባልነበሩበት ጊዜ በሌላ አነጋገር ስራ ባልሰሩበት ጊዜ የስራ አፈጻጸማቸውን በመሙላት አመልካች ድርጅት ለቅነሳ ተግባር ሊጠቀምበት ይችላል ወይም አይችልም? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ጉዳዩ በቀረበለት አካል በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የሚሰጠው ውሳኔ በተጠሪዋ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን በሌሎችም ሰራተኞች መብት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ክርክሩ የወል ባህርይ እንዲኖረው የሚያደርግ ነው።እንዲህ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ በቦርድ የስረ ነገር ስልጣን ስር የማይወድቅበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም።በመሆኑም ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ድርጅት የቅነሳ እርምጃውን የወሰድኩት የ30% በ70% ቀመር በትክክል ተገባራዊ እንዳደርግ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ኤጀንሲ በተሰጠኝ መመሪያ መሰረት ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም ይህንን የክርክር ነጥብ በማስረጃ ማስደገፍ ያልቻለ መሆኑ፣የቅነሳ እርምጃው የተከናወነውም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 29 (3) የተመለከቱትን ግልጽ መስፈርቶች መሰረት በማድረግ አለመሆኑ፣ይልቁንም ተጠሪዋን ከስራ ያሰናበተው በሕመም ምክንያት ለረዥም ጊዜ በስራ ላይ ያልነበሩ መሆኑን በስንብት ደብዳቤው ላይ በመግለጽ መሆኑ፣በተጠሪዋ ላይ የስንብት እርምጃ የወሰደውም ተጠሪዋ ስራ ላይ ባልነበሩበት ጊዜ የተሞላላቸውን የስራ አፈጻጸም ውጤት ጭምር በመጠቀም መሆኑ በቦርዱ የተረጋገጡ እና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት ያገኙ ፍሬ ነገሮች መሆናቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።አመልካቹም በዚህ ረገድ በሰበር አቤቱታው ላይ ያቀረበው የማስተባበያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክር የለም።እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የወሰደው እርምጃ ሕጋዊ ሊሆን አይችልም።በመሆኑም የቅነሳ እርምጃው የተከናወነው አግባብነት ባላቸው የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት አድርጎ አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም።

ሶስተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ለተጠሪዋ እና ለቤተሰባቸው አባላት የህክምና ወጪ አመልካች በጥቅል የገባውን የመድን ሽፋን ብር 7,000 /ሰባት ሺህ/ ተጠሪዋ እና የቤተሰባቸው አባላት ተጠቅመው ያጠናቀቁ ስለመሆኑ የመድን ሽፋን ከሰጠው ድርጅት በተጻፈ ደብዳቤ ተረጋግጦ እያለ አመልካች ለተጠሪዋ ተጨማሪ የህክምና ወጪ እንዲተካ ውሳኔ የተሰጠው አለአግባብ ነው በማለት ሲሆን ቦርዱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ሳይቀበሉ የቀሩት በግራ ቀኙ መካከል ባለው ውል መሰረት አመልካች የብር 7,000 /ሰባት ሺህ/ የህክምና ወጪ የመሸፈን ግዴታ ያለበት ለተጠሪዋ እና ለቤተሰባቸው አባላት በጥቅል ሳይሆን በነፍስ ወከፍ ነው በማለት ነው።አመልካች የመድን ሽፋን ከገባበት የገንዘብ መጠን ብር 7000 /ሰባት ሺህ/ ውስጥ ከአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ለተጠሪዋ በግል የብር 4,236 /አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት/ የህክምና ወጪ የተተካላቸው መሆኑ እና ቀሪው ብር 2,764 /ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ አራት/ የህክምና ወጪ የተተካው ደግሞ ለተጠሪዋ የቤተሰብ አባላት መሆኑ በተጠሪዋም ያልተካደ ሲሆን በቦርዱ ውሳኔ መሰረት አመልካች ለተጠሪ መተካት የሚጠበቅበት የህክምና ወጪ ብር 2,764 /ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ አራት/ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።አመልካች በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት ውስጥ ለተጠሪዋ እና ለቤተሰባቸው አባላት በጥቅል ሳይሆን በነፍስ ወከፍ የብር 7,000 /ሰባት ሺህ/ የህክምና ወጪ የመሸፈን ግዴታ የተጣለበት በየትኛው ደንብ እና ድንጋጌ መሰረት እንደሆነ ለይተው በመጥቀስ ተጠሪዋ በሰበር መልሳቸው ላቀረቡት ክርክር አመልካቹ በመልስ መልሱ የሰጠው ማስተባበያ የለም።አመልካች ድርጅት ለተጠሪዋ እና ለቤተሰባቸው አባላት በጥቅል የብር 7,000 /ሰባት ሺህ/ የመድን ሽፋን መግባቱ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ውል መሰረት ያደረገ ካልሆነ ደግሞ ልዩነቱን እራሱ የመሸፈን የውል ግዴታ ይኖርበታል።በመሆኑም ያልተከፈለው የሕክምና ወጪ ታስቦ አመልካች ለተጠሪዋ ሊከፍል ይገባል በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አራተኛውን እና የመጨረሻውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪዋ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆናቸው ተረጋግጦ እያለ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት እንዲከፈላቸው የተሰጠው ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ (2) (ሰ) ድንጋጌን እና በዚህ ረገድ የተሰጠውን የሰበር ገዥ ውሳኔ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ሊሻር ይገባዋል በማለት ነው።እንደተባለው የስራ ውሉ በሕገ ወጥ መንገድ የተቋረጠበት ሰራተኛ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 39 (1) (ለ) በተመለከተው መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ካላቸው ሰራተኞች ወስጥ የሚካተት ቢሆንም የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ የስራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ በተደራቢነት የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንደማይኖረው የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ማሻሻያ በሆነው አዋጅ ቁጥር 494/1998 በአንቀጽ 2 (ሰ) ስር ተደንግጎ ይገኛል።የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አግባብነት ያላቸውን የሁለቱን አዋጆች ድንጋጌዎች አገናዝቦ በመተርጎም የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የማይኖረው ስለመሆኑ ቀደም ሲል በቀረቡ ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ በመዝገብ ቁጥር 35197፣37048 እና በሌሎችም መዝገቦች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።

ተጠሪዋ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆናቸው ያልተካደ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ እና የሰበር ገዥ ውሳኔ መሰረት የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት የማግኘት መብት የማይኖረው መሆኑን ተቀብለው ነገር ግን ለተጠሪዋ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈል የወሰኑት አመልካች ድርጅት ለተጠሪዋ በጻፈው የስንብት ደብዳቤ ላይ ከፕሮቪደንት ፈንድ በተጨማሪ የስራ ስንብት ክፍያ እንደሚከፈላቸው የገለጸ መሆኑን መሰረት በማድረግ እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል። ውሳኔው አዋጁን እና የሰበር ገዥ ውሳኔን የሚጻረር ነው በሚል በጥቅሉ ከመከራከር በቀር የስንብት ደብዳቤው አነጋገር እና ይዘት ከላይ የተገለጸው ስላለመሆኑ አመልካች በሰበር ደረጃ ያቀረበው የማስተባበያ ክርክር የለም።

አመልካች በአስረጂነት ጠቅሶ የሚከራከርባቸው የአዋጁ ድንጋጌ እና የሰበር ገዥ ውሳኔዎች ደግሞ አሰሪው የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ለሆነ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት የመክፈል ግዴታ እንደሌለበት የሚያመለክቱ ከመሆናቸው በቀር አሰሪው በራሱ ፍላጎት የስራ ስንብት ክፍያውን በተደራቢነት እንዳይከፍል የሚከለክሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደሉም፡፡አመልካች የስንብት ክፍያው በተደራቢነት እንደሚከፈል ክርክር ከመጀመሩ በፊት በስንብት ደብዳቤው ላይ በግልጽ ፈቅዶ እያለ ተጠሪዋ ክስ ካቀረቡ በኃላ የስራ ስንብት ክፍያው ሊከፈል የማይችልበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ ያቀረበው ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር የስራ ስንብት ክፍያው እንዲከፈል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ከላይ የተጠቀሰውን አዋጅ እና የሰበር ገዥ ውሳኔ የሚጻረር ነው በማለት በደፈናው የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዋ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሆነው እያለ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ (2) (ሰ) ድንጋጌን እና በዚህ ረገድ የተሰጠውን የሰበር ገዥ ውሳኔ የሚጻረር ነው በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር በመዝገቡ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በምስራቅ ኦሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ በመዝገብ ቁጥር 867/01/2008 በ29/07/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 258827 በ21/02/2010 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 273765 በ16/04/2010 ዓ.ም. በተመሳሳይ ሁኔታ በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በምስራቅ ኦሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ በመዝገብ ቁጥር Mr/290/01/2009/3 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ26/04/2010 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡
3. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 132280

መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው
አልማው ወሌ
መስጠፋ አህመድ
አብርሃ መሰለ
ሰናይት አድነው

አመልካች፡- 1. አቶ አስቻለው አስማማው } የቀረበ የለም
2. አቶ አሸናፊ ሲርባሞ }

ተጠሪ፡- የደቡብ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሰረት አድርጎ የቀረበን የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች በሀዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ሕዳር 24 ቀን 2008 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከተጠሪ ጋር ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ የመሰረቱትን የስራ ግንኙነት አመልካቾች ከጳጉሜ 01 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ በጡረታ በመገለላቸው ምክንያት የተቋረጠ ቢሆንም ለጡረታ መብታቸው የተያዘላቸው የአገልግሎት ዘመን ከሐምሌ ወር 1988 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ ያለው ብቻ መሆኑን ገልፀው ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1988 ዓ/ም ድረስ በተጠሪ ድርጅት ለአገለገሉበት ጊዜ የስራ ስንብት ካሳ ክፍያ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካቾች ጋር የተደረገው የስራ ውል የተቋረጠው እድሜአቸው ለጡረታ ደርሶ መሆኑንና አመልካቾችም በጡረታ የወጡና የመብቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሰራተኞች መሆናቸውን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች በጡረታ የተገለሉና የጡረታ መብት ተጠቃሚ ሁነው እያለ ከ1969 ዓ/ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጀምሮ እስከ ሐምሌ 1988 ዓ/ም ድረስ ለአገለገሉበት ጊዜ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ሕጋዊ አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል:: የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ ለበርካታ አመታት አግልግሎት የሰጡ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለና ለዘላቂ የጡረታ መብት የተያዘው አገልግሎታቸውም ከሐምሌ 1988 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ ብቻ ሁኖ እያለ አመልካቾች ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሀምሌ 30 ቀን 1988 ዓ/ም ድረስ ለዘላቂ ጡረታ ላልተያዘላቸው ጊዜ ያቀረቡት የስራ ስንብት ክፍያ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በጡረታ የወጡ ሰራተኞች መሆናቸውን፣ ከተጠሪ ጋር ያደረጉት የስራ ውልም ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1988 ዓ/ም ድረስ የኮንትራት የስራ ውል በመሆኑ ይኼው ጊዜ ለጡረታ መብት አከባበር እንዲያዝላቸው ስልጣን ለአለው አካል አቅርበው ተቀባይነት ያጡና በስርዓቱም መሰረት በይግባኝ ወይም በሰበር ያልተለወጠ መሆኑን፣ ከሐምሌ ወር 1988 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2007 ዓ/ም መጨረሻ ያለው ጊዜ ለጡረታ መብታቸው ተይዞላቸው ከጳጉሜ 01 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ ከተጠሪ መስሪያ ቤት በጡረታ በመገለል የጡረታ መብትም ወዲያውኑ ተጠቃሚ የሆኑ መሆናቸውን ነው፡፡

በመሰረቱ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ የስራ ውል ከህግ ውጪ መቋረጡ ከሚያስከትላቸው ሕጋዊ ውጤቶች አንዱ የሥራ ስንብት ክፍያ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

377/96 አንቀጽ 43 (4) ከተቀመጠው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ የተደረገ የስራ ውል በሕግ አግባብ ከተቋረጠ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ከሕጉ ቅርጽና ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤቶች በተደረገው ክርክር ያልተካደው ወይም የተረጋገጠው አመልካቾች ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1988 ዓ/ም ድረስ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው የሥራ ውል ግንኙነት በኮንትራት ላይ የተመሰረተ መሆኑና ይህ ጊዜ ለጡረታ መብት አከባበር ለአመልካቾች እንዲያዝላቸው ለማህበራዊ ዋስትና ኤጂንሲ አመልካቾች አቅርበው አገልግሎታቸው ለጡረታ አይያዝላቸውም ተብሎ ውሳኔ ማግኘቱንና በበላይ የዳኝነት አካልም ያለመለወጡን ነው፡፡ አመልካቾች የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄውን ያቀረቡት በጡረታ ተገልለው የመብቱ ተጠቃሚነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ስለመሆኑም ያልተካደ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ የክፍያ ጥያቄውን ከሥር ጀምሮ ሲቃወም የመጣውም አመልካቾች መደበኛ የጡረታ ዕድሜ የደረሱና የጡረታ አበልም የሚከፈላቸው ናቸው፣ ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1988 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ ደግሞ የኮንትራት ውል የነበረበት ከመሆኑም በላይ ተጠሪው ሕጋዊ ሰውነቱን ያላገኘበት ጊዜ ነው በማለት ነው፡፡

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 "ን" ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ.494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ እና /ሸ/ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 39 እንደተደነገገው የሥራ ስንበት ክፍያ የሚከፈለው ሠራተኛው የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለው ከሆነ እንደዚሁም ሥራውን ሲለቅ መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ያልደረሰ ሲሆን ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ሥራቸውን የጡረታ መውጫ እድሜያቸው ደርሶ መብቱም ተከብሮላቸው በሕግ አግባብ የተሰናበቱ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 43 (4) እና ከማሻሻያ አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ እና /ሸ/ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካቾች ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1988 ዓ/ም የአገለገሉት ጊዜ የኮንትራት ጊዜ ነው ተብሎ ለጡረታ መብት ሊያዝላቸው አይገባም በሚል ዳኝነት በተሰጠበትና አመልካቾች የጡረታ መብት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ መደበኛ የጡረታ ዕድሜም ደርሰው የመብቱ ተጠቃሚ መሆናቸው ጭምር በተረጋገጠበት አግባብ ለጡረታ መብት ላልተያዘላቸው ጊዜ የሥራ ስንብት ካሳ ሊከፈለን ይገባል በማለት የሚያቀርቡት ጥያቄ የህግ መሰረት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስራ ስንብት ክፍያ የሚያገኙበት የሕግ አግባብ የለም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02989 ታህሳስ 08 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19216 የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 67526 በ04/12/08 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች ከ1969 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 1988 ላለው ጊዜ የስራ ስንብት ካሳ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 136571

መስከረም 29 ቀን 2010ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- እድገት ተስፋ ሁለገብ ሸ/ኃ/የተ/የህ/ሥ/ማህበር - የስራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ታመነ መኮንን ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቦዬ ለሜሳ/ባለቤታቸው አቶ ሐይሉ አስፋውና ወራሾች እነ አሉላ ሀይሉ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የሥር ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ጋር ከሐምሌ 28 ቀን 1978 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 11 ቀን 2008 ዓ.ም በተለያዩ የስራ መደቦች 1,300.00/አንድ ሺህ ሶስት መቶ ብር/ እየተከፈላቸው ሲሰሩ እንደነበረ ነገር ግን አመልካች ከሚሰሩበት የነበረ የስራ መደብ ሳይፈልጉ በማንሳት ፤ምክንያቱ ሳይነገራቸው፤የውድድር ስርዓት ሳያደርጉ፤የተመደቡት የስራ መደብ ለማታ ስራ የማይመችና ሞያቸው ወዳልሆነ የስራ መደብ የስራ ዝውውር ደብዳቤ የሚገልፅ ደብዳቤ የደረሳቸው መሆኑን፤በዚሁ ምክንያት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዝውውሩ ላይ ቅሬታ አቅርበው እያሉ አመልካች የስራ ውሉ ያለአግባብ ስላቆረጠብኝ የካሳ፤የስራ ስንብት ክፍያ፤ ክፍያ ለዘገየበት ክፍያ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ዝውውሩን ያደረገበት ምክንያት ተጠሪ የተዛወሩበት የስራ መደብ ላይ ለረጅም አመታት የሰሩበት እንደሆነ እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት የሚያሰራው የመዝናኛ ክበቡ የስራ ባህሪ መሆኑን ፤የተጠሪ ዋናው ምክንያታቸው ትምህርት ስለምማር አይመቸኝም የሚል መሆኑን፤ስራ እየሰሩ ምላሽ መጠበቅ ሲችሉ ከ14/03/08 ዓ.ም እስከ 11/04/08 ዓ.ም ስራ ትተው ቤታቸው መቀመጣቸው ትክክል እንዳልሆነ ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄም ጡረታ የሚዋጣላቸው በመሆኑ ሊከፈላቸው እንደማይገባ በመግለፅ የመከላከያ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ተጠሪ የተመደቡት በሙያቸው መሆኑን፣ የተመደቡት የስራ መደብ ለህይወታቸው አስጊ አለመሆኑን፤ተጠሪ ወደተመደቡበት ስራ ሄደው አለመስራታቸው፤በትምህርት ምክንያት ዝውውሩን የሚቃወሙ ስለመሆኑ እንደማያሳይ፤ ተጠሪ ቅሬታ አቅርበው ከስራ መቅረታቸው፣ ከስራ የቀሩበት በበቂ ምክንያት ነው የሚያስብል አለመሆኑን በምክንያትነት ጠቅሶ ተጠሪ ከ5 ተከታታይ ቀናት በላይ ከስራ መቅረታቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ለ/ መሰረት ስንብቱን ህጋዊ ያደርገዋል፤በተጠሪ የተጠየቁት ክፍያዎች የህግ ድጋፍ የሌላቸው ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት እንዲሰሩ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን፤ተጠሪ ላቀረቡት ቅሬታ ምላሽ ጠብቅ ሲባሉ ወደስራ ገበታቸው ያልገቡት ተጠሪ ላይ ጫና በሚያሳድር ሁኔታና መብታቸውን ባላከበረ መልኩ በመሆኑ ከስራ ገበታቸው ያለበቂ ምክንያት ቀርተዋል አያሰኝም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ስንብቱ ህገወጥ ነው፤ ስለሆነም የህገወጥ ስንብት ውጤት ክፍያዎቹ በተመለከተ የግራ ቀኙን ማስረጃ በማየት ውሳኔ እንዲሰጥበት ለስር ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥር 12 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሐምሌ 21 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ መስጠት መብታቸው በመታለፉ የቀረበ የመልስ መልስ የለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ከግራ ቀኙ ክርክርና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ነጥብ በጉዳዩ ላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ይሰሩበት ከነበረው የስራ መደብ ወደሌላ የስራ መደብ የተዛወሩ መሆናቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ እንደደረሳቸው ስራው በምሽት የሚሰራ በመሆኑ ለህይወታቸው አስጊ እንደሆነና ሌሎች ምክንያቶች በመግለፅ እንዲስተካከል አቤቱታ አቅርበው ምላሽ በመጠባበቅ እያሉ ከ5 በላይ ተከታታይ የስራ ቀናት ከስራ ቀርተዋል በማለት አመልካች የስራ ውሉ የተቋረጠ መሆኑን ከውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ በመሰረቱ የስራ ውል ሊቋረጥ የሚችልባቸው መንገዶች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 23 ስር ተመልክቷል፡፡ አንደኛው መንገድ በአሰሪው አነሳሽነት የሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ እንደሁኔታው በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ ሊደረግ የሚችል ሆኖ የምክንያቶቹ ዝርዝር እና አፈፃፀሙ ከአንቀፅ 26 እስከ 30 ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በሕብረት ስምምነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ተደርጎ የተወሰደ ጉዳይም በአሰሪው አነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 27/1/ተ/ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለዚህ በአዋጁ በተደነገጉ ምክንያቶችና ሁኔታዎች የሚፈፀም የስራ ውል ማቋረጥ ህጋዊ የስራ ማቋረጥ ሲሆን ከነዚህ ውጭ የሚደረጉ የስራ ውል ማቋረጥ ህገወጥ መሆኑን ከአንቀጽ 42 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአመልካችና ተጠሪ መካከል የተደረገው የስራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት መብትና ግዴታ ያቋቁማል፡፡ በህጉ አንቀጽ 12 የአሰሪው ግዴታ በአንቀጽ 13 ደግሞ የሰራተኛው በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ህገወጥ ድርጊት የተባሉት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሰሪና ሰራተኛ ቅደም ተከተል በአንቀጽ 14/1/ እና 14/2/ በዝርዝር ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ የአሰሪው ግዴታ ከተገለፁት ከስራው ጋር በተያያዘ የሰራተኛውን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅና ከአደጋ ለመከላከል የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች ሁሉ የመውሰድና እነዚሁንም እርምጃዎችን በሚመለከት ረገድ አግባብ ባላቸው ባለስልጣኖች የሚሰጡትን ደረጃዎች መመሪያዎች የመከተል በአሰሪው ላይ የተጣለ ግዴታ ነው፡፡ በሌላ በኩል አሰሪውና ሰራተኛው ህገወጥ ድርጊት ተብለው ከተገለፁት ውስጥ በህጉ አንቀጽ 14/1/ሠ/ በአሰሪው ሰራተኛውን በህይወቱ ላይ አደጋ ሊያደርስበት በሚችል አካኋን እንዲሰራ ማድረግ ህገወጥ ድርጊት መሆኑን የተመለከተ ነው፡፡ አሰሪው ግዴታው ካልፈፀመና ህገ ወጥ ድርጊት መፈፀሙ ከተረጋገጠ ሰራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ማቋረጥ በቂ ምክንያት ይሆናል በማለት በአንቀጽ 32/1/ለ ይደነግጋል፡፡ ይህ ከተረጋገጠ ደግሞ ሰራተኛው በአዋጁ መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን ከአሰሪው የማግኘት መብት አለው፡፡ ስለሆነም ከላይ እንደተጠቀሰው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካች አድራጎት የተጠሪን ህይወት ለአደጋ ያጋለጠ ስለመሆኑ አረጋግጧል፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ የሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 117169 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2/1/ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍ/ቤትን የማስገደድ ኃይል ያለውን ህግ ትርጉም ስጥቷል፡፡

ለዚህም አመልካች ዝውውሩን ተግባራዊ ያደረገው ትራንስፖርት አገልግሎት የማሟላት ግዴታውን ሳይወጣ ስለመሆኑ በማረጋገጥ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 57101 መጋቢት 27 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 173539 ታህሳስ 14 ቀን 2009 ዓ/ም በመሻር የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ከዚህ ፍርድ ቤት ግንቦት 29 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኮ/ቀ/ ምድብ ችሎት በመ/ቁ.74378 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰ/መ/ቁ.140677

ህዳር 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ብርሃኑ ጌቱ ጠበቃ ተፈሪ ፅጌ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት አ/ማ ሰራተኛ ማሕበር የቀረበ የለም ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የሥር ከሳሽ የአሁን አመልካች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በአስተዳደር ሙያ ስራ ተቀጥረው በወር 1712.00 /አንድ ሺህ ሰባት መቶ አስራ ሁለት ብር/ እየተከፈላቸው ኤ/አ/16/5/2014 ጀምሮ በካምቲን አስተዳደር ኃላፊ የስራ መደብ ተቀጥረው ሲሰሩ ፈቃድ እንዲወጡ ተደርጎ ከ04/04/16–13/04/16 በፈቃድ ቆይተው ሲመለሱ በብትድ/ሠ/መማ/ካ/04/07/16 በተፃፈ ደብዳቤ ከ14/04/16 ጀምሮ የስራ ውሉ ከህግ ውጭ እንዲቋርጥ በማድረጉ የስራ ስንብት ክፍያ፤የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፤የካሳ ክፍያ፤የዓመት እረፍት የመሳሰሉት አመልካች እንዲከፍል ተብሎ እንዲወሰንላቸው ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም ለቀረበው ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በቀረበው መቃወሚያ መሰረት አመልካች የስሪ መሪ በመሆናቸውን የቀረበው ክስ በስራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይችልም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካች የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም የስር ፍርድ ቤት ብይን ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሚያዚያ 13 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በታዘዘው መሰረት ሐምሌ 18 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ከግራ ቀኙን ክርክርና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ነጥብ አመልካች የስራ መሪ ናቸው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

የአመልካች ጥያቄ በተጠሪ ድርጅት በአስተዳደር ስራ ከመቀጠር በስተቀር አንድ የአስተዳደር ኃላፊ መስራት ያለበትን እንደ ሰራተኛ መቅጠር፤ማሰናበት እድገት መስጠት መቅጣት ስራዎችን ማከናውን የሚያስችል ስልጣን ባልተሰጠበት ሁኔታ ስራ መሪ የሚያስብል ምክንያት ባለመኖሩ አመልካች በአስተዳደር ስራ መደብ በመስራቱ ብቻ የስራ መሪ አያሰኝም፤በስር ፍርድ ቤቶች የስራ መሪ ነህ ለማለት የቻሉት በቀን 4/4/14 ለወ/ሮ እታገኝ እንድሪስ የጻፍኩትን መነሻ እንደሆነ በብይኑ ላይ ገልጸ አስቀምጦታል፣ ነገር ግን የዚህ ዓይነት ሌላ የአስተዳደር ስራ እንዲሰራ ተጠሪ ባላስረዳበት በዚህች ድብዳቤ መነሻ ብቻ የስራ መሪ ነህ በማለት የተሰጠ ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ የአመልካች ቅጥር ደብዳቤ የስራ መሪ መሆኑን ያስረዳል፣ እንዲሁም የአስተዳደር ኃላፊ፣ የክበቡ ዋና መሪ ፣የሰራተኞች አስተዳዳሪ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀጣሪም፣ አሰናባችም፣ ማስጠንቀቂያ ሰጪም የክበቡ የምግብ ዝግጅትና መሪ፤ በአጠቃላይ ለክበቡ ከአሁን አመልካች በቀር የመጨረሻ ባለስልጣን የለም ፣ መሪውና አስተዳዳሪው አመልካች በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/1/ሐ/ መሰረት ውሳኔ መስጠታቸው ባግባቡ ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሠረቱ የሥራ መሪ ማለት በሕግ ወይም እንደ የድርጅቱ የስራ ፀባይ በአሠሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣት የማስፈፀም ከነዚሁ በተጨማሪ ወይም እነዚሁኑ ሣይጨምር ሠራተኞን የመቆጣጠር የማዛወር፣ የማገድ፣ ለማሰናበት የመመደብ ወይም የስነ-ስርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውንና የሚወስን ግለሰብ ስለመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ ቁ. 377/96 3/2/ /ሐ/ ስር እና በማሻሻያ አዋጁ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/1/ /ሐ/ ሥር ተመልክቷል፡፡

አመልካች በአስተዳደር ሙያ ስራ የተቀጠሩ ስለመሆናቸውና ለወ/ሮ እታገኝ እንድሪስ ማስጠንቃቂያ መፃፋቸውን ሳይክዱ በአዋጁ እንደተመለከተው የስራ መሪ ተግባራትን ስለማከናወናቸው በተጠሪ የቀረበ ማስረጃ የለም፤ለአንድ ሰራተኛ ማስጠንቀቂያ በመጻፉ ብቻ የስራ መሪ አያሰኝም ከማለት ውጭ ክበቡን የሚያስተዳድረው፣ ሰራተኞች የሚቀጥረው፤ የሚያሰናብተው የማን እንደሆነ ፤የስራ ግንኙነታቸው ከማን እንደሆነ ፤እና ስለ ክበቡ አደረጃጀት /መዋቅር/ የገለጹት ነገር የለም፡፡ የአስተዳደር ኃላፊ፣ የክበቡ ዋና መሪ፣ የሰራተኞች አስተዳዳሪ ቀጣሪም፣ አሰናባችም፣ ማስጠንቀቂያ ሰጪም፣ የክበቡ የምግብ ዝግጅትና መሪ፣ በአጠቃላይ ለክበቡ ከአሁን አመልካች በቀር የመጨረሻ ባለስልጣን የለም፣ መሪውና አስተዳዳሪው አመልካች መሆናቸው ተገልፆ በተጠሪ ለቀረበው ክርክርም አመልካች ግልፅ የሆነ ማስተባበያ በመልስ መልሳቸው ያላቀረቡ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ለአንድ ሰራተኛ ማስጠንቀቂያ በመጻፉ ብቻውን የስራ መሪ ተብሎ ይገመታል በማለት የያዙት ምክንያት ለጉዳዩ በቂ ባይሆንም አመልካች የስራ መሪ ስለሆኑ ጉዳያቸው በስራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይችልም በማለት የሰጡት ውሳኔ ግን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ ከተመለከቱት ምክንያቶች አንፃር በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 61790 ሰኔ 15 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 173709 ጥር 16 ቀን 2009 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 140461

መስከረም 29 ቀን 2010ዓ.ም

ዳኞች፦

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች፦ አቶ ንጉሴ ዘርይሁን **-ቀረቡ**

ተጠሪ፦ የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን **-ወኪል አልቀረቡም**

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ፦ የስራ ክርክርን ይመለከታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 044/09 ጥር 30 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 138065 መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይህንኑ ፍርድ በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

በመዝገቡ ከተያያዙት የውሳኔ ግልባጮች መረዳት እንደሚቻለው የአሁኑ ተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ከድሲፕሊን ኮሚቴው የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ተመልክተው አመልካች ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ ባልታወቀ ምክንያት በስራ ገበታ ላይ አልተገኙም በማለት ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸው እንዲቋረጥ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ቅሬታውም በአጭሩ ከተጠሪ ፍቃድ ወስጄ እረፍት ላይ እያለሁ የጫማ ኢንፌክሽን እና የቁርጭምጭሚት ውልቃት ደርሶብኝ በህክምና ላይ መሆኔን አሳውቄ ተጠሪም እስከ ህዳር 30 ቀን 2007ዓ.ም ድረስ ደመወዝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከፈለኝ እና በህመሜም ምክንያት የመ/ቤቱን ማስታወቂያ መከታተል የማልችል መሆኔ እየታወቀ ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሌ እንዲቋረጥ መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ቢያዘውም ባለመቅረቡ የመከራከር መብቱ ታልፎ የይግባኝ ባይን ክርክር ሰምቶ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያስተላለፈው የስራ ስንብት ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምሮ አመልካች ከደረሰባቸው የጫማ ኢንፌክሽን እና የቁርጭምጭሚት ውልቃት አዳማ ሆስፒታል ታክመው ከህዳር 3/2007 እስከ ሚያዝያ 30/2007ዓ.ም ድረስ በህክምና ፍቃድ ላይ የነበሩ መሆናቸው፣ ሰኔ 2 ቀን 2007ዓ.ም ቁርጭምጭሚታቸው በብሎን ታስሮ እስከ ታህሳስ 6 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ በህክምና ክትትል ላይ የነበሩ መሆኑን፣ ነሀሴ 10 ቀን 2008ዓ.ም በተጻፈ አመልካች የስኳር ታማሚ እና በሶዶ ሆስፒታል ለ3ኛ ጊዜ ቀዶ ህክምና የተደረገላቸው እና በአዳማ ሆስፒታል በክትትል ላይ የሚገኙ መሆናቸውን እና መጋቢት 1ቀን 2008ዓ.ም እና ሚያዝያ 3ቀን 2008ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ከደረሰባቸው የጤና መታወክ የተሻላቸው መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ወደ ስራ እንዲያሰማራቸው ለተጠሪ የጠየቁበት ደብዳቤ እና ተጠሪ ሰኔ 2ቀን 2007ዓ.ም የጻፈላቸው የስንብት ደብዳቤ ግንቦት 23/2008ዓ.ም የደረሳቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ የአመልካችን የስራ ውል ለማቋረጥ ምክንያት ያደረገው አመልካች በስራ ገበታቸው አልተገኙም በማለት ታህሳስ 27/2007 እና ጥር 7/2007 ተደጋጋሚ ማስታወቂያ በማውጣት ሰኔ 2/2007 ዓ.ም በተጻፈ ከታህሳስ 17/2007ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሉ መቋረጡን የገለጸበት ደብዳቤ ግንቦት 23/2008ዓ.ም እንዲደርሳቸው በማድረግ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት አትቶ እና የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 42/5ን ጠቅሶ አመልካች በህክምና ላይ የነበሩ መሆናቸውን ለተጠሪ እንደገለጹ እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 42(3) መሰረት ለመጀመሪያዎቹ 3 ወራት ከሙሉ ደሞዝ ጋር፣ ለቀጣዩ 3 ወራት ከግማሽ ደሞዝ ጋር፣ ለመጨረሻዎቹ 2 ወራት ያለ ደሞዝ ተጠሪ ፍቃድ መስጠት ያለበት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከስራ ገበታቸው ከቀሩበት ከታህሳስ 17/2007ዓ.ም ጀምሮ 8 ወር ሲቆጠር እስከ ነሀሴ 16 ቀን 2007ዓ.ም ድረስ ተጠሪ አመልካችን የመጠበቅ ግዴታ ነበረበት በማለት ደምድሞ ከታህሳስ 17/2007ዓ.ም ጀምሮ አመልካች በነበራቸው የህክምና ፍቃድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት ለመጀመሪያዎቹ 3ወራት እና ቀጥሎ ላሉት 3 ወራት በአዋጁ መሰረት ክፍያ እንዲፈጽም፣ አመልካች የጠየቁት የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ላልተሰራ ጊዜ የሚከፈል አይደለም በማለት ውድቅ በማድረግ አመልካች ወደስራ ልመለስ ጥያቄንም በተመለከተ አመልካች ወደስራ ልመለስ በማለት ጥያቄ ያቀረቡት መጋቢት 1/2008ዓ.ም ሲሆን በአዋጁ መሰረት የአመልካች የስራ ውል ከሚቋረጥበት ነሀሴ 17/2007ዓ.ም በኃላ በመሆኑ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጠ፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሚያዝያ 10/2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት ተጠሪ ቀርቦ ባልተከራከረበት ባልጠየቀው ዳኝነት አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የኔን አቤቱታ ብቻ መርምሮ መወሰን ሲገባው ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡

ቅሬታቸው ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ውሳኔው እንዲፀና በመጠየቅ መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የጽሁፍ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ክርክሩ በተመራበት ሥርዓትም ሆነ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ስለመኖር አለመኖሩ መርምረናል፡፡

የአመልካች ቀዳሚ ቅሬታ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ቀርቦ ባልተከራከረበት የኔን ክርክር ብቻ መርምሮ መወሰን ሲገባው ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሲሆን አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ማጣራት አድረጎ የወሰነ በመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም እንዲባል ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ የድሲፕሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳቡን ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚያቀርበው ተገቢውን ማጣራት አድርጎ የምርመራውን ሙሉ ይዘት የሚያመልክት የምርመራ ሪፖርት በማዘጋጀት ስለመሆኑና፤ የምርመራው ውጤት የተከሳሹን ጥፋተኝነት የሚያረጋግጥ ከሆነ የውሳኔ ሃሳቡ ሊወሰድ የሚገባውን የቅጣት እርምጃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማመልከት እንደሚኖርበት፤ የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች የዲስፕሊን አፈፃፀምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት ለመደንገግ ከወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 77/1994 አንቀፅ 19 እና 49 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም በስር አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ክርክር ተጠሪ ቀርቦ ያልተከራከረ ቢሆንም አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሚመረምረው የዲሲፕሊን ኮሚቴው ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር አንጻር የሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን እና ያለመሆን ጋር በማገናዘብ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 347 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ተጠሪ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ቀርቦ ባይከራከርም ለዲሲፕሊን ኮሚቴው ክስ አቅርቦ ያስወሰነው እሱ ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ክርክር በኮሚቴው ውሳኔ ላይ ተያይዞ እንደሚገኝ አጠያያቂ ካለመሆኑም በተጨማሪ ይህንን አስመልክቶ የቀረበ ክርክር የለም፡፡

አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት በተመለከተ የፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 42(5) መሰረት ሰራተኛው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት እስካላጋጠመው ድረስ መታመሙን ለመ/ቤቱ ማሳወቅ እንዳለበት፣ በዚህ መልኩ መታመሙን ላሳወቀ የሙከራ ጊዜውን ለጨረሰ ሰራተኛ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 42(2) መሰረት ህመሙ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ባሉ ተከታታይ 12 ወር ውስጥ ለ8 ወራት ፍቃድ ሊሰጥ እንደሚገባ እና በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3)ላይም ለመጀመሪው የ3ወር ጊዜ ከሙሉ ደሞዝ ጋር ለሚቀጥለው 3 ወር ጊዜ ከግማሽ ደሞዝ ጋር ለተከታዩ 2 ወር ያለደሞዝ ፍቃድ ሊሰጥ እንደሚገባ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 79(1) ላይ በዚህ ጊዜ ውስጥ ወደ ስራ ለመመለስ ያልቻለ ሰራተኛ በህመም ምክንያት የስራ ውሉ ሊቋረጥ እንደሚገባ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በህመም ምክንያት ስራ ለመግባት ያለመቻላቸውን ለመ/ቤቱ ካሳወቁበት ከታህሳስ 17 ቀን 2007ዓ.ም ጀምሮ ህጉ እስሚፈቅደው 8ወር ጊዜ ድረስ በደሞዝ እና ያለደሞዝ ፍቃድ ሊሰጣቸው የሚገባ በመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ ያልተከፈላቸው ደሞዝ ታስቦ እንዲከፈላቸው አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ከወሰነ በኃላ የአመልካች ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄያቸው የቀረበው መጋቢት 1 ቀን 2008ዓ.ም ሲሆን የ8 ወር ጊዜው የሚያበቃው ነሀሴ 16 ቀን 2007ዓ.ም በመሆኑ ጊዜው ካለፈ በኃላ ያቀረቡት ወደስራ ልመለስ አቤቱታ በህጉ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሰኔ እና ይህንን ውሳኔ በትእዛዝ በማጽናት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያስችል የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ነጥብ ሳይኖር ይህ ችሎት የአመልካችን ቅሬታ የሚቀበልበትን መሰረታዊ ምክንያት አላገኘም፡፡

በመሆኑም ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት ይግባኙን በመሰረዝ የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 044/2009 ጥር 30 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 138065 መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትዕዛዝ የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ጊዜው ካለፈ በኃላ ያቀረቡት ወደ ስራ ልመለስ አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ በተሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁጥር 150947

ቀን 12/7/2010 ዓ/ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች - ሚሮና ኢንዳስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ - ጠበቃ ታደሰ ገመቹ ቀርቧል

ተጠሪ - ጫልቱ ዓለሙ፣ መሰረት አበራ፣ ብርቱካን ነገሥ እና አልማዝ አበበ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ሚሮና ኢንዳስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ ታህሳስ 16 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273118 ታህሳስ 2 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤት ከሳሾችና ተከሳሽ የተስማማንበት የምርት መጠን ከሳሾች መስራት አንደሚችሉና ሌሎችም ሰራተኞች እየሰሩ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ሳለ ተጠሪዎች ለመስራት እምቢተኛ በመሆናቸው የተሰናበቱ መሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ሆኖ ሳለ ህገወጥ ስንብት ነው ሲል መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በከሳሾች ያልቀረበውን ክርክር ራሳቸው በማንሳት የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.182 ድንጋጌ ውጪ ነው፡፡ ከሳሾች እንዲሰሩ የተፈለገው ምርት መጠን በ3 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ብቻ የሚሰሩት ሆኖ እያለ ከአቅማቸው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በላይ ነው ተብሎ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቀ. 377/96 አንቀጽ 61(1) ውጪ መወሰኑ አለአግባብ በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር ከሳሽ የአሁን ተጠሪዎች ጫልቱ ዓለሙ፣ መሰረት አበራ፣ ብርቱካን ነገሎ እና አልማዝ አበበ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ. የበረክ ወረደ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ሚሮና ኢንዳስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከሳሾች ካለጥፋታችን ጥር 29 ቀን 2009 ዓ/ም ከዚህ በፊት ሰርተን የማናውቀውን ከአቅማችን በላይ እንድንሰራ ሲነገረን ከአቅማችን በላይ ነው ስላልን ከስራ ያሰናበተን በመሆኑ ሊከፈለን የሚገቡ ክፍያዎችን ይከፈለን ሲሉ ክስ መስርተዋል፡፡ ተከሳሽም ከሳሾች ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቀ. 377/96 አንቀጽ 27(1ረ) መሰረት ስራ ለመስራት ችሎታ እያላቸው የስራው ውጤት በብዛትና በጥራት ላይ ከተስማማነው በታች በመስራታቸው ካለማስጠንቀቅያ ተሰናብተዋል፡፡ ከሳሾች እንደ ድርጅቱ እቅድ የቦልጋም ምርት 8 ዙር ከሬሜላ 11 ዙር እንዲያመርቱ ተስማምተን ሲሰሩ ቆይተው በኋላ አንሰራም በማለታቸው ካለማስጠንቀቅያ መሰናበታቸው ህጋዊ ስንብት በመሆኑ ክሳቸው ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የስር በኦሮሚያ ብ/ክ/መ. የበረክ ወረደ ፍ/ቤት አራት መዝገቦች የመ/ቁጥር 27507፣ 27548፣ 27506 እና 27509 በአንድ በማጣመር የመረመረ መሆኑን ገልጾ በመ/ቁጥር 27509 ላይ ሰኔ 8 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ተከሳሽ ከሳሾች ቦልጋም 8 ዙር ከረሜላ 11 ዙር ሲያመርቱ ቆይተው አንሰራም በማለታቸው ምርት ቀንሶብናል ቢልም ከ2000 ዓ/ም እስከ 2006 ዓ/ም ባሉት ጊዜያት ከ4 እስከ 7 ዙር ምርት ስያመርቱ እንደነበር የተረጋገጠ እንጂ ምርት እየቀነሰ የመጣ አይደለም፡፡ ተከሳሽ ምርት ለመጨመር ከፈለገ ማሽንና ሰራተኛ በመጨመር እንጂ ባለው ሰራተኛ ከአቅም በላይ በማሰራት አይደለም፡፡ ተከሳሽ ከሳሾችን ከአቅማችን በላይ ነው ስላሉ ብቻ ሳያረጋግጥ ከስራ ማሰናበቱ ህገወጥ ነው፡፡ ለከሳሾች ሊከፍል ይገባል ያለውን በማስላት እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ ከሳሽ የአሁን አመልካች ለፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ የፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 29694 አከራክሮ መስከረም 25 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ አሰሪው ማምረት ያለበት ምርት ኮታ ማውጣት፣ ለማምረት የሚያግዙ ዘመናዊ መሳሪያዎችን ማመቻቸት ብቻ ሳይሆን ከሚፈለገው ምርት ጥራትና መጠን በታች የሚሰራ ሰው ካለ የተለያዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጠና በመስጠት ምርታማነት መጨመር እያለበት ሌሎች ቡድን ስላመረቱ ብቻ ከሳሾችም ማምረት አለባቸው በሚል ከከሳሾች የቀረበውን ሀሳብ ባለመቀበል ከሳሾችን ከስራ ማሰናበቱ ህገወጥ የስራ ስንብት ነው መባሉ ባግባቡ ሲሆን ከሳሾች ሁሉም የጡረታ ዋስትና ተጠቃሚ መሆናቸው ተረጋግጦና ከሳሾችም ያልካዱ ሆኖ እያለ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ስህተት ነው ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማሻሻል ክፍያውን አስተካክሎ ወስኗል፡፡ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን አቅርቦ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273118 አከራክሮ ታህሳስ 2 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ከሳሾች ተከሳሽ እንደሚለው 8 ዙር ቦልጋም እና 11 ዙር ከረሜላ ሰርተው እንደማያውቁ እየተከራከሩ ሲሆን በስር ፍ/ቤትም የተሰሙት የግራ ቀኙ ምስክሮች ይህንኑ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ ከሳሾችን ከአቅማቸው በታች ሰርተዋል በማለት ከስራ ማሰናበቱ ማስረጃ ያልተደገፈና የህግ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት አይደለም ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ ተጠሪዎች በመደበኛ የስራ ሰዓታቸው ምርቱን በማሳደግ እንዲሰሩ በአመልካች የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ከአቅማችን በላይ ነው በማለት ለመስራት ፍቃደኛ አለመሆናቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የወሰኑበት አግባብ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 13(2) እና 27(1) አንጻር ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪዎች ጥር 4 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት ያቀረብነውን ክስ በማስረጃ አጣርቶ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት ተተርጉሞ የሰጠው ውሳኔ በመሆኑ ስህተት ያለበት አይደለም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይጽናልን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ጥር 24 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ተጠሪዎች እንዲሰሩ የሚፈልገውን 8 ዙር ቦልጋም እና 11 ዙር ከረሜላ መጠንና ጥራት ምርት ካሁን በፊት ተጠሪዎች አምርተው እንደማያውቁ እንድያውም የምርት መጠኑን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻሉ የመጡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪዎች ይህን 8 ዙር ቦልጋም እና 11 ዙር ከረሜላ መጠንና ጥራት ምርት ማምረት ስለመቻላቸው በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ ሰራተኞች በሙሉ እውቀታቸውና ብቃታቸው ሰርተውም እኩል የምርት ጥራትና መጠን ያመርታሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ አንደኛው ሰራተኛ ባመረተው ምርት መጠንና ጥራት መነሻነት ሌላውን ከአቅም በታች ሰርቷል ለማለት በቂ መሰፈርት አይሆንም ፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከአቅማቸው በታች መስራታቸው ባለማረጋገጡና ባላቸው እውቀትና ብቃት እያመረቱ ካለው ምርት በላይ እንዲያመርቱ በመጠየቃቸው እንዲያመርቱ የተጠየቁትን ምርት ለማምረት የሚቸገሩ መሆኑን በማሳወቃቸው የአሁን አመልካች ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑ ህገወጥ የስራ ስንብት እንደሆነ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273118 ታህሳስ 2 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ታህሳስ 17 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የበረሀ ወረዳ ፍ/ቤት የአፈጻጸም መ/ቁጥር 28532 የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የስር ፍ/ቤት እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይድረሳቸው ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የንግድ ሕግ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 139385

መጋቢት 12 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ መዋዕል ትኩዕ መርሻ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ ነገረፈጅ ፌቨን ቢኒያም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ከአክሲዮን ሽያጭ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ነው፡፡ የአሁን አመልካች /የሥር ከሳሽ/ ሰኔ 3 ቀን 2007 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ማኅበር /ለአሁን ተጠሪ/ አክሲዮን የመግዛት ፍላጎት እንዳላቸው አሳውቀው ተከሳሹም አክሲዮኖቹን ለመሸጥ የሚፈልግ አለ መጥተው መግዛት ይችላሉ በማለት ባደረገላቸው ጥሪ መሠረት ጥር 12 ቀን 2006 ዓ/ም የማኅበሩ አባል ከሆኑት ከአቶ ሰባጋዲስ ስዩም 3949 አክሲዮኖችን በመግዛት ብር 120,904.80 /አንድ መቶ ሃያ ሺህ ዘጠኝ መቶ አራት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም/ መክፈላቸውን፣ አቶ ሰባጋዲስ ስዩም እና ከሳሽ /የአሁን አመልካች/ ተከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ ባዘጋጀው የማዘዋወሪያ የውል ሰነድ ላይ ተፈራርመው ተከሳሽም በራሱ ማኅተም በማጽደቅ ዝውውሩን መመዝገቡን ገልጸው ተከሳሽ ማኅበር በ2006 ዓ/ም ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያከፋፈለውን ትርፍ ጨምሮ ሰርተፊኬት ላይ አስፍሮ እንዲሰጣቸው በቃልም ሆነ በጽሁፍ ቢጠይቁም ይህንን ለመፈጸም ፈቃደኛ ስላልሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተከሳሽ በአክሲዮን ማዘዋወሪያ የውል ሰነድ ላይ በራሱ ማኅተም ያጸደቀው የአክሲዮን ሽያጭ ከገዙዋቸው ግለሰብ በማስተላለፍ ወይም ከሚሸጣቸው አክሲዮኖች ላይ በመቀነስ መዝግቦ ሰርተፊኬት እንዲሰጣቸው ወይም አክሲዮኑን ለመግዛት ያወጡትን ገንዘብ ማግኘት ከነበረባቸው ትርፍ ክፍያ ጋር ብር 173,022.22 /አንድ መቶ ሰባ ሶስት ሺህ ሃያ ሁለት ብር ከሃያ ሁለት ሳንቲም/ ከነወለዱ እንዲከፍላቸው፣ ወጪና ኪሳራን እንዲተካ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ /የሥር ተከሳሽ/ ሰኔ 25 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ክሳሽ ያቀረቡት ማስረጃ የአክሲዮን ማስተላለፊያ ጥያቄ የሚቀርብበት ማመልከቻ ነው፣ ተከሳሽ ማኅበር የአክሲዮን ዝውውሩን አልመዘገበም፣ ለከሳሽም የሰጠው ማረጋገጫ የለም፣ ተከሳሽ ማኅበር በህጉ መሠረት ለመመዝገብ እና ለጠቅላላ ጉባዔ ለማቅረብ ሲያጣራ የሻጩ አክሲዮኖች ከሳሽ አክሲዮኖቹን ከመግዛታቸው በፊት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የታገደ በመሆኑ ዝውውሩ ሊፈጸም አልቻለም፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት 1ኛ/ ተከሳሽ ማኅበር ለከሳሽ ለ3949 አክሲዮኖች የአክሲዮን ሠርቲፊኬት ለከሳሽ ሊሰጥ ይገባል ወይስ አይገባም? 2ኛ/ የአክሲዮን ሠርተፊኬቱን የመስጠት ኃላፊነት የለበትም የሚባል ቢሆን ከሳሽ የጠየቁትን ክፍያ ተከሳሽ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሯል፡፡ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ ጥር 12 ቀን 2006 ዓ/ም የተደረገው የአክሲዮኖች ዝውውር ወይም ማስተላለፊያ ማመልከቻ ሠነድ ነው፡፡ በዚህ ሰነድ (መ) እና (ሠ) ሥር ዝውውሩን ያፀደቀው አካል ዝውውሩን ተቀብሎ የመዘገበው ሰው ስም እና ፊርማ ያረፈ፣ የተከሳሽ ማኅበር ማኅተም ያረፈበት ቢሆንም ይህ ሰነድ ግን በንግድ ህግ ቁጥር 331 /1/ እና 341 /2/ ሥር በአዛዥ ሁኔታ የተቀመጠውን በባለአክሲዮኖች መዝገብ የመመዝገብ ግዴታን የሚተካ ወይም ቀሪ የሚያደርግ አይደለም፡፡ በማመልከቻ ሰነዱ ላይ ዝውውሩ ፀድቋል ወይም ተመዝግቧል መባሉ ብቻውን ተከሳሽ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ከሳሽን በመመዝገብ ባለአክሲዮን አድርጓል የሚያስብል አይደለም፡፡ እነዚህ ተሸጡ የተባሉት አክሲዮኖችም ከሽያጭ ውሉ በፊት እንዳይሸጡ የእግድ ትዕዛዝ ከተሰጠባቸው ተከሳሽ ይህን ሁኔታ በመተላለፍ በአክሲዮኖች መዝገብ ዝውውሩን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መመዝገብ ግዴታ አለበት ሊባል አይችልም፡፤ ከሳሽ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ካልተመዘገቡ ደግሞ ተከሳሽ የአክሲዮን ሰርተፊኬት እንዲሰጥ የሚገደድበት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ ተከሳሽ የራሱን አክሲዮኖች ለመሸጥ ባልተስማማበት ሁኔታም ሌላ አክሲዮን በምትኩ እንዲሰጥ የሚጠየቅበትም ሆነ የሚገደድበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ከሳሽ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ጥያቄ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም በማለት ወስኗል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ከሳሽ አክሲዮኖቹን ለመግዛት ገንዘቡን የከፈሉት ለአቶ ሰባጋዲስ ስዩም ሲሆን እነዚህ ክፍያ የተፈጸመባቸው አክሲዮኖች የእግድ ትዕዛዝ ያለባቸው በመሆኑ ዝውውሩ ሊፈጸም አልቻለም፣ ይህ ከሆነ ደግሞ ክፍያውን እንዲከፍል መጠየቅ የሚቻለው ክፍያውን የወሰደውን አካል እንጂ ተከሳሽ ባለአክሲዮኑ በህጉ በተሰጠው መብት መሠረት አክሲዮኖችን ለመሸጥ በመጠየቁ ሁኔታዎቹን ስላመቻቸ ብቻ ክፍያውን ባልተቀበለበት ሁኔታ የሌላውን ሰው ኃላፊነት የሚወስድበት አግባብ የለም፣ ከዚህ በተጨማሪ የትርፍ ክፍያ ተከሳሽ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ባለአክሲዮን መሆኑ ለተረጋገጠ ሰው እንጂ እንዲሁም የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ እንዲከፍል ሊጠይቅ አይችልም፡፡ በመሆኑም ከሳሽ የጠየቁትን ክፍያ ተከሳሽ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ ሊከፍል አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈጽሞብኛል ያሉዋቸውን ቅሬታ ነጥቦችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ በዚህ ጉዳይ አከራካሪዎች አክሲዮኖች ለአመልካች ሊሸጡ የቻሉት ተጠሪ ባደረገው ጥሪ መነሻ ከመሆኑ አንጻር የሥር ፍርድ ቤቶች አክሲዮኖቹ እገዳ የነበረባቸው ናቸው በማለት ተጠሪን ከኃላፊነት ነፃ ማድረጋቸው መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ነሐሴ 1 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን የአመልካች ጠበቃም ጥቅምት 13 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን 1ኛ/ አመልካች ለገዙባቸው አክሲዮኖች ተጠሪ ሠርተፊኬት ሊሰጥ ይገባል ወይስ አይገባም? 2ኛ/ ሠርቲፊኬት ሊሰጥ አይገባም የሚባል ከሆነ አመልካች የከፈሉትን ገንዘብ ከነወለዱ ተጠሪ ሊመልስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉ ጭብጦች ተይዘው ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ተጠሪ ባደረገው ጥሪ መሠረት የአቶ ስባጋዲስ ስዩም አክሲዮን ድርሻ መግዛታቸውን ሲከራከሩ ተጠሪ ደግሞ በግለሰቦች የተያዙ የአክሲዮን ድርሻዎችን በተመለከተ ባለአክሲዮኖች መሸጥ በሚፈልጉበት በራሳቸው የሚያመጡትን የገዢ ማመልከቻ ተቀብሎ እና መርምሮ ለአጽዳቂ አካል ከማስተላለፍ ውጪ ገዢ እና ሻጭ የማገናኘትም ሆነ የማደራደር ሥራ እንደማይሰራ፣ ብሔራዊ ባንክ የሰነዶችና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የሚያጣራውን የምዝገባ ሥርዓት ተጠሪ ባንክ በውክልና እንዲሰራ በመመሪያ በሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት ተጠሪ ባንክም አቶ ስባጋዲስ ስዩም ከተባሉት የባንክ ባለአክሲዮን እና የአሁን አመልካች ተስማምተው በተጠሪ ጽ/ቤት በመቅረብ የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻ ቅጽ ሞልተው ለተጠሪ ባንክ ሲያቀርቡ የተቀበለ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ይህንን መከራከሪያ ብሔራዊ ባንክ ለባንኮች ታኅሳስ 20 ቀን 2001 ዓ/ም በቁጥር ሱዳ/ባሱመ/382/08 ካስተላለፈው መመሪያ አንጻር ተመልክተናል፡፡

በዚህ መመሪያ በግልጽ እንደተቀመጠው የተጠሪ የሥራ ድርሻ የሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት የሚያከናውነውን የማጣራት ሥራ በውክልና ማከናወን ነው፡፡ በመመሪያው የአክሲዮን ዝውውርን በተመለከተ በቁጥር 3 ሥር ከንዑስ ቁጥር 3.1.እስከ ንዑስ ቁጥር 3.6 የተቀመጠው ማናቸውም የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻዎች ለተጠሪ ባንክ በሚቀርቡበት ወቅት በተለይም በተራ ቁጥር 3.2 ላይ እንደተገለጸው የአክሲዮን ማኅበራቱ የአክሲዮን ዝውውር ጥያቄውን ተቀብለው በንግድ መዝገብ ላይ ከመመዝገባቸው እና ለ3ኛ ወገን ከማሳወቃቸው በፊት ማጣራት የሚገባቸውን ቅድመ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታዎችን ማጣራት እና ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ነው። በተያዘው ጉዳይ በአሁን አመልካች እና በአቶ ስባጋዲስ ስዩም መካከል ጥር 12 ቀን 2006 ዓ/ም የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻ ተፈርሞ ለአሁን ተጠሪ ባንክ ሲቀርብለት ሰነዱን ፈርሞ እና ማኅተም አድርጎ መቀበሉን ተጠሪ አይክድም። ተያይዞ ከቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ እንደተመለከትነው የቀረበውን የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻን መሠረት በማድረግ ባንኩ ማጣሪያ ሲያደርግ የአክሲዮን ዝውውር እንዲደረግ የቀረበው የአቶ ስባጋዲስ ስዩም የአክሲዮን ድርሻ በ2004 ዓ/ም ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተሰጠ እግድ ትዕዛዝ የታገደ መሆኑን ነው። የአሁን ተጠሪም ይህንን ለአመልካች ያሳወቀ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል። ይህንን የአሁን አመልካችም ክደው አልተከራከሩም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአክሲዮን ባለቤትነት የማጽደቅ ሥልጣን የጠቅላላ ጉባኤው እንጂ የተጠሪ ባንክ እንዳልሆነ በህግ የተደነገገ ነው። የአክሲዮን ባለቤትነት የሚመዘገበውም በጠቅላላ ጉባኤው ከፀደቀ በኃላ ነው። በዚህ ረገድ የተፈጸመ ስለመሆኑም አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ የለም። የአመልካች መከራከሪያ መሠረት የሚያደርገው የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻውን ተጠሪ ተቀብሎ በራሱ ፊርማና ማኅተም አረጋግጧል የሚል ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር በተመለከተ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው አመልካችና አቶ ስባጋዲስ ሥዩም ተፈራርመው ያቀረቡት የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻ የተጠሪ ባንክ አክሲዮን ማህበር ማኅተም ያረፈበት ቢሆንም ይህ ሰነድ ግን በንግድ ህግ ቁጥር 331 /1/ እና 341 /2/ ሥር በአዛዥ ሁኔታ የተቀመጠውን በባለአክሲዮኖች መዝገብ የመመዝገብ ግዴታን የሚተካ ወይም ቀሪ የሚያደርግ አይደለም፤ በአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻ ሰነዱ ላይ ዝውውሩ ፀድቋል ወይም ተመዝግቧል መባሉ ብቻውን ተጠሪ በባለአክሲዮኖች መዝገብ አመልካችን በመመዝገብ ባለአክሲዮን አድርጓል የሚያስብል አይደለም። ስለሆነም ተጠሪ ለአመልካች የአክሲዮን ባለቤትነት ሠርተፊኬት ለመስጠት የሚገደድበት ህጋዊ ሁኔታ የለም በማለት በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም።

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ከላይ በአንደኛው ጭብጥ በዝርዝር እንደተገለጸው በተጠሪ አክሲዮን ማኅበር ውስጥ ባለድርሻ የሆኑት አቶ ስባጋዲስ ስዩም እና አመልካች ተፈራርመው ያቀረቡትን የአክሲዮን ዝውውር ማመልከቻን ተጠሪ ሲያጣራ ከኢትዮጵያ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተጻፈው እግድ ምክንያት አክሲዮኑ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ የማይችል በመሆኑ የማጣራት ሂደቱን ባለማለፉ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ባልተወሰነበትና ባልፀደቀበት፣ በንግድ ህጉ መሠረት ምዝገባ ባልተደረገበት እንዲሁም ክርክር የቀረበበት ገንዘብ ለተጠሪ ባንክ ስለመሰጠቱ ወይም ገቢ ስለመደረጉ ማረጋገጫ ባልቀረበበት አመልካች የጠየቁትን ክፍያ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት በመሆኑ ሊከፍል አይገባም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት የወሰነውን ውሳኔ ስንመለከተው የሚነቀፍበት ምክንያት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለልም የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ በዝርዝር የተገለጹትን መሠረታዊ ነገሮችን በአግባቡ በማጤን የሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ.228396 በ13/4/2008 ዓ/ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.176245 ጥር 1 ቀን 2009 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ 348 /1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች የአክሲዮን ምስክር ወረቀት ሊሰጥ አይገባም፤ አመልካች የጠየቁትን ክፍያ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 127352

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ· አህመድ

አብርሃ መሰለ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡-

1. አቶ ታደሰ አይችሉህም
2. አቶ ደሳለኝ አስራደ
3. አቶ ንጉሴ አማረ
4. አቶ መስፍን በጋሻው

} የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-አቶ ዘውዴ ታደሰ -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአክሲዮን ማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄን አስመልክቶ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካቾቹ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18932 በ09/06/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 67288 በ13/08/2008 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪው በ19/04/2008 ዓ.ም. በተጸፈ ማመልከቻ እንደቀደም ተከተላቸው 1ኛ፣2ኛ፣5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች በነበሩት የአሁኖቹ አመልካቾች እና የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባልተደረጉት አቶ አባስ መሐመድ እና አቶ ገደፋው ጌጡ በተባሉ የስር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ላይ ክስ ያቀረቡት ከሳሽ እና ተከሳሾች በጋራ በመሆን የትምህርት ተቋማትን የማቋቋም ዓላማ ያለው አክታ ጠቅላላ ንግድ አክሲዮን ማህበር በመስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ማቋቋማቸውን፣በዚሁ መሰረትም ማህበሩ አክታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፍቶ በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ መሆኑን፣ማህበሩን በስራ አኪያጅነት የሚመሩትም ከሳሽ መሆናቸውን፣በማህበሩ እንቅስቃሴ ላይ ለመወያየት ከሳሽ በተደጋጋሚ ስብሰባ ቢጠሩም ተከሳሾቹ ለመገኘት ፈቃደኞች ሳይሆኑ መቅረታቸውን እና በትምህርት ቤቱ የስራ እንቅስቃሴ ምክንያት ከሳሽ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው በነበረበት ጊዜ እንኳ ተከሳሾቹ ስለጉዳዩ ቀርበው ያልጠየቁ መሆኑን እና እነዚህ ሁኔታዎችም በንግድ ሕጉ መሰረት ማህበሩን ለማፍረስ በቂ ምክንያት መሆናቸውን በመግለጽ ማህበሩ እንዲፈርስ እና አስተዳዳሪ ተሾሞለት ሂሳቡ እንዲጣራ እንዲደረግ እንዲወሰንላቸው በመጠየቅ ነው።

የስር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች በ10/05/2008 ዓ.ም.በሰጡት መልስ የከሳሹ ጥያቄ የእነርሱም ጥያቄ በመሆኑ በክሱ መሰረት ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌላቸው የገለጹ ሲሆን የአሁኖቹ አመልካቾች በበኩላቸው በ17/05/2008 ዓ.ም. በሰጡት መልስ ክሱ ሊቀርብ የሚገባው በማህበሩ ላይ እንጂ በእኛ በአባላቱ ላይ አይደለም፣ከሳሽ በተከሳሾቹ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የላቸውም የሚሉ የመቃወሚያ ነጥቦችን ካስቀደሙ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ስብሰባ የመጥራት ስልጣን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንጂ የከሳሹ አለመሆኑን፣ከሳሹ ስብሰባ ለመጥራት የሚያስችል ስልጣን ነበራቸው ቢባል እንኳ በሕጉ አግባብ ያከናወኑት ጥሪ አለመኖሩን፣የስብሰባ አለመደረግም ሆነ በቁጥጥር ስር ሲውል አልጠየቃችሁኝም በማለት ከሳሹ በክሱ የጠቀሷቸው ምክንያቶች በንግድ ሕጉ መሰረት አንድን ማህበር ለማፍረስ የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች አለመሆናቸውን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል።

ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦችን በብይን አልፎ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ክሱን ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አክሲዮን ማህበሩ ከተመሰረተበት መስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባም ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተካሄዶ እንደማያውቅ በተከሳሾቹ ያልተካደ መሆኑን፣እነዚህ ምክንያቶች ደግሞ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ14፣በንግድ ሕግ ቁጥር 217

https://t.me/ethiopianlegalbrief

(2)፣218 (2) እና 495 (3) መሰረት ማህበሩ እንዲፈርስ ለመወሰን የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች መሆናቸውን፣3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾችም በክሱ መሰረት ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌላቸው የገለጹ መሆኑን በዝርዝር አስፍሮ አክሲዮን ማህበሩ ትምህርት ቤት ከሚዘጋበት ሰኔ 30 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ እንዲፈርስ፣አስተዳዳሪ እንዲሾም እና ንብረቱ እንዲጣራ ውሳኔ ሰጥቶአል።በአሁኖቹ አመልካቾች ጠያቂነት ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በፍርድ ያጸናው ይህንኑ ውሳኔ ሲሆን አመልካቾቹ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አክሲዮን ማህበሩ ባልተከሰሰበት የማህበሩ አባላት ተከሰው ማህበሩ እንዲፈርስ የመወሰኑን አግባብነት ከንግድ ሕግ ቁጥር 495 ድንጋጌ አንጻር ተጠሪው ባሉበት ለመመርመር እንዲቻል ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል።

በዚህም መሰረት ተጠሪው በ19/04/2008 ዓ.ም.ባቀረቡት ክስ ማህበሩን ለማፍረስ የሚያስችል ነው በማለት የጠቀሷቸው ምክንያቶች ተጠሪው በማህበሩ ስራ አስኪያጅነታቸው ባደረጉት ጥሪ መሰረት የማህበሩ አባላት በስብሰባ ለመገኘት ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀርተዋል፣ ከማህበሩ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ተጠሪው በስራ አስኪያጅነታቸው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው በነበረበት ጊዜ የማህበሩ አባላት ቀርበው ስለጉዳዩ አልጠየቁም፣ዋስትና ለመግባትም ፈቃደኛነታቸውን አልገለጹም የሚሉ መሆናቸውን፣ማህበሩ ከተመሰረተበት መስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባም ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተከናውኖ አያውቅም የሚሉት ምክንያቶች በተጠሪው በኩል የቀረቡት በክስ ማመልከቻው ላይ ተገልጸው ሳይሆን ክሱ በተሰማበት ጊዜ በተደረገ ክርክር መሆኑን፣የስር ፍርድ ቤቶችም ማህበሩ እንዲፈርስ ለመወሰን የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች ናቸው በማለት የተቀበሉት ክሱ በተሰማበት ጊዜ በተጠሪው በኩል የቀረቡትን ምክንያቶች መሆኑን፣ማህበሩ ከተመሰተረበት መስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የተደረገ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድም ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አለመኖሩ በአመልካቾቹ ያልተካደ መሆኑን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና ይሁን እንጂ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ማህበሩ ያቋቋመው ትምህርት ቤት የስራ እንቅስቃሴ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በሆኑት ተጠሪ አማካይነት ሲከናወን የቆየ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።

የንግድ ሕጉ በአንድ በኩል ለሁሉም ዓይነት የንግድ ማህበራት ተፈፃሚነት ያላቸውን የማፍረሻ ምክንያት ያካተተ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ ዓይነት ንግድ ማህበር ካለው የተለየ ባህሪ አንጻር ለየማህበሩ ተፈጻሚ የሚሆኑ ተጨማሪ የማፍረሻ ምክንያቶችን አካቶ ይዞአል።በንግድ ሕጉ ስለ ንግዱ ማህበራት በጠቅላላው በሚናገረው ክፍል ከሚገኙት ቁጥር 217 እና 218 ድንጋጌዎች በተጨማሪ የአክሲዮን ማህበራት የሚፈርሱባቸው ምክንያቶች በንግድ ሕጉ በቁጥር 495 (1) ስር ተዘርዝረው ይገኛሉ።እነርሱም፡-

(ሀ) በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማኅበሩ እንዲቀጥል ካልተወሰነ በቀር በመመስረቻ ጽሁፍ የተወሰነው ጊዜ ሲደርስ፣

(ለ) ማህበሩ የተቋቋበት ስራ ሲያልቅ፣

(ሐ) በነገሩ መጥፋት ወይም የማህበሩ ጉዳይ (ዓላማ) ሊደረስበት የማይቻል ሲሆን፣

(መ) አስቀድሞ እንዲፈርሱ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ፈቅዶ ሲወስን፣

(ሠ) ከማህበረተኞቹ አንዱ ባቀረበው በቂ ምክንያት ማህበሩ እንዲፈርስ ፍርድ ቤቱ ሲያዝ

(ረ) በቁጥር 311 የተደነገጉት ውሳኔዎች እንደተጠበቁ ሆነው አክሲዮኖቹ ሁሉ በአንድ ማህበረተኛ እጅ ሲጠቃለሉ፣

(ሰ) የኪሳራ ክስ ሲጀመር እና

(ሸ) ከማህበሩ ዋና ገንዘብ ሶስቱ ሩብ ሲጠፋየሚሉ ናቸው።

ተጠሪው ካቀረቡት ክስ አንጻር ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል ለጉዳዩ አግባብነት ያለው “ከማህበረተኞቹ አንዱ ባቀረበው በቂ ምክንያት ማህበሩ እንዲፈርስ ፍርድ ቤቱ ሲያዝ” በሚል የተገለጸው ምክንያት ነው።ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ አክሲዮን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማህበሩ ባልተከሰሰበት የማህበሩ አባላት ተከሰው ማህበሩ እንዲፈርስ የመወሰኑን አግባብነት ከንግድ ሕግ ቁጥር 495 ድንጋጌ አንጻር ለማጣራት የሚል ነው።አንድ ማህበር እንዲፈርስ ክስ በሚቀርብበት ጊዜ እንደየክርክሩ ባህርይ እና እንደየአስፈላጊነቱ ማህበሩ የክርክሩ ተካፋይ መደረግ እንደሚገባው የሚታመን ቢሆንም ቁጥር 495 ድንጋጌ የማህበሩን የክርክር ተካፋይ መደረግ ጉዳይ አስመልክቶ የሚገልጸው ነገር የለም።በመሆኑም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባው ማህበሩ ከተመሰረተበት መስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የተደረገ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድም ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አለመኖሩ የአክሲዮን ማህበሩ እንዲፈርስ ለመወሰን የሚያስችል በቂ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ዓቢይ ነጥብ ነው።ከድንጋጌው አነጋገር እንደሚታየው ከማህበርተኞቹ አንዱ ባቀረበው በቂ ምክንያት ማህበሩ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፈርስ እንደሚችል ከመገለጹ በቀር በቂ ምክንያት ተብለው የሚወሰዱትን ሁኔታዎች ድንጋጌው ለይቶ አያመለክትም።በመሆኑም ማህበሩ እንዲፈርስ ለማድረግ የሚያስችል በቂ ምክንያት ነው በሚል ከማህበረተኞቹ በአንዱ የሚቀርበው ምክንያት በርግጥም በቂ መሆን አለመሆኑ በፍርድ ቤቶች በአግባቡ ሊጤን ይገባል።

በመሰረቱ የንግድ ማህበራት ለአባላቱ ትርፍ ከማስገኘት ዓላማ ባሻገር በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ገንቢ ሚና የሚጫወቱ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።የሕግ ጥበቃም አላቸው።በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የአክሲዮን ማህበር በትምህርት ዘርፍ የተሰማራ መሆኑ እና ትምህርት ቤት በማቋቋም ወደ እንቅስቃሴ የገባ መሆኑም ተረጋግጦአል።ይህም የማህበሩ ሕልውና ጉዳይ በተቀጣሪ ሰራተኞች፣በተማሪዎች እና በአካባቢው የትምህርት እንቅስቃሴ ላይ ጭምር በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ተጽዕኖ የሚኖረው መሆኑን የሚያመለክት ነው።በመሆኑም የማህበሩ መፍረስ አለመፍረስ ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ በቀረበ ጊዜ እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ከግምት መግባት የሚገባቸው መሆኑን እና ማህበሩ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚገባው ተከሰተ የተባለውን ችግር ማህበሩ እንዲፈርስ በመወሰን ካልሆነ በስተቀር በሌላ የሕግ አግባብ መፍታት ወይም ማስወገድ እንደማይቻል ሲረጋገጥ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ማህበሩ ከተመሰተረበት መስከረም ወር 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የተደረገ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባም ሆነ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ አለመኖሩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተረጋገጠ ቢሆንም ማህበሩ ያቋቋመው ትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ግን ስራ አስኪያጁ መደበኛ ባልሆነ መንገድም ቢሆን ከማህበሩ አባላት ጋር በሚያደርጉት ውይይት እየተከናወነ የነበረ መሆኑ ተረጋግጦአል። ተጠሪውም በክስ ማመልከቻቸው ስብሰባ ጠርቼ አባላቱ አልተገኙም ከማለት በቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ እንዲጠራ ጠይቀው የነበረ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም። የስር ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም። የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ እንዲጠራ ጠይቀው ነገር ግን ስብሰባ የመጥራት ስልጣን ያለው የማህበሩ አካል ስብሰባውን ለመጥራት ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ይህ መሆኑ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲከናወን ጥያቄ አቅርቦ ለማስወሰን የሚያስችል ከሚሆን በቀር በቀጥታ ማህበሩ እንዲፈርስ ለማድረግ የሚያስችል በቂ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው አይደለም። የሀዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርዱ ለይ በጠቀሰው የንግድ ሕግ ቁጥር 495 (3) ስር የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች የተረጋገጡ ስለመሆኑም መዝገቡ አያመለክትም። በመሆኑም ማህበሩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አለመደረግ ጉዳይ በሌላ የሕግ አግባብ ሊፈታ የሚችል ችግር ሆኖ እያለ በስር ፍርድ ቤቶች በቀጥታ አክሲዮን ማህበሩን ለማፍረስ እንደሚያስችል በቂ ምክንያት ተወሰዶ ማህበሩ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የንግድ ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ እና ማህበሩ የተቋቋበትን ዓላማ እንዲሁም የማህበሩ መፍረስ የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ውጤቶች ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18932 በ09/06/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 67288 በ13/08/2008 ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሮአል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ማህበሩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ወይም የማህበሩ የጠቅላላ ጉባኤ አለመደረግ በሌላ የሕግ አግባብ ሊፈታ የሚችል ችግር እንጂ በቀጥታ ማህበሩ እንዲፈርስ ለመወሰን የሚያስችል በቂ ምክንያት አይደለም በማለት ወስነናል።
3. ተጠሪውም ሆኑ የማህበሩ ሌላ አባል የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ወይም የማህበሩ የጠቅላላ ጉባኤ በፍርድ ኃይል እንዲከናወን ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም።
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ።
5. በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18932 የተያዘው ክርክር ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ01/10/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶአል።
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አበለት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 136030

ህዳር 20 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ምስራ መሐመድ፤ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.አቶ አብደላ፤ አሜ ቀረቡ

2 አቶ ፋሃሚ መሐመድ፣ በሌሉበት የታየ ነው

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የክርክሩ ምክንያት የአካል ጉዳት ካሳን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ በሆኑበት በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የ1ኛ ተከሳሽ /የአሁን 1ኛ ተጠሪ/ የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 32057 ኦሮ የሆነ በ2ኛ ተከሳሽ /በአሁን 2ኛ ተጠሪ/ ይሽከረከር የነበረ አይሱዙ መኪና በቀን 22/07/2007 ዓ/ም ከተፈቀደለት በላይ በፍጥነት በማሽከርከር ላይ እያለ ከግድግዳ ጋር በመጋጨት ድንጋይ ተፈናጥሮ የቀኝ አይኔ ላይ ጉዳት ስላደረሰብኝ የጉዳት ካሳ እና የተለያዩ ወጪዎችን ጨምሮ በድምሩ ብር 71,100.00 /ሰባ አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር/ ተከሳሾች የአሁኖቹ ተጠሪዎች/ እንዲከፍሉ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ /የሥር 1ኛ ተከሳሽ/ መኪናዬ የጭነት እንጂ የህዝብ አይደለም፣ ከሳሽ /የአሁን አመልካች/ በመኪናዬ አልተሳፈረችም በማለት ከተከራከሩ በኃላ መኪናው የሶስተኛ ወገን የኢንሹራንስ ሽፋን ስላለው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጣልቃ እንዲገባ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠይቀው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ መኪናው የሶስተኛ ወገን የኢንሹራንስ ሽፋን የሌለው መሆኑን በመግለጹና የሥር 1ኛ ተከሳሽም ማስረጃ ባለማቅረባቸው መድን ክክርክሩ እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን የአሁን 2ኛ ተጠሪም /የሥር 2ኛ ተከሳሽም/ ከሳሽን መጫናቸውን አምነው ጉዳት ግን እሳቸው በሚያሽከረክሩት መኪና እንዳልደረሰ ክደው በመከራከር ኃላፊነት የለብንም ብለዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪዎች /ተከሳሾች/ ኃላፊነት አለባቸው ብሎዋል፡፡ የጉዳት ካሳን በተመለከተ ግን አመልካች በማስረጃ አላስረዱም በማለት አልፎባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ወጪዎችን በተመለከተ ለህክምና፣ ለትራንስፖርት እንደዚሁም ለተለያዩ ነገሮች ከሳሽ /አመልካች/ ታወጣለች ተብሎ የተገመተ ብር 5,519.00 /አምስት ሺህ አምስት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር/፣ ክስ ለማዘጋጀት፣ ለኮፒ እና ለትርጉም በክርክሩ ምክንያት ታወጣለች ተብሎ የተገመተ ብር 3,500.00 /ሶስት ሺህ አምስት መቶ ብር/፣ ለሞራል ካሳ ብር 1000.00 /አንድ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 10,019.00 /አሥር ሺህ አሥራ ዘጠኝ ብር/ ተከሳሾች /ተጠሪዎች/ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች ይክፈሉ፡፡ የዳኝነት ክፍያ በተወሰነው ገንዘብ ታሪፍ ልክ ተከሳሾች/ተጠሪዎች/ ለከሳሽ /ለአመልካች/ እንዲከፍሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኗ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምሥራቅ ችሎት አቅርበው ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን ቀጥለውም አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ተዘግቶባቸዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመውብኛል ያሉዋቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ አመልካች ላይ የደረሰውን የአካል ጉዳት አስመልክቶ አግባብነት ያለው ህግ የትኛው ነው? የንግድ ህጉ ነው የሚባል ከሆነም የስሌቱ መጠን ከደረሰው ጉዳት አንጻር ከህጉ ቁጥር 598 (2) አኳያ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ይቅርብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው 1ኛ ተጠሪ ቀርበው ግንቦት 7 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ለመቀበል እምቢተኛ ሆነዋል ተብሎ ቃለ መኻላ ስለቀረበ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል። ለ1ኛ ተጠሪ መልስ አመልካች በቀን 05/10/2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል። አመልካች በ1ኛ ተጠሪ መኪና ላይ አልተሳፈሩም በማለት 1ኛ ተጠሪ ክደው ቢከራከሩም በወቅቱ መኪናውን ያሽከረክሩ የነበሩት 2ኛ ተጠሪ አመልካች በመኪናው ላይ ስለመሳፈራቸው አምነው ተከራክረዋል። ከዚህ በተጨማሪ የግራ ቀኙ ምስክሮችም አመልካች በ2ኛ ተጠሪ አማካይነት ይሽከረከር በነበረው በ1ኛ ተጠሪ መኪና ላይ ስለመሳፈራቸው ፣አመልካች በመኪና ላይ እንዳሉ ድንጋይ ዓይኔን መታኝ እያሉ ሲጮኹ እንደነበረ ከአመልካች ጋር አብረው ተሳፍረው ሲጓዙ የነበሩ ምስክሮች መመስከራቸውን ተያይዞ ከቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ተመልክተናል። ከዚህ በተጨማሪ ከድሬ ጮራ ሆስፒታል በቁጥር g/268424 በቀን 19/05/2008 ዓ/ም የተጻፈ የጽሁፍ ማስረጃ የአመልካች የቀኝ ዓይን ብሌን ቦታውን ለቋል፣በቋሚነት 48% ጉዳት ደርሶባታል ሲል ይገልጻል።

የምሥራቅ ሀረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ በአመልካች ዓይን ላይ ስለደረሰው ጉዳት ተጠሪዎችን ኃላፊ አድርጎዋቸዋል። ለወደፊት የታጣ ገቢ በማለት አመልካች የጠየቁትን ዳኝነት በተመለከተ ግን ከሳሽ ሥራቸው ምን እንደሆነ፣ እንደዚሁም ጤነኛ ሳሉ በወር ሲያገኙ የነበረው ገቢ ምን ያህል እንደሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ እና የተገለጸ ነገር የለም። እንደዚሁም ይህ በዓይናቸው ላይ የደረሰው ጉዳት ለወደፊት ሠርተው የሚያገኙትን ገቢ የሚከለክላቸው ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ነገር የለም በማለት በዚህ በኩል የተጠየቀውን ዳኝነት ውድቅ በማድረግ አልፎባቸዋል። ለተለያዩ ወጪዎች እና ሞራል ካሳ በድምሩ ብር 10,019.00 /አሥር ሺህ አሥራ ዘጠኝ ብር/ ተከሳሾች /ተጠሪዎች/ በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል። የአሁን የአመልካች ቅሬታ መሠረት የሚያደርገውም የጉዳት ካሳ ሳይወሰን በመታለፉ ምክንያት ነው። በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆን አለመሆኑን ከደረሰው ጉዳት እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር መመልከት ተገቢ ነው፡፡

በመሠረቱ ከላይ እንደተገለጸው በአመልካች ዓይን ላይ ጉዳት ስለመድረሱ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪዎችም ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ተደርገዋል፡፡ ይህ ኃላፊነት ሊታይ የሚገባው ደግሞ በንግድ ህጉ ስለ አጓዥ እና ተጓዥ በተደነገገው ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡ ምክንያቱም አመልካች ለመኪናው የትራንስፖርት ክፍያ ከፍለው ሲጓዙ በነበረበት ወቅት ድንጋይ ተፈናጥሮ በዓይናቸው ላይ ጉዳት በማድረሱ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የንግድ ህጉን መሠረት ያደረገና በውል ላይ የተመሰረተ ግንኙት በግራ ቀኙ መካከል ተመስርቷል ማለት ነው፡፡ የንግድ ህግ አንቀጽ 561 የማጓጓዝ ውል ማለት አጓጓዥ ዋጋ በመቀበል ሰውን፣ ጓዝንና እቃዎችን የተወሰነ ስፍራ ለማድረስ ግዴታ የገባበት ስምምነት ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የንግድ ህጉ አንቀጽ 595 ደግሞ አጓዥ ለመንገደኞች ያለበትን ኃላፊነት ያስቀምጣል፡፡ አጓዥ ከኃላፊነት የሚድንባቸው ምክንያቶች በአንቀጽ 596 ላይ የተቀመጡ ሲሆን የአጓዥ ኃላፊነት ከተረጋገጠ በአንቀጽ 599 ላይ የተመለከተው ልዩ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር የንግድ ህግ አንቀጽ 597 /1/ ላይ የተጎዳው ማንኛውም ዓይነት መንገደኛ ቢሆንም አጓዡ በአላፊነት ለአንድ መንገደኛ የሚከፍለው ገንዘብ መጠን ከ40,000.00 ብር /ከአርባ ሺህ ብር/ ሊበልጥ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ዓይን ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪዎች ኃላፊ መሆናቸው እስከተረጋገጠ ድረስ በንግድ ህጉ አንቀጽ 561 መሠረት በተመሰረተው በውል ግዴታ፣ በአንቀጽ 595 መሠረት በአጓዥነት ግዴታ መሠረት በአንቀጽ 597 /1/ ላይ የተደነገገውን ገንዘብ መጠን የመክፈል ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ የምሥራቅ ሀረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን አመልካች ሥራቸው ምን እንደሆነ፣ ጤነኛ ሳሉ በወር ሲያገኙ የነበረው ገቢ ምን ያህል እንደሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ እና የተገለጸ ነገር የለም፡፡ እንደዚሁም ይህ በዓይናቸው ላይ የደረሰው ጉዳት ለወደፊት ሠርተው የሚያገኙትን ገቢ የሚከለክላቸው ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ነገር የለም በማለት የደረሰው ድምዳሜ ከላይ የተመለከቱትን የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች ያገናዘበ ባለመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ ቀጥሎ ያሉት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይህንን ሳያርሙ ማለፋቸው ሲታይ የሚነቀፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለልም የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ነገሮችን በአግባቡ ሳያጤኑ በአመልካች ዓይን ላይ ለደረሰው ጉዳት ከሳ ሊከፈል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የምሥራቅ ሀረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.50296 በቀን 01/07/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 243965 በቀን 23/9/2008 ዓ/ም እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.248800 በቀን 29/2/2009 ዓ/ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች ዓይን ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪዎች ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የተወሰነው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. ለልዩ ልዩ ወጪዎች እና ለሞራል ካሳ በድምሩ ብር 10,019.00 /አሥር ሺህ አሥራ ዘጠኝ ብር/ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች እንዲከፍሉ ተብሎ የተወሰነው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. በንግድ ህግ አንቀጽ 561፣ 595 እና 597 /1/ መሠረት 40,000.00 /አርባ ሺህ/ ብር ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
5. ዳኝነት በተወሰነው ታርፍ ልክ ተጠሪዎች ይክፈሉ ብለናል፡፡
6. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጪ ኃላፊነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 134240

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ፍቃዱ በለጠ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አለሚቱ አድራሮ

2. ህፃን አማኑኤል ታምሩ

3. ህፃን ክብራለም ታምሩ ሞግዚት ወ/ሮ አለሚቱ አድራሮ } የቀረበ የለም

4. ወ/ሮ አሙሬ መሸ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎች በአመልካችና 2ኛ ተከሳሽ በነበረው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ላይ ያቀረቡት ክስ የአመልካች ንብረት የሆነው የሴ.ቁ 3-75918 ሲኖትራክ የጭነት መኪና በ03/05/2008 ዓ.ም ከጋምቤላ ወደ ቱፒ አሸዋ ጭኖ በመጓዝ ላይ እያለ በደቡብ ክልል ሸካ ዞን የኪ ወረዳ እርምጫ ቀበሌ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስሙ ጫቲ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ሲደርስ መንገድ ስቶ አቶ ታምሩ ገሊቶ መኖሪያ ቤት ላይ በመውጣት የ1ኛ ተጠሪ ልጅ የሆነውን ተሻለ ታምሩ የተባለውን ሌሊት በተኛበት ገጭቶ የገደለ በመሆኑ ይህ ሟች በግብርናና ንግድ ስራ ተሰማርቶ በሚያገኘው ገቢ ይጦራችን ስለነበረ በመሞቱ ምክንያት የተቋጠረውን ገቢ ለ1ኛ ተጠሪ ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ብር)፤ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 80,000.00 (ሰማንያ ሺህ ብር) በድምሩ 160,000.00 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ ብር) እንዲሁም ወላጅ አባታቸው አቶ ታምሩ ገሊቶም በ40 ዓመት እድሜያቸው በዚህ አደጋ ስለሞቱና ይጦራቸው ስለነበረ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ትምህርታቸውን እስከሚጨርሱ ብር 108,000.00 (አንድ መቶ ስምንት ሺህ ብር) እና 118,800.0 (አንድ መቶ አስራ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ብር) ለሁለቱ እንዲከፍሉ፤ 4ኛ ተጠሪ የሟች የአቶ ታምሩ ገሊቶ ወላጅ እናት የሆኑት ሟች ልጃቸው ለመጦሪና ለቀለብ ይሰጣቸው የነበረው ስለተቋረጠ ብር 51,000.00 (ሃምሳ አንድ ሺህ ብር) እሱ በመሞቱ የሞራል ካሳ ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) እና ለቀብር ማስፈፀሚያ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) በድምሩ ብር 499,800.00 (አራት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ብር) 2ኛ ተከሳሽ የጉዳት አድራሹ መኪና ባለቤት ከኢንሹራንስ ሽፋን ሰጭ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጋር ሆነው ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአመልካችና 2ኛ ተከሳሽ ከነበረው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት መልስ ተቀብሎ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ተከሳሾቹን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ተጠሪዎች በርትዕ ብር 236,000.00 (ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ብር) ሊከፈላቸው ይገባል፤ከዚህ ውስጥ 2ኛ ተከሳሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ ብር) ይክፈለው ቀሪ ብር 196,000.00 (አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር) አመልካች እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ይህንን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በትእዛዝ ሰርዞቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ህዳር 15 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎቸ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ጥር 2 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአመልካች ጥያቄ የጉዳት ካሳ መጠን የስር ፍርድ ቤቶች በርትዕ መወሰናቸው እንዲሁም የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ወንድማቸው ተሻለ ታምሩ ላይ በአመልካች መኪና በደረሰው የሞት ጉዳት ምክንያት የተቋረጠውን የመጦሪያ ቀለብ የመጠየቅ መብት ሳይኖራቸው አመልካች የጉዳት ካሳ እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095/1/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የሚጥስ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪዎች በኩል ደግሞ በጉዳቱ ምክንያት የተቋረጠባቸው ከፍተኛ የሆነ የመጦሪያና የቀለብ ገቢ በርትዕ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ህግን መሰረት ያደረገ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ ተጠሪ ልጃቸው ተሻለ ታመሩ ፤2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አባታቸው ታምሩ ገሊቶ እና ወንድማቸው ተሻለ ታምሩ በአመልካች መኪና ጉዳት ደርሶባቸው ህይወታቸው በማለፉ ምክንያት መጦሪያና የቀለብ ገቢ እንዲከፈላቸው የጠየቁ መሆናቸው፤የ4ኛ ተጠሪ ጥያቄ ደግሞ የሟች አቶ ታምሩ ገሊቶ ወላጅ እናት በመሆናቸው ካሳ የጠየቁ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በተመለከተ አከራካሪ አይደለም እንዲሁም ሟቾች በህይወት እያሉ በእርሻ ስራ፤በንብ ማነብና በንግድ ተሰማርተው ቤተሰቦቻቸው ያስተዳድሩ የነበሩ መሆናቸውና የተቋረጠ ቀለብና መጦሪያ መኖሩን ፍሬ ጉዳዩን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪዎች ለደረሰባቸው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከተረጋገጠ የጉዳት ካሳ የመክፈል ግዴታ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የካሳ መጠን ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታ መኖሩን ፍርድ ቤቱ ከተገነዘበ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2102 ድንጋጌ መሰረት በርትዕ መወሰን እንደሚቻል በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ አመልካች የካሳ መጠን አወሳሰን በተመለከተ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አጥብቀው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚከራከሩበት ነጥብ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በወንድማቸው ሞት ምክንያት ለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2095/1/ መሰረት መብት ሳይኖራቸው እንዲከፈላቸው የተሰጠ ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ በተጎጂው ላይ ከደረሰው የሞት አደጋ የተነሳ በራሳቸው ስም ሆነው በመተዳደሪያ ረገድ ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ የሚችሉት የተጎጂው ባል ወይም ሚስት፤ወይም ወላጆቹና ልጆቹ እንደሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.2095/1/ ይደነግጋል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸው መሰረት ያደረጉት አባታቸው አቶ ታምሩ ገሊቶ እና ወንድማቸው አቶ ተሻለ ታምሩ በአመልካች መኪና ጉዳት ደርሶባቸው በመሞታቸው ምክንያት ለተቋረጠባቸው መጦሪያና ቀለብ ገቢ እንዲከፈላቸው ነው፡፡ ወንድማቸው በመሞቱ ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ የሚያስችል መብት ሳይኖራቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ እያለ በአባታቸውና ወንድማቸው ሞት ምክንያት የተቋረጠባቸው መጦሪያና ቀለብ ገቢ አመልካች እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች የተቋረጠባቸው መጦሪያና ቀለብ ገቢ መኖሩን በማረጋገጥ የጉዳት ካሳ መጠን በርትዕ መሰረት በማድረግ መወሰናቸው በአግባቡ ሆኖ ነገር ግን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በወንድማቸው ሞት ምክንያት የጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብት ሳይኖራቸው ይህን ሳይለይ የተሰጠ ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12143 መስከረም 20 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04428 ጥቅምት 22 ቀን 2009ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በአባታቸው ላይ በደረሰው የሞት አደጋ ካልሆነ በስተቀር በወንድማቸው ላይ ከደረሰው የሞት አደጋ የተነሳ በራሳቸው ስም ሆነው በመተዳደሪያ ረገድ ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ አይችሉም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ስለሆነም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሟቾች አባታቸውና ወንድማቸው በመሞታቸው ምክንያት የተቋረጠባቸውን የቀለብና የመጦሪያ እንዲሁም የትምህርትና የህክምና ወጪ በርትዕ እያንዳንዳቸው ብር 80,000.00/ሰማንያ ሺህ ብር/ እንዲከፈላቸው የተሰጠ ውሳኔ ክፍል በማሻሻል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባው ለእያንዳንዳቸው ብር 40,000/አርባ ሺህ ብር/ በማለት ወስነናል፡፡
4. ተጠሪዎች ሊከፈላቸው ከሚገባ የሞት ጉዳት ካሳ፤የሞራል ካሳ እና ለቀብር ማስፈፀሚያ በድምሩ ብር 156,000.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ ብር/ ውስጥ 2ኛ ተከሳሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ብር 40,000.00 /አርባ ሺህ ብር/ እንዲከፍል ቀሪው ብር 116,000.00 (አንድ መቶ አስራ ስድስት ሺህ ብር) አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል ወስኗል፡፡
5. ከዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 20 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት በመ/ቁ.12143 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
6. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 137918

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- የድሬዳዋ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን -ዓቃቤ አቶ ዐቢይ ተሃድሶ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የዳሽን ባንክ አክሲዮን ማኅበር -ነ/ፈጅ አቶ አስራት አድማሱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የክርክሩ ምክንያት የካሳ ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበረ ሲሆን የክሱም ይዘት፡- ተከሳሽ /የአሁኑ አመልካች/ አውጥቶ ለነበረው የግንባታ ሥራ ጨረታ አፈጻጸም ተጫራቹ ለሚያስይዘው የዋስትና ገንዘብ አመልካች በጻፈው ደብዳቤ ከዳሽን ባንክ የሚቀርብ ማንኛውም ዓይነት ዋስትና ተቀባይነት የለውም በማለት መግለጹ እና ይህንንም ለተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ማሳወቁ የተጠሪን መልካም ስም ያጠፋ በመሆኑና ባንኩም የደንበኝነት ቅድሚያ ክፍያ እንዲሁም የመልካም ሥራ አፈጻጸም ፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ሊያገኝ ይችል የነበረውን ብር 417,117.71 /አራት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰባ አንድ ሳንቲም/ እንዲከፍልና ለፈጸመው ህገ ወጥ ድርጊት ማስተባበያ እንዲሰጥ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ የተጠሪን /የከሳሽን/ ስም አንስተን ሳይሆን ለህንፃው ተቋራጭ የቅበላ ደብዳቤ በገለጽንበት ወቅት ዋስትናን ማስያዝ በተመለከተ ከዳሽን ባንክ ጋር ካለን የፍርድ ቤት ክርክር አንጻር የማንቀበል መሆኑን ከመግለጽ ውጪ የከሳሽን ስም አላጠፋንም፣ ስም ሳይጠፋ መልካም ስሜ ጠፍቷል በማለት ያቀረበው ክስ በመሆኑ መብትና ጥቅም የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካቀረበ በኃላ በአማራጭ በሰጠው መልስ ከባንኩ ጋር ፍርድ ቤት ክርክር ስላለን ኮንትራክተሩ ጨረታ በማሸነፉ የአሸናፊነቱን የሚገልጽ ዝርዝር ደብዳቤ ላይ ከዳሽን ባንክ የሚቀርብ የመልካም ሥራ ዋስትናን በተመለከተ የማንቀበል መሆኑን ገልጸናል፡፡ በግልባጭ እንዲያውቁት የተደረጉትም መ/ቤቶች ቢሆኑ ካለን የሥራ ግንኙነት በብድር የተገኘ ገንዘብ በመሆኑ ስለጨረታ አሸናፊ እንዲያውቁት የተጻፈ ደብዳቤ ከመሆኑ ባሻገር የስም ማጥፋት ተግባር ያልፈጸምን ስለሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩን የሰማው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የሥር ተከሳሽን / የአሁኑን አመልካችን/ ጥፋተኛ በማድረግ ከሳሽ /ተጠሪ/ የጠየቀውን ብር 417,117.71 /አራት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰባ አንድ ሳንቲም/ 9% ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል እና ወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብቱን በመጠበቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህን ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኑ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ሰርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ እንዲሁም የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ተፈጽሞብኛል ያላቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርቧል፡፡ አጣሪው የሰበር አቤቱታውን መርምሮ ቀደም ሲል ከተጠሪ ባንክ ጋር ክስ ስለነበረን ጉዳዩም በፍርድ ቤት እየታየ ባለበት ሁኔታ ከዳሽን ባንክ የሚቀርበውን ዋስትና አንቀበልም ማለቱ ስም ማጥፋት ነው የተባለበት አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል አዟል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ሚያዚያ 12 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን አመልካቹም በቀን 26/09/2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ተመርምሯል፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ባለው ደብዳቤ ላይ የአሁኑ አመልካች **"የቅበላ ደብዳቤ"** በሚል ርዕስ ሥር **"ማሳሰቢያ"** በማለት ከተጠሪ ባንክ ማንኛውንም ዓይነት ዋስትና አንቀበልም በማለት ስለመጻፉ በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ይህ የተጻፈው መልእክት የተጠሪን መልካም ስም ያጠፋ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ሊታይ ይገባል፡፡

ደብዳቤው የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴን ሌሎች ሰዎች እንዲጠራጠሩ የሚያደርግ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ማንኛውም ምክንያታዊ ሰው ከደብዳቤው ሊረዳ የሚችለው ባንኩ በሥራው፣በሙያውና በሚሰጠው አገልግሎት ብቃት እና ታማኝነት እንደሌለው ነው፡፡ አመልካች የባንኩን ዋስትና የማይቀበልበትን ምክንያት አብራርቶ ቢጽፍ ኖሮ ምክንያቱ ግልጽ ሊሆንና የሚያነቡም ሰዎች ሊረዱ ይችሉ ነበር፡፡ ነገር ግን ደብዳቤው በጥቅሉ የባንኩን ዋስትና አንቀበልም በማለቱ ለተለያየ ጥርጣሬ የሚጋብዝ፣ ከባንኩ ጋር ደንበኝነት ለመፍጠር የሚፈልጉ ቢኖሩ እንኳን ባንኩን እንዲጠራጠሩ የሚደርግ፣ የተጠሪ ድርጅት ሥራ እንዲቀዘቅዝና የተቋቋመለትን ዓላማ እንዳይወጣ መሰናክል የሚፈጥር እንደሆነ ለመገንዘብ ያስችላል፡፡ ደብዳቤው ለተጠሪ ብቻ ተጽፎ የቀረ ሳይሆን ለተለያዩ አካላት ግልባጭ የተደረገ ነው፡፡ ይህ ደብዳቤ የደረሳቸው አካላት ከባንኩ ጋር የውል ግንኙነት ለማድረግ ቢፈልጉ የተላለፈው መልእክት ከፍተኛ ጥያቄን የሚፈጥርባቸው እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ አመልካች ይህን ደብዳቤ ሲጽፍ ግልባጭ ያደረገው ከአመልካች ጋር የሥራ ግንኙነት ያላቸው አካላት በመሆናቸው ነው በማለት ቢከራከርም በተጠሪ ላይ የሚያስከትለውን ውጤት በአግባቡ ማጤን ሲገባው ሳያጤን የጻፈው ደብዳቤ በመሆኑ በዚህ አኳኋን ሊስተባበል የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ደብዳቤውን የጻፈው ከተጠሪ ጋር በፍርድ ቤት ክርክር ስላለ ነው ይበል እንጂ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው የተጻፈው ደብዳቤ ይህንን አይገልጽም፡፡ ይህን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተመለከተ ተጠሪ ለዚህ ችሎት በሰጠው መልስ በአመልካች እና ጣና ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር መካከል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች የውል ጥሰት ፈጽሟል በሚል ባቀረበው ክስ በአመልካች ስም ተጠሪ ዘንድ ያለው የዋስትና ገንዘብ እንዳይከፈል እግድ እንዲሰጥለት ባንኩን 2ኛ ተከሳሽ አድርጎ ያቀረበ ክስ መሆኑን፣ ጉዳዩን ሲያይ የነበረው ፍርድ ቤት ክስ ከመስማቱ እና ክርክር ከመደረጉ በፊት በባንኩ ዘንድ ያለን ገንዘብ ለማሳገድ ካስፈለገ የእግድ አቤቱታ ከማቅረብ በቀር ባንኩን ተከሳሽ አድርጎ ማቅረቡ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ነው በሚል ክሱ ከኪሳራ ጋር አሰናብቶናል በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ አመልካች ይህንን መከራከሪያ በመልስ መልሱ በአግባቡ አላስተባበለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ከተጠሪ ጋር ክርክር ስለነበረን የጻፍኩት ደብዳቤ ነው በማለት አመልካች የሚያቀርበው ማስተባበያ ተገቢ አይደለም፡፡

በመሠረቱ የባንክ ሥራ ከፋይናንስ እንቅስቃሴ እና ለደንበኞቹ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር እጅጉን የተቆራኘ በመሆኑ በሥራ አፈጻጸሙ ላይ ያለው መልካም ስም የህልውናው መሠረት ነው፡፡ ህጉም ለዚህ መልካም ስም ጥበቃ ያደርጋል፡፡ ይህን መልካም ስም የሚያጎድፍ ተግባር መፈጸም ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ ይህም በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 2109 ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከላይ በግልጽ እንደተመለከተው አመልካች የጻፈው ደብዳቤ የተጠሪን መልካም ስም የሚነካ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህን ተመልክቶ አመልካችን ኃላፊ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡

በሌላ በኩል ካሳን በተመለከተ ተጠሪም በዚህ ደብዳቤ ምክንያት የደንበኝነት ቅድሚያ ክፍያ እንዲሁም የመልካም ሥራ አፈጻጸም ፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ሊያገኝ ይችል የነበረውን ብር 417,117.71 /አራት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰባ አንድ ሳንቲም/ እንዳጣ ገልጾ አመልካች እንዲከፍል ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶችም ተጠሪ የጠየቀውን ብር አመልካች እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን በአመልካች ላይ የደረሰውን ትክክለኛ ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ የማያስችል በሆነበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤት የተጠየቀውን ብር እንዳለ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ካሳው በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 2102 መሠረት ሊወሰን የሚገባው በርትዕ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መልክ አይቶ ያለመወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ካሳው ሊሰላ የሚገባው በርትዕ ነው ብለናል። በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1.የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በከ/መ/ቁ. 227957 በቀን 02/02/09 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በከ/መ/ቁ.180632 በቀን 04/05/2009 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሻሽሏል።

2.አመልካች ለተጠሪ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 2102 መሠረት በርትዕ ብር 50,000.00 /አምሳ ሺህ ብር/ ካሳ ሊከፍል ይገባል ተብሎ ተወስኗል።

የዚህ ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻሉ።

3.የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው።

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 137589

ሕዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡-በደሴ ከተማ የአራዳ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት -ዓ/ሕግ መላት መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.ወ/ሮ ዘይነባ ሰይድ -የቀረበ የለም

2.አቶ ቴዎድሮስ ፍቅሩ---የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አለአግባብ የተከፈለ ነው የተባለን ገንዘብ ለማስመለስ ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12630 በ08/11/2007 ዓ.ም.የተሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ አመልካችን ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ለክሱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ በማድረግ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22278 በ13/03/2008 ዓ.ም.የሰጠው እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01-03707 በ28/11/2008 ዓ.ም. በፍርድ፣እንዲሁም በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-15588 በ05/05/2009 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

1ኛ ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት በደሴ ከተማ በአራዳ ክፍለ ከተማ በቁጥር A-462 የተመዘገበ ቤት ከወ/ሮ ዘሀቡ ሁሴን ገዝተው ውሉን 1ኛ ተከሳሽ ለነበረው የአሁኑ አመልካች ሲያቀርቡ ቤቱ በባለሙያ በብር 276,644.50 በመገመቱ ለስም መዛወሪያ መክፈል የሚገባቸው ብር 13,832.20 ሆኖ ሳለ የአመልካች ሰራተኛ የሆነው የስር 2ኛ ተከሳሽ /የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ/ በማታለል ቁጥር 244271 በሆነው ደረሰኝ ላይ ብር 23,832.20 ጽፎ በመቀበል በፊደል ግን ብር 13,832.20 በሚል ሞልቶ የሰጣቸው መሆኑን እና በዚሁ አግባብ የስም ዝውውሩ የተፈጸመ መሆኑን ገልጸው አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ያለአግባብ የተቀበሉትን ገንዘብ ብር 10,000 በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሏቸው በመጠየቅ ነው፡፡2ኛ ተጠሪ ስላልቀረቡ ጉዳዩ የተሰማው በሌሉበት ሲሆን የአሁኑ አመልካች በበኩሉ ቀርቦ 2ኛ ተጠሪ በፈጸሙት ድርጊት በዲሲፕሊን ክስራ የተሰናበቱ መሆኑን እና ገንዘቡ ለ2ኛ ተጠሪ የግል ጥቅም የዋለ እንጂ ለአመልካች ገቢ ያልተደረገ መሆኑን ገልጾ በአመልካቹ ላይ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ድርጊቱ የተፈጸመው በሰራተኛው ጥፋት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (3) እና 2127 መሰረት አመልካች ኃላፊነት የለበትም በማለት የተጠየቀውን ገንዘብ 2ኛ ተጠሪ ብቻ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ውሳኔ አሻሽሎ አመልካችን ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ለክሱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ለማድረግ የቻለው 2ኛ ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸመው ስራውን በማከናወን ሂደት ውስጥ በመሆኑ አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (2) መሰረት ኃላፊነት አለበት በሚል ምክንያት ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ተጨማሪ ማጣራት ካደረገ በኃላ ይህንን ውሳኔ ሊያጸና የቻለው የክፍለ ከተማው የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና የስራ ሂደት በ02/06/2007 ዓ.ም. ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና ስራ ሂደቱ በዛፊው ደብዳቤ ለስም መዛወሪያ በ1ኛ ተጠሪ ስም ብር 23,832.20 ገቢ እንደተደረገ ያረጋገጠ ስለመሆኑ በተደረገው ተጨማሪ ማጣራት በመረጋገጡ አመልካቹ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (2) መሰረት ኃላፊነት አለበት መባሉ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ነው፡፡

በክልሉ ሰበር ችሎት በትዕዛዝ የጸናው ይኸው ውሳኔ ሲሆን አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ የመደረጉን አግባብነት ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (2) እና 2127 (1)

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሁም በመዝገብ ቁጥር 82154 ከተሰጠው የሰበር ገ/ኛ ውሳኔ አንጻር ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ የ2ኛ ተጠሪ መልስ የመስጠት መብት ታልፎ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው እና ጉዳዩም ለሰበር ክርክር ያስቀርባል የተባለው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2126 (2) እና 2127 (1) እንዲሁም በመዝገብ ቁጥር 82154 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በማድረግ ነው፡፡ተጠቃሹ ገ/ኛ ውሳኔ የመንግስት ሰራተኞች ናቸው የተባሉት ግለሰቦች ወደ ጉዳዩ ገብተው እንዲከራከሩ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነቱ የመንግስት ነው ወይስ የሰራተኞቹ ነው? ወይስ የሁለቱም ወገኖች ነው? የሚሉ ነጥቦች ተለይተው ውሳኔ እንዲያርፍባቸው በነጥብ የተመለሰን ጉዳይ የሚመለከት ነው፡፡በተጠቃሹ መዝገብ የመንግስት ተቋም ከነበረው አመልካች የቀረበው ክርክር ይዘትም የአመልካች ድርጅት ሰራተኞች ዕቃ አቅራቢ ከነበረው ተዋዋይ ወገን ጋር በመተባበር ለፈጸሙት ተግባር መንግስት ኃላፊ ሊሆን አይገባውም የሚል ይዘት ያለው መሆኑን በውሳኔው ላይ የሰፈረው የክርክሩ ይዘት ያመለክታል፡፡በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ የማይገባቸውን ክፍያ የፈጸሙት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር እና አመልካችን ለመጉዳት በማሰብ ስለመሆኑ በአመልካቹ በኩል የቀረበ ክርክር እና ማስረጃ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ የሚጠቁመው ነገር የለም፡፡በሰበር ደረጃም በዚህ ረገድ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ከዚህም በተጨማሪ በተያዘው ጉዳይ ተፈጸመ በተባለው ድርጊት ጉዳቱ የደረሰው በ1ኛ ተጠሪ ላይ እንጂ በመንግስት ላይ አይደለም፡፡በመሆኑም በሁለቱ ጉዳዮች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መለያየት አንጻር ገ/ኛ ውሳኔው ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት የሚኖረው አይደለም፡፡በሌላ በኩል የክፍለ ከተማው የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና የስራ ሂደት በ02/06/2007 ዓ.ም. ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና ስራ ሂደቱ በፃፈው ደብዳቤ ለስም መዛወሪያ በ1ኛ ተጠሪ ስም ብር 23,832.20 ገቢ እንደተደረገ ያረጋገጠ ስለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍርዱ ላይ አስፍሯል፡፡ አመልካች ይህ ደብዳቤ ሊጸፍ የቻለው 2ኛ ተጠሪ በሰጡት መረጃ መነሻ ነው የሚል ይዘት ያለው ክርክር ያቀረበ ቢሆንም በመሰረቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመንግስት ተቋማት ሰራተኞቻቸውን የመቆጣጠር እና የመከታተል ግዴታ ያለባቸው መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።ይህን ሳይፈጽሙ ቀርተው በተገልጋዮች ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ ጉዳዩ አይመለከተንም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም።አመልካች ከገንዘብ ጋር በተያያዘ የስራ መደብ ላይ ይሰሩ የነበሩት 2ኛ ተጠሪ ዋስ ለሚፈጽሙት ጥፋት ዋስ እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባው ነበር በማለት 1ኛ ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ላቀረቡት ክርክርም አመልካቹ በመልስ መልሱ ላይ የሰጠው ግልጽ ማስተባበያ የለም።በመሰረቱ ሊከፍል የማይገባውን ነገር የከፈለ ሰው እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2164 ስር ተመልክቷል። አመልካቹ ገንዘቡን የሚከፍል ከሆነም ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በሕጉ አግባብ መስርቶት የነበረውን የቅጥር ግንኙነት መሰረት አድርጎ በመጨረሻ ከ2ኛ ተጠሪ ማስተካት የሚችል ከመሆኑ በቀር ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ መሆን አይገባኝም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ጉዳይን የሚመለከት ነው ከሚባል በቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል።

ው ሳ ኔ

1. በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12630 በ08/11/2007 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ አመልካችን ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ለክሱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ በማድረግ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22278 በ13/03/2008 ዓ.ም. የሰጠው እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01-03707 በ28/11/2008 ዓ.ም. በፍርድ፣ እንዲሁም በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-15588 በ05/05/2009 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል።
2. በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12630 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ09/06/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 132017

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡- 1. አቶ ማቲያስ ወልደየስ
2. አቶ መሉሸዋ ጥላሁን } ጠበቃ ገለታ ደገፉ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ መላኩ መኬ ማዶ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 03-79472 አ.አ ሚኒባስ መኪናቸው ጥቅምት 5 ቀን 2006 ዓ.ም በ1ኛ አመልካች ይሽከረከር የነበረውና በ2ኛ አመልካች እና በስር 3ኛ ተከሳሽ የሆነው ኖህ የደረቅ ጭነት አ.ማ ተመዝግቦ የሚገኘው የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 03-27047 ኢት የተሳቢ ቁጥር 03-03870 ኢት የሆነው መኪና ላይ የተጫነው ኮንቴይነር በመልስ ሰጪ መኪና ላይ ወድቆ ከባድ ጉዳት በማድረሱ የስር ከሳሽ መኪናው የደረሰበት ጉዳት ለማስገመት ያወጣውን ብር 5,500.00 (አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) አደጋው የደረሰበት የሰሌዳ ቁጥር 03-79472 አ.አ የሆነውን ሊጠገን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማይችል በመሆኑ የመኪናው ከአደጋው በፊት የገበያ ዋጋው ብር 300,000.00 (ሶስት መቶ ሺህ ብር) ጉዳት የደረሰበት መኪና የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን ይህ መኪና በአማካይ በቀን ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር) የሚያስገባ በመሆኑ ጉዳቱ ከደረሰበት ከጥቅምት 5 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ክስ እስከቀረበበት ሕዳር 10 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ለ35 ቀናት ያጣውን ብር 10,500.00 (አስር ሺህ አምስት መቶ ብር)፤ ከህዳር 11 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የስር ከሳሽ ያጣውን ጥቅም የቀን ገቢ ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር) በዚህ ክስ ምክንያት የወጣውን ወጪ እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች ለቀረበው ክስ የሰጡት መልስ በተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት መድረሱን አምነው 1ኛ አመልካች አደጋ የደረሰበት መኪና ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ጥገና ተደርጎለት ወደነበረበት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲመለስ እና ተጠሪ ያጣውን የእለት ገቢ እንዲያገኝ ተጠሪን ከአፍሪካ ኢንሹራንስ ጋር በማገናኘት መኪናው ከአደጋ በፊት ወደነበረበት እንዲመለስ የተለያዩ በመኪና ጥገና ላይ የተሰማሩ እና በአደጋ ገማች ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን በማወዳደር የአፍሪካ ኢንሹራንስ በ87,000.00 (ሰማንያ ሰባት ሺህ ብር) ሊጠገን እንደሚችል ካረጋገጠ በኋላ መኪናው እንዲጠገን ተጠሪን ቢጠይቅም ፍቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ መኪናው በወቅቱ ሳይጠገን ቀርቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ መኪናው ጠቅላላ የወደመ በማስመሰል ያቀረበው የመኪናው ጠቅላላ ዋጋ ተጠሪ መኪናው ተጠግኖ ወደነበረበት በመመለስ ያገኝ የነበረውን የእለት ገቢ በተጠሪ እምቢተኝነት በመቅረቱ ተጠያቂ አይደለንም፤ተጠሪ አደጋው የደረሰበት መኪና ተጠግኖ ወደነበረበት እንደሚመለስ በአፍሪካ ኢንሹራንስ ከተረጋገጠ በኋላ በሌላ ድርጅት አስገምቻለሁ ይከፈለኝ በማለት ያቀረበው ብር 5,500.00 (አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ተጠሪ አለአግባብ ለመበልጸግ ሊጠገን የሚችል መኪና አስቁሞ ያቀረበው ክስ በመሆኑ በክሱ ምክንያት ያወጣውን የዳኝነት፤የጠበቃ አበልና የተለያዩ ወጭዎችን የማንጠየቅ ስለሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልንና ከወጪ ኪሳራችን ጋር እንዲወሰንልን በማለት አፍሪካ ኢንሹራንስ ጣልቃ እንዲገባ ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአፍሪካ ኢንሹራንስ ጣልቃ እንዲገባ ካደረገ በኋላ ግራ ቀኙ በማከራከርና የስር ከሳሽን ክስ በመስማት ጥር 8 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት አደጋ የደረሰበት መኪና ሊጠገን እንደሚችል በመረጋገጡ ተሽከርካሪውን ለማስጠገን ብር 112,183.00 (አንድ መቶ አስራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት ብር) የተገመተበትን ብር 5,500.00 (አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ተጠሪ ያጣውን የእለት ገቢ ከጥቅምት 10 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ የአንድ ቀን ሰርቪስ ቀን በመቀነስ ብር 131,200.00 (አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) ተጠሪ የወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብቱን በመጠበቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካቾች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች ነሐሴ 19 ቀን 2008 ዓ.ም በዛፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ጥር 23 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአመልካች ደንበኛ የሆነው የአፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ ተሸከርካሪው አስፈላጊ ጥገና ተደርጎለት ከአደጋ በፊት ወደነበረበት እንዲመለስ ያደረገው ጥረት በተጠሪ እምቢተኝነት ምክንያት አለመሳካቱን ገልፀው እየተከራከሩ እያለ ይህ ሳይጣራ አመልካቾች የተቋረጠ ገቢ እንዲከፍሉ በስር ፍርድ ቤት የተወሰነው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት መድረሱን አምነው 1ኛ አመልካች አደጋ የደረሰበት መኪና ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ጥገና ተደርጎለት ወደነበረበት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲመለስ እና ተጠሪ ያጣውን የእለት ገቢ እንዲያገኝ ተጠሪን ከአፍሪካ ኢንሹራንስ ጋር በማገናኘት መኪናው ከአደጋ በፊት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደነበረበት እንዲመለስ የተለያዩ በመኪና ጥገና ላይ የተሰማሩ እና በአደጋ ገማች ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን በማወዳደር የአፍሪካ ኢንሹራንስ በ87,000.00 (ሰማንያ ሰባት ሺህ ብር) ሊጠገን እንደሚችል ካረጋገጠ በኋላ መኪናው እንዲጠገን ተጠሪን ቢጠይቅም ፍቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ መኪናው በወቅቱ ሳይጠገን ቀርቷል። ስለሆነም ተጠሪ መኪናው ተጠግኖ ወደነበረበት በመመለስ ያገኘ የነበረውን የእለት ገቢ በተጠሪ እምቢተኝነት በመቅረቱ ተጠያቂ አይደለንም በማለት ተከራክረዋል። ከዚህ በተጨማሪ በሥር ፍርድ ቤት በጣልቃገብነት ተከራካሪ የነበረው አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ ጉዳቱ እንደደረሰ መኪናው ተጠግኖ ወደነበረበት ለመመለስ ያደረገው ጥረት በተጠሪ ተቀባይነት እንዳላገኘ ገልፆ ተከራክሯል። ተጠሪ ይህንን የሚያስተባብል ክርክርና ማስረጃ ከሥርም ሆነ ከዚያ በኋላ በተደረገው ክርክር ያላቀረበ መሆኑን ተገንዝበናል። ተጠሪ ይህንን ገንዘብ በቅንነት በመቀበል ቀረብኝ የሚሉትን ገንዘብ ከአመልካቾች መጠየቅ የሚችሉበት እድል ነበራቸው። በተበዳይ ላይ ለደረሰ ጉዳት የሚከፈለው ካሣ ለቅን ልቦና ተቃራኒ በሆነ አኳኋን ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል። ተጠሪ አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ ከአመልካች ጋር ያለውን የመድን ውል መሠረት በማድረግ እንዲቀበሉት የጠየቃቸውን ብር 87,000(ሰማንያ ሰባት ሺህ ብር) በቅንነት ቢቀበል ገቢ በመቋረጡ ምክንያት የደረሰባቸውን ኪሣራ ሊያስቀሩት ወይም ሊቀንሱት የሚችሉበት አቅም ይፈጥርላቸው ነበር። ሌላ ሰው ኃላፊ በሆነበት ድርጊት ወይም አደጋ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱን ለማስቀረት ወይም የጉዳቱን መጠን ቀላል ለማድረግ ግዴታና ኃላፊነት እንዳለበት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 2 ተበዳዩ በማስተዋል ቢሠራ ኖሮ የደረሰበትን ጉዳት ሊያግደው ወይም ሊያቀለው የሚችል ሲሆን በደረሰበት ጉዳት መጠን በሙሉ ካሣ ለመጠየቅ አይችልም በማለት በግልፅ ደንግጎታል። ተጠሪ በግጭቱ ጉዳት የደረሰበት መኪና በወቅቱ ተጠግኖ ወደ ስራ ቢመለስ በአደጋው ምክንያት ያቋረጠባቸውን የገቢ መጠን ለመቀነስ እየቻሉ ለማስጠገን እንቢተኛ ለመሆናቸው ምክንያት ኪሣራውን ለማስቀረት ወይም ሊያቀሉት እንዳልቻሉ ለመገንዘብ ችለናል። በዚህ ምክንያት የተቋረጠው ገቢ መጠን መጨመር የተጠሪ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2098 /1/ መሰረት በከፊል ኃላፊነት አለበት ብለናል።

ሲጠቃለል ተጠሪ በመኪናው መውደም ምክንያት የተቋረጠባቸውን የገቢ መጠን ለመቀነስ ወይም ለማቅለል የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2097 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚደነግገው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት በቅን ልቦናና በአስተዋይነት ያደረጉት እንቅስቃሴ የሌለ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ያልሰጡ በመሆኑ ውሳኔያቸው በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና ሊሻሻል የሚገባው ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35023 ጥር 8 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 166426 ግንቦት 22 ቀን 2008 ዓ/ም በውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተጠሪ መኪና ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ለተቋረጠው ገቢ አመልካቾች ሙሉ ሐላፊነት የለባቸውም፤ተጠሪው ከፊል ሃላፊነት አለባቸው ብለናል፡፡
3. የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ መኪናቸው ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ተጠሪ ለተቋረጠባቸው ገቢ ብር 131,400 (አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ አራት መቶ ብር) አመልካቾች እንዲከፍሉ በማለት የሰጡትን ውሣኔ አሻሽለን አመልካቾች የተቋረጠ ገቢ ብር 65,700(ስልሳ አመስት ሺህ ሰባት መቶ ብር) 9% ወለድ ጋር የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው ብለናል፡፡ ተሸከርካሪውን ለማስጠገን ብር 112,183.00 (አንድ መቶ አስራ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሶስት ብር) 9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ፤የተገመተበትን ብር 5,500.00 (አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) አመልካቾች ለተጠሪ እንዲከፍሉ፤የስር ጣልቃ ገብ አፍሪካ ኢንሹራንስ ለተጠሪ ከሚከፈለው ገንዘብ ውስጥ ብር 90,781.30 (ዘጠና ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ አንድ ብር ከሰላሳ ሳንቲም) እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ እንዲሁም ተጠሪ የወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብቱን በመጠበቅ የተሰጠ ውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሠብ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 134836

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አባተ ሀይሉ -ጠበቃ አዲስ ለገሰ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. አቶ አስረስ ረታ

2. አቶ ኑርዬ ሰማው

3. አቶ የሽምቢ ሰማው } የቀረበ የለም፡፡

4. አቶ ሀይሉ ከበደ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በአማራ ብ/ክ/መ/ ሰሜን ወሎ ዞን ራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን ከ1-3 ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተጠሪዎች አሻሽለው ባቀረቡት ክስ እነዚህ ተጠሪዎች የሚች ዘመ· ሰማው ወንድምና እህት መሆናችን በመዝገብ ቁጥር 01027488 በህጋዊ መንገድ ወራሽነታችንን አረጋግጠናል፡፡ ሚች ዘመ· ሰማው ከመሞቷ በፊት ከ4ኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት ነበሩ፤ የንብረት አስተዳደራቸውንም አስመልክቶ በየግላቸው ይዘው ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ በቀን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

20/03/2006 ዓ.ም ለአመልካች በ108 ካ/ሜ ቦታ ውስጥ ያለው የግል መኖሪያ ቤቷን በኑዛዜ ካስተላለፈች በኋላ 4ኛ ተጠሪ ጋር ንብረታቸውን የጋራ ለማድረግ ተስማምተው ቆቦ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት በቀን 30/05/2006 ዓ.ም ማስረጃ ያወጡ ሲሆን በኑዛዜ ለማንም ያልተሰጠውንና በቆቦ ከተማ 01 ቀበሌ በክሱ በአዋሳኝ የተገለፀው 253 ካ/ሜ ቦታ በጋራ የሰሩትን አሜሪካን ሞድ ቤት ጓዳና ሳሎን ያለው እና አንድ ሰርቪስ በብሎኬት የተሰራ ግምቱ ብር 500,000.00/አምስት መቶ ሺህ ብር/ የሚያወጣው ድርሻ 126.5 ካ/ሜ ከፍሎ እንዲሰጠን እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን 4ኛ ተጠሪም ለአቤቱታው የሰጡት መልስ ክርክር የተነሰበት ንብረት ያረፈበት የመኖሪያ ቤት ከእናቱ እሚሆይ ሙሽራ አባይ በውርስ ያገኘው እና አሜሪካ ሞድ የተባለው ቤትንም ከሚች ጋር ከመጋባቱ በፊት በግሉ የሰራው መሆኑን ገልፆ የተከራከረ ሲሆን የአሁን አመልካች በበኩሉ በክርክር ጣልቃ እንዲገባ ጠይቆ ተፈቅዶለት አከራካሪው ቤት 4ኛ ተጠሪ እና ሚች ዘሙ ሰማው በወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት በመቅረብ በ20/03/2006 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ያስተላለፉልኝ በመሆኑ በውርስ ሊጠየቁት የማይገባ ፤ኑዛዜውም በህግ በተደነገገው ኑዛዜ በተሰጠበት አይነት ግልፅ ተግባር ያልተሻረ መሆኑን በመግለፅ ያቀረቡት የሚች ንብረት ያለኑዛዜ ወራሽነት ጥያቄ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ኑዛዜው ብዙ ሰዎች በአንድ ላይ ስለአደረጉት እና በተዘዋዋሪ መንገድ ተሽሯል በማለት የፍ/ብ/ህ/ቁ.858 እና 900/1/ በመጥቀስ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቦታና ቤት ለተጠሪዎች ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ከ1-3 ተራ ቁጥር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠቀሱ ተጠሪዎች ሚያዚያ 2 ቀን 2009ዓ.ም፤4ኛ ተጠሪ መጋቢት 28 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ የአመልካች ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው በብዙ ሰዎች የተደረገ ስለሆነ እና በተዘዋዋሪ መንገድ የተሻረ ስለሆነ የሚች ድርሻ ቤትና ቦታ ከ1ኛ-3ኛ ያሉ ተጠሪዎች በውርስ ሊተላለፍ የሚገባው ነው በሚል የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ ክርክር ከተነሰባት ቤትና ቦታ ውስጥ የሚች ድርሻ የሆነው ለአመልካች በኑዛዜ የተላለፈ ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባል የሚል ሲሆን ከ1ኛ-3ኛ ያሉ ተጠሪዎች ደግሞ ለአሁን አመልካችና ወንድሙ በቀን 20/03/2006 ዓ.ም ኑዛዜ ሲያደርጉ በየግል ንብረታቸው በተለየ ሰነድ መናዘዝ ሲኖርባቸው ነገር ግን ሚች ዘሙ ሰማው የግል ንብረት ላይ 4ኛ ተጠሪ በኑዛዜ ሰነድ ላይ በጋራ ኑዛዜ አድርጎ በመገኘቱ ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርገው መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔው የተሰጠው በዚህ ረገድ ሆኖ ሳለ አመልካች ግን ከኑዛዜው ውጭ ለአገልግሎት ጽ/ቤት የየግል ንብረታቸውን በስምምነት የጋራ ማድረጋቸው እና ካርታ እና ፕላን ማውጣቸው በዝምታ እንደተሻረ አድርገው ማቅረባቸው ፍፁም ከስር ፍርድ ቤቶች ጭብጥ እና ውሳኔ ጋር የማይገናኝ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ሙሉ በሙሉ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የ4ኛ ተጠሪ መልስ ለልጆቻቸው የተደረገው ኑዛዜ ሊሻር አይገባም በማለት የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተገቢ በመሆኑ በመግለፅ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው ለክርክር ምክንያት የሆነው ሚች ዘሙ ሰማው ከ4ኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት የነበሩ መሆናቸው፤የንብረት አስተዳደራቸውን በተመለከተ በየግላቸው ይዘው ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ ሚች የግል ንብረቷን አስመልክቶ በቀን 20/03/2006 ዓ.ም ለአመልካች በ108 ካ/ሜ ውስጥ ያላትን የግል መኖሪያ ቤቷን ከ4ኛ ተጠሪ ጋር በኑዛዜ ከአስተላለፈች በኋላ ከ4ኛ ተጠሪ /የስር ተከሳሽ/ ንብረታቸውን አስመልክቶ የጋራ ማድረግ እንዳለባቸው ተስማምተው በቆቦ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት በኩል በቀን 30/05/2006 ዓ.ም ማስረጃ ያስወጡ መሆናቸው ፍሬ ጉዳዩን የማጣራትና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ በመሰረቱ ኑዛዜ ጥብቅ የሆነ የግል ጠባይ ያለው መሆኑን በፍ/ብ/ህ/ቁ.857 ስር ተደንግጓል፤የሟች ጥብቅ የሆነ እራሱ የሚፈፀመው ስራ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.858 ስር ብዙ ሰዎች አንድ በሆነ ጽሁፍ ማናዘዝ የማይቻል መሆኑን ተመልክቷል፡፡ ይህንንም ከፍ/ብ/ህ/ቁ.880 እና ተከታዮቹ ጭምር ተንፀባርቋል፤ አሁን በተያዘው ጉዳይ ሟች ዘመዱ ሰማው እና 4ኛ ተጠሪ ለአመልካችና ለወንድሙ በአንድ የኑዛዜ ጽሁፍ ላይ በጋራ ተናዘዋል፤ይህ ደግሞ ከላይ እንደተመለከትነው ኑዛዜ ጥብቅ የሆነ ሟች ብቻውን እራሱ የሚፈፅመው በመሆኑ በጋራ መናዘዝ በፍ/ብ/ህ/ቁ.858 የተደነገገ በመሆኑ ኑዛዜው ፈራሽ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶችም ኑዛዜው በቀን 20/03/2006 ዓ.ም የተደረገው ኑዛዜ ህጋዊነትን አስመልክቶ በሟች ዘመዱ ሰማው የግል ንብረት ላይ 4ኛ ተጠሪ የሆነው በግል ንብረቷ ላይ በአንድ የኑዛዜ ሰነድ ላይ ተናዘዘው መገኘታቸው እና ከፍ/ብ/ህ/ቁ.858፤857 እና 880 እና ተከታዩ ድንጋጌዎች አንፃር በመመርመር ሟች ዘመዱ ሰማው እና 4ኛ ተጠሪ ለአመልካች እና ለወንድሙ በአንድ የኑዛዜ ፅሁፍ የግል ንብረቷን በአንድ ላይ ተናዘው በመገኘታቸው የስር ፍርድ ቤቶች ኑዛዜውን ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ መስጠታቸው የሚነቀፍበት ህጋዊ ምክንያት የሌለበት በመሆኑ አመልካች ክርክር ከተነሰባት ቤትና ቦታ ውስጥ የሟች ድርሻ የሆነው ለአመልካች በኑዛዜ የተላለፈ ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባል በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል ስር ፍርድ ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ ሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0107811 መጋቢት 1 ቀን 2008 ዓ/ም እና በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17313 ሚያዚያ 17 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-14318 ጥቅምት 29 ቀን 2009 ዓ/ም በውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. ከዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 8 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0127811 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል። ይፃፍ።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ/138286

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች ፡ 1ኛ. ጫሉሜ መለታ - ቀረቡ

2ኛ. ሶበቂ መለታ - ቀረቡ

ተጠሪ፡ ጫለሺ ቀልበሳ - ወ/ድንቁጣ ጉተማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የገጠር መሬት ይዞታ የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የከሳሾች (አመልካቾች) ክስ ይዘት ባጭሩ የአመልካቾች አባት እና እናት ይዞታ የነበረ የገጠር መሬት የተጠሪ ባለቤት ሟች ቀጀል መለታ ከመሞቱ በፊት ከአመልካቾች እናት ጋር በጋራ ይዞ ሲጠቀም የቆየዉን ወንድማቸው ከሞተ በኋላ ተጠሪ ምንም መብት ሳይኖራት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ለብቻዋ እየተጠቀመች ስለሆነ ስፋቱ 1.5 ሄክታር የሆነ የገጠር መሬት እንድትለቅ እንዲወስን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የተጠሪ መልስ ባጭሩ የአመልካቾች አባት ከሞቱ 17 ዓመት በላይ መሆኑን እናታቸውም ከሞቱ 10 ዐመት በላይ ስለሆነው የአመልካቾች ክስ በይርጋ ሊቋረጥ እንደሚገባ ይህም ቢታለፍ የአመልካቾች አባት እና እናት ይህንኑ ይዞታቸውን በስጦታ ለተጠሪ ባል ለሟች ቀጀላ መለታ አስተላልፈው በዚህ ይዞታ ባልና ሚስት እስከ 2004 ዓ.ም. በጋራ ሲጠቀሙ ቆይተው የተጠሪ ባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሞት በዚህ ይዞታ ላይ ተጠሪ በስሟ የይዞታ ማረጋገጫ አግኝታበት የያዘችው በመሆኑ አመልካቾች መብት የላቸውም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክራለች ።

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው የአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት ይዞታው መሠረቱ የአመልካቾች አባት እና እናት ስለሆነና ሚስት (ተጠሪ) ባሏን መውረስ ስለማትችል ይዞታውን ለአመልካቾች ትልቀቅ ሌላውን የጋራ (የባልና ሚስት) ንብረት መካፈል ትችላለች ሲል ውሳኔ ሠጥቷል ።

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝታ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበች ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ መሬቱ የአመልካች አባት እና እናት መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ ለተጠሪ ባል ስጦታ ስለመደረጉ ማስረጃ አልቀረበም ሲል የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በከፊል በማሻሻል ሚስት ከባለቤቷ ጋር ስትጠቀም ስለ ቆየች ከዚህ ይዞታ ላይ 1/8 ይገባታል ሲል ወሰኗል።

ተጠሪ ሁለተኛ ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረቧ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ክርክር የተነሳበት ይዞታ በ1983ዓ.ም የአመልካቾች አባት እና እናት ለተጠሪ ባል በስጦታ ማስተላለፋቸዉ ፤ በ1996 ዓ.ም የተጠሪ ባል መሬቱን በስሙ አስለክቶ ማሰረጃ ማግኘቱንና የተጠሪ ባል ከሞተ በኋላ ይዞታው በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣት መሆኑን በማስረጃ መረጋገጡን ጠቅሶ ይዞታው የተጠሪና የሟች ባለቤቷ ቀጀላ ሙለታ ሆኗል ሲል የኦሮሚያ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 9 እና በደንብ ቁጥር 151/05 አንቀጽ 10 መሠረት ተጠሪ ባለመብት ስለሆነች መሬቱን ልታካፍልም ሆነ ልትለቅ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል ። አመልካቾች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኙም ። ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው።

የአመልካቾች የሰበር ቤቱታ ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ መሬት የአመልካቾች ወላጆች ይዞታ የነበረ እና አመልካቾች ሲጠቀሙበት የነበረ ስለመሆኑ የወረዳው መሬት እና አካበቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ምላሽ በሰጠበት ሁኔታ የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት አመልካቾች ሚች ወንድማቸውን ለመውረስ ያቀረቡት ጥያቄ የለም ወንድማቸውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመውረስ የሚያስችል የሕግ መሠረት የለም ማለቱ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል ተጠሪ መልስ እንድትሰጥ ተደርጓል ።

የተጠሪ መልስ ይዘት ባጭሩ የአመልካቾች እና የተጠሪ ባል የአባት እና የእናታቸውን ይዞታ በ1999 ዓ. ም ድርሻ ድርሻቸውን የተከፋፈሉ መሆኑን ፤ አመልካቾች የሚች ወንድማቸው ድርሻ የሆነ የውርስ ንብረት ለመካፈል ዳኝነት አለመጠየቃቸውን እና የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማስረጃ መዝኖ የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የለውም በማለት ተከራክራለች ።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተመለከተ ሲሆን እኛም አቤቱታ በቀረበበት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስሕተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ መርመረናል።

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለዉ አመልካቾች ክስ ያቀረቡት የአባት እናታቸዉ ይዞታ የሆነ እርሻ መሬት ተጠሪ መብት ሳይኖራት ስለያዘች እንድትለቅ እንዲወሰንላቸዉ ነዉ።ተጠሪ በበኩሏ ይህንን መሬት የአመልካቾች አባት እና እናት በስጦታ ለባለቤቷ በመስጠታቸዉ ከባሏ ጋር በስማቸዉ የይዞታ ማረጋገጫ አዉጥተዉ ሲጠቀሙ እንደነበር እና ባለቤቷ ከሞተም በኋላ በስሟ ደብተር ተሰጥቷት እየተጠቀመች መሆኗን ጠቅሳ ተከራክራለች። ይህንን የፍሬነገር ክርክር በማስረጃ የማጣራትና የመመርመር ሥልጣን የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች የተለያየ ድምዳሜ ላይ የደረሱ ሲሆን ፍሬነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመርመር ረገድ የመጨረሻ ስልጣን የተሰጠዉ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ክርክር የቀረበበትን ይዞታ የአመልካቾች አባት እና እናት ለተጠሪ ባል በስጦታ ሰጥተዉ ተጠሪ እና ባሏ ለረዥም ዓመታት ሲጠቀሙ መቆየታቸዉን አረጋግጧል።

ስለሆነም አከራካሪዉ ይዞታ ሥረ-መሰረቱ የአመልካቾች አባት እና እናት መሆኑ በአስተዳደር አካል ቢገለጽም ለተጠሪ ባል በስጦታ መተላለፉን የስር ፍ/ቤት በማስረጃ አረጋግጧል ።በዚህ አኳኋን ባልና ሚስት ሲጠቀሙበት የኖሩትን ይዞታ ባል ማለትም የአመልካቾች ወንድም ስለሞተ ተጠሪ የመዉረስ መብት የላትም ሲሉ አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር አግባብነት ባለዉ የመሬት አጠቃቀም አዋጅ ሆነ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት መሰረት ተቀባይነት ያለዉ አይደለም ።በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተረጋገጡት የሴቶች የእኩልነት መብት አንዱ መሬትን በመጠቀም ፤በማስተላለፍ፤በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ የሚደነግገዉ አንቀፅ 35(7) ነዉ ። ይህንኑ ሕገ መንግስታዊ መብት ለማስፈጸም የወጣዉ የኦሮምያ የገጠር መሬት አዋጅ ቁ/130/99 አንቀጽ 6(13) እና ደንብ ቁ/ 151/05 አንቀጽ 15 ይዘት አንደሚያስገነዝበን ባልና ሚስት በጋራ ሲጠቀሙበት ቆይተዉ ጋብቻቸዉ በአንደኛዉ ተጋቢ ሞት ምክንያት ሲቋረጥ በህይወት ያለዉ ተጋቢ በሌላ ሕጋዊ ምክንያት መብቱ ካልተቋረጠ በስተቀር ይዞታዉ በስሙ ተመዝግቦ ደብተር እንደሚሰጠዉና በዚህ ይዞታ መጠቀም መብቱ እንደሚቀጥል ነዉ ።

በተያዘዉ ጉዳይ ቀደም ሲል ይዞታዉ ለተጠሪ ባል በስጦታ ተላልፎ በተጠሪና በባለቤቷ ስም ተመዝግቦ በጋራ ሲጠቀሙበት ቆይተዉ የተጠሪ ባል ሲሞት ከ2000ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ ሰም ተመዝግቦ ተጠሪ እየተጠቀመችበት ስለመሆኑ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማስረጃ አረጋግጦ ተጠሪ መሬቱን ልትለቅ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘንም ። በዚሁ አግባብ ተከታዩን ወስነናል ።

<u>ዉሳኔ</u>

1-የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/239515 ላይ በ 02/10/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/248943 በ27/03/2009ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ/348(1) መሰረት ጸንቷል ።

2-ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ.131677

ጥቅምት 28 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡..1. ዳኜ መላኩ

2. ተፈሪ ገብሩ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የወ/ሮ ጌጤ ካሳ ወራሾች ወ/ሮ ኤፌሶን ወልዴ እና ወ/ሮ አምሳለ ከተማ ወ/ሮ፤ ወ/ሮ

ኤፌሶን ወልዴ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡-.የኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ መሬትና አስተዳደር ጽ/ቤት ዐ/ህግ ሰይፈ ስላሴ ገሪማ ቀርበዋል

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.127492 በ16/10/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች እና በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት ወ/ሮ ጸዳለ ካሳ እና ወ/ሮ ገነት ካሳ የመቃወም ተጠሪዎች፣የአሁን ተጠሪ ደግሞ የመቃወም አመልካች ሆነው ሲከራከሩ ነበር፡፡ የአሁን ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት ባቀረበዉ አቤቱታ የመቃወም ተጠሪዎች የግራ ቀኞቸዉ አባት የሻለቃ ካሳ ሃይሉ በወረዳ 24 ቀበሌ 09 የቤት ቁጥር 622 ስፋቱ 942 ካ.ሜ ይዞታ በተመለከተ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ሳይኖራቸዉ ባለይዞታ አይደሉም፣ ይዞታዉ ሊስተናገድ የሚገባዉ በነባር ይዞታ ሆኖ ሳለ የመቃወም ተጠሪዎች በግልግል ዳኝነት ባደረጉት ስምምነት ይዞታዉን ሶስት ቦታ ተካፍለዉ በ29/10/1993 ዓ.ም ፍ/ቤቱ ስምምነቱን አጽንቷል፡፡ ስለዚህ ይህ ዉሳኔ እንዲሻርልን፣ እስከ 500 ካ.ሜ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በነባር ይዞታ እንዲወስዱ እና ቀሪዉን 434 ካ.ሜ ይዞታ ግን በሊዝ አዋጅ መሰረት ሊወስዱ ይገባል ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

የመቃወም ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ በታዘዘዉ መሰረት 1ኛ የመ/ተጠሪ /የአሁን አመልካች/ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ቤትና ቦታ የአባታችን ንብረት ሲሆን በአባታችን ስም ግብር እየገበርን፣ ካርታ ለመዉሰድ ጥያቄ አቅርበን እየተጠባበቅን እንገኛለን፡፡ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 6 /3/ መሰረት አዋጁ በዉርስ በሚተላለፍ ንብረት ላይ ተፈጻሚነት የለዉም፣ስለዚህ የቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መልስ ባለማቅረባቸዉ መብታቸዉ ታልፏል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በሰጠዉ ዉሳኔ የመ/ተጠሪዎች የንብረት ክፍፍል ስምምነት ያደረጉት በ1993 ዓ.ም ሲሆን ፍ/ቤቱም ይህን ስምምነት ያጸደቀዉ በ1993 ዓ.ም በመሆኑ፣ የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 በአንቀጽ 6 መሰረት በዉርስ በሚተላለፍ ይዞታ ወይም ቤት ላይ ተፈጻሚነት ስለሌለዉ በፍ/ቤት የግልግል ዳኞች ስምምነትን ያጸደቀዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.360 /2/ መሰረት ጸንቷል በማለት ወስኗል፡፡

የሥር የመቃወም አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን መልስ ሰጭዎች በስምምነት የተከፋፈሉት የዉርስ ሀብት የተባለዉ ይዞታ የሰነድ አልባ በመሆኑ የሰነድ አልባ ይዞታዎች ስርዓት ሊከተል ስለሚገባ ይዞታዉ በስምምነቱ መሰረት ሊካፈል የሚችል መሆን አለመሆኑ በባለሙያ ማጣራት አለበት በማለት የሥር ዉሳኔ በመሻር ለሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በይግባኝ በማየት የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡--ወላጅ አባታችን ይህን መኖሪያ ቤትና ቦታ በ1952 በዉል ገዝተዉ ቤቶችን ሰርተዉ በ1962 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸዉ አመልካችና የሥር የመ/ተጠሪዎች ወራሽነታችንን አረጋግጠን የቤቱና ቦታዉ ባለሀብት ሆነናል፡፡ ይህን ቤትና ቦታ ለመከፋፈል በእርቅ ስምምነት ለመጨረስ ተስማምተን በዚህ መሰረት ስምምነት አድርገን ፍ/ቤቱም ስምምነቱ ከሕግና ሞራል የማይቃረን መሆኑን በማረጋገጥ ስምምነቱን በማጽደቅ ክርክሩ ተቋጭቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡት መመሪያዎች ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት በባለሙያ እንዲጣራ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲሻርልን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልኝ ወጪዎችን ተጠሪ እንዲተካልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ አቤቱታ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘዉ መሰረት የአሁን ተጠሪ ህዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ያስነሳዉ ይዞታን በተመለከተ የባለሙያ አስተያየት በመቀበል ዉሳኔ እንዲሰጥበት ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱ በአግባቡ ስለሆነ እንዲጸናልን ኪሳራ እንዲከፈልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ በተመለከተ የክፍፍል ስምምነቱ ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑን በባለሙያ ሊጣራ ይገባል የመባሉን አግባብነት እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአመልካች ወላጅ አባትና አዉራሽ የሆኑት ሻለቃ ካሳ ሃይሉ ለረጅም አመታት ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ቤትና ቦታ ይዘዉ ሲኖሩበት እንደነበር እና የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንደሌላቸዉ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ሻለቃ ካሳ ሃይሉ ይህን ቤትና ቦታ በተመለከተ የይዞታ ምስክር ወረቀት ባይኖራቸዉም ይዞታዉ የዉርስ ሀብት ስለመሆኑ ሌሎች ሰነድ ማስረጃዎች መቅረባቸዉን እና ይዞታዉም ሰነድ አልባ እንደሆነ የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ሻለቃ ካሳ መሞታቸዉን ተከትሎ የአሁን አመልካች እና በዚህ ችሎት ባለዉ ክርክር ተካፋይ ያልሆኑት ወራሾች ወራሽነታቸዉን በማረጋገጥ ይህን የዉርስ ሀብት የሆነዉን ቤትና ይዞታ በ1993 ዓ.ም በእርቅ ስምምነት ተከፋፍለዉ ይህን ስምምነታቸዉን ደግሞ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበዉ ፍ/ቤቱም ስምምነቱን በሕጉ አግባብ በማየት ማጽደቁን የሥር ዉሳኔ የሚያመለክተዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ እንግዲህ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ የፍርድ መቃወም አቤቱታ አመልካችና ሌሎች ወራሾች በስምምነት የመንግስትን ይዞታ ስለተከፋፈሉ በነባር ይዞታ አግባብ እና በሊዝ አዋጁ መሰረት እንዲፈጸም ዳኝነት መጠየቁን ክርክሩ ያሳያል፡፡ አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት በዚህ ጉዳይ የሊዝ አዋጁ ተፈጻሚነት የለዉም የሚል ነዉ፡፡ ስለሆነም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና ይህን አዋጅ ተከትለዉ የወጡት መመሪያዎች ተፈጻሚነት አላቸዉ ወይስ የላቸዉም? ይህን አዋጅ መነሻ በማድረግ ይዞታዉ በባለሙያ ሊጣራ ይገባል መባሉ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚሉት ነጥቦች ናቸዉ፡፡

በዚህ መሰረት የአሁን አመልካች እና ሌሎች ወራሾች የወላጅ አባታቸዉ ሻለቃ ካሳ ሃይሉ ወራሾች መሆናቸዉን፣ ይህን ቤትና ይዞታ በእርቅ ስምምነት በ1993 ዓ.ም ተካፍለዉ ስምምቱም በዛኑ ዓመት በፍ/ቤት የጸደቀ መሆኑን እና ይዞታዉም በነባር ይዞታ አግባብ የሚታይ እንደመሆኑ መጠን የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 6 /3/ መሰረት ተፈፃሚነት ያለዉ ሆኖ አይገኝም፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 /1/ ሥር እንደተመለከተዉ ማንኛዉም ሰዉ የከተማ መሬትን በአዋጁ ከተደነገገዉ የሊዝ ሥርዓት ዉጪ መያዝ እንደማይችል ደንግጎታል፡፡ እንዲሁም ነባር ይዞታዎች ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 6 መሰረት ወደ ሊዝ ስሪት የሚቀየሩበትን ሁኔታዎች በዝርዝር ደንግጎ እናገኛለን፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አዋጅ ቁጥር 6 /3/ ሥር እንደተመለከተዉ በነባር ይዞታ ላይ ያረፈዉ ንብረት ባለቤትነት በዉርስ አግባብ የሚተላለፍ እንደሆነ በአዋጁ የተመለከተዉ የሊዝ ስሪት ተፈጻሚነት እንደማይኖረዉ በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ በነባር ይዞታ ላይ ያረፈዉ ንብረት በዉርስ የሚተላለፍ እንደሆነ ወደ ሊዝ ሥሪት ማስገባቱ ከአዋጁ ዓላማ ጋር የማይሄድና አዋጁ ተፈጻሚነት ሊኖረዉ እንደማይገባዉ ነዉ፡፡ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም አዋጁን ተከትለዉ የወጡት መመሪያዎች ደግሞ ከአዋጁ ሊቃረኑ ይችላሉ ተብሎም ስለማይገመት፣ በነባር ይዞታ ላይ ያረፈዉ ንብረት ባለቤትነት በዉርስ አግባብ ሲተላለፍ መመሪያዎቹም ተፈጻሚነት ሊኖራቸዉ አይችልም፡፡

በዚህ ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወራሾች ያቀረቡትን የእርቅ ስምምነት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.277 /1/ በሚደነግገዉ አግባብ ሕግንና ሞራልን የማይቃወም መሆኑን በማረጋገጥ በማጽደቅ ከመዝገቡ እንዲያያዝ ያደርጋል ተብሎ ይገመታል፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር በዚህ ድንጋጌ አግባብ አለመፈጸሙን የሚያረጋግጥ ነገር ስለማቅረቡ መዝገቡ አያመለክትም፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ተፈጻሚነት የሌለዉ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች ነባር ይዞታዎች ወደ ሊዝ ስሪት የሚገቡበትን ሂደት በመጥቀስ ይዞታዉ በስምምነት ሊካፈል የሚችል መሆን አለመሆኑን በባለሙያ ሊጣራ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይገባል በማለት የሰጡት ዉሳኔ የአዋጁን ዓላማና የተፈጻሚነት ወሰን ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለአሁን አመልካች እና ለሌሎች ወራሾች የተላለፈዉ በነባር ይዞታ ላይ ያረፈዉ የዉርስ ንብረት በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 721/2004 ተፈጻሚነት የሌለዉ ሆኖ ሳለ በዚህ አዋጅ መሰረት የዉርስ ሀብቱ ያረፈበት ይዞታ በስምምነት የሚካፈል መሆን አለመሆኑን ባለመ·ያ እንዲያጣራ በማለት የሰጡት ዉሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.165672 በ5/7/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.127492 በ16/10/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.37664 በ3/2/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 132518

ቀን መስከረም 22/2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1ኛ. ተክሉ አስፍሃ

2ኛ. ሃለቃ ደስታ ሃ/ስላሴ

3ኛ. አቶ ገ/ትንሳኤ ጸሃዬ

4ኛ. አቶ ልብሰ ማሪያም አሳይ

5ኛ. ወ/ሮ ንግስቲ ገብሩ

6ኛ. አቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/አረጋዊ

7ኛ. ወ/ሮ ዮዲት ግርማይ

8ኛ. አቶ ገ/መድህን አባይ

9ኛ. አቶ ሃይላይ ገ/አምላክ

10ኛ. አቶ ወ/ገሪማ ገ/መድህን

11ኛ. ቄስ እቡይ ገ/እግዚአብሔር

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ስብሃቱ ገ/መስቀል } አልቀረቡም

2ኛ. ወ/ሮ ብርሃን ገ/ማሪያም }

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾችን ጨምሮ 17 ሰዎች የፍርድ ባለመብቶች፣ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ ሲሆኑ 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳው ባለቤትና የመቃወም አመልካች ነበሩ፡፡ የፍርድ ባለመብቶች በተለያዩ መዝገብ በ 1ኛ ተጠሪ ላይ ያስፈረዱትን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ለማስፈጸም የባለእዳውን ንብረት ጠቁመው በመቀሌ ከተማ በቀዳማዊ ወያኔ የሚገኙ 1ኛ/ በምስራቅ ገበያ፣ በሰሜን ታደሰ ኪዳኑ፣ በምእራብ መንገድ፣ በደቡብ ኣጽበሃ የሚዋሰን በ 32 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤትና ቦታ፣ 2ኛ/ በምስራቅ ግደይ ገ/መድህን፣ በሰሜን ታደሰ ኪዳኑ፣ በምእራብ ኣርያ መለሰ፣ በደቡብ መንገድ የሚዋሰን በ 311.75 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤትና ቦታ በፍርድ ባለእዳው ስም የሚታወቅ መኖሩን ገልጸው ስላቀረቡ ለአፈጻጸሙ እንዲውሉ ተገምተው እንዲቀርቡ በስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ተሰጥቷል።

የአሁን 2ኛ ተጠሪ ከፍርድ ባለእዳው ጋር ከ 1967 ዓ.ም ጀምሮ በትዳር የኖሩና ለአፈጻጸም ተገምተው እንዲቀርቡ የተባሉ ንብረቶች በጋራ ያፈሯቸው መሆኑን ገልጸው አመልካቾች ያስፈረዱት በፍርድ ባለእዳው ላይ በመሆኑ ንብረቶቹ የሚሸጡ ከሆነ መብታቸው የሚነካ በመሆኑ በድርሻቸው ላይ የተሰጠው ትእዛዝ እንዲነሳላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ አቅርበዋል። የፍርድ ባለመብቶች ለመቃወሚያው በሰጡት መልስ ተጠሪዎች በትዳር በነበሩበት ወቅት 1ኛ ተጠሪ የገቡት እዳ እንደባልና ሚስት እዳ የሚታሰብ በመሆኑ ከባል ወይም ከሚስት የግል እና የጋራ ንብረት ሊጠየቅ እንደሚችል በንግድ ሕግ አንቀጽ 19 ተደንግጎ የሚገኝ በመሆኑና ተቃዋሚ ነጋዴ በመሆናቸው እንዲሁም ከደደቢት ብድር ተቋም ተጠሪዎች በጋራ ተበድረው ስለነበር የጋራ እዳቸው ነው። በተጨማሪም 1ኛ ተጠሪ ከስር 7ኛ የአፈጻጸም ክሳሽ የወሰዱት በቼክ የንግድ ፈቃድ ከመመለሱ በፊት ስለሆነ ያቀረቡት ተቃውሞ ውድቅ ተደርጎ አፈጻጸሙ ይቀጥልልን በማለት ተከራክሩ።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር መርምሮ የንግድ ፈቃድ ከመመለሱ በፊት ቼክ ቆርጫለሁ የሚለው ብቻውን እዳውን የጋራ እዳ ስለማያደርገው እዳው ለትዳር ጥቅም መዋሉ በማስረጃ የተደገፈ ነገር ባለመኖሩ 2ኛ ተጠሪ በቤትና ቦታዎቹ ላይ ያላቸው ግማሽ ድርሻ በዓይነት ወይም በገንዘብ ግምት ይገባቸዋል በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል። አመልካቾች የአፈጻጸም ትእዛዙን በመቃወም ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት ያደረገ ተቃውሞ ሲቀርብ በአፈጻጸም በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት መብት አለኝ የሚል ተቃውሞ አለው ወይስ የለውም ተብሎ የሚታዘዝበት እንጂ እዳ የጋራ ነው የግል ተብሎ በማጣራት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚወሰንበት ስላልሆነ ንብረቶቹን ተጠሪዎች በጋብቻ ውስጥ በጋራ ያፈሯቸው መሆኑ ባልተካደበት እና በ 2ኛ ተጠሪ ላይ ባልተፈረደበት ሁኔታ ድርሻቸው ለአፈጻጸሙ የሚያዝበት አግባብ የለም በማለት በውጤት ደረጃ የስር ፍ/ቤትን ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- ለአፈጻጸም ክርክሩ መሰረት የሆነው እዳ ቼክን መሰረት ያደረገ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ነጋዴነታቸው ተረጋግጦ ቼክ ተሰጥቷቸው በንግድ ስራ ተሰማርተው የቆዩ ነጋዴ ናቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተጋቢዎች በትዳር እያሉ የመጣ እዳ የባልና ሚስት የጋራ እዳ ለመሆኑ በንግድ ሕግ አንቀጽ 19 ተመልክቷል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ራሳቸው ነጋዴ በመሆናቸው እዳው የሚመለከታቸው በመሆኑ እንዳለ ሆኖ በጋራ ጥቅም ላይ አለመዋሉም የማስረዳቱ ሸክም የራሳቸው ሆኖ እያለ ይህንን አላስረዱም፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በትግራይ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 90/2/ መሰረት 2ኛ ተጠሪ ባለቤታቸው እዳ የገቡ ለመሆናቸው ቀደም ብለው ያወቁ እንደነበርና ለባለገንዘቦችም ቤቶችን ትወስዳላችሁ ሲሉ እንደቆዩ እየታወቀ ይህንን ባወቁ በ 6 ወር ጊዜ ውስጥ ግዴታው ውድቅ እንዲደረግላቸው ጠይቀው አላስፈረሱም፡፡ ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ ነጋዴ እንደነበሩና ያለ ንግድ ፈቃድ ቼክ ከባንክ እንደማይሰጥ እየታወቀ ንግድ ቢሮውም ሆነ ባንኮቹ ሳይጠየቁ፣ እንደዚሁም 2ኛ ተጠሪ እዳውን ለጋራ ጥቅም አለመዋሉን ሳያስረዱና ተቃውሞ አቅርበው ባላስፈረሱበት ሁኔታ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይሻርልን የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ ቼክ የተሰጠው ተጠሪዎች ባልና ሚስት መሆናቸው ተረጋግጦ ሳለ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪም በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ መሆኑ በታወቀበት ሁኔታ እዳው የጋራ አይደለም የተባለበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ መልስ ባለማቅረቡ መብቱ ታልፎ 2ኛ ተጠሪ እና አመልካቾች መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ እንዲቀባበሉ በማድረግ ክርክር ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ 2ኛ ተጠሪ የሰበር መልስ ይዘት፡- አመልካቾች በቼክ ምክንያት ክስ ያቀረቡትና ያስፈረዱት በ 1ኛ ተጠሪ ላይ ሲሆን ሁሉም ቼኮች ደግሞ በ 1ኛ ተጠሪ ስም ከባንክ የወጡ ቼኮች እንጂ በ 2ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገቡ ቼኮች አይደሉም፡፡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 19 መሰረት ተበዳሪው ነጋዴ መሆን እንደሚገባው እና ነጋዴ ያልሆነ ባል ወይም ሚስት የሚበደረው ብድር ግን በዚህ የሕግ ድንጋጌ የማይሸፈን በመሆኑ ነጋዴ ያልሆነው ባል የወሰደው ብድር ነጋዴ ለሆነችው ሚስት ይመለከታታል ማለት አይደለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከንግድ ውጭ ብቻቸውን የቆረጡት ቼክ 2ኛ ተጠሪ አያውቁትም የሚል እንደመሆኑ መጠን እና 1ኛ ተጠሪ ቼኩን ሲቆርጡ 2ኛ ተጠሪ ሚስት ከመሆናቸው ውጭ ስለቼኮቹ የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከንግድ እንቅስቃሴ ውጭ በስማቸው የያዙት ቼክ በ 2ኛ ተጠሪ የንግድ ልውውጥ የተቆረጡ ቼኮች ናቸው የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ፤ እንዲሁም ቼኮቹ በንግድ ልውውጥ ምክንያት የተሰጡ መሆኑ ባልተረጋገጠበት በ 2ኛ ተጠሪ ድርሻ ለአፈጻጸሙ ሊውል ስለማይገባ አመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግ የሚል ነው፡፡ አመልካቾች አቤቱታቸውን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው 1ኛ ተጠሪ በሰጣቸው ቼኮች መነሻነት የአሁን አመልካቾች በ 1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው በተለያየ መዝገብ አስፈርደዋል፡፡ አመልካቾች ለአፈጻጸሙ እንዲውሉ የጠየቋቸው ክርክር ያስነሱ ንብረቶች በ 1ኛ ተጠሪ ስም የሚገኙ ቢሆንም ከ 2ኛ ተጠሪ ጋር በትዳር ውስጥ በነበሩበት ወቅት ያፈሯቸው የጋራ ንብረቶች በመሆናቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት እዳው የተጠሪዎች የጋራ እዳ አይደለም በማለት ውሳኔ የሰጠው ምንም እንኳ እዳው ከቼክ መስጠት ጋር የተያያዘ ቢሆንም ቼኮቹ በ 1ኛ ተጠሪ የተሰጡት 2ኛ ተጠሪ የንግድ ፈቃዳቸውን ከመለሱ በኋላ በመሆኑ የጋራ እዳ ነው ተብሎ ሊወሰድ አይችልም የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረስ ነው፡፡ ሆኖም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ያጸናው እዳው የጋራ እዳ አይደለም በማለት ሳይሆን ክስ ቀርቦ የተወሰነበት 1ኛ ተጠሪ ላይ ብቻ በመሆኑና 2ኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ባልተከሰሱበትና ባለእዳ ናቸው ተብሎ ሳይፈረድባቸው በአፈጻጸም ሊገደዱና ድርሻቸው ለአፈጻጸም ሊውል አይገባም በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ በጋብቻ በተሳሰሩ ባልና ሚስት መካከል ከአንዱ ጋር የውል ግዴታ የገባ ሰው በዋናው ክርክር ሁለቱን አጣምሮ ሊከስ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ተዋዋይ በሆነው ተጋቢ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የተጋቢዎች የጋራ እዳ ነው ወይስ የተወሰነበት ተጋቢ የግል እዳ ነው የሚለው ክርክር ሊነሳ የሚችለው በአፈጻጸም ወቅት እንጂ ሌላኛው ተጋቢ ሊከሰስም ሆነ ሊፈረድበት አይችልም፡፡ ይህ ለመሆኑም ከዚህን ቀደም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 22891 በማናቸውም ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት ያለው ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ ክርክር ባስነሱ ንብረቶች ላይ ያላቸው ድርሻ ለአፈጻጸም ይውላል ወይስ አይውልም ለማለት በቅድሚያ በአፈጻጸም መዝገቡ እየተፈጸመ ያለው እዳ የጋራ እዳ ነው ወይስ የ 1ኛ ተጠሪ የግል እዳ ነው? የሚለው ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እዳው የጋራ ነው ወይስ የግል የሚለው ክርክር በአፈጻጸም ወቅት ሊነሳ አይችልም በማለት 2ኛ ተጠሪ ሳይፈረድባቸው ድርሻቸው ለአፈጻጸም አይውልም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል ወደተያዘው ጭብጥ ስንመለስ በ 1ኛ ተጠሪ ላይ የተወሰነው የገንዘብ እዳ የጋራ እዳ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን በተመለከተ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የጋራ እዳ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ የ 2ኛ ተጠሪ ድርሻ ለአፈጻጸሙ ሊውል አይገባም በማለት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በዚህ ድምዳሜ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አከራካሪ በሆነው የፍሬ ነገር ጭብጥ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ አልሰጠበትም፡፡ ይህ ሰበር ችሎት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10/2/ መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ማረም በመሆኑ እዳው የተጠሪዎች የጋራ እዳ ነው ወይስ የ 1ኛ ተጠሪ የግል እዳ የሚለውን የፍሬ ነገር ጭብጥ ማስረጃ መዝኖ የሚያረጋግጥበት የሕግ አግባብ ካለመኖሩም በላይ የአመልካቾችን የይግባኝ መብት የሚያጣብብ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መመለሱ ተገቢ ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እዳው የጋራ ነው ወይስ የግል የሚለው ክርክር በአፈጻጸም ወቅት ሊነሳ አይችልም፤ 2ኛ ተጠሪ ሳይፈረድባቸው ድርሻቸው ለአፈጻጸም አይውልም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ እዳው የተጠሪዎች የጋራ እዳ ነው? ወይስ አይደለም? እንዲሁም በአፈጻጸም ክርክር ባስነሱ ንብረቶች ላይ 2ኛ ተጠሪ ያላቸው ድርሻ ለአፈጻጸሙ ሊውል የሚገባው መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ ግራቀኙ ያቀረቧቸውን ክርክሮችና ማስረጃዎች በመመዘን የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ለይግባኝ ሰሚው ችሎት መመለሱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 64323 ሰኔ 04 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ፣ በክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 85286 ሐምሌ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠ ትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል።
2. ከላይ በፍርድ ሃተታው በተገለጸው አግባብ አመልካቾች በ 2ኛ ተጠሪ ላይ ያስወሰኑት የገንዘብ እዳ የተጠሪዎች የጋራ እዳ ነው ወይስ የ 1ኛ ተጠሪ የግል እዳ? በሚለው ጭብጥ ላይ ግራቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ክርክር ባስነሱ ንብረቶች ላይ 2ኛ ተጠሪ ያላቸው ድርሻ ለአፈጻጸሙ መዋል መቻል አለመቻሉን አስመልክቶ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመሰለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት ይመለስለት ተብሏል።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው
በዕውቀት በላይ
እንዳሻው አዳነ
ሃይሉ ነጋሽ
እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ እለፋቸው ታምሩ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እመቤት ተሾመ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል አስመልክቶ የቀረበን አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ሲደረግ የነበረውን የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል በተመለከተ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት አፈጻጸሙን ለመራው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ የይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት በላከው ምላሽ ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የሚችል መሆኑን ገልጾ ክፍፍሉ ሲፈጸም ለግራቀኙ በደረሰው ንብረት የሐብት ማጋደል ስለሚኖርበት ግራቀኙ ልዩነቱን በማካካስ የሚፈጽሙት ነገር ካለ ሐሳባቸውን እንዲገልጹ መጥሪያ የተላከላቸው ቢሆንም የፍርድ ባለመብት ሃሳባቸውን ይዘው ቀርበው የፍርድ ባለእዳ ሀሳባቸውን ያላቀረቡ በመሆኑ አፈጻጸሙ በምን መንገድ መቀጠል እንዳለበት ፍ/ቤቱ ትእዛዝ እንዲሰጥበት በማለት ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራቀኙ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ካደረገ በኋላ በዋናው ውሳኔ ላይ የግራቀኙ የጋራ ንብረት ናቸው በማለት ፍርድ ያረፈባቸው ቤቶች ግራቀኙ ከተቻለ በዓይነት እንዲካፈሉት፤በዓይነት መካፈል ካልተቻለ ክፍፍሉን በተመለከተ በውሳኔው ላይ በተቀመጠው አማራጭ መሠረት እንዲካፈሉት በማለት የተሰጠ ውሳኔ ነው፤በፍርድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ቤቶቹ እኩል መካፈል እንደማይችሉ ተገልጿል፤የሐብት ማጋደል ባለበት ሁኔታ ግራቀኙ እንዲካፈሉ ለማድረግ የግራቀኙን ሥምምነት ይጠይቃል፤ግራቀኙ በሰጡት አስተያየት ሥምምነት የሌላቸው መሆኑን የገለጹ በመሆኑ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በውሳኔው ላይ በቀጣይ በተቀመጡት አማራጮች መሠረት ውሳኔውን እንዲያስፈጽም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የሥር ፍ/ቤት አፈጻጸሙ በፍርዱ በተቀመጡት ሌሎች አማራጮች መሠረት እንዲፈጸም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ ፍርዱ እንዳይፈጸም እና ዋጋ አልባ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፤የሚመለከተው አካል ፍርድ ያረፈባቸው ቤቶች ከዋናው ቤት ተነጥለው መሸጥ እንደማይችሉ፤ይዞታው ለሁለት እኩል ሲካፈል ለግራቀኙ ከ150 ካ.ሜ ያነሰ ቦታ ሊደርሳቸው ስለማይችል በዓይነት እኩል ማካፈል እንደማይቻል ያረጋገጠ በመሆኑ በፍርዱ በተቀመጡት ሌሎች አማራጮች መሠረት ፍርዱ ሊፈጸም አይችልም፤ፍ/ቤቱ ፍርዱን ለማስፈጸም ተስማሚ ነው የሚለውን ትዕዛዝ በመስጠት ፍርዱን ማስፈጸም ስላለበት ጉዳዩን በአግባቡ ካጣራ በኋላ ቤቶቹ የየራሣቸው የሆኑ ሁለት መግቢያ እና መውጫ በሮች ስላሏቸው ግራቀኙ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / ተካፍለው እንዲገለገሉባቸው ከማድረግ ውጪ ፍርዱ የሚፈጸምበት ሌላ አማራጭ ስለሌለ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / ክፍፍሉ እንዲፈጸም በማለት ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሲሰጥ ከቆየ በኋላ በሌላ አማራጭ መሠረት ፍርዱ ይፈጸም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የበታች ፍ/ቤቶች አከራካሪ የሆነው ቤት ሊካፈልም ሆነ ሊሸጥ የማይችል ነው፤ሊካፈል የሚችለው በተነጻጻሪ ካርታ ነው በማለት ባለሙያ አስተያየት በሰጠበት ሁኔታ በሌላ አማራጭ ይፈጸም በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 91(1)እና(2) እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሐብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ የጋራ ሐብቱ በዓይነት እንዲከፋፈል ይደረጋል፤እኩል ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ልዩነቱ በገንዘብ እንዲካካስ ይደረጋል በማለት ይደነግጋል፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች የሐብት ማጋደል ባለበት ሁኔታ ቤቱን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዓይነት ለማካፈል የግራቀኙ ሥምምነት ያስፈልጋል፤ግራቀኙ ስምምነታቸውን ባልሰጡበት ሁኔታ በዓይነት ማካፈል የማይቻል በመሆኑ በውሳኔው በቀጣይ በተቀመጠው የክፍፍል አማራጭ መሠረት ውሳኔው ሊፈጸም ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱ ቢሆንም የሚመለከተው አካል ቦታው በዓይነት ሲካፈል እያንዳንዳቸው 150 ካ.ሜ ማግኘት አለባቸው ሁለቱም ሠዎች የየራሣቸው መግቢያ እና መውጫ መንገድ ስላላቸው ሰዎቹ የሚሥማሙ ከሆነ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / መገልገል የሚችሉ መሆኑን ገልጿል፡፡ ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ ተጠሪ መጠለያ እና ቀለብ ለመንፈግ የቀረበ ነው ከማለት በቀር ክፍፍሉ በተነጻጻሪ ካርታ ቢፈጸም የሚያመጣባቸው ጉዳት መኖሩን በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ቤቶቹ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / መከፋፈል እንሚችሉ በሚመለከተው አካል እስከተገለጸ ድረስ በቤተሰብ ሕጉ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል በተቻለ መጠን ባልና ሚስት ንብረታቸውን በዓይነት የመካፈል መብታቸውን ባስጠበቀ መንገድ ሊፈጸም ይገባዋል የሚለውን የክፍፍል መርህ ባስጠበቀ መልኩ በዚሁ ቤቶቹ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / እንዲከፋፈሉ በዚሁ አግባብ ክፍፍሉ ሲደረግ የበለጠ ይዞታ የደረሰው ወገን ለሌላው ወገን ግምቱን እንዲከፍል በማድረግ ማስፈጸም ሲገባው በፍርዱ በተቀመጠው ሌላ አማራጭ መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም በማለት መወሰኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 117839 ሕዳር 12 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 193470 ሚያዝያ 18 ቀን 2009 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከላይ በፍርድ ሐተታው በተገለጸው መሠረት አፈጻጸሙን እንዲቀጥል ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

https://t.me/ethiopianlegalbrief

-የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ 117839 የሆነው መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ፡፡

-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 136872

መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ህፃን እስጢፋኖስ ኃይሉ ሞግዚት ወ/ሮ ብርቱካን ተረፈ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሽቱ ቦንገን-ጠበቃ ነገደ ለማ -ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በ21/11/2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ሟች አቶ ኃይሌ ተረፈ ውርስ እንዲጣራ አመልክተው ተጠሪ ባሉበት ወርሱ እንዲጣራ በማድረግ ግራ ቀኙ ሪፖርቱን አስመልክተው አስተያየት ከሰጡ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ሪፖርቱን መዝግቦታል፡፡ የአሁን ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ቁጥሩ 101 የሆነው የንግድ ኮንቴነር ሱቅና ከሱቁ የተገኘው የኪራይ ገንዘብ የሟችና የተጠሪ የጋራ ሀብት ስለሆነ ተጠሪ ግማሽ ድርሻ አላት በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥር 18 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት የካቲት 24 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ቁጥሩ 101 የሆነው የንግድ ኮንቴነር ሱቅ ላይ ተጠሪ ግማሽ ድርሻ አላት ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁን ተጠሪና ሟች ባልና ሚስት እንደነበሩና ጋብቻቸውም የተፈፀመው በ2001 ዓ.ም እንደሆነ፤ሟች አቶ ኃይሌ ተረፈ የንግድ ፍቃድ የተሰጣቸው ከጥር 5 ቀን 1998 ዓ.ም አንስቶ እንደሆነ፤ ለክርክር ምክንያት የሆነው ኮንቴነሩን/የንግድ ቤቱን/ በኪራይ ያገኙት ግን ጥር 18 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን የጉለሌ ክ/ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት የንግድ ምዝገባ ፍቃድ እና ግብይት ዋና ስራ ሂደት በ28/06/2008 ዓ.ም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በላከው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ለክርክር ምክንያት ሆነው የኮንቴነር ሱቁ በጋብቻ ውስጥ መንግስት በአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋም አደራጅቶ የሰጣቸው መሆኑን ፍሬ ጉዳዩን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ኮንቴነር ሱቁ /ንግድ ቤቱ/ ከጋብቻ በፊት የተገኘ የሟች የግል ንብረት በመሆኑ ኮንቴነር ሱቁና የኪራይ ገንዘብ ግማሹ የተጠሪ ድርሻ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መባሉ አግባብ አይደለም በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች የኮንቴነር ሱቁ እና ከሱቁ ኪራይ የተገኘው ገንዘብ የተጠሪና የሚች የጋራ ሀብት በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 46454 ሰኔ 22 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 170166 ሐምሌ 25 ቀን 2008 ዓ/ም በውሳኔ የተሻሻለው እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ በመ/ቁጥር 132640 ታህሳስ 28 ቀን 2009 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ከዚህ ፍርድ ቤት ጥር 29 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት በመ/ቁ. 28805 የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ.ቁ. 126411

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ተስፋጊዩርጊስ አዳነ -ጠበቃ ኤልያስ መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አሰፉ ግርማ -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የተጀመረዉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ፣ ወ/ሮ አለም መንግስተአብ ደግሞ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ከአሁኑ አመልካች ጋር እንደባልና ሚስት በመሆን አብረን የኖርን ስለሆነ ንብረት ሊያካፍለኝ ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካች ከተጠሪ ጋር በሕግ ጥበቃ በሚደረግለት ግንኙነት ውስጥ ያልነበሩና በጋራ ያፈሩት ንብረትም የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ሕጋዊ ሚስት ነኝ ያሉት ግለሰብም ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ጥያቄ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ፈቅዶላቸው ጣልቃ ገብተው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ አመልካች ከሁለቱም ሴቶች ጋር እንደባልና ሚስት የኖሩ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም የተሻለ ያስረዱና መጀመሪያ ከአመልካች ጋር መኖር የጀመሩት የአሁን ተጠሪ ናቸው በማለት አመልካችና ተጠሪ ንብረቱን እኩል ከተካፈሉ በኃላ የአሁኑ አመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከድርሻቸው ለስር ጣልቃ ገብ እንዲያካፍሏቸው ጣልቃ ገቧ መጠየቅ ይችላሉ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካችና የስር ጣልቃ ገብ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ እና በስር ፍርድ ቤት የተሰሙትን የተጠሪ ምስክሮችን በድጋሚ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ከአሁኗ ተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት መኖር የጀመሩት ከ1996 ዓ/ም ጀምሮ እንደሆነ ተጠሪ በምስክሮቻቸው ማስረዳታቸውን፣ አመልካች ከስር ጣልቃ ገብ ጋር እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር የጀመሩት ደግሞ ከ1995 ዓ/ም ጀምሮ በማስረጃ ተነግሯል ወደሚል ድምዳሜ ደርሶ የስር ፍርድ ቤት ሁለቱንም ሚስቶች ናቸው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተገቢ ቢሆንም በንብረት መብት ረገድ ቅድሚያ ደረጃ ሊሰጣቸው የሚገባው ግን የአሁኗ ተጠሪ ሳይሆኑ ለስር ጣልቃ ገብ ሁኖ እያለ ይኼው መታለፉ ያላግባብ ነው በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማሻሻል የጣውላ ቤት ድርጅትና 46 ካ/ሜትር የማህበር ቤት የአሁኑ አመልካችና የስር ጣልቃ ገብ የጋራ ሃብት ሁኖ ሊከፈል እንደሚገባ፣ ከአሁኑ አመልካች ድርሻ ግማሹን ማለትም ከጠቅላላ ንብረቱ ¼ኛው ለአሁኗ ተጠሪ እንዲያካፍሉ፣ ክፍፍሉም በአይነት ወይም ግምቱን በመክፈል ሊከናወን ይገባል በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ሲያከራክር ቆይቶ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት በተሠጠው ውሳኔ ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ በወሰነበት አግባብ ድጋሚ ይግባኝ ማቅረባቸው ስነ ስርዓታዊ አይደለም በሚል ምክንያት ወደ ፍሬ ነገሩ ሳይገባ የአመልካች ይግባኝ መዝገብ ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም አጣሪ ችሎቱ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ከተጠሪ ጋር በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት ግንኙነት ውስጥ የነበሩ ስለመሆኑ በሕጉ አግባብ ሳይረጋገጥና አመልካች ከ1988 ዓ/ም ጀምሮ ከሌላ ሴት ጋር በሕጋዊ ግንኙነት ያሉ መሆኑ የሚያሳዩ ማስረጃዎች በአግባቡ ሳይታዩ መታለፋቸውን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች ከ1996 እስከ 2004 ዓ/ም እንደባልና

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ነበር በማለት የሰጡት ውሳኔ እንዲሻር ቅድሚያ ዳኝነት የጠየቁ መሆኑንና በአማራጭ ደግሞ ብር 75,000.00 ተጠሪ እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ከንብረቱ ¼ኛ እንዲወስዱ የሚያደርግ የክፍፍል ውሳኔ መሰጠቱ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰዉ ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከተጠሪ ጋር በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ግንኙነት የለኝም፣ በስር ፍርድ ቤቶች መታየት የነበረባቸው ውሳኔዎች በማስረጃነት አልታዩም፣ የተጠሪ ምስክሮች ዘመዶቻቸው ሆነው በሐሰት የሠጡት የምስክርነት ቃል የማስረጃነት ዋጋ መሰጠቱ ያላግባብ ነው የሚሉ ነጥቦችን በማንሳት ስለመሆኑ ከሰበር አቤቱታቸው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የማስረጃ አሰማም ላይ ቅሬታ አድሮባቸው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠሪን ምስክሮች እንደገና የሰማ ሲሆን የተጠሪ ምስክሮችም በስር ፍርድ ቤት የሰጡትን የምስክርነት ቃል በመድገም አመልካች እና ተጠሪ እንደባልና ሚስት ሁነው ከ1995 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2004 ዓ/ም ድረስ አብረው የቆዩ መሆኑን፣ ከ1991 እስከ 1995 ዓ/ም መጀመሪያ ድረስ በፍቅር ጓደኝነት የቆዩ መሆኑን ማስረዳታቸውን፣ ምንም እንኳን የአሁኑ አመልካች የስር ጣልቃ ገብን ሚስቱ ናት በማለትና ንብረቶችን ደግሞ የሌላ ሚስቱና የግሌ ልጅ በሰጠችኝ ብር የተገዙ ናቸው የሚል ክርክር ቢያቀርቡም በስር ፍርድ ቤት የተሰሙት የአመልካች ምስክሮች ግን አመልካችና የስር ጣልቃ ገብ ባልና ሚስት እንደሆኑ፣ ጋብቻ ግን ሲፈጸም አለማወቃቸውን፣ የስር ጣልቃ ገብም አራት ልጆችን ወልደው ከአሁኑ አመልካች ጋር አብረው እንደሚኖሩ ያስረዱ መሆናቸውን፣ እነዚህ የአመልካች ምስክሮች አመልካች ከተጠሪ ጋር ግንኙነት የላቸውም በማለት ያላስረዱና ስለንብረቱም ያስረዱት ነገር ያለመኖሩን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የደመደመ መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ድምዳሜ የተያዘው ደግሞ ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲል የተጠሪ ምስክሮችን በድጋሚ በመስማት ፍሬ ነገሩን በሚገባ ከአጣራና በጉዳዩ በሕጉ አግባብ የቀረቡትን የግራ ቀኙን ማስረጃዎች ከመዘነ በኋላ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ድምዳሜ ደግሞ ከስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ጋር ተመሳሳይ ከመሆኑም በላይ በሕጉ አግባብ የተቆጠሩትንና የተሰሙትን ማስረጃዎችን በመመዘን የተያዘ በመሆኑ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሊለወጠው የሚችለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም ለዚህ ችሎት በሕጉ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረምን እንጂ የፍሬ ነገር ማጣራት ስህተት ወይም የማስረጃ ምዘና ስህተትን የሚመለከተውን ጉዳይ አይደለምና፡፡ በመሆኑም አመልካች ከተጠሪ ጋር ሕጉ ጥበቃ በሚያደርገው ግንኙነት ውስጥ አልነበርኩም በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታይ አይችልም በማለት አልፈነዋል፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖርን ግንኙነት ለማስረዳት የሚቀርበው ማስረጃ ግንኙነቱን የማሳየት ብቃት ያለው መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ከአረጋገጡ ሕጉ ግንኙነቱን ጥበቃ የሚያደርግለት መሆኑን ከክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 109፣110፣113፣ 117 እና ከሌሎች ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ጋር በሕጉ ጥበቃ ሊደረግ የሚገባው ግንኙነት ስላለመኖሩ በተጠቃሹ አዋጅ አንቀፅ 117 (4) ድንጋጌ አግባብ የማስረዳት ግዴታቸውን ያልተወጡ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ንብረቶቹ የግላቸው ስለመሆኑም በአዋጁ አንቀፅ 114 እና 97 ድንጋጌዎች መሰረት የማስረዳት ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡ አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ ባቀረቡት ክርክር ድርሻቸው ¼ኛ እንዲሆን በተሰጠው የውሳኔ ክፍል ግልጽ የሆነ ቅሬታ ያላቀረቡና ክፍፍሉም የእኩልነት መርህን ወይም የእያንዳንዱ ተጋቢ በንብረቱ ላይ የነበረውን አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ በማስገባት መኪናውን ነበረበት በማለት ያቀረቡት ክርክር ካለመኖሩም በላይ በሰበር አቤቱታቸው መጨረሻ ላይ የጠየቁት ዋናም ሆነ አማራጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ጥያቄ መጠንም በዚህ ረገድ የሚጠቅሰው ግልጽ የሆነ የዳኝነት ጥያቄ የሌለ በመሆኑ የሠበር አጣሪው ስለንብረት ክፍፍሉ የያዘውን ጭብጥ ተገቢነት ያልነበረው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የተሰጠው የግራ ቀኙ ክርክር በአግባቡ ተሰምቶና ፍሬ ነገሩም በሚገባ ተጣርቶ የግራ ቀኙን የማስረጃ ማቅረብና የማስረዳት ግዴታቸውን ባገናዘበ መልኩ ከመሆኑ ውጪ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻልበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአማራ ክልል በጎንደር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 0228 ጥር 29 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁጥር 01-16605 በ27/07/2007 ዓ/ም ተሻሽሎ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር አጣሪ ችሎት በመ.ቁ 03-56035 መጋቢት 01 ቀን 2008ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ከአሁኗ ተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት መኖር የጀመሩት ጊዜ በ1996 ዓ/ም ጀምሮ እንደሆነ ተጠሪ በምስክሮቻቸው አስረድተዋል፣ ከአሁኑ አመልካች ድርሻ ግማሹን ማለትም ከጠቅላላ ንብረቱ ¼ኛውን ለአሁኗ ተጠሪ እንዲያካፍሉ፣ ክፍፍሉም በአይነት ወይም ግምቱን በመክፈል ሊከናወን ይገባል ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለ

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 137853

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ በለጠ ነጋሽ-ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እጅጋየሁ ላቀው-ጠበቃ ጎሳዬ ነጋሽ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የህግ አሳዳጊዬ የሆኑት ወ/ሮ በለጤ ግዛው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቷ ሟች አሳዳጊዬ በህይወት ዘመንዋ ያፈራችውን የግል ቤትዋን እና የገጠር እርሻ መሬት ከአሁንዋ ተጠሪ ከአሳዳጊዬ ልጅ ጋር እኩል እንድንካፈል እንዲውሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ለአቤቱታው በሰጡት መልስ የሟች ንብረትም ይሁን ይዞታ ሁሉም በስጦታ ውል አግኝቻለሁ፤አመልካችም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የጉዲፈቻ ውሉ ስላልፀደቀ የመውረስ መብት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የተጠሪን መቃወሚያ በብይን ውድቅ በማድረግ የሟች ሀብትና የገጠር ይዞታ ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም በፊንፊኔ ዙሪያ ለኦሮሚያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ በሚችና በአመልካች መካከል በ1996 ዓ.ም የተደረገው የጉዲፈቻ ውል በኦሮሚያ ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 እና 83/1996 መሰረት እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ሰው የጉዲፈቻ ውል ሲደረግም ሆነ ፍርድ ቤት ሲያፀድቅ እድሜው 27 አመት እንደሆነ የውል ሰነድ ራሱ ያሳያል፤ ይህ ደግሞ ለህግ ተቃራኒ በመሆኑ አንድም መብት መስጠት አይችልም በማለት ፀድቋል የተባለው የጉዲፈቻ ውል ውድቅ በማድረግ አመልካች ከገጠር መሬት ይዞታ ውጭ ያለው የሚች ንብረት መውረስ አይችልም፤በሌላ በኩል የገጠር መሬትን አስመልክቶ የሚች ቤተሰብ ከሆነ የመውረስ መብት ያለው ስለሆነ ይህ ደግሞ በማስረጃ ከተጣራ በኋላ እንዲወሰን ጉዳዩን ለወረዳ ፍርድ ቤት መልሶታል።

የአሁን አመልካች የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በውሳኔ አጽንቶታል። በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም።

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። አመልካች የካቲት 8 ቀን 2009 ዓ.ም በዓራት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 20 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል። እንደመረመርነውም በዚህ ጉዳይ ወራሽነቱን ያረጋገጠበት መዝገብ ሳይሻር የውርስ ሀብት ለመጠየቅ ባስከፈተው መዝገብ ወራሽነት በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ በማድረግ መወሰናቸው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው ሚችና አመልካች በ1996 ዓ.ም የጉዲፈቻ ስምምነት ማድረጋቸው፤ስምምነቱም ለፍርድ ቤት ቀርቦ በመ/ቁ.498/96 ስምምነቱ ህጋዊ መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን፤ይህ ውሳኔ መቃወሚያ ቀርቦበት ያልተሻረ መሆኑን ከክርክሩ ሂደትና ከስር መዝገብ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ የአመልካች ጥያቄ የጉዲፈቻ ውሳኔ ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት የተወሰነ በውርስ አቤቱታ በተከፈተ መዝገብ እንደማስረጃ የቀረበውን ሰነድ መቃወም አትችልም፤የጉዲፈቻ ውሳኔ ስህተት ቢኖረው እንኳን በተወሰነበት መዝገብ ላይ መቃወሚያ ማቅረብ የምትችልበት እንጂ በዚሁ የውርስ ፋይል ላይ ማቅረብ የማይገባውን በመቀበል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ ደግሞ አመልካች በተሻረና ለጉዲፈቻነት በህግ በተቀመጠው ከ18 ዓመት እድሜ በላይ በ27 ዓመቱ የተደረገን የጉዲፈቻ ውል መነሻ በማድረግ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ከክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት ድረስ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ህግን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ እዚህ ሊታይ የሚገባው ነጥብ የጉዲፈቻ ውል ውሳኔ ፀንቶ ባለበት ሁኔታና ሳይሻር በውርስ ንብረት ክፍፍል በተጠየቀበት በሌላ መዝገብ የመታየቱ ጉዳይ ነው፡፡ የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለ አንቀጽ 202 መሰረት ከ18 ዓመት እድሜ በላይ የጉዲፈቻ ልጅ መሆን አንደማይችል ይደነግጋል፡ አመልካችም እድሜው 27 ዓመት የነበረ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ሚች ወ/ሮ በለጤ ግዛው አመልካችን የጉዲፈቻ ውል ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ፣ይህ ውሳኔ መብቴን ይነካል የሚል ወገን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41፤358 በክርክሩ ገብቶ መቃወም ወይም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላም ቢሆን መቃወሚያ በማቅረብ መጀመሪያ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሰረዝ ማድረግ እየተቻለ አመልካች ወራሽነቱን በማረጋገጥ የሚች ንብረት ድርሻውን በጠየቀበት መዝገብ ላይ የጉዲፈቻ ውል አስመልክቶ የተሰጠ ውሳኔ ላይ ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በፍርድ ቤት የፀደቀ /የተሰጠ/ ውሳኔው ሳይሰረዝ የተሻረበት አግባብ ስነስርዓት ህጉን ያልተከተለ በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለል ስር ፍርድ ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ ሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 36014 ጥር 14 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 24227 ህዳር 14 ቀን 2008 ዓ/ም በመሻር የሰጠው ውሳኔ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 227747 የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ/ም እና በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 242197 ህዳር 3 ቀን 2009 ዓ/ም በውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የሚች ወ/ሮ በለጤ ግዛው የጉዲፈቻ ልጅ ስላልሆነ ሊወርስ አይችልም በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል በመሻር በሱሉልታ ወረዳ ጎርፎ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ መኖሪያ ቤት የመውረስ መብት ስላለው ከተጠሪ ጋር እኩል ሊካፈሉ ይገባል ብለን ወስነናል፡፡
3. የስር ፍርድ ቤቶች በገጠር እርሻ መሬት ይዞታ በተመለከተ የሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት የመ/ቁ.36014 የሆነውን በማንቀሳቀስ የገጠር መሬት አዋጅ በሚያዘው መሰረት የግራ ቀኙ ማስረጃ እንደገና በማጣራት ውሳኔ እንዲሰጥበት የተመለሰው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 133736

ታህሳስ 26 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች---ዳኜ መላኩ

ተክሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-1ኛ አቶ መዚድ ተስፋዬ አህመድ

2ኛ አቶ መርዙቅ ተስፋዬ አህመድ ጠ/ወልደሰንላሴ ብርቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘይነባ ለካ ሱሩር ጠ/መሀዲ ሁሴን ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ከሣሽ አመልካቾች ሆነው ተከሣሽ ተጠሪ በመሆን በኪራይ ውል መነሻነት ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍርድ ቤት ቀርቦ የነበረው ክስ የሚያመለክተው በቂ/ክ/ከ/ወረዳ 18 ቁጥሩ 063/መ/ተመዝግቦ የሚያታወቀውን የፋብሪካ ውጤቶች የህንጻ መሳሪያ ንግድ ድርጅት የከሣሾች እህት ከሆነችው ወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዬ በወር ብር 5,000/አምስት ሺ ብር/ ከሚያዝያ 03/2003 ጀምሮ ተከሣሾች መከራየታቸውን ሆኖም ከሚያዝያ 03/2004 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጥቅምት 02/2005 ዓ.ም.ድረስ የአንድ ዓመት ኪራይ ብር 60000.00 /ስድሣ ሺ ብር/ አልከፈሉም፡፡ በተጨማሪም ጥቅምት 03ቀን 2005 ዓ.ም.እስከ ጥር 23/2005 ዓ.ም. ድረስ ያለውንም ኪራይ ብር 18,333.33 አልከፈሉም፡፡ ተከሣሽ እንዲከፍሉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ለመክፈል ፈቃደኛ አይደሉም ስለሆነም በድምሩ 78,333.33 / ሰባ ስምንት ሺ ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ብር ከሰላሳ ሶስት ሣንቲም/ ከወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከጥቅምት 03/2004 ጀምሮ ያለውን የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ሲሆን ክሱን ያቀረቡት 6 ወር ካለፈው በኋላ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የንግድ ቤቱ የከተማው አስተዳደር ንብረት ስለሆነ መቅረብ ያለበት በከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤት ነው፣ ከሣሾች ቤት አላከራዩንም ያከራዩን እህታቸው በመሆናቸው ቤቱ ለአሁን ተከሣሽ ይገባል በማለት አስተዳደሩ የወሰነው በአግባቡ በሚል እንጂ የኪራይ ውል አለ ብሎ አልወሰነም ስለሆነም የኪራይ ገንዘብ ለመጠየቅ የሚያስችል ውል ስለሌላቸው ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ግራ ቀኙን በቃል አከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን ከወሰነ በኋላ ቀሪውን መቃወሚያ አስመልክቶ ተከሣሽ ኪራዩን የተከራየሁት ከከሣሾች እህት ወ/ሮ አሰለፈች እንጂ ከከሣሾች አይደለም በሚል የተከራከሩ ሲሆን የኪራይ ውሉ ላይ ወ/ሮ አሰለፈች በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ድርጅት ለተከሣሽ አከራይቻለሁ የሚል ተገልጿል እንጂ ከሣሾችን በመጨመር ወይም ሞግዚትና አስተዳዳሪ መሆናቸውን በመግለጽ የተፈፀመ ባለመሆኑ ከሣሾች ይህን ውል መሠረት በማድረግ ክስ ያቀረቡት የመክሰስ መብት ሳይኖራቸው ነው በማለት በብይን መዝገቡን መዝጋቱን የመ/ቁ/ 22834 የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው የብይን ግልባጭ ያሣያል፡፡

አመልካቾች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢሉም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 177126 ሐምሌ 26 ቀን 2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ይግባኝ ቅሬታውን በትዕዛዝ ውድቅ ማድረጉን ተመልክተናል፡፡

አመልካቾች በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ፡- አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት የኪራይ ገንዘብን አስመልክቶ ባቀረቡት ክስ ላይ መብትና ጥቅም ያላቸው መሆኑን፣

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያቱም የንግድ ቤቱ የተከራይነት መብት የመጣው ከአመልካቾች ወላጆች ከአቶ ተስፋዩ አህመድ ናጂ እና ከወ/ሮ በላይነሽ ምሩሪ እንደሆነ የኪራይ ውሉ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡

የወራሽነት ማስረጃንም አቅርበዋል፣ የአውራሻቸውን መብት እና ግዴታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 826/2/ መሠረት ለወራሾች ተላልፏል፡፡ አመልካቾች አካለ መጠን ባላደረሱበት ጊዜ እህታቸው ወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዩ አካለመጠን ላላደረሱት ልጆች ሞግዚት ለመሆናቸው ሐምሌ 30 ቀን 1995 ዓ.ም. በመ/ቁ/ 1904/95 የተሰጠ ውሣኔን በማቅረብ ተረጋግጧል፡፡ ወ/ሮ አሰለፈች በውርስ የመጣውን ክርክር ያስነሳውን የንግድ ድርጅት ከቂ/ክ/ከ/ወ/8 ጋር ሲዋዋሉ እነ አሰለፈች ተስፋዩ በማለት የተከራዩ መሆኑን ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ተጠሪ ወራሽና ሞግዚት ከሆኑት ከወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዩ በተከራዩት የንግድ ቤት ላይ መብትና ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ በአ.አ.ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት ቂ/ክ/ከ/ ምድብ ችሎት በመ/ቁ/ 07615 እና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሁለት መዛግብት ተጣምረው በተሰጠው ፍርድ ቁጥሩ 063/መ/ ያሁን አመልካቾች ወላጆች አቶ ተስፋዩ አህመድና ወ/ሮ በላይነሽ ምሩሪ በጋብቻ እያሉ ለንግድ አገልግሎት በጋራ ተከራይተውት የነበረ መሆኑን የይግባኝ ባይ ወላጆች ሲሞቱ የተከራይነቱ መብት በሕይወት ላሉት ልጆቻቸው የተላለፈ መሆኑን፣ አመልካቾች አቅመ አዳም ባለመድረሳቸው እነ አሰለፈች ተስፋዩ በሚል እህታቸው ያደረጉት የኪራይ ውል ሌሎችንም የሚጭምር በመሆኑ መብት ያላቸው መሆኑን ስለሚያሳይ ስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምላቸው በጠበቃቸው አማካይነት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በሚል ጭብጥ ይዞ በመላኩ መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፡ አቤቱታው ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር ለተጠሪ ደርሷቸው መልስ እንዲያቀርቡ ከመጥሪያ ጋር የተላከላቸው ሲሆን ሚያዝያ 12 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበው ተያይዟል፡፡ ይዘቱም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ብቻ እንደተመለከትነው ፡- በወ/ሮ አሰለፈች በስሟ ላደረገችው የኪራይ ውል አመልካች እንዴት ከእኔ ጋር የቤት ኪራይ ውል አለኝ በማለት እንደሚችል ያላስረዳና ሊያስረዳም ስለማይችል የሰበር ችሎቱ ውሣኔውም ቢሆን ቤቱ ለአመልካች ይገባል ከማለት በቀር በእኔ እና በአመልካች መካከል ውል ማቋቋም ስለማይችል የአመልካችን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉ አግባብ ነው በማለት አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገብ ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበው አቤቱታ አጠቃላይ ክርክር እና አግባብነት ያለውን የህግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ የኪራይ ገንዘብ ይከፈለን የሚል ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የኪራይ ውል ማድረጋቸውን ገልፀው ነገር ግን ከአመልካቾች ጋር ሣይሆን ከእህታቸው ጋር የተዋዋልኩ እና ውሉም እነሱን ስለማይገልጽ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም ተብሎ ውድቅ እንዲሆንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በተከሣሽ ላይ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላችሁም በማለት በብይን ክሱን ውድቅ አድርጐታል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ማጽናቱን ተመልክተናል፡፡

የአመልካቾች ጥያቄ በአጣሪው ከተያዘው ጭብጥ አኳያ ስንመለከተው ክርክር የተነሳበት የንግድ ድርጅት ከአመልካቾች ወላጆች መብቱ በውርስ የተላለፈላቸው ሲሆን በጊዜው ህጋዊ ተግባር ለመፈፀም አመልካቾች አቅመ አዳም ያልደረሱ በመሆኑ ወራሽነታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በእህታቸው ወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዩ አማካይነት ከአስተዳደሩ ጋር የኪራይ ውል በንግድ ቤቱ ላይ “እነ ወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዩ” በሚል የተዋዋሉ በመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ወ/ሮ አሰለፈች የአመልካቾች ሞግዚት እና ወራሽም መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን በዚህ ክርክር ባስነሳው የንግድ ቤት ላይ ያላቸው መብት ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል ሲሆን ለሌላ ሰው ንብረቱን በሚያከራዩበት ጊዜ ይህንን የሞግዚትነት ሥልጣን ተላብሰው እንጂ በራሳቸው ሙሉ ስልጣን ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ግለሰቧ በዛ የንግድ ቤት ላይ ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል ድርሻ ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡

በዚህ ክርክር ባስነሳው የንግድ ቤት ላይ በስር ፍርድ ቤት በሌላ መዝገብ ክርክር ተደርጉበት እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የነበረ እና በሠ/መ/ቁ/ 84037 በሆነው መዝገብ ላይ ግንቦት 19/2005 ዓ.ም. ውሣኔ ተሰጥቶበታል፡፡

በዚህ የሰበር መዝገብ ላይ ፍርድ ቤቱ ለክርክሩ በሰጠው ማጠቃለያ ውሣኔ የንግድ ቤቱን የአመልካቾች ሞግዚት ለሌላ 3ኛ ወገን አሳልፈው ያከራዩት መሆኑን እና በመመሪያውም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለአስተዳደሩ እውቅና አሳልፈው ማከራየታቸው የተከራይነት መብቱን ወደ ተከራየው ሰው የሚያዛውር በመሆኑ ወ/ሮ አሰለፈች ይህንን በውርስ ለወራሾች የተላለፈላቸውን ንግድ ቤት ያለአስተዳደሩ እውቅና ማከራየታቸው በራሳቸው በኩል ያለውን የተከራይነት መብት የሚያቋርጥባቸው እንጂ የሌሎች በሞግዚትነት የሚያስተዳድሯቸውን ወራሾች መብት የሚነካ መሆን እንደሌለበት በመግለጽ ፣ በሰበር መዝገቡ ላይ አመልካች በዚህ በያዝነው መዝገብ ደግሞ ተጠሪ የሆኑት ግለሰብ በመመሪያው መሠረት ንግድ ቤቱን ከአስተዳደሩ በቀጥታ በራሷ ስም ለመከራየት እንደመብት ጥያቄ ለማቅረብ የማያስችላት ሁኔታ አይኖርም ስለሆነም አስተዳደሩ የሌሎች ወራሾችን የተከራይነት መብት ሊያስቀጥል በሚያስችል መልኩ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰዱ በአግባቡ ነው በማለት በስር የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ማጽናቱን የውሣኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

ከዚህ የምንረዳው ወ/ሮ አሰለፈች በስማቸው በሞግዚትነት የሚያስተዳድሯቸው ወራሾችን ንብረት ለተጠሪ አከራይተው እንኳን ቢሆን የተከራይ አከራይ መመሪያ ወ/ሮ አሰለፈችን ከሚመለከት በስተቀር ሌሎች ወራሾችን የሚመለከት እንደማይሆን እና ከአስተዳደሩ ጋር ሌሎች ወራሾች የመከራየት መብታቸው የሚቀጥል መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ወ/ሮ አሰለፈች ያከራዩት ንብረት በግላቸው መብት ያገኙበት ሣይሆን የሌሎችንም የሚጭምር በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

በዚህ ረገድ አመልካቾች በውርስ ባገኙት መብት መነሻነት የኪራይ ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍሉ የጠየቁ በመሆኑ ክርክር ባስነሳው የንግድ ቤት የኪራይ ውል መነሻነት ክስ በተጠሪ ላይ ለማቅረብ የሚያበቃ መብትና ጥቅም ያላቸው በመሆኑ መብትና ጥቅም የላችሁም በማለት የስር ፍርድ ቤት በብይን መዝገቡን መዝጋቱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንን ስህተት ሳያርም ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ ሊሻር የሚገባው ነው ብለን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/22834 በ18/6/08 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 177126 በ26/11/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈፀመበት ሆኖ በመገኙቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ አመልካቾች ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም አላቸው ብለናል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በብይን የዘጋውን መ/ቁ/ 22834 በማንቀሳቀስ አመልካቾች ያልተከፈለን የኪራይ ገንዘብ ተጠሪ ሊከፍሉን ይገባል በማለት ያቀረቡትን ክስ ከተጠሪ ጋር በሞግዚትነታቸው መነሻነት የኪራይ ውል የፈፀሙትን ወ/ሮ አሰለፈች ተስፋዩን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 41 መሠረት ወደ ክርክር እንዲገቡ በመጥራት በፍሬ ነገር ላይ በማከራከር ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 341/1/ መሠረት አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን እንዲወስን መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡
5. መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 130284

ጥቅምት 30 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡- 1.አቶ ክንፈ ሐጎስ

2. ቄስ ወረደ ሐጎስ

3. ወ/ሮ ለተብርሃን ገ/ሂወት

ከጠበቃቸው ሃይለ ገብረማርያም ጋር ቀረቧል፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዛፉ ሐጎስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በትግራይ ብ/ክ/መ/ በመቐለ ከተማ በዓይደር ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካቾች ለተጠሪ ተቃዋሚ ሆነው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባቀረቡበት የውርስ ማጣራት መቃወሚያቸው ውድቅ በማድረግ ያቀረቡት ውርስ ማጣራት ፀድቆ የወንድማቸው የወራሽነት ማስረጃ የተሰጣቸው መሆኑ በመግለፅ ወንድማቸው አቶ ዮሴፍ ሐጎስ በህይወት እያለ በመቐለ ከተማ ዓይደር ክፍለ ከተማ ቀበሌ ሰርፀ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ስፋቱ 250 ካ/ሜ ግምቱ ብር 300,000.00 /ሶስት መቶ ሺህ ብር/ የሆነው ከተጠሪ ትዳር ከመመስረታቸው በፊት የተፈራ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ የወራሾች ስለሆነ ተጠሪ ከዚህ ቤትና ቦታ እንዲወጡና ሌላ የውርስ ዕቃ ድርሻ እንዲያስረክቡን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ ለክሱ የሰጡት መልስ ከ1989 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ እንደ ባልና ሚስት ሆነን አንድ ላይ እየኖርን ቆይተን በህዳር 1996 ዓ.ም እስከ እለተ ሞታቸው 2005 ዓ.ም ከአቶ ዮሴፍ ሐጎስ ጋር በጋብቻ ስለነበርን በኤርትራ የሚኖሩ ክብሮም ዮሴፍና ዘካሪያስ ዮሴፍ የተባሉ የሚች ልጆች በሚች የሚታወቁ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዲያካፍሉኝ ለመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቤ፤ፍርድ ቤቱም አጣርቶ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤትና ቦታ ሆነ ሌላ የሚች ሀብት ግማሹ ለተጠሪ ግማሹ ደግሞ ለሚች ወራሾች እንዲሆን ወስኗል፡፡ የሚች ልጆች እያሉ አመልካቾች ወራሾች ሊሆኑ ስለማይችሉ ለመክሰስ መብት የሌላቸውና ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገሩ የሰጡት መልስ ደግሞ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤትና ቦታ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት እንጂ የሚች የግል ንብረት አይደለም፤ በሽምግልናም የጋራ ንብረት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የቀረበው ክስ ውድቅ በማድረግ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉ ተብሎ እንዲወሰንላቸው የመከላከያ መልሳቸው አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም በመጀመሪያ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት ዘግቶት እንደነበረ ነገር ግን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣንህ ነው በማለት በነጥብ ከተመለሰ በኋላ መቃወሚያዎቹ በብይን ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤትና ቦታ በከፍተኛ መቐለ ከተማ ፍርድ ቤት ግማሹ የሚች አቶ ዮሴፍ ልጆች ቀሪው ግማሽ ደግሞ ለተጠሪ እንዲሆን ተወስኖ በዚሁ ውሳኔ መሰረት በስማቸው የተመዘገበ በመሆኑና የከፍተኛ ፍርድ ውሳኔ እስካልተሻረ ድረስ አመልካቾች ሚች ልጆች የለውም በማለት ያቀረቡት ክርክርና የጠየቁት ዳኝነት አይገባቸውም ሲል ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለመቐለ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም አመልካቾች የሚች ወራሾች መሆናቸው የሚያረጋግጥ የፍርድ ቤት ውሳኔ ቅጂ ስላቀረቡ ተጠሪ በዚሁ የውርስ ማጣራት መቃወሚያ አቅርበው ውድቅ መደረጉ፤በመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ክብሮም ዮሴፍ እና ዘካሪያስ ዮሴፍ ራሳቸው ወይም በወኪላቸው ዳኝነት ጠይቀው ወይም ተከራክረው ሳይሆን ተጠሪ ራሳቸው በይዞታቸው ለሚገኘው ንብረት እነዚህ የሚች ልጆች ባለእኩል ናቸው በሚል በእነርሱ ላይ ክስ መስርተው በሌሉበት የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ አመልካቾች ነን ብለው ቢያረጋግጡም በቀጥታ ወራሾች አለን ብለው የቀረበ ተቃውሞ ስለሌለ ክብሮምና ዘካሪያስ ቀጥታ ወራሾች መሆናቸው ያቀረቡት የውርስ ማስረጃ ሆነ ክርክር ስለሌለ ህጋዊ ወራሾች ናቸው ለማለት ስለማይቻል፤አመልካቾች ግን የፍርድ ቤት የውርስ ማስረጃ ስላቀረቡ ወራሾች የማይሆኑበት ህጋዊ ምክንያት የለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤትና ቦታ ግማሹ አመልካቾች በወራሽነታቸው፤ ግማሹ ደግሞ ለተጠሪ እንዲሆን ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የሚች 1ኛ ደረጃ ወራሾች የሆኑ የሚች ልጆች መኖራቸው የፍርድ ቤት ውሳኔና አፈፃፀም ትእዛዝ ተረጋግጦ እያለ ፤ይህ የፍርድ ቤት ውሳኔና ትእዛዝ ደግሞ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ባልተቀየረበት 1ኛ ደረጃ ወራሾች እንደሌሉ ታስቦ የሚች ሀብት ድርሻ ለ2ኛ ደረጃ ለሆኑ ወራሾች እንዲሆን የተሰጠ ውሳኔ ህጋዊነት ስሌለው ሊሻር ይገባል በማለት የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች ሰኔ 10 ቀን 2008 ዓ.ም በዓፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 9 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ እንደመርመርነውም የአመልካቾች ጥያቄ በአመልካቾችና በተጠሪ መካካል ሲካሄድ የቆየው የውርስ ማጣራት ሂደት የፍ/ብ/ህ/ቁ.826 በሚያዘው መሰረት የውርስ ማጣራቱ ሂደት ሚች ይኖሩበት በነበረው ስፍራ ስልጣኑ በሚፈቅድለት የዓይደር ወረዳ ፍርድ ቤት እንጂ በከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ ተደርጎ ውሳኔ ያገኘ መባሉ፤ተጠሪ ወራሽ ናቸው ለተባሉት እናት አይደሉም ሞግዚትነትም ሆነ የውክልና ስልጣን የላቸውም በማለትያቀረብነው መቃወሚያ ግምት ውስጥ ሳይገባ ወራሽነቱ እንዲፀድቅ መደረጉ፤የዚህ ውርስ ተጠቃሚዎች ናቸው የተባሉት ከነአካቴው ያልተወለዱና በአካልም የሌሉ ሆን ተብሎ ተጠሪ ንብረቱን ያለ ጠያቂ ለብቻ ለማስቀረት በተንኮል የፈጠሩት ዘዴ ሆኖ እያለና ተጠሪም የልጆቹ መወለድና በሕይወት መኖር በተጨባጭ ባላረጋገጡበት እንዲያውም ወራሾች ናቸው የተባሉት በአካል ቀርበው ውርስ ባልጠየቁበት የፀደቀ በመሆኑ እና ሚች ወንድማችን ያለ አመልካቾች ሌላ ወራሽ የሌለው መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝና ሰበር ችሎቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ የሚች ልጆች እያሉ ወንድሞች ወራሾች ሊሆኑ ስለማይገባ የስር ፍርድ ቤቶች የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁን ተጠሪ ሚች ልጆች ላይ ባቀረቡት ክስ ጉዳዩን በሌሉበት ታይቶ ልጆች የሚች አባታቸው ወራሽ ናቸው በማለት ውሳኔ መሰጠቱ ግልፅ ነው፡፡ በሌላ በኩል የአሁን አመልካቾች የወንድማቸው ሚች አቶ ዮሴፍ ሐጎስ ወራሾች መሆናቸው በፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ እዚህ ሊታይ የሚገባው ነጥብ የወራሽነት ሰርተፊኬት በፍርድ ቤት ከተሰጠ በኋላ እውነተኛ የሚች ወራሽ ነኝ በማለት መቃወሚያ ሊቀርብበት የሚችል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በፍ/ህ/ቁ 996 (1) ወራሽ የሆነ ሰው ለሚቹ ወራሽ መሆኑንና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመላክት የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፍርድ ቤት ማመልከት የሚችል ሲሆን የተሰጠው የወራሽነት ምስክር ወረቀትም በፍ/ህ/ቁ/998(1) በተመለከተው

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሁኔታ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በፍ/ህ/ቁ/999 በተደነገገው መሰረት አንድ ሰው ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው ውርሱን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ ያደረገ እንደሆነ እውነተኛው ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት የውርስ ንብረቶች እንዲመለሱለት የወራሽነት ጥያቄ ክስ ማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ የውርስ ሰርተፊኬት አንድ ሰው የራሱን ወራሽነት ለማስረዳት የሚወስደው ማስረጃ እንጂ ሌሎች ወራሾች አለመኖራቸውን የሚሳይ ሰነድ አይደለም፡፡ በግራ ቀኙ የሚች ወራሾች መሆናቸው በማረጋገጥ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከማስረጃነት በዘለለ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ በሚያዘው መሰረት ከሌሎች ሰዎች ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ ያገኘና በፍርድ ያለቀ መቃወሚያ የማይቀርብበት ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም፡፡ ስለሆነም ትክክለኛ የሚች ወራሽ ማነው? የሚለውን ጭብጥ ተገቢውን ማጣራት ከተደረገበት በኋላ ነው እውነተኛ ወራሽ መለየት የሚቻለው፡፡ ስለዚህ ወራሾች የተባሉትን ግራ ቀኙ ባሉበት የሚች እውነተኛ ወራሽ ማን ነው? የሚለውን ጭብጥ ማጣራት ሳይደረግበት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 77320 ጥር 18 ቀን 2008 ዓ/ም የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 17334 ሰኔ 24 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በመሻር የዓይደር ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 4884 የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በትግራይ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበርሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 83740 ሚያዝያ 4 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የስር ፍርደ ቤቶች የአሁን ተጠሪ ግማሽ ድርሻ እንዲያገኙ የሰጡት ውሳኔ ክፍል በማፅናት፤የሚች አቶ ዮሴፍ ሐጎስ ድርሻ አመልካቾች ሊወርሱ አይገባም፤የልጆቹ ድርሻ ነው በማለት የተሰጠ ውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
3. የዓይደር ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የሚች ድርሻ ለመውረስ ትክክለኛ ወራሽ ማስረጃ የያዘ ማንነው ወይም የሚች እውነተኛ ወራሽ ማን ነው? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ፤የሚች ልጆች የተባሉት ስነስርዓት ህጉ መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥሪ ተደርጎላቸው ባሉበት ተገቢው ማጣራት አድርጎ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 137869

ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ቦንሲቱ ዱፌራ - ተወካይ አቶ ዓለማየሁ ዱፌራ -ቀረቡ ።

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ታምሪ ረጋሳ - ተወካይ አቶ ጋረደ አርጋሳ ቀረቡ ።

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

የክርክሩ ምክንያት ውርስ ይገባኛል የሚል ነው። የአሁኗ ተጠሪ በወሊሶ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆኑ አመልካች ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ ነበሩ። የክርክሩ መነሻ በአጭሩ የአሁኗ አመልካችና የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት ብርቁ ዱፌራ የሚች ባለቤቱ ልጆች ሆነው ንብረትና ይዞታ ከውርስ በማያያዝ የሚስትነት ድርሻዬን ሳያካፍሉኝ ስለያዙ እንዲለቁልኝ የሚል ነው።

የአሁን አመልካች ከሥር ሁለተኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን ያቀረቡት መልስ የቀረበው የጋብቻ ውል አባታችን የፈረመ አይደለም በማለት ተከራክረዋል። የወረዳ ፍርድ ቤት ግራ ቀኝ ክርክር አዳምጦ የሰው ማስረጃም ሰምቶ ከሳሽ የተከሳሾች ሚች አባት ሚስት ስለሆኑ የከሳሽን ድርሻ ይልቀቁላቸው በማለት ወስኖአል።

ይህንን ውሳኔ በመቃወም የሥር 1ኛ ተከሳሽ /የአሁኗ አመልካች /ይግባኝ ወስደው የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሳሽ ያቀረቡት የጋብቻ ውል በተከሳሽዋ በኩል የአባታችን ፊርማ አይደለም ተብሎ ተክዶ እያለ በሰነድ ምርመራ ላቦራቶሪ በኩል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይለይ የተሰጠው ውሳኔ ጉድለት አለው በማለት የሚች ውል ፊርማ የተካደው ተመርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በነጥብ ተመልሷል።

የወሊሶ ወረዳ ፍርድ ቤት የጋብቻ ውሉን ለኦሮሚያ ፖ/ሊስ ኮሚሽን ከላከ በኃላ የውሉ አርጂናል እንዲቀርብ በፖ/ሊስ በኩል በመጠየቁ የሥር ከሳሽ /የአሁኗ ተጠሪ/ አርጂናሉን /ዋናውን/ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ያለው ኮፒ መሆኑን በመግለጻቸው ከሳሽ ለማቅረብ ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን ተገንዝበን የቀረበው ክስ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ከሳሽ /ተጠሪ/ የሚች ዱፌራ ሰርቤሳ ሚስት አይደለችም ብለን የቀረበውን ክስ ውድቅ አድርገናል፣ሌላ ግንኙነት ካላቸው በንብረትና በይዞታ ጉዳይ ላይ ያሉዋቸውን መብት ከሳሽ ለማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግድም በማለት ወስኗል።

ይህን ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ጋብቻን ማረጋገጥ የሚቻለው በጋብቻ ወረቀት ሲሆን የጋብቻ ወረቀት ማስረጃ በሌለ ጊዜ ግን የጋብቻ ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ጋብቻ መኖርን ለማስረዳት እንደሚቻል የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለው አንቀጽ 93 /1/ ይደነግጋል። በይግባኝ ባይ /በአሁኗ ተጠሪ/ እና በተቃዋሚዎች አባት መካከል ጋብቻ መኖሩን ግራ ቀኝ ማስረጃዎች በሥር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ቀርበው መስክረዋል። በሌላ በኩል ሚች ለአሁኗ ተጠሪ ሚስቱ ነች ብለው ሲፈርሙላቸው ማየታቸውን በተጨማሪ ገልጸዋል። ስለሆነም በአሁኗ ተጠሪ እና በሚች ዱፌራ ሰርቤሳ መካከል ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ ጋብቻ መኖሩ ስለተረጋገጠ የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ የባለቤትነት ድርሻቸውን እንዲለቁላቸው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻር ወስኗል። የአሁኗ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ተቀብሎ ካከራከረ በኃላ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቷል። በመቀጠልም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበው ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከክፍተኛ ፍርድ ቤት እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጡትን ውሳኔ ለማስቀየር ሲሆን አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ተፈጽሞውብኛል ያሉዋቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ ተጠሪ ከሚች ጋር በጋራ ያፈሩት ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች በተመለከተ ግራ ቀኙ ባልተከራከሩበትና ምንም ማስረጃ ቀርቦ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ የሚስትነት ድርሻዋን እኩል ትካፈል ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በተወካያቸው በኩል በቀን 13/08/2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ የሰጡ ሲሆን የአመልካች ተወካይም በቀን 18/9/2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን በውሳኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ክርክሩ አስቀድሞ እስከ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት ድረስ ደርሶ የጋብቻ ውል ተጣርቶ እንዲወሰን የተመለሰ ሲሆን የወረዳ ፍርድ ቤትም የጋብቻ ውሉ ኮፒ ስለሆነ ኦርጂናሉ ካልቀረበ የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ፊርማውን ለመመርመር ያለመቻሉን ገልጾ ተጠሪ ኦርጂናል ውል እስካላቀረቡ ድረስ ተጠሪ የሚች ዱፌራ ሰርቤሳ ሚስት አይደሉም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ክርክር ላይ ትኩረት የተሰጠው ሚስትነት ክርክር ላይ እንጂ በንብረት ክርክር ላይ አይደለም፡፡ የንብረት ክርክር የሚደረገው የሚስትነት ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥ እንጂ አስቀድሞ ሊሆን አይችልም፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ ሚስት አይደሉም የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰ በመሆኑ ስለ ንብረት ጉዳይ ያነሳውም ሆነ በውሳኔው ላይ ያሰፈረው ነገር የለም፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን የተጠሪ ሚስትነት በሁኔታ ተረጋግጧል ካለ በኃላ ንብረትን በተመለከተ ውሳኔ አሳርፎበታል፡፡ ይህ አካሄድ ግራ ቀኙን ክርክር እና የክልሉን የቤተሰብ ህግ ድንጋጌን የተከተለ ነው ወይ? የሚለውን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች ተጠሪ ሚስት ናቸው ቢባል እንኳን ተጠሪ ከአመልካች አባታቸው ጋር ያላፈሩት የአባታቸው ግል ንብረታቸው በመሆኑ ተጠሪ አይመለከታቸውም በማለት ያቀረብነው ክርክር በአግባቡ ሳይጣራ ለተጠሪ ንብረት ይገባቸዋል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ይከራከራሉ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ይህ ክርክር በወረዳ ፍርድ ቤት የተነሳ ቢሆንም ከሚስትነት ክርክር ውጪ ንብረትን በተመለከተ ያልተጣራና ውሳኔ ያላረፈበት ነው፡፡ የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለው የባልና ሚስት ሀብት እንዴት እንደሚጣራ በአንቀጽ 112 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በአንቀጽ 112 (1) *መሠረት* ባልና ሚስቱ የጋብቻቸው መፍረስ በንብረት በኩል የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክተው በሚያደርጉት ስምምነት ወይም በጋብቻ ውላቸው *መሠረት* ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 1 *መሠረት* የተመለከተው የጋብቻ ውል ወይም ሌላ ስምምነት የሌለ ወይም በህግ ፊት የማይፀና ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የባልና ሚስት ሀብት የሚጣራው በአንቀጽ 113 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች *መሠረት* እንደሆነ የድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ ያመለክታል፡፡

በያዝነው ጉዳዩ በተጠሪ እና በሟች ባለቤታቸው አቶ ዱፌራ ሰርቤሳ /በአመልካች አባት/ መካከል ንብረትን በተመለከተ በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ በፍቺም ሆነ በሞት ምክንያት ሲፈርስ ንብረት የሚጣራበትን ሁኔታ በውል ወይም በስምምነት ለይተው ባላስቀመጡበት ሁኔታ አመልካች የሟች አባታችን የግል ንብረት ነው በማለት የሚከራከሩበት ንብረት ሳይጣራ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ የጠየቁት ንብረት ይገባቸዋል ሲል የወሰነው ውሳኔ *መሠረታዊ* የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም በግራ ቀኙ መካከል የተነሳውን የንብረት ይገባኛል ጥያቄ በተመለከተ ሊጣራ የሚገባው በኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለው በአንቀጽ 113 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች *መሠረት* ነው በማለት ይህ ችሎት ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ከተጠሪ ሚስትነት ጋር አያይዘው ያነሱትን ቅሬታ ነጥብ በተመለከተ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪ የሚስትነት ሁኔታ በክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለው አንቀጽ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

93 /1/ መሠረት የጋብቻ ጽሁፍ ባይኖርም ተጠሪ በሌላ አሳማኝ ማስረጃ ስላረጋገጡ ሚስት ናቸው ሲል የደረሰውን ድምዳሜ ይህ ችሎትም የሚስማማበት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ያሉት ፍርድ ቤቶች ንብረትን በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ በማግኘታችን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ ሲጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 35947 በቀን 24/6/2008 ዓ/ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 239363 በቀን 09/10/2008 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አጣሪ በመ/ቁ. 249031 በቀን 15/3/2009 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. በተጠሪ እና በሟች ባለቤታቸው አቶ ዱፌራ ሰርቤሳ መካከል ጋብቻ ነበረ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. ከላይ በፍርዱ ላይ በግልጽ እንደተገለጸው ክርክር የተነሳባቸው ንብረቶች በአግባቡ ሳይጣሩ የተጠሪ ሚስትነት ድርሻ ይገባቸዋል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሸሯል፡፡
4. ተጠሪ እና ባለቤታቸው ሟች አቶ ዱፌራ ሰርቤሳ በጋራ ያፈሩት ንብረቶች መኖር ያለመኖራቸውን፣ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ማን እንዳፈራቸው? ከጋብቻ በፊት ወይም ከጋብቻ በኃላ የተፈሩ መሆን ያለመሆናቸውን እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮችን በክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 በአዋጅ ቁጥር 83/96 እንደተሻሻለው አንቀጽ 113 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የወሊሶ ወረዳ ፍርድ ቤት አጣርቶ እንዲወስን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መልሰናል፡፡
5. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 135902

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፦

አልማው ወሌ

መ/ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች:- ወ/ሮ መስከረም ጫካ- የቀረበ የለም ከተባለ በኋላ ቀረቡ

ተጠሪዎች፦ 1.አቶ አክሊሉ ሽፈራው -ከማረሚያ ቤት ቀረቡ

2.ወ/ሮ ካኡሬ ከተማ- የቀረበ የለም ከተባለ በኋላ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ ::

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ፦ የባልና ሚስት ፍቺን ተከትሎ የቀረበ የንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በ1ኛተጠሪ ላይ ጥር 26 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር የነበረን ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ ሲሆን ተጠሪ ደብድቦ ጉዳት ስላደረሰብኝ በማረሚያ ቤት የሚገኝ በመሆኑ የጋራ ንብረታችንን ልንካፈል ስላልቻልን በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ 09 ቀበሌ የቤት ቁጥሩ አዲስ የሆነ ከጋብቻችን በፊት ለምልክት የሚሆን ጅምር ቤት የነበረው በጋብቻችን ወቅት ፈርሶ 4 ክፍል ሰርቪስ ቤት የሰራን ስለሆነ እና በጋራ ያፈራነው የቤት ቁሳቁስ ስላለን እንድንካፈል ይወሰንልኝ በተጨማሪም ተከሳሽ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈጸሙ ለጋብቻው መፍረስ ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ጋብቻው እንዲፈርስ በመጠየቁ ደብድቦ ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰብኝ ስለሆነ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 84 መሰረት የጉዳት ካሳ ብር 50,000.00 እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሆኑት የስር ተከሳሽ የሰጡት መልስ ከከሳሽ ጋር ጋብቻ ስንፈጽም የነበረን የጋብቻ ውል የጋራ ሀብታችንን የሚያስረዳልን ነው፤ የክርክሩን ቤት ከሳሽን ከማግባቴ በፊት የሰራሁት የግል ንብረቴ ነው፣ የካሳ ጥያቄውን በተመለከተ በማስረጃ ያልተደገፈ እና በምን ስሌት እንደተሰላም ስለማይታወቅ ውድቅ ይደረግልኝ የሚል ሲሆን የአሁን 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የጣልቃ ገብ ክርክር ከተከሳሽ ጋር በ1988 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመን በኦሮሚያ ክልል የነበረንን ቤት ሸጠን አሁን ክርክር የተነሳበትን ቤት በሰኔ ወር 2002 ዓ.ም ገዝተን ሳለ እኔ የተከሳሽን አባት ለማስታመም ገጠር በሄድኩበት ከሳሽ እና ተከሳሽ በዚህ ቤት አብረው የኖሩበት ቢሆንም ምንም አይነት መሻሻል ያልተደረገበት እና ቤቱንም እኔ እና ተከሳሽ በትዳር እያለን ያፈራነው ስለሆነ የቤቱ ግማሽ ድርሻ እንዳገኝ ይወሰንልኝ በማለት የጣልቃ ገብ ክርክራቸውን አቅርበዋል።

ፍርድ ቤቱም በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የቤቱ ቁሳቁስ ክርክር ያልቀረበበት ስለሆነ ከሳሽ እና ተከሳሽ እንዲካፈሉ ሲወስን የክርክሩን ቤት በተመለከተ ከሳሽ እና ተከሳሽ በባህላዊ ጋብቻ ሲጋቡ በሀብትሽ በሀብቴ በ80 ውል የተጋቡ መሆናቸውን የሚገልጽ የጋብቻ ውል የቀረበ ስለሆነ፤ የክርክሩን ቤት ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር ከመጋባታቸው በፊት ተከሳሽ እና ጣልቃ ገብ በትዳር እያሉ የገዙት መሆኑን እና ከሳሽ እና ተከሳሽ አብረው ሲኖሩበት ቤቱ ላይ የተለያየ እድሳት የተደረገበት መሆኑም ጭምር በምስክሮች ተረጋግጧል በማለት አትቶ ቤቱ የታደሰበትን ወጪ በተመለከተ ከሳሽ ከተከሳሽ ባለቤታቸው ጋር አብረው ሲኖሩ የተጠቀሙበት ግምት ቤቱ ከታደሰበት ወጪ የሚያንስ አይሆንም፤ ስለሆነም አለ የተባለው የእድሳት ወጪ የሚቻቻል ነው ብሎ ቤቱን በተመለከተ ግራ ቀኙ እንዲከፋፈሉ ውሳኔ ሰጥቷል። የካሳ ጥያቄውን በተመለከተ በዚህ መዝገብ የሚታየው የጋብቻ ፍቺ ውጤት በሆነው የጋራ እና የግል ንብረት ላይ በመሆኑ የካሳ ጉዳይ ባለመሆኑ ሊወሰን አይገባም ተብሎ ታልፏል።

የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ የክርክሩን ቤት የእድሳት ወጪ በተመለከተ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ እና ተከሳሽ በቤቱ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲኖሩ ከተጠቀሙበት ጥቅም ጋር ይቻቻል በማለት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ለቤቱ እድሳት እና ለማሻሻያ ስራው የወጣው ወጪ በባለሙያ ተገምቶ ግማሹን 1ኛ መልስ ሰጭ ለይግባኝ ባይ እንዲከፍሉ እንዲወሰን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት መልሶ ልኮለታል፡፡

የአሁን አመልካች ለዚህ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት በነዚህ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም የክርክሩ ቤት የኔ እና የ1ኛ ተጠሪ እንጂ 2ኛ ተጠሪን የሚመለከት ባልሆነበት ለ3 እንድንካፈል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እና ያቀረብኩትን የካሳ ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ሳይወስኑ ማለፋቸው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የፈጸሙ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎትም መዝገቡን መርምሮ ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሁፍ መልስ እና የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም በግራ ቀኙ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤቶች ካቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሰበር አጣሪው ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረነዋል፡፡

የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ የክርክሩን ቤት በተመለከተ የኔ እና የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ቤቱ ግን የአሁን አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ከመመስረታቸው በፊት የተሰራ መሆኑን በማመን አመልካች በሰጡት ቃል የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ይህንን ቤት በሀብትሽ በሀብቱ የባህላዊ የጋብቻ ውል የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት እንዳደረጉት እና በጋብቻቸው ጊዜም በክርክሩ ቤት ላይ ተጨማሪ ስራ መስራታቸው እና አመልካች እና 1ኛ ተጠሪም ከመጋባታቸው በፊት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በጋብቻ የነበሩ መሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ተደርጎ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡

በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ በነበሩበት ጊዜ የተፈራ ንብረት መሆኑ በመረጋገጡ፣ በፌደራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 62(1) መሰረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባል እና ሚስት በጋብቻቸው ጊዜ የተፈራ ንብረት የ1ኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው እስካለተብለ ድረስ የጋራቸው እንደሆነ የሚገመት መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ንብረቱ በተጠሪዎች ጋብቻ ጊዜ የተፈራ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት እንደሆነ በህጉ የሚገመት ሲሆን በ1ኛ ተጠሪ በኩል የክርክሩ ቤት የግል ንብረቴ ነው በማለት ተቃራኒ ክርክር ያልቀረበ ስለሆነ፣ አመልካችም በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 42(1) ተጋቢዎች ንብረታቸውን በተመለከተ በጋብቻ ውል መወሰን እንደሚችሉ በተደነገገው መሰረት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የጋብቻ ውል መነሻነት እና ከጋብቻቸው በኃላ በቤቱ ላይ በሰሩት ተጨማሪ ስራ የቤቱ የጋራ ባለሀብትነትን ይመሰርታሉ፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች በክርክሩ ቤት ላይ የባለቤትነት መብት ያላቸው መሆኑ በፍሬ ነገርም ሆነ በህግ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን ክፍፍሉን በተመለከተ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በነበራቸው ጋብቻ ላይ ህግ የሚከለክለውን በጋብቻ ላይ ጋብቻ በመፈጸም አመልካችን ያገቡ እና አመልካችም 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ትዳር እንዳላቸው ሳያውቁ ያገቧቸው እና 2ኛ ተጠሪም 1ኛ ተጠሪ ባለቤታቸው ሌላ ትዳር መመስረታቸውን ሳያውቁ በላያቸው ላይ አመልካችን ያገቡባቸው ከመሆኑ አንጻር በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተወስኖ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊሻሻል ይገባል ብለናል፡፡ ሌላው እና በአመልካች የቀረበውን የጉዳት ካሳ ጥያቄን በተመለከተ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎቱ የባልና ሚስት ፍቺን ተከትሎ የሚመጣ የንብረት ክፍፍልን የሚመለከት በመሆኑ የጉዳት ካሳ ጥያቄውን በዚህ ችሎት መወሰን አይቻልም በማለት ሳይወስን ማለፉ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ምንም ሳይወስን ማለፉ የጉዳት ካሳው ጥያቄ ከጋብቻ ፍቺው ጋር ተያይዞ የቀረበ እና ጉዳቱም የደረሰው ከፍቺው ጋር ተያይዞ መሆኑን አመልካች በስር ክርክራቸውም እያነሱት የቤተሰብ ህጉም ይህንኑ የካሳ ክፍያ ሊወሰን እንደሚገባ ደንግጎት እያለ እና አመልካችም ይህንኑ የቤተሰብ ህግ ላይ የተደነገገውን ድንጋጌ ጠቅሰው አቅርበው እያለ የስር ፍርድ ቤቶች በክርክሩ ላይ ተገቢውን ሳይወስኑ የሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 40986 ጥር 19 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 176260 ጥቅምት 30 ቀን 2009 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. በአጠቃላይ የንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ የክርክሩን ቤት ግምት 25 ፐርሰንት ለአሁን 1ኛ ተጠሪ ሆኖ የተቀረውን 75 ፐርሰንት አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ እኩል ይካፈሉ ብለናል፡፡

3. የጉዳት ካሳ ጥያቄውን በተመለከተ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አከራክሮ እና በማስረጃ አጣርቶ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል ይፃፍ፡፡

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5. የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 138837

ጥር 23 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ /ዶ/ር/

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች-----1ኛ አቶ ብሩክ ገ/ሥላሴ ቀረቡ

2ኛ አቶ ገ/ህይወት በርሄ አልቀረቡም

ተጠሪ----------አቶ ዳዊት ተሰማ ቡታ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በመኪና ሽያጭ ውል መነሻነት የታጣ ጥቅም ሊከፈለኝ ይገባል በሚል በአሁን አመልካቾች ከሣሽነት በተጠሪ ተከሣሽነት በስር የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀረበው ክስ የተሰጠው ውሣኔ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ በመሻሩ መነሻነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት ቀርቦ የነበረው ክስ እንደሚያስረዳው በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል የመኪና ሽያጭ ውል ተፈጽሞ የነበረ ሲሆን፣ የሠ.ቁ. 03-02-50764 ኢት የሆነውን ትራክተር የጭነት ተሽከርካሪን ለንግድ ሥራ አገልግሎት የሚውል በብር 1,700,000.00/ አንድ ሚሊዩን ሰባት መቶ ሺ ብር/ በ19/04/2006 ዓ.ም. በተፃፈ ውል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሽያጭ መፈፀማቸውን እና ከዚህ ገንዘብ ላይ ብር 500,000.00/ አምስት መቶ ሺ ብር/ ወዲያው ከፍለው መኪናውን መረከባቸውን፣ ቀሪ ገንዘቡን ስመ ንብረቱ ሲዛወር ሊከፍሉ መስማማታቸውን፣ መኪናው ከውጭ ሲገባ ቀረጥ ያልተከፈለበት በመሆኑ ለሥራ ሳይሰማራ መቆየቱን ገልፀው በ27/2/2007 ዓ.ም. የተፃፈ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን፣ ሆኖም ቀድመው አድርገውት የነበረውን ውል በመተው በ9/7/2007 ዓ.ም. ሌላ ውል መስማማታቸውን፣ የውሉም ይዘት ተሸከርካሪው ከተገዛበት ዋጋ ውስጥ አሁንም በውሉ ዕለት 850,000.00 ወዲያውኑ ከፍለው ከሣሽ ከዳሽን ባንክ ተሸከርካሪውን በዋስትና አስይዘው የተበደረውን ገንዘብ 500,000.00 ዕዳ ነፃ አድርገው ብር 140,000.00 በቼክ ቁጥር 3425633 በሆነ በቀን 09/07/2008 የተፃፈ ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ እንዲወስድ የሰጡት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የቀረጥ ገቢ ዕዳ ብር 200,000.00 መሆኑን ተከሣሽ የነገሯቸው በመሆኑ ከሽያጭ ገንዘቡ ላይ እንዲቆርጡ መስማማታቸውን፣ ሆኖም ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲጠይቁ 200,000.00 ሣይሆን ብር 489,000.00 /አራት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ ብር/ መሆኑ መገለፁን፣ በመሆኑም ብር 132,000.00/ አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ ብር/ ከተስማሙት ልዩነት የፈጠረ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ ከፍለው ስም እንዲያዛውሩ ቢጠይቋቸው ሊፈጽሙላቸው ያልቻሉ በመሆኑ በመኪናው ተጠቅመው ሊያገኙ የሚገባቸውን ጥቅም ያሳጧቸው በመሆኑ፣ ተሸከርካሪው በቀን ብር 6,000.00፣ በወር 180,000.00 የሚያስገባ በመሆኑ ገቢው በ8 ወር ተባዝቶ ብር 1,440,000.00/ አንድ ሚሊዩን አራት መቶ አርባ ሺ ብር/ ያጣነውን ገቢ እና ውሉን በማፍረሱ ምክንያት 20,000.00/ ሃያ ሺ ብር/ መቀጮ ጨምረው በድምሩ ብር 1,490,000.00/ አንድ ሚሊዩን አራት መቶ ዘጠና ሺ ብር/ እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው ክስ ማቅረባቸውን ተመልክተናል፡፡

ተከሣሽም ባቀረቡት መልስ መኪናውን የሸጥኩት ከቀረጥ ነፃ ለኢንቨስትመንት ያስገባሁት መሆኑን ነግሬ የቀረጡን ሊከፍሉ ተስማምተን ነው፡፡ እንድረዳቸው ጠይቀውኝ ሌላ ውል ተዋውለናል፡፡ ከመኪናው ዋጋ ላይ ብር 210,000.00/ ሁለት መቶ አስር ሺ ብር/ ቀንሼላቸው ተዋውለናል፡፡ ስለሆነም ክሱ ተገቢ አይደለም፡፡ የታጣውን ጥቅም መጠን በተመለከተም ተሸከርካሪው ከ9/7/2007 ዓ.ም. እረፍት እና ሰርቪስ ሳያስፈልግ እና ዕቃ ለመጫን እና ለማውረድ የሚቆምባቸው ቀናቶች ሳይታሰቡ በቀጣይነት የቀን ገቢ ብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

6,000.00 ይገኛል በማለት የጠየቁት ገቢ እና በውሉ መሠረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ያልተወጡት ከሣሾች ሆነው እያለ ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የጠየቁት ቅጣት ብር 20,000.00 የሕግ መሠረት ስለሌለው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በቃል ማከራከሩን እና የቀን ገቢውን ለማወቅም ተመሳሳይ ሥራ ከሚሰሩ ድርጅቶች በመጠየቅ እና በማስቀረብ ተከሣሽም አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ መዝገቡን መመርመሩን፣ ከተደረገው ክርክር እና ከቀረበው ማስረጃ በመነሳትም ለደረሰው ጉዳት ተከሣሽ ኃላፊ መሆኑን እና ጉዳቱም መካስ ያለበት በመሆኑ ከሣሾች ያጡትን ገቢ በቀረበው ማስረጃ መሠረት በማስላት እና ከተጠየቀው በመቀነስ ብር 132,000.00/ አንድ ሚሊዩን ሶስት መቶ ሃያ ሺ ብር / የ8 ወር ገቢ ተከሣሽ እንዲከፍል መወሰኑን ወደፊት ስም እስኪዛወር ድረስ የሚታሰብ መሆኑን በመግለጽ መወሰኑን የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 226982 ሰኔ 28 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው የውሣኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

የስር ተከሣሽ/ ተጠሪ/ ይግባኝ ብለው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና ጉዳዩን መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል በሕግ በተከለከለ ነገር ላይ የተፈፀመ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1678/ለ/ እና 1716/1/ መሠረት ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ በውሉ የተመከተው ግዴታ በአግባቡ አልተፈፀመም በሚል ምክንያት ይ/ባይ በውሉ መሠረት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 231/1/ሀ/ መሠረት የክስ ምክንያት የሌለው መሆኑን ገልፆ ነገር ግን ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ለመመለስ የሚያቀርቡትን ክስ የውሣኔው ግልባጭ የማያግድ መሆኑን በመግለጽ እና የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በመሻር መዝገቡን መዝጋቱን የመ/ቁ/ 131429 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ይህን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ በመቃወም እና በውሣኔው ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት አመልካቾች የካቲት 05 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- ሙሉ የክርክሩን ይዘት በመግለጽ ሊታረም ይገባዋል ሲሉ ያቀረቡት የህግ ስህተት የሚያመለክተው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 130 ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ ሀገር ለኢንቨስትመንት የገባ ዕቃ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊሸጥ ሊለወጥ ወይም ለ3ኛ ወገን መተላለፍ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ መተላለፍ የሚችልበትን አግባብ ደግሞ ዕቃው ሲሸጥ ያለበትን ቀረጥ በመክፈል እንደሆነ ደንግጓል፡፡ በአመልካቾች እና በተጠሪ መሃከል የተደረገው ውል ደግሞ ውል የተደረገበት ተሽከርካሪ ላይ ያለው ቀረጥ ብር 210,000.00 ብቻ ነው ወክላችሁኝ ቀረጡን ክፈሉ ብለው ከሸያጩ ብር ላይ ቆርጠን ተክተናቸው ልንከፍል ስንንቀሳቀስ ዕዳው ከተጠቀሰው በላይ 130,000.00 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ አከራካሪ ጭብጥ የነበረው በውሉ ላይ ከተገለጸው በላይ የሆነው የቀረጥ ብር ማን ይክፈል ቀረጡ ባለመከፈሉ ተሽከርካሪው በመቆሙ የታጣ ገቢ መክፈል የማን ግዴታ ነው የሚል ነው፡፡ አዋጁ የሚያስቀምጠው ከቀረጥ ነፃ የገባን ዕቃ መሸጥ ከተፈለገ ቀረጡን ቅድሚያ ከፍሎ ነፃ ማድረግ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የሰጠው ትርጉም የተሳሳተ ነው እንዲባልልን የሚሉ እና ሰፊ የይታረምልን ጥያቄን አንስተዋል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል በህግ የተለከለከ ነው በሚል የከሳሾች/አመልካቾች/ የስር ክስ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ሊመረመር ይገባል በማለት በማስቀረቡ ሊቀርብ ችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት የቀረበው አቤቱታ እና የማስቀረቢያ ነጥቡ ለተጠሪ እንዲደርስ እና የመከላከያ መልስ እንደያቀርቡ ከመጥሪያ ጋር የተላከላቸው ሲሆን ተጠሪም ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበው ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ አጠቃላይ ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በግራ ቀኙ መካከል ሁለት ጊዜ የሽያጭ ውል ክርክር ባስነሳው ተሽከርካሪ ላይ የተፈፀመ መሆኑ ያለማከራከሩን እና የመጀመሪያውን ውል ሁለተኛው ውል መተካቱን አመልካቾችም መኪና ከተጠሪ ተረክበውም ሙሉ ገንዘብ ባይሆንም ክፍያ መፈፀማቸውን ፣ የተሸጠው መኪና ግን ለኢንቨስትመንት የገባና ቀረጥ ያልተከፈለበት የነበረ መሆኑ አላከራከራቸውም፡፡ነገር ግን መታየት የሚገባው በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል ውል ለማድረግ በተፈቀደ ነገር ላይ የተደረገ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው ወይንስ አይደለም የሚለውን ሲሆን፣ ይህን አስመልክቶ ከተነሳው ክርክር ጋር አግባብነት ያለው ድንጋጌ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 30/1/ እንደሚደነግገው ከቀረጥ ነፃ የገባን ተሽከርካሪ መሸጥን የሚከለክል ባይሆንም ነገር ግን መሸጥ ከተፈለገ ቀረጡን ከፍሎ ነፃ ካደረገ በኋላ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን በግራ ቀኙ መካከል ግን የሽያጭ ውሉ የተደረገው ቀረጥ ሳይከፈልበት በፊት ውሉ የተደረገ እና ቀረጥ ያልተከፈለበት መሆኑ ሲረጋገጥ ደግሞ የቀድሞውን የሽያጭ ውል በሌላ ውል በመተካት ቀረጥ እንዲከፈልበት የተዋዋሉ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ከክርክሩ መረዳት ይቻላል፡፡

የህጉ አላማ ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር የሚገቡ ንብረቶች አንድን አላማ ለማሳካት ሲባል እንጂ እንደተፈለገ ሊሸጡ ሊለወጡ ወይም ለ3ኛ ወገን እንደማንኛውም ንብረት ሊተላለፉ የማይችሉ መሆናቸውን በማሰብ ሲሆን ይህን ለመቆጣጠር እና መንግሥትም ይህ ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ አገር የገባ ዕቃ ለታሰበለት አላማ ሳይውል ሲቀር በቀረጥ ነፃ መብት የሚጠቀመው ሰው ፣ወይንም የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በዛ ንብረት ላይ ያለውን የቀረጥ ነፃ መብት በመጠቀም ለሌላ እንዳያስተላልፍ ሊቆጣጠርበት እና ቀረጡን ማስከፈልና ገቢውን መሰብሰብ ተገቢ መሆኑን በመረዳት ከማንኛውም ዝውውር በፊት ቀረጡ እንዲከፈል አስገዳጅ ሁኔታን ማስቀመጡን እንረዳለን፡፡

ከዚህ ይህ ድንጋጌ ከተቀረፀበት አላማ አንፃር ስንመለከተው ከቀረጥ ነፃ መብትን በመጠቀም ወደ አገር የገባን ዕቃ ወደ ሌላ ማስተላለፍ ከተፈለገ ቀድሞ ቀረጡን በመክፈል ነፃ ማድረግን የሚጠይቅ በመሆኑ ይህ ሳይደረግ ወደሌላ ማስተላለፍ ግን በራሱ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ጥብቅ ክልከላ የተደረገበት መሆኑን ከድንጋጌው መረዳት የሚቻል በመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የመኪና ሽያጭ ውል በህግ ክልከላ በተደረገበት ነገር ላይ የተፀመ ነው በማለት የቀረበውን ክርክር የስር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ የሚነቀፍ እና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚያበቃ ሕጋዊ ምክንያት ባለመገኘቱ ሊፀና የሚገባው ነው ብለን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 131429 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ የተፈፀመበት መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
4. መዝገቱ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 131900

ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ

እንዳሻው አዳነ

እትመት አሠፋ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ዋዝሞ ዋሲራ

አመልካች፡- የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ኃይለመለኮት አበበ

ተጠሪ፡- የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር

- ጠበቃ ቢኒያም ተርፋ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28 መሠረት በተሰጠው የኪሣራ ማሸጋገር መብት መሠረት የኪሣራ ማካካሻ ከተደረገ በኋላ ቀሪው የትርፍ ግብር ብር 847,134.47 /ሥምንት መቶ አርባ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሠላሣ አራት ብር ከአርባ ሰባት ሳንቲም/ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ገቢ ከተደረገ በኋላ ተጠሪ የስም እና የካፒታል ለውጥ አድርጓል ከሚል መነሻነት አመልካች መሥሪያ ቤት የኪሳራ ማካካሻ አልቀበልም ማለቱ ተገቢ ስላልሆነ ሊሻር ይገባል በማለት ያቀረበውን ቅሬታ የተመለከተው የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የተጠሪ ስም እና የካፒታል መጠን የተቀየረው ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም በመሆኑ እና አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1 መሠረት በአንድ የግብር ዘመን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ በዚያው የግብር ዘመን ውስጥ በሚቀጥሉት የግብር ዘመናት ከተገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ የሚካካስ ይሆናል በማለት የደነገገ በመሆኑ ተጠሪ ኪሳራው ሊካካስለት ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የተጠሪ የስም እና የካፒታል ለውጥ የተደረገው የ2004 ዓ.ም የግብር ዘመን በተዘጋ በሁለተኛው ቀን ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም ነው፤እንደ ተጠሪ ዓይነቱ ድርጅት የካፒታል መጠን ከ25% በላይ ለማሣደግ ውስብስብ ሂደቶችን የሚጠይቅ ሆኖ ሳለ ተጠሪ የበጀት ዘመኑ ከተዘጋ ከአንድ ቀን በኋላ የካፒታል ለውጡን ያደረገ መሆኑ እና ድርጅቱ ቀደም ባሉት ዘመናት ለደረሰበት ኪሣራ ማካካሻ ሲደረግለት የነበረ መሆኑ ሲታይ ተጠሪ ግብርን ለማስቀረት የኪሳራ ማካካሻ ለማግኘት ከቅን ልቦና ውጪ አስቦ የፈጸመው መሆኑን የሚያሳይ ነው፤በመሆኑም ተጠሪ ግብርን ለማስቀረት ከቅን ልቦና ውጪ በመንቀሳቀስ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ ከአንድ ቀን በኋላ ለውጡን ያደረጉ ቢሆኑ ለውጡ የተደረገው በ2004 ዓ.ም እንደሆነ ስለሚቆጠር በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/2 መሠረት ቀደም ሲል ለነበሩት ዓመታት የተሰጠው የኪሣራ ማካካሻ መብት የተቋረጥ ነው በማለት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ቸሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የተጠሪ ሥም እና ካፒታል የተለወጠው ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም በ2005 ዓ.ም በጀት ዘመን በመሆኑ፤የኪሣራ ማካካሻ በማድረግ ሂሳቡን የዘጋው ከ2001 እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ በመሆኑ እና የኪሳራ ማካካሻ ካደረገ በኋላ ያገኘው ትርፍ ለአመልካች የከፈለ በመሆኑ ከ2005 ዓ.ም በፊት ላለው ዕዳ ሊጠየቅ አይችልም በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ ከመንግሥት ወደ ግል ባለቤትነት በሽያጭ ሲዘዋወር በአቶ አካሉ ገለታ በብር 18,600,000 /አሥራ ሥምንት ሚልየን ሥድሥት መቶ ሺህ ብር/ ተገዝቶ በዚሁ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥሙ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ቆይቶ ሠኔ 26 ቀን 2004 ዓ.ም በተፈረመ እና ሐምሌ 02 ቀን 2004 ዓ.ም በውልና ማስረጃ በጸደቀ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ቀደም ሲል ፋብሪካው የተገዛበት ገንዘብ እና በወ/ሮ መሠለች ኪዳኔ በተዋጣ ብር 15,600,000 / አሥራ አምሥት ሚልየን ሥድስት መቶ ሺህ ብር / በድምሩ ብር 34,200,000 / ሠላሳ አራት ሚልዮን ሁለት መቶ ሺህ ብር / በሆነ ካፒታል የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ ሀላፊነቱ የግል ማሕበር በሚል የተቋቋመ በመሆኑ ቀደም ሲል የነበረውን ፋብሪካ የካፒታል ባለቤትነት ድምጽ የመሥጠት መብት በዋጋ ወይም በቁጥር ከ25% በላይ ለውጦታል፡፡ የ2004 ዓ.ም የግብር ዘመን ግብር የሚከፈለው ከሐምሌ 01 ቀን 2004 ዓ.ም እሥከ ጥቅምት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ በመሆኑ ተጠሪ የ2002 ዓ.ም የ2004 ዓ.ም የግብር ዘመን ሲከፍል ኪሳራውን ያሸጋገረበት ጊዜ ተጠሪ በካፒታል ከ25% በላይ በተለወጠበት ጊዜ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/2 የካፒታል ባለቤትነት ወይም ድምጽ የመሥጠት መብት ከ25% በላይ ከተለወጠ ድርጅቱ በዚያው የግብር ዘመንም ሆነ ቀደም ባሉት የግብር ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት የኪሣራ ማሸጋገር መብቱ እንደሚቋረጥ በግልጽ የደነገገ ሆኖ ሳለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪ ሥም እና ካፒታል የተለወጠው ከ2001 እሥከ 2004 ዓ.ም ድረስ ባሉት የግብር ዘመናት ግብር ከፍሎ አጠናቆ ከዘጋ በኋላ ነው በማለት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የተጠሪ የኪሣራ ማሸጋገር መብት የተቋረጠ መሆን አለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28 (1) እና (2) ድንጋጌ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት አንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ አንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/2 ሕጉ ባስቀመጠው መሥፈርት እና መጠን በግብር ዘመኑ ውስጥ ለውጥ ቢደረግ በግብር ዘመኑም ሆነ ቀደም ባሉት ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት ኪሣራ የማሸጋገር መብቱ ይቋረጣል የሚለው ድንጋጌ ለውጡ የተደረገው በግብር ዘመኑ ውስጥ መሆን እንዳለበት በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በኢትዮጲያ ሕግ የግብር ዘመን የሚባለው ከሐምሌ 01 ቀን እስከ ሠኔ 30 ቀን ድረስ ነው፡፡ በሕግም ሆነ በአፈጻጸም አንደሚታየው የግብር መክፈያ ወቅት የግብር ዘመኑ አልቆ የቀጣዩ የግብር ዘመን መጀመሪያ ወር ላይ በመሆኑ በ2004 የግብር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዘመን ለተሰራ ሥራ ግብርን አስታውቆ የሚከፈለው በ2005 ዓ.ም የግብር ዘመን መጀመሪያ ወራት ላይ ነው። በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 28/2 መሠረት የኪሣራ ማሸጋገር መብት ሊቋረጥ የሚችለው የ2005 ዓ.ም የግብር ዘመን ለመክፈል ስንቀርብ እንጂ የ2004 ዓ.ም ግብር ለመክፈል ስንቀርብ አይደለም በማለት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል።

የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ የካፒታል መጠኑን ከ25% በላይ በማሳደግ የኢትዮጲያ ቅመማቅመም ፋብሪካ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚል የተቀየረ መሆኑን ግራ ቀኙን አላከራከረም። በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች የተለያዩ ውሳኔዎችን ሊሰጡ የቻሉት የተጠሪ የካፒታል መጠኑ ከ25% በላይ ያደገው በ2004 ዓ.ም ወይም በ2005 ዓ.ም የበጀት ዓመት ነው ከሚል መነሻነት ቢሆንም ምላሽ የሚያስፈልገው ዋነኛ ጭብጥ በአዋጁ አንቀጽ 28 ላይ የተሰጠው ኪሳራን የማሸጋገር መብት በመብቱ ተጠቃሚ የሆነው ኩባንያ አስቀድሞ ከነበረበት ኪሣራ በመውጣት የካፒታል ባለቤትነት መብቱ ወይም ድምጽ የመስጠት መብቱ ከ25% በላይ ባደገ ጊዜ ቀሪ ሊደረግ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ነው።

በመሠረቱ በአዋጁ የተሰጠው የኪሣራ ማሸጋገር መብት ኩባንያዎች ኪሣራ ውስጥ በገቡ ጊዜ ከገቡበት ኪሣራ እንዲወጡ ለማበረታታት እና በገበያው ተወዳዳሪ በመሆን ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ስለመሆኑ ከኪሣራ ማሸጋገር መብት ዓላማ እና ከግብር አዋጁ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ ይቻላል። ኩባንያው በኪሣራ ማሸጋገር መብት ተጠቃሚ ከሆነ በኋላ ከነበረበት ኪሣራ በመውጣት የካፒታል ባለቤትነት መብቱ ወይም ድምጽ የመስጠት መብቱ ከ25% በላይ ያደገ ለመሆኑ በተጨባጭ ከተረጋገጠ አስቀድሞ አግኝቶት የነበረው የኪሣራ ማሸጋገር መብት ቀሪ ሊሆን ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ነጥብ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው መሠረታዊ ነጥብ ነው። ለዚህ መሠረታዊ ነጥብ ምላሽ ለመሥጠት በአዋጁ የኪሣራ ማሸጋገር መብት አስመልክቶ የተቀመጠውን ድንጋጌ መመልከት አስፈላጊ ነው።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1 በአንድ የግብር ዘመን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ በዚያው የግብር ዘመን ውስጥ የታየው ኪሣራ በሚቀጥሉት ሦስት የግብር ዘመናት ከተገኘው ግብር የሚፈጸመው በመጀመሪያ ያጋጠመውን ኪሣራ በኋላ ካጋጠመው ኪሳራ አስቀድሞ በማካካስ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌም በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ የአንድ ኩባንያ የካፒታል ባለቤትነት ወይም ድምጽ የመሥጠት መብት በዋጋ ወይም በቁጥር ከ25% በላይ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተለወጠ እንደሆነ ኩባንያው በዚያው የግብር ዘመንም ሆነ ቀደም ባሉ የግብር ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት የንኡስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ያቋርጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ኩባንያው በደረሰበት ችግር ምክንያት ከገበያ እንዳይወጣ እና ተወዳዳሪ መሆን እንዲችል ተሰጥቶት የነበረው የኪሣራ ማሸጋገር መብት የካፒታል ባለቤትነት ወይም ድምጽ የመሥጠት መብት በዋጋ ወይም በቁጥር ከ25% በላይ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተለወጠ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ኩባንያው አስቀድሞ ከነበረበት ኪሣራ ወጥቶ በተጨባጭ ያደገ መሆኑ የሚገመት በመሆኑ በዚያው የግብር ዘመንም ሆነ ቀደም ባሉት የግብር ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት አስቀድሞ ተሰጥቶት የነበረው ኪሣራ የማካካስ መብት የሚቋረጥ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለውጡ የተደረገው በ2004 ዓ.ም የግብር ዘመን ስላልሆነ አስቀድሞ ያገኘሁት ኪሳራ የማካካስ መብት ሊቋረጥ አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የኪሳራ መብት ዓላማን ያላገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባው ለውጡ የተደረገው በ2005 ዓ.ም የግብር ዓመት ስለሆነ የተጠሪ የኪሳራ ማካካሻ መብት ሊቋረጥ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 124463 ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 166408 ጥር 12 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ግራቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ የየራሣቸውን ይቻሉ።።

መዝገቡ ተዘግቷል።። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 139334

ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነው

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የኢ/ገ/ን/ባለስልጣን

ተጠሪ፡- ሻንዶንግ ሃይወይ ኢንጂነሪንግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር የቀረበው ጉዳይ በአሁኑ አመልካች ተወስኖ የተሰጣቸው የግብር መጠን ላይ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረቡትን ጥያቄ መነሻ ያደረገ ክርክር ነው፡፡ ተጠሪ ለግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ያቀረቡት ቅሬታ ይዘት፡- በሱር ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዋና ተቋራጭነት በሚገነባው የሚሌ ጭፍራ አለወሃ የመንገድ ስራ ማሻሻል 2ኛ ፕሮጀክት በንኡስ ስራ ተቋራጭነት በሰሩበት ጊዜ ዋናው የስራ ተቋራጭ ለመንገድ ግንባታ አገልግሎት የሚውል ግብአት እያቀረበ ስራው ከተሰራ በኋላ በውሉ መሠረት ከንኡስ ስራ ተቋራጭ ገንዘብ እየተቀነሰ የተከፈለ በመሆኑ እንዲሁም የባንክ አገልግሎት ክፍያ በዋናው ስራ ተቋራጭ የተከፈለ ቢሆንም ከንኡስ ስራ ተቋራጭ እንዲቀነስ የውል ስምምነት ባደረጉት መሰረት የተከፈለ በመሆኑ የአሁኑ ተጠሪ ግብር እንዲከፍል የተጠየቀበት ገቢ ለማግኘት ያወጡት ውጭ ሆኖ ሊያገዝ ሲገባ ይህ ሳይያገዝ የተወሰነ ግብር በመሆኑ ፍትሃዊ አይደለም በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔው ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሰው አመልካች አላግባብ የጠየቃቸውን ክፍያ ጉባኤው ውድቅ እንዲያደርግላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የፌዴራሉ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ አመልካች መልስ እንዲሰጥ ካደረገ በኋላ በግራ ቀኙ መካከል የቀረበው ክርክርና ማስረጃ በመመርመር በሰጠው ውሳኔ በተጠሪ በኩል የጥሬ እቃ ክፍያ በሱር ኮንስትራክሽን ተቀንሶ ለመቅረቱ የክፍያ ሰርትፊኬት የቀረበ በመሆኑ እንዲሁም በተጠሪ እና በሱር ኮንስትራክሽን መካከል በተደረገው የውል ስምምነት ለባንክ አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ በይግባኝ ባይ የሚሸፈን በመሆኑና ገንዘቡ በሱር ኮንስትራክሽን ስም መከፈሉን የባንክ አሰራር ስለሆነ የግብአት ዋጋና የባንክ አገልግሎት ክፍያ ወጭ ዋና ስራ ተቋራጭ በሆነው በሱር ኮንስትራክሽን በወጭ አለመያዙ ተረጋግጦ ለአሁኑ ይግባኝ ባይ በወጭ ተይዞለት ግብሩ እንደገና ሊሰላ እንደሚገባ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ለግንባታ እቃ አቅርቦት ወጣ የተባለው ብር 34,371,218.06 እና ለባንክ አገልግሎት ክፍያ ወጣ የተባለው ብር 564,480.00 ለተጠሪ በወጪነት ሊያዝ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በመሻር የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸው ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡እንደመረመርነው በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነጥብም ተጠሪ በወጪነት እንዲያዝለት ያቀረበው ደረሰኝ በሌላ አካል የተመዘገበ በሆነበት ሁኔታ ወጪ ለማረጋገጥ በሌላ አካል የተመዘገበ ደረሰኝ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑ ከግብር አዋጁ መርህ አንፃር በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከክርክሩ ሂደት ለመረዳት እንደቻልነው ተጠሪ እንዲከፍል የተጠየቀውን የንግድ ትርፍ ግብርና የተጨማሪ እሴት ታክስ የ2011 እ.ኤ.አ. የግብር ዘመን መሆኑ ተጠሪ በዚሁ የግብር ዘመን ወጪ ማድረጉን በመግለፅ ያቀረበውን የሲሚንቶ፣የነዳጅ፤ሌሎች የግንባታ እቃ ወጪዎች ብር 34,371,218.06 (ሰላሳ አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰባ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አስራ ስምንት ከስድስት ሳንቲም) እና ለባንክ አገልግሎት የተፈፀመን ክፍያ ወጪ ብር 564,480 (አምስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ብር) በወጪነት እንዲያዝለት ጠይቆ አመልካች ውድቅ በማድረጉ መነሻ ያደረገ ክርክር ነው ፡፡

ግብር ከፋዩ ወጪዎችን ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ለንግድ ስራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ እንደሚደረግ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 20 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ግብር ከፋዩ ወጪውን ለማስረዳት ማረጋገጫ ማቅረብ እንዳለበት አከራካሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በወጪነት እንዲያዝለት እየጠየቀ ያለው በ2011 እ.ኤ.አ. የግብር ዘመን ወጪ አድርጌያለሁ በማለት፤ ማድረጉን ያረጋግጥልኛል በማለት ያቀረበውን የሲሚንቶ፣የነዳጅ፤ሌሎች የግንባታ እቃ ወጪዎች ብር 34,371,218.06 (ሰላሳ አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰባ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አስራ ስምንት ከስድስት ሳንቲም) እና ለባንክ አገልግሎት የተፈፀመን ክፍያ ወጪ ብር 564,480 (አምስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ብር) አጠቃላይ በተጠሪ ስም ወጪ ተደርገው የቀረቡ ሳይሆን ዋና ተቋራጭ በሆነው በሱር ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወጪ የተደረገ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 20 ስር እንደተደነገገው ወጪ አውጥቻለሁ የሚል አካል ወጪውን ማስረዳት የሚችለው በሚያቀርበው ህጋዊና ተቀባይነት ያለው ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የግዢ ደረሰኝ ማለት የሻጭና የገዢ ሙሉ ስም፣ የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር፣ተከታታይ ደረሰኝ ቁጥር፣የተሸጠው እቃ ወይም አገልግሎት አይነትና የታክሱ መጠን፣የሽያጩ ወይም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ መያዝ ያለበት ስለመሆኑ ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 22(2) እና ደረሰኝ አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 28/2001 አንቀፅ 4(1) ጣምራ ንባብ መረዳት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይቻላል፡፡ስለሆነም ግብር ከፋዩ ለንግድ ስራው ያወጣውን ወጪ ማረጋገጥ አለበት ሲባል ይህንን ለማረጋገጥ የሚቀርበው ህጋዊ ደረሰኝ ደግሞ ወጪ አውጥቻለሁ በሚለው አካል ስም መሆን እንዳለበት ከተጠቀሰው ድንጋጌ እና ከማስረጃ መርህ አንፃር ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም በሱር ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም ወጪ የተደረገ የሲሚንቶ፣የነዳጅ፣ሌሎች የግንባታ እቃ ወጪዎች እንዲሁም ለባንክ አገልግሎት ክፍያ ተጠሪ ገቢ ለማግኘት ያወጡት ወጭ ሆኖ ሊያዝ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ከገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌ ውጪ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 129915 የካቲት 10 ቀን 2009 ዓ/ም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠው ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 163541 ሰኔ 01 ቀን 2009 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 136092

መስከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ሙሉአለም ግዛው ወልዴ -ጠበቃ መሀመድኑር አበደሰረም -ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ ዙፋን ዘለቀ - ተልማ አቻሜ -ቀረቡ

2ኛ መስፍን አስፋው
3ኛ አልማዝ አስፋው
4ኛ ቱቱ አስፋው
5ኛ ሶስና አስፋው
} ጠበቃ አማረ ጋሳ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍርድ ለማስፈፀም የተደረገው ሀራጅ የተመለከቱ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍርድ ባለመብት አቤቱታ አቅራቢነት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመሀብት ወ/ሮ አመለወርቅ ኪየሱስ ወራሽ ወ/ሮ ዙፋን ዘለቀ ሲሆኑ የፍርድ ባለዕዳዎች ደግሞ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ ለአፈፃፀም አቤቱታ መነሻ የሆነው ክርክር የተነሳበት ቤት በ15/05/07 ዓ/ም በተደረገ ሀራጅ ሽያጭ አቶ እንግዳወርቅ አታክልቲ ብር 22,500,000,00 ዋጋ በመስጠት አሸናፊ ቢሆኑም ገንዘቡን ገቢ ስላላደረጉ በድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ መደረጉንና በዚሁ በ29/08/07 ዓ/ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተደረገው ጨረታ ላይ ለቀደመው ጨረታ የተጫራቾች ብዛት በ16 ቀንሶ 5 ብቻ መቅረባቸውን እነዚህም ተጫራቾች እውነተኛና በቂ አለመሆናቸውን ገልፀው ጨረታው እንዲዛወር ሲጠይቁ በፅሁፍ ያቅርቡ ተብለው በመግፍ ላይ እያሉ ከሌላ የመ/ቤቱ ሰራተኛ ጋር በመነጋገር አሸናፊ ለሆኑ አቶ ሙሉአለም ግዛው በብር 10,350,000 (አስር ሚሊዮን ሶስት መቶ አምሳ ሺህ) እንዲሸጥ ተደርጓል።ሁለተኛ ጨረታ አካሄድ ላይ ቅሬታ አቅርቤ በፅሁፍ እያደረግኩ እያለ አጫራቹ ሃሳባቸው በመቀየር ሀራጁ በጥድፍያና በተነንኮል እንዲካሄድ ያደረጉ ስለሆነ ጨረታው ፈርሶ ሌላ ጨረታ ይደረግልኝ በማለት ጠይቀዋል።የጨረታው አሸናፊ በበኩላቸው ጨረታውን ስርአቱን አሟልቶ የበለጠ ዋጋ አቅርቤ አሸናፊ ሆኛለሁ የማጭበርበር ተግባር አልተፈፀመም በማለት ተከራክረዋል ። ፍርድ ቤቱ ግራቀኙ ካከራከረ እና ምስክሮች ከሰማ በኋላ የጨረታ ሽያጭ አካሄድ ስርአትን በጉልህ ሁኔታ በጣሰና ነፃ ውድድር ባልነበረበት ውጤትን ለመፍጠር በሚያስችል ሁኔታ የቀድሞ የተጫራቾች መግባባት በሚታይበት የተደረገ ሽያጭ ሊፀና የሚገባ ባለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 445 መሰረት ጉድለት ያለበት ሽያጭ ስለሆነ በ29/08/07ዓ/ም የተደረገው አቶ ሙሉአለም ግዛው አሸናፊ የሆኑበት በአፈ/መ/ቁ. 16046 የተከናወነው ሀራጅ ሊፈርስ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ግራቀኙ አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ቅሬታው ባለመቀበል ሰርዞታል። ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ብይንና ትዕዛዝ በመቃወም የቀረበ ነው። የአመልካች የሰበር ቅሬታ ዋና ትኩረት፡- በፍርድ አፈፃፀም የማይንቀሳቀስ ንብረት ጨረታ ሽያጭ የሚፈርሰው በጨረታ ስርአቱ ላይ ግዙፍ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ወይም የማታለል ተግባር መኖሩ ከተረጋገጠ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ የጨረታው ሽያጭ እንዲፈርስ ያመለከቱት በጨረታው ጉዳት ደረሰብኝ ብለው ሳይሆን ቤቱ በ2ኛው ጨረታ ከተሰጠው ባነሰዋጋ የሚል በመሆኑ በህጉ አግባብ የተደረገው ጨረታ እንዲሰረዝ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው የስር ፍረድቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት አቅርበዋል። ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓአል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች በበኩላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በአግባቡ መሆኑ በመዘርዘር የሥር ፍርድ ቤት ብይን ይሁን ትዕዛዝ ስሕተት የለውም ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራቀኙ በሰበር ችሎት ያደረጉት የጽሑፍ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ብይን እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ዕልባት የሚያስፈልገው ጭብጥ የሥር ፍርድ ቤቶች ጨረታው እንዲሰረዝ የሰጡት ብይን እና ትዕዛዝ በሕጉ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከሥር የክርክር ሂደት መረዳት የተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሁነውን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02 የቤት ቁጥር 750 የሆነውን ቤት በ15/05/07 ዓ/ም በተደረገ ሀራጅ ሽያጭ አቶ እንግዳወርቅ አታክልቲ ብር 22,500,000,00 ዋጋ በመስጠት አሸናፊ ቢሆኑም ገንዘቡን ገቢ ስላላደረጉ በድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ መደረጉንና በዚሁ በ29/08/07 ዓ/ም በተደረገው ጨረታ ላይ ለቀደመው ጨረታ የተጫራቾች ብዛት መቀነሱ የጨረታው ተሳታፊዎችም እየተጠቃቀሱና እየተጠባበቁ ጨረታውን ማደረጋቸው በተደረገው የማጭበርበር ተግባር ምክንያት ቤቱ በመጀመሪያ ጨረታ ከተጠቀሰው ዋጋ ግማሽ በታች አሸናፊ መሆኑ በምስክሮች መረጋገጡ ከስር ፍርድ ቤቶች መዝገብ ለመረዳት ችለናል፡፡

በመሰረቱ በሀራጅ በተሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተፈጸመ ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ወይም ማጭበርበር ወይም ማታለል ድርጊት ካለ አቤቱታ የሚቀርብበት ሥርዓት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 445 ሥር ተደንግጓአል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተደረገው ጨረታ ግዙፍ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ወይም የማታለል ድርጊት መኖሩ አልተረጋገጠም በማለት አጥብቀው የሚከራከሩ ቢሆንም በሀራጅ አካሄድና ሽያጩ የተፈጸመበት ሥርዓት ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ወይም የማታለልና ማጭበርበር ድርጊት ስለመፈጸሙ በማስረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ ድምዳሜ ላይ የደረሰና ይህ ምክንያት ደግሞ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 445 እንደተመለከተው ጨረታው ለማፍረስ በቂ ምክንያት በመሆኑ ሲታይ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ የሕግ መሠረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 62246 በ25/04/2008 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 176451 በ20/03/2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ጥር 23 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡ ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ - 131084

ቀን - 25/04/2010

ዳኞች፡- ተክሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ጌታቸው ይርገቡስ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡-

1. በላይ ናማጋ፡ በሌለበት
2. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ነ/ፈ ፍርድ አወቅ አክሊሉ
3. አቶ በርሁን የማነ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስ መነሻ ያደረገ ነው፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ ወ/ሮ መቅደስ አበበ የፍርድ ባለ መብት በመሆን ባቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ምክንያት ቁጥሩ 150 የሆነው ቤት በዕዳው ምክንያት እንዲሸጥ በተወሰነው መሠረት ተሸጦ ገንዘቡ ገቢ ከተደረገ በኋላ፣ ቁጥራቸው 149 እና 151 የሆኑ ቤቶች ቁጥሩ 150 ከሆነው ቤት ጋር የተያያዙ ቢሆኑም የተለያዩ መሆናቸውን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ተጠሪዎች ተመሳጥረው የቤ/ቁ/ 149 እና 151 የሆኑትን ቤቶች 3ኛ ተጠሪ እንዲረከብ ያደረጉ በመሆኑ ቤቶቹን ከዳቦ ማሽን ጭምር ተጠሪዎች እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ቀርበዉ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን፣ 1ኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ፍርድን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠዉ እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አካል እንጂ እራሱን የቻለ የህግ ሰዉነት የተሰጠዉ ተቋም አለመሆኑን ገልፆ ሊከሰስ እንደማይገባዉ የተከራከረ ሲሆን፤ 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ቁጥሩ 150 የሆነዉን ቤት ተረክቦ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ አወጥቶበት ለ8 ዓመታት በእጁ አድርጎ የነበረ መሆኑን፣ አመልካች ቁጥሩ 151 የሆነዉ ቤት የግል ቤቱ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ዉድቅ ሆኖ እንዲወሰንለት በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሳያል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ በግራ ቀኝ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ፤ 1ኛ ተጠሪ ዳኛ ሆነዉ ጉዳዩን ሲያዩ በነበረበት ወቅት ለፈጸሙት ተግባር በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2138(ሐ) መሠረት ክስ ሊቀርብባቸዉ የማይገባ መሆኑን፣ 2ኛ ተጠሪም ፍርድ ለማስፈጸም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስር የተደራጀ አካል እንጂ እራሱን የቻለ የህግ ሰዉነት ያለዉ ባለመሆኑ ሊከሰስ አይገባም በማለት በሁለቱ ላይ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ያደረገ ሲሆን፤ ቁጥሩ 150 የሆነዉ ቤት ቁጥሩ 151 ከሆነዉ ቤት በተናጥል የሚገኝ መሆኑ እና ይዞታዉ የማን እንደሆነ የሚያሳይ የሰነድ ማረጋገጫ ማስረጃ አለማግኘቱን ገልፆ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ የይዞታ አስተዳደር እና የሽግግር ጊዜ አገልግሎት የላከለትን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያለዉ መሆኑን አላረጋገጠም በሚል ምክንያት 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ የቀረበዉንም ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 28/11/08 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበዉ የሰበር አቤቱታ፤ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች እንዲቀርቡ በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች ተጠሪዎችን አንድ ላይ አጣምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ክስ ለማቅረብ መሰረት ያደረገዉ ከወ/ሮ መቅደስ አበበ ጋር በነበራቸዉ ክርክር የፍርድ ባለ ዕዳ በመሆን በቀረበባቸዉ የአፈፃፀም ክስ 1ኛ ተጠሪ በወቅቱ ዳኛ በመሆን በአፈፃፀም መዝገብ ላይ በሰጠዉ ትዕዛዝ፣ 2ኛ ተጠሪ ፍርዱን በማስፈጸም ሂደት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት 3ኛ ተጠሪ እንዲረከብ በማድረጉ እና 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በመጀመሪያ በአፈፃፀም እንዲሸጥ ሳይወሰን ቁጥራቸዉ 149 እና 151 የሆኑትን ቤቶች መረከቡ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ አመልካች መብቴ ተጥሷል በሚል ላቀረበዉ ክስ ምክንያቱ ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በተጠሪዎች የተፈጸመ ተግባር መሆኑን ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ያቀረቡት ክስ ከመነሻዉም ተቀባይነት ያለዉ መሆን አለመሆኑ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻ ጭብጥ ይሆናል፡፡

በመሠረቱ በሌላ ሰዉ በተፈጸመ ድርጊት ምክንያት መብቱ የተጣሰበት ሰዉ መብቱን ለማስከበር አቤቱታዉን ስልጣን ላለዉ አካል የማቅረብ መብት ያለዉ ሲሆን፤ የሚቀርበዉም አቤቱታ የጉዳዩን ዓይነትና መሠረታዊ ባህርይ መሠረት በማድረግ በህግ የተዘረጋዉን ስርዓት ተከትሎ መሆን እንደሚገባዉ እሙን ነዉ፡፡ ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ አመልካች ክሱን ለማቅረብ በምክንያትነት የጠቀሰዉ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት በተጠሪዎች በተፈጸሙት ተግባራት ምክንያት መብቱ መጎዳቱን ነዉ፡፡ ለተያዘዉ ጭብጥ እልባት ለመስጠት ይቻል ዘንድም በአፈፃፀም ምክንያት የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሚያዝበትን እና የሚሸጥበትን ስርዓት በተመለከተ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በቅድሚያ ማየቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ፍርድን ለማስፈጸም ሲባል ንብረት ስለሚያዝበት፣ ስለሚሸጥበት ስርዓት እና ዉጤቱ በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ሕጉ ከአንቀጽ 404 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ ከድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት መረዳት የሚቻለዉም፤ ሂደቱ የሚመራዉ የአፈፃፀም መዝገቡን በያዘ ፍርድ ቤት ሲሆን ፍርድ ቤቱም በአፈፃፀም ምክንያት ንብረት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚሸጥበትን ሁኔታ እና ስርዓቱን በመከታተል እና እንደየአግባብነታቸዉ በስነ ስርዓት ሕጉ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ሂደቱን በመምራት የፍርድ ባለዕዳ፣ የፍርድ ባለ መብትን እና የገዥዉን መብቶች ባገናዘበ መልኩ የሽያጩ ሂደት መከናወኑን የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት መሆኑን ነዉ፡፡ ይህ ሂደትም የተሸጠዉ ንብረት በርግጥም እንዲሸጥ የተወሰነ ንብረት መሆን አለመሆኑ፣ ሂደቱ በህጉ የተመለከቱትን ስርዓቶች የተከተለ መሆን አለመሆኑ፤ ከሂደቱ ጋር በተያያዘ ከፍርድ ባለ መብት፣ ከፍርድ ባለ ዕዳ፣ ከገዥዉ እንዲሁም ከንብረቱ ጋር በተያያዘ መብት ወይም ጥቅም አለኝ ከሚል 3ኛ ወገን የሚቀርበዉን ተቃዉሞ መርምሮ ዉሳኔ መስጠትን ሁሉ የሚያካትት ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት እና መንፈስ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

በእርግጥ ከሽያጭ ሂደት ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤቱ ወይም በፍርድ አስፈፃሚዉ አካል በሚፈጸም ስህተት/ጥፋት ምክንያት የፍርድ ባለ መብት ወይም የፍርድ ባለ ዕዳ እንዲሁም የገዥዉ መብት ሊጎዳ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ይሁንና እነዚህ ስህተቶች የሚቃኑት በስነ ስርዓት ህጉ መሠረት አፈፃፀሙን በያዘዉ ፍርድ ቤት በመሆኑ፣ ሽያጩ በሚደረግበት ሂደት ወይም ከዉጤቱ ጋር በተያያዘ ስህተት (ጥፋት) በመፈጸሙ ምክንያት መብቱ ተጎድቷል የሚል ወገን የሚኖረዉ የህግ መፍትሔ ይህ እንዲስተካከልለት ጥያቄዉን አፈፃፀሙን ለያዘዉ ፍርድ ቤት ማቅረብ ነዉ፡፡

በመሆኑም አፈፃፀሙን የያዘዉ ፍርድ ቤት በዕዳ ምክንያት እንዲሸጥ ከተወሰነዉ ቁጥሩ 150 ከሆነዉ ቤት ሌላ አመልካች ለክርክሩ መነሻ ያደረጋቸዉ ሁለቱ ቤቶች ያላግባብ እንዲሸጡ በፍርድ ቤቱ ሌላ ትዕዛዝ መሰጠቱ ወይም ከተሸጠዉ ንብረት ዉጪ ሌላ ተጨምሮበት 3ኛ ተጠሪ ያላግባብ እንዲረከብ ተደርጎ ከሆነ እና በዚህ ምክንያት መብቱ የተነካ መሆኑን ካመነበት አፈፃፀሙን ለያዘዉ ፍርድ ቤት አቤቱታዉን ማቅረብ አለ፤ያም አፈፃፀሙን በያዘዉ ፍርድ ቤት የተፈጸመዉ ስህተት እንዲታረም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ መብቱን ማስከበር ነበረበት፡፡ ይሁንና ይህን ሳያደርግ የአፈፃፀም መዝገቡ ተዘግቶ ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት የተጎዳዉን መብቱን ለማስከበር በአዲስ መልክ ያቀረበዉ ክስ ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 231(1-ሀ) መሠረት ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ ከዉጤት አንፃር ሲታይ የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/174646 በቀን 01/09/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 45369 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት፣ የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 78629

ጥር 14 ቀን 2005 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

መስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአቶ ካሣ አበበ ወራሽ አቶ ሰለሞን ካሣ; ከጠበቃ አስናቀ ስፍራ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አያልነሽ ባይለየኝ ጠበቃ ሰለሞን ተሾመ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር በሌላ ሰው ሃብት አላግባብ መበልፀግ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ የስር ተከሣሽ (የአሁኑ ተጠሪ አውራሽ) አቶ ካሣ አበበ ገዳሙ ንብረትነቱ የከሣሽ የሆነ የሰ.ቁ. 3-16729 የሆነ የጭነት ተሽከርካሪ ወስደው ባለመመለሣቸው ቀደም ሲል በመ.ቁ. 03016 በተደረገ ክርክር ተከሣሽ ተሽከርካሪውን እንዲመልሱና እስከ 12/11/92 ዓ.ም ላለው ጊዜ ከተሽከርካሪው ያገኙትን ጥቅም ብር 366,000 ለከሣሽ እንዲከፍሉ መወሰኑን በውሣኔው መሠረት ከሣሽ መኪናውን በ01/10/98 ዓ.ም መረከባቸውን የተከሣሹን ንብረት በአፈፃፀም አሽጠው ብር 497,000 በእጃቸው መግባቱን ከዚህ ገንዘብ ላይ ከልዩ ልዩ ወጭ ጋር ተከሣሽ የሚከፍሉትን ገንዘብ ብር 413,580 ሲቀነስ ብር 83,470 በትርፍነት በእጃቸው የሚገኝ መሆኑንና በቀድሞው ክስ እና ውሣኔ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውስጥ ያልካተተውን የመኪናውን የገቢ ጥቅም በክስ መጠየቅ እንደሚችሉ በቀድሞው ውሣኔ ላይ መብት የተጠበቀላቸው መሆኑን በዝርዝር የሚገልጽ ሆኖ ተሽከርካሪው የሚያስገኘው ወርሀዊ የተጣራ ገቢ ብር 3000 (ሶስት ሺህ) መሆኑ በቀድሞው ክርክር ጊዜ በማስረጃ በተረጋገጠው መሠረት ከ30/10/92 ዓ.ም እስከ 01/10/98 ዓ.ም ድረስ ላለው የ71 ወር ጊዜ ብር 213,000 (ሁለት መቶ አስራ ሶስት ሺህ) የሚመጣ በመሆኑ በትርፍ በእጃው የሚገኘው የተከሣሽ ገንዘብ ተቀናሽ ተደርጐ ተከሣሽ ብር 129,530 (አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሰላሣ) እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሥር ተከሣሽ በበኩላቸው ክሱ በፍ.ህ.ቁ. 2143(1) መሠረት በሁለት አመት ይርጋ እንደሚታገድ እና ክስ የማቅረብ መብት የሚመነጨው ከሕግ እንጂ ከፍ/ቤቱ ውሣኔ እንዳልሆነ በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው በአማራጭም በፍሬ ነገሩ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ከውሉ ውጭ ኃላፊነት ክስን አስመልክቶ በፍ/ህ/ቁ. 2143(1) የተደነገገው የሁለት አመት የይርጋ ጊዜ አላግባብ መበልፀግ አስመልክቶ በሚቀርብ ክስ ጉዳዩ ተፈፃሚነት እንደሌለው ከፍ/ህ/ቁ. 2143(3) ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም በማለት ብይን ከሰጠ በኃላ በቀጣይ ቀጠሮዎችም የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ ከ12/11/92 ዓ.ም ጀምሮ ከሣሽ መኪናውን እስከተረከቡበት 01/10/98 ዓ.ም ድረስ ያለው ገቢ በወር በብር 3000 /ሶስት ሺህ/ ተሰልቶ በትርፍነት በከሣሽ እጅ የሚገኘው ገንዘብ ተቀናሽ ከተደረገ በኃላ ቀሪውን ብር 129,530 (አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሰላሣ) ከወለድና ልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲከፍሉ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአሁኑ አመልካች ያቀረቡለትን ይግባኝ ዘግቶ አሰናብቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ እና ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆኑ ሊሻሩ ይገባል በማለት ሲሆን ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ይርጋውንም ሆነ ፍሬ ነገሩን አስመልክቶ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሕግ ስህተት ያለበት ነው ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በዚህም መሠረት የይርጋ ጉዳይን በተመለከተ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት በፍ.ሕ.ቁ. 2143 (1) ሥር የተደነገገው የሁለት አመት የይርጋ ጊዜ አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ላይ ጭምር ተፈፃሚነት እንደሚኖረው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀደም ሲል በመ.ቁ. 34406 በ07/08/2000 ዓ.ም የትርጉም አስገዳጅነት ያለው ውሣኔ ሰጥቶ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንን ውሣኔ ወደ ጐን በመተው በፍ/ሕ/ቁ. 2143(1) የተመለከተው የሁለት አመት የይርጋ ጊዜ ለክርክር በቀረበው ጉዳይ ተፈጽሚነት የለውም ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መሆኑ እና ተጠሪው የሚከራከሩት ደግሞ በፍ.ሕ.ቁ. 2143(1) የተመለከተው የይርጋ ዘመን ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

እኛም አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ ለሚቀርቡ ክሶች አግባብነት ሊኖረው የሚገባውን የይርጋ ዘመን ለመለየት ያስችለን ዘንድ የግራ ቀኙን ክርክር እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 34406 የሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የፍ.ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ማየቱን ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሠረት የፍ.ሕ.ቁ. 2143

በን.ቁ (1) “ሥር ተበዳዩ ክስ ማቅረብ የሚችለው ካሣ የሚጠይቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2 አመት ድረስ ነው” በማለት

በን.ቁ (2) “ሥር ስለሆነም ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት የበለጠ እንደሆነ የካሣው ጉዳይ ክስ የይርጋ ዘመን ልክ በዚሁ መሠረት ይሆናል” በማለት እና

በን.ቁ.(3) ስር ደግሞ “ተበዳዩ የራሱ የሆኑትን ነገሮች የሚጠይቅበትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ በተነገሩት ድንጋጌዎች መሠረት የሚከራከርበት መብቱ የተጠበቀ ነው” በማለት ድንግጉ ይገኛል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 34406 የሰጠው ውሣኔ ደግሞ “……. ያለአግባብ ስለመበልፀግ የሚናገረው ምእራፍ የካሣ ጥያቄ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ አይናገርም” ነገር ግን አለአግባብ ስለመበልፀግና ከውል ውጭ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሚደርስ ኃላፊነት የሚናገሩት ድንጋጌዎች በአንድ አንቀጽ ውስጥ ተካተው መገኘታቸው እንዲሁም ያለአግባብ መበልፀግም ከውል ውጪ የሚደርስ ኃላፊነት በመሆኑ ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት ስር የተመለከተው የይርጋ ዘመን በተመሣሣይ አላግባብ መበልፀግን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው ይገባል…" የሚል ነው።

በሰበር ችሎቱ ውሣኔ ውስጥ አንደተገለፀው ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃለፊነት እና አላግባብ ስለመበልፀግ የሚናገሩት ድንጋጌዎች የሚገኙት በአንድ አንቀጽ ስር ነው። ይሁን እንጂ በፍ.ብሔር ሕጋችን ውስጥ የተለያየ የይርጋ ዘመንን የሚያቋቁሙ ድንጋጌዎች በአንድ አንቀጽ ውስጥ ተካትተው የሚገኙባቸው አጋጣሚዎች በመኖራቸው ድንጋጌዎቹ የሚገኙት በአንድ አንቀጽ ስር የመሆኑ ጉዳይ ብቻውን ተፈፀሚነት ሊደርግባቸው የሚገባው የይርጋ ዘመን ተመሣሣይ መሆን አለበት ወደሚል ድምዳሜ መድረስ የሚያስችል አይሆንም።

ከውል ውጪ የሚደርስ ኃለፊነት እና አላግባብ መበልፀግን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በአንድ አንቀጽ ውስጥ እንዲካተቱ የተደረገው የሚጋሯቸዋው ተመሣሣይ ባህሪያት ስላሏቸው እንደሆነ ይታመናል። ይርጋን በተመለከተ ግን የፍ.ሕ.ቁ. 2143(3) ጉዳዩን በተለየ ሁኔታ እና በግልጽ የደነገገ በመሆኑ በፍ.ሕ.ቁ. 2143(1) የተመለከተው የሁለት አመት የይርጋ ዘመን አላግባብ መበልፀግ አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ጉዳይ ተፈፃሚነት እንዳማይኖረው ተገንዝበናል።

ይህ ከሆነ ደግሞ አላግባብ ስለመበልፀግ የሚቀርቡ ክስችን አስመልክቶ በፍ.ሕጉ የተመለከተ የይርጋ ዘመን አለ ወይስ የለም ካለ ምን ያህል ወይም ስንት ነው የሚል ጥያቄ መነሣቱ የማይቀር ነው። ይህን ጥያቄ ለመመለስ በቅድሚያ መታየት የሚገባቸው አላግባብ በመበልፀግን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ሲሆኑ ከእነርሱ መካከል ይርጋን የሚመለከት ድንጋጌ የለም። ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ የሚገዛው የሕግ ክፍል ይርጋን አስመልክቶ በተለይ የሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ በሌለ ጊዜ በፍ.ሕ.ቁ. 1677(1) የተመለከተውን መርህ በመከተል ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባው በፍ.ሕ.ቁ. 1845 የተመለከተው የአስር አመት የይርጋ ዘመን ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀደም ሲል በመ.ቁ. 31748 በ28/06/2000 ዓ.ም የትርጉም አስገዳጅነት ያለው ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ያለው የሁለት አመት የይርጋ ጊዜ ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔ ሰጥቶ የነበረ መሆኑን ቀደም ሲል ተገልጽአል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው፤ ሆኖም የሰበር ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሣሣይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ እንደሚችል የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅን እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ስር ተደንግጓል፡፡ እኛም ይህንኑ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በዚህ መዝገብ የተያዘውን ክርክር ጨምሮ አላግባብ በመልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው የአስር አመት የይርጋ ዘመን መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም ከላይ በዝርዝር በተገለፁት ምክንያቶች በፍ.ሕ.ቁ. 2143(1) የተመለከተው የይርጋ ዘመን አላግባብ መልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በፍሬ ጉዳይ ረገድ የቀረበውን ክርክር በተመለከተ አመልካች የተጠሪ ንብረት በሆነ ተሽከርካሪ ገቢ አላግባብ የበለፀጉ መሆኑ እና የተሸከርካሪው የወር የተጣራ ገቢ በቀድሚው ክርክር ጊዜ ተረጋግጦ ውሣኔ አርፎበታል፡፡ ተሸከርካሪው በመሐል በሌላ ግለሰብ እጅ ገብቶ ነበረ በማለት አመልካች ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንደገለፀው ግለሰቡን በክስ መጠየቅ የሚችሉ ከመሆኑ ውጪ ጉዳዩ በተጠሪ መብት ላይ ለውጥ ማስከተል የሚችል አይደለም፡፡

በዚህም ሁኔታ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለውን ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፍ.ሕ.ቁ. 2143(1) በተመለከተው የይርጋ ዘመን አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 184727 በ24/10/03 የሰጠው ብይን እና ፍሬ ነገሩን አስመልክቶ በዚህ በመ.ቁ. 184727 በ17/04/04 የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 118043 በ27/07/04 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348/1 መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት ስለሚኖረው የይርጋ ዘመን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሠበር ችሎት በመቁ. 34406 ሰጥቶት የነበረው የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሠረት በመለወጥ አላግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ዘመን አስር አመት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በሰበር ደረጃ ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሣኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሠባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ.128035

ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡1.ዳኜ መላኩ

2. ተፈሪ ገብሩ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-.....ምስኪ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር-ጠበቃ አቶ አለሙ ገበየሁ ቀርበዋል

ተጠሪ፡-.....ቤካስ ኬሚካልስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር -ነ/ፈጅ አቶ አድነው ደቻሳ ቀርበዋል

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር የሚመለከት ሲሆን ለችሎቱ ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.120677 በ28/7/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት የአሁን ተጠሪ ክሳሽ፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሲሆን፣ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ተጠሪ የፈሳሽና ክሬም ዲተርጀንቶችንና ሳሙናዎችን በማምረት ለ18 ዓመታት ሲሸጥ የቆየ ሲሆን፤ተጠሪ ከሚያመርተዉና ብራይት ቤክስ ከሚለዉ ምርት ጋር ተመሳሳይ በሆነ ቢጫ ቀለም ባለዉ ጀሪካንና ቤስት ብራይት ብሎ አምርቶ ለገበያ እያቀረበ ስለሆነ ይህ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 8 መሰረት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር በመፈጸም የተጠሪን ጥቅም በመጉዳቱ፣አመልካች በፈጸመዉ ድርጊት የገንዘብ ቅጣት እንዲወሰንበት፣አመልካች ብራይት ቤካስ ጋር ከሚመሳሰለዉ ቤስት ብራይት በቢጫ ቀለም ጀሪካን ምስል መጠቀሙ ሕገ ወጥ ነዉ እንዲባልልን ፣አመልካች በማምረት በገበያ ላይ የተሰራጩት ምርቶች እንዲሰበሰቡ እና በዚህ ክርክር የወጣዉ ወጪና ኪሳራ እንዲጠበቅልን በማለት ከሷል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች ባቀረበዉ መልስ ተጠሪ የብራይት ቤካስ እና የቢጫ ጀሪካን ንግድ ምልክት ባለቤት ነኝ ማለቱ ሕጋዊ አይደለም፣ብራይት የሚለዉ ቃል ገላጭና የጋራ መጠቀሚያ እንጂ በአንድ ግለሰብ በብቸኝነት በንግድ ምልክትነት ሊመዘገብ የሚገባ አይደለም፤ በጀሪካን ላይ ያለዉ የቢጫ ቀለም የንግድ ምልክት ባለቤት ነኝ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም ፤ለተጠሪ የተሰጠዉ የጀሪካን ቀለም ዓይነት ቢጫና አረንጓዴ እንጂ በሙሉ ቢጫ ቀለም አይደለም፣ ተጠሪ የንግድ ምልክት መብት አለዉ ቢባል እንኳን የአመልካችና የተጠሪ የንግድ ምልክቶች ፍጹም የተለያዩ ናቸዉ፣ሁለቱም የንግድ ምልክቶች የተለያዩ ስለሆኑ ሸማቾቹን የሚያደናግር አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የዳኝነት ችሎቱ ጉዳዩን በመመርመር የሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች የግራቀኛቸዉ የምርት ማሸጊያ ጀሪካን ዲዛይኖች እና የቀለም ዉህድ ሸማቾችን የሚያደናግርና ተጽዕኖ የሚፈጥር፣የማይለያዩ እና ተመሳሳይነታቸዉ የሚጎላ በመሆኑ በንግድ ዉድድርና ሸማቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር አንቀጽ 8 /2፣ሀ/ ሥር ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ነዉ፤አመልካች ሸማቾችን የሚያደናግር እና ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር መፈጸሙ ስለተረጋገጠ በአዋጁ አንቀጽ 32 መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ እና አስተዳደራዊ ቅጣት መወሰን ተገቢ ነዉ፡፡ አመልካች ይህን ምርት ለገበያ ማቅረብ እንዲያቆም፣ አመልካች በፈጸመዉ ያልተገባ የንግድ ዉድድር በአዋጁ አንቀጽ 42 /3/ መሰረት ምርቱን አምርቶ ወደ ገበያ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በሰራባቸዉ አጠቃላይ ጊዜያት ዉስጥ ከሽያጭ ገቢ 5% እንዲቀጣ በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል የንግድ ዉድድር የሸማቾች ጥያቄ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጸመዉ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር አለ ለማለት የሚያስችል ነገር ስለሌለ የሥር ዉሳኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ከኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ጥበቃ የተደረገለት ቤስት በረኪና ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ብራይት ቤካስ የሚል ነዉ፣ አመልካች ግን ይህን የንግድ ምልክት በመተዉ ቤስት ብራይት በማለት ከተጠሪ ጋር ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ዉስጥ በመግባት ሸማቹን ሕዝብ የማደናገር ተግባር መፈጸሙ የተረጋገጠ ስለሆነ የይግባኝ ሰሚ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስተዳደራዊ ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ ስምንት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡--የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ የፈጸመዉ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ድርጊት በሌለበት እና በዚህ ረገድ ዐ/ሕግ ክስ ባላቀረበበት በቅጣት መልክ ከሽያጭ ገቢዉ 5% እንዲቀጣ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ ተሽሮ የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር ፍ/ቤት የካሳ መጠን ሳይጣራ 5% ካሳ ይከፈል ያለበት አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘዉ መሰረት ታህሳስ 13 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ ስምንት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ጽ/ቤት ጥበቃ የተሰጠዉ የንግድ ምልክት ‹‹ቤስት በረኪና›› እንደሆነ፣ ለተጠሪ የተሰጠዉ የንግድ ምልክት ደግሞ ‹‹ብራይት ቤካስ›› የሚል እንደሆነ የሥር ዉሳኔ ያሳያል፡፡ የአሁን ተጠሪ ስልጣን ባለዉ አካል ይህን ‹‹ብራይት ቤካስ›› /BRIGHT BEKAS/ የሚለዉ የንግድ ምልክት ጥበቃ የተሰጠዉ ሲሆን አመልካች ግን ስልጣን ባለዉ ሳያስመዘግብ ወይም ስልጣን ባለዉ ዘንድ ባላስመዘገበ ‹‹ቤስት ብራይት›› /BEST BRIGHT/ የሚል ምልክት በመጠቀም ምርቶቹን ለገበያ ማቅረቡ ተገቢ ያልሆነ የንግድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉድድር መፈጸሙን እና ሽማቹን ማህበረሰብ የሚያደናግር እንደሆነ በሥር የዳኝነት አካላት የቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ እንደሚያረጋግጥ የሥር ዉሳኔ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ምርቶቹን በማሸግ ለገበያ የሚያቀርብባቸዉ የጀሪካን ዲዛይኖች እና የቀለም ዉህድ በቀላሉ የማይለያይ እና ተመሳሳይነታቸዉ የሚጎላ በመሆናቸዉ ሽማቾችን የሚያደናግርና ተጽዕኖ የሚፈጥር ይህ ደግሞ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር መፈጸሙን የሚያረጋግጥ እንደሆነ በሥር የዳኝነት አካል የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ስለሆነም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የአሁን አመልካች የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 8 በመተላለፍ በተጠሪ ላይ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ተግባር መፈጸሙን የሥር የዳኝነት አካላት በማረጋገጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 መሰረት ተገቢ እርምጃ ሊወሰንበት እንደሚገባ አረጋግጧል፡፡ ይህ ችሎት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን የመጨረሻ ዉሳኔዎችን ከማረም ባለፈ ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ስለሌለዉ፣ በዚህ ምክንያት የሥር የዳኝነት አካላት ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር መቀበል አስፈላጊ ነዉ፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች ሸማቾችን የሚያደናግር እና ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ተግባር በተጠሪ ላይ መፈጸሙን በሥር የዳኝነት አካላት የተረጋገጠዉን ይህ ችሎትም ተቀብሎታል፡፡ ስለዚህ ይህ ችሎት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበዉን ቅሬታ አልተቀበለዉም፡፡

ሌላዉ መታየት ያለበት ጉዳይ የሥር የዳኝነት አካላት የአሁን አመልካች የአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 8 /2፣ ሀ/ በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር መፈጸሙን ያረጋገጡ ቢሆንም አስተዳደራዊ ቅጣት መወሰናቸዉ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት የአሁን አመልካች ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር መፈጸሙ ተረጋግጧል በማለት በአዋጁ አንቀጽ 42 /3/ መሰረት ምርቱን አምርቶ ለገበያ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሽያጭ ገቢዉ 5% እንዲቀጣ መወሰኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን በይግባኝ በማየት ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ይህን የሥር የዳኝነት አካል የዉሳኔ ክፍል ሳያርም ማጽናቱን የሥር ዉሳኔ ያመለክታል፡፡ በዚህ ረገድ የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 37 መሰረት ክስ የማቅረብ ስልጣን ያለዉ አካል ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በባለስልጣኑ የዳኝነት ችሎት አስተዳደራዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እርምጃ እንዲወስድና አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲጣል ክስ ሊያቀርብ የሚችለዉ የባለስልጣኑ ዓቃቤ ሕግ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ የአስተዳደራዊ ቅጣትን ለማስቀጣት ክስ ማቅረብ ያለበት ዐቃቤ ሕግ ነዉ እንጂ የአሁን ተጠሪ ዳኝነት የሚጠይቅበት እና በዚህም ጥያቄ መነሻነት በአመልካች ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት የሚወሰንበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም በዚህ ጉዳይ የባለስልጣኑ ዐ/ሕግ ያቀረበዉ ክስ በሌለበት አመልካች ለፈጸመዉ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ተግባር አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲወሰንበት በሕግ ስልጣን የተሰጠዉ ተገቢ የሆነ አካል ክስ ባላቀረበበት ክላይ የተጠቀሱት የዳኝነት አካላት የተጠሪን ጥያቄ ተቀበለዉ አስተዳደራዊ ቅጣት መወሰናቸዉ ከአዋጁ ዓላማ ዉጭ ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት በመ.ቁ.00041 በ7/1/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.120677 በ28/7/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል የንግድ ዉድድር የሸማቾች ጥያቄ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት በመ.ቁ.00007 በ17/3/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
3. የፌዴራል የንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ከሽያጭ ገቢዉ 5% አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲቀጣ የሰጡት የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ነገር ግን እነዚህ የዳኝነት አካላት የወሰኑት ሌላዉ የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉ ይቻሉ፡፡
6. በ2/9/2009 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ - 136245

ቀን - 23/05/2010

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- በደሌ ቢራ አ/ማህበር ነ/ፈጅ ወንድወሰን ክፍሉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ገብረመዲህን ገ/ሕይወት አልቀሩቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የተጀመረዉ በ ኢሉአባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉ ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ ከአመልካች ጋር ባደረጉት ቢራ የማከፋፈል ዉል መሠረት ተጠሪ ቁጥራቸዉ 7461491 እና 716,1487 የሆኑትን ቼኮች አስይዞ ባዶ ጠርሙሶችን በመዉሰድ ሲሰራ የነበረ ሲሆን በኋላ ላይ ብር 1,036,840.00 ጥሬ ገንዘብ አስይዞ አመልካችም በቼኮቹ ምትክ ብሩን ተቀብሎ ሁለቱን ቼኮች መልሶ የሰጠዉ መሆኑን፣ ይህ በእንዲህ እንዳለ ተጠሪ ስራዉን አቋርጦ የተረከባቸዉን ጠርሙሶች ለአመልካች የመለሰ ሲሆን፣ አመልካች በማስያዣነት ከወሰደዉ ገንዘብ ዉስጥ ብር 783,840.00 የከፈለዉ ሲሆን ቀሪዉን 253,000.00 ብር ግን ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ አላደረገም በሚል የከሰከሰዉ በመሆኑ ይሄዉ ገንዘብ ከ14/11/2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 15 ወለድ ጋር እንዲከፈለዉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነዉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠዉ መልስ፤ ተጠሪ በብር 1,036,840.00 ለሚገመት የገንዘብ መጠን ሁለት ቼኮችን አስይዞ ጠርሙሶቹን ከወሰደ በኋላ ቁጥሩ 7461487 ለሆነ ቼክ በጥሬ ገንዘብ ብር 783840 ገቢ ያደረገ ሲሆን፣ ቁጥሩ 7461491 ለሆነዉ ቼክ ብር 253,000.00 ገንዘቡን ገቢ ሳያደርግ በስህተት ገቢ እንደተደረገ ተቆጥሮ ሁለቱም ቼኮች የተመለሱለት መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይ ደረሰኝ ማቅረብ ያለበት መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ግራ ቀኝ ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ፤ ተጠሪ የሚጠበቅበትን ገንዘብ ብር 1036840.00 በመክፈሉ ምክንያት ቀደም ሲል አስይዞ የነበረዉ ሁለቱ ቼኮች ከምስጋና ጋር የተመለሱለት መሆኑን፣ አመልካች ገንዘቡ ገቢ መደረጉን ገልፆ ሁለቱን ቼኮች ለተጠሪ መመለሱ የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን እና ይህም ማስረጃ በፍ/ሕጉ አንቀጽ 2020 መሰረት በቂ መሆኑን ጠቅሶ አመልካች ለተጠሪ በክሱ የተመለከተዉን ብር 253,000.00 ከ14/11/2004 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ተጠሪ ገንዘቡን ካስያዘ በኋላ ቼኩን መልሶ ሊወስድ የቻለበት አግባብ ዋስትና እንጂ ዕዳን የማይመለከት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕጉ ከአንቀጽ 2018-2025 ያሉት ድንጋጌዎች ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የሌላቸዉ መሆኑን፣ በሌላ በኩል አመልካች ለተጠሪ በዓፈዉ ደብዳቤ በቼክ ቁጥር 746191 የተመለከተዉ ገንዘብ ሳይከፈል በስህተት እንደተከፈለ ተቆጥሮ ለተጠሪ የተመለሰለት መሆኑን እና ተጠሪ ደረሰኝ ካቀረበ በድጋሚ የሚታይለት መሆኑን የገለጸለት መሆኑን እና በርግጥም ተጠሪ ከፍሎ ቢሆን ኖሮ በባንክ እስቴትመንት ላይ ሊገኝ እንደሚችል በመግለጽ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 03/05/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃው አማካይነት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ብር 253,000.00 ገቢ ሳያደርጉ ቼኩ በስህተት የተመለሰላቸው መሆኑ እና በአመልካች ሲኒየር አካውንታንት የተጠሪ አካውንት ተፈትሾ ተጠሪ ገንዘቡ ገቢ አለመደረጉ ተረጋግጦ እያለ አመልካች ገንዘቡን እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን በመግለጽ ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኝ እንዲከራከሩ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸውን በጽሑፍ ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነውን ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ለብር 1,036,840.00 ቼክ አስይዞ ጠርሙሶቹን መውሰዱን፣ ከዚህ ውስጥ አመልካች ለተጠሪ ብር 783840.00 የከፈለው በመሆኑ ላይ ግራ ቀኝ ክርክር የላቸውም፡፡ ተጠሪ ለጠርሙስ መያዣ በሰጣቸው ሁለት ቼኮች ላይ የተመለከተውን ብር 1,036,840.00 በጥሬ ገንዘብ ለአመልካች መክፈሉን ገልፆ አመልካች ቼኮቹን ስመልስ ለተጠሪ በፃፈው ደብዳቤ ያረጋገጠ ስለመሆኑም ተገንዝበናል፤ አመልካችም ይህን አምኗል፡፡ አመልካች ለተጠሪ ሊመልስ ከሚገባው ገንዘብ ብር 253,000.00 ላለመክፈል በዋናነት የሚከራከረው ይህ ገንዘብ ገቢ ሳይሆን ገቢ እንደተደረገ ተደርጎ በደብዳቤው የተገለጸ እና ቼኩም በስህተት የተመለሰ መሆኑን፣ በስህተት የተከፈለ ስለመሆኑም በሌላ ጊዜ በተፃፈ ደብዳቤ ለተጠሪ መግለጹን ነው፡፡ በሌላ በኩል ገንዘብ የተከፈለ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ወይም ደብዳቤ ሰነዱን ባዘጋጀው ወይም ደብዳቤውን በፃፈው ሰው ላይ ማስረጃ እንደሚሆን በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2018(1) ስር ከተደነገገው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ህጉ ይህን ድንጋጌ በዚህ መልኩ ሲያስቀምጥም አንድ ሰው ገንዘብ መከፈሉን በተመለከተ የሚሰጠው የሰነድ ማስረጃ ወይም ደብዳቤ በርግጥም ገንዘቡ መከፈሉን አረጋግጦ ነው በሚል ሃሳብ እንደሆነ ይታመናል፡፡ አመልካች ቼኩ ለተጠሪ የተመለሰው እንዲሁም ደብዳቤውም የተፃፈው ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ ሳያደርግ መሆኑን እና ይህም ስህተት መሆኑን በኋላ ለተጠሪ በፃፈው ደብዳቤ የገለጸለት መሆኑን በመግለጽ ይከራከራል፤ ይሁንና በስር ፍርድ ቤት በሰጠው መልስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ አድርጎ ከሆነ ይህን የሚያሳይ ደረሰኝ ማቅረብ እንደሚገባው በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ አመልካች ቼኩ የተመለሰው በስህተት መሆኑን ገልፆ ለተጠሪ በፃፈው ደብዳቤም ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ ማድረጉን የሚያሳይ ደረሰኝ ካቀረበ በድጋሚ ሊያጣራ እንደሚችል አመልክቷል፡፡ ይህ በአጠቃላይ የሚያሳየው አመልካች ገንዘቡን ገቢ ሳያደርግ ገቢ እንዳደረገ ተቆጥሮ ቼኩ የተመለሰለት በስህተት መሆኑን ገልፆ ለተጠሪ የፃፈው ደብዳቤም ተጠሪ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ አለማድረጉን አመልካች እራሱ እርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ቼኩ ለተጠሪ የተመለሰለት በስህተት መሆኑን በመግለጽ አመልካች በኋላ ላይ የፃፈው ደብዳቤ ቀደም ሲል ገንዘቡ ገቢ መደረጉን አረጋግጦ ቼኩን ከምስጋና ጭምር ለተጠሪ በመመለስ የሰጠውን ማረጋገጫ ሊያስተባብል የሚችል አይደለም፡፡

ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኢሉአባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ፍርድ የግራ ቀኝ ክርክር እና የቀረበውን ማስረጃ መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 127837 በቀን 14/03/09 ዓ.ም በዋለው ችሎት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/207712 ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የኢሉአባቦራ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/24452 ላይ የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 135197

ጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ተክሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ፀሃይ መንክር

አመልካች፡ - አቶ ደለሳ ሌጆሳ - ቀረቡ
ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ፍቃዱ ጫላ - ቀረቡ
2ኛ. ወ/ሮ ማሚቱ ጀቤሳ - አልቀረቡም
መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 228415 ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም ያሳለፈውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በጉድሩ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች በጣልቃ ገብነት ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- የ2ኛ ተጠሪ ባለቤት አቶ ታሪኩ ፊጤ 2ኛ ተጠሪን ዋስ አድርገው በ19/05/2002 ዓ.ም በተፃፈ ውል ብር 10,000.00 ተበድረው ገንዘቡን እስከ 30/05/2004 ዓ.ም ከፍሎ የማይጨርስ ከሆነ ብር 30,000.00 የሚያወጣውን በኮምቦልቻ ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኝ ቤታቸውን እንድወስድ ተስማምተን ገንዘቡን በጊዜው ሳይመልሱልኝ በ2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ የቤቱን ስመሃብትነት ወደ ስሜ እንዲያዛውሩ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ቢታዘዝም ለክሱ የሰጡት መልስ የለም፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት በ01/10/06 በተደረገ ውል በብር 30,000.00 2ኛ ተጠሪና ልጃቸው ወ/ሮ ጌጤ ጀቤሳ (በሥር 2ኛ ጣልቃ ገብ) ከሸጡልኝ በኋላ በጋራ ለኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ማመልከቻ አስገብተን እያለ በመካከላችን ያለው ውል ሳይፈርስ ከከሳሽ ጋር የሃሰት ውል አዘጋጅተው በዚህ ቤት ላይ እየተከራከሩ ስለሆነ ወደክርክሩ ገብቼ የባለንብረትነት መብቴን እንዳስከብር በማለት ጠይቀዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጣልቃ ገብ ወደክርክሩ እንዲገቡ ተፈቅዶ 2ኛ ተጠሪ ለጣልቃ ገቡ አቤቱታ በሰጡት መልስ በመካከላችን ውል የለም፤ ቤቱን አልሸጥኩም፤ ገንዘብም አልወሰድኩም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል እና የሰነድ ማስረጃዎችን ይዘት ከመረመረ እና የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር አጣርቶ እንዲያቀርብ ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ከሳሽ ያቀረበው የውል ሰነድ የግዥና ሽያጭ ውል መደረጉን የሚገልፅ አይደለም፤ የከሳሽ ምስክር ቤቱን በዕዳ ለዋስትና አስይዞታል ቢሉም በእዳ ለዋስትና መያዙን የሚያሳይ በከተማ አስተዳደሩ የተመዘገበ ነገር የለም፤ የማይንቀሳቀስ ንብረት በዕዳ ሲያዝ በጽሁፍ ሆኖ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ ካልተመዘገበ ውጤት አይኖረውም፤ በመሆኑም ከሳሽ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሽ ከልጇ (በሥር 2ኛ ጣልቃ ገብ ሆነው የተከራከሩ ወ/ሮ ጌጤ ጀቤሳ) ጋር በመሆን ቤቱን ለአመልካች ሸጠው ስሙ እንዲዞር በከተማው አስተዳደር አስገብተው ከፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ስለተሰጠ ብቻ ስሙ ሳይዞር መቅረቱ ስለተረጋገጠ ተከሳሽ ቤቱን ለጣልቃ ገብ (የአሁን አመልካች) ሊለቁ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ውሳኔ በመቃወም ተጠሪዎች ቅሬታቸውን በይግባኝ ለሆሮ ጉድሩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ክርክሩን ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የብድሩ መክፈያ ጊዜ ጥር 30/2004 ዓ.ም ካለፈ በኋላ የብድር ውል መሆኑ ቀርቶ ወደ ሽያጭ ውል የሚለወጥ በመሆኑ፤ 2ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ ለቀረበው ክስ መልስ ባይሰጡም ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ቤቱን በህይወት ከሌለው ባለቤታቸው ጋር በመሆን አስይዘው ብር 10,000.00 በመበደር እና በተባለው ቀን ካልመለሱ ቤቱን ለመልቀቅ መስማማታቸውን ገልፀዋል፤ የ1ኛ ተጠሪ ጥያቄም ቤቱ ለዕዳው ይዋል የሚል ነው፤ በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች አልሸጥኩለትም ብለው እየተከራከሩ የሥር ፍርድ ቤት መያዣው አልተመዘገበም በሚል የከሳሽን (1ኛ ተጠሪን) ጥያቄ ውድቅ አድርጎ ቤቱ ለጣልቃ ገብ (ለአመልካች) እንዲለቀቅ መወሰኑ የህግ መሰረት የለውም በማለት ውሳኔውን ሽሮ ቤቱን 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ እንድትለቅ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው በ1ኛ ተጠሪ ባለቤት ስም የሚታወቀውን ቤት 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች በሽያጭ አስተላልፈው በገዥ (በአሁን አመልካች) ስም እንዲዛወር ለኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ማመልከታቸውን ስለማስገባታቸው አስተዳደሩ ለሥር ፍርድ ቤት ምላሽ የሰጠ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች አልሸጥኩም ብላለች፤ ሟች ባለቤቴ ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ አስይዞ ብር 10,000.00 ተበድሮ ለመመለስ ባለመቻሉ ተጨማሪ ብር 20,000.00 ከ1ኛ ተጠሪ ተቀብለናል ፤ ቤቱ ለዕዳችን እንዲውል ለ1ኛ ተጠሪ ሰጥተናል በሚል ተከራክረዋል በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የመሻሩን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ የሥር ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተሰዋውጠዋል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ተከራካሪዎቹ ወገኖች ካቀረቡት ክርክር እና የሥር ፍርድ ቤቶች ካረጋገጧቸው ፍሬ ነገሮች አንፃር በህጉ አግባብ የተቋቋመና መብትና ግዴታ የሚፈጥር ሽያጭም ሆነ የመያዣ ውል መኖር አለመኖሩን እንዲሁም የሥር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው ያሳለፉት ውሳኔ ህጉን መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የጣልቃገብ አቤቱታ ክርክር የተነሳበትን ቤት በ01/10/06 በተደረገ ውል በብር 30,000.00 ከ2ኛ ተጠሪ እና ከልጃቸው ገዝተው ለኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ማመልከቻ አስገብተው እንደነበር በመግለጽ የሚከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በመካከላችን ውል የለም፤ ቤቱን አልሸጥኩም፤ ገንዘብም አልወሰድኩም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ሽያጩን የካዱ በመሆኑ አመልካች እንደክርክራቸው የሽያጭ ውል መደረጉን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሰረቱ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ውል ማስተላለፍ ጥንቃቄ እና ጥበቃ የሚሻ በመሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሽያጭ ውል የሚደረግበት ስርዓት (ፎርም) የተለየና ጥብቅ መስፈርት የሚከተል መሆኑን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውሉ ሁለት መስፈርቶችን ማሟላት የሚጠበቅበት ሲሆን የመጀመሪያው ውሉ በጽሁፍ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ውሉ በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ፊት መከናወን የሚኖርበት መሆኑ ነው፡፡ ህጉ ይህ እንዲሆን የሚጠይቀው በተዋዋዮች መካከል በህግ ፊት የሚፀና ውል እንዲኖር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማድረግ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 21448 እና ሌሎችም በርካታ መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከፍሏል እንደተመለከተው አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት በውል የገዙ መሆኑን በማንሳት የሚከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው የሽያጭ ውል የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በግራ ቀኙ መካከል በህጉ መስፈርቶች መሰረት የሽያጭ ውል መደረጉን የሚያስረዳ ማስረጃ ማቅረባቸው አልተረጋገጠም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በመንደር የተደረገ ስምምነት በመያዝ ከአመልካችና ከልጃቸው (የሥር 2ኛ ጣልቃ ገብ) ጋር በመሆን በከተማው አስተዳደር ማመልከቻ አስገብተው ከፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ስለተሰጠ ስሙ ሳይዞር ቀርቷል መባሉ በህጉ አግባብ የተቋቋመ ውል አለ እንዲባል በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት የሚተካ አይሆንም፡፡ ስለሆነም በህጉ አግባብ የተቋቋመ የሽያጭ ውል በሌለበት የስር ፍርድ ቤት በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የሽያጭ ውል አለ በማለት ተጠሪ ለአመልካች ቤቱን ሊለቁ ይገባል ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የሥር ከሳሽ (የአሁን 1ኛ ተጠሪ) ባቀረቡት ክስ የ2ኛ ተጠሪ ባለቤት አቶ ታሪኩ ፊጤ በ19/05/2002 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል ብር 10,000.00 ተበድሮ ገንዘቡን እስከ 30/05/2004 ዓ.ም ከፍሎ የማይጨርስ ከሆነ ብር 30,000.00 የሚያወጣውን የተበዳሪ ቤት እንድወስድ ተስማምተናል፤ ገንዘቡን በጊዜው ሳይመልሱልኝ በ2006 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ 2ኛ ተጠሪ መያዣ የተደረገውን የቤቱን ስመሃብት ወደ ስሜ እንዲያዛውሩ ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርበዋል፡፡

የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ 2ኛ ተጠሪ ስመሃብት እንዲያዛውሩ በፍርድ እንዲወሰን ቢሆንም ሥም የማዛወር ተግባር የአስተዳደር ሥራ በመሆኑ ተጠሪ ስመሃብቱን ወደ ስሜ እንዲያዛውሩ ይወሰንልኝ በሚል ያቀረቡት አቤቱታ የክስ ምክንያት አለው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ የ1ኛ ተጠሪ ክስ በመያዣ ውሉ መሰረት የቤቱን ስመሃብት አስተዳደሩ እንዲያዛውርላቸው 2ኛ ተጠሪ ተገቢውን ይፈፅሙልኝ በሚል የቀረበ ከሆነም 2ኛ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ለክሱ በቀጥታ የሰጡት መልስ ባለመኖሩና ልጃቸውም የመያዣውን ውል ሳይሆን የሽያጩን ውል በማመን ይከራከሩ ስለነበር በቅድሚያ በህጉ ፊት የሚፀና ውል መኖር አለመኖሩን መመርመር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የማይንቀሣቀስ ንብረት መያዣ በማናቸውም አይነት ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆን ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ርስት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ማንኛውንም አይነት ውጤት እንደማያስገኝ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3052 ይደነግጋል፡፡ ከዚህም ሌላ በፍ/ብ/ህ/ቁ 3060 እንደተደነገገው ዕዳው እንዲከፈል በተወሰነበት ጊዜ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው የመያዣ መብት ያገኘበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይወስዳል የሚል ስምምነት ሁሉ ተቀባይነት እንደሌለው ተመልክቷል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ለሰጡት ብድር ቤቱን የፍታብሔር ህግ ቁጥር 3052 በሚደነግገው አግባብ መያዣ ስለማድረጋቸው የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም በህጉ አግባብ የተቋቋመ የመያዣ ውል አለ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡ በሌላም በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ለክሱ መልስ ባይሰጡም የብድር ዕዳው መኖሩን እና ቤቱም መያዣ መደረጉን በመግለፅ የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው እንደነበር በውሳኔው አመላክቶ ቤቱን 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲለቁ በማለት ውሳኔ ቢሰጥም ውሳኔው በፍ/ብ/ህ/ቁ 3060 በግልፅ የተደነገገውን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ቤቱ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲለቀቅ የተሰጠው ውሳኔ ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የሽያጭ ውል አለ በማለት ተጠሪ ለአመልካች ቤቱን ሊለቁ ይገባል ሲል የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስም ይዛወርልኝ ጥያቄን አላግባብ ተቀብሎ በህጉ ተቀባይነት የሌለውን ስምምነት መሰረት በማድረግ ውሳኔ ማሳለፉ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎቶች ይህን ሳያርሙ ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የጉድሩ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 17506 በ06/01/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 17718 በ08/07/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 205415 በ14/08/2007 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ እና የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 228415 በ21/02/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ይህ ውሳኔ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ከፈልን የሚሉትን ገንዘብ ለማስመለስ የሚያቀርቡት ክስ ቢኖር የሚከለክል አይሆንም ብለናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. በዘህ ፍርድ ቤት ስለተደረገው ክርክር ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ/ 136262

መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች ፤ ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች ፤ የቤንሻንጉል ጉ/ክልል ዓቃቤ ህግ

ተጠሪ ፤ መሀሪ ታደሰ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ፡፡

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ክርክር የሚመለከት ነው ፡፡ አመልካች ተጠሪ ላይ የመሰረተው ክስ ይዘት የወ/ህግአንቀጽ 631/1/ለ ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በ21/06/08 ዓ.ም ከቀኑ በ8፡00 ሰዓት ላይ እድሜው 8 ዓመት ከሆነው ግል ተበዳይ እያሱ ቦጋለ የተባለውን ህጻን ልጅ ሰዉነታችንን እንታጠብ በሚል ሰበብ አታሎ ወደ ወንዝ ወስዶ የግብረሰዶም ፈጽሟል የሚል ሲሆን ተጠሪ ክዶ በመከራከሩ ጉዳዩን በመጀመሪያ ዳኝነት የተመለከተው የፓዌ ወረዳ ፍ/ቤት በዓቃቤ ህግ ማስረጃ የተመሰከረና ተጠሪ በመከላከያ ማስተባበል አለመቻሉን አረጋግጦ በተከሰሰበት አንቀጽ የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቶ ቅጣትን በተመለከተ የተጠሪ እድሜ 15 ዓመት መሆኑን በሌላ በኩል የግል ተበዳይ እድሜ ከ13 ዓመት በታች ሆኖ ድርጊቱ የተፈጸመው በጫዋታ ውስጥ መሆኑን ምክንያት በማድረግ በ15 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሠኝቶ ለመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ ያስመዘገበዉ እድሜ 13 ሲሆን ፓዊ ሆስፒታል የተጠሪ እድሜ ከ14-16 መካከል የሚገመት መሆኑን በመግለጹ ሊወሰድ የሚገባዉ እድሜ 14 ዓመት እንደሆነ እና ቅጣቱም ሲወሰን ስለህጻናት መብት ደህንነት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህገ መንግስትና በወ/ህጉ አንቀጽ 157 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተመለከተዉን መሰረት በማድረግ የተጠሪ እድሜ ከ9-15 እድሜ ክልል ዉስጥ ከመሆኑ አኳያ ሊፈጸም የሚገባዉ የጥንቃቄ እርምጃ ብቻ ነዉ በማለት ተጠሪ እናቱ ዘንድ ሆኖ በፖሊስ በኩል ክትትል እንዲደረግበት በወ/ህ/ አንቀጽ 159/2/ መሰረት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም ፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮ ከፍተኛዉ ፍ/ቤት ተጠሪ ላይ የተላለፈዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ ተቀብሎ ቅጣትን በተመለከተ ለእናቱ በአደራ እንዲሰጥ የመወሰኑን አግባብነት በተመለከተ ከወ/ህ/ አንቀጽ 159 /2/ አንጻር ለመመርመር እንዲቻል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል ፡፡ተጠሪን በመወከል የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከላካይ ጠበቃ የሰጠዉ መልስ ባጭሩ በወ/ህጉ አንቀጽ 168/2/ መሰረት የቅጣቱ ጣሪያ 10 ዓመት ላይ እንዲወሰን ዓቃቤ ህግ የጠየቀዉ ተገቢ መሆኑን በሌላ በኩል ተጠሪ አካለ መጠን ያልደረሰ አጥፊ በመሆኑና በአካባቢዉ የፀባይ ማረሚያ ባለመኖሩ ፀባዩን በቅርብ ለመከታተል ለእናቱ እንዲሰጥ መደረጉ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡ መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለዉ የወ/ህግ አንቀጽ 631/1/ለ ተላልፎ መገኘቱ ተረጋግጦ ነዉ ፡፡በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ ልዩነት የተፈጠረዉና እዚህ ሰበር ችሎት ድረስ ያከራከረዉ የቅጣት ዉሳኔ በተመለከተ ነዉ ፡፡ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ የሚያስቀጣዉ ከ15-25 ኣመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ነዉ ፡፡ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን ሲፈጽም እድሜዉ 14 ኣመት ስለመሆኑ ማስረጃ የመመርመርና የማጣራት ስልጣን በህግ የተሰጠዉ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አረጋግጧል ፡፡ አቃቤ ህግ የተጠሪ እድሜ ከዚህ በላይ ስለመሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አላረጋገጠም እነዚህን በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬነገሮች መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ ጉዳዩ ለሰበር የቀረበዉ ከወ/ህ/አንቀጽ 159/2/ አንጻር ለመመርመር ነዉ ፡፡ የዚህን ድንጋጌ ይዘት ከመመርመራችን በፊት አጠቃላይ ስለወጣት ጥፋተኞች በወ/ህጉ የተመለከተዉን መሰረታዊ መርህ ማየት ተገቢ ነዉ ፡፡የወ/ህጉ አንቀጽ 52 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንደተመለከተዉ ህጻናትና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች የወንጀል ሃላፊነትና የቅጣት ሁኔታ ለይቶ በጠቅላላዉ ክፍል አስቀምጧል ፡፡ ይኸዉም እድሜያቸዉ ዘጠኝ ዓመት ያልሞላቸዉ ህጻናት በወንጀል ድርጊት በሃላፊነት እንደማይጠየቁ ፤እድሜያቸዉ ከ9-15 ዓመት የሆናቸዉ ወጣት አጥፊዎች ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኙም ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች እንደሚወሰዱባቸዉ ፤እድሜያቸዉ ከ15-18 ዓመት የሆኑት ወጣት አጥፊዎች የወንጀል ሃላፊነት እና መደበኛ ቅጣት እንደሚወሰንባቸዉ ነገር ግን የቅጣቱ መጠንና አተገባበሩ ላይ ከአዋቂ ሰዉ ልዩነት ያለዉ መሆኑን እንገነዘባለን ፡፡ ስለሆነም በወጣት አጥፊዎች ላይ የሚወሰነዉ ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች በእነዚህ ድንጋጌዎች የተመለከተዉን መርህ የተከተለ እንዲሆን ህጉ ያስገድዳል ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ድርጊቱን ሲፈጽም እድሜዉ 14 ኣመት መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ቅጣትን አስመልክቶ ተፈጻሚነት ያለዉ የወ/ህጉ አንቀጽ 53 መርህ እና ይህንኑ ተከትሎ በአንቀጽ 157-168 የተመለከተዉ ዝርዝር ሁኔታዎች ናቸዉ ፡፡ከዚህ አንጻር የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ላይ የተወሰነዉን የጥፋተኝነትና 15 ኣመት ጽኑ እስራት ቅጣት አጽንቶ አፈጻጸም በተመለከተ በወ/ህጉ አንቀጽ 159/2/ መሰርት በእናቱ ዘንድ ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግበት ትዕዛዝ መስጠቱ መነሻ ምክንያቱ በክልሉ ዉስጥ የወጣት ጥፋተኞች ፀባይ ማረሚያ ተቋም ባለመኖሩ ስለመሆኑ ተረጋግጧል ፡፡ በእኛም በኩል እንደተመለከትነዉ እድሜዉ ከ9-15 ኣመት የሆነ ወጣት ከባድ ወንጀል ፈጽሞ ቢገኝና የጥንቃቄ እርጃዎች ቢወሰንበት ይህ ሊፈጸም የሚገባዉ በጠባይ ማረሚያ ተቋም መሆን እንደሚገባ የወ/ህ/አንቀጽ 168/1/ሀ ያስገነዝባል ፡፡ ከዚህ ባሻገር በተለየ ሁኔታ ወደ እስር ቤት የሚላከዉ ጥፋተኛዉ አደገኛና ሰላምን የሚያዉክ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ከአንቀጽ 168/1/ለ ይዘት መረዳት ይቻላል ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ አግባብ ተጠሪ የፈጸመዉ ድርጊት ከባድ ወንጀል ቢሆንም አደገኛና ሰላምን የሚያዉክ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ለቤተሰብ ሊሰጥ አይገባም በማለት ዓቃቤ ህግ ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም ። በተመሳሳይ ሁኔታ ወጣት ጥፋተኛ ላይ የጥንቃቄ እርምጃዎች አፈጻጸም በተቻለ መጠን አጥፊዉን በማረም መልካም ዉጤት ሊያስገኝ በሚያስችል አግባብ ሊፈጸም እንደሚገባ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መ/ቁ/120332 ላይ ከሰጠዉ ፍርድ መገንዘብ ይቻላል ስለሆነም በክልሉ ዉስጥ ለወጣት ጥፋተኞች የሚያገለግል ጠባይ ማረሚያ ተቋም በሌለበት ሁኔታ ፤ተጠሪ አደገኛ መሆኑም ባልተረጋገጠበትና በወላጅ እናቱ ቁጥጥር ስር ሆኖ የጠባዩ ሁኔታ ክትትል ቢደረግበት የተሻለ ዉጤት የማይመጣ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ የወ/ህጉ ስለወጣት ጥፋተኞች የደነገገዉን የጥንቃቄ እርምጃዎች ያገናዘበ ዉሳኔ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚያሰኝ ሆኖ አላገኘንም ።

ከዚህ ባሻገር ዓቃቤ ህግም ሆነ የተጠሪ ተከላካይ ጠበቃ ተጠሪ ላይ የተወሰነዉ ቅጣት በወ/ህጉ አንቀጽ 168/2/ መሰረት እንዲታረም ያቀረቡትን ጥያቄ አግባብነት ተመልክተናል በዚህ ድንጋጌ እንደተመለከተዉ ወጣት ጥፋተኛ የፈጸመዉ ወንጀል ከባድነትና ጥፋቱንም በፈጸመበት ጊዜ የነበረዉን የእድሜ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ታስሮ የሚቆይበት ጊዜ ልክ ፍርድ ቤቱ እንደሚወስንና ጊዜዉም ከ1-10 ዓመት ሊደርስ እንደሚችል ይደነግጋል ። በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት አንቀጽ 631/1/ለ የሚያስቀጣዉ ከ15-25 ዓመት ጽኑ እስራት በመሆኑ ወንጀሉ ከባድ ሲሆን ተጠሪ ወንጀሉን ሲፈጽም እድሜዉ 14 ኣመት መሆኑና ድርጊቱም የተፈጸመዉ በጫዋታ መካከል መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነዉ ። የእስር ጊዜዉ ይህንን ፍሬነገርና ህጉን መሰረት አድርጎ መወሰን ሲገባ የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበትን ድንጋጌ ይዘት ብቻ መሰረት በማድረግ የ15 ኣመት እስራት መወሰናቸዉ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል በዚሁ አግባብ ተጠሪ ላይ በስር ፍ/ ቤት የተወሰነዉ የ15 ዓመት እስራት ቅጣት በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/195/2/ለ/2 መሰረት በማሻሻል በ2 ዓመት እስር እንዲቀጣ ወስነናል ፤የእስራት አፈጻጸሙን በተመለከተ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ ህግ ስህተት ባለመገኘቱ ጸንቷል ።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉሳኔ

1ኛ.በፓዋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ/09364 በ06/11/08 ዓ.ም በተጠሪ ላይ የተሰጠዉና እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት የጸናዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ ጸንቷል ።

2ኛ.እስር ቅጣቱ በወ/መ/ህግ/ስ/ስ ቁ/195 /2/ለ/2 መሰረት ወደ 2 ኣመት ተሻሽሏል አፈጻጸሙን በተመለከተ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ /ቤት በመ/ቁ/12794 በ15/02/09 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ ጸንቷል ።

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።።

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ.126529

ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1.ዓሊ መሐመድ

2. ተክሊት ይመሰል

3. ተፈሪ ገብሩ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች.....የሰቆጣ ወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት --- ዐ/ህግ አሳምር ጌጤ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ.....ቂስ ሙሉጌታ ተረፈ ------ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የአንድ ክላሽ መሳሪያ እና ከመሰል 30 ጥይት ግምት ለማስከፈል የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.03-11989 የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በሰቆጣ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ተከሳሽ በሰቆጣ ወረዳ ቀበሌ 02 ነዋሪ ሲሆን በቀበሌዉ ሚሊሻ በኩል የማዕከል አስተባባሪ ኃይል አመራር ሆኖ ከሰቆጣ ወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት በሞዴል 22 በ30/1/2007 ዓ.ም ወጪ አድርጎ የወሰደዉን የንምራ ቁጥር 8072 የሆነ ሰ/ከ/ክላሽ 1/አንድ/ ካዝና እና ከመሰል 30 ጥይት ጋር የወሰደ ስለሆነ ይህን የመንግስት የጦር መሣሪያ እንዲመልስ፣ ካልሆነ ግምቱን የክላሽ 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ እና ጥይቱን 100*30=3,000 /ሶስት ሺህ/ እንዲከፍል እንዲወሰንልን በማለት ክሷል፡፡

የሥር ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ በክሱ ላይ የተጠቀሰዉን ክላሽ ጠመንጃ በ30/1/2007 ዓ.ም በ6,000 /ስድስት ሺህ/ ብር ዋስትና በመፈጸም ማዉጣቱ አይካድም፣ ይሁን እንጂ በ20/8/2007 ዓ.ም ከሰቆጣ ከተማ 02 ቀበሌ ከቂስ ወልዴ አያሌዉ ቤት አድሬ መሳሪያዉ ጠፋኝ፣ ተከሳሽ በዚህ ምክንያት በወንጀል ተከስሼ የእስራት ቅጣት ተወስኖብኝ ስለምገኝ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድጋሚ ልከሰስ አይገባም፣ ተከሳሽ መጠየቅ ያለብኝ ወድጄ የፈረምኩት ብር 6,000 /ስድስት ሺህ/ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ይህን መሳሪያ መዉሰዱን ስላልካደ ግምቱን መክፈል ያለበትም በአማራ ብ.ክ.መ. መስተዳድር መመሪያ በ30/7/2007 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣዉ የመሳሪያ ግምት ለክላሽ ዋጋ 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ እና ለ30 ጥይት ብር 3,000 /ሶስት ሺህ/ በአጠቃላይ ብር 33,000 /ሰላሳ ሶስት ሺህ/ ተከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡የሥር ከሳሽ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በድምጽ ብልጫ በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ተከሳሽ ይህን ክላሽ መሳሪያ ሲረከብ በሥራ ላይ በነበረዉ መመሪያ ቁጥር 44/2001 አንቀጽ 17 /2/ መሰረት የክላሽ ዋጋ የተተመነዉ ብር 6,000 /ስድስት ሺህ/ እና የአንድ ጥይት ዋጋ ብር 10 የነበረ በመሆኑ በዚህ አግባብ ሲታይ የሥር ተከሳሽ የክላሽ መሳሪያ ዋጋ ብር 6,000 /ስድስት ሺህ/ እና የ30 ጥይት ዋጋ ብር 300 /ሶስት መቶ/ ለሥር ከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔዎች በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ15/7/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት በአጭሩ፡--ተጠሪ ያጠፋዉን የመንግስት የጦር መሣሪያ /ክላሽ/ ዋጋዉን መክፈል የሚገባዉ መሣሪያዉ ጠፋ ባለዉ ሚያዚያ 20 ቀን 2007 ዓ.ም በሥራ ላይ በነበረዉ የአማራ ክልል መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ባካሄደዉ 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 15ኛ መደበኛ ስብሰባ በማሻሻል ባወጣዉ የመንግስት የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን መመሪያ መሰረት መሆን ሲገባዉ መሣሪያዉ ለተጠሪዉ ሲሰጥ የነበረዉን የመሳሪያ ግምት መሰረት በማድረግ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣ተጠሪ የአከራካሪዉን የጦር መሳሪያ ግምት ሊከፍለዉ የሚገባዉ መሳሪያዉን ሲረከብ በነበረዉ መመሪያ ቁጥር 44/2001 ነዉ ወይስ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በተሻሻለዉ መመሪያ ሊሆን ይገባዋል፣ የሚለዉን ነጥብ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ቢታዘዝም ለተጠሪ መጥሪያ ለማድረስ ተጠሪ በቀበሌዉ እንደማይኖር ስለተረጋገጠ ምስክሮች ባሉበት ለሚስቱ መጥሪያ የተሰጠ መሆኑን አመልካች በአቤቱታ በማረጋገጡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል።

በዚህ መዝገብ የተደረገዉ ክርክር ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ ለክርክር መነሻ የሆነዉን የመንግስት የጦር መሳሪያ የሆነዉን በክሱ የተመለከተዉን ክላሽ ፊርሞ ከአመልካች ጽ/ቤት ከወሰደ በኋላ ሳይመልስ በመቅረቱ የአሁን አመልካች የዚህ መሳሪያ ከመሰል ጥይት ዋጋ ጋር እንዲከፈለዉ ባቀረበዉ ክስ ዳኝነት መጠየቁ መዝገቡ ያመለክታል። የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክርክር መሳሪያዉን መዉሰዱን ሳይክድ በ20/8/2007 ዓ.ም የጠፋበት እንደሆነ በመግለጽ፣ የመሳሪያዉን ዋጋ መክፈል ከአለበት መሳሪያዉን በተረከበ ጊዜ በነበረዉ ዋጋ ተመን መሆኑን እንደሚገባ ገልጾ ተከራክሯል።

ከዚህ አንጻር ሲታይ የአሁን ተጠሪ ይህን መሳሪያ በተረከበበት ወቅት በ30/1/2007 ዓ.ም በሥራ ላይ የነበረዉ መመሪያ ቁጥር 44/2001 ሲሆን፣ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 /2/ መሰረት የአንድ ክላሽ ዋጋ ብር 6,000 /ስድስት ሺህ/ እና የአንድ ጥይት ዋጋ ብር 10 /አስር/ መሆኑ ተደንግጓል። ነገር ግን የአማራ ብ/ክ/መ/ መስተዳድር ምክር ቤት መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ባካሄደዉ 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 15ኛ መደበኛ ስብሰባ የመንግስት የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን በማሻሻል ባወጣዉ መመሪያ ቁጥር 11/4050 በ30/7/2007 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣዉ መሰረት የአንድ ክላሽ ዋጋ ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ እና የአንድ ጥይት ዋጋ ብር 100 እንዲሆን ተወስኗል። ይህ ከሆነ ከመጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በክልሉ የመንግስት የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን በተመለከተ ተፈጻሚነት ያለዉ መመሪያ መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣዉ መመሪያ እንጂ የቀድሞ መመሪያ ቁጥር 44/2001 ሊሆን አይችልም። ይህ የተሻሻለ መመሪያ ከወጣ በኋላ የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን የተሻሻለ እና የተለወጠ በመሆኑ፣ በተጠሪ እጅ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የነበረዉ ክላሽ ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ እና የአንድ ጥይት ዋጋ ብር 100 /መቶ/ ነዉ እንጂ በቀድሞ መመሪያ የተመለከተዉ ዋጋ ሊሆን አይችልም፡፡ በተጠሪ እጅ የነበረዉ የክላሽ መሳሪያ ከመጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ዋጋዉ የተለወጠ በመሆኑ ተጠሪዉ መሳሪያ በተረከብኩ ጊዜ በነበረዉ ተመን ልጠየቅ ይገባል በማለት በሥር ፍ/ቤት የቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ መሳሪያዉ ጠፍቷል ባለ ወቅት ሚያዚያ 20 ቀን 2007 ዓ.ም እና አመልካች ክስ ባቀረበዉ ጊዜ በሥራ ላይ ያለዉ መመሪያ በመሆኑ፣ ተፈጻሚነት እና አግባብነት ያለዉ መመሪያ ይኸዉ መመሪ ሆኖ ሳለ የቀድሞ መመሪያ ቁጥር 44/2001 መሰረት በማድረግ ተጠሪ የዚህ የክላሽ መሳሪያ ግምት ይክፈል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.03-11989 የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሰቆጣ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.0-05073 ሐምሌ 7 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.01-02040 በ22/11/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የአሁን ተጠሪ መሳሪያዉ ጠፋብኝ ባለ ወቅት በሥራ ላይ ባለዉ የመንግስት የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን በተሻሻለዉ መመሪያ መሰረት የክላሽ ዋጋ ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ እና የአንድ ጥይት ዋጋ በብር 100 የ30 ጥይት 3,000 /ሶስት ሺህ/ በአጠቃላይ ብር 33,000 /ሰላሳ ሶስት ሺህ/ ብር ለአመልካች ይክፈል ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
5. አመልካች በዚህ ችሎት የደረሰበት ወጪና ኪሳራ የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 133667

ታህሳስ 24 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች---- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች -----ብዙአየሁ ሾኔ የቡና ተክል ልማት ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠ/መኮንን በቀለ

ተጠሪ----------ቢ.ዲ.ኤፍ.ኤስ. ኢትዩጵያ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር- አቶ ንጉስ ሁነኛው ባለቤት ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሁከት ይወገድልኝ ክስን መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ክርክሩ የጀመረው በሊሙ ኮሳ ወረዳ ፍ/ቤት ሆኖ ስር ከሣሽ የአሁን ተጠሪ ተከሣሽ ደግሞ አመልካች በመሆን ተከራክረው ተከሣሽ ሁከት እንዲያቆም የተሰጠው ፍርድ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች በመፅናቱ ምክንያት የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

በስር ቀርቦ የነበረው ክስ እንደሚያመለክተው ከ2000 ዓ.ም.ጀምሮ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ማስረጃ ያወጣሁበትን እና ልዩ ልዩ ተክሎችን ያለማሁበትን ይዞታዬን በ5000 ሄክታር ላይ የሚገኘውን ድንበሩ በክሱ ላይ የተገለፀው አዋሣኞች ያሉትን በምዕራብ በኩል ወደ ድንበሬ በመግባት መኖሪያ ቤቴን እና በ57 ሄክታር ላይ የሚገኘውን ቡና ግንቦት 2006 ዓ.ም. ድንበር አልፎ በመያዝ በምሥራቅ እና በደቡብ በኩል በማስፋፋት ይዞ የሚገኝ ስለሆነ ተከሣሽ ሁከት በመፍጠር ንብረቴን የያዘብኝ ስለሆነ ሁከት አቁሞ ይህንን ንብረቴን እንዲለቅልኝ እና የክሱን ወጪና ኪሣራ ጭምር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት የአሁን ተጠሪ ክስ አቅርቧል፡፡

ተከሣሽም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን ለክርክር መነሻ የሆነው መሬት ላይ ከሣሽ መብት የለውም፣ ምክንያቱም 57 ሄክታር መሬትን ጨምሮ 5000 ሄክታር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሬት በቀን 14/9/2006 ዓ.ም. በቁ DH/INV/J/883/06 ከኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በተሻፈ ደብዳቤ ከከሣሽ ላይ ተወስዶ ወደ መሬት ባንክ እንዲ ገባ ሆኗል ፣ ሌላው ክሱ ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ቀደም ብሎ መሬቱ በሚገኝበት ቀበሌ መታየት ያለበት በመሆኑ በቀጥታ ለፍርድ ቤቱ መቅረቡን እቃወማለሁ ፣ ክስ የቀረበበት ይዞታ በየትኛው ቀበሌ እንደሚገኝም አልገለፀም በመሆኑም ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል የሚሉትን መቃሚያዎች ካቀረበ በኃላ የፍሬ ነገር መልሱን አቅርቧል፡፡ ይዘቱም የገፋሁት መሬት የለም፣ በአለው የመንግሥት መመሪያ መሠረት የኪራይ ውል ለ45 ዓመት ፈጽሜ በ12/6/2002 ዓ.ም. የተሰጠኝ ደብዳቤ በሕጋዊ መንገድ ከዞኑ ኢንቨስትመንት መስተዳድር የተሰጠኝ ስለመሆኑ ማስረጃ ያለኝ ስለሆነ ከሣሽ በመሬቱ ላይ መብት ስለሌለው ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲል አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን በቃል ካከራከረ በኋላ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃሚያ ውድቅ ማድረጉን፣ ፍሬ ጉዳዩን አስመልክቶም ግራ ቀኙን ካዳመጠ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክሮች መስማቱን፣ በቀረበው ማስረጃም ከሣሽ ክርክር ከተነሳበት መሬት ውስጥ 57 ሄክታር መሬት እስከ ግንቦት ወር 2006 ዓ.ም.ይዞ እየተጠቀመበት የነበረ መሆኑን፣ ከ 2006 ዓ.ም. ግንቦት በኋላ ግን ተከሣሽ ይህንኑ መሬት ይዞ እየተጠቀመበት የሚገኝ መሆኑን ፍርድ ቤቱ መገንዘቡን፣ ተከሣሽ ግን ይዞታው የእኔ ነው ከማለት ውጭ ክርክር በተነሳበት መሬት ላይ ሁከት ስለመፍጠሩ እና ስላለመፍጠሩ የገለፀው ነገር አለመኖሩን፣ የተጠየቀው ዳኝነት የይዞታ ጥያቄ ሳይሆን የሁከት በመሆኑ ተከሣሽም ወደ ከሣሽ ይዞታ በመግባት አለቅም ማለቱ በምስክር የተረጋገጠ በመሆኑ ሁከት በመፍጠር በኃይል የያዘውን 57 ሄክታር የቡና መሬት እና የቆርቆሮ መኖሪያ ቤት ለከሣሽ ሊለቅ ይገባል ሲል በመ/ቁ/ 12766 ታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መወሰኑን የውሣኔው ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች ይግባኝ ብሎ ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም በመ/ቁ/ 34182 የካቲት 7 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና ይግባኙን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ አይደለም በሚል አጽንቶታል፡፡ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታም አጣሪው ጉዳዩን ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙን ችሎቱ አስቀርቦና አቤቱታውን መርምሮ የስር ፍርድ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤቶች ውሣኔ የተፈፀመበት መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት በመ/ቁ/ 240932 ጥቅምት 07 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲል ጥቅምት 25 ቀን 2009 ዓ.ም. የተሣፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች በአቤቱታው አጥብቆ ስህተት ናቸው በማለት የሚያነሳቸው ነጥቦች በአጭሩ፡- የክልሉ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዬን አከራክሮ ውሣኔ ለመስጠት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም፣ ምክንያቱም ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ መሠረት የተሰጣቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው በመሆኑም የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህን ስህተት ማረም ይጠበቅባቸው የነበረ በመሆኑ እንዲታረምልን፣

መደበኛ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብለው ለማከራከር ሥልጣን የላቸውም፣ ምክንያቱም ጉዳዩ የኢንቨስትመንት መሬትን የተመለከተ በመሆኑ ያለአግባብ ተይዞብኛል የሚል ወገን በቅድሚያ መሬቱን ለፈቀደው ኢንቨስትመንት ቦርድ አቅርቦ ውሣኔ ሳያሰጥ በቀጥታ ለመደበኛ ፍርድ ቤት መቅረብ አይችልም፡፡ በመሆኑም አስተዳደራዊ ውሣኔ ያላገኘን ጉዳይ በቀጥታ የወረዳ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ማከራከሩና ውሣኔ መስጠቱ ስህተት ነው ይባልልን፣

የጅማ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 43 መሠረት ወደ ክርክር እንዲገባ ጠይቀን መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረምልን ይገባል፣ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ ሁከት የፈጠረ ስለመሆኑ በአግባቡ አልተጣራም በሚል ሰፊ አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ክርክር የተነሳበት ይዞታ ለኢንቨስትመንት የተሰጠ ከመሆኑ አኳያ በቅድሚያ ለኢንቨስትመንት በቦርድ ቀርቦ እልባት ሊያገኝ ይገባዋል በማለት የሰበር መ/ቁ. 46220 ተጠቅሶ የቀረበው መቃወሚያ እና የጅማ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ በአመልካች የቀረበው ጥያቄ በሥር ፍ/ቤቶች የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ይቅረብ በሚል በያዘው ጭብጥ መነሻነት መዝገቡ ሊቀርብ ችሏል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታው እና የማስቀረቢያ ነጥቡ ለተጠሪ ደርሶት የመከላከያ መልሱን እንዲያቀርብ ከመጥሪያ ጋር የተላከለት በመሆኑ ጥር 08 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ በአጭሩ፡- አመልካች ጠቅሰው ያቀረቡት የሰበር ውሣኔ የሊዝ አዋጅን መሠረት ያደረገ እንጂ የገጠር መሬትን የሚመለከት ባለመሆኑ አግባብ አይደለም፣ የተፈጠረ ሁከት እንዲወገድ የቀረበውን ክስ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ብቻ ነው፣ ፍርድ ቤቱም ሁከት መፈጠር አለመፈጠሩን ጭብጥ በመያዝ አጣርቶ የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው፣ በዚህ ክርክር ሂደት ይዞታው በተጠሪ እጅ እንዴት እንደገባ እንዲመረመርለት አመልካች ሲያቀርብ የነበረው መከራከሪያ ከሰበር መ/ቁ፤ 70801 ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ መታለፉ በአግባቡ ነው፣ የሶስተኛ ወገንን ጣልቃ ገብነት አስመልክቶ ለቀረበው አቤቱታም የጅማ ዞን አስተዳደር በጉዳዩ ጣልቃ እንዲገባለት ጥያቄ አቅርበው ጉዳዩ በይግባኝ ደረጃ በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ እና በመታየት ውድቅ አድርጎ ያለፈውን አመልካች ግን ጭራሽ ይዜ ጉዳይ እንዳልታየ አድርጎ ያቀረበው አቤቱታ ስህተት በመሆኑ ውድቅ ይደረግልን በሚል መልስ ከሰጠው በአጭሩ መዝግበናል፡፡ አመልካችም የቀድሞውን አቤቱታ በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገብ ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ መልስ እና የመልስ መልሱን ከስር ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ውሣኔ እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በግራ ቀኙ መካከል እያከራከረ ያለው የኢንቨስትመንት መሬት መሆኑ ከላይ ተመልክተናል፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት አቅርቦት የነበረው ክስ ከላይ እንደተመለከትነው ይዞታን ገፍቶ በውስጡ ካለ የቆርቆሮ ቤት እና ተክሎች ጋር ይዞብኛል ሁከት ይወገድልኝ የሚል ሲሆን የስር ተከሣሽ /አመልካች / በፍሬ ጉዳይ ከመታየቱ በፊት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አለኝ በማለት በቅድሚያ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በቀጥታ ተቀብሎ ለማከራከር ሥልጣን የለውም ጉዳዩ በገጠር መሬት ላይ የተነሳ ክርክር በመሆኑ በቅድሚያ መሬቱን ለፈቀደው አካል ቀርቦ መታየት ይገባዋል የሚል እና ሌሎች መቃወሚያዎችን ጨምሮ ማቅረቡን ተመልክተናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አኳያ ለፍርድ ቤቱ የቀረበውን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች እና ተጠሪ ከመንግሥት በሊዝ የኢንቨስትመንት መሬት በኪራይ የያዙ መሆኑን ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ከያዝኩት የኢንቨስትመንት መሬት ላይ ተከሣሽ ገፍቶ 57 ሄክታር መሬት ይዞብኛል እንዲሁም በቦታው ላይ ያለ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የተሰራ ቤት እና ተክሎችንም የያዘብኝ ስለሆነ ሁከት ፈጥሮብኛል የሚል ሲሆን ስር ተከሣሽ በበኩሉ ገፍቼ የያዝኩት መሬት የለም ከመንግሥት በህግ አግባብ የተሰጠኝ ነው በማለት በፍሬ ነገር መልሱ አቅርቧል፡፡ ወደ ፍሬ ነገር ክርክራቸው ከመገባቱ በፊት በቅድሚያ መታየት ያለበት የቀረበው ጉዳይ የሚገዛበትን ህግ መመልከት ተገቢ ሲሆን ክርክር ያስነሳው መሬት የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል በመሆኑ የሚገዙበት ህግ ሊሆን የሚችለው የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 138/2000 ነው፡፡

በዚህ አዋጅ ላይ ሁለት ኢንቨስተሮች / ግለሰቦች/ የይገባኛል ክርክር በሚያነሱበት ጊዜ ምን እንደሚሆን የደነገገው ነገር የለም፡፡ በፌዴራል የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 32 ማንኛውም ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ካለው አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት አካል አቤቱታ የማቅረብ መብት ይኖረዋል ይላል ይህ ማለት ግን ሁለት ኢንቨስተሮች የይገባኛል ክርክር በሚያነሱበት ጊዜ ጉዳያቸው የት እንደሚዳኝ የሚገልጽ ድንጋጌ አላስቀመጠም፡፡ በመሆኑም የአመልካች እና የተጠሪ ጉዳይ በተጠቀሱት ሁለት አዋጆች ላይ አለመግባባት ሲፈጠር ማን እንደሚዳኛቸው ያልተቀመጠ በመሆኑ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት መሄዱ የግድ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በክልልም በፌዴራልም የሚሰጥ ሲሆን ክርክር ባስነሳው መሬት ላይ ግራ ቀኙ ያወጡት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የፌዴራል ከሆነ ጉዳያቸው ሊታይ የሚችለው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሲሆን፣ ፈቃድ ያገኙት ግን በክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ ከሆነ ደግሞ በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታይ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ከሁለቱ አንዱ ወገን የፌዴራል ተመዝጋቢ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6 መሠረት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ይሆናል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች እና ተጠሪ ኃላፊነቱ የተ/የግል ማህበር መሆናቸውን አሰያየማቸው የሚገልጽ ሲሆን የንግድ ማህበር እስከሆኑ ድረስ ተመዝጋቢነታቸው በፌዴራል መንግስት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የተነሳው ክርክር በሁለት የህግ ሰውነት ባላቸው አካላት መሃከል በመሆኑ በፌዴራልም ሆነ በክልሉ የኢንቨስትመንት አዋጅ ውስጥ በእንደዚህ አይነት አካላት መሃከል ግጭት /አለመግባባት /ሲፈጠር አለመግባባቱ የሚፈታበትን መንገድ በግልጽ ያልደነገገ በመሆኑ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት መሄዱ የግድ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ መቅረብ የነበረበት በፌዴራል ፍርድ ቤት መሆኑ የግድ ሆኖ በህገ መንግሥቱ ለክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳይን እንዲያዩ በተሰጠው ውክልና መሠረት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክሱ መቅረብና መስተናገድ ሲገባው የክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ሳይኖረው ተቀብሎ መወሰኑ እና የበላይ ፍርድ ቤቶችም የስር ፍርድ ቤት የፈፀመውን ስህተት ሳያርሙ ማለፋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የሊሙ ኮሳ ወረዳ ፍ/ቤት በ18/4/2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ፣ የጅማ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በ7/6/2008 ዓ.ም. በመ/ቁ/ 34182 ላይ የሰጠው ፍርድ እና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 240932 ጥቅምት 07 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በህግ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ውሣኔ ከማሰጠት የዚህ ፍርድ መሰጠት አያግዳቸውም፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ላወጡት ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
5. መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ካ/የ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 134681

ጥቅምት 21 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ሳዲቅ አብዱሪህማን

2 አቶ ቢሊሳ አብዱሪህማን ጠበቃቸው አቶ ዝናቡ አክሊሉ ቀረቡ

3 አቶ ኡስማን አህመድ

ተጠሪዎች፡- የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት - ዐቃቤ ህግ አቶ ኬኔዲ አለማየሁ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የክርክሩ ምክንያት ያለአግባብ የተወሰደ የካሳ ገንዘብ ይመለስ የሚል ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ለድሬዳዋ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ ሲሆን አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘትም፡- የአሁኑ አመልካቾች እና የዚህ ሰበር ተካፋይ ያልነበሩት የሥር 3ኛ ተከሳሽን ጨምሮ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ የሌላቸውን ንብረት ወይም ይዞታ በማስመዝገብ የሌላ ሰው የሆነውን ይዞታ የእኛ ነው በማለት ትርፍ ገንዘብ ብር 131,797.73 /አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከሰባ ሶስት ሳንቲም/ እንዲመልሱ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ተከሳሾች መጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬ ነገሩ ላይም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የድሬዳዋ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ክርክር እና የምስክሮችን ቃል እንዲሁም የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ የሥር ተከሳሾች ካላቸው ይዞታ መሬት ትርፍ መሬት በማስመዝገብ የወሰዱትን በክሱ ላይ የተጠቀሰውን ብር 131,797.73 /አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከሰባ ሶስት ሳንቲም/ ተመላሽ እንዲያደርጉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህን ውሳኔ በመቃወም የአሁኑ አመልካቾች ይግባኝ ለድሬዳዋ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የከተማ አስተዳደሩ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲሁም የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ለማስለወጥ ሲሆን ይዘቱም፡- የድሬዳዋ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የፍትሓብሔር ዳኝነትን በሚመለከት በቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33 ሥር ከተደነገገው ውጪ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚነሱ የፍትሓብሔር ክርክሮችን፣ የይዞታና ያልተገባ ጥቅም ተወስዷል በሚል የሚቀርቡ ክርክሮች ሰምቶ ማስረጃ ተቀብሎ የመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን ሳይኖራቸው የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አከራካሪ የሆነው የይዞታ ባለቤትነት ጥያቄው የሚታየው በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም የከተማው ሰበር ሰሚ ማየት ሲገባው ለከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቀረበበትንና የተያዘበትን አግባብነት ለማጣራት ተብሎ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም የግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የነገሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ እንደተገነዘብነው የሥር 1ኛ- 3ኛ ያሉት ተከሳሾች በቀድሞ ልኬት መሠረት 4.6647 ሄክታር ሲሆን የወሰዱት የመፈናቀያ ካሳ ብር 183,664.50 /አንድ መቶ ሰማኒያ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ተሰርቶ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በድጋሚ ጂ.ፒ.ኤስ መለኪያ መሥሪያ መሠረት የተለካው የመሬት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጠን 3.271 ሄክታር የመፈናቀያ ካሳ ክፍያ ብር 128,789.97 /አንድ መቶ ሃያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከዘጠና ሰባት ሳንቲም/ መከፈል ሲገባ በሌላቸው መሬት መጠን 1.304 ሄክታር በማስመዝገብ ብር 54,874.53 /አምሳ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ አራት ብር ከሃምሳ ሶስት ሳንቲም/ ትርፍ ገንዘብ ወስደዋል፣ የሥር 4ኛ ተከሳሽ /የአሁኑ 3ኛ አመልካች/ የሆኑት ደግሞ በቀድሞ ልኬት መሠረት 5.4570 ሄክታር ሲሆን የመፈናቀያ ካሳ ብር 190,995.00 /አንድ መቶ ዘጠና ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አምስት ብር/ ተሰርቶ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በአዲስ መልክ ሲለካ 3.2592 ሄክታር መሬት ሆኖ የመፈናቀያ ካሳ ግምቱ ብር 114,072. /አንድ መቶ አስራ አራት ሺህ ሰባ ሁለት ብር/ መክፈል ሲገባ በሌላቸው መሬት መጠን 2.1978 ሄክታር በትርፍነት በማስመዝገብ ብር 76,923.00 /ሰባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሶስት ብር/ ትርፍ ክፍያ ተፈጽሞላቸዋል የሚል ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ የሥር ከሳሽ /የአሁኑ ተጠሪ/ እንዲመለስ የጠየቀውን ገንዘብ የሥር ተከሳሾች /የአሁኑ አመልካቾች/ እንዲመልሱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ በዋናነት ሊታይ የሚገባው የሥር ፍርድ ቤት የቀረበውን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚል ነው፡፡ አንድ ፍርድ ቤት አንድን ጉዳይ አይቶ ለመወሰን በመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር ሥልጣን ሊኖረው ይገባል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ሥልጣንን በተመለከተ የአሁኖቹ አመልካቾች የራሳቸው ያልሆነን የሌላ ግለሰብን ይዞታ ጨምረው በማስለካት ከመንግሥት ተጨማሪ የካሳ ክፍያ የወሰዱ በመሆኑ ምክንያት የማይገባቸውንና የማይመለከታቸውን ስለወሰዱ እንዲመልሱ የቀረበ ክስ በመሆኑ በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 31 (1) እንደተመለከተው የከተማውን ማስተር ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የይዞታ ባለቤትነት፣ ፍቃድ አሠጣጥ ወይም ይዞታ አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ ክሶችን የማየት ሥልጣን የከተማው ፍርድ ቤት ስለሆነ ክስ መስርተን ውሳኔ ማሰጠታችን እንዲሁም የካሳው ጉዳይም ከይዞታው ጋር የሚገናኝ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትም ሥልጣኑን መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ አግባብ ስለሆነ የህግ ስህተት ስለሌለ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡ ለዚህ ሥልጣን ጉዳይ ዋና መሠረት ተደርጎ የተነሳውን የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ 416/1996 አንቀጽ 31 /1/ መመልከት ለክርክሩ ህጋዊ እልባት ለመስጠት ያስችላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የድሬዳዋ አስተዳር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 31 (1) ድንጋጌ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

- የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የይዞታ ባለቤትነት በተመለከተ የሚነሱ ክሶችን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን፣

- የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የፈቃድ አሰጣጥ በተመለከተ የሚነሱ ክሶችን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን፣

- የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የቦታ አጠቃቀም በተመለከተ የሚነሱ ክሶችን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን እንዳለው ተደንግጓል፡፡

ይህ ድንጋጌ በግልጽ እንደሚያመለክተው የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ለማስፈጸም ሲባል ከይዞታ ባለቤትነት፣ ከፍቃድ አሰጣጥ እና ከቦታ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚነሱ ክርክሮችን የከተማው ፍርድ ቤት ለማየት እንዲችል በህግ አውጪው የተሰጠ ሥልጣን ነው፡፡ ነገር ግን ከያዝነው ጉዳይ ወይም የክርክር ዓይነት ጋር ተያይዞ የተሰጠ የዳኝነት ሥልጣን አይደለም፡፡

በመሠረቱ አሁን እያከራከረ ያለው ጉዳይ በአዋጁ አንቀጽ 31 /1/ ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ሳይሆን አመልካቾች የራሳቸው የእርሻ ይዞታ መሬት ያልሆነ ወይም የይዞታው ባለቤት ያልሆኑበትን የሌላ ሰው እርሻ መሬት ይዞታ በትርፍ አስለክተው የማይገባቸውን ገንዘብ ወስደዋል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ በዚህ መሠረት ክርክሩ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የተነሳ የእርሻ መሬት ባለይዞታነት ይገባኛል ጥያቄን መሠረት በማድረግ የተነሳ በመሆኑና ባለይዞታው ማን እንደሆነ አከራክሮ በመለየት በትርፍ መሬት ይዞታ ተሰጥቶ የነበረው ትርፍ የካሳ ገንዘብ እንዲመለስ የሚለውን የፍትሓብሔር ክርክር የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 31 /1/ መሠረት ለከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ሥልጣን ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም የሥረ ነገሩን ለመስማት ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የሌለው በሆነ ጊዜ ስለሚፈጸም ሥነ ሥርዓት የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 9 በግልጽ ያስቀመጠውን ድንጋጌ የሥር ፍርድ ቤቶች ባለማጤን ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሥልጣን የላቸውም ተብሎ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያለአግባብ በማለፍ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር በመግባት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡

ውሳኔ

1. የድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.01913 ግንቦት 3 ቀን 2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት 01075 በቀን 19/3/2009 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 (1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤቶች አይተው ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን የላቸውም ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4. በቀን 12/04/2009 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡

5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይላክላቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ - 137353

ጥር 22 ቀን 2010ዓ.ም

ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ

ተክሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ አዛለች አጎናፍር ጠበቃ ሚልኪያስ ቡልቻ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ገብርኤል አካባቢ ቀበሌ ጽ/ቤት ዐ/ሕግ አይናዲስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ያላግባብ የተያዘ ቤት ይለቀቅልኝ በሚል የቀረበዉን ዳኝነት መሠረት በማድረግ የተሰጠዉን ፍርድ በመቃወም የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘትም፤ በጎንደር ከተማ ገብርኤል አካባቢ ክ/ከተማ በ 735 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያላቸዉን ቤት ተጠሪ ያላግባብ በመያዝ ለግለሰቦች እያከራየ መሆኑን፣ ቤቱ በመንግስት ያልተወረሰ መሆኑን ገልጸዉ እንዲመለስላቸዉ ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት የከንቲባ ጽ/ቤቱ ቤቱ እንዲመለስላቸዉ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም ተጠሪ ቤቱን ለማስረከብ ፍቃደኛ አለመሆኑን ጠቅሰዉ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክባቸዉ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸዉን የሚያሳይ ነዉ፡፡

ተጠሪ ለቀረበበት ክስ በሰጠዉ መልስ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለዉ የፐራይቬታይዘሽን ኤጀንሲ በመሆኑ ክሱ ለፍርድ ቤቱ ሊቀርብ እንደማይገባዉ እንዲሁም ክሱ በይርጋ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚታገድ ስለመሆኑ ገልፆ የመጀመሪያ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን፣ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ ማስረጃ አለማቅረቡን እና ቤቱ የሚገኝበት ቦታ ስፋትም አመልካች እንደሚሉት 735 ካ/ሜ ሳይሆን 182 ካ/ሜትር መሆኑን እና ቤቱም የመንግስት እንጂ የአመልካች አለመሆኑን በመግለጽ የቀረበዉ ክስ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ፤ ቤት ተወርሷል ወይስ አልተወረሰም የሚለዉን ጭብጥ በማስረጃ አጣርቶ የመወሰን ስልጣን የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ የመደበኛ ፍርድ ቤት አለመሆኑን እንዲሁም አመልካች ከክሳቸዉ ጋር አያይዘዉ ያቀረቡት የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታም በ1965 ዓ.ም የተሰጠ በመሆኑ በቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑን አያሳይም በማለት የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 26/08/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበዉ 3 ገጽ የሰበር አቤቱታ በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮም ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በሚል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት ለማጣራት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ እንዲከራከር በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ መዝገቡን ለማስቀረብ ከተያዘዉ ጭብጥ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከግራ ቀኝ ክርክር ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ላቀረቡት ክስ መሠረት ያደረጉት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግላቸዉ መሆኑን እና ተጠሪ ያላግባብ መያዙን ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የአመልካች አለመሆኑን በመግለጽ የተከራከረ መሆኑን ነዉ፡፡ የስር የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ ለማድረግ የቻለዉ በአንድ በኩል ቤቱ የተወረሰ መሆን አለመሆኑን በማስረጃ አጣርቶ ለመወሰን ፍርድ ቤት ስልጣን የለዉም በማለት በሌላ በኩል አመልካች ያቀረቡት ማመልከቻ በቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሠረቱ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የሌለዉ መሆኑን እንደተገነዘበ ይህኑን ጠቅሶ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር ከመግባቱ በፊት ተቀባይነት የሌለዉ መሆኑን ገልፆ የቀረበዉን የክስ አቤቱታ ከመመለስ አልፎ ፍሬ ነገርን በተመለከተ ዉሳኔ መስጠት እንደማይችል በፍ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 231(1-2) ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የስር ፍርድ ቤት በአንድ በኩል ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም እያለ፣ በሌላ በኩል ግን አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረቡም በማለት ፍሬ ነገሩን በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ አይደለም በማለት የሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት እንመልከት፡፡ በህግ ለሌላ አካል በግልጽ እስካልተሰጠ ድረስ በፍርድ የሚያልቁ ጉዳዮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን የፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ስር ከተመለከተዉ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከስልጣን ጋር በተያያዘ ክርክር ሲኖር ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያላቸዉ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ የማየት ስልጣን በህግ ለሌላ አካል የተሰጠ መሆኑ አለመሆኑን በአግባቡ የማረጋገጥ ግዴታ እና ኃላፊነት ያለባቸዉ ሲሆን፤ ይህን አለማድረግ በዜጎች ፍትሕ የማግኘት መብት ላይ አሉታዊ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል መሆኑንም መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡

የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም ሲል ለሰጠዉ ዉሳኔ በዋቢነት የጠቀሰዉ አዋጅ ቁጥር 110/87 እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 30631 የሰጠዉን ዉሳኔ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀጽ 4(1) እና (2) መሰረት ከአዋጅ ዉጪ የተወሰዱ ንብረቶችን የባለቤትነት ሁኔታ የማጣራትና የመወሰን ስልጣን ለፕራይቬታይዜሽን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኤጀንሲ ይሰጣል፤ አዋጅ ቁጥር 572/2000 ከአዋጅ ውጪ የተወሰዱ ንብረቶችን ለማስመለስ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እና ያላግባብ የተወረሱ የመንግስት ንብረቶችን እንደገና ለማስመለስ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን አይቶ የመወሰኑ ስልጣን የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይሁንና ያላግባብ በከተማ አስተዳደር ወይም በቀበሌ የተያዘን ቤት ለማስመለስ የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ ለየትኛዉ አካል እንደሚቀርብ በሁለቱም አዋጆች በግልጽ አልተደነገገም፡፡ ፍርድ ቤት በዋቢነት የጠቀሰዉ በሰ/መ/ቁጥር 30631 ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ሲታይ ከአዋጅ ውጪ የተወረሱትን ቤቶች ለማስመለስ የሚቀርብ ዳኝነትን እንጂ የምርጫ ቤት ያላግባብ ተይዟል በሚል የቀረበዉን ክርክር መነሻ ያደረገ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የጠቀሰዉ የሰበር ዉሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) አኳያ ለተያዘዉ ጉዳይ በዋቢነት ሊጠቀስ የሚገባዉ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ በከተማ አስተዳደር ወይም በቀበሌ ያላግባብ የተያዘን የምርጫ ቤት ለማስመለስ የሚቀርበዉን ክስ የማየት ስልጣን በህግ ለሌላ የመንግስት አካል ባልተሰጠበት ሁኔታ፣ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 30631 የሰጠዉ ዉሳኔም ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት የሌለዉ ሆኖ እያለ፤ መደበኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በሚል የደረሰበት ድምዳሜ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑን በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 00562 በቀን 01/03/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-22362 በቀን 11/09/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉን ፍርድ በማጽናት፣ የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን እንደገና በማንቀሳቀስ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢዉን ዉሳኔ ይሰጥበት ዘንድ መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 341(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ስ/ጌ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ.133309

ጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡...1.ዳኜ መላኩ

2. ተክሊት ይመሰል

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-..... አቶ ለማ ማሙዬ- ቀርበዋል

ተጠሪ፡-.....በአዳማ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 12 ጽ/ቤት -ነ/ፈጅ አቶ ነቢ ፈይሶ ቀርበዋል

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ የመንግስት ቤት ለማስለቀቅ የቀረበ ክስን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.232835 በ7/2/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ተከሳሽ የቤት ቁጥር 286.04 ከከሳሽ በዉል የተከራየ ቢሆንም በሚስቱ በወ/ሮ ዘነበች ተክሌ ስም የቤት ቁጥር 202 ሰርቶላት ተጠቃሚ አድርጓት እያለ በቀበሌ ቤት ዉስጥ መኖር ስለማይገባዉ ተከሳሽ ቤቱን እንዲለቅልን በማለት ክሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ባለቤቱ ያልተጠናቀቀ ቤት አግኝታ ነበር፣ ቤቱን አልገባንበትም፣ ይህ ቤት በእዳ ምክንያት በፍ/ቤት ዉሳኔ የተወሰደ ስለሆነ የመንግስት ቤት ሊለቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ በባለቤታቸዉ ስም የሰሩትን ቤት ወደ ልጃቸዉ ያዛወሩ ስለሆነ በዉላቸዉ እና በመመሪያዉ መሰረት የመንግስት ቤት ይዘዉ የሚቀጥሉበት አግባብ ስለሌለ ቤቱን ለከሳሽ እንዲለቅ በማለት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወስኗል፡፡ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በይግባኝ በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ባይ በሚስታቸዉ ስም የተሰራዉ ቤት በእዳ ምክንያት በፍ/ቤት ዉሳኔ በአፈጻጸም ከፍላጐታቸዉ ዉጭ ስለተወሰደ፣ ይህን ለልጃቸዉ በዘዴ አዛዉረዉ አስወስደዋል የሚባልበት ምክንያት ስለሌለ፣ ይህን የመንግስት ቤት ሊለቁ አይገባም በማለት የሥር ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት እና የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔዎችን በመሻር የሥር የወረዳ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስቀየር ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ18/2/2009 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሥር ፍ/ቤት ያልተነሳዉን ክርክር የኪራይ ዉል ጊዜ ገደብ ማለቁን በተመለከተ በማንሳት ቤቱን እንዲለቅ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካች በባለቤታቸዉ ስም ሰርቷል የተባለዉ ቤት ከአቅም በላይ በሆነና በእዳ ምክንያት በፍ/ቤት ዉሳኔ ከእጃችን መዉጣቱ እየታየ ቤት ነበራቸዉ በሚል ምክንያት የተከራየሁትን ቤት እንዲለቅ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎት አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ተጠሪ በ27/6/2009 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የሥር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትና የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለዉም ተብሎ እንዲጸናልን፣ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ተድርጎልን ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት የሚገባዉ ነጥብ የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነዉን የመንግስት ቤት እንዲለቁ የተሰጠዉ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡ ከሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች ግልባጭ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን አመልካች የመንግስት ቤት ከተጠሪ በኪራይ ዉል ተከራይተዉ ሲኖሩ እንደነበር፣ አመልካች በባለቤታቸዉ ስም በአዳማ ከተማ ዉስጥ የመኖሪያ ቤት መስራታቸዉ እና ይህን በባለቤታቸዉ ስም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተሰራዉን ቤት ያበደርኳቸዉን ገንዘብ አልከፈሉኝም በሚል በእዳ ምክንያት ልጃቸዉ በፍ/ቤት ክሷቸዉ ዉሳኔ ተሰጥቶ በአፈጻጸም ተወስዶብናል በማለት የፍ/ቤት ዉሳኔ ማቅረባቸዉን ያመለክታሉ፡፡

ነገር ግን በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ የቤት ኪራይ ዉል አንቀጽ 8 (6) እና በመመሪያ ቁጥር 10/2006 አንቀጽ 15.2 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አንድ የመንግስት ቤት ተከራይ የራሱ ቤት ካገኘ የመንግስት ቤትን በተከራይነት ይዞ መቀጠል እንደማይችልና የመንግስት ቤት መልቀቅ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንጻር የግራ ቀኞቸዉ ክርክር ሲታይ የአሁን አመልካች በባለቤታቸዉ ስም የሰሩትን ቤት የልጃችን እዳ አለበት በማለት እርስ በእርሳቸዉ ተካሰዉ እና እዳም እንዳለ አምነዉ ዉሳኔ እንዲሰጥ በማድረግ የምንከፍል ገንዘብ የለንም በማለት ቤቱን ለልጃቸዉ ማስረከባቸዉ ሲታይ፣ በባለቤታቸዉ ስም የሰሩትን ቤት እና የመንግስት ቤት ይዘዉ ለመቀጠል በማሰብ የተደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር የሚታመን ተግባር እንዳልሆነ የሥር ፍ/ቤቶች የረጋገጡት ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች በባለቤታቸዉ ስም የሰሩትን ቤት በዚህ አግባብ ወደ ልጃቸዉ ስም አዛዉረዉ የመንግስት ቤትን ይዘዉ የሚቀጥሉበት አግባብ የለም፡፡ የሥር የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት የመንግስት ቤት የኪራይ ዉል ዓላማ ካለመገንዘብ የተነሳ የኪራይ ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ እና ያልታደሰ በመሆኑ ዉሉ ተቋርጧል በማለት የያዘዉ አቋም ተገቢ ባይሆንም በዉጤት ደረጃ አመልካች የመንግስት ቤት በኪራይ ይዘዉ መቀጠል እንደሌለባቸዉ አቋም በመያዝ የሥር የወረዳ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ዉሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር የወረዳ ፍ/ቤት እና የሥር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች በኪራይ ዉል መነሻነት ሲኖሩበት የነበረዉን የመንግስት ቤት ለቀዉ ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የሰጡት ዉሳኔ በሕግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ነዉ ለማለት ስላልተቻለ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.232835 በ7/2/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 140538

መሥከረም 22 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-አቶ ወርቁ ታደሰ ⟶ጠበቃ ሱልጣን ሰይፍ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጅራተ ኢልፈታ ⟶ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በምዕራብ ሸዋ ዞን የባኮትቤ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰውን 0.25 ሔክታር መሬት ማረሚያ ቤት እያሉ በ2000 ዓ.ም አመልካች በሕገወጥ መንገድ ለከብቶች ግጦሽ የያዘባቸው መሆኑን በመግለጽ መሬቱን ለቀው እንዲያስረክቧቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ የአከራካሪው መሬት ስፋት አንድ ሔክታር መሆኑን፤ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ለ42 ዓመታት ይዘው የሚጠቀሙበት እና ተጠሪ ተጠቅሞበት የማያውቅ በመሆኑ ይርጋ የሚያግደው መሆኑን በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ መሬት በሚሰፈርበት ጊዜ ዳገታማ መሬት ነው ተብሎ ያልተሰፈረላቸው መሆኑን በመግለጽ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት የወረዳውን መሬት አጠቃቀም እና አሥተዳደር ጽ/ቤት አከራካሪው መሬት የማን እንደሆነ እና በማን ሥም እንደተሰፈረ አጣርቶ እንዲገልጽ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠቃሹ አካል ለፍ/ቤቱ በሰጠው ምላሽ አከራካሪው መሬት ለተጠሪ የተሰፈረ መሆኑ እና አመልካች ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ከብቶችን እያሰማራበት ያለ መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥቷል። የአመልካች ምስክሮች ለፍ/ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃል የመሬት ኮሚቴ መሬት የአርሶ አደሩ ነው ተብሎ በተመራበት ዘመን አከራካሪውን መሬት ለአመልካች የሰጠው መሆኑን፤መሬቱ የግጦሽ መሆኑን እና አመልካች ከብቶች የሚያሰማራበት መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል። የተጠሪ ምስክሮች ለፍ/ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃል አከራካሪው መሬት የተጠሪ መሆኑን እና አመልካች ለረጅም ጊዜ ከብቶችን ሲያሰማራበት የቆየ መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል። ፍ/ቤቱም በግራቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች እና በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የቀረበውን ማሥረጃ ከመረመረ በኋላ የቀረቡት ማሥረጃዎች አከራካሪው መሬት የተጠሪ መሆኑን ስለሚያረጋግጡ አመልካች መሬቱን ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሠኘት በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም። የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች ያቀረብኩት የይርጋ መቃወሚያ ታልፎ በፍሬጉዳይ ላይ የሰጠሁት አማራጭ መልስ ግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች አከራካሪውን መሬት ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች አከራካሪውን መሬት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በሕገወጥ መንገድ መያዙ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ታልፎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል። ተጠሪ በሰጡት መልስ ተጠሪ እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ በመሬቱ ስጠቀም እንደነበረ ተረጋግጧል፤አመልካች ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ መሬቱን ይጎለሀ በማለት ያቀረበው ክርክር ሐሰት ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡ አመልካች አከራካሪውን መሬት ለረጅም ጊዜ ከብቶችን በማሠማራት የሚጠቀምበት መሆኑ በሥር ፍ/ቤት ቀርበው ከተሰሙት የግራቀኙ ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡ የወረዳውን መሬት አጠቃቀም እና አሥተዳደር ጽ/ቤት ለፍ/ቤቱ በሰጠው ምላሽም አመልካች ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ አከራካሪውን መሬት ከብቶችን በማሠማራት የሚጠቀምበት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አከራካሪውን መሬት በሕገወጥ ውል መነሻነት የያዙት ስለመሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር የለም፡፡

የኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አሥተዳደር ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 32 አርሶአደሩ በመሬቱ ላይ ያለውን መብት ለማስጠበቅ በአሥራሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ.ቁ 43226፤79394 እና በሌሎችም መዝገቦች ላይ ሕገወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በሕጉ የተመለከተው የይርጋ የጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን መሬት ከአሥራሁለት ዓመት በላይ ከብቶችን በማሠማራት የሚጠቀሙበት መሆኑ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማሥረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አከራካሪውን መሬት ሕገወጥ በሆነ ውል መነሻነት የያዙት ስለመሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር የሌለ በመሆኑ አመልካች መሬቱን ለረጅም ጊዜ የሚጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽ የተጠሪ ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት አለው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አመልካች መሬቱን እንዲለቅላቸው ያቀረቡት ክስ በክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 32 በይርጋ የሚታገድ ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች አከራካሪውን መሬት ከአሥራሁለት ዓመት በላይ ይዞ የሚጠቀምበት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የተጠሪን ክስ በይርጋ ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች መሬቱን ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራው ክልላዊ መንግሥት በምዕራብ ሸዋ ዞን የባኮትቤ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20876 ሕዳር 08 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ፤በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 58734 ሕዳር 13 ቀን 2009 ዓ.ም በትዕዛዝ፤በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 254595 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ ክስ በይርጋ የታገደ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ **-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ ቁጥር 149962

ቀን 25/7/2010 ዓ/ም

ዳኞች

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች - አቶ ስለሽ ዋለልኝ -አልቀረበም

ተጠሪ - የአማራ ብ/ክ/መ. ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ ስሜነህ ታደሰ ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ህዳር 25 ቀን 2010 ዓ.ም በተሻሬ አቤቱታ የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 68301 ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ በስር ውሳኔ ሰጪ አካላት የተሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ መሆኑ በደንብ ቁጥር 104/2004 ተመልክቶ እያለ በአማራ ብ/ክ/መ. ሕገ መንግስት በክልል ጉዳይ የበላይና የመጨረሻ ስልጣን ያለው መሆኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግልጽ ተቀምጦ እያለ የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ማለቱ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከአማራ ብ/ክ/መ. የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የድስፒሊን ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ የአማራ ብ/ክ/መ. የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የምርምርና የህግ ዳይሬክቶሬት ባቀረበው ክስ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ለከፍተኛ ትምህርት በተላከበት ወቅት በሌላ የመንግስት መ/ቤት ተቀጥሮ ከሁለት የመንግስት መስሪያ ቤት ደሞዝ በመውሰድ የማጭበርበር የድስፕሊን ጥፋት ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ ተከሳሽም ሁለት ቦታ እንዳልሰራ የሚከለክል ህግ የለም፡፡ የሰራሁት የኢኮኖሚ ችግር ስለገጠመኝ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የኮሚሽኑ የድስፒሊን ኮሚቴ አከራክሮ ተከሳሽ በኮሚሽኑ ደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 72(19) ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለው ሌላ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሟል፡፡ በአንድ መንግስት ሁለት መ/ቤት ተቀጥሮ ከሁለት ቦታ ደሞዝ ማግኘት ህጋዊ አይደለም የተቀጠረው ዝውውር ሲፈፀም የተሰጣቸውን ክሊራንስ በመጠቀም በመሆኑ ማጭበርበር ፈጽሟል፡፡ ለትምህርት ተልኮ በቋሚነት ተቀጥሮ ሙሉ ጊዜውን ተጠቅሞ ትምህርቱን ይከታተላል ማለትም አይቻልም፡፡ በመሆኑም ጥፋተኛ ነው ብለነዋል፡፡ ቅጣቱ በደንቡ ቁጥር 104/2004 እንቀጽ 72(19) የተከሰሰ ቢሆንም በደንቡ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 72(13) ማጭበርበር ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ስላገኘነው በደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 71(ረ) መሰረት ከስራ ይሰናበት ሲሉ የውሳኔ ሃሳብ አቀረቡ፡፡ የበላይ ሃላፊውም የዲስፕሊን ኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ በማጽደቅ ከስራ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ለኮሚሽኑ ይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ኮሚሽነሩም ተከሳሽ የአሁን አመልካች ከስራ እንዲሰናበት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ለአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 68301 ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥረ ነገር ስልጣን በክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 67(2ሐ) ማንኛውም የክልሉ ፍ/ቤቶች በመጨረሻ በሚሰጧቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው፡፡ ሥልጣኑ ከተግባራዊነቱና የመንግስት ስልጣን ክፍፍል በተለይም ሕገ መንግስታዊ ትርጉምንም የመዳኘት ስልጣን ለፍ/ቤት ካለመስጠቱ አኳያ ከአስተዳደር አካሉ የሚነሱ ጉዳዮችን ሁሉ በሰበር የሚታይበት የህግ ስርዓት አለመዘርጋቱን የሚጠቁም ነው፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይልቁንም የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በፍ/ቤት የሚታረመው እንደ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 ያሉ ህጎች በፍ/ቤት እንዲታዩ በግልጽ ሲደነግጉና ሲመራ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በመርህ ሁሉም የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በፍርድ ቤት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 223/07 አንቀጽ 17(2) አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ለማስተናገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በአማራ ብ/ክ/መ. የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የተሰጠውን የዲስፕሊን ውሳኔ በሰበር የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከክልሉ ደንብ ቁጥር 104/04 አንቀጽ 75(3) እና ከኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(2/3) መሰረት መጣራት ያለበት በመሆኑ ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪም ጥር 15 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ መልስ በአማራ ብ/ክ/መ. ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 75(3) መሰረት የኮሚሽኑ የበላይ ሃላፊ በይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን የተደነገገ በመሆኑ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 67(2/3 ሐ/መ) መሰረት የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም ማለቱ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ጥር 28 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የስር የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍርድ ቤት ከተሰጡ የመጨረሻ ውሳኔና መሰረታዊ የህግ ስህተት ካላባቸው ውሳኔ ውጪ በአስተዳደራው ውሳኔ ሰጪ አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎችን ለማየት ሥልጣን የለኝም፡፡ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ስልጣን በአማራ ብ/ክ/መ. ህገ መንግስት አንቀጽ 67(2ሐ) ድንጋጌ መሰረት ማንኛውም ክልላዊ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ በሰጡባቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ በመሆኑ የአማራ ብ/ክ/መ. ሥነ ምግባርና ፀረ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሙስና ኮሚሽን የተሰጠውን የዲስፒሊን ውሳኔ ለማየት ሥልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ይሁንና የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(2) የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል ሲል ደንግጓል፡፡ አንቀጽ 80(3ለ) ደግሞ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት ለማየት ሥልጣን ይኖረዋል ሲል ደንግጎ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 9(1) ሕገ መንግስቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ እንደሆነና ማንኛውም ሕግ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር መቃረን እንደሌለበት ደንግጓል፡፡ የአማራ ብ/ክ/መ. ህገ መንግስት አንቀጽ 67(2ሐ) ድንጋጌ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3ለ) ጋር የሚቃረን አይደለም፡፡ ይሄውም የአማራ ብ/ክ/መ. ህገ መንግስት አንቀጽ 67(2ሐ) ድንጋጌ ማንኛውም ክልላዊ ፍ/ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል ሲል መደንገጉ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት በፍ/ቤቶች የተሰጡ የመጨረሻ ውሳኔ ብቻ እንደሆነ ትርጉም ሊሰጠው የማይገባና በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) ድንጋጌ መሰረት በክልል ጉዳዮች የተሰጡ የመጨረሻ ውሳኔም ጭምር የማየት ስልጣን እንዳለው ሊወሰድ የሚገባ ነው፡፡ እንዲሁም በተሻሻለው የአብክመ. የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 75(3) እና በሌሎችም አዋጆች "በይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል" በሚል ተገልጸው የሚገኙት ድንጋጌዎች በይግባኝ ደረጃ ቀርበው ለመታየት የማይችሉ የመጨረሻ ውሳኔዎች መሆናቸውን የሚገልጽ እንጂ በሰበር ሰሚው ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን ጉዳዮች ለማረም የሚቀርቡ ጉዳዮችን የሚጨምር አይደለም፡፡ በኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1) ስር እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ህገ መንግስቱ ማንኛውም ሰው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ ከሆነ ለፍ/ቤቶች አቅርበው ፍትህ የማግኘት መብት ሰጥቷቸዋል፡፡ በመሆኑም የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጪ አካላት የተሰጡ የዲስፕሊን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን መሆኑ የክልሉ ሕገ መንግስት ያልከለከለውና የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) ሥልጣኑ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳለው ደንግጎ እያለ ጉዳዩ በተሻሻለው የአብክመ. የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 104/2004 አንቀጽ 75(3) መሰረት ጉዳዩ በይግባኝ ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ሆኖ እያለና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን ጉዳዮችን ተቀብሎ የማየት ስልጣን እያለው ሥልጣን የለኝም ሲል አቤቱታውን መዝጋቱ ከህጉ ድንጋጌ ትርጉም ውጪ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 68301 ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአሁን አመልካች የቀረበለትን አቤቱታ የሰበር ሰሚው ችሎት ስልጣን በመሆኑ አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መልስንለታል፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.137939

ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች- ተክሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች - ፍፁም ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር -ጠበቃ አሸናፊ አርአያ -ቀረቡ

ተጠሪ - የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት - ነ/ፈ ፍቅሬ ተስፋዬ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ተጠሪ ጽ/ቤት ለአመልካች በቁጥር 714 በስሙ መዝግቦ የሰጠውን የኢንዱስትሪ ንድፍ ጥበቃ ሰርተፍኬት በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(2)(ሀ) የተቀመጠውን የአዲስነት መስፈርት አሟልቶ የተሰጠ ባለመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ያሳለፈውን ውሳኔ እና ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔው የሚነቀፍበት የህግ ስህተት የለም በማለት ያሳለፈውን ብይን በመቃወም ነው፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በላይነህ ደቻሳ የተባሉ ግለሰብ በጠበቃቸው በኩል ለተጠሪ ጽ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ለአሁን አመልካች በማመልከቻ ቁጥር ET/ID/2015/2433 በቀን 19/02/2008 ዓ.ም በቁጥር 714 ተመዝግቦ የተሰጠው ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት የአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(1)(2) ድንጋጌዎችን ሳያሟላ ያላግባብ የተሰጠው በመሆኑ ሰርተፍኬቱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ጽ/ቤትም አቤቱታውን ተቀብሎ አከራካሪ የሆነው ንድፍ በጽ/ቤቱ በመዝገብ ከመግባቱ በፊት በታይላንድ እና በኢትዮጵያ የሚታወቅ መሆኑን ከቀረቡት ማስረጃዎች ተገንዝቤያለሁ፤ ንድፉ አዲስነት አለው ሊባል የሚችል አይደለም በማለት የተሰጠው ሰርተፍኬት እንዲሰረዝ ተወስኗል፡፡

አመልካች የካቲት 13/2009 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተፈፀመ የሚሉትን የህግ ስህተት በመዘርዘር ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱ ባጭሩ፡-

https://t.me/ethiopianlegalbrief

- የኢንዱስትሪ ንድፍ ምዝገባም ሆነ ስረዛን በተመለከተ ተፈጻሚነት ያለው ህግ የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና ኢንዱስትሪ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 ሲሆን አዋጁ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ይሰረዝልኝ አቤቱታ ሊቀርብ የሚገባው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በግልፅ የደነገገ በመሆኑ የተጠሪ ጽ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ይሰረዝልኝ አቤቱታን የማየትም ሆነ የመወሰን ስልጣን ሳይኖረው ጉዳዩን ተቀብሎ በማየት ውሳኔ መስጠቱና የጽ/ቤቱ ዳይሬክተር ውሳኔውን ማፅደቃቸው የህግ መሰረት የሌለው ነው እንዲባል፤
- ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም ተጠሪ ጽ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገውን ህግ አላግባብ በመተርጎም በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(2) መሰረት "የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ህግ የአዲስነት መስፈርት ፍጹማዊ ወይም በየትም ቦታ ከታወቀ ንድፍ የተለየ እንዲሆን ይጠይቃል" ከማለቱም በተጨማሪ "የቀረበው ንድፍ በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ ሃገር አምሳያ ሊኖረው አይገባም " በማለት በአዋጁም ሆነ በማንኛውም ደንብም ሆነ መመሪያ ውስጥ ያልተገለፀ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት የአመልካች የኢንዱስትሪ ንድፍ አዲስነት፣ ፍፁማዊነት እና በሌላ ሃገር አምሳያ የሌለው ሊሆን ይገባዋል በማለት የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ይህን ትርጉም ተከትሎ የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ይህን ሳያሟላ የተሰጠ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ ስህተት በመሆኑ እንዲታረም፤
- አመልካች የኢንዱስትሪ ንድፍ ሠርተፍኬት የተሰጠኝ ጽ/ቤቱ በአግባቡ አጣርቶ እና መርምሮ ህግን በተከተለ መንገድ ሲሆን ተጠሪ ጽ/ቤት ሰርተፍኬት ለመስጠጥ የመረመረበት መንገድም ሆነ የምርመራው ውጤት ትክክል አይደለም የሚል ክርክር ሲመጣ የምርመራውን ውጤት፣ የምርመራውን ሂደት ሆነ ሌሎች ምርመራውን የተመለከቱ አጠቃላይ ማስረጃዎች በራሱ በተጠሪ እጅ እያሉ እና የአመልካችም ክርክር ጽ/ቤቱ አስቀድሞ ምርመራውን በትክክል ማድረጉን የሚገልፅ ሆኖ እያለ የተጠሪ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በእጁ ያለውን ማስረጃ ሳይመረምር (ሳያጣራ) የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፤
- እንዲሁም ተጠሪ ጽ/ቤት በአዋጅ እንዲያስፈጽማቸው ከተሰጡት የፖሊሲ አላማዎች በተቃራኒ የሰጠውን ሰርተፍኬት እና እሱን ተከትሎ የሚሰጠውን ጥበቃ በማመን ከፍተኛ ኢንቨስትመንት አውጥተው ስራ የሚሰሩትን ኢንቨስተሮች መተማመኛ እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ውሳኔ መስጠቱ ከተቋቋመለት አላማ እና ከመሰረታዊ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአዕምሯዊ ንብረት ፖሊሲ የሚጣረስና ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የአመልካችን የተመዘገበ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃ እንዲያደርግ ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል።

የሰበር ቅሬታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል። ተጠሪ ሚያዚያ 17/2009 ዓ.ም በተፃፈ መልስ፡-

- በተጠሪ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 320/95 ለተጠሪ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት መካከል የምዝገባ ማመልከቻዎችን በመቀበል አስፈላጊውን ምርመራ በማካሄድ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ሲሆን፤ ህጎቹ ያስቀመጧቸውን መስፈርቶች ሳያሟሉ የተመዘገቡ ማመልከቻዎች ላይ አቤቱታ ሲቀርብ ምዝገባውን የመሰረዝ ስልጣን (ፈራሽ የማድረግ) እንዳለው ተጠሪ የሚያስፈጽማቸውን ህጎች አውደ ንባብ (contextual interpretation) መሰረት በማድረግ የሰበር ችሎቱ አስቀድሞ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ተጠሪ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ ጥያቄን ተቀብሎ ያስተናገደው ህጉ በሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፤
- ተጠሪ የአዋጁን የአዲስነት መመዘኛ በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም ምዝገባው እንዲሰረዝ አድርጓል በሚል የቀረበውን ቅሬታ በተመለከተም አዋጁ ለጥበቃ ብቁነት ያስቀመጠው የአዲስነት ጠባይ ፍፁማዊ ወይም ሁሉን አቀፍ (absolute or qualified universal novelty) የተባለው ሲሆን ንድፉ አዲስ መሆኑ የሚረጋገጠው በኢትዮጵያ ወይም በቀረው የአለም ክፍል አምሳያ ከሌለው ነው፤ ፍፁማዊ መመዘኛ የተባለውም ፍለጋው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይወሰን በሁሉም የአለም ክፍል መሆኑን ለማመልከት ነው፤ ስለሆነም የኢንዱስትሪ ንድፉ አዲስ ነው የሚባለው በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ እና ከምዝገባ ቀን ወይም እንደ አግባቡ ከቀዳሚ ቀን በፊት ባለው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ያልተገለፀ ሲሆን በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ በህጉ በግልጽ የተመለከተውን በማዛባት የቀረበ ነው፤
- ለአመልካች የኢንዱስትሪ ንድፍ ሠርተፍኬት የተሰጠው ጽ/ቤቱ በአግባቡ አጣርቶ እና መርምሮ ሲሆን ተጠሪ በእጁ ያለውን ማስረጃ ሳይመረምር (ሳያጣራ) የሰጠው የመሰረዝ ውሳኔ ስህተት ነው በሚል የቀረበውን ቅሬታ በተመለከተም ተጠሪ ማመልከቻውን ለምዝገባ ለመቀበል ያካሄደው ምርመራ በአዋጁ አንቀጽ 48(1) የተመለከቱት መመዘኛዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ በመሆኑ፤ በፎርማሊቲ ምርመራ ላይ ብቻ የተመሰረተ የምዝገባ ሥርዓት በንድፉ አዲስነት ላይ የሚደረግን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍለጋ (search) እና የማሰረዳት ሽክም በገበያ ውስጥ ጥቅም አለን ወደሚሉ ሰዎች የማዛወር ውጤት ያለው በመሆኑ በምዝገባው ተገቢነት ላይ የሚነሳን ተቃዉሞ ለመፍታት ጽ/ቤቱ ምርመራ ያደርጋል፤ የአመልካች ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምዝገባም አዲስነት የለውም ተብሎ እንዲሰረዝ የተወሰነው በዚሁ አግባብ ነው፤

- ተጠሪ የሰጠው የኢንዱስትሪ ንድፍ ሰርተፍኬት እንዲሰረዝ አቤቱታ ሲቀርብ የራሱን አሰራር መከላከል እየተገባው እንዲሰረዝ ማድረጉ የተቋቋመበትን ዓላማ ይቃረናል መባሉም ስህተት ነው፤ አመልካች የንድፉ ፈጠራ የራሱ ቢሆን ኖሮ ንድፉ ከመመዝገቡ በፊት ታይላንድ ሀገር የሚገኘው ፓይኒር ኢንተርናሽል ኮርፖሬሽ አምርቶታል ተብሎ ለቀረበው አቤቱታ በቂ ማስተባበያ ማቅረብ በቻለ ነበር፤ አመልካች የቀረበበትን አቤቱታ በበቂ ሁኔታ ሳያስተባብል ስላስመዘገበ ብቻ ባለመብት የሚሆንበት አሰራር ፍትሃዊ አይሆንም፤ ስለሆነም የአመልካች የኢንዱስትሪ ንድፍ አዲስ አይደለም ተብሎ ምዝገባው እንዲሰረዝ የተሰጠው ውሳኔ እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔውን ማጽናቱ በአግባቡ ነው እንዲባል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር ግንቦት 18/2009 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ እና ግራ ቀኙ በሰበር ያደረጉትን ክርክር ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የችሎቱን ምላሽ የሚጠይቁት አብይ ነጥቦች ፡-

1ኛ) ተጠሪ ጽ/ቤት የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ አቤቱታን ተቀብሎ የማየትም ሆነ የመወሰን ስልጣን አለው ወይስ የለውም?

2ኛ) ስልጣን አለው ቢባል የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987 የአዲስነት መስፈርትን አስመልክቶ የደነገገው አላግባብ ተተርጉሞ ውሳኔ ተሰጥቷል? ወይስ አልተሰጠም?

3ኛ) ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረው ሰርተፍኬት እንዲሰረዝ የተወሰነው በህጉ አግባብ ተጣርቶ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡ በዚሁ ቅደመ ተከተል ተመልክናቸዋል፡፡

ቀዳሚውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች በቅሬታው በአዋጅ ቁጥር 123/1987 ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ አቤቱታ ሊቀርብ የሚገባው ለከፍተኛ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በግልፅ የደነገገ በመሆኑ የተጠሪ ጽ/ቤት የይሰረዝልኝ አቤቱታን የማየትም ሆነ የመወሰን ስልጣን ሳይኖረው ጉዳዩን ተቀብሎ በማየት ውሳኔ መስጠቱ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ስልጣን ሳይኖረው የሰጠው ውሳኔ እንዲሻር የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ ጥያቄውን ተቀብሎ ያስተናገደው ህጉ በሰጠው ሥልጣን መሰረት ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 59025 እና 71216 በሰጠው ትርጉም የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና ኢንዱስትሪ ንድፍ አዋጅ ቁጥር 123/1987’ን ጨምሮ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 320/1995 እና ጽ/ቤቱ የሚያስፈጽማቸውን ሌሎች አዋጆች ዝርዝር ይዘት በመመርመር አቤቱታ የሚቀርብበትን እና በይግባኝ የሚስተናገድበትን ሥርዓት በተመለከተ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ መስሪያ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ (የይሰረዝልኝ አቤቱታን ጨምሮ) ቅሬታ ያለው ወገን የሚኖረው መብት በይግባኝ ሥርዓት የማስከበር እንጂ ቀጥታ ክስ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አለመሆኑን፤ ይግባኙ መቅረብ ያለበትም ለፌዴራሉ ከፌተኛ ፍርዴ ቤት መሆኑን ወስኗል፡፡ ይኸው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት ለተያዘው ጉዳይም በተመሳሳይ ተፈጻሚ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪው ጽ/ቤት የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ አቤቱታን ተቀብሎ የማየትም ሆነ የመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ያቀረበው ቅሬታ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎች መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ተጠሪ ጽ/ቤት የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ሰርተፍኬት ይሰረዝልኝ አቤቱታን መርምሮ ለመወሰን ስልጣን አለው ብለናል፡፡

ሁለተኛው ነጥብ በአዋጅ ቁጥር 123/1987 የአዲስነት መስፈርትን አስመልክቶ የተደነገገው አላግባብ ተተርጉሞ ውሳኔ ተሰጥቷል በሚል የቀረበውን ቅሬታ የተመለከተ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታው “የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ህግ የአዲስነት መስፈርት ፍጹማዊ ወይም በየትም ቦታ ከታወቀ ንድፍ የተለየ እንዲሆን ይጠይቃል“ እንዲሁም “ንድፉ በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ ሃገር አምሳያ ሊኖረው አይገባም “ ተብሎ በተጠሪ ጽ/ቤት በኩል በህጉ ያልተገለፀ የተሳሳተ ትርጉም ተሰጥቶ ይህን ትርጉም ተከትሎ የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ይህን ሳያሟላ የተሰጠ በመሆኑ ሊሰረተዝ ይገባዋል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ ስህተት በመሆኑ እንዲታረም ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አዋጁ ለጥበቃ ብቁነት ያስቀመጠው የአዲስነት ጠባይ ፍፁማዊ ወይም ሁሉን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቀፍ መሆኑንና ንድፉ አዲስ መሆኑ የሚረጋገጠው በኢትዮጵያ ወይም በቀረው የአለም ክፍል አምሳያ ከሌለው ስለመሆኑ በህጉ የተደነገገ መሆኑን በማንሳት ተከራክሯል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(1) ድንጋጌ መሰረት አዲስነት እና ተግባራዊ ተፈፃሚነት ያለው ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ በአዋጁ መሰረት ጥበቃ እንደሚደረግለት ተመልክቷል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 46(2)(ሀ) እንደተደነገገውም አንድ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዲስ ነው የሚባለው …

> ”የንድፉ ዋና ዋና ባህሪያት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ እና ከምዝገባ ቀን ወይም እንዳግባቡ ከቀዳሚ ቀን በፊት ባለው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ያልተገለፀ ሲሆን ነው:: በንድፎቹ መካከል ያሉ የተለዩ ገፅታዎች ልዩነት በጥቃቅን ዝርዝሮች ከሆነ ተመሳሳይ ናቸው ተብለው ይወሰዳሉ“፡፡ የዚሁ ድንጋጌ እንግሊዝኛ ቅጅም
>
> “industrial design shall be considered new when the sum total of its essential features is different from that of another design known either in Ethiopia or abroad and has not been disclosed for more than one year before the date of filing of the application for registration or, where appropriate, before the priority date. Designs shall be deemed to be identical if their specific features differ only in immaterial details” በማለት ይደነግጋል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ንድፉ አዲስ መሆኑ የሚረጋገጠው በኢትዮጵያ ወይም በቀረው የአለም ክፍል አምሳያ ከሌለው ስለመሆኑ በህጉ የተደነገገ መሆኑን በማንሳት ያቀረበው ክርክር የሚነቀፍ ባይሆንም አንድ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ አዲስ ነው የሚባለው የንድፉን ዋና ዋና ባህሪያት መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ከፍ ሲል ከተመለከትነው የህጉ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የንድፉን ዋና ዋና ባህሪያት ለይቶ ተመሳሳይነት አላቸው ወይም የላቸውም በማለት መወሰን የሚቻለው ደግሞ የእያንዳንዱን ዲዛይን ዋና ዋና ባህሪያት በቅድሚያ በመለየት ከሌላው ጋር በማነፃፀር ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች የኢንዱስትሪ ንድፍ አዲስነት፣ ፍፁማዊነት እና በሌላ ሃገር አምሳያ የሌለው ሊሆን ይገባዋል በማለት የተሳሳተ ትርጉም ተሰጥቷል በማለት ያቀረበው ክርክር ከፍሲል የተመለከተውን የህጉን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባይኖረውም የአከራካሪው ንድፍ ዋና ዋና ባህሪያት ተለይተው የተሰጠ ውሳኔ ስለመሆኑ መዝገቡ ስለማያሳይ ውሳኔው በዚህ ረገድ ሊታረም ይገባል ብለናል።

ከዚህ ጋር የተያያዘው ሌላው ነጥብ ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረው ሰርተፍኬት እንዲሰረዝ የተወሰነው በህጉ አግባብ ተጣርቶ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው። ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው የንድፉን አዲስነት ለመወሰን የአከራካሪው ንድፍ ዋና ዋና ባህሪያት ተለይተው ሊታወቁ ይገባል። የአንድ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ዋና ዋና ባህሪያት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ መሆኑ የሚረጋግጠው ደግሞ በዘርፉ ያለውን የዳበረ እውቀት እና ልምድ መሰረት ዝርዝር ማጣራት በማድረግ ነው። ስለሆነም ክርክር ባስነሳው ንድፍ ዋና ዋና ባህሪያት ላይ እውቀቱ ያላቸው ባለሙያዎች የሚሰጡት ምስክርነት ለጉዳዩ ተቀባይነት ይኖረዋል። በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ጽ/ቤት ለአመልካች ሰርተፍኬት ሰጥቶት የነበረው በኢትዮጵያ ገበያ በኢንተርኔት በተደረገ ተመሳሳይ ንድፍ ፍለጋ ሪፖርት መሰረት ንድፉ አዲስ ነው ተብሎ ሲሆን ሰርተፍኬቱ የተሰረዘውም ሰርተፍኬቱ የተገኘበትን የምርመራ ሪፖርት ትክክለኛነት አመልካች (በላይነህ ደቻሳ) ሞግቶታል የአሁኑ አመልካችም ይህን ማስተባበል አልቻለም በሚል ነው። ተጠሪ ጽ/ቤት በዚህ መልኩ ሰርተፍኬት የሚሰጥና የሚሰርዝ ከሆነ አሰራሩ ህጉን የተከተለ ካለመሆኑም በላይ ተቋሙ በአዋጅ የተቋቋመለትን አላማ ዳር የማያደርስ በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም።

በአጠቃላይ ተጠሪ ጽ/ቤት በህጉ እንደተመለከተው የአከራካሪውን ንድፍ አዲስነት ለመወሰን የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ዋና ዋና ባህሪያት በመለየት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ ወይም ተመሳሳይነት ያለው ስለመሆኑ በዘርፉ ያለውን የዳበረ እውቀት እና ልምድ መሰረት በማድረግ ዝርዝር ማጣራት በማድረግ መወሰን ሲገባው በዚህ መልኩ ሳያጣራ እና ሳያረጋግጥ ውሳኔ ላይ መድረሱ ጉዳዩ የሚገዛበትን ህግ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል። ተከታዩንም ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በቁጥር ኢ/አ/ን ይ/ሰ/ኮ መ/ቁ 02/2008 ሚያዚያ 18/2008 ዓ.ም ለአመልካች በቁጥር 714 በስሙ ተመዝግቦ የተሰጠው ሰርተፊኬት በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46(2)(ሀ) የተመለከተውን

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአዲስነት መስፈርት አሟልቶ የተሰጠ ባለመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ፤ እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 180621 ያሳለፈው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ጉዳዩን በህጉ አግባብ በማጣራት የአከራካሪውን ንድፍ አዲስነት ለመወሰን የኢንዱስትሪያዊ ንድፉ ዋና ዋና ባህሪያት በመለየት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየ ወይም ተመሳሳይነት ያለው ስለመሆኑ በዘርፉ ያለውን የዳበረ እውቀት እና ልምድ መሰረት በማድረግ ዝርዝር ማጣራት አድርጎ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡተዘግቷል ወደመዝገብቤትይመለስ፡፡

ቅ/ህ የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የልዩነት ሃሣብ</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 5 ስር የተመዘገበው ዳኛ ከሌሎች ባልደረቦቼ የተለየሁትበት ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 46/2/ህ/ ስር የተደነገገውን የአዲስነት መስፈርት አሟልቶ የተሰጠ ባለመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተጠሪ አመልካች ባቀረበው የኢንዱስትሪ ንድፍ ጥበቃ ሰርተፍኬት ጥያቄ ላይ ምዝገባውን ተጠሪ ከአከናወነ በኋላ በተቃዋሚ ወገን በቀረበ አቤቱታ መነሻነት ምዝገባውን መሠረዙ ራሱ የሰጠውን የቀደመ ውሣኔ እራሱ የሚሰርዝበት አግባብ የለም ይህን ውሣኔ መስጠት የሚገባው መደበኛ ፍርድ ቤት ነበር በሚል የግል አቋም ያለኝ በመሆኑ ነው፡፡

ምክንያቱም ተጠሪ የአመልካችን የኢንዱስትሪ ንድፍ የመዘገበው እስከመጨረሻው ማጣራት አድርጐ እና አንድ ሥራ ሲመዘገብ ሊያሟላ የሚችለውን መስፈርት ሁሉ አሟልቶ ተቃዋሚ ካለም ንድፉ ከመመዝገቡ በፊት ማስታወቂያ አውጥቶ ተቃዋሚ ባለመኖሩ እና ራሱ ተጠሪ የሚጠበቅበት ማጣራት ከኢንተርኔት ጭምር ካጣራ በኋላ መመዝገቡን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንድን ተግባር በራሱ አጣርቶ የመስራት ኃላፊነት ያለበት ክፍል አጣርቻለሁ ብሎ ወስኖ በህግ አግባብ ምዝገባውን ካከናወነ በኋላ ምዝገባው በተከናወነበት እና ፈቃድ በተሰጠበት ጊዜ በሚሰጥ የጊዜ ገደብ ያልቀረበ እና ያልተቃወመን አካል ከጊዜ ገደቡ በኋላ በመምጣት ይህ ምዝገባ እንዲሰረዝ ቢጠይቅ መ/ቤቱ በራሱ ማጣራት የማያደርግ እና ጥያቄው እንደቀረበ የሚያስተናግድ እና ምዝገባ አከናውኖ ሰርተፊኬት የሚሰጥ ቢሆን ኑሮ ቅሬታ አቅራቢ የሚመጣ ቢሆን የሚቀበል እና እንደገና የምዝገባውን ሁኔታ የሚመለከትበት አግባብ የሚኖር ሲሆን ነገር ግን ራሱ አጣርቶ የወሰነውን ውሣኔ ተቃዋሚ በቀረበ ቁጥር እንደገና የራሱን ውሣኔ የሚመረምር እና የሚለውጥ ከሆነ ፍትሐዊነትን የሚያዛባ ይሆናል የሚል አቋም አለኝ፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተመሣሣይ ጉዳይ በመ/ቁ/ 71216 በሆኑት መዛግብት የሰጠውን ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀጽ 2/9/ እና 15 ፣ በአዋጅ ቁጥር 123/1987 አንቀጽ 2/1/ እና 54 ፣ በአዋጁ በሚገዙ ጉዳዩች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የመመልከት ሥልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን በግልጽ በማስቀመጥ ነገር ግን ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ/ 59025 በሆነው መዝገብ ላይ የህግ ትርጉም የተሰጠበት መሆኑን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የተሰጠ ውሣኔ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በእነዚህ ሁለት መዛግብት የቀረበው ክርክር የሚያመለክተው ቀጥታ ክስ ሊቀርብ ይገባል ወይንስ በይግባኝ ነው መታየት ያለበት የሚል መሆኑን ለእኔ ያስገነዝበኛል፡፡

1) ይህ ማለት ሁለት አይነት ጉዳይ ላይ ተጠሪ መ/ቤት ውሣኔ የሚሰጥ መሆኑን በመጀመሪያ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት አንድ ንድፍ ይመዝገብልኝ እና ሰርተፊኬት ይሰጠኝ የሚል አመልካች ሲመጣ ራሱም በማጣራት እና ተቃዋሚ ካለ በጋዜጣ ጭምር በመጥራት የሚያስተናግድ እና ምዝገባውን የሚያከናውን መሆኑን ሲሆን በዚህ የማስታወቂያ ጥሪ መሠረት የሚመጣ ተቃዋሚ ካለ ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን ክርክር ጭምር በመስማት የቀረበው ንድፍ ሊመዘገብ ይገባል ወይም ሊመዘገብ አይገባም በማለት ውሣኔ የሚሰጥ መሆኑን ስንገነዘብ ፣
2) ደግሞ ምዝገባ ከማድረጉ በፊት በራሱ አጣርቶ እና ተቃዋሚም ጠርቶ ሳይቀርብ ቀርቶ ምዝገባውን ካከናወነ እና ሰርተፊኬት ከሰጠ በኋላ የሚቀርብ ተቃውሞ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚስተናገድበት ሥርዓት ያለ መሆኑን ነው፡፡ በዚህ በሁለተኛው የምዝገባ ስርዓት ውስጥ በግራ ቀኝ የሚደረግ ክርክር በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥርዓት የሙግት አካሄድ አቤቱታ መልስ እና የመልስ መልስ ተደርጐ ተጠሪም ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ የሚያሳርፍበት ሥርዓት የለም፡፡

በእኔ አመለካከት በመጀመሪያው የምዝገባ ሂደት ተደርቶ ተቃዋሚ ቀርቦ ግራ ቀኝ ቀርበው ተከራክረው መልስ የመልስ መልስ እና ሙግት አከናውነው ተጠሪ የሚሰጠው ንድፉ ይመዝገብ ወይም አይመዝገብ በሚል ውሣኔ በይግባኝ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሄዱ ተገቢ ሊሆን ነው ባይ ነኝ፡፡

የሰ/መ/ቁ/ 59025 በሆነው መዝገብ ላይ ቀድሞ የተሰጠው ውሣኔ ከላይ በ1ኛ ነጥብ ላይ የተቀመጠውን የሚመለከት በመሆኑ አሁን ከቀረበው ጉዳይ የሚለይ እንጂ ተመሣሣይ ነው ሊባል የሚገባው ባለመሆኑ ቀድሞ በተጠቀሱት መዛግብት ላይ የተሰጠው የሰበር ሰሚ ችሎቱ ትርጉም ገዢ ሊሆን የሚገባው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ራሱ አጣርቶ ሌላ ተቃዋሚ በሕግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ሳይቀርብ የሰጠውን የንድፍ ምዝገባ እና ስርተፊኬት በሌላ ጊዜ ተቃዋሚ መጥቷል በሚል ራሱ መልሶ የሚሽርበት አካሄድ ተገቢ ባለመሆኑ ከዛም ሂደት በኋላ የሚቀርብ የምዝገባ መቃወሚያ ለመደበኛው ፍ/ቤት ተጠሪ ራሱም ንድፉን ካስመዘገብው ሰው ጋር ተከሳሽ በመሆን በቀጥታ ክስ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚገባ መሆን ይኖርበታል እንጂ በይግባኝ የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ ሆኖም አብላጫው ድምጽ ትርጉም የተሰጠበት የሰበር ውሣኔ ገዢ ነው በማለት አቋም የያዘ በመሆኑ በቀደመው ጊዜ በተመሣሣይ ጉዳይ ከላይ በተጠቀሱት የሰበር መዛግብት ላይ የሰጠው ውሣኔ በእኔ እምነት ሊተረም እና ሊስተካከል የሚገባው ነው በሚል ፫ ዳኛ ተቋቁሞ በ7 እና ከዛ በላይ በሆኑ ዳኞች ተመርምሮ አቋሙ ሊለወጥ የሚገባው ነው እንጂ ተጠሪ ራሱ ውሣኔ ሰጥቶ ራሱ ጉዳዩን እንደገና አይቶ የሚወስንበት አግባብ ሊኖር አይገባም ተጠሪ ጉዳዩን ያየው ያለስልጣኑ ነው እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በይግባኝ ደረጃ ተቀብሎ ማስተናገዱ ሊታረም የሚገባ ነው በሚል ከባልደረቦቼ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ - 136024

ጥቅምት 21 ቀን 2010ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ቢልልኝ ጌታነህ - ጠበቃ ፋንታሁን አባተ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ገብራይ ተከስተ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበዉ ክስ፤ የወፍጮ ድርጅቱን በዉስጡ ካሉት ሦስት የተለያየ የፈረስ ጉልበት ካላቸዉ ወፍጮዎች እና ሚዛን ጋር በወር ብር 7,000.00 ኪራይ እየከፈለ ከ26/11/2004 እስከ 26/11/2006 ዓ.ም ድረስ እንዲጠቀምበት ለአመልካች ማከራየቱን እና የኪራዩ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላም አመልካች የወፍጮ ድርጅቱን ከነሙሉ ዕቃዉ አለማስረከቡን እና ቀሪ የኪራይ ገንዘብም ያልከፈለዉ መሆኑን በመግለጽ አመልካች ወፍጮዎቹን፣ የወፍጮ ድርጅቱን እና ሚዛኑን እንዲመልስለት፣ እንዲሁም የዉሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ያለዉን የኪራይ ገንዘብ ብር 21,000.00 እና ወፍጮዎቹን እስኪረከባቸዉ ድረስ ያለዉ የድርጅቱ ኪራይ ታስቦ እንዲከፍለዉ ይወሰንለት ዘንድ የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ለክሱ መሠረት ያደረገዉ ዉል በ25/12/04 ዓ.ም በተደረገ ሌላ ዉል መተካቱን እና በኋለኛዉ ዉል መሠረትም የዉሉ ጊዜ እስከ 25/12/06 ዓ.ም

https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚቆይ በመሆኑ ተጠሪ ድርጅቱን እንዲለቅለት ከፈለገ የሦስት ወር ጊዜ መስጠት ስላለበት የመጠየቂያ ጊዜው ያልደረሰ መሆኑን፣ በወር ለመክፈል የተስማማዉ ኪራይም ብር 7,000.00 ሳይሆን ብር 350.00 መሆኑን እና ጊዜዉ ሲደርስ ወፍጮዎቹን ከነሚዛኑ ለተጠሪ እንደሚያስረክብ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ የቀረበዉን የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ፤ በኋላ ላይ ተደርጓል የተባለዉ ዉል በህግ አግባብ የመጀመሪያዉን ዉል የተካ አለመሆኑን በመግለጽ አመልካች ወፍጮዎቹን እንዲመልስ፣ እንዲሁም ከነሐሴ ወር 2006 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 08 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ ያለዉን ኪራይ ብር 30000.00 ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ የወፍጮ ድርጅቱ እንዲታሸግ የተደረገዉ በአመልካች ጥፋት ምክንያት መሆኑን በመግለጽ ከታህሳስ 09 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ያለዉን የኪራይ ገንዘብ ብር 110133.00 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 28/04/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃዉ አማካይነት በቀረበዉ የሰበር አቤቱታ፤ የወፍጮ ድርጅቱ ከታህሳስ 09 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት እንዳይሰጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታሽጎ እንዲቆይ ተደርጎ እያለ ለእነዚህ ጊዜያት ኪራይ እንዲከፈል በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተወስኖ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ገልፆ ታርሞ እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮም የወፍጮ ቤት ድርጅቱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታሽጎ በነበረበት ወቅት ያለዉን ኪራይ አመልካች እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ፣ ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ጥሪ ተደርጎለታል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ በቀን 20/06/09 ዓ.ም በጠበቃዉ አማካይነት ተዘጋጅቶ በቀረበ መልስ፤ ወፍጮ ቤቱ ሊታሸግ የቻለዉ በአመልካች

https://t.me/ethiopianlegalbrief

እምቢተኝነት ምክንያት በመሆኑ ድርጅቱ ታሸጎ ለቆየባቸዉ ጊዜያት ጭምር አመልካች ኪራዩን እንዲከፍል የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሊሻር አይገባዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በዚህ ላይ ያቀረበዉ የመልስ መልስም ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ መዝገቡን ለማስቀረብ ከተያዘ ጭብጥ፣ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የወፍጮ ድርጅት ከታህሳስ 09 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሳይሰጥ ታሽጎ የቆየ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ታሽጎ እንዲቆይ የተደረገዉም ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በግራ ቀኝ መካከል ሲደረግ በነበረዉ ክርክር ምክንያት ጉዳዩን የያዘዉ ፍርድ ቤት ታህሳስ 08 ቀን 2007 በሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ምክንያት በመሆኑም ላይ ግራ ቀኝ አልተካካዱም፡፡ በሌላ በኩል በግራ ቀኝ መካከል በተደረገ ዉል መሠረት አመልካች የወፍጮ ድርጅቱን ኪራይ ለመክፈል የሚገደደዉ እንዲሁም ተጠሪ ኪራዩን ከአመልካች የመጠየቅ መብት የሚኖረዉ ድርጅቱ የወፍጮ አገልግሎት ሲሰጥ ብቻ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በርግጥ የዉሉ ጊዜ ካበቃ በኋላም ቢሆን ተጠሪ ድርጅቱን እስከሚረከብበት ጊዜ ድረስ ያለዉን ኪራይ አመልካች ለመክፈል ይገደዳል፡፡ ይህም የሚሆነዉ ድርጅቱ የወፍጮ አገልግሎቱን የሚሰጥ ሲሆን ወይም አገልግሎቱ እንዳይሰጥ የተደረገዉ በአመልካች ጥፋት ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡

የወፍጮ ደርጅቱ ከፍ ሲል በተመለከቱት ጊዜያት አገልግሎት እንዳይሰጥ የተደረገዉ በአመልካች ጥፋት ምክንያት ሳይሆን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን ሲሰጥ የቻለዉም ድርጅቱ እንዲታሸግ እና አገልግሎት እንዳይሰጥ ታግዶ እንዲቆይ ተጠሪ በመጠየቁ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በአንድ በኩል ወፍጮዉ ተገቢዉን አገልግሎት እንዳይሰጥ እና ታሽጎ እንዲቆይ አስደርጎ እና በዚህም ምክንያት አመልካች ከወፍጮዉ ገቢ ባላገኘበት ሁኔታ፣ በሌላ በኩል ታሽጎ ለቆየበት ጊዜ ኪራይ እንዲከፈለዉ የጠየቀዉ ዳኝነት ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወፍጮዉ ታሽጎ ለቆየበት ጊዜ ያለዉን ኪራይ አመልካች እንዲከፍል የሰጠዉ

https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/174062 በቀን 15/02/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 133803 በቀን 20/04/09 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/122163 በቀን 07/01/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. ዕግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://t.me/ethiopianlegalbrief

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ቅፅ - 23

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች



ቅፅ - 23

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክረሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief



የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ-23

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ታህሣሥ 2012 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ድህረ-ገፅ፡-www.fsc.gov.et
ስልክ፡-+251-111-55-34-00
ፋክስ፡-+251-111-56-55-33
የመ.ሣ.ቁ. 6166
ነፃ የስልክ መስመር፡- 992

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief



<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

በአንድ ሀገር የህግ የበላይነት ሊረጋገጥ የሚችለው ህዝብና መንግስት በህግ የበላይነት መርህ ላይ እምነት ኖሯቸው ተግባራዊ ሲያደርጉት ነው። ቀልጣፋና ህግን መሠረት ያደረገ ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠትም ዳኞች ያለአንዳች ተፅዕኖ በነፃነትና በገለልተኝነት ከተጠያቂነት ጋር የሚቀርብላቸውን ጉዳይ መወሰን ይኖርባቸዋል።

የፌዴራል ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው የህግ ትርጉም በመስጠት የሚሰጡት ውሳኔ በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ዘንድ አስገዳጅነት እንደሚኖረውና አስገዳጅ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎችንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አሳትሞ ማሰራጨት እንዳለበት ይደነግጋል። ይህ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጣቸውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎች ተከታታይነት ባለው መልኩ አሳትሞ በማሰራጨት ላይ ይገኛል። አሁንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሳኔዎች በቅፅ 23 የሰበር ህትመት ታትመው እንዲቀርቡ የተደረጉ መሆኑንና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ድረገፅ www.fsc.gov.et ላይ የምታገኙት መሆኑን እየገለጽኩ በውሳኔዎቹ ጥራትም ሆነ ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የምትሰጡን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ለዳኝነት አገልግሎት አሰጣጣችን መሻሻልና ብሎም በቅርቡ እንደሀገር የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ አስመልክቶ ፍ/ቤታችንም የለውጡ አካል በመሆኑ የዳኝነት ነፃነትን፣ ገለልተኝነትንና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ ህዝቡ በፍ/ቤቱ ላይ የሚኖረው አመኔታ እንዲያድግ ለምናደርገው ጥረት ስለሚያግዘን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እገልፃለሁ። በዚህ አጋጣሚ ለወደፊቱ አስገዳጅ ውሳኔ የተሰጠባቸው የፍ/ቤት ውሳኔዎች ህትመት ሳይጠበቁ በተወሰኑ በጥቂት ቀናት ውስጥ በፍ/ቤቱ ድህረ-ገጽ እንደሚለቀቁ ማሳወቅ እንሻለን።

ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ማውጫ/ቅፅ-23/

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ቤተሰብ				**1**
1.	ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ያላገባ የሚል ማስረጃ መውሰድ በራሱ በሁለት ሰዎች መካካል የነበረውን የትዳር ሁኔታ ግንኙነት መኖሩን የሚያረጋግጠውን ማስረጃ የሚያስተባብል ስላለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 94-97	143325	አቶ አለማየሁ ተድላ እና ወ/ሮ ሜሮን ፋንታዬ	ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ.ም	2
2.	የባልና ሚስት ፍቺ ተፈጽሞ የንብረት ክፍፍል እስከሚደረግ ድረስ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረትም ሆነ ከዚህ ንብረት የሚገኝ ገቢ የጋራ ሆኖ የሚቆይ ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 89	153258	አቶ አህፈሮም ግርማይ እና ወ/ሮ ሀበን ፍስሐዬ	መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ/ም	6

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
3.	• አባትነትን በሕግ ግምት ወይም በመቀበል መንገዶች ለመወሰን ክርክር ሲነሳ የባህሪ ወሳኝ ቅንጣት (DNA) ውጤት እንደ መከላከያ ማስረጃ እንዲቀርብ በሕጉ በግልጽ የተቀመጠ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች በሕጉ የተረዘረጋውን ስርዓት ተከትለውና ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መሆኑን ሲያምኑበት ተግባራዊ ሊያደርጉት የሚችሉ ስለመሆኑ • የዘር የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ ውጤት በሕጉ በተመለከተው አግባብ በሕጋዊ ምክንያቶች ለማስረጃነት የሚቀርብ እንጂ በሕግ የተቀመጠውን ግምት እናት ስለካደች ብቻ ለማስረጃነት የሚቀርብ ማስረጃ ነው ተብሎ ድምዳሜ የሚደረስበት ስላለመሆኑ *የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95*	148570	ወ/ሮ ጃኖ ተሰማ እና አቶ አሊ ሰይድ	ግንቦት28 ቀን 2010 ዓ.ም	12

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አንቀፅ 181፣183(1) እና 155(1(ሀ))				
4.	የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ አንድ ሰው የልጁ አባት ወይም እናት አይደለም ለማለት የሚቀርብ ማስተባባያ ማስረጃ ሊሆን የሚችል ቢሆንም የሚከናወነው አባትነትን በሚመለከት የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚያስችሉ ቀዳሚ ሁኔታዎች ሲሟሉ ስለመሆኑ እና እናትነትን በተመለከተም በቤተሰብ ህግ ከአንቀፅ 153 እስከ 166 ድረስ የተዘረጋው ስርዓት የሚፈቅድ ሁኖ በፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከቱትን የማስረጃ አቀራረብ ስርዓቶችን መሰረት በማድረግ ሲቀርብ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀጽ 167-179	152719	ወ/ሮ ብርቱካን ታደሰ እና ወ/ሮ የሺእመቤት ታደሰ	መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ.ም	20
5.	ከባልና ከሚስት ባንዱ የተፈጸመውና ለፍቺው ምክንያት ሆኖ የተገኘው ጥፋት በሌላው ተጋቢ ላይ ጉዳት አስከትሎ ከተገኘ በዳዩ ላደረሰው ጉዳት ከጋራ ንብረት በካሳ መልክ ያንደኛውን ተጋቢ ድርሻ አብዛኛውን ወይም ሙሉውን በደል	152968	ሲ/ር ሐምዚያ ሱለይማን እና አቶ አያሌው በቀለ	መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም	29

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ለተፈጸመበት ወገን እንዲከፈል ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 83/96 አንቀጽ 111፣117				
6.	በጋብቻ ውስጥ የተደረገ የብድር ውል ከአንደኛው ተጋቢ እውቅና ውጪ የተደረገና የጋራ እዳ መሆኑ ፍሬነገር የማጥራትና ማስረጃን የመመዘን መርህን በተከተለ መንገድ ተረጋግጦ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ ፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2472	147930	ወ/ሮ ሰብለ ታምራ እና አቶ ግሩም ግዛቸው	28/9/2010 ዓ/ም	34
7.	በመርህ ደረጃ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚገባው ከባልና ሚስቱ አንደኛው ተጋቢ ወይም ሁለቱም ቢሆንም በህግ አግባብ ተቀባይነት ያለው ውክልና ማስረጃ ጋር የሚቀርብ የፍቺ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.58፣ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2199	150408	ወ/ሮ አመለወርቅ ፍቅሬ እና አቶ ተስፋሁን ታፈሰ	ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ.ም	39

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ውርስ				**44**
8.	• የፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 ስለ ኑዛዜ መነበብ እንዲሁም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው እንዲፈርስ አቤቱታ የሚያቀርቡበትን ሥርዓት እና ጊዜውን በሚመለከት የሚደነግግ እንጂ ኑዛዜ ከውርስ ተነቅለናል በማለት ኑዛዜው እንዲፈርስ የሚቀርብን ወይም የቀረበን አቤቱታን የሚመለከት ስላለመሆኑ • አንድ ኑዛዜ ከውርስ የመንቀል ውጤት ያለው በመሆኑ እንዲፈርስ የሚል የዳኝነት ጥያቄ ሊታይ የሚገባው በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1123 መሠረት እንጂ በፍትሐብሄር ህግ አንቀጽ 973 መሠረት ስላለመሆኑ	152134	ወ/ሮ ትግዕሥት ንጉሴ እና እነ አቶ አሰፋ ንጉሴ	ህዳር 24 ቀን 2011 ዓ/ም	45

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
9.	የውርስ ንብረት ክፍያ ከተደረገ በኋላ በክፍያ ውስጥ ያልገቡ በውርሱ ንብረት ውስጥ ገብተው የሚቆጠሩ አዲስ ሀብቶች የተገኙ እንደሆነ አዲስ የክፍያ ስርዓት መፈፀም የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1103፣1104	153231	እነ ወ/ሮ እልፊ ደበላ እና አቶ ንጉሴ ደበላ	መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም	53
10.	የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ በሚል አቤቱታ በተከፈተ መዝገብ ላይ ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም የሚል ተከራካሪ ወገን በሚቀርብበት ጊዜ ፍ/ቤቶች ወደ ኑዛዜው ይዘት እና ሕጋዊነት ሁኔታ ገብተው ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ያለባቸው በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን በሕጉ አግባብ በመስማትና በሚገባ በማጣራት ተገቢውን ዳኝነት መስጠታቸው ስነ ስርዓታዊ እንጂ በንብረት ክርክር ጊዜ የሚታይ ነው ተብሎ የሚታለፍ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 996	159474	አቶ እንደገና ተሾመ እና አቶ ረታ መልካ	ህዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም	59

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ውል				63
11.	የዉክልና ሰነዶችን ለማረጋገጥና ለመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ አካል የተረጋገጠ ሰነድ ሙሉ እምነት የሚጣልበት ማስረጃ ሆኖ ቅቡልነት ያለዉ ስለመሆኑና የሰነዱን ቅቡልነት መቃወም የሚቻለዉም በበቂ ምክንያት ፍርድ ቤት ሲፈቅድ ብቻ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ/922/08 አንቀጽ 23/1/	146457	ወ/ሮ ዘቢባ ሙሳ እና አቶ አማን በሪሶ	ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም	64
12.	በአደራ የተሰጠ ገንዘብ መኖርን ለማስረዳት ተቀባይነት የሚኖረዉ ማስረጃ በጽሑፍ የተደረገ የአደራ ዉል እንጂ በሌላ የሰዉ ወይም የሰነድ ማስረጃ ስላለመሆኑ የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2782 እና 2472(1)	149861	አቶ ቶዉፊቅ ላሉ እና አቶ ስራጅ ጀማል	30/09/2010	70
13.	በአንድ ውል ላይ የገደብ (የመቀጫ)ስምምነት በተደረገ ጊዜ ባለገንዘቡ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር ውሉ እንዲፈፀም እንዲሁም የመቀጮ ገንዘብ እንዲከፈል ለመጠየቅ የሚችል	162776	አቶ ሰለሞን መርደኪዮስ እና	ታህሳስ 26 ቀን2011 ዓ.ም.	74

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሲሆን ነገር ግን መቀጮ የሚከፈለው የውሉ መዘግየት ወይም ተጨማሪ ግዴታዎች ካሉ የእነሱ አለመፈፀም የመቀጮውን ክፍያ የሚያስከትል ሲሆን ስለመሆኑ ፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(1)(2)		አቶ ሲሳይ ለበኔ		
14.	አንድ ንብረት የገዛ ሰው የገዛውን ንብረት በፈለገው መልኩ መጠቀም የሚያስችል ሁኔታ መፈጠር ፤ ውሉ ከመደረጉ በፊት ችግሩ/ጉድለቱ እንዳለ ቢያውቁ ኑሮ ውሉን አይፈጽምም ነበር የሚያሰኝ በመሆኑ ጉድለት ያለበት ውሉ ነው ተብሎ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት መመለስ ያለባቸው ስለመሆኑ፡- ፍ/ብ/ሕ/ቁ 1815፣ፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2289	133398	አቶ ጉልላት ግዛው እና አቶ ጥላሁን ኃይሉ	ታህሳስ 26 ቀን 2010 ዓ.ም	80
15.	የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለዉ ልዩ ባህርይ አንፃር ንብረቱን ከአንድ ወደ ሌላ ሰዉ በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በሦስተኛ ወገን ላይ ህጋዊ ዉጤት ያስከትል ዘንድ ዉሉ	153664	ወ/ሮ አሻ ፋራህ እና እነ አብዱራህማን	መስከረም 29 ቀን 2011 ዓም	86

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በህግ አግባብ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ካልተመዘገበ ውሉ ፈራሽ የሚሆን ሲሆን ሻጩም በዉሉ ምክንያት የተቀበለዉን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ ይህን እንዲያደርግ ሌላ ክስ ማቅረብ ሳያስፈልግ በዚያው መዝገብ ላይ መወሰን የሚቻል ስለመሆኑ *በፍ/ሕ/ቁ አንቀጽ 2878*		ጣሂር (ሠዎች 9)		
16.	አንድ የባንክ ሠራተኛ በሥራው አጋጣሚ ያገኘውን የደንበኛ ገንዘብ ከህግ ውጭ ቀንሶ በማስተላለፍና በማውጣት መውሰዱ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሰራተኛው የወሰደውን ገንዘብ ዋሶቹ ከእርሱ ጋር በአንድነትና በነጠላ ገንዘቡን የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ 1920፣1922 እና 1933	145456	ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማሕበር እና እነ አቶ እዮብ ሙሉጌታ ቱሳና	24/09/2010 ዓ.ም	90
17.	በአንድ ውል ምክንያት ለደረሰ የጉዳት ኪሣራ ምክንያት ግራቀኙ ተዋዋይ ወገኖች መሆናቸው ከተረጋገጠ ለደረሰው	145523	ቻን ቹን ያን ኃላፊነቱ የተ/የግ/ማህበር	ሐምሌ 16 ቀን 2010 ዓ.ም	94

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የጉዳት ኪሣራ ሁለቱም ሃላፊነቱን መሸከም ያለባቸው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1799(1) ፣1802 (1)፣2090፣2091		እና ወ/ሪት ሞሚና ሁሴን		
18.	አንድ ዉክልና በላዩ ተዘርዝረዉ የተመለከቱትን ጉዳዮችና የነዚሁ ተከታታይ እና ተመሳሳይ የሆነዉን እንደ ጉዳዩ አይነትና እንደ ልማድ አሰራር አስፈላጊ የሆነዉን ማከናወን የሚያስችል ሲሆን ወካዩ የፈጸመዉ ተግባር የወካይና ተወካይ ጥቅሞችን ግጭት የሚያስከትል በሆነ ጊዜ 3ኛዉ ወገን ይህን ሁኔታ ያወቀና ሊያዉቅ የሚገባ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ ፍ/ሕ/ቁ 2206፣2187	134663	ጅማ ዩኒቨርሲቲ እና ቢሊሱማ ሚአ የዕዐዋት ዘር አቅራቢ ድርጅት	ጥር 21 ቀን 2010	98
19.	አንድ ጉዳይ ከውል መተካት አንፃር እንዲታይ ይተካል በተባለው እና ተተክቷል በሚባሉ ውሎች መካከል ያለው	148158	አቶ በትግሉ ከበደ እና	ግንቦት 30 ቀን 2010 ዓ.ም.	105

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የውለታ ጉዳይም ሆነ የውለታው ምክንያት በይዘቱ አዲስ መሆን እንዳለበትና ይህንኑ በውለታውም አይነት ሆነ ከውለታው ምክንያት አንፃር ታይቶ አዲስ የሆነው ውል ቀደም ሲል ተደርጎ በነበረው ውል ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች በማያጣራጥር አኳኋን ሊያስቀር የሚችል ፈቃድ ከተዋዋይ ወገኖች እንዲኖር አስፈላጊ ስለመሆኑ እና ውልን ከማሻሻል ጉዳይ አንፃር ሊታይ የማይገባ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1826 እና 1828		ሸሬ እንዳስላሴ ማረሚያ ቤት		
20.	በአንድ የብድር ዉል ላይ ያለ ፊርማ የኔ አይደለም የሚል ክርክር በመነሳቱ በብድር ዉሉ ላይ ያለዉን ፊርማ ተበዳሪው በመካዱ በፎረንሲክ ምርመራ የእሱ ፊርማ አለመሆኑ የተረጋገጠ ሰነድ ላይ ፊርማው የተበዳሪው ስለመሆኑ አበዳሪው በሰዉ ምስክሮች ላስረዳ በማለት የሚያቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው	156408	አቶ አክልሉ ጌታሁን እና ወ/ሮ ፍሪህይወት አሰፋ	24/01/2011ዓ/ም	109

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2006 እና 2472(1)				
21.	የፍርድ ማስፈጸሚያ ይሆናል የተባለን የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ሲጠቀምበት መቆየቱ የተረጋገጠበት የፍርድ ባለገንዘብ ለዚሁ ጊዜ ዉስጥ ከዋናዉ ገንዘብ በተጨማሪ የፍርድ ባለዕዳ ለባለገንዘቡ ወለድ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ፤ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ1803፣1751 እና 2478	136653	አቶ ገ/ሚካኤል በርሀ እና አቶ ገ/ዮሃንስ ወ/ጊዮርግስ	ግንቦት 23 ቀን 2010 ዓ.ም	113
22.	ስጦታ የሚደረገው ስጦታው በተደረገበት ቀን የአስተላላፊው /የሰጭው/ የራሱ በሆነ ሀብት ላይ ብቻ ስለመሆኑ የፍ.ሕ.ብሔር ህግ አንቀጽ 2427፤2451 /1/	149301	ወ/ሮ ውዴ ደሴ እና እነ አወቀ ደሴ	ግንቦት 27 ቀን 2010 ዓ/ም	118
23.	ገንዘብን በአደራ የማስቀመጥ ዉል (deposit fund) መነሻነት አደራ ያስቀመጠ ባንክ የአደራ አስቀማጩን ገንዘብ የመጠበቅ፣ ሲጠይቁ ወጪ አድርጎ የመክፈል እና	154115	ያዳኒ ራባ እና የኢትዮጵያ ንግድ	*መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም*	126

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ከአስቀማጩ ውጪ ለሌላ ሰው ያለመክፈል ከዉል የመነጨ ግዴታ ሲኖርበት ይህን ግዴታውን ባይወጣ አስቀማጩ ላይ ሊደርስ ለሚችል ጉዳት ከዉል የመነጨ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ባንኩ የሚቀርብለትን የክፍያ ጥያቄ ሲያስተናግድ፣ገንዘብ እንዲከፈለዉ ጥያቄዉን ያቀረበ ሰዉ በርግጥም አደራ አስቀማጩ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ የሚኖርበት ስለመሆኑ የንግድ ህግ 896 እና 897		ባንክ አንዋር መስጊድ ቅርንጫፍ		
24.	• አንድ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ መቀመጫ አዲስ አበባ ከተማ ኢትዮጵያ ከሆነ፤ጉዳዩም ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠበት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ከሆነ፤የዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና የአገሮች ልምድ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕጎች እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት ከሰጣቸዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተከራካሪ ወገኖች “የግልግል ዳኝነት	128086	የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና ኮንስታ ጆይንት ቬንቸር	ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም	130

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ጉባኤው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ነዉ" ብለው ቢስማሙም ውሳኔዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ከሆነ በሰበር ከመታየት የሚከለከልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ፤ • በተንኮል የተደረገ ዉል ፈራሽ የሚሆነዉ ከተዋዋዮቹ አንደኛዉ ወገን ዉሉ እንዲደረግ ያደረገዉ በሁለተኛዉ ተዋዋይ ላይ ተንኮል ባይደርስበት ኖሮ ዉል የማያደርግ እንደነበረ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704(1)፤1808(1) • የአንድ ዉል በፍ/ቤት ዉሳኔ የፈረሰ እንደሆነ የዉሉ መፍረስ የሚያስከትለዉ ዉጤት ተጣርቶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704(1)፤ 1808(1)፤1815				

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
		ከውል ውጭ ኃላፊነት			153
25.	የአካል ጉዳት ካሳ በርትዕ ሲወሰን ባጠቃላይ የተጎጂው የመስራት አቅሙ ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን መነሻ በማድረግ አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታዎች በተጎጂው የወደፊት ህይወት ላይ ሊያስከትሉ ስለሚችሉት አሉታዊ ተጽእኖ፤ ወቅታዊ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት እና ተጨባጭ የገንዘብ /ብር/የመግዛት አቅም በየጊዜው እየቀነሰ መሄዱ፤ ወደፊት ሊታጣ የሚችለው ገቢ ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተገናዝቦ መታየት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2102 እና 2153(ሀ))	152417	ወ/ሮ ሚሚ አበበ እና አቶ ታምራት /ማሙሽ/ ባልቻ	ግንቦት 17 ቀን 2010 ዓ.ም	154
26.	ከህግ አግባብ ውጪ ገንዘብ እንዲከፈል መደረጉን ተከትሎ የተሰጠ የወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔን መሰረት በማድረግ ገንዘብ ያለአግባብ እንዲከፈል ያደረገውን አካል ከውል ውጪ ኃላፊነት የተደነገገውን መሰረት	131804	የሰሜን ወሎ ዞን የቆቦ ጊራና ሽለቆ ልማት ፕሮግራም እና	መጋቢት 25/2010	163

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በማድረግ ያላግባብ እንዲከፈል የተደረገው ገንዘብ እንዲመለስ ለመጠየቅ የሚቻል ስለመሆኑ፡- የፍ/ብ/ህ/ቁ 2035		እነ አቶ አድነው አባተ (3 ሰዎች)		
27.	• አንድ ሰው በራሱ በኩል ምንም የገባው ግዴታ ባይኖርም በራሱ ጥፋት በሌላው ሰው ላይ ጉዳትን ካደረሰ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ እና ማንም ሰው ከራሱ ጥፋት የተነሳ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ላደረገው ጉዳት ኪሳራ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ •የፌዴራል ፖሊስ አባላት አግባብነት ባለው ሕግ እና ደንብ መሰረት ተሽከርካሪዎችን የማስቆም እና የመፈተሽ ስልጣን እና ኃላፊነት ያላቸው ቢሆንም ይህንን ኃላፊነት በሚወጡበት ጊዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2031(1) ስር የተመለከተውንና የሙያ ስራው የሚመራበትን ደንብ ማክበር የሚጠበቅባቸው	142630	እነ ሳጅን ግርማ መርጋ (3 ሰዎች) እና ወ/ሮ ደሀቦ መሐመድ	ሚያዚያ 11 ቀን 2010 ዓ.ም.	169

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2031 (1)፣ 2027 (1) እና 2028				
		ንግድ			**174**
28.	አንድ የንግድ ምልክት አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ የሌላ ዕቃዎችን አገልግሎችን በሚመለከት በሚገባ በሚታወቅ ወይም ኢትዮጵያ ዉስጥ ግልጋሎት ላይ ከዋለ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ወይም ትርጉሙን ከያዘ መመዝገብ የሌለበት ስለመሆኑ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 7(2)፤ 36(1)	143227	ደርሃም ኢንዱስትሪስ ካምፓኒ ሊሚትድ እና አሁጃን ኢንዱስትሪስ	21/09/2010	175
29.	በንግድ መደብር ውስጥ የሚገኙ ግዙፍነት ያላቸው እንደ መሳሪያዎች፣ የቤት ዕቃዎችና ሸቀጥ ያሉ ንብረቶች	153890	ወ/ሮ እመቤት ዳኛቸው	መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ.ም	179

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ባለሀብትነትን ንብረቱን በመግዛት ወይም በሌላ አኳኃን ያገኘው ወይም በኑዛዜ የተሰጠው ሰው ንብረቱን በእጁ ባደረገው ጊዜ የሚተላለፍለት ስለመሆኑና ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ የእነዚሁ ንብረቶች ባለሀብት ስለመሆኑ በሕጉ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1186 (1)፤ንግድ ሕጉ በቁጥር 128		እና እነ አቶ ይስማው ዘገየ (2 ሠዎች)		
30.	አንድ ባንክ በአደራ የተቀበለውን የደንበኛውን ገንዘብ የመጠበቅ ሕጋዊ ግዴታ ያለበትና ከሕግ ውጪ የደንበኛውን ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደረገ ሰው በባንኩ ገንዘብ ላይ ጉዳት ማድረሱ ከተረጋገጠ ደንበኛው ገንዘቡን ከባንኩ የማግኘት መብት በህግ የተጠበቀለት በመሆኑ ባንኩ ደንበኛውን በመተካት ወይም በራሱ ስም ሆኖ የደንበኛውን ገንዘብ ባልተገባ ወይም በወንጀል ተግባር ወጪ አድርጎ ለግል ጥቅሙ ባዋለው ሰው ላይ ክስ ቢያቀርብ ባንኩ	158539	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ምንዳይ ክፍሌ	ሕዳር 27 ቀን 2011 ዓ/ም	185

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በቅድሚያ የደንበኛውን ገንዘብ ስለመክፈሉ ወይም በደንበኛው የባንክ አካውንት ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም በሚል ክሱ ውድቅ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የንግድ ህግ አንቀፅ 896-902፤አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 52(1)				
31.	በአንድ ክስተት ከሁለት በላይ በሆኑ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት መድረሱ በመድን ሰጪና ተቀባይ መካከል በተደረገ የመድን ዉል መሰረት የመድን ሰጪዉ ግዴታ የኃላፊነት መጠን በመድን ዉሉ ላይ ከተመለከተዉ መብለጥ የሌለበት ስለመሆኑ የንግድ ህግ አንቀጽ 665(2)	149326	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ መብራቱ ጤናዉ	28/03/2011	192
32.	የንግድ ማህበር ስለሚፈርስበት አግባብ የንግድ ህግ ቁጥር 217፤218 እና 542	153981	ሚሲስ ሲያዎ ዶንግ እና እነ ሚስተር ዶንግዩ	መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም	197

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
			ቸን (2 ሰዎች)		
		ንብረት			**204**
33.	በባህላዊ መንገድ የሚታረስ መሬትን በዉል ማከራየት የሚቻለዉ ከ3 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ ዉሉም ዋጋ የሚኖረዉ በሚመለከተዉ አካል ተመዝግቦ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 10(2 እና 3)	150773	አቶ ሀይሉ ኪዳኑ እና እነ አቶ ቀጭኑ ዱጉማ	ግንቦት 27/2010ዓ/ም	205
34.	የከተማ መሬት ይዞታ አጠቃቀም ላይ የመወሰን ስልጣን በህግ ስልጣን በተሰጣቸዉ በሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታና በአስተዳደር አካል ያልተረጋገጠ መብት ይዞ ውሳኔ እንዲሰጥ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት	134343	እነ አቶ ቴዎድሮስ ዉብሸት (3ሰዎች) እና እነ የአዳማ ከተማ ቀበሌ 06 መስተዳድር ጽ/ቤት(5ሰዎች)	ግንቦት 27 ቀን 2010 ዓ.ም	210

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁ. 179/05 አንቀጽ 8				
35.	አንድ ባለይዞታ ወሰን አልፎ በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ያለአግባብ በመግባት የሰራው ግንባታ በሌላኛው ባለይዞታ ንብረት አጠቃቀም ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ በባለሙያ ከተረጋገጠ ባለሙያው ባለበት ተለክቶ በዚያው ልክ ወሰኑን ያለፈውን ግንባታ እንዲያፈርስ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1204፣1205፣1225/1/	159414	አቶ ሚሬሳ ኡብሳ እና አቶ ፍቃዱ ደበሎ	ታህሳስ 22 ቀን 2011ዓ.ም	215
36.	አንድ ሰዉ የኮንዶሚኒየም ግዥ ፈጽሟል ሊባል የሚችለዉ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ስምምነት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ብቻ ሲሆን ገዥዉ ቤቱን ለሦስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለዉ ቤቱን ከገዛ 5 ዓመት ሲሞላዉ ሲሆን ጊዜዉ የሚቆጠረዉ ዕጣ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን ገዥዉ የቤት ሽያጭ ዉል ከሚመለከተዉ የመንግስት አካል ጋር ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በአ/አ ከተማ አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች	158899	አቶ ክብሮም አደራ እና እነ ወ/ሪት ትዕግስት መንገሻ	26/03/2011	219

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ *7(6-ለ)*፣14(2)				
37.	የመንግስት ቤት ህጋዊ ተከራይ የሆነ ወላጅ የኮንደሚኒየም ቤት በደረሰው ጊዜ ከመንግስት የተከራየውን ቤት ለመንግስት የማስረከብ ግዴታ ያለበት በመሆኑ የወረዳው አስተዳደር ፅ/ቤት የመንግስት ቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ለተከራዩ ልጆች ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሀከት ተግባር የማይስብለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የመንግስት ቤቶችን ለማስተዳደር የወጣው መመሪያ ቁጥር 4/2009 ዓንቀፅ 15(ሐ(መ))	155664	አዲስ ከተማ ከተማ ወረዳ 9 ኮ/ቤቶች ልማት ጽ/ቤት እና አቶ ሻወል ወልዴ	ጥቅምት 30 ቀን 2011 ዓ.ም.	224
38.	የከተማ ይዞታን የማስተዳደር ስልጣን በህግ አግባብ የተሰጠው አካል ስልጣንና ኃላፊነቱን በህግ አግባብ አልተወጣም የሚል ክርክር ያለው ወገን ጉዳዩን ለፍ/ቤት የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37፣ 40(3)(4)፣79(1)	141625	ወ/ሮ አድና መላኩ እና የወልዲያ ከተማ አገልግሎት	ሐምሌ 26 ቀን 2010 ዓ.ም.	228

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እና 78(4)				
39.	• ማንኛዉም የቴሌኮሙንኬሽን ድርጅት የቴሌኮሙንኬሽን መስመር ሲዘረጋ መስመሩ የባለይዞታን ወይም የሌላ ህንጻ ላይ የሚዘረጋበት አስገዳጅ ሁኔታ ሲኖር አስቀድሞ ለባለይዞታዉ ወይም ለባለህንጻዉ በማስታወቅ የባለይዞታዉ ወይም የባለህንጻዉ ተቃዉሞ እንዳለ ሰምቶ ተገቢዉን የመወሰን ስልጣን ለኤጀንሲዉ የተሰጠ ስለመሆኑ • የቴሌኮሙንኬሽን ድርጅት የአንድ ባለይዞታ ይዞታ ውስጥ ገብቶ በቋሚነት ኮንቴነር ከተከለ ለተጠቀመበት ይዞታ ተገቢዉን ካሳ ለባለይዞታው የመክፈል ግዴታ አለበት የቴሌኮሙንኬሽን አዋጅ ቁ/49/89 አንቀጽ 18፣20/1/፣22/2/፣እና አዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 6	144901	ኢትዮቴሌኮም የሰሜን ምስራቅ ሪጅን እና ወ/ሮ በለጡ ወልደ ተገኝ	ሐምሌ 12 ቀን 2010 ዓ.ም	234

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት				238
40.	አንድ ተከሳሽ በሕግ አግባብ መጥሪያ የደረሰዉ እና እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ማወቁን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በሌለሁበት የተሰጠዉ ፍርድ ተነስቶ የመከላከያ መልስ ላቅርብ በማለት የሚያቀርበውን አቤቱታ በህግ በተቀመጠው አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ አልቀረበም በሚል ምክንያት ብቻ መከላከያ መልስና ክርክር አቅርቦ የመሰማትና ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት መንፈግ ያልተገባና ህጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78፣95 /2/	137704	አቶ መሀመድ ከማል እና አቶ በቀለ ወልዴ	የካቲት 14 ቀን 2010 ዓ.ም	239

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
41.	አንድ ውል አይፈርስም ተብሎ ከተወሰነ በኋላ በተደረገው ውል መነሻነት የወጣ ወጭ ካለ በማጣራት በዚያው መዝገብ ላይ መወሰን የሚገባው እንጂ በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ቀርቦና እንዲከራከሩበት መወሰን ለተራዘመ የክርክር ሂደት ስለሚጋብዝ በዚህ መነሻነት መዝገቡን መዝጋት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ	139187	አቶ መስፍን ዘርዓብሩክ እና እነ ወ/ሮ የወርቅዉሃ አለማየሁ	ግንቦት 30 ቀን 2010 ዓ.ም	246
42.	በአንድ ክስ አጠቃሎ ክስ ማቅረብ የሚቻለው በተቋቋመ መብት ላይ ተመስርቶ እንጂ ዳኝነት በተጠየቀበት ጊዜ ያልበሰለ ወይም ያልተረጋገጠ መብት ጭምር ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/፤216	142242	አይል ሊቢያ ኢትዮጵያ ሊሚትድ እና አቶ ኃይሉ ገ/ሕይወት	16/09/2010 ዓ/ም	253
43.	አንድ ኑዛዜ ከፀደቀ በኋላ በቀረበ ንብረት ክፍፍል ውስጥ ወራሾች ከአውራሻቸው በውርስ ሊያገኙት ከሚገባው ድርሻ ተገቢውን ያላገኙ መሆኑን ገልጸው በሚከራከሩበት ጊዜ ፍሬ	146503	ወ/ሮ ንጋቷ በየነ እና ወ/ሮ ሀረገወይን በየነ	ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ/ም	257

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ነገሩ ተጣርቶ ከሚለይ በስተቀር ኑዛዜው ፀድቋል በሚል ምክንያት ብቻ የሐብት ድርሻቸውን በተመለከተ የሥረ- ነገር ክርክሩ ቀድሞ ታይቷል ተብሎ ውድቅ ሊሆን የሚችልበት የስነ ስርዓት ሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5				
44.	አንድ ሰው መብቴን ይነካል በሚል የመቃወም አቤቱታ ያቀረበበት ዉሳኔ በሌላ አግባብ ከተሻረ እና መብትን ሊነካ የሚችል ዉሳኔ በሌለበት የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ ፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 358ፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 358	148270	እነ አቶ ቡልቻ ቱሉ እና አቶ ተመስገን መላቱ	30/09/2010	262
45.	ክርክርን በመስማት ላይ ያለ ፍርድ ቤት ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ፣ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ ካመነበት ክርክሩ በየትኛዉም ደረጃ ላይ ቢሆን ጣልቃ	144470	ናይል ትራንዚት ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና እነ ኒያላ ኢንሹራንስ	30/11/2010	266

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ገቡ ከክርክሩ ውጪ እንዲሆን ትዕዛዝ ከመስጠት የሚከለክለዉ ነገር የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ ከአንቀጽ 40-43		ኩባኒያ		
46.	አንድ ተከሳሽ የቀረበበት ክስ በይርጋ የሚቋረጥ መሆኑን ከጠቀሰ ከሳሹ ክሱ በሕጉ የተመለከተው ጊዜ ገደብ (ይርጋ) ያላለፈው መሆኑን፣ ጊዜው አልፎ ከሆነም ይርጋውን ሊያቋርጥ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩን በተገቢው ማስረጃ ለማስረዳት የሚችልበት እድል ሳይሰጠው የተከሳሽ መቃወሚያ ብቻ መሰረት ተደርጎ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ ብይን የሚሰጥበት አግባብ ስነ ስርዓታዊ ስላለመሆኑ ፍ/ብ/ሕ/ቁጥር1000፣1846፣1852እና1853፤የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 241፣ 244 እና 245(1)	154023	እነ ወ/ሮ ካሰች በቀለ እና እነ ውቢት ዘውዴ	*መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ.ም.*	269
47.	ይግባኝ የማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን የመንግስት ስራ ዝግ በሆነበት ቀን ላይ ያረፈ ሲሆንና በቀጣዩ የሥራ ቀን ይግባኙ	152845	አቶ መሀመድ መ·ህዲን እና	መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም	274

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ተዘጋጅቶ ሲቀርብ ይግባኙ እንዲከፈት መፍቀድ ሥነ-ሥርዓታዊ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1862፣ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323/2 ፣326		ዘምዘም አሊ		
48.	• አንድ ከሳሽ መብቱን ማግኘት የሚገባው ከየትኛው ተከሳሽ ላይ እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ የሚያጠራጥር ሁኔታ ያጋጠመው ሲሆን አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ሰዎች በህብረት በመክሰስ ሀላፊነቱ የሚመለከተው የትኛው እንደሆነ ተለይቶ እንዲወሰንለት ማመልከት ስለመቻሉ • ፍርድ ቤቶች በአንድ ክስ ላይ ስማቸው በተከሳሽነት ከቀረቡ መካከል ስማቸው ከመጠቀሱ ውጪ በግልፅ ዳኝነት አልቀረበባቸውም በሚል ምክንያት ብቻ አንዱን	139313	የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ ወ/ሮ መሰረት ፍቃዱ (2 ሰዎች)	መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም	278

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ወይም የተወሰኑትን ሀላፊነት የለባቸውም በማለት የሚደርሱበት መደምደሚያ ህጉን ያተከተለ ስለመሆኑ፡- የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 36(5)				
49.	ለአንድ ጉዳይ ለምስክርነት የተቆጠረ ሰው በፍርድ ቤት ጥሪ መሠረት ቀርቦ የመመስከር ግዴታ ያለበት ሲሆን ምስክሩ ሊቀርብ ካልቻለም ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ በታየው መንገድ ትዕዛዝ በመስጠት ምስክሩ በሕግ አግባብ ተገዶ ወይም ታስሮ እንዲቀርብ በማዘዝ ምስክርነቱን በመስማትና ተገቢ ነው ካለም በሌላ ማስረጃም ጭምር በማጣራት የቀረበለት ጉዳይ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 116፣118(2)(ለ)	153610	ወ/ሮ ፈይዛ ከሚል እና አቶ አብዲ አህመድ	መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም	284
50.	አንድ ተከሳሽ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ በመመርመር ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ መልሱን አዘጋጅቶ	154727	አቶ ተክላይ ፍሰሃ እና	ህዳር 26 ቀን 2011 ዓ.ም	296

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንዲያቀርብ የታዘዘው እና ቀጠሮ የተሰጠው ከ10 ቀን ባነሰ ጊዜ ውስጥ ከሆነ የተከሳሹን የመከላከልና የመከራከር የመሰማት መብቱን የሚነፍግ በመሆኑ በቂ ጊዜ ተሰጥቶት የመከላከያ መልሱን እና ክርክሩን እንዲያቀርብ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.240[2]		ወ/ሮ ለታይ ለገሠ		
51.	• አንድ ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ ምክንያት የሆኑት ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ ሲችል ቀንሶ ባስቀረው ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ የማይችል ስለመሆኑ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216(3)፤218	119851	እነ ወ/ሮ ሶፊያ መሀመድ እና አቶ እንድሪስ ጋሹ	መጋቢት 26 ቀን 2011ዓ.ም	300

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	• አንድ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343 መሰረት ወደ ስር ፍ/ቤት ተመልሶ ፍሬ ነገሩ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመቃወሚያው ላይ አስቀድሞ በተሰጠ ብይን ላይ ተጠቃሎ የሚቀርብ የሰበር አቤቱታ ህጉን መሰረት ያደረገና ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320(3)፤ **/የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ 90810 ፣ 76963፣ 125165 እና ሌሎችም በርካታ መዛግብት ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ውሳኔ ተለውጧል።/**				

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የዳኝነት ሥልጣን				**319**
52.	የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ በአንደኛው ወገን በቀረበ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሌላኛው ወገን በጋብቻ ጊዜ ካፈሩት ገንዘብና ንብረት ከፊሉ ከኢትዮጵያ ውጪ ይገኛል በማለት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ማቅረቡ ብቻውን ጉዳዩ የግል ዓለም አቀፍ ሕግን ተፈጻሚነት ጉዳይን/ conflict of laws/ የሚያስነሳ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ የማያደርስ እና የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን የማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከመሆን የማያስቀረው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ቁጥር 9፣17 ፤አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11 (2) (ሀ)	152590	ወ/ሮ እየሩሳሌም አስገዶም እና አቶ ተወልደ ኃ/ማርያም	*ጥቅምት 13 ቀን 2011 ዓ.ም.*	320
53.	የቀበሌ የንግድ ሱቅ አላግባብ ተይዞብኛል ይመለስልኝ በሚል	144242	አቶ ገዛህኝ አየለ	ግንቦት 30 ቀን	327

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ለክስ ምክንያት የሆነው ጉዳይ በግለሰቦች መካከል የተደረገ ውል ሲሆን ጉዳዩን ተቀብሎ የማየት የዳኝነት ስልጣን የከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ሳይሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 4፤የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33(1)(ረ)		እና እነ አቶ ኑረዲን ዓሊ	2009 ዓ.ም.	
54.	በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 መሠረት አግባብ ባለው አካል አስተዳደራዊ እርምጃዎች የተወሰደበት ማናቸውም ሰው በህግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ቅሬታ ካለው ጉዳዩን ማቅረብ የሚገባው ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንጂ በቀጥታ ክስ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊቀርብ የማይገባ ስለመሆኑ የንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓንቀፅ 46፤47(2)፤47(3)፤	145733	አቶ ኤበሳ አመንቱ ጃለታ እና እነ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት	ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም	330
55.	በአዋጅ ቁጥር 147/91 መሰረት አንድ ማሕበር ሕልዉናዉ	153617	አቶ ደሱ ታምሩ	መስከረም 21	335

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ካበቃ በኃላ ወይም መብትና ግዴታው የሕብረት ሥራ ማሕበር ወደ አልሆነ የንግድ ማሕበር ተላልፎ በሚገኝበት ወቅት ጉዳዩ በሽምግልና ዳኝነት የሚታይበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ እና መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 47 እና 49		እና ፊያ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር	ቀን 2011 ዓ.ም	
56.	የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ አላግባብ ተሰርዞብኛል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ጉዳዩ በቀጥታ ከመሬት ይዞታ ባለመብትነት ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ የተከራካሪ ወገኖች መደበኛ ነዋሪነት ወይም የተከራካሪው ወገን የፌዴራል መንግሥቱ ተመዝጋቢ መሆን ግምት ውስጥ ሳይገባ የክርክሩን ልዩ ባህርይ በማየትና የጉዳዩን ዓይነት መሠረት በማድረግ ንብረቱ የሚገኝበት የከተማ አሥተዳደር ፍ/ቤት የቀረበውን ክስ ተቀብሎ የመወሰን የሥረ-ነገር	142594	የደሴ ከተማ ዓይነሥውራን ማሕበር እና የኢትዮጲያ ዓይነሥውራን ብሔራዊ ማሕበር	ሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም	340

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 25 ፤አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1				
57.	የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን መርምሮ የማረም ስልጣን የሚኖረው በክርክር አመራር ረገድ ፍርድ ቤቶቹ የጣሱት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ መኖሩ ሲረጋገጥ እና ጥሰቱም መሰረታዊ የሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ የሐረሪ ክልል ፍርድ ቤቶች እና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 3/1988 /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 28	145128	እነ ወ/ሮ ኬሚያት ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር እና እነ አቶ አንዋር ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር	ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም.	350
58.	ዉልን መነሻ ያደረገ ያልተከፈለ ገንዘብ ለማስከፈል የቀረበ ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የማይወድቅ ስለመሆኑ	145053	እነ ወ/ሮ ስኳሬ ለገሰ እና የአዲስ አበባ ዉሃና	*24/9/2010ዓ.ም*	354

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41		ፍሳሽ ባለስልጣን		
59.	• የአንድ ጉዳይ ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸዉ እስከ ተረጋገጠ ድረስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ዉል ወይም ንብረት የሚገኘዉ በክልል ዉስጥ መሆኑ አንድን ጉዳይ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑን የማያስቀር ስለመሆኑ • አንድን ጉዳይ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሆኖ ነገር ግን የአካባቢ ስልጣኑ በክልሎች ስር የሚወድቅ ሲሆን እንደነገሩ ሁኔታ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዉክልና ጉዳዩን የማየት ስልጣን የሚኖራቸው ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(2)፤80(3-ሐ)	144613	እነ አቶ ያሲን ኢብራሂም (2ሰዎች) እና አቶ ኃይሉ ታዬ	30/09/2010	358

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እና 80(4)፤ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2)፤የፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 24 እና 25				
60.	ሥራ ላይ ባሉ ህጎች መሰረት በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የክልል ፍርድ ቤት ታይተው የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች መሰረታዊ የህግ ስህተት አለባቸው በሚል ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አልተቋቋመም፤ እንዲሁም በክልል የሰበር ስርዓት በዝርዝር ህጎች አልተቀመጠም በሚል ምክንያት ጉዳዮች በቀጥታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊቀርቡ የማይገባ ስለመሆኑና ሥራ ላይ ባሉት ህጎች አግባብ በክልል ሰበር ችሎት መታየት ያለባቸው ስለመሆኑ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ለ)፣የሐረሪ ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ70(2)(ሀ)፣የሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መ/ ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988፤የሐረሪ ክልል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ	157560	እነ ወ/ሮ አለምሸዋ አባተ አበበ እና እነ አቶ ሚሊዮን አባተ አበበ	መጋቢት 23 ቀን 2011 ዓ.ም.	363

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አዋጅ ቁጥር 3/1988 እና ማሻሻያ አዋጆች ቁጥር 8/1991 እና 17/1991 እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 68/1999 **/የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ 111887 ፣ 120858 እና ሌሎችም በርካታ መዛግብት ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ውሳኔ ተለውጧል።/**				
አፈፃፀም				369	
61.	አንድ ክርክር ያስነሳ ንብረት በአፈፃፀም ሂደት በጨረታ ከተሸጠና ገንዘቡም ለፍርድ ባለገንዘብ ከተከፈለ በኃላ በጨረታው ሂደት ጨረታውን ሊያስፈርስ የሚችል ጉድለት ካልተገኘ እንዲሁም ንብረቱ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ የተሰጠ ዕግድ በሕግ አግባብ ያልተመዘገበ መሆኑ ከተረጋገጠ	156758	የአብክመ ገቢዎች ባለስልጣን ዐ/ሕግ እና አቶ መስፍን ጥላሁን	*ሕዳር 26 ቀን 2011 ዓ.ም*	370

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የቀዳሚነት መብትን ለመጠቀም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሰረት የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ *በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418፣426፣445*				
62.	ባልና ሚስት በጋብቻ ዉስጥ ያፈሩት ቤት ፍቺን ተከትሎ እንዲከፋፈሉ ዉሳኔ ተሰጥቶ በአፈጻጸም ሂደት አንደኛው ወገን ድርሻ ከፍሎ ለማስቀረት የጠየቀና የተወሰነ ገንዘብ ብቻ ይዞ ቀርቦ ቀሪዉን ለመክፈል ጊዜ ከመጠየቅ በቀር ግዥዉን ለመፈጸምና የቅድሚያ ግዥ መብቱን በጊዜው ሳይጠቀም ከቀረ የቅድሚያ ግዥ መብቱ ሊጠበቅ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 430(1)	152339	ወ/ሮ እድገት ፎጊ እና ም/ኢ/ር አሻግሬ ወ/ማርያም	22/01/2011	377
63.	አንድ ሰው የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 ከመውጣቱ በፊት የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጠው ጠይቆ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ተዘጋጅቶ	152185	የቦሌ ክ/ከተማ አስ/የመሬት ልማት እና	28/01/2011ዓ/ም	381

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንዲሰጠው ውሳኔ ያገኘው አዋጁ በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ከሆነ የውሳኔው አፈፃፀም ሊቀጥል የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 37/1 መሠረት ሳይሆን በአዋጁ አንቀጽ 6/3/ በሊዝ ስሪት መሠረት ስለመሆኑ		ማናጅመንት ጽ/ቤት		
64.	የፍርድ አፈጻጸምን የሚመራ ፍ/ቤት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት እንደፍርዱ ይዘት እና መንፈስ ውጤት ባለው መልኩ ፍርዱን ከማስፈፀም በቀር የፍርዱን ይዘት በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆነ በማስፋት ፍርድን የመተርጎም ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 372፤378	152172	ኢትዮ ቴሌኮም ሠራተኞች የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር የሕብረት ሥራ ማሕበር እና እነ ሰለሞን እሸቱ	ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም	385
65.	አንድ ለክርክር ምክንያት የሆነ ንብረት በአፈፃፀም ምክንያት በሐራጅ እንዲሸጥ የአፈፃፀም መዝገቡን የያዘዉ ፍርድ ቤት ወስኖ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዥ ካልተገኘ ንብረቱን ባለ ገንዘቡ የመረከብ መብት ያለው ሲሆን ይህን ግምት	144272	የሻለቃ አሰፋ መንገሻ ህጋዊ ወራሾች እና አቶ ዮናስ ዳኜ	24/11/2010	391

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ማስተባበል የሚቻለው ደግሞ ባለገንዘቡ ቤቱን እንዲረከብ በሚል ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ስነ-ስርዓት ህጉ በሚፈቅደው አግባብ በሌላ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሻሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 428(2)				
66.	የዕርቅ ስምምነት ውል እንደዉሳኔ ተቆጥሮ በፍርድ ቤት ለአፈፃፀም አቅርቦ ለማስፈፀም ስምምነቱ ግልጽና የፈፃሚዉን አካል ግዴታ በማያሻማ ሁኔታ የሚገልጽ መሆን ያለበት ሲሆን ግልጽ ያልሆነ የእርቅ ስምምነት ሲቀርብ፣ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሌላ ተከራካሪ ወገን ክርክር እንኳ መስማት ሳያስፈልገዉ ክሱን ዉድቅ ማድረግ የሚችል ስለመሆኑ ፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3312(1)	146955	እነ አቶ ብሩክ ኃ/መስቀል እና አቶ ነብዩ ኃ/መስቀል	30/09/2010	398
67.	የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት አከራይ የሆነ ሰዉ ላልተከፈለዉ የዉዝፍ ኪራይ ክፍያ አከፋፈል ሲባል ተከራዩ	156389	አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ	ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም	402

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ለቤቱ ማገጫነት ወይም ለስፍራ ማልሚያነት ከሚጠቀምባቸዉ ዕቃዎች ላይ ዕቃዎቹ የራሱ ባይሆኑም ይህንኑ አከራዩ እስካላወቀ ወይም ማወቅ ነበረበት እስካልተባለ ድረስ በሕግ የተቋቋመ የመያዣ መብት ያለዉ መሆኑና በልዩ ሁኔታ ንብረቱ ለአፈጻጸም መዋል መቻል አለመቻሉ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተጣርቶና ተረጋግጦ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ ፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924፣2925፣2926(2)		ዩኒቨርሲቲ እና ወ/ሮ ሺወርቅ ሲባኒ		
68.	በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት በመጀመሪያ ጨረታ ሽያጭ ላይ ተወዳድሮ አሸናፊ የተባለ ገዥ ዋጋ ከፍሎ ግዥዉን ባለመፈጸሙ ድጋሚ ጨረታ ሲደረግ የሸያጭ ዋጋ ቢቀንስ በሁለተኛዉ እና በአንደኛዉ ጨረታ መካከል ለተፈጠረዉ የዋጋ ልዩነትና ኪሳራ የመክፈል ግዴታ ሁለተኛውን ጨረታ ተወዳድሮ አሸናፊ የሆነው ሰው ላይ የማይወድቅ ስላለመሆኑ	154222	አቶ ረሽድ አደም እና አቶ ታሪኩ አማረ	ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም	407

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ./429				
	የወንጀል ሕግ				**413**
69.	አንድ ምስክር በፖ/ሊስ በወንጀል ምርመራ ወቅት የሚሰጠዉ ቃል እንደመደበኛዉ የዳኝነት አካል ወይም የዳኝነት ነክነትወይም መሰል /quasi-judicial/ ተቋም ቃለ መሃላ ፈጽሞ የሚሰጥ የምስክርነት ቃል ባለመሆኑ ምስክሩ በፖ/ሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጠው የምስክርነት ቃል ፍ/ቤት ቀርቦ በመለወጡ ምክንያት የሀሰት ቃል የተኛዉ እንደሆነ በትክክል በሌላ ማስረጃ ሳይረጋገጥ የምስክሩ ቃል መለያየት ብቻዉን በቂ ማስረጃ በማድረግ ምስክሩ በሀሰተኛ የምስክርነት ቃል መስጠት ወንጀል የሚጠየቅበት የህግ መሰረት ስላለመኖሩ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/2/	153228	የአማራ ብ/ክ/መ/ፍ/ቤት ቢሮ እና እነ ፈንቱ ንጉስ	መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም	414
70.	አንድ ቼክ በሚወጣበት ጊዜ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር	149071	የፌደራል ጠቅላይ	መስከረም 24	421

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በቂ ስንቅ አለመኖሩ እየታወቀ ቼክ የተሰጠ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ከግል ተበዳዩ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያላቸው ስለሆነና ቼኩን የሰጠው በመተማመኛ መልኩ ነው በማለት ድርጊቱ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው በሚል በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(1) መሰረት የቀረበ ክስ ወደ ወንጀል ህግ አንቀፅ 693(2) በመቀየር ተከሳሹን ጥፋተኛ ማለት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23፤59 ድንጋጌ ያላገናዘበ ስለመሆኑ		ዓቃቤ ህግ እና አቶ አሰግድ አባ ቦራ	ቀን 2011 ዓ.ም.	
71.	“በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 27 መሰረት አግባብ ያለው አካል በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት እና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የሠባት የሥራ ቀናት የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ይኖረዋል” በማለት የተቀመጠው ሀሳብ በሕጋዊ መንገድ ለተያዙ	150803	በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ እና አቶ ንጉስ ሀይሉ	ሐምሌ 25 ቀን 2010 ዓ.ም	428

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የከተማ ቦታዎችን ለማስለቀቅ የተቀመጠውን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የመስጠት እና ካሣ የመክፈል ሥርዓት ማሟላት ሳያስፈልግ በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን ማስለቀቅ የሚቻልበትን ሥርዓት የሚደነግግ እንጂ የከተማ ቦታን ወሮ ለያዘ ሰው የወንጀል ሀላፊነትን የሚያስቀር ስላለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 26(4)፣27				
72.	በወንጀል ጉዳይ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አዲስ የወጣ ህግ ተከሳሹን የሚጠቅም በሆነ ጊዜ ተከሳሹ አዲሱ ህግ ተፈፃሚ እንዲሆን አቤቱታ ባቀረበ ጊዜ አዲስ የወጣው ህግ ተፈፃሚ እንዲሆን መደረግ ያለበት ስለመሆኑና በዚሁ ጉዳይ አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ በባህሪው እንደመደበኛ የክርክር ጉዳይ የሚታይ ሳይሆን በቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚችል በመሆኑ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የቀረበ አቤቱታ ነው በማለት ተቀባይነት የለውም የማይባል ስለመሆኑ	151034	አማረ ረታ እና የፌዴራል ጠ/አቃቤ ህግ	ጥቅምት 28 ቀን 2011ዓ.ም	432

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2)፣ የወ/ሕ/አንቀጽ 6 እና 9(1)፤ ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ15/1/				
73.	የዳኝነት ስራ አካሄድ ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች በተለይም አንድ ችሎት በያዘዉ መዝገብ ላይ ችሎት መድፈርን በተመለከተ ወዲያዉኑ ቅጣት ሊወስን ስለሚችልበት አግባብ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 449 ፣ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/480 እና 481	158613	ወ/ሮ ማስተዋል ሰፈረ እና የለም	ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም	436
74.	የአንድ ቼክ ሕጋዊነት ጥያቄ ባላስነሳበት ፤በዋናነት ደግሞ ቼኩ ተጽፎ እና ተፈርሞ መሰጠቱ ባልተካደበት ሁኔታ እንዲሁም ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈጸምበት ሰነድ ከመሆኑ አንፃር በወንጀል ጉዳይ ያለው ተጠያቂነት ቼክ በወጣበት ወይም ለክፍያ ለቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ መኖር ያለመኖሩን መሠረት ያደረገ እንጂ ለዋስትና የተሰጠ መሆን ያለመሆን በወንጀል ጉዳይ እንደ ሕጋዊ መከላከያ የሚወሰድ	152755	የፌደራል ጠቅላይ አቃቢ ህግ እና አቶ አፍራኖ ሁሌ	መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም.	439

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስላለመሆኑ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693(1)				
75.	አንድ የአሽከርካሪነት ሙያ ያለዉ ሰዉ የትራፊክ ደህንነት ደንብን ተላልፎ በተሸከርካሪዉ የኋላ የዉጭ አካል ላይ ሰው አሳፍሮ ሲያሽከረክር ተሳፋሪው ለመዉረድ ሲል መዉደቁ ወይም ለመዉረድ ሲል ዘሎ በመዉደቁ ለደረሰበት ጉዳት አሽከርካሪውን በቸልተኝነት ተጠያቂ ከመሆን የማያስቀረው ስለመሆኑ የወ/ሕ/አንቀጽ 24፣ 59፣543(3)፣ በትራፊክ ደህንነት ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 36(1)	156420	የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ፍ/ሕ ቢሮ ዐ/ሕግ እና አቶ መላኩ ያለዉ	ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም	446
76.	አንድ ተከሳሽ በአንድ ቸልተኝነትና በአንድ ድርጊት በደረሱ ጉዳቶች በተደራራቢ ወንጀሎች ሲከሰስ ሌላ የተለየ ሀሳብና ድርጊት መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ አንዱን በቸልተኝነት ሌላዉን ደግሞ ሆን ተብሎ ታስቦ በተፈጸመ ወንጀል ጥፋተኛ የሚደረግበት አግባብ እና	153690	አቶ ሀብታሙ ደስታ እና የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ	መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም	452

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ቅጣትን በሚመለከት ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመዉ ሲገኙ ቅጣት ሊወሰን የሚገባዉ ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ከተያዘ በኃላ እነዚህን በመደመር ድምሩ የቅጣት መጠን የሚያርፍበትን ዝቅተኛ የቅጣት እርከን በመለየት ስለመሆኑ የተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 22(1/ሀ)				
የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ					**457**
77.	• በአንድ የወንጀል ክስ ማመልከቻ ላይ ተጠቅሶ የቀረበ ድንጋጌና የክሱ ፍሬነገር ዝርዝር ላይ በስህተት የተጠቀሰ ወይም ሳይጠቀስ የታለፈ መሠረታዊ ነገር መኖሩ ሳይረጋገጥ ከወዲሁ አንቀጽ ካልተለወጠ በሚል ምክንያት ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ መስጠትና ይህ ካልተፈጸመ በሚል የክሱን መዝገብ መዝጋቱ ክስ እንዲሻሻል የሚደረግብትን ህጋዊ አላማ	155789	የፌዴራል ጠ/አቃቤ ህግ እና ተጠሪ፡- ነቢላ አህመድ	ጥቅምት 21 ቀን 2011 ዓ.ም	458

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ያላገናዘበ ስለመሆኑ • አንድ ተከሳሽ ላይ የቀረበ ክስ ሁለት ሆኖ 1ኛዉ ክስ ቀደም ሲል ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ተሻሽሎ ባለመቅረቡ የሚዘጋ ቢሆን ሁለተኛዉ ክስ ላይ ያለምንም ህጋዊ ምክንያት ዉሳኔ ሳይሰጥ ማለፍ ሥነ-ሥርዓታዊ ስላለመሆኑ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/112፣113/2/፣119				
78.	የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ለይግባኝ ማቅረቢያና ተያያዥ ጉዳዮች የጊዜ ገደብ ቢያስቀምጥም በመታየት ላይ ያለ መዝገብ መዘጋቱ አስፈላጊ ሆኖ ከተዘጋ በኃላ እንደገና መከፈቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በምን ያህል ጊዜ ዉስጥ አቤቱታ ሊቀርብበት እንደሚገባ በግልፅ ስላላስቀመጠ የጊዜ ገደቡ የሚወሰነው የጉዳዩን ሁኔታዎችና የአቤቱታዉን ዓይነት በመመልከት እንጂ መዝገቡን ለማንቀሳቀስ የቀረበዉ አቤቱታ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ የቀረበ ነው በማለት አቤቱታውን ውድቅ	156999	አቶ ከበደ ተሠራ እና የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ	ጥቅምት27/2011 ዓ/ም	463

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ማድረግ የይግባኝ ባዩን መብት የሚጣብብ ስለመሆኑ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 22(2)፤በወ/ሕ/አንቀጽ 6፣ 9(1)				
79.	በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2/ መሠረት አንድ ተከሳሽ ለፖሊስ የሚሰጠው የእምነት ቃል ለምርመራ ዓላማ ሲባል በምርመራ ጊዜ የተገኘ ማስረጃ በመሆኑ የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆን አለመሆኑ በፍ/ቤት ሊመረመር እና ሊመዘን የሚገባው እንጂ ከወዲሁ ተቀባይነት አለው ተብሎ ድምዳሜ የሚወሰድበት ስላለመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2/	152038	የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ እና ምንተስኖት ዶሩ	ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም	468
80.	• የአንድ ተከሳሽ ያለፈ የቅጣት ውሳኔ አሁን ከተከሰሰበት ጉዳይ ጋር በማያያዝ በዋስ ቢለቀቅ ተመሳሳይ ወንጀል ሊፈጸም ይችላል የሚል ግምት በመውሰድ የዋስትና ጥያቄን አለመቀበል አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ	132055	አቶ አህመድ ደርባቸው እና ፌዴራል ዐቃቤ ህግ	ጥቅምት8/2009 ዓ.ም.	473

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	• በሕግ በግልጽ ካልተደነገገ በቀር አንድ ተከሳሽ በፍርድ ዳኝነት በግልጽ እስካልታወቀ ድረስ የቀድሞ ጥፋተኝነቱ የማይገለፅ ስለመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ)፣138 (1)				
		ልዩ ልዩ			**477**
81.	የመጥፋት ውሳኔ ከተሰጠና የጠፋው ሰው ንብረት ለወራሾቹ ከተላለፈ በኋላ የመጥፋት ውሳኔ የተሰጠበት ሰዉ በህይወት ከተመለሰ ሌላ ማረጋገጫ ሳያስፈልገዉ ንብረቶቹ በሚገኙበት አካኋን መልሶ መዉሰድ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ህግ 168-173	153418	አቶ ጉደታ አሰፋ እና እነ ወ/ት ወደሬ ጉደታ	ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም	478
82.	አንድ የመሰረታዊ ማህበር አባል ሲሞት ዕጣው ወይም ጥቅሙ በማህበሩ መዝገብ ውስጥ በወራሽነት ለሰየመው ወይም ሚቹ ወራሽ ያልሰየመ ከሆነ በሕግ ለመውረስ ለሚችል ወራሹ የሚተላለፍ ሲሆን ይህም የሚሆነው ወራሹ	143045	እነ ወ/ሮ እሌኒ ወ/አማኑኤል እና እነ ወ/ሮ ወርቅነሽ	ግንቦት28 ቀን 2010 ዓ.ም	483

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የማህበሩ አባል ከሆነ ወይም ለመሆን ፈቃደኝነቱን ሲገልፅ ሲሆን ወራሹ የማህበሩ አባል ካልሆነ ወይም አባል ለመሆን የማይፈልግ ወይም የማይፈቀድለት ከሆነ የሚቹ የዕጣው ዋጋ እና ጥቅም የሚከፈለው ስለመሆኑ የጎብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁ.147/1991 አንቀጽ 19፣ 32		ብዙነህ		
83.	የሰውን ምስል ያለባለቤቱ ፈቃድ ለማስታወቂያ ሥራ በቴሌቭዥርን በማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ያዋለ አካል ምስሉን ከባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በመጠቀም ለሰራው ማስታወቂያ ተገቢውን ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 14፣የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27፣28፣ 29	156425	ዳሽን ባንክ እና ዶሪና አቫኪያን	ህዳር 14 ቀን 2011 ዓ.ም	488
84.	ከቅጅ መብት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች የሚጣሩበት አግባብም ሆነ ክርክሮቹን መሠረት በማድረግ የሚሰጡ ዉሳኔዎች የቅጅ መብት ጥበቃ አጠቃላይ ዓላማ መሠረት	153736	እነ አረቡ አብደላ (3 ሰዎች) እና	መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ.ም	493

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በማድረግ የቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ለማግኘት ስራዎቹ ማሟላት የሚጠበቅባቸዉ መመዘኛዎች መሟላታቸው አለመሟላታቸውን ስለ ቅጅ መብት ዕዉቀትና ልምድ ያላቸዉ ባለሙያዎች የተካተቱበትን አጣሪ ቡድን በማቋቋም እንዲያጣሩ በማድረግ የቅጅ መብት ጥሰት የተፈፀመ መሆን አለመሆኑን በማጣራት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 91(3) ፤አዋጁ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 2(8)፣2(30)፣ 4(1)(ለ)፣ 6(1)		አዱኛ ጓደ		
85.	በሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሠጣጥ፤አያያዝ እና አመዘጋገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ በወጣው መመሪያ ቁጥር 78/2004 መሠረት ለኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጥቆማ ሲቀርብ ወሮታ ስለሚከፈልበት አግባብ መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 16/1እና2፤17	153527	አቶ ስንዴው ታደሰ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ	መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም	503

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
86.	አንድ የሥራ ውሉ በገዛ ፈቃዱ የተቋረጠበት የሥራ መሪ ያልተጠቀመበት የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ ስለሚከፈልበት የሕግ አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2563	151082	ሚ/ር አሃም ማርቲን ብራዉን እና ሜድሮክ ፋዉንዴሽን ስፔሻሊስት ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ/ም	509
87.	አንድ ጠበቃ ደንበኛው ላይ በቀረበ ክስ “በተመሳሳይ ጉዳይ ሁለት ፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብ አይገባም ” በሚል በህግ የተፈቀደን መቃወሚያ ማቅረቡ የጥብቅና መ.ያን የሚያጎድፍ ተግባር ፈፅሟል ተብሎ በዲስፕሊን የሚያስቀጣው ተግባር ስላለመሆኑ የትግራይ ክልል የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁ/ 262/2007 አንቀጽ 30/23/	154371	አቶ አስፋዉ ተኽለ በሽሩ እና የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ	ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም	516

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
88.	የመንግሥት አካል ፊት ቀርቦ የተረጋገጠና የተመዘገበ ሰነድ በውስጡ የሚገኘው ይዘት ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀጽ 27 /1/	142851	እነ ወ/ሮ ወርቅነሽ ጌታቸው (2 ሰዎች) እና እነ አቶ ኮሬ ባዊ(2 ሰዎች)	ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ/ም	520

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤተሰብ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 143325

ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አለማየሁ ተድላ- የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሜሮን ፋንታዬ -ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳይ የቀረበው አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክሳቸው ይዘትም፡- ከአመልካች ጋር ጥር 22 ቀን 2003 ዓ.ም በባህላዊ መንገድ ጋብቻ ፈጽመው አብረው የቆዩ መሆኑን አሁን ግን በመካከላቸው በተፈጠረው አለመግባባት በትዳር መቀጠል የማይችሉበት ደረጃ ላይ ስለደረሱ ፍርድ ቤቱ የማሰላሰያ ጊዜ መስጠት ሳያስፈልጋቸው በመካከላቸው ያለው ጋብቻ ፈርሶ የፍቺ ውሳኔ እንዲወሰንላቸው አመልካች ላይ ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም ለቀረበው ክስ የሰጡት መልስ ተጠሪ ጋር የፈጸሙት ጋብቻ እንደሌለ ነገር ግን ተጠሪ ጋብቻ ተፈጸመበት ባሉበት እለት ለተጠሪ ቀለበት ሲያደርጉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተዘጋጀው ዝግጅት የቀለበት ስነስርዓት እና ወደፊት እንደሚጋቡ ቃልኪዳን የገቡበት የመተጫጨት ስርዓት አለመሆኑን እና ይህ እውነትም ተጠሪ በራሳቸው ጥቅምት 27 ቀን 2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ጽ/ቤት ቀርበው ያላገቡ መሆናቸውን ገልጸዋል፤ ይህም ማስረጃ አለማግባታቸውን የሚገልጽ በተጠሪ እጅ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ማስረጃ የሚያረጋግጡ መሆኑን ሌሎች ማስረጃዎች የሚያሳዩት ከተጠሪ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የመተጫጨት ግንኙነት መሆኑን ለመተጫጨት መፍረሱ ምክንያት ተጠሪ ስለሆኑ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ለአመልካች ወጪና ኪሳራ ሊከፍሉ ይገባል በማለት የመከላከያ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ በቀን 9/2/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአመልካችና ተጠሪ መካከል የትዳር ሁኔታ መኖሩን ስለተረጋገጠ በሁለቱም መካከል ጋብቻ አለ ብሎ ከወሰነ በኋላ ለዚህ ውሳኔ መነሻ የሆነው የፍቺ ጥያቄ በተመለከተ የአሁን አመልካች ከጅምሩ ምንም ጋብቻ የለንም ብለው የሚከራከሩ በመሆኑ የፍቺ ጥያቄው ላይ አዲስ መልስ እንዲሰጡበት ቀጠሮ መስጠት ሳያስፈልግ እንዲሁም የማሰላሰያ ጊዜ መስጠት ሳያስፈልግ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 82 መሰረት ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ሲል የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት በውሳኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 13 ቀን 2009 ዓ.ም በዛሬት አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ነሐሴ 23 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል። በመሠረቱ ጋብቻ ስለመፈፀሙ በቀዳሚነት ሊቀርብ የሚገባው የጋብቻ ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 94 ድንጋጌ ሲያስቀምጥ ጋብቻ ስለመኖሩ ይኸው ማስረጃ ከሌለ የጋብቻ ግንኙነት ስለመኖሩ በትዳር ሁኔታ ማረጋገጥ ስለመቻሉም የተጠቀሰው ሕግ በአንቀጽ 95 ደንግጓል። ይህ የጋብቻ መኖር አለመኖርን በተመለከተ ሊቀርብ የሚገባው የማስረጃ አይነትና ቅደም ተከተሉ ነው። የትዳር ሁኔታ መኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነም ሕጉ በአንቀጽ 96 ስር አስቀምጧል። በዚህም መሠረት የትዳር ሁኔታ ማለት አንድ ወንድና አንዲት ሴት የትዳር ሁኔታ አላቸው የሚባሉት ራሣቸውን እንደባልና ሚስት የሚቆጥሩና የሚኖሩ ከመሆናቸውም በላይ ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሁነው ሲገኙ መሆኑ ተደንግጓል። ይህንኑ በሕጉ የተመለከተውን ትርጓሜ ማስረዳት ከተቻለ ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የሕግ ግምት እንደሚወሰድ ተጠቃሹ ሕግ በአንቀጽ 97/1/ ስር በግልጽ አስቀምጧል። ይህ የሕግ ግምት በማስረጃ መረጋገጥ በሚገባቸው ፍሬ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው። በዚህ አግባብ የተወሰደውን የሕግ ግምት ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ማፍረስ የሚችልበት አግባብም በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 97/2/ ተመልክቷል።

የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያሰሟቸው ምስክሮች ጥር 22 ቀን 2003 ዓ.ም አመልካችና ተጠሪ በባህላዊ መንገድ ጋብቻ መፈጸማቸው፤ጋብቻው ከመፈጸሙ በፊት አመልካች በአካባቢው ባህልና ወግ መሰረት መስከረም 22 ቀን 2003 ዓ.ም የአገር ሽማግሌዎችን ወደ ተጠሪ ቤተሰቦች በመላክ ሽማግሌዎቹ ልጃችሁን ለልጃችን ስጡ በማለት ጥያቄ አቅርበው የተፈቀደላቸውና የሰርጉ ቀን የተወሰነ መሆኑ፤በሰርጉ ላይ ቀለበት የማድረግ ስነስርዓት ሲፈጸም አመልካች የዘላለም ሚስቴ ናት በማለት ቃልኪዳን ገብተው የተዘጋጀው ምሳ ከተበላ በኋላ አመልካች ወደ ተከራዩት ቤት መሄዳቸው ከዚያ ግዜ ጀምረው ከአሜሪካ ወደ አገር ቤት ሲመለሱም አብረው በዚሁ ቤት አንድ ላይ ይኖሩ እንደነበር በዝርዝር ያስረዱ ስለመሆናቸው ፍሬ ጉዳዩን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ተጠሪ በቀን 27/02/2007 ዓ.ም ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ያላገባ የሚል ማስረጃ መውሰዳቸው በራሱ በአመልካች እና ተጠሪ የጋብቻ ግንኙነት አለመኖሩን ያረጋግጣል የሚል ነው። ነገር ግን ከጥቅምት 27 ቀን 2007 ዓ.ም በፊት በአመልካችና

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠሪ የነበረውን የትዳር ሁኔታ ግንኙነት መኖሩን በማስረጃ የተረጋገጠውን የሚያስተባብል አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ህጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 126385 ጥቅምት 9 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 185798 ግንቦት 17 ቀን 2009 ዓ.ም በውሳኔ ያጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 153258

መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አህፈሮም ግርማይ -ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ሀበን ፍስሐዬ የቀረበ -የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት ነው፡፡ በአሁን አመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው ጋብቻ መፍረሱን ተከትሎ የአሁን ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ በአሁን ተጠሪ ስም ከተመዘገበው የአስመጪና ላኪ ንግድ በተገኘ ገቢ እንዲሁም በብድር በተገኘ ገንዘብ የተገዛ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ-2-21508 አ.አ የሆነው መኪና እንዲሁም ሌሎች ንብረቶችን በመጥቀስ ክፍፍል እንዲደረግ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካችም በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከንግድ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ ለትራንስፖርት፣ ለግብር እና ለትዳር ጥቅም ወጪ ወጥቶ የሚተርፍ ነገር የለም፡፡ ተሽከርካሪው እዳ ያለበት በመሆኑ እዳው ታሳቢ ተደርጎና አመልካች የከፈሉት ግምት ውስጥ ገብቶ ክፍፍሉ ቢደረግ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት ግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ እንዲሁም አግባብ ካላቸው አካላት መግለጫዎችን ጠይቆ ከመረመራቸው በኃላ ከአስመጪነትና ላኪነት ተገኝ ከተባለው ገቢ ለትዳር ጥቅም እና ለተለያዩ ጉዳዮች ያወጡዋቸው ወጪዎች ተቀናሽ ተደርገው ሊከፈሉ የሚገባው ገቢ ምን ያህል እንደሆነ በግልጽ በአሁን ተጠሪ አቤቱታ ላይ ያልሰፈረ በመሆኑ ጥያቄው ታልፏል፡፡ በሰሌዳ ቁጥር 2-21506 አዲስ አበባ ለሆነው መኪና በጋራ ከተከፈለው ብር 11,530.72 /አስራ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ብር ከሰባ ሁለት ሳንቲም/ ውስጥ ብር 5,765.15 /አምስት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከአስራ አምስት ሳንቲም/ የአሁን አመልካች ለአሁን ተጠሪ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታ የተሰማቸው የአሁን ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ቅሬታቸውም መሠረት ያደረገው ከአስመጪነት እና ላኪነት የተገኘው ገቢ በአግባቡ ተጣርቶ ድርሻዬ አልተወሰነልኝም፣ ተሸከርካሪውን በተመለከተ በትዳር ወቅት በጋራ በብድር የተገዛ ሲሆን የብድሩን አከፋፈል በትዳር ዘመናችን ጀምሮ የጋራ ንብረታችን ክፍፍል ሳናደርግ በቆየንባቸው ጊዜዎች ውስጥ ተከፍሎ ያለቀ በመሆኑ መኪናው የጋራ ተብሎ ሊወሰን ሲገባው የሥር ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የተከፈለውን ክፍያ የአሁን አመልካች /የሥር መልስ ሰጭ/ ከግላቸው እንዲከፍሉ ያለአግባብ ግምት በመውሰድ ቀደም ሲል ከተከፈለው ገንዘብ ግማሽ ለአሁን ተጠሪ /ለይግባኝ ባይ/ እንዲተላ በማለት መኪናውን ለአሁን አመልካች /ለመልስ ሰጭ/ እንዲሆን የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የሥር ፍርድ ቤት ቅሬታ በቀረበባቸው ነጥቦች ላይ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ይግባኙ መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ክርክራቸውን የሰማ ሲሆን የአሁን አመልካች /መልስ ሰጭ/ ጋብቻ ከፈጸምንበት ጊዜ ጀምሮ የፍቺ ውሳኔ እስከተሰጠበት ድረስ የአስመጪና ላኪ ንግድ ተሰርቶ የተገኘው የተጣራ ገቢ ብር 197,453.77 /አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ሶስት ብር ከሰባ ሰባት ሳንቲም/ መሆኑን ከገቢዎች ከቀረበው ማስረጃ ማረጋገጥ የሚቻል ሲሆን ለትዳር እና ተያያዥ ወጪዎች ይኸው ገንዘብ ወጥቷል፡፡ በመሆኑም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን ተጠሪ /ይግባኝ ባይ/ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለውም፡፡ መኪናውን በተመለከተ የአሁን አመልካች /መልስ ሰጭ/ ከፍቺ በኃላ ከፍተኛውን እዳ የከፈልኩና በመኪናው ላይ እዳ የሌለበት ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤት ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት መኪናውን ለአሁን አመልካች/ ለመልስ ሰጭ/ ይገባል ማለቱ በአግባቡ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ /ይግባኝ ባይ/ መኪናውን በጋራ ልካፈል ይገባል የሚሉ ካሆነ ከፍቺ በኃላ በግል የከፈልኩትን ብር 237,497.16 / ሁለት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም/ ተመላሽ አድርገውልኝ መኪናው ተሸጦ ብንካፈል ተቃውሞ የለኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የይግባኝ ሰሚው ክፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙ ያሰሙትን ክርክራቸውን ከመረመረ በኃላ ከአስመጪነትና ላኪነት ጋር የተያያዘውን ክርክር በተመለከተ በአግባቡ ሳይጣራ የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ በመልስ ሰጭ /በአሁን አመልካች/ ስም ተመዝግቦ ከሚገኘው የአስመጪና ላኪ ንግድ ተገኘ የተባለውን ገቢ በተመለከተ የተጣራ ገቢው ምን ያህል እንደሆነ ከተጣራው ገቢ ላይ የወጣ ወጪ መኖር አለመኖሩን፣ አለ ከተባለ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነና ግራ ቀኙ ሊከፍሉት የሚችሉት ተራፊ ገንዘብ /ንብረት/ መኖር አለመኖሩን የግራ ቀኙ ቀኙን ክርክር፣ የተሰበሰበውን ማስረጃ እንዲሁም እንደ አግባብነቱ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ በማስቀረብ ጭምር ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲወሰን ጉዳዩን በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት መልሶታል፡፡ መኪናውን በተመለከተ ደግሞ መልስ ሰጭ /የአሁን አመልካች/ ከፍቺ በኃላ የመኪናውን የብድር እዳ የከፈሉ ከመሆኑ ውጭ ይኸው የገንዘብ ምንጭ ከግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ያልተገኘ ይልቁንም መልስ ሰጭ / የአሁን አመልካች/ በግላቸው ከሌላ የገንዘብ ምንጭ በተገኘ ገቢ የተከፈለ መሆኑን በማንሳት ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ መልስ ሰጭ /የአሁን አመልካች/ ከግል ገቢያቸው የከፈሉ መሆኑን አላስረዱም ከተባለ ደግሞ ለመኪናው መግዣ ግራ ቀኙ የተበደሩትን ገንዘብ በተመለከተ የተከፈለውንና ከግራ ቀኙ የጋራ ሀብት የተገኘ ነው ተብሎ ግምት የሚወሰድ በመሆኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መኪና ግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ ተወስኗል በማለት ውሳኔውን ደምድሟል፡፡

ውሳኔውን በመቃወም የአሁን አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ተዘግቶባቸዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔዎቹን ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በጠበቃቸው በኩል በውሳኔዎቹ ላይ ተፈጽሞብኛል ያሉዋቸውን ቅሬታ ነጥበችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ ክርክር የተነሳበት መኪና በብድር ገንዘብ የተገዛ መሆኑ ባልተካደበትና ተጠሪም እዳው የጋራ ሆኖ ንብረቱን በጋራ ለመካፈል እየጠየቁ እያለ እዳው የጋራ ሳይባል ንብረቱ ብቻ የጋራ ነው የመባሉ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጠበቃቸው በኩል በ19/08/2010 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን የአመልካች ጠበቃም ግንቦት 10 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን መኪናው የጋራ ነው ተብሎ የተወሰነው እዳው ከባልና ሚስት ገቢ የተከፈለ በመሆኑ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መኪና አመልካችና ተጠሪ በትዳር ውስጥ አብረው እያሉ በብድር በተወሰደ ገንዘብ የተገዛ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ከመኪናው እዳ አከፋፈል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የአሁን አመልካች መኪናውን ለመግዛት ከተወሰደው እዳ ከፍተኛው የተከፈለው የአመልካችና ተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኃላ በመሆኑ መኪናው ለአመልካች የግል ሊባል ይገባል፡፡ የግል የማይባል ከሆነ ደግሞ ተጠሪ እዳውን ተጋርተው መኪናው የጋራ ሊሆን ይችላል በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ፍቺ ከተፈጸመ በኃላ የንብረት ክፍፍል ሳይደረግ ባለበት ሁኔታ ከአስመጪነትና ላኪነት ከተገኘው ገቢ እዳው ተከፍሎ ያለቀ በመሆኑ ተጠሪ የሚጋሩት እዳ የለም፣ መኪናው የጋራ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2- 21508 አ.አ የሆነ ተሽከርካሪ በተመለከተ አበዳሪ /አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም/ አመልካችና ተጠሪ ተለያይተው መኖር ከጀመሩበት ከጥር 13 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከጠቅላላ ብድር ምን ያህል እንደተከፈለ ተጠይቆ በቁጥር አ/ብ/ቁ/ተ/አ 091466 ሚያዚያ 25 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ማስረጃ ከ13/05/2006 ዓ/ም በኃላ በጥቅሉ ብር 238,469.29 /ሁለት መቶ ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ስልሳ ዘጠኝ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብር ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም/ መከፈሉን የገለጸ መሆኑን ተያይዞ ከቀረበልን የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ለመመልከት ተችሏል። ይህ የመኪና ብድር ገንዘብ የተከፈለው የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ከመሰጠቱ አስቀድሞ ነው። በዚህ ጊዜ የአመልካችና የተጠሪ የንግድ ሥራ የሚሠራበት የአስመጪነትና ላኪነት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በአሁን አመልካች አማካይነት ሲከናወን የነበረ መሆኑን አመልካች አይክዱም። ይህ ከሆነ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ እንዳስቀመጠውም እዳው የተከፈለው የባልና ሚስት የጋራ ከሆነው ከንግድ ሥራው ነው ተብሎ ግምት የሚወሰድ ነው። አመልካች እዳው የተከፈለው ከንግድ ሥራው አይደለም፣ ከግል ንብረቴ ወይም ገንዘብ ነው የሚል ክርክር አላቀረቡም። ከዚህ አንጻር አላስረዱም። አንድ ተከራካሪ ወገን ስለሚከራከርበት ፍሬ ነገር የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 255 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያስረዳሉ። ከዚህ ጋረ በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎትም በሰበር መዝገብ ቁጥር 44634 ላይበፍትሐብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል። ይህም ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ መሠረት በየትኛውም ደረጃ በሚገኙት ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት እንዳለው በግልጽ ተደንግጎ እንመለከታለን። ስለሆነም አመልካች የመኪናው የብድር ገንዘብ ከፍቺ በኃላ የተከፈለ በመሆኑ ተጠሪ የተከፈለውን ገንዘብ እስካልተኩ ድረስ መኪናው የጋራ ሊሆን አይገባም በማለት የሚከራከሩት ክርክር ከላይ በዝርዝር ከተመለከተው አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም። የሰበር አጣሪውም እዳው በዚህ መልክ የተከፈለ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ክርክርና ይዘት በአግባቡ ሳይመለከት ከፍቺ በኃላ አመልካች የግል ገንዘብ እንደከፈሉ አድርጎ ተጠሪ እዳውን ሳይከፍሉ መኪናውን እንዲካፈሉ መባሉ ተገቢ እንዳልሆነ አድርጎ የያዘው ጭብጥ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የባልና ሚስት ፍቺ ተፈጽሞ የንብረት ክፍፍል እስከሚደረግ ድረስ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት ንብረትም ሆነ ከዚህ ንብረት የሚገኝ ገቢ የጋራ ሆኖ እንደሚቆይ ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 89 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል አመልካች ከአስመጪነትና ላኪነት ጋር በተያያዘ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ሥር ፍርድ ቤት መመለሱ አግባብ እንዳልሆነ በሰበር ቅሬታቸው ያነሱትን አጣሪው በጭብጥነት ያልያዘ ሲሆን ይህ ችሎት ይህን ቅሬታ እንደተመለከተው ከሆነ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን መመለሱ በአግባቡ ነው በሚል ታልፏል፡፡

ሲጠቃለልም የክፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔም ሆነ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ የሚነቀፍ ሆኖ ስላላገኘነው የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 185503 በቀን 28/10/2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 146781 በቀን 30/02/2010 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ክርክር ለተነሳበት መኪና የተወሰደ ብድር ገንዘብ ከአመልካችና ከተጠሪ ገቢ የተከፈለ በመሆኑ መኪናው የጋራ ነው ተብሎ የተወሰነው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡
5. ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ 148570

ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጃኖ ተሰማ -ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አሊ ሰይድ -ቀረቡ፡፡

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአባትነትና የሞግዚትነት ጥያቄን የሚመለከት ክርክር ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአሁኗ አመልካች ላይ በመ/ቁ 50214269 በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሃብሩ ወረዳ ፍርድ ቤት ጥር 08 ቀን 2009 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች በሀብሩ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁጥር 427/2000 በ17/03/2000 ዓ/ም በዋለው ችሎት የወራሽነትና የሞግዚነት እንዲሁም የሚስት ማስረጃ ያገኙ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ኢብራሂም መሐመድ በሚል ወራሽነት ያሳወጁለት ከአሁኗ አመልካች ጋር በጸና ጋብቻ ውስጥ ሆነው የወለዱትና እያሳደጉ የነበሩ መሆኑን፣ ይህ ሁኖ እያለ አመልካች ህጻኑ ከመሐመድ ሁሴን እንደተወለደና ወራሽ መሆኑን፣ የሌላ ሰው ሚስት መሆናቸውን የህጻኑ ሞግዚት መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ የሚይዙበት አግባብ የሌለ መሆኑንና አመልካች እነዚህን ሁኔታዎችን የሚያሳይ ውሳኔ ያገኙ መሆኑን በሌላ ክርክር ጊዜ ማወቅ የቻሉ መሆኑን ጠቅሰው በመ/ቁጥር 427/2000 በ17/03/2000 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ውድቅ እንዲሆንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ጉዳዩ ቀድሞ ታይቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ችሎት ጭምር የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት መሆኑን፣ በጉዳዩ ላይ ተጠሪ መብትና ጥቅምም የሌላቸው መሆኑንና ሕጻኑ የሐጂ መሀመድ ሐሰን ልጅ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል። የሥር ፍርድ ቤትም የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጎ ከአለፈ በኋላ ክርክሩን መርቶ ተጠሪ ማስረጃዎቻቸውን ያሰሙ ሲሆን የአሁኗ አመልካች ግን በተደጋጋሚ ጊዜ ማስረጃዎቻቸውን እንዲያቀርቡ እድሉ ተሰጥቶአቸው ማስረጃዎቻቸውን በራሳቸው ጉድለት ሊያቀርቡ ባለመቻላቸው ይህንኑ መብታቸውን በማለፍ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኗ አመልካች ህጻኑን ከሚች አቶ መሐመድ ሀሰን የወለዱት ሳይሆን ከአሁኑ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ የወለዱት መሆኑ ተረጋግጦአል፣ በጋብቻ ውስጥ ለተወለደ ህጻን ደግሞ የደም ምርመራ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም ሲል ወስኗል። በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም። አመልካች የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ተሰርዞባቸዋል። የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ጉዳዩ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 115219 በሆነ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ መሆኑን፣ የአመልካች የማስረጃ ማሰማት መብት የታለፈውም ያላግባብ መሆኑ የሚዘረዝርና ህፃኑ የሚች ሀጂ መሐመድ ሀሰን ልጅ እንጂ ከተጠሪ የወለዱት ያለመሆኑን ጠቅሰው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ በመ/ቁጥር 427/2000 በ17/03/20000 ዓ/ም የተሠጠው ውሳኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታው ተመርምሮም ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ጉዳይ አመልካች ልጃቸው ኢብራሂም መሀመድ ወይም አቡበከር መሀመድ የሚች ሼህ መሀመድ ሀሰን ልጅ ነው፣ ልጁ የማን እንደሆነ የማውቀው እኔ እናቱ ነኝ ሲሉ ተጠሪ ደግሞ ልጁ የእኔ ነው ፣ ከአመልካች ጋር በነበረን ጋብቻ ውስጥ የተወለደ ነው የሚል ሲሆን ይህንን ለመለየት የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ሳይደረግ በጋብቻ ውስጥ በመወለዱ ብቻ የሕግ ግምት ወስዶ ልጁ የተጠሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክሱን ሊመሰርቱ የቻሉት ከአመልካች ጋር ሕዳር 10 ቀን 1995 ዓ.ም ተጋብተው በመርሳ ከተማ 01 ቀበሌ ይኖሩ እንደነበር፣ በጋብቻ ወቅት ስሙ አቡበከር አሊ /ኢብራሒም አሊ/ የተባለ ወንድ ልጅ ነሃሴ 25 ቀን 1996 ዓ.ም እንደወለዱ፣ ይህ ሁኖ እያለ አመልካች ህጻኑ የሚች ሼህ መሀመድ ሀሰን ልጅ ነው በማለት የወራሽነትና የሚስትነት ማስረጃ መውሰዳቸው አግባብ ያለመሆኑን ጠቅሰው በዚህ ረገድ በመ/ቁጥር 427/2000 በቀን 17/03/2000 ዓ/ም በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻርላቸው መሆኑን፣ ይህን ክስ ሲያቀርቡና ዳኝነት ሲጠየቁም አለኝ የሚሉትን ማስረጃ ከመቁጠራቸውም በላይ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራም ተደርጎ የልጁ አባትነታቸው እንዲረጋግጥላቸው መከራከራቸውን፣ አመልካች ህፃኑን ከተጠሪ እንዳልወለዱት፣ የሕፃኑ ትክክለኛ አባትም ተጠሪ ሳይሆኑ ሚች መሐመድ ሀሰን መሆናቸውን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 115219 በሆነው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሚያዚያ 11 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ ይዘቱም አመልካች ከተጠሪ ጋር የእስልምና ሃይማኖት በሚያዘው አግባብ በኒካ መጋባታችን አልተረጋገጠም በማለት ያቀረቡት ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች በሐይማኖቱ ስርዓት በፍሬ ነገር ደረጃ አጣርተው ውድቅ ያደረጉት በሐይማኖት ስርዓት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በሰበር ችሎቱ ተቀባይነት እንዳላገኘ፣የሕፃን አቡበከር /ኢብራሒም/ አባትነት በተመለከተ የሚች ሃጅ መሐመድ ሀሰን ልጅና ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ አስቀድሞ የተሰጠው ማስረጃ በሕጉ አግባብ መቃወሚያ ቀርቦበት ሳይሰረዝ የተጠሪ ልጅ ነው በማለት መወሰኑ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በማለት በዚህ ረገድ በክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በፋ/መ/ቁ 38933 በ21/07/2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 47160 ሰኔ 09 ቀን 2007 ዓ.ም የጸናው የውሳኔ ክፍል የተሻረ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ከተጠሪ ጋር ጋብቻ መስርተው የቆዩ መሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ/ቁጥር 115219

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት ጉዳይ ሲሆን አመልካች በዚህ መዝገብ ልጁ የተወለደው ከተጠሪ ሳይሆን ከሚች ሐጅ መሃመድ ሁሴን ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ስነ ስርዓታዊ በሆነ አግባብ በዚህ ሰበር ችሎት ተቀባይነት ያገኘ ከመሆኑ ውጪ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት ያገኘ አይደለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 115219 በዚህ ረገድ የሰጠው ውሳኔ ህጻኑ የሚች ሃጅ መሐመድ ሁሴን ልጅና ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ አስቀድሞ የተሰጠው ማስረጃ በሕጉ አግባብ መቃወሚያ ቀርቦበት ሳይሰረዝ የተጠሪ ልጅ ነው በማለት መወሰኑ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ ከመሻሩ ውጪ ተጠሪ በሕጉ አግባብ የሚያቀርቡትን መቃወሚያ ወይም ክርክር የገደበ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 115219 የሠጠውን ውሳኔ መሰረታዊ ይዘት፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ሙሉ ይዘትና ተጠሪ በሕጉ አግባብ ሊያቀርቡ የሚችሉትን መቃወሚያ ክርክር ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ነጥብ የማስረጃ የማሰማት መብታቸው ያላግባብ ታልፏል የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የሰው ምስክሮች እንዲያሰሙ መብታቸው የተጠበቀላቸው መሆኑን፣ ይህንኑ መብታቸውን ምስክር እስከመቀየር ድረስ ፍርድ ቤቱ ጠብቆላቸው ምስክሮችን እንዲያቀርቡ በተደጋጋሚ ታዘዘው በራሳቸው ጉድለት የተነሳ ሳያቀርቡ በመቅረታቸው የታለፈ መሆኑን የውሳኔው ግልባጭ የሚሳይ በመሆኑና አመልካችም ሕጋዊ ምክንያት ያላቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ ሳይኖር የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ስህተት መፈፀሙን በመጥቀስ የሰበር ቅሬታ ማቅረባቸው ተቀባይነት የሚያገኝበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡ በመሆኑም የማስረጃ ማሰማት መብት በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት የሚከናወንና ይህንኑ በህጉ የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት ተደርጎ የተከራካሪ ወገን መብት በፍርድ ቤት ሲጠበቅ ተከራካሪ ወገኑ ሕጋዊ ምክንያትና ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ በራሱ ጉድለት ማስረጃውን ሳያቀርብ የቀረ ተከራካሪ ወገን ማስረጃ የማሰማት መብት አልተጠበቀልኝም በማለት ቅሬታ የሚያቀርብበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተሰጣቸው በቂ ጊዜ ምስክሮቻቸውን ለማቅረብ ያልቻሉት በራሳቸው ጉድለት ስለመሆኑ ተረጋግጦ የማስረጃ ማሰማት መብታቸው የታለፈ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ቅሬታ ይህ ችሎት ሊቀበል የሚችልበትን የሕግ አግባብ ሳላላገኘ አልፈነዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመጣም አመልካች ከአብራካቸው የወለዱት ህጻን ኢብራሒም/አቡበከር/ የተባለ ከሚች ሐጂ መሐመድ እንጂ ከአሁኑ ተጠሪ የወለድኩት አይደለም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ጋር በፀና ጋብቻ ውስጥ ሁነው ህጻኑን የወለዱ መሆኑን በመጥቀስ በሕጉ ግምት የሕጻኑ አባት እኔ ነኝ በማለት የሚከራከሩ መሆኑን፣ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከሕዳር 10 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 26 ቀን 1996 ዓ/ም ድረስ ጋብቻ የነበራቸው መሆኑን፣ በመ/ቁጥር 104/95 በሆነው አመልካች እስከ ሰኔ 18 ቀን 1995 ዓ/ም ድረስ ከሚች ሐጂ መሐመድ ሁሴን ጋር በጋብቻ ውስጥ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡንና ህጻኑ ከሐጂ መሐመድ ሁሴን ሞት በኋላ አንድ አመት ቆይቶ ነሐሴ 25 ቀን 1996 ዓ/ም የተወለደ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ተገንዝበናል፡፡ የበታች ፍርድ ቤት ህጻኑ የተጠሪ ልጅ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱትም እነዚህን ፍሬ ነገሮችን መሰረት በማድረግና የደም ምርምራ አባት አለመሆኑን ለማረጋገጥ እንጂ አባትነትን ለማረጋገጥ በሕግ የተፈቀደ መንገድ አይደለም፣ በጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት ነው ተብሎ የሚገመተው እናትዬውን ያስቀመጠው ባል ነው የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ የአንድ ሰው አባትነት የሚረጋገጥባቸው መንገዶች በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 በአንቀጽ 136 ስር የተመለከቱ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ ማድረግ መሆኑ በተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ተመልክቷል፡፡ አባትነትን እንዲታወቅ ለማድረግ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች መካከልም አንዱ በሕግ የታወቀ ግንኙነት መኖር መረጋገጡ እንደሆነ በቤተሰብ ሕጉ በአንቀጽ 137 ስር ተመልክቷል፡፡ የወረዳው ፍርድ በሰጠው ውሳኔ ላይ የአመልካቹን አባትነት በፍርድ ለማረጋገጥ መሰረት ያደረገውን የክልሉን የቤተሰብ ሕግ ሲሆን ፍርድ ቤት በተጠሪው ምስክሮች በሰ/መ/ቁጥር 115219 እንዲሁም በሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንጻር የተጠሪ አባትነት በሕግ ግምት የሚወሰድበትና በዲ.ኤን.ኤ ምርመራም የሚስተባበልበት አግባብ የለም በሚል ምክንያት መሆኑን ከወረዳው ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አጥብቀው ከሚከራከሩባቸው ነጥቦች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ህጻኑ ከሐጂ መሀመድ ሁሴን የተፀነሰ እና ከመወለዱ ጊዜም ሆነ ከተፀነ በኋላ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው በመኖር ላይ ያልነበሩ መሆኑን በመጥቀስ ነው። ይሁን እንጂ ክርክራቸውን በማስረጃ ያላስደገፉ ከመሆኑም በላይ ከተጠሪ ጋር የነበራቸውን የጋብቻ ግንኙነት ጊዜ ያላገናዘበ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።

በመሰረቱ በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ስለመሆኑ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 137 እና 138 ስር ተመልክቷል። ህጻኑ የተፀነሰው ወይም የተወለደው አመልካች እንደሚከራከሩት ከሌላ ሰው ጋር በጋብቻ ውስጥ ባሉበት ጊዜ መሆኑ አልተረጋገጠም። ይልቁንም ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ውስጥ የነበሩ መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። አባትነትን በሕግ ግምት ወይም በመቀበል መንገዶች ለመወሰን ክርክር ሲነሳ የባህሪ ወሳኝ ቅንጣት (DNA) ውጤት እንደ መከላከያ ማስረጃ እንዲቀርብ በሕጉ በግልጽ የተቀመጠ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ዳኝነት ሰጪ የሆነው ፍርድ ቤት በሕጉ የተረዘረጋውን ስርዓት ተከትሎና ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መሆኑን ሲያምንበት ተግባራዊ ሊያደርገው የሚችለው መሆኑን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀፅ 183(1) እና 155(1(ሀ)) ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው። ከዚህ አንጻር ስንመለከተው የዘር የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ ውጤት በሕጉ በተመለከተው አግባብ በሕጋዊ ምክንያቶች ለማስረጃነት የሚቀርብ እንጂ በሕግ የተቀመጠውን ግምት እናት ስለካደች ብቻ ለማስረጃነት የሚቀርብ ማስረጃ ነው ብሎ ድምዳሜ የሚያዝበት አይደለም። በተያዘው ጉዳይ አመልካች የዘር የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ ውጤት ለማስረጃነት እንዲቀርብ በስር ፍርድ ቤት ያልጠየቁ ከመሆኑም በላይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሦበር አቤቱታ ላይም ይህንኑ በቅሬታ ነጥብነት ጠቅሰው የጠየቁት ዳኝነት ካለመኖሩም በላይ ይህ ችሎት ግራ ቀኙን በቃል ሲያነጋግራቸውም ተጠሪ ወጣ ገባ ይል ነበር የሚል ቃል ለችሎቱ በማስታወቅ የምራመራ ሂደቱ እንዲከናወን ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን የገለፁ ሲሆን ተጠሪ ግን ፈቃደኝነታቸውን የገለፁ መሆኑ ችሎቱ ተገንዝቧል። በዚህም ምክንያት የዘር የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ ሳይደረግ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የመሰጠቱን ጉዳይ በተመለከተ አጣሪው ችሎት በጭብጥነት የያዘው የክርክሩን ሂደት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ የህፃኑን በሕግ ግምት የተጠሪ ልጅ መሆኑን መሰረት ያላደረገ፣ በክልሉ የቤተሰብ ህግም በአንቀፅ 181 እና 183(1) ድንጋጌዎች በተመለከተው አግባብ ምርመራው እንዲደረግ የሚያስገድዱ ሕጋዊ ምክንያቶች ስለመኖራቸው ያለመረጋገጡን መሰረት ያላደረገ ሁኖ ተገኝቷል።

የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሚች ሐጂ መሀመድ ሁሴን ጋር እስከ ሰኔ 18 ቀን 1995 ዓ/ም ድረስ ጋብቻ ውስጥ እንደነበሩ ማስረጃ እንዳላቸው፣ ከተጠሪ ጋርም ከህዳር 10 ቀን 1995 ዓ/ም ጀምሮ ሕጋዊ ጋብቻ የነበራቸው መሆኑን የጊዜ መደራረብ መኖሩን ተገንዝቦ ሕጻኑ ከሚች ሐጂ መሀመድ ሁሴን ሊወለድ አይችልም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው በሕጉ የተመለከተውን የእርግዝና ጊዜ መሰረት አድርጎ ስለመሆኑ ከውሳኔ ይዘት ተገንዝበናል። በእርግጥ የልጆ አባት ነህ ተብሎ በሕግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በ300ኛውና በ180ኛው ቀናት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ስጋ ግንኙነት ላለመፈፀሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስረዳ እንደሆነ የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት እንደሚቻል በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 179 ስር የተመለከተ ሲሆን የተጠቃሹ ቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 139 በአንጻሩ ጋብቻ ከተፈጸመ ከ180 በኋላ ወይም ጋብቻው ከፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል በሚል በንኡስ ቁጥር አንድ ስር ከመንደንገጉም በላይ ለዚህ ተቃራኒ የሆነ የማስረጃ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ጭምር አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ በንዑስ ቁጥር ሁለት ስር በግልጽ አስፍሯል። ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ከሚች ሐጂ መሀመድ ሁሴን ጋር የነበራቸው ጋብቻ ሰኔ 18 ቀን 1995 በሞት ከፈረሰ በኋላ ህፃኑን ጋብቻው ከፈረሰ በ300ኛው ቀን ውስጥ የወለዱት ሳይሆን ይህ በሕጉ የተመለከተው ጊዜ ከአለፈ በኋላ ነሐሴ 25 ቀን 1996 ዓ/ም የወለዱ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ በተጠቃሹ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 139(2) ድንጋጌ አግባብም ተቃራኒ ማስረጃ ለማቅረብ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም። አመልካች የሕጻኑን ከተጠሪ መወለድ ክደው የሚከራከሩ መሆኑ ሲታይም የመካድ ክርክር እያቀረቡ ያሉ መሆኑን የሚያስገነዝብ ሁኖ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ሁኔታ ልጁ የተጠሪ ልጅ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ተገቢነት የሌለው መሆኑን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀፅ 185(5) እና 190 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ የምንረዳው ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለልም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተጠሪ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ ህፃን አቡበከር /አብራሒም/ ከአመልካች ወልደዋል ተብሎ የህጻኑ አባት ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻልበትን የሕግ አግባብ ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሐብሩ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0124269 በ29/07/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2112 በ28/09/2009 ዓ/ም ፣ በአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በሰ/መ/ቁ 03-19077 ሐምሌ 24 ቀን 2009ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡፡
2. የስር ፍርድ ቤቶች ሕፃን አቡበከር /ኢብራሒም/ የተጠሪ ልጅ ነው በማለት በሰጡት ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመ/ቁጥር 152719

መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ብርቱካን ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የሺእመቤት ታደሰ ከጠበቃ አበበ ማስረሻ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካችን የሻለቃ ታደሰ በላይነህ ልጅነትን በመቃወም ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡትን ክርክር መሠረት በማድረግ የተሰጠውን ውሳኔ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው የአሁኗ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥር 27 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የአመልካች የክስ ይዘት ሲታይም፡- ወላጅ አባታቸው ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህ ከወላጅ እናታቸው ከወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ ጋር በጋብቻ ውስጥ ሁነው በ 1964 ዓ/ም የወለዷቸው መሆኑን፣ የልደት ምስክር ወረቀትም ያላቸው፣ ከቤተሰቦቻቸው አሳድገው፣ አስተምረው የዳሯቸው መሆኑን፣ በሰፈር፣ በቤተዘመድ እና በወረዳም ልጅ ለመሆናቸው የሚታወቁ መሆኑን፣ ወላጆቻቸው ሲሞቱም ወራሽነታቸውን ሲያረጋግጡ የአሁኗ ተጠሪ በመቃወማቸው የወራሽነት ማስረጃውን የሰጠው ፍርድ ቤት አመልካችን ልጅነታቸውን አረጋግጠው እንዲቀርቡ በማዘዙ ምክንያት ክሱን ለማቅረብ የተገደዱ መሆኑን ጠቅሰው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሁለቱም ሟቾች ልጅ መሆናቸው በፍርድ ተረጋግጦ የልጅነት ውሳኔ እንዲሰጣቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪም ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ እንዲፈቀድላቸው በ17/07/2006 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ ጠይቀው ከተፈቀደላቸው በኋላ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ መነሻ አሻሽለው ባቀረቡት ክርክር ሟቾች ባልና ሚስት ቢሆኑም መሃን መሆናቸውን፣ አመልካች የሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ የወንድም ልጅ መሆናቸውን፣ ሟቾች ለተጠሪ ኑዛዜ ትተውላቸው ተጠሪ በፍርድ ቤት እንዲፀድቅ ማድረጋቸውንና አመልካች የሟቾች ተወላጅ ባልሆኑበት ሁኔታ ተጠሪ በሟቾች ኑዛዜ ወራሽነት ተጠቃሚ የሆኑበትን የውርስ ንብረት የሚጠይቁበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ተክራክረዋል፡፡ ለዚህ ክርክራቸው አሉኝ የሚሏቸውን የሠውና የሠነድ ማስረጃ ዘርዝረው ከማቅረባቸውም በተጨማሪ በ26/08/2008 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻም የዲ.ኤን.ኤ ምርምራ እንዲደረግ ትዕዛዝ እንዲሰጣቸው አመልክተው ፍርድ ቤቱም በ25/1/2/2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተጠሪን የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ጥያቄ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎ ብይን ሰጥቷል፡፡

ከዚህም በኋላ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ከአጣራ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የሟቾች ልጅ መሆናቸውን በሰውና በሰነድ ማስረጃ ሲያስረዱ ተጠሪ ይህንኑ አላስተባበሉም በሚል ምክንያት አመልካች የሟች ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህና የሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ ልጅ ናቸው በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ የታለፈው ሕጋዊ ባልሆነ ምክንያት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገሩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮ የአሁኗ አመልካች ከአቶ ገዛኽኝ በቀለ ጋር የዘረመል /D.N.A/ ምርመራ እንዲያደርጉ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲሰጥና የምርመራ ውጤቱ ሲቀርብለት የመሰለውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ የዲ.ኤን.ኤ ምርምራ ጥያቄ መጀመሪያ በሕጉ አግባብ ያላቀረቡና ጥያቄውን ከአቀረቡ በኋላም ምራመራው ከማን ጋር እንደሚከናውን የተለያዩ አቋም ይዘው ሲከራከሩ የቆዩ ከመሆናቸውም በላይ ከአመልካች ጋር ምርመራ እንዲያደርግ የታዘዘው ግለሰብም ፍርድ ቤቱ በምስክርነት የሰማውና የአመልካችን ተወላጅነት ያረጋገጠ ሁኖ እያለ ተገቢ ባልሆነ ስነ ስርዓትና ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንዲሚከተለው መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የተያዘው ጭብጥም ተጠሪ ባቀረቡት የጣልቃ ገብ አቤቱታ ላይ የዘረ መል ምርመራ እንዲደረግ ባልጠየቁበት ሁኔታና እንዲሁም አመልካች የዘረ መል ምርመራ አብረው እንዲያደርጉ የተባለው ግለሰብ ከሚች ጋር ያለው የቅርብ ዝምድና ሳይጣራ የዘረመል መርምራ እንዲደረግ የመታዘዙን አግባብነት የሚመለከት ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ከሚች ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህና ከወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ በጋብቻ ውስጥ ተወልጀአለሁ በሚል ይኼው በፍርድ እንዲረጋገጥላቸው መሆኑንና የአሁኗ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ተደርጎ ሚቾች ልጅ መውለድ የማይችሉና አመልካችም ከሚቾቹ ያልተወለዱ መሆኑን፣ ተጠሪ ከሚቾቹ የኑሃዜ ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን፣ ግራ ቀኙ አሉን የሚሏቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎቻቸውን ከማቅረባቸውም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ፍሬ ነገሩን ተገቢ ነው ባለው መንገድ ያጣራ መሆኑን፣ የአመልካች የሰው ምስክሮችም ሆኑ በተጠሪ በፍርድ ቤት ማጣሪያነት ቀርቦ እንዲመሰክር የተጠየቀው ምስክርም በማጣሪያ ምስክርነት ቀርቦ አመልካች የሚቾች ልጅ መሆናቸውን እንደሚያውቁ የመሰከሩ ሲሆን አመልካች በሰነድ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃነት በ15/04/2006 ዓ/ም የተሰጣቸውን የልደት ምስክር ወረቀት፣ ሚች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ አባል መሆናቸው ከተረጋገጠው ከምስራቅ በር እድር የቀረበው ሰነድም አመልካችን የእድርተኛ አብራክ ልጅ በሚል ተመዝግበው የሚገኙ መሆኑን እንደሚያሳይ፣ ከክፍሉ ቀበሌ የቀረበው የቤተሰብ ቅጽም አመልካች ልጅ ተብለው የተመዘገቡ መሆኑን እንደሚያሳይ፣ ከኮሪያ ዘማቾች የቀረበው ቅጽም አመልካችና ተጠሪ ልጅ ተብለው የተመዘገቡ መሆኑን እንደሚያሳዩ፣ በአመልካች በኩል የተሰሙት አራት የሰው ምስክሮች አመልካችን ሚቾች ያሳደጓቸው እንጂ ያልወለዷቸው መሆኑን፣ አመልካች አሉኝ የምትላቸው የኑዛዜ ተጠቃሚነት ሰነዶች ሲታይም ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህ በ13/03/94 ዓ/ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ በመ/ቁጥር 300/97 በ6/6/97 ዓ/ም በፍርድ ቤት የጸደቀ መሆኑን፣ ሚች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ በ13/1/95 ዓ/ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ደግሞ በመ/ቁጥር 38093/05 በ1/12/05 ዓ/ም ፀድቆ የነበረ ቢሆንም በአመልካች ተቃዋሚነት በ17/11/06 ዓ/ም የተሻረ መሆኑን የሚያስገነዝቡ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ በግልጽ ማስፈሩን ነው፡፡ ተጠሪ የአመልካችን የሚቾች ልጅነት ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ ጥያቄን ጣልቃ ገብተው ሲቃወሙ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ጥያቄ ያላቀረቡ መሆኑን፣ በ06/11/2007 ዓ/ም በስር ፍርድ ቤት ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታም በሚች ሻለቃ በሻ ታደሰ በላይነህ እና በአመልካች መካከል የዘረመል ምርመራ እንዲካሄድ የሚል ሲሆን በዚህ የተጠሪ ጥያቄ ላይ አመልካች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ አመልካች በ15/10/2008 ዓ/ም በሰጡት አስተያየት ተጠሪ ጣልቃ ለመግባት በጠየቁበት ማመልከቻ ያልጠየቁትና ስነ ስርዓታዊ ያልሆነ ጥያቄ መሆኑን፣ ሐምሌ 06 ቀን 2007 ዓ/ም አቀረብኩ ላሉት አቤቱታም አቶ ገዛኽኝ በቀለ በምስክርነት እንዲሰሙና ከአመልካች ጋር የዘረመል ምርምራ እንዲያደርጉ በማለት የጠየቁት ጥያቄም ግለሰቡ በማስረጃነት የተሰሙ በመሆኑና ግለሰቡ ከአመልካች ጋር የዘረመል ምርመራ ለማድረግ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለመኖሩን ገልጸው የተከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ከአንድ አባትና እናት መወለዱን በሕግ አግባብ በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የሚቀርበውን ክስ መቃወም የሚቻለው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት ነው፡፡ በአባት በኩል ያለውን መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ ወይም ክርክር በሚቀርብበት አግባብ ስለመሆኑ ከተሸሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከአንቀጽ 167 -179 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው። ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው የመካድ ክሱ የሚቀርበው አባት ነህ የተባለ ሰው ራሱ መሆኑ የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 174 ያስቀመጠ ሲሆን እርሱ የሞተ ወይም ችሎታ ያጣ ከሆነ ደግሞ በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 177 የተጠቀሱት ሰዎች እንደቅደም ተከተላቸው መሆኑን ነው። በሕጉ ከተመለከቱት ከእነዚህ ሰዎች ውጪ የመካድ ክስ ሌላ ሰው ሊያቀርብ የማይችል መሆኑን፣ በሕጉ የተፈቀደላቸው ሰዎች የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችሉትም የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 171 መሰረት የፍርድ ቤት ፍቃድ ሲያገኙ ነው። በመሆኑም ይህ በሕጉ የተመለከተው ፈቃድ የማግኘት ጉዳይ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው። ህጉ በእናትና በልጁ ያለው ግንኙነት እናትነት ለማረጋገጥ በመወለድ ብቻ እንደሆነ፣ ነገር ግን ይህን ሊሰተባበል አይቻልም ለማለት እንደማይቻል በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 163 ይደንግጋል። ፍርድ ቤቱም ይህን ለማስረዳት ተጨባጭነት ያለው ተግባር መኖሩን ካልረተጋገጠ በቀር ሊፈቅድ እንደማይቻል በተጠቃሹ ሕግ 164/2/ ስር በግልጽ ተመልክቷል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ሚች ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህ እና ሚች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተወለዱ መሆኑን አመልካች ገልፀው ተከራክረው በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት ምስክሮቻቸው ይህንኑ የመሰከሩላቸው ከመሆኑም በላይ ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች የቀረቡ ሲሆን ይህንን የሚያስተባብል ማስረጃ ተጠሪ ያለማቅረባቸውን የክርክሩ ሂደት ያሳያል። በጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት ባልየው ስለመሆናቸው የሕግ ግምት መኖሩን ከተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሠብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 126 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። በሕግ የልጁ አባት ነው የተባለው ሠው የልጁ አባት ሊሆን እንደማይችል በማያጠራጥር አኳኋን በማስረዳት ለመካድ እንደሚችልና በዚህ መሠረት የሚቀርበው የመካድ ክስ ግን ፍ/ቤት ካልፈቀደና ሊቀርብ እንደማይችል ከተሻሻለው የቤተሠብ ሕግ አንቀጽ 170 እና 171/1/ ድንጋጌ በግልጽ መረዳት ይቻላል። የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሠብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 176/1/ የእኔ ልጅ አይደለም የሚል የመካድ ክስ የልጁን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው 180 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት የሚል ይዘት ያለው ሲሆን በድንጋጌው "...በተለይ ማወቅ ከሚገባው...." የሚለው የድንጋጌው አገላለጽ የልጁን መወለድ ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ ተብሎ የሚተረጐም መሆኑን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ልጁ በሕጉ ግምት መሰረት አባት የተባለው ሰው ልጅ ያለመሆኑን በማናቸውም ጊዜ ወሬ ከሠማበት ወይም ጥርጣሬ ከተፈጠረበት ቀን ጀምሮ በሚል የተቀመጠ ባለመሆኑ የመካድ ክስ በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ ነው ተብሎ የማይወሰድ መሆኑን ሕጉ ያሳያል፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተወለደን ልጅ ባልየው አባት ነው ብሎ የተወሠደው የሕግ ግምት ጥብቅ ድንጋጌ በመሆኑ አባት አይደለም የሚል ጥያቄ ሲነሣ ይህንን በሚያጠራጥር አኳኋን ማስረዳት እንደሚጠበቅበትና የመካድ ክስ ለማቅረብ እንኳ የፍ/ቤት ፈቃድ እንደሚያስፈልግ መደንገጉ ሲታይ ሕጉ በጋብቻ ውስጥ የተወለደን ልጅ በማናቸውም ጊዜ ማንኛውንም ምክንያት በማቅረቡ መካድ እንዳይኖር ከፍተኛ ጥበቃ ያደረገ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ የሕጉ ጥብቅ ድንጋጌ እና ጥበቃ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ልጆች በወላጆቻቸው ተገቢ ባልሆነ ምክንያት ተክደው ወላጅ አልባ ሆነው እንዳይቀሩ፣ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እንዳይዳረጉ፣ በቤተሠብ መካከል የሚፈጠረውም ያለመተማመን ማህበራዊ ምስቅልቅሎች እንዳይፈጥር በወላጆችና በተወላጆች መካከል ለሚፈጠሩ መብቶችና ግዴታዎችን በአግባቡ ለማስተናገድ ሥርዓት ለማስያዝ ጭምር ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳይ በዕጃችን የተያዘው ጉዳይ ሲታይም የአሁኑ ተጠሪ አመልካች የሻለቃ ታደሰ በላይነህ ልጅ አይደሉም በማለት ተቃውሞአቸውን ለስር ፍርድ ቤት ሲያቀርቡ ከላይ በተጠቀሰው ህግ መሠረት አስቀድሞ የፍርድ ቤት ፍቃድ አላገኙም፤ በተጨማሪም ተጠሪ የኑዛዜ ተጠቃሚ ከመሆናቸው ውጪ በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 174 እና 177(3) ውስጥ ከተዘረዘሩት የመካድ ክስ ለማቅረብ ከተፈቀደላቸው ሰዎች ውስጥ የሚካቱ አይደሉም፡፡

አመልካች የሚች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ ልጅ ነኝ በማለት ያቀረቡትን ክርክር ተጠሪ የሚቃወሙበትን አግባብ ስንመለከተውም እናትነትን ለማስረዳት በተጠቃሹ አዋጅ ውስጥ ከአንቀጽ 163-166 ስር ስርዓቱ ተዘርግቷል፡፡ ይዘታቸውም በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው፡፡ በእናት በኩል ያለው ተወላጅነት በማንኛውም ባለጉዳይ በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ክርክር ሊደረግበት እንደሚችል ህጉ በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን የተጠቃሹ ህግ አንቀጽ 164 ድንጋጌ በተለይ ሲታይም በተወላጅነት ላይ ስለሚደረገው ክርክር የሚቀርበው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ የማይችል መሆኑን በንዑስ ቁጥር አንድ ድንጋጌ ስር ሲያስቀምጥ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ደግሞ በተወላጅነት ላይ ክርክር ለማድረግ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉት ተጨባጭነት ካላቸው የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው በሚል አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጦ ይገኛል። የአዋጁ አንቀጽ 165 ድንጋጌም ልጁ ተወላጅነቱን የሚያረጋግጥ የልደት ምስክር ወረቀትና ከዚህ ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ በተወላጅነቱ ላይ ለመከራከር ፈቃድ አይሰጥም በሚል በኃይለ ቃል ደንግጓል። እንዲሁም የአዋጁ አንቀጽ 166 ንዑስ ቁጥር አንድ በተወላጅነት ምክንያት የሚቀርበው ክስ በተወላጅነቱ ላይ ክርክር በተነሳበት ሰው ላይ ወይም በወራሾቹ ላይ ሊመሰረት እንደሚችል ያሳያል።

ከእነዚህ ድንጋጌዎች አቀራረፅ፣ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የአንድ ልጅ እናት እገሊት አይደለችም ወይም እኔ ነኝ የሚለው ክርክር የሚነሳው የመወለድ የምስክር ወረቀት ከሌለ ወይም የልጅነት ሁኔታ በሌለ ወይም ይህ ሁኔታ ክርክር የቀረበበት እንደሆነ ስለመሆኑ ነው። እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት የሕጉ ድንጋጌዎች ተወላጅነት ላይ የሚነሳን ክርክር የሚገዙ ሲሆን በተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ አንቀፅ 154 እስከ 162 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ስለልጅነት ማስረጃ /Proof of Filiation/ የሚገዙ እና ተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክር አግባብነት ካላቸው ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተለዩ ስለመሆኑ መገንዘብ የሚቻል ነው።

በመሠረቱ ስለልጅነት ቀዳሚ ማስረጃ የልደት ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 154 የሚያስገነዝብ ሲሆን የልደት ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ የልጅነት ሁኔታ በመኖሩ ልጅነት እንደሚረጋገጥ በተጠቀሰው አዋጅ በአንቀጽ 155 ስር የተመለከተ ሲሆን የልጅነት ሁኔታ መኖር የሚለው ትርጉም ደግሞ አንድ ሰው በማህበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 156 ስር በግልጽ ተቀምጧል። በዚህ አኳኋን የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ልጅ ነው ሲል የሕግ ግምት እንደሚወስድ፣ የሕግ ግምቱ ልጁ የተባለው ሰው ልጅ ሊሆን እንደማይችል ሊፈርስ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደሚችል በአዋጅ አንቀፅ 157 ንዑስ ቁጥር አንድና ንዑስ ሁለት ስር እንደቅደም ተከተሉ ተመልክቷል።

የደም ምርመራ (DNA) አንድ ሰው የልጁ አባት ወይም እናት አይደለም ለማለት የሚቀርብ ማስተባባያ ማስረጃ ሊሆን የሚችል ቢሆንም ይህ የሚከናወነው ደግሞ አባትነትን በሚመለከት የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚያስችሉ ቀዳሚ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፣ እናትነትን በተመለከተም በተጠቃሹ ህግ ከአንቀፅ 153 እስከ 166 ድረስ የተዘረጋው ስርዓት የሚፈቅድ ሁኖ በፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከቱትን የማስረጃ አቀራረብ ስርዓቶችን መሰረት በማድረግ ሊቀርብ የሚገባ ነው።

እንግዲህ በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት ይዘን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ የስር ፍ/ቤት አመልካች ሕግ ጥበቃ በሚያደረገው ጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑንና ሟች ሻለቃ ባሻ ታደሰ በላይነህና ሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበ በጋብቻ ውስጥ ሁነው አመልካችን መወለዳቸውን በአረጋገጠበት ሁኔታና በዚህ ግንኙነት ውስጥ የሚወለድ ልጅ አባት ተብሎ በሕጉ ግምት የሚወሰድበት ከልጁ እናት ጋር የተቀመጠው ወንድ መሆኑ፣ ይህ የህግ ግምት የሚፈርስበት አግባብም የመካድ ክስን በማቅረብ ሁኖ ክሱን ወይም መቃወሚያውን ለማቅረብ የሚችሉ ወገኖች ማንነትና ማቅረቢያ ጊዜውም በህጉ ተለይቶ ከመቀመጡም በላይ የመካድ ክስ እንዲቀርብ የሚፈቀደው በማያጠራጥር ሁኔታ ልጁ ከተወለደበት ወደኋላ ሲቆጠር በ300 እና 180 ቀናት ዉስጥ ከልጁ እናት ጋር ሩካቤ ሥጋ ግኙኝነት ያለመፈጸሙን ሲረጋገጥ ወይም በሌላ ማስረጃ የልጅ አባት መሆን አለመቻሉም ሲያሰረዳ አባት መሆኑ በሕጉ ጥብቅ በሆነ አግባብ ተመልክቶ እያለ፣ እንዲሁም ሟች ወ/ሮ ሙሉነሽ አበበም በሕጉ ከአንቀፅ 163 እስከ 166 አግባብ ተጠሪ መቃወሚያ ለማቅረብ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተገኝተው ፍርድ ቤቱ ፈቃዱን ባልሰጠበት ሁኔታ ከማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ውጪ፣ አመልካች ምርመራ እንዲያደርጉ የታዘዘው ግለሰብም በፍርድ ቤት ቀርቦ የአመልካችን ተወላጅነት ባረጋገጠበትና የዚህ ግለሰብ ዝምድናም ከሁለቱም ሟቾች ጋር ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ፤ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያለምንም መነሻ የባህሪ ወሳኝ ቅጣት (DNA) ምርመራ እንዲደረግ ተጠሪ ጥያቄ በሕጉ አግባብ አቅርበዋል ወደሚል ድምዳሜ ደርሶ የደም ምርመራ እንዲረግ ማዘዙ ከመነሻውም በሕጉ የተመለከተውን ስርዓት ያልተከተለ በመሆኑ በሕጉ ከተዘረጋው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስርዓት ውጪ እንዲከናውን ተደርጎ የነበረው ምርመራ ታልፎ በጉዳዩ ላይ በቀረቡት የሰውና የሰነድ ማስረጃ የአመልካች የሚኞች መሆናቸው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መወሰኑ ከውጤት አንጻር የሚነቀፍበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት፣ የስር ፍርድ ቤት ግን በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን መዝኖ አመልካች የሚኞች ልጅ ናቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 182625 ጥቅምት 17 ቀን 2010 ዓ/ም የሠጠው እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 150307 በ9/5/2010 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 21544 በ25/12/2008 ዓ/ም የሠጠው ብይንና ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁጥር 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትእዛዝ

11/07/2010 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.152968

መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ሲ/ር ሐምዚያ ሱለይማን -ቀረቡ::

ተጠሪ፡- አቶ አያሌው በቀለ-ጠበቃ ኩራባቸው ጎሳ ቀረቡ::

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ አዳማ ልዩ ዞን በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በቀን 14/02/2009 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በ1983 ዓ.ም ጀምሮ በባህል ተጋብተው ሲኖሩ አራት ልጆች ማፍራታቸው በመግለጽ አመልካች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ባህሪያቸው ስለቀየረ በተለያዩ ጊዜያት የሚደበድቧቸው፤የሚሰድቧቸው እንዲሁም የማያከብሯቸው በመሆኑ ጋብቻው ፈርሶ በጋራ አብረው ያፈሩት ንብረት ድርሻቸው እንዲወስነላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ራሷ ባህሪዋን ለውጣ እኔ ያልፈጸምኩት ድርጊት ፈጽመሃል በማለት እኔን መክሰሷ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትክክል አይደለም በማለት ትዳራችን በአመልካች ጥያቄ እና ፍላጎት በመሆኑ በእርሷ ምክንያት የሚፈርስ መሆኑ ተቆጥሮልኝ የሞራል ካሳ እንድትከፍለኝ በማለት ለአቤቱታው መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ ነገር ግን አመልካች የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት መዝገቡ ለጊዜው እንዲዘጋ በማመልከታቸው ምክንያት የማንቀሳቀስ መብታቸው በመጠበቅ ተዘግቶ የነበረ ሲሆን አመልካች የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስ በቀን 24/08/2009 ዓ.ም በተፃፈ ስለአመለከቱ ፍርድ ቤቱም ተዘግቶ የነበረው መዝገብ እንዲቀሳቀስ በማድረግ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ በቀን 28/09/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ የነበረው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ካደረገ ለጋብቻው መፍረስም ተጠሪ ምክንያት በመሆኑ በጋራ አፍርተው ካላቸው ንብረት ውስጥ ከተጠሪ ድርሻ 20 በመቶ ለአመልካች እንዲያካፍል እንዲሁም የሁለት ልጆች ቀለብ በወር ብር 1,500.00/ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኝ በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በማሻሻል በተከራካሪዎች መካከል የነበረው ጋብቻ በተጠሪው ጥፋት በመፍረሱ በጋብቻ ውስጥ 20 በመቶ ለአመልካች እንዲያካፍል በማለት የተሰጠው ወሳኔ ውድቅ በማድረግ የልጆች ቀለብ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥር 23 ቀን 2010 ዓ.ም በፃፈው አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 26 ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረውም የአመልካች ጥያቄ ልጆችን ለማሳደግ ደፋ ቀና ብዬ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት አካል ጉዳተኛ ልጅ በሰው እርዳታ የሚኖር አሸብር አያሌው የሚባለውን ለማሳደግ በጥረት ላይ እያለሁ እና አቅመ አዳም ያልደረሱ አዳን እና ኢለያላ አያሌው የሚባሉትን ለማሳደግ እና ለማስተማር በጥረት ላይ እያለሁ ይህ ተጠሪ በየጊዜው ረብሻ እየፈጠረ አፀያፊ ቃላት እየተናገረ ለዚህ ሁሉ ለትዳር መበተን ዋና ተዋናይ እራሱ ሆኖ እያለ፤እንዲሁም ከእኔ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረን ወይም ተጋብተን እየኖርን እያለን ከትዳር ውጭ ከሌላ ሴት ጋር በፈጸመው የግብረ ስጋ ግንኙነት አንድ ልጅ የወለደ ለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በማያሻማ ተመስክሮበት መከላከል ያልቻለ ስለሆነ በገንዘብ መቀጮ ተቀጥቶ እያለ ምንም አይነት ጥፋት እንዳልፈጸመ ሰው ንብረቱን እኩል እንድንካፈል የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት የተካሄደውን ክርክር እና ያቀረብኩትን አቤቱታ መርምሮ ከተጠሪ ድርሻ 20% /ሃያ በመቶ/ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል የተወሰነው የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ መደረጉ ምንም አይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 83/96 የፍቺው ምክንያት ለፍቺው አስፈላጊ ባይሆንም ለውጤቱ በተለይም ለጋራ ንብረት ክፍፍሉ ግን ግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል። ለምሳሌ ለፍቺው የተጠየቀው አንደኛው ወገን በፈፀመው ዝሙት ወይም ድብደባ ምክንያት ከሆነ ፍቺው ተወስኖ በሚደረገው የንብረት ክፍፍል ወቅት ንብረቱ በእኩል መከፋፈሉ ቀርቶ ይህንኑ ጥፋት ግምት ውስጥ ያስገባ ክፍፍል ማድረግ ይቻላል። ምክንያቱም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 83/96 አንቀጽ 111 ከባልና ከሚስት ባንዱ የተፈጸመውና ለፍቺው ምክንያት ሆኖ የተገኘው ጥፋት በሌላው ተጋቢ ላይ ጉዳት አስከትሎ ከተገኘ በዳዩ ላደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ይወስናል። ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ መሰረት ከጋራ ንብረት በካሳ መልክ ያንደኛውን ተጋቢ ድርሻ አብዛኛውን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም ሙሉውን በደል ለተፈጸመበት ወገን እንዲከፈል ሊወሰን ይችላል በማለት ተደንግጎ ይገኛል። በርግጥ በፍቺ ወቅት የሚኖረው የጋራ ሀብት ክፍፍል በአንጽ 117 እንደተመለከተው የጋራ ሀብቱ ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ አንቀጽ 111 የአንቀጽ 117 ልዩ ሁኔታ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል። ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች የፍቺ ውሳኔ እንዲሰጥ አቤቱታ ሲያቀርቡ እንደምክንያት ያቀረቡት ተጠሪ ባህሪያቸው በመቀየር በተለያዩ ጊዜያት የሚደበድቧቸው፤ የሚሰድቧቸው እና የማያከብሯቸው ከመሆናቸውም በላይ ከትዳር ውጭ ከሌላ ሴት ጋር በፈጸሙት የግብረ ስጋ ግንኙነት አንድ ልጅ የወለዱ መሆናቸው በዚህ ተግባራቸውም በአፋር ክልል ሎጊያ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.392/2009 በቀን 12/07/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጥፋተኛ በማለት በገንዘብ መቀጮ የቅጣት ውሳኔ የተወሰነባቸው መሆኑን በተጠሪ ከመታመኑም በላይ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶችም ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። ስለሆነም ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በአመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፍረስ በተጠሪ ጥፋት መሆኑና በአመልካች ጉዳት ስለመድረሱ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ ለአመልካች ካሳ የማይከፍሉበት ህጋዊ ምክንያት የለም። ሲጠቃለል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.269768 መጋቢት 7 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሻሽሏል።
2. በአመልካችና ተጠሪ የነበረው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ እና ተጠሪ ለልጆች ቀለብ በወር ብር 1,500.00/አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ፀንቷል።
3. ተጠሪ ለአመልካች ካሳ ሊከፍል አይገባም ሲል የሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል።
4. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.101604 ግንቦት 28 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ውስጥ በተከራካሪዎቹ መካከል የነበረው ጋብቻ በተጠሪ ጥፋት በመፍረሱ በጋብቻ ውስጥ በጋራ ከተፈራው ንብረት ውስጥ ተጠሪ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከድርሻው ውስጥ 20 በመቶ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት የተሰጠው ውሳኔ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.26872 ሰኔ 21 ቀን 2009 ዓ.ም በትእዛዝ ያጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡

5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. በቀን 17/08/2010 ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፣ ይፃፍ፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ ቁጥር 147930

ቀን 28/9/2010 ዓ/ም

ዳኞች:- አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች:- ወ/ሮ ሰብለ ታምራት - ከጠበቃ ቤተልሄም አያሌው - ቀርበዋል

ተጠሪ:- አቶ ግሩም ግዛቸው - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መስከረም 29 ቀን 2010 ዓ.ም በተባለ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 193012 ሐምሌ 5 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 117619 ህዳር 21 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታዋን በማቅረቧ ነው፡፡ ቅሬታዋም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የምትቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የምትለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶች በጋብቻ ውስጥ ስለተፈራው መኪና ገቢ በተመለከተ በማስረጃ አረጋግጬ እያለ መታለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተደረገ የብድር ውል ከአሁን አመልካች እውቅና ውጪ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተደረገ በመሆኑ ውድቅ መደረግ ሲገባው የጋራ እዳ መባሉ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው።

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካች ባቀረበችው ክስ ከተከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ጋር ያለን ጋብቻ ፈርሷል። በጋራ ያፈራነው ንብረት 1. መኪና የሰ/ቁጥር 3-26589 ኦሮ 2. የመኪና ገቢ በቀን 600 በወር 18000 የሾፌር ተቀንሶ ከ17/5/2006 ዓ/ም ጀምሮ ያለው 3. 20/80 የቤቶች ፕሮግራም በንግድ ባንክ የተቆጠበ ገንዘብ 4. ብር 186000 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቆጠበ 5. 61000 የእቁብ ገንዘብ ያካፍለኝ ስትል ጠይቃለች። ተከሳሽም መኪና የሰ/ቁጥር 3-26589 ኦሮ. የሆነ በብድር ገንዘብ የተገዛ በመሆኑ ብድሩ የጋራ እዳ ይሁን። ብር 180000 የተበደርነውን እዳ ያልከፈልን ስለሆነ የጋራ እዳ ነው ይባልልኝ። የቤት ቁሳቁስ ጠቅሶ የየግላቸው የሆነውን ለይቶ መካፈል እንደሌለበት መልስ ሰጥተዋል። የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 117619 ህዳር 21 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መኪና የሰሌዳ ቁጥር 3-26589 ኦሮ. በትዳር ውስጥ የተገዛና ከእዳም ነጻ መሆኗን በምስክሮች በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ የጋራ ንብረት ነው። የመኪና ገቢ አመልካች ለግል ጥቅሙ ያዋለው መሆኑን ከሳሽ ያላስረዳች በመሆኑ ታልፏል። ለኮንዶሚንየም ቤት የተጠራቀመ ገንዘብ የጋራ መሆኑን በተማመኑት መሰረት ይካፈሉ። የእቁብ ብር 40447.37 መኖሩ ተረጋግጧል እኩል ይካፈሉ። ተከሳሽ ብር 180000 የብድር እዳ የጋራ ይባልልኝ ያለው በተመለከተ በሰው ምስክሮች ብድሩ መኖሩ በመረጋገጡ የጋራ እዳ ነው። የቤት ቁሳቁስ ተዘርዝሮ የጋራ የሆኑትን የጋራ የግል ናቸው ያለውን የግል ነው ሲል ወስኗል። ከሳሽ የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ በመ/ቁጥር 193012 ሐምሌ 5 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል።

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል። መዝገቡም ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የብድር ውሉ በአበዳሪው ብቻ ምስክር አመልካች ስለ ብድሩ ያውቁ ነበር መባሉ የብድሩ ድንጋጌዎች መስፈርት ያሟሉ መሆን አለመሆኑን እና የመኪናው ገቢም ሙሉ በሙሉ መኪናው ካልተሸጠ አይከፈልም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ታህሳስ 20 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የመኪና ገቢ በተመለከተ መኪናው የተሸጠው በ14/6/2006 ዓ/ም ሲሆን የሽያጭ ውሉ የፈረሰው በ26/2/2007 ዓ/ም መሆኑን አመልካች ገልጻ እያለ ከ17/5/2006 ዓ/ም ጀምሮ የመኪና ገቢ ያካፍለኝ ብላ መጠይቁ ተገቢ አይደለም፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተበደርነው ብድር ለትዳር ጥቅም የዋለ መሆኑ የቤተሰብ ህጉ ግምት የሚያስቀምጥ ሆኖ እያለ እና አመልካች ለትዳር ጥቅም ያልዋለ መሆኑን ባለማስረዳቷ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ጥር 9 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም 1ኛ. የሰሌዳ ቁጥር 3-26589 ኦሮ. የመኪና ገቢ በተመለከተ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠው መኪናዋ ተሸጣ እንደነበረና የተሸጠችውም በ14/6/2006 ዓ/ም መሆኑን የዚች መኪና የሽያጭ ውሉ ደግሞ በ26/2/2007 ዓ/ም የፈረሰ መሆኑን ነው፡፡ የአሁን አመልካች የዚች መኪና ገቢ ግማሹ እንዲከፈለኝ ሲሉ የጠየቁት ከ17/5/2006 ዓ/ም ጀምሮ ያለውን በቀን 600 ብር ትከራያለች በሚል ሲሆን መኪናውን የተከራየው ራማ ኮንስትራክሽን ከ23/7/2006 ዓ/ም ጀምሮ 600 ብር ከአቶ ዳንኤል ቱፋ ላይ የተከራየ መሆኑን አሳውቋል፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች የመኪናዋ ገቢ ይከፈለኝ ስትል በጠየቀችበት ቀን በፊት በ14/6/2006 ዓ/ም ጀምሮ መኪናዋ የተሸጠችና የሽያጩም ውል በ26/2/2007 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ አመልካችና ተጠሪ መኪናዋን ያስመለሱ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር አለመኖሩና የአሁን ተጠሪ የመኪናዋን ገቢ መሰብሰቡ ባለመረጋገጡ የመኪናዋ ገዥ የነበረው ገቢዋን ሰብስቦ ከሆነም ከውሉ ጋር በተያያዘ የሚታይ ከሚሆን በቀር የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው ማለፉ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ 2ኛ. በስር ፍ/ቤት 180000 ብር የብድር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እዳ የጋራ እዳ ነው የተባለበትን ውሳኔ በተመለከተ ከ500 የኢትዮጵያ ብር በላይ የብድር ውል በጽሁፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም በመሐላ ካልሆነ በስተቀር ማስረዳት እንደማይቻል በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2472 ላይ ተደንግጎ ይገኛል። የአሁን ተጠሪ 180000 ብር ብድር የአሁን አመልካችና ተጠሪ አብረን ተበድረናል ሲል ለማስረዳት ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ በብድሩ ውል ላይ ያለው ፊርማ የአሁን አመልካች ፊርማ እንዳልሆነ በፎረንሲክ ምርመራ ተረጋግጧል። በብድር ውሉ ላይ ያሉት ሁለት ምስክሮችም ስለመመስከራቸው አያመለክትም። እንዲሁም የአሁን ተጠሪ መጀመሪያ ባቀረበው ክስ ጋር ያላቀረበውን ማስረጃ ባሻሻለው ክስ ጋር አያይዞ ማቅረቡም የብድር ውል ሰነዱን ህጋዊነት የማያሳይ ነው። ሌላው የአሁን ተጠሪ ብር 180000 ከአቶ ገናናው ተናገር ተበደርኩ የሚለው በ4/5/2006 ዓ/ም ሲሆን የአሁን አመልካች ከቤት የወጣችው በ17/5/2006 ዓ/ም መሆኑና በ18/11/2006 ዓ/ም በመሀላቸው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱ አላከራከረም። ተጠሪ ገንዘቡን ተበድሬያለሁ ከሚልበት ከ4/5/2006 ዓ/ም ጀምሮ አመልካች ከ12 ቀን በኋላ በ17/5/2006 ዓ/ም ከቤት ወጥታለች። ተጠሪ ገንዘቡን የተበደረው ለመኪና ማስጠገኛ መሆኑን ገልጾ ለመኪናዋ ማስጠገኛ ስለማዋሉ ግን ያቀረበው ማስረጃ የለም። በመሆኑም በአመልካችና በተጠሪ መሀከል አለመግባባት በተፈጠረበት ጊዜ ውስጥ የአሁን ተጠሪ የተበደረው የ180000 ብር ብድር ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ መረጋገጥ አለበት። በዚሁ መሰረት የስር ፍ/ቤት ብድሩ ስለመኖሩ የአሁን ተጠሪን ማስረጃ አበዳሪውን የሰው ምስክር ብቻ ሰምቶ የአሁን አመልካችና ተጠሪ ብድሩን ስለመበደራቸው አረጋግጫለሁ ሲል የጋራ እዳ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ፍሬነገር የማጥራትና ማስረጃን የመመዘን መርህ ባለመከተል የተሰጠው ውሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 193012 ሐምሌ 5 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 117619 ህዳር 21 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የብር 180000 ብድር እዳ የባልና ሚስት የጋራ እዳ መሆኑ ባለመረጋገጡ የአሁን አመልካችን የሚመለከታት አይደለም ብለናል፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.150408

ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አመለወርቅ ፍቅሬ - ጠበቃ ለገሰ ማሞ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋሁን ታፈሰ -የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የወላይታ ሰዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በወላይታ ሰዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር በቀን 3/6/2006 ዓ.ም በተፈጸመ ጋብቻ በቁጥር 240/270//2006 በቀን 12/06/2006 ዓ.ም በብሔራዊ የጋብቻ ስነስርዓት መሰረት ከሶዶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የጋብቻ ምስክር ወረቀት ወስደው ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ እንደማንኛውም ባለትዳር በአንድ ጣራ ስር መኖር ሳይጅምሩ ወደ አሜሪካን አገር መሄዳቸው በመግለጽ ለአለፉት አራት ዓመታት ከተጠሪው ጋር ምንም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓይነት ግንኙነት ሳይኖር በተለያየ ቦታ የሚኖሩ መሆናቸውና ልጆች ሆነ የጋራ ሀብት ያላፈሩ በመሆኑ በመካከላቸው ያለው ጋብቻ ፈርሶ የፍቺ ውሳኔ እንዲወሰንላቸው ተጠሪው ላይ ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም ለቀረበው ክስ የሰጡት መልስ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በህግ የፀና ጋብቻ ስለመኖሩ ሳይክዱ በጋብቻ ውስጥ መኖራችን ጥያቄ ማንሳት የሚችሉት ተጋቢዎች ወይም አንዳቸው እንጂ ሌላ ሰው የሚያነሳው ሀሳብ የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ ስለተጋቢዋ ሆኖ ጠበቃ የፍቺ ጥያቄ ማቅረብ የማይችል ስለሆነ ክሱ ወድቅ እንዲደረግ ይህ መቃወሚያ የሚታለፍ ከሆነ በህጉ መሰረት የሞራል ካሳ ተወስኖ የወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት ተጠብቆ እንዲወሰንላቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና አማራጭ መከላከያ መልሳቸው በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በቀረበው መቃወሚያ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በቀን 4/3/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካች ወንድም አስቀድሞ የተጻፈ ሕጋዊ ውክልና ሰነድ ሳይኖር አመልካችን ወክሎ የአመልካች ጋብቻ እንዲፈርስ ጠበቃን የመወከል መብት በህጉ አልተሰጠውም፤ ስለሆነም በተጠሪ የቀረበው መቃወሚያ ተገቢ ሁኖ ስለአገኘን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33/2/ እና 244/መ/ መሰረት የአመልካች ተወካይ ነኝ ባይ ክሱን ለማቅረብ መብት የለውም ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ ይህንን ብይን በመቃወም የአመልካች ተወካይ ይግባኞቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት ሳያገኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 4 ቀን 2010 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለወንድማቸው የሰጡት ውክልና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ ቀርቦ ባለበት የተሟላ ውክልና አልቀረበም በሚል ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው በማለት በአመልካች የቀረበው አቤቱታ ከውክልና አንፃር ለመጣራት ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዙት መሰረት የካቲት 21 ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መልስ አቅርበዋል። አመልካች ጠበቃ በተጠሪ የቀረበው መልስ ላይ የመልስ መልስ መስጠት የማይፈልጉ መሆኑን በመግለጻቸው ምክንያት የቀረበ የመልስ መልስ የለም።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል። በመሰረቱ በመርህ ደረጃ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚገባው ከባልና ሚስቱ አንደኛው ተጋቢ ወይም ሁለቱም ቢሆንም በህግ አግባብ ተቀባይነት ያለው ውክልና ማስረጃ ጋር የሚቀርብ የፍቺ ጥያቄ በህግ የተከለከለ አይደለም። ከባልና ሚስት አንዳቸው የፍቺ ጥያቄ እስካቀረቡ ድረስ ፍቺው ሊከለከል እንደማይቻልና ፍቺ ሊወሰን አይገባም የሚለውን ነጥብ መሰረት በማድረግ ብቻ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ እንደማይቻል በተሻሻለው ፌዴራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 112 ሆነ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 አንቀጽ 127 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። በሌላ በኩል ፍርድ ቤት የባልና ሚስትን ክርክር በሚያይበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ ሁኖ ካገኘው ባልና ሚስቱን በአንድነት ወይም በተናጠል ሲያነጋግር ወይም ጉዳዩን ሲመረምርና ምስክር ሲሰማ በዝግ ችሎት ያስችላል የሚለውን የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌ/አንቀጽ 110/ በመጥቀስ ጋብቻና ጋብቻ ፍቺ በውክልና ሊቀርብ አይችልም በማለት በተጠሪ የሚቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ ተጋቢዎችን የሚያነጋግራቸው አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ እንጂ የግድ ማናጋገር እንዳለበት የሚደነግግ ባለመሆኑ፤ጋብቻ በእንደራሴ መፈጸም በመርህ ደረጃ የማይቻል ቢሆንም ከተጋቢዎች አንደኛው ጋብቻው ለመፈጸም ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ በመግለጽ በግንባር ለመገኘት የማያስችለው ከባድ ምክንያት ሲያጋጥመው ጉዳዩ ለፍትህ ሚኒስትሩ ቀርቦ ሲረጋገጥ ጋብቻውን በእንደራሴ አማካኝነት መፈጸም እንደሚቻል በግልጽ በተሻሻለው ፌዴራል ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 12 ተደንግጓል። ጋብቻ ለመፈጸም በልዩ ሁኔታ በውክልና እንደሚቻል ህጉ እየፈቀደ የፍቺ ጥያቄ በውክልና ሊቀርብ አይችልም በማለት በተጠሪ በኩል የሚቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም። እዚህ ሊታይ የሚገባው ነጥብ የውክልናው ማስረጃ ህጋዊነት ነው። ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት የአመልካቹ ወኪል ሆነው የቀረቡት ሰው በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር በተሟጋችነት ሊቆሙ ስለሚችሉ ሰዎች በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለው ጥያቄ ነው።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሰረቱ በማናቸውም ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ለመከራከር ባለጉዳዩ ራሱ እንዲቀርብ የሚያስገድድ ሕግ ወይም በፍርድ ቤቱ የተሰጠ የተለየ ትዕዛዝ የሌለ በሆነ ጊዜ ባለጉዳዩ ራሱ ለመቅረብ የማይችል ወይም የማይፈቅድ ሲሆን ነገሩን ለማስረዳት፣ ለመከራከር፣ለሚጠየቀው ሁሉ በቂ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰው በዋናው ባለጉዳይ ተተክቶ በነገረ ፈጅነት፣በወኪልነት፣በጠበቃነት እንዲከራከር ለማድረግ እንደሚችል በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ.57 ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በዚሁ ሕግ በቁጥር 60፣61 እና 62 ስር የተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አበል ሳይሰጣቸው ስለሌላ ሰው ሆኖ በወኪልነት ወይም በነገረ ፈጅነት አቤቱታ ለማቅረብ፣ ለመከራከር፣ ለመሟገት እና ነገሩን ለመከታተል የሚችሉት የዋናው ባለጉዳይ ባለቤት፣ወንድም፣እህት፣ልጅ፣አባት ወይም አያት ስለመሆናቸው በቁጥር 58(1) ስር ተመልክቷል። በተያዘው ጉዳይ ስለአመልካቹ በመሆን ውክልና የተሰጣቸው የአመልካች ወንድም በመሆናቸው ከዋናው ባለጉዳይ ጋር በቁጥር 58(1) ከተመለከተው የዝምድና ግንኙነት መካከል አንዱን የሚያሟሉ ስለመሆኑ አከራካሪ ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን የውክልና ሰነድ ከውጭ ሀገር ተዘጋጅቶ የተሰጠ በመሆኑ ከሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንጻር መመርመሩ ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል። ከኢትዮጵያ ውጭ የተዘጋጁ ሰነዶች ትክክለኝነታቸው በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 1፣6፣23 እና 24 ድንጋጌዎች መሰረት በኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር እና በኢፌዴሪ የፍትህ ሚንስተር የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ጽ/ቤት መረጋገጥ እንዳለበት ተደንግጓል። አመልካች ለወንድሟቸው የሰጡት ውክልና ስልጣን በኢፌዴሪ ኢምባሲ ዋሽንግተን በቁጥር 05155/09 በቀን 14/07/2009 ዓ.ም የፊርማና ማህተም ትክክለኛነት ተረጋግጦ የተሰጣቸውን ውክልና የኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚንስተር በቁጥር 28456/10 በቀን 22/01/2010 ዓ.ም የፊርማ ማህተሙ ህጋዊነት ከተረጋገጠ በኋላ የኢፌዴሪ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በቁጥር ቅጽ/2330/10/2010 በቀን 22/01/2010 ዓ.ም ትክክለኛነቱ የተረጋገጠና የተመዘገበ የውክልና ማስረጃ መሆኑን በተጠሪ በኩል ማስተባበያ ያልቀረበበት መሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል። የተሰጠው ውክልና ማስረጃ ይዘትም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.58 እና በፍ/ብ/ህ/ቁ.2199 አመልካችን ፍቺን ጨምሮ በማናቸውም ጉዳዮች ወክሎ ለመከራከርም ሆነ ሌላ የህግ ባለሙያ ለመወከል እንደሚችሉ በውክልና ሰነድ ላይ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን ተገንዝበናል። በመሆኑም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ የውክልና ማስረጃው ፍትህ ሚንስተርና ውጭ ጉዳይ ሚንስተር ቀርቦ ማህተም ተደርጎ በባለስልጣን ፊርማ ተረጋግጦ የቀረበ ባለመሆኑ ሕጋዊነት የጎደለው ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው የቤተሰብ ህጉ የጋብቻ ፍቺ ክስ በወኪል ማቅረብ የማይከልክል ሁኖ እያለ እንዲሁም አመልካች ለወንድሟቸው የሰጡት ውክልና ማስረጃ የህጉን መስፈርት የሚያሟላ ሁኖ ተወካዩ በራሰቸው ወይም ጠበቃ በመወከል ክስ ለማቅረብና ለመከራከር የሚያስችላቸው ህጋዊ ውክልና በመያዝ ያቀረቡት ክስ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በወላይታ ሶዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 38955 ህዳር 4 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወላይታ ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 21387 ህዳር 19 ቀን 2010 ዓ.ም በትእዛዝ ያጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የወላይታ ሶዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

ቅ/ሀ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውርስ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ.ቁ. 152134

ህዳር 24 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ትግዕሥት ንጉሴ- የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ አሰፋ ንጉሴ
2 አቶ ሞላ ንጉሴ
3 አቶ አዳነ ንጉሴ — የቀረበ የለም
4 ወ/ሮ ሂሩት ንጉሴ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የነገሩ አመጣጥ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ከሥር 2ኛ አመልካች ሕፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ ጋር በመሆን ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ የአመልካቾች ወላጅ አባት አቶ ንጉሴ ቱሩፌ አመልካቾችንና ተጠሪዎችን ጨምሮ ስድስት ልጆችን መውለዳቸውን፣ ጥር 26 ቀን 2007 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን፣ አባታቸው ከመሞታቸው በፊት ለረጅም ጊዜ የካንሰር ህመምተኛ እንደነበሩ፣ ራሳቸውን በማያውቁበት ሁኔታ ውስጥ እያሉ 1ኛ ተጠሪ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ከሆኑት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቶ መኩሪያ አይተንፍሱ ጋር በመሆን መስከረም 6 ቀን 2007 ዓ/ም አስገድደው ኑዛዜ እንዲፈጽሙ ማድረጋቸውን ፣ ኑዛዜውም ትክክል ያልሆነና የሁሉንም ወራሾች መብት ያላከበረ መሆኑን፣ ተናዛዡም በተራ ቁጥር 5 እና 7 ላይ ጠቅሰው የተናዘዙት ንብረት በስማቸው የሌለ መሆኑን፣ እንዲሁም ኑዛዜው አመልካቾችን የመንቀል ውጤት ያለው በመሆኑ ኑዛዜው እንዲፈርስልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ሰኔ 15 ቀን 2008 ዓ/ም በጻፉት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አመልካቾች ኑዛዜው መኖሩን ሚች ከሞተበት ቀን ጀምሮ ያውቃሉ፣ ሚች ከሞተ 40 ቀን ሊሞላው ሳምንት ሲቀረው አመልካቾች በተገኙበት ኑዛዜው ተነቧል፣ በኑዛዜው መቃወሚያ ካላቸው በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት ኑዛዜው አይፀናም በማለት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችሉት እስከ ሶስት ወር ድረስ ነበር ፣ ነገር ግን አመልካቾች መቃወሚውን ያቀረቡት ኑዛዜው ከተነበበ ከአንድ ዓመት በኃላ ውርስ ሲጣራ ውርስ አጣሪው ጋር ነው፣ መቃወሚያውም ማቅረብ ካለበት የሚቀርበው ህጉ ባስቀመጠው ጊዜ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው፡፡ ስለዚህ መቃወሚያው በይርጋ ይታገዳል፡፡ አመልካቾችም ኑዛዜ ስለመኖሩ ከውርስ አጣሪ መሾም በፊት ያውቃሉ፡፡ በዚሁ ኑዛዜም ወራሽነታቸውን አስመስክረዋል፡፡ ኑዛዜውን የሚቃወሙ ከሆነ ይህንን ማቅረብ የሚችሉት የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ለሰጠው ለአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንጂ ለዚህ ፍርድ ቤት ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች ላቀረቡት መቃወሚያ አመልካቾች በሰጡት መልስ ኑዛዜው መኖሩን ያወቅነው ውርስ አጣሪ ዘንድ ነው፤ ኑዛዜው ተነበበ በተባለበት ቦታ አልነበርንም፡፡ ስለዚህ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ካወቅንበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን በህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ ላይ መቆጠር የሚጀምረው አካለ መጠን ከደረሰችበት ጊዜ አንስቶ ሊሆን ይገባል፤ የአዲስ አባባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾችን የኑዛዜ ወራሽ ያደረገው በወቅቱ ለፍርድ ቤቱ ቀርበው የነበሩት ጠበቃ ከአመልካቾች ባልተሰጣቸው ውክልና ያወጡትን ማስረጃ መሠረት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማድረግ ነው። የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች የኑዛዜ ይፍረስልኝ ጥያቄን የማየት ሥልጣን የላቸውም በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እንዲሁም ማስረጃዎችን መርምሮ በመዝገብ ቁጥር 56140 በሆነው በቀን 19/05/2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት ህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ ኑዛዜው ሲነበብ ክስ ለመመስረት የሚያስችል የእድሜ ደረጃ ላይ ባትደርስም ሞግዚትና አስተዳዳሪው የሆኑት ወ/ሮ ትግዕሥት ንጉሴ በቦታው የነበሩ መሆኑን የተጠሪዎች ምስክሮች በተሻለ ሁኔታ ስላስረዱ የሁለቱም አመልካቾች መብት በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት በይርጋ ይታገዳል ሲል ብይን ሰጥቷል።

ይህን ብይን ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች እና የሥር 2ኛ ይግባኝ ባይ ኤልሻዳይ ንጉሴ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል። የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ተቀብሎ ክርክራቸውን ከዳመጠ በኃላ በኮ/መ/ቁ. 193480 ጥቅምት 14 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት 1ኛ ይግባኝ ባይ /የአሁን አመልካች/ ያቀረቡት የኑዛዜ ይፍረስልኝ ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔን አጽንቷል። በሌላ በኩል የህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴን ይግባኝ በተመለከተ ክስ ሲመሰረት ዘጠኝ ዓመቷ የነበረ መሆኑ በመልስ ሰጪዎች /በአሁን ተጠሪዎች/ የተካደ አይደለም። የ2ኛ ይግባኝ ባይ እድሜ ይህ ከነበረ ደግሞ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1846 እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 57114 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው አካለ መጠን ከደረሰች በኃላ ነው። ህጉ ሞግዚት ካለ መደበኛው የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ይፈጸምባቸዋል በማለት አልደነገገም። በሞግዚቶች ቸልተኝነትና ተገቢ ያልሆነ ሥራ መብታቸው እንዳይጎዳ በሚል እሳቤ ነው። በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት የሁለተኛ ይግባኝ ባይ ጥያቄም በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ብይን ተገቢ ስላልሆነ 2ኛ ይግባኝ ባይና መልስ ሰጪዎችን ያሉዋቸውን ሌሎች ክርክሮች እና ማስረጃዎች ሰምቶ የመሰለውን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲወስን በማለት በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት መልሶታል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካች አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ፡- ኑዛዜው ከሩብ በላይ ጉዳት አድርሶብኛል ሊፈርስ ይገባል በሚል ለቀረበ ክስ የፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት አድርገው የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን እና ውሳኔ ተገቢ አይደለም ፣ የፍትሓብሔር ህግ አንቀጽ 973 ተፈጻሚ የሚሆነው ውርስ ተከፍቶ ውርስ አጣሪ ከተሾመ በኃላ የሚፈጸም ድንጋጌ ሆኖ እያለ ኑዛዜ በማን እና መቼ ተነሷል የሚለውን ነጥብ የሥር ፍርድ ቤቶች በፍትሓብሄር ህግ ቁጥር 946፣ 965 አንጻር ሳይመረምሩ ብይን እና ውሳኔ መስጠታቸው አግባብነት የለውም፣ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በከፊል የተሻሻለው ውሳኔ ከአመልካች ውጪ ክርክሩ እንዲቀጥል ማድረጉ የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 40 ድንጋጌን ያላገናዘበ ነው፣ ከኑዛዜው ተጠቃሚ የሆነ ሰው ኑዛዜው እንዳይፈርስ የተንኮል ሥራ የሰራ መሆኑን፣ ከጠበቃ ጋር ተመሳጥሮ የሌሎች ወራሾች መብት ሲያሳጣ የነበረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በቀረበበት ሁኔታ፣ በዚሁ ተግባሩ በወንጀል ተከሶ እንዲከላከል ብይን በተሰጠበት ሁኔታ እሱ /1ኛ ተጠሪ/ ቀጥሮ የሚያሰራቸው ሠራተኞች እና ባለቤቱ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ብቻ መሠረት ተደርጎ የተሰጠ ፍርድ መሠረታዊ ማስረጃ ምዘና ግደፈት ያለበት ስለሆነ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻር እና በኑዛዜ ላይ ተገቢውን ህጋዊ ክርክር እንዲያቀርብ እንዲደረግልኝ እንዲሁም በዚህ የሰበር ቅሬታ ምክንያት ያወጣሁትን ወጪና ኪሳራ እንዲተኩልኝ እንዲወሰንልኝ እጠይቃለሁ የሚል ነው።

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ አመልካች ተደረገ ስለተባለው ኑዛዜ አላውቅም እያሉ ኑዛዜውን በወቅቱ ስላልተቃወሙ ይርጋ ያግዳቸዋል የመባሉ እና ኑዛዜው አመልካችን ከውርስ የሚነቅል ነው የሚለው አቤቱታም ከፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1123 (1) አንጻር ሳይታይ የመታለፉ አግባብነት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል።

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው 1ኛ ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በጠበቃቸው በኩል በቀን 20/7/2010 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን አመልካችም ሚያዚያ 16 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል። 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ መጥሪያ ደርሶዋቸው ቀርበው ለመከራከር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሚያዚያ 17 ቀን 2010 ዓ/ም በተሰጠው ትዕዛዝ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል።

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ወይስ አልተፈጸመበትም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል። ለክርክሩ ምክንያት የሆነውንና መስከረም 6 ቀን 2007 ዓ/ም ከሚች ተሰጠ የተባለውን ኑዛዜ በተመለከተ አመልካች ያወቁት ውርስ እንዲጣራ ሲደርግ ውርስ አጣሪ ዘንድ እንደሆነ፣ ኑዛዜውን ሚች ያልሰጡትና ሀሰተኛ መሆኑን፣ ከአመልካችና ከህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ ለጠበቃ ውክልና ሳይሰጥ ውክልና እንደተሰጠ በማድረግ ለአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበው ኑዛዜውን መሠረት በማድረግ ወራሽነትን ተጠሪዎች ማስወሰናቸውን፣ ይህን ሀሰተኛ ተግባር የፈጸሙ ጠበቃም ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አቤቱታ ቀርቦባቸው በጉባኤ ከታየ በኃላ በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 24/3/ለ/2 መሠረት 2 ዓመት ከ6 ወር ከጥብቅና አገልግሎትና የማማከር ተግባር እንዲታገዱ የተደረገ መሆኑን፣ ጠበቃዋ ያስወሰኑት የወራሽነት ማስረጃን በተመለከተ ውሳኔውን ለሰጠው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች /ህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴን ጨምሮ/ አቤቱታ አቅርበው በአሁን አመልካች እና በህፃን ኤልሻዳይ ላይ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል የከተማው ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 2940/07 በቀን 9/2/2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠረዘ መሆኑን፣ እንዲሁም የአሁን 1ኛ ተጠሪ እና ጠበቃዋ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ተከሰው እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠ መሆኑን አመልካች አጥብቀው ይከራከራሉ፡፡ ጠበቃዋ በፈጸሙት ድርጊት ጉባኤው ቅጣት የወሰነባቸው መሆኑን እንዲሁም ከአሁን አመልካች እና ከህጻን አልሻዳይ ንጉሴ ውክልና ሳይሰጣቸው እንደተሰጠ በማድረግ ጠበቃዋ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኑዛዜውን መሠረት በማድረግ አቤቱታ አቅርበው ያስወሰኑት ውሳኔ አመልካችን እና ህጻን አልሻዳይ ንጉሴን በሚመለከት የተሠረዘ መሆኑን ይህ ችሎት ተመልክቷል፡፡

በመሠረቱ የአሁን አመልካች እና የሥር 2ኛ አመልካች ህፃን ኤልሻዳይ አቤቱታ ኑዛዜው በማስገደድ የተደረገ እንዲሁም ከውርስ የነቀለ በመሆኑ እንዲፈርስ የሚል ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን የተጠሪዎች ክርክር አመልካቾች ኑዛዜው ሲነበብ በቦታው ላይ ስለነበሩ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት በ3 ወር ውስጥ ኑዛዜው እንዲፈርስ ጥያቄ ስላልቀረበ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ ከዚህ ክርክር ተነስተን የአሁን አመልካችም ሆነ የህፃን አልሻዳይ አቤቱታ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት የሚታይ ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል፡፡ የፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 ስለ ኑዛዜ መነበብ እንዲሁም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው እንዲፈርስ አቤቱታ የሚያቀርቡበትን ሥርዓት እና ጊዜውን በሚመለከት የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ኑዛዜው ከውርስ ነቅሎኛል /ነቅሎናል/ በማለት ኑዛዜው እንዲፈርስ የሚቀርብን ወይም የቀረበን አቤቱታን የሚመለከት አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካችም ሆኑ ይርጋው አያግድም ተብሎ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጣት ህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ መሠረታዊ አቤቱታ ይዘት ኑዛዜው ከውርስ የመንቀል ውጤት ያለው በመሆኑ እንዲፈርስ የሚል ነው፡፡ ይህ የዳኝነት ጥያቄ ሊታይ የሚገባው በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1123 መሠረት ነው እንጂ በተጠቀሰው ህግ አንቀጽ 973 መሠረት አይደለም፡፡ የክርክሩ ይዘት እንደሚያመለክተው የአመልካቾች አባት ኑዛዜ ሠጡ የተባለው በ6/7/2007 ዓ/ም ሲሆን የሞቱት ደግሞ በ26/1/2007 ዓ/ም ነው፡፡ ኑዛዜው እንዲፈርስ ዳኝነት የተጠየቀው ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ/ም ነው፡፡ ይህም በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1123 /3/ መሠረት ጊዜው ያላለፈበት መሆኑን በግልጽ የሚያመለክት ነው፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆኑም የአመልካች ጥያቄ ይህን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መታየት ሲገባው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 973 ድንጋጌ ተወስዶ አቤቱታው በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠው ብይንም ሆነ ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 82525 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን ይህም ትርጉም በየትኛውም ደረጃ በሚገኙት ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 494/97 አንቀጽ 2(1) በግልጽ ተደንግጓል።

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ብይንም ሆነ ውሳኔ የአቤቱታውን ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ አመልካችን ኑዛዜው ከውርስ የነቀለ ነው ወይስ አይደለም? የነቀለ ነው የሚባል ከሆነ ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? የሚለው ጭብጥ ተይዞ ጉዳይ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል።

በመጨረሻም የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ነገሮችን በአግባቡ ሳያጤኑ የሰጡት ብይንም ሆነ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ውሳኔ

1.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 193480 ጥቅምት 14 ቀን 2010 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 (1) መሠረት ተሻሽሏል።

2.የህፃን ኤልሻዳይ ንጉሴ አቤቱታ በይርጋ አይታገድም ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል።

3.የአሁን አመልካች አቤቱታ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 973 መሠረት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

4.የአመልካች አቤቱታ በይርጋ ሊታገድ የሚችልበት ህጋዊ መሠረት ስለሌለው አመልካችን ኑዛዜው ከፍ/ህ/ቁ 1123 አንፃር ሲታይ አመልካችን ከ1/4ኛ በላይ የጐዳ ውርስ ነው ወይስ አይደለም? የጐዳ ነው የሚባል ከሆነ ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? የሚለውን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አጣርቶ እንዲወስን በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡

5. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

6. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

7. ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ፋ/ዘ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች

ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 153231

መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ እልፊ ደበላ- ቀረቡ

2. ወ/ሮ ደስታ ደበላ - ቀረቡ

3. ወ/ሮ ሽብሬ ደበላ - ቀረቡ

4. ወ/ሮ ትርንጎ ደበላ - ቀረቡ

5. ወ/ሮ መገርቱ ደበላ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ንጉሴ ደበላ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ወጫሌ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው። በስር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ። የአመልካቾች ክስ ይዘትም ሟች አቶ ደበላ ሄዩ በቀን 13/12/2003 ዓ.ም በሞት ከዚህ አለም የተለዩ መሆናቸው በመግለጽ ተጠሪ ከዚህ በፊት የተወሰነልን መልሶ በመያዝ የባለይዞታነት ማስረጃ ወስዶበት ድርሻችንን ስለከለከለን እንዲሁም የአባታችን ይዞታ ረስተን ውሳኔ ሳይሰጥበት ሳናውቅ የአባታችን የመሬት ይዞታ በእጁ ይዞ ስለሚገኝ ድርሻቸውን ተከፍሎ እንዲሰጠን ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል። በመጀመሪያ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ የሰጠው ውሳኔ እና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም የአሁን ተጠሪ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ በኋላ በቀን 28/02/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር በሽማግሌዎች አማካኝነት ከዚህ በፊት ተከፋፍሎላቸው የነበረውን ተጠሪ መልሶ ይዞባቸዋል? ወይስ አልያዘም? ተደብቆ ያለው ይዞታ አለ? ወይስ የለም? ይዞታው አመልካቾች ሳያውቁ ከውርስ ክፍፍል የቀረ ነው ? ወይስ እያወቁ ነው የተውት? ይዞታው የሚገኝበት መደበቅ የሚችልበት ቦታ ነው? የሚሉ ነጥቦች በግራ ቀኙ ማስረጃ ከተጣሩ በኋላ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረት ለወረዳ ፍርድ ቤት መልሶታል።

ፍርድ ቤቱም የተዘጋው መዝገብ አንቀሳቅሶ በተመለሱት ነጥቦች ላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ተጠሪ ያለ አመልካቾች ፈቃድ እነሱ ሳያውቁ በይዞታቸው ላይ በሀይል ቤት የሰራ ስለሆነ በተጠሪ ወጪ በክሱ ተራ ቁጥር 1ኛ ላይ የሚገኝበት ቦታ እና አዋሳኙ በተገለጸው ይዞታ ላይ የተሰራውን ቤት በማፍረስ ለከሳሾች/አመልካቾች/ ይዞታውን እንዲለቅ፤በክሱ ከ2ኛ እስከ 6ኛ እና 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ይዞታዎች የወላጅ አባታቸው መሆናቸውና፤ ከሳሾች የይዞታዎቹ አዋሳኝ የማያውቁ መሆናቸውና እናታቸው ጋር በመሆክ ጡሪ ከተማ ያደጉ ስለሆነ ማወቅ አለመቻላቸውን እና የተደበቀ መሆኑን ስለተረጋገጠ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1103 በመጠቀስ ወራሾች እኩል እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን ተጠሪ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አቤቱታቸው ለሰሜን ሽዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ሁኖ አልተገኘም በማለት በውሳኔ አጽንቶታል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸው አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በማሻሻል በክሱ ተራ ቁጥር 1ኛ እና 7ኛ የተጠቀሱት ይዞታዎች በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ በማጽናት በክሱ ተራ ቁጥር 2-6 እና 8ኛ የተመለከቱት ይዞታዎች ላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ለአመልካቾች ሊያካፍል አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት የጉዳዩ አከራካሪ የሆነው የውርስ ይዞታ ተረስተው የታለፉና በድጋሚ መጠየቁ አግባብነት ያለው ነው ብለው የወሰነውን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሬት የማይረሳ ነው ልጠይቁ አይገባም ያለበት አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾችና ተጠሪ የሚች ወላጅ አባታቸው አቶ ደበላ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸው፤አመልካቾች በተጠሪ እጅ የሚገኙትን የውርስ ንብረትና ይዞታዎች ክፍፍል እንዲደረግ ዳኝነት በመጠየቃቸው ምክንያት ግራ ቀኙ በስምምነት ክፍፍል ማድረጋቸው በመግለጽ ነገር ግን ከውሳኔ በኋላ ለአመልካቾች በደረሳቸው ይዞታ ላይ ተጠሪ በሀይል ቤት በመስራቱ እንዲሁም የተረሱ ይዞታዎች ድርሻቸው እንዲያካፍላቸው ዳኝነት በመጠየቃቸው ምክንያት የግራ ቀኙ ክርክር ከተደረገ በኋላ ተጠሪ በአመልካቾች ድርሻ ላይ ቤት መስራቱን በማረጋገጥ የሰራውን ቤት በራሱ ወጪ አፍርሶ ይዞታው ለአመልካቾች እንዲለቅ መስጠቱን ተገንዝበናል በዚህ ረገድ የቀረበ አቤቱታ የለም፡፡ አከራካሪ የሆነው አመልካቾች በክሳቸው ከ1ኛ እስከ 6ኛ እንዲሁም 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱትን ይዞታዎችን በሚመለከት ነው፡፡ አመልካቾች ከውሳኔ በኋላ ክስ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማቅረብ በምክንያትነት የጠቀሱት የውርስ ይዞታዎች የሆኑትን መኖራቸው ባለማወቅቸው መሆኑን የተረሱ የውርስ ሀብት መጠየቅ እንደሚቻል የፍ/ብ/ህ/ቁ.1103፤1104 ስለሚፈቅድ በዚሁ አግባብ የቀረበ ክስ መሆኑን በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በተጠሪ እጅ የሚገኙትን ክፍፍል ሳይደረግባቸው የቀሩትን እኩል እንዲከፋፈሉ የሰጠው ውሳኔ በመቃወም ጉዳዩ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ተጠሪ ጉዳዩ ውሳኔ ካገኘ በኋላ በድጋሚ የቀረበ ነው በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር በፍሬ ነገር ዳግም ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረት ለስር ፍርድ መልሶታል። የተመለሰለት ፍርድ ቤትም የተዘጋው መዝገብ አንቀሳቅሶ የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ለክርክር ምክንያት የሆኑት ይዞታዎች ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ ሲል የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፀና ቢሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 216/3/ አንጻር ተመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር በክሱ ከ1ኛ እስከ 6ኛ እና 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ይዞታዎች ተጠሪ ለአመልካቾች ሊያካፍል አይገባም ሲል ወስኗል። የአመልካች አቤቱታ መሰረት ያደረገው በስር ፍርድ በተጠሪ ያልተነሳ ጉዳይ በማንሳት የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በአግባቡ አጣርቶ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

በመሰረቱ አንድ ተከራካሪ ወገን ከአንድ የክስ ምክንያት የመነጨ የመብት ጥያቄ ካለው እና በአንድ ክስ የሚጠቃለል የክስ ምክንያት ሆን ብሎ በመቀነስ ያስቀረ ከሆነ በድጋሚ በተመሳሳይ ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 216 /3/ ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት የምንገነዘበው ነው። የአንድ ክስ ምክንያት መከፋፈል ባለጉዳዮች ጊዜ፣ ወጪና ጉልበት አላስፈላጊ ጫና እና የማጉላላት ውጤት እንዳለው መረዳት ይቻላል። የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ/ዓይነተኛ ዓላማ /main purpose / ጉዳዮችን በህግ አግባብ በመምራት በተቻለ አጭር ጊዜ ውጤታማ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፍትሃዊ ውሳኔ መስጠት ስለመሆኑ ከአጠቃላይ የህጉ ድንጋጌዎች የምንረዳው ነው። ከአንድ ጉዳይ የመነጨ የመብት ጥያቄ የሚያቀርቡ ተከራካሪ ወገኖች ክሱን ለመመስረት መነሻ የሆነባቸው ጉዳይ አጠቃልለው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ከአንድ የክስ ምክንያት የሚመነጭ ክርክር ከፋፍለው ከቀረቡ /spilting of claim/ በድጋሚ በተመሳሳይ ጉዳይ ሌላ ክስ የማቅረብ መብት የሚሰጣቸው አይደለም፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.216 መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ መመርመሩ ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በሁለት ምክንያት ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ አንደኛው ይህ ጉዳይ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው ሁለት ጊዜ መሆኑን ከክርክሩ ሂደትና ከውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ላይ በተጠሪ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 216 መሰረት በማድረግ ያቀረቡት ክርክር ካለመኖሩም በላይ ጉዳዩ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ጉዳዩ እንደገና ወደ ፍሬ ነገር ገብቶ እንዲጣራ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረት ሲመልስ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.216 ጥያቄ አልነበረም፡፡ አንድ ተከሳሽ ለቀረበለት ክስ በዝርዝርና በግልፅ መቃወምና መካድ እንደለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.83 ተመልክቷል፡፡ በይግባኝ ደረጃም ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.329/1/ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳውን ክርክርና ያልቀረበውን አዲስ ነገር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መቀበል እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182/2/ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎቹ በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልፅ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ መስጠት እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የክልሉ ሰበር ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፤ በሌላ በኩልም የውርስ ንብረት ክፍያው ከተደረገ በኋላ በክፍያ ውስጥ ያልገቡ በውርሱ ንብረት ውስጥ ገብተው የሚቆጠሩ አዲስ ሀብቶች የተገኙ እንደሆነ አዲስ የክፍያ ስርዓት መፈጠም እንደሚቻል ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1103 እና 1104 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በወጫሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 24658 ሚያዚያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም እና በሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 55692 ግንቦት 24 ቀን 2009 ዓ.ም ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 268679 ህዳር 4 ቀን 2010 ዓ.ም በውሳኔ የተሻሻለው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በክሱ በ1ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰውን የይዞታ መሬት ተጠሪ ለአመልካቾች እንዲለቅ የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. በክሱ ከ2ኛ እስከ 6ኛ እንዲሁም 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ይዞታዎች የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክሱ ከ2ኛ እስክ 6ኛ እንዲሁም 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ይዞታዎች አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ በማለት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ/ 159474
ህዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
መስጠፋ አህመድ
አብርሃ መሰለ
ፈይሳ ወርቁ
ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ እንደገና ተሾመ- የቀረበ የለም፡፡
ተጠሪ፡- አቶ ረታ መልካ - ታልፏል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ኑዛዜን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ሟች እማሆይ ውቢቱ ኃ/ማሪያም በ3/09/2009 ዓ/ም አድርገውት ያለፉት ኑዛዜ መሠረት ተደርጐ የወራሽነት ማስረጃ ይሰጣቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው ሶስት ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ጠይቀው ሟች ወላጅ እናታቸው መሆናቸውን፣ የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን በፍርድ ቤት ያረጋገጡ መሆኑን፣ አመልካች አለኝ የሚሉት ኑዛዜም ሕጋዊ አይደለም የሚሉበትን ምክንያት ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ተጠሪ ጣልቃ ገብተው በአቀረቡት መከራከሪያም የአሁኑ አመልካች አለኝ የሚሉትን መከራከሪያ ነጥብ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በፍትሃ ብሔር ሕጉ መሰረት ኑዛዜ ይመዝገብልኝ፣ ይሻርልኝ፣ እንዲሁም መጠኑ ይቀነስልኝ በማለት ዳኝነት ከሚጠየቅ በስተቀር ይረጋገጥልኝ መባሉ የህግ ድጋፍ የለውም በሚል ምክንያት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ላይ ከአሁኑ አመልካች ይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በስር ፍርድ ቤት ብይን ላይ ጉድለት የለውም በማለት በትእዛዝ የአመልካችን ይግባኝ የሰረዘ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎትም በበታች ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ሲል የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የስር ፍርድ ቤት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የኑዛዜ ወራሽነት እንዲረጋገጥላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀብሎ ምስክሮችን ከሰማ በኋላ በተጠሪ ጣልቃ ገብነት መነሻ የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ ተብሎ ዳኝነት አይጠየቅም ሲል መዝገቡን መዘጋቱም ሆነ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳያርሙ መቅረታቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸውም በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው እንዲታለፍ ተደርጎአል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ዳኝነት እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ፍርድ ቤት የሚቀርብ አይደለም በማለት የሰጡት ዳኝነት የሕግ መሰረት ያለው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከተው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የታቻለው አመልካች ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት ሟች አደረጉ በተባለው ኑዛዜ መሠረት በማድረግ የወራሽነት ማስረጃ (የምስክር ወረቀት) ይሰጠኝ (የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 996(1) በማለት መሆኑን፣ ይኼው መነሻ ተደርጎም የአመልካች ምስክሮች ሁሉ ተሰምተው የነበሩ መሆኑን፣ ከዚህ በኋላም የአሁኑ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ሕጋዊ አይደለም የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው የተከራከሩ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በፍትሐብሔር ሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርበው ክስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ከሚቀርበው ጥያቄ (አቤቱታ) የተለየ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ጥያቄዎቹ የተለያዩ በመሆናቸውም የተለያዩ ውጤት ነው ያላቸው፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 996(1) እንደተደነገገው ወራሽ ነኝ የሚል ማንኛውም ሰው የወራሽነት ምስክር ወረቀት ይሰጠው ዘንድ ለፍ/ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከመቀበሉ በፊት ጠያቂው ማስረጃዎቹን ሁሉ እንዲያቀርብ በማድረግ እና አስፈላጊ መስሎ የታየውን ዋስትና እንዲሰጥ በማስገደድ ጭምር ዋስትናውን ካገኘ በኋላ የተጠየቀውን የምስክር ወረቀት ሊሰጥ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 996(2) ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቱ የአመልካቹን ጥያቄ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት በማድረግ ሰጥቶት የነበረው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ሊሰረዝው እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁ.998(1) የተቀመጠው ድንጋጌ ያመለክታል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ማስረጃው ከተሰጠ በኋላ ማስረጃው የተሰጠው ከህግ ውጪ ነው የሚል ወገን ክርክሩን ከአቀረበ ነው። ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ እንደሚቻለው የምስክር ወረቀቱ በጠያቂው አቤቱታ መነሻነት የሚሰጥ ቢሆንም የተሰጠው ያለአግባብ ነው የሚል መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩንና መቃወሚያው ተገቢ ሆኖ ከተገኘም የምስክር ወረቀቱ የሚሰረዝ መሆኑን ነው።

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበት ፍ/ቤት ጥያቄውን ተቀብሎ የምስክር ወረቀቱን ከመስጠቱ በፊት ይኼው ማስረጃ እንዳይሰጥ ተጠሪ ተቃውሞ አቅርበዋል። በሕግ አግባብ የተደረገ ኑዛዜ በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የፍርድ ቤትን ቡራኬ የማያስፈልገው መሆኑን ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17058 እና በሌሎች መዝገቦች አስገዳጅ የህግ ትርጉም መስጠቱን ይታወቃል። ይህ የሚሆነው ግን ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም የሚል ተከራካሪ ወገን በቀረበበት አግባብ አይደለም። ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17058 የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የኑዛዜውን ህጋዊነት የሚቃወም ወገን በንብረት ክርክር ጊዜ ክርክሩን ሊያነሳ የሚችል መሆኑን የሚያመላክት ነው። ይህም የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማትና ፍትህ የማግኘት መብትን ሁሉ ያገናዘበ ነው ሊባል የሚችል ነው። በመሆኑን ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ጥያቄ በፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ እስከሆነ ድረስ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን ባከበረና የሥነ ስርዓት ሕጉን መሰረታዊ አላማ ባገናዘበ መልኩ ሊስተናገድ ይገባል።

በሌላ በኩል የኑዛዜ ወራሽነት እንዲረጋገጥለት አቤቱታ አቅርቦ ማስረጃ ያሰማ ወገን ማስረጃውን ከማግኘቱ በፊት ማስረጃው እንዳይሰጥ የሚል ተከራካሪ ወገን ከቀረበ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር በሕጉ አግባብ ተመልክቶ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባው እንጂ ከመነሻውም የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ የሚል አቤቱታ መቅረብ አልነበረበትም በማለት መዝገቡን ሊዘጋው የሚገባው አይደለም። ምክንያቱም ማስረጃው እንዳይሰጥ የሚል ወገን ቀርቦ ስለኑዛዜው ፎርማሊቲ ሳይሆን ስለኑዛዜው ሕጋዊነት (ኑዛዜው የሚሻርባቸውን ወይም ውድቅ የሚሆንባቸውን ምክንያቶች በሚመለከት) ክርክር ከአነሳ በዚህ ረገድ ጭብጦችን ይዞ ተገቢውን ዳኝነት መስጠትን የሚጠይቅ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነውና፡፡ ስለሆነም የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ የሚለው ጥያቄ በፍርድ ቤት እንዲቀርብ ሕጉ የግድ አይልም ሲባል ከኑዛዜ ፎርማሊቲ ጋር ተያይዞ የሚታይ እንጂ ስለኑዛዜው ሕጋዊነት ጭምር ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የኑዛዜ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ በሚል አቤቱታ በተከራተ መዝገብ ላይ ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም የሚል ተከራካሪ ወገን ከቀረበ ደግሞ ፍ/ቤቱ ወደ ኑዛዜው ይዘት እና ሕጋዊነት ሁኔታ ገብቶ ውሳኔ መስጠትን የግድ የሚል በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን በሕጉ አግባብ በመስማትና በሚገባ በማጣራት ተገቢውን ዳኝነት መስጠት ስነ ስርዓታዊ እንጂ በንብረት ክርክር ጊዜ የሚታይ ነው ተብሎ የሚታለፍ አይደለም፡፡ ክርክሩ በንብረት ክርክር ጊዜ የሚታይ ነው ብሎ መዝገቡን መዝጋትም ክርክሮች በአነስተኛ ወጪ፣ በተፋጠነ ጊዜና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መሰጠት አለባቸው ከሚለው የስነ ስርዓት ሕጉ መሰረታዊ ዓላማ ጋርም አብሮ የማይሄድ በመሆኑ ተገቢነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 07129 በ3/05/2010 ዓ/ም ተሰጥቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28578 በ22/05/2010 ዓ/ም፣ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 27964 በ25/08/2010 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 07129 ቀጥሎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት እንዲሁም አስፈላጊ ሁኖ ሲያገኘው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማስቀረብና ክርክሩን ስነ ስርዓቱ በሚፈቅደው አግባብ ጭምር በመመራት በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጸፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር---146457

ቀን-ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘቢባ መሳ

ተጠሪ፡- አቶ አማን በሪሶ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የከተማ ቦታ ይዞታ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በአዳማ ከተማ 01 ቀበሌ ዉስጥ የሚገኘዉን የካርታ ቁጥሩ 10690/06 የሆነዉ 180 ካ.ሜ የመኖሪያ ቤት ቦታ በአዳማ ከተማ መስተዳድር ተሰጥቶ በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘዉን ተጠሪ ምንም መብት ሳይኖረዉ ቦታዉ ላይ ቤት መስራቱን አይቼ ግንባታዉን እንዲያቆም ብጠይቀዉም ፈቃደኛ ስላልሆነ ግንባታዉን በራሱ ወጪ አፍርሶ ይዞታዉን ይልቀቅልኝ የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት አስመልክቶ አመልካች መንግስት አካል ጋር በመቅረብ በዉክልና ቁጥር 052125 በቀን 01/02/2008 ዓ.ም ለአቶ ፋአድ ጀማል መሳ ይዞታዉንና ንብረቷን እንዲሸጥ፣ እንዲለዉጥ፣ ለ3ኛ ወገን በማንኛዉም ሁኔታ እንዲያስተላልፍ ዉክልና ሰጥታዉ፤ እሱም ዉክልና አቶ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አህመድ ለሚባል አሳልፎ ሰጥቶ ውክልናዉ ሕጋዊ መሆኑን አረጋግጩ በቀን 05/07/2008 ዓ.ም በተጻፈ የግዥ እና ሽያጭ ዉል በብር 250,000 ተስማምቼ ገዝቼ ዉሉም ስልጣን ባለዉ አካል ጸድቆ የሊዝ ዉሉ ወደ ስሜ ተዛዉሮ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶኝ ባለይዞታ የሆንኩበትና አመልካች ሳይቃወሙ የገነባሁት ቤት ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ መርምሮ ተጠሪ ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ አመልካች ስልጣን ባለዉ አካል ፊት ለመሸጥ ዉክልና ከተሰጠዉ ሰዉ ጋር ተዋዉሎ የገዛና በአመልካች ስም የነበረዉ ወደ ተጠሪ ተዘዋዉሮና ተመዝግቦ የሚታወቅ በመሆኑ እንዲሁም አመልካች ከኢሜግሬሽን እና የዜግነት ጉዳዮች ጽ/ቤት ያቀረቡት ማስረጃም ቢሆን ከአመልካች ጋር ሳይሆን ከአመልካች ተወካይ ጋር ዉሉ የተደረገ በመሆኑና ተጠሪ አመልካች ከአገር መኖር አለመኖሯን የማወቅ ግዴታ የሌለዉ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ይዞታዬን በሕገ-ወጥ መንገድ ይዟል በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ ጉዳዩን የተመለከተዉ የአዳማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም አቤቱታዉ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ዉሳኔዉን ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ የመኖሪያ ቤት ቦታዬ እንዲሸጥም ሆነ እንዲለወጥ የሰጠሁት ሕጋዊ ዉክልና እንደሌለ እየተከራከርኩ እና ዉክልናዉ ተሰጥቶኛል በተባለበት ወቅትም ሀገር ዉስጥ ያልነበርኩ መሆኔን በመግለጽ የኢሚግሬሽን እና የዜግነት ጉዳዮች ቢሮ በቀን 22/03/09 ዓ.ም ለአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመግለጽ ተጽፎ እያለ ጉዳዩ በሚገባ ሳይጣራ ሀሰተኛ በሆነ ዉክልና ስሙ ከአመልካች ጋር የሚመሳሰል በመሆኑ ብቻ ተጠሪ በዚህ ዉክልና መሠረት በግዢ ዉል የያዘዉ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ፍትህ ቢሮ በቀን 15/02/2009 ዓ.ም ለወረዳዉ ፍ/ቤት በጻፈዉ ደብዳቤ አመልካች በአካል ቀርባ የዉክልና ቁጥሩ 052125 የሆነ በቀን 01/02/2008 ዓ.ም ዉክልና ሰጥታለች በማለት ስለገለጸ ብቻ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ዉክልና ሰጥታለች በተባለበት ቀን በአገር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያልነበርኩ መሆኔን ስልጣን ከተሰጠዉ አካል በተጻፈ ደብዳቤ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ዉሳኔዉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይሻርልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ዉክልናዉ ተሰጠ በተባለበት ጊዜ በሀገር ዉስጥ አልነበርኩም በማለት ከኢሚግሬሽን የተጻፈ መግለጫ ያቀረበችዉና በዉክልናዉ ላይ ያለዉ ፊርማ በፎረንሲክ እንዲመረመር የጠየቀችዉ በስር ፍ/ቤት የታለፈበትና ዉድቅ የተደረገበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ከኢሚግሬሽን የመጣ ደብዳቤ እና የፎረንሲክ ምርመራን ከፍትሕ ቢሮ ከመጣዉ ደብዳቤ ጋር አመሣዝኖ ዉሳኔ መስጠት የስር ፍ/ቤት ማስረጃን የመመዘን ስልጣን እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላልሆነ አቤቱታዉ ዉድቅ ይደረግልኝ፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በሕገ-ወጥ መንገድ ያለእኔ ፈቃድ የተደረገ የሽያጭ ዉል ይፍረስልኝ የሚል እስካልሆነ ድረስ የሚያዘዉ ጭብጥ ከቀረበዉ ክስ አንጻር ተጠሪ ንብረቱን የያዘዉ በሕገ-ወጥ መንገድ ነዉ ወይስ በሕጋዊ መንገድ የሚለዉ ነዉ፡፡ ለዚህ በማስረጃነት ያቀረብኩት አመልካች እራሷ ለወንድሟ የሰጠችዉን ዉክልና፣ ወንድሟ ለአቶ አህመድ የሰጠዉን ዉክልና፣ በእኔና በ2ኛ ተወካይ መካከል የተደረገ ሕጋዊ የሽያጭ ዉል እንዲሁም የሊዝ ዉል፣ በስሜ የተሰጠኝ ካርታና ፕላን እና የግንባታ ፈቃድ ነዉ፡፡ ዉክልናዉ ሕጋዊ ስለመሆኑ የፍትህ ቢሮ እና ማዘጋጃ ቤቱ ተጠይቆ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህ መሠረት ተደርጎ ማስረጃ ተመዝኖ የተሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህትት ተፈጽሞበታል የሚባል አይደለም፡፡ ኢሚግሬሽን መስሪያ ቤት በ01/03/2009 ዓ.ም በጻፈዉ ደብዳቤ ላይ በግልጽ እንዳመለከተዉ አመልካች በአካል ቀርባ አገር ዉስጥ ስለመኖሯ አረጋግጦ ሳይሆን ካላቸዉ ዳታ ዉስጥ ባደረገዉ ማጣራት መሆኑን ገልጽዋል፡፡ ይህ ማስረጃ በአካል ቀርባ ከሰጠችዉ ዉክልና ጋር ተመዝኖ የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ፡፡ በ01/03/2009 ዓ.ም በተጻፈዉ ደብዳቤ አመልካች በ5/03/2014 ወደ ሮም መሄዷን የገለጸ ሲሆን በ22/03/2009 ዓ.ም በጻፈዉ ደብዳቤ ላይ ደግሞ አመልካቿ በ09/02/2014 ወደ አገር ዉስጥ ገብታ በ05/06/2014 ከአገር መዉጣቷን ወይም ካናዳ መሄዷንና አገር ዉስጥ ተመልሳ ያልገባች መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይህም እርስ በርሱ የሚጋጭ ነዉ፡፡ በፎረንሲክ ፊርማዉ መጣራት ነበረበት የሚለዉም ቢሆን ዉክልናዉ የመንደር ዉል ሳይሆን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጣን ከተሰጠዉ የመንግስት አካል ተረጋግጦ የቀረበ በመሆኑ ክርክሩ ተገቢነት የለዉም። ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ይጽናልኝ የሚል ነዉ። አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል።

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል። መርምረን እንደተረዳነዉ በስር ፍ/ቤት አመልካች ክስ ያቀረቡት ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ ይዞታዬን በመያዝ የገነባዉን ግንባታ በራሱ ወጪ እንዲያፈርስ የሚጠይቅ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ይዞታዉ አስቀድሞ የአመልካች የነበረ ቢሆንም በሕጋዊ መንገድ የዉክልና ስልጣን ካለዉ ሰዉ ጋር ተዋዉሎ መግዛቱንና ሕጋዊ ባለይዞታ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል። የስር ፍ/ቤትም አመልካች ስልጣን ባለዉ የመንግስት አካል ጋር ቀርባ የዉክልና ቁጥሩ 052125 በሆነ ጥቅምት 01 ቀን 2008 ዓ.ም ለአቶ ፉአድ ጀማል ሙሳ ይዞታዉንና ንብረቱን እንዲሸጥ፣ እንዲለዉጥና ለ3ኛ ወገን በማንኛዉም መንገድ እንዲያስተላልፍ ዉክልና መስጠቷን፤ ተወካይዋ ደግሞ በተሰጠዉ ዉክልና መሠረት ለአቶ አህመድ በሪሶ ቁጥሩ 152845 በቀን 06/03/2008 ዓ.ም ምስራቅ ሸዋ ፍትሕ መምሪያ ቀርቦ ዉክልና መስጠቱን እንዲሁም አቶ አህመድ በሪሶ ደግሞ መጋቢት 05 ቀን 2009 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ባደረገዉ የሽያጭ ዉል ይዞታዉን ለተጠሪ ሸጦለት ቅድመ ሁኔታዎቹ ተሟልቶ የሊዝ ዉሉ ወደ ተጠሪ ስም መዛወሩንና የይዞታ ማረጋገጫና የግንባታ ፈቃድ የተሰጠዉ መሆኑ አረጋግጧል። ዉክልናዎቹ ትክክለኛ መሆናቸዉ እና በአግባቡ ሽያጭና የስም ዝዉዉር ተደርጎ ይዞታዉ ለተጠሪ መተላለፉን የምስራቅ ሸዋ ፍትሕ መምሪያና በአዳማ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት ተጠይቀዉ አረጋግጠዋል።

አመልካች አጥብቃ የምትከራከረዉ ዉክልና ሰጥታለች በተባለችበት ወቅት አገር ዉስጥ ያልነበረች መሆኑን ኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳዮች መስሪያ ቤት አረጋግጦልኛል እንዲሁም በዉክልናዉ ላይ ያለዉ ፊርማ የእኔ አይደለም፤ በፎረንሲክ ይመርመርልኝ በሚል ነዉ።

በመሠረቱ አንድ የዉክልና ሰነድ ሰነዶችን ለማረጋገጥና ለመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት እንዲሰጥና እንዲመዘገብ ያስፈለገበት ዋናዉ ምክንያት ዉክልናዉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ትክክለኛ እና በወካዩ አማካይነት የተሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ ውክልናን መሠረት ተደርገዉ የሚፈጸሙ ሕጋዊ ተግባራት የተሳለጡ እንዲሆኑ ለማስቻልና ውክልናዉ በወካይ አልተሰጠም የሚል አላስፈላጊ ክርክርና ጥርጣሬዎችን ለማስወገድ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ በአዋጅ ቁ/922/08 አንቀጽ 23/1/ ላይ እንደተደነገገዉ በሰነድ መዝጋቢዉ አካል የተረጋገጠዉ ሰነድ ሙሉ እምነት የሚጣልበት ማስረጃ ሆኖ ቅቡልነት ያለዉ ነዉ፡፡ ይህንን ሰነድ ቅቡልነት መቃወም የሚቻለዉም በበቂ ምክንያት ፍርድ ቤት ሲፈቅድ ብቻ እንደሆነ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ ሁለት ስር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ሰነዱን የሚቃወሙበት በቂና ህጋዊ ምክንያት ካላቸዉ ሰነዱ እንዲሰረዝ በህግ አግባብ ከሚጠይቁ በስተቀር በሚመለከተዉ አካል የተረጋገጠ የዉክልና ሰነድ ቅቡልነት ሊኖረዉ አይገባም የሚለዉ ክርክር ስለሰነዶች ምዝገባ የወጣዉን አዋጅ ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ከተወካይ ጋር ዉል የሚገባ ሰዉ ዉክልናዉ በተወካይ የተሰጠና ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን ከማረጋገጥ ባለፈ ወካይ ውክልናዉ በተሰጠበት ወቅት በአገር ዉስጥ መኖር አለመኖራቸዉንና ፈርማዉ የወካይ መሆን አለመሆኑን የሚያጣራበት አግባብ የለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ተጠሪ ይዞታዉ በሽያጭ ዉል ተላልፎልኛል ያለበት ዉክልና በአመልካች ያልተሰጠና የሀሰት ነዉ በማለት የሚከራከሩት የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳዩች መስሪያ ቤት አመልካች ከአገር የወጣችበትና ወደ አገር የገባችበትን ቀን የገለጸ በመሆኑ ዉክልና በተሰጠበት ጊዜ በአገር ያልነበርኩ በመሆኔ ዉክልናዉን ልሰጥ አልችልም ፈርማዉ የእኔ ባለመሆኑ በፎረንሲክ ይመርመርልኝ የሚል ነዉ፡፡ ዉክልናዉ ሰነዶችን ለማረጋገጥና ለመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ተሰጥቶ ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካች ከአገር የወጡበትና ወደ አገር የገቡበትን ጊዜ በማረጋገጥ እንዲሁም በዉክልናዉ ላይ ያለዉ ፈርማ በፎረንሲክ ቢመረመርና ልዩነት አለዉ ቢባል እንኳ ዉክልናዉ በአመልካች አልተሰጠም የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አይሆንም፡፡ ስለሆነም አመልካች ከአገር የወጡበትን እና ወደ አገር የገቡበትን ጊዜ በማስረዳት እንዲሁም በዉክልና ሰነዱ ላይ ያለዉ ፈርማ ከአመልካች ከተለመደዉ ፈርማ ጋር ልዩነት ያለዉ መሆን ያለመሆኑን በማስመርመር ዉክልናዉ በአመልካች አልተሰጠም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻል ባለመሆኑ፤ የስር ፍ/ቤት ዉክልናዉ በአመልካች የተሰጠና ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን ሰነዶችን ለመመዝገብና ለማረጋገጥ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስልጣን ተሰጥቶት ውክልናዉን የመዘገበዉን አካል በመጠየቅና በማረጋገጥ እንዲሁም በዉክልናዉ መሠረት የሽያጭ ዉል ተፈጽሞ ይዞታዉ ወደ ተጠሪ ስም በሕግ አግባብ ተላልፎ ተጠሪ ባለይዞታ የሆነበት መሆኑን በማረጋገጥ የአመልካችን ክስ ዉድቅ ማድረጉ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል ተጠሪ ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ በሕግ አግባብ ተላልፎለት የባለይዞታነት መብት መፍጠሩን በማረጋገጥ፤ አመልካች ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ የያዘብኝን ይዞታ ይልቀቅልኝ በማለት ያቀረቡትን ክስ ዉድቅ በማድረግ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉም ዉሳኔ ሆነ በየደረጃዉ ጉዳዩን የተመለከቱት የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዉን ማጽናታቸዉ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ ዉሳኔዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም። በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ዉሳኔ</u>

1. በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 98982 ታሕሳስ 18 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 25546 የካቲት 16 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 263062 ግንቦት 22 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል።
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 149861

ቀን - 30/09/2010ዓ.ም

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- አቶ ቶዉፊቅ ላሉ - ቀርበዋል ።

ተጠሪ፡- አቶ ስራጅ ጀማል - ቀርበዋል ።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረዉ በስልጤ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል። የአመልካች ክስም በአጭሩ በ2004 ዓ.ም ወደ አረብ አገር ስሄድ ዋጋቸዉ በድምሩ ብር 19,000.00 የሚያወጣዉን አንድ በሬ፣ አንዲት ላም ከነጥጃዋ እና አንዲት ሴት አህያ ተከሳሽ እንዲጠብቅልኝ አደራ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም መኖሪያ ቤት እና ንግድ ቤት እንዲገዙልኝ አረብ አገር ሆኜ ብር 320,000.00 የላኩላቸዉ ቢሆንም ተከሳሽ ብር 120,000.00 መልሰዉልኝ ቀሪዉን ገንዘብ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆኑም፤ በመሆኑም ከብቶቹን እንዲሁም ቀሪዉን ገንዘብ ብር 200,000.00 ተከሳሽ እንዲመልሱ ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ።

ተጠሪ ለቀረበባቸዉ ክስ በሰጡት መልስ በክሱ የተጠቀሱትን ከብቶች ከከሳሽ በአደራ አልተቀበልኩም፤ ከሳሽ ቤት እንዲገዛላቸዉ ዉጭ አገር ሆነዉ የላኩልኝ ገንዘብ የለም፤ ተከሳሽ ተከፍሎኛል ያሉት ብር 120,000.00 ብድር የሰጠሁት ነዉ በማለት የቀረበባቸዉ ክስ ዉድቅ እንዲሆን በማለት ተከራክረዋል። በበኩላቸዉ ባቀረቡት የተከሳሽ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሳሽነት ክስ በብድር መልክ በባንክ ሂሳባቸዉ ገቢ ያደረግኩትን ገንዘብ ብር 120,000.00 ከሳሽ እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ከተጠሪ የተበደርኩት ገንዘብ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ከግራ ቀኝ የቀረበዉን ክርክር እንዲሁም ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች ከብቶቹን ለተጠሪ አደራ መስጠቱን ለማስረዳት ቀርበዉ የተሰሙት የሰዉ ምስክሮች ቃል የተለያየ እና እርስ በርሱ የሚጋጭ በመሆኑ በግራ ቀኝ መካከል በህግ አግባብ የተደረገ የአደራ ዉል ስለመኖሩ አለመረጋገጡን፤ እንዲሁም ከብር 500 በላይ የሆነ ጥሬ ገንዘብን በአደራ የመስጠት ዉል ስለመኖሩ ማስረዳት የሚቻለዉ በጽሑፍ በተደረገ ዉል መሆኑን እና አመልካች በዚህ መልኩ ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን (የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2782(1) እና 2472(1) በዋቢነት በመጥቀስ) የአመልካችን ክስ ዉድቅ ያደረገ ሲሆን፤ ተጠሪ ለአመልካች ብር 120000.00 አበድሬያለሁ ያሉትንም በተመለከተ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2472(1) መሠረት ይህን የሚያስረዳ በጽሑፍ የተደረገ የብድር ዉል አለመኖሩን ጠቅሶ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱንም ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በማጽናቱ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎት የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 20/03/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ የሰበር አቤቱታ በስር በክልሉ በየደረጃዉ ባሉት ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ዉሳኔዎች እና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ናቸዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ነዉ፡፡ እኛም የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጡትን ዉሳኔ አግባብነት ከግራ ቀኝ ክርክር እና

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ላቀረቡት ክስ መሠረት ያደረጉት ተጠሪ የተለያዩ ከብቶችን ሊጠብቁላቸዉ በአደራ መቀበላቸዉን እንዲሁም ቤት እንዲሰሩላቸዉ አመልካች የላኩትን ገንዘብ ተቀብለዉ አለመመለሳቸዉን ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸዉ ከብቶቹንም ሆነ ገንዘቡን ከአመልካች በአደራ አለመቀበላቸዉን ገልጸዉ የተከራከሩ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በመሆኑም አመልካች በክሱ የተመለከቱትን ከብቶችም ሆነ ገንዘቡን ለተጠሪ በአደራ መልክ የሰጣቸዉ ስለመሆኑ በቅድሚያ የማስረዳት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ ከብቶቹን በአደራ መስጠታቸዉን በተመለከተ አመልካች የሰዉ ምስክሮችን አቅርበዉ ያሰሙ ሲሆን፣ የወረዳዉ ፍርድ ቤትም አመልካች ያቀረቧቸዉን የሰዉ ምስክሮች ቃል በመመዘን፣ የቀረቡት የሰዉ ምስክሮች ቃል የተለያየ እና እርስ በእርሱ የሚጋጭ መሆኑን ጠቅሶ የአደራ ዉል በመካከላቸዉ ስለመደረጉ አላስረዱም በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ተመልክተናል፡፡ በሌላ በኩል በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3-ለ) እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተትን በማረም ላይ የተገደበ በመሆኑ ከፍሬ ነገር ጋር በተያያዘ በስር ፍርድ ቤቶች የቀረቡትን ማስረጃዎች ድጋሚ ሊመዝን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለሆነም አመልካች በክሱ የተመለከቱትን ከብቶች ለተጠሪ በአደራ ስለመስጠቱ አልተረጋገጠም በሚል የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የማይቻል በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

ከዉጭ አገር የተላከ ገንዘብን በተመለከተ አመልካች የሚከራከሩት ተጠሪ የንግድ እና የመኖሪያ ቤት እንዲሰሩላቸዉ ገንዘቡን መላካቸዉን ነዉ፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ ተጠሪ የተላከላቸዉ የአደራ ገንዘብ አለመኖሩን ገልጸዉ ተከራክረዋል፡፡ የስር የወረዳዉ ፍርድ ቤት በዉሳኔዉ እንዳመለከተዉም፣ በአደራ የተሰጠ ገንዘብ መኖሩን ለማስረዳት ተቀባይነት የሚኖረዉ ማስረጃ በጽሑፍ የተደረገ የአደራ ዉል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2782 እና 2472(1) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁንና አመልካች በዚህ መልኩ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በሌላ የሰዉ ወይም የሰነድ ማስረጃ ደግሞ ይህን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ የስልጤ ወረዳ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ሰበር ችሎት የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት፣ በቅደም ተከተል፣ የሰጡት ፍርድ እና ትዕዛዝ በህግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘንም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 08453 በቀን 20/12/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የስልጤ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/11642 በቀን 19/06/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/13236 በቀን 25/09/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት፣ የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ምክንያት የወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
3. በዚህ ችሎት በቀን 30/05/2010 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ ዕግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

አ/ጉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.162776

ታህሳስ 26 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች - ተክሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች - አቶ ሰለሞን መርደኪዮስ- ቀረቡ::

ተጠሪ - አቶ ሲሳይ ለበኔ- አልቀረቡም::

በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጉዳይ ከሰ/መ/ቁ 162774 ጋር በማጣመር መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታዎቹ መቅረብ ምክንያት የሆነው ክርክር የተጀመረው ተጠሪ በአመልካች ላይ በደቡብ ክልል አርባ ምንጭ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት ክስ፡- ከገኔ ዩናይትድ የመኪና አስመጪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር በነበረን ውል መሰረት ቅድመ ክፍያ ብር 160,000.00 (መቶ ስድሳ ሺህ) በመክፈል ሚኒባስ መኪና ለመውሰድ ስጠባበቅ ድርጅቱ የኢኮኖሚ ችግር ገጥሞት ሊፈጽም ባለመቻሉ የአሁኑ አመልካች ለድርጅቱ ከሚከፍለው ብር 254,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ አራት ሺህ) ውስጥ የእኔን ገንዘብ ሊከፍል የዕዳ ማስተላለፍ ውል አድርገናል፡፡ ነገር ግን አመልካች ብር 4,000.00 (አራት ሺህ) ብቻ ከፍሎ ሌላውን ስልላከፈለ ቀሪውን ብር 156,000.00 (መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ) ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም በውሉ ከተመለከተው ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) መቀጮና ክርክሩ ካስከተለው ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ በውሉ መሰረት የዕዳ መክፈያ ጊዜ ገና ወደፊት ነው፤ በየሳምንቱ ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ) ለመክፈል የተስማማን ሲሆን የሁለት ሳምንት ብር 4,000.00 (አራት ሺህ) እንደከፈልኩ ውሉ እንደተቋረጠ አድርጎ መክሰሱ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያላግባብ ነው፤ ዕዳው በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሳይሆን በ80 ሳምንታት የሚከፈል ነው፤ መኪናዬ ላይ የደረሰው ብልሽት ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት መሆኑን እያወቀ ክስ መመስረቱም ያላግባብ ነው፤ ስለሆነም በየሳምንቱ ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ) እየከፈልኩ ዕዳውን እንድጨርስ ይወሰን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ እንደውሉ ግዴታውን ያልተወጣ ተከሳሽ ስለመሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠና ተከሳሽ በመኪናው መበላሸት ምክንያት እንደውሉ አለመፈጸሙን የገለፀ ቢሆንም ስለመኪናው መበላሸት በውሉ ላይ ያልተገለፀ በመሆኑ መከላከያ ሊሆን አይችልም፤ በሌላ በኩል በውሉ አንቀጽ 6 መሰረት መቀጮ ብር 50,000.00 ሊከፍል እንደሚገባ የተመለከተ ቢሆንም ይህ የመቀጮ ገንዘብ የተጋነነ እና ለህግና ለሞራል ተቃራኒ በመሆኑ ሊሻሻል ይገባል በማለት ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ያልከፈሉትን ብር 156,000.00 ከ9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ እንዲሁም ከሳሽ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር እንዲያቀርቡ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን ተጠሪ በውል የተመለከተው የመቀጮ ገንዘብ እንዲከፈል አለመወሰኑን በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተከሳሽ የውል ግዴታውን በአግባቡ አለመወጣቱ በማስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ በውል የተመለከተው መቀጮ ሊከፈል አይገባም መባሉ አላግባብ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አሻሽሎ በውላቸው የተቀመጠውን ብር 50,000.00 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም ጉዳዩን መርምሮ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን ተጠሪ ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ የሰበር ችሎቱ የግራቀኙን ክርክር መርምሮ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች ዋናውን ገንዘብ ብር 156,000.00 እና በውላቸው የተስማሙበትን ብር 50,000.00 ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል፤ መቀጮ እንዲከፍሉ የተወሰነ በመሆኑ ወለድ 9% ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው። አመልካች ነሓሴ 18/2010 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ገና ወደፊት ሰማንያ ሳምንት የክፍያ ጊዜ ላለው ዕዳ መቀጮ እንድከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲፀና ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል።

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ጥቅምት 29/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ውሳኔ የተሰጠው በመካከላችን የተደረገውን ውል እና የቀረበውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ በመሆኑ እንዲሁም የሰበር ቅሬታው የተፈጸመውን የህግ ስህተት የሚያሳይ ባለመሆኑ ውድቅ ተደርጎ ውሳኔው እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል። አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል።

በሌላ በኩል በሰ/መ/ቁ 162774 የተያዘው ጉዳይ የወጪና ኪሳራን የተመለከተ ነው። ተጠሪ በአርባ ምንጭ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወጪ ዝርዝር አቅርበው ፍርድ ቤቱ ዝርዝሩን መርምሮ ውሳኔ ባገኘው አጠቃላይ ብር 206,000.00 ላይ የጠበቃ አበል 7% ብር 14,420.00፣ የዳኝነት ብር 4,850.00፣ የምስክር አበል ብር 100.00፣ የቴምብር ብር 52.00 በድምሩ ብር 19,422.00 (አስራ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ሃያ ሁለት) የአሁን አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል። ይግባኙ የቀረበለት የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጠበቃ አበል አሻሽሎ 5% ብር 10,300.00 ሊሆን ይገባል በማለት ሌላውን ዝርዝር ተቀብሎ በአጠቃላይ ብር 15,302.00 (አስራ አምስት ሺህ ሶስት መቶ ሁለት) ወጪ እንዲተካ ወስኗል። የክልሉ ሰበር ችሎትም ይህን ውሳኔ ተቀብሎታል። በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ነሃሴ 12/2010 ዓ.ም ለዚህ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ቅሬታ የሥር ፍርድ ቤቶች የመቀጮውን ብር 50,000.00 አካተው የጠበቃ አበል እንዲታሰብበት ማድረጋቸው ስህተት ስለሆነ የጠበቃ አበል መታሰብ ያለበት ከዋናው ዕዳ ብር 156,000.00 ላይ ብቻ መሆን አለበት ተብሎ እንዲታረም ጠይቀዋል። ተጠሪ ውሳኔው እንዲፀና በመከራከር መልስ ሰጥተዋል።

ጉዳዩ ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ሲሆን በበኩላችን ቅሬታ በቀረበባቸው ውሳኔዎች የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመረመርነው የዕዳ ማስተላለፍ ውል መደረጉና ስምምነት ከተደረገበት ገንዘብ ውስጥ አመልካች ብር 4,000.00 (አራት ሺህ) ብቻ ከፍለው ቀሪውን ብር 156,000.00 (መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ) ያልከፈሉ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ለክሱ በሰጡት መልስ ዕዳው በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሳይሆን በ80 ሳምንታት የሚከፈል መሆኑንና በየሳምንቱ ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ) እየከፈልኩ ዕዳውን እንዲያጠናቅቁ እንዲደረግ ተከራክረው የነበረ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ማስረጃውን ተመልክቶ ዕዳውን በአንድ ጊዜ እንዲከፍሉ ሲወስን የበኩላቸውን ይግባኝ ለበላይ ፍርድ ቤቶች አላቀረቡም፡፡ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ቅሬታ ያቀረቡት የአሁን ተጠሪ ሲሆኑ ቅሬታቸውም በውል የተመለከተው የመቀጮ ገንዘብ እንዲከፈል አለመወሰኑን የተመለከተ ነበር፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች ገና ወደፊት ሰማንያ ሳምንት የክፍያ ጊዜ ያለው ዕዳ ነው በማለት በዚህ ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ክርክር የምንቀበለው አይሆንም፡፡

ይልቁንም የዚህን ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚጠይቀው ቀዳሚ ጭብጥ እንደውሉ እንዲፈፀም እንዲሁም የመቀጮ ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠው ውሳኔ ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ያልተከፈላቸው ቀሪ ብር 156,000.00 (መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ) ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም በውሉ ከተመለከተው ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) መቀጮ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የተለያየ ውሳኔ የሰጡ ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ሰበር ችሎት አመልካች ዋናውን ገንዘብ ብር 156,000.00 እና በውላቸው የተስማሙበትን ብር 50,000.00 መቀጮ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ነገር ግን መቀጮ እንዲከፍሉ የተወሰነ በመሆኑ ወለድ 9% ሊከፍሉ አይገባም ብሏል፡፡

የገደብ (የመቀጫ) ስምምነት በተደረገ ጊዜ ባለገንዘቡ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር ውሉ እንዲፈፀም እንዲሁም የመቀጮ ገንዘብ እንዲከፈል ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(1) ሥር የተደነገገ ሲሆን በዚህ ረገድ ባለገንዘቡ ያለው መብት ግን የተገደበ መሆኑን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(2) መገንዘብ ይቻላል፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(2) እንደተመለከተው፡-

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

"ኪሳራው የተወሰነው ለሥራው አፈፃፀም መዘግየት ብቻ ወይም ለተጨማሪ ግዴታዎች አለመፈፀም ካልሆነ በቀር ባለገንዘቡ ውሉ እንዲፈፀምና (ገደቡን) መቀጮውንም እንዲቀበል ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ለመጠየቅ አይችልም" ።

የድንጋጌው የእንግሊዝኛ ቅጅም፡--

"He may not require both the enforcement of the contract and the penalty unless the penalty was provided in respect of delay or the non-performance of a collateral obligation" በማለት ይደነግጋል።

ከፍሲል ከተጠቀሰው ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(1) የተመለከተው ድንጋጌ ተጠቃሚ ለመሆን መቀጮ የሚከፈለው የውሉ መዘግየት ወይም ተጨማሪ ግዴታዎች ካሉ የእነዚህ አለመፈፀም የመቀጮውን ክፍያ የሚያስከትል ሲሆን ነው። በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ ባደረጉት ስምምነት የውል ግዴታውን ያልተወጣ ወገን ውሉን ላከበረው ወገን መቀጮ ብር 50,000.00 ለመክፈል የተስማሙ መሆናቸውን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ይህ በመዘግየት የሚከፈል ኪሳራ ስለመሆኑና ከተጨማሪ ግዴታዎች አለመፈፀም ጋር የሚያያዝ ስለመሆኑ በማረጋገጥ የተሰጠ ውሳኔ የለም። ይህ በሆነበት ሁኔታ ዋናው ዕዳ ተከፍሎ እንደውሉ እንዲፈፀም እና መቀጫ (ገደብ) ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ) እንዲከፈል መወሰኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1890(2) ድንጋጌን እና የውሉን ይዘት እንዲሁም የግራቀኙን ክርክር መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መቀጮ እንዲከፈል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል።

በሌላ በኩል ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤቶች የመቀጮውን ብር 50,000.00 አካተው የጠበቃ አበል እንዲታሰብበት ማድረጋቸው ተገቢ ስለማይሆን የጠበቃ አበል 5% መታሰብ ያለበት በዋናው ዕዳ ብር 156,000.00 ላይ መሆን አለበት ብለናል። ስለሆነም ተከታዩንም ወስነናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል መንግስት የአርባ ምንጭ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 22052 በ29/01/2009 ዓ.ም፤ የጋሞ አካ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 32690 በ27/04/2010 ዓ.ም፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 22190 በ18/07/2010 ዓ.ም እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 26735 በ20/11/2010 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አመልካች ዋናውን ዕዳ ብር 156000.00 (መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ) የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ከ29/01/2009 ዓ.ም ጀምሮ ዕዳው ተከፍሎ እስካለቀበት ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ በማለት ወስነናል፡፡
3. ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ በተመለከተ የአርባ ምንጭ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 22858 በ06/07/2010 ዓ.ም፤ የጋሞ አካ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 33355 በ26/08/2010 ዓ.ም፤ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 27034 በ30/11/2010 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡ ውሳኔ ባገኘው ብር 156,000.00 (መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ) ላይ የጠበቃ አበል 5% ብር 7800.00፣ የዳኝነት ብር 4,850.00፣ የምስክር አበል ብር 100.00፣ የቴምብር ብር 52.00 በአጠቃላይ የአሁን አመልካች ብር 12,802.00 (አስራ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሁለት) ወጪ ለተጠሪ እንዲተኩ ወስነናል፡፡
4. ሌላውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ተገልብጦ ከሰ/መ/ቁ 162774 ጋር ይያያዝ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር 133398

ታህሳስ 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች :- ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች :- አቶ ጉልላት ግዛው - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ :- አቶ ጥላሁን ኃይሉ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሆኖ በስር ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ ደግሞ አመልካች በመሆን በመኪና ሽያጭ ውል መነሻነት ተከራክረዋል፡፡

በስር ቀርቦ የነበረው ክስ የሚያመለክተው ከሣሽ የሠ.ቁ. 02-99421 አ.አ. የሆነውን የተከሣሽን የጭነት ተሽከርካሪ ምንም ዓይነት ችግር የሌለበት መሆኑን አረጋግጠው ታህሳስ 06 ቀን 2005 ዓ.ም. በተፈረመ የመኪና ሽያጭ ውል መግዛታቸውን እና ከቤት መኪናነት ወደ ግል ተሽከርካሪነት ለማዛወር ለሚመለከተው የትራንስፖርት ጽ/ቤት ሲጠይቁ መኪናው በባለሙያ ተመርምሮ የመኪናው ቁጥርና ሻንሲ የተመታ መሆኑ ስለተረጋገጠ የተጠቀሰው እንደማይሠጣቸው የተገለፀላቸው በመሆኑ መኪናው ጉድለት እንዳለበት እያወቀ ከሣሽ ወደ ስህተት በመምራት ውሉን እንድንፈራረም ያደረጉት ያለአግባብ ስለሆነ ውሉም ሊፈፀም በሚችል አቅም ያልተመሠረተ ስለሆነ የመኪና ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ፣ ተከሣሽ ከሽያጭ ጋር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያያዘ ከሣሽ ላይ የተቀበለውን የሽያጭ ገንዘብ ከሣሽ መኪናውን ከገዛው በኋላ ለማስተካከል ያወጡትን ወጭ በአጠቃላይ ከሕጋዊ ወለድ ከክርክር ወጪና ኪሣራ ጭምር እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው የጠየቁ መሆኑን ተመልክተናል፡፡

ተከሣሽ በሰጡት መልስ መኪናውን መሸጣቸውን ማመናቸውን ነገር ግን ሊብራ ወደ ገዢ ሳያዛውሩ የተባለው ችግር በመኪናው ላይ ያለ መሆኑን በፍፁም እንደማያውቁ፣ በባለሙያ ተመርምሮ የተላለፈ መሆኑን፣ ከሣሽ ከተረከበው ጀምሮ በእጃቸው ሆኖ ጋራዥ እንደነበረ፣ ጉድለቱ ሲሸጥ ያልነበረ መሆኑን ኃላፊነቱም ለገዢ የተላለፈ መሆኑን፣ በመግለጽ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት አቅርበዋል፡፡ ወደ ነበርንበት ለመመለስም አንችልም ብለዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ውሉ ጉድለት ያለበት ነው ወይንስ አይደለም ? መኪናውን ከሣሽ ከገዛ በኋላ ወጪ አጥቷል ወይንስ አላወጣም የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቷል፡፡

አጠቃላይ ክርክሩን ከተመለከተ በኋላም በግራ ቀኙ መሐከል የመኪና ሽያጭ ውል መኖሩ አለማከራከሩን፣ በሽያጭ ውሉ ላይ ጉድለት አለ ወይንስ የለም የሚለው በቅድሚያ መለየት የሚገባ መሆኑን እና የተሸጠው መኪና ሻንሲ እና ቁጥር የተመታ በመሆኑ መሸጥ መለወጥ የማይቻል መሆኑ በመንገድ ትራንስፖርት ዕ/ቤትም ከኮድ 2 ወደ ኮድ 3 መለወጥ እንደማይቻል መከልከሉን በመያዝ የተሰሙ ምስክሮችን ቃል ሲመረመርም መኪናው ከመሸጡ በፊት በባለሙያ/መካኒክ/ የተመረመረ ቢሆንም መካኒክ ሲመረምር ሻንሲው የተመታ መሆኑን መለየት ይችላል ብለው ተከሣሽም ያነሱት ክርክር የሌለ እና የተረጋገጠም ባለመሆኑ ከቀረበው የማስረጃ ክብደት አንፃር የሠ.ቁ. ኮድ 2-99421 አአ የሻንሲ ቁጥር YN 52-009146 የሞተር ቁጥር 3Y-02313681 በማስመሰል የተመታው ከሽያጭ ውሉ በፊት በተከሣሽ እጅ ላይ እያለ የነበረ ጉድለት መሆኑን ፍ/ቤቱ ግንዛቤ መውሰዱን ገልጿል፡፡

ይህ ጉድለት ውል እንዲፈርስ ምክንያት ይሆናል ወይ የሚለውን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2289 ሻጭ ዋቢ ሊሆንባቸው የሚገባቸው ጉድለቶች የሸጠው ነገር ለደንበኛው አገልግሎት ወይም ለንግድ ሥራ ጥራትነት የሌለው ዕቃ ከሆኑ በማለት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚደነግግ በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ሻጭ ዋቢ ሊሆንለት የሚችል ጉድለት የተገኘበት ስለሆነ ሊፈርስ የሚገባው ውል ነው በሚል ወስኗል። ወጪን በተመለከተ ግን ከሣሽ ወጪዎችን ያስረዱልኛል ብለው ያቀረቧቸውን ደረሰኞች እያንዳንዳቸውን በመመልከት የቀረበውን ወጪ ያስረዱም በማለት ውድቅ አድርጐ መኪናው የተሸጠበትን ገንዘብ ብር 110000.00/ አንድ መቶ አስር ሺ ብር/ እና ብር 5798.00/ አምስት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ብር/ በመጨመር ተከሣሽ ለከሣሽ እንዲመልስ፣ ከሣሽ ደግሞ የሠ.ቁ. 2-99421 አ.አ. የሆነውን ተሽከርካሪ አሁን ባለበት ሁኔታ ለተከሣሽ እንዲያስረክቡ መሆኑን በመ/ቁ/ 39866 ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም. የሰጠው የውሣኔ ግልባጭ ያመለክታል።

አመልካች ይግባኝ ቢሉም ይግባኝ ቅሬታውን የመረመረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና አከራክሮ በመ/ቁ/ 156835 ህዳር 16 ቀን 2008 በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በሚል ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል።

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው የካቲት 11 ቀን 2008 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል። ይዘቱም በአጭሩ፡- ክርክር ያስነሳውን ተሽከርካሪ እዳ እና እገዳ የሌለበት መሆኑ ተረጋግጦ ከሣሽ በስማቸው አዛውረዋል፣የባለቤትነት ደብተርም ተጠሪ በስማቸው አውጥተዋል።

ተጠሪ መኪናውን ሲገዙ በተለመደው አሰራር የራሳቸውን ባለሙያ አምጥተው አስመርምረዋል። ውሉ ከተደረገ ከ5 ወር በኋላ በ09/07/2005 ዓ.ም. የመኪናውን አገልግሎት ከኮድ 2 ወደ ኮድ 3 ለመቀየር ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ የመኪናው ሞተርና ሻንሲ የተመታ መሆኑን የተገለፀላቸው ቢሆንም አመልካች ይህ ጉድለት ስለመኖሩና መቼ እንደተከሰተም የሚያውቁት ነገር የለም። ከቅን ልቦና ውጭ ያቀረቡት ጥያቄ ውሉ በመሳሳት የተደረገ ነው ሊባል አይችልም። ሽያጩ የተደረገው በታህሳስ 06 ቀን 2005 ዓ.ም. ሲሆን ተጠሪ መኪናውን እስካሁን ድረስ እየተጠቀሙበት የሚገኙ ከመሆኑ አኳያ የመኪና ሽያጭ ውሉ በመፍረስ ወደነበርንበት እንዲመለሱ ቢደረግ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀሙ አዳጋች ነው በሚል የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመው ስህተት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎት ሊጣራ የሚገባውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡ ለችሎቱ እንዲቀርብ በማድረጉ ሊቀርብ ችሏል፡፡ አቤቱታው ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር ለተጠሪ ደርሶ መልስ እንዲያቀርቡ ከመጥሪያ ጋር የተላከላቸው በመሆኑ ጥር 24 ቀን 2009 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ካቀረቡት በጥቂቱ፡- ውል እንዲፈርስ ክስ ያቀረብኩት ውሉ ከተደረገ እና መኪናውን ከተረከብኩ ከ3 ቀን በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም መኪና ከተረከብኩ ከ3 ዓመት በኋላ ውል እንዲፈርስ ክስ አላቀረብኩም፣ መኪናውን በትራንስፖርት ቅርንጫፍ ባለሙያ አስመርምረው አላስረከቡኝም፣ በመኪናው ላይ ጉድለት ያለበት መሆኑ የታወቀው ተጠሪ መኪናውን ከቤት አገልግሎት ወደ ንግድ ተሽከርካሪነት ለመለወጥ አስቤ መኪናው በትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ባለሙያ በተመረመረበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ አግባብ በመሆኑ የተፈፀመበት የህግ ስህተት የለውም ተብሎ አቤቱታው ውድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም አጠቃላይ የቀረበውን ጉዳይ አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ከላይ በስር የቀረበው ክስ ላይ ታህሳስ 06 ቀን 2005 ዓ.ም. ክርክር ያስነሳውን ተሽከርካሪ ሽያጭ ውል ግራ ቀኙ በማድረግ የሽያጭ ገንዘቡንም ብር 110000.00 ሻጭ መቀበላቸውን ገዢም መኪናውን መረከባቸውን የተካደ ባለመሆኑ አለማከራከሩን ተመልክተናል፡፡ ሆኖም መኪናው በተገቢው ርክክብ ከተደረገ በኋላ ስመ ሀብትም ከዞረ በኋላ የመኪናውን አገልግሎት ለመቀየር ለትራንስፖርት ባለሥልጣን ጥያቄው ቀርቦ ሲፈተሽ ግን የሻንሲው ቁጥር የተመታ መሆኑ በመረጋገጡ በቀይ ሰሌዳ ላይ የተመዘገበ በመሆኑ አገልግሎቱን ማግኘት እንደማይቻል ለተጠሪ የተገለፀላቸው በመሆኑ ውሉ ጉድለት ባለበት ንብረት ላይ የተፈፀመ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ ጠይቀዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አሁን እያከራከረ ያለው ጭብጥ መኪናው ከሻጭ ወደ ገዢ ከመተላለፉ በፊት በመካኒክ ተፈትሾ የተላለፈ በመሆኑ ኃላፊነት ለገዢ ተላልፏል ሊባል ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለው ነጥብ ላይ ይሆናል፡፡

በስር ፍርድ ቤት መኪናው በአግባቡ ተጠሪ ራሣቸው ባመጡት ሜካኒክ ተፈትሾ እና ተነድቶ ጉድለት የሌለበት መሆኑ ተረጋግጦ ገዢ የተረከቡ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ይህ የመካኒክ ፍተሻ የሻንሲ እና የሞተር ቁጥር ኦርጅናልነት ጨምሮ የሚያረጋግጥ ነው ወይንስ አይደለም የሚለው በአመልካች በስር ክርክር የተደረገበት ባይሆንም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ግን ተነስቶ የነበረ በመሆኑ በዚህ መልኩ አመልካች መኪናው ተፈትሾ ለገዢ መተላለፉን ስለማስረዳታቸው የተቀመጠ ነገር የለም፡፡

በኑሮ ልማድ እውቀት እንደሚታወቀው መካኒክ የሚፈትሸው ጉድለት ከመኪናው ጤነኝነት ማለትም አገልግሎት መስጠት እና አለመስጠት ጋር በተያያዘ እንጂ የሻንሲን እና የሞተርን ቁጥር ኦርጅናልነትን የሚጨምር አይደለም፡፡ ይህ ማለት አመልካች መኪናውን ሲሸጡ ይህ ጉድለት መኖሩን ያውቁ ነበር ለማለትም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም አመልካችም በአቤቱታቸው እንደገለፁት መኪናው የተላለፈላቸው ከሌላ ሰው መሆኑን የገለፁ በመሆኑ ይህን ምርመራ የመካኒክ ምርመራ የሚያካትት ቢሆን ኑሮ ቀድመው የሚያውቁበት እድል ይኖራቸው ነበር፡፡

ሆኖም አመልካች ጉድለቱ መኖሩን በፍፁም አላውቅም በማለት ይከራከሩ እንጂ ጉድለቱ የለም አላሉም፣ እያነሱ ያሉት ርክክብ ከተፈፀመ በኋላ ከእጄ ወጥቶ በተጠሪ እጅ ገብቷል ስለሆነም ኃላፊነት ተላልፏል የሚል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ኃላፊነት ተላልፏል ጉድለቱ አይመለከተኝም ለማለት ደግሞ ቀድሞ ጉድለቱ ያለመኖሩን በእርግጠኝነት ማረጋገጥ የሚገባው ኃላፊነቱ ከተላለፈ በኋላ ነው ጉድለቱ የደረሰው የሚለው ወገን መሆን ይኖርበታል፡፡

እንዲህ ከሆነ ጉድለቱ መኖሩ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ጉድለት ደግሞ ገዢን አንድ የንብረት ባለቤት ሊያገኝ የሚችለውን መብት የሚቀንስ ወይም ጨርሶ የሚያሳጣ ከሆነ ውሉ የተፈፀመው በመሳሳት በመሆኑ የማይፈርስበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ይህን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተሽከርካሪ ተጠሪ የአገልግሎት ዘርፍ በመቀየር ሥራ ላይ ለማዋል የማይችሉ እና በትራንስፖርት ባለሥልጣን አባባል ቀይ ሰሌዳ ላይ የተመዘገበ በመሆኑ የገዙትን ንብረት ስም ብቻ ማዛወራቸው ንብረቱን ህግ በሚፈቅደው መልክ በመቀየር ሊጠቀሙ የማያስችላቸው አዳጋች ነገር ተፈጥሮባቸዋል፡፡ ስለሆነም የገዙትን ንብረት በፈለጉት መልኩ መጠቀም የማያስችል ሁኔታ መፈጠር ደግሞ ውሉ ከመደረጉ በፊት ችግሩ/ጉድለቱ እንዳለ ቢያውቁ ኑሮ ውሉን አይፈጽሙም ነበር የሚያሰኝ በመሆኑ ጉድለት ያለበት ውሉ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት እንዲፈርስ መወሰኑ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 መሠረት ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊያስብል የሚችል ምክንያት አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማጽናት አቤቱታውን አልተቀበልነውም ስለሆነም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 156835 ህዳር 16 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማጽናት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡት ወጪ ካለ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡
4. መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 153664

ቀን - 29/01/2011

ዳኞች፡-

ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ አሻ ፋራህ -ጠበቃ ጣሂር ሼህ አብዱላህ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ አብዱራህማን ጣሂር
2. ዮሱፍ አሊ ዩሱፍ
3. ሀሰን አሊ ዩሱፍ
4. ሳላህ ኢብራሂም
5. ሮዉዳ አሊ ዩሱፍ
6. ረሺድ አሊ ዩሱፍ
7. ኢስማሃን አሊ ዩሱፍ
8. በድሪያ ኢብራሂም ግራድ
9. ሀሰን ኢብራሂም ኢጋል

አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረዉ በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል መንግስት በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ ተጠሪዎች ከሳሽ፣ አመልካች እና በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነዉ አቶ ሰኢድ አሊ፣ በቅደም ተከተል፣ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪዎች ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ እናቶቻችን ከአያታችን የወረሱት እና በዉርስ ሊተላለፍልን የሚገባ ቦታ 2ኛ ተከሳሽ በህገ ወጥ መንገድ ለ1ኛ ተከሳሽ በሽያጭ በማስተላለፉ ዉሉ ፈርሶ ቦታዉ ይመለስልን የሚል ነዉ፡፡ ተከሳሾች ለፍርድ ቤቱ ቀርበዉ በሰጡት መልስ፤ ቦታዉ ለ2ኛ ተከሳሽ በተለይ ከእናቱ የተሰጠዉ መሆኑን፣

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሳሾች ከቦታዉ የዉርስ ድርሻ የሌላቸዉ መሆኑን፣ ቦታዉን 2ኛ ተከሳሽ ቆርቆሮ ቤት ሰርቶበት በህጋዊ መንገድ ለ1ኛ ተከሳሽ የሸጠ በመሆኑ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ እና ቆርቆሮ የተሰራበት ቦታ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ባደረጉት የሽያጭ ዉል መሠረት በአመልካች እጅ እንደሚገኝ በማስረጃ መረጋገጡን ገልፆ ቤትና ቦታዉ የአመልካች ነዉ በማለት የተጠሪዎችን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ ለክስ ምክንያት የሆነዉ ዉል በሚመለከተዉ አካል ዘንድ የተመዘገበ እና የተፈረመም አለመሆኑን፣ ተጠሪዎች ወራሾች መሆናቸዉን እና ለስር 2ኛ ተከሳሽ ለብቻዉ የተሰጠ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ ንብረቱ ለተጠሪዎች ሊመለስላቸዉ ይገባል፤ አመልካች በቦታዉ ላይ ቤት ለሰራችዉ ቤት ግምቱን ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ፤ አመልካች በዉሉ ምክንያት ያጣችዉ መብት ካለ በስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ ክስ የማቅረብ መብት አላት በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ያቀረበች ሲሆን፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎት የስር 2ኛ ተከሳሽ በሽያጭ ዉሉ መሠረት የወሰደዉን ገንዘብ ለአመልካች ሊመለስ ይገባል በሚል ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በዚህ ረገድ የሰጠዉን የዉሳኔ ክፍል ብቻ በመሻር ቀሪዉን በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 05/06/2010 ዓ. ም ተዘጋጅቶ በጠበቃዋ አማካይነት በቀረበ አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ፤ ተጠሪዎች ወራሾች መሆናቸዉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ፣ እንዲሁም በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ ዉል ተገቢዉን ፎርም ያሟላ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ የቀረበዉ ክርክር በሌለበት ሁኔታ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች በፋፊን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረዉን ዉሳኔ በመሻር የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ተከራክራለች፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቤት እና ቦታ በአመልካች እጅ ሊገባ የቻለዉ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ባደረጉት የሽያጭ ዉል መሠረት ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት ቤትና ቦታዉ ከአያታቸዉ በዉርስ ሊተላለፍላቸዉ የሚገባ መሆኑን ሲሆን፣ አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ በበኩላቸዉ ቤትና ቦታዉ ለስር 2ኛ ተከሳሽ (ሽያጭ) በግል የተሰጠዉ እንጂ የዉርስ ሀብት አለመሆኑን ገልጸዉ የተከራከሩ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይሁንና ቤትና ቦታዉ ቀደም ሲል የተጠሪዎች አያት የነበረ ሆኖ ለተጠሪዎች በዉርስ የተላለፈላቸዉ እንጂ ለስር 2ኛ ተከሳሽ በግል የተሰጠዉ ያለመሆኑን ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን በተሰጣቸዉ በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉ ይህ ከሆነ፣ በአመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ መካከል የተደረገዉ እና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል ህጋዊ ዉጤት የሚያስከትል መሆን ያለመሆኑን ስለ ጉዳዩ ከሚደነግገዉ የፍትሐብሔር ህጉ ድንጋጌ ጋር አገናዝቦ ማየቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንደሚታወቀዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለዉ ልዩ ባህርይ አንፃር፣ ንብረቶቹን ከአንድ ወደ ሌላ ሰዉ ለማስተላለፍ የሚደረጉ አሠራሮች እና ስርዓቶች ጥብቅ መሆን እንዳለባቸዉ ይታወቃል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ከአንዱ ወደ ሌላ ሰዉ ማስተላለፍ ስለሚቻልበት ሁኔታ በተመለከተ በፍትሐብሔር ህጋችን የተለያዩ አንቀፆች የተደነገጉ ድንጋጌዎችም ይህኑን የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ ከእነዚህም ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ በህጉ አንቀጽ 2878 ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ለሌላ ሰዉ ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በሦስተኛ ወገን ላይ ህጋዊ ዉጤት ያስከትል ዘንድ ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡ የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተም፣ ተጠሪዎች ከቤቱ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር ያደረገችዉ ዉል ህጋዊ ዉጤት ያስከትል ዘንድ የሽያጭ ዉሉ በህግ አግባብ የተመዘገበ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለባት፡፡ ሆኖም ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ዉል በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ያልተመዘገበ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ለክርክሩ ምክንያት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሆነዉ ዉል የሚጸናበት የህግ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የደረሱበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል የሚባል ከሆነ ደግሞ የስር 2ኛ ተከሳሽ (ሻጭ) ሰዒድ አሊ ዩሱፍ በዉሉ ምክንያት የተቀበለዉን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ ይህን እንዲያደርግ ሌላ ክስ ማቅረብ ሳያስፈልግ በዚሁ መዝገብ ላይ መወሰን የሚቻል በመሆኑ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠዉን የዉሳኔ ክፍል በመሻር የደረሰበት ድምዳሜም በአግባቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቤትና ቦታ የተጠሪዎች የዉርስ ድርሻ ያለበት መሆኑ እስከተረጋገጠ እና አመልካች ቤትና ቦታዉን ለመግዛት ያደረጉት ዉልም በህግ አግባብ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ያልተመዘገበ በመሆኑ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የስር 2ኛ ተከሳሽ የሸያጩን ገንዘብ ለአመልካች እንዲመልስ በሚል የተሰጠ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 05-1-101/09 በቀን 04/03/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
3. አመልካች ቦታዉን ከተረከቡ በኋላ ላካሄዱት ተጨማሪ ግንባታ ያወጡትን ወጪ በተመለከተ ወጪዉ እንዲመለስላቸዉ ሊያቀርቡ የሚችሉትን ክስ ይህ ዉሳኔ አይከለክልም፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ
የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ 145456

ቀን 24/09/2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-

ዳኜ መላኩ

ተሽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡ ..... ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማሕበር ነገረ ፈጅ ቤተልሔም ማትሞስ -ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡..... 1ኛ. አቶ እዮብ ሙሉጌታ ቱሳና

2ኛ. ወ/ሮ መድሃኒት ሙሉጌታ ቱሳና } የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ ዋስትናን መሰረት ያደረገ ክርክር ሲሆን የጀመረው በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር አመልካች ከሳሽ፣ ተጠሪዎች እና በዚህ መዝገብ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነውን አቶ ፈቃዱ ሙሉጌታ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡
2. አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ፈቃዱ ሙሉጌታ የአመልካች ሠራተኛ በመሆን በወላይታ ቅርንጫፍ ተመድቦ እየሰራ በነበረበት ጊዜ ከባንኩ አሠራር ውጭ የአቶ ጀመሬ መኛ ሎጊሶን ከሆነው ሂሣብ ቁጥር የባለ ሂሣቡን ስምና ፊርማ በማስመሰል ፈርሞ ወደ አመልካች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባንክ ሻሸመኔ ቅርንጫፍ በማዛወር ብር 50,000 በህገወጥ መንገድ በመውሰዱ ገንዘቡን እንዲከፍል፤ የአሁኑ ተጠሪዎች ዋስ በመሆናቸው ገንዘቡን በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

3. የስር ተከሳሾች ባቀረቡት የመከላከያ መልስ በስር 1ኛ ተከሳሽ ስምና ፊርማ የተደረገ የገንዘብ ዝውውር የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡
4. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም በክሱ የተጠቀሰው ገንዘብ በስር 1ኛ ተከሳሽ ወጭ ተደርጐ መወሰዱን ተረጋግጦ በወንጀል የተቀጣ መሆኑን፤ የአሁኑ ተጠሪዎችም ዋስ ስለመሆናቸው ያልተካደ መሆኑን በመግለጽ ብር 50,000 በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ከአከራከረ በኃላ የስር 1ኛ ተከሳሽ ድርጊቱ የፈፀመው ለደንበኞች አገልግሎት እየሰጠ ሳይሆን ለራሱ የአመልካች ደንበኛ በመሆን እንደሆነ፤ የሻሸመኔ ቅርንጫፍም ባለመብት ባለማጣራት የከፈለው በመሆኑ ዋሶቹ ተጠያቂነት የለባቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡
5. አመልካች ሐምሌ 25 ቀን 2009 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፀመ ያለውን የህግ ስሕተት በዝርዝር ያቀረበ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱ ሲታይም የአሁኑ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያላነሱት ክርክር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለውሳኔ መነሻ ማድረጉ ተገቢ አለመሆኑን፤ የስር 1ኛ ተከሳሽ ገንዘቡ የወሰደው ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ መሆኑን በመግለጽ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ እንዲሻር አመልክቷል፡፡ ጉዳዩን የመረመረው አጠሪ ችሎትም የአሁን ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸውም ተብሎ የተወሰበት አግባብ ባሉበት ማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች 03/05/2010 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

6. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡
7. እንደመረመረነውም የአሁኑ ተጠሪዎች በስር 1ኛ ተከሳሽ ለነበሩት አቶ ፈቃዱ ሙሉጌታ ዋስ ስለመሆናቸው፤ የገንዘብ መጠኑም እስከ ብር 50,000 ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከስር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ተጠሪዎች ከባንክ ገንዘብ አልወጣም የሚል ክርክር ሳያቀርቡ ነገር ግን ገንዘቡ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልወጣ በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር የተረጋገጠው የስር 1ኛ ተከሳሽ የአቶ ጀመሬ መጃን ፊርማ ለማስመሰል ብር 50,000 በህገወጥ መንገድ ማውጣቱን ገንዘቡም ከሻሸመኔ ቅርንጫፍ ወጭ አደረጎ መውሰዱን ነው፡፡ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች ተጠያቂ ሊሆኑ አይገባም ለማለት እንደምክንያት የጠቀሰው ድርጊቱ የተፈፀመው አገልግሎት እየሰጠ ሳይሆን እንደደንበኛ ቀርቦ ገንዘብ ሲያወጣ ተገቢ ማጣራት አልተደረገም በሚል ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው የስር 1ኛ ተከሳሽ በአመልካች ባንክ የወላይታ ቅርንጫፍ ሰራተኛ በመሆን ሲሰራ እንደነበር፤ ከዚህ ቅርንጫፍ ባንክ ደንበኛ ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ ወጭ አድርጎ ወደ ሻሸመኔ ቅርንጫፍ በማስተላለፍ ወጭ አድርጎ መወሰዱን ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው የስር 1ኛ ተከሳሽ ከሚሰራበት ቅርንጫፍ ባንክ ያለው የደንበኛ ሂሣብ ቁጥር በሕገወጥ መንገድ ገንዘብ በመወሰድ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ በማስተላለፍ ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ ማዋሉን ነው፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ ድርጊት ከሻሸመኔ ቅርንጫፍ ገንዘብ ማውጣት ብቻ ተነጥሎ የሚታይ ሳይሆን የወላይታ ቅርንጫፍ ሰራተኛ በመሆን ከህግ ውጭ ከደንበኛ ሂሣብ ገንዘብ ቀንሶ ማስተላለፍንና ወጪ አድርጎ መወሰዱን አብሮ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች የስር 1ኛ ተከሳሽ ዋሶች መሆናቸው አልተካደም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪዎች የስር 1ኛ ተከሳሽ በሥራው አጋጣሚ ያገኘው የደንበኛ ገንዘብ ከህግ ውጭ ቀንሶ በማስተላለፍና በማውጣት መውሰዱ በተረጋገጠበት ሁኔታ ከኃላፊነት ነፃ የሚያደርጋቸው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የፌዴራል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ የስር 1ኛ ተከሳሽ ድርጊት ህጋዊ ውጤት እና የተጠሪዎች የግዴታ አድማስ መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች የስር 1ኛ ተከሳሽ የወሰደው ብር 50,000 በአንድነትና በነጠላ ሊከፍሉ ይገባል፡፡ በመሆኑም የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነትና በነጠላ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ እያለባቸው ከኃላፊነት ነፃ ማድረጋቸው የፍ/ሕ/ቁ 1920፣1922 እና 1933 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው ብለናል፡፡ በዚሕም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደቡብ ችሎት በመ/ቁ 238695 03/06/2009 ዓ/ም የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 26861 በ23/01/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በመሻር የተሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 140694 በ03/09/2009 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ከስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ፈቃዱ ሙሉጌታ ጋር በአንድነትና በነጠላ በዋስትና ውሉ የተመለከተውን ብር 50,000 የመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 26861 በ23/01/2009 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ ጸንቷል፡፡
4. ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. የዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

አ/ገ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.145523

ሐምሌ 16 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ቻን ቹን ያን ኃላፊነቱ የተ/የግ/ማህበር

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ሞሚና ሁሴን -ጠበቃ ፈለቀ ዋጎ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመ/ደ/ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌ/መ/ደ/ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ ያቀረቡት የክስ አቤቱታ በአመልካችና ተጠሪ መከካል የመጋዝን ኪራይ መኖሩን በመግለጽ አመልካች የተከራየውን መጋዝን ከውሉ ጊዜ መጠናቀቅ በኋላ መጋዘኑን ሳይለቅልኝ ማሽኑን በማስቀመጡ መጋዘኑን በወር ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ ላከራየው እችል የነበረ ሲሆን በዚሁ ስሌት እስኪያስረክበኝ ድረስ ታስቦ እንዲከፍለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁን አመልካች ለቀረበበት ክስ መልስ የሰጠ ሲሆን በበኩሉ የብር 1,537,322.00/አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ብር/የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ተጠሪ ከሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 2005 ዓ.ም ድረስ አመልካች ማሽኑን እንዳያወጣ የከለከሉ በመሆኑ የጠየቁት የዚህ ወቅት ኪራይ ሊከፈል አይገባቸውም፤ሆኖም ከመስከረም 2006 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ማውጣት እየቻለ ስላላወጣ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ እስከ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ላለው ጊዜ በወር ብር 10,000.00/አስር ሺህ ብር/ሒሳብ የሶስት ዓመት ከአምስት ወር ብር 410,000.00/አራት መቶ አስር ሺህ ብር/ ሊከፍል ይገባል እንዲሁም ተጠሪ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር እንዲያቀርቡ፤በአመልካች በኩል የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ በተመለከተ ተጠሪ የባትሪ ድንጋይ ማምረቻ ማሽኑን ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል ቀሪዎቹ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ አመልካች በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 22 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፈው አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች እስከ ሚያዚያ 2009 ዓ.ም ድረስ ከመጋዝኑ ዕቃውን ሊያወጣ ያልቻለው በተጠሪ ጥፋት ስለመሆኑ በክርክር ሂደት የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑ ከታወቀ የአሁን አመልካች ክስ ከቀረበበትን የኪራይ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም እንዲሁም የአሁን ተጠሪ ከዚሁ መጋዝን ኪራይ ጋር በተያያዘ በአመልካች ላይ የኪራይ ገንዘብ ይከፈለኝ ክስ አቅርበው ብር 240,000.00 በመ/ቁ.196134 ማስወሰናቸውን እራሳቸው በክሳቸው ላይ ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ ከሳሽ በዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነ ክስ ማስቀረት ይቻል ዘንድ ከኪራይ ገንዘቡ ክስ ጋር በመጋዝን ያለውን ዕቃ አውጥቶ መጋዝኑን እንዲያስረክብኝ ይወሰንልኝ በማለት የተጠቃለለ ክስ በማቅረብ ጉዳቱን የመቀነስ ግዴታውን አልተወጣም በማለት አመልካች በቀረበው ክርክር ላይ ዳኝነት ሳይሰጥበት በዝምታ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ህዳር 20

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

እንደመረመርነው አመልካች የ3 ዓመት ከ5 ወር የኪራይ ገንዘብ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝቶታል። ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና ተጠሪ መካከል የመጋዘን ኪራይ ውል የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ከሐምሌ 20 ቀን 2001 ዓ.ም እስከ ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ለሶስት ዓመት መሆኑ፤ተጠሪ የውሉ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ሰኔ 5 ቀን 2004 ዓ.ም ያልተከፈላቸው የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈላቸው ክስ መሰርተው አመልካች ብር 240,000.00 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነ መሆኑ፤በዚሁ ክስ መጋዘኑን እንዲያስረክባቸው ዳኝነት ያልጠየቁ መሆናቸው፤ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ሚያዚያ 10 ቀን 2005 ዓ.ም ክስ ማቅረባቸው፤ተጠሪ የኪራይ ገንዘብ ካልተከፈለኝ በሚል ምክንያት አመልካች ተከራይቶ ከነበረው መጋዘን ውስጥ ያለውን ዕቃ እንዳያወጣ የከለከሉ ስለመሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው። ተጠሪ የመጋዘኑ የኪራይ ዋጋ ይታሰብልኛል በሚል ብቻ መጠበቅ ሳይኖርባቸው መጋዘኑ እንዲለቀቅላቸው ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ መጠየቅ ነበረባቸው። በፍ/ብ/ህ/ቁ 1802 እንደሚደነግገው ተጠሪ የጉዳት ኪሣራ የመቀነስ ግዴታ ነበረባቸው። አመልካችም ዕቃዎቹ ከመጋዘኑ እንዲያወጣ በህግ አለመጠየቁ ለደረሰው የጉዳት ኪሣራ አስተዋጾ አላቸው። በመሆኑም ለደረሰው የጉዳት ኪሣራ ሃላፊነት የአመልካች ብቻ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የጉዳት ኪሣራ አመልካች ብቻ እንዲከፍል መወሰኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1799(1) እና 1802 (1) እንዲሁም ተበዳዩ የሚካሰው ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ኪሣራ መሆን ስለሚገባው ለደረሰው ጉዳት ሃላፊነት ያለበት ሰው ታውቆ የተጎዳው ወገን ከደረሰበት ጉዳት ጋራ ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ መክፈል ሲለሚገባው ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2090 እና 2091 መሰረት ሲመዘን ህጋዊ ውሳኔ ነው ለማለት የሚቻል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አይደለም፡፡ ለደረሰው የጉዳት ኪሣራ ምክንያቶቹ ከላይ እንደተገለጸው አመልካችም ተጠሪም በመሆናቸው ለደረሰው የጉዳት ኪሣራ ሁለቱም ሃላፊነቱን መሸከም አለባቸው፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤት በተጣራው የኪራይ ዋጋ በብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ታስቦ የስድስት ወር አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት በዚህ መሰረት አመዛዝኖ መወሰን ሲገባው የተጠሪ ጉዳት የመቀነስ ሃላፊነት ግምት ውስጥ ሳይገባ አመልካች ብቻ ሙሉውን የጉዳት ኪሣራ እንዲከፍሉ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.134483 መጋቢት 5 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.140438 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ.ም በትእዛዝ ያፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ከመስከረም 2006 ዓ.ም እስከ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ3 ዓመት ከ5 ወር የኪራይ ሂሳብ በድምሩ ብር 410,000.00 /አራት መቶ አስር ሺህ ብር/ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የስድስት ወር ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ ብር/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. የተቀሩት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች አልተነኩም፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.134663

ጥር 21 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች - ተክሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሃይ መንክር

አመልካች - ጅማ ዩኒቨርሲቲ -ነ/ፈጅ ጌታቸው ነጋሽ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ - ቢሊሱማ ሚአ የዕፀዋት ዘር አቅራቢ ድርጅት -አቶ ቢሊሱት ሚአ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ አቶ ካሳሁን መሰለ፤ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ የአሁን አመልካች ነበሩ፡፡

ተጠሪ ያቀረበው ክስ ይዘት፡- የተለያዩ ችግኞችን ለማቅረብ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ውል የፈፀምኩ ሲሆን ስራውን መስራት ስለበዛብኝ 1ኛ ተከሳሽ ይህን ሥራ እንዲሰራልኝ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ እነሱም የችግኝ ዘር መቅረብን አስመልክቶ ጨረታ ላይ እንዲሳተፍ፤ የጨረታ ሰነድ እንዲገዛ እንዲያስገባ፤ ገንዘብ ፈርሞ እንዲወስድ፤ የወሰደውንም ገንዘብ በድርጅቱ ሥም (በቢሊሱማ ሚአ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዳአ ቅርንጫፍ ሂሳብ ቁጥር 1000070736679) ገቢ እንዲያደርግ ውክልና ስልጣን ሰጥቸዋለሁ፤ ይሁን እንጂ 1ኛ ተከሳሽ የሰጠሁትን ውክልና ስልጣን በህገወጥነት በመጠቀም ከ2ኛ ተከሳሽ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጅማ ቅርንጫፍ ሂሳብ ቁጥር 10005222 ከሆነው ብር 420,763.00 (አራት መቶ ሃያ ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ሶስት) በቀን 30/12/2006 ዓ.ም ወጪ በማድረግ ወደራሴ ሂሳብ ገቢ ማድረግ ሲገባቸው 2ኛ ተከሳሽ በቀጥታ ወደ ግሉ ሂሳብ ቁጥር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቢሾፍቱ ቅርንጫፍ ሂሳብ ቁጥር 216501041892 አዙሮ ወስዷል፤ 1ኛ ተከሳሽ ባለው ውክልና ስልጣን መሰረት ይህን ገንዘብ ወደራሴ ሂሳብ እንዲመልስ ብጠይቀውም ፍቃደኛ ስላልሆነ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘቡን ሊከፍለኝ ይገባል፤ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ችግኞች ለማቅረብ ስንስማማ የገንዘብ ክፍያ ሊከፈለኝ የሚገባውን ገንዘብ በሂሳብ ቁጥር 1000070736679 ገቢ እንዲያደርጉ ተስማምተን እያለ ከውሉ ውጪ ሆነ ብለው እኔን ለመጉዳት ገንዘቤን ወደ 1ኛ ተከሳሽ ሂሳብ በማስገባታቸው የአንድነት ተጠያቂነት አለባቸው፤ ስለሆነም ተከሳሾች ብር 420,763.00 (አራት መቶ ሃያ ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ሶስት) እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የሥር 1ኛ ተከሳሽ በሰጡት መልስ ብዙ ወጪ አውጥቼ ከቢሸፍቱ ከተማ እስከ ጅማ ከተማ ተመላልሼ ጨረታውን አሸንፌ ውል ተዋውዬ የተለያዩ እፅዋቶችን ከተለያየ ቦታ ገዝቼ አቅርቤያለሁ፤ ከሳሽ ገንዘብ ለመክፈልም ሆነ እፅዋቶችን ለማቅረብ ያደረገው አስተዋፅኦ የለም፤ ከጅማ ዩንቨርሲቲ የተከፈለውን የሽያጭ ዋጋ ከከሳሽ ጋር ተስማምተን ለተለያዩ የግዥ ዋጋዎች ክፍያ ውሏል፤ የጽሁፍ ደብዳቤ እኔ እየፈረምኩ የከሳሽ ባለቤት የድርጅቱን ማህተም መታልኝ 2ኛ ተከሳሽ ገንዘቡን በስሜ ባለው ሂሳብ እንዲያስገባ ጠይቄ ገንዘቡ እንዲገባ ተደርጎ ያለብን እዳ የተከፈለ ሲሆን የቀረው ትርፍ ጥቂት ስለሆነ ከከሳሽ ጋር ሂሳብ እንድንሰራ እና የሚከፈለኝን ክፍያ ከፍሎኝ እንዲያጠናቅቅ ከሳሽን ስጠይቀው ፈቃደኛ አልሆነም፤ ስለሆነም በሂሳብ ባለሙያ ተጣርቶ ያወጣሁት ገንዘብ እንዲቻቻል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአሁን አመልካች በበኩሉ በሰጠው መልስ ከከሳሽ ጋር በተደረገው ውል መሰረት ለቀረበው ችግኝ በውሉ የተገለፀውን ብር 420,763.00 ከፍያለሁ፤ ከሳሽ ስራውን የሚሰራው በተወካዩ 1ኛ ተከሳሽ በኩል ነው፤ 1ኛ ተከሳሽ ገንዘቡን መውሰድ እንደሚችል የውክልና ሰነዱ ይገልፃል፤ ይህ በመሆኑ ገንዘቡን ለ1ኛ ተከሳሽ ለመክፈል የህግ መሰረት ያለኝ ሲሆን በተሰጠው ውክልና ላይ የተመሰረተ ነው፤ የሚከፈለው ገንዘብ ወደተወካዩ ሂሳብ እንዳይገባ በሚል በውክልና ሰነዱ አልተገለፀም፤ በፌዴራል ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 6(5) መሰረት ከብር 50,000.00 የሚበልጥ ክፍያ ወደሚከፈለው ሰው ባንክ ሂሳብ ቁጥር በማሳለፍ ክፍያ መፈፀም እንዳለበት ይደነግጋል፤ በዚሁ መሰረት ተወካይ የሂሳብ ቁጥር 216501041892 አቅርበው ገንዘቡ ተላልፏል፤ የከሳሽ ተወካይ ክፍያ እንዲፈፀምለት የጠየቀበት ደብዳቤ በከሳሽ ማህተም ተደግፎ የቀረበ ነው፤ ስለሆነም ከሳሽ እኔን መክሰሱ ተገቢ አይደለም ብሏል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ 1ኛ ተከሳሽ ሂሳብ እንዲሰራ እና እንዲቻቻሉ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፤ ከሳሽ የሰጠው ውክልና ገንዘብ ወደራሱ ሂሳብ ቁጥር እንዲያስገባ የሚል አይደለም ስለሆነም ወደራሱ ሂሳብ ገንዘቡ እንዲገባ ማዘዙ ከውክልና ስልጣኑ በላይ አልፎ ለራሱ ጥቅም እንደሰራበት የሚያረጋግጥ በመሆኑ የወሰደውን ገንዘብ ሊመልስ ይገባል፤ 2ኛ ተከሳሽን (አመልካችን) በተመለከተም ገንዘቡን ወደ 1ኛ ተከሳሽ ሂሳብ ያስተላለፈ መሆኑን ያልካደ በመሆኑ፤ ይህን ያደረኩት በተፃፈልኝ ደብዳቤ ተመስርቼ ነው ይበል እንጂ 1ኛ ተከሳሽ በውክልና ስራውን እየሰራ መሆኑን ከውክልናው መረዳት የሚቻል ሲሆን የተሰጠው ውክልና ደግሞ ከችግኝ ሽያጭ የሚገኝ ገንዘብ ወደ ከሳሽ ሂሳብ ቁጥር መግባት እንዳለበት ተገልጾ የሂሳብ ቁጥሩም በውክልናው ላይ የተጠቀሰ በመሆኑ፤ ውክልናው ገንዘብ መግባት ያለበትን የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1ኛ ተከሳሽ መቀየር የሚችል ስለመሆኑም የተገለፀ ነገር ባለመኖሩ፤ 1ኛ ተከሳሽ ገንዘቡን በራሴ ሂሳብ አስገባው በማለት ያቀረበው ደብዳቤ ላይ የተመታው ማህተም መጀመሪያ ከሳሽ ፕሮፎርማ ሲያስገባ በፕሮፎርማው ላይ ካለው ማህተም የተለየ መሆኑን መረዳት ሲችል ገንዘቡን ወደ 1ኛ ተከሳሽ ማስገባቱ ስህተት ነው ኃላፊነትም አለበት ብሏል። በአጠቃላይ ሁለቱም ተከሳሾች ከችግኝ ሽያጭ የተገኘውን ገንዘብ በከሳሽ ባንክ ሂሳብ ማስገባት እያለባቸው ይህን ባለማድረጋቸው የአንድነትና ነጠላ ግዴታ አለባቸው በማለት ብር 420,763.00 ከ 13% የጠበቃ አበል እና ልዩ ልዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል።

ይግባኙ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክሩን ሰምቶ የአሁን አመልካች በተወካዩ ደብዳቤ ሲቀርብለት በደብዳቤው መሰል ትዕዛዝ ለመስጠት ሙሉ ስልጣን እንዳለው ማየትና ለተጠሪ ደውሎ ማጣራት ነበረበት የሚል ምክንያት በመጨመር የሥር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አጽንቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች ህዳር 28/2009 ዓ.ም ያቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ተጠሪ ለስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ካሳሁን መለሰ ችግኝ እንዲያቀርብ፤ በጨረታ ላይ እንዲሳተፍ፤ የግዢ ትዕዛዝ እንዲቀበል፤ ገንዘብ እንዲቀበል እና የተቀበለውን ገንዘብ በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ እንዲያደርግ ውክልና በሰጠበት ሁኔታ ተወካዩ ለአሁን አመልካች ችግኝ አቅርቦ የተከፈለውን ብር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

420,763.00 ወደ ተወካዩ የባንክ ሂሳብ ገቢ በማድረጉ አመልካች ከሥር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ለክስ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ ክፈል የመባሉን አግባብ ከግራ ቀኙ የውል ግንኙነት አንጻር ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል። ግራ ቀኙም የሥር ክርክራቸውን በማጠናከር በጽሁፍ ተለዋውጠዋል።

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል። እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት ችግኝ የማቅረብ ስራውን መስራት ስለበዛብኝ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ይህን ሥራ እንዲሰራልኝ የችግኝ ዘር መቅረብን አስመልክቶ ጨረታ ላይ እንዲሳተፍ፤ የጨረታ ሰነድ እንዲገዛ እንዲያስገባ፤ ገንዘብ ፈርሞ እንዲወስድ፤ የወሰደውንም ገንዘብ በድርጅቱ ሥም ገቢ እንዲያደርግ ውክልና ስልጣን ሰጥቸዋለሁ፤ ይሁን እንጂ ከአመልካች ጋር ችግኞች ለማቅረብ ስንስማማ የገንዘብ ክፍያ በሂሳብ ቁጥሬ ገቢ እንዲያደርጉ ተስማምተን እያለ ከውሉ ውጪ ገንዘቤን ወደ 1ኛ ተከሳሽ ሂሳብ በማስገባታቸው ተጠያቂነት አለባቸው፤ ገንዘቡን ብር 420,763.00 (አራት መቶ ሃያ ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ሶስት) እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው። አመልካች በበኩሉ ከተጠሪ ጋር በተደረገው ውል መሰረት ለቀረበው ችግኝ በውሉ የተገለፀውን ብር 420,763.00 ከፍያለሁ፤ ተጠሪ ስራውን የሚሰራው በተወካዩ በኩል ነው፤ ተወካዩ ገንዘቡን መውሰድ እንደሚችል በውክልና ሰነዱ ተገልጿል፤ በዚሁ መሰረት ተወካይ የሂሳብ ቁጥር 216501041892 አቅርበው ገንዘቡ ተላልፏል፤ ተወካይ ክፍያ እንዲፈፀም የጠየቁበት ደብዳቤ በተጠሪ ማህተም ተደግፎ የቀረበ ነው በማለት ተከራክሯል። የሥር ፍርድ ቤቶች በተጠየቀው ዳኝነት መሰረት አመልካች ገንዘቡን ለመክፈል ከተወካዩ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት በማለት የወሰኑት የአመልካች መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው።

ከፍሲል እንደተገለፀው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገው ውል መሰረት ለቀረበው ችግኝ በውሉ የተመለከተው የብር 420,763.00 ክፍያ አመልካች ለተጠሪ ተወካይ መክፈሉ ፤ ተጠሪ ስራውን የሚሰራው በተወካዩ በኩል መሆኑ፤ እንዲሁም ተወካዩ ገንዘቡን መውሰድ እንደሚችል በውክልና ሰነዱ ስልጣን የተሰጠው መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም። ተጠሪ በውሉ ላይ የገንዘብ ክፍያ በሂሳብ ቁጥሬ ገቢ እንዲያደርጉ ተስማምተን እያለ ከውሉ ውጪ አመልካች ገንዘቤን ወደ ተወካይ ሂሳብ በማስገባቱ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠያቂነት አለበት በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ከውሉ በኋላ ነሃሴ 12/2006 ዓ.ም ለተወካዩ በሰጡት ውክልና ገንዘቡን እንዲቀበል እና የተቀበለውን ገንዘብ በድርጅቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርግ ውክልና መስጠታቸውን አላስተባበሉም፡፡ የውክልና ሰነዱም ይህን የሚያሳይ ነው፡፡ ይልቁንም የሥር 1ኛ ተከሳሽ (ተወካይ) በተሰጠው ውክልና መሰረት ገንዘቡን መውሰዱን ሳይክድ ከአሁን ተጠሪ ጋር የመቻቻል እና የሂሳብ እናድርግ ጥያቄ ማቅረቡ ለክሱ መነሻ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ለውክልናው 3ኛ ወገን የሆነውን የአሁን አመልካችን ሳይሆን በወካይ እና ተወካይ መካከል የተፈጠረን የጥቅም ግጭት የሚመለከት ነው፡፡

ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2206 ፣ 2187 እና ተያያዥ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ውክልናው በላዩ ተዘርዝረው የተመለከቱትን ጉዳዩችና የነዚሁ ተከታታይ እና ተመሳሳይ የሆነውን እንደ ጉዳዩ አይነትና እንደ ልማድ አሰራር አስፈላጊ የሆነውን ማከናወን የሚያስችል ሲሆን ተወካዩ የፈፀመው ተግባር የወካይና ተወካይ ጥቅሞችን ግጭት የሚያስከትል በሆነ ጊዜ 3ኛው ወገን ይህን ሁኔታ ያወቀና ሊያውቅ የሚገባ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ኃላፊነት የሚኖርበት አይሆንም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ውል ካደረገ በኋላ ለወኪሉ የሰጠው ውክልና ችግኝ እንዲያቀርብ፤ በጨረታ ላይ እንዲሳተፍና የግዢ ትዕዛዝ እንዲቀበል የሚል ብቻ ሳይሆን ገንዘብ እንዲቀበል እና የተቀበለውን ገንዘብ በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ እንዲያደርግ ስልጣን የሚሰጥ ነው፡፡ አመልካች በውል ግዴታው መሰረት ብር 420,763.00 ብር ለተጠሪ ተወካይ ከፍሏል፡፡ ስለሆነም አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ ተወካይ መክፈሉ (በባንክ ሂሳቡ ማስገባቱ) ውሉን እና የውክልና ሰነዱን መሰረት ያደረገ አይደለም የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ በቀር አመልካች ውክልናውን ተከትሎ ክፍያ ለተወካይ የፈፀመው በወካይ እና ተወካይ መካከል ያለውን የጥቅም ተቃርኖ እያወቀ ወይም ማወቅ እየተገባው ነው የሚሰኝ ስለመሆኑ ክርክር እና ማስረጃ አልቀረበም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የውሉን ገንዘብ ለተጠሪ ተወካይ በመክፈሉ ከተወካዩ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት በማለት የደረሱበት መደምደሚያ በክርክሩ የተረጋገጠውን ፍሬነገር እና ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የህጉን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድንጋጌዎች ይዘት መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለን በአብላጫ ድምጽ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42179 ሰኔ 28/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 250095 ህዳር 20/2009 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሻሽሏል፡፡
2. የአሁን አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገውን ውል እና ተጠሪ ለተወካያቸው የሰጡትን የውክልና ስልጣን መሰረት በማድረግ የውሉን ገንዘብ ለተወካይ የከፈለ በመሆኑ ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሐሳብ ልዩነት

እኛ ስማችን በአራተኛ እና በአምስተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኞች አመልካች በተጠሪ ተወካይ ሂሳብ ቁጥር ገቢ በማድረጉ ከተወካዩ ጋር በአንድነት እና በነጠላ ለተጠሪ ሃላፊነት የለበትም በሚለው በአብላጫው ድምጽ ድምዳሜ ስለማንስማማ በሃሳብ ተለይተናል፡፡

አቶ ካሳሁን መሰለ የተጠሪ ተወካይ በመሆን ከአመልካች ጋር ያደረገው የችግኝ ሽያጭ ውል በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2189/1/ እና 2199 መሰረት አመልካች እና ተጠሪ መካከል እንደተደረገ ስለሚቆጠር፣ አመልካች ችግኙን ስረከብ ተጠሪ ገንዘቡን የማግኘት መብት ያለው ሲሆን አመልካችም ገንዘቡን ለተጠሪ የመክፈል ተነጻጻሪ ግዴታ እንደሚኖርበት ይታወቃል፡፡ ተጠሪ ለተወካዩ በሰጠው የውክልና ስልጣን ተወካዩ ገንዘብ ፈርሞ እንዲወስድ ጭምር ስልጣን የሚሰጥ ቢሆንም፣ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተደረገ የችግኝ አቅርቦት ውል አመልካች ገንዘቡን በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ እንዳለበት ተስማምቶ የተጠሪ የባንክ ሂሳብ ቁጥር የተሰጠው ሲሆን፣ አመልካች ይህ ስለመሆኑ ክዶ አልተከራከረም፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ መስማማቱን ሳይክድ ገንዘቡን በተወካዩ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ለማድረግ የቻለው ተወካዩ ይህን እንዲያደርግ በደብዳቤ የገለጸለት መሆኑን በመጥቀስ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ገንዘቡ በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲሆን ግራቀኝ ሲስማሙ በምክንያት ነው ተብሎ ስለሚታመን አመልካች ይህን ስምምነት የማክበር ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ ለተወካዩ የሰጠው ውክልና ገንዘብ እንዲቀበል ጭምር የሚያካትት ቢሆንም፣ ገንዘቡ በተወካዩ ሂሳብ ገቢ እንዲደረግ ግራቀኝ በተለየ ሁኔታ ያደረጉት ግልጽ ስምምነት በውክልና ሰነድ ላይ ከተመለተው የውክልና ስልጣን በልዩ ሁኔታ መታየት ያለበት በመሆኑ የማይፈጽምበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ገንዘቡን በተጠሪ የሂሳብ ቁጥር ገቢ ለማድረግ ከተጠሪ ጋር ባደረገው ስምምነት ግዴታ ገብቶ እያለ ከስምምነቱ ውጪ በሆነ ሁኔታ በተጠሪ ሂሳብ ገቢ ማድረግ ያለበትን ገንዘብ በተወካዩ የባንክ ሂሳብ ገቢ በማድረጉ ገንዘቡን ከተጠሪ ተወካይ ጋር በአንድነት እና በነጠላ ለተጠሪ የማይከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ በዚህም ምክንያት ከባልደረቦቻችን በሃሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.148158

ግንቦት 30 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች - ዳኜ መላኩ
ተክሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)
ቀነአ ቂጣታ
አብዬ ካሳሁን

አመልካች - አቶ በትግሉ ከበደ
ተጠሪ - ሽሬ እንዳስላሴ ማረሚያ ቤት

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 96204 በ30/10/2009 ዓ.ም ያሳለፈውን ትዕዛዝ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በሽሬ እንዳስላሴ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በተጠሪ ተቋም ለሚገኙ የህግ ታራሚዎች መንግስት በመደበላቸው በጀት መሰረት ከቀን 15/05/2007 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ዓመት ምግብ አብስዬ ለማቅረብ ከተጠሪ ጋር ውል አድርገናል፤ በሂደት ደግሞ በቀን 23/07/2007 ዓ.ም በውሉ መሰረት እየመገብኩ እንደነበር በማረጋገጥ ከቀን 24/07/2007 ዓ.ም ጀምሮ ከሸንኩርት አቅርቦት ተቀንሶ ወደ በርበሬ፣ ስኳር እና ስጋ እንዲሸጋሸግ፤ በዚህ መሰረት የስጋ አቅርቦት ከነበረበት በተጨማሪ አንድ ጊዜ በወር ከተሸጋሸገው ዋጋ ስጋ እንዳቀርብ፤ ውል ከመሻሻሉ በፊት ሳይቀርቡ የቀሩ ውዝፍ አቅርቦት በማጣጣም በቀጣይ በስጋ መልክ እንዳቀርብ ተስማምተናል፤ ነገር ግን ተጠሪ ከተሻሻለው ስምምነት ውጪ ስጋ አላቀረብክም በማለት መክፈል የሚገባውን ብር 230,472.00 አላግባብ የቀነሰብኝ በመሆኑ እንዲሁም በትርፍ ያቀረብኩት የሥጋ ዋጋ ብር 152,712.55 ስላልከፈለኝ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ያላቀረቡት አስቤዛ እና ስጋ በስምምነቱ መሰረት በግራሙ ተለክቶ ባላቀረቡት ልክ ክፍያው የተቀነሰ እንጂ ከውል ውጭ ያስቀረሁት ገንዘብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና የምስክሮቻቸውን ቃል እንዲሁም የሰነድ ማስረጃውን መርምሮ በግራቀኙ መካከል የተደረገው የተሻሻለ ውል በወር አንድ ጊዜ አምስተኛ ሆኖ የሚቀርብ ስጋ ለአንድ ታራሚ 700 ግራም ከሳሽ እንዲያቀርብ የሚያስገድድ ስለሆነ፤ ውሉ ከመሻሻሉ በፊት የነበሩ ውዝፍ አቅርቦቶች በስጋ መልክ እንዲቀርቡ ተስማምተው ውዝፍ የስጋ አቅርቦት በተሻሻለው ውል መሰረት ማቅረብ የነበረበትን አመልካች ስላላቀረበ፤ እንዲሁም ሌሎች ለክስ ምክንያት የሆኑ አቅርቦቶች አልቀረቡም ተብሎ በተጠሪ የተቆረጠው ገንዘብ ከሳሽ ግዴታውን ባለመፈፀሙ ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል፤ ስለሆነም አመልካች በውሉ መሰረት መቅረብ የነበረባቸውን ስላላቀረበ ለክስ ምክንያት የሆነው ገንዘብ ተጠሪ ቆርጦ ማስቀረቱ ውሉን መሰረት ያደረገና አግባብነት ያለው ነው በማለት የክሱን ገንዘብ ተጠሪ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ቅሬታቸውን ለሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 21/2010 ዓ.ም ያቀረቡት ማመልከቻ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተፈፀመው የመጀመሪያ ውል በሌላ ውል ተሻሽሎ እያለ ክፍያው ግን በመጀመሪያው ውል መሰረት እንዲፈፀም በሥር ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1826 እና ተከታዮች አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክርና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በስር ፍርድ ቤቶች በተላለፈው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን አመልካች ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ከተሻሻለው ስምምነት ውጪ ስጋ አላቀረብክም በማለት መክፈል የሚገባውን ገንዘብ አላግባብ የቀነሰብኝ በመሆኑና በትርፍ ላቀረብኩት የሥጋ ዋጋም ስላልከፈለኝ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ያላቀረቡት አስቤዛ እና ስጋ በስምምነቱ መሰረት በግራሙ ተለክቶ ባላቀረቡት ልክ ክፍያው የተቀነሰ እንጂ ከውል ውጭ ያስቀረሁት ገንዘብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙ በዚህ መልኩ የተካካዱበትን ፍሬ ነገር በማስረጃ ያጣራው የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ስምምነት ባደረጉባቸው ውሎች መሰረት ማቅረብ የነበረባቸውን ስላላቀረቡ የክሱን ገንዘብ ተጠሪ ቆርጦ ማስቀረቱ ውሉን መሰረት ያደረገና አግባብነት ያለው ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ የፍሬ ነገር መደምደሚያ ተቀብሎታል፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው የመጀመሪያው ውል በሌላ ውል ተሻሽሎ እያለ ክፍያው በመጀመሪያው ውል መሰረት እንዲፈፀም በሥር ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1826 እና ተከታዮች አኳያ ለመመርመር በሚል ሲሆን መዝገቡ እንደሚያሳየው የቀደመው ውል መሻሻል የተደረገበት በአቅርቦት እንጂ በዋጋ ጉዳይ አይደለም፡፡ በቀደመው ውል ከነበረው የቀይ ሽንኩርት፣ ቲማቲም እና አትክልት አቅርቦቶች ላይ በመቀነስ በምትኩ ወደ በርበሬ ስኳርና ስጋ አቅርቦት እንዲጨመር መስማማታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠውም አመልካች ማቅረብ የነበረባቸውን እንዳላቀረቡ ተረጋግጧል በሚል እንጂ ጉዳዩ ከክፍያ ልዩነት አንፃር ታይቶ አይደለም፡፡ ከዚህም ሌላ ጉዳዩ ከውል መተካት አንፃር እንዲታይ ይተካል በተባለው እና ተተክቷል በሚባሉት ውሎች መካከል ያለው የውለታ ጉዳይም ሆነ የውለታው ምክንያት በይዘቱ አዲስ መሆን እንዳለበትና ይህንኑ በውለታውም አይነት ሆነ ከውለታው ምክንያት አንፃር ታይቶ አዲስ የሆነው ውል ከዚህ ቀደም ተደርጎ በነበረው ውል ላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች በማያጣራጥር አኳኋን ሊያስቀር የሚችል ፈቃድ ከተዋዋይ ወገኖች እንዲኖር አስፈላጊ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1826 እና 1828 የተደነገገ ሲሆን ውልን የማሻሻል ጉዳይ ግን ከዚህ አንፃር ሊታይ እንደማይገባ መገንዘብ ይቻላል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሥር ፍርድ ቤት ከፍሲል እንደተገለፀው አመልካች በውሎቹ መሰረት ማቅረብ የነበረባቸውን ስላላቀረቡና ግዴታቸውን አለመፈፀማቸው በማስረጃ ተረጋግጧል ለክስ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ተጠሪ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት የወሰነው ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን ባለው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ካለ ከሚመለከት በቀር መሰል የፍሬ ነገር ክርክርን መርምሮ እና ማስረጃ መዝኖ ውሳኔ የሚሰጥም አይደለም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በገቡት ውል መሰረት አለማቅረባቸውና ባንደሉት አቅርቦት ልክ ተጠሪ ክፍያ መቀነሱ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ውሉን እና ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የሽረ እንዳስላሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 13740 ህዳር 15/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 21259 መጋቢት 6/2009 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 96204 በ30/10/2009 ዓ.ም የተላለፈው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ. 156408

ቀን፡- 24/1/2011ዓ.ም

ዳኞች፡..1. ተክሊት ይመሰል

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራው

5. አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡.፡- አቶ አክሊሉ ጌታሁን ጠበቃ ክፍለ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፍሬህይወት አሰፋ ጠበቃ ቸርነት ተገኝ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

1. ጉዳዩ የብድር ዉል መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን የጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻ ነዉ፡፡ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 226304 ሚያዝያ 12 ቀን 2007ዓ.ም ባቀረቡት ክስ የአሁን ተጠሪ በብድር የወሰዱት ብር 200,000 እንዲመለስላቸዉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በ23/2/2008ዓ.ም በሰጡት መልስ ከአመልካች የወሰዱት ብድር አለመኖሩን፣ ለተጠሪ እናት የተላከዉ ብር 60,000 ፈርመዉ የተቀበሉት ብድር አለመሆኑን በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲሆን አመልክቷል፡፡
2. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት የስር ፍ/ቤትም በተጠሪ ተፈረመ የተባለዉ ሰነድ በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ ዘርፍ እንዲመረመር የተደረገ ሲሆን በዉሉ ላይ ያለዉን ፊርማ የተጠሪ /ተከሳሽ/ አለመሆኑን መረጋገጡን በመግለጽ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረጉት የብድር ዉል የለም፡፡ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰዉ ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተደረገ የብድር ዉል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለም፣ ተከፈለ የተባለዉ ብር 60,000 ከብድር ዉሉ ጋር ግንኙነት የለዉም በማለት የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

3. የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔና ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡ አመልካች መጋቢት 24 ቀን 2010ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የብድር ስምምነት መኖሩን የሚያስረዱ ተጨማሪ ምስክሮች እንዳያቀርቡ እንደተከለከሉ፣ የብድር ዉል ለማስረዳት የቀረበዉ ሰነድ ባልተካደበት ለምርመራ መላኩ፣ የምርመራ ዉጤቱም እንደ መጨረሻ ብቸኛ መረጃ ተደርጎ መወሰዱ በህጉ አግባብ አይደለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የአመልካች አቤቱታ የመረመረዉ አጣሪ ችሎትም የብድር ዉል ሲፈረም የነበሩ ምስክሮች ሳይሰሙ ተጠሪ ሊጠይቁ አይገባም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ከሰ/መ/ቁ. 114553 አንፃር እንዲመረመር በድምጽ ብልጫ ለዚህ ችሎት አስቀርቦታል፡፡ ተጠሪ ሰኔ 7 ቀን 2010ዓ.ም በሰጡት መልስ በስር ፍ/ቤት የብድር ዉል የሌለ መሆኑን ተረጋግጦ የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸና አመልክቷል፡፡ አመልካች አቤቱታቸዉን የሚደግፍ የመልስ መልስ ሰኔ 22 ቀን 2010ዓ.ም አቅርቧል፡፡

4. ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸዉ ሲሆን እኛም የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ፍርድ ላይ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

5. እንደመረመርነዉም የአመልካች መሰረታዊ የዳኝነት ጥያቄ በብድር የተወሰደዉ ብር 200,000 እንዲመለስላቸዉ የሚያመለክት ነዉ፡፡ ተጠሪ ብድር አለመዉሰዳቸዉን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በህጉ አግባብ የተቋቋመ የብድር ዉል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለዉ ብድር ዉል ነዉ፡፡ አመልካች /ከሳሽ/ የብድር ዉል መኖሩን ለማስረዳት ተጠሪም የተበደሩ መሆኑን ከተረጋገጠ ክፍያ መፈፀማቸዉን ለማስተባበል መቅረብ ያለበት የማስረጃ ዓይነት ምን መሆን እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በብድር የተሰጠዉ ገንዘብ ከብር 500,00 በላይ ከሆነ ብድሩን ለማስረዳት የብድር ዉል መቅረብ ያለበት ሲሆን የብድር ዉሉ ካልቀረበ ደግሞ ተበዳሪዉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ቤት ካላመነ ወይም በቃለ መሀላ ስር ሆኖ ቃሉን ካልሰጠ በስተቀር በሌላ አግባብ ማስረዳት እንደማይቻል ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ አመላለሱ በተመለከተም ተመሳሳይ የማስረጃ መርህ የሚከተል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2472(3) ደንግጓአል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ብር 200,000 ማበደራቸው በመግለጽ ክስ ቢያቀርቡም የብድር ዉሉ በተጠሪ አልታመነም፡፡ የብድር ዉል የተባለዉ ሰነድ በፎረንሲክ ምርመራ የተደረገለት ሲሆን በሰነድ ላይ ያረፈዉ ፊርማ የተጠሪ አለመሆኑን ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ተጠሪ ወሰዱት የተባለዉ ብር 60,000 ብድር ክርክሩ የተያያዘ አለመሆኑን የስር ፍ/ቤት ማረጋገጡን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት በሰነድ ላይ የተመለከቱ ምስክሮች ሳይሰሙ ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በሚል ነዉ፡፡ በመሰረቱ ዉሉ በጽኑፍ እንዲሆን በህጉ በተመለከተበት ሁኔታ ሰነድ ራሱ አስረጂ መሆኑን ነገር ግን ሰነድ የተቀደደ፣ የተሰረቀ፣ የጠፋ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ ዉሉ በምስክሮች ማስረዳት የሚቻልበት ስርዓት ተመልክቷል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ሰነድ ቀርቧል፡፡ በሰነዱ ላይ ያረፈዉ ፊርማ ግን የተጠሪ አለመሆኑን ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አመልካች በተጠሪ ተክዶ በፎረንዚክ ምርመራ ተጠሪ ፊርማ አለመሆኑን የተረጋገጠዉ ሰነድ ላይ ያለዉ ፊርማ የተጠሪ ስለመሆኑ በሰዉ ምስክሮች ለማስረዳት ያቀረቡት አቤቱታ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2006 እና 2472(1) ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት ያላገናዘበ ነዉ ብለናል፡፡

6. አመልካች ሌላ ያቀረቡት አቤቱታ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ 114553 በሰጠዉ ዉሳኔ የብድር ዉል መኖሩን በሰዉ ምስክሮች ማስረዳት እንደሚቻል የሚያሳየዉ ገዥ ዉሳኔ ታልፏል የሚል ነዉ፡፡ የሰ/መ/ቁ. 114553 አስቀርበን እንደመረመርነዉም በብድር ዉሉ ላይ ያለዉ ፊርማ የኔ አይደለም የሚል ክርክር በመነሳቱ በብድር ዉሉ ላይ ያለዉ ፊርማ ተመርምሮ የተበዳሪ ስለመሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን መነሻ በማድረግ እንዲሁም ተጨማሪ ማጣራት በማድረግ ዉሳኔ መስጠቱን የሚያሳይ እንጂ የተካደዉ ፊርማ የተበዳሪ ስለመሆኑ ሳይንሳዊ በሆነ የምርመራ ዘዴ ሳይረጋገጥ የሰዉ ምስክሮች ብቻ በማዳመጥ ዉሳኔ አለመስጠቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ መሰረት የሌለዉ መሆኑን ከሚያሳይ በቀር የሰበር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉሳኔዉ በጭብጥ ከተያዘዉ ጉዳይ አንድና ተመሳሳይ ነዉ ተብሎ የሚወስድበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ አመልካች በሰበር ቅሬታቸዉ ብር 60,000 መከፈሉን ክርክር ያልቀረበበት ነዉ፡፡ ያሉ ቢሆንም ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት መልስ ብር 60,000 ለተጠሪ እናት የተላከ እንጂ በብድር ወሰዱት የተባለዉ ብር 200,000 ከፊል ክፍያ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ክሱን ለማስረዳት የብድር ዉል የተባለዉን ከማቅረብ ዉጭ በቃለ መሀላ ስር ሆነዉ ተጠሪ እንዲያረጋግጡ ያቀረቡት ክርክር ስለመኖሩ መዝገቡ አያሳይም፡፡ በዚህ ሁሉም ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል በህጉ አግባብ የተቋቋመ የብድር ዉል የለም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ህግን ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 226304 በ18/2/2010 የሰጠዉ ፍርድ፣ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. በመ/ቁ. 186042 በ 14/6/2010ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለዉ ወጪና ኪሳራ ካለ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉ ይቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሸምሱ ሲርጋጋ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡አቶ ገ/ሚካኤል በርሀ

ተጠሪ፡ አቶ ገ/ዮሃንስ ወ/ጊዮርግስ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የአፈጻጸም ክርክር ላይ ልዩ ልዩ ወጪና ወለድ ክፍያ የሚመለከት ነዉ፡፡ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ አመልካች የፍርድ ባለእዳ ተጠሪና ሌሎች በዚህ መዝገብ ያልተጠሩ ሰዎች የኢት/ልማት ባንክን ጨምሮ ፍርድ ባለመብቶች ሆነዉ የአመልካች ንብረት የሆነዉን በመቀሌ ከተማ የሚገኝ የእንጨትና የብረታ ብረት ስራ ድርጅት ከነቤቱ በሀራጅ ለማሸጥ ሲንቀሳቀሱ ተጠሪ የፍርድ ባለገንዘቦችን ብር ለመክፈል ተስማምቶ ንብረቱን ያለጨረታ ለማስቀረት እንዲችል ፍርድ ቤቱን ጠይቆ የመቐለ ማእከላዊ ፍርድ ቤት ፈቅዶለት ንብረቱን በ27/10/1999 ዓ.ም በተሠጠ ትእዛዝ የተረከበ ሲሆን አመልካች ይህንን በመቃወም ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ችሎት ያቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ሰበር ችሎቱም በመ/ቁ/45733 በ29/11/02 ዓ.ም በሰጠዉ ፍርድ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳን ተክቶ ለባለመያዣ ባንክ ገንዘቡን ከፍሎ ንብረቱን ካስለቀቀ እና ለሌሎች ባለገንዘቦች ገንዘባቸዉን ከከፈለ በኋላ የፍርድ ባለእዳዉን ንብረት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለጨረታ እንዲረከብ ሳይሆን ጨረታ ተከናውኖ ራሱም ከፈቀደ በጨረታው ተካፋይ ሆኖ ሊሆን ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ጨረታ እንዲከናወን በትእዛዝ መልሷል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የአመልካች ንብረት በጨረታ ከተሸጠ በኋላ ተጠሪ ቀደም ሲል ለፍርድ ባለገንዘቦች የከፈለው ገንዘብ እስከነወለዱ ከሽያጭ ገንዘብ ላይ እንዲከፈለው በመጠየቁ የመቐሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ዋናው ፍርድ ላይ ለባለገንዘቦቹ የተፈረደው ዋና ገንዘብ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ወለድ እንደሚታሰብ ስለተወሰነ ተጠሪ በጊዜው ገንዘቡን ለባለገንዘቦች ከራሱ ወጪ አድርጎ ስለከፈለ ወለድ ሊያገኝ ይገባል ካላ በኋላ ወለዱ ሊታሰብ የሚገባው ከመቼ ጀምሮ ነው ለሚለው ጥያቄ ላይ በአብላጫ ድምጽ ተጠሪ ድርጅቱን ከተረከበበት ከ27/10/99 ዓ.ም እስከ 13/03/08 ዓ.ም ማለትም አመልካች ዋናውን ገንዘብ በሞዴል 85 እስከ አስያዘበት ጊዜ ድረስ ያለውን ወለድ በባንክ ምጣኔ መሰረት ተሰልቶ ለተጠሪ እንዲከፈል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡አናሳው ድምጽ ወለድ ለተጠሪ ሊታሰብ እንደሚገባ ተስማምቶ ጊዜውን በተመለከተ ግን በከፍተኛ ፍርድ ቤት በ27/10/99 ዓ.ም በተሰጠ ትእዛዝ ተጠሪ ድርጅቱን እንዲረከብ ተደርጎ በእጁ መግባቱ ተረጋግጦ የአፈጻጸም መዝገብ ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጨረታ ሊካሄድ ይገባል በሚል ይህንን ትእዛዝ እስከሻረበት 29/11/02 ዓ.ም ድረስ ላለው ጊዜ ተጠሪ ድርጅቱን በእጁ አድርጎ ሲጠቀም ስለነበር ወለድ ሊታሰብ አይገባም ይልቁንም ወለድ ሊታሰብለት የሚገባው በ29/11/02 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ገንዘቡን በሞዴል 85 እስከአስያዘበት ጊዜ ድረስ መሆን አለበት የሚል ሀሳብ አስፍሯል፡፡

አመልካች በዚህም ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ የቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች ሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በግራቀኙ መካከል በነበረው የገንዘብ ክርክር የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/01885 በ17/10/08 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በባንክ እዳ ዋስትና ተይዞ የነበረውን አከራካሪ ቤት የተረከቡት በ13/03/08 ዓ.ም ቢሆንም የባንኩን ወለድ ከ27/10/99 እስከ 13/03/08 ዓ.ም ታስቦ ይክፈሉ መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል በሚል ሰበር አጣሪ ጭብጥ ይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ መጥሪያ ደርሶ ተለዋጭ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀጠሮም ጠይቀዉ በተሰጠዉ ተለዋጭ ቀጠሮ መልስ ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡

መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ተጠሪ ቀደም ሲል በመቐሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/01885 በ27/10/99 ዓ.ም በሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት አከራካሪዉን ቤትና ድርጅት እንዲረከብ የተደረገዉ ከአመልካች የሚፈለግ የኢት/ልማት ባንክ ብድር ብር 740,963.00 ፣የወ/ሮ ስላስ በርሄ እዳ ብር 80,688.00፣የአቶ ስዩም ተሰማ እዳ ብር 125,568.00 እና የተጠሪዉ ገንዘብ ብር 177,561.00 በድምሩ ብር 1,134,780.00 በመክፈሉ ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ተችሏል፡፡በዚሁ አግባብ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳን/የአመልካቹን /ንብረት ተረክቦ ስመ ሀብቱም በስሙ ተመዝግቦለት ንብረቱን እየተጠቀመ የቆየ ሲሆን አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ተጠሪ የአመልካችን ንብረት ያለጨረታ መረከቡ ተገቢ አይደለም ተብሎ በሰበር መ/ቁ/45733 ዉሳኔ ተሰጥቶ በንብረቱ ላይ ጨረታ እንዲደረግ ወደ ስር ፍርድ ቤት መመለሱም ተረጋግጧል፡፡ይህንን ተከትሎ አመልካች በተጠሪ እጅ ያለዉ ቤትና ድርጅት በጨረታ እንዲሸጥ ትእዛዝ እንዲሰጥ ለከፍተኛዉ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ በክርክር ላይ እያለ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ክርክር የተነሳበትን ቤትና ድርጅት በተጠሪ ስም በመያዣ ይዞ ብር 1,700,000 መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ ዉል ያበደረዉ መሆኑን ገልጾ የቅድሚያ መብት ያለዉ በመሆኑ በጨረታ እንዳይሸጥ በጣልቃ ገብነት ስለመከራከሩና እስከ ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ደርሶ ባንኩ ንብረቱ እግድ ያለበትንና ሰበር መ/ቁ/45733 ዉሳኔ የተሰጠበትን በሚጻረር ሁኔታ በመያዣነት መያዙ ከቅን ልቦና ዉጪ ነዉ ተብሎ ስለመወሰኑ ሰበር መ/ቁ/80258 ላይ በ07/09/05 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ ይዘት ያስረዳል፡፡ ከዚህም ባሻገር ተጠሪና ባለቤቱ የሆነችዉ ወ/ሮ/ ኪሮስ ሲባጋድስ እግድ ያለበትን ንብረት እግድ እንደሌለበት አስመስለዉ ለባንክ መያዣ አስይዘዉ ብድር ወስደዋል ተብለዉ በማታለል ወንጀል ተከሰዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ የተላለፈባቸዉ ስለመሆኑም የፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ከዚህ መዝገብ ጋር ተያይዟል፡፡ከዚህ በኋላ አመልካች ቤቱ ከተጠሪ እጅ ወጥቶ በጨረታ እንዲሸጥ ሲጠይቁ ተጠሪ ለፍርድ ባለገንዘቦች የከፈለዉን ገንዘብ በሞዴል 85 እንዲያስይዙ የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/01885 ላይ ትእዛዝ መስጠቱንና አመልካችም ገንዘቡን በ13/03/08 ዓ.ም በሞዴል 85 ማስያዙ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነዉ፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንግዲህ አከራካሪዉ ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ወለድ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? ወለድ ሊከፍል ይገባል ከተባለስ ከመቼ ጀምሮ ይታሰብለታል? የሚለዉ ነዉ ።በመሰረቱ ባለእዳ ወለድ ሊከፍል የሚገደደዉ በዉል ሲገለጽ ወይም በፍርድ ሲወሰን አለ.ያም በህግ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን እንደሆነ ከፍ/ብ/ህግ አንቀጽ1803፣1751 እና 2478 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል።በመሆኑም አመልካች የፍርድ ባለእዳ መሆኑና የፍርድ ባለመብቶች ገንዘብ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ወለድ እንዲታሰብ በዋናዉ ክርክር መዝገብ ፍርድ መሰጠቱ እና ተጠሪ አመልካችን ተክቶ ለፍርድ ባለገንዘቦች ገንዘቡን መክፈሉ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ ዋናዉ ገንዘብ ተጠቃሎ እስከ ከፈለዉ ድረስ ዋናዉን ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ወለዱንም ጭምር ማግኘት እንዳለበት በፍርድ የተላለፈለት መብት ከመሆኑ አኳያ በመርህ ደረጃ ተቀባይነት ያለዉ ነዉ። ነገር ግን ተጠሪ የአመልካችን ንብረት ከ27/10/99 ዓ .ም ጀምሮ በእጁ አድርጎ እስከ 13/03/08 ዓ.ም ድረስ ላለፉት 9 ዓመታት ንብረቱን በእጁ አድርጎ እየተጠቀመበት መሆኑን በመግለጽ ወለድ ሊታሰብ እንደማይገባ አመልካች አጥብቆ መከራከሩን መዝገቡ ያስረዳል።ስለሆነም በእርግጥም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በ27/10/99ዓ.ም በተሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት የአመልካችን ንብረት በእጁ አድርጎ ሲጠቀም በቆየበት ጊዜ ከዋና ገንዘብ በተጨማሪ ለገንዘቡ ወለድ እንዲታሰብ ማድረግ ተጠሪ ያለአግባብ እንዲበለጽግ አመልካች ደግሞ ያለአግባብ እንዲጎዳ የሚያደርግ እንደሆነ መረዳት አዳጋች አይደለም።

ስለሆነም ለተጠሪ ወለድ መታሰብ አለበት ቢባል እንኳን ወለድ ከመቼ ጀምሮ ሊታሰብ ይገባል የሚለዉን ለመወሰን ተጠሪ የአመልካችን ንብረት በሰበር ችሎት በመ/ቁ/45733 በተሰጠ ፍርድ መሰረት መልሶ ለአመልካች ያስረከበበት ወይም ከተጠሪ እጅ ወጥቶ በሃራጅ የተሸጠበት ቀን በግልጽ ሊታወቅ ይገባል።በዚህ ረገድ ደግሞ አመልካች ቤቱና ድርጅቱ በሃራጅ እንዲሸጥ ገንዘቡን በሞዴል እንዲያስዝ የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ መስጠቱን እና ቤቱና ድርጅቱ ከተጠሪ እጅ ወጥቶ ወደ ሐራጅ ስርዓት እንዲገባ የተደረገዉ በ13/03/08 ዓ.ም ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ መሰጠቱን ገልጾ አመልካች ያቀረበዉን ክርክር የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚያስለዉጥ ክርክርና ማስረጃ በተጠሪ በኩል አልቀረበበትም።ከዚህም ባሻገር ቀደም ሲል ተጠሪ ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመ/ቁ/ 81191 በ05/05/08 እና በመ/ቁ/52053 በ04/06/08 ዓ.ም በተሰጠ ትእዛዝ የተጠሪ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወለድ ጥያቄ ዉድቅ ተደርጎ ያደረዉን ንብረቱ በጨረታ ከተሸጠ በኋላ በሂሳብ መተሳሰብ ሰበብ የወለድን ጉዳይ እንደአዲስ በተጠሪ በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ተቀብሎ በ17/10/08 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ ወለድ ከ27/10/99 ዓ.ም እስከ 13/03/08 ዓ.ም ድረስ ይታሰብለት ማለቱ ፍርድ ቤቱ ራሱ በ05/05/08 ዓ.ም ከሰጠዉ ትእዛዝ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ስነስርዓታዊ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የፍርድ ማስፈጸሚያ ይሆናል የተባለዉን የአመልካችን ንብረት ተጠሪ ከ27/10/1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 13/03/08 ዓ.ም ማለትም ለፍርድ ባለገንዘቦች የከፈለዉ ዋና ገንዘብ በሞዴል እስከተያዘበት እለት ድረስ ንብረቱን በእጁ አድርጎ ሲጠቀምበት የነበረ ከመሆኑም በተጨማሪ በባንክ በመያዣ አስይዞ ገንዘብ ብድር የወሰደበት መሆኑ ጭምር በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በአመልካች ንብረት ሲጠቀም መቆየቱ ተረጋግጦ እያለ ለዚሁ ጊዜ ዉስጥ ከዋናዉ ገንዘብ በተጨማሪ አመልካች ለተጠሪ ወለድ እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምጽ የተሰጠዉ ዉሳኔ እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናዉ ፍትሃዊና ምክንያታዊ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1ኛ/የመቐሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/01885 ላይ በ17/10/08 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/87641 በ09/03/09 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/ተጠሪ በአመልካች ንብረት ሲጠቀም መቆየቱ ስለተረጋገጠ አመልካች ወለድ የመክፈል ሃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መቁ149301

ግንቦት 27 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ውዴ ደሴ- ጠበቃ አቶ አለማየሁ የኔት ቀረበ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1.አወቀ ደሴ
2 አዲስ ደሴ } የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በአዊ ብሔረሰብ ዞን የባንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች ሲሆኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ከሳሾች /የአሁን ተጠሪዎች/ በ14/07/2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ወላጅ አባታቸው አቶ ደሴ ካሰ እና እናታቸው ወ/ሮ እምየ በላይ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ገልጸው የውርስ ንብረቶችን 1ኛ/ 56 ዘንግ ቆርቆሮ ቤት ግምቱ ብር 6,000 /ስድስት ሺህ ብር/፣ ሳር ቤት ግምቱ ብር 3,000 /ሶስት ሺህ ብር/፣100 ባህርዛፍ ግምቱ ብር 3,000 /ሶስት ሺህ ብር/ 2ኛ/ አዋሳኙን ጠቅሰው በተለያዩ በአምስት ቦታዎች የሚገኝ የእርሻ መሬት ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ ይዘው ያሉትን የውርስ ድርሻ እንዲሰጡዋቸው ፈቃደኛ ሆነው ስላልተገኙ ድርሻቸውን እንዲሰጡ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ በቀን 12/09/2009 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ይኸውም የከሳሾች እናት በ1993 ዓ/ም ስለሞቱ የእናታቸውን ድርሻ ለመጠየቅ መብታቸው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000/1/ መሠረት በሶስት ዓመት ይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ ለፍሬ ነገሩ በሰጡት መልስ ቆርቆሮ ቤቱን በተመለከተ ከሚች አባታቸው በቀን 18/6/2007 ዓ/ም በተደረገ የሥጦታ ውል መሠረት ተከሳሽ ከባለቤታቸው ጋር የሰሩት በመሆኑ ከሳሾችን አይመለከታቸውም፣ሳር ቤቱን ድርሻቸውን መካፈል ይችላሉ፣ከሳሾች አዋሳኞችን ጠቅሰው ካቀረቡት የእርሻ መሬት መካከል በክሳቸው ተራ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሱትን አራት ቀዳ መሬት አባታቸው በሥጦታ ውል የሰጡ በመሆኑ ከሳሾችን አይመለከታቸውም የተቀረውን የእርሻ መሬት በተመለከተ የእናታቸው ድርሻ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ የአባታቸውን ድርሻ ከተከሳሽ ጋር መካፈል ይችላሉ፣ባህርዛፉንም በተመለከተ ድርሻቸውን መካፈል እንደሚችሉ ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የባንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት በይርጋ መቃወሚያ ላይ ማስረጃዎችን ሰምቶ ግራ ቀኙ እናት ከሞቱ በኃላ ክርክር የተነሳባቸው ንብረቶች አባታቸው እስከ ሞቱበት 2007 ዓ/ም ድረስ በእጃቸው የቆየ በመሆኑ እና የሥር ከሳሽ ከአባታቸው ጋር አብረው ቢኖሩም ንብረቶቹን የያዙት ከእሳቸው ሞት በኃላ በመሆኑ ይርጋ ሊያገድ አይችልም ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ ፍሬ ነገሩንም በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮ፣ ምስክሮችን ቃል ሰምቶና ሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ የቆርቆሮ ቤት አባታቸው በውል በሰጡት ቦታ ላይ ተከሳሽ እና ባለቤታቸው የሰሩበት መሆኑ ስለተረጋገጠ ለከሳሾች አይገባም፣ ተከሳሽ አባቷ በሥጦታ ሰጥቶኛል ያለችውን 4 ቀዳ መሬት በተመለከተ ሚች ሥጦታ ቢሰጥም እንኳ የራሱን ድርሻ እንጂ የሌሎችን ልጆች በሚጎዳ መልኩ መስጠት የለበትም፣ ማለትም የእናታቸውንም ሆነ የራሱን ድርሻ ማለት ነው፡፤ የሳር ኪዳን ቤት፣የባህርዛፍ ተክል የሚቾቹን ተከሳሽ መያዟን እና ያለ መሆኑን ያመነች በመሆኑ ባመነችበት መሠረት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 242 መሠረት በዓይነት ወይንም በግምት ድርሻቸውን ለከሳሾች ልትሰጥ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች /የሥር ከሳሽ/ ውሳኔውን ቅር ተሰኝተው ለአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡የይግባኝ ቅሬታ ይዘትም፡- የእናታቸው ድርሻ በይርጋ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀሪ መሆን ሲገባው በብይን መታለፉ አግባብ አይደለም፤ አባቴ በሥጦታ የሰጠኝን አራት ቀዳ መሬት ከሳሾችም እንዲካፈሉ መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙን ተቀብሎ ክርክራቸውን ከሰማ በኃላ በይርጋ አይታገድም መባሉ ተገቢ እንደሆነና ሟች ለአሁን አመልካች በሥጦታ የሰጡትን አራት ቀዳ የእርሻ መሬት አመልካች /ይግባኝ ባይ/ ለመልስ ሰጪዎች /ለአሁን ተጠሪዎች/ ታካፍል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ተቀብሎ ክርክራቸውን ከሰማ በኃላ ለይግባኙ ምክንያት የሆነው አራት ቀዳ መሬት የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ወላጆች መሆኑን፣ እናታቸው በ1993 ዓ/ም መሞታቸውን፣ ወላጅ አባታቸው ደግሞ በ2007 ዓ/ም መሞታቸውን፣ መልስ ሰጭ /የአሁን አመልካች/ ደግሞ ሁሉንም መሬቶች በሥጦታ አግኝቻለሁ በማለት መከራከሯን ተመልክተናል፡፡ በመርህ ደረጃ ማንም ሊያስተላልፍ የሚችለው ያለውንና የእርሱ የሆነን እንጂ የእርሱ ያልሆነን ለማስተላለፍ አይችልም፡፡ ስለሆነም የአመልካች አባት ከእሳቸው ድርሻ ውጪ ያለውን የባለቤታቸውን ድርሻ በሥጦታ ማስተላለፍ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የአሁን መልስ ሰጭ /የአሁን አመልካች/ በሥጦታ ሊተላለፍላት የሚገባው የወላጅ አባታቸው ድርሻ የሆነው ሁለት ቀዳ መሬት ብቻ እንጂ የወላጅ እናታቸው ድርሻ የሆነው ሁለት ቀዳ መሬት ግን ይግባኝ ባዮችና መልስ ሰጭ እንደየ ድርሻቸው መብት ያላቸው ስለሆነ በአዋጁ ከተመለከተው አንጻር መካፈል የሚችል ከሆነ እንዲከፋፈሉት፣ ለመካፈል የማይችል ከሆነ ግን በሚስማሙት መንገድ እንዲጠቀሙ በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ የአሁን አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው ተዘግቶባቸዋል፡፡

የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታም ውሳኔውን በመቃወም ሲሆን በጠበቃቸው በኩል የቀረበ የሰበር አቤቱታ ይዘቱም በአጭሩ፡- ሟች ወላጅ እናታችን የሞተችው ነሐሴ 16 ቀን 1993 ዓ/ም ሆኖ እያለ ከ15 ዓመት በላይ ቆይተው ያቀረቡትን ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት እየተቃወምኩ እያለ በብይን መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል፣ሟች ደሴ ካሰ ለአመልካች አራት ቀዳ ይዞታ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሬት በሥጦታ ሲያስተላልፍ ተጠሪዎች የሚች እናታችን እማሆይ እምየ በላይ ድርሻ ጭምር በሥጦታ ማስተላለፍ ተገቢ ባለመሆኑ የሥጦታ ውል እንዲፈርስ በማለት በሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኝነት አልጠየቁም፡፡ አመልካች በቀን 16/03/2005 ዓ/ም የተሰጠ እና በሚመለከተው አካል የፀደቀ የሥጦታ ውል አቅርባ ይህም ውል በፍርድ ፈራሽ ሳይሆን ባልተጠየቀ ዳኝነት ሟች ደሴ ካሰ የሚች ባለቤቱን ድርሻ ጭምር ይዞታ ማስተላለፍ አይችልም በማለት ለአመልካች በሥጦታ የተላለፈልኝን አራት ቀዳ ይዞታ ጭምር ለተጠሪዎች ልታካፍል ይገባል በሚል የተሰጠው ውሳኔ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ያልጠየቁት ዳኝነት ላይ የተሰጠው ውሳኔ በመሆኑ የህግ ስህተት አለበት እንዲባልልኝ የሚል ነው፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ በተጠሪዎች በኩል በክስ ቁጥር 2 እና 3 ላይ የተጠቀሰው የይዞታ መሬት ለአመልካች በሥጦታ የተላለፈና ሥጦታም መመዝገብ ያለበት አካል ተመዝግቦና ለአመልካች በተላለፈበት ሁኔታ የሥጦታ ውሉ ሳይፈርስ የውርስ ንብረት ነው የተባለበት አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርገጎላቸው በጠበቃቸው በኩል በ23/4/2010 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ አካራካሪውን መሬትና ሀብት ሟች አባታችን አስከሞቱበት 2007 ዓ/ም ድረስ በእሳቸው እጅ የነበረ መሆኑን፣ እሳቸውም የእናታችንን ድርሻ ጭምር በሥጦታ ማስተላለፋቸውን ግራ ቀኙ ሳንካካድ፣ ሥጦታ ውሉም በህግ መሠረት ሊጸና የማይችል በመሆኑ ሊፈጸም አይገባም በሚል በቂ መቃወሚያ ቀርቦበት ይህ ስለመሆኑም ተረጋግጦ የይዞታ መሬቱን ጨምሮ ሌሎች ሀብቶች የውርስ ሀብት ተብሎ በድርሻችን ልክ እንድንከፋፈል መወሰኑ ስህተት የሌለበት ስለሆነ በቂ ወጪና ኪሳራም ታስቦልን በነፃ እንድንሰናበት በማለት ተከራክረዋል፡፡

የተጠሪዎችን መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን አመልካች ባለመቅረባቸው ከፈለጉ የመልስ መልስ ከምርመራ ቀጠሮ ቀን በፊት እንዲያቀርቡና ለተጠሪዎች እንዲያደርሱ ታህሳስ 25 ቀን 2010 ዓ/ም ታዞ የመልስ መልስ አላቀረቡም፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን ሟች ለአመልካች በሥጦታ ከሰጡት አራት ቀዳ መሬት የግራ ቀኙን የእናታቸውን ድርሻ ሟች አባታቸው ለአሁን አመልካች በሥጦታ ሊሰጡ አይችሉም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ህጋዊ መሠረት አለው ወይስ የለውም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን አራት ቀዳ የእርሻ መሬት በተመለከተ ይዞታው የወላጆቻቸው ስለ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ ነገር ግን ከዚህ ጋር በተያያዘ የአሁን አመልካች ሁለት መከራከሪያዎችን ያነሳሉ፡፡ የመጀመሪያው የአመልካችና የተጠሪዎች እናት በ1993 ዓ/ም ስለሞቱ የአሁን ተጠሪዎች እናታቸው ከሞቱ ከ15 ዓመት በኃላ ያቀረቡ ክስ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ ለዚህ መቃወሚያ የአሁን ተጠሪዎች ለሥር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ የእናታቸው ድርሻ እስከ አባታቸው ሞት ማለትም እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ በአባታቸው እጅ የቆየ በመሆኑና የሥር ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ እጅ ተይዞ ያልቆየ በመሆኑ በይርጋ አይቋረጥም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት የሟች እናታቸው ድርሻ አባት እስከሞቱበት እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ በአባታቸው እጅ የቆየ እንጂ የአሁን አመልካች ይዘው የቆዩበት ባለመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000/1/ መሠረት በሶስት ዓመት ይርጋ ሊቋረጥ አይችልም በማለት ብይን ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ዋናው ጉዳይ ውሳኔ ሲያገኝ ይህን ብይን የመጀመሪያ የይግባኝ ቅሬታ አድርገው ቢያቀርቡም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአዊ ብሔረሰብ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አጽንቶበታል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ አላቀረቡም፡፡ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ለዚህ የሰበር ምክንያት የሆነው መሬት ለአሁን አመልካች በሥጦታ የተሰጣቸው በመሆኑ ለተጠሪዎች አይገባም ተብሎ ስለተወሰነ የይርጋውን ክርክር አመልካች ትተውታል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች አራት ቀዳ መሬት ለአሁን አመልካች ይገባል ተብሎ መወሰኑን በመቃወም ይግባኝ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የእናታቸውን ድርሻ አባታቸው ለአሁን አመልካች በሥጦታ ሊሰጡ አይችሉም ተብሎ ተወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበው ተዘግቶባቸዋል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት አቤቱታ ላይ አንዱ የቅሬታ ነጥብ ይርጋን የተመለከተ ነው፡፡ ይህ ቅሬታ ነጥብ /ጥያቄ/ ሥነ ሥርዓታዊ ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ይኸውም ከላይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደተገለጸው የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ ቅሬታን በተመለከተ የወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ተገቢ ነው ብሎ ሲያፀና የአሁን አመልካች ይግባኝ አላሉበትም። ይልቁንም በዋናው ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያሉት

የአሁን ተጠሪዎች ናቸው። በመሆኑም ይርጋን በተመለከተ የአሁን አመልካች ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ባላሉበት ሁኔታ አሁን ለዚህ ችሎት ይህን በተመለከተ በቅሬታነት ማንሳታቸው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ስለ ይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት የደነገገውን አንቀጽ 320 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎችን የተከተለ ባለመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት ያለው አይደለም።

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት የሁለተኛ ቅሬታ ነጥብ አባታቸውም በህግ አግባብ ከሰጡት አራት ቀዳ መሬት ላይ ሁለቱ ቀዳ የእናታቸው ስለሆነ ግራ ቀኙ እኩል ይካፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተጠሪዎች የሥጦታ ውል ይፍረስልን ብለው ባልጠየቁት ዳኝነት ላይ የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው። ለዚህ የቅሬታ ነጥብ የአሁን ተጠሪዎች ለዚህ ችሎት በሰጡት መልስ አካራካሪውን መሬትና ሀብት ሚች አባታችን እስከሞቱበት 2007 ዓ/ም ድረስ በእሳቸው እጅ የነበረ ሲሆን እሳቸውም የእናታችንን ድርሻ ጭምር በሥጦታ ማስተላለፋቸውን ግራ ቀኙ ሳንካካድ፣ ሥጦታ ውሉም በህግ መሠረት ሊጸና የማይችል በመሆኑ ሊፈጸም አይገባም በሚል በቂ መቃወሚያ ቀርቦበት ይህ ስለመሆኑም ተረጋግጦ የይዞታ መሬቱን ጨምሮ ሌሎች ሀብቶች የውርስ ሀብት ተብሎ በድርሻችን ልክ እንድንከፋፈል ተወስኗል በማለት ተከራክረዋል። አመልካችና ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ከተከራከሩባቸው ንብረቶች መካከል የአሁን አራት ቀዳ መሬት አንዱ ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ይህ መሬት የአባታቸው ብቻ ሳይሆን የሚች እናታቸው ድርሻ ጭምር ያለበት ስለሆነ ለአሁን አመልካች በሥጦታ መሰጠቱ ህጋዊ አይደለም በማለት መከራከራቸውን የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል። ሥጦታው መብታችንን የሚጎዳ ስለሆነ በህግ ይሁንታ ሊሰጠው አይገባም የሚል ክርክር እስከ ቀረበ ድረስ ሥጦታው እንዲፈርስ የተለየ የዳኝነት ጥያቄ ሊቀርብ ይገባል የሚለው የአመልካች ክርክር ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግራ ቀኙ አባት አራት ቀዳ መሬት ለአሁን አመልካች ሲሰጡ የግራ ቀኙ እናት ድርሻ እንዳለ የአሁን አመልካችም አይክዱም። ነገር ግን ይህን በተመለከተ አመልካች ይርጋን አንስተው ቢከራከሩም ጥያቄኣቸው ወድቅ ሆኖባቸዋል። ይህ ከሆነ አባት ከራሳቸው ድርሻ አልፈው ሟች ባላቤታቸውን ድርሻ ጭምር ለአሁን አመልካች ሊሰጡ ይችላሉ ወይ? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነው። የአመልካች አባት ድርሻቸውን በሥጦታ ለአመልካች መስጠት ይችላሉ እንጂ የባለቤታቸውን ማለትም የግራ ቀኙን እናት ድርሻ ሊሰጡ የሚችሉበት የህግ አግባብ አይኖርም። በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2427 " ከንብረቶቹ አንዱን የሚለቅበት" በማለት የተደነገገውም ይህንኑ የሚያሳይ ነው። እንዲሁም የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2451 /1/ የተመለከተው ጽንሰ ሀሳብም አስተላላፊው /ሰጭ/ የራሱ የሆነን ሀብት ብቻ ሊያስተላልፍ እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው። በያዝነው ጉዳይ ሟች ደሴ ካሳ ለአሁን አመልካች ሥጦታ ያደረጉት የአሁን ተጠሪዎችን ወላጅ እናት ድርሻ መሬት ነው። ይህም ደግሞ ከፍ ሲል ከተመለከተው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2451 /1/ አንጻር ሲታይ አግባብነት ያለው አይደለም። ፡

በመጨረሻም ለአሁን አመልካች በሥጦታ ሊተላለፍላቸው የሚገባው የወላጅ አባታቸው ድርሻ የሆነው ሁለት ቀዳ መሬት ብቻ እንጂ የወላጅ እናታቸው ድርሻ የሆነው ሁለት ቀዳ መሬት ሊሆን ስለማይችል ግራ ቀኙ እንደየድርሻቸው ሊካፈሉት ይገባል በማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔም ሆነ ይህ ውሳኔ በአቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ መዝጋቱ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 45274 በቀን 13/11/2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/አ/መ/ቁ. 70347 በቀን 20/2/2010 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ፀንቷል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የአመልካች አባት ከድርሻቸው ውጪ ያለውን የእርሻ መሬት ለአሁን አመልካች በሥጦታ ሊሰጡ አይችሉም፤የሟች እናታቸውን ድርሻ የሆነው ሁለት ቀዳ የእርሻ መሬት ለግራ ቀኙ ሊሆን ይገባል ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሥረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ቅ/ሀ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 154115

ቀን - 25/01/2011

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- ያዳኒ ራባ -አልቀረቡም ከተባለ ተወካይ ሰመረ ገ/ህይወት ቀርበዋል

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንዋር መስጊድ ቅርንጫፍ -አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በመጋቢት ወር 2007 ዓ.ም የባንክ ደብተራቸዉን ይዘዉ ባደሩበት አልጋ ላይ ረስተዉ መሄዳቸዉን ተከትሎ ተጠሪ በባንክ ደብተራቸዉ ላይ ያለዉን ገንዘብ ማንነቱ ላልታወቀ ሰዉ በመክፈል የገንዘብ እና የሞራል ጉዳት ያደረሰባቸዉ መሆኑን ጠቅሰዉ ተጠሪ ያላግባብ የከፈለዉን ብር 46,900.00 እንዲሁም የሞራል ካሳ ብር 20,000.00 እንዲከፍል ይወሰንላቸዉ ዘንድ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ለክሱ በሰጠዉ መልስ፤ ገንዘቡ የተከፈለዉ አመልካች ከሞሉት ፎርም እና ከፊርማቸዉ ናሙና ጋር በማመሳከር ተገቢዉ ጥንቃቄ ተደርጎ ለአመልካች ለእራሳቸዉ የተከፈለ መሆኑን፣ እንዲሁም ደብተሩ ጠፍቶ አራት ወር ሲቆይ አመልካች ደብተሩ ስለመጥፋቱ ለፖሊስ አመልክተዉ ሂሳቡ እንዲታገድላቸዉ አለማድረጓቸዉን በመጥቀስ ኃላፊነት የለብኝም ሲል ተከራክሯል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ፤ አመልካች ደብተሩ የጠፋባቸዉ ስለመሆኑ ለተጠሪ የማሳወቅ ግዴታ እያለባቸዉ ይህን ባለማድረግ የሂሳብ ደብተሩ ሦስተኛ ወገን እጅ ገብቶ ገንዘቡን ሌላ ሰዉ እንዲያወጣ ምክንያት በመሆናቸዉ ተጠሪ ገንዘቡን እንዲከፍል የሚገደድበት ምክንያት የለም በማለት የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በቀን 15/06/2010 ተዘጋጅቶ በተወካያቸዉ አማካይነት በቀረበ የሰበር አቤቱታ፤ ተጠሪ ተገቢዉን ማጣራት እና ጥንቃቄ ሳያደርግ ከአመልካች የሂሳብ ደብተር ወጪ አድርጎ ለሌላ ሰዉ ከፍሎ እያለ እና ገንዘቡን የከፈለዉ የባንኩ ሠራተኛም በዚህ ጉዳይ ላይ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ እያለ አመልካች ደብተሩ መጥፋቱን ሪፖርት የማድረግ ግዴታቸዉን አልተወጡም የሚል ምክንያት በመጥቀስ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በሚል በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ ያደረገዉ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም አቤቱታዉን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ክክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሂሳብ ቁጥር 1000065634159 ያስቀመጡትን ገንዘብ የያዘ የባንክ ደብተር መጥፋቱን እና ባንኩ በሂሳብ ደብተሩ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ለ3ኛ ወገን መክፈሉን ሲሆን፤ ተጠሪም የባንክ ደብተር ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ወጪ አድርጎ የከፈለ ስለመሆኑ ክዶ አልተከራከረም፡፡ የተጠሪ ክርክር የነበረዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርጎ ለአመልካች እራሷ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መክፈሉን እና የሂሳብ ደብተሩ ስለመጥፋቱ አመልካች ለተጠሪ የማሳወቅ ግዴታቸዉን አለመወጣታቸዉን ሲሆን፤ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ አመልካች ደብተሩ ስለመጥፋቱ ለተጠሪዉ ባንክ ሪፖርት የማድረግ ግዴታቸዉን አለመወጣታቸዉን ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያስገነዝባል፡፡

በመሠረቱ በግራ ቀኝ መካከል ተደርጎ ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነዉ ግንኙነት መሠረቱ በንግድ ህጉ አንቀጽ 896 እና 897 ስር የተመለከተዉ ገንዘብ በአደራ የማስቀመጥ ዉል (deposit fund) ነዉ፡፡ በዚህ ዉል መሠረትም ተጠሪ አደራ አስቀማጭ እንደመሆኑ የአመልካችን ገንዘብ የመጠበቅ፣ አመልካች ሲጠይቁ ወጪ አድርጎ የመክፈል እና ከአመልካች ዉጪ ለሌላ ሰዉ ያለመክፈል ከዉል የመነጨ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ይህን የማድረግ ግዴታዉን ባለመወጣት በአመልካች ላይ ሊደርስ ለሚችል ጉዳት ከዉል የመነጨ ኃላፊነት እንደሚኖርበትም ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ማንኛዉም ባንክ የሚቀርብለትን የክፍያ ጥያቄ ሲያስተናግድ፣ ገንዘብ እንዲከፈለዉ ጥያቄዉን ያቀረበ ሰዉ በርግጥም አደራ አስቀማጩ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ ተጠሪ በአመልካች የባንክ ሂሳብ ላይ የሚገኘዉን ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ገንዘብ ወጪ አድርጎ ክፍያ የፈጸመ ስለመሆኑ ክዶ እስካልተከራከረ ድረስ፣ ከኃላፊነት ሊድን የሚችለዉ ገንዘቡን የከፈለዉ በባንኩ በተዘረጋዉ ደንብና አሰራር መሠረት አስፈላጊዉን ጥንቃቄ ሁሉ አድርጎ ተከፋይ አመልካች መሆኑን በማረጋገጥ ክፍያዉን የፈጸመ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ነዉ፡፡ በርግጥ አመልካች ደብተሩ ስለመጥፋቱ ለተጠሪ ባንክ የማሳወቅ ግዴታ እንዳለባቸዉ ይታወቃል፡፡ ይሁንና፣ ተጠሪ የአመልካችን ገንዘብ በአደራ የመጠበቅ ባለበት ግዴታ መሠረት ተገቢዉን ጥንቃቄ ባለማድረግ ገንዘቡን ለሌላ ሰዉ በመክፈሉ ምክንያት በአመልካች ጉዳት መድረሱ ከተረጋገጠ፣ አመልካች ደብተሩ ስለመጥፋቱ ለተጠሪ አለማሳወቃቸዉ የተጠሪን ኃላፊነት ሊያስቀር የሚችል አይሆንም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት ተይዞ በማስረጃ ተጣርቶ እልባት ሊሰጠዉ የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ፣ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ገንዘብ የከፈለዉ አስፈላጊዉን ጥንቃቄ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማድረግ ተከፋዩ አመልካች መሆኑን በማረጋገጥ መሆን አለመሆኑ ነዉ። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ደብተራቸዉ ስለመጥፋቱ ለተጠሪ የማሳወቅ ግዴታቸዉን አልተወጡም በሚል የፍ/ሕጉን አንቀጽ 1752 ድንጋጌ ያለቦታዉ በመጥቀስ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህኑን በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል። በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል።

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 50523 በቀን 20/04/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 193272 በቀን 25/03/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል።
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ገንዘብ ከአመልካች የባንክ ሂሳብ ወጪ አድርጎ ሲከፍል በባንኩ በተዘረጋዉ ደንብና ስርዓት መሠረት ክፍያዉ ለአመልካች የተከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ በሚያስችል ደረጃ አስፈላጊዉን ጥንቃቄ በማድረግ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ የግራ ቀኝን ማስረጃ እንዲሁም፣ እንዳስፈላጊነቱ፣ ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎችን ጭምር አስቀርቦ በመመርመር ባንኩ አደራ አስቀማጭ ከመሆኑ አንፃር ክፍያን በመፈጸም ረገድ እንዲያደርግ ከሚጠበቅበት ጥንቃቄ አንፃር በማገናዘብ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል።
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡...1.ተክሊትይመሰል

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራው

5. አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡-.....የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት....ጠበቃ ዶ/ር ዘውድነህ በየነ እና ነ/ፈጅ አቶ አስራት መኮንን ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡-.....ኮንስታ ጀይንት ቬንቸር.....ጠበቃ አቶ ወሰንየለህ ትጉህ ቀርበዋል፡፡

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

1. ይህ ክርክር የተጀመረዉ በዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ኔዘርላንድ (ሄግ) የሚገኘዉ ቋሚ የግልግል ዳኝነት ፍ/ቤት የሚያስተዳደረዉ መቀመጫዉ አዲስ አበባ ከተማ ኢትዮጵያ የሆነዉ ሲሆን፣የአሁን አመልካች ተከሰሽ፣የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በመ.ቁ.2013-32 ሚያዚያ 28 ቀን 2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ግንቦት 6 ቀን 2016) የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

2.የጉዳዩአመጣጥሲታይከሳሽ ኮንስታ ጀይንት ቬንቸር ባቀረበዉ ክስ ከተከሳሽ የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት ጋር የባቡር መስመር ጥገና ዉል ህዳር 20 ቀን 1999 ዓ.ም (November 29, 2006) ተስማምተን ነበር፡፡ ከሳሽ በዉሉ መሰረት ስራዉን እየሰራ የነበረ ቢሆንም በተከሳሽ ጥፋት በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 65 መሰረት ዉሉ ተቋርጧል፡፡ በዚህ ዉል መሰረት ከሳሽ ሰርቶ ክፍያ ያልተፈጸመባቸዉ ሥራዎች እና በተከሳሽ ጥፋት ፕሮጀክቱ በመዘግየቱ በከሳሽ ላይ ጉዳት የደረሰ በመሆኑ፣ ተከሳሽ ካሳ በአጠቃላይ 21,076,081.00 (ሀያ አንድ ሚሊዮን ሰባ ስድስት ሺህ ሰማኒያ አንድ) ዩሮ ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈለን እንዲሁም ተከሳሽ ክፍያዉን ላዘገየበት ተጠያቂ ነዉ እንዲባልልን በማለት ከሷል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ኮንስታ ከተከሳሽ ጋር ዉሉን ያደረገዉ በተንኮል ወይም በማጭበርበር ተግባር ሲሆን፣ በተጨማሪም ኮንሰታ የእሽሙር ማህበር በዉሉ መሰረት መፈጸም የነበረባቸዉን ግዴታዎች አንድም ያልፈጸሙ በመሆኑ እና በዚህ ምክንያት ተከሳሽ ላይ ጉዳት የደረሰ በመሆኑ ከሳሽ የጉዳት ካሳ ለተከሳሽ ሊከፍለን ይገባል በማለት ተከራክሯል።

4. በሌላ በኩል የተከሳሽ ከሳሽ ባቀረበዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የከሳሽ ተከሳሽ በግንባታ ዉል መሰረት ባለመፈጸሙ ብር 66,444,384 ዩሮ ከወለድ ጋር እንዲከፍለን በማለት ጠይቋል፤ በአማራጭ የከሳሽ ተከሳሽ ይህን ዉል ያደረገዉ በተንኮል ወይም በማጭበርበር በመሆኑ ዉሉ እንዲሰረዝ (invalidate) ተደርጎ ወደ ነበርንበት እንዲንመለስ፣ በዚህም የከሳሽ ተከሳሽ በባቡር መስመር ጥገና ዉል መሰረት ሥራዉን በአግባቡ ያላጠናቀቀ ስለሆነ ለዚህ ሥራ ተብሎ የተከፈለዉን 27,674,384.00 (ሀያ ሰባት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰማኒያ አራት) ዩሮ ከወለድ ጋር እንዲከፍለን፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍለን በማለት ከሷል። በዚህ ክስ ላይ የከሳሽ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ የተከሳሽ ከሳሽ ያቀረበዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት በዝርዝር ተከራክሯል።

5. ከዚህ በኋላ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር ምስክሮችን በመስማት የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ ዉሉ በማጭበርበር የተደረገ ነዉ ለተባለዉ እና የጂሲኤፍ በኮንስታ ጂቪ የነበረዉ ተሳትፎና ለዉሉ መቋረጥ ተጠያቂነት የለበትም፣ ተከሳሽ ግን ለባቡር መስመር ሥራ ዉል መቋረጥ ተጠያቂነት አለበት፣ እንዲሁም በእያንዳንዱ ነጥቦች ላይ ዉሳኔ በማስጠት፣ ተከሳሽ 20,664,767 (ሀያ ሚሊዮን ስድስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት) ዩሮ ዉሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከሚከፈልበት ቀን ድረስ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍለዉ፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ደግሞ ተቀባይነት የለዉም በማለት ዉድቅ በማድረግ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ።

6. የአሁን አመልካች ግንቦት 18 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አስራ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል። የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡ በአዉሮፓ የልማት ፈንድ ሕግ መሰረት የግልግል ዳኝነት ጉባኤ የሰጠዉ ፍርድ በአገራቱ በሚገኙ ፍ/ቤቶች እንደተሰጠ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጨረሻ ፍርድ እንደሚቆጠር ስለሚያመለክት እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.42239 ላይ በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ችሎቱ ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን ስላለዉ የሰበር አቤቱታዉ ለዚህ ችሎት ለማቅረብ ችለናል። የባቡር መስመር ጥገና ዉሉ 114 ኪ.ሜ ለማስጠገን የተስማመን ሲሆን፣ ለፕሮጀክቱ ፋይናንስ የተገኘዉ ከአዉሮፓ ልማት ፈንድ ነዉ። ከዚህ ዉል የሚነሱ አለመግባባቶች በአዉሮፓ ልማት ፈንድ የሥነሥርዓት ሕግ የሚመራ ሲሆን፣ የዉል ስምምነቱን የሚገዛዉ የኢትዮጵያ ሕጎች እና የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ መቀመጫ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ስለሆነ አቤቱታዉ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ ችሏል። በዚህ ምክንያት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) መሰረት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉን ፍርድ ለማረም ስልጣን ይሰጠዋል። እንዲሁም በአዉሮፓ ልማት ፈንድ የስነስርዓት ሕግ (EDF Rules)፣ የአዉሮፓ የፍርዶች አፈጻጸም ሰርዓት የኢክሲድ ኮንቬንሽን (ICSID Convention)፣ የኒዉዮርክ ኮንቬንሽን የሚባሉት የዓለም አቀፍ ስምምነቶች በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ ፍርዱ በተሰጠ አገር በሚገኝ አግባብነት ባለዉ ፍ/ቤት ፍርዱን ማስመርመር እንደሚቻል ያስገነዝባሉ። ስለሆነም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.42239 በሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን አለዉ። እነዚህ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደሚያመለክቱት ፍርዱን ከሰጠዉ አንድ ደረጃ ከፍ ባለ አካል ሳይመረመር የሚፈጸመዉ ፍርድ ፍትሓዊና ተቀባይነት ያለዉ የፍትሕ ሥርዓት ስለመኖሩ ዋስትና የማይሰጥ መሆኑን ነዉ። አመልካች ባቀረበዉ ቅሬታ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በሰጠዉ ዉሳኔ የፈጸመዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ናቸዉ ያላቸዉ የሚከተሉት ናቸዉ።

6.1. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ የግንባታ ዉል ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 12.7 መሰረት በኮንስታ ጀቪ የዉስጥ አወቃቀር (የአክስዮን ድርሻ ክፍፍልን ጨምሮ) የሚደረግ ማናቸዉም ለዉጥ አስቀድሞ ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ ይጥላል። እንዲሁም የግንባታ ዉሉ ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 64.2 (h) መሰረት ኮንትራክተሩ በዉሉ ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 12.7 የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ የተንኮል ተግባር መፈጸሙን ማረጋገጥ ሳያስፈልግ አመልካች ዉሉን ማፍረስ እንደሚችል ይደነግጋል። አመልካች ለክርክሩ ምክንያት ለሆነዉ የግንባታ ዉል ባወጣዉ ጨረታ ተጠሪ በጨረታዉ ለመወዳደር ባቀረበዉ የመወዳደሪያ ሰነድ የእሽሙር ማህበሩ ስምምነት ላይ ተጫራቹ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኮንስታ ጆይንት ቬንቸር የተመሰረተዉ 70% የአክስዮን ድርሻ በያዘዉ ኮንሶርዚዮ ኮንስታ እና 30% የአክስዮን ደርሻ በያዘዉ ጂሲኤፍ በሚባሉት ኩባንያዎች ናቸዉ። አመልካች ከተጠሪ ጋር የግንባታ ዉሉን የፈጸመዉ በቅንጂቱ ዉስጥ ሁለቱ ድርጅቶች ያቀናጁትን እዉቀትና ሀብት እንዲሁም በተናጠል ያላቸዉ የግንባታ ግዴታ ደርሻ የዉሉ መሰረታዊ ጉዳይ ነዉ። አመልካች ይህን የተጠሪ የሁለቱ ድርጅቶች ቅንጂት ባይኖር ኖሮ ተጠሪዉ ከመነሻዉ የጨረታዉን መወዳደሪያ መስፈርትም አያሟላም፣ አመልካችም ከተጠሪ ጋር የግንባታ ዉል ሊፈራረም አይችልም ነበር። ነገር ግን ተጠሪ ይህን ቅንጅት በተመለከተ ሶስት ስምምነቶችን በማድረግ ይህን ቅንጅት ወደ ማፍረስ ደረጃ ደርሷል። በዚህ መሰረት ሐምሌ 27 ቀን 1998 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ኦገስት 3 ቀን 2006) በተፈረመዉ የሚስጥር ስምምነት ቁጥር 1 መሰረት የጂሲኤፍን የአክስዮን ድርሻ ወደ 0.1% ዝቅ ለማድረግ ተስማምቷል፣ ህዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 24 ቀን 2006) በተደረገዉ የምስጥር ስምምነት ቁጥር 2 የጂሲኤፍ የአክስዮን ድርሻ ወደ 0.2% ዝቅ እንዲል አድርጓል፤ መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ማርች 20 ቀን 2007) በተፈረመዉ የምስጥር ስምምነት ቁጥር 3 መሰረት ጂሲኤፍ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ዩሮ ክፍያን በመቀበል ተሳትፎዉን እስካሁን ድረስ በተፈጸመዉ ብቻ እንዲገደብ አድርጎታል። ይህም ድርሻ ለይስሙላ የተቀመጠ ነዉ። ተጠሪ ጨረታዉን ማሸነፉ የተገለጸለት መስከረም 19 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 29 ቀን 2006 ዓ.ም) ሲሆን፣ የባቡር መስመር ግንባታ ዉል የተደረገዉ ህዳር 20 ቀን 1999 ዓ.ም ነበር። አመልካች የተጠሪ የቅንጂት ለዉጥ ያወቃዉ በ2006 ዓ.ም እና በ2007 ዓ.ም ነበር። ተጠሪ እነዚህን ምስጥራዊ ስምምነቶች ማድረጉን አልካደም። ተጠሪ በክፉ ልቦና የዉሉ መሰረታዊ የሆነዉን የለዉጥ መረጃ ከአመልካች መደበቁን ያሳያል፣ ይህ ደግሞ ተጠሪ ከጨረታ በፊትና በኋላ ሆነ ተብሎ የማታለል፣ የማጭበርበርና የተንኮል ተግባር መፈጸሙን የሚያረጋግጥ በመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1696 እና 1704 የሚጥስ እና ዉሉ እንዲፈርስ የሚያደርግ ምክንያት ነዉ። የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ ተጠሪ የተንኮል ተግባር አልፈጸመም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነዉ።

6.2. የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ የናቪጋንት የአማካሪ ድርጅት ባለሙያዎች የኢትዮጵያ የፍትሓ ብሔር ሕግ ቁጥር 1799-1801 የተመለከተዉን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳት ካሳ አሰላል ሳያዉቁ ያቀረቡትን ሪፖርት መሰረት በማድረግ፣ በኢትዮጵያ ሕግ የተመለከተዉን የጉዳት ካሳ አሰላል ታሳቢ ሳያደርግ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ።

6.3. የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ ከግራ ቀኞቸዉ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከወገንተኝነት በጸዳ ሁኔታ በእኩልነት በመመዘን መዳኘት ሲገባዉ ቅን ልቦና በጎደለዉ አካሄድ የተጠሪን ማስረጃዎች ሙሉ ለሙሉ በመቀበል፣ የአመልካችን ማስረጃዎች ሳይመዝን መጣሉ የማስረጃ አቀባበል፣ የማስረጃ ምዘና ደንቦችን የሚጥስ ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ።

6.4. የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የተሟላ ዲዛይን ሰርቶ ግንባታዉን የማጠናቀቅ ኃላፊነት የተጠሪ መሆኑን በግንባታ ዉሉ ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 12.1 እና 17.1 የተመለከተዉን በኢትዮጵያ ሕግ ስለዉሎች አተረጓጎም የተደነገገዉን ወደ ጎን በመተዉ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ።

6.5. የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ ወገንተኝነትና የጥቅም ግጭት እያለበት ተጠሪ በዉሉ መሰረት 27 ሚሊዮን ዩሮ ከወሰደ በኋላ አንድ ሜትር እንኳን ተቀባይነት ያለዉ የባቡር መስመር ጥገና ሥራ ሳይሰራ ፕሮጀክቱ ለዘገየበት ተብሎ ተጨማሪ 20 ሚሊዮን ዩሮ ይከፈለዉ መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ። ስለሆነም አመልካች የሚጠይቀዉ ዳኝነት ከፍ ሲል በተጠቀሱት በእነዚህ ምክንያቶች ሁሉ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአብላጫዉ ድምጽ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን፣ በዚህ ክርክር ምክንያት አመልካች ያወጣዉን ወጪዎች ተጠሪ እንዲከፍለን እንዲወሰንልን በማለት ተከራክሯል።

7. የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በመመርመር ፣ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን እንዳለዉ በመግለጽ፣ የተጠሪ ድርጅት የተቋቋመዉ ኮንስታ የ70% ድርሻ እና ጂሲኤፍ የ30% ድርሻ ይዘዉ ሲሆን በመካከላቸዉ የአወቃቀር ለዉጥ መደረጉን ተጠሪ ለአመልካች ሳያሳዉቅ ይህ ደግሞ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ሰነድ አንቀጽ 12.7 እና 64.2 መሰረት ዉል እንዲቋረጥ የሚደርግ ሆኖ ሳለ በግልግል ጉባኤዉ ተቀባይነት ማጣቱ፣ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ይህ የተጠሪ ተግባር በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704 መሰረት የተንኮል ተግባር አይደለም የመባሉን አግባብነት፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘው መሰረት አስራ ዘጠኝ ገጽ መልስ አቅርቧል።

የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡

7.1. ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.42239 ላይ የሰጠው ውሳኔ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት የለውም።

7.2. በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሰረት ይህ ችሎት በመደበኛ ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሳኔ እንጂ የግልግል ውሳኔዎችን እንደማይመለከት በግልጽ ያስቀመጠ ስለሆነ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ ለማየት አይችልም።

7.3. የአውሮፓ የልማት ፈንድ የስነስርዓት ሕግ አንቀጽ 33 እና 34 ድንጋጌዎች መሰረት የተሰጠው ውሳኔ በተዋዋይ ወገኖች ላይ አስገዳጅነት ያለው እና የመጨረሻ መሆኑን እና በአባል አገሩ የአፈጻጸም ሕግ መሰረት ሊፈጸም የሚገባው መሆኑን እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ በዚህ ሰበር ሊታይ የሚችል አይደለም። እንዲሁም የኢክሲድ እና የኒውዮርክ ኮንቬንሽኖች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ እንዲያይ ስልጣን የሚሰጡት አይደለም። የኢክሲዲ ኮንቬንሽን እና የኢዲኤፍ ስነስርዓት በሽምግልና የተሰጡ ፍርዶች በአገራዊ ፍ/ቤቶች እንዳይከለሱና ሊፈጸም የሚገባ መጨረሻ ፍርድ መሆኑን ያስገነዝባሉ። በግራ ቀኞቹ መካከል በሽምግልና ዳኝነት የተሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ አመልካች ውሳኔው በዚህ ችሎት እንዲታይለት ያቀረበው አቤቱታ በሽምግልና ዳኝነት አለምአቀፍ ደረጃ አውቅና ያገኘ መርህ እና ተሞክሮ የሚጻረር ስለሆነ ተቀባይነት የለውም። አመልካች እንደሚለው የግልግል ዳኝነት መቀመጫው አዲስ አበባ ነው በሚለው መነሻ ብቻ ፍርዱን እና ይዘቱን ወደ መመርመር ማለፍ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነትን ጭምር የሚጥስ ነው። ስለዚህ በዚህ ረገድ የሽምግልና ዳኝነት ፍርድ የሕግ ስህተት ያለው መሆኑን አመልካች ያላስረዳ ስለሆነ ጥያቄው ውድቅ እንዲደረግልን።

7.4. የግንባታ ውሉ በተንኮል የተደረገ ነው ለተባለው የተጠሪ የህብረቱ ጥንክርና አቋም አንጻር የግንባታ ውሉ ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 12 (7) እና 64 (2፣h) አንጻር ሊታይ ተጠሪ ያደረገው የሕግ ሰውነት ለውጥ ስለሌለ፣ በተፈጥሮውም ላይ ሆነ በቁጥጥር ላይ ያደረገው ለውጥ የለውም፣ የድርሻው መጠን ቢለዋወጥም ቁጥጥር የተጠሪ ሆኖ ስለቆየ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቁጥጥር ለዉጥ አልተደረገም፡፡ አመልካች ለእነዚህ የዉሉ ድንጋጌዎች የሰጠዉ ትርጉም የተሳሳተ ነዉ፡፡ ተጠሪ እነዚህን የዉሉን አንቀጽ ተላልፏል ቢባል እንኳን ግዴታዉን መተላለፉ ብቻ ዉሉን እንደጣሰ ከማስረዳት ባለፈ እነዚህ የዉል ግዴታዎች በመጣስ የማታለልና የማጭበርበር ወይም የተንኮልን ተግባር ፈጽሟል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም፡፡ አመልካች ይህ የዉል ድንጋጌ አለመከበሩም ከአምስት አመት በፊት እራሱ ለተጠሪ በጻፈዉ ደብዳቤዎች አዉቆ እና የዉሉ አፈጻጸም እያስቀጠለ ቆይቶ አሁን የዉሉ መጣስ ማጭበርበር ነዉ ዉሉ ይፍረስልን በማለት ያቀረበዉ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፡፡

7.5. በተጠሪ እና በጂሲኤፍ መካከል የተደረገዉ የእሽሙር ማህበር ስምምነት እና የተደረጉት ለዉጦች የአክስዮን ደርሻ መቀነስ ጉዳይ በተጨባጭ ምክንያት እንጂ አመልካችን ለመጉዳት በተንኮል የተደረገ ድርጊት አልነበረም፡፡ በኮንስታ እና በጂሲኤፍ መካከል የተደረገዉ ስለሥራ ተግባራት፣ እና ስለትርፍና ኪሳራ ክፍፍል የሚደረግ የዉስጥ ስምምነት ባለድርሻዎቹ ለአመልካች ባላቸዉ የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ላይ ዉጤት የሚኖረዉ አይደለም፡፡ ይህን የዉስጥ ስምምነት ለማድረግ ደግሞ የአመልካችን የቅድሚያ ስምምነት የሚጠይቅ አይደለም፡፡ አመልካች የጂሲኤፍን የተቀነሰ ሚና እያወቀ የተቃወመዉ ነገር በሌለበት አሁን ያቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ ነዉ፡፡ ኮንስታ ፕሮጀክቱን በዉጤታማነት ለማከናወን የሚያስችለዉን ልምድና ያፈጻጸም ሪከርድ ያለዉ ነዉ፡፡

7.6. የኦላፍ ሪፖርት የተዘጋጀዉ ዉሉ ከተቋረጠ ከዓመታት በኋላ እና የግልግል ዳኝነቱ በሂደት ላይ እያለ ሲሆን ሪፖርቱም በመጨረሻ ጸድቆ በደይሬክተር ጀኔራል እንዲዘጋ የተደረገ አይደለም፡፡ ይህ ሪፖርት የዉሉ ድንጋጌ መጣሱን ከማመልከትና በሂደቱ ዉስጥ የተለያዩ ወገኖች የአሰራር ግድፈት መፈጸማቸዉን ከማመልከት ዉጪ የተንኮል ተግባር መኖሩን የሚጠቅስ ነገር የለም፡፡

7.7. ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704 መሰረት የፈጸመዉ የተንኮል ተግባር ስለሌላ አመልካች ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ ተጠሪ የትርፍና የሥራ ድርሻ ክፍፍልን አስመልክቶ በባለድርሻዎች መካከል የተደረገዉን ስምምነት ሳይገልጽ ቢቀር እንኳን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1705 መሰረት በግራ ቀኞቸዉ መካከል ልዩ ግንኙነት ስለሌለ ዉሉ ፈራሽ የሚሆንበት ሁኔታ የለም፡፡ አመልካች በፕሮጀክቱ ላይ የጂሲኤፍን አለመኖር እያወቀ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉሉ እንዲቀጥል አድርጎ እያለ አሁን ያቀረበዉ ክርክር ከክፍያ ግዴታ ለማምለጥ ነዉ፡፡ አመልካች በዚህ ምክንያት የዉል ይፍረስልን ጥያቄ በግልግል ጉባኤዉ ተቀባይነት ማጣቱ በሕጉ አግባብ ስለሆነ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉ የመከራከሪያ ነጥብ የሕግ መሰረት የሌለዉ ስለሆነ ዉድቅ እንዲደረግልን፡፡

7.8. የአሁን አመልካች የግልግል ጉባኤዉ ስለዉሎች አተረጓጎም፣ ስለጉዳት ካሳ ስሌት እና የማስረጃ አቀባበልና ምዘና በተመለከተ የኢትዮጵያ ሕግ ወደ ጎን ትቷል በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ እንዲሁም የግልግል ጉባኤዉ ወገንተኝነትና የጥቅም ግጭት የሚታይበት ነዉ በማለት አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለዚህ ይህ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም ተብሎ አቤቱታዉ ዉድቅ እንዲደረግልን፣ ይህ ካልሆነ ተጠሪ ያቀረባቸዉን ክርክሮች በመቀበል የሽምግልና ጉባኤዉ አብላጫዉ ድምጽ የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸናልን፣ የጠበቃን አበል ጨምሮ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡

9. የአሁን አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የካቲት 21 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ አስራ ስምንት ገጽ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

10. የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት የሚገባቸዉ ጉዳዮች በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የሰጠዉን ዉሳኔ በሰበር የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? በሁለተኛ ደረጃ ግራ ቀኞቸዉ መካከል የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? ዉጤቱስ ምን ይሆናል? የሚሉት ነጥቦች መሆናቸዉን ተገንዝበናል፡፡

11. የመጀመሪያዉን ጭብጥ በተመለከተ ይህ ችሎት ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን የሚመለከት ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ይህን ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የፈጸመዉን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አለዉ የሚል ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ እና በአባል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አገር የሚፈጸም እንጂ በፍ/ቤት ለክለሳ የሚቀርብ ስላልሆነ ይህ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

12. እንደሚታወቀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 ዓ.ም አንቀጽ 80 (3) (ሀ) መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለባቸውን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር የማየትና የማረም ስልጣን ይኖረዋል በማለት ደንግጓታል፡፡ በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት ማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ሥር ተመልክቷል፡፡ ይህም ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት ቀርቦ ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ማናቸውም ጉዳዮች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታረም እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ሥር እንደተመለከተው በዚህ ድንጋጌ በተመለከተው አግባብ የተሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ በሰበር የማየት ስልጣን እንዳለው ያሳያል፡፡

13. ከፍ ሲል እንደተመለከተው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመደበኛ ፍ/ቤት፣ በሕግ ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካል እና በሕግ አግባብ በተቋቋመ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ማናቸውንም ጉዳዮች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው እንደሆነ በሰበር አይቶ የማረም ስልጣን እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ችሎት የፍሬ ነገር ስህተት፣ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ እና በውሳኔው ላይ ምንም ተጽህኖ የሌለውን ቀላል የሕግ ስህተት በሰበር የማየት ስልጣን እንደሌለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

14. ይህ በእንዲህ እንዳለ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ በፍርድ ቤት የማሳረሙ ጉዳይ ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ከአገሮች ልምድ አንጻር ማየቱ አስፈላጊ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ፍርድ እንደተሰጠ ሶስት ውጤቶችን ያስከትላል፡

1. ተሸናፊው ወገን በፈቃደኝነት እንደፍርዱ መፈጸም፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. አሸናፊዉ ወገን በዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት የተሸናፊዉ ወገን ንብረት ባለበት አገር ፍርዱ እንዲጸድቅ፣ እዉቅና እንዲያገኝ ወይም እንዲፈጸምለት ይፈልጋል፡፡

3. በአለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ተሸናፊዉ ወገን ፍርዱ በተሰጠበት አገር ፍርዱ እንዲሰረዝ ማድረግ ናቸዉ፡፡

15. በዚህ መሰረት ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንጻር ሲታይ የኒዉዮርክ ስምምነት አንቀጽ 5 (New York Convention Art 5) መሰረት የግልግል ጉባኤ ብይን እዉቅና እና ተፈጻሚነት የሚነፈግበትን ሁኔታዎች ወይም ምክንያቶች ተዘርዝረዉ እናገኛለን፡፡ ኢትዮጵያ ይህን ስምምነት ያልፈረመች ብትሆንም ስምምነቱ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ የሰጠዉን ብይን እዉቅና ሊከለከል እና ለመፈጸም እምቢ የሚባልባቸዉን ምክንያቶች ያስቀምጣል፡፡

16. የዩኒስትራል ሞዴል ሕግም (UNCITRAL MODEL LAW) የግልግል ጉባኤ ብይን ወይም ዉሳኔ ሊሰረዝ የሚችልበትን ምክንያቶች ያመለክታል፡፡ ይህን ብይን ወይም ዉሳኔ ለማሰረዝ የሚቀርብ አቤቱታ መቅረብ የሚገባዉ የግልግል ዳኝነት መቀመጫ በሆነዉ ፍርድ ቤት እንደሆነ የዚህ አንቀጽ 34 ይደነግጋል፡፡ የግልግል ዳኝነት ሲታይ በነበረዉ ቦታ ያለዉ ፍርድ ቤት በሂደቱ ላይ የተቆጣጣሪነት ስልጣን ስለሚኖረዉ ሂደቱ ፍትሓዊ እና ከሙስና የጸዳ መሆኑን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህን ሕግ ተከትሎ አገሮች የየራሳቸዉ ሕጎች ያወጡ ሲሆን፣ የግልግል ብይን የሚታረምበት ዓይነት እና ደረጃ ከአገር አገር እንደሚለያይ መገንዘብ ያስፈልግል፡፡ በዚህ መሰረት የዩኒስትራል ሞዴል ሕግ አንቀጽ 34 የግልግል ብይን ዉድቅ የሚደረግበትን ምክንያቶች ያስቀምጣል፡፡

17. በአዉሮፓ ልማት ፈንድ ስነስርዓት ሕግ (EDF Rules) የአዉሮፓ የልማት ፈንድ የስነስርዓት ሕግ አንቀጽ 33 (1፣ 3) መሰረት የሽምግልና ዳኝነቱ በጽሑፍ የሚደረግ ሆኖ በተዋዋይ ወገኖች ላይ የመጨረሻና ገዢ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ የዚህ ሕግ አንቀጽ 34 ማየቱም አስፈላጊ ነዉ፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ሳይዘገዩ ፍርዱን ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸዉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ እያንዳንዱ የኤሲፒ አገር ወይም አባል አገር አኢዬፍ የስነስርዓት ሕጎች መሰረት የተሰጠ ፍርድን እዉቅና ሰጥቶ ልክ በግዛቱ ዉስጥ የሚገኙ ፍ/ቤቶች ወይም ፍትህ አካላት እንደሰጡት ፍርድ በመቁጠር በግዛቱ ዉስጥ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ አለባቸዉ፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

18. የኒፎርም አርብትሬሽን አክት ክፍል 23 (Uniform Arbitration Act section 23) መሰረት የግልግል ብይን በማመልከት ለፍ/ቤት ብይኑን ለማሰረዝ የሚቻልባቸዉን ምክንያቶችን ያሳያል።

19. የፓነማ ስምምነት (Inter-American Convention On International Commercial Arbitration (B-35) (Panama Convention) የሚባለዉ በአንቀጽ 5 እና 6 ሥር እንደተመለከተዉ የግልግል ብይን የታየበት ሕግ አገር፣ ይህን ብይን እዉቅና ለመንፈግና ተፈጻሚነቱን እምቢ ማለት የሚልባቸዉን ምክንያቶች አስቀምጧል።

20. የአሜሪካ የፌዴራል የግልግል ሕግ (The Federal Arbitration Act (USA)) የግልግል ዳኝነት ብይን የሚታረምበትን በጠባብ ምክንያቶች መሆኑን ያመለክታል። በሕጉ ክፍል 10 (ሀ) ሥር የግልግል ብይን የሚሰረዝበትን ምክንያቶች ይዘረዝራል። በዚህ ድንጋጌ ሥር የሕግ ስህተት አልተመለከተም። የአሜሪካ ፍ/ቤቶች እና ተከራካሪ ወገኖች በፌዴራል የግልግል ሕግ ከተመለከተዉ በላይ ሰፋ ያለ የግልግል ብይን የሚታረምበትን ምክንያቶች ያስቀምጣሉ። እንዲሁም የክልል ሕግ አዉጪዎች የግልግል ብይኑ ሥራ ነገር የሚታረምበትን ማሻሻያዎች እንዲካተቱ አድርጓል። ሕግ አዉጭዉ ፍ/ቤት በምን ምክንያቶች የግልግል ብይን መሰረዝ እንዳለበት መወሰን እንደሚገባዉ በዚህ ዘርፍ የዳበረው የህግ ልምድ ያስገነዝበናል።(የሕግ ምሁራን ይገልጻሉ።)

የፌዴራል ፍ/ቤቶች የግልግል ዳኛ በሰጠዉ ብይን ግልጽ የሆነ ሕግ የመተዉ ሁኔታ የሚታይበት እንደሆነ (manifest disregard of the law) ብይኑን የሚሰርዙበትን ምክንያት አግባብ ተግባራዊ አድርጓል። የግልግል ዳኛዉ ሕግን በግልጽ ወደ ጎን ትቷል የሚባለዉ፡ ሀ) ጉዳዩ ግልጽ በሆነ አግባብነት ባለዉ የህግ መርህ የሚገዛ እንደሆነ እና ለ) የግልግል ዳኛዉ አስቦ/አዉቆ በጥንቃቄ ትኩረት ሳይሰጠዉ የቀረበ እንደሆነ ነዉ። የግልግል ብይን በሕግ ስህተት ምክንያት የሚታረምበት ምክንያት አንዱ ሕጋዊነት ሲሆን ብይኑ በሕግ ስህተት ምክንያት እንዲታረም በሕግ ስልጣን የተሰጠ ወይም አስገዳጅ የሆነ የህግ ትርጉም የተሰጠበት እንደሆነ ነዉ። የአሜሪካ የፌዴራል የግልግል ሕግ አንቀጽ 10 (ሀ) ሥር የተዘረዘሩት ምክንያቶች የሕግ ስህተት የሚያካትት አይደለም። የኒዉ ጀርሲ የግልግል ሕግ የግልግል ዳኛ ሕግን ተፈጻሚ በሚያደርግበት ጊዜ ጉልህ የሆነ ስህተት የፈጸመ እንደሆነ ፍርድ ቤት ይህን የግልግል ብይን እንደሚሰርዝ ተመልክቷል። በዚህ መሰረት ፍ/ቤት የግልግል ብይን ግልጽ የሆነ የሕግ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስህተት ያለበት እንደሆነ በጠባቡም ቢሆን ብይኑን ከማረም የሚከለክለው ሕግ እንደሌለ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

21. እ.ኤ.አ. 1996 የወጣው የእንግሊዝ የግልግል ሕግ አንቀጽ 69 (England Arbitration Act 0f 1996) ተከራካሪ ወገኖች የሕግ ስህተት በማንሳት ለፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብ የግልግል ብይን እንዲታረም መጠየቅ እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡

22. በሲዊዘርላንድ ኢንተርካንቶናል የግልግል ሕግ አንቀጽ 36 ደግሞ የግልግል ብይን የተሰጠው በተሳሳታ የፍሬ ነገር ድምዳሜ መሰረት በማድረግ የሆነ እንደሆነ ወይም ግልጽ የሆነ የሕግ ወይም ርትዕ ጥሰት የተፈጸመበት እንደሆነ ፍ/ቤት ብይኑን እንዲሰርዝ የሚፈቀድ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

23. ከኢትዮጵያ አንጻር ሲታይ ከክርክር አፈታት ዘዴዎች መካከል አንዱ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንደሆነ የኢትዮጵያ የፍትሓ ብሔር ሕግ፣ የፍትሓ ብሔር ስነስርዓት ሕግ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎችን ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር የፍትሓ ብሔር ሕግ አንቀጽ 3325-3346 እንዲሁም የፍትሓ ብሔር ስነስርዓት ሕግ ቁጥር 315-319 እና አንቀጽ 350-357 ድንጋጌዎችን ያስገነዝባሉ፡፡ የግልግል ዳኝነት የሚታየው በኢትዮጵያ ሕግ እስከሆነ ድረስ እነዚህ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑ አከራካሪ አይሆንም፡፡ የፍትሓ ብሔር ሕጉ መሰረታዊ መብት የሚደነግግ ሲሆን የፍትሓ ብሔር ስነስርዓት ሕጉ ደግሞ ይህን መሰረታዊ መብት ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል የስነስርዓት ደንቦችን የሚደነግግ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው በሕግ አግባብ ተቋቁሞ የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር ሰምተው አጣርተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.318 ሥር በተመለከተው መሰረት ብይን ወይም ውሳኔ መስጠት እንደሚችል ተደግጓል፡፡ ይህ ብይን ወይም ውሳኔ ልክ በፍርድ ቤት እንደሚሰጥ ብይን ወይም ውሳኔ ዓይነት መወሰን እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው በሰጠው ብይን ወይም ውሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት ወይም እንዲሰረዝ አቤቱታ የሚቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.350-357 ሥር በተመለከተው አግባብ እንደሆነ የዚህ ሕግ አንቀጽ 319 (1) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው የግልግል ዳኝነት ጉባኤው በኢትዮጵያ አገር እና በዚህ አገር ሕግ አግባብ የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር አይቶ ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ፣ በዚህ ብይን ወይም ውሳኔ ያልተስማማ ወይም ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኝ የሚልበት ወይም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ እንዲሰረዝለት የሚጠይቅበት ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን እና የግልግል ብይን ወይም ውሳኔ ከሕግ የሚቃረን ወይም ኢ-ፍትሓዊ ቢሆንም እንኳን ዝም ተብሎ የሚፈጸም ነዉ ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ከእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለዉ የግልግል ብይን ወይም ውሳኔ በሕጉ በተመለከተዉ አግባብ እና ምክንያቶች በፍ/ቤት ታይቶ ሊታረም እንደሚችል ነዉ እንጂ በምንም መልኩ ሊታረም የማይችል የመጨረሻ ውሳኔ ነዉ ለማለት የሚቻልበት ሁኔታ የለም፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካች በናሽናል ሞተርስ ኮርፖሬሽን እና በተጠሪ ጄኔራል ቢዝነስ ዲቨሎፕመንት መካከል በነበረዉ ክርክር በሰ.መ.ቁ.21849 ላይ ህዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠዉ ውሳኔ ተዋዋይ ወገኖች (ተከራካሪ ወገኖች) በግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ታይቶ የተሰጠዉ ውሳኔ የመጨረሻ ነዉ በማለት የተስማሙ በመሆኑ፣ የግልግል ዉሳኔዉ እንደዉሉ በእራሱ የመጨረሻ ውሳኔ በመሆኑ በሰበር ቀርቦ ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት መወሰኑን ማየት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይሄው ችሎት በአመልካች ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የግ/ማህበር እና በተጠሪ ዳኒ ድሪሊንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል በነበረዉ ክርክር በሰ.መ.ቁ.42239 ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠዉ ውሳኔ ተከራካሪ ወገኖቹ የግልግል ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ብለዉ ቢስማሙም፣ በግልግል ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ ለዚህ ችሎት ቀርቦ የማይታይበት የህግ ምክንያት የለም በማለት በሰ.መ.ቁ.21849 የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በመለወጥ ወስኗል፡፡

24. የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ብይን ላይ ቅሬታ ያለዉ ተከራከሪ ወገን መቃወሚያዉን የሚያቀርብባቸዉ መንገዶች በፍ/ብ/ሕ/ቁ.350-357 ሥር ተመልክቷል፡፡ እነዚህም፡

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.351 ሥር በተዘረዘሩት የይግባኝ ምክንያቶች ለመደበኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፣ ነገር ግን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.350 (2) መሰረት ማንኛዉም ተከራካሪ ወገን አዉቆ፣ ገብቶት ወይም ተረድቶ ይህን የይግባኝ መብቱን መተዉ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

2. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.355 መሰረት የግልግል ብይን እንዲሻርልኝ በማለት ለፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ ይህ ድንጋጌ ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.356 ሥር የተዘዘሩትን ምክንያቶች የያዘ መሆን እንዳለበት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያመለክታል። ፍ/ቤቱም በድንጋጌው ስር የተዘረዘሩት ሁኔታዎች መከሰታቸውን ያረጋገጠ እንደሆነ የግልግል ብይኑን መሰረዝ እንደሚችል ያሳያል።

3. ተከራከሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ነዉ ብሎ ቢስማሙም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ ከማሳረም እንደማያግዳቸዉ ይህ ችሎት በበርካታ መዛግብት የሰጣቸዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያስገነዝባል።

ከእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ ከግልግል ብይን ላይ ይግባኝ የሚባልበት እና ብይኑ እንዲሻር ወይም እንዲሰረዝ በመጠየቅ መካከል ልዩነት መኖሩን ነዉ። ፍ/ቤት የግልግል ብይን የሚሰረዝበት ወይም የሚያነሳበት አግባብ የሥነሥርዓት እና የስልጣን ትክክለኛነት የሚቆጣጠርበት መንገድ ነዉ። የግልግል ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.356 መሰረት ለመሻር ወይም ለማንሳት ምክንያት የሆኑት ሁኔታዎች ለይግባኝ ምክንያቶች ሊሆኑ እንደማይችሉ መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ።የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የግልግል ብይን ያጸናል ወይም በሶስት ወር ጊዜ ዉስጥ ድጋሚ አይቶ እንዲወስን ለግልግል ዳኝነት ጉባኤ ይመልሳል።

25. ከዚህም በላይ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት ለችሎቱ በተሰጠዉ የስልጣን ወሰን ዉስጥ እስከሆነ ድረስ ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጣቸዉ አካላት በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸዉ እንደሆነ ቅሬታቸዉን የሚያሰሙበት መድረክ ነዉ። በዚህ ረገድ በአመልካች ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የግ/ማህበር እና በተጠሪ ዳኒ ድሪሊንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል በግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ታይቶ የተሰጠዉን ዉሳኔ በተመለከተ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከግራ ቀኙቸዉ የቀረበዉን ክርክር መሰረት በማድረግ በሰ.መ.ቁ.42239 ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የግልግል ብይን በተመለከተ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ ተመሳሳይ የሕግ አፈጻጸም እና ትርጉም እንዲኖር ከማድረግ አንጻር ቅሬታዉ ለዚህ ችሎት መቅረብ የለበትም አይባልም። ይህ ደግሞ ለዚህ ችሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት እና በአዋጅ ቁጥር 454/1997 ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር ማየት ያስፈልጋል። የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በሰጠዉ ዉሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.351 እና 356 ሥር በተመለከቱት ምክንያቶች ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለዚህ ችሎት ቀርቦ የማይታይበት እና የማይታረምበት የሕግ አግባብ የለም፣ ችሎቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንዳለዉ በማለት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል። ይህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ደግሞ የፌዴራል ፍ/ቤቶች እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2 (4) መሰረት ሕግ በመሆኑ አስገዳጅነት ያለዉ ነዉ። ስለሆነም ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ነዉ ብሎ ቢስማሙም፣ ከዉሳኔዉ ቅሬታ ያለዉ ተከራካሪ ወገን ጉዳዩን ለሰበር ከማቅረብ የሚያግደዉ እንዳልሆነ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ ከማረም የሚከለክለዉ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

26. እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለዉጭ አገር የግልግል ብይን እዉቅና ለመስጠት እና ተፈጻሚ ለማድረግ የሚቀርበዉን አቤቱታ ለመመርመር ስልጣን እንዳለዉ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11 (2፣ ሐ) ሥር ተመልክቷል። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.461 ለብይኑ እዉቅና ላለመስጠት እና ተፈጻሚ ላለማድረግ ሥር ስድስት ምክንያቶች መዘርዘሩን ማየት ይቻላል።

27. በመሆኑም ከፍ ሲል በዝርዝር እንደተመለክተነዉ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ብይን ወይም ዉሳኔ በሕጉ በተመለከቱት ጠባብ ምክንያቶችም ቢሆንም በፍርድ ቤት ቀርቦ ከመታረም የሚድን እንዳልሆነ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ የአገሮች ልምድ እና የኢትዮጵያ ሕግ የሚያስገነዝበዉ ጉዳይ ነዉ። አገሮች የየራሳቸዉን ነበራዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የግልግል ብይን ግልጽ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ወይም ጉልህ የሆነ የፍትሕ መጓደል ያስከተለ እንደሆነ እንዲሁም ከሕዝብ ጥቅም (public policy) አንጻር በማየት፣ በየፍርድ ቤቶቻቸዉ ይህን ብይን የሚያሳርሙበት ስርዓት መዘርጋታቸዉን ማየት ይቻላል። ይህ ማለት ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ብይን የመጨረሻ ነዉ ብሎ ቢስማሙም እንኳን ፣ፍትሕ የማግኘት መብት እና ፍትሓዊነትን የማስፈን ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ ለተከራካሪ ወገኖች ነጻ ፈቃድ የሚተዉ ባለመሆኑ፣ ብይኑ በፍጹም ለፍ/ቤት ቀርቦ ሊታረም አይችልም ለማለት የሚቻል አይሆንም። ስለሆነም የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ብይን ወይም ዉሳኔ በሕጉ በተመለከቱት ምክንያቶች ብቻ ለፍ/ቤት አቅርቦ እንዲታይ እና እንዲታረም ማድረግ እንደሚቻል ነዉ። ነገር ግን በፍ/ቤት የግልግል ብይን የማሳረም ወይም የማሰረዙ ጉዳይ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባኤን የሚያቋቁሙበት ዓላማ ሙሉ ለሙሉ ዋጋ በሚያሳጣ መልኩ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆን እንደሌለበት መገንዘብ ያስፈልጋል። ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸዉ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንዲታይላቸዉ ከሚፈልጉባቸዉ ምክንያቶች መካከል የተሰወኑትን ለመጥቀስ በመረጡት ገላጋይ ዳኞች ለመዳኘት ካላቸዉ ፍላጎት፣ የተከራካሪ ወገኖች ነጻነት፣ ጊዜያቸዉን ለመቆጠብ እና ወጪን ለመነቀስ የሚሉት ናቸዉ። ከዚህም በላይ የግልግል ብይን በፍ/ቤት ሊታረም ይገባል ሲባል በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለዉን የንግዱን ማህበረሰብ ዝንባሌ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢንቨስትመንት ከመሳብ አንጻር ያለዉን ተጽኖ ከግምት ያስገባ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነዉ። የግልግል ዳኝነት ጉባኤ በፍ/ቤት ከመታየት የማይድን ቢሆንም እነዚህን ሁኔታዎች ታሳቢ በማድረግ በሕጉ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በጠባቡ መሆን እንዳለበት መረዳት ያስፈልጋል።

ሲጠቃለል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ መቀመጫ አዲስ አበባ ከተማ ኢትዮጵያ እስከሆነ ድረስ እና ጉዳዩም ታይቶ ዉሳኔ የተሰጠበት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት በመሆኑ፣ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና የአገሮች ልምድ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕጎች እና ይህ ችሎት በበርካታ መዛግብት ከሰጣቸዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር፣ ተከራካሪ ወገኖቹ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ ብሎ ቢስማሙም ዉሳኔዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ በሰበር ከማየት የሚከለክለዉ የሕግ መሰረት የለም። በመሆኑም ተጠሪ ይህ ችሎት ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም ብለናል።

28. ሁለተኛዉን ጭብጥ በተመለከተ ግራ ቀኙቸዉ መካከል የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? ዉጤቱስ ምን ይሆናል? የሚለዉ ነጥብ እንደሚከተለዉ የሚታይ ይሆናል።

29. በአዉሮፓ ልማት ፈንድ ስነስርዓት (EDF Rules) አንቀጽ 14.1 መሰረት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የኢትዮጵያ ሕግን ተግባራዊ ማድረግ እና የኢትዮጵያ ሕግ እስከፈቀደ ድረስ የንግድ ልማድ ከግምት ዉስጥ መግባት እንደሚገባ ተመልክቷል። ስለሆነም ለተያዘዉ ጭብጥ ምላሽ ለመስጠት በዚህ ጉዳይ የኢትዮጵያ የዉል ሕግን መፈተሽ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

30. እንደሚታወቀዉ በሕግ ፊት የሚጸና ዉል አለ ለማለት ማሟላት ካለባቸዉ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ተዋዋይ ወገኖች ጉደለት የሌለበትን ስምምነት ማድረግ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1678 /ሀ/ ሥር ተመልክቷል። ተዋዋይ ወገኖች የሚገቧቸዉን ግዴታዎች ፈቅደዉ እና አዉቀዉ መሆን እንዳለበትም የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1679 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ። በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ዉሎች ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች ላይ ሕግ እንደሚሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 /1/ ድንጋጌ የሚያስገነዝበዉ ጉዳይ ነዉ። ተዋዋይ ወገኖች ዉልን ሲዋዋሉ የፈቃድ ጉድለት መኖር እንደሌለበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1696 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያመለክታሉ። በዚህ መሰረት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1696 ሥር እንደተመለከተዉ ዉል የሚያፈርሰዉ ከተዋዋዮቹ ወገኖች የአንደኛዉ መፍቀድ በስህተት፣ በድንገተኛ ተንኮል ወይም በኀይል የተገኘ ሲሆን ነዉ በማለት ይደነግጋል።

31. ዉል ሲደረግ የተዋዋይ ወገን የፈቃድ ጉድለት ከሚያስከትሉት ምክንያቶች መካከል የተንኮል ተግባር አንዱ ነዉ። በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704 (1) መሰረት በተንኮል የተደረገ ዉል ፈራሽ የሚሆነዉ ከተዋዋዮቹ አንደኛዉ ወገን ዉሉ እንዲደረግ ያደረገዉ በሁለተኛዉ ተዋዋይ ላይ ተንኮል ባይደርስበት ኖሮ ዉል የማያደርግ እንደነበረ ሲገለጽ ነዉ በማለት ይደነግጋል።

32. በዚህ መሰረት አሁን ወደ የተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በግራ ቀኙቸዉ መካከል የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ተጠሪ በፈጸመዉ የተንኮል ተግባር የተደረገ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ በቅድሚያ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ። በዚህ መሰረት ይህን የባቡር መንገድ ጥገና ሥራ ለመሥራት ጨረታዉን ተወዳድረዉ ያሸፉት የእሸሙር ማህበር የተቋቋመዉ በኮንስታ ኮንሶርዞ እና ጂሲኤፍ (GCF) ሆነዉ የኮንስታ ጀቪ (consta JV) በሚል የእሸሙር ማህበር ነዉ። በዚህ የእሸሙር ማህበር ኮንሶርዚዮ ኮንስታ 70% የአክስዮን ድርሻ እና ጂሲኤፍ ደግሞ 30% የአክስዮን ደርሻ መያዛቸዉ ተገልጾ መሆኑ ተረጋግጧል። ይህን ጨረታ ተክትሎ ህዳር 19 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ህዳር 29 ቀን 2006) በተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ በአጠቃላይ በብር 40,433,056.70 ዩሮ ተስማምቷል። በዚህ የዉል ስምምነቱ የሚሰሩ በርካታ ሥራዎች ተዘርዝሮ እናገኛለን።

33. ይህ በእንዲህ እንዳለ ኮንሰታ እና ጂሲኤፍ መካከል ይህን ቅንጅት በተመለከተ ሶስት ምስጥራዊ ስምምነቶች መደረጋቸዉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ። በዚህ መሰረት ሐምሌ 27 ቀን 1998 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ኦገስት 3 ቀን 2006) በተፈረመዉ የሚስጥር ስምምነት ቁጥር 1 መሰረት የጂሲኤፍን የአክስዮን ድርሻ ወደ 0.1% ዝቅ ለማድረግ ተስማምቷል፣

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ህዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 24 ቀን 2006) በተደረገዉ የሚስጥር ስምምነት ቁጥር 2 የጂሲኤፍ የአክስዮን ድርሻ ወደ 0.2% ዝቅ እንዲል አድርጓል፤ መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ማርች 20 ቀን 2007) በተፈረመዉ የሚስጥር ስምምነት ቁጥር 3 መሰረት ጂሲኤፍ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ዩሮ ክፍያን በመቀበል ተሳትፎዉን እስካሁን ድረስ በተፈጸመዉ ብቻ እንዲገደብ ማድረጉ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪም ቢሆንም እነዚህ ስምምነቶች መደረጋቸዉን የካደ ነገር የለዉም፡፡ ከዚህም በላይ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በሰጠዉ ዉሳኔ እነዚህ ምስጥራዊ ስምምነቶች መደረጋቸዉን በዉሳኔዉ አረጋግጧል፡፡ በዚህ ረገድ የአዉሮፓ አንቲ-ፍራዉድ ቢሮ (OLAF) ባዘጋጀዉ የመጨረሻ ሪፖርት ይህ ዉል ከመፈረሙ አምስት ቀን ቀደም ብሎ ጂሲኤፍ በኮንስታ ጂቪ ያለዉን ተሳትፎ ከ30% ወደ 0.2% ዝቅ ማድረጉን እና በዚህም ተጠሪዉ የጠቅላላ ዉል ክፍል አንቀጽ 12.7 መጣሱን አረጋግጧል፡፡ የአሁን ተጠሪ እነዚህን ስምምነቶች ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ ቢኖርበትም የአዉሮፓ አንቲ-ፍራዉድ ቢሮ (OLAF) ባደረገዉ ምርመራ ባይደርስበት እና ይፋ ባያደርጋቸዉ ኖሮ ተደብቀዉ እንደሚቀሩ ተረጋግጧል፡፡

34. እንግዲህ የአሁን ተጠሪ ለባቡር መስመር ሥራዉ አመልካች ያወጣዉን ጨረታ ተወዳድሮ እና ጨረታዉን አሸንፎ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ያደረገዉ በኮንሶርዚዮ ኮንስታ 70% የአክስዮን ድርሻ እና ጂሲኤፍ 30% የአክስዮን ደርሻ ባላቸዉ አባላት የተዋቀረ የእሽሙር ማህበር መሆኑን ለአመልካች በመግለጽ እንደሆነ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ነገር ግን ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ የእሽሙር ማህበሩ ዉስጥ የጂሲኤፍ የአክስዮን ድርሻ እና ተሳትፎ 30% ሳይሆን 0.2% መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የአሁን ተጠሪ አመልካች ባወጠዉ ጨረታ ሲሳተፍ እና ዉል ሲያደርግ የእሽሙር ማህበሩ አባላት የሌላቸዉን የአክስዮን ድርሻ እና የተሳትፎ መጠን እንዳላቸዉ ለአመልካች በመግለጽ ያደረገ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የአሁን ተጠሪ ጨረታዉን ሲወዳደር እና ዉል ሲያደርግ ለአመልካች ትክክል ያልሆነ ወይም ሐሰተኛ ገለጻ ወይም መግለጫ መስጠቱን ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ አመልካች ስለተጠሪ የእሽሙር ማህበር አደረጃጀት እና አወቃቀር ትክክል ያልሆነ ግንዛቤ እንዲወስድ እና የተሻለ ተወዳዳሪ አድርጎ በመዉሰድ ጨረታዉን እንዳሸነፈ በመቁጠር ዉል አብሮ እንዲያደርግ ያደረገዉ መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካች ስለእሽሙር ማህበሩ ያልሆነ አቋም እንዲይዝ በማድረግ፣ ተጠሪዉ ለሥራዉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብቃት እንዳለዉ በመቁጠር ጨረታዉን አሸንፎ ዉል እንዲያድርግ ያደረገዉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የአሁን ተጠሪ በፈጸመዉ የተንኮል ተግባር አመልካች የባቡር መስመር ሥራ ዉል ከተጠሪ ጋር እንዲያደርግ ያደረገዉ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በፈጸመዉ የተንኮል ወይም የማጭበርበር ተግባር አመልካች ከተጠሪ ጋር ይህን ዉል ሊያደርግ የቻለ በመሆኑ፣ በአመልካች በኩል ዉሉን ሲያደርግ የፈቃድ ጉድለት መኖሩን የሚያረጋግጥ ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የአሁን ተጠሪ ተግባር የተንኮል ወይም የማጭበርበር ተግባር አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ እና የአሁን ተጠሪ የተንኮል ተግባር የለም በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

35. ሌላዉ መታየት ያለበት ጉዳይ የአሁን ተጠሪ የእሽሙር ማህበሩ ዉስጥ የጂሲኤፍ አክስዮን ድርሻ እና የሥራ ተሳትፎ 0.2% ሆኖ እያለ 30% እንደሆነ የሚገልጽ ሐሰተኛ መግለጫና ማስረጃ በማቅረብ በፈጸመዉ የተንኮል ተግባር አመልካች ወደ ዉሉ እንዲገባ ያደረገዉ ለዉሉ መሰረታዊ የሆነ ነገር (essential or material) ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 12.7 እና 64.2 (h) ድንጋጌዎች መታየት እንዳለባቸዉ ተገንዝበናል፡፡ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 12.7 እንደሚያመለክተዉ የሥራ ተቋራጩ የእሽሙር ማህበር ወይም ከሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ ሰዎች ማህበር እንደሆነ፣ እነዚህ ሰዎች ሁሉም በተዋዋይ ባለስልጣን አገር ሕግ መሰረት በዉሉ መሰረት ለመፈጸም የአንድነትና የነጠላ ግዴታ አለባቸዉ እና በተዋዋይ ባለስልጣን ጥያቄ ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዱን እንደማህበሩ መሪ ሆኖ ከባለስልጣኑ ጋር በመስራት የእሽሙር ማህበሩን ወይም ማህበሩን ለማስገደድ ነዉ፡፡ የእሽሙር ማህበሩ ወይም የማህበሩ አወቃቀር ወይም አደረጃጀት ያለ ተዋዋይ ባለስልጣኑ ቅድሚያ ፈቃድ ሊለወጥ አይችልም፡፡ ይህ ድንጋጌ እንደሚያስገነዝበዉ የእሽሙር ማህበር አባላት በማህበሩ ባላቸዉ የአክስዮን ድርሻ መጠን በዉሉ የሚመለከታቸዉን ግዴታዎቻቸዉን መወጣት እንዳለባቸዉ ነዉ፡፡ ከእነዚህ አባላት መካከል አንዱ የሌለዉን ወገን ግዴታ ሸፍኖ ሊወጣ እንደሚችል የሚያመለክት ነገር የለዉም፡፡ የማህበሩ አባላት ደርሻቸዉን እና ተሳትፎአቸዉን ለመቀየር ከፈለጉ መጀመሪያ የአመልካች ፈቃድ ማግኘት እንደሚገባቸዉ ያስገድዳል፡፡ ይህ ማለት የዚህ የእሽሙር ማህበር አባላት የአክስዮን ድርሻ ወይም የስራ ተሳትፎ መጠን ካለ አመልካች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እወቅና ሊለወጥ እንደማይችል ያመለክታል። ይህ የሚያመለክተዉ የአሁን አመልካች ከተጠሪ ጋር ዉል ሲያድርግ የእሽሙር ማህበር አባላት አደረጃጀታቸዉን እና አወቃቀራቸዉን ኮንስታ 70% የአክስዮን ድርሻ እና ጂሲኤፍ 30% የአክስዮን ድርሻ ጠብቀዉ እያንዳንዳቸዉ በዉሉ የገቡትን ግዴታ እንደሚፈጽሙ በማመን መሆኑ ግልጽ ነዉ። የአሁን ተጠሪ ጨረታዉን ሲወዳደር እና አሸንፎም ዉል ከአመልካች ጋር ሲያደርግ በዚህ የድርሻ መጠን እና በዚህ መሰረት በዉሉ የተመለከተዉን ግዴታዎቻቸዉን በሥራዉ ቦታ በመገኘት ለመወጣት እንደሆነ ግልጽ ነዉ። አመልካች የዚህ ማህበር አባላት ድርሻ ጨረታዉን ሲወዳደሩና ዉል ሲያደርጉ የተገለጸዉን አለመሆኑን ቢያዉቅ ይህ ዉል ያደርጋል ተብሎ አይታሰብም። በዚህ ረገድ የአዉሮፓ አንቲ-ፍራዉድ ቢሮ (OLAF) ባዘጋጀዉ የመጨረሻ ሪፖርት በዉሉ የተመለከተዉን ሥራ ለመስራት ኮንስታ ብቻዉን የቴክኒካል ችሎታ ወይም ብቃት ስለሌለዉ ዉሉ እንደማይሰጠዉ እና በፐርሰንት የተመለከተዉ የተሳትፎ መጠን እያንዳንዱ አባል የሚፈጽመዉን ሥራ ድርሻ መሆኑን እና የኮንስታ አባላት የጠቅላላ የዉል ክፍል አንቀጽ 12.7 መጣሳቸዉን አረጋግጧል። ከዚህም በላይ የጂሲኤፍ ሥራ አስኪያጅ የሆነዉ ሚ/ር ሮሲ የተባለዉ የተጠሪ ምስክር በሰጠዉ የምስክርነት ቃል የጂሲኤፍ ድርሻ ወደ 0.2% መቀነሱን የአሁን አመልካች እና የአዉሮፓ ህብረት ቢያዉቁ ኖሮ ዉሉ ለተጠሪ እንደማይሰጥ መመስከሩን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል። የአሁን ተጠሪ ሆነ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ይህ ድርጊት ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 12.7 እንደሚጥስ መሆኑን ቢያምኑም የተንኮል ወይም የማጭበርበር ተግባር እንዳልሆነ መግለጻቸዉን መዝገቡ ያሳያል።

36. ከዚህ አንጸር ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 64.2 (h) እንደሚደነግገዉ በሌላ አካል እስካልተጠቀሰ ድረስ ተዋዋይ ባለስልጣን ለሥራ ተቋራጩ የሰባት ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ዉሉን በማቋረጥ እና የስራ ተቋራጩን ከሥራ ቦታ ከሚያባርርባቸዉ ምክንያቶች አንዱ የዉሉ አካል ሆኖ የተመዘገበ ካልሆነ በቀር የስራ ተቋራጩን ሕጋዊ ሰዉነት፣ ተፈጥሮ እና የቁጥጥር ለዉጥ የሚያስከትል ማንኛዉም የማህበሩ አደረጃጀት ወይም መዋቅር ለዉጥ እንደሆነ ይገልጻል። በመሆኑም ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 12.7 እና አንቀጽ 64.2 (h) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እንደሚያስገዝበዉ የተጠሪ የእሽሙር ማህበር ዉስጥ የአባላቱ ድርሻ ለዚህ ዉል መደረግ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ የሆነ ነገር (essential or material) መሆኑን ያስገነዝባል። ስለሆነም የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር ጂሲኤፍ በማህበሩ ዉስጥ የነበረዉ ድርሻ መቀነሱ እና የዉሉ አንቀጽ 12.7 የሚጥስ ቢሆንም ለዉሉ መሰረታዊ የሆነ ነገር አይደለም፣ ኮንስታ ብቻዉን ይህን ሥራ ለመስራት ሙሉ አቅም አለዉ በማለት ያቀረበዉ ክርክር እና የግልግል ጉባኤዉ በሰጠዉ ዉሳኔ ይህ ድርጊት የሚያደርሰዉ ጉዳት የለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎችን ድንጋጌዎች የሚጥስ ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል።

37. የአሁን ተጠሪ የእሽሙር ማህበሩ ዉስጥ ጂሲኤፍ የነበረዉን ድርሻ በተንኮል ከአመልካች በመደበቅ ዉል ያደረገ በመሆኑ፣ ይህ ደግሞ ለዉሉ መሰረታዊ የሆነ ነገር በመሆኑ፣ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ። የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1704 (1) ሥር የተመለከተዉ የተንኮል ተግባር በዉሉ ላይ ተጽኖ የማይፈጥር ተራ ወይም ቀላል ነገር ሳይሆን መሰረታዊ የሆነ ነገር መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል። የአሁን ተጠሪ የእሽሙር ማህበሩ ዉስጥ የጂሲኤፍ የሌለዉን ድርሻ እንዳለዉ በመግለጽ አመልካች በማያዉቀው ሁኔታ ወደ ዉሉ እንዲገባ ባያደርገዉ ኖሩ ዉሉን የማያደርግ መሆኑን ያመለክታል። ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን ተጠሪ የፈጸመዉ የተንኮል ተግባር በግራ ቀኛቸዉ መካከል በተንኮል የተደረገዉን ዉል ለማስፈረስ በቂ ምክንያት ይሆናል። አመልካች በዚህ ምክንያት ዉሉ እንዲፈርስለት ለመጠየቅ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1808 (1) ሥር ተመልክቷል። ፍ/ቤትም በሕጉ አግባብ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ከመስጠት የሚከለክለዉ ነገር እንደሌለ መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በፈጸመዉ የተንኮል ተግባር አመልካች የባቡር መስመር ሥራ ዉል እንዲያደርግ ያደረገዉ በመሆኑ፣ ይህ ዉል ፈራሽ ነዉ፣ በግራ ቀኛቸዉ መካከል ህዳር 19 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ህዳር 29 ቀን 2006) የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ሊፈርስ ይገባል ብለናል።

38. ይህ በእንዲህ እንዳለ ተጠሪ የባቡር መስመር ሥራ ዉል ከተደረገ በኋላ መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. ማርች 20 ቀን 2007) በተፈረመዉ የሚስጥር ስምምነት ቁጥር 3 መሰረት ጂሲኤፍ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ዩሮ ክፍያን በመቀበል ተሳትፎዉን እስካሁን ድረስ በተፈጸመዉ ብቻ እንዲገደብ ማድረጉን የቀረበዉ ማስረጃ የሚያረጋግጥ መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል። በዚህ ረገድ የአሁን ተጠሪ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባቀረበው ክርክር ጂሲኤፍ አምስት አመት በኢትዮጵያ በስራ ቦታ እንደሌለ እያወቀ ሥራው እንዲቀጥል አድርጓል በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ረገድ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ጂሲኤፍ በሥራ ቦታ መገኘት አለመገኘቱን ለአመልካች ማሳወቅ የሚገባው ተጠሪ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ ይህ የሚስጥር ስምምነት መደረጉን እና ጂሲኤፍ በሥራው ቦታ ያልነበረ መሆኑን ከአመልካች ሸሽጎ እንደቆየ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ የሚያሳያው ተጠሪ ዉሉ ከተደረገ በኋላም የተንኮል ተግባሩን የገፋበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ጉዳይ ነው፡፡

39. እንደሚታወቀው አንድ ዉል በፍ/ቤት ዉሳኔ የፈረሰ እንደሆነ የዉሉ መፍረስ የሚያስከትለው ዉጤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1815 መሰረት መወሰን እንዳለበት ያመለክታል፡፡ ነገር ግን አሁን የተያዘው ጉዳይ ሲታይ በግራ ቀኞቹው መካከል የተደረገው የባቡር መስመር ሥራ ዉል እንዲፈርስ እስከተወሰነ ድረስ ዉጤቱ ምን ይሆናል? የሚለው ነጥብ ሲታይ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ከዚህ አንጻር ጭብጥ በመያዝ የዉሉ መፍረስ የሚያስከትለውን ዉጤት አጣርቶ ዉሳኔ ያልሰጠበት በመሆኑ፣ በዚህ ረገድ ይህ ችሎት የዉሉ መፍረስ የሚያስከትለው ዉጤት በተመለከተ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለው ነገር ካለመኖሩም በላይ በዚህ አግባብ ተጣርቶ የቀረበ ግልጽ የሆነ ነገር ስለሌለ ጉባኤው ድጋሚ አይቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት መመለስም የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የዚህ ዉል መፍረስ የሚያስከትለውን ዉጤት በተመለከተ መብት አለኝ የሚል ወገን ካለ በሕጉ አግባብ ከሚጠይቅ በስተቀር በዚህ መዝገብ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ አልተገኘም ብለናል፡፡

40. ሲጠቃለል የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ከፍ ሲል በተመለከተው ምክንያት በግራ ቀኞቹው መካከል የተደረገው የባቡር መስመር ሥራ ዉል ፈራሽ ማድረግ ሲገባው ይህ ዉል ሊፈርስ አይገባም በማለት አመልካች በዉሳኔው የተጠቀሰውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍለው የሰጠው ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. ዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ኔዘርላንድ (ሄግ) የሚገኘው ቋሚ የግልግል ዳኝነት ፍ/ቤት የሚያስተዳደረው መቀመጫው አዲስ አበባ ከተማ ኢትዮጵያ የሆነው በመ.ቁ.2013-32 ላይ ሚያዚያ 28 ቀን 2008 ዓ.ም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

(እ.ኤ.አ. ግንቦት 6 ቀን 2016) የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በግራ ቀኛቸዉ መካከል ህዳር 20 ቀን 1999 ዓ.ም (November 29, 2006) የተደረገዉ የባቡር መስመር ሥራ ዉል የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በፈጸመዉ የተንኮል ተግባር የተደረገ ስለሆነ ዉሉ ፈራሽ ነዉ ብለናል፡፡
3. የዉል መፍረስ የሚያስከትለዉን ዉጤት በተመለከተ መብት አለኝ የሚለዉ ወገን በሕግ አግባብ መብቱን ከመጠየቅ ይህ ዉሳኔ አያግደዉም ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
6. በ22/9/2008 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጌ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከውል ውጭ ኃላፊነት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ. 152417

ግንቦት 17 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሚሚ አበበ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ታምራት /ማሙሽ/ ባልቻ - ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ክርክሩ በተጀመረበት በምንጃር ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች ሲሆኑ ተከሳሽ ደግሞ የአሁኑ ተጠሪ ነበሩ፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ በቆንጨራ የቀኝ እጃቸውንና የቀኝ ጭንቅላቸውን በመምታት የቀኝ እጃቸው መዳፍ ማጠፊያ አንጓ እንዲቆረጥ በማድረጋቸው በከባድ የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል ተከሰው በፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑን፣ በዚህ የወንጀል ድርጊት በደረሰባቸው የአካል ጉዳት ምክንያትም ስራ ሰርተው ያገኙት የነበረው ገቢ የቀረባቸውና ስራ ስርተው መኖርም ያልቻሉ መሆኑን ጠቅሰው ብር 300,000.00(ሶስት መቶ ሺህ ብር) ካሳ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪም በሕጉ አግባብ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤትም ተገቢ ናቸው ያላቸው የአመልካች እድሜና የገቢ መጠን በማስረጃ እንዲጣሩ ለማድረግ ማስረጃዎቹ ከሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርቡ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት ትዕዛዝ ሲስጥ ቆይቶ የአመልካች ጠበቃ ተገቢውን ሊፈጽሙ ባለመቻላቸው በዚህ ረገድ ማስረጃዎችን ያልሰማ ሲሆን በኃላፊነት ረገድ ግን በተጠሪው ላይ በወንጀል ጉዳይ በፍርድ ቤት የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረት አድርጎ ተጠሪን ለክሱ ኃላፊ ያደረገ ሲሆን ካሳውን በተመለከተ የአመልካች ጠበቃ በርትዕ እንዲወሰን ያቀረቡትን ጥያቄ ካሳ በርትዕ የሚወሰነው በልዩ ሁኔታ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለውና አመልካችም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 አግባብ የካሳ መጠኑን ለማስረዳት ያልቻሉ መሆኑን ጠቅሶ ለአካል ጉዳት የተጠየቀውን ካሳ በማለፍ የሞራል ጉዳት ካሳ ብቻ ብር 1000.00(አንድ ሺህ ብር) አመልካች እንዲከፈላቸው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበውም ተጠሪ በህጉ አግባብ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ ተጠሪ በሌሉበት እንዲታይ ከተደረገ በኃላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የጉዳት ካሳ መጠኑ በርትእ ሊወሰን የሚችል አይደለም በማለት የደረሰበትን ድምዳሜ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ጠቅሶ የአካል ጉዳት ካሳውን በርትእ አስልቶ ብር 40,000.00(አርባ ሺህ ብር) በማድረግ ወስኖአል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ አመልካች የአሁኑን የሰበር አቤቱታውን ያቀረቡትም በአካል ጉዳት ካሳ መጠን አወሳሰን ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል በማለት ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም የካሳ መጠኑ አወሳሰኑን ተገቢነት ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸውም ባለመቅረባቸው መልስ በጽሑፍ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ለክርክሩ በተያዘው ጭብጥ መሰረት ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 14 ሥር “ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት የመኖር፣የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው” ተብሎ የተቀመጠ ሲሆን አንቀጽ 16 የአካል ደህንነት መብት ምን እንደሆነ ያብራራል፡፡ ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት እንዳለው የሃገሪቱ የበላይ ሕግ ያስገነዝባል፡፡ መንግስትም ሆነ ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው የአካል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ደህንነት የመጠበቅ የሕግ ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ህግ በመተላለፍ በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለደረሰው የአካል ጉዳት ተጐጂው ካሳ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ በህገ-መንግስቱ የተቀመጠው ይህን የሰብአዊ መብት ከሚያረጋግጡ ዝርዝር ሕጐች ውስጥ በፍ/ሕጉ ውስጥ የጉዳት ካሳን አስመልክቶ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ይገኙበቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰው በጥፋቱ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ላደረሰው ጉዳት ኃላፊ ሆኖ ካሳ ሊከፍል እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ. 2028 አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም በመርህ ደረጃ የጉዳት ካሳ ሊከፍል የሚገደደው በጥፋቱ ጉዳት ያደረሰ ሰው ሲሆን በአንዳንድ የተለያዩ ጉዳዮች ደግሞ አንድ ሰው ጥፋት ሳይኖርበትም ኃላፊ እንደሚሆን ከፍ/ሕ/ቁ. 2066 እና ተከታዮቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ በራሳቸው አድራጎት በአመልካች አካል ላይ ለአደረሱት ጉዳት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በራሱ ጥፋት በሰው አካል ላይ ለደረሰ ጉዳት ኃላፊ የሆነ ሰው ለደረሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ግዴታ በፍትሐብሔር ሕጉ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ሊታይ የሚገባው የካሳው መጠን ነው፡፡ ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነ ሰው የሚከፍለው የካሳ መጠን ከጉዳቱ ጋር ተመዛዛኝ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ሕ/ን/ቁ. 2090 እና 2091 ስር ተመልክቷል፡፡ ወደፊት ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ጉዳት የተረጋገጠ ከሆነ እስኪፈፀም መጠበቅ ሳያስፈልግ ካሳው ሊከፈል እንደሚገባ የፍ/ሕ/ቁ. 2092 ይናገራል፡፡ በሌላ በኩል ካሳ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን አለበት ሲባል መታየት ያለበት በአጠቃላይ በተጐጂው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ የመስራት ኃይል ቅነሳ አንፃር እንጂ ከጉዳቱ በፊት ሲሰራው የነበረውን ስራ ላለመስራት ጉዳቱ ያስከተለው ልዩ ጫናና የቅነሳ መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት አለመሆኑን ለዚህም ምክንያት የሚሆነው እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ስራ ለመስራት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ አንድ ሰው ለመኖር የተለያየ ፋይዳና ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ እንደሆነ ይህ የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 19338 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በመሰረቱ ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን ፣ መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090 ፣ 2091 ፣ 2092 ፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበትና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 ድንጋጌ አግባብም ጉዳት የደረሰበት ሰው የጉዳት ካሳ መጠኑን በትክክል ማስረዳት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በአደጋ ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት ሰው ለደረሰበት ጉዳት ሊከፈል የሚገባው የካሣ መጠን በትክክል ለመወሰን የሚያስችል ማስረጃ ያልቀረበ ወይም የካሣውን መጠን በማስረጃ አጣርቶ ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ዳኞች ካሣውን በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2102 መሠረት በርትዕ ሊወሰኑ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው የርትእ መርህ ፍትሕን ለማስፈን ዳኞች በሕግ ከተደነገገው በመውጣት ወይም ሕጉ ራሱ በአንዳንድ ተለይተው በተገለጹ ጉዳዮች ላይ ርትዕን እንዲከተሉ ሲፈቅድ ከሕግ ይልቅ ህሊናቸው ትክክል ነው የሚለውን እንዲመርጡ እንዲወስኑ የሚፈቅድ ነው፡፡ ስለሆነም ርትዕ የሚያመለክተው የተፈጥሯዊ ሕግጋትን በመጠቀም ፍትሕን መስጠት ሲሆን መሰረታዊ አላማውም በሕግ ያለውን ክፍተትን መሙላት ወይም የሕግን ጥብቅ ደንብ ፍትሐዊ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ርትእ አይነተኛ አላማውና ግቡ ሕግ ትክክለኛ ፍትሕ ላያስገኝ ስለሚችል አከራካሪ ለሆነው ጉዳይ እንደማስረጃዎቹና አከባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታዎች በሕግ ድንጋጌ ስር መታጠር ሳያስፈልግ ፍትሕ ለማስገኘት ነው ተብሎ ይታሰበል፡፡ ስለሆነም አስቀድሞ እርግጠኛ በመሆን ደንብ ማስቀመጥ በማይቻልበት ሁኔታ፣ግልጽና ቁልጭ ያል መፍትሔ ለመስጠት የሚቻልበት አጋጣሚ ሲኖር፣ጉዳት አድራሹ ድርጊቱን የፈጸመበት ምክንያት ከቁጥጥሩ ውጭ በሆነ ጊዜ ባደረሰው ጉዳት መጠን ካሳ መክፈል ከህሊና ግምት ውጭ በሚሆንበትና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች ሲያጋጥሙ ርትዕ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ረገድ በሕግ የማይተካ ሚና ያለው መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ካሳ በርትእ ሲወሰን በዘፈቀደ ሊሆን የማይገባው ሲሆን በርትዕ የተሰጠ ውሳኔም በበላይ ፍርድ ቤት ሊሻር የሚገባው ይህንኑ የርትእ መሰረታዊ አላማ እግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የካሳ መጠን ላይ ይግባኝ የሌለው መሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2152 ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኙ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 ስር ተገልጸዋል፡፡ ስለሆነም የጉዳት ካሣ መጠን በዝቷል ወይም ያንሣል በሚል ቅሬታ ማቅረብ የሚቻለው በፍትሃ ብሔር ሕግ ቁጥር 2153 ስር የተመለከቱት የተለዩ ሁኔታዎች ማለትም የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያለአግባብ በመያዝ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሣኔ የተሰጠበት ከሆነ፣ ያለአግባብ የሆነውን የአገማመት ስርዓት በመከተል የተሰጠ ከሆነ፣ የተወሰነው የካሣ መጠን በግልፅ ከአዕምሮ ግምት ውጪ የሆነና የተወሰነውም በማድላት ወይም በዝንባሌ መሆኑ በእርግጥ ሆኖ የተገኘ ከሆነ እና የተሰጠው የጉዳት ካሣ በሂሳብ መሣሣት የሆነ እንደሆነ በመሆኑና እነዚህ ነጥቦች ባልተረጋገጡበት ሁኔታ ግን በፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 2152 ስር እንደተመለከተው ይግባኝ በሕጉ የተፈቀደ አይደለም፡፡ ስለሆነም የጉዳት ካሳ መጠን ውሳኔ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መወሰን ያለበት ሲሆን ይህም የጉዳት ካሳ ሕግ መሰረታዊ አላማን የሚያሳካ ነው ተብሎ ይታሳበል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ፍርድ ቤቶች የጉዳት ካሳ መጠኑን መወሰን ያለባቸው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት ብቻ እንጂ የጉዳት ካሳ መጠኑ ከፍ የማለቱን ወይም ሌላ ግምታዊ የሆነ ምክንያት መሰረት በማድረግ ሲሆን አይገባም፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ተጠሪ በወንጀል ድርጊት በአመልካች ላይ የአካል ጉዳት ያደረሱባቸው ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አከራካሪ የሆነው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካሳው በርትእ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን ከአመነ በኃላ መጠኑን ብር 40,000.00 እንዲሆን በርትእ ሲወሰን እግምት ውስጥ ሊገቡ ይገባቸው የነበሩትን ሁኔታዎች በአግባቡ የያዘ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ችሎቱ የጉዳት ካሳ መጠኑ በርትዕ ሲወሰን ምን ምን ሁኔታዎችን ማገናዘብ አለበት? የሚለውን ነጥብ መመርመር አስፈላጊ መሆኑን ያመነበት ሲሆን ይህንኑ በአግባቡ ለመመለስም አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በአመልካች ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት 40% ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ላይ 40% የአካል ጉዳት መድረሱን ቢያረጋግጥም አመልካች ከጉልበት ስራ ምን ያህል ገቢ እንደሚያገኙ በማስረጃ አለመረጋገጡን፣በዚህ ስራ የተሰማራ ሰው ገቢ በአመክንዩ በመውሰድ እንዲሁም በአገራችን የአንድ ሰው የእለት ገቢ በአማካኝ ተወስዶ ካሳው መሰላት ያለመበት መሆኑን፣ በዚህ ረገድ ግን ግልጽ የሆነ ማስረጃና የሂሳብ ቀመር ያለመቅረቡን ገልጾ ለእነዲዚህ አይነት ችግር ሕጉ መፍትሄ መዘርጋቱን ጠቅሶ ካሳው በርትዕ መወሰን እንደአለበት ከዘረዘረ በኃላ ይህ በሕጉ የተዘረጋው መፍትሔ ስለጉዳቱ ምን ያህል ኪሳራ እንደሚከፈል በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ ዳኞቹ የነገሮቹን ተራ ሁኔታዎችንና ተጎጂውም ያደረገውን ጥንቃቄ አመዛዝነው በመገመት የኪሳራውን ልክ እንደሚወስኑ የሚደንግግ መሆኑን፣ ከዚህ አንጻር ሲታይም ተጠሪ የአመልካችን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንገት ለመምታት ሲሰነዝሩ አመልካች ሲከላከሉ የአካል ጉዳቱ የደረሰባቸው መሆኑ በሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ የካሳውን መጠን የወሰነ መሆኑን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ምክንያት ጉዳዩ ወንጀል መሆኑንና የወንጀሉ ድርጊት ሲፈፀም አመልካች ሊያደርጉት የሚገባውን ምክንያታዊ ጥንቁቁና በተጠሪ የተሰነዘረው መሳሪያ በአንገታቸው ላይ ቢያርፍ ኖሮ ሊያስከትለው የሚችለውን የከፋ ውጤት ያላገናዘበ ሆኖ ይታያል፡፡ ሕጉ ተጎጂው ያደረገው ጥንቃቄ ማመዛዘን የጉዳት ካሳ መጠኑን በርትዕ ሲወሰን ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ የፈለገው የከፋውን ውጤት ለማስወገድ የሚደረገውን ጥንቃቄ ሳይሆን ጉዳቱን በማስከተል ረገድ በተጎጂ በኩል የተደረገውን ያልተገባ ድርጊትን መሆኑን ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ለሕይወታቸው አደገኛ የሆነውን የተጠሪን ድርጊት በእጃቸው ሲከላከሉ በእጃቸውና በጭንቅላቸው ጉዳት መድረሱ በማናቸውም መመዘኛ አመልካች ለጉዳቱ መድረስ ተገቢ ያልሆነ ጥንቃቄ አድርገዋል ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ይህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ምክንያት ከፍትሃ ብሔር ሕግ ቁጥር 2153 (ሀ) ድንጋጌ አንጻር ሲታይም ፍርድ ቤቱ የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያለአግባብ በመያዝ ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን የሚያሳይ እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2152 ድንጋጌ አኳያ ሲታይም ለይግባኝና ለሰበር መሰረት የሚሆን የሕግ ጉዳይ ሆኖ አግኝተናል፡፡ አንድ የአካል ጉዳት ካሳ መጠኑ በርትዕ እንዲወሰን የግድ የሚል ሆኖ ሲገኝም የጉዳት ካሳ መጠኑ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጠጣኝ እንዲሆን ተደርጎ ሊወሰነው አይችልም ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ጉዳት መድረሱ በተጨባጭ እስከተረጋገጠ ድረስ ለተጐጂው ከደረሰበት ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ሊከፈለው እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 ስር በመርህ ደረጃ ከመቀመጡም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 (ሀ) ድንጋጌ ስር ዳኞች ሊገምቱ የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያላግባብ በመያዝ ውሳኔ ከሰጡ ወይም ሊገምቱ የሚገባቸውን ትክክለኛውን መንገድ ትተው ያላግባብ የሆነውን ያገማመት መንገድ ይዘው የተገኙ እንደሆነ በካሳ መጠን ውሳኔው ላይ ይግባኝ የሚፈቀድ መሆኑን መደንገጉ የካሳ መጠን አወሳሰን በዘፈቀደ ሊበዛ ወይም ሊያንስ የማይገባ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡

አመልካች ላይ የደረሰው አካል ጉዳት ሙሉ ለሙሉ የመስራትን ችሎታቸውን ያሳጣ ነው ባይባልም በ40% የመስራት ችሎታቸውን የቀነሰ ስለመሆኑ በሕክምና

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተረጋግጧል፡፡ በእርግጥ ለዚህ ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ለመወሰን አስቸጋሪ ቢሆንም የካሳውን መጠን በትክክል ለመወሰን ያልተቻለ እንደሆነ የካሳው መጠን በርትእ ሊወሰን እንደሚችል የፍ/ሕ/ቁ. 2102/1/ ያመለክታል፡፡ የጉዳት ካሳ መጠን ሲወሰን መታየት ያለበት ተገኂው ከጉዳቱ በፊት ያገኘው ገቢ ሳይሆን በጉዳቱ ምክንያት ወደፊት በመስራት ችሎት ላይ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ መሆኑ ደግሞ የሚታወቅ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የጉዳት ካሳ መጠኑን በርትዕ ለመወሰን እግምት ውስጥ ሊወስዱ ሰለሚገባቸው ፍሬ ነገሮች የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2102 በዝርዝር አላመላከተም፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ደግሞ የቀረቡት ማስረጃዎችና ፍሬ ነገሮች በአግባቡ በማመዛዘን ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 ስር የካሳ መጠኑ ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት ተብሎ የተቀመጠው መርህ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ የካሳው ውሣኔ መሰጠት ያለበት መሆኑን ከውል ውጪ ሃላፊነትን በተመለከተ ከተቀመጡ አጠቃላይ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም መሰረታዊ ዓላማና መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

በዚሁ መርህ መነሻ አመልካች ላይ የደረሰውን የአካል ጉዳት አስመልክቶ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ስንመለከት ከአመልካች አካላቸው ውስጥ 40% ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ በሕክምና ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ጉዳቱ ሲደርስ የነበራቸው እድሜና ስራ ሰርተው ሲያገኙት የነበረው የገቢ መጠን ያልተረጋገጠ ቢሆንም አመልካች ወደፊት በተለያዩ አማራጮች የሥራ እድሎች ሊኖሯቸው እንደሚችል ነባራዊ ሐቅ አመላካች ከመሆኑም በላይ የወደፊት ኑሮአቸውን ለማሸነፍም ከፍተኛ ውድድር ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ይታመናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ባለሙሉ አካል የሆነ ሰውና ከሰውነት ክፍሎች ውስጥ አስፈላጊውን አካል በአደጋ ምክንያት ያጣ ሰው እኩል ተወዳዳሪ ናቸው ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ካሳ በርትዕ ሲወሰን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታዎችንና እነዚህ ነባራዊ ሁኔታዎች በአመልካች የወደፊት ህይወት ላይ ሊያስከትሉ ስለሚችሉት አሉታዊ ተእጽኖ ግምት ውስጥ ማስገባት የካሳ መጠን አወሳሰን ፍትሐዊ ያደርገዋል፣ ሕግ አውጪው ሊያሳካ ያሰበውን ግብም ለማሳካት ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

ስለሆነም አመልካች ለቋሚ የአካል ጉዳት መዳረጋቸው ለካሣ ገንዘብ መጠን አወሳሰን እግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባ ከመሆኑም በላይ ሌላው መሠረታዊ ጉዳይ ዛሬ ያለንበት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት እና ተጨባጭ የገንዘብ /ብር/ የመግዛት አቅም በየጊዜው እየቀነሰ መሄዱ ወደፊት ሊታጣ የሚችለው ገቢ ሲወሰን ግንዛቤ ውስጥ የማይገባበት ህጋዊ ምክንያትም የለም፡፡ ስለሆነም ካሳ በርትዕ ሲወሰን ከእነዚህ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተገናዝቦ መታየት ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡

ባአጠቃላይ አመልካች ላይ የደረሰው ጉዳት ቋሚ የአካል ጉዳት እንደመሆኑ እና የአካል ጉዳት በተፈጥሮ እንደ ንብረት በገበያ ዋጋ ሊተመን የማይችል በመሆኑ የካሣ ገንዘብ ሊሰላ የሚገባው ባጠቃላይ የመስራት አቅሙ ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን መነሻ በማድረግ እና ከላይ በዝርዝር የተመለከትናቸው የሕጉ መንፈስና ዓላማ ግብ ለማድረስ በሚያስችል አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡

ስለዚህም አመልካች ላይ የደረሰ ዘላቂ ጉዳት 40% /አርባ በመቶ/ የመስራት ኃይል ማጣታቸውን በዝርዝር ከተመለከቱት የሕጉ ሕሣቤዎች እና የተጎጂዋን ግለሁኔታ በአግባቡ ሳያመዛዝኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153(ሀ) ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ምክንያት በመያዝ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ) ብቻ ለአመልካች ለአካል ጉዳት እንዲከፈል የወሰነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2102 እና 2153(ሀ)) ድንጋጌዎችን በጣሰና ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ የተቀመጠውን ሕግ አጠቃላይ ዓላማ ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የተፈፀመው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡ ከላይ የተመለከቱትን ምክንያቶችን እግምት ውስጥ ስናስገባ በአመልካች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት በርትዕ ሊወሰን የሚገባው የካሳ መጠን ብር 200,000.00(ሁለት መቶ ሺህ ብር) ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሰሜን ሸዋ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፋ/መ/ቁ 0124895 ጥቅምት 17 ቀን 2010 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 030-9010 ታህሳስ 24 ቀን 2010 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት በርትዕ ሊወሰን የሚገባው የካሳ መጠን ብር 200,000.00(ሁለት መቶ ሺህ ብር) ነው በማለት ተጠሪ ይህንኑ ገንዘብ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህ ችሎት ውሳኔ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሀጋዊ ወለድ(9%) ጋር ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

ሠ/አ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 131804

መጋቢት 25 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡-ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- በሰሜን ወሎ ዞን የቆቦ ጊራና ሽለቆ ልማት ፕሮግራም-የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ አድነው አባተ-የቀረበ የለም፡፡

2 አቶ ወንድወሰን ተፈራ
3 አቶ ተስፋየ ጭቋላ } በሌሉበት የታየ ነው፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ ተጠሪዎች ያለአግባብ እንዲከፈል ያደረጉትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ተብሎ የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በሰሜን ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተጠቀሱ ተከሳሾች ናቸው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪዎችን ጨምሮ በ16 ተከሳሾች ላይ ክስ ያቀረበባቸው ሲሆን 25 ጣልቃ ገቦች ወደ ክርክሩ በመግባት ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች /የሥር ከሳሽ/ በቀን 23/12/2005 ዓ/ም ጽፎ ባቀረው ክስ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ፣ የአሁን 2ኛ ተጠሪ የመስኖ ልማት ዋና የሥራ ሂደት መሪ እና የአሁን 3ኛ ተጠሪ ደግሞ የግዢ፣ ፋይናንስ፣ ንብረት እና የሰው ኃይል አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሂደት መሪ ሆነው ሲሰሩ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከግር መመሪያና ደንብ ውጪ ለ6 ሞተር ሳይክሎች ግር ብር 158,850 እንዲከፈል በማድረጋቸው፣ ለባለሙያዎች ለሥልጠናና ለትምህርታዊ መስክ ጉብኝት ለአንድ ሠራተኛ በቀን የሚከፈለው ብር 70 ሆኖ እያለ በቀን ብር 200 የውሎ አበል ለ56 ቀን ብር 47,580 ያለአግባብ እንዲከፈል በማድረጋቸው፣ መልቀቂያ ተሰጥቶ የተሰናበተውን አንድ ሠራተኛ ያለ ምንም ማስታወቂያ በድጋሚ እንዲቀጠር በማድረግ ለሶስት ወር ብር 2,562 እንዲከፈል በማድረጋቸው፣ በ1994 ዓ/ም በወጣው የጽ/ቤቱ የሠራተኞች መተዳደሪያ ማኑዋል መሠረት ጊዜያዊ የቅጥር ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈለው የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ብቻ መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ ተከሳሾች /ተጠሪዎች/ ግን ለ17 የጽ/ቤቱ ሠራተኞች ከጊዜያዊ ወደ ቋሚ ቅጥር ተሸጋግረው የተሻለ ጥቅም አግኝተው እያለ ከሥራ እንደተሰናበቱ በመቁጥር ለአገልግሎት ካሳ ክፍያ በማለት በድምሩ ብር 17,588.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ ያለአግባብ እንዲከፈል በማድረጋቸው እንዲሁም ሌሎችንም የማይገቡ ክፍያዎችን እንዲከፈሉ በማድረግ ሥልጣናቸውን ያለአግባብ በመጠቀምና ተገቢ ያልሆነ አሠራር በመሥራት የመንግሥት ገንዘብ እንዲከፈል በማድረጋቸው በወንጀል ተከሰው መቀጣታቸውን ገልጾ በድምሩ ብር 368,335.97 /ሶስት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ አምስት ብር ከዘጠና ሰባት ሳንቲም/ በነጠላ እና በአንድነት እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪዎችም ለቀረበባቸው ክስ መልሳቸውን በጽሁፍ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ በመ/ቁ. 09881 በሆነው በቀን 8/02/2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአሁን ተጠሪዎችን ኃላፊ በማድረግ ብር 350,777.75 /ሶስት መቶ አምሳ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ሳባት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም/ እንዲከፍሉ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ለ17 ሠራተኞች የተከፈለውን ብር 17,588.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ በተመለከተ ሠራተኞቹ በክርክሩ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር በጠየቁት መሠረት ወደ ክርክሩ በመግባት አምነው የተከራከሩ በመሆናቸው ለአሁን 2ኛ እና ለ3ኛ ተጠሪዎች እንዲመልሱ ካለ በኃላ በዚህ ረገድ ከቀረበባቸው ክስ ተጠሪዎችን ከኃላፊነት ነፃ በማድረግ ወስኗል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁን አመልካች ጊዜያዊ የቅጥር ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈለው የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ብቻ ሆኖ እያለ አስራ ሰባቱ ሰራተኞች ከጊዜያዊ ቅጥር ወደ ቀሚ ተሸጋግረው የተሻለ የኢኮኖሚ ዋስትና አግኝተው እያለ የአገልግሎት ካሳ በሚል ብር 17,558.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ ያለአግባብ እንዲከፈል በማድረጋቸው ተጠሪዎች በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተደርገው ተቀጥተው እያለ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ሳይወስን በዝምታ ያለፈው ያለአግባብ ነው በማለት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ የይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤት የሥር ጣልቃ ገቦች ያመኑትን የሥራ ስንብት ክፍያ ለ2ኛ እና 3ኛ መልስ ሰጪዎች /ለአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች/ እንዲመልሱ ወስኖ መልስ ሰጪዎችን /ተጠሪዎችን/ ከኃላፊነት ነፃ ማድረጉ ስህተት ቢሆንም ቅሬታ የቀረበበትን ገንዘብ የሥር ጣልቃ ገቦች የወሰዱና የተጠቀሙበት መሆኑ በክርክር ሂደት የተረጋገጠ በመሆኑ ይግባኝ ባይ/አመልካች/ ሊጠይቅ የሚችለው ጥቅም ከመልስ ሰጪዎች /ከአሁን ተጠሪዎች/ ጋር የሚገኝ ባለመሆኑ በውጤት ደረጃ የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ አልተቀበልነውም በማለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 337 መሠረት ዘግቶበታል፡፡

አመልካች ውሳኔውንም ሆነ ትዕዛዙን ቅር በመሰኘት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው በቀረበው ጉዳይ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም በማለት አቤቱታውን ሰርዞበታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም፡- ተጠሪዎች ሥልጣናቸውን ያለአግባብ ተጠቅመው በፕሮጀክቱ ላይ ያደረሱትን ኪሳራ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ በቀረበው ክስ መሠረት በማስረጃ ተረጋግጦ እያለና በ1994 ዓ/ም በወጣው የፕሮጀክቱ ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 17 (5) መሠረት ጊዜያዊ የቅጥር ሠራተኞች የሥራ ስንብት ክፍያ መፈጸም ያለበት የሥራ ውል ሲቋረጥ ብቻ መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ ተጠሪዎች ግን በ23/03/1999 ዓ/ም በቃለ ጉባዔ የጽ/ቤቱ 17 ሠራተኞች ከጊዜያዊ ቅጥር ወደ ቋሚ ተሸጋግረውና የተሻለ የሥራ ዋስትና አግኝተው እያለ ከስራ እንደተሰናበቱ በመቁጥር የአገልግሎት ከሳ ክፍያ በማለት በድምሩ ብር 17,558.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቶ አምሳ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ እንድከፈል በማድረጋቸው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ 407 /2/ መሠረት በሰሜን ወሎ ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው ተረጋግጦ ቅጣት ተወስኖባቸዋል፡፡ ህግን በመተላለፍ በአመልካች ፕሮጀክት ላይ ያለአግባብ ገንዘብ እንድከፈል አዘው ላደረሱት ጉዳት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2035 በጥፋት ላይ የተመሠረተ ውል ሳይኖር ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑና ያለአግባብ የተከፈለ ብር ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 68613 በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈና መሠረታዊ የህግ ጥሰት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በመሠረቱት ክስ በ1994 ዓ/ም በወጣው የአመልካች ጽ/ቤት የሠራተኞች መተዳደሪያ ማኑዋል መሠረት ጊዜያዊ የቅጥር ሰራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈለው የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ብቻ መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ ለ17 የጽ/ቤቱ ሠራተኞች ከጊዜያዊ ወደ ቋሚ ቅጥር ተሸጋግረው የተሻለ ጥቅም አግኝተው እያለ ከሥራ እንደተሰናበቱ በመቁጥር የአገልግሎት ካሳ ክፍያ በማለት በድምሩ ብር 17,558.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ ያለአግባብ እንዲከፈል በማድረጋቸው በወንጀል ተከሰው ተቀጥተዋል፡፡ ይህን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉን በማለት አመልካች ባቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ላይ ሥር ፍርድ ቤት በፍርዱ ላይ ያለአግባብ የካሳ ክፍያ የወሰዱ ጣልቃ ገቦች ይህን አምነዋል፡፡ ያመኑትን ገንዘብ ለአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል በማለት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ የማለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው የአሁን 1ኛ ተጠሪ ቀርበው በቀን 26/05/2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ላቀረቡት መልስ የአመልካች ወኪል የሆነው የክልሉ ዐቃቤ ህግ በቀን 11/07/2009 ዓ/ም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ሰኔ 7 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት መልስ የመስጠት መብታቸው እንዲታለፍ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ተጠሪዎች ለ17 ሠራተኞች እንዲከፈላቸው ያደረጉትን ብር 17,558.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ እንዲመልሱ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ገንዘብ ለአስራ ሰባቱ ሠራተኞች እንዲከፈል ማድረጋቸው መመሪያው የጊዜያዊ ሠራተኛ የቅጥር ውል ሲሰረዝ ተገቢውን ጥቅማ ጥቅም ሠራተኛው ያገኛል ስለሚል በመመሪያው መሠረት የተፈጸመ ነው በማለት የአሁን ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው በ1994 ዓ/ም የወጣው የፕሮጀክቱ ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 17 (5) መሠረት ጊዜያዊ የቅጥር ሠራተኞች የሥራ ስንብት ክፍያ መፈጸም ያለበት የሥራ ውል ሲቋረጥ ብቻ መሆኑ በግልጽ ተደንግጎ እያለ ተጠሪዎች ግን በ23/03/1999 ዓ/ም በቃለ ጉባዔ የጽ/ቤቱ 17 ሠራተኞች ከጊዜያዊ ቅጥር ወደ ቋሚ ተሸጋግረውና የተሻለ የሥራ ዋስትና አግኝተው እያለ ከስራ እንደተሰናበቱ በመቁጥር የአገልግሎት ክሳ ክፍያ እንዲከፈል ማድረጋቸው ህግን የጣሰ ተግባር ስለሆነ ለሠራተኞቹ ያለአግባብ እንዲከፈላቸው ያደረጉትን ገንዘብ ሊመልሱ ይገባል በማለት ነው፡፡

ይህ የተጠቀሰው መመሪያ ቁጥር 17/5/ ለጊዜያዊ ሠራተኞች የሥራ ስንብት እንዲከፈል የሚፈቅደው ከሥራቸው የተሰናበቱ እንደሆነ ነው፡፡ የዚህ መመሪያ ቁጥር 17/5/ ዓላማም ሠራተኞቹ ከሥራ ከተሰናበቱ በኃላ የሚገጥማቸውን የኢኮኖሚ ችግር ለማቃለል ታስቦ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ ሠራተኞቹ ግን በአመልካች ድርጅት ውስጥ በጊዜያዊነት ይሠሩ ከነበረበት በቋሚነት ተቀጥረው እንዲሰሩ ሲደረግ የሥራ ስንብት እንዲከፈላቸው ማድረግ የመመሪያውን ዓላማና መንፈስ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ተጠሪዎቹ በዚህ እና በሌሎችም በፈጸሙዋቸው ድርጊት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተደርጎው ቅጣት ተወስኖባቸዋል፡፡ ይህ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ለፍትሐብሔር ክርክር ደግሞ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ ይህም ማስረጃ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 68613 ላይ ከሰጠው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ሲታይ የሚገባው ነው። የሥር ፍርድ ቤቶችም የተያዘውን ጉዳይ ከዚህ አንጻር ያለመመልከታቸው ሲታይ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም።

በመጨረሻም የሥር ፍርድ ቤቶች የሥር ጣልቃ ገቦች የሆኑት አስራ ሰባቱ ሰራተኞች ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ገንዘቡ መወሰዳቸውን ባመኑት መሠረት ለአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲመልሱ ሲል የሰጠው ውሳኔ ግልጽ ባይሆንም ተጠሪዎች የአመልካች ድርጅት ገንዘብ ከህግ አግባብ ውጪ እንዲከፈል በማድረጋቸው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2035 መሠረት ተጠያቂነት አለባቸው። ስለሆነም ተጠሪዎች ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ቀጥሎ ያለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.09881 በቀን 08/02/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 01-03596 በ10/06/2008 ዓ/ም እንዲሁም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 03-14560 ሐምሌ 6 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽሯል።
2. ለአስራ ሰባቱ ሰራተኞች ያለአግባብ የተከፈለውን ብር 17,558.02 /አስራ ሰባት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ስምንት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም/ የአሁን ተጠሪዎች በነጠላና በአንድነት ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ ተወስኗል።
3. ተጠሪዎች ለአመልካች የከፈሉትን ገንዘብ ከአስራ ሰባቱ ሠራተኞች ላይ የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሳኔ አይከለክልም ብለናል።
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው።

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 142630

ሚያዝያ 11 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡-

1. ሳጅን ግርማ መርጋ
2. ሳጅን ደጀኔ ገሬ
3. ሳጅን ቱፋ ቁፋ

የፌዴራል ፓሊስ ነ/ፊ መብራቱ በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ደሀቦ መሐመድ-ተወካይ አብዲ ዑመር በV.C. ከሐረር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በ1ኛ አመልካች ከሳሽነት የተነሳ የጉዳት ካሳ ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካቾቹ በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48204 በ20/07/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 244291 በ26/01/2009 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡የአሁኖቹ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የአሁኗ ተጠሪ ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሳቢያ በተጨማሪ ተከሳሽነት ወደ ክርክሩ የገቡ ናቸው፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

1ኛ አመልካች በተጠሪዋ ላይ ክስ ያቀረቡት ንብረትነቱ የተጠሪዋ የሆነ የሰሌዳ ቁጥር 3-32111 ኦሮ የሆነ ተሽከርካሪ በ08/10/2006 ዓ.ም.ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት ላይ ኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ ተገኝቶ ሾፌሩ እንዲቆም ሲጠየቅ ፈቃደኛ ባለመሆን በፍጥነት አልፎ ሲጓዝ የኋላ ጎማ ወልቆበት የ1ኛ አመልካችን አግር ከግራ ጉልበት መገጣጠሚያቸው ላይ መትቶ የ10% ቋሚ የአካል ጉዳት ያደረሰባቸው መሆኑን ገልጸው ለህክምና፣ለምግብ እና ለመጠጥ የወጣ ወጪ ብር 20,000፣ለቀሪ 32 ዓመታት የወር ደመወዛቸው ብር 2,019 በ10% ታስቦ ለተቋረጠባቸው ገቢ ብር 77,529.60 እንዲሁም የሞራል ካሳ ብር 1,000 እና ወጪ ብር 1,000 በድምሩ ብር 99,529.60 /ዘጠና ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከስድሳ ሳንቲም/ ተጠሪዋ እንዲከፍሏቸው በመጠየቅ ሲሆን ተጠሪዋ በበኩላቸው በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጡት መልስ ጉዳቱ የደረሰው በራሳቸው በ1ኛ አመልካች ጥፋት መሆኑን፣መከሰስ የሚገባቸው ሾፌሩ እና አመልካቹን ቀጥሮ የሚያሰራው የመንግስት አካል እንጂ ተጠሪዋ አለመሆናቸውን፣ አመልካቹ ከጉዳቱ በኃላም በስራቸው ላይ ሆነው ደመወዛቸውን እያገኙ በመሆኑ የተቋረጠባቸው ገቢ አለመኖሩን፣ተጠሪ ኃላፊነት አለባቸው ቢባል እንኳ በሽምግልና ድርድር ለ1ኛ አመልካች ብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ/ የከፈሉ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ከመከራከራቸውም በላይ በ1ኛ አመልካች ድርጊት ምክንያት ተሽከርካሪያቸው ተገልብጦ ጉዳት በመድረሱ ተሽከርካሪውን ወደ ነበረበት ለመመለስ ያወጡትን ወጪ ብር 40,000 /አርባ ሺህ/ 1ኛ አመልካች እንዲከፍላቸው እና ተጠሪዋ በገቢዎች እና ጉምሩክ አስተዳደራዊ መመሪያ መሰረት ተገቢውን መቀጫ ከፍለው ተሽከርካሪው እንዲለቀቅ ደብዳቤ ከተጻፈ በኃላ አመልካቾቹ ተሽከርካሪውን ይዘው ለ11 ቀናት በስልጣናቸው በማቆማቸው የ11 ቀናት የተቋረጠ ጥቅም በቀን ብር 6,000 ሂሳብ ብር 66,000 /ስድሳ ስድስት ሺህ/ እንዲከፍሏቸው እንዲወሰን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል።

ፍርድ ቤቱም በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ላይ የአመልካቾቹን መልስ ተቀብሎ ክሱን እና የሁለቱንም ወገኖች ምስክሮች ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በ1ኛ አመልካች ላይ ጉዳት ሊደርስ የቻለው ተሽከርካሪው እየተነዳ እያለ 1ኛ አመልካች ተሽከርካሪውን ለማስቆም በማሰብ ወደ ተሽከርካሪው የወረወሩት ጎማ ተፈናጥሮ እግራቸውን በመምታቱ ምክንያት እንደሆነ መረጋገጡን፣ሾፌሩም ተሽከርካሪውን በጎማው ላይ መንዳት በመቀጠላቸው ተሽከርካሪው ተገልብጦ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተሸርካሪውም ላይ ጉዳት መድረሱ መረጋገጡን፣ተጠሪ በአስተዳደራዊ ውሳኔ የገንዘብ መቀጮ ከፍለው ተሸከርካሪው እንዲለቀቅ በደብዳቤ ከታዘዘ በኃላ አመልካቾቹ ለ11 ቀናት ማስቆማቸው መረጋገጡን፣በ11 ቀናት ውስጥ የተቋረጠው ገቢ ተጠሪ እንደሚሉት ብር 66,000 ሳይሆን ብር 13,200 /አስራ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ/ እንደሆነ መረጋገጡን፣በዚህ ሁኔታ በሁለቱም ወገኖች ላይ ለደረሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2098 ድንጋጌ መሰረት ሁለቱም ወገኖች ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን፣ተጠሪዋ ቀደም ሲል ብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ/ ለ1ኛ አመልካች መክፈላቸው በመረጋገጡ ለህክምና፣ለምግብ እና ለመጠጥ የወጣ ወጪ ብር 20,000 /ሃያ ሺህ/ እንዲከፈላቸው 1ኛ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ለቀሪ 32 ዓመታት የወር ደመወዛቸው ብር 2,019 በ10% ታስቦ የሚገኘው ጉዳት ካሳ ብር 77,529.60 /ሰባ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከስድሳ ሳንቲም/ ተጠሪዋ ለ1ኛ አመልካች መክፈል የሚገባቸው መሆኑን፣በሌላ በኩል በተጠሪዋ ተሸከርካሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት 1ኛ አመልካች ብር 40,000 /አርባ ሺህ/ ለተጠሪዋ መክፈል የሚገባቸው መሆኑን በዝርዝር ገልጾ ይህንኑ ገንዘብ በማቀናነስ እና ለተቋረጠው ጥቅም ደግሞ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችን ኃላፊ በማድረግ ተጠሪዋ ብር 37,529.60 /ሰላሳ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከስድሳ ሳንቲም/ ለ1ኛ አመልካች እንዲከፍሉ እና 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ደግሞ ለተጠሪዋ የተቋረጠ ጥቅም ብር 13,200 /አስራ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ/ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በአመልካቾቹ አቅራቢነት ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2098 ድንጋጌን ጠቅሶ ሁለቱም ወገኖች ኃላፊነት አለባቸው እስካለ ድረስ በተጠሪዋ ተሸከርካሪ ላይ የደረሰውን ጉዳት አጋማሽ ማለትም ብር 20,000 /ሃያ ሺህ/ ተጠሪዋ እንዲሸከሙ መወሰን ሲገባው ሙሉውን ብር 40,000 /አርባ ሺህ/ 1ኛ አመልካች እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን ገልጾ ውሳኔውን በዚህ አግባብ ብቻ በማሻሻል ተጠሪዋ ለ1ኛ አመልካች ሊከፍሉ የሚገባው ብር 59,529.60 /ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ከድሳ ሳንቲም/ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡አመልካቾቹ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ 1ኛ አመልካች ኃላፊነታቸውን እየተወጡ በነበረበት ሁኔታ፣ለደረሰባቸው የአካል ጉዳትም ካሳ በተወሰነላቸው ሁኔታ እንዲሁም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዋ ተሸከርካሪውን ያስለቀቁት አስተዳደራዊ ቅጣት ከፍለው መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በተሸከርካሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት 1ኛ አመልካች ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቾቹ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ሲሆኑ በሰበር አቤቱታቸው ላይ አጥብቀው የሚከራከሩትም መደበኛ ስራችንን በማከናወን ላይ እያለን ተሸከርካሪው በሾፌሩ ጥፋት ተገልብጦ ለደረሰበት ጉዳት ኃላፊነት ሊኖርብን አይገባም በማለት መሆኑን የሰበር አቤቱታቸው ይዘት ያመለክታል፡፡በመሰረቱ አንድ ሰው በራሱ በኩል ምንም የገባው ግዴታ ባይኖርም በራሱ ጥፋት በሌላው ሰው ላይ ጉዳትን ካደረሰ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ እና ማንም ሰው ከራሱ ጥፋት የተነሳ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ላደረገው ጉዳት ኪሳራ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2027 (1) እና 2028 ስር ተመልክቶል፡፡ አመልካቾቹ በፌዴራል ፖሊስ አባልነታቸው አግባብነት ባለው ሕግ እና ደንብ መሰረት ተሸከርካሪዎችን የማስቆም እና የመፈተሽ ስልጣን እና ኃፊነት ያላቸው ቢሆንም ይህንን ኃላፊነት በሚወጡበት ጊዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2031 (1) ስር እንደተመለከተው የሙያ ስራው የሚመራበትን ደንብ ማክበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ አመልካች ተሸከርካሪውን ለማስቆም የሞከሩበት ቦታ የፍተሻ ጣቢያ አለመሆኑ እና ጊዜውም ከሌሊቱ 10:00 ሰዓት መሆኑ ተረጋግጦአል፡፡ተሸከርካሪውን የፍተሻ ጣቢያ ባልሆነ ቦታ አስቁሞ መፈተሹ አስፈላጊ እና ተገቢ ነበር ቢባል እንኳ ማስቆም የነበረባቸው በተሰጣቸው ሙያዊ ስልጠና መሰረት ተገቢውን መንገድ እና ስርዓት በመጠቀም ነው፡፡ይሁን እንጂ 1ኛ አመልካች ተሸከርካረውን ለማስቆም የሞከሩት ከፊት ለፊቱ ጎማ በመወርመወር መሆኑ እና ተሸከርካሪው ሊገለበጥ የቻለውም ሾፌሩ በተወረወረበት ጎማ ላይ በመንዳቱ መሆኑ ተረጋግጦአል፡፡1ኛ አመልካች መደበኛ ስራዬን በማከናወን ላይ እያለሁ ተሸከርካሪው በሾፌሩ ጥፋት ተገልብጦ ለደረሰበት ጉዳት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኃላፊነት ሊኖርብኝ አይገባም ከማለት በቀር ተሸከርካሪውን ለማስቆም የተጠቀሙበት ዘዴ አግባብነት ባለው ሕግ እና ደንብ መሰረት በሙያው የተፈቀደ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡በሰበር አቤቱታቸውም ቢሆን በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ይልቁንም በከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት ወደ ተሸከርካሪው ጎማ መወርወራቸውን ሳይገልጹ ነገር ግን ጉዳቱ የደረሰባቸው ሾፌሩ እንዲቆም ሲጠየቅ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ ተሸርካሪውን በፍጥነት ሲነዳ የኃላ ጎማ ወልቆበት መሆኑን በክሳቸው ላይ በማስፈር መሆኑን የከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ ያመለክታል፡፡1ኛ አመልካች ተሸከርካሪውን ለማስቆም የሞከሩት ከፊት ለፊቱ ጎማ በመወርመወር መሆኑ እና ተሸከርካሪው ሊገለበጥ የቻለውም በዚሁ ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠው ተጠሪዋ ባቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሰረት 1ኛ አመልካች ለተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ በከፊል ኃላፊ መደረጋቸው የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48204 በ20/07/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 244291 በ26/01/2009 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ወሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንግድ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 143227

ቀን - 21/09/2010

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- ደርሂም ኢንዱስትሪስ ካምፓኒ ሊሚትድ-ጠበቃ አብደላ አሊ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አሁጃን ኢንዱስትሪስ -ጠበቃ ያሬድ ለገሰ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንግድ ምልክት ፈራሽ ሊሆን ስለሚችልበት ሁኔታን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በኢፌዲሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለጽ/ቤቱ ያቀረበዉ አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ፡- ለፍራፍሬ መጠጦችና ጭማቂዎች ወዘተ የሚያገለግለዉና በስሙ ተመዝግቦ የሚታወቀዉን RANI የሚባለዉን የንግድ ምልክት በንግድ ምልክት እና ምዝገባ ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 36 ስር የተመለከቱትን የምዝገባ መስፈርት ከመሠረቱም ባልተሟላበት ሁኔታ በተከሳሽ ስም መመዝገቡ ተገቢ ባለመሆኑ ፈራሽ ሊሆን ይገባል ሲል ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነዉ፡፡ አመልካች በበኩሉ የመጀመሪያ መቃወሚያዎች ናቸዉ የሚላቸዉን ክርክሮች በማስቀደም፣ ከፍሬ ነገር ጋር በተያያዘም የንግድ ምልክቱ በከሳሽ ስም ተመዝግቦ የነበረ ቢሆንም በወቅቱ ባለማደሱ ምክንያት መብቱና ማጣቱን፤ በተከሳሽ ስም ሊመዘገብ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቻለዉም በአዋጅ ቁጥር 501/1998 ተፈቅዶለት መሆኑን ጠቅሶ ሊሰረዝ አይገባዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ጽ/ቤትም በዚህ መልኩ ከግራ ቀኝ የቀረበዉን ክርክር መሠረት የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመርመር እንዲሁም አስፈላጊዉን የማጣሪያ ጥናት ማድረጉን ጠቅሶ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 7(2) እና 36 መሠረት ለአመልካች ለመጀመሪያ ጊዜ የተመዘገበዉ RANI የንግድ ምልክት ምዝገባ መጀመሪያዉንም ቢሆን በሦስተኛ ወገን የቅድሚያ መብት ምክንያት ሊመዘገብ የማይገባ ስለመሆኑ ፈራሽ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የጽ/ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ሲሆን፣ አመልካች በቀን 08/10/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃዉ አማካይነት በቀረበ 4 ገጽ የሰበር አቤቱታ በአዋጁ መሠረት በስሙ ተመዝግቦ የሚገኘዉ RANI የንግድ ምልክት እንዲሰረዝ በሚል በጽ/ቤቱ ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ነዉ፡፡ እኛም በአመልካች ስም የተመዘገበዉ የንግድ ምልክት እንዲሰረዝ በሚል የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ከግራ ቀኝ ክርክር እንዲሁም ስለጉዳዩ ከሚደነግጉ ህጎች አንፃር መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ ራኒ (RANY) የንግድ ምልክት በአመልካች ስም በ22/01/99 ዓ.ም ከመመዝገቡ በፊት በተጠሪ ስም ከ16/11/80 ዓ.ም እስከ 16/10/86 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ አእምሯዊ ጽ/ቤት ተመዝግቦ የነበረ ስለመሆኑ አመልካች አይክድም፡፡ አመልካች ይህን ሳይክድ የንግድ ምልክቱ በተጠሪ ጥያቄ ምክንያት ሊፈርስ አይገባዉም በማለት አጥብቆ ከሚከራከርባቸዉ ነጥቦች ዉስጥ አንዱ የንግድ ምልክቱ በተጠሪ ስም ቢመዘገብም በወቅቱ ባለመታደሱ ተጠሪ መብቱን አጥቷል በማለት ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩሉ ምዝገባዉ ከመሠረቱም ስለ 3ኛ ወገኖች የቅድሚያ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብት በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 7(2) ስር የተመለከተዉን ድንጋጌ የማያሟላ መሆኑን በመግለጽ እንዲፈርስ መወሰኑ በአግባቡ ነዉ በማለት ይከራከራል፡፡

በመሠረቱ የኢፌዲሪ አእምሯዊ ጽ/ቤት አንድን የንግድ ምልክት ከመመዝገቡ በፊት ማጣራት የሚገባቸዉን ሁኔታዎች አዋጁ በአንቀጽ 6 እና 7 ስር የሚደነግግ ሲሆን፣ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ከመሠረቱ ሳያሟላ የተደረገ ምዝገባ ፈራሽ ሊደረግ እንደሚገባዉም የአዋጁ አንቀጽ 36(1) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ የአዋጁ ድንጋጌ በአንቀጽ 7(2) ስር የተመለከተዉ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የንግድ ምልክቱ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ የሌላ ዕቃዎችን አገልግሎቶችን በሚመለከት በሚገባ በሚታወቅ ወይም ኢትዮጵያ ዉስጥ ግልጋሎት ላይ ከዋለ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ወይም ትርጉሙን ከያዘ መመዝገብ የለበትም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በተጠሪ ስም የሚታወቅ ራኒ (RANY) የንግድ ምልክት ምርት ወደ አገር ዉስጥ መግባት ከጀመረ ረጅም ጊዜ እንዳስቆጠረና ምርቶቹም የአመልካች እንደሆኑ ጽ/ቤቱ በአዲስ አበባ የተለያዩ የገበያ ማዕከላት እንዲሁም ድሬዳዋን ጨምሮ በሌሎችም ከተሞች ባደረገዉ ጥናት ያረጋገጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይህም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የንግድ ምልክት በተጠሪ የሚታወቅ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም ራኒ (RANY) የሚባል የንግድ ምልክት ከመሠረቱም በአመልካች ስም የተመዘገበዉ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 7(2) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ሳያሟላ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 36(1) መሠረት በተጠሪ ጥያቄ መሠረት እንዲፈርስ መደረጉ በአግባቡ ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በኢፌዲሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጸንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል የተመለከቱትን የአዋጁን ድንጋጌዎች የተከተለ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/174339 በቀን 14/07/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ በኢፌዲሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት፣ የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰመ/ቁ. 153890

መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-ወ/ሮ እመቤት ዳኛቸው - ጠበቃ ተፈራ ኢሬንሳ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ይስማው ዘገየ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ ሙሉነሽ ዳኛቸው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በተጠሪዎቹ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ክርክር ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ የነበሩት የአሁኗ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 183086 በ13/10/2009 ዓ.ም.የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ በአንጻሩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43050 በ04/02/2009 ዓ.ም.የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 145578 በ12/04/2010 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት ነው፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጠሪዎቹ መካከል የነበረው ጋብቻ በ07/07/2007 ዓ.ም. በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በወረዳ 4 ክልል ከቅዱስ ሚካኤል መረዳጃ ዕድር በኪራይ በተገኘው ቤት ውስጥ በሚገኙት የመጠጥ ግሮሰሪ ዕቃዎች እና ገቢ የክፍፍል ጉዳይ ላይ ተጠሪዎቹ በክርክር ሂደት ላይ እያሉ የአሁኗ አመልካች የንግድ ፈቃዱን በስማቸው አውጥተው ስራውን እያከናወኑ የሚገኙበትን ግሮሰሪ ተጠሪዎቹ እንደራሳቸው ንብረት በመቁጠር የራሳቸው ባልሆነ ንብረት ላይ የክፍፍል ጥያቄ ማቅረባቸው ተገቢ አለመሆኑን ገልጸው በግሮሰሪው ላይ የቀረበው የክፍፍል ጥያቄ ውድቅ ይደረግልኝ ሲሉ በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ተከራክረዋል።የአመልካቿ እህት የሆኑት 2ኛ ተጠሪ የጣልቃ ገቧን አቤቱታ ደግፈው የተከራከሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ተጠሪዎቹ ጣልቃ ገቧን ለመርዳት አምጥተው አብረዋቸው ስላደጉ እንደልጃቸው በመቁጠር የንግድ ፈቃዱን በስማቸው ከማውጣታቸው ውጪ ጣልቃ ገቧ ግሮሰሪውን ለመቋቋም የሚያስችል የፋይናንስ አቅም የሌላቸው መሆኑን፣የግሮሰሪ ዕቃዎቹ የራሳቸው ስለመሆኑም ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን ገልጸው የጣልቃ ገብነት አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ የተከራከሩ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል።

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የተጠሪዎቹን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ጣልቃ ገቧ ከተጠሪዎቹ ጋር እንደልጅ ሆነው በጥገኝነት ይኖሩ የነበረ ስለመሆኑ እና ግሮሰሪውን ያቋቋሙት፣ስራውንም ይሰሩ የነበሩት ተጠሪዎቹ ስለመሆናቸው በ1ኛ ተጠሪ ምስክሮች የተገለጸ መሆኑን፣የግሮሰሪው መገልገያ ቁሳቁሶች ከፊሎቹ በ1ኛ ተጠሪ ስም፣ደግሞ በ2ኛ ተጠሪ ስም የተገዙ መሆኑን የሚያመለክቱ ደረሰኞች በ1ኛ ተጠሪ በኩል በማስረጃነት የቀረቡ መሆኑን፣ጣልቃ ገቧ የግሮሰሪ ድርጅቱን ያቋቋሙት ከቤተሰብ በተሰጣቸው ገንዘብ ስለመሆኑ ገልጸው የመሰከሩት የ2ኛ ተጠሪ ምስክር የ2ኛ ተጠሪ ወንድም ከመሆናቸውም በላይ ብቸኛ ምስክርም በመሆናቸው ገለልተኛ ናቸው ለማለት የማይቻል መሆኑን፣የንግድ ፈቃዱ እና የግብር ደረሰኞቹ በጣልቃ ገቧ ስም መሆኑ ብቻ ግሮሰሪውን በራሳቸው ስም አደራጅተዋል የሚያሰኝ አለመሆኑን ገልጾ የጣልቃ ገቧን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶአል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህንን ውሳኔ በመቃወም ጣልቃ ገቧ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የግሮሰሪው ቁሳቁሶች የተሟሉት ለጣልቃ ገቧ ከቤተሰብ አንድ ጊዜ ብር ሃያ ሺህ፣ሌላ ጊዜ ደግሞ ብር አስራ አምስት ሺህ በተላከ ገንዘብ ስለመሆኑ በጣልቃ ገቧ አንድ ምስክር የተገለጸ መሆኑን፣የዚህን ምስክር ቃል የሚያስተባብል በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር እና በ1ኛ ተጠሪ በኩል የተሰሙት ምስክሮች አንዳቸውም 1ኛ ተጠሪ የግሮሰሪ ዕቃዎቹን ገዝተዋል ወይም ሰጥተዋል የሚል ምስክርነት ባልሰጡበት ሁኔታ የጣልቃ ገብነት ጥያቄው ውድቅ የተደረገው አለአግባብ መሆኑን ገልጾ በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር በንግድ መደብር ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎች የንግድ በመደብሩ አካል ተደርገው የሚቆጠሩ ስለመሆኑ በንግድ ሕጉ በአንቀጽ 128 የተመለከተ መሆኑ ገልጾ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በወረዳ 4 ክልል ከቅዱስ ሚካኤል ዕድር በመከራየት አመልካች የግሮሰሪ ንግድ የሚያከናውኑበት የንግድ መደብር ዕቃዎች የአመልካች ንብረት ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት 1ኛ ተጠሪ በተራቸው ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ 2ኛ ተጠሪ በክርክሩ መጀመሪያ ላይ ግረሰሪው የጋራ ንብረት መሆኑን ገልጸው ሲከራከሩ ከቆዩ በኃላ የአመልካቿ ነው በማለት መከራከር የጀመሩት የጣልቃ ገብነት ጥያቄው ከቀረበ በኃላ መሆኑን በማከል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተገለጹትን ፍሬ ነገሮች መሰረት አድርጎ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር በአንጸሩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቶአል።

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ክርክር የተነሳበት ግሮሰሪ የንግድ ፈቃድም ሆነ ግብሩ እንዲሁም የቤት ኪራይ ውሉ ጭምር በአመልካች ስም መሆኑ ባልተካደበት ሁኔታ የተደራጀው በተጠሪዎቹ ነው በሚል ብቻ ንብረቱ የተጠሪዎቹ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ግሮሰሪ የተቋቋመበትን የንግድ ቤት ኪራይ ውል አከራዩ የተዋዋለው ከአመልካቿ ጋር መሆኑ፣የንግድ ፈቃዱ ከጅምሩ የተሰጠው እና ግብሩም የሚከፈለው በአመልካቿ ስም መሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡በንግድ ሕጉ በቁጥር 127 (2) (ሀ) እና (ለ) ስር የተጠቀሰው የንግድ ቤቱ ስም እና የሚነገድበት የተለየ የንግድ ማስታወቂያ ሰሌዳም የሚታወቀው በአመልካቿ ስም ስለመሆኑ በሰበር አቤቱታው የቀረበው የክርክር ነጥብ በ1ኛ ተጠሪ አልተካደም፡፡አግባብነት ባለው ሕግ እና ደንብ መሰረት የንግድ ፈቃድ የሚሰጠውም ፈቃድ ጠያቂው ለንግድ ስራው የሚያስፈልገውን ካፒታል ጨምሮ ተገቢ መስፈርቶችን መሟላቱ ከተረጋገጠ በኃላ እንደሆነ የሚታመን ነው፡፡እነዚህ ሁኔታዎችም አመልካቿ የግሮሰሪ ድርጅቱን እራሳቸውን ችለው ያቋቋቀሙ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችሉ ናቸው፡፡የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔ ላይ እንደገለጸው በንግድ መደብር ውስጥ ግዙፍነት ያለው እንደ መሳሪያዎች፣የቤት ዕቃዎችና ሸቀጥ እንደሚገኙበት በንግድ ሕጉ በቁጥር 128 ተመልክቶአል፡፡እነዚህ የግሮሰሪው መገልገያ ዕቃዎች በሕጉ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ተብለው የሚታወቁ ናቸው፡፡

የዚህ ዓይነቶቹ ንብረቶች ባለሀብትነትም ንብረቱን በመግዛት ወይም በሌላ አኳኃን ያገኘው ወይም በኑዛዜ የተሰጠው ሰው ንብረቱን በእጁ ባደረገው ጊዜ የተላለፈለት እንደሚሆን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1186 (1) ስር ተመልክቶአል፡፡አመልካቿ እነዚህን ንብረቶች በስማቸው በሚታወቀው የግሮሰሪ የንግድ መደብር ውስጥ ይዘው መገኘታቸው ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ የእነዚሁ ንብረቶች ባለሀብት ስለመሆናቸው በሕጉ ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡2ኛ ተጠሪ ከስር ጀምሮ የአመልካቿን አቋም ደግፈው የሚከራከሩ መሆኑን የመዝቡ ግልባጭም ሆነ የሰበር ክርክራቸው ያመለክታል፡፡አመልካቿ የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ከማቅረባቸው አቀድሞ 2ኛ አመልካች ግሮሰሪው የጋብቻ ውጤት መሆኑን አምነው የክፍፍል ጥያቄ አቅርበው ነበር መባሉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብቻውን የክርክር አቋማቸውን የቀየሩት እህታቸው የሆኑትን አመልካች አለአግባብ ለመጥቀም በማሰብ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም፡፡

ከስር ጀምሮ አመልካቿን በመቃወም በመከራከር ላይ የሚገኙት 1ኛ ተጠሪ በተመሳሳይ ስያሜ የሚታወቁ ዕቃዎች የተገዙባቸውን ደረሰኞች በማስረጃነት ከማቅረብ በቀር ዕቃዎቹን በራሳቸው ገንዘብ ገዝተው ወደ ግሮሰሪው ያስገቡት እራሳቸው ስለመሆናቸው ያስረዱ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡በዚህ አግባብ ካላስረዱ ደግሞ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደገለጸው የዕቃዎቹ ባለሀብት አመልካች ስለመሆናቸው በሕጉ የሚወሰደውን ግምት አስተባብለዋል ሊባል አይችልም፡፡በ1ኛ ተጠሪ ምስክሮች በተነገረው መሰረት በግሮሰሪው ውስጥ ይሰሩ የነበሩት ተጠሪዎች መሆናቸው ብቻውን ግሮሰሪው የእነርሱ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም፡፡የንግድ ቤቱ ኪራይ፣የንግድ ፈቃዱ እና ሌሎችም ባለሀብትነትን የሚያመለክቱ መሰረታዊ ጉዳዮች በአመልካቿ ስም እንዲሆን ያደረግነው ባለን ቤተሰባዊ ግንኙነት ነው ከማለት በቀር እንደክርክራቸው ግሮሰሪው የተቋቋመበት የገንዘብ ምንጭ ሙሉ በሙሉ የእነርሱ ከሆነ ግሮሰሪው ከተጋቢዎቹ በአንዳቸው ስም እንዲቋቋም ለማድረግ ያልቻሉበት አሳማኝ እና ሕጋዊ እና ምክንያት ስለመኖሩ 1ኛ ተጠሪ ከስር ጀምሮ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡በመሆኑም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተደረሰበት እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይት ያገኘው ድምዳሜ በክርክሩ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች እና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የግሮሰሪ መደብር በተመለከተ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 183086 በ13/10/2009 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ በአንጻሩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43050 በ04/02/2009 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 145578 በ12/04/2010 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 183086 በ13/10/2009 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ፀንቶአል።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ።
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል።

ቅ/ሀ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።**

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 158539

ሕዳር 27 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡-1. አልማው ወሌ
2. ሙስጠፋ አህመድ
3. አብርሃ መሰለ
4. ፈይሳ ወርቁ
5. ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ-ነ/ፈጅ ኪዳኔ መካሻ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-1. አቶ ምንዳይ ክፍሌ
2. አቶ ጌታቸው መኮንን
3. አቶ ዳንኤል አየለ

} በሌሉበት የሚታይ ነው፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባንክ አደራ የተቀመጠ ገንዘብን ለማስመለስ የቀረበን ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በባንኩ የሕግ ባለሞያነት፣ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ የህግ ካውንስሊግ የባንክ ክለርክ/ረዳት/ ሁነው ሲያገለግሉ እንደነበር፣ ተጠሪዎች በስራቸው አጋጣሚ ያገኙትን መረጃ በመጠቀም አቶ ሃይሉ መኮንን ከተባሉ የባንኩ ኢ.ሲ.ኤ ቅርንጫፍ ደንበኛ ሂሳብ ውስጥ ብር 258,764.11 ብር ወጪ በማድረግ ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸውን፣ በዚህ ጉዳይም የወንጀል ክስ ቀርቦባቸው ቅጣት የተጣለባቸው መሆኑን ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥም 1ኛ ተጠሪ ብር 86,248.70 እንዲሁም መግዛ ክፍሌ የተባሉ ግብረአበር ብር 20,000.00 ገቢ አድርገው ብር 152,497.41(አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ሰባት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም) የቀረ መሆኑን በመጥቀስ ይህንኑ ገንዘብ ከመጋቢት 12 ቀን 1999 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ ጥሪ ቢደረግላቸውም ባለመቅባቸው ክርክሩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ሁነው በመገኘታቸው ተገቢው የወንጀል ቅጣት የተወሰነባቸው መሆኑን በመ/ቁጥር 90239 የተሰጠ ውሳኔ የሚያረጋግጥ መሆኑን፣ በወንጀል ጥፋተኛ መባልን የሚያሳይ ማስረጃም በተመሳሳይ ጉዳይ የፍትሃ ብሔር ክስ ሲቀርብ ለጉዳዩ አግባብነትና ብቃት ያለው ማስረጃ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ ግልባጭ ንባብና በዚህ ረገድ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37184 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለመረዳት የሚቻል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ ተጠሪዎች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ከአመልካች ደንበኛ ሂሳብ ላይ ያላግባብ ተቀናሽ በማድረግ ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸውን አመልካች በአቀረባቸው ማስረጃዎቸው ያስረዳ መሆኑን ከደመደመ በኋላ አመልካች ተጠሪዎች ከአመልካች ደንበኛ ሂሳብ ላይ ገንዘብ በመውሰድ ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸውን ከመግለፅ እና ይህንን ሊያስረዳ የሚችል ማስረጃ ከማቅረብ ባለፈ አመልካች ገንዘቡን ለደንበኛው መተካቱን ግልፆ ያቀረበው ክስ የለም፣ ገንዘቡ ለደንበኛው ገቢ ተደርጎ ከሆነም ማረጋገጫ እንዲያቀርብ በፍርድ ቤቱ ቢታዘዝም የቀረበ ማስረጃ የለም የሚሉ ምክንያቶችን አስፍሮ አመልካች የደረሰበት ጉዳት አለ፣ ገንዘቡም ሊተካለት የሚገባ ባለመብትም ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ ባለመኖሩ ክሱ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር በነበራቸው የስራ ግንኙነት ምክንያት ከአመልካች ደንበኛ ገንዘብ ያላግባብ ወጪ አድርገው ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው ምክንያት በወንጀልም ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑን የሚያሳይ የፍርድ ቤት ውሳኔ ለማስረጃነት ቀርቦ እያለ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና ፍርድ ቤቱም ማስረጃውን ከተቀበለ በኋላ አመልካች የደንበኛውን ገንዘብ ከሚጠብቅበት የጊዜ ገደብ፣ በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገንዘቡን ያስቀመጠ ባለመብት ካልቀረበ ገንዘቡ ወደ ብሄራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት ከመሆኑ አንፃር ሳያገናዝብና ተጨማሪ ማስረጃ ለማቅረብም ጥያቄ ቀርቦ እያለ ይህንኑ ባላገናዘበ መልኩ አመልካች በተጠሪዎች የጎደለውንና ለግል ጥቅማቸው የዋለውን የደንበኛውን ገንዘብ ስለመክፈሉ ወይም ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች፣ ባንኩ የደንበኛውን ገንዘብ ለመጠበቅ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ እንዲሁም የተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ ስርዓትን ያልተከተለ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ለቅሬታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ሰበር አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲያስቀርብ ከተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ ጋር በተያያዘ ጭብጥ የያዘ ቢሆንም በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች አንጻር ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ነጥብ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት አግባብ የሕግ መሰረት ያለው መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው ተጠሪዎች የባንኩ ሰራተኛ በመሆን ሲሰሩ በነበረበት ወቅት የተሰጣቸውን ሃላፊነት በማጉደል ከአመልካች ደንበኛ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ በማውጣት ለግል ጥቅማቸው አውለዋል በሚል ምክንያት ሲሆን ለዚህም ተጠሪዎች በወንጀል የተቀጡ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረቡን፣ የስር ፍርድ ቤትም በተጠሪዎች ላይ የተላለፈ የወንጀል ጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔን የሚያሳይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ በተመሳሳይ ጉዳይ የፍትሃ ብሄር ክስ ሲቀርብ ለዚሁ ክስ አግባብነት ያለውና ብቃት ያለው ማስረጃ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 እና በዚህ ረገድ ይህ ችሎት ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መረዳቱን ገልጸ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ለደንበኛው ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፣ ገንዘቡን ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ በፍርድ ቤቱ ሲታዘዝም ሊያቀርብ አልቻለም በሚል ምክንያት አመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት የለም፣ ገንዘቡ ሊተካለት የሚገባ ባለመብትም ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም በሚል ድምዳሜ ክሱን ውድቅ ያደረገው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሣኔ በዚያው ጉዳይ በፍትሐብሔር በማስረጃነት አግባብነት እና ብቃት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2149 ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ያስገነዝበናል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል የተሰጠ ውሣኔ በፍትሐብሔር ለቀረበው ክስ በማስረጃነት አግባብነት የሚኖረው በወንጀል ክሱ በወንጀል ፍ/ቤት ተከሣሹ ጥፋተኛ ተብሎ ከተወሰነ ስለመሆኑ እና ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት የወንጀል ክስ ማስረጃ አመዛዘን መርህ ከፍትሐብሔር የበለጠ ጠንካራና የማያሻማ ማስረጃ የሚጠይቅ መሆኑ ነው፡፡ ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስም በወንጀሉ ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎችም በፍትሐብሔሩ ጉዳይም የቀረቡና የተሰሙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በወንጀሉና በፍትሐብሔር ጉዳይ የተሰሙት ማስረጃዎች የተለያዩ ከሆነ እና በወንጀል ጉዳይ ክስ የቀረበበት ነጥብም ከፍትሐብሔሩ ክስ ጋር ግንኙነት የሌለው ከሆነ በወንጀል ክስ ተጠያቂ መሆን ሁል ጊዜ በፍትሐብሔሩ ክስ ኃላፊነትን የማያስከትል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና አላማ ያስገነዝበናል፡፡ ይህ ስለመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 46386 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍ/ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2149 ድንጋጌ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን በወንጀል ጉዳይ የቀረበ ማስረጃ ክብደት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ለፍትሐብሔሩ ክርክር ብቃት ያለው ማስረጃ መሆኑና በፍትሐብሔር ክብደት ሊሰጠው አይገባም የተባለ ማስረጃ ለወንጀሉ ክስ ሲቀርብ ክብደት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ተጠሪዎች ለክርክሩ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነትና ብቃት ያለው ማስረጃ መሆኑን አምኖበት ያለፈው መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ከአመልካች ደንበኛ የባንክ ሂሳብ ገንዘብ አውጥተው ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸው በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ ከአመልካች ደንበኛ መብት አንጻር ሲታይ ለክሱ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የሥር ፍርድቤትም ይህንኑ የተቀበለው መሆኑን ከውሳኔው ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው የአመልካች ደንበኛ ገንዘብ በተጠሪዎች ያላግባብ መወሰዱንና ለግል ጥቅማቸው የዋለ መሆኑን ተቀብሎ አመልካች ገንዘቡን ለደንበኛ ስለመተካቱ የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም በሚል አቢይ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም የሕጉ ጥያቄ የሚሆነው አመልካች በተጠሪዎች የተወሰደውንና ለግል ጥቅማቸው የዋለውን የደንበኛውን ገንዘብ ለማስመለስ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ለደንበኛው መክፈሉን ወይም ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ በሕጉ የተጣለበት ቅድሚያ ሁኔታ አለ? ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ ባንክ በአደራ የተቀበለውን የደንበኛውን ገንዘብ የመጠበቅ ህጋዊ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በንግድ ህጉ ከቁጥር 896 እስከ 902 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ ባንኩና ደንበኛው የአደራ ስምምነት ውል መግባታቸውን በመግለጽ በውሉ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር ባንኩ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ባንኩ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ የደንበኛውን ገንዘብ የባንክ ስራ የሚጠይቀውን አሰራርና ስርዓት በመከተል መጠበቅና ደንበኛው ገንዘቡን ሲጠይቅም መመለስ ነው፡፡ ባንክ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በደንበኛው ገንዘብ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተጠያቂነት የሚኖርበት መሆኑንም ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎቸው መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ባንኩ የደንበኛውን መብትና ጥቅም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስከበር የሚገባው ተገቢውን ጥንቃቄ ወይም የተለመደ አሠራር በመከተል ሲሆን ይህም ባልተገባ መንገድ በደንበኛው ገንዘብ ላይ ጉዳት ያደረሱትን ሰዎች በመከላከል፣ ክስ በማቅረብ ጭምር ስለመሆኑ ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 52(1) ከተጣለበት ግዴታና ከላይ ከተጠቀሱት የንግድ ህግ ድንጋጌዎች ትክክለኛ አፈፃጸም የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

ባንኩ ከህግ ውጪ የተወሰደውን የደንበኛውን ገንዘብ የወሰደ ሰው በተገቢው ጊዜ ክስ አቅርቦ መብቱን ሊያስከበርለት የሚገባ መሆኑን ሕጉ የጣለበት ግዴታ ሲሆን የደንበኛውን ገንዘብ ደንበኛው በሕጉ አግባብ ባለመጠቀሙ ባንኩ ራሱ የሚጠቀመው ሳይሆን ወይም ለዛለለሙ ባንኩ ይዞ የሚጠብቀው ሳይሆን በሕጉ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ማለፉ ከተረጋገጠ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ የሚያደርገው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 592/2000 በግልፅ ያሳያል፡፡ ስለሆነም አመልካች የደንበኛውን ገንዘብ የመጠበቅ ሕጋዊ ግዴታ ያለበትና ከሕግ ውጪ የደንበኛውን ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ባደረገ ሰው ወይም ደግሞ የአመልካች ሰራተኞች በስራቸው አጋጣሚ ያገኙትን እድል በመጠቀም በባንኩ ገንዘብ ላይ ጉዳት ማድረሳቸው ከተረጋገጠ ደንበኛው ከባንኩ ገንዘቡን የማግኘት መብት በህግ የተጠበቀለት በመሆኑ ባንኩ ደንበኛውን በመተካት ወይም በራሱ ስም ሁኖ የደንበኛውን ገንዘብ ባልተገባ ወይም በወንጀል ተግባር ወጪ አድርጎ ለግል ጥቅሙ በአዋለው ሰው ክስ ቢያቀርብ ባንኩ በቅድሚያ የደንበኛውን ገንዘብ ስለመክፈሉ ወይም በደንበኛው የባንክ አካውንት ገቢ ስለማድረጉ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም ተብሎ ክሱ ውድቅ የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም ባንኩ በን/ሕ/ቁጥር 896 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች በሕግ የተጣለበት ግዴታ ያለው ሲሆን ደንበኛው በሕጉ በተመለከተው አግባብ ገንዘቡን የመጠቀም ወይም የማንቀሳቀስ ተግባር ከአቆመም ለብሔራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት ስለሆነ ያለግባብ የተወሰደውን የደንበኛውን ገንዘብ አመልካች ባንክ ለራሱ ጥቅም ሊያውል የሚችልበት እድል የለምና፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ባንክ ሰራተኞቹ ሁነው የደንበኛውን ገንዘብ በወንጀል ተግባር በወሰዱት ተጠሪዎች ላይ ገንዘቡን ለማስመለስ ያቀረበውን ክስ ተጠሪዎች ስለመውሰዳቸው የሚያሳይ ማስረጃ አቅርቦ እያለና የደንበኛውን ገንዘብ የመጠበቅ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ግዴታና መተካት ደግሞ በሕግ የተጣለበት፣ እንዲሁም ባንኩ የተወሰደውን ገንዘብም ሆነ ቀሪውን የደንበኛውን ገንዘብ ለራሱ ጥቅም ሊያውል የሚችልበት የህግ ማእቀፍ በሌለበት ሁኔታ ባንኩ ለደንበኛው ገንዘቡን ስለመተካቱ የሚያሳይ ማስረጃ እስካላቀረበ ድረስ ጉዳት ደርሶበታል ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም ተብሎ ክሱን ውድቅ በማድረግ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33 ድንጋጌን መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ፣ እንዲሁም ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 ድንጋጌን መሰረት ተደርጎ የተሰጠ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

<u>ውሣኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 252399 ሕዳር 13 ቀን 2010 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 211978 ሚያዚያ 11 ቀን 2010 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስ በሕጉ አግባብ ያስረዳ በመሆኑ ተጠሪዎች ለክሱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ናቸው፣ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ብር 152,497.41(አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም) ይህ ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ(9%) ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ብለናል።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ባንኩ የራሱን ይቻል ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።
የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 149326

ቀን - 28/03/2011

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መብራቱ ጤናው - አልቀረቡም፡፡

ጣ/ገብ ተጠሪ፡- አረብ ኮንትራክተርስ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአንድ ክስተት ከሁለት በላይ በሆኑ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት መድረሱ መድን ሰጪው በመድን ዉሉ ላይ ከተመለከተው የኃላፊነት ጣሪያ በላይ እንዲከፍል ምክንያት የሚሆን መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ በቀን 10/04/09 ዓ.ም አዘጋጅተው በጣ/ገብ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ቁጥሩ 3-69511 የሆነዉ የተከሳሽ ተሸከርካሪ ወደ ኋላ ተንሸራትቶ በንብረታቸዉ ላይ በብር 150,800.00 የሚገመት ጉዳት ያደረሰ መሆኑን ጠቅሰዉ ተከሳሽ ይህኑን ገንዘብ እንዲከፍላቸዉ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ጣ/ገብ ተጠሪ ለቀረበበት ክስ በሰጠዉ መልስ ጉዳት መድረሱን ሳይክድ፣ የደረሰዉ ጉዳት ግምቱ የተጋነነ ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር የተከራከረ ሲሆን፣ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲገባ በማለትም ጠይቋል። አመልካችም በክርክሩ ጣልቃ በመግባት፣ በከሳሽ የተጠየቀዉ ጉዳት መጠኑ በባለሙያ ተገምቶ ያልቀረበ መሆኑን፣ እንዲሁም በተመሳሳይ ጉዳይ በሌላ መዝገብ በክርክር ላይ ያሉ መሆኑን እና የኃላፊነት መጠኑ ከብር 100,000.00 ስለማይበልጥ ፍርድ ቤቱ ይህኑን ግምት ዉስጥ እንዲያስገባ በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በደረሰዉ አደጋ ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሰ ጉዳት በብር 130,800.00 ስለመሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ፣ አመልካች በመድን ዉሉ በተመለከተዉ ጣሪያ ልክ ብር 100,000.00 እንዲከፍል፣ ቀሪዉን ለዳኝነት የተከፈለዉን ገንዘብ ጨምሮ የአሁን ጣ/ገብ ተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል። አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም።

አመልካች በቀን 06/03/2010 ዓ.ም በወኪሉ አማካይነት ባቀረበዉ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ የመድን ዉል መሠረት አመልካች በአንድ ክስተት በሦስተኛ ወገን ላይ ለደረሰ ጉዳት ለመክፈል የገባዉ ግዴታ እስከ ብር 100,000.00 ብቻ መሆኑን፤ በተመሳሳይ አደጋ ምክንያት ንብረትነቱ የአቶ አርአያ ገ/መድህን የሆነዉ የሰ/ቁጥሩ 1-33616 በሆነዉ ባጃጅ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት መድረሱን ተከትሎ በመ/ቁጥር 00044 ላይ ክስ ቀርቦ አመልካች ብር 54,951.00 እንዲከፍል መወሰኑን፤ ይህም አመልካች በአንድ ክስተት ሊከፍል ከሚገባዉ ጣሪያ በላይ ብር 54,951.00 እንዲከፍል መደረጉን የሚያሳይ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ይህኑን ግምት ዉስጥ እንዲያስገባ አመልካች ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ አመልካች መክፈል ከሚገባዉ በላይ እንዲከፍል የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል። አቤቱታዉ ተመርምሮም አመልካች በመድን ዉሉ ከተመለከተዉ ጣሪያ በላይ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል። በዚህ መነሻነት መዝገቡ ከተመረመረ በኋላ፣ በስር ተከሳሽ የነበረዉ በዚህ ችሎት ተጠሪ ሆኖ ጣልቃ እንዲገባ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ጣ/ገብ ተጠሪ በቀን 24/01/2011 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ መልስ በዚህ ችሎት በሚደረግ ክርክር ጣልቃ እንዲገባ የተደረገበት አግባብ ኢ-ስነስርዓታዊ መሆኑን፣ እንዲሁም የአመልካችን የኃላፊነት መጠን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አለመሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመለል፣ ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ፣ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ አጥብቆ የሚከራከረዉ በጣ/ገብ ተጠሪ ተሽከርካሪ ምክንያት በአንድ ጊዜ የሚደርስ አደጋ ከሁለት እና ሁለት በላይ ሠዎች ላይ ጉዳት ቢደርስም የኃላፊነቱ መጠን ከብር 100,000.00 ሊበልጥ እንደማይገባ፣ ይሁንና በተሽከርካሪዉ አማካይነት በተፈጠረ አደጋ ምክንያት ከተጠሪ ሌላ በሦስተኛ ወገን ላይ ለደረሰ ጉዳት ተከስሶ ብር 54,591.00 እንዲከፍል መደረጉን እና ይህም ለተጠሪ እንዲከፈል ከተወሰነዉ የገንዘብ መጠን ጋር ሲደመር የአመልካችን ኃላፊነት በመድን ዉሉ ከተመለከተዉ በላይ ብር 154,951.00 የሚያደርስ መሆኑን ነዉ፡፡ ያስቀርባል የተባለዉም ይህኑን ለማጣራት ነዉ፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ ላይ የሚሰጥ ዉሳኔ በጣ/ገብ ተጠሪ መብት ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ዉጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ይህኑን ግምት ዉስጥ በማስገባት አመልካች ጣ/ገብ ተጠሪን ተጠሪ ማድረግ ሲገባዉ አላደረገም፡፡ ይህ በመሆኑም ጣ/ገብ ተጠሪ በዚህ ችሎት እየተደረገ ባለዉ ክርክር በተጠሪነት እንዲቀርብ መደረጉ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 40(5) መሠረት በአግባቡ በመሆኑ ጣ/ገብ ተጠሪ በዚህ ችሎት በተጠሪነት መጠራቱ ከስነ ስርዓት ዉጪ መሆኑን በመግለጽ የሚያቀርበዉ ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

ወደ ዋናዉ ጉዳይ ስንመለከት ከላይ እንደተገለጸዉ በግራ ቀኝ መካከል በቀን 24/03/2008 ዓ.ም በተደረገ የሦስተኛ ወገን መድን ዉል በፊደል “ሰ“ ለንብረት ጉዳት ካሳ በሚል በተመለከተዉ ርዕስ ስር በአንድ ክስተት በሦስተኛ ወገን ላይ ለደረሰ የንብረት ጉዳት ካሳ የአመልካች ኃላፊነት እስከ ብር 100,000.00 ስለመሆኑ በግልጽ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተመልክቷል፡፡ በጣ/ገብ ተጠሪ ተሸከርካሪ በተፈጠረዉ አደጋ ምክንያት በተጠሪ ንብረት ላይ በብር 130,800.00 የሚገመት ጉዳት የደረሰ ሲሆን፣ በተመሳሳይ አደጋ በአቶ አርአያ ገ/ማርያም የባጃጅ ተሸከርካሪ ላይ መድረሱን ተከትሎ በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00044 ላይ ክርክር ተደርጎ ፍርድ ቤቱ በአደጋዉ ምክንያት በባጃጁ ላይ ለደረሰ ጉዳት ብር 54,951.00 አመልካች እንዲከፍል መወሰኑን እና በዉሳኔዉ መሠረትም የተፈጸመ ስለመሆኑ ከግራ ቀኝ ክርክር ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይሁንና ይህ መሆኑ የአመልካችን የኃላፊነት ጣሪያ ከፍ ሲል በተመለከተዉ አግባብ በግራ ቀኝ መካከል በተደረገ የመድን ዉል ከተመለከተዉ ከብር 100,000.00 በላይ ሊያደርግ አይችልም፡፡ ስለሆነም የስር የጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባዉን የካሳ መጠን ሲወስን ይህኑን ግምት ዉስጥ ማስገባት ነበረበት፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህን ባለማድረግ በአንድ በኩል አመልካች ለአቶ አርአያ ገ/መድህን 54,951.00 እንዲከፍል ወስኖ እያለ በሌላ በኩል ለተጠሪም ብር 100000.00 እንዲከፍል በማድረግ የአመልካችን የኃላፊነት መጠን እስከ ብር 154,951.00 ሊያደርስ የሚችል ዉሳኔ መስጠቱ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉን የመድን ዉል እንዲሁም የኢንሹራንስ ሰጪዉ ግዴታ የኃላፊነት መጠን በመድን ዉሉ ላይ ከተመለከተዉ መብለጥ እንደሌለበት በንግድ ህጉ አንቀጽ 665(2) ስር የተመለከተዉን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1. በጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00043 በቀን 24/09/2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 260035 በቀን 14/02/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንጽ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በሌላ መዝገብ ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ለአቶ አርአያ ገ/መድህን የከፈለዉ ብር 54,951.00 ተቀንሶ፣ አመልካች ለተጠሪ ብር 45,049.00 (አርባ አምስት ሺህ አርባ ዘጠኝ ብር) ሊከፍል ይገባል ተብሏል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. ጣ/ገብ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ በተወሰነዉ ላይ ብር 54,951.00 ተጨምሮ ብር 85,751.00 (ሰማኒያ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ አንድ ብር) ለተጠሪ ይክፈል ብለናል፡፡
4. የዳኝነት እና ኪሳራ ክፍያን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ የዉሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
5. በአጣሪ ችሎት ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
6. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 153981

መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ሚሲስ ሲያዎ ዶንግ - ጠበቃ ሃፍቶም ከሰተ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ሚስተር ዶንግዩ ቸን

2. አቢስንያ ቴክኖሎጂ አዳፕቴሽን ሴንተር ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጠበቃ አብዱራህማን አልአቂብ- ቀረቡ፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪዎች ክስ ይዘትም አመልካች በሁዋ ኢ ስሜንት የተወሰነ የግል ማህበር ውስጥ ስራ አስኪያጅ ሲሆኑ የተሸሙት ለአራት ዓመታት በመሆኑ፤ ምንም ዓይነት የባለአክስዮኖች ስብሰባ ጠርተው የማያውቁ በመሆናቸው፤ ዓመታዊ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሒሳብ ሪፖርትም ሆነ የትርፍ ክፍፍል ተደርጎ የማያውቅ በመሆኑ፤ ሽያጭ እየደበቁና ግብር እየሰወሩ በገቢ ሰብሳቢ ቢሮ ድርጅቱ እንዲቀጣ ያደረጉ በመሆናቸው ከስራ አስኪያጅነታቸው ይሻርልን፤የድርጅቱ ሒሳብና ሁኔታ ኦዲት እንዲደረግልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

የስር ተከሳሽ የነበሩት አመልካች በሰጡት መልስ የድርጅቱ ባለአክስዮኖች በ03/10/2001፤ 20/07/2002 እና በ23/11/2003 ዓ.ም በተደረጉ ውሳኔዎች ማህበሩ የማቋቋም ውሳኔዎች ተሻሽሏል፤2ኛ ተጠሪ ምንም ገንዘብ አላወጣም፤ስራ አስኪያጅ የማንሳት ጉዳይ በባለአክስዮኖች ስብሰባ ላይ አብላጫ ድምፅ ድጋፍ ሳያገኝ በመቅረቱ ያልተተካ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል አይደለም፤በመመስረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ስብሰባ የመጥራት ኃላፊነት የሁሉም ባለአክስዮኖች ግዴታ ነው፤አመልካች ስብሰባ ተጠርተው ቀርተው አያቁም፤ስብሰባውም እ.ኤ.አ ዲሴምበር 27 ቀን 2014 እና ጃንዋሪ 20 ቀን ተደርጓል፤የሁሉም በጀት ዓመት ሒሳብ ተደርጓል፤ትርፍ ክፍፍል ተደርጎ ተጠሪዎች ገንዘብ ወስደዋል፤ከስራ አስኪያጅነት ሊያስነሳ የሚችል ጥፋት አልሰራሁም፤የድርጅቱ ሒሳብ በየዓመቱ ኦዲት ተደርጎ ግብር የሚከፈል ሁኖ እያለ በ3ኛ ወገን የሚመረመርበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ካቀረቡ በኋላ ድርጅቱ በስድሳ ሚልዮን ቢቋቋም አመልካችና 1ኛ ተጠሪ እያንዳንዳችን 45% ድርሻ ሲኖረን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ 10% ድርሻ ነበራቸው፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች ባደረግነው ስምምነት ከ14 ሚልዮን በላይ መዋጮ ያዋጣሁ ቢሆንም ተጠሪዎች መዋጮ ያልከፈሉ በመሆናቸው በተለያየ ጊዜ በተደረጉ ስምምነቶች መዋጮው እንዲከፍሉ /ሌላ ግለሰብ እንዲከፍልላቸው ጭምር/ የተስማማ ቢሆንም ምንም ዓይነት መዋጮ አዋጥተው የማያውቁ በመሆናቸው እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 22 ቀን 2015 ከተደረገው ስብሰባ ጀምሮ የሒሳብ ሪፖርት ፀድቆ ትርፍ ክፍፍል እንዲደረግ በተያዘው አጀንዳም ምንም ስምምነት መድረስ አልቻለም በስራ አስኪያጅ ይነሳ ጉዳይ ከፍተኛ አለመግባባት ተፈጥሯል፤ በውጭ ኦዲተር የተሰራውን የማህበሩ ሒሳብ ተጠሪዎች ለማጽደቅ እምቢተኛ ሁኗል፤ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ መነሻነትም የማህበሩ ህልውና አደጋ ላይ ወድቋል፤በአጠቃላይ በመዋጮ፤ስራ አስኪያጅ ሹመት፤ትርፍ ክፍፍል፤በኦዲት ሪፖርትና የማህበሩ አመራር ዙሪያ በአባላት መካከል አለመግባባት እና ብርቱ ጭቅጭቅ የተፈጠረ በመሆኑ ማህበሩ እንዲፈርስ እና ንብረት አጣሪ እንዲሾም የተከሳሽ ከሳሽነት አቅርበው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪዎች በበኩላቸው ማህበሩ ሊፍርስ አይገባውም የሚል መልስ ሰጥቷል። ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩ ላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ማህበሩ ሊፍርስ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በማስቀደም የተፈጠረው ግጭት መሰረታዊ ግጭት አይደለም፤አንዱ ማህበርተኛ በወሰነው ወይም በሰራው ሌላው ደስተኛ ወይም ተጠቃሚ ካለመሆኑ የተነሳ አለመግባባት ነው፤ማፍረስ የመጨረሻ መፍትሔ ነው፤የተጠቀሱ ምክንያቶች አለመግባባት እና ብርቱ ጭቅጭቅ ፈጥሯል የሚባሉ አይደሉም በማለት ማህበሩ ሊፍርስ አይገባውም፤በመቀጠል አመልካች ከተሾሙ አንስቶ 4 ዓመት ያለፈባቸው በመሆኑ፤ድርጅቱ እንዳልተቀጣ ቢገልጹም የተወሰነ ገንዘብ እንደከፈለ ማመናቸው፤በየዓመቱ ስበሰባ እየጠሩ የሒሳብ እና የስራ ሪፖርት ያቀረቡ ስለመሆናቸው ያቀረቡት ክርክር የለም በማለት ክስራ አስኪያጅነታቸው ሊነሱ ይገባል በማለት ወስኖ የድርጅቱ ሁኔታና ሒሳብ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ በኦዲተር እንዲጣራ ሲል የሰጠው ውሳኔ በመቃወም አመልካች ይግባኛቸው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሀ/ቁ.337 መሰረት በትእዛዝ ሰርዞታል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። አመልካች የካቲት 13 ቀን 2010 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 25 ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካችም አቤቱታቸው በማጠናከር የመልስ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል። ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አመልካች ከስራ አስኪያጅነት ኃላፊነታቸው እንዲነሱ ያቀረቡት መሰረት በማድረግ የማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 10.4 መሰረት ከአራት ዓመት በኋላ ሌላ ስራ አስኪያጅ እንደሚመረጥ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የደረሱበት ድምዳሜ ከመሆኑም በላይ በአጣሪው ችሎትም በጭብጥነት ያልተያዘ ከመሆኑ አንፃር አመልካች ስራ አስኪያጅ እንዲመረጥ የተሰጠ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩበት ጉዳይ በማህበሩ አባላት መካከል ብርቱ ጭቅጭቅ ተፈጥሮ እያለ ማህበሩ ሊፍርስ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው የአመልካችን የማህበሩ ይፍረስ ጥያቄ እና ምክንያት በንግድ ህጉ አንድ ማህበር ስለሚፈርስበት ሁኔታ ከተደነገጉት አንቀጽ 217 እና 218 ጋር በአግባቡ አገናዝበው የሰጡት ውሳኔ እና አተረጓጎም ምንም አይነት የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቿ ምክንያታቸውን በዝርዝር በመግለጽ ሂሳቡ ተጣርቶ ማህበሩ እንዲፈርስ እንዲወሰን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ በቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በግራ ቀኙ መካከል ዝርዝር ክርክር ከተደረገ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማህበሩን ለማፍረስ የሚያስችል በቂና ሕጋዊ ምክንያት ያልተገኘ መሆኑን እንዲሁም የንግድ ማህበሮች መቋቋምና በተለያዩ የንግድ፤የኢኮኖሚ ስራዎች ላይ መሰማራት፤ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ እድገትና እንቅስቃሴ ወሳኝ የሆነ ሚና ያላቸው ሲሆን የሀገራት ኢኮኖሚ እድገትም ከንግድ ማህበሮች መቋቋም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በመሆኑም የንግድ ማህበሮች መቋቋም፤መስፋፋት ብሎም መፍረስ ከማህበርተኞች መብትና ጥቅም አልፎ በሶስተኛ ወገኖች /ሰራተኞች፤ከማህበሩ ጋር የውል ግዴታ በሚገቡ ሰዎች በገንዘብ ጠያቂዎች ወዘተ../መብትና ጥቅም ላይ እንዲሁም በአጠቃላይ የሀገር ኢኮኖሚ እድገትና እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ የንግድ ማህበራት ጉዳይ በተለይም የንግድ ማህበራት መፍረስ ጉዳይ በአግባቡ እና በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ገልጾ አመልካቿን ጥያቄ በቀን 15/02/2010 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በተሰጠ ውሳኔ ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት በቀን 29/05/2010 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በመሰረቱ የንግድ ማህበሮች ከተቋቋሙ በኋላ እንደየአግባብነቱ በማህበርተኞቹ ስምምነት፣ በሕግ በተመለከተው ምክንያትና በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፈርሱ የሚችሉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሆን የንግድ ሕጉ ለሁሉም ማህበሮች ተፈፃሚነት ያላቸው የማፍረሻ ምክንያት ያስቀመጠ ከመሆኑ በተጨማሪ እያንዳንዱ ንግድ ማህበር ካለው የተለየ ባህሪ አኳያ ለየማህበራቱ ተፈፃሚ የሚሆን ተጨማሪ የማፍረሻ ምክንያቶች አካትቶ ይዟል፡፡ በንግድ ሕጉ ስለ ንግድ ማህበሮች በጠቅላላው በሚናገረው ክፍል የሚገኘው ቁጥር 217 ማህበር በሕግ ወይም በስምምነት ሊፈርስ የሚችልበትን ቁጥር 218 ደግሞ በፍርድ ቤት አማካኝነት የሚፈርስበትን ምክንያቶች ያመለክታሉ፡፡ ማህበሩ የተቋቋመበትን ጉዳይ ከፈፀመ ወይም ለመፈፀም ባልቻለ ጊዜ፣የንግድ ማህበሩ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ከመድረሱ በፊት ማህበርተኞቹ ማህበሩ እንዲፈርስ ተስማምተው ከወሰኑ፣ማህበርተኞቹ ማህበሩ እንዲቀጥል ካልተስማሙ በቀር ማህበሩ የተቋቋመበት ዘመን ሲያበቃ ማህበሩ ሊፈርስ ይችላል፡፡ ማህበሩ የሚቆይበት ዘመን ከመድረሱ በፊት ትክክለኛ ምክንያቶች ኖረውት ከማህበርተኞቹ አንዱ ጥያቄ ሲያቀርብ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፈርስ የሚችል ሲሆን ከማህበርተኞቹ አንዱ ተግባሩን (ግዴታዎቹን) ከመፈፀም በብዙ ማስተጓጎል፣በአካል ጉድለት ወይም በማይድን ህመም ምክንያት ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት የማህበሩን ስራ ለመስራት አለመቻሉ፣ በማህበርተኞቹ መካከል ብርቱ ጭቅጭቅና አለመስማማት መፈጠሩ እንደትክክለኛ ምክንያት ሊወሰዱ እንደሚችሉ የንግድ ህግ ቁጥር 218 (2) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ድንጋጌው "ብርቱ ጭቅጭቅና አለመስማማት" የሚለው ሐረግ ምን እንደሚያመላክት የሚያስቀምጠው ግልፅ መመዘኛ የሌለ ቢሆንም ሐረጉ ማህበሩ ከተቋቋመበት መሰረታዊ አላማና ከማህበርተኞቹ አብሮ የመስራት አጠቃላይ ሁኔታ አንጻር ታይቶ ሊተረጎም የሚችል መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ስለሆነም ብርቱ ጭቅጭቅ ሲባል በማህበርተኞቹ መካከል ያለ ማንኛውም አለመግባባት ሳይሆን ማህበርተኞች አብረው ለመስራት የማያስችላቸው ወይም ማህበሩ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት የማያስችለው እና ለስራው አስፈላጊ ከሆነ ጉዳይ ጋር የተገናኘ መሰረታዊ ግጭትና አለመግባባት መኖሩን የሚያመለክት ነው ተብሎ የሚወሰድ መሆኑ ይታመናል፡፡ ሐረጉ በዚህ አግባብ መተርጎም ያለበት ካልሆነ ማህበራት ተገቢው የሕግ ጥበቃ ተደርጎላቸው ለአገር ኢኮኖሚ የሚያበረክቱት ሚና የጎላ አይሆንም፡፡ በሌላ አገላለፅ ሐረጉ ማህበሩ ተገቢውን ስራ ለማከናወን የሚያስችል ሁኔታ ውስጥ መኖሩን በሚያሳይ መልኩ ካልተተረጎመ ማህበራት ተገቢ ባልሆኑ ምክንያቶች ሁሉ እንዲፈርሱ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የማድረግ አጋጣሚን ሁሉ ሊፈጥር የሚችል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሕጉ መሰረታዊ ዓላማ ያለመሆኑ ይታመናል፡፡

ሌላው በተጠቃሹ ድንጋጌ ስር የተጠቀሱት የማህበር ማፍረሻ ምክንያቶች ተዘርዝረው የተጠቀሱ ሳይሆን አመልካች በመሆናቸው በተለይ "ትክክለኛ ምክንያት" የሚለው የድንጋጌው ሃረግ ሰፊና ትርጉም የሚያሻው በመሆኑ በስራ አስኪያጆቹ ግዙፍ ጥፋት ሲፈፀም፣ስራው የሚጠይቀው ቅን ልቦና ሲጠፋ፣ የማህበሩ ገንዘብ ለግል ጥቅም ሲውል፣ለማህበሩ ገቢ መሆን የሚገባው ገንዘብ አለማድረግን የመሰሉት ምክንያቶች ከተከሰቱና የተፈጠረው ችግርም ማህበሩን ከማፍረስ ውጪ በሌላ ሁኔታ ወይም አግባብ መፍትሔ የማያገኝ መሆኑን ፍርድ ቤቱን የሚያሳምን ከሆነ ማህበሩ ሊፈርስ የሚችልበትን አግባብ የሚያሳዩ ናቸው ተብሎ ሊወሰዱ የሚችሉ ምክንያቶች ናቸው፡፡ የተወሰነ አላፊነት ያለው የግል ማህበር የሚፈርስባቸው ምክንያቶችም በንግድ ሕጉ በቁጥር 542 ስር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ እንደየ ጉዳዮቹ አግባብነት የሚቀርበውን ምክንያት መከሰቱን በማስረጃ ማረጋግጥና ስለመከሰቱ ከተረጋጋጠ ደግሞ የምክንያቱን በቂነት በአግባቡ ሊመረምር የሚገባው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ማህበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት የጠየቁት አባላት የአክስዮን መዋጮ አልከፈሉም፤ለማህበሩ ሊዋጣ የሚገባውን ገንዘብ በተመለከተ በተለያየ ጊዜ ስምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም አባላቱ በስምምነቱ መሰረት መዋጮ አልከፈሉም፤የከሳሽ ተከሳሽ ማህበሩ ያላቸውን 55% አብላጫ ድምጽ በመጠቀም ከተከሳሽ ከሳሽ የተለየ አቋም ስለሚይዙ ማህበርተኞች መስማማት የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፤ አመልካች ስራ አስኪያጅ እንዲሻር እና በፍርድ ቤት ክስ በማቅረባቸው ምክንያት ድርጅቱ አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ በአጠቃላይ በማህበሩ አስተዳደር እና አካሄድ ዙሪያ በአባላት መካከል አለመግባባት እና ብርቱ ጭቅጭቅ ተፈጥሯል የሚሉ ምክንያቶችን መሆናቸው የስር ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ እንደሚታየው እነዚህ ምክንያቶች ማህበሩን ለማፍረስ የሚያስችሉ በቂና ሕጋዊ ምክንያቶች ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ አይደሉም፡፡ በአመልካች የተነሱ ምክንያቶችም ከማህበሩ መፍረስ በመለስ ባሉ እርምጃዎች እልባት ማግኘት የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የማህበሩ ሕልውና እንዲቀጥል መደረግ የሚገባው ከመሆኑ በቀር ማህበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.225884 ጥቅምት 15 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.205876 ጥር 29 ቀን 2010 ዓ.ም በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዘገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ካ/የ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ንብረት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር ፡-150773

ቀን፡-ግንቦት 27/2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች:- አቶ ሀይሉ ኪዳኑ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ቀጭኑ ዱጉማ ጠበቃ ሙሉቀን ግዛቸው ቀረቡ

2. አቶ ተሰማ አለማየሁ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ አቅርበዉት የነበረዉ ክስ ይዘት፡- ክርክር ያስነሳዉን መሬት በ1989 ዓ.ም በዉሳኔ አግኝቼ እየተጠቀምኩበት የቆየሁ ሲሆን የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ መሬቱን በ2005 ዓ.ም ከሕግ ዉጪ ይዞ ስለሚገኝ ይልቀቅልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በበኩሉ ክርክር ያስነሳዉ መሬት በቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ዉስጥ ይገኝ የነበረ ሲሆን ወደ ኦሮሚያ ከተካለለ በኃላ በጉቶ ጊዳ ወረዳ ግብር እየከፈልኩ ስጠቀምበት የቆየሁት በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ መብት የሌለዉ በመሆኑ ክስ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየዉ የጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ክርክር ያስነሳዉን መሬት ለ1ኛ ተጠሪ እንዲለቅ ወስኖ የነበረ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔዉን በመሻር አመልካች መሬቱን በኮንትራት ወስጀበታለሁ የሚለዉ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ካደረገ በኃላ የመሬቱ ባለይዞታ ማን እንደሆነና በምን መልኩ በአመልካች እጅ እንደገባ አጣርቶ ተገቢዉን እንዲወስን በነጥብ መልሶለታል፡፡

2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ተደርጎ በሰጠዉ መልስ ክርክር ያስነሳዉን መሬት ከ1ኛ ተጠሪ በኮንትራት ለ5 ዓመት ወስጄ በመሃል ስታመም ለአመልካች ለ10 ዓመት በኮንትራት የሰጡት እንጂ የአመልካች አይደለም በማለት 1ኛ ተጠሪን በመደገፍ ተከራክሯል፡፡

የወረዳዉ ፍ/ቤት ክርክርና ማስረጃዉን መርምሮ 1ኛ ተጠሪ ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ በእጁ አድርጎ ሲያዝበት የነበረ ይዞታዉ ለመሆኑ አላስረዳም በማለት ክስ ለማቅረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) መሰረት መብት የለዉም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተዉ የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ አመልካች ክርክር ያስነሳዉን መሬት ከ2ኛ ተጠሪ ለ15 ዓመት በኮንትራት ወስጄ የያዝኩት ነዉ በማለት የተከራከረ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ መሬቱን ከ1ኛ ተጠሪ በኮንትራት ወስጄ ለአመልካች በኮንትራት ሰጠሁኝ ያለ በመሆኑ፤ እንዲሁም በክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 መሠረት የኪራይ ዉሉ በሚመለከተዉ አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ አመልካች መሬቱን ለ1ኛ ተጠሪ ይልቀቅ በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የአሁኑ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ኮንትራት የሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በሌለበት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና መሬቱን በ01/09/1998 ዓ.ም በተጻፈ የኮንትራት ዉል ከ2ኛ ተጠሪ ተከራይቼ ስጠቀምበት የቆየሁ ስለሆነ ለመክሰስ መብት የነበረዉ 2ኛ ተጠሪ እንጂ 1ኛ ተጠሪ አይደለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ይችላል ቢባል እንኳ ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ አልፈዉ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ 2ኛ ተጠሪ ይዞታዉ የራሱ መሆኑን ገልጾ አከራየኝ እንጂ ጠያቂ ሲመጣ መሬቱን እንደምለቅ ባልተዋዋልኩበት እንድለቅ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ ይዞታዉ የ1ኛ ተጠሪ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ባልቀረበበት መሬቱን ልቀቅ መባሌ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ዉሳኔዉ ተሸሮ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል በተነሳዉ የገጠር እርሻ መሬት ጉዳይ የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የኮንትራት ዉሉ ከ1999 ዓ.ም በፊት መፈጸሙ እየታወቀ የክልሉን የመሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 በመጥቀስ ዉሉ ባለመመዝገቡ ፈራሽ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ ክርክራቸዉን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰበር መልሳቸዉ ያቀረቡት ክርክር ይዘት፡- ክርክር ያስነሳዉ መሬት 3 ሄክታር የአርሶ አደር የእርሻ መሬት መሆኑ ተረጋግጦ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/99 መሠረት ለዚህን ያህል ጊዜ የአርሶ አደር መሬት ማከራየት አይቻልም ተብሎ አመልካች መሬቱን እንዲለቅ መወሰኑ ተገቢ ነዉ፡፡ በአካባቢዉ ባለመኖሬ እስክመለስ እንዲጠቀምበት ለ2ኛ ተጠሪ ሰጠሁት እንጂ ለሌላ 3ኛ ወገን እንዲያከራይ ባለመሆኑ የኪራይ ዉሉ አይጸናም፡፡ አመልካች መሬቱን በዉል የያዘና የያዘዉም በ1998 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ያቀረበዉ ቅሬታ ተገቢነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ የ1ኛ ተጠሪን ክርክር በመደገፍ መልስ አቅርቧል፡፡

የግራቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነዉ ግራቀኙን ያከራከረዉ ይዞታ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ግንቦት 01 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የኪራይ ዉል ለ15 ዓመት ተከራይቶ የያዘዉ መሆኑን የገለጸ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ መሬቱ የ1ኛ ተጠሪ መሆኑን አረጋግጦ ለ5 ዓመት ተከራይቶ በመታመሙ ምክንያት ለአመልካች ለ15 ዓመት ማከራየቱንና መሬቱ ለ1ኛ ተጠሪ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊመለስለት እንደሚገባ ተከራክሯል። የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ክርክር ያስነሳውን መሬት ለተጠሪ ሊለቅ ይገባል በማለት ሲወስን የሰጠዉ ምክንያት አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ግንቦት 01 ቀን 98 ዓ.ም ያደረጉት የኪራይ ዉሉ፤ የመሬት ኪራይ ዉልን ለመመዝገብ ስልጣን ባለዉ አካል አልተመዘገበም በሚል ነዉ። የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉና የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ፤ የኪራይ ዉሉ ከ1999 ዓ.ም በፊት የተደረገ ሆኖ ሳለ አዋጅ ቁጥር 130/99 በመጥቀስ ዉሉ ባለመመዝገቡ ፈራሽ ነዉ መባሉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ።

በመሠረቱ በክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 10(2 እና 3) መሠረት በባህላዊ መንገድ የሚታረስ መሬትን በዉል ማከራየት የሚችለዉ ከ3 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ ዉሉም ዋጋ የሚኖረዉ በክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ተመዝግቦ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑ የተመለከተ ሲሆን ይህ አዋጅ ከመደንገጉ በፊት ሥራ ላይ የነበረዉ አዋጅ ቁጥር 56/94 አንቀጽ 11(2 እና 4) ስር በተመሳሳይ በባህላዊ መንገድ የሚለማን መሬት አርሶ አደሩ ማከራየት የሚችለዉ ከ3 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ በአካባቢዉ መሬትን ለማስተዳደር ስልጣን ባለዉ አካል ሲረጋገጥ መሆኑ ተደንግጓል። ከእነዚህ አዋጆች ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ አዋጅ ቁጥር 130/99 ከመዉጣቱ በፊትም ሆነ በኃላ አርሶ አደሩ በባህላዊ መንገድ የሚያለማዉን መሬት ማከራየት የሚችለዉ ከ3 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ ዉሉ ዋጋ እንዲኖረዉ በሚመለከተዉ አካል ተመዝግቦ መረጋገጥ የሚገባዉ መሆኑን ነዉ።

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ክርክር ያስነሳውን መሬት ለ15 ዓመት ከ2ኛ ተጠሪ ተከራየሁ ከማለቱም በላይ የኪራይ ዉሉ በሚመለከተዉ አካል ያልተመዝገበና ያልተረጋገጠ ነዉ። ይህ ዉል በአዋጅ ቁጥር 56/94 አንቀጽ 11(2 እና 4) ሆነ አሁን ሥራ ላይ ባለዉ አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 11(2 እና 3) መሠረት ሕጋዊ ዉጤት የሌለዉ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪን ሊያስገድድ የሚችል አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ለ5 ዓመት ተከራየሁት የሚለዉን መሬት በሌለዉ መብት ለ15 ዓመት ሊያከራይ የሚችልበት አግባብ የለም። ከዚህ አንጻር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ መሬቱን ይልቀቅ ብሎ መወሰኑም ሆነ በየደረጃዉ ጉዳዩን የተመለከቱት ፍ/ቤቶች ይህንኑ ዉሳኔ ማጽናታቸዉ የሚነቀፍ አይደለም።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል አመልካች ክርክር ያስነሳዉን የገጠር መሬት ለ1ኛ ተጠሪ እንዲለቅ የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ ዉሳኔዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45979 ጥቅምት 27 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 213383 ሕዳር 13 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 274283 ሕዳር 27 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠዉ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በጉቱ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት የተጀመረዉ አፈጻጸም ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ በዚህ ችሎት የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጸፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/134343

ግንቦት 27 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡1ኛ/አቶ ቴዎድሮስ ዉብሸት

2ኛ/ወ/ሮ ፍሬህይወት ዉብሸት

3ኛ/አቶ ሚካኤል ዉብሸት

ተጠሪዎች፡ 1ኛ/የአዳማ ከተማ ቀበሌ 06 መስተዳድር ጽ/ቤት

2ኛ/አቶ መኩሚል ከሊል

3ኛ/ወ/ሮ ዓለም ሃጎስ

4ኛ/ወ/ሮ አይሻ ከድር

5ኛ/አቶ ሻምበል ሃይሉ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ በዉርስ የተላለፈ የከተማ ይዞታና ቤት ከመንግስት ቤት ጋር ተቀላቅሎ ስለሚገኝ የመንግስት ቤት ፈርሶ ለአጠቃቀም በሚያመች አኳኋን ይዞታዉ ስፋት ተስተካክሎ የይዞታ ማረጋገጫ ለወራሾች እንዲሰጥ የቀረበ የዳኝነት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄ የሚመለከት ነዉ።በዚህ ጉዳይ ከሳሾች የአሁኖቹ አመልካቾች ሲሆኑ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ከ2-5 ያሉት ተጠሪዎች ጣልቃ ገብ በመሆኑ ተከራክረዋል። የአመልካቾች ክስ ይዘት ባጭሩ በአዳማ ከተማ ቀበሌ 06 ዉስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 233.06 የሆነ መኖርያ ቤት ይዞታ ስፋቱ 101 ካ.ሜ ከአያታቸዉ ከወ/ሮ ፀሐይ ካሳ በስጦታ የተላለፈላቸዉ መሆኑን ገልጸዉ ይዞታዉና ቤቱ ከመንግስት ቤት ጋር ተቀላቅሎ ስለሚገኝ ለ1ኛ ተጠሪ ጉዳዩ በአቤቱታ ቀርቦ ቃለ ጉባኤ ተይዞ የመንግስት ቤት ፈርሶ ይዞታዉ ሰፍቶ ከፊሉ ለመንገድ እንዲሆን ሌላዉ ለአመልካቾች ይዞታ ተጨምሮ 260 ካ.ሜ ሆኖ የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጥ ስለተወሰነ በዚሁ መሰረት እንዲፈጸም ዉሳኔ እንዲሰጥ ዳኝነት ጠይቀዋል።

በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ የከተማ መሬት የማስተዳደርና የመቆጣጠር ስልጣን የአዳማ ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ኤጀንሲ እንጂ የተከሳሹ ባለመሆኑ ስልጣን በሌላቸዉ የቀበሌዉ አመራሮች የተሰጠ ዉሳኔ ወይም ቃለጉባኤ ተፈጻሚነት እንደሌለዉ፣አመልካቾች እንዲፈርስ የጠየቁት የመንግስት ቤት የማስተዳደር ስልጣን የመንግስት ቤቶች አስተዳደር አካል በመሆኑና የሌሎችን መብትና ጥቅም የሚመለከት ስለሆነ ተቀባይነት እንደሌለዉ በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል።ከ2-5ኛ ላሉት ተጠሪዎች ከመንግስት ቤቶቹን ተከራይተዉ የሚኖሩበት መሆናቸዉን ገልጸዉ ክርክሩ መብታቸዉን የሚመለከት በመሆኑ ወደ ክርክር በጣልቃ ገብነት ገብተዉ ቤቶቹ እንዲፈርሱ ዉሳኔ ሊሰጥ እንደማይገባ ተከራክረዋል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካቾች በንብረታቸዉ የመገልገል ህገ መንግስታዊ መብት እንዳላቸዉ እና ይዞታቸዉ ለአጠቃቀም በሚያመች መልኩ ችግሩ እንዲፈታ በቀበሌ አመራር ኮሚቴ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረት የመንግስት ቤቶች እንዲፈርሱና ለአመልካቾች ይዞታ ተጨምሮ በ260 ካ.ሜ ይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል። የቀበሌ ቤት ለሚፈርስባቸዉ ሰዎች መስተዳድሩ መፍትሔ እንዲሰጥ የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል። በዚህ ዉሳኔ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ለአዳማ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ በማቅረባቸዉ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ጉዳዩ የከተማ መሬት ይዞታ ላይ መሬት እንዲሰጥ እና ይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጥ የሚል ከመሆኑ አኳያ ይህም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የከተማዉ እስታንዳርድና ማስተር ፕላን ጋር የሚታይ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ የመወሰን ስልጣን የለዉም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመሻር ተጠሪዎችን አሰናብቷል፡፡አመልካቾች ለኦሮሚያ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባቀረቡት ይግባኝ ላይ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የአመልካቾች ጥያቄ ፍትህ የማግኘት መብት ጥያቄ ነዉ በሚል አስተዳደሩ ባለዉ መመሪያ መሰረት ይዞታ ተስተካክሎ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ በወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ በከፍተኛዉ ፍርድ ቤት መሻሩ ተገቢ አይደለም በማለት የከፍተኛዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመሻር የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡በዚህ ዉሳኔ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ በማቅረባቸዉ ሰበር ችሎቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በቀበሌዉ ኮሚቴ በ15/12/06 ዓ.ም የተያዘዉ ቃለጉባኤ አስተዳደራዊ መፍትሄ የሚያመለክት እንጂ በቀጥታ ፍርድ ቤት ቀርቦ የሚፈጸም ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ተቀብለዉ በቃለ ጉባኤ መሰረት ይፈጸም በማለት የሰጡት ዉሳኔ የህግ መሰረት የለዉም በማለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ በሰበር ችሎቱ ተሽሯል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸዉ ይዘት ባጭሩ ጉዳዩ አዲስ ማስረጃ ጥያቄ ሳይሆን በእጃችን ያለዉ ይዞታ በመመሪያዉ መሰረት ይካፈልልን የሚል የፍትህ ጥያቄ ስለሆነ ፍርድ ቤት ማየት አይችልም መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም የሚል ሲሆን አቤቱታቸዉ ተመርምሮ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ማየት አይችሉም በማለት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሻሩ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በ1ኛ ተጠሪ ወኪል በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በሰበር ችሎቱ የተያዘዉ ጭብጥ ላይ ሰበር ችሎቱ የሚወስነዉ ሆኖ የአመልካቾች ይዞታ ከቀበሌ ቤት ጋር ሳይቀላቀል ማስረጃ ቢሰጣቸዉ ተቃዉም እንደሌለዉ ገልጸዋል፡፡ከ2–5 ያሉትን ተጠሪዎች በጠበቃቸዉ አማካኝነት የሰጡት መልስ የአመልካቾች ጥያቄ የቀበሌ ቤትና ይዞታ ተጨምሮ ይዞታ ተስተካክሎ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ የሚል ስለሆነ በዚህ ጉዳይ የመወሰን ስልጣን የአዳማ ከተማ መስተዳድር ስለመሆኑ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲጸና ተከራክረዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥና ግራቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ::መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ከአያታቸዉ በዉርስ ያገኙት የቤት ቁ/233.06 በ101 ካ.ሜ ላይ ያረፈ ቤት ከመንግስት ቤት ጋር የተቀላቀለ ስለሆነ ካርታና ፕላን ማሰራት እንዳልቻሉ ጠቅሰዉ ተቀላቅሎ የሚገኘዉ የመንግስት ቤት ፈርሶ ይዞታቸዉ ላይ 157 ካ/ሜ ተጨምሮ በ260 ካ.ሜ ይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ ነዉ::ለዚህም መነሻ የደረጉት የ1ኛ ተጠሪ በኮሚቴ ጉዳዩን አይቶ ቃለጉባዔ ይዞ ዉሳኔ ስለመስጠቱ ነዉ::ይህን ቃለጉባኤ አስመልክቶ በአንድ በኩል ቀጥታ ፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የሚሰጥ ነዉ ወይስ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ሀሳብ ሆኖ በሚመለከታቸዉ የአስተዳደር አካላት ተቀባይነት ሲያገኝ የሚፈጸም ነዉ የሚል ጥያቄ የተነሳበት በሌላ በኩል ደግሞ የቀበሌ ቤት እንዲፈርስ እና ለአመልካቾች ተጨማሪ ይዞታ እንዲሰጥ የቀበሌዉ ኮሚቴ ተፈጻሚነት ያለዉ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉ የህግ መሰረት አለዉ ወይ የሚለዉ መሰረታዊ ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ ቀርቧል:: ስለሆነም እነዚህ አስተዳደራዊ መዋቀር እና ስልጣን ተከትሎ መፍትሄ ወይም ምላሽ የሚያገኙ ሆኖ አመልካቾች የጠየቁት ዳኝነት በፍርድ ቤት ዉሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ ነዉ የሚለዉ መመርመር ተገቢ ነዉ::

በመሰረቱ የዳኝነት ስልጣን ከህግ የሚመነጭ መሆኑ ልብ ይለዋል::በሌላ በኩል ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሰልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለዉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንገስት አንቀጽ 37/1/ በግልጽ ደንግጓል::ከዚህ አንጻር አመልካቾች በፍርድ በዳኝነት አካል ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት በማቅረብ ፍትህ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት ያላቸዉ መሆኑ አከራካሪ አይደለም ::በዚህ መዝገብ የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የአመልካቾች ጥያቄ በዉርስ ያገኙት ቤትና ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ የማግኘት መብት ተነፍገዉ ሳይሆን ይዞታቸዉ 101 ካ/ሜ ብቻ በመሆኑ በዚህ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ማሰራት ባለመቻሉና ለአጠቃቀም አመቺ ባለመሆኑ ተቀላቅሎ ያለዉ የቀበሌ ቤት እንዲፈረስና ተጨማሪ ይዞታ ተሰጥቶአቸዉ በ260 ካ.ሜ የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ እንዲወሰን የሚል ነዉ:: በዚህ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ከመስጠቱ በፊት መብትና ጥቅም ያላቸዉ ወገኖች እንዲሁም የከተማ መሬት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይዞታ አጠቃቀም ላይ የመወሰን ስልጣን በህግ ስልጣን የተሰጣቸዉ የአስተዳደር አካላት ዉሳኔ አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል፡፡በተለይም የክልሉ ከተማ መሬት አስተዳደር አካል በአዋጅ ቁ/179/05 አንቀጽ 8 በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት እንዲሁም እንዲፈርሱ እየተባለ ያለዉ የቀበሌ ቤት የሚያስተዳድረዉ አካል እና በቤቱ ዉስጥ የሚኖሩት ሰዎች እጣፈንታ በሚመለከት ስልጣን በተሰጠዉ አካል ባልተወሰነበት ሁኔታ የአመልካቾችን ጥያቄ ብቻ መሰረት በማድረግ ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉ የህግ መሰረት የለዉም ። አመልካቾች በጉዳዩ ላይ አስተዳደራዊ መፍትሄ ከሚመለከታቸዉ አካላት መጠየቅና ማስወሰን እየተገባቸዉ በአስተዳደር አካል ያልተረጋገጠ መብት ይዘዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲሰጣአቸዉ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም በማለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1ኛ /የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በሰበር መ/ቁ/233806 ላይ በ14/02/09 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰበር መ/ቁ159414

ታህሳስ 22 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡አቶ ሚሬሳ አብሳ

ተጠሪ፡ አቶ ፍቃዱ ደበሎ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ድንበር ተላልፎ የተሰራ ግንባታ የሚመለከት ነዉ፡፡በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡የተጠሪ ክስ ይዘት ባጭሩ አመልካች ከወሰን 50ሳ.ሜ በመራቅ ቤቱን መገንባት ሲገባዉ 75.ሳ.ሜ ወደ ተጠሪ አስጠግቶ ግድግዳ በማቆሙ የቤቱ ፍሳሽ ወደ ተጠሪ ግድግዳ እየፈሰሰ የተጠሪን ግድግዳ አበላሽቷል በሚል አመልካች ግንባታዉን እንዲያፈርስ እንዲወሰን ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካች በበኩሉ በራሱ ይዞታ ላይ እንጂ በተጠሪ ይዞታ ላይ ግንባታ እንዳላደረገ በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ክርክሩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የጎቡ ሰዮ ወረዳ ፍ/ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ሰምቶ በተጠሪ በኩል ከቀረቡት ምስክሮች ሁለቱ አመልካች ድንበር አልፎ የሰራዉ ቤት ፍሳሽ የተጠሪ ግድግዳ ላይ የሚፈስ ስለመሆኑ ሲመሰክሩ ሁለት ምስክሮች ማን ድንበር እንዳለፈ እንደማያዉቁ መስክረዋል፡፡በአመልካች በኩል የቀረቡት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምስክሮች አመልካች ድንበር አላለፈም በመካከላቸዉም 1ሜትር ክፍት ቦታ አለ በማለት በመመስከራቸዉ ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ አወሳሰን እንዲረዳ በባለሙያ ታይቶ ዉጤት እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ የወረዳዉ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ባለሙያ አጣርቶ አመልካች ወደ ተጠሪ ይዞታ 9ሳ.ሜ በ13ሜ በማለፍ የገነባዉ ቆርቆሮ ፍሳሽ በተጠሪ ግድግዳ ላይ እየፈሰሰ ጉዳት ማድረሱን መግለጫ በመስጠቱ አመልካች ወሰን አልፎ የሰራዉን እንዲያፈርስና በባለሙያ ተለክቶ1ሜ.በመራቅ እንዲገነባ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተሉ ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የግራቀኙ ምስክሮች ቃል ሲታይ የአመልካች ምስክሮች አመልካች ድንበር አለማለፉን ስለመመስከራቸዉ እና በባለሙያ ተለክቶ ከቀረበዉ ሪፖርት ይዘት ባላገናዘበ ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት አመልካች1ሜ.ገብቶ እንዲገነባ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በተጠሪ ከተጠየቀዉ ዳኝነት ዉጪ ነዉ በሚል ምክንያት ዉሳኔዉ እንዲታረም ጠይቋል፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በተጠሪ በኩል በተጠየቀዉ ዳኝነት መሰረት የተወሰነ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡በተጠሪ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በከተማ ፕላን መሰረት በመኖሪያ ቤት መካከል ያለዉ ርቀት 50ሳ.ሜ መሆኑ የሚታወቅ ስለመሆኑና አመልካች 75ሳ.ሜ ወደ ተጠሪ ግድግዳ ተጠግቶ በመስራቱ በድምሩ ከ1ሜ በላይ ስለሚሆን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካች በመልስ መልሱ ላይ ክርክር የተነሳበት ይዞታ የገጠር መንደር ስለሆነ በከተማ ፕላን መሰረት ሊታይ አይገባም በማለት የተጠሪ ክርክር ዉድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ይዘት ከላይ ባጭሩ ከላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን እንደመረመርነዉ አመልካችና ተጠሪ በይዞታቸዉ በድንበር የሚዋሰኑ መሆኑ አከራካሪ አይደለም ፡፡ተጠሪ ክስ ያቀረበዉ ከአመልካች በሚዋሰንበት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በምስራቅ በኩል አመልካች 50ሳ.ሜ ወደ ራሱ ይዞታ ገብቶ ግንባታ ማድረግ እየተገባዉ 75ሳ.ሜ ወደ ተጠሪ ይዞታ ገብቶ በመገንባቱ ከአመልካች ቆርቆሮ ጣሪያ ላይ የሚፈሰዉ ፍሳሽ በተጠሪ ግድግዳ ላይ እየፈሰሰ ጉዳት ስላደረሰ ይህንኑ እንዲያፈርስ ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካች ወደ ተጠሪ ይዞታ አልገባሁም በማለት የተከራከረ ቢሆንም ከግራቀኙ ምስክሮች ቃል ባሻገር የባለሙያ መግለጫ እንዳረጋገጠዉ አመልካች 9ሳ.ሜ ስፋት በ13ሜትር ቁመት ወደ ተጠሪ ይዞታ ገብቶ የገነባ ስለመሆኑና ከቤቱ ጣሪያ የሚወርደዉ ፍሳሽ የተጠሪ ግድግዳ ላይ እንደሚፈስና ጉዳት እንዳደረሰ ተገልጧል፡፡

ግራቀኙ የሚከራከሩበት ይዞታ የገጠር መሬት ይዞታ ሆኖ የመኖሪያ መንደር ላይ የተገነባ ቤት ወሰን አጠቃቀም የሚመለከት ስለመሆኑ ከክርክሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ስለሆነም ክርክር የተነሳበት ይዞታና ቤት የሚገኝበት ቦታ በከተማ አስተዳደር የተዋቀረ ባለመሆኑ ጉዳዩ በከተማ አስተዳደር ፕላን መሰረት የሚታይ ባይሆንም በፍ/ብ/ህጉ ስለንብረት አጠቃቀም መብትና ግደታዎች የተደነገገዉን ተመርኩዞ እልባት መስጠት የሚገባ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡በዚሁ አግባብ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1204 እና 1205 ላይ እንደተደነገገዉ ባለሀብቱ ሀብቱን በሚገባ ለመገልገል ሰፊ መብት ያለዉ ቢሆንም በህግ የተጣሉ ገደቦች እንደተጠበቁ ስለመሆኑ ያሥገነዝባል፡፡ከእነዚህ ገደቦች አንዱ በፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 1225/1/ ላይ እንደተመለከተዉ ባለሀብቱ በሀብቱ በሚገልገልበት ጊዜ የጎረቤቱ ርስት ጥቅም የሚቀንስበትን ወይም የሚጎዳበትን ማንኛዉንም ከመጠን ያለፈ ነገር ከመስራት መጠበቅ እንደሚገባ ያስገድዳል፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ወሰን በማለፍ ከገነባዉ ቤት ቆርቆሮ /ጣሪያ/ ላይ የሚፈሰዉ ፍሳሽ የተጠሪ ግድግዳ ላይ እየፈሰሰ ጉዳት ማድረሱ በስር ፍርድ ቤት በባለሙያ ታይቶ የተረጋገጠ ስለመሆኑ መዝገቡ ያሥረዳል፡፡ስለሆነም ይህ የአመልካች ድርጊት የተጠሪ ንብረት አጠቃቀም ላይ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ የህግ መሰረት ያለዉ ነዉ፡፡ከዚህ ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ተጠሪ የጠየቀዉ ዳኝነት እና በማስረጃ የተረጋገጠዉን መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡በመሰረቱ ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባዉ ከሳሽ ወገን በግልጽ ዳኝነት በጠየቀበት አግባብ እና በተከሳሽ እምነት ወይም በማስረጃ በተረጋገጠ ልክ መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ስ/ስ ህግ አንቀጽ 182፣224፣234፣242 እና 273 ድንጋጌዎች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ስለሆነም በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ክርክር ተጠሪ ክስ ያቀረበዉ አመልካች 75 ሳ/ሜ ወደ ተጠሪ ይዞታ ገብቶ የደረገዉን ግንባታ እንዲያፈርስ በሚል ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካች ወደ ተጠሪ ይዞታ አልገባሁም በሚል የተከራከረ ሲሆን አመልካች በራሱ ይዞታ ላይ የገነባዉ ቤት ጣሪያ ወደ ተጠሪ ይዞታ ወሰን አልፎ የገባዉ 9ሳ.ሜ ስፋት በ13ሜ.ቁመት መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ በዚሁ ልክ ዉሳኔ መስጠት እየተገባ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ቤቱን አፍርሶ አንድ ሜትር ገብቶ እንዲሰራ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ በተጠሪዉ ከተጠየቀዉ ዳኝነት ወጪ በመሆኑና ከፍ/ብ/ስ/ስ ህግ አንቀጽ 182/1/ድንጋጌ የሚጻረር በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/የጎቡ ሳዮ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ11244 ላይ በ26/03/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ ይህንኑ በማጽናት የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተል በመ/ቁ 46059 እና 277027 ላይ የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/አመልካች የተጠሪ ይዞታ ላይ ወሰን አልፎ የሰራዉ ቤት 9ሳ.ሜ.ስፋት በ13ሜ.ቁመት ያለአግባብ ወደ ተጠሪ ይዞታ የገባ ስለመሆኑ በባለሙያ በተረጋገጠዉ መሰረት ባለሙያ ባለበት ተለክቶ በዚሁ ልክ ወሰኑን ያለፈዉን ግንባታ እንዲያፈርስ በማለት ወስነናል፡፡

3ኛ/በዚህ ችሎት ተሻሽሎ በተወሰነዉ መሰረት እንዲያስፈጽም ለጎቡ ሳዮ ወረዳዉ ፍ/ቤት ግልባጭ ይተላለፍ ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡

4ኛ/በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 158899

ቀን - 26/03/2011

ዳኞች፡-ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ክብሮም አደራ -- ጠበቃ አስቻለው ሽፈራው ቀርበዋል

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሪት ትዕግስት መንገሻ --- ጠበቃ ኑር ሠይድ

2. አቶ አክሊሉ ወልዱ ---- ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በህግ የተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ሳይጠናቀቅ የተደረገ የኮንዶምንየም ቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ በሚል የቀረበን ክስ መነሻ በማድረግ የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በቅደም ተከተል 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 21/10/2008 ዓ.ም አዘጋጅታ ያቀረበችዉ ክስ ይዘትም በአጭሩ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከተማ ሰሚት ሳይት ከመንግስት ያገኘሁትን የኮንዶሚኒየም ቤት 1ኛ ተከሳሽ ወኪሌ ከነበረዉ 2ኛ ተከሳሽ ግንቦት 05 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገ ዉል የገዛሁት ነዉ በማለት ወደ ስሙ እንዲዞር ክስ መስርቶብኛል፤ ይሁንና የአዲስ አበባ ከተማ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባወጣው አዋጅ ቁጥር 19/97 መሠረት አምስት ዓመት ሳይሞላው የተደረገ በመሆኑ ምክንያት የሽያጭ ውሉ የህግ ተቃራኒ ነው ተብሎ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ዕጣው የደረሰው ሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም ሆኖ የሽያጭ ውሉ የተደረገው አምስት ዓመት ካለፈው በኋላ ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ 2ኛ ተጠሪም አመልካች ካቀረበው ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ክርክር በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የኮንዶሚኒም ቤት የደረሰው ሰው በሽያጭ ማስተላለፍ የሚችለው ቤቱን ከገዛ (በዕጣ ካገኘ) በኋላ አምስት ዓመት ሲሞላው ስለመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 65140 ላይ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ጊዜው መቁጠር የሚጀምረው ዕጣው ከደረሰ በኋላ መሆኑን፤ በዚህም መሠረት ለ1ኛ ተጠሪ ዕጣው የደረሰው ሚያዝያ 20/2002 ዓ.ም ሲሆን፣ የሽያጭ ውሉ የተደረገው ደግሞ ግንቦት 25/2007 ዓ.ም በመሆኑ ውሉ የህግ ተቃራኒ ነው ሊባል የሚችል አይደለም በማለት የቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ይግባኙ በ1ኛ ተጠሪ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዛችው ነሐሴ 28 ቀን 2002 ዓ.ም ሲሆን፣ የሽያጭ ውሉ የተደረገው ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ የሽያጭ ውሉ የተደረገው በአ/አበባ ከ/አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 19/97 ዓ.ም መሠረት የአምስት ዓመት ጊዜ ያልተጠናቀቀ መሆኑን፣ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዋቢነት የጠቀሰው የሰበር ውሳኔም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን ጠቅሶ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠን ውሳኔ በመሻር ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሽያጭ ውል ፈርሶ ግራ ቀኙ ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ ባለመቀበል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በቀን 22/09/2010 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበው አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ያስቀርባል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመባሉም ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ 1ኛ ተጠሪ ላቀረበችዉ የዉል ይፍረስልኝ ዳኝነት ጥያቄ መሠረት ያደረገችዉ ቤቱን የገዛችዉ ነሀሴ 28/2002 ዓ.ም ሲሆን የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ ግን ግንቦት 25/2007 ዓ.ም በመሆኑ በአ/አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 19/97 መሠረት አምስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ የተደረገ መሆኑን ሲሆን፤ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ዉሉ የተደረገዉ አምስት ዓመት ከሞላዉ በኋላ ነዉ በማለት የሚከራከሩት ቀኑ የሚቆጠረዉ ቤቱ በዕጣ ለ1ኛ ተጠሪ ከደረሰበት ከሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ እንጂ ዉሉ ከተደረገበት ከነሐሴ 28/2002 ዓ.ም ጀምሮ አለመሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ዕጣዉ ለ1ኛ ተጠሪ የደረሰዉ ሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም ሲሆን፣ ከመንግስት ጋር ዉል የተደረገዉ ነሐሴ 28/2002 ዓ.ም በመሆኑ ላይ ግራ ቀኝ ክርክር የላቸዉም፡፡ በመሆኑም ይህ የአምስት ዓመት ጊዜ የሚቆጠረዉ ዕጣዉ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ነዉ? ወይስ ዕጣዉ የደረሰዉ ሰዉ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ስምምነት ካደረገበት ቀን ጀምሮ ነዉ? የሚለዉ እልባት የሚያስፈልገዉ ጭብጥ ነዉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 19/97 የኮንዶሚኒየም ቤት የደረሰዉ ሰዉ ለ3ኛ ወገን በሽያጭ ሊያስተላልፍ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት ገዥዉ ጠቅላላ ዋጋዉን ከፍሎ ቢያጠናቅቅም፣ ቤቱን ለሦስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለዉ ቤቱን ከገዛ አምስት ዓመት ሲሞላዉ ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 14(2) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ይሁንና የቤት ግዥ ተፈጽሟል ሊባል የሚችለዉ ዕጣዉ ከወጣ በኋላ ነዉ ወይስ ዕጣዉን ተከትሎ ከሚመለከተዉ የአስተዳደሩ አካል ጋር ዉል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ ለሚለዉ ጥያቄ አዋጁ ምላሽ አይሰጥም፡፡ በመሆኑም ቤት ፈላጊዎችን ስለ መመዝገብ እና ቤቶችን ለቤት ፈላጊዎች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከማስተላለፍ ጋር በተያያዘ በአዋጁ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መወሰኑ አስፈላጊ ይሆናል። የከተማ አስተዳደሩ ቤት ፈላጊዎችን በአዋጁ በተመለከተዉ አግባብ ለይቶ ከመዘገበ በኋላ የከተማዉን አስተዳደር ቤቶች ለቤት ፈላጊዎች ስለሚያስተላልፍበት ሁኔታ አዋጁ በአንቀጽ 6 እና 7 ስር ይደነግጋል። በዚህም መሠረት የማስተላለፊያ መንገዶች ሁለት ሲሆኑ፣ የመጀመሪያዉ የቅድሚያ መብትን ከማግኘት ጋር በተያያዘ በአዋጁ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች ለሚያሟሉት ሰዎች ቅድሚያ በመስጠት ሲሆን፤ ሁለተኛዉ በዕጣ ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 6 እና 7(6-ለ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። በተለይም የአዋጁ አንቀጽ 7(6-ለ) "ኤጀንሲዉ ዕጣ አወጥቶ የሚገዛዉን ቤት ከለየ ቤት ፈላጊ ጋር ባዘጋጀዉ ዉል መሠረት እንዲፈራረም ለጽ/ቤቱ ወይም በሚፈረም መሠረታዊ ዉል መሠረት ለሌላ አግባብ ላለዉ አካል ዉክልና ይሰጣል" በማለት ይደነግጋል። በአጠቃላይ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለዉ፣ ዕጣ ከከተማዉ አስተዳደር ጋር የቤት ግዥ ዉል ለማድረግ መብት የሚሰጥ እንጂ እራሱ የቤት ግዥ ዉል አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ከዚህም አልፎ የአዋጁ አንቀጽ 7(11) ድንጋጌ፣ ቤት ግዥ ቅድሚያ ክፍያ ፈጽሞ የቤት ሽያጭ ዉል ከተፈራረመ በኋላ ለአበዳሪ ተቋም በዋስትና አስይዞ የቤቱ መግዣ ቀሪ ገንዘብ በተመለከተ ከአበዳሪ ተቋም ጋር ዉል እንደሚያደርግ ሲያመለክት፤ የአዋጁ አንቀጽ 9 የቤት ግዥ ዉል ከመፈረሙ በፊት ቤት ገዥዉ የቅድሚያ ክፍያ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል። በእነዚህ ሁለቱ ድንጋጎች ስር "የቤት ሽያጭ ዉል ከተፈራረመ" እንዲሁም "የቤት ግዥ ዉል" በሚል ከተገለጹት ሐረጎች መረዳት የሚቻለዉም፣ አንድ ሰዉ የኮንዶሚኒየም ግዥ ፈጽሟል ሊባል የሚችለዉ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ስምምነት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑን ነዉ። በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 14(2) ስር ገዥዉ ቤቱን ለሦስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለዉ ቤቱን ከገዛ 5 ዓመት ሲሞላዉ ነዉ በሚል የተቀመጠዉ ጊዜ የሚቆጠረዉ ዕጣ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን፣ ገዥዉ የቤት ሽያጭ ዉል ከሚመለከተዉ የመንግስት አካል ጋር ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ ነዉ ማለት ነዉ።

ከላይ እንደተገለጸዉ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ በአዋጁ የተመለከተዉ የአምስት ዓመት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ነዉ በሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰዉ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 65140 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመጥቀስ ነዉ፡፡ ይሁንና ሰበር ሰሚዉ ችሎት በተጠቃሹ መዝገብ ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ “ዉሉ ከተደረገበት ጊዜ” ካለ በኋላ በቅንፍ ዉስጥ “ዕጣ ከደረሰበት ጊዜ” ጀምሮ ያለ ቢሆንም፣ ጊዜዉ የሚቆጠረዉ ዉሉ ከተደረገበት ጊዜ ነዉ ወይስ ዕጣ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ነዉ የሚለዉን ነጥብ በጭብጥነት ይዞ ተገቢዉን ትንታኔ አልሰጠበትም፡፡ በመሆኑም ችሎቱ በአዋጁ አንቀጽ 14(2) ስር የተመለከተዉ የአምስት ጊዜ የሚቆጠረዉ ዕጣዉ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 መሠረት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የኮንዶሚኒየም ሽያጭ ዉል የተደረገዉ በአዋጁ አንቀጽ 14(2) ስር የተመለከተዉ የአምስት ዓመት ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ነዉ በሚል ምክንያት ሊፈርስ የሚገባዉ ነዉ በማለት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ፣ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 194652 በቀን 30/06/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ፤ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁጥር 156961 ላይ በቀን 09/09/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 155664

ጥቅምት 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 9 ኮ/ቤቶች ልማት ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡-አቶ ሻወል ወልዴ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የመንግስት ቤትን የሚመለከት ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን ጉዳይ በማየት ዉሳኔ መስጠታቸዉ ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በስር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 447 የሚገኘውን የመንግስት ቤት ከተከሳሽ ላይ ከ1967 ዓ/ም በፊት የከሳሽ ወላጅ አባት አቶ ወልዴ ብራሮ ተከራይተው እንደነበሩ፤የከሳሽ አባት እና እናት በዚሁ ለክሱ ምክንያት በሆነው ቤት ውስጥ አብረው ሲኖሩ ከሳሽን ጨምሮ 7 ልጆች እንደወለዱና ከሳሽ እዚሁ አከራካሪው ቤት የሚኖር መሆኑ ቤቱን የተከራዩት አባቱ መስከረም 1 ቀን 1982 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል፡፡ከሳሽ ወላጅ አባቱ ወራሽ መሆኔን በፍ/ቤት ተወስኖ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት ከእናቱ ጋር አብሬ የምኖር ስሆን እናቱ ከወንድሞቹና እህቶቹ ጋር 2 ክፍል እኔ ደግሞ 4 ክፍል ይዘን እየኖርንበት እንገኛለን፡፡ወላጅ አባቱ በሞት ከተለየ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በኋላ የኪራይ ውሉን በእናቱ ስም በማድረግ ገንዘብ እየሰጠሁኝ ኪራይ ስከፍል ቆይቻለሁ ቤቱንም እንዳይፈርስ ብዙ ገንዘብ በማውጣት አሳድሸዋለሁ፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ እናቱ ኮንደሚኒየም ቤት ስለደረሳት ተከሳሽ በ3 ቀናት ውስጥ ቤቱን እንድናስረክብ የማናስረክብ ከሆነ ግን ቤቱ እንደሚታሸግ የሚገልፅ ማስጠንቀቅያ የሰጠን በመሆኑ ይህን ተግባር በከሳሽ ላይ ሁከት መፍጠር ስለሆነ የተፈጠሩብኝ ሁከት እንዲወገድልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል ፡፡ ተከሳሽ ለቀረበው ክስ በሰጠው መልስ ከሳሽ አከራካሪ በሆነው ቤት መብት የለውም ፡፡አከራካሪ የሆነው ቤት ህጋዊ ተከራይ ወ/ሮ ፈለቀች ቂጫ ስለሆኑ እሳቸው ኮንደሚኒየም ቤት የደረሳቸው ስለሆነ ቤቱን ለቀዋል ስለሆነም በመመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 3/2007 መሰረት ቤቱ ለመንግስት ማስረከብ ስለሚገባቸው ይህን ለማስፈፀም ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ መስጠታችን የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክሱንና በግራ ቀኙ የቀረበውን ማሰረጃ ተመልክቶ እና አጠቃላይ ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ተከሳሽ ለከሳሽ አከራካሪው ቤት ለቀው እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሁከት ተግባር ስለሆነ ሁከት ሊወገድ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሲሚ ፍርድ ቤት እንዲሁም አቤቱታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቶቹ የአመልካችን አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዘውታል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በቀን 14/07/2010 ዓ/ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርቧል የአቤቱታው ይዘት፡- አከራካሪው የሆነው መኖሪያ ቤት ተከራይ የነበሩት የተጠሪ አባት ከሞቱ በኋላ ወደ ተጠሪ እናት ተላልፎ በተጠሪ እናት ስም ኪራይ ሲከፈልበት የቆየ ሲሆን የተጠሪ እናት ኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት ሲደርሳቸው ቤቱን ለአመልካች ማስረከብ ሲገባቸው ልጃቸው ለሆነው ተጠሪ እንዲኖሩበት መደረጉ እና የስር ፍርድ ቤቶችም ውሳኔ መስጠታቸው ከመመሪያው ውጪ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ መሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸውን ተለዋውጠዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር ችሎቱ ከተያዘው ጭብጥ፤ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው አከራካሪው የሆነው በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 447 የሚገኘውን የመንግስት ቤት ተከራይ የነበሩት የተጠሪ (ከሳሽ) ወላጅ አባት አቶ ወልዴ ብራሮ እንደነበሩ እሳቸው በ1982 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የኪራይ ውሉ የከሳሽ እናት ወደ ሆኑት ወ/ሮ ፈለቀች ጫካ እንደተዛወረ የኪራይ ውሉም በሳቸው ስም እንደሚከፈል ተጠሪ ከነ ቤተሰቦቹ በተጠቀሰው ቤት ውስጥ የሚኖር መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

የመንግስት ቤቶች ለማስተዳደር የወጣው መመሪያ ቁጥር 3/2007 ስር እንደተመለከተው ማንኛውም የመንግስት ቤት ተከራይ የኮንደሚኒየም ቤት ባለእድል ሲሆን ቤቱን ለቆ ማስረከብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መነሻ ያደረገው ነጥብ ተጠሪ በአባታቸው በኩል የተከራይነት መብት አላቸው በማለት ሲሆን በመመሪያው እንደተጠቀሰው ወላጅ አባት ሲሞት የተከራይ መብት ወደ እናት (ሚስት) እንደሚተላለፍ የሚያሳይ ነው ። በዚህ መሰረትም የቤቱ ተከራይ የነበሩት አቶ ወልዴ ብራሮ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ባለቤታቸው የሆኑት ወ/ሮ ፈለቀች ጫካ ህጋዊ ተከራይ እና የኪራይ ገንዘቡም በስማቸው የሚከፈል መሆኑ ተጠሪ ግን ቤቱ ውስጥ መኖሩ እንጂ ከአመልካች ጋር ህጋዊ ውል ያለው ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃም ሆነ ክርክር የለም ። ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 4/2009 ዓንቀፅ 15(ሐ(መ)) ውሉ ከኔ ጋር እንዲቀጥል ይደግፈኛል በማለት ሲሆን ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት እንደቻልነው በነበረው መመሪያ መሰረት ወላጅ አባት ሲሞት የተከራይ መብት ወደ እናት (ሚስት) እንዲተላለፍ የሚፈቅድ መሆኑ ፣ በዚህ መሰረትም የቤቱ ተከራይ የነበሩት አቶ ወልዴ ብራሮ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ባለቤታቸው የሆኑት ወ/ሮ ፈለቀች ጫካ ህጋዊ ተከራይ እና የኪራይ ገንዘቡም በስማቸው የሚከፈል መሆኑ ተጠሪ ግን ቤቱ ውስጥ መኖሩ እንጂ ከአመልካች ጋር ህጋዊ ውል የሌለው መሆኑ የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 2/2010ም ሆነ ከዚሁ ከተሻሻለው መመሪያ በፊት የነበረው መመሪያ የቤት ተከራይነት መብት ለልጅ የሚተላለፈው ህጋዊ ተከራይ የሆነው ወላጅ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ እንጂ ኮንደሚኒየም ደርሶት ቤቱ ሲለቅ ባለመሆኑ በተያዘው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳይ ህጋዊ ተከራይ የነበሩት የተጠሪ እናት ወ/ሮ ፈለቀች ጫካ ኮንደሚኒየም ቤት አግኝተው ከተከራዩት ቤት ከለቀቁ ቤቱ በመመሪያው መሰረት አከራይ ለሆነው አመልካች መመለስ አለባቸው፡፡ ስለሆነም አከራካሪ የሆነውን የመንግስት ቤት ህጋዊ ተከራይ የሆኑት የተጠሪ እናት በመሆናቸው እሳቸው የኮንደሚኒየም ቤት ከደረሳቸው ከመንግስት የተከራዩት ቤት ለመንግስት የማስረከብ ግዴታ ያላቸው በመሆኑ እና ተጠሪ አከራካሪው ቤት በተመለከተ መብት ያለው መሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ አመልካች ለከሳሽ አከራካሪውን ቤት ለቀው እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ህጋዊ ተግባር ነው፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሁከት ተግባር ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ሰበር ችሎት በመ.ቁጥር 27641 ታህሳስ 16 ቀን 2010 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በማፅናት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች አከራካሪውን ቤት በተመለከተ የሰጠው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር አይደለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 141625

ሐምሌ 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አድና መላኩ

ተጠሪ፡- የወልዲያ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ከክልሉ ፍትህ ቢሮ ፍሬህይወት አበባቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0104064 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም ጉዳዩ በቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የሰጠውን ብይን ፣የሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 19155 በቀን 27/04/2009 ዓ.ም በፍርድ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 03-16739 በ27/06/2009 ዓ/ም በትእዛዝ በማጽናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የዳኝነት ሥልጣንን የሚመለከት ሲሆን በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱ ይዘትም፡- በወልዲያ ከተማ 06 ቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኘውና አዋሳኙ በክሳቸው የተጠቀሰው ቦታ እንዳላቸውና በዚህ ቦታ ላይ ቤት ያላቸው፣ ባህር ዛፍና ሁለት እግር ጽድ ያፈሩ መሆኑን ይዞታውን ለረዥም ጊዜ ይዘው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚገኙበት ሁኔታ ተጠሪ ህግና መመሪያን መሰረት ሳያደርግ፣ ለአመልካችም 500 ካ/ሜትር ይዞታ ሳይጠብቅላቸው ቦታውን እየሸነሸነ ለግለሰቦች እየሰጠ እንደሚገኝ፣ በቦታው ላይ የሰሩትን ቤት ያለምንም ምክንያት በዶዘር መጋቢት ወር 2007 ዓ/ም ያፈረሰባቸውና አቤቱታቸውን ለሚመለከተው አካል አቅርበው የሚመለከታቸው አካላት እንደማንኛውም ባለይዞታ 500 ካ/ሜትር ይዞታ ለአመልካች እንዲጠበቅላቸው አስተዳደራዊ ውሳኔ የሰጡ መሆኑንና በዚህ አግባብ እንዲወሰንላቸው ለተጠሪም ሆነ ለሚመለከተው አካል አመልክተው መፍትሔ ያላገኙ መሆኑን ገልጸው ለክሱ ምክንያት ከሆነው ነባር ይዞታ ላይ 500 ካ/ሜት እንዲጠበቅላቸው፣ ከሕግ ውጪ በዶዘር ለፈረሰባቸው ቤት ግምት ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር)፣ የባህር ዛፉና የፅዱ ግምትም እንዲከፈላቸው እንዲሁም ከ500 ካ/ሜትር በላይ ላለው ይዞታም ካሳ እንዲከፈላው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 እና በአዋጅ ቁጥር 455/97 መሰረት በፍርድ ቤት በቀጥታ ክስ የሚታይ ያለመሆኑን፣ አመልካች በቦታው ላይ መብት የሌላቸው መሆኑንና ሌሎች የክርክር ነጥቦችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ስልጣንን መሰረት አድርጎ የተነሳውን የተጠሪን መቃወሚያ መርምሮ አመልካች የከተማ ቦታ ይዞታን እንዲለቁ የተደረጉ በመሆኑ ጉዳዩ መታየት ያለበት በከተማ አስተዳደሩ ስር ለተቋቋመ የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አካል ነው እንጂ ለፍርድ ቤት አይደለም የሚል ምክንያት አስፍሮ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በቀጥታ ክስ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ሲል በብይን የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ተገቢ ነው በማለት አጽንቶታል፡፡ በመጨረሻም አመልካች የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው በአጣሪው ችሎት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የአመልካች ክስ መሰረታዊ ይዘት ከሕግ ውጪ የተወሰደው ቦታና የወደመው ንብረት በሕጉ አግባብ ታይቶ ባለይዞታነታቸው መብት እንዲጠበቅላቸውና ለወደመው ንብረት ደግሞ ካሳ እንዲከፈል የሚያሳይ ሁኖ እያለ የክሱን መሰረታዊ ይዘት ሳይገነዘቡ ጉዳዩ በቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካች በሕገ ወጥ መንገድ ቦታዬ ተወስዶአል፣ ንብረቴም ወድሟል በማለት ያቀረቡት ክስ በአስተዳደራዊ መልኩ ብቻ የሚታይ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና የሊዝ ደንብ ቁጥር 103/2004 በመጥቀስ የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክር ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች ከነባር ይዞታቸው ውስጥ በሕጉ አግባብ ሊጠበቅላቸው የሚገባው ይዞታ መብት ያልተጠበቀላቸው መሆኑንና በይዞታው ላይ የነበሩ ንብረቶችም ኪሳራ ሳይከፈላቸው በዶዘር የወደሙባቸው መሆኑን ጠቅሰው ክስ የመሰረቱ መሆኑን፣ ተጠሪ የሚከራከረው ደግሞ ጉዳዩ ከህግ ውጪ የተያዘውን የከተማ ቦታ የማስለቀቅ ጉዳይ በመሆኑ ለተጠሪ በሕጉ ከተሰጠው ስልጣን አንፃር ጉዳዩ የከተማ ቦታን ማስለቀቅ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ አካል ከሚቀርብ በስተቀር በቀጥታ ክስ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

ፍርድ ቤቶች በህግ የሚቋቋሙ በመሆናቸው የዳኝነት ስልጣናቸው የሚመነጨውም ከህግ ነው፡፡ የማንኛውም ፍርድ ቤት ስልጣን በህግ ተወስኖ የሚሰጥ በመሆኑ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ተቀብሎ ከማስተናገዱ በፊት ጉዳዩን /ክሱን/ ለማየት በህግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ በህግ የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረ የሚሰጥ ውሳኔ የህግ መሰረት ያለው ነው ለማለት አይቻልም፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የጠየቁት ዳኝነት ከነባር ይዞታቸው ውስጥ 500 ካ/ሜትር እንዲጠበቅላቸውና በይዞታው ላይ የነበረው ንብረትም ከሕግ ውጪ በመወደሙ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ ተጠሪም ይዞታውን ከሕግ ውጪ በመያዙ መውሰዱንና አመልካች በሕግ አግባብ የያዙት ይዞታ ደግሞ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠበቀላቸው መሆኑን ገልጸ ጉዳዩ የከተማ ቦታን ከማስተዳደር ስልጣኑ ጋር የተያያዘና በከተማ ቦታ ማስለቀቅ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ አካል ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለት የሚከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ ካሳን አስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችና ይግባኝ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 11 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በከተማ አስተዳደር የከተማ መሬት ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ካለ ካሳውን አስመልክቶ የሚቀርበው ቅሬታ ለዚህ አስተዳደራዊ አካል የሚቀርብ ስለመሆኑ ሕጉ የሚደነግግ ሲሆን የከተማው አስተዳደራዊ አካል ካሳውን አስመልክቶ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ እንደሚችልም ሕጉ ደንግጎ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑም ሕጉ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በአዋጁ መሰረት ይዞታው የተወሰደው ያለአግባብ ነው በሚል መሬት እንዲለቀቅ በተላለፈው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ በአዋጁ ውስጥ አልተካተተም፡፡

የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 በአንቀፅ 26(1) ስር አግባብ ያለው አካል ከቦታው ለሚነሳው ንብረት ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ እንዲከፈል በማድረግ የከተማ ቦታ ይዞታን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የማስለቀቅና የመረከብ ስልጣን እንደሚኖረው ሲደነግግ በተጠቃሹ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር አራት ስር ደግሞ አግባብ ያለው አካል በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታ በአዋጁ አንቀጽ 27 መሰረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ በመስጠትና ካሳ መክፈል ሳያስፈልግ የሰባት ቀናት የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ስልጣን እንደሚኖረው ተመልክቶአል፡፡ የማስለቀቂያ ትዕዛዝን ወይም ማስጠንቀቂያ የሚመለከቱ አቤቱታዎች አቀራረብን በተመለከተም አዋጁ በአንቀጽ 28 ስር ያሰፈረ ሲሆን በአቤቱታዎች ላይ ስለሚኖረው ይግባኝም በአዋጁ አንቀፅ 29 ስር ሰፍሮ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 721/2004 በሕገ ወጥ መንገድ የተያዙ የከተማ ቦታዎችን እንዲለቀቁ የሚደረግበት ስርዓት በግልጽ የተመለከተ ሲሆን አግባብ ያለው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ለይግባኝ ሰሚው ጉባኤው ማቅረብ እንደሚችል ሕጉ መደንገጉ ጉዳዩ በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት የሚሄድበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው አካል ጉዳዩን የሚያስተናግደውም አቤቱታው በቅድሚያ መሬቱን እንዲለቅ ትዕዛዝ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለሰጠው አካል ቀርቦ መስተናገዱ ሲረጋገጥ መሆኑን በአዋጁ የከተማ ቦታን ማስለቀቅ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ የተዘረጋው ስርዓት ያስገነዝበናል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ክሱን የመሰረቱት የነባር ይዞታ ባለመብትነት እንዲጠበቅላቸውና በተጠሪ የወደመ ንብረት ካሳ እንዲከፈላቸው ሲሆን የክሳቸው መሰረታዊ ይዘት የሚያስገነዝበውም የነባር ይዞታ መብትን የሚመለከቱ ህጎች የጠበቁላቸው መብቶች ሳይከበሩላቸው ሕጉቹ ተጥሰው ይዞታው የተወሰደባቸው መሆኑንና ይዞታው ሲወሰድም በላዩ ላይ የሰፈረው ንብረት የወደመባቸው መሆኑን በመሆኑ ነባር ይዞታን የሚመለከቱ ሕጎችንና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2035 ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ጥያቄአቸውን መመርመርን የግድ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ የከተማ ይዞታን የማስተዳደር ስልጣን በሕጉ አግባብ የተሰጠው ቢሆንም ስልጣንን እና ኃላፊነቱን በሕጉ አግባብ አልተወጣም የሚል ክርክር ያለው ወገን ግን ጉዳዩን በፍርድ ቤት ወስዶ መብቱን ከማስከበር የሚከለከል ያለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37፣ 40(3)(4)፣79(1) እና 78(4) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

አመልካች ክሳቸውን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርቡ የቻሉትም የሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት የነባር ይዞታ ባለመብትነታቸው እንዲጠበቅላቸው አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥተው እያለ ተጠሪ ውሳኔውን ባለማክበሩ ምክንያት መሆኑን ከክሳቸው መግለፃቸው ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀፅ 26ከ፣ 27 እና 28 ድንጋጌዎች በተመለከተው አካል በሚመለከተው አካል በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ አላቸው ለማለት የማያስችል በመሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ በተዘረጋው የይግባኝ ጉባኤ መብታቸውን ማስከበር አለባቸው ሊባሉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ይልቁንም እሚመለከተው አካል መስኖባቸው እያለ በተጠሪ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ሕጎቹ ተጥሰው የይዞታና የንብረት መብታቸው እንደተነካባቸው አመልካች በክሳቸው መጥቀሳቸውና ተጠሪም በሕጉ አግባብ ስልጣኑን በመጠቀም የወሰደው እርምጃ መሆኑን ጠቅሶ መከራከሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246፣ 247 እና 248 ድንጋጌዎች አግባብ የተጠሪ እርምጃ ሕጉን ተከትሎ የተከናወነ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን ማጣራትን የግድ የሚል በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 ወይም አዋጅ ቁጥር 455/97 ድንጋጌዎች አግባብ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት በቀጥታ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ስለሆነም ከአመልካች ክስ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ ይዘት ስንነሳ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይንም ሆነ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ብይን በማጽናት የተሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል። በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0104064 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 19155 በቀን 27/04/2009 ዓ.ም በፍርድ፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 03-16739 በ27/06/2009 ዓ/ም የጸናው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል።
2. የወልዲያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0104064 ክርክሩን እንዲቀጥል በማድረግ ከስልጣን ውጪ የቀረቡትን የግራ ቀኙን ሌሎች የክርክር ነጥቦችን በመመርመርና በማጣራት ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1 መሰረት መልሰን ልከንለታል። ይጸፍ።
3. በዚኅ ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/144901

ሐምሌ 12 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ኢትዮቴሌኮም የሰሜን ምስራቅ ሪጅን

ተጠሪ፡- ወ/ሮ በለጡ ወልደ ተገኝ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ የተከለዉን ኮንቴነር እንዲያነሳ የቀረበዉን ክስ መነሻ በማድረግ የአማራ ክልል ጠ/ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪ ይዞታ ለተጠቀመበት ተገቢዉን ካሳ እንዲከፍል መወሰኑን ተከትሎ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል እንዲታረም የቀረበ አቤቱታ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ ክርክሩ የተጀመረዉ በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ያቀረበችዉ ክስ ይዘት ባጭሩ ያለተጠሪ ፈቃድ ለጊዜዉ ነዉ በሚል አመልካች በተጠሪ ይዞታ ዉስጥ ገብቶ የቴሌ ሳጥን/ኮንቴነር/ በመትከሉ ይዞታየን ለመጠቀም አልቻልኩም በሚል ያጣሁትን ጥቅም ግምት ብር 20,700 ከፍሎ ሳጥኑን እንዲያነሳ እንዲወስን በማለት ዳኝነት የጠየቀች ሲሆን አመልካች በበኩሉ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለዉም የሚልና ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚላቸዉን መከራከሪያዎች አንስቶ በፍሬነገር ረገድም ሳጥኑ የተተከለዉ በከተማ አስተዳደር ተፈቅዶ ስለመሆኑ ገልጾ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ጉዳን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን ያከራከረዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን የመጀመሪያ መቃወሚያ ዉድቅ ካደረገ በኋላ ስለጉዳዩ ከከተማዉ አስተዳደር መግለጫ ጠይቆ ከተማዉ አስተዳደር አመልካች የተጠሪ ይዞታ ዉስጥ ገብቶ 9.20 ካ.ሜ ተጠቅሞ የቴሌ ሳጥን መትከሉንና በዚህ ይዞታ ላይ እንዲተክል ከተማ አስተዳደሩ እንዳልፈቀደለት ስላላረጋገጠ አመልካች ለተጠቀመዉ ቦታ በአካባቢዉ የሊዝ ዋጋ ለተጠሪ እንዲከፍል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ለተጠሪ በአዋጅ 49/89 እና 455/97 መሰረት ካሳ የመክፈል ግደታ አለበት በሚል ካሳ መጠን ላይ የስር ፍርድ ቤት አጣሪቶ እንዲወስን መልሶለታል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የዳኝነት ስልጣን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤት የቀረበዉ መቃወሚያ መታለፉ ተገቢ አለመሆኑ፣ክሱ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ እና በፍሬነገር ረገድ አመልካች ክስ ያቀረበችበት ይዞታ ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ የተፈቀደ ሆኖ አመልካች ኋላ ላይ በቆርቆሮ አጥር ወደ ይዞታዋ ያስገባች ስለመሆኑ የተተከለዉ ሳጥን በከተማ አስተዳደር ተፈቅዶ በቋሚነት የሚቀመጥ እንጂ በጊዜያዊነት አለመሆኑንና ተጠሪ ኮንቴነሩ እንዲነሳ ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢነት እንደሌለዉ በመዘርዘር በመጨረሻም ተጠያቂዉ የከተማዉ አስተዳደር መሆን አለበት በሚል የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲታረም ጠይቋል፡፡የአመልካች ሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አከራካሪዉ መስመር የተዘረጋዉ ከ5 ዓመት በፊት መሆኑንና ተጠሪ ይዞታዉን ከዚያ በኋላ አስፋፍተዉ የያዙት ነዉ በማለት አመልካች ያቀረበዉ ክርክር በስር ፍርድ ቤት መታለፉን አግባብነት ለመመርመር ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲትሰጥ ተደርጓል፡፡ተጠሪ መጥሪያ ተልኮላት መልስ አላቀረበችም፡፡በዚሁ መልስ የማቅረብ መብት ታልፎ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡

መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ አመልካች ክስ በቀረበበት ይዞታ ላይ ኮንቴነር መትከሉ አልተካደም፡፡አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ በአዋጅ ቁ/49/89 መሰረት ጉዳዩ መታየት ያለበት በራሱ በአመልካቹ ድርጅት መሆን እንዳለበትና ድርጊቱም የህግ ድጋፍ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያለዉ ስለመሆኑ ነዉ፡፡ በመሰረቱ ማንኛዉም የቴሌኮሙንኬሽን ድርጅት የቴሌኮሙንኬሽን መስመር ሲዘረጋ የከተማዉን ፕላን ተከትሎ የመዘርጋት ሃላፊነት እንዳለበት የቴሌኮሙንኬሽን አዋጅ ቁ/49/89 አንቀጽ 22/2/ በግልጽ ያስገነዝባል፡፡ከዚህ ባሻገር መስመሩ የባለይዞታን ወይም የሌላ ህንጻ ላይ የሚዘረጋበት አስገዳጅ ሁኔታ ሲኖር አስቀድሞ ለባለይዞታዉ ወይም ለባለህንጻዉ በማስታወቅ የባለይዞታዉ ወይም የባለህንጻዉ ተቃዉሞ እንዳለ ሰምቶ ተገቢዉን የመወሰን ስልጣን ለኤጀንሲዉ የተሰጠ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 18 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ዉስጥ ገብቶ ኮንቴነር መትከሉና ይዞታዉ የተጠሪ ህጋዊ ይዞታ ስለመሆኑ ደግሞ የከተማዉ አስተዳደር ያረጋገጠ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነዉ ፡፡አመልካች ኮንቴነር የተከልኩት በከተማዉ አስተዳደር ፈቃድ ነዉ በማለት የተከራከረ ቢሆንም ከተማዉ አስተዳደር አመልካች ኮንቴነር የተከለበት ይዞታ የተጠሪ የግል ይዞታ እንጂ ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ የተፈቀደ ይዞታ አይደለም በማለት ምላሽ መስጠቱንም በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነዉ፡፡ስለሆነም አመልካች ኮንቴነር ከተከለ በኋላ ተጠሪ ቦታዉን አስፋፍተዉ በመያዝ ወደ ይዞታዋ አስገብታለች የሚለዉ ነጥብ የፍሬነገር ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳና በማስረጃ ያልተረጋገጠ ፍሬነገር በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበዉ ክርክር ተገቢነት ያለዉ ሆኖ አላገኘንም ፡፡ አመልካች በአዋጁ መሰረት ጉዳዩ በኤጀንሲዉ በኩል እንዲታይ ለማድረግም አስቀድሞ ለተጠሪ የሰጠዉ ማስታወቂያ ስለመኖሩ ካለማስረዳቱም በተጨማሪ ጊዜያዊ ነዉ እያለ ተጠሪ እንዲጠባበቁ ያደረገ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ክርክር የተቀረበበት ነዉ፡፡

በመሆኑም አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ የተከለዉ ኮንቴነር በቋሚነት የሚቀጥል እስከሆነ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 20/1/ መሰረት ተገቢዉን ካሳ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ስለዚህም የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠዉን ፍሬነገር መሰረት በማድረግ አመልካች ለተጠቀመበት የተጠሪ ይዞታ ተገቢዉን ካሳ እንዲከፍል ዉሳኔ መስጠቱና የካሳዉ መጠን ተጣርቶ እንዲወሰን ለስር ፍርድ ቤት መመለሱ በአዋጅ ቁ/49/89 አንቀጽ 20/1/ እና አዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 6 መሰረት ተገቢ ሆኖ ስላገኘን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉሳኔዉ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚህ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉ ሳ ኔ፡፡

1ኛ/የአማራ ብ/ክ/ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/01-0471 በ03/09/09 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ በጥር 9 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ እግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ.137704
የካቲት 14 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1.ዳኜመላኩ
2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
3. ቀነዓ ቂጣታ
4. ተሾመ ሽፈራው
5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ መሀመድ ከማል - ቀርበዋል
ተጠሪ፡- አቶ በቀለ ወልዴ - ከጠበቃ አቶ ምስጋኑ ሙለታ ጋር ቀርበዋል፡፡

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በሌለሁበት የተሰጠ ፍርድ እንዲነሳልኝ የሚል አቤቱታ መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.06184 በ8/3/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣የአሁን አመልካች ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ፣በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ 2ኛ ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ታህሳስ 9 ቀን 2007 ዓ.ም የተደረገዉ የድርጅት ሽያጭ ዉል እንዲፈጸምልኝ በማለት በጠየቀዉ ዳኝነት፣ 1ኛ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጎ፣ 2ኛ ተከሳሽ እንደዉሉ ቢፈጸም አልቃወምም በማለታቸዉ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በመ.ቁ.18073 በ4/7/2007 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ በ8000 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈዉ የዱቄት ፋብሪካ ከነመገልገያ ማሽኖቹ ጭምር ታህሳስ 9 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ዉል መሰረት ለከሳሽ እንዲፈጸም በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ዉሳኔ ተከትሎ 1ኛ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ ባቀረበዉ አቤቱታ የፍ/ቤቱ መጥሪያ እንዲደርሰኝ ተገቢ ጥረት አልተደረገም፣ መጥሪያ አልደረሰኝም፣ ክርክሩን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስላልሰማሁት ተከሳሽ በሌለሁበት በጋራ ንብረት ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 መሰረት እንዲነሳልኝ በማለት አመልክቷል። በዚህ አቤቱታ ላይ ከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ተከሳሽ በቀበሌ በኩል መጥሪያ ተልኮለት በቀበሌዉ እንደሌለ አረጋግጦ ጽፏል፤ በአዲስ ዘመን ጋዜጣም ጥሪ ተደርጎለታል፣ የፍ/ቤቱ መጥሪያ ለ1ኛ ተከሳሽ ሚስት ለሆነችዉ ለ2ኛ ተከሳሽ ደርሷት ቀርበ ስለተከራከረች መጥሪያ ለእርሱም እንደደረሰ ይቆጠራል፤ ተከሳሽ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ ላይ ላቀረበዉ ክስ ከመልስ ጋር የሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በማያያዝ ግንቦታ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ስለተሰጠ ተከሳሽ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ዉሳኔዉን ያወቀ ስለሆነ አቤቱታ ያቀረበዉ በ23/10/2007 ዓ.ም ስለሆነ ዉሳኔዉን ካወቀ ከ3 ወር በኋላ ስለሆነ አቤቱታዉ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል።

የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ብይን 1ኛ ተከሳሽ መጥሪያ በቀበሌ በኩል ቢላክለትም በቀበሌዉ እንደማይኖር ቀበሌዉ ደብዳቤ ጽፏል፤ በጋዜጣም ጥሪ ተደርጎለት አልቀረበም፤ በዚህ ጉዳይ የተከሳሽ ባለቤት የሆነችዉ ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ ቀርባ ስለተከራከረች ተከሳሽም ክርክሩን እንደሰማ የሕግ ግምት ያስወስዳል፤ ተከሳሽ ክርክሩን የሰማሁበት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከመልስ ጋር በቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ ነዉ የሚባል ከሆነ ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም አዉቋል ስለሚያስብል 1ኛ ተከሳሽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 መሰረት አቤቱታዉን ያቀረበዉ ሰኔ 23 ቀን 2007 ዓ.ም ስለሆነ ይህ ደግሞ ከሁለት ወር በላይ ስለሆነ አቤቱታዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 /1/ መሰረት በአንድ ወር ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል። የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበላቸዉን ቅሬታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች የካቲት 7 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ፣ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.162148 ላይ በነበረን ክርክር በሌለሁበት ዉሳኔ መሰጠቱን ያወቅኩት ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ሳይሆን ግንቦት 22 ቀን 2007 ዓ.ም ትዕዛዙ በደረሰኝ ጊዜ ነዉ። እኔ በሌለሁበት ዉሳኔ መሰጠቱን እንዳወቅኩኝ ሰኔ 13 ቀን 2007 ዓ.ም በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳልኝ ለሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረብኩኝ ቢሆንም የፍ/ቤቱ ሰራተኞች እስከ ሰኔ 22 ቀን 2007 ዓ.ም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በስብሰባ ላይ የነበሩ በመሆኑ በዚህ ምክንያት ሊዘገይ መቻሉን እየተከራከርኩኝ የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ሳይቀበሉ መወሰናቸዉ ተገቢ አይደለም። አመልካች በባለቤቱ በኩል ክርክር እንዳለ ያዉቃል ለተባለዉ ከባለቤቱ ጋር ተጣልቼ የነበረ እና ባለቤቱ ይህን ድርጅት አሳግዳዉ የነበረ ሲሆን ከተጠሪ ጋር በመመሳጠር እግድ እንዲነሳ በማድረግ ስም ዝዉዉር እንዲደረግ አድርጓል። የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ክርክር እንዳለ ያዉቃል በማለት የጠቀሱት በማስረጃ ባልተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ፣የሥር ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ፣ በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተነስቶ ተገቢ መከራከሪያ አቅርቤ ዉሳኔ እንዲሰጥ በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች ከሚስቱ ጋር በጋብቻ ፍቺ ክርክር ጋር ባለበት ሚስቱ መጥሪያዉ ደርሷታል ጉዳዩን ታዉቃለች በመሆኑም አመልካችም ጉዳዩን ያዉቃል ተብሎ ግምት ተወስዶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 መሰረት የቀረበዉን የአመልካች ጥያቄ ዉድቅ የመደረጉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ16/5/2010 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አመልካች ያቀረበዉ በማስረጃ ያልተረጋገጠ እና አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር ተቀባይነት የሌለዉ ስለሆነ ዉድቅ ሆኖ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች መጥሪያ ሳይደርሰኝ በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ ያደረገዉ በቀበሌዉ እንደሌለ ተረጋግጧል፣ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት አልቀረበም፣ በሚስቱ ቀርባ ስለተከራከረች ክርክሩን እንደሰማ በሕግ ግምት ይወሰዳል፣ ዉሳኔዉን ካወቀዉ ከአንድ ወር በላይ ስለሆነ አቤቱታዉ ተቀባይነት የለዉም በሚሉት ምክንያቶች መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል።

እንደሚታወቀዉ ስለመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት በተመለከተ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 94--110 ድንጋጌዎች ሥር ተመልክቷል። ከእነዚህ ድንጋጌዎች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አቀራረጽና ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ የመጥሪያ አደራረስ ሂደት በቅድም ተከተል አራት ደረጃዎች እንዳሉት የሚያሳይ መሆኑን ነዉ፡፡ እነዚህም አንደኛ መጥሪያዉን ለተከሳሹ ለራሱ ማድረስ /የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.95 /3/፣ ሁለተኛ መጥሪያዉን ለተከሳሹ ሊሰጥ ይችላል ተብሎ ለሚገመት ሰዉ ማድረስ /አንቀጽ 99-101/፣ ሶስተኛ በፖስታ በኩል ለተከሳሽ እንዲደርሰዉ በማድረግ /አንቀጽ 106/፣አራተኛ በምትክ የመጥሪያ አደራረስ ዘዴን በመጠቀም ለተከሳሹ እንዲደርሰዉ ማድረግ እንደሚቻል /አንቀጽ 105/ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የመጥሪያ አደራረስ ዘዴዉ ወይም ሥርዓት በዚህ ቅደም ተከተል ካልተፈጸመ ለተከሳሹ መጥሪያዉ በሕጉ አግባብ ደርሶታል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለአመልካች መጥሪያ እንዲደርሰዉ የወሰደዉን እርምጃ ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ቀድም ሲል ሲኖርበት የነበረዉን ቀበሌ ዉስጥ እንደማይኖር የተረጋገጠ በመሆኑ እና ከተጠሪ ጋር በፌዴራል ፍ/ቤት ክርክር ላይ እንደነበሩ የሚታወቅ ስለሆነ፣ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለአመልካች በአድራሻዉ እንዲደርሰዉ ተገቢዉን ጥረት እንዲያደርግ ማድረግ ነበረበት፡፡ ፍ/ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ የመጥሪያ አደራረስ ዘዴ በአግባቡ ሳይፈጸም አራተኛ ደረጃ የመጥሪያ አደራረስ ዘዴ ማለትም ምትክ የመጥሪያ አደራረስ ዘዴ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ማድረጉን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ የሥር ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.95 /3/ በሚደነግገዉ መሰረት የአሁን አመልካች ክርክሩን አዉቀዉ ቀርበዉ መከራከሪያዉን እንዲያቀርብ ተጠሪ መጥሪያዉን ለአመልካች ለራሱ እንዲያደርስ ተገቢዉን ጥረት እንዲያደርግ ማድረግ ሲገባዉ ይህ ሳይደረግ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ማድረጉ ከላይ የተመለከቱትን የሥነሥርዓት ሕጎችን የተከተለ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የፍ/ቤቱ መጥሪያ ለአመልካች እንዲደርሰዉ ተገቢዉ ጥረት ሳይደረግ በጋዜጣ ጥሪ መደረጉ በሕግ የተመለከተዉን የመጥሪያ አደራረስ ዘዴን ያልተከተለ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የፍ/ቤቱ መጥሪያ በሕጉ አግባብ ለአመልካች ደርሶታል ክርክሩን አዉቆታል የሚያስብል አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካች ሚስት የነበረችዉ የሥር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ በዋናዉ ጉዳይ ቀርባ እስከተከራከረች ድረስ አመልካች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክርክሩን እንዳወቀ የሕግ ግምት ያስወስዳል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አደርጓታል፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ በዚህ ጉዳይ አመልካች እና ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ ሁለቱም ተከሳሾች የነበሩ ስለሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.95/2/ መሰረት ለእያንዳንዳቸዉ መጥሪያ እንዲደርሳቸዉ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በዚህ አግባብ ትዕዛዝ በመስጠት የሥር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ ለአመልካች የተላከዉን መጥሪያ ፈርማ መቀበሏን የሥር ዉሳኔ የሚያመለክተዉ ነገር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ለአሁን አመልካች የተላከዉን መጥሪያ ለወ/ሮ ዘምዘም ስለመሰጠቱ ሳያረጋግጥ ወ/ሮ ዘምዘም ራሳቸዉ ተከሳሽ ስለነበሩ መጥሪያ ደርሷቸዉ ቀርበዉ ስለተከራከሩ አመልካችም ክርክሩን እንደሚያዉቅ የሕግ ግምት እንደሚያስወስድ በመግልጽ መወሰኑ የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.101 ሥር እንደተመለከተዉ የፍ/ቤት መጥሪያ የተላከለትን ተከሳሽ ማግኘት ያልተቻለ ወይም መጥሪያ ተቀባይ የሚሆን ወኪል የሌለዉ እንደሆነ ከተከሳሹ ጋር አብሮት ከሚኖረዉ አካላ መጠን ከደረሰ ቤተሰቡ ላንዱ መስጠት እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ በዚህ ረገድ የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የሥር ፍ/ቤት የሥር 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ ለአመልካች የተላከዉን መጥሪያ ፈርሞ ስለመቀበላቸዉ ያረጋገጠዉ ነገር ካለመኖሩም በላይ በወቅቱ የአሁን አመልካች ከሚስቱ ጋር በፍ/ቤት የፍቺ ክርክር እንደነበራቸዉ እና በግንኙነታቸዉ መካከል ችግር እንዳጋጠመዉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በአመልካች እና በሚስቱ መካከል በነበረዉ የፍቺ ክርክር ላይ ዉሳኔ ባይሰጥም፣ የፍቺ ክርክር በመኖሩ በመካከላቸዉ ሰላማዊ ግንኙነት ይኖራቸዋል ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሁኔታ ወ/ሮ ዘምዘም ኑሪ የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለአመልካች በአግባቡ ያደርሳሉ ተብሎ የሕግ ግምት ለመዉሰድ የሚያስደፍር አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህን ሁኔታ በመገንዘብ ተጠሪ የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለአመልካች ለማድረስ ተገቢዉን ጥረት እንዲያደርግ ማድረግ ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ ለሚስቱ መጥሪያ ደርሷት ቀርበ ስለተከራከረች ለአመልካችም መጥሪያ እንደደረሰ ግምት በመዉሰድ አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡

በመጨረሻም የሥር ፍ/ቤት የአመልካች በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ ውድቅ ያደረገበት ምክንያት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በነበረዉ ክርክር ተጠሪ ከተሰጠዉ መልስ ጋር በቀረበ የሰነድ ማስረጃ ነዉ ያወቅኩኝ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚል ከሆነ በዛ ክርክር መልስ የተሰጠዉ ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ስለሆነ አመልካች አቤቱታዉን የቀረበዉ ሰኔ 23 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ የአንድ ወር ጊዜ አልፎበታል በማለት ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም እንዳላወቀ እና ግንቦት 22 ቀን 2007 ዓ.ም በችሎት ጸሐፊ በኩል ትዕዛዝ ሲደርሰዉ እንዳወቀ በዚህ መነሻነትም ለሥር ፍ/ቤት በጊዜ አቤቱታዉን እንዳቀረበ በመግለጽ እየተከራከረ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ በቀረበዉ ክርክር አመልካች ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ችሎት ቀርበዉ የመከላከያ መልስና የሰነድ ማስረጃ ተቀብሎ ዉሳኔ መሰጠቱን አዉቋል የሚል ሳይሆን አመልካች የዉሳኔ ግልባጭ መጠበቅ ሳያስፈልገዉ ማወቅ ይችል ነበር የሚል ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ያወቀ መሆኑን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ በማስቀረብ ወይም በሌላ አግባብ በማጣራት ያረጋገጠ ነገር መኖሩን የሥር ዉሳኔ አያመለክትም፡፡ ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ እና ከግራ ቀኙቸዉ ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን አመልካች ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በችሎት ቀርበዉ ተጠሪ ያቀረበዉን የመከላከያ መልስና የሰነድ ማስረጃ በመቀበል፣ እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም አዉቆታል ለማለት የሚያስችል ነገር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በእርግጠኝነት የአሁን አመልካች ግንቦት 12 ቀን 2007 ዓ.ም እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ማወቁን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ባላረጋገጠበት፣ እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን በግምት በዚህ ቀን መሰጠቱን አዉቆታል፣ አመልካች በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ አቤቱታዉን ስላላቀረበ ዉድቅ ነዉ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 ዓላማ የሚቃረን ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በሕግ አግባብ መጥሪያ የደረሰዉ መሆኑን እና እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን በእርግጠኝነት ያወቀበት ቀን እስካልተረጋገጠ ድረስ የመከላከያ መልስና ክርክር በማቅረብ የመሰማትና ፍትሕ የማግኘት መብት ሕገ መንግስታዊ መብት ስለሆነ አሳማኝና በቂ ባልሆነ ምክንያት ሊነፈግ አይገባም፡፡ በዚህ ረገድ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 ፍትሕ የማግኘት መብት ሕገ መንግስታዊ መብት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች በሕግ አግባብ መጥሪያ የደረሰዉ እና እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ማወቁን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ባላረጋገጡበት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በሌለሁበት የተሰጠዉ ፍርድ ተነስቶ የመከላከያ መልስ እንዳቀርብ በማለት የቀረበዉን አቤቱታ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ አልቀረበም በሚል ምክንያት ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.18073 በ10/3/2008ዓ ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.15040 በ17/5/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚችሎት በመ.ቁ.06184 በ8/3/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች በሕግ አግባብ መጥሪያ የደረሰዉ እና እርሱ በሌለበት ዉሳኔ መሰጠቱን ያዉቅ እንደነበር ባልተረጋገጠበት፣ በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳልኝ በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ አልቀረበም በማለት ዉድቅ ማድረጉ በሕግ አግባብ ሆኖ ስላልተገኘ፣የመከላከያ መልስ የመቅረብ የመከራከርና ፍትሕ የማግኘት መብቱ ሊነፈግ ስለማይገባ የሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.18073 በ4/7/2007 ዓ.ም አመልካች በሌለበት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 (2) መሰረት ሊነሳ ይገባል ብለናል፡፡
3. የሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ የአሁን ተጠሪ የቀረበዉ ክስና ማስረጃ ለአመልካች እንዲደርሰዉ በማድረግ አመልካች የመከላከያ መልስ እንዲያቀርብ በማድረግ፣ በሕጉ አግባብ ተከራካሪ ወገኖቹን በማከራከርና በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 /1/ መሰረት ተመልሶለታል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
5. ግራና ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ፡-139187

ግንቦት 30 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ

ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- አቶ መስፍን ዘርዓብሩክ ጠበቃ ዘበነ ፍቅሬ ቀረቡ

ተጠሪ፡-1. ወ/ሮ የወርቅዉሃ አለማየሁ

2. ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ጥላሁን

3. አቶ አሰግድ ጥላሁን ጠበቃ ያሬድ ዘርይሁን ቀረቡ

4. ወ/ሮ አደይ አፈወርቅ

5. ወ/ት ሜሮን አፈወርቅ

6. አቶ ዳንኤል ተቀባ አልቀረቡም

7. ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ለማ አልቀረቡም

8. አቶ ሩዶለፍ ጆርዳኖ አልቀረቡም

9. ወ/ሮ መዓዛ ዘዉዴ አልቀረቡም

10. የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስትያን ጠበቃ በሬሳ በየነ ቀረቡ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነበር፡፡ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ከሳሽ፤ከ1ኛ እስከ 9ኛ ተጠሪዎች ተከሳሾች እንዲሁም 10ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ዉል ፈርሶ ቤት ለመረከብ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በአሁኑ አጠራር ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር CKS02/114/2321/227/606/7561/01 ተመዝግቦ የሚገኝ በ986 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የተገነባ ቁጥሩ 169 የሆነ ቤት ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል አቶ ጥላሁን ልዑልሰገድ ከተባሉት አሁን በህይወት ከሌሉት ከ1ኛ ተጠሪ ባለቤት ከ2ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎች አውራሽ በብር 400,000 (አራት መቶ ሺህ ብር) መግዛታቸውን፤ከገዙም በኋላ ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት ማሻሻያ ማድረጋቸውን፤ስመሃብቱ ወደ ገዥው ሳይዞር አመልካች በኢትዮ-ኤርትራ ግጭት ምክንያት ከአገር ውስጥ መውጣታቸውን፤ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 114/91 ክስ አቅርበው የካቲት 27 ቀን 1992 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ ከአመልካች ጋር አድርገውት የነበረው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ በማስወሰንና ካርታ እንደጠፋባቸው በማስመሰል አዲስ ካርታ አውጥተው ሰኔ 28 ቀን 1997 ዓ.ም ለ6ኛው ተጠሪ በሽያጭ በብር 450,000 (አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ማስተላለፋቸውን፤ከዚህ በኋላ 6ኛው ተጠሪ ባለቤታቸው ከሆኑት 7ኛ ተጠሪ ጋር ሆነው ነሐሴ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ለ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች በብር 5,100,000 (አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ብር) በሽያጭ ያስተላለፉት መሆኑን ጠቅሰው ከዚህ ሁሉ በኋላ አመልካች ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በመዝገብ ቁጥር 195189 ከሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር በመከራከር ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም የተደረገው ውል ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ነሐሴ 24 ቀን 2005 ዓ.ም የተወሰነ በመሆኑ ሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ ሰኔ 28 ቀን 1997 ዓ.ም ከ6ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል እንዲሁም 6ኛው ተጠሪ ከባለቤታቸው 7ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ነሐሴ 26 ቀን 2000 ዓ.ም ያረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ 8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ለአመልካች እንዲያስረክቡ፤አመልካች ከቤቱ ያገኙ የነበረውን ጥቅም ወደፊት አስልተው የመጠየቅ መብታቸው እንዲጠበቅላቸውና የክርክሩ ወጭና ኪሳራ እንዲታሰብላቸው ዳኝነት በመጠየቅ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡

ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ጥር 01 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ቤት ልረከብ በማለት ክስ ያቀረቡ ቢሆንም በአከራካሪው ቤት መብት ያላቸው ለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረቡም፤ህገ ወጥና ለህሊና ተቃራኒ የሆነ ውል ለማስፈረስ የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ነው፤አመልካች አከራካሪውን ቤት ከአገር ውስጥ ሲወጡ በአደራ የሰጡት ሰው ካለ መክሰስ እየተገባቸው ተጠሪዎችን መክሰሳቸው ተገቢ አይደለም በማለት በመቃወሚነት ጠቅሰው በፍሬ ጉዳዩም ላይ ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም የተደረገው ውል በአዋዋይ ፊት የተደረገ አለመሆኑን፤ አመልካች አቤቱታ አቅርበው ውሉ ሊፈርስ አይገባም ቢባልም ይግባኝ ማቅረባቸውን ገልፀው አመልካች ካሳ ከሚጠይቁ በስተቀር ውሉን አስመልክቶ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው መልስ አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል 6ኛ ተጠሪ ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ፤7ኛ ተጠሪ ነሐሴ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ መልስ እንዲሁም 8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ጥር 01 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን የሁሉም መልስ በይዘት ደረጃ ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ አከራካሪውን ቤት ህጉን ተከትለው እና ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው የገዙ መሆናቸውን ገልፀው ቤቱም ወደ ሌላ ወገን ተላልፎ እንደሚገኝ በመጥቀስ ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ያቀረቡት ነበር፡፡ የአሁን 10ኛ ተጠሪ ከ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ቤቱ የተላለፈላቸው መሆኑን ጠቅሰው ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ መልሳቸውን አቅርበው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚዎችን ጥቅምት 16 ቀን 2008 ዓ.ም በብይን ውድቅ በማድረግ አልፎ በዋናው ጉዳይ የግራቀኙን ተከራካሪዎች ክርክርና ማስረጃ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር በመዝገብ ቁጥር 138454 ሰኔ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች ከሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር ያደረጉት የቤት ግዥ ውል ሶስተኛዉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወገን በሆኑት ከ6ኛ እስከ 9ኛ ባሉት ተጠሪዎች ላይ መቃወሚያ ሊሆን የሚችለዉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2878 መሠረት በመዝገብ ተመዝግቦ ሲገኝ ብቻ ስለመሆኑና በዚሁ ረገድ ሦስተኛ ወገን ገቿዎች ተገቢዉን ማጣራትና ጥንቃቄ አድርገዉ ቤቱን ከባለሀብት የገዙ ስለሆነ በቅን ልቦና የተደረገ ዉል ከመሆኑ አኳያ 6ኛ ተጠሪ ከሚች ጋር ያደረጉት ውልም ሆነ 8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ከ6ኛና 7ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ዉል ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ሲከራከሩ የቆዩ ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ ለማስለወጥ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት አልተገኘም ሲል የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ጉዳዩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የፈፀሙትን መሠረታዊ ህግ ስህተት ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሠረታዊ የህግ ስህተት በመዘርዘር አቤቱታቸው አቅርበዋል፡፡

በሰበር አጣሪው ችሎት ትዕዛዝ መሠረት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አግባብነት ለማጣራት ተጠሪዎች ቀርበው መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ አግባብ ተጠናቋል፡፡ እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች በመሠረታዊነት የሚከራከሩት ከ1ኛ ተጠሪ ባለቤት እንዲሁም ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች አውራሽ ከሆኑት አቶ ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር ባደረግነው የቤት ሽያጭ ውል የገዛሁትን ቤት ሚች አቶ ጥላሁን ልዑልሰገድ ከ6ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል እንዲሁም 6ኛ ተጠሪ ከባለቤታቸው 7ኛ ተጠሪ ጋር ሆነው ከ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ ቤቱን እንዲያስክቡኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ከመዝገብ ምርመራው መገንዘብ እንደተቻለው አከራካሪውን ቤት አመልካች ለመግዛት ሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ ለመሸጥ ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም ስምምነት አድርገው ነበር፡፡ ከዚህ ስምምነት በኋላ ሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ በመዝገብ ቁጥር 114/91

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ክስ አቅርበው የካቲት 27 ቀን 1992 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውሉ ስምምነት እንዲፈርስ አስወስነዋል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በኋላ አዲስ ካርታ አውጥተው ሰኔ 28 ቀን 1997 ዓ.ም ለ6ኛው ተጠሪ በሽያጭ በብር 450,000 ማስተላለፋቸውም ተረጋግጧል፡፡ 6ኛው ተጠሪ ባለቤታቸው ከሆኑት 7ኛ ተጠሪ ጋር ሆነው ነሐሴ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ለ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች በብር 5,100,000 በሽያጭ ማስተላለፋቸውም ግልፅ ነው፡፡ አመልካች ይህ ሁሉ ከተከናወነ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በመዝገብ ቁጥር 195189 ከሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር በመከራከር ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ነሐሴ 24 ቀን 2005 ዓ.ም አስወስነዋል፡፡ በመሆኑም ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ አመልካች ከሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል ሊፈርስ እንደማይገባ ነሐሴ 24 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ የሽያጭ ውሉ ፈርሷል የሚል ተፈፃሚነት ያለው ውሳኔ በነበረበት ጊዜ ማለትም በ1997 ዓ.ም እና በ2000 ዓ.ም በቤቱ ላይ የተደረጉ የሽያጭ ውሎች ላይ የሚያስከትለው የህግ ውጤት ምንድን ነው? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

በመሠረቱ 6ኛ ተጠሪ ከሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር የአከራካሪውን ቤት ሽያጭ ውል በፈፀሙ ጊዜ ሚቹ ከአመልካች ጋር ያደረጉት ውል ከመፍረሱም በላይ አከራካሪው ቤት አዲስ ካርታ በሚች ጥላሁን ልዑልሰገድ ስም ወጥቶለት በሻጭ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ አመልካችም ቢሆኑ አልካዱም፡፡ አመልካች ከሚች ጋር አድርጌ ነበር የሚሉት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል 6ኛው ተጠሪ ቤቱን ከሚች በገዙ ጊዜ ተመዝግቦ እንዳልነበረም አከራካሪ አይደለም፡፡ በመሆኑም 6ኛው ተጠሪ ቤቱን ሲገዙ ተገቢውን ጥንቃቄ አላደረጉም፤የቅን ልቦና ጉድለት ነበረባቸው ሊባሉ አይችሉም፡፡ በቅን ልቡና ለሆነ ሶስተኛ ወገን የተሰራ ሥራ ውጤት ጠቃሚ ከሆነ እንደረጋ እንደሚቀር በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1816 ሥር ተደንግጎ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 25165 እንዲሁም በሌሎች መዝገቦች ላይ በማይንቀሳቀስ ንብረት ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው ግዥ የሚፈፅሙ የቅን ልቦና ገዥዎችን መብት ለመጠበቅ የሚያስችል አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ 6ኛው ተጠሪ ቤቱን የገዙት በቅን ልቦና ላይ ተመስርተውና ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው ከመሆኑም በላይ አመልካች የአከራካሪውን ቤት ሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቃወሚያ በሚሆን አግባብ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2878 መሠረት አስመዝግበው እንዳልተገኙ በሥር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ሟች ለ6ኛ ተጠሪ ያደረጉትም ሆነ ከዚያ በኋላ የተደረገው የሽያጭ ውል ሊፈርስ እንደማይገባ በሥር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ የሚነቀፍበት መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍርድ ቤቶች በአከራካሪው ቤት ላይ ሟች ከ6ኛ ተጠሪ ጋር እንዲሁም 6ኛ ተጠሪ 8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጓቸው ውሎች እንደጸኑ ይቀራሉ ብለው ሲወስኑ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ባልና ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች አውራሽ የከፈሉት ገንዘብና ተያያዥነት ያላቸውን ወጭዎች በተመለከተ በዚሁ መዝገብ ግልፅ ውሳኔ ሳይሰጡ ማለፋቸውን ከመዝገቡ ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ክስ ሲያቀርቡ ሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ ከ6ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል እንዲሁም 6ኛ ተጠሪ ከ8ኛና 9ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል ፈርሶ አከራካሪውን ቤት ለመረከብ ቢሆንም ከሟች ጋር በአደረጉት ውል መነሻነት ያወጡት ወጭ እንዳለ በክሳቸው አመልክተዋል፡፡ ክስ ሲያቀርቡም አስፈላጊውን የክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት አሟልተውና የዳኝነት ክፍለው እንዳቀረቡ የሚታመን ነው፡፡ ይህ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ውሉ አይፈርስም ካለ በኋላ አመልካች ለሟች የከፈሉት ገንዘብና እንደጸና እንዲቀር የተወሰነውን ውል መሠረት አድርገው ያወጡት ወጭ ካለ በማጣራት በዚሁ መዝገብ ላይ መወሰን ሲገባው በሌላ መዝገብ በአዲስ ክስ ቀርቦና ተከራክረውበት እንዲወሰን ለተራዘመ የክርክር ሂደት በመጋበዝ መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 138454 ሰኔ 01 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 130303 ጥር 26 ቀን 2009 ዓ.ም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ከሟች ጥላሁን ልዑልሰገድ ጋር ግንቦት 27 ቀን 1989 ዓ.ም በአደረጉት ውል መነሻነት ያወጡት ወጭ በተመለከተ በሌላ መዝገብ ክስ አቅርበው እንዲጠይቁ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሮ አመልካች ያወጡት ወጭ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ምን ያህል ነው? የሚለውን ነጥብ አመልካችንና ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎችን በዚሁ መዝገብ በማከራከር ካጣራ በኋላ ተገቢውን እንዲወስን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይመለስለት ብለናል። ሌላው የውሳኔ ክፍል አልተነካም።

3. ሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ማ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 142242

ቀን 16/09/2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተክሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡- አይል ሊቢያ ኢትዮጵያ ሊሚትድ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሉ ገ/ሕይወት የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው መሰረታዊ ጭብጥ አመልካች የንግድ ድርጅት ለመረከብ ባቀረበው ክስ ላይ የተቋረጠ ጥቅም አጣምሮ መጠየቅ ይችል ነበር ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 እና 33(2) ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡
2. አመልካች ቀደም ሲል በተጠሪ ላይ በመ/ቁ. 76340 ባቀረበው ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17/18 ክልል የሚገኘውንና በቤት ቁጥር 387 የተመዘገበውን የነዳጅ፣ የዘይት ማደያና የመኪና እጥበት ማከናወኛ የንግድ ድርጅት እንዲያስረክቡት ዳኝነት ጠይቆ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገው ክርክር አመልካች ንብረቱን እንዲረከብ ውሳኔ መስጠቱን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

3. አመልካች ንብረቱ እንዲረከብ ከተወሰነ በኋላ ከታህሳስ 4 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ድርጅቱን በፍርድ እስከተረከበበት ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ከነዳጅ ጣብያው አገልግሎት፣ ከነዳጅ፣ ዘይት ሽያጭ ማግኘት የነበረበት ገቢ በድምሩ ብር 971,394.04 ጥቅም የተቋረጠ በመሆኑ ተጠሪ እንዲከፍሉ በክ/መ/ቁ. 111441 ክስ አቅርቧል። የአሁኑ ተጠሪ ባቀረቡት የመከላከያ መልስ አመልካች መጀመሪያ ባቀረበው ክስ የተቋረጠ ጥቅምና ኪሳራ መጠየቅ እየቻለ ክሱን ነጣጥሎ ያቀረበ እንደሆነ፤ መጀመሪያ ባቀረበው ክስም የኪሳራ ጥያቄ ወደፊት ለመጠየቅ እንዲፈቀደለት ያቀረበው ጥያቄ በዝምታ የታለፈ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216/4/ እና 5(3) መሰረት ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል።
4. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለትን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ፍሬ ጉዳዩ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች ብር 912,487.43 ከሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል። ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታቸውን አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካች የተቋረጠ ጥቅም ለወደፊት እንዲጠይቅ መብቱ እንዲጠበቅለት ያቀረበው ጥያቄ በዝምታ የታለፈ በመሆኑ በድጋሚ ክስ ሊያቀርብ የሚችልበት የሕግ አግባብ አይኖርም በማለት የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮአል።
5. አመልካች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ግንቦት 14 ቀን 2009 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ንብረቱ ለማስመለስ ባቀረበው ክስ ላይ የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፈለው ግልጽ ዳኝነት ባልጠየቀበት እና የክስ ምክንያት ባልበሰለበትና ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ክስ መቅረብ ነበረበት የሚባልበት የህግ ምክንያት የሌለ መሆኑን እየታወቀ የስር ፍ/ቤት የዳኝነት ጥያቄው በዝምታ ታልፏል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በሕጉ አግባብ አይደለም ተብሎ እንዲሻርለት አመልክቷል። የአመልካች አቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎትም አመልካች ያቀረበው ክስ መብት ሊያቋቁም የሚችል ፍሬ ነገር ባልነበረበት አጠቃለህ ልትከስ ይገባ ነበር ተነጣጥሎ የቀረበ ክስ ነው ተብሎ በድጋሚ ሊቀርብ አይገባውም የመባሉን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 እና 33(2) አንጻር ለመመርመር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል። ተጠሪም ታህሳስ 20 ቀን 2010 ዓ.ም ባቀረበው መልስ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የኪሳራውን ጥያቄ ወደፊት ነጥሎ ለማቅረብ በውሳኔ እንዲታወቅለት የመጀመሪያው ክስ ላስተናገደው ፍ/ቤት ያቀረበው ጥያቄ ሳይፈቀደለት የታለፈ በመሆኑ የካሳው ጥያቄ ነጥሎ ማቅረብ አይችልም በማለት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ተብሎ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

6. የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

7. እንደመረመርነውም አመልካች መጀመሪያ ባቀረበው ክስ የነዳጅ ጣቢያው እንዲረከብ እንዲሁም የገቢና ትርፍ ማጣት ኪሳራ ወደፊት እንደሚጠይቅ በውሳኔ እንዲታወቅለት ማመልከቱን ከቀረበው ክርክር ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው የአመልካች የካሳ ጥያቄ በዝምታ ታልፏል የሚል ነው፡፡ በመሰረቱ በአንድ ክስ የሚጠቃለሉ ጉዳዮች አጠቃሎ ክስ ማቅረብ የሚገባ ስለመሆኑ፤ በዚህ አግባብ ያልቀረበው ክስ እንደገና የክስ ምክንያት ሊሆን እንደማይገባ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት ያስገነዝበናል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ እንደምንገነዘበው አጠቃሎ ክስ ማቅረብ የሚቻለው በተቋቋመ መብት ላይ ተመስርቶ እንጂ ዳኝነት በተጠቀበት ጊዜ ያልበሰለ ወይም ያልተረጋገጠ መብት ጭምር ማቅረብ እንደማይቻል ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች መጀመሪያ ያቀረበው ክስ መሰረታዊ የዳኝነት ጥያቄው የነዳጅ ማደያው መረከብ ስለመሆኑ አጠቃላይ ካደረጉት ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ የነዳጅ ጣቢያው የባለቤትነት ጥያቄ ባልተመለሰበት ሁኔታ የጥቅም ማጣት ወይም ኪሳራ መጠየቅ ግምታዊ የዳኝነት ጥያቄ ከሚሆን ውጭ የተረጋገጠ መብት/ጥቅም ቀንሶ ማስቀረትን የሚያሳይ ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች ነዳጅ ማድያው ለመረከብ ባቀረበው ክስ ለወደፊት የሚጠይቀው መብት መኖሩን ማመለከቱ መጀመሪያ ባቀረበው ክስ ላይ የተቋረጠ ጥቅም እንዲወሰንለት ግልጽ ዳኝነት ጠይቋል ለማለት አይቻልም፡፡ አመልካች ያልበሰለ ወይም ያልተረጋገጠ መብት በመጀመሪያ ክሱ ላይ አጠቃሎ አላቀረበም ተብሎ በስር ፍ/ቤት መወሰኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

8. አመልካች መጀመሪያ ባቀረበው ክስ የነዳጅ ጣቢያው የባለቤትነት መብት አከራካሪ የነበረ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የባለቤትነት መብት በሚያከራክርበት ሁኔታ ደግሞ አመልካች ባልተረጋገጠ መብት ላይ ተመስርቶ የገቢና ትርፍ ማጣት ኪሳራ የሚጠይቅበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ አመልካች መብቱን ወደፊት የሚጠይቅ ስለመሆኑ በክሱ ላይ ማመልከቱ ዳኝነት ጠይቋል የሚያስብል አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበው ክስ ተነጣጥሎ የቀረበ ነው፤ የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘቱ አልተረጋገጠም በማለት የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ መሻሩ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ እና 216 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ አመልካች የገቢና ትርፍ ማጣት ኪሳራ ለመጠየቅ ያቀረበው ክስ እንደገና (በድጋሚ) የቀረበ አይደለም ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ. 132137 በ 24/06/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 111441 በ 07/11/2008 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በመሻር የተሰጠ ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው የገቢና ትርፍ ኪሳራ ይከፈለኝ የዳኝነት ጥያቄ እንደገና (በድጋሚ) የቀረበ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 132137 በመክፈት ግራቀኙ በፍሬ ጉዳዩ ያቀረቡትን ክርክር መሰረት በማድረግ ተገቢ ህጋዊ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሰረት መልሰንለታል፡፡ የውሳኔ ግልባጭ ይድረስ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.146503

ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ንጋቷ በየነ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሀረገወይን በየነ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ይገባኛል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበሩት አቶ ብርሃኑ በየነ ሲሆኑ አመልካችና ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

አቶ ብርሃኑ በየነ መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ/ም በአመልካችና በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት ሟች አቶ በየነ ተ/ማሪያም መስከረም 04 ቀን 1997 ዓ/ም የተውት ኑዛዜው በፍርድ ቤት ቀርቦ መጋቢት 19 ቀን 1997 ዓ/ም መፅደቁን ጠቅሰው ኑዛዜ ያረፈበትን በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 199 የሆነ ቤት በኑዛዜው መሰረት እንዲከፋፈሉ ይወሰነው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችና ተጠሪ በሰጡት መልስም በኑዛዜው መሰረት ክፍፍሉ ቢደረግ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ክፍፍሉን የማይቃወሙ መሆኑን የጠቀሱ ቢሆንም ንብረቱ የእናታቸው ድርሻም ያለበት፣ የአሁኗ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ለብቻቸው ይዘው እየተጠቀሙ ለማከፋፈል ፈቃደኛ ያልሆኑ መሆኑንና የሚች ሌላ ተተኪ ወራሽ መኖሩንም ጭምር ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የውርስ አጣሪን ሹሞ ጉዳዩ እንዲጣራ ከአደረገ በኋላ ሪፖርቱ በ22/06/2008 ዓ/ም ለፍርድ ቤቱ የቀረበ ሲሆን በዚህ ሪፖርት ላይም አስተያየት እንዲሰጥበት አድርጎ የአሁኗ ተጠሪና የሥር ከሳሽ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ሲገልፁ የአሁኗ አመልካች ግን አለኝ የሚሉትን ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ለክፍፍል ጥያቄው መሰረት የሆነው ኑዛዜ በፍርድ ቤት የፀደቀ መሆኑንና ኑዛዜው ሲፅድቅም አመልካች የነበሩ በመሆኑ በኑዛዜው ህጋዊነት ላይ የሚያቀርቡት ተቃውሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ አንጻር ተቀባይነት የለውም፣ አመልካች ሌላ የሚች ተተኪ ወራሽ አለ በማለት ያቀረቡት አስተያየትም የቀረበ ወራሽ በሌለበትና አመልካች ስለመወከላቸው የሚያሳይ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ የአሁኗ አመልካች ያቀረቡትን ተቃውሞ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በዚህም ምክንያት የውርስ አጣሪው ሪፖርት ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አይደለም በማለት አጽድቆታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም አመልካችንና ተጠሪን ብቻ ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች ክርክር በፍርድ ቤት የጸደቀውን ኑዛዜ ያላገናዘበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ አግባብ ተቀባይነት የለውም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሠጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የበታች ፍርድ ቤቶች ሚች አቶ በየነ ተ/ማሪያም መስከረም 04 ቀን 1997 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ የአመልካችና የተጠሪ ወላጅ እናት የሆኑትንና የሚቹ ሚስት የነበሩትን ሚች ወ/ሮ የሺ ብሩ በሚስትነታቸው ያላቸውን ድርሻ የሚያሳጣ የሕግ አግባብ በሌለበት ሁኔታ ኑዛዜው መፅደቁ አመልካች የእናታቸውን ድርሻ በተመለከተ ቀድመው ተከራክረው የመጨረሻ ፍርድ እንዳገኙ የሚያስገነዝብ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የኑዛዜውን ይዘትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌን ባላገናዘበ መልኩ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ የተደረገ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ቀርቦ ከመያያዙም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተጨማሪ ስለንብረቱ ክፍፍልና የኑዛዜው ይዘት ግራ ቀኙ በቃል እንዲሰሙ ተደርጎአል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል።

በሥር ፍ/ቤቶች ከተሰጡት ውሳኔዎች እና አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ካቀረበችው አቤቱታ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ኑዛዜን በተመለከተ ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቶአል የሚለው የተጠሪ መቃወሚያ ሚች አቶ በየነ ተ/ማሪያም አከራካሪ ንብረት ላይ ያደረጉት የኑዛዜው ይዘትን የሚመለከት የጉዳዩ ሥረ-ነገር ላይ ክርክር መደረጉን አያመለክትም። አመልካች እና ተጠሪ የእናታቸውን ድርሻ በሚመለከተው የውርስ ሃብቱ ክፍፍል ላይ ተከራክረው የኑዛዜውን ይዘት መሰረት ያደረገ ውሳኔ ተሰጥቶአል የሚል አባባልም የለውም። በአመልካችዋ የሰበር አቤቱታ ጭምር እንደተገለጸው ቀደም ሲል በአቶ ብርሃኑ በየነ በቀረበው የውርስ ሐብት ልካፈል ጥያቄ የግራ ቀኙ ወላጅ አባት ድርሻ የሆነው ቤት ላይ ውሳኔ ተሰጥቶ በዚሁ አውራሽ ድርሻ ላይ ግራ ቀኙ ክፍፍል ያደረጉ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ቢሆንም የሚች አቶ በየነ ተ/ማሪያም ሚስት የነበሩትና የአመልካችና የተጠሪ ወላጅ እናት ሚች ወ/ሮ የሺ ብሩ በቤቱ ላይ ያላቸውን ድርሻ በተመለከተ ግን ኑዛዜው በፍርድ ቤት ሲፀድቅ በግልፅ ተለይቶ የተጠቀሰ ነገር የለም። ሚች ወ/ሮ የሺ ብሩ ኑዛዜው ባረፈበት መኖሪያ ቤት ላይ ግማሽ ድርሻ /50%/ ያላቸው መሆኑ በውርስ አጣሪውም የውሳኔ ሃሳብ የቀረበበት ሲሆን የአሁኑ ተከራካሪ ወገኖችም ሆነ በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት ግለሰብ ያቀረቡት የተለዩ ክርክር ስላለመኖሩ ከክርክሩ ሂደት ለመረዳት ችለናል። ሚች አቶ በየነ ተ/ማሪያም ባደረጉት ኑዛዜም የአሁኗ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሚገኝበት ግቢ ውስጥ ያሉትንና በወር በብር 400.00 (አራት መቶ) የሚከራዩትን ሁለት ክፍሎችን እንዲወስዱ ሲናዘዙ ".....ከኔ ድርሻ የሚታሰብ ሁኖ....." የሚል ሐረግ ያሰፈሩበት መሆኑን የኑዛዜው ሰነድ ይዘት ያሳያል። ይህ የኑዛዜው ሰነድ ይዘት ኑዛዜው ሲፀድቅ ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ ያረፈበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ነገር የሌለው ከመሆኑም በላይ የሐረጉ ይዘትና መንፈስ ሚች ወ/ሮ የሺ ብሩ በክፍሎቹ ያላቸውን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድርሻ የሚያሳጣ መሆን ያለመሆኑን፣ ከሌላው የውርሱ ክፍል ላይ በእነዚህ ክፍሎች ላይ ወ/ሮ የሺ ብሩ ያላቸው ድርሻ እንዲካካስ ታስቦ የተቀመጠ መሆን ያለመሆኑን የውርስ ንብረቱ ላይ ሚች ወ/ሮ የሺ ብሩ ግማሽ ድርሻ አላቸው ተብሎ ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ አንጻር ታይቶ እልባት ሊያገኝ የሚገባው እንጂ ኑዛዜው በመጽደቁ ብቻ የመጨረሻ ፍርድ አግኝቶአለ ተብሎ የሚታለፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡እንግዲህ የክርክሩ አጠቃላይ ይዘትና ሊታዩ የሚገባቸው ነጥቦች እነዚህ መሆናቸው ከተረጋገጠ በተጠሪ የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የተጠሪ መቃወሚያ የተመሰረተው በኋላ የቀረበው ክስ(ጥያቄ) በቀድሞው የኑዛዜ ይጽደቅልን ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቶአል በሚለው ላይ ነው፡፡ ይህን መቃወሚያ ለመወሰን አግባብነት ያለው ድንጋጌ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 በመሆኑ ከቀረበው መቃወሚያ ፍሬ ነገር ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡ በተጠቀሰው ድንጋጌ አባባል በኋላ የቀረበው ጉዳይ ቀድሞ በቀረበው ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቶአል ሊባል የሚችለው በሁለቱም የተነሳው ክርክር ሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አንድ አይነት ከሆነ ነው፡፡ በዚህ መዝገብ በያዝነው ጉዳይ የሆነው ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ በቀድሞው ክስ ተነስቶ የነበረው ክርክር የሚች አቶ በየነ ተ/ማሪያም ኑዛዜ ይፀድቅልን የሚል ሲሆን፣ በሁለተኛው ክስ የተነሳው ግን ክስ በተመሰረተበት ንብረት ላይ ሚች ወ/ሮ የሺ ብሩ ድርሻ አላቸው? ወይስ የላቸውም?፣ የሚች አቶ በየነ ተ/ማሪያም የኑዛዜ ይዘት የሚች ወ/ሮ የሺ ብሩን ድርሻ ለሌሎች ወራሾች የሚያስተላልፉበት የሕግ አግባብ አለ? ወይስ የለም? የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ኑዛዜ ፀድቆአል በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ የሕግ ድጋፍ ያለው አይደለም፡፡ በአመልካች የእናት ድርሻ እንካፈል በሚል ለቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በመከሪከሪያነት ያቀረቡት የክርክሩንና የሚች አቶ በየነ ተ/ማሪያም ኑዛዜ የሚተረጎምበትን አግባብ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ አመልካች ከእናታቸው ሊያገኙት የሚገባው የሐብት ድርሻ በተመለከተ የሥረ- ነገር ክርክር ቀድሞ ታይቶአል ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ እንዲሁም አመልካች ኑዛዜው ከፀደቀ በኋላ በቀረበው ክፍፍል ውስጥ ከእናታቸው በውርስ ሊያገኙት ከሚገባው ድርሻ ተገቢውን ያላገኙ መሆኑን ገልጸው የሚከራከሩ በመሆኑ ይህም ፍሬ ነገሩ ተጣርቶ ከሚለይ በስተቀር ኑዛዜው ፀድቆአል በሚል ምክንያት ብቻ ከወዲሁ ውድቅ ሊሆን የሚችልበት የስነ ስርዓት ሕግ አግባብ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለም፡፡ ሲጠቃለልም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ከተጠሪ ጋር ሊካፈሉ ስለሚገባው የእናታቸው የውርስ ንብረት ላይ ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው የክርክሩን ይዘትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ስር የተመለከቱትን መመዘኛዎችን ያላሟላ በመሆኑ አቤቱታ የቀረበበት የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 232931 በ25/04/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 193316 በ08/10/09 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካች የእናታቸውን ድርሻ በተመለከተ ያቀረቡት የክፍፍል ጥያቄ ውድቅ የተደረገው ያላግባብ ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች የሚች ወ/ሮ የሺ ብሩን የውርስ ሃብት በተመለከተ ያቀረቡትን ክርክር በፍርድ ሐተታው ላይ በተመለከተው አግባብ ተመልክቶና በሚገባ አጣርቶ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጸፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር መጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 148270

ቀን - 30/09/2010

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዬ ካሳሁን

አመልካቾች፡- 1. አቶ ቡልቻ ቱሉ - ቀርበዋል፡፡

2. ወ/ሮ ወርቁ አብዲሳ - ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ተመስገን መላቱ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል::

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ብ/ክልላዊ መንግስት መስተዳደር በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን 2ኛ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መቃወሚያ ይዘትም በአጭሩ በኡኬ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኘዉን እና አዋሳኞቹ በአቤቱታዉ ላይ የተመለከቱትን ቤት እና ይዞታ በተመለከተ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/29375 የሰጠዉ ዉሳኔ መብታቸዉን የሚነካ መሆኑን ጠቅሰዉ ወደ ክርክሩ ገብተዉ ተከራክረዉ እንዲወሰንላቸዉ መጠየቃቸዉን የሚያሳይ ነዉ፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ በቀረበዉ አቤቱታ መነሻነት የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ቀደም ሲል ሰጥቶ የነበረዉን ዉሳኔ በመሻር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት እና ይዞታ አመልካቾች በጋራ የሰሩት ነዉ በማለት ወስኗል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለምሥ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የይግባኝ መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ በወረዳዉ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ይህ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሶ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ያቀረበ ሲሆን፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎት በበኩሉ ተጠሪዎች ባልና ሚስት መሆናቸዉን እና 2ኛ ተጠሪ ጉዳዩ መብቴን ይነካል የሚትል ከሆነ ክርክርሩ በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት ጣልቃ ገብታ መከራከር እየቻለች ይህን ሳታደርግ ቀርታ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ያቀረበችዉን የመቃወም አቤቱታ በመቀበል የወረዳዉ እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ሽሯል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቀበል ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 09/02/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃቸዉ አማካይነት በቀረበ 4 ገጽ የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ 2ኛ አመልካች ለወረዳዉ ፍርድ ቤት ላቀረቡት የመቃወም አቤቱታ መሠረት ያደረገችዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በ1ኛ አመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገዉን ክርክር መሠረት በማድረግ በመ/ቁ/29375 በቀን 07/06/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል በማለት ነዉ፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በ1ኛ አመልካች ላይ ያቀረበዉ ክስ ሲሆን፣ተሰጥቶ የነበረዉ ዉሳኔም 1ኛ አመልካች ቤትና ቦታዉን ለተጠሪ ይልቀቅ የሚል ስለመሆኑ ከግራ ቀኝ ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁንና 1ኛ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለምሥ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝ ተቀባይነት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባለማግኘቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/209425 በቀን 30/06/09 ዓ.ም በዋለው ችሎት በወረዳው እና በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ውሳኔዎች በመሻር መወሰኑን ተመልክተናል፡፡ አመልካቾች በዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ አጥብቀው ከሚከራከሩባቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱ ለመቃወም አቤቱታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሻሩን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበን እያለ ችሎቱ ይህን ሳያጣራ ውሳኔ መስጠቱን ሲሆን፣ ተጠሪም በጽሑፍ በሰጠው መልስ ቀደም ሲል በስር ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በይግባኝ መሻሩን በተመለከተ ክዶ ካለመከራከሩም በላይ ይህ ችሎትም የዉሳኔውን ግልባጭ አስቀርቦ ተመልክቶታል፡፡

በሌላ በኩል አንድ ሰው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የመቃወም አቤቱታ መቅረብ የሚችለው መብቱን የሚነካ ውሳኔ ሲኖር ብቻ ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 358 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት የመቃወም አመልካች አቤቱታ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤቶች ግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ከሚጠበቅባቸው ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ የመቃወም አመልካችን መብት የሚነካ ውሳኔ መኖር አለመኖሩን ነው፡፡ የተያዘውን ጉዳይ በተመለከተ 2ኛ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የመቃወም አቤቱታ ለወረዳው ፍርድ ቤት አቅርባ ጉዳዩ በክርክር ባለበት ወቅት ለመቃወም አቤቱታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ በ1ኛ አመልካች ይግባኝ ባይነት በዞን እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት በሂደት ላይ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩ በከፍተኛ ወይም በጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ በሂደት ላይ እያለ በጎን ለወረዳው ፍርድ ቤት የቀረበው የመቃወም አቤቱታ ከመነሻውም ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከመቅረቡ በፊት ለመቃወም አቤቱታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሽሯል፡፡ አመልካቾች ይህን ለሰበር ሰሚው ችሎት ገልፀው መከራከራቸውን ክርክሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የ2ኛ አመልካችን መብት ነክቷል ተብሎ ለመቃወም አቤቱታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ የተሻረ መሆን አለመሆኑን ማጣራት ነበረበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በበኩላችን እንደተመለከትነው 2ኛ አመልካች ላቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ምክንያት የሆነው ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሽሯል፡፡ በመሆኑም ለመቃወም አቤቱታ ምክንያት የሚሆን ውሳኔ የለም፡፡ የተሻረን ውሳኔ መነሻ በማድረግ የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ አይኖርም፡፡ ስለሆነም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለመቃወም አቤቱታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሻሩን እና የ2ኛ አመልካቾን መብት ሊጎዳ የሚችል ውሳኔ አለመኖሩን አረጋግጦ የቀረበን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል እንዲሁም ይህኑን መሠረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ውሳኔዎች በመሻር መወሰን ሲገባው ይህን ባለማድረግ የ2ኛ አመልካች የመቃወም አቤቱታ አቀራረብ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በሚል መንፈስ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/261961 በቀን 29/01/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም የጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/29375 በቀን 10/04/09 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የምስ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/42673 በቀን 23/06/09 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. 2ኛ አመልካች መብቴን ይነካል በሚል የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡበት ውሳኔ በሌላ አግባብ ስለተሻረ እና መብቷን ሊነካ የሚችል ውሳኔ ስለሌለ የ2ኛ አመልካች የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡
3. የሰበር አጣሪ ችሎት በቀን 13/02/2010 ዓ.ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 144470

ቀን - 30/11/2010

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

አመልካች፡- ናይል ትራንዚት ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ተጠሪዎች፡- 1. ኒያላ ኢንሹራንስ ኩባኒያ

2. አጉል ትራንዚት

3. አቶ ኑሩ ኡመር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኢንሹራንስ ዉልን መሠረት በማድረግ በመድን ሰጪዉ የተከፈለን የጉዳት ካሳ መድን ሰጪዉ በመድን ገቢዉ ተተክቶ በተጠየቀ የመዳረግ መብት ጋር በተያያዘ የቀረበን ክርክር መሠረት በማድረግ የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር 2ኛ ጣልቃ ገብ የነበሩት አቶ ኪዳኔ ታረቀኝ እና የአሁን 3ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ ሊገቡ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ነዉ፡፡

አመልካች በቀን 23/04/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ፣ ስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ አመልካች ከፈለገ ከእነርሱ ላይ ክስ መስርቶ ካሳ መጠየቅ ይችላል በሚል ከክሱ እንዲሰናበቱ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪዎች በየበኩላቸዉ በጽሑፍ በሰጡት መልስ፣ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚሉባቸዉንም ምክንያቶች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመዘርዘር መልስ ሰጥተዋል፤ አመልካች ያቀረበዉ የመልስ መልስም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ እኛም የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠዉን ብይን አግባብነት እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ፣ አመልካች ከደንበኛዉ ጋር ባደረገዉ የዕቃ አስተላላፊነት ዉል መሠረት የሚጠበቅበትን ግዴታ ባለመወጣቱ ለደንበኛዉ የከፈለዉ የጉዳት ካሳ እንዲተካለት ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ የተለያዩ የመጀመሪያ እና የፍሬ ነገር ክርክሮችን ካቀረበ በኋላ የማጓጓዝ ስራዉ የተከናወነዉ በስር 2ኛ ጣ/ገብ በነበረዉ፣ አቶ ኪዳኔ ታረቀኝ፣ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ የጠየቀ ሲሆን፣ አቶ ኪዳኔ ታረቀኝም በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ በመግባት በሰጠዉ መልስ ያሁን 3ኛ ተጠሪ መኪና በጭነቱ ቦታ የነበረ መሆኑን ጠቅሶ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ በማለት መጠየቁን ነዉ፡፡ የስር ፍርድ ቤት የስር 2ኛ ጣልቃ ገብ፣ አቶ ኪዳኔ ታረቀኝ፣ እንዲሁም የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ በማድረግ ክርክር ከሰማ በኋላ 3ኛ ተጠሪ እና የስር 2ኛ ጣልቃ ገብ ከክርክሩ እንዲወጡ ብይን መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ በሌሎች ሰዎች መካከል በመካሄድ ላይ ባለዉ ክርክር ጣልቃ መግባት ስለሚቻልበት ሁኔታ የፍ/ሥ/ሥርዓት ህጋችን ከአንቀጽ 40-43 ባሉት ድንጋጌዎች የተመለከቱ ሲሆን፤ ክርክሩን በመስማት ላይ ያለዉ ፍርድ ቤትም ሌላ ሦስተኛ ወገን በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ሊገባ የሚገባ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ በድንጋጌዎቹ ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ግምት ዉስጥ የማስገባት ግዴታ የሚጠበቅበት ሲሆን፤ ይህን የሚያደርገዉም 3ኛዉ ወገን ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡ ይህ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ 3ኛ ወገን ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ፣ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ ካመነበት ክርክሩ በየትኛዉም ደረጃ ላይ ቢሆን ጣልቃ ገቡ ከክርክሩ ዉጪ እንዲሆን ትዕዛዝ ከመስጠት የሚከለክለዉ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ወደ ኋላ ተመልሶ ከክርክሩ ዉጪ እንዲሆኑ ትዕዛዝ መስጠቱ ኢ-

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስነስርዓታዊ ነዉ በማለት አመልካች እያቀረበ ያለዉ ቅሬታ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም።

ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገዉ 3ኛ ተጠሪ በክርክሩ እንዳይቀጥል አለመደረጉ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ጭብጥ ስንመለከት፤ የስር 2ኛ ጣልቃገብ፣ አቶ ኪዳኔ ታረቀኝ፣ 3ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ሲጠይቅ በምክንያትነት የጠቀሰዉ ጉዳት የደረሰበትን ማሽነሪ የጫነዉ የ3ኛ ተጠሪ መኪና መሆኑን ነዉ። ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ በሌሎች ሰዎች መካከል በመካሄድ ላይ ባለዉ ክርክር ጣልቃ መግባት ስለሚቻልበት ሁኔታ የፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 40-43 ይደነግጋል። የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ የስር 2ኛ ጣልቃ ገብ ያሁን 3ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ሲጠይቅ፣ በህጉ አንቀጽ 43 መሠረት 3ኛ ተጠሪ ከእርሱ ጋር በድርሻ ካሳዉን ለመክፈል የሚገደድበትን የዉል ወይም የህግ ምክንያት ስለመኖሩ አልገለጸም። አሊያም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ሲደረግ በነበረዉ ክርክር መሠረት ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የተጠሪዎች በክርክሩ ጣልቃ መግባት፣ በፍት/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 40 መሠረት፣ የግድ መሆኑን የሚያሳይ የህግ ምክንያት አልቀረበም። ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪዎችን ከክርክሩ ዉጪ በማድረግ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ብይን በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ ተከታዩ ተወስኗል።

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/111574 በቀን 19/07/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ብይን፤ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/141787 በቀን 29/09/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) ፀንቷል።
2. በዚህ ችሎት በቀን 30/05/2010 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል።
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ
የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት
ሠ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 154023

መስከረም 23 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈ.ይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ ካሰች በቀለ
2. ወ/ሮ ባንቻየሁ በቀለ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-1. ውቢት ዘውዴ- ቀረቡ ፡፡

2. ትግስት ዘውዴ- ወኪል ደሳለኝ ታምራት ቀረቡ ፡፡

3. ልቡ በቀለ-ቀረበ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች ከወላጅ አባታቸው ከሟች ቁስ በቀለ ሀ/ወልድ በውርስ ሊያገኙ የሚገባውን ይዞታና ግምታቸው ብር 19,000.00 የሚሆኑ ከብቶችን በ25/11/2005 ዓ/ም በተደረገ ኑዛዜ መሰረት የነቀላቸው መሆኑን ጠቅሰው ኑዛዜው ፈርሶ ድርሻቸውን እንዲያካፍላቸው ይወሰን ዘንድ የአቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ የሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52916 በ20/06/2009 ዓ/ም በይርጋ ውድቅ አድርጎ ብይን ሰጥቶ በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28914 በ7/11/2009 ዓ/ም በውሳኔ፣ የኦሮሚያ ብሔረዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 270369 በ14/03/2010ዓ.ም. በትዕዛዝ ማጽናታቸው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካቾች በ13/06/2010 ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

አመልካቾች በ12/07/2008 ዓ/ም ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘቱ ሲታይም የአመልካቾችና የ3ኛ ተጠሪ ወላጅ አባታቸው ሟች ቄስ በቀለ ሀ/ወለድ መሆናቸውን፣ ሟች በሕይወት እያለ በ25/11/2004 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ አመልካቾችን ከውርስ የነቀሉ መሆኑን ጠቅሰው ኑዛዜው ፈርሶ አመልካቾች ከሟቹ የገጠር መሬት ይዞታና ከብቶች ድርሻቸውን እንዲያገኙ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፣ የኑዛዜ ወራሽነታቸውም ቀድሞ በፍርድ ያለቀ በመሆኑ አመልካቾች አዲስ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ ያለመሆኑን ጠቅሰው የተከራከሩ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ግን የአመልካቾችን ክስ ተገቢ መሆኑን በማመን ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች በመስማትና ለጉዳዩ ተያያዥነት አላቸው ያላቸውን የመ/ቁጥር 35076 እና 31290ን አስቀርቦ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች ኑዛዜው እንዲፈርስ የጠየቁት ከሶስት አመት በኋላ መሆኑ ተረጋግጧ በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካቾች በወላጅ አባታቸው ኑዛዜ ከውርስ የነቀለ መሆኑን ጠቅሰው ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ በተሰጠው የብይን ክፍል ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በአባታቸው በ25/11/2004 ዓ/ም የተደረገው ኑዛዜ ከውርስ የነቀላቸው መሆኑን፣ ይዞታውንም በስምምነት ተካፍለው ሲጠቀሙ የነበረ ከመሆኑም በላይ ክርክሩም እኩል ደረጃ ላይ በማይገኙ ወራሾች መካከል ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን መስጠታቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካቾች አከራካሪውን የውርስ ንብረት መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ/ም ተደረገ በተባለ ስምምነት ተካፍለው ሲጠቀሙ የነበረ ከመሆኑ አንጻር ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች በመቅረባቸውም ግራ ቀኙ በዕሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክርና ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ብይን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎትን ምላሽ የውርስ ንብረት በስምምነት ክፍፍል ተደርጎበት የነበረ መሆን ያለመሆኑና በተለያዩ መዝገቦች በክርክር ላይ የቆዩት ወገኖች በይርጋው አቆጣጠር ላይ የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ሳይለይ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ብይን መሰጠቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ወላጅ አባታቸው ከሕግ ውጪ ከውርስ የነቀሉና ከውርስ ንብረቶች መካከል የሚችን ይዞታና ባህርዛፍ ከሚች ቁስ በቀለ ሀ/ወልድ ተወላጆች ልጆችና ወራሾች ጋር በሽማግሌ ለመከፋፈል ስምምነት አድርገው በስምምነቱ መሰረት ክፍፍል ተደርጎ ይዞታዎቹን በመጠቀም ላይ የሚገኙና የገጠር መሬት ባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተርም ያወጡበት ሁኖ እያለ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው መባሉ ያላግባብ ነው በሚል ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ደግሞ በአመልካቾች የተጠቀሰው ስምምነት የሌለ መሆኑን፣ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ የአመልካቾችን ክርክር ደግፈው የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አመልካቾች አለ የሚሉት ስምምነት የለም ከማለት ውጪ ይህ ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ መሆኑን በዚህ ችሎት ባቀረቡት የመልስ ማመልከቻቸው ገልፀው ያልተከራከሩ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤትም በአመልካቾች በኩል የተጠቀሰው የክፍፍል ስምምነት መኖር ያለመኖሩን በግልጽ ለይቶ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር የለም፡፡

በመሆኑም የአመልካቾች የወላጅ አባታቸውን የውርስ ንብረት ድርሻ ለመካፈል ያቀረቡት ጥያቄ የይርጋ ጊዜ ያለፈበት መሆን ያለመሆኑን አመልካቾች በክሳቸው እና በቃል ክርክራቸው ጊዜ የገለጿቸው ፍሬ ነገሮች በተለይም መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ/ም ተደረገ የተባለ የክፍፍል ስምምነት መኖር ያለመኖሩና በዚህ ስምምነት መነሻ ድርሻ ድርሻቸውን ይዘው የሚገኙ፣ የይዞታ ማረጋጋጫ ደብተርም ከሚመለከተው አካል በሕግ አግባብ የተሰጣቸው መሆን ያለመሆኑ በማስረጃ ሳይነጥር ሊወሰን ይችል የነበረ አይደለም፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካቾች ይዞታውን ሲጠቀሙ የነበረ መሆኑን፣ የወራሽነት መብታቸውን ለማስከበርም በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31290 እና 35076 ክርክር የነበረ መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል። በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቾች የክርክር ነጥብ ደግሞ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1852 አንጻር ምን አይነት ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል በስር ፍርድ ቤት በጭብጥነት ተይዞ መታየት የነበረበት መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል። አንድ ተከሳሽ የቀረበበት ክስ በይርጋ የሚቋረጥ መሆኑን ከጠቀሰ ክስ አቅራቢ ወገን ክሱ በሕጉ የተመለከተው ጊዜ ገደብ (ይርጋ) ያላለፈው መሆኑን፣ ጊዜው አልፎ ከሆነም ይርጋውን ሊያቋርጥ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩን በተገቢው ማስረጃ ለማስረዳት የሚችልበት እድል ሳይሰጠው የተከሳሽ መቃወሚያ ብቻ መሰረት ተደርጎ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ ብይን የሚሰጥበት አግባብ ስነ ስርዓታዊ ያለመሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 241፣ 244 እና 245(1) ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000፣ 1846፣ 1852 እና 1853 ድንጋጌዎች ጋር አጣምረን በምናነብበት ጊዜ የምገነዘበው ጉዳይ ነው። ስለሆነም በተከሳሽ ወገን በቀረበ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የሚገምተው ማስረጃ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ መስጠት ወይም የተቆጠረ ማስረጃ ካለም መስማት የሚችል ስለመሆኑ በስነ ስርዓት ሕጉ በአንቀጽ 245 (1) ከተመለከተው ድንጋጌም የምንችለው ጉዳይ ሁኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች አለን የሚሉትን ስምምነት ሰነድ ትክክለኛነትና ሕጋዊነት አጣርቶና በሕጉ አግባብ ለአመልካቾች የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ካለም እንዲቀርብ አድርጎ እንዲሁም በመ/ቁጥር 31290 እና 35076 በተደረጉ ክርክሮች ይርጋው ሊቋረጥ የሚችል መሆን ያለመሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1852 ድንጋጌ አንጻር በመመርመር ሕጋዊ ውጤቱን ሳይለይ የአመልካቾችን የወላጅ አባታቸውን የውርስ ንብረት ድርሻ እንድንካፈል ይወሰንልን የሚለውን ክስ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 (1) ድንጋጌን ጠቅሶ ውድቅ ማድረጉ ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት የተከተለ ሁኖ አልተገኘም። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ብይን ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ከአመልካቾች የክርክር ነጥቦች ጋር ያላገናዘበ ሁኖ እያለ ማጽናታቸውም ተገቢ ሁኖ አልተገኘም። በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. በሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52916 በ20/06/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28914 በ7/11/2009 ዓ/ም በውሳኔ፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 270369 በ14/03/2010 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል።
2. የሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 52916 ቀጥሎ አመልካቾች በወላጅ እናታቸው ድርሻ ላይ ያቀረቡትን ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ተገቢውን ምላሽ ለመሰጠት በዚህ ችሎት የፍርድ ሐተታ ላይ በተመለከተው አግባብ ይዞታው መጋቢት 13 ቀን 2005 ዓ/ም ተደረገ በተባለ ስምምነት በአመልካቾች ተይዞ ቆይቷል ወይስ አልቆየም፣ አመልካቾች ይዞታውን ከኑዛዜ ተጠቃሚዎች ጋር ክፍፍል አድርገው ከሚመለከተው አካል የይዞታ ማረጋገጫ አውጥተውበት ይገኛሉ? ወይስ አይገኙም?፣የይዞታ ማረጋገጫ አግኝተው ከሆነ ሰነዱ የተሰጣቸው የሕግ አግባብ ምንድን ነው?፣ በመ/ቁጥር 31290 እና 35076 ሲካሄዱ በነበሩት ክርክሮች ሲሳተፉ የነበሩ ተከራካሪ ወገኖች እነማን እንደሆኑና በጉዳዮቹ ላይ የተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘቱ ምን እንደሚል፣ እንዲሁም በይርጋው ላይ የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ምን እንደሆነ በመመርመርና በግራ ቀኙ እና አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ሁሉ እንዲጣሩ ካደረገ በኃላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ላይ ተገቢውን ብይን እንዲሰጥ እና ክሱ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም የሚባል ከሆነም በፍሬ ጉዳዩ ረገድ የቀረበለትን ክርክር በአግባቡ አጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰናል። ይጸፍ።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ፋ/ዘ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ 152845

መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- አቶ መሀመድ በሀዲን-አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- ዘምዘም አሊ-አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የይግባኝ ጊዜን የሚመለከት ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ያቀረበው ታሕሳስ 16 ቀን 2010 ዓ.ም ላቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የይግባኝ ማስፈቀጃ ምክንያት ያቀረበ ቢሆንም የይግባኝ ማስፈቀጃ ምክንያቱ በቂ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 326 መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የፌዴራሉ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት በመ.ቁ 00079 በቀን 15/02/2010 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አመልካች የይግባኝ ማመልከቻ አቅርቤ ግልባጩ የተሰጠኝ በቀን 13/04/2010 ዓ.ም በእለተ አርብ ነው፤አመልካች ቅዳሜ እና እሁድ የመንግሥት ሥራ ዝግ ስለሆነ ታሕሣሥ 16 ቀን 2010 ዓ.ም የይግባኝ ቅሬታዬን ለፍ/ቤቱ ያቀረብኩ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የይግባኝ ጊዜው አልፏል በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቱ አመልካች ይግባኙን በቀን 16/04/10 ዓ.ም ማቅረቡን በገለጸበት ሁኔታ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው አልፏል በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ይግባኝ የተጠየቀበት ውሳኔ የተሰጠው በቀን 15/02/10 ዓ.ም ሲሆን አመልካች ይግባኙን ያቀረበው በቀን 16/04/10 ዓ.ም በመሆኑ በራሱ ችልተኝነት የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፤የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ የሚቆጠረው ቀኖቹን በተከታታይ በመቁጠር እንጂ ቅዳሜ እና እሁድን በመተው አይደለም፤አመልካች በበቂ ምክንያት የተደገፈ የይግባኝ ማስፈቀጃ ያላቀረበ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ይግባኝ የተጠየቀበት ውሳኔ የፌዴራሉ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት በመ.ቁ 00079 በቀን 15/02/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሆኑ፤አመልካች ግልባጭ እንዲሰጠው የጠየቀው በቀን 12/04/10 ዓ.ም መሆኑን፤አመልካች የመዝገብ ግልባጭ የተሰጠው በቀን 13/04/2010 ዓ.ም በእለተ አርብ መሆኑ እና ይግባኙን ያቀረበው በቀን 16/04/2010 ዓ.ም መሆኑን የድሬዳዋ ፌዴራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት በቀን 13/04/10 ዓ.ም የጻፈው መሸኛ ደብዳቤ ያሳያል፡፡ ከደብዳቤው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ታሕሣሥ 12 ቀን 2010 ዓ.ም እና ታሕሣሥ 13 ቀን 2010 ዓ.ም የሆኑን ሁለቱ ቀናት በአመልካች ጥፋት ያልባከኑ መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የይግባኝ አቤቱታ አቀራረብ የሚመራው በሥነ-ሥርአት ሕጉ በተዘረጋው ሥርአት መሠረት ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 323/2 ድንጋጌ የመጀመሪያ ደረጃው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ፤ብይን ወይም ትእዛዝ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን የይግባኙን አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማቅረብ ያለበት ይግባኝ በሚባልበት ጉዳይ ላይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተፈረደ በ60 ቀን ውስጥ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ያላቀረበ ተከራካሪ ወገን ይግባኙ እንዲከፈት ይግባኝ ማስፈቀጃ ማቅረብ እንዳለበት የዚሁ ሕግ ቁጥር 324 ያስገነዝበናል፡፡ የይግባኝ ማስፈቀጃ የቀረበለት ፍ/ቤትም በዚሁ ሕግ ቁጥር 326 መሠረት ይግባኝ ጠያቂው ይግባኙን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻለበትን ምክንያት በቂ መሆን አለመሆኑን መርምሮ ይግባኙ እንዲከፈት ሊፈቅድ ወይም ሊከለክል እንደሚችል ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ይግባኝ አመልካች የፌዴራሉ ከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት በመ.ቁ 00079 በቀን 15/02/2010 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ መጠየቅ ይችል ዘንድ ግልባጭ እንዲሰጠው የጠየቀው የ60 ቀኑ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሳያልፍ በቀን 12/04/10 ዓ.ም ሲሆን የመዝገብ ግልባጭ የተሰጠው ደግሞ በቀን 13/04/2010 ዓ.ም በእለተ አርብ በመሆኑ ይግባኙ የሚቀርብበት የመጨረሻው ቀን የመንግስት ሥራ ዝግ በሆነበት ቀን ላይ አርፏል፡፡አመልካችም በቀጣዩ ቀን ታሕሳስ 16 ቀን 2010 ዓ.ም ይግባኙን አቅርቧል፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበው ምክንያት በቂ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 326 መሠረት መዝገቡን የዘጋው ቢሆንም የይግባኝ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ከሆኑት ስልሳ ቀናት ውስጥ ሁለቱ ቀናት በአመልካች ችግር የባከኑ ካለመሆናቸው ባሻገር ይግባኝ የማቅረቢያው የመጨረሻ ቀን የመንግስት ስራ ዝግ በሆነበት ቀን ላይ ያረፈ በመሆኑ፤የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1862 ግዴታው የሚፈጸምበት ቀን ከአንድ የበአል ቀን ጋር ከገጠመ በዓል ባልሆነበት በማግስቱ ባለው የሥራ ቀን እንደሚተላለፍ በሚደነግገው አግባብ በተመሣሣይ ሁኔታ አመልካችም ጊዜ ሳያባክን በቀጣዩ የሥራ ቀን ይግባኙን አዘጋጅቶ ያቀረበ ከመሆኑ እና ይግባኝ ሕገ መንግስታዊ ዋስትና ያለው መብት ከመሆኑ አኳያ አመልካች ይግባኙ እንዲከፈት ያቀረበው ምክንያት በቂ ነው ተብሎ ይግባኙ እንዲከፈት መፍቀድ ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት ይግባኙ እንዲከፈት መፍቀድ ሲገባው አመልካች ይግባኙ እንዲከፈት ያቀረበው ምክንያት በቂ አይደለም በማለት መዝገቡን መዝጋቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 00039 ታሕሳስ 30 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ይግባኙ እንዲከፈት ያቀረበው ምክንያት በቂ ምክንያት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 326/1 መሠረት ይግባኙን እንዲያቀርብ ተፈቅዶለታል፡፡
3. አመልካች የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በአሥር ቀን ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ያቅርብ ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.139313

መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች - ዳኜ መላኩ
ተክሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
ቀነአ ቂጣታ
ፀሃይ መንክር

አመልካች - የኢትዮጵያ አየር መንገድ አልቀረቡም
ተጠሪዎች - 1ኛ. ወ/ሮ መሰረት ፍቃዱ ተወካይ አበበች ዘመድኩን ቀረቡ
2ኛ. ገልፍ አየር መንገድ ጠ/ ዮዲት ጉርጂ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሳለፉት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሣሽ ሲሆኑ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት በታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም ከሳውዲ አረቢያ ወደ ኢትዮጵያ በአየር መንገዱ ተሳፍሬ ግምታቸው ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) የሚያወጡ ልብሶች እና ቁሳቁሶች በመያዝ የመጣሁ ሲሆን የመጣው ዕቃ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ ሴክሽን ከሌላ ዕቃ ጋር በመለዋወጡ ጠፍቷል፤ እነሱ ደግሞ 2ኛ ተጠሪን ጠይቂ እያሉ እያመላለሱኝ ይገኛሉ፤ በመሆኑም ንብረቴ በመጥፋቱ የንብረቱ ግምት ይከፈለኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
2. አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ዕቃውን ሊረከብ የቻለው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባለው የማመቻቸት ስምምነት መሰረት ነው፤ በዚህ ስምምነት የአመልካች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኃላፊነት ዕቃው መጥፋቱን ለ2ኛ ተጠሪ ማሳወቅ ብቻ ነው፤ በዚህም መሰረት አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ አሳውቋል፤ ስለሆነም ኃላፊነት የለብኝም፤ በሌላም በኩል የዕቃው ግምት ብር 30,000.00 ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

3. 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ ከአመልካች ጋር ባላቸው ስምምነት መሰረት አመልካች የ2ኛ ተጠሪ የካርጎ ወኪል ነው፤ የ2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት ዕቃውን የማጓጓዝ ብቻ ነው እንጂ ዕቃዎቹ በአግባቡ መጫናቸውን እና መውረዳቸውን በሚመለከት የአመልካች ኃላፊነት ነው፤ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ ስለጉዳዩ ያሳወቀው ነገር የለም፤ ዕቃው የጠፋው በአመልካች ካርጎ ሴክሽን ውስጥ ከሌላ ዕቃ ጋር በመቀያየሩ ነው፤ ስለሆነም ዕቃው የጠፋው በአግባቡ ከተጓጓዘ በኃላ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ምንም ኃላፊነት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡
4. ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው ንብረት የጠፋው በ2ኛ ተጠሪ ጥፋት ሳይሆን በአመልካች ካርጎ ክፍል "ዕቃ ተቀያይሮ" መሆኑ የታመነ ፍሬ ነገር በመሆኑ የመካስ ኃላፊነት ያለበት አመልካች ነው፤ ሊከፍል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተም አመልካች ዕቃው በጠፋ ጊዜ ከሳሽን ያስፈረማቸው ሰነድ ላይ የጠፋው ዕቃ የዋጋ ግምት በማለት ያሰፈሩት 4,500 የሳውዲ ሪያል ወይም ብር 26,426.00 (ሃያ ስድስት ሺህ አራት መቶ ሃያ ስድስት) በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ ከነወለዱ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡
5. በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ የይግባኝ ክርክሩን ከሰማ በኃላ አመልካች ኃላፊ ነው ተብሎ ገንዘቡን እንዲከፍል መወሰኑን የተቀበለው ሲሆን 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ ውል የፈፀመ በመሆኑ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ ቢኖርበትም ከሳሽ ባቀረቡት ክስ ላይ ስሙ ከመጠቀሱ ውጪ የዳኝነት ጥያቄ ያልቀረበበት በመሆኑ ከፍ/ብሄር ስነ ስርዓት አንፃር በግልፅ ባልተጠየቀ ዳኝነት የካሳ ገንዘቡን 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍል የሚወሰንበት አግባብ የለም፤ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ በውጤት ደረጃ ሊፀና ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

6. የሰበር ቅሬታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች መጋቢት 12/2009 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር ማመልከቻ ዕቃው ከሳውዲ አረቢያ ወደ አዲስ አበባ የመጣው በ1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪ መካከል ባለው የማንገዝ ውል መሰረት በመሆኑ፤ በዋርሶው ስምምነት አንቀጽ 18(2) መሰረት አንገቡ ዕቃውን አንጉዞ መብት ላለው ሰው እስከሚያስረክብ ድረስ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የሚደነግግ በመሆኑ፤ አመልካች ዕቃውን ሊረከብ የቻለው ዕቃውን ከ2ኛ ተጠሪ ተረክቦ 2ኛ ተጠሪን በመወከል ለ1ኛ ተጠሪ ለማስረከብ በገቡት የማመቻቸት ውል ከመሆኑ ወጪ በ1ኛ ተጠሪ እና በአመልካች መካከል የውልም ሆነ የህግ ግንኙነት ባለመኖሩ አመልካች ኃላፊነት አለበት ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ አመልካች ኃላፊነት የለበትም በሚል እንዲወሰን ጠይቋል።
7. ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ 2ኛ ተጠሪ የንብረቱ አንሺር ሆኖ እያለ ከኃላፊነት ውጪ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።
8. 1ኛ ተጠሪ ሚያዚያ 16/2009 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች የ1ኛ ተጠሪን የንብረት ግምት ከፍሎ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባላቸው ግንኙነት መሰረት 2ኛ ተጠሪን ከሶ ከመጠየቅ ውጪ የ1ኛ ተጠሪን ንብረት አልከፍልም በማለት ያቀረበው አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል።
9. 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ሚያዚያ 25/2009 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ዕቃው የጠፋው በአመልካች አየር መንገድ ካርጎ ሴክሽን ክፍል ውስጥ ከሌላ ዕቃ ጋር ተቀያይሮ መሆኑ በአመልካች በራሱም የታመነ በመሆኑ አመልካች በቸልተኝነት ከሌላ እቃ ጋር በማቀያየር እንዲጠፋ ማድረጉ አመልካችን በኃላፊነት ከሚያስጠይቀው ውጪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ግንኙነት የለውም፤ 2ኛ ተጠሪ ዕቃውን አላንገዘም እንጂ አንጉዟል ቢባል እንኳ ዕቃው የጠፋው በአግባቡ ከተራገፈ በኋላ በአመልካች ካርጎ ሴክሽን ክፍል ውስጥ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ምንም አይነት ኃላፊነት የለበትም በማለት ተከራክሯል። አመልካቹም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

10. ከፍሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥና በሰበር የተደረገውን ክርክር ሲሆን በበኩላችን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ውል የፈፀመ በመሆኑ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ እንደሚኖርበት ወስኖ ነገር ግን ከሳሽ ባቀረቡት ክስ ላይ ስሙ ከመጠቀሱ ውጪ የዳኝነት ጥያቄ አልቀረበበትም በሚል ገንዘቡን 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍል የሚወሰንበት አግባብ የለም በማለት መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡
11. ይህን ጭብጥ ለመወሰን የሥር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተቀበሉትን እና ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የዋርሶ ስምምነት (በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ቁጥር 4 እንደተሻሻለ) ተገቢ ድንጋጌዎችን ይዘትና ትርጉም እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ መርምረናል፡፡
12. ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለው የሥር ሁለቱም ተከሳሾች ዕቃው ስለመጥፋቱ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ይልቁንም የየበኩላቸውን ክርክር በማቅረብ ኃላፊነት እንደሌለባቸው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች አከራካሪውን ንብረት መረከቡን እና ከእጁ የጠፋ መሆኑን ሳይክድ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ከከሳሽ ጋር የማንገዝ ውል ያደረገው 2ኛ ተጠሪ ሊሆን እንደሚገባና ዕቃውን ሊረከብ የቻለው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባለው የማመቻቸት ስምምነት መሰረት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ነገር ግን አመልካች ንብረቱን የተረከበ መሆኑና የጠፋውም በአመልካች ዕቃ ማስቀመጫ ካርጎ ሴክሽን ውስጥ የመሬት መስተንግዶ ስራ ግዴታውን በሚፈጽምበት ጊዜ ከሌላ ዕቃ ጋር ተቀያይሮ መሆኑ ያልተካደ በመሆኑ በዚህ መልኩ በአመልካች ጥፋት ለጠፋው ንብረት አመልካች ኃላፊ የማይሆንበት የህግ ምክንያት የለም፡፡
13. በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ዕቃውን አላንገዝኩም እንጂ አንጉዘሃል ብባል እንኳ ዕቃው የጠፋው በአመልካች እጅ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የተከራከረ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ዕቃውን በውል በማንገዝ ከውል የመነጨ ኃላፊነት እንዳለበት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ በ2ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበ ቅሬታ የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ካሳውን ሊከፍል አይገባም በማለት የወሰነው በቀረበው ክስ በግልጽ ዳኝነት አልጠየቀበትም፤ ከፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ድንጋጌዎች አንጻር በግልጽ ባልተጠየቀ ዳኝነት 2ኛ ተጠሪ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካሳውን እንዲከፍል የሚወሰንበት ምክንያት የለም በሚል ነው። ይሁን እንጂ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የአሁን አመልካችን እና 2ኛ ተጠሪን በተከሳሽነት በመሰየም ኃላፊነት ያለበት ወገን ተለይቶ እንዲወሰንላቸው ባቀረቡት ክስ ተንጉዞ የመጣው ዕቃ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ ሴክሽን ከሌላ ዕቃ ጋር በመለዋወጡ የጠፋ በመሆኑና አመልካችም 2ኛ ተጠሪን ጠይቂ እያለ እያመላለሳቸው መሆኑን ጠቅሰው የንብረቱ ግምት እንዲከፈላቸው መጠየቃቸውን ክሱ መረዳት ይቻላል። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 36(5) እንደተደነገገው ከሳሽ መብቱን ማግኘት የሚገባው ከየትኛው ተከሳሽ ላይ እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ የሚያጠራጥር ሁኔታ ያጋጠመው ሲሆን አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ሰዎች በህብረት በመክሰስ አላፊነቱ የሚመለከተው የትኛው እንደሆነ ተለይቶ እንዲወሰንለት ለማመልከት ይችላል። ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ በዚህ አግባብ በሁለቱ ተከሳሾች ላይ ክስ ማቅረባቸው የሚነቀፍ ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ በክሱ ስሙ ከመጠቀሱ ውጪ የዳኝነት ጥያቄ አልቀረበበትም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ እና ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም።

14. በአጠቃላይ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ 2ኛ ተጠሪን በተከሳሽነት ስሙን ከማስገባት ውጪ በሱ ላይ ዳኝነት ስላልጠየቁ 2ኛ ተጠሪ ካሳ ሊከፍል አይገባም በማለት የተደረሰበት መደምደሚያ የቀረበውን ክስ እና ከፍሲል የተጠቀሰውን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል። ተከታዩንም ወስነናል።

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 102697 ሀምሌ 8 ቀን 2008 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ፤ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 182461 መጋቢት 1/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።
2. በ1ኛ ተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት 2ኛ ተጠሪ ከውል የመነጨ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ተረጋግጦ ከተወሰነ በኋላ የዳኝነት ጥያቄ አልቀረበበትም ገንዘቡን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊከፍል አይገባም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የዳኝነት ጥያቄውን እና ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ተሽሯል፡፡

3. አመልካች ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ብር 26,426.00 (ሃያ ስድስት ሺህ አራት መቶ ሃያ ስድስት) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለ1ኛ ተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
5. መጋቢት 20/2009 ዓ.ም በዋለ ችሎት በሥር ፍርድ ቤት በመ/ቁ 153294 የተጀመረው አፈፃፀም እንዲታገድ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 153610

መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፈይዛ ከሚል ጠበቃ ልሣነወርቅ ተኪ- ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ አህመድ -ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጠተናል፡፡

ፍርድ

የክርክሩ ምክንያት የፍቺ ውጤት የሆነው የንብረት ክርክር ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች የካቲት 10 ቀን 2007 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በ23/04/2007 ዓ/ም በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ መፍረሱ፣ በትዳር ውስጥ ከሚያዚያ 1995 ዓ/ም ጀምሮ ከቤት እስከወጡበት የካቲት 2006 ዓ/ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ ን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 12 ክልል ውስጥ ባለአንድ ፎቅ ዘመናዊ ቪላ ቤት፣ የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ፣ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ A-13872 የሆነና ግምቱ ብር 550,000 የሚያወጣ ያሪስ መኪና፣ በሀሰን ላውንደሪ ንግድ ቤት ውስጥ በአቶ ሰኢድ መሀይን ዳኝነትና በአቶ ኤልያ ሰይድ ጸሓፊነት ብር 480,000.00 የእቁብ ገንዘብና የቤት ቁሳቁሶችን ያፈሩ መሆኑን ዘርዝረው ክፍፍሉ እንዲደረግ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ ዳኝነት የተጠየቀበት ቤት የተሰራው በ12/01/1994 ዓ/ም ሆኖ አመልካችና ተጠሪ ደግሞ በሸሪዓ ህግ መሰረት የተጋቡት ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም በመሆኑ ንብረቱ የተፈራው ከጋብቻ በፊት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሆኑን፣ ቤቱን ለመስራት የሚያሥችላቸው ገቢ ስላልነበራቸውም አባታቸውን በላውንደሪ ስራ ስለሚረዱ ቤቱን ከጋብቻ በፊት ወላጅ አባታቸው አቶ አህመድ መሃመድ ሰርተው የሰጧቸው መሆኑን የእቁብ ገንዘብ በጋብቻ እያሉ ታህሳስ 29 ቀን 2004 ዓ/ም ደርሶአቸው ለትዳራቸው ለጋራ ጥቅም ያዋሉት መሆኑን በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13 ክልል ውስጥ በቤት ቁጥር 069 በአቶ መሃመድ ይማም ዳኝነት፣ በአቶ እንድሪስ አለሙ ጸሐፊነት፣ በአቶ ወንድሜነህ አለሙ ሰብሳቢነት የነበረው እቁብም ለመክፈል ባለመቻላቸውም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 38976 ክስ ቀርቦባቸው ገንዘቡን እንዲከፍሉ ታህሳስ 30 ቀን 2005 ዓ/ም ተወስኖባቸው ከወጪ ኪሳራ ጋር ብር 149,365.95 እንዲከፍሉ በመገደድ መኪናውን ሸጠው እዳውን ከከፈሉ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ ለትዳር ጥቅም ያዋሉ መሆኑን፣ አመልካች ከቤት የወጡት የካቲት 26 ቀን 2006 ዓ/ም ሳይሆን ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ/ም መሆኑን፣ በአቶ ሀሰን ላውንደሪ በአቶ ሰይድ መዘይን ዳኝነት በአቶ ኤልያስ ሰይድ ጸሐፊነት በሚሰበሰብ እቁብ ውስጥ የሌሉበት መሆኑን እና የቤት ቁሳቁሶችን ቢካፈሉ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ዘርዝረው ተከራክረዋል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን ሰባት ጭብጦችን በመመስረት የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል ሰምቶና ጉዳዩን መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ ሲፈርስ በሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም የተደረገ ጋብቻ ፈርሷል የተባለ ቢሆንም ተጠሪው የጋብቻ ሰርተፊኬት ጋብቻው በሐይማኖት ስርዓት ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ተፈፅሞ በውልና ክብር መዝገብ ሹም አገልግሎት በ09/09/2003 ዓ/ም ተመዝግቦ ህጋዊ መረጃ እንደተሰጣቸው የሚያሣይ ማስረጃ ያቀረቡና አመልካችም ይህንን ማስረጃ አልካዱም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ እና ቀድሞ በፍቺ ጊዜ ጋብቻው የተፈጸመበት ጊዜ ሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም ነው ተብሎ የተሰጠውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 208 ስር የሚወድቅ ስህተት ነው በማለት ይህንኑ ስህተት ነው ያለውን ጊዜ አርሞ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻው የተፈጸመው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ነው፣ ቤቱ የተሰራውም ከዚህ በፊት መሆኑ ስለተረጋገጠ የተጠሪ የግል ሃብቱ ነው፣ አመልካች ከቤት የወጣችው ከየካቲት 2006 ዓ/ም በፊት ነው፣ በጋብቻ ጊዜ የጋራ እዳ የነበራቸው መሆኑ ተረጋግጧል። ኮድ ቁጥር 2 A-13872 መኪና ለጋራ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እዳ የተሸጠ መሆኑ ስላልተረጋገጠ መኪናው የጋራቸው ነው፣ እቁቡን በተመለከተም የወጣላቸው መሆን ያለመሆኑንና የገንዘብ መጠን ምን ያህል እንደሆነ አመልካች ያላስረዱና ተጠሪ ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ መሆኑም ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ የቤት ዕቃዎችን በተመለከተ በተጠሪ በታመነው መሰረት እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል። ከዚህ ውሳኔ ውስጥ በጋብቻ ጊዜ፣ በቤቱና በእቁቡ ላይ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የአሁኗ አመልካች ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን ለፌዴደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 208 መሰረት የጋብቻውን ጊዜ ማረመ፡ ፍፁም የሥነ ስርዓት ህጉንና መሰረታዊ የዳኝነት አሰራር መርህን ያልተከተለ መሆኑን ከገለጸ በኋላ በውጤት ደረጃ ግን ለጋብቻ መኖር መቅረብ ያለበት የጋብቻ ምስክ ወረቀት በመሆኑ ይኼው ሰነድ መቅረቡ ተገቢ እንደሆነ ዘርዝሮ ጋብቻው የተፈፀመው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍልና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በቤቱ ላይ ተሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል። የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የሥር ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ጋብቻ እንዲፈርስ ውሳኔ በሰጠበት ጊዜ ጋብቻው በሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም መሆኑን በግልጽ አስፍሮ ውሳኔ በሰጠበት እና በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔም በይግባኝ ባልተለወጠበት ሁኔታ በንብረት ክርክር ጊዜ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ተቀብሎ ጋብቻው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም የተፈጸመ ነው በማለት መወሰኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 208 ጋር አብሮ በማይሄድ ምክንያት ከመሆኑም በላይ አመልካችና ተጠሪ ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ግንኙነት ፈጥረው በ1996 ዓ/ም አመልካች አርግዘው በ1997 ዓ/ም ልጅ የወለዱ መሆኑና ቤቱም ተጠሪ በ1994 ዓ/ም በጨረታ ባገኙት ቦታ ላይ በትዳር ውስጥ መሰራት ተጀምሮ ቤቱ ተሰርቶ የተጠናቀቀው በ2000 ዓ/ም መሆኑ ከሚመለከተው አካል ለስር ፍርድ ቤት በተላከው ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ እያለ ይኼው ማስረጃና በጉዳዩ ላይ የተሰሙት ምስክሮች ቃል በአግባቡ ሳይታይ መታለፉን፣ የእቁብ ገንዘብን በተመለከተ አመልካች የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ፈጽመው ምስክሮችን አላቀረቡም የተባለው አመልካችም መጥሪያውን ለእቁቡ ዳኛና ሰብሳቢ ለማድረስ ጥረት አድርገው ምስክሮቹ አውቀው እየተደበቁ ስላስቸገሩኝ በሚኖሩበት ወረዳ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስተዳደር በኩል እንዲደርሳቸው በማለት በቃለ መሃላ አቤቱታ አመልካች አቅርበው እያሉ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ በማየት ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው ምስክሮቹ በአመልካች ጉድለት እንዳልቀረቡ በመቁጠር ውሳኔ መስጠቱ ያላግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡ እንዲሁም የሥር ፍርድ ቤትና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መዛግብትም እንዲመጡ ተደርጎ የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት መዝገብ መጥቶ የሥር ፍ/ቤት የመዝገብ ግልባጭ የያዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሥፈልጋቸው አበይት ጭብጦች የሥር ፍርድ ቤት በፍቺ ውሳኔ የለየውን የጋብቻ ጊዜ በንብረት ክርክር ጊዜ በመመልከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 208 መሰረት ማረሙ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተጠሪ የግሉ ነው በማለት የወሰነበት አግባብና እቁቡን በተመለከተ የተሰጠው ዳኝነት ተገቢ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት እያንዳንዳቸውን ነጥቦች በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

የመጀመሪያውን የጋብቻ ጊዜውን በተለመከተ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ሁለት ጊዜ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን የክርክ ሂደት ያስገነዝባል፡፡ ይኼውም አንዱ በፍቺ ውሳኔ ጊዜ ሲሆን በዚህ ጊዜ ጋብቻው በሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም የተፈጸመ መሆኑን ማረጋገጡን አምኖ ጋብቻው እንዲፈርስ መወሰኑን በ23/04/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ያስገነዝባል፡፡ ሁለተኛው ውሳኔ በንብረት ክርክር ጊዜ የተሰጠ ሲሆን በዚህ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው ተጠሪው ጋብቻው የተፈፀመው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ነው በማለት ተከራክረው በዚህ ረገድም የጋብቻ ምስክር ወረቀት ለማስረጃነት አቅርበው ይኼው የሰነድ ማስረጃ ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም የተፈፀመው ጋብቻ ግንቦት 09 ቀን 2003 ዓ/ም በውልና ክብር መዝገብ ስም አገልግሎት መመዝገቡን የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሶና ቀድሞ በፍቺ ውሳኔ ጊዜ ጋብቻው ሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም የተፈፀመ ነው የተባለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 208 ድንጋጌ መሠረት ሊታረም ይገባዋል በማለት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሠጠው ውሳኔ ነው ። ከዚህም መረዳት የሚቻለው የሥር ፍርድ ቤት በፍቺ ውሳኔ ላይ ጋብቻው የተፈጸመው ሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም መሆኑን በግልጽ ዳኝነት ሰጥቶ ከቆዩ በኃላ በስርዓቱ መሰረት በበላይ ፍ/ቤት ባልተለወጠበት ሁኔታ በንብረት ክርክር ጊዜ ጋብቻዉ የፈፀመዉ ጥር 20 ቀን 1997ዓ.ም ወደሚለዉ ድምዳሜ የደረሰና ለዚህ ዉሳኔ አሰጣጥ ተገቢ ነዉ ብሎ በዋቢነት የጠቀሰው ድንጋጌም የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 208 መሆኑን ነዉ።

የክርክሩ መነሻ ጋብቻን መሰረት ያደረገ ሲሆን የሚመራውም በተሻሻለዉ የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ድንጋጌዎችና በፍታብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ እንዲሁም አግባብ ባላቸው የአዋጅ ቁጥር 25/1988 ድንጋጌዎች መሠረት ነው። በአዋጅ ቁጥር 25/1988 እንደተመለከተዉ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረ ክርክር ተገቢዉን ዉሳኔ ካገኘ በኃላ በይግባኝ የሚታየዉ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ሲሆን ይህ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ነዉ። በዉሳኔዉ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚለዉ ወገን አቤቱታን ማቅረብ ያለበት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነዉ። የፌ/ከ/ፍ/ቤት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ታይቶ የተሰጠዉን ዉሳኔ ከሻረዉ ግን በዉሳኔዉ ላይ ቅሬታ ያለበት ወገን ይግባኙን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ማቅረብ እንደሚችልም በአዋጁ ተመልክቷል። ይህ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ቅሬታ ያለዉ ተከራካሪ ወገን ከዚህ በኃላ አቤቱታዉን ሊያቀርብ የሚችለዉ ለሰበር ችሎት ነዉ። ከዚህ ዉጪ በሆነ ሁኔታ ዉሳኔዉ ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል አይችልም። ይህ እንግዲህ አጠቃላይ ሂደቱ (ስርአቱ) ሲሆን ዉሳኔዉን በመቃወም ወደ በላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት ወይም አቤቱታ ለማቅረብ የሚፈልግ ተከራካሪ ወገን ውሳኔውን በሰጠዉ ፍ/ቤት ሊታረም የሚገባ ወይም የሚችል ስህተት አለ ብሎ ካመነ ወደ በላይ ፍ/ቤት አቤት ከማለቱ በፊት ዉሳኔዉን ለሰጠዉ ፍ/ቤት አቤቱታ የሚያቀርብበት ስርአት እንዳለም ይታወቃል። የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 208 ጥያቄ የሚነሳዉም እዚህ ላይ ነዉ።

የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 208 ርእሱ እንደሚያመለክተዉ “ስህተት ስለማረም” በሚል የተደነገገ ነዉ። በዚህ ድንጋጌ መሰረት አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤት (ዉሳኔዉን የሰጠዉ) ሊያርም ወይም ሊያስተካክል የሚችለዉ በሰጠዉ ዉሳኔና ትእዛዝ ላይ የአፃፃፍ ስህተት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቁጥር አግባፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት መኖሩን ካረጋገጠ ብቻ ነዉ። ይህ ደግሞ ግልጽ ነዉ። በክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ እና ተያያዥነት ባለዉ ጉዳይ ላይ አከራክሮ የሰጠዉን ዉሳኔ ስህተትን ማረም በሚል ሊያሻሽል ወይም ሊለዉጥ አይችልም።

በያዝነዉ ጉዳይ እንደምናየዉ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ የሰጠበት ክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረዉ ጋብቻ የተፈፀመበት ጊዜን የሚመለከት ይህንንም ፍ/ቤቱ ከመረመረዉ በኃላ በ 23/4/2007ዓ.ም በሰጠዉ የፍቺ ዉሳኔ ጊዜዉ ሚያዝያ 1995ዓ/ም የሚል ግልጽ ዉሳኔ ሰጥቶበታል። ይህ ዉሳኔ በበላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ወይም በሰበር ስርዓት ቀርቦ ስለመለወጡ የሚያሳይ ክርክርም ሆነ ማስረጃ ተጠሪ አላቀረቡም። በ 23/4/2007ዓ.ም የፍቺ ዉሳኔ ከተሰጠ በኃላም ተጠሪ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 208 የተመለከተዉን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የጋብቻ ጊዜዉ እዲሻሻል አቤቱታ አላቀረቡም። ጉዳዩ በቤተሰብ ሕጉ የሚገዛ እንደመሆኑ መጠን የጋብቻዉን ጊዜ በፍቺ ዉሳኔ ለይቶ መወሰን ጋብቻዉ በንብረት ላይ ስለሚኖረዉ ህጋዊ ዉጤት ለመወሰን እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነዉ። ተጠሪ በፍቺ ጊዜ ጋብቻው የተፈፀመዉ ሚያዝያ ወር 1995ዓ/ም ነዉ ተብሎ በግልጽ የተወሰነዉን የዉሳኔ ክፍል በበላይ ፍ/ቤት ሳያስቀይሩ በንብረት ክፍፍል ላይ ክርክር ሲደረግ የጋብቻዉ ጊዜ 1995ዓ/ም ሳይሆን ጥር 20 ቀን 1997ዓ/ም በማለት ያቀረቡት ክርክር በይዘቱ ሲታይ በፍቺ ዉሳኔ ላይ የተሰጠዉን መሰረታዊ የፍርድ ይዘት የሚቀይር እንጂ በተሰጠዉ ዉሳኔና ትእዛዝ ላይ የአግባፍ ስህተት የቁጥር አግባፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት እንዲታረም የቀረበ ነዉ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም። ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤትም በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤት የተከተለዉ የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ የስነ ስርዓት ሕጉንና መሰረታ የዳኝነት አሰራር መርህን ያልተከተለ መሆኑን እያረጋገጠ ለጋብቻ መኖር መቅረብ ያለበት የጋብቻ ምስክር ወረቀት ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በተጠሪ በኩል በይግባኝ ስርዓት ወይም በመስቀለኛ ይግባኝ አግባብ ጊዜዉን ጠብቆ የቀረበለት አቤቱታ በሌለበት በመሆኑ በህግ አግባብ ያልቀረበለትን ክርክርና ማስጃ በመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ መቀበል የሚቻልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ያላገናዘበ በተለይም በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.342 አግባብ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ ምክንያቱን ለዉጦ የሚያጸናዉ በሕግ አግባብ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበ ክርክርና ማስረጃ መኖሩን በማረጋገጥ ስለመሆኑ የተመለከተዉን ድንጋጌም ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የተጠሪ ጥያቄ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት የሚስተናገድ ባልሆነበት ሁኔታና የጋብቻውን ጊዜ በፍቺ ውሳኔ ጊዜ ለይቶ መወሰን በንብረት ክፍፍሉ ክርክር ላይ የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎችን በትክክል ለመተግበር የሚያስችል በሆነበት ሁኔታ ይህንኑ በጣሰ መልኩ ጋብቻው የተፈፀመው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ.ም ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መወሰኑም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይኼው የስር ፍርድ ቤት የፍርድ አሰጣጥ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 208 ድንጋጌ የወጣ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የጋብቻ መኖር በቅድሚያ ለማስረዳት የሚቻለው የጋብቻ ምስክር ወቀት በማቅረብ ነው በሚል ምክንየት ብቻ በስነ ስርዓት ሕጉ ያልቀረበውን ክርክርና ማስረጃ በመቀበል በውጤት ደረጃ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የተቀበለበት አግባብ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻው የተመሰረተው በሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም ነው ወደሚል ድምዳሜ ደርሰናል፡፡

ቀጥለን የተመለከትነው በጋብቻ ውጤቶች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ተገቢነት ሲሆን በአመልካች እስከዚህ ችሎት ከሚከራከሩባቸው ንብረቶች መካከል አንዱ በኢዲስ አበባ ከተማ ን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ክልል ውስጥ የሚገኘውና ባለአንድ ፎቅ ዘመናዊ ቪላ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ ይህን ቤት የግል ንብረት ነው በማለት የሚከራከሩት ቤቱ የተሰራው በ12/01/1994 ዓ/ም ነው፣ ጋብቻው ደግሞ ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ነው የተፈፀመው በሚል ነው፡፡ ሆኖም ጋብቻው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ.ም ነው የተፈፀመው የሚለው የተጠሪ ክርክር ከላይ በዝርዝር በተመለከተው ስነ ስርዓታዊ በሆነ ምክንያት ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን ቤቱ የተሰራው በ12/01/1994 ዓ/ም የሚለው ክርክር ግን በስር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ የተሰሙት ምስክሮች ከሰጡት የምስክርነት ቃልና የክፍሉ የመንግስት አስተዳደር አካል ለስር ፍርድ ቤት ከሰጠው ማስረጃ አንፃር ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ሶስት ምስክሮችን ያሰሙ ሲሆን የሰጡት የምስክርነት ቃልም ሲታይ 1ኛው ምስክር አመልካች ጸንሰው እያለ በ1996 ዓ/ም በን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ አካባቢ ቤት መስራት ጀምረዋል፣ በ1997 ዓ/ም ቤቱ ተሰርቶ ሳይጠናቀቅ ገብተዋል በማለት ሲመሰክሩ 2ኛው ምስክራቸው ደግሞ በ1997 ዓ/ም የአመልካችና የተጠሪ ቤተሰብ ቅልቅል ተደርጎ በዚያ ዝግጅት ቤት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መገኘታቸውን፣ ቤቱ በተወሰነ መልኩ ያለማለቁን፣ ሆኖም መቼ እንደተጀመረ እና እንደአለቀ የማያውቁ መሆኑን ገልፀው ሲመሰክሩ 3ኛ ምስክር ሁነው አመልካች የሰጡት የምስክርነት ቃል ደግሞ ጋብቻቸውን ናዝሬት ከተማ በ1995 ዓ/ም አድርገው ጥር ወር 1996 ዓ/ም ማርገዛቸውን፣ የካቲት ወር 1997 መውለዳቸውን ከጋብቻ በፊት ተጠሪ በ1994 ዓ/ም የቤቱን መሰሪያ ቦታ በጨረታ እንዳገኘ እንደነገሯቸው፣ ከተጋቡ በኃላ በ1995 ዓ/ም ቁፋሮ እንዳዩና በ1997 ዓ/ም ቤቱ ተሰርቶ ጥቂት ነገር ሲቀር የቤተሰብ ቅልቅል ተደርጎ ቤቱ እንደገቡ፣ ቤት ከተገባ በኋላ እንደተሰራ መመስከራቸውን የሚያሳይ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግለባጭ ተመልክተናል። ተጠሪ በበኩላቸው ሁለት ምስክሮች ያሰሙ ሲሆን 1ኛው ምስክራቸው ወላጅ አባታቸው መሆኑን ገልፀው በሰጡት የምስክርነት ቃል ጋብቻው በ1997 ዓ/ም እንደተፈጸመ፣ አመልካችና ተጠሪ በሚኖሩበት ቤት አቶ ጫላ በተባለው መሃንዲስ በ1994 ዓ/ም ቤቱን ለማሰራት ውል ተዋውለው መሃንዲሱም በ1996 ዓ/ም መግቢያ ላይ አጠናቅቆ ቤቱን ያስረከባቸው መሆኑን፣ ቤቱንም ልጃቸው የሆኑት ተጠሪ በላውንደሪ ስራ ስለሚያገለግሏቸው በራሱ ገንዘብ ያሰሩለት መሆኑን የመሰከሩ ሲሆን የተጠሪ ሁለተኛው ምስክር ደግሞ ቤቱን የሰሩ መሆናቸውን ገልጸው በሰጡት የምስክርነት ቃል ቤቱን ሰኔ 10 ቀን 1994 ዓ/ም በተደረገ በግንባታ ውል ከተጠሪ አባት ጋር እንዳደረጉ፣ ግንባታውን አንድ አመት ከሁለት ወር ፈጅቶባቸው በ1995 ዓ/ም መጨረሻ አካባቢ ለተጠሪ አባት ማስረከባቸውንና ቤቱንም ያሰሩት የተጠሪ አባት መሆናቸውን፣ ቤቱ ሊጠናቀቅ አከባቢ አመልካች መጥተው ማየታቸውን፣ ቤቱ ሙሉ በሙሉ አልቆ ያስረከቡ መሆኑን ዘርዝረው መስክረዋል። በ2ኛው የተጠሪ ምስክርና በተጠሪ ወላጅ አባት መካከል ሰኔ 10 ቀን 1994 ዓ/ም የተረገው የግንባታ ውልም ለማስረጃነት እንዲቀርብ ተደርጎአል። በሌላ በኩል በአዲስ አበባ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በሊዝ ደንብ ቁጥር3/87 መሰረት የቦታ ቁጥር 4073/93 የግንባታ ስራ ፈቃድ ውል ከተጠሪ ጋር የተደረገ የቦታ ካርታ እና የቦታ አቀማመጥን የሚገልፅ በ01/13/93 ዓ/ም የተዘጋጀ፣ የመኖሪያ ቤት ስራ ለመስራት በቀን 23/01/1994 ዓ/ም የተሰጠ ፈቃድ ለስር ፍርድ ቤት የላከ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጂንሲ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በቁጥር የማ/ን/ም/መ/ኤ 590/2008 በቀን 09/05/2008 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የይዞታ ካርታው በቀን 12/01/94 ዓ/ም እንደተሰጠ፣ የግንባታ ፈቃድ ደግሞ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በ23/01/94 ዓ/ም መሰጠቱንና ስለግንባታው መኖር በ12/10/2000 ዓ/ም የተረጋገጠ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ መግለፁን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተመልክተናል፡፡ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ካላይ የተመለከቱትን ሲሆኑ ቀጥሎ መነሳት ያለበት የህግ ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት እነዚህን ፍሬ ነገሮችን ከተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ዳኝነት ሰጥቶቷል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለውን ነው፡፡

በመሠረቱ የተጋቢዎችን ንብረትን ሃብት አስመልክቶ የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 የጋራ ንብረት እና የግል ንብረት የሚመራበትን ስርዓት ይደነግጋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62 /1/ ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኙዋቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናሉ በማለት የደነገገ ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብታቸው ነው ካልተባለ በስተቀር ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ክርክር የተነሳበት ቤት የተሰራበት ቦታ በሊዝ ውል የተገኘው ከሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም በፊት መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ግንባታው የተጀመረውና የተጠናቀቀው የግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ አብረው ባሉበት ወቅት ስለመሆኑ የአመልካች የሰው ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጂንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቁጥር የማ/ን/ም/መ/ኤ 590/2008 በቀን 09/05/2008 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳበቤ ከሰጠው መግለጫ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ቃል ሲታይ ግን የሚመለከተው አካል ከሰጠው መግለጫ ጋር አብሮ የማይሄድ በመሆኑ የማስረጃነት ዋጋ ሊሰጠው የሚችል አይደለም፡፡ ተጠሪና አመልካች ከሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም በፊት በፍቅር ግንኙነት ውስጥ የነበሩ መሆኑና አመልካች በግልጽ ጠቅሰው ያቀረቡትን ክርክርም ተጠሪ ማስተባበያ ክርክር ያላቀረቡበት መሆኑን የተገነዘብን በመሆኑ ተጠሪ የመንግስትና የህዝብ ንብረት የሆነውን ይዞታ በሊዝ ውል በስማቸው ወስደው ቆይተው በቦታው ላይ ንብረቱን ያሰፈሩት ከአመልካች ጋር ሕጉ ጥበቃ በሚያደርገው ግንኙት ውስጥ መሆኑ ተረጋግጧል፤ ስለሆነም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 57፣62 እና

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

63 ድንጋጌዎች አግባብ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት ሊባል የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመጨረሻ የተመለከትነው በእቁቡ ላይ የተሰጠውን ውሳኔን ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲያቀርቡ ክፍፍል እንዲደረግ ዳኝነት የጠየቁት በሀሰን ላውንደሪ የንግድ ቤት ውስጥ በአቶ ሰይድ መሀይን ዳኝነት በአቶ ኤልያስ ሰይድ ፀሓፊነት የሚጣለውን የእቁብ ገንዘብ ብር 480,000.00 ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ረገድ በቀረበው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ላይ መልስ ሲሰጡ እቁቡ ታህሳስ 29 ቀን 2004 ዓ/ም ደርሶአቸው ለጋራ ትዳር ጥቅም ያዋሉ መሆኑን ከዚህ ውጪ በእቁቡ የሌሉበትና ክሱ ሐሰት መሆኑን ገልፀዋል፡፤ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አመልካች ራሳቸው በሰጡት የምስክርነት ቃል የእቁቡ ገንዘብ ስንት እንደሆነና መቼ እንደወጣላቸው በእርግጠኝነት ያልገለጹ መሆኑንና የእቁቡ ዳኛ እና ፀሐፊዎች ቀርበው እንዲያስረዱ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቶላቸውም ትዕዛዙም አድርሰው ምስክሮቹ ቀርበው እንዲያስረዱ ያላደረጉ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ አጥብቀው የሚከራከሩት የእቁቡ ዳኛ እና ፀሓፊ ለምስክርነት እንዲቀርቡ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ለማድረስ ጥረት ቢያደርጉም ምስክሮቹ አውቀው እየተደበቁ ስለአስቸገሯቸው ይህንኑ ለስር ፍርድ ቤት በቃለ መሃላ አሳውቀው ምስክሮቹ በሚኖሩበት ወረዳ አስተዳደር በኩል መጥሪያው እዲደርሳቸው ተደርጎ እንዲቀርቡ እንዲደረግላቸው ጠይቀው እያለ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው ትዕዛዝ ሳይኖር ምስክሮቹን አመልካች አላስቀረቡም ማለቱ ስህተት ነው በሚል መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ቀርቦም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ማመልከቻ መኖር ያለመኖሩንና የስር ፍርድ ቤት ተገቢው ብይን የሰጠበት ጉዳይ መሆን ያለመሆኑን ስንመለከትም አመልካች ለምስክሮቹ መጥሪያው በክፍሉ የወረዳው አስረዳደር በኩል እንዲደርሳቸው እንዲታዘዝላቸው መጠየቃቸውንና የሥር ፍ/ቤት በዚህ ጥያቄ ላይ ተገቢውን ትዕዛዝ ሳይሰጥ አልፎ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ ምስክር ማስረጃ እንደመሆኑ መጠን የሚቀርበው በፍርድ ቤት መጥሪያ ተደርጎለትና ይኼው መጥሪያም ምስክሩን ማስረጃዬ ነው ብሎ የቆጠረው ሰው በስነ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስርዓት ህጉ ከቁጥር 96 እስከ 102 ድረስ ስለመጥሪያ አደራረስ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን በመከተል መጥሪያውን ለምስክሩ እንዲያደርሰው በማድረግ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 116 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ለአንድ ጉዳይ ለምስክርነት የተቆጠረ ሰው ደግሞ በፍርድ ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርቦ የመመስከር ግዴታ ያለበት ሲሆን ምስክ ሊቀርብ ካልቻለም በሕግ አግባብ ተገዶ የሚቀርብ መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከቁጥር 116 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ምስክሩ በጥሪው መሠረት ላለመቅረብ ሆነ ብሎ እየተሰወረ ያስቸገረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ በታየው መንገድ ትዕዛዝ በመስጠት ተጠሪው ምስክር ተገዶ ወይም ታስሮ እንዲቀርብ ማዘዝ እንደሚገባው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 118(2)(ለ) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናይ የሥር ፍርድ ቤት ምስክሮችን ያላስቀረበው በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትሎ ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች እንዲቀርቡ የጠየቋቸው የዕቁብ ዳኛ እና ፀሐፊ ቀርበው መሰማታቸው ክርክሩ ከሚመራበት የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111፣ 249 እና 257 አኳያ እንደዚሁም ከማስረጃ አቀራረብና አቀባበል አኳያ ተገቢነት ያለው ሆኖ ሳለ የሥር ፍር ቤት እነዚህን ምስክሮች ሳይሰማ ለዚህ የሠበር አቤቱታ ምክንያት በሆነው የእቁብ ጉዳይ ውሳኔ መስጠቱም ሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ የፍርድ አመራር ጉድለት በይግባኝ ሳያርም መቅረቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረው ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ሣያጣሩ /ሣያነጥሩ/ መወሰን ደግሞ የፍርድ አካሄዱን ያልተሟላ የሚያደርግና የተከራካሪ ወገንን የመከራከር መብት የሚያጣብብ፣ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀም በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግንተናል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ ከተመለከቱት መረታዊና ህጋዊ ምክንያቶች አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤቶች ክርክር የተነሳበት ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው፣ እቁቡም በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 88409 ሚያዚያ 17 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 182989 መስከረም 13 ቀን 2010 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻው የተመሰረተው ጥር 20 ቀን 1997 ዓ/ም ነው ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር በፍቺው ወሳኔ መሰረት ጋብቻው ሚያዚያ ወር 1995 ዓ/ም ጀምሮ ያለ ነው ብለናል፡፡
3. በን/ስ/ላ/ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ክልል ውስጥ የሚገኘውና የቤት ቁጥር አዲስ የሆነው ክርክር የተነሳበት ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ ክፍፍሉም በቤተሰብ ሕጉ በተመለከተው አግባብ ሊከናወን ይገባል ብለናል፡፡
4. የእቁብ ገንዘቡን በተመለከተ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ነጥብ ላይ ብቻ ክርክሩን በመ/ቁጥር 188409 እንዲቀጥል አድርጎ የእቁቡን ዳኛ እና ጸሃፊ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 118(2)(ለ) አግባብ እንዲቀርቡ አድርጎ ምስክርነታቸውን በመስማትና ተገቢ ነው ካለም በሌላ ማስረጃም ጭምር ከአጣራ በኋላ አግባብነት ካለው የቤተሰብ ህግ ድንጋጌች አንፃር በመመልከት በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. በሌሎች የንብረት ክርክሮች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
6. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትእዛዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 12 ቀን 2010ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡ ይፃፍ

መዝገቡ ተዘግቶአል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ስ/ጌ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ.154727

ህዳር 26 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡.....1. ተክሊት ይመሰል
2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
3. ቀነዓ ቂጣታ
4. ተሾመ ሽፈራው
5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡.....አቶ ተክላይ ፍሰሃ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡.....ወ/ሮ ለታይ ለገሠ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የጀመረዉ በትግራይ ክልል ሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሽሬ እ/ስላሴ ምድብ ችሎት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.98593 በ14/6/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ በሽሬ እ/ስላሴ ከተማ 04 ቀበሌ ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን በ140 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያለዉን ቤት በብር 250 ሺህ ሸጠዉልኝ ገንዘቡን ተቀብለዉ ስመ ሀብቱን ሊያዛዉሩልኝ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ቤትና ቦታዉን ስመ ሀብት እንዲያዛዉሩልኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ከሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ቢሰጥም ተከሳሽ መጥሪያ ተቀብለዉ ያለ በቂ ምክንያት መልስ ይዘዉ ሳይቀርቡ በመቅረታቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡ ነገር ግን ተከሳሽ ክስ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ በቃል ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የከፍተኛዉ ፍ/ቤት የከሳሽ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት እና በመሐንዲሶች ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ሁለት ክፍል ማሻሻያ እና ሽንት ቤት ያለበትን ቦታ ለከሳሽ ሸጠዉ ከሳሽ ደግሞ በቦታዉ ላይ ሕንጻ ገንብተዉ ስለሚገኙ የሕንጻዉ ባለቤት ከሳሽ በመሆኑ፣ ቤትና ቦታዉ የከሳሽ በመሆኑ ተከሳሽ ስመ ሀብቱን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወደ ከሳሽ እንዲያዛውር በማለት ወስኗል። ይህ ጉዳይ በይግባኝ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች በ26/6/2010 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረበብኝ ክስ ላይ በ15/9/2010 ዓ.ም መልስ እንዲቀርብ ያዘዘ ሲሆን አመልካች በዚህ ቀን በችሎት ፊት ቀርቤ መልሴን በጽሑፍ አዘጋጅቼ ለማቅረብ ጊዜ ስላጠረብኝና ከጠበቃ ጋር ተማክሬ በቀጣይ ቀጠሮ መልስ እንዳቀርብ እንዲታዘዝልኝ የጠየቀኩኝ ሲሆን ፍ/ቤቱ መልሴን እንዳቀርብ ማዘዝ ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ የሰጠዉ ዉሳኔ እና የሥር የጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በማጽናት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ። ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ተሸሮ የጠየቅኩት ዳኝነት እንዲወሰንልኝ በማለት በዋናዉ ክርክርም በዝርዝር ቅሬታቸዉን አቅርቧል።

ይህ ችሎት ጉዳዩን በማየት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ23/9/2010 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የአሁን ተጠሪ በዋናዉ ጉዳይ ላይ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ነዉ የሚሉበትን ምክንያቶች በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክሯል። አመልካች የመልስ መልስ ስላላቀረበ ታልፏል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት የአሁን አመልካች በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ መታለፉ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል። በዚህ መሰረት የስር የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ሲታይ የአሁን አመልካች የፍ/ቤቱ መጥሪያ ደርሶት ያለ በቂ ምክንያት መልሱን ይዞ እንዳልቀረበ በመግለጽ መልስ የመስጠት መብቱን ማለፉን ያሳያል። በሌላ በኩል ከስር የጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር በፖሊስ በኩል የፍ/ቤትን መጥሪያ ለአመልካች በ8/9/2009 ዓ.ም የሰጠሁት ስለሆነ ለ15/9/2009 ዓ.ም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መልሱን ይዞ ለመቅረብ በቂ ጊዜ እንደነበረዉ ገለጸ ተከራክሯል። አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር በ10/9/2009 ዓ/ም መጥሪያ ቢመጣለትም አንብቡልኝ ብላቸዉ ሊያነቡልኝ ፈቃደኛ አልሆኑም፤ አመልካች በ13/9/2009 ዓ/ም ፍ/ቤት ቀርቦ በመታመሜ ምክንያት መልስ ለማዘጋጀት አልቻልኩም ስለዚህ ከባለሙያ ተማክሬ መልሴን እንዳቀርብ ብሎ እንዳመለከቱ፤ አመልካች መጥሪያዉን ቢቀበል ኖሮ ለ15/9/2009 ዓ/ም መልስ አዘጋጅቶ ለመቅረብ እንደሚችል በመግለጽ መታለፉ ተገቢ መሆኑን በመግለጽ የስር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። ስለዚህ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር እንኳን ቢሆን አመልካች መልሱን ይዞ እንዲቀርብ እየተደረገ ያለዉ በስምንት ቀናት ዉስጥ እንደሆነ እና አመልካች ከባለሙያ ተማክሮ መልሱን ለማቅረብ ጊዜ እንዳልበቃዉ በመግለጽ ፍ/ቤቱ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጠዉ እንዳመለከተ ማየት ይቻላል። አመልካች የቀረበበትን ክስና ማስረጃ በመመርመር ተገቢ ነዉ ያለዉን መልስ ለማቅረብ ከተሰጠዉ ቀጠሮ ከ10 ቀን በፊት ሊደርሰዉ እንደሚገባዉ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.240 [2] ያስገነዝባል። ከዚህ አንጻር የአሁን አመልካች መልሱን እንዲያቀርብ የታዘዘዉ እና ቀጠሮ የተሰጠዉ ከ10 ቀን ባነሰ ጊዜ ዉስጥ መሆኑን ያሳያል። ይህ ደግሞ አመልካች በሕግ በተመለከተ ጊዜ ዉስጥ ተገቢዉን ዝግጅት በማድረግ መልሱን አዘጋጅቶ እንዲቀርብ የሚያስችለዉ ጊዜ ሆኖ አይገኝም። ይህ ደግሞ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 መሰረት የተጠበቀዉን መብት የሚነፍግ ነዉ። ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች በሕጉ አግባብ ተገቢዉን የመከላከያ መልሱን እንዲያቀርብና ሙሉ ክርክሩን እንዲያቀርብ ማድረግ ሲገባቸዉ የመከላከልና የመከራከር መብቱን በመንፈግ ዉሳኔ መስጠታቸዉን መገንዘብ ተችሏል።

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች የመከላከያ መልሱን ሳያቀርብ እና ክርክሩን አቅርቦ ሳይሰማ የሰጡት ዉሳኔ የመከላከልና የመከራከር የመሰማት መብቱን የነፈገ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። በዚህ ምክንያት የሚከተለዉ ተወስኗል።

ዉ ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.24388 በ11/12/2009 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የትግራይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት በመ.ቁ.98593 በ14/6/2010 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት ተሽሯል።

2. በትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ መሰረት የአሁን አመልካች የመከላከያ መልሱን እና ክርክሩን እንዲያቀርብ በማድረግ፤ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር፤ ጉዳዩን በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ' 343 [1] መሰረት ተመልሶለታል።
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረስ።
4. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።
5. ይህ ዉሳኔ ታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ/ም ተነብቧል።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.119851
መጋቢት 26 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች- መዓዛ አሸናፊ
ሰለሞን አረዳ
ተክሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ፀሃይ መንክር

አመልካቾች - 1ኛ. ወ/ሮ ሶፊያ መሐመድ
2ኛ. አቶ አህመድ መሐመድ
3ኛ. ወ/ሮ ዘብይዳ መሐመድ

ተጠሪ - አቶ እንድሪስ ጋሹ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውልን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ተጠሪ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

1. ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ከሚኾች ሐጂ መሐመድ ሰይድ እና ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ (የአሁን አመልካቾች ወላጆች) ጋር ሚያዚያ 21 ቀን 1974 ዓ.ም በተፃፈ የቤት ሽያጭ ውል በቀድሞው ወረዳ 24 ቀበሌ 09 የቤ/ቁጥር 312 የሆነ ቤት በብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ) ገዝተው በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ምክንያት ስም እንዲዛወርላቸው በተዋዋዩቹ ላይ ነሃሴ 23/1983 ዓ.ም ክስ መስርተው በክልል 14 መስተዳደር ወረዳ 24 ፍርድ ቤት በትዕዛዝ መ/ቁ 742/83 ታህሳስ 25/1986 ዓ.ም ስም እንዲዛወር ውሳኔ ተሰጥቷል፤ ይህን ውሳኔ ለማስፈፀም በቀድሞ ተከሳሾች ወራሾች (የአሁን አመልካቾች) ላይ አቤቱታ አቅርበው በፍ/ብ/መ/ቁ 1422 በ15/03/97 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ሊፈጸም የማይችል ውሳኔ ነው ተብሎ መዝገቡ መዘጋቷል፤ ስለሆነም ተከሳሾች የሻጮች ወራሾች ስለሆኑ ቤቱን እና ለስም ማዛወር የሚጠቅሙ የቤቱን ሰነዶች እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

2. አመልካቾች ለክሱ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጉዳዩ ከዚህ በፊት ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 መሰረት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውድቅ እንዲደረግ፤ ውሉን መሰረት በማድረግ በሚቾች ላይ መስርተውት በነበረው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 217(3) እና 218 ሁሉንም ጥያቄ አጣምረው ሊያቀርቡ ይገባ ነበር፤ እንዲሁም ጉዳዩ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ እና በፍ/ብ/ህ/ቁ 2892(3) መሰረት በአንድ ዓመት ይርጋ የታገደ ነው እንዲባል ጠይቀዋል፡፡ በፍሬ ጉዳዩም በሰጡት መልስ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 12(1) ላይ በግልጽ እንደሰፈረው የከተማ ቤት በሽያጭ የሚተላለፍ ከሆነ መንግስት የግዥ ቀዳሚነት መብት አለው፤ ይህም በመሆኑ በ1974 ዓ.ም የሚደረግ የቤት ሽያጭ ፍጹም አልነበረም፤ ከሳሽ ውልን አደረኩ ባሉበት ጊዜ አውራሻችን በሚኒስቴሩ የፀደቀ ንብረት የላቸውም፤ በዚህም መሰረት የተከሳሾች አውራሽ ንብረቱን ለማስተላለፍ መብት አልነበራቸውም፤ ስለሆነም ውሉ ሐሰተኛ ወይም ህገወጥ ነው፤ በአጠቃላይ የቀረበው ክስ በህጉ አግባብ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ ይሁንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

3. ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት በአመልካቾች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ዝርዝር ክርክር ውድቅ በማድረግ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እና ሰነዶችን እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡ አመልካቾች መቃወሚያዎቹ መታለፋቸውን እና በፍሬ ጉዳዩ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ጉዳዩን በይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ ተገቢ መሆኑን፤ ነገር ግን ፍሬ ጉዳዩ ባግባቡ ተጣርቶ አለመወሰኑን በመጥቀስ በድጋሚ አጣርቶ እንዲወስን ወደ ስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መልሷል፡፡

4. በዚህ መልኩ የተመለሰለት የሥር ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን ተመልክቶ የቀደመ ውሳኔውን በድጋሚ አሳልፏል፡፡

5. ይህ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አመልካቾች መቃወሚያዎቹ የታለፉት አላግባብ መሆኑን እና በፍሬ ጉዳዩ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም መቃወሚያዎችን በተመለከተ አስቀድሞ ውሳኔ የሰጠባቸው በመሆኑ በጊዜው ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊጠይቁባቸው ይገባ እንደነበር፤ በፍሬ ጉዳዩ ተጣርቶ የተሰጠው ውሳኔም ግድፈት እንደሌለበት ወስኗል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

6. የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው። አመልካቾች ህዳር 8/2008 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ መቃወሚያዎቹ በመታለፋቸውም ሆነ በፍሬ ጉዳዩ ተፈፀሙ የሚሏቸውን የህግ ስህተቶች ዘርዝረው አቅርበዋል።
7. አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አከራካሪው ቤት በአመልካቾች እጅ ስለመኖሩ ባልተካደበት የቤት ሽያጭ ገንዘቡም አልተከፈለም ተብሎ ቀደም ሲል በመ/ቁ 742/83 በተሰጠ ፍርድ ላይ በተመለከተበት እና በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 1422 ስመሃብት ይዛወር ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ሊፈፀም የማይችል ነው ተብሎ አፈፃፀሙ በተዘጋበት የስር ፍርድ ቤቶች ክሱን ዳግም በ2004 ዓ.ም በተከፈተ መዝገብ አስተናግደው የቤት ሽያጭ ውሉ ህጋዊ ስለሆነ አመልካቾች ቤቱን እና ኦሪጅናል ካርታውን ለተጠሪ ያስረክቡ በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።
8. ተጠሪ በሰጡት መልስ በቅድሚያ የሰበር አቤቱታውን አቀራረብ በተመለከተ መቃወሚያዎችን አቅርበዋል። የመቃወሚያው ይዘት አመልካቾች ለሰበር አቤቱታ መነሻ ያደረጉት ቀደም ሲል የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ 126113 በ26/06/2005 ዓ.ም ክርክር አድርጎ ውሳኔ የሰጠባቸው ነጥቦች ላይ ማለትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 መሰረት የቀረበውን መቃወሚያ፤ የይርጋ ክርክሩን፤ የሽያጩን ገንዘብ ክፍያ እንዲሁም በህግ የታወቀ መብት እና የሥም ዝውውር ጥያቄን በተመለከተ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አግባብ በወቅቱ ይግባኝ አልተባለበትም (የሰበር አቤቱታ አልቀረበበትም) ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል። ይህ ከታለፈም በጉዳዩ ላይ ፍርድ የተሰጠው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 23018 በ22/09/04 ዓ.ም እና በከፍተኛው ፍርድ ቤት በ26/06/2005 ስለሆነ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት ነው ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ ብለዋል። በፍሬ ጉዳዩም ዝርዝር መልሳቸውንም አቅርበዋል።
9. አመልካቾች ባቀረቡት የመልስ መልስ ቅሬታቸውን በማጠናከር ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠው ስልጣን አንፃር በተለይም የህግ ድንጋጌዎችን ወጥነት ባለው መልኩ እንዲተረጎሙ ከማድረግ አኳያ የህግ ጥያቄዎች ለችሎቱ መቅረባቸው የሚነቀፍበት ምክንያት ሊኖር እንደማይገባ በመግለፅ በሰበር አቤቱታው አቀራረብ ላይ የተነሳው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም እንዲባል ጠይቀዋል። በሌሎች ነጥቦች ላይም የሥር ክርክራቸውን በማጠናከር አቅርበዋል።

10. የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችን ጉዳዩን መርምረናል። እንደመረመርነው ተጠሪ የሰበር አቤቱታው አቀራረብ በተመለከተ ያነሱት መቃወሚያ ይህ ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ የሰጣቸውን አስገዳጅ ትርጉሞች መሰረት በማድረግ የቀረበ በመሆኑ ከዚህ አንፃር ሰበር ችሎቱ አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳዮች ያሳለፋቸው ገዥ ትርጉሞች በአዋጅ ቁጥር 454/1997 መሰረት በድጋሚ ሊታዩ የሚገባ መሆን አለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

11. ተጠሪ ባቀረቡት መልስ አመልካቾች ለሰበር አቤቱታ መነሻ ያደረጉት ቀደም ሲል የከፍተኛው ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ ፍሬ ጉዳዩ በአግባቡ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደስር ፍርድ ቤት ሲመልስ በመቃወሚያዎቹ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቶበት የነበረ በመሆኑ በመቃወሚያዎቹ ላይ በዚህ መልኩ በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ በወቅቱ የሰበር አቤቱታ አልቀረበበትም ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል። አመልካቾች በበኩላቸው ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠው ስልጣን አንፃር የህግ ጥያቄዎች ለችሎቱ መቅረባቸው የሚነቀፍበት ምክንያት ሊኖር እንደማይገባ በመግለፅ መከራከሪያው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል።

12. ስለሆነም ውሳኔ የሚሻው ጉዳይ በእንዲህ አይነቱ ክርክር በመቃወሚያው ላይ የተሰጠውን ውሳኔ መነሻ ያደረገ የሰበር ቅሬታ መቅረብ ያለበት መቼ ነው? የሚለው ነው። ይህም ማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመቃወሚያው ላይ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ/የሰበር አቤቱታ ለበላይ ፍርድ ቤቶች ለማቅረብ ወደታች ፍርድ ቤት የተመለሰውንና በፍሬ ነገሩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት የተመለሰውን ክርክር ውጤት መጠበቅና የተጠቃለለ ቅሬታ ማቅረብ ይገባል? ወይስ ወደስር ፍርድ ቤት የተመለሰው ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚሰጠውን ውሳኔ መጠበቅ ሳያስፈልግ በመቃወሚያው ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ያለውን ቅሬታ ወዲያውኑ/በቀጥታ ማቅረብ ይገባል? የሚለው ነው።

13. ይህንኑ ነጥብ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አስቀድሞ ከተያዘው አቋም እና ከተሰጠው ትርጉም፤ ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ አላማና ከሰበር ችሎት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ኃላፊነት፤ እንዲሁም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ የክርክር አመራር እና የቅሬታ አቀራረብ መሰረታዊ መርሆዎች አንፃር መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

14. ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ አስቀድሞ በሰጠው ትርጉም ለክሱ በሚቀርቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ በይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔን በመቃወም የሰበር አቤቱታ መቅረብ የሚገባው ወዲያውኑ ማለትም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በህግ በተደነገገው የሰበር ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ ከሚሆን በቀር በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ሥር ፍርድ ቤት በመለሰው ክርክር ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ውጤት ጠብቆ የሚቀርብበት ህጋዊ ምክንያት እንደሌለ፤ ስርዓቱን ጠብቆ በጊዜው የይግባኝ (ሰበር) ክርክሩን መቀጠል ሲገባ በዚህ መልኩ አቤቱታ የማቅረብ መብታቸውን በራሳቸው ጊዜ በመተው ወደስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተመልሶ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመቃወሚያው ላይ አስቀድሞ በተሰጠው ውሳኔ ላይ አጠቃለው የሚያቀርቡት አቤቱታ የህግ መሰረት እንደሌለው በሰ/መ/ቁ 90810 ፣ 76963፣ 125165 እና ሌሎችም በርካታ መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

15. ለዚህ መደምደሚያ እና ትርጉም መሰረት የተደረገው ከመቃወሚያው ጋር በተያያዘ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 320(3) መሰረት ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ብይን/ትዕዛዝ ነው የሚባል አይደለም፤ እንዲሁም በዚህ መልኩ በበላይ ፍርድ ቤቶች የሚሰጠው ውሳኔ በህግ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት በበላይ ፍርድ ቤት እስካልተለወጠ ድረስ በግራቀኙ ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ በአጠቃላይ የሰበር ችሎቱ የቀደመ አቋም በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ወደ ስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገሩ ረገድ ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት የተላከውን ጉዳይ ውጤት ሳይጠብቅ በመቃወሚያው ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የሰበር ቅሬታውን/ይግባኙን ማቅረብ ይኖርበታል፤ ይህን ሳያደርግ ከቀረ የፍሬ ነገር ክርክሩን ውጤት ጠብቆ መጀመሪያ ያልተጠቀመበትን የሰበር አቤቱታ/ይግባኝ የማቅረብ መብት እንደገና በማንሳት ሊጠቀምበት አይችልም የሚል ነው፡፡ ይህ ትርጉም የሰበርን አላማ ከግንዛቤ ባስገባ መልኩ በጥንቃቄ ሊታይ ይገባል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

16. በመሰረቱ የሰበር ስርዓት የመዘርጋት አላማ በአንድ ሀገር ውስጥ ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጎም እና አፈጻጸም መኖሩን በማረጋገጥ የህግ የበላይነትን ማስፈን ነው። ይህን ማድረግ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ ሊቆይ የማይችልበትን ሁኔታ መፍጠር ነው። የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ጸንቶ እንዲቆይ ማድረግ ህብረተሰቡ በዳኝነት አካሉ እምነት እንዳይኖረው የሚያደርግ በመሆኑ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ እንዲቆይ መፍቀድ በዳኝነት አካሉ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያስከትላል። በመሆኑም የሰበር ሥርአቱ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ፀንቶ እንዳይቆይ በማድረግ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ እና የዳኝነት አካሉ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚታመን እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል።

17. በዚህ መሰረታዊ ምክንያት ህገ-መንግስቱ የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሆኑንና ፍርድ ቤቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም "የመጨረሻ ውሳኔ" ለማረም የሰበር ችሎቱ ስልጣን ያለው መሆኑን በአንቀጽ 80(3(ሀ)) ስር ደንግጓል። በተለይ አዋጅ ቁጥር 454/1997 ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጥ የህግ ትርጉም ይኸው ችሎት ራሱ በሌላ ጊዜ እስካልለወጠው ድረስ በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅ ስለመሆኑ በአንቀፅ 2(4) ስር ደንግጓል። ይህም የሰበር ስርዓት በዳኝነት ስልጣን ተዋረድ በመጨረሻ እርከን ላይ ሆኖ ህጎች በትክክልና በወጥነት መተርጎማቸውንና መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሲሆን በውጤቱም ሰበር ህጋዊ ያልሆኑ ውሳኔዎች ጸንተው እንዳይቆዩ የሚደረግበት ሥርዓት ነው።

18. ከዚህም ሌላ ሰበር መደበኛ የይግባኝ ማቅረቢያ አሰራር ሳይሆን ፍርድ ቤቶች በመጨረሻ ውሳኔዎቻቸው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ፈጽመዋል በሚባልበት ልዩ ሁኔታ ብቻ የህጉ አተረጓጎም ወይም አተገባበር የሚቃናበት ነው። በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በተሳሳተ መልኩ የሰጧቸውን ውሳኔዎች ሰበር ችሎቱ ሊያስተካክል የሚችልበት ወይም በማናቸውም ሁኔታ ስህተት የተፈፀመባቸው ውሳኔዎች ቀሪ ሊሆኑ የሚችሉበት መንገድ እንዲጠብ የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም።

19. በሌላም በኩል ከፍሲል እንደተገለፀው የሰበር ችሎቱ የተቋቋመው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም "የመጨረሻ ውሳኔ" ለማረም ነው። በእጃችን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ካለው ጉዳይ ጋር በተያያዘ በክርክሩ ላይ "የመጨረሻ ውሳኔ" ተሰጥቷል ሊባል የሚችለው መቼ ነው? የሚለው በአግባቡ ሊታይ ይገባል። ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 ንዑስ ቁጥር (1) እና (2) ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ የወሰነው የበታች ፍርድ ቤት ጠቃሚ የሆነውን ጭብጥ ሳይዝ ወይም ጉዳዩን ሳይመረምርና ሳይረዳ ያለፈው መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካረጋገጠ የተዘለሉለትን ጭብጦችና ፍሬ ነገሮች ለይቶ እንደገና እንዲመረምርና እንዲያጣራው ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሶ ይልክለታል፤ በዚህ መልኩ እንደገና እንዲያይ የተላከለት ፍርድ ቤትም በትዕዛዙ መሰረት ዳኝነቱን ካየ በኃላ ያጣራውን ነገር ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መልሶ ይልካል በማለት ይደነግጋል። ከድንጋጌው መገንዘብ እንደሚቻለው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 መሰረት ጉዳዩ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተመልሶ የሚላከው ተጣርቶ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት እንዲመለስ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተዘለሉለትን ጭብጦችና ፍሬ ነገሮች ለይቶ እንደገና እንዲመረምርና እንዲያጣራው ሲመልስ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቷል የሚባልበት የህግ አግባብ አይኖርም። የመጨረሻ ውሳኔ ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ ደግሞ የሰበር አቤቱታ እንዲቀርብ ማድረግ ከፍሲል የጠቀስናቸውን የህጉን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም።

20. ከዚህም ሌላ መቃወሚያውን መሰረት ያደረገ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የሚኖረው ቅሬታ ተከራካሪው ወገን ወደስር ፍርድ ቤት በተመለሰው ክርክር አሸናፊ ከሆነ ቀሪ ሊሆን የሚችልበት እድል በመኖሩ ስህተቱ ሊታረም የሚገባው ወዲያውኑ በሚቀርብ የሰበር አቤቱታ ብቻ ነው ሊባል የሚችልበት ምክንያት አይኖርም።

21. በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት በመቃወሚያው ላይ የሰጠውን ብይን በማጽናት ነገር ግን በፍሬ ነገሩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ሲመልስ በመቃወሚያው ላይ የተሰጠውን ውሳኔ የሚመለከት የሰበር/ይግባኝ ቅሬታ ወዲያውኑ ካልቀረበ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም የተባለበት አግባብ በአንድ በኩል በስረ ነገሩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሰበር ችሎቱ ተያያዥነት ያላቸውንና ተጠቃለው ቢቀርቡ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአንድ መዝገብ ውሳኔ ሊያገኙ የሚችሉ ጉዳዮችን በተነጣጠለ መልኩ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ያደርጋል። ይህም በተከራካሪዎች ላይ ተጨማሪ እንግልትና ወጪን እንዲሁም በችሎቱ ላይ አላስፈላጊ የሥራ ጫናን የሚፈጥር ነው። በተለይ እንዲህ አይነት ክርክሮች ከክልል ፍርድ ቤቶች የሚነሱ ሲሆን ተከራካሪዎች በአንድ መዝገብ በተነሱ ክርክሮች ሁለት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት መመላለስ እንዲኖርባቸው የሚያድርግ ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጣርቶ እንዲወሰን ወደስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መመለሱን ተቀብለው የጉዳዩን መጠናቀቅ በቅን ልቦና ሲጠባበቁ በመቃወሚያው ላይ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተትን ወዲያውኑ አላቀረባችሁም በሚል በሰበር ለማሳረም እንዳይችሉ የተደረጉት ባለጉዳዩች በርካቶች መሆናቸውንና በዚህ ምክንያት ፍትህ መጓደሉን መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም አስቀድሞ በሰበር ችሎቱ የተያዘው አቋም የሥነ ሥርዓት ህጉን መንፈስ በተለይም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 እና 320 ድንጋጌዎችን ይዘት እና የሰበር ስርዓቱን አላማ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም።

22. በእነዚህ ምክንያቶች ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ሥር ፍርድ ቤት በመለሰው ክርክር ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ውጤት ጠብቆ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመቃወሚያውም ሆነ በፍሬ ነገሩ ላይ የተጠቃለለ የሰበር አቤቱታ መቅረቡ ህጉን የተከተለ ከመሆኑም በላይ በአንድ ጉዳይ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በተበታተነ ሁኔታ ክርክር እንዳይካሄድ የሚያደርግ፤ የተከራካሪዎችን መብት በተሻለ የሚያስከብር እና የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ፀንቶ እንዳይቀር የሚያደርግ በመሆኑ አስቀድሞ የተሰጠው ትርጉም ሊለወጥ ይገባል ብለናል።

23. ስለሆነም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት ቀደም ሲል በዚህ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 90810 ፣ 76963፣ 125165 እና ሌሎችም በርካታ መዛግብት ተሰጥቶ የነበረውን ትርጉም ለውጠናል። ይኸውም ፡- ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 መሰረት ወደስር ፍርድ ቤት በተመለሰበት ሁኔታ ለክሱ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠ ውሳኔን በመቃወም የሰበር አቤቱታ መቅረብ የሚገባው ወዲያውኑ ማለትም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በህግ በተደነገገው የሰበር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ ከሚሆን በቀር በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ሥር ፍርድ ቤት በመለሰው ክርክር ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ውጤት ጠብቆ ተጠቃሎ የሚቀርብበት ምክንያት የለም ተብሎ የተሰጠው ትርጉም ተለውጧል። ወደስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ተመልሶ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመቃወሚያው ላይ አስቀድሞ በተሰጠው ብይን ላይ ተጠቃሎ የሚያቀርበው አቤቱታ ህጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሊባል አይገባም ብለናል።

24. በተያዘውም ጉዳይ አመልካቾች ለክሱ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ በመደረጉ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ በወቅቱ የሰበር አቤቱታ አልቀረበበትም ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ በተጠሪ በኩል የቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም ብለናል።

25. ከፍሲል እንደተገለፀው ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ከአመልካቾች ወላጆች ጋር ሚያዚያ 21 ቀን 1974 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል አከራካሪውን ቤት ገዝተው በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ምክንያት ስም እንዲዛወርላቸው ክስ መስርተው በትዕዛዝ መ/ቁ 742/83 ታህሳስ 25/1986 ዓ.ም ስም እንዲዛወር ውሳኔ አሰጥተው እንደነበር፤ ይህን ውሳኔ ለማስፈፀም አቤቱታ አቅርበው በፍ/ብ/መ/ቁ 1422 በ15/03/97 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ሊፈጸም የማይችል ውሳኔ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉን በመጥቀስ አመልካቾች የተዋዋዮች (የሻጮች) ወራሾች ስለሆኑ ቤቱን እና ለስም ማዛወር የሚጠቅሙ የቤቱን ሰነዶች እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል። አመልካቾች በበኩላቸው ለክሱ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጉዳዩ ከዚህ በፊት ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ፤ ውሉን መሰረት በማድረግ በሚቾች ላይ መስርተውት በነበረው ክስ ሁሉንም ጥያቄ አጣምረው ሊያቀርቡ ይገባ ነበር፤ እንዲሁም ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው እንዲባል የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም በህጉ አግባብ የተደረገ ውል ባለመኖሩ ቤቱንም ሆነ ሰነዶችን ልናስረክብ አይገባም የሚሉበትን መከራከሪያ በማንሳት ተከራክረዋል።

26. በበኩላችን አመልካቾች ካቀረቧቸው መቃወሚያዎች መካከል ለክሱ መቅረብ ምክንያት የሆኑት ነገሮች ላይ ሁሉ በሙሉ ተጠቃሎ መቅረብ ይገባው ነበር በሚል የቀረበውን ክርክር መርምረናል። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216(2) እንደተደነገገው ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በሙሉ በክሱ ማመልከቻ ላይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጠቃሎ ማቅረብ እንደሚገባው የሚደነግግ ሲሆን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216(3) ደግሞ ከሳሹ ሊከስበት ሲችል ሆነብሎ በመቀነስ ባስቀረው ነገር እንደገና ሌላ ክስ ለማቅረብ እንደማይችል ይደነግጋል። የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ተጣምረው ስለሚቀርቡ ክሶችም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 218 ሥር ተደንግጓል። በመሆኑም ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑት ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን ማቅረብ ሲችል ቀንሶ ባስቀረው ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ እንደማይችል ከድንጋጌዎቹ መገንዘብ ይቻላል።

27. በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ የሸያጭ ውል ነው ያሉትን መሰረት በማድረግ የቤቱ ስም እንዲዛወርላቸው ክስ መስርተው በትዕዛዝ መ/ቁ 742/83 ታህሳስ 25/1986 ዓ.ም ስም እንዲዛወር ውሳኔ አሰጥተው ነበር። በሌላ በኩል ለአሁኑ ክርክር ምክንያት የሆነውን ክስ በማቅረብ አመልካቾች የተዋዋዮች (የሻጮች) ወራሾች ስለሆኑ ቤቱን እና ለስም ማዛወር የሚጠቅሙ የቤቱን ሰነዶች እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት መጠየቃቸውን ተገንዝበናል። በሁለቱም ክስ የዳኝነት ጥያቄ የቀረበው ውሉን መሰረት በማድረግ እንደውሉ ተፈጽሞ ስመሃብቱ እንዲዞርና ቤቱንና የቤቱን ሰነዶች ለመረከብ ነው። ስለሆነም ተጠሪ የቀደመው ውሳኔ በአፈጻፀም ውድቅ ሲደረግባቸው እንደገና በሁለተኛው ክስ ያቀረቡት ጥያቄ በመጀመሪያው ክስ ተጠቃሎ ሊጠየቅ የሚገባው ነበር። በመጀመሪያው ክስ አጠቃለው ሊያቀርቡት ሲገባ ሁለተኛ ክስ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 አንጻር የማይቻል በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን የክስ መቃወሚያ ተቀብለው ክሱን ውድቅ ሊያደርጉት ሲገባ ይህን አልፈው ፍሬ ጉዳዩን በመመልከት አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እና ሰነዶችን እንዲያስረክቡ በማለት ያሳለፉት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. በዚህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 90810 ፣ 76963፣ 125165 እና ሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ወደ ስር ፍርድ ቤት የተመለሰው ፍሬ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት በመቃወሚያዎቹ ላይ በተሰጠ ውሳኔ የሰበር አቤቱታ ወዲያውኑ ካልቀረበ የፍሬ ጉዳዩን የመጨረሻ ውሳኔ ጠብቆ የሚቀርበው አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም ተብሎ የተሰጠው አስገዳጅ ትርጉም የሰበር ችሎቱ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተቋቋመበትን ዓላማ ዳር የሚያደርስ ሆኖ ስላላገኘነውና ህጉንም መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ አስቀድሞ የተሰጠው ይህ ትርጉም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(4) መሰረት ተለውጧል፡፡ በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ ገዥ ይሆናል ብለናል፡፡

2. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 መሰረት ጉዳዩ ወደስር ፍርድ ቤት ተመልሶ በፍሬ ነገሩ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመቃወሚያው ላይ አስቀድሞ በተሰጠው ብይን ላይ ተጠቃሎ የሚያቀርበው የሰበር አቤቱታ ህጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሊባል አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በመጀመሪያው ክስ አጠቃለው ሊያቀርቡት ሲገባ ሁለተኛ ክስ ማቅረባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 አንጻር የማይቻል በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን የክስ መቃወሚያ ተቀብለው ክሱን ውድቅ ሊያደርጉት ሲገባ ይህን አልፈው ፍሬ ጉዳዩን በመመልከት አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እና ሰነዶችን እንዲያስረክቡ ያሳለፉት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 23018 ሚያዚያ 29/2006 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 153710 ጥቅምት 15 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሽሯል፡፡
4. ከሥር ፍርድ ቤቶች የተላኩት መዛግብት በመጡበት አግባብ ይመለሱ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ስለተደረገው ክርክር ግራቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰጠ የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የስድስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የልዩነት ሀሳብ</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር አምስት ላይ የተጠቀሰዉ ዳኛ የአብላጫዉ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በሚከተሉት ምክንያቶች በመለየት የልዩነት ሀሳብ አስቀምጫለሁ፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በክልል 14 መስተዳደር ወረዳ 24 ፍርድ ቤት በመ.ቁ.742/83 ታህሳስ 25 ቀን 1986 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ በአሁን ተጠሪ (ከሳሽ) እና በሚኾች ሐጂ መሐመድ ሰይድ እና ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ (ተከሳሾች) መካከል ሚያዚያ 21 ቀን 1974 ዓ.ም በተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል በቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 09 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 312 ሆነዉ ስመ ሀብቱ ወደ ከሳሽ እንዲዛወር በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ ይህ ዉሳኔ እንዲፈጸምላቸዉ የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡት ቢሆንም በመ.ቁ.1422 በ15/3/1997 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ ዉሳኔዉ ሊፈጸም አይችልም ተብሎ ተወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን ተጠሪ (የሥር ከሳሽ) በአሁን አመልካቾች (በሥር ተከሳሾች) ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ ተከሳሾች በቤት ሽያጭ ዉሉ መሰረት ቤቱን እና ቤቱን የሚመለከቱትን ሰነዶች እንዲያስረክቡኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን አመልካቾች (የሥር ተከሳሾች) በዚህ ክስ ላይ በሰጡት መልስ ይህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ታይቶ ዉሳኔ ያገኘ በመሆኑ አሁን የቀረበዉ ክስ ድጋሚ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፤ ከሳሽ ከዚህ ቀደም ክስ ሲያቀርቡ ጉዳያቸዉን በአንድ ላይ አጠቃልሎ ማቅረብ ሲገባቸዉ በመከፋፈል አሁን ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለዉም፤ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በማንሳት የተከራከሩ ሲሆን፤ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ክርክራቸዉን አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካቾች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ዉድቅ በማደረግ፤ በፍሬ ጉዳይ አመልካቾቹ ቤቱን እና ቤቱን የሚመለከቱትን ሰነዶች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ዉድቅ በማድረግ የሰጠ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ በማለት በማጽናት፤ ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተ ግን በአግባቡ ተጣርቶ ዉሳኔ የተሰጠበት ባለመሆኑ ጉዳዩን ድጋሚ ተጣርቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ለሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ውሳኔ መሰረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ የግራ ቀኞቸዉን በማከራከርና በማጣራት የቀደመዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች መታለፋቸዉ ተገቢ እንዳልሆነ በመግለጽ እና በዋናዉ ጉዳይ ላይ የተሰጠዉንም ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን፤ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ውሳኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ስለመታለፋቸዉ የቀረበዉን ቅሬታ በተመለከተ ይህ ፍ/ቤት አስቀድሞ ዉሳኔ የሰጠባቸዉ በመሆኑ በጊዜዉ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሊጠይቁባቸዉ ሲገባቸዉ አሁን ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፤ የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ ሲታይ ተጣርቶ የተወሰነ በመሆኑ ግድፈት የለዉም በማለት በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ያነሷቸዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ማለፋቸዉ ተገቢ አይደለም እና በዋናዉ ጉዳይ ዝርዝር ቅሬታቸዉን በማቅረብ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡ ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ የአሁን አመልካቾች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በተመለከተ የተሰጠዉን ዉሳኔ አሁን ለዚህ ችሎት ቅሬታ ሊያቀርቡ እንደማይችሉ እና በዋናዉ ጉዳይም የሥር ፍ/ቤት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ እኔ ይህ ጉዳይ በሚከተለዉ አግባብ መታየት አለበት ብዬ የልዩነት ሀሳቤን አስቀምጣለሁ፡፡

ሀ. አስገዳጅ ሕግ ትርጉም የሚለወጥበት አግባብ በተመለከተ፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ የሆኑትን ጉዳዮች በተመለከተ በሰ.መ.ቁ.90810፣ 76963፣ 125165 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ አስቀድሞ በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ተከትሎ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ በመሆኑ ዉሳኔዉን በመቃወም የሰበር አቤቱታ መቅረብ የሚገባዉ ዉሳኔዉ ከተሰጠ ቀን ጀምሮ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሕጉ በተቀመጠ የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ ገደብ ውስጥ መሆን አለበት እንጂ በፍሬ ጉዳይ ወደ ሥር ፍ/ቤት የተመለሰውን ውሳኔ ውጤት ጠብቆ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንደማይቻል ውሳኔ ሰጥቶበታል። በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥራቸውን ሲያከናውኑ መቆየታቸዉ ግልጽ ነዉ። በመሆኑም በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በርካታ ባለጉዳዮች ባለመብት ሆነዉ ሌሎች ደግሞ በክርክሩ መሸነፋቸዉ የማይካድ ሀቅ ነዉ። እንግዲህ አሁን በተያዘዉ ጉዳይ ይህ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መለወጥ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ።

እንደሚታወቀዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2 (4) መሰረት ፣የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠዉ የህግ ትርጉም በየትኛዉም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል። ሆኖም የሰበር ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፣ በማለት ደንግጎታል። ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት አምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ የሚሰጡት የህግ ትርጉም በማናቸዉም ፍ/ቤት ላይ የአስገዳጅነት ዉጤት እንዳለዉ፣ ሕግ እንደሆነ የሚያመለክት ሲሆን፣ ችሎቱ ግን በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ የቀደመዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መለወጥ እንደሚችል ነዉ። ችሎቱ በዚህ ድንጋጌ አግባብ የዳኝነት ሥራዉን እያከናወነ የሚገኝ ቢሆንም አስገዳጅ የህግ ትርጉም ማለት ምን ማለት እንደሆነ? እና ይህ ትርጉም ደግሞ የሚለወጥበት አግባብ ግልጽ የሚያደርግ ዝርዝር መመሪያ ቢዘጋጅለት ተገቢ መስሎ ይታየኛል። ምክንያቱም ችሎቱ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ከሰጠ በኋላ እና ፍ/ቤቶች በዚህ አግባብ የዳኝነት ሥራቸዉን እያከናወኑ እና ባለጉዳዮች ደግሞ ክርክራቸዉን እያቀረቡ ባሉበት ሁኔታ በቀላሉ ተነስቶ ይህን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚለዉጥ ከሆነ ወጥነት ያለዉ የህግ ትርጉም ከመስጠት አንጻር አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚኖረዉ መገመት አያዳግትም። ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የህግ ድንጋጌ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚለወጥበት አግባብ በግልጽ ባይመለከትም በወቅቱ የነበሩት የማህበራዊ ሁኔታዎች መለወጥ፣ ወይም የሕጉ አካባቢያዊ ሁኔታ ሲለወጥ፣ የቀደመዉ ዉሳኔ ከወቅታዊ ፖሊሲዎች ጋር የሚጣጠሙትን ዉሳኔዎች ማመንጨት ሲያቅተዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መለወጥ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስፈላጊ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ይህ ችሎት የቀደመዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ባጠቃላይ ካለዉ ነበራዊ ሁኔታ ወይም እዉነታ ጋር የማይሄድ መሆኑን የተገነዘበ እንደሆነ ይህን የህግ ትርጉም መለወጥ ይችላል ተብሎ ይታመናል።

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የቀረበለትን ቅሬታ ተከትሎ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ የሰጠ እና ዋናዉን ጉዳይ ወደ ሥር ፍ/ቤት የመለሰ እንደሆነ፣ ፍ/ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ ተከራካሪ ወገን ዉሳኔዉ እንደተሰጠ የሰበር አቤቱታ በሕጉ በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ዉስጥ ማቅረብ እንዳለበት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ፣ አሁን ባለዉ ሁኔታ ይህን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመለወጥ የሚያስችል የተለወጠ ማህበራዊ ሁኔታ፣ የሕጉ አካባቢያዊ ሁኔታ መለወጥ ወይም ወቅታዊ የፖሊሲ ሁኔታ መለወጥ፣ እንዲሁም ባጠቃላይ ያለዉ ነበራዊ ሁኔታ መለወጥን የሚያሳይ ነገር የለም። ስለሆነም ይህ ችሎት በዚህ ጉዳይ አስቀድመዉ የተሰጡትን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመለወጥ የሚያስችለዉ በቂ ምክንያት የለም።

ለ. ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ስለመሆኑ፡

እንደሚታወቀዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ.244 (2) ሥር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ተዘርዝረዉ እናገኛለን። ፍ/ቤት ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ በፊት ከተከራካሪ ወገን የቀረበለትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ መስጠት እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 (1) ሥር ተመልክቷል። አንድን ክርክር ተቀብሎ እያያ ያለዉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ አግባብ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ፣ ተከራካሪ ወገኖችን በዋናዉ ጉዳይ ማከራከርና ማጣራት የቀጠለ እንደሆነ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320 (3) መሰረት በዚህ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ማቅረብ እንደማይቻል እና በዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሲሰጥ አንድ ላይ አጠቃልሎ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በተሰጠዉን ዉሳኔ ላይ ቅሬታዉን ማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል።

ነገር ግን አንድን ጉዳይ መጀመሪያ ያየዉ ፍ/ቤት የቀረበለትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ያደረገ እና ከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረበ እንደሆነ፣ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የቀረበዉ ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ መሆን የለበትም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉን ዉድቅ በማድረግ እና በሥረ ነገር ላይ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት የሚመልስበት አግባበ እንዳለ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ጉዳይ መጀመሪያ የቀረበለት ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉን ባለመቀበል ዉድቅ በማድረግ፤ በዋናዉ ጉዳይ ግራ ቀኞቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ የሰጠ እንደሆነ፣ ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረበ እንደሆነ እና ፍ/ቤቱም ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመቀበል በማጽናት እና የሥር ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ ላይ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከርና በማጣራት ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ሊመልስለት እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከእነዚህ ሁለት ዉሳኔዎች መገንዘብ የሚቻለዉ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ መሆኑን ነዉ፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ፡፡ ስለሆነም በዚህ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ ተከራካሪ ወገን ይግባኙን ወይም የሰበር አቤቱታዉን በሕግ በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ዉስጥ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ወይም ለሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረብ እንደሚገባዉ ነዉ፡፡

ሐ. ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ለዛ ፍ/ቤት በዛ ጉዳይ ላይ ዉሳኔዉ የመጨረሻ ዉሳኔ እስከሆነ ድረስ እንደአግባብነቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 ወይም 358 ዉሳኔዉን ለሰጠ ፍ/ቤት በሚቀርብ አቤቱታ ወይም ፣ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ካልቀረበ፣ ዉሳኔዉ እንደጸና የሚቆይ እና በተከራካሪ ወገኖች ላይ አስገዳጅነቱ እንደሚቀጥል ግልጽ ነዉ፡፡ ይህ ዉሳኔ በሕግ አግባብ ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት እስካልተሻረ ድረስ በተከራካሪ ወኖቹ ላይ አስገዳጅነቱን የሚያስቀር ነገር አይኖርም፡፡

መ. ከፍ ሲል በፊደል ‹‹ለ›› ላይ በተመለከቱት ሁለት ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ ላይ ግራ ቀኞቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ለሥር ፍ/ቤት መልሶለት እንደሆነ፣ የሥር ፍ/ቤት የሚያየዉ ጭብጥ ተይዞ የተመለሰለትን የፍሬ ጉዳይ ክርክር እንጂ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን የሚያይበት አግባብ አይኖርም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ ድጋሚ አይቶ ዉሳኔ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚሰጥበት አግባብ ስለማይኖር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.328 መሰረት የይግባኝ ምክንያት ተደርጎ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታ የሚቀርብበት አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡ የሥር ፍ/ቤት እንደጭብጥ በመያዝ ዉሳኔ ያልሰጠበትን ጉዳይ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ደግሞ የሚያይበት አግባብ እንደማይኖር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329(1) ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም ይግባኝ ባይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 327 መሰረት በዚህ ጉዳይ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ሊያቀርብበት አይችልም ማለት ነዉ፡፡ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከዚህ ቀደም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ በመስጠቱ ድጋሚ የሚያይበት አግባብ ስለማይኖር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ምንም ዓይነት ዉሳኔ ስለማይሰጥ ቅሬታዉ ለሚቀጥለዉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ወይም ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርብበት አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡

ሠ. በዚህ አግባብ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በተመለከተ ድጋሚ አይቶ ዉሳኔ ባልሰጠበት እና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም በዚህ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ መስጠት በማይችልበት ሁኔታ፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የሚቀርበዉን ቅሬታ ተቀብሎ የሚያይበት አግባብ የለም፡፡ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ እና የሥር ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ ግራ ቀኞቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ እንዲሰጥ አስቀድሞ ከሰጠዉ ዉሳኔ ላይ በወቅቱ በሕግ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ወይም የሰበር አቤቱታ ለሰበር አቤቱታ ያልቀረበ እንደሆነ፣ ዋናዉ ጉዳይ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ዉሳኔ ካገኘ በኋላ፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት አስቀድሞ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ለማቅረብ፣ በማስፈቀጃ እስካልሆነ ድረስ፣ የይግባኝ ማመልከቻ ወይም የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ ስለሚያልፍበት ተቀባይነት ሊኖረዉ አይችልም ማለት ነዉ፡፡

ረ. ተከራካሪ ወገኖች ላይ ከሚደርሰዉ እንግልት እና ክርክሩ ከሚያስከትለዉ ወጪ አንጻር ሲታይ እንደሚታወቀዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ የሚሰጠዉ ፍ/ቤቱ ወደ በፍሬ ነገር ላይ ማስረጃ ከመቀበሉ ወይም የሰዉ ምስክሮችን ከመስማቱ በፊት ወይም ወደ ዋናዉ ክርክር ሳይገባ ከጅምሩ ለመቋጨት የሚያስችል በመሆኑ የተከራካሪ ወገኖችን እንግልት እና ለወጪ የመጋለጥ ሁኔታን የሚቀንስ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 (3) ሥር የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ በመስጠት በዋናዉ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን አጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥ የመለሰ እንደሆነ፣ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ሙሉ ክርክር በማካሄድ ማስረጃ በማቅረብ፣ ምስክሮች በመስማት፣ ጉዳዩን ለማጣራት ከሚፈጀዉ ወጪ እና ጊዜ ከመቀነስ አንጻር ወደ ሥር ፍ/ቤት ሄዶ ከመከራከር ይልቅ አንድ ጊዜ እስከተጀመረ ድረስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት አቅርቦ ጉዳዩ መቋጫ እንዲያገኝ ማድረጉ ተገቢ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከራካሪ ወገኖች በዋናዉ ጉዳይ በመከራከር ጊዜያአቸዉንና ገንዘባቸዉን ከመጨረስ ይልቅ ክርክሩ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚያልቅ ከሆነ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት በማቅረብ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ማድረጉ ተገቢ ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻርም ሲታይ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ማቅረቡ ተገቢ እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

ሸ. ሌላዉ መታየት ያለበት ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) ድንጋጌ መሰረት ዋናዉ ጉዳይ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ተጣርቶ እንዲወሰን ተብሎ የተሰጠ ዉሳኔ፣ የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኘ ጉዳይ ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት አይገባም ወይ? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ በእርግጥ በዚህ ድንጋጌ አግባብ ዉሳኔ የተሰጠ እንደሆነ ግራ ቀኞቸዉ ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ጉዳዩ ተጣርቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ ነገር ግን አንድ ጉዳይ በዚህ ድንጋጌ አግባብ ወደ ሥር ፍ/ቤት ሲመለስ ከናካቴዉም ሙሉ በሙሉ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል አይደለም ብሎ መደምደም ተገቢ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ግልጽ ሕግን በመጣስ ጉዳዩ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ድጋሚ ተጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በመለሰዉ ጉዳይ ላይ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ከመከራከር ይልቅ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ማቅረቡ ተገቢ ነዉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ስለዚህ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ ሁሉ ላይ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ማቅረብ አይችልም ብሎ መደምደም ተገቢ ሆኖ አይታየኝም፡፡

ሸ. ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አሁን ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ የሆኑትን ጉዳዮች በተመለከተ በሰ.መ.ቁ.90810፣ 76963፣ 125165 እና

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም አሁን ባለዉ ሁኔታ መለወጡ ተገቢ መስሎ አላገኘሁትም፡፡

ቀ. የአሁን አመልካቾች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት እያለ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ እንደሰጠ በሕግ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ ዉስጥ የሰበር አቤቱታቸዉን ለሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረብ እየቻሉ፣ በዚህ ረገድ ግልጽ የሆነ የሰበር ዉሳኔ እያለ ቅሬታቸዉን በወቅቱ አለማቅረባቸዉ ወይም የተዉት በቅን ልቡና ነዉ የሚያስብል ምንም ነገር ስለሌለ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡

በ. በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካቾች የፌዴራል የከፍተኛ ፍ/ቤት አስቀድሞ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም በሕግ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ የሰበር አቤቱታ ባላቀረቡበት፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አሁን ዋናዉን ጉዳይ አከራክሮ ዉሳኔ ከመስጠት በስተቀር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን ድጋሚ አይቶ ዉሳኔ ባልሰጠበት፣ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያቀርቡበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካቾች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፣ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መነሻ በማድረግ የሚሻርበት አግባብ አይኖርም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔዎች በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ በመሆኑ ሊጸኑ ይገባል ብዬ የአብላጫዉ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በመለየት የልዩነት ሀሳቤን አስቀምጣለሁ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ፋ/ዘ **የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡**

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የዳኝነት ሥልጣን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መዝገብ ቁጥር 152590

ጥቅምት 13 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ፀጋይ አስማማው

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ እየሩሳሌም አስገዶም -ጠበቃ መስፍን አሰፋ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ተወልደ ኃ/ማርያም -ጠበቃ ጋሻው አሰፋ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ተጠሪው በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የክፍፍል ጥያቄ ያቀረቡባቸው ንብረቶች በአሜሪካን አገር የሚገኙ በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሳ መሆኑን፣የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11 (2) (ሀ) ድንጋጌ የተሰጠው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን ገልጾ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በሚል መዝገቡን ዘግቶ በመመለስ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 44434 በ20/04/2010ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 206713 በ09/05/2010 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት ነው፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ በፍቺ መፍረሱን ተከትሎ አመልካቿ በ24/08/2009 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ክስ ያቀረቡት የጋራ ንብረት ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግላቸው በመጠየቅ ሲሆን አመልካቹ በበኩላቸው ለክሱ በ02/10/2009 ዓ.ም. መልስ ከመስጠታቸው በተጨማሪ በአመልካቿ ስም በአሜሪካን አገር የተቀመጠ ነው የተባለ የጋራ ገንዘብ እና ንብረት ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግላቸው በመጠየቅ የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱም በተከሳሽ ክሳሽነት ክሱ ላይ የአመልካቿን መልስ ከተቀበለ በኃላ የሥረ ነገር ስልጣንን በተመለከተ ከግራ ቀኙ የቀረበ መቃወሚያ ባይኖርም ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት መርምሮ ተገቢውን ብይን ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑን፣የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ በቀረበ ጊዜ የፍርድ ቤቱ የሥረ ነገር ስልጣን የሚወሰነው አንደኛው ወገን ያቀረበውን ከፍተኛ የሀብት ግምት መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ዋናውን ክስ ከተከሳሽ ክሳሽነት ክሱ ነጥሎ ለማስተናገድ የሚቻልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ አለመኖሩን፣የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ የቀረበበት ገንዘብ እና ንብረት በአሜሪካን አገር እንደሚገኝ የተገለጸ በመሆኑ የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግ ጉዳይን የሚያስነሳ መሆኑን፣የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11 (2) (ሀ) ድንጋጌ የተሰጠው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን በመገለጽ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 9 (1) እና (2)፣231 (1) (ለ)፣245 (2)፣17 (3) እና 30 (1) ድንጋጌዎችን፣እንዲሁም በመዝገብ ቁጥር 83169 እና 37339 የተሰጡ የሰበር ገዥ ውሳኔዎችን በአስረጂነት ጠቅሶ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን በብይን ዘግቷል።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ ያሰናበተው ሲሆን አመልካቿ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈራውን ንብረት በመጥቀስ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲያቀርቡ ተጠሪ ደግሞ በአሜሪካን አገር የተፈራው ንብረት ጭምር ተካቶ ክፍፍል እንዲፈጸም የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ ማቅረባቸውን ተከትሎ ሁለቱም ክሶች የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሱ እንደሆነ በመቁጠር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በሚል የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታው የቀረበበት ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በስረ ነገሩ ለመዳኘት ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የክስ ማመልከቻ የቀረበለት እንደሆነ ተከሳሽ ወገን መቃወሚያ ባያቀርብ እንኳ በቁጥር 231 በተነገረው ድንጋጌ መሰረት ማመልከቻው ተቀባይነት የለውም በማለት መመለስ የሚገባው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 9 ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ ለሥረ ነገር ሥልጣን ጉዳይ መነሻ የሆነው ዋናው ክስ ሳይሆን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በሆነ ጊዜም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 9 ድንጋጌ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚነት የሚኖረው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 17 (3) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡የግል አለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11 (2) (ሀ) ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው አንዱ ነጥብ ሁለቱም ክሶች ማለትም ዋናው እና የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ የግል ዓለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሱ እንደሆነ በመቁጠር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በሚል የመወሰኑን አግባብነት ማጣራት ነው፡፡

ይሁን እንጂ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዋናው ክስ የቀረበባቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ጉዳይ ከተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም ከማለት በቀር ዋናው ክስ ጭምር የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚያስነሳ ነው የሚል አቋም አልያዘም፡፡ሁለቱ ክሶች ተጠቃለው በአንድ ፍርድ ቤት ሊታዩ ይገባል ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰውም የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 17 (3) ድንጋጌን በመዝገብ ቁጥር 83169 የተሰጠውን የሰበር ገዥ ውሳኔ በአስረጂነት በመጥቀስ ነው፡፡በመሆኑም እነዚህን ፍሬ ነገሮች አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤቶች የተያዘው አቋም በራሱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ይሁን እንጂ በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በርግጥ የግል አለም አቀፍ ሕግ የተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ በአግባቡ ሊጤን የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩ የግል አለም አቀፍ ሕግ የተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው ተጠሪው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ያቀረቡበት ገንዘብ እና ንብረት የሚገኘው በአሜሪካን አገር ነው መባሉን ብቻ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የብይኑ ይዘት ያመለክታል፡፡ተጠሪውም በሰበር መልሳቸው ላይ ገንዘቡ እና ንብረቱ በአሜሪካን አገር የሚገኝ ነው ከመባሉ በተጨማሪ ተጠሪው የአሜሪካን አገር ዜግነት ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው ጉዳዩ “Foreign element” ያለው በመሆኑ የሕግ ግጭት አያስነሳም ለማለት አይቻልም ከማለት በቀር የተለየ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡እንደሚታወቀው አንድ ጉዳይ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት ጉዳይን /conflict of laws/ የሚያስነሳ ነው ሊባል የሚችለው አንድን ጉዳይ የሚገዙት ለክርክሩ አወሳሰን አግባብነት ያላቸው የተለያዩ አገሮች ሕጎች ክርክሩ በተለያየ አግባብ እንዲፈታ የሚደነግጉ መሆኑ ሲረጋገጥ፣በዚህም ምክንያት የተለያዩ አገሮች ሕጎች ግጭት ወይም ተቃርኖ /conflict of laws/ መኖሩ ሲረጋገጥ እና ከእነዚህ የተለያዩ አገሮች ሕጎች መካከል ክርክሩ ሊወሰን የሚገባው በየትኛው አገር ሕግ መሰረት ነው? የሚል ጥያቄ አከራካሪ ሆኖ ሲቀርብ መሆኑን የግል ዓለም አቀፍ ሕግ አጠቃላይ መርሆዎች ያመለክታሉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ የግራ ቀኙ ጋብቻ የተፈጸመው በኢትዮጵያ ውስጥ አይደለም በሚል በተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክር ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭም ሆነ የሰበር መልሳቸው የሚጠቁመው ነገር የለም፡፡የፍቺ ውሳኔም የተሰጠው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡በፍቺ ክርክር ጊዜ ስለሕጎች ግጭት ወይም ተቃርኖ በተከራካሪ ወገኖችም ሆነ በፍርድ ቤቱ የተነሳ ጉዳይ የለም፡፡በመሰረቱ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኃላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ፣በአንፃሩ ግን ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው እንደሚሆኑ፣እንዲሁም የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በስተቀር ባልና ሚስት ከተጋቡ በኃላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት የጋራ ሀብታቸው እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 213/1992 በወጣው የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 57 እና 62 (1) እና (2) ስር ተመልክቷል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ አመልካቿ ክስ ያቀረቡትም ከላይ በተመለከቱት የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረት የጋራ ናቸው የተባሉት ንብረቶች ክፍፍል እንዲደደረግላቸው በመጠየቅ ነው።ተጠሪው ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የጠየቁትም በአመልካቿ ስም በአሜሪካን አገር የተቀመጠ ነው የተባለ የጋራ ገንዘብ እና ሀብት ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግላቸው በመጠየቅ ነው።ጋብቻ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ተጋቢዎቹ በጋራ ያፈሩትን ንብረት የባለሀብትነት መብት በተመለከተ የአሜሪካን አገር ሕግ ጉዳዩን የሚገዛው ከኢትዮጵያ ሕግ በተለየ ሁኔታ ነው በሚል በተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክር የለም።የስር ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ የለም።ጉዳዩን በሚገዙት የሁለቱ አገሮች ሕጎች መካከል ግጭት ወይም ተቃርኖ አለ ካልተባለ ደግሞ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የቀረበበት ገንዘብ እና ንብረት የሚገኘው በአሜሪካን አገር ነው መባሉ እና ተጠሪው የአሜሪካን አገር ዜግነት ያላቸው መሆኑ ብቻውን ጉዳዩ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም።ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩትን በአሜሪካን አገር የሚገኝ ነው የተባለ ገንዘብ እና ንብረትን በተመለከተ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የሚሰጥ ውሳኔ በአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች ሊፈጸም ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ጥያቄ ደግሞ ራሱን የቻለ የፍርድ አፈጻጸም ጥያቄ እንጂ ተመሳሳይ ጉዳይን ከሚገዙ የተለያዩ አገሮች ሕጎች ግጭት ወይም ተቃርኖ ጋር በቀጥታ የሚያያዝ ጉዳይ አይደለም።እንደ ስር ፍርድ ቤቶች አቋም ጉዳዩ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ተስተናግዶ ውሳኔ ቢሰጥ እንኳ በአሜሪካን አገር ይገኛሉ የተባሉትን ገንዘብ እና ንብረት አስመልክቶ የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ ራሱን ችሎ የሚነሳ ጥያቄ መሆኑን ማስቀረት የሚችል አይደለም።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ መዝገቡን በብይን የዘጋው በመዝገብ ቁጥር 37339 የተሰጠውን የሰበር ገቿ ውሳኔ በአስረጂነት በመጥቀስ ነው።በመሰረቱ አስቀድሞ በቀረበለት ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ቀጥለው በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው በሁለቱ ጉዳዮች ለክርክር የቀረቡት የሕግ እና የፍሬ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነገር ነጥቦች ተመሳሳይነት ያላቸው በሆነ ጊዜ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡በመዝገብ ቁጥር 37339 የተሰጠው ገዥ ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩ ቀድሞውኑ በአንድ መዝገብ ተስተናግዶ ውሳኔ ማግኘት የነበረበት ነው በሚል ክሱን አልቀበልም ማለቱ ተገቢ አለመሆኑ ተገልጾ ጉዳዩ እንዲታይ የተመለሰበት እንጂ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ነው የተባለ ንብረት ከፊሉ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኝ መሆኑ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ተብሎ ትርጉም የተሰጠበት አይደለም፡፡በውሳኔው የመጨረሻ ፓራግራፍ የሰፈረው የውሳኔው ክፍልም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተያዘውን አቋም ለማመላከት ታስቦ የሰፈረ ነው የሚባል እንጂ ሰበር ችሎቱ እራሱ ጉዳዩን በጭብጥነት ይዞ ገዥ ውሳኔ ያሳረፈበት አይደለም፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠቃሹን የሰበር ችሎት ውሳኔ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ነው የተባለ ንብረት ከፊሉ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኝ መሆኑ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ ነው ተብሎ ትርጉም እንደተሰጠበት አድርገው በመውሰድ የያዙት አቋም የውሳኔ ትክክለኛ ዓላማ እና ይዘት መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. ጉዳዩን የማየት የስነ ነገር ስልጣን የለኝም በሚል መዘገቡን ዘግቶ በመመለስ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 44434 በ20/04/2010 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 206713 በ09/05/2010 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ብይን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙ በጋብቻቸው ጊዜ ካፈሩት ገንዘብና ንብረት ከፊሉ በአሜሪካን አገር ይገኛል መባሉ ብቻውን የግል ዓለም አቀፍ ሕግን ተፈጻሚነት ጉዳይን የሚያስነሳ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የቀረበበትን ጉዳይ ጭምር የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው በማለት ወስነናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

4. መዝገቡን አንቀሳቅሶ ክርክሩን ቀጥሎ በማየት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 (1) መሰረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
5. የውሳኔ ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዘገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች- ተክሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
አብዬ ካሳሁን

አመልካች - አቶ ገዛህኝ አየለ - አልቀረቡም
ተጠሪዎች - 1ኛ. አቶ ኑረዲን ዓሊ - ቀረቡ
2ኛ. አቶ አይደር ከድር - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት የአሁን 1ኛ ተጠሪ አላግባብ ተይዞብኛል የሚሉት በከተማው ቀበሌ 04 አስተዳደር ክልል የሚገኘውን ቁጥሩ 027 የሆነ የቀበሌ የንግድ ሱቅ እንዲመለስላቸው ያቀረቡትን ክስ ተመልክቶ የአሁን አመልካች ሱቁን ለከሳሽ (1ኛ ተጠሪ) እንዲያስረክቡ ያሳለፈውን ውሳኔ እና ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔው ግድፈት አልተገኘበትም በማለት የቀረበለትን አቤቱታ ባለመቀበል ትዕዛዝ በመስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 29/2009 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ አከራካሪው ጉዳይ የቀበሌ ቤት ሆኖ ዕያለ የስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው በማለት ክርክሩን አይቶ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

በበኩላችን አመልካች በዳኝነት ስልጣን ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ክሱ የቀረበው የድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 04 አስተዳደር በሚያስተዳድረው በቀበሌው ክልል የሚገኘውን ቁጥሩ 027 የሆነ የንግድ ሱቅ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለማስመለስ ሲሆን ከክሱ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው ዳኝነት የተጠየቀው የሥር 1ኛ ተከሳሽ (የአሁን 2ኛ ተጠሪ) በከሳሽ ከተሰጠው የውክልና ስልጣን ውጪ በቤቱ በራሱ ሥም የንግድ ፍቃድ ከማውጣቱም በላይ ለ2ኛ ተከሳሽ (አሁን አመልካች) በአደራ ሰጥቶት የሚገኝ በመሆኑ እንዲመልስልኝ ብጠይቀውም ለመመለስ ፈቃደኛ ስላልሆነ ከመንግስት የተከራየሁትን የንግድ ሱቅ እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ በመግባት የውሉን ይዘት መርምሮ ቤቱ ለከሳሽ እንዲመለስ ወስኗል፡፡

በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33(1)(ረ) እንደተደነገገው የከተማው አስተዳደር የሚያስተዳድራቸው ሆኖ ለንግድ፣ ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ካሉ የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክሶችን ተመልክቶ ለመወሰን የድሬደዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ለክሱ ምክንያት የሆነው በግለሰቦች መካከል የተደረገ ውል ሲሆን ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ የተሰጠውም ከውሉ ጋር በተያያዘ በቀረበው ክርክር ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ከፍ ሲል በተጠቀሰው ድንጋጌ የሚሸፈን አይሆንም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 4 ሥር እንደተመለከተውም በቀጥታ ወይም በግልፅ ካልታገዱ በቀር መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሁሉ የፍትሐ ብሔርን ክስ ተቀብለው ለማከራከር ሥልጣን አላቸው፡፡

በአጠቃላይ ጉዳዩ በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ሊታይ ይገባል በሚል በአመልካች የቀረበው መከራከሪያ ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ እና ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ህጎች ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 60477 ሚያዚያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12730 ሰኔ 20 ቀን 2009 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ህዳር 6/2010 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

አ/ጉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 145733

ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመካዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ ኤበሳ አመንቴ ጃለታ -

ተጠሪዎች፡- 1. የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት

2. የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ አካባቢ ንግድና እንዲስቱሪ ፅ/ቤት

መዝገቡ የተቀጠረዉ ለምርመራ ነዉ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 26794 ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ነዉ፡፡

ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች እንደነበሩ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ክስ ይዘት፡- በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 108 ከግለሰብ ላይ በመከራየት ከ2ኛ ተከሳሽ መ/ቤት በተሰጠኝ የዋና ምዝገባ ምስክር ወረቀት የንግድ ስራ ፍቃድ የሆቴል ድርጅት በማቋቋም አገልግሎት ላይ እያለሁ ከሳሽ ለ2009 ዓ/ም የግብር ዘመን ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሊከፈል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚገባውን የመንግስት ግብር በመክፈል እና ለ2009 ዓ/ም የግብር ዘመን የንግድ ስራ ፍቃድ እንዲታደስ የሚፈቅድ ክሊራንስ በመቀበል 2ኛ ተከሳሽ ጥያቄ በቀረበለት በአጭር ጊዜ ውስጥ የከሳሽን ንግድ ስራ ፍቃድ ማደስ ሲገባው አላግባብ ለረጅም ጊዜያት ሲያጉላላኝ ከቆየ በኋላ በቀን 28/04/2009 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ የአካባቢ ፅ/ቤት የንግድ ስራ ፍቃድህ እንዲታገድ ስላሳወቀኝ የንግድ ስራ ፍቃድህ አናድስም በማለት ክልከላ ከማድረጉ በላይ የንግድ ስራ ፍቃድህ ታግዷል በማለት በቀን 28/04/2009 ዓ/ም የተፃፈ የማሳወቂያ ደብዳቤ ሰጥቶኛል፡፡ ስለሆነም የንግድ ስራ ፍቃዴን ያገዱኝ እና እንዳይታደስ የከለከሉኝ ያለአግባብ ስለሆነ ክልከላው ተነስቶ የንግድ ስራ ፍቃዳቸው እንዲታደስ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በበኩላቸው በስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች በመሆን በሰጡት መልስ በከሳሽ የንግድ ድርጅት ላይ በተደጋጋሚ በተደረገ የድምፅ ልኬት ከሳሽ የሚለቀቀው የድምፅ ማጉያው ድምፅ ከሚፈቀድው ድምፅ ልኬት በላይ በመሆኑ በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ የድምፅ ብክለት እያደረሰ ስለመሆኑ በባለሞያ የተረጋገጠ በመሆኑ የተወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ በአግባቡ መሆኑ በመግለፅ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካች የንግድ ስራ ፍቃድ የታገደውና እንዳይታደስ የተከለከለው ከህግ ውጪ ነው በማለት የስር 2ኛ ተከሳሽ የነበረው አዲስ ከተማ ክ/ከተማ የንግድ ፅ/ቤት ተጠሪን የንግድ ስራ ፍቃድ ያገደውና እንዳይታደስ የከለከለው ከህግ ውጪ ነው ፡፡ የአመልካች የንግድ ስራ ፍቃድ ሊታደስ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመቀጠል ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓንቀፅ 46 መሠረት አግባብ ባለው አካል አስተዳደራዊ እርምጃዎች የተወሰደበት ማናቸውም ሰው በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 47 ንኡስ አንቀፅ 3

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሠረት በህግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ቅሬታ ካለው ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ያለበት ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንጂ በቀጥታ ክስ ለአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አሁን በአመልካች የቀረበው አቤቱታ ይህ ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የአመልካች ቅሬታ ይዘት ባጭሩ ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀፅ 46 እና 47 መሰረት በአስተዳደር አካል የተወሰዱት ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው በህግ ጉዳይ ላይ ስልጣን ላለው ፍርድቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይገባል ሲባል ጉዳዩ መቅረብ ያለበት ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንጂ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አይደለም በማለት ውሳኔ መስጠቱ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 79 መሰረት የተቀመጠውን መብት የጣሰና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት እንዲታይ በመደረጉ 1ኛ ተጠሪ መልስ በፅሁፍ የሰጠ ሲሆን ለ2ኛ ተጠሪ አመልካች መጥሪያ ባለመውሰዳቸው አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ቅሬታ እንዳልፈለገው ተቆጥሮ የታለፈ ስለመሆኑ መዝገቡ ያመለክታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም በሰበር አጣሪው ችሎት እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል ፡፡ እንደመረመርነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ በመሆን ያቀረበው ክስ ከ2ኛ ተከሳሽ መ/ቤት በተሰጠኝ የዋና ምዝገባ ምስክር ወረቀት የንግድ ስራ ፍቃድ የሆቴል ድርጅት በማቋቋም አገልግሎት ላይ እያለሁ ከሳሽ ለ2009 ዓ/ም የግብር ዘመን ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሊከፈል የሚገባውን የመንግስት ግብር በመክፈል እና ለ2009 ዓ/ም የግብር ዘመን የንግድ ስራ ፍቃድ እንዲታደስ የሚፈቅድ ክሊራንስ መነሻነት 2ኛ ተከሳሽ የከሳሽን ንግድ ስራ ፍቃድ ማደስ ሲገባው የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ የአካባቢ ፅ/ቤት የንግድ ስራ ፍቃድህ እንዲታገድ ስላሳወቀን የንግድ ስራ ፍቃድህ አናድስም በማለት ክልከላ ከማድረጉ በላይ የንግድ ስራ ፍቃድህ ታግዷል በማለት በቀን 28/04/2009 ዓ/ም የተፃፈ የማሳወቂያ ደብዳቤ እንደደረሰው በመግለፅ እና የንግድ ስራ ፍቃዳቸውን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዳይታደስ የከለከለው ያለአግባብ መሆኑ ጠቅሰው የንግድ ስራ ፍቃዳቸው እንዲታደስ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓንቀፅ 46 መሠረት አግባብ ባለው አካል አስተዳደራዊ እርምጃዎች የተወሰደበት ማናቸውም ሰው በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 47 ንኡስ አንቀፅ 3 መሠረት በህግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ቅሬታ ካለው ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ያለበት ለአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንጂ በቀጥታ ክስ ለአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑ ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለመረዳ እንደተቻለው ተጠሪዎች የአመልካችን የንግድ ስራ ፍቃድ እንዳይታደስ በመከልከል የወሰዱት እስተዳደራዊ እርምጃ በተመለከተ አመልካች በቀጥታ ለአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኝነት መጠየቃቸው አግባብነት ነው ?ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ መመርመሩ አስፈለጊ መሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓንቀፅ 46 እንደተመለከተው አዋጅ፣አዋጅን ተከትለው የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ተላልፎ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ አግባብ ያለው አካል በአዋጁና አዋጁን ለማስረፊፀም በሚወጣ ደንብ በተመለከተው መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወስድ የሚደነግግ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አግባብ ያለው ባለስልጣን የበላይ ሃላፊ የቀረበውን አቤቱታ ሰምቶ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ እንዳለበት በተጠቀሱት ቀናት ውስጥ የበላይ ሃላፊው ውሳኔውን ያላሳወቀው እንደሆነ ቅሬታ አቅራቢው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረብ እንደሚችል በዚሁ አዋጅ ዓንቀፅ 47(2) የተመለከተ ሲሆን ፤አግባብ ያለው ባለስልጣን በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም ምላሽ ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው ውሳኔ በተሰጠ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት በህግ ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል በዚሁ አዋጅ ዓንቀፅ 47(3) ስር ተደንጓል፡፡ ከዚሁ ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት የሚቻለው አግባብ ያለው ባለስልጣን ውሳኔ ያገኘ እና በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን በህግ ጉዳይ ላይ ብቻ ይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳለው ነው፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተያዘው ጉዳይ በቀን 28/04/2009 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የንግድ ስራ ፍቃድህ አናድስም፤ የንግድ ስራ ፍቃድህ ታግዷል በማለት ተጠሪ በቀን 28/04/2009 ዓ/ም የተፃፈ ደብዳቤ ለአመልካች የደረሰው በመሆኑ አመልከች በዚሁ አስተዳደራዊ እርምጃ ቅር የተሰኘ ከሆነ በንግድ ምዝገባ ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓንቀፅ 47(3) መሰረት ይግባኝ የማቅረብ መብት እንጂ በቀጥታ ለአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ስለማይችሉ የስር ፍርድቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1.በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 26794 ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡

2 . በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር---153617

ቀን-መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ደሱ ታምሩ

ተጠሪ፡- ፊያ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- የተጠሪ አባላት እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ስራ ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር በሚል ተደራጅተን ስንሠራ ቆይተን ወደ ፊያ ጠቅላላ ስራ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በሚል ወደ ንግድ ማህበር ቀይረናል፡፡ አመልካች የዚህ ማህበር ስራ አስኪያጅ በመሆን ከሰኔ ወር 2003 ዓ.ም እስከ መጋቢት 26 ቀን 2006 ዓ.ም ሲሠራ በቆየበት ወቅት በተለያየ ምክንያት የወሰደዉና ማህበሩ ላይ ጉዳት ያደረሰዉን በጠቅላላዉ ብር 83,517.18 ይክፈለን የሚል ነዉ፡፡

አመልካች በሰጠዉ መልስ በስራ አስኪያጅነት የሠራሁት ማሕበሩ የሕብረት ሥራ ማህበር በነበረበት ወቅት እንጂ የንግድ ማህበር ከሆነ በኃላ ሥራ አስኪያጅ አቶ አለማየሁ አዱኛ ነበር፡፡ ዳኝነት የተጠየቀባቸዉን ገንዘቦች ለመክፈል በወቅቱ የሂሳብ ሠራተኛ ወይም ገንዘብ ያዥ ስላልነበርኩ ለመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኃላ መርምሮ አመልካች ተጠሪ ዳኝነት የጠየቀዉን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘብ ለመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ብር 83,517.18 ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ አመልካቾች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ አመልካች ኃላፊነት አስከትሏል የተባለዉን ድርጊት የፈጸመዉ የተጠሪ ማህበር ወደ ንግድ ማህበር ከመቀየሩ በፊት እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ስራ ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር በነበረበት ወቅት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 47 እና 49 መሠረት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለዉ የሽምግልና ዳኝነት አካል እንጂ ለመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖረዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ያቀረበዉን ይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ክስ በተመሠረተበት ወቅት ተጠሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሕብረት ሥራ ማሕበር መሆኑ ቀርቶ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 147/91 የሚተዳደር ሳይሆን በንግድ ሕጉ የሚገዛ በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ የሚታየዉ በሽምግልና ዳኝነት ነዉ በማለት መደበኛ ፍ/ቤት የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የለዉም ሲል የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ መሻሩ ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ ዉሳኔዉን ሽሮ የፍሬ ጉዳይ ይግባኙን ተመልክቶ ተገቢዉን ይወስን ዘንድ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመለስ ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ዉሳኔዉን ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- በእናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ስራ ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር እና በፈያ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል በዉልም ሆነ በሕግ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ሳይኖር እንዲሁም ግንኙነት እንዳላቸዉም ክርክርም ሆነ ማስረጃ ቀርቦ ባልተረጋገጠበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ከመጀመሪያዉ ክሱን ለማቅረብ የቻለዉ የቀድሞ የሕብረት ሥራ ማህበሩ መብትና ግዴታዎች በሙሉ ወደ አሁኑ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመለወጡ ምክንያት መሆኑን በግራ ቀኙ ከቀረበዉ ክርክር እና ማስረጃ መገንዘብ ይቻላል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ የተሳሳተ ነዉ፡፡ የሕብረት ሥራ ማህበሩ ከፈረሰ ከዓመታት በኋላ ክስ የቀረበዉ በሌላ ማህበር ስም ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ኃ/የተ/የግል ማህበሩን የሚመለከቱትን ብቻ በመለየት ክስ አልመሠረተም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት በሕብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49(3) እና የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 91745 የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሚቃረን መልኩ የሰጡት ዉሳኔ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የተጠሪ ድርጅት ቀደም ብሎ እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ሥራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሕብረት ሥራ ማህበር ነበር በማለት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሲወሰን ምንም ዓይነት ማስረጃ ሳይቀርብና በሕብረት ሥራ ማህበርና ኃ/የተ/የግ ማህበር መካከል ያለዉ ልዩነት ከግንዛቤ ዉስጥ ሳይገባ ነዉ በማለት አመልካች ያቀረበዉን ቅሬታ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የሰጠዉ መልስ ይዘት፡- እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ስራ ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር በጥቃቅንና አነስተኛ ሲደራጅ የነበረዉ ስያሜ ሲሆን በ2004 ዓ.ም ወደ ፈያ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር በሚል የስያሜ ለዉጥ አድርጓል፡፡ በሁለቱ መካከል የስም ለዉጥ እጂ የአባላትም ሆነ የንብረት ልዩነት በሌለበት ሁኔታ ምንም የሕግ ግንኙነት የላቸዉም የሚለዉ ቅሬታ ተገቢነት የለዉም፡፡ የቀድሞ ማህበር አባላቱንና ንብረቱን በመያዝ የተጠሪን ንግድ ማህበር መስከረም ወር 2006 ዓ.ም ሲቀየር አመልካች እስከ መጋቢት 2006 ዓ.ም በሥራ አስኪያጅነት አገልግለዉ ከማህበር አባልነት ተሰናብተዋል፡፡ አመልካች ሥራ አስኪያጅ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ ላደረሱት ጉድለት በአንድ ላይ ከሚጠየቁ በቀር ተጠሪ ክስ ማቅረብ ያለበት ለይቶ ነዉ የሚለዉ ክርክር ተገቢነት የለዉም፡፡ ስለሆነም አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ ተገቢነት የሌለዉ በመሆኑ ዉድቅ ይደረግልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተገነዘብነዉ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ሲያቀርብ የጠየቀዉ ዳኝነት ፊያ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ተብሎ ከመመዝገቡ በፊት እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ሥራ ኃ/የተ/የህብረት ሥራ ማህበር በሚል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚታወቅበት ወቅት አመልካች የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሠራ ለግል ጥቅሙ ያዋለዉንና በሌላ መንገድ በድርጅቱ ላይ ያደረሰዉን ጉዳት በድምሩ ብር 83,517.18 እንዲከፍለዉ ሲሆን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ሙሉን ገንዘብ እንዲከፍል ወስኖበታል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ሳይገባ ለክሱ መነሻ የሆነዉ ነገር ማሕበሩ የሕብረት ሥራ ማሕበር በነበረበት ወቅት የተፈጸመ ተግባርን መነሻ ያደረገ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 149/91 አንቀጽ 49 እና 47 መሰረት ስልጣን የተሰጠዉ ለሽምግልና ዳኝነት አካል በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ዓይቶ ለመወሰን ስልጣን የለዉም በማለት ዉሳኔዉን ሽሮታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ክርክሩ እየተደረገ ያለዉ ከሕብረት ሥራ ማሕበር ጋር ሳይሆን ኃላፊነቱ ከተወሰነ የግል ማሕበር ጋር በመሆኑ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ዓይቶ የመወሰን ስልጣን አለዉ በማለት የከፍተኛዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ተመልክቶ እንዲወሰን መልሶለታል፡፡

በመሠረቱ በአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 47 እና 49 መሠረት ጉዳዩ በቅድሚያ በእርቅ ካላለቀ በሽምግልና ዳኝነት የሚታየዉ በአንድ ማሕበር እና በአባላቱ ወይም በቀድሞ አባሉ ወይም በአመራሩ ወይም በቀድሞ አመራሩ ወይም ከሌላ ማሕበር ጋር ክርክር ሲኖር ነዉ፡፡ አንድ ማሕበር ሕልዉናዉ ካበቃ በኃላ ወይም መብትና ግዴታዉ የሕብረት ሥራ ማሕበር ወደ አልሆነ የንግድ ማሕበር ተላልፎ በሚገኝበት ወቅት ክርክሩ በሽምግልና ዳኝነት ይታያል የሚል የሕግ ድንጋጌ ባለመኖሩ መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የሆነዉ የአሁኑ ተጠሪ ከሕብረት ሥራ ማሕበር የተላለፈልኝ መብትና ግዴታ አለኝ አለ እንጂ ራሱ ኃ/የተወሰነ የግል ማሕበር በመሆኑ ጉዳዩን ለሽምግልና ዳኝነት ለመወሰድ የሚገደድበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የሕብረት ሥራ ማሕበሩ የቀድሞ አባል በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 47 እና 49 መሠረት በሽምግልና ዳኝነት ሊታይ ይገባል በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተገቢነት የለዉም፡፡

ሌላዉ ግራ ቀኙን ያከራከረዉና የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ ተጠሪ የቀድሞዉ እናብብ ጠቅላላ የኮንስትራክሽን ሥራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሕብረት ሥራ ማሕበር መብትና ግዴታ የተላለፈለት ድርጅት ስለመሆኑ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማስረጃ ሳይቀርብና በሁለቱ ማሕበራት መካከል ያለዉ ልዩነት ከግንዛቤ ዉስጥ ሳይገባ ዉሳኔ መሠጠቱ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ጭብጥ በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ዓይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን አለዉ ሲል ወሰነ እንጂ በሁለቱ ማሕበራት መካከል የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ መኖሩን አስመልክቶ በማስረጃ የተደገፈ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን የፍሬ ጉዳይ ክርክር ዓይቶ አልወሰነም፡፡ ይልቁንም ይግባኝ ሰሚዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን ተመልክቶ እንዲወሰን መልሶለታል፡፡

በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሰረት ለዚህ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን አይደለም፡፡ አመልካች ያነሳውን የፍሬ ጉዳይ ክርክርን በተመለከተ ገና የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበትና በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ታይቶ እንዲወሰን የተመለሰ በመሆኑ በዚህ ረገድ የመጨረሻ ውሳኔ ባልተሰጠበት ጉዳይ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ በሰበር የሚታይ አይሆንም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ የሕብረት ስራ ማህበር አለመሆኑን በማረጋገጥ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን አለው በማለት የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን ተመልክቶ እንዲወስን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መመለሱ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 149468 ጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ 142594

ሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመካዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- የደሴ ከተማ ዓይነ ሥውራን ማሕበር

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ዓይነ ሥውራን ብሔራዊ ማሕበር

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የመ.ቁ 142594 እና 156658 የሆኑ መዝገቦች ተጣምረው ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተሰረዘን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታን በሚመለከት የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ አመልካች፤በዚህ የሰበር ክርክር የሌለ የደሴ ከተማ አሥተዳደር ኢን/ከ/ል/አገ/መምሪያ ተጠሪ የአሁን አመልካች ደግሞ ጣልቃገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪው በ1952 ዓ.ም የተቋቋመ እና በበጎ አድራጎት ድርጅት እና ማሕበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ ማሕበር መሆኑ፤ማሕበሩ በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ቅርንጫፍ ማሕበራት ያሉት እና በደሴ ከተማ ውስጥም የኢትዮጵያ ዓይነሥውራን ብሔራዊ ማሕበር የደቡብ ወሎ ዞን ዓይነሥውራን ቅርንጫፍ ማሕበር ያቋቋመ መሆኑን፤ማሕበሩ በደሴ ከተማ ቧንቧ ውሃ ክፍለ ከተማ ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ የያዘውን ይዞታ ካርታ አውጥቶ እና ግንባታ ገንብቶ አትክልት በመትከል ከሠላሣ ሥድሥት ዓመታት በላይ የሚጠቀምበት መሆኑን፤የሥር ተጠሪው ምንም ዓይነት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖረው የተጠሪን ካርታ በመሠረዝ በአሁን ወቅት በሌላ ባልተቋቋመ እና ሕጋዊ ሰውነት በሌለው በደሴ ከተማ አሥተዳደር በደቡብ ወሎ ዞን ዓይነሥውራን ማሕበር ሥም ካርታ እንዲሰራ ያደረገ መሆኑን በመግለጽ የተጠሪ ካርታ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የሥር ተጠሪ በሰጠው መልስ ተጠሪው ማሕበር ቅርንጫፍ ለመክፈት የተፈቀደለት ስለመሆኑ ማሥረጃ ያላቀረበ መሆኑን፤ቦታው በቅድሚያ ለደሴ ዓይነሥውራን ማሕበር ት/ቤት መሥሪያ መሆኑን እና ለደሴ ከተማ እና አካባቢዋ ዓይነሥውራን ማሕበር በ1972 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የተወሰኑ ግለሰቦች በቂ ባልሆነ ምክንያት ሥያሜውን በተጠሪ ሥም በመቀየር ከታለመለት ዓላማ ውጪ ቤቱን በማከራየት ተጠሪው ሲጠቀምበት የነበረ መሆኑን፤የከተማው ከንቲባ ጽ/ቤት ባቋቋመው አጣሪ ቡድን አማካኝነት ተጣርቶ በቀረበው አሥተያየት ጉዳዩ ተመርምሮ ተጠሪ ከተመለከተው ዓላማ ውጪ በማከራየት የሚጠቀምበት በመረጋገጡ ካርታው መሰረዙ የአካባቢውን ዓይነሥውራን ተጠቃሚ የሚያደርግ እና ሕጋዊ ተግባር መሆኑን በመግለጽ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የአሁን አመልካችም ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር አመልክቶ ተፈቅዶለት ባቀረበው ክርክር ተጠሪ ክስ ያቀረበበት ጉዳይ አሥተዳደራዊ ጉዳይ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን፤ሥረዛ የተደረገበት ካርታ የኢትዮጵያ ዓይነሥውራን ብሔራዊ ማሕበር የደቡብ ወሎ ዞን ዓይነሥውራን ቅርንጫፍ የሚል እና በአዋጁ መሠረት ቅርንጫፍ ስለመሆኑ ማሥረጃ ያልቀረበበት በመሆኑ ተጠሪው ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የሌለው መሆኑን፤አከራካሪው ይዞታ የተሰጠው ለወሎ ክፍለ ሐገር ዓይነሥውራን ት/ቤት መሆኑን፤ የተጠሪ ማሕበር ሥያሜውን ወደ ደሴ ከተማ ዓይነሥውራን ማሕበር በሚል በ1999 ዓ.ም ካርታ ተሰርቶ እየተጠቀመ የተወሰኑ ግለሰቦች በቂ ባልሆነ ምክንያት ካርታ ሰጪውን በማሣሣት የተቀየረ መሆኑ በመረጋገጡ ወደ ቀድሞው እንዲመለስ ውሳኔ ማሳለፉ ሕጋዊ ተግባር መሆኑን፤ተጠሪ ይዞታውን ለሌላ 3ኛ ወገን በማከራየት ገንዘቡን ለተወሰኑ ግለሰቦች መጠቀሚያ ማድረጉ ስለተረጋገጠ ካርታው እንዲሰረዝ የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ መሆኑን እና አመልካች በክልሉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማሕበራት አዋጅ መሠረት ተመዝግቦ ሕጋዊ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሠውነት የተሰጠው መሆኑን በመግለጽ የተጠሪው ክስ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል። ተጠሪም አመልካች ላቀረበው የጣልቃገብነት መከራከሪያ መልስ ሰጥቷል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ የተመለከተው በደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ምሥክሮችን ከሰማ እና ጉዳዩን የሚመለከት የተለያየ የሰነድ ማሥረጃ በትዕዛዝ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ የግራቀኙን ክርክር እና ማሥረጃ መርምሮ የቀረቡት ማሥረጃዎች የሚያሳዩት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቦታ ለዓይነስውራን ት/ቤት በሚል ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ በጊዜው እውራን ተራድኦ ድርጅት በአሁኑ ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ አይነስውራን ብሔራዊ ማሕበር ለተባለው ለአሁን ተጠሪ ማሕበር የተሰጠው መሆኑን፤ተጠሪ በቀድሞው የኢትዮጵያ አይነስውራን ብሔራዊ ማሕበር የወሎ ክ/ሐገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአሁኑ ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ ዓይነስውራን ብሔራዊ ማህበር የደቡብ ወሎ ዞን አይነስውራን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያለው መሆኑን እና ይኸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከብሔራዊ ማሕበሩ ጋር በመሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቦታ እንዲሰጠው፤ካርታ እንዲሰራለት እና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀ መሆኑን፤ቦታው ከተሰጠው በኋላም በብሔራዊ ማሕበሩ ስም የሊዝ ውል በመግባት እና የግንባታ ፈቃድ በማውጣት በቦታው ላይ ግንባታ ያከናወነ እና ቦታው ለአመልካች የተሰጠ ስለመሆኑም የሥር ተከሳሹም ሆነ የከንቲባው ጽ/ቤት የሚያውቁ እና የፈቀዱ መሆኑን በመሆኑ ቦታው ለተጠሪ የተሰጠ ነው፤የሥር ተከሳሽ ካርታው የተሰረዘው ቦታው የአመልካች ነው በሚል ቢሆንም ቦታው ሲሰጥም ሆነ ካርታው ሲሰራ አመልካች ቦታው እንዲሰጠው ያመለከተ እንዲሁም ቦታውን የተረከበ ስለመሆኑ ያላስረዳ በመሆኑ የሥር ተከሳሹ ካርታውን ያመከነው ከሕግ ውጪ ነው፤አመልካች ሕጋዊ ሰውነት ያገኘው እና ቦታው ይገባኛል በማለት አቤቱታ ያቀረበው ከጥር ወር 2006 ዓ.ም ወዲህ በመሆኑ አመልካች ባልነበረበት ወቅት ለተገኘ መብት ባለመብት አያደርገውም፤የተጠሪ ካርታ መክኖ በደሴ ከተማ አሥተዳደር እና የደቡብ ወሎ ዞን ዓይነስውራን ማሕበር በሚል የተሰራ ቢሆንም በዚህ ስም የሚጠራ እና የተመዘገበ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ማሕበር የሌለ ስለመሆኑ በሚመለከታቸው አካላት የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ክስ በቀረበበት ቦታ ላይ መብት እና ጥቅም የለውም ሲል ወስኗል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል። ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪው በፌዴራል መንግሥት የተመዘገበ ማሕበር በመሆኑ እና ዋና መሥሪያ ቤቱም አዲስአበባ በመሆኑ ተጠሪ የመሰረተው ክስ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6 መሠረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚታይ ነው፤በሕገመንግሥቱ በተሠጠው ውክልና መሠረት የተጠሪ ክስ በክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚታይ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም ተጠሪ ሥልጣን የለውም በማለት ወስኗል።

ተጠሪ በበኩሉ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ክልሎች በሥራቸው ያሉትን ከተሞች ለማቋቋም፤ለማደራጀት፤ሥልጣን እና ተግባራቸውን ለመወሰን እንዲችሉ የወጣው አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፤የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፤የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፤የቦታ አሠራር እና አጠቃቀም ሕግጋት ደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ጉዳዮች የመዳኘት ፍትሐብሔራዊ ሥልጣን ያለው የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት መሆኑን ይደነግጋል፤ አከራካሪው ጉዳይ በደሴ ከተማ ቧንቧ ውሃ ክፍለከተማ የሚገኘውን ይዞታ ካርታ እና ፕላን ሊሰረዝብን አይገባም የሚል በመሆኑ በከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት የሚታይ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በፍሬነገሩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን በማለት ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መልሶለታል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የመ.ቁ 142594 በሆነው መዝገብ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይዙቱም በፌዴራል መንግሥት የተቋቋሙ እና የተመዘገቡ የንግድ ማሕበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ ውሳኔ ለመስጠት የሥረ ነገር ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፤ክርክሩ ከማንኛውም የክስ ምክንያት የመነጨ ቢሆንም የክርክሩ ተሳታፊ በፌዴራል መንግሥት የተመዘገበ ከሆነ ወይም መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያየ ክልል በሆነ ተከራከሪዎች መካከል የተነሳ ክርክር የማየት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፤ተጠሪ የፌዴራል መንግሥት የተመዘገበ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ማሕበር በሆኑ እና መደበኛ መቀመጫውም አዲስ አበባ በመሆኑ፤አመልካች ደግሞ በአማራ ክልል የተመዘገበ ማሕበር በመሆኑ ክርክሩን የማየት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ሆነው ሳለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የከተማው ፍ/ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አላቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ በፌዴራል መንግሥት የተመዘገበ ማሕበር ሆኖ ሳለ የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለው የመባሉን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የከተማው ፍ/ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አላቸው በማለት የሥር ይግባኝ ሰሚው የከተማው ፍ/ቤት በፍሬነገሩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን በማለት ጉዳዩን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመለሰው መሠረት ጉዳዩ የተመለሰለት የሥር ይግባኝ ሰሚው የከተማው ፍ/ቤት ዋናውን ጉዳይ አይቶ የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በዋናው ጉዳይ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የመ.ቁ 151771 በሆነው መዝገብ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች በመ.ቁ 151771 ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘት ተጠሪ በፌዴራል መንግሥቱ የተመዘገበ ማሕበር ስለመሆኑ እና መደበኛ መቀመጫውም አዲስ አበባ ከተማ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች በቀረበው የምዝገባ የምሥክር ወረቀት ተረጋግጧል፤አመልካች ደግሞ በአማራ ክልል በደሴ ከተማ አሥተዳደር የተመዘገበ በመሆኑ ክርክሩን የማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው የፌዴራል ፍርድ ቤት ነው፤የከተማው ፍ/ቤቶች የይዞታ መብት አጠባበቅን የሚመለከት ክርክር የማየት ሥልጣን ያላቸው ቢሆንም አዋጅ ቁጥር 25/88 ን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጣቸውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች በማይቃረን ሁኔታ እንጂ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ሊሆን አይገባውም፤በመሆኑም አመልካች በመ.ቁ 142594 ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ምላሽ ሳያገኝ በፍሬጉዳዩ ላይ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ፤ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ፡-

1. የደሴ ከተማ አሥተዳደር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበውን ክስ ተቀብሎ ለመወሰን የሚያስችል የሥረ-ነገር ሥልጣን አላቸው? ወይስ የላቸውም?
2. የሥር ፍ/ቤቶች በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

የፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 (2)እና(6) መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን፤በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች እና ማሕበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን ተቀብለው የማስተናገድ ሥልጣን እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፤የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፤የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፤የቦታ አሠራር እና አጠቃቀም ሕግጋት ደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ጉዳዮች የመዳኘት ፍትሐብሔራዊ ሥልጣን ያለው የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ሁለቱም አዋጆች የየራሣቸውን ዓላማ ይዘው የወጡ ከመሆናቸው አኳያ በመዝገቡ የተያዘው ጉዳይ በየትኛው ፍ/ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን ሥር ሊታይ እንደሚገባ መለየት አስፈላጊ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 (2)እና(6) መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን፤በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ድርጅቶች እና ማሕበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮች በማለት የተገለጸው ሀሳብ የጉዳዮች ዓይነት ምንም ይሁን ምን ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ ክርክርን፤በፌዴራል መንግሥት የተመዘገበን ማሕበር የሚመለከት ክርክርን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፤የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፤የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፤የቦታ አሠራር እና አጠቃቀም ሕግጋት ደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ጉዳዮች የመዳኘት ፍትሐብሔራዊ ሥልጣን ያለው የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት መሆኑን በመግለጽ የሚደነግግ ሲሆን ለጉዳዩ ዓይነት ትኩረት በመስጠት በድንጋጌው ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮች በከተማው አሥተዳደር ፍ/ቤቶች የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር እንዲታዩ ታሳቢ በማድረግ የተደነገገ ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5 (2)እና(6) መሠረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቀው መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ ወይም በፌዴራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች እና ማሕበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ማናቸውም ዓይነት ክርክሮችን ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያሻው መሠረታዊ ነጥብ በመሆኑ አዋጆቹ ከወጡለት ዓላማ አንጻር በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል እንዲሁም በፌዴራል መንግሥቱ ተመዝጋቢ የሆነ ማሕበር ተከራካሪ የሆነበት ነው ተብሎ አካላት ክስ የቀረበበት ጉዳይ በደሴ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ይዞታን በሚመለከት የተሰጠን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አላግባብ ተሰርዞብናል በማለት የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ከመሬት ይዞታ ባለመብትነት ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ይህንኑ በሚመለከት የሚቀርብ ክስ በከተማው ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚታይ እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ ወይም በፌዴራል መንግሥቱ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች እና ማሕበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮች በፌዴራል ፍ/ቤቶች የሥረነገር የዳኝነት ሥልጣን የሚታዩ መሆናቸው የሚደነግግ ቢሆንም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 52/2/ለ ለክልሎች በተሰጠው ሕግ የማውጣት ሥልጣን መሠረት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የወጣው አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 ደግሞ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፤የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፤የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፤ የቦታ አሠራር እና አጠቃቀም ሕግጋት ደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ጉዳዮች በከተማው ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚታዩ መሆናቸውን የሚደነግግ በመሆኑ በመዝገቡ የተያዘው ጉዳይ በየትኛው ፍ/ቤት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን ሊታይ ይገባል የሚለውን ለመለየት የክርክሩን ልዩ ባህርይ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አከራካሪ የሆነው ጉዳይ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተሰጠን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስረዛን የሚመለከት ሲሆን አከራካሪ የሆነው ይዞታ የሚገኘውም በደሴ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 25 የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የሚቀርበው ክስ ንብረቱ በሚገኝበት ቦታ ላስቻለው ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ክልሎች በሕገመንግሥቱ በተሰጣቸው ሕግ የማውጣት ሥልጣን መሠረት የወጣው አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 ደግሞ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፤የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፤የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፤የቦታ አሠራር እና አጠቃቀም ሕግጋት ደንቦች እና መመሪያዎች አፈጻጸምን የሚመለከቱ ጉዳዮች በከተማው ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚታዩ መሆናቸውን የሚደነግግ በመሆኑ፤ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት በመሆኑ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 25 የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የሚቀርበው ክስ ንብረቱ በሚገኝበት ቦታ ላስቻለው ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት የሚደነግግ በመሆኑ አከራካሪ ከሆነው ጉዳይ አንጻር የተከራካሪ ወገኖች መደበኛ ነዋሪነት ወይም የተከራካሪው ወገን የፌዴራል መንግሥቱ ተመዘጋቢ መሆን ግምት ውስጥ ሳይገባ የጉዳዩን ዓይነት መሠረት በማድረግ አዋጅ ቁጥር 91/96 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 226/07 አንቀጽ 57/1 መሠረት የከተማው አሥተዳደር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቶች ተጠሪ ያቀረበውን ክስ ተቀብለው የመወሰን የሥረነገር ሥልጣን አላቸው ብለናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

ዋናውን ጉዳይ በተመለከተ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማሥረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች አከራካሪው ቦታ ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ በጊዜው እውራን ተራድኦ ድርጅት በአሁኑ ወቅት ደግሞ ለአሁን ተጠሪ የተሰጠው መሆኑን፤ተጠሪ በቀድሞው የኢትዮጵያ አይነስውራን ብሔራዊ ማሕበር የወሎ ክ/ሐገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአሁኑ ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ ዓይነስውራን ብሔራዊ ማህበር የደቡብ ወሎ ዞን አይነስውራን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያለው መሆኑን እና ይኸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከብሔራዊ ማሕበሩ ጋር በመሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቦታ እንዲሰጠው፤ካርታ እንዲሰራለት እና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀ መሆኑን፤ቦታው ከተሰጠው በኋላም በብሔራዊ ማሕበሩ ስም የሊዝ ውል በመግባት እና የግንባታ ፈቃድ በማውጣት በቦታው ላይ ግንባታ ያከናወነ እና ቦታው ለተጠሪ የተሰጠ መሆኑን፤ቦታው ለተጠሪ ሲሰጥም ሆነ ካርታው ሲሰራ አመልካች ቦታው እንዲሰጠው ያመለከተ እንዲሁም ቦታውን የተረከበ ስለመሆኑ ያላስረዳ መሆኑን፤የሥር ተከሳሽ ካርታውን ያመከነው ከሕግ ውጪ መሆኑን፤አመልካች ሕጋዊ ሰውነት ያገኘው እና ቦታው ይገባኛል በማለት አቤቱታ ያቀረበው ከጥር ወር 2006 ዓ.ም ወዲህ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ክስ በቀረበበት ቦታ ላይ መብት እና ጥቅም የለውም ሲሉ ወስነዋል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት ለዚህ ችሎት የተሰጠው ሥልጣን መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ አከራካሪ የሆነው ይዞታ የተጠሪ መሆኑ እና ለተጠሪ ተሰጥቶ የነበረው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አላግባብ የተሰረዘ መሆኑን፤አመልካች ክስ በቀረበበት ቦታ ላይ መብት እና ጥቅም የሌለው መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ እና ይህ ችሎትም ፍሬነገርን የማጣራት እና ማሥረጃን የመመዘን ሥልጣን የሌለው በመሆኑ በየደረጃው ያሉ የክልሉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤቶች ዋናውን ጉዳይ በተመለከተ በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0316061 መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም የከተማው ፍ/ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አላቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 16958/07 ግንቦት 29 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ.ቁ 1150/09 ሚያዝያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-18027 መጋቢት 21 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. ሚያዝያ 08 ቀን 2010 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

-መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.145128

ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡-

1. ወ/ሮ ኬሚያት ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር ቀረበ በ v.c ከሐረር
2. ወ/ሮ ፍርደውሳ ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ አንዋር ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር } የቀረበ የለም
2. ወ/ሪት መሊካ ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር }

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከልጅነት ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን አመልካቾቹ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 72/09 በ19/04/2009 ዓ.ም.የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17/2009 በ30/08/2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኖቹ ተጠሪዎች ከሌሎች ሶስት ተወላጆች ጋር በመሆን የሚች ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር ልጆች እና ወራሾች መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው በክርክር ላይ እያሉ ተጠሪዎቹ ልጆች መሆናቸውን አናውቅም በማለት የአሁኖቹ አመልካቾች በተቃዋሚነት መቅረባቸውን፣ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በማስረጃ ካጣራ በኃላ የሌሎቹን ተወላጆች ጥያቄ ተቀብሎ ውሳኔ ሲሰጥ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ግን ልጅነታቸው አልተረጋገጠም በሚል ጥያቄአቸውን ውድቅ ያደረገው መሆኑን፣በተጠሪዎቹ አቅርራቢነት ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር እንዲሁም የሚቹ ወንድሞች ናቸው የተባሉትን ሶስት ግለሰቦች አስቀርቦ በማጣሪያ ምስክርነት ከሰማ በኃላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ተጠሪዎቹ ከተለያዩ እናቶች በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ለጉዳዩ አግባብነት አለው ያለውን ሃይማኖታዊ ሕግ እና ድንጋጌ ጠቅሶ ተጠሪዎቹ የሚች ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር ልጆች እና መጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ናቸው በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፣ይህንን ውሳኔ በመቃወም አመልካቾቹ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾቹ ያቀረቡት የዲ.ኤን.ኤ. ምርመራ ይደረግልን ጥያቄ በስር ሸሪዓ ፍርድ ቤት የመታለፉን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል።

በዚህም መሰረት ተጠሪዎቹ የሚች ሼክ አብዱልጀባር ሼክ ጋቱር ልጆች መሆናቸውን አናውቅም በማለት የአሁኖቹ አመልካቾች ከስር ጀምሮ የሚከራከሩ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ ተጠሪዎቹ የሚቹ ልጆች እና ወራሾች ናቸው ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው የሚቹን ሶስት ወንደሞች በማጣሪያ ምስክርነት ከሰማ በኃላ 1ኛ ተጠሪ በሚች እና ወ/ሮ አሊያ ኑሬ በሚባሉ ሴት መካከል በነበረ ጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑ እና 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በሚች እና ወ/ሮ አሻ አብዶ በሚባሉ ሴት መካከል በነበረ ጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑ መረጋገጡን ገልጾ እና ለጉዳዩ አግባብነት አለው ያለውን ሃይማኖታዊ ሕግ በአስረጂነት በመጥቀስ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው፡፡እንደሚታወቀው የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስራቸውን የሚያከናውኑት በሸሪዓ ሕግ እና በሐገሪቱ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ መሰረት ስለመሆኑ የክልሉን ፍርድ ቤቶች እና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 3/1988 /እንደተሸሻለ/ በአንቀጽ 28 ስር ተመልክቷል፡፡ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን መርምሮ የማረም ስልጣን የሚኖረው በክርክር አመራር ረገድ ፍርድ ቤቶቹ የጣሱት ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ መኖሩ ሲረጋገጥ እና ጥሰቱም መሰረታዊ የሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት አለው ያለውን የማጣሪያ ማስረጃ በመስማት እንዲሁም ለጉዳዩ አወሳሰን የሚረዱ የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርመር እና የአመልካቾቹን ተጨማሪ የመከላከያ ምስክሮች ጭምር ሰምቶ ሃይማኖታዊ ሕጉን መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በክርክር አመራር ስነ ስርዓታዊ ጉዳዮች ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ሃይማኖታዊ ሕጉን መሰረት በማድረግ የተሰጠውን ውሳኔ አስመልክቶ ደግሞ ይህ ችሎት ጉዳዩን ሊመረምር የሚችልበት አግባብ አይኖርም፡፡በአመልካቾቹ የቀረበውን የዲ.ኤን.ኤ. ምርመራ ይደረግልን ጥያቄ በማለፍ ተጠሪዎቹ በጋብቻ የተወለዱ መሆናቸውን በማስረጃ አጣርቶ በሃይማኖቱ ሕግ መሰረት የልጅነት እና የወራሽነት ውሳኔ መስጠቱም ፍርድ ቤቱ በክርክር አመራር ረገድ ጥሰት ፈጽሞአል የሚያሰኝ አይደለም፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 72/09 በ19/04/2009 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የክልሉ ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17/2009 በ30/08/2009 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ በመዝገብ ቁጥር 16506 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ21/11/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶአል፡፡
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት እና በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ. 145053

ቀን፡- 24/9/2010ዓ.ም

ዳኞች፡- ተክሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

አብዬ ካሳሁን

አመልካቾች፡- 1ኛ ወ/ሮ ስኳሬ ለገሰ
2ኛ ወ/ሮ ፋንቱ ተዘራ
3ኛ አቶ ፀጋዬ ወ/ተንሳይ
4ኛ ወ/ሮ ጥሩወርቅ አሰፋ
} ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ዉሃና ፍሳሽ ባለስልጣን- የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

1. ጉዳዩ ዉዝፍ የዉሀ ፍጆታ ሂሳብ ለማስከፈል የቀረበ ክስ የሚመለከት ሲሆን የተጀመረዉ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች እና በዚህ መዝገብ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑትን 1ኛ የአ/ከ/ክ/ከተማ ወረዳ 7 አስተዳደር ጽ/ቤት 2ኛ ወ/ሮ ሽቶ መሀመድ 3ኛ አቶ ጳዉሎስ አለማየሁ ተከሳሾች ነበሩ፡፡
2. የአሁኑ ተጠሪ ከቀረበዉ ክስ መረዳት የተቻለዉ የአሁኑ አመልካቾች እና በስር 6ኛ እና 7ኛ ተከሳሾች የነበሩትን ጨምሮ ከጥቅምት 2006 እስከ ጥር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

2008ዓ/ም ድረስ የተጠቀሙበት ዉሀ ፍጆታ ብር 5895.55 ያልከፈሉ በመሆኑ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

3. አመልካቾች መጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ጉዳይ የበኩላቸዉን የመከላከያ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍ/ቤቱ የሥረ ነገር ስልጣን የለዉም ያሉ ሲሆን በፍሬ ገዳዩም በተጠሪ ክስ የተጠቀሰዉ ሂሳብ የቤት ቁጥር 1180 ሳይሆን የቤት ቁጥር 797 ነዉ የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡
4. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት የሥር ፍ/ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉ በብይን ካለፈ በኃላ አመልካቾች አገልግሎት ያገኙ መሆኑ በማረጋገጡ ተጠሪ በክሱ የጠቀሰዉ ብር 5895.55 ይክፈሉ ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች ይህ ዉሳኔ በመቃወም ለከተማዉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ አቤቱታ አቅርበዉ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ የክርክሩ መሰረታዊ ይዘት ዉል መነሻ ያደረገ በመሆኑ የከተማዉ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን የላቸዉም በማለት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሽሯል፡፡ በመቀጠል በሰበር ስልጣኑ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአዲስ አበባ ፍ/ቤቶች ስረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ መሆኑን በመግለጽ የይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ በድምጽ ብልጫ በመሻር የመ/ደ/ፍ/ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነዉ፡፡
5. አመልካቾች ሐምሌ 17 ቀን 2009ዓ.ም በዓፉት የሰበር አቤቱታ የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ሥልጣን የሌላቸዉ መሆኑን ያሳያል ያሉትን ምክንያት በመዘርዘር ዉሳኔዉ እንዲሻር ጠይቋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት አጣሪ ችሎትም አመልካቾች ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ የተደረገበት አግባብ ተጠሪ ባለበት ማጣራት ይቻል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀረበዉ ሲሆን ተጠሪም ጥቅምት 09 ቀን 2010ዓ.ም ባቀረበዉ መልስ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸና አመልክቷል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

6. የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ይዘት ያለዉ ሲሆን እኛም በስር የከተማዉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡
7. እንደመረመርነዉም በስር ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ከቀረበዉ ክስ መገንዘብ የተቻለዉ የአሁኑ አመልካቾች የተጠቀሙበትን የዉሃ ፍጆታ እንዲከፍሉ የሚጠይቅ ነዉ፡፡ የክሱ መሰረታዊ ይዘት ዉል መነሻ ያደረገ ክርክር ነዉ፡፡ የከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ለመሻር መነሻ ያደረገዉ ክርክሩ በሁለት የከተማዉ አስተዳደራዊ ተቋማት የተነሳ ከሚል እሳቤ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነዉ የአሁኑ አመልካቾች በስር 1ኛ ተከሳሽ ከነበረዉ ቤት የተከራዩ መሆኑ እንዲሁም ከአሁኑ ተጠሪ የዉሃ አገልግሎት የሚያገኙ ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ ተጠሪ ክስ ያቀረበዉ በዉሉ መሰረት የዉሃ ፍጆታ ሂሳብ እንዲከፈለዉ ነዉ፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የዉሃ አገልግሎት መስጠቱ አመልካቾች ደግሞ ተጠቃሚዎች ከመሆናቸዉ አንፃር የተገለገሉበት ሂሳብ የመክፈል ግዴታ ያላቸዉ መሆኑን ተጠቅሶ የቀረበዉ ክርክር መነሻዉ ዉል እንጂ የሁለት ተቋማት ክርክር ስለመሆኑ መዝገቡ አያሳይም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሥር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዉሳኔዉ እንደገለፀዉ ክርክሩ ዉል መነሻ ያደረገ ያልተከፈለ ገንዘብ ለማስከፈል የቀረበ ክስ ከመሆኑ አንፃር የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ያላቸዉ ስለመሆኑ የሚሳይ አንዳችም የህግ መሰረት ያለዉ ክርክር አልቀረበም፡፡ በሌላ በኩል የከተማዉ ሰበር ሰሚ ችሎት አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሠ) የተረጎመበት አግባብ የድንጋጌዉ መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያልተከተለ ነዉ፡፡ የስረ ነገር ስልጣን ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በራሱ ጊዜ የሚያነሳ ስለመሆኑም የፍ/ሕ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 9(2) እና 231 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት ያስገነዝቡናል፡፡ በመሆኑም የከተማዉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩ ዉል መነሻ ያደረገ መሆኑን መገንዘብ እየተገባዉ ጉዳዩ በከተማዉ ፍ/ቤቶች የሚታይ ነዉ በማለት የደረሰበት መደምደሚያ አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 ያላገናዘበ ነዉ ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ውሳኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 26796 ሰኔ 29 ቀን 2009ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 26581 በ 12/08/2009ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የዉል ጉዳይ የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን የላቸዉም በማለት ወስነናል፡፡
3. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 26581 በ 12/08/2009ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 144613

ቀን - 30/09/2010

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

አብዬ ካሳሁን

አመልካቾች፡-1.አቶ ያሲን ኢብራሂም ቀርበዋል

2.አቶ ጌቱ እሸቱ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሉ ታዬ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት መስተዳደር በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልክቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአጭሩ በጉንዶ መስቀል ከተማ ቀበሌ 02 ዉስጥ ያለኝን 200 ካ/ሜትር መሬት ተከሳሾች ያላግባብ የያዙብኝ በመሆኑ ይህኑን መሬት እንዲለቁ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካቾች በበኩላቸዉ ከሳሽ በቦታዉ ላይ የነበራቸዉን መብት በ1995 ዓ.ም ለእህቱ አሰገደች ታዬ መስጠቱን እና አሰገደች ይዞታዉን ለሌላ ሰዉ በሽያጭ ዉል ካስተላለፉላቸዉ ሰዉ ገዝተዉ የያዙት እንጂ የከሳሽ አለመሆኑን ገልፀዉ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ከግራ ቀኝ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ፣ አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቦታ በህገ ወጥ መንገድ የያዙ መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ በላዩ ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን ለተጠሪ እንዲለቁ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይህን ውሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ባለማግኘቱ አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን፣ ሰበር ሰሚው ችሎት መዝገቡን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በሚል ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ የፍሬ ነገር ክርክሩን በተመለከተ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በትዕዛዝ የፀናውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 04/11/09 ዓ.ም በጠበቃቸው አማካይነት ተዘጋጅቶ በቀረበ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንልት ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቀርበው ግራ ቀኝ ክርክራቸውን በጽሑፍ ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተው ነው፡፡ ይህ ችሎትም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ ተቀብሎ የማየት ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ስልጣን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን በሚደነግገው አንቀጽ 5(2) ስር፣ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሰበር ስልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው የክልል ጉዳዮች ላይ እንደሆነ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3-ሐ) ስር ተመልክቷል፡፡ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶችን ስልጣን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 141/2000 ሲሆን፣ የዚህ አዋጅ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 26(1-ሠ) የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የዳኝነት ስልጣን የክልል ጉዳዮችን በተመለከተ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ የተገደበ ስለመሆኑ ይደነግጋል። ከዚህ የምንረዳዉ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ባላቸዉ የዉክልና ስልጣን መሠረት የፌዴራል ጉዳዮችን አይተዉ የሚሰጧቸዉ የመጨረሻ ዉሳኔዎችን ተቀብሎ ለማየት ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ።

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት የአመልካቾች አድራሻ በኦሮሚያ ክልል ደራ ወረዳ ጉንዶ መስቀል ከተማ ቀበሌ 02 ሲሆን፣ የተጠሪ አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 06 መሆኑ ተረጋግጧል። ይህም የሚያሳየዉ ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ መሆኑን ነዉ። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለዉ ለማለት ሁለት ምክንያቶችን የጠቀሰ ሲሆን፣ የመጀመሪያዉ ምክንያት በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 መሠረት አዲስ አበባ ክልል አይደለም የሚል ነዉ። በእኛ በኩል እንደተመለከትንዉ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 የፌዴሬሽኑ አባላት የሆኑትን ዘጠኙን ክልሎች በመዘርዘር በአንቀጽ 50(4) ሁሉም ክልሎች የራሳቸዉ አስተዳደር እንደሚኖራቸዉ ይደነግጋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በአንቀጽ 49 (2) ስር አዲስ አበባ ከተማ ራሱን በእራሱ የማስተዳደር ሙሉ ስልጣን እንዳለዉ እና ዝርዝሩ በህግ እንደሚወሰን ይደነግጋል። በዚህም መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 87/89 እንዲሁም ይህን አዋጅ አሻሽሎ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 361/95 መሠረት አዲስ አበባ ከተማ ራሱን በእራሱ በማስተዳደር ላይ ይገኛል። ከዚህም የምንረዳዉ ኦሮሚያ እና አዲስ አበባ የየራሳቸዉ የሆነ የአስተዳደር ስልጣን ክልል ያላቸዉ መሆኑን ነዉ። በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2) ስር "በተለያዩ ክልሎች" በሚል የተመለከተዉም በተለያዩ የአስተዳደር ክልሎች ዉስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ለማለት እንደሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ። በመሆኑም የዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስልጣን ክልል ዉስጥ የሚኖሩትን አያጠቃልልም ሊባል የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም።

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የጠቀሰዉ ሁለተኛዉ ምክንያት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ንብረት የሚገኘዉ በኦሮሚያ ክልል ዉስጥ እና ዉሉም የተደረገዉ በኦሮሚያ ክልል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉስጥ መሆኑን ነዉ፡፡ በመሠረቱ ንብረቱ የሚገኝበትን ወይም ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታ ግምት ዉስጥ በማስገባት የሚወሰነዉ የአካባቢ ስልጣን እንጂ የስረ ነገር ስልጣን አለመሆኑን ከፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 24 እና 25 ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ የሚኖሩ መሆናቸዉ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ዉል ወይም ንብረቱ የሚገኘዉ በክልሉ ዉስጥ መሆኑ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑን አያስቀርም፡፡ ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሆኖ ግን የአካባቢ ስልጣኑ በክልሎች ስር የሚወድቅ ሲሆን፣ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(2) እና 80(4) መሠረት፣ እንደነገሩ ሁኔታ፣ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዉክልና ጉዳዩን የማየት ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ንብረት እንዲሁም ዉሉ የተደረገዉ በኦሮሚያ ደራ ወረዳ ጉንዶ መስቀል ከተማ 02 ቀበሌ መሆኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በዉክልና ለማየት ስልጣን ባለዉ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ የማድረግ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል ቢሆንም የስረ ነገር ስልጣኑን የፌዴራል ከመሆን አያስቀርም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ የጠቀሰዉ ምክንያት የህግ መሠረት ያለዉ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ የአስተዳደር ክልል ዉስጥ የሚኖሩ መሆናቸዉ ተረጋግጦ እያለ እና በዚህም ምክንያት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሆኖ እያለ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በህግ ተቀባይነት የሌላቸዉን ምክንያቶች በመጥቀስ ጉዳዩን ተቀብሎ በማከራከር የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉ ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/263017 በቀን 19/10/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል።
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ጉዳይ ተቀብሎ ለማየት ስልጣን የለዉም ብለናል።
3. አመልካቾች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸዉ በህግ ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ለማቅረብ ያላቸዉን መብት ይህ ዉሳኔ አያስቀርም።
4. ይህ ችሎት በቀን 26/01/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዕግድ ተነስቷል።
5. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ማ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.157560

መጋቢት 23 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ
ሰለሞን አረዳ
ተክሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ፀሃይ መንክር

አመልካቾች፡ - 1ኛ. ወ/ሮ አለምሸዋ አባተ አበበ
2ኛ. ወ/ሮ ስንታየሁ አበራ መኮንን } ጠበቃ መታሰቢያ ሐይልዬ ቀረቡ
3ኛ. አቶ አንተነህ አበራ መኮንን
4ኛ. አቶ በሐይሉ አበራ መኮንን

ተጠሪዎች፡ - 1ኛ. አቶ ሚሊዮን አባተ አበበ } 1ኛ ተጠሪ በራሳቸውና ስለ
2ኛ ተጠሪ ቀረቡ
2ኛ. ወ/ሮ ፍሬህይወት ፀጋ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15897 ህዳር 15 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 04236 መጋቢት 11 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት በመሻር ባሳለፈው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ በመሆኑ ጉዳዩ በዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ታይቶ በክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ የተፈፀመው ስህተት ይታረምልን በማለት አመልካቾች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በሐረር ከተማ ቀበሌ 09 ውስጥ የሚገኘውንና በይዞታችን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ባቆየነው ቦታ ላይ የሰራነውን ግምቱ ብር 60000.00 (ስድሳ ሽህ) የሆነ ሶስት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ተጠሪዎችን አስጠግተናቸው እንደ ኪራይ የሚታሰብ ብር 500.00 (አምስት መቶ) እየከፈሉ ይኖሩበት ነበር፤ ይሁን እንጂ በይዞታችን ላይ በገንዘባችን የሰራነውን ይህን ሶስት ክፍል ቤት ስመ ሃብት ወደራሳቸው ለማዞር እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆኑን ስለደረስንባቸው ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የበኩላቸውን መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የከፍተኛው ፍርድ ቤት መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አከራካሪውን ቤት አመልካቾች በራሳቸው ይዞታ በህጋዊ የግንባታ ፈቃድ መሰረት የሰሩት ስለመሆኑ በሰውና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች በቤቱና ቤቱ በተሰራበት ይዞታ ላይ ምንም ዓይነት መብት የላቸውም በማለት ተጠሪዎች ቤቱን ለቀው ለአመልካቾች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ባለስልጣን ተጣርቶ እንዲቀርብ ካደረገና የግራቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ክርክር ያስነሳው ቤትና ቦታ ከአሁን አመልካቾች ህጋዊ ይዞታ ውጪ በመሆኑና ይኸው ቦታም በመንግስት ይዞታነት ሥር ያለ በመሆኑ አመልካቾች በህጋዊ መንገድ ካርታ ተሰጥተውበት ካለው ይዞታ ውጪ በሆነ የመንግስት ይዞታ ላይ በጨረቃ ቤትነት ተገንብቶ ባለው ሰነድ አልባ ቤት ላይ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታው በቀጥታ ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ሚያዚያ 26 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር ማመልከቻ የሐረሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ሰኔ 21/2010 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ውሳኔው በህጉ አግባብ የተሰጠ ነው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተብሎ እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡አመልካቾችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡም ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ እንደመረመርነው ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ነው የሚባልበት ምክንያት የሌለ ሲሆን የክልል ጉዳይ መሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ያለው መሆኑም ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የተያዘው ጉዳይ በክልሉ ሰበር ችሎት ሳይታይ በቀጥታ ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳዩች በሰጠው ትርጉም ምክንያት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አስቀድሞ ያሳለፋቸው ገዥ ትርጉሞች በአዋጅ ቁጥር 454/1997 መሰረት በድጋሚ ሊታዩ የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 111887 ሚያዚያ 25/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የሰበር ችሎት በህግ አግባብ ሳይቋቋም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በሰበር አቤቱታ ስርዓት ሊያስተናግዱ የሚችሉበት አግባብ ሊኖር እንደማይችል፤ በሐረሪ ክልል የሰበር ስርዓት በዝርዝር ህጎች በግልጽ ያልተቀመጠና ያለው አሰራርም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያለመኖሩን የሚያስገነዝብ በመሆኑ፤ በውስን ጉዳዮች ላይ ብቻ በክልሉ ሰበር ችሎት ተቋቁሟል እየተባለ የሰበር ስርዓት ተግባራዊ የሚሆንበት አግባብ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም በማለት የክልሉ ሰበር ችሎት ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ በመሻር የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ወገን አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚገባው በቀጥታ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነው በማለት ወስኗል፡፡ በተመሳሳይም በሰ/መ/ቁ 120858 ህዳር 8/2009 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ በሐረሪ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያልተቋቋመ መሆኑን፤ በሐረሪ ክልል የሰበር ስርዓት በዝርዝር ህጎች ያልተቀመጠና ያለው አሰራርም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያለመኖሩን የሚያስገነዝብ መሆኑን በመግለጽ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ መወሰኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ጉዳዩ ሊቀርብ የሚገባው በቀጥታ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስለመሆኑ ተወስኗል፡፡ በነዚህና በመሰል መዛግብት በተሰጠው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አስገዳጅ ትርጉም ምክንያት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዮችን በሰበር ማየቱን እንዳቆመ ተገንዝበናል። በተያዘው ጉዳይም የሰበር አቤቱታው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሳይቀርብ በቀጥታ ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ምክንያት ነው። ስለ ፍርድ ቤቶች ጣምራነት እና ስልጣን በሚደነግገው የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ሥር እንደተመለከተው የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንደሚኖረውና ዝርዝሩ በህግ እንደሚወሰን ይደነግጋል። በተመሳሳይ የሐረሪ ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ 70(2)(ሀ) በማንኛውም የክልሉ ፍርድ ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር የማየት ሥልጣን እንዳለውና ዝርዝሩ በህግ እንደሚወሰን ይደነግጋል።

በዚህ መልኩ በህገመንግስታቱ የተቋቋመው እና ሥልጣኑ የተለየውን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተመለከቱ ዝርዝር ህጎች መውጣታቸውን ከክልሉ ፍርድ ቤቶች የማቋቋሚያ አዋጆችና ማሻሻያቸው መገንዘብ ይቻላል። የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 ምዕራፍ ሁለት ስለመደበኛ ፍርድ ቤቶች መቋቋምና ስለዳኝነት ስልጣናቸው የሚደነግግ ሲሆን በአንቀጽ 3(1) ሥር የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቋቋሙ ተመልክቷል። የችሎቶቹን አሰራር በሚደነግገው አንቀጽ 7(1) ሥር ደግሞ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ችሎቶች እንደሚኖራቸው ተመልክቷል። የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን የሚዘረዝረው የአዋጁ አንቀጽ 15 በንዑስ ቁጥር 3 ስር ደግሞ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የክልሉ ፍርድ ቤት የተሰጠን የመጨረሻ ፍርድ ወይም ውሳኔ በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን እንዳለው ይደነግጋል። ከዚህም በቀር የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 እና ማሻሻያ አዋጆች ቁጥር 8/1991 እና 17/1991 እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 68/1999 ማሻሻያ ካደረገባቸው ጉዳዮች አንዱ የክልሉን ሰበር ችሎት የተመለከተ ነው። በዚህ መሰረት በቀዳሚው አዋጅ ቁጥር 3/1988 አንቀጽ 15(3) የተመለከተው ተሰርዞ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

"መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የክልሉ ፍርድ ቤት የተሰጠን የመጨረሻ ፍርድ ወይም ውሳኔ በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል። የሰበር አቤቱታ አቀራረብ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት እና በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነስርዓት ስለ ይግባኝ አቀራረብ በተደነገጉት መሰረት ነው" በሚል ተተክቷል።

ከፍሲል የተጠቀሱት የፌዴራሉም ሆነ የክልሉ ህገመንግስቶች እንዲሁም የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ እና ማሻሻዎች ሁሉ የክልሉ ሰበር ችሎት መቋቋሙን፤ የሰበር ችሎቱን ሥልጣን እና ለሰበር ችሎቱ አቤቱታ የሚቀርብበትን ስርዓት ሁሉ በህግ መደንገጉን የሚያሳዩ ናቸው። የሰበር ችሎቱን ዝርዝር አደረጃጀትና አሰራር ሥርዓት መደንገጉ ለክልሉ ህግ አውጭ አካል የተተወ በመሆኑ በዚህ መልኩ ዝርዝር ህጎች እንዲወጡ ማድረግ ተገቢ ሲሆን እስካሁን በክልሉ ህግ አውጭ አካል በወጡት አዋጆ መሰረት የክልሉ ሰበር ችሎት በአግባቡ ተደራጅቶ አገልግሎት የማይሰጥበት የህግ ምክንያት የለም። ሥራ ላይ ባሉት ህጎች አግባብ ችሎቱ እንዲደራጅና አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግም ከፍርድ ቤቱ ኃላፊዎች የሚጠበቅ ነው።

ይህ ከሆነ ደግሞ ሥራ ላይ ባሉት ህጎች መሰረት በክልሉ ሰበር ችሎት ታይተው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ሲቀርብ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አልተቋቋመም፤ እንዲሁም በክልሉ የሰበር ስርዓት በዝርዝር ህጎች አልተቀመጠም በማለት ውድቅ መደረጉና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ እንዳይወሰን መደረጉ፤ እንዲሁም ጉዳዩች ሊቀርቡ የሚገባው በቀጥታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስለመሆኑ የተሰጠው ትርጉም ከፍሲል የተጠቀሰውን የህገመንግስቱንና የፍርድ ቤቱን ማቋቋሚያ አዋጆች የተከተለ ባለመሆኑ አስቀድሞ የተሰጠው ትርጉም ሊለወጥ ይገባል ብለናል።

ስለሆነም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት ቀደም ሲል በዚህ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 111887 ሚያዚያ 25/2008 ዓ.ም፤ በሰ/መ/ቁ 120858 ህዳር 8/2009 ዓ.ም እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ መዛግብት ሰጥቶት የነበረውን ትርጉም ለውጠናል። በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ ገዥ ይሆናል ብለናል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በዚህ ምክንያት አመልካቾች የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ባሳለፈው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ በመሆኑ በሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ በቅድሚያ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊያቀርቡ ይገባል በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በዚህ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 111887 ሚያዚያ 25/2008 ዓ.ም፤ በሰ/መ/ቁ 120858 ህዳር 8/2009 ዓ.ም እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ መዛግብት ሰጥቶት የነበረው ትርጉም የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት ከላይ በፍርዱ በተመለከተው መሰረት ለውጠናል፡፡
2. አመልካቾች የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ባሳለፈው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ በመሆኑ በሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊስተናገድና ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ነው ብለናል፡፡
3. መስከረም 7/2011 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈፃፀም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር--156758
ቀን-ሕዳር 26 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የአብክመ ገቢዎች ባለስልጣን ዐ/ሕግ

ተጠሪ፡- አቶ መስፍን ጥላሁን

ይህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ አቶ በላይ አካለ ከሚከራከሩበት የሰ/መ/ቁ 156757 ጋር ከአንድ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ የተነሱ ጉዳዮች በመሆናቸዉ መዝገቦቹ ተጣምረዉ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የአፈጻጸም ጉዳይ ሆኖ የተጀመረዉ በአማራ ክልል በባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት ተጠሪ የፍርድ ባለመብት፤ አቶ ነጋሽ ዉዱ እና ሻ/ል ክ/ጎርጊስ ዘነበ የፍርድ ባለዕዳዎች፤ አቶ በላይ አካለ የጨረታ አሸናፊ ሲሆኑ የአሁኑ አመልካች ደግሞ የመቃወም አመልካች ነበር፡፡ አመልካች ያቀረበዉ መቃወሚያ ይዘት፡- በፍርድ ባለዕዳዎች ስም የሚገኘዉ የድንጋይ ወፍጮ ወይም ክሬሸር የፍርድ ባለዕዳዎች ባልከፈሉት የግብር ዕዳ ብር 2,324,972.07 ምክንያት በደብዳቤ ቁጥር ገቢ 1214/01/06 መጋቢት 22 ቀን 2006 ዓ.ም እና በቁጥር ዘልል/ቀመ/2801/06 በቀን 23/07/06 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 78(2) ለአመልካች በተሰጠዉ ስልጣን ዕግድ ተሰጥቶበት እያለ ወፍጮዉ የሚገኝበት ዘንዘልማ ቀበሌ ሆኖ ሳለ ተጠሪ ፍ/ቤቱን በማሳሳት ንብረቱ ለማይገኝበት ለሕዳር 11 ቀበሌ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ መደረጉ ሆን ተብሎ በመሆኑ ጨረታዉ ተሰርዞ ንብረቱን እንድንረከብ፤ ንብረቱ የድንጋይ ወፍጮ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንደመሆኑ የሽያጭ ጨረታውም ሆነ የዕግድ ትዕዛዙ በግልጽ ማስታወቂያ ለሕዝብ ይፋ ያልተደረገና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 414(2) እና 425(2) ድንጋጌዎችን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ጨረታው ተሠርዞ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 81(1) መሰረት አመልካች የቀደምትነት መብት ያለው በመሆኑ ንብረቱን እንድንረከብ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 መሰረት ጨረታ እንዲፈርስ ጥያቄ መቅረብ የሚችለው በአሻሻጡ ስርዓት ላይ ግዙፍ የሆነ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ የማጭበርበር ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ ሲሆን ይህ ባልሆነበት የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ አቤቱታው መቅረብ የነበረበት ንብረቱ በጨረታ ከመሸጡና ለሦስተኛ ወገን ከመተላለፉ በፊት ሆኖ ሳለ ከተሸጠ በኃላ የቀረበው አቤቱታ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 ድንጋጌ አንጻር ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የጨረታው አሸናፊ በበኩሉ ጨረታውን በሕጋዊ መንገድ ተወዳድሬ አሸንፌ የጨረታው ዉጤት ቀርቦ በችሎት ጨረታው ጸድቆ ገንዘቡን በሙሉ ለፍርድ ባለመብት ከፍዬ የድንጋይ ወፍጮውን እንድረከብ ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል፡፡ ይህ በሆነበት ጨረታው እንዲሰረዝ የቀረበው አቤቱታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 እና 445 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ የሚል ነው፡፡

የስር ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር መርምሮ የድንጋይ ወፍጮ ወይም ክረሸሩ ከአለበት ቦታ ተነቅሎ ገዥው አካል ወደ ፈለገበት ቦታ ሊወሰድ የሚችል በመሆኑ የሚንቀሳቀስ ንብረት ነው፤ አመልካች አቤቱታውን ያቀረቡት ንብረቱ በጨረታ ከተሸጠ በኃላ በመሆኑና ንብረቱ የሚገኝበትን የዘንዘልማ ቀበሌን በበላይነት የሚያስተዳድረው የሕዳር 11 ክፍለ ከተማ በመሆኑ የጨረታው አካሄድ ተገቢ በመሆኑ ጨረታው ሊፈርስ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ክረሸሩ በመሬት ላይ የተተከለ በመሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት መሆኑን፤ ይህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 424(2) እና 454(2) መሰረት የጨረታው ማስታወቂያ በጋዜጣ ከ30 ቀን ባላነሰ ጊዜ ሊነገር የሚገባው መሆኑን በመግለጽ ጨረታው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 መሰረት ጉድለት ያለበት በመሆኑ ጨረታው ፈራሽ ነው፤ ክሬሸሩ የድንጋይ ወፍጮ መቼና በማን እንደተከበረ፣ ማን ምን ያህል ባለገንዘብ ነው የሚሉትን አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን ለስር ፍ/ቤት በመመለስ ወስኗል። በዚህ ውሳኔ ቅር በመሠኘት ተጠሪ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የተመለከተው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ክሬሸር የድንጋይ ወፍጮ የመኪና ዓይነት በመሆኑ ተንቀሳቃሽ ንብረት እንጂ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለመሆኑ ለ15 ቀናት የጨረታ ማስታወቂያ አየር ላይ እንዲቆይ ተደርጎ የተሸጠና የፍ/ብ/ስ/ሥ/ሕ/ቁ 426 ድንጋጌን ያሟላ በመሆኑ ጨረታው ሊፈርስ አይገባም በማለት የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመሻር እና የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል። ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘታቸው ለማስለወጥ ነው።

አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የድንጋይ ወፍጮው ተተክሎ የሚሠራውና የሚገኘው በዘንዘልማ ቀበሌ ሆኖ እያለ እና ይህ ንብረትም አስቀድሞ በግብር ዕዳ ተከብሮ እያለ ተጠሪ ፍ/ቤቱን በማሳሳት ንብረት የማይገኝበትና ገቢ ተቋሙ ሊያውቅ በማይችልበት ሕዳር 11 ቀበሌ ጨረታ እንዲወጣ በማድረግ ጨረታውን እንዲከናወን ያደረጉ መሆኑ እየታወቀ ሁለቱ ቀበሌዎች ራሳቸውን የቻሉ ቀበሌዎች ሆነው እያለ በአንድ ቀበሌ ሥር እንዳሉ ተደርጎ ጨረታው ሊፈርስ አይገባም ያለበት አግባብ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም። ክሬሸሩ ከመሬት ተተክሎ የሚሠራ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሆኖ እያለ እንደሚንቀሳቀስ ንብረት ይቆጠራል ተብሎ መወሰኑ ስህተት ነው። ስለሆነም ጨረታው ሕግን ያልተከተለ በመሆኑ ጨረታው እንዲፈርስ ይወሰንልኝ የሚል ነው።

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤት አከራካሪውን ክሬሸር ወፍጮ አስመልክቶ የቅድሚያ መብት አለኝ ሲል ያቀረበው መቃወሚያ ጉዳዩ በጨረታ ተሸጦ የተፈጸመ ነው ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት የአፈጻጸም ንብረት የመሸጥ ስነ ስርዓት መጠበቁንና የተሸጠው ንብረትስ የሚንቀሳቀስ ነው ወይስ የማይንቀሳቀስ ነው የሚለውን ነጥብ በመለየት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 424-426 እና 445 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስና የመልስ መልሰ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተጠሪ የሰጡት መልስ ይዘት፡- ክሬሸር የድንጋይ ወፍጮ ድንጋይ በሚገኝበት ቦታ እየተዘዋወረ የሚሠራ ነዉ፡፡ ወፍጮዉም ለሥራዉ ሲባል ከመሬቱ ጋር የተያያዘ ቢሆንም ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር ወፍጮዉ ሳይጠፋ እና አጉል ሳይሆን ምንም ብልሽት ሳይደርስበት ከመሬት ለመለያየት የሚችል ማሽን በመሆኑ ተንቀሳቃሽ ንብረት እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1132(2) መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ነዉ የሚባል አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል የድንጋይ ወፍጮዉ በሞተር የሚሠራ በመሆኑ እንደመኪና እና የኮንስትራክሽን ማሽኖች ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ምዝገባ የሚያስፈልገዉ ቢሆንም ጨረታዉ ሲሸጥ በተንቀሳቃሽ ንብረት ጨረታ ስርዓት የሚከናወን ነዉ፡፡ ወፍጮዉ የሚገኘዉ ባሕርዳር ከተማ ሕዳር 11 ክ/ከተማ በመሆኑ ለሕዳር 11 ቀበሌ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ታዛቢ ፖሊስ ባለበት ጨረታዉ የተካሄደ በመሆኑ ስህተት የለዉም፡፡ ቀበሌዉ ትዕዛዙ ሲደርሰዉ ንብረቱ በክልል ስር አይገኝም በማለት አላስፈጽምም አለማለቱ ንብረቱ በክልሉ ስር የሚገኝ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንዲሁም በጨረታዉ የተሸጠዉ ንብረት የሚገኝበትን ቦታ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚለዉ ጉልህ የሆነ የማታለል ወይም የማታለል ተግባር መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 መሰረት ጨረታዉን ሊፈርስ የሚያስችል ምክንያት አይደለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ተደርጎ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

በመዝገብ ቁጥር 156757 አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታም ሆነ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ለማጣራት የተያዘዉ ነጥብ ተመሳሳይ ሲሆን የጨረታዉ አሸናፊ ነዉ የተባሉትና በዚህ መዝገብ ተጠሪ የሆኑት አቶ በላይ አካል የሰጡት መልስ የድንጋይ ወፍጮዉ ራሱን ችሎ ከመሬቱ ጋር ተለያይቶ አገልግሎት መስጠት የሚችልና ከመሬቱ ጋርም ሲለያይ አጉል የማይሆንና የማይጠፋ መሆኑን አረጋግጦ የክልሉ ሰበር ሰሚ የሰጠዉ ዉሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1132(2) ድንጋጌን ያገናዘበ ነዉ፡፡ አመልካች በቅድሚያ መብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለዉ ከሚሸጠዉ ንብረት ላይ ገንዘቡን በማግኘት ወይም ንብረቱን ቀድሞ በመሸጥ እንጂ ንብረቱ ተሸጦ ለሌሎች ባለመብቶች ከተሰጠ በኃላ የቅድሚያ መብቱን የጨረታ ማፍረሻ ምክንያት ሊያደርገዉ አይችልም፡፡ ዘንዘልማ ቀበሌ በሕዳር 11 ክፍለ ከተማ ዉስጥ ያለ በመሆኑ አመልካች እንደሚሉት በማጭበርበር የተሠራ ሳይሆን አመልካች ራሳቸዉ ዕግዱን ለሚመለከተዉ አካል አለማድረሳቸዉን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚያረጋግጥ ነዉ። ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ይጽናልን የሚል ነዉ። አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል። መርምረን እንደተረዳነዉ ክርክር ያስነሳዉ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሆነዉ የድንጋይ ወፍጮ ወይም ክረሸር የፍርድ ባለመብትን ገንዘብ ለማስከፈል ተብሎ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊዉ ከተለየና ገንዘቡን ከከፈለ በኃላ ገንዘቡ ለፍርድ ባለመብቶች ተከፍሎ ገሸርዉ ንብረቱን እንዲረከብ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ርክክቡ ከመፈጸሙ በፊት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረበዉ አቤቱታ የቅድሚያ መብት ያለዉና ንብረቱን ከዚህ በፊት ያሳገደዉ መሆኑን እንዲሁም የጨረታ ሽያጩ አፈጻጸም ሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ ማስታወቂያ ያልተነገረና ጉድለት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ጨረታዉ ይፍረስ የሚል ነዉ። በተለይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጨረታዉ ጉድለት የለበትም ለማለት የሰጠዉ ምክንያት ክርክር ያስነሳዉ ንብረት ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሆኑና የሀራጅ ጨረታ ማስታወቂያዉ ተለጥፎ 15 ቀናት የቆየ በመሆኑ ጨረታዉ ጉድለት የሌለበት በመሆኑ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል። ከዚህ አንጻር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ያስነሳዉ ክሬሸር ወይም የድንጋይ ወፍጮ የሚንቀሳቀስ ንብረት ነዉ በሚል መደምደሚያ ላይ በመድረስ የጨረታ ሽያጩ ጉድለት የለዉም ማለቱ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? እንዲሁም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ንብረቱን አስቀድሞ ማሳገዱንና በሕግ የቅድሚያ መብት ያለዉ መሆኑን በመግለጽ ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚሉ ነጥቦች የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ አብይ ጭብጦች ናቸዉ።

ክርክር ያስነሳዉ የድንጋይ ወፍጮ ወይም ክሬሸር የተሸጠበት የጨረታ ሂደት ጉድለት አለበት ወይስ የለበትም የሚለዉን ለመመለስ በቅድሚያ ንብረቱ የሚንቀሳቀስ ንብረት ነዉ ወይስ የማይንቀሳቀስ ንብረት ነዉ የሚለዉ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባዉ ነዉ። በመሠረቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1130 እና 1132 መሠረት የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የሚባሉት መሬትና ቤት ወይም ከእነዚህ ነገሮች ጋር በግዙፍነት የተያያዘ ሆኖ የተባለዉ ነገር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይጠፋና አጉል ሳይሆን ለመለያየት የማይቻል ሲሆን መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከዚህና በሌሎች ድንጋጌዎች ከተቀመጡት ዉጭ ያሉ ንብረቶች ተንቀሳቃሽ ንብረቶች መሆናቸዉ አሻሚ አይደለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ክርክር ያስነሳዉ ክሬሸር ወይም የድንጋይ ወፍጮ ግብዓት ባለበት ቦታ እየተንቀሳቀሰና እየተተከለ ድንጋይ የሚፈጭ ሲሆን ከሚፈጨዉ የድንጋይ ቦታ ጋር ሳይነጣጠል ተተክሎ ካለበት ቦታ ወይም ጥሬ ዕቃ የመጠቀም መብት ጋር ካልተሸጠ በቀር ራሱን ችሎ እስከተሸጠ ድረስ የማይንቀሳቀስ ንብረት ነዉ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም ክሬሸሩ ከተተከለበት የድንጋይ ማዉጫ ቦታ የመጠቀም መብት ጋር የተሸጠ መሆኑን የሚገልጽ ነገር በሌለበት ሁኔታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ነዉ ሊባል የሚችል ባለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ተንቀሳቃሽ ንብረት ነዉ መባሉ ስህተት አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ስለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር በወጣ አዋጅ ቁጥር 177/91 እና በአዋጁ መሠረት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ቁጥጥርና ምዝገባ እንዲሁም የባለቤትነት ደብተር አሰጣጥ አስመልክቶ በወጣዉ መመሪያ አንቀጽ 3(1/ለ) መሰረት ክሬሸር እንደአስፓልት ሚክሲንግ ፕላንትና ክሬን ሁሉ ከቦታ ወደ ቦታ እየተወሰደና እየተተከለ የሚሠራ ምዝገባና የባለቤትነት ደብተር የሚሰጠዉ ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት መሆኑ ተመላክቷል፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 3(2) መሰረት ከምዘገባና ቁጥጥሩ ዓላማዎች ዉስጥ አንዱ መሳሪያዎቹ ለዋስትና መያዣና ለተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚዉልበትን ሁኔታ ማመቻቸት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከተጠቀሱት የአዋጁና የመመሪያዉ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ክሬሸር ወደ 3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ ወይም እንዳይሸጥ የሚታገደዉ ክሬሸሩ ለሚገኝበት ቀበሌ ወይም የአስተዳደር አካል ደብዳቤ በመጻፍ ሳይሆን ክሬሸሩን ለሚመዘግበዉና የስም ዝዉዉር በማድረግ የባለቤትነት ደብተር ከሚሰጠዉ አካል ዘንድ ዕገዳዉ እንዲመዘገብ በማድረግ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ክሬሸሩ ለሚገኝበት ቀበሌ ደብዳቤ በመጻፉ ብቻ ንብረቱ በሕግ ፊት የጸናና ንብረቱ ወደ 3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ የሚያግድ ዕግድ ነበረበት ለማለት አይቻልም፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከላይ ከተገለጸዉ አንጻር የድንጋይ ወፍጮዉ ወይም ክሬሸሩ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሳይሆን ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት ነዉ የተባለ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 426 መሠረት የጨረታዉ ማስታወቂያዉ ተለጥፎ ለ15 ቀናት የቆየ መሆኑ በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ የጨረታዉ ሂደት ጉድለት አለበት ሊባል የሚችል አልሆነም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሰረት የመቃወም አቤቱታ ያቀረበዉ ንብረቱ በሀራጅ ጨረታ ከተሸጠና ገንዘቡም ለፍርድ ባለገንዘቦች ከተከፈለ በኋላ የቀረበ በመሆኑ አመልካች በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 78(2) መሠረት ያለዉን የቀዳሚነት መብት ሊጠቀም አይችልም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ መወሰኑ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በተገለጸዉ አግባብ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት የመቃወም አቤቱታዉን ያቀረበዉ ክርክር ያስነሳዉ ክሬሸር በጨረታ ከተሸጠና ገንዘቡም ለፍርድ ባለገንዘብ ከተከፈለ በኋላ በመሆኑ፤ በጨረታዉ ሂደትም ጨረታዉን ሊያስፈርስ የሚችል ጉድለት ባለመገኘቱ እንዲሁም ንብረቱ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ የተሰጠ ዕግድ በሕግ አግባብ ያልተመዘገበ በመሆኑ የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 03-61518 ጥር 28 ቀን 2010 ዓ.ም እና 03-61481 የካቲት 02 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጣቸዉ ዉሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡

2. የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ ከተወሰነዉ የሰ/መ/ቁ 156757 ጋር ይያያዝ ተብሏል፡፡

3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር---152339

መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ እድገት ፎጊ - ጠበቃ መሐመድ ሲራጅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ም/ኢ/ር አሻግሬ ወ/ማሪያም - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው አፈጻጸምን የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል በየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን ተከትሎ የነበራቸው ቤት ግምቱ ብር 53,000 ሆኖ ከቀረበ በኃላ ተጠሪ ብር 2000 ጨምሮ በብር 55,000 ለማስቀረት የጠየቀ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው በብር 60,000 ለማስቀረት ጠይቀው ሁለቱም ገንዘብ ለማምጣት በሚል ሄደው ተጠሪ ገንዘብ ይዞ ቢመለስም አመልካች ሳይቀርቡ ቀርተዋል፡፡ ሀራጅ ጨረታ ወጥቶ በሁለተኛው ጨረታ መ/ር አብነት ወልዴ በብር 54,184 ብር ያሸነፉ ሲሆን ተጠሪ አመልካች ከፍዬ አስቀራለሁ ባሉት መሠረት ድርሻውን ብር 30,000 በአንድ ጊዜ ከፍለው የሚያስቀሩ ቢሆን የማይቃወም መሆኑን የገለጸ ሲሆን አመልካች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብር 12,000 ይዘዉ መቅረባቸዉንና ልጆች ስላሏቸዉ ቀሪዉን ለመክፈል ጊዜ እንዲሰጣቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ግራ ቀኙ ያቀረቡት የቅድሚያ ግዥ መብት የሕግ ድጋፍ የለዉም በማለት የጨረታ አሸናፊ የሆነዉ መ/ር አብነት ወልዴ ብር 54,184 ከፍሎ ቤቱን እንዲረከብ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ቅር ተሰኝተዉ ቅሬታ በየደረጃዉ ላሉ ፍ/ቤቶች ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ዉሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- በወረዳዉ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ማዘጋጃ ቤት መጋቢት 04 ቀን 2006 ዓ.ም በባለሙያ ገምቶ ያቀረበዉ ግምት 38,000 ሲሆን በቀጠሮ ከተጠሪ ድርሻ ዉስጥ 12,000 ይገፍ ብቀርብም ተጠሪ ሳይቀርብና እንደፍርዱ እንዲፈጸምለት ሳይጠይቅ ከሰባት ዓመት በኃላ እንሰትና የጓሮ አትክልት አልምቼበት እያለሁ በ2010 ዓ.ም እኔ ባላወቅኩበት ሁኔታ ብር 53,000 ነዉ ተብሎ ተገምቶ በላዬ ላይ መሸጡ ተገቢ ባለመሆኑ የአፈጻጸም ትዕዛዙ ይሻርልኝ፡፡ አንድ መኖሪያ ቤት ያለአግባብ ሦስት ዙር መገመቱ ስህተት ነዉ፡፡ ከፍቺ በኃላ ያለማሁትን የጓሮ አትክልት በብር 816 የተገመተ ቢሆንም ሳይታሰብልኝ ቀርቷል፡፡ በአጠቃላይ በቤቱ የመኖር መብቴ እንዲከበርልኝ በቀደምትነት የመግዛት መብቴ ይጠበቅልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የጨረታ መነሻ ዋጋ ከታወቀ በኃላ ግራቀኙ ይሸጥ የተባለዉን ንብረት ይህንኑ ዋጋ በማጣቀስ ያስቀሩት እንደሆነ የቅድሚያ መብት መብታቸዉን በማረጋገጥ ረገድ ስርዓቱን ከተከተለ በኃላ የቅድሚያ መብት ሊሰጥ አይገባም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ አግባብነት ከሁሉም በላይ ንብረቱ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ከመሆኑ እና አመልካች ከሐራጅ መሸጫ ዋጋ የተሻለ ዋጋ ላቅርብ እያሉ ጥያቄያቸዉ የመታለፉን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 430 ድንጋጌ አፈጻጸም አንጻር ለማየት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት፡- በሕጋዊ መንገድ በማዘጋጃ ባለሙያ ተገምቶ፤ የጓሮ አትክልት ግምት ብር 816 መሆኑንን የአመልካችም መብት በቅድሚያ ተጠብቆላት እኔን ድርሻ ሰጥታ እንድትጠቀም ቢፈቀድላትም በቀጠሮ ሳትቀርብ ቀርታለች፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች የእኔን መብት በመጋፋቷና በተደጋጋሚ መሰናክል በመፍጠሯ በሀራጅ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጨረታ ቤቱ ተሸጦ ድርሻዬ ብር 26,500.0 ተረክቤ የእሷን ድርሻ በሥር ፍ/ቤት ተቀምጦላት እያለ ባለቀ ጉዳይ ያቀረበችዉ ቅሬታ ተገቢነት የሌለዉ በመሆኑ የሰበር አቤቱታዋ ዉድቅ ይደረግልኝ የሚል ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነዉ ግራ ቀኙ በጋራ በጋብቻ ዉስጥ ያፈሩትን ቤት ፍቺን ተከትሎ እንዲከፋፈሉ ዉሳኔ የተሰጠ ሲሆን በአፈጻጸም ሂደት ቤቱ በማዘጋጃ ቤት ብር 51,8161 ተገምቶ ቀርቧል፡፡ ተጠሪ ብር 2,000 ጨምሮ ለመግዛትና የአመልካችን ድርሻ ከፍሎ ለማስቀረት የጠየቀና ገንዘብ ይዞ የቀረበ ሲሆን አመልካች በብር 60,000 ለማስቀረት ጠይቃ ተጠሪም ፈቃደኛ ቢሆንም አመልካች ብር 12,000 ይዛ በመቅረብ ቀሪዉን ለመክፈል ጊዜ ከመጠየቅ በቀር ግዥዉን ለመፈጸምና የቅድሚያ ግዥ መብት ልትጠቀም አልቻለችም፡፡ ከዚህም በኃላ የስር ፍ/ቤት ቤቱን ሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ጨረታዉን በብር 53,000 ያሸነፈዉ መ/ር አብነት ወልዴ ገንዘቡን ከፍሎ ቤቱን በአፈጻጸም እንዲረከብ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ከሸያጭ ገንዘቡ ድርሻዉን የወሰደ ሲሆን አመልካች ድርሻዋን ባለመዉሰዷ በአደራ በመስሪያ ቤቱ ግዥና ፋይናንስ ክፍል እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ አመልካች አጥብቃ የምትከራከረዉ በ2003 ዓ.ም በማዘጋጃ ቤት ተገምቶ በቀረበዉ ግምት መሠረት ብር 12,000 ለመክፈል ይገፍ ቀርቤና ሌላዉን በሂደት ለመክፈል ጠይቄ ባለሀብት ከቤቱ ተፈናቅዬ ቤቱን ገዥዉ እንዲረከብ ትዕዛዝ መሠጠቱ ስህተት ነዉ በሚል ነዉ፡፡

በመሠረቱ አመልካች ክርክር ያስነሳዉን ቤት የቅድሚያ ግዥ መብት ጠይቃ አልተከለከለችም፡፡ እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 430(1) መሠረት በሀራጅ ጨረታዉ ለመሳተፍ ጠይቃ አልተከለከለችም፡፡ አመልካች ለመግዛት በጠየቀችዉ ብር 60,000 እንድታስቀር ተጠሪ ስምምነቱን ገልጾ የነበረ ሲሆን አመልካች የተጠሪን ድርሻ ለመክፈል ይዛ የቀረበችዉ ገንዘብ ብር 12,000 ብቻ በመሆኑ ቤቱን ልታስቀር አልቻለችም፡፡ ጊዜ ተሰጥቶኝ በሂደት ልክፈል የሚለዉ ክርክርም ቢሆን ባለገንዘብ በሆነዉ በተጠሪ ፈቃድ ላይ የሚመሠረት በመሆኑ ጊዜ እንዲሰጥ ሊገደድ አይችልም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ግምት መክፈል የነበረብኝ በ2003 ዓ.ም በነበረዉ ግምት ነዉ የሚለዉ ክርክሯም የሕግ መሠረት የለዉም፡፡ ምክንያቱም ፍርዱ እስካልተፈጸመ ድረስ ቤቱ በአመልካች እጅ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቢቆይም የጋራ ሀብት በመሆኑ በቆይታ የሚመጣዉ የግምት ጭማሪ ሁለቱንም የሚጠቅም በመሆኑ ነዉ፡፡

ሌላዉ አመልካች ከቤቱ ልፈናቀል አይገባም በማለት ብትከራከርም ቤቱን በሀራጅ ጨረታ ተሳትፎ ግዥ የፈጸመዉ ተጠሪ ሳይሆን መ/ር አብነት ወልዴ በመሆኑ ገዥዉ ተከራካሪ ባልሆነበትና በተጠሪነት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ባልተደረገበት ሁኔታ የሀራጅ ሽያጩ ሊሠረዝ ወይም የአመልካች የቅድሚያ ግዥ መብት ሊጠበቅ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች አቤቱታ ተገቢነት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ካቀረቡት የሰበር አቤቱታ አንጻር የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1ኛ. በየም ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06376 መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03196 ጥቅምት 08 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 09299 ታሕሳስ 24 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በስር ፍ/ቤት የተጀመረዉ አፈጻጸም ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ ጥር 10 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

3ኛ. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ 152185

መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ጽ/ቤት

ተጠሪ፡- አቶ ደገፉ ምሰኔ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ፍርድ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 105067 አመልካች ለተጠሪው የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ አዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ይህን ውሳኔ መነሻ በማድረግ ለከፈቱት የአፈጻጸም ክስ አመልካች በሰጠው መልስ ካርታው ሊሰጣቸው የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 721/2004 መሠረት ወደ ሊዝ ስሪት በማስገባት በመሆኑ ተጠሪ ሊከፍሉት የሚገባ ክፍያ አለ በማለት ገልጿል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ጉዳዩ ሳይፈጸም የቆየው በአመልካች ችግር መሆኑን እና ከአዋጁ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በቀድሞ ሕግ መሠረት ሊስተናገዱ የሚገባ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አፈጻጸሙን የመራው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግራቀኙ መካከል ያለውን የአፈጻጸም ክርክር መርምሮ ተጠሪ በተለያየ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ከመውጣቱ በፊት አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው የጠየቁ መሆኑን እና ሊፈጸምላቸው እንዳልቻለ በመ.ቁ 105067 ከተሰጠው ውሳኔ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታው ሊሰጣቸው የሚገባው በአዋጁ አንቀጽ 6 መሠረት ሳይሆን በአንቀጽ 37/1/ መሠረት ነው ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪ ካርታ የወሰዱበት ጊዜ እንጂ የጠየቁበት ጊዜ ወደ ሊዝ ስሪት ገብተው የሚስተናገዱበትን ጊዜ የማይወስን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የካርታ መስተንግዶ ጠየቅኩ ያሉበት ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 2001 ጊዜ ሲሆን በዚህ ወቅት አዋጅ ቁጥር 272/94 እና የከተማ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 1/94 በሰነድ አልባ የሚስተናገዱ አካላት ወደ ሊዝ ስሪት ስለሚገቡበት ሁኔታ እና የካርታ መስተንግዶ ስለሚያገኙበት አግባብ የተደነገገ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች ይህን አልፈው ተጠሪ ያለ ሊዝ ክፍያ እና ስሪት ካርታ እንዲሰጣቸው የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 721/2004 አተገባበር አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የገዛሁት እና ውሉ ተመዝግቦ ማስረጃ እንዲሰጠኝ የጠየቅኩት ንብረት ሰነድ አልባ አይደለም፤ቤቱ በፍቃድ እና በፐላን የተሰራ እና በሻጭ ስም የተመዘገበ ነው፤አመልካች መስሪያ ቤት ጉዳዩ እንዳይፈጸም በማድረግ ሊዝ እስኪታወጅ አቆይቶታል፤ጊዜው የተራዘመው በአመልካች ጥፋት እንጂ በተጠሪ ጥፋት አይደለም፤አመልካች ውሉን ያስገባሁት እና እንዲመዘገብልኝ የጠየቅኩት ከአዋጁ በፊት ስለሆነ ሊፈጸምልኝ የሚገባው ውሉን ባስገባሁበት ወቅት በነበረው ሕግ መሠረት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

ተጠሪ ንብረቱ በስማቸው ተመዝግቦ የባለቤትነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው በማለት በአመልካች ላይ ክስ ያቀረቡት በመስከረም ወር 2008 ዓ.ም መሆኑን፤ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 105067 በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ይፈጸምልኝ በማለት ሲመላለሱ የቆዩ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪው የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ አዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው በማለት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ተጠሪ በየትኛው ሕግ መሠረት ሊስተናገዱ እንደሚገባ በውሳኔው ላይ ለይቶ ያላስቀመጠ መሆኑን፤ተጠሪ ይህንኑ ውሳኔ መሠረት በማድረግ የአፈጻጸም ክስ የከፈቱ መሆኑን እና የስር ፍ/ቤቶችም ተጠሪ ሊስተናገዱ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 37/1/ መሠረት ነው በማለት የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሰጡ መሆኑን ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ ችለናል፡፡

የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 6/3 በነባር ይዞታ ላይ የሰፈረ ንብረት ባለቤትነት ከውርስ በስተቀር በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሰው ከተላለፈ ንብረቱ የተላለፈለት ሰው የቦታው ባለይዞታ መሆን የሚችለው በሊዝ ስሪት መሰረት ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 37/1 ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ቀደም ሲል ቀርበው በእንጥልጥል ላይ ያሉ የከተማ ቦታ ጥያቄዎችን በሚመለከት አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ በቀድሞ ሕግ መሠረት ውሳኔ መስጠት አለባቸው በማለት ይደነግጋል፡፡

የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ከመውጣቱ በፊት አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው የጠየቁ በመሆኑ እና ሊፈጸምላቸው ያልቻለ በመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታው ሊሰጣቸው የሚገባው በአዋጁ አንቀጽ 6 መሠረት ሳይሆን በአንቀጽ 37/1 መሠረት ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱ ቢሆንም ተጠሪ አስተዳደሩ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጥያቄዬን አልተፈጸመልኝም በማለት በመደበኛው ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡ በመሆኑ የተጠሪ ጉዳይ ከአስተዳደሩ እጅ መውጣቱን የሚያሳይ እንጂ በአዋጁ አንቀጽ 37/1 በተገለጸው አግባብ ቀደም ሲል ቀርቦ በእንጥልጥል ላይ እንደነበረ ሊወሰድ የሚገባ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ክስ ያቀረቡት አዋጅ ቁጥር 721/2004 ከወጣ በኋላ በ2008 ዓ.ም ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠውም ተጠቃሹ አዋጅ በስራ ላይ እያለ በመሆኑ የተጠሪ ጉዳይ ሊስተናገድ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 37/1 መሠረት ሳይሆን በአዋጁ አንቀጽ 6/3 በሊዝ ስሪት መሠረት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባቸው ተጠሪ ሊስተናገዱ የሚገባው በአዋጁ አንቀጽ 37/1 መሠረት ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 119226 መጋቢት 11 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 188394 ጥቅምት 16 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አፈጻጸሙ ሊቀጥል የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 37/1 መሠረት ሳይሆን በአዋጁ አንቀጽ 6/3 በሊዝ ስሪት መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. ጥር 17 ቀን 2010 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ካ/የ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ 152172

ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም ሠራተኞች የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር የሕብረት ሥራ ማሕበር

ተጠሪዎች፡- እነ ሰለሞን እሸቱ (191 ሰዎች)

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ውሳኔ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በሕብረት ሥራ ማሕበራት ማደራጃ በሽምግልና ዳኝነት ታይቶ ታሕሣስ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ ይህንኑ ውሳኔ መነሻ በማድረግ አፈጻጸሙን የመራው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ፍርዱን ላለመፈጸም የተጠሪዎች ድርሻ ተለይቶ አልቀረበም በማለት የሰጠው ምክንያት ተጠሪዎች ለግልግል ዳኞች አቤቱታ ሲያቀርቡ 191 ሰዎች አንድ ላይ ሆነው ሲሆን ውሳኔም ያገኙት በጠቅላላው ለ191 ሰዎች በመሆኑ ድርሻቸውን ስለሚያውቁት እና ሊከፋፈሉት ስለሚችሉ የተሰጠው ምክንያት ተቀባይነት የለውም በማለት የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በግልግል ዳኞች ውሳኔ መሠረት ለተጠሪዎች ብር 5,361,749.61 ወጪ አድርጎ ይክፈላቸው፤አመልካች ከአዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ ለተገባው አክሲዮን ባለድርሻ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሆናቸው ባለመብቶቹ የደረሰበት የገንዘብ መጠን የሚገባቸውን ሠርተፍኬት በየስማቸው አዘጋጅቶ ይስጣቸው በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ማሕበሩ 7200 አባላት ያሉት ሲሆን የትርፍ ክፍፍል ለአባላቱ የሚከፋፈለው በሕብረት ስራ ማሕበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 45 እና በማሕበሩ ደንብ አንቀጽ 46 መሠረት አባሉ በማሕበሩ ካፒታል ውስጥ ያለውን የእጣ እና ቁጠባ መጠን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የሽምግልና ዳኞችም ይህንኑ መሠረት አድርገው በውሳኔአቸው ተ.ቁ 2 እና 7 ላይ ተጠሪዎች ከማሕበሩ በወጡበት 2003 ዓ.ም ያልተከፋፈለ ትርፍ ብር 2,179,133.05 ድርሻቸው ተሰልቶ እንዲከፈላቸው የሚለው ውሳኔ በመለወጥ የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠጠቱ ተገቢ አይደለም፤እንዲሁም የማሕበሩ አባል ሲሞት ቤተሰቦቹ በዕዳ እንዳይጠየቁ ያዋጡትን ብር 3,155,216.56 የአጠቃላይ የማሕበሩ አባላት ገንዘብ ታስቦ ይከፈል በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ እና ከሳሾች የማህበር አባል በነበሩበት ጊዜ ለተገዛው የአክሲዮን ድርሻ በደረሰበት ካፒታል መጠን ሰርተፍኬት አዘጋጅቶ ይስጣቸው ተብሎ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ከዋናው ውሳኔ ውጪ የተሰጠ በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የሽምግልና ዳኞች በቀን 28/04/09 በሰጡት ውሳኔ ተጠሪዎች ከብር 5,361,749.61 ውስጥ ድርሻቸው ተለይቶ ሊከፈላቸው እንደሚገባ ተወስኖ እያለ የአፈጻጸም ችሎቱ ይኸው ገንዘብ ሙሉ በሙሉ የተጠሪዎች ድርሻ እንደሆነ ተቆጥሮ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ማዘዙ ፍርዱን የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪዎች መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪዎች በሽምግልና ዳኞቹ ውሳኔ መሠረት የሚገባን ድርሻ ተለይቶ ከነወለዱ እንዲከፈለን እና በአዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ ከተገዛው የብር 7,500,000 አሁን የተደረሰበትን ካፒታል ጨምሮ የአክሲዮን ድርሻችንን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስረጃ እንዲሰጠን እንጂ የማይገባንን እና ውሳኔ ያልተሰጠበትን ክፍያ እንዲሰጠን ስላልጠየቅን በሽምግልና ዳኞቹ ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸምልን የሚል ነው፡፡

አመልካች በሰጠው የመልስ መልስ ተጠሪዎቹ ከአዲስ አንተርናሽናል ባንክ ከተገዛው ሼር በስተቀር የ 2003 ዓ.ም የትርፍ ክፍፍል ብር 2,179,133.05 እና የማሕበሩ አባል ብድሩን ሳይከፍል ቢሞት ለዕዳ መሸፈኛ የተዋጣው ብር 3,155,216.56 የጠቅላላ የማሕበሩ ገንዘብ መሆኑን አምነው በሽምግልና ዳኞች ውሳኔ መሠረት እንዲከፈላቸው መልስ መስጠታቸው የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪዎች ያልጠየቁትን ከሽምግልና ዳኞች ውሳኔ ውጪ ክፍያ እንዲከፈላቸው ትዕዛዝ መስጠታቸውን የሚያሳይ ነው፤ተጠሪዎች ከአዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ ማሕበሩ የገዛውን አክሲዮን በተመለከተ አሁን በደረሰበትን ካፒታል ተዘጋጅቶ ሰርተፍኬት እንዲሰጠን በማለት የሰጡት ምላሽ ግን ከሽምግልና ዳኞቹ ውሳኔ ውጪ ስለሆነ በዚህ አግባብ ያቀረቡት መከራከሪያ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል በማለት የተያዘውን የብር 5,361,749.61 የአፈጻጸም ትዕዛዝ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የአፈጻጸም ትዕዛዝ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ውሳኔ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በሕብረት ሥራ ማሕበራት ማደራጃ በሽምግልና ዳኝነት ታይቶ ታሕሣስ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሆኑን፤ተጠሪዎች የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡት በውሳኔው መሠረት ይፈጸምልን በሚል መሆኑን፤አፈጻጸሙን የመራው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች የተጠሪዎች ድርሻ ተለይቶ ባለመቅረቡ ፍርዱን ለመፈጸም አለመቻሉን በመግለጽ ያቀረበውን ምክንያት ለግልግል ዳኞች አቤቱታ ያቀረቡት አንድ መቶ ዘጠና አንዱ ተጠሪዎች በመሆናቸው እና ድርሻቸውን የሚያውቁት በመሆኑ ፍርዱን ላለመፈጸም የተሰጠው ምክንያት ተቀባይነት የለውም በማለት የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በግልግል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች ውሳኔ መሠረት ለተጠሪዎች ብር 5,361,749.61 ወጪ አድርጎ እንዲከፍላቸው በማለት የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ ችለናል፡፡

አመልካች ገንዘቡን በሚመለከት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከረው ማሕበሩ 7200 አባላት ያሉት ሲሆን የትርፍ ክፍፍል ለአባላቱ የሚከፋፈለው አባሉ በማሕበሩ ካፒታል ውስጥ ያለውን የእጣ እና ቁጠባ መጠን መሠረት በማድረግ ሲሆን የሽምግልና ዳኞችም ውሳኔ የሰጡት ተጠሪዎች ከማሕበሩ በወጡበት 2003 ዓ.ም ያልተከፋፈለ ትርፍ ብር 2,179,133.05 ድርሻቸው ተሰልቶ እንዲከፈላቸው፤የማሕበሩ አባል ሲሞት ቤተሰቦቹ በዕዳ እንዳይጠየቁ ያዋጡትን ብር 3,155,216.56 የአጠቃላይ የማሕበሩ አባላት ገንዘብ ታስቦ ይከፈላቸው የሚል ሆኖ ሳለ ከኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በግልግል ዳኞች ውሳኔ መሠረት ለተጠሪዎች ብር 5,361,749.61 ወጪ ተደርጎ እንዲከፈላቸው በማለት የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ከውሳኔው ይዘት ውጪ ነው በሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ለዚህ ችሎት በሰጡት መልስም የአፈጻጸም ክስ ያቀረብነው በሽምግልና ዳኞቹ ውሳኔ መሠረት የሚገባን ድርሻ ተለይቶ ከነወለዱ እንዲከፈለን አልጠየቅንም በማለት የአመልካችን አቤቱታ በመደገፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በመሰረቱ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደ ፍርዱ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑ፤አፈጻጸሙን የሚመራው ፍ/ቤትም በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት እንደፍርዱ ይዘት እና መንፈስ ውጤት ባለው መልኩ ፍርዱን የሚያስፈጽም በቀር የፍርዱን ይዘት በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆኖ በማስፋት ፍርድን የመተርጎም ስልጣን እንደሌለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 372፤378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የስር ፍ/ቤት የሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ከዋናው ውሳኔ ይዘት ውጪ ነው በማለት የሚከራከር ከመሆኑ አኳያ የስር ፍ/ቤት የአፈጻጸም ትዕዛዝ በዋናው ፍርድ መሠረት የተሰጠ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተው መርምረናል፡፡

ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ውሳኔ በቂርቆስ ክፍለከተማ አስተዳደር በሕብረት ሥራ ማሕበራት ማደራጃ በሽምግልና ዳኝነት ታይቶ ታሕሣስ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ሲሆን በውሳኔው ገጽ 9 ተ.ቁ 2 ላይ ተጠሪዎች ከማሕበሩ በወጡበት የ2003

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓ.ም በጀት ዓመት ያልተከፋፈለ ትርፍ ብር 2,179,133.05 መሆኑ የሚያሳይ የኦዲት ሪፖርት የቀረበ በመሆኑ በቀረበው የኦዲት ሪፖርት ውጤት መሠረት ተጠሪዎች ድርሻቸው ተሰልቶ የትርፍ ክፍፍሉ በየድርሻቸው መሠረት ከነወለዱ እንዲሰጣቸው የሚል ሲሆን፤በዚሁ ገጽ ተ.ቁ 3 ላይ በኢንሹራንስ ስም የመድን ዋስትና በማለት ከአባላት የተሰበሰበው ገንዘብ በመንግስት ኦዲተሮች ተመርምሮ የተገኘው ገንዘብ ብር 3,155,216.56 የተሰበሰበው ተጠሪዎች ለማሕበሩ እያንዳንዳቸው እየከፈሉ ያጠራቀሙት ብር 5 እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ከማሕበሩ ከቆጠቡት ገንዘብ ሲበደሩ ከጠቅላላው ብድር ላይ 1% እና 5 ብር ከነወለዱ ታስቦ ተጠሪዎች ከማሕበሩ እስከወጡበት 2003 ዓ.ም ድረስ ያላቸው ሂሳብ በነፍስወከፍ እንዲከፈላቸው የሚል ነው፡፡ ከውሳኔው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ካልተከፋፈለው የማሕበሩ የ2003 ዓ.ም በጀት ዓመት ትርፍ ብር 2,179,133.05 እና በኢንሹራንስ ስም የመድን ዋስትና በማለት ከአባላት የተሰበሰበው ብር 3,155,216.56 ውስጥ የተጠሪዎች ድርሻ ተሰልቶ እንዲከፈላቸው በማለት ውሳኔ መሰጠቱን እንጂ በኦዲት ሪፖርተ መሠረት የተገለጸው የ2003 ዓ.ም በጀት ዓመት ትርፍ ብር 2,179,133.05 እና በኢንሹራንስ ስም የመድን ዋስትና በማለት ከአባላት የተሰበሰበው ብር 3,155,216.56 የተጠሪዎች ድርሻ ስለሆነ ይከፈላቸው በማለት የተሰጠ ውሳኔ አለመሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም የማሕበሩ የ2003 ዓ.ም በጀት ዓመት ትርፍ ብር 2,179,133.05 እና በኢንሹራንስ ስም የመድን ዋስትና በማለት ከአባላት የተሰበሰበው ብር 3,155,216.56 በተመለከተ አፈጻጸሙ ሊቀጥል የሚገባው ተጠሪዎች ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ያላቸው ድርሻ በቅድሚያ በሂሳብ ባለሙያ ተሰልቶ እና ተለይቶ እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ተገቢ የሆነ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ አግኝተናዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት ፍርዱን በውሳኔ መሠረት ማስፈጸም ሲገባው ውሳኔ ያረፈበት ጠቅላላ ገንዘብ የተጠሪዎች ድርሻ እንደሆነ በመቁጠር የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በግልግል ዳኞች ውሳኔ መሠረት ለተጠሪዎች ብር 5,361,749.61 ወጪ አድርጎ እንዲከፍላቸው በማለት ትዕዛዝ መስጠቱ፤ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ ስለፍርድ አፈጻጸም የተደነገጉትን የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 40148 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ፤ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 193484 ጥቅምት 09 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በግልግል ዳኞች ውሳኔ መሠረት ለተጠሪዎች ብር 5,361,749.61 ወጪ አድርጎ እንዲከፍላቸው በማለት የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡ ከዚህ ውጪ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ አልተነካም፡፡

3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቂርቆስ ክፍለከተማ አስተዳደር በሕብረት ሥራ ማሕበራት ማደራጃ በሽምግልና ዳኝነት ታይቶ ታሕሣስ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የማሕበሩ የ2003 ዓ.ም በጀት ዓመት ትርፍ ብር 2,179,133.05 እና በኢንሹራንስ ስም የመድን ዋስትና በማለት ከአባላት የተሰበሰበው ብር 3,155,216.56 አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ መሠረት ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ ተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባ ድርሻ ተለይቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ፍርዱን እንዲያስፈጽም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 343/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/ - 144272

ቀን - 24/11/2010

ዳኞች፡-

ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዩ ካሳሁን

አመልካች፡- የሻለቃ አሰፋ መንገሻ ህጋዊ ወራሾች - ወኪል ወ/ሮ ክብሬ አሰፋ -ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ዮናስ ዳኜ -በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረዉ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች 1ኛ ተከሳሽ፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት አርባ ምንጭ ከተማ ማዘጋጃ ቤት፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ በላይ አስራቴ በቅደም ተከተል ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡

ተጠሪ በቀን 06/08/2008 ዓ.ም አዘጋጅቶ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉ ክስ ይዘት በአጭሩ በአርባ ምንጭ ከተማ ስፋቱ 3,200.00 ካ/ሜትር የሆነዉ ቦታ በህጋዊ መንገድ በ1976 ዓ.ም ተሰጥቶት በቦታዉ ላይ የተሻለ ድርጅት ለመገንባት በዝግጅት ላይ እያለ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ንብረቱን የሚመለከቱ የተለያዩ ሰነዶችን በቤት ዉስጥ ትቶ ወደ ኤርትራ መሄዱን፤ አባቱ አቶ ዳኜ መክበብ በተሻረ ዉክልና ድርጅቱን እና ቤቱን በባንክ በማስያዝ ከ3ኛ ተከሳሽ ባንክ ገንዘብ ከተበደረ በኋላ ገንዘቡ ሙሉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሙሉ ተከፍሏል በሚል የስር 3ኛ ተከሳሽ ለ1ኛ ተከሳሽ ማስረከቡን፣ 2ኛ ተከሳሽ ያላግባብ ካርታ በመስጠት እንዲሁም 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን በሽያጭ ለ4ኛ ተከሳሽ ያስተላለፉ መሆኑን በመጥቀስ ዉሉ ፈርሶ የቤቱ ካርታ ወደነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ እና ይዞታዉን ከእነ ጋራዥ ድርጅቱ እንዲያስረክቡት ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ለቀረበባቸዉ ክስ በሰጡት መልስ የከሳሽ አባት፣ አቶ ዳኜ መክበብ፣ ከከሳሽ በተሰጣቸዉ ዉክልና መሠረት ቤቱን አስይዞ ከ3ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ሲበደሩ አባታቸዉ የዋስትና ግዴታ ገብተዉ የነበረ መሆኑን፤ አቶ ዳኜ መክበብ የብድር ገንዘቡን ባለመክፈላቸዉ ገንዘቡን እንዲከፍሉ የተሰጠዉን ዉሳኔ ተከትሎ ቤቱ በአፈፃፀም በጨረታ እንዲሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ የነበረ ቢሆንም ቤቱ ሊሸጥ ባለመቻሉ አበዳሪዉ 3ኛ ተከሳሽ ባንክ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በጨረታዉ መነሻ ዋጋ ቤቱን ተረክቦ ለብዙ ዓመታት ሲያስተዳድረዉ ከቆዩ በኋላ አመልካቾች በዋስትና ግዴታዉ ምክንያት ሊሸጥ ይችል የነበረዉን የአባታቸዉን ንብረት ለማስቀረት ሲባል የባንኩን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ በመሸፈናቸዉ 3ኛ ተከሳሽ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት እንዳስረከባቸዉ እና ቤቱም በስማቸዉ እንዲሆን መደረጉን፤ አመልካቾች በዚህ መልኩ የተረከቡትን ቤት በህግ አግባብ ለስር 4ኛ ተከሳሽ በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑን ጠቅሰዉ ተከራክረዋል፡፡ ሌሎች ተከሳሾችም በክሱ ኃላፊነት የለብንም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የተጠሪ አባት፣ አቶ ዳኜ መክበብ፣ ቤቱ ከ3ኛ ተከሳሽ ባንክ ለተበደሩት የገንዘብ ዕዳ መክፈያ እንዲሆን የጠየቁት ቤቱ የእራሴ ነዉ በሚል እንጂ ከተጠሪ ባገኙት ዉክልና መሰረት ባለመሆኑ አባቴ የእኔን ቤት በመያዣ አስይዞታል በሚል ተጠሪ ያቀረበዉን ክርክር አለመቀበሉን፤ አመልካቾች ለቤቱ መያዝ ምክንያት የሆነዉን እዳ በመክፈላቸዉ 3ኛ ተከሳሽን ተክተዉ የቤቱ ባለቤት ሊሆኑ የሚችሉበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን፤ ይሁንና የስር 4ኛ ተከሳሽ ቤቱን የገዛዉ በቅን ልቦና በመሆኑ የሽያጭ ዉል ይፍረስ በሚል ከሳሽ ያቀረበዉ ዳኝነት ተቀባይነት እንደሌለዉ፤ አመልካቾች ዕዳዉን ሙሉ በሙሉ በመክፈላቸዉ ቤቱ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተሸጠበት ብር 600,000.00 ውስጥ ብር 412,309.42 ተመላሽ ተደርጎላቸዉ ቀሪዉ ብር 187,690.58 አመልካቾች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ይግባኝም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 27/10/2009 ዓ.ም አዘጋጅተዉ በጠበቃቸዉ አማካይነት ባቀረቡት 5 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርብ ጥሪ የተደረገለት ቢሆንም ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ንብረትነቱ የራሱ የሆነዉን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት አባቱ፣ አቶ ዳኜ መክበብ፣ ህጋዊ የሆነ የዉክልና ስልጣን ሳይኖራቸዉ ለባንክ መያዣ አድርገዉ ገንዘብ መበደራቸዉን የስር 3ኛ ተከሳሽ ባንክም በዚህ አግባብ በእጁ የገባዉን ቤት ያላግባብ ለአመልካቾች ማስተላለፉ እና አመልካቾችም መብት ሳይኖራቸዉ ቤቱን ለስር 4ኛ ተከሳሽ በመሸጥ ያደረጉት ዉል መብቱን የሚነካ መሆኑን ሲሆን፤ አመልካቾች በበኩላቸዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የአባቱ፣ የአቶ ዳኜ መክበብ፣ እንጂ የተጠሪ አለመሆኑን እና ቤቱ ለአመልካቾች እንዲተላለፍ የተደረገዉም የብድር ዕዳዉ ባለመከፈሉ ምክንያት ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ በፍርድ ቤት በተሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረት ገዥ ባለመገኘቱ አበዳሪዉ ባንክ (የስር 3ኛ ተከሳሽ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቤቱን ሲያስተዳድረዉ ከቆዩ በኋላ አመልካቾች የባንክ ዕዳዉን በመሸፈናቸዉ በስማቸዉ እንዲሆን አድርጎ በዚህም መሠረት የቤቱ ባለ ሀብት በመሆን ለስር 4ኛ ተከሳሽ በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑን ገልጸዉ የተከራከሩ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በስር 3ኛ ተከሳሽ የነበረዉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በመያዣነት ይዞ ለተጠሪ አባት ገንዘብ አበድሮ የብድር ገንዘቡ ባለመመለሱ ክስ ቀርቦበት በመ/ቁ/614/82 መጋቢት 8 ቀን 1984 ዓ.ም በተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት እንዲፈጸምለት አበዳሪዉ ባንክ ባቀረበዉ የአፈፃፀም ክስ መነሻነት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/176/85 ላይ ጥቅምት 1 ቀን 1988 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤቱን በሐራጅ ሸጦ ለፍርድ ባለ መብት ዕዳዉን በማስከፈል እንዲያስፈጽም ዉክልና መስጠቱ፤ በዚህም መሠረት ቤቱ እንዲሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ቢወጣም ገዥ ባለመገኘቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤቱን እንዲረከብ እና የስም ዝዉዉርም እንዲደረግ ፍርዱን እንዲያስፈጽም ዉክልና የተሰጠዉ የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መስጠቱ፤ በዚህም ንግድ ባንክ ቤቱን ተረክቦ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ ሲያስተዳድረዉ የነበረ መሆኑ፤ ይህ ከሆነ በኋላ የተጠሪ አባት ለተበደረዉ ገንዘብ የአመልካቾች አባት ሻለቃ አሰፋ መንገሻ ዋስ በመሆን በአዲስ አበባ የሚገኘዉን ቤታቸዉን ለባንክ መያዣ ሰጥተዉ የነበረ በመሆኑ እና ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ቤት የብድር ዕዳዉን መክፈል ባለመቻሉ የአመልካቾች አባት ቤት በዕዳ ምክንያት መሸጥ የለበትም በሚል ምክንያት አመልካቾች የባንኩን ዕዳ ሙሉ በሙሉ በመክፈላቸዉ ባንኩ ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነዉን ቤት እንዲረከቡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/176/85 መስከረም 25 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረት አመልካቾች ቤቱን ሰኔ 23 ቀን 1998 ዓ.ም የተረከቡ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ተጠሪም ይህ ስለመሆኑ ክዶ አልተከራከረም። በመሠረቱ በአፈፃፀም ምክንያት በሐራጅ እንዲሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዥ ካልተገኘ ባለ ገንዘቡ ንብረቱን የመረከብ መብት እንዳለዉ እና የአፈፃፀም መዝገቡን የያዘዉ ፍርድ ቤትም ይህ እንዲሆን የማዘዝ ስልጣን እንዳለዉ በፍ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 428(2) ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ያስገነዝባል። በዚህም መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ባንክ እንዲሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዥ ባለመገኘቱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የስር 3ኛ ተከሳሽ (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ) መረከቡ ከተረጋገጠ የቤቱ ባለ መብት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነዉ ተብሎ ይገመታል። ይህን ግምት ማስተባበል የሚቻለዉ ባንኩ ቤቱን እንዲረከብ በሚል ተሰጥቶ የነበረዉ ትዕዛዝ ስነ-ስርዓት ህጉ በሚፈቅደዉ አግባብ በሌላ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሻሩ ሲረጋገጥ እንደሆነ ይታመናል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ ጋር በተያያዘ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክርክር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀን 25/01/98 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሻለቃ አሰፋ መንገሻ ወራሾች ዕዳውን አጠቃለው መክፈላቸውን ባንኩ ማረጋገጡን ጠቅሶ ቤቱ ለተጠሪ እንዲመለስለት ሲል ትዕዛዝ መስጠቱን ሲሆን፤ አመልካቾች በበኩላቸው ተሰጠ የተባለው ትዕዛዝ በሦስት ዳኛ መሆን ሲገባው በአንድ ዳኛ የተሰጠ ከመሆኑም በላይ ከ 6 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤቱን ተረክቦ እንዲያስተዳድረው ተሰጥቶ የነበረውን ትዕዛዝ በመሻር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በበኩሉ በዚህ መልኩ የተሰጠውን ትዕዛዝ የተቀበለ መሆኑን በውሳኔው የገለጸ ቢሆንም፣ የዚህን ትዕዛዝ ህጋዊነት ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች እንዲሁም አመልካቾች በዚህ ረገድ ካቀረቡት ክርክር አንፃር በማገናዘብ ተገቢውን ማጣሪያ በማድረግ አለመሆኑን የውሳኔው ይዘት ያስገነዝባል፡፡ ይህ በአጠቃላይ የሚያሳየው የስር 3ኛ ተከሳሽ፣ ማለትም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በዕዳ ምክንያት መረከቡ በተረጋገጠበት እና ይህ መሆኑ ባንኩን በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት የሚሰጠው ሆኖ፣ ባንኩ የቤቱ ባለቤት እንዲሆን የተደረገበት ትዕዛዝ በሌላ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በህግ አግባብ የተሻረ መሆኑ ሳይረጋገጥ፣ የስር ፍርድ ቤት ባንኩ በቤቱ ላይ መብት አለኝ በሚል ምክንያት ለአመልካቾች ያስተላለፈበት አግባብ ህገ ወጥ ነው በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ነው፡፡

በሌላ በኩል፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸው፣ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክሱን ሲያቀርብ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የእኔ ነው በሚል ነው፡፡ ይሁንና አመልካቾች ቤቱ ለእርሱ ሳይሆን የአባቱ የአቶ ዳኜ መክበብ መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ በጠየቀው ዳኝነት መሰረት ሊወሰንለት የሚችለው የቤቱ ባለቤት እርሱ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ምንም እንኳ ቤቱ በስሙ (በተጠሪ) ተመዝግቦ የሚታወቅ ቢሆንም፣ የተጠሪ አባት፣ አቶ ዳኜ መክበብ ቀደም ሲል በአፈፃፀም መዝገብ ላይ ባቀረቡት አቤቱታ፣ ቤቱ ሊመዘገብ የቻለው በወቅቱ ከአንድ ቤት በላይ ስለማይፈቀድ በተጠሪ ስም እንዲሆን ተደረገ እንጂ ቤቱ የተጠሪ ሳይሆን የእራሳቸው መሆኑን ገልጸው ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ መሰጠቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የቤቱ ባለ ሀብት የተጠሪ አባት እንጂ ተጠሪ አለመሆኑን የተቀበለ ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ፍርድ ቤቱ በአንድ በኩል ቤቱ የአባቱ እንጂ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪ አይደለም እያለ፣ በሌላ በኩል ግን ቤቱ ከተሸጠበት ገንዘብ በውሳኔው የተመለከተው የገንዘብ መጠን ለተጠሪ እንዲከፈል ያለበት ምክንያትም ግልጽ አይደለም። የቤቱ ስመ ሀብት በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ፣ የስር ፍርድ ቤት ቤቱ የተጠሪ ሳይሆን የተጠሪ አባት ነው በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰውም በግራ ቀኝ ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ አንፃር በአግባቡ በማጣራት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

በአጠቃላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት የስር 3ኛ ተከሳሽ ባንክ በዕዳ ምክንያት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተረክቦ በስሙ አድርጎ የነበረው እና ይህ በሌላ ትዕዛዝ መሻሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ባንኩ ቤቱን ለአመልካቾች ለማስተላለፍ መብት የለውም በሚል የደረሰበት ድምዳሜ፤ እንዲሁም ተጠሪ የቤቱ ባለ ሀብት መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በውሳኔው የተመለከተው ገንዘብ እንዲከፈለው በሚል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል።

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19212 በቀን 12/08/09 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 23541 በቀን 04/05/09 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል።
2. የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ፣ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የተጠሪ ነው? ወይስ የአባቱ የአቶ ዳኜ መክበብ? የአቶ ዳኜ መክበብ ነው የሚባል ከሆነ ተጠሪ ከጠየቀው ዳኝነት አንፃር የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው? ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት የስር 3ኛ ተከሳሽ ባንክ እንዲረከብ በሚል ቀደም ሲል ፍርዱን በሚያስፈጽም ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ትዕዛዝ ተከትሎ ባንኩ ቤቱን ተረክቦ ሲያስተዳድር ከቆዩ በኋላ ቤቱ ለተጠሪ ይመለስ በሚል የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 33/88 በቀን 27/10/98 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ አንድ ትዕዛዝ ሊሻር ወይም ሊሻሻል የሚችልበትን ስርዓት የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማገናዘብ አጣርቶ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 146955

ቀን - 30/09/2010

ዳኞች፡-

ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አብዩ ካሳሁን

አመልካቾች፡- 1. አቶ ብሩክ ኃ/መስቀል
2. አቶ ኤሊያስ ኃ/መስቀል } አልቀረቡም
3. አቶ ኢዩብ ኃ/መስቀል

ተጠሪ፡- አቶ ነብዩ ኃ/መስቀል -ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የእርቅ ስምምነት ይፈጸምልኝ በሚል በቀረበዉ ክስ መነሻነት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ፣ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ ይዘትም በአጭሩ በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 09 ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ እና ቁጥሩ 7251 የሆነዉ ቤት ግራ ቀኝ በዉርስ አግኝተን የጋራችን የሆነዉን ቤት በተመለከተ በ19/10/07 ዓ.ም በመካከላችን የተደረገ የእርቅ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስምምነት ዉል ይፈጸምልን የሚል ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የእርቅ ስምምነቱ እንዲፀድቅ ቀደም ሲል ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን፣ ከሳሾች የእርቅ ስምምነት ነዉ በማለት ያቀረቡትም የቤቱን ካርታ የማይገልጽ በመሆኑ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ካርታ የሌለዉ እና ብረትነቱም የመንግስት ሆኖ ቀበሌ የሚያስተዳድረዉ መሆኑ መረጋገጡን ገልፆ አመልካቾች ክስ የማቅረብ መብት የላቸዉም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም፣ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት አመልካቾች ለክሳቸዉ መሠረት ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በየትኛዉ ላይ እንደሚፈጸም የማያመለክት መሆኑን ጠቅሶ የቀረበዉን ይግባኝ ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 23/12/09 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃቸዉ አማካይነት በቀረበዉ ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመለከት፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት በግራ ቀኝ መካከል በ19/10/2007 ዓ.ም ተደረገ የተባለዉን የእርቅ ስምምነት ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ስምምነቱ ለአፈፃፀም ቀርቦ ተቀባይነት ማጣቱን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ መልኩ ካቀረቡት ክርክር አኳያ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት ተይዞ እልባት ማግኘት የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ በፍርድ ቤት ሊፈጸም የሚችል በግራ ቀኝ መካከል የተደረገ የእርቅ ስምምነት መኖር አለመኖሩ ነዉ፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ክስ ዉድቅ ያደረገዉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለክርክሩ ምክንያት ለሆነዉ የእርቅ ስምምነት መነሻ የሆነዉ ቤት ካርታ የሌለዉ እና የመንግስት መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከቤቱ ባለቤትነት ጋር በተያያዘ በግራ ቀኝ የተነሳ ክርክር ሳይኖር ከፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 182 በሚዛረር መልኩ ክክርክሩ ጭብጥ ዉጪ በመዉጣት ዉሳኔ መስጠቱን በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ ብለናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች ለክሳቸዉ መሠረት ያደረጉት የእርቅ ስምምነት ተገቢዉን የፍሬ ነገር መግለጫ ያልያዘ እና ስምምነቱ በየትኛዉ ቤት ላይ እንደሚፈጸም የማያመለክት ስለመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አረጋግጦ ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉን ትዕዛዝ መስጠቱን ተመልክተናል፡፡ አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት አቤቱታም ተጠሪ ስምምነቱ ሊፈጸም የሚችል ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ሳይከራከር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ይህን ዉሳኔ መስጠቱ አግባብ አለመሆኑን የተከራከረ ቢሆንም፣ ስምምነቱ ግልጽና ሊፈጸም የሚችል ስለመሆኑ ገልጸዉ አልተከራከሩም፡፡ እኛም ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን የእርቅ ስምምነት አስቀርበን እንዳየነዉ እርቅ ስምምነቱ ስለየትኛዉ ቤት፣ እንዲሁም ተጠሪ በእርቅ ስምምነቱ መሠረት እንዲፈጽም የሚጠበቅበት ግዴታ ምን እንደሆነ በተብራራ መልኩ አያስቀምጥም፡፡ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3312(1) መሠረት እንደዉሳኔ ተቆጥሮ በፍርድ ቤት ለአፈፃፀም አቅርቦ ማስፈጸም ይቻል ዘንድ ስምምነቱ ግልጽና የፈፃሚዉን አካል ግዴታ በማያሻማ ሁኔታ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ በዚህ ዓይነት ግልጽ ያልሆነ የእርቅ ስምምነት ሲቀርብ፣ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሌላ ተከራካሪ ወገን ክርክር እንኳን መስማት ሳያስፈልገዉ ይህኑን ጠቅሶ ክሱን ዉድቅ ማድረግ ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ቤቱ የመንግስት ነዉ በሚል የስር ፍርድ ቤት የደረሰበትን ድምዳሜ ማረም ሲገባዉ ይህን አለማረሙ ስህተት ቢሆንም፣ አመልካቾች ለክሳቸዉ መሠረት ያደረጉት ስምምነት ግልጽ እና የተብራራ አይደለም በሚል ምክንያት የቀረበለትን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ትዕዛዝ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/189984 በቀን 20/10/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/101014 በቀን 03/02/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ቤቱ የመንግስት ነዉ በማለት የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
2. ይህ ችሎት በቀን 13/03/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር. 156389
ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ነ/ፈጅ ፈየራ ኦልጅራ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሺወርቅ ሲባኒ ጠበቃ ሲሳይ ወ/ዮሐንስ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የአፈጻጸም ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች ፍርድ ባለመብት፣ አቶ ደርቤ መኮንን የፍርድ ባለዕዳ ሲሆኑ የአሁን ተጠሪ ደግሞ የመቃወም አመልካች ነበሩ፡፡ አመልካች የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ነው ባለው የቡና ማሽን ላይ አፈጻጸሙ እንዲቀጥልለት የጠየቀ ሲሆን የአሁን ተጠሪ የቡና ማሽኑ የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ሳይሆን የራሳቸው ንብረት እንደሆነና እንዲለቀቅላቸው በመጠየቅ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ለአቤቱታው በሰጡት መልስ የፍርድ ባለዕዳው ይህንን ንብረት ከአመልካች በተከራየው ቤት ውስጥ የሚጠቀምበት ስለሆነና የፍርድ ባለዕዳ የቤት ኪራይ ስላልከፈለና አመልካች ንብረቱ የሌላ ሰው መሆኑን አስቀድሞ ስለማያውቅ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 መሠረት ውሳኔው ሊፈጸምበት ስለሚገባ አቤቱታው ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶ ክርክር ያስነሳዉ የቡና ማሽን የፍርድ ባለዕዳዉ ሳይሆን የተጠሪ መሆኑ ስለተረጋገጠ ንብረቱ ላይ ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቶ ለተጠሪ ይልቀቅ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ አመልካች ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ዉሳኔዉን በማጽናት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2925 መሰረት አመልካች የቡና ማሽኑን ለኪራይ ዕዳ አከፋፈል ዋስትና እንዳይዝ የሚከለክሉ ነገሮች ስለመኖራቸዉ በጭብጥነት ይዞ ማጣራት ሲገባዉ ንብረቱ የተጠሪ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል እና አመልካች ማሽኑ የተጠሪ አለመሆኑን አላስተባበለም በሚል ብቻ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት በበኩሉ አመልካች የቡና ማሽኑ የተጠሪ ስለመሆኑ የሚያዉቅ መሆኑ በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን ከደመደመ በኃላ ተጠሪ ማሽኑን በፍርድ ባለዕዳ ማከራየቷን ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ የለባትም፤ የግል ንብረቷ መሆኑን አስረድታለች በሚል የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ማጽናቱ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የሌለዉን የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1193(2)ን በመጥቀስ አመልካች የቡና ማሽኑን ለፍ/ባለዕድዉ ዕዳ መክፈያነት መያዝ አይቻልም ብሎ የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይሻርልን የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ከስር የፍርድ ባለዕዳ ጋር ተከራክሮ ለማስፈጸሚያነት ያስያዙት የቡና ማሽን የአሁኑ ተጠሪ ንብረቱ የግሌ ነዉ በማለት የኪራይ ዉል በማቅረባቸዉ ብቻ ለአፈጻጸም ሊዉል አይገባም መባሉን ከፍ/ሕ/ቁ 1193(1) እና 2924 አንጻር ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ለአቤቱታዉ የሰጡት መልስ ይዘት፡- አንድ ንብረት ላይ ፍርድ ሊፈጸም የሚችለዉ የባለዕዳዉ ንብረት መሆኑ ሲረጋገጥ ሲሆን ክርክር ያስነሳዉ የቡና ማሽን የፍርድ ባለዕዳዉ ሳይሆን የግሌ መሆኑ ተረጋግጦ እንዲለቀቅልኝ በስር ፍ/ቤት መወሰኑ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተገቢ ነዉ። አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1193(1) መሰረት ክርክር ያስነሳዉ ንብረት የፍርድ ባለዕዳዉ መሆኑን ግምት በመዉሰድ ለአፈጻጸም እንዲዉል የጠየቀ ቢሆንም ተጠሪ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1193(2) መሰረት አመልካች የያዘዉ ግምት ልክ አለመሆኑን በበቂ ማስረጃ በማስረዳት ያስተባበልን በመሆኑ ንብረቱ እንዲለቀቅ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል። አመልካች ባቀረበዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል።

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል። የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች የንግድ ቤቱን ለፍርድ ባለዕዳ አከራይቶ የነበረ ሲሆን የፍርድ ባለዕዳ ያልከፈለዉ ዉዝፍ ኪራይ በመኖሩ ክስ አቅርቦበት አስወስኗል። አመልካች የተወሰነለት ገንዘብ አፈጻጸም የፍርድ ባለዕዳዉ በተከራየዉ ቤት ዉስጥ ይሠራበት በነበረዉ የቡና ማሽን ተሸጦ እንዲፈጸምለት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸዉ የቡና ማሽኑ የፍርድ ባለዕዳዉ ንብረት ሳይሆን የራሳቸዉ ንብረት በመሆኑ ለአፈጻጸም ሊዉል እንደማይገባና ሊለቀቅላቸዉ እንደሚገባ በመጠየቅ ተከራክረዋል። የስር ፍ/ቤት ማስረጃ ከሰማ በኃላ የቡና ማሽኑ የፍርድ ባለዕዳዉ ሳይሆን የተጠሪ መሆኑን ካረጋገጠ በኃላ ለአፈጻጸም ሊዉል ስለማይገባ ለተጠሪ ይለቅላቸዉ በማለት ወስኗል። አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ ንብረቱ የፍርድ ባለዕዳዉ ባይሆንም አመልካች ይሸዉ ንብረት የሌላ ሰዉ መሆኑን አውቆ የነበረ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስና በተከራየዉ ቤት ዉስጥ የሚጠቀምበት እስከሆነ ድረስ ላልተከፈለ የቤት ኪራይ አከፋፈል ሊውል ይገባል በማለት ነዉ።

በመሠረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 ተከታዮች ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በመርህ ደረጃ አንድ ፍርድ በአንድ ንብረት ላይ ሊፈጸም የሚችለዉ ንብረቱ የፍርድ ባለዕዳዉ ንብረት መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ። በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 ያንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት አከራይ የሆነ ሰዉ ባለፈዉ ዓመት ላልተከፈለዉ ኪራይና ላለበትም ዓመት ስድስት ወር ሊከፈለዉ ለሚገባዉ ኪራይ ዋስትና ለቤቱ ማጌጫ ከሚያገለግሉት ዕቃዎችም ሆነ ለስፍራዉ ማልሚያ ከሚጠቅሙት መሳሪያዎች ላይ የመያዣ መብት ያለዉ መሆኑን ሲደነግግ፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2926(2) ደግሞ በስዉር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም በኃይል የተወሰዱትን ዕቃዎች ሳይቀሩ አከራይ በአስር ቀን ውስጥ በፍርድ በማስያዝ የአከራዩን መብቶች በቀደምትነት መክፍያ እንዲሆኑ ማድረግ የሚችል መሆኑን፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2925 አከራዩ የዕቃዎቹ ባለሀብትነት የተከራዩ አለመሆኑን አውቆ እንደሆነ ወይም ማወቅ ይገባዉ ኑሮ እንደሆነ በዕቃዎቹ ላይ የመያዣ መብቱ ሊፈጸም እንደማይችልና የራሱ አለመሆናቸዉን ያወቀዉ ዉሉ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ የሆነ እንደ ሆነ ዉሉ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ እንዲፈርስ ካላመለከተ በቀር በእነዚህ ዕቃዎች ላይ ይዞ የማቆየት መብቱ ይቀርበታል ተብሎ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከነዚህ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻለዉ የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት አከራይ የሆነ ሰዉ ከላይ ለተገለጸዉ ጊዜ ላልተከፈለዉ የዉዝፍ ኪራይ ክፍያ አስፋፈል ሲባል ተከራዩ ለቤቱ ማጌጫነት ወይም ለስፍራ ማልሚያነት ከሚጠቀምባቸዉ ዕቃዎች ላይ ዕቃዎቹ የራሱ ባይሆኑም ይህንኑ አከራዩ እስካላወቀ ወይም ማወቅ ነበረበት እስካልተባለ ድረስ በሕግ የተቋቋመ የመያዣ መብት ያለዉ መሆኑና በልዩ ሁኔታ ለአፈጻጸም ሊያዉላቸዉ የሚችል መሆኑን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ክርክር ያስነሳዉ የቡና ማሽን የፍርድ ባለዕዳዉ ንብረት ሳይሆን የተጠሪ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም የፍርድ ባለዕዳዉ ለተከራየዉ ቤት ማልሚያነት ይጠቀምበት የነበረ መሆኑ እስካልተካደና እስከተረጋገጠ ድረስ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንጻር ለአፈጻጸም ሊዉል የሚገባዉ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ሳይጣራና ሳይረጋገጥ ንብረቱ የባለዕዳዉ ሳይሆን የተጠሪ ነዉ ስለተባለ ብቻ ለአፈጻጸም ሊዉል አይገባም ተብሎ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም የቡና ማሽኑ የተጠሪ መሆኑ ቢረጋገጥም የፍርድ ባለዕዳዉ ለተከራየዉ ቤት ማልሚያ የሚጠቀምበት መሣሪያ በመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት፡-

1. አመልካች በቡና ማሽኑ ላይ የመያዣ መብት ያለዉ መሆን ያለመሆኑ?
2. አመልካች የተወሰነለት የኪራይ ገንዘብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 መሠረት የመያዣ መብት የሚያሰጠዉ መሆን አለመሆኑ?
3. እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2925 ድንጋጌ አንጻር አመልካች ቤቱን ሲያከራይ የቡና ማሽኑ የፍርድ ባለዕዳዉ ወይም የተከራዩ አለመሆኑን ያዉቅ የነበረ መሆኑ ወይም ማወቅ ይገባዉ የነበረ ወይም ዉሉ ጸንቶ በቆየበት ወቅት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይህንኑ አዉቆ የነበረ መሆን ያለመሆኑ? በቅድሚያ በማስረጃ ሊጣራና ሊረጋገጥ ይገባል።

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት ክርክር ያስነሳዉ የቡና ማሽን የፍርድ ባለዕዳዉ ሳይሆን የተጠሪ መሆኑን ቢያርጋግጥም ከአመልካች ክርክርና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2924 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንጻር ንብረቱ ለአፈጻጸም መዋል መቻል አለመቻሉ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ሳይጣራና ሳይረጋገጥ ንብረቱ ለአፈጻጸም ሊዉል አይገባም ተብሎ መወሰኑ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎች ይዘት ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በለመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሮ አጣርቶ እንዲወስን ለስር ፍ/ቤት መመለሱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ዉሳኔ</u>

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 23545 ግንቦት 29 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 264744 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል።
2 ከላይ በፍርድ ሀተታዉ በተገለጸዉ አግባብ ግራ ቀኙን አከራክሮና በማስረጃ አጣርቶ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት ጉዳዩ ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይመለስለት ተብሏል። ይጻፍ።
3 ሚያዚያ 02 ቀን 2010 ዓ.ም አፈጻጸሙ ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።
4 የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሰ/ጌ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰበር መ/ቁ154222

ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-አቶ ረሽድ አደም

ተጠሪ፡-አቶ ታሪኩ አማረ

መዝገቡ ለምርምራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ፡፡

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት በመጀመሪያ ጨረታ ሽያጭ ላይ ተወዳድሮ አሸናፊ የተባለዉ ገዥ ዋጋ ከፍሎ ግዥዉን ባለመፈጸሙ ድጋሚ ጨረታ ሲደረግ የሽያጭ ዋጋ ቢቀንስ ልዩነት የመክፈል ሃላፊነት የሚመለከት ክርክር መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የፍርድ ባለእዳ የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን የፍርድ ባለመብት ወ/ሮ ብሻሸ አዲሱ መካከል በነበረዉ የአፈጻጸም ክርክር የፍርድ ባለእዳ ንብረት የሆነ ቤት በጨረታ እንዲሸጥ በተሰጠ ትእዛዝ መሰረት በመጀመሪያ ጨረታ ላይ የአሁኑ አመልካች ወንድም የሆነዉ አቶ ከሊል አደም በጨረታዉ ተወዳድሮ ቤቱን በብር 200,000 አሸናፊ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ ባለመቻሉ ሁለተኛ ጨረታ እንዲወጣ ሲደረግ የአሁኑ አመልካች ተወዳድሮ በብር 137,000 አሸናፊ ሆኖ ሽያጩ እንዲከናወን በመደረጉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/ 429/2/ መሰረት ተጫራቹ በመጀመሪያ ጨረታ እና በሁለተኛ ጨረታ መካከል ያለዉን የዋጋ ልዩነት ብር 63,200 አመልካች እንዲከፍል ተጠሪ አቤቱታ አቀረበ፡፡ የአፈጻጸም መዝገቡን የያዘዉ የመቱ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን አስተያየት ከተቀበለ በኋላ የአመልካች ወንድም በመጀመሪያዉ ጨረታ የተወዳደረዉ ለአመልካች ስለመሆኑ በመግለጹና አመልካችም ይህንኑ አምኗል በሚል በሁለቱም ጨረታ የተወዳደረዉ አመልካች ነዉ በሚል የዋጋ ልዩነቱን ብር 63,200 የአሁኑ አመልካች እንዲከፍል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/429/2/ መሰረት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለኢሉባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካች ወንድም በአመልካች ስም ጨረታ እንዲወዳደር ግልጽ ዉክልና መስጠቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ልዩነቱን የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2205 ዋቢ በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሽሯል፡፡በሌላ በኩል በስር ፍርድ ቤት ቀርቦ ከደመወዙ ተቆርጦ ይከፈል በማለት ቃሉን የሰጠዉን በመጀመሪያ ጨረታ አሸናፊ ተብሎ ግደታዉን ያልተወጣዉ ሰዉ ላይ የመጠየቅ መብት ጠብቆለታል፡፡የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ በማቅረቡ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች በህግ አግባብ ለወንድሙ የሰጠዉ ዉክልና ባይኖርም ወንድሙ የሆነዉ ከሊል አደም በሰጠዉ ሀሳብና አመልካች በሰጠዉ ሀሳብ መሰረት የዋጋ ልዩነቱን የመክፈል ሃላፊነት የአመልካች ነዉ በማለት የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡አመልካች በዚህ ቅር ተሰኝቶ ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ሰበር ችሎቱ ግራቀኙን አከራክሮ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ አመልካች በህግ አግባብ ለወንድሙ አቶ ከሊል አደም የሰጠዉ ዉክልና ሳይኖር አቶ ከሊል አደም በመጀመሪያዉ ጨረታ በራሱ ስም ተወዳድሮ አሸናፊ ነዉ ለተባለበት አመልካች ሃላፊነት ሊወስድ እንደማይገባ ፣አቶ ከሊል አደም በመጀመሪያ ጨረታ አሸናፊ ተብሎ ግዴታዉን ባለመወጣቱ ካስያዘዉ ገንዘብ ላይ ተቀንሶ ገቢ መደረጉን በሁለተኛ ጨረታ እንዳይወዳደር መደረጉ እና አቶ ከሊል አደም የዋጋ ልዩነት ከደመወዙ ተቀንሶ ገቢ ይደረግ እያለ ባለበት ሁኔታ አመልካች እንዲከፍል መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ በሚል የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ እንዲታረም ጠይቋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በመጀመሪያ ጨረታ ተወዳድሮ ካሸነፈ በኋላ ክፍያዉን ሳይፈጽም የቀረዉ የአመልካች ወንድም ሆኖ ሳለ በዚሁ ምክንያት ድጋሚ ጨረታ ወጥቶ አመልካች ተወዳድሮ ባነሰ ዋጋ በማሸነፉ አመልካች ልዩነት እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/429 አንጻር ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡በተጠሪ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በመጀመሪያዉ ጨረታ ላይ አመልካችና ቤተሰቦቹ እንደተወዳደሩ፣ አቶ ከሊል አደም ለአመልካች በሚል እንደተወዳደረ በስር ፍርድ ቤት ላይ መግለጹና አመልካችም ይህንኑ በፍርድ ቤት ስለማረጋገጡ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡የአመልካች ጠበቃ ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ ክርክር ይዘት ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ከመዝገቡ እንደተገነዘብነዉ አከራካሪዉ ጉዳይ በመጀመሪያ ጨረታ እና በሁለተኛ ጨረታ መካከል የንብረቱ ዋጋ ልዩነት ሲፈጠር ሃላፊነት የሚከተለዉን ወገን የመለየት ጉዳይ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ስ/ህግ አንቀጽ 429 ላይ በጨረታ ለገዛዉ ንብረት ዋጋዉን ሳይከፍል ወይም ግዴታዉን ሳይፈጽም የቀረ ገዢ ንብረቱ በሁለተኛ ጨረታ ሲሸጥ ለጎደለዉ ገንዘብ በሃላፊነት የሚጠየቅበት ሁኔታ ተደንግጓል፡፡በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ሁለት ላይ እንደተደነገገዉ ንብረቱ እንደገና በሚሸጥበት ጊዜ ዋጋ የቀነሰ እንደሆነ በመጀመሪያ ጨረታ ንብረቱን የገዛዉና ዋጋዉን ያልከፈለዉ ተጫራች የፍርድ አፈጻጸም እዳ በሚከፈልበት ዓይነትና ሁኔታ ልዩነቱንና ኪሳራዉን እንዲከፍል እንደሚገደድ ተመልክቷል፡፡ስለዚህም የዋጋ ልዩነቱንና ኪሳራዉን የመክፈል ግደታ የተጣለዉ በመጀመሪያ ጨረታ ተወዳድሮ የጨረታዉ አሸናፊ ነዉ የተባለዉ ሰዉ ላይ ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ክርክር በመጀመሪያ ጨረታ ተወዳድሮ የጨረታዉ አሸናፊ ነዉ የተባለዉ እና በዚሁ አግባብ ግዴታዉን ያልተወጣዉ የአመልካች ወንድም የሆነዉ አቶ ከሊል አደም ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ክርክር ሂደት የተገለጸ ጉዳይ ነዉ፡፡አከራካሪ የሆነዉ ጉዳይ የአመልካች ወንድም በመጀመሪያ ጨረታ የተወዳደረዉ ለአመልካች ወይስ ለራሱ ጥቅም ነዉ የሚለዉ ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የአመልካች ወንድም በስር ፍርድ ቤት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቀርቦ የተጫረተዉ በራሱ ስም ቢሆንም ለአሁኑ አመልካች ጥቅም ስለመሆኑ ገልጾ ገንዘቡን በወቅቱ ገቢ ማድረግ ባለመቻሉ ለሚፈጠረዉ የዋጋ ልዩነት ከራሱ ደመወዝ ተቀንሶ ገቢ እንዲደረግ የጠየቀ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት የዚህ ሰዉ ጥያቄ ያለፈበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበዉ ክርክር የመጀመሪያ ጨረታ ላይ እንዳልተወዳደረ፣ ወንድሙ አቶ ከሊል አደም በጨረታዉ በአመልካች ስም እንዲወዳደር ዉክልና ያልሰጠ ስለመሆኑ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ላይ ቀርቦ ወንድሙ ለእሱ እንደተወዳደረ አምኗል በማለት በመዝገብ ላይ ያሰፈረዉ ትክክል እንዳልሆነ አጥብቆ ተከራክሯል፡፡ስለሆነም የአመልካች ወንድም በመጀመሪያዉ ጨረታ የተወዳደረዉና አሸናፊ የተባለዉ ለራሱ ጥቅም ወይስ ለአሁኑ አመልካች ጥቅም ነዉ የሚለዉን ጥያቄ ለይቶ በመወሰን ረገድ በየደረጃዉ ክርክሩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የተለያየ መነሻ በመያዝ የተለያየ ዉሳኔ ማስጠታቸዉን ከላይ ተመልክተናል፡፡ይሕም አንዱ ፍርድ ቤት ግራቀኙ በችሎት በሰጡት ሀሳብ ለአመልካች ጥቅም ስለመሆኑ ታምኗል የሚል መነሻ የያዘ ሲሆን ሌላኛዉ ደግሞ በመጀመሪያ ጨረታ አመልካች ግልጽ ዉክልና መስጠቱ አልተረጋገጠም በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ ባንድ ጉዳይ ላይ ሃላፊነት የሚመነጨዉ ከህግ ወይም ከዉል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ከዚህ መዝገብ ክርክር እንደተገነዘብነዉ የአመልካች ሃላፊነት ምንጩ በአመልካችና በወንድሙ መካከል በነበረዉ ግንኙነት ወንድሙ ለፈጸመዉ ተግባር እንደወኪል ታይቶ ሃላፊነት እንዲወስድ የሚል ክርክር ነዉ፡፡በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2079 እንደተደነገገዉ የሌላ ሰዉ እንደራሴ በመሆን ስራዎችን የመፈጸም ስልጣን የሚገኘዉ ከህግ ወይም ከዉል ነዉ፡፡ዉክልናዉ በዉል የተሰጠ እንደሆነ ተወካዩ በወካዩ ስም ህጋዊ ስራዎችን እንዲሰራ የሚደረግበት ዉል መኖሩን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2099 ይገልጻል፡፡ በዉል የሚሰጥ ዉክልና ጠቅላላ ዉክልና ወይም ልዩ ዉክልና ተብሎ በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 2002 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡በተለይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ ከማስተዳደር ስልጣን ያለፈ ተግባር ማከናወን የሚቻለዉ በልዩ ዉክልና ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2005/2/ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ክርክር አከራካሪዉ ጉዳይ የአመልካች ወንድም የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመግዛት በመጀመሪያ ጨረታ ላይ የተወዳደረዉ በራሱ ስም ቢሆንም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለአመልካች ጥቅም ነዉ በሚል የአመልካች ወኪል ሆኖ እንደተወዳደረ ተወስዶ ሃላፊነቱ የአመልካች መሆን አለበት ወይስ አይደለም የሚል ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የአመልካች ወንድም አቶ ከሊል አደም በመጀመሪያ ጨረታ የተወዳደረዉ በራሱ ስም ከመሆኑም በተጨማሪ ከአመልካች የተሰጠዉ ግልጽ ዉክልና ስለመኖሩ የቀረበ ማረጋገጫ የለም፡፡በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ አቶ ከሊል አደም በአንድ በኩል በራሱ ስም መጫረቱን እየገለጸ ፤ በሌላ በኩል ለወንድሜ ነዉ የተጫረትኩት ገንዘቡን መክፈል አልችልም ከደመወዝ ይቆረጥ በማለቱና አመልካች ስር ፍርድ ቤት ቀርቦ ይህንኑ አምኗል በሚል ምክንያት ነዉ፡፡እዚህ ላይ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ አመልካች በግልጽ ለወንድሙ አቶ ከሊል አደም በዚህ በግልጽ ዉክልና መስጠቱ ባልተረጋገጠበትና ስር ፍርድ ቤት ላይ የተመዘገበዉ ቃል አመልካች በግልጽ የመጀመሪያዉ ጨረታ ላይ ሃላፊነት የወሰደበት ሁኔታ በሌለበት ፍርድ ቤቱ አመልካች አምኗል የሚል በመመዝገብ አመልካችን ሃላፊ ማድረግ ተገቢ አይደለም የሚል ነዉ፡፡በዚህም ላይ ጉዳዩን በተለያየ ደረጃ የተመለከቱት የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በፍርድ ቤት ቀርቦ በችሎት ላይ የተመዘገበ ቃል እምነት የሚጣልበት ነዉ ወይስ አይደለም በሚለዉ ነጥብ ዙሪያ የተለያየ አቋም መዉሰዳቸዉ ከመዝገቡ ላይ ይታያል፡፡ከላይ እንደተመለከትነዉ ይህ ጉዳይ የፍትሓብሔር ክርክርም ቢሆን ሃላፊነትን የሚያሥከትል ከመሆኑ አኳያ አመልካች በዚህ ጉዳዩ ላይ የሰጠዉ ቃል አሻሚና አከራካሪ ከሆነ እሱን ሃላፊነት ዉስጥ የሚያስገባ ሊሆን አይገባም፡፡በሌላ በኩል የአመልካች ወንድም የሰጠዉ ቃል ቢሆን ራሱ ሃላፊነት የሚወስድበት ከሚሆን በስተቀር በራሱ ስም ጨረታዉን መወዳደሩን ግልጸ እርስ በርሱ የሚጣረስ ሃሳብ ማቅረቡ በግልጽ እየታየ ወንድሙ ለፈጸመዉ ተግባር አመልካች ሃላፊነት እንዲወስድ ለመወሰን የሚያስችል የህግ መሰረት የለዉም፡፡ሲጠቃለል በዚህ ጉዳይ አመልካች በመጀመሪያ ጨረታ በራሱ ወይም በህጋዊ ወኪል አማካይነት ስለመወዳደሩና ስለማሸነፉ በበቂ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ወይም ሃላፊነት ስለመዉሰዱ አጣራጣሪና አከራካሪ በሆነበት ሁኔታ ዉስጥ በሁለተኛዉ እና በአንደኛዉ ጨረታ መካከል ለተፈጠረዉ የዋጋ ልዩነት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ /429/2/ መሰረት ሊከፍል የሚገደድበት የህግም ሆነ የዉል ግንኙነት ምክንያት ባለመኖሩ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች አመልካች ሃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይገባል ብለናል፡፡በሌላ በኩል የኢሉባቦር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዉሳኔዉ ላይ እንዳመላከተዉ ተጠሪ ከአቶ ከሊል አደም ላይ የሚጠይቀዉ መብት በዚህ ዉሳኔ የተገደበ አይሆንም ብለናል፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/210226 ላይ በ28/06/09ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/268042 ላይ በ09/04/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 348/1/መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/የኢሉባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/29822 ላይ በ19/03/09 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡ይጻፍ፡፡

3ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወንጀል ሕግ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/153228

መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፤የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትህ ቢሮ

ተጠሪዎች፡1ኛ/ፈንቱ ንጉስ

2ኛ/ታድሎ ጥላሁን

3ኛ/ምናለ ዳኛዉ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ተጠሪዎች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/2/ ተላልፈዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ቃል ሰጥተዋል ተብሎ ከቀረበባቸዉ ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ፍርድ አግባብነት ለመመርመር የቀረበ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ እነ ቂስ ወርቁ ገላዬ /9 ሰዎች/በተጠረጠሩበት የደን እንጨት መቁረጥ ወንጀል የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፎገራ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ላይ በምስክርነት ቀርበዉ ተጠርጣሪዎቹ ጥር 24 ቀን 2008 ዓ.ም ከቀኑ 6፡30 ላይ ፎገራ ወረዳ ምንጡራ ቀበሌ ሸንበቆ ጎጥ ከተባለዉ ቦታ የማህበራት የተፈጥሮ ደን የሆነዉን ሁሉም ተከሳሾች መጥረቢያ በመያዝ ደኑን ሲጨፈጭፉ አይተናል በማለት ቃል ከሰጡ በኋላ የአቃቤ ህግ ምስክር ሆነዉ በፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃላቸዉን በ07/10/08 ዓ.ም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲሰጡ ሁሉም ተከሳሾች መጥረቢያ ይዘዉ ሲቆርጡ አላየንም በማለታቸዉ ደን ቆርጠዋል ተብለዉ ክስ የቀረበባቸዉ ተከሳሾቹ በ21/10/08 ዓ.ም በተሰጠ ፍርድ በነጻ እንዲሰናበቱ ስለተወሰነ ተጠሪዎች የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 453/2/ ተላልፈዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ሰጥተዋል በሚል ክስ የቀረበባቸዉ ሲሆን ተጠሪዎች ክሱን ክደዉ ስለተከራከሩ ክሱን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ሰምቶና መርምሮ ተጠሪዎች የተመሰከረባቸዉን በመከላከያ ማስረጃ አላስተባበሉም በማለት በተከሰሱበት አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ናቸዉ በማለት እያንዳንዳቸዉ በ6ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረባቸዉ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን አከራክሮ የተጠሪዎች ድርጊት ጥፋት መሆኑን ለማስረዳት በአቃቤ ህግ በኩል የቀረበዉ ማስረጃ ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጡት የምስክርነት ቃል እና ከዚህ ጋር ማነጻጸሪያ ሆኖ የቀረበዉ ተጠሪዎች ፍርድ ቤት ቀርበዉ ቃለ መሃላ ፈጽመዉ የሰጡት ምስክርነት ቃል ብቻ ስለመሆኑ ገልጾ በፖሊስ የምርመራ ወቅት የሚሰጠዉ ምስክርነት ቃል ፍርድ ቤት ከተሰጠ ምስክርነት ቃል ጋር ተነጻጽሮ የትኛዉ ትክክለኛ ነዉ የሚለዉን ለመለየት ተጨማሪ ማስረጃ እንደሚያስፈልግ ከዚህም ባሻገር ከጅምሩም ቢሆን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 453 የሚሸፍነዉ ዳኝነት ወይም ዳኝነት ነክነት ባለዉ ሂደት ላይ የሚሰጥ ምስክርነትን ቃል የሚመለከት ስለመሆኑና ፖሊስ ስልጣንና ተግባር እንዲሁም የወንጀል ምርመራ ሂደት ዳኝነት ነክነት ያለዉ ተግባር ነዉ ተብሎ በዚህ አንቀጽ ስር ሊሸፈን እንደማይገባ በማተት የስር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ያስተላለፈዉን የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በመሻር ተጠሪዎች በነጻ እንዲሰናበቱ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የፖሊስ ተቋም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ተቋም አይደለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ትርጉም የፖሊስ ተቋም በወንጀል ጉዳይ የመጀመሪያ የምስክርነት ቃል የሚሰጥበትና አቃቤ ህግም ይህንኑ መሰረት አድረጎ ክስ የማቅረብ ወይም ያለማቅረብ ጉዳይ ዉሳኔ የሚሰጥበት ስለሆነ በስር ፍርድ ቤት የፖሊስ ተቋም የዳኝነት ነክነት ተግባር የሚፈጸሚበት አይደለም ተብሎ የተሰጠዉ ትርጉም መሰረታዊ የህግ ስህተት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተፈጸመበት ነዉ በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡የአመልካች ሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ተጠሪዎች እነ ቂስ ወርቁ ገላየ 9 ሰዎች በተከሰሱበት የደን መቁረጥ ወንጀል ምርመራ በፎገራ ወረዳ ፖ/ሊስ ጽ/ቤት ቀርበዉ ወንጀሉ ሲፈጸም የተመለከቱ መሆኑን መስክረዉ በፍ/ቤት ደግሞ የአቃቤ ህግ ምስክር ሆነዉ ቀርበዉ በፖ/ሊስ የሰጡትን ቃል በመለወጣቸዉ ከቀረበባቸዉ ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ የተሰጠዉ ዉሳኔ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 453/2/ አያሟላም ተብሎ ዉድቅ መደረጉ አግባብነት ከመሰረታዊ ማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በቀበሌዉ ዉስጥ በህዝብ ተመራጭነት በተሰጣቸዉ ሃላፊነት ድርጊቱ በፖ/ሊስ እንዲጣራ ከመጠየቅ ወጪ የድርጊቱን ፈጻሚ ማንነነት እንደማያዉቁ ለፖ/ሊስ ገልጸዉ እያለ ፖ/ሊስ በማስፈራራትና በማንገራገር እነሱ ያላሉትን ቃል በመመዝገብ ሳያነብላቸዉ እንዳስፈረማቸዉ ጠቅሰዉ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ትክክለኛዉን እዉነታ የምስክርነት ቃል የሰጡ ስለሆመኑና የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ መሰረት አድርጎ በነጻ ማሰናበቱ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ትርጉም ስህተት ተፈጽሟል ወይ? የሚለዉን አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለዉ ተጠሪዎች ላይ የቀረበዉ ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/2/ ተላልፈዉ በፖ/ሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ፍርድ ቤት ቀርበዉ በመለወጣቸዉ ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል በመስጠት ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ ነዉ፡፡የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በፖ/ሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ ተከሳሾች ደን ሲቆርጡ አይተናል ብለዉ መስክረዉ ፍርድ ቤት ቀርበዉ አላየንም በማለታቸዉ ሁለቱን የምስክርነት ቃል በማነጻጸር ልዩነት መኖሩን አረጋግጦ ፍርድ ቤት ቀርበዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ቃል ሰጥተዋል በሚል በተከሰሱበት አንቀጽ ስር የጥፋተኝነት ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንን ዉሳኔ የሻረዉ በዋናነት የማስረጃ ምዘና መሰረት አድርጎ ሳይሆን የፖ/ሊስ ተቋም የወንጀል ምርመራ ስራ በወንጀል ህግ አንቀጽ 453 ድንጋጌ መሰረት የዳኝነት ነክነት በሚለዉ ትርጉም የሚሸፈን መሆን አለመሆኑን በመመርመር ስለመሆኑ ከዉሳኔዉ ይዘት መገንዘብ ተችሏል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለሆነም በዚህ ችሎት ሊመረመር የሚገባዉ ነገር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፖሊስ የወንጀል ምርመራ ስራ የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት በሚለዉ ሐረግ የሚሸፈን አይደለም በማለት የሰጠዉ ትርጉም አግባብነት ላይ ነዉ።እንደሚታወቀዉ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስራ ዉስጥ የፖሊስ ተቋም በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ እንደሆነ እሙን ነዉ።ከፖሊስ ተቋም ዋነኛ ተግባር ዉስጥ ወንጀልን መከላከል እንዲሁም ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ተገቢዉን ምርመራ ማድረግና ወንጀለኛዉን አድኖ ለህግ በማቅረብ ብሎም ፍርድ ማሰጠት እንዲሁም ፍርዱን ማስፈጸም ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ተግባርና ሃላፊነት ስለመሆኑ የፖሊስ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጆችና የወ/መ/ስ/ስ/ህግ ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነዉ።ስለሆነም በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርዓት ዉስጥ የፖሊስ ተቋም ሚና ከፍተኛ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን ከቀረበዉ ክርክር አንጻር ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ የሰጡትን የምስክርነት ቃል በፍርድ ቤት ቀርበዉ ለዉጠዋል በሚል ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል የሚለዉ የአቃቤ ህግ ክስ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 453 ስር የሚሸፈን መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲረዳን የድንጋጌዉ የተቀረጸበትን ሃይለቃል ማየት ይገባል። የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/1/ ላይ የተደነገገዉ ‹‹የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ስርዓት በሚካሄድበት ጊዜ ምስክር ሆኖ የቀረበ ማንም ሰዉ ማንኛዉንም ተከራካሪ ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት አስቦ ሀሰተኛ ምስክርነት ወይም ልዩ አዋቂነት አስተያት የሰጠ እንደሆነ ወይም እዉነቱን የደበቀ እንደሆነ ሀሳቡ ከግቡ ባይደርስም ...›› በዚህ ደንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብሎ እንደሚቀጣ እንዲሁም የተፈለገዉ ዉጤት የተገኘ እንደሆነ በንኡስ አንቀጽ ሁለት ስር በተደነገገዉ አግባብ የሚቀጣ ስለመሆኑ ተመልክቷል።የእንግሊዝኛዉ ቅጂም እንዲህ ይነበባል።‹‹453/1/ whoever being a witness in **judicial** or **quasi-judicial proceeding** knowingly makes or gives a false statement or expert opinion or hides the truth whether to the advantage or the prejudice of any party thereto...>>.በሚል ይገልጻል።

በዚህ ድንጋጌ ዉስጥ ከተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ መሰረታዊ ፍሬነገሮች ዉስጥ አከራካሪ ሆኖ የቀረበዉ ድርጊቱ የተፈጸመዉ ዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት የሚለዉ ሃይለቃል የፖሊስ የወንጀል ምርመራ ስራን ያካትታል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይ የሚለዉ ነዉ።ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ‹‹ዳኝነት›› እና ‹‹ዳኝነት ነክነት›› ለሚለዉ ቃል ትርጉም መፈለግ ግድ ይላል።የእነዚህ ቃላት ትርጉም በሀገራችን የህግ ኮዶች ወይም መዝገበ ቃላት ላይ በቀጥታ ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ ተመሳሳዩን የእንግሊዘኛ ትርጉም መመልከት ተመራጭ ሆኖ አግኝተናል።በዚህ ረገድ ታዋቂዉ የህግ መዝገብ ቃል BLAKS LAW DECTIONARY ላይ እንደተተረጎመዉ፡-

‹‹JUDICIARY-the branch of government invested with judicial power›› በማለት ትርጉም የሰጠ ሲሆን ‹‹QUASI-JUDICIAL ..hold hearings, weigh evidence; and draw conclusions from them, as basis for their official action, and to exercise discretion of judicial nature>>.በሚል ትርጉም ሰጥቷል።

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የመጀመሪያዉ የዳኝነት ስራ የሚያከናዉን የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አንደኛዉ የመንግስት አካል ወይም መደበኛዉን ፍርድ ቤት የሚያመለክት ሲሆን የዳኝነት ነክነት ስራ የሚካሄድበት ደግሞ በዳኝነት መልክ ወይም መሰል ሁኔታ ክርክር የሚሰማበት፣የቀረበለት ማስረጃ ተመዝኖ ከድምዳሜ የሚደረስበትና የበኩሉን ዉሳኔ የሚሰጥበት ሂደት የሚከናወንበት ተቋም የሚመለከት ነዉ።በዚህ ረገድ ተጠቃሽ የሆኑት ተቋማት እንደግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፣የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ቦርድ፣ የግለግል ተቋማትና ሌሎችም መሰል ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸዉ አስተዳደራዊ ተቋማት ስለመሆናቸዉ ሀገራችንን ጨምሮ የተለያዩ ሀገሮች ልምድ ያመላክታል። ይህ በዘርፉ በተደረጉ ጥናቶችና በርካታ ጽሁፎች ላይም የሚጠቀስ ነዉ። ከዚህም ባሻገር የተሻሻለዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሀተታ ዘምክንያት ላይ እንደተመለከተዉ ቀደም ሲል ስራ ላይ የነበረዉ የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 447 ስር ሀሰተኛ ምስክርነትን አስመልክቶ የተደነገገዉ ያስተዳደር ፍትሐ ብሔር፣የወንጀል ወይም የሽምግልና ዳኝነት፣ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስነስርዓት የሚፈጸምበት በሚል የተዘረዘረዉ የተንዛዛ በመሆኑ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት በሚል በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453 ስር ተሻሽሎ የቀረበ ስለመሆኑ ተገልጿል።ከዚህም አንጻር ሲታይ የወንጀል ምርመራ ሂደት በዚህ አንቀጽ ስር እንዲሸፈን ያልተደረገ ስለመሆኑ ነዉ።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሲጠቃለል የዳኝነት ነክነት ያለዉ ስርዓት የሚካሄድበት የሚለዉ ሀረግ ጥቅል ትርጉም ዳኝነት መሰል ተግባር የሚከናወንበት ሂደት የሚያመላክት ሲሆን በህጉ የተለየ ሁኔታ ካልደነገገ በስተቀር በስነስርዓት ህጉ በተደነገገዉ አግባብ ክርክር የሚመራበትና ምስክርም ሲሰማ እዉነትን ለመመስከር ቃለመሃላ ፈጽሞ ቃሉን የሚሰጥበት አካሄድ የሚከተል መሆኑን መገንዘብ አዳጋች አይደለም ።ከዚህ ጋር በተያያዘ በፖሊስ በወንጀል ምርመራ ወቅት ምስክሩ የሚሰጠዉ ቃል ልክ እንደመደበኛዉ የዳኝነት አካል ወይም የዳኝነት ነክነት ወይም መሰል ተቋም ቃለ መሃላ ፈጽሞ የሚሰጥ የምስክርነት ቃል ካለመሆኑም በተጨማሪ ምስክሩ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ የሰጠዉ የምስክርነት ቃል እና በፍርድ ቤት የሰጠዉ የምስክርነት ቃል መካከል ልዩነት በተፈጠረ ጊዜ በፖሊስ የሰጠዉ የምስክርነት ቃል እዉነት ነዉ ነገር ግን በፍርድ ቤት የሰጠዉ የምስክርነት ቃል ሀሰት ነዉ ለማለት የምስክሩ ቃል መለያየት ብቻዉን በቂ ማስረጃ ነዉ ብሎ ለመዉሰድ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም።በእርግጥ አንድ ምስክር ለፖሊስ የሰጠዉን ቃል ፍ/ቤት ሲቀርብ ከቀየረ ከሁለቱ አንዱ የሀሰት ቃል መሆኑ እሙን ነዉ።ሆኖም አመልካች ክስ ከመመስረቱ በፊት ከሁለቱ ቃሎች መካከል የሀሰት ቃል የትኛዉ እንደሆነ በትክክል በሌላ ማስረጃ ማስረዳት ይጠበቅበታል።

በዚህ መዝገብ በተያዘዉም ጉዳይ ተጠሪዎች በፖሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጡት የምስክርነት ቃል እዉነተኛ የሆነዉን ለዉጠዉ በፍርድ ቤት ቀርበዉ የሀሰት የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል በማለት አቃቤ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 453/2/ መሰረት በማደረግ ያቀረበዉን ክስ ለማስረዳት ያቀረበዉ ማስረጃ ተጠሪዎች በፖሊስ ምርመራ ላይ የሰጡት ቃል እና በፍርድ ቤት የሰጡትን ቃል በማነጻጸር እንደመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የመረመረዉ አማራ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድንጋጌዉ በፖሊስ የወንጀል ምርመራ ሂደት የተሰጠን የምስክርነት ቃል በቀጥታ ከፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል በማነጻጸር የጎለኛዉ የሀሰት ቃል ነዉ ለማለት በፖሊስ የተሰጠ ቃል የዳኝነት ነክነት ከሚለዉ የሚያጠቃለል አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ላይ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም።በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉ ሳ ኔ

የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/17096 በ05/10/09 ዓ.ም የሰተጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት ክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/70512 ላይ በ26/03/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/195/2/ለ/2 መሰረት ጸንቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 149071

መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ

ተጠሪ፡- አቶ አሰግድ አባ ቦሬ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 003731 በቀን 27/10/2009 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 145134 መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ አቅርቧል ይዘቱም፡- አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ ግንቦት 23 ቀን 2008 ዓ/ም በግምት ከጥዋቱ 4፡30 ሰዓት አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ካቴድራል ት/ቤት ተብሎ ከሚጠራ አካባቢ ለግል ተበዳይ አቶ ጊቱ ተፈራ ቁጥሩ 20552352 የሆነ እና ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሂሳብ ቁጥር 002865000101 በ01/03/2009 ዓ/ም የሚመነዘር የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) ፅፎና ፈርሞ ከሰጠው በኋላ የግል ተበዳይ በ02/03/2009 ዓ/ም ቼኩን ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ የለውም በመባሉ የሚያዝበት ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ደርሶት ተቃውሞ እንደሌለው ገልፆ፣ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ደርጊቱን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ የአመልካች ምስክሮች እንዲሰሙ ባዘዘው መሠረት ምስክር ቀርበው በሰጡት የምስክርነት ቃል ተጠሪ በ23/09/08 ዓ/ም 4፡00 ሰዓት ላይ ካንትሪ ታወር የግል ተበዳይ ቢሮ ውስጥ 5ኛ ፎቅ መጥቶ ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ በሂሳብ ቁጥር 002865000101 በ01/03/2009 ዓ/ም የሚመነዘር የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) ፅፎና ፈርሞ ከሰጠኝ በኋላ ለመመንዘር ባንክ ስሄድ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ባንክ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ የሌለ መሆኑን የተለገፀላቸው መሆኑን መስክረዋል ፣ አመልካች በፖሊስ ጣቢያ የሰጠው ቃል እና ሰጥቷል የተባለው ቼክም ባንኩ ከሠጠው ማረጋገጫ ጋር በሰነድ ማስረጃነት ቀርበው ፍ/ቤቱ እንዲከላከል በሰጠው ብይን ተጠሪ የመከላከል ምስክሮች አቅርቧል፡፡ ምስክሮቹም ተከሳሽ ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያላቸው መሆኑ እቃ በዱቤ የሚመጣና ለመተማመኛ ደግሞ ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ ስለመሆኑ መስክርዋል፡፡ተከሳሽ እና የግል ተበዳይ የሚያደርጉት የንግድ ግንኙነት በዱቤ ሽያጭ መሆኑ ሰነድ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያላቸው ስለሆነና ቼኩን የሰጠው በመተማመኛ መልኩ እንጂ የሚመነዘር አለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ቼኩ በቸልተኝነት የተሰጠ ነው በማለት የቀረበበት ክስ ፍርድ ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113 መሰረት በመቀየር ተከሳሽን በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(2) ስር ጥፋተኛ በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ተከሳሽን፡፡ በስድስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህንን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ29/02/2010 ዓ.ም በተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ፡- ተጠሪ በወ/ህ/ዓንቀፅ 693(1) መሰረት ጥፋተኛ ሊባል ሲገባው በቸልተኝነት የተፈፀመ ሊያስብል በወ/ህ/ዓንቀፅ 59 መሰረት የሚያሳይ ማስረጃ ሳይኖር በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(2) ስር በመቀየር የስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተሸሮ ተጠሪ በተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ቅጣት እንዲሰጥበት አመልክቷል ። ጉዳዩ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪ ቀርቦ በፅሁፍ መልስ እንዲሰጥ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ መልስ በፅሁፍ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የአሁኑ ተጠሪ ቼኩን ለግል ተበዳይ የሰጡት በነበራቸው ቤተሰባዊ ግንኙነት እንዲሁም የዱቤ ሽያጭ ቼክ ይሰጥ የነበረው በመተማመኛ መልኩ እንጂ የሚመነዘር አለመሆኑ ተመስክሯል ተብሎ በክሱ ላይ የተመለከተውን ወ/ህ/ዓንቀፅ 693(1) ወደ በወ/ህ/ዓንቀፅ 693(2) በመቀየር ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው በማለት የተወሰነበት አግባብነት ለመመርመር ሲሆን ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት እንደተቻለው ተጠሪ ለግል ተበዳይ ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ የሚመነዘር በሂሳብ ቁጥር 002865000101 በ01/03/2009 ዓ/ም የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) ፅፎና ፈርሞ የሰጠ መሆኑ የግል ተበዳዩ ለመመንዘር ባንክ ስሄድ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ባንክ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ የሌለ መሆኑን የተለገፀላቸው መሆኑን ፣ ተጠሪ በፖሊስ ጣቢያ የሰጠው ቃል እና ሰጥቷል የተባለው ቼክም ባንኩ ከሠጠው ማረጋገጫ ጋር በሰነድ ማስረጃነት ቀርበው ፍ/ቤቱ እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪ የመከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ተከሳሽ ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያለቸው መሆኑ እቃ በዱቤ የሚመጣና ለመተማመኛ ደግሞ ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ ስለመሆኑ መመስከራቸው ነው፡፡ ይህንን የተረጋገጠው ፍሬነገር መነሻ በማድረግ መርምረናል፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ፍ/ቤት ማስረጃ በመመዘንና ፍሬነገር በማጣራት ሥልጣኑ በደረሰበት ደምዳሜ ተጠሪ ለግል ተበዳይ ቼክ ፈርሞ መስጠቱ ሳይክድ ለዋስትና ነው የሰጠሁት በማለቱ ፍርድቤቱ ይህ የተከሳሽ እና የግል ተበዳይ ጋር ያለው የግል ግንኙነት መነሻ በማድረግ ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው በማለት ተጠሪ የተከሰሰበትን የህግ ዓንቀፅ በመቀየር የጥፋተኛ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የተያዘው ጉዳይ አመልካች ባቀረበው ክስ ተጠሪ በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ እንደሌለው እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ ፍርድቤቱ ተከሳሽ ፈፀመ የተባለው ወንጀል ሆነ ብሎ ሳይሆን በቸልተኝነት ነው ለማለት እንደምክንያት የወሰደው ከግል ተበዳይ ጋር የቤተሰባዊ ግንኙነት ያለቸው መሆኑ እቃ በዱቤ የሚመጣና ለመተማመኛ ደግሞ ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ ይህንን የወንጀል ድርጊት የፈጸመዉ በቸልተኝነት ነዉ ለማለት በወ.ሕ.ቁ.59 /1/ መሰረት ቸልተኝነት መኖሩን የሚያሟሉ ወይም የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች በሥር ፍ/ቤት አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ስለሆነም ተጠሪ የፈፀመው የወንጀል ተግባር በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው ወይስ ሆነ ብሎ የተፈፀመ ነው የሚለውን ጭብጥ መታየት ያለበት ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት የተከሰሱበት የህግ ድንጋጌ የወ.መ.ህግ ቁጥር 693/1/ን በምንመለከትበት ጊዜ ርዕሱ “የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት“ የሚል ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ ሥር የተደነገገው ማንም ሰው ቼክ በሚያወጣበት ወይም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ያለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ /የሰጠ / እንደሆነ በሚል ተደንግጓል፡፡

በመሰረቱ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(1) ሥር የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል ለማቋቋም እንደመስፈርት የተወሰዱት አንደኛው ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በሰጪ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ በቼኩ የተጠቀሰውን መጠን ገንዘብ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለመክፈል የሚያስችል የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩ ነው።በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቼኩ ማውጣቱ አልተካደም ቼኩ በወጣበት ጊዜ ይሁን በግል ተበዳይ ለክፍያ በቀረበበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ስለመኖሩ ያቀረበው ክርክር የለም ። የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰበት የህግ አንቀፅ በመቀየር ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው ለማለት የቻለው ተጠሪ ቼኩ የተሠጠው ለባንክ ቀርቦ እንዲመነዘር ሣይሆን በተከሳሽ እና ተበዳይ መካከል ባለው የብድር ግንኙነት ለዋስትና መያዣ መሰረት ተደርጎ ቼክ በገደብ የተሠጠ ነው በማለት መሆኑ ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት ችለናል።

ይህ የሁለቱም ግንኙነት በፍትሃብሄር ክርክር ላይ ቼክ ለክፍያ ሲቀርብ (ገንዘብ ሲጠየቅ) ሊቀርቡበት ከሚችሉት መቃወሚያዎች አንዱ ቢሆንም ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ እያወቀ ቼክ የሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ በቼኩ የተጠቀሰውን መጠን ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩ እስከተረጋገጠ ድረስ የተፈፀመው ወንጀል ሆነ ብሎ የተፈፀመ እንጂ በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው የሚባል አይደለም ። ስለሆነም በቼክ አውጪው እና ተቀባዩ የሚኖረው ግላዊ ግንኙነት መሰረት በማድረግ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 67947 በሰጠው ገዥ (አሳሪ) የሕግ ትርጉም ቼክ በወንጀል ጉዳይ እንደዋስትና ተሰጥተዋል በማለት እንደመከላከያ ሊቀርብ እንደማይችል ፍርድ ሰጥተዋል።

በተያዘው ጉዳይ ተሰጠ በተባለው ቼክ ለማን እንደሚከፈል ከየትኛው ባንክ እንደሚከፈል እንዲሁም ተጠሪ ፈርሞ የገንዘብ መጠኑ ተገልፆ የተሰጠ እና ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ እያወቀ ቼክ የሰጠ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ተከሳሹ ባላቸው የግል ግንኙነት መሰረት በማድረግ ብቻ ወንጀሉ የፈፀመው በቸልተኝነት ነው ለማለት አይቻልም ። ምክንያቱም ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈጸመበት ሕጋዊ ሰነድ ነው። ይህ በመሆኑም ሕግ አውጭው በቼክ ላይ የሚፈፅመው ወንጀሎች ሕጋዊ ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑ በግልፅ ከመደንገጉ በተጨማሪ ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈፅምበት ምንም ቅድመ ሁኔታ የማይቀመጥበት ሰነድ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል ። ከዚህ አንጻር ሲታይ የአሁን አመልካች የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ያለመኖሩን እያወቀ ቼክ ያወጣ /የሰጠ / መሆኑና ቼኩን ለክፍያ ተበዳይ ሲያቀርበውም በቂ ገንዘብ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የለውም ተብሎ መመለሱን በሚመለከት የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰዉ ምስክሮች ቃል እና የሰነድ ማስረጃ በመመዘን በበቂ ሁኔታ እንደ ክሱ ያስረዱ መሆናቸዉን በማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ እንዲከላከል ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ ባላስተባበለበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰበትን የህግ አንቀፅ በመቀየር የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(2) ጥፋተኛ ማለቱ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(1) እንዲሁም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23፤59 የተመለከተውን የህግ ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በቀረበበት ክስ በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(1) ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኛ ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የተቀየረ በመሆኑ በዚሁ አግባብ በተጠሪ ላይ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ሊስተካከል ይገባል ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለው ወንጀል ሕግ አንቀጽ 693(1) በመሆኑ ቅጣቱ ሊሰላ የሚገባው ጥፋተኛ በተባለበት የህግ ድንጋጌ ነው ፡፡ተጠሪ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት የህግ ድንጋጌ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የወንጀል ደረጃና እርከን የወጣለት ስለሆነ የገንዘብ መጠኑ ብር 4,517,117.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) በመሆኑ የእስራት ቅጣት መነሻ እርከኑ 23 የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከኑ 6 ይሆናል፡፡

በከሳሽ (አመልካች) በኩል የቀረበ እና በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ማክበጃ ስለሌለ የቅጣት እርከኑ ከተያዘው መነሻ እርከን ከፍ አላለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የቀድሞ ሪከርድ የሌላቸው መሆኑ እና ቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያ የተያዘላቸው በመሆኑ የእስራት ቅጣት መነሻ እርከኑ ከእርከን 23 ወደ እርከን 21 እንዲሁም የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከኑ ወደ እርከን 4 ዝቅ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም በእርከን 21 ስር ባለው ፍቅድ ስልጣን ከ5 አመት እስከ 6 አመት ስለሆነ ተጠሪ ጥፋተኛ በተባለበት የህግ ድንጋጌ ያስተምረዋል የተባለውን የአምስት አመት ፅኑ እስራት እና የአራት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይገባል ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ላይ የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 003731 ሰኔ 27 ቀን 2009 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሳኔ ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14134 መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም. የፀናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ክስ በቀረበበት የህግ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ሁሉ የሚታሰብላቸው ሆኖ በአምስት አመት ፅኑ እስራት እና በአራት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል ፖሊስ ተጠሪ በሚገኙበት በመያዝ ለሚመለከተው ማርሚያ ቤት እንዲያሰረክብ ፣ ማረሚያ ቤቱም ከፌዴራል ፖሊስ ተረክቦ ተጠሪን በጉዳዩ ላይ ቀድሞ የታሰሩበት ጊዜ ካለ ታሳቢ በማድረግ የተወሰነውን የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣትን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ የገንዘብ ቅጣቱ የሚመለከተው የፋይናንስ ክፍል ያስፈፅም ብለናል ፡፡ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ 150803

ሐምሌ 25 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ-አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ንጉስ ሀይሉ-አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ወንጀል ነው፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪው የአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 35/1/ለ ድንጋጌን በመተላለፍ ማንም ሳይፈቅድለት በቀን 06/07/08 ዓ.ም ከቀኑ 10፡00 ሠዓት በሐወልቲ ክፍለከተማ ቀጠና 10 ስፋቱ 11.28 ሜ^2 የሆነ የመንግሥት መሬት ጨምሮ ቤት ስለሰራበት በፈጸመው የከተማ ቦታ ያለአግባብ መያዝ ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበውን ክስ የተመለከተው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐወልቲ ፍ/ቤት ተጠሪን በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ሆኖ ስላገኘው ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 በማስላት በሠባት ዓመት ጽኑ እሥራት እና በብር 40,000 / አርባ ሺህ ብር / የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ የሰሩትን የድንጋይ አጥር እንዲያፈርሱ በቃል የተነገራቸው ከመሆኑ በቀር የተሰጣቸው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ7 ቀን የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ የለም፤አዋጁ የሰባት ቀን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት እንዳለበት የሚደነግግ ሆኖ ሳለ እና ተጠሪ በቃል በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት የሰሩትን የድንጋይ አጥር አፍርሰው ሳለ የሥር ፍ/ቤት በአዋጁ የተቀመጠው ማሥጠንቀቂያ የመስጠት ቅድመሁኔታ ባልተሟላበት ሁኔታ የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን በነጻ አሰናብቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶቸ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው የቀረበላቸው ፍ/ቤቶች የሥር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንተዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አስቀድሞ የመሬት ወረራ ወንጀል ለመስራት አስቦ መሬትን የወረረ ሰው ማሥጠንቀቂያ ካልተሰጠው በቀር በወንጀል ጥፋተኛ ሊባል አይገባም የሚል ድንጋጌ በአዋጁ ባልተቀመጠበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው የሥር ፍ/ቤቶች ለተጠሪ ማሥጠንቀቂያ አልተሰጠም በሚል ምክንያት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአሁን ተጠሪ የከተማ ይዞታውን የያዘው ከሕግ ውጪ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 721/04 አንቀጽ 27 መሠረት ማሥጠንቀቂያ ባልተሠጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በአዋጁ አንቀጽ 26/4 እና 27/2 የተቀመጠው ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ በአዋጁ አንቀጽ 35/1/ለ የተቀመጠው ቅጣት ክብደት አኳያ ተጠሪን የመሰሉ ሰዎች ማስጠንቀቂያ በመስጠት አሥተዳደራዊ መፍትሔ ለማምጣት እና በማስጠንቀቂያ ከተግባሩ እንዲቆጠብ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ በመገንዘ ተጠሪን በነጻ ማሰናበታቸው ተገቢ ነው፤ይህ የሚታለፍ ከሆነም ተጠሪ ለረዜው የሰራሁትን አጥር ያፈረስኩ እና የፈጸምኩት ተግባርም ቀላል ስለሆነ ጥፋተኛ ልባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 686/1 ከመግሥት ፈቃድ ውጪ የመንግሥትን ቦታ መያዝ ወንጀል በሚል ሊሆን ይገባል፤ይህ የሚታለፍ ከሆነም ይዞታው ከባለቤቱ ይዞታ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አጠገብ የሚገኘውን ቦታ ክረምቱ እስኪያልፍ በሚል ለማገዶ የተሰራ እንጂ ቦታውን ለማካተት ስላልሆነ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ቅጣቱም ቀሎ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ ሲባል እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

ተጠሪ የአዋጁን አንቀጽ ከአዋሳኞቸው ጎን ያለውን የመንግሥት ቦታ ወደ ራሣቸው ይዞታ በመቀላቀል የድንጋይ አጥር የሰሩበት መሆኑ በወረዳው ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 35/1/ለ ማንም ሰው አዋጁን ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ የከተማ ቦታን አጥሮ ከያዘ ግንባታ ካካሄደበት ወይም ከአዋሳኝ ይዞታው ጋር ከቀላቀለ ከሠባት እሥከ አሥራ አምሥት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 40,000 እሥከ 200,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 26/1 አግባብ ያለው አካል ከቦታው ለሚነሳው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ እንዲከፈል በማድረግ የከተማ ቦታ ይዞታን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የማስለቀቅ እና የመረከብ ሥልጣን ይኖረዋል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 4 አግባብ ያለው አካል በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት እና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የሠባት የሥራ ቀናት የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ይኖረዋል በማለት ይደነግጋል፡፡

የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቶች ተጠሪ የሰሩትን የድንጋይ አጥር እንዲያፈርሱ በቃል የተነገራቸው ከመሆኑ በቀር የተሰጣቸው የ7 ቀን የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ የለም፤በአዋጁ አንቀጽ 26/4 ላይ የተቀመጠው የሰባት ቀናት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ ባልተሟላበት ሁኔታ እና ተጠሪ በቃል በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት የሰሩትን የድንጋይ አጥር ባፈረሱበት ሁኔታ ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ አይደለም ከሚል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መደምደሚያ ላይ የደረሱ ቢሆንም በአዋጁ አንቀጽ 26/4 ላይ አግባብ ያለው አካል በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት እና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የሠባት የሥራ ቀናት የጽሑፍ ማሥጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ይኖረዋል በማለት የተቀመጠው ሀሳብ በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት በሕጋዊ መንገድ ለተያዙ የከተማ ቦታዎችን ለማስለቀቅ የተቀመጠውን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የመስጠት እና ካሣ የመክፈል ሥርዓት ማሟላት ሳያስፈልግ በሕገወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታን ማስለቀቅ የሚቻልበትን ሥርዓት የሚደነግግ እንጂ የከተማ ቦታን ወሮ ለያዘ ሰው የወንጀል ሀላፊነትን የሚያስቀር አይደለም። በመሆኑም የሥር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የአዋጁን አንቀጽ 26/4 ድንጋጌን ያለአግባብ በመተርጎም ለተጠሪ የተሰጠው የሰባት ቀናት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ውሳኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመቐለ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20165 ሐምሌ 26 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 88023 ግንቦት 02 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 98220 ጥቅምት 10 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል።
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የሐወልቲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07743 ሠኔ 01 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል።
3. የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችን በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል።
-መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ/151034

ጥቅምት 28 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አማረ ረታ

ተጠሪ፡- የፌደራል ጠ/አቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ በወንጀል ጉዳይ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አዲስ የወጣዉ ህግ ተከሳሹን የሚጠቅም በሆነ ጊዜ እንዴት ይፈጸማል የሚል ነዉ፡፡ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ አመልካች በጉሙሩክ አዋጅ ቁ/622/01 ስር ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት ዉሳኔ ተላልፎበት በማረሚያ ቤት ቅጣቱን እየፈጸመ እያለ አዲስ የወጣዉ የጉሙሩክ አዋጅ ቁ/859/06 ለተመሳሳይ ጥፋት የደነገገዉ ቅጣት አመልካችን የሚጠቅም ስለሆነ በአዲሱ አዋጅ መሰረት ቅጣቱ እንዲታይለት ለፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ ተቀባይነት ባለማግኘቱና ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ በማጽናቱ ነዉ፡፡

የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ አመልካች አዋጅ ቁ/622/01 አንቀጽ 95/1/ሐ/እና 2 በመተላለፍ እሽጎችን መፍታትና ምልክቶችን ማንሳት እንዲሁም አንቀጽ 101/3 በመተላለፍ የማንገዝ ሃላፊነት ባለመወጣት ጥፋተኛ ተብሎ በፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በ16,000ብር እና 24 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ስለመወሰኑና በዚህ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ብቻ በማሻሻል18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰኑን ፣ይህንኑ ቅጣት እየፈጸመ እያለ አዲስ የወጣዉ አዋጅ ቁ/859/06 በዚህ ጉዳይ ከቀድሞ አዋጅ ያነሰ ቅጣት የሚያስቀጣ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 22/2/ መሰረት አዲሱ አዋጅ ተፈጻሚ እንዲሆን አቤቱታ ማቅረቡንና የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ተቀብለዉ ቅጣቱን ማሻሻል ሲገባቸዉ አቤቱታዉን አናስተናግድም ማለታቸዉ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩን ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 22/2/ እና ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 6 እና 9 እንዲሁም ከአዋጅ ቁ/859/06 አንቀጽ 170 እና 171 አንጻር ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ አቃቤ ህግ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡በአቃቤ ህግ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በአዲሱ አዋጅ መሰረት መነሻ ቅጣቱ ተከሳሽን የሚጠቅም መሆኑ ታይቶ ማሻሻያ ቢደረግለት ተቃዉሞ እንደሌለዉ ገልጿል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ በወንጀል ጉዳይ የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ የሚደረገዉ መቼ ነዉ እንዲህ ዓይነት አቤቱታስ እስከ መቼ መቅረብ ይችላል የሚሉት ነጥቦች መታየት ያለባቸዉ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑ በሀገራችን ህገ መንግስት እና በወንጀል ህግ በግልጽ የተደነገገ ከመሆኑም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተደንግጎ የሚገኝ አለም አቀፍ ቅቡልነት ያለዉ መርሆ መሆኑ ይታወቃል፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህገ መንግስት አንቀጽ 22 /1/፣የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ህግ አንቀጽ 5 እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ15/1/ይመለከታል፡፡ከዚህ መርህ ልዩ ሁኔታ ተብሎ የተደነገገዉ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣዉ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣዉ ሰዉ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣዉ ህግ ተፈጻሚ እንዲሆን የማድረግ ጉዳይ ነዉ፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ22/2/፣የወንጀል ህጉ አንቀጽ 6 እንዲሁም የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች አለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 15/1 ሁለተኛ ፓራግራፍ ይመለከታል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ህጉ ተከሳሽን መብትና ጥቅም በተሻለ ሁኔታ ማስከበርን መሰረት ያደረገ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስለመሆኑና በወንጀል ጉዳይ ህግ መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተከሳሽን በሚጠቅም አኳኋን ሊተረጎም ይገባል የሚለዉን ቅቡልነት ያለዉ የወንጀል ህግ አተረጓጎም መርህ የተከተለ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለዚህም ቅጣትን በሚመለከት አዲሱ የወንጀል ህግ ከመውጣቱ በፊት በተፈፀመ ወንጀል ከተፈረደበት እና ሆኖም ግን ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ስራ ላይ ከነበረው ወንጀል ህግ ይልቅ አዲሱ ህግ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቀልለትና ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ይሄው በአዲሱ ህግ ላይ ያለው ቅጣት የሚፈጽምበት ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ ቁ. 6 ድንጋጌ ይዘት የሚያስገነዝብ ስለመሆኑ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 95438 ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡በሌላ በኩል አዲስ የወጣዉ ህግ የቀድሞዉን ህግ የሻረዉ እንደሆነና በቀድሞ ህግ ወንጀል የነበረዉ ድርጊት በአዲሱ ህግ ይኸዉ ድርጊት ወንጀልነቱ ቀሪ ከሆነ ወይም የማያሥቀጣ ከሆነ በቀድሞ ህግ ተፈርዶበት ቅጣቱ እንደማይፈጸም ወይም እየተፈጸመ ከሆነም ቅጣቱ አፈጻጸም ወዲያዉኑ እንደሚቋረጥ የወንጀል ህግ አንቀጽ 9/1/ በግልጽ ደንግጓል፡፡

ስለሆነም ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ኋላ የወጣዉ የወንጀል ህግ ተከሳሹን ወይም የተቀጣዉን ሰዉ የሚጠቅም መሆን አለመሆኑ መመዘኛ ተደርጎ መታየት ያለበት ስለመሆኑ ነዉ፡፡ኋላ የወጣዉ ህግ የቀድሞዉን ህግ በመሻር የድርጊቱን ወንጀልነት ቀሪ በማድረጉ በቀድሞ ህግ የተሰጠዉ ፍርድ ቀሪ ነዉ በሚል በግልጽ ህጉ ደንግጎ እያለ ኋላ የወጣዉ ህግ ቅጣት ማቅለሉን መሰረት በማድረግ ተቀጪዉ ያቀረበዉ አቤቱታ ሊስተናገድ አይገባም የሚለዉ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 22/2/ እና የወንጀል ህጉን ልዩ ሁኔታ አንቀጽ 6 ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ መታየት ያለበት ጉዳይ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ተከሳሹ ወይም ተቀጪዉ አቤቱታ ማቅረብ የሚጠበቅበት የጊዜ ገደብ መኖር አለመኖሩ ላይ ነዉ፡፡በመሠረቱ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ለይግባኝ ማቅረቢያና ተያያዥ ጉዳዮች የጊዜ ገደብ ቢያስቀምጥም ፍርድ አግኝቶ የተዘጋ መዝገብ በኃላ እንደገና መከፈቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በምን ያህል ጊዜ ዉስጥ አቤቱታ ሊቀርብበት እንደሚገባ በሕግ የጊዜ ገደብ አልተቀመጠም፡፡ ይህ በሚሆንበት ወቅት የጊዜ ገደቡ የሚወሰነዉ የጉዳዩን ሁኔታዎችና የአቤቱታዉን ዓይነት በመመልከት እንጂ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ የቀረበዉ አቤቱታ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ተቀባይነት የለውም በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ አይደለም፡፡ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2)፣ የወ/ሕ/አንቀጽ 6 እና 9(1)ን መሠረት በማድረግ አቤቱታ ያቀረበበት ጉዳይ በባህሪዉ እንደመደበኛ የክርክር ጉዳይ የሚታይ ሳይሆን አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚችል መሆኑን ህጉ ግልጽ የጊዜ ገደብ አለማስቀመጡ የሚያሳይ ነዉ፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በቀድሞ የጉምሩክ አዋጅ ቁ/622/01 አንቀጽ 95/1/ሐ እና 2 እንዲሁም አንቀጽ 101/3/ በተደራራቢ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛነትና የቅጣት ዉሳኔ ተሰጥቶ ቅጣቱን በመፈጸም ላይ እያለ አዲስ የወጣዉ የጉምሩክ አዋጅ ቁ/859/06 አንቀጽ 170እና 171 የድርጊቱን አስቀጪነት እንዳለ ይዞ ነገር ግን ቅጣቱን በማሻሻሉ አመልካች የጎለኛዉ ህግ ይጠቅመኛል በሚል ለስር ፍርድ ቤት አቤቱታ ሲያቀርብ ፍርድ ቤቱ እንዲህ ዓይነት አቤቱታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከላይ በዝርዝር የተመለከተዉን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ እና የወንጀል ህጉን ዓላማና ይዘት ያላገናዘበ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1ኛ/የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/81283 ላይ በ06/04/2008 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/002346 ላይ በ20/03/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በመሰረዝ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ተመርምሮ ተገቢዉ ዉሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡን በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/195 /2/ሀ መሰረት ለፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት መልሰናል ፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰበር መ/ቁ/158613

ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ማስተዋል ሰፈረ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ አማራ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት ተጠሪ ለችሎት ስራ እንቅፋት ሆናለች በማለት ጥፋተኛ ናት በሚል የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይህም ከማህደሯ ጋር እንዲያያዝ ትእዛዝ በመስጠቱ እና አመልካች ይህንን ትእዛዝ ለማስለወጥ አቤቱታ በማቅረቧ የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ አግባብነት ከወንጀል ህግ አንቀጽ 449 አንጻር ለመመርመር እንዲቻል ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበ ነዉ፡፡

እኛም የቀረበዉን አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ ይዘት እና አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ፍርድ ቤቱ ለትእዛዙ መሰረት ያደረገዉ መነሻ ምክንያት አመልካች የፍርድ ቤቱ ንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆና ለዳኞች የሚሰጥ የሞባይል ካርድ ለዳኞች ቢሮ ድረስ ለማቅረብ ፈቃደኛ አልሆነችም በሚል ምክንያት ጉዳዩን ችሎት ቀርባ እንድታስረዳ ስትጠራም ችሎት ለመቅረብ እምብተኛ ከመሆኗም በተጨማሪ በፖሊስ ተጠርታ ስትቀርብም ተገቢዉን ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኗ ለችሎት ስራ እንቅፋት ሆናለች በሚል ምክንያት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣትና ከማህደሯ እንዲያያዝ ትእዛዝ ስለመስጠቱ ገልጧል፡፡ችሎቱ ይህንን የቅጣት ውሳኔ ሲሰጥ የህግ መሰረቱ ግልጽ ባለመሆኑ አከራካሪ ሆኖ ቀርቧል፡፡ለዚህም ነዉ በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 449 አንጻር አግባብነቱን መመርመር ያስፈለገዉ፡፡

በመሰረቱ የዳኝነት ስራ አካሄድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ዓይነትና ቅጣታቸዉ የሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 443 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ እንደተመለከተዉ እንደጉዳዩ ባሕርይና ጥፋት ዓይነት ቅጣት የሚጣልበት ሲሆን በተለይ ችሎት መድፈርን አስመልክቶ ችሎቱ በያዘዉ መዝገብ ላይ ወዲያዉኑ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት አግባብ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 449 እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/480 እና 481 በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትም ሲታይ የዳኝነት ስራ በማከናወን ያለዉን ዳኛ በማናቸዉም መንገድ ማወክ፣መስደብ ፣ማፈዝ፣ መዛትና በመሰል ሁኔታ እንቅፋት መፍጠር እንዲሁም የዳኝነት ስራ አካሄድ ስነስርዓት አለማክበር፣ለችሎቱ ክብርና ለዳኝነት ስራ መልካም አመራር ተቃራኒ የሆነ ጠባይ የሚያሳይ ማንኛዉም ሰዉ ፣ የችሎት ተግባርና ስራ የሚያደናቅፉና ተገቢዉን ክብር ለማይሰጡ ለማይታዘዙና ተገቢዉን ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆን የችሎቱን ስራ የሚያደናቅፍን ማንኛዉም ሰዉ በዚያዉ መዝገብ ወዲያዉኑ ተገቢ ቅጣት መጣል የሚያስችል ነዉ፡፡የነዚህ ድንጋጌዎች ዋነኛ ዓላማ የችሎቱን ስራ አካሄድ በማስከበር ያለእንቅፋት የዳኝነት ስራዉን ማሳለጥ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በዚህ መዝገብ ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የሞባይል ካርድ ለችሎቱ ዳኞች የማቅረብ አስተዳደራዊ ግዴታ ወይም የስራ ሃላፊነት አልተወጣችም በሚል ምክንያት ወደ ችሎቱ እንድትጠራ መደረጉ የተገለጸ ሲሆን ከጅምሩ አስተዳደራዊ የስራ ሃላፊነት አለመወጣት አለ ከተባለ በአስተዳደራዊ ስነ ስርዓት ጉዳዩ ተጣርቶ ተገቢዉ እንዲወሰን ማድረግ እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ከዚህ አልፎ ግን ችሎቱ ምክንያቱን ለመገንዘብ ፈልጎ ወደ ችሎት እንድትቀርብና ተገቢዉን ምላሽ እንድትሰጥ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ አመልካች ችሎት ቀርባ የችሎቱን ትእዛዝ አልቀበልም ማለቷ እንዲሁም ለችሎቱ ተገቢዉን ክብር አለመስጠቷ ከተረጋገጠ እና ችሎቱ ይህ ተግባሯ ጥፋት ነዉ ብሎ ካመነበት ቅጣት ሊወሰን የሚችለዉ ለድርጊቱ ማቋቋሚያ ድንጋጌ በመለየት በወ/ህጉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አንቀጽ 443 ወይም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 480 ወይም 481 በተደነገገዉ አግባብ ሊሆን ይገባል።ከዚህ ዉጪ በህግ በግልጽ ባልተደነገገ አግባብ የሚጣል ቅጣት የህግ መሰረት የለዉም ።በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጥና ይህም ከማህደሯ ጋር እንዲያያዝ በማለት የሰጠዉ የቅጣት ዉሳኔ የህግ መሰረት የሌለዉ ስለሆነ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተናል።ነገርግን አመልካች የፈጸመችዉ ድርጊት በአስተዳደራዊ መንገድ ተጣርቶ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድበት ነዉ ወይስ የችሎቱን ስራ መድፈር ነዉ? በሚለዉ ላይ በመለየት ተገቢና አስተማሪ ዉሳኔ መስጠትን ይህ ዉሳኔ ቀሪ አያደርገዉም ብለናል። በዚሁ አግባብ ተከታዩን ትእዛዝ ሰጥተናል።

<u>ትእዛዝ።</u>

1ኛ/የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ/03-75294 በ11/08/2010 ዓ.ም አመልካች ላይ የሰጠዉ የቅጣት ትእዛዝ ተሽሯል።

2ኛ/ አመልካች የፈጸመችዉ ድርጊት በአስተዳደራዊ ስነስርዓት ወይም በችሎት መድፈር የሚሸፈን ነዉ የሚለዉን በመለየት ተገቢዉን የመወሰን ጉዳይ ይህ ዉሳኔ ቀሪ አያደርገዉም ብለናል።
3ኛ/ይኸዉ እንዲታወቅ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ይተላለፍ ብለናል።ይጻፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ።

ሰ/ጌ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 152755

መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ

ተጠሪ፡- አቶ አፍራኖ ሁሌ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው ስለሆነም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273802 በቀን 26/03/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናቱ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ሁለት የተለያዩ መዝገቦች ክስ አቅርቧል፡፡ በመዝገብ ቁጥር 25117 የቀረበው ክስ ይዘቱም፡- አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 692/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሂሳብ ቁጥሩ ዝግ ሆኖ 1,000,000 የሆነ በቼክ ቁጥር BA.712880 የሆነ ብር 1,189,875 የቼክ ቁጥር AB.712880 ሰጥቶ የማታለል ወንጀል ስለፈፀመ ተከሷል የሚል ነው፡፡በመዝገብ ቁጥር 25121 የቀረበው ክስ ደግሞ ይዘቱም፡- አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሚያዝበት በቂ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገንዘብ ሳይኖረው የብር 535,000 የሆነ ቁጥሩ BA.0776503 ቼክ ፈርሞ ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ እንዲመነዘር ሰጥቶ ቼኩ ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተዘጋ መሆኑ የተረገጠ ስለሆነ የሚያዝበት ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ደርሶት ተቃውሞ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ የተጠሪ ተቃውሞ በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ ተጠሪ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ደርጊቱን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ የተጠሪ ምስክሮች እንዲሰሙ ባዘዘው መሠረት የአመልካች ምስክር ቀርበው የግል ተበዳይ እና 2ኛ የዓ/ህግ ምስክር ብር 500,000 በተከሳሽ ሂሳብ ገቢ ያደረጉ መሆናቸው ብር 35,000 በእጁ ከሰጡት በኋላ ቼኩን ፈርሞ የሰጣቸው መሆኑ ተበዳይ ቼኩን በመያዝ ባንክ ሲሄድ ገንዘብ የለውም ስለተባሉ ቼኩን ያስመቱ መሆናቸው ፣ ተጠሪ ሰጥቷል የተባለው ቼክም ባንኩ ከሠጠው ማረጋገጫ ጋር በሰነድ ማስረጃነት ቀርበው ፍ/ቤቱ እንዲከላከል በሰጠው ብይን አመልካች የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ ቀን ያልተፃፈበት ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ ስለመሆኑ መስክርዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አመልካች ባንክ በቂ ገንዘብ ሳይኖረው ቼክ የሰጠ መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ እና በመከላከያ ማስረጃው ስላልተከላከለ ቼኩ ላይ ቀን ያልተጻፈበት መሆኑ ከወንጀሉ ነፃ አያደርገውም በማለት በቀረበበት ክስ ጥፋተኛ ነው በማለት ቅጣቱ በመዝገብ ቁጥር 25117 ጋር በማጣመር አስልቷል፡፡ በዚህ መሰረት በመዝገብ ቁጥር 25117 ተጠሪ የተከሰሰበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 692/1/ ጥፋተኛ በማለት በአራት ዓመት ከአምስት ወር እስራት እና በብር ሰባት ሺህ የገንዘብ መቀጮ መነሻ ይዟል፡፡ በመዝገብ ቁጥር 25121 ጥፋተኛ ለተባለበት የህግ ድንጋጌ የስምንት ዓመት ከአምስት ወር እስራት እና በብር አስራ አምስት ሺህ የገንዘብ መቀጮ መነሻ ቅጣት ይዟል፡፡በተጠሪ በኩል የቀረበ 3 የቅጣት ማቅለያ በመቀበል ተከሳሽ በስድስት አመት ፅኑ እስራት እና በብር 2,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ መሰረት በማድረግ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ያከራከረ ሲሆን ተጠሪን በተመለከተ በመዝገብ ቁጥር 25117 የስር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ቅጣቱን በማሻሻል ተከሳሽ በአንድ አመት ፅኑ እስራት እና በብር 2,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል። በሌላ በኩል በመዝገብ ቁጥር 25121 የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር ተከሳሽ በቀረበበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሚያዝበት ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል በነፃ እንዲሰናበት ውሳኔ ሰጥቷል።አመልካች የስር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች በ17/05/2010 ዓ.ም በተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል። የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ፡- ተጠሪ በ1ኛ ክስ በመዝገብ ቁጥር 25117 ላይ የማታለል ወንጀል ክስ ዓንቀፅ 692(1) የስር ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔውን ያፀኑ ቢሆንም ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት እርከን የወጣለት ስለሆነ ደረጃ 8 እርከን 20 ስር የሚወድቅ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እና 4 ማቅለያ መጠቀሙ ስህተት ነው ሊታረም ይገባል ።
2ኛ ክስ በተመለከተ ተጠሪ በቂ ስንቅ ሳይኖረው የግል ተበዳይ ኑረዲን አብዱል ሰመድ የተበደረውን ገንዘብ በቀን 28/08/2008 ዓ/ም ለክፍያ የሚቀርብ ቼክ በቀን 12/02/2008 ፅፎ እንደሰጠ ተረጋግጦ እያለ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት 2ኛ የዓ/ህግ ምስክር ቼኩ የሰጠው ለዋስትና ነው በማለት ምስክርነት ቃል ሰጥቷል በማለት ተከሳሽን በነፃ ማሰናበቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል አቅርበዋል።የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪ ቀርቦ በፅሁፍ ተከራክረዋል።
የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል ።በአጣሪው ችሎት የተያዘው ጭብጥ ተጠሪ ለግል ተበዳይ የሰጠው ቼክ ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ የተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተዘጋ እና በቂ ሂሳብ የሌለው መሆኑ በምስክሮች በተረጋገጠበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቼኩ የተሰጠው ለመተማመኛ ነው በማለት በነፃ ያሰናበተበት አግባብ ከወንጀል ህግ ዓንቀፅ 693(1) አንፃር ለመመርመር ነው ። እኛም ጉዳዩ እንዲጣራ ከተያዘው ጭብጥ ብቻ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረት በማድረግ መርምረናል ።እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25121 የነበረው ክርክር ሲታይ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ሳይኖረው የብር 535,000 የሆነ ቁጥሩ BA.0776503 ቼክ ፈርሞ ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ እንዲመነዘር ሰጥቶ ቼኩ ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ በተከሳሽ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተዘጋ መሆኑ የተረገጠ ስለሆነ የሚያዝበት ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው። ይህን ክስ ለማስረዳት የቀረቡት የከሳሽ ዓ/ህግ ምስክሮች በበኩላቸው ተጠሪ በቂ ስንቅ ሳይኖረው የግል ተበዳይ ኑረዲን አብዱል ሰመድ እና 2ኛ የዓ/ህግ ማስረጃ ብር 500,000 በተከሳሽ ሂሳብ ገቢ ያደረጉ መሆናቸው ብር 35,000 በእጁ ከሰጡት በኋላ በቀን 28/08/2008 ዓ/ም ለክፍያ የሚቀርብ ቼክ በቀን 12/02/2008 ፅፎ እና ፈርሞ የሰጣቸው መሆኑ ተበዳይ ቼኩን በመያዝ ባንክ ሲሄድ ገንዘብ የለውም ስለተባሉ ቼኩን ያስመቱ መሆናቸው ፣ ተጠሪ ሰጥቷል የተባለው ቼክም ባንኩ ከሠጠው ማረጋገጫ ጋር በሰነድ ማስረጃነት ቀርበው ፍ/ቤቱ እንዲከላከል በሰጠው ብይን አመልካች የመከላከል ምስክሮች አቅርቦ ቀን ያልተፃፈበት ቼክ ለብድር ዋስትና የሰጠ ስለመሆኑ መመስከራቸው መሰረት በማድረግ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ በማለት የቅጣት ውሳኔ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን ተጠሪ ቼኩን ለግል ተበዳይ የሰጠው ለመተማመኛ መሆኑ በዓ/ህግ 2ኛ ምስክር የተገለፀ በመሆኑ ተከሳሽ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት በነፃ ያሰናበተው ስለመሆኑ ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል።

ተጠሪ ለግል ተበዳይ ቼክ ፈርሞ መስጠቱ ሳይክድ ነገር ግን ቼኩ የተሰጠው ለዋስትና ዓላማ ነው በማለት ተከራክረዋል ። በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ፍ/ቤት ማስረጃ በመመዘንና ፍሬነገር በማጣራት ሥልጣኑ በደረሰበት ደምዳሜ ተጠሪ ቼክ ፈርሞ መስጠቱ ለዋስትና የሰጠሁት ነው የሚለው ክርክርም ተቀባይነት እንደሌለው ቼኩ ፈርሞ መስጠቱ የተረጋገጠ እና በቼኩ ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ ጥፋተኛ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአንፃሩ ቼኩ ለዋስትና የተሰጠ መሆኑ የዓ/ህግ 2ኛ ምስክር ተገልፀዋል በማለት ተከሳሽ በተጠቀሰበት የህግ ዓንቀፅ ጥፋተኛ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሊባል አይገባም ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሱ ምክንያት ተጠሪ በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

በመሰረቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ .የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 693(1) ሥር የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል ለማቋቋም እንደመስፈርት የተወሰዱት አንደኛው ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ በሰጪ በቼክ አውጭው ሂሣብ ቁጥር በቂ ስንቅ አለመኖሩ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ በቼኩ የተጠቀሰውን መጠን ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቼኩ ማውጣቱ አልተካደም ቼኩ በወጣበት ጊዜ ይሁን በግል ተበዳይ በክፍያ በቀረበበት ጊዜ የሚያሲዝበት በቂ ገንዘብ ስለመኖሩ ያቀረበው ክርክር የለም ፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 67947 በሰጠው ገዥ (አሳሪ) የሕግ ትርጉም ቼክ በወንጀል ጉዳይ እንደዋስትና ተሰጥተዋል በማለት እንደመከላከያ ሊቀርብ እንደማይችል ፍርድ ሰጥተዋል ፡፡ በቼክ አውጪው እና ተቀባዩ የሚኖረው ግላዊ ግንኙነት /personal relation/ በፍትሐብሄር ጉዳይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም በወንጀል ጉዳዮች ተፈፃሚነት እንደሌለው ከላይ በተመለከተው የሰበር ውሳኔ ተገልጸዋል ፡፡ በመሆኑም አንድ በቼክ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰው ግለሰብ ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ የሚሆነው ከላይ የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋያ ፍሬ ነገሮች እንደሌሉ በሌላ አገላለጽ ቼኩ ሊወጣ ወይም ለክፍያ ሲቀርብ በቂ ስንቅ ያለው ስለመሆኑ በማስረዳት ብቻ ሲሆን ከዚህ ሌላ ፍርድ ቤቱ የሚቀበለው ሌላ ሕጋዊ ምክንያት ከሌላ በስተቀር ከተጠያቂነት ነፃ የሚያደረግ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈጸመበት ሕጋዊ ሰነድ ነው፡፡

ይህ በመሆኑም ሕግ አውጭው በቼክ ላይ የሚፈፅመው ወንጀሎች ሕጋዊ ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑ በግልፅ ከመደንገጉ በተጨማሪ ቼክ እንዳቀረበ ክፍያ የሚፈፅምበት ምንም ቅድመሁኔታ የማይቀመጥበት ሰነድ ነው ፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት ክርክር ሂደት እንደተገነዘብነው ተጠሪ ቼክ ለግል ተበዳይ መስጠቱ አልካደም ፡፡ተሰጠ በተባለው ቼክም ለማን እንደሚከፈል ከየትኛው ባንክ እንደሚከፈል እንዲሁም የገንዘብ መጠኑ በግልጽ የሰፈረ ስለመሆኑ አላከራከረም ፡፡ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ በነፃ ለማሰናበት እንደ መሰረታዊ ነጥብ የወሰደው ቼኩ ለዋስትና መያዣነት ለግል ተበዳይ የተሰጠ ስለሆነ የወንጀል ተጠያቂነት አያስከትልም በሚል ነው፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሥር የክርክር ሂደት መረዳት እንደተቻለው ተጠሪ የእምነት ክህደት ቃሉ ሲሰጥ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቼክ ፈርሞ መስጠቱ አልካደም ። ተጠሪ የቼኩ ሕጋዊነት ሳይቃወም ቼኩ የተሰጠበት ዓላማ መሠረት በማድረግ መከራከሩን ተገንዝበናል ከላይ እንደተመለከተው ቼክ እንደቀረበ ክፍያ የሚፈጸምበት ሰነድ ከመሆኑ አንፃር በወንጀል ጉዳይ ያለው ተጠያቂነት ቼክ በወጣበት ወይም ለክፍያ ለቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ መኖር ያለመኖሩን መሠረት ያደረገ እንጂ ለዋስትና የተሰጠ መሆን ያለመሆን በወንጀል ጉዳይ እንደ ሕጋዊ መከላከያ የሚወሰድ አይደለም ። የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ለክርክሩ መሠረት የሆነው ቼክ በተጠሪ ተጽፎ ተፈርሞ መሰጠቱ እያረጋገጠ ቼክ ለዋስና መስጠት የወንጀል ተጠያቂነት አያስከትልም ከሚል ድምዳሜ የደረሰው አጠቃላይ የክርክሩ ባሕሪ ያላገናዘበ ነው። ምክንያቱም ተጠሪ ቼክ ማውጣቱ አልካደም ። ቼክ የተሰጣት የግል ተበዳይም በስማቸው የታዘዘ ክፍያ መሆኑን አረጋግጠዋል ። በሌላ በኩል የሚከፈለው የገንዘብ መጠንና ከፋይ ባንክ በግልጽ ተመልክቷል ። ተጠሪ የቼኩ ሕጋዊነት ጥያቄ ባላነሳበት ፤በዋናነት ደግሞ ቼኩ ጽፎ እና ፈርሞ መስጠቱ ባልካደበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤት የሕግ ትርጉም እና ድምዳሜ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 693(1) ሥር የተመለከተው መሰረታዊ የወንጀሉ መቋቋያ ፍሬነገሮች ያላገናዘበ ፤በተጠሪ የተሰጠው ቼክ ሕጋዊነት ባላከራከረበት ተጠሪም ቼኩን መስጠቱ ባልካደበት ጥፋተኛ አይደለም በማለት በነፃ እንዲሰናበት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል። ስለሆነም ተጠሪ በዓቃቤ ሕግ ጠቅሶ ባቀረበው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693(1) ሥር በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 195(2) (ሀ) መሠረት ጥፋተኛ ነው ብለናል።

በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 257881 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 273802 ህዳር 26 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የጸናዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 25121 በነበረው ክርክር የወንጀል ህግ አንቀጽ 693/1/መሰረት ጥፋተኛ ሊባል ይገባል ብለናል፡፡
3. በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 25117 የካቲት 15 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ፀንቷል፡፡
4. በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈፅም አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ተመላሽ ይደረግ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁጥር---156420

ቀን- ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች:- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ ዐ/ሕግ

ተጠሪ፡- አቶ መላቱ ያለዉ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረዉ አመልካች በካፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ የክሱ ይዘት፡- የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቦንጋ ከተማ 03 ቀበሌ ታሕሳስ 02 ቀን 2009 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በሚያሽከረክረዉ ኮድ 3-88132 በሆነዉ ሀይሉክስ ቶዮታ መኪና ላይ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ለመቆጣጠር የወጣዉን ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 36(1) የተመለከተዉን በመተላለፍ ሚች ተማሪ ወርቁ ኮንሰን በኋለኛዉ የመኪና ክፍል አሳፍሮ በማሽከርከር ላይ እያለ ሚች ወድቆ በጭንቅላቱና ጀርባዉ ላይ በደረሰዉ ከባድ ጉዳት ሕይወቱ ያለፈ በመሆኑ በፈጸመዉ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

በስር ፍ/ቤት ተጠሪ የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ክሱን ክዶ በመከራከሩ የአመልካች ምስክሮች ተሰምተዉና የሰነድ ማስረጃ ቀርቦ ተጠሪ በተከሰሰበት አንቀጽ ስር እንዲከላከል ብይን የተሰጠ ሲሆን ተጠሪ የመከላከያ ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ የስር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የተጠሪ ምስክሮች የተመሠከረበትን ያህል አላስተባበሉም በማለት ተጠሪን የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ የጥፋተኝነት ዉሳኔ በመስጠት ተጠሪ በ3 (ሦስት) ዓመት ከ3 (ከሦስት) ወር ጽኑ እስራት እና በብር 2000(ሁለት ሺህ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ተጠሪ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ያቀረበዉን ይግባኝ የተመለከተዉ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ሚች መኪናዉ ሳይቆም ዘሎ እወረዳለሁ ሲል ወድቆ የሞተ በመሆኑና ተጠሪ ሚችን ከላይ በመጫኑ ደንብ መተላለፍ የፈጸመ ቢሆንን ተጠሪ ሚችን ከላይ በመጫኑ ብቻ ለሚች ሞት በቸልተኝነት ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት ተጠሪ በነጻ ሊሰናበት ይገባል በማለት በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ በመሻር በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ የተመለከተዉ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አቅርቦ ካከራከረ በኋላ መርምሮ ዉሳኔዉን በማጽናት ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ተጠሪ መጫን በተከለከለ የመኪና የዉጭ ክፍል ላይ ሚችን እንደጫነዉ በጉዞ ላይ እንዳለ ሚች ወድቆ ጉዳት የደረሰበትና በዚያዉ ምክንያት መሞቱ ተረጋግጧል፡፡ የመንገድ ደህንነትን ለመጠበቅ የወጣዉን ደንብ ቁጥር 208/03 አንቀጽ 36(1) በመርህ ደረጃ በመኪናዉ የዉጭ ክፍል ላይ የሚያሳፍር ሰዉ በማናቸዉም ሁኔታዎች ጉዳት ሊደርስባቸዉ የሚችል መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ መግለጹን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪ ይህን ጥንቃቄ ማድረግ ግዴታ እያለበት ይህንን ክልከላ በመተላለፍ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባዉ ይህን ተላልፎ ሰዉ በመጫኑ የሞት ጉዳት መድረሱ እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪ ነጻ እንዲሰናበት መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለዉሳኔዉ መሠረት ያደረገዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 24 ሲሆን በተሳሳተ ሁኔታ በመገንዘብ ነዉ፡፡ ተጠሪ በመኪናዉ የላይኛዉ ክፍል ላይ ሰዉን በመጫን ዉድቆ ሕይወቱ ሊያልፍ እንደቻለ እየተረጋገጠ የስር ፍ/ቤት በምክንያትና ዉጤት መካከል ግንኙነት የለም ማለቱ ስህተት ነዉ፡፡

የስር ፍ/ቤት ድርጊቱ አደጋ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የወ/ሕ/አንቀጽ 58(3) እና 59 በሚገባ ያላገናዘበ ነዉ፡፡ ምክንያቱም የተጠሪ ድርጊት ጉዳት ይደርሳል ቢል የተከለከለን ድርጊት አይደርስም በሚል ባለማገናዘብ በቸልተኝነት የመኪና የዉጭ ክፍል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ላይ ሟችን በመጫን ወድቆ የሞተ መሆኑ በሚገባ እስከተረጋገጠ ድረስ የሀሳብ ክፍሉ ቸልተኝነት መሆኑ በቀላሉ መረዳት እየተቻለ አደጋ ነዉ መባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ሰዉ ለመጫን ባልተፈቀደ ቦታ ላይ ሕጻኑን ከኃላ ጭኖ ሲያሽከረክር ለመዉደቅ የተጋለጠና የሚከልለዉ ነገር በሌለበት ወድቆ መሞቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ በኃላ በኩል መጫን ቸልተኝነት አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት ከጥፋተኝነትም ሆነ ከቅጣት በነጻ ያሰናበተበትን አግባብነት ከወ/ሕ/አንቀጽ 59 እና ሰበር ሰሚዉ ችሎት በሰ/መ/ቁ 52075 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠርቶ ሊቀርብ ባለመቻሉ በሌለበት ጉዳዩ ከመታየቱም በላይ በዚሁ ችሎት እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ሊቀርብ ባለመቻሉ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡ ተጠሪ ሲያሽከረክረዉ በነበረዉ ፒካፕ ትዮታ መኪና ከኋለኛዉ ክፍል ላይ አሳፍሮ ሲያሽከረክር ሟች ወድቆ መሞቱ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ሟችን ከኋለኛዉ የመኪና አካል አሳፍሮ ያሽከረክር የነበረዉ የትራፊክ ደህንነት ደንብ ቁጥር 208/03 አንቀጽ 36(1) ስር በመኪና የኋለኛ አካል ላይ ሰዉ አሳፍሮ ማሽከርከር የሚከለክለዉን ደንብ በመተላለፍ ጭምር መሆኑ አሻሚ አይደለም፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሟች ላይ ለደረሰዉ የሞት ጉዳት ተጠሪን በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ያደረገ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪን በነጻ ሲያሰናብት የሰጠዉ ምክንያት ሟች ከመኪናዉ ዘሎ በሚወርድበት ጊዜ መዉሰድ ይገባዉ የነበረ ጥንቃቄ ርምጃ ባለመዉሰዱ የደረሰ ሞት እንጂ ተጠሪ የሟችን መሞት ለማስቀረት ማድረግ እያለበት ያላደረገዉ ወይም ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ የተገኘ ዉጤት መሆኑ ያልተረጋገጠ እንዲሁም የሟች ከመኪና ዘሎ መዉረዱ ብቻ እንጂ በተጠሪ በኩል የተፈጸመ ቸልተኝነት የለም በማለት ነዉ፡፡ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ አብይ ጭብጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ተጠሪ ሟችን በሚያሽከረክረዉ መኪና ከኋላ ዉጭ ላይ ጭኖ ሲያሽከረክር ወድቆ የሞተ መሆኑን በተረጋገጠበት ለሟች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሞት ምክንያቱ የተጠሪ ቸልተኝነት አይደለም ተብሎ በነጻ እንዲሰናበት መወሰኑ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በወ/ሕ/አንቀጽ 59(1/ ሀ እና ለ) መሰረት አንድ ሰዉ በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር ፈጽሟል የሚባለዉ ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን ወይም ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ፣ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈጸመ እንደሆነ ነዉ፡፡ በተለይ ከአደራጊዉ የግል ሁኔታ አንጻር ሲታይ ሊደረጉ ይገባል ተብሎ በአግባቡ የሚጠበቁበትን ጥንቃቄዎች ያላደረገ እንደሆነ ቸልተኝነት አለዉ እንደሚባል ተመልክቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ሟችን ከሚያሽከረክረዉ ተሽከርካሪ የኋለኛ የዉጭ ክፍል ላይ አሳፍሮ ሲያሽከረክር ሟች ከተሽከርካሪዉ ወድቆ ሕይወቱ ማለፉ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ሟችን አሳፍሮበት ይጓዝ የነበረዉ ክፍል ላይ ሰዉ አሳፍሮ ማሽከርከር በትራፊክ ደህንነት ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 36(1) የተከለከለ ተግባር መሆኑ ተደንግጓል፡፡ የትራፊክ ደህንነት ደንቡ ይህን ተግባር የከለከለበት ዋናዉ ምክንያት ለተሳፋሪ ደህንነት አደገኛ በመሆኑ በሰዉ ሕይወት ወይም አካል ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል መሆኑ እሙን ነዉ፡፡ ተጠሪ የአሽከርካሪነት ሙያ ያለዉ ሰዉ እንደመሆኑ መጠን ይህን ደንብ ተላልፎ ሰዉን ከኋላ መጫን አደገኛና ተገቢዉ ጥንቃቄ ሊያደርግበት የሚገባዉ ሆኖ እያለ ሟችን በደንብ በተከለከለ የተሽከርካሪዉ አካል ላይ አሳፍሮ ጭኖ ሲሄድ ሟች ወድቆ ለደረሰበት ጉዳት ተጠሪ በቸልተኝነት ተጠያቂ ነዉ፡፡ ሟች ለመዉረድ ሲል መዉደቁ ወይም ለመዉረድ ሲል ዘሎ መዉደቁ የተጠሪን ቸልተኝነት አያስቀረዉም፡፡ ምክንያቱም ሟች ለተሽከርካሪ ያለዉ ግንዛቤ አናሳ ሊሆን ከመቻሉ አንጻር ተሽከርካሪ በጉዞ ላይ እያለ መዉረድ የሚያስከትለዉን ጉዳት ላይገነዘብ ይችላል፡፡ ደንቡ በተጠሪ ላይ ወይም በአሽከርካሪዉ ላይ በዋናነት ግዴታ የጣለዉ ሰዎች መንገዛቸዉን እንጂ ከላይ መሳፈር ሊያስከትልባቸዉ የሚችለዉን ጉዳት በአግባቡ ላይገነዘቡ ስለሚችሉ ነዉ፡፡ ሟች ተሽከርካሪዉ በጉዞ ላይ መዉረድ ወይም ዘሎ መዉረድ አደገኛ ዉጤት ያለዉ መሆኑን ቢያዉቅና የተሳሳተ ግንዛቤ ባይኖረዉ ኖሮ በጉዞ ላይ ካለ ተሽከርካሪ ዘሎ ባልወረደ ነበር፡፡ እንዲሁም ለሟች ጉዳት ዋናዉ ምክንያት የሟች ከተሽከርካሪዉ መዉረድ ብቻዉን ሳይሆን ተሽከርካሪዉ በጉዞ ላይ መሆኑ ነዉ፡፡ ስለሆነም የሟችን ሞት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ያስከተለዉ በዋናነት ተጠሪ በትራፊክ ደህንነት ደንብ ጭምር አደገኛ ዉጤት እንደሚያስከትል ግንዛቤ ዉስጥ ገብቶ በተከለከለ ስፍራ ወይም የመኪናዉ የኃላ የዉጭኛ አካል ላይ ሚችን አሳፍሮ በመሄድ በፈጸመዉ ቸልተኝነት ምክንያት ሚች ለመዉረድ ሲል ወድቆ በመሞቱ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ ጥፋተኛ ማለቱ ተገቢ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጥፋተኝነት ዉሳኔዉን በመሻር ተጠሪን በነጻ ማሰናበቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) በተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ወንጀሉ ደረጃ የወጣለት በመሆኑ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ደረጃ 1 እርከን 21 ተወስዶ የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ባለመኖሩ በተጠሪ በኩል በቀረቡት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ዉስጥ 4 ምክንያቶችን በመዉሰድና 4 እርከን በመቀነስ እርከን 17 ስር የ3 ዓመት ከ3 ወር የጽኑ አስራት ቅጣትና በገንዘብ የብር 2,000 መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመገኘቱ እንዳለ ተወስኗል፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ በትራፊክ ደህንነት ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 36(1) የተመለከተዉን ግልጽ ክልከላ በመተላለፍ በተሽከርካሪዉ የኃላ የዉጭ አካል ላይ ሚችን አሳፍሮ ሲያሽከረክር ሚች ለመዉረድ ሲል ወድቆ በደረሰበት ጉዳት የሞተ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪን በነጻ ማሰናበቱ የወ/ሕ/አንቀጽ 24፣ 59 እና የወ/ሕ/አንቀጽ 543(3) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻርና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ሊጸና የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ 049653 ግንቦት 02 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 05297 ጥር 30 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ የሰጠዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ተሽሯል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

2. የከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14375 የካቲት 02 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ እና ቅጣት ዉሳኔ ጸንቷል።
3. የዞኑ ፖሊስ መምሪያ ተጠሪን በማፈላለግ ይዞ ለሚመለከተዉ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብና ማረሚያ ቤቱም ተጠሪ ከዚህ በፊት የታሰረዉ መታሰቡ ሳይቀር የተወሰነበትን የ3(ሦስት) ዓመት ከ3(ሦስት) ወር የጽኑ እስራትና የብር 2000(ሁለት ሺህ) የገንዘብ መቀጮ ቅጣት እንዲያስፈጽም ታዟል። ይጻፍ። መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ሀብታሙ ደስታ - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በተሽከርካሪ በቸልተኝነት ሰዉ የመግደል፣ በሰዉ አካል ላይ ጉዳት ማድረስና በመገናኛና በማጓጓዣ ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀሎችን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረዉ በአፋር ክልል አዉሲረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ አመልካች ላይ ቀርበዉ የነበሩ ክሶች 3 ሲሆኑ 1ኛ ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቀን 14/04/2009 ዓ.ም ከቀኑ 9፡45 ሰዓት ላይ ኤሊዳር ከተማ ለመግባት 6 ኪ.ሜትር ሲቀረዉ ኮድ 3-78217 ኢት የሆነ የመከላከያ ደብል ጋቢና ኒሳን መኪና እያሽከረከረ በቸልተኝነት በተቃራኒ አቅጣጫ ሲጓዝ ከነበረ ኮድ 3-86206 ኢት የሆነ ገልባጭ መኪና ጋር በመጋጨቱ ጭኗቸዉ ከነበሩ ሰዎች መካከል ኢንጅነር ሀጎስ ገ/ጊዮርጊስ የተባለዉ ሕይወቱ በማለፉ በፈጸመዉ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡ 2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) የተመለከተዉን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በፈጸመዉ ግጭት በግል ተበዳይ ሂሩት ሰለሞን ላይ የላይኛዉና የታችኛዉ መንጋጋ አጥንት ስብራትና በታችኛዉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መንጋጋ በግራ በኩል ያለዉ አንድ ጥርሷ በመዉለቁ በፈጸመዉ ታስቦ በሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡ 3ኛ ክስ ደግሞ የወ/ሕ/አንቀጽ 506(1/መ) የተመለከተዉን በመተላለፍ በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ ባደረሰዉ ግጭት የሚያሽከረክረዉ ተሽከርካሪ ጋቢና ሙሉ በሙሉ በመጨፍለቁ፣ ቻንሲዉ በመታጠፉና የሞተር ሳፖርቶ በመቆረጡ እንዲሁም በሰ.ቁ 3-86206 ኢት መኪና ላይም አሻንታሪ ቦሊስትራ፣ ስፕሪይ ጋቢናና ራዲያተር መሰበርና በር መታጠፍ በድምሩ ብር 1,100,000 ግምት ያለዉ የንብረት ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ መገናኛዎችና መንገዳገዶች ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ የወንጀል ድርጊቶቹን አለመፈጸሙን ገልጾ ጥፋተኝነቱን ክዶ የተከራከረ ሲሆን የዐ/ሕግ ማስረጃዎች ተሰምተዉ አመልካች እንዲከላከል ብይን የተሰጠ ሲሆን አመልካች የመከላከያ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ አመልካችን በተከሰሱበት ሦስቱም ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ በ7(ሰባት) ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 500 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝቶ ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ በ3ኛ ክስ ጉዳቱ ሆን ተብሎ የደረሰ ሳይሆን በቸልተኝነት መሆኑን በመግለጽ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የሕግ ድንጋጌ ከወ/ሕ/አንቀጽ 506 ወደ አንቀጽ 505(3) በመለወጥ ቅጣቱን በማሻሻል አመልካች በ5 ዓመት ከ1 ወር እስራት እና በብር 1,000 እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህንኑ ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 61(3) አንጻር በአንድ ቸልተኝነት በተፈጸመ ድርጊት በሦስት ተደራራቢ ክስ ጥፋተኛ መደረጌ ተገቢ አይደለም፡፡ በ1ኛ ክስ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል በሚል በወ/ሕ/አንቀጽ 543(2) ስር ጥፋተኛ ተብዬ በተመሳሳይ ድርጊት ለደረሰ የአካል ጉዳት የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) ስር ሆን ብሎ የአካል ጉዳት በማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ መባሌ ተገቢ አይደለም፡፡ እንዲሁም በወ/ሕ/አንቀጽ 23(2) እና 57 መሠረት ወንጀሎችን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች ጋር ተገናዝቦ ተገቢዉ ትርጉም ተሰጥቶት ዉሳኔዉ ይሻርልኝ፡፡ ቅጣቱም ቢሆን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ተደርጎ ያልተወሰነ በመሆኑ ቅጣቱ ቀልሎ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲወሰንና የሚወሰነዉ ቅጣትም እስከአሁን የፈጸምኩት ግምት ዉስጥ ገብቶ በገደብ እንዲሆንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የቀረበዉ ክስ መኪና በቸልተኝነት በማሽከርከር ጉዳት ማድረስ ሆኖ ሳለ በ2ኛ ክስ በወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) ስር ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነበት አግባብ ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ያቀረበዉ መልስ፡- አመልካች በቀረበበት ሦስት ክሶች የተጠቀሰዉን ጉዳት ያደረሰዉ በአንድ የቸልተኝነት ድርጊት ቢሆንም በሕግ ጥበቃ በሚደረግላቸዉ ሦስት የተለያዩ መብቶች ላይ የተፈጸመ በመሆኑ በተደራራቢ ክስ ጥፋተኛ መደረጉ ተገቢ ነዉ፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት በ3ኛ ክስ አንቀጹን ለዉጦ ጥፋተኛ ማለቱም ሆነ ቅጣት መወሰኑ ተገቢ ነዉ፡፡ በቅጣት አሰላል ላይ የተፈጸመ ስህተት የሌለ ከመሆኑም በላይ ቅጣት የሚገደብ ከሆነ ለማህበረሰቡ አስተማሪ ሊሆን ስለማይችል የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ይደረግልን የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ መርምረናል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች የሚያሽከረክረዉን ተሽከርካሪ በቸልተኝነት በማሽከርከር በፈጸመዉ ግጭት አንድ ሰዉ የሞተ ሲሆን አንድ ሰዉ ላይ ደግሞ ከባድ የአካል ጉዳት ከመድረሱም በላይ በተጋጩት ሁለት መኪኖች ላይ ጉዳት መድረሱ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉም ሆነ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች የአንድ ሰዉ ሕይወት እንዲያልፍ ያደረገዉም ሆነ ከባድ የአካል ጉዳት በሰዉ ላይ ያደረሰዉ በቸልተኝነት በማሽከርከር በፈጸመዉ ግጭት መሆኑ አሻሚ ባልሆነበት አመልካች በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) የተመለከተዉን በመተላለፍ ሆን ተብሎ በተፈጸመ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ነዉ፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በመሠረቱ አንድ ተከሳሽ በአንድ ቸልተኝነትና በአንድ ድርጊት በደረሱ ጉዳቶች በተደራራቢ ወንጀሎች ሲከሰስ ሌላ የተለየ ሀሳብና ድርጊት መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ አንዱን በቸልተኝነት ሌላውን ደግሞ ሆን ተብሎ ታስቦ በተፈጸመ ወንጀል ጥፋተኛ የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ተሽከርካሪዉን በቸልተኝነት በማሽከርከር በፈጸመዉ ግጭት በ1ኛ ክስ የተመለከተዉ የሰዉ ሕይወት በማለፉ የወ/ሕ/አንቀጽ 543(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቸልተኝነት በፈጸመዉ ግድያ ከተከሰሰና ጥፋተኛ ከተባለ በተመሳሳይ ቸልተኝነትና ድርጊት በ2ኛ ክስ የተገለጸዉ ከባድ የአካል ጉዳት ሲደርስ ደግሞ የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) የተመለከተዉን በመተላለፍ ሆን ተብሎ በተፈጸመ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በ2ኛ ክስ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) የተመለከተዉን በመተላለፍ ሆን ተብሎ በተፈጸመ ከባድ የአካል ጉዳት ሳይሆን የወ/ሕ/አንቀጽ 559(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቸልተኝነት በተፈጸመ የአካል ጉዳት ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች በ2ኛ ክስ በስር ፍ/ቤት ጥፋተኛ የተባለበት የሕግ አንቀጽ በወ/መ/ሕ/ስ/ቁ 113(2) መሠረት ተለዉጦና ተሻሽሎ በወ/ሕ/አንቀጽ 559(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላዉ ቅጣትን የተመለከተዉ ሲሆን ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመዉ ሲገኙ ቅጣት ሊወሰን የሚገባዉ በተሻሻለዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 22(1/ሀ) መሠረት ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ከተያዘ በኋላ እነዚህን በመደመር ድምሩ የቅጣት መጠን የሚያርፍበትን ዝቅተኛ የቅጣት እርከን በመለየት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የስር ፍ/ቤቶች ለእያንዳንዱ ወንጀል ቅጣቱን ጨርሰዉ ካሰሉ በኃላ በመደመር የወሰኑ መሆኑ ስህተት ነዉ፡፡ በመሆኑም ቅጣቱን እንደገና ማስላቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁም መሠረት በ1ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 543(2) ተላልፏል ተብሎ ጥፋተኛ ለተባለበት በስር ፍ/ቤት የተያዘዉ ደረጃ 4 እርከን 16 ሆኖ የ3 ዓመት ከ2 ወር እስራት መነሻ ቅጣት እንዳለ ይዘናል፡፡ እንዲሁም በ3ኛ ክስ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት የ1 ወር እስራት መነሻ ቅጣት የያዘዉን እንዳለ ወስደናል፡፡ 2ኛ ክስን በተመለከተ የወ/ሕ/አንቀጽ 559(2) ደረጃ 2 እርከን 8 ስር መነሻዉን 1 ዓመት ከ2 ወር እስራት ተይዟል፡፡ ለሦስቱም ክሶች የተያዘዉ መነሻ ቅጣት ሲደመር ዉጤቱ 4 ዓመት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከ5 ወር ይመጣል፡፡ ይህም እርከን 19 ላይ ያርፋል፡፡ በአመልካች ላይ የተያዘ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፡፡ አራት የቅጣት ማቅለያዎች በስር ፍ/ቤት የተያዙለት በመሆኑ እንዳሉ ወስደን 4 እርከን ሲቀነስ እርከን 15 ላይ ያርፋል፡፡ ፍቅድ ስልጣኑ ከ2 ዓመት ከ9 ወር እስከ 3 ዓመት ከ3 ወር በመሆኑ አመልካች ቅጣቱ ተሻሽሎለት በመነሻው በ2 ዓመት ከ9 ወር እስራት ሊቀጣ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት አመልካች ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰው በቸልተኝነት መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት በ2ኛ ክስ የወ/ሕ/አንቀጽ 555(ሀ) ተላልፏል ተብሎ ሆን ተብሎ በተፈጸመ ከባድ ጉዳት የማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ መባሉም ሆነ ቅጣት ተሰልቶ የተወሰነው የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 22(1/ሀ) የተመለከተውን ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዉሲረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነሐሴ 03 ቀን 2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 4390 ታሕሳስ 11 ቀን 2010 ዓ.ም ተሻሽሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በ2ኛ ክስ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉ የወ/ሕ/አንቀጽ 559(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ በቸልተኝነት ከባድ አካል ጉዳት በማድረስ ወንጀል ነዉ ተብሎ ተሻሽሏል፡፡
3. በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ተወስኖ የነበረዉ የ5 ዓመት ከ1 ወር እስራት እና የብር 1000 የገንዘብ መቀጮ ተሻሽሎ አመልካች በ2(ሁለት) ዓመት ከ9(ዘጠኝ) ወር እስራትና በብር 1000(አንድ ሺህ) እንዲቀጣ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡ በዚሁ ቅጣት መሠረት እንዲያስፈጽም አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡
4. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::

አ/ጐ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ/155789

ጥቅምት 21 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች ፡ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- የፌዴራል ጠ/አቃቤ ህግ

ተጠሪ፡- ነቢላ አህመድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የወንጀል ክስ የሚሻሻልበት አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች ተጠሪ ላይ ያቀረበዉ ክስ 1ኛ/የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2/ሀ በመተላለፍ ድንጋይ ወርዉራ የግል ተበዳይ አመለወርቅ ታደሰ ደረቷንና የቀኝ እግሯን በመምታት ቀላል የአካል ጉዳት በማደረስ ፣2ኛ/ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 615 በመተላለፍ በአንደኛዉ ክስ የተጠቀሰችዉን የግል ተበዳይ አስነዋሪ ስድብ ሰደበቻት በማለት ተደራራቢ ክስ ያቀረባበት ሲሆን ተጠሪ የእምነት ክደት ቃል ከመስጠቷ በፊት መቃወሚያ በሚል ምክንያት በአንደኛዉ ክስ ላይ ድንጋጌዉና የተፈጸመዉ ድርጊት አይጣጣምም በማለቷ የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንኑ መቃወሚያ በመመርኮዝ አቃቤ ህግ 1ኛዉን ክስ አንቀጽ 556/2/ሀ ወደ አንቀጽ 560/1/ አሻሽሎ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ አቃቤ ህግ የተሻሻለ ክስ ባለማቅረቡ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/122/3/ መሰረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አቃቤ ህግ ይህንኑ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ይግባኝ ቅሬታ ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ቀርቦ በዚህ ላይ ሲሆን የአቃቤ ህግ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት የወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2/ሀ እና 560/1/ ማቋቋሚያ ፍሬነገሮችን በአግባቡ ሳያገናዝብ የሰጠዉ ትእዛዝ ተገቢ ባለመሆኑ እንዲታረም የሚል ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክሱ ካልተሸሻለ አላይም በማለት የስር ፍርድ ቤት መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢነት ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲትሰጥ ተደርጓል፡፡ተጠሪም የተፈጸመዉ ድርጊት የእጅ እልፊት ነዉ በሚል የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክራለች፡፡አቃቤ ህግ ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ፍርድ ቤት ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ የሚሰጠዉ በምን አግባብ ነዉ? ህጋዊ ዉጤቱስ ምንድነዉ? የሚለዉ መታየት ያለበት ነጥብ ሆኖ አግኝተናል፡፡ የወንጀል ክስ ማመልከቻ አዘጋጃጀት አስመልክቶ ይዙቱና ዓይነቱ በምን አኳኋን እና ዝርዝር ሊኖረዉ እንደሚገባ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት አንቀጽ 111 እና 112 ላይ ተመልክቷል፡፡ከነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ክሱ በዝርዝር እንዲገልጽ ከሚጠበቅባቸዉ መሰረታዊ ፍሬነገሮች ዉስጥ በክሱ የተጠቀሰዉ የወንጀል ህግ ድንጋጌ እና ተከሳሹ የፈጸመዉ የወንጀል ተግባር የክሱ ፍሬነገር ከህጉ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንዳለበት ነዉ፡፡ የክሱ አዘገጃጀትና ዝርዝር ይዘት ላይ መገለጽ የሚገባዉ መሰረታዊ ነገር ባለመገለጹ ተከሳሹን ያሳሳተዉ እንደሆነ ወይም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የማይቻል ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም ማመልከቻ በቀረበለት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ፣ እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል በወ/መ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 118 እና 119/1/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ ስለሆነም ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ የሚሰጠዉ በክስ ማመልከቻ ፎርም ወይም በክሱ ማመልከቻ ላይ ስለወንጀሉ አስፈላጊ ዝርዝር ዉስጥ ስህተት ሲገኝ ወይም ሳይጠቀስ ሲቀርና ይህም

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መሰረታዊ ነገር ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ስለመሆኑ እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ ሰጥቶ ኣቃቤ ህግ የተሻሻለ ክስ አዘጋጅቶ ያላቀረበ እንደሆነ ተከሳሹ ለጊዜዉ እንደሚለቀቅ የወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/122/3/ ድንጋጌ ይገልጻል፡፡ ስለሆነም በፍ/ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ክሱ ተሻሽሎ ያልቀረበ እንደሆነ ዉጤቱ መዝገቡን ለጊዜዉ በመዝጋት ተከሳሹን መልቀቅ እንደሆነ ህጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ በ1ኛዉ ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2/ሀ ተጠቅሶ በክሱ ዝርዝር ላይ ደግሞ ተጠሪ በሰዉ አካልና ጤና ላይ ጉዳት ለማድረስ አስባ የግል ተበዳይ አመለቀወርቅ ታደሰ ላይ ድንጋይ ወርዉራ ደረቷንና የቀኝ እግሯን በመምታት የህመም ስሜት አንዲሰማት በማድረግ ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈጽማለች የሚል ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ይህ ድንጋጌ ወደ 560/1/ ተለዉጦ ክሱ ተሻሽሎ መቅረብ አለበት በማለት ትእዛዝ የሰጠዉ በኣቃቤ ህግ በኩል የቀረበዉ ክስ ዝርዝር ስህተት ስላለበት ወይም መጠቀስ ያለበት መሰረታዊ የክሱ ፍሬነገር ባለመጠቀሱ ሳይሆን ተፈጸመ የተባለዉ ድርጊት ክስ የቀረበበትን ድንጋጌ አያቋቁምም ከሚል መነሻ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሰረቱ ክስ እንዲሻሻል የሚደረግበት ምክንያት እና አቃቤ ህግ ያቀረበዉን ክስ በማስረጃ አረጋግጧል ወይስ አላረጋገጠም? በአቃቤ ህግ ማስረጃ የተረጋገጠዉ የድርጊቱ አፈጻጸምና ዉጤቱ በየትኛዉ የህግ ድንጋጌ የሚሸፈን ነዉ? የሚለዉ ጉዳይ በየራሱ ተለያይቶ የሚታይ ስለመሆኑ ከወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/119 እና 113/2/ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የክስ ማመልከቻ እንዲሻሻል የሚደረገዉ ከላይ በተገለጸዉ አግባብ በክሱ ዝርዝር ላይ መገለጽ የሚገባዉ መሰረታዊ ጉዳይ ሳይገለጽ የቀረ እንደሆነ ወይም ደግሞ ያለአግባብ የተገለጸዉ ነገር ተከሳሹን የሚያሳስት ነዉ ተብሎ ሲታሰብ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል አቃቤ ህግ በክሱ መሰረት የድርጊቱን ፍሬነገር በማስረጃ ማስረዳት ወይም አለማስረዳት እና ዉጤቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ድምዳሜ ላይ ሊደርስ የሚገባዉ የአቃቤ ህግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ እንደሆነ ከወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.141 መገንዘብ አዳጋች አይደለም፡፡ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 112 ላይ እንደተገለጸዉ ደግሞ የክስ ማመልከቻ ስለወንጀሉና ስለሁኔታዉ የሚሰጠዉ ዝርዝር መግለጫ ወንጀለኛዉ የፈጸመዉ ተግባር ወንጀል ከሚያደርገዉ ህግ አነጋገር ጋራ በጣም የተቀራረበ መሆን አለበት ሲል ህግ አዉጪዉ በጥንቃቄ የተመለከተዉ የተፈጸመዉ ድርጊት የተጠቀሰዉን ድንጋጌ ማቋቋሚያ ፍሬነገር ማሟላት አለማሟላት ፍርድ ቤቱ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በማስረጃ የሚያረጋግጠዉ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ለዚህም ነዉ አቃቤ ህግ በክሱ በገለጸዉ ልክ ሳይሆን ከዚያ ባነሰ ሁኔታ ወይም ክስ ባይቀርብበትም በአማራጭ ክስ ሊቀርብበት የሚችል ድንጋጌ የሚሸፈን የወንጀል ፍሬነገር መፈጸሙ በማስረጃ በተረጋገጠ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነዉ ወደሚለዉ ድንጋጌ ለመለወጥ እንዲችል በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/113/2/ ስልጣን የተሰጠዉ፡፡ ከዚህም በሻገር አቃቤ ህግ እንደክሱ አቀራረብ በማስረጃ ማስረዳት ካልቻለ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን በነጻ የማሰናበት ስልጣን በህጉ የተሰጠዉ ነዉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ ላይ 1ኛዉ ክስ የተጠቀሰዉ ድንጋጌ እና በክሱ ዝርዝር የተገለጸዉ ፍሬነገር ላይ ጉድለት ወይም ስህተት ስለመኖሩ አልተገለጸም ፡፡ይልቁንም በግል ተበዳይ ላይ የደረሰዉ ጉዳት መጠነኛ ነዉ የሚል ምክንያት ብቻ ነዉ ፡፡በድርጊቱ ምክንያት የግል ተበዳይ ላይ የደረሰዉ ጉዳት መጠን የሚረጋገጠዉ በማስረጃ ስለሚሆን ከወዲሁ ማስረጃ ሳይሰማ ድምዳሜ ላይ መድረሱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም አመልካች በክሱ ማመልከቻ ላይ ጠቅሶ ያቀረበዉ የወንጀል ህጉ ድንጋጌና የክሱ ፍሬነገር ዝርዝር ላይ በስህተት የተጠቀሰ ወይም ሳይጠቀስ የታለፈ መሠረታዊ ነገር መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ የተፈጸመዉ ድርጊትና አግባብነት ያለዉ ድንጋጌ የትኛዉ ነዉ የሚለዉ የክሱ ማቋቋሚያ ፍሬነገር መሟላት አለመሟላት ማስረጃ ተሰምቶ የሚለይና ፍርድ ቤቱ በህጉ አግባብ ዉሳኔ የሚሰጥበት ሆኖ እያለ ከወዲሁ አንቀጽ ካልተለወጠ በሚል ምክንያት ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ መስጠትና ይህ ካልተፈጸመ በሚል የክሱን መዝገብ መዝጋቱ ክስ እንዲሻሻል የሚደረግብትን ህጋዊ ምክንያት እና አላማ ያገናዘበ ሆኖ አላገኘንም፡፡ከዚህም ባሻገር ተጠሪ ላይ የቀረበዉ ክስ ሁለት ሆኖ እያለ 1ኛዉ ክስ በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ተሻሽሎ ባለመቅረቡ የሚዘጋ ቢሆን እንኳን ሁለተኛዉ ክስ ላይ ዉሳኔ ላለመስጠት ፍርድ ቤቱ ምንም ዓይነት ህጋዊ ምክንያት ሳይኖረዉ ማለፉም የክርክር አመራር ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉ ሳ ኔ

1ኛ/የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/112647 ላይ በ24/06/09 ዓ.ም እና በ08/07/09 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/194971 በ02/04/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/195/2/ሀ መሰረት ተሰርዟል፡፡

2ኛ/የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ክርክሩን ሰምቶ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በወ/መ/ስ/ስ ህግ ቁ/ 195/2/ሀ መሰረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ.156999

ጥቅምት 27/2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ከበደ ተሠራ ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ ዮሐንስ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የጉዳዩ መነሻ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በ25 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ተወስኖ ቅጣቱን በመፈጸም ላይ የሚገኙ መሆኑን ገልጸዉ ጥፋተኛ የተባሉበትን ሕግ የተካዉ የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቅጣቱን አሻሽሎ የወጣ በመሆኑ ከሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 22(2)፣ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 6(9) እና ከአዲሱ አዋጅ አኳያ ታይቶ ቅጣቱ እንዲቀነስላቸዉ ማመልከታቸዉ ነዉ፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ በአመልካች ላይ በመጨረሻ የቅጣት ዉሳኔ የሰጠዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለእያንዳንዱ ጥፋት መነሻ ቅጣት በመያዝ ዉሳኔ ባለማስተላለፉ ይህ ፍቤት ቅጣቱን በአዲሱ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት እንደገና ለማስላት መቸገሩን ገልጾ አመልካች አቤቱታዉን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ መስተናገድ ይኖርባቸዋል በማለት በአብላጫ ድምጽ አቤቱታዉን ባለመቀበል ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙ ያስቀርባል በማለት በክርክር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሂደት ላይ እያለ አመልካች በይቅርታ በመለቀቃቸዉ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ሆኖም ለአመልካች የተሰጠዉ ይቅርታ በስህተት ነዉ ተብሎ በመሠረዙና አመልካች ወደ ማረሚያ ቤት የተመለሱ በመሆኑ የተዘጋዉ መዝገብ ተከፍቶ እንዲንቀሳቀስ አመልካች ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በአመልካች በአቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጥበት የተደረገ ሲሆን አመልካች በራሳቸዉ የተዉትን ይግባኝ መልሰዉ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ አይችሉም፡፡ አመልካች የይግባኝ ቅሬታዉ መሰረዙን ካወቁና ወደ እስር ቤት ከተመለሱ ከ9 ወር በላይ የሆነዉ በመሆኑ አመልካች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ያቀረቡት ምክንያት በቂና አሳማኝ ባለመሆኑ ጥያቄዉ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ለሁሉም ጉዳዮች የጊዜ ገደብና በቂ ምክንያት ያለዉ መሆኑ ሲታይ የተዘጋዉ መዝገብ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ በጊዜ ገደቡና በበቂ ምክንያት ተደግፎ ሊቀርብ የሚገባዉ በመሆኑ አመልካች መዝገቡ ከተዘጋ ከ8 ወር በላይ ቆይቶ የተዘጋዉ መዝገብ ይንቀሳቀስልኝ በማለት ያቀረበዉ ጥያቄ በቂ ምክንያት በሌለዉ ሁኔታ የቀረበ በመሆኑ ተገቢነት የለዉም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡
የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በትዕዛዙ ላይ እንዳሰፈረዉ በዚህ አግባብ የተዘጋ መዝገብ በምን ያህል ጊዜ መከፈት እንዳለበት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ አመልካች ይቅርታዉ ከተሰረዘባቸዉ በኃላ ያለአግባብ የተሰረዘባቸዉ መሆኑን በመጥቀስ የይቅርታ አዋጁ ባስቀመጠዉ አግባብ አቤቱታ ለሚመለከተዉ አቅርበዉ ዉጤቱን ሲጠባበቁ ብዙ ጊዜ ወስዶባቸዋል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት አካል ፈጥኖ መልስ ሰጥቷቸዉ ቢሆን ኖሮ የይግባኙ መዝገብ እንዲንቀሳቀስ ወዲያዉኑ ማመልከት ይችሉ ነበር፡፡ የሥነ-ሥርዓት ሕግ በራሱ ግብ ካለመሆኑም በላይ በጭፍጫፊ የሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች መሠረታዊ የሆነ የተከሳሽ መብት ሊነካ አይገባም፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ የፈጸመዉ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሮ ይግባኙን ተመልክቶ እንዲወስን ይመለስለት የሚል ነዉ፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 96 እና 97(3)ን ተላልፈዉ ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ከተላለፈባቸዉ በኃላ ጥፋተኛ የተባሉበት አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 ስለተሻሻለ በወ/ሕ/አንቀጽ 6 እና 9(1) እንዲሁም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2) መሠረት የተወሰነባቸዉ ቅጣት እንዲሻሻልላቸዉ ለስር ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዉ ዉድቅ ሲደረግባቸዉ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዉ በመታዬት ላይ እያለ አመልካችን መንግስት በይቅርታ የፈታቸዉ በመሆኑ የይግባኝ መዝገቡ እንዲዘጋላቸዉ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ከተዘጋ በኃላ መንግስት ለአመልካች ሰጥቶ የነበረዉን ይቅርታ በማንሳቱ እና አመልካች ወደ እስር በመግባታቸዉ ምክንያት የተዘጋዉ የይግባኝ መዝገብ ተከፍቶ እንዲታይላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ ይህን የሚከለክል ግልጽ ሕግ መኖሩ ሳይገለጽ አቤቱታዉ ዉድቅ የተደረገበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች መዝገቡን ያስዘጉት ይቅርታ ስለተደረገላቸዉ ሲሆን በሳምንት ዉስጥ ይቅርታዉ በስህተት የተሰጠ መሆኑ ተገልጾ ወደ እስር እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ አመልካች ይቅርታዉ መሰረዙን ካወቁ ከ8 ወር በኃላ አቤቱታ ሊያቀርቡ የቻሉበት ምክንያት ስለመኖሩ አላቀረቡም፡፡ አመልካች በወ/ሕ/አንቀጽ 6፣ 9(1) እና በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 22(2) የተቀመጠዉን መብት ማስጠበቅ የሚችሉት በስነ-ስርዓት ሕጉ የተቀመጠዉን መርህ ተከትሎ አቤቱታ በስርዓቱ ሲቀርብ ነዉ፡፡ የአመልካች አቤቱታ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ዉስጥ ያልቀረበ በመሆኑ አቤቱታዉ ተቀባይነት ማጣቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸዉ ላይ ይቅርታዉ ቀሪ መደረጉን እንዳወቁ መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ያላመለከቱት በይቅርታ አዋጁ መሠረት አቤቱታ ለሚመለከተዉ አካል አቅርበዉ ዉጤቱን ሲጠባበቁ መሆኑን ቢገልጹም በስር ያልተነሳ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለሆነም በስር የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ቀደም ብሎ ጥፋተኛ የተባለበትን ሕግ የተካዉ አዲሱ አዋጅ ለጥፋቱ የተቀመጠዉን ቅጣት አሻሽሎ የወጣ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2) መሰረት ቅጣቱ አዲስ በወጣዉ አዋጅ ድንጋጌ አግባብ እንደገና እንዲሰላለት ነዉ፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታዉን ተቀብሎ ከመረመረ በኃላ ተፈጻሚ በመሆን ላይ ያለዉን ቅጣት የወሰነዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቅጣቱን ሲወስን መነሻ ቅጣት በመያዝ ባለማስላቱ አዲሱን ሕግ ተፈጻሚ ለማድረግ እንደሚችገር ገልጾ አመልካች አቤቱታዉን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዉ መስተናገድ እንዳለባቸዉ በመጥቀስ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ያቀረቡት ይግባኝ ያስቀርባል ተብሎ በመታየት ላይ ባለበት ወቅት አመልካች በይቅርታ በመለቀቃቸዉ የጉዳዩ መታየት አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ይቅርታዉን የሰጠዉ አካል ይቅርታዉ በስህተት የተሰጠ መሆኑን በመግለጽ ይቅርታዉን በማንሳቱና አመልካች ቅጣቱን መፈጸም እንዲጀምሩ ከተደረገ ከ8 ወር በኃላ አመልካች የተዘጋዉ መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸዉ ቢጠይቁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዘግይቶ የቀረበ አቤቱታ ነዉ በማለት ሳይቀበላቸዉ ቀርቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች መዝገቡ እንደገና ተከፍቶ እንዲንቀሳቀስላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ ከ8 ወር በላይ ዘግይቶ የቀረበ ነዉ በማለት ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉን ቀጥለን እንመልከት፡፡

በመሠረቱ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ ለይግባኝ ማቅረቢያና ተያያዥ ጉዳዮች የጊዜ ገደብ ቢያስቀምጥም በመታየት ላይ ያለ መዝገብ መዘጋቱ አስፈላጊ ሆኖ ከተዘጋ በኃላ እንደገና መከፈቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በምን ያህል ጊዜ ዉስጥ አቤቱታ ሊቀርብበት እንደሚገባ በሕግ የጊዜ ገደብ አልተቀመጠም፡፡ ይህ በሚሆንበት ወቅት የጊዜ ገደቡ የሚወሰነዉ የጉዳዩን ሁኔታዎችና የአቤቱታዉን ዓይነት በመመልከት እንጂ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ የቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ አይደለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ መዝገቡ እንዲዘጋ ምክንያት የሆነዉ የአመልካች ጥፋት ወይም ይግባኙን አለመፈለግ ሳይሆን ይቅርታዉን የሰጠዉ አካል የፈጸመዉ ስህተት ነዉ፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሁም የተዘጋዉ መዝገብ ከምን ያህል ጊዜ በኃላ ሊከፈት እንደሚችልና እንደማይችል በግልጽ በሕጉ ያልተደነገገ መሆኑ አመልካች ፈጥኖ አቤቱታዉን እንዳያቀርብ የሚያደርገዉ ከመሆኑ አንጻር በሕጉ ክፍተት ምክንያት አመልካች መብቱን ሊያጣ አይገባም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 22(2)፣ የወ/ሕ/አንቀጽ 6 እና 9(1)ን መሠረት በማድረግ አቤቱታ ያቀረበበት ጉዳይ በባህሪዉ እንደመደበኛ የክርክር ጉዳይ የሚታይ ሳይሆን አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ሊስተናገድ የሚችል ከመሆኑም በላይ አቤቱታዉን በቀጥታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረብ ማስወሰን እንዲችል ከፍተኛዉ ፍ/ቤት በዉሳኔዉ የገለጸበት ከመሆኑ አንጻር መዝገቡ እንደገና አይንቀሳቀስም መባሉ ምክንያታዊ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የተዘጋዉ መዝገብ እንዲንቀሳቀስለት የጠየቀበትን አቤቱታ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በግልጽ የጊዜ ገደብ ባልተቀመጠበትና ለመዝገቡ መዘጋትም ዋናዉ ምክንያት የይቅርታ ሰጪዉ አካል ስህተት እንጂ የአመልካች ቸልተኝነት ወይም ይግባኙን አለመፈለጉ ባልሆነበት ሁኔታ የተዘጋዉን መዝገብ ለማንቀሳቀስ አመልካች በቂ ምክንያት አላቀረበም በማለት የሰጠዉ ትዕዛዝ የአመልካችን መብት የሚያጣብብና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 141372 ሚያዚያ 04 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተዘገዉን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ በይግባኙ ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር ተገቢዉን እንዲወስን ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ተመላሽ ይደረግ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ 152038

ሕዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ

ተጠሪ፡- ምንተስኖት ዶሩ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ የተሰጠን የእምነት ቃል የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 665/1 ድንጋጌን በመተላለፍ የስርቆት ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረበውን ክስ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ብሎ ክዶ በመከራከሩ የዓቃቤሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ በዓቃቤሕግ በኩል የቀረቡት ምስክሮች የግል ተበዳይ እና የደረጃ ምስክሮች ሲሆኑ የግል ተበዳይ ተከሳሽን አላውቀውም ድርጊቱን ሲፈጽም አላየሁም ያለ ሲሆን ሌሎቹ ሁለት ምስክሮች የፖሊስ ጣቢያው ባልደረቦች ሆነው ተከሳሽ ለፖሊስ በነጻ ፈቃዱ ቃሉን ሰጥቷል በማለት የመሰከሩ ቢሆንም ምስክሮቹ የሰጡት ቃል በሌላ ገለልተኛ አካል የተሰጠ ቃል ስላልሆነ እና በሌላ ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ምስክርነታቸውን አልተቀበለውም በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት ብይን ሰጥቷል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል። ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ዓቃቤሕግ ክሱን ለማስረዳት ያቀረበው 1ኛ ምስክር ተጠሪ ድርጊቱን ሲፈጽም አላየሁም በማለት የመሰከረ ሲሆን ሌሎቹ ምስክሮች ተጠሪ ለፖሊስ የሰጠውን ቃል ይዘት ለማስረዳት ከመቅረባቸው በቀር ድርጊቱ ሲፈጸም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ያዩ አይደሉም፤ምስክሮቹ ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ለፖሊስ ቃል ሲሰጥ መግለጻቸው ብቻ ለፖሊስ የተሰጠው ቃል በሌላ አግባብነት ባለው ማስረጃ ተደግፏል ማለት አይቻልም፤ለፖሊስ የተሰጠ የተከሳሽነት ቃል ብቻውን በሌላ አግባብ በሆነ ማስረጃ ባልተደገፈበት ሁኔታ የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ለማሳየት በቂ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በማጽናት ወስኗል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ብሎ ክዶ የተከራከረ በመሆኑ አመልካች ምስክሮችን እና ተጠሪው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የተሰጠውን ቃል አቅርቦ አሰምቷል፤የአመልካች ምስክሮች ተጠሪው በነጻ ፈቃዱ ወንጀሉን እንደፈጸመ በዝርዝር ቃሉን የሰጠ እና ወንጀሉ የተፈጸመበትን ቦታ መርቶ ያሳየ መሆኑን በመግለጽ በመሰከሩበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የሰጠውን ቃል የሚደግፍ ማስረጃ ዓቃቤ ሕግ አላቀረበም በማለት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ዓቃቤ ሕግ ባቀረባቸው ምስክሮች ተጠሪ ወንጀሉን መፈጸሙን ለመርማሪ ፖሊስ ቃሉን በፈቃዱ ሲሰጥ በደረጃ ማስረጃነት የነበሩ ፖሊሶች ቀርበው ከማስረዳታቸውም በላይ ወንጀሉን እንዴት እንደፈጸመ መርቶ ሲያሳይ የነበሩ መሆናቸውንም ጭምር አስረድተው ባለበት ሁኔታ ዓቃቤ ሕግ ገለልተኛ በሆነ ሁኔታ አላስረዳም ተብሎ በነጻ የመሰናበቱን አግባብነት ከመሠረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የፖ/ሊስ ባልደረቦች ሲሆኑ ድብደባ የፈጸሙብኝ በመሆኑ በድብዳባ ለፖ/ሊስ የሰጠሁት ቃል ማስረጃ ሊሆንብኝ አይገባም፤ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ቃል ከመስጠቴ በፊት መብት እና ግዴታዬ የተነገረኝ ስለመሆኑ ከፖ/ሊሶች በስተቀር በሌላ ደጋፊ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ክሱን አስረድቷል ሊባል ስለማይችል የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሰጠው የመልስ መልስ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ቃሉን ለፖ/ሊስ ከመስጠቱ በፊት የሚሰጠው ቃል በፍ/ቤት በማስረጃነት እንደሚቀርብበት የተገለጸለት እና ይህንኑ ተገንዝቦ ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ በፊርማው አረጋግጧል፤ተጠሪ ለፖ/ሊስ የሰጠሁት ቃል በተጽእኖ የተገኘ ነው በማለት የሚከራከር ቢሆንም በተጽእኖ ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ የሚያስረዱለት ምስክሮች አስቀርቦ ባላሰማበት ሁኔታ በደፈናው በፖ/ሊሶች የደረጃ ምስክርነት የተሰጠ ነው ሊባል አይችልም፤ምስክር የሆኑት የፖ/ሊስ አባላትም በጣቢያው በተለያየ የስራ መደብ ተመድበው የሚሰሩ እንጂ መርማሪ ፖ/ሊሶች ባልሆኑበት ሁኔታ ገለልተኛ አይደሉም የሚል ግምት መወሰዱ ተገቢ አይደለም በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በመሠረቱ መርማሪ ፖ/ሊስ የተሰራውን ወንጀል በሚያውቅበት ወይም በጥርጣሬ በሚረዳበት ጊዜ ሁሉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ ላይ ስለፖ/ሊስ ምርመራ በተደነገጉት ድንጋጌዎች አግባብ የምርመራ ተግባሩን እንደሚፈጽም ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 22 እና 23 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ማንነቱ እና አድራሻው ከተረጋገጠ በኋላ የተጠረጠረበትን ወንጀል በሚመለከት ቃል ለመስጠት ነጻ እንደሆነ እና ፈቅዶ የሚሰጠው ማንኛውም ቃል በማስረጃነት የሚቀርብ መሆኑ ጠያቂው ፖ/ሊስ ለተጠያቂው ሊነግረው እንደሚገባ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 ይደነግጋል፡፡ መርማሪው ፖ/ሊስ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ከተጠሪጣሪው የሚቀበለው

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቃልም ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረውን ሰው ለመመርመር ዓላማ የሚውል መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወንጀል መፈጸሙን በማወቅ ወይም በመጠርጠር ምርመራ የተጀመረ እንደሆነ ምርመራው ተጠርጣሪው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የሚሰጠውን ቃል መሠረት በማድረግ ብቻ የሚጠናቀቅ ሳይሆን እንደ አስፈላጊነቱም ስለተጠርጣሪው ማንኛውንም ተገቢነት ያለውን ማስረጃ መስጠት የሚችል ምስክር በመመርመር፤የተጠርጣሪውን ቤት በመበርበር ወይም ዕቃ በመያዝ ወይም ተጠርጣሪው ቃሉን ለፍ/ቤት እንዲሰጥ በማድረግ ምርመራው የሚከናወን መሆኑን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 30፤32 እና 35 ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡ ሲሆን በነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ የሚደረገው ምርመራ ዓላማም ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረውን ሰው መመርመር እና ምርመራውን በተገቢው ሁኔታ አከናውኖ ክስ ለማቅረብ ስልጣን ለተሰጠው ዓቃቤ ሕግ ራፖር መላክ እንደሆነ የፖሊስ ምርመራን አስመልክቶ ከተደነገጉት የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ዓቃቤ ሕግ በተጠርጣሪው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል በቂ ምክንያት መኖሩን ተረድቶ ክሱን ያቀረበ እንደሆነ በምርመራ ጊዜ የተገኙ ማስረጃዎች ክሱ በቀረበለት ፍ/ቤት ተመርምረው እና ተመዝነው የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችሉ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች መሆን አለመሆናቸው ውሳኔ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ተከሳሹ የሚሰጠው የእምነት ቃልም ለምርመራ ዓላማ ሲባል በምርመራ ጊዜ የተገኘ ማስረጃ በመሆኑ የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆን አለመሆኑ በፍ/ቤቱ ሊመረመር እና ሊመዘን የሚገባው እንጂ ከወዲሁ ተቀባይነት አለው ተብሎ ድምዳሜ የሚወሰድበት አይደለም፡፡

በያዝነው ጉዳይ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች የግል ተበዳይ እና የደረጃ ምስክር የተባሉ ሌሎች ሁለት ምስክሮች ሲሆኑ የግል ተበዳይ የመኪናው ስፖኪዮ የተሰረቀበት መሆኑን በመግለጽ ከመመስከሩ በቀር ተጠሪ ድርጊቱን ሲፈጽም አይቻለሁ በማለት የሰጠው የምስክርነት ቃል የለም፤ሌሎች ሁለት ምስክሮችም ተጠሪው በነጻ ፍቃዱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ቃሉን ሲሰጥ አይተናል በማለት የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ቢሆንም ምስክሮቹ ያስረዱት ተጠሪ ሰጥቶታል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የተባለውን ያንኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የተሰጠውን ቃል ነው። ምስክሮቹ ወንጀሉ ተፈጽሞበታል በተባለው አካባቢ ያልነበሩ እና ተጠሪ ወንጀሉን ሲፈጽም ያላዩ ከመሆናቸውም ባሻገር ተጠሪ ለፖሊስ ሰጥቶታል ከተባለው ቃል ውጪ ተጠሪ ወንጀሉን እንደፈጸመ የሚያውቁ መሆናቸውን በመግለጽ የሰጡት የምስክርነት ቃል እስከሌለ ድረስ ምስክሮቹ ተጠሪ ወንጀሉን እንደፈጸመ አስረድተዋል ሊባል አይችልም።

በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ የሚሰጠው ቃልም እንደማንኛውም ማስረጃ ተመርምሮ እና ተመዝኖ የቀረበውን ክስ ለማስረዳት የሚችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆን አለመሆኑ በፍ/ቤቱ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው። ተጠሪ ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች ክሱን ያስረዳልኛል በማለት ያቀረበውን ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 ድንጋጌ መሠረት ለፖሊስ ሰጥቶታል የተባለውን ቃል መርምሮ እና መዝኖ ክሱን ለማስረዳት በቂ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎታል። በሌላ በኩል ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸመ ስለመሆኑ የሚያስረዳ አግባብነት ያለው ሌላ ማስረጃ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ያቀረበ ስለመሆኑ መዝገቡ አያመለክትም። በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ የሰጠውን ቃል እንደማንኛውም ማስረጃ መርምረው እና መዝነው ማስረጃው ክሱን ለማስረዳት በቂ አይደለም በማለት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ውሳኔ

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 103704 የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 177314 ጥቅምት 09 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል።

- **መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

አ/ጉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 132055
ጥቅምት 8/2009 ዓ.ም.

ዳኞች- ዓሊ መሐመድ
ተክሊት ይመሰል
ክፍለጽዮን ማሞ
ሰናይት አድነው
ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች - አቶ አህመድ ደርባቸው ጠበቃ ሬድዋን ከማል

ተጠሪ - ፌዴራል ዐቃቤ ህግ- ሙሉ ተስፋ ከበደ - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው አመልካች በተጠሪው በቀረበባቸው የቼክ ማጭበርበር ወንጀል ጋር ተያይዞ ጉዳዩን የያዘው ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱ የሚሰማበት ተለዋጭ ቀጠሮ በመስጠቱና ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) የዋስትና መብት ተጠብቆላቸው እንዲከራከሩ ለፍርድ ቤቱ በማመልከታቸው ነው፡፡

ተጠሪ የአመልካችን የዋስትና መብት ጥያቄ ተቃውሟል ተጠሪ በመቃወሚያል አመልካች ቀደም ሲል በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ በማውጣት ወንጀል ተከስሰው የሦስት ወር እስራት በ2 ዓመት ገደብ የተፈረደባቸው ሲሆን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሌላ የቼክ ማጭበርበር ወንጀል ድርጊት ፈጽመዋል ተብሎ ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ ስለዚህ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 67 (ለ) መሠረት የዋስትና መብት ጥያቄአቸው ውድቅ ሊሆን ይገባዋል ሲል ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ቀደም ሲል የቅጣት ገደባቸው ሳያበቃ አሁን ከተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ጋር ተመሳሳይ የሆ ወንጀል ፈጽመው የተቀጡ መሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 67 (ለ) መሠረት ሌላ ወንጀል ይፈጽሙ ይሆናል ተብሎ የሚገመት በመሆኑ የዋስትና ጥያቄው አልተቀበልነውም ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካችን ቅሬታ ባለመቀበል ወስኖአል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ን በተሳሳተ መንገድ ተርጉመውታል ይታረምልኝ ሲሉ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ቀደም ሲል የተቀጡበት ወንጀል በዚህ መዝገብ እያከረከረ ካለው የወንጀል ክስ ጋር የተለያየ ሆኖ እያለ በድጋሚ በተመሳሳይ ወንጀል ተከስሷል መባሉ አለአግባብ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

አመልካች በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ ቢደረግም እዚያው ሆነው የቼክ ማጭበርበር ድርጊት ከመፈጸም የሚያግዳቸው ነገር እንደማይኖር፣ ይልቁንም በዋስ ተለቅቀው ቼክ እንዲያንቀሳቅሱ መከልከሉ አማራጭ መሆኑን ገልጸው በዋስ የመለቀቅ ሕገመንግስታዊ መብታቸው እንዲከበርላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው በዋስ ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ የሚችል ስለመሆኑ ግምት ሊያስወስድ የሚችል ባህርይ ወይም የነገሮች ሁኔታ ሳይኖር የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 67 (ለ) ን በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ ዋስትና በሕገመንግሥቱ ዕውቅና ያገኘ መብት ቢሆንም በሕግ ሊገደብ እንደሚቻል የታወቀ ነው ብሏል፡፡ አመልካች ከዚህ ቀደም በቼክ አታላይነት ወንጀል በብር 5000 መቀጮ የ3 ወር እስራት በ2 ዓመት ገደብ የተቀጡ ሲሆን አሁንም እንደገና የግል ተበዳይን እምነት በመጠቀም የወጡት ቼክ እንዳይከፈል ሂሳቡ እንዲዘጋ በማድረጋቸው በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት በአንድ ዓይነት የሕግ ድንጋጌ ተከስሰው ቀርበዋል፡፡ አመልካች በዋስ ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ይፈጽማሉ ከሚል ግምት ከዚህ የበለጠ ማሳመኛ ምክንያት ሊኖር አይችልም ሲል ተጠሪ መቃወሚያውን አቅርቧል፡፡ በፍ/ቤቶች ውሳኔ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለትም ተከራክሯል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍ/ቤት በፀናው ውሳኔ የአመልካች የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት ያለፈውን የወንጀል ሪከርድ በማየት አሁንም ተመሳሳይ ወንጀል ከመሥራቱ ይቆጠባል ተብሎ አይገመትም በሚል ነው፡፡

ሆኖም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ስር የተደነገገው የዋስትና መብት ገደብ በተከሳሹ ያለፈ የወንጀል ታሪክ ላይ የሚመሠረት አይደለም፡፡ ይልቁንም የድንጋጌው ዓላማ በእጅ ላይ ያለውን የክሱ ሂደት ሊያደናቅፍ ይችላል ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ በዋስ የመለቀቅ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መብቱን ለመገደብ ነው። የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ከንዑስ ቁጥሮች (ሀ) እና (ሐ) ጋር በአንድነት ሊነበብ ይገባል ሕጉ የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት እየገደበ ያለው በዋስትና ወረቀት ላይ የሰፈሩትን ግዴታዎች አይፈጽምም ተብሎ ሲገመት ወይም ዋሶችን ሊያባብል ይችላል ወይም ሊያስፈራራ ይችላል ወይም ማስረጃዎችን ሊያጠፋ ይችላል ተብሎ ተከሳሹ ሲገመት ነው። የቁጥር 67 (ለ) ድንጋጌም ከንዑስ ቁጥሮች (ሀ) እና (ሐ) ጋር በጣምራ ሲነበብ "ሌላ ወንጀል ሊሠራ ይችላል ተብሎ ሲገመት" የሚለው ድንጋጌ ከተያዘው ክስና ከተጀመረው የፍርድ ሂደት ጋር በተያያዘ ጠባብ የሕግ ትርጉም በተጣጣመ መልኩ እንደሆነ ግልፅ ነው።

ፍ/ቤቶቹ የተከሳሾችን ያለፈ የቅጣት ውሳኔ ካሁን ከተከሰሰበት ጉዳይ ጋር በማያያዝ በዋስ ቢለቀቅ ተመሳሳይ የቼክ ወንጀል ሊፈጸም ይችላል የሚል ግምት በመውሰድ የዋስትና ጥያቄውን አለመቀበላቸው አግባብ ያለው ሆኖ አላገኘነውም። ፍ/ቤቶቹ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ በተከሰሱበትን ጉዳይ ለማድበስበስ ማስረጃ ለማጥፋት፣ ወይም ራሱ ለመሰወርና ከፍርድ ለማምለጥ በአጭር የተያዘውን የፍርድ ሂደት ለማደናቀፍ የወንጀል ድርጊት ይፈጸማል ለማለት የሚያስችል አሳማኝ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ን የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት መወሰናቸው ሊታረም የሚገባው ነው።

በሌላ በኩል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 138 (1) ሕጉ በግልጽ ካልደነገገ በቀር ተከሳሹ በፍርድ ዳኝነት በግልጽ እስከአልታወቀ ድረስ የቀድሞ ጥፋተኝነቱ አይገለጽም ሲል ደንግጓል። ድንጋጌው የተከሳሽን ንጽሕ ሆኖ የመገመት ሕገመንግሥታዊ መብት የሚያመለክት ሲሆን በተጨማሪም ዳኞች የወንጀል ጉዳይ በሚመረምሩበት ጊዜ በተከሳሹ የጥፋተኝነት ሪከሪድ ጫና አድሮባቸው የተሳሳተ ውሳኔ እንዳይሰጡ ለማድረግ የሰፈረ ነው።

አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ስለአመልካች የቀድሞ የጥፋተኝነት መዝገብ ሲያቀርብ ፍ/ቤቶች ከላይ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ መሠረት እንዳልቀረበ በመቁጠር ሊወሰን ሲገባ ሕጉን በመጣስ በአመልካቹ የጥፋተኝነት መዝገብ ላይ በመመሥረት ማከራከራቸውን መወሰናቸውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ነው።

በዚህ መሠረት የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 21/07/2008 ዓ.ም በወ/መ/ቁ. 146424 የሰጠውና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም በቀን 29/09/2009 ዓ.ም በወ/ይ/መ/ቁ. 127657 ያፀናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ዋስትና በማስያዝ በዋስ ተለቅቀው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ተወስኗል፡፡
3. ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔውን እንዲያስፈጽም ታዟል፤ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ልዩ ልዩ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰበር መ/ቁ153418

ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ጉደታ አሰፋ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ወ/ት ወደሬ ጉደታ

2ኛ/ወ/ት ፋኖስ ጉደታ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የመጥፋት ዉሳኔ ከተሰጠና ንብረቱ ለወራሾቹ ከተላለፈ በኋላ የመጥፋት ዉሳኔ የተሰጠበት ሰዉ ሲመለስ ንብረቶቹን የሚያገኝበት ሁኔታ በጊዜ የተገደበ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነት የሚመለከት ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁኑ አመልካች ጠፍቷል በሚል በፍርድ ቤት ዉሳኔ በማሰጠት ተጠሪዎች የአመልካቹን የመሬት ይዞታ በእጃቸዉ አድርገዉ ሲጠቀሙ ከቆዩ በኋላ አመልካች ቀርቦ የመጥፋት ዉሳኔ ተሰርዞ በተጠሪዎች እጅ የገባዉን ይዞታ እንዲመልሱ እንዲወሰን ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መቃወሚያ ይዞታዉ በእጃቸዉ ከገባ 20 ዓመት በላይ ስለሆነ የአመልካች ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል የሚል ሲሆን የወረዳዉ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክር ሰምቶ አመልካች ጠፉ የተባለዉ በ15/09/1989 ዓ.ም ስለመሆኑ በመ/ቁ/126/99 ላይ በ25/05/1999 ዓ.ም ዉሳኔ ስለመሰጠቱ እና አመልካች አቤቱታ ያቀረበዉ በ24/08/2009 ዓ.ም በመሆኑ 10 ዓመት አልፎበታል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሚል በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 172 እና 173/1/ መሰረት የአመልካች ጥያቄ በይርጋ ታግዷል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ የይርጋ መቃወሚያ ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ህጉን በአግባቡ ያላገናዘበ ነዉ የሚል ሲሆን ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ አቤቱታዉን ከፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 171 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አግባብ ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ በመያዝ በጽሑፍ መልስ እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች ላይ የመጥፋት ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ቀርቦ ንብረቶቹ እንዲመለሱለት ያቀረበዉ አቤቱታ በፍ/ብ/ህግ ቁ/171 እና 173 መሰረት በአስር ዓመት ይርጋ ቀሪ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ትእዛዝ ተገቢነት ለመመርመር ነዉ፡፡

በፍትሓብሔር ህግ ዉስጥ ስለሰዉና ስለሰዎች መብት በሚደነግገዉ አንደኛ መጽሓፍ ዉስጥ አንዱ የተፈጥሮ ሰዉ ላይ የመጥፋት ማስታወቂያ ዉሳኔ የሚሰጥበትና ዉጤቱን የሚደነግገዉ አንቀጽ 154 እስከ 173 ድንጋጌዎች የሚመለከት ነዉ፡፡አንድ የተፈጥሮ ሰዉ በህይወት መኖር አለመኖሩ አጠራጣሪ ሲሆንና በሕይወት ስለመኖሩ ወሬዉ ከጠፋ ሁለት ዓመት የሞላዉ እንደሆነ የመጥፋት ዉሳኔ የሚሰጥበት ስርዓትና በዚህም ፍርድ ቤቱ ተገቢዉን ማጣሪያ አድርጎ የጠፋዉ ሰዉ መሞት የሚመስል ሆኖ የታየዉ እንደሆነ ጠፍቷል ሲል እንደሚያስታዉቅ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 157/1/ ተመልክቷል፡፡በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚሰጠዉ የመጥፋት ማስታወቂያ የሚያስከትለዉ ዉጤት እንደሞተ ሰዉ ተገምቶ መብትና ግደታዎቹ ለወራሾች የሚተላለፍ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 154፣163 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡በዚህ አግባብ የመጥፋት ማስታወቂያ ሲነገር ጠፋ የተባለዉ ሰዉ እንደሞተ ግምት ተወስዶ ጋብቻዉ እንደሚፈርስ እና

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በእሱ መሞት መብት የሚተላለፍላቸዉ ሰዎች በመብታቸዉ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 163 እና 165 ላይ ተደንግጓል፡፡በሌላ በኩል ጠፉ የተባለዉ ሰዉ በህግ እንደሞተ ግምት የሚወሰድ ስለመሆኑና ነገር ግን ደግሞ ሰዉየዉ በህይወት ቢገኝ ወይም የሞተዉ ጠፉ ከተባለበት ቀን በኋላ ቢሆን ይህ ግምት ሊፈርስ እንደሚችል በማሰብ ንብረቶቹን በይዞታቸዉ ያደረጉ ሰዎች ዋስትና ወይም ግዴታ እንዲገቡ እንዲሁም ንብረቶቹን እንደመልካም አባት እንዲጠብቁ ህግ የሚያሥገድድ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 165፣166 እና 168 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ ስለሆነም በአንድ በኩል የመጥፋት ዉሳኔ ሲሰጥ ጠፉ የተባለዉ ሰዉ እንደሞተ ተቆጥሮ መብቱ በህግ አግባብ ለባለመብቶች እንደሚተላለፍ በሌላ በኩል ደግሞ ጠፉ የተባለ ሰዉ በህይወት ቢገኝ በሚል ወይም የመጨረሻ ወሬዉ የተሰማበት ሌላ ጊዜ ቢሆን በሚል ህሳቤ መብቱ እንዳይጎዳ ህጉ ተገቢዉን ጥንቃቄ ማድረጉን እንገነዘባለን፡፡ይህንንም ተከትሎ የመጥፋት ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ የመጥፋት ዉሳኔ ዉጤት የሚቀርበት ምክንያቶች በፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 170 ላይ ተዘርዝሯል፡፡ከእነዚህ ዉስጥ አንዱ ጠፉ የተባለዉ ሰዉ በሕይወት መገኘቱ ወይም መመለሱ ነዉ፡፡ ጠፉ የተባለዉ ሰዉ በህይወት ከተመለሰ ንብረቶቹ በሚገኙበት አኳኋን መልሶ መዉሰድ እንደሚችል የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 171/1/ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ይህ ድንጋጌ የጊዜ ገደብ አላስቀመጠም፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የመጥፋት ማስታወቂያ በመ/ቁ/126/99 ላይ በ25/05/1999 ዓ.ም የተሰጠ ሲሆን የመጨረሻ ወሬ ተሰማ የተባለዉ በ15/09/1998 ዓ.ም መሆኑ በዉሳኔዉ ላይ ተገልጧል፡፡አመልካች ይህንን በመቃወም አቤቱታ ያቀረበዉ በ24/08/09 ዓ.ም ሲሆን አቤቱታዉም ተጠሪዎች የመጥፋት ማስታወቂያ ያሰጡት በድብቅ ስለመሆኑና መሬቱን እስከ 1996 ሲጠቀም ቆይቶ በአጋዥ ሰጥቶ ሲጠቀም የቆየና ስራ ፍለጋ ሌላ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ ሲሄድ ልጆቹ አጋዥ ከተሰጠዉ አቶ አሰፋ ገለታ ላይ ተቀብለዉ ለ 4ዓመት ከተጠቀሙ በኋላ አመልካች ተመልሶ ሲጠይቅ 10 ዓመት እንዳለፈዉ ተደርጎ መወሰኑ ስህተት ነዉ ህጉም ይህንን ገደብ አላስቀመጠም የሚል ነዉ፡፡አመልካችም ይህንኑ መሰረት አድርጎ ንብረቶቹ እንዲመለሱለት ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት የ10 ዓመት ጊዜ አልፎበታል በሚል የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

172 ዋቢ በማድረግ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ የፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 172 ድንጋጌ ይዘት ሲታይ መጥፋቱን በሚወስነው ፍርድ ውስጥ ከተወሰነው የመጨረሻ ወሬዎች ከተሰሙበት ጊዜ ወዲህ አስር ዓመት ያለፈ እንደሆነ መሞቱ የመጨረሻ ወሬዎች በተሰሙበት ሳይሆን በሌላ ቀን ለመሆኑ ማስረጃ ለማቅረብ የሚችለው ጠፋ የተባለው ሰው ራሱ ወይም ስለመጥፋቱ የተሰጠው ፍርድ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን በኋላ ልዩ የሆነው ወኪል ብቻ ነው ይላል፡፡የዚህ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ የ10 ዓመት ጊዜ ገደብ የሚያያዘው ጠፋ የተባለው ሰው እንደሞተ ሰው ተገምቶ መብቶቹ ስለሚተላለፉ እና በመብቶቹ ሊሰሩ የሚችሉ ወገኖች ላይ ይርጋና የመሳሰሉት የጊዜ ጉዳዮች አከራካሪ በሆነ ጊዜ ትክክለኛውን ጊዜ በሚመለከት መከራከሪያ ሊቀርብበት የሚችለውን ወገን ለማመላከት የተቀመጠ እንጂ ጠፋ የተባለው ሰው ራሱ ተመልሶ ቢመጣ ወይም በሕይወት ቢገኝ መብቱን ለመጠየቅ የሚገድበው ድንጋጌ ሆኖ የተቀረጸ አይደለም፡፡በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ችሎት ጠፋ የተባለው ሰው ንብረት ዉርስ ጋር በተያያዘ ይርጋ ክርክር አስመልክቶ በሰበር መዝገብ ቁ/126975 ላይ የሰጠውን ዉሳኔ ማገናዘብ ይቻላል፡፡

ስለዚህም የሰዉየዉ መጥፋት ማስታወቂያ ወይም ዉሳኔ ተሰጥቶ 10 ዓመት ካለፈዉ በህይወት የመኖር ግምት ይበልጥ መሞቱ ስለሚያመዝን ንብረቱን በእጅ ያደረጉ ሰዎች ላይ በአንቀጽ 168 እና 169 ላይ የተጣሉት ገደቦች እንደማይሰሩ አመላካች ድንጋጌ እንደሆነ ከአንቀጽ 173 ጣምራ ንባብ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡በመሆኑም ጠፋ የተባለዉ አመልካች በሕይወት ከተመለሰ ሌላ ማረጋገጫ ሳያስፈልገዉ ንብረቶቹ በሚገኙበት አኳኋን መልሶ መዉሰድ እንደሚችል የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 171/1/ በግልጽ የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ ዉሳኔ ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ስለዚህም የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 172 ተመርኩዞ የአመልካች ጥያቄ በ10 ዓመት ይርጋ ታግዷል በሚል የሰጠዉ ዉሳኔ የድንጋጌዉን ይዘትና ዓላማ በአግባቡ ያገናዘበ ሆኖ አላገኘንም፡፡በዚሁ መሰረት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉሳኔ

1ኛ/ የሲ.ያ/ዋዩ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/0113197 ላይ በ29/02/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የአማራ ክልለ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 0125264 ላይ በ18/3/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 030-9082 ላይ የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ 348/1/መሰረት ተሽሯል ።

2ኛ/ የአመልካች አቤቱታ በ10ዓመት ይርጋ አልታገደም ብለናል።

3ኛ/ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ወደ ፍሬ ጉዳዩ ገብቶ በተጠሪዎች እጅ የገባዉን ንብረት አጣርቶ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ.341/1/መሰረት መልሰንለታል። ይጻፍ

4ኛ/ በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ካ/የ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 143045

ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡-

1. ወ/ሮ እሌኒ ወ/አማኑኤል - ከጠበቃ አሰፋ ደሪብሳ ጋር ቀረቡ፡፡

2. ህፃን ሰለማዊት ከበደ ሞግዚት 1ኛ አመልካች ወ/ሮ እሌኒ ወ/አማኑኤል -ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ ወርቅነሽ ብዙነህ - ቀረቡ፡፡

2. ህፃን እፀገነት ከበደ ሞግዚት 1ኛ ተጠሪ ወ/ሮ ወርቅነሽ ብዙነህ - ቀረቡ፡፡

3. ሰላም ሁለገብ አገልግሎት ኃ/የተ/ህ/ስራ ማህበር -ጠበቃ እንዳልካቸው ሞላ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነበሩ፡፡ በስር ፍርድ ቤት ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- 1ኛ አመልካች ከሚች አቶ ከበደ ጌታቸው ጋር እንደባልና ሚስት አብረው በመኖራቸው፤ 2ኛ አመልካች ደግሞ የሚች ልጅ በመሆኗ በ3ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ አቶ ከበደ ጌታቸው ያለው የእጣ ድርሻ 50% የሚገባቸው መሆኑን፤ እንዲሁም 2ኛ አመልካች ሚች ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር የሌለው ቤት የአቶ ከበደ ጌታቸው ድርሻ 2ኛ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ የየካ ምድብ ፍትሐብሔር ችሎት በመ/ቁ.70021 በ8/7/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የቀረበውን የውርስ ሪፖርት በማጽደቅ ውሳኔ በመሰጠቱ በዚሁ መሰረት በተለይ የ3ኛ ማህበር ሂሳብ ተጣርቶ በሕብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 19/3/ መሰረት የእቃው ዋጋና ያስገኘው ጥቅም ሂሳቡ ተጣርቶ ክፍፍል እንዲደረግ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው በህዳር 8 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ መከላከያ መልስ ክሳሾች እንዲከፈላቸው የጠየቁት ቤት ሆነ የአክስዮን ድርሻ በእጃችን ያለ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ፤1ኛ ከሳሽ ከሚች አቶ ከበደ ጌታቸው ጋር ልጅ ከመውለዳቸው በቀር እንደ ባልና ሚስት አብረው አልኖሩም፤ክስ የቀረበበት ቤትም በሚች ወላጆች አጥር ግቢ ውስጥ አንድ ጥግ ይዞ የተሰራ እንጂ ራሱን የቻለ የራሱ የከተማ ቦታ ይዞታ ማረጋገጫ የተሚላለት ቤት አይደለም፡፡ ይህ ቤት የለም እንጂ አለ የሚባል ከሆነ በተጣራው መሰረት ክፍፍል ቢደረግ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑ፤የህብረት ስራ ማህበሩም ከ1ኛ ከሳሽ የምትወለደውን ልጅ እንጂ 1ኛ ከሳሽን የሚመለከት አይደለም፤ ስለሆነም ያለአግባብ የቀረበ ክስ በመሆኑ ውድቅ ተደርጎልን ወጪና ኪሳራ ተከፍሎን መዝገቡ ተዘግቶ እንድንሰናበት በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ለክሱ የሰጠው ምላሽ በተመለከተ 3ኛ ተከሳሽ የህብረት ስራ ማህበር እንጂ አክስዮን ማህበር አይደለም፤ ሚች አቶ ከበደ ጌታቸው የማህበሩ አባል የነበሩ መሆናቸው በመግለጽ የውርስ ሀብቱ ባለድርሻ ወገኖች ጉዳያቸውን በፍርድ ቤት ጨርሰው አስወስነው ቢመጡ 3ኛ ተከሳሽ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እና በማህበሩ ደንብ መሰረት ከመፈፀም በስተቀር ባለድርሻ ነን ባዮች በሚያደርጉት ክርክር የሚሳተፍበት አግባብ የሌለ በመሆኑ በ3ኛ ተጠሪ የቀረበው ክስ ውድቅ ተደርጎ እንዲወሰንላቸው ዘንድ ተከራክሯል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር መርምሮ ከሰላም ሁለገብ አገልግሎት ኃ/የተ/የግ/ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ያለው ጥቅም ወይም ድርሻ እኩል እንዲካፈሉ ተወስኗል፤እንዲሁም ከዚሁ ዕጣ የተገኘ የተጣራ ትርፍ ብር 45,895.81/ አርባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም/ አመልካቾች፤1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እኩል እንዲካፈሉ፤በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነው የውርስ ሀብት መሆኑ በፍርድ ቤት የተረጋገጠው ቤት 2ኛ ከሳሽ 1/4ኛ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ ከተቻለ በዓይነት በስምምነት ግምቱን ይህ ካልተቻለ ቤቱ ተሸጦ ድርሻዋ እንዲከፈል ሲል የሰጠው ውሳኔ በመቃወም አመልካቾች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካቾች ሰኔ 5 ቀን 2009 ዓ.ም በዛሬት አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በአንድ ላይ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ ለብቻው ነሐሴ 22 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም አቤቱታቸው በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች አቶ ከበደ ጌታቸው በ3ኛ ተጠሪ ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ያላቸው ድርሻ ውስጥ ለአራቱ ማለትም ለአመልካቾችና 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው 1/4ኛ የሚደርሳቸው መሆኑን በውርስ ማጣራት ተረጋግጦ በፍርድ ቤት የጸደቀ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የሚያከራክረው የማህበሩ አባል ሲሞት ወደ ወራሾች የሚተላለፍ ምንድነው የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡ በአመልካቾች በኩል ሟች ባለው የዕጣ ድርሻ የሚያስገኘው ትርፍ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የማህበሩን ካፒታሉ/

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረቶች/ ተጣርቶ ሊከፈልን ይገባል የሚል ሲሆን በ3ኛ ተጠሪ ደግሞ በማህበራት አዋጅ 147/1991 አንቀጽ 32 መሰረት የማህበራት ንብረት ለአባላቱም ሆነ ለሌላ ወገን የሚከፋፋል ባለመሆኑ የአመልካቾች ጥያቄ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም በስር ፍርድ ቤት የተካሄደው ክርክር እና የቀረቡትን ማስረጃዎችን ይዘት መመልከቱ አስፈላጊ ሁኖ ስለአገኘው የፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት ከየካ ምድብ ችሎት የመ/ቁ. 104042 የሆነው መዝገብ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ከስር መዝገብ መገንዘብ የተቻለው በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቤት የውርስ ሀብት ከሆነው ቤት የተሰበሰበው የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈል የቀረበው ጥያቄ በስር ፍርድ ቤቶች በዝምታ መታለፉ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ሊታረም የሚገባው ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ ሌላውን ነጥብ በተመለከተ ሟች አቶ ከበደ ጌታቸው በማህበሩ 155 ዕጣ ያንዱ ዕጣ ዋጋ ብር 100.00/አንድ መቶ ብር/ መሆኑን በዚሁ ስሌት መሰረት የሟች ድርሻ የተጣራ ትርፍ ብር 45,895.81/ አርባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም/ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት መቅረቡን ተገንዝበናል፡፡ ተጣርቶ የቀረበው የተጣራ ትርፍ ድርሻ ሲሆን የአመልካቾች ዳኝነት ጥያቄ ከማህበሩ የሚገኘው የትርፍ ድርሻ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የማህበሩ ካፒታል የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጣርቶ ድርሻቸው እንዲከፈላቸው ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት በማድረግ ተገቢውን ማጣራት ተደርጎ ውሳኔ የተሰጠ ውሳኔ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡ አንድ የመሰረታዊ ማህበር አባል ሲሞት ዕጣው ወይም ጥቅሙ በማህበሩ መዝገብ ውስጥ በወራሽነት ለሰየመው ወይም ሟቹ ወራሽ ያልሰየመ ከሆነ በሕግ ለመውረስ ለሚችል ወራሹ ይተላለፋል፡ ይህም የሚሆነው ወራሹ የማህበሩ አባል ከሆነ ወይም ለመሆን ፈቃደኝነቱን የገለጸ እንደሆነ ነው፡፡ ወራሹ የማህበሩ አባል ካልሆነ ወይም አባል ለመሆን የማይፈልግ ወይም የማይፈቀድለት ከሆነ የሟቹ የዕጣው ዋጋ እና ጥቅም እንደሚከፈለው በአዋጁ አንቀጽ 19 ስር ተመልክቷል፡፡ በአጠቃላይ “**የዕጣው ዋጋ እና ጥቅም ይከፈለዋል**” የሚለውን የህጉ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ አመልካቾች በማህበሩ የሚቀጥሉ መሆናቸው አለመሆናቸው?፤ ሊቀጥሉ የማይፈልጉ ከሆነ ከማህበሩ ካፒታል /የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት/ ተጣርቶ የሚሰጣቸው መሆን አለመሆኑ? በሚሉት ነጥቦች ላይ ተገቢውን ጭብጥ ሳይመሰረትና ሳይጣራ በስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የክርክር አመራርና የዳኝነት አሳጣጥ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ስርዓትን ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል። ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 104042 ሰኔ 9 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 182433 መጋቢት 26 ቀን 2009 ዓ.ም በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348 /1/ መሠረት ተሻሽሏል።
2. ሚች በማህበሩ 155/አንድ መቶ ሃምሳ አምስት/ ዕጣዎች ያሉት መሆኑን የተጣራ ትርፍ ብር 45,895.81 /አርባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም/መሆኑን እንዲሁም የውርስ ሀብት ከሆነው በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቤት 2ኛ አመልካች 1/4ኛ ድርሻ በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ፀንቷል።

3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአጠቃላይ "**የዕጣው ዋጋ እና ጥቅም ይከፈለዋል**" የሚለውን የህጉ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ አመልካቾች በማህበሩ የሚቀጥሉ መሆናቸው አለመሆናቸው?፤ሊቀጥሉ የማይፈልጉ ከሆነ ከማህበሩ ካፒታል /የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት/ ተጣርቶ የሚሰጣቸው መሆን አለመሆኑ? በሚሉት ነጥቦች ላይ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ እና በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 136 መሰረት የሚመለከተው የህብረት ስራ ማህበራት ባለሙያ ምስክርነት /ማብራሪያ/ እንዲቀርብ በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት፤ እንዲሁም የውርስ ሀብት ከተባለው ቤት ኪራይ የተሰበሰበ መኖሩን አለመኖሩን አጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረት ተመልሶለታል።
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ።

መ/ይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ. 156425
ህዳር 14 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
መስጠፋ አህመድ
አብርሃ መሰለ
ፈይሳ ወርቁ
ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-ዳሸን ባንክ- ነ/ፈጅ ዐሥራት አድማሱ ቀረቡ፡፡
ተጠሪ፡- ዶሪና አቫኪያን-የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የግለሰብን ፎቶ በቴሌቭዥን ከማሳየት ጋር ተያይዞ የተነሳውን የጉዳት ካሳን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች የከሳሽን እውቅናና ፈቃድ ሳያገኝ የተጠሪን ፎቶ በ2006 ዓ/ም ከሚያዚያ ወር ጀምሮ በሰኔ እና በሐምሌ ወራት በነበረው የብራዚሉ ዓለም ዋንጫ የእግር ኳስ ጨዋታዎች የሚተላለፍበት ጊዜ ተጠሪ ከእነባለቤታቸው የአመልካችን ባንክ አገልግሎት ሲጠቀሙና ተጠቅመው ሲወጡ የሚያሳይ ማስታወቂያ በማሰራት በቀን ከሁለት እስከ ሶስት ጊዜ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን እንዲተላለፍ ማድረጉን ገልፀውና ተመጣጣኝ ካሳ ሊከፈላቸው የሚገባው መሆኑን ጠቅሰው ብር 400,000.00(አራት መቶ ሺህ) እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም አድራጎቱ ሕግን የጣሰ ያለመሆኑን፣ አመልካች በማስታወቂያው የተጠቀመው የተጠሪን ፎቶ ወይም ምስል ሳይሆን አጠቃላይ የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴ መሆኑን፣ በማስታወቂያው ላይ የነበረው ቪዲዮም ከአንድ ደቀቂ የበለጠ እርዝማኔ የሌለውና ለአንድ ሰንከድ ብቻ የሚታይ መሆኑን፣ አመልካች ሆን ብሎና አላማ አድርጎ የተጠሪን ምስል ያለመቅረፁንና የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንም የግለሰቦችን ነፃነት የሚዳፈሩ ድርጊቶችን የማያስተላልፍ መሆኑን፣ የተጠሪ ምስል በመታየቱም አመልካች ያገኘው ጥቅም ያለመኖሩንና ተጠሪም ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን፣ ተጠሪ ለአመልካች በሰጡት ማስጠንቀቂያ ከገለፁት ገንዘብ ውጪ በክሳቸው ላይ መጠየቃቸውም ክሳቸው ታዓማኒነት የሌለው መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን፣ በህጉ ያላቸው መፍትሄም ድርጊቱን ማስቆም እንጂ ካሳ መጠየቅ ያለመሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ቀረፃው የባንኩን እንቅስቃሴ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንጂ ተጠሪን ትኩረት ያላደረገ መሆኑን ና ቪዲዮውም የታየው ለአጭር ደቂቃ ብቻ ስለመሆኑ በማስረጃዎቹ አስረድቷል በሚል ድምዳሜ የተጠሪን ክስ ውድቅ ያደረገው ሲሆን በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸውን አመልካች በመጠቀም የውጭ ሀገር ባንኮች የክፍያ ካርዶችን ሀገር ውስጥ ላሉ ወይም ለሚመጡ ደንቦች ካርዶችን በመጠቀም ምቾትን የጠበቀ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪን ከእነባለቤታቸው ተጠቅሞ ማስታወቂያ እያስነገረ መሆኑ ማስታወቂያው ተጠሪን ዒላማ ያደረገ ሊባል የሚችል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ አመልካች የተጠሪን ምስል ከፍቃዳቸው ውጪ በመጠቀም ለሰራው ማስታወቂያ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) ድንጋጌ አግባብ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የካሳ መጠኑንም ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ ብር) ሊሆን ይገባል ሲል ወስኗል። በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባታል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ከቀረበው ክርክር ይዘትና በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ በመሄድ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ማድረጉ የክርክር አመራርና የማስረጃ ምዘና ስርዓትን ያልተከተለና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(1)(2) ድንጋጌዎችን ይዘት ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው። የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው የካሳ ጉዳይ ውሳኔ አግባብነት ስለጉዳዩ አግባብነት ካለው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(1)(2) ድንጋጌዎች ትክክለኛ አፈፃጸም አንጸር ለማየት ይቻል ዘንድ በሚል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበ ሲሆን ተጠሪ በመቅረባቸውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የክርክሩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል።

ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ተጠሪ የተጠሪን ምስል ለማስታወቂያ ስራ የተጠቀመበት ስለመሆኑና ይህንንም ሲያደርግ ከተጠሪ ተገቢውን ፈቃድ ያላገኘ መሆኑ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እንዲሁም ተጠሪ የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸውን አመልካች በመጠቀም የውጭ ሀገር ባንኮች የክፍያ ካርዶችን ሀገር ውስጥ ላሉ ወይም ለሚመጡ ደንቦች ካርዶችን በመጠቀም ምቾትን የጠበቀ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪን ከእነባለቤታቸው ተጠቅሞ ማስታወቂያ እያስነገረ መሆኑ ማስታወቂያው ተጠሪን ዒላማ ያደረገ ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች መገንዘቡን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰውን ድምዳሜ የሻረው መሆኑን፣ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበትን ድምዳሜም ፍሬ ነገርን የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ሙሉ በሙሉ የተቀበለው መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል። በመሆኑም ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች አግባብ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው በመሆኑ ሁለቱም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን የደረሱበትን ድምዳሜ የማይቀበልበትን አግባብ ስላላገኘ አመልካች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን መሰረት ያላደረገ ነው በማለት ያቀረበውን ቅሬታ አልፈነዋል።

ወደ ህጉ ስንመጣ የፍትሃ ብሔር ሕጉ የሰው መብቶች በሚል ከአንቀፅ 8 እስከ 10 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ጠቅላላ መርሆዎችን ያስቀመጠ ሲሆን እነዚህ መርሆዎች ደግሞ ተጠቃሹ ሕግ ከቁጥር 11 እስከ 30 ድረስ በደነገጋቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑ ናቸው፡፤ ከአንቀፅ 11 እስከ 30 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ስር ከተካተቱት የሰው መብቶች መካከል ደግሞ ከሰው አካል ደህንነት እና ከሰው ነፃነት ጋር የተያያዙ ተጠቃሽ መሆናቸውን ድንጋጌዎቹ ያሳያሉ። በዚህም መሰረት በፍ/ሕ/ቁጥር 11፣ 13፣ ከ27 እስከ 30 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ከሰው ነፃነት ጋር የተያያዙ መብቶችን የሚጠብቁ ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ የሰው ስእል/ምስል/ በተመለከተ ጥበቃ የሚያደርገው ቁጥር 27 ተጠቃሽ ነው። ይህ ድንጋጌ ባለፎቶግራፉ/ባለምስሉ/ ካልፈቀደ በቀር የማንም ሰው ፎቶግራፍ/ምስል/ በሕዝብ አደባባይ ሊለጠፍም ሆነ ሊባዛ ወይም ሊሸጥ እንደማይችል ይደነግጋል። የሰው ምስል/ፎቶ/ ከማባዛት ጋር ተያይዞ በልዩ ሁኔታ የተቀመጡት ነጥቦች በቁጥር 28 ስር የተዘረዘሩት ሲሆኑ እነዚህም የባለስእሉ/ምስሉ ሰው ታዋቂነት፣ ህዝባዊ ስራ ጋር መያያዝ፣ በፍርድ ወይም በፖሊስ መስሪያ ቤቶች ጋር የተያያዙ ምክንያቶች ጉዳዩን አስፈላጊ ማድረጋቸው፣

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ወይም ለኪነ ጥበብ፣ ለስልጣኔ አስተዳደግ ወይም ለትምህርት መስጫ ጥቅም ወይም በሕዝብ ስብሰባ ላይ ከተፈፀመ ስርዓት ጋር ግንኙነት ባለው ምክንያት መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በዚህ ድንጋጌ በተጠቀሱት ሁኔታዎች የሰው ፎቶ/ምስል/ ማባዛት የተፈቀደ ሲሆን በህዝብ አደባባይ መለጠፍ ወይም ማሳየት ወይም መሸጥ ግን ያለ ባለቤቱ ፍቃድና እውቅና የማይቻል መሆኑን በሕጉ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የፍ/ሕ/ቁጥር 29 ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 28 ስር ከተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች ውጪ ከባለፎቶው ወይም ምስሉ ፍቃድ ውጪ ምስሉን/ፎቶውን ማሳየት/exihibition/ ወይም መሸጥ ክልክል መሆኑንና ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ ደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር መብቱ የተጣሰበት ሰው የሚኖረው መፍትሄም ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት መብቱ የተጣሰበት ሰው ምስሉ /ፎቶው በአደባባይ እንዳይለጠፍ ወይም እንዳይታይ ወይም እንዳይሸጥ የሚያደርግ ዳኝነት እንዲሰጥለት መጠየቅ ወይም ካሳ መጠየቅ የሚችል መሆኑን በንዑስ ቁጥር ሁለት እና ንኡስ ቁጥር ሶስት ስር በግልጽ አስቀምጦ ይታያል፡፡ በአጠቃላይ በፍትሃብሔር ሕጉ በዚህ ረገድ የተቀመጡ ድንጋጌዎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 14 እንዲሁም አገሪቱ በተቀበለቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ጥበቃ የተደረገውን የሰዎች የአካል ደህንነትና የነጻነት መብቶችን የሚደግፉ በመሆኑ ተግባራዊ ሲደረጉም የድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ፣ ሊያሳኩ ያሰቡትን መሰረታዊ ዓላማ ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ይህንኑ ይዘን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣም አመልካች የተጠሪን ምስል በቴሌቭዥን ለማስተዋወቅ ያለተጠሪ ፈቃድ መጠቀሙ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 27 ድንጋጌ ስር ባለፎቶግራፉ ወይም ባለስዕሉ ካልፈቀደ በቀር የማንም ሰው ፎቶግራፍ ወይም ስዕል በሕዝብ አደባባይ ሊለጠፍም ሆነ ሊባዛ ወይም ሊሸጥ እንደማይቻል የተመለከተ በመሆኑና በፍ/ሕ/ቁጥር 28 ስር የተመለከተው ልዩ ሁኔታ ስለመኖሩም አመልካች ጠቅሶ ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የሌለ በመሆኑ የተጠሪ ምስል ጥቅም ላይ ለዋለበት የማስታወቂያ ስራ አመልካች ካሳ የማይከፍልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ሌላው በዚህ ሰበር አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የከሳ መጠኑ ሲሆን ካሳው የሚከፈልበትን አግባብ በተመለከተም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የሕጉ ክፍል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29 (2) ድንጋጌ ስር አስፍሯል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በርትዕ አስፈላጊ ሁኖ ሲታይ ስዕሉን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአደባባይ በመለጠፍ፤ በማሳየትና በመሸጥ የተጠቀመው ሰው በዚሁ ምክንያት ያገኘው ሀብት ተመላሽነት በሚሆንበት መጠን ዳኞች ካሳ እንዲከፍል ሊወስኑበት እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች የካሳውን መጠን ተገቢነት የለውም በማለት በመከራከሩና ተጠሪዎችም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 በተመለከተው አግባብ ትክክለኛውን የካሳ መጠን በማስረጃ ያለማስረዳታቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የካሳውን መጠን ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) እንዲሆን የወሰነ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የካሳ መጠኑን የተጠሪ ምስል በማስታወቂያው ከተገለጸው ከአመልካች ተግባር ጋር የሚኖረውና ሊያስገኝ ከሚችለው ጥቅም አንፃር፤ከነባራዊው ሁኔታ በመነሳት በመመርመር በተጠሪ የተጠየቀውን የካሳ መጠን የበዛ ሁኖ ማግኘቱን ጠቅሶ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) የካሳ መጠን ሊሆን እንደሚገባ ወስኗል፡፡ ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች የካሳ ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 29(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡ ሲጠቃለልም ካሳን አስመልክቶ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸውን የጉዳት ካሳ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 180602 በ16/04/2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 153194 በ28/06/2010 በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ለክሱ ኃላፊ ተብሎ በርትዕ ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ እንዲከፍል በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ - 153736

ቀን - 28/01/2011ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

አመልካቾች፡- 1. አረቡ አብደላ ┐ ጠበቃ በቀለ ተፈራ እና ታምሬ ኃይሌ

2. ታከለ ለገሰ ┘

3. አማረ ኪ. -አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- አዱኛ ጓዴ- ከጠበቃ ሰለሞን ጋር ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካቾች ደግሞ፣ በቅደም ተከተል፣ ከ1-3ኛ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በቀን 01/07/07 ዓ.ም አዘጋጅተዉ ለፍርድ ቤቱ ባቀረቡት ክስ፡- ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በገበያ ላይ የነበሩ እና እንደገና ተሻሽለዉ በ2006 ዓ.ም ታትመዉ በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ከተመዘገቡት አድቫንስድ ዎርሊድ ኢንግሊሽ ቡክ 1 እና 2 መጽሀፎችን አዘጋጅተዉ መጽሐፎቹም በ 15,000 ኮፒ ታትመዉ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ገበያ ላይ መዋላቸዉን እና በገበያ ተቀባይነት አግኝተዉ ኮፒዎቹ ሙሉ እንደተሸጡ፤ ይሁንና ያለ ከሳሽ ፈቃድ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ምሳሌዎችን፣ አገላለፆቹን እና ማብራሪያዎቹን ቃል በቃል እና በማመሳሰል በቀጥታ ከከሳሽ መጽሐፎች በመቅዳት ኢክስትሪም ስሪዬስ እንግሊሽ ፎር ግሬድ 11-12 በሚል ርዕስ አዘጋጅተዉ መሸጣቸዉን እና 1ኛ ተከሳሽም መጽሐፎቹን ማሳታሙን፤ ከሳሽ ያዘጋጃቸዉ 8,000.00 መጽሐፎችም በዚህ ምክንያት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ገዥ አጥተዉ በከሳሽ ላይ የብር 200,000.00 ኪሳራ መድረሱን ጠቅሰዉ ብር 100,000.00 የሞራል ኪሳራን ጨምሮ ብር 300,000.00 ተከሳሾች እንዲከፍሉ፣ እንዲሁም የታተሙት እንዲወገዱ እና ለወደፊትም እንዳይታተሙ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል።

1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ፤ ከከሳሽ መጽሐፍ አልተገለበጠም እንጂ ተገልብጧል ቢባል እንኳ ከሳሽ የስራዬ አካል ናቸዉ የሚላቸዉ ጽንሰ ሃሳቦች ከብሔራዊ ፈተና የተወሰዱ ጥያቄዎች እና ምሳሌዎች፣ ማብራሪያዎች እና አገላለፆች የህዝብ ንብረት መሆናቸዉን፤ በመጽሐፎቹ መካከል መመሳሰል አለ ቢባል እንኳ ስራዎቹ የእንግሊዘኛ መማሪያ መፅሀፍት፣ ካሪኩለም፣ ሀገር አቀፍ ፈተናዎችን መሠረት በማድረግ የታወቁ ሳይንሳዊ የቋንቋ አፃፃፍ መርሆ ስርዓትና ህግ በመከተል ተቀራራቢ የእንግሊዘኛ ትምህርት ዝግጅት ባላቸዉ መምህራን የተዘጋጁ በመሆናቸዉ ምክንያት መሆኑን ጠቅሰዉ ከሳሽ የቅጅ መብት እንደሌላቸዉ፣ የተጠየቀዉ የጉዳት ካሳ መጠንም ማስረጃን መሰረት ያላደረገ መሆኑን ጠቅሰዉ የተከራከሩ ሲሆን፤ 2ኛ ተከሳሽም 1ኛ ተከሳሽ ካቀረቡት ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ ክርክር በማንሳት ተከራክረዋል። 3ኛ ተከሳሽ ባለመቅረባቸዉ ክርክሩ በሌሉበት ታይቷል።

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ተጠሪ ያቀረቧቸዉ ማስረጃዎች አመልካቾች ከተጠሪ መጽሀፍ ቃል በቃል ወስደዋል ከማለት ዉጪ ምን ያህል ፐርሰንት እንደተወሰደ፣ የትኛዉ አገላለጽ፣ የትኛዉ ምሳሌ እና ማብራሪያ በቀጥታ እንደተወሰደ እንዲሁም የቋንቋ አፃፃፍ መርሆዎች እና ጽንሰ ሃሳቦቹ በአገላለጽ፣ ማብራሪያ እና ምሳሌዎቹ በተለያየ አገላለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገር፣ የአሠራር ሂደቱ እና ዘዴዉ፣ ተጠሪ ያወጣዉ ማዉጫ እና ምዕራፍ በተለየ ሲስተም የተብራራ እና የተተነተነ መሆኑ እንዲሁም ከግራመር አጠቃቀም ሁኔታ አንፃር ሲታይ የአመልካች ስራ በቀጥታ ከተጠሪ የተወሰደ መሆኑን በአግባቡ የሚያስረዳ ማስረጃ አለመቅረቡን ጠቅሶ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል።

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ተጠሪ ካዘጋጃቸዉ መጽሐፍት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማሳያ ምሳሌዎችንና ማብራሪያዎችን በቀጥታ ምንጭ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሳይጠቅሱ ወስደዉ በጽሑፋቸዉ የተጠቀሙ ስለመሆኑ ተጠሪ ካቀረባቸዉ የሰዉ ምስክሮች በተጨማሪ የኮተቤ ዩንቨርሲቲ ኮሌጅ ለቂርቆስ ክ/ከተማ ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዲቪዝዮን በላከዉ ደብዳቤ የተረጋገጠ መሆኑን፤ ይህም በአገራችን የቅጅ መብት ጥበቃ የተደረገዉ ለሃሳብ አገላለጽ ቅርጽ ከመሆኑ እና ከቅጅ መብት ጥበቃ አስፈላጊነት አንፃር ሲታይ የተጠሪ የቅጅ መብት በተጠሪ የተጣሰ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን በመጥቀስ አመልካቾች ኃላፊነት አለባቸዉ በሚል የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሮ በአመልካቾች ላይ ሊወሰድ የሚገባዉን እርምጃ በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ተገቢዉን እንዲወስን ሲል መዝገቡን ወደ ስር ፍርድ ቤት በመመለስ ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በቀን 07/06/2010 ዓ.ም አዘጋጅተዉ ባቀረቡት 8 ገጽ የሰበር አቤቱታ የተጠሪ ስራዎች በአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 6(1)(ሀ) ስር የተመለከተዉን የወጥነት መመዘኛ የማያሟላ መሆኑን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፖሊስን የምርመራ መዝገብ በማስረጃነት ያስቀረበበት ሂደትም የአመልካቾችን የመከራከር መብት የሚያጣብብ መሆኑን፣ 1ኛ አመልካች የመጽሐፎቹ አሳታሚ ወይም አዘጋጅ ስለመሆናቸዉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ “አረቡ አብደላ ኤክስትሪም ቡክ ሲሪየስ” የሚል በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያልነበረዉን አዲስ ስያሜ በመስጠት 1ኛ አመልካች ኃላፊነት እንዳለባቸዉ መወሰኑን እና ሌሎችንም ነጥቦች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ አመልካቾች የቅጅ መብት ጥሰት ፈጽመዋል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አከራክሮ ለመወሰን ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርበዉ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም፡-

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

1. ተጠሪ ለክሱ መሠረት ባደረጋቸዉ ሁለቱ መጽሐፎች ላይ የቅጅ መብት አላቸዉ ወይስ የላቸዉም? መብት አላቸዉ የሚባል ከሆነ አመልካቾች የቅጅ መብት ጥሰት ፈጽመዋል አልፈጸሙም?
2. 1ኛ አመልካች ለተጠሪ ስለሚኖረዉ ኃላፊነት ተለይቷል ወይስ አልተለየም? የሚሉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸዉ ጭብጦች ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡

በመሠረቱ የቅጅ መብት አጠቃላይ ዓላማ የፈጠራ ባለሞያዎች የፈጠራ ስራዎቻቸዉን ለማከናወን ያፈሰሱትን ዕዉቀት፣ ጊዜና ሀብት እንዲያካክሱና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ሆነዉ ለተጨማሪ የፈጠራ ስራ እንዲነሳሱ በማድረግ ቀጣይ የፈጠራ ስራን በማበረታት ኢንቨስትመንት እንዲበረታታ አቅም ለመፍጠር ሲሆን፤ ኢ- ቁሳዊ ከሆኑ የንብረት መብቶችም አንዱ ገጽታ ነዉ፡፡ በመሆኑም መንግስት በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 91(3) ስር የተመለከተዉን ኪነጥበብን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጅን ለማስፋፋት ባለበት ግዴታ መሠረት፣ የቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/96 አወጥቶ ስራ ያዋለ ሲሆን፤ ለአዋጁ መዉጣት አስፈላጊ ከሆኑት ምክንያቶች ዉስጥም አንዱ የስነ ጽሑፍ፣ የኪነ ጥበብ እና ተመሳሳይ የፈጠራ ስራዎች የአንድ አገር ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ሳይንሳዊ እና ቴክኖሎጂያዊ ልማት በማፋጠን ረገድ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸዉ የሚበረታቱበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ስለመሆኑ ከአዋጁ መግቢያ ላይ ከተመለከተዉ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን አጠቃላይ ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድም አዋጁ የቅጅ መብትን የሚያስገኙ ስራዎች፣ ጥበቃ የማይደረግላቸዉ ስራዎች ዓይነት፣ የቅጅ መብት ጥበቃ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎችን ጨምሮ የተለያዩ ድንጋጌዎችን ያስቀምጣል፡፡ አዋጁ የስራዉ አመንጪ በስራዉ ላይ የሚኖራቸዉን ኢኮኖሚያዉ እና የሞራል መብቶችን የሚደነግግ ሲሆን፤ ኢኮኖሚያዊ መብት ስራዉን የማባዛት፣ የመከወን፣ ብሮድካስት የማድረግ፣ ወደ ሌሎች ስራዎች የመለወጥና ሌሎች ብቸኛ መብቶችን የሚያካትት ሲሆን፤ የሞራል መብቱ ደግሞ የፈጠራ ስራዉ አመንጪ የመባል፣ ስራዎቹ እንዳይዛቡ የማድረግና መሰል መብቶችን የሚያካትት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 7 እና 8 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ በመሆኑም ያለፈቃዱ በአዋጁ አንቀጽ 7(1) ስር የተመለከቱት ተግባራት በሌላ ሰዉ እንዳይፈጸሙ የስራዉ አመንጪ የመከልከል መብት ያለዉ ሲሆን፤ በዚህ ስር ከተመለከቱት ዉስጥም አንዱ ስራን ማመሳሰል፣ ማቀናበር ወይም ወደ ሌላ ዓይነት መቀየር የማይቻል መሆኑን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በተመለከተ በአንቀጽ 7(1)(ሐ) ስር የተመለከተዉ ነዉ። የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄም ይህኑን መሠረት ያደረገ ሆኖ በመጽሐፎቹ ላይ የተመለከቱትን ምሳሌዎች፣ አገላለጾችን እና ማብራሪያዎችን አመልካቾች ያለ ተጠሪ ፈቃድ ወስደዉ ኢክስትሪም እንግሊሽ ፎር ግሬድ 11-12 በሚል መጽሐፍ አካተዉ አሳትመዋል የሚል ሲሆን፤ አመልካቾች በበኩላቸዉ ኃላፊነት የለብንም ሲሉ አጥብቀዉ የሚከራከሩት የተጠሪ መጽሐፍቶች የትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀዉን ካሪኩለም፣ ሲለበስ፣ የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍት፣ የመምህር መምሪያን ይዘትና ዓላማን መሠረት በማድረግ የታወቀና ሳይንሳዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ አፃፃፍ ስርዓትን እና ሰዋሰዉ መርህን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የተጠሪ ስራ በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ የተመለከተዉን የወጥነት መመዘኛ የማያሟላ መሆኑን፤ እንዲሁም በመጽሐፎቹ መካከል መመሳሰል አለመኖሩን ስለመሆኑ የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት ያስገነዝባል።

የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የሰዉ ምስክር የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻ የተጠሪን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ሲወስን እንደ ምክንያት የጠቀሰዉ የተጠሪ መጽሐፎች መርሆዎቹ እና ጽንሰ ሃሳቦቹ በአገላለጽ፣ ማብራሪያ እና ምሳሌዎች በተለያየ አገላለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገሩ፣ የአሠራር ሂደቱ፣ የአሠራር ዘዴዉ፣ ማዉጫዉ እና ምዕራፉ፣ እንዲሁም የግራመር አጠቃቀሙ የተጠሪ ስራ ስለመሆኑ፤ እንዲሁም የተጠሪዎች መጽሐፎች ቀጥታ ከተጠሪ ስራዎች የተገለበጡ ስለመሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ሲሆን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ አመልካቾች ኃላፊነት አለባቸዉ በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ አመልካቾች ያዘጋጁት መጽሐፍ ተጠሪ ካዘጋጃቸዉ መጽሐፎች ጋር ከፍተኛ መመሳሰል ያለ ስለመሆኑ የኮቴቤ ዩኒቨርሲቲ ቀደም ሲል ለወንጀል ምርመራ ዓላማ ለፖሊስ ጽ/ቤት ጽፎ የነበረዉ ደብዳቤ የሚያስረዳ መሆኑን በመጥቀስ ስለመሆኑ ከየዉሳኔዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል።

ከቅጅ መብት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች የሚጣሩበት አግባብም ሆነ ክርክሮቹን መሠረት በማድረግ የሚሰጡ ዉሳኔዎች፣ ከፍ ሲል የተመለከተዉን፣ የቅጅ መብት ጥበቃ አጠቃላይ ዓላማ መሠረት ሊያደርጉ የሚገባ በመሆኑ፤ የተጠሪ ስራ ወጥነት ያለዉ መሆን አለመሆኑ እንዲሁም የአመልካቾች ስራዎች ከተጠሪ ስራዎች የተወሰዱ መሆን አለመሆኑ ይህኑን ግምት ባስገባ መልኩ መጣራት አለበት የሚል እምነት አለን።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 2(30) የቅጅ መብት ጥበቃ የሚደረግላቸዉን ስራዎች ዓይነት ሲዘረዝር፣ የአዋጁ አንቀጽ 6 በስራዎቹ ላይ የቅጅ መብት ጥበቃ ለማግኘት አስፈላጊ የሆኑ መመዘኛዎችን ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ሰዉ የቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ለማግኘት፣ ስራዎቹ ሁለት መመዘኛዎቹን ማሟላት የሚጠበቅባቸዉ ሲሆን፤ የመጀመሪያዉ ወጥ (original) መሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛዉ ግዙፍነት ያለዉ መሆኑ ነዉ፡፡ ወጥነት በስራ አመንጪዉ የተሰራዉ ስራ ሙሉ በሙሉ ከሌሎች ስራዎች ያልተቀዳ መሆን እንዳለበት የሚገልጽ ሃሳብ ሲሆን፤ ስራዎቹ ከሌሎች ስራዎች ጋር በፍጹም መመሳሰል የለባቸዉም ማለት እንዳልሆነ ግን መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ ይልቁንም ስራዉ ወጥነት ያለዉ መሆን አለመሆኑን በማረጋገጥ ረገድ መታየት የሚገባዉ ነጥብ፣ በስራዉ ላይ የተለየ የባለ ስራዉ ችሎታ (skill)፣ ጉልበት (labour) ስራ ላይ መዋሉ፤ እንዲሁም፣ በተለይም በአዋጁ አንቀጽ 4(1)(ለ) ስር ከተመለከተዉ አንፃር ሲታይ፣ የስራዉ ባለቤት ስራዉን ሲሰራ የራሱ የሆነ የአገላለጽ መንገድ፣ ዘዴ እና ስታይል የተጠቀመ መሆን አለመሆኑ ስለመሆኑ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ ግዙፋዊ መሆን አለበት ሲልም፣ ስራዉ በሃሳብ ደረጃ የቀረ ሳይሆን በወረቀት ላይ የሰፈረ ሊሆን ይገባል ለማለት እንደሆነ ከድንጋጌዉ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ በአዋጁ የተመለከቱት የወጥነት እና የግዙፋዊነት መስፈርቶች መሠረተ ሃሳብ ከላይ የተመለከቱ ሲሆኑ፣ የስራዉ አመንጪ የሰራዉ ስራ እነዚህን መስፈርቶች ማሟላቱ ከተረጋገጠ ያለ ምንም ሌላ ቅድመ ሁኔታ የቅጅ መብት ጥበቃ የሚሰጠዉ ስለመሆኑም አዋጁ ያመለክታል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ አመልካቾች የተጠሪ ስራ የወጥነትን መስፈርት አላሟላም በማለት የሚከራከሩት፣ የተጠሪ መጽሐፍቶች የትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀዉን ካሪኩለም፣ ሲለበስ፣ የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍት፣ የመምህር መምሪያን ይዘትና ዓላማን መሠረት በማድረግ የታወቀና ሳይንሳዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ አፃፃፍ ስርዓትን እና ሰዋሰዉ መርህን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሠረት ያደረጉ መሆኑን ነዉ፡፡ በርግጥ ተጠሪ መጽሐፎቹን ሲያዘጋጅ፣ እነዚህኑን መሠረት አድርጎ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና፣ እላይ እንደተመለከተዉ፣ ተጠሪ የራሱን የተለየ ችሎታ እና ጉልበት እንዲሁም የአፃፃፍ ስታይል እና የአፃፃፍ ዘዴ በመጠቀም መጽሐፎቹን ማዘጋጀታቸዉ ከተረጋገጠ፤ መጽሐፎቹ ትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀዉን ካሪኩለም፣ ሲለበስ፣ የተማሪዎች መማሪያ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መጽሐፍት፣ የመምህር መምሪያን ይዘትና ዓላማን መሠረት በማድረግ የታወቀና ሳይንሳዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ አፃፃፍ ስርዓትን እና የሰዋሰዉ መርህን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሠረት በማድረግ ማዘጋጀታቸዉ ብቻ፣ በአዋጁ አንቀጽ 6(1) መሠረት፣ ስራቸዉ የወጥነትን መስፈርት አያሟላም ወደሚል ድምዳሜ የሚወስድ አይሆንም፡፡ በሌላ አገላለጽ ተጠሪ ከላይ የተመለከቱትን ስራዎች፣ ጽንሰ ሃሳቦችን እና መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ያዘጋጁት ለክርክሩ መነሻ የሆኑት መጽሐፎች ይዘት፤ ተጠሪ በዝግጅቱ ሂደት የራሳቸዉን የተለየ ችሎታ፣ ጉልበት፣ የአፃፃፍ ዘይ እና ስታይል መጠቀማቸዉን የሚያሳይ ከሆነ በመጽሐፉ ላይ የቅጅ መብት የማያገኙበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ መጽሐፎች የወጥነትን መስፈርት የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት ተይዞ በማስረጃ ተጣርቶ እልባት ማግኘት የነበረበት ትክክለኛ ጭብጥ፣ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት የተጠሪ መጽሐፎች ቀደም ሲል የተሰሩ ስራዎችን እንዲሁም የእንግሊዘኛ አፃፃፍ መርሆዎችን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሠረት ያደረጉ መሆን አለመሆናቸዉ ሳይሆን፣ መጽሐፎቹ በይዘታቸዉ የተጠሪን የተለየ ችሎታ፣ የአፃፃፍ ዘይ እና ስታይል የሚያሳዩ መሆን አለመሆናቸዉ ነዉ፡፡ ይሁንና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አስፈላጊዉን ማጣሪያ ሳያደርግ አመልካቾች በዚህ መልኩ ያቀረቡትን ክርክር በደፊናዉ በመቀበል የተጠሪን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ማድረጉን ተመልክተናል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ቢሆን፣ አመልካቾች ያዘጋጁት መጽሐፎች ተጠሪ ካዘጋጃቸዉ መጽሐፎች ጋር የሚመሳሰሉ መሆን አለመሆኑን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን የተመለከተ ሲሆን፣ የተጠሪ ስራ በአዋጁ አንቀጽ 6(1) ስር የተመለከተዉን የወጥነት መስፈርት የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር ያልመረመረ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም ለክርክሩ መነሻ የሆኑት የተጠሪ መጽሐፎች የወጥነት መስፈርት የሚያሟሉ መሆን አለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በጭብጥነት ተይዞ በማስረጃ ተጣርቶ እልባት ያልተሰጠዉ ሆኖ አግኝተንዋል፡፡

የተጠሪ መጽሐፎች ከላይ በተመለከተዉ ጭብጥ መሠረት ተጣርተዉ የወጥነትን መስፈርት የሚያሟሉ መሆናቸዉ ከተረጋገጠ፣ ቀጥሎ የሚመጣዉ ጥያቄ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ባዘጋጁት መጽሐፍ በተጠሪ መጽሐፎች የተመለከቱትን አገላለፆች፣ ምሳሌዎች እና ማብራሪያዎች ወስደዉ የመጽሐፎቹ አካል ማድረግ አለማድረጋቸዉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ነው። በዚህ ረገድ የተጠሪ ክርክር በመጽሐፎቹ መካከል መመሳሰል የለም እንጂ አለ እንኳ ቢባል ስራዎቹ የእንግሊዝኛ መጽሐፍት፣ የመምህር መመሪያ፣ አገር አቀፍ ፈተናዎችን መሠረት በማድረግ የታወቁ ሳይንሳዊ የቋንቋ አፃፃፍ መርሆ፣ ስርዓትና ህግ በመከተል ተቀራራቢ የእንግሊዝኛ ትምህርት ዝግጅት ባላቸዉ መምህራን የተዘጋጀ በመሆኑ ምክንያት እንደሚሆን በመግለጽ የሚከራከሩ ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል። በመሰል ጉዳይ የቅጅ መብት ጥበቃ መብት የሚሰጠዉ ሃሳቡ ሳይሆን፣ ሃሳቡ የተገለጸበት ቅርጽ፣ የተገለጸበት መንገድ እና ዘዴ ስለመሆኑ በቅጅ መብት ጥበቃ ተቀባይነት ያገኘ መርህ ነው። አንድ ሰዉ አንድን መጽሐፍ ሲያዘጋጅ፣ መጽሐፉ ተነባቢ እንዲሆን እና አንባቢዉ በቀላሉ ሊረዳ እንዲችል ሃሳቡን የሚገልጽበት የራሱ የሆነ ዘዴ እና ስታይል ይጠቀማል። የስራ አመንጪዉ ይህን ሲያደርግም ለስራዉ ጊዜ ሰጥቶ፣ የተለየ ችሎታዉን (skill) እና ጉልበቱን (labor) ተጠቅሞ በመሆኑ በቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ አንቀጽ 2(8) መሠረት በስራዉ ላይ የቅጅ መብት ባለቤት ይሆናል። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ ተጠሪ መጽሐፎቹን ሲያዘጋጅ የእንግሊዝኛ መጽሐፍት፣ የመምህር መመሪያ እንዲሁም ሳይንሳዊ የቋንቋ አፃፃፍ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ሆኖ ግን የራሱን የተለየ ችሎታ በመጠቀም፤ አንባቢ (ተማሪ) በቀላሉ እንዲረዳዉ ማድረግ በሚያስችል መልኩ፣ በመጽሐፎቹ ለተጠቀማቸዉ አገላለጾች፣ ምሳሌዎች እና ማብራሪያዎች የቅጅ መብት ጥበቃ ያገኛል። በመሆኑም አመልካቾች ለተገቢ አሠራር እና ዓላማ የስራዉን ምንጭ እና የተጠሪን ስም በመጥቀስ ስራዉን መጠቀም ከሚችሉ በስተቀር (የአዋጁ አንቀጽ 10 ይመለከታል)፣ ተጠሪ በመጽሐፉ ያካተታቸዉን አገላለጾች፣ ምሳሌዎች እና ማብራሪያዎችን እንዳለ በመዉሰድ የመጽሐፎቻቸዉ አካል ማድረግ ይችሉ ዘንድ የቅጅ መብት አዋጁ አይፈቅድላቸዉም። ይህን ማድረጋቸዉ ከተረጋገጠ በተጠሪ ላይ ለደረሰ ጉዳት ኃላፊ የማይሆኑበት ምክንያት የለም። በመሆኑም፣ አመልካቾች በመጽሐፎቹ የተጠቀሙባቸዉ ምሳሌዎች፣ አገላለጾች እና ማብራሪያዎች ከተጠሪ መጽሐፍ የተወሰዱ መሆን አለመሆናቸዉ በጭብጥነት ተይዞ በማስረጃ ተረጋግጦ መወሰን የሚገባዉ ነው። ይሁንና፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ አላጣራም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህኑን በጭብጥነት በመያዝ የቅጅ መብት ተጥሷል በሚል ድምዳሜ ላይ ሲደርስ በዋነኛነት የጠቀሰዉ ማስረጃ ከኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ተልኳል የተባለን ደብዳቤ ነው። ይህ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ለወንጀል ምርመራ ዓላማ የተፃፈ ከመሆኑም በላይ አመልካቾች በማስረጃዉ ላይ አስተያየት ያልሰጡበት በመሆኑ ብቻዉን እምነት የሚጣልበት አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ከተጠሪ መጽሐፍ ምሳሌዎችን፣ ማብራሪያዎችን እና አገላለፆችን ወስደዉ በመጽሐፎቻቸዉ በመጠቀም የቅጅ መብት ጥሰት የፈጸሙ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ ተረጋግጧል ለማለት አይቻልም፡፡

ወደ ሁለተኛዉ ጭብጥ ስንመለስ፣ ተጠሪ 1ኛ አመልካችን 1ኛ ተከሳሽ አድርገዉ ክስ ሲያቀርቡ መጽሐፎቹን አሳትሟል በሚል ነዉ፡፡ 1ኛ አመልካች በበኩሉ መጽሐፎቹን አለማሳተሙን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ መጽሐፎቹን ያሳተመ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዞ ወደ ማጣራቱ አልሄደም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ አላጣራም፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ሲል በዝርዝር ከተመለከቱት ዝርዝር ምክንያቶች አንፃር ሲታይ፣ በስር በከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጡት ዉሳኔዎች መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ሆኖ ስላገኘን ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክ/መ/ቁጥር 162017 በቀን 02/02/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፤ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 148704 በቀን 21/05/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም ስለ ቅጅ መብት ዕዉቀትና ልምድ ያላቸዉ ባለሙያዎች የተካተቱበትን አጣሪ ቡድን በማቋቋም እንዲያጣሩ በማድረግ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት የተመለሰለት ሲሆን፣ መጣራት ያለባቸዉ ጭብጦቹም፡-

2.1. የተጠሪ መጽሐፍቶች የትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀዉን ካሪኩለም፣ ሲለበስ፣ የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍት፣ የመምህር መምሪያን ይዘትና ዓላማን መሠረት በማድረግ የታወቀና ሳይንሳዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ አፃፃፍ ስርዓትን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

እና ሰዋሰዉ መርህን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሆኖ ግን በዝግጅቱ ሂደት የራሳቸዉን (የተጠሪን) የተለየ ችሎታ፣ ጉልበት፣ የአፃፃፍ ዘይ እና ስታይል የተጠቀሙ መሆን አለመሆኑን በማረጋገጥ የተጠሪ ስራ ወጥነት ያለዉ መሆን አለመሆኑን፤

2.2. የተጠሪ ስራ የወጥነትን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ አመልካቾች ተጠሪ በመጽሐፎቻቸዉ የተጠቀሙባቸዉ ምሳሌዎች፣ ማብራሪያዎች እና አገላለፆች ከተጠሪ መጽሐፎች የተወሰዱ መሆን አለመሆናቸዉን፤

2.3. 1ኛ አመልካች ለተጠሪ ኃላፊነት ያለበት መሆን አለመሆኑ ናቸዉ፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

4. ይህ ችሎት በቀን 21/10/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ
የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ.መ.ቁ 153527

መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ ስንዴው ታደሰ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ

ነ/ፈጅ ዳኛቸው ጌቴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 05 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 23848 ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 01005837 ሕዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ምክንያት የወሮታ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የቀረጥ እና ታክስ እንዲሁም ወለድ እና ቅጣት መጠናቸው በግምት ብር 2,475,000 /ሁለት ሚልዬን አራት መቶ ሰባ አምስት ሺህ / የሆኑ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከቀረጥ ነጻ የገቡ የፏበል ዱቄት ፋብሪካ ማሽነሪዎች ያላግባብ ለሶስተኛ ወገን ተላልፈዋል በማለት ለተጠሪው መስሪያ ቤት ጥቆማ የሰጠ መሆኑን፤በጥቆማው መሠረት ምርመራ ተደርጎ ንብረቶቹ ለሶስተኛ ወገን መተላለፋቸው የተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ ከዚሁ የገንዘብ መጠን ላይ ብር 495,000 / አራት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ብር / እንዲከፈለው ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ ባልሰበሰበው ቀረጥ እና ታክስ የወሮታ ክፍያ እንዲፈጽም የማይገደድ መሆኑን፤ከቀረጥ ነጻ የገቡትን ዕቃዎች ድርጅቱ ለብድር ዋስትና በማስያዝ ከዳሽን ባንክ ብድር ተበድሮ ድርጅቱ ብድሩን መመለስ ባለመቻሉ ባንኩ በአዋጅ 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በሕጋዊ ጨረታ ለቅን ልቦና 3ኛ ወገን ያስተላለፋቸው መሆኑን፤በመመሪያ ቁጥር 78/2004 ከቀረጥ ነጻ የገባን ዕቃ በማስተላለፍ የቀረበን ጥቆማ ክፍያ የሚፈጸመው ዕቃው ከተያዘ በኋላ ቀረጥ እና ታክስ ተሰልቶ ከሚገኘው ገንዘብ ሆኖ ሳለ ባልተያዘ ንብረት እና ባልተሰበሰበ ቀረጥ እና ታክስ ላይ ወሮታ እንዲከፈል የቀረበው ክስ ሕጋዊ አለመሆኑን እና በክሱ የተገለጸው የገንዘብ መጠን ያልታወቀ እና ምንም ዓይነት ማስረጃ ያልቀረበበት መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ዕቃዎቹ ለብድር በያዘው ዳሽን ባንክ ተሸጠው ለ3ኛ ወገን የተላለፉ በመሆኑ ንብረቶቹን በመያዝ እና በመሸጥ ቀረጥ እና ታክስ ለመሰብሰብ የሚቻል አይደለም፤ድርጅቱም ስራ ስላቆመ ሌሎች ንብረቶችን ማግኘት አልተቻለም፤በመመሪያ ቁጥር 78/2004 መሠረት ወሮታ የሚከፈለው ዕቃው ከተያዘ በኋላ ተሰልቶ ከሚገኘው ገንዘብ ላይ ነው፤ባንኮች ብድራቸውን ለማስመለስ ቀዳሚ መብት ስላላቸው ዕቃው የተሸጠ በመሆኑ ባልተያዘ እና ባልተሰበሰበ ቀረጥ እና ታክስ ላይ የሚከፈል ወሮታ የለም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች በሰጠሁት ጥቆማ መሠረት ምርመራ ተጣርቶ ማሽነሪዎቹ ለሌላ ሶስተኛ ወገን መተላለፋቸው ተረጋግጧል፤

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አመልካች በሕግ የተፈቀደልኝን 20% የወሮታ ክፍያ ተጠሪ እንዲከፍለኝ የጠየቅኩ ቢሆንም ተጠሪ መስሪያ ቤት ንብረቶቹን ገቢ ማድረግ ሲኖርበት ሀላፊነቱን ሳይወጣ ባንኮች ንብረቱን ለመሸጥ መብት አላቸው የሚል ምክንያት በመስጠት ለመክፈል ፈቃደኛ አይደለም፤ጥቆማ የቀረበባቸው ማሽነሪዎች ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ መግባታቸው እና ቀረጥ እና ታክሳቸው ሳይከፈል ወደ 3ኛ ወገን የተላለፉ መሆኑ አልተካደም፤ ከቀረጥ ነጻ ሆኖ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ ቀረጥ እና ታክሱ ሳይከፈልበት ተመሳሳይ የቀረጥ ነጻ መብት ለሌለው ማንኛውም ሰው ማስተላለፍ ወይም የቀረጥ ነጻ መብት ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ መገልገል ወይም በሌሎች ሰዎች ይዞታ እና አገልግሎት እንዲውል ማድረግ የተከለከለ ሲሆን ይህንኑ የተላለፈ ማንኛውም ሰውም የወንጀል ሀላፊነት አለበት፤ባንኮች የቀረጥ ነጻ መብት በሕጉ ከተቀመጠው ዓላማ ውጪ እንዲያውሉ አልተፈቀደላቸውም፤ባንኩ ንብረቶቹን በዋስትና ሲይዝ ከቀረጥ ነጻ የገቡ መሆናቸውን ያውቃል፤ተጠሪ ጥቆማው ከደረሰው በኋላ ምርመራውን በአግባቡ ባለማከናወኑ መጠኑ ሊታወቅ ያልተቻለ ቢሆንም አመልካች ተገቢውን ጥቆማ የሰጠሁ በመሆኑ ወሮታው ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ከቀረጥ ነጻ የገባው ዕቃ ለባንክ ብድር መያዣ በመዋሉ ምክንያት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2008 እና አዋጅ ቁጥር 859/2008 መሠረት የጠየቁት የወሮታ ክፍያ ሊያገኙ አይገባም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የንጋት ጸሐይ ዱቄት ፋብሪካ ከዳሽን ባንክ ጋር ለፈጸመው የብድር ውል ማሽነሪዎቹን በዋስትና ያስያዘው ጥቅምት 29 ቀን 1999 ዓ.ም በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አዋጅ ቁጥር 622/2001 እና 859/2006 ሳይሆን በወቅቱ የነበረው አዋጅ ቁጥር 60/90 ነው፤ድርጅቱ ዕቃዎቹን በዋስትና ባስያዘበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 / እንደተሻሻለው / ከቀረጥ ነጻ የገቡ ዕቃዎችን ለባንኩ ብድር በመያዣነት ሊውሉ እንደሚችሉ በግልጽ የሚፈቅድም ሆነ የሚከለክል ድንጋጌ የለውም፤ዕቃዎቹም ከቀረጥ ነጻ የገቡ ስለመሆናቸው ባልተረጋገጠበት እና በማስረጃ ባልተደገፈበት ሁኔታ የጠቋሚ ወሮታ የሚከፈልበት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

አግባብ የለም፤መመሪያ ቁጥር 78/2004 የወጣውም አዋጅ ቁጥር 622/2001 ለማስፈጸም ሲሆን ድርጊቱ ተፈጸመ የተባለው ደግሞ አዋጅ እና መመሪያው ከመውጣቱ በፊት በመሆኑ ጠቋሚው ከመጀመሪያውኑ ወሮታ የማግኘት መብት አልተጎናጸፈም፤ድርጅቱ ምን ዓይነት ዕቃዎችን እንዳስገባ? መቼ እዳስገባ? ምን ያህል ቀረጥ እና ታክስ መክፈል እንደነበረበት? ያልተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ሳይረጋገጥ ወሮታ የሚከፈልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፤ዕቃዎቹ በቀረጥ ነጻ የገቡ ናቸው የሚባል ቢሆን እንኳን ከቀረጥ ነጻ የገቡ ዕቃዎችን ባንክ ዋስትና ይዞ በሚሸጥበት ጊዜ ወሮታ ይከፈላል የሚል ሕግ የለም፤ግለሰቡ ከመጀመሪያውም የሰጠው መረጃ እንጂ ጥቆማ አይደለም፤በመመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 5/1/ሀ በህዝብ የሚታወቁ ሕገወጥ ዕቃዎች የሚገኙባቸውን ቦታዎች መጠቆም ባለመብት የሚያስደርግ ጥቆማ አይደለም፤ከቀረጥ ነጻ የገቡ ቢሆንም በሕጋዊ ሁኔታ ወደ 3ኛ ወገን የሚተላለፉበት ሁኔታ አለ፤ይህ በሕግ የተቀመጠ ልዩ ሁኔታ እያለ ለመንግስት ተጨባጭ ማስረጀ ባልሰጠበት እና መንግስት ከጥቆማው ያገኘው ጥቅም በሌለበት ሁኔታ ወሮታ ሊከፈል አይገባም፤በመመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 16/1 እና 2 አንድ ጠቋሚ ወሮታ ሊሰጠው የሚችለው ሕገወጥ ዕቃው ከተያዘ እና ለባለስልጣኑ ገቢ ከተደረገ ነው፤ወሮታ ማግኘት የሚችለውም ለባለስልጣኑ ገቢ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ነው፤የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር በባንክ በዋስትና የተያዙ ንብረቶች ሲሸጥ የተገኘው ገቢ በቅድሚያ የባንክ እዳ ለመሸፈን በማዋል ቀሪ ገንዘብ ካለ ብቻ ለመንግስት ዕዳ ክፍያ እንዲውል የወሰነ በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም የሚል ነው።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል።

አመልካች ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደ ሐገር ውስጥ የገቡ የፏበል ዱቄት ፋብሪካ ማሽነሪዎች አላግባብ ለሶስተኛ ወገኖች ተላልፈዋል በማለት ለተጠሪው መስሪያ ቤት ጥቆማ የሰጠ መሆኑን፤ንብረቶቹ የተላለፉለት የንጋት ጸሐይ ዱቄት ፋብሪካ ከዳሸን ባንክ ጋር ለፈጸመው የብድር ውል ጥቅምት 29 ቀን 1999 ዓ.ም ማሽነሪዎቹን በዋስትና ያስያዘ መሆኑን፤ተበዳሪው ድርጅት ከባንኩ የተበደረውን ገንዘብ መክፈል ስላቃተው ባንኩ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአዋጅ 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ንብረቶቹን በሕጋዊ ጨረታ ለቅን ልቦና 3ኛ ወገን ያስተላለፋቸው መሆኑን፤ከቀረጥ ነጻ ገብተዋል የተባሉት ዕቃዎች ምን ዓይነት ዕቃዎች እንደሆኑ? መቼ እንደገቡ? የቀረጥ እና ታክስ መጠናቸው ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ መሆኑን እና ተጠሪው መስሪያ ቤት ከንብረቶቹ የሰበሰበው የቀረጥ እና ታክስ ክፍያ የሌለ መሆኑን ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ ችለናል፡፡

የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሠጣጥ፤አያያዝ እና አመዘጋገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 16/1እና2 ድንጋጌ ለባለሥልጣኑ በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ያለጥቆማ ሕገወጥ ዕቃው ከተያዘ እና ለባለስልጣኑ ገቢ ከተደረገ ጠቋሚው፤ያዥው፤ትብብር እና ድጋፍ ያደረጉት በሙሉ በመመሪያው መሠረት ወሮታ የሚከፈላቸው መሆኑን፤የወሮታው ክፍያ የሚከፈለውም ሕገወጡ ዕቃ በመመሪያው አንቀጽ 17 መሠረት ለባለስልጣኑ ገቢ ከሆነበት ቀን ጀምሮ መሆኑን በመግለጽ ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደ ሐገር ውስጥ የገቡ የፏበል ዱቄት ፋብሪካ ማሽነሪዎች አላግባብ ለሶስተኛ ወገኖች ተላልፈዋል በማለት ለተጠሪው መስሪያ ቤት ጥቆማ የሰጠ መሆኑን በመግለጽ የወሮታ ክፍያው ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የሚከራከር ቢሆንም ከቀረጥ ነጻ ገብተዋል የተባሉት ንብረቶች የተላለፉለት የንጋት ጸሐይ ዱቄት ፋብሪካ ከዳሸን ባንክ ጋር በፈጸመው የብድር ውል ጥቅምት 29 ቀን 1999 ዓ.ም ማሽነሪዎቹን በዋስትና አስይዞ ከባንኩ የተበደረውን ገንዘብ መክፈል ስላቃተው ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ንብረቶቹን በሕጋዊ ጨረታ ለቅን ልቦና 3ኛ ወገን ገዢ በሽያጭ ያስተላለፋቸው በመሆኑ፤ከቀረጥ ነጻ ገብተዋል የተባሉት ዕቃዎች ምን ዓይነት ዕቃዎች እንደሆኑ? መቼ እንደገቡ? የቀረጥ እና ታክስ መጠናቸው ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ ከመሆኑም ባሻገር ተጠሪው መስሪያ ቤት ከንብረቶቹ የሰበሰበው የቀረጥ እና ታክስ ክፍያ የለም፡፡

የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሠጣጥ፤አያያዝ እና አመዘጋገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 16/2 የወሮታው ክፍያ የሚከፈለው ሕገወጡ ዕቃ በመመሪያው አንቀጽ 17 መሠረት ለባለስልጣኑ ገቢ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ነው በማለት የሚደነግግ በመሆኑ እና አመልካች ጥቆማ ሰጥቸበታለሁ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሚለው ከቀረጥ ነጻ ሆኖ የገባው ዕቃ ባንኩ ላበደረው ብድር መክፈያ ይውል ዘንድ በሽያጭ የቅን ልቦና ገዢ ለሆነ 3ኛ ወገን የተላለፈ እና ለተጠሪው መስሪያ ቤት ያልገባ እና ቀረጥ እና ታክስ ያልተሰበሰበበት በመሆኑ በመመሪያው መሠረት ለአመልካች ሊከፈል የሚችል የወሮታ ክፍያ ስለማይኖር የስር ፍ/ቤቶች ይህንኑ መሠረት በማድረግ አመልካች ወሮታ እንዲከፈለው ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 23848 ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 01005837 ሕዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

- **መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጐ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መ/ቁ 151082

ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ሚ/ር አሂም ማርቲን ብራዉን- ጠበቃ ምንዳዬ አንጀሎ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሜድሮክ ፋዉንዴሽን ስፔሻሊስት ኃ/የተ/የግ/ማህበር- ጠበቃ አብደላ ዓሊ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ የሥራ ውሉ በገዛ ፈቃዱ የተቋረጠበት የሥራ መሪ ያልተጠቀመበትን የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ የሚከፈልበት የሕግ አግባብ መኖር ያለመኖሩን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ከሳሽ፣ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን የአመልካች የክስ ይዘትም፡- አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸዉን የስራ ዉል ከሚያዝያ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በገዛ ፍቃዱ ያቋረጠ ቢሆንም ተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎችን ያልፈጸመለት መሆኑን ገልፆ፣ ከ05/03/2004 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ያለዉን የ5 ወር ደመወዝ ብር 1,243,758.34፣ የ280 ቀናት የዓመት እረፍት ክፍያ ብር 2,108,984.98፣ የአንድ ዓመት የቤት ኪራይ ብር 228,366.67፣ የልጆች ትምህርት ቤት ክፍያ ብር 242,894.00፣ ቀሪ የአየር ጉዞ ትኬት ብር 1,140,000.00፣ ለስራ ጉዞ ያወጡትን ወጪ ብር 192,925.59፣ የተለያዩ ክፍያዎች ብር 69,881.87፣ የ3 ወር ደመወዝ በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት ብር 652,148.20፣ በድምሩ ብር 5,686,034.00 ተጠሪ እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም፡- በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ ዉል ተፈፃሚነት ያለዉ ህግ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሆኑን የተስማሙ መሆኑን እና ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ የሚታይ ከሆነ ደግሞ የቀረበዉ የተለያዩ ክፍያዎች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ የሚሆኑ መሆኑን እንደ መጀመሪያ መቃወሚያ ካነሳ በኋላ ፍሬ ነገሩን በተመለከተም አመልካች ለሰሩባቸዉ ጊዜያት ደመወዝ ሲከፈላቸዉ የነበረ መሆኑን፣ አመልካች ከደመወዝ ጋር በተያያዘ በፈጸሙት ህገ ወጥ ተግባር ለ6,000.00 ዩሮ የጀርመንና የኢትዮጵያ መንግስታት የገቢ ግብር እንዳያገኙ ያደረጉ መሆኑን፣እንዲሁም ስራዉን ያቋረጡረት በራሳቸው ፍቃድ በመሆኑ የ3 ወር ደመወዝ ክፍያ በካሳ መልክ ሊከፈላቸዉ የማይገባ መሆኑን፣ የዓመት እረፍት ክፍያም በሁለት ዓመት ባለመጠየቁና በሚመለከተዉ አካል ፍቃድ ያልተላለፈለት በመሆኑ ሊከፈላቸው የማይገባ መሆኑን፣ በዉሉ መሠረት አመልካች በራሳቸዉ ቤት እየኖሩ ስለሆነ በዉሉ መሠረት ሊከፈላቸዉ የሚገባ ደመወዝ አለመኖሩን፣ የት/ቤት ክፍያ የሚከፈለዉ ዕድሜያቸዉ ከ14 ዓመት በታች ለሆኑት ሕፃናት በመሆኑ እና ለእነማን እንደሚከፈል በክሱ በግልጽ ያልተመለከተ በመሆኑ ለት/ት ቤት ክፍያ በሚል የቀረበዉ ተቀባይነት የሌለዉ መሆኑን፣ አመልካች ለእረፍት ወይም ለስራ መዬዳቸዉ ባልተገለጸበት ሁኔታ የጉዞ ትኬት በማለት የጠየቁትም ተገቢነት የሌለዉ መሆኑን እና ልዩ ልዩ ክፍያዎች በሚል ያቀረቡትም አግባብነት የሌለው ነው የሚሉትን ምክንያቶችን በማንሳት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ የቀረበዉን የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ፤ ለአመልካች ደመወዝ ስለመከፈሉ ተጠሪ በማስረጃዉ ያላስረዳ በመሆኑና መጠኑንም በተመለከተ ስላልተከራከረ ብር 1,243,758.34፣ የ280 ቀናት የዓመት እረፍት አመልካች መዉሰዳቸውን ገልጾ ተጠሪ ባለመከራከሩ ብር 2,108,984.98፣ አመልካች የቤት ኪራይ ሲከፍል የነበረ መሆኑ በመረጋገጡ ብር 228,366.67፣ አመልካች ከአዲስ አበባ ፍራንክፈርት የደርሶ መልስ የአዉሮፕላን ትኬት እንደሚሰጣቸዉ በቅጥር ዉሉ ላይ በተመለከተዉ እና በአመልካች በቀረበዉ ትኬት መሠረት ብር 1,140,000.00፤ በድምሩ ብር 4,721,109.99 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት ሲወስን ቀሪዎቹን የክፍያ ጥያቄዎችን ግን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ አመልካች የጠየቁትን የ 5 ወር ደመወዝ የከፈለ መሆኑን በተመለከተ አመልካች ተገቢ ክርክርና ማስረጃ ያቀረበ ባለመሆኑ ይሄዉ እንዲከፈል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ ያለመገኘቱን፣ የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጠዉ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ በተመለከተም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክርክር አመልካች የዓመት እረፍት ወስደው መጠቀማቸውን ገልፆ ያልተከራከረ በመሆኑ አመልካች የዓመት እረፍቱን በየዓመቱ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል በማለት በይግባኝ ክርክር ደረጃ የሚያቀርበዉ ክርክር በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 329(1) መሠረት ተቀባይነት ያለዉ ክርክር ያለመሆኑን፣ አዋጅ ቁጥር 377/96 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሌለዉ በመሆኑ አመልካች የዓመት ፍቃድ ጠይቀው እንዲተላለፍላቸው ባላስፈቀደበት ሁኔታ የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል መጠየቅ አይችልም በማለት የአዋጁን አንቀጽ 79 በመጥቀስ የሚያቀርበዉ ክርክርም ተቀባይነት የለሌለው ቢሆንም አመልካች ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት የ280 ቀናት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ የህግ መሠረት የሌለው ነው በማለት በዚህ ረገድ የተሰሠጠውን የውሳኔ ክፍል ውድቅ ያደረገው አድርጎታል፡፡ እንዲሁም የኪራይ ቤት ክፍያና የአየር ትኬት ለአመልካች እንዲከፈል ተብሎ መወሰኑም ያላግባብ መሆኑን ጠቅሶ በዚህ ረገድ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ ተጠሪ ለአመልካች የ5 ወር ከ15 ቀን ደመወዝ ብር 1,243,758.34 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ስምንት ከ34/100) ብቻ ከየካቲት 05 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ወስኖል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የአመልካች የዓመት ፍቃድ የተሰጣቸዉ ስለመሆኑ ተጠሪ ባላስረዳበት ሁኔታ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ የማይከፈልበት ምክንያት የሌለ መሆኑን፣ የቤት ኪራይና የጉዞ ትኬት ክፍያ ዉሳኔም ዉሉን መሠረት ያደረገ ሁኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መሻሩ ያላግባብ መሆኑን በመግለጽ በአጠቃላይ በእነዚህ ነጥቦች ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው ታርሞ በእነዚህ ነጥቦች ላይ የስር ፍርድ ቤት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሰይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመት እረፈት በገንዘብ ተቀይሮ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን በፍትሃብሔር ሕጉ አልተመለከተም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም የግራ ቀኝን ክርክር ለሰበር አቤቱታው ምክንያት ከሆነዉ ውሳኔ እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት ለመሆኑ ላይ ግራ ቀኝ ያልተካካዱ መሆኑን፣ አመልካች ያቀረቧቸዉን የተለያዩ ክፍያዎች ላለመክፈል የአሁኑ ተጠሪ ካቀረባቸዉ ክርክሮች ዉስጥ አንዱ በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ የቅጥር ዉል ላይ ተፈፃሚነት ያለዉ ህግ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሆኑ በዉሉ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች ያቀረቧቸዉ የክፍያ ጥያቄዎች በአዋጁ መሠረት በይርጋ ቀሪ የሚደረጉ ናቸዉ የሚል የነበረ ቢሆንም አመልካች የተቀጠሩበት ስራ በባህርዉ የስራ መሪ በሚል በአዋጅ ቁጥር 377/96 ስር የተመለከተዉ ዓይነት በመሆኑ ላይ ግራ ቀኝ ክርክር የሌላቸው ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 377/96 የስራ መሪን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት እንደሌለዉ ይሄዉ አዋጅ በአንቀጽ 3(2-ሐ) ስር በግልጽ መደንገጉን፣ በአዋጁ አንቀጽ 3 ስራ የተመለከተዉ የአዋጁ ተፈፃሚነት ወሰን በህግ አዉጭዉ አካል የተወሰነ፤ መወሰንም የሚገባዉ በመሆኑ የአዋጁን ተፈፃሚነት የመወሰን ጉዳይ በተዋዋይ ወገኖች በድርድር የሚወሰን ሊሆን እንደማይችል በምክንያትነት ይዞ በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ የቅጥር ዉል አንቀጽ 10 በቅጥር ዉሉ ተፈፃሚነት ያለዉ የአሠሪና ሠራተኛ ህግ ነዉ በሚል የተመለከተ ቢሆንም፣ ይህ የዉል ቃል የአፈፃፀም ወሰኑን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 3(2-ሐ) ስር ከተመለከተዉ ድንጋጌ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለዉ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ይሄንኑን በምክንያትነት በመጥቀስ የቀረበዉ ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የአሁኑ ተጠሪ የሚያቀርበዉ መከራከሪያ ተገቢነት የለውም በማለት ማለፉን እና በዚህ ረገድ በአሁኑ አመልካችም ሆነ በተጠሪ በኩል የቀረበ የሰበር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቅሬታ የሌለ መሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጠዉ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክርክር አመልካች የዓመት እረፍት ወስደው መጠቀማቸውን ገልፆ ያልተከራከረ በመሆኑ አመልካች የዓመት እረፍቱን በየዓመቱ ሲጠቀምበት ቆይቷል በማለት ተጠሪ በይግባኝ ሰሚው ችሎት ያቀረበው ክርክር አዲስ ክርክር ነው ተብሎ ውድቅ የሆነ ከመሆኑም በላይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የሌለዉ በመሆኑ አመልካች የዓመት ፍቃድ ጠይቀው እንዲተላለፍለት ባላስፈቀደበት ሁኔታ የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል መጠየቅ አይችልም በማለት የአዋጁን አንቀጽ 79 በመጥቀስ ተጠሪ የሚያቀርበዉ ክርክርም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያለማግኘቱን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ ችሎት እንዲታይ ወደ ተያዘው መሰረታዊ ጭብጥ ስንመጣም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት የ280 ቀናት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ የህግ መሠረት ያለው አይደለም በማለት የሠጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ተመልክተናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት እንደገለጸው የዓመት እረፍት አንዱ ዓላማዉ ሠራተኛዉ የእረፍት ጊዜ ተጠቅሞ ብቁ በሆነ የአእምሮና የአካል ሁኔታ ወደ ስራዉ እንዲመለስ ማድረግ ነዉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የዓመት እረፍት ሠራተኛዉ የሚያርፍበት ጊዜ እንጅ የእረፍት ጊዜዉን በስራ ላይ አሳልፎ እረፍቱ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጠዉ መጠየቅ አይደለም፡፡ ይህ በመሆኑም በመርህ ደረጃ የእረፍት ጊዜ ወደ ገንዘብ ሊቀየር የማይችል ስለመሆኑ እና ወደ ገንዘብ የሚቀየሩት በየህጎቹ በተመለከቱት ሁኔታዎች ብቻ ስለመሆኑ የአሠሪና ሠራተኞን ግንኙነት በሚገዙ በተለያዩ አዋጆች ተቀባይነት ያገኘ መርህ ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት ያለዉ ህግ በፍትሐብሔር ህጉ የስራዎች አገልግሎት ለመስጠት የሚደረጉ ዉሎች በሚል ርዕስ ከአንቀጽ 2512 ጀምሮ የተደነገገዉ ሲሆን፣ በዚህ ርዕስ ከአንቀጽ 2560-2565 ስር የተመለከቱት ስለ የዓመት እረፍት በተለይ የሚደነግጉ ሲሆን፣ የዓመት እረፍት ከዓመት ዓመት ሊተላለፍ ስለሚችልበት ሁኔታ እንዲሁም የዓመት እረፍት ሲተላለፍ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈል የሚቻል መሆን አለመሆኑ በእነዚህ ድንጋጌዎች ስር አልተመለከተም፡፡ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ የቅጥር ዉል ስለ የዓመት እረፍት የሚደነግገዉ የዉሉ አንቀጽ 5(ሀ እና ለ) ለአሁኑ አመልካች በዓመት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የ42 ቀን የዓመት እረፍት የሚሰጣቸዉ መሆኑን እና የዓመት እረፍት የሚሰጥበትም ጊዜ በግራ ቀኝ መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚወሰን መሆኑን የሚደነግግ ቢሆንም፣ የአሁኑ አመልካች ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሊሰጥ ስለሚችልበት ሁኔታ በተለይ የማይደነግግ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይህ ማለት ግን አመልካች ሳይጠቀሙበት ከዓመት ዓመት የተላለፈ የእረፍት ጊዜ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጣቸው ለመጠየቅ የሚያስችል ከህግም ሆነ ከዉል የመነጨ መብት የላቸውም ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ጉዳዩን ይገዛሉ ብሎ ከጠቀሳቸው የፍትሃብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መካከል ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2563 ድንጋጌ ውሉ በተቋረጠ ጊዜም ሰራተኛው የሚገባውን የእረፍት ጊዜ ለማግኘት መብት አለው የሚል ይዘት ያለው መሆኑ ይህ መብት ተግባራዊ የሚሆነው በገንዘብ ተቀይሮ ነው ተብሎ ከሚተረጎም በስተቀር ሌላ ሰራተኛው የመብቱ ተጠቃሚ አይሆንም የሚል ትርጉም የሚያሰጥ አይደለም፡፡ ስለሆነም ለአመልካች የመብት ጥያቄ ሕግ ጥበቃ አድርጎ እያለና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2563 ድንጋጌም ይዘትና መንፈሱ ሲታይ ውሉ መቋረጡ እስከተረጋገጠ ድረስ የአመት እረፍትን የማግኘት መብቱን የጠበቀ መሆኑን የሚያስገነዝብ ሁኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ድንጋጌው ተግባራዊ የሚሆንበትን አግባብ ሳያገናዝብ የአመልካች ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም ተጠሪ አመልካች የእረፍት ጊዜአቸውን መጠቀማቸውን ወይም በሕጉ አግባብ የተጠቀሙ መሆኑን ሳያስረዳ የገንዘብ መጠኑ ከፍተኛ መሆኑን በመጥቀስ በተጠሪ ላይ ኪሳራ ሊያደርስ የሚችል በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የአቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመት እረፈትን በተመለከተ የሰጠው የውሳኔ ክፍል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2563 ድንጋጌን የጣሰ እና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘውም ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/138726 በቀን 18/04/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 138029 በ22/01/2010 ዓ/ም የተሻሻለው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የዓመት እረፍትን በተመለከተ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠው የዉሳኔ ክፍል ተሸሮ በዚህ ረገድ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 348 መሰረት ፀንቷል
3. የመኖሪያ ቤት ኪራይ እና ቀሪ የጉዞ ትኬት ክፍያን በተመለከተ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 348 መሰረት ጸንቷል፡፡
4. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የ5 ወር ከ15 ቀን ደመወዝ ብር 1,243,758.34 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ስምንት ከ34/100) እና የ280 ቀናት የዓመት እረፍት ብር 2,108,984.98 እንዲከፍል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
5. በዚህ ችሎት በተደረገዉ ክርክር የወጣዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ሰበር መ/ቁ154371

ህዳር 28 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ አስፋዉ ተክለ በሸሩ

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የጥብቅና ሙያ የዲስፕሊን ጥፋት የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች አዋጅ ቁ/262/07 አንቀጽ 30/23/ ተላልፎ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ፈጽሟል በሚል የክልሉ የጠበቆች የዲስፕሊን ጉባኤ የጥፋተኛነት ዉሳኔ ሰጥቶ በዚህም ብር ሶስት ሺህ የገንዘብ መቀጮ የወሰነበት ሲሆን የክልሉ ፍትህ ቢሮ ሃላፊ ይህንኑ በማጽናታቸዉ አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ የአመልካች ደንበኛ ተከሳሽ ፍፁም ገ/መድህን በተከሰሰበት ቀላል ስርቆትና በቸልተኛነት የመሸሸግ ወንጀል በሐድነት ክ/ከ ክርክር ላይ መሆኑን በመግለጽ መቃወሚያ ማቅረብ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ነዉ ተብሎ የቅጣት ዉሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም የሚል ነዉ፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በአመልካች ደንበኛና በአቃቤ ህግ መካከል በተመሳሳይ ጉዳይ በሌላ ፍርድ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቤት ቀጠሮ ላይ መሆኑን ገልጾ መከራከሩ ፍትህን የሚያዛባ ተግባር ነዉ ተብሎ ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡በተጠሪ በኩል ያቀረበዉ መልስ ባጭሩ የአመልካች ደንበኛ በኩሓ ክ/ከ/ወረዳ ፍርድ ቤት የተከሰሰዉ ንብረትነቱ የአቶ ሃይላይ ገ/ሕይወት የሆነ የብሎኬት ማምረቻ ዲናሞ ሸሽጎ በመገኘቱ ስለመሆኑ፤በሌላኛዉ ጉዳይ በሓድነት ክ/ከ/ ወረዳ ፍ/ቤት የተከሰሰዉ ንብረትነቱ የአቶ ሃይሉ ግርማይ የሆኑ ሁለት ስላተርሽ የሚባል ማሽን ሸሽጎ በመገኘቱ ስለመሆኑና በሁለቱም መዝገብ የአመልካች ደንበኛ የተከሰሰዉ በመሸሸግ ወንጀል ቢሆንም ንብረቶቹ የተለያዩና ባለቤቶቹም የተለያዩ ስለሆነ ይህንን ሓቅ እያወቀ መቃወሚያ ማቅረቡ ፍትህን የሚያሳስት ተግባር ስለሆነ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ነዉ ተብሎ መቀጣቱ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካችም አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ ክርክር ይዘት ከላይ ባጭሩ ተገለጸ ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ የአመልካች ደንበኛ በሁለት ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ጉዳይ ክስ ሊቀርብባቸዉ አይገባም በማለት አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ የክስ ክርክር የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ነዉ በሚል የተሰጠዉ ቅጣት ዉሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ከአዋጁ አንጻር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡የትግራይ ክልል የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁ/262/2007 ላይ የድስፕሊን ጥፋቶች ዓይነትና የሚወሰዱ እርምጃዎችን አስመልክቶ በክፍል ሶስት አንቀጽ 30 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት የአዋጁን አንቀጽ 30/23/ተላልፈዉ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ፈጽመዋል በሚል ነዉ፡፡የአዋጁ አንቀጽ 30 የሚደነግገዉ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶችን በመዘርዘር ሲሆን ንኡስ አንቀጽ 23 ስር የተመለከተዉ <u>የጥብቅና ሙያን የሚያጎድፍ ተግባር በደንበኛዉ ወይም በሌላ ሰዉ ላይ መፈጸም</u> ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት መሆኑን የሚደነግግ ነዉ፡፡ከዚህ ድንጋጌ አንጻር የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ምንነት አመላካች ቃል ወይም ትርጉም በግልጽ በአዋጁ ላይ የተመለከተ ባይሆንም አመልካች ደንበኛቸዉ በተመሳሳይ ጉዳይ በሁለት ፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መቃወሚያ ማቅረባቸዉ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ነዉ በሚል መቀጣታቸዉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበዉ ክስ መነሻዉ የአመልካች ደንበኛ አቶ ፍጹም ገ/መድህን በሁለት ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ሁኔታ በመሸሸግ ወንጀል መከሰሳቸዉን ተከትሎ አመልካች በደንበኛቸዉ ላይ በተመሳሳይ ጉዳይ ሁለት ፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብ አይገባም በሚል መቃወሚያ ማቅረባቸዉ የአዋጁን አንቀጽ 30/23/ በሚያሟላ ሁኔታ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ነዉን? የሚለዉ መታየት ያለበት ነዉ፡፡የአመልካች መቃወሚያ ነጥብ ደንበኛቸዉ በመሸሸግ ወንጀል በሓድነት ክ/ከ/ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሰዉ ቀጠሮ ላይ ስለሆነ በተመሳሳይ የመሸሸግ ወንጀል በኩሓ ክ/ከ/ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ መቅረቡ ተገቢ ስላልሆነ መዝገቡ እንዲዘጋ የሚል ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡በአቃቤ ህግ በኩል የተሰጠዉ ምላሽ ሁለቱም ክሶች የመሸሸግ ወንጀል ቢሆኑም የግል ተበዳይ እና ንብረቱ የተለያየ ስለሆነ አንድ ዓይነት ክስ አይደለም የሚል ነዉ፡፡

በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/130 ላይ እንደተመለከተዉ የክሱ ማመልከቻ ላይ ተከሳሹ መቃወሚያ ሊያቀርብ ከሚችልባቸዉ ምክንያቶች አንዱ በዚሁ ነገር ክስ በሌላ ፍርድ ቤት ተጀምሮ በቀጠሮ ላይ ያለ መሆኑን መሰረት በማረጋገጥ ሲቻል ነዉ፡፡የአመልካች ጠበቃ በሁለት ፍርድ ቤቶች በመሸሸግ ወንጀል ክስ የቀረበበት መሆኑ አላከራከረም፡፡ ስለሆነም በሁለቱ ፍርድ ቤቶች የተያዘዉ ክስ አንድ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን እና የቀረበዉ መቃወሚያ በህግ ተቀባይነት አለዉ ወይስ የለዉም የሚሉ ነጥቦች መዝገቡን ለያዘዉ ፍርድ ቤት የተተወና ፍርድ ቤቱ አጣርቶ ብይን የሚሰጥበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች በዚህ መልክ ያቀረቡት መቃወሚያ በህግ የተፈቀደ ስለመሆኑ ከወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ/130/2/ሀ ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ የአመልካች ደንበኛ በሁለት የተለያዩ ፍርድ ቤቶች የተከሰሱት በመሸሸግ ወንጀል መሆኑን መሰረት አድርገዉ አመልካች መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን እንደአቃቤ ህግ ክርክር የክሶቹ ዝርዝር ይዘት ሲታይ የተሸሸገዉ ንብረት ዓይነትና የንብረቶቹ ባለቤቶች የተለያዩ መሆንን መሰረት አድርጎ የክሱ ነገር አንድ ነዉ ወይሥ አይደለም የሚለዉን ለይቶ መቃወሚያዉ የወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ130 2/ሀ ድንጋጌ ይዘት ያሟላል ብሎ መቀበል ወይም ዉድቅ ማድረግ ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ የሚሰጥበት ስለመሆኑ ከወ/መ/ስ/ስ/ህግ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ቁ/131 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የአመልካች ደንበኛ ላይ በሁለት ፍርድ ቤቶች በመሸሸግ ወንጀል ክስ ቀርቦ ያለ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች በህግ የተፈቀደዉን መቃወሚያ ማቅረባቸዉን የሚያሳይ እንጂ አመልካች የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር መፈጸማቸዉን የሚያረጋግጥ ባለመሆኑ የአመልካች ተግባር በአዋጅ ቁ/262/07 አንቀጽ 30/23/ስር የሚያሥቀጣ ሆኖ አላገኘንም፡፡ስለዚህም በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ዉሳኔ

1. በዚህ ጉዳይ አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ ክርክር የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ፈጽመዋል በሚል የትግራይ ክልል የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ በ06/01/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/101364 ላይ በ06/06/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ይጻፍ፡፡
2. አመልካች በደንበኛቸዉ ላይ ለቀረበዉ የወንጀል ክስ ያቀረቡት መቃወሚያ ምክንያት በህግ የተፈቀደ በመሆኑ ፍርድ ቤት መርምሮ ዉሳኔ የሚሰጥበት እንጂ የጥብቅና ሙያ የሚያጎድፍ ተግባር ነዉ ተብሎ በዲስፕሊን የሚያስቀጣ ተግባር አይደለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጌ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

የሰ/መቁ.142851

ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ወርቅነሽ ጌታቸው
2 አቶ አስፋው አምደ } ጠበቃ አቶ ታደለ ገ/መድህን-ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ኮሬ ባዊ
2. ወ/ሮ ፀሐይ ባዊ } 1ኛ ተጠሪ ከጠበቃቸው አቶ አብዱረሃማን መሐመድ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የነገሩ አመጣጥ የንግድ ማኅበር ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበውና የታየው በግልግል ዳኝነት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች /የሥር አመልካቾች/ ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የተሻሻለ የክስ አቤቱታ የሽርክና ውል በመፈራረም "ፕላዛ አዲስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር" የተባለ ማኅበር ለማቋቋም በምንቀሳቀስበት ሂደት ውስጥ ተጠሪዎች በሽርክና ውል ለመሳተፍ የፈለጉ በመሆኑና አመልካቾችም በመስማማታቸው ይህንኑ አስመልክቶ መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመናል፤ በፕላዛ አዲስ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሥር ከሚጠቃለሉት ንብረቶችና ፈቃዶች ጭምር የህንፃው ሥራ ሙሉ ለሙሉ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተጠናቀቀና ለሆቴሉ ሥራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና እቃዎች ሁሉ ከተሟሉ በኋላ አጠቃላይ የንብረቱ ዋጋ ብር 130,000,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ሚሊዮን/ እንዲሆን እንደዚሁም ከዳሽን ባንክ የተወሰደ ብድር በተጠቀሰው የማጎበሩ ካፒታል ውስጥ የተካተተ መሆኑን ተዋዋይ ወገኖች ተስማምተናል፤ ከዚህ ካፒታል ውስጥ የተጠሪዎች ድርሻ 40% ወደ ገንዘብ ሲቀየር ብር 52,000,000 /አምሳ ሁለት ሚሊየን/ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የባንክ እዳው 40% ድርሻ ብር 24,000,000 /ሃያ አራት ሚሊየን/ ሲቀነስ ተጠሪዎች ቀሪውን ብር 28,664,000 /ሃያ ስምንት ሚሊየን ስድስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ/ ለመክፈል ተስማምተው መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም በተደረገ የመግባቢያ ሰነድ ሲፈረም ከፊል ክፍያ ፈጽመው የሚፈለግባቸውን ቀሪ እዳ የመመሥረቻ ጽሁፉና መተዳደሪያ ደንብ ከመሻሻሉ በፊት ለመክፈል ግዴታ ገብተዋል፤ ይሁንና ተጠሪዎች የሚቀርባቸውን እዳ የመመሥረቻ ጽሁፉና የመተዳደሪያ ደንቡ ከመሻሻሉ በፊትም ሆነ በኋላ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆኑም፤ ተጠሪዎች በውሉ መሰረት ሊከፍሉ የሚገባቸውን በራሳቸው የታመነ ብር 6,399,782.07 /ስድስት ሚሊየን ሶስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ ሁለት ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም/፣ ለሆቴል አግልግሎት ለሚውሉ እቃዎች ግዢ ከትራንስፖርት ጭምር ብር 3,230,687.70 /ሶስት ሚሊየን ሁለት መቶ ሰላሳ ሺህ ስድስት መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሰባ ሳንቲም/ ውስጥ የተጠሪዎች 40% ድርሻ ብር 1,292,275.10 /አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ አምስት ብር ከአስር ሳንቲም/ እና ለከስተም ክሊራንስ ኮንሰልታንሲ ከወጣ ብር 167,052.09 /አንድ መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ ሃምሳ ሁለት ብር ከዜሮ ዘጠኝ ሳንቲም/ የተጠሪዎች ድርሻ ብር 66,820.83 /ስልሳ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ብር ከሰማኒያ ሶስት ሳንቲም/ በድምሩ ብር 7,758,878.00 /ሰባት ሚሊየን ሰባት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ስምንት/ አልከፈሉም፤ በመግባቢያ ሰነዱ አንቀጽ 3 መሠረት የውሉን አፈጻጸም ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ ወገን የውሉን ብር 130,000,000 /አንድ መቶ ሰላሳ ሚሊየን/ 10% የቅጣት ገንዘብ ውሉን ላከበረ ወገን ለመክፈል ግዴታ መገባቱን ገልጸው በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1731 እና 1971 መሠረት ለውሉ አፈጻጸም የአንድነትና የነጠላ ኃላፊዎች መሆናቸው ተረጋግጦ ከላይ የተዘረዘረውን ብር 7,758,878.00 /ሰባት ሚሊየን ሰባት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ስምንት/ የመመሥረቻ ጽሁፉና የመተዳደሪያ ደንቡ ከተሻሻለበት ቀን

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ፣ የጠበቃ አበል፣ የትርጉም፣ የዳኝነትና ልዩ ልዩ ወጪና ኪሳራ ጨምረው እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

የአሁን ተጠሪዎች ታኅሳስ 20 ቀን 2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ አመልካቾች በስምምነቱ መሠረት ህንፃውን ሙሉ በሙሉ የማጠናቀቅ፣ የሆቴሉን እቃና መሳሪያ የማሟላት፣ የሆቴሉ ይዞታ የነበረውን ቦታ በ241 ካሬ ሜትር አስቀንሰው በማስመዝገባቸው በገበያ ዋጋ ለተቀነሰው ቦታ ክፍያ የመፈጸምና በውል መሠረት ሊፈጽሟቸው የሚገቡ ግዴታዎች ስላሉባቸው ግዴታዎቹን ፈጽመናል ሳይሉ ወይም ለመፈጸም ዝግጁነታቸውን ሳይገልጹ መክሰስ እንዳይችሉ የፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1757 የሚያግዳቸው ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ. 39568 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ ይህ እንዳለ ሆኖ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ፊት መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ/ም ላይ የተፈረመው የማኅበሩ የተሻሻለው የመመስረቻ ጽሁፍ ላይ የማህበሩ ካፒታል ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል በማለት የተገለጸ በመሆኑ ተጠሪዎች ለ40 በመቶ ድርሻቸው የሚፈለግባቸውን የገንዘብ መዋጮ ለመክፈላቸው በቂ ማረጋገጫ ነው፤ በሌላ በኩል ተጠቃሹን ገንዘብ ተከሳሾች ይከፍላሉ ያሰኘው ከሳሾችና ተከሳሾች ከግልግል ዳኝነት ጉባኤው ውጪ ክርክራቸውን በሙግት ሳይሆን በእርቅ ይፈታ እንደሆነ ለመሞከር መግባባት ላይ በደረሱበት ወቅት አለመግባባት አስነስተዋል በተባሉ ነጥቦች ላይ የከሳሾችን አመለካከት ወደ ቀና መንገድ ለመመለስ “ ሰጥቶ መቀበል” በሚል ቅን አስተሳሰብ ተከሳሾች ጥቅምት 20 ቀን 2008 ዓ/ም በጻፉት ማመልከቻ ተጠቃሹን ገንዘብ እንዲከፍሉ ከሳሾችም ደግሞ የመስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም ስምምነትን በመተግበር ግዴታቸውን በቅን መንፈስ እንዲወጡ ለማግባባት ይረዳል በሚል የገለጹት እንጂ ግዴታ የገቡበት አይደለም። ስለዚህ አዋዋይ በተገኘበት የተፈረመው ሰነድ ገንዘብ በተከሳሾች መከፈሉ ግራ ቀኙ “ ሁሉንም ተጠቃሚ ሊያደርግ” በሚችል የእርቅ ድርድር ወቅት እንከፍላለን ያሉት ገንዘብ በፍርድ ቤት፣ በፍርድ ሰጭ አካል፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤት እንደታመነ ወይንም በቃለ መኻላ እንደተረጋገጠ እዳ ተቆጥሮ ተጠያቂነት ያስከትላል የሚለው የከሳሾች አካሄድ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከዚህ በኃላ የአሁን ተጠሪዎች 14 ነጥቦችን በማንሳት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ያቀረቡ ሲሆን የአሁን አመልካቾችም /የከሳሽ ተከሳሾችም/ ከሥልጣን ጋር ተያይዞ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም ለፍሬ ነገሩ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የግልግል ጉባኤ በተከሳሽ ከሳሽነት ከቀረቡት አስራ አራት ነጥቦች መካከል በተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 7 እና 14 ላይ የቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄዎችን ለመመልከት ሥልጣን እንዳላቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ በተራ ቁጥር 5፣ 6፣ 11፣ 12 እና 13 ሥር ተጠቅሰው የቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄዎችን መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም በተደረገው መግባቢያ ሰነድ መሠረት የግልግል ዳኝነት አካሉ ለመመልከት ሥልጣን እንደሌለው እንዲሁም በተራ ቁጥር 8፣ 9 እና 10 ሥር ተጠቅሰው የቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄዎችን በተመለከተ የክስ ምክንያት የሌላቸው መሆኑን ገልጾ ጥር 26 ቀን 2008 ዓ/ም ብይን ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኃላ የግልግል ጉባኤው በፍሬ ነገሩ ላይ ግራ ቀኙን በማከራከርና ምስክሮችን በመስማት እንዲሁም ሰነዶችን በመመርመር አመልካቾች ተጠሪዎች በጽሁፍ አምነዋል በማለት እንዲከፍሏቸው የጠየቁትን ብር 6,399,782.07 /ስድስት ሚሊየን ሶስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ ሁለት ብር ዜሮ ሰባት ሳንቲም/ በተመለከተ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 4,276,900 /አራት ሚሊየን ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ/ የሚሆነው በመግባቢያ ሰነዱ ላይ ተጠሪዎች ላይ ከተጣለው ግዴታ ጋር ግንኙነት የለውም በማለት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት ሳይቀበለው የቀረ ሲሆን ቀሪውን ብር 2,122,882.00 /ሁለት ሚሊየን አንድ መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ሁለት/ ክፍያ ጥያቄን በተመለከተ ተጠሪዎች በመግባቢያ ሰነድ፣ በተለያዩ ደረሰኞች እንዲሁም ቼክ የሚፈለግባቸው ክፍያዎችን ከፍለው በሰነዶች ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ ስለሆነ አመልካቾች ገንዘብ አልተከፈለንም በማለት ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልንም፤ አመልካቾች ለሆቴሉ አስፈላጊ የሆኑ እቃዎችና መሳሪያዎችን ለማሟላት አወጣን ያሉትን ገንዘብ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የጠየቁትን በተመለከተ መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም በተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ እቃዎችና መሳሪያዎችን የማሟላት ግዴታ የአመልካቾች በመሆኑ የጠየቁትን ክፍያ በሚመለከት ይህ ክፍያ ሆቴሉ በተገመተበት ሰላሳ ሚሊየን ብር ውስጥ የሚጠቃለል

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከሚሆን በቀር ለብቻው ተነጥሎ በመውጣት በተጠሪዎች ክፍያ እንዲፈጸምበት ሊጠየቅ የሚችልበት ሆኖ አልተገኘም፤ አመልካቾች ያቀረቡት ለስተምስ ኪሊራንስ እና ኮንሰልተንሲ የተከፈለ ብር 66,820.83 ይከፈለን ጥያቄ የውል ድጋፍ የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡትን የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ በተመለከተ የግልግል ጉባኤው ሥልጣን አለኝ በማለት የተመለከታቸውን ነጥቦችን በተመለከተ 1ኛ/ ስፋቱ 1280 ካሬ ሜትር የሆነ ለመኖሪያነት በአሁን አመልካቾች ስም የተሰጠውን ይዞታ ካርታ ሲዘጋጅ ስፋቱ 1039 ሆኖ የተሰራ በመሆኑ የ241 ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ ሽያጭ ዋጋ ተመን ብር 6,319,261 /ስድስት ሚሊየን ሶስት መቶ አስራ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ/ የአሁን አመልካቾች ይክፈሉ በማለት የአሁን ተጠሪዎች የጠየቁትን በተመለከተ የግልግል ጉባዔው የተጠቀሰውን ቦታ በተመለከተ በቦሌ ክፍሌ ከተማ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሚያዝያ 3 ቀን 2008 ዓ/ም በጻፈው ደብዳቤ የይዞታው ስፋት የቀነሰው በመንገድ ጥናት ምክንያት መንገድ የሚወስደው ተቆርጦ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ገልጾ ተጠሪዎች ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የቀነሰው የይዞታ ስፋት በአካባቢው የሊዝ ዋጋ ተሰልቶ ድርሻቸው የይዞታ ዋጋ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን ጥያቄ የግልግል ጉባኤው አልተቀበለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፣ 2ኛ/ ከመተዳደሪያ እና መመሥረቻ ጽሁፍ ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር በተመለከተ መተዳደሪያ ደንቡ እና መመሥረቻ ጽሁፉ የተሻሻለ መሆኑ ማረጋገጡን፣ ተጠሪዎች በተሻሻለው ጽሁፍና ደንብ ውስጥ መካተት የሚገባቸው ጉዳዮች አልተካተቱም የሚሉ ከሆነ በንግድ ህጉ እና በተሻሻለው የመመሥረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት አጀንዳ አስይዘው እንዲካተቱ ለመጠየቅ የሚችሉ ከሚሆኑ በስተቀር በመግባቢያ ሰነዱ መሠረት መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ/ም ቃለ ጉባኤ ተይዞ የተሻሻለ መመሥረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ የቀረበ በመሆኑ አልተሻሻለም የሚያስብል በቂ ምክንያት የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበ የተጠሪዎች ክርክር ጉባኤው አልተቀበለውም በማለት አስቀምጧል። 3ኛ/ ከህንጻ ጋር በተያያዘ ህንጻው ጥራት የሚጎለው ከመሆኑ እንዲሁም አስፈላጊ መሳሪያዎችና እቃዎች ካለመሟላታቸው ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር በተመለከተ የህንፃው ሥራ ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቅ አለመጠናቀቁን ለመረዳት ይቻል ዘንድ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው በጉዳዩ ላይ

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ከተጠሪዎች የተቆጠሩ ምስክሮችን አስቀርቦ ማዳመጡን እንዲሁም የሆቴሉን ህንፃ ቦታው ድረስ ሄዶ መመልከቱን ገልጾ አመልካቾች በክርክራቸው ሆቴሉ ስለመጠናቀቁና እቃዎችና መሳሪያዎችም አለመሟላታቸው ሆቴሉ ባለ4 ኮከብ የሚል ደረጃ የተሰጠው ስለመሆኑ አስረጅ ነው በማለት የተከራከሩ ቢሆንም በተለይም ሆቴሉ የኮከብ ደረጃ ሲሰጠው ሆቴሉ ሳያልቅ እንዳለቀ፣ ለሆቴሉ ሥራ አስፈላጊ መሳሪያዎችና እቃዎች ሳይኖሩና ሳይሟሉ እንዳሉና እንደተሟሉ ተደርጎ የተሰጠው መሆኑን የተጠሪዎች ምስክሮች በተለይም 2ኛ ምስክራቸው በማያሻማ መልኩ ያስረዱ በመሆኑ አመልካቾች ሆቴሉ ስለመጠናቀቁና አስፈላጊ እቃዎችና መሳሪያዎችም የተሟሉለት ስለመሆኑ የተሰጠው ባለ4 ኮከብ ደረጃ ነው በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ ጉባኤው አልተቀበለውም ካለ በኋላ አመልካቾች መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም በተፈረመ የመግባቢያ ሰነድ መሠረት የሆቴሉን ሥራ ሙሉ ለሙሉ ባለማጠናቀቃቸው እና ለሆቴሉ የሚያስፈልጉ እቃዎችና መሳሪያዎችንም ባለማሟላታቸው በራሳቸው ወጪ የህንፃውን ሥራ ሊያጠናቅቁና አስፈላጊ እቃዎችና መሳሪያዎችንም ሊያሟሉ ይገባል ሲል የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ፍርድ ሰጥቷል፡፡ 4ኛ/ ተጠሪዎች አመልካቾች ከሆቴሉ ከውል ወጪ ገንዘብ ወጪ አድርገዋል ተብሎ የቀረበውን በተመለከተ የግልግል ጉባኤው ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር ካለፈቃዳችን ከሆቴሉ የወጣ ወጪ ከነወለዱ ተመላሽ ይደረግ ቢሉም ምን ያህል ገንዘብ፣ መቼ እንደወጣ ግን በግልጽ በክርክራቸው አላመለከቱም፣ ይልቁንም አመልካቾች በጥሬ ገንዘብ ከሆቴሉ ያወጡትን ያሳውቁን ማለታቸው በግልጽ ምን ያህል ገንዘብ እንደወጣ እየጠቀሱ ክርክራቸውን እያቀረቡ እንዳልሆነ ያሳያል፣ ይህ ብቻ ሳይሆን ከሆቴሉ ያለፈቃዳቸው ገንዘብ ስለመውጣቱ ለማስረዳት ያቀረቡት አስረጅም የለም፡፡ ስለዚህ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ ግልጽ ያልሆነና የማስረጃ ድጋፍም የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም በማለት ወስኗል፡፡ 5ኛ/ አመልካቾች ከተጠሪዎች እውቅና ውጪ ከዳሽን ባንክ በብድር የወሰዱትን ብር 2,000,000.00 /ሁለት ሚሊየን/ በተመለከተ ተጠሪዎች ተጠያቂነት እንደሌለባቸው ገልጸው ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ምንም እንኳን የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ጥር 26 ቀን 2008 ዓ/ም በመዝገቡ ላይ በሰጠው ብይን ከብር ሁለት ሚሊየን ጋር በተያያዘ የተነሳውን ክርክር ተመልክቶ ለመዳኘት ሥልጣን አለኝ ያለ ቢሆንም ግራ ቀኙ መጋቢት 12 ቀን 2008

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

ዓ/ም ባስመዘገቡት ክርክር ለክስ መነሻ የሆነው ገንዘብ መግባቢያ ሰነዱን መሰረት አድርጎ የተነሳ አለመሆኑን ከብይኑ በኃላ ያረጋገጡ በመሆኑ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ተጠሪዎች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ተመልክቶ ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም በማለት በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 9/2/ መሠረት በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪዎችን ክርክር ውድቅ አድርጓል ሲል ወስኗል፡፡

በግልግል ጉባኤ 2ኛ ዳኛ የሆኑት አመልካቾች ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ያቀረቡት ብር 6,399,782.07 በተመለከተ በተጠሪዎች በጽሁፍ የታመነ እዳ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው እዳው የታመነበት ሁኔታ ግምት ውስጥ ገብቶ እንዲሁም ተጠሪዎች እዳ ከፍለናል በሚል ያቀረቧቸው ማስረጃዎች በጽሁፍ ከመታመኑ በፊት የተከፈሉ ናቸው፤ በመሆኑም በቅርብ በጽሁፍ የታመነ እዳ ለማስተባበል በቂነት የላቸውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ለአመልካቾች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ከአብላጫ ድምፅ ተለይተዋል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች 1ኛ/ የግልግል ጉባዔው አመልካቾች ግዴታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ተብሎ የቀረበውን መቃወሚያ የግልግል ጉባዔው አልፎ ጉዳዩን መመልከቱ ያለአግባብ ነው፣ 2ኛ/ የ241 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ፣ 3ኛ/ የሥር መልስ ሰጪዎች /የአሁን አመልካቾች/ ለሆቴሉ መኝታ ለተገለገሉበትና ለሆቴሉም ምግብ ለተጠቀሙበት ለሆቴሉ ወይም ለማኅበሩ ገንዘቡን እንዲከፍሉ ይወሰንልን በሚል የተጠየቀውን ዳኝነት ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ያለአግባብ እንደሆነ፣ 4ኛ/ ከማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሻሻል እና ከሆቴሉ ስያሜ ጋር የተነሳውን ክርክር የግልግል ዳኝነት ተመልክቶ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም፣ 5ኛ/ የአሁን አመልካቾች ከዳሽን ባንክ የወሰዱትን ብር 2,000,000 /ሁለት ሚሊየን/ ጋር በተያያዘ ግልግል ጉባኤው ሥልጣን አለኝ በማለት ካከራከረ በኋላ ተመልሶ ሥልጣን የለኝም ማለቱ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፡፡ 6ኛ/ ውል ያላከበረ ወገን የ130,000,000 ብር 10% እንደሚከፍል መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም በተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ላይ በተቀመጠው መሠረት የአሁን አመልካቾች ውሉን ባለማክበራቸው በውሉ የተጠቀሰውን ገንዘብ እንዲከፍሉ የተጠየቀውን ዳኝነት የግልግል ጉባኤው በግልጽ ውሳኔ መስጠት ሲገባው በዝምታ ማለፉ ያለአግባብ ነው በማለት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በሌላ በኩል የአሁን አመልካቾች ያቀረቡት መስቀለኛ ይግባኝ 1ኛ/ ብር 7,758,878.07 የአሁን ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የጠየቁት ዳኝነት ውድቅ መደረጉን የሚመለከት ሲሆን 2ኛው ከሆቴሉ አገልግሎት አሰጣጥ እና እቃዎች አለመሟላት ጋር በተያያዘ የግልግል ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ በየበኩላቸው ያቀረቡትን ይግባኝ ተቀብሎ ካከራከረ በኃላ የቀረቡትን ቅሬታዎችን መርምሮ የግልግል ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት እንዲሁም ከውል አለመፈጸም ጋር የተነሳውን የአንድ መቶ ሰላሳ ሚሊየን 10% ውሳኔ ሳይሰጥ በዝምታ ታልፏል የተባለውን በተመለከተ ጉባኤው በግልጽ የሰጠው ውሳኔ ባይኖርም በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገው ውል ባህርይ፣ እንዲሁም መልስ ሰጪዎች /የአሁን አመልካቾች/ የሰጡት የውል ድንጋጌ የትኛው እንደሆነ ግልጽ ሆኖ የማይታወቅ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ መልስ ሰጪዎች /የአሁን አመልካቾች/ ውሉን ጥሰዋል ተብሎ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም አመልካቾች ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የጠየቁትን ብር 6,399,782.07 በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካቾች ተፈጽሞብናል ያሏቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ ተጠሪዎች በጽሁፍ ያመኑትን አይከፍሉም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ መቃወሚያ እና በአማራጭ ክፍያው ስለመፈጸሙ ዝርዝር መልስ አቅርበው የተከራከሩ ሲሆን የአመልካቾች ጠበቃም ጥቅምት 17 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበው ተከራክረዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን የአመልካቾችን የቅሬታ ነጥብ የግልግል ጉባዔው ከሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ እንዲሁም በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክር አንጻር

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

መርምረናል፡፡ በግልግል ጉባዔም ሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሰጡት ውሳኔዎች ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ወይስ አልተፈጸመበትም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡የአሁን አመልካቾች ካቀረቡት ዳኝነት መካከል ከብር 6,399,782.07 /ስድስት ሚሊየን ሶስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ ሁለት ብር ዜሮ ሰባት ሳንቲም/ ውስጥ 4,263,460 /አራት ሚሊየን ሁለት መቶ ስልሳ ሶስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ / ብር በተመለከተ በመግባቢያ ሰነዱ ላይ በአሁን ተጠሪዎች ላይ ከተጣለው ግዴታ ጋር ግንኙነት የሌለው ነው በማለት የግልግል ጉባኤው አልፎታል፡፡ ቀሪውን ገንዘብ በተመለከተ ግን የአሁን ተጠሪዎች በመግባቢያ ሰነድ፣ በተለያዩ ደረሰኞች እንዲሁም በቼክ ለአሁን አመልካቾች ከፍለዋል ሲል በማስረጃ አረጋግጦ የአሁን ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ወስኗል፡፡ የግልግል ጉባዔው ውሳኔ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው የግልግል ጉባዔው መመልከት አልችልም ካለው ገንዘብ ውጪ ያለው በተለያዩ ሰነዶች ገቢ የሆነ መሆኑንና ይህም ገቢ ስለመደረጉ በሰነዶች ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑን ነው፡፡ የግልግል ጉባኤው መስከረም 15 ቀን 2006 ዓ/ም ከተደረገው የመግባቢያ ሰነድ ውጪ ነው ያለውን ገንዘብ በተመለከተ አመልካቾች መብትና ጥቅም ካላቸው ለፍርድ ቤት አቅርበው ከሚያስወስኑ ውጪ መሠረታዊ የህግ ስህተት እንደተፈጸመ አድርገው ለዚህ ችሎት ያቀረቡትን ስንመለከት ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ እንዲሁም ተጠሪዎች ለመክፈል በጽሁፍ አምነው የነበረውን ገንዘብ በቃለ መኻላ ሥር ሆነው ስለመክፈላቸው ቃል በመስጠታቸውና በክርክር ሂደት ያቀረቡትን ማስረጃዎችን የግልግል ጉባዔው ተቀብሎ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በሚል የቀረበውን ቅሬታ በተመለከተ ተጠሪዎች የሚፈለግባቸውን ድርሻ ከፍለው ስለመክፈላቸውም በሰነዶችና ምዝገባ ጽ/ቤት ከተመዘገበ በኋላ የምንከፍል ገንዘብ አለብን በማለት በጽሁፍ መተማመኛ ቢሰጡ ይህ ከአዋጅ ቁጥር 334/1995 አንጻር መታየት ያለበት ነው፡፡ በዚህ አዋጅ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ፊት ቀርቦ የተረጋገጠና የተመዘገበ ሰነድ ደግሞ በውስጡ ስለሚገኘው ይዘት ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ስለመሆኑ በአንቀጽ 27/1/ ሥር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የሥር ግልግል ጉባኤም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

www.fsc.gov.et
https://t.me/ethiopianlegalbrief

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር የተመለከቱትን መሠረታዊ ነገሮችን የግልግል ጉባኤው ተመልክቶ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ አከራክሮ በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. የግልግል ጉባኤው ጥር 26 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ብይን እና ሰኔ 13 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 130348 በ18/08/2009 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በግልግል ጉባኤውም ሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሰጡት ውሳኔዎች ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች ቅፅ - 24

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ውሳኔዎች



ቅፅ- 24

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክረሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት



የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ-24

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ታህሣሥ 2013 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ድህረ-ገፅ፡-www.fsc.gov.et
ስልክ፡-+251-111-55-34-00/+251111733031
ፋክስ፡-+251-111-56-55-33
የመ.ሣ.ቁ. 6166
ነፃ የስልክ መስመር፡- 992



<u>የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

በአዋጅ ቁ. 454/1997 አንቀጽ 2 ሥር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በሁሉም ደረጃ ባሉት የፌደራል እና ክልል ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት እንዳለው በግልጽ ተደንግጓል። የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ዓላማዎችም በሀገሪቱ ውስጥ የሚወጡ ህግጋት ወጥነት ባለው መንገድ እየተተረጎሙ ሥራ ላይ እንዲውሉ እንዲሁም ተመሳሳይ የፍሬ ነገር እና የህግ ክርክር ያለባቸው ጉዳዮች ተመሳሳይ የፍርድ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለማስቻል ነው። እንደዚህ ዓይነቱ አካሄድ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን በዋናነት ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት የፍርድ ውሳኔዎች ጥራት፣ ተገማችነትና ተዓማኒነት እንዲጨምር ይረዳል፤ የፍርድ ቤቶችና የባለጉዳዮች ጊዜ፣ ጉልበት እና ገንዘብ አላስፈላጊ ላልሆኑ ወጪዎችና ብክነት እንዳይዳረጉ ያግዛል ፤ የህግና ፍትህ ስርዓቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ በተናበበ መልኩ እየዳበረ እንዲሄድ የበኩሉን አስተዋጽዖ ያደርጋል። እነዚህ ዓላማዎች ለማሳካት ይቻል ዘንድ አዋጁ በአንቀጽ 2 ሥር በሰበር ችሎቱ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች አሳትሞ ለሁሉም ፍርድ ቤቶች የማሰራጨት ኃላፊነት ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሰጥቷል። በዚህ መሰረት የሰበር ችሎቱ አስገዳጅ ውሳኔዎች በጥራዝ መልክ እየታተሙ ያሉ ሲሆን እነሆ አሁን 24ኛ ቅጽ ላይ ደርሷል። ከዚህ በተጨማሪም ውሳኔዎቹ ለሁሉም አካላት በሁሉም ቦታ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ በፍርድ ቤቱ ድህረ ገጽ ላይ እንዲለቀቁ ይደረጋል።

ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት እያደገና እየዳበረ እንዲሄድ አስገዳጅ የሆኑ የሰበር ውሳኔዎች ለሁሉም አካላት ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ወሳኝ ቢሆንም ብቻውን ግን በቂ አይደለም። ከሁሉም በላይ ፍርድ ቤቶች በሚያሳልፏቸው የፍርድ ውሳኔዎች ላይም ሆነ አጠቃላይ በዳኝነት ሥርዓቱ ላይ ምርምር፣ ምሁራዊ ክርክሮችና ትችቶችን ማድረግ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም በዚህ ረገድ ፍርድ ቤታችን ከሁሉም ባለድርሻ አካላት እና የህግ ባለሙያዎች የሚቀርቡትን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን ከወዲሁ ለመግለጽ እወዳለሁ፤ አመሰግናለሁ።

ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ መንግስቱ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር መልዕክት

ክቡራን የሰበር ውሳኔዎች ቅጾች አንባብያንና ተጠቃሚዎች!

በቅድሚያ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጣቸው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎች መታተም ከጀመሩበት ከ1997 ዓ.ም አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ገንቢ አስተያቶችንና ትችቶችን በመሰጠት አብራችሁን በመዝለቃችሁ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ስም ልባዊ ምስጋናችንን ማቅረብ እንፈልጋለን።

አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠባቸው የሰበር ሰሚ ውሳኔዎች ለተመሳሳይ ጉዳዮች ውሳኔ ለመስጠት ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በተጨማሪ ለህግ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መማሪያነት፣ ለተለያዩ ህግ እና ህግ ነክ ለሆኑ ጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲሁም ለሌሎች ህግን ማወቅ ለሚፈልጉ አካላት የሚሰጡት ጥቅም ሊለካ የሚችል አይደለም። ነገር ግን የውሳኔዎቹ መታተም ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ለህብረተሰቡ ከሚሰጡት ጥቅም በተጨማሪ የህትመቱና የውሳኔዎቹ ባለቤት የሆኑት ፍ/ቤቶችም በውሳኔዎቹ ላይ በሚቀርቡ አስተያየቶችና ውሳኔዎቹን መሰረት አድርገው በሚሰሩ የጥናትና ምርምር ስራዎች ተጠቃሚ መሆናቸው የማይካድ ሃቅ ነው። ይህም ለፍትህ ስርዓቱ መሻሻል እንደዚሁም ለዚሁ ለሰበር ስርዓት መዘመን ጉልህ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለን እናምናለን።

በዚህም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የጥናትና ህግ ዳጋፍ ዳይሬክቶሬት እነዚህንና ሌሎች ህትመቶችን አሳትሞ በማሰራጨት ረገድ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ጥረት የሚያደርግ ሲሆን አንባብያንና ተጠቃሚዎችም እንደከዚህ ቀደሙ አስተያየቶችን በመስጠት ተሳትፏችሁ እንዳይለየን በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን።

አመሰግናለሁ!

አሮን ደጎል ሃብቱ

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ማውጫ /ቅፅ 24/

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት				1
1.	ፍ/ቤቶች የፍ/ቤቱን የስራ ቋንቋ የማይችሉ ተከሳሾች በቀረቡላቸው ጊዜ አስተርጓሚ በመመደብ ክሱ በሚገባቸው ቋንቋ በዝርዝር የመንገር እና በጠበቃ ታግዘው የመከራከር መብት እንዳላቸው፤ ጠበቃ ለማቆም የሚያስችል ዓቅም ከሌላቸው በመንግሥት ወጪ ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳላቸው የመንገር ሀላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ አንቀጽ 9/4 እና 13(1)(2)፣20፣የሲቪል እና የፖለቲካ መብት አንቀጽ 14	160916	አቶ ቦጃ በየነ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ	ታሕሣሥ 30 ቀን 2011 ዓ.ም	2
2.	ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በሽማግሌዎች እንዲታይ ወደውና ፈቅደው ከተስማሙ በኋላ ሽማግሌዎች የሰጡት ውሳኔ ባለበት ሁኔታ በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት ይግባኝ በመጠየቅ እንዲታረም ከማድረግ በስተቀር አዲስ ክስ ማቅረብ ተገቢ ስላለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3325፣የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 244/2/ረ/	161062	አቶ መህዲ ሸረፋ እና አቶ ሻፊ ሸረፋ	26/04/2011 ዓ/ም	7
3.	ከሳሽ ወገን ክስ በሚሰማበት ወቅት ያላቀረበው ማስረጃ መኖሩን በበቂ ምክንያት በማስደገፍ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ባገኘበት ሁኔታ ተከሳሽ የመከላከያ መልሱን እንዲያሻሽል የሚያቀርበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ	160314	የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና	30/09/2011	10

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በተሟላ መልስ ባልተከራከረበት ሁኔታ ተከሳሽ ከሳሽ ባቀረበው ሰነድ ላይ አስተያየቱን በጽሁፍ ብቻ ያቅርብ ብሎ የመደመጥ መብቱ ሊታለፍ የማይገባው ስለመሆኑ የፌዴራል ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ፤ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ91፤137(1) ፣223፣256		ቢጋና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር		
4.	አንድ የግልግል ጉባኤ ከቤቶች የባለሀብትነት መብት ጋር የተያያዘ የመፋለም ክርክርን ተቀብሎ ውሳኔ ለመስጠት የዳኝነት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 እና 78፤የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 ፣3325 ፣3329	137302	ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ እና አቶ ተመስገን ደምሴ	ታህሳስ 26 ቀን 2010 ዓ.ም	15
5.	በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የተቋቋሙ የጎብረት ሥራ ማኅበራት ከሳሽ በመሆን የሚያቀርቧቸዉን ክሶች በተመለከተ የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሳይሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11(1/ለ) እና 14(2)፤የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ)፤በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 46/2004 /የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997 መሰረት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁጥር 90421 ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም ውሳኔ ተለውጧል።/	165289	ወ/ሮ ወሰኔ ገብረዮሐንስ እና የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ቀበሌ 11/12/08 የሸማቾች ኃላ/የተ/የጎብረት ሥራ ማኅበር	መጋቢት 29 ቀን 2012 ዓ/ም	22

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
6.	• የወራሽነት የምስክር ወረቀትን በተመለከተ የሚቀርብ የተቃውሞ አቤቱታ የማስረጃውን ትክክለኛነት እና ህጋዊነት ከማረጋገጥ ያለፈ አንድምታ የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ማስረጃውን የሰጠው ፍርድ ቤት የማስረጃው ይሰረዝልኝ ጥያቄን ማስተናገድ የሚገባው ስለመሆኑ • በሐሰት ለተገኘ የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ የአስር አመት የይርጋ ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000፣1677፣1845 እና 1846 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 እና 359	161650	አቶ ኃይለገብርኤል አየለ እና ወ/ሮ ፀሐይ አየለ	ሚያዚያ 29 ቀን 2011 ዓ/ም	33
7.	አንድ ተከራካሪ ወገን በፍ/ቤት ፈቃድ ክሱን የተወ እና አዲስ ክስ ባቀረበ ጊዜ በቀረበው አዲስ ክስ ላይ በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የቀረቡት እና በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች ተመርምረው እና ተመዝነው ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ አስቀድሞ በፍ/ቤት ፈቃድ በተዘጋው መዝገብ ላይ ቀርበው በነበሩ ማስረጃዎች መሠረት ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ ስላለመኖሩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278	161301	እነ አቶ አዲስ አልታሰብ እና የፋርጣ ወረዳ ቋልሀ ቀበሌ አስ/ጽ/ቤት	ሚያዝያ 30 ቀን 2011 ዓ.ም	38
8.	አንድን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ሲሰማ በነበረበት ፍርድ ቤት በክሳሽነትም ሆነ ተከሳሽነት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ተከራካሪዎች በቀረቡበት	165616	አቶ ፈለቀ ታደሰ እና	ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ/ም	43

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መዝገብ ላይ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በተናጠል ይግባኝ ያቀረበ እንደሆነ በአንድ በይግባኝም ሆነ በሰበር ችሎት በቀረበ ጉዳይ ላይ በመዝገቡ ላይ ያልቀረቡት ቀድሞ የክርክሩ አካል የነበሩት አካላት በሌላ መዝገብ ላይ ቀርበው ከሆነ ተገቢ ማጣራት እና ክትትል ተደርጎ መዝገቦቹ ተጣምረው እንዲታዩ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 331		እነ አቶ ሣሙኤል ሱሊቶ		
9.	ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር በቅን ልቦና እና እውነትነት ባለው ማስረጃ የማይከራከሩ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው ነገር እውነት መሆኑን ባልተረዱ እና ፍፁም ድብቅ በሆነባቸው ጊዜ እውነት ላይ ለመድረስ በሀሰተኛ ማስረጃ እና በሃሰተኛ ተከራካሪዎች ቅን ልቦና መጉደል ምክንያት እውነትን የያዙ ሰዎች ላይ ያልተገባ ፍርድ እንዳይሠጥ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ትክክለኛ ነው ያሉትን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ	168094	አቶ ምስጋናው አሰጌ እና እነ አቶ አይናዲስ አሰጌ	ታህሳስ 22 ቀን 2012 ዓ.ም.	47
10.	የአፈፃፀም ችሎት በፍርድ ባለመብትና በፍርድ ባለዕዳ መካከል አንድን ቤት በዓይነት ለመካፈል ስምምነት እንደሌለ በማረጋገጥ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሰጠ እና ግራቀኙም በቀረቡት ተጫራቾች ሐራጁ እንዲቀጥል በፊርማቸው አረጋግጠው ቤቱ የተሸጠ ከሆነ የሐራጁ የሽያጭ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወይም በማጭበርበር ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ስላለመሆኑ	165775	የአቶ ተሾመ ጎርፌ ወራሽ መቅደስ ተሾመ እና ወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኝ	የካቲት 29 ቀን 2011ዓ.ም	53

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445				
11.	አንድን ክስ በመጀመሪያ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የተሰጠን ዉሳኔ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከሻረው በኋላ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተገቢዉን እንዲወስን መመለስ ሲገባው ያን ሳያደርግ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ራሱ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ ሊፈጠር የሚችለዉን ስህተት ለማሳረም ይግባኝ የማቅረብ መብትን ከማስፋት አንፃር ታይቶ ተፈፃሚነት ሊኖረዉ የሚገባውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ አንቀፅ 341 ድንጋጌን ትክክለኛ አፈፃፀም ያልተከተለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ አንቀፅ 341	163166	አቶ መስጠፉ መሐመድ እና አቶ ናስር ኢሳ	ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም	58
12.	ለአንድ ክስ መሻሻል ወይም ለክርክሩ መለወጥ ቀደም ሲል የቀረበን የክስ ምክንያት በሌላ የክስ ምክንያት በመቀየር ለመሟገት ማቅረብ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ነው በሚል ክስ እንዲሻሻል የሚፈቀድበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ /በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91/1/2/	161736	አቶ ተጫነ ካሳ እና እነ አቶ ባህረ ሀፍቱ	ግንቦት 29ቀን 2011 ዓ.ም	61
13.	• ፍ/ቤቶች ተከራካሪ ወገኖች በሚያቀርቡት ክስ ላይ ያቀረቡትን መቃወሚያ እና በክሱ መነሻነት የቀረበ የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ ካለ ራሱን ችሎ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ክርክር ስለሆነ የተከሳሽ	173416	እነ አቶ ዮሐንስ ዘውዴ አበራ እና	ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም	68

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ከሳሽነት ክሱ ላይ ተገቢውን ሀተታ በማስፈር አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ ወይም ብይን መስጠት የሚገባቸው ስለመሆኑ • በተከራካሪዎች ለዳኝነት በቀረበ ጉዳይ ላይ ፍ/ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት ወይም በተከራካሪዎቹ በሚቀርብ መቃወሚያ መነሻነት የስረ ነገር ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ካረጋገጡ መዝገቡን የስረ ነገር ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ሊያስተላልፉ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 17(3) እና 91(5)፤ 182(3)		ወ/ሮ ተናኜ ማንያህልሀል ላቀው		
14.	• ከመደበኛ ፍ/ቤት ውጭ አንድን ጉዳይ የማየት የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል ጉዳዩን ማየት እንደማይቻል ገልጾ ከመለሰው ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለሌላ አካል ተሰጥቷል የሚል ክርክር እስካልቀረበበት ድረስ መደበኛ ፍ/ቤቱ ይህን ጉዳይ ማየት አልችልም በሚል መመለስ የማይቻል ስለመሆኑ • የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በኤጀንሲው የሚታይ ጉዳይ አይደለም በሚል አረጋግጦ የመለሰው ጉዳይ በስልጣኑ ላይ ሌላ ክርክር እስካልቀረበበት ድረስ ፍ/ቤቶች ተቀብለው ማስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 37፣78(2) እና 79(1)	169716	እነ ወ/ሪት ሰላማዊት ይልማ እና እነ የኢ/ያ ቀይ መስቀል ማህበር ቢታጅራ ቅርንጫፍ	ጥቅምት 24 ቀን 2012 ዓ.ም	72
15.	አንድ የእርቅ ስምምነት በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ከተመዘገበ በኋላ የእርቅ	162106	ወ/ሮ ሙሉ ወንድሙ	ጥር 30/ 2011 ዓ.ም	79

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስምምነቱ የፀደቀበት መዝገብ ባለበት ሁኔታ የእርቅ ስምምነቱን ለማሰረዝ በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ማቅረብ የሚቻልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 274፣277		እና እነ ወ/ሮ ዘመኗ ድንቁ		
16.	በፍርድ ቤት ከቀረበ ክርክር ጋር በተያያዘ ከአስተዳደር ክፍል የሚሰጥ መግለጫ እንደየአግባብነቱ ለፍርድ ቤቱ ከቀረቡት ሌሎች የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ጋር ተገናዝቦ የሚወሰድ እንጂ በራሱ የመጨረሻ ማስረጃ ስላለመሆኑ	169522	አቶ ሲራጅ አባፎጊ እና እነ አቶ አባቦር አባጨብሳ	29/3/2011ዓ/ም	85
17.	በይግባኝ ደረጃ ግራ ቀኝ ወገኖች ለክርክር በተቀጠረበት ቀን ባለመቅረባቸው ተዘግቶ የነበረ መዝገብ በይግባኝ ባዩ አመልካችነት ሲከፈት መልስ ሰጪው እንዲያውቀው ሳይደረግ በሌለበት ውሳኔ መስጠት እና መልስ ሰጪው በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለት የሚያቀርበውን አቤቱታ በቂ ባልሆነ ምክንያት ውድቅ ማድረግ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ አንቀጽ 233	169407	በኬሚካል ኢንዳስትሪ ኮርፖሬሽን ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ እና አቶ ይትባረክ ተካ	29/9/2011 ዓ/ም	92
18.	በሐሰት ማስረጃ የተሰጠ ፍርድ እንዲነሳ የሚቀርብ ጥያቄ በዳግም ዳኝነት ጥያቄ ቀርቦ ከሚስተናገድ በቀር መደበኛ(አዲስ) ክስ በማቅረብ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠየቅበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 6	166205	ገ/ኢየሱስ ሙሉነህ እና እነ አቶ ወልዴ አቡቴ	29/09/2011ዓ/ም	95

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
19.	አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ ነጥብ ለይቶ እስከመለሰ ድረስ የሥር ፍ/ቤቱ በበላይ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ መሰረት ግራ ቀኝ ተካራካሪ ወገኖችን በማከራከር ፣ በመስማት፣ ተገቢውን ጭብጥ በመመስረት እና በማስረጃ በማጣራት ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.246-249፣341(1)	166617	አቶ ገ/መድህን መልካ ጻድቅ እና እነ አቶ ቀነኒ ዲባባ	ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም	98
20.	አንድ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ድርሻን መሰረት በማድረግ የቀረበ ሲሆን አመልካቹ በድርሻው ተመስርቶ ዳኝነት እስከጠየቀ ድረስ ከድርሻው ውጪ ያለውን ግምት መሰረት አድርጎ ዳኝነት እንዲከፍል የሚደረግበት የህግ አግባብ ስላለመኖሩ እና የውርስ ንብረቱ ጠቅላላ ግምት የፍርድ ቤቱን የስረ ነገር ስልጣን ለመወሰን የግድ የሚባልበት የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 14 ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 17 እና 225	167589	ወ/ሮ ጽጌ ታደሰ እና እነ ወ/ሮ አልማዝ ሳህሌ	ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም	102
21.	ግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት አለመግባባታቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (Substantive Law) እንዲሁም በውጪ ሃገር የሥነ-ሥርዓት ህግ መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በውጭ ሃገር ለመቋጨት በተስማሙት መሰረት የተቋቋመው	155880	አግሪኮም ኢንተርናሽናል ኩባንያ እና የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች	ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም	105

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የግልግል ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ታይቶ እንዲታረም የሚቀርብ የሰበር ማመልከቻ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 (በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 እንደተሻሻለ)፤ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 458(ሀ) እና 461(1)(ሀ)		ኮርፖሬሽን		
22.	አንድ በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ለማስፈጸም በኢትዮጵያ እና ፍርዱን በሰጠዉ ፍርድ ቤት አገር መካከል ይህን አስመልክቶ የተደረገ ስምምነት (bilateral agreement) ባይኖርም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 458 ስር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉ ከተረጋገጠ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ፍርዱን ተቀብለዉ ማስፈጸም የሚችሉ ስለመሆኑ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456፣458	161597	ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ እና አቶ ዘሪሁን ተፈራ	ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ.ም	118
ቤተሰብ					**122**
23.	በፍርድ ቤት የጸደቀ የጉዲፈቻ ውል ስምምነት በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ፅ/ቤት ተመዝግቦ የጉዲፈቻ ሰርተፍኬት ስለሚሰጥበት አግባብ አዋጅ ቁጥር 760/2004 አንቀፅ 70(2)፣ መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንቀፅ	173628	እነ አቶ ወ/ጨርቆስ በጋሻው እና በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር	ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም	123

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	43(3)		የወረዳ 13 የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ፅ/ቤት		
24.	በልጅ ቀለብ አወሳሰን ጊዜ የከፋዩን የተጣራ የገቢ መጠን በማጣራት ተገቢ ነው የሚባለው የቀለብ ገንዘብ መጠን መወሰን የሚገባው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት በአንቀጽ 36(2)፣አዋጅ ቁጥር 213/1992 የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 113	172784	አቶ አቡበከር አህመድ መሐመድ እና ወ/ሮ ሳራ ሱፍያን አብዱረህማን	ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም.	127
25.	የኮንደምኒየም ቤት እጣ ከጋብቻ በፊት ወጥቶ የኮንዶሚኒየም ቤቱ የሸያጭ ውል የተፈረመው ወይም የተደረገው በጋብቻ ውስጥ በሆነበት ሁኔታ ለቤቱ የተከፈለው ገንዘብ ምንጭ የሆነው ወገን የግሉ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ቤቱ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት ነው ሊባል የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 255	153405	ወ/ሮ ፅጌ በንቲ እና አቶ ተስፋዬ ታደሰ	ግንቦት13 ቀን 2011 ዓ.ም	131
26.	የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የዉጭ ዜጎች የሀገሪቷን ባህል፣ቋንቋ፣እሴት እንደማያዉቁ የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ አድራጊዎች በጉዲፈቻ የሚወስዱትን ኢትዮጵያዊ ሕፃን የሀገሩን ባህል፣ወግ ፣ልማድና በማህብረሰቡ እሴት ታንፆ እንዳያድግ ተፅዕኖ በማድረግ፣ፍቅር በመንፈግ ለስነ-ልቦናዊና ማሕበራዊ ችግር ያጋልጧቸዋል ብሎ በማሰብ የኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራዎች በሀገር እድገት እና ብልጽግና እንዲሁም ለወገኖቻቸዉ ኑሮ መሻሻል ያላቸዉን ሚና	189201	እነ አቶ ወንድወሰን ታደሰ ይስማ እና የለም	መጋቢት 02 ቀን 2012 ዓ/ም	136

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ባለመገንዘብ ኢትዮጵያውያንን በጉዲፈቻ እንዳይወስዱ መከልከል አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የሕፃናት መብት ኮንቬንሺን አንቀጽ 20 ፤የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደህንት ቻርተር አንቀጽ 24(ለ)፣24(ረ) ፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 36(5)፤ አዋጅ ቁጥር 1070/2010 መቅድም (preamble)፤ ከተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 193፣ 194(3)(መ) ፤ የዉጭ ዜጎችን በትዉልድ ሀገራቸዉ ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 270/1994 አንቀፅ 5 እና 6				
27.	ከወራሾቹ አንዱ ለውርስ የሚከፍለው እዳ ያለበት እንደሆነ የውርስ ንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የውርስ እዳ ሊቀነስ የሚገባ ስለመሆኑ በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1014፤1090	144585	እነ ወ/ሮ ሀና ካሳዬ እና ወ/ሮ ዘነበች ከሳዬ	ግንቦት 13 ቀን 2010 ዓ/ም	142
አሰሪና ሰራተኛ					**149**
28.	አንድ የመንግስት ሰራተኛ በተከሰሰበት የዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ከስራ እንዲሰናበት ካልተወሰነበት በስተቀር ከሥራ በታገደበት ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ የሚከፈለው ስለመሆኑ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 72 (4)	161880	አቶ አብርሃም ዴአ እና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት	ታህሳስ 23 ቀን 2011 ዓ.ም.	150

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
29.	የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር አጥንቶ ስራ ላይ ባዋለው በነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ/JEG/ የመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ለአንድ የሥራ መደብ የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጅት በግልጽ ተቀምጦ እያለ ተጨማሪ የትምሕርት ዓይነትን አካቶ ሰራተኞችን ማወዳደር የድልድል መመሪያውን የሚጥስ ስለመሆኑ	173887	የኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ እና አቶ ዋቅጋሪ ጥላሁን	24/10/2011 ዓ/ም	153
30.	አንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ባወጣው የቅጥር ማስታወቂያ መሰረት ተወዳድሮ አሸናፊነቱ ተረጋግጦ ቅጥር የፈፀመ ሰራተኛ ቅጥሩ የቅጥር ስርዓት ለመግዛት የወጣው ህግን ባልተከተለ መንገድ የተፈፀመ መሆኑ ከተረጋገጠ ስህተቱ የቀጣሪው መንግስት መስሪያ ቤት ቢሆን እንኳን ቅጥሩ ፀንቶ የሚቆይበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ 56/2010 አንቀፅ 94	165886	አቶ አምባቸው ተፈራ እና ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 9 ፕብሊክ ሰርቪስና የሠው ሃብት ልማት	የካቲት 11 ቀን 2011 ዓ/ም	157
			ንብረት		**160**
31.	አንድ የመንግስት የንግድ ቤት ኪራይ መብት ክልጅነት ጀምሮ በአውራሼ ዘንድ አድጌያለሁ እንዲሁም የኑዛዜ ወራሽ ነኝ በማለት በዉርስ ሊተላለፍና የንግድ ቤት የኪራይ መብት ተጠቃሚ ሊያደርግ የማይችል ስለመሆኑ በአ/አ/ከ/አስ/የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር	164326	አቶ አበበ ዘገየ እና ከተማ ክ/ከተማ ወ/07 ክ/የቤቶች ልማት ጽ/ቤት	28/05/2011	161

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 24				
32.	አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ አርሶ አደር በሕግ አግባብ ካሳ ተከፍሎት ወይም ምትክ መሬት ተሰጥቶት እንዲለቅ ከሚደረገው በቀር በመንግስት ወይም በአስተዳደር አካላት ፍላጐት ብቻ ከመሬቱ ሊነቀል የማይችል ሲሆን መሬቱ ለሌላ አርሶ አደር ከመስጠቱ በፊት አስቀድሞ ባለይዞታ የነበረን ሰው ከመሬቱ መነቀልን እንዳያስከትልበት በተገቢው ጥንቃቄ ተደርጐ መጣራት ያለበት ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40/4/	162083	ወ/ሮ አበቡ ተመስገን እና እነ አቶ በሬ አባተ /አምስት ሰዎች/	ሚያዚያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም	164
33.	በአንድ የገጠር መሬት ሕግ ላይ የስነ አእምሮ ችግር ያለባቸው ሰዎች የመሬት ተጠቃሚነት መብት እንዲቀጥል ለማድረግ በሕጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች የስነ አእምሮ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል በፍትሐብሔር ሕግ ላይ ስለፍርድ ክልከላ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር አጣጥሞ በማየት በፍ/ቤት የተሰጠ የፍርድ ክልከላ ውሳኔ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ *የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/1/፣አንቀጽ 11/5 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) እና (በ)፣አዋጁን ለማስፈጸም የወጠው ደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8*	178664	የአቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት ሞግዚት አቶ ኪዳነማሪያም ሐይሉ እና ወ/ሮ አሚት አጽብሃ	ግንቦት 28 ቀን 2012 ዓ.ም	169
34.	አንድ ቤት በዓዋጅ 47/67 መሰረት ከተወረሰ በኋላ የተወረሱ ቤቶችን	165314	የድሬደዋ ከተማ አስ/ቀበሌ	30/09/2011	175

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ለመመለስ በወቅቱ ስልጣን የነበረዉ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ቤቱ እንዲመለስ የወሰነው ዉሳኔ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ምትክ ቤት እንዲሰጥ መወሰኑ ብቻ የተወረሰ ቤት ይመለስ ማለት ስላለመሆኑ		03 እና ወ/ሮ ስንዱ ሳልቫቶር		
35.	ከመሬት ይዞታ ጋር በተያያዘ ግጭትና አለመግባባት ሲኖር ጉዳዩ አስቀድሞ በቀበሌ አስተዳደር አማካይነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች ምርጫ በስምምነት በሽማግሌዎች ታይቶ እንዲፈታ ማድረግ ለተከራካሪ ወገኖች የተፈቀደ አማራጭ እንጂ አስገዳጅ ስላለመሆኑ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 12፤በአሮሚያ ክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ/ 130/99 አንቀጽ 16፣17	169648	አቶ ተሻለ ዋቆ እና አቶ ንጉሴ ቦንቱ	ሰኔ 21 ቀን 2011 ዓ/ም	179
36.	በባለመሬቱ ወይም በባለይዞታዉ ፈቃድ አትክልቶችን በሌላ ሰው ይዞታ ላይ የተከለ ሰዉ ከባለይዞታው ጋር ባለው ስምምነት መሠረት የመሬቱ አላባ ተጠቃሚ እንደሆነና ከስምምነቱ ዉጪ አትክልቶቹ እንዲነሱ ሲደረግ ካሳ የሚገባው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 40(3 እና 4)፣የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1175፣1176	164489	አቶ አባዝናብ አባድማ እና አቶአባተማም ሼህ ሸኩር	ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም	183

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
37.	የሊዝ ውል እንዲቋረጥ የተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ባልተሻረበት ሁኔታ በሊዝ ውል የተያዘ መሬት ለማስለቀቅ የመሬት አስተዳደር አካል መሬቱን ለመረከብ እንዲቻለው የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነዉ ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1149/3/፤የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ አዋጅ ቁ/721/04 አንቀጽ 25	158527	ወ/ሮ ዘይነባ ሀሰን እና እነ የቢሸፍቱ ከተማ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ	ጥር 27 ቀን 2011 ዓ.ም.	187
38.	የገጠር መሬት ባለይዞታዎች መካከል የሚደረግ ማንኛዉም የልዉዉጥ ዉል አግባብ ባለዉ የወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ በሀሰተኛ መረጃ ላይ መሰረት በማድረግ አስተዳደሩን በማሳሳት የተገኘ የይዞታ ደብተርና የተደረገው ምዝገባ ህጋዊ ዉጤት የማይኖረዉ እና በህግ ፊት በማይጸና ዉል የያዘ ወገን መሬቱን እንዲለቅ የሚደረግ ስለመሆኑ በአማራ ብ/ክ/መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ/252/09 አንቀጽ 20/3/	161676	አቶ መልካሙ አበራ እና ቂስ ዳምጤ በየነ	የካቲት 25 ቀን 2011ዓ.ም	191
39.	የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከታወጀ በኋላ ባለው የመሬት ስሪት መሰረት የፍ/ብ/ህ/ቁ/1065 መሬትን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው ቀድሞ በስጦታ የተወሰደን ይዞታ በዓይነት ወደ ውርስ ይዞታ እንዲመለስ በማድረግ ሳይሆን የይዞታውን መጠን በልኬት በመለየት መጠኑ ከአጠቃላይ የውርስ ይዞታው ውስጥ ለስጦታ ተቀባዩ ከሚደርሰው ድርሻ ላይ እንዲቀነስ በማድረግ	169030	እነ አቶ አሰፋ ሰቦቃ እና እነ አቶ ከበደ ሰቦቃ	ህዳር 30/2012ዓ.ም	194

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 40፤ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1065፤ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጁ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 9(2) እና ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 10(10				
40.	ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የእርሻ መሬቱ የተወሰደበት ሰው ካሳም ሆነ ትክ መሬት ባለማግኘቱ በአስተዳደር አካል መፍትሄ ሳይሰጠው ለፍርድ ቤት አቤቱታውን ሲያቀርብ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አከራክሮ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባዉ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 37፤ከአዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 3/1/	168556	አቶ ተሾመ ድለንሌ እና እነ የቀርሳ ማሊማ ወረዳ ገጠር መ/ባለስልጣን ጽ/ቤት	ሰኔ 14 ቀን 2011 ዓ.ም	201
41.	አንድ ባለይዞታ አንድን ይዞታ በስጦታ አግኝቶ ለረጅም ዓመታት ይዞ በሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ዕዉቅና ሲጠቀምበት የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ በክልል ከተሞች ዉስጥ የተሟላ ሰነድ የሌላቸዉና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን በማጣራት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ለመስጠት ተሻሽሎ በወጣ መመሪያ ቁጥር 8/2007 መሠረት የመስተናገድ መብት ያለው ስለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ለመስጠት ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 8/2007 አንቀጽ 4(5)	169864	ወ/ሮ ብርሃን ማለዳ እና የባህር ዳር ከተማ ጣና ክ/ከተማ	28/09/2011	204
42.	አንድ ሰው የገጠር መሬት በሕጋዊ መንገድ የያዘ ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ	179827	ካሱ ምስጋናው	ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም	209

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ጊዜ ድረስ መሬቱን የያዘው በሕገወጥ መንገድ መሆኑ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያን በስነ-ስርዓት መቃወሚያነት ሊያነሳ የማይችል ስለመሆኑ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 እና 2/39		እና ጥላዬ አስረስ		
ንግድና ኢንሹራንስ					**214**
43.	አንድ የመድን ገቢ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር መድን የተገባለት ተሽከርካሪ ላይ አደጋ መድረሱን በተገባለት የመድን ዉልም ሆነ በሕግ የተመለከተዉን ለመድን ሰጭዉ አደጋን የማሳወቅ ቅድመ ሁኔታ በአግባቡ አሟልቶ እያለ መድን ሰጪው ለ3ኛ ወገን የከፈለውን ካሳ መድን ገቢው መልሶ ለመድን ሰጪው የሚከፍልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	161598	አቶ ሰለሞን በቀለ እና ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጄኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ	የካቲት 13ቀን 2011 ዓ.ም	215
44.	የኢንሹራንስ ፖለሲ የኢንሹራንስ ዉል አካል በመሆኑ በኢንሹራንስ ፖሊሲዉ ላይ የተመለከተዉ ቃል የኢንሹራንስ ዉል ቃል ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1733፣የንግድ ሕግ ቁጥር 657(1 እና 2)	160602	አቶ ነጋ ባንቲሁን እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ጎንደር 30 ቀን 2012 ዓ/ም	222
45.	የመድን ድለላ አገልግሎት የኮሚሽን ክፍያ ስለሚከፈልበት አግባብ የንግድ ህግ አንቀጽ 56(1)፣ የመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 አንቀጽ	158262	ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ	ሀምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም.	232

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	2(19)		እና ጀነራል ኢንሹራንስ ብሮከርስ		
46.	• የአክሲዮን መተላለፍ ገዥና ሻጭን ለማስገደድ በጽሁፍ መደረግ ያለበት ሲሆን ማህበሩን ለማስገደድና የተላለፈለት ሰዉ በባለአክሲዮንነት ሙሉ መብት ለመጠቀም ስለአክሲዮን መተላለፉ ማህበርተኞች የተስማሙበት ዉሳኔ በአክሲዮኖች መዝገብ ሊመዘገብ የሚገባው ስለመሆኑ • የአክሲዮኖች መተላለፍ በ3ኛ ወገን ላይ መቃወሚያ ሊሆን የሚችለዉ ስለአክሲዮኖች መተላለፍ ዉል ሲኖር ወይም ማህበርተኞቹ የአክሲዮኖችን መተላለፍ ተቀብለዉ የተስማሙበት ሰነድ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ተረጋግጦ መመዝገቡ ሳይሆን የአክሲዮኖቹ መተላለፍ በንግድ ሚኒስቴር የአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ሲመዘገብ ስለመሆኑ የንግድ ሕግ አንቀጽ 522 እና 523 /3/	103472	የኢት/ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ኢትዮጵያ ታመነ እና እነ አቶ ጌታነህ ምናለ	27/01/2008 ዓ.ም	238
47.	በአንድ የአፈፃፀም መዝገብ የፍርድ ባለዕዳ የነበሩ ኃ/የተ/የግ/ማህበር አክሲዮኖች በፍ/ቤት በተሰጠ ዕግድ ትዕዛዝ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፉ ከመታገዳቸው በፊት አክሲዮኖቹ ለሌላ ወገን በሽያጭ ስለመተላለፋቸዉ ፤በንግድ ሚኒስቴር የአክሲዮን መዝገብ ላይ ስለመመዝገባቸው ካልተረጋገጠ	154564	እነ አብዱሰላም ሰይዱ አብዶ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ግንቦት 28ቀን 2011 ዓ.ም	244

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አክሲዮኖች በሀራጅ ተሸጠዉ ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል የተሰጠ የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲነሳ የሚቀርብ መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የንግድ ሕግ ቁጥር 522፣523(3)				
48.	አንድ ባንክ ለደንበኛው ክፍያ የፈጸመዉ በዋናነት ተከፋዩ ሰዉ ብቻ ያዉቀዋል ተብሎ የሚገመተዉን ፍሬነገር ማለትም ገንዘቡን የላከዉ ሰዉ ማንነት፣የተላከዉ ገንዘብ መጠን፣የሚስጥር ቁጥር እና የተላከለት ሰዉ ስም እና ተከፋዩ ሰዉ የሰጠዉ መረጃ ተዛማጅና ትክክል መሆናቸዉ በተለመደዉ አሰራር መሰረት በማረጋገጥ እስከሆነ ድረስ ክፍያዉን የተቀበለዉ ሰው ሀሰተኛ የቀበሌ መታወቂያ ይዞ የቀረበ ለማይገባው ሰዉ ነዉ በሚል ምክንያት ባንኩ በድጋሚ ገንዘቡን እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 2/2/መ/፣ 53	188419	አባይ ባንክ አ.ማ እና አቶ ማርቆስ ጋትሮ	መስከረም 25 ቀን 2012ዓ.ም	252
			ውል		**257**
49.	አንድ ውል ለተፈለገው ዓላማ ሳይውል ከቀረ ለውል መሠረዝ ምክንያት የሚሆን ሲሆን ውሉ ከተሰረዘ በኋላ ተዋዋይ ወገኖች ከውል በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ የማድረግ ውጤት የሚያስከትልና ውሉ	161153	ወጋገን ባንክ አ.ማ. እና የኢትዩጵያ የንግድ እና	ሚያዝያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም	258

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በመሠረዙ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ካለ ለደረሰ ጉዳት በካሣ መልክ አንዱ ለሌላው የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1771/2/፣1788፣1790፣1791፣1799፣1815		የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት		
50.	• አንድ ውል እንደ ውሉ ባለመፈፀሙ ለደረሰ ጉዳት ኪሳራ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ተዋዋይ ወገን ሊከፍል የሚገባውን የኪሳራ መጠን ለመወሰን በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የውል ዓይነት፣የነበራቸውን ግንኙነት እንዲሁም ቀድሞ የሚታወቁ ሁኔታዎች ሁሉ ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ስለመሆኑ • አንድ የኪራይ ውል እንደ ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰ ኪሳራ የሚቆረጠው በኪራይ ውል ስሌት ተመን መሰረት ሲሆን የኪራዩን ገንዘብ ልክ ለመወሰን አግባብነት የሚኖረው ማስረጃ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት የሚወሰኑት ታሪፍ በመሆኑ ለተመሳሳይ ቤት የሚታወቅ ታሪፍ ቢኖር በመጠየቅ እንዲሁም ታሪፍ ከሌለ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ	169077	መይ ሪል ስቴት ዴቨሎፕመንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ያየህ ይራድ ፍቅሬ	ሰኔ 28ቀን 2011 ዓ.ም.	268

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በፍ/ብ/ህ/ቁ 1771፣1799፣1801፣2950(2)				
51.	የቤት ኪራይ እንዲከፈል መጠየቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ካልተጠየቀ የቤት ኪራይ ክፍያ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለዉ የሕግ ግምት፣ ሁለት ዓመቱ ሳይደርስ ባለገንዘቡ ገንዘቡ እንዲከፈለዉ ባለዕዳዉ ላይ ክስ አቅርቦ እንደሆነ እዳዉ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለው የህግ ግምት ቀሪ ስለሚያደርገው ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024(መ)፣2025 (ለ)	168198	አፍሪካ ክንፉ መረዳጃ እድር እና እነ አቶ ዮሴፍ ደበበ	ሠኔ 24 ቀን 2011ዓ.ም	273
ከውል ውጪ ኃላፊነት					**277**
52.	የአንድ ሕንጻ ባለሀብት ወይም ባለይዞታ ሕንጻው ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ያልታሰበ ድንገተኛ ነገር ቢያደርስ ሕንጻው ለሚያደርሰው ጉዳት ከውል ወጪ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ጉዳት የደረሰበት ባለንብረትም የኢንሹራንስ ውል ያለው ከሆነ ኢንሹራንስ ድርጅቱ ለደረሰው ጉዳት ተገቢውን ከፍያ ከከፈለ በኋላ ጉዳት በደረሰበት ሰው ተተክቶ የህንፃውን ባለሀብት ለመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2088 ፣2077፣ የንግድ ህግ 683	161417	ፀሀይ ኢንሹራንስ አ/ማ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም	278

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
53.	• የአንድ ባለሙያ ማስረጃ በቀረበ ጊዜ በዋናነት የሚመረመረው የባለሙያው ገለልተኛነት እና ሙያዊ ብቃት ሲሆን ሁለቱን መስፈርቶች ካሟላ ማስረጃው የፍሬ ነገሩን መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ ከፍተኛ ግምት የሚሠጠው (high probative value) ማስረጃ በመሆኑ ለባለሙያ ማስረጃ ውጤት ሳይሰጥ ውጤቱን አለመቀበል የማስረጃ ምዘና መርህ ስህተት ስለመሆኑ • በአንድ በተዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመር ምክንያት ለደረሰ ጉዳት ኃላፊነቱን የሚወስደው የኤሌክትሪክ መስመሩን የዘረጋው አካል እንጂ ሌላ ሰው በቤቱ በዘረጋውና ባለቤት ላልሆነበት የኤሌክትሪክ መስመር አጥፊ ሳይሆኑ ኃላፊ ስለመሆን በተደነገገው የውል ውጭ ኃላፊነት ክፍል ኃላፊ ሊሆን የማይገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2066 — 2086	175142	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሠሜን ሪጅን ሑመራ ዲስትሪክት እና አቶ ወሉ ገ/ሔር	ግንቦት 24 ቀን 2012 ዓ/ም	282
		ግብር			**286**
54.	የግብር አስገቢ ባለስልጣን አንድ ግብር ከፋይ ገቢውን በየጊዜው እያሳወቀ ግብሩን እየከፈለ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም ብሎ ካመነ በግብር ከፋዩ የቀረቡ ማንኛውንም መግለጫዎች ሰነዶች እና የሂሳብ መዝገቦች በማናቸውም ጊዜ	153016	ወ/ሮ ከበደች ዘሚካኤል እና የአራዳ ክፍለ ከተማ	ጥር 30 ቀን 2011 ዓ.ም.	287

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በመመርመርና በማረጋገጥ በግብር ከፋዩ የተገኙትን የግብይት ማስታወሻዎች በባለሙያዎች በማስመርመር ተጨማሪ ግብር መወሰኑ ስላመቻሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 38/2፣66		አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት		
55.	• በንግድ የግብር ዘመን የደረሰ ኪሳራ ሊሸጋገር የሚችለው ከሚቀጥሉት ሶስት የግብረ ዘመናት ውስጥ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ መጀመሪያ ያጋጠመው ኪሳራ በኋላ ካጋጠመው አስቀድሞ በማካካስ ሊሸጋገር የሚችል እና ይህም በማናቸውም ሁኔታ ከሁለት ሶስት ዓመታት ከሚቆጠሩ ስድስት ዓመታት በላይ ሊሸጋገርና ሊቀናነስ የማይችል ስለመሆኑ • የአንድ ግብር ከፋይ ኪሳራ ሊሸጋገር የሚችለው በግብር ባለሥልጣን አዲት ተደርጐ ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም በውጭ አዲተር የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ ሲቀርብ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1/ እና /3/፣በደንብ ቁጥር 78/1994 እንደተሻሻለው አንቀጽ	161867	የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን እና ሱፐር ማክስ አብቲካል ሚዲያ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር	ሚያዚያ 25 ቀን 2011 ዓ.ም.	293

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
የወንጀል ሕግ					
56.	አንድ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት አድራሹ በህግ ቁጥጥር ሥር ውሎ በዋስ በመፈታቱ ላይ ቅሬታ ቢኖረው በህግ በተቀመጠው ሥነሥርዓት መጠየቅ እንጂ ለምን በዋስ ተፈታ፣እንደገና ጉዳት ያደርስብኛል በሚል ትንበያ፣እንዲሁም ፍትህ ተደክሟል በሚል በራሱ ፍትህን ለማስፈጸም ግድያ በፈፀመበት ሁኔታ የደረሰበት ጉዳት ወንጀል ለመፈጸም ቀስቃሽ ሆኗል በሚል ቅጣትን አቅልሎ መወሰን ተከሳሹን የማያስተምር እና ፍትህን በራሱ መፈጸሙ ምክንያታዊ እንደሆነ እንዲሰማው የሚያደርግ ፣ሌላውን ማኅበረሰብ ፍትህን በራሱ እንዲያስፈጽም የሚገፋፋ ወይም መጥፎ አርአያ የሚሆን፣ዋነኛው የወንጀል ህግ ዓላማ የሆነውን የህዝብን ሠላምና ደኅንት የማስጠበቅ ዓላማ እንዳይሳካ የሚያደርግ ስለመሆኑ	171943	የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እና ኪዳኔ ቶላ	ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ/ም	298
57.	በአንድ የወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ የሆነ ሰው የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ያልቀረበበት፣ ጥፋቱን አምኖ የተፀፀተና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ሲታይ ቅጣትን በገደብ ለማቆም የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በአብዛኛው ያሟላ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት የቅጣቱ መገደብ ላይ ባለማመኑ የቀረበለትን የገደብ ጥያቄ ውድቅ ሲያደርግ ቅጣቱ እንዳይገደብ የሚያደርጉ ምክንያቶችን ባለመግለፁ ብቻ ጉዳዩ ወደ ስር ፍ/ቤት መመለስ አስፈላጊ ስላለመሆኑ	169726	አቶ ፍቅሩ ደሌሳ እና የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ	ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም	305

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
58.	አንድ ተከሳሽ ማንኛውም የንግድ ዕቃን ከመደበኛው የግብይት አሰራር ውጭ በማናቸውም ማጓጓዣ ከተፈቀደ የስርጭት መስመር ውጭ ሲያጓጉዝ የተያዘ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥበት፤ዕቃውም የተፈቀደ የስርጭት መስመር ያለው መሆን አለመሆኑና ከመስመር ውጪ ሲጓጓዝ የነበረ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በወንጀል ጥፋተኛ ሊባል የማይገባው ስለመሆኑ የነጋዴዎች እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/	168067	ሰይድ አሊ አበጋዝ እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የንግድ እና ሸማቾች ዓቃቤ ሕግ	29/09 / 2011 ዓ.ም.	313
59.	አንድን ዕቃ ከውጪ የሚያስመጣ ሰው ለጉምሩክ ሥርዓት አፈጻጸም ሲባል ስለሚያስመጣው ዕቃ አስፈላጊ የሆኑ መግለጫዎችን በመስጠት በዲክላራሲዮን ላይ በማስመዝገብ ወደ ሐገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች በላኪው እና በአስመጪው መካከል በሚደረግ ስምምነት ወደ ሐገር ውስጥ የሚገቡ ከመሆናቸው አኳያ ወደ ሐገር ውስጥ እንዲገባ የተደረገው ዕቃ አስመጪው በዲክላራሲዮን ካስመዘገበው ዕቃ የበለጠ ዋጋ ያለው ሆኖ በተገኘ ጊዜ አስመጪው የተላከውን ዕቃ ሊያውቅ የሚችልበት ሁኔታ የለም ተብሎ ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 13/4/፣169/2/	163069	የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ እና እነ ክኤሳድ ጠቅላላ የንግድ ሥራ ኃላ/የተ/የግ/ማሕበር	ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም	318
60.	ከተገኘ ገቢ የሚከፈል ግብርንና የተሰበሰበን ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ደረሰኞች ሐሰተኛ መሆናቸው ብቻ አንድን ተከሳሽ ጥፋተኛ ሊያስብለው	181958	አቶ ገበያው ሽቱ እና	ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓም	324

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የማይችልና ሐሰተኛ ደረሰኝ ናቸው የተባሉት ደረሰኞች አፈጣጠርና ለገቢ ሰብሣቢው መስሪያቤት አቀራረብ ሂደት ላይ የተከሳሹን ድርሻና በሕግ የተጣለበት ግዴታ ከወንጀል ህግ መሰረታዊ መርህና የወንጀል ማስረጃ ምዘና መርህን በተከተለ መንገድ ሊመረመር የሚገባው ስለመሆኑ ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(1) ፤የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 22፣49፣50 (1)		የሰሜን ሸዋ ዞን ገቢዎች ዐ/ህግ		
61.	በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ መሰረት በሰው መግደል ወንጀል በተመሰረተ ክስ ላይ የግል ተበዳይ ህይወት በጠፋበት እና ወንጀሉ የአካል ጉዳት ማድረስ ስለመሆኑ በማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የተከሳሾች የሀሳብ ክፍል ከባድ የአካል ጉዳት ለማድረስ ነው በሚል የክሱን የህግ ድንጋጌ ወደ አንቀጽ 556/2/ሀ ዝቅ በማድረግ የሚሰጥ የቅጣት ውሳኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	164030	የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ እና እነ ሀብታሙ በለጠ (3 ሰዎች)	ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ/ም	332
62.	አንድ ሰው ለብዝበዛ ዓላማ ሲባል በሕገ-ወጥ መንገድ ሰዎችን የማዘዋወር ወንጀል ፈፅመኻል ሊባል ስለሚችልበት አግባብ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 909/07 አንቀጽ 3/2/ሀ/	167965	አህመድ ኢብራሂም እና የኦሮሚያ ክልል ዐ/ህግ	ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም	343
63.	የአራጣ ወንጀል የተፈጥሮ ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን በህግ የሰውነት መብት	167805	የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ	ጥቅምት 26 ቀን	351

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በተሰጠው ድርጅት/ማህበር/ ላይም ተፈጻሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 712/1/ሀ/		እና እነ አቶ ታደሰ ኪዳነማርያም	2012 ዓ.ም	
64.	አንድ ተከሳሽ አስቀድሞ በፈጸመዉ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በአመክሮ ከተፈታ አምስት ዓመት ያለፈዉ ቢሆንም ለፍ/ቤት የመሰየም ጥያቄ አቅርቦ ባልተሰየመበትና ቅጣቱም ከፍርድ መዝገብ ተሰርዞ እንዳልተሰጠ ባልተቆጠረበት ሁኔታ የጥፋተኝነቱ ሪከርዱን በቅጣት ማክበጃነት መያዝ ተገቢ ስለመሆኑ በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) ፣84(1/ሐ)፣ 232፣ 233	161791	ታምሬ አበራ ረጋሳ እና የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ	የካቲት 25 ቀን 2011 ዓ.ም	356

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
65.	ከአንድ የወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ ንብረት የሚወረሰው ወይም ለመንግስት ገቢ የሚደረገው በወንጀል ህጉ እና በወንጀል ስ/ስ/ህጉ መሠረት በቅጣት መልክ በመሆኑ ንብረቱ የሚወረስ መሆን አለመሆኑ ውሳኔ ማግኘት ያለበት በወንጀል መዝገብ እንጂ በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠን ውሳኔ ብቻ መነሻ በማድረግ በአዲስ መልክ በሚቀርብ የፍትሐብሔር ክርክር ስላለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 98፤100(1) እና 140	137908	የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ እና ወ/ሮ ፀሐይ አሰፋ	21/05/2010	360

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
66.	አንድ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈፅመሃል ተብሎ የተከሰሰ ተከሳሽ ድርጊቱን ለመፈጸም የተጠቀመበት መሳሪያ የሌለ መሆኑ በማስረጃዎች በተረጋገጠበት ሁኔታ በከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 555 ፣556(1)	168166	አቶ ይገዙ ቡርዜ እና የደቡብ/ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ፍትህ ቢሮ ዓቃቤ ህግ	ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም.	367

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
67.	ቅጣት ሊገደብ የሚችለው ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት፤ የወንጀሉ ክባድነት/ the gravity of the crime/ በማየት፤ በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ ሲታመን እና በአጠቃላይ ቅጣት ስለሚገደብባቸው ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 192፣194፣196/2/ እና 197	171403	መላኩ ያዕቆብ እና የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ	ሕዳር 22 2012 ዓ.ም	372

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
68.	አንድ ሰው በፈጸመው ወንጀል ምክንያት በማረሚያ ቤት በመሆኑ በሕፃናት ልጆቹ ላይ የሚደርሰውን ቁሳዊም ሆነ ኅሊናዊ ጫና ለማስቀረት ሲባል እንዲሁም ሕጻናቱ የወላጆቻቸውን እንክብካቤ እና ድጋፍ አግኝተው እንዲያድጉ ለማድረግ ሲባል፤ ፍ/ቤቶችም የሕጻናት ደኅንነት በቅድሚያ የማረጋገጥ ሕገመንግስታዊ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ በወንጀለኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት በመገደብ ህፃናቱ ተገቢውን የወላጅ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችል ዘንድ በወንጀል ህጉ ቅጣት ለማገድ የተቀመጡትን ሁኔታዎች በማረጋገጥ የተወሰነውን ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ የሚገባ ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 36/2፤የወንጀል ህግ አንቀጽ 192፣194፤የዓለም አቀፉ የህፃናት መብቶ፤ች ስምምነት የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 44/25 እንደ ኤሮፓውያን አቆጣጠር 1989 የወጣው አንቀጽ 7 (1)፤ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 18	177216	አቶ ገብርኤል ፓራቶሪ አንቶንዮ እና የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ	ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ/ም	378

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
69.	ዓቃቤ ሕግ የሚያቀርበው የክስ አቤቱታ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ያልቀረበ ሆኖ ሲገኝ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ክሱ በህጉ አግባብ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ እና ዓቃቤ ሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ ሳይደረግ በሕጉ አግባብ ተዘጋጅቶ ያልቀረበው ክስ የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ተከሳሹ በሕግ አግባብ ተዘጋጅቶ ባልቀረበው ክስ ጥፋተኛ ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 118 እና 119/1/	165440	አየለ ሀፊቦ እና የደቡብ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ	ጥር 27 ቀን 2012 ዓ.ም	387

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
70.	የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ድንጋጌ እና የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 መሰረት ዓቃቤ ሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 መሠረት የአንድ ተከሳሽን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን ስለመሆኑ እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ በተደነገገው መሠረት ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ በተረጋገጠ ጊዜ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብል የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ የሚዛወር ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23/2/፣የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007አንቀጽ 3 ፣አንቀጽ 13/3 እና 13/1/ሐ	162738	እነ አቶ መሐመድ ያዕቆብ ከድር አልይዘአ እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጸረ ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤሕግ	መጋቢት 30 ቀን 2012 ዓ.ም	393

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
71.	አንድ ተከሳሽ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ክስ የቀረበበት ስለመሆኑ አውቋል የሚል ግምት ሊወሰድ የሚገባው ሐገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ጥሪ የተደረገለት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ እንጂ በአንድ ክልል ብቻ ተደራሽ በሆነ ጋዜጣ ብቻ ጥሪ መደረጉን መጥሪያ እንደደረሰው ማረጋገጫ አድርጎ በመውሰድ እና መጥሪያ ደርሶታል የሚል ግምት በመውሰድ ጉዳዩን ተከሳሹ በሌለበት አይቶ ውሳኔ መስጠት በሕገ-መንግስቱ ለተከሰሱ ሰዎች የተጠበቁላቸውን መሠረታዊ መብት የሚነካ ስለመሆኑ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 161፣199(ሀ)	173967	አቶ አማኑኤል ገ/ጊዮርግስ እና የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤሕግ	መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም	413
የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ					
72.	የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ አንቀፅ 63 እና 67 በተከሳሾች ላይ ስላላቸው ተፈጻሚነት	182266	የደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓ/ሕግ እና አሸብር ዳጌታ ሄሎ	ጥቅምት 19 ቀን 2012 ዓ.ም	420

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
73.	አንድ ድርጊት ከመፈፀሙ በፊት፣ ሲፈፀም ወይም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኃላ ዐቃቤ ህግ ስላቀረበው ክስ ማስረጃ ይሆነኛል በማለት በሕጉ አግባብ ያቀረበውን ማስረጃ በማስረጃነት ሊቀርብ የማይችልና ተቀባይነት የሌለው (Inadmissible evidence) ነው የሚል ግልፅ ክልከላ የሚያደርግ የሕግ ድንጋጌ በሌለበት የማስረጃው አስረጂነት ዋጋ ሳይታይና ሳይመዘን በደፈናው ማስረጃው ከተከሳሾች ጋር አብሮ ተከሳሽ የነበረ ነው፤ የተከሳሾችን የመከላከል መብት ይጎዳል በሚል ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ውድቅ ማድረግ የማስረጃ ተቀባይነት፤አግባብነትና ምዘና መርህን፤ የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን ያልተከተለ ስለመሆኑ ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 108-122፣የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 እና የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 41፣43	163947	የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እና እነ አቶ ጌታቸው ዋለልኝ	ሐምሌ 15 ቀን 2011 ዓ.ም.	430
74.	• በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መሰረት በተመሰረት ክስ ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ይህ ብይን የተሰጠበት ድንጋጌ አማራጭ ቅጣትን ያስቀመጠ ሆኖ በተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የስነ ስርአትና የማስረጃ ህግ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ሁለተኛ ሀሳብ ላይ ከአራት አመት በላይ በሚል የተደነገገውን ቅጣት	182050	የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ህግ እና ብርጋዴር ጀነራል ሐድጉ ገ/ጊዮርጊስ	ታሕሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም	437

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንደ መነሻ ቅጣት በመውሰድ የቅጣት መነሻቸው አራት ዓመት የሆነ በጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን የሚመለከት እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ ዋስትናን መፍቀድ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የተሻሻለው የጸረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1/ • ተከሳሹ በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰው የጉዳት መጠንን በተመለከተ አቃቤ ህግ ክስ በመሰረተበት የህግ አንቀጽ በተከሳሹ የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰውን የጉዳት መጠን አለመግለጹ ተከሳሽ በዋስትና ቢለቀቅ ዋስትናውን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም የሚል ግምት በመውሰድ የዋስትና መብትን የማያስከለክል ስለመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67				
75.	አንድ ተከሳሽ ጥፋተኛ ቢባል በቀላል እሥራት፤ ከ12 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት ወይም ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ የሚችል በመሆኑ ተመራጭ የሚሆነው የፍርድ ሂደት ተከሳሹ በተከሰሰበት ድንጋጌ የተቀመጠው ከፍተኛ ቅጣት ሊቀጣ ይችላል ብሎ ከወዲሁ በማሰብ ጉዳዩን በሌለበት እንዲታይ ማድረግ ሳይሆን የተከሳሽ በችሎት ተገኝቶ የመከራከር መብት ከሚጣስ ይልቅ ተከሳሽ እስኪገኝ ድረስ	179416	ሀለቃ ንጉሴ አብርሃ እና የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ	ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም	454

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍርድ ሂደቱ እንዳይካሄድ በማድረግ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 20/4፣ ዓለም ዓቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14፣የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 162(2)				
76.	አንድ ወንጀል ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ የሚሰጠዉ በክስ ማመልከቻ ፎርም ወይም በክሱ ማመልከቻ ላይ ስለወንጀሉ አስፈላጊ ዝርዝር ዉስጥ ስህተት ሲገኝ ወይም ሳይጠቀስ ሲቀርና ይህም መሰረታዊ ነገር ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ አንቀጽ 111፣112፣118 እና 119/1/	171521	የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ እና ወ/ሮ ትርሃስ መስፍን ገ/እግዚአብሔር	ታኅሳስ 23 ቀን 2012 ዓ/ም	459
ልዩ ልዩ					
77.	የእርሻ የኢንቨስትመንት መሬት በሚመለከተው አካል እውቅና በሕግ አግባብ መብት ከሚተላለፍበት ስርአት ውጭ በኪራይ ለኢንቨስትመንት ሥራ የተገኘ መሬት በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የማይቻል ስለመሆኑ የተሻሻለው ትግራይ ክልል የኢንቨስትመንት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 2፣22/5/፤24፣26/4/	159062	አቶ መረሳ ወ/ማርያም እና ቄስ ወ/ጊዩርጊስ ኪዳኔ	ጥር 30ቀን 2011 ዓ.ም	466
78.	በጉምሩክ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት በመጋዘን ገብተው ሊወጡ ያሉ ዕቃዎች ዉስጥ የኮንትሮባንድ ዕቃ መኖሩን ጠቁሞ በማስያዝ ምክንያት	169729	የገቢዎች ሚኒስቴር እና	ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም.	471

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ለጠቋሚ ስለሚከፈለው የወሮታ ክፍያ አግባብነት የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 56 እና 132 ፤የህገ ወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና ወሮታ ክፍያን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 2(7)፣19(ለ)		አቶ አስራት አሰግድ		
79.	በውጭ ሀገር ሥራና ሰራተኛ አገናኝነት ሥራ ዋስትና የሚሆን ገንዘብ በማስያዝ ከኢፌዴሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፈቃድ አውጥቶ የሚሰራ ኤጀንሲ የዋስትና ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግለት ለማድረግ ኤጀንሲው ፈቃዱን መመለስ አለመመለሱ፤ አስቀድሞ የተሰጠው ፈቃድ ካልተመለሰ ፈቃድ ሳይመለስ የዋስትና ገንዘብ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆን አለመሆኑ፤ እንዲሁም ኤጀንሲው ለሥራ ወደ ውጪ አገር ለላካቸው ዜጎች መብትና ደህንነት ማስከበሪያ በባንክ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅለት ሊያሟላ የሚገባቸው ሁኔታዎች የተሟሉ መሆን አለመሆኑን ከክርክርና ማስረጃ አንጻር ታይቶና በአግባቡ ተገናዝቦ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ የውጪ ሀገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 አንቀጽ 60(5)፣ አንቀጽ 78	171530	የኢፌዴሪ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና አቶ ሱልጣን ጃቢር መሀመድ	ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ.ም.	478
80.	በፍርድ ክልከላ የተደረገበት ሰው ክልከላው እንዲወሰን ያደረጉት ምክንያቶች በቀሩ ጊዜና የተከለከለው ሰው ንብረቱን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚችል የሆነ እንደሆነ በተደረገው ክልከላ ምክንያት ሌላ አዲስ ክስ ማቅረብ	167560	አቶ ቢቂላ አያኖ እና	30/09/2011	482

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የማይችል ቢሆንም የተደረገው ክልከላ እንዲነሳለት አቤቱታ ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ህግ ቁጥር 351(1) ፣377፣378		አቶ አሊቢ ቂላ		

ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

የሰ.መ.ቁ 160916
ታሕሣሥ 30 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ ቦጃ በየነ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት አመልካች የኦሮሚያ ክልል የቡና ጥራትና ንግድ ቁጥጥር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 160/2002 አንቀጽ 13/2፤19(1)(2)(5)(6) እና 23(6) ድንጋጌን በመተላለፍ ሆን ብሎ አስቦበት በቀን 26/05/2010 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 3፡00 ሰዓት በምዕራብ ጉጂ ዞን ገላና ወረዳ ፖሬ ከተማ ልዩ ቦታው ኬላ በተባለው ሕገ-ወጥ ቡና ንብረትነቱ የአመልካችበሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-38518 አ.አ በሆነ የጭነት መኪና ግምቱ ብር 6፣3520 የሆነ 14 ኩንታል ታጥቦ የተቀሸረ ቡና በመጫን ለጊዜው እጁ ካልተያዘ ሹፌር ጋር በመሆን ያለምንም ፈቃድ ከቡናው ላይ ሌላ ዕቃ በመጫን በማንገዝ ላይ እያለ ተይዟል የሚል ነው፡፡

አመልካች ቀርቦ ማንነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ክሱ የደረሰው መሆኑን ለችሎቱ የገለጸ መሆኑን፤ ችሎቱም በሚገባው ቋንቋ የዓቃቤሕግን ክስ አንብቦለት ገብቶኛል በማለት ከገለጸ በኋላ መቃወሚያ የሌለው መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ድርጊቱን እንዳልፈጸመ እና ከመኪናው ረዳት እና ሹፌር ጋር ወደ ዲላ ከተማ በመንገዝ ላይ እንዳለ ህገወጥ ቡና ጭነሃል በማለት የተያዘ መሆኑን እና መኪናው ምን እንደጫነ የማያውቅ መሆኑን በመግለጽ ክሱን ክዶ የተከራከረ መሆኑን፤ ፍ/ቤቱም የዓቃቤሕግን ምስክሮች ሰምቶ አመልካች የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል በማለት ብይን የሰጠ መሆኑን፤ አመልካች የመከላከያ ምስክር እንዲያቀርብ እድል ቢሰጠውም የመከላከያ ምስክር የለኝም በማለት ቅጽ ሞልቶ ያቀረበ መሆኑን እና ፍ/ቤቱም መከላከያ ምስክር ማቅረብ መብት እንጂ ግዴታ

አይደለም በማለት የአመልካችን ምስክር የማቅረብ መብት አልፎ አመልካችን ጥፋተኛ በማለት በሶስት ዓመት ጽኑ እሥራት እና በብር 25,000 መቀጮ እንዲቀጣ የወሰነ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የስር ፍ/ቤት አመልካች በጠበቃ እንድከራከር በራሱ ተነሳሽነት ሊያመቻችልኝ ሲገባ በዝምታ አልፎታል፤ አመልካች መንግስት ጠበቃ እንዲያቆምልኝ ያቀረብኩትን ጥያቄ በማለፍ የግል ጠበቃ እንዳቆም ጊዜ ሳይሰጠኝ በማልሰማው እና መናገር በማልችለው ቋንቋ ያለአስተርጓሚ የተከሰስኩበትን ነገር ሳላውቅ የተሰጠው ውሳኔ አመልካች በሕገ-መንግስቱ የተሰጠኝን መብት የሚነፍግ ነው፤ አመልካች የተከሰስኩበት ሕግ ከተጠረጠርኩበት ወንጀል ጋር አግባብነት የለውም፤ አመልካች መኪናውን አላሽከረከርኩም የጫነውንም ነገር አላወቅኩም፤ ሹፌሩ መኪናውን ትቶ በመሸሹ በመኪናው አጠገብ ስለተገኘሁ ብቻ ጥፋተኛ ልባል የማይገባ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች እነኚህን ሁኔታዎች ሳያገናዝቡ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የመኪናው ባለቤት ቢሆንም ለሾፌር ሰጥቶ ሲያሽከረክር ከነበረበት ሾፌሩ ማምለጡ ተረጋግጦ ባለበት፤ አመልካች የቡና ነጋዴ ወይም አምራች መሆኑ ባልተረጋገጠበት፤ በሌላ በኩል አመልካች የቡናውን መጫን ያውቅ የነበረ መሆኑ ባልተረጋገጠበት እና በሚገባው ቋንቋ በአግባቡ ስለመተርጎሙ እና የመከላከል መብቱን ስለማወቁ ጥርጣሬ በፈጠረ ሁኔታ የመከላከል መብቱ ታልፎ የመኪናው ባለቤት በመሆኑ ብቻ ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 እና ከተጠቀሰው አዋጅ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የመኪናው ባለቤት ሆኖ ፈቃድ ሳይኖረው በክሱ የተጠቀሰውን ቡና በሌላ ዕቃ ስር ጭኖ ሲሄድ መያዙ ተረጋግጦበታል፤ ቡናው የተጫነው ከአመልካች ዕውቅና ውጪ ነው የሚለው ክርክር አሳማኝ አይደለም፤ ቡናው በሌሊት የተጫነ እና ከሌላ ዕቃ ስር የተጫነ በመሆኑ አመልካች የወንጀል ሀሳብ እንዳለው የሚያሳይ ነው፤ አመልካች በአዋጁ መሠረት ሀላፊነት ስላለበት የመኪናው ባለቤት ስለሆንኩ ተጠያቂ ልሆን አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክር አግባብነት የለውም፤ ፍ/ቤቱ ለአመልካች ክሱን ካነበበለት በኋላ በሚገባው መልኩ በድጋሚ የተነበበለት መሆኑ ተገልጿል፤ የክልሉን ፍ/ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/200 አንቀጽ 17/2 ፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም የሚገደደው የተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት በማያንስ የሚያስቀጣ ከሆነ እና በራሱ ጠበቃ ለማቆም የማይችል ከሆነ ነው፤የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ አመልካችን የሚጠቅም በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። እኛም በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የአመልካች የመሰማት መብት ተጠብቆ የተሰጠ ውሳኔ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል።

በመሠረቱ የተከሰሱ ሰዎች በሕግ የመሰማት መብት / the right to fair trial / ያላቸው ሲሆን ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍ/ቤት በመቅረብ ጉዳዩ በዝግ ችሎት እንዲታይ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ከሌለ በቀር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት ያላቸው መሆኑን የሕገመንግሥቱ አንቀጽ 20/1 ድንጋጌ ያስገነዝበናል። ኢትዮጲያ የተቀበለችው የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ዓለምዓቀፍ የቃልኪዳን ሰነድ አንቀጽ 14 ድንጋጌም .....everyone shall be entitled to a fair and public hearing by a competent, independent and impartial tribunal established by law..... በማለት ይደነግጋል። ይህ መብት በሕገ-መንግስቱም ሆነ ኢትዮጲያ በተቀበለችው ዓለምዓቀፍ ስምምነት እውቅና የተሰጠው መሠረታዊ መብት እንደሆነ እና በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶችም ይህን መሠረታዊ የሆነ መብት የማክበር እና የማስከበር ሀላፊነት እንዳለባቸው ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 9/4 እና 13(1)(2) ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል።

የተከሰሱ ሰዎች ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና በጽሑፍ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን፤ በፍርድ ሂደት ባሉበት ወቅት በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር እና በምስክርነት እንዲቀርቡ ያለመገደድ፤ የቀረበባቸውን ማንኛውንም ማስረጃ የመመልከት፤ምስክሮችን የመጠየቅ፤ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ፤ ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ፤በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል፤ ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግስት ጠበቃ የማግኘት መብት፤ ይግባኝ የመጠየቅ እና የፍርዱ ሒደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ሁኔታ በመንግስት ወጪ ክርክሩ እንዲካሄድላቸው የመጠየቅ መብት ያላቸው ስለመሆኑ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 20 በዝርዝር የተደነገገ ሲሆን የሀገራቱ ሕግ አካል በሆነው የሲቪል እና የፖለቲካ መብት አንቀጽ 14 ድንጋጌም ላይ በዝርዝር ተመልክቷል።

የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ክስ በአግባቡ ተረድተው ክሱን መከላከል የሚችሉትም ክሱ በሚገባቸው ቋንቋ በዝርዝር ሲነገራቸው እና በጠበቃ ሲታገዙ እንደሆነ ግልጽ ነው። በመሆኑም ፍ/ቤቶች የፍ/ቤቱን የስራ ቋንቋ የማይችሉ ተከሳሾች በቀረቡላቸው ጊዜ አስተርጓሚ በመመደብ ክሱ በሚገባቸው ቋንቋ በዝርዝር የመንገር እና በጠበቃ ታግዘው የመከራከር መብት እንዳላቸው፤ ጠበቃ ለማቆም የሚያስችል ዓቅም ከሌላቸው በመንግሥት ወጪ ጠበቃ የማግኘት መበት እንዳላቸው የመንገር ሀላፊነት አለባቸው።

የአመልካች ዋነኛ ክርክር የስር ፍ/ቤት አመልካች በጠበቃ በመታገዝ እንድከራከር አላደረገም፤ አመልካች የፍ/ቤቱን የስራ ቋንቋ የማልችል ሲሆን ያለአስተርጓሚ የተከሰስኩበትን ነገር ሳላውቅ

የተሰጠው ውሳኔ ሕገ-መንግስታዊ መብቱን የሚጻረር ነው የሚል ሲሆን ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤት ባደረገው ክርክር ፍ/ቤቱ ለአመልካች ክሱን ካነበበለት በኋላ በሚገባው መልኩ በድጋሚ የተነበበለት መሆኑ ተገልጿል፤ የክልሉን ፍ/ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/200 አንቀጽ 17/2 ፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠበቃ ለማቆም የሚገደደው የተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት በማያንስ የሚያስቀጣ ከሆነ እና በራሱ ጠበቃ ለማቆም የማይችል ከሆነ ነው በማለት ከሚከራከር እና በስር ፍ/ቤት ውሳኔም ላይ አመልካች በሚገባው ቋንቋ ክሱ በድጋሚ ተነቦለታል በሚል ከመገለጹ በቀር አመልካች የፍ/ቤቱን የስራ ቋንቋ የማይችል ከመሆኑ አኳያ የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግሥቱ በተጠበቀላቸው መብት መሠረት አስተርጓሚ ተመድቦለት ክሱ የተነበበለት እና እንዲረዳው የተደረገ መሆኑን፤በጠበቃ የመወከል መብት እንዳለው እና በግሉ ጠበቃ ማቆም የማይችል ከሆነ በመንግስት ወጪ ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳለው የተነገረው መሆኑን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይዘት አያመላክትም፡፡ አመልካች አስተርጓሚ ተመድቦለት ክሱን እንዲረዳው እስካልተደረገ እና በጠበቃ እስካልታገዘ ድረስ የቀረበበትን ክስ በአግባቡ ተረድቶ ክሱን ለመከላከል ይችላል ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካች የቀረበበትን ክስ በአግባቡ ተረድቶ መከላከል ይችል ዘንድ ለአመልካች አስተርጓሚ እንዲመደብ በማድረግ፤ አመልካች ጠበቃ የማቆም መብት እንዳለው እና ጠበቃ ለማቆም የሚያስችል አቅም ከሌለው በመንግስት ወጪ ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳለው በመንገር ጉዳዩ እንዲታይ ማድረግ ሲገባው ይህን ሳያደርግ የሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዲሪ ሕገመግስቱ እና ኢትዮጲያ በተቀበለቻቸው ዓለምዓቀፍ ስምምነቶች ለከተሰሱ ሰዎች የተጠበቁትን መሠረታዊ መብቶች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራው ክልላዊ መንግሥት የገላና ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 03750 በቀን 13/06/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የምዕራብ ጉጂ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00832 በቀን 30/06/2010 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 260947 መጋቢት 13 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284002 ግንቦት 21 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል ።
2. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 20 ላይ ለተከሰሱ ሰዎች የተጠበቁላቸው መሠረታዊ መብቶች ሳይከበሩ የሚሰጥ ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡
3. የገላና ወረዳ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አውቆ ለአመልካች አስተርጓሚ እንዲመደብለት በማድረግ፤ አመልካች በግሉ ጠበቃ

ማቆም የሚችል ከሆነ በግሉ ጠበቃ እንዲያቆም በማድረግ፤ አመልካች በግሉ ጠበቃ ማቆም የማይችል ከሆነ በመንግሥት ወጪ ጠበቃ እንዲመደብለት በማድረግ አመልካች የቀረበበትን ክስ እዲረዳው ካደረገ በኋላ ጉዳዩን አይቶ ተገቢውን እንዲወስን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

-በአመልካች ላይ የተላለፈው የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሻረ እና ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ የተወሰነ በመሆኑ ተጠሪ ይህ ውሳኔ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በአሥራ አምሥት ቀን ጊዜ ውስጥ መዝገቡን እንዲያንቀሳቅስ ታዟል፡፡

-የገላና ወረዳ ፍ/ቤት የአመልካችን አቆያየት በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሠረት በማድረግ ተገቢውን ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 161062

ቀን 26/04/2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ /ዶ/ር/

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ መህዲ ሸረፋ ጠበቃ መስፍን አለማየሁ ቀረቡ::

ተጠሪ፡- አቶ ሻፊ ሸረፋ - የቀረበ የለም::

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

1. በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ነጥብ በዘመድ ሽማግሌ ውሳኔ መቋጫ ያገኘው ጉዳይ የውሳኔው ተገቢነት የሚመረምርበት ሥርዓት መኖር አለመኖሩን ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በስር አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 104286 ህዳር 08 ቀን 2008 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ ባጭሩ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር አዲስ ካርታ ቁጥር 1648-11/9/4/7 የሆነውን ቤት ለተጠሪ እንዲያስተዳድሩለት በአደራ የሰጡዋቸው ቢሆንም ተጠሪ እንዲያስተዳድሩ የተሰጣቸው ቤት በስማቸው ካርታ ያሰሩ በመሆኑ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡
2. የአሁን ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ነገሩ ዝርዝር መልስ ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ ይዘት ሲታይም ጉዳዩ በዘመድ ሽማግሌዎች ተመርምሮ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ በፍርድ ቤት ድጋሚ ክስ ሊቀርብ አይገባም በማለት መከራከራቸውን የሚያመለክት ነው፡፡
3. በዚሕ አግባብ ክርክሩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች እና ተጠሪ የሚከራከሩበት ጉዳይ ጥቅምት 20 ቀን 2008 ዓ.ም በዘመድ ሽማግሌዎች ውሳኔ ማግኘቱን፤የውሳኔው ይዘትም ንብረቱ የጋራ ስለሆነ ከተስማሙ በስምምነት እንዲጠቀሙበት፤የማይስማሙ ከሆነ ግን ቤቱን ሸጠው እንዲከፋፈሉ መወሰናቸውን፤አመልካች

ሽማግሌዎች መምረጣቸውን ሳይክዱ ሽማግሌዎች በሰጡት ውሳኔ ላይ አልፈረምኩም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ በብይን ውድቅ አድርጎታል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤት ብይን አጽንቷል።የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔና ብይን በመቃወም ለማሳረም ነው።

4. አመልካች ሀምሌ 6 ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱ እንደተመለከትነው ሽማግሌዎች ጭብጥ በመለየት የግራቀኙ ማስረጃ በመስማት ውሳኔ ያልሰጡ ስለመሆኑና፤በሽማግሌዎች ጉዳዩ እንዲታይ ወላጅ አባታቸው ጫና ያሳደሩ በመሆኑ ብይኑ ተሽሮ በፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነው።የአመልካች አቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎትም በ18/12/2010ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ጉዳዩ በዘመድ ሽማግሌ ታይቷል የመባሉ አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ማጣራት ይቻል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪም በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ጥቅምት 20 ቀን 2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበው ጉዳዩ በሽማግሌዎች ተመርምሮ ከተወሰነ በኋላ አመልካች ይግባኝ እንዳልጠየቁ ፤ጉዳዩም በሚገባ ተጣርቶ የተወሰነ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ብይንና ፍርድ ሊጽና ይገባል በማለት ተከራክሯል።አመልካች ህዳር 13 ቀን 2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል።ፍርድ ቤቱም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት የኮ/መ/ቁ 104286 በማስቀረብ ተመልክቷል።

5. ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን እና ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል።

6. መዝገቡ እንደመረመርነው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ስምምነት ጉዳዩ በዘመድ ሽማግሌዎች ውሳኔ እንዲያገኝ ፈቃድ የሰጡ ቢሆንም ሽማግሌዎች ግራቀኙ ሳያነጋግሩ በውሳኔውም ሳይፈርሙ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ተገቢ አይደለም በሚል ነው።ተጠሪ በበኩላቸው የዘመድ ሽማግሌዎች ጉዳዩን አጣርተው የሰጡት ውሳኔ በመሆኑ ሊነቀፍ አይገባም በማለት ተከራክሯል።ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች እና ተጠሪ ጥቅምት 20 ቀን 2008 ዓ.ም ለዘመድ ሽማግሌዎች የዕርቅ ስልጣን መስጠታቸውን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም።በግራቀኙ የተመረጡ ሽማግሌዎች ጥቅምት 20 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጡት ውሳኔ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት የጋራ ንብረት በመሆኑ እንደ መጀመሪያው ተስማምተው እንዲኖሩ ካልተስማሙ ግን ንብረቱ የታላቅና የታናሽ የጋራ ንብረት ስለሆነ ሽጠው በጋራ በእኩል እንዲካፈሉ በሙሉ ድምጽ መወሰናቸውን የሚያሳይ ነው።አመልካች ይህ ውሳኔ መኖሩን ሳይክዱ ውሳኔ በተሰጠበት ሂደት ተሳትፎ ያልነበራቸው በተለይም ማስረጃ ሳያቀርቡ መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ክርክር ማቅረባቸውን ተመልክተናል።

7. በመሰረቱ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በዘመድ ዳኛ ለመጨረስ መስማማት እንደሚችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3325 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡አመልካች ጉዳያቸው በሽማግሌዎች እንዲታይ ወደውና ፈቅደው ከተስማሙ በኋላ ሽማግሌዎች የሰጡት ውሳኔ ባለበት ሁኔታ አዲስ ክስ ማቅረባቸው በሕጉ አግባብ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ አመልካች ሽማግሌዎች የሰጡት ውሳኔ የሚነቅፍ ነገር ካለው በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት ይግባኝ በመጠየቅ ከሚያሳርሙ በስተቀር አዲስ ክስ ማቅረብ ተገቢ አለመሆኑን፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበለት ፍርድ ቤትም በዚህ ጉዳይ ብይን መስጠቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 244/2/ ረ/ ያገናዘበ ነው ከሚል በቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት በተመለከተ የቤተ ዘመድ ሽምግልና ዳኞች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 350 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በሚፈቅደው አግባብ ይግባኝ ጠይቀው ውሳኔውን ስለማሻራቸው ያቀርቡት ክርክር የለም እንዲህ ከሆነ ደግሞ የፀና የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ውሳኔ ባለበት ሁኔታ በሕጉ ያልተመልከቱ መስፈርቶች በመጥቀስ ውሳኔውን መቃወም ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች የሽምግልና ዳኝነት ውሳኔ ከሚያሳርሙ በስተቀር በውሳኔው አልፈረምኩም በሚል ምክንያት በድጋሚ ክስ ማቅረብ የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡት ክስ በድጋሚ የቀረበ ነው በማለት የሰጡት ብይን እና ውሳኔ በሕጉ አግባብ ነው ከሚል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚሕም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 104286 በ03/05/2009 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 182345 በ13/10/2010 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል ዕግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይፃፍ፡፡ የስር ፍ/ቤት መዝገብ በመጣበት አካኋን ይመለስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ተመለሰ ውሳኔ በ02/05/2011 ዓ/ም ተነበበ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ160314

ቀን 30/09/2011

ዳኞች፡ ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡ የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት-ነ/ፈጅ አሸናፊ ፊጣ

ተጠሪ፡ ቢጋና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር- አልቀረቡም ።

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የኮንስትራክሽን መስሪያዎች ኪራይ ውል የተመለከተ ሲሆን የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ በኮ/መ/ቁ138392 ባቀረበው ክስ መነሻ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር ሰኔ እና ሐምሌ 2002 ዓ.ም በተደረገው ውል ዲኤስቢ3-ዲዜድ 0279 ባለ 305 የፈረስ ጉልበት ዲ 8ቢ0342ባለ 305የፈረስ ጉልበት በሰዓት ብር 1437.50 ለመክፈል በመስማማት የተከራየ ቢሆንም ክፍያው አጠቃልሎ ባለመክፈሉ ብር 875,158.63 የ3 ዓመት ወለድ ታስቦ ብር 1,111,451.46 እንዲሁም ክስ ከተመሰረተበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ እንዲከፈለው እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡
2. አመልካች ባቀረበው መልስ፡- ክፍያ ለመጠየቅ የተጠሪ ተወካይ እና የአመልካች ኦፕሬተር የፈረሙት ሰነድ መቅረብ እንደሚገባ አዲስ አበባ ለተሰሩ ስራዎች ተገቢ ክፍያ መፈፀሙ አመልካች የሚያውቀው ሌላ ክፍያ የሌለ መሆኑን፣ ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት ያዘጋጀው የጊዜ መቆጣጠሪያ ማጠቃልያ ራሱ ያዘጋጀው በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ2016 መሰረት ተቀባይነት እንደሌለው፣ ከውሉ በስተቀር ሌላ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ውሉ ስራ መሰራቱን አያሳይም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን አመልክቷል፡፡

3. በዚሁ መልኩ ክርክሩ የቀረበለትን ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም በፍርድ ቤት ትእዛዝ የቀረበው ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ለተጠሪ ያልከፈለው ገንዘብ መኖሩ ባቀረበው ማስረጃ አስረድቷል፡፡ክሱ በተሰማበት ቀን ከሳሽ አለኝ የሚለውን የሰዓት መቆጣጠሪያ ቅጾች ከመግለጫ ጋር እንዲያቀርብ በ03/8/2006 ዓ.ም ታዞ ግንቦት 30 ቀን 2008 ዓ.ም አቅርቧል፡፡አመልካች የቀረበው ማስረጃ በዋና መስሪያ ቤት የሌለ በመሆኑ በሀሰት የተዘጋጀ ሊሆን ስለሚችል እንዲመረመር ባቀረበው ጥያቄ መሰረት በፎረሲክ ተመርምሮ ውጤቱ የቀረበ ሲሆን በሰነዱ ያለው ፊርማ ከአንድ በስተቀር በአመልካች ሰራተኞች መፈረሙን ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ማስረጃው በመጀመርያ ክርክር አልቀረበም የሚል መቃወሚያ ያቀረበ ቢሆንም በፍርድ ቤት ትእዛዝ የቀረበ በመሆኑ ክርክሩ ተገቢነት የለውም፡፡ አመልካች ያልከፈለው ዋና ገንዘብ ወለድ በድምር ብር 1,105,507.12 እንዲከፍል የነዳጅ በተመለከተ እንዲከፈለው ክሱ በሚሰማበት ጊዜ አልጠየቀም፡፡ በህጉ አግባብ የመከላከያ መልስ ለማሻሻል ጥያቄ ከሚቀርብ በስተቀር አዲስ ክርክር ማቅረብ አይቻልም በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት ያላገኘ በመሆኑ ውሳኔው እና ትእዛዙ በመቃወም ለማሳረም ይህ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡
4. አመልካች በ21/10/2010 ዓ.ም የተፃፈ 7 ገጽ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱ ሲታይም የስር ፍርድ ቤት ውሉ ካለው ስታንዳርድ /ኖርም/ አንጻር መተርጎም እንደነበረበት ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ ክስ ሲያቀርብ በእጁ የነበረ ከመሆኑ አንፃር በሂደት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱ በህጉ አግባብ አለመሆኑን፣ የመከላከያ መልስ ለማሻሻል ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ መደረጉ የቀረበበት ክስ የመከላከል መብት የሚያጣብብ መሆኑን፣ የነዳጅ ክፍያ በተመለከተ ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ የግራ ቀኙ ስምምነት መሰረት ያላደረገ መሆኑን የክፍያ ስርዓቱ ውጤታማ የስራ ሰዓት ግምገማ መሰረት በማድረግ ስሌቱ ቢሰራ ሊከፈል ይገባ የነበረ ብር 217,274.71 ብቻ እንደሆነ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ እንዲሻር መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም አመልካች ተጨማሪ ማስረጃ በመቃወም አቤቱታው ለማሻሻል ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለማግኘቱን አግባብነት እንዲሁም ክፍያው መሰራት ያለበት የስራ ዓይነትና ዋጋ መሰረት በማድረግ ነው ወይስ ተሰራ የተባለው ሰዓት በማሰላት ብቻ ነው? የሚል አከራካሪ ጭብጥ ከውሉ አንቀጽ 8.1 እና 8.2 አንፃር አግባብነቱ ተጠሪ ባለበት መመርመር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም ጥቅምት 20 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረበው መልስ አመልካች መልሱ ለማሻሻል ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ መሆኑ፣ በቀረበው ሰነድ አስተያየት መስጠቱን ክፍያውም ተደምሮ አማካይ በመውሰድ የሚሰራ እንጂ በውጤታማነት የስራ ሰዓት ብቻ ተመርኩዞ የሚወሰን አለመሆኑን የተሰራውን ስራ መጠን የሚያሳይ ሰነድ ቀርቦ የተወሰነ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ ሊነቀፍ አይገባም በማለት

ተከራክሯል፡፡ አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስ አቤቱታው አቤቱታውን አጠናክሯል፡፡ ችሎቱም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲመች የከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁ 138392 በ14/09/2011 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

5. የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለው ሲሆን እኛም ግራ ቀኙ በጽሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡
6. ከክርክሩ ሂደት መረዳት የተቻለው አመልካች እና ተጠሪ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ኪራይ ውል ማድረጋቸውን ያላከራከረ ቢሆንም ተጠሪ እንዲከፈለው ዳኝነት የጠየቀበት የገንዘብ መጠን በተመለከተ ግን ክርክር መነሳቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ለውሳኔ መሰረት የሆነውን የሰነድ ማስረጃ ተጠሪ ክሱ ሲመሰርት አያይዞ ያላቀረበው ከመሆኑ አንፃር በክርክር ሂደት እንዲያቀርብ መፈቀዱ ስነ ስርዓታዊ አይደለም በሚል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ቀሪ ክፍያ አለ የሚባል ቢሆን ስሌቱ መሰራት ያለበት ባቀረበው ሰዓት ድምር ሳይሆን ውጤታማ የስራ ሰዓት ግምገማ መሠረት በማድረግ ነው የሚል ክርክር ማቅረቡን መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ከክሱ በኋላ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ላይ አስተያየቱን የሰጠ በመሆኑ የመከላከያ መልሱ ለማሻሻል ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ማጣቱ በአግባቡ ስለመሆኑ ቀሪ ክፍያ በተመለከተም በተደረገው ማጣራት ያልተከፈለ ገንዘብ መኖሩን ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ ሊነቀፍ አይገባም ብሏል፡፡
7. በመሰረቱ መብት ለማስከበር ክስ የሚመሰርት ሰው ክሱን ለማስረዳት ይጠቅማል ያለውን ማስረጃ ዓይነት እና ዝርዝር ሁሉ መጀመርያ ከሚያቀርበው ክስ ጋር አያይዞ ማቅረብ ያለበት ሲሆን በእጁ የሌሉ ማስረጃዎች ካሉ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ማቅረብ እንዲቻል የሚገኙበት መስርያ ቤት (ስፍራ) ጭምር በመግለጽ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ137(1) እና 223 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት እና መንፈስ ያስገነዝቡናል፡፡ የከሳሽ ወገን መጀመሪያ ያላቀረበው ማስረጃ ካለ በልዩ ሁኔታ በቂ ምክንያት መኖሩን በማስረዳት በፍርድ ቤት ፈቃድ ሊቀርብ እንደሚችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ137(2) እና 256 ጥምር ንባብ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ፍርድ ቤት ማስረጃ በማስቀረብ የሚመረምርበት ስርአት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ145 እና 256 ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ክስ በሚሰማበት ወቅት ያልቀረበ ሰነድ መኖሩን በመግለጽ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ማግኘቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ተጠሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ ከተፈቀደለት በኋላ አመልካች የመከላከያ መልስ ለማሻሻል ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ መደረጉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት ይጠቅመኛል ያለውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ክስ በመሰረተበት ቀን ያላቀረበበት በቂና ህጋዊ ምክንያት ምን እንደሆነ የስር ፍርድ ቤት በ3/8/2006 በሰጠው ትእዛዝ ግልጽ አላደረገም፡፡ ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት በመጀመሪያ ቀጠሮ ያላቀረበው

ማስረጃ በሂደት እንዲያቀርብ ከተፈቀደ አመልካችም የቀረበውን ማስረጃ አግባብነት እና ተአማኒነት ለመቃወም እንዲችል የመከላከያ መልሱ እንዲያሻሽል ሊፈቀድ ይገባ ነበር፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያ ያልቀረበው ማስረጃ ለውሳኔው መሰረት ከተደረገ አመልካችም ይህ ማስረጃ ተገቢ አለመሆኑን ለማሳየት ወይም ለመከላከል እኩል የመደመጥ መብት ሊነፈግ አይገባም፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን የመራበት አግባብ በህጉ የተዘረጋውን ጥብቅ የክርክር አመራር ስርዓት የተከተለ ባይሆንም የተጠሪ ማስረጃ እንዲቀረብ በፈቀደበት ሁኔታ አመልካችም የበኩሉን ማስተባብያ ለማቅረብ ይችል ዘንድ የመልስ ማሻሻል ጥያቄ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል፡፡ አመልካች በተሟላ መልስ ባልተከራከረበት ሁኔታ ተጠሪ ባቀረበው ሰነድ ላይ አስተያየቱን በጽሁፍ ብቻ ያቅርብ ተብሎ የመደመጥ መብቱ ሊታለፍ አይገባም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ ያቀረበው አዲስ ማስረጃ የክርክሩ ይዘት እና ጭብጥ ሊለውጥ የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በ23/10/2006 ዓ.ም ያቀረበው የመከላከያ መልስ የማሻሻል መሰረታዊ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ የፌዴራል ህገ መንግስት አንቀጽ 37 እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ91 ያላገናዘበ ነው ብለናል በመሆኑም አመልካች የተሟላ ክርክር ለማቅረብ እንዲችል የመከላከያ መልሱ እንዲያሻሽል ሊፈቀድለት ይገባል ብለናል፡፡

8. አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተፈፀመ ያለው ሌላ መሰረታዊ ስህተት ክፍያው የተሰራበት ስሌት ተገቢነት ነው፡፡ አመልካች ካቀረበው ክርክር መገንዘብ የተቻለው ቀሪ ክፍያ የተሰራበት ስሌት ውሉን መሰረት አላድረገም በሚል ነው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው በዝርዝር እንደገለጸው ክፍያው የአከፋፈል ስታንዳርድ እና ኖርም የተከተለ አይደለም በሚል ነው፡፡ተጠሪ በበኩሉ ክፍያው በአግባቡ ተሰልቶ የቀረበ በመሆኑ የአመልካች ክርክር ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ውሳኔ እንደተመለከትነው የክፍያው ስሌት የተሰራው አጠቃላይ የተሰራው ሰዓት በመደመር መሆኑን ከሚያሳይ ውጭ በአመልካች አቤቱታ እንደተገለጸው ውጤታማ የስራ ሰዓት ግምገማ መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ተጣርቶ የተወሰነ ስለመሆኑ መዝገቡ አያሳይም፡፡ በመሆኑም ቀሪ ክፍያ መኖሩን ከተረጋገጠ በውሉ መሰረት ክፍያ ሊፈፀም የሚገባው አመልካች እንደሚለው ውጤታማ የስራ ሰዓት ግምገማ መሰረት በማድረግ ነው ወይስ ተጠሪ እንደሚከራከረው የስራ ሰዓት ተደምሮ አማካይ በመውሰድ ነው? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ውሉ መሰረት በማድረግ በሚቀርብ የባለሞያ ማብራሪያ መሰረት ተጣርቶ የሚወሰን እንጂ ከወዲሁ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ የሚደረግበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በመሆኑም የክፍያ ስርዓቱ በውሉ መሰረት መከፈል አለመከፈሉን በድጋሚ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት መጀመሪያ ጉዳዩን የተመለከተው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበው ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ተቀብሎ አመልካች ያቀረበው የመከላከያ መልስ ማሻሻያ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ እንዲሁም ክፍያ የተጠየቀው በውሉ መሰረት መሆን አለመሆኑን በአግባቡ ሳያጣራ መወሰኑ

እየታወቀ ይኸው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትእዛዝ መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ተከታዩን ወሰነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ138392 በ26/06/2010 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/ብ/ይ/መ/ቁ156988 በ30/09/2010ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ሽረናል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው የመከላከያ መልስ የማሻሻያ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በህጉ አግባብ አይደለም ብለናል፡፡
3. አመልካች በተሟላ ሁኔታ ለመከራከር እንዲያስችለው መልሱን እንዲያሻሽል አዘናል፡፡
4. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋው የመ/ቁ138392 በማንቀሳቀስ አመልካች መልሱን ካሻሻለ በኋላ በፍርድ ይዘቱ እና መንፈስ እንዲጣሩ የተለዩ ነጥቦች መሰረት በማድረግ ክፍያ የተጠየቀው በውሉ መሰረት ነው ወይስ አይደለም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ እና ተያያዥ ነጥቦች በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ በማጣራት እንዲሁም አግባብነት ካለው ተቋም ተገቢ ነው ያለውን ማስረሰጃ በማሰባሰብ ወይም ባለሞያ በመመደብ በማጣራት ተገቢ ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ343(1) በሚያዘው መሰረት መልሰንለታል፡፡
5. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
6. የውሳኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡
7. መዝገቡ ሲሰራ ቆይቶ በ6/10/2011 ዓ.ም ተነበበ፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/አ

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ
ተክሊት ይመሰል
ቀነዓ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ - ጠበቃ አቶ ዳኛቸው ቱሉ ቀርበዋል፡፡
ተጠሪ፡- አቶ ተመስገን ደምሴ - ጠበቃ አቶ ብርሃኑ ታዬ ጋር ቀርበዋል፡፡

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለችሎቱ ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.132562 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በግልግል ጉባኤ ዳኞች ዘንድ የአሁን አመልካች የመቃወም አመልካች፣የአሁን ተጠሪ ደግሞ የመወቃወም ተጠሪ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ችሎት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመ.ቁ.110552 አስቀርቦ እንደተመለከተዉ፤ ይህ ጉዳይ የተጀመረዉ የአሁን ተጠሪ በሥር ተከሳሽ ዶ/ር አብነት ግርማይ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ሲሆን፣ የክሱም ይዘት በአጭሩ፡- በከሳሽ እና ተከሳሽ መካከል ሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም / June 30/2005 GC/ በተደረገዉ የኪራይ ዉል ተከሳሽ በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 15 /በአሁኑ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 4 አስተዳደር/ ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 414 የሆነዉን ሕንጻ ተከራይተዉ ሲጠቀሙበት ቆይተዉ የኪራይ ዉሉ የተቋረጠ በመሆኑ ለቤቱ እድሳት ከሳሽ ያወጣዉን ወጪ እንዲከፍሉኝ፣ ያልተከፈለዉን ዉዝፍ የኪራይ ክፍያ እንዲከፍሉኝ፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት በቤት ጥበት ምክንያት ተጎዳብኝ በማለቱ 5 ክፍል በከሳሽ ተሰርቶ ሲገለገልበት ከቆየ በኋላ ነባሩን በር በብሎኬት ዘግቶና አጥሩን አፍርሶ ሌላ መዉጫ በር በመስራት የሚገለገልበት ያላስረከበዉን 5 ክፍል ቤት እንዲያስረክብ፣ በእነዚህ ክፍሎች ላይ የኪራይ ክፍያ በገበያ ዋጋ እንዲከፍለኝ በማለት ከሷል፡፡ ተከሳሽ በበኩሉ ባቀረበዉ መልስ አምስት ክፍል ቤቶችን በተመለከተ ከሳሽ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ መብትና ጥቅም የለዉም፣ ተከሳሽ ቤቱን የሚመለከተዉ አካል በማስፈቀድ የሰራ ነዉ በማለት እና በሌሎች ነጥቦች ላይ መከላከያ ክርክራቸዉን አቅርቧል፡፡

ከዚህ በኋላ የግልግል ጉባኤዉ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሕንጻ ኪራይ ዉሉን መሰረት በማድረግ የዉዝፍ ኪራይ ክፍያ፣ ለሕንጻዉ እድሳት እንዲሁም ወጪና ኪሳራ በተመለከተ ሊከፈል ይገባል ያለዉን ገንዘብ በመወሰን፣ ተከሳሽ በኪራይ ዉሉ መሰረት ከተከራየዉ ዋናዉ ቤት ይዞታ ዉጭ ባለዉ ቦታ የተሰሩትን 5 ክፍሎች በከሳሽ የተሰሩ መሆናቸዉን የሰዉ ምስክሮች ያረጋገጡ ስለሆነ ተከሰሽ በዉል የያዛቸዉንና በርክክብ ወቅት ያላስረከባቸዉን አምስት ክፍል ቤቶችን ከነአጥር ግቢዉ ለከሳሽ እንዲያስረክብ እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ዉሳኔ በኋላ የመቃወም አመልካች ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አቅርቧል፡፡ የመቃወሚያ አቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 4 ክልል ዉስጥ የሚገኝ በ950 ካ.ሜ ቦታ ስፋት ላይ ያረፈዉ ቤት በእነ ወ/ሮ አየለች ወርቁ ስም ተመዝግቦ ካርታ የተሰጠበትን የመቃወም አመልካች በሽያጭ ዉል ገዝተዉ የተላለፈላቸዉ እና የሊዝ ዉል ከቦሌ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የፈጸሙበትን፣ እንዲሁም የቤቱን ስመ ሀብት ወደ አመልካች ለማዛወር በሂደት ላይ እያለሁ፣ ይህ ቤት እንደፍርድ ባለዕዳ ንብረት ተቆጥሮ የአፈጻጸም ትዕዛዞች የተሰጠበት ስለሆነ እነዚህ አምስት ክፍል ቤቶች የመቃወም አመልካች ንብረት ስለሆኑ የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

በዚህ የመቃወሚያ ማመልከቻ ላይ ከሳሽ አቶ ተመስገን ደምሴ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ መልስ ያቀረቡ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወምያ በአጭሩ፡ የመቃወም አመልካች ወደ ክርክሩ ለመግባት መብትና ጥቅም የላቸዉም፣ ይህ ጉዳይ የግልግል ጉባኤ የሰጠዉ ዉሳኔ በይግባኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.110552 በ10/3/2008 ዓ.ም በሰጠዉ ፍርድ ጸንቷል፤ አመልካች በአፈጻጸም ላይ ጣልቃ ገብተዉ መብታቸዉን ማስከበር ነበረባቸዉ፣ የመቃወም አመልካች የዚህ ንብረት ባለሀብት ስለመሆናቸዉ ካርታ አላቀረቡም፣ አመልካች በዉል ገዝቻለሁ ያሉት ቤት የቤት ቁጥር የለዉም፤ የመቃወም አመልካች አቤቱታ ዉሳኔ ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር የሚገናኝ አይደለም ጉባኤዉ የመቃወም አቤቱታዉን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለዉም፣ እንዲሁም በአማራጭ መልስ እንዳቀረቡ ተመልክቷል፡፡ ተከሳሽ ዶ/ር አብነት ግርማይ በወረዳዉ አስተዳደር በኩል መጥሪያና አቤቱታዉ በድርጅቱ ቤት ላይ ቢለጠፍም ባለመቅረባቸዉ ሳይከራከሩ ቀርተዋል፡፡

በመቀጠል የግልግል ጉባኤዉ፣ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር፣ የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃ በመመዘን፣ አስቀድመዉ የተሰሙትን የሰዉ ምስክሮች ቃል በመመርመር፣ በሰጠዉ ብይን ከሳሽ እነዚህን ቤቶች መስራታቸዉን በምስክሮች ቃል ያስረዱ ሲሆን የመቃወም አመልካች ይህን የሚያስተባብል ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ የመቃወም አመልካች ክስ ባቀረቡት አምስት ክፍል ቤቶች ላይ በዉል ወይም በሕግ የተረጋገጠ መብትና ጥቅም የላቸዉም በማለት ከሳሽ ያቀረበዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል አቤቱታቸዉን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33 /2/ /3/ እና 244/2፣ መ/ መሰረት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የሥር የመቃወም አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ

ውሳኔ ምክንያቱን በማስቀመጥ የግልግል ጉባኤውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በ29/5/2009 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡ ለክርክር ምክንያት የሆኑት በ950 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፉት 5 ክፍል ቤቶች በእነ ወ/ሮ አየለች ወርቁ ስም የተመዘገበ እና በሽያጭ ለአመልካች የተላለፈ እንዲሁም አመልካች ከቦሌ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ጋር የሊዝ ውል ፈጽመዋል፡፡ አመልካች ይህን ንብረት በእጃቸው አድርገው የሚቆጣጠሩ እና የሚያስተዳደሩ ሆኖ ሳለ የግልግል ጉባኤው እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ንብረቱ የአሁን ተጠሪ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ እንዲታረምልን፣ የጠበቃ አበል ከወጪ ጋር እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት በዚህ ጉዳይ የሚጣራ ነጥብ አለ በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ባዘዘው መሰረት መጋቢት 4 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ በዚህ ጉዳይ የግልግል ጉባኤው የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ ጉዳዩን በሕግ አግባብ አጣርተው የሰጡት ውሳኔ እና የህግ ስህተት የሌለባቸው ስለሆኑ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የሥር ውሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸውን ክርክር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ‹‹የግልግል ጉባኤው ይህን ጉዳይ ተቀብሎ ግራ ቀኞቸውን አከራክሮ የመወሰን ስልጣን አለው ወይስ የለውም?›› የሚለውን ነጥብ እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለው መርመሮታል፡፡ ይህ ችሎት የሰበር አጣሪ ችሎት በጉዳዩ ፍሬ ነገር ከያዘው ጭብጥ አስቀድሞ የስልጣን ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ የስልጣን ጥያቄን እንደጭብጥ ለመያዝ ችሏል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም የዳኝነት ጥያቄን የሚያይ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆኑን በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ማረጋገጥ እንደሚገባው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.9 /2/ ሥር ተመልክቷል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤት የስልጣን ጥያቄ በማንሳት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው እንደሆነ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 /2፣ ሀ/ እና 245 /2/ መሰረት ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሎ መወሰን እንደሚገባው ተደንግጓል፡፡ ይህ ደግሞ ለግልግል ጉባኤውም የሚሰራ በመሆኑ የስልጣን ጉዳይ ምላሽ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ አግባብ እንደመረመርነው የግልግል ጉባኤው በከሳሽ አቶ ተመስገን ደምሴ እና በተከሳሽ ዶ/ር አብነት ግርማይ መካከል ያለውን ክርክር ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን ያገኘው ሁለቱ ግለሰቦች ሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም / June 30/2005 GC/ ባደረጉት የሕንጻ ኪራይ ውል መነሻነት መሆኑን ከሥር ውሳኔዎች ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚህ ውል አንቀጽ 11 በአከራዩ እና ተከራዩ መካከል ከውሉ ጋር ተያይዞ የሚነሱትን ግጭቶች በስምምነት ለመፍታት፣ ይህ ካልተቻለ ጉዳዩ ግራ ቀኞቸው

በሚመርጡት ገላጋይ ሽማግሌዎች ታይቶ ውሳኔ እንደሚሰጥበት መስማመታቸዉን ያመለክታል፡፡ የሕንጻ ኪራይ ዉሉ የተፈጻሚነት አድማስ ደግሞ በዉሉ አንቀጽ 1 የተመለከተ እና የቤት ቁጥር 414 ሕንጻ ከነግቢ እና በጊዜያዊነት የተሰሩትን ተገጣጣሚ ግንባታዎችን እንደሚመለከት እና ይህን የሚያመክት አባሪም የዉሉ አካል እንደሆነ ያሳያል፡፡ በዚህ ዉል የአከራይ እና የተከራይ መብትና ግዴታ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የግልግል ጉባኤዉ በዚህ ጉዳይ ስልጣን ሊኖረዉ የሚችለዉ በዉሉ የተፈጻሚነት ወሰን ድረስ እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡

እንደሚታወቁ ተዋዋይ ወገኖች የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1678 ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን በማሟላት ዉል የተደረጉ እንደሆነ፣ በሕግ የተቋቋመዉ ዉል ዉሉን ባቋቋሙት ተዋዋይ ወገኖች መካከል ሕግ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 /1/ ሥር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ አንድ ዉል አስገዳጅነት የሚኖራዉ ዉሉን ፈቅደዉና ተስማምተዉ በተዋዋሉ ተዋዋይ ወገኖች ላይ እንጂ የዉሉ አካል ባልሆኑት ሶስተኛ ወገኖች ላይ አስገዳጅነትም ሆነ ተፈጻሚነት እንደሌለዉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን ተጠሪ እና የሥር ተከሳሽ ዶ/ር አብነት ግርማይ መካከል የተደረገዉ የኪራይ ዉል ተፈጻሚነት ዉሉን ባደረጉት ተዋዋይ ወገኖች ብቻ ላይ ነዉ፤ በዚህ ዉል መነሻነት የሚነሳዉም አለመግባባት በግልግል ጉባኤዉ ታይቶ ዉሳኔ ሊሰጥ የሚችለዉ በእነዚህ ሰዎች መካከል ብቻ ነዉ፡፡ በዚህ የኪራይ ዉል መሰረት የኪራይ ክፍያ፣ የቤቱ እድሳትና የጥገና ጉዳይ፣ ተከራይ በዉሉ በግልጽ ተገልጾ የተረከበዉን ሕንጻ፣ ክፍሎች እና ዕቃዎች ከማስረከብ ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች የሚያጠቃልል እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ በአከራይ እና ተከራይ መካከል አለመግባባት የተነሳ እንደሆነ በዚህ ዉል አግባብ ሊፈታ እንደሚገባ ግልጽ ነዉ፡፡ እነዚህ ተዋዋይ ወገኖች በኪራይ ዉል ምክንያት በመካከላቸዉ የሚነሳዉን አለመግባበት በገላጋይ ሽማግሌዎች እንዲታይላቸዉ መስማማታቸዉ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3325 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት ያለዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸዉ የሚነሳዉን አለመግባባት በሽምግልና ዳኝነት ለመጨረስ መስማማታቸዉ የሕጉን ዓላማ የተከተለ እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ የሽምግልና ዳኝነት ስልጣን በጠባቡ መተርጎም እንዳለበት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3329 ሥር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ከእነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ ተዋዋይ ወገኖች በምን አግባብ የገላጋይ ዳኞችን መምረጥ እንደሚችሉም በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም በዚህ አግባብ የተቋቋመዉ የግልግል ጉባኤ ስልጣን ሊኖረዉ የሚችለዉ በዚህ አግባብ ተስማምተዉ ገላጋይ ዳኞችን መርጠዉ ስልጣን በሰጡት ወገኖች ብቻ ላይ እና በዚህ አግባብ እንዲታይላቸዉ በተስማሙበት ጉዳይ ወሰን ድረስ ብቻ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንጻር አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ባቀረቡት መቃወሚያ በከሳሽ እና በተከሳሽ በተደረገዉ ክርክር መነሻነት የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል፣ እነዚህ ለክርክር ምክንያት የሆኑት አምስት ክፍል ቤቶች የፍርድ ባለዕዳ የዶ/ር አብነት ግርማይ ንብረት ሳይሆኑ አመልካች በሽያጭ ዉል ከሌሎች ግለሰቦች ገዝተዉ የተላለፉላቸዉ እና የሊዝ ዉል የፈጸሙበት የግል

ሀብታቸዉ እንደሆነ በመግለጽ ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ በበኩላቸዉ ባቀረበዉ ክርክር እነዚህ ቤቶች የራሱ ንብረት መሆናቸዉንና ባለሀብት ተጠሪ እንደሆኑ ምስክሮች አረጋገጠዋል፣ አመልካች መብት እንደሌላቸዉ በመግለጽ ነዉ፡፡ ከዚህ ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለዉ ግራ ቀኙቸዉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1204-1206 ባሉት ድንጋጌዎች አግባብ የባለሀብትነት መብት በተመለከተ የመፋለም ክርክር ማቅረባቸዉን የሚያመለክት እንደሆነ ነዉ፡፡ እንዲሁም ከጅምሩም በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል እነዚህን አምስት ክፍል ቤቶች በተመለከተ ሲካሄድ የነበረዉ የመፋለም ክርክር እንደነበር የቀደመዉ የግራ ቀኙቸዉ ክርክር፣ መቃወሚያ ያቀረበበት የግልግል ጉባኤዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ የሚያስገነዝብ ጉዳይ ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ ክርክር የግልግል ጉባኤዉም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ እንደሰጡ ቢገለጽም የዉሳኔያቸዉ ይዘት ሲታይ ግን ለክርክር ምክንያት የሆኑት አምስት ክፍል ቤቶች ማን እንደሰራቸዉ፣ ቤቶች የማን ንብረት እንደሆኑ የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎች በመመዘን እንዲሁም አስቀድሞ የተሰሙትን የተጠሪን የሰዉ ምስክሮች በመመርመር የባለሀብትነት መብት ላይ ዉሳኔ እንደሰጡ የዉሳኔዎቹ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ ምላሽ የማግኘት ያለበት ጉዳይ የግልግል ጉባኤዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተነሳዉን የአምስት ክፍል ቤቶችን የባለሀብትነት መብት ጋር የተያያዘ የመፋለም ክርክር ተቀብሎ ግራ ቀኙቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ ለመስጠት የዉልም ሆነ የሕግ ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ለክርክር ምክንያት የሆኑት አምስት ክፍል ቤቶችን በተመለከተ በኪራይ ዉሉ እንደተሸፈኑ ሳይሆን የሥር ተከሳሽ እነዚህን ቤቶች አጥር ሰርተዉ ሌላ በር ከፍተዉ በሕገ ወጥ መንገድ ሲገለገሉበት እንደነበር እና የኪራይ ዋጋም ቢሆን በኪራይ ዉሉ ላይ የተመለከተዉ ሳይሆን በገበያ ዋጋ በወር በብር 25 ሺህ ብር ታስቦ እንዲከፈላቸዉ መጠየቃቸዉን ያሳያል፡፡ የዚህ የዳኝነት ጥያቄ እንደሚያመለክተዉ እነዚህ ቤቶች በኪራይ ዉሉ የተካተቱ ነበር ወይ? የሚለዉን ጥያቄ የሚያነሳ ነዉ፡፡ ከዚህም በላይ እነዚህን ቤቶች በተመለከተ በከሳሽ እና ተከሳሽ መካከል የመፋለም ክርክር መነሳቱን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በአሁን ተጠሪ እና በሥር ተከሳሽ ዶ/ር አብነት ግርማይ መካከል የተደረገዉ የሕንጻ ኪራይ ዉል ተፈጻሚነት ያለዉ በእነዚሁ ተዋዋይ ወገኖች ላይ እንጂ የአሁን አመልካች ላይ እንዳልሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ ይህ ዉል የሚፈጥረዉ መብትና ግዴታ አመልካችን የማይመለከት እና ዉሉን መነሻ ያደረገ አለመግባባት ቢከሰትም በገላጋይ ዳኞች እንዲፈታ ለማድረግ የሚገደዱበት አግባብ አይኖርም፡፡ እንዲሁም የአሁን አመልካች እነዚህን የግልግል ዳኞች መርጠዉ ጉዳያቸዉ እንዲታይላቸዉ ስልጣን የሰጡት ነገር ባለመኖሩ የግልግል ጉባኤዉ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ለመዳኘት የህግ ስልጣን የለዉም፡፡ ይህ ሲባል ግን የግልግል ጉባኤዉ የአመልካችን መቃወሚያ ከጅምሩ ስልጣን የለኝ በሚል ምክንያት ዉድቅ እንዲያደርግ ሳይሆን አመልካች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ መሰረት በማድረግ አስቀድሞ እነዚህ አምስት ክፍል ቤቶችን በተመለከተ የባለሀብትነት መብት ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.360 /2/ መሰረት ተገቢውን በመወሰን ነው፡፡ ይህ ማለት የግልግል ጉባኤው በኪራይ ውል የተመለከቱትን ቤቶች የባለሀብትነትን መብት በተመለከተ የመፋለም ክርክርን ሰምቶ ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን እንደሌለው በመገንዘብ በእነዚህ አምስት ክፍል ቤቶች ላይ አስቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ ማንሳት ይገባው ነበር፡፡

የአሁን አመልካች በበኩላቸው የራሴ ንብረት ናቸው የሚሏቸውን እነዚህን ቤቶች በተመለከተ በገላጋይ ዳኞች እንዲታይላቸው የተስማሙት ነገር የለም፣ የመረጡትም የገላጋይ ዳኛ አለመኖሩን የሥር ውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን አመልካች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 እና 78 መሰረት ነጻና ገለልተኛ በሆነ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳያቸው ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ሕገ መንግስታዊ መብት አላቸው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ ውሳኔ የሰጠው የግልግል ጉባአው ለአመልካች ነጻና ገለልተኛ የዳኝነት አካል ነው ለማለት ስለማይቻል ነው፡፡ አመልካች በሕገ መንግስቱ የተጠበቀላቸው በሕግ በተቋቋመ ነጻና ገለልተኛ የዳኝነት አካል በሆነው የመደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት መብት የሚነፈጉበት አግባብ የለም፡፡

በመሆኑም የግልግል ጉባኤው ለክርክር ምክንያት የሆኑትን አምስት ቤቶችን በተመለከተ የባለሀብትነትን የመፋለም ክርክር ሰምተው መወሰን ስልጣን እንደሌለው በመገንዘብ አስቀድሞ በእነዚህ ቤቶች ላይ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር ግራ ቀኞቹ በዚህ ጉዳይ ከፈለጉ ክርክራቸውን ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚችሉ በመጠቆም መወሰን ሲገባው፣ ባልተሰጠው ስልጣን እነዚህን አምስት ቤቶች በተመለከተ ማስረጃ በመመዘን ተጠሪ ባለሀብት ናቸው በማለት ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በበኩሉ ከስልጣን አንጻር ጉዳዩን በመመርመር የግልግል ጉባኤውን ብይን ማረም ሲገባው ከዚህ ይልቅ የራሱን ዝርዝር ምክንያቶችን በማከል የሥር ብይን በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

ሲጠቃለል የግልግል ጉባኤው የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለሀብትነት የመፋለም ዳኝነት ጥያቄን ተቀብሎ ግራ ቀኞቹን አከራክሮ የመወሰን ስልጣን ሳይኖረው ለክርክር ምክንያት የሆኑት አምስት ክፍል ቤቶች የአሁን ተጠሪ ንብረት ናቸው፣ አመልካች ግን መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆኑ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የግልግል ጉባኤው እነዚህን አምስት ክፍል ቤቶች በተመለከተ ጥር 25 ቀን 2007 የሰጠው የውሳኔ ክፍል እና መስከረም 4 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና ይህን ብይን በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.132562 ጥር 25 ቀን 2009 ዓ.ም

የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የግልግል ጉባኤዉ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን አምስት ክፍል ቤቶችን በተመለከተ የባለሀብትነት የመፋለም ክርክር ሰምቶ ለመወሰን ስልጣን የለዉም ብለናል፡፡
3. የአሁን ተጠሪም ሆነ የአሁን አመልካች አሁን ለክርክር ምክንያት የሆኑትን እነዚህን አምስት ክፍል ቤቶች በተመለከተ ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት ክስ አቅርበዉ መብታቸዉን ከመጠየቅ ይህ ዉሳኔ የሚያግዳቸዉ አይሆንም ብለናል፡፡
4. የግልግል ጉባአዉ ጥር 25 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት አምስት ክፍል ቤቶች ዉጭ በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
5. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለግልግል ጉባኤዉ እና ለሥር ፍ/ቤት ይድረስ ብለናል፡፡
6. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
7. በ30/5/2009 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/አ

የሠ/መ/ቁጥር 165289

መጋቢት 29 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ደረጀ አያና

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡-ወ/ሮ ወሰኔ ገብረ ዮሐንስ

ተጠሪ፡- የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ቀበሌ 11/12/08 የሽማቾች ኃላ/የተ/የኅብረት ሥራ ማኅበር

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለው የፍርድ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሆኖ በዚህ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ አመልካች በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 08 ክልል ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 915/ለ የሆነ ቤት በወር 15 ብር ኪራይ ተከራይታ ከ1998ዓ/ም ጀምሮ የቤት ኪራይ መክፈል አቋርጣለች፡፡ቤቱን ሰርቶ የሚያከራየውና የሚያስተዳድረው የሕዝብ ሱቅ መዝናኛ ክበብ ሲሆን በኋላ የቀበሌው ባለአደራ ቦርድ ሲያስተዳድረው የነበረውን በደንብ ቁጥር 46/2004 የወረዳው ሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ተረክቦ እንዲያስተዳድር የተደረገ ሲሆን ተከራይ በቤት ኪራይ ውሉ መሰረት የቤት ኪራይ ገቢ ባለመክፈል የያዙትን ቤት እንዲያስረክቡና ያለባቸውን ውዝፍ ኪራይ ብር 1320.00፣ የውሉን መቀጮ ብር 5000.00 እና ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ በቀጣይ የሚኖረውን ኪራይ እንድትከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች ለክሱ ባሰማችው ክርክር ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ላገኝ የቻልኩት በ1982 ዓ/ም በወቅቱ የነበሩት የቀድሞ ከፍተኛ 16 የቀበሌ 08 አመራሮች የነበረውን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት በማሰብ

ባዶ ቦታዎችን በመምረጥና በሂደት ባለቤቶች የምንመልሰዉን ብር 29,000.00 ከቀድሞ ከፍተኛ 16 ቀበሌ 08 ሕብረት ሱቅ ወጭ ሆኖ ለሌሎች ሰዎች ጭምር እንዲሰጠን አድርገዉ በግምት 5 በ6 በሆነ ቦታ ላይ የነበረዉን ቤት ሙሉ ለሙሉ አፍርሰን የወሰድነዉን ብር በኪራይ መልክ ከፍለን ጨርሰናል። ለዚህ ቤት ካርታ ሊሰራልኝ በመጨረሻ ሂደት ላይ ይገኛል። ተጠሪ ያቀረባቸዉ ማስረጃዎች ይህንን ቤት መረከቡን አያሳዩም። በመሀከላችን ምንም አይነት የቤት ኪራይ ዉል ሳይኖር ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነዉን መኖሪያ ቤት በባለቤትነት የሚያስተዳድር መሆኑን ማስረጃ ሳያቀርብ በደፈናዉ በአሁን ሰዓት በሥራ ላይ የሌለና ለ6 ወራት ብቻ በሥራ ላይ የነበረ ደንብ ቁጥር 46/2004 በመጥቀስ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ያቀረበዉ ክስ የሕግና ማስረጃ ድጋፍ የለዉም ተብሎ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክራለች።

የሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 40079 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 20/01/2010ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት የቀድሞ ሕብረት ሱቅ ሲያስተዳድረዉ የነበረና የአሁን ተጠሪ የማስተዳደር ሥልጣን ያገኘዉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 46/2004 መሰረት ሆኖ በቀን 28/01/2005ዓ/ም በተዘጋጀ መረካከቢያ ሰነድ በመረከብ እንደሆነ ተጠሪ በማስረጃ ያስረዳዉን ተጠሪ ታቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ አለማስተባበሏን፣ አመልካች በዚህ ቤት ላይ በቀን 24/05/2003ዓ/ም ከየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/12/08 የህ/ሱ/መ/ተ/ጽ/ቤት ጋር የኪራይ ዉል ማድረጓን ከማስረጃዎቹና ከቤቱ ማኅደር ማረጋገጡን እንዲሁም አመልካች ከተጠሪ ጋር የኪራይ ዉሉን አለማደሷ የቀድሞዉን የኪራይ ዉል ቀሪ የሚያደርገዉ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2968/1 መሰረት የቀድሞዉን የኪራይ ዉል ላልተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም የሚያደርግ እንደሆነ፤ አመልካች የኪራይ ዉሉን ሳያስፈረሱ የቤቱ ባለይዞታ ነኝ በማለት ያቀረበችዉ ክርክር በሰ/መ/ቁጥር 46947 ላይ በተሰጠዉ ትርጉም መሰረት ተቀባይነት እንደሌለዉ፤ በአንጻሩ ተጠሪ ያቀረባቸዉ ማስረጃዎች የተጠሪ ቤቱን የማከራየት መብት ከሕግ የመነጨ እንደሆነና አመልካች ዉሉን አለማደሷ ተከራይታ የነበረዉን ቤት እንስትወስድና ኪራይ ሳትከፍል እንድትገለገል የሚፈቅድ የሕግ ድጋፍ የለም፤አመልካች ቤቱ የራሷ መሆኑን ከተጠሪ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ አላረጋገጠችም በማለት አመልካች አከራካሪዉን በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 08 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 915/ለ የሆነ ቤት ለተጠሪ እንድታስረክብ ወስኖ ተጠሪ ዉዝፍ ኪራይ እንዲከፈለዉ የጠየቀዉን ዳኝነት በይርጋ ታግዷል በማለት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል።

እንዲሁም አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበች ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 205269 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 16/02/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ክሱ ከቤት ኪራይ ዉል ጋር የተያያዘና አልተከፈለም የተባለዉን ኪራይ ለማስከፈልና ቤቱን ለማስለቀቅ የቀረበ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን አለዉ በሚል ከዚህ አኳያ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ ፍሬ ነገሩን የሚመለከተዉን የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ አመልካች የቤት ባለቤትነትን የመፋለም ክስ ማቅረብ እንደምትችል በመግለጽ አመልካች ቤቱን እንድታስረክብ

በሥር ፍርድ ቤት የተወሰነዉን በማጽናት ወስኗል፡፡በዚህ መሰረት በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል አመልካች በቀን 04/03/2011 ዓ/ም ጽፋ ያቀረበችዉ የሠበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

የሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሌሎች መዝገቦች ላይ የቀረቡትን ተመሳሳይ ጉዳዮችን በተመለከተ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን ዉድቅ ቢያደርግም ይህንን ጉዳይ በተመለከተም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 90421 በሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን እደሌለዉ በማወቅ ሥልጣን የለኝም በማለት ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ሥልጣን አለዉ ቢባል እንኳን ያለዉ ስልጣን የኪራይ ጉዳይን በተመለከተ ብቻ በመሆኑ ይህም ቢሆን የተጠሪ ኪራይ የመጠየቅ መብት በይርጋ ቀሪ ሆኗል ሲል በወሰነበት ከክሱ ጋር ግንኙነት የሌለዉን ነጥብ በማንሳት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ታስረክብ ብሎ ዉሳኔ መስጠቱና ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ እንዲያርም ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስህተቱን ሳያርም ዉሳኔዉን ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በሰጠዉ ዉሳኔ በሥራ ላይ የሌለዉን ደንብ ቁጥር 47/2004 በመጥቀስ ዉሳኔ መስጠቱ፤ ተጠሪ ከንግድና ኢንዱስትሪ በቀን 28/01/2005ዓ/ም በተጻፈ መረካከቢያ ቅጽ 17 ክፍሎችን ተረክቤያለሁ ከሚል በስተቀር የትኞቹን ቤቶች እንደሆኑ የቤት ቁጥሮች ባልተጠቀሰበት፣ማን አስረካቢና ተረካቢ እንደሆነ በአግባቡ ሳይገለጽ፤ አመልካች ከተጠሪ ጋር ምንም አይነት የቤት ኪራይ ዉል ስምምነት ባላፈጸምኩበትና ተጠሪም በቀን 06/10/2006ዓ/ም ይህንኑ ባረጋገጠበት ማስረጃ በአግባቡ ሳይመረመርና ከሚመለከተዉ አካል ማስረጃ እንዲጣራልኝ በጠየኩት መሰረት ሳይፈጸም ምስክሮቹን ሳይሰማ የሰጠዉ ዉሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ተብሎ እንዲታረምልኝና ለክሱ መነሻ የሆነዉ ቤት የአመልካች የግል ቤት ነዉ ተብሎ እንዲወሰን እንዲሁም አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንድታስረክብና ኪራይም እንድትከፍል የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሻርላት በመጠየቅ አቤቱታዋን አቅርባለች፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ ያቀረበዉን ክስ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አይተዉ የወሰኑበትን አግባብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳዉ የሚገኙ የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች ገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የህብረት ሥራ ማኅበር ለማስተላለፍ ካወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 ድንጋጌዎች እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 190421 ከሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ መጣራት ያለበት በመሆኑ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ብሎ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 17/04/2011 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለዉም በሚል በሥር ፍርድ ቤት በመቃወሚያነት ያላነሳችዉን ክርክር በሰበር ደረጃ እንድታነሳ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 182/2 እና 329 አይፈቅድላትም፡፡ክሱ የቤት ኪራይ ለማስከፈልና ቤቱን ለማስለቀቅ የቀረበ በመሆኑ

በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸዉ።በመሆኑም ክሱ በስር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ታይቶ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም። የፍሬ ነገር ክርክር በተመለከተ አመልካች ለክሱ መነሻ የሆነዉ ቤት ባለቤት መሆኗን የሚያስረዳ ምንም አይነት ማስረጃ አላቀረበችም። አመልካች በማስረጃነት ያቀረበችዉ ሰነዶች አመልካች ለክሱ መነሻ በሆነዉ ቤት ላይ የባለቤትነት መብት እንዳላት የሚያስረዱ አይደሉም።በአንጻሩ ተጠሪ ለክሱ መነሻ የሆነዉን ቤት ከቀበሌ የሕዝብ ሱቅና መዝናኛ ተቋም ጋር ስለመከራየቷ የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረቡና በአንጻሩ አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆኗን የሚያሳይ ማስረጃ በማቅረብ ባለማስረዳቷ ክርክሯ የሕግ መሰረት የለዉም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ነጥሮ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ። ስለሆነም ከቀረበዉ የክስ ምክንያት አንጻር አመልካች ቤቱን እንድትለቅ በመወሰኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ ስህተት የለም ተብሎ አመልካች ያቀረበችዉ የሰበር አቤቱታ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል። አመልካች በተጠሪ በቀረበ መልስ ላይ በቀን 17/05/2011 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክራለች።

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር እና አመልካች በኪራይ የያዘችዉን አከራካሪዉን ቤቱ ለተጠሪ ታስረክብ ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል።

በመጀመሪያም ጉዳዩን የመዳኘት የሥረ ነገር ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ነዉ ወይስ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነዉ? የሚለዉን ጭብጥ መርምረናል። ተጠሪ ክሱን ያቀረበዉ አመልካች ተከራይታ የያዘችዉን በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 08 ክልል ዉስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 915/ለ የሆነ በመዝናኛ ክበብነት የሚያገለግል ቤት ኪራይ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኗ ዉዝፍ ኪራይ ከፍላ ቤቱን እንድታስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ። እንዲሁም ቤቱን የማስተዳደር ስልጣን ያገኘዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 መሰረት ቀደም ሲል በባለአደራ ቦርድ ሲተዳደሩ የነበሩ መሰል ቤቶችን ተረክቦ እንዲያስተዳድር በተሰጠዉ መብት መሰረት እንደሆነ በመግለጽ ደንቡን ጠቅሶ መከራከሩን የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች ይዘት ያሳያል። በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 9/1 እና 231(1/ለ) ስር በተደነገገዉ መሰረት የክስ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት የሥረ ነገር ዳኝነት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን የክስ አቤቱታዉን በመመርመር የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የሌለዉ መሆኑን ሲያረጋግጥ ተከሳሹን ሳይጠራ የክስ አቤቱታዉ ተቀባይነት የለዉም በማለት መመለስ ይጠበቅበታል።የሥረ ነገር ሥልጣን ያለዉ መስሎት ተከሳሹ መልስ እንዲሰጥ አድርጎ ተከሳሹ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት የሚያስችል የዳኝነት ሥልጣን የለዉም የሚል መቃወሚያ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 244(2/ሀ) ሲያቀርብ ወይም በዚህ አግባብ በተከሳሹ መቃወሚያ ባይቀርብም እንኳ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን እንደሌለዉ

በተረዳበት ጊዜ ሥልጣን የለኝም በማለት መወሰን እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 9/2 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ በአስገዳጅነት የተደነገገበት ምክንያት የሥረ ነገር ዳኝነት ስልጣን የሌለዉ ፍርድ ቤት ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚያስችል ብቃት የለዉም የሚል አጠቃላይ ግንዛቤ ሕግ አዉጭዉ በመያዙ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለዉም የሚል መቃወሚያ ካለማቅረቧም በተጨማሪ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ያየዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን የመዳኘት የስረ ነገር ሥልጣን እንዳለዉ በመቁጠር ተጠሪ ያቀረበዉን ክስ ተቀብሎ ዉሳኔ መስጠቱን ከክርክሩ ተረድተናል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበችዉ ይግባኝ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ የሰጠዉ ሥልጣን ሳይኖረዉ ነዉ የሚል ቅሬታ ያቀረበች ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ከዚህ አንጻር የተነሳዉን ቅሬታ መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ከኪራይ ዉል ጋር በተያያዘ ኪራይ ለማስከፈልና ቤት ለማስለቀቅ የቀረበዉን ክስ የመዳኘት ስልጣን አለዉ በማለት የአመልካችን ቅሬታ ዉድቅ በማድረግ መወሰኑን ከዉሳኔዉ ተመልክተናል፡፡ አመልካች ከዚህ አኳያ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበችዉን ቅሬታ በስር ፍርድ ቤቶች ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 182/2 እና ቁጥር 329 ስር በተደነገገዉ አግባብ በሰበር ደረጃ ሊነሳ የሚገባ ክርክር አይደለም በማለት ተጠሪ የተከራከረ ቢሆንም አመልካች ከዚህ አኳያ ያነሳችዉ ክርክር የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣንን የሚመለከት እንጂ ፍሬ ነገርን የሚመለከት አዲስ ክርክር ባለመሆኑ ከላይ እንደተገለጸዉ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 9/2ን መንፈስና ዓላማ ከግምት በማስገባት እንዲህ አይነት መከራከሪያ በሰበር ደረጃም ሊነሳ የሚችል ነዉ በማለት በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበዉን ክርክር ባለመቀበል የስር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን ያላቸዉ መሆን አለመሆኑን ከዚህ ቀደም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 53551፣ በሰ/መ/ቁጥር 65706 እና በሰ/መ/ቁጥር 90421 ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም አንጻር መርምረናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 53551 እና በሰ/መ/ቁ. 65706 ላይ በሰጠዉ ትርጉም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ባሉት ቀበሌያት የተደራጀ ባለአደራ ቦርድ ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ ሆኖ የቀበሌ የሕዝብ ሱቆች ተብለዉ የሚታወቁ ቤቶችን እንዲያስተዳድር በከተማ አስተዳደሩ የተቋቋመ በመሆኑ ከከተማዉ የቀበሌ አስተዳደር አንደ አንዱ አስፈጻሚ አካል የሚቆጠር በመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ) መሰረት የከተማ አስተዳደሩ ከሚያስተዳድራቸዉ የመንግስት ቤቶች ጋር የተያያዙ ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን የተሰጠዉ ለከተማ ፍርድ ቤቶች በመሆኑ የሕዝብ ሱቅ የከተማ አስተዳደሩ የሚያስተዳድረዉ እንደመሆኑ ከሕዝብ ሱቁ ጋር በተያያዘ የሚነሳ ክርክር የመዳኘት ስልጣን ያለዉ የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ናቸዉ በማለት ወስኖ እንደነበር ከዉሳኔዉ ተመልክተናል፡፡

እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 90421 በተሰጠዉ ትርጉም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳዉ የሚገኙ የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች ገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የሕብረት ሥራ ማኅበራት ለማስተላለፍ

በከተማ አስተዳደሩ ሐምሌ 05 ቀን 2004 የወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የሕዝብ ሱቅ የሚተዳደረዉ በቀበሌ የሕዝብ መዝናኛ ማእከላት ባለአደራ ቦርድ በመሆኑ ባለአደራ ቦርዱ የሕዝብ ሱቆችንና ሌሎች መዝናኛ ማእከሎችን በተመለከተ የሚያቀርበዉን ክስ ተቀብለዉ የማየት ሥልጣን ያላቸዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ነዉ ተብሎ በሰ/መ/ቁጥር 65706 ላይ ትርጉም መሰጠቱን በመጥቀስ የከተማ አስተዳደሩ በየወረዳዉ የሚገኙ የሕዝብ ሱቆችንና ሌሎች ገቢ ማስገኛ ተቋማትን ባወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 ወደ ሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበራት አስተላልፏል፡፡በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 መሰረት ለሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበራት የተላለፉትን ንብረቶችና ገንዘብ ማኅበራቱ ለሕዝብ በሚጠቅም መንገድ የሚያስተዳድሩ መሆኑን የመቆጣጠርና የእርምት እርምጃ የመዉሰድ ሥልጣን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በደንብ ቁጥር 46/2004 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ባህሪያትም ሆነ በአሰራሩ የሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበራት በባለአደራ ቦርድ ሲተዳደሩ የነበሩትን የሕዝብ ሱቆችንና ሌሎች ገቢ ማስገኛ ተቋማት፣ንብረት፣ የሠራተኞችንና መብትና ግዴታ በመረከብ በሚጠቅም መንገድ የማስተዳደር ኃላፊነት ስላለበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግበት የሕዝብ አገልግሎት ሰጭ ተቋም በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 65706 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ባለአደራ ቦርዱ በከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ክስ ለማቅረብ ይችላል የተባሉ ጉዳዮችን በተመለከተ የሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበር ክስ የማቅረብ መብት አለዉ፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶችም በዚህ አግባብ የሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበር የወረዳዉን የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት የኪራይ ዉል አፈጻጸም በተመለከተ የሚቀርብ ክስ መርምሮ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለዉ በማለት መወሰኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት የሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔዎች እና በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ካቀረበዉ ክስ ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደሩ የቀበሌ የሕዝብ መዝናኛ ማእከላት ባለአደራ ቦርድ ሲተዳደሩ የነበሩት የሕዝብ ሱቆች፣ ሌሎች የመዝናኛ ማእከሎች እና ንብረቶች በከተማ አስተዳደሩ ሐምሌ 05 ቀን 2004 ዓ/ም የወጣዉን ደንብ ቁጥር 46/2004ን ተከትሎ በየወረዳዉ ለተቋቋሙት ለሸማቾች ሕብረት ሥራ ማኅበራት መተላለፋቸዉን ነዉ፡፡ በደንቡ አንቀጽ 11 ስር የባለአደራ ቦርድ መብትና ግዴታዎች ለሸማቾች ሕብረት ሥራ ማኅበራት እንደተላለፉ መደንገጉም የሚያሳየዉ ይህንኑ ነዉ፡፡ እንዲሁም በዚሁ ደንብ አንቀጽ 12 ስር እንደተደነገገዉ ከባለአደራ ቦርድ ጋር የተደረጉ ዉሎች ደንቡ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ዉስጥ ከሸማቾች ሕብረት ሥራ ማኅበር ጋር መታደስ እንዳለበት በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በሰ/መ/ቁጥር 53551 እና በሰ/መ/ቁ. 65706 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ባሉት ቀበሌያት ተደራጅቶ የነበረዉ የቀበሌ የሕዝብ መዝናኛ ማእከላት ባለአደራ ቦርድ እንደ ከተማዉ የአስፈጻሚ አካል ሊቆጠር የሚችል መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አከራካሪዉ ጉዳይ የቀበሌ የሕዝብ መዝናኛ ማእከላት ባለአደራ ቦርድ መብትና

ግዴታ በደንብ ቁጥር 46/2004 የተላለፈላቸዉ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንደ ከተማዉ አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ሊቆጠሩ የሚችሉ መሆን አለመሆኑ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በአዋጅ ቁጥር 147/1991(ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 ተተክቷል) በተደነገገዉ መሰረት በነጻ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ዉስጥ ተመሳሳይ ፍላጎት ባላቸዉ ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሕብረት በመፍጠር ገንዘብን፣ዕዉቀትን፣ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች ፍላጎቶቻቸዉን እርስ በእርስ በመደጋገፍ ለማሟላትና ሌሎች በአዋጁ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በፈዴራል ደረጃ ወይም በክልል ደረጃ ኃላፊነቱ የተወሰነ ሆነዉ የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣የአባላት ስም ዝርዝርና ፊርማቸዉን፣ የማኅበሩን ሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ስምና ፊርማቸዉን፣ የማኅበሩን ዕቅድ፣የመነሻ ካፒታሉን...ወዘተ የሚሉ በአዋጁ የተዘረዘሩትን ሌሎች ሰነዶችን በማቅረብ በመመዝገብ የሚቋቋሙ ሕጋዊ ሰዉነት ያላቸዉ ድርጅቶች እንደሆኑ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 በአንቀጽ 9 እና 10 ወይም በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 10 እና 11 የተደነገገዉ ያሳያል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለዉ ምንም እንኳን የኅብረት ሥራ ማኅበራት የተቋቋሙበት ዓላማ የንግድ ሥራ በመስራት ለአባላቱ ጥቅም ከማስገኘት ባሻገር ለሕብረተሰቡ የሚጠቅሙ ሌሎች ተግባራትን በመፈጸም ማኅበራዊ ችግሮችን መፍታት ጭምር ቢሆንም የተቋቋሙት ግን እንደአስተዳደር አካል በመሆን ሳይሆን ኃላፊነቱ የተወሰነ ሕጋዊ ሰዉነት ያላቸዉ ድርጅቶች ወይም የኅበረት ሥራ ማኅበራት ሆነዉ እንደሆነ ነዉ፡፡

እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የተቋቋሙ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የከተማዉን ነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ከመቀነስ አንጻር ያላቸዉን ፋይዳ ከግምት በማስገባት የከተማ አስተዳደሩ ደንብ ቁጥር 46/2004ን በማዉጣት ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደሩ የቀበሌ የሕዝብ መገናኛ ማእከላት ባለአደራ ቦርድ ሲተዳደሩ የነበሩትን የሕዝብ ሱቆች፣ ሌሎች የመገናኛ ማእከሎች እና ንብረቶች ከሐምሌ 05 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ በየወረዳዉ ለተቋቋሙት ለሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት አስተላልፏል፡፡ በሌላ አነጋገር እነዚህ ማኅበራት በዚህ ደንብ የቀበሌ አስፈጻሚ አካል ሆኖ ተቋቁሞ በነበረዉ ባለአደራ ቦርድ ሲተዳደሩ የነበሩ ንብረቶችን የማስተዳደር መብት (በቦርዱ ሲተዳደሩ የነበሩ ቤቶችን የማከራየትና የማስተዳደር መብት ጨምሮ) መወረሳቸዉ(በሕግ ማግኘታቸዉ) ከላይ እንደተመለከተዉ ሕጋዊ ሰዉነት ኖሯቸዉ ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሆነዉ የተቋቋሙበትን ህልዉናዊ ማንነታቸዉን (identity of legal personality) የሚቀይር አይደለም፡፡ እንዲሁም ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የከተማ አስተዳደሩ ያወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 ዓላማም ባለአደራ ቦርዱ የነበረዉ መብትና ግዴታ በከተማ አስተዳደሩ ለሚገኙ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚተላለፍበትንና በቀጣይ ማኅበራቱ ከባለአደራ ቦርዱ የተረከቡትን ገንዘብና ንብረት የከተማ አስተዳደሩን ነዋሪዎች በሚጠቅሙ ተግባራት ላይ የሚያዉሉበትን ሁኔታ መደንገግ እንጅ በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙትን የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን የከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካል

የማድረግ ወይም የማኅበራቱን የባለቤትነት መብት ለከተማ አስተዳደሩ በማስተላለፍ ማኅበራቱን በከተማ አስተዳደር ባለቤትነት የሚተዳደሩ የልማት ድርጅቶች (enterprises) የማድረግ ዓላማ ደንቡ የለዉም፡፡ በተጨማሪም በደንብ ቁጥር 46/2004 አንቀጽ 5 ሥር የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በደንቡ መሰረት የተረከቡትን ገንዘብና ንብረቶች ለሕዝብ በሚጠቅም መልኩ እያስተዳደሩ የሚገኙ መሆን አለመሆኑን የመቆጣጠርና የእርምት እርምጃ የመዉሰድ ሥልጣን ለከተማ አስተዳደሩ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ተሰጥቷል፡፡የዚህ ድንጋጌ ዓላማም የሚያመላክተዉ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያስተዳድሩትን ንብረትና ገንዘብ ለሕዝብ ጥቅም ማዋላቸዉን ማን ቁጥጥር እንደሚያደርግባቸዉና ማን የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወስድባቸዉ ለአንድ ተለይቶ ለሚታወቅ አስተዳደር አካል ኃላፊነትና ተግባር መስጠት እንጂ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያስተዳድሩትን ቤቶች በተመለከተ ከተፈጸሙ ዉሎች ጋር በተያያዘ ኪራይ ለማስከፈልና ቤቶችን በሕግ አግባብ ክስ መስርቶ ለማስለቀቅ በቢሮዉ በኩል ካልሆነ በራሳቸዉ ምንም መፈጸም እንዳይችሉና ማኅበራቱን የቢሮዉ ተቀጽላ ተቋም የማድረግ ዓላማ ያለዉ ድንጋጌ እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡ እንዲሁም በዚህ ድንጋጌ መሰረት በቢሮዉ ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግባቸዉ መደረጉ በቀጥታ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ኃላፊነታቸዉ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሆነዉ የተደራጁትን ማኅበራት በሕግ ያሳካሉ ተብሎ የታቀደዉንና የተቋቋመበትን ዝርዝር ዓላማዎች በማስቀረት እንደ ሕዝብ አገልግሎት ሰጭ አስተዳደር አካል የሚያስቆጥራቸዉ አይደለም፡፡

ከዚህ በላይ በደረስነዉ ድምዳሜ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የሚገኙት የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንደ ከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካል ወይም በከተማ አስተዳደር ባለቤትነት የሚተዳደር የልማት ድርጅቶች (enterprises) የሚቆጠሩ አይደሉም፡፡ ባለአደራ ቦርዱ ሲያስተዳድር የነበረዉን ንብረትና ገንዘብ የማስተዳደር ሥልጣን የተላላፈላቸዉ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት በተለይም የሕዝብ ሱቆች፣ ሌሎች የመዝናኛ ማእከሎች እና ንብረቶች በተመለከተ በተፈጸመ የኪራይ ዉሎች የሚመነጩ መብቶችን ከመጠየቅ እና ቤቶችን ከተከራዮቹ አስለቅቆ ተረክቦ ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ ዳኝነት በመጠየቅ የሚያቀርቧቸዉን ክሶች በተመለከተ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን ይኖራቸዋል ተብሎ በተጠቃሹ ደንብ ቁጥር 46/2004 ላይ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚያስተዳድሩትን ቤቶች እና እነዚህን ቤቶች በማከራየት ከሚፈጽሙት ዉሎች ጋር በተያያዘ ወይም በጠቅላላዉ በከተማ አስተዳደሩ ዉስጥ የተቋቋመ የኅበረት ሥራ ማኅበራት ክሳሽ በመሆን የሚያቀርቧቸዉን ክሶች በተመለከተ የመዳኘት ሥልጣን የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ነዉ ተብሎ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995(በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 408/1996) ስር በግልጽ አልተደነገገም፡፡

በሌላ በኩል በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11(1/ለ) እና 14(2) ስር እንደተደነገገዉ በሌላ ሕግ ለሌሎች አካላት የተሰጠዉ የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ

አንቀጽ 3 እና 5 ሥር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ ጉዳዮች ናቸዉ ተብለዉ ከተዘረዘሩት ጉዳዮችና ከተዘረዘሩት ሕጎች ከሚመነጩ ጉዳዮች ዉጭ ሆነዉ በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬዳዋ ከተሞች ዉስጥ የሚነሱ ሌሎች የፍትሐብሔር ጎዳዮችን የመዳኘት ሥልጣን ግምታቸዉ እስከ ብር 500,000.00 ድረስ የሆኑት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግምታቸዉ ከዚህ በላይ የሆኑት ደግሞ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሚዳኙ ተገልጾ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ሥልጣን ሆኖ በግልጽ ተለይቶ ተደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከሳሽ የሆነዉ የየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ቀበሌ 11/12/08 የሸማቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የጎብረት ሥራ ማኅበር (የአሁን ተጠሪ) ምንም እንኳን ለክሱ መነሻ የሆነዉን ቤት የማስተዳደር ሥልጣን ያገኘዉ የከተማዉ አስፈጻሚ አካል ከነበረዉ የቀበሌ ባለአደራ ቦርድ ቢሆንም ይህ ማኅበር የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ(አስተዳደር) አካል ካለመሆኑም በተጨማሪ ይህ ማኅበር የሚያስተዳድረዉን የቀድሞ የሕዝብ ሱቆች፣ ሌሎች የመዝናኛ ማእከሎች እና ንብረቶች ኪራይ ዉል ጋር በተያያዘ ኪራይ ለማስከፈልና በኪራይ ዉል ተይዘዋል ያላቸዉን ቤቶች ለማስለቀቅ የሚቀርበዉን ክስ የመዳኘት ስልጣን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች አልተሰጣቸዉም፡፡በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ) ስር የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሆኖ የተደነገገዉ በከተማ አስተዳደሩ መዋቅር ሥር በሚገኙ አስተዳደር አካላት የሚተዳደሩ የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን የሚመለከት እንጂ ንብረትነታቸዉ የመንግስት የሆኑ ቤቶች ሆነዉ በሕግ የማስተዳደር ሥልጣን ለሸማቾች ጎብረት ሥራ ማኅበራት የተሰጡትን ቤቶች ጋር በተያያዘ በማኅበራትና በግለሰቦች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የሚመለከት ድንጋጌ አይደለም፡፡

ከዚህ በመቀጠል የተመለከትነዉ በሰበር/መ/ቁጥር 90421 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ ለድንጋጌዉ የተሰጠዉ ትርጉም አሁን በያዝነዉ መዝገብ ከተሰጠዉ ትርጉም እንዴት ይጣጣማል? የሚለዉን ነዉ፡፡ ከላይ በሰፊዉ እንደተገለጸዉ የሸማቾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የጎብረት ሥራ ማኅበራት የአሁኑን ተጠሪ ጨምሮ የአስተዳደር አካል አለመሆናቸዉ፣ ከባለአደራ ቦርዱ የተላለፉለትን የቀድሞ የሕዝብ ሱቆች፣ ሌሎች የመዝናኛ ማእከሎች እና ንብረቶች ኪራይ ዉል ጋር በተያያዘ እና በኪራይ ዉል የተያዙ ቤቶችን ለማስለቀቅ የሚቀርቡ ክሶች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ይዳኛሉ በሚል በከተማ አስተዳደሩ ደንብ ቁጥር 46/2004 ላይ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ እንዲሁም በጠቅላላዉ በከተማ አስተዳደሩ ዉስጥ የተቋቋመ የጎበረት ሥራ ማኅበራት ከሳሽ በመሆን የሚያቀርቧቸዉን ክሶች በተመለከተ የመዳኘት ሥልጣን የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ነዉ ተብሎ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995(በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 408/1996) ላይ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ ይልቁንም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11(1/ለ) እና 14(2) መሰረት የተያዘዉን አይነት ጉዳይ (የአከራካሪዉ ንብረት ግምት መጠን እየታየ) የመዳኘት የሥረ ነገር ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ከፍተኛ እና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች እንደሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም አሁን ባለን ሥርዓት በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ የፍርድ ቤቶች ሥልጣን ከሕግ የሚመነጭ በመሆኑ የተያዘዉን አይነት ጉዳይ የመዳኘት ስልጣን በሕግ ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች አልተሰጠም፡፡ይልቁንም ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 454/1997 እንደገና እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 10/4 ስር በተደነገገዉ መሰረት ቀደም ሲል በሰበር/መ/ቁጥር 90421 ላይ እንዲህ አይነት ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ነዉ ተብሎ ተሰጥቶ የነበረዉን ትርጉም ለዉጠን በዚህ በያዝነዉ መዝገብ ላይ የተሰጠዉ ትርጉም ገዥ ይሆናል ብለናል፡፡በዚህ መሰረት አመልካች በሰበር/መ/ቁጥር 90421 ላይ የተሰጠዉን ትርጉም መሰረት በማድረግ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዉ ይባልልኝ በማለት ያቀረበችዉን ክርክር አልተቀበልንም፡፡ ክርክሩ በስር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመዳኘቱ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በመቀጠልም አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ዉዝፍ ኪራይ ከፍላ ታስረክብ ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ተብሎ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበችዉን ቅሬታ በተመለከተ እንደመረመርነዉ የአንድን ፍሬ ነገር መኖርና አለመኖር በተመለከተ የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመርምርና በመመዘን በሕግ የተሰጣቸዉን ሥልጣን ተጠቅመዉ የማረጋገጥ ኃላፊነት የተጣለባቸዉ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ ባዩት የሥር ፍርድ ቤቶች ላይ ነዉ፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በአመልካች ባለቤትነት የሚታወቅ ሳይሆን አመልካች በኪራይ ዉል መነሻ ይዛ የኪራይ ዉሉ ጊዜ ተጠናቆ ዉሉ ላልተወሰነ ጊዜ ቢራዘምም የኪራይ ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆን ይዛ የቆየችዉ ቤት እንደሆነ የስር ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ እንዲሁም ቤቱን የማስተዳደርና በቀጣይ የኪራይ ዉሉን የመዋዋል መብት ለተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወጣዉ ደንብ ቁጥር 46/2004 እንደተሰጠዉ ከግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃዎች በማረጋገጥ ላልተወሰነ ጊዜ ተራዝሞ የነበረዉ የኪራይ ዉል ቀሪ ሆኖ አመልካች ዉዝፍ ኪራይ ከፍላ ቤቱን ለተጠሪ እንድታስረክብ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ ያዩት የሥር ፍርድ ቤቶች ማስረጃዎችን መዝነዉ ዉሳኔ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም አመልካች አከራካሪዉን ቤት በኪራይ ዉል ሳይሆን የቤቱ ባለቤት በመሆን እንደያዘች የሚያሳይ ከተጠሪ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ ካለማስረዳቷም በተጨማሪ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 223(1/ሀ) እና 145 ስር በተደነገገዉ አግባብ የቤቱ ባለቤት መሆኑን የሚያሳይ አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ምን እንደሆነና ማስረጃዉ የሚገኝበትን ቦታ በማመላከትና በመዘርዘር ከመልሷ ጋር ባቀረበችዉ የማስረጃ መግለጫዋ ላይ ገልጻ ተከራክራ እያለች የታለፈበት መሆኑን በበታች ፍርድ ቤት ያሰማችዉና በዚኅ ችሎት ያቀረበችዉ ክርክር አያሳይም፡፡ በተጨማሪም የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ የኪራይ ዉሉን መሰረት ያደረገ በመሆኑና የኪራይ ዉሉ መኖሩ በተረጋገጠበት በሕጉ አግባብ የተቋቋመዉ የኪራይ ዉል በሕጉ አግባብ እስካልፈረሰ ድረስ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አስገዳጅነት ያለዉ በመሆኑ አመልካች የኪራይ ዉሉን ሳታስፈርስ ተጠሪ የኪራይ ዉሉን መሰረት በማድረግ ባስከፈተዉ መዝገብ ላይ የቤት ባለቤትነትን የመፋለም ክርክር ማቅረቧ ተገቢ አይደለም ተብሎ በሥር ፍርድ ቤቶች የተያዘዉ አቋምም የሚነቀፍ አይደለም፡፡

ስለሆነም አመልካች የአከራካሪዉ ቤት ባለቤት ነኝ በማለት ያቀረበችዉ ክርክርም ሆነ ማስረጃዎችን በሚመለከት ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ይህ ችሎት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ክርክር የመዳኘት ስልጣን ስላልተሰጠዉ ከዚህ አኳያ ያቀረበዉን ክርክር አልተቀበልነዉም፡፡በመሆኑም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 40079 ላይ በቀን 20/01/2010ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 205269 ላይ በቀን 16/02/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ጉዳዩን የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነዉ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

- የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ዉሳኔዉ ይታተም ዘንድ ለሕግና ጥናት ክፍል ግልባጩ ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም/ቶ

የሠ/መ/ቁ. 161650

ሚያዚያ 29 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ ኃይለገብርኤል አየለ - ጠበቃ ትዕግስት ላዕከ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀሐይ አየለ - ጠበቃ ወይንሸት መንግስቱ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ጳጉሜ 01 ቀን 2009 ዓ/ም ባቀረቡት ማመልከቻ፡- አመልካች ከሟች አቶ አየለ ግዛው ያለመወለዳቸውንና ምንም አይነት የደም ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ገልፀው አመልካች የሟቹ ወራሽ ነኝ በማለት በሐሰት ያገኙት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ መቃወሚያ በሰጡት መልስም ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቱ ስልጣን እንደሌለው እና ወራሽነታቸውን በ1997 ዓ/ም አረጋግጠው ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ከተጠሪ ጋር በፍርድ ቤት ክርክር ላይ የነበሩ ሁኖ እያለ መቃወሚያው መቅረቡ በይርጋ በታገደ ጉዳይ መሆኑን የሚያሳዩ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ለአመልካች በመ/ቁጥር 1463/97 ሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ/ም የሰጠውን የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ የማስተናገድ ስልጣን እንዳለው ገልጾ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን መቃወሚያ ያለፈው ሲሆን ይርጋውን በሚመለከት ግን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 (1) እና 1000 (2) ድንጋጌዎች መሆናቸውን ከለየ በኋላ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ጥያቄው በጊዜ ገደቡ ውስጥ ያልቀረበ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የተጠሪን መቃወሚያ በይርጋ የታገደ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኃላ የአሁኗ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኗ ተጠሪ የሚች ንብረት ስለመያዛቸው

ገልፀው በተከራከሩበትና የአሁኑ አመልካችም ይህንኑ የተጠሪ ክርክር ባላስተባበሉበት ሁኔታ በአመልካች የተነሳው የይርጋ ክርክር በተጠሪ ላይ ሊታሰብባቸው አይገባም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ተጠሪ በአመልካች የወራሽነት ማስረጃ ላይ መቃወሚያ ለማቅረብ ይርጋ አያግዳቸውም በማለት ወስኖ ፍሬ ነገሩን የስር ፍርድ ቤት አጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን መልሶለታል፡፡ የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ከተጠሪ ጋር በተለያየ እርከን በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ሲከራከሩ የቆዩና ተጠሪም በአመልካች የወራሽነት ማስረጃ ውሳኔ ላይ መቃወሚያ ሳያቀርቡ ለረዥም አመታት በቆዩበት ሁኔታና ተጠሪ የሟችን የውርስ ንብረት ስለመያዛቸው በማስረጃ ሳይረጋገጥ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ድንጋጌ ተጠቅሶ መቃወሚያው በይርጋ የሚታገድ አይደለም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች ተጠሪ ያቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ በይርጋ ሊታገድ ይችላል ወይስ አይችልም? ከተባለስ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ ምን ይህል ነው? የሚሉት ሁነው ተገኝተዋል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ለመቃወሚያው አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች የሟች አቶ አየለ ግዛው ወራሽ ነኝ በማለት በመ/ቁጥር 1463/97 በ14/11/1997 ዓ/ም ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ ሲሆን ተጠሪ ይህ ማስረጃ ከሕግ ውጪ የተገኘ ነው በማለት ማስረጃው እንዲሰረዝላቸው የመቃወሚያ አቤቱታ ያቀረቡት ጳጉሜ 01 ቀን 2009 ዓ/ም መሆኑን፣ ከዚህ በፊት ደግሞ አመልካችና ተጠሪ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2007 ዓ/ም ድረስ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በክርክር ላይ የነበሩ መሆኑን፣ አመልካች የሟች አቶ አየለ ግዛው ልጅ ነኝ የሚል አቋም ያላቸው ቢሆንም ተጠሪ ደግሞ ይህንኑ በመቃወም አመልካች የሟቹ ልጅ አይደሉም በማለት የሚከራከሩ በመሆኑ ግራ ቀኙ የአቶ አየለ ግዛው ተወላጆች ናቸው በማለት ከወዲሁ መደምደም የማይቻል መሆኑን፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተጠሪ መቃወሚያ በይርጋ ሊታገድ የሚችል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ የሟቹን ንብረት መያዛቸውን አመልካች አላስተባበሉም በሚል አቢይ ምክንያትና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 (1) ደንጋጌን በዋቢነት በመጥቀስ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በተያዘው ጉዳይ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው አንዱ የሕግ ማዕቀፍ በአዋጅ ቁጥር 361/95 እና ይህንኑ አዋጅ ባሻሻለው አዋጅ ቁጥር 408/96 የተዘረጋው ስርዓት ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 41 ድንጋጌ አግባብ የወራሽነት ማስረጃ፣ የሞግዚትነት ምስክር ወረቀት ማስረጃ የመስጠት የስረ ነገር ስልጣን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የተሠጠ መሆኑን በግልጽ ያሳያሉ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በወራሽነት ምስክር ወረቀትና በሞግዚትነት ስልጣን ላይ የማስረጃ

ወረቀት ውሳኔ መስጠት የሚችሉ መሆኑ በሕጉ ተመልክቷል። ከዚህም በላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የተቃውሞ አቤቱታ የሚቀርበው በፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተሰጠው የውሳኔ ትርጉም (አንቀፅ 3 ይመልክቷል) መሰረት ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ከተሰጠ እና ውሳኔው የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑ ሲረጋገጥና አቤቱታው ውሳኔው ከመፈፀሙ በፊት ከቀረበ ነው። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አይነተኛ አላማ ማስረጃው ትክክለኛነቱና ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ በማስረጃነቱ (Declaratory Judgement) በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ሳይሆን ከላይ እንደተገለፀው ሊፈፀም በሚችል ውሳኔ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን መብትና ጥቅምን ማስከበር ነው።

ከላይ እንደተገለጸው አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41/1//ሸ/ በአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀፅ 2/1/ እንደተሻሻለው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት በሚቀርብ አቤቱታ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው የተደገገ ሲሆን ተቃውሞ የቀረበበት ውሳኔ የተሰጠውም በሕጉ በተደለደለው የዳኝነት ስልጣን መሰረት ነው። በሌላም በኩል የተቃውሞ አቤቱታው ያስከተለው የሕግ እና የፍሬ ነገር ክርክር ይዘት ሲታይ ከወራሽነት የምስክር ወረቀቱ የዘለለ እንድምታ የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ማስረጃውን የሰጠው ፍርድ ቤት የማስረጃው ይሰረዝልን ጥያቄ ማስተናገድ ያለበት መሆኑን በመግለጽ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 105211 በቀረበው ጉዳይ ላይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) ድንጋጌ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል። በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የስረ ነገር ስልጣን ጥያቄን ለመወሰን መርህ የሆነው የክሱን ምክንያት ይዘት መመልከት አስፈላጊ መሆኑንና በዚህም መሰረት ከይዘቱ ውጭ የሆኑ ሌሎች የማያመሳስሉ ሁኔታዎች መኖር ጉዳዮች በተመሳሳይ የስረ ነገር ስልጣን ስር ያርፋሉ የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ መሆኑ ከተረጋገጠ ማስረጃውን የሰጠው ፍርድ ቤት የማስረጃው ይሰረዝልኝ ጥያቄን ማስተናገድ የሚገባው መሆኑን፣ ሆኖም የማስረጃው ይሰረዝልኝ ጥያቄ ከማስረጃው መሰረዝ ባለፈ በሌሎች ህጋዊ መብቶች ውጤት ላይ ሁሉ አንድምታ ያለው፣ ማስረጃውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ያልተሰጠውን ጉዳይ የሚመለከትና ሌሎች ሕጎች የሚነካ የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር የሚመለከት መሆኑ ከተረጋገጠ ግን ማስረጃውን የሰጠው ፍርድ ቤት ማስረጃው ይሰረዝልኝ በሚል መነሻ ስልጣኑ ስር የማያወድቀውን ጉዳይ ሊመለከተው የማይገባ መሆኑን ችሎቱ መወሰኑን ከውሳኔው ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው። ስለሆነም የወራሽነት የምስክር ወረቀትን በተመለከተ የሚቀርብ የተቃውሞ አቤቱታ የማስረጃውን ትክክለኛነት እና ህጋዊነት ከማረጋገጥ ያለፈ አንድምታ የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ብቻ ማስረጃውን በሰጠው ፍርድ ቤት የሚስተናገድ ይሆናል። የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ማስረጃውን በሰጠው ፍርድ ቤት የሚስተናገድ ነው ከተባለ እና መቃወሚያው የሚቀርበውም ከላይ በተገለጸው አግባብ ከሆነ ክርክሩ የሚመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 359 ስር በተደነገገው አግባብ በመደበኛው የክርክር አመራር ስርዓት ነው።ከዚህ አንጻር ሲታይ መደበኛ ክርክር ላይ በሕጉ አግባብ የተነሳ የይርጋ መቃወሚያ ሲኖር ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌን

በመለየት በመቃወሚያው ላይ ተገቢው ብይን መስጠት ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244 እና 245 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባሉ፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው አንድ እውነተኛ የሆነ ወራሽ ትክክለኛው ወራሽ መሆኑ ታውቆለት ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የውርሱን ንብረት በእጁ ያደረገው ሰው የውርሱን ንብረት እንዲለቅ ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ ስለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት በግልጽ ያሳያል፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ ክስ የሚች አቶ አየለ ግዛው የውርስ ንብረት በአሁኑ አመልካች ስለተያዘ ይለቀቅልኝ የሚል ይዘት የሌለው ሲሆን በአመልካች ላይ የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ የቀረበው አመልካች ከሚች አቶ አየለ ግዛው ጋር ምንም ዓይነት የተወላጅነት ግንኙነት ሳይኖራቸው አመልካች የሚቹ ልጅ ነኝ በማለት የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ የሚል መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ ሊደረግ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለውም፡፡

ተጠሪ በዚህ መልኩ ያቀረቡት አቤቱታ በምን ያሕል ጊዜ መቅረብ እንዳለበት በውርስ ሕጉ ድንጋጌዎች በግልጽ አልተመለከተም፡፡ የውርስ ሕጉ በዚህ ረገድ ክፍተት ካለበት ወደ ጠቅላላ ሕግ በመሄድ ለጉዳዩ እልባት መስጠት በሕግ አተረጓጎም መርህ /principles of legal interpretation/ የተፈቀደ ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሕጉ ጠቅላላ ስለውሎች ከተደነገገው አንፃር መመልከት የግድ ይላል፡፡ በዚህ ክፍልም ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆንም በውል ሕግ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዳላቸው በቁጥር 1677/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በውል ሕግ ደግሞ ዋናው የይርጋ ድንጋጌ በቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡ የይርጋ አቆጣጠር ጊዜ መነሻ ሊሆን የሚችለው ጊዜም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1846 ድንጋጌ አግባብ ሊታይ የሚችል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ አመልካች ከሕግ ውጪ የወራሽነት ማስረጃ አግኝተዋል በማለት ማስረጃውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ለአመልካች የሰጠውን የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ የመቃወሚያ አቤቱታ ያቀረቡት ጳጉሜ 01 ቀን 2009 ዓ.ም. ሲሆን አመልካች ይህንን ማስረጃ ያገኙ መሆኑን ያወቁት ደግሞ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑን የክርክሩ ሂደት በግልፅ ያሳያል፡፡ አመልካች ያያዙት የወራሽነት ማስረጃ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው እንደመሆኑ መጠን ተጠሪ ይህ ማስረጃ ከሕግ ውጪ ለአመልካች መሰጠቱን ከአወቁበት ጊዜ ጀምሮ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጠሪ አቤቱታውን የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ተጠሪ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ጉዳዩን የሚያውቁ በመሆኑ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በአስር አመት ጊዜ ውስጥ መቃወሚያውን ማቅረብ የሚችሉ በመሆኑና የአስር አመት ጊዜ ሳያልፍ በ2009 ዓ/ም መቃወሚያቸውን ያቀረቡ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድበት አግባብ የለም፡፡

ስለሆነም የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000 ድንጋጌ ለውሳኔው ዋቢ ማድረጉ ተገቢ ባሆንም ክሱ በይርጋ የታገደ አይደለም

በማለት የደረሰው ድምዳሜ ግን ከውጤት አንጻር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 28169 ሰኔ 05 ቀን 2010 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ከውጤት አንጻር በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በሐሰት ለተገኘ የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1677 እና 1845 ድንጋጌዎች መሰረት የአስር አመት የይርጋ ጊዜ ነው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ያቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ መቃወሚያ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ.መ.ቁ 161301

ሚያዝያ 30 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካቾች፡- 1. አቶ አዲስ አልታሰብ

2. ወ/ሮ አለም ታደሰ

ተጠሪ፡- የፋርጣ ወረዳ ቋልህ ቀበሌ አስ/ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የመሬት ይዞታን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ተከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡-አመልካቾች አዋሳኙ በክሱ ተ.ቁ 1 ላይ የተገለጸውን 2.5 ቃዳ መሬት ወረው የያዙ እና የሚጠቀሙበት መሆኑን፤ አዋሳኙ በክሱ ተ.ቁ 2 ላይ የተጠቀሰውን 10 ቃዳ መሬት ደግሞ 1.5 ቃዳ ገፍተው የሚጠቀሙበት መሆኑን በመግለጽ ይዞታውን እንዲያስረክቡ እና የምርት ዘመን አላባ ግምት እንዲከፍሉ ይወሰንልት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካቾች በሰጡት መልስ ከአሁን በፊት በጉዳዩ ላይ የተከራከሩ እና ድጋሚ ክስ ሊቀርብ የማይገባ መሆኑን፤ ጉዳዩ በመሬት አመቻች ያልታየ እና በእርቅ ያለቀ መሆኑን፤ ከሁለት ዓመት በላይ የሰብል ግምት ሊጠየቁ የማይገባ መሆኑን በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ በተጠቀሰው የምርት ዘመን በመሬቱ ላይ የተመረተ ምርት የሌለ መሆኑን፤ ከሳሽ የሕዝብ ግጦሽ ያዙ በሚል ክስ ካቀረበ በኋላ የእርሻ መሬት አስመስሎ ክስ ማቅረቡ እርስ በእርሱ የሚጋጭ መሆኑን፤ ክስ የቀረበበት መሬት የተከሳሽ ወላጅ አባት መሆኑን እና መሬቱ

የግጦሽ መሬት ነው በሚል ጭቅጭቅ ተነስቶ የተወሰነላቸው መሆኑን በመግለጽ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋርጣ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ምስክር እንዲያሰማ ታዞ ማቅረብ ባለመቻሉ መብቱን በማለፍ የአመልካቾችን ምስክሮች የሰማ መሆኑን፤ ከዚህ በኋላ የመሬቱን መጠን በሚመለከት ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ የታዘዘ እና ክሱ ተሻሽሎ የቀረበ መሆኑን፤ ፍ/ቤቱ በመቀጠል የግራቀኙ ምስክሮች እንዲሰሙ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን፤ በዚሁ መሠረት ተጠሪ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ መሆኑን እና አመልካቾችም አስቀድሞ አቅርበውት ከነበረው መልስ እና ምስክሮች ውጪ ሌላ መልስ እና ምስክር እንደሌላቸው የገለጹ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካቾች ምስክሮች የጠቀሱት መሬት ተመሳሳይ አይደለም፤ አመልካቾች መሬቱ የእነርሱ ስለመሆኑ የሚገልጽ የይዞታ ማስረጃ አላቀረቡም፤ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል 1ኛው መሬት የወል መሬት መሆኑን፤ ሁለተኛውን መሬት ከራሳቸው ይዞታ በመነሳት በስተምዕራብ በግምት 1.5 ቃዳ የገፉ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ የላከ በመሆኑ አመልካቾች የአከራካሪው መሬት ባለይዞታ ነን በማለት ያቀረቡት ክርክር በክልሉ የገጠር መሬት ሕግ መሠረት ተቀባይነት ስለሌለው መሬቱን እንዲለቁ እና የአዝመራ ግምት እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡ አመልካቾች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ክሱ የተስተካከለው የመሬቱን መጠን አስመልክቶ እስከሆነ ድረስ አጠቃላይ የተደረገውን ክርክር እና ስነ ስርዓት ሊለውጠው የሚችል ባለመሆኑ የተጠሪ ምስክሮች እንዲሰሙ መደረጉ ተገቢ አልነበረም፤ ሆኖም አስቀድሞ በነበረው ማስረጃ መሠረት ጉዳዩ ሲታይ መሬቶቹ የወል ናቸው መባሉ ተገቢ ነው፤ ከሳሽ ክስ በማሻሻል ሒደት ምስክር ማሰማቱ ስነስርዓታዊ አይደለም ስለተባለ የሰብል ግምት ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ መሬቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው አካል አቅርቦት የነበረውን እና የተወውን ክስ የቀበሌው አስተዳደር ውክልና ሰጥቶኛል በሚል ክስ መመስረቱ አግባብ አይደለም፤ ተጠሪ በምን አግባብ ክስ እንዳቀረበ ሳይመረመር በደፈናው አመልካቾች ያቀረብነው መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም፤ አስቀድሞ የተዘጋው ክስ በድጋሚ ከሚንቀሳቀስ በቀር ፍሬጉዳዩ እና ጭብጡ አንድ በሆነ ጉዳይ በድጋሚ የቀረበው ክስ አግባብ አይደለም፤ ጉዳዩ አስቀድሞ በመሬት አመቻች ኮሚቴ ሳይታይ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም፤ አመልካቾች ጉዳዩ አግባብነት ባላቸው አካላት እንዲጣራ ጠይቀን ተቀባይነት አላገኘንም፤ የተወሰነ ነዋሪ መሬቱ የሕዝብ

ግጦሽ መሬት ነው በማለት ለፍትሕ ጽ/ቤት አመልክቶ ጉዳዩ እንዲጣራ በተሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት ክስ የተነሳበት መሬት የአመልካቾች መሆኑ ተረጋግጧል፤ ዐቃቤሕግ ጉዳዩ ውሳኔ ሊሰጥበት ሲል ክሱን እንዳዘጋ በገለጽንበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት አስቀድሞ የተዘጋውን መዝገብ እና የተጣራበትን ሪፖርት በትዕዛዝ አስቀርቦ ማየት ሲገባው ይህ ሳይደረግ ውሳኔ መሰጡቱ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ቀደም ሲል በስር ፍ/ቤት በመ.ቁ 17143 በአሁን አመልካች ላይ የቀረበው ክስ በክሳሽ ጥያቄ ከተዘጋ በኋላ በድጋሚ በመ.ቁ 17497 ክስ ቀርቦ ፍ/ቤቱ በቀን 14/02/09 በዋለው ችሎት ተጣርቶ እንዲቀርብለት በሰጠው ትዕዛዝ የመሬት አስተዳደር በ18/02/09 የተጻፈ ሪፖርት ባቀረበበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መመዘን ያለበት ማስረጃ በተዘጋው መዝገብ የቀረበውን ነው በማለት ተጣርቶ የቀረበው ሪፖርት ሳይመዘን የወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በቅድሚያ በወረዳው መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ክስ ቀርቦ መሬቱ የማነው የሚለው ሊረጋገጥ የሚገባው መሬትን ለማስተዳደር በሕግ ስልጣን ባለው የመሬት አስተዳደር መስሪያ ቤት ባለሙያ ሊሆን ይገባው ነበር፤ ይህ ታልፎ ጉዳዩ በምትክ ዳኛ እንዲጣራ መደረጉ በአግባቡ ካለመሆኑም ባሻገር ምትክ ዳኛው በመሬቱ ተጠቃሚ የሆነውን ማህበረሰብ በትቸታው ባላካተተ መልኩ አጣርቶ ያቀረበው ማስረጃ የተሳሳተ መሆኑ በፍትሕ ማሻሻያ ኮሚቴ መረጋገጡ እና ክሱ ሲመሰረትም የአዋሳኝ ችግር የነበረበት መሆኑ ግምት በማስገባት ጉዳዩን እንደገና አጣርተን ክስ ማቅረብ ያግዝ ዘንድ ክስ እንድናነሳ ይፈቀድልን በማለት ዓቃቤሕግ ያቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ መዝገቡን የዘጋ መሆኑን ተከትሎ አከራካሪው መሬት የወል መሬት መሆኑን ስልጣን ባለው አካል በሚገባ አጣርቶ ማስረጃ እንዲሰጥ ተደርጓል፤ ተጠሪ ማስረጃውን መሠረት በማድረግ የወል መሬት ተጠቃሚዎችን ወክሎ ክስ ማቅረብ ያለበት የቀበሌው አስተዳደር መሆኑን በመረዳት በአዲስ መልክ ቀበሌው ጽ/ቤቱን ክሳሽ በማድረግ ክሱ መቅረቡ አግባብ ነው፤ የተጠሪ ምስክር መሰማት በተመለከተ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ምላሽ የተሰጠው በመሆኑ በድጋሚ መቅረቡ አግባብ አይደለም፤ አመልካቾች አከራካሪውን መሬት በውርስ ስለማግኘታቸው ምንም ዓይነት ማስረጃ አላቀረቡም፤መሬቱ የወል ስለመሆኑ በአግባቡ ተረጋግጧል፤ጉዳዩ በቅድሚያ በገላጋይ ሽንጎ እንዲታይ በክልሉ ሕግ በአስገዳጅነት ያልተቀመጠ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

አከራካሪውን መሬት በተመለከተ ቀደም ሲል ቀርቦ የነበረው ክስ ከሳሽ የነበረው ወገን ባቀረበው ጥያቄ በፍ/ቤት ፈቃድ የተቋረጠ መሆኑን፤ በመቀጠልም የአሁን ተጠሪ አዲስ ክስ ያቀረበ መሆኑን፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ይዞታው የእነርሱ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አለማቅረባቸውን እና ምስክሮቻቸውም የጠቀሱት መሬት ክስ ከቀረበበት መሬት ጋር ተመሳሳይ አለመሆኑን እና የሚመለከተው የአስተዳደር አካል 1ኛው መሬት የወል መሬት መሆኑን፤ ሁለተኛውን መሬት ከራሳቸው ይዞታ በመነሳት በስተምዕራብ በግምት 1.5 ቃዳ የገፉ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ የላከ መሆኑን በመግለጽ አመልካቾች መሬቱን እንዲለቁ እና የአዝመራ ግምት እንዲከፍሉ በማለት የወሰነ መሆኑን፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ክሱ የተስተካከለው የመሬቱን መጠን በሚመለከት ብቻ በመሆኑ አጠቃላይ የተደረገውን ክርክር እና ስነ ስርዓት ሊለውጠው የሚችል ባለመሆኑ የተጠሪ ምስክሮች እንዲሰሙ መደረጉ ተገቢ አለመሆኑን፤ ሆኖም አስቀድሞ ቀርቦ በነበረው ማስረጃ መሠረት ጉዳዩ ሲታይ መሬቶቹ የወል ናቸው መባሉ ተገቢ መሆኑን በመግለጽ ከሳሽ ክስ በማሻሻል ሐዲት ምስክር ማሰማቱ ስነስርዓታዊ አይደለም ስለተባለ የሰብል ግምት ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በማሻሻል የወሰነ መሆኑን ክርክሩ ሐዲት መገንዘብ ችለናል፡፡

በመሠረቱ ክስ ከቀረበ በኋላ በማናቸውም ጊዜ ከሳሹ ያቀረበውን ክስ በማንሳት ከተከሳሾቹ አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ከክሱ ውጪ ለማድረግ ወይም ያቀረበውን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል ለመተው እንደሚችል ፍ/ቤቱም ተከሳሹ ባቀረበው ነገር በከፊል ወይም በሙሉ አዲስ ክስ ለማቅረብ ሊያስፈቅድለት የሚችል በቂ ምክንያት ያለው ሲሆን ስለጉዳዩ ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ በመስጠት ከሳሹ በሙሉ ወይም በከፊል በተወው ነገር አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችልበትን መብቱን በመጠበቅ ያቀረበውን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲተው ሊፈቅድለት የሚችል መሆኑን፤ በዚሁ መሠረት በፍርድ ቤቱ ፈቃድ እንደገና ለሚቀርቡ ክሶች ሁሉ የመጀመሪያው ክስ እንዳልቀረበ ተቆጥሮ የይርጋው ዘመን የሚታሰበው በአዲሱ ክስ መሠረት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278 ድንጋጌ ያስገነዝበናል፡፡ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው አንድ ተከራካሪ ወገን በፍ/ቤት ፍቃድ ክሱን የተወ እና አዲስ ክስ ያቀረበ በሆነ ጊዜ በቀረበው አዲስ ክስ ላይ በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የቀረቡት እና በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች ተመርምረው እና ተመዝነው ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ አስቀድሞ በፍ/ቤት ፍቃድ በተዘጋው መዝገብ ላይ ቀርበው በነበሩ ማስረጃዎች መሠረት ውሳኔ የሚሰጥበት አይደለም፡፡

አመልካቾች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር አስቀድሞ ቀርቦ በነበረው እና ውሳኔ ሊሰጥበት ሲል ዓቃቤሕግ ባዘጋው የክስ መዝገብ ክስ የቀረበበት መሬት የአመልካቾች መሆኑ ተረጋግጧል፤ የስር ፍ/ቤት አስቀድሞ የተዘጋውን መዝገብ እና የተጣራበትን ሪፖርት በትዕዛዝ አስቀርቦ ማየት ሲገባው ይህ ሳይደረግ ውሳኔ መሰጠቱ አግባብ አይደለም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም አስቀድሞ ቀርቦ የነበረው ክስ በፍ/ቤት ፍቃድ የተተወ በመሆኑ እና ተጠሪ ባቀረበው አዲስ ክስ መነሻነት በግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች

እና በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት የቀረቡ ማስረጃዎች ተመርምረው እና ተመዝነው ውሳኔ የሚሰጥበት ከመሆኑ አኳያ አመልካቾች በዚህ አግባብ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል በማለት የያዘው ነጥብ አስቀድሞ ቀርቦ የነበረው ክስ በከሳሽ ጥያቄ ከተዘጋ በኋላ በድጋሚ በቀረበው ክስ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ የመሬት አስተዳደር በ18/02/09 የላከው ሪፖርት ሳይመዘን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊመዘን የሚገባው ማስረጃ በተዘጋው መዝገብ የቀረበው ነው በማለት ተጣርቶ የቀረበውን ሪፖርት ሳይመዘን የማለፉን አግባብነት ለማጣራት በሚል ቢሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሰጠው በፍ/ቤት ፍቃድ በተተወው መዝገብ ላይ ቀርቦ የነበረውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ሳይሆን የመሬት መጠኑን አስመልክቶ ክሱ ተሻሽሎ ከመቅረቡ በፊት ቀርቦ የነበረውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ በመሆኑ ውሳኔው በአግባቡ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 63639 ሰኔ 29 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረተ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ነሐሴ 03 ቀን 2010 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ም

የመ/ቁ 165616

ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ፈለቀ ታደሰ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሣሙኤል ሱሊቶ በሌሉበት፡፡

2. ወ/ሮ አየለች አቤቦ ወኪል አቶ ተካልኝ ጴጥሮስ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ የመኖሪያ ቤት መስሪያ የምሪት ቦታ ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በፍ/ር/ ሰበር መ/ቁ/10579 ላይ ነሐሴ 17/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አንደኛ ተጠሪ በሆሳዕና ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ህዳር 06/2009 ዓም የአሁን አመልካችን 1ኛ ተከሳሽ፤ ሆሳዕና ከተማ ማዘጋጃ ቤትን እና የሻቾ ዱና ክፍለ ከተማ ማዘጋጃ ቤትን እንደቅደም ተከተላቸው 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በማድረግ አሻሽለው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ነው፡፡ የክሱ ይዘት በአጭሩ በሆሳዕና ከተማ ከ1997-1999 በተደረገ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ሽንሸና በሻቾ ዱና ክፍለ ከተማ በሻቾ ዱና ቀበሌ ባለወልድ ሳይት ዕጣ ቁጥር 57 የሆነ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር የተጠቀሰው ቦታ የደረሳቸው መሆኑን፤ በዚሁ ይዞታ ላይ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሽ የሆኑት

አስተዳደር ክፍሎች ለአሁን አመልካች በመወገን ቦታውን ደርበው የሰጧቸው መሆኑን በመግለፅ ይዞታው የ1ኛ ተጠሪ/ከሳሽ/ ነው ተብሎ በቦታው ላይ ካርታ እንዲሰጣቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት ቀርበው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ይዞታ በህጋዊ መንገድ አግኝተው ቤት ሰርተውበት ይዘው የሚገኙ መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ይዞታ ከሳሽ ለነበሩት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በህጋዊ መንገድ የተሸነሸነ ስለመሆኑ ማረጋገጡን በምክንያትነት ጠቅሶ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በይዞታው ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡ እና አስተዳደር ክፍሉም በቦታው ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰርቶ እንዲሰጣቸው ሲል ወስኗል፡፡

በዚሁ ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ በተናጠል ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለያየ መዝገብ ላይ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ በመ/ቁ/17602 ላይ የካቲት 21/2010 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቶ ከዚያ በኋላ በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች ቅሬታቸው ተቀባይነት ባለማግኘቱ በዚህ መዝገብ ላይ ለሰበር ቀርቧል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን 2ኛ ተጠሪ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ በመ/ቁ/17696 ላይ ተስተናግዶ የካቲት 09/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ የተሻለ መብት ያላቸው የአሁን 2ኛ ተጠሪ ናቸው በማለት ተወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን 1ኛ ተጠሪ እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ አቤቱታ አቅርበው በሰ/መ/ቁ/165588 ላይ ህዳር 27/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቅሬታው ለሰበር ክርክር አያበቃም ተብሎ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ መዝገብ ላይ ህዳር 12/2011 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ ለአሁን አመልካች ካርኒ በቅድሚያ የተቆረጠ ለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ ይዞታውን እንዲያስረክቡ የተወሰነበት አግባብ ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆ አኳያ በዚህ ሰበር ችሎት ሊመረመር የሚገባ መሆኑ በመታመኑ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታሂል ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት አንደኛ ተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ባለማቅረባቸው መብታቸው የታለፈ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ጥር 03/2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ እንዲሁም አመልካች ጥር 24/2011 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት በስር ፍርድ ቤቶች የነበረውን የክርክር አመራር እና ውጤቱ

ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ በዚሁ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/165588 ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የሚያመጣው ለውጥ በቅድሚያ ሊፈተሽ የሚገባው መሆኑ ታምኗል፡፡

ከጉዳዩ አመጣጥ መረዳት እንደሚቻለው የሆሳዕና ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ በተናጠል ይግባኝ ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ በሁለት የተለያዩ መዝገቦች ላይ አከራክሮ ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ይግባኝ ባቀረበበት መዝገብ ላይ በመልስ ሰጪነት የተቆጠሩት የአሁን ተጠሪዎች ሲሆኑ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ይግባኝ ባሉበት መዝገብ ላይ ደግሞ መልስ ሰጪ የነበሩት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ናቸው፡፡

አንድን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ሲሰማ በነበረ ፍርድ ቤት በከሳሽነትም ሆነ በተከሳሽነት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ተከራካሪዎች በቀረቡበት መዝገብ ላይ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ አንዱ ተከራካሪ በጠቅላላው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት የሚችል መሆኑን እና በዚህ ዓይነት ሁኔታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ባላቀረቡት ተከራካሪዎች ላይም የሚፀናባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 331 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ችግሩ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በተናጠል ይግባኝ ያቀረበ እንደሆነ ነው፡፡

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያየ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት እድል እንዳይፈጠር ፍርድ ቤቶች ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በአንድ በይግባኝም ሆነ በሰበር ችሎት በቀረበ ጉዳይ ላይ በስር ፍርድቤቶች በርካታ ተከራካሪዎች የነበሩ መሆኑ መዝገቡ የሚያሳይ ከሆነ ሌሎች በመዝገቡ ላይ ያልቀረቡት ቀድሞ የክርክሩ አካል የነበሩት አካላት በሌላ መዝገብ ላይ ቀርበው ከሆነ ተገቢ ማጣራት እና ክትትል ተደርጎ መዝገቦቹ ተጣምረው እንዲታዩ ማድረግ በዚህ ሰበር ችሎትም ጭምር በአሰራር የዳበረ የሙግት አመራር ልምድ በመሆኑ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች መሰል አሰራር ሊከተሉ ይገባል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ በቀረበለት ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት ተከራካሪ የነበሩት ሁለት አካላት ተቀራራቢ በሆነ የመዝገብ ቁጥር ላይ በተናጠል ይግባኝ አቅርበው እያለ ፍርድ ቤቱ ሁለቱን መዝገቦች አጣምሮ መወሰን ሲገባው በቀናት ልዩነት በአንደኛው መዝገብ ላይ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር በሌላኛው ላይ ደግሞ በማፅናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ ከላይ ከተጠቀሰው የዳኝነት ሙግት አመራር ሥርዓት አንፃር አግባብ ያልሆነ እና የሚነቀፍ ተግባር ነው፡፡

ያም ሆኖ ግድፈቱ ቀጥሎ በነበረው ክርክር በተሰጠው ውሳኔ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ስለመኖሩ ለመለየት በሰር ፍርድ ቤት ክርክር ወቅት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን እና ያንን መሰረት በማድረግ የተሰጡትን ውሳኔዎች ይዘት በጥንቃቄ መፈተሹ ተገቢ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሰረት ይግባኝ ሰሚው የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በሻረበት የመ/ቁ/17602 ላይ ክርክር የተነሳበትን ይዞታ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ይዘው ሁለት ክፍል ቤት ሰርተውበት እየኖሩበት ለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ክርክር ወቅት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን፤ በአንፃሩ ሌላው ተከራካሪ ወገን ከይዞታው ጋር በተያያዘ የምሪት ካርኒ እና እጣ የደረሳቸው ለመሆኑ አስረጂ የሚሆኑትን ሰነዶች አቅርበው የሚከራከሩ መሆኑን፤ ከዚህ አኳያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት መሰረት መሬት የመንግስት እና የህዝብ ንብረት በመሆኑ በመሬት ላይ የይዞታ መብት አለን ከሚለው ይልቅ ይዞታውን በእጁ አድርጎ ንብረት ያፈራበት ሰው የተሻለ መብት ያለው ስለመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/105125 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በዋቢነት ጠቅሶ ይዞታው ለአሁን 2ኛ ተጠሪ ይገባል ማለቱን እና ይኸው ውሳኔ እዚህ ሰበር ችሎት ደርሶ በሰ/መ/ቁ/165588 ላይ የፀና መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በተመለከተ በዚህ መዝገብ ላይ ተከራካሪ የሆኑት ሶስቱም አካላት የይገባኛል ክርክር ባቀረቡበት ሁኔታ በፍሬ ነገር ደረጃ ይዞታውን በተጨባጭ በእጃቸው አድርገው ንብረት አፍርተዉበት ያሉት 2ኛ ተጠሪ መሆናቸው ከተረጋገጠ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/105125 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አኳያ በውጤት ደረጃ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን የሚያስለውጥ አይደለም። በመሆኑም ምንም እንኳን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመራበት ሁኔታ ከሙግት አመራር ሥነ ሥርዓት አኳያ የሚነቀፍ ቢሆንም የሥነ ሥርዓት ግድፈቱ በውሳኔው ይዘት እና ውጤት ላይ የሚያመጣው ለውጥ አለመኖሩ የተረጋገጠ በመሆኑ እና ግድፈቱ አመልካችን ያሳጣው መሰረታዊ መብት ባለመኖሩ መሰረታዊ የሚባል ስህተት ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በፍ/ር/ሰበር መ/ቁ/10579 ላይ ነሐሴ 17/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል።

ት ዕ ዛ ዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
2. መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 168094

ታህሳስ22 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ምስጋናው አሰጌ

ተጠሪ፡- 1ኛ አቶ አይናዲስ አሰጌ

2ኛ አቶ በልስቲ አይናዲስ አሰጌ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ ሊቀርብ የቻለው የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በአማራ ክልል የደጋ ዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪዎች በውርስ ያገኘሁት መሬቴን ቀምተው ቤት የሰሩበት በመሆኑ ቤቱን አፍርሰው መሬቴን እንደያስረክቡ ይወሰንልኝ ብለው ባቀረቡት ክስ በወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ከፀና በኋላ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተሽሮ በይርጋ አይታገድም የተባለውንም መሬት አስመልክቶ በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ አመልካች አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

በወረዳ ፍ/ቤቱ ቀርቦ የነበረው ክስ በአጭሩ በዳሞት ጽዩን ቀበሌ ውስጥ 1ኛ/ በምስራቅ ዋሌ በሰሜን መዋጮ በደቡብ አለሙ ወልዲያ ጐጥ አማጋው 1 ጥማድ መሬት፣ 2ኛ በምዕራብ ዋሌ በሰሜን ዋሌ በደቡብ ዋሌ በወልዲያ ጐጥ ዋሌ 1 ጥማድ መሬት፣3ኛ በምዕራብ ሞላ በሰሜን አለሙ በደቡብ አይናዲስ በወልዲያ ጐድ ጉርድ 2 ጥማድ መሬት በሚች አባቴ አቶ አሰጌ መንግሥቱ አጥብቸ አስታምሜ ጡሬ የቀበርኩት ሥለሆነ እኔም በዚሁ ፍ/ቤት ህጋዊ የውርስ ማረጋገጫ ወራሽነቴን አረጋግጬ የያዝኩትን ተከሣሾች የቀሙኝ እና ቤት የሠሩብኝ በመሆኑ ቤቱን አፍርሰው እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሾች በበኩላቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን፣ ሚች በስሙ የተቆጠረለት መሬት ሲሆን እኛም የወረስነው ነገር የሌለ በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም፣ መሬቱን በ1996 ዓ.ም የመሬት ማረጋገጫ ደብተር በኂላም አረንጋዴ ደብተር አስመዝግቤ የያዝኩት እንጂ የሚችን መሬት በውርስ የያዝነው ነገር የለም፣ መሬቱን ከያዝነውም 15 ዓመት በላይ ነው በመሆኑም በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል፣ መቃወሚያው ከታለፈም ክስ የቀረበበት የውርስ መሬት የሚች አቶ አሰጌ መንግሥቱ መሬት ሳይሆን የኛ ይዞታ ስለሆነ እና ከያዝነውም ከ15 ዓመት በላይ በመሆኑ ከሳሽ ያወጣው ውርስ እንዲታይልን እና የውርስ መሬት ለመጠየቅ ስለማይችል መዝገቡ ይዘጋልን ሲሉ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የሚያከራክረው መሬት የማን ነው? ከመቼ ጀምሮ ተከሣሾች ያዙት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል አይገባም ?ተከሣሾች መሬቱን ሊለቁ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉ ሰፊ ጭብጦችን ከመሰረተ በኂላ የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቷል፡፡

የአካባቢ ገ/መ/አስ/ማንባታ/አጠ//ጽ/ቤትን ክርክር ስላስነሳው ይዞታ ጠይቆ ምላሽ ያገኘ እና የሰው ምስክሮችን ቃል በማገናዘብ መርምሮ ክርክር ያስነሳው ይዞታ ቀደም ሲል የአ/ይ አሰጌ መንግሥቱ እና እ/ይ እቴነሽ አለምነህ ሆኖ የተደለደለው በ1989ዓ.ም.መሆኑን፣ አ/ይ አሰጌ መንግሥቱ በ1994 ዓ.ም. መሞታቸውን፣ ከሣሽ እና 1ኛ ተከሣሽ የሚችን መሬት ተካፍለው ይዘውት የነበረ እና የያዙትም በክሱ ተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰውን 1ኛ ተከሣሽ መያዙን 2ኛ እና 3ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሱትን ሁለት መሬቶች ከሣሽ የያዘና በ2008 ዓ.ም. ከጥር ወር ወዲህ የቀሙት መሆኑን፣ 2ኛ ተከሣሽ የቤተሰብ አባል ያልነበረ ከወላጅ አባቱ ከ1ኛ ተከሣሽ ጋር ያደገ መሆኑን ተከሣሽ የያዘውን መሬት ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ይዞት ቤት ሰርቶበት እስከዛሬ ድረስ ይዞት የሚገኝ መሆኑን ሌሎችን ግን ተከሣሾች ይዘውት የማያውቁ እና የከሣሽ ድርሻ ሆኖ እያለ በ2008 ከጥር ወዲህ የቀሙት መሆኑ በምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑ ብይን ሰጥቶ በክሱ ተራ ቁጥር 3 ስር የተጠቀሰውን መሬት በተመለከተ 1ኛ ተከሣሽ ከ10 ዓመት በላይ ይዞት ስለሚገኝ በ3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል፣ በተ.ቁ. 1ኛ እና 2ኛ ላይ የተመለከቱትን ይዞታዎች ግን ተከሣሾች በጉልበት ከከሣሽ የቀሙት መሆኑ ስለተረጋገጠ ለቅቀው እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡

የስር 1ኛ ተከሣሽ የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱ ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና ጉዳዩን መርምሮ የወረዳ ፍ/ቤቱ በይርጋ አይታገድም በማለት የስር ተከሣሾች ለቅቀው እንዲያስረክቡ ሲል የሰጠውን የውሣኔ ክፍል እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የሰጠውን የማጽናት ውሣኔ በመሻር በአዋሣኝ የተጠቀሱት ሁለት መሬቶችም ጭምር በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ከላይ በተጠቀሰው የሰበር ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ ታህሳስ 2 ቀን 2011 ዓ.ም የተፃፈ 5 ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል። ይዘቱም በአጭሩ፡- በስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች ምንም አይነት ማስረጃ ያላቀረቡ እና ምስክሮችም ያላሰሙ፣ ምስክር የተሰማውም የእኔ ሆኖ እያለ እና በፍርዱም ላይ በገለፀበት ሁኔታ ተጠሪዎች በስር ወረዳ ፍ/ቤት ሁለት የመከላከያ ምስክር እንዳሰሙ አድርገው አቤቱታ ስላቀረቡ በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ውሣኔን ተመልክቶ የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፣

የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ የእጅ ጽሁፍ ኮፒ ሆኖ የሚታይ ባለመሆኑ መዝገቡን አስቀርቦ መርምሮ መወሰን ሲገባው ወይም በእጁ የሚገኘውን አስቀርቦ መመርምር ሲገባው ይህን ሳያደርግ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን እና በሁለቱ ውሣኔዎች መካከል ያለው ልዩነት ናቸው ያሏቸውን 9 ነጥቦችን ለይተው በአቤቱታው ላይ በማሳየት የስር ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔ በሃሰተኛ ውሣኔ ላይ መሠረት ተደርጎ የተሰጠ በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል ሲሉ በጥብቅ ጠይቀዋል።

አቤቱታው በአጣሪው ተመርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ጭብጥ በመያዙ መነሻነት መዝገቡ ለችሎቱ ሊቀርብ ችሏል።

ተጠሪዎችም አቤቱታው ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር እንዲደርሳቸው ተደርጎ መጋቢት 24 ቀን 2011 ዓ.ም. በአንድነት የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካችም የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚሁ ተጠናቋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች እና ከመልስ እና የመልስ መልሱ እንዲሁም ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን መርምረናል።

እንደመረመርነውም አመልካች በወረዳ ፍ/ቤቱ አቅርበውት የነበረው ክስ ከላይ እንደተመለከትነው በተለያዩ ቦታዎች አዋሳኙን ጠቅሶ የተለያየ መጠን ያላቸው መሬቶችን ተጠሪዎች ቀምተውኛል፣ በመሆኑም የሰሩትን ቤት አፍርሰው መሬቴን ይልቀቁልኝ የሚል ክስ ያቀረቡ ሲሆን፣ ተጠሪዎችም ክርክሩ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያነሱና በፍሬ ጉዳዩም ላይ ሙሉ መልሳቸውን አቅርበዋል። ፍ/ቤቱም ከውሣኔው መረዳት እንደተቻለው በአመልካች በኩል የቀረቡ ምስክሮችን የሰማ እና በተጠሪዎች በኩል ግን በመልሳቸው ላይ የማስረጃ ዝርዝር ያላቀረቡ በመሆኑ ምስክር ያለመስማቱን አትቷል።

ወረዳ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ መሬቱን እንዲለቁ አዋሳኞችን ጠቅሶ የወሰነ ሲሆን ይህ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ያልተለወጠ ቢሆንም ተጠሪዎች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር

አቤቱታ በማቅረባቸው መነሻነት ውሣኔው ተሸሮ የቀረበው ጉዳይ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ሊለቁና ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከአቤቱታው ጋር የቀረበለት የወረዳ ፍ/ቤት ውሣኔ የተለወጠ እና ሃሰተኛ ውሣኔ በመሆኑ መዝገቡን አስቀርቦ እና መርምሮ ሊወስን ሲገባው ይህን ሳያደርግ በመወሰኑ ስህተት ፈጽሟል በሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች መዛግብት ሳይቀርብ እና ሳይመረመር ሊወሰን የማይችል መሆኑን ችሎቱ ስለተረዳው የደጋዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት እና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መዛግብትን ከሚገኙበት እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ተሰጥቶ መዛግብቱ ቀርበው ከጉዳዩ ጋር አብሮ ተመርምሯል፡፡

በዚህ መሠረት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተመርምሮ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ትክክል ግልባጭ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦለት የውሣኔውን ትክክለኛነት አረጋግጦ ስለመወሰን አለመወሰኑ መመልከት ተገቢ ሆኖ አግኝተነው በጭብጥነት በመያዝ መርምረናል፡፡

በመሆኑም የስር የደጋ ዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት መ/ቁ/ 12826/09 በ7/9/2009 ዓ.ም.በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በችሎቱ ዳኛ የእጅ ጽሁፍ የተፃፈ እና 5 ገጽ ያለው ሲሆን፣ በዚሁ መዝገብ ውስጥ በአሁን ተጠሪዎች በ12/04/2009 ዓ.ም. በእጅ የተፃፈ 2 ገጽ መልስ ተያይዟል፡፡ ከዚህ መልስ ጋር የተያያዘ የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ የሌለ መሆኑንም ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የወረዳ ፍ/ቤቱ የፍርድ ሃተታውን ሲጽፍ በአሁን አመልካች በኩል የቀረቡ ምስክሮችን የሰማ እና ከተጠሪዎች መልስ ጋር የተያያዘ የማስረጃ ዝርዝር የሌለ በመሆኑ ምስክር ያለመስማቱን ገልጿል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 68465 ታህሳስ 3 ቀን 2011 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ፍርድ ገጽ 2 10ኛ መስመስር ላይ " የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ-----" የሚል ሃረግ ያለ መሆኑን ከውሣኔው መረዳት ተችሏል፡፡

እንዲሁም በገጽ 3 ላይ 8ኛ መስመር "------ የአመልካች ሁለቱ እንዲሁም የተጠሪው 1ኛ እና 3ኛ ምስክሮች ------" በማለት አትቷል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤት ተከሣሾች በነበሩት ግለሰቦች ማስረጃ ዝርዝር ያልቀረበ እና ምስክርም ያልተሰማ መሆኑ በውሣኔው ላይ ተገልጾ እያለ እንዴት የክልሉ ሰበር ተጠሪዎች እንዴት ምስክር ሳያሰሙ ምስክር እንዳሰሙ ተደርጐ ውሣኔ ተሰጠላቸው? የሚለውን ለማጣራት የሰበሩ ክርክር ሲከናወን ለአሁን አመልካች በስር ፍ/ቤት ተወስኗል ሲሉ የስር ሰበር አመልካቾች አቅርበውት የነበረው ውሣኔ ኮፒን መመልከት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ቀርቦልን ስንመለከተው የወረዳ ፍ/ቤቱ ዳኛ ጽሁፍ ያለመሆኑን፣ የገፁም ብዛት የሚለያይ፣ ከውሣኔው ውስጥ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ምስክር

አቅርበው አስምተው የተወሰነ መሆኑን የሚያሳዩ ሃረጎች የገቡበት እና የተለያዩ ልዩነቶች ያሉበት መሆኑን ተመልክተናል፡፡

ችሎቱ ይህን ተመልክቶ ብቻ ያበቃ ሳይሆን የአሁን 2ኛ ተጠሪ የአመልካች ተወካይ በተገኙበት በችሎት በዳኞች ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ በስር ወረዳ ፍ/ቤት ራሱ ከ1ኛ ተጠሪ አባቱ ጋር እየቀረበ እንደተከራከረ፣ የውሣኔ ግልባጭም በኮፒ ከችሎቱ እንደወሰደ የፍ/ቤቱም ማህተም ያረፈበት መሆኑን፣ ባቀረቡት መልስ ላይ የማስረጃ ዝርዝር እንዳቀረቡ እና በዚሁ መሠረት 3 ምስክሮችን አቅርበው ማሰማታቸውን ፣ የምስክሮችን ስም ጭምር ጠቅሶ እንደገለፀ ለችሎቱ ያስረዳ ሲሆን፣ በችሎቱ በስር ፍ/ቤት መዝገብ ላይ ቀርቦ የነበረውን መልሳቸውን እንዲያይና እንዲያረጋግጥ ሲጠየቅም ይህን ያቀረብን አይመስለኝም በማለት ለችሎቱ ተናግሯል፡፡

አንድ ሙግት በተከራካሪ ወገኖች መካከል መከናወን ያለበት በቅን ልቦና እና ማስረጃን በማቅረብ መሆን ያለበት ሲሆን፣ ይግባኝ የሚባልበት በሆነ ጊዜም በስር ፍ/ቤት የተከናወነው ክርክር እውነትነቱን ይዞ መቀጠል ያለበት መሆኑ የክርክር አመራር ስነ ስርአት መሆኑ ይታወቃል፡፡

ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡትን ክርክር በቅን ልቦና እና እውነትነት ባለው ማስረጃ የማይከራከሩ በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው ነገር እውነት መሆኑን ባልተረዱ እና ፍፁም ድብቅ በሆነባቸው ጊዜ እውነት ላይ ለመድረስ የሚያደርጉት ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ በቀረበላቸው ማስረጃም እውነተኛውን ውሣኔ እንዳይሰጡ የሚገድባቸው ከመሆኑም በላይ እውነትን የያዙ ሰዎች በሀሰተኛ ማስረጃ እና በሃሰተኛ ተከራካሪዎች ቅን ልቦና መጉደል ምክንያት እውነትን የያዙ ሰዎች ላይ ያልተገባ ፍርድ እንዲሰጡ የሚያደርግ በመሆኑ ፍትህ እንዲዛባ፣ ማህበረሰቡም በፍ/ቤቶች ላይ እምነት እንዳይኖረው የሚያደረግ አደገኛ አካሄድን የሚፈጥር መሆኑ እሙን ነው፡፡

ወደ ቀረበው ጉዳይ ስንመለስ የስር ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲለወጥ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔው እንዲሻር መነሻ የሆነው ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ከአቤቱታው ጋር የቀረበለት በተጠሪዎች የተቀየረው እና ምስክር ሳያሰሙ ምስክር እንዳሰሙ ተደርጐ የተለወጠው ውሣኔ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እውነተኛውን ክርክር እንዳይመለከት እና ተገቢውን ውሣኔ እንዳይሰጥ ወይም በሌላ አነጋገር የተዛባ ውሣኔ እንዲሰጥ የተደረገ መሆኑን ለመመልከት ችለናል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረው ትክክለኛ ውሣኔ ሳይበረዝ ሳይከለስ ቀርቦለት ቢሆን ኑሮ አሁን የደረሰበት መደምደሚያ ላይ ላይደርስ ይችል ይሆናል የሚል ግምት ያስነሳል፡፡ የአመልካችም ክርክር ከዚህ የራቀ አይደለም፡፡

አመልካች የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ መልስ ሲያቀርቡ አሁን ያነሱትን መከራከሪያ ሊያነሱ ያልቻሉት ደግሞ ይህን ያወቁት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔ ተገልብጦ ከተሰጣቸው በኋላ

በመሆኑ ተጠሪዎች በፈፀሙት የተንኮል አሰራር አመልካችን ብቻ ሳይሆን ፍ/ቤቱንም እንዳጭበረበሩና ተገቢ ያልሆነ ፍትህ ለማግኘት ሲሉ የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ ሃረጐች ለእነሱ በሚያመች መልኩ እንደቀየሩ ባደረግነው ማጣራት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔ የሰጠው የወረዳ ፍ/ቤቱ ትክክለኛ ውሣኔ ሳይደርሰው እና የተለወጠ ውሣኔ ደርሶት መሆኑን ያረጋገጥን በመሆኑ በዚህ የተለወጠ ውሣኔ ምክንያት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ እውነተኛ ፍርድን መሠረት በማድረግ የተሰጠ እና እውነት ላይ ለመድረስ በሚያዳግት ውሣኔ ላይ ተመስርቶ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ሊሻር የሚገባው ነው ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 68465 ታህሳስ 3 ቀን 2011 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ /ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በውሣኔ የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ የደጋ ዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት መ/ቁ/ 12826 የሆነውን መዝገብ በማስቀረብ እና በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠውን እውነተኛ የዳኛ ውሣኔ በመመልከት ከቀረበለት አቤቱታ ጋር በማገናዘብ እና የአሁን አመልካችን በተገቢው ውሣኔ ላይ መልስ በማሰጠት ትክክለኛ ነው ያለውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 341/1/ መሠረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የአሁን ተጠሪዎች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በደጋዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 12826/2009 በቀን 07/09/09 ዓ.ም የተሰጠ ነው ተብሎ የቀረበው ውሳኔ በፍ/ቤቱ ያልተሰጠ ለመሆኑ ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤት መዝገብን አስቀርቦ ያረጋገጠ በመሆኑ የክልሉ ፖሊስ በተጠሪዎች እንዲሁም ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ባላቸው አካላት ላይ ተገቢውን የወንጀል ምርምራ እንዲያከናውን ታዟል፤ ይጻፍ፡፡
2. የአራዳ ፖሊስ 2ኛ ተጠሪን ለክልሉ ፖሊሰ እንዲያስረክብ ታዟል፤ ይጻፍ
3. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ.ቁ 69774 የሆነው መዝገብ እና የደጋ ዳሞት ወረዳ ፍ/ቤት የመ.ቁ 01012826/2009 የሆነው መዝገብ በመጡበት አኳኋን ወደ መጡበት ይመለሱ፡፡

- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ.መ.ቁ 165775

የካቲት 29 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡-ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- የአቶ ተሾመ ጎርፌ ወራሽ መቅደስ ተሾመ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኝ ወራሽ ጣሰው ተሾመ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ አፈጻጸምን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት የአሁን አመልካች ደግሞ የፍርድ ባለዕዳ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች ለስር አፈጻጸም ችሎቱ ባቀረቡት አቤቱታ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በመጀመሪያው አማራጭ በዓይነት የማካፈል ስራ ሳይሰራ ንብረቱን በሐራጅ እንዲሸጥ ማድረጉ አግባብ ስላልሆነ የሀራጅ ሽያጩ ታግዶ በዓይነት እንድንካፈል ትዕዛዝ ይሰጥላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አፈጻጸሙን የመራው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ ፍ/ቤቱ ከሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ውጪ እየተደረገ ያለ የአፈጻጸም ሂደት ስለመኖሩ የቀረበ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ ሐራጁ የሚታገድበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታቸውውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች እና ተጠሪ የውርስ ሐብት በሆነው ንብረት ላይ እኩል ድርሻና መብት አለን፤ ክፍፍሉን በተመለከተ ወደ ሌሎች አማራጭ መሔድ የሚቻለው ፍርድ ያረፈበት ቤት መካፈል የማይችል ከሆነ ነው፤ ቤቱንማካፈል እየቻለ በሐራጅ ቢሸጥ የአመልካችን መብት ይጎዳል፤ የክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በቀን

12/01/10 ዓ.ም ጽፎ በላከው ማስረጃ በመመሪያ ቁጥር 12/2006 መሠረት መካፈል የሚችል መሆኑን ገልጾ ሳለ በዚሁ አግባብ ክፍፍሉ መፈጸም ሲገባው የመጨረሻውን አማራጭ በመጠቀም በሐራጅ እንዲሸጥ መደረጉ ተገቢ አይደለም፤ ቤቱ በሐራጅ ቢሸጥ ዋጋው በጣም አነስተኛ ስለሚሆን እና በቤቱ እንዳልገለገል የሚያደርገኝ በመሆኑ ቤቱ በሐራጅ መሸጡ ቀርቶ በዓይነት እንድካፈል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ቤቱ መካፈል መቻል አለመቻሉን በተመለከተ ከአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ ለቀረበው ጥያቄ በመመሪያ ቁጥር 12/2006 መሠረት መካፈል ይችላል የሚለው ምላሽ ውጤቱ ባልታወቀበት ተጠቃሹ ቤት በጨረታ እንዲሸጥ መወሰኑ ዋናውን ውሳኔ ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የማይቻል መሆኑን የክፍለከተማው የሰነድ አልባ ይዞታዎች ዴስክ ቦታው ድረስ መሐንዲስ በመላክ አረጋግጧል፤ ቤቱን በዓይነት እኩል መካፈል የማይቻለው በአንድ በኩል ያለው ቤት በብረት እና በብሎኬት በጥራት የተሰራ ትልቅ ቪላ ቤት ሲሆን በሌላ አቅጣጫ ያሉት ቤቶቸ ደግሞ በእንጨት እና በጭቃ የተሰሩ ያረጁና እየፈራረሱ ያሉ ቤቶች በመሆናቸው ነው፤ ይህንኑ ለመግለጽም የሰነድ አልባ ይዞታዎች የተጠቀመው አገላለጽ ቤቶቹ የተሰሩበት ቁስ ወይም ማቴሪያል የሚል ነው፤ ቤቱ በዓይነት መካፈል የማይችል እና ግራቀኛችን በስምምነት መካፈል ያልቻልን በመሆኑ በሐራጅ እንዲሸጥ ታዟል፤ መመሪያ ቁጥር 12/2006 የይዞታ አሰጣጥ መመሪያ እንጂ የውርስ ሀብት የሆነ የቤት ክፍፍል መመሪያ አይደለም፤ ቤቱ በሐራጅ ከተሸጠበት ከነሐሴ 28 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በውሳኔው ለአመልካች እንዲከፈላቸው የተወሰነው 9 በመቶ ወለድ በተጠሪ ላይ እየቆጠረብኝ በመሆኑ አመልካች አላግባብ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን አከራካሪውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

አከራካሪ የሆነው ቤት ግማሽ ድርሻ የአቶ ተሾመ ጎርፌ መሆኑ እና ግማሹ ድርሻ ደግሞ የሟች ወ/ሮ ተናኜ ተሾመ በመሆኑ የሟች ወ/ሮ ተናኜ ተሾመ ግማሽ ድርሻ ወራሻቸው ለሆኑት የወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኘሁ ድርሻ ነው በማለት የተወሰነ መሆኑን፤ በመዝገቡ ተከራካሪ የሆኑት አቶ ተሾመ ጎርፌ እና ወ/ሮ ፈሰሰች ወንድማገኘሁ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው በአመልካች በኩል መቅደስ ተሾመ በተጠሪ በኩል ደግሞ ጣሰው ተሾመ ተተኪ ወራሽ በመሆን ክርክሩ የቀጠለ መሆኑን የሥር መዝገብ የሚያሳይ ሲሆን የአሁን አመልካች አፈጻጸሙን ለመራው ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት በመጀመሪያው

አማራጭ መሠረት በዓይነት የማካፈል ስራ ሳይሰራ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ መደረጉ አግባብ ስላልሆነ የሐራጅ ሽያጩ ታግዶ በዓይነት እንድንካፈል ይደረግልኝ በሚል ነው፡፡

አመልካች በዚህ አግባብ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቤቱ በዓይነት መካፈል የሚችል መሆን አለመሆኑን ተጣርቶ እንዲቀርብለት ለክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠቃሹ አካል በቀን 12/01/10 ዓ.ም በጻፈው ምላሽ ካርታው ወጪ ያልሆነ ሰነድ ስለሆነ በሰነድ አልባ ዴስክ እንጂ በኛ በኩል ለማካፈል የማንችል መሆኑን እየገለጽን ነገርግን በመመሪያ ቁጥር 12/2006 መሠረት መካፈል የሚችል መሆኑን እንገልጻለን የሚል ምላሽ የሰጠ መሆኑን፤ ይህንኑ ምላሽ መነሻ በማድረግ የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ ክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሰነድ አልባ ፕሮጀክት ዴስክ ቤቱን በዓይነት እንዲያካፍል በማለት ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን፤ ትዕዛዙ የተላለፈለት የክፍለከተማው ሰነድ አልባ ዴስክም በቀን 21/06/2010 ለዳይሬክቶሬቱ በሰጠው ምላሽ ቦታው ድረስ በመገኘት ለመካፈል በተደረገው ጥረት መሠረት ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የተሰራበት ቁስ / ማቴርያል / ስለሚለያይ ለማካፈል ተቸግረናል በማለት ምላሽ የሰጠ መሆኑን፤ የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬም በግራቀኙ መካከል ስምምነት የሌለ መሆኑን በመግለጽ ቤቱ በብር 32,1,279.13 የጨረታ መነሻ ዋጋ በሐራጅ እንዲሸጥ በማለት ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን፤ በዚሁ መሠረት አከራካሪው ቤት ለጨረታ የቀርበ እና አመልካች እና ተጠሪ በቀረቡት ተጫራቾች ጨረታው እንዲቀጥል በማለት በፊርማቸው አረጋግጠው ወ/ት ራሔል ሞገስ የተባሉ ግለሰብ በብር 6,850,000 /ስድስት ሚልዬን ስምንት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር / ጨረታውን ያሸነፉ እና ገንዘቡን ገቢ ያደረጉ መሆኑን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአፈጻጸም መዝገብ እና የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የአፈጻጸም መዝገብ አስቀርበን በማየት መገንዘብ ችለናል፡፡

በመሠረቱ የውርስ ሐብት ክፍያን በሚመለከት በተቻለ መጠን በዓይነት የሚከፋፈል ስለመሆኑ፤ በዓይነት መካፈል የማይችል ከሆነ እና በባለመብቶቹ መካከል ስምምነት ከታጣ ንብረቱ በሐራጅ ተሸጦ ክፍፍሉ የሚፈጸም ስለመሆኑ የውርስ ክፍፍልን አስመልክቶ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የሽያጭ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወይም በማጭበርበር ተፈጽሟል በማለት እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ ማመልከቻ ማቅረብየሚቻል መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ የየራሳቸውን መስመር በመከተል የንብረቱ ባለቤቶች የነበሩት ተተኪ ወራሾች ሲሆኑ የክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ካርታው ወጪ ያልሆነ ሰነድ ስለሆነ በሰነድ አልባ ዴስክ እንጂ በኛ በኩል ለማካፈል የማንችል መሆኑን እየገለጽን ነገርግን በመመሪያ ቁጥር 12/2006 መሠረት መካፈል የሚችል መሆኑን እንገልጻለን የሚል ምላሽ በመስጠቱ የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ ክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት

ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሰነድ አልባ ፕሮጀክት ዴስክ ቤቱን በዓይነት እንዲያካፍል በማለት ትዕዛዝ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠቃሹ አካል ቦታው ድረስ በመገኘት ለማካፈል በተደረገው ጥረት መሠረት ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የተሰራበት ቁስ / ማቴርያል / ስለሚለያይ ለማካፈል የተቸገረ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ ሰጥቷል። ይህንኑ ተከትሎ ቤቱን በዓይነት ለመካፈል በግራቀኙ መካከል ስምምነት የሌለ በመሆኑ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ተሰጥቶ አመልካች እና ተጠሪ በቀረቡት ተጫራቾች ጨረታው እንዲቀጥል በማለት በፊርማቸው አረጋግጠው ወ/ት ራሔል ሞገስ የተባሉ ግለሰብ በብር 6,850,000 /ስድስት ሚልዬን ስምንት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር / ጨረታውን አሸንፈው ገንዘቡን ገቢ አድርገዋል።

አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር ክፍፍሉን በተመለከተ ወደ ሌሎች አማራጭ መሔድ የሚቻለው ፍርድ ያረፈበት ቤት መካፈል የማይችል ከሆነ ነው፤ ቤቱ መካፈል እየቻለ በሐራጅ ቢሸጥ መብቴን ይጎዳል በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም የክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ካርታው ወጪ ያልሆነ ሰነድ ስለሆነ በሰነድ አልባ ዴስክ እንጂ በኛ በኩል ለማካፈል የማንችል መሆኑን እየገለጽን ነገርግን በመመሪያ ቁጥር 12/2006 መሠረት መካፈል የሚችል መሆኑን እንገልጻለን የሚል ምላሽ የሰጠ ከመሆኑ አኳያ፤ ይህንኑ ምላሽ መነሻ በማድረግ የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ ክፍለከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሰነድ አልባ ፕሮጀክት ዴስክ ቤቱን በዓይነት እንዲያካፍል በማለት ትዕዛዝ የሰጠ ከመሆኑ አኳያ፤ ትዕዛዙ የተላለፈለት የክፍለ ከተማው ሰነድ አልባ ዴስክም ቦታው ድረስ በመገኘት ለመካፈል በተደረገው ጥረት መሠረት ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የተሰራበት ቁስ / ማቴርያል / ስለሚለያይ ለማካፈል የተቸገረ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ የሰጠ ከመሆኑ አኳያ እና የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱም በግራቀኙ መካከል ስምምነት እንደሌለ በማረጋገጥ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የሰጠ እና አመልካች እና ተጠሪ በቀረቡት ተጫራቾች ሐራጁ እንዲቀጥል በፊርማቸው አረጋግጠው ቤቱ በብር 6,850,000 /ስድስት ሚልዬን ስምንት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር / የተሸጠ ከመሆኑ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445 በተገለጸው አግባብ የሐራጁ የሽያጭ ሥርዓት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወይም በማጭበርበር ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ ያልተገኘ ከመሆኑ አኳያ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 250862 ሐምሌ 24 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና ይህንን ትዕዛዝ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 219963 ሕዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል።

2. ሕዳር 20 ቀን 2011 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

-የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ.ቁ 250862 የሆነው መዝገብ እና የፌዴራል ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት መ.ቁ 29549 የሆነው መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ

-መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሳ/ፀ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

የሰ/መ/ቁ - 163166

ቀን - 30/09/2011

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ መስጠፉ መሐመድ

ተጠሪ፡- አቶ ናስር ኢሳ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የተጀመረዉ በሆሮ ወረዳ ዞን ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም በአጭሩ፡- አባቴ አቶ መሐመድ አባያሲን በሻምቡ ከተማ 01 እና 02 ቀበሌ ዉስጥ ያለዉን ንብረቶቹን እንዲጠብቁ እና እንዲያከራዩ ለተከሳሽ ዉክልና ሰጥተዉ በ2004 ዓ.ም ከሞት የተለዩ ሲሆን፣ ከአባታችን ሞት በኋላም የአባቴ ወራሾች ለተከሳሽ ተመሳሳይ ዉክልና ሰጥተናል፤ ይሁንና ተከሳሽ የከተማዉን አስተዳደር በማሳሳት በሻምቡ ከተማ ቀበሌ 02 ዉስጥ የሚገኘዉ እና አዋሳኞቹ በክሱ የተመለከተዉን እና በዉርስ የሚተላለፍልኝን ሁለት ክፍል የንግድ ቤት በስሙ በማድረግ እየተጠቀመበት የሚገኝ በመሆኑ ቤቱን እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ፡- ከሳሽ አባቱ ከሞተ ከ 9 ዓመት በኋላ የወራሽነት መብት አለኝ በሚል ያቀረበዉ ክስ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) መሰረት በይርጋ ይታገዳል የሚል የመጀመሪያ መቃወሚያ በማስቀደም ፍሬነገሩን በተመለከተም የከሳሽ አባት በህይወት እያሉ ቤቱን ለባንክ አስይዘዉ የተበደሩትን ገንዘብ ባለመመለሳቸዉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤቱን ለመሸጥ ያወጣዉን ጨረታ ተወዳድሬ ከባንክ የገዛሁት የግሌ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የወረዳዉ ፍርድ ቤት ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የአመልካች አባት ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩበት ከ 8 ዓመት በኋላ አመልካች ያቀረበዉ ክስ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) መሰረት በይርጋ ቀሪ ነዉ በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለሆሮ ጉዱሩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት መዝገቡን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ ክሱ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን ጠቅሶ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠዉን ዉሳኔ የተቸ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ከባንክ ገዝቶ የያዘ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ በማጽናት ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ያቀረበዉ አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በቀን 23/12/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በሆሮ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲሁም በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን መርምረን የወረዳዉ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ ክሱ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) መሰረት በሦስት ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን ነዉ፡፡ ከላይ እንደተገለጸዉ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን ጠቅሶ ግን የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉን ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ ሊያፀና የቻለዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ቤቱ የማን እንደሆነ የከተማዉን አስተዳደር ጠይቆ ያረጋገጠ በመሆኑ ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ መመለስ ላላስፈላጊ ወጪ እና ድካም ከሚዳርግ ዉጪ ሌላ ፋይዳ የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ በእኛ በኩል እንደተመለከትነዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ከፍሬ ነገር ክርክር ጋር በተያያዘ በግራ ቀኝ የቀረቡትን ክርክሮች እና ማስረጃዎች ይዘት በዉሳኔዉ ያሰፈረ ቢሆንም የቀረቡትን የሰዉ ማስረጃዎች ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር በመመዘን እና በመመርመር የሰጠዉ ዉሳኔ የለም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341 ክስን በመጀመሪያ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የተሰጠን ዉሳኔ ይግባኝ ሰሚዉ ሽሮ የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተገቢዉን እንዲወስን ሊመልስ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ የክርክሩን ፍሬ ነገር በተመለከተ ዉሳኔ መስጠት ማለት ደግሞ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ብቻ እንዳልሆነ እና የቀረቡትን ማስረጃዎች ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር በማገናዘብ፣ መርምሮ እና መዝኖ በፍሬ ነገር ረገድ ድምዳሜ ላይ

መድረስን እንደሚያካትት ግልጽ ነው፡፡ የህጉ አንቀጽ 341 ድንጋጌ አፈፃፀም ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ ሊፈጠር የሚችለዉን ስህተት ለማሳረም ይግባኝ የማቅረብ መብትን ከማስፋት አንፃር ታይቶ ተፈፃሚነት ሊኖረዉ ይገባል፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታይ የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳዉ ፍርድ ቤት ክሱን በይርጋ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉን ዉሳኔ ማረሙ ተገቢ ሆኖ ግን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ የግራ ቀኝን ክርክር ከቀረቡት የተለያዩ ማስረጃዎች አንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ ማስረጃም ካለ እንዲቀርብ በማድረግ መርምሮ እና መዝኖ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341(1) መሰረት መመለስ ሲገባዉ ይህን ባለማድረግ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ የዚህን ድንጋጌ ትክክለኛ አፈፃፀም መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የሆሮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19041 በቀን 01/10/09 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 21964 በቀን 14/05/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 283705 በቀን 28/09/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ተሽረዋል፡፡
2. የሆሮ ወረዳ ፍርድ ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ተጠሪ የያዘዉ ከአመልካች አባት እንዲሁም ከአመልካች በአደራ ነዉ ወይስ ከባንክ ገዝቶ ነዉ የሚለዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ ማስረጃም ጭምር በማስቀረብ ከመረመረ በኋላ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/አ

የሰ/መ/ቁ.161736

ግንቦት29 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች-፡ተክሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ፀሐይ መንክር

አመልካች - አቶ ተጫነ ካሳ

ተጠሪዎች - 1ኛ. አቶ ባህረ ሀፍቱ
2ኛ. አቶ ሀጎስ ሀፍቱ
3ኛ. አቶ ወርቁ አዲሱ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ አቤቱታ ማሻሻልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን አመልካች በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ በትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሑመራ ምድብ ችሎት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶች መዝገብ ግልባጭ እንደሚያሳየው የአሁን አመልካች 3ኛ ተጠሪ ለሆኑት አቶ ወርቁ አዲሱ ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር በአንድ የውል ሰነድ ገንዘብ ስለሰጠኋቸው በ3ኛ ተከሳሽነት አካትቼ ክሱን አሻሽዬ ላቅርብ በማለት አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ክሱ እንዲሻሻል ፈቅዷል፡፡ ነገር ግን አመልካች በ28/03/2010 ዓ.ም የተሻሻለ ክስ ሲያቀርቡ በአጭር ስርዓት እንዲታይ ቀርቦ የነበረውን የብድር ክስ ምክንያት በመቀየር ያላግባብ የመበልፀግ ክስ አድርገው አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ አመልካች አሻሽለው ያቀረቡትን ክስ ባለመቀበል በቀደመው የክስ ምክንያት 3ኛ ተከሳሽን ጨምረው የተሻሻለውን ክስ እንዲያቀርቡ በ18/05/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቶ ቀጠሮ ለውጧል፡፡ ነገር ግን አመልካች ክሱን በማሻሻል አቅርቤያለሁ ከዚህ ውጪ ማሻሻል አልችልም፤ በቀደመው ክስ ክርክርም አልቀጥልም በማለታቸው ይህን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ በአመልካች ጉድለት ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ አልተፈፀመም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 199(2) መሰረት መዝገቡ እንዲዘጋ ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን በመቃወም ቅሬታቸውን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች ክሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ በምክንያትነት የጠቀሱት ተከራካሪ ወገንን ጨምሮ ለማቅረብ መሆኑንና በዚህም መነሻ ከተፈቀደ በኋላ አመልካች በከሰሱበት ጉዳይ ከህግ የመነጨ መብት ያላቸው መሆኑን ለማሳየት ይረዳ ዘንድ በክስ ምክንያታቸው ላይ ለውጥ አድርገው ማቅረባቸው ሲታወቅ በሃገራችን የሙግት አመራር ስርዓት ፍርድ ቤቶች በእራሳቸው አነሳሽነት ከሚጫወቱት ሚና እና ፍትህ ከማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት አንጻር ታይቶ ጉዳዩ ሊስተናገድ ይገባል? ወይስ አስቀድሞ በተያዘው አቅጣጫ መሰረት አመልካች ፈጽመው ሊቀርቡ አልቻሉም በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 199(2) መሰረት ጉዳዩ በጅምሩ ሊቋጭ ይገባል? የሚለውን ለይቶ ለመወሰን እንዲቻል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ግራቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ቅሬታ ከቀረበበት ብይን እና ተገቢነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች ጉድለት ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ አልተፈፀመም በማለት መዝገቡ እንዲዘጋ ብይን የሰጠው አስቀድሞ የቀረበው የብድር ክስ ምክንያት ሳይለወጥ 3ኛ ተከሳሽን ጨምረው የተሻሻለውን ክስ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች በራሴ አሻሽዬ ካቀረብኩት ውጪ ክሱን ማሻሻል አልችልም በቀደመው ክስም ክርክሩን አልቀጥልም በማለታቸው ነው፡፡ የዚህን ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚሻውም የሥር ፍርድ ቤት የተሻሻለውን ክስ ውድቅ ለማድረግ የሕግ መሠረት ነበረው? መዝገቡ መዘጋቱስ በአግባቡ ነው? አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡

ክሱ እንዲሻሻል በስር ፍርድ ቤት የተፈቀደበት ምክንያት 3ኛ ተጠሪ የሆኑት አቶ ወርቁ አዲሱ ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር በአንድ የውል ሰነድ ገንዘብ ስለሰጠኋቸው በ3ኛ ተከሳሽነት አካትቼ ላቅርብ በማለት አመልካች አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ስለተቀበለው መሆኑ በብይኑ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህን ተከትሎ አመልካች ባቀረቡት የተሻሻለ አቤቱታ ግን የብድሩን ክስ ወደ ያላግባብ የመበልፀግ ክስ ቀይረው አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ በቀደመው የክስ ምክንያት ተከሳሽ ጨምረው የተሻሻለውን ክስ እንዲያቀርቡ ቢያዝም ከዚህ ውጪ ማሻሻል እንደማይችሉ ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም የክስ አቤቱታ ሲሻሻል ዳኝነት የተጠየቀበት የክሱ ምክንያት መለወጥ የሚቻል መሆን አለመሆኑን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91(1) እንደተደነገገው ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ተገቢ ሆኖ ካገኘው ተከራካሪዎቹ ወገኖች ክሳቸውን እንዲያሻሽሉና ክርክራቸውን እንዲለውጡ ሊፈቅድላቸው ይችላል፡፡ ስለሆነም የዚህ አይነት መብት ለተከራካሪዎቹ ወገኖች የሚሰጠው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራው ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ሆኖ በተገመተ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

የእንግሊዘኛው ቅጅ፡-

"The court may at any time before judgment allow either party to alter or amend his pleading ..... and all such amendments shall be made as may be necessary for the purpose of determining the real questions in dispute" **በማለት ይደነግጋል፡፡**

ከድንጋጌው መገንዘብ እንደሚቻለው ተከራካሪው ክሱን ለማሻሻል ወይም ክርክሩን ለመለወጥ የሚችለው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ክስ የቀረበበትን ጉዳይ ይበልጥ ግልጽ የሚያደርገው እንዲሁም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑ በፍርድ ቤቱ ሲታመንበት ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ የሚፈቀድበት መሰረታዊ ማጠንጠኛ በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ክርክር ለመወሰን አስፈላጊ የሚሆን (for the purpose of determining the real questions in dispute) *መሆኑ* **ነው፡፡**

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በቀደመው ክሳቸው ዳኝነት የጠየቁት የብድር ገንዘብ እንዲመለስላቸው ሲሆን ክሱን ለማሻሻል በምክንያትነት የጠቀሱትም 3ኛ ተጠሪ የሆኑት አቶ ወርቁ አዲሱ ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር በአንድ የውል ሰነድ ገንዘብ ስለወሰዱ በ3ኛ ተከሳሽነት ተካተው እንዲቀርቡ ለማድረግ ነው፡፡ ብድሩ ከተካደ በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪ የሚሆነው ጉዳይ (the real questions in dispute) **ብድር አለ? ወይስ የለም? የሚለው ነው፡፡ ስለሆነም የክሱ *መሻሻል* ወይም የክርክሩ *መለወጥ* ይህን (የብድሩን ጉዳይ) ይበልጥ የሚያብራራው ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ሊሆን ይገባል፡፡ ነገር ግን አመልካች አሻሽለው ባቀረቡት ክስ የብድር ክስ ምክንያቱን በመቀየር ያላግባብ የመበልፀግ ክስ አድርገው አቅርበዋል፡፡ ይህ ደግሞ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራው ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ነው የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡**

በመሆኑም በሃገራችን የሙግት አመራር ስርዓት አቤቱታ የሚሻሻለው ጉዳዩን ይበልጥ ለማብራራት ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሲሆን አመልካች የብድሩን የክስ ምክንያት ቀይረው ያላግባብ በመበልፀግ ክስ ለመሚገት መቅረባቸው በሥነ ስርዓት ህጉ የተዘረጋውን የማሻሻያ ሥርዓት የተከተለ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የተሻሻለውን ክስ አለመቀበሉ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ክሱን እንዲያሻሽል የተፈቀደለት ወገን ይህንኑ ካላቀረበ ክሱን የማሻሻል ወይም ሙግቱን የመለወጥ መብቱ እንደሚቀርና የዚህም ውጤት በቀደመው ክስ ክርክሩን መቀጠል መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91(2) **ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክሱን በህጉ አግባብ ብቻ እንዲያሻሽሉ ተጠይቀው አሻሽለው ካቀረቡት ውጪ ማሻሻል እንደማይችሉና አስቀድመው ባቀረቡት ክስ ክርክሩን ለመቀጠል እንደማይፈልጉ መግለፃቸውን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ በአመልካች ጉድለት መዝገቡን**

መዝጋቱ በሥነ ሥርዓቱ አግባብ ጉዳዩን መምራቱን ከሚያሳይ በቀር የህግ ስህተት ፈጽሟል የሚያሰኘው አይደለም፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱ የጠቀሰው ሌላው ምክንያት ፍርድ ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት የሚጫወቱት ሚና እና ፍትህ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በራሳቸው አነሳሽነት የሚጫወቱት ሚና ሊተገበር የሚችለው በሥነ ሥርዓት ህጉ አግባብ ሲሆን በህጉ በግልጽ ያልተደነገገ ሲሆን ተፈጥሯዊ የሆኑትን መርሆች (Principles of Natural Justice) መከተልም ተገቢ ነው፡፡ የዳኞች ክርክር የመምራት ሚና በሥነ ሥርዓት ህጉና ተፈጥሯዊ የሆኑ መርሆችን በመከተል የተወሰነ በመሆኑ ጉዳዩን በዚህ ስርዓት መምራት ፍትህ የማግኘት መብትን የሚያረጋግጥ ነው ከሚባል በቀር መብቱን የሚጥስ ነው የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡

በአጠቃላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በህጉ አግባብ በመምራት ብይን የሰጠ በመሆኑና የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህን መቀበላቸው የሚነቀፍ ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል የምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሑመራ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 14280 በ22/05/2010 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 104354 በ17/08/2010 ዓ.ም እና የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 107559 በ25/10/2010 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ለተካሄደው ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የልዩነት ሀሳብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር ሶስት እና አምስት ላይ የተጠቀስን ዳኞች በዚህ ጉዳይ የአብላጫ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በሚከተለዉ ምክንያት ተለይተን የልዩነት ሀሳብ አስቀምጠናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን አመልካች (የሥር ከሳሽ) መጀመሪያ ባቀረበዉ ክስ የብድር ዉል መሰረት በማድረግ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች (የሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች) ገንዘብ እንዲከፍሉት ዳኝነት መጠየቃቸዉን ነዉ፡፡ ነገር ግን የአሁን አመልካች ክስ ለማሻሻል ባቀረበዉ ጥያቄ የአሁን 3ኛ ተጠሪ (የሥር 3ኛ ተከሳሽ) ይህን ገንዘብ ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት በመግለጽ እሱን አካትቶ ክሳቸዉን አሻሽለዉ ለማቅረብ ጠይቋል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም የአሁን አመልካች ክሳቸዉን ለማሻሻል ያቀረቡትን ጥያቄ በመቀበል የተሻሻለዉን ክስ እንዲያቀርቡ

በ18/5/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ትዕዛዝ ፈቅዶለት ነበር፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ የአሁን አመልካች የተሻሻለዉን ክስ ባቀረበ ጊዜ የተሻሻለዉ ክስ ከቀደመዉ ክስ ጋር አንድ ስላልሆነ ተቀባይነት የለዉም በማለት አመልካች ከፈለገ በቀደመዉ ክስ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሲሰጥ፣ አመልካቹ በቀደመዉ ክስ መቀጠል እንደማይፈልግ በመግለጹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.199 (1) መሰረት መዝገቡን መዝጋቱን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ችሎት የአብላጫ ድምጽ በበኩሉ አመልካች አሻሽሎ ያቀረበዉ ክስ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 (1) መሰረት ተቀባይነት የለዉም በማለት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

እኛ ይህን ጉዳይ እንደመረመርነዉ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የብድር ዉል መሰረት በማድረግ ገንዘብ እንዲከፈለዉ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ ያቀረበዉን ክስ አሻሽለዉ የአሁን 3ኛ ተጠሪን አካትተዉ ገንዘቡን ተጠሪዎች እንዲከፍሉት ለመጠየቅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 (1) መሰረት ያቀረበዉን ጥያቄ ተቀብሎ አመልካች የተሻሻለዉን ክስ እንዲያቀርብ ፈቅዶለታል፡፡ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ትዕዛዝ አመልካች ክሱን አሻሽሎ 3ኛ ተጠሪን አካትተዉ ገንዘብ እንዲከፈለዉ መጠየቅ እንደሚችል ከፈቀደ በኋላ ተሻሽሎ የቀረበዉ ክስ የክስ ምክንያት ከቀደመዉ ክስ ጋር አንድ ስላልሆነ ተቀባይነት የለዉም የሚልበት እና አንድ ጊዜ የፈቀደዉን መልሶ ትዕዛዙን በማንሳት የሚከለክልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የተሻሻለዉን ክስ ማቅረብ እንደሚችል ከፈቀደለበት በኋላ በራሱ ተነሳሽነት ይህን ትዕዛዝ በማንሳት የተሻሻለዉን ክስ አልቀበልም በማለት የራሱን ትዕዛዝ ከሕግ ዉጭ መልሶ የሚሽርበት የሕግ አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ክሱን ለማሻሻል ያቀረበዉን ምክንያት ተቀብሎ መጀመሪያ ያቀረበዉን ክስ እንዲተዉ እና የተሻሻለ ክስ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ተሻሽሎ የቀረበዉን ክስ ባለመቀበል አመልካች ከፈለገ በመጀመሪያዉ ክስ እንዲቀጥል የሚያደርግበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

እንደሚታወቀዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 (1) እንደሚደነግገዉ ‹‹ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸዉም ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ተገቢ ሆኖ ካገኘዉ ተከራካሪዎቹ ወገኖች ክሳቸዉን እንዲያሻሽሉና ክርክራቸዉን እንዲለዉጡ ሊፈቀድላቸዉ ይችላል፡፡ ስለሆነም የዚህ ዓይነት መብት ለተከራካሪዎቹ ወገኖች የሚሰጠዉ የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትሕን ለመስጠት የሚረዳ ሆኖ በተገመተ ጊዜ ብቻ ነዉ፡፡ ይህንንም በሚፈቅድበት ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየዉን ኪሳራ ለመወሰን ይችላል››፡፡ በማለት ይደነግጋል፡፡ አንድ ተከራካሪ ወገን ክስ ከቀረበ በኋላ ወሳኝ የዳኝነት ጥያቄ የቀረበት መሆኑን በሂደት የተገነዘበ እንደሆነ ክስ አሻሽሎ መብቱን መጠየቅ እንዲችል እድል የሚሰጥ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የክስ ማሻሻል የማይፈቀድበት ሁኔታ አንዱ የክስ ማሻሻል ጥያቄዉ የክርክሩን ጭብጥ ለመወሰን ምንም የማይጠቅም እንደሆነ ብቻ ነዉ፡፡ የዚህ ድንጋጌ እንግለዘኛዉ ቅጅ “The amendment of pleading shall not be allowed when the amendment is not necessary for the purpose of determining the real questions in dispute” የሚል ነዉ፡፡ ይህ ማለት ፍ/ቤት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳል ብሎ የሚገምት እንደሆነ ወይም የክርክሩን

መሰረታዊ ጭብጥ ወይም ጥያቄ ለመወሰን የሚያስችል እንደሆነ አቤቱታ ማሻሻል መፍቀድ እንዳለበት የሚያመለክት ነዉ፡፡ እንዲሁም ይህ ድንጋጌ በክስ ማመልከቻ ላይ በሚፈጠረዉ ስህተት የተከራካሪ ወገኖች መሰረታዊ መብቶች እንዳይጎዳ ሕጉ ሰፊ ማዕቀፍ እንደዘረጋ የሚያሳይ ነዉ፡፡ ፍ/ቤት ደግሞ በዚህ አግባብ ክስ እንዲሻሻል ሲያደርግ የሌላኛዉ ወገን መብት እንዳይጎዳ በቂ ነዉ ያለዉን ኪሳራ መወሰን እና ተሻሽሎ በቀረበዉ ክስ ላይ ተገቢ ክርክር እንዲያቀርብ እድል መስጠት አለበት፡፡ ከዚህ ዉጪ ግን አንድ ተከራካሪ ወገን ክሱን ለማሻሻል በቂ ምክንያት ያለዉ መሆኑን እየገለጸ፣ ሕጉም ደግሞ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ክስ ማሻሻል እንደሚቻል በግልጽ እያመለከተ፣ ይህን ድንጋጌ ከመጠን በላይ አጥብቦ በመተርጎም ክስ እንዳይሻሻል እና ተሻሽሎ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ የተከራካሪ ወገን ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት እና መሰረታዊ መብቱን ማሳጣት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡
በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች በዚህ ጉዳይ 3ኛ ተጠሪን ጨምሮ ተጠሪዎች ገንዘቡን እንዲከፍሉት ለመጠየቅ ክሱን ለማሻሻል ያቀረበዉ ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ከተፈቀደለት በኋላ የቀደመዉ ክስ አመልካች ገንዘብ እንዲከፈለዉ የጠየቀዉ የብድር ዉል መሰረት በማድረግ ሲሆን በተሻሻለዉ ክሰ ደግሞ ያለ አግባብ መበለጸግ መሰረት በማድረግ ስለጠየቀ፣ የተሻሻለዉ ክስ ከቀደመዉ ክስ ስለሚለይ ተቀባይነት የለዉም በማለት አመልካች ከፈለገ በቀደመዉ ክስ ክርክሩን እንዲቀጥል ሲጠየቅ፣ በመጀመሪያ ክስ ክርክሩን መቀጠል እንደማይፈልግ በመግለጹ ክሱን ዉድቅ ማድረጉን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ ጉዳይ የክርክሩ መሰረታዊ ጭብጥ የአሁን አመልካች ከተጠሪዎች አለኝ የሚለዉን ገንዘብ የሚያስመልስበት አግባብ ነዉ፡፡ አመልካች መጀመሪያ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ ክስ ሲያቀርብ የብድር ዉል እንደሆነ የጠቀሰ ቢሆንም 3ኛ ተጠሪን ወደ ክሱ በሚጨምርበት ጊዜ ደግሞ ያለ አግባብ መበልጸግ መሰረት በማድረግ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ስለዚህ አመልካች ከተጠሪዎች ሊከፍሉኝ ይገባል የሚለዉን ገንዘብ መኖሩን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የማረጋገጥ ኃላፊነት የእሱ ቢሆንም ይህን መብቱን ለመጠየቅ ግን መጀመሪያ ባቀረበዉ ክስ ላይ የተፈጠረዉን ስህተት በማረም በተሻሻለዉ ክስ ‹‹ያለ አግባብ መበልጸግ›› መሰረት በማድረግ መጠየቁ እና ተጠሪዎች ደግሞ በዚህ በተሻሻለዉ ክስ ተገቢዉን ክርክር የማቅረብ እና ክርክሩ ለዘገየበት ተገቢ የሆነ ኪሳራ የሚከፈላቸዉ ከተደረገ መብታቸዉ የሚጎዳበት አግባብ አይኖርም ማለት ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ገንዘብ ተጠሪዎች እንዲከፍሉት ለመጠየቅ በሚያስችለዉ አግባብ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ ማድረግ ማለት ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ወይም የክርክሩን ወሳኝ ጥያቄ ወይም ጭብጥ ለመወሰን የሚያስችል ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 (1) ሥር የተመለከተዉን መስፈርት የሚያሟላ ሆኖ እናገኛለን፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የተሻሻለዉን ክስ ተቀብሎ ተጠሪዎች ተገቢ ክርክራቸዉን እንዲያቀርቡና ተገቢ ኪሳራ እንዲከፈላቸዉ በማድረግ ግራ ቀኞቸዉን በሕጉ አግባብ የማከራከርና የመሰማት መብታቸዉን በማረጋገጥ አጣርቶ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ መስጠት ይገባቸዉ ነበር፡፡ ነገር ግን የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ በዚህ አግባብ በማየት አመልካች ያቀረበዉን የተሻሻለዉን ክስ ተቀብሎ ግራ ቀኞቸዉን አከራክሮ ጉዳዩን አጣርቶ

መወሰን ሲገባቸዉ ዉድቅ በማድረግ መዝገቡን መዘጋታቸዉ፣ አመልካች በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 መሰረት ፍትሕ የማግኘት መብቱን እና መሰረታዊ መብቱን የሚነፍግ እንዲሁም ከፍ ሲል የተጠቀሰዉን የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌን የሚጥስ ነዉ፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሮ የአሁን አመልካች ያቀረበዉ የተሻሻለዉ ክስ በመቀበል ለተጠሪዎች ተገቢ ኪሳራ ተቆርጦላቸዉና ክርክራቸዉን እንዲያቀርቡ በማድረግ ጉዳዩ ተጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ለሥር ፍ/ቤት መመለስ ነበረበት ብለን የአብላጫ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በመለየት የልዩነት ሀሳባችን አስቀምጠናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሳ/ፀ

የሰ/መ/ቁ. 173416

ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች ፡ 1ኛ አቶ ዮሐንስ ዘውዴ አበራ

2ኛ ወ/ሮ አህላም መሐመድ አብዱልአዚዝ

3ኛ አቶ አራዶም መብራቱ ወልዱ

4ኛ አሕላም ትራዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ጠ. ገ/እግዚአብሄር ኪዳኔ-ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡ ወ/ሮ ተናኜ ማንያህልሀል ላቀው - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በተከሳሽ ከሳሽነት የቀረበ ክርክርን ይመለከታል፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቾች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ተጠሪ ሰኔ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የተሻሻለ ክስ ከሐምሌ 1 ቀን 2008 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ያልተከፈለ ውዝፍ የቤት ኪራይ ብር 480,000.00 (አራት መቶ ሰማንያ ሺ) ከ9% ወለድ ፣ ቤቱን እስኪያስረክቡ ድረስ የሚታሰብ ኪራይ እና መቀጮ ብር 10,000.00 (አስር ሺ) እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት የመከላከያ መልስ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ወለድን ጨምሮ ዳኝነት የተጠየቀበት ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ብር 512,400.00 (አምስት መቶ አስራ ሁለት ሺ አራት መቶ) ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት መቃወሚያቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የ1 ዓመት ወለድ በባለሞያ ተሰልቶ ውጤቱ እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን ወለዱ ብር 43,200.00 (አርባ ሶስት ሺ ሁለት መቶ) መሆኑን በማረጋገጥ መቀጮ እና ዋናውን ገንዘብ ጨምሮ ጠቅላላ ዳኝነቱ ብር 533,900.00(አምስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺ ዘጠኝ መቶ) ስለሆነ ጉዳዩን አይቶ

ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል። አመልካቾች በጉዳዩ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት በመሰረዙ በዚሕ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል።

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘት ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ብር 632,000.00 (ስድስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ) እንዲከፈላቸው በመሰረቱት ክስ መነሻነት አመልካቾች በተከሳሽ ከሳሽነት ብር 162,194.16 (አንድ መቶ ስልሳ ሁለት ሺ አንድ መቶ ዘጠና አራት ብር ከ16/100) እንዲወሰንልን ዳኝነት የጠየቅን ሲሆን ፍ/ቤቱ አመልካቾች ያነሳነውን መቃወሚያ በመቀበል ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በሚል ብይን ሲሰጥ ያቀረብነው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በዝምታ በመታለፉ ለችሎቱ አቤቱታ ያቀረብን ቢሆንም የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ይመልከተው በማለት በሰጠው ትዕዛዝ የተፈፀመውን የሕግ ስህተት በማረም የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ላይ አከራክሮ እንዲወስን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል።

ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን በዝምታ የማለፉን አግባብነት ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(3) አንፃር ለመመርመር ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ታዟል። ተጠሪም በመልሳቸው የአመልካቾች ዳኝነት በዝምታ የታለፈ እንጂ በድጋሜ የቀረበ ክስ ነው ተብሎ ውድቅ ባለመደረጉ የስር ፍ/ቤት ብይን ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል። አመልካቾች በመልስ መልሳቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንፃር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በስር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ ከቀረቡ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል።

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁበት የገንዘብ መጠን ከፍ/ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን በላይ በመሆኑ አመልካቾች ባቀረቡት መቃወሚያ መሰረት ፍ/ቤቱ መዝገቡን በብይን ዘግቶታል። እንዲሁም በስር በነበረው ክርክር አመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበው የነበረ መሆኑም ግራ ቀኙን አላከራከረም። የአመልካች ቅሬታ የስር ፍ/ቤት ያቀረቡትን መቃወሚያ ተቀብሎ የተጠሪን ክስ ቢሰርዘውም ያቀረብነውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በዝምታ ማለፉ እና አከራክሮ አለመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚል ነው። በመሰረቱ ፍ/ቤቶች በተከራካሪዎች የሚነሱ የክርክር ነጥቦች በአንድ ጭብጥ ተካተው ሊወሰኑ ከሚችሉት በቀር ክርክሮቹን በአግባቡ መርምሮ የቀረቡትን ጭብጦች በየራሳቸው መወሰን እና ተገቢውን ሀተታ በማስፈር የብይን ወይም የፍርዱ አካል ሊያደርጓቸው የሚገባ ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(3) ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል። አመልካቾች በተጠሪ ክስ ላይ ያቀረቡት መቃወሚያ እና በክሱ መነሻነት ያቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ እራሱን ችሎ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ክርክር ነው። በመሆኑም የስር ፍ/ቤት አመልካቾች ያቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት

ክስ ላይ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ ወይም ብይን አለመስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝንተነዋል፡፡

ሌላው በጉዳዩ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ነጥብ አመልካቾች በቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ የስር ፍ/ቤት አከራክሮ ሊወስን ይገባ ነበር በማለት የሚያነሱት መከራከሪያ ነው፡፡ በተከራካሪዎች ለዳኝነት በቀረበ ጉዳይ ላይ ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም በተከራካሪዎቹ በሚቀርብ መቃወሚያ መነሻነት የስረ ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑን ካረጋገጠ መዝገቡን የስረ ነገር ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ሊያስተላልፍ የሚገባ መሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 17(3) እና 91(5) መገንዘብ ይቻላል፡፡ መዝገቡ ስልጣን ወዳለው ፍ/ቤት መተላለፍ አለበት ከተባለ የተላለፈለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ከየት ጀምሮ መቀጠል አለበት የሚለውን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ስልጣን ወዳለው ፍ/ቤት በሚተላለፍ መዝገብ ውስጥ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ብቻ ተጠናቆ የክስ መሰማት ሂደቱ ካልተጀመረ መዝገብ የተላለፈለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ከቆመበት መቀጠሉ ችግር አይኖረውም፡፡ ነገር ግን ጉዳዩን ሲመለከተው የነበረው ፍ/ቤት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ያለው የጽሁፍ ክርክር ካበቃ በኃላ ከክስ መስማት ጀምሮ ያሉ የክርክር ሂደቶችን ካደረገ በኃላ ከሆነ ከክስ መስማት ጀምሮ የተደረጉት ሂደቶች ስልጣን በሌለው ፍ/ቤት የተደረጉ በመሆኑ ሂደቶቹ በተላለፈው መዝገብ ውስጥ ቢኖሩም መዝገቡ የተላለፈለት ፍ/ቤት ከክስ መስማት ጀምሮ ያሉትን የክርክር ሂደቶች እንዳልተደረጉ በመቁጠር እንደገና ሂደቱን ከክስ መስማት ጀምሮ መቀጠል አለበት፡፡

በዚህ መሰረት የፌደራል መ/ደ/ፍ ቤት ተጠሪዎች ክስ ሲያሻሽሉ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑን ሲያረጋግጥ እንዳለ መዝገቡን ስልጣን ወዳለው ፍ/ቤት እንዲተላለፍ ማድረግ ሲገባው ስልጣን የለኝም ካለ በኃላ መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የስነ ስርዓት ሕግ ግድፈት የተፈፀመበት ነው፡፡ የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት የስነ ስረዓት ህጉን ተከትሎ መዝገቡን እንዳለ ስልጣን ወዳለው ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያስተላልፍ ኖሮ የአመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አብሮ የሚተላለፍ በመሆኑ ለቅሬታ ምክንያት የሆነውም ጉዳይ በዚያው እልባት ማግኘት ይችል ነበር፡፡

አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ያቀረብነው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ ፍ/ቤቱ አከራክሮ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ በቀረበው ክስ ላይ የስረ ነገር ስልጣን ስለሌለው ከስነ ስርዓት ሕጉ ዋና አላማዎች መካከል አንዱ ክርክሮች በአነስተኛ ወጪ በአጭር ጊዜ እና በተፋጠነ ሁኔታ ተጠቃለው መፍትሔ እንዲያገኙ ማስቻል ሲሆን፤ ይህም ትክክለኛ ፍትህ ላይ ለመድረስ አስፈላጊ ስለሆነ በስረ ነገር ስልጣኑ ስር ያሉትን መርጦ የማየትና ከስረ ነገር ስልጣኑ በላይ የሆኑት ጉዳዮች ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይቅረብ በማለት ትዕዛዝ መስጠት አይችልም፡፡ ምክንያቱም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የቀረበ እንደሆነ የፍ/ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን የሚወሰነው ከተከራካሪዎቹ አንደኛው ወገን ያቀረበው ከፍተኛ የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 17(3) ተመላክቷል፡፡ በመሆኑም

የአመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ተጠሪ ካቀረቡት ክስ ጋር ተጠቃሎ ታይቶ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 43175 በቀን 27/09/2010 በዋለው ችሎት የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 223476 በቀን 21/05/2011 በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡትን ክስ አከራክሮ ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን ፀንቷል፡፡
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተጠሪ ክስ እና አመልካቾች ያቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተጠቃሎ ውሳኔ እንዲያገኝ የመዝገብ ቁጥሩ 43175 የሆነውን መዝገብ ስልጣን ላለው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ያስተላልፍ ብለናል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤቱም የቀረበውን ክስ እንዲሁም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መርምሮ ተገቢ የመሰለውን ይወስን፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

ት እ ዛ ዝ

ውሳኔው እንዲታተም ለጥናትና ህግ ስራ ክፍል ይተላለፍ፡፡

የውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ169716

ጥቅምት 24/2012 ዓም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ኃይሉ ነጋሽ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡-1. ወ/ሪት ሰላማዊት ይልማ (9 ሰዎች)

ተጠሪዎች፡-1. የኢትዮጵያ ቀይመስቀል ማህበር ቡታጅራ ቅርንጫፍ ነ/ፈጅ አቶ ሳመኑኤል ቀረቡ፡፡

2. የቡታጅራ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ዐ/ህግ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣንን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካቾች የቀረበለትን ክስ በተመለከተ የተጠሪዎችን መልስ ከሰማ በኋላ በመ/ቁ/10273 ላይ ታህሳስ 26/2010 በዋለው ችሎት "ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም" በማለት የሰጠው ብይን በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ይግባኝ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁጥር 09874 ላይ የካቲት 07/2010 ዓ.ም በመፅናቱ እና የክልሉ ሰበር ችሎትም በሰ/መ/ቁ/10581 ላይ ሚያዝያ 26/2010 በዋለው ችሎት "በጉዳይ ላይ የሰበር ስልጣን የለኝም" በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች ለቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ አውራሻቸው አቶ ይልማ ሳህሌ በህይወት እያሉ በቡታጂራ ከተማ ቀበሌ 04 ውስጥ በ1,275 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ የንግድ ድርጅት ቤት የነበራቸው መሆኑን፤ በወቅቱ ድርጅቱን ባጋጠመው መጠነኛ የስራ መቀዛቀዝ ድርጅቱ ታድሶ በአዲስ መልክ ስራ እስኪጀምር ድርስ በመዘጋቱ በጊዜው የነበሩት የቀበሌ ተመራጮች ያለአንዳች መመሪያ እና ትዕዛዝ እንዲሁም አዋጅ ከሚፈቅደው ውጭ ቤቱን ሰብረው ለወዛደሮች ቡና ቤት እንዲሰሩበት እንዳደረጉ፤ በዚሁ ምክንያት

አውራሻቸው ቤቱ ያለአግባብ የተወሰደባቸው መሆኑን ገልፀው እንዲመለስላቸው ለተለያዩ አካላት አቤቱታ ሲያቀርቡ የቆዩ መሆኑን፤ ንብረቱ የአውራሻቸው ስለመሆኑ እና ያለአግባብ የተወሰደባቸው መሆኑንም በሚመለከተው አካል ተጣርቶ የተረጋገጠ ቢሆንም የያዙ አካላት ቤቱን ለቀው ንብረቱን ለባለሃብቱ ማስረከብ ሲገባቸው የአሁን 1ኛ ተጠሪ በምን አግባብ እንደያዘ ባልታወቀበት ሁኔታ ቤቱን ይዞ ያለአግባብ እየተገለገለበት ያለ መሆኑን፤ ይህንኑ ገልፀው ቤቱን እንዲያስረክባቸው ቢጠይቁም ፈቃደኛ አለመሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገዶ ቤቱን እንዲያስረክባቸው እና ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በመያዙ የቀረባቸው ገቢ በወር በብር 1,000(አንድ ሺህ) ታስቦ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል።

የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ተገቢ ነው ያለውን የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ ቤቱን የተረከበው ከአሁን 2ኛ ተጠሪ መሆኑን ገልፆ በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ እንዲገባለት ጠይቋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪን በጣልቃገብነት የክርክሩ አካል አድርጎ መልስ ካሰጠ በኋላ ክርክር የተነሳበት ቤት በመንግስት እጅ ቆይቶ በአሁን 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 12/1999 ዓ.ም የተላለፈ መሆኑን፤ ከዚህ ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ ቤቱ በመንግስት ቁጥጥር ስር ሆኖ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠውም በጊዜያዊነት ለመሆኑ እንዳረጋገጠ፤ በመንግስት እጅ ባለ ቤት ወይም ይዞታ ላይ በመንግስት እና በግለሰቦች መካከል የሚነሳን ክርክር የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው በአዋጅ ቁጥር 110/1987 እና 572/2000 መሰረት የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤት አለመሆኑን ጠቅሶ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቷል።

በዚሁ ብይን ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 337 መሰረት ሰርዟል። አመልካቾች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱ ከተከራካሪ ወገኖች ውስጥ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ተቋም በመሆኑ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን እና የክልሉ ሰበር ችሎት የሰበር ስልጣን ያለው በክልል ጉዳይ ላይ ብቻ መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ የሰበር ስልጣን የለኝም ሲል መልሷል።

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ነው። አመልካቾች ጥር 22/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በዚህ ሰበር ችሎት ሊታረም ይገባል ያሉትን ነጥቦች ዘርዝረው አቅርበዋል። የአቤቱታው ፍሬ ቃልም ክርክር የተነሳበት ቤት የመንግስት ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ በሌለበት፤ በአዋጅ፣ በመመሪያ በቀላጤ አልያም በትዕዛዝ ስለመወረሱም የቀረቡት ማስረጃዎች በአግባቡ ሳይመረመሩ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ክርክሩ ከመንግስት ጋር በመሆኑ የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ማለቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/37281 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አኳያ አግባብ አይደለም፤ የክልሉ ሰበር ችሎትም ከአሁን 1ኛ ተጠሪ የቀረበለት ክርክር ሳይኖር 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል መንግስት

የተመዘገበ ተቋም በመሆኑ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ነው በሚል የሰበር ስልጣን የለኝም ማለቱ አግባብ አይደለም የሚል ነው።

በአመልካቾች የተጠየቀው ዳኝነት ያለአግባብ የተያዘብን ቤት ይለቀቅልን የሚል ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን የለንም ያሉበት አግባብ ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በሰበር አጣሪ ችሎት በመታዘዙ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ እንደቅደም ተከተላቸው ሰኔ 22 እና 21 ቀን 2011 ዓ.ም የተፃፈ አንድ አይነት ይዘት ያለው የተናጠል መልስ አቅርበዋል።

ፍሬ ቃሉም አመልካቾች በዚሁ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ/159230 ላይ የሰበር አቤቱታ አቅርበው ጊዜ ያለፈበት አቤቱታ ነው ተብሎ ውድቅ የተደረገባቸው በመሆኑ ድጋሚ አቤቱታ ሊያቀርቡ አይገባም፤ ክርክር የተነሳበት ቤት ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት እጅ(በአሁን 2ኛ ተጠሪ) የሚገኝ በመሆኑ እና እንደዚህ አይነት ክርክርን የማየት ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 110/1987 መሰረት ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የተሰጠ በመሆኑ እና ይኸው ሰበር ችሎትም በሰ/መ/ቁ/23608 እና 31682 ላይ ተመሳሳይ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ የስር መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የለም ማለታቸው ተገቢ ነው፤ የክልሉ ሰበር ችሎትም የስረ ነገር ስልጣንን በተመለከተ ከተከራካሪዎች የሚነሳን ጥያቄ ሳይጠብቅ አይቶ ስልጣን የለኝ ማለቱ የሚነቀፍ አይደለም የሚል ነው።

አመልካቾች ሐምሌ 19/2011 ዓ.ም በሰጡት የመልስ መልስ ቀደም ሲል ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ጊዜው ያለፈበት ነው ተብሎ ውድቅ ቢደረግም በውሳኔው ላይ ጊዜ ያለፈበት አቤቱታ ቀርቦ እንዲታይ መጠየቅ የሚቻል ስለመሆኑ በመገለፁ ይኸው መነሻ ተደርጎ ጊዜ ያለፈበት አቤቱታ ቀርቦ እንዲታይ ማስፈቀጃ ቀርቦ በሰ/መ/ቁ/168197 ላይ በተፈቀደው መሰረት ይህ መዝገብ ሊከፈት የቻለ መሆኑን በመግለፅ በተቀረው ቀደም ሲል የቀረበው የሰበር አቤቱታ በማጠናከር ተከራክረዋል።

በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

በመጀመሪያ አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታ ቀደም ሲል ቀርቦ ጊዜ ያለፈበት ነው ተብሎ ውድቅ ተደርጓል በሚል የቀረበውን መቃወሚያን አስመልክቶ በግራ ቀኙ የተጠቀሱትን መዛግብት ችሎቱ አስቀርቦ ተመልክቷል። በዚሁ መሰረት በእርግጥም አመልካቾች በዚህ መዝገብ ላይ ያቀረቡትን አቤቱታ ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ/159230 ላይ አቅርበው አቤቱታው ጊዜ ያለፈበት መሆኑ ተረጋግጦ በህጉ አግባብ ጊዜ ያለፈበት የሰበር አቤቱታ ቀርቦ እንዲታይ ከሚጠየቅ በቀር በቀረበው አግባብ ሊታይ አይገባም ተብሎ ውድቅ መደረጉን፤ በዚሁ ምክንያት አመልካቾች በሰ/መ/ቁ/168197 ላይ የማስፈቀጃ አቤቱታ አቅርበው ጥር 14/2011 ዓ.ም የተፈቀደ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። በመሆኑም በዚህ መዝገብ ላይ

የቀረበው አቤቱታ የህግ ሥረዓቱን ጠብቆ የቀረበ በመሆኑ ከዚህ አኳያ በተጠሪዎች የቀረበውም መከራከሪያ ችሎቱ አልተቀበለውም፡፡

ዋናውን ጉዳይ በተመለከተ በመሰረቱ በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 79(1) ይደነግጋል፡፡ የዳኝነት ስልጣን በመርህ ደረጃ የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ቢሆንም ተለይተው በታወቁ ጉዳዮች ላይ በልዩ ህግ የዳኝነት ሥልጣን ለሌላ አካል ሊሰጥ የሚችል ለመሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እናም ዳኝነትን በተመለከተ መሰረታዊ ስልጣኑ የመደበኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ዳኝነት በተጠየቁበት ጉዳይ ላይ የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ከማለታቸው በፊት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በልዩ ህግ ለሌላ አካል የተሰጠ ለመሆኑ በተገቢው መንገድ አጣርተው ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ ሳይጣራ ስልጣን የለኝምበሚል የሚወሰድ እርምጃ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 የተረጋገጠውን ፍትህን የማግኘት መሰረታዊ መብትን የሚጥስ በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የአመልካቾች ጥያቄ ክርክር የተነሳበት ቤት ከአዋጅ ውጭ በወቅቱ በነበሩ የቀበሌ ሹማምንት ትዕዛዝ ለወዛደሮች ተሰጥቶ የነበረ በመሆኑ እንዲመለስ በቀረበ አቤቱታ መነሻነት የቤቱ አያያዝ ህገ ወጥነት ቢረጋገጥም ሊመለስልን ሲገባ ለአሁን 1ኛ ተጠሪ የተላለፈ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ሊያስረክበን ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪዎች በቀረበለት መቃወሚያ መሰረት ክርክር የተነሳበት ቤት በመንግስት እጅ የነበረ እና ለአሁን 1ኛ ተጠሪ በጊዜያዊነት በመንግስት ተላልፎ የተሰጠ በመሆኑ ጉዳዩ የማየት የስረ ነገረ ስልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ብሏል፡፡ በእርግጥ ከአዋጅ ቁጥር 47/1967 ውጭ በመመሪያ፣ በቀላጤ ወይም በትዕዛት የተወሰዱ ንብረቶችን በሚመለከት የሚነሳ ክርክርን አይቶ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጄንሲ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 110/1987 አንቀፅ 4(1) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡

ሆኖም ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም ከማለቱ በፊት ክርክር የተነሳበት ቤት/ንብረት/ በተመለከተ የተነሳው ጥያቄ በትክክል በኤጀንሲ ሥልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ፤ ከሆነም በዚያ ረገድ የተደረገ ክርክር እና የተወሰደም አቋም ካለም ከግራ ቀኙ በሚቀርቡለት ክርክር እና ማስረጃ በተገቢው ሁኔታ ሊያጣራ ይገባል፡፡

ይህ ችሎም ይህንኑ መሰረት በማድረግ የክርክሩን አመጣጥ ከስረ መሰረቱ ፈትሿል፡፡ በዚሁ መሰረት ክርክር የተነሳበትን ቤት በተመለከተ የአሁን አመልካቾ ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ይልማ ሳህሌ ቤቱ እንዲመለስላችው በደርግ ዘመነ መንግስት ለሸዋ ክፍለ ሀገር ከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር አቤቱታ ያቀረቡ መሆኑን፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ጉዳዩን አጣርቶ እንዲያቀርብለት ለቡታጅራ ልዩ ከፍተኛ

ከነማ ጽ/ቤት ጥቅምት 14/1981 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱን፤ ጽ/ቤቱ ጉዳዩ በቀበሌ ፍርድ ሸንጎ እንዲጣራ ካደረገ በኋላ ሰኔ 24/1981 ዓ.ም ትዕዛዙ ለሰጠው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሰጠው ምላሽ ክርክር የተነሳበት ቤት የአመልካቾ አባት ዘግተው በመሄዳቸው ምንክያት ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ በቀበሌ የተያዘ ስለመሆኑ ማረጋገጡን ገልፆ መመሪያ እንዲሰጥበት መጠየቁ እና ከዚህ በኋላ የተሰጠ ውሳኔ አለመኖሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ይኸው ቤት እንዲመለስላቸው የአመልካቾች አባት ሐምሌ 29/1988 ዓ.ም የተፃፉ አቤቱታ ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ጥያቄ አቅርበው ኤጀንሲ መስከረም 12/1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቤቱ ከአዋጅ ውጭ በመመሪያ፣ በቀላጤ ለመወሰዱ ወይም በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አስፈፃሚ አካል ስለመፈቀዱ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ ኤጀንሲው ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በሚል ምክንያት መዝገቡን መዝጋቱን እና ይኸው ውሳኔ በይግባኝ በኤጀንሲ ስር ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶች ማስፈፀሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ ቀርቦ መስከረም 22/1999 ዓ.ም በምክንያት ተጠናክሮ የፀደቀ መሆኑን ከመዝገቡ ውስጥ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከጉዳዩ አመጣጥ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው ክርክር የተነሳበት ቤት ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት እጅ የነበረ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሰረት ለመወረሱ የቀረበ ክርክርም ሆነ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ እናም በአዋጅ ቁጥር 110/1987 መሰረት በዚህ መልኩ ከአዋጅ ውጭ በመመሪያ፣ በቃላጤ አልያም በቃል ትዕዛዝ የተወሰዱ እና በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉትን ንብረቶች በተመለከተ የሚነሳን ክርክር ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣኑ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን አጀንሲ ነው፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ ኤጀንሲው የዳኝነት ስልጣን የለኝም ብሎ የመለሰበት አግባብ ግልፅ አይደለም፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ “በልዩ ህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል የቀረበለትን የዳኝነት ጥያቄን አስመልክቶ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት ቢመለስ እና ተመሳሳይ የዳኝነት ጥያቄ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ቢቀርብ ውጤቱ ምን ይሆናል?” የሚለውን ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡ መርሆው ይህ ቢሆንም ይህንኑ ስልጣን ለፍርድ ቤቶች የሰጠው ህገ መንግስት በልዩ ሁኔታ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለሌላ አካል ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ እውቅና የሰጠ በመሆኑ ይኸው የህገ መንግስቱ ድንጋጌ በፍርድ ቤቶች በአግባቡ ሊከበር ይገባል፡፡ ሆኖም ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ አንድን ጉዳይ የማየት በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ጉዳዩን አላይም ብሎ ከመለሰ የዳኝነት ተፈጥሮአዊ ስልጣን የፍርድ ቤት በመሆኑ እና ፍትህ የማግኘት መብት በህገ መንግስቱ የተረጋገጠ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለሌላ የዳኝነት አካል ተሰጥቷል የሚል ክርክር እስካልቀረበ ድረስ መደበኛ ፍርድ ቤት በተመሳሳይ መልኩ ጉዳዩን ሊመልስ አይገባም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 37964 ላይ ጥር 27/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስልጣን ሥር የሚወድቅ አይደለም በሚል በኤጀንሲው የተረጋገጠ ጉዳይን በተመለከተ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለሌላ የዳኝነት አካል የተሰጠነው በሚል ክርክር እስካልቀረበ ድረስ ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆኑ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ የማየት የስር ነገር የዳኝነት ስልጣን በልዩ ህግ የተሰጠው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ጉዳዩ ከቀረበለት ከ10 ዓመት በኋላ በኤጀንሲ ሥልጣን ስር አይወድቅም ብሎ የመለሰ ለመሆኑ ማስረጃ ቀርቦ መዝገብ ውስጥ እያለ እና ስልጣኑ ለሌላ የዳኝነት አካል ተሰጥቷል በሚል በተከራካሪ ወገኖች የቀረበ ክርክር በሌለበት ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ማለቱ የቀረበውን ማስረጃ እና የፍርድ ቤቶችን ተፈጥሮአዊ ባህሪን ያላገናዘበ ነው፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ስህተቱን ከዚህ አኳያ አይቶ ማረም ሲገባው አቤቱታውን መሰረዙ የአመልካቾን ፍትህ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት የገፈፈ መሰረታዊ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም የክልሉ ሰበር ችሎት በቀረበው ጉዳይ ላይ የሰበር ስልጣን የለኝም ያለውን በተመለከተ በአመልካቾም እንደ አንድ የሰበር ቅሬታ የተነሳ በመሆኑ አንድ ነገር ማለቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት የዳኝነትት ስልጣን በፌዴራል እና በክልል የተከፈለ ሲሆን የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሰበር ስልጣን የተሰጣቸው በክልል ጉዳይ ላይ ብቻ ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 80(3(ለ)) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን በፌዴራል ጉዳዮች ላይ ስለመሆኑ እና ከዚህ ውስጥ አንዱ በፌደራል መንግስት የተመዘገቡ ተቋማት የክርክር ተካፋይ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ስለመሆኑን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 5(6) ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በህግ በክልሎች እስከሚቋቋሙ ድረስ የዳኝነት ስልጣናቸው እንደቅደም ተከተላቸው ለክልል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ መሆኑን የህገ መንግስቱ አንቀፅ 78(2) እና 80(4 እና 5) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳይ ላይ በይግባኝ አይቶ የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የሚቀርበው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስለመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁር 25/1988 አንቀፅ 10(3) ይደነግጋል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል መንግስት የተቋቋመ ድርጅት በመሆኑ ተቋሙ ተካፋይ የሚሆንበት የፍርድ ቤት ክርክር የፌዴራል ጉዳይ ይሆናል፡፡ በፌደራል ጉዳይ ላይ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ ከላይ በተጠቀሰው የህግ መንግስቱ እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት

የሰበር ስልጣን ያለው ይህ ችሎት ነው፡፡ የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣንን በተመለከተ ስልጣን ያለው መሆን ስላለመሆኑ የማረጋገጥ ቀዳሚ ኃላፊነት የፍርድ ቤቶች በመሆኑ የተከራካሪ ወገኖችን መቃወሚያ ወይም መከራከሪያ የሚጠብቅ አይደለም፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰበር ስልጣን የለኝም ማለቱ ህጉን በአግባቡ በመተርጎም ተግባራዊ ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ምክንያት ባለመኖሩ ከዚህ አንፃር የቀረበውን የአመልካቾችን መከራከሪያ ችሎቱ አልተቀበለውም፡፡

ሲጠቃለል ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የቡታጂራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/10273 ላይ ታህሳስ 26/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ/09874 ላይ የካቲት 07/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፀደቀው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካቾች ክስ ያቀረቡበትን ጉዳይ በተመለከተ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቢሆንም ኤጀንሲው በስልጣኔ ስር አይወድቅም በማለት የመለሰ በመሆኑ እና የዳኝነት ተፈጥሯአዊ ስልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስትም የተረጋገጠ በመሆኑ የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የማየት የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡

3. የቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቾች በቀረበለት ክስ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በመስማት የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት ተወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1.የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡

2.የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

3.መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

አ/ኃ

የሰ/መ/ቁ.162106

ጥር 30 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ተሻሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ /ዶ/ር/

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉ ወንድሙ ተወካይ ዘላለም አበበ

1ኛወ/ሮ ዘመኗ ድንቁ

2ኛ አቶ እንግዳሰው ክብረት } የሁሉም ተወካይ 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ፡፡

3ኛ አቶ ክብረት ባልቻ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

1. በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የእርቅ ውል ስለማስፈረስ የቀረበ ክስ የሚመለከት ክርክር ሲሆን የጀመረው በኦሮሚያ ክልል አሰላ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ በአመልካች እና ከ2ኛ-3ኛ በተጠቀሱ ተጠሪዎች በመዝገብ ቁጥር 01410 በ19/7/2010 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው ። የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ባጭሩ በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሣሽ የነበረ በዚህ መዝገብ 2ኛ ተጠሪ ሆኖ የተመዘገበው ባለቤታቸው መሆኑን ገልጸው፤ ባለቤታቸው ከወላጅ አባቱ በ500 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤትና ይዞታ በ26/9/1999 ዓ.ም በተደረገ የስጦታ ውል ያገኙት የጋራ ንብረት ያላቸው ሲሆን ፤ይኸው ቤት በማስያዝ ከባንክ ገንዘብ የተበደሩ መሆኑን ጠቅሰው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ውል ሰጪ አመልካች ደግሞ ውልተቀባይ በመሆን በ3/6/2008 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ውል የባልና ሚስት በሆነው ንብረት የተደረገ በመሆኑ የእርቅ ውል በሌላቸው መብት የተደረገ በመሆኑ እንዲፈርስ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

2. የሥር ተከሳሾች ያቀረቡት የመከላከያ መልስ እንደተመለከተው 2ኛ ተጠሪ የእርቅ ውል በጋራ ንብረት የተደረገ በመሆኑ ውሉ ቢፈርስ እንደማይቃወም ሲገልጽ 3ኛ ተጠሪም የእርቅ ውል ሌላ ሰው ንብረት የተደረገ እኔም ደካማ ሽማግሌ በመሆኔ ውል ስለመደረጉ አላውቅም ብሏል፡፡ የአሁኑ አመልካች በበኩላቸው የአሁን 1ኛ ተጠሪ የእርቅ ስምምነት እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉን፤ የስጦታ ውሉ እንደሚያውቁት፤ የሶስታ ውል መደረጉን ካወቁ በኃላ ክስ አቅርበው በአመልካች፤2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ3/6/2008 ዓ.ም በተደረገው የእርቅ ስምምነት 2ኛ ተጠሪ 100 ካሬ ሜትር ብቻ ወስዶ ሌላው መሬት እንዲለቅ መስማማታቸውን ገልጸው የእርቅ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት መከራከራቸውን መዝገቡ ያሳያል፡፡
3. በዚህ አግባብ ክርክሩ የቀረበለትን የአሰላ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የእርቅ ስምምነቱ የ1ኛ ተጠሪ መብትና ጥቅም የሚጎዳ በጋብቻ ንብረት ላይ የተደረገ ነው በማለት ስምምነቱን በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርደ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቤቱታ አቅርበው ተቀባይነት አላገኘም ፡፡ በመቀጠልም አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ የአመልካችን አቤቱታ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት በትዕዛዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 30/2010 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርበው የእርቅ ውሉ የሚፈርስበት አንዳችም ሕጋዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን ተደረገ የተባለው የስጦታ ውልም የጋራ ንብረት ባለተለየበት የተሰጠ በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካችአቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎትም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 253020 የተሰጠው ውሳኔ በፀናበት ሁኔታ በተመሳሳይ ጭብጥ ነገር ግን በሌላ መ/ቁ 289813 ውሳኔ የሰጠበት አግባብ ተጠሪዎች ባሉበት ጉዳዩን ማጣራት ይቻል ዘንድ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው በ14/02/2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበው የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲፃፍ አመልክተዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡
4. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡
5. እንደመረመርነውም አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በሕግ አግባብ የተደረገ በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም በሚል ነው፡፡ ከዚህ በተያያዘም የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ባቀረቡት የአፈፃፀም መዝገብ ጣልቃ ገብተው በየደረጃው ክርክር ሲደረግ ቆይቶ በመ/ቁ253020 በ20/10/2010 ዓ.ም የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ አዲስ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም የሚል ክርክርም ቀርቧል፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገቡ መረዳት የተቻለው አመልካች፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ03/06/2008 ዓ.ም የእርቅ ስምምነት

አድርጓል ለዚህ እርቅ ውል መነሻ የሆነው ጉዳይ የአሁኑን 3ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት የሆነውን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከአመልካች እውቅና ውጭ ሰጥቷል በማለት ስጦታው ለማስፈረስ በወረዳ ፍርድ ቤት ክስ በማቅረባቸው ነው፡፡አመልካች፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጉዳያቸው በእርቅ የቋጨ በመሆኑ የእርቅ ስምምነቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 277/1/ መሠረት ተመዝግቦ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ አመልካች በ03/06/2008 ዓ.ም በተደረገው የእርቅ ስምምነት መሠረት እንዲፈጸምላቸው የአፈፃፀም መዝገብ ከፍቷል፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ያቀረቡት አፈፃፀም መብትና ጥቅሜ የሚነካ ነው በማለት የክርክሩ ተከፋይ ሆናለች፡፡ ጉዳዩ መጀመሪያ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤት የእርቅ ስምምነቱ ፍርድ/ውሳኔ/ ስላልሆነ የአመልካች መቃወሚያ ተገቢነት የለውም በማለት ስምምነቱን በመሻር ቤቱ የ1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ነው በማለት የወሰነ ሲሆን አመልካች ይግባኝ ቢጠይቁም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

6. አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራቀኙ ከአከራከረ በኋላ በመዝገብ ቁጥር 3770 በሆነው ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 277/1/ የተመዘገበ የእርቅ ውል የአፈጻጸም ክስ ምክንያት መሆኑ እየታወቀ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የተዘጋው መዝገብ የእርሷን መብት የሚጎዳ ከሆነ በዛ መዝገብ የእርቅ ውል እንዲሻር ከመጠየቅ በቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 ያቀረበችው መቃወሚያ ማስተናገድ የክርክር አመራር ሥርዓት ያልተከተለ የአመልካች መብት የሚያሳጣ ነው በማለት ውሳኔውን ሽሮ 1ኛ ተጠሪ አለኝ የምትለውን ህጋዊ መብት ካለ ልትጠይቅ እንደምትችል በትዕዛዝ ክፍሉ አመላክቷል፡፡

7. በክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ያደረጉት የእርቅ ውል በፍርድ ቤት የተመዘገበ መሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 253020 በ20/01/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ግልባጭ አረጋጋጭ ነው፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የእርቅ ስምምነቱ ለማሰረዝ አዲስ ክስ ማቅረቧን መዝገቡ ያመላክታል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአፈፃፀም መዝገብ ጣልቃ መግባት ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሽሯል ፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በእርቅ ስምምነት የተዘጋው መዝገብ በመቃወም ያቀረቡት አቤቱታ ስለመኖሩ መዝገቡ አያሳይም፡፡ አመልካች፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ባደረጉት የእርቅ ስምምነት 2ኛ ተጠሪ 100 ካሬ ሜትር ብቻ ወስዶ ቀሪው 400 ካሬ ሜትር እንዲመልስ የተዋዋሉ መሆኑን ከቀረበው ክርክር ተገንዝበናል በመሠረቱ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በእርቅ መቋጨት እንደሚችሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 274 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ የእርቅ ስምምነቱ በፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 277/1/ መሠረት ተረጋግጣ ከተመዘገበ በእርቁ መሠረት እንዲፈጽም ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ላይ የተገለጸው ህግ 277/2/ በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የእርቅ ስምምነት የአፈፃፀም ክስ ሊቀርብበት የሚችል ህጋዊ ውጤት ያለው ተግባር መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ያደረጉት ስምምነት መነሻ

በማድረግ የተዘጋው መዝገብ ከሚያንቀሳቅሱ በቀር አዲስ ክስ ማቅረባቸውን በሕጉ የተዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት የተከተለ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አመልካች የእርቅ ስምምነት የፀደቀበት መዝገብ ላይ መቃወሚያ አቅርበው የስጦታ ውል ያለ መሆን አለመሆኑን አለ ከተባለም የጋራ ነው የተባለውን ንብረት 3ኛ ተጠሪ ብቻቸውን ሊሰጡ የሚችሉበት ህጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን ተመርምሮ ከሚወሰን በቀር የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ክስ አቅርበው በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶችም የክርክሩ ይዘትና ባሕሪ በአግባቡ ሳይገናዘቡ የእርቅ ስምምነቱ እንዲሻር መወሰናቸው በሕጉ የተዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት ያልተከተለ መሠረታዊ የህግ ስሕተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ አመልካች፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ3/6/2008 ዓ.ም ያደረጉት የእርቅ ስምምነት የፀደቀበት መዝገብ ከሚያንቀሳቅሱ በስተቀር አዲስ ክስ ማቅረብ የሚችሉበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በኦሮሚያ ክልል የአሰላ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 01410 በ14/06/2010 ዓ.ም፤ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 79705 በ29/08/2010 ዓ.ም ፤ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ስሚ ችሎት በመ/ቁ289813 በ03/11/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የእርቅ ስምምነት የፀደቀበት መዝገብ ባለበት ሁኔታ በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡
3. 1ኛ ተጠሪ የእርቅ ስምምነት የፀደቀበት መዝገብ የማንቀሳቀስ መብታቸው ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. የውሳኔ ግልባጭ ተረጋግጦ ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ ብለናል፡፡
6. ውሳኔው በ26/06/2011 ዓ.ም ተነበበ፡፡

መዝገቡ ዘግተን ወደ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

<u>የልዩነት ሃሳብ</u>

እኔ ስሜ በአራተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰዉ ዳኛ 1ኛ ተጠሪ የእርቅ ስምምነት በጸደቀበት መዝገብ ላይ የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ ከሚችችል በቀር አዲስ ክስ ማቅረብ አትችልም በሚለዉ በአብላጫዉ ድምዳሜ ስለማልስማማ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

1ኛ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በስር ፍርድ ቤት የጠየቁት ዳኝነት የአሁን 2ኛ ተጠሪ የባልና ሚስት የጋራ ንብረታቸዉ የሆነውን የቤት መስሪያ ቦታ ለአመልካች እና ለ3ኛ ተጠሪ በመስጠት ያደረጉት የእርቅ ስምምነት በፍርድ ኃይል እንዲፈርስ ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ ዳኝነት የተጠየቀበት ስምምነት በባህሪው በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3307 ስር በተመለከተዉ ድንጋጌ ስር የሚወቅድ ሲሆን፣ ይህ ድንጋጌም ተዋዋይ ወገኖች አንዱ ላንዱ አንድን ነገር ትቶ ወይም ሰጥቶ የተጀመረዉን ክርክር የሚያቆሙበት ወይም የሚፈጠረውን ክርክር አስቀድመው የሚያሰቀሩት አንድ ውል ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በህግ ተለይቶ ከተመለከቱት ሁኔታዎች በቀር ውሎች ተፈፃሚነታቸዉ ውሉን ባደረጉት ሰዎች ላይ ብቻ የተገደቡ ስለመሆናቸው በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1711፣ 1731 እና 1952(1) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም የተፈጠረዉን ወይም ሊፈጠር የሚችለውን ክርክር ለመጨረስ ግራ ቀኝ የሚያደርጓቸዉ ስምምነቶች የስምምነቱ አካል ያልሆነውን 3ኛ ወገን ሊያስገድድ የማይችል መሆኑን ያሳያል፡፡ የሦስተኛ ወገንን መብትና ጥቅም በሚነካ መልኩ የሚደረግ የእርቅ ስምምነትም ህገ ወጥ ነዉ፡፡ በመሆኑም በአመልካች፣ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል ተደርጎ በፍርድ ቤት የፀደቀው እና 1ኛ ተጠሪ ላቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ መሠረት ያደረጉት ስምምነቱን ካደረጉት ሰዎች አልፎ 1ኛ ተጠሪን ሊያስገድድ የሚችልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

አብላጫው ድምጽ 1ኛ ተጠሪ ስምምነቱ በጸደቀበት መዝገብ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ እንጂ አዲስ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው በፍርድ ቤት የጸደቀ ስምምነት እንደ ፍርድ ተቆጥሮ ሊፈጸም የሚችል መሆኑን ነዉ፡፡ በርግጥም ግልግል በተዋዋይ ወገኖች ይግባኝ ሳይኖረዉ መጨረሻ ሆኖ እንደተፈረደ ፍርድ እንደሚቆጠር በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3312 ስር የተመለከተ ሲሆን፤ በፍርድ ቤት የፀደቀ የእርቅ ስምምነት እንደ ፍርድ እንደሚቆጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 277(2) ስርም ተመልክቷል፡፡ ይሁንና እንደ ፍርድ ሆኖ አስገዳጅ የሚሆነው በተዋዋይ ወገኖች ላይ ብቻ ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡ በግራ ቀኝ ስምምነት ተደርጎበት በፍርድ ቤት በጸደቀ የእርቅ ስምምነት ላይ የተመለከተ ዉሳኔ ግራ ቀኝ ወደው እና ፈቅደዉ ያደረጉትን ስምምነት መሻሻ ያደረገ ውሳኔ እንጂ መደበኛ የሙግት ሂደትን ተከትሎ የህግ እና የፍሬ ነገር ክርክር ተደርጎበት በፍርድ ቤት ተለይቶ የተሰጠ ፍርድ/ውሳኔ ባለመሆኑ እንደ መደበኛ ፍርድ/ውሳኔ ሊታይ የሚገባውም አይደለም፡፡ በመሆኑም እንደ ፍርድ/ውሳኔ እንደሚቆጠር ከፍ ሲል በተመለከቱት ድንጋጌዎች የተመለከተው የእርቅ ስምምነቱን ያደረጉ ሰዎች ሊገደዱበት እንደሚገባ

እና በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በድጋሜ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት እንደሌለዉ ለማስገንዘብ ያህል እንጂ መደበኛውን የፍርድ ሂደት ተከትሎ በፍርድ ቤቱ በእራሱ እንደተሰጠ ፍርድ እንዲወሰድ ታስቦ ነው ለማለትም አይቻልም።

በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረታዊ ዓላማ እና አስፈላጊነት አንድ ክርክር በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 40፣ 41 እና 43 መሠረት ጣልቃ ለመግባት መብት ያለዉ ወገን በተለያየ ምክንያት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ መብቱን ለማስከበር ያልቻለ ወገን ውሳኔው ከተሰጠ በኋላም ቢሆን ወደ ክርክሩ ገብቶ መብቱን እንዲያስከብር ለማስቻል ነዉ። በዚህ መልኩ የቀረበ የመቃወም አቤቱታ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ክርክሩ የሚሰማው የመጀመሪያ ክርክር በተሰማበት ሥነ ሥርዓት መሠረት ስለመሆኑም የህጉ አንቀጽ 360 ድንጋጌ ያስገነዝባል። ከላይ እንደተገለጸው የእርቅ ስምምነትን በማጽደቅ የሚሰጥ ውሳኔ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸው የደረሱበትን ውሳኔ እንጂ ፍርድ ቤት በክርክር ሂደት አረጋግጦ የሚሰጥ ውሳኔ ባለመሆኑ መብት ያለዉ ወገን በክርክሩ ወቅት ከፍ ሲል በተመለከቱት የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት ጣልቃ ሊገባ ይችላል ተብሎ አይጠበቅም። በዚህ መልኩ ጣልቃ እንዲገባ የማይጠበቅበት ሰው ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ሊያቀርብ አይችልም።

ከዚህ ሁሉ የምንረዳው በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 358 እና ተከታዮቹ ስር ከመቃወም አቤቱታ አቀራረብ ጋር በተያያዘ የተደነገገው ድንጋጌ መደበኛ የክርክር ሂደትን ተከትሎ በፍርድ ቤት የተሰጠን ውሳኔ ታሳቢ በማድረግ የተቀረጸ መሆኑን ነዉ። ከዚህ አንፃር ሲታይ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች፣ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገ የእርቅ ስምምነት መብቱን ይነካል የሚሉ ከሆነ፣ የእርቅ ስምምነት በጸደቀበት መዝገብ ላይ የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልግ፣ አዲስ ክስ አቅርበዉ ስምምነቱ እንዲፈርስ ከመጠየቅ ሊከለከሉ የሚችሉበት የህግ ምክንያት የለም። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የ1ኛ ተጠሪን ክስ ተቀብለዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የእርቅ ስምምነት ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጡት በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚያስችል የህግ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ሊጸና ይገባል የሚል እምነት ስላለኝ ከሌሎች ባልደረቦቼ በሃሳብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት።

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 169522

ህዳር 29 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ሲራጅ አባፎጊ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡ 1. አቶ አባቦር አባጨብሳ

2. አቶ ነዚፍ አባጨብሳ

3. ወ/ሮ ሙራዴ አባጨብሳ

4. አቶ ኑሩ አባጨብሳ

5. አቶ መጫ አባጨብሳ

} የቀረበ የለውም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የገጠር መሬት ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/300663 ላይ ታህሳስ 15/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰቃ ወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ በአሁን አመልካች የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት ክርክር አያስቀርብም በማለት የሰጠው የመጨረሻ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ታህሳስ 03/2009 ዓ.ም ፅፈው በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ በሰቃ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ መግኛ ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ውስጥ

የተጠቀሰውን የገጠር መሬት ይዞታ ወላጅ እናታቸው ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ተጠቅመውበት ሲሞቱ ተላልፎላቸው እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ ግብር እየከፈሉበት እና የተለያዩ አትክልቶችን ተክለው አልምተው በመጠቀም ላይ እያሉ የአሁን 1ኛ ተጠሪ መስከረም 2009 ዓ.ም ወደ ይዞታው ገብተው በኃይል በመያዝ ቤት መስራት ሲጀምሩ ለቀበሌ አመልክተው የጀመሩትን ግንባታ እንዲያቆሙ ቢነገራቸውም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገደው የጀመሩትን ግንባታ አፍርሰው ይዞታውን እንዲያስረክቧቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ታህሳስ 12/2009 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ክርክር የተነሳበትን ይዞታ ለአሁን አመልካች እናት በኪራይ የሰጧቸው ከመሆኑ ውጭ ይዞታው የራሳቸው ለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያላቸው መሆኑን በመግለፅ ልለቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የካቲት 17/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ የጀመሩትን ግንባታ አፍርሰው መሬቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ በአሁን 1ኛ ተጠሪ ይግባኝ የቀረበለት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 343(1) መሰረት በነጥብ መልሷል፡፡ በዚሁ መነሻነት የወረዳው ፍርድ ቤት በታዘዘው መሰረት ጉዳዩን አጣርቶ ህዳር 28/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቀደመው ውሳኔ መሰረት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ ስላለው የክርክር ሂደት መዝገቡ የሚገልፀው ነገር ባይኖርም አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ጉዳዩ እስከዚህ ሰበር ችሎት ደርሶ የፀና መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በዚሁ መሰረት አመልካች የአፈፃፀም መዝገብ ከፍተው ጉዳዩ በሂደት ላይ እንዳለ የአሁን ከ2ኛ እስከ 5ኛ ተጠሪዎች በመቃወም አመልካችነት ይቀርባሉ፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም በመቃወም አቤቱታው ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ጥቅምት 28/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክር የተነሳበት ይዞታ በአቶ አባጨብሳ አባጎሹ ስም ግብር ሲገበርበት የነበረ ለመሆኑ እና በክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 5(5) መሰረት ለአሁን 1ኛ ተጠሪ እና ስር ፍርድ ቤት የመቃወም አመልካቾች የተላለፈ መሆኑን አረጋግጫለሁ በማለት ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ለአሁን ተጠሪዎች ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት ድረስ የፀና ለመሆኑ ከመዝገቡ ይዘት እንዲሁም የሰበር አጣሪ ችሎቱ አስቀርቦ ከመዝገብ ጋር ካያያዛቸው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔዎች ይዘት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥር 20/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል

ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የአሁን ከ2ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ተጠሪዎች በመቃወም አመልካችነት ባቀረቡት አቤቱታ ላይ መጋቢት 17/2010 ዓ.ም በሰጡት የፅሁፍ መልስ ያቀረቧቸውን አምስት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በመዘርዘር የወረዳው ፍርድ ቤት በመቃወሚያዎቹ ላይ ብይን ሳይሰጥ ያለፈ መሆኑን፤ ክርክር የተነሳበት ይዞታን በተመለከት በአስተዳደር ክፍል ተጣርቶ እንዲቀርብ የተሰጠው ትዕዛዝ እሳቸው በሌሉበት የአሁን ተጠሪዎች እና ሽማግሌዎች በተገኙበት ብቻ በአንድ ወገን በቀረበ ማስረጃ ላይ ተንተርሶ የቀረበ ከመሆኑም በላይ በዚሁ ማስረጃ ላይ ተገቢውን ክርክር ለማቅረብ እድል ያልተሰጣቸው መሆኑን፤ ማስረጃውም ስለዚሁ ክርክር ስለተነሳበት ይዞታ ቀደም ሲል ከአንዲም ሶስት ጊዜ ተጣርቶ ከቀረበው የአስተዳደር ክፍል ሪፖርት ጋር የሚቃረን መሆኑን፤ የወረዳው ፍርድ ቤት እነዚህን ሁኔታዎች አልፎ ውሳኔ መስጠቱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ሆነ የክልሉ ሰበር ችሎት ያለማረማቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ ቤት ሰርተው ሲጠቀሙበት የነበረ ለመሆኑ ከወረዳው መሬት አስተዳዳር የቀረበው ማስረጃ እየገለፀ የስር ፍርድ ቤት ይህንን ማስረጃ አልፎ መሬቱ አይገባቸውም በማለት የወሰነበት አግባብ ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሑፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ወኪላቸው በሆኑት 2ኛ ተጠሪ በኩል መጋቢት 24/2011 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች በስር ፍርድ ቤት አቅርቤ ብይን ሳይሰጥበት ታልፋል ብለው በዘረዘሯቸው መቃወሚያዎች ላይ ዝርዝር መልስ በመስጠት ክርክር የተነሳበት ይዞታ የቤተሰቦቻቸው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ሚያዝያ 25/2011 ዓ.ም በሰጡት የመልስ መልስ ተጠሪዎች በሰበር ማስቀረቢያ ነጥቡ ላይ የሰጡት መልስ ባለመኖሩ እንዳመኑ ተቆጥሮ በአቤቱታው መሰረት ሊወሰን ይገባል የሚል እና ቀድሞ ያቀረቡትን መከራከሪያ የሚያጠናክር ምክንያት በማከል ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በማስቀረቢያ ነጥቡ ሳይወሰን ከሰበር ቅሬታው አኳያ በስር ፍርድ ቤቶች የነበረውን የክርክር አመራር ፈትሿል፡፡

በዚሁ መሰረት የአሁን አመልካች በአሁን ከ2ኛ እስከ 5ኛ ባሉት ተጠሪዎች በቀረበ የመቃወም አቤቱታ ላይ መጋቢት 17/2010 ዓ.ም በሰጡት መልስ በዝርዝር አምስት፤ በይዘት

ደረጃ ደግሞ አራት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ማቅረባቸውን፤ እነዚህም 1ኛ/ የመቃወም አመልካቾቹ ከአሁን 1ኛ ተጠሪ ጋር በተለያየ ደረጃ ክርክር ሲደረግ ያውቁ የነበረ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/56795 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ቀድመው የሚያውቁን ክርክር ውጤት ጠብቀው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ ሊያቀርቡ አይችሉም፤ 2ኛ/ የመቃወም አመልካቾቹ ከአቤቱታቸው ጋር ያቀረቧቸው የግብር ካርኒዎች የእነርሱን ስም የማይጠራ በመሆኑ እና ወራሽ ለመሆናቸውም ያቀረቡት ማስረጃ ባለመኖሩ መቃወሚያ ባቀረቡበት ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም፤ 3ኛ/ የመቃወም አመልካቾቹ በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም አላቸው ቢባል እንኳን ክርክር የተነሳበትን ይዞታ ከ12 ዓመት በፊት ከእናቴ ተላልፎልኝ ይገር እየተገለገልኩበት ያለሁ በመሆኑ በክልሉ መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 32 መሰረት ጥያቄያቸው በይርጋ ይታገዳል፤ 4ኛ/ አመልካቾች ይዞታው በውርስ ተላልፎልናል የሚሉ ከሆነ ማንን እንደወረሱ እና አውራሻቸው መቼ እንደሞቱ በአቤቱታቸው ውስጥ አልጠቀሱም፤ ይህ መሆኑም አቤቱታው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 216 መሰረት ተሟልቶ ያልቀረበ እና አመልካች ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1000 አኳያ ማቅረብ የሚችለውን መከራከሪያ ያጣበበብኝ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል መሆኑን የሰበር አጣሪ ችሎቱ አስቀርቦ ከመዝገብ ካያያዘው ሰነድ ለመረዳት ተችሏል።

የቀረበው መቃወሚያ ይህ ሲሆን ጉዳዩን የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት የመቃወም አመልካቾች ዋናው ክርክር ሲካሄድ ያውቁ ነበር በማለት በቀረበው መቃወሚያ ላይ ብቻ ትዕዛዝ ሰጥቶ ስለ ሌሎቹ ምንም ሳይል ማለፉን ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ ለመገንዘብ ተችሏል።

አንድን ክርክር የሚሰማ ፍርድ ቤት በተከራካሪ ወገን በተለያየ የክርክር ደረጃ የሚቀርብለትን መከራከሪያ በተመለከተ ስለመቀበሉም ሆነ ስላለመቀበሉ ምክንያትን መሰረት ያደረገ ግልፅ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል። በተለይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በባህሪው ወደ ዋናው ክርክር መግባት ሳያስፈልግ የተጀመረውን ክርክር በመጀመሪያው የክርክር ምዕራፍ ላይ የማቋረጥ ውጤት ያለው በመሆኑ ጉዳዩን የሚያየው የዳኝነት አካል የቀረበውን መቃወሚያ ያልተቀበለበትን ግልፅ ምክንያት ሳያሰፍር ወደ ፍሬ ነገር ክርክር ሊሸጋገር እንደማይገባ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/244 እና 245 ደንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መረዳት ይቻላል። ይህ ሳይፈፀም በዝምታ ታልፎ በፍሬ ነገር ላይ አከራክሮ መወሰን ተከራካሪዎችን አስፈላጊ ላልሆነ እንግልት እና ወጪ የሚዳርግ ጉልህ የሆነ የጉዳይ አመራር እና የሥነ ሥርዓት ግድፈት በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም።

አሁን በቀረበው ጉዳይ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የወረዳው ፍርድ ቤት በአመልካች ከቀረበለት በርካታ መቃወሚያዎች ውስጥ በአንዱ ላይ ብቻ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሌሎቹን በዝምታ አልፎ በፍሬ ነገር ላይ ውሳኔ መስጠቱ እንዲሁም በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶችም ይህንን ስህተት ሳያርሙ ማለፋቸው መሰረታዊ የፍትሐብሔር ጉዳይ የሙግት አመራር ሥነ ሥርዓት ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ክርክር የተነሳበት ይዞታ በተመለከተ ተጣርቶ እንዲቀርብ በወረዳው ፍርድ ቤት በተለያየ ጊዜ በተሰጠ ትዕዛዝ መነሻነት የሰቃ ጮቆርሳ ወረዳ የገጠር መሬት አጠቃቀም ጽ/ቤት በቁጥር BUB/244/2010 ህዳር 19/2010 ዓ.ም በሰጠው መግለጫ የአሁን አመልካች እናት ከ30 ዓመት በፊት ይዘው ቤት ሰርተውበት ሲጠቀሙበት ቆይተው እሳቸው ሲሞቱ ወደ አመልካች የተላለፈ መሆኑን፣ አመልካችም አትክልት ተክለውበት የመንግስት ግብር እየገበረ ያለ እና ይዞታው በመንገድ ግንባታ ምክንያት በተነካ ጊዜም አመልካቹ ካሳ የተከፈለው መሆኑን የገለፀ ሲሆን ሰኔ 13/2010 ዓ.ም በሰጠው መልስ ደግሞ በይዞታው ላይ ላለፉ ሃምሳ ዓመታት ግብር ሲከፈል የነበረው በአቶ አባጨብሳ አባጎሽ ስም መሆኑን እና ክርክር በሚደረግበት ወቅትም ይዞታው በመቃወም አመልካቾች እጅ የነበረ ስለመሆኑ አጣርቶ ሪፖርት ማቅረቡን ለመረዳት ተችሏል፡፡

እነዚህ በወራት ልዩነት ከአንድ አስተዳደር መስሪያ ቤት የተሰጡ ማረጋገጫዎች በይዘት ፍፁም ተቃራኒ ሲሆኑ ጉዳዩን በያዘው ፍርድ ቤት በምን መልኩ እንዲህ ዓይነት ማረጋገጫ ሊሰጥ እንደቻለ እንኳን ለማጣራት የተወሰደ እርምጃ ስለመኖሩ መዝገቡ የሚገልፀው ነገር የለም፡፡

በመሰረቱ በፍርድ ቤት ከቀረበ ክርክር ጋር በተያያዘ ከአስተዳደር ክፍል የሚሰጥ መግለጫ እንደየአግባብነቱ ለፍርድ ቤቱ ከቀረቡት ሌሎች የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ጋር ተገናዝቦ የሚወሰድ እንጂ በራሱ የመጨረሻ ማስረጃ አይደለም፡፡ ከአስተዳደር ክፍል የሚሰጥ መግለጫ በራሱ የመጨረሻ ነው የሚባል ከሆነ በፍርድ ቤት ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ወሳኙ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት ሳይሆን አስተዳደር ክፍሉ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ በህገ መንግስት በዳኝነት ሊያልቁ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን የዳኝነት ስልጣን ለሌላ አካል አሳልፎ የመስጠት ውጤትን የሚያስከትል በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ከአስተዳደር ክፍል በሚቀርቡላቸው መግለጫዎች አቀባበል እና ምዘና ላይ ጥብቅ ጥንቃቄ ሊወስዱ ይገባል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የተስተዋለው ይኸው ከላይ የተጠቀሰው ስጋት ነው፡፡ መጀመሪያ ክርክር የተነሳበት ይዞታ የአሁን አመልካች ስለመሆኑ በምስክሮች አረጋግጫለሁ የሚል መግለጫ ሲቀረብ ለአመልካች ተወሰነ፡፡ በኋላ ላይ ደግሞ ይዞታው የመቃወም አመልካቾች አባት ለመሆኑ

አጣርቻለሁ ሲባል ለተጠሪዎች ተወሰነ፡፡ እናም ጉዳዩን በትክክል ለመግለፅ ፍርድ ቤቱ በአስተዳደር ክፍል የተወሰነውን ውሳኔ ተቀብሎ መዘገበ ከሚባል በቀር በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ውሳኔ ሰጥቷል ማለት አይቻልም፡፡

በፍርድ ቤት ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ የአስተዳደር ክፍል እገዛ ካስፈለገም ተጣርቶ እንዲቀርብ የሚሰጠው ትዕዛዝ ከሞላ ጎደል አስተዳዳር ክፍሉ ክርክር ከተነሳበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ በእጁ የሚገኙ ሰነዶች ላይ ብቻ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ ባለፈ አስተዳደር ክፍል በፍርድ ቤት በቀረበ ጉዳይ ላይ ምስክር ሰምቶ አልያም በቃለጉባኤ እያጣራ እንዲያቀርብ የሚሰጥ የውክልና ትዕዛዝ አግባብነት የለውም፡፡ አከራካሪው ነጥብ በምስክር የሚጣራ ከሆነ ምስክሮችን አስቀርቦ በሥ/ሥርዓት ህጉ መሰረት ምስክሮቹን ጠይቆና መርምሮ ማጥራት ያለበት ፍርድ ቤት እራሱ እንጂ ሌላ አካል አይደለም፡፡

እናም የስር የወረዳው ፍርድ ቤት አንድም በአስተዳደር ክፍሉ በምስክር እና ቃለ ጉባኤ ተጣርቶ የቀረበለትን መግለጫ ሙሉ በሙሉ ከመቀበሉም በላይ በተለያየ ጊዜ የቀረቡት መግለጫዎች ፍፁም ተቃራኒ በሆኑበት ሁኔታ ልዩነቱ እንዴት ሊፈጠር እንደቻለ በአግባቡ ሳያጣራ እና የቀረበለትን ሪፖርት ይዘት ከቀረቡት ሌሎች ማስረጃዎች ይዘት ጋር በተገቢው ሁኔታ ሳያገናዝብ አልፎ ከአስተዳደር ክፍል መግለጫ ጋር የሚለዋወጥ ውሳኔ መስጠቱ ህግን ያልተከተለ ብቻ ሳይሆን ፍትሕንም በእጅጉ የጎዳ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/300663 ላይ ታህሳስ 15/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰቃ ወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ያፀናበትን ትዕዛዝ በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሰቃ ሬሙቆርሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በአሁን አመልካች በአሁን ከ2ኛ እስከ 5ኛ ባሉት ተጠሪዎች የመቃወም አቤቱታ ላይ መጋቢት 17/2010 ዓም ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ተገቢውን ብይን እንዲሰጥ ተወስኗል፡፡

3. በውሳኔ ተራ ቁጥር ሁለት መሰረት በሚሰጥ ብይን የአሁን አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚታለፍ ቢሆን፡-

3.1 የወረዳው የገጠር መሬት አስተዳዳር ጽ/ቤት ክርክር ከተነሳበት ይዞታ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል ህዳር 19/2010 እና ሰኔ 13/2010 በሰጠው መግለጫ እርስ በራሱ የሚጋጭ መግለጫ የሰጠበትን ምክንያት በማጣራት፤

3.2 የወረዳው የገጠር መሬት አስተዳደር ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በተመለከተ የተደራጀ ማህደር በእጁ ካለ ከማህደሩ በመመርመር ነባር ይዞታነቱ የማን እንደሆነ፣ በይዞታው ላይ አግባብነት ያለው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማን ከመቼ ጀምሮ እንዳለው፤ ይህ ከሌለ በይዞታው ላይ ግብር በማን ስምና ከመቼ ጀምሮ እየተከፈለ እንዳለ በአግባቡ ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማዘዝ፤ እና

3.3. ከላይ በተመለከተው ሁኔታ ተጣርቶ የሚቀርብለትን ሪፖርት ቀድሞ በግራ ቀኙ ከተሰሙት ምስክሮች ቃል ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ተጨማሪ ምስክር በመስማት ወይም ማስረጃ በማስቀረብ ማስረጃዎቹን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ መርምሮ እና መዝኖ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 343(1) መሰረት መዝገቡ ይመለስለት፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ም

የሰ/መ/ቁጥር 169407

ቀን 29/9/2011 ዓ/ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች - በኬሚካል ኢንዳስትሪ ኮርፖሬሽን መገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ነገረ ፈጅ ወዳጄ ማሞ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ - አቶ ይትባረክ ተካ፡- ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ጥር 15 ቀን 2011 ዓ.ም በተሻሬ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 185419 ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤት በአመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ክርክር በ5/6/2010 ዓ/ም በቃል ክርክር በተያዘው ቀጠሮ ቀን ግራ ቀኙ ባለመቅረባችን መዝገቡ ተዘግቶ እያለና መዝገቡ ተከፍቶ ክርክር የቀጠለ መሆኑ ሳይነገረኝ በሌለሁበት የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ውሳኔው ተነስቶ ክርክር እንዳደርግ መወሰን ሲገባ አቤቱታዬን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ሲሆን ተከሳሽ የአሁን አመልካች ነው፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ላይ የአሁን ተጠሪ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች በሌለበት የሰጠውን ውሳኔ የአሁን አመልካች በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ ሲል በማመልከቱ ነው፡፡ መልስ ሰጪ የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው አቤቱታ በ5/6/2010 ዓ/ም ለቃል ክርክር ለያዘው

ቀጠሮ ግራ ቀኛችን ባለመቅረባችን መዝገቡ የተዘጋ ሲሆን ሳይነገረኝ በሌለሁበት የሰጠው ውሳኔ መብቴን የሚጎዳ በመሆኑ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ ሲል ጠይቋል። ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪም ለቃል ክርክር እንዲቀርብ የተላከለት መጥሪያ የደረሰው መሆኑን አልካደም። የአፈጻጸም ክስ ቀርቦበት ከፊጸመልኝ በኃላ በሌለሁበት የተሰጠብኝ ውሳኔ ይነሳልኝ ሲል ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል። የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 185419 ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ለመ/ሰጪ ለቃል ክርክር እንዲቀርብ መጥሪያ ደርሶት በቃል ክርክር ጊዜ ሁለቱም ባለመቅረባቸው መዝገቡ የተዘጋ ሲሆን ይግባኝ ባይ መዝገቡ እንዲከፈትለት ምክንያቱን ገልጾ መዝገቡ ተከፍቶለት ክርክሩ እንዲቀጥል ያስፈቀደ ሲሆን መ/ሰጪም ይህንኑ መፈጸም ነበረበት። መ/ሰጪ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጽም ክስ ቀርቦበት ለይግባኝ ባይ ከፈጸመ በኃላ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌውም ሲል አቤቱታ ውድቅ አድርጓል።

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል። መዝገቡም ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ጉዳይ በይግባኝ የተመለከተው የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች መጥሪያ ተልኮለት ሳይቀርብ የቀረ ቢሆንም የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ከይግባኝ ባይ ክርክር ጋር በመመርመር የወሰነ መሆን አለመሆኑን ከመሰረታዊ የክርክር አመራር ስነ ሥርዓት ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል። መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል። ተጠሪ መጋቢት 19 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል። አመልካችም ሚያዝያ 1 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲሆን፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል። እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ መብቴ ተጎድቷል ሊታረምልኝ ይገባል ሲል ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቧል። የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለግራ ቀኙ ክርክር እንዲያቀረቡ በተቀጠረበት ቀን ሁለቱም ባለመቅረባቸው መዝገቡ ተዘግቷል። የይግባኝ ቅሬታ የሚያቀርበው ሰው፣ የተወሰነበት ወገን ወይም ይግባኝ የሚባልበት ውሳኔ መብቱን ጎድቶታል የሚለው ወገን ሲሆን፣ በውሳኔው ተጠቃሚ የሆነው ወገን እንዲጸናለት የሚከራከር እንጂ ይግባኝ የሚጠይቅበት ሁኔታ አይኖርም። እንደዚሁም የይግባኝ መዝገብ የተዘጋ እንደሆነም መዝገቡ እንዲከፈትለት የሚጠይቀው ሰው፣ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መብቴን ጎድቶታልና መዝገቡ ተንቀሳቅሶ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይታረምልኝ የሚለው ወገን እንጂ በውሳኔ ተጠቃሚ የሆነው ወገን የተዘጋው መዝገብ እንዲከፈት የሚገደድበት አግባብ የለም። የተዘጋው መዝገብ ከተከፈተ በኋላ ሌላው ወገን መዝገቡ መንቀሳቀሱን አውቆ ቀርቦ እንዲከራከሩ ሊደረግ እንደሚገባ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ አንቀጽ 233 ድንጋጌ በተመሳሳይ ለይግባኝ ክርክር ጊዜም እንደነገሩ አግባብ መፈጸም አለበት። ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ የፈጸመ ተከራካሪ ወገን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ቅሬታ

ለማቅረብም ሆነ አቤቱታ ለማቅረብ የሚከለክለው የህግ ድንጋጌ የሌለና የትኛውንም ወገን የሚጎዳም አይደለም፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የህግ መሰረት በሌለው ምክንያት ግራ ቀኙ ለክርክር በተቀጠረው ቀን ባለመቅረባቸው ተዘግቶ የነበረው መዝገብ በይግባኝ ባዩ አመልካችነት ሲከፈት መ/ሲጨ እንዲያውቀው ሳይደረግ በሌለበት ውሳኔ መስጠቱ እና አመልካች በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለት ያቀረበውን አቤቱታ በቂ ባልሆነ ምክንያት ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 185419 ሚያዝያ 25 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአሁን አመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ያስቀርባል በተባለው ጭብጥ የአሁን አመልካች ክርክሩን እንዲያቀርብ በማድረግ ካከራከረ በኋላ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ166205

ቀን 29/09/2011ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች ፡- አቶ ገ/ኪየሱስ ሙሉነህ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- 1ኛ አቶ ወልዴ አቡቴ - አልቀረቡም፡፡

2ኛ ወ/ሮ አዳነች ዱላ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

<u>ፍርድ</u>

1. በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የቤት ክርክር የሚመለከት ሲሆን የጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የሆሳዕና ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር አመልካች ከሳሽ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፦ አንደኛ ተጠሪ የሀሰት ማስረጃ አቅርበው በ21/08/2006 ዓ/ም በተሠጠው ውሳኔ ከነበራቸው ይዞታ 48 ካ.ሜ ወስደዋል፡፡ ይሁንና 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት እና ለውሳኔ መሰረት የሆነው ማስረጃ የሐሰት መሆኑን በፍርድ ቤት ተረጋግጦ በወንጀል ተከሰው 4 ዓመት ከ5 ወር የተቀጡ በመሆኑ ፍርዱ ተሽሮ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን እንዲያስረክቧቸው እንዲሁም ካሣ ለመጠየቅም የመክሰስ መብት እንዲጠበቅላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
2. 1ኛ ተጠሪ ክሱ ፍርድ ባገኘው ጉዳይ በድጋሚ የቀረበ መሆኑን፣ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠው ፍርድ ከፍ/ህግ ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ ሲያመለክቱ፤2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ለክርክሩ መሰረት የሆነው ይዞታ ጨምሮ 500 ካ.ሜ ከ1ኛ ተጠሪ የገዙ በመሆኑ

ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ ጠይቀው ፍርድ ቤቱም አቤቱታው ተቀብሎ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ አሏል።

3. በዚህ መልኩ ክርክሩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ የገዙት በመሆኑ የአመልካች ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ ቅሬታ እና ሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሳረም ነው።
4. አመልካች በ23/03/2011 ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ እንዲሻር አመልክቷል። የአመልካች አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ያቀረበው ሲሆን ተጠሪዎች የበኩላቸውን መልስ በማቅረብ ውሳኔው እንዲጸና ጠይቀዋል። የመልስ መልስም ቀርቧል።
5. ከስር የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለው ሲሆን እኛም በየደረጃው ጉዳዩን የተመለከቱት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ፍርድ እና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ክርክሩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል።
6. እንደመረመርውም፦ ከመዝገቡ እንደተረዳነው የአመልካች መሰረታዊ የዳኝነት ጥያቄ በሐሰት ማስረጃ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ የሚጠይቅ ነው። የስር ፍርድ ቤት የተጠየቀው ዳኝነት ባሕሪ እና ይዘት ሳያገናዝብ ይዞታው 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛተጠሪ በግዢ ያገኙት በመሆኑ ሊለቁ አይገባም በማለት መወሰኑን ያሳያል። አመልካች በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክስ መገንዘብ የተቻለው 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ተከራክረው ለተሰጠው ፍርድ መሰረት የሆነው ማስረጃ ሀሰተኛ ሰነድ ላይ የተመሰረተ ነው የሚል ነው። የስር ፍርድ ቤት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ የቀረበ አቤቱታ መሆኑን ተገንዝቦ በዚሁ አግባብ ስላልቀረበ መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በመደበኛ (አዲስ) ክስ በማስተናገድ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም። የ2ኛ ተጠሪ የመብት ጥያቄም በውሳኔ ተዘጋ በተባለው መዝገብ ህጋዊ ውጤት ከሚታይ በስተቀር በዚህ መዝገብ ጣልቃ ገብ በመሆን የሚከራከሩበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም። በመሆኑም አመልካች የዳግም ዳኝነት ጥያቄው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ6 መሰረት አቅርበው ከሚስተናገዱ በስተቀር አዲስ ክስ በማቅረብ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቁበት የሕግ አግባብ አይኖርም። የስር ፍርድ ቤትም ክሱ ውድቅ ማድረግ ሲገባው የአመልካች ክስ ተቀብሎ እንደ አዲስ ክስ ማስተናገዱ፤ ይኸው ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች መጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት መፈጸሙን የሚያሳይ በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው። በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

ውሳኔ

1. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የሆሳዕና ከተማ የመጀመርያ ደረጃ በመ/ቁ 23099 በ20/04/2010 ዓ/ም፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ17695 በ18/5/2010 ዓ/ም፣ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ10056 በ09/1/2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጡት ፍርድ እና ትዕዛዝ ተሽሯል።
2. የአመልካች መሰረታዊ የዳኝነት ጥያቄ በዳግም ዳኝነት እንዲታይ የቀረበ ሁኖ ሳለ በአዲስ ክስ መስተናገዱ በሕጉ አግባብ አይደለም በማለት ወስነናል።
3. አመልካች ይሁን 2ኛ ተጠሪ በሌላ አግባብ መብታቸው ለማስከበር የሚያቀርቡት ክርክር ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል።
4. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል።
5. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይተላለፍ።

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ዮ/መ

የሰ/መ/ቁ.166617

ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡.... ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡..... . . አቶ ገ/መድህን መልከጻድቅ ፡- ጠበቃ አየለ ቦጋለ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡..... . . 1. አቶ ቀነኒ ዲባባ ፡- የቀረበ የለም፡፡

2. አቶ ዘሪሁን ሳምሶን ጌታቸዉ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣የአሁን አመልካች ተከሳሽ፣የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.212821 ህዳር 11 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪዎች) ባቀረቡት ክስ በከሳሾች እና በተከሳሽ መካከል ጥቅምት 3 ቀን 1980 ዓ.ም በተደረገ የወለድ አገድ ዉል በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 4 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 752 የሆነዉን የከሳሾችን ቤት ከተከሳሾች ብር 20,000 (ሀያ ሺህ) ተቀብለን ቤቱን አስረክበን የተበደርን ሲሆን የብድሩ ጥቅምት 3 ቀን 1990 ዓ.ም ልንከፍል ተስማምተን ብሩን ተቀብለን ቤቱን ያስረከብን ሲሆን፣ ተከሳሽ ገንዘቡን ወስዶ ቤቱን እንዲያስረክበን ብንጠይቀዉም ፈቃደኛ ስላልሆነ ገንዘቡን ተቀብለዉ፣ ቤቱን እንዲስረክበን፣ ቤቱን አከራይተን የሚናገኘዉን ጥቅም ብር 10,000 እንዲከፍለን በማለት ክሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ ጥቅምት 3 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ ከ17 ዓመት በኋላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነዉ፤ በዉሉ ላይ በተመለከተዉ መሰረት ከሳሾች ገንዘቡን በጊዜ ካልመለሱ ተከሳሽ ቤቱን ሸጠዉ ገንዘቡን መዉሰድ እንደሚችል ስለተስማማን በዚህ መሰረት ታህሳስ 5 ቀን 2007 ዓ.ም ለአቶ መላኩ ዮሐንስ የሸጥኩኝ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ ቤቱ ለከሳሾች ሊመለስ ይገባል የሚል ከሆነ ከሳሾች የወሰዱትን የብድር ገንዘብ ብር 20,000 (ሀያ ሺህ) ከጥቅምት 3 ቀን 1980 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በመ.ቁ.177014 በ18/8/2009 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት ከሳሾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ያለበት አግባብ ሕግን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የሥር ዉሳኔ ዉሳኔ ተሽሯል በማለት በዋና ጉዳይ አከራክሮ እንዲወሰን በማለት ለሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ድጋሚ በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ በከሳሾች እና በተከሳሾች መካከል ጥቅምት 3 ቀን 1980 ዓ.ም የተደረገዉ የወለድ አገድ ዉል ሕጋዊ ዉጤት የሌለዉ በመሆኑ ከሳሾች የተበደሩትን ብር 20,000 (ሀያ ሺህ) ለተከሳሽ በመክፈል ተከሳሽ ደግሞ የቤት ቁጥር 752 የሚታወቀዉን ለከሳሾች እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ በዚህ ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ዉሳኔ በመሻር ግራ ቀኞቸዉን በዋኛዉ ጉዳይ አከራክሮ እንዲወሰን በመለሰለት መሰረት ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞችንን በጉዳዩ ላይ አከራክሮ መወሰን ሲገባዉ ግራ ቀኞችንን ሳያከራክርና የቀረበዉን ማስረጃ ሳይመረምር የሰጠዉ ዉሳኔ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ (መመሪያ) እና የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች የጣሰ ስለሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት በዝርዝር ቅሬታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ፍርድ መሰረት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 ድንጋጌ አፈጻጸም ከመሰማት መሰረታዊ መብት አንጻር ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መጋቢት 16 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ ዉሳኔዉ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስ በተመለከተ የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ

በመቀበል ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት መወሰኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመር የሥር ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ክስ በይርጋ ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም በማለት በመሻር የሥር ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ ግራ ቀኞቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት የመለሰለት መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ አግባብ የተመለሰለትን ጉዳይ በመ.ቁ.228538 በ2/5/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ተጠሪዎች መዝገብ እንዲከፈትላቸዉ መጠየቃቸዉን በመግለጽ፣ ተጠሪዎች ለአመልካች መጥሪያ እንዲያደርሱ፣ መዝገቡን መርምሮ ለመስራት ለየካቲት 16 ቀን 2010 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት የካቲት 16 ቀን 2010 ዓ.ም ዉሳኔ መስጠቱን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበላይ ፍ/ቤት በሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት ግራ ቀኞቸዉን ሳያከራክር ዉሳኔ መስጠቱን ያመለክታል፡፡

እንደሚታወቀዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) እንደሚያመለክተዉ ‹‹ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ ወይም ዉሳኔ የሰጠዉ ፍርድ ቤት ነገሩን የወሰነዉ ክርክር ዉስጥ ሳይገባ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለትን መቃወሚያ ብቻ መሰረት በማድረግ ሲሆንና ይህ ፍርድ ወይም ዉሳኔ በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የተለወጠ እንደሆነ ክርክሩ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በማድረግ መታየት የሚገባቸዉን ነጥቦች ለይቶ እንደገና እንዲታይ ለማዘዝ ይችላል›› በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በይርጋ ዉድቅ ያደረገ ቢሆንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በማየት የሥር ዉሳኔ በመሻር ግራ ቀኞቸዉን በዋናዉ ጉዳይ አከራክሮ ዉሳኔ እንዲሰጥበት የመለሰ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ የህግ ድንጋጌ መሰረት ዉሳኔ የሰጠ መሆኑን እና ዉሳኔዉም ሕግን የተከተለ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት ዉሳኔ ለመስጠት በሕግ ስልጣን እስከተሰጠዉ እና በዚህ አግባብ የሥር ዉሳኔ በመሻር የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ድጋሚ እንዲያይ ነጥብ ለይቶ እስከመለሰ ድረስ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ዉሳኔ መሰረት የመፈጸም ኃላፊነት እንዳለበት የሚያከራክር አይሆንም፡፡ ይህ ማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበላይ ፍ/ቤት በሰጠዉ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ መሰረት ግራ ቀኞቸዉን አከራክሮ ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበላይ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ግራ ቀኞቸዉን ማከራከር እንዳለበት ነዉ፣ ይህም ግራ ቀኞቸዉ ክርክራቸዉን እንዲያሰሙ እና ዋና የክርክር የመስማት ሂደት መከናወን እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ ፍ/ቤቱ በዋናዉ የክርክር መስማት ሂደት ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.246-249 ድንጋጌዎች መሰረት ጭብጦችን መመስረት፣ ግራ ቀኞቸዉ ክሳቸዉን እና መልሳቸዉን ሲያቀርቡ የጠቀሱትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ ማድረግና መመርመር፣ ፍርድ እና ዉሳኔ የመስጠት ተግባራትን ይፈጽማል ማለት ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ

ስንመለስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ መነሻ በማድረግ መዝገቡ የተንቀሳቀሰ መሆኑን ለተከራካሪ ወገኖች በማሳወቅ ዉሳኔ መስጠቱን እንጂ በዚህ አግባብ ግራ ቀኞቸዉ ክርክራቸዉን እንዲያሰሙ እና ዋናዉን የክርክር መስማት ሂደት ያካሂደበት ሁኔታ የለም፡፡ ፍ/ቤቱ በዚህ አግባብ አለመፈጸሙ ደግሞ ከፍ ሲል በተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የበላይ ፍ/ቤት ከሰጠዉ ዉሳኔ የሚቃረን ስለሆነ የሕግ ድጋፍ የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበላይ ፍ/ቤት ማለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ግራ ቀኞቸዉን ሳያከራክር፣ ሳይሰማቸዉ፣ ጭብጥ ሳይመሰርት እና በማስረጃ ሳያጣራ ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀሪመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.228538 በ16/6/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.212821 ህዳር 11 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ መሰረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር፣ ጭብጥ በመያዝ፣ ጉዳዩን በማስረጃ በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. የመ.ቁ.228538 ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 167589

ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጽጌ ታደሰ - ጠበቃ ውቤ ጓዴ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-

1. ወ/ሮ አልማዝ ሳህሌ ወኪል ግርማ ታደሰ ቀረቡ፡፡
2. አቶ ሰይፉ ታደሰ
3. አቶ ግርማ ታደሰ - ቀረቡ፡፡
4. አቶ ደረጀ ታደሰ - ወኪል ግርማ ታደሰ ቀረቡ፡፡
5. አቶ ወንድወሰን ታደሰ
6. ወ/ሮ ዘውድነሽ ታደሰ } አልቀረቡም፡፡
7. አቶ አሳምነው ታደሰ
8. አቶ ብሩክ ታደሰ - ወኪል ግርማ ታደሰ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ከውርስ ድርሻ ክፍፍል ጥያቄ የተነሳውን የስረ ነገር ስልጣን ጉዳይ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ ከውርስ በጠቅላላ የተገመተ ሃብት ሊተላለፍላቸው የሚገባውን ድርሻቸው ብር 274,333.00 (ሁለት መቶ ሰባ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) መሆኑን በመለየት ተጠሪዎች እንዲያካፍሏቸው ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የዳኝነት ገንዘቡንም በዚሁ ገንዘብ መጠን በታሪፉ መሰረት ብር 5,593.33 ከፍለው ፋይሉን ከአስከፈቱ እና ለችሎቱ ከቀረበ በኋላ ችሎቱ ክሳቸውን መርምሮ ከሳሽ ባቀረቡት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ክፍያ የሚፈፀመው በውርሱ ቤት ወይም አክሲዮን ተገምቶ እና ተሸጦ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የክፍያ ውሳኔ የሚሰጠው በቴክኒካዊ መንገድ ለቤቱና ለአክሲዮኑ ስለሆነ ሊከፈል የሚገባው ዳኝነትም ሆነ ጉዳዩ ሊቀርብበት የሚገባው ፍርድ ቤት የሚወሰነው በንብረቱ ጠቅላላ ግምት በመመሰረት እና ሁሉንም ንብረት ለማካፈል ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንጂ ለፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ

ቤት ሊሆን እንደማይገባው ደምድሞ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 231(ለ) መሰረት ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ዳኝነት በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ውርስ ተጣርቶ የወራሾች ድርሻ በተለየበት ሁኔታ አመልካች ድርሻቸውን ተጠሪዎች እንዲያካፍሉ ያቀረቡት ክስ የውርስ ንብረቱን ጠቅላላ ግምት መሰረት በማድረግ የፍርድ ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን የሚታይ ነው ተብሎ መወሰኑ ከዳኝነት አከፋፈል እና በዳኝነት ከሚጠየቅ መብት አንፃር ተገቢነት የሌለው ነው የሚል ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም፡-የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት የአመልካቾችን ክስ መዝጋቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲመሰርቱ ከውርስ ጠቅላላ የተገመተ ሃብት ድርሻቸውን ከሌሎች ወራሾች ይደርሰኛል ያሉትን መጠኑን በግልጽ በመለየትና በመጥቀስ ሲሆን ዳኝነት የጠየቁትም ድርሻቸውን ተከሳሾች እንዲያካፍሏቸው ይወሰን ዘንድ የውርስ ቤትና አክሲዮን ግምት ከብር 4,000,000.00 (አራት ሚሊዮን ብር) በላይ መሆኑን ተጠሪዎች ገልፀው የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

አመልካች የጠየቁት የውርስ ንብረት አይነቱንና ግምቱን ለይተው ድርሻቸው የሆነውንና ከብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር) በታች የሆነውን ብር 274,333.00 (ሁለት መቶ ሰባ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰለሳ ሶስት ብር) እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ነው፡፡ የተያዘውን ጉዳይ መሰረት ያደረገው የገንዘብ መጠን ሲታይ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 14(1(ሀ)) ድንጋጌ መረዳት የምንችለው ሲሆን አመልካች ከድርሻቸው ውጪ ያለውን ግምት መሰረት አድርገው ዳኝነት የሚጠይቁበት የሕግ አግባብም የለም፡፡ የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን መሰረት የሚያደርገው የጉዳዮችን ክብደትና ቅለት መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ከሳሹ ከሚጠይቀው ዳኝነት ውጪ ያለው እና ከሳሹ ከሚጠይቀው ንብረት ጋር ተያያዥነት ያለው ንብረት ግምት ሁሉ መሰረት ተደርጎ የፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን እንዲታይ የሚስገድድ የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ አመልካች ድርሻቸውን ለይተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 225 መሰረት ተገቢውን ዳኝነት ከፍለው በድርሻቸው ላይ ክርክር ከሚያቀርቡ በስተቀር ፍርድ ቤቱ ውርሱ ሲጣራ የውርስ ንብረት ስለመሆኑ በተረጋገጠው ንብረት ላይ ሌላ ክርክር የሚመራበት ሁኔታም የሌለ ሲሆን ተጠሪዎቹም ቢሆኑ ክርክር የቀረበባቸው ንብረቶች የውርስ ሃብት

አይደሉም የሚል ክርክር ያቀረቡ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ ከተጠሪዎች ውጪ ያለወገን መብት ቢኖር እንኳን አመልካች በድርሻቸው ተመስርተው ዳኝነት እስከጠየቁ ድረስ በሕጉ አግባብ የሚጠየቁበት ከሚኖር በስተቀር የንብረቱ ጠቅላላ ግምት የፍርድ ቤቱን የስረ ነገር ስልጣን ለመወሰን የግድ የሚልበት የሕግ መሰረት የለም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄውን ያቀረቡት ድርሻቸውን መሰረት በማድረግ በመሆኑና የተጠሪ ድርሻ ደግሞ ከብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር) በታች በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 14፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 17 እና 225 እና ሌሎች የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ክሱን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት የህግ መሰረት የሌለውን መስፈርት በመጥቀስ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን መዝጋቱም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤትን የሕግ መሰረት የሌለውን ብይን መቀበሉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68766 በ21/02/2010 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 205383 በ07/3/2011 ዓ/ም የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68766 ክርክሩን ቀጥሎ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ.155880

ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች - መዓዛ አሸናፊ

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች - አግሪኮም ኢንተርናሽናል ኩባንያ -ጠበቃ አለሙ ደነቀው ቀረቡ::

ተጠሪ- የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን-ጠበቆች ሜሮን ሰለሞን እና ዶ/ር ዘውድነህ በየነ ቀረቡ::

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የስንዴ ግዢ ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተደረገው ግራ ቀኙ እ.ኤ.አ ኖቨንበር 25/2011 ባደረጉት ስምምነት መሰረት አለመግባባታቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (Substantive Law) እንዲሁም በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በእንግሊዝ ሃገር ለመቋጨት በተስማሙት መሰረት ነው፡፡

1. የአሁን ተጠሪ ለግልግል ጉባኤው ባቀረበው ክስ 200,000 ሜትሪክ ቶን ስንዴ ለማቅረብ አመልካች የውል ግዴታ ገብቶ ማቅረብ ባለመቻሉ ጥቅምት 9/2005 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቼ ውሉን በማቋረጥ ሌላ ግዢ ፈጽሜያለሁ፤ ስለሆነም በፈፀምኩት አዲስ ግዢ ምክንያት ለ 11,549,000.00 (አስራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር ተጨማሪ ወጪ ተዳርጌያለሁ፤ ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡
2. አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ስንዴውን ለማቅረብ ያልቻልኩት ስንዴውን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን የባንክ የመተማመኛ ሰነድ (L/C) ተጠሪ አስተካክሎ በወቅቱ ለማቅረብ ባለመቻሉ በራሱ ጥፋት ነው፤ የራሱን ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ ውሉን ለማቋረጥም ሆነ ኪሳራ ለመጠየቅ አይችልም፤ ከዚህም ሌላ ውሉ በሚተዳደርበት በኢትዮጵያ ህግ መሰረት ተገቢው ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ተጠሪ ውሉን ሊያቋርጥ አይችልም፤ ስለሆነም ካሳ እንድከፍል ሊጠይቀኝ አይችልም፤ ይህ የሚታለፍ ቢሆንና የደረሰ ጉዳት አለ ከተባለ ተጠሪ ሊጠይቅ የሚችለው ለ200,000 ሜትሪክ ቶን የዋጋ መጠን በተሰጠው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ሰነድ (Performance Bond) ማለትም 5,855,000.00 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ብቻ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

3. ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የግልግል ጉባኤ ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ተጠሪ ውሉን ያቋረጠው በአግባቡ ነው፤ ውሉን ለማቋረጥ የተሰጠው ማስጠንቀቂያም የኢትዮጵያ ህግ የሚጠይቀውን የሚያሟላ ነው፤ እንዲሁም ተጠሪ የጠየቀውን የካሳ መጠን የማይከፍልበት ምክንያት የለም በማለት አመልካች ለተጠሪ 11,549,000.00 (አስራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ) የአሜሪካ ዶላር እንዲከፍል የካቲት 20/2010 ዓ.ም ባሳለፈው ፍርድ ወስኗል፡፡
4. የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 18/2010 ዓ.ም በተሻሻለ የሰበር ማመልከቻ ውሳኔው የተሰጠው በኢትዮጵያ ህግ ላይ ተመስርቶ መሆኑንና ውሳኔውም የመጨረሻና በሁለቱ ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑ መደንገጉን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42239 ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ጉዳዩን ተቀብሎ ለመዳኘት እንደሚችልና ህገመንግስታዊ ሥልጣን ያለው መሆኑን ጠቅሶ ማመልከቻውን አቅርቧል፡፡
5. አመልካች በሰበር ማመልከቻው በ09/02/2005 ዓ.ም ተሰጠ የተባለው ማስጠንቀቂያ በ16/02/2005 ዓ.ም ከተጠሪ በተላከ መልዕክት የተነሳና የተሰረዘ በመሆኑ፤ ይህም ባይሆን ማስጠንቀቂያው የተሰጠው ተጠሪ የራሱን ግዴታ ሳይወጣና በቂ ጊዜም ሳይሰጥ የፍትሐብሔር ህጉንና የሰበር ውሳኔዎች ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች ሳያሟላ ስለሆነ በአግባቡ ባልተቋረጠ ውል ላይ ተመስርቶ አመልካች 11,5490,00.00 (አስራ አንድ ሺህ አምስት መቶ አርባ ዘጠኝ) የአሜሪካ ዶላር እንዲከፍል የተሰጠው የግልግል ጉባኤ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ ይህ የሚታለፍ ከሆነም ለደረሰው ጉዳት መከፈል ያለበት ለ 200,000 ሜትሪክ ቶን ስንዴ ግራቀኙ ካደረጓቸው ውሎች ተለይቶ በተሰጠው የፐርፎርማንስ ቦንድ ገንዘብ መጠን ማለትም 5,855,000.00 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ብቻ ነው ተብሎ እንዲወሰን አመልክቷል፡፡
6. የሰበር ማመልከቻው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ተዋዋይ ወገኖች ውሉን በተናጠል ለመሰረዝ (Unilateral Cancillation of Contract) ስለሚችሉበት አግባብ በሰበር መዝገብ ቁጥር 57280 ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አኳያ ተገቢነቱን መርምሮ ለመወሰን በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡
7. ተጠሪ መስከረም 22/2011 ዓ.ም በተሻሻለ መልስ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበውን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬነገሩም መልስ ሰጥቷል፡፡
8. ተጠሪ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ ባቀረበው የመቃወሚያ ክርክር የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ኢትዮጵያ ውስጥ ባልሆነ የግልግል ዳኝነት የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ

ለኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲታይ የሚቀርብበት የህግ መሰረትም ልምድም የለም፤ የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ እንደ ኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ እንዲቆጠር በተዋዋዮች መካከል የተደረገ ስምምነት ስለሌለ ውሳኔውን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንደተሰጠ ውሳኔ ቆጥሮ በመሰረታዊ የህግ ስህተት ስም ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የሚደረግበት የህግ መሰረት የለም፤ ጉዳዩ በሰበር እንዲታይ የሚቀርብበት የህግ አግባብ የለም እንጂ አለ እንኳ ቢባል ሊቀርብ ይገባ የነበረው የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ ሆኖ በተመረጠውና በተዋዋይ ወገኖች ተቀባይነትን ባገኘው እ.ኤ.አ በ1996 በፀደቀው የዩናይትድ ኪንግደም የአርቢትሬሽን ህግ መሰረት ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የንግድ ችሎት ብቻ ነበር፤ አመልካች የግልግል ዳኝነት አካሉ የመጀመሪያ ጉባኤ (First Tier Tribunal) በሰጣቸው ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ከአንዱም ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታውን ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ንግድ ችሎት አቅርቦ ውድቅ ተደርጎበታል፤ አመልካች እ.ኤ.አ. በፌብሪዋሪ 27 ቀን 2018 በአምስት ዳኞች የተላለፈውን የ GAFTA የግልግል ዳኝነት የይግባኝ ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔ ቀሪ እንዲደረግ፣ እንዲሻር ወይም እንዳይፈፀም ለማድረግ አቤቱታውን ማቅረብ የነበረበት የግልግል ጉባኤው መቀመጫ ሀገር ህግ በሚፈቅደው መሰረት ሥልጣን ላለው ለለንደኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ንግድ ችሎት ነበር፤ ስለሆነም ይህ የሰበር አቤቱታ ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ አመልካች በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠውን ውሳኔ በመጥቀስ አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም በሁለቱ መዛግብት ክርክር ያስነሳው ጉዳይ፣ የውሉ ሁኔታዎች እና የግልግል ጉባኤው መቀመጫ ፈጽሞ የተለያየ በመሆኑ በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠው ገዢ ትርጉም በዚህ መዝገብ ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም፤ ሰበር ችሎቱ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልባቸው ናቸው የተባሉ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎችን ተቀብሎ ማየት የሚችለው የመጨረሻውን የግልግል ዳኝነት ወሳኔ ያስተላለፈው የግልግል ዳኝነት አካል ህጋዊ መቀመጫ (Juridical or Legal Seat) በኢትዮጵያ ከሆነ ብቻ ነው፤ ከዚህም ሌላ ተዋዋይ ወገኖች ውሳኔያቸውን የሚገዛው መሰረታዊ (የሥረ ነገር) ህግ (Substantive Law) የኢትዮጵያ ህግ በመሆኑና የኢትዮጵያ ህግ ሲተረጎም ደግሞ መሰረታዊ ስህተት ከተፈጸመበት ሊያቃና የሚችለው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ነው ከሚል ግንዛቤ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ በግራቀኙ የተመረጠው መሰረታዊ ህግ የኢትዮጵያ ህግ ቢሆንም ክርክር ሂደቱን የሚገዛው የሥነ ሥርዓት ህግ ደግሞ የግልግል ዳኝነት አካሉ (የ GAFTA የአርቢትሬሽን የሥነ ሥርዓት ህግ) ህጋዊ መቀመጫ ሀገር ህግ በመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት “መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል” የተባለውን የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ውሳኔ የማየት ሥልጣን የለውም፡፡ በተዋዋይ ወገኖች የአርብትሬሽን የሥነ ሥርዓት ህጎች የሚወሰኑትም ከፍርድ ቤቶች ጣልቃ ገብነት ለመራቅ ሲባል ነው፡፡ በሌላም በኩል አመልካች በአቤቱታው የገለፀው ጥቅምት 9/2005 ዓ.ም የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ጥቅምት 16/2005 ዓ.ም በተባለ ደብዳቤ ተነስቷል? ወይስ አልተነሳም? የሚለው ክርክር ማስረጃን የሚመለከት በመሆኑና

ውሳኔም የተሰጠው ማስረጃዎቹ ታይተው በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክር የህግ ክርክር አይደለም ለሰበር ችሎቱ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሊታይ የሚችል አይደለም ተብሎ ውድቅ ይደረግልን በማለት መቃወሚያውን አቅርቧል፡፡

9. ተጠሪ ከዚህም ሌላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ዝርዝር መልስ ሰጥቷል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ ሲታይ በተጠሪ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ አልተነሳም፤ በግራ ቀኙ መካከል በተገባው ውልና የውል ማራዘሚያ መሰረት አመልካች ሥንዴውን ማቅረብና ማጠናቀቅ የነበረበት ጊዜ ባለማቅረቡ ተጠሪ ጥቅምት 13/2005 ዓ.ም ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፤ ከዚህ በኋላ በአመልካች በቀረበ ጥያቄ መሰረት ተጠሪ ጥቅምት 16/2005 ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤም ማስጠንቀቂያውን ያለቅድመ ሁኔታ አንስቻለሁ የሚል ሳይሆን ቅድመ ሁኔታዎችን በግልጽ አስቀምጦ ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ማስጠንቀቂያው ሊቀር እንደሚችል ገልጾ ነው፤ አመልካች ሁኔታዎችን ያላሟላ መሆኑንና ጥቅምት 13/2005 ዓ.ም የተሰጠው ማስጠንቀቂያ የፀና ስለመሆኑ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው አጣርቶ ውሳኔ ሰጥቶበታል፤ ስለሆነም ማስጠንቀቂያው ተነስቷል ወይም ተሰርዟል በማለት ያቀረበው ክርክር የውልም ሆነ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ የተሰጠው ማስጠንቀቂያም በፍትሐብሔር ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንዲሁም በሰ/መ/ቁ 57280 የተሰጠውን የህግ ትርጉም ባሟላ መልኩ የተደረገ ነው፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ህጋዊ ግዴታ ባይኖርበትም ተጠሪ በአግባቡ ህጉን የተከተለ ማስጠንቀቂያ የሰጠ በመሆኑና የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ማስረጃዎችን መርምሮ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ያልተነሳ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲሁም ተጠሪ የሚጠበቅበትን የውል ግዴታ ቢወጣም አመልካች ግን ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን በማስረጃ አረጋግጦ የወሰነ በመሆኑ ቅሬታው ውድቅ ይደረግ፡፡ የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትና (ቦንዱ) በተመለከተም በአመልካች አቤቱታ የተጠቀሰው መጠን ስህተት ነው፤ በውሉ አንቀጽ 13 እንደተቀመጠው የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትናው የሚገባው የውሉን ዋጋ 10% መሆኑን ስለሚደነግግ ይህ ሲሰላ 14,637,500.00 የአሜሪካ ዶላር ይሆናል፤ አመልካች የ200,000 ሜትሪክ ቶን ስንዴ ዋጋን መሰረት በማድረግ ያስቀመጠው የዋስትና ገንዘብ መጠን የተሳሳተ እና የውል መሰረት የሌለው ነው፤ ውሉ የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትና (ቦንድ) መጠኑን ሲያስቀምጥ የዋሱን ኃላፊነት መጠን ለመገደብ እንጂ የጉዳቱን መጠን ለመገደብ እንደሆነ ያስቀመጠው ነገር የለም፤ ከቦንዱ በላይ ጉዳት ቢደርስ ተጨማሪ ካሳ መጠየቅ አይቻልም የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ነገርም የለም፤ በተጨማሪም በውሉ አንቀጽ 17 ላይ liquidated damage የተቀመጠ ሲሆን ይህም በአንቀጽ 13 ላይ የተቀመጠው የጉዳት ካሳ የመልካም ሥራ አፈጻፀም ዋስትና ሰነድ የጉዳት መጠኑን በአጠቃላይ ለመገደብ የተቀመጠ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡

10. አመልካች ጥቅምት 23/2011 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ በመቃወሚያው ላይ የበኩሉን ክርክር አቅርቧል። በዚህም መሰረት የጋፍታ የግልግል ጉባኤ (ቦርድ) የሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ የሚዳኝበትን የኢትዮጵያ ህግ የጣሰ ነው በማለት የቀረበን ቅሬታ በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 እና በአዋጅ ቁጥር 454/97 መሰረት ለማየት ሥልጣን ያለው ሰበር ሰሚው ችሎት ነው። ሁለቱ ወገኖች ጉዳያቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (substantive law) መሰረት ለመገዛት ፈቃደኛነታቸውን በውል ከገለፁ የኢትዮጵያን ህግ አስመልክቶ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩ ከሰበር ሰሚው ስልጣን ውጪ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም። ይህ ያልተገደበ የሰበር ስልጣን ፍርዱ በየትም ቦታ ቢሰጥ ወይም ውሳኔ የሰጠው አካል የተከተለው ሥርዓት (Procedure) ምንም ይሁን የተሰጠው ውሳኔ የኢትዮጵያ የህግ መስፈርቶችን አያሟላም የሚል ጥያቄ ከተነሳ ውሳኔ የሚሰጠው በህግ ስልጣን የተሰጠው ሰበር ሰሚ ችሎት ብቻ ነው። ተዋዋዮች በአንድ የግልግል ተቋም አማካኝነት በተወሰነ ሃገር ለመዳኘት ፈቃድ መስጠታቸው የግልግል ተቋሙ የሚመራበትን ሥርዓት (procedure) መቀበላቸውን ከሚያረጋግጥ በቀር መሰረታዊውን ህግ በተመለከተ ያላቸውን መብት ተነፍገዋል ማለት አይደለም። አመልካች በተለያዩ ጊዜያት ይግባኝ ሲያቀርብ የነበረው ለለንደኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው አሁንም በዚያው መሰረት ሊያቀርብ ይገባል ተብሎ በተጠሪ በኩል የቀረበውን ክርክር በተመለከተም ፍሬ ነገርን ወይም መሰረታዊ (የስረ ነገር) የህግ ስህተትን አስመልክቶ ለለንደን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረብነው አንዳችም ይግባኝ የለም። በርግጥ ጉዳዩ በግልግል ጉባኤ በመታየት ላይ እያለ ሁለት የሥነ ሥርዓት ጥያቄዎች ላይ በመመስረት አቤቱታ ለለንደን ፍርድ ቤት አቅርበናል፡- ይኸውም በመጀመሪያ ጉዳዩ ለግልግል ጉባኤ በቀረበበት ወቅት የአቤቱታ ማቅረቢያው ጊዜ አልፏል በማለት፣ ሁለተኛ ደግሞ ክርክሩ አልቆ ውሳኔውን ከመስማታችን በፊት ተዋዋይና ከሳሽ ወገን የነበረው የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት አስቀድሞ ፈርሶ እያለ በፈረሰው ድርጅት ሥም ሲካሄድ የነበረው ክርክር እንደተካሄደ ሊቆጠር አይገባም በማለት የቀረበ የሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ነው። የዚህ አይነት የሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ደግሞ ክርክሩ የሚካሄድበትን ሥርዓት መሰረት በማድረግ በይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት መቅረቡ በአግባቡ ነው። ስለሆነም ተጠሪ ያቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል። ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም አመልካች የቀደመ ክርክሩን በማጠናከር ውሉ የተቋረጠው ያላግባብ ስለሆነ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ ውድቅ እንዲደረግ። ይህ የሚታለፍ ከሆነም የካሳው መጠን በመልካም ሥራ አፈጻፀም ቦንዱ ላይ የተቀመጠው የገንዘብ መጠን 5,855,000.00 (አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል።

11. የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ የጽሁፍ ክርክር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ክርክራቸውን በቃል ሰምቷል። ጉዳዩንም የሠበር

አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

12. እንደመረመርነው በሰበር አጣሪ ችሎቱ እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ ፍሬ ጉዳዩን የተመለከተ ቢሆንም ከዚህ በፊት የችሎቱን ምላሽ የሚጠይቀው ነጥብ የአሁን ተጠሪ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር ነው፡፡ ይህን ጭብጥ ለመመለስ ግራቀኙ በገቡት ስምምነት መሰረት ጉዳዩ በግልግል ጉባኤ ውሳኔ ያገኘበትን አግባብ እና የተሰጠውን ውሳኔ ተፈጥሮ፤ መሰል የአማራጭ ሙግት መፍቻ ዘዴዎችን በመጠቀም በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች አቤቱታ የሚቀርብበትን ሁኔታ፤ እንዲሁም በሀገራችን የተዘረጋው የሰበር ስርዓት አላማና የህጉን ማእቀፍ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

13. በሀገር ውስጥ የግልግል ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ተከራካሪዎቹ ጉዳያቸውን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ ይግባኝ የሚሉበትና ውሳኔው እንዲሻር ማመልከቻ የሚቀርብበት ሂደት በሥነ ሥርዓት ህጉ ተመልክቷል፡፡ ከፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ህጉ ግልጽ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት እንደሚቻለው የግልግል ውሳኔው እንዲሻር የሚቀርበውን ማመልከቻ በመቀበል እንዲሁም የአፈፃፀም ክርክሩን በመወሰን ፍርድ ቤቶች የግልግል ዳኝነት ሂደትን ይቆጣጠራሉ፡፡ ፍርድ ቤቶች የግልግል ዳኛ በመሾም፣ በመሻር፣ ጉዳይን ወደ ግልግል በመምራት እንዲሁም ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ፍርዱን ሊመረምሩ የሚችሉበት ሁኔታ በህጉ ተደንግጓል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ ከአንቀጽ 350 እስከ 354 ስለ ይግባኝ፤ ከአንቀጽ 355 እስከ 356 ብይኑ ስለሚሻርበት እና ማመልከቻው ስለሚቀርብበት ሁኔታ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ፍርድ ቤቶች የግልግል ዳኝነቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ማሳካቱና እና በህጉ አግባብ ጉዳዩን መርቶ መወሰኑን እንዲያረጋግጡ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በአንፃሩ እነዚህ ድንጋጌዎች በውጪ ሀገራት የተሰጡ የግልግል ዳኝነቶችን በቀጥታ ይመለከታሉ ባይባልም የሥነ ሥርዓት ህጉ ከአንቀጽ 456 እስከ 461 ድረስ ከውጪ አገር ስለሚመጡ የግልግል ውሳኔዎች አፈፃፀም ሂደትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡

14. በሌላ በኩሉ በዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ያለው ልምድ እና የዳበረ የግልግል ዳኝነት ህግጋት ያላቸው የበርካታ ሀገራት ህጎች እንዲሁም አለምአቀፍ ስምምነቶች እንደሚያረጋግጡት የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እንደመደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተቆጥረው የግልግል ውሳኔዎችን በፍርድ ውሳኔ ለማስቀረት (setting aside) ወይም ለማሰረዝ (annulment) አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በተዋዋይ ወገኖች መካከል ይኸው በስምምነት ሲደገፍ፣ ተዋዋይ ወገኖች በመረጡት የግልግል ዳኝነት የሥነ ሥርዓት ህግ (Institutional Arbitration Rule) ይኸው ሲደገፍ፣ እንዲሁም የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ ሀገር (Juridical or Legal Seat) ህግ ይህንኑ የሚደግፍ ሲሆን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ በእንግሊዝ ሀገር መሆኑ

እንዲሁም ግራቀኙ ባደረጉት ስምምነት ውስጥ የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ እንደ ኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሆኖ እንዲቆጠር የተደረገ ስምምነት አለመኖሩ አላከራከረም፡፡ የተመረጠው የግልግል ዳኝነት መቀመጫ ሀገር ህግም ቢሆን በግልግል ጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ በዚያው ሀገር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ እንዲቀርብ የሚፈቅድ ነው፡፡ ስለሆነም የግልግል ጉባኤው ውሳኔ እንዲሻር/እንዲሻሻል አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት በቀጥታ የቀረበው ይህን የሚፈቅድ ህግ እንዲሁም የተዋዋይ ወገኖች ሥምምነት በሌለበት ነው፡፡

15. ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች የግልግል ዳኝነት አካሉ የመጀመሪያ ጉባኤ (First Tier Tribunal) በሰጣቸው ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ከአንዱም ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታውን ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ንግድ ችሎት አቅርቦ ውድቅ ተደርጎበታል፤ በመጨረሻው ውሳኔ ላይም ቅሬታው ሊቀርብ የሚገባ በዚሁ አግባብ ነው በማለት ተጠሪ የተከራከረ ሲሆን አመልካች በሰጠው መልስ ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታ ለለንደን የከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቦ እንደነበር ሳይክድ ያቀረበው ይግባኝ የስነ ሥርዓት ጉዳዮችን በተመለከተ ብቻ እንደነበርና ፍሬ ነገርን ወይም መሰረታዊ (የስረ ነገር) የህግ ስህተትን አስመልክቶ ለለንደን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ እንደሌለ ተከራክሯል፡፡ እንደሚታወቀው በአንድ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የማለት መብት መሰረታዊ መብት ሆኖ የሚቆጠር ሲሆን የይግባኝ መብቱ ዝርዝር አፈፃፀም ግን የሚወሰነው በሥነ ሥርዓት ህጎች ነው፡፡ ስህተቱ የሥነ ሥርዓትም ሆነ የፍሬ ነገር ቢሆን ሊሰማና ሊታረም የሚችለው ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ባለው የሥነ ሥርዓት ደንብ እየተመራ ነው፡፡ ስለሆነም የግልግል ዳኝነቱ አካል የሚመራበት ሥነ ሥርዓት ላይ ግራ ቀኙ ስምምነት አድርገው በዚሁ አግባብ ሁለት ጊዜ የይግባኝ አቤቱታ ለለንደኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረቡ ባላከራከረበት ሁኔታ አመልካች ፍሬ ነገርን ወይም መሰረታዊ የህግ ስህተትን አስመልክቶ ለመደበኛው ፍርድ ቤት ያቀረብኩት ቅሬታ የለም በማለት ያቀረበው ክርክር የሥምምነታቸውን ይዘት እና ጉዳዩ የሚገዛበትን ህግና ልምድ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

16. በሌላ በኩል አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ሁለቱ ወገኖች ጉዳያቸውን በኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ (substantive law) መሰረት ለመገዛት ፈቃደኛነታቸውን በውል ከገለፁ የኢትዮጵያን ህግ አስመልክቶ ክርክር ቢነሳ ጉዳዩ ከሰበር ሰሚው ስልጣን ውጪ የሚሆንበት የህግ መሰረት የለም፤ ይህ የሰበር ስልጣን ፍርዱ በየትም ቦታ ቢሰጥ ወይም ውሳኔ የሰጠው አካል የተከተለው ሥርዓት (Procedure) ምንም ይሁን የተሰጠው ውሳኔ የኢትዮጵያ የህግ መስፈርቶችን አያሟላም የሚል ጥያቄ ከተነሳ ውሳኔ የሚሰጠው ሰበር ሰሚ ችሎቱ ብቻ ነው በሚል ነው፡፡ ለዚህ ክርክራቸው መሰረት የሚያደርጉትም በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም እና የህገ መንግስቱን አንቀጽ 80 እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 454/97 ድንጋጌን ነው፡፡ በእርግጥ በኢትዮጵያ ሁኔታ በግልግል ጉባኤ የሚሰጥ የመጨረሻ ውሳኔ አስገዳጅና ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ በተከራካሪዎች ስምምነት የተደረገበት ቢሆን ጉዳዩ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባል

ወይስ አይገባም? የሚለው ነጥብ አከራካሪ ሆኖ ይታያል፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ ሰጥቶት የነበረውን አስገዳጅ ትርጉም በፓናል ችሎት በመለወጥ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በሰ/መ/ቁ 42239 *ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ* እና *ዳኒ ድሪሊንግ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ* መካከል በተደረገው ክርክር ሰበር ችሎቱ የግልግል ውሳኔን የመጨረሻነት እንዲሁም በግልግል ዳኝነት አካላት የተሰጡ ውሳኔዎችን በተመለከተ ፍርድ ቤቶች ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና አስመልክቶ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶ ወስኗል፡፡ በዚህም መሰረት "..... *አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ውስጥ ተካተው የሚገኙ ሲሆን እነዚህን የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ፍርድ ቤቶች የሚያበረታቱበት አጋጣሚ እንዳለ ሁሉ የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ መኖሩን.....፤ ከዚህ አኳያ አንድ ጉዳይ ለሰበር የመቅረቡ ሁኔታ በህገ መንግስቱ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ ሥልጣን በመሆኑ የሰበር ስርዓቱ ሊጫወተው ከተፈለገው ወቢይ ዓላማ አንፃር ሲታይ ጉዳያቸው በግልግል ዳኝነት እንዲታይላቸው የተስማሙ ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው በማለት ስለተስማሙ ብቻ ጉዳዩ በሰበር ሥርዓቱ እንዳይታይ ፍላጎት አሳይተዋል ተብሎ መሰረታዊውን የህግ ስህተት ላለማሳረም ምክንያት ሊሆን የሚችል አይደለም....*" በማለት የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ)፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10፣ እና አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በማድረግ ወስኗል፡፡ ነገር ግን ሊታይ የሚገባው ይህ ውሳኔ ለተያዘው ጉዳይ ያለው ተገቢነትና አስገዳጅነት ነው፡፡ ከውሳኔው መገንዘብ እንደሚቻለው በጉዳዩ ላይ በሰበር ችሎቱ ውሳኔ የተሰጠው የግልግል ችሎቱ መቀመጫ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ተከትሎ በመሆኑ አሁን በእጃችን ካለው ጉዳይ ጋር የተገናኘ አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ ባደረጉት የግዥ እና ሽያጭ ውል የግልግል ዳኝነት መቀመጫውን በእንግሊዝ ሀገር ለንደን ከተማ ያደረገ የግልግል ተቋም የመረጡ ሲሆን በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት ለመዳኘትም ተስማምተዋል፡፡ በሰ/መ/ቁ 42239 የተሰጠው ውሳኔ ደግሞ ይህን መሰረት አድርጎ የተሰጠ ባለመሆኑ ከተያዘው ጉዳይ ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ ተመሳሳይ የፍሬ ነገር ወይም የህግ ክርክሮች በሌሉበት ሁኔታ አስቀድሞ የተሰጠ የሰበር ውሳኔ በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚ እንዲሆን የሚደረግበት የህግ አግባብ እንደሌለም ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(4) ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

17. በሌላ በኩል የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የግልግል ጉባኤ ውሳኔ (APPEAL AWARD NO: 4496 & 4515) መግቢያ ላይ በተራ ቁጥር 1.4 ሥር የሚከተለው ተመልክቷል፡-

> "As the seat of the arbitration is in England and an Award subject to English procedural and Ethiopian substantive law, it therefore follows that it is an English Award for the purpose of recognition and enforcement

under the terms of the 1958 New York Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards"

የዚህ የአማርኛ ትርጉምም እንደሚከተለው ይነበባል፡-

> "የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ቦታ እንግሊዝ ሀገር በመሆኑና የዳኝነቱ ሂደት የሚመራው በእንግሊዝ የሥነ ስርዓት ህግ፣ የውሉን ይዘት በተመለከተ ግን ተፈፃሚው የኢትዮጵያ ህግ በመሆኑ፤ የግልግል ውሳኔው እንደ እንግሊዝ አገር ውሳኔ ተቆጥሮ ውሳኔው ዕውቅና የሚያገኘውና ተፈፃሚም የሚሆነው ከአንድ አገር ውጪ የተሰጠን ውሳኔ አፈፃፀም በተመለከተ በ1958 የወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ነው"

18. ከዚህ የግልግል ጉባኤ ውሳኔ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው የግልግል ውሳኔው ከአንድ አገር ውጪ የተሰጠ ውሳኔ (በእንግሊዝ) ተደርጎ የሚወሰድና ውሳኔው ዕውቅና የሚያገኘውና ተፈፃሚም የሚሆነው በ1958 የወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን መሰረት ስለመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ለሰበር ክርክሩ አወሳሰን ሲባል ይህ የግልግል ጉባኤው ውሳኔ ተፈጥሮና በ1958 የወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን በሀገራችን የህግ ሥርዓት ያለውን ቦታ በአግባቡ መመርመር ይጠይቃል፡፡

19. ከሀገር ውጪ የሚሰጡ የግልግል ውሳኔዎችን በሃገራት ውስጥ በማስፈፀም ረገድ እ.ኤ.አ በ1958 የወጣው ለግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች ዕውቅና መስጠትና ማስፈፀምን የሚመለከት የኒውዮርክ ኮንቬንሽን (The New York Convention on the Recognition and Enforcement of Arbitral Awards) እንደ ትልቅ ስኬትና እመርታ ይወሰዳል፡፡ በርካታ የዘርፉ ተመራማሪዎች እንደሚመሰክሩለትም ከሁሉም ሃገራት ፍላጎት ጋር በሚስማማ መልኩ የግልግል ውሳኔዎች በቀላሉ የሚፈፀሙበትን መንገድ ዘርግቷል ተብሎ ይታመናል፡፡ በሃገራችንም ከኢኮኖሚው እድገት ጋር ተያይዞ ድንበር ተሻጋሪ የንግድ ልውውጦች እየተጠናከሩ በመሆኑና ግዙፍ ኩባንያዎች የገበያ አድማሳቸውን በማስፋት ወደ ሃገራችን በማቅናት መዋዕለ ንዋያቸውን እያፈሰሱ በመሆኑ ይህን ዘላቂ ለማድረግ፤ በተለይም ኢትዮጵያ የዓለምአቀፉ የንግድ ማህበር (World Trade Organization) አባል ለመሆን በምታደርገው ጥረት አንዱ መመዘኛ ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ፤ እንዲሁም አለመግባባቶች በግልግል መቋጨታቸው ከሚኖረው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አንፃር ሃገራችን የኒውዮርኩን ኮንቬንሽን ለማጽደቅ በሂደት ላይ መሆኗ ይታወቃል፡፡

20. የኒዮርኩ ኮንቬንሽን እስካሁን በሃገራችን አልፀደቀም ማለት ግን በህግ ሥርዓታችን ውስጥ ምንም ቦታ አልተሰጠውም ማለት እንዳልሆነ ተገቢነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በማየት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሀገራችን ውስጥ በግልግል ጉባኤዎች የሚሰጡ ውሳኔዎች የሚፈፀሙት የፍርድ ውሳኔዎች በሚፈፀሙበት መንገድ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 319 በግልጽ ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል ከውጪ ሀገር የሚመጡ የግልግል ውሳኔዎች የሚፈፀሙበት ራሱን የቻለ ሥርዓት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ከአንቀጽ 456 እስከ 461 ተደንግጎ ይገኛል፡፡

21. ከኒዮርኩ ስምምነት ይዘትና ከሃገራችን ህጎች መገንዘብ እንደሚቻለው በውጭ ሃገራት የሚሰጡ የግልግል ውሳኔዎችን በማስፈፀም ረገድ የኢትዮጵያ ህግ ከኒዮርክ ስምምነት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ መመሳሰሉን ለማሳየት የሚከተሉትን ነጥቦች በማነፃፀር ማንሳት ይቻላል፡-
    - የስምምነቱ አንቀጽ 1(3) ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 458(ሀ) እና 461(1)(ሀ)
    - የስምምነቱ አንቀጽ 3 ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 461(1) ይዘት ጋር
    - ከኒውዮርኩ ስምምነት በዋናነት የሚጠቀሱት በአንቀጽ 5 ሥር የተጠቀመጡት ሁኔታዎች ሲሆኑ እነዚህ ሁኔታዎች ከኢትዮጵያ ህግ ጋር በእጅጉ የሚመሳሰሉ መሆኑን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 461(1)(ለ)-(ሠ) ከተዘረዘሩት ጋር በማነፃፀር መረዳት ይቻላል፡፡

22. በዚህ መልኩ በኒውዮርክ ስምምነት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 461 መካከል የቃል በቃል መመሳሰል እንዴት ሊፈጠር ቻለ የሚለውን በአግባቡ ማየትም ያስፈልጋል፡፡ በኒውዮርክ ስምምነት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ መካከል ላለው መመሳሰል በምክንያትነት የሚጠቀሰው የሥነሥርዓት ህጉ የወጣው የኒውዮርኩ ስምምነት በወጣ በጥቂት አመታት ውስጥ መሆኑ ነው፡፡ የሥነ ሥርዓት ህጉ እ.ኤ.አ በ08/10/1965 የወጣ ሲሆን የኒዮርክ ስምምነት ለፊርማ ክፍት የሆነው እ.ኤ.አ በ31/12/1958 ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ህግ አውጭው በውጪ ሃገራት የተሰጡ የግልግል ውሳኔዎችን ለማስፈፀም እንዲሁም አፈፃፀሙን ለመቃወም ሊጠቀሱ የሚችሉ ምክንያቶችን ከኒዮርክ ስምምነት ሊወስድ መቻሉ ይታመናል፡፡

23. ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ግራቀኙ ያደረጉትን ስምምነት ተከትሎ የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ እንደ እንግሊዝ አገር ውሳኔ የተቆጠረ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ለማሳረም በሚል ለዚህ ፍርድ ቤት መቅረቡ ተገቢ ባይሆንም ውሳኔው ፅውቅና የሚያገኘውና ተፈፃሚም የሚሆነው ከአንድ አገር ውጪ የተሰጠን ውሳኔ አፈፃፀም በተመለከተ በ1958 በወጣው የኒዮርክ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን መሰረት በመሆኑ በዚህ አግባብ አቤቱታ ሊቀርብና ሊስተናገድ አይገባም ማለት ግን አይሆንም፡፡

24. በአጠቃላይ ግራቀኙ ወገኖች በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በእንግሊዝ ሃገር ክርክራቸውን ለመቋጨት የተስማሙ በመሆኑና የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ የተሰጠውም ይህን ስርዓት ተከትሎ በመሆኑ፤ አመልካቹም በግልግል ጉባኤው ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታውን በውል ስምምነታቸው እና በህግ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ለንደን ለሚገኘው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታውን በየጊዜው ያቀርብ እንደነበር የተረጋገጠ በመሆኑ፤ አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ሰበር ችሎት ለማቅረብ በዋቢነት በጠቀሰው የሰ/መ/ቁ 42239

የተሰጠው የህግ ትርጉም የግልግል ጉባኤው መቀመጫ በተዋዋዮች በስምምነት ወይም ከህግ በተሰጠ ስልጣን በውጪ ሀገር እንዲሆን ተደርጎ በውጪ ሀገር የተሰጠ ፍርድን የሚመለከት ባለመሆኑ፤ እንዲሁም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 (በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 እንደተሻሻለ) የተሰጠው መሰረታዊ የህግ ስህተትን የማረም ስልጣን የተያዘውን ጉዳይ የሚመለከት ባለመሆኑ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አመልካችና ተጠሪ እ.ኤ.አ ኖቬንበር 25/2011 ባደረጉት ስምምነት መሰረት አለመግባባታቸውን በ Grain and Feeds Trading association (GAFTA) የሥነ ሥርዓት ህግ 125 (GAFTA Rules NO. 125) መሰረት በሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል በእንግሊዝ ሃገር ለመቋጨት በተስማሙት መሰረት የተቋቋመው ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ (APPEAL AWARD NO: 4496 & 4515) በኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ታይቶ እንዲታረም የቀረበው የሰበር ማመልከቻ በግራቀኙ የተደረገውን ስምምነት እና ህጉን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2)(ሀ) እና 245(2) መሰረት ወስነናል፡፡
2. አመልካች ለዳኝነት ከከፈለው ብር 1,605,760.10 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰምስት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ ብር ከአስር ሳንቲም) ላይ በደንቡ መሰረት የሚቀነሰው ሂሳብ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪው ገንዘብ ለአመልካች እንዲመለስ ብለናል፡፡ የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ይህን ተከታትሎ ያስፈጽም፡፡
3. ውሳኔው ሀምሌ 5/2011 ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡
4. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የልዩነት ሀሳብ

ውል የተዋዋይ ወገኖችን ነፃነት የሚያሳይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ተዋዋይ ወገኖች ውል በሚያደርጉበት ጊዜ ውሉ ህግን እና ሞራልን የሚቃረን መሆን ሊቃረን አይገባም፡፡

አመልካችና ተጠሪ ጉዳያቸውን በግልግል ለማሳየት መስማማታቸው የዳኝነቱ አገር እና የስነ ስርአት ህግ መምረጣቸው ጤናማ የውል ስምምነት ሲሆን ነገር ግን ከተዋዋዮች አንዱ የኢትዮጵያ መንግስት

መ/ቤት ሆኖ የተዋዋሉበት ነገር ለኢትዮጵያ ሆኖ የተዋዋሉበት ነገር ለኢትዮጵያ እና ህዝቦቿ ጥቅም እንዲሰጥ መሆኑ ተረጋግጦ አለ እንዲሁም የሚፈፀመውም በኢትዮጵያ ሆኖ አመልካችን እንደ አንድ ተዋዋይ ግለሰብ በማሰብ የኢትዮጵያ ፍ/ቤት በማንኛውም ደረጃ ጉዳዩ ቢቀርብለት የማየት ስልጣን እንደሌለው አድርጎ መዋዋል ህግን እና ሞራልን የሚጋፋ እንዲሁም ብሄራዊ ጥቅምን የሚጎዳ ከመሆኑም በላይ በውጭ አገር የተሰጠው ፍርድ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ ግድፈት በተፈፀመበት ጊዜ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት አይታይም አይልም እንጂ የግልግል ዳኝነቱ መቀመጫም ሆነ የሚመራበት ስነ ስርአት ህግ በኢትዮጵያ ባለመሆኑ እና የሚሰጠው ፍርድም የለንደን ፍርድ እንደሆነ መቆጠሩ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ፍርዱ ላይ መሰረታዊ የህግ ጥሰት ተፈጽሟል የሚል ወገን አቤቱታ ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ የማየት ስልጣን የለውም የሚባል ከሆነ ኢትዮጵያን በራሷ ጥቅም ላይ ጉዳይዋን እንዳታይ ያገለለ ከመሆኑ አንፃር ውሉ በራሱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ የሆነ ውል በመሆኑ ከመነሻው ተቀባይነት ማግኘት ያልነበረበት ውል ነው ባይ ነኝ፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጉዳዩ በግልግል እንዲታይ፣ መስማማታቸው በስምምነታቸው መሰረትም የግልግል ዳኝነቱ ህጋዊ መቀመጫ አገር ለንደን መሆኑን እና ግልግሉ የሚመራበትን የስነ ስርአት ህግ የመረጡ መሆኑ እና ውሳኔው በኢትዮጵያ እንደተሰጠ ፍርድ እንደማይቆጠር በመስማማታቸው ላይ ልዩነት እንደሌላቸው ተረድቻለሁ፡፡

ነገር ግን በዚህ መልኩ ተዋዋይ ወገኖች የተዋዋሉ መሆኑ እና በተለይ መንግስት በሚያስተዳድረው መ/ቤት የተወከሉ የስራ ኃላፊዎች ጉዳዩ በውጭ አገር እንዲታይ እና በውጭ አገር ህግም እንዲመራ የተስማሙበትን ልዩ ምክንያት ሳያስቀምጡ በአገር ጥቅም ላይ ስምምነት በማድረጋቸው ብቻ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች በተለይም የሰበር ሰሚ ችሎቱ ስልጣን የለውም ለማለት የሚቻልበት አግባብ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡

ግራ ቀኙ የስነ ስርአት ግድፈት ሲፈጽም ለለንደን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማለት የሚችሉ መሆኑ የተዋዋሉ በመሆኑ አመልካች በለንደን በስነ ስርአት ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማለቱን አልካደም፣ ተጠሪም በስነ ስርአት ጉድለት ብቻ ሳይሆን በፍሬ ነገር ላይም ይግባኝ ብሏል ቢልም በምን አይነት ፍሬ ነገር ላይ ይግባኝ እንዳለ ባልገለፀበት እና በአብላጫው ድምጽ እንደተገለጸው ሁለት ጊዜ ለለንደን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ የተባለው በስነ ስርአት ግድፈት ላይ መሆኑ የሚያስረዳ ሆኖ እያለ በፍሬ ጉዳይ ላይ ይግባኝ እንዳለ በመቁጠር በስምምነቱ መሰረት ጉዳዩ የሚታየው በለንደን አገር እና በለንደን ፍ/ቤት ብቻ ነው መባሉ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡

እንዲሁም ክርክር ያስነሳው ጉዳይ ሰንዶን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመጣት ሆኖ ስንዶውን የሚጠቀሙት ኢትዮጵያውያን ሆነው እያለ እንዲሁም የግልግል ጉባኤው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ለዛው አገር ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ የሚቀርብ መሆኑን ይግለጽ እንጂ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት የሰበር ስልጣንን በሚያስቀር

መልኩ ስለመዋዋላቸው የሚያሳይ ነገር ሳይኖር አመልካች ቀደም ሲል በስነ ስርአት ግድፈት ምክንያት ለከፍተኛ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ለዛው ይግባኙን ላየው ፍ/ቤት ደግሞ አቤቱታ እንዲያቀርብ ስምምነቱን ማድረጉ በራሱ ኢትዮጵያ ምንም አይነት ተሳትፎ እንዳይኖራት ተደርጎ ውል የተደረገ መሆኑን ከማሳየቱም በላይ አመልካች በኢትዮጵያ የሚገኝ የመንግስት ተቋም እንደመሆኑ መጠን በኢትዮጵያ መሰረታዊ የሆኑ ህጎች የመዳኘት መብት ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እና አመልካች ውል ውስጥ ሲገባ ማንኛውንም መብት የተወ መሆኑን ባልገለጸበት ሁኔታ የአመልካቾች ጥያቄም የኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግ ተጥሶብናል በሚል አቤቱታ አቅረበው ባለበት፣ በስምምነታቸውም የስነ ስርኣት ግድፈት ሲኖር ይግባኝ ማለት እንደሚችሉ እንጂ መሰረታዊ ህግ ሲጣስ ለለንደን ፍ/ቤት ይግባኝ ይላሉ ተብሎ ውል ባልተገባበት ሁኔታ በተለይ ተዋዋይ ወገኖች መንግስታዊ አካላት ከሆኑ የሚዋዋሉትን ውሎች የመንግስትን እና የአገሪቱን ጥቅም በሚያስጠብቅ ሁኔታ መዋዋል ያለባቸው መሆኑ ስለታመነበት የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግን ለማቋቋም እና ስልጣኑን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6/4/ለ/ መሰረት የፌዴራል ጠ/ዐቃቤ ህግ ውሎችን እንዲመረምር መደረጉ ከብሄራዊ ጥቅም አንፃር በራሱ በዚህ መልኩ የሚፈፀሙ ውሎች በአገር ጥቅም ላይ ጉዳት ሊያድርሱ የሚችሉ ከመሆኑ አኳያም ሲታሰብ የአገሪቱ የመጨረሻ የሆነው ፍ/ቤት በውጭ አገር የተሰጠን ፍርድ የግልግል ዳኝነቱ አገር በመመረጡ እና የስነ ስርአት ህጉ በመመረጡ እንዲሁም ፍርዱ በኢትዮጵያ እንደተሰጠ ፍርድ ይቆጠራል በሚል በውሉ ባለመገለፁ መሰረታዊ የህግ ጥሰት እንዲታረም የቀረበን አቤቱታ ባለመቀበል ፍ/ቤቱ ስልጣን የለውም ተብሎ በአብላጫው የተሰጠው ፍርድ ተገቢ አይደለም በማለት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ተብሎ ብይን ተሰጥቶ ወደ ዋናው ጉዳይ ተገብቶ ሊመረመር ይገባ ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁጥር 5 ስር የተሰየምኩት የችሎት ዳኛ በአብላጫው ድምጽ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 161597

ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ

ተጠሪ፡- አቶ ዘሪሁን ተፈራ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በውጪ ሀገር የተሰጠ ፍርድ የሚፈፀምበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 19/07/2009 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የአፈፃፀም አቤቱታ የአሜሪካን የዲስትሪክት ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን የባልና ሚስት ፍቺና ንብረት ክፍፍል ክርክር መርምሮ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በቀን 1/02/2013 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ መሠረት ተጠሪ እንዲፈፅሙ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ በውጪ ሀገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈፀም ሊሟሉ ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ እንዲፈፀም የተጠየቀውን ፍርድ የሰጠው ፍርድ ቤት የሚገኝበት ሀገር በኢትዮጵያ የተሰጠውን ፍርድ የሚፈፅም መሆኑ ሲረጋገጥ በመሆኑ ይህንኑ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች የሚሰጡት ውሳኔ በአሜሪካን ፍርድ ቤቶች የሚፈፀሙ ስለመሆን አለመሆኑ እንዲሁም ይህንኑ በተመለከተ የሁለቱ ሀገራት የሁለትዮሽ ስምምነት ስለመኖር አለመኖሩ ለፍ/ቤቱ እንዲገለፅ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በቀን 01/03/2010 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶ በቀን 10/04/2010 ዓ.ም በተፃፈ ምላሽ በሁለቱ ሀገራት መካከል ፍርድን ለማስፈፀም የሚያስችል ስምምነት አለመኖሩ የተገለፀ በመሆኑና የኢትዮጵያ ፍርዶችም በአሜሪካን ሀገር የማይፈፀሙ ስለመሆኑ በቀን 27/04/2010 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ስለተገለፀ አመልካች ያቀረቡት የፍርድ ይፈፀምልኝ አቤቱታን አልተቀበልኩትም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት

አመልካች ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርቡም የይግባኝ አቤቱታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም እነዚህ በስር ፍርድ ቤት የተሰጡትን ውሳኔዎች ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገፅ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች ዘርዝረው በማቅረብ እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በሁለቱ ሀገሮች መካከል የአንዱን ሀገር ፍርድ እንዴት እንደሚፈፀም የጋራ ስምምነት የለም ተብሎ ተረጋግጦ እያለ በተዘረጋለት ስርዓት ጉዳያችንን ሊያስተናግድ ሲገባ "የተለየ ስምምነት ከሌለ..." የሚለውን ሀረግ በስህተት በመተርጎም ፍርዱ ሊፈፀም አይገባም በማለት መወሰኑ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪው ተመርምሮ አመልካች በአሜሪካን ሀገር ፍ/ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ መሠረት አድርገው በኢትዮጵያ ፍ/ቤት ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ በሁለቱ ሀገራት መካከል ፍርድን ለማስፈፀም የሁለትዮሽ ስምምነት የለም ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ሀ/ቁ. 256 እና ተከታዮቹ አንፃር ለማጣራት መዝገቡ ለሠበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በጉዳዩ ላይ አመልካች መልስ እንዲሰጥበት በጋዜጣም ጭምር ጥሪ ቢደረግለትም ሊቀርብ ባለመቻሉ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፎ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ከተያዘው ጭብጥና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ ይህ ጉዳይ በዉጭ አገር የተሰጠ ፍርድ የሚፈጸምበትን ሁኔታ የሚመለከት ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ የተመለከተው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ በሁለት ዓብይት ምዕራፎች የተመለከተ ሲሆን፣ በምዕራፍ 1 ላይ የተመለከተው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የተሰጠን ፍርድ በማስፈፀም ረገድ ተፈጻሚነት ያላቸው ድንጋጌዎች ሲሆን፣ በምዕራፍ 2 (ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 456 እስከ 461 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች) ደግሞ በውጭ ሀገር የተሰጠ ፍርድ ወይም ብይን የሚፈፀምበትን ሁኔታ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በዉጭ አገር የተሰጠን ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ከማስፈጸም ጋር በተያያዘ መሠረቱ (principle) በህጉ አንቀጽ 456 ላይ የተመለከተ ሲሆን፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ “በኢንተርናሲዮናል ስምምነት በተለየ እንዲፈጸም የሚደረግ ልዩ ህግ ከሌለ በቀር ከኢትዮጵያ ዉጪ የተሰጠ የፍርድ ዉሳኔ ወይም ብይን የሚፈጸመዉ በዚህ ህግ በተመለከተዉ ድንጋጌ መሠረት ነዉ” በማለት የሚያስቀምጥ ሲሆን፣ የድንጋጌዉ የእንግሊዝኛ ትርጉምም “Unless otherwise expressly provided by international law conventions, foreign judgments may not be executed in Ethiopia except in accordance with the provisions of this chapter” በማለት ያስቀምጣል፡፡ የዉጭ አገር ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሊፈጸሙ የሚችሉባቸዉ ሁኔታዎችም

በህጉ አንቀጽ 458 ላይ ተመልክተዋል። እነዚህም ሁኔታዎች እንዲፈጸም የተጠየቀውን ፍርድ የወሰነዉ ፍርድ ቤት የሚገኝበት አገር በኢትዮጵያ የተሰጠዉን ፍርድም የሚያስፈጽም መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ፍርዱ የተሰጠዉ በህግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት መሆኑ ሲታወቅ፤ የፍርድ ባለዕዳዉ ቀርቦ መቃወሚያዉን ለማሰማት መብት የተሰጠዉ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ፍርዱ የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለዉ መሆኑ ሲታወቅ እና የፍርዱ መፈጸም ለህዝብ ሞራልና ጸጥታ ተቃራኒ ያለመሆኑ ሲታወቅ ስለመሆኑ በድንጋጌዉ ላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል።

ከእነዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ፣ በዉጭ አገር የተሰጠ ፍርድ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሊፈጸም የሚችለዉ በመርህ ደረጃ በኢትዮጵያ እና ፍርዱን በሰጠዉ ፍርድ ቤት አገር መካከል ይህን አስመልክቶ የተደረገ ስምምነት (bilateral agreement) መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን፣ በልዩ ሁኔታ በህጉ አንቀጽ 458 ስር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተዉ ሲገኙ ነዉ። በመሆኑም በህጉ አንቀጽ 458 የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉ ከተረጋገጠ ምንም እንኳ የዉጭ አገር ፍርድ የሚፈጸምበትን ሁኔታ በተመለከተ የተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት ባይኖርም፣ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ፍርዱን ተቀብለዉ ማስፈጸም የሚችሉ መሆኑን ነዉ። ስለሆነም በዉጭ አገር የተሰጠን ፍርድ እንዲያስፈጽም ጻኝነት የቀረበለት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት በቅድሚያ እንዲያጣራ የሚጠበቅበት ለአፈፃፀም የቀረበዉን ፍርድ በሰጠዉ ፍርድ ቤት አገር እና በኢትዮጵያ መካከል የፍርድ አፈፃፀምን አስመልክቶ የተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት መኖር አለመኖሩን፣ ስምምነት የሌለ መሆኑ ከተረጋገጠ በህጉ አንቀጽ 458 ላይ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆን አለመሆኑን ነዉ።

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበዉን የአፈፃፀም ጥያቄ ዉድቅ ያደረገዉ፣ ከፍርድ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ እና በአሜሪካን ሀገር መካከል የተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት አለመኖሩንና በኢትዮጵያ የተሰጡ ፍርዶች በአሜሪካ የማይፈጸሙ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከጻፈለት ደብዳቤ ማረጋገጡን ነዉ። ይሁንና ከላይ እንደተገለጸዉ የሁለትዮሽ ስምምነት መኖር ብቸኛዉ ቅድመ ሁኔታ አይደለም። በመሆኑም የአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የተሰጡትን ፍርዶች የሚፈጽሙ መሆን ያለመሆኑን ጨምሮ ሌሎች በህጉ አንቀጽ 458 ላይ የተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች በተጨባጭ ማስረጃ ሊረጋገጡ የሚገባቸዉ ናቸዉ። የአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የሚሰጡትን ፍርድ የሚፈጽሙ መሆን ያለመሆኑና ሌሎች በህጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ፍርድ ቤቱ የአፈፃፀም አቤቱታዉን ተቀብሎ ለማስተናገድ ስልጣን ያለዉ መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ ሊረጋገጡ የሚገቡ መሠረታዊ የፍሬ ነገር ጭብጦች በመሆናቸዉ እና ፍሬ ነገሩን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ የማስረጃ ዓይነት በህግ ተለይቶ የተወሰነ እስካልሆነ ድረስ፣ ፍርድ ቤቱ ማናቸዉንም ማስረጃ በማስቀረብ እና በመመርመር እነዚህን ፍሬ ነገሮች የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል። ይህ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እነዚህን ፍሬ ነገሮች በዚህ መልኩ አጣርቶ መወሰን ሲገባዉ፣ ከኢፌዲሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀረበዉን ደብዳቤ ብቻ መሠረት

በማድረግ የሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 193868 በቀን 14/06/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 156444 በቀን 30/08/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ፣ የአሜሪካን አገር ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የተሰጠዉን ፍርድ የማስፈጸም ልምድ ያላቸዉ መሆን ያለመሆኑን ሌሎች በህጉ አንቀጽ 458 ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች አመልካች በሚያቀርቡትና ስለጉዳዩ ማስረዳት የሚችል ማንኛዉንም ማስረጃ በማስቀረብ እና በመመርመር ተገቢ ነዉ የሚለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ. 173628

ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- 1. አቶ ወ/ጨርቆስ በጋሻው ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ቅድስት በለጠ
3. ወ/ሮ ዘውዲቱ በቀለ - ወኪል አያሌው ዋልቴ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የወረዳ 13 የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ፅ/ቤት - ታልፏል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍርድ ቤት በፀደቀው የጉዲፈቻ ውል መሰረት የጉዲፈቻ ልጆች ወላጆች ስም ሳይቀር ውሉ ተመዝግቦ ሰርቲፊኬት ይሰጠኝ ጥያቄ ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት ክርክሩ የጀመረውም የአሁኑ አመልካቾች ሲሆኑ በአሁኑ ተጠሪ ላይ በ11/12/2010 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ የአሁኑ አመልካቾች በ12/12/2009 ዓ/ም ባደረጉት የጉዲፈቻ ውል ስምምነት የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ከአብራካቸው ያፈሯቸውን ተማሪ ብሌን ወ/ጨርቆስ፣ ተማሪ ቢታንያ ወ/ጨርቆስ፣ ተማሪ ማህሌት ወ/ጨርቆስ እና ተማሪ ኑሀሚን ወ/ጨርቆስ የተባሉ ልጆቻቸውን ለአሁኗ 3ኛ አመልካች እንደ ልጆቻቸው አድርገው እንዲያሳድጉ በተወካያቸው በአቶ አያሌው ዋልቴ አማካኝነት በጉዲፈቻ መስጠታቸውንና ይህ ውል በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 206723 በ30/09/2010 ዓ/ም በተሰጠ ውሳኔ መጽደቁን፣ ይህንኑ መሰረት በማድረግም ጉዲፈቻ የተደረጉት ልጆች የወላጅ አባታቸውና እናታቸው ስም ሳይለወጥ የጉዲፈቻ ውሉን መዝግቦ የጉዲፈቻ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ የአሁኑን አመልካች ሲጠይቁ የጉዲፈቻ ተቀባይ በወካያቸው አማካኝነት የጉዲፈቻ ሰርቲፊኬት ሊቀበሉ እንደማይችሉ፣ የጉዲፈቻ ተደራጊዎች የአባት ስም ሳይቀር የጉዲፈቻ ሰርቲፊኬት እንደማይሰጥ በቁጥር የካ/ክ/ክ/1013/ወ/ኩ/260/10 በ12/11/2010 በተፃፈ ደብዳቤ የገለፃላቸውና ይህ የተጠሪ አድራጎት ምንም የህግ መሰረት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው የተጠሪ ክልከላ የሕግ መሰረት የሌለው መሆኑ ተረጋግጦ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የጉዲፈቻ ተደራጊ ልጆቹን የአባትና የእናት ስም ሳይቀይሩ የጉዲፈቻ ውሉን በመመዝገብ ሰርተፍኬቱን እንዲሰጡና ሰርተፍኬቱ ላይ የዘገዩ የሚል ሳይፃፍ እንዲሰጥ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአሁኑን ተጠሪ ከመጥራቱ በፊት ውሉ በፍርድ ቤት የፀደቀ መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶና

ከጉዲፈቻ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ራሱን በቻለ ልዩ ችሎት የሚታዩ በመሆኑ ለዚሁ ችሎት ማቅረብ ወይም በውሳኔው መሰረት ይፈፀም የሚባል ከሆነም ውሳኔውን ለሰጠው ችሎት ወይም ለአፈፃጸም ችሎት ከሚቀርብ በስተቀር በዚህ ችሎት የሚታይ አይደለም በማለት የአመልካቾችን ክስ ውድቅ አድርጎታል። በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበውም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ ተጠሪ በጉዲፈቻ አድራጊ ተወካይ በኩል የቀረበውን የሰርተፊኬት ይሰጠኝ ጥያቄ አልፈፅምም ማለቱ በጉዳዩ ላይ ቀድሞ ፍርድ በተሰጠበት ጊዜ በወኪል በኩል የተደረገ የጉዲፈቻ ውል መሆኑንና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2199 ስር የተመለከተውን እንዲሁም በወሳኝ ኩነቶች አዋጅ በዚህ ረገድ ክልከላ ያለመደረጉን መሰረት ያላገናዘበ ነው በሚል ምክንያት ተገቢነት እንደሌለው ገልጾ በዚህ በኩል የቀረበውን የተጠሪን ክርክር ውድቅ ያደረገው ቢሆንም የጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃናት የአባትና አያት ስም ግን በጉዲፈቻ አድራጊ የአባት እና አያት ስም ሳይቀየር ሰርተፍኬቱ አይሰጥም መባሉ በአዋጅ ቁጥር 760/2004(በአዋጅ ቁጥር 1049/2009 እንደተሻሻለ) በአንቀፅ 70(2) መሰረት በወጣው መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንቀጽ 30 ክፍል 4 ንዑስ ክፍል 3 አንቀፅ 43 ድንጋጌ ተገቢ ነው በማለት ወስኗል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ የጉዲፈቻ ተደራጊ ህጻናት አባትና አያት ስም በጉዲፈቻ አድራጊዋ አባትና አያት ስም ሳይቀየር የጉዲፈቻ ሰርተፊኬት አልሰጥም በማለት የፈጸመው ክልከላ በሕጉ መሰረት ነው ተብሎ መወሰኑ ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ቤት የፀደቀ መሆኑን፣ መመሪያው ሌሎች ሕጎችን መሻር የማይገባው መሆኑን ጭምር ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል። እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ቁጥሩ 139051 የሆነ መዝገብ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ቁጥሩ 217446 የሆነ መዝገብ እንዲመጣ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካቾችን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው መሰረታዊ ጭብጥ አንጻር እንዲሚከተለው ተመልክተናል። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካቾች የጉዲፈቻ ውሉን አስመልክቶ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ተጠሪ ሰርቲፊኬት እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ በተጠሪ ተቀባይነት በማጣቱ ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት አፈጻጸሙ በአዋጅ ቁጥር 760/2004 መሰረት በወጣው መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንጻር ነው ማለቱ ቀድም ብሎ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 206723 በሰጠው ውሳኔ ላይ ተፅእኖ አለው? ወይስ የለውም? የሚል ነው።

በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 760/2004 የወጣበትን መሰረታዊ አላማ በአዋጁ መግቢያ ላይ የተጠቀሰ ሲሆን ይኼው አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 1049/2009 ተሻሽሎ ይገኛል። በማሻሻያ አዋጁ በአንቀፅ 70(2) ስር አግባብ ያለው የፌዴራል አካል አዋጁንና በአዋጁ መሰረት የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ እንደሚችል ደንግጓል። በአዋጁ አንቀፅ 2(7) ስር ደግሞ አግባብ ያለው አካል

ማለት ደግሞ በአዋጁ አንቀፅ መሰረት የተቋቋመ ወይም የተሰየመ የክልል አካል መሆኑ፣ በአንቀፅ 5 ስር ደግሞ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ተግባራትን በክልል ደረጃ የሚመራ፣ የሚያስተዳድርና የሚደግፍ እንዲሁም የምዝገባ መረጃዎችን አግባብ ባለው የፌደራል አካል የሚያስተላልፍ አካል መሆኑን በእያንዳንዱ ክልል የሚቋቋም ወይም የሚሰየም መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 2(11) ክልል ማለት የአዲስ አበባን አስተዳደር እንደሚጨምር ተደንግጓል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁኑ ተጠሪ በአዲስ አበባ አስተዳደር ስር የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ተግባራትን ለመምራት፣ ለማስተዳደርና ለመደገፍ እንዲሁም የምዝገባ መረጃዎችን አግባብ ባለው የፌደራል አካል ለማስተላለፍ የተሰየመ አካል መሆኑ ግልፅ ሲሆን ይህ አካል አዋጅ ቁጥር 760/2004 በአዋጅ ቁጥር 1049/2009 እንደተሻሻለ ለማስፈጸም ወይም አዋጁን ተከትሎ የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስችል መመሪያ ማውጣት የሚችል መሆኑን ሕግ አውጪው ስልጣን ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ከወጡት መመሪያዎች መካከል ደግሞ መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንዱ ሲሆን ይህ መመሪያ በክፍል 4 ንዑስ ክፍል አንቀፅ 43 ንዑስ ቁጥር 3 ስር የጉዲፈቻ አድራጊዋ ሴት ከሆነች የጉዲፈቻ ልጅ ስም ከጉዲፈቻ ውል ላይ የተፃፈው ስም፣ የአባት ስም የጉዲፈቻ አድራጊዋ አባት ስም እና የጉዲፈቻ አድራጊዋ አያት ስም እንደሚመዘገብ ደንግጓል፡፡ በፍርድ ቤት የፀደቀውን የጉዲፈቻ ውል በሚመለከት ደግሞ በንዑስ ክፍል አራት አንቀጽ 50፣51፣ 52፣53 እና 54 ስር የዘረዘረ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች የጉዲፈቻ ተደራጊ ልጆች የአባት ስምና የአያት ስም በፍርድ ቤት ከጸደቀው የጉዲፈቻ ስምምነት ግልባጭ ታይቶ የሚመዘገብ መሆኑን የሚያሳይ ግልጽ ድንጋጌ የለም፡፡ በመሆኑም በፍርድ ቤት የጸደቀ የጉዲፈቻ ውል ስምምነት በተጠሪ ተመዝግቦ የጉዲፈቻ ሰርቲፊኬት ሊሰጥ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 760/2004 አንቀፅ 70(2) ድንጋጌ አግባብ በተጠሪ በወጣው መመሪያ ቁጥር 7/2010 ክፍል አራት ንዑስ ክፍል ሶስት አንቀፅ 43(3) ድንጋጌ መሰረት እንጂ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 206723 የጉዲፈቻ ውሉ ስምምነት ሲያጸድቅ በውሉ ላይ ስለሕጻናቱ አባትና አያት ስም በሰፈረው አግባብ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪ መመሪያውን ጠቅሶ የአመልካቾችን ጥያቄ ለማስተናገድ የማይችል መሆኑን ማሳወቁም በፍርድ ቤት የተሰጠን ውሳኔ ካለመፈፀም ጋር የሚያገናኘው ምክንያት የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ በአመልካቾች መካከል የተደረገው የጉዲፈቻ ውል ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን በመመርመር የስምምነት ሰነዱን ከማረጋገጥ(AUTHENTICATE) ውጪ በአዋጅ ቁጥር 760/2004 ድንጋጌዎች እና በመመሪያ ቁጥር 7/2010 አግባብ ስለጉዲፈቻ ውል ሰርቲፊኬት አሰጣጥ በጭብጥነት ይዞ የሰጠው ዳኝነት የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 206723 የሠጠው ውሳኔ የጉዲፈቻ ውል ስምምነት መኖሩን የሚያሳይ በመሆኑና ይህ ሰነድ ደግሞ ውሉ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ እንደመሆኑ መጠን በዚሁ ውል መሰረት ስልጣን ያለው አካል የጉዲፈቻ ውል ሰርቲፊኬት ሲሰጥ በመመሪያው መሰረተ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ማድረጉ በሕጉ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር መወጣቱን ከሚያሳይ በቀር ለሕግና ለፍርድ ቤት ውሳኔ ተቃራኒ የሆነ ተግባር ፈፅሟል ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ መመሪያው ከ1952ቱ የፍትሃ ብሔር ሕጋችን በኃላ በወጣው በአዋጅ ቁጥር 760/2004 አንቀፅ 70(2) መሰረት የወጣ

ከመሆኑም በላይ በፍትሃብሔር ሕጉ 41 ስር የተመለከተውን ድንጋጌን ሊቃረን የሚችል ነው ተብሎ የሚደመደምበትን አግባብ ስላለገኘን አመልካቾች ከሕግ ደረጃና አፈጻጸም አንጻር ያነሱትን ክርክርም ለመቀበል የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካቾች ጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃናት የሚወሰዱት ወደ አሜሪካን አገር መሆኑን ጠቅሰው ከህፃናቱ መብትና ጥቅም አንጻር ያቀረቡት ክርክር ሲታይም በመሰረቱ ጉዲፈቻ ውል እንዲደረግና የሕግ ጥበቃ እንዲደረግለት ያስፈልገው በዋናነት የሕፃኑን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል እንደሆነ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትም ሆነ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም ዓቀፍ ስምምነቶች ህፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ለሕፃናት ጥቅም ደህንነት (best interest of the child) ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ መሆኑ በመርህ ደረጃ ማስቀመጣቸውን፣ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 36/5/ ስር መንግስት ለእንለማውታን ልዩ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው፣በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ስርአት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋማት እንዲመሰረቱ እንደሚያበረታታ መደንገጉን፣ከፍ ሲል የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሁሉ የጉዲፈቻ ጉዳይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት መሆኑንና በድንጋጌ አተረጓጎም ላይ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ፣ በዚህም መሰረት የጉዲፈቻ ስምምነት ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በልጁ አኗኗርና አያያዝ እንዲሁም ወደፊት ሕይወቱ ላይ በተጨባጭ ጉዳት እንዳይኖር ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳት እንደሌለም ማረጋገጥ ሲቻል እንደሆነ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 44101 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ ያወጣው መመሪያ ቁጥር 7/2010 ክፍል አራት ንዑስ ክፍል ሶስት አንቀፅ 43(3) ድንጋጌም ጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃናት በሚሄዱበት አገር በተገቢው መንገድ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ያደረጋል ተብሎ ከሚታሰብ በስተቀር በሕጻናቱ አኗኗርና አያያዝ እንዲሁም ወደፊት ሕይወቱ ላይ በተጨባጭ ጉዳት የሚያስከትል፤ ወደፊትም ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ነው ሊያሰኝ የሚችል ሁኔታ መኖሩን ለመገንዘብ የሚያስችል ምክንያት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካቾችን ክርክርም አልተቀበልነውም፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 217446 በ26/06/2011 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ህ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

አ/ን

የሰበር መዝገብ ቁጥር 172784

ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-አቶ አቡበከር አህመድ መሐመድ - ተወካይ ወ/ሮ ሰዓዳ አብደላ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ሳራ ሱፍያን አብዱረህማን - ጠበቃ ሀኒፍ ይህደጎ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከልጅ ቀለብ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ለአንድ ልጅ ቀለብ ከግንቦት ወር 2010 ዓ.ም. ጀምሮ በየወሩ ብር 10,000 /አስር ሺህ/ እንዲከፍሉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 85022 በ24/08/2010 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 219131 በ05/06/2011ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪዋ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ14/05/2010 ዓ.ም. ባቀረቡት ክስ ፍቺ እንዲወሰን እና አመልካቹ በሶስት የንግድ ፈቃዶች በመሥራት በወር በአማካይ ብር 100,000/ አንድ መቶ ሺህ/ ገቢ የሚያገኙ መሆኑን ገልጸው በጋብቻው ለተወለደው የሶስት ወር ዕድሜ ላለው ልጃቸው በየወሩ ብር 20,000 /ሃያ ሺህ/ ቀለብ እንዲከፍሉ እንዲወሰን የጠየቁ ሲሆን አመልካቹ በበኩላቸው በ20/06/2010 ዓ.ም. በሰጡት መልስ የፍቺ ጥያቄውን የማይቃወሙ መሆኑን እና የወር ገቢያቸው ግን ተጠሪዋ እንደሚሉት ሳይሆን በወር ከብር 5,000 /አምስት ሺህ/ የማይበልጥ መሆኑን ገልጸው በተጠሪዋ የቀረበው የተጋነነ የልጅ ቀለብ ጥያቄ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ክሱ

የቀረበለት ፍርድ ቤትም በጊዜያዊነት የብር 4,000 /አራት ሺህ/ የልጅ ቀለብ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ የአመልካቹ ገቢ ተጣርቶ እንዲቀርብ አድርጎ በሚመለከተው አካል የተገለጸውን የአመልካች ገቢ መጠን በአስረጂነት በመጥቀስ የፍቺ ውሳኔ በሰጠበት ቀን አመልካቹ ለአንድ ልጅ ቀለብ ከግንቦት ወር 2010 ዓ.ም. ጀምሮ በየወሩ ብር 10,000 /አስር ሺህ/ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል።በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ የጸናው ይኸው ውሳኔ ሲሆን አመልካቹ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት ለቀለብ አወሳሰኑ መሠረት ያደረገው ከገቢዎች አስተዳደር ጽ/ቤት የተላከው ማስረጃ የአመልካቹን ጠቅላላ ገቢ እንጂ ልዩ ልዩ ተቀናሽ ወጪዎችን ያላገናዘበ ከመሆኑ አንጻር የቀለብ አወሳሰኑን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ክርክሩ የተስተናገደበትን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ጭምር አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል።

በዚህም መሰረት የልጅ ቀለብ አወሳሰን ጥንቃቄ የሚያስፈልገውና የሕፃናትን ደህንነትና ጥቅም የሚያረጋግጥ መሆን እንደሚገባው የሚታወቅ ሲሆን የሕፃናትን ጉዳይ በሚመለከት የሚወሰዱ እርምጃዎች እና የሚሰጡ ውሣኔዎች በሙሉ የሕፃናትን ጥቅም ተቀዳሚ ያደረጉ መሆን ያለባቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት በአንቀጽ 36(2) ስር ይደነግጋል።በሕጻናት መብት አጠባበቅ እና አወሳሰን ረገድ አገሪቱ ያፀደቀቻቸው የአገሪቱ የሕግ አካል የሆኑ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችም ከግምት መግባት እንደሚገባቸው የሚያጠያይቅ አይደለም።ፍርድ ቤት ጋብቻ እንዲፈርስ ሲወስን ውሳኔ ሊያሳርፍባቸው ከሚገቡ ቀዳሚ ጉዳዮች መካከል አንዱ የልጆች አስተዳደግ፣የትምህርት፣የጤና፣የቀለብ እና የአጠቃላይ አኗኗራቸው ጉዳይ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 213/1992 በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 113 (1) ስር የተመለከተ ሲሆን በቀለብ አወሳሰን ረገድም ውሳኔው በሚሰጥበት ጊዜ የነበረው የወላጆች የገቢ፣የዕድሜ፣የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ፣እንዲሁም የልጆቹ ዕድሜ፣ጥቅማቸው እና ፍላጎታቸው ከግምት መግባት የሚገባቸው ስለመሆኑ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ስር ተመልክቷል።ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሰረት ስለልጆች አያያዝ እና አጠባበቅ የሚሰጠው ውሳኔ የሁኔታዎች መለዋወጥን ምክንያት በማድረግ በሚቀርብ ጥያቄ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ የሚችል ስለመሆኑም በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) ስር ተደንግጎ ይገኛል።

በተያዘው ጉዳይ የአመልካቹን ወርኃዊ የገቢ መጠን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ክርክር ያቀረቡ ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በቀለብ አወሳሰኑ ረገድ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ያስችለው ዘንድ በደቡብ ወሎ ዞን የደሴ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት የአመልካቹን የ2009 ዓ.ም. ዓመታዊ ገቢ አጣርቶ እንዲገልጽ በ14/07/2010 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ

መሠረት አመልካቹ የሂሳብ መዝገብ ያቀረቡ መሆኑን እና ዓመታዊ ገቢያቸው ብር 1,817,379.04 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ አስራ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ከዜሮ አራት ሳንቲም/ መሆኑን ገልጾ ጽ/ቤቱ በቁጥር አወ/አሰ/ክት/7213/2010 በ02/08/2010 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል።ፍርድ ቤቱ ከገቢዎች ጽ/ቤት በቀረበው ምላሽ ላይ የግራ ቀኙን የጽሁፍ አስተያየት ከተቀበለ በኋላ የቀለብ ውሳኔ የሰጠው በጽ/ቤቱ የተገለጸውን ዓመታዊ ገቢ ወደ ወርኃዊ ገቢ በመለወጥ አመልካቹ ብር 151,448 /አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺህ አራት መቶ አርባ ስምንት/ ወርኃዊ ገቢ አላቸው በማለት መሆኑን ከዋናው መዝገብ ተመልክተናል።ይሁን እንጂ በደቡብ ወሎ ዞን የደሴ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት የአመልካቹን ዓመታዊ ገቢ ከመግለጹ በቀር ይህ ዓመታዊ ገቢ ተገቢ ተቀናሾች ሁሉ ታሳቢ ተደርገው ከግብር በኋላ የተገኘ የተጣራ ገቢ ስለመሆኑ ለይቶ ያልገለጸ መሆኑን ከስር መዝገብ ጋር ተያይዞ ከሚገኘው የደብዳቤው ይዘት እና ግራ ቀኙ በደብዳቤው ላይ በጽሁፍ ካቀረቡት አስተያየት ተገንዝበናል።የተጣራ መሆኑ ያልተረጋገጠን የገቢ መጠን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ የቀለብ ውሳኔ ደግሞ የከፋዩን ትክክለኛ የመክፈል አቅም ያገናዘበ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም።በመሆኑም የቀለብ መጠኑ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊመለስ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል።

በሌላ በኩል የተጣራ ዓመታዊ ገቢያቸው ብር 154,235.43 /አንድ መቶ ሃምሳ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ከአርባ ሶስት ሳምቲም/ መሆኑን እና የተጣራ ወርኃዊ ገቢያቸው ደግሞ ብር 12,860.45 /አስራ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ስድሳ ከአርባ አምስት ሳምቲም/ መሆኑን አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ላይ የገለጹ መሆኑን መሠረት በማድረግ ይህ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የሚከፍሉት በስር ፍርድ ቤት በተወሰነባቸው መጠን መሠረት መሆኑ እንደተጠቀበ ሆኖ ትክክለኛው የቀለብ መጠን በስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ እስኪወሰን ድረስ አመልካቹ ከሐምሌ ወር 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የተጣራ ወርኃዊ ገቢዬ ነው በማለት የገለጹትን ገቢ አጋማሽ ብር 6,430.22 /ስድስት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ከሃያ ሁለት ሳንቲም/የልጅ ቀለብ እየከፈሉ እንዲቆዩ ማድረጉ ተገቢ መሆኑን ተገንዝበናል። ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. አመልካቹ ለአንድ ልጅ ቀለብ ከግንቦት ወር 2010 ዓ.ም. ጀምሮ በየወሩ ብር 10,000 /አስር ሺህ/ እንዲከፍሉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 85022 በ24/08/2010 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 219131

በ05/06/2011ዓ.ም. በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካች የሚከፍሉት ወርኃዊ የልጅ ቀለብ የገንዘብ መጠን ብር 10,000 /አስር ሺህ/ ነው በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የአመልካቹን የተጣራ የገቢ መጠን አጣርቶ ተገቢ ነው የሚለውን የቀለብ ገንዘብ እንዲወስን ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሠረት በፊዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
4. ይህ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የሚከፍሉት በስር ፍርድ ቤት በተወሰነባቸው መጠን መሠረት መሆኑ እንደተጠቀበ ሆኖ ትክክለኛው የቀለብ መጠን በስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ እስኪወሰን ድረስ አመልካቹ ከሐምሌ ወር 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የተጣራ ወርኃዊ ገቢዬ ነው በማለት የገለጹትን ገቢ አጋማሽ ብር 6,430.22 /ስድስት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ከሃያ ሁለት ሳንቲም/ የልጅ ቀለብ እየከፈሉ እንዲቆዩ ወስነናል፡፡
5. በቀሪ ጉዳዮች ረገድ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
6. የውሳኔው ቅጂ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለፊዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለፊዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ.153405

ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ፅጌ በንቲ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ ፡- አቶ ተስፋዬ ታደሰ - ጠበቃ አቶ ይልማ በየነ ቀረቡ ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ የፍቺ ውጤትን የሚመለከት ነው ፡፡ ጉዳዩ የጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ነው ፡፡ የአሁን አመልካች ታህሳስ 5 ቀን 2005 ዓ/ም ያቀረቡት የክስ አቤቱታ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ ህዳር 19 ቀን 2005 ዓ/ም በተሰጠ ውሳኔ መፍረሱን ፣ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ በነበሩ ጊዜ ያፈሩት የጋራ ንብረት የሆነው በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13/14 ብሩህ ተስፋ ቁጥር 1 በሚባለው ሳይት ላይ የህንፃ ቁጥር B6/10 የኮንደሚኒየም ቤት ከየካ ክፍል ከተማ የቤቶች ማስተላለፍ ጽ/ቤት ጋር ህዳር 20 ቀን 2000 ዓ/ም በተደረገው የሽያጭ ውል መግዛታቸውን፣የቤቱ ካርታ በተጠሪ ስም የተሰጠውም በየካቲት 10 ቀን 2002 ዓ/ም መሆኑን ገልጸው በተጠሪ ስም የተመዘገበ ቢሆንም በጋብቻ ውስጥ የተፈራ በመሆኑ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል የአሁን ተጠሪም መጋቢት 23 ቀን 2005 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የኮንደሚኒየሙን ቤት የተመዘገቡት ፣ እጣው የወጣው አጠቃላይ ክፍያውን አጠናቀው የከፈሉት አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸውን ከመፈጸማቸው በፊት መሆኑን አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ የፈጸሙት በህዳር 19 ቀን 2000 ዓ/ም ከቀኑ 8፡15 ሰዓት እንደሆነ ፣ ለኮንደሚኒየም ክፍያ የተከፈለው ግን ጠዋት መሆኑን ፣ ለዚህም አመልካች በቤቱ ባለቤትነት ሳይሆን በምስክርነት የፈረሙ መሆኑን ገልጸው የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ይደረግ በማለት ተከራክሯል ፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኃላ የቤቱ እጣ የወጣው ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 51893 ፣ 46606 እና 75562 በሰጣቸው ውሳኔዎች መሰረት ለኮንደሚኒየም ባለቤትነት ዋናው ጉዳይ እጣ መውጣቱ ነው ። ስለዚህ ቤቱ የአሁን ተጠሪ የግል ሀብት ነው ሲል ወስኗል ። አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል ። ይግባኙ የቀረበለት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል ።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስቀየር ሲሆን አመልካች በጠበቃቸው በኩል ጥር 30 ቀን 2010 ዓ/ም የተጻፈ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻ የተፈጸመው ህዳር 19 ቀን 2000 ዓ/ም ሲሆን የኮንደሚኒየም ቤቱን አስመልክቶ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የየካ ክፍለ ከተማ የቤቶች ማስተላለፍ ጽ/ቤት ጋር የሽያጭ ውል የተፈራረመው ህዳር 20 ቀን 2000 ዓ/ም በጋብቻ ውስጥ ነው ። የቤቱ ሽያጭ ዋጋ ብር 29,087.10 /ሀያ ዘጠኝ ሺህ ሰማኒያ ሰባት ብር ከአስር ሳንቲም/ የተከፈለው በጋብቻ ውስጥ ነው ። ይህ ገንዘብ የተከፈለውም አመልካች በተበዳሪነት በፈረሙት የብድር ውል መሰረት ህዳር 19 ቀን 2000 ዓ/ም አመልካች እና ተጠሪ ሆነን ከወ/ሮ ትዕግስት ሐዋዝ በብድር ካገኘነው ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ላይ ወጪ ተደርጎ ነው። የስር ፍርድ ቤቶች ቤቱ የጋራ አይደለም በማለት የወሰኑት የቤቱ ቅድመ ክፍያ የተፈጸመውና የሽያጭ ውሉ የተደረገው በጋብቻ ውስጥ ቢሆንም የኮንዶሚኒየም እጣው ለተጠሪ የደረሰው ከጋብቻ በፊት ነው በሚል ምክንያት ነው። እጣ መውጣት ለብቻው የቤት ባለቤት አያደርግም የቤት ባለቤትነት የሚገኘው በነባ ሳይሆን በግዢ በመሆኑ እጣው የደረሰው ሰው ከሚመለከተው መንግስት አካል ጋር የሽያጭ ውል ተዋውሎ የሽያጩን ገንዘብ ካልከፈለ እድሉ ከሚያመልጠው በቀር እጣው ብቻ ባለሀብት ሊያደርገው አይችልም ። በመሆኑም የቤቱ ባለቤት ለመሆኑም የቤቱ ባለቤት ለመሆን ዋናው ጉዳይ የሽያጭ ውሉን ማድረግና ክፍያውን መፈጸም ነው። አሁን በተያዘው ጉዳይም የሽያጭ ውሉ የተፈረመውና ክፍያ የተፈጸመው በጋብቻ ውስጥ በመሆኑ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ቤቱ የጋራ አይደለም ብለው መወሰናቸው ስህተት ነው። የኮንዶሚኒየም ቤቱን ከመንግስት ከተረከብን በኋላ በጋብቻው ውስጥ የልጋ ስራ ተሰርቷል ፣ ቻክ ተደርጎ ቀለም ተቀብቷል ለመኝታ ቤት እና ለሻኞ ቤት ሁለት በሮች ተገጥመዋል ፣ ሻኞ ቤት እና ሽንት ቤት ሙሉ እቃ ተሟልቶበት በሴራሚክ ተሰርቷል ፣ ለማዕድ ቤቱ ኪችን ካቢኔት ተስርቷል ፣ ሌሎች የማጠናቀቂያ ስራዎች ተሰርተዋል። ይህን የማጠናቀቂያ ስራ ለመስራትም ብር 80,200 /ሰማኒያ ሺህ ሁለት መቶ ብር/ ወጪ ተደርጓል። ይህን ስራ ለመስራት ከባለሙያ ጋር የተደረገው ውል በማስረጃነት ለስር ፍርድ ቀርቧል። የቤቱ ወጪ የተሸፈነው አመልካችና ተጠሪ በጋራ በተበደርነው ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ መሆኑን ክርክር እንዲሁም የጽሁፍ ማስረጃ አቅርቤ ምስክሮችን ዘርዝሬ እያለሁ የስር ፍርድ

ቤቶች ግን በተለይም የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ለቤቱ መገኘት ያደረጉት አስተዋጽኦ የለም በማለት ቤቱ የጋራ አይደለም ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው።

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች የአካራካሪው የኮንደሚኒየም ውል የተፈረመው ፣ የቤት ሽያጭ ዋጋ የተከፈለውም በጋብቻ ውስጥ በጋራ በተፈረመ ብድር ነው በማለት ያቀረበችው ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች የቤቱ እጣ የወጣው ከጋብቻ በፊት ነው በሚል ብቻ የሰበር መዝገብ ቁጥር 43988 ተጠቅሶ የመወሰኑን አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል ።

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ/ም የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቤቱታው ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበ ነው የሚል ሲሆን አማራጭ መልስ ይዘትም በአጭሩ የኮንደሚኒየም እጣ ቅድመ ክፍያ እና የማጠቃለያ ክፍያ በሙሉ የተፈጸመው ከጋብቻ በፊት ከግል ገንዘቤ ሲሆን አመልካች በኮንደሚኒየም የቤት ሽያጭ ዋጋ የተከፈለው በጋራ በተፈረመ የብድር ውል በተገኘ ገንዘብ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ከእውነታው ውጪ ከመሆኑም በላይ በሀሰት የቀረበ ክርክር ነው ። አመልካች የኮንደሚኒየም ቤት ሙሉ ክፍያ ከግል ገንዘቤ ከከፈልኩ በኋላ ያውም በማላውቀው እና ባልፈረምኩት የብድር ውል በተገኘ ገንዘብ ቤት ክፍያ እንደተፈጸመ ተደርጎ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም። የሰበር መዝገብ ቁጥር 43988 ውሳኔ ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት የለውም። አመልካች በሽያጭ ውል ላይ የፈረሙት የምስክርነት ነዉ የቤት እድሳትም የተከናወነዉ አመልካች እንደሚሉት በብድር ገንዘብ ሳይሆን ተጠሪ አሜሪካ ሀገር ከሄድኩ በኋላ በላኩት ገንዘብ ሲሆን የቤቱ ጠቅላላ ዋጋ ብር 29,087.10 /ሃያ ዘጠኝ ሺህ ሰማኒያ ሰባር ብር ከአስር ሳንቲም /ስለሆነ ብር/ 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የምትበደርበት ምክንያት የሌለ ከመሆኑም በላይ እድሳቱም ቢሆን ለቤቱ ከተከፈለዉ ብር 29,087.10 በላይ ብር 80,000 ከቤቱ ዋጋ ከሶስት እጥፍ በላይ ወጭ አድርጌበታለሁ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በሀሰት የቀረበ ከመሆኑም በላይ ሊታመን የማይችል በመሆኑ በዚህ በኩል የቀረበዉ አቤቱታ የህግ ክርክር ሳይሆን የፍሬ ነገር እና የማስረጃ በመሆኑ ለዚህ ሰበር ሊቀርብ አይገባም። ሲጠቃለልም የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነዉ። የአመልካች ጠበቃም ሚያዚያ 02 ቀን 2011 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።

የነገሩ አመጣጥ የክርክሩ ሂደት በአጭር ከላይ እንደተገለጸዉ ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ የኮንድሚንየም ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነዉ ተብሎ በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ ህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ወይስ አልተፈጸመበትም የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል። በቅድሚያ ግን በተጠሪ ጠበቃ ከሰበር አቤቱታ ጊዜ ማለፍ ጋር አያይዘዉ ያነሱትን መቃወሚያ በተመለከተ የአመልካች ጠበቃ በሰጡት የመልስ መልስ ጉዳዩ በሌላ መዝገብ በስር ክርክር ካለዉ ጉዳይ ጋር የተያያዘ በመሆኑ አመልካች በቀረቡ ጊዜ የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ ተዘግቷል።

በመሆኑም አመልካች በሌላ መዝገብ ያለዉ ክርክር ማለትም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ. 79982 የነበረዉ ክርክር ተጠናቆ በቀን 25/04/2011 ዓ/ም ዉሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ ከዚህ መዝገብ ጋር ተያይዞ ቀድሞ በተሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት ጉዳዩ ከቆመበት እንዲቀጥል ጥር 10 ቀን 2011 ዓ/ም አቤቱታ በመቅረቡ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ ጋር የተነሳዉ ክርክር ይህ ችሎትም እንደተመለከተዉ ለቤቱ ግዢ እና ተጠሪን ወደ አሜሪካን አገር ለመሸኘት ተወስዷል ተብሎ አመልካች ተጠሪ እንዲከፍሉ ተብሎ የቀረበ የብድር ገንዘብ ክስ ምክንያት ያደረገ ክርክር ቀደም ሲል እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ ደርሶ በሰበር መዝገብ ቁጥር 117975 ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የሚጣሩ ነጥቦች ተለይተዉ በስር ፍ/ቤት ቤት ተመልሷል፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ ችሎት ጉዳዩን አጣርቶ በኮ/መ/ቁ. 79982 በቀን 25/04/2011 ዓ/ም ዉሳኔ መሰጠቱን ከተደረገዉ ክርክር ይዘት እንዲሁም ከዉሳኔዉ የተመለከትን በመሆኑም በዚህ ምክንያት ለዚህ ሰበር መነሻ የሆነዉ አቤቱታ ተዘግቶ መቆየቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ከዚህ ጋር አያይዘዉ ያነሱትን ቅሬታ አግባብነት ያለዉ ሆኖ አላገኘነዉም፡፡

በሌላ በኩል ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተዉ በግራ ቀኙ መካከል ጋብቻ የተፈጸመዉና ለክርክሩ ምክንያት ለሆነዉ ቤት ክፍያ የተከፈለዉ ህዳር 19 ቀን 2000 ዓ/ም ነዉ፡፡

ተጠሪ ይህንን ሳይክዱ የሚከራከሩትን የኮንድሚንየም ቤት ገንዘብ ጠዋት ከተከፈለ በኃላ ጋብቻ ከሰአት በኃላ ተፈጽሟል የሚል ነዉ፡፡ በአንድ ቀን ዉስጥ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ህጋዊ ድርጊት እንደተፈጸመና ይህም ልዩነት ልያመጣ እንደሚችል ተጠሪ ቢከራከሩም በስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ላይ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የኮንደምንየም ቤቱ ክፍያ እና የቤቱ ሽያጭ ዉል የተፈጸመዉ ጋብቻ ዉስጥ መሆኑ ነዉ፡፡የስር ፍ/ቤቶችም ዉሳኔያቸዉ ይህንን አምነዉ ተቀብለዋል፡፡የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የኮንደምንያም ቤቱ የተጠሪ የግል ንብረት ነዉ በማለት ሊደመድም የቻለዉ እጣዉ ከጋብቻ በፊት የደረሰ በመሆኑ ነው የሚል ነው፡፡ የኮንደምኒየም ቤት እጣው ብቻ ከጋብቻ በፊት መድረስ ክፍያ ባልተፈጸመ ሁኔታ ተጠሪን ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቤት ብቸኛ ባለመብት ሊያደርግ ይችላልን? የሚለዉን ምላሽ ሊያገኝ የሚገባዉ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት አቅርቦ የተከራከሩት ክርክር ይሁንታ የሚሰጠው ነዉ የሚል ነዉ፡፡ ምክንያቱም እጣ መዉጣት ለብቻዉ የቤት ባለቤት አያደርግም፡፡ የኮንድምንየም ቤት ባለቤትነት የሚገኘዉ በነጻ ወይም እጣዉ በመዉጣቱ ብቻ ሳይሆን በግዢ በመሆኑ ገንዘቡ ሲከፈል ነው ፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለጸው ገንዘብ የተከፈለው በጋብቻ ውስጥ ነው፡፡ ይህ የተከፈለው ገንዘብም በብድር የተገኘ መሆኑንና የብድር ውሉንም አያይዘው ማቅረባቸው አመልካች አጥብቀው ተከራክረዋል ፡፡ ተጠሪ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር ለኮንደሚኒየም ቤቱ የተከፈለው ገንዘብ የግላቸው ስለመሆኑ የተከራከሩ ቢሆንም ይህንን በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ አላረጋገጡም ፡፡ በአንድ ክርክር ላይ መብትና ጥቅም አለኝ የሚል ተከራካሪ ወገን ይህንን የማስረዳት ሸክም የእራሱ ስለመሆኑ ከማስረጃ ህግ መርህ የምንገነዘበው ነው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 255 እና ተከታዮቹ

ድንጋጌዎችም ይህንን መርህ የሚያጠናክሩ ናቸው ። በፍትሐብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44634 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል ። በመሆኑም ለክርክሩ ምክንያት ለሆነው ቤት የተከፈለው ገንዘብ ምንጭ የተጠሪ የግል መሆኑን ካላስረዱ በስተቀር ቤቱ የተጠሪ የግል ነው ሊባል የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም ።ከዚህ በተጨማሪ የአካራካሪው ኮንደሚኒየም ቤት የሽያጭ ውል የተፈረመው ወይም የተደረገው በጋብቻው ውስጥ ነው። የቤት ባለቤትነት ወይም የቤቱ ካርታ በተጠሪ ስም የተሰጠውም የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ/ም ሲሆን ይህም አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ አብረዉ እያሉ ነው። እነዚህ ሁሉ ተዳምረው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የጋራ ንብርት እንደሆነ አረጋጋጭ ናቸው።

በመጨረሻም የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን በአግባቡ ሳያጤኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ኮንደሚኒየም ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ። በመሆኑም ቀጥሎ ያለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ.103524 በቀን 28/02/07 ዓ/ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.163552 በቀን 20/4/2010 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል።
2. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ኮንደሚኒየም ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ተወስኗል ።
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
4. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው።
5. ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሰ/ጥ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 189201

መጋቢት 02 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች ፡-ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- ---1. አቶ ወድወሰን ታደሰ ይስማ

2. ወ/ሮ ወይንሸት ደስታ አጠረዉ } የሌሎችም ወኪል 2ኛ አመልካች ቀርበዋል

3. ወ/ሪት ጥሩነሽ በቀለ ስዩ

ተጠሪ ፡- የለም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሆኖ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል ፡፡

ፍ ር ድ

ኢትዮጵያዊ እናት እና አባት የሆኑት 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች በትዉልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነት አሜሪካዊ የሆኑት የ2ኛ አመልካች እህት 3ኛ አመልካች የ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ልጅ የሆነችዉን ተማሪ ኤፍራታ ወንደሰን ቤተሰብ ለልጅ የሚያደርገዉን ሁሉ ከልጅነቷ ጀምሮ ካለችበት ሀገር ሆና ስትንከባከባት የነበረች እና በምትኖርበት ሀገርም ልጇ መሆኗን የተለያዩ ፍርሞችን መመላቷን አንስተዉ በአመልካቾች መካከል የተደረገዉ የተማሪ ኤፍራታ ወንደሰን የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲፀድቅላቸዉ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 103957 በ2/11/2011 በዋለዉ ችሎት የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 የተከለከለ ነዉ በማለት አቤቱታዉን ባለመቀበል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ ነባሩ የዉጭ ጉዲፈቻን በአዋጅ ቁጥር 1070/2010 መተካት ያስፈለገዉ ሕጉን ከብሔራዊ የሕፃናት ፖሊሲ ጋር ለማጣጣም ሆኖ ለሕጉ መሻሻል መሠረት የሆነዉ ፖሊሲ ይዘትም ኢትዮጵያዊያን ህፃናት የትዉልድ አከባቢያቸዉን ባህል፣ልማድ፣ወግ እና ማህበራዊ እሴቶችን ጠብቀዉ እንዲያድጉ የተቀረፀ ሲሆን ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን የዉጭ ሀገር ዜጎች እንደ ሀገራቱ ዜጋ በኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ፣አስተዳደርዊ ጉዳዮች እንዲሳተፉ ህግ ወቶ በመንቀሳቀስ ላይ እያሉ የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻን የሚከለክል የህግ ማሻሻያ መደረጉ እና ይህ ክልከላ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን የዉጭ ሀገር ዜጎችን እንደማይመለከት በግልጽ አለመደንገጉ ዕገዳዉ እነሱንም የሚጨምር መሆኑን ያመላክታል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 337 መሠረት በመዝገብ

ቁጥር 237661 ላይ ታህሳስ 16 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነዉ በማለት በሰበር እንዲታረምላቸዉ አመልካቾች ጥር 14 ቀን 2012 ዓ.ም ጠይቀዋል።

አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፥-ተጠቃሹ አዋጅ የከለከለዉ በአመልካቾች መካከል የተደረገዉ የጉዲፈቻ ዉል ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለሌላ ሀገር ዜጋ በጉዲፈቻ ሲሰጥ ሆኖ እያለ የጉዲፈቻ ዉል ሰጪዎች ኢትዮጵያዊያን ሲሆኑ 2ኛ የጉዲፈቻ ዉል ሰጪ የጉዲፈቻ ዉል ተቀባይ ታላቅ እህት ሆኖ ባለዉ የመረዳዳት ባሕህል በጉዲፈቻ ልትወስዳት የፈለገችዉን ተማሪ ኤፍራታ ወንደሰን በእናት እና አባት ለልጅ መደረግ የሚገባዉን ሁሉ እያደረገች አሁን እስካለችበት እድሜ የምትንከባከባት እና በምትኖርበት ሀገርም ልጂ በማለት ፎርማሊትዎችን አሟልታ የጉዲፈቻ ዉሉን መፅደቅ ብቻ የምትጠባበቅ መሆኑን ገልፀዉ ያቀረቡት የጉዲፈቻ ዉል እንዲፀድቃላቸዉ ጠይቀዋል።የሰበር አጣሪ ችሎቱም የጉድፈቻ ጥያቄ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን የሆኑትን የዉጭ ሀገር ዜጎችን ያካትታል ወይስ አያካትትም የሚለዉን ከአዋጅ ቁጥር 1070/2010 እና ቤተሰብ ህጉ አላማ እና አተረጓገም አንፃር ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጧል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ከላይ የተጠቀሰዉን የሚመስል ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን 3ኛ አመልካች የጉዲፈቻ ዉሉን ለመቀበል አይችሉም ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን /አለመሆኑን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር እንደሚከተለዉ መርምሯል።ጉዲፈቻ ከሥጋ መወለድ ዉጭ ወይንም የደም ትስስር ሳይኖር በህግ ልጅነት ወይንም የልጅ ቤተሰብ ግንኙነት የሚፈጠርበት ህጋዊ ተግባር (juridical act) ነዉ።ይህ ተግባር ጥንታዊ ሆኖ የተስፋፋዉ እና ብዙ ሀገሮች የህግ ሥርዓታቸዉ አካል ማድረግ የጀመሩት ከ2ኛ ዓለም ጦርነት ወዲህ ነዉ።በኢትዮጲያም የጉዲፈቻ ባህል በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል።በጥንቱ ዘመን ጉዲፈቻ ይደረግ የነበረዉ ጉዲፈቻ አድራጊዉን በእርጅና ጊዜ ለመርዳት፣ወራሽ እንዲያገኝ ፣ዘሩ እንዲቀጥል፣ሴት ወይንም ወንድ ልጅ ለሌላቸዉ ለመስጠት ወዘተ ሆኖ በአጠቃላይ ለጉዲፈቻ አዲራጊዉ ጥቅም ተብሎ የሚደረግ ነበር።በተፈጥሮ እና ሠዉ ሰራሽ ክስተቶች ምክንያት መፈናቀል እየበዛ ሲመጣ ወላጅ አልባ ለሆኑት እና ተጥሎ የተገኙ ህፃናትን ለመታደግ ጉዲፈቻ እዉነተኛ የቤተሰብ ተቋም እየሆነ መጧል።በዘመናዊዉ ሕግ የጉዲፈቻ ዓላማ የሕፃናት ደህንነትን (best interst of the child) በማስጠበቅ ሕፃናት በሥጋ ከወለዷቸዉ ቤተሰብ ዉጭ ተተኪ ቤተሰብ እንዲያገኙ ለማስቻል ነዉ።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ እ. ኤ. አ ታህሳስ 20 ቀን 1989 ዓ.ም ፀድቆ መስከረም 2 ቀን 1990 ዓ.ም በሥራ ላይ የዋለዉ ኢትዮጵያም ተቀብላ ያፀደቀችዉ የሕፃናት መብት ኮንቬንሺን አንቀጽ 20 ላይ እንደተገለጸዉ ተዋዋይ ሀገሮች ከቤተሰባቸዉ ለተለዩ ሕፃናት አማራጭ እንክብካቤ የሚያገኙበት መንግስት ማዘጋጀት ያለበት መሆኑንና ከዚህ ዉስጥ ጉዲፈቻ አንዱ መሆኑን

አንቀጽ 20 የሚደነግግ ሲሆን በአንቀጽ 21(ለ) መሠረት የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ የሚፈቀደዉ ሕፃናት በሀገር ዉስጥ አማራጭ እንክብካቤ የሚያገኙበት ማዕከል የሌለ እንደሆነ መሆኑን ያስረዳል።በሀገር ዉስጥ እና በዉጭ ሀገር የሚደረግ ጉዲፈቻ እኩል ጥበቃ የሚደረግላቸዉ መሆኑን፣ጉዲፈቻ ዉስጥ ተሳትፎ ያላቸዉ አካላት የማይገባ ጥቅም እንዳያገኙ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑና የሕጉን ዓላማ ለማራመድ በሀገሮች መካከል የሁለትዮሽ እና ሌሎች ስምምነቶች እንደሚደረጉ አንቀጽ 21(ሐ)፣(መ) እና (ሠ) ይደነግጋል።የአፍርካ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 24(ለ) የሕፃናት መብቶች ስምምነቶች በተቀበሉ ወይንም ባፀደቁ ሀገራት መካከል የዉጪ ሀገር ጉዲፈቻ እንደመጨረሻ አማራጭ የሚደረግ መሆኑና አንቀጽ 24(ረ) ሥር ጉዲፈቻ የተደረገዉ የሕፃናት ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን መዘርጋት ግዴታ መሆኑን ያስረዳል።እነዚህ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ የሕግ አካል መሆናቸዉን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(4) ይደነግጋል። የሕጻናት መንት ኮንቬንሽን በአዋጅ ቁጥር 11/1984 የጸደቀ ሲሆን የአፍሪካ ሕጻናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 283/1994 ጸድቋል። በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ስምምነቶች የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ በሀገር ዉስጥ አማራጭ ሕፃናት ከወላጆቻቸዉ ዉጭ እንክብካቤ የሚያገኙበት መንገድ በማይኖርበት ወቅት የሚደረግ ሆኖ ሕፃናቱ ለተለያየ የሰበአዊ መብት ጥሰት እንዳይጋለጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት መሆኑን ያስረዳሉ።

መንግስት እንለ ሙታን በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት እንደሚያመቻች ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 36(5) ይደነግጋል።የቤተሰብ ሕጉን ለማሻሻል ካስፈለጉት ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ ለሕፃናት ደህንነት ቅድሚያ ለመስጠት መሆኑ ከተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መግቢያ መገንዘብ ይቻላል።በዚህ አዋጅ አንቀጽ 194(3)(መ) መሠረት ጉዲፈቻ አድራጊዉ የዉጭ ሀገር ዜጋ ሊሆን የሚችለዉ ሕፃኑ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚያድግበት ሁኔታ አለመኖሩ ሲረጋገጥ ሆኖ አፈፃፀሙም በአንቀጽ 193 ሥር ተመላክቷል።የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ ለ17 ዓመታት በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ሚያዚያ 2009 ዓ/ም የወጣዉ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የህፃናት ፖሊሲ በአስቸጋሪ ሁኔታ ዉስጥ የሚገኙት ህፃናት *በኢትዮጵያ ባህል፣በአስባቢያቸዉ ወግ ፣ልማድና በማህብረሰባዊ እሴት ታንፀዉ እንዲያደጉ* ለማድረግ በአገር ዉስጥ ባሉ አማራጭ የድጋፍ እና እንክብካቤ አገልግሎቶች ማለትም በማህብረሰብ አቀፍ ድጋፍ እና እንክብካቤ፣በሀገር ዉስጥ ጉዲፈቻ፣በአደራ ቤተሰብ እና በመልሶ ማቀላቀል እና ማዋሀድ ፕሮግራሞች *ብቻ* እንዲደረግ ማድረግ ከዝርዝር ዓላማዎቹ ዉስጥ አንዱ ነዉ።ፖሊሲዉ ዉስጥ እንደ ዋና ዋና ጉዳዮች ከተጠቀሱት መካከል በአስቸጋር ሁኔታ ዉስጥ ያሉት ሕፃናት የሚደገፉበትን የሚመለከት ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች ወላጆቻቸዉን ያጡ ተንከባካቢ የሌላቸዉ ሕፃናት የቤተሰብ ፍቅር ፣ እንክብካቤ እና ጥበቃ አግኝተዉ መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸዉ ተሟልተዉ እንዲያድጉ ለማድረግ የሚያስችሉ እንክብካቤ የሀገር ዉስጥ ጉዲፈቻ፣የአደራ ቤተሰብ እና በማህብረሰብ አቀፍ ድጋፍ እና እንክብካቤ ፕሮግራሞችን በማስፋፋት

ለሕይወታቸዉ ጠቃሚ የሆኑ የምክር አግልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲስፋፉ እና ተደራሽ በማድረግ የኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ አገልግሎቶችን በጥራት፣ በስፋት በወቅቱ እንዲደርሳቸዉ በማድረግ እንደየ ችግራቸዉ ዓይነት በማህበረሰቡ ያሉ እሴቶችን በመቀመርና በማስፋፋት በሀገር ዉስጥ ባሉ አመራጭ የድጋፍ እና እንክብካቤዎች ዚደዎች ብቻ እንደሚደገፉ ተመላክቷል።ሀገር ዉስጥ ምርጫ ሲጠፉ ተፈቅዶ የነበረዉ የዉጪ ሀገር ጉዲፈቻ ሙሉ ለሙሉ በማስቀረት ለችግሩ ሀገራዊ መፍትሔ ብቻ በመስጠት የፖሊሲ ምርጫ የተወሰደበት ዋናዉ ምክንያት የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ የተፈጥሮ ቤተሰብ ፍቅር እና እንክብካቤን የማይተካ ከመሆኑም በላይ የዚህ አማራጭ ተጠቃሚ የሆኑት ሕፃናት በማያዉቁት ቋንቋ፣ባህል እንዲያድጉ በመደረጋቸዉ ለማንነት ቀዉስ ፣ለስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ችግሮች ሲጋለጡ በመታየታቸዉ የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻ ተመራጭ የድጋፍ እና እንክብካቤ ዜዴ እንዳልሆነ ፖሊሲዉ ያመለክታል።ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ በተሻሻለዉ የቤተሰብ ህግ ላይ ማሻሻያ እንደሚደረግ ተገጿል።የዉጭ ሀገር ጉዲፈቻን በሚመለከት የተሻሻለዉን የቤተሰብ ሕግ አንቀጾችን ማሻሻል ያስፈለገዉ በፖሊሲዉ እና በሕጉ መካከል የሚቃረኑ ሀሳቦች በመኖራቸዉ ሁለቱን ስነዶች ለማጣጣም መሆኑ ህጉ ሲወጣ ከተያዘዉ ቃለጉባኤ እና የተሻሻለዉን የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 193 እና 194(3)(መ)ን የሻረዉ አዋጅ ቁጥር 1070/2010 መቅድም (preamble) መረዳት ተችሏል።

የዉጭ ሀገር ዜግነት ያላቸዉ ትዉልደ ኢትዮጵያዊን በሚመለከት በተቀረፀዉ የዲያስፖራ ፖሊሲ በንግድ፣ቱሪዝም፣በዕዉቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣የዉጭ ምንዛሪን በማስገኘት ብሎም *በሀገር ገጽታ ግንባታ* ረገድ ዲያስፖራዉ ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነት ተጥሎበታል።የፖሊሲዉ ዓላማ በዉጭ ሀገር የሚኖሩት ኢትዮጵያዊ እና ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ከትዉልድ ሀገሩ ጋር ያለዉን ትስስር በማጠናከር በልማት፣ሰላምና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጠንካራ ተሳታፊ ሆኖ ራሱን ጠቅሞ ትዉልድ ሀሩን በመጥቀም በጋራ ለማደግ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ነዉ።ፖሊሲዉን ለማስፈፀም ከወጡት ሕጎች ዉስጥም የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የዉጭ ዜጎችን በትዉልድ ሀገራቸዉ ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 270/1994 አንዱ ሲሆን የሕጉ ዓላማ ተብሎ በአዋጁ መቅድም(preamble) እንዲሁም በቁጥር 3 ከተገለፀዉ መረዳት እንደሚቻለዉ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን ከትዉልድ ሀገራቸዉ ጋር ያላቸዉ ግንኙነት እንዲጠነክር የሚፈልጉ በመሆኑ በዉጭ ዜጎች ላይ የተጣሉት የመብት ገደቦች ለማላላት የተለያዩ መብቶች እና ጥቅማ ጥቅሞች ባለቤቶች በማድረግ *ለትዉልድ ሀገራቸዉ* እድገት እና *ለወገኖቻቸዉ* ኑሮ መሻሻል አስተዋጽኦ እንድያደርጉ ለማስቻል መሆኑ ተገልጿል።በዚሁ አዋጅ በቁጥር 5 ሥር የተጠቀሱት መብቶችም ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት፣ ሀገር ዉስጥ ለመቆየት እና ለመኖር የመግቢያ ቪዛ እና የመኖሪያ ፈቃድ የማይጠየቁ መሆኑ፣ያለ ሥራ ፈቃድ ኢትዮጵያ ዉስጥ ተቀጥሮ መስራት፣የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን፣የዉጭ ሀገር ዜጎች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚገድቡ ህጎች፣አሠራር፣ልምድ ልዩነት ሳይደረግባቸዉ የኢኮኖሚ፣የማህበራዊ እና አስተዳዳራዊ ጥቅሞችን ማግኘት እንዲችሉ እና እንደ ሀገር ዉስጥ ባለሀብት መቆጠር ከፈለጉ ለሀገር ዉስጥ ባለሀብት በተፈቀዱ የኢንቬስትመንት መስኮች መሳተፍ

እንደሚችሉ ያስረዳል።በቁጥር 6 ሥር በመንግስት ደረጃ በሚደረግ ምርጫ መምረጥም ሆነ መመረጥ፣በሀገር መከላከያ፣የሀገር ደህንነት በዉጭ ጉዳይና መሰል የፖ/ስትሳ መሥሪያ ቤቶች በመደበኛነት ተቀጥሮ መሥራት እንደማይችሉ ገደብ ተጥሏል።የባንክ ሥራ አዋጅን ለማሻሻል የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1159/2012 ህጉን ለማሻሻል ያስፈለገዉ የዉጭ ሀገር ዜግነት ያላቸዉ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን በባንኩ ዘርፍ እንዲሳተፉ እና የባለቤትነት ድርሻ እንዲኖራቸዉ ለማድረግ መሆኑን የአዋጁ መቅድም (preamble) ያስረዳል።የዲያስፖራ ፖሊሲን ለማስፈፀም እና የኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራዎችን መብት እና ጥቅም ማስከበር ዓላማዉ ያደረገ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ በሚል ስያሜ የህግ ሰዉነት ያለዉ የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 432/2011 ተቋቁሟል።

ሕግ አዉጭዉ የህፃናቱን ደህንነት አስጠብቅበታለሁ ብሎ የያዘዉ አቋም ሕዝብ በተወካዮቹ በኩል ያደረገዉ የፖ/ሊሲ ምርጫ ከዲሞክራሲ መርህ አንፃርም ሆነ ከኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 50(3) ድንጋጌ መሠረት በፌዴራል መንግስቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል የወጣ ሕግ በመሆኑ እንዲሁም ከሥልጣን ክፍፍል መርህ (principle of separation of power) አንፃርም የፍርድ ቤት ሥራ ህግ ማዉጣት ስላልሆነ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል የወጣዉ ሕግ መከበር ያለበት ሆኖ ህግ ሲወጣ ሁሉንም ጉዳዮች እንዲገዛ አጠቃላይ(general) ባህርይ ስላለዉ ህጉ ሳይቀየር ለህጉ አዲስ ትርጉም በመስጠት በህጉ እና ተጨባጭ በሕብረተሰቡ ኑሮ መካከል ያለዉን ክፍተት በትርጉም በመሙላት ለቀረቡላቸዉ ጉዳዮች እልባት በመስጠት ህግ አዉጭዉን ማገዝ የፍርድ ቤቶች የሥራ ግዴታ ነዉ።በሌላ በኩል ሕፃናትን አስመልክቶ የሚወሰዱ ማንኛዉም እርምጃዎች የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ እንዳለበት የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 36(2) የሚያስረዳ ሲሆን ይህ ችሎትም አግባብነት ያላቸዉን ሕጎች በመመርመር የሕፃናት መብት እና ጥቅም ለማስከበር በቀደምትነት መርህ የሕፃናት ጥቅምና ደህንት (best interest of the child) ስለመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 23632,35710 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት አስገዳጅ ዉሳኔ ሰጥቷል።

ወደተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራዎች ለሀገር እድገት እና ብልጽግና በሀገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ሀገር ትልቅ ኃላፊነት የተጣለባቸዉ በሆነ ምክንያት ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸዉን ቢያጡም ትዉልድ ሀገራቸዉ ኢትዮጵያ ስለሆነች እና ዜጎቿም ወገኖቻቸዉ ስለሆኑ ነዉ።በትዉልድ ሀገራቸዉም እንደ ዉጭ ዜጋ እንዳይታዩ ልዩ መብት እና ጥቅማ ጥቅሞች ተክብሮላቸዋል።ሕጉ መብቶቻቸዉን ዘርዝሮ በመቀጠል ገደብ ማስቀመጡ ዝርዝሩ ሙሉ አለመሆኑን ማሳያ ነዉ።የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የዉጭ ዜጎች ከኢትዮጵያዊያን ዜጎች መብቶች ዉስጥ ጥቂቶቹ ስለተቀነሱባቸዉ ሙሉ በሙሉ እንደ ሌላ የዉጭ ሀገር ዜጋ ማየት ተገቢ አይሆንም።በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊ ማንነት ያላቸዉን የዉጭ ዜጎች ትልቅ ሀገራዊ ኃላፍነት የተጣለባቸዉ የሀገርቷን ባህል፣ቋንቋ፣እሴት እንደማያዉቁ

የውጭ ሀገር ጉዲፈቻ አድራጊዎች በጉዲፈቻ የሚወስዱትን ኢትዮጵያዊ ሕፃን የሀገሩን ባህል፣ወግ ፣ልማድና በማህብረሰቡ እሴት ታንፀዉ እንዳያድግ ተፅኖ በማድረግ፣ፍቅር በመንፈግ ለስነ-ልቦናዊና ማሕበራዊ ችግር ያግልጣቸዋል ብሎ በማሰብ የሥጋ ዘመዶቻተዉን በጉዲፈቻ እንዳይወስዱ መከልከል የተጣላባቸዉን ኃላፊነት ካለመረዳት የሚመነጭ ነዉ።ትዉልደ ኢትዩጵያዊያኑ እና በጉዲፈቻ የሚወሰዱት ኢትዩጵያዊያን ሕፃናት የጋራ ባህል እና ማንነት ያላቸዉ ሆኖ በዜግነት ብቻ የሚለያዩ ስለሆኑ የህፃናቱ የቀደመ ማንነት በሌላ አዲስ ማንነት ለመቀየር ፍላጎት ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም። በተያዘዉ ጉዳይ 3ኛ አመልካች በጉዲፈቻ ለመቀበል ለምትፈለገዉ ልጅ አክስት ስትሆን ምንም የህግ ግዴታ ሳይኖርባት በማህብረሰቡ ዉስጥ ባለዉ የመረዳዳት ባህል እናት እና አባት ለልጅ የሚያደርጉትን ሁሉ እያደረገች እና እንደ ልጇ በምትኖርበት ሀገር ያስመዘገበች መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል።3ኛ አመልካች እና በተማሪ ኤፍራታ ወንደሰን መካከል የደም ግንኙነት መኖሩ፣ሕጋዊ ግዴታ ሳይኖርባት ስትረዳት መቆየቷ በራሱ ለቆየዉ የመረዳዳት እሴታችን ያላትን ቦታ ማሳያ መሆኑ፣የሚጋሩት የጋራ ባሕል ያላቸዉ መሆኑ ለጉዲፈቻ ተደራጊዋ ከቤተሰዋ ጋር ከትዉልድ ሀገሯ የመዉጣት ያክል ሆኖ እያለ እና 3ኛ አመልካች የምትኖረዉ አሜርካ ሀገር ብዙ ትዉልደ ኢትዩጵያዊያን ያሉበት መሆኑ ታዳጊዋን ኢትዩጵያዊ ማንነቷን ይዛ በመልካም ስብዕና ለማደግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መኖሩ መልካም አጋጣሚ ሆኖ እያለ የኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራዎች በሀገር እድገት እና ብልጽግና እንዲሁም ለወገኖቻቸዉ ኑሮ መሻሻል ያላቸዉን ሚና ባለመገንዘብ የህጻኗን የደህንት ቀደምትነት መብት በመንፈግ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል።

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 237661 በ16/04/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሠጠዉ ብይን እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 103957 በ02/11/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሠጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ ህግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል።
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋዉን መዝገብ ቁጥር 103957 በማንቀሳቀስ 3ኛ አመልካች ተማሪ ኤፍራታ ወንደሰን በጉዲፈቻ ለማሳደግ የሚያስችላቸዉን መስፈርት ማሟላት አለማሟላታቸዉን በማጣራት ተገቢ ነዉ የሚለዉን ዉሳኔ ይሰጥ ዘንድ መዝገቡ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ ህግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰንለታል።
3. የመዝገቡ ትክክለኛ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረስ።

መዝገቡ ዉሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፍርማ አለበት።

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ.144585

ግንቦት 13 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ሀና ካሳዬ

2. ወ/ሮ ገነት ካሳዬ - ጠበቃ አካል ዶይሰማ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ዘነበች ከሳዬ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የነገሩ አመጣጥ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ የአሁን አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የሥር ከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ መጋቢት 6 ቀን 2008 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ከሳሽ የሚች እናታቸው የወ/ሮ እልፍነሽ ሌይ ብቸኛ ወራሽ መሆናቸውን፣ የሚች አናታቸው የውርስ ሀብት በመ/ቁ. 97412 ተጣርቶ ግንቦት 26 ቀን 2007 ዓ/ም መጽደቁን፣ ሚች እናታቸው ከሚች አቶ ካሳዬ ደሳለኝ ጋር በትዳር አብረው የቆዩ በመሆናቸው የሚች አቶ ከሳዬ ድርሻ በወራሾቻቸው በኩል በመ/ቁ. 62253 ተጣርቶ የቀረበ መሆኑን፣ የሚቾቹን የውርስ ንብረት የውርስ አጣሪ ተሹሞ ያጣራ መሆኑንና በፍርድ ቤት መጽደቁን፣ ተከሳሾች ከጥቅምት 22 ቀን 2002 ዓ/ም እስከ ሀምሌ 19 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ እንዲሁም ከግንቦት 1 ቀን 2005 እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ ከመኖሪያ ቤትና ወፍጮ በወር ብር 20,513 /ሃያ ሺህ አምስት መቶ አስራ ሶስት/ ለ31 ወር ሲሰበስቡ መቆየታቸውን፣ በአጠቃላይ ብር 20,513 X 31 ወር = 635,903 /ስድስት መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሶስት/ ብር መሰብሰቡን ገልጸው የከሳሽ ድርሻ ብር 211,967 /ሁለት መቶ አስራ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሰባት ብር/ ከእነ ወለዱ ተከሳሾች እንዲከፍሉ እንዲሁም ለክርክሩ የወጣውን ወጪ እንዲተኩ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሾች ሚያዝያ 26 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የወፍጮ ቤት ገቢን በተመለከተ ሚች ከሞቱበት ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ወፍጮ ቤት እስከተከራየበት መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ ያለው ብር ሲሰባሰብ ቢቆይም ከቤት ኪራይና የወፍጮ ቤት ኪራይ ከሚገኘው ገቢ ውስጥ ለመንግሥት የሚከፈል እዳ፣ የከሳሽ ወላጅ እናት በህይወት እያሉ የወሰዱትን ለቀለብና ለህክምና የወጣ በፍርድ ቤት የተወሰነውን ተቀንሶ ድርሻቸውን ብር 2,865.15 /ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከአስራ አምስት ሳንቲም/ ስለሚደርሳቸው መውሰድ ይችላሉ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የቤት ኪራይ በተመለከተ በመዝገብ ቁጥር 62253 ላይ ግራ ቀኙ በተገኙበት የተጣራው ንብረት ውስጥ የቤት ኪራይ በአጠቃላይ ብር 435,430 /አራት መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ/ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በንብረት አስተዳዳሪዎች እጅ አለ የተባለው ብር 176,840 /አንድ መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ አርባ/ ሲሆን በተከሳሾች እጅ የሚገኘው ብር 258,590 /ሁለት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ብር/ መሆኑ ነው፡፡ የወፍጮ ቤት ገቢን በተመለከተ ከውርስ አጣሪ ሪፖርት ለመረዳት የተቻለው ጣልቃ ገብ የነበሩ የአሁን ከሳሽ እናት ያቀረቡት ገቢ ብር 618,750 /ስድስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር/ ሲሆን በወቅቱ በውርስ አጣሪ መዝገብ ቁጥር 62253 ላይ ተጠሪዎች የነበሩ የአሁን ተከሳሾች በኩል የታመነ ነው የተባለው ብር 432,960.16 /አራት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም/ ነው፡፡ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ በንብረት አስተዳዳሪዎች እጅ የነበረው ብር 133,860 /አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ብር/ ስለሆነ ተከሳሾች በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ያመኑት ገቢ ቢወሰድ እንኳን በውርስ አስተዳዳሪዎች እጅ የነበረው ሲቀነስ ብር 299,100 /ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ብር / ይሆናል፡፡ ስለዚህ ከቤት ኪራይ 258,590 /ሁለት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ብር/ እና ከወፍጮ ብር 299,100 /ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ብር / ሲደመር ብር 557,690 /አምስት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ብር/ ይሆናል፡፡ በውርስ አጣሪ ሪፖርት በወጪነት የተያዘው በጋራ ብር 7,051 /ሰባት ሺህ አምሳ አንድ ብር/ ሲሆን ይህ እዳ ለሶስት ሲካፈል ብር 2,350 /ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ሃምሳ ብር/ ይሆናል፡፡ ለከሳሽ አውራሽ ቀለብ ተብሎ የታሰበው ብር 7,890 /ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ብር/ ስለሆነ የከሳሽ ድርሻ ወጪ ብር 10,240 /አስር ሺህ ሁለት መቶ አርባ ብር/ ይሆናል፡፡ ይህ ወጪ ከከሳሽ ወጪ የሚተካ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አጠቃላይ ገቢ ብር 557,690 /አምስት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ብር/ ለ3 ሲካፈል ብር 185,896.66 /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የከሳሽ ብር 10,240 /አስር ሺህ ሁለት መቶ አርባ ብር/ ሲቀነስ ብር 175,656.66 /አንድ መቶ ሰባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከውርስ አጣሪ ሪፖርት ተረድቷል፡፡ ስለዚህ ተከሳሾች ለከሳሽ በፍርድ ቤት ቀርቦ በፀደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት መሠረት ብር 175,656.66

/አንድ መቶ ሰባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር/ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካቾች ይህን ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኛቸውን ሰርዞባቸዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ውሳኔውን ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካቾች አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ፡- የውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ላይ በወጪነት /በእዳነት/ የተመዘገበውን ብር 185,455.25 /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም/ ፍርድ ቤቱ በኮ/መ/ቁ. 62253 ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ/ም ያለማንም ነቀፋ እና ተቃውሞ አጽድቆት እያለ የሥር ፍርድ ቤት በወጪነት ሳይዝ ዝም ብሎ ማለፉ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች የተጠሪ ድርሻ የሆነን ወጪ (እዳ) የምንወስድበት የህግ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የገንዘብ መጠን በፀደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት መሠረት ከሚደርሳቸው የውርስ ድርሻ ብር 185,896.66 /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ ላይ ወጪዎችን /እዳዎችን/ ተቀናሽ በማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ለተጠሪ ሊከፈላቸው የሚገባው የገንዘብ መጠን ብር 185,896.66 - ብር 61,818.21 - ብር 10,240 = 113,838.21 /አንድ መቶ አስራ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሃያ አንድ ሳንቲም/ ሆኖ እያለ ብር 175,656.66 ይከፈል መባሉ አግባብነት የሌለው ውሳኔ በመሆኑ እና ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣን የሌለው በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ የጉዳዩ አከራካሪ የሆነውን የውርስ ንብረት ለማቆየት አመልካቾች በውርስ አጣሪ በተራ ቁጥር 7 ላይ የተጠቀሰውን ወጪ ሳይቀንስ ወይም ሳይተቸው በማለፍ ይክፈሉ ያለበት አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል ጥቅምት 16 ቀን 2010 ዓ/ም ባቀረቡት መልስ የአመልካቾች ክርክር ስሌትን፣ ፍሬ ነገርን እና ማስረጃን የተመለከተ እንጂ የህግ ትርጉም ጥያቄ የሚያስነሳ ስላልሆነ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሚታይበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ተራ ቁጥር 7 ላይ ተጠቅሶ በፍርድ ቤትም የፀደቀውን እዳ ብር 185,455.25 በተመለከተ ዘጠኙ ባለጉዳዮች የደረሱበት እና ፍርድ ቤቱም ያፀደቀው ስምምነት በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የውርስ እዳውን እኩል ለመክፋፈል ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ብር 185,455.25 እዳ ለዘጠኝ እኩል ሲካፈል ተጠሪ የሚደርስባቸው ብር 20,6006.00 /ሃያ ሺህ ስድስት መቶ ስድስት ብር/ እንጂ ብር 61,818.25 /ስልሳ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም/ አይደለም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር የአሁን ተጠሪ ሊከፈለኝ ይገባል ሲሉ ያቀረቡት የውርስ ሀብት ገቢ

ድርሻ መጠን በግልጽ የተቀመጠ ቢሆንም ከውርስ ሀብቱ እዳ ላይ በውርስ አጣሪው ሪፖርት መሠረት ሊከፍሉት የሚገባ ያልከፈሉት ወይም ቀድመው ያላቻቻሉት የእዳ ድርሻ መኖሩን አመልካቾች ያቀረቡት ምንም ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 329 በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሊቀበል እንደማይችል ተቀምጧል፡፡ ከብር 185,455.25 የውርስ እዳ ላይ ያልተከፈለ ወይም ያልተቻቻለ የተጠሪ የእዳ ድርሻ አለ የሚለው የአመልካቾች ክርክር ሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳ ክርክር በመሆኑ ደግሞ በይግባኝ ላይም ሆነ በሰበር ችሎት ሊቀርብ የሚችል አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን በውርስ አጣሪ የተረጋገጠውና በፍርድ ቤት የፀደቀው የውርስ እዳ ከውርስ ንብረት ገቢ ላይ ሳይቀነስ ለአሁን ተጠሪ ድርሻቸው እንዲከፈል የተወሰነበት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ የአሁን አመልካቾች አባት፣ የተጠሪ እናት እንዲሁም ሌላኛዋ የአመልካቾች አባት ሚስት ንብረት እንዲጣራ ተደርጎ በኮ/መ/ቁ. 62253 ግንቦት 28 ቀን 2006 ዓ/ም በተጻፈ ሪፖርት ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት መቅረቡን፣ ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ሪፖርት በኮ/መ/ቁ. 62253 ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ/ም ማጽደቁን ተመልክተናል፡፡ የውርስ አጣሪው ባቀረበው ሪፖርት ተራ ቁጥር 7 ላይ ከጥቅምት 22/2002 እስከ ግንቦት 28/2006 ዓ/ም ድረስ ያለው ጠቅላላ ወጪ ብር 185,455.25 /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ አራት መቶ አምሳ አምስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም/ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በወቅቱ በህይወት የነበሩት የአሁን ተጠሪ አውራሽ ይህን ወጪ እንደማይቃወሙ በመግለጽ መስማማታቸውን የውርስ አጣሪው ሪፖርት ያስረዳል፡፡ ይህም የውርስ እዳ በፍርድ ቤት መጽደቁ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር አራት ነጥቦችን ያነሱ ሲሆን የመጀመሪያው የአመልካቾች አቤቱታ የስሌት ጉዳይ ስለሆነ ለሰበር ክርክር ብቁ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህንን ክርክር ስንመለከት የስሌት ስህተትን መሠረት ያደረገ ክርክር አይደለም፡፡ ምክንያቱም የአመልካቾች ክርክር የታወቀና የተረጋገጠ የውርስ እዳ እያለ እዳው በድርሻ ልክ ሳይቀነስ ተጠሪ ከውርስ ንብረት የሚገኘውን ገቢ ብቻ ሊካፈሉ አይችሉም በማለት የሚከራከሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ተጠሪ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ሌላኛው መከራከሪያ ነጥብ አመልካቾች ለሰበር ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ነገርን የሚመለከት ስለሆነ ችሎቱ ሊያየው አይገባም የሚል ነው፡፡ የአመልካቾች ክርክር ደግሞ የተረጋገጠና በፍርድ ቤት የፀደቀ የውርስ እዳ እያለ ተጠሪን የሚመለከተው የውርስ እዳው ድርሻ ሳይቀነስ ከውርስ ንብረት የተገኘውን ገቢ ድርሻ እንዲወስዱ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡ የውርስ እዳዎች አከፋፈል ቅድም ተከተል በፍትሓብሔር ህግ ቁጥር 1014 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ውስጥ በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ እንዲሁም ከወራሾቹ አንዱ ለውርስ የሚከፍለው እዳ ያለበት እንደሆነ እዳው በድርሻው ውስጥ ይታሰባል በማለት የፍትሕብሔር ህግ ቁጥር 1090 በግልጽ

ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች የምንመለከተው የውርስ እዳ ካለ የውርስ ንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የውርስ እዳ ሊቀነስ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የውርስ እዳ ስላለ ከውርስ ንብረት ገቢ ላይ የሚደርሳቸው ድርሻ ላይ ተቀንሶ ለተጠሪ የሚገባቸው እንዲከፈል መደረግ ሲገባው አልተደረገም በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ነጥብ እንደ ተጠሪ አባባል ፍሬ ነገርን የሚመለከት ክርክር ሳይሆን ከላይ እንደተገለጸው የህግ መሠረት ያለው ወይም የህግ ነጥብን የሚመለከት ክርክር ነው፡፡ ተጠሪ ለዚህ ሰበር ያቀረቡት ሶስተኛው የመከራከሪያ ነጥብ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ. 62253 ላይም ሆነ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ተከራካሪ ወገን ሆነው የቀረቡት ግለሰቦች ብዛት በዚህ የሰበር ክርክር ላይ አመልካቾች እና ተጠሪ ሆነው የቀረቡትን ጨምሮ አንድ አመልካች፣ ሶስት ተጠሪዎች እና አምስት ጣልቃ ገቦች በአጠቃላይ ዘጠኝ ባለጉዳዮች ናቸው፡፡ በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ተራ ቁጥር 7 ላይ ተጠቅሶ በፍርድ ቤትም የፀደቀውን ብር 185,455.25 /አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ አራት መቶ አምሳ አምስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም/ በተመለከተ ዘጠኝ ባለጉዳዮች የደረሱበት እና ፍርድ ቤቱም ያፀደቀው ስምምነት በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የውርስ እዳውን እኩል ለመክፋፈል ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ብር 185,455.25 እዳ ለዘጠኝ እኩል ሲካፈል ለተጠሪ የሚደርሳቸው ድርሻ ብር 20,606.45 እንጂ ብር 61,818.45 አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህንን መከራከሪያ ነጥብ ከውርስ አጣሪው ሪፖርት እና ሪፖርቱ ከፀደቀው ውሳኔ ላይ ተመለክተናል፡፡ የውርስ አጣሪው ንብረትን ሲያጣራ በአመልካችነት፣ በተጠሪነት እና በጣልቃ ገብነት የተመዘገቡት የሟች አቶ ካሳ ደሳለኝ ልጆች ሰባት ሲሆኑ ወ/ሮ እልፍነሽ ሄይ ማለትም የአሁን ተጠሪ አውራሽ እናት እና ወ/ሮ ገላዬ በጋሻው የሟች አቶ ካሳዬ ደሳለኝ ሚስቶች ነበሩ፡፡ ይህን መሠረት በማድረግ የውርስ አጣሪው የውርስ ንብረቱ በአመልካቾች አባት እና በሁለቱ ሚስቶች አስተዋፅኦ የተፈራ በመሆኑ እኩል ሶስት ቦታ እንዲካፈል በሪፖርቱ ተራ ቁጥር 8 ላይ አስተያየቱን የገለጸ መሆኑንና ይህም ፍርድ ቤት ቀርቦ ማጽደቁን ተመልክተናል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት ለሶስት እኩል የሚካፈል ከሆነ የውርስ እዳም ሶስት ቦታ እኩል ከሚካፈል ወጪ ለዘጠኝ የሚካፈልበት ህጋዊ መሠረት የለም፡፡ የአሁን ተጠሪ እንደሚሉትም እዳው ለዘጠኝ እኩል እንዲካፈል ስለመስማማታቸው የውርስ አጣሪው ሪፖርት በፍጹም አያሳይም፡፡ ይልቁንም በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ እያንዳንዱ ወጪዎች በሙሉ የሚች የውርስ ሀብት ጠብቆ ለማቆየት የተደረገ ስለመሆኑ የመደምደሚያ ሀሳብ ስለተደረሰ ተጠሪዎች የአሁን አመልካቾች/ ወጪ በማለት ያቀረቡት በሙሉ ቢመዘገብ የሥር አመልካችም፣ 1ኛ ጣልቃ ገብ /የአሁን ተጠሪ እናትም/ እንደማይቃወሙ በመግለጽ መስማማታቸውን ነው፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ የውርስ እዳው የሚካፈል ቢሆን እንኳን ለዘጠኝ ሰው ሊካፈል ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የተጠሪ የመጨረሻ መከራከሪያ ነጥብ የውርስ እዳ ስለመኖሩ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት አንስተው አልተከራከሩም የሚል ነው፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ እንደተመለከትነው የአሁን

አመልካቾች በመልሳቸው ላይ የወፍጮ ቤት ገቢን በተመለከተ ሚች ከሞቱበት ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ወፍጮ ቤት እስከተከራየበት መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ/ም ድረስ ያለው ብር ሲሰባሰብ ቢቆይም ከቤት ኪራይና የወፍጮ ቤት ኪራይ ከሚገኘው ገቢ ውስጥ ለመንግሥት የሚከፈል እዳ፣ የከሳሽ ወላጅ እናት በህይወት እያሉ የወሰዱትን ለቀለብና ለህክምና የወጣ በፍርድ ቤት የተወሰነውን ተቀንሶ ድርሻቸውን ብር 2,865.15 /ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከአስራ አምስት ሳንቲም/ ስለሚደርሳቸው መውሰድ ይችላሉ በማለት መከራከራቸውን ያሳያል፡፡ በዚህ ክርክር ላይ በግልጽ እንደተገለጸው የውርስ እዳ መኖሩን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የውርስ እዳ እንደነበረ አንስተው አልተከራከሩም፣በዚህ ችሎት አንስተው የተከራከሩት ክርክር ነው በማለት ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ላይ የተመዘገበውን የአመልካቾችን ክርክር ይዘት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለልም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት ተጠሪ የጠየቁትን የውርስ ንብረት ገቢን በተመለከተ የውርስ አጣሪውን ሪፖርት መሠረት በማድረግ የወሰነ ሲሆን ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን በውርስ አጣሪው ተጣርቶ ከቀረበ በኋላ በፍርድ ቤቱም የፀደቀውን የውርስ እዳ ሳይቀንስ ከውርስ ንብረት ላይ ከሚገኘው ገቢ ላይ ለተጠሪ ድርሻቸው እንዲከፈል የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይህ ውሳኔ በይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ስህተቱን ሳያርም ይግባኙን መሠረዙ ሲታይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ያለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 111280 በቀን 03/04/09 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 182802 በቀን 25/08/2009 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የከሳሽ አውራሽ ወጪ ብር 10,240 /አስር ሺህ ሁለት መቶ አርባ ብር/ ከተጠሪ ድርሻ ላይ እንዲቀነስ ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. በውርስ አጣሪ ሪፖርት በተራ ቁጥር 7 ላይ የተገለጸው የውርስ እዳ ብር 185,455.25 በኮ/መ/ቁ. 62253 ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓም የፀደቀው የውርስ ንብረት ክፍፍል ለሶስት እኩል እንዲካፈል በተወሰነው መሠረት እዳውም ለሶስት እኩል ተካፍሎ በሚደርሰው ድርሻ ልክ የአሁን ተጠሪ ብር 61,818.45 /ስልሳ አንድ ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/ እዳቸው ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. ለተጠሪ ሊከፈላቸው ይገባል ተብሎ ከተወሰነው ብር 175,656.66 /አንድ መቶ ሰባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም/ ላይ ብር 61,818.45 /ስልሳ አንድ ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/ ተቀንሶ ብር 113,838.21

/አንድ መቶ አስራ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ስምንት ብር ከሃያ አንድ ሳንቲም/ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር አመልካቾች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡

5. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቅ/ሀ

አሥሪ እና ሠራተኛ

የሰ/መ/ቁ.161880

ታህሳስ 23 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

መ·ስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-አቶ አብርሃም ዴአ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነ/ፈጅ አባተ ደጀኔ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከስራ የማሰናበት የዲሲፕሊን ውሳኔን በመቃወም የተነሳ የመንግስት አስተዳደር ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በመስሪያ ቤቱ ዲሲፕሊን ኮሚቴ የቀረበላቸውን የውሰኔ ሀሳብ በመቀበል የተቋመ· የበላይ ኃላፊ በአመልካቹ ላይ ያስተላለፉትን የጥፋተኛነት እና ከስራ የማሰናበት የዲሲፕሊን ውሳኔ በማጽናት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፐብሊክ ሠርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 073/2010 በ16/08/2010 ዓ.ም የሰጠው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 157439 በ19/11/2010 ዓ.ም በትዕዘዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

አመልካቹ በተጠሪው ተቋም የዲሲፕሊን ኮሚቴ ዘንድ ክስ የተመሰረተባቸው በመስሪያ ቤቱ በሙሉ ሰዓት ሰራተኛነት ተቀጥረው በማገልገል ላይ እያሉ ከተጠሪ ተቋም የተሰጣቸው ፈቃድ ሳይኖር በቀን ክፍለ ጊዜ ለአንድ ዓመት ተኩል አካባቢ ያህል ግማሽ ቀን በትምህርት ላይ የነበሩ መሆኑ በመረጋገጡ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 68 (1) ስር የተደረነገገውን ተላልፈው ሆን ብለው የአሠራር ሥነ ሥርዓት ወይም የመንግስት ፖሊሲ ባለመከተል በስራ ላይ በደል የማድረስ ጥፋት ፈጽመዋል ተብለው ሲሆን የዲሲፕሊን ኮሚቴው የአመልካቹን መልስ ከተቀበለ እና ጉዳዩን በማስረጃ ካጣራ በኃላ አመልካች ድርጊቱን መፈጸማቸው በማስረጃ የተረጋገጠባቸው መሆኑን ገልጾ

በአዋጁ አንቀጽ 67(1)(ረ) በተመለከተው መሰረት ከስራ እንዲሰናበቱ በማለት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።የውሳኔ ሀሳቡ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ተቀባይነት በማግኘቱ አመልካቹ ከስራ እንዲሰናበቱ የተወሰነ ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የተጠሪ ተቋም ውሳኔ በአስተዳደር ፍርድ ቤት በፍርድ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደግሞ በትዕዛዝ በመጽናቱ ነው።

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በየሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪው መስሪያ ቤት የአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤታችንን ሳያሳውቁ በቀን ክፍለ ጊዜ ትምህርት ተከታትለዋል በሚል ከስራ ኦንዲሰናበቱ የወሰነበትን አግባብነት ከፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 67(1) ስር ከተዘረዘሩት የቅጣት ዓይነቶች አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. በአመልካቹ ላይ የተወሰደው የዲሲፕሊን የጥፋተኛነት እና የስንብት ውሳኔ ሊሻር ይገባል ወይስ አይገባም?
2. ለአመልካቹ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈል ይገባል ወይስ አይገባም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ ጉዳዩን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል።

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪ ተቋም በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ በቀረበለት የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በአመልካቹ የዲሲፕሊን የጥፋተኛነት እና ከስራ የማሰናበት ውሳኔ ያስተላለፈው እና በአስተዳደር ፍርድ ቤትም ይኸው ውሳኔ እንደጸና ሲከራከር የነበረው አመልካቹ በተጠሪ መስሪያ ቤት በሙሉ ሰዓት ሰራተኛነት ተቀጥረው በማገልገል ላይ እያሉ ከተጠሪ ተቋም የተሰጣቸው ፈቃድ ሳይኖር በቀን ክፍለ ጊዜ ለአንድ ዓመት ተኩል አካባቢ ያህል ግማሽ ቀን በትምህርት ላይ የነበሩ መሆኑ በመረጋገጡ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 68(1) ስር የተደነገገውን ተላልፈው ሆን ብለው የአሠራር ሥነ ሥርዓት ወይም የመንግስት ፖሊሲ ባለመከተል በስራ ላይ በደል የማድረስ ጥፋት መፈጸማቸው በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ነው።ሁለቱ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተጠሪ ተቋም የተላለፈውን ውሳኔ ያጸኑትም ይህንኑ ክርክር በመቀበል ነው።ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በአጣሪው ችሎት ጭብጥ የተያዘው የቅጣቱን ተመጣጣኝነት እና አግባብነት ለማጣራት በሚል ቢሆንም ተጠሪ ተቋም በሰጠው መልስ ላይ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ያሳረፉ ቢሆንም አመልካች ከስራ እንዲሰናበቱ ከመወሰኑ በፊት የነበራቸውን አፈጻጸም፣ከጥፋታቸው የታረመ መሆኑን ከግምት በማስገባት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆናቸው ምክንያት የደረሰባቸውን ችግር ከግምት በማስገባት ወደ ቀድሞ ምድብ ስራቸው ቢመለሱ የማይቃወም መሆኑን ገልጿል።በመሆኑም በአመልካቹ ላይ የተላለፈውን የጥፋተኛነት እና ከስራ የማሰናበት ውሳኔ አግባብነት

በተመለከተ ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ ሳያስፈልግ የዲሲፕሊን ጥፋተኛነት ውሳኔውም ሆነ የማሰናበት ውሳኔው ተሽሮ አመልካቹ ወደ ቀድሞ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል።

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የተጠሪውን መልስ ከተመለከቱ በኃላ ያልተከፈላቸው ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ተጠብቆ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው አመልካቹ በመልስ መልሳቸው ጠይቀዋል።የመንግስት ሰራተኛው በተከሰሰበት የዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ከስራ እንዲሰናበት ካልተወሰነበት በስተቀር በእግዱ ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ያለወለድ የሚከፈለው ስለመሆኑ በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 70 (4)ስር ተመልክቶአል።ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ከ06/04/2010 ዓ.ም. ጀምሮ የተሻረ እና በአዋጅ ቁጥር 1064/2010 የተተካ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይህ አዲሱ አዋጅም በዚህ ረገድ የያዘው ድንጋጌ ተመሳሳይ መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 72(4) ድንጋጌ ያመለክታል።ከላይ በመጀመሪያው ጭብጥ ላይ እንደተመለከተው በአመልካቹ ላይ ተላልፎ የነበረው የዲሲፕሊን ጥፋተኛነት እና ከስራ የማሰናበት ውሳኔ የተሻረ እስከሆነ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 70(4) ስር በተመለከተው መሰረት ከስራ እንዲሰናበቱ ከተወሰነበት ጥቅምት 21 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ውሳኔ እስከተሰጠበት /ወደ ስራ እስከሚመለሱበት/ ቀን ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ያለወለድ ታስቦ ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሳ ኔ

1. በመስሪያ ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ የቀረበላቸውን የውሰኔ ሀሳብ በመቀበል የተቋመ የበላይ ኃላፊ በአመልካቹ ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኛነት እና ከስራ የማሰናበት የዲሲፕሊን ውሳኔ፣ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፐብሊክ ሠርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 073/2010 በ16/08/2010 ዓ.ም የሰጠው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 157439 በ19/11/2010 ዓ.ም በትዕዘዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. አመልካች ወደ ቀድሞ ስራቸው እንዲመለሱ እና ከስራ እንዲሰናበቱ ከተወሰነበት ጥቅምት 21 ቀን 2010 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ስራ እስከሚመለሱበት ቀን ድረስ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ያለወለድ ታስቦ እንዲከፈላቸው ወስነናል።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቤ/ፍ

የሰ/መ/ቁጥር 173887

ቀን 24/10/2011 ዓ/ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ ነ/ፈ ደነቀ ጉታ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- አቶ ዋቅጋሪ ጥላሁን - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መጋቢት 17 ቀን 2011 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 039/2011 ታህሳስ 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 169597 መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶች የሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ባጠናው የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ የመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የአሁን ተጠሪ ባከራከረው የስራ መደብ ተፈላጊውን የትምህርት ዝግጁነት የማያሟላ መሆኑ ታውቆ እያለ የአመልካችን መ/ቤት ሥራና መብት በሚጥስ ሁኔታ ተጠሪ ተወዳድሮ ምደባ እንዲደረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል ሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት ሲሆን ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ቅሬታ መልስ ሰጪ የአሁን አመልካች በድልድል (JEG) አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ካለአግባብ የተሰጠኝ የስራ ምደባ ተገቢ ባለመሆኑ ጅማ ቅርንጫፍ በሚገኘው አቤቱታና ቅሬታ ማስተናገጃ ቡድን መሪ ደረጃ XIV ስራ መደብ ላይ ተወዳድሬ ምደባ ላገኝ ሲገባ እንዳልወዳደር መደረጉ ካለአግባብ በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ መ/ሰጪም ይግባኝ ባይ ለጠየቀው

የስራ መደብ የተቀመጠውን የትምህርት ዝግጁነት የማያሟላ በመሆኑ በስራ መደብ ላይ ለውድድር አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ቅሬታው ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 039/2011 ታህሳስ 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ላከራከረው የስራ መደብ አቤቱታና ቅሬታ ማስተናገጃ ቡድን መሪ ደረጃ XIV ስራ መደብ በተዘጋጀው ፎርም 14 የስራ መዘርዝር ላይ በመ/ሰጪ መ/ቤት የድልድል አፈጻጸም (JEG) መመሪያ መሰረት በማድረግ ለስራ መደቡ የተጠየቀው የትምህርት ዝግጁነት፣ በማናጅመንት በህዝብ አስተዳደር፣ በሰው ሀብት ሥራ አመራር እና በሳይኮሎጅ የመጀመሪያ ዲግሪ እና 8 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ነው፡፡ ይግባኝ ባይ ያለው የትምህርት ዝግጅት በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው መሆኑ ታውቋል፣ ላከራከረው የስራ መደብ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሰው ብቁ መሆን አለመሆኑን አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጥ ተጠይቆ በስራ መደቡ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን እና አላማውን ለማስፈጸም የሚከለክል አለመሆኑን አንዲሁም ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አደረጃጀት ስራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ክፍል የተሰጠው ማብራሪያ ላከራከረው የስራ መደብ በተዘጋጀው ፎርም 14 የስራ መዘርዝር ላይ ተጨማሪ የትምህርት ዓይነት የሚያስፈልግ ከሆነም በተቋሙ ጠያቂነት መተካት የሚቻል መሆኑን ገልጾ አቅርቧል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሰው የትምህርት ዝግጁነት በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪ ባለመገለጹ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሰው ባከራከረው የስራ መደብ ላይ እንዳይወዳደር መደረጉ ለጉዳዩ አግባብ ያለውን ነጥብና የስራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን የመንግስት ሰራተኞች የስራ ድልድል መመሪያ መሰረታዊ መርህና ዓላማን ያላገናዘበና የሜሪቱን ስርዓት ያልተከተለ በመሆኑ አልተቀበልነውም፣ የመ/ሰጪ ውሳኔ ተሽሯል፡፡ ባከራከረው የስራ መደብ ላይ እንደገና ይ/ባይንም በማወዳደር ምደባ እንዲደረግ ሲል ወስኗል፡፡ መ/ሰጪ የአሁን አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ በመ/ቁጥር 169597 መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት የተጠሪ የትምህርት አይነት ኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ደረጃ ዲግሪ ለክርክር ምክንያት በሆነው የስራ መደብ ዝርዝር ውስጥ ባልተካተተበት እና ሲቪል ሰርቪስ ተጠይቆ ተጨማሪ የትምህርት ዓይነት የሚያስፈልግ ከሆነ በተቋሙ ጠያቂነት ማካተት እንደሚቻል ምላሽ በሰጠበት ሁኔታ እና በዚህ አግባብ እንዲካተት ባልተደረገበት የስር ፍ/ቤት የተጠሪ የትምህርት ዝግጅት ለአከራካሪው የስራ መደብ የሚጋብዘው መሆኑን አመልካችን አሳውቆ በ15 ቀን ውስጥ "በጄኢጂ" አፈጻጸም መመሪያ መሰረት በስራ መደቡ ላይ እንዲመደብ የወሰነበትን አግባብ ከፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር በነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ የመ/ሠ/ድ/አ/መ/ ግንቦት 2008 ዓ/ም ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሚያዝያ 25 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲሆን፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ባከራከረው የስራ መደብ አቤቱታና ቅሬታ ማስተናገጃ ቡድን መሪ ደረጃ XIV ላይ ተወዳድሮ ለመመደብ የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አጥንቶ ስራ ላይ ባዋለው፣ በነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ የመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጁነት በማናጅመንት በህዝብ አስተዳደር፣ በሰው ሀብት ሥራ አመራር እና በሳይኮሎጅ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው መሆኑ አላከራከረም፡፡ ባከራከረው የስራ መደብ በመመሪያው መሰረት ተወዳድሮ ለመመደብ በተዘጋጀው ፎርም 14 የስራ መዘርዝር ተፈላጊው የትምህርት ዝግጁነት በማናጅመንት በህዝብ አስተዳደር፣ በሰው ሀብት ሥራ አመራር እና በሳይኮሎጅ የትምህርት ዓይነት ብቻ ተጠቅሶ የተቀመጠ ሲሆን ዝርዝሩ ተመሳሳይ ሌላ የትምህርት ዓይነትን በሚጋብዝ መልኩ የተቀመጠ አይደለም፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች ላከራከረው የስራ መደብ ተፈላጊው የትምህርት ዓይነቶች ሲሆኑ ጥናት ተደርጎ ለቦታው ትክክለኛው የትምህርት ዓይነቶች መሆናቸው ተለይቶ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አደረጃጀት ስራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ክፍልም በፍ/ቤት ጥያቄ የተሰጠው ማብራርያም መ/ቤቱ የአሁን አመልካች የሚጠይቅ ከሆነ በተጨማሪነት ለቦታው የሚያስፈልግ የትምህርት ዓይነት ካለ በጥናት የሚካተት መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን የኢኮኖሚክስ የትምህርት ዓይነት ለቦታው በጥናት በወጣው መመሪያ መዘርዝሩ መሰረት ተፈላጊ የትምህርት ዓይነት ነው የሚል መልዕክት የለውም፡፡ ሌላው በፍ/ቤት ጠያቂነት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቀረበውም ሙያዊ አስተያየት ሲሆን ላከራከረው የስራ መደብ ኢኮኖሚክስ የትምህርት ዓይነት ሊሰራ እንደሚችል ሙያዊ አስተያየት መስጠቱ፣ ጥናት ተደርጎበት ላከራከረው የስራ መደብ ተፈላጊ የትምህርት ዓይነቶች ተብለው ተዘርዝረው የተቀመጠውን መመሪያ በመጣስ ተጨማሪ የትምህርት ዓይነት በፍ/ቤት እንዲጨመርበት ለመወሰን የሚያበቃ ምክንያት አይደለም፡፡ ይህ ሆኖ የአመልካች መ/ቤት የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ተጠንቶ ስራ ላይ ከዋለው መመሪያ በግልጽ አስቀምጦ ካለው ውጪ ላከራከረው የስራ መደብ ተወዳድሮ ለመመደብ አስፈላጊ የሆነው የትምህርት ዝግጁነት በግልጽ ተዘርዝረው እያሉና ትርጉም ባላስፈለገበትና ባላከራከሩበት ሁኔታ የአሁን አመልካች መ/ቤት ሌላ ተጨማሪ የትምህርት ዓይነት እንደሚያስፈልገው ባልጠየቀበት በግልጽ በመመሪያው ከተዘረዘሩት ውጪ የትምህርት ዓይነት ኢኮኖሚክስ ተካቶ እንዲወዳደር መወሰኑ የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ሚኒስቴር በነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ የመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ሲቪል ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 039/2011 ታህሳስ 25 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ

ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 169597 መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአሁን ተጠሪ ላከራከረው የስራ መደብ አቤቱታና ቅሬታ ማስተናገጃ ቡድን መሪ ደረጃ XIV ላይ የአመልካች መ/ቤት ጂማ ቅርንጫፍ ተወዳድሮ ለመመደብ በኢኮኖሚክስ የትምህርት ዓይነት የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አጥንቶ ስራ ላይ ባዋለው፣ በነጥብ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ የመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የትምህትር ዝግጁነት ስለማያሟላ በአመልካች መ/ቤት መከልከሉ ተገቢ ነው ብለናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. በዚህ ችሎት 273313 ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

5. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

6. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 165886

የካቲት 11 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- አቶ አምባቸው ተፈራ - ቀረቡ::

ተጠሪ፡- ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 9 ፕብሊክ ሰርቪስና የሠው ሃብት ልማት - የቀረበ የለም::

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ከመንግስት ሰራተኛ ቅጥር መሰረዝ ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፕብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሐምሌ 25 ቀን 2010 ዓ/ም ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ከተጠሪ ጋር ለስራ መደቡ በወጣው ማስታወቂያ አግባብ ተወዳድረው ተቀጥረው ከጥር 09 ቀን 2010 ዓ/ም ጀምሮ በመስራት ላይ እያሉ ተጠሪ በቁጥር ል/ክ/ከ/ወ/09/ፕ/ሠ/የሰ/ሃ/ል/148/10 እና በቁጥር ል/ክ/ከ/ወ-9/ፕ/ሰ/የሰ/ሃ/ል/145/10 በቀን 16/11/2010 ዓ/ም በተፃፉ ደብዳቤዎች እና ል/ክ/ከ/ወ-9/ፕ/ሰ/የሰ/ሃ/ል/160/10፣ ል/ክ/ከ/ወ-9/ፕ/ሰ/የሰ/ሃ/ል/159/10 በቀን 25/11/2010 በተጻፈ ደብዳቤ መደቡ ላይ ቅጥሩ የተፈፀመው መስፈርቶችን ሳታሟሉ ነው በሚል ምክንያት ቅጥሩን የሰረዘባቸው መሆኑን ዘርዝረው የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም ቅጥሩ የተሰረዘው የሚመለከተው አካል ኢንስፔክሽን ስርቶ ቅጥሩ የተፈመፀው ከመመሪያው ውጪ መሆኑን በማረጋገጡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የአስተዳደር ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ከአጣራ በኋላ አመልካች የተቀጠሩበት መንገድ በሚመለከተው አካል የወጣውን መመሪያ ያልተከተለ መሆኑ በኢንስፔክሽን በመረጋገጡና የሚመለከተው አካል ቅጥሩ እንዲሰረዝ አስተዳደራዊ ውሳኔ በአስተላለፈው አግባብ ተጠሪ ቅጥሩን መሰረዙ ለጉዳዩ ቀጥተኛ

ተፈፃሚነት ካለው ከአዋጅ ቁጥር 56/2010 አንቀፅ 94 ድንጋጌ አንጻር የሚነቀፍበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡፡ እንዲሁም የሰበር አቤቱታቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች ቀድመው ይሰሩበት የነበረውን ስራ ለቀው ተጠሪ መስሪያ ቤት በአወጣው ማስታወቂያ ተወዳድረው አሸናፊነታቸው ተረጋግጦ ቅጥሩ ከተፈጸመና ከስድስት ወራት በላይ በስራ ላይ ቆይተው የአፈፃጸም ችግር ባላሳዩበት ሁኔታ ቅጥሩ መመሪያውን ያልተከተለና የስራ መደቡ የሚጠይቀውን መመዘኛ አመልካች ሳያሟሉ የተፈፀመ ነው ተብሎ መሰረዙ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀም ያለመፈፀሙን በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ከተጠሪ ጋር ቅጥር የፈፀሙት ተጠሪ በአወጣው ማስታወቂያ መሰረት ተወዳድረው አሸናፊነታቸው በመረጋገጡ ቢሆንም ይህ ሂደት ግን የቅጥር ስርዓት ለመግዛት የወጣው መመሪያን ያልተከተለ መሆኑን በኢንስፔክሽን የተረጋገጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ቅጥሩ በማናቸውም ጊዜ የሚሰረዝ መሆኑን በከተማው አስተዳደር ምክር ቤት በወጣውና የመንግስት ሰራተኞችን ጉዳይ በሚገዛው አዋጅ ቁጥር 56/2010 አንቀፅ 94 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ አዋጁ የቅጥር ስርዓቱን ባልከተለ መንገድ የተፈፀመ ቅጥር ስህተቱ የቀጣሪው መንግስት መስሪያ ቤት ቢሆን እንኳን ቅጥሩ ፀንቶ የሚቆይበት አግባብ መኖሩን የሚያስገነዝብ አይደለም፡፡ በዚህ መልኩ ያለመደንገጉ ደግሞ ስራንና ሰራተኛን ከማገናኘት በተጨማሪ ከሕግ ውጪ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጸሙ የመንግስት ሰራተኞች የቅጥር ውሎች ፀንተው እንዳይቆዩ ለማድረግ የታሰበ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም አመልካች መጀመሪያውን የተቀጠሩት ከህግ ውጪ በወጣው የውድድር መስፈርት መሆኑን እያመኑ ስህተቱ እርሳቸውን እንደማይመለከት በማድረግና ይኼው ተግባር ቀድሞ በነበራቸው የስራ እድል ላይ የፈጠረውን ችግር በማንሳት ለጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 56/2010 አንቀፅ 94 ድንጋጌ ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደማይገባ አድርገው የሚያቀርቡት ክርክር በሕግ ፊት ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ ስለሌለ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችንና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ህግ መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. **በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ እና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 985/2010 በ09/01/2011 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 29035 በ28/02/2011 ዓ/ም፣ በከተማው ይግበኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 29323 በ13/03/2011 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡**
2. **ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡**

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

ንብረት

የሰ/መ/ቁ - 164326

ቀን - 28/05/2011

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ አበበ ዘገየ - ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወ/07 ኮ/የቤቶች ልማት ጽ/ቤት - በሌለበት፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የመንግስት ቤት ኪራይ መብት በውርስ ሊተላለፍልኝ ይገባል በሚል የቀረበውን ክርክር መሠረት በማድረግ የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት የቀረበን አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ታህሳስ 20 ቀን 2009 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ በአ/ከ/ክ/ከተማ ወረዳ 7 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤ/ቁጥር 634 ተከራይተዉ የነበሩት እናታቸዉ በሞት መለየታቸዉን ተከትሎ ወራሽነት ያረጋገጡ ቢሆንም የሚች ልጅ አይደለህም በሚል ምክንያት ተጠሪ የኪራይ መብቱን በስማቸዉ ለማድረግ ፊቃደኛ አለመሆኑን ጠቅሰዉ ይህኑን ተገዶ እንዲፈጸምለት ይወሰንለት ዘንድ የጠየቀዉን ዳኝነት መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡

ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት የታየ ሲሆን፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ስለጉዳዩ ከሚመለከተዉ መመሪያ እና ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ከፊሉ የመኖሪያ ቤት ሲሆን ከፊሉ የንግድ ቤት መሆኑ መረጋገጡን እና ከንግድ ቤቱ ከኋላ በኩል የሚገኙትን ሁለት ክፍል የመኖሪያ ቤቶች የመከራየት መብት እንዲተላለፍላቸዉ፤ በሌላ በኩል አመልካች የሚች የእህት ልጅ በመሆን ከሚች ዘንድ አደጉ እንጂ ከሚች ያልተወለዱ በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 24 መሠረት የንግድ ቤቱን የመከራየት መብት የሌላቸዉ መሆኑን ገልፆ የንግድ ቤቱን በተመለከተ የቀረበዉን ዳኝነት

ውድቅ በማድረግ ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ለከተማዉ ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት በቅደም ተከተል ያቀረበዉ አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 06/02/2011 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ አመልካች ከሚች ጋር ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቤት ዉስጥ ረዘም ላለ ጊዜ መኖራቸዉ ተረጋግጦ እያለ እና በዚህም መሠረት በመመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 15(1)(ሐ) እና አንቀጽ 24 መሠረት የኪራይ መብቱ ሊተላለፍልኝ እየተገባ የስር ፍርድ ቤት ይህን ጥያቄዬን ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ታርሞ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል።

አቤቱታዉ ተመርምሮም አመልካች የኑዛዜ ወራሽነትን አረጋግጠዉ ባቀረቡበትና ኑዛዜዉ ባልተሸረበት ሁኔታ የኪራይ መብቱ ሊተላለፍላቸዉ አይገባም በሚል የተሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ፣ ተጠሪ እንዲቀርብ ጥሪ የተደረገለት ቢሆንም ቀርቦ መልስ ባለመስጠቱ መልስ የመስጠት መልስ ታልፏል።

ከስር ጀምሮ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም አቤቱታዉ ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከአመልካች ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመረዉም አመልካች በሚች ዘንድ ያደጉ እና የሚች የኑዛዜ ወራሽ መሆኑ እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ከፊሉ የንግድ ቤት መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል። አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት ከልጅነታቸዉ ጀምሮ በሚች ዘንድ አድገዉ እና የሚች የኑዛዜ ወራሽ በመሆናቸዉ የንግድ ቤቱም እንደሚገባቸዉ በመግለጽ ነዉ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 24 የቀበሌ ንግድ ቤትን ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ ስለሚቻልበት ሁኔታ ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተከራይ በመሞቱ ምክንያት የንግድ ቤቱ ለ3ኛ ወገን ሊተላለፍ የሚችለዉ ለሚች ህጋዊ ባል ወይም ሚስት እንዲሁም ለሚች ህጋዊ ወራሽ ስለመሆኑ በንዑስ አንቀጽ "ሀ" እና "ለ" ስር ተመልክቷል። አመልካች በሚች ዘንድ ያደጉ ቢሆንም ከሚች የተወለዱ ባለመሆናቸዉ የሚች ህጋዊ ወራሽ ሊሆኑ አይችሉም። በመሆኑም አመልካች በሚች ዘንድ ማደጋቸዉ እና የሚች የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸዉ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ የንግድ ቤት የኪራይ መብት ተጠቃሚ ሊያደርጋቸዉ የሚችል አይደለም። አመልካች በአቤቱታቸዉ የሚጠቅሱት የመመሪያዉ አንቀጽ 39 ድንጋጌም የቀበሌ የመኖሪያ ቤት ከፊሉን ወደ ንግድ ቤት መቀየር ስለሚቻልበት ሁኔታ የሚደነግግ እንጂ ከፊሉ የንግድ ቤት በሆነዉ ቤት ዉስጥ ከሚች ዘንድ ያደገ ሰዉ በቀጥታ የንግድ ቤቱ የኪራይ

መብት ሊተላለፍለት እንደሚችል ስለማይደነግግ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት አቤቱታም ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ በስር በየደረጃዉ ባሉት ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ይህኑን መመሪያ ገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 27955 በቀን 26/07/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የከተማዉ የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቅደም ተከተል የሰጡትን ዉሳኔ እና ትዕዛዝ፣ በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁጥር 162083

ሚያዚያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንደሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች ፡- ወ/ሮ አበቡ ተመስገን - ወኪል መኩርያው አዱኛ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ በሬ አባተ ወኪል አስቻለው አልቀረቡም፡፡

2. አቶ አስችሏል አለም

3. መ/ሬ ማረጌ ፍቃዱ

4. አቶ ማስሬ አለማየሁ

5. አቶ ሰማኝ ባህሩ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ለዚህ ሰበር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በአማራ ክልል በዋድላ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ከወል ይዞታ ላይ በአዋሳኝ ተለይቶ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶን የያዝነውን ይዞታችንን አመልካች በሀምሌ ወር 2009ዓ.ም አርሳ ሁከት ስለተፈጠረችብን ሁከት ይወገድልን የሚል ነው፡፡

አመልካች በበኩላቸው በሰጡት መልስ ክስ የቀረበብኝ መሬት በ1983 ዓ.ም የተሰጠሁት የይዞታ መሬት ክሱ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በይዞታ ማረጋገጫ ደብተሬ ላይ ያስመዘገብኩት ይዞታዬ ስለሆነ የራሴን መሬት ማረሴ ሁከት ሊባል ስለማይችል ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዋድላ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና የወረዳው የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በባለሙያ አጣርቶ ባቀረበው ሪፖርት ደልዳይ ኮሚቴ አባላት ይዞታው በ1983ዓ.ም ለአመልካች ባለቤት የተደለደለ ይዞታ ነው ሲሉ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ የወል ይዞታ መሬት የነበረ መሆኑንና ለተጠሪዎች በ2009 ዓ.ም ተሰጥቶ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰራላቸው መሆኑን መግለፁን ተከትሎ ማስረጃውን መዝኖ አመልካች የተጠሪዎችን ይዞታ በማረስ የፈጠሩት ሁከት ይወገድ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተው የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘታቸው ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ተጠሪዎች በተሰጠን የጋራ መሬት ላይ ሁከት ተነሳብን ብለው የሀሰት ማስረጃ ከማቅረብ ውጪ ለብዙ ዓመታት ይዘው ለመቆየታቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ለ26 ዓመታት በእጄ የቆየውንና የመንግስት ግብር ስገብርበት የነበረ መሆኑን፤የተሰጠኝ የይዞታ ማረጋገጫ ይህንኑ መሬት በውስጡ አቅፎ እንደሚይዝ እየገለፅኩ በስር ፍ/ቤት ለማስረጃዬ ልዩ ትርጉም ተሰጥቶ ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ የተጠሪዎች ክስ አቀራረብ መሬቱ በጥቅምት ወር 2009 ዓ.ም በእጃቸው የገባ የጋራ መሬት መሆኑን ይግለጹ እንጂ በእጃቸው ስለመግባቱ ያቀረቡት አስረጂ የለም፡፡ የአመልካች ምስክሮቹ ይዞታው አስቀድሞ ለሚች ባለቤቱ ተደልድሎ እንደነበርና ሲሞት እኔ መጠቀም እንደቀጠልኩ በሚገባ አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ሁከት ይወገድ ሲሉ የሰጡት ውሣኔ ስህተት በመሆኑ ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የመሬት አስተዳደር በ19/03/2010 ዓ.ም በተፃፈ ሪፖርት በ1983 ዓ.ም ደልዳይ ኮሚቴ ለተከሳሽ ተሰጠ እንዳሉ የአካባቢው ህብረተሰብ ደግሞ የወል መሬት ነው ብለን ከማለት ያለፈ መሬቱን በትክክል የማን እንደሆነ አጣርቶ ባልገለፀበት ሁኔታ የአመልካች ክርክር ውድቅ የተደረገበት አግባብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ይዘት የስር ፍ/ቤት ለቀበሌው አስተዳደር በሰጠው ትእዛዝ መሠረት አስተዳደሩ ለክቶና አጣርቶ በሰጠው መልስ ይዞታው ተጣርቶ የተሰጠን መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የወል መሬቱ ጥቅምት 16 ቀን 2009 ዓ.ም መሬቱ ተለክቶ የተሰጠን የወረዳው የመሬት ዴክስ ኃላፊና የቀበሌ መሬት አጠቃቀም የቀበሌው የመሬት መሀንዲስ ዋና ኃላፊ ባሉበት የአካባቢውም ህዝብ እና አመልካች ባሉበት የተሰጠን የልማት መሬት እንጂ ተጠሪዎች ባልነው ብቻ የተሰጠን አይደለም፡፡ በወቅቱ አመልካች አልተቃወመችም፡፡ ስለሆነም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጐ የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ

ይጽናልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ግራ ቀኙን ያከራከረው ክርክር ያስነሳው ይዞታ ለተጠሪዎች በ2009 ዓ.ም ከመሰጠቱ በፊት ይዞታው የአመልካች ነው ወይስ የወል ይዞታ የነበረ ነው የሚለው ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ክርክር ያስነሳው ይዞታ ከ2009 ዓ.ም በፊት የወል መሬት ነበር የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው የወረዳው የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት አጣርቶ በላከው ሪፖርት ላይ በ1983 ዓ.ም መሬቱ ለአመልካች ባለቤት የተደለደለ መሆኑን ቢገልፁም የአካባቢው አብዛኛው ሕብረተሰብ መሬቱ የወል ይዞታ መሆኑን መግለፃቸውንና አመልካች ይዞታውን ተደለደልን የሚሉት በ1983 ዓ.ም ቢሆንም የይዞታ ማረጋገጫ ያወጡት ግንቦት 20 ቀን 2009 ዓ.ም መሆኑ አስቀድሞ የተደለደሉት መሬት መሆኑን አያሳይም በሚል ነው፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩትም ሆነ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘው ጭብጥ ክርክር ያስነሳው ይዞታ በ1983 ዓ.ም ለአመልካች ባለቤት የተደለደለ መሆኑን የመሬት ደልዳይ ኮሚቴዎች በገለፁበት እና የአካባቢው ሕብረተሰብ የወል መሬት ነው ባሉበት ሁኔታ በአግባቡ ሳይጣራ አመልካች መሬቱን ማረሳቸው የሁከት ተግባር ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ የፌዴራሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40/4/ የኢትዮጵያ አረሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ መሆኑ በግልጽ ተደንግጐ ይገኛል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ አርሶ አደር በሕግ አግባብ ካሳ ተከፍሎት ወይም ምትክ መሬት ተሰጥቶት እንዲለቅ ከሚደረገው በቀር በመንግስት ወይም በአስተዳደር አካላት ፍላጐት ብቻ ከመሬቱ ሊነቀል አይችልም፡፡ መሬቱ ለሌላ አርሶ አደር ከመሰጠቱ በፊት አስቀድሞ ባለይዞታ የነበረን ሰው ከመሬቱ መነቀልን እንዳያስከትልበት በተገቢው ጥንቃቄ ተደርጐ መጣራት አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ በ1983 ዓ.ም የመሬት ደልዳይ ኮሚቴ የነበሩ ሰዎች ክርክር ያስነሳው መሬት ለአመልካች ባለቤት ተደልድሎ ይዘው ሲገለገሉበት የቆዩ መሆናቸውን በማጣራት ሂደት ከመገለፃቸውም በላይ ዘግይቶም ቢሆን ለአመልካች በግንቦት 20 ቀን 2009 ዓ.ም የተዘጋጀ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የአካባቢው ሕብረተሰብ ይዞታው ለተጠሪዎች ከመሰጠቱ በፊት ጽ/ቤት የአመልካች ይዞታ ሳይሆን የወል ይዞታ መሆኑ በማጣራት ሂደት ለወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ገልፀዋል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት ይህን አከራካሪ የሆነ ጉዳይ ለመለየት ተገቢው ማጣራት ማድረግ ሲገባው ለአመልካች ዘግይቶ የይዞታ ማረጋገጫ መሰጠቱ ላይ በመመስረት ይዞታው የውል ይዞታ ነበር የሚል

ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ዘግይቶ ለአመልካች መሰጠቱ በምንም መልኩ ይዞታው የአመልካች ያልነበረ መሆኑን አያረጋግጥም፡፡ ምክንያቱም አመልካች ይዞታው የተሰጣቸው በ2009 ዓ.ም ነው የሚል ክርክር የላቸውም ይልቁንም ክርክር ያስነሳው ይዞታ ክርክር ያላስነሳውና አሁንም በአመልካች እጅ የሚገኝ ሕጋዊ ይዞታቸው አካል መሆኑን እና የይዞታ ማረጋገጫ ዘግይቶ ቢሰጣቸውም በ1983 ዓ.ም ጀምሮ ይዞታውን ተደልድለው እያረሱ ሲጠቀሙበት ቆይተው በ2009 ዓ.ም ላይ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ክርክር ያስነሳውን ይዞታ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ተደልድለው ሲጠቀሙበት የቆዩ ከሆነ ከይዞታቸው ያለመነቀል መብታቸውን ለማስከበር በቅድሚያ ከ2009 ዓ.ም በፊት ክርክር ያስነሳው ይዞታ ለምን አገልግሎት ይውል እንደነበር የይዞታው አዋሳኝ መሬት ወይም ይዞታ ያላቸውን ሰዎች በማጣሪያ ምስክርነት በማስቀረብ ለግራ ቀኙ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ እድል በሚፈጥር መልኩ ማጣራቱ ተገቢ ነበር፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች ክርክር ያስነሳው ይዞታ በ2009 ዓ.ም ለተጠሪዎች ከመሰጠቱ በፊት ለምን አገልግሎት ይውል እንደነበር ማን ሲገለገልበት እንደነበርና ከመቼ ጀምሮ የሚለውን ክርክር ያስነሳው ይዞታ አዋሳኝ መሬቶችን ባለይዞታዎችን በማጣሪያ ምስክርነት በማስቀረብና በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ሲገባው ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ግንቦት 20 ቀን 2009 ዓ.ም ዘግይቶ መሰጠቱ ላይ በመመስረት ይዞታው የወል ይዞታ ነበር በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ አመክኗዊ ካለመሆኑም በላይ በአግባቡ ሳይጣራ ውሣኔ መሰጠቱ በፌዴራሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/4/ የተመለከተውን የአርሶ አደር ከመሬት ያለመነቀል መብት ሊጥስ የሚችል በመሆኑ በአግባቡ ሳይጣራ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ተሽሮ እንደገና ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1ኛ. በዋድላ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14292 ታህሳስ 24 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 23130 መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ውሣኔ እና በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.03-21728 ሐምሌ 28 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ውሣኔ የፀናው ውሣኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. ከላይ በፍርድ ሀተታው በተገለጸው አግባብ ክርክር ያስነሳው ይዞታ በ2009 ዓ.ም ለተጠሪዎች ከመሰጠቱ በፊት የአመልካች የእርሻ መሬት ይዞታ ነው ወይስ የወል ይዞታ ነበር የሚለውን የይዞታውን አዋሳኝ መሬት በባለይዞታዎችን በማጣሪያ ምስክርነት በማስቀረብ እና በማጣራት ወይም በሌላ ተገቢ ነው ባለው መንገድ በማጣራት ተገቢውን ይወስን ዘንድ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343/1/ መሰረት ጉዳዩን ለዋድላ ወረዳ ፍ/ቤት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3ኛ. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል። መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ተመላሽ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ብ/ግ

የሰ.መ.ቁ 178664

ግንቦት 28 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የአቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት ሞግዚት አቶ ኪዳነማሪያም ሐይሉ

ተጠሪዎች፡- ወ/ሮ አሚት አጽብሃ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 05 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 107657 መጋቢት 25 ቀን 2011 ዓ.ም ሞግዚት የሆኑለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት መሬቱ ከሚገኝበት አካባቢ ውጪ በአማራ ክልል የሚኖር እና የስነ-አእምሮ ችግር እንዳለው መሬቱ ባለበት ማሕበረሰብ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 ውጭ የስነ አእምሮ ችግር እንዳለው ማስረጃ ቀርቧል በሚል ምክንያት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሐድነት ቀበሌ መሬት ዳኝነት ነው፡፡ በመሬት ዳኝነቱ በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉ 4 ግለሰቦች ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ 5ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በመሬት ዳኝነቱ ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ሞግዚት የሆኑላቸው አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት በሐድነት ቀበሌ አዋሳኙ በክሱ የተገለጸውን በእንፎ ጎጥ ውስጥ የሚገኘውን የእርሻ መሬት እና በማይ ዝሕልቶ የሚገኘውን የመስኖ መሬት ቀደም ሲል በወላጅ አባታቸው በሰማዕት ታጋይ ገ/ሕይወት ሀይሉ ስም የነበረ መሆኑን፤ ይህንኑ መሬት ሕጋዊ ወራሽ በመሆን የያዙት መሆኑን፤ ከባድ የስነ አእምሮ ችግር ያለባቸው እና በሞግዚት የሚተዳደሩ መሆኑን፤ ከ1ኛ እስክ 4ኛ ያሉት ተከሳሾች አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/5(ለ)(ሐ) ድንጋጌን በመጣስ

መሬቱን ለተጠሪ ያደሉባቸው መሆኑን በመግለጽ መሬቱን እንዲያስረክቧቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

የስር ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተከሳሾች በሰጡት መልስ፡- አከራካሪውን መሬት በ1983 ዓ.ም ታጋይ ገ/ሕይወት ሀይሉ የታደሉት መሆኑን እና በሕይወት እስከነበሩበት ጊዜ ድረስ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን፤ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላም ለሌላ ሰው ተሸጋሽጎ የነበረ መሆኑን፤ አመልካች በውርስ ይገባኛል ብሎ ተቃውሞ በ2001 ዓ.ም በውርስ ያገኘው መሆኑን፤ መሬቱን እንደወረሰው ወደ ምዕራብ ጎጃም የሄደ መሆኑን፤ በአዋጁ እና በደንቡ መሠረት ተጠንቶ መሬቱ የተሸጋሸገ መሆኑን፤ የአእምሮ ችግር አለኝ የሚለው ሆነ ብሎ በተንኮል መሆኑን፤ ሕመምተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ የሕክምና ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑን፤ አመልካች የውክልና መብታቸው ሲዘጋባቸው እንደገና የአእምሮ ችግር አለበት በማለት ክስ የመሰረቱ መሆኑን፤ መሬቱን ሕግ እና መመሪያ ተከትለው ያሸጋሸጉት መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ መሬቱ የሰማዕት ታጋይ የነበረ በመሆኑ በሕይወት እስከነበሩበት ጊዜ ድረስ የመጠቀም መብት የነበራቸው መሆኑን፤ አባታቸው በሞት ከተለዩ በኋላ ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የማይችል መሆኑን፤ አመልካች በክሱ የገለጸው የሰማእት ታጋይ ተጠቃሚ መሆኑን የሚያሳይ ሳይሆን ወራሽ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን፤ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ቀበሌውን ለቆ ወደ ሌላ አገር ስለሄደ በቀበሌው እና በጎጥ መሬቱ ተጠንቶ ለ7 ዓመት የጠበቁት መሆኑን ፤ አመልካች ከሁለት ዓመት በላይ አካባቢን ስለለቀቅ በመሬቱ የመጠቀም መብት የሌለው መሆኑን፤ ግለሰቡ ከቀበሌአቸው ለቃቂ መሆናቸው እና በስነ አእምሮ ሕመም ምክንያት እንደተለዩ ተጠንቶ መሬቱ በሽግሽግ እንዲሰጥ የተወሰነ መሆኑን እና ተጠሪ መሬት ስላልነበራቸው የተሰጣቸው መሆኑን፤ አመልካች ከዚህ በፊት በውክልና ክስ አቅርበው ውክልናው ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ ከተደረገባቸው በኋላ የስነ አእምሮ ችግር አለበት በማለት ከሌለ አካባቢ የፍ/ቤት ማስረጃ በማቅርብ ያቀረቡት ክስ ተገቢ ስላልሆነ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት የመሬት ዳኝነት የግራቀኙ ምስክሮች እንዲሰሙ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የአመልካች ምስክሮች አከራከሪው መሬት አመልካች ሞግዚት የሆኑለት አባት የታጋይ ገ/ሕይወት ሀይሉ የነበረ እና ለተጠሪ የተሸጋሸገ መሆኑን በመግለጽ የመሰከሩ ሲሆን የተጠሪ እና የስር ተከሳሾች ምስክሮች ደግሞ አከራካሪው መሬት የታጋይ ገ/ሕይወት ሀይሉ የነበረ መሆኑን እና ልጁ በ2001 ዓ.ም የወረሰው መሆንኑ፤ አመልካች ለሰባት አመታት ወደ አማራ ክልል ስለሄደ በጎጥ ተጠንቶ መሬቱ ለተጠሪ የተሸጋሸገ መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል። የመሬት ዳኝነቱም ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል መዝኖ ሽግሽጉ ሕጋዊ ስለሆነ አከራካሪው መሬት ለተጠሪ ሊጸናላት ይገባል በማለት ወስኗል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለምስራቅ ዞን ጋንታ አፈሹም ወረዳ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ሞግዚት የሆኑለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት የሰማዕት ታጋይ አባቱን መሬት ወርሷል፤ ግለሰቡ የአእምሮ ችግር ያለበት በመሆኑ በሞግዚት ሊተዳደር እንደሚገባ እና የሕግ ክልከላ እንደተደረገበት የሚያሳይ የፍ/ቤት ውሳኔ እንዳቀረበ መዝገቡ ያሳያል፤ የገጠር መሬት ተጠቃሚነት ሊቋረጥ የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/1 መሰረት ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 11/2-9 ላይ ካሉት ምክንያቶች ውጪ እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል፤ የአመልካች ክስ በማስረጃ ተደግፎ ቀርቦለት እያለ ሽግሽጉ ሕጋዊ ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ አግባብ አይደለም በማለት የመሬት ዳኝነቱ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ አከራካሪው መሬት ለአቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት ሊሆን ይገባል ሲል ወስኗል።

ተጠሪ በበኩላቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም። ተጠሪ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል። የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ አከራካሪውን መሬት ወርሶ መሬቱ ባለበት ቦታ ሆኖ በመሬቱ ካልተጠቀመበት እና አካባቢውን ከለቀቀ በደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 15/2 መሠረት መሬቱ ሊሸጋሸግ እንደሚችል ተደንግጓል። አመልካች መሬቱ ከሚገኝበት አካባቢ ውጪ በአማራ ክልል የሚኖር እና የስነ-አእምሮ ችግር እንዳለው መሬቱ ባለበት ማሕበረሰብ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 ውጭ የስነ አእምሮ ችግር እንዳለው ማስረጃ ቀርቧል በሚል ምክንያት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ የመሬት ዳኝነቱ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፦ አመልካች ሞግዚት የሆንኩለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት የሚች ሰማእት ገ/ሂወት ልጅ እና ሕጋዊ ወራሽ ነው፤ የሰማእት ልጅ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/5/ሐ መሠረት በሕይወት እስካለ ድረስ የተጠቃሚነት መብት አለው፤ በአዋጁ አንቀጽ 11/5/ሰ ከባድ የአእምሮ ችግር ያለው ከሚኖርበት ቀበሌ ለቆ ሌላ ቀበሌ ወይም ከተማ የሔደ ሰማዕት ታጋይ እና ሚሊሻ መሬት የመጠቀም መብት አለው፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአእምሮ ችግር እንዳለበት ለማስረዳት የቀረበውን ከአማራ ክልል ወረዳ ፍ/ቤት የተሠጠውን ማስረጃ በደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 መሠረት ተቀባይነት የለውም ማለቱ አግባብ አይደለም፤ ደንብ ቁጥር 85/2006 የፍ/ቤት ማስረጃ እንዳይቀርብ ግልጽ ክልከላ ባላስቀመጠበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃው ተቀባይነት የለውም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአሁን አመልካች የአእምሮ ሕመምተኛ መሆኑ ባለበት አካባቢ ታውቆ በሞግዚት የሚተዳደር ሆኖ ሳለ ክርክር የተነሳበት መሬት ባለበት አካባቢ ባለው

ማሕበረሰብ ስላልተረጋገጠ መሬቱ ለአመልካች አይገባም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከክልሉ አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/5(ሐ) እና ከደንብ ቁጥር 85/2006 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች አስቀድመው በውክልና ክስ አቅርበው መዝገቡ ከተዘጋባቸው በኋላ የስነ አእምሮ ችግር አለበት በሚል ምክንያት ሞግዚት ነኝ ብለው መቅረባቸው አግባብ አይደለም፤ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ሕግ መሠረት መሬቱ ከሚገኝበት ማህበረሰብ ወይም በሕክምና ቦርድ ያልተሰጠ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው አመልካች ሞግዚት የሆኑለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት የሚች ታጋይ አባቱ የነበረውን መሬት የወረሰ መሆኑን፤ ግለሰቡ አካባቢውን ከለቀቀ ከሰባት ዓመት በላይ መሆኑን፤ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በሚመለከታቸው የአስተዳደር አከላት መሬቱ ተጠንቶ ለተጠሪ የተሸጋሸገ መሆኑን፤ አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት ባለበት የስነ አእምሮ ሕመም ምክንያት የሕግ ክልከላ እና አሳዳሪነትና ሞግዚትነት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ስለራሱ ደህንነት እና ስለንብረቱ አጠባበቅ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 359/1 መሠረት አመልካች አሳዳሪ እና ሞግዚት ሆነው የተሾሙለት መሆኑን ነው፡፡
ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች በማስረጃነት ያቀረቡትን የፍ/ቤት ውሳኔ ተቀብሎ አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት የስነ አእምሮ ሕመም ያለበት በመሆኑ አካባቢውን የለቀቀ ቢሆንም የመሬት ተጠቃሚነቱ ሊቋረጥ አይገባም በማለት የወሰነ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ አመልካች መሬቱ ከሚገኝበት አካባቢ ውጪ በአማራ ክልል የሚኖር እና የስነ-አእምሮ ችግር እንዳለው መሬቱ ባለበት ማሕበረሰብ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 ውጭ የስነ አእምሮ ችግር እንዳለው ማስረጃ ቀርቧል በሚል ምክንያት የመሬቱ ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት ባለበት የስነ አእምሮ ሕመም ምክንያት የሕግ ክልከላ እና አሳዳሪነትና ሞግዚትነት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ስለራሱ ደህንነት እና ስለንብረቱ አጠባበቅ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 359/1 መሠረት አመልካች አሳዳሪ እና ሞግዚት ሆነው ተሹመውለታል በማለት ከአማራ ክልል ዱርቤቱ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው የፍ/ቤት ውሳኔ ግለሰቡ የመሬት ተጠቃሚነት መብቱ እንዳይቋረጥ ለማድረግ

የሚያስችል ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው። በመሆኑም ለዚሁ መሠረታዊ ጭብጥ ምላሽ መስጠት ያስችለን ዘንድ ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ሕጎች እና አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል።

በመሠረቱ መከልከሉ ለጤናው እና ለጥቅሙ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ እንዲሁም ስለዕብዱ ሰው ወራሾች ጥቅም ዕብድ ሰው እንዲከለከል / እንዲጠበቅ / ዳኞች ፍርድ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን፤ ዳኞች የአንዱን ሰው መከልከል ከመፍረዳቸው በፊት ክልከላውን ለማድረግ የግድ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ተረድተው አሳዳሪ እና ሞግዚት የሚሾሙለት መሆኑን እና ይህንኑ ውሳኔ የሚሰጠውም የስነ-አእምሮ ችግር አለበት የተባለው ሰው በሚገኝበት አካባቢ ያለ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ስለ ፍርድ ክልከላ የሚደነግጉት የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 351 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝቡናል። እነዚህ ድንጋጌዎች የስነ አእምሮ ችግር ያለበትን ሰው እና ወራሾች ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል በልዩ ሁኔታ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ሲሆኑ ተፈጻሚነታቸውም የፍርድ ክልከላ የተደረገበት ሰው ለጤናው እና ለጥቅሙ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ማናቸውም ጉዳይ ላይ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል።

በሌላ በኩል የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11/1 በአዋጁ ከተፈቀዱት ምክንያቶች ውጪ ከሚኖርበት ቀበሌ ከሁለት ዓመት በላይ ወደ ሌላ ቀበሌ ወይም ከተማ የለቀቀ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱ ተነስቶ የሚተዳደር መሆኑ ይደነግጋል፤ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 11/5 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) እና (በ) ከባድ የሥነአእምሮ ችግር፤ የአካል ጉዳት ያለባቸው እና ራሣቸው ለማረስ የማይችሉ ጧሪ እና ተንከባካቢ አጥተው ቀበሌአቸውን የለቀቁ እና በቀበሌው ሥራ አስፈጻሚ የሚታመንባቸው በነበራቸው የገጠር የመሬት ይዞታ ያላቸው የተጠቃሚነት መብት የተጠበቀ እንደሆነ ይደነግጋል። አዋጁን ለማስፈጸም የወጠው ደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 ድንጋጌም እነዚህ ግለሰቦች ያላቸው በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የሚጠበቅላቸው መሬታቸው በሚገኝበት ቦታ ባለው ሕብረተሰብ የሚታመንበት ከሆነ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በሕክምና ቦርድ የተፈረመ ማስረጃ ሲቀርብ ነው በማለት ይደነግጋል።

በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅም ሆነ አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ላይ ከላይ በተገለጸው አግበብ የተደነገገ ቢሆንም የስነ አእምሮ ችግር ያለበት ሰው ለጤናው እና ለጥቅሙ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ማናቸውም ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን በማለት በፍትሐብሔር ሕጉ ላይ ስለፍርድ ክልከላ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ በፍ/ቤት የተሰጠ የፍርድ ክልከላ ውሳኔ ተቀባይነት አይኖረውም ወደሚል ድምዳሜ የሚወስደን አይደለም። ይልቁንም በክልሉ የገጠር መሬት ሕግ ላይ የስነ አእምሮ ችግር ያለባቸው ሰዎች የመሬት ተጠቃሚነት መብት እንዲቀጥል ለማድረግ የተቀመጡትን መስፈርቶች የስነ አእምሮ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል

በፍትሐብሔር ሕጉ ላይ ስለፍርድ ክልከላ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር ተጣጥሞው ሲታዩ አመልካች ሞግዚት እና አስተዳዳሪ የሆኑለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት በሚኖርበት አካባቢ ካለው ዱርቤቱ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው የፍርድ ክልከላ ውሳኔ የመሬት ተጠቃሚነቱ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል ሕጋዊ እና ተቀባይነት ያለው ማስረጃ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባው አመልካች ሞግዚት እና አስተዳዳሪ የሆኑለት አቶ ጸጋይ ገ/ሕይወት መሬቱ ከሚገኝበት አካባቢ ውጪ በአማራ ክልል የሚኖር እና የስነ-አእምሮ ችግር እንዳለው መሬቱ ባለበት ማሕበረሰብ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 13/8 ውጭ የስነ አእምሮ ችግር እንዳለው ማስረጃ ቀርቧል በሚል ምክንያት የመሬቱ ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በትግራይ ብሔራው ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 107657 መጋቢት 25 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ዞን የጋንታ አፈሹም ወረዳ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 16243 ግንቦት 22 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 23813 ሠኔ 11 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ - 165314

ቀን - 30/09/2011

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የድሬዳዋ አስ/ቀበሌ 03 ጽ/ቤት - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ስንዱ ሳልቫቶር - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የተጠሪ ክስ ይዘትም በአጭሩ፡- በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 03 ቁጥሩ 315 ሆኖ ንብረትነቱ የሚች እናቴ የወ/ሮ ለምለም ሞገስ የነበረዉ ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት በመንግስት የተወረሰ ሲሆን ቤቱ እንዲመለስላቸዉ ወላጅ እናቴ ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በየደረጃዉ ላሉ ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ አካላት ባመለከቱት መሰረት ተገቢዉ ማጣራት ተደርጎ ተፈቅዶላቸዋል፤ አዋጁን የማስፈጸም ስልጣን ያለዉ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ በዉሳኔዉ መሠረት ቤቱን ለሚች እንዲያስረክቡ በተዋረድ ለሚገኙት አካላት ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም ተከሳሽ ቤቱን የያዙትን ሰዎች አስለቅቆ አላስረከበም፣ ይልቁንም ቤቱን አከራይቶ ኪራይ እየሰበሰበ ይገኛል፤ በመሆኑም ተከሳሽ የኪራይ ዉሉን አቋርጦ ቤቱን የያዙትን ሰዎች አስለቅቀዉ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠዉ መልስ፡- ቤቱ በአዋጅ ተወርሶ መንግስት የሚያስተዳድረዉ መሆኑን እና የተወረሰዉ ቤት እንዲመለስ ጥያቄ አቅርቦ ቤቱ እንዲመለስለት ስልጣን ባለዉ አካል የተወሰነለት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርቦ ባለመብት መሆኑን ሳያረጋግጥ ከሳሽ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና የቤቱን ማህደር ጨምሮ ሌሎች የተለያዩ ማስረጃዎችን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የተጠሪ አዉራሽ ወ/ሮ ለምለም ሞገስ አከራካሪዉ ቤት በአዋጅ ከተወረሰባቸዉ በኋላ በወቅቱ ስልጣን ባለዉ አካል ሌላ ቤት የሌላቸዉ መሆኑ ተረጋግጦ ቤቱ የተመለሰላቸዉ መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ አመልካች ተከራዮችን አስለቅቆ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ በማለት ወስኗል፡፡ በአመልካች አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኝን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 05/03/2011 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የተወረሱ ቤቶችን የማስመለስ ስልጣን ያለዉ የከተማና ቤቶች ልማት ሚኒስቴር ብቻ እንጂ በስሩ የሚዋቀሩ የአስተዳደር እርከኖች ጭምር አለመሆኑን ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም የሰጠበት ከመሆኑም በላይ ስልጣን አላቸዉ እንኳ ቢባል የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የሐረርጌ ክ/ሀገር ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት የወሰነዉ በተወረሰዉ ቤት ምትክ ተለዋጭ ቤት እንዲሰጥ የሚል ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የተወረሰ ቤት ለተጠሪ አዉራሽ እንዲመለስ እንደተወሰነ በማድረግ ተጠሪ ቤቱን እንዲረከቡ የሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሶ ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮም ቤቱ ለተጠሪ አዉራሽ እንዲመለስ ሳይታዘዝ እና ይልቁም የተወሰነዉ ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸዉ በሚል በሚመለከተዉ አካል የተሰጠዉን ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤቶች የተረጎሙበትን አግባብ ግራ ቀኝ በተገኙበት አከራክሮ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት በቀን 22/04/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ፀንቶ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በቀን 17/05/2011 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ በአጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ መሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ቤቱን እንዲያስረክቧቸዉ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ሚች እናታቸዉ ቤቱ እንዲመለስላቸዉ ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ለሚመለከተዉ አካል ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ቤቱ እንዲመለስላቸዉ በስራና ቤቶች ሚኒስቴር የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ እንዲመለስላቸዉ የወሰነ መሆኑን ግን በየደረጃዉ ያሉ የከተማዉ መስተዳደር አካላት ቤቱን ሊያስረክቧቸዉ ፍቃደኛ አለመሆናቸዉን ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ቤቱ በመንግስት የተወረሰ እና ለሚች እንዲመለስ ስልጣን ባለዉ አካል የተሰጠ ዉሳኔ አለመኖሩን ገልፆ

ይከራከራል፡፡ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ቤቱ ከተወረሰ በኋላ ለተጠሪ አዉራሽ የተወሰነ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዞ ግራ ቀኝ ካቀረቧቸዉ ማስረጃዎች በተጨማሪ ከድሬዳዋ አስተዳደር መሬት ልማት ቢሮ ቤቱን የሚመለከት ማህደር አስቀርቦ የመረመረ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ሚያዝያ 18/1977 ዓ.ም በድሬዳዋ ከተማ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር ምክር ቤት ለከፍተኛ ከነማ ወኪል የተፃፈዉ ደብዳቤ አከራካሪዉ ቤትና ቦታ በሚች ወ/ሮ ለምለም ሞገስ ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን፣ ከዚህ ቦታና ቤት በስተቀር በስማቸዉ ተመዝግቦ የሚገኝ በእርሱ ዘንድ አለመኖሩን መግለጹን፤ በመቀጠልም በቁጥር ለተቀፍፍ/2/1/78 በ25/04/1978 ዓ.ም የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የሐረርጌ ክ/ሀገር ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት በፃፈዉ ደብዳቤ የተጠሪ አዉራሽ ቤቱ እንዲመለስላቸዉ ማመልከታቸዉን ተከትሎ በቦታዉ ላይ በግንባር ተገኝቶ በመመልከት የቤቱ አሰራር ለድርጅት ሆኖ ያገኘዉ መሆኑን እና ከአዋጁ በፊትም በድርጅትነት ተይዞ የነበረ መሆኑን ማረጋገጡን፣ በዚህም ምክንያት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ምክር ቤቱ አጠቃላዩን ተረክቦ ምትክ ቤት ለተጠሪ አዉራሽ እንዲሰጣቸዉ ያስታወቀ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም በግልጽ የሚያሳየዉ የተወረሱ ቤቶችን ለመመለስ በወቅቱ ስልጣን የነበረዉ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ለሚች ለምለም ሞገስ (ለተጠሪ አዉራሽ) እንዲመለስ አለመወሰኑን፣ ይልቁንም ስልጣን ያለዉ የከተማ አስተዳደር ምትክ ቤት እንዲሰጣቸዉ መወሰኑን ነዉ፡፡ ለሚች ምትክ ቤት ይሰጥ ማለት የተወረሰ ቤት ይመለስ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች የተጠሪ አዉራሽ ሌላ ቤት የሌላቸዉ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በወቅቱ ስልጣን በነበረዉ አካል ተመልሶላቸዋል በሚል ድምዳሜ ላይ ሲደርሱ ምንን መነሻ አድርገዉ እንደሆነ ግልጽ አይደለም፡፡

ተከሳሽ በከሳሽ የቀረበበትን ክስ ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ከሳሽ ክሱን በማስረጃዎቹ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 258(1) እና 259(1) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የሚደርሱበት ድምዳሜ የቀረቡትን ማስረጃዎች መሠረት ሊያደርግ እንደሚገባ እሙን ነዉ፡፡ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት መሰረታዊ መርህም ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ከተወረሰ በኋላ ለአዉራሻቸዉ የተመለሰ መሆኑን የሚያሳይ ስልጣን ባለዉ አካል የተወሰነ ዉሳኔ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ተጠሪ ባላቀረቡበት ሁኔታ እና ፍርድ ቤት በተጨማሪነት ያቀረባቸዉ ማስረጃዎችም ቤቱ ከተወረሰ በኋላ ለአዉራሻቸዉ የተመለሰ መሆኑን የማያስረዳ ሆኖ እያለ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በሚል በስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 59375 በቀን 22/01/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13594 በቀን 05/02/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. ምትክ ቤት አስመልክቶ ተጠሪ መብቴን ለማስከበር የሚያቀርበው ጥያቄ ካለ በዚህ ውሳኔ ምክንያት አይታገድም፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሳ/ፀ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰበር መዝገብ ቁጥር 169648

ሰኔ 21 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ተሻለ ዋቆ

ተጠሪዎች፡-1ኛ. አቶ ንጉሴ ቦንቱ

2ኛ. አቶ አብደላ ቦንቱ

3ኛ. አቶ ነገሥ በዳሶ

4ኛ አቶ አቡ ነገሥ

5ኛ. አቶ ገመቹ ካይሞ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተመለከተ ጉዳይ ሆኖ የተጀመረው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ የአሁን ተጠሪዎች ተከሳሾች ሁነው ሲከራከሩ እንደነበረ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ አመልካች በስር ተከሳሾች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ተከሳሾች መብት ሳይኖራቸው በነጌሌ አርሲ ወረዳ በመራሮ ሀዊሎ ቀበሌ የሚገኝ አዋሳኙ በክሳቸው ላይ የተጠቀሰውን ሁለት ሄክታር እርሻ መሬት ተከሳሾች ከ2004 ዓ/ም ጀምረው ያለአግባብ የያዙብኝ ስለሆነ እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ከመሬት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ማንኛውም ክስና ክርክር በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1990 ዓንቀፅ 16 መሰረት የመጀመሪያው ክርክር መነሳት ያለበት በቀበሌ ሽማግሌዎች በኩል በመሆኑ አመልካች ካቀረበው ክስ ጋር የቀበሌ ሽማግሌዎች የእርቅ

ውጤት እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም ጎዱሮ ቀበሌ የእርቅ ውጤት ያቀረበ በመሆኑ እና የከሳሽ መሬት የሚገኝበት በመራሮ ሀዊሎ ቀበሌ በመሆኑ የዚሁ ቀበሌ የሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት ማቅረብ ያለበት ሆኖ እያለ ያልቀረበ በመሆኑ አመልካች (ከሳሽ) የመራሮ ሀዊሎ ቀበሌ የሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት ሲያቀርብ ክስ የማቅረብ መብት አለው በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ቅሬታቸውን ለምእራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የሰበር አቤቱታቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው ያቀረቡ ቢሆንም የአመልካች አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዘውታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘታቸው ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 20/05/2011 ዓ/ም የተፃፈ 2 ገፅ አቤቱታ አቅርበዋል ፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ተጠሪዎች የአመልካች ይዞታ የሆነውን ሁለት ሄክታር መሬት በህገ ወጥ መንገድ የያዙ መሆናቸው በ3/11/2009 ዓ/ም እና 26/2/2010 ዓ/ም የአካባቢው ሽማግሌዎች ያጣሩልን ሆኖ እያለ የወረዳው ፍርድ ቤት ይህ ይዞታ የማን ነው ግራ ቀኙን ማስረጃ አድምጦ ሳይለይ እና ያቀረብኩት ማስረጃ ሳይሰማ መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ከ2ኛ ተጠሪ በስተቀር ሌሎቹ ተጠሪዎች ቀርበው በፅሁፍ ተከራክረዋል ፡፡ 2ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ተልኮለት መልስ ስላላቀረበ መልስ በፅሁፍ የመስጠት መብቱ የታለፈ ስለመሆኑ መዝገቡ ያመለክታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡ ከመዝገቡ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች ክስ ያቀረበዉ ይዞታ መሬቱ ያለአግባብ በተጠሪዎች መያዙን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች ይዞታውን እንዲያስረክቡት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ስልጣኑ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበው ክስ የተጠቀሰው ይዞታ መሬቱ በሽማግሌ እንዲለቁለት ጠይቆ ተጠሪዎች ፍቃደኞች ባለመሆናቸው ፍርድቤቱ ውሳኔ እንዲሰጥ የጠየቀ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር በክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ/130/99 አንቀጽ 16 መሰረት የመጀመሪያው ክርክር መነሳት ያለበት በቀበሌ ሽማግሌዎች በኩል በመሆኑ አመልካች ካቀረበው ክስ ጋር የቀበሌ ሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት እንዲያቀርብ ትእዛዝ ተሰጥቶት የጎዱሮ ቀበሌ የእርቅ ውጤት ያቀረበ በመሆኑ እና የከሳሽ መሬት የሚገኘው በመራሮ ሀዊሎ ቀበሌ በመሆኑ የዚሁ ቀበሌ የሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት ስላላቀረበ ክሱ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አሁን መታየት ያለበት ጉዳይ የገጠር መሬት ይገባኛል ክስ ፍርድቤት ለማቅረብ የሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት መቅረብ ግዴታ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ከህጉ ጋር መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሬት የመጠቀም መብት፣መብቱን በዉርስ የማስተላለፍና መሰል መብቶች አስመልክቶ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የተደነገገዉን መርህ ተከትሎ የወጣዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 ሲሆን ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ዝርዝር ህጎች የሚወጡት በክልል እንደሚሆን በአዋጁ አንቀጽ 17 ላይ ተመልክቷል፡፡ የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮች በሚመለከታቸዉ ተከራካሪ ወገኖች በዉይይትና በስምምነት እንዲፈታ ጥረት የሚደረግ ስለመሆኑ እና በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በተከራካሪ ወገኖች በተመረጠ ሽምግልና ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ በተደነገገዉ መሰረት እንደሚወሰን በአዋጁ አንቀጽ 12 ላይ ተደንግጓል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 17 መሰረት በኦሮሚያ ክልል መንግስት ወጥቶ በስራ ላይ ያለዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ/ 130/99 ከመሬት ይዞታ ጋር በተያያዘ ግጭትና አለመግባባት የሚፈታበትን ስርዓት የሚደነግገዉ አንቀጽ 16 ስር እንደተመለከተዉ በመጀመሪያ በቀበሌ መስተዳደር አማካይነት በሽማግሌ እንዲታይ የሚደረግ ስለመሆኑ እና ይህም የግራ ቀኙን ስምምነት መሰረት የሚያደርግ ስለመሆኑ በዚህም የሽማግሌዎች የእርቅ ዉጤት ያልተስማማ ወገን የሽማግሌዎችን ዉሳኔ በማያያዝ ክሱን ለወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት የሚደረገዉ የግራ ቀኙን ስምምነት ሲኖር እንጂ በአስገዳጅነት ሁኔታ የገጠር መሬት ክርክር በቀበሌ አስተዳደር ክስ ወይም አቤቱታ ቀርቦ ዉሳኔ እንደሚሰጥ ቀጥሎም ለመደበኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንደሚቀርብ ተደርጎ አሳሪ ወይም ጥብቅ የሆነ ስነስርዓት የተዘረጋ አይደለም ፡፡

ስለሆነም በተያዘዉ ጉዳይ ጉዳዩ አስቀድሞ በቀበሌ አስተዳደር አማካይነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች ምርጫ በስምምነት በሽማግሌዎች ታይቶ እንዲፈታ ማድረግ ለተከራካሪ ወገኖች የተፈቀደ አማራጭ እንጂ አስገዳጅ ባለመሆኑ ጉዳዩ በመጀመሪያ ስልጣኑ የተመለከተው የአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ካቀረበው ክስ ጋር የሽማግሌዎች የእርቅ ውጤት ባለማቅረቡ አመልካች ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ መወሰኑም ሆነ በየእርከኑ ያሉት የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ሳያርሙ ማፅናታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1ኛ/ የኦሮሚያ ክልል የአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 34612 ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ/ም ውሳኔ ተሰጥቶ ፣የምእራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 38111 ሃምሌ 03 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 299015 ጥቅምት 22 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/ የአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በስር ከሳሽ (አመልካች) በኩል የቀረበውን ክስ ተቀብሎ ሊያስተናግድ ይገባል ብለናል፡፡ስለሆነም የተዘጋውን መዝገብ ቁጥር 34612 በማንቀሳቀስ በጉዳዩ ላይ አከራክሮ ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3ኛ/ በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁጥር164489

ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ አባዝናብ አባድማ -ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አባተማም ሼህ ሽኩር - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት አላባ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በደቡብ ክልል በየም ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- አመልካች ምንም መብት ሳይኖራቸውና የግል ንብረቱ የሆነውን ባሕር ዛፍ ለጥቅም የደረሰውን በጥቅምት ወር 2009 ዓ.ም መንጥሮ ለ3ኛ ወገን በመሸጥ ላይ ሳሉ በሕግ ያስቆምኳቸው ሲሆን ቆርጠው የወሰዱትና የሸጡብኝ የባሕር ዛፍ ምርት ጠቅላላ ዋጋው ብር 17,400 በመሆኑ ግምቱን ይክፈለኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች በበኩላቸው በሰጡት መልስ ክስ የቀረበብኝ የባህር ዛፍ ንብረት ይዞታ የእኔ እንጂ የተጠሪ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ተደርጎ ባቀረብኩት ማስረጃ መሠረት ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የየም ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ እንዲሁም የባህር ዛፉ ይዞታ የማን ነው የሚለው በወረዳው እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኃላ ይዞታው የአመልካች መሆኑ በመረጋገጡ ቆርጦ የወሰደውንና የሸጠውን ባህር ዛፍ ግምት ሊከፍል አይገባም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተው የየም ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ በ1997/98 ዓ.ም በነበረው የመጀመሪያ ደረጃ የመሬት

ልኬት ወቅት ለተጠሪ ይዞታዉ ተለክቶ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቶት የነበረ ሆኖ እያለ በ2006 ዓ.ም ልኬት ያለአግባብ በአመልካች መመዝገቡ ስለተረጋገጠ፤ ተጠሪ በባህር ዛፉ በጋራ ለመጠቀም ይዞታዉን ለአመልካች ሰጥቶ ባህር ዛፉን የተከሉ መሆኑን ተጠሪ የተናገረዉን መሠረት በማድረግ የተቆረጠዉ ባህር ዛፍ የጋራ ነዉ በማለት ግምቱ በባለሙያ ተገምቶ እኩል ይከፋፈሉ በማለት የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመቀጠል አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ዉሳኔዉን በማጽናት ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ዉሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘታቸዉ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀጽ 12(1) መሰረት ጉዳዩ በቅድሚያ በቀበሌ አስተዳደር የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ በእርቅና ድርድር ሳይታይ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ በዉሳኔዉ ይዞታዉ የተጠሪ ነዉ ብሎ ሲወሰን ለዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ የወረዳዉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት በ1997/98 ዓ.ም መሬት ሲለካ ተጠሪ በስሙ ተለክቷል ብሏል፡፡ ነገር ግን በ2006 ዓ.ም የወረዳዉ መሬት በጅፒኤስ ዘመናዊ መሳሪያ ሲለካ በስሜ መለካቱን፤ ሲለካም ተጠሪ ተቃዉሞ እንዳላሰማ በጻፈዉ ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡ ይዞታዉ የእኔ መሆኑን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ አቅርቤያለሁ፡፡ ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አቅርቦ ባላስረዳበት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ተሽሮ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ ሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አከራካሪዉ ይዞታ ለአመልካች ከተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ አንጻር ሳይሆን የስር ፍ/ቤቶች በገመድ ልኬትና በኮምፒዩተር መመዝገብና አለመመዝገብ ላይ ትኩረት በማድረግ የተሰጡት ዉሳኔ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘት በስር ፍ/ቤት አመልካች በማስረጃነት ያቀረበዉ ሀሰተኛ ማስረጃ ነዉ፡፡ በወረዳ ደረጃ እስከ ቦታዉ ድረስ እንዲጣራ ሲደረግ አመልካች ምንም ዓይነት ይዞታ እንደሌላቸዉ ተገልጿል፡፡ አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ በድብቅ በሀሰት ተዘጋጅቶ የተሰጠ ነዉ፡፡ የባህር ዛፍ ንብረቱም በአያቴ ዘመን ተተክሎ አባቴ እየተጠቀመበት ቆይቶ ሲሞት በተራዬ መጠቀም ከጀመርኩ 40 ዓመት ያስቆጠረና የገበርኩበትን አመልካች ሳይመለከታቸዉ ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የሌለዉ በመሆኑ ዉሳኔዉ ስህተት የለዉም ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነዉ በስር ፍ/ቤት ተጠሪ አመልካች ባህር ዛፉን ቆርጦ የሸጠበት መሆኑን ገልጾ ግምቱ ብር 17,400 እንዲከፍለዉ የጠየቀ ሲሆን አመልካች ባህር ዛፉ የራሱ መሆኑን በመግለጽ ግምት

ሊከፍል እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የወረዳ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የቀረቡ ማስረጃዎችንና የወረዳው እርሻና የተፈጥሮ ሀብት መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የጻፈዉን ደብዳቤ መርምሮ ይዞታው የተጠሪ የነበረ ቢሆንም በ1979 ዓ.ም ጀምሮ ለአመልካች ሰጥቶት አመልካች ባህር ዛፉን በእጁ ተክሎ ሲጠቀምና ግብር ሲከፈል መቆየቱ ተረጋግጧል በሚል የተጠሪን የባህር ዛፍ ግምት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የልዩ ወረዳው ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ምንም እንኳ ይዞታው በ2006 ዓ.ም በተደረገው ልኬት በአመልካች ተመዝግቦ የተገኘ ቢሆንም በ1997/98 ዓ.ም በተደረገው ልኬት በተጠሪ ተመዝግቦ የሚታወቅ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ በሕግ አግባብ ይዞታው ሳይወሰድበት ለአመልካች ሊተላለፍ የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን እንዲሁም ተጠሪ ለእኩል ለመጠቀም ለአመልካች መስጠቱን በቃል መግለጹን በመጥቀስ ይዞታው የተጠሪ ሆኖ አመልካች እኩል ለመጠቀም ባህር ዛፉን ያለማው ነው በሚል የባህር ዛፉ ግምት በባለሙያ ተገምቶ ግማሹን ለተጠሪ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩትም ሆነ አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል የተባለው አመልካች በ2006 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶት እያለ በ1997/98 ዓ.ም በነበረው ልኬት ወቅት በኮምፒዩተር መመዝገብ አለመመዝገቡ ላይ ትኩረት በመስጠት ይዞታው የተጠሪ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነዉ፡፡

በመሠረቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(3) የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ እንደሆነና መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ሀብት መሆኑ የተመለከተ ሲሆን አርሶ አደሮች በነጻ መሬት የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብት ያላቸው መሆኑ በዚሁ አንቀጽ 4 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 456/97"ም" ቢሆን ባለይዞታ አርሶ አደር የመሬት ይዞታውን በስጦታም ሆነ በዉርስ ለቤተሰቡ አባል ካልሆነ ወይም በሕግ በተፈቀደው መሠረት ለተወሰነ ጊዜ በማከራየት ካልሆነ በቀር ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ አይችልም፡፡ በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1175 የባለመሬቱን ወይም የባለይዞታዉን ፈቃድ በመጣስ አትክልቶችን የተከለ ሰው በአትክልቶቹ ላይ ምንም ዓይነት መብት እንደሌለዉና ካሳ መጠየቅ እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን ቁጥር 1176 ደግሞ በባለመሬቱ ወይም በባለይዞታው ፈቃድ አትክልቶቹን የተከለ ሰው በስምምነታቸው መሠረት ተጠቃሚ እንደሆነና ከስምምነቱ ዉጪ እንዲነሱ ሲደረግ ካሳ እንደሚገባው ተደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ባህር ዛፍ የተተከለበትን ይዞታ በራሱ ስም በመያዝ እና በ2006 ዓ.ም ይዞታዉን በስሙ ከማስመዝገቡ በፊት ይዞታው በ1997/98 ዓ.ም በክልሉ በነበረው የመሬት ልኬት ወቅት በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የነበረ መሆኑንና ይዞታው በአመልካች እጅ ሊገባ የቻለው በግራ ቀኙ መካከል ባህር ዛፍ አመልካች እንዲያለማና ለእኩል ለመጠቀም በነበረ ስምምነት መሆኑን ማስረጃ ለመመዘንና ፍሬ ነገርን ለማረጋገጥ ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች በዚህ አግባብ በእጁ የገባዉን ይዞታ በስሙ በድብቅ ማስመዝገቡና የይዞታ ማረጋገጫ ማዉጣቱ፤ ይዞታው ከተጠሪ በሕግ አግባብ የተላለፈለት መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ያለአግባብ የይዞታ ማረጋገጫ

ስለተሰጠዉ ብቻ የተጠሪን ባለይዞታነት መብት አያስቀርም፡፡ እንዲሁም በሕግ አግባብ ካልሆነ በቀር የአስተዳደር አካሉ ተጠሪን ከመሬት ይዞታዉ ከሕግ ዉጪ አፈናቀሎ ለአመልካች ይዞታ ማረጋገጫ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን በማረጋገጥ አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ ለእኩል ለመጠቀም በነበረ ስምምነት ያለማዉን ባህር ዛፍ ለብቻዉ ቆርጦ መዉሰዱን በማረጋገጥ የባህር ዛፉ ግምት በባለሙያ ተጣርቶ ግማሹ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት የሰጠዉና በየደረጃዉ የጸናዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የየም ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይዞታዉ የተጠሪ ሆኖ በአመልካች እጅ ሊገባና በ2006 ዓ.ም በስሙ አስመዝግቦ ባህር ዛፍ አልምቶ ቆርጦ ሊሸጥ የቻለዉ ከተጠሪ ጋር በነበራቸዉ ስምምነት መሆኑን በማረጋገጥ ያለአግባብ በአመልካች ስም መመዝበሩ የተጠሪን ባለይዞታነት ሊያስቀር አይችልም በማለት ባህር ዛፉ ተገምቶ ግማሹን ግምት ለተጠሪ ይክፈል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 40(3 እና 4)፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1175 እና ተከታዮችን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1ኛ. በየም ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03255 ሚያዚያ 04 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 10591 ግንቦት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 10772 ነሐሴ 25 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በስር ፍ/ቤት የተጀመረዉ አፈጻጸም ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ ታሕሳስ 10 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

3ኛ. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሳ/ፀ

ሰ/መ/ቁ. 158527

ጥር 27 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-ወ/ሮ ዘይነባ ሀሰን

ተጠሪ፡-1ኛ/የቢሸፍቱ ከተማ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ

2ኛ/የኦሮሚያ የመሬት ልማትና ማ/ኤጀንሲ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ በሊዝ ዉል የተያዘ መሬት ለማስለቀቅ በተጠሪዎች የተሰጠዉ ማስጠንቀቂያ የሐኩት ተግባር ነዉ በሚል አመልካች ተጠሪዎች ላይ ያቀረበችዉ ክስ የሚመለከት ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኗ አመልካች ስትሆን ተጠሪዎች ተከሳሾች ናቸዉ፡፡የአመልካች ክስ ይዘት ባጭሩ በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ዉስጥ 11,000ካ.ሜ ይዞታ ለሪል እስቴት ግንባታ የሚዉል በ27/05/2000ዓ.ም በተደረገ ዉል የተሰጣት ካርታ ቁ/28/29 የተመዘገበዉን በቦታዉ ላይ ሁለት ትልልቅ መጋዝን ተሰርቶበት እና ሌሎች የግንባታ እቃዎች ያሉበትን ተጠሪዎች በ24/05/08 ዓ.ም እና በ26/05/08ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በ7 ቀን ዉስጥ ንብረት በማንሳት ቦታዉን እንዲትለቅ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸዉ የሁከት ተግባር ነዉ በሚል ሁከት እንዲወገድ ዳኝነት የጠየቀች ሲሆን በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ አመልካች በሊዝ ዉሉ መሰረት ግንባታዉን በ6 ወር ጊዜ ዉስጥ ባለመጀመሯ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ ባለመፈጸሟ ካርታዉ እንዲሰረዝና መሬቱ ወደ መንግስት እንዲመለስ የተወሰነ ስለመሆኑና የአመልካች ይዞታ መብት የተቋረጠ ስለሆነ ክስ የማቅረብ መብት እንደሌላት እንዲሁም የተጻፈዉ ደብዳቤም በሊዝ አዋጅና ደንብ እንዲሁም ተዛማጅነት

ባላቸዉ መመሪያዎች መሰረት ለተከሳሾች የተሰጠ ስልጣን መሰረት ስለመሆኑ በመግለጽ ድርጊቱ የሁከት ተግባር ሊባል አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በቦታዉ ላይ የተሰራዉ ግንባታ መጠን እና ዋጋ ግምት በባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ በቦታዉ ላይ ያለዉ ንብረትና ግንባታ ግምት ብር 2,233,875.00 ስለመሆኑና ይህም ካጠቃላይ ግንባታ አንጻር ሲሰላ 2.92% መሆኑን እንደሚያሳይና አመልካች ግንባታ አልጀመረችም በሚል የተሰጠዉ ማስጠንቀቂያ ተገቢ አይደለም በማለት ሁከት እንዲወገድ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ስር ተከሳሾች ይህንን ዉሳኔ በመቃወም ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ክስ የቀረበበትን ይዞታ አመልካች በሊዝ ዉል መሰረት ያገኘች ስለመሆኑና በሊዝ ዉሉ መሰረት በጊዜዉ ሳታለማ በመቅረቷበ12/07/2006 ዓ.ም በተደረገ ስብሰባ የሊዝ ዉሉ እንዲቋረጥ እና ይዞታ ማረጋገጫ እንደተሰረዘ ተወስኖ በ23/10/06ዓ.ም እንደተገለጸላት የተረጋገጠ ስለመሆኑና መሬቱ እስካሁን በእጇ ላይ የቆየ ቢሆንም የሊዝ ዉሉ ከተቋረጠ ቀን ጀምሮ መብት የላትም በማለት የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1140 እና 1149 ላይ የተደነገገዉን ምርኩዝ በማድረግ ስር ተከሳሾች መሬቱን ለማስለቀቅ የሰጡት ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነዉ ሊባል አይገባም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሽሯል፡፡

አመልካች በበኩሏ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ በማቅረቧ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር ሰምቶ የሊዝ ዉሉ በ2006 ዓ.ም የተሰረዘ ቢሆንም ይዞታዉ እስከ አሁን ድረስ በአመልካች እጅ ይገኛል በሚል ምክንያት የከፍተኛዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡ተጠሪዎች ጉዳዩን ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአቤቱታ አቅርበዉ ሰበር ችሎቱም ጉዳዩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ በሊዝ አዋጅ ቁ/721/04 አንቀጽ 22 እና በደንብ ቁ/182/08 አንቀጽ 39/7 መሰረት በሊዝ ዉሉ መሰረት ግንባታ ካልተጀመረ አስተዳደሩ መሬቱን መልሶ መዉሰድ እንደሚችል ስለመደንገጉ፣የአመልካች ዉል በ2006 ዓ.ም ከተሰረዘ ጊዜ ጀምሮ ንብረቷን ለማንሳት ከሁለት ዓመት በላይ ጊዜ እንደነበራት እንዲሁም የሊዝ ዉሉ መሰረዝ የለበትም በሚል ለክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ አቤቱታ አቅርባ ከሆነም እግድ ከመጠየቅ ወጪ የሊዝ ዉል መብት በተቋረጠበት ሁኔታ የአስተዳደር አካል ተግባር በፍ/ህግ አንቀጽ 1149/3/ መሰረት ተገቢ በመሆኑ ሁከት የለም በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በቦታዉ ላይ የሰራችዉ ግንባታ መጠን 2.92% መሆኑ በባለሙያ ተረጋግጦ በቀረበበት ሁኔታ የተጠሪዎች ድርጊት ሁከት አይደለም መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ከፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1149 እና አዋጅ ቁ/721/04 እና ደንብ ቁ/182/08 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች

መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ አመልካች በ29/08/2000ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ዉል በከተማዉ ዉስጥ ዋና መንገድ ዳር ላይ 11,000ካ/ሜ መሬት ለሪል እስቴት ግንባታ መዉሰዷን ፣በአዋጅ ቁ/272/94 አንቀጽ 15/1 እንዲሁም 721/04 አንቀጽ 25/1/ሀ እና ደንብ ቁ/119/99 አንቀጽ 10/5 እንዲሁም 155/05ና ማሻሻያዉ ደንብ ቁ/182/08 መሰረት በተገቢዉ ጊዜ ዉስጥ ግንባታ ሳይገነቡና ወደ ስራ ሳይገቡ በመቅረታቸዉ መሬቱ ወደ መሬት ባንክ እንዲመለስ መወሰኑና ንብረታቸዉን እንዲያነሱ ማስጠንቀቂያ መሰጠቱ ህጋዊ ተግባር ስለመሆኑ በመዘርዘር የሑከት ተግባር የለም በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካችም አቤቱታዋን በማጠናከር በጠበቃ አማካይነት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርመረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ አመልካች በ2000 ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ዉል 11,000ካ.ሜ ይዞታ ከከተማዉ አስተዳደር መረከባቸዉና የይዞታ ማረጋገጫ ቁ.28/29 የተሰጣቸዉ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡አመልካች በሊዝ ዉሉና በህጉ መሰረት ግንባታ አላከናወኑም ለተገልጋዩ አላማ አልዋለም በሚል ምክንያት የሊዝ ዉሉ እንዲቋረጥና የይዞታ ማረጋጫ ካርታ እንዲሰረዝ በ12/07/2006ዓ.ም በክልሉ የሚመለከተዉ አካል ዉሳኔ መሰጠቱም በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡አመልካችም ይህንን ፍሬነገር በግልጽ ሳይክዱ ለክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ አቤቱታ አቅርበዉ ዉሳኔ በመጠባበቅ ላይ ስለመሆናቸዉ ገልጸዉ ተከራክረዋል፡፡አቤቱታ የቀረበለት የሊዝ ቦርድ የተለየ ዉሳኔ ስለመስጠቱ አመልካች አስረጂ አላቀረቡም፡፡ስለሆነም የሊዝ ዉሉ እንዲሰረዝ ና ይዞታዉ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ የተሰጠ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ተከትሎ የከተማዉ አስተዳደር መሬቱን ለመረከብ ሲል በ24/05/08 እና በ26/05/08ዓ.ም የሰጠዉ ማስጠንቀቂያ የሑከት ተግባር ነዉ ሊባል አይችልም በማለት የኦሮሚያ ክልል ሰበር ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነት ከህጉ ጋር በማገናዘብ እንመለከታለን፡፡

በመሠረቱ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ይዞታው ለመንጠቅ ወይም በይዞታው ላይ ሁከት ለመፍጠር የሚፈፀምን ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ወይም ተገቢው መብት እንዲመለስለት ህጉ ከዘረጋቸው መንገዶች አንዱ የይዞታ ክስ /Possessory action/ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1149/1/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ በቀጥታ ወይም በጠባቂ ይዞታ ሲኖረውና ይህንኑ ሁኔታ በኃይል ሲነጠቅ ወይም በይዞታዉ ስር ባለንብረት የመጠቀም መብቱ የሚያዉክ ተግባር ሲፈጸም ነው፡፡ እንዲሁም የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም ዓይነት መብት የሌለው ሰው ሲይዝ ስለመሆኑም ተጠቃሹ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ አቅራቢ ማረጋገጥ ያለበት ንብረቱ በህግ አግባብ በይዞታው የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የኃይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጢር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ነው፡፡ ይህ የድንጋጌው መንፈስ የሚያስረዳው የሁከት ተግባር የሚኖረው ባለይዞታ የሆነው ሰው በይዞታው ሥር በሚገኘው

ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ሲፈጥርበት ወይም ረብሻ ሲፈጥርበት መሆኑን ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች ይዘት የሚያሣዩትም ይህንኑ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ከላይ ከተገለፀው ነጥብ በተጨማሪ የሚያስገነዝቡት ነጥብ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅራቢ የተሻለ የይዞታ መብት ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥ ያለበት መሆኑን ነው፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ክስ የቀረበበትን ይዞታ የመጠቀም መብት ያገኙት በ29/08/2000 ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ዉል መነሻ ስለመሆኑና በሊዝ ዉል እና በህጉ አግባብ ተገቢዉን ግንባታ በወቅቱ አለማፈጸማቸዉ በሚመለከተዉ አካል ተረጋግጦ የሊዝ ዉሉ እንዲሰረዝ እና መሬቱ ወደ መንግስት ይዞታ እንዲመለስ በ12/07/06ዓ.ም በሚመለከተዉ አካል ዉሳኔ ተሰጥቶ ያደረ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡በስራ ላይ ባለዉ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የሚደነግገዉ አዋጅ ቁ/721/04 አንቀጽ 25 መሰረት የሊዝ ዉል ስለምቋረጥበትና የሚያስከትለዉ ዉጤት በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ይህንን አስተዳደራዊ ዉሳኔ የሚቃወም ወገን ይግባኝ ስለሚያቀርብበት ስርዓትም በአዋጁ ላይ ተደንግጓል፡፡አመልካች የሊዝ ዉሉ መሰረዙን በመቃወም ለሚመለከተዉ አካል አቤቱታ አቅርበዉ ምላሽ በመጠባበቅ ላይ ስለመሆናቸዉ ከመግለጽ ዉጪ የተሰጠ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ስለመኖሩ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ስለሆነም የሊዝ ዉሉ እንዲቋረጥ በ12/07/2006 ዓ.ም የተሰጠዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ባልተሻረበት ሁኔታ ተጠሪዎች መሬቱን ለመረከብ እንዲቻላቸዉ አመልካቿ ንብረታቸዉን እንዲያነሱ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸዉ በሊዝ አዋጁና ይህን ተከትሎ የወጡትን ማስፈጸሚያ ደንብና መመሪያ የተከተለ እና ድርጊታቸዉም በህግ የተሰጠ ስልጣን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑ አኳያ በፍ/ብ ህግ አንቀጽ 1149/3/ ጋር ሲታይ የሁከት ተግባር ነዉ ሊባል የማይቻል መሆኑን ያሥገነዝባል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/ የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/270624 በ29/08/2010 ዓ.ም የሰተዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/ በዚህ መዝገብ ላይ በ06/10/10 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትእዛዝ ተነስተዋል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም/ቶ

ሰበር መ/ቁ161676

የካቲት 25 ቀን 2011ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንደሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ መልካሙ አበራ

ተጠሪ፡- ቄስ ዳምጤ በየነ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የገጠር መሬት ይዞታ የሚመለከት ነዉ፡፡በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የተጠሪ ክስ ይዘት ባጭሩ በስሙ የተመዘገበዉን አዋሳኙ እና መጠኑ በክሱ ዝርዝር የተገለጸዉን የእርሻ መሬት በህገወጥ ልዉዉጥ ምክንያት አመልካች ይዞ ስለሚገኝ እንዲለቅ እንዲወሰን የሚል ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበዉ ክርክር ልዉዉጥ የተደረገዉ ግንቦት 25 ቀን 2000ዓ.ም መሆኑንና ክሱ በ10ዓመት ይርጋ መታገድ ያለበት ስለመሆኑ እንዲሁም ተጠሪ በልዉዉጥ ዉል የወሰደዉን መሬት እየተጠቀመ ስለመሆኑ በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ የሚል ነዉ፡፡

የግራቀኙን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ምስክር ሰምቶ እና ከወረዳዉ መሬት አስተዳደር መረጃ አጣርቶ ክስ የቀረበበት መሬት ለተጠሪ የተደለደለ ስለመሆኑ፣በግራቀኙ መካካል የተደረገዉ የመሬት ልዉዉጥ ዉል በሚመለከተዉ የመሬት አስተዳደር አካል ያልተመዘገበ ስለመሆኑና አመልካች በሃሰተኛ መረጃ በዚህ መሬት ላይ ደብተር የተሰጠዉ ስለመሆኑ በማረጋገጥ የልዉዉጥ ዉል የተደረገዉ በ25/09/2000ዓ.ም በመሆኑና ክስ የቀረበዉ በ22/03/2010ዓ.ም በመሆኑ ዉል ከተደረገበት አንስቶ ክስ እስከቀረበበት ያለዉ ጊዜ 10ዓመት ያልሞላዉ ስለሆነ አመልካች ያቀረበዉ 10ዓመት ይርጋ ዉድቅ በማድረግ የልዉዉጥ ዉል በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁ/252/09 አንቀጽ 20/3/ መሰረት ያልተመዘገበ በመሆኑ ተፈጻሚነት የለዉም

በማለት አመልካች በልዉዉጥ ምክንያት የያዘዉን የተጠሪ መሬት እንዲለቅ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተሉ ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ክርክሩ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች ሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክርክር ያስነሳዉ የይዞታ ቅይይር መደረጉ በተጠሪ ታምኖ ባለበት እንዲሁም ልዉዉጡ ያልተመዘገበ ቢሆንም ይህንን ደረጃ አልፎ የይዞታ ማረጋገጫ በተሰጠበት ሁኔታ ይዞታዉን አመልካች ይልቀቅ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ታዟል፡፡በተጠሪ በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ ባህላዊ ልዉዉጥ የተደረገ ቢሆንም አመልካች ሁለቱንም መሬት ይዞ አልሰጥም በማለቱ በሽማግሌም ተጠይቆ እምቢተኛ በመሆኑ ልዉዉጡ ያልተመዘገበ በመሆኑ ቀሪ ሆኖ ወደነበሩበት እንዲመለሱ መወሰኑ ተገቢ ስለመሆኑ ተከራክሯል፡፡አመልካችም አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም በሰበር አጣሪ የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ለክርክር መነሻ የሆነዉ ጉዳይ በግራቀኙ መካከል የተደረገ የመሬት ልዉዉጥ ዉል ተፈጻሚነት በሚመለከት ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የተሰጠዉ ክስ የቀረበበት መሬት የተጠሪ ስለመሆኑ፣የመሬት ልዉዉጡ ያልተመዘገበ ስለመሆኑና አመልካች በሀሰተኛ መረጃ በዚሁ መሬት ደብተር ያገኘ መሆኑ በሚመለከተዉ የመሬት አስተዳደር አካል ስለተረጋገጠ አመልካች የተጠሪን መሬት እንዲለቅ ዉሳኔ መስጠቱን ነዉ፡፡

በአማራ ብ/ክ/መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ/252/09 አንቀጽ 20/3/ ላይ እንደተመለከተዉ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች መካከል የሚደረግ ማንኛዉም የልዉዉጥ ዉል አግባብ ባለዉ የወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ ያለበት ስለመሆኑ ነዉ፡፡በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ክርክር ከጅምሩም ተጠሪ ክስ ያቀረበዉ የልዉዉጥ ዉል መደረጉን ሳይክድ በህገወጥ የልዉዉጥ ዉል ምክንያት አመልካች የያዘዉን የተጠሪ መሬት እንዲለቅ እንዲወሰን ነዉ፡፡ከዚህም ባሻገር አመልካች የራሱን መሬት ለተጠሪ ሳያስረክብ በለዉጥ ምክንያት የያዘዉንና የራሱን መሬት ድርቦ መያዙም በክርክሩ ሂደት የተገለጸ ነዉ፡፡

ስለሆነም ዉሉ ህገወጥ ነዉ ተፈጻሚነት የለዉም የሚለዉ የተጠሪ ክርክር ዉል መኖርን መነሻ ያደረገ ስለሚሆን ተጠሪ ዉሉን አምኗል የሚለዉ የሰበር አጣሪ ችሎት ጭብጥ የክርክር መነሻ ከመሆኑ አኳያ፣ይህም የልዉዉጥ ዉል በህጉ አግባብ ያልተፈጸመ ስለመሆኑ እንዲሁም አመልካች በዚህ ይዞታ ላይ ደብተር ያገኘዉ በሀሰተኛ መረጃ ላይ መሰረት በማድረግ አስተዳደሩን በማሳሳት ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከመሬት አስተዳደር አካል ጭምር በቀረበ ማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬጉዳይ በመሆኑ በሀሰተኛ

መረጃ ላይ ተመስርቶ የተመዘገበ ደብተር መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁ/252/09 አንቀጽ 34/5/መሰረት በሀሰተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ ፣ የተደረገ ምዝገባ ህጋዊ ውጤት ስለማይኖረው እና በህግ ፊት በማይፀና ውል የያዘውን የተጠሪ መሬት አመልካች እንዲለቅ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1ኛ/ በፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ/29546 ላይ በ12/06/2010 ዓ.ም የተሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት የደቡብ ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/65196 ላይ በ01/10/2010ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/79074 ላይ በ12/11/2010ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የመ/ቁ. 169030

ህዳር 30/2012 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡ 1.አቶ አሰፋ ሰቦቃ ጠበቃ አቶ ከበደ ቱፋ ቀርበዋል፡፡

2. አቶ ታደሰ ሰቦቃ

3. ወ/ሮ ቀነኒ ሰቦቃ

4. ወ/ት ኩሜ ሰቦቃ

ተጠሪዎች፡ 1.አቶ ከበደ ሰቦቃ ቀርበዋል፡፡

2. አቶ ኩማ ሰቦቃ

3. ወ/ሮ አለሚ ሰቦቃ አልቀረቡም፡፡

4. ወ/ሮ ደስታ ሰቦቃ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት የውርስ ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/282886 ላይ ጥቅምት 19/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በሚል ለማስለወጥ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከሳሽ፤ 1ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ዳሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 27141 ላይ በክርክር ላይ እያሉ ጉዳዩ በእርቅ ስምምነት ጨርሰው ስምምነቱን ለፍርድ ቤቱ አቅርበው በስምምነቱ መሰረት ውሳኔ ተሰጥቶ መዝገቡ ይዘጋል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በእርቅ በተዘጋው መዝገብ ላይ በመቃወም በአመልካችነት ቀርበው መዝገቡ ተከፍቶ ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ የአሁን 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በጣልቃ ገብነት በመቅረባቸው ፍርድ ቤቱ የክርክሩ አካል አድርጓቸው የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ በመስማት እንዲሁም ክርክር ስላልተነሳበት ይዞታ ጉዳይ ከሚመለከተው አስተዳደር ክፍል ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በውሳኔውም ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የውርስ ይዞታ በአጠቃላይ 16(አስራ ስድስት) ቀርጥ መሆኑን፤የአሁን አመልካቾች ወላጆቻቸው በህይወት እያሉ ለእያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ መሬት ተሰጥቷቸው ይዘው እየተጠቀሙበት ስለመሆኑ እንዲሁም የአሁን 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ክርክር በቀረበበት ይዞታ ላይ ወላጆቻቸው እስከሞቱበት ድረስ በጥገኝነት ሲኖሩ የነበረ ለመሆኑ ከወረዳው መሬት አስተዳደር የተገለፀለት መሆኑን፤ የግራ ቀኙ የሰው ምስክሮችም የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ወላጆቻቸው በህይወት እያሉ ለእያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ መሬት ተሰጥቷቸው ይዞታውን በእጃቸው አድርገው እየተጠቀሙበት ያሉ መሆኑን፤ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች በወረዳው መሬት አስተዳደር በተገለፀው አኳኋን በይዞታው ላይ ከወላጆቻቸው ጋር በጥገኝነት ይኖሩ የነበረ ለመሆኑ ያረጋገጡ መሆኑን በመጥቀስ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች በይዞታው ላይ ጥገኛ በመሆናቸው፤ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ደግሞ ቀድሞ በወላጆቻቸው በተሰጣቸው ሁለት ቀርጥ መሬት ላይ የቀዳሚነት መብት ያላቸው መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች በክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 2(16) እና 5(5) እንዲሁም ይህንኑ አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 3(13) መሰረት እያንዳንዳቸው አንድ ሄክታር (አራት ቀርጥ) እንዲወስዱ፤ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ቀድሞ ለእያንዳንዳቸው የተሰጣቸው ሁለት ቀርጥ መሬት ከአጠቃላይ የውርስ ይዞታው ውስጥ ከወጣ በኋላ ቀሪውን አራት ቀርጥ ለስምንቱም ወራሾች የሚከፋፈል ቢሆን በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ መሰረት የመሬት መበጣጠስን የሚያስከትል በመሆኑ ግራ ቀኙ በጋራ ሊጠቀሙበት ይግባል ብሏል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የይግባኝ አቤቱታውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዟል፡፡

በዚሁ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን የሰበር ክርክር ከሰማ በኋላ ከላይ በተጠቀሰው የመዝገብ ቁጥር እና ቀን በዋለው ችሎት ለአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ተሰጥቷል የተባለውን ስጦታ በተመለከተ በክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም

ህግ መሰረት የሚፀና የስጦታ ውል ባይኖርም ከውርስ ሃብት ስጦታ ከተቀበሉ በኋላ ከቀሪ የውርስ ሃብት ለመካፈል የጠየቁ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1066 መሰረት ስጦታውን ወደ ውርስ ሃብት ሊመልሱ ይገባል፤ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾችም የቅድሚያ መብት ያላችው መሆኑን ቢረጋገጥም በቀዳሚነት መብታቸው ሊደርሳቸው የሚገባው የድርሻ መጠን እንደውርስ ሃብቱ ስፋት እና ወራሾች ብዛት የሚወሰን እንጂ እያንዳንዳቸው አንድ ሄክታር እንዲያገኙ የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ደንብ የማያስገድድ መሆኑን በመጥቀስ እያንዳንዳቸው አንድ ቀርጥ መሬት በቀዳሚነት ሊደርሳቸው ይገባል፤የተቀረውን 14 ቀርጥ መሬት ስምንቱም ወራሾች እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ጥር 08/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ዘርዝረው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የቅሬታው ፍሬ ቃልም በእርቅ ባለቀ እና በተፈፀመ ጉዳይ ላይ የስር ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 እና 41 ቀላቅለው መወሰናቸው ከሥነ ሥርዓት ውጭ ነው፤ተጠሪዎች የራሳቸው የእርሻ መሬት ያላቸው ለመሆኑ እና በአውራሾቻችን መሬት ላይ በጥገኝነት የምንኖረው አመልካቾች ለመሆናችን በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ እያለ ይዞታውን እኩል እንድንካፈል መወሰኑ ከክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 9 እና ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 10 ድንጋጌ ውጭ ከመሆኑም በላይ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/109776 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈ በመሆኑ ውሳኔው ተሸሮ በይዞታው ላይ የቅድሚያ መብት አላችሁ ተብለን ለእያዳንዳችን አንድ ሄክታር መሬት ሊወሰንልን ይገባል የሚል ነው፡፡

የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በክልሉ ሰበር ችሎት በአሁን ተጠሪዎች የቀረበው ቅሬታ የአሁን አመልካቾች የውርስ ይዞታው ላይ ቀድሞ የተሰጣቸው መሬት እያላቸው በድጋሚ ከውርሱ ሊካፈሉ አይገባም የሚል ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ችሎት ከዚህ ጭብጥ ውጭ በመውጣት ስጦታውን አፍርሶ ሁሉም ወራሾች እኩል ይካፈሉ በማለት የወሰነበት አግባብ ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች መጋቢት 20/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች በወረዳው ፍርድ ቤት አቅርበው የነበረው ክርክር በእርቅ ስለማለቁ እንጂ በእርቁ መሰረት ለመፈፀሙ የተረጋገጠ ነገር ባለመኖሩ በጉዳዩ ላይ በመቃወም አመልካችነት ቀርበን መስተናገዳችን በአግባቡ ነው፤አመልካቾች ሂደቱ ከሥነ ሥርዓት ውጭ ነው ቢሉም በምን አግባብ ከሥነ ሥርዓት ውጭ እንደሆነ ለይተው የገለፁት ነገር የለም በማለት በተቀረው የክልሉ ሰበር ችሎት በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠን ፍሬ ነገር መሰረት አድርጎ የወሰነ በመሆኑ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ሞግተዋል፡፡ አመልካቾችም በመልስ መልሳቸው የሰበር ቅሬታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በማስቀረቢያው ነጥብ ሳይወሰን አጠቃላይ የክርክሩ ይዘት መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት የክልሉ ሰበር ችሎት የጠቀሰው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1066 ክርክር ለተነሳበት ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን አለመሆኑ በቅድሚያ ሊታይ የሚገባ ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የክልሉ ሰበር ችሎት የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ከውርስ ሃብቱ ቀድሞ ስጦታ የተቀበሉ ቢሆንም ከተቀረው ውርስ ለመካፈል የጠየቁ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ/1066 መሰረት ቀድሞ በስጦታ የተቀበሉትን ይዞታ ወደ ውርስ መልስው ከሌሎች ወራሾች ጋር ሊካፈሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በእርግጥ ከሟች ወደታች የሚቆጠሩ የጋራ ወራሾች ውስጥ መመለስ የለብህም ተብሎ ቀድሞ ከሟቹ ያገኘውን ችሮታ/ስጦታ/ ካልሆነ በቀር ስጦታ ተቀባዩ ውርሱን የሚቀበል ከሆነ ተቀብሎት የነበረውን ንብረት ዋጋ ከውርሱ ውስጥ መልሶ ማግባት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1065 ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ዓላማ የሟች ወደታች የሚቆጠሩ ወራሾች ሟች በህይወት እያለ ከውርስ ሃብቱ ቀድሞ ስጦታ የተቀበሉ ቢሆንም በሟቹ የውርስ ሃብት ላይ ከሚኖራቸው ተነፃፃሪ መብት አኳያ ወራሾችን በተቻለ መጠን እኩል ማድረግ ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት እና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡

መሰረታዊ ዓላማው ይህ ቢሆንም ሊስተዋል የሚገባው ነጥብ ውርሱን የተቀበለው ወራሽ እንዲመልስ የሚገደደው በስጦታ የተቀበለውን ንብረት በዓይነት ሳይሆን የንብረቱን ግምት ነው፡፡ የንብረቱን ግምት መመለስ ሲባልም ወራሹ ቀድሞ በስጦታ የተቀበለው ንብረት ተገምቶ በውርስ ሀብት ክፍፍል ከተቀረው ንብረት ጋር ተደምሮ ወራሾቹ እኩል ድርሻ እንዲኖራቸው ይደረጋል ለማለት እንጅ ወራሹ የንብረቱን ግምት ይከፍላል ማለት እንዳልሆነ ከፍ/ብ/ህ/ቁ/1066 እስከ 1074 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቀድሞ ከሟች ስጦታ የተቀበለ ወደታች የሚቆጠር ወራሽ ከሌሎች ስጦታ ካልተቀበሉ ወራሾች የሚለየው አብይ ጉዳይ ስጦታ ተቀባዩ ከውርስ ንብረቱ ውስጥ በዓይነት የሚደርሰውን ቀድሞ የሚያውቅ ሲሆን ሌሎች ወራሾች ግን በንፅፅር የሚደርሳቸውን ድርሻ መጠን እንጂ በዓይነት የሚደርሳቸውን ንብረት የማያውቁ መሆኑ ነው፡፡ እናም በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከውርስ ንብረት ስጦታ የተቀበለ ወራሽ የንብረቱ ዋጋ ወደ ውርሱ ለመመለስ ንብረቱ ሊገመት የሚችል ሊሆን ይገባል ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የውርስ ሀብት የገጠር እርሻ መሬት ሲሆን የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ቀድመው በስጦታ ወስደዋል የተባሉትም ይህንኑ የገጠር መሬት ይዞታን ነው፡፡ እነዚህ አመልካቾች የተቀረውን የአውራሾቻቸውን የይዞታ ውርስ ለመቀበል ከፈለጉ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1065 መሰረት ወደ ውርሱ ሊመልሱ የሚገደዱት በስጦታ የተቀበሉትን ይዞታ በዓይነት ሳይሆን የይዞታውን ግምት ዋጋን ነው፡፡ ሆኖም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 40(3) የገጠርም ሆነ ከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ መሆኑን እና መሬት የማይሸጥ

የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት መሆኑ የተደነገገ በመሆኑ በዋጋ ሊገመት የሚችል አይደለም፡፡

ከዚህ አኳያ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከታወጀ በኋላ ባለው የመሬት ስሪት መሰረት የፍ/ብ/ህ/ቁ/1065 እና ተከታዮቹ መሬትን በሚመለከት ተፈፃሚነት የለውም ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ህገ መንግስቱ ከመታወጁ በፊት የነበሩት የሀገሪቱ ህጎች በህግ አግባብ ተፈፃሚነታቸው እስካልተሻረ ድረስ ከህገ መንግስቱ ጋር በተጣጣመ መልኩ ስራ ላይ ሊውሉ በሚችሉበት አኳኋን ሊተረጎም ይገባል፡፡ በዚሁ አግባብ መሬትን በተመለከተ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1065 ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው ቀድሞ ከሚች ስጦታ የተቀበለ ወደታች የሚቆጠር ወራሽ ውርሱን ለመቀበል ፍቃደኛ ከሆነ ቀድሞ የተቀበለው የመሬት ይዞታ መጠን በአካባቢው የመሬት ልኬት ልማድ መሰረት ተለክቶ ከተቀረው የውርስ ይዞታ ላይ ከሚደርሰው ድርሻ ጋር እንዲጣጣም በማድረግ በሚል ሲተረጎም ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት ወራሹ ቀድሞ በስጦታ የተቀበለው ይዞታ ከአጠቃላይ የውርስ ይዞታው ከሚደርሰው ድርሻ መጠን በታች ከሆነ ከተቀረው የውርስ ይዞታ ላይ የሚቀረውን መጠን ያክል እንዲካፈል፤ ስጦታው ከድርሻው በላይ ከሆነ ደግሞ ቀድሞ የተቀበለውን ስጦታ ብቻ ይዞ እንዲቆይ ይደረጋል ማለት ነው፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ ሊቃኝ ሲገባ የክልሉ ሰበር ችሎት 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ቀድመው በስጦታ የተቀበሉትን የእርሻ መሬት ወደ ውርሱ መልሰው ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲካፈሉ መወሰኑ ለውሳኔው መሰረት ካደረገውን የፍ/ብ/ህ/ቁር 1065 ድንጋጌ መንፈስ ውጭ ከመሆኑም በላይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስትን የመሬት ስሪት ባህሪን ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከመሬት ጋር በተያያዘ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1065 ድንጋጌ ተፈፃሚነት በይዞታ መጠን ልኬት ማቻቻል ነው ከተባለ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የውርስ ይዞታ ክፍፍል በምን መልኩ ሊመራ ይገባል የሚለው ቀጥሎ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው፡፡ይህንኑ ነጥብ በአግባቡ ለመፍታት በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡትን መነሻ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር በሰው እና በሰነድ ማስረጃዎች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የውርስ ይዞታ በጠቅላላው 16 ቀርጥ ሲሆን ወራሾች ደግሞ 8 መሆናቸውን፤የአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የግራ ቀኙ ወላጆች በህይወት እያሉ ለእያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ መሬት የሰጧቸው መሆኑን፤ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ በጥገኝነት ሲኖሩ የነበረ መሆኑን እና ሌሎች ወራሾች የራሳቸው ይዞታ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ በጥገኝነት ሲኖሩ የነበረ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ እና በቀዳሚነት መብት ሊደርሳቸው የሚገባውም የድርሻ መጠን በክልሉ ሰበር ችሎት እንደተገለፀው ከውርስ ይዞታው ስፋት እና ወራሾች ብዛት አኳያ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ በክለሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጁ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 9(2) እና

ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 10(10) መሰረት እያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ ሊደርሳቸው እንደሚገባቸው ታምኗል፡፡ የሚቀረው 12 ቀርጥ መሬት ለሁሉም ወራሾች እኩል ሲካፈል ለ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የሚደርሳቸው የይዞታ መጠን ቀድሞ በስጦታ ከተቀበሉት መጠን በታች በመሆኑ በስጦታ ያገኙትን የይዞታ መጠን ይዘው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ ይኸው ከቀሪ የውርስ ይዞታ ላይ ሲነሳ የሚቀረው 8 ቀርጥ ሲሆን በተቀሩት ስድስት ወራሾች መካከል የሚካፈል ይሆናል፡፡

በመሆኑም በዚሁ ስሌት መሰረት 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የግራ ቀኙ ወላጆች በህይወት እያሉ እያንዳንዳቸው ያገኙትን ሁለት ቀርጥ መሬት ይዘው እንዲቆዩ፤ ለ3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ለእያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ መሬት በቀዳሚነት መብት ተነስቶላቸው ቀሪውን ስምንት ቀርጥ 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች ከአሁን ተጠሪዎች ጋር እኩል እንዲካፈሉ ማድረጉ ፍትሐዊ ሆኖ የተገኘ በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከታወጀ በኋላ ባለው የመሬት ስሪት መሰረት የፍ/ብ/ህ/ቁ/1065 መሬትን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው ቀድሞ በስጦታ የተወሰደውን ይዞታ በዓይነት ወደ ውርስ ይዞታ እንዲመለስ በማድረግ ሳይሆን የይዞታውን መጠን በልኬት በመለየት መጠኑ ከአጠቃላይ የውርስ ይዞታው ውስጥ ለስጦታ ተቀባዩ ከሚደርሰው ድርሻ ላይ እንዲቀነስ በማድረግ ነው፡፡

2. በውሳኔ ተራ ቁጥር አንድ ስር ከተገለፀው አካያ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/282886 ላይ ጥቅምት 19/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሎ፡-

2.1. 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች (አቶ አሰፋ ሰቦቃ እና አቶ ታደሰ ሰቦቃ) የግራ ቀኙ ወላጆች በህይወት እያሉ የሰጧቸውን እያንዳንዳቸው ሁለት ቀርጥ መሬት ይዘው እንዲጠቀሙበት፤

2.2. 3ኛ እና 4ኛ (ቀነኒ ሰቦቃ እና ኩሜ ሰቦቃ) ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ ጥገኛ የቤተሰብ አባል በመሆናቸው እና የቅድሚያ መብት ያላቸው በመሆኑ እያንዳንዳቸው ከውርስ ይዞታው ሁለት ቀርጥ መሬት እንዲካፈሉ፤እና

2.3. የተቀረውን ስምንት ቀርጥ መሬት 3ኛ እና 4ኛ አመልካቾች እንዲሁም የአሁን ተጠሪዎች በክልሉ ገጠር መሬት ድልድል መመዘኛ መሰረት የመሬት መበጣጠስን የማያስከትል ከሆነ እኩል እንዲካፈሉ፤ ካልሆነ በስምምነት በጋራ እንዲጠቀሙበት ተወስኗል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. ውሳኔው መሻሻሉን እንዲያውቅ የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡

2. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ታ

የሰ.መ.ቁ 168556
ሰኔ 14 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሀይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- አቶ ተሾመ ድለንሴ

ተጠሪዎች፡-1.የቀርሳ ማሊማ ወረዳ ገጠር መ/ ባለስልጣን ጽ/ቤት

2. **የቀርሳ ወርኮ ቀበሌ ገ/ማ//ጽ/ቤት**

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር መሬት ይዞታ ለህዝብ መንገድ ስራ በሚል ከአመልካች ላይ በመወሰዱ ካሳና ትክ መሬት እንዲሰጠው አመልካች ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁ/455/97 መሰረት የሚታይ እንጂ የፍርድ ቤት ስልጣን አይደለም በማለት የሰጠውን ብይን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በማጽናቱ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል እንዲታረም አቤቱታ የቀረበበት ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ለመንገድ በተወሰደው መሬት ምትክ ቦታ ወይም ካሳ ስላልተሰጠኝ በፍ/ቤት ይወሰንልኝ የሚል ሆኖ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ስለመቋቋሙ፡ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ከአዋጅ ቁ/ 455/97 አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተድርጓል፡፡በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበው መልስ ባጭሩ በአዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 11/1/መሰረት ለአስተዳደር አካል ቅሬታ ቀርቦ ውሳኔ ሳይሰጥ ለፍርድ ቤት መቅረቡ ተገቢ አለመሆኑንና ቅሬታ ሰሚ አስተዳደራዊ አካል አልተቋቋመም ቢባል እንኳን ቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎበታል በሚል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የተከራከረ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ከአመልካች ይዞታ ላይ 110ሜ በ12ሜ የሆነ የእርሻ መሬት ለህዝብ መንገድ የተወሰደበት መሆኑን ገልጾ ቀበሌው የወል መሬት የሌለው በመሆኑ ትክ መሬት ሊሰጠው እንዳልቻለ እንዲሁም ለዚህ ተብሎ የተያዘ በጀት ባለመኖሩ ካሳም እንዳልተከፈለ ገልጾ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡አመልካችም አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የእርሻ መሬት ይዞታዉ ላይ ለህዝብ መንገድ ተብሎ የተወሰደዉን መሬት ትክ መሬት ወይም ካሳ እንዲከፈለዉ ለአስተዳደር አካላት አቤቱታ አቅርቦ ምላሽ በማጣቱ ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲሰጠዉ ዳኝነት የጠየቀ ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ተጠሪዎችም የአመልካች መሬት በከፊል ለህዝብ መንገድ ስራ መዋሉን አልካዱም፡፡ ነገር ግን በቅድሚያ በአሥተዳደሩ በተቋቋመ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊታይ ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ መሰረት አድርገዉ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በዳኝነት የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ዉሳኔ የሰጡ ስለመሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሰረቱ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት እና የተፈጥሮ ሀብት የባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 40/3/ ላይ ተደንግጓል፡፡ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸዉ ያለመፈናቀል መብታቸዉ የተከበረ ስለመሆኑና አፈጻጸሙ በዝርዝር ህግ የሚወሰን መሆኑን አንቀጽ 40/4/ ላይ ተደንግጓል፡፡ይህንኑ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ተከትሎ የወጣዉ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ456/97 አንቀጽ 5/3/ እንዲሁም በስራ ላይ ያለዉ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁ/130/99 አንቀጽ 5/1 እና 5 ድንጋጌዎች እንደሚያስገነዝቡት በገጠር መሬት የመጠቀም የይዞታ መብት የሚገኘዉ በመንግስት በሚደረግ ድልድል፤በዉርስ ወይም በስጦታ ነዉ፡፡ስለሆነም የገጠር መሬት ላይ የይዞታ መብት አለኝ የሚል ሰዉ ከእነዚህ በአንደኛዉ አግባብ ይዞታዉን ያገኘ እንደሆነ ያለገደብ መሬቱን የመጠቀም ፤በመሬቱ ላይ ያፈራዉን ንብረት የመሸጥ፤የመለወጥና የማስተላለፍ መብት እንዳለዉ እና ይህም መብት ሊቋረጥ የሚችለዉ መሬቱ ለበለጠ የህዝብ ጥቅም ሲፈለግ ስለመሆኑና ለዚህም ካሳ እና ትክ መሬት እንደሚሰጠዉ ትክ መሬት መስጠት ካልተቻለ መልሶ ማቋቋሚያ ካሳ እንደሚከፈለዉ አዋጅ ቁ/ 130/99 አንቀጽ 6/1፣10፣11እና 12 ድንጋጌዎች ይዘት ያሥገነዝባሉ፡

ሕገ-መንግሥቱን መሠረት በማድረግ የወጣው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና የንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 455/ 1997 አንቀጽ 2/1 'ካሣ' ማለት የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ ለሚወሰንበት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ለሰፈረው ንብረት በዓይነት ወይም በገንዘብ ወይም በሁለቱም የሚከፈል ክፍያ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 11/1/ ተቃራኒ ንባብ የመሬት ነክ አቤቱታ ሠሚ አሥተዳደራዊ አካል በተቋቋመባቸው ከተሞች የካሣ መጠንን አስመልክቶ አቤቱታ የሚቀርበው በከተማው አሥተዳደር ለተቋቋመ የመሬት ነክ አቤቱታ ሰሚ አሥተዳደራዊ አካል መሆኑን ነገር ግን አቤቱታ ሰሚ አካል ባልተቋቋመባቸዉ የከተማ አስተዳደርና የገጠር መሬት አስመልክቶ ቅሬታዉን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ አሥተዳደሩ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በወሰደው የእርሻ መሬት ይዞታ ላይ ካሳ ያልተከፈለዉ ወይም ትክ ቦታ ያልተሰጠዉ መሆኑን መሰረት አድርጎ ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ከክርክሩ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ከጅምሩም ካሳ ወይም ትክ መሬት ያልተሰጠዉ መሆኑና ለዚህም አስተዳደራዊ መፍትሄ ፍለጋ ያቀረበዉ አቤቱታ ምላሽ ያልተሰጠዉ መሆኑን ነዉ፡፡በመሰረቱ ከአዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 3/1/ላይ እንደተደነገገዉ የገጠር መሬት ሲሆን የወረዳዉ አስተዳደር መሬቱን ከማስለቀቁ በፊት ተገቢዉ ካሳ ስለመከፈሉ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን የአመልካች የእርሻ መሬት ለመንገድ ስራ መወሰዱ በተጠሪዎች የታመነ ጉዳይ ሆኖ ካሳም ሆነ ትክ መሬት ለአመልካች ስለመሰጠቱ ክርክር ያልቀረበበት ሆኖ በአስተዳደር አካልም መፍትሄ ካልተሰጠዉ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሲቀርብ የዳኝነት ስልጣን የለዉም የሚለዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 37 ላይ የተመለከተውን የዜጎች ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን የሚጻረር ነው፡፡

በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት ዳኝነት የጠየቀበት ጉዳይ የገጠር መሬት ይዞታ ላይ በመሆኑ በህገ መንግስትና በአዋጅ ቁ/455/97 አንቀጽ 11/1/ ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝቦ ሲታይ መደበኛዉ ፍርድ ቤት አከራክሮ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባዉ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የለኝም በሚል የሰጠዉ ብይንና ይህንኑ በማጽናት የበላይ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ቀርሳ ማሊማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20990 ጥቅምት 27 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤የደቡብ ም/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 42674 በ17/07/2010ዓ.ም የሰጠው ዉሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ290177 በ06/12/2010ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የቀርሳ ማሊማ ወረዳ ፍ/ቤት ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው አግባብ ጉዳዩን አከራክሮ ተገቢውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ - 169864

ቀን - 28/09/2011

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ወ/ሮ ብርሃን ማለዶ

ተጠሪ፡- የባህር ዳር ከተማ ጣና ክ/ከተማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የተጀመረዉ በባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የአመልካች ክስ ይዘትም በአጭሩ፡- በባሕር ዳር ከተማ ጣና ክ/ከተማ ክልል ዉስጥ በ1988 ዓ.ም በስጦታ ተሰጥቶኝ በእጄ አድርጌ ግብር እየከፈልኩ ለረጅም ዓመታት ብሎኬት የማምረት ስራ እየሰራሁና ትንሽ መኖሪያ ቤትም በመስራት ስጠቀምበት የቆየሁ ሲሆን በነባር ይዞታነትም ቀበሌዉ አረጋግጦ ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶኛል፤ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ግብር እየከፈልኩ የንግድ ፍቃድ አዉጥቼ የብሎኬት ስራ ስሰራ የቤ/ቁጥር D-247 በሚል ተሰጥቶኝ የዉሃ እና የቴሌ አገልግሎት ክፍያዎችን እየከፈልኩ እና ቦታዉን ህጋዊ አድርጌ በመያዜ በመመሪያ ቁጥር 8/2007 መሠረት የይዞታ ማረጋገጫ ከተሰጠኝ በኋላ ተከሳሽ ያለበቂ እና ህጋዊ ምክንያት በቀን 22/10/2009 ዓ.ም በፃፈዉ ደብዳቤ ይዞታዬን ማምከኑ መብቴን የሚጥስና ይዞታዬንም የሚያሳጣኝ በመሆኑ ማረጋገጫዉ ሊመክን አይገባም እንዲባልልኝ እንዲሁም ቋሚ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰርቶ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ የመጀመሪያ መቃወሚያዎች ናቸዉ የሚላቸዉን ክርክሮች በማስቀደም ለክሱ በሰጠዉ መልስ፡- ከሳሽ መመሪያ ቁጥር 8/2007 ሰነድ አልባና የተሟላ ሰነድ የሌላቸዉን ይዞታዎች በተመለከተ የወጣውን መስፈርት ባለማሟላታቸው አጣሪ ኮሚቴዉ ባለይዞታ አይደሉም በማለት ያቀረበዉን የዉሳኔ

ሃሳብ በመቃወም እስከ ከንቲባ ጽ/ቤት ቀርቦ ታይቶ ባለይዞታ አለመሆናቸዉ በመረጋገጡ የይዞታ ማረጋገጫ አልተሰጣቸውም፤ አመራሩ አዲስ በመሆኑ በ2009 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ለከሳሽ የሰጣቸዉ ቢሆንም በድጋሚ ማጣራት ተደርጎ ያላግባብ መሆኑ ተረጋግጦ ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ.ም እንዲመክን መደረጉን እና ይህም ተገቢ መሆኑን፤ ከሳሽ ያቀረቡት የስጦታ ዉልም ህጋዊ ባለመሆኑ በማስረጃነት የሚያገለግል አለመሆኑን፤ ባለ ይዞታዎቹ አቶ መለስ ካሴ እና ልጆቹ ትክና ካሳ ተከፍሎአቸዉ ቦታዉን እንዲለቁ መደረጉን፤ ቦታዉ የመንግስትና የህዝብ በመሆኑ በቦታዉ ላይ ተሰራ የተባለዉ ቤትም ህገ ወጥ መሆኑን ጠቅሶ የቀረበበት ክስ ዉድቅ እንዲሆንለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ከሳሽ ቦታዉ በስጦታ የተሰጣቸዉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አለማቅረባቸዉን እና ሌሎች ከሳሽ ያቀረቧቸዉ ሰነዶችም ሰነድ የሌላቸዉና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን በማጣራት ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ የሚሰጥበትን ሁኔታ በተመለከተ በመመሪያ ቁጥር 8/2007 አንቀጽ 4(5) ላይ የተመለከተዉን መስፈርት የሚያሟላ ማስረጃ ከሳሽ አለማቅረባቸዉ በመጥቀስ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለባህር ዳር ከተማ ነክ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎትም መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 23/05/2011 ዓ.ም ተጽፎ በጠበቃቸዉ አማካይነት በቀረበ አምስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር በክልሉ በየደረጃዉ ባሉት ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ *መሠረታዊ* የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታዉ ተመርምሮም ቀደም ሲል በመ/ቁጥር 2847 ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ አሁን በተያዘዉ ጉዳይ ላይ ያለዉን ተፈፃሚነት እንዲሁም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከመመሪያ ቁጥር 8/2007 አንፃር አገናዝቦ ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ቀርቦ ግራ ቀኝ ክርክራቸዉን በጽሑፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቦታ ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ይዘዉ የሚገኙ ስለመሆኑ ተጠሪ ክዶ አልተከራከረም፡፡ አመልካች በቦታዉ ላይ በሰሩት ቤት ቁጥር ላይ የንግድ ፍቃድ በማዉጣት የብሎክት ማምረቻ ስራ ሲሰሩበት እንደነበረ ጠቅሰዉ አመልካች ያቀረቡት ክርክርም በተጠሪ

አልተካደም፡፡ አመልካች በይዞታዉ ላይ የሰሩት ቤት ህገ ወጥ መሆኑን ጠቅሶ የሰጠዉ ማስጠንቀቂያ ሁከት ነዉ በሚል አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡትን የሁከት ይወገድልኝ ክስ መሠረት በማድረግ የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2847 ላይ በቀን 01/03/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች በቦታዉ ላይ ግንባታ ያከናወኑት አግባብ ባለዉ የከተማ አስተዳደር አካል የግንባታ ፍቃድ ተሰጥቶአቸዉ መሆኑን አረጋግጦ ሁከት እንዲወገድ የሚል ዉሳኔ መስጠቱን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ መልኩ ለሰጠዉ ዉሳኔ መነሻዉ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሆኖ ለተሰጠዉ ዉሳኔ በምክንያትነት የተጠቀሰዉ አመልካች ቤቱን የገነቡት ስልጣን ያለዉ አካል በሰጣቸዉ የግንባታ ፍቃድ መሠረት መሆኑ እንጂ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቦታ ላይ ህጋዊ ባለይዞታ መሆናቸዉ ተረጋግጦ ባለመሆኑ ለያዝነዉ ጉዳይ መነሻ የሆነዉ ክስ እንዳይቀርብ የሚከለክለዉ (resjudicata) ባይሆንም፣ ዉሳኔዉ አመልካች በቦታዉ ላይ ቤት የሰሩት በተጠሪ ዕዉቅና እና ፍቃድ ስለመሆኑ አረጋጋጭ ነዉ፡፡ ከዚህም አልፎ አመልካች ቦታዉን የያዙት በ1988 ዓ.ም አጎታቸዉ አቶ መለስ ካሴ ሰጥቷቸዉ ስለመሆኑ በሰዉ እና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ስጦታዉን አድርገዋል የተባሉት ሰዉም በምስክርነት ቀርበዉ ቦታዉን ለአመልካች እንደሰጡ ማስረዳታቸዉን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ቦታዉን ሰጥተዋል የተባሉት አቶ መለስ ካሴ ቦታዉን ለመንግስት አስረክበዉ ትክ ቦታ ለእርሳቸዉ እና ለቤተሰባቸዉ ተሰጥቷል የሚል ክርክር ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት አንስቶ የተከራከረ ቢሆንም ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረበም፡፡

ይህ ሁሉ የሚያሳየዉ አመልካች ይዞታዉ ወደ ከተማ ከመጠቃለሉ በፊት ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ ይዞታዉን በእጃቸዉ አድርጎ ሲጠቀሙበት እንደነበረ እና ቦታዉ በከተማ ስር ከገባ በኋላም ለረጅም ዓመታት በቤትና ቦታዉ ላይ የንግድ ፍቃድ በማዉጣት እና በከተማዉ ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ አካላት ዕዉቅና ተሰጥቶ የግንባታ ፍቃድ ሁሉ በማዉጣት ቤት ሰርተዉ ሲጠቀሙበት የነበሩ መሆኑን ነዉ፡፡ የሚመለከተዉ አካል በቦታዉ ላይ ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ለአመልካች ሊሰጥ የቻለዉም ይህኑን እዉነታ ግምት ዉስጥ በማስገባት እንደሆነ ይታመናል፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠዉ ሰዉ በይዞታ ማረጋገጫዉ ላይ በተመለከተዉ ንብረት ላይ የባለቤትነት/የባለይዞታነት መብት እንዳለዉ የሚገመት ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1195 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ የፍሬ ነገር ግምት ጀርባ ያለዉ መሠረተ ሃሳብም የሚመለከተዉ አካል የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃን ሲሰጥ በህግ የተዘረጋዉን ተገቢዉን ስርዓት ተከትሎ የይዞታ ማረጋገጫዉ ማስረጃ የተሰጠዉ ሰዉ በማስረጃዉ ላይ በተመለከተዉ ንብረት ላይ መብት ያለዉ መሆኑን በማረጋገጥ ነዉ ተብሎ ስለሚታመን ስለመሆኑ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ የይዞታ ማረጋገጫዉ ማስረጃ የሰጠ አካል በህጉ አንቀጽ ማስረጃዉ የተሰጠዉ ያላግባብ መሆኑን ከተረዳ የባለለቤትነት/የይዞታ ማረጋገጫዉን የማምከን ስልጣን ያለዉ ቢሆንም፣ ማስረጃዉን ለማምከን የሚያስችል በቂ እና በህግ ተቀባይነት ያለዉ ምክንያት ሊኖረዉ እንደሚገባ በህጉ አንቀጽ 1196 ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መንፈስ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

የተያዘዉን ጉዳይ በተመለከተ ተጠሪ ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረዉን ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ማምከን የቻለዉ አመልካች መመሪያ ቁጥር 8/2007 ሰነድ አልባና የተሟላ ሰነድ የሌላቸዉን ይዞታዎች በተመለከተ የወጣዉን መስፈርት ባለማሟላታቸዉ እና የይዞታ ማረጋገጫዉን የሰጠዉ አመራርም አዲስ መሆናቸዉን ሲሆን፣ የስር የክልሉ ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ለሰጡት ዉሳኔ መሰረት ያደረጉን አመልካች ቦታዉ በስጦታ የተሰጣቸዉ መሆኑን እና በህግ አግባብ የያዙ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረባቸዉን እና ይዞታዉ ህጋዊ እንዲሆን በመመሪያ ቁጥር 8/2007 አንቀጽ 4(5) ላይ የተመለከተዉን መስፈርት አመልካች አለመሟላታቸዉን ስለመሆኑ ተመልክተናል። መመሪያ ቁጥር 8/2007 ዓ.ም በክልሉ ከተሞች ዉስጥ የተሟላ ሰነድ የሌላቸዉና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን በማጣራት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ለመስጠት ተሻሽሎ የወጣ ነዉ። ይህ መመሪያ በክፍል ሁለት የተሟላ ሰነድ የሌላቸዉና የሰነድ አልባ ይዞታዎች መለያ መስፈርቶችን ይደነግጋል። ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ይዞታ የገጠር የእርሻ መሬት የነበረ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለዉ ድንጋጌ በአንቀጽ 4(5) ላይ የተመለከተዉ ነዉ። ይህ ድንጋጌ "በአርሶ አደር የእርሻ መሬት ይዞታ ላይ ያልተሰራ ቤት ሆኖ ነገር ግን ከተማዉ ወይም ቀበሌዉ በምሪት የተያዙ ህጋዊ ይዞታዎች ስለመሆናቸዉ ማረጋገጫ የሚሰጣቸዉ ሆነዉ ለሦስተኛ ወገን የተላለፉና የባህላዊ ግዥ ወይም ስጦታ ዉል ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ እና ቤት የተሰራባቸዉ ይዞታዎች" በማለት ይደነግጋል። አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ ያገኙት ከመንግስት በምሪት ሳይሆን በስጦታ መሆኑን በመግለጽ ይከራከራሉ። መሬቱን በስጦታ ከአጎታቸዉ ስለማግኘታቸዉ ባቀረቡት ማስረጃ አረጋግጠዋል። የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህን ስጦታ ዉድቅ ለማድረግ በምክንያትነት ከጠቀሰዉ ዉስጥ አንዱ የስጦታ ዉሉ በሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል ዘንድ አለመመዝገቡን ነዉ። ይሁንና ከፍ ሲል የተመለከተዉ ድንጋጌ "የባህላዊ ግዥ ወይም ስጦታ" በሚል ሲደነግግ ይዞታዉ የእርሻ መሬት ሲሆን አንድ ሰዉ በስጦታ የሰነድ አልባ ይዞታ መብት ያለዉ መሆኑን ለማስረዳት የገጠር መሬትን በስጦታ ለማስተላለፍ በሚመለከተዉ ህግ የተመለከተዉን ጥብቅ ድንጋጌ መከተል አስፈላጊ አለመሆኑን ለማስገንዘብ እንደሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ። ይህ የሆነበት ምክንያትም አንድ ሰዉ ይዞታዉ በገጠር ቀበሌ ስር በነበረበት ወቅት ለረጅም ጊዜ ይዞ ሲጠቀምበት የነበረዉን መሬት ቦታዉ በከተማ ስር በመግባቱ ምክንያት እንዳይፈናቀል ጥበቃ ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ ይታመናል። ከመመሪያዉ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ትርጉምም ይህኑን ግምት ዉስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል የሚል እምነት አለን።

በአጠቃላይ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ በስጦታ አግኝተዉ ለረጅም ዓመታት ይዘዉ በሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ዕዉቅና ሲጠቀሙበት የነበረዉ ይዞታ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በመመሪያ ቁጥር 8/2007 መሰረትም ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም በሚል በከተማዉ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምፅ የፀናው ዉሳኔ

በግራ ቀኝ ክርክር የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር እንዲሁም የመመሪያ ቁጥር 8/2007 አንቀጽ 4(5) ትክክለኛ አፈፃፀም ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የብህር ዳር ከተማ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 2945 በቀን 17/08/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት 1041/2010 ዓ.ም በቀን 15/09/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፤ እንዲሁም የአማ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 78578 በቀን 12/03/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤትና ይዞታ በተመለከተ ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረው ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ሰኔ 22 ቀን 2009 ዓ.ም ከተጠሪ በተፃፈ ደብዳቤ መምከኑ በአግባቡ አይደለም ብለናል፡፡
3. አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤትና ይዞታ ላይ በክልሉ ከተሞች ውስጥ የተሟላ ሰነድ የሌላቸውና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን በማጣራት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ለመስጠት ተሻሽሎ በወጣ መመሪያ ቁጥር 8/2007 መሠረት የመስተናገድ መብት አላቸው ብለናል፡፡
4. ይህ ችሎት በቀን 11/07/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ 179827

ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሾሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- ካሱ ምስጋናው ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- ጥላዬ አስረስ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሠኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጋዞ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 0104609 ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ.ም የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 01-07464 ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0326324 የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የገጠር ሣር መሬት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጋዞ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በጋዞ ወረዳ 11 ቀበሌ ልዩ ስሙ ግመል ተራራ ከሚባለው ቦታ የሚገኘውን እና አዋሳኙ በምስራቅ የምንሹ አዳነ ሳር፤ በምዕራብ የሞላልኝ ደሳለኝ ሣር፤ በደቡብ የመኮንን ታረቀ እርሻ በሰሜን ወንዝ የሆነውን የሳር መሬት በ1983 ዓ.ም በተመን የተሰጣቸው እና በይዞታ ማረጋገጫ የተመዘገበላቸው ይዞታቸው መሆኑን እና ተጠሪ መሬቱን ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ የነጠቃቸው መሆኑን በመግለጽ በፍርድ ሀይል እንዲመለስላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ የአመልካች ክስ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና ስለጉዳዩም ከወረዳው መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ተጠሪ ክስ የቀረበበትን መሬት ከ20 ዓመት በላይ የያዘ መሆኑን በቀረበው ማስረጃ ተረጋግጧል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 69302 በአርሶ አደሮች መካከል የሚነሱ የገጠር መሬት ክርክሮች በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ የክልሉ የገጠር መሬት ሕግ አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጽ 55 ከሕግ ውጪ እና በወረራ የተያዙ መሬቶችን አስመልክቶ የይርጋ መቃወሚያ ተፈጻሚ እንደማይሆን የሚያመለክት ቢሆንም ተጠሪ ይዞታውን የያዘው ባለይዞታዎቹ በሰጡት መሬት በመቀላቀል በመሆኑ በአዋጁ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ውጪ ነው፤ አመልካች መሬቱን በ1983 ዓ.ም የተሰጣቸው ቢሆንም መሬቱን ከ1984 ዓ.ም በኋላ ያልተጠቀመበት እና ተጠሪ እንዲመልስላቸው ያልጠየቁ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋለ በስር ፍ/ቤት ከተሰማው ማስረጃ ተጠሪ ይዞታውን የያዘው ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያው በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጽ 55 መሠረት ሕጋዊ ውጤት የለውም፤ አመልካች የአከራካሪው መሬት ባለይዞታ ስለሆነች ተጠሪ መሬቱን ለአመልካች ሊለቅ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍ/ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አከራካሪው መሬት በ1983 ዓ.ም ለአመልካች የተሰጠ ቢሆንም መሬቱን ትታው በመሄድዋ በሌሎች ግለሰቦች እጅ ከወደቀ በኋላ ከይዞታቸው በማዋጣት በ1984 ጀምሮ ሰጥተውት ከ20 ዓመት በላይ ይዞ የሚጠቀምበት በመሆኑ መሬቱን ይዞ ሲጠቀምበት የነበረው በሕገወጥ መንገድ ነው የሚያስብል ሆኖ አልተገኘም በማለት የስር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች በተራቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አከራካሪው የሳር መሬት በ1983 ዓ.ም ለአመልካች በድልድል የተሰጠኝ ሲሆን የይዞታ ማረጋገጫውም በስሜ ተመዝግቧል፤ ተጠሪ ምንም መብት ሳይኖረው መያዙ በተረጋገጠበት ሁኔታ የወረዳው ፍ/ቤት እና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በክሱ የተገለጸው የመሬት አዋሳኝ ለአመልካች ጥቅምት 06 ቀን 2004 ዓ.ም በተሰጣቸው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተራቸው ተ.ቁ 11 ተመዝግቦ እያለ የወረዳው

መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የመሬቱ አዋሳኝ የተለየ መሆኑን እና መሬቱ በ1983 ዓ.ም ለአመልካች እና ለእናታቸው የተሰጠ ቢሆንም ተጠሪ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ እየተጠቀመበት ቆይቷል በሚል የሰጠውን ምላሽ መሠረት በማድረግ የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ አከራካሪውን መሬት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በመያዝ ግብር የምገብርበት እና የምጠቀምበት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፤ የይዞታው አዋሳኝ በአመልካች ደብተር ላይ መመዝገቡ አመልካች መብት እንዳላት የማያሳይ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የተሰጠው ወሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው። አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

አከራካሪው የሳር መሬት በ1983 ዓ.ም ለአመልካች እና ለእናታቸው ለወ/ሮ ሙሉ ወርቁ የተሰጠ መሆኑን፤ ተጠሪ አከራካሪውን መሬት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ይዞ የሚጠቀምበት መሆኑን፤ ተጠሪ መሬቱን ሊይዝ የቻለው ካሳ አበበ ምላሹ አዳነ እና ሞላልኝ ደሳለኝ የተባሉ የአካባቢው ሰዎች ሳራችንን ጠብቅልን በማለት ሁለት ሁለት ዘንግ ሰጥተውት ስለነበር በዚሁ ምክንያት ክስ የተመሰረተበትንም መሬት የያዘ መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል። በመሆኑም በስር ፍ/ቤት ከተረጋገጠው ፍሬነገር አንጻር በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 ድንጋጌ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የገጠር መሬትን አስመልክቶ በሚቀርቡ ክርክሮች ላይ የይርጋ ተፈጻሚነትን አስመልክቶ ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 69302 እና በሌሎችም በርካታ መዛግብት በሰጠው ውሳኔ የገጠር መሬትን አስተዳደር እና አጠቃቀም በሚመለከት የወጡ ሕጎች የእርሻ መሬት ባለይዞታና የመጠቀም መብቱ በሌላ ሰው ተደፍሮብኛል የሚል አርሶ አደር የመሬት ባለይዞታነትና የመጠቀም መብቱን ለማስከበር ክስ ማቅረብ ያለበት በስንት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ የማይደነግጉ ቢሆንም የይርጋ ሕግ ድንጋጌ በሕገ መንግስቱ በተደነገገው የአርሶ አደሮች የመሬት ባለይዞታነት እና የመጠቀም መብት በማያጣብብ ሁኔታ አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ሊተረጎም እንደሚገባው፤ ማንኛውም አርሶ አደር ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በእርሻ መሬት

ላይ ያለውን የይዞታና የመጠቀም መብት ለማስከበር ተገቢውን ትጋት የማድረግ ግዴታ ያለበት መሆኑን፤ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1677/1/ እና 1845 የተደነገገው የአሥር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ አርሶ አደሮች በሕገ መንግስቱ የተከበረላቸውን የመሬት ባለይዞታነትና በመሬት የመጠቀም መብት በፍርድ ከስሰው ለማስከበር ሰፋ ያለ ዕድል የሚሰጥ መሆኑን እና ይዞታውን በሌላ ሰው የተነጠቀ አርሶ አደር ወይም ወራሾቹ ይዞታው በሌላ ሰው ከህግ ወይም ከውል ውጭ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ውስጥ የእርሻ መሬት የባለይዞታነትና የመጠቀም መብቱን ለማስከበር ክስ ካላቀረበ ክሱ በአሥር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ እንደሚታገድ በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1 መሠረት በየትኛውም እርከን ላይ ላሉ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በሌላ በኩል የተሻሻለው የአማራ ብሔራዉ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 የገጠር መሬትን በወረራ ወይም በሌላ ማናቸውም ሕገወጥ በሆነ መንገድ ይዞ በመገልገል ላይ የሚገኝ ማናቸውም ሰው መሬቱን እንዲለቅ በማንኛውም ሌላ ሰው ወይም ስልጣን ባለው የመንግስት አስተዳደር አካል ሲጠየቅ ወይም በመደበኛ ፍ/ቤ ሲከሰስ የይርጋ ጊዜ ገደብን በስነ-ስርዓት መቃወሚነት ሊያነሳ አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ሕግ አንቀጽ 2/39 ሕገወጥ ይዞታ ማለት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የተያዘ እና አግባብ ባለው አካል እውቅና ያልተሰጠው ማናቸውም የገጠር መሬት ይዞታ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡

የተሻሻለው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁ/252/09 ስራ ላይ የዋለዉ ከጥቅምት 20 ቀን 2010ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ እና አመልካች ክስ ያቀረቡት የካቲት 20 ቀን 2010 ዓ.ም በመሆኑ ይርጋን አስመልክቶ በዚህ ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ 69302 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሻሽሎ ከወጣው የክልሉ የገጠር መሬት ሕግ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተገናዝቦ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርሱ የቻሉት አከራካሪው መሬት በ1983 ዓ.ም ለአመልካች የተሰጠ ቢሆንም መሬቱን ትታው በመሄድዋ በሌሎች ግለሰቦች እጅ ከወደቀ በኋላ ከይዞታቸው በማዋጣት በ1984 ዓ.ም ጀምሮ ለተጠሪ ሰጥተውት ከ20 ዓመት በላይ ይዞ የሚጠቀምበት በመሆኑ ተጠሪ ይዞታውን የያዘው በሕገወጥ መንገድ ነው ሊባል አይችልም በሚል ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ አከራካሪውን መሬት በክልሉ የገጠር መሬት ሕግ መሠረት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ተፈቅዶላቸው በሕጋዊ መንገድ የያዙት ስለመሆኑ ወይም አመልካች ፈቅደውላቸው የያዙት ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬነገር የለም፡፡ ተጠሪ አከራካሪውን መሬት በሕጋዊ መንገድ የያዙት ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ጊዜ ድረስ ተጠሪ መሬቱን የያዙት በሕገወጥ መንገድ መሆኑ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 እና 2/39 መሠረት የይርጋ መቃወሚያን በስነ-ስርዓት መቃወሚያነት ሊያነሱ

አይችሉም፡፡ በመሆኑም የወረዳው ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ አከራካሪውን መሬት የያዘው በሕገወጥ መንገድ ነው ሊባል ስለማይችል የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት ብይን መስጠታቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ ተሻሽሎ የወጣውን የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 እና 2/39 ድንጋጌዎች ይዘት ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በአማራ ብሔራው ክልላዊ መንግስት የጋዞ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 0104609 ግንቦት 29 2010 ዓ.ም በሰጠው ብይን የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 01-07464 ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0326324 የሰጠው ትዕዛዝ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 24741 በቀን 13/10/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

ንግድና ኢንሹራንስ

የሠ/መ/ቁ161598

የካቲት 13 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡....ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡..... አቶ ሰለሞን በቀለ፡- ጠበቃ አቶ ዜና ደባሱ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡..... ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ፡- የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣የአሁን አመልካች ተከሳሽ፣የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.214848 በ5/11/2010 ዓ.ም የሰጠዉን ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ባቀረቡት ክስ የተከሳሽ ንብረት የሆነዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A77230 አ.አ የሆነዉ ተሽከርካሪ ከከሳሽ የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን የተሰጠዉ ሲሆን፣ ይህ ተሽከርካሪ በ16/11/2008 ዓ.ም በቂርቆስ ክ/ከተማ መስከረም ማዞሪያ አካባቢ የ3ኛ ወገን ንብረት የሆነዉን የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A70206 አ.አ የሆነዉን ተሽከርካሪ ገጭቶ ጉዳት በማድረሱ ከሳሽ ብር 23,573.93 ለተጎጅዉ የከፈለ በመሆኑ፣ ተከሳሽ በመድን ዉሉ መሰረት ጉዳት መድረሱን ለከሳሽ የማሳወቅ ግዴታዉን ያልተወጣ ስለሆነ፣ ይህን ገንዘብ ክሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ተከሳሽ እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልን በማለት ከሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ የመድን ዉል መኖሩንና አደጋዉ መድረሱን በማመን ለፖሊስ ደብዳቤ የጻፈዉ በተከሳሽ አማካይነት አደጋ መድረሱን በማወቁ ነዉ፣ ተሽከርካሪዉ ወደ ተከሳሽ ስም መዛወሩን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ በከሳሽ እጅ መገኘቱ ነዉ፣ ለደረሰዉ አደጋ ኃላፊነቱ የከሳሽ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ ለተከሳሽ ተሽከርካሪ በሰጠዉ የ3ኛ ወገን የመድን ዉል ተከሳሹ ተጠቃሚ በመሆኑ፣ በዉሉ የተጣለበትን ቅድመ ሁኔታ ማለትም የደረሰዉን አደጋ ለከሳሽ የማሳወቅ ግዴታ የመወጣት ኃለፊነት አለበት፤ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 799/05 አንቀጽ 17 [1] መሰረት የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች መካከል አደጋን የማሳወቅ ግዴታ ነዉ፡፡ ተከሳሽ ፖሊስ የአደጋዉን ዝርዝር ሁኔታ ለከሳሽ እንዲገልጽ መጠየቃቸዉ አደጋ መድረሱን ከሳሽ እንዲያዉቅ የማድረግ ግዴታቸዉን ተወጥቷል ለማለት ስለማይቻል፤ ተከሳሽ በመድን

ዉልም ሆነ በአዋጁ አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን ስላልተወጣ፣ ከሳሽ በሕግ የተጣለበትን አደጋ የደረሰበትን 3ኛ ወገን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የመካስ ኃላፊነት ለመወጣት አደጋዉ ለደረሰበት 3ኛ ወገን የከፈለዉን ብር 23,573.93 ክስ ከቀረበበት ከ6/4/2010 ዓ.ም ጀምሮ ክፍያዉ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍል፣ የተለያዩ ወጪዎችንም እንዲከፍል ወስኗል። የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የቀረበለትን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ይህን ዉሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማሻር ነዉ።

የአሁን አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ከተጠሪ የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን የተሰጠዉ የአመልካች ንብረት የሆነዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A77230 አ.አ የሆነዉ ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን ንብረት በሆነዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A70206 አ.አ ተሸካርካሪ ላይ የግጭት አደጋ በማድረስ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን በአመልካች ተሽከርካሪ ላይ አሽከርካሪ የነበረዉ አቶ ካሱ ወርዶፋ አማካኝነት የግጭት አደጋ በ16/11/2008 ዓ.ም መድረሱን ወዲያዉኑ በወቅቱ ማሳወቁን ተጠሪ አምነዉ ተከራክሯል። ተጠሪዉ በዚህ መሰረት አደጋ መድረሱን የአመልካች ተሽከርካሪ ሾፌር በማሳወቃቸዉ አደጋዉ በደረሰ በአራተኛዉ ቀን በ20/11/2008 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ለቂርቆስ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ በአመልካች አማካኝነት የግጭት አደጋዉ መመዝገቡን ማሳወቁንና ዝርዝር ሁኔታዉን እንዲያሳዉቀዉ ጥያቄዎችን ጽፏል። በዚህ መሰረት የፖሊስ መምሪያዉ በ20/11/2008 ዓ.ም የተጻፈ የትራፊክ አደጋ ሪፖርት መስጫ ፎርም ቅጽ ቁጥር 005/02 ለተጠሪ ያሳወቀበት ሰነድ በተጠሪ እንደማስረጃ የቀረበ ጉዳይ ነዉ። በመሆኑም የአሁን አመልካች በመድን ዉሉም ሆነ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 17 [1] መሰረት አደጋን የማሳወቅ ግዴታ ተሰጥቶ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ይህን ግዴታዉን ስላልተወጣ የአሁን ተጠሪ ለ3ኛ ወገን የከፈለዉን የካሳ ገንዘብ እንዲከፍለዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን፣ ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣በዚህ ጉዳይ አመልካች ተሽከርካሪዉ ያደረሰዉን የግጭት አደጋ በወቅቱ ለመድን ሰጪ ለሆነዉ ለተጠሪ አላሳወቀዉም ተብሎ ተጠሪ ያወጣዉን ወጪ ሊተካ ይገባል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት መስከረም 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የአሁን አመልካች በመድን ዉሉ እና ህግ የተመለከተዉ አደጋዉን ለመድን ሰጪ ለሆነዉ ለተጠሪ አደጋዉ በደረሰ በአስር ተከታታይ ቀናት የማሳወቅ ግዴታዉን ያልተወጡ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነዉ፤ ተጠሪ አደጋ መድረሱን ሊያዉቅ የቻለዉ ጉዳት የደረሰበት 3ኛ ወገን የካሳ ክፍያ እንዲፈጸምለት በጠየቀበት ወቅት ነዉ እንጂ አመልካች በተጠሪ ኩባንያ አደጋ ማሳወቂያ ቅፅ በመሙላት ያሳወቀዉ ነገር መኖሩን ያቀረበ ማስረጃ የለም። ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ተብሎ የሚነቀፍ ባለመሆኑ፣

አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ ሆኖ፣ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ የአመልካች ንብረት የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A77230 አ.አ ለሆነዉ ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን መስጠቱ ያልተካደ ፍሬ ነገር ነዉ። ይህ ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን ንብረት በሆነዉ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A70206 አ.አ ተሸካርካሪ ላይ የግጭት አደጋ በማድረስ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን እና በዚህ ምክንያት የአሁን ተጠሪ በመድን ዉሉ መሰረት ጉዳት ለደረሰበት 3ኛ ወገን ካሳ የከፈለ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነበር። ይህን ተከትሎ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ አመልካች በመድን ዉሉ መሰረት ለተጠሪ አደጋ የማሳወቅ ግዴታዉን ስላልተወጣ ለ3ኛ ወገን የከፈልኩትን ብር 23,573.93 ከሕጋዊ ወለድ ጋር አመልካች እንዲከፍለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል። አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር በዉሉ መሰረት አደጋዉን ለተጠሪ የማሳወቅ ግዴታ ስለተወጣሁኝ ይህን ገንዘብ መክፈል የለብኝም በማለት ተከራክሯል። የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በመመርመር በሰጡት ዉሳኔ አመልካች በዉሉ እና በሕጉ አግባብ አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን ስላልተወጣ ተጠሪ በክሱ የጠቀሰዉን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈለዉ ወስኗል። እንግዲህ እነዚህ ጉዳዮች በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ሲሆኑ በሕጉ አግባብ ሲታይ የአሁን አመልካች በመድን ዉሉ እና ስለተሸከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን የወጣ አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 17 [1] መሰረት አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን አልተወጣም ተብሎ የተጠየቀዉን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፈል የመወሰኑን አግባብነት መመርመሩ ተገቢ ነዉ።

እንደሚታወቀዉ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 17 [1] ሥር እንደተመለከተዉ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካልኖረ በስተቀር መድን ተገቢዉ መድን የተገባለት ተሽከርካሪ አደጋ መድረሱን ወዲያዉኑ ወይም ቢዘጋይ በአስር ቀን ዉስጥ ለመድን ሰጭዉ ማስታወቅ አለበት። ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የ3ኛ ወገን መድን ዉል ገቢዉ መድን የተገባለት ተሽከርካሪ አደጋ ያደረሰ እንደሆነ አደጋ መድረሱን ለመድን ሰጭዉ በሕጉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ የማሳወቅ ግዴታ የተጣለበት መሆኑን ነዉ። በመሆኑም አንድ የመድን ገቢዉ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በሕግ የተጣለበትን ለመድን ሰጭዉ አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን ካልተወጣ በ3ኛ ወገን የመድን ዉል ተጠቃሚ ለመሆን በሕግ የተመለከተዉን ቅድመ ሁኔታ እንዳልተወጣ ስለሚያስቆጥረዉ መብቱን የሚያጣበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በግራ ቀኞቸዉ መካከል በተደረገዉ የ3ኛ ወገን የመድን ዉል መሰረት አመልካች ለተጠሪ አደጋ የማሳወቅ ግዴታ እንደተጣለበት ያልተካደ ጉዳይ ነዉ። የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር የተሸከርካሪ አደጋ መድረሱን ለክፍሉ ፖሊስም ሆነ ለተጠሪ

ማሳወቁን ገልጸ ተከራክሯል። ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር በክሱ የተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ አደጋ ማድረሱን ያወቅኩት የሶስተኛ ወገን ካሳ እንዲከፈለዉ ጥያቄ በማቅረቡ ነዉ እንጂ አመልካች አደጋዉን ለተጠሪ የማሳወቅ ግዴታዉን አልተወጣም በማለት ተከራክሯል።

በዚህ ረገድ ከሥር ፍ/ቤት መዝገብ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ በሶስተኛ ወገን ተሽከርካሪ ላይ የግጭት አደጋ ያደረሰዉ በ16/11/2008 ዓ.ም ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪ ስለተሽከርካሪዉ ግጭት ጉዳይ ፖሊስ ዝርዝር መግለጫ እንዲሰጠዉ በ20/11/2008 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የጠየቀ መሆኑን ነዉ። በዚህ መሰረት የቂርቆስ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ በቂ/ፖ/መ/11/1002/08 በ20/11/2008 ዓ.ም በጻፈዉ የትራፊክ አደጋ ሪፖርት መግለጫ ፎርም ቅጽ ቁጥር 005/02 የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ ስላደረሰዉአደጋ ዝርዝር መግለጫ ለተጠሪ ማሳወቁን ማየት ይቻላል። ይህ ማለት ተጠሪ አደጋዉ እንደደረሰ በአራት ቀን ዉስጥ ስለአደጋዉ እንዲያዉቅ የተደረገ መሆኑን ነዉ። የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር ይህ ተሽከርካሪ አደጋ ማድረሱን ያወቅነዉ ጉዳት የደረሰበት ሶስተኛ ወገን ካሳ እንዲከፈለዉ ጥያቄ በማቅረቡ ነዉ ይባል እንጂ ይህ ሶስተኛ ወገን መቼ እንዳሳወቀዉ፣ አደጋዉን ያሳወቀበት ቅጽ እንደማስረጃ ማቅረቡን የሥር ፍ/ቤት መዝገብ የሚያሳየዉ ነገር የለም። ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር አደጋ መድረሱን ማሳወቅ የሚቻለዉ በተጠሪ ኩባንያ በተዘጋጀዉ ቅጽ በመሙላት ብቻ ነዉ የሚል እስከሆነ ድረስ ስለአደጋዉ ማድረስ ሌላ ወገን ያሳወቀዉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ማቅረቡን የሥር ዉሳኔ የሚያሳየዉ ነገር የለም። ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን አመልካች ተቀጣሪ የሆነዉ አሽከርካሪ የነበረዉ አቶ ካሱ ወርዶፋ ተሽከርካሪዉ ያደረሰዉን አደጋ ወዲያዉኑ ለክፍሉ ፖሊስ ሪፖርት አድርጎ ማሳወቁን እና ፖሊስ ደግሞ ስለአደጋዉ ዝርዝር መግለጫ ለተጠሪ ማሳወቁን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧል። ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ የአሁን ተጠሪ በተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ሶስተኛ ወገን ስለአደጋዉ ለተጠሪ ያሳወቀዉ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ በሥር ፍ/ቤት እስካላቀረበ ድረስ፣ ክርክሩን በማስረጃ የማስረዳት ኃላፊነቱን ተወጥቷል ለማለት ያዳግታል። ስለሆነም የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን ንብረት በሆነዉ ተሽከርካሪ ላይ ባደረሰዉ የግጭት አደጋ ጉዳት ማድረሱን እና ለዚህ ተሽከርካሪ በተጠሪ ዘንድ የ3ኛ ወገን የመድን ዉል የተገባለት መሆኑን ለክፍሉ ፖሊስ ያሳወቁ መሆኑን፣ በዚህ ሂደትም በተሽከርካሪዉ አደጋ ስለመድረሱ ተጠሪ እንዲያዉቅ የተደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የአሁን አመልካች በተቀጣሪዉ አሽከርካሪ በኩል ስለአደጋዉ መድረስና ተሽከርካሪ በተጠሪ ዘንድ የሶስተኛ ወገን የመድን ዉል የተገባለት መሆኑን ወዲያዉኑ ለክፍሉ ፖሊስ ባያሳዉቀዉ እና አደጋዉ ስለመድረሱ ለተጠሪ እንዲታወቅ ባይድረግ ኖሮ፣ ይህ ተሽከርካሪ በተጠሪ ዘንድ የሶስተኛ ወገን የመድን ሽፋን ያለዉ መሆኑን ለማወቅ አስቸጋሪ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም።

በዚህ መሰረት የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ በ3ኛ ወገን ተሽከርካሪ ላይ የግጭት አደጋ ያደረሰዉ በ16/11/2008 ዓ.ም ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በዚህ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ በኩል ወዲያዉኑ ስለአደጋዉ ለክፍሉ ፖሊስም ሆነ ለተጠሪ በማሳወቁ፣ ተጠሪ የክፍሉ ፖሊስ ስለአደጋዉ ዝርዝር

መግለጫ እንዲሰጠዉ ጠይቆ፣ ፖ/ሊስ ደግሞ በ20/11/2008 ዓ.ም በተጻፈ የአደጋ ዝርዝር መግለጫ ለተጠሪ ማሳወቁን ከሥር መዝገብ መገንዘብ ይቻላል። ይህ ማለት ተጠሪ የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ አደጋዉ እንደደረሰ በአራት ቀን ዉስጥ እንዲያዉቅና ስለአደጋዉ ዝርዝር መግለጫ ያገኘ መሆኑን ነዉ። ይህ ከሆነ ደግሞ በመድን ዉሉም ሆነ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ ሕግ መሰረት ስለአደጋዉ መድረስ ወዲያዉኑ ወይም ቢዘጋይ በአስር ቀን ዉስጥ ለተጠሪ እንዲታወቅ መደረግ አለበት የሚለዉ ጉዳይ መሟላቱን የሚያስገነዝብ ነዉ። የአሁን ተጠሪ አደጋዉ እንደደረሰ በአራት ቀን ዉስጥ ስለአደጋዉ ዝርዝር መግለጫ እስካወቀ ድረስ፣ በመድን ዉሉም ሆነ በሕጉ የተቀመጠዉ የቅድመ ሁኔታ መሟላቱን ያሳያል። ተጠሪ ስለአደጋዉ መድረስ በዚህ አግባብ እንዲያዉቅ የተደረገና አደጋዉ መድረሱን አዉቆ ተገቢዉን ሁሉ ለመፈጸም ወይም እርምጃ ለመዉሰድ የሚያችለዉ እስከሆነ ድረስ፣ በመድን ዉሉም ሆነ በሕጉ የተቀመጠዉ ቅድመ ሁኔታ አልተሟላም በማለት የሚያቀርበዉ ክርክር የህግ ድጋፍ የለዉም። ስለሆነም የአሁን ተጠሪ አደጋዉ እንደደረሰ በአራት ቀን ዉስጥ ስለአደጋዉ ዝርዝር መግለጫ እንዲያዉቅ የተደረገ እስከሆነ ድረስ፣ አመልካች በመድን ዉሉም ሆነ በሕጉ የተመለከተዉን አደጋ የማሳወቅ ግዴታዉን አልተወጣም በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም። በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች በመድን ዉሉም ሆነ በሕግ የተጣለበትን መድን ሰጭ ለሆነዉ ለተጠሪ አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን አልተወጣም በማለት ተጠሪዉ ለ3ኛ ወገን የከፈለዉን ገንዘብ መልሶ እንዲከፍለዉ የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ሁኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን ተጠሪ የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ በሶስተኛ ወገን ተሽከርካሪ ላይ የግጭት አደጋ ያደረሰ መሆኑን አደጋዉ እንደደረሰ በአራት ቀን ዉስጥ እንዲያዉቅ መደረጉ በማስረጃ ተረጋግጦ እና በመድን ዉሉም ሆነ በሕጉ የተመለከተዉ አደጋን የማሳወቅ ቅድመ ሁኔታ ተሟልቶ እያለ፣ አመልካች አደጋን የማሳወቅ ግዴታዉን አልተወጣም በማለት ተጠሪዉ ለሶስተኛ ወገን የከፈለዉን ገንዘብ መልሶ እንዲከፍለዉ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል።

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.258901 በ19/7/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.214848 በ5/11/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል።
2. የአመልካች ንብረት ለሆነዉ ተሽከርካሪ በተገባለት የመድን ዉልም ሆነ በሕጉ የተመለከተዉን ለመድን ሰጭዉ አደጋን የማሰወቅ ቅድመ ሁኔታ በአግባቡ ተሟልቶ እያለ የአሁን ተጠሪ ለ3ኛ ወገን የከፈለዉን ካሳ አመልካች መልሶ ለተጠሪዉ የሚከፍልበት አግባብ የለም ብለናል።
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።

4. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።
5. የመ.ቁ.258901 የሆነዉ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ይመለስ።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሠ/ኃ

<u>የልዩነት ሃሣብ</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 5 ስር የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሀሣብ እና ውሣኔ በሚከተለው ምክንያት ተለይቻለሁ።

ኢንሹራንሶች ለደንበኞቻቸው የሚሰጡትን የመድን ሽፋን ታማኝ በመሆን አደጋ በደረሰባቸው ጊዜ ወይም ሲያደርሱ እንደውሉ ሊሸፍኑላቸው እንደሚገባና በሰበብ በአስባብ ሽፋን አልሰጥም በማለት ቅን ተዋዋዩችን ጉዳት ላይ እንዳይጥሉ መጠንቀቅ ተገቢ መሆኑን አምናለሁ።

ኢንሹራንሶች ኘሪሚየም ከደንበኞቻቸው የሚሰበስቡ ሲሆን ከቅን ልቦና ውጭ በሆነ ሁኔታ አንዳንድ ደንበኞችም ኢንሹራንሱን ላልተገባ ክፍያ እንዳይዳርጉትም በእኩልነት ሊታይ ይገባል ባይ ነኝ። በዚህ መሠረት አመልካች ከተጠሪ ጋር ውል ሲያደርጉ አደጋን የማሳወቅ ግዴታ እንደ ቅድመ ሁኔታ በሕግም ሆነ በውላቸው የተቀመጠ መሆኑን አላውቅም የሚል ክርክር የላቸውም። ይልቁንም አመልካች የሚከራከሩት አደጋ መድረሱን ለፖሊስ አሳውቄአለሁ በሚል ነው።

በመድን ሸጪው እና በመድን ገቢው መካከል የሚኖረው ግንኙነት የሚገዛው በግራ ቀኙ ውል ሲሆን ኢንሹንሱ/ መድን ሰጪው/ ላይ መድን ገቢው አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ ለኢንሹራንሱ/ መድን ሰጪው / በንግድ ሕግ አንቀጽ 670 እና ውሉ የተደገረው የ3ኛ ወገን ሽፋንን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 799/ አንቀጽ 17/1/ መሠረት አደጋ ከደረሰ እስከ 5 ቀን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር መድን ገቢውን ካጋጠመው ቢበዛ እስከ 10 ቀን አደጋን የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት የሚደነግገውን መሠረት በማድረግ የማሳወቅ ግዴታውን መድን ገቢው እንዲወጣ የተዋዋሉ መሆኑን ተመልክተናል።

በግራ ቀኙ ውል የማሳወቅ ግዴታ በመድን ገቢው ላይ የተጣለና በሕግም ይህ ግዴታ የተቀመጠ ከሆነ መድን ገቢው የማሳወቅ ግዴታውን መወጣት ይኖርበታል።

በተያዘው ጉዳይ አመልካች እያሉ ያሉት አደጋ በደረሰ ጊዜ ለፖሊስ አደጋውን በሹፌሬ አማካይነት አሳውቄአለሁ በኢንሹራንሱ ጠያቂነትም ፖሊስ ለኢንሹራንሱ አሳውቋል የሚል ክርክር ያነሱና በውል እና በሕግ የተጣለብኝን ግዴታ ተወጥቻለሁ የሚል ነው።

ነገር ግን ውሉ የተቋቋመው በኢንሹራንስ ሰጭውና እና በመድን ገቢው የአሁን አመልካች መካከል እንጂ ፖሊስ የውሉ አካል አይደለም፡፡ ሕጉ ጥበቃ የሚያደርገውም በኢንሹንራስ ገቢው እና በኢንሹራንስ ሰጪው መካከል ያለውን ውል እና ተዋዋዩችን ነው፡፡

በተለይ በተለይ የቀረበውን ጉዳይ ማሳወቅ ግዴታ መወጣትን ልዩ የሚያደርገው በ3ኛ ወገን መኪና ላይ ተለጣፊ በሆነው የ3ኛ ወገን ቦሎ ላይ ኢንሹራንስ ገቢው አደጋ በደረሰ ጊዜ ለኢንሹንራንስ /መድን ሰጪው የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በመድን ገቢውና በመድን ሰጪው መካከል በህግ በአስገዳጅ ሁኔታ የተደነገገውን በውላቸው ላይ ማስቀመጣቸው የማሳወቅ ግዴታን የማይደራደሩበት መሆኑን ለማመልከት እንጂ ውሉም ባይኖር እንኳን በህግ የማሳወቅ ግዴታ የመድን ገቢው ዋነኛ ግዴታ ነው፡፡ እንዲሁም በተዋዋዩች መካከል ያለን ግዴታ ሌላ ወገን ተወጥቶታል የሚለው አተረጓጎም በተለይ በኢንሹራንስ እና በደንበኞቻቸው መካከል የሚደረጉ ውሎችን ዋጋ ችግር ላይ የሚጥል ይሆናል፡፡ የማሳወቅ ግዴታ ይህን ያህል ትኩረት ተሰጥቶት በውል እና በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት እስከሆነ ድረስ ይህን ግዴታ መወጣት ያለበት ወገን መወጣት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ግዴታውን ባልተወጣበት እና በሕግ እና በውል በአስገዳጅ ሁኔታ በተደነገገበት ለፖሊስ አሳውቁአለሁ በመሆኑም ግዴታህን አልተወጣህም ልባል አይገባም በማለት ተጠሪ ያቀረበውን የመዳረግ ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን መከራከር ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በመሆኑም አብላጫው ድምጽ ለፖሊስ ካሣወቀ ከአላማው አንፃር እንዳሳወቀ ይቆጠራል በማለት የሰጠውን ውሣኔ ባለመቀበል ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ሊፀና እንጂ ሊሻር አይገባውም ነበር በሚል የሃሣብ ልዩነት ከአብላጫው ሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነብብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 160602

ጎዳር 30 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ ነጋ ባንቲሁን

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኢንሹራንስ ካሳ የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ዳኝነት ስልጣን የዳኘው የግልግል ጉባኤ ሲሆን በጉባኤው የአሁን አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነው አመልካች በስር የግልግል ዳኝነት ጉባኤ በቀን 01/10/2008 ዓ/ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ድርጅት በ15/11/2006 ዓም በተደረገ የኢንሹራንስ ውል ከ16/11/2006 ዓ/ም እስከ 7/5/2007 ዓ/ም የሚቆይ በዉሉ በተመለከቱት የአደጋ ምክንያቶች ጉዳት በደረሰ ጊዜ ብር 10,528,000.00 ካሳ ለማግኘት ከተጠሪ የመድን ሽፋን መግኘታቸውን፤ በዚህ የኢንሹራንስ ውል የተሰጠው የሽፋን አይነት እሳት እና መብረቅ፣ ጎርፍ፣ ውርጭ፣ ንፋስ፣ አውሎ ንፋስ፤ እና ከ35 ሚ.ሜ በላይ በሆነ ከባድ ዝናብ ምክንያት በጥጥ አዝዕርት ላይ ጉዳት ወይም ጥፋት ቢደርስ ካሳ የሚከፈላቸው መሆኑን ገልፀው የአመልካች የጥጥ አዝዕርት ከቀን 01/03/2006 ዓ/ም እስከ 03/13/2006 ዓ/ም ድረስ በአካባቢው በዘነበው ከባድ ዝናብና ጎርፍ እንዲሁም በቀን 25/1/2007 ዓም በዘነበው ከባድ ዝናብ ምክንያት የአመልካች የጥጥ ማሳ በጎርፍ በመጥለቅለቁና ሙሉ ለሙሉ በጎርፍ በመውደሙ አመልካች ለተጠሪ ጉዳቱን ወዲያውኑ በማሳወቅ በመድን ውሉ መሰረት የጉዳት መነሻ 25% ተቀንሶ ኢንሹራንስ የተገባለት መጠን 75% ብር 7,896,000.00 በጥጥ አዝርዕት ላይ ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል ፡፡

የአሁን ተጠሪ ድርጅት የአመልካች ክስ ደርሶት በቀን 14/10/2008 ዓ/ም በሰጠው መልስ አመልካች በቀን 15/11/2006 ዓ.ም ተፈርሚል ሲሉ የጠቀሱት የመድን ውል ፖሊሲ ጊዜያዊ ውል መሆኑን፤ ይህ ጊዜያዊ ውል የመጨረሻው ውል እስከሚዘጋጅ ድረስ የሚያገለግል መሆኑን፤ይህ ጊዜያዊ ውል የተሰጠው እርሻው በባለሙያ እስኪታይና እስከሚመረመር ድረስ እንዲያገለግል መሆኑን፤ በዚሁ

መሰረት ጊዜያዊ ውሉ በቀን 08/12/2006 ዓ/ም የባለሙያ ሪፖርት ከተዘጋጀ በኋላ ለጥጥ እርሻው የሚከፈለው የዐረቦን መጠን አመልካች መጀመሪያ ከከፈሉት የዐረቦን መጠን ላይ ተጨማሪ የሚያስከፍል መሆኑን ቢገለፅላቸውም ከሳሽ የሰሊጡን ተጨማሪ ክፍያ ብቻ በመክፈል የጥጡን ተጨማሪ ክፍያ ባለመክፈላቸው በቀን 12/12/2006 ዓ.ም ጊዚያዊ የመድን ውሉ ተሰርዞ በዋናዉ ውል የተተካ መሆኑን፤ጊዜያዊ ውሉ በሌላ ውል ከተተካ በኋላ በጥጥ አዝርዕት ላይ የደረሰውን ጉዳት በሚመለከት ተፈፃሚነት ያለው ጊዜያዊ ውሉ ሳይሆን ዋናው ውል መሆኑን፤ በዚህ ውል መሰረት በውሉ ሰንጠረዥ ሽፋን የተሰጣቸው የአደጋ ምክንያቶች እሳት እና የመብረቅ አደጋ፤ጎርፍ፤በረዶ የቀላቀለ አውሎ ንፋስ እና ቁር/ውርጭ/ ብቻ መሆኑን ጠቅሶ ከ35 ሚ.ሜ. በላይ የሆነ ከባድ ዝናብ መዝነብና መጥለቅለቅ ዝናባማ አውሎ ንፋስ የተሰኙት የአደጋ ምክንያቶች በአመልካች እና በተጠሪ በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተፈጸመ ውል በሽፋኑ አለመካተታቸውን፤ በመድን ውሉ በተመለከተው ትርጉም መሰረት ጎርፍ አለመከሰቱን እና የመድን ውል ሽፋን የሚሰጣቸውና የማይሸፍናቸው አደጋዎች፤ቅድመ ሁኔታዎች፣ ማግለያዎችና ትርጓሜዎችን የሚይዘው ዝርዝር የመድን ፖሊሲው የመድን ውሉ ሰንጠረዥ አካል ሆኖ ሳይነጣጠል ሊቀርብ የሚገባው በመሆኑ በቀን 12/12/2006 ዓ.ም ከተፈረመው ዋናው ውል ውጭ የቀረበ ክስ ነዉ ተብሎ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ያየው የግልግል ጉባኤ ግራ ቀኙን አከራክሮና ምስክሮች ሰምቶ በሰጠውውሳኔ አመልካች ለክሳቸው መሰረት ያደረጉት የመድን ውል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 657/3 በተመለከተዉ መሰረት ዋናው የመድን ውል እስከሚፈጸም ድረስ የተደረገ አስገዳጅነት ያለውውል እንደሆነ እና ይህ ጊዜያዊ ውል አደጋው ከመድረሱ በፊት በዋናውውል መተካቱን እንዳረጋገጠ በመግለጽ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የመድን ውል በቀን 12/12/2006ዓ.ም የተፈጸመውውል ነዉ በሚል በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡እንዲሁም በዚህ ውል መሰረት ተጠሪ ካሳ ለመክፈል የሚገደደው በእሳት፣ በመብረቅ፣ በጎርፍ፣ በበረዶ በቀላቀለ አውሎ ንፋስ እና ቁር(ዉርጭ) ምክንያቶች የደረሰ ጉዳት ቢኖር ብቻ ነው በሚል ከባድ ዝናብና የውሃ መጥለቅለቅ የሚሉ የአደጋ ምክንያቶች በጊዜያዊ ውሉ ሽፋን የተሰጣቸው ቢሆኑም ከዋናውውል የተቀነሱ የሽፋን አይነቶች ስለሆኑ በከባድ ዝናብና በውሃ ማጥለቅለቅ በአመልካች የጥጥ አዝዕርት ላይ ለደረሰ ጉዳት ተጠሪ የመድን ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ እንዲሁም በመድን ውሉ ለጎርፍ በተሰጠ ትርጉም መሰረት ጎርፍ የሚባለዉ ከመደበኛ የውሃ ማፍሰሻ ቦታ ወጥቶ እርሻውን ሲጎዳ በመሆኑ በዚህ አግባብ የጥጥ ማሳው በጎርፍ መጎዳቱን አመልካች በማስረጃ እንዳላስረዱና በውሉ ለ"ጎርፍ" የተሰጠው ትርጉም ግልጽ በመሆኑ መተርጎም አስፈላጊ አይደለም በማለት በውሉ መሰረት በጎርፍ የደረሰ ጉዳት የለም በሚል ከዚህ አኳያ የተጠየቀውን የካሳ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በከፊል በረዶ በቀላቀለ አውሎ ንፋስ ምክንያት በ15 ሄክታር የጥጥ ማሳ ላይ ለደረሰው ጉዳት ብር 180,000.00 ተጠሪ ለአመልካች ካሳ እንዲከፍል በቀን 14/04/2010ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

ከላይ በተገለጸው መሰረት በግልግል ጉባኤ በተሰጠ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 152280 ላይ አከራክሮ በቀን 29/08/2010ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው የፍርድ ውሳኔ የግልግል ጉባኤውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በዚህ አግባብ በተሰጡ ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን በቀን 25/10/2010ዓ.ም ጽፈዉ ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የሚከተለውነው፡፡

የጎርፍ ውሃ እና የዝናብ መጥለቅለቅ በሚመለከት በመድን ውሉ በተራ ቁጥር 2.1.2 ላይ ለጎርፍ የተሰጠ ትርጉም እንዲሁም በተራ ቁጥር 2.1.7 ላይ ደግሞ የዝናብ መጠን በየራሳቸው ተለይቶ የመድን ዋስትና ሽፋን ተሰጥቶ ሳለ በእነዚህ ምክንያቶች ለደረሰ ጉዳት የመድን ሽፋን አልተሰጠም ተብሎ በጉባኤውና በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ትርጉም ግልጽ የሆነ የሕግ ስህተት እንደሆነ፤ በአመልካች የጥጥ አዝዕርት ላይ ጉዳት ያደረሰው ጎርፍ ከደምቢ ዶሎ እና ከላሬ ወረዳ ከዘነበው ከባድ ዝናብ የመጣ መሆኑን ከጋምቤላ ክልል የአደጋ መከላከል መስሪያ ቤት በቀን 08/07/2007ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የተረጋገጠውን ተጠሪ ሳያስተባብል አመልካች በሰነድ ማስረጃ አላስረዳም በሚል እና ውሃው ከቆመበት ፈንቅሎ ካልወጣ ጎርፍ እንደማይባል የተሰጠው ትርጉም የጎርፍ መነሻው ከባድ ዝናብ ብቻ መሆኑን የዘነጋ እና ውሃ በውስጣዊ ንቅናቄ ከቆመበት ፈንቅሎ ሲወጣ ማእበል እንጂ ጎርፍ ሊባል እንደማይችል እየታወቀ ከእውነታው የራቀ ትርጉም መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንደሆነ፤ በጊዜያዊና በዋናውውል መካከል ልዩነት አለመኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ውል የተባለውን አመልካች እንደማያውቁና እንዳልፈረሙና ስምምነታቸዉን ያልሰጡበት ውል እንደሆነ በመግለጽ እንደማያስገድዳቸው ላቀረቡት ክርክር ዋጋ ሳይሰጥ መታለፉ እንዲሁም በጎርፍ ተጥለቅልቆ የጥጥ እርሻው መጎዳቱ ከመንግስት ተቋም በመጣ ማስረጃና በተጠሪ ምስክር ጭምር ተመስክሮ የተረጋገጠዉ ታልፎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንደሆነ፤

እንዲሁም የተጠሪ ምስክሮች የክረምት ጊዜ ካለፈ በኋላ ሄደው ያዩትን በመግለጽ የሰጡትን ምስክርነት ቃል ጎርፍና የውሃ መጥለቅለቅን ለመተርጎም መጠቀማቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን፤ አመልካች ሁለተኛውን ውል አለመፈረማቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለቱም ውሎች ላይ ጎርፍም ሆነ የውሃ መጥለቅለቅ የመድን ሽፋን የተሰጣቸው የአደጋ ምክንያቶች ሆነው እያለና በባለሙያ ምስክርነት ቃል እና ከጋምቤላ ክልል መንግስት ተቋማት ከተሰጡ ማስረጃዎች መካከል የተፈጠረ ልዩነት ካለም በሌላ ገለልተኛ ማስረጃ ማረጋገጥ እየተቻለ በዚህ አግባብ በማስረጃ እንዲረጋገጥ ሳይደረግ የተደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ተብሎ የግልግል ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ የተሰጠውውሳኔ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በማየት የሰጠውውሳኔ ተሽረው በጠየቁት መሰረት ተጠሪ ካሳ እንዲከፍላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታውን፣ በግልግል ዳኝነት የተሰጠ ውሳኔ እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የተሰጠ ውሳኔ መርምሮ በአመልካች የጥጥ አዝርዕት ላይ የደረሰ ጉዳት በጎርፍ ምክንያት መሆኑ በተከራካሪ ወገኖች የተካደ ባለመሆኑ ግራ ቀኙ በመድን ውል ላይ ለጎርፍ ከሰጡት ትርጓሜ አንፃር የተሰጡትን ውሳኔዎች አግባብነት ለመመርመር መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 01/04/2011ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን የመልሱ ይዘት በአጭሩ የሚከተለውነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘው ጭብጥ በአመልካች የጥጥ አዝርዕት ላይ በጎርፍ ምክንያት ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑ በተከራካሪ ወገኖች የተካደ አይደለም በሚል መነሻ ቢሆንም ተጠሪ ከስር ክርክር ጀምሮ አንድም ጊዜ ጎርፍ ስለመድረሱ ያላመነና በማስረጃ አስደግፎ የተከራከረበት በመሆኑ የሰበር አጣሪው ጎርፍ መከሰቱ የታመነ ነው በማለት መዝገቡ ያስቀርባል ማለቱ ስህተት እንደሆነ፤ሰበር ሰሚ ችሎቱ ተቀብሎ ማስተናገድ የሚገባው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸውን ጉዳዮች ብቻ ሆኖ እያለ አመልካች በጥጥ እርሻዬ ላይ ጎርፍ ስለመከሰቱ በጋምቤላ ክልል በሚገኙ መስሪያ ቤቶች በተሰጡ ማስረጃዎች ተረጋግጦልኝ እያለ ጎርፍ አልተከሰተም በሚል አለአግባብ ታልፎብኛል በሚል ያቀረቡት ቅሬታ ግን በማስረጃ እና በፍሬ ነገር ክርክር ላይ የተመሰረተ ነው ተብሎ ውድቅ እንዲደረግለት፤ አመልካች ለጎርፍ በፖሊሲዉ ላይ በተራ ቁጥር 2.1.2 ለውሃ መጥለቅለቅ ደግሞ በተራ ቁጥር 2.1.7 ስር የመድን ሽፋን ተሰጥቶታል በሚል የጠቀሱት በቀጥታ ሽፋን ሊሰጣቸው የሚችሉ የአደጋ ስጋቶች (risks coverable) ናቸው እንጂ ሽፋን የተሰጠው ተለይቶ የተቀመጠበት ሰንጠረዥ እንዳልሆነና በቀን 12/12/2006 ዓ.ም በተደረገ ውል ላይ ባለ ሠንጠረዥ ላይ የውሃ መጥለቅለቅ ሽፋን ያልተሰጠው አደጋ እንደሆነ፤ የመጀመሪያውውል በራሱ ጊዜያዊ ውል መሆኑ በግልጽ የተመለከተበት እንደሆነ፤ ሊሰጥ የሚገባው የመድን ሽፋን ዓይነት እና የአመልካች የሚከፈል አቅም ከግምት ገብቶ አመልካች መክፈል ያለባቸዉ አርቦን ተሻሽሎ ዋና ዉል እንደሚፈጸም በጊዜያዊ ዉሉ ላይ በተገለጸዉ መሰረት ዋናውውል የተፈጸመ መሆኑን፤ በዋናውውል ላይ የውሃ መጥለቅለቅ የመድን ሽፋን ያልተሰጠው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የውሃ መጥለቅለቅ የመድን ሽፋን ተሰጥቶታል ቢባል እንኳን በውሉ አንቀጽ 2.1.7 ስር እንደተገለጸው መጥለቅለቁ መከሰት ያለበት ከ35ሚ.ሜ በላይ በሆነ ከባድ ዝናብ የተከሰተ መጥለቅለቅ መሆን ይገባዋል፤ ሆኖም ጉዳቱ ደረሰ በተባለባቸው ቀናት በዚህ ልክ ዝናብ አለመዝነቡን ለጉባኤውበቀረበው ማስረጃ ስለተረጋገጠና ከመነሻውም በዋናውውል የውሃ መጥለቅለቅ የመድን ሽፋን ያልተሰጠው በመሆኑ ከዚህ አንጻር የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት እንደሌለው፤ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም የእርሻ ባለሙያ የምርመራ ሪፖርት እንዲሁም በተጠሪ ሶስተኛ የሞያ ምስክር በተሰጠ ምስክርነት በ5 ሄክታር የአመልካች እርሻ ላይ አነስተኛ የውሃ መጥለቅለቅ እና መታቆር እንዲሁም በከፍተኛ ሁኔታ በአረም መወረርን ጠቀሰ እንጂ እርሻው በሙሉ ተጥለቀለቀ አለማለቱን፤ የውሃ ማቆር ደግሞ ከውሃ መጥለቅለቅ የሚለይና ሽፋን ያልተሰጠው መሆኑ፤ጎርፍም ያልተከሰተ

መሆኑን፤አመልካች በደፈናው በውሃ መጥለቅለቅ የጥጥ ሰብሌን አወደመብኝ ከማለት ባሻገር በስር ያቀረቧቸውም ምስክሮች በእርሻው ላይ አደጋ እንደተከሰተ በቀን 03/13/2006 ዓ.ም በስልክ ሪፖርት መደረጉን ከመመስከር ባለፈ ስለ አደጋው አደራረስ፣የአደጋ ምክንያትም ሆነ የጉዳት መጠን ምንም እንዳላስረዱና በአመልካች የሙያ ምስክሮች ተመስክሮ የተረጋገጠዉን የማስተባበል አቅም ያለው ምስክርነት እንዳልሆነ በመግለጽ ቅሬታው የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ጉዳይ እንጂ የህግ ስህተትን የተመለከተ አይደለም ተብሎ ውድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

አመልካችም በቀን 23/04/2011 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ ግራ ቀኝ ያደረጉት ክርክር ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ ሲሆን እኛም ጉዳዩን ሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ እና ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ የኢንሹራንስ ዉል በቀን 15/11/2006 ዓ.ም የተደረገዉ ነዉ ወይስ በቀን 12/12/2006 ዓ.ም የተደረገዉ ነዉ? እንዲሁም በአመልካች የጥጥ ማሳ ላይ ጉዳት የደረሰው በኢንሹራንስ ውሉ ሽፋን በተሰጠው የአደጋ ምክንያት መሆን አለመሆኑንና ከዚህ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የግራ ቀኝ ክርክር መሰረት ያደረገው በግራ ቀኝ መካከል የተደረጉትን የኢንሹራንስ ውሎች ሲሆን አመልካች የኢንሹራንስ ካሳ ለማስከፈል በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ መሰረት ያደረጉት በቀን 15/11/2006 ዓ.ም የተደረገ የኢንሹራንስ ውል ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ይህ በቀን 15/11/2006 ዓ.ም የተደረገ የኢንሹራንስ ውል ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ውል እንደሆነና አገልግሎቱም የአመልካች አረቦን የመክፈል አቅማቸው ከግምት ገብቶ አመልካች መክፈል ያለባቸው አረቦን ተሻሽሎ ዋና ውል እንደሚፈጸም በጊዜያዊ ውሉ ላይ በተገለጸው መሰረት ዋናውውል እስከሚደረግ ድረስ የኢንሹራንስ ሽፋን ለመስጠት የተዘጋጀ ጊዜያዊ ውል እንደሆነና በክሱ የተጠቀሰው አደጋ ከመድረሱ በፊት ይህ ጊዜያዊ ውል በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተፈረመ ዋና ውል ስለተተካ አመልካች ለክሳቸዉ ጊዜያዊ ውሉን መጠቀማቸዉ አግባብ አይደለም በሚል ተከራክሯል፡፡አመልካች ከዚህ ጋር ተያይዞ ተጠሪ በቀን 12/12/2006ዓ.ም ተደረገ ያለውን የኢንሹራንስ ውል ስላልፈረምኩ አያስገድደኝም በሚል ተከራክረዋል፡፡

በንግድ ሕግ ቁጥር 657/3 ስር እንደተደነገገው ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ማረጋገጫ ማለት የኢንሹራንስ ፖሊሲው ወይም የፖሊሲዉ ተጨማሪ ጽሁፍ ከመፈረሙ በፊት ለጊዜዉ ማረጋገጫ መድን እንዲሆን የሚሰጥ ጽሁፍ(ሰነድ) ሲሆን ዓላማውም ኢንሹራንስ ሰጪውና እንሹራንስ ገቢው አንዱ ለአንዱ ግዴታ እንደገቡ የሚያሳይ ማረጋገጫ ሰነድ፡፡ ይህ ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ማረጋገጫ በኢንሹራንስ ስራ ዘርፍ በሰፊው ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ማረጋገጫ ሰነድ (Cover Note) ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ዋና (መደበኛ) የኢንሹራንስ ውል እና ፖሊሲ ማዘጋጀት የሚቻለውስለሚከፈለው

አርቦን መጠን፣ስለአደጋ ተጋላጭነት ሁኔታና መንስኤዎች፣ስለማግለያዎች፣ ስለካሳ መጠን በባለሙያ ጥናት ከተደረገ እና ተዋዋዮች ከተዳራደሩ በኋላ በሆነ ጊዜ እነዚህ ተግባራት እስከሚጠናቀቁ እና ዋናውውል እስከሚፈጸም ድረስ ኢንሹራንስ የሚገባለት ነገር ያለሽፋን እንዳይቀመጥ በሰነዱ በግልጽ ለተመለከተው የተወሰነ ጊዜ ስለሚከፈል አርቦን መጠን እና በሰነዱ በተገለጹት ምክንያቶች ዋናው የኢንሹራንስ ውል እስከሚፈረም ድረስ አደጋ በደረሰ ጊዜ ስለሚከፈል ካሳ ተገልጾ የሚሰጥ ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ላይ ግራ ቀኝ በቀን 15/11/2006 ዓ.ም በውል ቁጥር ጂኤኤም/4/አርኤልሲአር/0001/14 በተዋዋሉት የሰብል መድን ዋስትና ላይ በአመልካች የጥጥና ሰሊጥ ሰብል ላይ በእሳትና መብረቅ፣ በጎርፍ፣ በኃይለኛ ንፋስና ውርጭ፣ በረዶ በቀላቀለ አውሎ ንፋስ፣አዉራ በቀላቀለ አውሎ ንፋስ፣በአውሎ ንፋስ እና መጥለቅለቅ (በቀን ከ35ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከፍተኛ ዝናብ) በሆኑ የአደጋ ምክንያቶች ከቀን 16/11/2006 እስከ 07/07/2007 ዓ/ም ድረስ ባለው ጊዜ ጉዳት ሲደርስ በጥጥ አዝእርት ላይ ለሚደርስ ጉዳት እስከ ብር 10,528,000.00 (በውሉ መሰረት 25% የሚቀነስ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) ካሳ ለመክፈል ተጠሪ ግዴታ መግባቱን ፣አመልካችም የዚህን 2.5% አርቦን ለመክፍል መስማማታቸውን፤ እንዲሁም ኢንሹራንስ የተገባላቸዉ ሰብሎች በእርሻ ባለሙያ/ሰርቬየር ከተመረመረ (ከታየ) በኋላ ከላይ በዚህ ውል ሰንጠረዥ በተገለጸው መድን የተገባለት ንብረት/ጥቅም ማስተካከል እንደሚቻል ስምምነት ማድረጋቸዉን እና ይህም ውል ጊዜያዊ የመድን ውል እንደሆነና የሚያገለግለውም የመጨረሻው የመድን ውል እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ ብቻ እንደሆነ በውሉ ላይ በግልጽ ተመልክቶ ስምምነት መደረጉን ከውሉ ሰነድ እና ጉዳዩን በመጀመሪያ ዳኝነት ስልጣን ያየው የግልግል ጉባኤ ከሰጠውውሳኔ ይዘት ተገንዝበናል፡፡

እንዲሁም ተጠሪ አጥብቆ እንደሚከራከረው በቀን 15/11/2006ዓ.ም ውል ከተደረገ በኋላ በባለሙያ እንዲጣራ ተደርጎ ለክሱ መነሻ የሆነው አደጋ ከመድረሱ በፊት ጊዜያዊ ውሉ ሊሻሻል እንደሚገባ እና አመልካች የጥጡን ተጨማሪ የአርቦን ክፍያ እንዲከፍሉ ተጠይቀው ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ጊዜያዊ ውሉ ተሰርዞ በቀን 12/12/2006ዓ/ም በተደረገ ዋና የኢንሹራንስ ውል መሰረት የአርቦን ክፍያውበቀድሞው መጠን እንዲቀጥል በዚህ ዋና ውል የጊዜያዊ ውሉ ሰንጠረዥ ተሻሽሎ ሽፋን የተሰጣቸው የአደጋ ምክያቶች(ምንጮች) ደግሞ እሳት እና መብረቅ፣ጎርፍ፣በረዶ የቀላቀለ አውሎ ንፋስ እና ቁር/ውርጭ እንዲሆን መደረጉን በመግለጽ ለክርክሩ ተፈጻሚነት ያለው ይህ ዋናው የኢንሹራንስ ውል ነዉ በሚል ተከራክሯል፡፡

እንደሚታወቀው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1711 ስር በግልጽ እንደተደነገገው ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት አላቸው፡፡በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ወሎች ደግሞ ባቋቋሚቸው ሰዎች መብትና ግዴታን ስለሚጥሉ

እንደሕግ ሆነው እንደሚያገለግሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731/1 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው በግራ ቀኝ መካከል በቀን 15/11/2006 ዓ.ም የተደረገው የኢንሹራንስ ውል ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ማረጋገጫ ሰነድ (Cover Note) እንደሆነና የሚያገለግለውም ዋናው(በሰነዱ ላይ የመጨረሻ ተብሎ የተገለጸው)የኢንሹራንስ ውል እስከሚደረግ ብቻ እንደሆነ በሰነዱ ላይ በግልጽ የተመለከተና በዚህ አግባብ በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተጠሪ በተፈረመ ዋና የኢንሹራንስ ውል መተካቱን መረዳት ችለናል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው አደጋ የደረሰው ደግሞ አመልካች በክሳቸው ላይ እንደገለጹት ከቀን 01/13/2006ዓ.ም እስከ ቀን 03/13/2006ዓ.ም ድረስ እና በቀን 25/01/2007ዓ.ም በእርሻ ቦታ አካባቢና በአጎራባች አገር በዘነበ ከባድ ዝናብ መጥለቅለቅ እና ጎርፍ ምክንያት ስለሆነ ዋናውውል ከተደረገ በኋላ የደረሰ አደጋ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ እንዲህ አይነት የኢንሹራንስ ውል አደራረግና የመድን ሽፋን አሰጣጥ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 657/3 ስር የተፈቀደ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ግራ ቀኝ የመጀመሪያዉን ውል ፈቅደው የተስማሙበት በመሆኑ ለግራ ቀኝ ክርክር እንደ ሕግ ሆኖ ሊያገለግል የሚገባው በቀን 15/11/2006 ዓ.ም የተደረገው ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ውል ሳይሆን ይህንን ውል የተካው በቀን 12/12/2006ዓ.ም የተደረገውዋናው የኢንሹራንስ ውል እንደሆነ አረጋግጠናል፡፡

እንዲሁም አመልካች ዋናውን ውል ስላልፈረምኩና ስምምነቱን ስላልገለጽኩ ይህ ውል አያስገድደኝም በሚል የተከራከሩ ቢሆንም ይህንን ፍሬ ነገር በግራ ቀኝ ማስረጃ የማረጋገጥ ስልጣን ያለው የግልግል ጉባኤ በማስረጃ እንዳረጋገጠው ተጠሪ የተሻሻለውን ተጨማሪ የአርቦን ክፍያ እንዲከፍሉ አመልካችን ጠይቆ አመልካች ተጨማሪ የአርቦን ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ሰንጠረዥ ላይ ከተዘረዘሩት የአደጋ ምክንያቶችን መካከል የተወሰኑትን በመቀነስ በጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ዉሉ ላይ የተገለጸዉ የአርቦን ክፍያ እየተከፈለ የኢንሹራንስ ሽፋኑ እንዲቀጥል ዋናውን ውል በመፈረም ተጠሪ ለአመልካች ማሳወቁን የግልግል ጉባኤው የቀረቡለትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ ማረጋገጡን በውሳኔው አስፍሯል፡፡ መድን ሰጭው በሚያዘጋጀውፖሊሲላይ እራሱ መፈረም እንዳለበት በንግድ ሕጉ ቁጥር 657 ላይ ከመመልከቱ በስተቀር መድን ገቢው መፈረም እንደሚገባው ያልተመለከተ በመሆኑ በውል ማቅረቢያ /offer/ ሰነዱ ጊዜያዊ ውሉ ከመደረጉ በፊት በነበረው ላይ አመልካች (ኢንሹራንስ ገቢው)ከፈረሙና በዋናው የኢንሱራንስ ዉልና ፖሊሲው ላይ ደግሞ ተጠሪ (ኢንሹራንሰ ሰጭው) ከፈረመ በሁለቱ መካከል የመድን ውል ስለመደረጉ በቂ አስረጂ በመሆኑ የኢንሹራንሲ ዉልን ልዩ ባህሪ ከግምት ማስገባት የሚገባ በመሆኑ አመልካች በቀን 12/12/2006 ዓ.ም የተደረገውን የኢንሹራንስ ውል ስላልፈረምኩ አያስገድደኝም በማለት ያቀረቡት ክርክር በግልግል ጉባኤ ተቀባይነት ማጣቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡በመሆኑም ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለውውል በቀን 12/12/2006ዓ.ም የተደረገው የኢንሹራንስ ውል ነው ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም፡፡

በአመልካች የጥጥ ማሳ ላይ ጉዳት የደረሰው በኢንሹራንስ ውሉ ሽፋን በተሰጠው የአደጋ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? በሚል የያዝነውን ጭብጥ እንደመረመርነው ከዚህ በላይ በተገለጸው መሰረት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የኢንሹራንስ ውል በቀን 12/12/2006ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚህ የኢንሹራንስ ውል መሰረት ሽፋን ያገኙት የአደጋ ምክንያቶች ደግሞ እሳት እና መብረቅ፣ጎርፍ፣በረዶ የቀላቀለ አውሎ ንፋስ እና ቁር/ውርጭ ብቻ ናቸው፡፡አመልካች በጥጥ ሰብላቸው ላይ ጉዳት ያደረሱ ምክንያቶች ናቸውብለውበክሳቸው ከለጹት ውስጥ አንዱ በከባድ ዝናብ የጥጥ ማሳው መጥለቅለቅና ሙሉ በሙሉ መውደም የሚለውነው፡፡ በውሃ መጥለቅለቅ የተከሰተ ጉዳት በመጀመሪያው ጊዜያዊ ሽፋን የኢንሹራንስ ውል ሽፋን የተሰጠው ቢሆንም በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተደረገ ዋና የኢንሹራንስ ውል ግን ሽፋን የተሰጠው የአደጋ ምክንያት አይደለም፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው በቀን 12/12/2006 ዓ.ም የተደረገው የኢንሹራንስ ውል በመሆኑ አመልካች በውሃ መጥለቅለቅ የአደጋ ምክንያት መነሻ በጥጥ ማሳዬ ላይ ጉዳት ስለደረሰብኝ በሚል የጠየቁትን ካሳ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በግልግል ጉባኤው መወሰኑና ይሄዉ በይግባኝ ታይቶ መጽናቱ አግባብነት ያለው በመሆኑ ከዚህም አኳያ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ የመድን ሽፋኑን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ አልተቀበልንም፡፡

ሌላዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻ አከራካሪው ነጥብ አመልካች በጥጥ ማሳዉ ላይ ጉዳት አደረሰ ብለው የገለጹት ሁለተኛው የአደጋ ምክንያት ጎርፍ ሲሆን የግልግል ጉባኤውና ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የወሰነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደግሞ የተጠሪን ክርክር ተቀብለው ምንም እንኳን በጥጥ ሰብሉ ላይ በጎርፍ ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት ካሳ ለመክፈል በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተደረገ ዋናዉ የኢንሹራንስ ዉል ሽፋን የተሰጠ ቢሆንም በዚህ ዉል ላይ ለጎርፍ በተሰጠዉ ትርጉም መሰረት በጎርፍ የደረሰ ጉዳት የለም በሚል አመልካች በዚህ የአደጋ ምክንያት መነሻ የጠየቁትንም ካሳ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት ወስነዋል፡፡ ከዚህም አኳያ የተነሳዉን ክርክር እንደመረመርነው በጎርፍ ምክንያት በአመልካች የጥጥ ማሳ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተጠሪ የመድን ሽፋን መስጠቱ በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተደረገ ዋናው የኢንሹራንስ ውል ላይ በግልጽ የተመለከተ ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠሪም የካደው ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ ግራ ቀኙን ያከራከረው በኢንሹራንስ ፖሊሲው የትርጉም ክፍል ተራ ቁጥር 1 ስር ለ"ለጎርፍ" የተሰጠው ትርጉም ነው፡፡ የተሰጠው ትርጉም ይዘት የሚከተለውነው፡-

Flood shall mean loss of or damage to the crop insured caused by the overflow of water from the normal confine of any natural or artificial water course(other than water thanks, apparatus or pipes) or lakes. Reservoir, canal or dam whether resulting from storm or tempest (as defined herein) or otherwise. ይህም ጎርፍ ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰዉ ሰራሽ መንገድ ውሃ ከተገደበበት ስፍራ(የዉሃ ታንከር፣ ቧንቧ ወይም መሰል ቁስ(apparatus) ሳይጨምር) ከሀይቅ፣ ከማጠራቀሚያ(Reservoir)፣ ከውሃ ማስተላለፊያ (canal) ወይም ከግድብ(

dam) በማእበል አማካኝነት(storm or tempest) ወይም በሌላ ምክንያት ውሃ ሞልቶ በመፍሰስ ኢንሹራንስ በተገባለት ሰብል ላይ የሚያደርስ ጥፋት ወይም ጉዳት ነው የሚል የአማርኛ ቋንቋ ትርጉም ያለዉ ነው፡፡ ግራ ቀኝ ይህንን ትርጉም ተስማምተው የተቀበሉት በኢንሹራንስ ፖሊሲው የትርጉም ክፍል ነው፡፡ በንግድ ሕግ ቁጥር 657/1 ስር እንደተደነገገው የኢንሹራንስ ውሉ በኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ በሚባል ጽሁፍ መደገፍ ይገባዋል፡፡ይህ ከላይ የተጠቀሰው "ጎርፍ" ለሚለው ቃል ትርጉም የሚሰጠውም ግራ ቀኝ በቀን 12/12/2006ዓ.ም ባደረጉት ዋና ውልም ሆነ በመጀመሪያው ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ሽፋን ውል አካል አድርገው(የኢንሹራንስ ውሎቹን አስደግፈው) የተስማሙበት የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ ሲሆን ግራ ቀኝም ይህንኑ አልተካካዱም፡፡ በዚህ የኢንሹራንስ ፖሊስ ላይ የተመለከተው ነገር ግራ ቀኝ ተጨማሪ በሆነ ጽሁፍ በሌላ አግባብ ካልተስማሙ በቀር ሊለወጥ እንደማይችል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 657/2 ሥር ተደንግጓል፡፡ከላይ በተገለጸው መሰረት በተጠቀሰው አግባብ ለጎርፍ ትርጉም የሚሰጠው የኢንሹራንስ ውል ፖሊስ ተጨማሪ በሆነ ጽሁፍ የተለወጠ ስለመሆኑ በግራ ቀኝ የቀረበ ክርክር የለም፡፡

በተጨማሪም አመልካች ከዚህ ጋር አያይዘው እየተከራከሩ ያሉት ውሃው ከቆመበት ከውስጣዊ ንቅናቄ ፈንቅሎ ካልወጣ ጎርፍ እንደማይባል በዘፈቀደ ትርጉም የሚወጣለት ሳይሆን ጎርፍ በዓለም ደረጃ የሚታወቀው በከባድ ዝናብ መነሻ የሚከሰት ክስተት ሆኖ እያለ ከእውነታው የወጣ ትርጉም መሰጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በሚል ነው፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1733 ስር ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ የተዋዋዮቹ ፈቃድ ምን እንደነበር ዳኞች ለመተርጎም እንደማይችሉ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ በንግድ ሕጉ ቁጥር 657(1 እና 2) መሰረት የኢንሹራንስ ፖሊሲው የኢንሹራንስ ውሉ አካል በመሆኑ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ላይ የተመለከተው ቃል የኢንሹራንስ ውል ቃል ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ በመሆኑ፣ በፖሊሲው ላይ ግራ ቀኝ ከላይ በተመለከተው መሰረት ጎርፍ ለሚለዉ ቃል ጠባብ ትርጉም በመስጠት እስከተዋዋሉና በዚህ አግባብ ለቃሉ ጠባብ ትርጉም በመስጠት መዋዋልን የሚከለክል ሕግ ባለመኖሩ፣ በፖሊሲው ለጎርፍ የተሰጠው ትርጉም ግልጽ አይደለም በሚል በአመልካች የቀረበ ክርክር ባለመኖሩና የተሰጠውም ትርጉም ግልጽ በመሆኑ ጎርፍ በነባራዊው ዓለም በትርጉሙ በተጠቀሰው ሁኔታ ብቻ የሚከሰት አይደለም የሚል ክርክር በአመልካች በመነሳቱ ብቻ በግራ ቀኝ መካከል እንደ ሕግ የሚያገለግለዉ የውል ቃል በሰፊው እንዲተረጎም የሚያስችል የሕግ መሰረት የለም፡፡

በመሆኑም ምንም እንኳን በጎርፍ አደጋ ኢንሹራንስ በተገባለት የጥጥ አዝእርት ላይ የሚከሰት ጉዳት በቀን 12/12/2006ዓ.ም በተደረገ የኢንሹራንስ ውል የመድን ሽፋን የተሰጠው የአደጋ ምክንያት ቢሆንም ግራ ቀኝ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ላይ ለጎርፍ በሰጡት ትርጉም መሰረት በአመልካች የጥጥ አዝእርት ላይ ጉዳት ያደረሰው ጎርፍ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ መንገድ ውሃ ከተገደበበት ስፍራ(የውሃ ታንከር፣ ቧንቧ ወይም መሰል ቁስ(apparatus) ሳይጨምር) ከሀይቅ፣ ከማጠራቀሚያ(

Reservoir)፣ ከውሃ ማስተላለፊያ (canal) ወይም ከግድብ(dam) ላይ በማእበል አማካኝነት(storm or tempest) ወይም በሌላ ምክንያት ውሃ ሞልቶ በመፍሰሱ ምክንያት የተከሰተ ጎርፍ አለመሆኑን ፍሬ ነገርን በማስረጃ አጣርቶና መዝኖ የማረጋገጥ ስልጣን ያለው የግልግል ጉባኤ በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ መስጠቱና ይሄውውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3 ስልጣን የተሰጠው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያርም እንጂ ከማስረጃ ምዘና ጋር በተያየዘ የሚቀርቡለትን የፍሬ ነገር ስህተት እንዲያርም ባለመሆኑ አመልካች ጎርፍ ስለመከሰቱ በማስረጃ አስረድቻለሁ ሲሉ ያቀረቡት ክርክር በኢንሹራንስ ፖሊሲው የተቀመጠውን የጎርፍ ትርጉም ያላገናዘበ ከመሆኑም በተጨማሪ ፍሬ ነገርን ከቀረበው ማስረጃ አንጻር መርምሮና መዝኖ የማረጋገጥ የዳኝነት ተግባር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡እንዲሁም የማስረጃ ምዘና ስርዓትና መርህ ተከትሎ የግራ ቀኝን ማስረጃ ከመመዘን አንጻር የግልግል ጉባኤውም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጡት ውሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልፈጸሙም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የግልግል ዳኝነት ጉባኤ በቀን 14/04/2010 ዓ.ም የሰጠውውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 152280 ላይ በቀን 29/08/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግልግል ዳኝነት ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት የሰጠውን የፍርድ ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደራጃ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

   - የውሳኔው ግልባጭ ለግራ ቀኝ ይሰጣቸዉ፡፡
   - ውሳኔው ይታተም ዘንድ ግልባጩ ለፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡
   - መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ.158262

ሀምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች ፦ መዓዛ አሸናፊ
ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ኑረዲን ከድር

አመልካች ፦ ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ - ጠ/ቴዎድሮስ ተስፋዬ

ተጠሪ ፦ ጀነራል ኢንሹራንስ ብሮከርስ - ጠ/ተካልኝ ዓለሙ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪና ስራ አስኪያጂ ወ/ሮ ጌጤነሽ ኃ/ማሪያም በአሁን በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የተጠሪ ክስ ይዘት፡- ኢስት አፍሪካ አትዮጵያ ሊሚትድ የተባለው ኩባንያ በስሩ የሚገኙ ድርጅቶችን የመድህን ሽፋን በተመለከተ የተለያዩ አገልግሎቶች ለማግኘት ሰኔ 23 ቀን 1996 ዓ.ም (ጁን 30/2004) በተፃፈ ከሳሽን መርጦ የወከለ መሆኑን ለተከሳሽ አሳውቋል፤ ይህም ሌሎች በአዋጅ ቁጥር 86/1988 አንቀጽ 11 የተመለከቱትን በመድን ድለላ መስክ የሚከናወኑ ተግባራትን የሚያጠቃልል ሲሆን ከሳሽ ይህን የመድን ገቢውን አደራ በመቀበል ከመስከረም 21 ቀን 1997 ዓ.ም (ኦክቶበር 2004) እስከ ሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም (ጁን 30/2005)፣ ከሰኔ 24ቀን 1997 ዓ.ም (ጁላይ 1/2005) እስከ ሰኔ 23/1998 ዓ.ም (ጁን 30/2005) እንዲሁም ከሰኔ 24/1998 ዓ.ም (ጁላይ 1/2006) እስከ ሰኔ 23 ቀን 1999 ዓ.ም (ጁን 30 ቀን 1997) ላሉት ሶስት ዓመታት በደንበኛው ስር የሚገኙ 22 ድርጅቶች የመድን ሽፋናቸውን ከተከሳሽ እንዲያገኙ አድርጌያለሁ፤ ከሳሽ እነዚህን በርካታ የመድን ፖሊሲዎች በተመለከተ የካሳ ክፍያና ሌሎች የውል አስተዳድርን (contract administration) የሚመለከቱ ተግባራትን አከናውኗል፤ ተከሳሽ በከሳሽ አማካኝነት በመጣለት የመድህን ሥራ ብር 7,262,987.79 አረቦን ከደንበኛው ላይ ተቀብሏል፤ ከዚህ የአረቦን ገንዘብ ላይ የመድህን ድለላ ኮሚሽን ለከሳሽ መክፈል ይገባዋል፤ በመድህን ገበያው እንደሚሰራበት አንድ መድህን ሰጪ ደንበኛው ከሚከፍለው የአርቦን መጠን ላይ ለግል ተሸከርካሪዎች መድን 12.5%፣ ለንግድ ተሸከርካሪዎች መድን 10%፣ ለእሳትና መብረቅ 17.5% እንዲሁም ለሌሎች የመድን ፖሊሲዎች 15% የድለላ ኮሚሽን መክፈል አለበት፤ በዚህ መሰረት ተከሳሽ ለቀረበለት የኮሚሽን ክፍያ ጥያቄ በሰጠው ምላሽ በከሳሽ ያገኘውን የድለላ አገልግሎት የሚያምን ቢሆንም መድን ገቢው የተከሳሽ ኩባንያ ባለአክሲዮን በመሆኑ ኮሚሽን ያለመክፈል የውስጥ

መመሪያ አለን በሚል ክሳሽን የማይመለከት ምክንያት አቅርቧል፤ ነገር ግን ተከሳሽ ለክሳሽ የሚከፍለውን ኮሚሽን አስመልክቶ የብሮከር ኮድ ቁጥር 01G00135 ሊከፈለው የሚገባውን የኮሚሽን ገንዘብ የሚያሳይ መረጃ አውጥቷል፤ እንዲሁም ከኮሚሽኑ ገንዘብ ላይ ብር 5,085.00 ለክሳሽ ከፍሏል፤ ቀሪውን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ አይደለም፤ ስለሆነም ተከሳሽ ላገኘው አገልግሎት መክፈል ያለበትን ብር 1,057,908.31 (አንድ ሚሊዮን ሃምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ከ31/100) የኮሚሽን ክፍያ ከነወለዱ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው።

አመልካች ለክሱ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር መልስ አቅርቧል። አመልካች በሰጠው መልስ ኢስት አፍሪካ (ኢትዮ) ሊሚትድ ለመድን ሥራ ከሳሽን ወክሏል በሚል የተገለፀውን በተመለከተ እ.ኤ.አ በ30/06/2004 በመድን ገቢው በተፃፈው ደብዳቤ የመጨረሻ አንቀጽ ስር ጀነራል ኢንሹራንስ ብሮከርና አማካሪዎች የመ/ቤቱን የመድህን ፍላጎት እንዲያጠናና እንዲመረምር በድርጅቱ የተመደበና ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑን ከመግለጽ በቀር የተለያዩ የመድን ሽፋኖችን ለማግኘት ከሳሽን የመረጠ ስለመሆኑ አያስረዳም፤ ከዚህ በተቃራኒ ደብዳቤው መድን ገቢው ከተከሳሽ ጋር የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው ሲሆን ወደፊትም የሚኖረውን ግንኙነት እራሱ እንደሚያሳውቅ አረጋግጧል፤ በንግድ ህግ ቁጥር 56(1) መሰረት የድለላ ስራ ማለት ውል የሚዋዋሉ ሰዎችን ፈልጎ የሚያገናኝና የሚያዋውል ሲሆን የመድን ስራን ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ መሰረት ደግሞ በመድህን ገቢዎች ወይም የጠለፋ ዋስትና ለማግኘት ጥያቄ በሚያቀርቡ ሰዎች ስም የመድህን ንግድ ስራን ከመድህን ሰጪው ጋር የሚያገናኝ እና የመድን ውል ለመዋዋል ለሚፈልጉ ቅድመ ዝግጅትን የሚያመቻች ነው፤ በተያዘው ጉዳይ ግን ከሳሽ ከፍሲል ከተመለከቱት ድርጊቶች የትኛውንም አልፈፀመም፤ መድን ገቢው የተከሳሽ ኩባንያ መስራች ባለአክሲዮን ሲሆን በስሩ ያሉት ድርጅቶች ንብረት በተከሳሽ በኩል የኢንሹራንስ ሽፋን ሲሰጣቸው የነበረው ያለ መድን ድለላ ነው፤ ተከሳሽ የድለላ ክፍያ የሚፈጽመው በህግ ላይ በተመለከተው መሰረት አዲስ ደንበኛ አምጥተው ለሚያገናኙ ደላሎች ብቻ ነው፤ ተከሳሽ ለከሳሽ የኮሚሽን ጥያቄ የሰጠው ደብዳቤ በየትኛውም መመዘኛ ከሳሽ መድን ገቢውን ከተከሳሽ ጋር የሚያገናኝ ስራ መስራቱን አያረጋግጥም፤ ስለሚከፈለው ገንዘብ መረጃ አውጥቷል የተባለውን በተመለከተም በብሮከር ኮድ ቁጥር 01/J00135 የወጣውን መረጃ ተከሳሽ አያውቀውም፤ ተከፈለ የተባለው ገንዘብም ለከሳሽ ያልተከፈለና ከመድን ገቢው ጋር የተገናኘ አይደለም፤ መድን ገቢው የሚያስተዳድራቸው ንብረቶች የተከሳሽ መድን የነበራቸው ሲሆን ሽፋኑ የተሰጠውም ሆነ የሚታደሰው ካለምንም አገናኝ በመሆኑ ከሳሽ ክስ ባቀረበበት ጉዳይ የድለላ ስራ አልሰራም በመሆኑም ተከሳሽ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም፤ ተከሳሽ ለክሱ ኃላፊ ነው ቢባል እንኳ በመድን ስራው አማካኝነት ተከሳሽ ገቢ አግኝቷል የተባለ ቢሆንም ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፤ ከሳሽ ያለምንም የሂሳብ ሰነድ እና የሰራውን ስራ የሚገልጽ ማስረጃ ያቀረበው የገንዘብ መጠን ተቀባይነት የለውም፤ ስለሆነም ከሳሽ የጠየቀው የገንዘብ መጠን በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነም ለከሳሽ ሊከፈል የሚገባው ክፍያ መድን ገቢው የከፈለው የአርቦን ክፍያ እና ከሳሽ በመድን ገቢው በተፃፈው ደብዳቤ ላይ በተመለከቱት ድርጅቶች ስም ያስገባው የኢንሹራንስ

ሽፋንና የተከፈለ የአርቦን ክፍያ በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ተለይቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በሚቀርበው ምላሽ መሰረት እንዲወሰን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሳሽ ያቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ ሚያዚያ11/2005 ዓ.ም ብይን ተሰጥቶበታል፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም ተከሳሽ ለከሳሽ የተጠየቀውን የድለላ ኮሚሽን የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? ኃላፊት አለበት ከተባለስ ሊከፍል የሚገባው የገንዘብ መጠን ምን ያህል ሊሆን ይገባል? የሚሉ ጭብጦች በመያዝ ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ የመድን ውል ደንበኛው ከመግባቱ በፊት ጨረታ አውጥተው የመድን ውል እንዲፈጸም እና የመድን ውሎች ስለሚታደሱበት አግባብ ከተከሳሽ ጋር በመነጋገር ውሉ እንዲታደስ የማድረግ፤ ደንበኛውን በመድህን ውል ዙሪያ የማማከር እንዲሁም የካሳ ጥያቄዎች ሲኖሩ ተከታትሎ የማስፈፀም ስራዎችን ከደንበኛው ውክልና በመውሰድ ሲሰራ የነበረ መሆኑ በከሳሽ በኩል ከቀረቡት ለተከሳሽ የተፃፉ ደብዳቤዎች፤ ተከሳሽ ለከሳሽ ከፃፈው ደብዳቤ፤ ከመድን ገቢው ለፍርድ ቤቱ ከተሰጠው ምላሽ፤ እንዲሁም ምስክሮች በሰጡት ቃል የተረጋገጠ ሲሆን ተከሳሽ ይህን የሚያስተባብል ማስረጃ አላቀረበም፡፡ በመሆኑም የመድን ስራን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 746/2004 አንቀጽ 2(19) አንፃር ከሳሽ ደንበኛው የሆነውን ኢስት አፍሪካ ሊሚትድ ግሩፕ በመወከል ከ1996 ዓ.ም እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ የመድን የደላላነት ሥራዎች የሰራ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ስራው የተሰራው የተከሳሽ ኩባንያ ዋና ባለአክሲዮን ለሆነ ወገን በመሆኑ የድለላ ኮሚሽን ልከፍል አይገባም በማለት ተከሳሽ ቢከራከርም ይህን ይደግፋል የሚለውን የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ አያይዞ ካለማቅረቡም በላይ ውሳኔው አለ ቢባል እንኳ ተከሳሽ በራሱ አስተዳደር አካል የተላለፈንና ሌሎች አካላትን የማይገዛ ውሳኔን መሰረት በማድረግ ከኃላፊነት የሚድንበት አግባብ የለም፤ ስራዎቹ መሰራታቸው እስከተረጋገጠ እና በስራውም አማካኝነት ተከሳሽ ገቢ ማግኘቱ ከተረጋገጠ የኮሚሽን ክፍያ የማይከፍልበት አግባብ አይኖርም፡፡ በመሆኑም በተጠሪ ለተሰሩት የመድህን ደላላነት ስራዎች ወይም አገልግሎቶች አመልካች ኮሚሽን የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡ ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በተመለከተም ከሳሽ በማስረጃነት የተከሳሽን የዳታ ቤዝ ግልባጭ ያቀረበ ሲሆን ተከሳሽ ማስረጃውን እንደማያውቀውና ከዳታቤዙ የወጣ አለመሆኑን ክዶ ቢከራከርም ብሄራዊ ባንክ ጉዳዩን አጣርቶ እንዲገልጽ ታዞ ማስረጃው ከተከሳሽ ኩባንያ ዳታ ቤዝ የወጣ መሆኑን አረጋግጧል፤ ተከሳሹም ከዳታ ቤዝ የተገኘው ማስረጃ ይዘት ላይ ምንም አይነት ክርክር አላቀረበም፤ በመሆኑም በማስረጃው የተመለከተውን ብር 1,057,908.31 (አንድ ሚሊዮን ሀምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ብር ከ31/100) የመጨረሻው የድለላ ስራ ከተሰራበት ህዳር 25/1999 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት አመልካች ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ተብሎ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሚያዚያ 18/2010 ዓ.ም በተሻሬ የሰበር አቤቱታ የበታች ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር አቅርቧል፡፡ አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ህግ አዋጅ ቁጥር 86/1986 ነው ወይስ ይህን አዋጅ የተካው አዋጅ ቁጥር 746/2004፤ ተጠሪ ለሰጠው አገልግሎት አመልካችን የመጠየቅ መብት አለው ቢባል የአሁን አመልካች ባቀረበው ክርክር እንደገለፀው ለተሰራው ሥራ ሊከፈል የሚገባው ክፍያ በገለልተኛ ባለሙያ ይጣራልኝ በማለት ያቀረበው ክርክር ታልፎ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለማየት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ጥቅምት 9/2011 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በኃላፊነትም ሆነ በመጠን ረገድ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የሰበር ቅሬታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከፍሲል የተገለፀው ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው ተጠሪ አመልካቹ ካገኘው የአርቦን ክፍያ ገቢ መክፈል ያለበትን የመድን ድለላ አገልግሎት የኮሚሽን ክፍያ ብር 1,057,908.31 (አንድ ሚሊዮን ሃምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ከ31/100) ከነወለዱ እንዲከፍል እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን ሲሆን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ክስ ባቀረበበት ጉዳይ የድለላ ስራ አልሰራም ስለሆነም ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም፤ አመልካች ለክሱ ኃላፊ ነው ቢባል እንኳ በመድን ስራው አማካኝነት አመልካች ያገኘውን ገቢ የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፤ ተጠሪ ያለምንም የሂሳብ ሰነድ ያቀረበው የገንዘብ መጠን ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነም ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው ክፍያ በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ተለይቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በሚቀርበው ምላሽ መሰረት እንዲወሰን በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ከፍሲል የተገለፀውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 አንቀጽ 2(19) ስር እንደተደነገገው “የመድን ደላላ” ማለት ኮሚሽን በማስከፈል በመድን ገቢው ሰው ስም የመድን ውል ለመዋዋል የሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶችን የሚያመቻች፤ የመድን ውል ቀጣይ አስተዳደርና እድሳትን በሚመለከት እገዛ የሚያደርግ፤ እንዲሁም በመድን ውለታና በካሳ ክፍያ ጥያቄ ላይ ለመድን ገቢው የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ የተሻረው የመድን ስራ ስለመፍቀድና ስለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 2(11) ለ“መድን ደላላ” የሰጠው ትርጓሜ ይዘትም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ከዚህም ሌላ በንግድ ህጉ ስለደላሎች ትርጓሜ በሚሰጠው አንቀጽ 56(1) ስር “ደላላ” ማለት ውል የሚዋዋሉ ሰዎችን ይልቁንም እንደ ሽያጭ፣ ኪራይ፣ ኢንሹራንስ፣ የማመላለሻ ውልንና እንደዚህ ያሉትን ውሎች የሚዋዋሉ ሰዎችን ፈልገው የሚያገናኙና የሚያዋዉሉ ራሱን የቻለ የሞያ ተግባራቸው አድርገው ጥቅም ለማግኘት የሚሰሩ ሰዎች ወይም ይህንኑ የደላልነት ሥራ የሚሰራ የንግድ ማህበር ነው በማለት ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ የመድን ውል እንዲፈጸም እና እንዲታደስ የማድረግ፤ የመድን ውሎች ስለሚታደሱበት አግባብ ከአመልካች ጋር በመነጋገር ውሉ እንዲታደስ የማድረግ፤ ደንበኛውን በመድህን ውል ዙሪያ የማማከር እንዲሁም የካሳ ጥያቄዎች ሲኖሩ ተከታትሎ የማስፈፀም ስራዎችን ከደንበኛው ውክልና በመውሰድ ሲሰራ የነበረ መሆኑ ከተግባፏቸው ደብዳቤዎች፤ ፍርድ ቤቱ ካስቀረበው ማስረጃ እንዲሁም ምስክሮች በሰጡት ቃል በማረጋገጥ ተጠሪ ደንበኛው የሆነውን ኢስት አፍሪካ ሊሚትድ ግሩፕ በመወከል ከ1996 ዓ.ም እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ የመድን የደላላነት ሥራዎች የሰራ መሆኑንና በስራውም አማካኝነት አመልካች ገቢ ማግኘቱን በማረጋገጥ በተጠሪ ለተሰራው የመድህን ደላላነት ስራ አመልካች ኮሚሽን የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት ወስኗል። የሥር ፍርድ ቤት እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰው ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን ባለው ስልጣን መሰረት በማጣራትና በማስረጃ በማረጋገጥ ነው። እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ካለ ከሚመለከት በቀር መሰል የፍሬ ነገር ክርክርን መርምሮ እና ማስረጃ መዝኖ ውሳኔ የሚሰጥ ስላለመሆኑ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 80(3(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ግልፅ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል። ተጠሪ የመድን ውል እንዲፈጸም እና እንዲታደስ የማድረግ፤ ደንበኛውን በመድህን ውል ዙሪያ የማማከር እና የካሳ ጥያቄዎች ተከታትሎ የማስፈፀም ስራዎችን ሲሰራ የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ከፍሲል ከተጠቀሰው የህጉ ትርጉም አንፃር ኮሚሽን የሚያስከፍል የድለላ ሥራ መስራቱን መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም በተጠሪ ለተሰራው የመድህን ደላላነት ስራ አመልካች ኃላፊነት አለበት ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት የሚታረም የህግ ስህተት የለም ብለናል።

በሌላ በኩል የክፍያውን መጠን በተመለከተ ከፍሲል እንደተጠቀሰው ተጠሪ ብር 1057908.31 (አንድ ሚሊዮን ሃምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ከ31/100) ከነወለዱ እንዲከፈለው የጠየቀ ሲሆን አመልካች በበኩሉ በስር ፍርድ ቤት ለክሱ በሰጠው መልስ በመድን ስራው አማካኝነት አመልካች ያገኘውን ገቢ የሚያስረዳ ማስረጃ ስላልቀረበ ተጠሪ ያለምንም የሂሳብ ሰነድ በክሱ ያቀረበው የገንዘብ መጠን ተቀባይነት የለውም እንዲባል፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነም ክፍያው በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ተለይቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጠይቋል። የከፍተኛው ፍርድ ቤት ባሳለፈው ውሳኔ እንደተመለከተው በአመልካች ዳታ ቤዝ ተገኘ የተባለን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ተጠሪ የጠየቀውን ክፍያ ከነወለዱ እንዲከፈል ከመወሰኑ በቀር ኮሚሽን ለተጠየቀበት የድለላ ስራ ክፍያ አወሳሰን በሚረዳ መልኩ ተጠሪ ያሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋንና በመድን ገቢዎች የተከፈለ የአርቦን ክፍያ እንዲሁም ለጉዳዩ ተግባራዊ የሚሆነው የኮሚሽን መጠን በዝርዝር በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ተለይቶ እንዲቀርብ ተደርጎ ከስምምነታቸው እና ከህጉ እንዲሁም ከቀረበው ክርክር አንጻር ተለይቶ ውሳኔ አለመሰጠቱን ተገንዝበናል።

ስለሆነም ጉዳዩ ከዚህ አንጻር ሳይታይና ሳይጣራ እንዲሁም ዝርዝር ምክንያት ሳይሰጥ በዳታ ቤዝ ተገኘ የተባለን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ብቻ ተጠሪ የጠየቀውን ብር 1,057,908.31 (አንድ ሚሊዮን

ሃምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ከ31/100) ከነወለዱ አመልካች እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 86785 ሚያዝያ 11/2005 ዓ.ም ያሳለፈው ብይንና ታህሳስ 17 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 153508 መጋቢት 12/2010 እና ይህን በማረም ግንቦት 10 ቀን 2010 ዓ.ም ያስተላለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተጠሪ ለተሰራው የመድህን ደላላነት ስራ አመልካች ኃላፊነት አለበት ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዳታ ቤዝ ተገኘ የተባለን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ብቻ ተጠሪ የጠየቀውን ብር 1,057,908.31 (አንድ ሚሊዮን ሃምሳ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስምንት ከ31/100) ከነወለዱ አመልካች እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ተሽሯል፡፡
4. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ኮሚሽን ለተጠየቀበት የድለላ ስራ ክፍያ አወሳሰን በሚረዳ መልኩ ተጠሪ ያሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋንና በመድን ገቢዎች ለአመልካች የተከፈለ የአርቦን ክፍያ መጠን፤ እንዲሁም ለጉዳዩ ተግባራዊ የሚሆነውን የኮሚሽን መጠንና ለተጠሪ ተከፋይ ስለሚሆነው ገንዘብ በዝርዝር በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
5. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት መልኩ ይመለስ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ.103472

ቀን 27/01/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሠለ

አመልካች፡- የኢት/ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ኢትዮጵያ ታመነ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ጌታነህ ምናለ

2. ወ/ሮ የአልጋነሽ አበጀ

3. ዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል/ማ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የዕግድ ትእዛዝ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ አመልካች በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች /1ኛ እና 2ኛ/ ላይ ክስ መስርቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.154/ለ/ መሠረት የእግድ ትእዛዝ ከተሰጠ በኃላ የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ የዕግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ባቀረበው አቤቱታ ነው፡፡

የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ባልተከሰሰንበት እና በማይመለከተን እዳ ምክንያት በአመልካች ስም ያለው ንብረት /ቤት/ እንዲታገድ የተደረገው በአግቡቡ ስላልሆነ ዕግዱ ይነሳ የሚል ሲሆን የአሁኑ አመልካች በበኩሉ የሰጠው መልስ መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በተሠጠው የእግድ ትእዛዝ መሠረት በንግድ ማህበሩ ተከሳሽ /1ኛ ተጠሪ/ አባል መሆን አለመሆናቸው ተጣርቶ እግዱ እንዲመዘገብ በታዘዘው መሠረት ለፍርድ ቤቱ ምላሽ ሰጥተናል ባሉት ደብዳቤ በግልፅ ተከሣሾች የንግድ ማህበሩ አባል አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርበው ሲሆን ፍ/ቤቱ በወቅቱ ተገቢውን ብይን ይሰጥበት ነበር ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ማስረጃ ዝርዝር የንግድ ማህበሩ የካቲት 9/2005 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ በተያዘው ቃለ ጉባኤ በግልፅ እንደተመለከተው 1ኛ ተከሣሽ የነበረው አቶ ጌታነህ ምናሉ በማህበሩ የነበረው የአክሲዮን ድርሻና የማህበሩን የሥራ አስኪያጅነት ሥልጣን ለአቶ

ይታየው ታደሰ ያስረከበ መሆኑ ያሳያል ሆኖም 1ኛ ተከሣሽ የፍ/ቤቱ የዕግድ ትእዛዝ የማህበሩ ሥራ እስኪያጅ ነኝ በማለት ፈርሞ የተቀበለ በመሆኑ በወቅቱም የከሣሽ ባለሙያዎች ወደ ንግድ ማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ሲሄዱ 1ኛ ተከሣሽን ያገኘኋቸው በመሆኑ የእግድ ትእዛዙ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ 1ኛ ተከሣሽ የማህበሩ አባል እና ሥራ አስኪያጅ የነበረና የእግድ ትእዛዝ ከተሠጠ በኃላ አመልካች ሆን ብለው የባንኩን ጥቅም ለመጉዳት በመነሣሣት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን፡፡ የአባላቱ አክሲዮን ሽያጭ በቃለ ጉባኤ ተይዞ በሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት እየፀደቀ እንድተላለፈ የተገለፀ ቢሆንም የዕግድ ትእዛዝ የተሰጠበት ፋብሪካ ስመ ሀብቱ ሊተላለፍ የሚችለው ፋብሪካው በሚገኝበት የቡራዩ ከተማ አስተዳደር በማስመዝገብ በመሆኑ አመልካች ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ያቀረበው ቃለ ጉባኤ የፋብሪካው ባለቤት አያደርገውም፡፡ የዕግድ ትእዛዙን ለማስመዝገብ ባደረግነው እንቀስቃሴ የንግድ ማህበሩን በበላይነት የሚያስተዳድረው የኦሮሚያ እንቨስትመንት ኮሚሽን የንግድ ማህበሩ ከፍተኛ የአክሲዬን ድርሻ ያላቸውና የድርጅቱ ባለቤቶች 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች መሆናቸውን ያረጋገጠልን በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በባንኩ ላይ ውጤት የለውም ተብሎ ውድቅ ይደረግልን የሚል ነው፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ አመልካች የተመሠረተው መስከረም 1998 ዓ.ም በወ/ሮ ስርጉት እንግዳወርቅ 900 አክሲዬን እና በወ/ሮ ሀድራት ሲባኒ 100 አክሲዬን በብር 1,000,000 ካፒታል ሲሆን 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች ንግድ ማህበሩን የተቀላቀሉት መጋቢት 13/2003 ዓ.ም በተያዘ ቃለ ጉባኤ የወ/ሮ ስርጉትን የአክሲዮን ድርሻ 1ኛ ተከሣሽ የወ/ሮ ሀድራት ሲባኒን የአክሲዬን ድርሻ 2ኛ ተከሣሽ በመግዛት የአክሲዬን ሽያጩ መጋቢት 14/2003 ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ተመዝግቧል፡፡

1ኛ ተከሣሽ ይህንን የአክሲዬን ድርሻቸዉን መስከረም 12/2005፣ታህሳስ 22/2005 እና የካቲት 9/2005 በተያዘ ቃለ ጉባኤ በሽያጭ ለሌሎች በሽያጭ አስተላልፈው የካቲት 9/2005 ከማህበሩ የተሰናበቱ ሲሆን 2ኛ ተከሣሽም የነበረችውን የአክሲዬን ድርሻ ታህሳስ 22/2005 በተደረገ የማህበሩ ስብሰባ ለሌሎች ሰዎች በሽያጭ አስተላልፈው ከማህበሩ የተሰናበቱ መሆኑን እና ቃለ ጉባኤው በሚመለከተው የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ዋና መ/ቤት መመዝገቡን አመልካች ካቀረበው ማስረጃ ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል ከሳሽ በአመልካች የንግድ ማህበር ስም በሚንቀሳቀሰው ፋብሪካ/ቤት/ ላይ መጋቢት 24/2005 ዓ.ም በፍ/ቤት የዕግድ ትእዛዝ የሰጠው 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች በንግድ ማህበሩ የነበራቸውን የአክሲዬን ድርሻ በሽያጭ ለሌሎች ሰዎች አስተላልፈው ከማህበሩ ከተሰናበቱ በኃላ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

ከሳሽ አሣግጅያለው ያለው ቤት ይዞታ ያለው ራሱን ችሎ የሕግ ሠውነት ባለው አመልካች ስም እንጂ ክስ በቀረበባቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች ስም አይደለም ስለሆነም 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች

የአክሲዮን ድርሻቸውን ሸጠው ከማህበሩ አባልነት በመሠናበታቸው ምክንያት የማህበሩ ንብረት ደግሞ የሚመዘገብበት አግባብ የለም በማለት የዕግድ ትእዛዝ እንዲነሣ ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ያለውን ቅሬታ በይግባኝ ለማሳረም ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርቦ ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ ያለውን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለማሳረም አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ይዘት ፡- የአሁኑ ተጠሪ የአክሲዬን ድርሻ ቃለ ጉባኤ መሠረት በውልና ማስረጃ በማፅደቅ የአክሱዬን ድርሻ ማስተላለፋቸውን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም የአክሲዬን ድርሻ በውልና ማስረጃ ሊያልፍ የሚችል ቢሆንም በከሳሽ የታገደው ፋብሪካን ማስተላለፍ የሚቻለው ፋብሪካው በሚገኝበት በቡራዩ ከተማ አስተዳዳር ሽያጩን በተመለከተ በማስመዝገብ እንጂ በውልና ማስረጀ በማፅደቅ ብቻ ባለመሆኑ አመልካች ለክርክር መነሻ ለሆነው ንብረት ባለቤት አያደርገውም፡፡ ቤቱን ለማሳገድ በተንቀሳቀስንበት ወቅት በቡራዬ ከተማ አስተዳደር እንኳን ተጠሪ የፋብሪካው ባለቤት መሆናቸውን የሚገልፅ ምንም ዓይነት ማስረጃ አለመኖሩ እንዲሁም ለሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የዕግድ ትእዛዙን ባስገባንበት ጊዜ ተጠሪ የንብረቱ ባለቤት ነው ተብሎ ያልተገለፀልን ከመሆኑ በተጨማሪ የንብረቱ ባለቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች መሆናቸውን በሰነድ ጭምር አረጋግጠናል በመሆኑም አመልካች /የአሁኑ ተጠሪ/ ያቀረበው ሰነድ ሐሰተኛ በመሆኑ በባንኩ ላይ ሕጋዊ ውጤት የለውም እንዲባልልን አቤቱታ ብናቀርብም የስር ፍ/ቤት በዝምታ አልፎታል የአክሲዬን ድርሻ ሲተላለፍ የተላለፈላቸው በአክሲዬኖች የአክሲዬኑ ንብረት በሆኑት የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በሚገኙበት የመንግስት አስተዳደር /የስመ ንብረት ዝውውርን የሚያደርገው አካል/ መገለጽ የለበትም ማለቱ እና በአሁኑ ተጠሪ ውስጥ ያለው የአክሲዬን ድርሻ መተላለፉ ሕጋዊነቱ ይጣራልን ብለን ያቀረብነው መቃወሚያን በማለፍ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውድቅ ይደረግልን የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ይቅረብ የተባለው 1ኛ ተጠሪ ዕግድ በተሰጠበት ንብረት ላይ መስከረም፣ታህሳስ እና የካቲት 2005 ዓ.ም በተያዘው ቃለ - ጉባኤና ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በተረጋገጠ የሽያጭ ለሌላ 3ኛ ወገን ያስተላለፈ እና የእግድ ትእዛዙም መጋቢት 24/2005 ዓ.ም የተሰጠው ባለሀብትነቱ በሽያጭ ከተላለፈ በኃላ በመሆኑ አስቀድሞ የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ሊነሳ ይገባል በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ዳኝነት የሽያጭን ስምምነት በሰነዶች ማረጋገጫ ማረጋገጥ የሚያስከትለው ውጤት በተዋዋይ ወገኖች መካከል ነው ወይስ 3ኛ ወገን በሆነው አመልካች ላይም ህጋዊ ውጤት ያስከትላል?ንብረቱ ተላለፈ የሚባለውን ውልን ከማረጋገጥ ባሻገር በሚመለከተው

የመንግስት መ/ቤት ስመ ሀብቱ ከሻጩ ወደ ገዥው የተላላፈ መሆኑ በሚያመለክተው ሁኔታ የምዝገባ ስርዓቱ መከናወኑ ሲታወቅ? ከሚሉ ነጥቦች አንጻር ለማየት ተብሎ ነው።

የ3ኛ ተጠሪ መልስ ይዘት መጋቢት 24/2005 ዓ.ም በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ጌታነህ ታምሩ በዶዶላ ኢንተርናሽናል ትራዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማ. ውስጥ ያለው ድርሻ የተከሳሾች ስም ተመዝግበው የሚገኝ መሆኑ ተጣርቶ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ለ 3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ የሚል ነው። ተጠሪ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ሆኖ እንደተፈጥሮ ሰው በራሱ የመከሰስ፣የመክሰስ፣ ንብረት የማንቀሳቀስ መብት ያለው ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ሆኖ የተቋቋመ ነው ። አቶ ጌታሁን ምናለ እና 3ኛ ተጠሪ ሁለት የተለያዩ ራሳቸውን የቻሉ የሕግ ሰውነት ያላቸው ናቸው በአቶ ጌታነህ ምናለ አኪሲዬን ድርሻ ላይ የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ የሚመለከተው አቶ ጌታነህን ብቻ ነው የ3ኛ ተጠሪ አክሲዬንም ሆነ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲከበር የተሰጠ ትእዛዝ የለም የእግድ ትእዛዝ የተሰጠበት አክሲዬን ከእግዱ በፊት በሌላ ወገን ተላልፋል። 3ኛ ተጠሪ የስር ተከሣሽ ባለመሆኑ የማገጃ ትእዛዝ አይመለከተውም። ማንኛውም አኪሲዬን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ከተመዘገበ ይተላለፋል እንጂ እንደገና በቡራዮ ከተማም ሆነ በሌላ ማዘጋጀ ቤት ቀጣይ ምዝገባ እንደሚፈፀምበት የሚደነግግ ሕግ የለም በተጠሪ ስም የተመሠረተ ግንባታ እንጂ ፋብሪካ የለም። የባንኩን ጥቅም ለመጉዳት ተጠሪ የፈፀመው ሕገ ወጥ ድርጊት የለም ። የፋብሪካው ላይ የተሰጠ ምንም አይነት እግድ ስለለሌ በቡራዮ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሚከናወን የምዝገባ ሥርዓት የለም የሚል ነው።

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መልስ አላቀረቡም የአመልካች የመልስ መልስ ተያይዟል በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው አጠቃላይ ክርክር ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመዘገበው ሲሆን እኛም ክርክራቸውን ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የአመልካች አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት ይቅረብ ከተባለበት ነጥብ እና አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር እንደሚከተለው መርምረናል ።

እንደመረመርነውም 3ኛ ተጠሪ በብር 1,000,000/አንድሚሊዬን ብር / በ1998 ዓ.ም የተመሠረተ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ 800 አክሲዬኖችን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ 100 አክሲዬን ከወ/ሮ ስርጉት እንግዳወርቅ ገዝተው 1ኛ ተጠሪ ማህበሩን በስራ አስኪያጅነት ሲመሩት ቆይተው የአክሲዬን ድርሻቸውን መስከረም 12/2005፣ታህሳስ 22/2005 እና የካቲት 9/2005 ዓ.ም በተደረገ የማህበሩ ስብሰባ ላይ በተያዘ ቃለ ጉባኤ በሽያጭ ለሌሎች ሰዎች አስተላልፈው ከማህበሩ የካቲት 9/2005 ዓ.ም የተሰናበቱ መሆኑ እና ቃለ ጉባኤው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ የተመዘገበ ቢሆንም መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም ከፍ/ቤት የተሰጠውን የዕግድ ትእዛዝ 1ኛ ተጠሪ የተቀበለ መሆኑ፣አመልካች የዕግድ ትእዛዙን ለማስመዝገብ ባደረጉት እንቅስቃሴ የ 3ኛ ተጠሪ ማህበር ከፍተኛ አክሲዮን ድርሻ ያላቸውና የድርጅቱ ባለቤቶች 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መሆናቸውን የኦሮሚያ ኢንቨስት መንት ኮሚሽን ለአመልካች ያረጋገጠላቸው መሆኑ፣1ኛ ተጠሪ ከዚህ በላይ እንደተመዘገበው በ 3ኛ ተጠሪ ማህበር የነበራቸውን የአክሲዬን ድርሻ

በሽያጭ ለሌላ ሰው ማስተላለፋቸው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑ በማህበሩ ባለአክሲዮኖች መካከል ወይም በማህበሩ እና በባለአክሲዬን መካከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ካልሆነ በቀር በንግድ ሕጉ አንቀፅ 522 በተመለከተው መሠረት የአክሲዮን መተላለፉ በዕሑፍ ተረጋግጦ በባለ አክሲዬኖች መዝገብ ላይ ካልተፃፈ በ 3ኛ መገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን የማይችል መሆኑ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የ 1ኛ ተጠሪ የአክሲዬን ድርሻ ለሌሎች ሰዎች በሽያጭ መተላለፍ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ መመዝገቡ ብቻውን በ 3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡ ሌላው 3ኛ ተጠሪ በስር ፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የዕግድ ትእዛዝ እንዲነሳለት የቀረበው አቤቱታ ይዘት በስሜ ያለው ንብረት /ቤት/ እንዲታገድ የተደረገው በአግባቡ ስላልሆነ ዕግዱ ይነሳልኝ በሚል ሲሆን በዚህ ሰበር ችሎት ባደረገው ክርክር ወይም በሰጠው መልስ ላይ ደግሞ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ የ1ኛ ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ ላይ ነው፡፡ ተጠሪ እና 3ኛ ተጠሪ ሁለት የተለያዩ ራሳቸውን የቻሉ የሕግ ሰውነት ያላቸው ናቸው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ላይ የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ የሚመለከተው 1ኛ ተጠሪን ብቻ ነው፡፡ የ3ኛ ተጠሪ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲታገድ የተሰጠ ትእዛዝ የለም ብሎ የተከራከረው በስር ፍ/ቤት ዕግድ ትእዛዝ እንዲነሳለት ከቀረበው አቤቱታ ጋር የሚጋጭ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ በመልሱ እንደገለፀው የእግድ ትእዛዝ የተሰጠው በ1ኛ ተጠሪ የአኪሲዮን ድርሻ ላይ ከሆነ እና የ3ኛ ተጠሪ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በፍ/ቤቱ ትእዛዝ ያልተገደበ ከሆነ 1ኛ ተጠሪ በሚመለከት ጉዳዩ 3ኛ ተጠሪ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በፍ/ቤቱ ትእዛዝ ያልተገደበ ከሆነ 1ኛ ተጠሪን በሚመለከት ጉዳይ 3ኛ ተጠሪ የዕግድ ይነሣልኝ አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌለው መሆኑን ተጠሪው ካቀረበው መልስ መረዳት ይቻላል ::

ከዚህ በላይ እንደተመዘገበው የ1ኛ ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ ሽያጭ በባለአኪስዮኖች መዝገብ ላይ ያልተፃፈ በመሆኑ በንግድ ሕግ አንቀፅ 522 መሠረት ሶስተኛ ወገኖች የአክሲዬን ሽያጭ መፈፀሙን ወይም የ1ኛ ተጠሪ አክሲዬን ድርሻ በሽያጭ ወደ ሌላ ሰው መተላለፉን የሚያውቁበት መንገድ ባለመኖሩ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡ የ1ኛ ተጠሪ የአኪሲዬን ድርሻ ለሌላ ሰው በሽያጭ ስለመተላለፉ ማህበርተኞችም የተስማሙበት ውሣኔ በንግድ መዝገብ ላይ መመዝገብ እንዳለበት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 523 /3/ የተመለከተ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የ1ኛ ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ ሽያጭ ጉዳይ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ከመመዝገቡ በቀር በንግድ ሕጉ አንቀጽ 522 እና 523 /3/ በተመለከተው መሠረት ያልተመዘገበ በመሆኑ 3ኛ ወገን በሆነው በኢት/ንግድ ባንክ /አመልካች/ ላይ መቃወሚያ ሊሆነው አይችልም የስር ፍ/ቤቶች የአክሲዮን ሽያጩ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑን እና ሽያጩ የተደረገው የዕግድ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት መሆኑን ብቻ በመውሰድ የዕግድ ትእዛዙ እንዲነሳ የሰጡት ትእዛዝ ከ3ኛ ወገን መብት ጋር በአግባቡ ባለማገናዘብ የተሰጠ ስህተት በመሆኑ መሠታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ሊታረም ይገባል ብለናል ::

ው ሣ ኔ

1. **የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ.134151 መጋቢት 12 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ.100764 በቀን 25/09/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል ።**
2. **በስር ፍ/ቤት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ሊነሳ አይገባም ብለናል ።**
3. **መዝገቡ ዕልባት ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ ።**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።።

መ/ብ

የሰ/መ/ቁጥር---154564

ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካቾች:- 1. አቶ አብዱሰላም ሰይዱ አብደ

2. አቶ ጥላሁን አቻምየለህ ይርሳው

3. አቶ ሰይዱ አብደ አድጎ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት፤ አቶ ጌታነህ ምናለ እና ወ/ሮ አልጋነሽ አበጀ የፍርድ ባለዕዳዎች ሲሆኑ የአሁን አመልካቾች ደግሞ የመቃወም አመልካቾች ነበሩ፡፡ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ይዘት፡- የፍርድ ባለዕዳዎች በዶዶላ ኢንተርናሽናል ትራዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ዉስጥ ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ ተሸጦ ለተጠሪ እንዲከፈል በሚል የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የፍርድ ባለዕዳዎች በማህበር ዉስጥ 1ኛ የፍርድ ባለዕዳ ከነበራቸው 800 አክሲዮኖች ዉስጥ ለ1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች እንደቅደም ተከተላቸው 266፣ 100 እና 434 አክሲዮኖችን በሽያጭ አስተላልፈው በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በቁጥር ዋ/መ/5533/4ለ/05 የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም ያስተላለፉ ሲሆን 2ኛ የፍርድ ባለዕዳ ደግሞ ከነበራቸው 100 አክሲዮኖች ዉስጥ ለ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች እንደቅደም ተከተላቸው 67 እና 44 አክሲዮኖችን በሽያጭ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ

ጽ/ቤት በቁጥር ዋ/መ/5992/4ለ/05 ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም ቀርበዉ አስተላልፈዉ ከማህበሩ ተሰናብተዋል፡፡ የአክሲዮን ድርሻቸዉ ስለመተላለፉም በንግድ መዝገብ ላይ ተመዝግቧል፡፡ ስለሆነም የፍርድ ባለዕዳዎች የአክሲዮን ድርሻ የሌላቸዉና ትዕዛዙ የተሰጠዉ በአመልካቾች ሀብትና የአክሲዮን ድርሻ ላይ በመሆኑ የአፈጻጸሙ ትዕዛዝ ይነሳልን የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ ለመቃወሚያዉ በሰጠዉ መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት አክሲዮኖች የታገዱት የፍ/ባለመብት ባቀረበዉ ክስ መነሻነት በመ/ቁ 134151 መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም ነዉ፡፡ በወቅቱ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ባደረስንበት ወቅት 1ኛ የፍርድ ባለዕዳ የዶዶላ ኢንተርናሽናል ትራዲንግ ማህበር ሥራ አስኪያጅ ነበሩ፡፡ በወቅቱ በእግዱ ምክንያት በማህበሩ ስም የሚገኝ ቤት መታገዱን ገልጾ ማህበሩ እግዱ እንዲነሳለት የጠየቀ ሲሆን በስር ፍ/ቤት ዕግዱ እንዲነሳ ተደርጎ የሰበር አቤቱታ አቅርበንበት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 522 መሰረት የአክሲዮን መተላለፉ በጽሁፍ ተረጋግጦ በባለአክሲዮኖች መዝገብ እስካልተመዘገበ ድረስ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ አይሆንም ተብሎ እግዱ እንዲነሳ የተባለበት ትዕዛዝ በዉሳኔ ተሽሯል፡፡ በወቅቱ አመልካቾች የማህበሩ አባላት መሆናቸዉን ማህበሩ የገለጸ በመሆኑ ጉዳዩ ፍጻሜ ማግኘቱን እያወቁ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418(1) መሰረት ዉድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ የአክሲዮኖቹ ሽያጭ በንግድ መዝገብ ላይ ተመዝግቧል የሚል ክርክር ቢያቀርቡም የምዝገባ ቀናት ተብለዉ የተጠቀሱት ቃለ-ጉባኤዎቹ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገቡበት ቀን እንጂ በንግድ ሕጉ መሠረት በንግድ መዝገብ መመዝገባቸዉን አያሳይም፤ የቀረበዉ ማስረጃ በቃለ ጉባኤዎቹ ላይ የንግድ ሚኒስቴር ማህተም መደረጉን ከሚያሳይ በቀር የአክሲዮን ማስተላለፉ በንግድ ሕግ ቁጥር 523 መሠረት መመዝገቡን አያሳይም፤ የቀረበ የሰነድ ማስረጃም የለም፡፡ አሁን በማስረጃነት የተያያዘዉ ከንግድ ሚኒስቴር የተሰጠዉ ሰነድም አመልካቾች ይህንን አቤቱታ ከማቅረባቸዉ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ መሆኑ ሲታይ አስቀድሞ ያስመዝገቡ ለማስመሰል እየጣሩ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም አቤቱታዉ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤት የአመልካቾችን የመቃወም አቤቱታ እና የተጠሪን መልስ መርምሮ በአክሲዮኖች ላይ ዕግድ በተሰጠበት ወቅት የፍርድ ባለዕዳዎች በማህበሩ የነበራቸዉን የአክሲዮን ድርሻ በሽያጭ ለሌላ ሰዉ ስለማስተላለፋቸዉ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ከመመዝገቡ በቀር በወቅቱ የአክሲዮን ማስተላለፍ የንግድ ሕግ ቁጥር 523 መሠረት የተመዘገበ አለመሆኑን የሚያስገነዝበን በመሆኑና ካልተመዘገበ ደግሞ የተጠሪን ጨምሮ ባሉ ሌሎች 3ኛ ወገኖች ላይ በመቃወሚያነት ሊቀርብ የማይገባ በመሆኑ ቀደም ሲል የፍርድ ባለዕዳዎች በዶዶላ ኢንተርናሽል ትራዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ዉስጥ ያላቸዉ የአክሲዮን ድርሻ በሀራጅ ጨረታ ተሸጦ ገንዘቡ ለተጠሪ እንዲከፈል በሚል የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እንዲነሳላቸዉ አመልካቾች ያቀረቡት መቃወሚያ ዉድቅ ተደርጓል በማለት አፈጻጸሙን እንዲቀጥልበት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካቾች ቅሬታ ቢያቀርቡም ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የፍርድ ባለዕዳዎች በአክሲዮን ማህበሩ ውስጥ የአክሲዮን ድርሻ መኖሩ ተረጋግጦ ሳይታገድ በሰበር መ/ቁ 103472 በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ አይነሳም መባሉ የፍርድ ባለዕዳዎች በአክሲዮን ማህበሩ ውስጥ የአክሲዮን ድርሻ አላቸዉ ለማለት የሚያስችል በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ አመልካቾች የማህበሩን አክሲዮኖች ከሌሎች ባለአክሲዮኖች በመግዛት በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበዉ በ29/08/2005 ዓ.ም በተመዘገበ ቃለ ጉባኤ እንዲሁም ሚያዚያ 29 ቀን 2005 በተደረገ ምዘገባ በንግድ መዝገብ አስመዝግበን የያዝን ሲሆን የማህበሩን አክሲዮን አሳድገን የማህበሩን የአክሲዮን ድርሻ ሙሉ በሙሉ ይዘን እንገኛለን፡፡ የፍርድ ባለዕዳዎች በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በቀን 18/06/2005 ዓ.ም እና በ01/05/2005 ዓ.ም ከማህበሩ ያላቸዉን ድርሻ ከእኛ በፊት የአክሲዮን አባላት ለነበሩ ግለሰቦች በሽያጭ አስተላልፈዉ የተሰናበቱ እና የአክሲዮን ድርሻዉም ስለመተላለፉ በንግድ መዝገብ ላይ በ15/01/2005 ዓ.ም፣ በ01/05/2005 ዓ.ም በ19/06/2005 ዓ.ም በሽያጭ ስለመተላለፉ ተመዝግቧል፡፡ በሰ/መ/ቁ 103472 ላይ የተሰጠዉን የዕግድ አይነሳም ትዕዛዝ መኖሩን አመልካቾች ያወቅነዉ የስር ፍ/ቤት የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠዉ ትዕዛዝ የፍርድ ባለዕዳዎች ድርሻ በሀራጅ ተሸጦ ለፍርድ ባለመብት እንዲከፈል የሚለዉ ትዕዛዝ ከደረሰን በኋላ ስለሆነ አመልካቾች ተከራካሪ ባልሆኑበት ማህበሩ መብትና ጥቅም የለዉም የተባለበት ዉሳኔ መሠረት የባለዕዳዎች አክሲዮን ድርሻ መኖሩ ተረጋግጦ ባልታገደበት ባለዕዳዎች የአክሲዮን ድርሻ አላቸዉ መባሉ ስህተት ነዉ፡፡

የስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረብነዉን የክስ አቤቱታ መደበኛዉን የክስ መስማት ሂደት ሳይከተልና ያቀረብነዉን ክስና ማስረጃ በተገቢዉ ሳይመዝን የሰጠዉ ዉሳኔ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 86133 እና 87833 ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም የጣሰ በመሆኑ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የአክሲዮን መተላለፉ በሚገባ ሁኔታ በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ጽ/ቤት ፀድቆ መተላለፉን 3ኛ ወገኖች በሚያዉቁት ሁኔታ የተመዘገበ ሆኖ እያለ አልተመዘገበም መባሉ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም ንግድ ሚኒስቴር መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም በጻፈዉ ማስረጃ የአክሲዮን መተላለፉን 3ኛ ወገኖች እንዲያዉቁ በንግድ ሚኒስቴር የንግድ መዝገብ ላይ ስለመመዝገቡ የስር ፍ/ቤት በፍርድ ሀተታዉ አረጋግጧል፡፡ የአክሲዮን መተላለፍ ለዉጡና ማሻሻያዉ በሕግ እንዲመዘገብ በተቀመጠዉ አስገዳጅ የምዝገባ ጊዜያት የሚመዘገብ ሆኖ እያለ የምዝገባዉ ጊዜዉ አልተጠቀሰም በሚል ሽያጩ በንግድ መዝገብ ላይ አልተመዘገበም መባሉ ስህተት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ ይሻርልን የሚል ነዉ፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ ከዚህ ቀደም በአሁኑ ተጠሪ፣ በፍርድ ባለዕዳዎችና በማህበሩ መካከል የነበረዉ ዕግድ ይነሳልን ክርክር አሁን ክርክር ባስነሳዉ የአክሲዮን ድርሻ ላይ ነዉ ወይስ የማህበሩ ንብረት በሆነዉ ቤት ላይ? ይህ ክርክር እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በዉሳኔ በተቋጨ ጊዜ የአሁን አመልካቾች የክርክር ተካፋይ ነበሩ ወይስ አልነበሩም? የአሁን አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መነሻ የክርክር ተካፋይ የሆነዉ ክርክሩ በሚታይበት ጊዜ የአሁን አመልካቾች የአክሲዮን ድርሻ

ሽያጭ በዉልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ ከመሆኑም በላይ በንግድ ሕጉ ቁጥር 522 መሠረት የአክሲዮኖቹ መዝገብም ላይ የተመዘገበ ነዉ በሚል አቅርበዉ የሚከራከሩ እንደመሆኑ መጠን አሁን በግራ ቀኙ የተነሳዉ ክርክር አስቀድሞ በሰበር ሰሚዉ ችሎት ቀርቦ ዉሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነዉ ማለት ይቻላል? አይቻልም? የአክሲዮን ድርሻ በሽያጭ ለመተላለፉስ ይኸዉ በሽያጭ የማስተላለፍ ተግባር በ3ኛ ወገን ላይ ዉጤት ያስከትል ዘንድ በንግድ ሚኒስቴር አማካኝነት በባለ አክሲዮኖች መዝገብ ላይ ተመዝግቧል ሲል ያቀረበዉ ክርክር በንግድ ሕግ ቁጥር 523 የተመለከተዉን መስፈርት ያሟላ ነዉ ወይስ አይደለም? ከሚሉት ነጥቦች አንጻር ጉዳዩ ይታይ ዘንድ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቀባበል እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰበር መልሱ ያቀረበዉ ክርክር ይዘት፡- ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በመ/ቁ 134151 መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ መሠረት በፍርድ ባለዕዳዎች በእነ አቶ ጌታነህ ምናለ ስም በዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ዉስጥ ተመዝግበዉ የሚገኙ አክሲዮኖቹን በአግባቡ እንዲታገዱ አድርጓል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ ለማህበሩ እንዲደርስ የተደረገ ሲሆን በወቅቱ የዕግድ ትዕዛዙን የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ነኝ በማለት ፈርመዉ የተቀበሉት አቶ ጌታነህ ምናለ ናቸዉ፡፡ ማህበሩ አክሲዮኖቹ በሽያጭ ለሌላ 3ኛ ወገን በመተላለፋቸዉ ምክንያት ለማገድ አልችልም በማለት ለስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ምላሽ የዕግድ ትዕዛዙን መቀበሉን ያመለክታል፡፡ በወቅቱ ማህበሩ በንብረቱ ላይ የተላለፈዉ የዕግድ ይነሳልኝ ሲል ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም የዕግድ ትዕዛዙ የተላለፈዉ በማህበሩ ቤት ላይ ሳይሆን በባለዕዳዎቹ የአክሲዮን ድርሻ ላይ ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤትም ሚያዚያ 12 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ የአክሲዮን ድርሻዎቹ እንዲታገዱ በ24/07/2005 ዓ.ም የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ነዉ፡፡

በሰ/መ/ቁ 103472 ሰበር ሰሚ ችሎት እግዱ ሊነሳ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የአክሲዮኖቹ ሽያጭ በንግድ ሕግ ቁጥር 522 እና 523(3) መሰረት ባለመመዝገቡ በ3ኛ ወገን ላይ በመቃወሚያነት ሊቀርብ እንደማይችል ገልጾ ነዉ፡፡ በመሆኑም የተሰጠዉ ዉሳኔ የፍርድ ባለዕዳዎቹ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች መሆናቸዉን በተዘዋዋሪ መንገድ ያመለከተ ነዉ፡፡ በተጠቀሰዉ የመዝገብ ቁጥር ሰበር ሰሚ በሰጠዉ ዉሳኔ ማህበሩ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የለዉም አላለም፡፡ አመልካቾችም በዚህ መዝገብ ተከራካሪ አልነበርንም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የለዉም፡፡ ማህበሩ የአክሲዮን መተላለፉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት መመዝገቡን ብቻ በመግለጽ ሲከራከር ቆይቷል፡፡ ችሎቱም በጽ/ቤቱ ብቻ መመዝገቡ በቂ አለመሆኑን ገልጾ ዉሳኔ ሲሰጥ ደግሞ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ከማህበሩ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌላቸዉ በማስመሰል በቃለ-ጉባኤዉ የሚኒስትሩ መስሪያ ቤት ማህተም እንዲያርፍባቸዉ ጥያቄ ባቀረቡት መሠረት ማህተም ያረፈባቸዉን ቃለ ጉባኤዎች ለስር ፍ/ቤት በማቅረብ ምዝገባ እንደተከናወነ አድርገዉ የሚያቀርቡት ክርክር አግባብነት የለዉም፡፡

አመልካቾች በስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ በአግባቡ ታይቶና ተመርምሮ ዉሳኔ የተሰጠበት ነዉ፡፡ የአክሲዮን መተለለፍ የተደረገባቸዉን ቃለ ጉባኤዎች

በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበቡትን ቀን በንግድ መዝገብ የተመዘገቡበት ቀን እንደሆነ በማስመሰል እንዲሁም አቤቱታዉን ለፍ/ቤቱ ከማቅረባቸዉ ከአንድ ቀን በፊት ቃለ ጉባኤዎቹ በማህተም ተረጋግጦ እንዲሰጣቸዉ ጠይቀዉ የንግድ ሚኒስቴር ማህተም ያረፈባቸዉን ቃለ ጉባኤዎች በማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ ማህተም ማረፉ በንግድ ሕጉ ቁጥር 523 መሠረት በንግድ መዝገብ መመዝገብን አያረጋግጥም፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤት አክሲኖቹ በአግባቡ መታገዳቸዉ እና ማህበሩ ያካሄደዉ የአክሲዮን ማስተላለፍ በሕጉ መሰረት በአግባቡ አለመመዝገቡ ተረጋግጦ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡

አመልካቾች በበኩላቸዉ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዙ ጭብጦች አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ የፍርድ ባለዕዳዎች በዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ዉስጥ የነበራቸዉ የአክሲዮን ድርሻዎች የታገዱ መሆኑን፤ የፍርድ ባለዕዳዎች በማህበሩ ዉስጥ የነበራቸዉን አክሲዮኖች በሽያጭ ለአመልካቾች የ1ኛ የፍርድ ባለዕዳ 750 አክሲዮኖች መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም፣ 26 አክሲዮኖች ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም እና 24 አክሲዮኖች የካቲት 19 ቀን 2005 ዓ.ም እንዲሁም የ2ኛ የፍርድ ባለዕዳ አክሲዮኖች ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም የተላለፉበት ቃለ-ጉባኤ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ተመዝግቦ የተላለፈ መሆኑ፤ ማህበሩ በስር ፍ/ቤት በተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ቤቱ መታገዱን ገልጾ የፍርድ ባለዕዳዎች የአክሲዮን ድርሻቸዉን ለሌሎች ሰዎች አስተላልፈዉ ከማህበሩ በመልቀቃቸዉ የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳለት ጠይቆ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 103472 መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የአክሲዮን መተላለፉ በንግድ ሚኒስተር በንግድ መዝገብ አልተመዘገበም በማለት በንግድ ሕግ ቁጥር 522 እና 523 መሰረት የአክሲዮን ሽያጩ እስኪመዘገብ ድረስ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ስለማይችል የእግድ ትዕዛዙ ሊነሳ አይገባም በማለት የወሰነ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ነዉ፡፡

አመልካቾች የፍርድ ባለዕዳዎች የአክሲዮን ድርሻ በሀራጅ ተሸጦ ለተጠሪ ይከፈል ተብሎ የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት የፍርድ ባለዕዳዎች የነበሩ አክሲዮኖች በሽያጭ አስቀድሞ የተላለፉላቸዉና መተላለፋቸዉም በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ጽ/ቤት እና በንግድ ሚኒስቴር የንግድ መዝገብ የተመዘገበ በመሆኑ የአፈጻጸም ትዕዛዙ እንዲነሳ ሲሆን የስር ፍ/ቤት የአፈጻጸም ትዕዛዙ ሊነሳ አይገባም በማለት ለሰጠዉ ዉሳኔ በዋናነት የሰጠዉ ምክንያት የፍርድ ባለዕዳዎች የአክሲዮን ድርሻቸዉን ለአመልካቾች በሽያጭ ያስተላለፉበት ቃለ-ጉባኤ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ ቢሆንም በንግድ ሕግ ቁጥር 522 እና 523 አግባብ የፍርድ ባለዕዳዎች አክሲዮን በሽያጭ እንዳይተላለፍ በስር ፍ/ቤት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም ከተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ በፊት በንግድ ሚኒስቴር የንግድ መዝገብ መመዝገቡን

የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካለመቅረቡም በላይ በሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 103472 የአክሲዮኖች ማስተላለፍ ሂደት በአክሲዮኖች መዝገብ አለመመዝገቡን ያረጋገጠበት ነዉ በማለት የአመልካቾችን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉን ነዉ፡፡ አመልካቾች አጥብቀዉ የሚከራከሩበትም ሆነ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ አብይ ጭብጥ የስር ፍ/ቤት ክርክር ያስነሱ የማህበሩ አክሲዮኖች ወደ አመልካቾች በሽያጭ መተላለፋቸዉ የፍርድ ባለዕዳዎች አክሲዮኖች ወደ 3ኛ ወገን እንዳይታለፉ በስር ፍ/ቤት የእግድ ትዕዛዝ ከመሰጠቱ በፊት በንግድ ሚኒስቴር አክሲዮኖች መዝገብ ላይ አልተመዘገበም በማለት የደረሰበት ድምዳሜም ሆነ የአመልካቾችን መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ሲሆን በተጨማሪም እንደአስፈላጊነቱ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዙ ሌሎች ጭብጦችን ጭምር ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

በመሠረቱ የንግድ ሕግ ቁጥር 522 የአክሲዮኖች መተላለፍ በጽሁፍ የተረጋገጠ መሆን አለበት፤ መተላለፉም በአክሲዮኖቹ መዝገብ ላይ ካልተጻፈ በቀር ማህበሩና ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን አይችልም በማለት ሲደነግግ ቁጥር 523(3) ደግሞ አክሲዮን የተላለፈለት ለማህበሩ ባዕድ ለሆነ ሰዉ ሲሆን ማህበርተኞቹ የተስማሙበት ዉሳኔ በንግድ መዝገብ ላይ እንዲመዘገብ ያስፈልጋል በማለት በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ የአክሲዮን መተላለፍ ገዥና ሻጭን ለማስገደድ በጽሁፍ መደረግ ያለበት ሲሆን ማህበሩን ለማስገደድና የተላለፈለት ሰዉ በባለአክሲዮንነት ሙሉ መብት ለመጠቀም ስለአክሲዮን መተላለፉ ማህበርተኞች የተስማሙበት ዉሳኔ በአክሲዮኖች መዝገብ ሊመዘገብ ይገባል፡፡ እንዲሁም በ3ኛ ወገኖች ላይ እንደመቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለዉ የአክሲዮኖቹ መተላለፍ በንግድ ሚኒስቴር የአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ሲመዘገብ ነዉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ከዚህ ቀደም አሁን ክርክር ባስነሱ አክሲዮኖች መተላለፍ ላይ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 103472 ግልጽ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ የአክሲዮኖች መተላለፍ በ3ኛ ወገን ላይ መቃወሚያ ሊሆን የሚችለዉ ስለአክሲዮኖች መተላለፍ ዉል ሲኖር ወይም ማህበርተኞቹ የአክሲዮኖችን መተላለፍ ተቀብለዉ የተስማሙበት ሰነድ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ተረጋግጦ መመዝገቡ ሳይሆን በአክሲዮኖች መዝገብ መመዝገቡ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካቾች አክሲዮኖቹ የተላለፉላቸዉ መሆኑ በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበዉም ሆነ በንግድ ሚኒስቴር በአክሲዮኖች መዝገብ የተመዘገበዉ የስር ፍ/ቤት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ነዉ የሚለዉን ክርክር ለማረጋገጥ ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃዎች ማህበሩ የፍርድ ቤቱ የዕግድ ትዕዛዝ እንደደረሰዉ በቁጥር ARD/316/05 በ05/09/2005 ዓ.ም በጻፈዉ ደብዳቤ የፍርድ ባለዕዳዎቹ የማህበሩ አባል እንዳልሆኑና የአክሲዮን ድርሻ የሌላቸዉ መሆኑን የገለጸበት፤ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የፍርድ ባለዕዳዎች አክሲዮኖች ወደ አመልካቾች በሽያጭ መተላለፋቸዉን የሚገልጸዉ ቃለ-ጉባኤ በቁጥር ዋ/መ/5992/4ለ/05 ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም የተመዘገበበት እና የንግድ ሚኒስቴር መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም ለዶዶላ ኢንተርናሽናል ትራዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በጻፈዉ ደብዳቤ ማህበሩ በ1998 ዓ.ም ሲቋቋም ጀምሮ የንግድ ምዝገባና

ፈቃድ አወጥቶ በመስራት ላይ መሆኑንና በተለያዩ ጊዜያት ማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ ለዉጡንና የአክሲዮን ማስተላለፍ የሚያደርግባቸዉን ቃለ-ጉባኤ በማጸደቅ የተመዘገበ መሆኑን ጠቅሶ፤ የቀረቡት ቃለ-ጉባኤ ሰነዶችም ማህተም አርፎና ተረጋግጠዉ የተመዘገቡ መሆኑን የገለጸበት ናቸዉ፡፡ ከእነዚህ ሰነዶች መካከል በንግድ ሕጉ ቁጥር 522 መሠረት የአክሲዮን መተላለፉ በ3ኛ ወገኖች መቃወሚያ በሚሆን መልኩ በአክሲዮኖች መዝገብ ላይ በስር ፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ከተሰጠበት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በፊት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የለም፡፡ ይህን ማስረጃ የማቅረብና የማስረዳት ኃላፊነት የአመልካቾች ሲሆን የአክሲዮን መተላለፉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ጥር 01 ቀን 2005 ዓ.ም መመዝገቡ እንደተረጋገጠ ሁሉ በአክሲዮኖች መዝገብ የተመዘገበበትን ግልጽ ቀን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ በቻሉ ነበር፡፡ የስር ፍ/ቤት የቀረቡለትን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ የአክሲዮኖች መተላለፍ ፍ/ቤቱ ዕግድ ከሰጠበት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በፊት በአክሲዮኖች መዝገብ መመዝገቡ አልተረጋገጠም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ካለመኖሩም በላይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃን ለመመዘንና ፍሬ ነገርን ለማረጋገጥ ስልጣን የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች ከደረሰቡበት የፍሬ ነገር ድምዳሜ ዉጪ ማስረጃ ለመመዘንና ፍሬ ነገርን ወደ ማረጋገጥ የሚገባበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

ክርክር ያስነሱ አክሲዮኖች ወደ አመልካቾች በሽያጭ የተላለፉት በስር ፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ከተሰጠበት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በፊት ቢሆንም በአክሲዮኖች መዝገብ አለመመዝገቡ በስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠዉ አንጻር ሲታይ በንግድ ሕግ ቁጥር 522 እና 523(3) መሠረት የአክሲዮን ሽያጩ በተጠሪ ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ምንም እንኳ የአክሲዮን ሽያጩ የተከናወነዉም ሆነ የማህበሩ አባላት ተስማምተዉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበዉ ተጠሪ በአክሲዮኖቹ ላይ የዕግድ ትዕዛዝ ካሰጠበት መጋቢት 24 ቀን 2005 ዓ.ም በፊት ቢሆንም ከዚህ ቀን በፊት በአክሲዮኖች መዝገብ ላይ መመዝገቡ አለመረጋገጡን በመግለጽ አመልካቾች አክሲዮኖች በሀራጅ ተሸጠዉ ለተጠሪ እንዲከፈሉ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲነሳ ያቀረቡትን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል በተያዙ ሌሎች ጭብጦች ላይ ምላሽ መስጠቱ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ ታልፏል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት የፍርድ ባለዕዳዎች የነበሩ የዶዶላ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር አክሲዮኖች በስር ፍ/ቤት በተሰጠ ዕግድ ትዕዛዝ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፉ ከመታገዱ በፊት አክሲዮኖቹ ለአመልካቾች በሽያጭ ስለመተላለፋቸዉ በንግድ ሚኒስቴር የአክሲዮን መዝገብ ላይ ስለመመዝገቡ አልተረጋገጠም በማለት የአመልካቾችን መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉ የንግድ ሕግ ቁጥር 522 እና 523(3) ድንጋጌዎችንና እነዚህን ድንጋጌዎችን አስመልክቶ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 103472 በተመሳሳይ አክሲዮኖች በሽያጭ መተላለፍ ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም ያገናዘበ በመሆኑ

ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 142286 ጥቅምት 01 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መ/ቁ 149467 ታሕሳስ 10 ቀን 2010 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰበር መ/ቁ/188419

መስከረም 25 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኘ

አመልካች፡- አባይ ባንክ አ.ማ

ተጠሪ፡- አቶ ማርቆስ ጋትሮ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ በሃዋላ የተላከ ገንዘብ ባንኩ ለማይገባ ሰዉ ከፍሏል በሚል ባንኩ ሃላፊ መደረጉን የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ ፤የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡መዝገቡ እንደሚያሳየዉ የተጠሪ የክስ ምክንያት እ.ኤ.አ በ10/12/2018 ወይም እ.ኤ.አ በ01/04/2011 ዓ.ም ከሊባኖስ ሀገር እህቱ በአሰሪዋ በአቶ ኤልያስ ኢልሀበር አማካይነት በዌስተርን ዩኒየን ገንዘብ መላኪያ አማካኝነት 675 የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ ምንዛሪ ብር 18,839 የላከችለት ገንዘብ አመልካች ለማይገባው ሰው ስለከፈለ ገንዘቡ ለእኔ የተላከ ስለመሆኑ ከኢትዮ ቴሌኮም ማረጋገጫ የተቀበልኩ በመሆኑ በቸልተኝነት ለሌላ ሰው የከፈለውን ገንዘብ ከወለድና ወጪ ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ የሰጠው መልስ ተጠሪ የሚጠበቅባቸውን ህጋዊነትን በማረጋገጥ የደረሳቸውን ግላዊ ሚስጥር ቁጥር ኮድ ይዘው በማቅረባቸው ባንኩ ባለው አሰራር ክፍያውን ለሚገባው ሰው በ02/04/2011ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ገላን ኮንዶሚኒየም ቅርንጫፍ ለተጠሪ ከፍሏል፣ስለዚህ ከውጭ ሀገር ገንዘብ ሲላክ ለተቀባይ ግለሰብ የሚደርሰው ሚስጥር ቁጥርና የሚጠይቅ ልዩ ኮድ ያለ ሲሆን በዚሁ መሰረት ክፍያ የተፈፀመ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ክሱን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የወላይታ ሶዶ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ገንዘቡን አድራሻዉና ማንነቱ ላልታወቀ ሰው ያለአግባብ የከፈለ መሆኑን በማስረጃ ስለተረጋገጠ አመልካች

ለተጠሪ የተላከለትን ገንዘብ የመክፈል ሃላፊነት አለበት በማለት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት አፅንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ያቀረበው ቅሬታ ይዘት ባጭሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ባንኮች በየትኛውም ግለሰብ ስም በዌስተርን ዩኒየን አማካኝነት ገንዘብ የተላከለት ሰው የመረጠው ባንክ በአካል ቀርቦ ክፍያ እስኪጠይቅበት ድረስ በግለሰቡ ስም ገንዘብ ስለመላኩ እና ስለተላከለት ገንዘብ መጠን ሊያውቅ የሚችልበት ምንም አይነት መንገድ የለም፡፡በዚሁ መሰረት ባንኮች ክፍያ የሚፈፅሙት ገንዘቡ በስሙ የተላከለት ሰው የገንዘብ መቀበያ የሚስጥር ቁጥር እና ማንነቱን የሚያሳይ መታወቂያ ይዞ ለቀረበ ሰው ነው፡፡ይህ የሚሆነው ገንዘብ የተላከለት ሰው ወይም ገንዘብ የላከው ሰው የሚስጥር ቁጥር ለሌላ ሶስተኛ ሰው አሳልፎ ይሰጣሉ ተብሎ ስለማይገመት እና አሳልፎ ከሰጡም መቆጣጠሪያ ዘዴ ስለማይኖር ነው፡፡ገንዘቡ ከተላከለት ሰው ጋር ትክክለኛ የሚስጥር ቁጥር ለባንኩ በማቅረብ ለተፈፀመ ክፍያ ባንኩ ያለአግባብ ለማይመለከተው ሰው ክፍያ ፈፅሟል የሚያስብል አይደለም፡፡ተጠሪ ማንነታቸውን የሚያሳይ የቀበሌ መታወቂያ እና የሚስጥር ቁጥር ይዘው በመቅረባቸው አመልካች የተላከለት ገንዘብ ክፍያ ፈፅሟል፣ከተጠሪ ውጪ የሚስጥር ቁጥሩ ሊያውቅ የሚችል ሌላ ሰው የሌለ በመሆኑ አመልካች ክፍያውን የፈፀመው የባንክ አሰራር ተከትሎ ስለሆነ ክፍያ የተፈፀመው ላልተገባ ሰው ነው ተብሎ የተሰጠዉ ውሳኔ ስህተት በመሆኑ ተሽሮ አመልካች ገንዘቡን ለመክፈል ሃላፊነት የለበትም በማለት እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዌስተርን ዩኒየን አማካኝነት ገንዘብ የተላከለት ሰው በአካል ቀርቦ ክፍያ እስኪጠይቅ ድረስ በግለሰቡ ስም ገንዘብ ስለመላኩና ስለተላከው ገንዘብ መጠን ሊታወቅ የሚችልበት መንገድ እንደሌለ፣ገንዘብ በስሙ የተላከለት ሰው የገንዘብ መቀበያ የሚስጥር ቁጥር እና ማንነቱን የሚያሳይ መታወቂያ ይዞ ቀርቦ መክፈሉ በተረጋገጠበት ሁኔታ ክፍያው የተፈፀመው ለሌላ 3ኛ ወገን ነው ተብሎ አመልካች በድጋሚ ይክፈል የመባሉን አግባብነት ከባንክ አሰራር ሂደት አንፃር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

በተጠሪ በኩል የቀረበው መልስ ባጭሩ በስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማጣራት የሰውና የሰነድ ማስረጃ በማቅረብ አመልካች ገንዘቡን ከፍሎለታል ለተባለው ግለሰብ በትክክል የወላይታ ዞን ዳሞት ፑላሣ ወረዳ የሌራ ቀበሌ ነዋሪ መሆኑ አለመሆኑን ለማጣራት በወቅቱ ያቀረበው መታወቂያ ወረቀት ላይ የፈረሙትና የታተመው ማህተም ህጋዊ መሆን አለመሆን ለማጣራት የቀበሌው አስተዳደርና የቀበሌዉ ስራ አስኪያጅ በሰጡት ምስክርነት ቃላቸው ግለሰቡ የሌራ ቀበሌ ነዋሪ አለመሆኑ ተገቢ ማጣራት በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ስህተት አልተፈፀመም፡፡ገንዘቡ ለእኔ እንደተላከ በተጠሪ ስልክ

የተላከውን መልዕክት ከኢትዮ ቴለኮም ወደ ወረቀት ተቀይሮ በመጣ ማስረጃ ተረጋግጧል፣የሚስጥር ቁጥር በተመለከተ ቀደም ብሎ የሚስጥር ቁጥሩ ለባንኩ ስለሚደርስና ተቋሙ ከፍቶ የማየት እድል ከፍተኛ ስለሆነ ገንዘቡን እንደፈለገ እንዲያደርግ የሚከለክል የለም፡፡ የሚስጥር ቁጥር ይዞ የሚመጣ ሰው ማንነት በሚገባ የማረጋገጥ ሃላፊነት የአመልካች ሆኖ እያለ የክፍያ ሂደት ላይ በተገቢዉ ሳያጣራ መረጃዎችን በአግባቡ መፈተሽ ሲገባ ለእኔ የተላከውን ገንዘብ ባልታወቀ ሁኔታ ለሌላ ሰው ስለከፈለ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የህግ ስህተት የለውም ተብሎ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዘዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነው ለክሱ ምክንያት የሆነዉ ገንዘብ በአመልካች በኩል ለተጠሪ እንዲከፈል በሃዋላ የተላከ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡የሥር ፍርድ ቤት ገንዘቡ የተከፈለለት ሰዉ ይዞ የቀረበዉ መታወቂያ ከተባለዉ ቀበሌ አስተዳደር የተሰጠ አለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ገንዘቡ ለተገቢዉ ሰዉ አልተከፈለም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን የዉሳኔዉ ይዘት ያሣያል፡፡አመልካችም አጥብቆ የሚከራከረዉ ክፍያ የተፈጸመዉ በባንኩ አሰራር መሰረት በተገቢዉ መረጃ ማጣራት ተደርጎ ስለሆነ በሃላፊነት የሚያስጠይቅ ጥፋት የለም በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ የደንበኞችን ገንዘብ በሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጪ ማስተላላፍ ስራ ከባንክ ስራዎች አንዱ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 2/2/መ/ ላይ ተመልክቷል፡፡ባንክ በአደራ የተቀበለውን የደንበኛውን ገንዘብ የመጠበቅ ህጋዊ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በንግድ ህጉ ከቁጥር 896 እስከ 902 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ሲታይ ባንኩና ደንበኛው የአደራ ስምምነት ውል መግባታቸውን በመግለጽ በውሉ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር ባንኩ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ ለታዘዘለት ሰዉ የማድረስ ወይም ለባለአደራዉ የመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ባንኩ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ ማለትም የደንበኛውን ገንዘብ የባንክ ስራ የሚጠይቀውን አሰራርና ስርዓት በመከተል መጠበቅና ሲጠይቅም ገንዘቡን መክፈል ነው፡፡ባንክ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በደንበኛው ገንዘብ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተጠያቂነት የሚኖርበት መሆኑንም ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ባንኩ የደንበኛውን መብትና ጥቅም ማስከበር የሚገባው ተገቢውን ጥንቃቄ ወይም የተለመደ አሠራር በመከተል እንዳለበት በሌላ በኩል ባልተገባ መንገድ በደንበኛው ገንዘብ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ መከላከል ጭምር በህግ ግዴታ የተጣለበት ስለመሆኑ እና እዉነታዎችን በማረጋገጥ ረገድ ተገቢዉን ትጋት ማድረግ ያለበት መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 53 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ክፍያ የፈጸመዉ አስፈላጊዉን መረጃ ከገንዘብ ጠያቂዉ በማጣራት ስለመሆኑ በተለይም የላኪዉን ማንነት፣የተላከዉን ገንዘብ መጠን እና የሚስጥር ቁጥር ገንዘቡን ለመቀበል ከቀረበዉም ሰዉ በማረጋገጥ ክፍያ የፈጸመ ስለመሆኑ አላከራከረም።የስር ፍርድ ቤትም እነዚህ ፍሬ ነገሮች ከማጣራት አንጻር ባንኩ ስህተት ፈጽሟል አላለም።ነገር ግን ፍርድ ቤቱ አመልካችን ሃላፊ ያደረገዉ በዋናነት ተከፋዩ ወይም ገንዘቡን ተቀብሏል የተባለዉ ሰዉ ተጠሪ ሳይሆን በተጠሪ ስም ሀሰተኛ የቀበሌ መታወቂያ ይዞ የቀረበ ሌላ ሰዉ ነዉ በማለት ነዉ።ባንኩ ክፍያ የፈጸመዉ በባንኩ ያለዉ መረጃ ገንዘቡን ለመቀበል ከቀረበዉ ሰዉ መረጃ በማጣራት ስለመሆኑ እና የተላከለት ሰዉ ማንነት መታወቂያዉን በመመልከት በማገናዘብ አረጋግጦ ስለመሆኑ ይህም በባንኩ የተለመደዉ አሰራር መሰረት የተፈጸመ መሆኑን በመግለጽ ሃላፊነት እንደሌለበት አጥብቆ ተከራክሯል። በመሰረቱ ባንኩ የተከፋዩን ማንነት ለማረጋገጥ መታወቂያዉ የቀበሌዉ ማህተም የተደረገበት እና የሚመለከተዉ ሃላፊ ስምና ፊርማ ያለበት መሆኑን በምልከታ ከማረጋገጥ በስተቀር ማህተሙ የቀበሌዉ ነዉ ወይስ አይደለም፤ፊርማዉ የሚመለከተዉ ሃላፊ ነዉ ወይስ አይደለም በሚል ተጨማሪ ምርመራ እንዲያደረግ የሚያስገድድ የህግ ምክንያት የለም። የባንክ የስራ ባህርይም ይህንን የሚፈቅድ አለመሆኑ ይታወቃል።ባንኩ ክፍያ ሲፈጽም በዋናነት እንዲያረጋግጥ የሚጠበቀዉ ተከፋዩ ሰዉ ብቻ ያዉቀዋል ተብሎ የሚገመተዉን ፍሬነገር ማለትም ገንዘቡን የላከዉ ሰዉ ማንነት፤የተላከዉ ገንዘብ መጠን፤የሚስጥር ቁጥር እና የተላከለት ሰዉ ስም ነዉ።እነዚህ ፍሬ ነገሮች በባንኩ ካለዉ መረጃ ጋር በማዛመድ ተመሳሳይ መሆናቸዉ ከተረጋገጠ መረጃ ይዞ የቀረበዉ ሰዉ ትክክለኛ ተከፋይ ነዉ ተብሎ እንደሚታሰብ እና ገንዘብ ተቀባዩን ማንነት የሚያሳይ መታወቂያ አቅርቦ እንዲከፈለዉ ከታዘዘለት ሰዉ ስም ጋር አንድ መሆኑ ከታወቀ ባንኩ ተገቢዉን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቷል ተብሎ ተጠያቂ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የለም።በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መ/ቁ/ 41535 ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ እንደሚያሳዉ ባንኩ የተለመደዉን አሰራርና ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርጎ ክፍያ ከፈጸመ የሰነዶቹን ህጋዊነት አላረጋገጠም ተብሎ በድጋሚ እንዲከፍል ሃላፊነት የለበትም ሲል ዉሳኔ መስጠቱን ልብ ይለዋል።

ስለሆነም ተከፋዩ ይዞ የቀረበዉ መታወቂያ ላይ ያለዉ ፊርማ እና ማህተም የቀበሌዉ አይደለም የሚል በሰዉ ምስክር ከመገለጹ ዉጪ ሌሎቹ መረጃዎች ማለትም የተላከዉ ገንዘብ መጠን፣የላኪዉ ስም እና የሚስጥር ቁጥሩ እንዲሁም ተከፋይ ሰዉ ስም ስህተት ነዉ አልተባለም።እነዚህ አስፈላጊና ወሳኝ መረጃዎች ከተከፋዩ ሌላ ሰዉ ሊያዉቅ የሚችልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ባንኩ ለማይገባዉ ሰዉ ክፍያ ፈጽሟል ሊባል አይችልም።በዚህም ሁኔታ ለማይገባ ሰዉ ተከፍሎ ቢሆን እንኳን የተታለለዉ መረጃዉን ያለአግባብ ያባከነዉ ተጠሪ ነዉ ከሚባል በስተቀር ባንኩ ነዉ ሊባል አይችልም።

ሲጠቃለል አመልካች ክፍያ የፈጸመዉ በባንኩ የተያዙት መረጃዎች እና ተከሳዩ ሰዉ የሰጠዉ መረጃ ተዛማጅና ትክክል መሆናቸዉ በተለመደዉ አሰራር መሰረት በማረጋገጥ እስከሆነ ድረስ ክፍያዉን የተቀበለዉ በተጠሪ ስም ሀሰተኛ የቀበሌ መታወቂያ ይዞ የቀረበ ሌላ ሰዉ ነዉ በሚል ምክንያት ባንኩ ድጋሚ ገንዘቡን ለተጠሪ እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ስለባንክ ክፍያ አፈጻጸም የተለመደዉን አሰራር እና የተረጋገጡ መሰረታዊ ፍሬ ነገር ጉዳዮችን እንዲሁም ህጉን ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 43492 ላይ በ21/02/1012ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና ይህንኑ በማጽናት የደ/ብ/ብ/ህ/ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/32198 ላይ 17/04/2012ዓ.ም የሰጠው ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

ው-ል

የሰበር መዝገብ ቁጥር 161153

ሚያዝያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተክሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-ወጋገን ባንክ አ.ማ. ነ/ፈጅ ቢኒያም ትዕግስቱ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢትዩጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ነ/ፈጅ ሠላም ሠጠኝ አደራ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ለዚህ የሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በግልግል ዳኞች ጉባዔ ሲሆን አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ እና የተከሣሽ ከሣሽ በመሆን የተከራከሩ እና ክርክሩም መሠረት ያደረገው የቤት ኪራይን መነሻ በማድረግ ነው፡፡

አመልካች አቅርቦት የነበረው ክስ የሚያሳየው ከተጠሪ ላይ ለባንክ አገልግሎት የሚውል ቤት በወር በብር 33,890.05 / ሰላሳ ሶስት ሺ ስምንት መቶ ዘጠና ብር ከዜሮ አምስት ሣንቲም / ተከራይቶ የ6 ወር ክፍያ በአንድ ጊዜ መክፈሉን እና ቤቱን ለሥራ አመቺ ለማድረግ ሲሞክር የክ/ከተማ መሬት ማኔጅመንት የግንባታ ፈቃድ የላችሁም በሚል ሥራውን በ16/04/2008 ዓ.ም. አስቁሟል፡፡

ተጠሪ/ተከሣሽ/ የግንባታ ፈቃድ እንዲጠይቅና እንዲያስፈቅድ ብንጠይቀውም ፈቃደኛ ባለመሆኑ የውል መሠረታዊ አላማ እንዳይፈፀም ያደረገ በመሆኑ የግንባታ ፈቃድ እንደማያገኝ ቀድሞ ቢያውቅ ኖሮ የማይዋዋል በመሆኑ፣ የተከራየውንም ቤት እንዳልተጠቀምኩበት እያወቀም ውዝፍ ኪራይ እንደሚጠይቅ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኝ ውሉን አቋርጧል፡፡

በመሆኑም ቅድሚያ ክፍያ የከፈልኩትን ብር 203,343.00 /ሁለት መቶ ሶስት ሺ ሶስት መቶ አርባ ሶስት ብር/ እና ቤቱን ለማስተካከል ያወጣሁትን ወጪ ብር 37,956.02/ ሰላሳ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አምሳ ስድስት ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ በድምሩ ብር 241,299.02 /ሁለት መቶ አርባ አንድ ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ ማስጠንቀቂያ ከሰጠሁበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሣሽ በሰጠው መልስ ቤቱን ማከራየቱ እውነት ነው ከሣሽ የተከራየውን ቤት ተረክቧል ለአገልግሎት የማዋል የራሱ ኃላፊነት ነው፡፡ የተከራየውን ቤት ከጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም.ጀምሮ ለአገልግሎት ማዋል ይገደዳል፡፡ ለክፍሎች ማሻሻያ ያወጣውን ተከሣሽ አይሸፍንም፡፡ በውሉ ላይ ስለማሻሻያ ፍቃድ ስለማስገኘት ቀድሞ አልተደራደረም፡፡ በመሆኑም ለ10 ወራት የተከራየውን ቤት ይዞ የኪራይ ገንዘብ ይመልስልኝ ያለው ተቀባይነት የለውም ፡፡ ቤቱን ሲረከብ ለባንክ አገልግሎት እንደሚያውል ስለማመኑ የውሉ አንቀጽ 3 ያሳያል፣ ለከሣሽ እድሳት እንዲፈቀድ የበኩሌን ጥረት አድርጌያለሁ በመሆኑም ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሣሽ በበኩሉ ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ የተከራየውን ቤት ጣራ እና የአንድ ጐን ግድግዳ ወደ ነበረበት ሊመልስ ስለሚገባ ብር 60,530.00 ወደ ነበረበት ለመመለስ ወጪ ያደረኩ በመሆኑ፣ የጥገናው ሥራ ተጠናቆ ወደ ሥራ ሊገባ የቻለው ጥቅምት 16/2009 ዓ.ም. በመሆኑ ቤቱ በነበረበት ተረክቤ ቢሆን ከሣሽ እንደለቀቀ ወዲያው አከራይቼ አገኝ የነበረ ቢሆንም እስከ ጥቅምት 2009 ሊቆይ የቻለው በከሣሽ ተከሣሹ ባፈረሰው ክፍል ምክንያት በመሆኑ ከሐምሌ 27 ቀን 2008 እስከ ጥቅምት 16 ቀን 2009 ዓ.ም. ድረስ ኪራይ ሊከፍል ስለሚገባ፣ ያልከፈለውን የ4 ወር ኪራይ ብር 135,562.00፣ የፈረሰው ቤት ወደ ነበረበት እስኪመለስ እና እስኪከራይ ያጣሁት ኪራይ ብር 84,726.25፣ ቤቱን ወደነበረበት ለመመለስ ያወጣሁት 60,530.00፣ በአጠቃላይ 280,818.25/ ሁለት መቶ ሰማንያ ሺ ስምንት መቶ አስራ ስምንት ብር ከሣያ አምስት ሣንቲም/ ከግልግል ጉባኤው የዳኝነት ወጪ ጋር ይክፈለኝ ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የከሣሽ ተከሣሽ መልስ ያቀረበ ሲሆን ቤቱን ለባንክ አገልግሎት በሚውል መልኩ በራሱ ወጪ ተገቢውን እድሳት ለማድረግ ግዴታ ገብቷል፡፡ ይህንንም አከራይ የሆነው የተከሣሽ ከሣሽ በውሉ እውቅና በመስጠት በጉዳዩ ላይ በህግ የሚጣሉበትን ሀላፊነቶች ለመወጣት ግዴታ ገብቷል፡፡ ይህ የውል ግዴታ በአግባቡ እንዲፈፀም የተከሣሽ ከሣሽ እንደ ንብረቱ ባለቤት የሚመለከተው የመንግሥት አካል ተገቢውን የግንባታ ፍቃድ የማውጣት በህግ የተጣለበት ግዴታ ያለበት ቢሆንም ግዴታውን አልተወጣም፡፡

ከዚህም የተነሳ በውሉ አፈፃፀም ላይ አይነተኛ እና መሠረታዊ ውል መጣስ ከተከሣሽ ከሣሽ በኩል የተፈፀመ በመሆኑ የኪራይ ውል ፈርሶ ግራ ቀኛችን ወደነበርንበት ሁኔታ መመለስ አለብን፣ ያልተከፈለ

የኪራይ ክፍያ ይከፈለኝ ጥያቄ አግባብነት የለውም፣ የተከሣሽ ከሣሽ የግንባታ ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል እንዲያወጣ በማሳሰብ ቤቱን የማስተካከል ሥራው ከቆመበት ከ16/4/2008 ዓ.ም. ጀምሮ ያለው የቤት ኪራይ ክፍያ የከሣሽ ተከሣሽ ያልተጠቀመበት መሆኑን እንዲያውቅ በጽሁፍ ያሳወቀ በመሆኑ ሲታይ የተከሣሽ ከሣሽ ጥያቄ አግባብነት የለውም፣ ወደ ነበርንበት የምንመለስ ከሆነ ደግሞ ለ3ኛ ወገን ቤቱ ባለመከራየቱ ሊከፈል ይገባል በማለት የቀረበው ተገቢ አለመሆኑን፣ ቤቱ ወደ ነበረበት ለመመለስ ወጣ የተባለው ብር 60,530.00 ማን እንደገመተው የማይታወቅ መሆኑ ለቀረበው የተከሣሽ ተከሣሽነት ክስ ከሣሽ ተጠያቂ ሊሆን አይገባም በማለት መልስ አቅርቧል።

ጉባዔው የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ 4 ጭብጦችን ይዞ ጉዳዩን የመረመረ ሲሆን በዚሁ መሠረት፡-

1. ተከራይ የተከራየውን ቤት ለባንክ ሥራ ሳይጠቀምበት የቀረው በማን ጥፋት ነው? የሚለውንን ጭብጥ አስመልክቶ ፡- በውሉ ላይ ስለ ግንባታ ፈቃድ ማስገኘት አለማስገኘት የተቀመጠ ነገር የሌለ መሆኑን፣ የተከራየው ቤት የግንባታ ፈቃድ ያስፈልገው እንደነበረ የሚያውቅ ሆኖ ነገር ግን ተከሣሽ ፈቃዱን ከሚመለከተው አካል ተከሣሽ ያስገኝልኛል የሚል እምነት የነበረው በመሆኑ መሆኑን በቃል ክርክር ከሣሽ ማስረዳቱን፣ ሆኖም በውሉ አንቀጽ 9/2 በተከሣሽ ላይ አንዣራዊ ግዴታን የሚጥል መሆኑን በልማድም ፣ፍትሕ ቅን ልቦና እና የውሉ አይነት የሚያስከትሉትን ነገሮች ጭምር መሆኑን እንዲሁም በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 አንቀጽ 4/4 መሠረት የግንባታ ፈቃድ የሚጠይቀው ባለንብረቱ ከመሆኑ አንፃር በውሉ ባይገለፅም በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1713 መሠረት በልማድና በአሰራር የግንባታ ፈቃድ የመጠየቅ ግዴታ የአከራዩ/የተከሣሽ በመሆኑ የግንባታ ፈቃድ የመጠየቅ ግዴታ አከራይ የሚኖርበት መሆኑን፣ ነገር ግን የግዴታው ባህሪን አስመልክቶ የግንባታ ፈቃዱን ለማስገኘት ተገቢ ትጋት ማድረግ ወይስ ፍቃዱን ማግኘት ነው የሚለውን ስንመለከት አከራይ ፍቃድን ለማግኘት ትጋት ማድረግን እንጂ ፈቃድ መስጠቱ በ3ኛ ወገን እጅ ያለ ነገር በመሆኑ ፈቃድ የማስገኘት ግዴታ የሌለበት በመሆኑ ከሣሽ ከተከራየሁ በኋላ ሣልጠቀም የቀረሁት በተከሣሽ ጥፋት ነው በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በሚል ወስኗል።
2. ተከራይ ቤቱን ከተረከበ በኋላ ለተከራየበት ዓላማ ሳይጠቀም መቅረቱ ውሉ ጸንቶ እስከቆየበት ጊዜ ድረስ ያለውን ኪራይ ላለመክፈል በቂ ምክንያት ሊሆን ይችላል ወይስ አይችልም ? በሚል ለተያዘው ጭብጥ ውሉ በግራ ቀኙ መፈረሙን አለመካካዳቸውን፣ ከሣሽ ውሉ በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው ቢልም በሁኔታ ላይ ግን የተመሠረተ ውል አለመሆኑን፣ ለዚህም የውሉ አንቀጽ 4.1 ላይ የተገለፀው ኃይለ ቃል የሚያሳይ መሆኑን፣ ከሣሽም ቤቱን ተረክቦ ይዞ እንደነበረ አለመካዱን፣ ቤቱን በመያዜ ብቻ ሳይሆን አድሼ ሥራ ላይ ሳውል ነው በማለት ከሣሽ ያነሳውን በተመለከተ ውሉን ሲዋዋል ገና ቤቱን ማሻሻል እንዳለበት የሚያውቅ መሆኑን፣

እድሳት የጀመረው ተከሣሽን ፈቃድ እንዲያወጣለት ሳይጠይቅ መሆኑ፣ የግንባታ ፈቃድ አለመገኘት የሚያስከትለውን ኃላፊነት አውቆ አመዛዝኖ እና ተቀብሎ ወደ ውል የገባ በመሆኑ የግንባታ ፈቃድ እንደማያገኝ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ከሣሽ ውሉን አቋርጦ ቤቱን ለአከራዩ መልሶ የሚደርስበትን ኪሣራ መቀነስ ሲገባው አከራይ ውሉን እስኪያቋርጥ ድረስ በዝምታ መቀመጡ ተገቢ እንዳልሆነ ገልጾ አስቀድሞ ተቀብሎ የነበረውን የኪራይ ገንዘብ ብር 203,343.00 ተከሣሽ ሊመልስ አይገባም፡፡ እንዲሁም ውዝፍ የቤት ኪራይ ብር 135,562.00 ከሣሽ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ሲል ወስኗል፡፡

3. የቤት ዕድሳትን አስመልክቶ ከሣሽ ያፈረሰውን ወደ ነበረበት የመመለስ ኃላፊነት ያለበት መሆን ያለመሆኑን አስመልክቶ ከውላቸው አንቀጽ 9/2/ አንፃር መርምሮ በአከራይ በኩል ያልተፈፀመ የውል ወይም የህግ ግዴታ የሌለ በመሆኑ የማሻሻያ ሥራው የተቋረጠው በ3ኛ ወገን ምክንያት መሆኑን፣ አከራይም የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የተቻለውን ጥረት ያደረገ በመሆኑ ለማሻሻያ ያወጣሁትን ብር 37,956.00 ተከሣሽ ሊተካልኝ ይገባል በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው፣በአንፃሩ የተከራየውን ቤት ለሥራው ለማዋል በሚል የቤቱን ጣራ፣ ወለል እና ግድግዳ ከሣሽ የማፍረስ ሥራ ጀምሮ የተቋረጠ በመሆኑ ተከራይ አከራይ ቤቱን ወደነበረበት ለመመለስ የሚያወጣውን ወጪ በገንዘብ ተተምኖ ሊካስ የሚችል በመሆኑ እናየመተካት ኃላፊነትም የከሳሽ መሆኑን ፣ በግምቱም መስማማቱን ተከራይ በደብዳቤ ስለገለፀ ብር 60,503.00 ለተከሳሽ ከሣሽ ሊከፍል ይገባል በሚል ወስኗል፡፡

4. ቤቱን ወደ ነበረበት ለመመለስ በፈጀው ጊዜ ውስጥ ሳይከራይ በመቅረቱ ተከራይ ለታጣው ገቢ ኃላፊነት አለበት የለበትም የሚለውን አስመልክቶ፡- የኪራይ ውሉ የፈረሰው በአከራይ ጥፋት ነው በማለት ተከራይ ይከራከር እንጂ ውሉ የተቋረጠው በተከራይ ጥፋት መሆኑ ድምዳሜ ላይ የተደረሰ በመሆኑ፣ እድሳት ሳይደረግለት ሊከራይ ይችላል ለማለት አዳጋች በመሆኑ ቤቱ ሳይከራይ የቀረው በአከራይ ጥፋት ነው ማለት ስለማይቻል እንዲሁም የኪራይ ውሉ የተቋረጠው ተከራይ የኪራይ ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ በውሉ አንቀጽ 19.1 እና 3 መሠረት የተከራይ አከራይ ጥፋት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2944 መሠረት አከራይ ቤቱን እንደገና ለማከራየት ለሚወስድበት ጊዜ ሊከፈል የሚገባውን የኪራይ ገንዘብ ተከራዩ እንዲከፍል የሚያስገድድ በመሆኑ የ2 ወር ተኩል ኪራይ ብር 84,726.25 ተከራይ/ከሣሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ጉባኤው ወስኗል፡፡

በውሣኔው ቅር ተሰኝቶ አመልካች ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታውን አልተቀበለውም፡፡

አመልካች በግልግል ጉባኤው ተፈጽሟል ያላቸውን የህግ ስህተቶች በመዘርዘር በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሐምሌ 09 ቀን 2010 ዓ.ም. የተፃፈ 4 ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ይዘቱም በአጭሩ፡- ተከራይ በውል የተሰጠውን የተከራየውን ቤት አድሶ እና አስተካክሎ የመጠቀም መብት እንዲሰራበት የግንባታ ፈቃድ ያላቀረበ አከራይ መሠረታዊ የውል መጣስ የፈፀመ በመሆኑ ውሉ በፍ/ህ/ቁ/ 1884 መሠረት ፈራሽ ሆኖ ተዋዋይ ወገኖች ውሉ ከመፈፀሙ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ ሲገባ ውዝፍ ኪራይ እንድከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፣ አመልካች በውል ያገኘውን መብት እንዲሰራበት እና የውሉም መሠረታዊ አላማ እንዲሳካ ተጠሪ በህግ የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣቱ መሠረታዊ የውል መጣስ ተፈጽሞ እና አመልካች ቤቱን በማደስ እና በማስተካከል ሂደት ውስጥ ያወጣው ገንዘብ ብር 37,956.02 ለኪሳራ ተዳርጎ እያለ የስር የዳኝነት አካላት ተጠሪን ይህንን ገንዘብ ሊተካ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፣ በተጠሪ በኩል የተፈፀመ የውል መጣስ የለም በሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶ የሁለት ወር ኪራይ እንድከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፣ተጠሪ ቤቱን ወደ ነበረበት ለመመለስ ያወጣውን ወጪ አመልካች እንዲተካለበት ያቀረበውን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አስመልክቶ ተጠሪ ባቀረበው የገንዘብ መጠን ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ሊያወጣ እንደሚችል ማመኑ ኃላፊነቱን ተቀበለ ማለት ባለመሆኑ የተፈፀመ የውል መጣስ በሌለበት ኃላፊ መባሌ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲል ሰፊ አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የተከራየውን ቤት ለተከራየበት አላማ ሳይጠቀምበት በመቅረቱ ውሉ ጸንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ተከራይ የቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ አለበት መባሉ የኪራይ ውሉ አፈጻጸም በሁኔታ ላይ የተመሰረተ አይደለም የሚያሰኝ መሆን ያለመሆኑን ግራ ቀኙ ከተዋዋሉት ውል አንፃር አግባብነቱን ለመመርመር ለሰበር ችሎት ይቅረብ በሚል ጭብጥ በመያዙ መዝገቡ ሊቀርብ ችሏል፡፡

በዚሁ መሠረት አቤቱታው እና ማስቀረቢያ ነጥቡ ለተጠሪ እንዲደርስ ተደርጐ መስከረም 25 ቀን 2011 ዓ.ም. የተፃፈ 5 ገጽ መልስ ተጠሪ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- በውሉ አንቀጽ 9.2 መሠረት ቤቱ በደህና ሁኔታ ላይ መሆኑን ተመልክቶ የተዋዋለ ሆኖ እያለ፣ አገልግሎት መስጠት የማይችል ጅምር ቤት እንዳስረከበው እና ይህንንም ለማጠናቀቅ የሚያስችል ሥራ የግንባታ ፈቃድ ሊወጣለት ባለመቻሉ በውሉ አለመከበር ምክንያት ተጠሪ እንደሆነ ለማስመሰል ጥረት አድርጓል፡፡ አመልካች ለተጠሪ ሳያሳውቅና ስምምነት ሳያገኝ በራሱ ተነሳሽነት እና ፅቅድ ብቻ የተከራየውን ቤት በአንድ ገጽ ያለውን ግድግዳ እና ጣሪያውን አፍርሶበደንብ አስከባሪዎች እንዲቆም ተደርጓል፣ ይህ አፍርሶ የመስራት ተግባር በውል ስምምነታችን ውስጥ ያልተገለፀ ሲሆን አመልካች ማፍረስ ሳያስፈልገው የውስጥ ሥራ ብቻ በመስራት መጠቀም ማደራጀት እየቻለ ያለተጠሪ ፈቃድ በማፍረስ ሕገወጥ እና የውል ጥሰት በመፈፀሙ የሚመለከተውን አካል የግንባታ ፈቃድ ቢጠየቅም ፈቃድ

ለመስጠት ፈቃድ በመከልከሉ ያለአግባብ ያፈረሰውን ወደ ነበረበት ለመመለስ እንጂ በውል የተቀመጠ አይደለም፡፡

አፍርሶ መስራት በተዋዋዮቹ የታሰበ ጉዳይ አለመሆኑን፣ የግንባታ ፈቃዱም ቢገኝ አመልካች ምን ዓይነት ግንባታ ለማከናወን ፈልጎ እንደነበረ ራሱ ለተጠሪ ግልጽ አለመሆኑ፣ በውሉም ላይ እድሳትን በተመለከተ የተጠሪን ፈቃድ ማግኘት ያለበት መሆኑ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጠው ተጠሪ በንብረቱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት አስቀድሞ ለመከላከል እድል እንዲያገኝ መሆኑን፣ የተከፈለው የኪራይ ገንዘብ አመልካች ለያዘው ክፍል ሲሆን ክፍሉ በአመልካች ባይያዝ ኖሮ ለሌላ ተከራይ በማስተላለፍ ገቢ ያገኝ የነበረ መሆኑ፣ ተጠሪ በጥፋቱ ምክንያት ክሶ ውሉን አቋርጦ መሄድ ሲገባው ቤቱ እንደፈረሰ ጥሎ ሄዷል፡፡ በዚህ ሁኔታ የ4 ወር ኪራይ እንዲከፍል መወሰኑ ቤቱንም ወደ ነበረበት ለመመለስ የወጣውን ወጪ እንዲተካ መደረጉ የተፈፀመበት ስህተት ስለሌለ አቤቱታው ውድቅ ሆኖ በግልግል ዳኝነቱ የተሰጠው ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት መልሱን አቅርቧል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሱን አቅርቦ ከመዝገብ ተያይዞ የጽሁፍ ክርክሩ በዚህ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልስ ከስር የግልግል ጉባዔው ውሣኔ በግራ ቀኙ ከተደረገ የውል ስምምነት እና አጠቃላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገ የቤት ኪራይ መኖሩን፣ ቤቱን አመልካች የተከራየው ለባንክ ሥራ አገልግሎት መሆኑ እና አከራይ የ6 ወር ኪራይ ቀድሞ መቀበሉ እንዲሁም ተከራይ የተከራየውን ቤት መረከቡ በግራ ቀኙ አልተካደም፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የቤት ኪራይ ውል ጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም. የተፈረመ እና አከራይ የ6 ወር ኪራይ በወር 33,890.50 ተባዝቶ የተከፈለው ሲሆን አመልካች ደግሞ የተከራየውን ቤት ተረክቧል፡፡ በዚህ ውል አንቀጽ 3.1 መሠረት አመልካች ቤቱን የተከራየው ለባንክ ሥራ አገልግሎት መሆኑ ተገልጿል፡፡ አመልካች የተረከበው ቤት ለባንክ ሥራ አገልግሎት በሚሆን መልኩ በቢሮ የተከፋፈለ ሳይሆን የወለል ስፋቱ 84.2 ካሬ ሜትር መሆኑን ውሉ ያሳያል፡፡

አመልካች በውል ስምምነቱ መሠረት ቤቱን ለሥራው አመቺ ለማድረግ ተጠሪን ፈቃድ መጠየቅ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ በውሉ አልተገለፀም፡፡ ይልቁንም አመልካች ተጠሪን ፈቃድ ለመጠየቅ የሚገደደው በተከራየው ክፍል ላይ የግንባታ ማሻሻያ የቅርጽ ወይም የይዘት ለውጥ ማድረግ ከፈለገ ስለመሆኑ በውሉ አንቀጽ 11.1 ላይ ከተመለከተው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ መሠረት አመልካች ክፍሎችን ለሥራ አመቺ ለማድረግና ወደ ሥራ ለማስገባት ስንቀሳቀስ በአስተዳደሩ ተከልክያለሁ፣ የተከለከልኩበት ምክንያትም የግንባታ ፈቃድ የለህም በሚል ሲሆን ተጠሪ የቤቱ ባለቤት በመሆኑ የግንባታ ፈቃድ ማውጣት ሲገባው ፈቃድ ሊያስገኝልኝ አልቻለም በመሆኑም የግንባታ ፈቃድ የማያስገኝልኝ መሆኑን ባውቅ ኖሮ ቀድሞውንም ውሉን አልዋዋልም ነበር በማለት የሚከራከሩበት ሲሆን፣ተጠሪ የግንባታ ፈቃዱን ለማስገኘት የራሱን ጥረት ማድረጉን ነገር ግን የግንባታ ፈቃድ የሚሰጠው 3ኛ ወገን በመሆኑ ማስገኘት የግድ ማሰራት አለበት ሊባል የሚችል አለመሆኑን የግልግል ዳኝነት ጉባዔው አረጋግጦ ወስኗል፡፡

እንግዲህ ግራ ቀኝ ያልተካካዱበት እና በግልግል ዳኝነት ጉባዔው የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን፣ አመልካች የቤቱን ኪራይ እንዲከፍል በሚል በግልግል ዳኝነት ጉባዔው የተሰጠ ውሣኔ አመልካች በእርግጥም ይህን ለመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በማረጋገጥ ነው ወይ? የሚለው ነጥብ የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ለክርክሩ መነሻ የሆነው የኪራይ ውል ዓላማ ለኪራይ ውሉ ምክንያት የሆነው ቤት ለባንክ አገልግሎት ማዋል ነው፡፡ የግንባታ ፈቃድ በመከልከሉ ምክንያት ለቤቱ ክፍፍል/ partition/ ባለመሠራቱ ቤቱን ለባንክ አገልግሎት ማዋል አልተቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት ውሉ ለተፈለገው ዓላማ ሳይውል መቅረቱ ከፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1788 ለውሉ መሠረዝ ምክንያት ይሆናል፡፡ ለመሠረዙ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን አንድ ውል ከተሰረዘ ተዋዋይ ወገኖች ከውል በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ የማድረግ ውጤት እንደሚያስከትል በፍ/ብሄር ሕጉ አንቀጽ 1815 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር የያዝነውን ጉዳይ ስንመለከት የሚመለከተው የአስተዳደር አካል የግንባታ ፍቃድ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገ ውል መሠረታዊ ዓላማ የሚነካ መሆኑን ተከትሎ ውሉ መሠረዙ አመልካች በኪራይ የያዘውን ቤት በተረከበበት ሁኔታ ለተጠሪ የመመለስ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ በኪራይ ውሉ ምክንያት የተቀበለውን ገንዘብ ለአመልካች መልስ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ይህ በመርህ ደረጃ ሲሆን ውሉ በመሠረዙ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ካለ ለደረሰ ጉዳት በካሣ መልክ አንዱ ለሌላው የመክፈል ግዴታ በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1771/2/፣1790 እና 1791 ላይ ከተመለከተው ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ውሉ የተሰረዘው ተጠሪ የግንባታ ፈቃዱን የማስገኘት በውሉ የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣቱ ምክንያት መሆኑን በመግለጽ የሚከራከር ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ የግንባታ ፍቃዱ የተከለከለው የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ፍቃደኛ ባለመሆኑ እንጂ በበኩሉ በውሉ የሚጠበቅበትን ግዴታ ባለመወጣቱ አይደለም በማለት ይከራከራል፡፡ የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ ተገቢውን ትጋት ከማድረግ በዘለለ ተጠሪ የግንባታ ፈቃዱን የማስገኘት ግዴታ እንደሌለበት

የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጦ የወሰነ መሆኑን ስለተገነዘብን ውሉ ሊሰረዝ የቻለዉ በተጠሪ ምክንያት ነው በሚል አመልካች እያቀረበ ያለው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካች የቤቱን ኪራይ መክፈል ግዴታ ያለበት መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ተጠሪ ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አመልካች የቤቱን ኪራይ መክፈል ግዴታ አለበት በማለት ለጠየቀው ዳኝነት መሠረት ያደረገው አመልካች የቤቱን ደረጃ በማሳደግ ደንበኛውን ወደሚሰጠው አገልግሎት ለመሳብ ያደረገው ጥረት ያልተሳካለት መሆኑን እያወቀ ቤቱን ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ በውል ስምምነቱ ባለመቀጠል ሊመጣበት የሚችለውን ግዴታ ለመቀነስ ጥረት አለማድረጉን እና ይልቁንም በራሱ ጥናት ላይ ለመመስረት የቤቱን አቀማመጥ ጠቀሜታን ግምት ውስጥ በማስገባት ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዳይዙበት በውል ስምምነቱ መግፋቱን መርጦ መቆየቱን ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች ቤቱ በእጁ በነበረበት ወቅት ያለውን የቤቱን ኪራይ በካሽ መልክ ለተጠሪ ለመክፈል የሚገደደው ለውሉ መሠረዝ ምክንያት ከሆነ ወይም ውሉ መሰረዙን እያወቀ ቤቱን በተገቢው ጊዜ ለተጠሪ በማስረከብ ሊመጣ የሚችለውን ጉዳት እንደመቀነስ ቤቱን ያለአግባብ በእጁ ያቆየ ስለመሆኑ ተጠሪ ካቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አንፃር የተረጋገጠ ሲሆን ነው፡፡

አመልካች ተጠሪ በዚህ መልኩ ላቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ቤቱን የማስተካከል ሥራው ከቆመበት ከ16/04/2008 ዓ.ም. ጀምሮ የቤቱን ኪራይ ያልተጠቀመበት መሆኑን በደብዳቤ ተጠሪን ያሳሰበ መሆኑን እና ቤቱን 3ኛ ወገን ለመከራየት ስላለመለፈለጉ ተጠሪ በማስረጃ አስደግፎ ማቅረቡን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ግራ ቀኝ በዚህ መልኩ ያቀረቡትን ክርክር በጭብጥነት ይዞ በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ ይልቁንም ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው አመልካች የቤቱን ኪራይ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው የግንባታ ፍቃድ አለመገኘቱ የሚያስከትለውን ኃላፊነት አውቆ እና አመዛዝኖ ወደ ውል መግባቱን እንዲሁም የግንባታ ፍቃድ እንደማይገኝ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ውሉን አቋርጦ ቤቱን ለአከራይ /ለተጠሪ/ በማስረከብ የሚደርስበትን ኪሳራ እንደመቀነስ ውሉ እስኪቋረጥ ድረስ በዝምታ መቀመጡን ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የቤቱ ኪራይ መሠረታዊ አላማ ለባንክ አገልግሎት መሆኑን እና ውሉ በተደረገበት ወቅት ቤቱ ለባንክ አገልግሎት በሚውል መልኩ ክፍፍል ተደርጐበት ያልተዘጋጀ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት እና ለባንክ አገልግሎት በሚውል መልኩ ክፍፍል ማድረግ ግዴታ መሆኑን እና ይህን ለማድረግ የግንባታ ፈቃድ አስፈላጊ መሆኑን ግራ ቀኙአምነውበት በውላቸው አንቀጽ 9.2፣9.8፣11.1 እና 11.6 አመልክተዋል፡፡

ይህ በሆነበት ሁኔታ አመልካች የግንባታ ፍቃድ አለመገኘቱ የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት አውቆ እና አመዛዝኖ የገባበት መሆኑን እንደአንድ ምክንያት በመውሰድ አመልካች ኃላፊነት እንዳለበት በግልግል ጉባዔው የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የግንባታ ፍቃድ የተከለከለው መቼ እንደሆነ እና የግንባታ ፍቃድ ባለመገኘቱ ቤቱ አገልግሎት እየሰጠ እንዳልሆነ አመልካች ለተጠሪ ያሳሰበው መሆን አለመሆኑን እንዲሁም ተጠሪ ደብዳቤው የደረሰው መሆን አለመሆኑን የደረሰው ከሆነ መቼ እንደደረሰው እና ቤቱን በተገቢው ጊዜ ከአመልካች ተረክቦ ለሌላ በማከራየት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በመቀነስ ረገድ ተጠሪ በኩል ያደረገው ጥረት ስለመኖሩ በፍትሐብሄር ህጉ አንቀጽ 1802 መሠረት ባልተጠራበት ሁኔታ አመልካች ቤቱን በተገቢው ጊዜ አላስረከበም በሚል የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የሰጠው ምክንያትም ተገቢነት የሌለው ነው፡፡

በአጠቃላይ ውሉ መሠረዙን ተከትሎ ተጠሪ ከቤቱ ኪራይ ማግኘት ይችል የነበረውን ገቢ በማጣት ለደረሰበት ጉዳት አመልካች የቤቱን ኪራይ በካሣ መልክ ለመክፈል የሚገደደው በበኩሉ የፈፀመው ጥፋት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ከግራ ቀኝ ክርክር አኳያ አግባብነት ያላቸውን ጭብጦች በመያዝ አመልካች ኃላፊነት ያለበት መሆን አለመሆኑን አረጋግጦ አመልካች እንዲከፍል የሚገደደዉን የካሳ መጠንም በፍ/ብሄር ሕጉ አንቀጽ 1799 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት አስልቶ መወሰን ነበረበት ። በመሆኑም የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በሌሎች ጭብጦች ላይ የሰጣቸው ውሣኔዎች በአግባቡ በመሆናቸው እኛም የምንቀበለው ሆኖ አመልካች የቤቱን ኪራይ እንዲከፍል በሚል የተሰጠው የውሣኔ ክፍል ግን ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ምክንያቶች አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የግልግል ጉባዔ ጥቅምት 4 ቀን 2010 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 205218 ግንቦት 23 ቀን 2010 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ከፍሎ የነበረው የቤት ኪራይ ብር 203343.00/ ሁለት መቶ ሶስት ሺ ሶስት መቶ አርባ ሶስት ብር/ ሊመለስለት አይገባም፣ አመልካች በተጨማሪ ብር 135562.00/ አንድ መቶ ሰላሳ አምስት ሺ አምስት መቶ ስድሳ ሁለት ብር/ ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል በሚል የተሰጠው የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

3. ከላይ በፍርድ ሃተታው በተመለከተው መሠረት አመልካች የተከራየው ቤት የግንባታ ፈቃድ በመከልከሉ ምክንያት ለተገቢው ዓላማ አለማዋሉን ያወቀው መቼ ነው? ለተፈለገው አላማ አለማዋሉን እንዳወቀ ተጠሪ ይህንኑ እንዲያውቅ አድርጓል ወይ?አመልካች ተጠሪ ይህን እንዲያውቅ አድርጐ ከሆነ ተጠሪ ቤቱን በተገቢው ጊዜ ያልተረከበው ለምንድን ነው? ተጠሪ ቤቱን በተገቢው ጊዜ መረከብ እየቻለ ይህን አለማድረጉ በፍትሐብሄር ሕጉ ምን ውጤት አለው:? የሚሉትን ነጥቦች ግራ ቀኙ ካቀረቡት ማስረጃ አንፃር በመመርመር ተገቢ ነው ያለውን ሕጋዊ ውሣኔ እንዲወስን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 343/1/ መሠረት ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ሰበር ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት እና ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው ይድረስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 169077

ሰኔ 28ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች -ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

አመልካች ፡- መይ ሪል ስቴት ዴቨሎፕመንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ተጠሪ፡- አቶ ያየህ ይራድ ፍቅሬ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው የህንፃ ክፍል ሰርቶ የማስረከብ ውል መሻሻት ክስ ቀርቦ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የአሁን አመልካች አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክብ እና በውሉ መሰረት ቤቱን በጊዜው ባለማስረከቡ በተጠሪ ላይ በኪራይ ማጣት የደረሰውን ኪሳራ እንዲከፍል፤ እንዲሁም የኪራዩ መጠን ተጣርቶ እንዲወሰን በማለት ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ኪራይን በተመለከተ ተጠሪ የሚገነባው ቤት በወር ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) ይከራይ እንደነበር ጠቅሰው ቤቱን ማስረከብ ከነበረበት የካቲት 2000 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ አግባብ ተሰልቶ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ኪራይ ሊከፍል የማይገባበትን ምክንያት እና የኪራዩ መጠን በማስረጃ የተደገፈ አለመሆኑን በማንሳት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳበት ቤት ስፋት እና ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው በአካባቢው የሚገኙ ቤቶች በምን ያህል እንደሚከራዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ በቅድሚያ ለቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 8 አስተዳደር ፍትህ ጽቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ ጽ/ቤቱ በቁጥር ቀ/ክ/ከ/ወ/08/ፍ/ጽ/ቤት 1353/09 በቀን 29/05/2009 ዓ.ም በላከው ምላሽ ከአካባቢው በተገኘው መረጃ ከ2000 ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ ባለሁለት መኝታ 83 ካ.ሜ የህንጻ ቤት በአማካይ ከብር 8,000.00 እስከ 10,000.00 እንደሚከራይ እንዲሁም 115 ካ.ሜ ከብር 12,000.00 እስከ 15,000.00 እንደሚከራይ ገልጿል፡፡ ፍርድ ቤቱ የቀረበው ማስረጃ አከራካሪውን ጭብጥ በተፈለገው ሁኔታ እና ደረጃ አጣርቶ ለመወሰን የሚያስችል አይደለም በማለት በድጋሚ ተጣርቶ እንዲቀርብ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ትዕዛዝ ሰጥቶ ባለስልጣኑ በቁጥር ሞዕ/3-20/10/17833 በቀን 14/09/2009 ዓ.ም በፃፈው ምላሽ ስፋቱ 152.2 እና

152.6 የሆኑ ቤቶች በ2007 ዓ.ም ርክክብ ተደርጎ የተከራዩበትን ዋጋ የገለፀ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ክርክር የተነሳበት ቤት ስፋት 225 ካ.ሜ በመሆኑ የቀረበው ምላሽ ጉዳዩን ለመወሰን የሚያስችል አይደለም በማለት አልፎታል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ የኪራዩን መጠን በተመለከተ ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸውን አቅርበው እንዲያስረዱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ በአካባቢው በደላላነት እንደሚሰሩ የገለፁ አንድ ምስክር አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ምስክሩ በሰጡት ቃል ቤቶቹ ከ2000 እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ ከ2,000.00 የአሜሪካ ዶላር ጀምሮ እንደሚከራዩ መስክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ያቀረባቸው ሁለት ምስክሮች ከ2000 — 2005 ዓ.ም ድረስ በአካባቢው ቤቶች ተሰርተው ባለመጠናቀቃቸው እንደማይከራዩ መስክረዋል፡፡ በመጨረሻ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ፍርድ የአመልካች ምስክሮች የሰጡትን ቃል ውድቅ በማድረግ የተጠሪ ምስክር ከጠቀሱት ዋጋ ላይ መነሻውን 2,000.00 የአሜሪካ ዶላር በመያዝ ኪራዩ ሊሰላ ይገባል ብሏል፡፡ በዚህ መሰረት በወቅቱ በነበረው የምንዛሬ መጠን አስልቶ ከየካቲት 2000 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2005 ዓ.ም ላለው ጊዜ ብር 1,768,407.60 (አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ስድሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰባት ብር ከስድሳ ሳንቲም) ኪሳራ በኪራይ መልክ ከነወለዱ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

ጥር 13/2011 ዓ.ም የቀረበው የሰበር አቤቱታ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች እንደውላቸው ቤቱን በጊዜው ሰርቶ ባለማስረከቡ በተጠሪ ላይ በደረሰው የገንዘብ ጉዳት ሊከፍል የሚገባውን የካሳ መጠን በኪራይ መልክ አስልቶ ለማስከፈል የፌ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከመንግስታዊ ተቋማት ስለኪራዩ መጠን የሚገልጽ ማስረጃ ካስቀረበ በኃላ ወደጎን በመተው በአንድ ሰው ምስክርነት ቃል ላይ ብቻ ተንተርሶ የሰጠውን ዳኝነት ከማስረጃው አግባብነት አንፃር ተገቢ መሆን አለመሆኑንና ተያያዥ ጉዳዮችን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ሚያዚያ 25/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ ቅሬታው ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው የግራ ቀኙ ግንኙነት ውልን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ እንደውሉ ያልተፈፀመለት ወገን እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት በጥቅም መቋረጥ መልኩም ሆነ በሌላ ሁኔታ ኪሳራ የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1771 ሥር በመርህ ደረጃ

ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በውሉ መሰረት ቤቱን በጊዜው ለተጠሪ ባለማስረከቡ በተጠሪ ላይ በኪራይ ማጣት መልክ የደረሰውን ኪሳራ እንዲከስ ተጠሪ መጠየቃቸውና የሥር ፍርድ ቤትም በዚሁ መሰረት ውሳኔ ላይ መደረሱ የህጉን ይዘትና መንፈስ የተከተለ አይደለም የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአንዳሩ የውል ጥሰት ሲኖር ሊከፈል የሚገባውን ኪሳራ አቆራረጥ በተመለከተ በህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች፤ እንዲሁም ኪሳራው የሚቆረጠው በኪራይ ስሌት ተመን ነው ቢባልና ግራቀኙ አስቀድመው የተመኑት ኪራይ ልክ ባይኖር ኪራዩን ለመወሰን አግባብነት የሚኖረው ማስረጃ ምን አይነት ነው የሚሉትን በተመለከተ ከህጉ ጋር አያይዞ በመመልከት የሥር ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በመመርመር ውሳኔ ላይ ሊደረስ እንደሚገባ ተገንዝበናል፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁ 1771 ሥር በመርህ ደረጃ የተደነገገው የውል አለመፈፀም ስለሚያስከትለው የጉዳት ኪሳራ የተመለከተው ቢኖርም የሚከፈለው ኪሳራ የሚታሰበው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1799 ሥር እንደተደነገገው አእምሮ ያለው ሰው ውሉ ባለመፈፀሙ ይደርሳል ብሎ በሚገመተው አስተያየት ልክ ነው፡፡ በዚህ አኳኋን የውሉ መሰረቶች ናቸው ተብለው የሚያዙት የውሉን አይነት መመልከት ብቻ ሳይሆን የተዋዋዮችን የሙያ፣ ሥራ፣ ከዚህ በፊት የነበራቸውን ግንኙነት፣ ባለዕዳው የሚያውቃቸውን ሁኔታዎች እና ማናቸውንም አጋጣሚ ሁኔታዎች ሁሉ በመመልከት ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ኪሳራው ባለገንዘቡ በደረሰበት እርግጠኛ ጉዳት ልክ እንዲሆን አድርጎ መወሰን የሚቻል ቢሆንም እንዲህ አይነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው ግን ባለገንዘቡ ውል ሲያደርግ ጉዳቱን ይበልጥ የሚያከብዱበትን ልዩ ልዩ ምክንያቶች ለባለዕዳው አስቀድሞ ያስታወቀ ሲሆን መሆኑን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1801 ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት በውሉ የተመለከተውን የማስረከቢያ ጊዜ እና በተጠሪ የተጠየቀውን የኪራይ ኪሳራ ብቻ በመመልከት በተጠሪ ላይ ይደርሳል ያለውን እርግጠኛ ጉዳት ልክ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በቀር እንደ ህጉ ድንጋጌዎች የውሉን አይነት፣ የተዋዋዮችን ሥራና የነበራቸውን ግንኙነት እንዲሁም ከቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አንፃር ባለዕዳ የሆነው የአሁን አመልካች የሚያውቃቸውን ሁኔታዎች ሁሉ እንዲሁም ጉዳቱን የሚያከብዱ ሁኔታዎች አስቀድሞ እንዲያውቅ የተደረገበት ሁኔታ መኖር አለመኖሩን ሁሉ በማጣራት ውሳኔ ላይ መደረሱን መዝገቡ አያሳይም፡፡ ክርክሩ ከፍሲል በተጠቀሰው የህግ አግባብ ታይቶ እና ጉዳዩ በአግባቡ ተጣርቶ ኪሳራው ካልተወነ ውሳኔው ህጉን መሰረት ያደረገ ነው ሊባል አይችልም፡፡

በሌላም በኩል ኪሳራው የሚቆረጠው በኪራይ ውል ስሌት ተመን መሰረት ነው ቢባልና ግራቀኙ አስቀድመው የተመኑት የገንዘብ ልክ ባይኖር የኪራዩን ገንዘብ ልክ ለመወሰን አግባብነት የሚኖረው ማስረጃ ምን አይነት እንደሆነ በህጉ ተመልክቷል። በፍ/ብ/ህ/ቁ 2950(2) የቤት ኪራይ ልክ በሚያጠራጥር ጊዜ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት በወሰኑት ታሪፍ መሰረት ወይም የተወሰነ ታሪፍ ከሌለ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል ሊወሰን እንደሚገባ ይደነግጋል። ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች እንደውሉ ቤቱን በጊዜው ሰርቶ ባለማስረከቡ በተጠሪ ላይ በደረሰው የገንዘብ ጉዳት ሊከፍል የሚገባውን የካሳ መጠን በኪራይ መልክ አስልቶ ማስከፈል ተገቢ መሆኑ ከታመነበትና የኪራዩ መጠን አከራካሪ በሆነበት የፌ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከመንግስታዊ ተቋማት ስለኪራዩ መጠን የሚገልጽ ማስረጃ ካስቀረበ በኃላ ይህን ወደጎን በመተው በደላላነት የተሰማሩ ሰው የሰጡት ምስክርነት ቃል ላይ ተንተርሶ የሰጠው ዳኝነት ከማስረጃው አግባብነት አንፃር ሲታይም ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም።

በአጠቃላይ የአሁን አመልካች እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት በሚል የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ቢሆንም ሊከፈል የሚገባውን የኪሣራ መጠን በመወሰን ረገድ ግን በግራቀኙ መካከል የተደረገውን የውል አይነት፣ የነበራቸውን ግንኙነት እንዲሁም የአሁን አመልካች አስቀድሞ የሚያውቃቸውን ሁኔታዎች ሁሉ በማጣራት ውሳኔ ላይ አለመደረሱ እንዲሁም ኪሳራው የሚቆረጠው በኪራይ ውል ስሌት ተመን መሰረት ነው ቢባልም የኪራዩን ገንዘብ ልክ ለመወሰን አግባብነት የሚኖረው ማስረጃ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት የወሰኑት ታሪፍ ስለመሆኑ ወይም የተወሰነ ታሪፍ ከሌለ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል ሊወሰን እንደሚገባ በህጉ ተመልክቶ እያለ በዚህ አግባብ ጉዳዩ ሳይታይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 134470 ግንቦት 24 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 161698 ጥቅምት 15/2011 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል።
2. የአሁን አመልካች እንደውሉ ባለመፈፀሙ በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኪሳራ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ተብሎ አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ነው ብለናል።
3. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ሊከፈል የሚገባውን የኪሣራ መጠን በመወሰን ረገድ በግራቀኙ መካከል የተደረገውን የውል አይነት፣ የነበራቸውን ግንኙነት እንዲሁም የአሁን አመልካች አስቀድሞ የሚያውቃቸው ሁኔታዎች ሁሉ ኪሳራውን ለመወሰን ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ተገንዝቦ ይህን መነሻ በማድረግ የህጉን

ይዘትና መንፈስ ተከትሎ ውሳኔ እንዲሰጥ፤ ኪሳራው የሚቆረጠው በኪራይ ውል ስሌት ተመን መሰረት ነው ስለተባለም የኪራዩን ገንዘብ ልክ ለመወሰን አግባብነት የሚኖረው ማስረጃ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት የወሰኑት ታሪፍ በመሆኑ ለተመሳሳይ ቤት የሚታወቅ ታሪፍ ቢኖር በመጠየቅ እንዲሁም ታሪፍ ከሌለ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል በአግባቡ አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡

4. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ያስከተለውን ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ን

የሰ.መ.ቁ.168198

ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡.... ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡..... . ..አፍሪካ ክንፉ መረዳጃ እድር፡- ሺፈታ በለጠ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡..... . .1. አቶ ዮሴፍ ደበበ የቀረበ የለም፡፡

2. አቶ ኤርሚያስ ጌታቸዉ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር።ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.214403 ታህሳስ 9 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን አመልካች)ባቀረበዉ ክስ ተከሳሾች ከ1/6/2007 ዓ.ም እስከ 30/11/2009 ዓ.ም ድረስ ያለዉን ዉዝፍ ኪራይ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ወለድን ጨምሮ ብር 464,887.50 እንዲከፍሏቸዉ ጠይቋል።

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሾች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከሳሽ ያቀረበዉ የኪራይ ይከፈለኝ ጥያቄ በ2 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለሆነ መዝገቡ እንዲዘጋልን በማለት ተከራክሯል። ከሳሽ በዚህ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በሰጠዉ ምላሽ ይህ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025 (ለ) መሰረት በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተከሳሾች በተነሳዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በሰጠዉ ብይን ከዚህ ቀደም በግራ ቀኙቸዉ መካከል በተደረገዉ ክርክር ተከሳሽ ቤቱን እንዲለቁ እና ኪራይ እንዲከፍሉ የተጠየቀ ሲሆን ፍ/ቤቱ እስከ 30/11/2007 ዓ.ም ያለዉን ኪራይ የወሰነ ቢሆንም ከ1/12/2007 ዓ.ም ጀምሮ ላለዉ ጊዜ ዉዝፍ ኪራይ ጠይቋል ለማለት

ስለማይቻል፣ ከሳሽ ከ1/6/2007 ዓ.ም እስከ 30/11/2007 ዓ.ም የጠየቀዉን ዉዝፍ የቤት ኪራይ ይከፈለኝ ጥያቄ በ2 አመት ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል።

የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ ማመልከቻ በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለማሻር ነዉ።

የአሁን አመልካች በ25/4/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እስከ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እስከ 26/10/2009 ዓ.ም ድረስ ስንከራከር ስለነበርን በክርክር ላይ የቆየን በመሆኑ፣ በዚህ ምክንያት በ1/6/2007 ዓ.ም እስከ 30/11/2009 ዓ.ም ያለዉ ጊዜ በተመለከተ የ2 ዓመት ይርጋ የማይመለከተዉ ነዉ። የሥር ፍ/ቤቶች ከዚህ ቀደም የተሰጠዉን ዉሳኔ እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025(ለ) ያላገናዘበ ስለሆነ ተሽሮ ታርሞ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች ያቀረበዉ ዉዝፍ የቤት ኪራይ ክፍያ ጥያቄ በ2 ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 እና 2025 አንጻር ፣ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት መጋቢት 4 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበዉ ዉዝፍ የቤት ኪራይ ይከፈለኝ ጥያቄ በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 በ2 ዓመት ጊዜ ዉስጥ ያልተከፈለ የቤት ኪራይ እንደተከፈለ የህግ ግምት ይወሰድበታል በሚለዉ ድንጋጌ ሥር የሚወድቅ ስለሆነ የተሰጠዉ ዉሳኔ ምንም ዓይነት የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ይህ ችሎት የግራ ቀኙቸውን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች እና ተጠሪዎች የቤት ኪራይ ክፍያ በተመለከተ ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲከራከሩ ቆይተዉ፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.128939 ሰኔ 26 ቀን 2009 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል። በዚህ ዉሳኔ ተጠሪዎች ከየካቲት 1 ቀን 2007 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30/2007 ዓ.ም ድረስ ያልከፈሉትን የቤት ኪራይ እና በቀጣይም የዉሉ ጊዜ በዉሉ መሰረት ለአመልካች እንዲከፍሉ

ወስኗል። ከዚህ መግንዘብ የሚቻለዉ ግራ ቀኞቹዉ ከሥር ፍ/ቤቶች ጀምሮ እስከዚህ ችሎት ድረስ እስከ ሰኔ 26 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በቤት ኪራይ ክፍያ ሲከራከሩ እንደነበር የሚያመለክት ነዉ። ከዚህ በኋላ አመልካች ሐምሌ 22 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ክስ ተጠሪዎች ከየካቲት 1 ቀን 2007 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ያለዉን ዉዝፍ የቤት ኪራይ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ለማስከፈል ክስ ማቅረቡን ተግነዝበናል። ይህ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን በሕጉ አግባብ መርምረናል።

እንደሚታወቀዉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 (መ) መሰረት ዕዳዉ እንዲከፈል መጠበቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ሳይከፈል የቀረ ገንዘብ እንደተከፈለ ከሚቆጠሩት ጉዳዮች አንዱ የቤቶች ኪራይ ዕዳ እንደሆነ ያመለክታል። የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ሲታይ የቤት ኪራይ ክፍያ ሳይከፈል ሁለት ዓመት ያለፈ እንደሆነ እና ከዚህ አንጻር መቃወሚያ የቀረበ እንደሆነ፣ ይህ የቤት ኪራይ ክፍያ እንደተከፈለ ስለሚቆጠር፣ የዚህ የቤት ኪራይ ክፍያ ይከፈለኝ ጥያቄ ተቀባይነት የሚያጣ ይሆናል ማለት ነዉ። ይህ ደግሞ የይርጋ ጉዳይ ሳይሆን የቤት ኪራይ ክፍያዉ እንደተፈጸመ በሕግ ግምት የሚወሰድበት መሆኑን ነዉ። ነገር ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025 ሥር የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረብ ይህን የሕግ ግምት ቀሪ ማድረግ እንደሚቻል ተመልክቷል። ከእነዚህ ሁኔታዎች ዉስጥ አንዱ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (ለ) ሥር የተደነገገዉ ፣በሕግ የተደነገገዉ የጊዜ ዉሳኔ ሳይደርስ ባለገንዘቡ ገንዘቡን እንዲከፍለዉ ባለዕዳዉን ከፍርድ ቤት አስጠርቶ እንደሆነ እዳዉ እንደተከፈለ መቆጠሩ ቀሪ ይሆናል፣ በማለት ይደነግጋል። ከዚህ አንጻር አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ከዚህ ቀደም ተጠሪዎች ቤቱን እንዲለቁ እና ዉዝፍ የቤት ኪራይ እንዲከፍሉት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲከራከሩ ቆይተዉ ሰኔ 26 ቀን 2009 ዓ.ም ዉሳኔ ያገኘ እና እስከ 30/11/2007 ዓ.ም ድረስ ያለዉ የኪራይ ክፍያ እንዲከፍሉ የተወሰነ መሆኑ ሲታይ አመልካች የቤት ኪራይ እንዲከፈለዉ ተጠሪዎችን ከፍ/ቤት አስጠርቶ ሲከራከሩ ቆይቶ በኋላ ዉሳኔ የተሰጠበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ። በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2024 (ለ) መሰረት የቤት ኪራይ እንዲከፈል መጠየቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ያልተጠየቅ የቤት ኪራይ ክፍያ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለዉ የሕግ ግምት፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2025 (ለ) ሥር የተመለከተዉ ሁኔታ መኖሩን የሚያስረዳ ማስረጃ የቀረበ እንደሆነ የቤት ኪራይ ክፍያዉ እንደተከፈለ ይቆጠራል የሚለዉ ግምት ቀሪ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ። ስለዚህ የአሁን አመልካች የቤት ኪራይ ክፍያ እንዲከፈለዉ ያቀረበዉ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድበት የህግ አግባብ የለም።

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ዉዝፍ የቤት ኪራይ እንዲከፈለዉ በተጠሪዎች ላይ የቀረበዉ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድበት የህግ አግባብ በሌለበት ክሱ በሁለት ዓመት

ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ በመ.ቁ.46706 በ10/7/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.214403 ታህሳስ 9 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ የአሁን አመልካች ያቀረበዉ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ባለመሆኑ፣ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት ተመልሶለታል።
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
4. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሠ/ን

ከውል ውጪ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁጥር 161417

ቀን 12/9/2011 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች ፡- - ፀሀይ ኢንሹራንስ አ/ማ ነ/ፈ ቀሮሚሳ ፍሌ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- - የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - የቀረበ የለም ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ሐምሌ 10 ቀን 2010 ዓ.ም በተሻፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 205570 ሚያዝያ 17 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 39741 ጥቅምት 8 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ አመልካች ክስ ያቀረበው ከተጠሪ ህንጻ ላይ የወደቀ ፍራሽ የደንበኛዬ መኪና ላይ ወድቆ በመኪናው ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ሲሆን የውል ወይም ከውል ወጪ የሚል ነገር ሊነሳ አይችልም፡፡ በውል ምክንያት ነው ክስ የሚቀርበው ከተባለ እንኳ ወደ ውል ችሎት ወይም መብት ይጠበቅልኛል እንጂ የስር ፍ/ቤቶች በደፈናው ክሴን ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም፡፡ የአመልካች ደንበኛ የተከራየው ቤት ለቢሮ የሚሆን ክፍል እንጂ መኪና ማቆሚያ ቦታ አይደለም፡፡ መኪና ማቆሚያ ቦታ ማንኛውም የተጠሪ ተጠቃሚ የሆነው ሰው ሁሉ የሚጠቀምበት በመሆኑ እንደውል የሚቆጠር ባለመሆኑ ክሴ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካች ባቀረበው ክስ ንብረትነቱ የተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ከሆነው ህንጻ ላይ የህንጻው ፍርስራሽ ወድቆ የከሳሽ ደንበኛ በሆነው መኪና ላይ ወድቆ ጉዳት አድርሶበታል። ከሳሽ ከደንበኛው ጋር ባለው ውል መሰረት ብር 38853.19 ለማስጠገኛ ከፍሏል። ተከሳሽ ሊከፍለኝ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ከ16/6/2007 ዓ/ም ጀምሮ ከወለድ ጋር እንዲከፍለኝ ሲል ጠይቋል። ተከሳሽም የከሳሽ ደንበኛ ጉዳት አድርሷል በተባለው ህንጻ ላይ ተከራይ ያለ በመሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2088(1) መሰረት ሊጠይቀኝ አይችልም። በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2089 ጥቅም በሌለው ግንኙነት ህንጻው ለሚያደርሰው ጉዳት የህንጻው ባለቤት ጥፋት ከሌለበት ሃላፊነት የለበትም። ተከሳሽና የከሳሽ ደንበኛ ውል ያለን በመሆኑ እና በተከሳሽ ጥፋት ምክንያት ጉዳት የደረሰ ባለመሆኑ ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም። ካለጨረታ የተደረገ ጥገና ተከሳሽን የሚጎዳ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ። ከሳሽ ተተክቶ መጠየቅ የሚችለው ደንበኛው ባለው መብት በመሆኑና ደንበኛው ሊጠይቅ የማይችለውን መዳረግ ስለማይችል ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል። የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 39741 ጥቅምት 8 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088(1) እና (2) እንዲሁም በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2077 መሰረት የከሳሽ ደንበኛ ከተከሳሽ ጋር የቤት ኪራይ ውል የነበራቸው በመሆኑ ከተከራየው ህንጻ ላይ በወደቀው ፍራሽ ምክንያት በደረሰው ጉዳት የሚጠይቀው ባላቸው ውል መሰረት በማድረግ እንጂ ከውል ውጪ ሃላፊነት ህጎች በመጠቀም አይደለም። ከሳሽም ደንበኛው በሌለው መብት ሊተካ አይችልም። በመሆኑም ተከሳሽ ከውል ውጪ የሚመነጭ ሃላፊነት የለበትም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጎታል። ከሳሽ የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 205570 ሚያዝያ 17 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙም ሰርዞታል።

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል። መዝገቡም ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት ጉዳት የደረሰበት መኪና ባለቤት ለጉዳቱ መንስኤ ከሆነው የህንጻው ባለቤት ጋር የኪራይ ውል ግንኙነት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088(2) ከውል የመነጨ ክስ የማቅረብ መብት ያለው በመሆኑ የአሁን አመልካች በዚህ መብት በመዳረግ ከግራ ቀኙ የኪራይ ውል ስምምነት አድማስ እና ተፈጻሚነት ካላቸው ህጎች አንጻር ክርክሩ ሊመራ ይገባ ነበር ወይስ አልነበረም? ከዚህ አንጻር አመልካች ደንበኛው ባለው ከውል የመነጨ ግዴታ ክስ የማቅረብ መብት ሊዳረግ ይገባል ወይስ አይገባም ከሚለው ነጥብ አንጻር ለመመርመር ሲባል ቀርቧል። መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል። ተጠሪ ጥቅምት 14 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል። አመልካችም ህዳር 13 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲሆን፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ደንበኛ የሆነው በአሁን ተጠሪ ህንጻ ላይ ተከራይቶ የነበረ መሆኑ፣ የአሁን አመልካች ደንበኛ መኪና ቆማ ባለችበት ከተጠሪ ህንጻ ላይ የወደቀው የህንጻው ፍርስራሽ ወድቆባት ጉዳት ያደረሰበት መሆኑ አላከራከረም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በአሁን አመልካች ደንበኛ እና በተጠሪ መሀከል የቤት ኪራይ ውል ያለ በመሆኑ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088(2) ድንጋጌ መሰረት የአመልካች ደንበኛ ተጠሪን ሊጠይቀው የሚችለው በመሀላቸው ባለው የገቡት የውል ግዴታ መሰረት በመሆኑና የአሁን አመልካችም በደንበኛው ተዳርጎ ክስ ማቅረብ የሚችለው ደንበኛው ባለው መብት ልክ በመሆኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ከውል ውጪ ኃላፊነት ተቀባይነት የለም በሚል ክሱን ውድቅ አድርገውታል፡፡ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088(1) ጉዳቱን ካደረሰው አደገኛ ኢንዱስትሪ፣ ወይም እንስሳ፣ ወይም ሕንጻ ወይም ሌላ ነገር ግንኙነት ያለውና በሕግ በኩልም ለነዚሁም ሃላፊ ከተባለው ሰው ጋራ ተዋውያለሁ የሚለው ሰው አሥጊ የሆኑ ነገሮችን በመፍጠር ወይም በእንስሳዎች ወይም በሕንጻዎች ወይም በሌላ ነገሮች ለሚደርሱ ጉዳቶች የኃላፊነትን ደንቦች በመጥቀስ ከኃላፊነት ለመዳን እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ህንጻን በተመለከተ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተገናኘ ጉዳቱን ያደረሰው ህንጻ ኃላፊ ከሆነው ሰው ጋር የውል ግንኙነት ባለው ሰው ምክንያት ለሚደርሱ ጉዳቶች ይሄው ሰው ከኃላፊነት መዳን እንደማይችል የሚደነግግ ሲሆን በዚህ ጊዜ ጉዳቱን ያደረሰው ሰው ኃላፊነት የሚመራው በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088(2) በሚደነግገው መሰረት በመሀላቸው ባለው ውል መሰረት እንደሆነ የሚደነግግ ነው፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2077(2) ድንጋጌም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2088 ድንጋጌ የሚያመለክተው ከህንጻ ባለቤት ወይም ኃላፊ ከሆነው ሰው ጋር ውል ባደረገው ሰው ምክንያት የሚመጣ የጉዳት ሃላፊነት የሚመራው ባደረገው ውል መሰረት መሆኑን እንጂ ስለ ህንጻው ባለቤት ወይም ኃላፊ የሆነው ሰው የሚያወራ አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2077(1) ያንድ ሕንጻ ባለሀብት ወይም ባለይዞታ ሕንጻው ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ያልታሰበ ድንገተኛ ነገር ቢያደርስም፣ ይህ ሕንጻ በሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሆነ ደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ጉዳት ያደረሰው ሕንጻ ባለቤት መሆኑን እና ከህንጻው ላይ የወደቀው ፍርስራሽ በአመልካች ደንበኛ መኪና ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን አያስተባብልም፡፡ እንዲሁም የጉዳቱን መጠን በተመለከተ አመልካች የጠየቀው የመኪናዋ ማስጠገኛ ዋጋ በጨረታ የተደረገ ጥገና ባለመሆኑ ይጎዳኛል ከማለት ውጪ፣ ጉዳት የደረሰባት መኪና የተጠገነችው ከጨረታ ወጪ ስለመሆኑና ከተጠየቀው የማስጠገኛ ዋጋ አነስተኛ ዋጋ የቀረበ ስለመሆኑም ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ የለም፡፡ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2077(1) ድንጋጌ መሰረት የአሁን ተጠሪ ሕንጻው ለሚያደርሰው ጉዳት ከውል ወጪ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን የአሁን አመልካችም ከደንበኛው ጋር ካለው የኢንሹራንስ ውልና ከንግድ ህጉ አንቀጽ 683 ድንጋጌ የመነጨ ተተክቶ የአሁን

ተጠሪን ለመጠየቅ መብት አለው፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር ክርክሩን ካለመገንዘብ ከህጉ ድንጋጌ ትርጉም ውጪ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 205570 ሚያዝያ 17 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 39741 ጥቅምት 8 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአሁን ተጠሪ ከህንጻው ላይ የወደቀው ፍርስራሽ በአሁን አመልካች ደንበኛ መኪና ላይ ላደረሰው ጉዳት ከውል ውጪ ኃላፊነት አለበት፡፡ የተጠሪ ህንጻ ላደረሰው ጉዳት የአሁን አመልካች በደንበኛው ተተክቶ የጉዳት ካሳ መጠየቅ ይችላል፡፡ የተጠሪ ህንጻ በአመልካች ድንገተኛ መኪና ላይ ላደረሰው ጉዳት ለመኪና ማስጠገኛ የወጣውን ወጪ ብር 38853.19 ተጠሪ ለአሁን አመልካች ይክፈለው፡፡ ተጠሪ አመልካች እንዲከፍለው ከጠየቀበትና ሊከፍለው ፍቃደኛ ካልሆነበት ከ16/6/2007 ዓ/ም ጀምሮ ከ9 % ወለድ ጋር ክፍያውን እስኪፈጽም ድረስ ታስቦ እንዲከፍለው ብለናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 175142

ግንቦት 24 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሠሜን ሪጅን ሑመራ ዲስትሪክት

ተጠሪ ፡- አቶ ወሉ ገ/ሔር

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በቃፍታ ሑመራ ወረዳ ማይ ከድራ ከተማ ቀጠና 02 በምኖርበት ቤት የካቲት 18 ቀን 2009 ዓ/ም በአመልካች የተዘረጋ የኤሌክትሪክ መሥመር በተነሳ የእሳት ቃጠሎ መኖሪያ ቤቴ ስለወደመ ግምቱ ብር 49,500.00 ካሣ እንዲከፈለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የሠጠው መልስ ተጠሪ ለጉዳቱ ሊጋለጡ የቻሉት ከአመልካች ድርጅት ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደምበኛ የሆኑ አቶ ማማይ ተገኝ ለግል ቤታቸው ሊጠቀሙበት ከተሠጣቸው ኤሌክትሪክ ሀይል፤ ከሕግ ውጭ ከቆጣሪው ስበው ሲጠቀሙ አደጋው ከወ/ሮ አከዛ ተስፋይ ቤት ውስጥ በራሳቸው ችግር ምክንያት የተፈጠረ ስለሆነ ልንጠየቅ አይገባም፡፡ የተዘረጋው መስመር ደረጃውን የጠበቀ በመሆኑና ጥፋት ስላልፈጸምን ለክሱ ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክሯል፡፡

የምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሑመራ ምድብ ችሎት የግራቀኙን ማስረጃ በመስማትና የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱን በመመልከት የቃጠሎ አደጋው ከወ/ሮ አከዛ ቤት መነሳቱ አልተረጋገጠም፡፡ ቢረጋገጥ እንኳን ተጠሪ ጥፋት የሌለባቸው በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2086 መሠረት አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት፡፡ በመኖሪያ ቤታቸው ላይ ለደረሠው ጉዳት ካሣ ብር 42,700.00 ከወጭና ኪሣራ ብር 3,500.00

ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ከተጠሪ ጋር የውል ግንኙነት የለንም፡፡ በፎረንሲክ ምርመራ አደጋው የተነሳው ከወ/ሮ አከዛ ቤት ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ለክሱ ኃላፊ ልንባል ስለማይገባ ውሳኔው ይሻርልን፤ አላግባብ የኤሌክትሪክ ሀይል ያከፋፈሉት አቶ ማማይ ተገኘ ጣልቃ እንዲገቡ ጠይቀንም መታለፉ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች ለተጠሪ ቆጣሪ ያልሠጠና በራሳቸው ጊዜ ከሌላ ሠው ስበው ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለብኝም በማለት እየተከራከረ ለክሱ ኃላፊ መሆኑ ከፍ/ሕ/ቁ. 2086(2) እና 2098(1)(2) አኳያ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ የተጠሪ መልስ የአመልካች መስመር ተቆርጦ ወደ መኖሪያ ቤት ወድቆ የተነሳ ቃጠሎ ነው፡፡ ጥፋቱ የእኔ የተበዳይ ስለመሆኑ እስካላረጋገጠ ድረስ ለጉዳቱ አመልካች ተጠያቂ ነው፡፡ ያጠፋሁት ጥፋት ደግሞ ስለሌለ ውሳኔው ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ለክሱ ኃላፊ መባሉ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ የጠየቁት ዳኝነት ከውል ውጭ ኃላፊነትን መሠረት ያደረገ ሲሆን በአመልካች የተዘረጋ በኤሌክትሪክ መሥመር ምክንያት በተነሳ የእሳት ቃጠሎ ቤቱ ስለወደመ ካሣ እንዲከፍለኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች ያቀረበው መከራከሪያ ተጠሪ ለጉዳቱ ሊጋለጡ የቻሉት የአመልካች ድርጅት አሠራርና ደንብ በመጣስ ሌላ ግለሠብ ቆጣሪ ለተጠሪዎች እና ለሌሎች ግለሠቦች የኤሌክትሪክ ገመድ በመዘርጋት ኤሌክትሪክ ሀይል በመስጠታቸው እና አደጋውም ከወ/ሮ አከዛ ተስፋይ ቤት ውስጥ በራሳቸው ችግር ኤሌክትሪክ ሰርኪዩት ሾርት ምክንያት የተፈጠረ ስለመሆኑ የትግራይ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ባደረገው የፎረንሲክ ቃጠሎ ማጣራት አረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የአመልካች ደምበኛ አይደሉም፡፡ ኤሌክትሪክ ሀይል የሚጠቀሙትም በሕገ-ወጥ መንገድ በተቀጠለ ገመድ ስለሆነ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ነው፡፡

በፍ/ሕ/ቁ. 2069(1) መሠረት እንደተመለከተው አንድ ሠው ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር በመዘርጋት በሌላ ሠው ላይ ጉዳት ካደረሠ ለጉዳቱ ኃላፊ ነው፡፡ የኤሌክትሪክ መስመሩን የዘረጋው ሰው ጥፋት ባይኖርበትም የንብረቱ ባለቤት በመሆኑ አጥፊ ሳይሆን አላፊ ስለመሆን በተደነገገው ክፍል ስር በተመለከተው አግባብ ለጉዳቱ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ ከኃላፊነት ለመዳን በፍ/ሕ/ቁ 2086(2) እንደተመለከተው ጉዳቱ የደረሠው በተበዳዩ ጥፋት መሆኑን ማስረዳት አለበት፡፡ በሥር ፍርድ ቤቶች የተወሰነውም አመልካች ለዘረጋው የኤሌክትሪክ መስመር ለሚያስከትለው ጉዳት ኃላፊነት አለበት በማለት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሕግ ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበውን ፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱን ባለመቀበል ማስረጃ መዝነው አመልካች በዘረጋው የአሌክትሪክ መሥመር ጉዳት ደርሷል በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም። ነገር ግን ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ ወይም በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፤ በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎም ስህተትና ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ይሆናል።

ጉዳት ያደረሠው ተጠሪ እና ሌሎች ግለሠቦች ከአመልካች ደምበኛ ሳይፈቀድላቸው ስበው በወሰዱትና ቤታቸው ወስጥ በዘረጉት የኤሌክትሪክ መሥመር ሀይል ስለመሆኑ በትግራይ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን በባለሙያ በተደረገ የፎረንሲክ ቃጠሎ ምርመራ ውጤት ተረጋግጧል። የባለሙያ ማስረጃ በቀረበ ጊዜ በዋናነት የሚመረመረው የባለሙያው ገለልተኛነት እና ሙያዊ ብቃት ሲሆን ሁለቱን መስፈርቶች ካሟላ ማስረጃው የፍሬ ነገሩን መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ ከፍተኛ ግምት የሚሠጠው (high probative value) ማስረጃ እንደሆነ ተቀባይነት ካላቸው የማስረጃ ምዘና መርሆዎች የምንረዳው ነው። የሥር ፍርድ ቤቶች ከኤሌክትሪክ አደጋ ጋር በተያያዘ የሚደርስ ጉዳት የአደጋውን መንሥዔ ለማወቅ ሙያ የሚጠይቅ ሆኖ እያለ ለባለሙያ ማስረጃው ውጤት ሳይሰጡ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱን አለመቀበላቸው የማስረጃ ምዘና መርህ ስህተት ነው። የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱ ቃጠሎ ሊያስነሳ የሚችሉ ሁኔታዎች እንዳልነበሩ፣ የቃጠሎው ምክንያት በኤሌክትሪክ ሰርኪዩት ሾርት ምክንያት አቀጣጣይ ሀይል መሆኑን፣ ቃጠሎው ከወ/ሮ አከዛ ቤት ተነስቶ ወደ ሌሎች ቤት እንደተሸጋገረ እና በአመልካች በዘረጋው ፖል ገመድ ላይ ቃጠሎው ጉዳት አድርሶ የተበጠሰ ስለመሆኑ በተመሳሳይ የቃጠሎ አደጋ ይሕ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 175139 ውሳኔ በሠጠበትና በተያዘው መዝገብ የተረጋገጠ ነው። ይህም ጉዳት ያደረሠው አመልካች የዘረጋው የኤሌክትሪክ መሥመር አለመሆኑን ያሳያል።

አመልካች ራሱ ለዘረጋው የኤሌክትሪክ መሥመር ኃላፊነት ይወስዳል እንጂ ግለሠቦች በቤታቸው ለዘረጉትና ባለቤት ላልሆነበት የኤሌክትሪክ መሥመር አጥፊ ሳይሆኑ ኃላፊ ስለመሆን በተደነገገው የውል ውጭ ኃላፊነት የፍትሐ ብሔር ሕግ ክፍል (ከፍ/ሕ/ቁ 2066 - 2086) ስር ኃላፊ ሊሆን አይችልም። የፍ/ሕ/ቁ 2069(1) ኃላፊነትን በግልጽ ያቋቋመው የኤሌክትሪክ መሥመሩን የዘረጋው ሠው

ላይ ነው። ይህም አጥፊ ሳይሆኑ ኃላፊ ስለመሆን ከውል ውጭ የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት የሚከተለው የኤሌክትሪክ መሥመሩን ባለቤት እንጂ የኤሌክትሪክ ሀይሉን ባለቤት አለመሆኑን ያሳያል። የኤሌክትሪክ ሀይሉ ባለቤት ኃላፊነት ሊኖርበት የሚችለው ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ካላደረገና ጥፋት ከፈጸመ ብቻ ነው።

አመልካች በዘረጋው ከቆጣሪው በመለስ ባለው መስመር ላይም ላደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የሚኖርበት ቆጣሪ ለሠጠው ደምበኛ ላይ ለደረሠ ጉዳት ነው። ተጠሪ የአመልካች ደምበኛ እና ፈቃድ ወስደው የኤሌክትሪክ መሥመር ያስገቡ አይደሉም። ከአመልካች ፈቃድ ውጭ ተጠሪ እና ወ/ሮ አከዛ ተስፋይ በራሳቸው በዘረጉት የኤሌክትሪክ መሥመር ምክንያት ለደረሠ ጉዳት አመልካች ኃላፊነት የለበትም። ስለሆነም አመልካች ለጉዳቱ ከውል ውጭ የፍትሐብሔር ኃላፊነት ሳይኖርበት ኃላፊ እንዲሆን የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 110766 ጥር 10 ቀን 2011 ዓ.ም እና የምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሐመራ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 15158 መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም የሠጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል።

2. አመልካች ለጉዳት ካሣው ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ተወስኗል።

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሱን እንዲችል ብለናል።

ት ዕ ዛ ዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ።
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የወንጀል ሕግ

የሰ/መ/ቁ 153016

ጥር 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- ወ/ሮ ከበደች ዘሚካኤል

ተጠሪ፡- የአራዳ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 21 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 27532 ታሕሳስ 19 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ግብርን የሚመለከት ሲሆን የአሁን አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በዚህ የሰበር አቤቱታ የተያዘውን ጉዳይ በተመለከተ ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት በአጭሩ በአራዳ ክፍለ ከተማ በመኪና ጌጣጌጥ ንግድ ስራ የተሰማሩ መሆኑን፤ ከተጠሪው ሚያዝያ 26 ቀን 2008 ዓ.ም ተወስኖ በደረሳቸው የአዲት ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ኮሚቴው ቅሬታቸውን ሳይመረምር ውሳኔውን ያጸናው መሆኑን፤ በድርጅታቸው ውስጥ በአደራ ተቀምጠው በተገኙ የቀድሞ ባለቤታቸው የግል ማስታወሻዎች ላይ በመንተራስ ቀደም ሲል ከ2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ያሳወቁትን ዓመታዊ ሽያጭ ገቢ በመቀየር ፈጽሞ ባልሰሩት እና ባላገኙት ገቢ ብር 1,698,297.96 ግብር እና ታክስ ወለድ እና መቀጫ እንዲከፍሉ የተጠየቁ መሆኑን እና የራሳቸው ባልሆነ የግኝት ምንጭ በመንተራስ ተገቢውን የመረጃ ማጣራት ስራ ሳይሰራ የተወሰነባቸው መሆኑን፤ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አሳሽ ቡድን ከድርጅቱ የሌላ ግለሰብ ማስታወሻዎች ሲወስድ የአመልካች አለመሆኑን

ያስረዱ ቢሆንም በድጋሚ ተጠርተው በድርጅቱ በተገኙት ሰነዶች ላይ የድርጅቱን ማህተም እንዲያሳርፉ የተገደዱ መሆኑን በመግለጽ ሰነዱን መሰረት በማድረግ የተሰጠው የግብር ውሳኔ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች እና ሌሎች በአካባቢው በተመሳሳይ ስራ ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች አየር በአየር ግብይት እንደሚያከናውኑ እና ምንጩ ያልታወቀ ሀብት እንደሚያንቀሳቅሱ በተደረገው ጥናት መሠረት በግብር ከፋይዋ ድርጅት በአካል በመገኘት ባደረገው ድንገተኛ ፍተሻያገኛቸውን ሰነዶች ለጉዳዩ አግባብነት አዲት በማድረግ በደረሰበት ውጤት መሠረት እና በቀን ገቢ ግምት መሠረት ለዘጉት የሀገር ውስጥ ችርቻሮ ንግዳቸው ያላሳወቁት ገቢ መኖሩ ተደርሶበት ከ2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ላሉት የግብር ዘመናት ያቀረቧቸው የሂሳብ መዝገቦችን አስተካክሎ ተጨማሪ ግብር የወሰነ መሆኑን፤ የግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት በአመልካች ድርጅት በአካል በመገኘት ንግድ ባካሄዱባቸው ወቅት ያዘጋጇቸው ማስታወሻ ደብተሮች ያገኘ መሆኑን፤ አመልካች ሰነዶቹ የባለቤታቸው ለመሆኑ ምንም ዓይነት ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን፤ በተቃራኒው ደብተሮቹ የተገኙት በድርጅታቸው ውስጥ ከመሆኑም በላይ በውስጣቸው የያዙት መረጃ አመልካች ስለሚሸጡት የመኪና ጌጣጌጥ ዕቃዎች ዓይነት እና ዝርዝር ዋጋ ዕቃዎቹ ለማን እንደተሸጡ በቅድሚያስለተፈጸሙ ክፍያዎች እና ስለቀሪ ክፍያዎች የሚሳዩ መረጃዎች መሆናቸውን፤ በሚስጥር ከተደረገው የብርበራ ቀን በኋላ አመልካችን ጨምሮ በተመሳሳይ ንግድ ላይ የተሰማሩ 15 ግብር ከፋዮች አየር ባየር ንግድ እንደሚያከናውኑ እና ምንጩ ያልታወቀ ሐብት እንደሚያንቀሳቅሱ በጥናት የተደረሰበት መሆኑን እና ማስታወሻዎቹ ለአመልካች ተሰጥተው የራሳቸው የሆኑትን አራት ደብተሮች የለዩ እና ማሕተም ያሳረፉበት መሆኑን በመግለጽ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ አመልካችዋ ገቢ ደብቀዋል በማለት ግብር እና ታክስን ለመወሰን የተጠቀመው እና መነሻ ያደረገው የአመልካች ናቸው የተባሉትን አራት ማስታወሻ ደብተሮች የአመልካች መሆኑን በመጥቀስ ነው፤ በግብር አወሳሰን ስርዓት ውስጥ የታክስ ስወራን ለመከላከል እንደመረጃ የሚወስድበት አግባብ ግብር ከፋዮች በየእለቱ የሚያከናውኑትን የዕለት ከዕለት ሽያጭ በግል ማስታወሻም ሆነ በሌሎች አማራጭ ሂሳባቸውን የሚከታተሉበት እና የሚያውቁበት እንዲሁም ሌሎች የግል ጉዳዮችንም የሚያገዘበት ሁኔታ ሊሆን እንደሚችል ታሳቢ ሊደረግ የሚገባ ከመሆን ባለፈ የተደበቀ ገቢ መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ የመሆን ብቃት ሊኖረው እና ፍትሐዊ የአወሳሰን ዘዴ መሆኑን በአግባቡ ማረጋገጥን የሚጠይቅ ነው፤ በግል ማስታወሻ ደብተር ከተጠቀሰው ገንዘብ መጠን ውስጥ በሀሰተኛ ደረሰኝ ግብይት የተፈጸመበት ግኝት ወይም ያለደረሰኝ የዱቤ ሽያጭ ወይም የእጅ በእጅ ሽያጭ የተሸጠ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የሚያሳይ ውጤት በሌለበት የግል ማስታወሻ ላይ የተጻፈውን የተለያየ ይዘት ያላቸውን ሁኔታዎች ብቻ በመውሰድ ግብር እና ታክስ እንዲወሰን መደረጉ አመልካች በየዓመቱ ካሳዩት እና

ካሳወቁት የገቢ ዕድገት አንጻር የሚጣጣም እና ፍትሐዊ ሆኖ አልተገኘም፤ አመልካች በደረሰኝ ግብይት አለማከናወናቸውን የሚያሳይ ተጨባጭ ግኝት ስለመኖሩም አብሮ ሊታይ ይገባል፤ የግል ማስታወሻ መያዝ የተለመደ የግል ጉዳይ ከመሆኑ አንጻር በግብር ከፋዮች ዘንድ የእጅ ማስታወሻ ከተገኘ ግብር ይጣልብኛል የሚል ስጋት ወደ መፍጠር የሚያመዝን ከመሆን በዘለለ በትክክለኛ ግኝት ላይ የተመሰረተ ሕጋዊ ውሳኔ ለመስጠት የሚያረጋግጥ ማስታወሻ አይደለም በማለት ይህንኑ መሠረት ተደርጎ የተሰጠውን የግብር ውሳኔ ሽሮታል፡፡

የአሁን ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለአዲአበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ተጠሪ በመቀጠል ለአዲስአበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የኢንተሊጀንስ ዳይሬክቶሬት በአካባቢው ተመሣሣይ የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎችን የንግድ ድርጅት ላይ ባደረገው ድንገተኛ ብርበራ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን የግል ሰነዶች ከአመልካች የንግድ ድርጅት ስለመገኘታቸው እና እነዚህም ሰነዶች የአመልካች ስለመሆናቸው የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ተቀብሎ እነዚህ ሰነዶች የግል ሰነዶች በመሆናቸው ተጠሪ በእነዚህ የግል ሰነዶች ብቻ ገቢን ደብቀዋል ለማለት የማይቻል እና የተጠሪን ገቢ በየዓመቱ የ26% ዕድገት ያሳየ በመሆኑ በእጅ ጽሑፍ በግል ማስታወሻ ደብተር ላይ የተጻፈን የቁጥር ጽሑፍ ብቻ እንደገቢ በመውሰድ ተጨማሪ ግብር መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት ነው፤ ይሁን እንጂ የተጠሪ ጽ/ቤት በእነዚህ የተጠሪ የግል ማስታወሻዎች ላይ ተመስርቶ ተጨማሪ ግብሩን የወሰነው በጥናት ላይ ተመስርቶ እና እነዚህ ሰነዶች ተጠሪ ከሚነግዱበት ንግድ ጋር በቀጥታ የተገናኘ እና በሒሳብ አዋቂ ተረጋግጦ እና ማስረጃ ቀርቦ በመሆኑ የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ የገቢ ግብር አዋጅን አንቀጽ 38/2/ሀ እና 66/5 እንዲሁም የፍ/ብ/ህ/ቁ 1677/1፤2017 እና 2018 ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ እና የስር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የተጠሪ ጽ/ቤት በቁጥር 29-4-1/2685/08 በቀን 26/08/08 ዓ.ም ለአመልካች ወስኖ የሰጣቸው ተጨማሪ የንግድ ትርፍ ግብር ፍሬግብር ወለድ እና መቀጫን ጨምሮ እና የተጨማሪ እሴት ታክሱን ፍሬግብሩን ወለድ እና መቀጫውን ጨምሮ የተሰጣቸውን የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የአዲስአበባ ከተማ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተፈጸመን የሕግ ስሕተት ማረም እንጂ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም፤ በብርበራ የተገኙት ሰነዶች የአመልካች አለመሆናቸውን ለጉባኤው ማስረጃ አቅርቤአለሁ፤ ጉባኤውም ደብተሮቹ

የአመልካች ናቸው አላለም፤ ደብተሮቹ የአመልካች ናቸው ባልተባለበት ሁኔታ የአመልካች እንደሆኑ ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም፤ አመልካች ያላሳወቅኩት ወይም የደበቅኩት ገቢ የለም፤ የሒሳብ መዝገቤ ተቀባይነት አግኝቶ ግብር እና ታክሱ ስለመወሰኑ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አልካደም፤ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ባለው የግብር ዘመን ዓመታዊ ገቢዬ እየጨመረ የሄደበት ሁኔታ እንጂ አመልካች የቀነስኩት ገቢ እንዳለ በተጨባጭ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ የአዲስአበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት ሰነዱ የአመልካች መሆኑ ተረጋግጧል በማለት የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ እና የስር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰጡትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ገቢያቸውን አሳውቀው ሳለ ከድርጅታቸው ተገኘ የተባለውን የግል ማስታወሻ ከሚደረገው ግብይት ግንኙነት አለው ተብሎ ግብር እንዲከፍሉ የመደረጉን አግባብነት ከግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 38 እና 66/5 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ ደብተሮቹ የአመልካች መሆናቸውን ጉባኤው ባረጋገጠበት ሁኔታ የንግድ እንቅስቃሴአቸውን በሚያሳዩት በእነዚሁ ደብተሮች ላይ ተመርኩዘን በኦዲት የወሰነው ተጨማሪ ግብር በሕጉ አግባብ በመሆኑ እና ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከርበት የግብር ታክስ አሰራር ስርዓት መከበር ጉዳይ በመሆኑ የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች እና በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

ተጠሪው መስሪያ ቤት ከ2003 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ላሉት የግብር ዘመናት አመልካች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዝገቦችን መርምሮ እና አስተካክሎ ተጨማሪ ግብር ሊወስን የቻለው አመልካች እና ሌሎች በአካባቢው በተመሳሳይ የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች አየር በአየር ግብይት እንደሚያከናውኑ በተደረገው ጥናት በግብር ከፋይዋ ድርጅት በአካል በመገኘት ባደረገው ፍተሻ ንግድ ባካሄዱባቸው ወቅት ያዘጋጇቸው ማስታወሻ ደብተሮች አግኝቻለሁ፤ አመልካች ሰነዶቹን ለይተው ማሕተም አሳርፈውበታል፤ ሰነዶቹ አመልካች ስለሚሸጡት የመኪና ጌጣጌጥ ዕቃዎች ዓይነት እና ዝርዝር ዋጋ ዕቃዎቹ ለማን እንደተሸጡ በቅድሚያ ስለተፈጸመ ክፍያዎች እና ስለቀሪ ክፍያዎች የሚሳዩ መረጃዎች ናቸው በሚል መሆኑን፤ አመልካች በበኩላቸውም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተጨማሪ ያሳወቃውን የግብር ውሳኔ ልከፍል አይገባም በማለት የሚከራከሩት በብርበራ የተገኙት ሰነዶች

የአመልካች አይደሉም፤ አመልካች የደበቅኩትም ሆኖ ያላሳወቅቱም ገቢ የለም በሚል መሆኑን፤ የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤው አመልካች ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተጨማሪ እንዲከፍሉ ያሳወቃቸውን የግብር ውሳኔ ሊከፍሉ አይገባም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው ሰነዱ የተደበቀ ገቢ መኖሩን የሚያሳይ ሰነድ የመሆን ብቃት የለውም፤ በግል ማስታወሻ ደብተር ከተጠቀሰው ገንዘብ መጠን ውስጥ በሀሰተኛ ደረሰኝ ግብይት የተፈጸመበት ግኝት ወይም ያለደረሰኝ የዱቤ ሽያጭ ወይም የእጅ በእጅ ሽያጭ የተሸጠ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የሚያሳይ ውጤት በሌለበት የግል ማስታወሻ ላይ የተጻፈውን የተለያየ ይዘት ያላቸውን ሁኔታዎች ብቻ በመውሰድ ግብር እና ታክስ እንዲወሰን መደረጉ አመልካች በየዓመቱ ካሳዩት እና ካሳወቁት የገቢ ዕድገት አንጻር የሚጣጣም እና ፍትሐዊ ሆኖ አልተገኘም በሚል መሆኑን፤ ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የስር ፍ/ቤትም ሰነዶቹ የአመልካች የግል ሰነዶች መሆናቸው ጉባኤው ተቀብሎታል፤ የተጠሪ ጽ/ቤት በእነዚህ የተጠሪ የግል ማስታወሻዎች ላይ ተመስርቶ ተጨማሪ ግብሩን የወሰነው በጥናት ላይ ተመስርቶ እና እነዚህ ሰነዶች ተጠሪ ከሚነግዱበት ንግድ ጋር በቀጥታ የተገናኘ እና በሒሳብ አዋቂ ተረጋግጦ እና ማስረጃ ቀርቦለት በመሆኑ አመልካች የተጠየቁትን ተጨማሪ ግብር ሊከፍሉ ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ መሆኑን ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ ችለናል፡፡

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 38/2 ድንጋጌ እንደሚያመለክተው በማንኛውም ሌላ ሕግ ውስጥ ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎች ቢኖሩም የግብር አስገቢው ባለስልጣን በማንኛውም ጊዜ በግብር ከፋይ የቀረቡ ማንኛውንም መግለጫዎች ሰነዶች እና የሂሳብ መዝገቦች ለማረጋገጥ ሕጋዊ ሥልጣን የተሰጣቸው ተቆጣጣሪዎችን ወደ ግብር ከፋዩ የንግድ ወይም የሙያ ስራ ቦታ በመላክ ገቢ እና ወጪን የሚያሳዩ ሰነዶችን፤ ለንግድ የተከማቹ ዕቃዎችን፤ ሌሎች ዕቃዎችን፤ ወይም የሒሳብ መዛግብትን እና ሰነዶችን ለማመሳከር እና ለመመርመር እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 66/5 በገቢ ማስታወቂያው ላይ የተመለከተው እና በዘመኑ መከፈል ያለበት ግብር፤ በግብር አስገቢው ባለስልጣን የተወሰነው ግብር ሆኖ ይቆጠራል፤ ሆኖም የግብር አስገቢው ባለስልጣን ስህተት ወይም ያልተካተተ ገቢ ያለ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ውሳኔውን በዚያው መጠን በማሻሻል የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ይሰጣል በማለት ይደነግጋል፡፡

በያዝነውም ጉዳይ አመልካች ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም ያቀረቡትን የሂሳብ ሰነዶች በመመርመር ከአመልካች ግብይት ጋር በማገናዘብ ያላሳወቁት ገቢ አለ በሚል ግምት በአመልካች ድርጅት በመገኘት ንግድ ባካሄዱበት ወቅት ያዘጋጃቸውን ማስታወሻዎች በንግድ ድርጅቱ ውስጥ ማግኘታቸውን ይኸው አመልካች ስለሚሸጡት የመኪና ጌጣጌጥ ዕቃዎች፤ ለማን እንዴት እንደተሸጠና ክፍያን የተመለከተ መሆኑን እና የተገኙት ማስታወሻዎችም ከአመልካች ስለመሆኑ በድርጅቱ እንዲረጋገጥ ካደረጉ በኋላ ተጨማሪ ግብር የተወሰነ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአዋጅ 286/94 አንቀጽ 38 እና 66/1/ የተመለከተ ነው፡፡በዚህም መሰረት ተጠሪ ይህንኑ በአዋጁ በተመለከተው መሰረት በማድረግ አመልካች ገቢውን በየጊዜው እያሳወቀ ግብሩን እየከፈለ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም ብሎ በማመመኑና እነዚህን

ሠነዶች እና የሂሳብ መዝገብ በማናቸውም ጊዜ ለመመርመርና ለማረጋገጥ የሚችል በመሆኑ በአመልካች የተገኙትን የግብይት ማስታወቀሻዎች በተጠሪ ባለሙያዎች ተመርምረው ተጨማሪ ግብር መወሰኑ የገቢ ግብር አዋጁን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም ። በዚህ መሠረት ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 27532 ታሕሳስ 19 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ 161867
ሚያዚያ 25 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች :-የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን

ተጠሪ :-ሱፐር ማክስ አብቲካል ሚዲያ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 24 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በመ/ቁ ከሱ-1019 ነሐሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 185869 በቀን 04/07/2010 እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 155956 በቀን 24/08/2010 ዓ.ም በማጽናታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የንግድ ትርፍ ግብርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በ21/02/2007 ዓ.ም የደረሰውን የ2010 ዓ.ም የግብር ዘመን የንግድ ትርፍ ግብር በመቃወም ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቢያቀርብም ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ያቀረበው ይግባኝ ይዘት ድርጅቱ በኤሌክትሮኒክስ ነክ አታሚነት ዘርፍ ሐምሌ 16/2000 በተሰጠው ፈቃድ ሲዲ እና ዲቪዲ፤ ኦዲዩ ቪዲዬ እና ተያያዥ ምርቶችን የሚያመርት መሆኑን፤ ለዚሁ ተግባር በኢንቨስትመንት ማበረታቻው በመጠቀም የማምረቻ ማሽን ዕቃዎችን ያስገባ መሆኑን፤ በዚህም ለ2000 ዓ.ም በጀት ዓመት ቀሪው 14 ቀን ቢሆንም የ2000 ዓ.ም የሐብትና ዕዳ መግለጫ ለግብር አስገቢው መ/ቤት አሳውቋል፤ ሆኖም በዚህ ዘመን ንግድ ፈቃድ የወሰደበት እንጂ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ማምረትና መሸጥ ያልተጀመረበት ሆኖ ሳለ የሐብትና ዕዳ መግለጫ ሲዘጋጅ ለምስረታና ማሽነሪ ግዢ የወጡትን ወጪዎች በበጀት ዓመቱ የደረሰ ኪሳራ እንደሆነ የሚያሳይ ሰነድ ቀርቧል፤ ግብይት ባልተደረገበት በጀት ዓመት ሊታይ እና ሊያዝ የሚችል ኪሳራ

አለመኖሩ የሚታወቅ በመሆኑ በ2001 በበጀት ዓመት ላይ ሊያገዝ የሚገባ በመሆኑ ማስተካከያ እንዲደረግ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን አሳውቀናል፣ በ2001 እና በ2002 በጀት ዓመት ኪሳራ የታየ እና በ2003 ትርፍ ማስመዝገብ የጀመርን መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ አመልካች በ21/07/07 በተጻፈ የንግድ ትርፍ ግብር ማስታወቂያ በ2002 ዓ.ም ግብር የሚከፍልበት ትርፍ አለ በማለት ግብር ፤ወለድና መቀጫ በማስላት በድምሩ ብር 824317.41 እንድንከፍል በግብር ውሳኔ አሳውቆናል ስለሆነም በ2000 በጀት ዓመት ኪሳራ ተብሎ የቀረበው በ2001 በቀረበው የሂሳብ ሰነድ የተስተካከለ በመሆኑና ኪሳራ ደርሶበታል የሚባለው ማምረት እና ግብይት መፈፀም ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ ኪሳራው የደረሰው በ2001 ዓ.ም ይባልልን፣ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1/ መሠረት ኪሳራው ለሶስት ተከታታይ ዓመት የሚሸጋገር በመሆኑ በ2002 የግብር ዘመን ኪሳራ አለመድረሱ በሒሳብ በባለሙያ ተረጋግጦ ቀርቦ ኪሳራ የለም በ2001፤ የደረሰውም ኪሳራ ወደ 2002 ማሸጋገር አትችሉም ተብሎ አቤቱታው ውድቅ የተደረገው ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች በሰጠው መልስም ግብር ከፋዩ የሚያቀርበው መረጃ በግብር ህጉ በደንብ እና በመመሪያ መሠረት መሆን የሚጠበቅበት በ2000 ዓ.ም ግብይት መፈፀም አልጀመርኩም ይበል እንጂ እንደጀመረ አረጋግጠናል፣ ለዘመኑ ኪሳራ ተብሎ የተገለፀው በእርጅና ቅናሽ ላይ መቀነስ የነበረበት ገንዘብ መጠን ነው፣ ማስተካከያ ቀርቧል ይበል እንጂ አልቀረበም፣ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1/ እና /3/ ኪሳራ ሊሸጋገር የሚችልበትንና ሁኔታና ጊዜ የተደነገገ ሲሆን በደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 12 ደግሞ ኪሳራው ሊሸጋገር የሚችለው በግብር ባለሥልጣኑ ኦዲት ተደርጐ ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም በውጭ ኦዲተር የተመረመረ ሂሳብ ሲቀርብ በመሆኑ ተጠሪ የ2000 ግብር ዘመን የሂሳብ መዝገቡ በባለሥልጣኑ ኦዲተር ስላልተረጋገጠ ያልተያዘላቸው ሲሆን የ2001 ኪሳራ ግን በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ በመሆኑ በባለሥልጣኑ ባይረጋገጥም በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ በመሆኑ ኪሳራው ተይዞለት በ2003 ካገኘው ትርፍ ተካክሶ ግብር የተወሰነ በመሆኑ ተጠሪ እንደሚለው አይደለም፤ ይህም የተጠሪ ጥያቄ እርስ በርሱ የሚጋጭ ነው፤ ኪሳራ የሚሸጋገረው ወደ ተገኘበት የግብር ዘመን ነው፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ተገቢ በመሆኑ ይጽናልኝ፣ ተጠሪ በ2000፣ በ2001፣ በ2002 የግብር ዘመን ኪሳራ ያሳወቀ በመሆኑ በተጠቀሰው አንቀጽ መሠረት የ2002 ኪሳራ ሊሸጋገር አይችልም ብሏል፡፡

የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔው የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ በ2000 ዓ.ም የምስረታ ወጪን በስህተት የኪሳራ ማሳወቂያ ላይ በመሙላት የተፈጠረውን ስህተት ማረሚያ የሚሆን የ2001 ዓ.ም የሐብትና ዕዳ መግለጫ ላይ ማስተካከያ አቅርቤያለው በሚለው ላይ የሂሳብ መግለጫው በድጋሚ ታይተው እንዲቀርቡ ለተከራካሪዎች ታዞ የአሞላል ስህተቱ የማስተካከያ እርምጃ ተጠሪ የወሰደ መሆኑን፣ መቼ የሚለውም የቀረበው ማስተካከያ ላይ ሲታይ በ2001 ዓ.ም የሐብት እና ዕዳ ማሳወቂያ ላይ እንደሆነ ጉባዔው የተገነዘበ መሆኑን ገልጾ የ2000 ዓ.ም ኪሳራን በስህተት ማሳወቁን ከቀረበው ሰነዶች እና ተፈፀመ የተባለው ስህተት ማስተካከያ ማቅረቡም በግራ ቀኙ የተረጋገጠ፤ በ2000 ዓ.ም

ኪሳራ ደርሷል ተብሎ የተያዘው በስህተት እንደሆነ በጉባዔው የተረጋገጠ በመሆኑ ኪሳራው የደረሰው በ2001 እና በ2002 ዓ.ም በመሆኑ በዚሁ አግባብ የግብር ኃላፊነት ተስተካክሎ እንዲሰላ ጉባዔው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማና ከመረመረ በኋላ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔውን ውሳኔ ሲያፀናው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በይግባኝ ቀርቦ ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልገው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙን ዘግቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በ2000 ዓ.ም ኪሳራ በስህተት ለአመልካች ያሳወቀ ስለመሆኑ ከቀረቡት ሰነዶች ጉባዔው የተረዳ መሆኑን የገለፀ ቢሆንም በአንድ የግብር ዘመን የቀረበ ሂሳብ መዝገብ ስህተት ካለበት ማስተካከያ መቅረብ ያለበት በቀጣዩ የግብር ዘመን ሆኖ ተቀባይነት የሚያገኘውም ግብር የሚከፈልበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሲያጸድቀው እና ማስተካከያ ሲሰጥበት ነው ተጠሪ ይህንን አላስረዳም፣ ማስተካከያውም መቅረብ ያለበት በ2001 ማሳወቅ የነበረበት በመሆኑ አያገለግልም፤ የቀረቡትን ማስረጃዎች በሚገባ አልተመዘኑም፤ በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በተከራካሪዎች ወገኖች ያልተነሳን የንግድ ፈቃድ መኖርና ማረጋገጥ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሠጥቷል፤ በ2000 ኪሳራ ተደርጐ የቀረበው የሂሳብ መግለጫ የእርጅና ቅናሽ ተብሎ ለአመልካች ያሳወቀ ስለመሆኑ የፍሬ ነገር ክርክሩን በሚያጣራው አካል የተረጋገጠ ነው በማለት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም የምስራቅ ቅርንጫፍ የግብር አወሳሰን አሰባሰብ እና ክትትል የሥራ ሂደት የሂሳብ መዝገቡ ላይ ምንም ማስተካከያ እንዳልቀረበ አረጋግጧል፣ ስለሆነም ለጉባዔው ተጣርቷል የተባለበት ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ከግብር አዋጁ 286/94 አንቀጽ 28/1/ አንጻር ለመመርመር ተጠሪ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት በሰጠው መልሱ በ2000 ዓ.ም ድርጅቱ ገና የንግድ ሥራውን ለመጀመር ቅድመ ዝግጅት ሂደት ላይ የቆየበት ጊዜ በመሆኑ በሐብትና ዕዳ ማሳያ ላይ ኪሳራ በመገለጹ እና በተግባር ኪሳራ ሳይደርስ አመልካች የወሰደ ቢሆንም በ2001 የሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ተደርጓል፣ ይህ በጉባዔውም ተረጋግጧል ተወስኗል፤ በሂሳብ አያያዝ ረገድ የተፈፀሙ ስህተቶች ደግሞ የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ የህግ ጉዳይ ባለመሆኑ በአዋጅ 286/94 አንቀጽ 112/1/ እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320/1/ መሠረት ይግባኙ የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ተጠሪ ስህተቱን በቀጣዩ የግብር ዘመን በ2001 አሳውቀናል፡፡ ስለሆነም በአዋጁ አንቀጽ 28 መሠረት እንድንስተናገድ የሶስት የግብር ዘመን ኪሳራ አልተጠየቀም ፤የክርክሩም ጭብጥ አይደለም፤ ጉባዔው በስህተት የቀረበውም አጣርቶ በሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች እና ሰነዶች ጭምር የተረጋገጠ በመሆኑ የተሰጠ ውሳኔ ነው ፤ይግባኝ ሰሚው ፌ/ከ/ፍ/ቤት ይህንኑ ነው ያፀናው ስለሆነም

ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም በጽሁፍና በቃል በነበረው ክርክር ድርጅቱ ኪሳራ ሊደርስበት የሚችለውን የንግድ ሥራ ቁመና የነበረውን በማረጋገጥ የተሰጠ እንጂ አንደ አዲስ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ አይደለም፣ ተጠሪ በ2000 ዓ.ም የተፈጠረውን ስህተት እንደተረዳ በ2001 የሂሳብ መግለጫ ላይ ማስተካከያ አሳውቀናል ማስረጃውም ለሥር ፍ/ቤት የቀረበ እንጂ በ2002 የቀረበ አይደለም ማስተካከያው ዘገየ በሚል ምክንያት የግብር ኃላፊነት መጣል ተቀባይነት ያለው አይደለም፤ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የፍሬ ነገርን የማጣራት ሥልጣን የጉባዔው ነው በማለት የሰጠው እንጂ የከፍተኛው ፍ/ቤት ሥልጣን የለውም አላለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡ አመልካችም አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በኤሌክትሮኒክስ ነክ አታሚነት ዘርፍ ሐምሌ 16 ቀን 2000 ዓ.ም ፈቃድ የወሰደ መሆኑንና በዚሁ ዘመን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ያልጀመረበት ቢሆንም የ2000 በጀት ዓመት የሀብትና ዕዳ መግለጫ ሲዘጋጅ የካፒታል ዕቃዎች እና የእርጅና ቅናሽ ተቀናናሽ መሞላት ካለበት ፎርም ኪሳራ ማሳወቂያ ላይ የተላለፈና ስህተት በ2001 የድርጅቱ ሂሳብ መግለጫ ማሳወቁን ይህም በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔውም መረጋገጡን በተጨማሪም በሰነዶች እና በግራ ቀኙ መረጋገጡን ስለሆነም የ2001 የደረሰው ኪሳራ ታስቦ ወደ 2002 የግብር ዘመን ሊሸጋገር የሚገባ በመሆኑ ይኸው ተሰልቶ ግብሩ እንዲወሰን የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡

በመሠረታዊነት በንግድ የግብር ዘመን የደረሰ ኪሳራ ሊሸጋገር የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 28/1/ እና /3/ እንደተመለከተው ከሚቀጥሉት ሶስት የግብረ ዘመናት ውስጥ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ መጀመሪያ ያጋጠመው ኪሳራ በኋላ ካጋጠመው አስቀድሞ በማካካስ ሊሸጋገር የሚችል እና ይህም በማናቸውም ሁኔታ ከሁለት ሶስት ዓመታት ከሚቆጠሩ ስድስት ዓመታት በላይ ሊሸጋገርና ሊቀናነስ እንደማይችል እና በደንብ ቁጥር 78/1994 እንደተሻሻለው አንቀጽ 12 መሠረት የግብር ከፋዩ ኪሳራ ሊሸጋገር የሚችለው በግብር ባለሥልጠኑ ኦዲት ተደርጐ ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ ሲቀርብ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የሂሳብ ሪፖርት በ2000፣ በ2001 እና 2002 የግብር ዘመን የሐብትና ዕዳውን ሲያሳውቅ የ2000 ዓ.ም የሐብትና ዕዳ መግለጫው ሲዘጋጅ ድርጅቱ ሐምሌ 16/2000 ዓ.ም የንግድ ፈቃዱን የወሰደ በመሆኑ የካፒታል ዕቃዎች እና የእርጅና ቅናሽ ተቀናናሽ መሙላት ሲገባው የኪሳራ ማሳወቂያ ፎርም መሙላትና ማስተላለፉን ይህንኑ ስህተት በ2001 ሂሳብ ላይ ያሳዩ መሆኑን፤ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ማስረጃዎችን በመመርመር መገንዘቡን፣ በተጨማሪም በተከራካሪ ወገኖች

የተረጋገጠ በመሆኑ በ2000 ኪሳራ ደርሳል ተብሎ የወሰደው ስህተት መሆኑን ማረጋገጡን ጉባዔው ፍሬ ነገሩንና ማስረጃዎችን በሚመዝን ጊዜ አረጋግጧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 112/1/ መሠረት ደግሞ በጉባዔው በተሰጠ ውሳኔ ላይ በህግ ረገድ ስህተት ነው በማለት የሚቀርበው ብቻ ይግባኙ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ የሚታይ በመሆኑና ይኸው ፍሬ ነገር እና ማስረጃ በመመዘን የተደረሰበት ድምዳሜ በፌደራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የፀና በመሆኑ ይህ ችሎትም እንዳለ በመቀበል በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት የተባለውን ብቻ መርምረናል፡፡

በዚህ መሠረት ተጠሪ ኪሳራውን ያሳወቀው በ2001 ስለሚሆን ይኸው በ2001 በጀት ዓመት በተጠሪ የደረሰው ኪሳራ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 28/1/ እና /3/ በሚቀጥሉት ሶስት የግብር ዘመናት ውስጥ በሚገኝ ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ያጋጠመው ኪሳራ በኋላ ካጋጠመው አስቀድሞ በሚካካስ የሚሸጋገር በመሆኑ በአመልካች አዲት ተደርጐ ተቀባይነት ካገኘ ወይም ተጠሪ በውጭ ኦዲተር የሂሳብ መግለጫው ያቀረበ ከሆነ ኪሳራው ሊሸጋገርለት የሚገባ ነው፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በ2000 በጀት ዓመት ኪሳራ በስህተት ያሳወቀ ስለመሆኑና በ2000 ደርሷል የተባለው ኪሳራ በ2001 ዓ.ም ያሳወቀው መሆኑን በግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ በፍሬ ነገር እና ማስረጃ ምዘና ወቅት የተረገገጠ በመሆኑ ኪሳራው በሚቀጥለው ሁለት ሶስት ዓመት በማሸጋገር የንግድ ትርፍ ግብሩ ተሰልቶ እንዲወሰን በማለት በስር ፍቤቶች የሰጡት ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 28/1/ እና /3/ ፣ 112 እና ደንብ ቁጥር 78/1994 እንደተሻሻለው አንቀጽ 12 የተመለከተውን መሠረት ያደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ መሠረት የሚከተለውን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በመ/ቁ ከሱ-1019 ነሐሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠውን እና በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 185869 በቀን 04/07/2010 እንዲሁም በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 155956 በቀን 24/08/2010 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ.171943

ህዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ኪዳኔ ቶላ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 161002 በቀን 12/04/2011 ዓ.ም በሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች እንዲታረምለት የካቲት 10 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የነገሩ አመጣጥ የወንጀል ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡የአሁን ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረ ሲሆን የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ እና በሌሎች ሁለት ተከሳሾች ላይ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) እና 539 (1)(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ በሚች ሙሉጌታ ይመር ላይ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ክዶ ተከራክሯል፡፡ የግራ ቀኙ ማስረጃዎች ከተሰሙ በኋላ ተጠሪ የዐቃቤ ህግን ክስና ማስረጃ አላስተባበለም ተብሎ በተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ ሥር ከግብረ አባሮቹ ጋር የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ቅጣትን በተመለከተ በአሁን ተጠሪ ላይ የ18 ዓመት ከ6 ወር የጽኑ እስራት ቅጣት ተወስኖበታል፡፡

በዚህ የአሁን ተጠሪ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡የይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ ሚች በተጠሪ ላይ ጉዳት ቢያደርስም ተጠሪ ይህን ተከትሎ ብቀላ ከመፈጸም ይልቅ በህግ አግባብ ለህግ ማቅረብና መከታተል

ሲገባው በራሱ እርምጃ መውሰዱ የብቀላ ድርጊት መፈጸሙን የሚያሳይ ነው፡፡ ሆኖም ግን የደረሰበት ጉዳት የወንጀል ድርጊቱን ለመፈጸም ስሜት ቀስቃሽ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህ ረገድም መልስ ሰጭ /የአሁን አመልካች/ ጉዳቱ በህክምና ከተረጋገጠበ ቅጣት ማቅለያነት ቢያዝ የሚደግፍ መሆኑን የገለጸ ሲሆን የጉዳቱን ደረጃ የህክምና ማስረጃውን ተክቶ መገመት ባይቻልም ጉዳቱን መገንዘብ እስከተቻለ ድረስ ይኸው ምክንያት በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል በዚህ ረገድም የሥር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ መሻሻልና መቀነስ ያለበት ነው፡፡የቅጣት ማቅለያውን አያያዝ በተመለከተ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ቢሰላ አንድ እርከን ብቻ የሚያስቀንስ በመሆኑና በዚህ ሁኔታ የሚቀነሰው ቅጣት ደግሞ ከእርከን 36 ላይ አንድ እርከን ተቀንሶ በእርከን 35 ፍቅደ ሥልጣን ከ16 ዓመት ከ6 ወር እስከ 19 ዓመት ከ6 ወር በሚያስቀጣው ሊቀጣ የሚችል በመሆኑና ይህም ከቅጣት ማቅለያው መሠረታዊነት አንጻር ሲታይ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው በመውጣት በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 27 (1) መሠረት ሊወሰን የሚገባው ነው፡፡በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0001008 ሚያዚያ 4 ቀን 2010 ዓ.ም ያስተላለፈው የ18 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ተሻሽሎና ተቀንሶ ይግባኝ ባይ /የአሁን ተጠሪ/ በዚህ ጉዳይ የታሰረው በሚታሰብ በ12 /አስራ ሁለት/ ዓመት ጽኑ እሥራት ሊቀጣ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በቅጣት ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡አመልካች የካቲት 10 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርቧል፡፡የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅጣቱን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ ሲወስን የጠቀሰው የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን አንቀጽ 27 (1) ሲሆን ይህ አንቀጽ ደግሞ ፍርድ ቤት ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው ውጪ ቅጣት ሊወስን የሚችለው የወንጀሉ አፈጻጸምም ሆነ ባህሪው በመመሪያው መሠረት ቅጣትን መወሰን የወንጀል ህግ ዓላማ እና ግብ የማያሳካ ነው ብሎ ሲያምን እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን የፈጸመው በቂም በቀል መሆኑን እና ሟች ጉዳት አድርሶብኝ በዋስ ተለቀቀ በሚል ምክንያት ፍትህ በራሱ ለማስፈጸም ያደረገው መሆኑን እራሱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ያመነበት ስለመሆኑ በውሳኔው ላይ ያካተተው ከመሆኑ አንጻር የአካል ጉዳቱን እንደ አንድ ማቅለያ ከመያዝ ባለፈ ከመመሪያው ወጥቶ ቅጣት እንዲወስን የሚያደርግ አይደለም፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቅጣቱን ከመመሪያው ውጪ ወጥቶ የወሰነበትን ምክንያት ፍርድ ቤቱ አላስቀመጠም፡፡ስለሆነም የመመሪያውን አንቀጽ በአግባቡ መተግበር ሲገባው ምክንያቱን በዝርዝር ሳያስቀምጥ በደፈናው ቅጣቱን ከመመሪያው ውጪ በማውጣት መወሰኑ መመሪያውን ያልተከተለ ነው፡፡በዚህም ምክንያት ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት የወንጀል ህግ ቁጥር 539 (1) (ሀ) በመተላለፍ ከባድ የግድያ ወንጀል መፈጸሙ ተረጋግጦ ጥፋተኛ በተባለበት ሁኔታ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ላይ የደረሰበት ጉዳት ወንጀሉን ለመፈጸም ስሜቱን የሚቀሰቅስነው፣በቅጣት ማቅለያ ሊያዝ የሚገባ ነው ካለ በቅጣት ማቅለያነት ተቀብሎ ቅጣት ማሻሻል ሲገባው ከቅጣት መመሪያው በመውጣት ቅጣቱን ከ18 ዓመት ወደ 12 ዓመት በማሻሻል የወሰነበትን አግባብነት ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 27 እና ከወንጀል ህግ ቁጥር 539 (1) (ሀ) ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ተብሎ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ለተጠሪ ባለበት ማረሚያ ቤት በኩል ጥሪ ተደርጎለት በቀን 22/11/2011 ዓ.ም የተጻፈ 2 ገጽ መልስ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ይዘቱም በአጭሩ፡- ሟች በተጠሪ ላይ ጉዳት ካደረሰ በኋላ በህግ ቁጥጥር ሥር ከሆነ በኃላ በዋስ መለቀቁ ስሜት ቀስቃሽና በፍትህ በደል የደረሰብኝ መስሎ ቢታየኝ እንኳን የሚያስገርም አይደለም፡፡ምክንያቱም በወቅቱ የነበረው የፍትህ ሂደትና ሥርዓት ሚዛናዊነት የሌለው ሲሆን ተጠሪ ከበቀል ስሜት ውጪ የነበርኩኝ ሆኖ በሟች ላይ የከፋ ጉዳት ለማድረስ የሚያስችል አቅም ያልነበረኝ መሆኑ ግምት ውስጥ ገብቶ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡አመልካቹም መስከረም 26 ቀን 2012 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን ጉዳዩን አጣሪው የያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሁም አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ሟች ሙሉጌታ ይመር የአሁን ተጠሪን እጅ በመምታት ጉዳት አድርሷል ተብሎ በፖሊስ ተይዞ በጊዜ ቀጠሮ መቆየቱን፣ከዚያም በዋስትና መለቀቁን፣ሟች ከዚህ በፊት ደብድቦ በቀኝ እጅ ላይ ጉዳት አድርሶብኛል በሚል የአሁን ተጠሪ ቂም በመያዝ ከሥር ፍርድ ቤት 2ኛ እኛ 3ኛ ተከሳሾች ጋር በመሆን ሟችን መንገድ ላይ ጠብቀው ከምሽቱ 4፡30 ላይ የአሁን ተጠሪ በፍልጥ እንጨት የሟችን ጭንቅላት መምታቱን፣ሌሎች ሁለቱ ተከሳሾች ሟችን ተባብረው መምታታቸውን፣ሟች ሲወድቅ ወደ ሶስተኛ ተከሳሽ ቤት በመሄድ ቢላዋ ይዘው ሟች ወደ ወደቀበት ቦታ በመመለስ የአሁን ተጠሪ /የሥር 1ኛ ተከሳሽ/ የሟችን የግራ እጁን በቢላዋ ወግቶ ስብራት በማድረስና የተለያየ ሰውነት ክፍሉን በቢላዋ በመውጋት የገደሉት መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ተነስተን የሟችን አገዳደል ስንመለከት የአሁን ተጠሪ ሟች ደብድቦ በእጁ ላይ ጉዳት አድርሶብኛል በሚል ቂም በመያዝ፣እንዲሁም ለምን በዋስትና ተለቀቀ በሚል ፍትህ እንደሌለ በመቁጠር የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችን በማስተባበር በመንገድ ላይ ጠብቀው ሟችን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ የገደሉ መሆናቸውን ነው፡፡ሟች ተመቶ ከወደቀ በኋላ ወደ ሶስተኛ ተከሳሽ ቤት በመሄድ ቢላዋ ይዘው በመምጣት ሟችን በወደቀበት የአሁን ተጠሪ ወጋግቶ እንዲሞት ማድረጉ የተፈጸመውን የወንጀል ድርጊቱን ክብደት የሚያሳይ ነው፡፡ይህ የወንጀል አፈጻጸም ታይቶ የአሁን ተጠሪን /የሥር 1ኛ ተከሳሽን/ ጨምሮ ሶስቱም ተከሳሾች በተከሰሱበት የህግ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ

ተብለዋል፡፡ቅጣትንም በተመለከተ የወንጀል ድርጊት አፈጻጸማቸው ታይቶ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ የ18 ዓመት ከ6 ወር የጽኑ እሥራት ቅጣት ወስኖበታል፡፡የአሁን ተጠሪ የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡የጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ይግባኙን ተቀብሎ ክርክራቸውን ካዳመጠ በኋላ ሚች በአሁን ተጠሪ /ይግባኝ ባይ/ ላይ ያደረሰ ጉዳት ካለ በህግ አግባብ ማስከበር እየተቻለ በበደል አድራሹ ላይ እርምጃ መውሰድ እና የብቀላ ድርጊት መፈጸም የተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌን የሚያሟላ ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔን አጽንቶታል፡፡ቅጣትን በተመለከተ ግን ሚች በአሁን ተጠሪ ላይ ያደረሰው ጉዳት ስሜትን የሚቀሰቅስ በመሆኑ ቅጣት ሊቀልለት ይገባል በማለት ከቅጣት መመሪያው በመውጣት ተጠሪ በ12 /አስራ ሁለት/ ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ ተጠሪ ከፈጸመው የወንጀል አፈጻጸም እንዲሁም ከወንጀል ህግ ዓላማ እና ግብ አንጻር ሲታይ ተገቢ ነው ወይ? የሚለውን በቅድሚያ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ሚች የአሁን ተጠሪን በመደብደብ በእጁ ላይ ጉዳት ካደረሰ በኋላ በህግ ቁጥጥር ሥር ውሏል፡፡በጊዜ ቀጠሮ ምርመራ ከተደረገ በኋላ በዋስትና ተለቋል፡፡በጊዜ ቀጠሮ ቆይቶ በዋስትና ከተለቀቀ በኋላ የአሁን ተጠሪ በሚች ላይ የግድያ ወንጀል መፈጸሙ ሲታይ በከፍተኛ ስሜት ቀስቃሽነት ወንጀሉን ፈጽሟል ሊያስብል የሚችል አይሆንም፡፡ምክንያቱም ተጠሪ የዚህን ዓይነት ድርጊት የፈጸመው ወንጀሉ እንደ ተፈጸመ ወዲያውኑ ቢሆን ኖሮ ፍርድ ቤቱ የያዘውን ዓይነት ግንዛቤ ሊወስድ ይችል ነበር፡፡ነገር ግን በሚች ላይ የግድያ ወንጀል የተፈጸመው ሚች በተጠሪ ላይ ጉዳት አድርሶ ከቆየ በኋላ ነው፡፡ይህ ተረጋግጦ ተጠሪ በወንጀል ህግ አንቀጽ 539 (1) (ሀ) ሥር ጥፋተኛ ተደርጎ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ተወስዶ የ18 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እሥራት ቅጣት ሊወሰን ችሏል፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይህን ቅጣት በማሻሻል ተጠሪ በ12 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ መወሰኑ ከወንጀል ህግ መሠረታዊ ዓላማ እንዲሁም ከቅጣት መመሪያው ዓላማ አንጻር ሲታይ ይገባል፡፡የወንጀል ህግ ዓላማ እና ግብ በወንጀል ህግ አንቀጽ 1 ተዘርዝሮ ተቀምጧል፡፡የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ ዓላማ ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡ይህን ዓላማ ለማሳካት ከተቀመጡ ስልቶች መካከል አንዱ በአጥፊዎች ላይ ተገቢውን ቅጣት መወሰን ነው፡፡

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ነው፡፡ስለዚህ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ውስጥ ቅጣት ግብ ሳይሆን የወንጀል መከላከሉን ግብ ለማሳካት የተቀመጠ አንዱ ስልት ነው፡፡ይህንን የሚያደርገው በመጀመሪያ ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ነው፡፡ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ፣ ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፅሙ እርምጃዎችን በመውሰድ ነው፡፡ ይህም ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ወንጀል አድራጊው ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም የሚያደርግ (prevention)፣ ሌሎችን ወንጀል ከመፈጸም

እንዲቆጠቡ የሚያደርግ (deterrence)፣ እንዲሁም ወንጀል አድራጊን ማረም (rehabilitaiton)እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው ቅጣት የወንጀል ሕግ ማስፈጸሚያ አንዱ መሰረታዊ መሳሪያ እንደሆነ ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የቅጣት አወሳሰን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ / Manual/ እንደሚያወጣ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 (4) ተደንግጓል፡፡ይህን ድንጋጌ ተከትሎ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ወጥቶ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ይህ መመሪያ ተሸሮ የተሻሻለ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ወጥቶ ወይም ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ይገኛል፡፡የዚህ መመሪያ ዓላማና ግብ በአንቀጽ 3 ሥር ተቀምጧል፡፡የመመሪያው ዓላማ የዳኝነት አካሉ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ውጤታማና ተገማችነት ያለው ቅጣት የሚሰጥበትን ሥርዓት መመሥረት ነው፡፡የመመሪያው ግቦች ደግሞ በተቀራራቢና ተመሳሳይ የወንጀል ጉዳዮች መካከል ተቀራራቢነት ያለው ቅጣት እንዲወሰን ማድረግ፤እንደወንጀሉ ክብደትና አደገኛነት የቅጣት ተመጣጣኝነት ማረጋገጥ ናቸው፡፡ይህን ዓላማ እና ግብ ለማሳካት የቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ ለወጣላቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ዝርዝር መስፈርቶችን አስቀምጧል፡፡የወንጀል ደረጃ ከወጣላቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መካከል አንዱ አንቀጽ 539 ነው፡፡ለወንጀል ህግ አንቀጽ 539 (1) (ሀ) ሁለት የወንጀል ደረጃዎች፣እንዲሁም ለወንጀል ደረጃዎቹ የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ ተዘርዝሮ ተቀምጧል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ተከሶ ጥፋተኛ ለተደረገበት የወንጀል ህግ አንቀጽ 539 (1) (ሀ) በቅጣት መመሪያው መሠረት በደረጃ 1 የተዘረዘረውን የወንጀል ደረጃ መግለጫ መሠረት በማድረግ የእሥራት ቅጣት መነሻ እርከን 38 ላይ እንዲያርፍ ተደርጎ እንደተወሰደ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያሳያል፡፡ይህ ከሆነ በኋላ ለተጠሪ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ተይዞ በእርከን 36 ከተቀመጠው የፍቅድ ሥልጣን በ18 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት ቅጣት ተጠሪ እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡

ከዚህ መመሪያ ውጪ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት ሁኔታ በተመለከተ በአንቀጽ 27 (1) ላይ ተደንግጓል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጀመሪያው ፍርድ ቤቱ የወንጀል ሕጉን የቅጣት ዓላማ እና ግብ የማያሳካ ነው ብሎ ካመነ ከመመሪያው ውጪ በመውጣት ቅጣት ሊወስን ይችላል፡፡የወንጀል ህጉ ዓላማ እና ግብ ምን እንደሆነ ከፍ ብሎ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በአንቀጽ 27 (1) የተቀመጠው ሁለተኛው መሠረታዊ ነገር መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ የማይችልበትን ምክንያት ፍርድ ቤቱ በዝርዝር በማስቀመጥ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከመመሪያው ውጪ በመውጣት ቅጣት የወሰነ ቢሆንም የወንጀል ህጉን ዓላማ እና ግብ ለማሳካት የሚያስችል ነው ብሎ ለመውሰድ የሚቻል እንዳልሆነ ይህ ችሎት ግንዛቤ ወስዶበታል፡፡ይኸውም ከወንጀሉ ከባድነት እና ተጠሪ ከፈጸመው የወንጀል አፈጻጸም አንጻር ሲመዘን ከመመሪያው ውጪ የተወጣው የወንጀል ህጉን ዓላማ እና ግብ የሚያሳካ

አይደለም፡፡ከዚህ በተጨማሪ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ የማይችልበትን ምክንያት በዝርዝር አላስቀመጥም፡፡ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሚች በተጠሪ እጅ ላይ ያደረሰው ጉዳት ወንጀል ለመፈጸም ቀስቃሽ ሆኗል የሚል ነው፡፡ይህ ምክንያት አስፈላጊ ከሆነ በቅጣት ማቅለያነት ከሚያዝ በስተቀር ከላይ በተገለጸው መሠረት ተጠሪበሚች ላይ ወንጀሉን የፈጸመው ውሎ አድሮ ከቆይታ በኋላ በመሆኑ ይሁንታ የሚሰጠው አይደለም፡፡

በመጨረሻም ሚች በተጠሪ ላይ ድብደባ በመፈጸም በእጁ ላይ ጉዳት በማድረሱ በህግ ቁጥጥር ሥር ውሎ በዋስ በመፈታቱ ላይ ቅሬታ ቢኖረው በህግ በተቀመጠው ሥነ-ሥርዓት መጠየቅ እንጂ ለምን በዋስ ተፈታ፣እንደገና ጉዳት ያደርስብኛል በሚል ትንበያ፣እንዲሁም ፍትህ ተዳክሟል በሚል በራሱ ፍትህን ለማስፈጸም ግድ ያፈጽማል፡፡ይህ ሆኖ ባለበት ቅጣትን አቅልሎ መወሰን ተጠሪን የማያስተምር እና ፍትህን በራሱ መፈጸሙ ምክንያታዊ እንደሆነ እንዲሰማው የሚያደርግ፣ሌላውን ማኅበረሰብ ፍትህን በራሱ እንዲያስፈጽም የሚገፋፋ ወይም መጥፎ አርአያ የሚሆን፣ዋነኛው የወንጀል ህግ ዓላማ የሆነውን የህዝብን ሠላምና ደኅንነት የማስጠበቅ ዓላማ እንዳይሳካ የሚያደርግ በመሆኑ የተጠሪ ድርጊት ሊነቀፍ የሚገባ ነው፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይየተጠቀሱትን መሠረታዊ ነገሮችን በአግባቡ ሳያጤን ከቅጣት መመሪያው ውጪ በማውጣት የወሰነው የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን የፈጸመው ሚች በተጠሪ እጅ ላይ ጉዳት በማድረሱ ስሜቱን ቀስቅሶታል የሚባል ከሆነ አንድ የቅጣት ማቅለያ ቢያዝለት አመልካች እንደማይቃወም በክርክር ሂደት ያስመዘገበ በመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ከተያዙት ሁለት ማቅለያዎች በተጨማሪ ሊያዝለት ይገባል፡፡ይህም ሲቀነስ ከእርከን 36 ወደ እርከን 35 ዝቅ ይላል፡፡በዚህ እርከን የተቀመጠው የፍቅድ ሥልጣን 16 ዓመት ከ6 ወር- 19 ዓመት ከ6 ወር ነው፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. ተጠሪ 16 ዓመት ከ6 ወር የጽኑ እሥራት ቅጣት እንዲቀጣ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
2. በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጸም ተጠሪ ለሚገኙበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡
3. ቅጣት ተሻሽሎ የተወሰነ መሆኑን ተጠሪ እንዲያውቅ ባለበት ማረሚያ ቤት በኩል ይድረሰው፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ይድረስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁጥር169726

ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች:- አቶ ፍቅሩ ደሌሳ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ አለመስጠት ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ሙሉ አርጋዉ፣ ሰርግነሽ በዛ እና በአሁኑ አመልካች ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ አመልካች ላይ የቀርበዉ 2ኛ ክስ ሲሆን ይዘቱ፡- በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) ስር የተመለከተዉን በመተላለፍ የስር 1ኛ ተከሳሽን የንግድ ሥራ እንዲቆጣጠር፣ እንዲያስተዳድር፣ ሙሉ ዉክልና ወስዶ በንግድ ቤቱ ደረሰኝ መሰጠቱን መቆጣጠር ሲገባዉ ይህንን ሳያደርግ የቀረ በመሆኑ በፈጸመዉ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ዉጪ ግብይት እንዲከናወን የመርዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ጥፋተኝነቱ በራሱ በማረጋገጡ ፍርድ ቤቱ አመልካችን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134(1) መሠረት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08/አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) ስር ጥፋተኛ በማድረግ በአንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲወስን የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ሳይቀበለዉ ቀርቷል፡፡ አመልካች የገደብ ጥያቄዉ በስር ፍ/ቤት በመታለፉ ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህንኑ የዉሳኔ ክፍል በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ድርጊቱ የተፈጸመዉ አመልካች ዕቃ ለመግዛት በወጣሁበት ወቅት በስር 2ኛ ተከሳሽ መሆኑን፤ ነገር ግን በዉክልናዉ መሰረት ስራዉን ስከታተል የነበርኩት እኔ ስለሆንኩ መቆጣጠር ስለነበረብኝ ይህንን ባለማድረጌ ጥፋተኛ ነኝ ብያለሁ፡፡ የቀድሞ ጥፋተኝነት ሪኮርድ የሌለብኝ፤ ድርጊቱን በማመን መጸጸቴን በተግባር ማሳየቴን፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪነቴን እንዲሁም በልማት በመሳተፍ መልካም ሰዉ መሆኔን በማስረጃ አረጋግጫለሁ፡፡ ይህ በወ/ሕግ አንቀጽ 192 መሰረት ቅጣቱን በገደብ በማድረግ የአመልካችን ፀባይ ቢፈተን አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ በቂ ነዉ የሚያስብል በቂ ምክንያት ቢኖርም የስር ፍ/ቤት በምን ምክንያት ሊቀበለዉ እንዳልቻለ እንኳን ሳይገልጽ ማለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 46382 በሰጠዉ ትርጉም መሠረት ቅጣቱ ቢገደብልኝ እና አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ ጸባዬ ቢፈተን ዳግመኛ ወንጀል እንደማልፈጽም የሚያሳዩ በቂ ምክንያቶች እያሉኝ የገደብ ጥያቄ መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይሽዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሮ ቅጣቱ ይገደብልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤት የተከሰሱበትን ወንጀል አምነዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ ከተሰጠ በኃላ ቅጣቱ እንዲገደብላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች በዝምታ ያለፉበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀጽ 128፣ 131(1/ለ)፣ ከወ/ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አንጻር ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ያቀረበዉ መልስ፡- የስር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረባቸዉን የቅጣት ማቅለያዎችን ተቀብሎ ቅጣት በማቅለል የወሰነ ሲሆን ቅጣቱ እንዲገደብ ትዕዛዝ አለመስጠቱ ብቻ መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል አያስብልም፡፡ የወ/ሕ/አንቀጽ 192 ፍ/ቤቱ የነገሮችን ሁኔታ ዓይቶ ጥፋተኛዉ በጽኑ ማስጠንቀቂያ ቢታለፍ ይሻላል ብሎ ሲያምን የሚወስነዉ እንጂ አመልካች እንዳቀረቡት እንደመብት ሊጠየቅ የሚገባዉ አይደለም፡፡ አመልካች ባጠፋዉ ጥፋት በግሉ መታረሙን ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን ሌሎች የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ከተመሳሳይ ድርጊት እንዲቆጠቡ በማስተማር የሕዝብና የመንግስትን ጥቅም ማስጠበቅን ታሳቢ አድርጎ ቅጣት ሊጣል እንደሚገባ የሚታመን በመሆኑ የቅጣት ዉሳኔ አለመገደቡ ከወንጀል ሕጉ አላማ ጋር የተጣጣመ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ በሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 46382 የተሰጠዉ ዉሳኔ ከዚህ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የለዉም፡፡ ስለሆነም ዉሳኔዉ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔን አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ መርምረናል፡፡ በዚህም መሠረት መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች በፌዴራል የታክስ አስተዳደር

አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) የተመለከተዉን በመተላለፍ የስር 1ኛ ተከሳሽን የንግድ ሥራ እንዲቆጣጠር ሙሉ ዉክልና ወስዶ በንግድ ደርጅቱ ደረሰኝ መሰጠቱን መቆጣጠር ሲገባዉ ይህንን ሳያደርግ በመቅረቱና ግብይቱ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ዉጪ መከናወኑ በአመልካች የእምነት ቃል ተረጋግጦ በተጠቀሰዉ የሕግ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ መባሉም ሆነ በአንድ ዓመት ጽኑ እስራት መቀጣቱ ላይ አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የለም፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉም ሆነ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ ከወ/ሕ/አንቀጽ 192 ድንጋጌ አንጻር አመልካች ቅጣት እንዲገደብለት ያቀረበዉን ጥያቄ የስር ፍ/ቤት በዝምታ ሳይቀበለዉ መቅረቱ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

የወንጀል ቅጣት በገደብ ለማቆየት በሕጉ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ እንደሚገባ በወ/ሕ/አ/197(1) እና(2) ተመልክቷል፡፡ አንድ ተከሳሽ ቅጣቱ ሊገደብለት የሚችለው በመልካም ጠባይ እንደሚመራ ግዴታ የሚቀበል መሆኑ መረጋገጥ እንዳለበት፤ በጥፋቱ ያደረሰውን ጉዳት እና የፍ/ቤት ወጪ ለመክፈል ማረጋገጫ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፤ ጥፋተኛው ለገባበት ግዴታ አፈፃፀም አንደ መተማመኛ መስጠት እንዳለበት ሕጉ አስገደጅ መስፈርት አስቀምጧል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት ከዚህን ቀደም በሰ/መ/ቁ 94404 በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አንድ ጥፋተኛ በተወሰነ ገደብ ከእስር ለመፍታት በሕጉ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ማረጋገጥ ያለበት ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ሆኖም በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች ተሟልተዉ መገኘት አንድ አጥፊ የተወሰነበት እስራት የግድ ይገደብለታል ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ቅጣትን በገደብ ለማቆሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 190 የተመለከተው መሰረታዊ መርህ ከወ/ሕ/አንቀጽ 192 እና 196 ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባል፡፡

በመርህ ደረጃ የወንጀል ቅጣት የሚገደበው የወንጀለኛው ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ ሊሆን የሚችል መሆኑን ፍ/ቤቱ ማረጋገጥና ማመን ሲችል መሆኑን የወ/ሕ/አንቀጽ 190 ድንጋጌ ያስገናዝበናል፡፡ እንዲሁም በአንድ ወንጀል ፈፃሚ ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይፈጸም የሚታገደው ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠበቀም ማሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ በቂ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያምን መሆኑ በወ/ሕ/አንቀጽ 192 ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቅጣትን እንዳይፈጽም ለማገድ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 196 የተዘረዘሩት የወል ድንጋጌዎች በአግባቡ ሊታዩ እንደሚገባ ከድንጋጌው መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ሲመረጥ ምክንያቱን በውሳኔው ማካተት እንዳለበት የተከሳሹ የቀደመ ታሪክ፤ የጠበዩና የዓመሉ አካሄድ ሲመዘን ጊዜ መስጠቱ መልካም ውጤት የሚያስገኝ መስሎ ካልታየው የማገጃ ትዕዛዝ እንደማይሰጥ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ከምንም በላይ ጉዳዩን ያየዉ

ፍ/ቤት የአጥፊዉን ጠባይና የዓመሉን ሁኔታ ሲመዝን ቅጣትን ማገድ መልካም ዉጤት የሚያስገኝ መሆኑን ካላመነ ወይም ካልገመተ በቀር የተወሰኑ መስፈርቶች ስለተሟሉ ብቻ ቅጣት ማገድ ነበረበት ሊባል አይችልም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ያልቀረበበት፣ ጥፋቱን አምኖ ተፀፀተና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ሲታይ በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በአብዛኛው ያሟላ ቢሆንም በወ/ሕ/አንቀጽ 190 እና 192 ድንጋጌዎች መሠረት በአመልካች ላይ የተወሰነው ቅጣት ሳይፈጸም ቢገደብ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠበዩም ማሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ በቂ መሆኑን የስር ፍ/ቤት ባለማመኑ የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ሳይቀበል ቀርቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት በዝምታ ማለፉ ወይም ምክንያት አለመስጠቱ ተገቢ ባይሆንም ይህ ችሎት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት የመንግስት ገቢን በመሰብሰብ አቅም ላይ ያለዉን አሉታዊ ተጽእኖ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች በአብዛኛዉ ተሟልተዉ ተገኝቷል በሚል ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር ለአመልካችም ሆነ በተመሳሳይ ድርጊት ላይ ሌሎች እንዳይሳተፉ ከማድረግ አንጻር ቅጣት ማገዱ መልካም ዉጤት ያመጣል የሚል እምነት ለመጣል አልቻለም፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ዉድቅ ሲያደርግ ምክንያት ስላልሰጠ ብቻ ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት መመለሱ የተለየ ዉጤት የሚያመጣ ባለመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት አመልካች የወሰነዉን የአንድ ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ዉሳኔ ሳይገደብ መቅረቱ ከወ/ሕ/አንቀጽ 190፣ 192 እና 197 ድንጋጌዎች አንጻር የሚነቀፍ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ በአብላጫ ድምፅ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 262072 ጥቅምት 14 እና 15 ቀን 2011 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 225003 ታሕሳስ 09 ቀን 2011 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ) መሠረት ጽንቷል፡፡
2. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

<u>የልዩነት ሐሳብ</u>

ስሜ በተ.ቁ 5 ላይ የተገለጸው ዳኛ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የቅጣት ገደብ ጥያቄ በዝምታ በማለፍ በሰጠው ውሳኔ ላይ አብላጫው ድምጽ በደረሰበት መደምደሚያ በሀሳብ ስለተለየሁ የሀሳብ ልዩነቴን እንደሚከተለው አስፍራለሁ፡፡

አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ጥፋተኝነቱ በራሱ በማረጋገጡ ፍርድ ቤቱ አመልካችን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 134(1) መሠረት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08/አንቀጽ 128 እና 131(1/ለ) ስር ጥፋተኛ በማድረግ በአንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲወስን የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ሳይቀበለዉ አልፎታል፡፡

አመልካች ድርጊቱን ማመኑ እና በፈጸመው ድርጊት ምክንያት የተጸጸተ መሆኑ፤ የቀድሞ ጥፋተኝነት ሪኮርድ የሌለበት መሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ሲሆን አብላጫው ድምጽም አመልካች የቀድሞ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ያልቀረበበት፣ ጥፋቱን አምኖ የተፀፀተና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ሲታይ በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በከፊል ያሟላ መሆኑን በመግለጽ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡ አብላጫው ድምጽ የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ያልተቀበለው የስር ፍ/ቤት በዝምታ ማለፉ ወይም ምክንያት አለመስጠቱ ተገቢ ባይሆንም ይህ ችሎት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት የመንግስት ገቢን በመሰብሰብ አቅም ላይ ያለዉን አሉታዊ ተጽእኖ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች በአብዛኛዉ ተሟልተዉ ተገኝቷል በሚል ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር ለአመልካችም ሆነ በተመሳሳይ ድርጊት ላይ ሌሎች እንዳይሳተፉ ከማድረግ አንጻር ቅጣት ማገዱ መልካም ዉጤት ያመጣል የሚል እምነት ለመጣል አልቻለም በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ሕጉ ዓላማ ወንጀል እንዳይፈጸም ማድረግ ሲሆን ይህንንም የሚያደርገው ስለወንጀሎች እና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነ ጊዜ ደግሞ ወንጀል ፈጻሚዎች ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ እና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቅጣት ሲገደብ የፍርዱ ውሳኔ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ከሌላው ውጤት ጋር ነዋሪ የሚሆን በመሆኑ ቅጣትን መገደብ በወንጀለኛው ላይ ቅጣት እንዳይፈጸም የማድረግ ውጤት ብቻ ያለው ሳይሆን ወንጀለኛው ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲታቀብ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ቅጣትን መገደብ የወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ ከሚሳካባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡

ቅጣት ሊገደብ የሚችለውም ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ

በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ከተደነገጉት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግ ፍ/ቤቶች ቅጣትን ለመገደብ የሚያስችሉ የተለያዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስባት እንዳለባቸው፤ እነዚህም ሁኔታዎች ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፤ጥፋቱ በመቀጮ፤ በግዴታ ስራ ወይም ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል መሆኑና በዚህ ውሳኔ ብቻእስከ መጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን ‘ያመነበት’ እንደሆነ፤ እንዲሁምጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግም የሚታገድ መሆኑናስለጠባዩም መሻሻል አንድ ዕኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱ ከአፈፃፀምም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን፤እነኚህም ሁኔታዎች ጥፋተኛው ከዚህ በፊት የጽኑ እሥራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እሥራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነ እና እንደገናም በተከሰሰበት ወንጀል ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት እንደሆነ ወይም ጥፋተኛው ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ሆኖ በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት አመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ነው በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ድንጋጌ ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በሕጉ ከተመለከቱት ከእነኚህ ሁኔታዎች ውጪ ጥፋተኛው ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት በመንግስት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽእኖ እንዲገደብ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ተብሎ በሕጉ ላይ አልተገለጸም፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 የወንጀሉ ከባድነት / the gravity of the crime /፤ በወንጀል ድርጊት መደጋገም ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እና በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚችለው እምነት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት የሚባለው ፍ/ቤቱ ቅጣቱ እንዲገደብ አቋም ከያዘ በኋላ ቅጣቱ ተገድቦ የሚቆይበትን የፈተና ጊዜ ለመወሰን / ….. to fix the probation period ….. / እንጂ ቅጣቱን ለመገደብ ሊሟላ ይገባል ተብሎ የተቀመጠ ቅድመ-ሁኔታ አይደለም፡፡

በመሠረቱ ከባድ ወንጀሎች ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194/1/ለ ድንጋጌም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ጥፋተኛው አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ቅጣትን ማገድ አይቻልም በማለት በግልጽ መደንገጉ ከመነሻውም ቢሆን ከባድ ወንጀል የፈጸመ ወንጀለኛ በሚጣልበት ከፍተኛ የቅጣት መጠን ምክንያት ቅጣት ሊገደብለት የማይችል በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 ላይ የተገለጸው ‘የወንጀሉ ክብደት’ የሚለው ቃል ለፈተናው ጊዜ አወሳሰን ታሳቢ የሚደረግ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ቅጣቱን ለመገደብ በመመዘኛነት የተቀመጠ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 የተመለከቱት ቅድመ-ሁኔታዎች ፈተና የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች እንደሆኑ ከድንጋጌው ርዕስ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን እነኚህ ሁኔታዎች መሟላት አለመሟላታቸው ሊረጋገጥ የሚችለው ፍ/ቤቱ ከተከሳሹ የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ በመነሳት ቅጣቱን መገደብ እንዳለበት ሲያምን እና ጥፋተኛው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ላይ የተመለከቱትን ቅድመ-ሁኔታዎች እንደሚያሟላ ማረጋገጫ እንዲሰጥ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192፤196/1 እና 197 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጥፋተኛው በድንጋጌው የተመለከቱትን ቅድመ- ሁኔታዎች ማሟላት አለማሟላቱን ማረጋገጥ የሚቻለውም ጥፋተኛው ራሱ በራሱ ተነሳሽነት በሕጉ የተመለከቱትን ቅድመ-ሁኔታዎች ያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ጥፋተኛው በሕጉ የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲያሟላ እድል በሰጠው ጊዜ ነው፡፡

ፍ/ቤቱ በጥፋተኛው ላይ የሚጣለውን ቅጣት ለጊዜው ማገድ ለወደፊቱ ጥፋቱን ለማረም እንደሚችል ሊያምን ወይም ላያምን የሚችለው የጥፋተኛውን የቀድሞ ታሪኩ፤ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ አስመልክቶ በችሎቱ የተረጋገጡትን እውነታዎች መነሻ በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤቶች በሕግ እና በተገቢ ምክንያት የተደገፈ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው በመሆኑ አመልካች ቅጣቱን ለማስገደብ ያቀረባቸው ምክንያቶች ፍ/ቤቱን የሚያሳምኑ ናቸው ወይም አይደለም ለማለት ሕግን መሠረት በማድረግ እና አግባብነት ያለውን ምክንያት በመስጠት ሊሆን ይገባል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ድርጊቱን ማመኑ እና በፈጸመው ድርጊት ምክንያት የተጸጸተ መሆኑ፤ የቀድሞ ጥፋተኝነት ሪኮርድ የሌለበት መሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ እነኚህ ሁኔታዎች የተከሳሹን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ እና ቅጣቱ ቢገደብ የአመልካችን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ የሚያስችሉ አሳማኝ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ በዝምታ ከማለፉ በቀር የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ለማስከልከል የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ያለ ስለመሆኑ በውሳኔው ላይ አልገለጸም፡፡ አብላጫው ድምጽ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ዓይነት የመንግስት ገቢን በመሰብሰብ አቅም ላይ ያለዉን አሉታዊ ተጽእኖ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197 የተመለከቱ መስፈርቶች በአብዛኛዉ ተሟልተዉ ተገኝቷል በሚል ቅጣቱ ሳይፈጸም ቢቀር ለአመልካችም ሆነ በተመሳሳይ ድርጊት ላይ ሌሎች እንዳይሳተፉ ከማድረግ አንጻር ቅጣት ማገዱ መልካም ዉጤት ያመጣል የሚል እምነት ለመጣል አልቻለም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ ቢሆንም ይህ ምክንያት በሕጉ ቅጣትን እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ተብሎ ያልተገለጸ ከመሆኑ አኳያ የስር ፍ/ቤት ቅጣቱ እንዳይገደብ የሚያደርጉ ሕጋዊ ምክንያቶች ያሉ መሆን አለመሆኑን አረጋግጦ በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ሊመለስለት ይገባ ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በመሆኑም የእነኚህን ሁኔታዎች የአመልካቹን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ አሳማኝ እና በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሆነው ሳለ አመልካች በራሱ ተነሳሽነት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ላይ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ከሆነ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ወይም እንዲያሟላ በማድረግ ቅጣቱን መገደብ ሲገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተቀመጠውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ከተፈጸመው ወንጀል ጋር ሲታይ ቅጣቱን ለመገደብ አላመንኩበትም በማለት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መታረም ይገባው ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

መዝገቡ ከተዘጋ በኃላ ሊቀርብ የቻለው ይህ ችሎት በዚሁ መዝገብ ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በልዩነት ድምጽ ላይ በመጨረሻው *ፖ*ራግራፍ/ አንቀጽ/ የተካተተው ሀሳብ በአጻጻፍ ስሕተት የገባ በመሆኑ ይህንኑ ለማስተካከል ነው፡፡ በመሆኑም በልዩነት ድምጽ ላይ በመጨረሻው *ፖ*ራግርፍ/ አንቀጽ/ የተካተተው ሀሳብ በአጻጻፍ ስሕተት የገባ በመሆኑ ከልዩነት ድምጽ እንዲወጣ በሚል ተስተክክሏል በዚሁ መሠረት ይጻፍ፡፡

ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ.ም.

የሰ/መ/ቁ 168067

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካቾች:- ሰይድ አሊ አበጋዝ

ተጠሪ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የንግድ እና ሸማቾች ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 24 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሠብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0202449 ሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 026018 ጥቅምት 05 ቀን 2011 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0323711 ጥቅምት 22 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሠብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ክሶች ሁለት ሲሆኑ ይዘታቸውም 1ኛ ክስ አመልካች የንግድ ፈቃድ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ድንጋጌን በመተላለፍ በቀን 01/09/2009 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 1፡30 ሰዓት በባቲ ወረዳ አስተዳደር 015 ሞቱማ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኡላኡላ በሚባል ቦታ ግምቱ ብር 58500 የሆነ 9 ጥቅል ጂአመምብራን የሰሌዳ ቁጥሩ አ.አ-3-30687 በሆነ አይሱዙ መኪና በመጫን ለመሸጥ ኬላ ጥሶ ይዞ ሲሄድ በሕብረተሰቡ እገዛ መኪናውን በማስቆም እጅ ከፍንጅ ያለንግድ ፈቃድ ንግድ መፈጸም ወንጀል ተከሷል የሚል ሲሆን 2ኛ ክስ ደግሞ በአሁን አመልካች እና በስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በነበሩት ላይ የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ተከሳሾች

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና የንግድ ሕግ አንቀጽ 118/1/ እና የነጋዴዎች እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ድንጋጌን በመተላለፍ በቀን 13/09/2009 ዓ.ም በባቲ ወረዳ አስተዳደር 015 ሞቱማ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኡላኡላ በሚባል ቦታ አመልካች ባለሀብት በመሆን፤ የስር 2ኛ ተከሳሽ የሰሌዳ ቁጥሩ አ.አ 3-30687 የሆነው መኪና አሽከርካሪ በመሆን 3ኛ ተከሳሽ ደግሞ የመኪናው ረዳት በመሆነ ጂኦመምብራን 9 ጥቅል ግምቱ ብር 58500 የሚያወጣ የማዘዋወር ወይም የመደበቅ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

ክሱ አመልካቾች እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ አመልካች ድርጊቱን የፈጸመ መሆኑን ሆኖም የተያዘው ዕቃ የወንድሙ መሆኑን እና ንግድ ፈቃድ ያለው መሆኑን በመግለጽ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት የተከራከረ ሲሆን ሌሎቹ ተከሳሾችም ድርጊቱን የፈጸሙ መሆኑን ሆኖም አመልካች ንግድ ፈቃድ እንዳለው ስለገለጸላቸው ዕቃውን የጫኑ መሆኑን በመግለጽ ጥፋተኛ አይደለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የዓቃቤ ሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች 1ኛ ክስን በተመለከተ መኪናው ጭኖ እየሄደ መያዛቸውን እንጂ እየነገደበት መሆኑን ያላስረዱ በመሆኑ አመልካች ከ1ኛ ክስ መከላከል ሳያስፈልገው በነጻ ተሰናብቷል፤ 2ኛ ክስን በተመለከተ ግን ተከሳሾች ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ስለተረጋገጠባቸው እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ ተከሳሾችም ክሱን ይከላከልልናል ያሉትን ማስረጃ አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች የተያዘው ጅኦመምብራን የአመልካች ወንድም መሆኑን እና አምጣልኝ ተብሎ የተላከ እና ይዞ ሲመለስ የተያዘ መሆኑን፤ ወንድሙ የሚነግድበት እና ንግድ ፈቃድ ይዞ ፍ/ቤት በመሄድ ሲከራከር እንደነበር መመስከራቸው ምስክሮቹ ሀሰተኛ እና ተደራጅተው የቀረቡ መሆኑን መረዳት ይቻላል፤ አመልካች የዕቃው ባለንብረት በመሆን እና ንግድ ፈቃድ ስለሌለው የተያዘውን ዕቃ ወደ ፖሊስ እንደወሰዱት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የመሰከሩ በመሆኑ ተከሳሾች በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3 እና 43/3 መሠረት ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት በማስላት የእስር ቅጣቱን ወደ ገንዘብ ቅጣት በመለወጥ እና ከገንዘብ ቅጣቱ ጋር በመደመር አመልካች በብር 1500 የገንዘብ መቀጮ የስር ተከሳሾች ደግሞ እያንዳንዳቸው በብር 2000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ እና የተያዘው 9 ጥቅል ጂኦመምብራን ተሸጦ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በየደረጃው ላሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዙቱም አመልካች የተከሰሰከባቸው የአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ነጋዴ በሆነ ሰው ላይ ነው፤ አመልካች ከ1ኛው ክስ

ነጻ የሆነው ነጋዴ አይደለም ወይም የንግድ ስራ አልሰራም ተብሎ ነው። በመሆኑም አመልካች ነጋዴ ሳይሆን ጥፋተኛ መባሉ ከሕግ ውጪ ነው። በአዋጁ አንቀጽ 24/4/ ድንጋጌ መሠረት ወንጀል የሆነው ተግባር እጥረት ያለበት መሆኑ በንግድ ሚኒስቴር በወጣ የሕዝብ ማስታወቂያ የተገለጸ የንግድ ዕቃን ለግል ወይም ለቤተሰብ ፍጆታ ከሚውል በላይ በሆነ መጠን ከተፈቀደው የስርጭት መስመር ውጪ ሚንቀሳቀስ ወይም እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ነው። ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ ጂኦሜምብራን የተባለው ዕቃ የንግድ ሚኒስቴር ባወጣው ማስታወቂያ እጥረት ያለበት ስለመሆኑ መገለጹን አልጠቀሰም ይህንንም አላስረዳም። ዕቃውም የተፈቀደ የስርጭት መስመር ያለው መሆኑ እና ከዚህ ከተፈቀደው መስመር ውጪ ሲንቀሳቀስ የነበረ መሆኑን አላረጋገጠም። በመሆኑም አመልካች በተገለጸው ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ ልባል አይገባም። የአመልካች መከላከያ ምስክሮች ዕቃው የአመልካች ወንድም ንብረት መሆኑን እና ዕቃውን ወደ ወንድሙ እየወሰድኩ የነበረ መሆኑን በሚገባ አስረድተው ሳለ ፍ/ቤቱ ምስክርነቱ በሀሰት የተሰጠ ነው በማለት ውድቅ ማድረጉ አግባብ አይደለም። በመሆኑም የስር ፍ/ቤት አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ እና የንብረት ውርስ ውሳኔ በመሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት በአሁን አመልካች ላይ በቀረበው 1ኛ ክስ ጭኖ መሄዱ እንጂ እየነገደበት መሆኑን አልተረጋገጠም ተብሎ ነጻ ከተባለ በኋላ በ2ኛው ክስ ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ጂኦመምብራን የንግድ ሚኒስቴር በገበያ ላይ እጥረት አለባቸው በሚል በገለጻቸው እና ዋጋ እና የስርጭት ሁኔታቸውን በወሰናቸው የንግድ ዕቃዎች ውስጥ የተካተተ አይደለም። ይህ ዕቃ ምንም እንኳን በየደረጃው ያለ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል በሚል እንዲሁ ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግበት ቢሆንም በን/ው/ሸ/ጥ/አ/ቁ 813/2006 አንቀጽ 25 እና 26 መሠረት የንግድ ሚኒስቴር ጥናት አድርጎ ዋጋቸው እና የስርጭት ሁኔታቸው እንዲወሰን ለሚንስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ በማስፈቀድ በማስታወቂያ በገለጻቸው የንግድ ዕቃዎች ውስጥ የተካተተ ባለመሆኑ እና የአዋጁን አንቀጽ 24 በመጥቀስ የወንጀል ሀላፊነትን መወሰን የማይቻል በመሆኑ ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር የመሰለውን ቢወስን አንቃወምም የሚል ነው። አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፤ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር እና በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው የአመልካች አቤቱታ የቀረበው በሁለተኛው ክስ ጥፋተኛ መባሉን አስመልክቶ ሲሆን የክሱ ይዘትም አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ በመተላለፍ በቀን 13/09/2009 ዓ.ም ከባቲ ወረዳ አስተዳደር 015 ሞቱማ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኡላኡላ ከሚባል ቦታ አመልካች ባለሀብት በመሆን በሰሌዳ ቁጥሩ አ.አ 3-30687 በሆነ መኪና 9 ጥቅል ጂአመምብሬን ግምቱ ብር 58500 የሚያወጣ አዘዋውሯል ወይም የመደበቅ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል በመሆኑ አመልካች የወንጀል ድርጊቱንን ፈጽመዋል ተብሎ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ በመተላለፍ ተጠያቂ መደረጋቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው መሆኑን ነው።

በመሰረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) ስር ተደንግጓል። በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ፍሬ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ስር ተደንግጎ ይገኛል። ይህም ከሳሹን ወገን በወ/ሕ/አ. 23 (2) ስር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን የሚያስገነዘብ ሲሆን ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቷል ሊባል የሚችለውም በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 በተመለተከው የማስረጃ መለኪያ መሰረት ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው።በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 142 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ይዘት ሲታይም ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 በተመለከተው የማስረጃ መለኪያ መርህ መሰረት በበቂና አሳማኝ ሁኔታ አስረድቶ ሲገኝ መሆኑን ያስገነዝባል።

በያዝነው ጉዳይ በመሰረታዊነት በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ማንኛውም የንግድ ዕቃን ከመደበኛውን የግብይት አሰራር ውጭ በማናቸውም ማጓጓዣ ከተፈቀደው የስርጭት መስመር ውጭ ሲጓጓዝ ከተገኘ እንደተከማቸ ወይም እንደተደበቀ የንግድ ዕቃ የሚቆጠር በመሆኑ ይህንን ሲያጓጉዝ የተገኘ ነጋዴ መሆን ይገባዋል። ከዚህ አንጻር የወንጀሉ ፍሬ ነገር የሆኑትን አመልካች ጂአሜምብሬን የተባለው ዕቃ የንግድ ዕቃ

መሆኑን አለመሆኑን፤ ከመደበኛው የግብይት አሰራር ውጭ ሲያንጓጉዝ የተያዘ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት አልተረጋገጠም አመልካችና ተጠሪም በዚሁ ፍርድ ቤት ባደረጉት የጽሁፍ ክርክር የንግድ ሚኒስቴር ባወጣው ማስታወቂያ እጥረት ያለበት ስለመሆኑ አለመገለጹን፤ ዕቃውም የተፈቀደ የስርጭት መስመር ያለው መሆን አለመሆኑንና ከዚህ መስመር ውጪ ሲጓጓዝ የነበረ መሆኑን አለመረጋገጡን ገልጸዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው አለመገኘታቸውን ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ይዘትና መንፈስ መሰረት የማስረዳት ግዴታውን ባልተወጣበት ሁኔታ አመልካች እንዲከላከል መደረጉም ሆነ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸው ከተሰሙ በኃላም አልተከላከለም ተብሎ በወንጀሉ ጥፋተኛ ተደርገው እንዲቀጡ መወሰኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2) እና በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ስር ከተመለከተው የማስረጃ ምዘና መርህ ጋር የማይሄድ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሠብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0202449 ሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 026018 ጥቅምት 05 ቀን 2011 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0323711 ጥቅምት 22 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 24/3/ እና 43/4/ ተላልፏል በማለት በቀረበበት 2ኛ ክስ ጥፋተኛ አይደለም ብለናል፡፡
3. በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ወሳኔ የተሻረ በመሆኑ የተወሰነበት የገንዘብ መቀጮ ብር 1500 / አንድ ሺህ አምስት መቶ/ ለመንግስት ገቢ ከሆነ ተመላሽ እንዲሆን ብለናል ፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ሳ/ፀ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 163069

ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ አልቀረበም

ተጠሪዎች፡- 1.ክኤሳድ ጠቅላላ የንግድ ሥራ ኃላ/የተ/የግ/ማሕበር ┐ ጠበቃቸው ወርቅነህ በረደድ

2. አቶ ሀይሉ አስገዶም ┘ ቀረቡ ::

3. አቶ ክብሮም ሀይሉ አስገዶም - ቀረቡ::

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 23 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 247746 ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ.ም ተጠሪዎችን ከቀረበባቸው ክስ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ በማሰናበት የሰጠው ብይን እና ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 209526 ሠኔ 19 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪዎች ላይ ያቀረባቸው ክሶች ሁለት ሲሆኑ ክሳቸውም፡-

<u>በ1ኛ ክስ፡-</u> የአሁን 1ኛ ተጠሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/1 እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 169/2 እና 173 ድንጋጌን በመተላለፍ ከቻይና ሐገር በዲክላራሲዮን ቁጥር ሲ-2195/2016 በቀን 12/12/2008 ዓ.ም እና በደረሰኝ ቁጥር ኤ.ኤች 16ኤ081 በቀን 20/10/08 ዓ.ም ብዛቱ 6372 ደርዘን ኦ.ኤል ፕላስቲክ ጆግ ወደ ሐገር ውስጥ ለማስገባት አሳውቆ የነበረ ሲሆን በኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የአዲስአበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫች ጽ/ቤት በቀን 18/12/08 ዓ.ም በአካል ሲፈተሽ

በሰነድ ላይ ያልተገለጸ ብዛቱ 3186 ደርዘን ኩባያ በመገኘቱ ተደብቀው የተገኙት የዕቃዎች ዋጋ 11,182.86 ዶላር ወይም 247,646.67 ብር መሆኑን እና ይህም በሰነዱ ከተገለጸው አጠቃላይ የዕቃው ዋጋ 11,278.44 ዶላር ወይም 333001.43 ብር ጋር ሲነጻጸር የዋጋ ልዩነቱ ከ50% በላይ ወይም 99% ሆኖ በመገኘቱ በፈጸመው የማጭበርበር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው።

<u>2ኛ ክስ፡-</u> የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/1 እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 169/2 ድንጋጌን በመተላለፍ 2ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪ ማሕበር ስራ አስኪያጅ በመሆን፤ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በውክልና ማሕበሩን ሲመሩ ተገቢውን የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋት የድርጅቱን ጥቅም በሕገወጥ መንገድ ለመምራት በማሰብ 1ኛ ተጠሪ በ1ኛ ክስ የተገለጸውን ወንጀል እንዲፈጽም በማድረጋቸው በፈጸሙት የማጭበርበር ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው።

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው የአመልካችን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ በላኪው በኩል የተጠየቀው ጆግ ብቻ እንጂ ኩባያ የማይጨምር በመሆኑ ላኪው ያልተጠየቀውን ኩባያ በመላኩ በስህተት መሆኑን በመግለጽ የእርማት ደብዳቤ ወደ ሐገር ውስጥ ተልኮ በባለስልጣኑ የወንጀል ምርመራ ክፍል የደረሰ ስለመሆኑ በዓቃቤሕግ ምስክርም ተገልጿል፤ በአካላዊ ፍተሻ የተገኙት ጆጎች መጠን ደረጃ ልዩነት ሳይኖራቸው ግማሽ በሚሆን መጠን ላይ ባሉት ጆጎች ውስጥ አራር አራት ኩባያዎች መገኘታቸው በተከሳሽም ሆን ብለው ኩባያዎቹን ደብቆ ለማስገባት የወንጀል ሐሳብ የነበራቸው መሆኑን አያሳይም፤ ከድርጅት ሀላፊዎች አንጻር በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ የቀረበው ክስ የሚነቀፍ ባይሆንም ልዩነቱ 99% መሆኑ ክስ የቀረበበት ዕቃ በስህተት ምክንያት የተፈጠረ መሆኑን የሚጠቁም እንጂ አስቀድሞ በሰነዶች ያልተጠቀሱትን ኩባያዎች በድብቅ ወደ ሐገር ውስጥ ለማስገባት ሃሳብ የነበረቻው መሆኑ በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ እና ተገውን ቀረጥ እና ታክስ በማስከፈል እና አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ተገቢ በመሆኑ እና በተከሳሾች ላይ በወንጀል ተጠያቂነት ረገድ ጠንካራ በቂ እና አሳማኝ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ የወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ የለም በማለት ተጠሪዎችን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ከቀረበባቸው ክስ በነጻ አሰናብቷቸዋል። አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ወደ ሐገር ሲገባ ተደብቆ የተገኘው የዕቃ ዋጋ በሕጋዊ መንገድ ወደ ሐገር ከገቡት ዕቃዎች ዋጋ ጋር ሲነጻጸር 99% ባላይ መሆኑ ተረጋግጧል፤ ልዩነቱ ሊፈጠር የቻለውም በአካላዊ ፍተሻ በሕጋዊ ዕቃ ውስጥ ተደብቀው ብዛታቸው 3186 ኩባያዎች በጆጎቹ ውስጥ ተደብቆ የተገኘ መሆኑን አስረድተናል፤ ይህም የተጠሪዎችን ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ክፍል የሚያረጋግጥ ነው፤ የስር

ፍ/ቤት 1ኛ የዓቃቤሕግ ምስክር በወቅቱ 3ኛ ተጠሪ ዕቃው በስህተት እንደተላከላቸው በመግለጽ የእርምት ደብዳቤ ወደ ምርመራ ክፍል አስገብተው የነበረ መሆኑን ገልጿል ከማለት ውጪ ማስረጃው ቀርቦ የነበረ መሆን አለመሆኑን አላረጋገጠም፤ ላኪው ድርጅት ለትርፍ የሚሰራ ከመሆኑ አንጻር ይህን ያህል ልዩነት ያለውን ዕቃ ክፍያ ሳይፈጸምለት በስሕተት ይልካል ብሎ ድምዳሜ መውሰድ ተገቢነት የለውም ፤ ስሕተቱ መፈጸሙን በተመለከተም ከላኪው ድርጅት የተገለጸ ነገር የለም፤ ስሕተቱ ተፈጸመ ቢባል እንኳን ተጠሪዎች ወንጀል የመፈጸም ሀሳብ ባይኖራቸው ዕቃው ወደሐገር ውስጥ ገብቶ ከመፈተሹ በፊት ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ያሳውቁ ነበር እንጂ ድርጊቱ መፈጸሙ ከታወቀባቸው በኋላ መከራከሪያ ሆኖ ሊቀርብ አይገባም የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ከውጪ ሐገር ወደ ሐገር ውስጥ ፕላስቲክ ጆግ ለማስገባት አሳውቆ ውስጡ ኩባያ መገኘቱ ባልተካደበት ሁኔታ ተጠሪዎች ክሱን እንዲከላከሉ ብይን ሳይሰጥ በነጻ የመሰናበታቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪዎች መልስ ይዘት በአጭሩ፡- እሸጉ በምስክሩ ፊት ሲከፈት ጉምሩክ አስተላላፊው በቦታው የነበረ ሲሆን ተጪዎች በቦታው አልነበሩም፤ ተጠሪዎች በቦታው የተገኙት ዕቃው ልዩነት ተገኝቶበታል ከተባለ በኋላ ነው፤ 3ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ ስም ያዘዙት ጆግ ብቻ እንደሆነ እና ኩባያውን እንደማያውቁት እና በስሕተት አንደተላከ ገልጸው የማስተካከያ ደብዳቤ ለባለስልጣኑ የወንጀል ምርመራ ገልጸዋል፤ 2ኛ ምስክርም በዲክላራሲዮን የተመዘገበው ዕቃ ጆግ ብቻ መሆኑን፤ በአካላዊ ፍተሻ ኩባያ የያዙ መሆናቸውን፤ የተገኘው ዕቃ አስቀድሞ ከተገለጸው ጋር ሲነጻጸር 99% መሆኑን ገልጸዋል፤ ተጠሪዎች በጆኒቹ ከለላነት ኩባያውን ወደ ሐገር ለማስገባት ሀሳብ እንደነበራቸው አልተረጋገጠም፤ ዕቃው ወደ ሐገር የገባው በስሕተት መሆኑን የአመልካች ምስክር አረጋግጧል፤ የተገኘው ጆግ መጠን ከታዘዘው ጋር ምንም የዓይነትም ሆነ የደረጃ ልዩነት ሳይኖራቸው ግማሽ መጠን ባለው ጆግ ውስጥ አራት አራት ኩባያ መገኘቱ በተጠሪዎች በኩል ኩባያ አለመታዘዙ እና በላኪው ስሕተት ምክንያት ችግሩ የተፈጠረ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው፤ አስመጪው የሚያስመጣቸው ዕቃዎች እንዲመጡለት የሚያደርገው ሐገር ውስጥ በመሆን ከባንክ ጋር በሚደረግ ግንኙነት ሲሆን ተጠሪዎች እንዲላክልን የጠየቅነው በግር ሰነድ የተመለከቱትን እቃዎች ብቻ ነው፤ ላኪው አገር የሚልከውን ምስክር ወረቀት እና የቅድመ ጭነት ምርመራ ሲቀርብ እና ዕቃው በአካል ሲፈተሽ ምን እንደመጣ ከምናውቅ በቀር አስቀድመን ልናውቅ የምንችልበት ሌላ መንገድ የለም፤ ዕቃው ተጠሪዎች ባለንበት አልታሸገም ፤ ተጠሪዎች የወንጀል ሀሳብ የነበረን ስለመሆኑ በክሱ እና በማስረጃው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ዕቃው በ1ኛ ተጠሪ ስም መምጣቱን መነሻ በማድረግ ተጠያቂ ልንሆን አይገባም የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ ያቀረበው ብዛታቸው 6372 ደርዘን የሆኑ ፕላስቲክ ጆግ ወደ ሐገር ውስጥ ለማስገባት አሳውቀው በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተደረገው አካላዊ ፍተሻ በሰነድ ላይ ያልተገለጹ ብዛታቸው 3186 ደርዘን ኩባያዎች ተገኝተዋል፤ ተደብቀው የተገኙት የዕቃዎች ዋጋ 11,182.86 ዶላር ወይም 247,646.67 ብር መሆኑን እና ይህም በሰነዱ ከተገለጸው አጠቃላይ የዕቃው ዋጋ 11,278.44 ዶላር ወይም 333001.43 ብር ጋር ሲነጻጸር የዋጋ ልዩነቱ 99% ሆኖ በመገኘቱ በጉምሩክ ማጭበርበር ወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል በሚል ሲሆን ዕቃው ከጂቡቲ ወደ ቃሊቲ ጉምሩክ ገብቶ እሸጉ ሲፈታ በተደረገው አካላዊ ፍተሻ በሰነድ ከተገለጸው ውጪ ብዛታቸው 3186 ኩባያዎች በጆኒቹ ውስጥ የተገኙ መሆኑ እና ተደብቀው የተገኙት የዕቃዎች ዋጋ 11,182.86 ዶላር ወይም 247,646.67 ብር መሆኑን እና ይህም በሰነዱ ከተገለጸው አጠቃላይ የዕቃው ዋጋ 11,278.44 ዶላር ወይም 333001.43 ብር ጋር ሲነጻጸር የዋጋ ልዩነቱ 99% በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 13/4 ዲክላራሲዮኑ ከተመዘገበ በኋላ ለማጭበርበር በማሰብ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የተፈጸመ ግድፈት በአዋጁ መሠረት ያስቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 169/2 ተደብቆ የተገኘው ዕቃ በዲክላራሲዮን ላይ ከተገለጸው ጠቅላላ ዋጋ 50% በላይ ሆኖ ከተገኘ ዕቃዎችን በመደበቅ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ወደ ሐገር በማስገባት ወይም ከሐገር ለማስወጣት የሞከረ ማናቸውም ሰው ከአምስት ዓመት በማያንስ እና ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር 50,000 በማያንስ እና ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡

የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎችን መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ ያሰናበታቸው በላኪው በኩል የተጠየቀው ጆግ ብቻ እንጂ ኩባያ የማይጨምር በመሆኑ ላኪው ያልተጠየቀውን ኩባያ መላኩ በስህተት መሆኑን በመግለጽ የእርማት ደብዳቤ ወደ ሐገር ውስጥ ተልኮ በባለስልጣኑ የወንጀል ምርመራ ክፍል የደረሰ ስለመሆኑ በዓቃቤሕግ ምስክርም ተገልጿል፤ በአካላዊ ፍተሻ የተገኙት ጆኒች መጠን ደረጃ ልዩነት ሳይኖራቸው ግማሽ በሚሆን መጠን ላይ ባሉት ጆኒች ውስጥ አራር አራት ኩባያዎች መገኘታቸው በተከሳሻም ሆን ብለው ኩባያዎቹን ደብቆ ለማስገባት የወንጀል ሐሳብ የነበራቸው መሆኑን አያሳይም በማለት ነው፡፡ በመሠረቱ አንድን ዕቃ ከውጪ የሚያስመጣ ሰው ለጉምሩክ ሥርዓት አፈጻጸም ሲባል ስለሚያስመጣው ዕቃ አስፈላጊ የሆኑ መግለጫዎችን በመስጠት በዲክላራሲዮን ላይ ማስመዝገብ ያለበት ስለመሆኑ እና ወደ ሐገር ውስጥ የሚገባው ዕቃ በዲክላራሲዮን ላይ ከተመዘገበ በኋላ ለማጭበርበር በማሰብ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የተፈጸመ ግድፈት የሚያስቀጣ መሆኑን ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር

859/06 አንቀጽ 13/4 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ አግባብ ተመዝግበው ወደ ሐገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች በላኪው እና በአስመጪው መካከል በሚደረግ ስምምነት ወደ ሐገር ውስጥ የሚገቡ ከመሆናቸው አኳያ ወደ ሐገር ውስጥ እንዲገባ የተደረገው ዕቃ አስመጪው በዲክላራሲዮን ካስመዘገበው ዕቃ የበለጠ ዋጋ ያለው ሆኖ በተገኘ ጊዜ አስመጪው የተላከውን ዕቃ ሊያውቅ የሚችልበት ሁኔታ የለም ተብሎ ክሱ የቀረበበት ተከሳሽ መከላከል ሳያስፈልገው ከወዲሁ በነጻ ሊሰናበት ይገባል ተብሎ ድምዳሜ የሚወሰድበት አይደለም፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎችን መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ ያሰናበተው በላኪው በኩል የተጠየቀው ጆግ ብቻ እንጂ ኩባያን አይጨምርም፤ ላኪው ያልተጠየቀውን ኩባያ መላኩ በስህተት መሆኑን በመግለጽ የእርማት ደብዳቤ ወደ ሐገር ውስጥ ተልኮ በባለስልጣኑ የወንጀል ምርመራ ክፍል የደረሰ በመሆኑ በአካላዊ ፍተሻ የተገኙት ጆጎች መጠን ደረጃ ልዩነት ሳይኖራቸው ግማሽ በሚሆን መጠን ላይ ባሉት ጆጎች ውስጥ አራት አራት ኩባያዎች መገኘታቸው ተጠሪዎች ሆን ብለው ኩባያዎቹን ደብቀው ለማስገባት የወንጀል ሐሳብ የነበራቸው ስለመሆኑ አያሳይም በማለት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎችን በዚህ አግባብ በነጻ ያሰናበታቸው ቢሆንም ተጠሪዎች በአዋጁ መሠረት በዲክላራሲዮን አስመዝግበው ላስገቡት ዕቃ ትክክለኛነት ሀላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፤ ተጠሪዎች በዲክላራሲዮኑ ላይ ወደ ሐገር ውስጥ ለማስገባት በዲክላራሲዮን ካስመዘገቡት ፕላሲቲክ ጆጎች ውጪ ብዛታቸው 3186 ኩባያዎች በጆጎቹ ውስጥ የተገኙ መሆኑ እና ተደብቀው የተገኙት የዕቃዎች ዋጋ 11,182.86 ዶላር ወይም 247,646.67 ብር መሆኑን እና ይህም በሰነዱ ከተገለጸው አጠቃላይ የዕቃው ዋጋ 11,278.44 ዶላር ወይም 333001.43 ብር ጋር ሲነጻጸር የዋጋ ልዩነቱ 99% በመሆኑ፤ ዕቃው ወደ ሐገር ውስጥ የሚገባው በላኪው ድርጅት እና በተጠሪ መካከል በሚደረግ ስምምነት በመሆኑ፤ ላኪው ደርጅት በንግድ ላይ የተሰማራ አትራፊ ድርጅት ከመሆኑ አኳያ ከተጠሪዎች ዕውቅና ውጪ ክፍያ ያልተፈጸመባቸውን እና እንዲላኩ ያልተጠየቁ ዕቃዎችን ይልካል ተብሎ አስቀድሞ ድምዳሜ ላይ መድረስ የማይቻል በመሆኑ፤ ግብይቱ በባንክ መፈጸሙ ተጠሪዎች የተላከው ዕቃ በዲክላራሲዮን ከተመዘገበው ዕቃ የተለየ ዕቃ መሆኑን ሊያውቁ አያስችላቸውም ተብሎ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የማያስችል በመሆኑ፤ ተጠሪዎች በእርግጥም ዕቃው በስሕተት የገባ ነው የሚሉ ከሆነ በአካላዊ ፍተሻ በሰነድ ከተገለጸው ዕቃ ውጪ ሌላ ዕቃ እንደገባ ከመረጋገጡ በፊት አስቀድመው ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አለማሳወቃቸው በክሱ የተገለጸውን የወንጀል ድርጊት የመፈጸም ሀሳብ እንደነበራቸው አመላካች ነው ከሚባል በቀር ዕቃው በስሕተት የገባ ነው ብሎ ከወዲሁ ለመደምደም እና ተጠሪዎች የቀረበባቸውን ክስ ሳይከላከል ከወዲሁ በነጻ ለማሰናበት የሚያስችል ባለመሆኑ ተጠሪዎች የቀረበባቸውን ክስ ሊከላከሉ ይገባል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ ተጠሪዎችን በክሱ የተገለጸውን ወንጀል የፈጸሙ ስለመሆናቸው ያረጋገጠ ሆኖ ሳለ ተጠሪዎችን መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ ማሰናበቱ፤

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

4. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 247746 ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ.ም ተጠሪዎችን ከቀረበባቸው ክስ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ በማሰናበት የሰጠው ብይን እና ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 209526 ሠኔ 19 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ብይን በወ/መ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
5. ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ማስረጃ ተጠሪዎች በክሱ የተገለጸውን የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸማቸው በበቂ ሁኔታ ያረጋገጠባቸው በመሆኑ ተጠሪዎች የቀረበባቸውን ክስ ሊከላከሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
6. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎችን በነጻ በማሰናበት የሰጠው ብይን የተሻረ እና ተጠሪዎች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ የተወሰን መሆኑን አውቆ ተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ የግራቀኙን ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በብይን የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ ተጠሪዎች መከላከያ ማስረጃ ካላቸው አስቀረቦ ሰምቶ ተገቢውን እንዲወስን ታዟል፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 181958

ታሕሳስ 20 ቀን 2012 ዓም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ጳውሎስኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ገበያው ሽቴ ጠበቃቸው፡- አቶ ብናልፈው ነጋ ቀርበዋል::

ተጠሪ፡- የሰሜን ሸዋ ዞን ገቢዎች ፀ/ህግ፡- አልቀረቡም::

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ከተገኘ ገቢ የሚከፈል ግብርንና የተሰበሰበን ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያን ለገቢ ሰብሣቢው ተቋም ገቢ አለማድረግ እንዲሁም ሐሰተኛ ወይም አሣሣች የክፍያ ደረሰኝ ማቅረብን በሚመለከት የቀረበ የወንጀል ክስን የሚመለከት ሲሆን አመልካች ልዩ ልዩ ግብይት መፈፀሜን ያረጋግጡልኛል በሚል ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ያቀረባቸው ደረሰኞች እንዲታተሙ ፍቃድ ያልተሰጠባቸው፣በቀሪውና ለከፋይ በሚሰጠው ደረሰኝ የተፃፈው የገንዘብ መጠን የተለያዬ መሆኑን እንዲሁም የቀንና የቁጥር ቅደም ተከተል መዛባት ምክንያት በማድረግ መከፈል የነበረበትን ግብር አለመክፈል፣ ሃሰተኛ ወይም አሣሳች ደረሰኝ ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ማቅረብ እና ከልዩ ልዩ ግብይቶች የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ክፍያ በወቅቱ አሣውቆ ገቢ አለማድረግ ሶስት የወንልጆ ድርጊቶችን የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ በስምንት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራትና በአንድ መቶ ሺህ ብር መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ ተብሎ እንዲታረም የቀረበ ክርክርን ይመለከታል፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ግንቦት 29 ቀን 2009 ዓ.ም በተፃፈ ክሱ የአሁን አመልካች ደብረ ብርሃን ከተማ በኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ኪራይ የንግድ ስራ የተሰማራ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆኑን በመዘርዘር፡-

- በ1ኛ ክስ በ2005ዓ.ም የግብር ዘመን 1,409,349.95 ብር ግብር የሚሰበሰብበት ገቢ አግኝቶ 485,322.49 ብር ግብር በወቅቱ መክፈል ሲገባው ባለመክፈሉ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀፅ 97 የሚደነግገውን ተላልፎ ግብር አለመክፈል፡-

- በ2ኛ ክስ አመልካች በ2005ዓ.ም 1,409,349.95 ብር ዋጋ ያለው ግብይት በመፈፀሙ ከዚህ ውስጥመክፈልየነበረበትን ተጨማሪ እሴት ታክስ አንሶ እንዲከፈል በማቀድ ከአቶ ያለው አበበ፣ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ እንዲሁም ከአቶ ተፈሪ ባንቱ ጋር በገባቸው የገልባጭ መኪና ኪራይ ውሎች ገንዘብ የከፈለ እንዲሁም ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም የተሸከርካሪ ጎማ ገዝቶ ክፍያ የፈፀመ በማስመሰል በታክስ ማስታወቂያ ወቅት 19 ሀሰተኛና የተጭበረበሩ ደረሰኞች ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ በማቅረቡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 50(3)(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ለገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ሃሰተኛና የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ማቅረብ፡-
- በ3ኛ ክስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነው አመልካች ከልዩ ልዩ ገቢዎች የሰበሰበውን 4517.49 ብር በሐምሌ ወር 2005ዓ.ም ለገቢ ተቋሙ አሣውቆ መክፈል ሲገባው ባለመፈፀሙ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ አለማድረግ በጥቅሉ ሶስት ወንጀሎችን ፈፅሟል የሚሉ ክሶችን አቅርቦበታል፡፡

አመልካች ክዶ በመከራከሩ የስር ፍርድ ቤት የሆነው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ካዳመጠ በኋላ አመልካች በሁለተኛው ክስ ከተዘረዘሩት 19 ደረሰኞች መካከል ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም ተሰጥቶኛል ሲል ያቀረበው አንድ ደረሰኝ እንዲሁም ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ ተሰጥቶኛል በሚል ያቀረባቸው ሰባት ደረሰኞች እውነተኛ መሆናቸው ተረጋግጧል፤ ቀሪዎቹ ከአቶ ያለው አበበ የቀረቡት ደረሰኞች በበራሪው ላይ የተፃፈው የገንዘብ መጠን በቀሪው ላይ አለመፃፉን፣ አቶ ያለው አበበ ደረሰኞችን እንዲያሳትም ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ያልተሰጠው መሆኑን የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል የተዛባ መሆኑ፤ እንዲሁም ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ ተሰጥቶኛል በሚል የቀረቡት አምስት ደረሰኞች በበራሪው ላይ የተፃፈው የገንዘብ መጠን በቀሪው ላይ አለመፃፉን ተፈሪ ሰንደቁ ደረሰኙን እንዲያሣትም ፈቃድ አለማግኘቱን የደረሰኝ ቁጥርና የተሰጡበት የቀን ቅደም ተከተል መዛባቱ ደረሰኞች ላይ የተከናወነው የፎረንሲክ ምርምራ አረጋግጧል፤ አመልካችም ደረሰኞቹን ግለሰቦች ሰጡኝ ከሚል በስተቀር ግለሰቦች እንዲያሣትሙ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑንና በተሰጡት ደረሰኞች ላይ የተፃፈባቸው ገንዘብ በቀሪዎቹ ላይ ስለመፃፉ ሕጋዊ ስለመሆናቸው አላስረዳም ስለሆነም ሀሰተኛ በሆኑት አስራ አንድ ደረሰኞች መክፈል የነበረበትን 192,534.43 ብር ግብር አለመክፈሉ ሀሰተኛ ደረሰኝ ማቅረቡ እንዲሁም 4517.49 ብር ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ገቢ ማድረግ ሲገባው ገቢ አለማድረጉ ተረጋግጧል በሚል በሶስቱም ክሶች ጥፋተኛ ብሎ በስምንት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራትና በአንድ መቶ ሽህ ብር ቅጣት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት በማጣቱ ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 30ቀን 2011ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታቸው አመልካች ከአቶ ያለው አበበ፣ ከአቶ ተፈሪ በንቲ፤ ከአቶ ታፈረ ሰንደቁ ጋር የመኪና ኪራይ ውል ስለመግባቱ የውል ሰነዶችን በማቅረብ፣ ለተጠቀሱት ሰዎች ክፍያ በመፈፀም ወጪ ያወጣ ስለመሆኑ ደረሰኞችን በማቅረብ፤ ያለው አበበና ተፈሪ በንቲ ከአመልካች ጋር በገቡት የመኪና ኪራይ ውል መሰረት ገንዘብ ተቀብለው ደረሰኝ ስለመስጠታቸው ለገቢ ሰብሣቢው መስሪያቤት አረጋግጠው ሣለ፤ አቶ ተፈሪ ሰንደቁ የኪራይ ዋጋ መቀበሉንና ደረሰኝ መስጠቱን ሣይክድ ገንዘቡን አመልካች እንደፃፈው ቢገልፅም በፎረንሲክ በተደረገው ምርምራ ደረሰኙን ራሱ ፅፎ ያወጣው ስለመሆኑ በተረጋገጠበት፤ አቶ ሁሴን ኢብራሂም የተገዛውን ጎማ በሚመለከት በቀረበው አንድ ደረሰኝ ግብይት አልፈፀምኩም ቢሉም እንዲሁም ከአቶ ተፈረ ሰንደቁ የተሰጡት ሰባት ደረሰኞች በፎረንሲክ ተመርምረው እውነተኛ ደረሰኞች መሆናቸው በተረጋገጠበት ጥፋተኛ መባላቸው፤ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ሐሰተኛ ማስረጃ ማቅረብ ጥፋት የሚባለው ግብር ላለመክፈል የሌለን ፍሬ ነገር እንዳለ አስመስሎ ማቅረብን በሚመለከት ሲሆን አመልካች ደረሰኞችን ያቀረባቸው በወጪ እንዲያዝላቸው ሆኖ ሣለና ደረሰኞች ያለፈቃድ መታተማቸው በቀሪና በበራሪው ላይ የተለያዩ መጠን ያለው ገንዘብ መፃፉ የቀን ቅድም ተከተል መዛነፉ ደረሰኞችን ሃሰተኛ ሊያስብላቸው የማይችል ሆኖ ሣለ፣ በበራሪውና በቀሪው ላይ አስተካክሎ መፃፍ የአመልካች ግዴታ ሣይሆን፤ ይልቁንም አመልካች ባቀረበው ማስረጃ ግብይት በመፈፀም ወጪ ማውጣቱን ባረጋገጠበት፤ አመልካች ከአቶ ሁሴን ኢብራሒም ያቀረበው ደረሰኝ ትክክለኛ በመሆኑ ተጠያቂነት የለበትም ከተባለ በኋላ በ3ኛው ክስ ጥፋኛ መባሉ በቀረቡበት ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን በመዘርዘር እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎት አመልካች ከተጠቀሱት ሰዎች ጋር ግብይት መፈፀሙ በተረጋገጠበት፤ በአስራ አንዱ ደረሰኞች ላይ ተረጋገጠ የተባለው የቀንና የቁጥር ቅድም ተከተል መዛባት፣ በቀሪዎች ላይ የገንዘብ መጠን አለመፃፍ፣ ከሚመለከተው ተቋም ደረሰኞች እንዲታተሙ ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሆን በተለይም ደረሰኞችን ከሰጡት ሰዎች ጋር የወንጀል ተሣትፎ የነበረው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት አመልካችን በሃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል ስለመሆን አለመሆኑና የሶስተኛው ክስ መሰረት የሆነው ደረሰኝ በፎፈረንሲክ ምርምራ ትክክለኛ መሆኑ በተረጋጠበት በሶስቱም ክሶች ጥፈተኛ ተብሎ ቅጣት የመወሰኑን ተገቢነት ተመርምሮ እንዲወሰን ተጠሪም የመልስ ክርክር እንዲያቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ መዝገቡ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ መስከረም 30ቀን 2011 (ፍርድ ቤቱ የአፃፃፍ ስህተት እንደሆነ ግንዛቤ ወስዶበታል)በተፃፈ መልሱ ለቀረቡበት ክሶች ምክንያት የሆኑት ደረሰኞች መካከል ስምንቱ አጠራጣሪ በሆነ የፎረንሲክ ምርምራ ውጤት ሐጋዊ ናቸው መባሉ ተገቢ አለመሆኑን፤ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ

በመሆኑ ግብይትም ሊፈፅም የሚገባው ከሌሎች ባት ተመዝጋቢዎች ሆኖ ሣለ ከሕግ ውጪ ከተርን ኦቨር ታክስ ተመዝጋቢዎች ጋር ግብይት ፈፅሞ በወጪ እንዲያዝለት ደረሰኝ ማቅረቡ ከመነሻው ሕገ ወጥ መሆኑን፣ ደረሰኞች አንዲታተሙ ከገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ፈቃድ ያልተሰጠባቸው መሆኑ መረጋጡን፤ የአመልካችና ደረሰኙን የሰጡት ሰዎች የወንጀል ተሣትፎ ከጅምሩ የዐ/ሕግ ክስ መሰረት አለመሆኑን፤ የሶስትኛውን ክስ በሚመለከት አመልካች በወቅቱ ገቢ አሣውቆ ስለመክፍሉ ማረጋገጫ አለማቅረቡን ያቀረበው ደረሰኝም በ2005ዓ.ም ግብይት ስለመፈፀሙ አለመረጋገጡን በጥቅሉ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን በሶስቱም ክሶች ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት በመወሰኑ የፈፀመው መሰረታዊ የሕግ ስህትት የለም ተብሎ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት የመልስ ክርክሩን አቅርቧል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ ክርክሩን አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ውሣኔ እንዲሰጥበት ለለዬው ማስቀረቢያ ነጥብ መልስ ለመስጠት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ምርመረናል፡፡

እንደሚታወቀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ)ና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 እንደሚደነግጉት የክልልና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲሁም የዳኝነት ስልጣን በሕግ የተሠጣቸው ሌሎች አካላት የቀረበላቸውን ጉዳይ አከራክረው የመጨረሻ ውሣኔ ሲሰጡ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፃማቸው በክርክር ሂደት ሲረጋገጥ የማረም ስልጣን ለዚህ ችሎት ተሠጥቶታል፡፡ በዚህ መሰረት በያዝነው ክርክር የዚህ ችሎት ስልጣን አከራካሪ የሆነ ፍሬ ነገርን በማስረጃ ማጣራት ሣይሆን የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ክርክር መርምረው ውሳኔ ሲሰጡ የፈፀሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ካለ ማረም መሆኑን ከወዲሁ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

የወንጀል ሕግ አንድ ሰው በሕግ አድርግ ወይም እንዳታደርግ ብሎ የሚደነግግ መደረግ ያለባቸውንና መደረግ የሌለባቸውን ድርጊቶች በዝርዝር የሚያመለክትና በመደረጋቸውና ባለመደረጋቸው የተነሣ የድርጊቱን ፈፃሚዎች የሚቀጣ የቅጣቱን መጠንና ዓይነት የሚወሰን ሕግ ነው፡፡ ይህም ማለት ወንጀል ድርጊት ተፈፅሟል የሚባለው በወንጀል ሕግ የተከለከሉ ድርጊቶችን መፈፀም ወይም እንዲፈፀሙ የተታዘዙ ድርቶችን አለመፈፀም ነው፡፡

ከዚህ መርህ በመነሣት ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸው የሶስቱም ክሶች መነሻቸው ሀሰተኛ ወይም አሣሣች ደረሰኝ ማቅረቡ እንደሆነ የስር ፍርድ ቤቱ የውሣኔ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 50(1) ለታክሱ ባለስልጣን ሰራተኛ አንድን ነጥብ በሚመለከት የሐሰት ወይም አሳሳች ማስረጃ ያቀረበ ወይም ማስረጃው አሣሣች እንዳይሆኑ መካተት የሚገባቸውን ነገሮች ቀንሶ ያስቀረ ወንጀል እንፈጸመ የሚቆጠርበት መሆኑና በዚሁ አዋጅ በአንቀፅ50(3)

(ሀ)ና(ለ) ድንጋጌ መሰረት የሐሰት መግለጫው የተሰጠው እንዲካተት የሚገባው ነገር ያልተካተተው ሆነ ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ወንጀል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የቅጣቱ መጠን ከፍ እንደሚል ይደነግጋል። እነዚህን ድንጋጌዎች ተላልፏል በሚል በአመልካች ላይ የቀረቡትን ክሶች የአመልካች ድርጊት ወንጀል መሆን ያለመመሆናቸው ሊወሰን የሚገባው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(2) የተደነገጉትን የወንጀል ማቋቋሚያ መመዘኛዎችና በአንቀፅ 58(1)(ሀ) ላይ የተደነገገውን ድርጊቱ ወንጀል ነው ለማለት ታስቦ የተፈፀመ መሆን እንደሚገባው የተደነገገውን መርህ ግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባል።

ይህ ከሆነ ተጠሪ ዐ/ሕግ ያቀረበውን ክስ ማስረዳት የሚጠበቅበት አመልካች ሃሰተኛ ደረሰኙን ማቅረቡን ብቻ ሣይሆን ሃሰተኛ ደረሰኙን በማዘጋጀት ተሳትፎ ማድረጉን ወይም ራሱ በክሱ ላይ እንደጠቀሰው አመልካች ግብር ቀንሶ እንዲከፍል እና የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ላለማድረግ በማሰብ ሃሰተኛ መሆኑን እያወቀ ገቢ ማድረጉን ማስረዳት ይኖርበታል።

ይህ ሆኖ ሣለ የግራቀኙን ክርክር ከስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ግልባጭ ጋር በማገናዘብ ስንመረምረው ዐ/ህግ በክሱ ላይ ሃሰተኛ ናቸው የሚላቸውን ደረሰኞች ለአመልካች ቆርጠው የሰጡት ሰዎች በክልሉ ውስጥ ሕጋዊ ነጋዴዎች ከመሆናቸውም በላይ እነዚህ ደረሰኞች ከእነሱ የወጡ ስለመሆኑ ደረሰኙን በሰጡት ሰዎች አልተካደም። ይህም ሆኖ የስር ፍርድ ቤት ደረሰኞቹ ሀሰተኛ ናቸው አመልካችም ጥፋተኛ ነው ለሚለው መደምደሚያ ያበቁት ሶስት ምክንያቶች ናቸው። እነዚህም በተለምዶ ቀሪ እና በራሪ በሚባለው ወይም ለከፋዩ በሚሰጠውና ከጥራዙ ጋር በሚቀረው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ መበላለጥ በአንዳንዶች ላይ ለከፋዩ በተሰጠው ላይ ተፅፎ በቀሪው ላይ ያለመፃፍ፤ የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል መዛነፍ እና ደረሰኙን የሰጡት ሰዎች ከገቢ ሰብሣቢው መስሪያ ቤት ደረሰኞችን እንዲያሣትሙ ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሆኑ ናቸው።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(1) ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው በሕግ እንዲያደርግ (እንዲፈፅም) ወይም እንዳያደርግ(እንዳይፈፅም) በሕግ ግዴታ የተጣለበትን ተላልፎ የሚያስቀጣ ድርጊት ፈፅሞ ሲገኝ ወንጀል እንፈጸመ ታምኖበት ቅጣትም እንደሚወሰንበት ይደነግጋል። ስለሆነም ከላይ ለቀረቡት ደረሰኞች ሐሰተኛ መሆናቸው ብቻ አመልካችን ጥፋተኛ ሊያስብለው ስለማይችል የስር ፍርድ ቤት ሐሰተኛ ደረሰኝ ናቸው በተባሉት ደረሰኞች አፈጣጠርና ለገቢ ሰብሣቢው መስሪያቤት አቀራረብ ሂደት ላይ የአመልካችን ድርሻና በሕግ የተጣለበት ግዴታ ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(1) መርህ አንፃር ሊመረመር ይገባል።

እነዚህ ደረሰኞች ከተጠቀሱት ነጋዴዎች ለአመልካች የተሰጡበት በመካከላቸው በነበረው የአከራይና ተከራይ ግብይት ምክንያትና አመልካች ተከራይ(ገዥ) ደረሰኙን ያወጡት ሰዎች ደግሞ አከራይ(ሻጭ) እንደነበሩ የግራቀኙ ማስረጃና የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ ያስገነዝባል። ይህ ከሆነ ለከፋዩ በሚሰጠውና ከጥራዙ ጋር በሚቀረው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ መበላለጥ አንዳይኖር ማድረግ፣

ለከፋዩ በተሰጠው ደረሰኝ የተፃፈውን ገንዘብ መጠን በቀሪው ላይ መፃፍ፣ የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል መዛነፍ እንዳይኖር መጠንቀቅ፣ ደረሰኞች እንዲታተሙ ፈቃድ የወጣባቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ የአመልካች ግዴታ ሊሆን ይገባዋልን የሚለው የግራቀኙ የክርክር ነጥብ በመሆኑ ሊመረመር ይገባዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ማንም ምክንያታዊ ሰው በኑሮ ልማድ እንደሚገነዘበውና አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 22 እንደሚደነግገው ትክክለኛ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነው ሻጭ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ የምክንያታዊ ገዥ ሃላፊነት ለከፈለው ገንዘብ ደረሰኝ እንዲሰጠው ከመጠየቅ በዘለለ ደረሰኞች ፈቃድ ወቶባቸው መታተማቸውን ወይም ለከፋዩ በተሰጠው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ በቀሪው ላይ መፃፍ አለመፃፉን፣ የደረሰኞች ቅድም ተከተል ስለመጠበቁ ወይም አለመጠበቁ የማረጋገጥ ግዴታ የገዥ ስለመሆኑ ዐ/ሕግ በክሱ ላይ የጠቀሣቸው አዋጆች አልደነገጉም፡፡ በሌላ በኩል ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ደረሰኞች በማዘጋጀት ረገድ አመልካችና ደረሰኞችን ያወጡት ሰዎች ወንጀል ለመፈፀም ስምምነት ለማድረጋቸውና አመልካችም ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ ወይም ደረሰኙን በማዘጋጀት ወይም ሐሰተኛ መሆናቸው እያወቀ ግብሩን አሣንሶ ለመክፈል በማሰብ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ ዐ/ህግ አላስረዳም፡፡

ተጠሪ ካቀረባቸው ማስረጃዎች መካከል የተጠሪ ምስክር በጥቅሉ ሁሉም ደረሰኞች ሃሰተኞች መሆናቸውን የመሰከረ ሲሆን ሃሰተኛ ናቸው ያለበት ምክንያት ለክሱ ምክንያት ከሆኑት 19 ደረሰኞች ውስጥ አስራ አንዱ የቀን እና የቁጥር ቅደም ተከተል የተዛነፈባቸው እንዲሁም እንዲታተሙ ፈቃድ ያልተሰጠባቸውና ለአመልካች በተሰጠው ድርሻ ገንዘብ ተፅፎ በቀሪው ላይ ባለመፃፉ ቢፃፍም ተበላልጦ መፃፉን ምክንያት በማድረግ ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ሆኖም አመልካች ደረሰኞች በእጁ የገቡት ደረሰኞችን ከሰጡት ሕጋዊ ነጋዴዎች ጋር በፈፀመው ግብይት ስለመሆኑ በግራ ቀኙ ማስረጃ በተረጋገጠበት፤ በአንዛሩ ተጠሪ አመልካች ያቀረባቸውን ደረሰኞች ሐሰተኛ ስለመሆናቸው እያወቀ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ ባልተረጋገጠበት የአመልካች ግዴታ ባልሆኑ ከላይ በተጠቀሱት መመዘኛዎች ደረሰኞች ሕጋዊ አይደሉም በሚል ብቻ አመልካችን ጥፋተኛ ሊያደርገው የሚችል ማስረጃና ክርክር ባልቀረበበት በ1ኛ እና በ2ኛ ክሶች ስለመፈፀሙ በበቂ ሁኔታ ተመስክሮበታል በሚል እንዲከላከል ብይን መሰጠቱና በኋላም አልተከላከለም በሚል ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሶስተኛውን ክስ በሚመለከት የተጠሪ ክስ መሰረት የሚያደርገው ከልዩ ልዩ ግብይት የተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ በሐምሌ ወር 2005ዓ.ም ለገቢ ተቋሙ አሣውቆ ገቢ ማድረግ ሲገባው ባለማድረጉ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 49 ድንጋጌን ተላለፏል የሚል ነው፡፡ አመልካች የሰበሰብኩትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ባለመድረጌ የተፈጠረ ችግር ሣይሆን ልዩነቱ የተከሰተው ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም ጎማ ስገዛ የከፈልኩትን ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ አቅርቤ ተጠሪ ሐሰተኛ ነው በሚል ለመያዝ ፈቃደኛ አለመሆኑ ተከትሎ የመጣ ችግር እንደሆነ ይከራከራል፡፡

በተጠሪ ገቢ ያልሆነው ገንዘብ ምንጭ አመልካች ከአቶ ሁሜን ኢብራሒም ጋር በነበረው የጎማ ግኘር ግብይት ነው በሚለው ክርክር ላይ ግልፅ ተቃውሞ ሣያቀርብ አመልካች ከሁሴን ኢብራሒም ጋር የጎማ ግኘር የፈፀመው በ2005ዓ.ም ሣይሆን በ2006ዓ.ም መሆኑን ራሱ አቶ ሁሴን ኢብራሂም አረጋግጧል ይህ ደግሞ የ2006 ደረሰኝን ለ2005ማቅረቡ ጥፋት እንደሆነ ይከራከራል። ሆኖም በአመልካች ጠያቂነት ደረሰኙ በፎረንሲክ ሲመረመር እውነተኛ ደረሰኝ ስለመሆኑ ተረጋግጧል። ምርምራው የተደረገው አንድ ነጠላ ፍሬ ነገርን ለማረጋገጥ ታስቦ ስለመሆኑ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የአንድ ደረሰኝ በፎረንሲክ ላቦራቶር ተምርምሮ እውነተኛ ነው ከተባለ የወጣበትን ቀን ጨምሮ በደረሰኙ ላይ የተፃፉትን ፍሬ ነገሮች በሞላ የሚያጠቃልል ነው። ስለሆነም የሶስተኛው ክስ መሰረት አመልካች ከአቶ ሁሴን ኢብራሂም የተቀበለው ደረሰኝ መሆኑ ባልተካደበት፣ ይህ ደረሰኝ በተጠሪ በኩል ሃሰተኛ ነው በሚል ተቀባይነት በማጣቱ ክርክር ተደርጎበት እውነተኛ መሆኑ በተረጋጠበት የስር ፍርድ ቤትም የምርመራውን ውጤት ውድቅ ባላደረገበት የደረሰኙ እውነተኛ መሆን የአመልካች ክርክር ተገቢ መሆኑን ባረጋገጠበት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 149(2) መሰረት አመልካችን በነፃ ማሰናበት ሲገባ ጥፋተኛ ማለቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም።

ሲጠቃለል ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸውን 1ኛና 2ኛ ክሶች በሚመለከት አመልካች ከሕጋዊ ነጋዴዎች ጋር ግብይት በመፈፀሙ ለከፈለው ክፍያ ከነጋዴዎች ደረሰኝ መቀበሉን ባስረዳበት የእሱ ግዴታ ባልሆኑ መመዘኛዎች ማለትም ለከፋዩ በሚሰጠውና ከጥራዙ ጋር በሚቀረው ደረሰኝ ላይ የተፃፈው ገንዘብ መበላለጥ፣ ለከፋዩ በተሰጠው ደረሰኝ የተፃፈውን ገንዘብ መጠን በቀሪው አለመፃፍ፣ የቁጥርና የቀን ቅደም ተከተል መዛነፍ መኖር፣ ደረሰኞቹ እንዲታተሙ ፈቃድ የወጣባቸው አለመሆናቸው በሚሉት መመዘኛዎች ተመዝነው ሀሰተኛ ናቸው የተባሉትን ደረሰኞች ለገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት አመልካች ስለቀረበ ብቻና ደረሰኞቹ ሃሰተኛ ስለመሆናቸው እውቅና ኖሮት ስለማቅረቡ ግምት የሚያስወስዱ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው በተጠሪ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገንዘብ ልዩነቱ የተፈጠረው ገቢ ሰብሣቢ መስሪያ ቤቱ ትክክለኛውን ደረሰኝ ሀሰተኛ ነው በሚል አልይዝም በማለቱ እንደሆነ በተረጋገጠበት የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት መወሰኑ የይግባኝ ክርክሩን የመረመረው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህን አለማረሙ ፍርድ ቤቶች ሊተገብሩት የሚገባውን መሰረታዊ የወንጀል ማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል።

<u>ውሣኔ</u>

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0239664 በሆነው ሰኔ 28ቀን 2011ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካችን በቀረቡበት ሶስት ክሶች ጥፋተኛ ብሎ በስምንት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራትና በአንድ መቶ ሺህ ብር እንዲቀጣ

የወሰነው ውሳኔና ይህን ተከትሎ አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ ክርክር የመረመረው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20465 በሆነው ሐምሌ 18ቀን 2011ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ)(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች በተጠሪ ከቀረቡበት ክሶች ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች በነፃ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደብረ ብርሀን ማረሚያ ቤት አመልካች በሌላ ወንጀል የማይፈለግ ከሆነ ላሬውኑ ከእስር እንዲፈታው ታዟል፤ ይፃፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይለመስ፡፡የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 164030

ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ

ተጠሪዎች፡- 1. ሐብታሙ በለጠ

2. ያደለው ቻላቸው

3. ተመስገን ታደሰ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 11 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0218981 መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሀሳብ በሚች ላይ መጠነኛ የሆነ የአካል ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ ሳይሆን በአንቀጽ 556/2/ሀ ነው፤1ኛ ተጠሪም ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ነው በማለት 1ኛ ተጠሪን በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እሥራት፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን እንደቅደም ተከተላቸው ደግሞ በስድስት ወር እና በስምንት ወር እሥራት እንዲቀጡ ሲል የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 78191 ሠኔ 28 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪዎች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና 539/1/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ሰውን ለመግደል አስቀድመው ሀሳብ በመያዝ እና ሟች 2ኛ ተጠሪን በቦክስ በመምታት በተማሪዎች መሀል አዋርዶታል ልንበቀለው ይገባል በሚል ሀሳብ ተነሳስተው የ3ኛ ተጠሪ የእህት ልጅ የሆነውን 1ኛ ተጠሪን በስልክ ደውለው ከጠሩ በኋላ ሟችን እንዲበቀልላቸው በማግባባት የሟችን ፎቶ በማሳየት ሚያዝያ 21 ቀን 2009 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 1፡50 ሠዓት በባሕርዳር ከተማ ቀበሌ 10 ልዩ ቦታው ጌታቸው ግሮሰሪ አካባቢ የ5ኛ ዓመት የኢንጅነሪንግ ተመራቂ ተማሪ የሆነውን ሟች ተመስገን ተሾመን ከጓደኞቹ ጋር እራት በልቶ ሲመለስ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሟችን ለ1ኛ ተጠሪ ጠቁመው ካሳዩት በኋላ 1ኛ ተጠሪም ተደብቆ ቆይቶ ሟችን በድንጋይ ግንባሩ ላይ በመምታት የገደለው ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በመላ ሀሳባቸው እና ድርጊታቸው የወንጀሉን ውጤት በመቀበል ሟች እንዲገደል ያደረጉ በመሆኑ በፈጸሙት በዋና ወንጀል አደራጊነት ክሳድ የሰው ግድያ ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበውን ክስ የተመለከተው የባሕርዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎችን በተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 539/1/ሀ ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ በማለት 1ኛ ተጠሪ በአሥራ ስምንት ዓመት ጽኑ እሥራት፤ 2ኛ ተጠሪ በአሥራ ስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት፤ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በአሥራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም 1ኛ ተጠሪ ለብቻ፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ አንድ ላይ በመሆን በተለያየ መዝገብ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ተጠሪዎች በተለያየ መዝገብ ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ አጣምሮ ግራቀኙን ካካራከረ በኋላ በዓቃቤ ሕግ በኩል በማስረጃነት የቀረበው የተጠሪዎች የእምነት ቃል የሚያሳየው ሟች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር በሚኖርበት ዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ የተጣሉ እና 3ኛ ተጠሪን በመሳደቡ እና ለመደብደብ በመሞከሩ፤ 2ኛ ተጠሪንም በቦክስ ፊቱ ላይ መቶ ምልክት ስላደረገበት ሟች ከዚህ ድርጊቱ እንዲቆጠብ 1ኛ ተጠሪ ቀለል ያለ ጉዳት አድርሶ እንዲያስፈራራው ፈልገው ነው፤ ምንም እንኳን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከሟች ጋር ቀደም ሲል ተጣልተው የነበረ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ ሟችን በድንጋይ ፈራ ተባ እያለ እና ለመምታት እያወላወለ አንድ ጊዜ መቶት መሮጡ የሚያሳየው 1ኛ ተጠሪ ሟችን ቀላል ጉዳት አድርሶ እንዲያስፈራራላቸው አስበው ለ1ኛ ተጠሪ አሳይተውት ሟች በድንጋይ ተመቶ የሞተ መሆኑን ነው፤ በመሆኑም የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሀሳብ ሟች ቀለል ያለ ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ እንጂ እንዲሞት ስላልሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/2 እና 58/3 በተቀመጠው አግባብ ሊቀጡ የሚገባው በሀሳባቸው ልክ በመሆኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2/ሀ መሠረት ነው፤ 1ኛ ተጠሪም ሟችን ለመግደል አስቀድሞ ሀሳብ እንደነበረው ዓቃቤሕግ አላስረዳም፤ የድርጊት አፈጻጸሙም የተለየ ጨካኝነቱን እና ነውረኝነቱን የሚያሳይ ስላልሆነ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 መሠረት ነው በማለት 1ኛ ተጠሪ

በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እሥራት፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንደቅደም ተከተላቸው ደግሞ በስድስት ወር እና በስምንት ወር እሥራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል። አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፦ ተጠሪዎች ወንጀሉን የፈጸሙት ሚች 2ኛ ተጠሪን በተማሪ መሐል በቦክስ መቷል በሚል ቂም መሆኑን፤ ለ1ኛ ተጠሪ የሚችን ፎቶ ያሳዩት እና 1ኛ ተጠሪ ለመምታት በዝግጅት ላይ እንዳለ 3ኛ ተጠሪ የሴት ልጅ በለው በማለት ይዞት በነበረው ድንጋይ ግንባሩን የመታው መሆኑን፤ ሚች በደረሰበት ምት ምክንያት ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን አስረድተናል፤ ሚች በቀን 26/07/09 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ 3ኛ ተጠሪ እወጋሃለሁ እያለ ሲዝትበት የነበረ እና ተረጋግቶ መማር እንዳልቻለ ለሚማርበት ዩኒቨርሲቲ በአቤቱታ መግለጹ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎቸ ሚችን ለመግደል ቀድመው ሃሳብ የነበራቸው መሆኑን ያሳያል፤ የሀሳብ ክፍል ሊረጋገጥ የሚችለው ከድርጊት አፈጻጸም ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እነኚህን ሁኔታዎች ሳያገናዝቡ ተጠሪዎች ሚችን አስቀድሞ የመግደል ሀሳብ አልነበራቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አስቀድሞ የነበረውን ቂም ምክንያት በማድረግ 1ኛ ተጠሪ እንዲበቀልላቸው በመንገራቸው የፈጸሙት መሆኑ በተመሰከረበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪዎችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ መሠረት ጥፋተኛ ያለማለቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም 1ኛ ተጠሪ መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2/ሀ መሠረት ነው፤ 1ኛ ተጠሪም ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 መሠረት ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሀሳብ ሚች ቀለል ያለ ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ እንጂ እንዲሞት አልነበረም፤ 1ኛ ተጠሪም ሚችን ለመግደል አስቀድሞ የነበረው ሀሳበ እንደነበረው ዓቃቤሕግ አላስረዳም፤ የድርጊት አፈጻጸሙም የተለየ ጨካኝነቱን እና ነውረኝነቱን አያሳይም በሚል ነው። በመሆኑም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪዎች የተከሰሱበትን የሕግ አንቀጽ ለመቀየር የሰጠው ምክንያት ተገቢ ነው ወይስ

አይደለም ለሚለው የክርክሩ መሠረታዊ ነጥብ ምላሽ ለመስጠት በዓቃቤሕግ በኩል በስር ፍ/ቤት የቀረቡትን የሰው ምስክሮች ቃል እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። በዚሁ መሠረት፡-

1ኛ የዓቃቤሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ይዘት፡- በዕለቱ ሟችን እና ሌሎች ጓደኞቹን እራት ለመብላት ሲጠብቃቸው የነበረ መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ ስልክ ደውሎ አንጠጣም ወይ ያለው መሆኑን፤ ምስክሩም እራት በልቼያለው መሆኑን፤ ጓደኞቹን እየጠበቀ ሳለ ስልክ የደወሉለት መሆኑን፤ ተነስቶ ሲሄድ 2ኛ ተጠሪ ደውሎ እራት አልበላህም ወይ ያለው መሆኑን፤ ምስክሩም አዎ ሲለው ብላና እንጠጣለን ያለው መሆኑን፤ ምስክሩም ስጨርስ እደውላለሁ ብሎት የሄደ መሆኑን፤ እራት ከሚበሉበት ቦታ ሲደርስ ጓደኞቹ ሲጠብቁት የነበረ መሆኑን፤ ምግቡ እስኪደርስ ድረስ ስልክ የተደወለለት እና የአባቱ ስልክ መሆኑን፤ ምግቡን እየተሻሙ ስለሚበሉ ስልኩን ድምጽ አልባ አድርጎ ኪሱ ውስጥ ያስገባ መሆኑን፤ በልተው ሲወጡ ሟችን ስልክ ሲያወራ የነበረ መሆኑን፤ ሟች እና 2ኛ ተጠሪ የዶርማቸው ልጆች በመሆናቸው እናስታርቃቸው ያሉ መሆኑን እና ሾላ ዛፍ ያለበት ቦታ ሲደርሱ አንድ ሜትር ሟች ወደ ኋላ ቀረት ያለ መሆኑን፤ ከዚያም ካ የሚል ድምጽ የሰሙ መሆኑን፤ ደንግጠው ዞር ሲሉ ሟች ወደፊት ተንደርድሮ ሲወድቅ ከዚያን ቀን በፊት አይተውት የማያውቁ ልጅ ስላዩ ተከትለውት የሄዱ መሆኑን፤ ሟችን ክሊኒክ የወሰዱት መሆኑን እና ሪፈር ተጽፎላቸው ሆስፒታል ሲደርሱ ሟች ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን፤ 1ኛ ተጠሪ ተጠሪዎች ደውለው ሚሽን እንዳሉት እና መጠጥ ቤት ሲጠጡ አምሽተው የሟችን ፎቶ ያሳዩት መሆኑን፤ ሟች አዋርዶኛል ሰድቦኛል ብመታው ሪከርድ አለብኝ ተመራቂ ስለሆንኩ አካዳሚክ ዲስሚሳል ሊያጋጥመኝ ይችላል፤ ሟችን አስፈራራልኝ ምታልኝ ያሉት መሆኑን፤ ከሾላ ስር ተደብቆ ፈርቶ ሊተወው ሲል ፊት ለፊት ሆኖ ስኳር ሽሚዝ የለበሰው ነው አንተ የሴት ልጅ በለው ሲለው አይኔን ጨፍኖ በድንጋይ እንደመታው ሲናገር የሰማ መሆኑን በመግለጽ መመስከሩን የሚያሳይ ነው። ሌሎች ምስክሮችም በተመሳሳይ የመሰከሩ መሆኑን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ያሳያል።

የዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል የጻፈው የአስከሬን ምርመራ ማስረጃ ሟች በድብደባ ምክንያት ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን፤ አስከሬኑ በጋዝ ክምችት ያለ እና መበስበስ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን፤ በቀኝ ግንባሩ በኩል ሁለት ቦታ በትንሹ የአጥንት ጉዳት የሚታይ መሆኑን በጭንቅላቱ ቆዳ ውስጥ ደም የፈሰሰ መሆኑን፤ የራስ ቅሉ ያልተሰበረ መሆኑን፤ ጭንቅላቱ ተከፍቶ ሲታይ አንጎሉ ከደም ጋር የተቀላቀለ ወደ ፈሳሽነት የተቀየረ መሆኑን ለሞት ያበቃው የጭንቅላት ጉዳት እና የአንጎል ጉዳት መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ሚች ከሚማርበት ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተላከ ማስረጃ ሚች የ5ኛ ዓመት የመካኒካል ኢንጅነሪንግ ተማሪ መሆኑን፤ በአንድ ዶርም ውስጥ የሚኖረው 2ኛ ተጠሪ የዛቻ ወንጀል ፈጽሞብኛል በማለት መረጃ የሰጣቸው መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 35 መሠረት የሰጠው ቃል ይዘት፡- ተጠሪዎች ስልክ ደውለው ዛሬ ተልዕኮ አለ መምጣት አለብህ ያሉት መሆኑን፤ የምን ተልዕኮ ብሎ ሲጠይቃቸው ስትመጣ ይነገርሃል ያሉት መሆኑን እና ኮንሰርት ለማየት ስመጣ እደውልልሃለሁ ያላቸው መሆኑን፤ በመቀጠልም 3ኛ ተጠሪ ደውሎለት 10:00 ሰዓት ላይ የተገናኙ መሆኑን እና መጠጥ የገዛለት መሆኑን፤ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር እየተደዋወለ ልጁን እየተከታተልከው ነው ወይ ያለው መሆኑን እና ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ተገናኝተው የሄዱ መሆኑን፤ 1ኛ ተጠሪም ወደ ኮንሰርት ሄዶ ረብሻ ስለነበር ሳይገባ የቀረ መሆኑን፤ በመቀጠልም መጠጥ ቤት ገብቶ ሲጠጣ የነበረ መሆኑን፤ 3ኛ ተጠሪም ስልክ ደውሎ ሙን ላይት ከሚባለው ቦታ እንድትመጣ ያለው መሆኑን፤ ካሉት ቦታ ላይ ሄዶ መጠጥ የጠጣ መሆኑን፤ ወዲዚህ ለምን መጣን ሲላቸው 3ኛ ተጠሪ እኔ የተጣላሁት ልጅ አለ፤ ከሰው መሃል ክብሬን ገፎኛል በቦክስ መቶ ጥሎኛል ያለው መሆኑን፤ በምን ምክንያት ተጣላችሁ ሲለው በብሔር ምክንያት ነው እናንት ጉረኞች ናችሁ የተለየ ምን አላችሁ ብሎኛል ያለው መሆኑን፤ አንተም ሰው ነህ እሱም ሰው ነው ሲለው ፈርቼ እንዳይመስልህ ግቢ ፈርመናል በሀምሳ ቀን ሌላ ጥፋት ከተገኘብን ያባርሩናል ያለው መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ ለሚች ጓደኛ ስልክ ደውሎ ለእራት ትመጣላችሁ ወይ ያለው መሆኑን እና እንመጣለን ሲለው ደስ ያለው መሆኑን፤ ሚች እና ጓደኞቹ እራት ወደሚበላበት ቦታ ሲያልፉ ያሳዩት መሆኑን፤ ብዙ ጠብቆ አልወጣ ሲለው ታክሲ አላገኝም ልሂድ ያላቸው መሆኑን፤ ከዚያም ሚች እና ጓደኞቹ ሲወጡ 2ኛ ተጠሪ ደውሎ ስልክ ደውሎ ስልክ የሚያናግረው ነው መጣልህ ያለው መሆኑን እና ዞር ብሎ በድንጋይ ከኋላው በኪል አንድ ጊዜ የመታው መሆኑን በመግለጽ ቃሉን የሰጠ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 35 መሠረት የሰጠው ቃል ይዘት፡- በዕለት ግጭት ከሚች ጋር ከአንድ ወር በላይ የተጣሉ መሆኑን፤ የጠቡ ምክንያት ሙዚቃ ከፍቶ ዶርም ውስጥ ስፖርት ሲሰራ ሚች ጠላ ቤት አስመሰላችሁት ያላቸው መሆኑን፤ የሎከር በር ተዘግቶ ስለነበር ዘጋ አድርጎት ሲልፍ አንተ ዕብድ ነህ ወይ ሲለው እብድ አይደለሁም ያለው መሆኑን፤ ሚችም ትረብሻለህ ሲለው ተያይዘው በጥፊ ሲመታው ሚችም በቦክስ የመታው መሆኑን እና ፊቱ ላይ የተሰፋ መሆኑን፤ ሌሎች ጓደኞቹ በድርጊቱ ይናደዱ የነበረ መሆኑን፤ እሱም ዋጋ ከፍለን እንመረቅ ሳንመረቅ እንዳንቀር ያላቸው መሆኑን፤ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ስለጠቡ ያወሩ መሆኑን እና ከፊቱ ላይ የሆነ ምልክት መኖር አለበት በማለት ሚችን እንዲመታው የነገረው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

3ኛ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት የሰጠው ቃል ይዘት፡- ካምፓስ ግቢ ውስጥ 2ኛ ተጠሪ መዚቃ ከፍቶ ስፖርት ሲሰራ ሚች መዚቃውን ቀንስ በማለት ተጣልተው 2ኛ ተጠሪ ዓይኑ አካባቢ

የተመታ እና ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ሲነግረው ተናዶ 1ኛ ተጠሪን ዘንዘልማ ከተባለ ቦታ ወደ ባሕርዳር ከተማ እንዲመጣ ስልክ የደወለለት መሆኑን፤ ሟች ግቢ ውስጥ መቶ እንደዘረረው እና በተማሪዎች ፊት እንዳዋረደው የነገረው መሆኑን፤ ቀለል ያለ ጉዳት እንዲደርስበት የነገው መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪም ከሟች ጋር የተነሳውን ፎቶ ያሳየው መሆኑን እና በጣም እንዲጎዳ ሳይሆን እንዲደነግጥ አድርገህ ቀለል ያለ ጉዳት አድርስበት ያለው መሆኑን፤ ቀይ እስኳር ሽሚዝ የለበሰው ነው በማለት ያሳዩት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገ ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቁሙት ሕጋዊ፤ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (1) እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሲሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወ/ሕ/አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል መማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቷል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሠረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡ ተከሳሽ ባቀረበው መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ፍሬነገር በቂ እና አሳማኝ ሊባል በሚችል ማስረጃ ካላስተባበለም ጥፋተኛ እንደሚባል ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 149/1 ድንጋጌ ይዘት መዘገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ዓቃቤሕግ ያቀረባቸው የሰው ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት የሚያስገነዝቡት በሟች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል አስቀድሞ ጸብ የነበረ መሆኑን፤ በሟች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ጸብ ከተፈጠረ በኋላ ሟች ለማማርበት ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በአንድ ዶርም ውስጥ የሚኖረው 2ኛ ተጠሪ የዛቻ ወንጀል ፈጽሞብኛል በማለት ያሳወቀ መሆኑን፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ስልክ ደውለው ዛሬ ተልዕኮ አለ መምጣት አለብህ በማለት 1ኛ ተጠሪን የጠሩት መሆኑን፤ የምን ተልዕኮ ብሎ ሲጠይቃቸው ስትመጣ ይነገርሃል ያሉት መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ ለሟች ጓደኛ ስልክ ደውሎ ለእራት ትመጣላችሁ ወይ ያለው መሆኑን እና እንመጣለን ሲለው ደስ ያለው መሆኑን፤ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጥሪ መሠረት 1ኛ ተጠሪ ወደ ተባለው ቦታ ሲሄድ መጠጥ የገዛለት መሆኑን፤ 3ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር እየተደዋወለ ልጁን እየተከታተልከው ነው ወይ ያለው መሆኑን እና ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ተገናኝተው የሄዱ መሆኑን፤ 3ኛ ተጠሪም ስልክ ደውሎ ሙን ላይት ከሚባለው ቦታ እንድትመጣ

ያለው መሆኑን፤ ካሉት ቦታ ላይ ሄዶ መጠጥ እየጠጡ ወዲዚህ ለምን መጣን ሲላቸው 3ኛ ተጠሪ እኔ የተጣላሁት ልጅ አለ፤ ከሰው መሃል ክብሬን ገፎኛል በቦክስ መቶ ጥሎኛል ያለው መሆኑን፤ በምን ምክንያት ተጣላችሁ ሲለው በብሔር ምክንያት ነው እናንት ጉረኞች ናችሁ የተለየ ምን አላችሁ ብሎኛል ያለው መሆኑን፤ በመቀጠልም ፊርቹ እንዳይመስልህ ግቢ ፈርመናል በሀምሳ ቀን ሌላ ጥፋት ከተገኘብን ያባርሩናል ያለው መሆኑን፤ ሚች እና ጓደኞቹ እራት ወደሚበላበት ቦታ ሲያልፉ ያሳዩት መሆኑን፤ ከዚያም ሚች እና ጓደኞቹ ሲወጡ 2ኛ ተጠሪ ደውሎ ስልክ የሚያናግረው ነው መጣልህ ያለው መሆኑን እና ዞር ብሎ በድንጋይ ከኋላው የመታው መሆኑን እና ሚች ወደፊት ተንደርድሮ የወደቀ መሆኑን እና በጭንቅላቱ ላይ በደረሰበት ጉዳት ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት ቀርበው የተሰሙት የዓቃቤሕግ ማስረጃዎች የሚያስገነዝቡት ከላይ የተመለከተውን ነው የምንል ከሆነ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 35 መሠረት ለፍ/ቤት በሰጡት ቃል፤ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27/2 መሠረት ለፖሊስ በሰጠው ቃል ሀሳባችን የነበረው በሚች ላይ ቀላል ጉዳት እንዲደርስ ነበር በማለት ያስመዘገቡት ቃል ብቻውን ተነጥሎ ተጠሪዎች ሊቀጡ የሚገባው በሀሳባቸው ልክ ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ነው ወይ? የሚለው የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ነው፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ሀሳብ በሚች ላይ ቀለል ያለ ጉዳት እንዲደርስ ነበር ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ ቢሆንም ተጠሪዎች ክሱን እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/3 መሠረት ለፍ/ቤቱ በሰጡት ቃል ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ከመካዳቸው በቀር ሀሳባችን የነበረው በሚች ላይ ቀላል ጉዳት እንዲደርስበት ነበር በማለት የሰጡት ቃል ካለመኖሩም በላይ ሀሳባቸው በሚች ላይ ቀላል ጉዳት እንዲደርስ ስለመሆኑ በሌላ ደጋፊ ማስረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይዘት አያሳይም፡፡ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጥሪ መሠረት ድርጊቱን የፈጸመው 1ኛ ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 35 መሠረት በሰጠው ቃልም ተጠሪዎች በሚች ላይ ቀለል ያለ ጉዳት እንዲያደርስበት የነገሩት ስለመሆኑ በመግለጽ የሰጠው ቃል የለም፡፡ ይልቁንም ሚች እና 2ኛ ተጠሪ በዩኒቨርሲቲው ዶርም ውስጥ መዚቃ ከፍታችኋል በሚል ተጣልተው ሚች እና 2ኛ ተጠሪ የተደባደቡ እና በዚህ ምክንያት በመካከላቸው አለመግባባት የተፈጠረ መሆኑ፤ ሚች 2ኛ ተጠሪ ዛቻ ይፈጽምበት እንደነበረ ለዩኒቨርሲቲው ቀደም ብሎ ያሳወቀ መሆኑ፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ስልክ ደውለው ዛሬ ተልዕኮ አለ መምጣት አለብህ በማለት 1ኛ ተጠሪን የጠሩት መሆኑ፤ 3ኛ ተጠሪ ሚች ከሰው መሃል ክብሬን ገፎኛል በቦክስ መቶ ጥሎኛል የተጣላነው በብሔር ምክንያት ነው እናንት ጉረኞች ናችሁ የተለየ ምን አላችሁ ብሎኛል ያለው መሆኑ፤ በመቀጠልም ፊርቹ እንዳይመስልህ ግቢ ፈርመናል በሀምሳ ቀን ሌላ ጥፋት ከተገኘብን ያባርሩናል ያለው መሆኑ፤ 3ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር እየተደዋወለ ሚች እራት ወደሚበላበት ቦታ መምጣት አለመምጣቱን ለማረጋገጥ መከታተላቸው፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች 1ኛ ተጠሪን መጠጥ በመጋበዝ ሚች ራት በልቶ እስኪወጣ

ድረስ እንዲጠብቅ ማድረጋቸው እና ሟች ከጓደኞቹ ጋር እራት በልቶ ሲመለስ ስኳር ሽሚዝ የለበሰው እና ስልክ የሚያወራው ነው በማለት ሟችን ለይተው ማሳየታቸው ዓቃቤሕግ ባቀረባቸው ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች መረጋገጡ ሲታይ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ ባቀረበው የወንጀል ክስ ውስጥ የገለጻቸውን ፍሬ ጉዳዮች ትክክለኛነት ተጠሪዎች ስለመፈጸማቸው ለማሳየት ያቀረባቸው ማስረጃዎች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና ተያያዥነት ያላቸው እና የተጠሪዎች ሀሳብ በሟች ላይ ቀላል ጉዳት እንዲደርስ ሳይሆን ሟችን የመግደል ሀሳብ እንደነበር የሚያሳይ ነው። የተጠሪዎች ሀሳብ የመግደል ሀሳብ ከነበረ ቀጥሎ መታየት ያለበት ተጠሪዎች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በየትኛው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ነው? የሚለው ነው።

አንድ ሰው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) መሠረት ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው ሰውን ለመግደል አስቀድሞ የነበረው ሐሳብ ወይም ምክንያት፤ ለመግደል የተጠቀመበት መሣሪያ ወይም ዘዴ፤ ያገዳደሉ ሁኔታ ወይም ግድያው የተፈጸመበት ቅጣትን የሚያከብድ ጠቅላላ ምክንያት አንቀጽ 84 ወይም 86 ስር ሲታይ ወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ነው በማለት ይደነግጋል። ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ላይ የተጠቀሱት ነጥቦች እያንዳንዳቸው ራሣቸውን ችለው የሚቆሙ መሆኑን ነው።

በያዝነው ጉዳይ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በሟች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት መነሻነት የያዙትን ቂም መሠረት በማድረግ 1ኛ ተጠሪን ተልዕኮ አለ በማለት በመጥራት እና ሟችን ለይተው በማሳየት ሟች በድንጋይ ተመቶ እንዲሞት ለማድረግ ዋናውን ዕቅድ ያቀነባባሩ እና የወንጀሉ ዋና ጠንሳሽ መሆናቸው የተረጋገጠ በመሆኑ የ1ኛ ተጠሪ የወንጀል ድርጊት በሟች ላይ የሚያመጣውን ውጤት ሙሉ ለሙሉ መቀበላቸውን የሚያሳይ ነው። ወንጀሉ ቂምን መሠረት በማድረግ ሶስቱም ግብረአበሮች ተሳታፊ ሆነው የፈጸሙት በመሆኑ እና ሟች ጭንቅላቱን በድንጋይ ተመቶ በጭንቅላቱ ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ሕይወቱ ያለፈ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 539/1/ሀ ድንጋጌ መሠረት ነው። በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሀሳብ በሟች ላይ መጠነኛ የሆነ የአካል ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539/1/ሀ ሳይሆን በአንቀጽ 556/2/ሀ ነው፤ 1ኛ ተጠሪም ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ነው በማለት 1ኛ ተጠሪን በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እሥራት፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን እንደቅደም ተከተላቸው ደግሞ በስድስት ወር እና በስምንት ወር እሥራት እንዲቀጡ ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል።

ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0218981 መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 78191 ሠኔ 28 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባሕርዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 04-04796 ሕዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ታሕሳስ 04 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል፡፡

ትዕዛዝ

- የፌዴራል፤ የክልሉ እና የአዲስ አበባ ፖሊስ 2ኛ እና 3ኛ ተጠዎችን በተገኙበት ቦታ ይዘው ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት እንዲያስረክቡ ታዟል፡፡
- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አስተዳደርም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በፖሊስ ተይዘው ሲቀርቡለት 1ኛ ተጠሪም በማረሚያ ቤት የሚገኝ በመሆኑ ሶስቱም ተጠሪዎች በዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት የታሰሩት ካለ ታሳቢ በማድረግ በዚህ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ መሠረት ተከታትሎ ቅጣቱን እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስለገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የልዩነት ሀሳብ

በተራ ቁጥር 4 እና 5 ላይ የተመዘገበው ዳኞች በዚህ መዝገብ በቀረበው ጉዳይ አከራካሪ በሆነው ጭብጥ አብላጫ ድምፅ የያዙት የስራ ባልደረቦቻችን በሰጡት ውሣኔ ስላልተስማማን ለልዩነት ያበቁንን ምክንያቶች ከዚህ ቀጥሎ አስፍረናል፡፡

በመዝገቡ ላይ ከቀረቡት ክርክሮች መካከል ዋናውና በመካከላችን አከራካሪ የነበረው ነጥብ ተጠሪዎች ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት ሊወሰንባቸው የሚገባው የባህር ዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሰጠው ፍርድ በከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ነው ወይስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አሻሽሎ እንደወሰነው 1ኛ ተጠሪ በተራ የሰው ግድያ ወንጀል፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ታስቦ በሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀል የሚለው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሆነው የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከሟች ጋር የነበራቸውን ቂም መነሻ በማድረግ ሶስቱም የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ /ሀ/ ና አንቀጽ 539/1/ /ሀ/ የተመለከተውን ክልከላ ተላልፈው ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅመው የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት

የይግባኝ አቤቱታ መነሻነት የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቀረበው የዐ/ህግ ማስረጃ አመልካቾች ድርጊቱ መፈፀማቸው ተረጋግጦባቸው የዐ/ሕግ ማስረጃ ያላስተባበሉ በመሆናቸው የጥፋተኝነት ፍርድ መሰጠቱ ተገቢ ሆኖ ሣለ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው ግን 1ኛ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 እና 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ታስቦ በሚፈፀም ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ነው ሲል የከፍተኛው ፍርድ ቤቱን ውሣኔ አሻሽሏል፡፡ ይህ ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር በሚ ችሎት ተመርምሮ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለመሆኑ ትእዛዝ ተሰጥቶበታል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች የወንጀል ድርጊት መፈፀማቸው ስለተረጋገጠባቸው የጥፋተኝነት ፍርድ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ ሣለ አከራካሪ የነበረውና ለልዩነታችን ምክንያት የሆነው ተጠሪዎች ወንጀል መፈፀማቸውን ለማስረዳት ዐ/ሕግ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር አንፃር ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በየትኛው ድንጋጌ ነው፡፡ ዐ/ሕግ ባቀረበው ማስረጃ 1ኛ ተጠሪ ይህን ድርጊት የፈፀመውም 2ኛ ና 3ኛ ተጠሪዎች ሚች ሁለተኛ ተጠሪን ደብድቦት ስለነበር በዚህ ድርጊት በሁለተኛ ተጠሪ የደረሰውን የሞራል ጉዳት ለማካካስ በማሰብ 1ኛ ተጠሪ ሚችን እንዲያስፈራራቸውና እንዲያስደነግጥላቸው ስለጠየቁት ለማስፈራራትና ለማስደንገጥ አስቦ ፈራ ተባ እያለ አንድ ጊዜ ድንጋይ ወርውሮ የሚችን ጭንቅላት መምታቱን በዚህ ምት ምክንያት ሚች ለሞት መብቃቱ የስር ፍርድ ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539 ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው የሰው ግድያ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ ጥፋተኛ የሚባለውና የሚቀጣው የሰው መግደል ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት አስቀድሞ ሰውን ለመግደል በማሰብ የነበረውን ሃሳብና ሃሳቡን ከፍፃሜ ለማድረስ ያደረገውን ዝግጅት እንዲሁም የተጠቀሰበትን መሣሪያ ለወንጀሉ መፈፀም ያበቃውን ምክንያትና አገዳደሉን ሁኔታ ወይም አድራጊውን ጨካኝነት ወይም ነውረኝነት ግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አድራጊው ወንጀል ለመፈፀም ማሰብ ብቻ ሣይሆን አስቀድሞ መግደል አለብኝ ብሎ ማቀድን መዘጋጀትን እና ባቀደው መሰረት መፈፀሙ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ተከሳሽ በእነዚህ መመዘኛዎች መሰረት ድርጊቱን የፈፀመ ስለመሆኑ በቅድሚያ የማስረዳት ሀላፊነቱ የዐ/ሕግ ስለመሆኑ የታመነ ነው፡፡

በሌላ በኩል ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት የድርጊት ፈፃሚውን ወንጀል ለመፈፀም የነበረውን ሐሳብና በተፈፀመው ድርጊት የተገኘውን ውጤት ለማግኘት አስቦ አድራጊው ድርጊቱን ስለመፈፀሙ በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ፤ ነገር ግን አድራጊው መፈፀም ካሰበው ድርጊት ለተፈፀመው ድርጊት ባስከተለው ውጤት ተጠያቂ ሊሆን እንደማይገባ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23፤32/2/፤58 ይደነግጋል፡፡

በተያዘው መዝገብ ቅድሚያ የማስረዳት ሃላፊነቱን ለመወጣት ማስረጃ ያቀረበው ዐ/ሕግ ባቀረበው ማስረጃ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች 1ኛ ተጠሪ ሚችን እንዲገልላቸው ፍፁም ሐሳብ ያልነበራቸው መሆኑን፤

1ኛ ተጠሪም ድረጊቱን የፈፀመው ሚችን ለመግደል አስቦ ሣይሆን 2ኛና 3ኛ ተጠሪዎች በነበሩት መሰረት ለማስፈራራትና ለማስደንገጥ ብሎ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

ይህ ከሆነ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሚች በ1ኛ ተጠሪ እንዲገደል አስቀድሞ ሐሳብ የነበራቸው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበትና ይልቁንም ዐ/ሕግ ራሱ ባቀረበው ማስረጃ 1ኛ ተጠሪ ሚችን እንዲያስፈራራላቸው አስበው የጠየቁትና በዚሁ መሰረት ማስፈራራት ድረጊቱን ለመፈፀም አስቦ 1ኛ ተጠሪ በፈፀመው ድርጊት ሚች ስለሞተ ብቻ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅመዋል በሚል 1ኛ ተጠሪም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በለመኑት መሰረት ሚችን ለማስፈራራት አስቦና አቅዶ ይህን ለመፈፀም ሚችን አንድ ጊዜ በድንጋይ ሲመታው ስለሞተ ከላይ የተዘረዘሩት የከባድ የሰው መግደል ወንጀል ማቋቋሚያ ከሆኑት መመዘኛዎች መካከል አንዱም ሣያሟላ በከባድ የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት የወሰነባቸው የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ እንዲፀና መደረጉ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህን የጣሰ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ ነው በሚል ምክንያት ከባልደረቦቻችን የተለየ ሐሳብ ስለያዝን፤ ይልቁንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ተላልፎ ተራ የሆነ የሰው ግድያ ወንጀል ፈፅሟል በሚል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች 1ኛ ተጠሪ በሚች ላይ እንዲፈፀም የፈለጉትን ድርጊት መጠየቅ አለባቸው በሚል የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2/ ተላልፈው ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀል እንዲፈፀም መስማማታቸውን ድርጊቱ እንዲፈፀም ማድረጋቸው ተረጋግጧል በሚል የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ በማሻሻል መወሰኑ ተገቢ ነበር በሚል በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 167965

ሕዳር 26 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች/ቾች፡- አሕመድ ኢብራሂም ንጉሴ - አልተጠሩም፡፡

ተጠሪ/ዎች፡- የኦሮሚያ ክልል ዓቃቤ ሕግ - ዐ.ህግ ምዕራፍ ወርቁ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 09 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284629 ጥቅምት 12 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል በቀረቡበት ስድስት ክሶች ተሳትፎ ውጤቱንም የወሰደ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 60/ሐ እና 184/2 ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ነው ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ክሶች ስድስት ሲሆኑ ይዘታቸውም፡-

<u>1ኛ ክስ</u>፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ጉቱ በተባለ ልዩ ቦታ በቀን 30/04/10 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 5፡00 ሰዓት ማንነቱ ካልታወቀ እና ለጊዜው በቁጥጥር ስር ያልዋለ ግለሰብ የግል ተበዳይ አሲያ አባጋሮ ሱቅ ሄዳ ስትመለስ አብዱልቃድር አባጋሮ ጥሩ ስራ አግኝቶልሻል አትፈልጊም ወይ? የሚደርስሽ ጥሩ ስራ እና ጥሩ ቦታ

ነው በማለት በማባበል፤ አልፋው ስትገባ በማግስቱም መጥቶ በማባበል ነገ ስለምትሄዱ በማለዳ 1ኛ ተከሳሽ ጋር አደርሳችኋለሁ በማለት፤ በማግስቱም ከቤት በማስወጣት ስሙ ካልታወቀ ግለሰብ ጋር በመሄድ 1ኛ ተከሳሽ ከሌላ ሰው ጋር በመሆን ተቀብሎ አመልካች ቤት በማምጣት በመሸሸግ፤ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ያልዋለች የአመልካች ባለቤት ጋር ተበዳይዋን ፎቶ በማንሳት አትፍሪ ችግር የለም ሲቸግርሽ ለእኔ ትነግሪኛለሽ ፎቶሽን ደግሞ ብትጠፊ ትፈለጊበታለሽ ከሁለት ሳምንት በኋላ ወደ ውጪ ሐገር ሄደሽ እንድትሰሪ አደርግሻለሁ በማለት ወደ ሰው ቤት አሳልፈው በመስጠት ከሰዎች ጋር በስልክ እየተግባቡ ፖሊስ ባደረገው ክትትል የተያዘ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

2ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለጸው ሁኔታ ስሙ እና ማንነቱ ያልታወቀ ግለሰብ የግል ተበዳይ ሩሴ አባሲመንን በቀን 03//05/10 ከቤት በማውጣት ስሙ ካልታወቀ ግለሰብ ጋር ሄዳ 1ኛ ተከሳሽ ስሙ ካልታወቀው ግለሰብ ተቀብሎ ነቀምቴ ከተማ በማሳድር በቀን 04/05/10 አመልካች ቤት በማሳደር ሸሽጎ በቁጥጥር ስር ካልዋለች የአመልካች ባለቤት ጋር በ1ኛ ክስ የተገለጸውን ድርጊት በመፈጸም ላይ ሳሉ ፖሊስ ባደረገው ክትትል ስለተያዙ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

3ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ነብያት መሐመድን በቀን 03/05/10 ከቀኑ በግምት 8፡00 ሰዓት 1ኛ ተከሳሽ ከበደሌ ከተማ ወደ ነቀምቴ ከተማ እየተጓዘች ሳለ ከጎንዋ በመቀመጥ ጊምቢ ከተማ ጥሩ ስራ አለ ወደዚያው አደርስሻለሁ በማለት በሌሎች ክሶች ላይ የተገለጹትን ተበዳዮች ሲሳያት በደላላ እጅ ወደ ሌላ ሰው ቤት አልገባም እንጂ ስራ እፈልጋለሁ ስትለው የደላላ እጅ አላውቅም በማለት በድጋሚ አባብሏት በነቀምቴ ከተማ አሳድሯት በቀን 04/05/2010 በግምት 3፡00 ሰዓት በአመልካች ቤት በማምጣት ሸሽገው ከአመልካች ባለቤት ጋር በቤታቸው ሸሽገው 1ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ተቀብሎባት አመልካች እና ባለቤቱ ደግሞ ፎቶ በማንሳት አትፍሪ ስትጠፊ ትፈለጊበታለሽ ከሁለት ሳምንት በኋላ ወደ ውጪ ሐገር እንድትሰሪ እናደርግሻለን በማለት ወደ ሌላ ሰው ቤት አሳልፈው ለመስጠት በስልክ እየተግባቡ ሳሉ በፖሊስ ክትትል ስለተያዙ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

4ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን ወ/ት ሳቢቃ ካማል የተባለችውን የግል ተበዳይ በቀን 30/04/10 ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ተበዳይ ሱቅ ሄዳ ስትመለስ 1ኛ ተከሳሽ በመንገድ አስቁሟት አዲስአበባ አደርስሻለሁ እዚያ ሄደሽ ጥሩ ስራ ሰርተሽ ገንዘብ ታገኛለሽ

እራስሽንም ቤተሰብሽንም ትረጃለሽ በማለት፤ እማራለሁ አልሄድም ስትለው ሐሙስ ቀን ድረስ ተማሪ ከዚያ በኋላ ትሄጃለሽ በማለት በቀን 03/05/10 ጠዋት እንዲሄዱ በመንገር፤ ተበዳይዋ ቤተሰቦችዋን ደብቃ ከቤት ወጥታ እንድትሄድ በማድረግ በ6ኛ ክስ ላይ ከተገለጸችው የግል ተበዳይ ጋር 1ኛ ተከሳሹ በመኪና አሳፍሮአቸው ነቀምት ከተማ አሳድሯት በማግስቱም በአመልካች ቤት በማምጣት ሸሽገው ለጊዜው በቁጥጥር ስራ ካልዋለች የአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን በራሳቸው ቤት ውስጥ በመሸሸግ፤ 1ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ተቀብሎ አመልካች እና ባለቤቱ ደግሞ ፎቶ በማንሳት ወደ ውጪ ትሄጃለሽ በማለት በማባበል ወደ ሌላ ሰው ቤት አሳልፎ ለመስጠት ከሌሎች ሰዎች ጋር በስልክ እየተግባቡ ሳሉ በፖሊስ ክትትል የተያዙ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

5ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ወ/ት ለይላ አህመድ የተባለችውን 1ኛ ተከሳሽ ጓደኛዋን ሳቢቃ ከማል በሕገወጥ መንገድ ለማዘዋወር በተደጋጋሚ ሲጠይቃት ቆይቶ በቀን 02/05/10 ከቀኑ በግምት 5፡00 ሰዓት መንገድ ላይ አግኝቷት ጊምቢ ወደ ተባለ ጥሩ ሐገር አደርስሻለሁ እዚያ ገንዘብ አግኝተሽ እራስሽን ችለሽ ቤተሰብሽንም ትረጃለሽ በማለት በማባበል በማግስቱ ጉዞ ስለሆነ ተዘጋጂ በማለዳ ተነስተን እንሄዳለን እኔ ቶባ ከተማ እጠብቅሻለሁ በማለት በቀን 03/05/10 ዓ.ም ጠዋት ከቤት በማውጣት 1ኛ ተከሳሽ መኪና አሳፍሯት ነቀምት ከተማ አሳድሯት በማግስቱ ወደ አመልካች ቤት በማምጣት ሸሽገው ለጊዜው ካልተያዘችው የአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን ከላይ ባሉት ክሶች በተገለጸው ሁኔታ የተያዙ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

6ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ካልዋለች አለውያ ሰዒድ ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ወ/ት አይሻ አህመድ የተባለችውን በጓደኛዋ ሳቢቃ ከማል በቀን 02/05/10 ዓ.ም የሐሰት ቃል በመንገር በማታለል በማግስቱ ከቤት በማውጣት በ4ኛ ክስ ተበዳይ ከሆነችው ከሳቢቃ ከማል ጋር በመሆን 1ኛ ተከሳሽ መኪና አሳፍሮ ነቀምት ከተማ አሳድሯት በማግስቱ በአመልካች መኖሪያ ቤት በማምጣት ሸሽገው 1ኛ ተከሳሽ ገንዘብ ተቀብሎባት ካልተያዘችው የአመልካች ባለቤት ጋር በመሆን ከላይ ባሉት ክሶች በተገለጸው ሁኔታ የተያዙ በመሆኑ በፈጸመው በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ማዘዋወር ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ተቀብለውታል የተባለው የገንዘብ መጠን በክሱ ውስጥ አልተገለጸም በማለት ክሱን ተቃውመው ክሱ በዚህ አግባብ እንዲሻሻል የተደረገ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡ አመልካች የእምነት ክሕደት ቃሉን ሲጠየቅም በዓቃቤሕግ ክስ መሠረት

ድርጊቱ ያልተፈጸመ መሆኑን፤ በቀን 4/5/10 ዓ.ም ፖሊስ ተበዳዮችን በ2ኛ ተከሳሽ ቤት ሄዶ ሲቆጣጠር 1ኛ ተከሳሽ በ2ኛ ተከሳሽ ቤት የሚቀመጥ ልጅ ስላለው ወደ 2ኛ ተከሳሽ ቤት ሄዶ በር ሲያንኳኳ ወደ ራሱ ቤት ያስገባቸው ቀድሞውኑ 1ኛ ተከሳሽን ስለሚያውቅ እንጂ ስለተበዳዮቹ የሚያውቀው ነገር የሌለ መሆኑ እና 1ኛ ተከሳሽም ማዘዋወሩን የሚያውቀው ነገር የሌለ መሆኑን፤ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የተባለውን ወንጀል ያልፈጸመ መሆኑን፤ በአመልካች ቤት ቆይተው የሄዱት አንድ ሰዓት ለማይበልጥ ጊዜ መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክሕደት ቃሉን የሰጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃዎች ሰምቷል፡፡

ፍ/ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ 1ኛ ተከሳሾች ተበዳዮችን ጥሩ ገንዘብ ታገኛላችሁ በማለት ተስፋ ስጥቶአቸው መልምሎ በማጓጓዝ ወደ ግምቢ ከተማ ማምጣቱን፤ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ከሰዎች ጋር በስልክ መነጋገሩን እና ተበዳዮችን ከ1ኛ ተከሳሽ ተቀብሎ በድርጊቱ መሳተፉን ስላስረዳ ተከሳሾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የስር 1ኛ ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለት ያስመዘገበ መሆኑን እና አመልካች ደግሞ ሁለት መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ፍ/ቤቱም በመቀጠል የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የዓቃቤሕግ ምስክሮች ከጥርጣሬ በላይ በሆነ መልኩ ተከሳሾች የተከሰሱበትን ወንጀል መፈጸማቸውን አስረድተዋል፤ የአመልካች መከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል አጠራጣሪ ነው፤ አመልካች ተመልምለው የተስፋ ቃል ተሰጥቶአቸው ተጭነው ወደ ቤቱ የመጡትን ተበዳዮችን ከ1ኛ ተከሳሽ ተቀብሎ በር ከፍቶ መቀበሉ ዋሳችሁ እኔ ነኝ የምትቸገሩት ነገር የለም ከ2-3 ዓመት ከሰራችሁ ወደ ውጪ ሐገር እልካችኋለሁ በማለት የተስፋ ቃል መስጠቱ የተረጋገጠ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ መሠረት በስድስቱም ክሶች ጥፋተኞች ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት በማስላት በ 25 ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 10000 መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በመቀጠል ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- በተጠሪ ምስክሮች እንደተገለጸው የግል ተበዳይ ናቸው የተባሉት ወጣት ሴት ሰራተኞች ወደ ጉምቢ ከተማ የመጡት በቤት ሰራተኝነት አገልገልው የሚገባቸውን ተመጣጣኝ ደመወዝ ለማግኘት ከመሆኑ በቀር ለብዝበዛ ዓላማ አይደለም፤ ደመወዛችን ተመጣጣኝ አይደለም ባሉም ጊዜ ሥራውን አቋርጠው የመሄድ ሙሉ መብት አላቸው፤ ይህም በማናቸውም የቤት ሰራተኛ የቅጥር ግንኙነት የተለመደ ተግባር ነው፤ በመሆኑም የወንጀሉ ማቋቋሚያ ግዙፋዊ ፍሬነገር ባልተሟላበት

ሁኔታ የጥፋተኝነት ውሳኔ መሠጠቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካች የግል ተበዳዮችን ያየሁት ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ሆነው ወደ ቤቱ በመጡ ጊዜ ነው፤ የስር 1ኛ ተከሳሽ ልጅ በእኔ ቤት ተቀጥራ ትሰራ የነበረ በመሆኑ ልጁን ለመጠየቅ ነው የሚል ግንዛቤ ነበረኝ፤ የልጁ ቀጣሪ ከመሆኔ ውጪ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ሌላ ምንም ዓይነት ግንኙነት የለኝም፤ አመልካች በቤቱ እንዳለሁ በቁጥጥር ስር በዋልኩበት ጊዜ የሞባይል ስልኬ ወዲያው የተያዘ በመሆኑ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር አስቀድሞ የነበረ ግንኙነት ቢኖረኝ ኖሮ ተጠሪ በቴሌኮም ማስረጃ ከማስረዳት የሚያግደው ነገር አልነበረም፤ ፎቶ አንስተሀል የሚለው እውነት ቢሆን ኖሮ ተጠሪውም የፎቶግራፍ ማስረጃውን እንደማስረጃ ያቀርበው ነበር፤ ፎቶግራፍ ማንሳቴ ተረጋግጦ ቢሆን ኖሮ እንኳን ይህን ማድረጌ ብቻ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የእድሜየን ግማሽ ማረሚያ ቤት እንዳሳልፍ የሚያደርገኝ አይደለም፤ አመልካች ስለግለሰቦቹ ከተማ መምጣት ምንም እውቀት ያልነበረኝ በመሆኑ ወደ ውጪ አገር ትሄዳለችሁ ልል የምችልበት መነሻ ሁኔታ ስለሌለ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ለመፈጸም ሀሳብ የነበረው ለመሆኑ እና በድርጊቱም ስለመሳተፉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 909/07 አንቀጽ 3/2/ሀ መሠረት በቀረቡበት ስድስት ክሶች ጥፋተኛ የመባሉን አግባባነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ከስር 1ኛ ተከሳሽ፤ ለጊዜው ካልተያዘች ባለቤቱ እና ማንነቱ ካልታወቀ ግለሰብ ጋር በመሆን ስራ ሰርታችሁ ትለወጣላችሁ በማለት ስድስት ሴት ልጆችን መልምሎ በመኪና ወደ ነቀምት ከተማ ወስዷቸው ካሳደሯቸው በኋላ በማግስቱ ወደ ጊምቢ ከተማ አስገብቶ በማቆየት ለልጆቹ ምግብ ከሰጡ በኋላ ሥራ ሰርታችሁ ትለወጣላችሁ፤ ከ 2 ወይም 3 ዓመት በኋላ ወደ ውጪ አገር ትሄዳላችሁ በማለት ለማስታወሻ የሚሆን ፎቶ አንስቶአቸው እንደነበር እና ከብር 1000 እስከ 1500 ብር ይዛችሁ ትመጣላችሁ በማለት ስልክ ከሌላ ሰው ጋር እየተደዋወለ ሳለ ድንገት ፖሊሰ ደርሶባቸው እጅ ከፍንጅ እንደተያዙ ያስረዳን በመሆኑ ለብዝበዛ ዓላማ ሊያውል እንደነበር አመላካች ነው፤ አመልካች በዓቃቤሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ፍሬነገር ባቀረበው ማስረጃ ያላስተባበለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶቹ አመልካችን ጥፋተኛ በማለት የሰጡት ውሳኔ ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል በማለት የተያዘው ነጥብ አመልካች ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ለመፈጸም ሀሳብ የነበረው ለመሆኑ እና በድርጊቱም ስለመሳተፉ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 909/07 አንቀጽ 3/2/ሀ መሠረት በቀረቡበት ስድስት ክሶች ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር በሚል በመሆኑ የዐቃቤሕግ ምስክሮች አመልካችን በሚመለከት በስር ፍ/ቤት የሰጡትን የምስክርነት ቃል ይዘት መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። የተጠሪ ምስክሮች ለስር ፍ/ቤት የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት ጠቅለል ብሎ ሲታይ ማንነቱን የማያውቁት ሰው ትሄዳላችሁ ብሎ ያባበላቸው መሆኑን እና ወደ ሌላ ከተማ ጉዞ ሲያደርጉ የጉዞ ወጪ ሲሸፍን የነበረው 1ኛ ተከሰሳሽ መሆኑን፤ ካሉበት ከተማ ወደ ጊንቢ ከተማ የአመልካች ባለቤት ወደ ሆነችው አለውያ ቤት የገቡ መሆኑን እና ስትጠፉ ትፈለጉበታላችሁ ተስተካከሉ ብለው ፎቶ ያነሳቸው መሆኑን፤ሐገሪቱ ጥሩ ናት ሰርታችሁ ትለወጣላችሁ ከ2 እስከ 3 ዓመት ስትሰሩ ደግሞ ወደ ውጪ አገር ትሄዳላችሁ ያላቸው መሆኑን፤ 1ኛ ተከሳሽ ስልክ ሲደወልለት አንተ የምትለውን ልጆች አምጥቼልሀለሁ ያላቸው መሆኑን፤ የአመልካች ባለቤት አሲያ እና ሳቢቃ አስቀራቸዋለሁ ሌሎቹን እንደፈለግክ አድርግ ያለች መሆኑን፤ ስልክ ደውላም ገንዘብ ይዘሽ ነይ ያለች መሆኑን እና አሲያን እና ሳቢቃን አስቀርተው ከቤት እየወጡ ሳሉ ፖሊሰ የመጣባቸው መሆኑን በመግለጽ የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን 6ኛ ምስክር ደግሞ በጊምቢ ከተማ የአመልካች ባለቤት ቤት ሲባል መረጃ ሰምተው ሄደው በቤት ውስጥ ያሉ ልጆች አምጧቸው ሲባል ሰዎቹን ያመጧቸው መሆኑን፤ 1ኛ ተከሳሽን ሲያናግሩ ከጅማ ዞን የአመልካችን ባለቤት ላነጋግራት መጥቻለሁ ያላቸው መሆኑን፤ ፖሊስ ጽ/ቤት ልጆቹን የወሰዷቸው መሆኑን እና ፖሊስ ሲመረምራቸው 1ኛ ተከሳሽ በፈለጋችሁበት ቦታ ገንዘብ ታገኛላችሁ ብሎ አባብሎ አምጥቶናል በማለት ገልጸዋል በማለት የመሰከረ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በመሠረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቁሙት ሕጋዊ፤ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (1) እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወ/ሕ/አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል መማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል። ይህም ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቶአል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሠረት ተከሳሹ ወንጀል

መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው። ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.142 መሠረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 141 ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል።

አመልካች የተከሰሰበት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን እና ስደተኞችን በሕገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ማንኛውም ሰው በኢትዮጲያ የግዛት ክልል ውስጥም ሆነ ከኢትዮጲያ የግዛት ክልል ውጪ ለብዝበዛ ዓላማ ሲባል በአገር ውስጥ ስራ እና ሰራተኛን ለማገናኘት ወይም ለስራ ወይም ለስራ ልምምድ ወደ ውጪ አገር ለስራ መላክ በሚል ሽፋን ዛቻን ሀይልን ወይም ሌላ ማናቸውም ዘዴ በመጠቀም፤ በማገት፤ በመጥለፍ ወይም በተንኮል በማለታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት ሰዎችን የመለመለ ያጓጓዘ፤ ያዘዋወረ፤ ያስጠለለ፤ ወይም የተቀበለ እንደሆነ እና ይህም ድርጊት በሕጻናት በሴቶች ወይም በአእምሮ ወይም በአካል ጉዳተኞች ላይ የተፈጸመ እንደሆነ ከ 25 ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት ወይም እድሜልክ ጽኑ እስራት እና ከብር 200000-500000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተከሰሰን ሰው ጥፋተኛ ለማለት ተከሳሹ በድንጋጌው በተገለጸው አግባብ ድርጊቱን የፈጸመ ስለመሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥበት ይገባል።

የብዝበዛ ዓላማ ማለት ደግሞ በሌሎች ሰዎች ዝሙት አዳሪነት መጠቀም ወይም ማናቸውም ዓይነት ወሲባዊ ብዝበዛን፤ የጉልበት ብዝበዛን የግዳጅ ስራን ወይም አገልጋይነት፤ ባርነት ወይም ባርነት መሰል ተግባር፤ የወሲብ አገልጋይነትን ጨምሮ ሰውን የማይገባ አገልጋይ ማድረግ፤ በመያዣነት መያዝ ወይም አሳልፎ ለሌላ መስጠት፤ የሰው ልጅን አካል ማውጣት ወይም መወሰድ፤ አስገድዶ በልመና ተግባር ማሰማራት ወይም ሕጻናትን ለወታደራዊ አገልግሎት ማሰማራት እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 2/4 ላይ ከተሰጠው ትርጉም መገንዘብ ይቻላል።

በያዝነው ጉዳይ ክሱን ለማስረዳት የቀረቡት የዓቃቤሕግ ምስክሮች ካሉበት ከተማ ወደ ጊንቢ ከተማ የአመልካች ባለቤት ወደ ሆነችው አለውያ ቤት የገቡ መሆኑን እና ስትጠፉ ትፈለጉበታላችሁ ተስተካከሉ ብለው ፎቶ ያነሳቸው መሆኑን፤ ሐገሪቱ ጥሩ ናት ሰርታችሁ ትለወጣላችሁ ከ2 እስከ 3 ዓመት ስትሰሩ ደግሞ ወደ ውጪ አገር ትሄዳላችሁ ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ከመመስከራቸው በቀር አመልካች በተከሰሰበት የአዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 3/2/ሀ ድንጋጌ አግባብ አመልካች ለብዝበዛ ዓላማ ሲል ዛቻን ሀይልን ወይም ሌላ ማናቸውም ዘዴ በመጠቀም፤ በማገት፤ በመጥለፍ ወይም በተንኮል በማታለል ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት በሕገወጥ መንገድ ያዘዋወራቸው መሆኑን በመግለጽ የሰጡት የምስክርነት ቃል የለም። አመልካች በሕጉ በተገለጸው አግባብ የግል ተበዳዮችን በሕገወጥ መንገድ

ስለማዘዋወሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ የተከሰሰበትን የሕግ ድንጋጌ ጥሷል በማለት ጥፋተኛ ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ አመልካች ከቀረበበት ክስ በነጻ ሊሰናበት ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች አመልካች በሕጉ አግባብ ድርጊቱን ስለመፈጸሙ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 35700 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም አመልካችን በሚመለከት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ፤ ይህን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 214895 በቀን 11/08/2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284629 ጥቅምት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ከተከሰሰበት ክስ በነጻ እንዲሰናበት ወስነናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 35700 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም አመልካችን በሚመለከት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ፤ ይህን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 214895 በቀን 11/08/2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 284629 ጥቅምት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በነጻ እንዲሰናበት የተወሰነ መሆኑን አውቆ አመልካችን ከእስር እንዲለቅ ታዟል፡፡ ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስለገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ.167805

ጥቅምት 26/2012 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ኃይሉ ነጋሽ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡ 1. አቶ ታደሰ ኪዳነ ማርያም

2. አቶ ዳንኤል ኃይለ ቀርበዋል፡፡

3. አቶ ኪሮስ ፀጋይ

4. አቶ ብርሃነ ፀጋይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የአራማ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/100969 ላይ ጥቅምት 02/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በሽረ እንዳስላሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪዎች ላይ የ1996 ዓ.ም የወንጀለ ህግ 712(1(ሀ)) ጠቅሶ ባቀረበው የአራማ ወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ የአሁን ተጠሪዎች "ወልደ ገብርኤል አልጋሁን እና ጓደኞቻቸው ዕጣን ለቀማ ሕብረት ሽርክና ማህበር" ለተባለው ተበዳይ በሽረ እንዳስላሴ ከተማ ውስጥ በተለያዩ ቀናት የተለያየ መጠን ያለውን ገንዘብ በአራማ በማበደር የአራማ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ክሱን እንዲከላከሉ አድርጎ የመከላከያ ማስረጃቸውን ከሰማ በኋላ ተጠሪዎች የተከሰሱበትን የአራማ ወንጀል ያልፈፀሙ ለመሆኑ የዐቃቤ ህግ ማስረጃን በሚያስተባብል መልኩ አስረድተዋል በሚል ከተከሰሱበት ወንጀል በወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁጥር 149(2) መሰረት በነፃ አሰናብቷል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታው በወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁር 195(1) መሰረት ሰርዟል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የመዝገብ ቁጥር እና ቀን በዋለው ችሎት የአራጣ ወንጀል የሚፈፀመው የተበዳይን ችግር፣ የበታችነት፣ ወይም የገንዘብ ችግር፣ ወይም መንፈሰ ደካማነት ወይም ልማድ ወይም ችሎታ ማጣትን መሰረት ተደርጎ መሆኑን፣ እነዚህ ተግባራት ሊኖሩ የሚችሉት በተፈጥሮ ሰው ላይ መሆኑን፣ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የአራጣ ወንጀል ተፈጽሟል የተባለው በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው ማህበር ላይ በመሆኑ በወንጀል ህጉ ስለ አራጣ ወንጀል ከአንቀፅ 712-715 ድረስ የተደነገጉት ለተፈጥሮ ሰው እንጂ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል ተፈፃሚነት የለውም፣ በፍሬ ነገር ደረጃም በግራ ቀኙ መካከል የአራጣ ብድር ግኑኝነት ያልነበረ ለመሆኑ በመከላከያ ማስረጃ በመረጋገጡ ተጠሪዎች ከክሱ በነፃ መሰናበታቸው ተገቢ ነው በማለት በውጤት ደረጃ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በአብላጫ ድምፅ አፅንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 15/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ችሎት ትርጉም ላይ ያለውን ቅሬታ በመጥቀስ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ፍሬ ቃሉም በወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ስር “ማንኛውም ሰው” ተብሎ የተጠቀሰው የተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል የሚያጠቃልል ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ችሎት የድንጋጌው ተፈፃሚነት ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ነው ብሎ መተርጎሙ አግባብ ባለመሆኑ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጣቸው ድርጅቶችም ተፈፃሚነት አለው በሚል ተተርጉሞ ተጠሪዎች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ሊቀጡ ይገባል የሚል ነው፡፡

የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ ከወንጀል ህግ አንቀፅ 23(2) እና 712(1(ሀ)) ጋር ተገናዝቦ ተመርምሮ በዚህ ችሎት ትርጉም እንዲሰጥበት በዚህ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመታዘዙ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ ለብቻው፣ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ በጋራ ሰኔ 03/2011 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ዘርዘር ያለ ሲሆን አጠቃላይ ፍሬነገሩ በሁለት ነጥብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የመጀመሪያው የአራጣ ወንጀልን የሚያቋቁሙት ድንጋጌዎች ስር የተቀመጡት መመዘኛዎች የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ በመሆናቸው እና የአራጣ ብድር ተሰጥቷል የተባለው ለማህበር በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት በአተረጓጎም ረገድ የፈፀመው ስህተት የለም የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው በስር ፍርድ ቤቶች በነፃ የተለቀቁት ከተበዳይ ጋር ተራ የብድር ውል ግኑኝነት እንጂ የአራጣ ብድር ያልነበረ ለመሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ በመሆኑ ውሳኔው የሚነቀፍ አይደለም የሚል ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 14/2011 ዓ.ም በሰጠው የመልስ መልስ ቀደም ሲል ያቀረበውን የቅሬታ ነጥብ የሚያጠናክርበትን ምክንያት በማከል በቀረበው ቅሬታ መሰረት እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡

በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ ተጠሪዎች በተከሰሱበት የወንጀል ህጉ አንቀፅ 712 ስር "ማንም ሰው" ተብሎ የተጠቀሰው የወንጀል ፈፃሚውን ማንነት የሚመለከት እንጂ የተባዳዩን ማንነት የሚገልፅ አይደለም፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ያለበት የወንጀል ህጉ ስድስተኛ መፅሃፍ፣ ምዕራፍ ሶስት፣ ክፍል ሶስት "የጎሊናን ወይም የሰውን ችግር መሰረት በማድረግ የሚፈፀሙ ወንጀሎች" በሚል አርዕስት ስር በመሆኑ ዞሮ ዞሮ የአራጣ ወንጀል የሚፈፀምበት ተበዳይ ሰው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በህግ አስተምህሮ ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው እና በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ማህበር/ድርጅት/ ስለመሆኑ በችሎቱ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት በልዩ ዓላማ የመብት እና ግዴታ ባለቤት እንዲሆን የተደረገ ቢሆንም የሚንቀሳቀሰውም ሆነ ስራውን የሚከውነው በተፈጥሮ ሰው አማካኝነት ነው፡፡ ድርጅቱን ለማንቀሳቀስ በህግም ይሁን በውል ስልጣን የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው በተሰጠው የስልጣን ክልል ውስጥ ለድርጅቱ ጥቅም እና መብት እስከሰራ ድረስ በተሰራው ስራ ተጠቃሚውም ሆነ ተጎጂው ድርጅቱ ይሆናል፡፡

ይህ በመሆኑም ነው ከድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሰራተኞች አንዱ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት ያለአግባብ በመጠቀም በተለያየ የወንጀል ተሳትፎ ደረጃ ወንጀል አድርገው በተገኙ ጊዜ በእንደራሴዎቹ የተሳትፎ ደረጃ ልክ ድርጅቱ እራሱ ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣ ስለመሆኑ በወንጀል ህግ አንቀፅ 23(3) እና 34 ስር የተደነገገው፡፡ እናም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት የመብት እና ግዴታ ባለቤት በመሆኑ በህግ በግልፅ በተደነገገ ጊዜ በወንጀል ተከስሶ ሊቀጣ እንዲሁም እንደማንኛውም የተፈጥሮ ሰው የወንጀል ድርጊት ተጎጂ ሊሆን ይችላል ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ትርጉም የአራጣ ወንጀልን የሚያቋቁሙት ፍሬ ነገሮች በባህሪያቸው የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ በመሆኑ ድንጋጌው በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ድርጅት ተፈፃሚነት የለውም የሚል ነው፡፡ በእርግጥ የአራጣ ወንጀል የሚፈፀመው የተበዳዩን ችግርተኝነት፣ የበታችነት፣ ወይም የገንዘብ ችግሩን ወይም መንፈሰ ደካማነቱን ወይም ልምድ ወይም ችልታ የሌለው መሆኑን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ አንቀፅ ስር የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተብለው የተጠቀሱት በአማራጭ መስፈርትነት የተቀመጡ ሲሆን አንዳንዶቹ በትክክልም የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከቱ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ እንደ አግባብነታቸው በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካልም የሚሰሩ ናቸው፡፡ ለአብነት ያክል

“መንፈሰ ደካማነት” እና “የበታችነት” የሚለው የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከት ሲሆን “ችግርተኝነት ወይም የገንዘብ ችግር” የተባለው ደግሞ ለተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው አካል ሊፈፀም የሚችል ነው፡፡

እናም የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮቹ በአማራጭነት የተቀመጡ በመሆናቸው እንደ ነገሩ ሁኔታ እና አግባብነት መመዘኛው ለተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ለተሰጠው ድርጅት/ማህበር/ ተግባራዊ ከሚደረግ በቀር ድንጋጌው ተፈፃሚነቱ ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ነው የሚባል አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በተጠሪዎች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ በቀረበበት አግባብ ተረጋግጧል አልተረጋገጠም የሚለው ቀጥሎ የሚታይ ሆኖ በድርጊቱ ተበዳይ ተብሎ የተጠቀሰው የንግድ ማህበር እንደራሴዎች በክሱ ውስጥ የተጠቀሰውን ገንዘብ ከተጠሪዎች ሲበደሩ የነበረው ድርጅቱ አጋጥሞት በነበረው ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ምክንያት መሆኑን ከክርክሩ አጠቃላይ አመጣጥ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የአንድ ድርጅት እንደራሴዎች ድርጅቱ ባጋጠመው የገንዘብ ችግር ምክንያት በአራጣ ገንዘብ ከተበደሩ እና ይህ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጥ ከተቻለ የንግድ ድርጅቱ በአራጣ ወንጀል ድርጊት ተበዳይነት የማይጠቀስበት ምክንያት የለም፡፡

በመሆኑም የትግራይ ሰበር ችሎት የወንጀል ህጉን አንቀፅ 712 የተረጎመበት መንገድ የድንጋጌውን አጠቃላይ ይዘት እና መንፈስ ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል የወንጀሉን ድርጊት በተመለከተ ማስረጃና ፍሬ ነገርን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ያላቸው በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ማስረጃዎች መርምረውና መዝነው በተጠሪዎች እና በተበዳይ ድርጅት መካከል የነበረው ግንኙነት የተራ ብድር እንጂ የአራጣ ብድር አለመሆኑን ያረጋገጡ ለመሆኑ ከቀረበው የመዝገብ ግልባጭ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ሊባሉ ይገባል ከማለት ባለፈ የስር ፍርድ ቤቶች የአራጣ ወንጀል አልተፈፀመም ለማለት በተጓዙበት መንገድ እና በደረሱበት ድምዳሜ ውስጥ የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ምን እንደሆነ ለይቶ ያላመለከተ በመሆኑ ተጠሪዎችን ነፃ በመልቀቅ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት አልተቻለም፡፡

ሲጠቃለል ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/100969 ላይ ጥቅምት 02/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በወንጀል ህግ አንቀፅ 712(1(ሀ)) ስር

የተመለከተው የአራጣ ወንጀል ተፈፃሚነት የተፈጥሮ ሰው በሆነ ተበዳይ ላይ ብቻ ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ ተሽሮ የተቀረው በወንጀል ህግ ሥነ ሥረዓት ቁጥር 195(2) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በወንጀል ህግ አንቀፅ 712 ስር የተመለከተው የአራጣ ወንጀል በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት/ማህበር/ ላይ ሊፈፀም ይችላል፡፡

ትዕዛዝ

1. ውሳኔው መሻሻሉን እንዲያውቅ የዚህ ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዮ/መ

የሰ/መ/ቁጥር---161791

ቀን- የካቲት 25 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች:- ታምሬ አበራ ረጋሳ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የወንጀል ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን ጨምሮ በ10 ተከሳሾች ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች 8ኛ ተከሳሽ የነበረ ሲሆን አመልካችን የሚመለከተው 3ኛ ክስ ሆኖ ይዘቱ፡- የስር 1ኛ፣ 4ኛ፣ 7ኛ፣ 8ኛ(ተጠሪ)፣ 9ኛ እና 10ኛ ተከሳሾች የወ/ሕ/አንቀጽ 32(1/ሀ) እና 669(3/ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለሐምሌ 18 ቀን 2006 ዓ.ም አጥቢያ ሌሊት ባልታወቀ ሰዓት በቦሌ ክ/ከተማ ገርጂ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ከሚገኘው መ·ለጌ ኃ/የተ/የግል ማህበር ውስጥ ተጠሪና 10ኛ ተከሳሽ ያላቸውን የስራ ኃላፊነት ተጠቅመው 1ኛ እና 9ኛ ተከሳሾች የግል ተበዳይ በሆነው ድርጅት ውስጥ ተመድበው የጥበቃ ሥራቸውን እንዲሰሩ በማድረግ ሁኔታዎችን ካመቻቹ በኃላ እኚሁ ተከሳሾች አይሱዙ ይዘው በመምጣት ከድርጅቱ መጋዝን ውስጥ የተለያዩ ብዛትና ዓይነት ያላቸው የሕጻናት ወተቶች እና የሕጻናት ንጽህና መጠበቂያ ዳይፐር አጠቃላይ ግምታቸው ብር 1,092,950 የሚሆን በመኪና ጭነው ከወሰዱ እና ጥበቃዎቹም ለትብብራቸው እያንዳንዳቸው ብር 30,000 ከተቀበሉ እንዲሁም 7ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች የተጫነውን ዕቃ በሌላ ሰው መጋዝን አራግፈው ከሄዱ በኃላ የተያዙ ስለሆነ በግብርአበርነት በፈጸሙት የከባድ ስርቆት ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካችም ሆነ የስር ተከሳሾቹ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ወንጀሉን አለመፈጸማቸውን ገልጸው ክደው ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪ ምስክሮችና ማስረጃዎች ከተሰሙ በኃላ አመልካችና የስር ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠ ሲሆን የስር ፍ/ቤት የአመልካችንና የሌሎች ተከሳሾችን ማስረጃዎች ከሰማ በኃላ መርምሮ በተከሰሱበት አንቀጽ ስር ጥፋተኛ በማድረግ አመልካች በ11 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሠኘት ያቀረበውን ይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ መነሻ ቅጣቱን ከእርከን

29 ወደ እርከን 26 ዝቅ በማድረግ በአንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያትና አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በመያዝ እርከን 26 ስር በ8 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ አመልካች ታስሮ በነበረበት ወቅት በፖሊስ የሰጠዉን የተከሳሽነት ቃል ሲሆን ሕገ-መንግስቱንና ሕግን ባልተከተለ መንገድ በግዳጅ የተገኘ ማስረጃ በመሆኑ የጥፋተኝነት ዉሳኔዉ ሊሻር ይገባል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ በአመልካች ላይ ሰዉ በመግደል ወንጀል የተጣለዉ ቅጣት የ5 ዓመት ጊዜ ያለፈዉና የቅጣት ዉሳኔዉ የተሰረዘ በመሆኑ የአመልካች የቀድሞ ሕይወቱ መልካም እንደነበረ ስለሚገመት የተፈጸመዉም የወንጀል ድርጊት በሀሳብ ደረጃ የተለያዩ ስለሆነ እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ ተደርጎ እንዲያዝልኝ፡፡ ለሌሎች የስር ተከሳሾች በወንጀሉ በዋና አድራጊነት ተሳታፊ የነበሩ ቢሆንም ከወንጀሉ ያገኙት ጥቅም አነስተኛ መሆንና በትምህርት ያልገፉ መሆናቸዉ ታይቶ አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ተይዞላቸዉ ቅጣት የተቀነሰላቸዉ ስለሆነ ይኸዉ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ለአመልካች የማይያዝበት ምክንያት ባለመኖሩ ማቅለያ ምክንያቱ ተይዞልኝ ቅጣት ይቅለልልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ቀደም ሲል በ2001 ዓ.ም ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣዉ በግድያ ወንጀል ሲሆን በዚህ መዝገብ ደግሞ ከባድ ስርቆት ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ወንጀል መፈጸም ልማድ በማድረጉ በማለት ማክበጃ የያዘበት አግባብ ከወ/ሕ/አንቀጽ 84 አንጻር እንዲሁም ቅጣቱን ጨርሶ ከተፈታ 5 ዓመት ያለፈዉ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ተገንዝቦ እያለ ሪኮርድ አለበት በማለት በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) ማቅለያ ሳይዝ ያለፈበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የሰጠዉ መልስ ይዘት፡- አመልካች በሰዉ መግደል ወንጀል ጥፋተኛ የተባለዉ እና የተቀጣዉ በ16/03/2001 ዓ.ም ሲሆን የተፈታበት ጊዜ በተመለከተ ሁለት ሦስተኛ ቅጣቱን ፈጽሞ በአመክሮ ተፈታ እንኳ ቢባል የሚፈታዉ በ2004 ዓ.ም በመሆኑ ከተፈታ በኃላ 5 ዓመት ስንቆጥር እስሩ የሚጠናቀቀዉ በ2008 ዓ.ም ነዉ፡፡ አመልካች የወ/ሕ/አንቀጽ 669(3/ለ) የተመለከተዉን ተላልፎ ወንጀል ፈጽሟል የተባለዉ ሀምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም በአመክሮ ተፈትቶ በአንድ ዓመቱ በመሆኑ ፍርዱ ተሠርዞልኛል የሚለዉ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት በወ/ሕ/አንቀጽ 67 መሠረት ደጋጋሚ ነዉ በሚል ቅጣቱን በመሰለዉ ማክበድ ሲችል ማለፉ አመልካችን የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳዉ ባለመሆኑ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ዉሳኔዉ ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በሰጠዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ክርክር ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካቾችን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ ይግባኝ ሰሚዉ የፌዴራል

ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ለፈጸመዉ የከባድ ስርቆት ወንጀል መነሻ ቅጣቱን በስር ፍ/ቤት ተይዞ ከነበረዉ መነሻ እርከን ከሆነዉ እርከን 28 ዝቅ በማድረግ እርከን 26 ላይ መነሻ እርከን ከያዘ በኃላ አመልካች አስቀድሞ በሰዉ ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ 5 ዓመት መቀጣቱን በመጥቀስ በወ/መ/ሕ/ቁ 84(1/ሐ) መሰረት ወንጀል መፈጸምን ሙያዉ አድርጎ ይዞታል በማለት አንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የያዘበት ከመሆኑም በላይ በወ/ሕ/አንቀጽ 232 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ስለመሰየሙ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) መሠረት የዘዉትር ባህሪው መልካም ነዉ ለማለት ባለመቻሉ በቅጣት ማቅለያነት ሊይዝለት አለመቻሉን በመግለጽ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑን ብቻ በወ/ሕ/አንቀጽ 86 መሰረት አንድ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በመያዝ እርከን 26 ስር በ8(ስምንት) ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል። አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉም ሆነ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች አስቀድሞ ጥፋተኛ የተባለበትና የተቀጣበት የግድያ ወንጀል በወ/ሕ/አንቀጽ 84(1/ሐ) መሰረት በማክበጃነት መያዙ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? በአግባቡ አይደለም የሚባል ቢሆን በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) መሰረት ተጨማሪ አንድ የቅጣት ማቅለያ ያለመያዙ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸዉ።

በመሠረቱ የወ/ሕ/አንቀጽ 84(1/ሐ) ወንጀለኛዉ በቀድሞ ጥፋተኛነቱ፣ ወንጀልን ማድረግ ሙያ ወይም ልማድ አድርጎ መያዙ፣ ወይም የወንጀሉ አፈጻጸም ዘዴ፣ ጊዜ፣ ቦታና አፈጻጸሙ አኳኋን፣ በተለይም በሌሊት ወይም በሽብር ወይም በሁከት ለአደጋ ሽፋን ወይም በጦር መሳሪያ ወይም በሌላ አደገኛ መሣሪያ ወንጀሉን በማድረግ የተለየ አደገኝነቱን አሳይቶ እንደሆነ ይላል። ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ በድንጋጌዉ መሠረት በቅጣት ማክበጃነት ሊያዙ ከሚችሉት ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ ወንጀለኛዉ አስቀድሞ ጥፋተኛ የተባለበት ሪኮርድ መኖሩ አደገኝነቱን የሚያሳይ ሲሆን ማክበጃ ምክንያት ሊያዝበት የሚችል መሆኑን ነዉ። በሌላ በኩል አስቀድሞ የነበረዉ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ከፍርድ መዝገብ እንዲሰረዝና ወደፊትም እንዳልተፈረደበት ለመቆጠር በወ/ሕ/አንቀጽ 232 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት መሰየም የሚኖርበት ሲሆን ቅጣቱ ጽኑ እስራት ሲሆን በአመክሮ ከተፈታበት ጊዜ አንስቶ የ5 ዓመት ጊዜ ያለፈዉ እንደሆነና የመሰየም ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ነዉ። መሠየም የሚገኘዉ በመልካም ሥራ ነዉ እንጂ በይገባኛል አለመሆኑም በተጠቀሠዉ አንቀጽ ሥር ተመልክቷል።

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በግድያ ወንጀል ጥፋተኛ የተባለዉ ሕዳር 03 ቀን 2001 ዓ.ም ሲሆን በአመክሮ የተፈታዉ መጋቢት 23 ቀን 2001 ዓ.ም ነዉ። አመልካች በከባድ ስርቆት ተሳትፎ የተገኘዉ ደግሞ ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በመጀመሪያዉ ወንጀል በአመክሮ ከተፈታ 5 ዓመት እንዳለፈዉ ነዉ። ሆኖም አመልካቹ ለመሰየም የሚያበቃዉ የ5 ዓመት ጊዜ ያለፈዉ ቢሆንም ለፍ/ቤቱ የመሰየም ጥያቄ ካለማቅረቡም በላይ በወ/ሕ/አንቀጽ 233 መሰረት ሌሎች ለመሰየም የሚያበቁ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉ አልተረጋገጠም። መሰየምም የሚገኘዉ በመልካም ሥራ ነዉ እንጂ ጊዜዉ በማለፉ ብቻ አይደለም። ስለሆነም አመልካች አስቀድሞ ጥፋተኛ በተባለበት ወንጀል ባልተሰየመበትና ቅጣቱም ከፍርድ መዝገብ ተሰርዞ እንዳልተሰጠ ባልተቆጠረበት ሁኔታ በሪኮርድነት ተይዞ በቅጣት ማክበጃነት

በወ/ሕ/አንቀጽ 84(1/ሐ) መሠረት መያዙ ተገቢ አይደለም ሲል ያቀረበው መከራከሪያ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ክርክሩን አልተቀበልንም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች አስቀድሞ በፈጸመው ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በአመክሮ ከተፈታ 5 ዓመት ያለፈው ቢሆንም ባለመሰየሙ ምክንያት የጥፋተኝነቱ ሪኮርዱ ያልተሰረዘና በማክበጃነት የተያዘበት በመሆኑ በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) መሰረት የአመልካች የቀድሞ ባህሪው መልካም ነው ሊባል የማይችል ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) መሰረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የሚያገበት አግባብ የለም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የተወሰነውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማጽናት በወ/ሕ/አንቀጽ 84(1/ሐ) መሰረት አንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት መያዙም ሆነ በወ/ሕ/አንቀጽ 82(1/ሀ) መሰረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አለመያዙ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት ባለመኖሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 002643 ግንቦት 01 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ለ/2/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ተመላሽ ይደረግ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ/ - 137908

ቀን - 21/05/2010

ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ

ተክሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀሐይ አሰፋ ከጠበቃ ደመነ ቱንኤ ጋር ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ሰበብ ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅት በተገኘዉ ገንዘብ ያፈሩት ሀብት እና ንብረት እንዲመልሱ እንዲሁም በሕፃናት ላይ ለደረሰዉ የሞራል ካሳ ገንዘብ እንዲከፍሉ የቀረበዉን ክስ መሠረት በማድረግ የተሰጠዉን ፍርድ በመቃወም የቀረበ የሰበር አቤቱታን የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ የተጀመረዉ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ክስ ይዘትም በአጭሩ፤ ተጠሪ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ፊቃድ ሳይኖራቸዉ ያላቸዉ በማስመሰል ፀሐይ አሰፋ የሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከል በሚል ስያሜ ከ1983 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ ቁጥራቸዉ 282 የሚሆኑ ወላጅ አልባ ሕፃናትን ለሌላ ድርጅት አሳልፈዉ የሰጡ መሆናቸዉን፣ በዚህ ምክንያት ከአርባ ምንጭ ከተማ 1000 ካ/ሜትር ቦታ ወስደዉ 800,000.00 ብር የሚገመት ቤት መገንባታቸዉን፣ ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ገንዘብ በማግኘት የተለያዩ ንብረቶችን በህገ ወጥ መንገድ ማፍራታቸዉን፣ በዚህም ምክንያት በወንጀል ተከስሰዉ ጥፋተኛ ተብለዉ የተቀጡ በመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 100(1) መሠረት በህገ ወጥ መንገድ ያፈሩትን ንብረት ለመንግስት ገቢ ማድረግ ያለባቸዉ በመሆኑ የተለያዩ ንብረቶች ዋጋ ብር 1,916,300.00፣ በ282

ሕፃናት ላይ ለደረሰ የሞራል ጉዳት ካሳ ብር 282,000.00 እንዲከፍሉ እና በአርባ ምንጭ ከተማ በ1000 ካ/ሜትር ላይ ያረፈዉን ቤት እና ቦታዉን ለመንግስት እንዲያስረክቡ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነዉ፡፡

ተጠሪ ለቀረበባቸዉ ክስ በሰጡት መልስ፤ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ናቸዉ የሚሏቸዉን ነጥቦች ካነሱ በኋላ፣ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ/ንብረት ለመንግስት ገቢ ማድረግ የሚቻለዉ በወንጀሉ ማቋቋሚያ ድንጋጌ ላይ በግልጽ የተመለከተ ሲሆን በመሆኑ እና ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 433 ድንጋጌ ንብረት የሚወረስ ስለመሆኑ የማይደነግግ መሆኑን፣ ተጠሪ ካላቸዉ የሰብአዊነት እና የእናትነት ፍቅር በመነሳሳት ወላጆቻቸዉን በሞት ያጡ እና በችግር ላይ ያሉትን ሕፃናት በሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ተጣርቶ በሚቀርብላቸዉ መሠረት ተቀብለዉ ወደ ሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ከማስተላለፍ በስተቀር በስማቸዉ የሚታወቅ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት የሌላቸዉ መሆኑን፣ ተጠሪ እ.ኤ.አ ጥር 10/2007 እስከ እ.ኤ.አ ነሐሴ 05/2011 ዓ.ም ድረስ ከኤስ ኦ ኤስ አንፋንትስ ኢትዮጵያ ጋር የስራ ዉል በመፈጸም የድርጅቱ የአርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ኃላፊና ተጠሪ በመሆን ሲሰሩ መቆየታቸዉን፣ ድርጅቱ የተጠሪን የመኖሪያ ቤት ተከራይቶ ሲሰራ መቆየቱን እና አመልካች በክሱ የጠቀሳቸዉ 282 ሕፃናትም ድርጅቱ በስሙ የተረከባቸዉ እንጂ በግል ያልተረከቡ መሆኑን፣ ችግረኛ ሕፃናትን ተቀብለዉ በግል ገንዘባቸዉ በራሳቸዉ መኖሪያ ቤት የሚያሳድጉ መሆኑን ተገንዝቦ የአርባ ምንጭ ከተማ ማዘጋጃ ቤት 1000 ካ/ሜ ቦታ የሰጣቸዉ ሲሆን በቦታዉ ላይ የተሰራ ቤት በግላቸዉ የሰሩት መኖሪያ ቤት እንጂ የሕፃናት ማሳደጊያ ቤት አለመሆኑን፣ በ25 ሕፃናት ስም በየወሩ ሲላክ የነበረዉ 120.00 ብር በኢ/ንግድ ባንክ አ/ምንጭ ቅርንጫፍ ሂሳብ ቁጥር 1033 ገቢ ሲደረግ የነበረዉም በድርጅቱ ባለሙያ ህጋዊነቱ ተጣርቶ ሂሳቡ የተዘጋ መሆኑን፣ ተጠሪ ለስራ ሲጠቀሙበት የነበረዉ እና አመልካች በክሱ የጠቀሰዉ መኪናም የልጃቸዉ መሆኑን፣ አመልካች በክሱ የዘረዘራቸዉ ሌሎች የተለያዩ ቁሳቁሶችም የተጠሪ የግል ንብረቶች መሆናቸዉን፣ ለ282 ሕፃናት የተጠየቀ የሞራል ካሳም የህግ መሠረት የሌለዉ መሆኑን በመጥቀስ የቀረበባቸዉ ክስ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ግራ ቀኝ ያቀረቡትን ክርክር እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን እንዲሁም የሰዉ ምስክሮችን አቅርቦ ከሰማ እና ከመረመረ በኋላ፤ በአርባ ምንጭ ከተማ 1000 ካ/ሜትር ቦታ ለተጠሪ ሊሰጥ የቻለዉ ለወላጅ አልባ ሕፃናት ማሳደጊያነት መሆኑ ስለተረጋገጠ ተጠሪ ይህን ቦታ ሊመልሱ እንደሚገባ፣ በቦታዉ ላይ የተገነባ ቤት በህገ ወጥ መንገድ በተገኘ ገንዘብ ስለመሆኑ አመልካች በማስረጃዎቹ ያላስረዳ መሆኑን እና ተጠሪ ቤቱን የሠራዉ ያለማንም ተቃዉሞ መሆኑ ስለተረጋገጠ የግንባታዉ ወጪ ተገምቶ ሲቀርብ አመልካች እንዲከፍል በማለት የወሰነ ሲሆን፤ ሌሎች የተለያዩ ንብረቶችን ተጠሪ በህገ ወጥ መንገድ ያፈሩ መሆኑን አመልካች ያላስረዳ መሆኑን በመግለጽ በዚህ ረገድ የቀረበዉን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ

ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበዉ አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህኑን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች በቀን 10/06/09 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ፤ ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ስም በአርባ ምንጭ ከተማ በተሰጣቸዉ ቦታ ላይ የሰሩት በሕፃናት ስም ከተለያዩ ድርጅቶች በተገኘ ገንዘብ መሆኑ እየታወቀ ቤቱን በተመለከተ መንግስት ካሳ ከፍሎ መሬቱን እንዲወስድ መወሰኑ፣ መኪናዉን እና ለሕፃናት ማሳደጊያ የሚሆኑ የተለያዩ ቁሳቁሶች ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት በተቋቋመ ኮሚቴ ታሽጎ እያለ ተጠሪ ገንጥለዉ መዉሰዳቸዉ ተረጋግጦ እያለ አመልካች እንደ ክሱ አላስረዳም በሚል ምክንያት ዉድቅ መደረጉ እንዲሁም ተጠሪ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆናቸዉ እና በወንጀል ፍሬ የተገኘ ሀብት ደግሞ ሊወረስ እንደሚገባ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ዉሳኔ ሰጥቶ እያለ ተጠሪ ኃላፊነት የለባቸዉም ሲል በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተወስኖ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቶ የተወሰነ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሶ ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አቤቱታዉ ተመርምሮም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ከወንጀል ዉሳኔዉ ጋር ተገናዝበዉ የታዩ መሆን አለመሆናቸዉን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ቀርበዉ እንዲከራከሩ ጥሪ የተደረገላቸዉ ሲሆን፣ በዚህም መሠረት በቀን 24/09/2010 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በጠበቃቸዉ አማካይነት በጽሑፍ በቀረበ መልስ፤ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ፀንቶ እንዲወሰንላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ይህ ችሎትም ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘታቸዉ ብቻ ከ1000 ካ/ሜትሩ የከተማ መሬት ዉጪ ያሉትን እና አመልካች በክሱ ያመለከታቸዉ ንብረቶችን ወይም የንብረቶቹን ዋጋ ለመንግስት ገቢ እንዲያደርጉ ለመጠየቅ የሚያስችለዉ መብት አለዉ ወይስ የለዉም? መብት አለዉ የሚባል ከሆነ በክሱ የተዘረዘሩትን ንብረቶች ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም በህገ ወጥ መንገድ ያፈሩ መሆን አለመሆኑ ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር በስር ፍርድ ቤት በአግባቡ ተጣርቷል ወይ? የሚሉ ጭብጦች የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡

በመግቢያዉ እንደተመለከተዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ላቀረበዉ ክስ መሠረት ያደረገዉ 1ኛ ተጠሪ ፊቃድ ሳይኖራቸዉ ፊቃድ ያላቸዉ በማስመሰል የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት በስማቸዉ በማድረግ

ሕፃናትን በመውሰድ ለሌላ ድርጅት ሲሰጡ የነበረ በመሆኑ በወንጀል ተከሰዉ ጥፋተኛ መባላቸዉን፣ ይህን ህገ ወጥ ድርጊት በመፈጸም ከተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ባገኙት ገንዘብ የተለያዩ ንብረቶችን በማፍራታቸዉ እና የከተማ ቦታ በመዉሰዳቸዉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 100(1) መሠረት ንብረቱ ለመንግስት ገቢ መደረግ የሚገባዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ። ይህንን መሠረት በማድረግም ተጠሪ ለመንግስት ገቢ ሊያደርጉ ይገባል የሚላቸዉን ንብረቶች ዝርዝር በማቅረብ ግምቱን እንዲከፍል፤ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም የተሰጣቸዉን 1000 ካ/ሜትር ይዞታም እንዲመልሱ የጠየቀ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል።

በመሠረቱ በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ በወንጀል ህጉ ከተመለከቱት የቅጣት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አንዱ ስለመሆኑ ንብረት ስለሚወረስበት ሁኔታን የሚመለከቱ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ከሚገኙበት የህጉ ሁለተኛ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች አጠቃላይ አወቃቀር እና ይዘት መረዳት ይቻላል። በወንጀል ጉዳይ ንብረት ወይም ሀብት ሊወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ የሚቻልባቸዉ ሁኔታዎች፤ ቅጣቱ ንብረት መዉረስን እንደሚያካትት በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል በግልጽ የተደነገገ ሲሆን፣ የጥፋተኝነት ዉሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ስራ ወንጀለኛዉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘዉ ንብረት ሲኖር፣ አንድ ሰዉ ለወንጀል ስራ እንዲነሳሳ ወይም ወንጀሉን ለመስራት እንዲረዳዉ ወይም ወንጀሉን ለፈጸመበት ዋጋ እንዲሆነዉ የተሰጠዉ ወይም ሊሰጠዉ የታቀደዉ ንብረት ሲኖር፣ ወንጀልን ለመፈጸም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም ለወንጀል ተግባር ያገለገሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ አደገኛ የሆኑ ነገሮች ሲሆኑ ስለመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 98፣ 100(1) እና 140 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል። ንብረት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ማድረግ በወንጀለኛዉ ላይ ሊጣሉ ከሚችሉ ቅጣቶች አንዱ በመሆኑም፣ ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔን ተከትሎ ንብረት ወይም ሀብት እንዲወረስ ወይም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን መወሰን የሚችሉት እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አቃቤ ህግ ሊወረሱ የሚገባቸዉን ንብረቶች ዝርዝር በወንጀል ክሱ ካመለከተ፣ ንብረቶቹም ከፍ ሲል በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ የተገኙ ስለመሆኑ በወንጀል ፍርድ ሂደት ከተረጋገጠ እና በወንጀል መዝገቡ ላይ አቃቤ ህግ ንብረቶቹ እንዲወረሱ ካመለከተ ስለመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች እንዲሁም በወንጀል ሥ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 211 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት እና መንፈስ መረዳት ይቻላል።

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ አመልካች በተጠሪ ላይ ላቀረበዉ ክስ መሠረት ያደረገዉ 1ኛ ተጠሪ ፊቃድ ሳይኖራቸዉ ፊቃድ ያላቸዉ በማስመሰል የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት በስማቸዉ በማድረግ ሕፃናትን በመዉሰድ ለሌላ ድርጅት ሲሰጡ የነበረ በመሆኑ በወንጀል ተከሰዉ ጥፋተኛ መሆናቸዉን ነዉ። በርግጥ ተጠሪ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 433 ስር ጥፋተኛ ተብለዉ የተወሰነባቸዉ ስለመሆኑ ግራ ቀኝ አልተካካዱም። ይሁንና በወንጀል

ህጉ አንቀጽ 433 መሠረት ጥፋተኛ በሆነ ሰዉ ላይ የሚጣል ቅጣት ንብረት መዉረስን ወይም ለመንግስት ገቢ ማድረግን እንደሚያካትት በድንጋጌዉ አልተመለከተም፡፡ ተጠሪ ፍቃድ ሳይኖራቸዉ ሕጻናትን በማሳደግ ስራ ላይ በመሰማራት በፈጸሙት የወንጀል ተግባር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኙት ንብረት ካለ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 98(2) መሠረት ሊወረስ የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም፣ ይህ የሚሆነዉ፣ ከላይ በተገለጸዉ ምክንያት፣ አቃቤ ህግ የወንጀል ክሱን ሲያቀርብ ተጠሪ ጥፋተኛ በተባሉበት ድርጊት ምክንያት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ያፈሩት ንብረት ስለመኖሩ ገልፆ በዚህ መልኩ ተጠሪ ያፈሩት ንብረትም በወንጀል መዝገቡ ላይ ተረጋግጦ ንብረቱ እንዲወረስም በወንጀል መዝገቡ ላይ አቃቤ ህጉ በሚያቀርበዉ የቅጣት አስተያየት መሰረት ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሲሰጥ ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጪ፣ በወንጀል መዝገብ ላይ ቀርቦ ክርክር ተደርጎበት ተረጋግጦ በቅጣት መልክ ንብረት እንዲወረስ የወንጀል መዝገቡን በያዘዉ ፍርድ ቤት ባልታዘዘበት ሁኔታ፣ ቀደም ሲል በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠዉን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ መሠረት በማድረግ በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶችን ተጠሪ ለመንግስት ገቢ እንዲያደርጉ በፍትሐብሔር መዝገብ ዳኝነት የጠየቀበት አግባብ የወንጀል ድርጊትን መነሻ በማድረግ ንብረት ሊወረስ የሚችልበትን ዓላማ መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ በፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ምክንያት በመንግስት ላይ ያደረሱት ፍትሐብሔራዊ ጉዳት ካለ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2035 እና 2162 መሠረት ኃላፊነት የሚኖርባቸዉ በመሆኑ አመልካች የደረሰዉን ጉዳት ጠቅሶ በተጠሪ ላይ ክስ እንዳያቀርብ የሚከለክለዉ የለም፡፡ ይሁንና ይህ ሂደት የሚመራዉ በመደበኛዉ የፍትሐብሔር የሙግት ስርዓት በመሆኑ፣ ክርክሩ በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ የተመለከቱትን ደንቦች እና መርሆዎች የተከተለ ሊሆን ይገባል፡፡ በህጉ ከተመለከቱት ደንቦች ዉስጥም ከሳሽ ለክሱ መነሻ በሆነዉ ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሀብት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆኑን የማሳየት ግዴታ አንዱ እና ዋነኛዉ ነዉ፡፡ የዚህ መርህ ጠቀሜታ ጉዳት ከደረሰበት ሰዉ በቀር አንድ ሌላ ሰዉ ስለ እርሱ ሆኖ ወይም እርሱን ተክቶ ክስ እንዳይመሰርት ለማድረግ በመሆኑ ክሱ የሚቀርብለት ፍርድ ቤትም ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆን አለመሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት (የፍ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 33/2/ እና 231/1-ሀ/ ድንጋጌዎች ይመለከቷል)፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ በክሱ ከጠቀሳቸዉ ንብረቶች ዉስጥ አንዱ በአርባ ምንጭ ከተማ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም ለተጠሪ ያላግባብ የተሰጠ 1000 ካ/ሜትር ቦታ ሲሆን፣ ተጠሪ በፈጸሙት ህገ ወጥ ድርጊት መሬቱ በእጃቸዉ የገባ መሆኑን አረጋግጦ አመልካች መንግስትን ወክሎ መሬቱ እንዲመለስ ለማስወሰን ክስ ለማቅረብ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣን ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 106/99 መሠረት ስልጣን ያለዉ ከመሆኑም በላይ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ተጠሪ ያቀረቡት አቤቱታ ባለመኖሩ ይህን በተመለከተ የተሰጠዉን ዉሳኔ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይሁንና ከመሬቱ ውጪ ያሉትን ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተ አመልካች ለክሱ መሠረት ያደረገዉ ተጠሪ በሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ስም ከተለያዩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ባገኙት ገንዘብ ተጠሪ በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶች ማፍራታቸዉን ነዉ፡፡ አመልካች ይህን ክስ ሲያቀርብ ተጠሪ ከሌሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች ባገኙት ገንዘብ ንብረቶቹን ማፍራታቸዉ የአመልካችን መብት እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል ያልገለጸ ከመሆኑም በላይ፣ ተጠሪ ሕፃናትን የማሳደግ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸዉ ፈቃድ ያላቸዉ በማስመሰል የፈጸሙት ድርጊት እዉነት መስሎአቸዉ እርዳታዉን ሲያደርጉ የነበሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ስም በክሱ አላመለከተም፡፡ አመልካች እነዚህን በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ጭምር ወክሎ መከራከር የሚችል ስለመሆኑም አልገለጸም፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ወደ ዋናዉ ክርክር ከመግባቱ በፊት አመልካች በክሱ ካመለከታቸዉ ንብረቶች ጋር በተያያዘ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ነበረበት፡፡

የፍሬ ነገር ክርክሩን በተመለከተ አመልካች በክሱ ባመለከተዉ እና ለመንግስት እንዲመለስ በተወሰነዉ 1000 ካ/ሜ ቦታ ላይ ለሕፃናት ማሳደጊያ የሚሆኑ የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ቤት መሰራቱን፣ ለዚሁ ዓላማ የሚዉሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች መኖራቸዉ፣ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-20744 የሆነ መኪና በተጠሪ ስም ተገዝቶ በእጃቸዉ የሚገኝ እና ለስራዉ የሚጠቀሙበት ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከተረጋገጠ ተጠሪ እነዚህን ንብረቶች ሊያፈሩ የሚችሉበት ሌላ የተለየ ገቢ ያላቸዉ መሆን አለመሆኑ በተጨማሪ ማስረጃ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባዉ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ከወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ ንብረት የሚወረሰዉ ወይም ለመንግስት ገቢ የሚደረገዉ በወንጀል ህጉ እና በወንጀል ስ/ስ/ህጉ መሠረት በቅጣት መልክ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ ንብረቱ የሚወረስ መሆን አለመሆኑ ዉሳኔ ማግኘት ያለበት በወንጀል መዝገብ እንጂ በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ብቻ መነሻ በማድረግ በአዲስ መልክ በሚቀርብ የፍትሐብሔር ክርክር ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ በፈጸሙት የወንጀል ድርጊት ምክንያት ያፈሯቸዉ ንብረቶች የአመልካችን ጥቅም ወይም መብት የሚነካ ከሆነ ክሱ የሚቀርበዉ እና ሙግቱም የሚመራዉ መደበኛዉን የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት በተከተለ መንገድ በመሆኑ፣ አመልካች መብት ወይም ጥቅም ያለዉ መሆኑን በክሱ በግልጽ ሳያሳይ እና ፍርድ ቤቱም ይህን በቅድሚያ ማረጋገጥ ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ ከከተማ ቦታ ዉጪ ያሉትን ንብረቶች በተመለከተ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር ገብቶ አከራክሮ ያዉም በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶች ለማፍራት የሚያስችላቸዉ ተጠሪ የተለየ ገቢ ያላቸዉ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ ሳይረጋገጥ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11871 በቀን 21/04/08 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/11000 ላይ እንዲሁም የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/26888 የሰጧቸዉን ዉሳኔዎች በማጽናት፣ የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአርባ ምንጭ ከተማ የተሰጣቸዉን 1000 ካ/ሜትር ቦታ ተጠሪ እንዲመል በሚል የተሰጠዉን የዉሳኔ ክፍል በማጽናት፤ ቀሪዉን የዉሳኔ ክፍል በመሻር ወስነናል፡፡
3. የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚል የገለፃቸዉ ድርጅቶች እነ ማን ናቸዉ? አመልካች ከ1000 ካ/ሜትር ቦታ ዉጪ ቀሪዎቹን ንብረቶችን በተመለከተ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለዉ ከህግ የመነጨ መብት አለዉ ወይስ የለዉም? አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብት ያለዉ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር የሚገባ ከሆነ በ1000 ካ/ሜትር ቦታ ላይ የተገነቡትን ቤቶች ጨምሮ ሌሎች በክሱ የተመለከቱትን ንብረቶች ለማፍራት የሚያስችላቸዉ ተጠሪ የተለየ የገቢ ምንጭ አላቸዉ ወይስ የላቸዉም? በሚሉት ጭብጦች ላይ የግራ ቀኝ ክርክር እና ተጨማሪ ማስረጃዎችን በመስማት እንዲሁም የፍ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደዉ መሠረት ጭብጦቹን በአግባቡ አጣርቶ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉን ተገቢዉን ሁሉ በማድረግ ጉዳዩን አጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ም/ቶ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 168166

ግንቦት 28 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካቾች፡- አቶ ይገዙ ቡርዜ

ተጠሪ፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ፍትህ ቢሮ ዓቃቤ ህግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወንጀልን ይመለከታል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ የተጀመረው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የአርባ ምንጭ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ በቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- አመልካች የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(1) የተመለከተውን በመተላለፍ መስከረም 17 ቀን 2009 ዓ.ም ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በውሃ ምንጭ ቀበሌ እባያ ግሮሰሪ ውስጥ የግል ተበዳይ ፀጋ ወይሾ የተባለውን በቦክስና በቴስታ ግራ በኩል አገጩን በመምታት የግራ መንጋጋ አጥንት እንዲሰበር በማድረጉ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ ቀርቦበታል፡፡

አመልካች የእምነት ክህደት ቃሉ ሲጠየቅ ድርጊቱ አለመፈፀሙ ክዶ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የዐቃቤ ሕግ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካች የተከሰሰበት የህግ ዓንቀፅ በመቀየር የወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(1) እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡ ተከሳሾች መከላከያ ማስረጃ አቅርበው ያሰሙ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ከመረመረ በኋላ የቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ በመመዘን ተከሳሽ የቀረበበት ክስ ተከላክሏል በማለት በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ቅሬታው ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡ በመቀጠል ተጠሪ የተሰጠውን

ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር አመልካች በዓ/ህግ የቀረበበት ወንጀል የፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ምስክሮችም አልተከላከለም በማለት ክስ በቀረበበት የህግ ዓንቀፅ ወንጀል ህግ ዓንቀፅ 555(ሐ) ስር የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቷል ፡፡ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማስላት አመልካችን በሁለት አመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተፈፀመ ያለውን ስህተት በመዘርዘር ያቀረበ ሲሆን የቅሬታው መሰረታዊ ነጥቦች ሲጠቃለሉ፡- የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ወንጀል መፈፀሜ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲሁም የግራ ቀኙ ማስረጃ የመዘነበት አግባብ እና የስር ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ለመሻር የሰጠው ምክንያት መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ያልተከተለ በመሆኑ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑ ገልፀው ሊታረም እንደሚገባ መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪ ቀርቦ በፅሁፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለው ሲሆን ይህ ችሎትም አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ፣ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ያስቀርባል በማለት የተያዘው ጭብጥ ብቻ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው መዝገቡ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል በተያዘው ጭብጥ በአሁኑ አመልካች ተፈፀመ የተባለው ድርጊት አፈፃፀም እና ከተጠቀሙት መሳሪያ አንፃር ጥፋተኛ መባል ያለበት በወንጀል ህግ አንቀጽ 555(ሐ) ነው ?ወይስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 556 (1) መሰረት ነው ? በሚል አግባብ ሲታይ አመልካች በቦክስ እና በቴስታ በመምታት በግል ተበዳዩ አካል ላይ ጉዳት ስለማድረሱ በሥር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር በማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን ዋናው ምላሽ የሚያስፈለገው ጉዳይ ግን በማስረጃዎች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንጻር አግባብነት ያለውን የወንጀል ህግ አንቀጽ የመለየቱ ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ላይ በስር ፍርድ ቤት የተሰሙት የዓ/ህግ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሲታይ አመልካች በክሱ በተገለጸው ቦታና ጊዜ በተከሳሽ ግሮሰሪ እየተዝናኑ እያለ ሽንት ቤት ደርሶ ሲመለስ ባጃጅ ውስጥ ታሞ የተኛውን ጓደኛቸውን ተከሳሽ ውጣ ሲል ባጃጁ የኛ ነው ብሎ የግል ተበዳይ ሲናገረው ተከሳሹ አንድ ጊዜ በግራ ጉንጩ ላይ በቦክስ እና በቴስታ የመታው መሆኑ መስክረዋል፡፡ በአንፃሩ የተከሳሽ መከላከያ ምስክሮች የላሜራ ብረት መትቶት ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ገልፀው የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል፣ ጉዳቱን የሚያመለክት የሃኪም ማስረጃም ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር የተያያዘ መሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አመልካች በክሱ በተገለጸው የቦታ፣የጊዜ እና የወንጀል አፈጻጸም ዝርዝር መሰረት የግል ተበዳይ የሆነውን ፀጋ ወይሶ በቦክስ እና በቴስታ የመታው

መሆኑ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ መረጋገጡን፣በአመልካቹ በኩል ቀርበው የተሰሙት የመከላከያ ምስክሮችም በዐቃቤ ሕግ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ የተመሰከረውን የወንጀል ፍሬ ነገር ለማስተባበል ያልቻሉ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

አሁን ከዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጉዳይ በአመልካች መፈጸሙ የተረጋገጠው የወንጀል ተግባር የሚሸፈነው በወንጀል ህግ አንቀፅ 555 ስር ነው? ወይስ በወንጀል ህግ አንቀፅ 556(1) ስር ነው? የሚለው ነጥብ ነው:: በተያዘው ጉዳይ ድርጊቱ የተፈፀመው እና አመልካች ጉዳት ለማድረስ የተጠቀመበት መሳሪያ በተመለከተ በእርግጥም የከባድ የአካል ጉዳት ወንጀል ነው? ወይስ የቀላል የአካል ጉዳት የሚያቋቁም ነው? የሚለውን መለየት እንዲቻል ለድርጊቱ አፈፃፀምና አመልካች የተጠቀሙበት መሳሪያ ድርጊቱ የተፈፀመበት የተበዳይ የሰውነት ክፍል እንዲሁም የወንጀሉ አፈፃፀም ሁኔታ መታየት ያለበት ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ህጉ አንቀፅ 23(2) በግልፅ ተደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ህጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ህጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሀሳብ ክፍል ጋር በህጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ መሆናቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ሌላው ወንጀል ክርክር አንድ ሰው ክሱን እንዲከላከል ወይም ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው ዐቃቤ ህግ በህጉ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታውን የተወጣ መሆኑን ሲረጋገጥ መሆኑም የሚታወቅ ነው፡፡ የወ/መ/ህ/ስ/ስ/ህ/ቁ 141 ድንጋጌ አቀራረፅና ይዘት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 111 እና 112 ድንጋጌዎች ተጣምሮ ሲታይም በወንጀል ጉዳይ ዐቃቤ ህግ እንደክሱ በበቂ ሁኔታ የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህን በህጉ የተመለከተውን የማስረጃ መለኪያ መስፈርት መሰረት በማድረግ የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙን የፈፀመውን ሰው ማንነት እና በአፈፃፀሙ ላይ የነበረውን የተሳትፎ ደረጃ ማረጋገጥ የግድ ይላል፡፡ ዐቃቤ ህግ የተከሳሽን የአእምሮ ክፍል ሊያስረዳ የሚችለው የድርጊቱን አፈፃፀም በማረጋጥ ሲሆን ከድርጊቱ አፈፃፀም ድርጊት ፈፃሚው ወንጀሉን ሲፈፅም የነበረውን የአእምሮ ሁኔታ ፍርድ ሰጪው አካል ሊረዳ የሚችል መሆኑም የሚታመን ነው፡፡

ይህንኑ የህጉን ይዘትና መንፈስ ይዘን ወደዚህ ጉዳይ ስንመለስም ከመዝገቡ ይዘት ለመረዳት እንደተቻለው ተፈፀመ የተባለው ድርጊት አመልካች ስለመፈፀሙ የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን አመልካች ወንጀሉን ለመፈፀም የተጠቀመበት መሳሪያ የሌለና በቦክስና በቴስታ የመታ በመሆኑ ከቀረቡት የዓ/ህግ ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ታስቦ የሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ሐ) መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ በማንኛውም ሌላ መንገድ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን በሌላ ሰው ላይ ያደረሰ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡ አንድ ሰው ይህንን ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብና የድርጊት አፈጻጸም መሰረት ወንጀል ፈጽሞ ቢገኝ እና ይህም ሁኔታ በማስረጃ ሲረጋገጥ ተከሣሽ በዚህ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ሊባል የሚችል መሆኑን የሕጉ ይዘት ያሳያል ፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች የግል ተበዳይ ለሆነውን ፀጋ ወይሶ ላይ አስቦ በተበዳይ አካል ላይ ጉዳት ያደረሰ ቢሆን ጉዳት ያደረሰው በቦክስ እና በቴስታ መሆኑ እና ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን በተበዳይ ላይ ያደረሰ መሆኑ ያልተረጋገጠ በመሆኑ፣ይህ ተግባር ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 555 ከተመለከተው ውጪ ስለሆነ አመልካች የፈፀመው ተግባር ወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(1) የተመለከተውን የህግ ድንጋጌ በመጣስ መሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

ስለሆነም የአመልካች የወንጀል ድርጊት በስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ የማይሸፈን በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካችን በወንጀል ህግ ዓንቀፅ 555(ሐ) ጥፋተኛ በማለት ቅጣት መወሰኑ አግባብ ስላልሆነ፣ በተረጋገጠው የአመልካች የወንጀል አድራጎት የወንጀል ህግ አንቀጽ 556(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

በአመልካች ላይ ተጥሎ የነበረው የጥፋተኝነት ውሳኔ የተለወጠ ስለሆነ የቅጣት ውሳኔውም ሊስተካከል ይገባል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የወንጀል ደረጃና እርከን የወጣለት በመሆኑ በመመሪያው ዓንቀፅ 26 መሰረት የቅጣት አሰላል ስነ ስርአት ቅደም ተከተል ሲታይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የወንጀሉ ደረጃ ሊወሰን ስለሚገባው አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የህግ ድንጋጌ የወንጀል ህግ አንቀጽ 556(1) አንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ የሚያስቀጣ በመሆኑ በቀላል እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡

ስለሆነም አመልካች በሰው አካል ወይም ጤና ላይ አስቦ ቀላል ጉዳት ያደረሰ ስለሆነ የወንጀሉን ደረጃ 1 እርከን 2 የሚያርፍ ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት የቀረበና ተቀባይነት ያገኘ የቅጣት ማክበጃም ማቅለያም ስላልነበረ የቅጣት እርከኑ አልጨመረም አልቀነሰም ስለሆነም የወንጀሉን አፈጻጸም እና የደረሰውን ጉዳት ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ጉዳይ የታሰረበት ካለ የሚታሰብለት ሆኖ አመልካች ለፈፀመው ወንጀል በሶስት ወር ቀላል እስራት ሊቀጣ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የስር ፍ/ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመት በመሆኑ በማሻሻል ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

ውሳኔ

1 . በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 27905 ታህሳስ 05 ቀን 2011 ዓ.ም. የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195/ለ/2/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2 .አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 556(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ነው በማለት በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ካለ ታሳቢ ሆኖ በሶስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ተወሰኗል፡፡

3 .በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀም አመልካች ለሚገኙበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሠበር መዝገብ ቁጥር 171403

ሕዳር 22 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች/ቾች፡- መላኩ ያዕቆብ፡- አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ/ዎች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ፡- ዐ/ህግ ኤፍሬም ደመቀ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በጠበቃው አማካኝነት የካቲት 14 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎባቀረበው የሰበርአቤቱታየስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን የቅጣት ገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2 ድንጋጌን በመተላለፍ በቀን 08/2010 ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በንፋስስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 01 ልዩ ቦታው ሲፈን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሰ.ቁ ኮድ 2-7769 አ.አ የሆነ ሞተር ሳይክል እያሽከረከረ ከቀኝ ወደ ግራ በማቋረጥ ላይ የነበሩትን ሟች ሸዋ ቀና ጥላሁን ቅድሚያ ሰጥቶ ማለፍ ሲገባው ሟችን ቅድሚያ በመከልከል በሞተር ሳይክሉ የፊት ለፊት አካል የግራ ጎናቸውን በመግጨት በሞተሩ አካል ሟችን ወደፊት ጎትተቶ በመውሰድ አስፓልት ላይ እንዲወድቁ በማድረግ ሟች ስለታማ በሆነ ግዑዝ ቁስ አካል በራሳቸው፤ በደረታቸው እና በሆዳቸው ላይ በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት በቀን 09/08/2010 ዓ.ም ሕይወታቸው አንዲያልፍ ያደረገ በመሆኑ በፈጸመው በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች ክሱ ተነቦለት ክሱን ሳይቃወም ወንጀሉን የፈጸመ እና ጥፋተኛ መሆኑን እና ቅድሚያ በመከልከል ሚችን የገጫቸው መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክሕደት ቃሉን ሰጥቷል። ዓቃቤሕግ ባመነው መሠረት ጥፋተኛ ይባልልን በማለት በገለጸው መሠረትም ፍ/ቤቱ አመልካች ድርጊቱን የፈጸመ ስለመሆኑ ሙሉ በሙሉ አምኗል በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2/ ጥፋተኛ ብሎታል። ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማስላት በዓቃቤሕግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም በማለት፤ አመልካች የዘወትር ባሕርይው መልካም መሆኑ፤ ክሱን ያመነ መሆኑ ፤ ከሚች ቤተሰቦች ጋር በመታረቅ ካሳ የከፈለ መሆኑን የሚያሳይ የእርቅ ስምምነት የቀረበ በመሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ፤ በማሕበረሰቡ በጎ ተግባራት እና ልማት ተሳታፊ መሆኑ፤ አደጋው ከደረሰ በኋላ ሚችን ወደ ሕክምና ቦታ መውሰዱን እና ለመርማሪ ፖሊስ እጁን መስጠቱ በድምሩ ስድስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ በአንድ ዓመት ከሁለት ወር ቀላል እስራት እና በብር 500 መቀጮ እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን የገደብ ጥያቄውን በሚመለከት ግን ከአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ተቀባይነት የለውም በማለት ወድቅ አደርጎታል። አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ፖሊስ ጣቢያም ሆነ ፍርድ ቤት በመቅረብ ቃሌን በማመን ሰጥቻለሁ፤ መጸጸቴንም አሳይቻለሁ፤ የሚችን ሕይወት ለማትረፍ ኮንትራት ታክሲ ይገፍ ወደ ሕክምና ቦታ ወስጃለሁ፤ አደጋው ከደረሰ በኋላም ሞተር ሳይክሉን በመሸጥ የሚችን ቤተሰብ ክሻለሁ፤ አመልካች ባለትዳር ስሆን ቅጣቱ በተላለፈበት ወቅትም ባለቤቴ የ 9 ወር እርጉዝ ነበረች፤ የሶስት ልጆች አባት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪም ነኝ፤ የወንጀል ሪከርድ የለኝም፤ ከሚች ቤተሰቦች ጋርም የታረቅኩ ሲሆን በገደብ ብለቀቅ የገደቡን ሁኔታ በሚገባ እንደሚሟላ አረጋግጫለሁ። በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብ ያቀረብኩትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የተከሰሰበትን ወንጀል አምኖ የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት፤ ከሚች ቤተሰብ ጋር እርቅ ፈጽሞ በካሰበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የቅጣት ገደብ ጥያቄውን አሁን ካለው የአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ተቀባይነት የለውም በሚል ያለፈበትን አግባብነት በወንጀል ሕግ ቁጥር 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ..መ.ቁ 94404፤85596 እና 34280 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የስር ፍ/ቤት ከወንጀሉ አፈጻጸም እና እየደረሰ ካለው የትራፊክ አደጋ አንጻር የአመልካች ቅጣት መታገድ የጥፋተኛውን ጸባይ ለማረም በቂ አይደለም፤ ሌሎችንም አያስተምርም የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፤ አመልካች ከፈጸመው የወንጀል ድርጊት ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 153597 የቅጣት መገደብ እና አለመገደብ ነባራዊ ሁኔዎች ታይተው የወንጀል ሕግ ግብን ከማስፈጸም አንጻር ሊሆን እንዲሚገባ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት አሁን ካለው የአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ቅጣቱ ሊገደብ አይደገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ያስቀርባል ተብሎ የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች የቀረበበትን ክስ ሙሉ በሙሉ ያመነ እና በድርጊቱም መጸጸቱን እና ጥፋተኛ ሊባል የሚገባ መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክሕደት ቃሉን የሰጠ መሆኑን፤ ፍ/ቤቱም አመልካች ባመነው መሠረት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2 ጥፋተኛ ያለው መሆኑን፤ አመልካች አደጋው ከደረሰ በኋላ ሚችን ወደ ሕክምና ቦታ የወሰደ እና ለመርማሪ ፖሊስ እጁን የሰጠ መሆኑ፤ የዘወትር ባሕርይው መልካም መሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ፤ በማሕበረሰቡ በጎ ተግባራት እና ልማት ተሳታፊ መሆኑ፤ ከሟች ቤተሰቦች ጋር በመታረቅ ካሳ የከፈለ መሆኑን የሚያሳይ የእርቅ ስምምነት የቀረበ በመሆኑ፤ የሟች ባለቤትም በችሎት ቀርበው ከአመልካች ጋር የታረቁ መሆኑን፤ አመልካች ሁሉንም እርዳታ ያደረገላቸው እና አሁንም እያገዛቸው ያለ መሆኑን በመግለጽ ቃላቸውን የሰጡ መሆኑን በስር ፍ/ቤት ከተረጋገጠው ፍሬነገር መገንዘብ ይቻላል፡፡

የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብ ያቀረበው ምክንያት ቅጣት ስለሚገደብባቸው ሁኔታዎች በሕጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለመሆኑን መዝኖ ሳይሆን የአመልካች የቅጣት ገደብ ጥያቄ ከአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ተቀባይነት የለውም በማለት መሆኑን ከውሳኔ ይዘት መገንዘብ ችለናል፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ሕጉ ዓላማ ወንጀል እንዳይፈጸም ማድረግ ሲሆን ይህንንም የሚያደርገው ስለወንጀሎች እና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነ ጊዜ ደግሞ ወንጀል ፈጻሚዎች ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ እና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቅጣት ሲገደብ የፍርዱ ውሳኔ በወንጀለኞች መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ከሌላው ውጤት ጋር ነዋሪ የሚሆን በመሆኑ ቅጣትን መገደብ በወንጀለኛው ላይ ቅጣት እንዳይፈጸም የማድረግ ውጤት ብቻ ያለው ሳይሆን

ወንጀለኛው ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲታቀብ የማድረግ ውጤት ስላለው ቅጣትን መገደብ የወንጀል ሕጉ ዓላማ እና ግብ ከሚሳካባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡

ቅጣት ሊገደብ የሚችለውም ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ከተደነገጉት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግ ፍ/ቤቶች ቅጣትን ለመገደብ የሚያስችሉ የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው፤ እነዚህም ሁኔታዎች ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፤ጥፋቱ በመቀጮ፤ በግዴታ ስራ ወይም ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል መሆኑና በዚህ ውሳኔ ብቻእስከ መጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን ‘ያመነበት’ እንደሆነ፤ እንዲሁምጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግም የሚታገድ መሆኑናስለጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱ ከአፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን፤እነኚህም ሁኔታዎች ጥፋተኛው ከዚህ በፊት የጽኑ እሥራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እሥራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነ እና እንደገናም በተከሰሰበት ወንጀል ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት እንደሆነ ወይም ጥፋተኛው ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ሆኖ በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት አመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ነው በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ድንጋጌ ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በሕጉ ከተመለከቱት ከእነኚህ ሁኔታዎች ውጪ የወንጀሉ ከባድነት ወይም ጥፋተኛው ያደረሰው አደጋ አሳሳቢነት ቅጣት እንዲገደብ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ነው ተብሎ በሕጉ ላይ አልተገለጸም፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 የወንጀሉ ከባድነት / the gravity of the crime /፤ በወንጀል ድርጊት መደጋገም ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እና በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚችለው እምነት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት የሚባለው ፍ/ቤቱ ቅጣቱ እንዲገደብ አቋም ከያዘ በኋላ ቅጣቱ ተገድቦ የሚቆይበትን የፈተና ጊዜ ለመወሰን / ….. to fix the probation period ….. / እንጂ ጥፋተኛው ፈጽሞታል ከተባለው ወንጀል ወይም አድርሶታል ከተባለው አደጋ ጋር እየተገናዘበ ቅጣትን ለመገደብ ሊመዘን ይገባል ተብሎ እንደመስፈርት የተቀመጠ አይደለም፡፡

በመሠረቱ ከባድ ወንጀሎች ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194/1/ለ ድንጋጌም ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ጥፋተኛው አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ቅጣትን ማገድ አይቻልም በማለት በግልጽ መደንገጉ ከመነሻውም ቢሆን ከባድ ወንጀል የፈጸመ ወንጀለኛ በሚጣልበት ከፍተኛ የቅጣት መጠን ምክንያት ቅጣት ሊገደብለት የማይችል በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 ላይ የተገለጸው 'የወንጀሉ ክብደት' የሚለው ቃል ለፈተናው ጊዜ አወሳሰን ታሳቢ የሚደረግ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ጥፋተኛው የፈጸመው ወንጀል አሳሳቢነትን የሚመለከት አለመሆኑን እና ቅጣቱን ለመገደብበመመዘኛነት የተቀመጠ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 የተመለከቱት ቅድመ-ሁኔታዎች ፈተና የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች እንደሆኑ ከድንጋጌው ርዕስ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን እነኚህ ሁኔታዎች መሟላት አለመሟላታቸው ሊረጋገጥ የሚችለው ፍ/ቤቱ ከተከሳሹ የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ በመነሳት ቅጣቱን መገደብ እንዳለበት ሲያምን እና ጥፋተኛው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ላይ የተመለከቱትን ቅድመ-ሁኔታዎች እንደሚያሟላ ማረጋገጫ እንዲሰጥ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192፤196/1 እና 197 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጥፋተኛው በድንጋጌው የተመለከቱትን ቅድመ- ሁኔታዎች ማሟላት አለማሟላቱን ማረጋገጥ የሚቻለውም ጥፋተኛው ራሱ በራሱ ተነሳሽነት በሕጉ የተመለከቱትን ቅድመሁኔታዎች ያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ጥፋተኛው በሕጉ የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች እንዲያሟላ እድል በሰጠው ጊዜ ነው፡፡

ፍ/ቤቱ በጥፋተኛው ላይ የሚጣለውን ቅጣት ለጊዜው ማገድ ለወደፊቱ ጥፋቱን ለማረም እንደሚችል ሊያምን ወይም ላያምን የሚችለው የጥፋተኛውን የቀድሞ ታሪኩ፤ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ አስመልክቶ በችሎቱ የተረጋገጡትን እውነታዎች መነሻ በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤቶች በሕግ እና በተገቢ ምክንያት የተደገፈ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው ከመሆኑ አመልካች ቅጣቱን ለማስገደብ ያቀረባቸው ምክንያቶች ፍ/ቤቱን የሚያሳምኑ ናቸው ወይም አይደለም ለማለት ሕግን መሠረት በማድረግ እና አግባብነት ያለውን ምክንያት በመስጠት ሊሆን ይገባል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የቀረበበትን ክስ ሙሉ በሙሉ ያመነ እና በድርጊቱም መጸጸቱን እና ጥፋተኛ ሊባል የሚገባ መሆኑን በመግለጽ የእምነት ክሕደት ቃሉን የሰጠ መሆኑን፤ ፍ/ቤቱም አመልካች ባመነው መሠረት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2 ጥፋተኛ ያለው መሆኑን፤ አመልካች አደጋው ከደረሰ በኋላ ሚችን ወደ ሕክምና ቦታ የወሰደ እና ለመርማሪ ፖሊስ እጁን የሰጠ መሆኑ፤ የዘወትር ባሕርይው መልካም መሆኑ፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ፤ በማሕበረሰቡ በጎ ተግባራት እና ልማት ተሳታፊ መሆኑ፤ ከሚች ቤተሰቦች ጋር በመታረቅ ካሳ የከፈለ መሆኑን የሚያሳይ የእርቅ ስምምነት የቀረበ በመሆኑ፤ የሚች ባለቤትም በችሎት ቀርበው ከአመልካች ጋር የታረቁ መሆኑን፤

አመልካች ሁሉንም እርዳታ ያደረገላቸው እና አሁንም እያገዛቸው ያለ መሆኑን በመግለጽ አረጋግጠዋል፡፡ እነኚህ ሁኔታዎች የተከሳሹን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ እና ቅጣቱ ቢገደብ የአመልካችን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ የሚያስችሉ አሳማኝ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብለት ያቀረባቸው ምክንያቶች የአመልካቹን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ አሳማኝ እና በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሆነው ሳለ ቅጣቱን መገደብ ሲገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተቀመጠውን መስፈርት መሠረት በማድረግ የአመልካች የቅጣት ገደብ ጥያቄ ከአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ሕጉ ቅጣት ስለሚገደብባቸው የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የስር ፍቤቶች በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የአንድ ዓመት ከሁለት ወር ቀላል እስራት ቅጣት በሁለት ዓመት ገደብ ይቆይ በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና 197/1 መሠረት ወስነናል፡፡

ውሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 221242 ታሕሳስ 04 ቀን 2011 ዓ.ም በአመልካች ላይ ያስተላለፉትን የቅጣት ውሳኔ በማጽናት አፈጻጸሙን በሚመለከት ግን ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት ቀሪ እስራት ሳይፈጸም ለሁለት ዓመት እንዲገደብ በማለት ወስነናል፡፡

ትዕዛዝ

አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 መሠት የብር 1500 / አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር /መተማመኛ ዋስትና እንዲያሲዝ ታዟል፡፡ይኸው ሲፈጸም የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካችን ከእሥር እንዲለቅ ታዟል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 177216

ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ገብርኤል ፓራቶሪ አንቶንዮ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ለምርመራ ለ23/4/2012 ዓ.ም የተቀጠረ ሲሆን ከቀጠሮ በፊት ቀርቦ ሊመረመር የቻለው የአመልካች ጠበቃ ህዳር 09 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ አመልካች በከፍተኛ የደም ግፊት ህመም በመሰቃየት ላይ የሚገኝ እና ባለቤቱም የካንሰር ህመም ታማሚ በመሆኗ ምክንያት ህጻናት ልጆቻቸው በችግር ውስጥ የሚገኙ መሆኑን በመግለጽ ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ በዋስ እንዲቆዩ እንዲፈቀድለት በመጠየቁ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ለምርመራ የተያዘው ቀነ ቀጠሮ ተሰብሮ ጉዳዩ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበርችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 003364 በቀን 20/02/2011 ዓ.ም በሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ፣እንዲሁም በ 10/03/2011 ዓ.ም በሰጠው የቅጣት ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር166293 ሚያዚያ 25 ቀን 2011 በቀን 5/10/2010 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች እንዲታረምላቸው ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የነገሩ አመጣጥ የወንጀል ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡የአሁን ተጠሪ ግንቦት 28 ቀን 2009 ዓ.ም ያቀረበው የክስ ይዘትም፡-የሥር ተከሳሽ/የአሁን አመልካች/ ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የሚያስችል ህጋዊ የሥራ ፈቃድ ሳይኖረው ወ/ሮ እመቤት ይልማ ገ/የሱስ የተባለችውን የግል ተበዳይ ወደውጭ ሀገር ዱባይ እንደሚልካት በመግለጽ ከምትኖርበት አዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ነዋሪ የሆነችውን ፓስፖርት፣ሁለት ጉርድ ፎቶግራፍ እና የህክምና የምርመራ ውጤት እንደሚያስፈልጋት በመግለጽ ስምንት ሺህ ብር እንደሚያስፈልግ በመነጋገር ሂደቱን

ካስጨረሰ በኃላ ህዳርወር 2008 ዓ.ም ስልክ በመደወል ቪዛሽ መጥቷል ታህሳስ 3 ቀን 2008 ዓ.ም ከንጋቱ 12፡.00 ሰዓት ወደ ዱባይ በራራ ስለምታደርግ አየር መንገድ መገኘት እንዳለባት ከገለጸላት በኃላ የግል ተበዳይም አሁን አልተዘጋጀሁም፣ለአንድ ሳምንት አራዝምልኝ በማለት በጠየቀችው መሠረት አራዝሞላት የበረራው ቀን ሳይደርስ ቀደም ብላ የግል ተበዳይ ከ2ኛ እና ከ3ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክሮችጋር በመሆን ወደተከሳሽ የባለቤቱ እህት ሜሮን ኃይሉ መኖሪያ ቤት ቀኑን በትክክል በማያስታውሱበት ታህሳስ ወር 2008 ዓ.ም በመሄድ የመላኪያውን ገንዘብ በመስጠት የአየር ቲኬትና ቪዛ ተቀብ ለው ከተመለሱ በኃላ በታህሳስ 10 ቀን 2008 ዓ.ም ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ በኩል ወደ ዱባይ ሀገር እንድት ሄድ ካደረገ በኃላ ዱባይ ሀገር አሠሪዋ የግል ተበዳይ ጭንቅላቷ ላይ በብረትድስት በመምታት የፈነከተቻት ና ያቆሰለቻት፣ሁለት እጅዋን በቢላዋ የወጋቻት ና እንዲቆስል ያደረገች በመሆኑ፣እንዲሁም የሠራችበትን የአራት ወር ደሞዝዋንም ያልከፈለቻት ና ከፍተኛ ስቃይ እና ጉዳት እንዲ ደርስባት ያደረገው በመሆኑ በፈጸመው በህገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊን ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀል ተከሷል የሚልነው፡፡

የአሁን አመልካች ፍርድ ቤት ቀርቦ የእምነት ክህደት ሲጠየቅ የወንጅል ድርጊቱን አልፈጸምኩም፣ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት አስመዝግቧል፡፡ ዐቃቤ ህግ የሰው ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተከሳሽን እንዲከላከል ብይን ሰጥቶ መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ና ማስረጃዎችን መርምሮ ተከሳሽ በበኩሉ በጣቢያ የሰጠሁትን የእምነት ቃል ተገድጄ የሰጡት በመሆኑ ፍርድቤቱ እንዲያይልኝ ያለውን በሚመለከት ቃሉን ተገዶ የሰጠው ለመሆኑ በማስረጃ አስደግፎ ያላቀረበ በመሆኑ ና በእለቱ በቦታው አልነበረም የሚለው መከራከሪያ ዐቃቤ ህግ ካቀረቡት ማስረጃዎች ጋር ሲመዘን ተከሳሽ በዐቃቤ ህግ የቀረበበትን ክስ በመከላከያ ማስረጃ ተከላክሏል የሚያስብል በቂ ምክንያት ያላገኘን በመሆኑ አልተከላከለም ብለን ፈርደናል፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ ቁጥር 598 (2) ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በህገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያንን ለሥራ ወደ ውጭ አገር መላክ ወንጀል በመፈጸሙ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ጥፋተኛ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሏል፡፡ ዐቃቤ ህግ ያቀረበ የቅጣት ማቅለያ የለም፡፡ ተከሳሽ የወንጀል ሪከርድ የሌለ መሆኑን፣የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑን፣በተለያዩ የበጎ አድራጎት ተግባራት እና ማሕበራዊ ተሳትፎ ያበረከተውን፣እንዲሁም በቤተክርስቲያን ያገለገለበትን አራት የቅጣት ማቅለያዎችን ፍርድ ቤቱ ተቀብሏል፡፡ፍርድ ቤቱ የእሥራት መነሻ እርከን 22 ይዟል፡፡ከዚህ ላይ አራት የቅጣት ማቅለያን በመቀነስ እርከን 18 ላይ እንዲያርፍ ካደረገ በኃላ ተከሳሽ በ3 ዓመት ከ7 ወር /ሶስት ዓመት ከሰባት ወር/ ጽኑ እሥራት እናብር 500. 00 /አምስት መቶብር/ ሊቀጣ ይገባል በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 149 (5) መሠረት የቅጣት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካች በጥፋተኝነትም ሆነ በቅጣት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡የይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን ተቀብሎ ግራቀኙን ካከራከራቸው በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሚያስለውጥ በቂ ና አሳማኝ የሆነ የፍሬነገርም ሆነ የህግ ስህተት የሌለ ሆኖ ስላገኘነው በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነሥርዓት ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሠረት አጽንተናል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የጥፋተኝነት እንዲሁም የቅጣት ውሳኔውን በመቃወም ነው፡፡የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርቧል፡፡ይዘቱም በአጭሩ የተጠሪ ምስክሮች ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፣አመልካች ባቀረባቸው ማስረጃ በሚገባ ተከላክሏል፡በተጠሪ በኩል ተጠቅሶ የቀረበው ክስ የወንጀል ህግ ቁጥር 598 (2) ድንጋጌን በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል የሚል ሆኖ በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ስለመድረሱ የቀረበ የህክምና ማስረጃ የለም፣ክስ በቀረበበት ፍርድ ቤትም በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት ተመርምሮ እንዲቀርብ አመልካች ቢጠይቅም ፍርድ ቤቱም ያለአግባብ ሳይቀበል ቀርቷል፡፡በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት በማስረጃ ባልተጠራበት ይህ ድንጋጌ ተጠቅሶ ክሰ መቅረቡ የፍትህ መጓደል አምጥቷል፡፡በግል ተበዳይ ላይ የአካል ጉዳት አለመድረሱ ቢረጋገጥ በአመልካች ላይ የሚጠቀሰው የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 2 መሆኑ ቀርቶ ንዑስ አንቀጽ 1 ይሆን ነበር፡፡በዚህ ምክንያት በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ይቀንስ ነበር ማለት ነው፡፡ስለሆነም የግል ተበዳይ የአካል ጉዳት ደርሶባታል የሚያስብል የማያጠራጥር ማስረጃ በዐቃቤ ህግ በኩል ስላልቀረበ በአመልካች ላይ ተፈጻሚ መሆን የሚገባው ድንጋጌ አንቀጽ 598 (1) ሆኖ፣ቅጣቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ታሳቢ ሊደርግ ይገበዋል ካለ በኃላ የሚጠይቀው ዳኝነት በማለት 1ኛ/ የሥር ችሎቶች የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ ውድቅ ተደርጎ አመልካች በነፃ ይሰናበትልን ዘንድ እና እናመለክታለን፡፡ 2ኛ/ የሰበር ሰሚ ችሎቱ የጥፋተኝነት ውሳኔውን የሚያፀናው ከሆነ ተፈጻሚ የሚሆነው አንቀጽ ግን 598 (1) ነው ካለ በኋላ፣በሥር ፍርድ ቤት ታሳቢ የተደረጉትን 4 (አራት) የቅጣት ማቅለያዎች ግምት ውስጥ አስገብቶ ውሳኔውን ይቀንስልን ዘንድ እናመልክታለን የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የሥር ፍርድ ቤት የግል ተበዳይ የደረሰባት ጉዳት ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የአሁኑ አመልካችን በወንጀል ህግ ቁጥር 598 (2) ሥር ጥፋተኛ በማለት የወሰነበት አግባብነት ከወንጀል ህግ ቁጥር 598 (1) አንጻር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በቀን 3/2/2012 ዓ.ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ ሰጥቷል፡፡የመልሱ ይዘትም በአጭሩ ዐቃቤ ህግ ባቀረባቸው ማስረጃዎች የግል ተበዳይ በአመልካች ወደ ውጭ አገር የተላከች መሆኑን፣ከተላከች በኃላም የሰብአዊ መብት ጥሰት እና የአካል ጉዳት እንደደረሰባት አስረድቷል፡፡

በአመልካች በኩል የቀረቡት የመከላከያ ማስረጃዎች ይህን ያስተባበሉ አይደሉም፡፡ አመልካች ከቀረቡት ማስረጃዎች አንጻር በወንጀል ህግ አንቀጽ 598 (2) ጥፋተኛ መባሉ አግባብ ነው፡፡ ስለሆነም ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አግባብ ነው በማለት እንዲያፀናልን የሚል ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃም ጥቅምት 12 ቀን 2012 ዓ.ም በሰጠው የመልስ መልስ በግል ተበዳይዋ ላይ ደረሰ የተባለው የአካል ጉዳት ምሆነ ሌላ የሰብአዊ መብት ጥሰት የግል ተበዳይዋ ከሰጠችው ምስክርነት ቃል በስተቀር በሌላ በምንም ዓይነት ማስረጃ አልተረጋገጠም፡፡የግል ተበዳይዋ የምትሰጠው ቃል ደግሞ ብቻውን ተወስዶ አመልካችን በ ንዑስ ቁጥር 2 ሥርተጠያቂ ሊያደርገው አይችልም፡፡ሌላው ቢቀር በግል ተበዳይዋ ላይ የአካል ጉዳት የደረሰ መሆን አለመሆኑ በህክምና ማስረጃ ሊረጋገጥ እየቻለ የሥር ፍርድ ቤት የህክምና ምርመራ ሊደረግ አይገባም በማለት የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ብቻ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም፡፡በመሆኑም የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የሰጡት ቃል ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህግ ቁጥር 598 (2) 'ን' መሰረት በማድረግ የመሠረተውን ክስ የሚደግፍ ባለመሆኑ አመልካች ልጠየቅ የሚገባው በወንጀል ህግ ቁጥር 598 (1) ሥር ነው፡፡ ስለዚህ ችሎቱ ይህንን ተገንዝቦልን አመልካችን ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በአንቀጽ 598(1) ሥር ነው እንዲባልልን እናመለክታለን በማለት ተከራክሯል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት ከላይ እንደ ተገለጸው ሲሆን ጉዳዩን የሰበር አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ የፍሬ ነገር ክርክርን መሠረት በማድረግ ከማስረጃ ጋር ተያይዞ የጥፋተኝነት ውሳኔው ተገቢ አይደለም ተብሎ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ የሰበር አጣሪው በጭብጥነት አልያዘውም፡፡ ይህ ችሎትም ይህ ተገቢ እንደሆነ ያምናል፡፡ ነገር ግን የሰበር አጣሪው የያዘውን የህግ መከራከሪያ ነጥብን በተመለከተ በሥር ፍርድ ቤት እና በዚህ ችሎት የተነሳውን ክርክር እንዲሁም ተያይዞ የቀረበውን ውሳኔ እና አግባብነት ያለውን ህግ መሠረት በማድረግ ተመልክተናል፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 598 (1) ማንም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በማናቸውም ሌላ ህገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላከ እንደሆነ፣ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ና ከሃያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል ሲል ይደነግጋል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረት ፈቃድ ሳይኖር ወይም በህገወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊ ዜጋን ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወንጀል ሆኖ ተደንግጓል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 598 (2) በዚህ ድርጊት ምክንያት የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ፣በህይወትዋ ወይም በአካልዋ ላይ ጉዳት የደረሰባት እንደሆ ነቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ና ከሃምሳ ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል በሚል ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ ወደ ውጭ አገር የተላከችው ኢትዮጵያዊት በሰብአዊ መብቷ፣በአካል ደኅንነትዋ ወይም በህይወትዋ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ታሳቢ በማድረግ ቅጣቱን ከፍ አድርጎ አስቀምጧል፡፡ የወንጀል ህግ ቁጥር 598 ንዑስ ቁጥር 1 እና 2

የሚለየው በተላከችው ኢትዮጵያዊት ላይ በደረሰው የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣በህይወት ወይም በአካል ላይ የደረሰውን ጉዳት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የአሁን አመልካች የግል ተበዳይ ወ/ሮ እመቤት ይልማ ገ/የሱስ የተባለችውን ወደ ዱባይ ከላካት በኃላ የግል ተበዳይ አሠሪዋ ጭንቅላቷ ላይ በብረትድስት በመምታት የፈነከተቻትና ያቆሰለቻት ስለመሆኑ የዐቃቤ ህግ ክስ ያስረዳል፡፡ ይህን በተመለከተ የግል ተበዳይ የመሰከረች ቢሆንም በህክምና ማስረጃ መረጋገጥ ሲገባው ያለመረጋገጡ የሚያጠራጥር እንደሆነ አመልካች አጥብቀው ይከራከራሉ፡፡ በክርክር ሂደትም በግል ተበዳይ ላይ የአካል ጉዳት መድረስ ያለመድረሱ የህክምና ምርመራ እንዲደረግ ጠይቀው በፍርድ ቤት በኩል የተከለከለ መሆኑ የፍትህ መጓደልን ያስከተለ መሆኑን አመልካች በቅሬታነት አንስተዋል፡፡በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ካለ የህክምና ምርመራ እንዲ ደርግ አመልከች መጠየቁን ተጠሪ ሳይክድ ቁስሉ ከዳነ በኃላ የህክምና ምርመራ ሊደረግ ስለማይችል የሥር ፍርድ ቤት ጥያቄውን ውደቅ ማድረጉ ተገቢ ነው በማለት ተጠሪ ተከራክሯል፡፡ በመሠረቱ ከሳሽ በክሱ የጠቀሳቸውን ፍሬ ነገሮችን አግባብነት ባለው ማስረጃ የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑ የማስረጃ ህግ መሠረታዊ መርህ ነው፡፡ ዐቃቤ ህግ በክሱ ላይ ያቀረበውን ፍሬ ነገር በአግባቡ ካላስረዳና ጥርጣሬን የሚፈጥር ከሆነ ተጠቃሚው ተከሳሽ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ አመልካች ፈቃድ ሳይኖራው የግል ተበዳይን ወደ ውጭ ሀገር መላኩ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ አመልካች ጥፋተኛ ሊደረግ የሚገባውም በወንጀል ህግ ቁጥር 598 (1) እንጂ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አይደለም፡፡በመሆኑም አመልካች በወንጀል ህግ ቁጥር 598 (2) መሠረት ጥፋተኛ መደረጉ መሠረታዊ የሆነ ህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡ ስለዚህ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 113 (2) መሠረት አመልካች የተከሰሰበትን የህግ አንቀጽ ቀይረን በወንጀል ህግ ቁጥር 598 (1) ሥር ጥፋተኛነው ብለን በወንጀል ህግ ቁጥር 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ወስነናል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ የወንጀል ህግ ቁጥር 598 በቅጣት መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ደረጃ የወጣለት ነው፡፡አመልካች ጥፋተኛ የተደረገበት የወንጀል ህግ ቁጥር 598 (1) ደረጃ 1፣እርከን 21 ሥር ያርፋል፡፡ለአመልካች በሥር ፍርድ ቤት የተያዘው አራት የቅጣት ማቅለያ ተቀንሶ እርከን 17 ላይያርፋል፡፡በዚህ እርከን ላይ ያለው ፍቅድሥልጣን 3 ዓመት ከ3 ወር - 3 ዓመት ከ11 ወር ነው፡፡ በዚህ ፍቅድ ሥልጣን መሠረት በአመልካች ላይ 3 ዓመት ከ3 ወር /ሶስት ዓመት ከሶስት ወር/ ጽኑ እስራት ቅጣት ተወስኗል፡፡

በሌላ በኩል ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ አመልካች ከማረሚያ ቤት ከላከው አቤቱታ እና የአመልካችም ባለቤት በችሎት በአካል ቀርባ ችሎቱ አይቶ ካረጋገጠው አመልካች በከፍተኛ የደም ግፊት ሕመም ታማሚ መሆኑን፤ ባለቤቱም የካንሰር ታማሚ መሆንዋ እና ጡትዋ በካንሰር ሕመም ምክንያት የተቆረጠ እና የኬሞትራፒ መደሃኒት በመውሰድ ላይ የምትገኝ መሆኑን እና ሕጻናት ልጆቻቸውም

በችግር ውስጥ የሚገኙ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም በአመልካች ላይ የተላለፈውን ቅጣት አፈጻጸም በተመለከተ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ እልባት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረታዊነት ቅጣት ሊገደብ የሚችለውም ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ከተደነገጉት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግ ፍ/ቤቶች ቅጣትን ለመገደብ የሚያስችሉ የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው፤ እነዚህም ሁኔታዎች ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፤ጥፋቱ በመቀጮ፤ በግዴታ ስራ ወይም ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

የአመልካች የዘወትር ባሕርይ መልካም መሆኑ፤ በተለያዩ የበጎ አድራጎት ተግባራት ማሕበራዊ ተሳትፎ የሚያደርግ መሆኑ እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ከመሆኑ አኳያ እነኚህ የአመልካቹ ግላዊ ሁኔታዎች በወንጀል ሕጉ ቅጣትን ለመገደብ ከተቀመጡት ቅድመሁኔታዎች ውስጥ አመልካች ከፊሉን የሚያሟላ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በከፍተኛ የደም ግፊት ሕመም በመሰቃየት ላይ የሚገኝ እና ባለቤቱም በካንሰር ህመም ምክንያት ጡትዋ ተቆርጦ የኬሞትራፒ ሕክምና በመውሰድ ላይ የምትገኝ በመሆኑ እና ሕጻናት ልጆቻቸውም በችግር ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው በወንጀል ሕጉ ቅጣት ስለሚገደብበት ሁኔታዎች አስመልክቶ በተደነገጉት ድንጋጌዎች ብቻ ሳንገደብ ጉዳዩን እንደሚከተለው አይተናል፡፡

አመልካች በተጠቀሰው ህመም ምክንያት ህክምና የሚከታተል ስለመሆኑም ከአቤቱታው ጋር ተያይዘው የቀረቡት የህክምና ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡ አመልካች በፈጸመው የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ተወስኖበት በማረሚያ ቤት የሚገኝ ሲሆን የባለቤቱ መታመም ተጨምሮ በልጆቻቸው አስተዳደግና እንክብካቤ ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን አንጻር እንዴት ይታያል? የሚለውን እንመልከት፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 36 (1) (ሐ) ሕፃናት ወላጆቻቸውን ወይም አሳዳጊዎቻቸውን የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ከተቀመጡት ፍሬ ነገሮች ውስጥ አንዱ ህፃናት የወላጆቻቸውን እንክብካቤ የማግኘት መብት ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ህፃናት በአእምሯቸውና በአካላቸው ያልበሰሉ

ለጋ በመሆናቸው የወላጆች ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ታሳቢ ያደረገ እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡ ሌላኛው መሠረታዊ ነገር ህፃናት ለአንድ አገር እድገትና ልማት የወደፊት ተስፋ እንዲሁም አገር ተረካቢዎች በመሆናቸው በመልካም አስተዳደግ ማደግ የሚገባቸው በመሆኑ ወላጆች በቅርበት ሆነው መከታተል፣ መቆጣጠርና ማሳደግ የሚገባቸው በመሆኑ ነው፡፡

ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ በተጨማሪ ኢትዮጲያ በአዋጅ ቁጥር 10/1984 ያጸደቀችው ዓለምአቀፍ የሕጻናት መብት የቃልኪዳን ሰነድ ስምምነት ወላጆች በህፃናት አስተዳደግ እና እንክብካቤ ላይ ያላቸውን ሚና በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ የዓለም አቀፉ የህፃናት መብቶች ስምምነት የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 44/25 እንደ ኤሮፓውያን አቆጣጠር 1989 የወጣው አንቀጽ 7 (1) ማንኛውም ህፃን ወላጆቹን የማወቅና ከወላጆቹ እንክብካቤ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ለህፃናት አስተዳደርና አያያዝ ሁለቱም ወላጆች የጋራ ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 18 (1/) ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌም ለህፃናት አስተዳደግና አያያዝ ወላጆች ያላቸውን ኃላፊነት ያስቀምጣል፡፡ የኮንቬንሽኑ አንቀጽ 18 (2) በዚህ ስምምነት የተመለከቱትን የህፃናት መብቶች ተፈጻሚነትን ለማረጋገጥ ህጻናትን የማሳደግ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማድረግና ለማበረታታት ተዋዋይ አገሮች ለወላጆችና ለህጋዊ አሳዳሪዎች ተገቢውን እርዳታ ያደርጋሉ ሲል ያስቀምጣል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ለህፃናት መልካም አስተዳደግ መሠረቱ ወላጆች መሆናቸውን ነው፡፡

በሌላ በኩል የሕጻናት መብት የቃልኪዳን ሰነድ ስምምነትቱ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 36/2 ድንጋጌ ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፤ በፍርድ ቤቶች፤ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕጻናት ደሕንነት በቀደምትነት መታሰብ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ከላይ እንደተገለጸው አመልካች በፈጸመው ወንጀል ምክንያት የቅጣት ውሳኔ ተላልፎበት ቅጣቱን በማረሚያ ቤት በመሆን በመፈጸም ላይ የሚገኝ ሲሆን ባለቤቱ ደግሞ በካንሰር ሕመም ምክንያት ጡትዋ ተቆርጦ የኬሞቴራፒ መድሃኒት በመውሰድ ላይ የምትገኝ በመሆኑ በሕፃናት ልጆቻቸው ላይ የሚደርስባቸውን ቁሳዊም ሆነ ኅሊናዊ ጫና መገመት አያዳግትም፡፡

የአመልካች ልጆች አንድም አባታቸው በማረሚያ ቤት የሚገኝ በመሆኑ እናታቸውም በሕመም ምክንያት በሕክምና ላይ የምትገኝ በመሆኑ ምክንያት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት እና አገሪቱ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ እና አሕጉራዊ የሕፃናት መብቶች ስምምነቶች ሕጻናቱ የተጠበቀላቸውን የወላጆቻቸውን እንክብካቤ የማግኘት መብት የሚያሳጣቸው ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካች እና በባለቤቱ ላይ በተከሰተው ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ከአብራካቸው በተወለዱ ህፃናት ላይ የሚደርስባቸውን ችግር ወይም የሕይወትና የኑሮ ጫና፣ እንዲሁም የኅሊና ጉዳት ታሳቢ በማድረግ ሕጋዊ መፍትሔ መስጠት የሚያስፈልግ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች በፈጸመው ወንጀል ምክንያት በማረሚያ ቤት በመሆኑ እና ባለቤቱም በካንሰር ሕመም ምክንያት ጡትዋ ተቆርጦ የኬሞቴራፒ መድሃኒት በመውሰድ ላይ የምትገኝ በመሆኑ በሕፃናት ልጆቻቸው ላይ የሚደርሰውን ቁሳዊም ሆነ ኅሊናዊ ጫና ለማስቀረት ሲባል እንዲሁም ሕጻናቱ የወላጆቻቸውን እንክብካቤ እና ድጋፍ አግኝተው እንዲያድጉ ለማድረግ ሲባል፤ ፍ/ቤቶችም የሕጻናት ደሕንነት በቅድሚያ የማረጋገጥ ሕገመንግስታዊ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ በአመልካች ላይ የተወሰነውን ቅጣት በመገደብ ህፃናቱ ተገቢውን የወላጅ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችል ዘንድ የተወሰነውን ቅጣት እንዳይፈጸም ለማገድ በወንጀል ህግ ቁጥር 194 መሠረት የሚከለክል ህጋዊ ምክንያት ያለመኖሩን ተመልክተናል። ፍርድ ቤት በአንድ ሰው ላይ የቅጣት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የቅጣት ውሳኔውን ለመገደብ እንደሚችልና የቅጣት ውሳኔው ሊገደብ የሚገባው ምን መሰረታዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 192 ላይ መሰረታዊ መርሁ ተቀምጧል። ስለሆነም በአመልካች ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለመገደብ የሚከለክል ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ ቅጣትን መገደብን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ አመልካች ያልፈፀመው ቀሪው የእስራት ቅጣት በሶስት ዓመት የጊዜ ገደብ ሊገደብለት ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥተናል። ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል።

ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 003364 ጥቅምት 20 ቀን 2011 ዓ.ም እና ሕዳር 10 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 166293 በቀን 25/08/11 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል።
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀልሕግቁጥር 598 (1) ነው በማለት ወስነናል። በዚሁ መሠረት በአመልካች ላይ የተላለፈው የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ በሶስት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ እና ቀሪው የእስራት ቅጣት አፈጻጸም በሶስት ዓመት የጊዜ ገደብ እንዲገደብ በማለት ወስነናል።
3. የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የገንዘብ መቀጮ ቅጣት በዚህ ውሳኔ አልተነካም።

ትዕዛዝ

1. አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 መሠት የብር 3000 / ሶስት ሺህ ብር /መተማመኛ ዋስትና እንዲያስይዝ ታዟል።ይኸው ሲፈጸም የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካችን ከእሥር እንዲለቅ ታዟል።
2. የውሳኔው ግልባጭ አመልካች ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት እና ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው።

3. አመልካች በማረሚያ ቤት የሚገኝ በመሆኑ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በፍ/ቤቱ መልእክት ክፍል በኩል ለአመልካች ይድረሰው፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ.መ.ቁ 165440

ጥር 27 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አየለ ሀፊቦ

ተጠሪዎች፡- የደቡብ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 06 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የዱና ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 09609 ግንቦት 06 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ግንቦት 07 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 18276 ጥር 05 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 11028 ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዱና ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ፤ ሌሎች አራት ግለሰቦች ደግሞ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በሌሎች ተከሳሾች ላይ በስር ፍ/ቤት ካቀረባቸው ክሶች ውስጥ አመልካችን የሚመለከተው 1ኛ እና 3ኛ ክስ ሲሆን ይዘታቸውም፡-

1ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፤60/ለ እና 462/2/ሀ በመተላለፍ ጥር 17 ቀን 2010 ዓ.ም ጌምቤራ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ደሪሎ ኒሪም የተባለ ግለሰብ በፍ/ቤት መያዣ ትዕዛዝ ለመያዝ የሄዱት የፖሊስ አባላት ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ካዋሉት በኋላ አመልካች እነዚህ ፖሊሶች ያለእኔ ዕውቅና የመጡ ስለሆነ ተጠርጣሪውን መያዝ እና መውሰድ አይችሉም በማለት ፖሊሶቹን ተባብረው በመያዝ እና በመምታት እስረኛውን አስመልጠዋል የሚል ሲሆን፡-

3ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፤ 60/ለ እና 441 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ለፈጸመው ድርጊት የክፍሉን ፖሊሶች በሀይል እና በማስገደድ ስራቸውን እንዳይሰሩ በማድረጋቸው በፈጸሙት የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የዱና ወረዳ ፍ/ቤት አመልካችን እና የስር ተከሳሾችን ጥፋተኛ ሆነው ስላገኛቸው በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት በማስላት ለ1ኛ ክስ ድርጊቱ የተፈጸመው በቡድን እና በጸጥታ አስከባሪ አካላት ላይ በመሆኑ የጽኑ እሥራት አማራጭ ተወስዷል በማለት፤ የወንጀል ደረጃውን መካከለኛ በማለት በእርከን 15 ላይ በማሳረፍ፤ ምንም እንኳን አመልካች ያነሳሳ ቢሆንም በቀጥታ የፖሊሱን አካል ያልያዘ በመሆኑ መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት ከአስር ወር በመያዝ፤ ለ3ኛ ክስ የወንጀሉን ደረጃ መካከለኛ በማለት በእርከን 6 ላይ በማሳረፍ አንድ ዓመት እስራት የተወሰደ ቢሆንም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/ለ መሠረት አንድ ጽኑ እስራት እና አንድ ቀላል እሥራት ተደራርበው በተፈጸሙ ጊዜ ቀላል እስራት ታጥፎ መደመር ያለበት በመሆኑ ቀላል እስራቱን ወደ ስድስት ወር ጽኑ እስራት በመቀየር በድምሩ ሶስት ዓመት ከአራት ወር በመያዝ በእርከን 17 ላይ በማሳረፍ፤ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ባለመቀበል እና ለአመልካች ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ ቅጣቱን አቅሎ በእርከን 15 ላይ በማሳረፍ አመልካች በሁለት ዓመት ከአስራ አንድ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ክሱን አላስተባበለም በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2 እና 441/2 ድንጋጌ ጥፋተኛ ብሎታል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ ደግሞ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2/ሀ የአመልካች ድርጊት አፈጻጸም በጠለፋ የተጠረጠረን ግለሰብ ለማስመለጥ በሕግ አስከባሪ አካላት ላይ በቡድን የተፈጸመ ወንጀል በመሆኑ በከባድ ሊቀጣ ይገባል በማለት የወንጀሉን ደረጃ መካከለኛ በማለት መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት ከስድስት ወር በመያዝ፤ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 441/2 የወንጀል ደረጃውን መካከለኛ በማለት መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት በመያዝ፤ አመልካች ጥፋተኛ ለተባለበት ሕግ የተያዙትን መነሻ ቅጣቶች በመደመር አራት ዓመት ከስድስት ወር መነሻ ቅጣት በመያዝ እና በእርከን

19 ላይ በማሳረፍ፤ አመልካች የተያዘለት ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በመያዝ ቅጣቱን አቅሎ በእርከን 17 ላይ በማሳረፍ በሶስት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ዓቃቤሕግ ባቀረባቸው ምስክሮች አመልካች ወንጀል የፈጸምኩ ስለመሆኔ አላስረዳም፤ የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች የቀረበብኝን ክስ እንድከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ባቀረብኩት መከላከያ ማስረጃ የአቃቤሕግን ክስ አስተባብዬ ሳለ ጥፋተኛ መባሌ አግባብ አይደለም፤ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ አልገለጸም፤ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረብኩት አቤቱታ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔው አግባብ አይደለም የሚል ሆኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ካጸና በኋላ ባልታወቀ ምክንያት ባልተጠየቀ ዳኝነት የቅጣት ውሳኔውን አምስት ዓመት ከሁለት ወር ብሎ በመያዝ ከፍ በማድረግ ቀንሶ እንዳሻሻለ በማድረግ የሶስት ዓመት ከሶስት ወር እሥራት እንድቀጣ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት አመልካች በሁለት ዓመት ከአስራ አንድ ወር እስራት እንዲቀጣ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በስር ፍ/ቤት ከተወሰነበት ቅጣት በላይ በሦስት ዓመት ከሦስት ወር እንዲቀጣ በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት ስላልቀረበ በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካችን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ምክንያት ከሆነው ውሳኔ፤ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ፡-

1. የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረው 3ኛ ክስ አቀራረብ በወንጀል ስነስርዓት ሕጉ ስለክስ አቀራረብ በተቀመጡት ድንጋጌዎች አግባብ የቀረበ ነው? ወይስ አይደለም?
2. በየደረጃው ያሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች በአመልካች ላይ ቀርቦ የነበረውን 3ኛ ክስን አስመልክቶ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በስር ተከሳሾች ላይ አቅርቦት የነበረው 3ኛ ክስ ይዘት ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፤ 60/ለ እና 441 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ለፈጸመው ድርጊት የክፍሉን ፖሊሶች በሀይል እና በማስገደድ ስራቸውን እንዳይሰሩ በማድረጋቸው በፈጸሙት የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 441፡- ማንም ሰው፡-

ሀ/ አንድ የመንግስት ሰራተኛ የስራ ግዴታው የሆነውን ተግባር እንዳያከናውን በዛቻ፤ በማስገደድ ወይም በሀይል ድርጊት ያሰናከለ ወይም ይህን ግዴታውን እንዲያከናውን ወይም ማድረግ የሌለበትን እንዲያደርግ ያስገደደ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የመንግስት ሰራተኛን ወይም በስራው የሚረዳውን ሰው የደበደበ ወይም የሀይል ወይም የማስገደድ ድርጊት ወይም ማናቸውንም ሌላ የማስገደድ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ፤

ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡

ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ንዑስ (ሀ) እና (ለ) ላይ የተቀመጡት የወንጀል ማቋቋሚያ መስፈርቶች ራሳቸውን ችለው የተቀመጡ መስፈርቶች መሆናቸውን ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ባቀረበው 3ኛ ክስ ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 441 በመተላለፍ የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል ከማለት በቀር ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 ላይ በተለያየ ንዑስ ቁጥር ላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ውስጥ የትኛውን የንዑስ ቁጥር ድንጋጌ እንደተላለፉ በክሱ ላይ ለይቶ አላመለከተም፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳው ፍ/ቤትም አመልካችን በ3ኛ ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 መሠረት ጥፋተኛ ከማለት በቀር አመልካች ጥፋተኛ የተባለበትን የድንጋጌውን ንዑስ ቁጥር ለይቶ አላመለከተም፤ በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም 3ኛን ክስ በሚመለከት አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441/2 ጥፋተኛ ሲለው ይህን ያደረገበትን ምክንያት አልገለጸም፡፡

በመሠረቱ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ የሚቀርበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ በምን አኳኃን መቅረብ እንዳለበት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 111 እና 112 ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤሕግ በሚያቀርበው ክስ ላይ በዝርዝር እንዲገልጽ ከሚጠበቅበት መሰረታዊ ፍሬነገሮች ውስጥ ተከሳሹ ተላልፎታል የተባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና ተከሳሹ የፈጸመዉ የወንጀል ተግባር በመሠረታዊነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ክሱ በዚህ አግባብ ተዘጋጅቶ እስካልቀረበ ጊዜ ድረስ ተከሳሽ የሆነው ወገን ክሱን በአግባቡ ሊረዳ እና ክሱን ሊከላከል አይችልም፡፡ ይህም በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ የተጠበቀላቸውን የቀረበባቸውን ክስ የመረዳት እና የመከላከል መሠረታዊ መብት የሚጸረር ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ዓቃቤሕጉ ያቀረበው የክስ አቤቱታ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት ያልቀረበ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በራሱ አነሳሽነት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ ቁጥር 118 እና 119/1 ላይ በተገለጸው አግባብ ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ዓቃቤሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ እስካልተደረገ ጊዜ ድረስ በሕጉ አግባብ ተዘጋጅቶ ያልቀረበው ክስ የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ተከሳሹ በሕግ አግባብ ተዘጋጅቶ ባልቀረበው ክስ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 3ኛውን ክስ በተመለከተ ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 441 በመተላለፍ የመንግስት ስራ በሀይል ድርጊት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል ከማለት በቀር ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 ላይ በተለያየ ንዑስ ቁጥር ላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ውስጥ የትኛውን የንዑስ ቁጥር ድንጋጌ እንደተላለፉ በክሱ ላይ ለይቶ አላመለከተም፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው 3ኛ ክስ የተለያዩ ንዑስ አንቀጾች ያሉት እና በንዑስ አንቀጾቹ ላይ የተቀመጡት የወንጀል ማቋቋሚያ መስፈርቶች ራሳቸውን ችለው የተቀመጡ መስፈርቶች በመሆናቸው አመልካች ተላልፎታል የተባለው ንዑስ አንቀጽ ተለይቶ በክስ አቤቱታው ላይ እስካልተገለጸ ጊዜ ድረስ አመልካች የቀረበበትን ክስ በአግባቡ ሊረዳ አይችልም፡፡ ዓቃቤሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ እስካልተደረገ ጊዜ ድረስ በሕጉ አግባብ ተዘጋጅቶ ያልቀረበው ክስ የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ተከሳሹ በሕግ አግባብ ተዘጋጅቶ ባልቀረበው ክስ መነሻነት ጥፋተኛ ሊባል አይገባም፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ተጠሪ ያቀረበው ክስ በሕጉ መሠረት የቀረበ አለመሆኑን ሲረዳው ክሱ እንዲሻሻል ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው አመልካች በተከሰሰበት ሕግ ከተቀመጡት ንዑስ አንቀጾች ውስጥ አመልካች የተላለፈውን የሕግ ድንጋጌ ሳይለይ በደፈናው አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441 መሠረት ጥፋተኛ ማለቱ፤ ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይሕንኑ ሳያርም እና ምንም ዓይነት ምክንያት ሳይሰጥ አመልካችን በ3ኛው ክስ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 441/2 ጥፋተኛ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ዓቃቤሕግ በአመልካች ላይ ያቀረበው 1ኛ ክስ በሕጉ አግባብ የቀረበ እና አመልካች በክሱ ላይ የተመለከተውን ድርጊት ስለመፈጸሙ ተረጋግጦበት ክሱን ያልተከላከለ በመሆኑ አመልካች 1ኛውን ክስ በሚመለከት ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካች ላይ 3ኛ ክስን በተመለከተ ያስተላለፉትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር 1ኛ ክስን በሚመለከት ብቻ ቅጣቱን እንደሚከተለው አስልተናል፡፡

በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በ1ኛ ክስ ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2/ሀ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 462/2/ሀ የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ በማለት መነሻ ቅጣት ሁለት ዓመት ከስድስት ወር የተያዘለት በመሆኑ ይህ መነሻ በእርከን 12 ላይ የሚያርፍ ነው፤ በአመልካች ላይ ተቀባይነት ያገኘ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፤ አመልካች

በስር ፍ/ቤት ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የተያዘለት በመሆኑ ቅጣቱ ሲቀል በእርከን 10 ላይ ያርፋል፤ በእርከን 10 ያለው ፍቅደ ስልጣን ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት ነው፡፡ በዚህ እርከን ስር አመልካችን ያርማል ሌሎቹንም ያስጠነቅቃል ብለን ያመንበትን አመልካች በአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የዱና ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 09609 ግንቦት 06 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ግንቦት 07 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 18276 ጥር 05 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 11028 ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል ፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ከ3ኛ ክስ በነጻ ተሰናብቷል፡፡
3. አመልካች ከ3ኛ ክስ በነጻ የተሰናበተ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ በአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡

ትዕዛዝ

- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በአመልካች ላይ በስር ፍ/ቤቶች ተላልፎ የነበረው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ አመልካች በአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነ መሆኑን አውቆ በተሻሻለው ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡
- በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ.ቁ 18276 የሆነው መዝገብ በመጣበት አካሄን ወደ መጣበት ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ 162738

መጋቢት 30 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- 1. አቶ መሐመድ ያዕቆብ ከድር አልይዘአ

2. አቶ ዘውዴ ጂዳ

3. አቶ እሸቱ አበበ

4. አቶ ኡመር መሐመድ

5. አቶ ዳምጠው ለማ

6. አቶ መሐመድ አወል ጀማል ከድር

7. አቶ ሀይሌ ተሰማ አያኔ

8. አቶ ዳምጠው ጆግና

9. ወ/ሮ ገነት ሁስማን ሼካ

10. ወ/ሮ ሀዋ አደም

11. አቶ ዘውዴ ሽመልስ ለገሰ

12. አቶ መሐመድ ቃሲም ገርቢ

13. አቶ አብዱልቃድር ከድር አሎ

14. አቶ አበራ ቶሎሳ ጋሹ

15. ወ/ሮ ቀመሪያ ገሮ ሐቤቤ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጸረ ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በጠበቆቻቸው አማካኝነት ነሐሴ 17 ቀን 2010 ዓ.ም ተጽፎ በቀረበ የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22898 አመልካቾች ያቀረብነውን መቃወሚያ በማለፍ የሰጠው ብይን፤ በዚሁ መዝገብ በቀን 10/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በቀን 11/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 278007 በቀን 21/09/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት በመጠየቃቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሙስና ወንጀልን በሚመለከት የቀረበ ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አመልካቾችን ጨምሮ በ38 ተከሳሾች ላይ ክስ ያቀረበ ሲሆን የአሁን አመልካቾች እንደ ቅደም ተከተላቸው 1ኛ፤ 2ኛ፤ 3ኛ፤ 4ኛ፤ 5ኛ፤ 6ኛ፤ 7ኛ፤ 8ኛ፤ 9ኛ፤ 12ኛ፤13ኛ፤14ኛ፤16ኛ፤19ኛ እና 21ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች እና ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ባላቀረቡ ቀሪ ተከሳሾች ላይ በስር ተከሳሾች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ክሶች 11 ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ስድስቱ ክሶች አመልካቾችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይዘታቸውም፡-

<u>1ኛ ክስ፡-</u> አመልካቾች እና የስር 10ኛ፤11ኛ፤15ኛ እና 20ኛ ተከሳሾች የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/3 ድንጋጌን በመተላለፍ የሮቤ ከተማ ማኔጅመንት፤ የሮቤ ከተማ መሬት አስተዳደር እና ማኔጅመንት ሆነው ሲሰሩ የማይገባቸውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በመንግስት እና በሕዝብ ጥቅም ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው አመልካቾች እና የስር 10ኛ፤11ኛ፤15ኛ ተከሳሾች በቀን 01/10/2007 ዓ.ም ቃለጉባኤ በመያዝ፤ የስር 10ኛ፤ 11ኛ እና 20ኛ ተከሳሾች እንዲሁም የአሁን 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች በያዙት ቃለጉባኤ መሬት የመንግስት እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሐብት እና የማይሸጥ የማይለወጥ መሆኑን እያወቁ፤ የገጠር መሬት ወደ ከተማ መሬት ሲካለል በፌዴራል አዋጅ 455/97 ፤ 721/2004፤ በኦሮሚያ የመሬት አዋጅ ቁጥር 130/99፤ ደንብ ቁጥር 155/2005 እና መመሪያ ቁጥር 9/2005 መሠረት መፈጸም እንዳለበት እያወቁ ሕግ የሚፈቅድላቸው በማስመሰል በከተማ ስር የገባውን የገጠር መሬት 45% መሬት የገበሬ ነው፤ 55% መሬት ደግሞ የመንግስት ነው ተብሎ ተከፋፍሎ የቆየ እና ይህን መሬት ገበሬው በሽያጭ ሲያስተላልፍ የቆየ መሆኑን በያዙት ቃለጉባኤ ገልጸው እያለ ሕገወጥ ግንባታ እና የድሮ ይዞታ በማስመሰል ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም ስፋቱ 247,161 እና 997 ፐሎት መሬት 76 ለሆኑ ገበሬዎች በመስጠት ለእነዚህ ገበሬዎች በሕጉ አግባብ ለእያንዳንዳቸው 500 ካ.ሜ መሬት ተስጥቷቸው ቢሆን ኖሮ ስፋቱ 894,970

እንዲሰጥ በማድረግ መንግስት ሊያገኝ የሚችለው ገቢ 199,277.70 ስላሳጡት ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው።

<u>2ኛ ክስ፡-</u> አመልካቾች እና የስር 10ኛ፤11ኛ፤15ኛ ተከሳሾች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/3 በመተላለፍ በ1ኛው ክስ ውስጥ በተወሰነው ውሳኔ መሠረት ቁጥራቸው 308 ለሆኑ ሰዎች በድምሩ ስፋቱ 120,000 የሆነ መሬት እንዲሰጥ በመወሰን፤ 1ኛ እና 11ኛ ተከሳሾች፤ 14ኛ አመልካች እና የስር 36ኛ ተከሳሽ ደግሞ መሬት በወሰዱ እና በከተማው አስተዳደር መካከል የተደረገውን ሕገወጥ ውል በማጽደቅ፤ 27ኛ፤ 28ኛ እና 29ኛ ተከሳሾች በሕገወጥ በተላለፈው በዚህ መሬት ላይ ካርታ በማዘጋጀት፤ የስር 10ኛ፤ 11ኛ፤ 23ኛ እና 36ኛ ተከሳሾች እና 13ኛ እና 14ኛ አመልካቾች ደግሞ በሕገወጥ መንገድ በተሰጠ መሬት ላይ የተዘጋጀን ካርታ በማጽደቅ፤16ኛ አመልካች እና 20ኛ፤ 24ኛ፤ 26ኛ፤ 28ኛ፤ 30ኛ፤ 31ኛ፤ 38ኛ ተከሳሾች ሕገወጥ የሆነን ቅጽ በመሙላት፤ በአጠቃለይ ተከሳሾች በጋራ በመሆን ሕዝብና መንግስት እኩል ሊጠቀሙበት የሚገባውን ይዞታ ሕግ እና መመሪያ በመተላለፍ ስፋቱ 65,755 የሆነ መሬት ለግለሰቦች እንዲሰጥ በማድረግ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ 14,624,569.75 አሳጥተዋል የሚል ነው።

<u>3ኛ ክስ፡-</u> 17ኛ እና 18ኛ ተከሳሾች የአዋጁን አንቀጽ 9/1/ለ ድንጋጌ በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በቀን 01/07/07 እና 03/09/07 በያዙት ቃለጉባኤ ሕገወጥ የመሬት አሰጣጡን ስራ ላይ የማዋል ድርጊት በመገምገም ሕገወጥ ስራው እንዲቀጥል አድርገዋል የሚል ነው።

<u>4ኛው ክስ፡-</u> 1ኛ እና 8ኛ አመልካቾች እንዲሁም 10ኛ፤17ኛ እና 18ኛ ተከሳሾች የኦሮሚያ ከተማ መሬቶችን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣውን ደንብ ቁጥር 155/2005 አንቀጽ 59/1 ድንጋጌን በመተላለፍ በ3ኛ ክስ የተገለጸውን ቃለጉባኤ በመያዝ ሕገወጥ የሆነውን 45/55 ተብሎ የሚታወቀውን አሰራር በስራ ላይ እንዲውል አድርገዋል የሚል ነው።

<u>5ኛ ክስ፡-</u> 10ኛ፤ 11ኛ፤ ፤20ኛ ተከሳሾች፤ 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/3 ድንጋጌን በመተላለፍ የሮቤ ከተማ አስተዳደር እና ማኔጅመንት ኮሚቴዎች በመሆን እና 17ኛው ተከሳሽ የገቢዎች የባለስልጣን ሀላፊ በመሆን የሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/3 በመተላለፍ 10ኛ፤11ኛ፤20ኛ ተከሳሾች እና 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች በቀን 14/09/2007 በያዙት ቃለጉባኤ ገበሬዎች ከድርሻቸው መሬት ላይ የሸጡትን ይዞታ የድሮ ይዞታ በማስመሰል ክፍያ እንዲፈጸምበት በመወሰን ለገቢዎች ባለስልጣን በመላክ፤ 17ኛው ተከሳሽ በተለያዩ ጊዜዎች ሲይዟቸው በነበሩት ቃለ ጉባኤዎች በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን እያወቀና እያየ ይህ ክፍያ እንዲፈጸም አድርጓል የሚል ነው።

6ኛ ክስ፡- 1ኛ እና 15ኛ አመልካቾች 10ኛ፤ 11ኛ እና ከ22ኛ እስከ 25ኛ ያሉ ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና የሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/1/ሐን በመተላለፍ 15ኛ አመልካች እና ከ22ኛ እስክ 25ኛ ያሉት ተከሳሾች ሕገወጥ በሆነ መንገድ የአጣሪ ኮሚቴ ሆነው በመመረጥ መመሪያው እንደሚከለክላቸው እያወቁ እንደ ሕጋዊ ኮሚቴ እራሳቸውን በመቁጠር በሮቤ ከተማ መሬት ማኔጅመንት ኤጀንሲ በሚጣራ የመኖሪያ ቤት ክምችት በቀን 11/01/07 ቁጥሩ 1076/k13/2007 በሆነ እና ለባሌ ዞን መሬት ማኔጅመንት እና ልማት ኤጀንሲ በተጻፈ ደብዳቤ 530 ሰዎች ብቻ ተጣርተው የተላከ ሆኖ ሳለ 56 ሰዎችን በመጨመር እና ሌሎች ሰዎችን በመቀነስ አጣርተው ልከዋል የሚል ነው፡፡

የአሁን 4ኛ፤5ኛ፤8ኛ፤10ኛ አመልካቾች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ ጉዳያቸው በሌሉበት የታየ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፤ 1ኛ፤ 2ኛ፤ 3ኛ፤ 6ኛ፤7ኛ ፤9ኛ ፤11ኛ ፤12ኛ፤13ኛ ፤14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች ችሎት ቀርበው ክሱ ተነቦላቸው አንዲረዱት ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ አቅርበው በብይን ውድቅ ተደርጓል፡፡ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሲጠየቁም ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት ክደው በመከራከራቸው ፍ/ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ማስረጃዎች ሰምቷል፡፡

ፍ/ቤቱ የዓቃቤሕግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል እና ዓቃቤሕግ ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ድረስ ያሉት ክሶች ተከሳሾች 45/55 የተባለን አሰራር በስራ ላይ እንዲውል መወሰናቸውን እና በስራ ላይ ከማዋላቸው ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በዚህ አሰራር መሬት ተሰጥቷቸዋል የተባሉት ሰዎች በተለያዩ ክሶች የተገለጹ ቢሆንም በተያዘው ቃለ ጉባኤ የተጣሩ ሰዎች እራሳቸው ናቸው፤ ይህም በአንድ በሕግ በተጠበቀ መብት ላይ የተፈጸመን ወንጀል ከግብ ለማድረስ ተቀላቅለው የተፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች መሆናቸውን የሚሳይ ነው፤ በሌላ በኩል ድርጊቶቹ ሲያይዋቸው የነበሩትን ችግሮች ለመቅረፍ የተደረጉ በመሆኑ ከሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ስልጣንን አላግባብ ከመጠቀም ድንጋጌ ጋር የሚያያዝ ሳይሆን የመንግስት ስራን በማያመች መንገድ ከመስራት ጋር የሚያያዙ ናቸው፤ ስለዚህ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ባሉት ክሶች በተደራራቢ ወንጀል ተከላከሉ ሊባሉ አይገባም፤ በዚሁ መሠረት ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ክሶች እንደ አንድ ክስ ታይተው አመልካቾች እና 10ኛ፤11ኛ እና 20ኛ ተከሳሾች የወንጀሉ ድርጊት በስራ ላይ እንዲውል የተወሰነውን ቃለ ጉባኤ በመያዛቸው እና በማጽደቅ እንዲሁም 10ኛ፤ 11ኛ፤20ኛ ተከሳሾች እና 13ኛ እና 14ኛ አመልካቾች በስራ ላይ በማዋል ውሎችን እና የተለያዩ ሰነዶችን በማዘጋጀት እና በማጽደቅ መሳተፋቸው የተረጋገጠባቸው በመሆኑ በአዋጁ 881/2007 አንቀጽ 13/3 ስር እንዲከላከሉ በማለት ብይን የሰጠ ሲሆን፤ 6ኛ ክስን በተመለከተ ደግሞ የቀረበው ማስረጃ 15ኛ አመልካች እና ከ22ኛ እስከ 24ኛ ያሉት ተከሳሾች የቴክኒክ ኮሚቴ በመሆን ሁለት ጊዜ የማጣራት ስራ ሰርተው ለከፍተኛው ኮሚቴ ያቀረቡ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፤ ይህ ኮሚቴ የመሬት ክምችትን ለማስመለስ በወጣው መመሪያ ቁጥር 12/2007 አንቀጽ 8/1 መሠረት መቋቋም ካለበት መስሪያ ቤቶች በሙሉ አልተቋቋመም፤ ይህም ይህን

ኮሚቴ ያቋቋመው የቤቱ ከፍተኛ ኮሚቴ የመንግስትን ስራ አመቺ ባልሆነ መንገድ መምራቱን የሚያሳይ ስለሆነ 1ኛ አመልካች እና 10ኛ እና 11ኛ ተከሳሾች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/1/ሐ ስር እንዲከላከሉ፤ ከ15ኛ አመልካች እና ከ22ኛ እስከ 24ኛ ያሉት ተከሳሾችን ደግሞ አጣርተው ለበላይ ኮሚቴ ማቅረባቸው ብቻውን እራሱን ችሎ እንደ ወንጀል ድርጊት የሚወሰድ አይደለም በማለት ዓቃቤሕግ ያቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ መካላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ እንዲሰናበቱ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚሁ መሠረት 1ኛ አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/3 መሠረት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን ክሱን ለመከላከል ያስችለናል ያሉትን የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበዋል አሰምተዋል የሰነድ ማስረጃም አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከ1ኛ እስከ 13ኛ ያሉት አመልካቾች እና 15ኛ ተከሳሽ ከ1998 እስከ 2001 ዓ.ም በስራ ላይ የነበረውን እና ፍጻሜ ሳያገኝ የቀረውን 45/55 የተባለ ሕገወጥ አሰራር በ21/09/2007 በሮቤ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በያዙት ቃለ ጉባኤ በሕገወጥ መንገድ ለሰዎች ተላልፎ የነበረን መሬት ማስረጃ እንዲሰጥበት ማስደረጋቸው በቀረበው የሰነድ ማስረጃ በግልጽ ተረጋግጧል፤ 10ኛ፤ 11ኛ፤ 20 ተከሳሾች እና 14ኛ እና 15ኛ አመልካቾች በተመሳሳይ ቀን በ21/09/2007 በሮቤ ከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ጽ/ቤት በተያያዘ ቃለ ጉባኤ ይህ በሕገወጥ መንገድ የተሰጠ የመሬት ይዞታ በከንቲባው ጽ/ቤት በተያዘ ቃለ ጉባኤ አቅጣጫ በተመሳሳይ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፤ ተከሳሾች ቀርበው የተከራከሩት ድርጊታችን ሕጋዊ ነው በማለት እንጂ ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት አልተከላከሉም፤ ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓላማ 45/55 የተባለው ሙሉ በሙሉ በሕገመንግስቱ እና በሕጉ መሠረት ወደ ኋላ ተመልሶ መፍትሄ የሚሰጠው ከሆነ በተለይም በመንግስት ላይ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፈተና ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፤ በከተማ አስተዳደሩ ስሕተት ምክንያት ከገበሬው መሬት የገዙ ሰዎች እና አብዛኛው ገበሬ በዚህ መሬት ላይ ከ2005 ዓ.ም በፊት ግንባታ የገነባበት እና መሬቱን ያለማው በመሆኑ ይህንን ማሕበረሰብ የመንግስት መዋቅር በፈጠረው ስሕተት ምክንያት ማፈናቀል እና የሚገባቸውን የካሳ ክፍያ መክፈል ከፍተኛ ፈተና ነው፤ በመሆኑም የአመልካቾች ድርጊት ወንጀል ቢሆንም አመልካቾች ይህን ወንጀል የፈጸሙበት ዓላማ ከፍተኛ ሊያስብለው የሚችል አይደለም፤ ከአመልካቾች ስልጣን ጋር በተያያዘም ሁሉም አመልካቾች የከተማ አስተዳደሩ አመራሮች ቢሆኑም ከተማዋ የዞን ከተማ ያልሆነች እና ተጠሪነቷም ለዞን የነበረ ስለሆነ ስልጣናቸው በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2/5 ድንጋጌ መሠረት ከፍተኛ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፤ በመሆኑም ወንጀሉን ከሚያከብዱት ምክንያቶች መካከል የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ ብቻ ነው በማለት አመልካቾችን እና 10ኛ፤ 11ኛ፤ 15ኛ 20ኛ ተከሳሾችን የተከሰሱበትን የሕግ አንቀጽ በመለወጥ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/2 መሠረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

6ኛን ክስን በሚመለከት የቴክኒክ ኮሚቴው በመመሪያ ቁጥር 12/2007 መሠረት መቋቋም ካለባቸው ተቋሚት ተወካይ ተሟልቶ ያልተቋቋም መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ የቴክኒክ ኮሚቴውን ያቋቋመው አካል የመንግስትን ስራ አመቺ ባልሆነ መንገድ በመምራት የሚጠየቅ ይሆናል፤ የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት መመረጣቸውን በቀን 10/06/2007 ዓ.ም የጻፈው 2ኛ አመልካች አልተከሰሰም፤ 1ኛ አመልካች በሕጉ አግባብ ባልተመረጠ በዚህ ኮሚቴ የቀረበውን ቃለጉባኤ በማጽደቅ በ30/07/07 በበላይ ኮሚቴው የተያዘን ቃለ ጉባኤ የመራው እና በሸኚ ደብዳቤ ለዞን የላከው 1ኛ አመልካች መሆኑ ተረጋግጧል፤ 10ኛ እና 11ኛ ተከሳሾች ይህንን ቃለ ጉባኤ መያዛቸው እና ይህ በሕገወጥ መንገድ የተመረጠው ኮሚቴ ያቀረበው ውጤት እንዲጸድቅ ማድረጋቸው ተረጋግጧል፤ የ1ኛ አመልካች መከላከያ ማስረጃዎች ይህ ኮሚቴ በሕጉ አግባብ ባለመመረጡ የተፈጠረ ችግር ስለሌለ ድርጊቱ ሕገወጥ አይደለም በማለት የመሰከሩ ቢሆንም በዚህ ማጣራት ውስጥ የአጣሪ ኮሚቴው ስላልተከሰሰ እንጂ ፕሎትን የመዝለል ችግሮች የተፈጠሩ መሆናቸው በዓቃቤሕግ 7ኛ ክስ እና ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ መረዳት የሚቻል በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/1/ሐ ስር ጥፋተኞች ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡፡

በመቀጠልም ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማስላት 1ኛ አመልካች በስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 20,000፤ 2ኛ፤3ኛ፤6ኛ፤7ኛ፤9ኛ እና ከ11ኛ-15ኛ ያሉት አመልካቾች በስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 15,000 ፤ 4ኛ፤5ኛ፤8ኛ፤10ኛ በሰባት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 16,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካቾች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ያጸና ሲሆን በቅጣት ረገድ ግን ቅጣቱን አሻሽሎ 1ኛ አመልካች በአምስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት እና በብር 7,000 የገንዘብ መቀጮ ከ2ኛ እስከ 15ኛ ያሉት አመልካቾች ደግሞ በአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እና በብር 5,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የአመልካቾች ድርጊት ወንጀል ነው ተብሎ በሕግ አልተደነገገም፤ አከራካሪው መሬት በመንግስት ፈቃድ በከተማ ነዋሪዎች እጅ የገባው በ1998 ዓ.ም ሲሆን ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ.ም ድረስ ግንባታ ገንብተውበታል፤ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም በሃላፊነት ስንመደብ ይዞታው ባዶ ቦታ አልነበረም፤ መንግስት ከከተማው ነዋሪዎች ጋር በገባው ውል መሠረት ነዋሪዎቹ ክፍያ ከፍለው ደረሰኝ ይዘው ነበር፤ አመልካቾች በያዝነው ቃለጉባኤ የወሰነው ከ1998 ዓ.ም እስከ 2001

ዓ.ም ድረስ ለክሱ መነሻ የሆነው መሬት ባለይዞታ የሆኑ ነዋሪዎች የሊዝ አዋጅ ከመታወጁ በፊት በመሬቱ ላይ ግንባታ ፈጽመው አልምተው እየተገለገሉበት ለሚገኙት ነዋሪዎች ብቻ መንግስት በውል በገባው ግዴታ መሠረት በሕጉ አግባብ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰጣቸው ነው፤ የጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት ስራው በአስቸኳይ እንዲሰራ ያዘዘ በመሆኑ ድርጊቱ እንደ ወንጀል ሊቆጠር አይገባም፤ አመልካቾች ባዶ መሬት ሰጥተዋል የሚል ክስ አልቀረብንም፤ አመልካቾች ከ2004 ዓ.ም በኋላ በተያዘ ይዞታ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጥ ያስተላለፍነው ውሳኔ ሳይኖር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት መመሪያ አመልካቾችን አይመለከትም ማለቱ አግባብ አይደለም፤ የስር ፍ/ቤት 3ኛ፤ 4ኛ፤ 5ኛ እና 16ኛ ተከሳሾች በሕዝባዊ ድርጅት ስር የሚመደበው የኦህዴድ ተሿሚዎች በመሆናቸው አዋጁም በእነሱም ላይ ተፈጻሚነት አለው ማለቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካቾች ክሱን እንድትከላከሉ በማለት የተሰጠው ብይንም ሆነ ክሱን ተከላክለን ሳለ አልተከላከላችሁም በማለት የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብ አይደለም፤ በ21/09/2007 በተፈረመ ቃለ ጉባኤ የፈጸምነው ድርጊት ወንጀል ተብሎ ባልተከሰስንበት ይህን ቃለጉባኤ መነሻ በማድረግ ጥፋተኛ መባላችን አግባብ አይደለም፤ ወንጀሉን ለማቋቋም የሚያስችሉ ፍሬነገሮች አልተሟሉም፤ በቅጣትም ረገድም የዓቃቤሕግን ማክበጃ በመቀበል እና አመልካቾች ያቀረብነውን ማቅለያዎችን ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ 45/55 በሚል ይዞታቸው ለልማት ለተወሰደባቸው ሰዎች ማካካሻነት በ1998 ዓ.ም የተሰጠ እና ሕጋዊ እንዲሆንላቸው ገበሬዎቹ መንግስትን ጠይቀው በዚህ መነሻነት መስመር ለማስያዝ አመልካቾች በስራ በሃላፊነት በቃለ-ጉባኤ የወሰኑት ውሳኔ ሕገወጥ ነው በሚል ጥፋተኛ የመባላቸውን አግባብነት ከተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካቾች መሬት ከአርሶ አደር ሲነጠቅ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሳ መክፈል እና በሕግ አግባብ የተፈቀደለትን መሬት መስጠት ሲገባቸው ይህን አለማድረጋቸው፤ ከአርሶ አደሩ በሕገወጥ መንገድ 3ኛ ወገኖች ከገበሬው የገዙትን መሬት ለመንግስት ገቢ ሳያደርግ ሽያጭ ማካሄዳቸው፤ ከአርሶ አደሩ መሬት የገዙትን ሰዎች ነባር ይዞታ ወይም የድሮ ይዞታ በማለት ማስተናገዳቸው፤ የክልሉን የመሬት ሕግ መመሪያ በመጣስ በክሱ የተመለከተውን ድርጊት መፈጸማቸው የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 መከሰሳቸው እና ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ ነው፤ በ45/55 መሬት በእጃቸው የገባው አርሶ አደሮች በድሮ ይዞታ ስር መውሰድ ሲገባቸው በሊዝ ስር እንዲገባ መደረጉ፤ ከአርሶአደሮች በፊት መሬት በሕገወጥ መንገድ የገዙና በከተማው አስተዳደር እውቅና ተሰጥቶአቸው ማስረጃ የተሰጣቸው በሕገወጥ ይዞታ እና ውዝፍ ስር የሚካተቱ አይደሉም፤ ከጠቅላይ ሚኒስቴር መ/ቤት የተላለፈው መመሪያ የሚመለከተው ከ2004 ዓ.ም

በፊት የነበረውን ሕገወጥ ይዞታና ውዝፍ እንጂ አመልካቾች የፈጸሙትን ድርጊት የማይመለከት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚለው ነው፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በአመልካቾች ላይ የቀረቡት ክሶች የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራት ደግሞ የሙስና ወንጀል ነው፡፡ የሙስና ወንጀል በልዩ ሕግ የተደነገገ ሲሆን ሕጉ ከወጣለት ዓላማ አንጻር በአዋጁ ወንጀል ናቸው ተብለው የተደነገጉት ድንጋጌዎች ወንጀል መሆናቸውን ለማሳየት የራሱ የሆነ መስፈርት በልዩ ሕጉ የተቀመጠለት ከመሆኑ አኳያ የስር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ክሱን እንዲከላከሉ ብይን መስጠታቸው፤ አመልካቾች መካላከያ ማስረጃ ካሰሙ በኋላም በዓቃቤሕግ ማስረጃ የተረጋገጠባቸውን ፍሬነገሮች አላስረዱም በማለት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፋቸው ከሙስና ወንጀሎች አዋጅ፤ ከመደበኛው የወንጀል ሕግ እና ከወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕጉ እንዲሁም የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ ከተጠበቁላቸው መሠረታዊ መብቶች ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ፡-

1. የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?
2. የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ተገቢ ነው ከተባለ አመልካቾች ባቀረቡት መከላከያ የቀረበባቸውን ክስ ተከላክለዋል? ወይስ አልተከላከሉም? የሚሉት ናቸው፡፡

<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡-

በአመልካቾች ላይ የቀረቡት ክሶች የመንግስት ስራን በማያመች አኳሃን መምራትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ዓቃቤሕግ አመልካቾች በክሱ የተገለጸውን ድርጊት ስለመፈጸማቸው ለማስረዳት የሰው ምስክሮችን እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? ለሚለው ነጥብ ምላሽ ከመስጠታችን በፊት ከመነሻውም ቢሆን ዓቃቤሕግ አመልካቾች በክሱ የተመለከተውን ድርጊት ፈጽመዋል ለማለት ማስረዳት የሚጠበቅበት ምንድነው? የሚለው መሠረታዊ ነጥብ ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙለት ሕጋዊ፤ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ

ተከሳሹ ወንጀል ለመስራት የነበረውን የሀሳብ ክፍል የማስረዳት ሸክም ያለበት መሆኑን እና ይህን ካላስረዳ በቀር ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል ብይን መስጠት የማይቻል መሆኑን ነው።

በሌላ በኩል የሙስና ወንጀሎች በፈጣን ሁኔታ የመቀያየር ባሕርይ ስላላቸው አጠቃላይ ወንጀሎችን በሚደነግገው የወንጀል ሕግ ውስጥ እንዲካተቱ ከማድረግ ይልቅ ራሱን በቻለ አዋጅ እንዲደነገጉ ተመራጭ ሆኖ በመገኘቱ በሐገራችን የሙስና ወንጀሎች አዋጅ በልዩ ሕግ ወጥቶ የተለያየ ማሻሻያ ሲደረግበት ቆይቷል። ይህንኑ መሠረት በማድረግም የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ወጥቶ ስራ ላይ ውሏል።

የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር የሙስና ወንጀሎቹ የተፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈጸመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሶስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሶስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል በማለት ይደነግጋል። ይህም የሙስና ወንጀል በሙስና ወንጀል አድራጊው እና በወንጀሉ በሚጠቀመው ሰው መካከል ስምምነት የሚፈጸም በመሆኑ ዓቃቤሕግ ወንጀሉ መፈጸሙን በበቂ ሁኔታ የማስረዳት ሸክም ከባድ የሚያደርግበት በመሆኑ ክሱ የቀረበው ያለአግባብ ነው የሚለው ወገን የዓቃቤሕግ ክስ ትክክል አለመሆኑን ያስረዳ ዘንድ የማስረዳት ሸክሙ ይዛወርበታል። ይህም ዓቃቤሕግ ክስ ሲመሰርት በሌሎች ወንጀሎች ላይ ከተጣለበት በመደበኛነት ከሚታወቀው የማስረዳት ሸክም ወጣ ያለ ልዩ ሁኔታ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ከላይ ከተመለከቱት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 ድንጋጌ እና የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 ድንጋጌ ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤ ሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 መሠረት የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን መሆኑን፤ ይልቁንም በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብለው የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ የሚዛወር መሆኑን ነው። ስለሆነም ዓቃቤሕግ ማስረዳት የሚጠበቅበት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን ብቻ እንጂ ተከሳሹ ወንጀል ለመፈጸም የነበረውን የሃሳብ ክፍል አለመሆኑን እና የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል አላስረዳህም ተብሎ ተከሳሹን መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት ነጻ ሊያወጣው የሚችል አይደለም።

ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ዓቃቤሕግ በሕጉ አግባብ የተጣለበትን አመልካቾች በተከሰሱበት ድንጋጌ ላይ የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን አስረድቷል? ወይስ አላስረዳም? ለሚለው ነጥብ ምላሽ ለመስጠት በስር ፍ/ቤት የተሰሙትን የዓቃቤሕግ ማስረጃዎች ይዘት መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1ኛ የዓቃቤሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት ፡-

ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ጉዳዩን ያጣሩ መሆኑን፤ የሮቤ ከተማ ማስተር ፕላን የሮቤ ዙሪያ ቀበሌ እና ሆራ ቦቃን የሚያቅፍ መሆኑን፤ በከተማው ማስተር ፕላን ስር ያለ ቢሆንም በሲናና ወረዳ እና በሮቤ ከተማ መካከል ርክክብ ያልተፈጸመ በመሆኑ የከተማው አስተዳደር በመሬቱ ላይ ማዘዝ አይችልም በማለት የመለሱ መሆኑን፤ ባክሎግ ለማስመለስ የተቋቋሙ ኮሚቴዎችን እና ቃለጉባኤ ያዩ ቢሆንም ሰው ሲፈርም ያላዩ መሆኑን፤ በቴክኒክ ኮሚቴ ውስጥ የተቋቋሙት አዋጁ የማይፈቅድላቸው መሆናቸውን፤ በአንድ ኮሚቴ የተደረገው ማጣራት 530 ሰዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ኮሚቴ ደግሞ 56 ሰዎችን ጨምሮ ያቀረበ መሆኑን፤ 45/55 የሚለው አሰራር ገበሬው ካለው መሬት 45% የሚወስድ ሲሆን 55% ለመንግስት የሚገባ መሆኑን፤ በ21/09/2007 ዓ.ም የተጻፈን ቃለጉባኤ መነሻ በማድረግ የከተማ አስተዳደር በገንዘብ ሊከፈል የሚችል ክፍያ ስለሌለው እንዲፈቀድልን በማለት የኦሮሚያ መሬት ልማት እና ማኔጅመንትን እና ዞኑን በደብዳቤ የጠየቁ መሆኑን፤ ለደብዳቤዎቹ የተሰጠ ምላሽ ማግኘት ያልቻሉ መሆኑን፤ 45/55 የሚባል አሰራር በሕግ የሌለ መሆኑን፤ ካሳ የሚከፈልበት መንገድ በሕጉ የተቀመጠ ቢሆንም በሕጉ መሠረት ያልተከፈለ መሆኑን፤ በገበሬው መሬት ላይ በከተማው አስተዳደር እና በሲናና ወረዳ መካከል ርክክብ ያልተደረገ መሆኑን፤ 45/55 የተባለው አሰራር በሮቤ ከተማ እና በሲናና ወረዳ መካከል ሲስፋፋ የነበረው ከ1998ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም መሆኑን፤ ከሲናና ወረዳ ወደ ሮቤ ከተማ በገባ መሬት የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት የተሰሩ መሆኑን፤ ገበሬው በ45/55 ከተሰጠው መሬት ለግለሰብ አስተላልፎ አብዛኛው እጅ ከ2007 ዓ.ም በፊት ግንባታ የተገነባበት መሆኑን፤ መንግስት በወሰደው 55% መሬት ላይ ማስረጃ አለመመርመራቸውን፤ በ2004 ዓ.ም እና በ2005 ዓ.ም በገበሬው እና በከተማው አስተዳደሩ መካከል ክርክር ተነስቶ የነበረ መሆኑን፤ 45/55 የተባለው አሰራር የሕዝብን ጥያቄ እንመልሳለን በሚል የተሰራ ቢሆንም መንግስት የሕዝብን ጥያቄ የሚመልስበት መመሪያ ያለው መሆኑን፤ 45/55 የተባለው አሰራር ሲጀመር አመልካቾች በከተማው አስተዳደር በሀላፊነት ላይ ያልነበሩ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ይዘት ፡-

በአብዛኛው 1ኛ ምስክር ከሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ምስክርነት የሰጡ ሲሆን በከንቲባው የሚመራው ኮሚቴ 530 ሰዎች በባክሎግ መሬት ማግኘት የሚገባቸው መሆኑን ያጣራ መሆኑን፤ 2ኛው ኮሚቴ 56 ሰዎችን ጨምሮ ያጣራ መሆኑን፤ 32 ሰዎች መሬት ተሰጥቷቸዋል

የተባለውን በሚመለከት ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን፤ በቃለ ጉባኤ ላይ 45/55 የተባለው አሰራር በተመለከተ ገበሬው የ45% ድርሻውን ለግለሰቦች ማስተላለፍ ይችላል በማለት የተገለጸ ቢሆንም በምን አግባብ እንዲሚያስተላልፍ የማያውቁ መሆኑን፤ አመልካቾች 45/55 በስራ ላይ እንዲውል እንዲፈቀድላቸው ላቀረቡት ጥያቄ የተሰጠ መልስ ያላዩ መሆኑን፤ 79 ለሆኑ ገበሬዎች በ45/55 መሬታቸው የተሰጣቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

3ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ይዘት ፡-

ከ76 ገበሬዎች ጋር በተያያዘ የቀረበው ማስረጃ በከተማው ድንበር ያሉ ገበሬዎች ቤተሰቦች ስፋት፤ መሬቱ አገልግሎቱ እና ደረጃው ምን እንደሆነ የሚገልጽ ነገር የሌለው መሆኑን፤ ገላጭ ነገር ባለማግኘታቸው ምክንያት በደንብ 155/2005 መሠረት ከ200 ካ.ሜትር በላይ ያለው ገበሬ በኪራይ ስርዓት፤ ከዚህ በላይ ከሆነ 500 ካ.ሜ ለባለይዞታው ተሰጥቶ ከዚህ የቀረው ደግሞ የመንግስት መሬት ስለሚሆን መንግስት ከዚህ መሬት ሊያገኝ የሚገባው ገቢ ነው በማለት ያሰሉ መሆኑን፤ የሮቤ ከተማ የከተማው ኤጀንሲ ከተዘጋጀ በኋላ 3ኛ ደረጃ የነበረች መሆኑን ከሐምሌ ወር 2007 ዓ.ም ጀምሮ ወደ 2ኛ ለደረጃ ያደገች መሆኑን፤ መሬቱ በመመሪያው መሠረት ቢተላለፍ ኖሮ 1ኛ ደረጃ ወይም 2ኛ ደረጃ በማለት ለይተው በዞኑ ኮሚቴ በተያዘው ቃለ ጉባኤ ላይ ተንተርሰው የሰሩ መሆኑን፤ የሮቤን ከተማ ስታንዳርድ ትልቁን በ 200 ካ.ሜ ወስደን በደንብ ቁጥር 155/2005 መሠረት የመሬቱ ይዞታ ባለቤት ለሆነው ገበሬው 500 ካ.ሜ ይጸድቅለታል፤ ከ500 ካ.ሜ በላይ የሆነው ይወሰድበታል፤ 105 ካ.ሜ ከሆነ ተመዝግቦ ይቀመጣል፤ በዚህ መሠረት መንግስት ማግኘት ይገባው የነበረውን ገንዘብ አስልተው ያስቀመጡ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

4ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ለፍ/ቤቱ የሰጠው የምስክርነት ቃል ይዘት ፡-

የሮቤ ከተማ መሬት ማኔጅመንት የመዝገብ ቤት አግልግሎት አቀናጅ መሆናቸውን፤ በኦሮሚያ ጸረ ሙስና ኮሚሽን 311 ሰዎችን በሚመለከት እንዲያጣሩ ተጠይቀው 47 ሰዎችን ማግኘት ያልቻሉ መሆኑን፤ 47ቱ ሰዎች ስራ በነበረበት ጊዜ ደረሰኝ ቆርጠው መዝገብ ያስከፈቱ መሆኑን፤ ውል ሳይሞሉ የቀሩ ብዙ ሰዎች የነበሩ መሆኑን፤ ውል ተሞልቶላቸው ባለስልጣኑ ሳይፈርምበት የቀረባቸው ሰዎችም የነበሩ መሆኑን፤ 47ቱ ሰዎች መሬት አላቸው ተብሎ የመጣላቸው ቢሆንም በመዝገብ ውስጥ ግን የሌለ መሆኑን፤ የተለያዩ ሰዎች እየመጡ ለመስተናገድ ይጠይቁ የነበረ እና ስራው ይቁም ስለተባለ ልናስተናግዳችሁ አንችልም እያሉ ይመልስዋቸው የነበረ መሆኑን፤ ፍቃድ ያላቸው ሰዎች ብቻ ደረሰኝ የቆረጡ መሆኑን፤ 47ቱ ሰዎች ደረሰኝ ያላቸው ከመሆን ውጪ ለይተው የማያውቋቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ዓቃቤ ሕግ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት፡-

ዓቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት በርካታ የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን ዋነኞቹ አመልካቾች 45/55 የተባለ አሰራር እንዲፈቀድላቸው የያዟቸው ቃለጉባኤዎች እና ቃለ ጉባኤዎችን መሠረት በማድረግ ለበላይ አካል የጻፏቸው ደብዳቤዎች፤ በ45/55 ከገበሬዎች ተወስዷል የተባለው መሬት የገበሬው ድርሻ ነው የተባለው 45% በውሉ መሠረት ያልተላለፈ መሆኑን፤ በሰነድ ማስረጃ መሠረት የ76ቱ ገበሬዎች መሬት ይዞታ 919100 እንደሆነ የባክሎግ አጣሪ ኮሚቴው ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤት በሙሉ ያልተቋቋመ መሆኑን፤ በቴክኒክ ኮሚቴው ሁለት ጊዜ የተጣራው ልዩነት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ሪፖርት፤ ከከተማው መስፋፋት ጋር ተያይዞ በሮቤ ከተማ ስር የታቀፉት የገጠር ቀበሌዎች ላይ በሲናና ወረዳ እና በሮቤ ከተማ አስተዳደር መካከል ርክክብ አለመከናወኑን የሚያሳይ ደብዳቤ ለመሬት ክምችት ከተመዘገቡት 642 ሰዎች መሃከል 530 ሰዎች መሬት እንዲያገኙ መደረጉን፤ 98 ሰዎች ማግኘት የሌለባቸው መሆኑን መረጋገጡን እና በዚህ ረገድ እየተሰራ ያለው ስራ ያልተጠናቀቀ መሆኑን የሚያሳይ ቃለጉባኤ፤ ከተለያዩ ሰዎች ጋር የተደረጉ ውሎች ናቸው፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው የዓቃቤ ሕግ የሰው ምስክሮች ለፍ/ቤቱ ከሰጡት የምስክርነት ቃል እና ዓቃቤሕግ ካቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ አመልካቾች በተከሰሱበት የሙስና ሕግ ድንጋጌ ላይ የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን ያረጋገጠ መሆኑን ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ መደበኛውን የወንጀል ሕግ ወይም ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት ልዩ መስፈርትን የማያስቀምጡ ልዩ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ክስ ሲያቀርብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 መሠረት የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብለው የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ የሚዛወር በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ክሶች እንደ አንድ ክስ ታይተው አመልካቾች የወንጀሉ ድርጊት በስራ ላይ እንዲውል የተወሰነውን ቃለ ጉባኤ በመያዛቸው እና በማጽደቃቸው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/3 ስር እንዲከላከሉ፤ 1ኛ አመልካች ደግሞ ስድስተኛውንም ክስ በተጨማሪ እንዲከላከል በማለት ብይን መስጠቱ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>

የስር ፍ/ቤት አመልካቾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ በአግባቡ ነው ከተባለ አመልካቾች ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ የቀረበባቸውን ክስ ተከላክለዋል? ወይስ አልተከላከሉም? የሚለው ሁለተኛው መሠረታዊ ጭብጥ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ካቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ አንጻር

በአግባቡ ታይቶ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ይዘት በቅድሚያ መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1ኛ አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142/3 መሠረት ለፍ/ቤቱ የሰጠው ቃል ይዘት፡-

አመልካቾች የመጡት በ2007 ዓ.ም መሆኑን፤ የከተማው አስተዳደር ለገበሬው ይዞታ ካሳ ለመክፈል የገንዘብ ችግር ስለነበረበት 45/55 የተባለው አሰራር ከ1998 እስከ 2000 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተጀመረ መሆኑን፤፤ 55% የገበሬውን መሬት መንግስት ወስዶ ያለማው መሆኑን፤ 45% ደግሞ ለ3ኛ ወገን የተላለፈ መሆኑን፤ ወደኋላ ያለው 10 ዓመት ግንባታ ተገንብቶበት የለማ በመሆኑ፤ የሰብልን ካሳ ለመክፈል መሬቱ 10 ዓመት እዳሪ የነበረ በመሆኑ፤ የንብረት ካሳ ለመክፈል ንብረቱ በከተማ አስተዳደር ተወስዶ የራሱ መሆን የነበረበት በመሆኑን ምክንያት በአዋጅ 455/97 መሠረት ተፈጻሚ ያልተደረገ መሆኑን፤ የከተማ አስተዳደሩ እስከ ክልል መንግስት ድረስ ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፤ ከክልሉ እና ከከተማው አስተዳደር ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ሲታይ የነበረ መሆኑን ፤ መንግስት ባክሎግ የነበረበት በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 721/2007 በስራ ላይ ለማዋል የጠቅላይ ሚንስትሩን ቢሮ በመጠየቅ የጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮም ጉዳዩ ለመጨረሻ ጊዜ መልስ እንዲያገኝ በጻፈው ደብዳቤ ፍቃድ የተሰጠ መሆኑን፤ በቀን 18/05/2007 ከጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮ ለክልሉ ፕሬዝደንት ጽ/ቤት በቀጥታ በተጻፈ ደብዳቤ ላይ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦችን የያዘ ሲሆን እነኚህም 1ኛ ደረሰኝ ያላቸው ባክሎግ ደረሰኝ ቆርጠው መሬት ሳይገኙ የቀሩ ተስተናግደው ምላሽ እንዲሰጣቸው፤ 2ኛ መሬት ይዘው ቤት የሰሩት ሰዎች ሙሉ ሰነድ ሳይኖራቸው የቀሩት ለመጨረሻ ጊዜ እንዲስተናገዱ የሚል መሆኑን፤ በዚህ ደብዳቤ ላይ በመመሰረት የፕሬዝደንት ጽ/ቤት ለክልሉ ኢንደስትሪ እና ከተማ ልማት ቢሮ እና ለክልሉ መሬት ኤጀንሲ በቀን 05/06/2007 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ለማስተናገድ እንዲችሉ በማለት የጻፈ መሆኑን፤ ይህን ለማስፈጸምም ሁለቱ ቢሮዎች እቅድ በማውጣት በየደረጃው ላሉ ኦረንቴሽን በመስጠት ወደ ስራ እንዲገባ አቅጣጫ የተቀመጠ መሆኑን፤ የክልሉን ሕግ እና መመሪያ መሠረት በማድረግ በባክሎግ በሕገወጥ ግንባታ እና ነባር ይዞታ ላይ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ መሆኑን፤ ለገበሬው በካሳ የተሰጠው 45% ከከተማ መስተዳድሩ ጋር የፊጸሙት ውል በእጃቸው የነበረ በመሆኑ በመግለጽ ቃሉን መስጠቱን የሚያሳይ ነው፡፡

1ኛ መካላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት፡-

በ1998 ዓ.ም በሮቤ ከተማ አባገዳ አዳራሽ ሰብስበው ከተማዋ ዞን ስለሆነች ልትለቁ ይገባል ያሏቸው መሆኑን፤ መሬቱን አንለቅም ሲሉ ልማትን ማደናቀፍ አትችሉም መንግስት እንዲሁም ሊወስድባችሁ ስለሚችል ካሳችሁን 45/55 እናደርግላችኋለን ያሏቸው መሆኑን፤ ካርኒ ሳይቆረጥላቸው በመቅረቱ ከ2005 እስከ 2006 አቤቱታ ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑን፤ መፍትሄ እንዲሰጣቸው በየጊዜው ለነበሩ የክልሉ ፕሬዝደንቶች በተለያየ ጊዜ አቤቱታ ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑን፤ ሀላፊዎቹም እናንተ ጥፋት

አልፈጸማችሁም ጥፋት የፈጸሙት እራሳችን እዛ ያስቀመጥናቸው ሰራተኞቸ ናቸው ከባክሎግ ጋር አንድ ላይ ተደምሮ እንዲስተካከልላችሁ እናደርጋለን ያሏቸው መሆኑን፤ በ1998 ዓ.ም ተሸንሽኖ የነበረን መሬት እና ቤት የተሰራበትን ዞረው እያሳዩ አጣርተው ለይተው ካርኒ ይቆረጥላቸው የሚል ድምጽ የተሰማ መሆኑን፤ ከዚህ በኋላ በአዳራሽ ሰብስበው ሊዝ የቆረጡባቸው መሆኑን ፤ አመልካቾችም በ1998 ዓ.ም የተመሩትን ሰዎች ወደ ኋላ ተመልሰው በ2007 ዓ.ም ሊዝ ያስከፈሏቸው መሆኑን ፤ ወደ ሊዝ በመለሷቸው ጊዜ 45/55 የተባለው ይዞታ ሁሉም ቤት የነበረበት መሆኑን፤ ለመንግስት የሰጡት መሬት የተለያየ ተቋማት ተሰርቶበት ሙሉ ለሙሉ ለመንግስት ጥቅም የዋለ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

2ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት

45/55 የተባለውን አሰራር በተመለከተ ከ1ኛ ምስክር ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ምስክርነት የሰጡ ሲሆን በተጨማሪም አብዛኛው ሰው በወቅቱ የግብርና ስራ አቁሞ ስለነበረ ቀለብ ያልነበረው መሆኑን፤ ሕዝቡ ለሰባት ስምንት ዓመታት እርሻ አቁሞ የራሱን መሬት እየገዛ የነበረ መሆኑን፤ የራሳችንን መሬት ሰጥተናችሁ መልሰን እንገዛለን ሲል የነበረ መሆኑን፤ አመልካቾች ወደ ሊዝ ስርዓት ይገባል 45/55 በሚለው ስርዓት አይፈጸምም ብለዋቸው የነበረ መሆኑን፤ በአመልካቾች የተሸነሸነ መሬት የሌለ መሆኑን፤ አመልካቾች በሊዝ ክፍያ ያስከፈሉበት ዓላማ የሕዝብን ችግር ለመፍታት መሆኑን፤ መሬት ወደ ከተማ ሲመለስ የመሬት ንጥቂያ በዝቶ የነበረ እና ግለሰቦች የተለያየ ማስረጃዎች አሰርተው በሰዎች ላይ ክርክር እያቀረቡ የነበረ መሆኑን፤ ዋስትናችን ምንድነው? በምን እንከላከላለን? በከተማ ድንበር ውስጥ አስገብታችሁ እንዳናገዝ ከልክላችሁናል ውል ሞልተናል ይህንን ውል ማፍረስ አንችልም የሚሉ ነጥቦችን አንስተው በእጃቸው ላይ ያለው ይዞታ እንዲጸድቅላቸው የጠየቁ መሆኑን፤ 45/55 ን እንደዳታ ተጠቅመው ውል የፈጸሙላቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

3ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት በአጭሩ፡-

45/55 የተባለውን አሰራር በተመለከተ ከ1ኛ እና 2ኛ ምስክር ከሰጡት ቃል ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ምስክርነት የሰጡ ሲሆን በተጨማሪም ከላይ ካሉት ጋር ተመሳሳይ በሆነ 45/55 ውል በፈረሙበት እለት ለሌላ ሰው ያስተላለፉ መሆኑን፤ በይዞታው ላይ ቤት የተገነባበት መሆኑን፤ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ካርኒ መቁረጥ ቆሟል በማለት የከለከሏቸው መሆኑን፤ መሬቱ በተወሰደባቸው ጊዜ አመልካቾች ያልነበሩ መሆኑን፤ አመልካቾች ከመምጣታቸው በፊት የፈጸሙት ውል እያለ አንፈጽምም በማለት በሊዝ ያስከፈሏቸው መሆኑን፤ በበፊቱ ውል እንዲፈጸምላቸው ሲጠየቁ መመሪያ ይከለክለናል ያሏቸው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

4ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት፡-

በወቅቱ የከተማው አስተዳደር ለገበሬው ካሳ ለመክፈል ገቢ ያልነበረው መሆኑን፤ ገበሬው የራሱን ግንባታ ሲገነባበት ሌላውን ደግሞ አሳልፎ ለሰው ሲሰጥ የነበረ መሆኑን፤ መሬት የመስጠት ጉዳይ ከቀን 16/09/2001 ዓ.ም ጀምሮ በወቅቱ በነበሩት የክልሉ ፕሬዝደንት በነበሩት የቆመ መሆኑን፤ ምስክሩ መሬት መስጠት ከቆመ ከአንድ ወር በኋላ ከንቲባ የሆኑ መሆኑን፤ ገበሬው በተለያየ ጊዜ እየቀረበ በመሬታቸው ላይ ማሕተም ተመቶበት ከንቲባ እና የማዘጋጃ ቤቱ ባለሙያ የፈረመበትን ውል ይዞ በመምጣት ካርኒ ቆርጣችሁ ባለይዞታችንን አረጋግጡልን በማለት ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፤ ከገበሬው ላይ መሬትን በስጦታም ሆነ በሽያጭ የወሰዱትም ተመሳሳይ ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበረ መሆኑን፤ ገበሬው መልስ ሊያገኝ ስላልቻለ እስከ ክልል አስተዳደር ድረስ በመሄድ ሲጠይቅ የነበረ መሆኑን፤ በ2007 ዓ.ም ምርጫ ሲቃረብ ጥያቄውን ለመመለስ መንግስት ባስተላለፈው መመሪያ በመንተራስ አመልካቾች የገበሬዎቹን ጥያቄ የመለሱ መሆኑን፤ አመልካቾች ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2001 ዓ.ም በተሰራው ስራ ውስጥ ድርሻ የሌላቸው መሆኑን፤ የነባር ይዞታው ባለቤት ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የድሮ ይዞታ የመንግስት ክፍያን ከፍሎ ባለይዞታነቱ እንዲረጋገጥ የተደረገ መሆኑን፤ ከገበሬው ላይ ተላልፎለት መሬት ያገኘ ሰው ደግሞ የሊዝ መነሻ ዋጋ ክፍያን ከፍሎ ባለይዞታነቱ እንዲረጋገጥ የተደረገ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው።

5ኛ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት፡-

ምስክሩ የማዘጋጃ ቤቱ ስራ አስኪያጅ የነበሩ መሆኑን፤ ተንጠልጥለው የቆዩ ጉዳዮችን በሚመለከት የሚፈጸሙበትን ሁኔታ ስልጠና የወሰዱ መሆኑን፤ በጠቅላይ ሚንስቴር እና በክልል ደረጃ የተጻፉ ደብዳቤዎች ስለነበሩ 45/55 በዚህ ሊስተናገድ የሚችል መሆኑን፤ በ1997 እና በ1998 አካባቢ የከተማዋ ገቢ ከ 4,000,000 የማይበልጥ የነበረ በመሆኑ ለ10 ዓመት ወደ ኋላ ተመልሰው ካሳ መክፈል የማይቻል መሆኑ፤ መንግስት መሬት መስጠትን አግዶ ገበሬዎች የራሳቸውን ድርሻ መሬት ሲወስዱ የነበረ መሆኑን፤ መንግስትም የራሱን ድርሻ ወስዶ ሲያለማበት የቆየ መሆኑን፤ እስከ 500 ካ.ሜ ካርኒ ሲቆረጥበት የቆየ መሆኑን ፤ በወቅቱ የእገሌ ቤተሰብ ነኝ በማለት ደረሰኝ ይቆረጥልኝ በማለት አቤቱታ ሲያቀርቡ ካርኒ በመቁረጥ ይስተናገዱ የነበረ መሆኑን፤ ከሚፈቀደው ስታንዳርድ በላይ የጸደቀ የሌለ መሆኑን፤ ገበሬው ወደ ከተማ አስተዳደሩ እንዲሁም ወደ ክልሉ አስተዳደር በመሄድ ሃላፊዎች ያነጋገረ መሆኑን፤ የሕዝቡ ቅሬታ በመብዛቱ በአባገዳ አዳራሽ ሰብስበው አናግረዋቸው የደንብ ስለወጣ በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ ይሰጣችኋል ያሏቸው መሆኑን፤ ለአመራሩም ኦረንቴሽን የተሰጠ መሆኑን፤ አመልካቾች ሳይጠናቀቅ ተንጠልጥሎ የቆየን ነገር ሕጋዊ መስመር አስይዘው ከማጠናቀቅ ውጪ 45/55ን በአዲስ መልክ የሰሩት ነገር የሌለ መሆኑን፤ 45/55 የተባለው አሰራር በዞንም በክልልም እንደጥሩ ምሳሌ ተወስዶ የነበረ መሆኑን፤ ገበሬው በራሱ ድርሻ ላይ ማስረጃ ያለው መሆኑን፤ ገበሬው ወደ ኋላ ተመልሶ በሊዝ እንዲከፍል ስለተደረገ የተጎዳው ገበሬው እንጂ በመንግስት ላይ የደረሰ ጉዳት የሌለ መሆኑን፤ ከከተማ አስተዳደር ጋር ውል የሌላቸው ሰዎች ሕጋዊ ያልተደረጉ መሆኑን፤ ግንባታ

የፈጸሙ እና ከገበሬው ውጪ ያሉ ሰዎች ደግሞ በሊዝ ስርዓት ባለቤትነታቸው የተረጋገጠ መሆኑን፤ ከገበሬው ጋር የተለያዩ ውሎች ሲደረጉ የነበረ መሆኑን፤ መንግስት 55% መብት እንዳለው ሁሉ ገበሬውም በ45% ላይ ሊያዝበት መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

6ኛ መከላከያ ምስክር የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘት፡-

.45/55 የተባለውን አሰራር በተመለከተ ሌሎች ምስክሮች ከሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር በተመሳሳይ የመሰከሩ ሲሆን በተጨማሪም መንግስት በ2007 ዓ.ም በሊዝ መሸጋገሪያ ጊዜ ተይዘው የነበሩ መሬቶች በሊዝ መመሪያ ተጠቃለው እንዲስተናገዱ፤ በድሮ ይዞታ እና በሕገወጥ ግንባታ መካከል ተንጠልጥሎ የነበረ ይዞታ መፍትሔ እንዲያገኝ አቅጣጫ ያስቀመጠ መሆኑን፤ አስቀድሞ መሬቱ የገበሬው የራሱ የእርሻ መሬት ስለሆነ ገበሬው መሬቱን መኖሪያ ቤት ለማድረግ፤ በስጦታ ለማስተላለፍ መብት አለው፤ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም 45/55 ን በማስቀጠል ለገበሬው ካሳ ሳይከፍሉ የወሰዱት መሬት የሌለ መሆኑን፤ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም የሰሩት ነገር መሬቱ አስቀድሞ ስለተሰጠ ማስረጃ ብቻ መስጠት እንጂ መሬት ያልሰጡ መሆኑን፤ መጀመሪያ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በተደረገ ውል በተሰጠ መሬት ላይ መሟላት ያለበት መስፈርት በሙሉ መሟላቱን አረጋግጠው ሳይት ፕላን እና ማስረጃ የሰጡ መሆኑን በመግለጽ መመስከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች በተጨማሪም በምስክሮቻቸው የተገለጸውን የምስክርነት ቃል የሚደግፍ የሰነድ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡

እንግዲህ ከላይ በተገለጸው መሠረት አመልካቾች ደርጊቱን ለመፈጸም የቻሉበትን ምክንያት ካስረዱ አመልካቾች ባቀረቡት መከላከያ ማስረጃ የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መርታችኋል በማለት እንዲከላከሉ በተሰጠው ብይን መሠረት ተከላክለዋል ወይስ አልተከላከሉም ለማለት አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው እንዲያስተባብሉት የሚጠበቀው ምንድነው? የሚለው ለጉዳዩ አወሳሰን መሠረታዊ ነጥብ ነው፡፡ በተያዘው መሠረታዊ ጭብጥ ላይ ምላሽ ለመስጠት ከላይ በመጀመሪያው ጭብጥ ላይ የገለጽነውን የማስረዳት ሸክም ወደ አመልካቾች የተላለፈበትን ምክንያት በድጋሚ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

አመልካቾች እንዲከላከሉ በማለት ብይን የተሰጠባቸው የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 13/3 እና 13/1/ሐ ድንጋጌ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ስልጣንን ወይም ሀላፊነትን ተጠቅሞ የመንግስትን ስራ በማያመች አኳሃን መምራት ወንጀል ነው፡፡ ዓቃቤሕግ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 መሠረት የተከሳሹን የሀሳብ ክፍል እንዲያረጋግጥ የተጣለበት የማስረዳት ሸክም ለሙስና ወንጀሎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ የማይሆን እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙ በተረጋገጠ ጊዜ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር ለመፈጸም የነበረውን የሀሳብ ክፍል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ እንዲያስተባብለው የማስረዳት ሸክሙ ወደ ተከሳሹ ይዞራል፡፡ ይህም ማለት አመልካቾች ድርጊቱን

የፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ነው በማለት አስቀድሞ ተይዞባቸው የነበረውን የሕግ ግምት ስራውን የመሩት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት አለመሆኑን እና ስራውን በሚያመች አኳኋን የመሩ መሆኑን ሊያሳይ የሚችል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በሙስና ወንጀሎች ግዙፋዊ ፍሬነገሩ መፈጸሙ በተረጋገጠ ጊዜ ተከሳሹ በድንጋጌው የተመለከተውን ግዙፋዊ ፍሬነገር መፈጸሙን የሕግ ግምት የሚያዝበት መሆኑ፤ ተከሳሹም ይህን አስቀድሞ የተያዘበትን የሕግ ግምት ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ሊያስተባብለው የሚችል በመሆኑ ፍ/ቤቶች ይህንኑ መሠረት በማድረግ ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ተገቢውን ሚዛን የጠበቀ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም በአንድ በኩል የሙስና ወንጀሎች አዋጅ የሕዝብ እና የመንግስትን ጥቅም ለማስጠበቅ የወጣ በመሆኑ ወንጀሉን ፈጽመዋል ተብለው ክስ የቀረበባቸው ሰዎች ወንጀሉን የፈጸሙ መሆኑ በተረጋገጠባቸው ጊዜ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ያለባቸው በመሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የተከሰሱ ሰዎች የመሰማት መብታቸው ተጠብቆ በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ መሆናቸው በማስረጃ እስካልተረጋገጠ ድረስ ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት ያላቸው መሆኑ ነው፡፡

ይህንኑ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደተመለከትነው አንድ ሰው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ሲል ስራን በማያመች አኳኋን መርቷል ለማለት ስራውን በሚያመቸ አኳሃን ለመምራት የሚያስችል ሕግ እና የተዘረጋ ስርዓት መኖሩ እና ተከሳሹ ይህንኑ ሕግ እና ስርዓት ተላልፎ ስራውን በማያመች አኳኋን የመራ መሆኑ ሊረጋገጥበት ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ 45/55 የተባለው አሰራር ከ1998 እስከ 2001 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተጀመረ መሆኑን፤ አመልካቾች ወደ ሀላፊነት የመጡት በ2007 ዓ.ም መሆኑ፤ የከተማው አስተዳደር ለገበሬው ይዞታ ካሳ ለመክፈል የገንዘብ ችግር ስለነበረበት 45/55 የተባለው አሰራር የተጀመረ መሆኑን፤ በዚሁ መሠረት 45% ገበሬው በካሳ መልክ እንዲወስደው 55% የገበሬውን መሬት ደግሞ መንግስት እንዲወስድ የተደረገ መሆኑን፤ መንግስት በወሰደው 55% ድርሻው ላይ የተለያዩ ተቋማትን በመገንባት ያለማው መሆኑን፤ ገበሬው ደግሞ ድርሻው በሆነው 45% ከፊሉን ራሱ የወሰደ ከፊሉን ደግሞ ለ3ኛ ወገን ያስተላለፈ መሆኑን፤ ገበሬው ከከተማው አስተዳደር ጋር ውል ፈጽሞ የነበረ መሆኑን፤ ወደኋላ ያለው 10 ዓመት በመሬቱ ላይ ግንባታ ተገንብቶበት የለማ በመሆኑ፤ የሰብልን ካሳ ለመክፈል መሬቱ 10 ዓመት እዳሪ የነበረ በመሆኑ ምክንያት በአዋጅ 455/97 መሠረት ተፈጻሚ ያልተደረገ መሆኑን፤ የከተማ አስተዳደሩ እስከ ክልል መንግሰት ድረስ ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፤ ከክልሉ እና ከከተማው አስተዳደር ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ሲታይ የነበረ መሆኑን ፤ መንግስት ምላሽ ያልሰጠበት ባክሎግ የነበረበት መሆኑ፤ ገበሬው ተደራጅቶ በተለያየ ጊዜ ለነበሩ የክልሉ ፕሬዝደንቶች ጥያቄ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን፤ ሀላፊዎቹም እናንተ ጥፋት አልፈጸማችሁም ጥፋት የፈጸሙት እራሳችን እዛ

ያስቀመጥናቸው ሰራተኞች ናቸው ከባክ ሎግ ጋር አንድ ላይ ተደምሮ እንዲስተካከልላችሁ እናደርጋለን ያሏቸው መሆኑን፤ ገበሬው አስቀድሞ በነበረው አሰራር መሠረት ካርኒ እንዲቀረጥለት ሲጠይቅ አመልካቾች ይህንኑ ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልነበሩ መሆኑን፤ የገበሬው ጥያቄ ገፍቶ እስከ ጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት ድረስ የደረሰ መሆኑን፤ የጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮም ጉዳዩ ለመጨረሻ ጊዜ መልስ እንዲያገኝ በጻፈው ደብዳቤ ደረሰኝ ያላቸው ባክሎግ ደረሰኝ ቆርጠው መሬት ሳያገኙ የቀሩ ተስተናግደው ምላሽ እንዲሰጣቸው፤ መሬት ይዘው ቤት የሰሩት ሰዎች ሙሉ ሰነድ ሳይኖራቸው የቀሩት ለመጨረሻ ጊዜ እንዲስተናገዱ የሚል መሆኑን፤ ይህንኑ መሠረት በማድረግ የክልሉ ፕሬዝደንት በጻፈው ደብዳቤ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ለማስተናገድ እንዲችሉ በማለት የጻፈ መሆኑን፤ አመልካቾች ሳይጠናቀቅ ተንጠልጥሎ የቆየን ነገር ሕጋዊ መስመር አስይዘው ከማጠናቀቅ ውጪ 45/55 የተባለውን አሰራር በአዲስ መልክ ያልሰሩ መሆኑን፤ ገበሬው በራሱ ድርሻ ላይ ማስረጃ ያለው መሆኑን፤ ከከተማ አስተዳደር ጋር ውል የሌላቸው ሰዎች ሕጋዊ ያልተደረጉ መሆኑን፤ ግንባታ የፈጸሙ እና ከገበሬው ውጪ ያሉ ሰዎች ደግሞ በሊዝ ስርዓት ባለቤትነታቸው የተረጋገጠ መሆኑን፤ አመልካቾች በ2007 ዓ.ም የሰሩት ስራ መሬቱ አስቀድሞ ስለተሰጠ ማስረጃ ብቻ መስጠት እንጂ መሬት ያልሰጡ መሆኑን፤ መጀመሪያ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በተደረገ ውል በተሰጠ መሬት ላይ መሟላት ያለበት መስፈርት በሙሉ መሟላቱን ተረጋግጦ ማስረጃ የተሰጠ መሆኑን አመልካቾች ካቀረቡት መከላከያ ማስረጃ ይዘት መገንዘብ ይቻላል።

ገበሬው ተገቢ የሆነ ካሳ ሳይከፈለው ከእርሻ መሬቱ ያለመፈናቀል መብት እንዳለው በሕገ-መንግስቱም ሆነ በክልሉ የመሬት ሕግ የተደነገገ ቢሆንም ገበሬው ከይዞታው ላይ እንዲነሳ በተደረገ ጊዜ ከተማዋ ካሳ ለመክፈል የሚያስችል የገንዘብ አቅም ያልነበራት መሆኑ፤ 45/55 የተባለው አሰራር በሕግ ያልተደነገገ ቢሆንም በወቅቱ የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ ሲባል በወቅቱ በነበሩ ሀላፊዎች ሲተገበር የነበረ መሆኑ፤ ይህንኑ ተከትሎ መሬቱ ከፊሉ በገበሬው እጅ ከፊሉ ደግሞ ለተለያዩ ግለሰቦች የተላለፈ መሆኑን፤ በከተማው አስተዳደር ስሕተት ምክንያት ከገበሬው መሬት የገዙ ሰዎች እና አብዛኛው ገበሬ በዚህ መሬት ላይ ከ2005 ዓ.ም በፊት ግንባታ የገነባበት እና መሬቱን ያለማው በመሆኑ ሕብረተሰቡን ለማፈናቀል እና የሚገባውን የካሳ ክፍያ ለመክፈል ከፍተኛ ማሕበራዊ ቀውስ የሚፈጥር እና መንግስታዊ ኢኮኖሚውም ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያመጣ መሆኑን፤ ከጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤትም ሆነ ከክልሉ ፕሬዝደንት ለጉዳዩ መፍትሔ እንዲሰጥ በደብዳቤ የተገለጸ በመሆኑ፤ አመልካቾች ውሳኔ ሳይሰጥባቸው ተከማችተው ያሉ ጉዳዮችን ለመፍታት የነደፉትና የተገበሯቸው አሰራሮች መሆናቸውን በግራ ቀኙ የቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ደግሞ ሆነ ብለው ወይም በቸልተኝነት አንዱን አካል ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ከመነጨ ሀሳብ የተፈጸመ ተግባር ስለመሆኑ አስቀድሞ ተወስዶ የነበረውን የህግ ግምት ጥያቄ ላይ የሚጥል ነው። አመልካቾች በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ መሠረት አድርገው የሠጧቸው ውሳኔያቸው ምንም ይሁን ምን የነበረውን ክፍተት በተገቢው አግባብ ለመድፈን

የተፈጸመ መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ ስራውን የሰሩት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት ነው የሚያስብል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካቾች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስነናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካቾችን በሚመለከት በመ.ቁ 22898 በቀን 10/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝት ውሳኔ እና በቀን 11/01/2010 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 260202 በቀን 04/04/2010 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 278007 በቀን 21/09/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካቾች ከቀረበባቸው ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ ተወስኗል፡፡

ትዕዝዝ

የሚመለከተው ማረሚያ ቤት የስር ፍ/ቤቶች በአመልካቾች ላይ አስተላልፈውት የነበረው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካቾች በነጻ እንዲሰናበቱ የተወሰነ መሆኑን አውቆ አመልካቾችን በዛሬው እለት ከእስር እንዲፈጹ ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡

የፍ/ቤቱ ሬጅስትራር የዚህን ውሳኔ ግልባጭ ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት በአስቸኳይ እንዲልክ ታዟል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የልዩነት ሃሳብ

ስማችን በአራተኛ እና አምስተኛ መስመር ላይ የተጠቀሰው ዳኞች አብላጫው ድምጽ አመልካቾችን ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ለማለት በጠቀሰው ምክንያት እና በደረሰበት ድምዳሜ ያልተስማማን በመሆኑ የልዩነት ሀሳባችንን በሚከተለው መልኩ አስፍረናል፡፡

ከቀረበው ክስ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቾች መጀመሪያ የተከሰሱት በተሰጣቸው የመንግሰት የስራ ኃላፊነት ላይ ሆነው የቀረበላቸውን ጥያቄ በተመለከተ በክሱ ዝርዝር የተጠቀሱን የፌዴራል እና የክልል አዋጅ ደንብ እና መመሪያን መሰረት አድርገው ምላሽ መስጠት ሲገባቸው ይህንን ወደ ጎን በማለት የማይገባቸውን ጥቅም ለራሳቸው ለማግኘት ወይም በሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የተሰጣቸውን

ስልጣን ያለአግባብ በመጠቀም በህግ ያልተመለከተን እና 45% 55% የሚባል አሰራርን በመዘርጋት በህዝብ እና መንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ነው።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካቾች ቃለ ጉባኤ ይዘው ስራ ላይ ያዋሉት 45% 55% የተባለው አሰራር የህግ መሰረት የሌለው መሆኑን ማረጋገጡን ሆኖም ድርጊታቸው ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም ሳይሆን የህግ መሰረት የሌለውን አሰራር በመዘርጋት የመንግስት ስራ በማያመች፣ መንገድ መምራት ወንጀልን ነው በሚል ክስ የቀረበበትን አንቀጽ ቀይሮ እንዲከላከሉ አዟል።

አመልካቾች በመከላከያ ማስረጃቸው 45% 55% የተባለው አሰራር እነርሱ ወደ ኃላፊነት ከመምጣታቸው በፊት የነበረ መሆኑን ከመግለጽ ባለፈ አሰራሩ የህግ ማዕቀፍ ያለው ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ከዚህ አኳያ ያረጋገጡት ነገር የለም። ቀድሞ የነበረ ብልሹ አሰራር በቃለ ጉባኤ እውቅና ሰጥቶ ማስቀጠል ደግሞ የወንጀል ክስ መከላከያ ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ የለም።

አብላጫው ድምፅ አመልካቾችን ጥፋተኛ ከተባሉበት ወንጀል በነፃ ለመልቀቅ በምክንያትነት የጠቀሰው አመልካቾች የመንግስትን ስራ በማያመች መንገድ መርተዋል በሚል ጥፋተኛ ለማለት ቀድሞ ‹‹የሚያመች አሰራር ሊኖር ይገባል›› የሚል ነው። ሆኖም የቀረበው ክስ በራሱ አመልካቾች የሰሩት ስራ ሊመራ እና ምላሽ ሊያገኝ ይገባ የነበረው በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱትን የፌዴራል እና የክልል ህግጋት መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ተገልጿል። ከዚህ በላይ ምን አይነት አሰራር እንደተፈለገ ግልጽ አይደለም። አመልካቾችም ቢሆኑ በቃለ ጉባኤ ያስቀጠሉት ብልሹ አሰራር ከእነርሱ በፊትም የነበረ መሆኑን ከመግለጽ ባለፈ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው የተባሉት የህግ ማዕቀፎች መፍትሄ ለመስጠት አላስቻሉንም የሚል መከራከሪያ አላቀረቡም። ከዚህ አንፃር መከራከሪያ ቀርቦ ቢሆን እንኳን ህግ ክፍተት በህግ አግባብ ስልጣን ባለው አካል ስራን በሚያሳልጥ መልኩ እንዲታረም ከሚደረግ በቀር ‹‹ህጉ አላሰራኝም›› በሚል ሽፋን ህግ በቃለ ጉባኤ ተተክቶ የሚሰራበት አግባብ የለም።

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ህግ ወደ ጎን ትተው የህግ መሰረት የሌለውን አሰራር ስራ ላይ በማዋል የመንግስትን ስራ በማያመች መንገድ መርተዋል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ሊሻር አይገባውም በሚል ከስራ ባልደረቦቻችን በሀሳብ ተለይተናል።

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ፋ/ዘ

የሰ.መ.ቁ 173967

መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሾሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- አቶ አማኑኤል ገ/ጊዮርግስ

ተጠሪዎች፡- የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 07 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ምዕራባዊ ዞን የሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22620 መጋቢት 05 ቀን 2011 ዓ.ም አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠ ውሳኔ ይነሳልኝ በሚል የቀረበን ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ አመልካች የአዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 4/5 ድንጋጌን በመተላለፍ ሕገወጥ ማንቀሳቀሻ በተጭበረበረ ሰነድ መስራት ወንጀል ፈጽሟል በማለት ያቀረባቸውን ስድስት ክሶች የተመለከተው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ምዕራባዊ ዞን የሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ተፈልጎ በአድራሻው ሊገኝ ስላልቻለ በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ስላልቀረበ በሌለበት ጉዳዩን በማየት በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ በማለት በ18 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት ባቀረበው አቤቱታ በሌለበት ታይቶ የተሰጠውን ውሳኔ ያወቀው በቀን 23/05/11 ዓ/ም በሕመም ምክንያት አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ መሆኑን፤ በጊዜ ቀጠሮ ጊዜ ዋስ የሆኗቸው ግለሰብ በሽሬ ከተማ የሚገኙ ቢሆንም አመልካችን እንዲያቀርቡ ያልተጠየቁ መሆኑን፤ በሌሉበት ጉዳያቸው እንዲታይ የተደረገው ከትግራይ ክልል ውጪ ሽፋን በሌለው በመቃልሕ ጋዜጣ

መሆኑን በመግለጽ በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ ተሰርዞ ጉዳያቸው ባሉበት እንዲታይ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ተጠሪ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ካደረገ እና የአመልካችን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ምስክሮቹ አመልካች በሐምሌ ወር 2008 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ሄዶ የታከመ እና ኒሞኒያ የተገኘበት መሆኑን፤ በኋላም እስከ 2009 ዓ/ም ድረስ ቆይቶ ለስራ ወደ ዱባይ የሄደ እና በ2010 ዓ.ም ወደ መቀሌ ተመልሶ እስከ ሚያዝያ ወር ድረስ ይኖር እንደነበር አስረድተዋል፤ ይህንኑ የሚያሳይ የሕክምና ማስረጃም ቀርቧል፤ አመልካች መጀመሪያ ክስ ቀርቦበት በመደበኛ መጥሪያ እንዲቀርብ ፖሊስ በቀጠሮ እንዲቀርብ ያዘዘው መሆኑን ለፍ/ቤቱ በጻፈው ምላሽ አሳውቋል፤ አመልካች የክስ ቻርጅ ደርሶት በመጥሪያ ሳይቀርብ በመቅረቱ ፖሊስ በእስር እንዲያቀርበው ከታዘዘ ጠፍቶ እንደተሸሸገ መረዳት ይቻላል፤ የክፍሉ አስተዳደር ጽ/ቤት አመልካች በአድራሻው እንደሌለ የገለጸ በመሆኑ አመልካች በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለታል፤ አመልካች ባስመዘገበው ቀበሌ እንደሌለ ተረጋግጦ ፍ/ቤቱ በምትክ መጥሪያ አጠራር ስርዓት አመልካችን በሚጠቅም መንገድ የጋዜጣ ጥሪ ያደረገለት እና ያልቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የፈጸመው የስነ ስርዓት ስሕተት የለም በማለት የአመልካች አቤቱታው ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ፖሊስ መጥሪያ ሰጥቸዋለሁ ብሎ ወረቀት ስለጻፈ መጥሪያ ደርሶላል ቢልም ፖሊስ አልነገረኝም፤ አመልካች የፈረምኩበትንም ማስረጃ አላቀረበም፤ ፖሊስ ነግሬዋለሁ ብቻ ማለቱ እንደነገረኝ ማረጋገጫ አይደለም፤ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 125 በግልጽ እንደተደነገገው ተከሳሽ በእስር እንዲቀርብ ትዕዛዝ የሚሰጠው ተከሳሹ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ መጥሪያ እንደደረሰው ማረጋገጫ ከቀረበ በኋላ ነው፤ ፖሊስ በእስር እንዲያቀርበኝ በፍ/ቤት ሲታዘዝ በእስር እያቀረብኩት ነው ብሎ በቀን 3/01/2009 ምላሽ የሰጠ ቢሆንም ይህን ምላሽ የሰጠው አመልካችን ሳይዝ ነው፤ ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች ነግሬለሁ ባለበት ሰዓት አመልካች በሽሬም ከተማ ሆነ በትግራይ ክልል አልነበርኩም፤ አመልካች በወቅቱ አዲስ አበባ ውስጥ እንደነበርኩ ባቀረብኳቸው ማስረጃዎች ያስረዳሁ ቢሆንም የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን ማስረጃ ሳይመዝን አልፎታል፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የአመልካች ማስረጃዎች በአግባቡ ሳይመዝን የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት መጥሪያ ለአሁን አመልካች በቀጥታ መድረሱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ፖሊስ አመልካች ወደ ፍ/ቤት እንዲቀርብ ነግሬዋለሁ በማለት ሪፖርት ማድረጉን መሠረት በማድረግ እና በጋዜጣ መጥሪያ መውጣቱን በቂ አድርጎ በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 125 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር

ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ፖሊስ ለፍ/ቤቱ በሰጠው ምላሽ አመልካች በቀጠሮው ቀን እንዲቀርብ የተነገረው መሆኑን ምላሽ ገልጿል፤ ፍ/ቤቱም አመልካች እንዲቀርብ መጥሪያ ደርሶት ስላልቀረበ ታስሮ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ የክፍሉ አስተዳደር ጽ/ቤት አመልካች ባስመዘገበው አድራሻ እንደሌለ በመግለጽ ምላሽ ልኳል፤ አመልካች በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ሊቀርብ ስላልቻለ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተላልፎበታል፤ ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች እንደነገረው ምላሽ የሰጠ በመሆኑ መልስ የላከ በመሆኑ አመልካች ከፍትሕ ራሱን ደብቆ ተሸሽጎ እንደነበር የሚያመለክት ነው፤ አመልካች በሕክምና ላይ እንደቆየ ለማሳየት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ጉንፋን እና ኒሞንያ በሽታ እንዳለበት ከሚያሳዩ በቀር በጤና ጣቢያው ተኝቶ ታክሟ እንደነበር አያሳዩም፤ አመልካች በትግራይ ክልል ባሉ ሆስፒታሎች ሕክምና ማግኘት ይችል ነበር፤ የአመልካች ምስክሮች ዘመዶቹ በመሆናቸው ገለልተኛ ምስክሮች አይደሉም፤ የስር ፍ/ቤት መጥሪያ አደራረስን አስመልክቶ የፈጸመው የስነ ስርዓት ስሕተት ስለሌለ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች ካቀረበው አቤቱታ እና የስር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ካደረጋቸው ነጥቦች አንጻር የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልገው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ የስር ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለት እና ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበውን አቤቱታ ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች የነገረው መሆኑን አሳውቋል፤ የክፍሉ አስተዳደር አመልካች ባስመዘገበው አድራሻ የሌለ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ ሰጥቷል፤ ፍ/ቤቱ አመልካችን በሚጠቅም መልኩ በምትክ መጥሪያ አደራረስ በመቃልህ ጋዜጣ እንዲጠራ አድርጎ አመልካች ባለመቅረቡ በሌለበት እንዲታይ ማድረጉ የፈጸመው የስነስርዓት ስሕተት የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 161 የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው አንድ ክስ ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠ እንደሆነ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል ዝርዝር፤ ነገሩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሹ ሳይቀርብ ቢቀር በሌለበት የሚፈረድ መሆኑን የሚገልጽ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ወይም ለተከሳሹ የሚደርስ መስሎ ከታየዉ

መጥሪያዉ የሚደርስበትን ሌላ መንገድ ፍርድ ቤቱ ሊያዝ እንደሚችል በዚሁ ሕግ ቁጥር 162 ላይ በግልጽ ተመልክቷል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሚደረግ የጋዜጣ ጥሪም ጉዳዩን አመልካች በሌለበት ለማየት የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ ነው። ይህን ሥርዓት ተከትሎና በዚሁ ሕግ ቁጥር 163(3) መሠረት እንደ ማንኛዉም ደንበኛ ክስ ታይቶ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ በሕጉ ቁጥር 197 እስከ 202 በተመለከቱት ምክንያቶች ፍርዱ ዉድቅ እንዲደረግ ተከሳሹ ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚችል በቁጥር 164 ተመልክቷል። ተከሳሹ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ ተደርጎ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ያቀረበው ማመልከቻ የሚፈቀደው እንዲቀርብ መጥሪያ ያልደረሰዉ እንደ ሆነ ወይም ራሱ ወይም ጠበቃዉ ከዐቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት መቅረብ አለመቻሉን ያስረዳ እንደ ሆነ ነዉ በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 ላይ ተደንግጓል።

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ፖሊስ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለአመልካች የነገረው መሆኑን ለፍ/ቤቱ ያሳወቀ መሆኑን እና የክፍሉ አስተዳደር አመልካች ባስመዘገበው አድራሻ የሌለ መሆኑን በመግለጽ ምላሽ የሰጠ መሆኑን በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ በግልጽ ሰፍሯል። በአመልካች ላይ የቀረበው ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 161 ላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች በሌለበት የሚታይ ከመሆኑ አኳያ ፍ/ቤቱ በቀጣይነት አመልካች በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ትዕዛዝ መስጠቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 162 አግባብ የተሰጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ ፍ/ቤቱ የፈጸመው ስሕተት የለም። ሆኖም ፍ/ቤቱ ለተከሳሽ የጋዜጣ ጥሪ ያስተላለፈው በመቃልህ ጋዜጣ ከመሆኑ አኳያ ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳለት የሚያቀርበው ማመልከቻ ስለሚፈቀድባቸው ምክንያቶች አስመልክቶ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 (ሀ) ላይ "መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ" በማለት ከተቀመጠው መስፈርት እና የተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ ከተጠበቁላቸው መሠረታዊ መብቶች ገር በማገናዘብ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ነው።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20/4 የተከሰሱ ሰዎች ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ሲታይ በችሎት ተገኝተው የቀረበባቸውን ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረበባቸውን ምስክሮችን የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበዉ እንዲሰመላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው። ከዚህ ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ የወንጀል ጉዳዮች ተከሳሽ በተገኘበትና የመከላከል መብቱ በተጠበቀበት ሁኔታ ማካሄድ መርሁ ሲሆን ልዩ ሁኔታው ደግሞ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 161 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት አንድ ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ በተወሰነ ጊዜ በመርሁ የተቀመጠዉን የተከሳሽን የመከራከር መብት ለማረጋገጥ ሲባል ፍርዱ እንደገና ተነስቶ ጉዳዩ እንደገና የሚታይበት ስርዓት በቁጥር 197 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተቀመጠ በመሆኑ በተቻለ መጠን ተከሳሹ በእርግጠኝነት መጥሪያ ደርሶት በችሎት የመገኘትና የመከራከር መብቱን አዉቆ መተዉ እስካልተረጋገጠ ድረስ ይህ መብቱ ሊነፈግ አይገባም። በመሆኑም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 (ሀ) ላይ "መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ" በሚል የተቀመጠውን መስፈርት መሠረት በማድረግ ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ ባመለከተ ጊዜ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ ተከሳሹ የፍ/ቤቱን

መጥሪያ ሰምቶ ያልቀረበ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሲሆን ፍ/ቤቱም ይህንን የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት፡፡

ስለሆነም ከላይ ከተገለጹት ድንጋጌዎች እና ምክንያቶች አንጻር የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 199(ሀ) ተከሳሹ በትክክል መጥሪያ ደርሶት የመከራከር መብቱን አውቆ በመተዉ መቅረቱ አሻሚ ባልሆነ መልኩ ዐ/ሕግ በሚያቀርበዉ በቂ ማስረጃ ካልተረጋገጠ በቀር ማወቅ ነበረበት ወይም ሊያዉቅ ይችላል የሚል ግምት በመዉሰድ ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበዉ ማመልከቻ ዉድቅ ሊደረግ አይገባም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገዉ አመልካች በአገር ዉስጥ አለመኖሩ ተረጋግጦ በምትክ መጥሪያ አጠራር ስርዓት በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ያልቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ የፈጸመው የስነስርዓት ስሕተት የለም በሚል ነዉ፡፡ ሆኖም አመልካች ጥሪ የተደረገለት በክልሉ ብቻ ተደራሽ በሆነው መቃልህ ጋዜጣ እንጂ ሐገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ አይደለም፤ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ክርክርም ለአመልካች ጥሪ የተላለፈበት መቃልህ ጋዜጣ ሐገር ዓቀፍ ስርጭት ያለው ስለመሆኑ አላረጋገጠም፤ ይልቁንስ አመልካች ባቀረባቸው ማስረጃዎች በጤና ችግር ምክንያት ከክልሉ ውጪ እንደነበር በኋላም በስራ ምክንያት ከኢትዮጲያ ውጪ እንደነበር አስረድቷል፡፡ አንድ ተከሳሽ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ክስ የቀረበበት ስለመሆኑ አውቋል የሚል ግምት ሊወሰድ የሚገባው ሐገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ጥሪ የተደነገለት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ እንጂ በክልሉ ብቻ ተደራሽ በሆነው ጋዜጣ ብቻ ጥሪ መደረጉ ተከሳሹ ክስ እንደቀረበበት አውቋል የሚል ግምት የሚያስወስድ አይደለም፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 162 ተከሳሹ በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችልበትን ቅድመ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ሐገራዊ ስርጭት በሌለው መቃልህ ጋዜጣ ለአመልካች ጥሪ ማስተላለፉን ለአመልካች መጥሪያ እንደደረሰው ማረጋገጫ አድርጎ በመውሰድ እና መጥሪያ ደርሶታል የሚል ግምት በመውሰድ አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 199(ሀ) ድንጋጌ ይዘትና በሕገመንግስቱ ለተከሰሱ ሰዎች የተጠበቁላቸውን መሠረታዊ መብቶች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ምዕራብ ዞን የሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 22620 መጋቢት 15 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና መጋቢት 19 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም መጋቢት 05 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የስር ፍ/ቤት አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ ያቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት ክርክሩ አመልካች ባለበት ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ በማለት ወስነናል፡፡
3. የሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ አመልካች ባለበት ክርክሩን ቀጥሎ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ

የሰ/መ/ቁ. 182266

ጥቅምት 19 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ሃይሉ ነጋሽ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዷለም

አመልካች፡- የደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓ/ሕግ የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪዎች፡- አሸብር ዳጌታ ሄሎ(42 ሰዎች)

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 06 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 178178 ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ተጠሪዎች በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰን ሰው ዋስትና በሚመለከት የቀረበ ክርክር ነው፡፡ የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ ተጠሪዎች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ፤ 35 እና 239 ድንጋጌን በመተላለፍ ሕዳር 20 ቀን 2011 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 3፡30 እስከ ቀኑ 9፡00 ሰዓት በደቡብ ክልል በቀድሞ ጋሞ ጎፋ ዞን በሳውላ ከተማ አዲሱን የዞን ምስረታ ማብሰሪያ እና ቀደም ሲል ከተለያዩ አመራር እና ከአካባቢ ማሕበረሰብ ጋር የተፈጠረውን ቅሬታ ለመፍታት እንዲሁም በአካባቢው ሰላም እና ቀጣይ ልማት ዙሪያ ውይይት ለማድረግ የክልሉ ደ.ኢ.ህ.ዴን ጽ/ቤት ባስቀመጠው አቅጣጫ እና በተያዘው ፕሮግራም መሠረት በሳውሎ ከተማ ሚልንየም አዳራሽ በተዘጋጀው ስብሰባ የተለያዩ የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ የፓርላማ አባላት፣ የክልል ቢሮ ሀላፊዎች የዞን አመራሮች እንዲሁም የተለያዩ ምሁራን እና ግለሰቦች ተጋብዘው በተጠቀሰው ቀን በስብሰባ ቦታ ሁሉም ተሰብሳቢዎች በተገኙበት፣ እኛ ባልተገኘንበት ስብሰባ አይደረግም፤

ከተሳታፊ ባለስልጣናት የምንፈልጋቸው ሰዎች አሉ በማለት ከጸጥታ ሀይል ቁጥጥር ውጪ በመሆን ወደ ስብሰባ አዳራሽ በመግባት ስብሰባውን በመበተን ተሳታፊዎችን ከስብሰባ አዳራሽ እንዲወጡ አድርገዋል፤ የተሸከርካሪ እንቅስቃሴ እንዳይደረግ መንገድ ዘግተዋል፤ በጸጥታ ሀይሎች ላይ ድንጋይ በመወርወር መከላከል እንዳያደርጉ በማድረግ መኪኖችን ሰበረዋል፣ ሱቆችን ሰብረው ዘርፈዋል፤ ንግድ ቤቶች እና የመንግስት መስሪያቤቶች እንዲዘጉ አድርገዋል፤የተፈጠረው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳያስከትል ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት እንዲያልፍ በአምስት ሰዎች ላይ ደግሞ የአካል ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት ስለሆኑ በሕብረት በፈጸሙት ሕገመንግስታዊ ስልጣንን ማሰናከል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች ክሱ ከተነበበላቸው በኋላ የተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ከአስራ አምስት አመት በማይበልጥ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና የሰው ሕይወት ያለፈው በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63(1)መሠረት የዋስትና መብታቸውን የሚያስከለክል ምክንያት የሌለ መሆኑን፤ ምናልባት ፤ ቋሚ አድራሻ ያላቸው እና የቤተሰብ ሀላፊዎች በመሆናቸው ጥቂቶቹ ደግሞ ተማሪዎች በመሆናቸው፤ ምስክሮች ታባብላላችሁ እንዳይባሉ ምስክሮች የፖሊስ አባላት በመሆናቸው እና ከመካከላቸው በዋስትና የተለቀቁ ሰዎች መኖራቸው የተከሰሱበት ሕግ ዋስትና የማያስከልከል መሆኑ አመላካች መሆኑን በመግለጽ በዋስ ሆነው እንዲከራሩ ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ተጠሪዎች ባቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ላይ በሰጠው አስተያያት ተጠሪዎች የተከሰሱበት የህግ አንቀጽ እስከ አስራ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና በተከሳሾች ቀጥታ ድርጊት ባይሆንም የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈበት ጉዳይ ስለሆነ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63(1) መሠረት ሊከለከሉ ይገባል፤ ፍ/ቤቱ ይህንን በበቂ ምክንያት የሚያልፈው ቢሆን ተከሳሾች ቢለቀቁ ቀጠሮ አክብረው ሊቀርቡ የማይችሉ በመሆኑ፤ በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ተቋሙን ሲረብሹ የነበሩ እና በጊዜ ቀጠሮም ፍ/ቤት ሲመላለሱ የሳውላ ከተማ ፖሊሶች ላይ ሲዝቱ ስለነበር በዋስትና ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ስለሚችሉ እና ምስክሮች ላይ ተጽእኖ ሊያደርሱ ስለሚችሉ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የተጠሪዎችን የዋስትና ጥያቄ እና አመልካች በጉዳዩ ላይ የሰጠውን አስተያየት ከመረመረ በኋላ ተጠሪዎች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 239 ድንጋጌ የተከሰሱ ሲሆን የፈጠሩት ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳያስከትል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት ማለፍ መንስኤ መሆኑን የሚያሳይ እና ድንጋጌው እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ሊያስቀጣ የሚችል በመሆኑ ያቀረቡት የዋስትና መብት ጥያቄ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63(1)መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

ተጠሪዎች ይህንን ብይን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪዎች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 239 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ 15 ዓመት ሊቀጡ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል፤ ወንጀል የተፈጸመበት ሰው የሞተ እንደሆነ ከሚለው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መመዘኛ ሲታይ በተጠሪዎች በተፈጸመው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳይመጣ ለማስቆም በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደ እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ በመሆኑ ተጠሪዎች በሕይወት ማለፍ ቀጥተኛ በሆነ የግድያ ወንጀል ተጠያቂ አይደሉም፤ በሞቱት ሰዎች ላይ ሀላፊነት የሌለባቸው እና ተጠያቂነታቸው የሕገመንግስታዊ ስልጣንን ተግባራዊነት ማሰናካል ከሆነ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 በተጠሪዎች ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው አይደለም፤ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 አኳያ በተጠሪዎች ላይ ሌላ የዋስትና መከላከያ ምክንያት በዓ/ህግ እስካልቀረበ ድረስ የተከሰሱበት ክስ የዋስትና መብት ይከለክላል መባሉ አግባብ አይደለም በማለት ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ለብር 20,000 የዋስትና ግዴታ በመግባት ጉዳያቸውን በውጪ ሆነው እንዲከታተሉ ሲል ወስኗል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም ተጠሪዎች በፈጸሙት የሕገመንግስታዊ ስርዓት ተግባራዊነት ማሰናከል ወንጀል ለማስቆም ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት አልፏል፤ ተጠሪዎች ራሳቸው በቀጥታ ሟቾችን ባይገድሉም ተጠሪዎች ሁከት እና ብጥብጥ ባይፈጥሩ ኖሮ የሰው ሕይወት አያልፍም ነበር፤ ተጠሪዎች በፈጸሙት ድርጊት ምክንያት የሰው ሕይወት ያለፈ በመሆኑ በወ/ሕ/ቁ 24/1 መሠረት በምክንያት እና ውጤት መካከል ግንኙነት አለ፤ ተጠሪዎች አስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል የተከሰሱ በመሆናቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት የዋስትና መብታቸው ሊከለከል ይገባል፤ ይህ ቢታለፍ እንኳን አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/(ሀ)(ለ)(ሐ) መሠረት ተገቢ ምክንያት በመስጠት የተከሳሾች የዋስትና መብት ሊነፈግ ይገባል በማለት መቃወሚያ አቅርቦ ሳለ የስር ፍ/ቤት አይቶ መወሰን ሲገባው ማለፉ አግባብ አይደለም፤ ተጠሪዎች በዋስትና ቢለቀቁ በአካባቢያቸው በከፍተኛ ሁኔታ ሰላም እና መረጋጋትን ወደ ማይመለስ ቀውስ ውሥጥ ሊያስገቡ የሚችሉ የተደረጀ ቡድን በመሆናቸው የስር ፍ/ቤት ወሳኔ ተሸሮ ማረሚያ ሆነው ጉዳያቸውን ሊከታተሉ ይገባል የሚል ነው። አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ እንደሚገባው ስለታመነበት ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለዚህ ሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል። እንደመረመርነው በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘው ነጥብ፤አመልካች በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች

የቀረበውን የዋስትና ጥያቄ በመቃወም የተከራከረው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 እና 63 መሠረት በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤቱ አንቀጽ 63ን መሠረት በማድረግ የተጠሪዎችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 በተከሳሾች ላይ ተፈጻሚነት የለውም በተጠቃሹ ሕግ አንቀጽ 67 መሠረት ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተከሰሱበት ድንጋጌ የዋስትና መብት አያስከለክልም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የወሰነበትን አግባብነት ከተጠቀሱት የስነ-ስርዓት ድንጋጌዎች እና ከመሠረታዊ የክርክር አመራር ሥነ-ሥርዓት ጋር በማገናዘብ ለመጣራት በሚል ነው።

በመሠረቱ የዋስትና መብት በሕገ መንግስት ጥበቃ ከተደረጉት የተያዙ ሰዎች መሠረታዊ መብቶች አንዱ ነው። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6/ ስር የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው መሠረታዊ መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋሰትና መረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ይኸው የሕገ መንግስቱ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል። በመሆኑም የዋስትና መብት መሠረታዊ የሆነ ሕገ መንግስትዊ መብት ቢሆንም ፍጹም መብት ሳይሆን በሕጉ አግባብ ሊነፈግ የሚችል ነው። ስለሆነም የዋስትናው ጥያቄ ተቀባይነት አለው ወይም የለውም የሚለው ላይ ውሳኔ የሚሰጠው ፍርድ ቤት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ረገድ አግባብነት ያለውን ልዩ ሕግ መሠረት አድርጎ ጉዳዩን ሊመዝነውና ተገቢውን ውሳኔ ሊልሰጥ እንደሚገባ ግልጽ ነው።

በያዝነው ጉዳይ በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች የቀረበውን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 "ን" መሠረት በማድረግ የተጠሪዎችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 በተከሳሾች ላይ ተፈጻሚነት የለውም በተጠቃሹ ሕግ አንቀጽ 67 መሠረት ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተከሰሱበት ድንጋጌ የዋስትና መብት አያስከለክልም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል።በስር ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች ፈጽመውታል የተባለው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 239 ድንጋጌን በመተላለፍ የሕገመንግስታዊ ሥልጣንን ተግባራዊነት ማሰናከል ወንጀል ምክንያት በተፈጠረው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳይመጣ ለማስቆም ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት ማለፉ የሚመለከት ነው።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች ዋስትና መብት እንዲከበርላቸው ውሳኔ የሰጠው የቀረበው ክስ የዋስትና መብት የማያስከለክል በመሆኑና በተፈጠረው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳይመጣ ለማስቆም ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት ማለፉ ተጠሪዎችን ቀጥተኛ በሆነ የግድያ ወንጀል

የማያስጠይቃቸው በመሆኑ የወ/መ//ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 በተጠሪዎች ላይ ተፈጻሚነት የለውም በማለት ነው።።

በመሰረቱ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው ማንኛውም የተያዘ ሰው የተከሰሰበት ወንጀል የሞት ቅጣትን ወይም አሥራ አምሥት ዓመት ወይም በላይ በሆነ ጽኑ እስራት የማያስቀጣው ከሆነና ወንጀል የተፈጸመበት ሰው በደረሰበት ጉዳት የማይሞት የሆነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ለመልቀቅ ይችላል በማለት ይደነግጋል ። ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ተከሳሹ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ በሞት ወይም ከ15 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ እና ጉዳት የደረሰበት ሰው የሞተ እንደሆነ በዋስትና መልቀቅ የማይቻል መሆኑን ፤ሆኖም ተከሳሹ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ በሞት ወይም ከ15 ዓመት እና በላይ የማያስቀጣ እና ጉዳት የደረሰበት ሰው ያልሞተ እንደሆነ ተከሳሹን በዋስትና መልቀቅ የሚቻል መሆኑን ነው።።

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች የተከሰሰበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 239 ድንጋጌን በመተላለፍ ሆኖ ድንጋጌው እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣ ቢሆንም በተጠሪዎች ተግባር የሞተ ሰው ስሌለ እና ሞቱ የተባሉት ሁለት ሰዎች በሌላ አካል በተወሰደ እርምጃ መሞታቸው የተረጋገጠ መሆኑ በዚሁ ጉዳይም በተጠሪዎች ላይ ክስ ያልቀረበና በዓ/ህግ በኩል ያልተገለፀ በመሆኑ፣ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 63/1 የተመለከቱት ተከሳሹ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ በሞት ወይም ከ15 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ እና ጉዳት የደረሰበት ሰው የሞተ እንደሆነ የሚሉት ቅድመ ሁኔታዎች አልተሟሉም። በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 ላይ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች አልተሟሉም በማለት ከድምዳሜ ላይ መድረሱ በአግባቡ ነው ብለናል። በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 171880 በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2 መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሰጠው የህግ ትርጉም ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት እንዳለው ተመልክተናል።

አመልካች የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክር በተመለከተ ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ላይ ክርክር ያልቀረበበት መሆኑ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ በማስቀረብ ያረጋገጥን በመሆኑ ፍርድቤቱ "በወ/መ/ሥ/ሥ/ግ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መከልከያ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ" በማለት የገለፀው ሲታይ አመልካች በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ባልተከራከረበት ጉዳይ የተጠሪዎች የዋስትና መብት ለመከልከል የቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም ስለሆነም የስር ፍ/ቤቱ የተጠሪዎችን የዋስትና መብት እንዲከበርላቸው እና ተጠሪዎች በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ብለናል።

በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19/6/ እና በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 63 እና 67 መሠረት በማድረግ የሰጠው ብይን ሕጉ የሰጠውን ሥልጣን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር በህግ አተረጓጐምና አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም መሠረት በአብላጫ ድምፅ ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1/ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 178178 በቀን 30/11/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 75/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2 / ነሃሴ 10 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሰጠ የእግድ ትእዛዝ ተጠሪዎች በነበሩበት ማረምያ ቤትሆነው ጉዳያቸው እንዲከታተሉ ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደመዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

ቤ/ፍ የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የልዩነት ሀሳብ

ስሜ በተ.ቁ 1 ላይ የተገለጸው ዳኛ አብላጫው ድምጽ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካቾች የተከሰሱበት ወንጀል በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት ዋስትናን አያስከለክልም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል የደረሰበት መደምደሚያ እኔም የምስማማበት ነው፡፡ ሆኖም የተጠሪዎች መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት ክርክር ያልቀረበበት መሆኑ የጠቅላይ ፍ/ቤቱን መዝገብ በማስቀረብ ያረጋገጥን ስለሆነ አመልካች በስር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ባልተከራከረበት ጉዳይ የዋስትና መብትን ለመከልከል የቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ሲል በደረሰበት መደሚደሚያ በሐሳብ ስለተለየሁ የሀሳብ ልዩነቴን እንደሚከተለው አስፍራለሁ፡፡

ዓቃቤ ሕግ በአሁን ተጠሪዎች ላይ ክስ ያቀረበው ተጠሪዎች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ ጉ 32/1/ሀ፤ 35 እና 239 ድንጋጌን በመተላለፍ ሁከት እና ብጥብጥ በመፍጠር የሕገ መንግስታዊ ስልጣንን ተግባራዊነት ማሰናከል ወንጀል ፈጽመዋል፤ ተከሳሾች የፈጠሩት ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳያስከትል ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ የሁለት ሰዎች ሕይወት አልፏል በሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ የተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ከአስራ አምስት አመት በማይበልጥ እስራት የማያስቀጣ በመሆኑ እና የሰው ሕይወት ያለፈው በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው

እርምጃ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት የዋስትና መብታቸውን የሚያስከለክል ምክንያት የሌለ መሆኑን፤ ቋሚ አድራሻ ያላቸው እና የቤተሰብ ሀላፊዎች መሆናቸው፤ ጥቂቶቹ ደግሞ ተማሪዎች መሆናቸው፤ ምስክሮች ታባብላላችሁ እንዳይባሉ ምስክሮች የፖሊስ አባላት በመሆናቸው እና ከመካከላቸውም በዋስትና የተለቀቁ ሰዎች መኖራቸውን በመግለጽ በዋስ ሆነው እንዲከራከሩ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ተጠሪዎች ባቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ላይ በሰጠው አስተያያት ተጠሪዎች የተከሰሱበት የህግ አንቀጽ እስከ አስራ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና በተከሳሾች ቀጥታ ድርጊት ባይሆንም የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት ሊከለከሉ ይገባል በማለት አስተያየት የሰጠ ሲሆን ፍ/ቤቱ ይህን በበቂ ምክንያት የሚያልፈው ቢሆን ተከሳሾች ቢለቀቁ ቀጠሮ አክብረው ሊቀርቡ የማይችሉ በመሆኑ፤ በማረሚያ ቆይታቸው ተቋሙን ሲረብሹ የነበሩ እና በጊዜ ቀጠሮም ፖሊሶች ላይ ሲዝቱ ስለነበር በዋስትና ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ስለሚችሉ እና ምስክሮች ላይ ተጽእኖ ሊያደርሱ ስለሚችሉ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት አስተያየት የሰጠ መሆኑን የስር ውሳኔ በግልጽ ያሳያል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሾች በፈጸሙት የሕገ መንግስታዊ ስልጣን ተግባራዊነት ማሰናከል ወንጀል ምክንያት የተፈጠረው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳያመጣ ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ ምክንያት የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ በመሆኑ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ያደረገው በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ ዋስትናውን ለማስከልከል የሚያስችሉ በቂ ሁኔታዎች አሉ በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ያቀረባቸውን ምክንያቶች አልመረመረም፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ተጠሪዎች በፈጸሙት ሁከት እና ብጥብጥ ምክንያት የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ ቢሆንም ተጠሪዎችን ቀጥተኛ በሆነ የግድያ ወንጀል ተጠያቂ የማያደርጋቸው በመሆኑ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 በተጠሪዎች ላይ ተፈጻሚነት የለውም ካለ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መከልከያ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተጠሪዎች የዋስትና መብት ሊነፈግ አይገባም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ መሆኑ የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡

ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ የተጠሪዎችን የዋስትና መብት የተቃወመው በአንድ በኩል የተጠሪዎች የዋስትና መብት በሕግ የተከለከለ ነው በማለት ሲሆን ይህ የሚታለፍ ከሆነም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት የተጠሪዎችን የዋስትና መብት ሊያስከለክል የሚችል ሁኔታ አለ በማለት እንደሆነ የስር ውሳኔ ይዘት የሚያመለክት በመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 አኳያ የዋስትና መከልከያ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተከሰሱበት ክስ

የዋስትና መብት ይከለክላል መባሉ አግባብ አይደለም በማለት የሰጠው ወሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ዋስትናን አስመልክቶ አግባብነት ካላቸው ሕጎች እና ፍ/ቤቶች ክርክርን በመምራት ረገድ ሊኖራቸው ከሚገባው ተግባር እና ሀላፊነት ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል።

በመሠረቱ የተያዙ ሰዎች በሕገ-መንግስቱ ጥበቃ ከተደረጉላቸው መብቶች አንዱ የዋስትና መብት ነው። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6 የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው መሠረታዊ መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል። በሕገ-መንግስቱ ልዩ ጥበቃ የተሰጠው ይህ መብት መሠረታዊ ዓላማውም ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኝነቱ ሳይረጋገጥበት በእስር እንዳይቆይ ማድረግ ነው። በመሆኑም የዋስትና መብት መርህ መፍቀድ ሲሆን ልዩ ሁኔታው ደግሞ መከልከል ነው።

ይህን መሠረታዊ መብት አስመልክቶ የመወሰን ስልጣን እና ሃለፊነት የተሰጣቸው ፍ/ቤቶችም በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው የሚያቀርበውን የዋስትና መብት ጥያቄ እና ከሣሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግም በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን አስተያየት ከሕገ መንግስቱ መሠረታዊ ዓላማ እና ዋስትናን አስመልክቶ በልዩ ሕጎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ መርምረው ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ይህንኑ ተግባራዊ ሲያደርጉም በመርህ ደረጃ የዋስትናን መብት መፍቀድ ያለባቸው ሲሆን በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ግን የዋስትናን መብት በልዩ ሁኔታ ሊነፍጉ ይችላሉ። እነዚህም ምክንያቶች አንደኛው ተከሳሽ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስትና ለመለቀቅ የሚከለክል ሲሆን በወ/መ//ሥ/ሥ/ሕቁ 63 የሕግ ክልከላን መሠረት በማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ተከሳሹ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስ መለቀቅን የማይከለክል ቢሆንም ተጠርጣሪው ቢለቀቅ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 የተገለፁትን ተግባራት ይፈጽማል ተብሎ ሲታመን ነው።

ፍ/ቤቶች ተከሳሹ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል የዋስትናን መብት የሚያስከለክል ሆኖ ባገኙት ጊዜ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1ን መሠረት በማድረግ የተከሳሹን የዋስትና መብት ከከለከሉ / ከነፈጉ / ከመነሻውም ቢሆን የተከሳሹ የዋስትና መብት የተከለከለው በሕግ በመሆኑ ዋስትናን ሊያስከለክሉ ይችላሉ ተብለው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች መመርምር እና መመዘን አይጠበቅባቸውም። ሆኖም ተከሳሽ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል ዋስትናን የማያስከለክል ከሆነ እና ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 ላይ የተመለከተቱትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ የተከሳሹን የዋስትና መብት ጥያቄ ተቃውሞት ከሆነ ግን ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የተከሳሽን የዋስትና መብት ለማስከልከል የቀረቡት ምክንያቶች ዋስትናውን ለማስከልከል የሚያስችሉ በቂ እና ሕጋዊ ምክንያቶች መሆን አለመሆናቸውን መርምሮ እና መዝኖ ውሳኔ ሊያሳርፍበት ይገባል።

እንግዲህ የዋስትናን መብት ለመፍቀድ ወይም ለመንፈግ / ለመከልከል / የሚያስችሉ መሠረታዊ ድንጋጌዎች ከላይ የተመለከቱት ሲሆኑ እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ጥያቄው መቅረብ ያለበት ለየትኛው ፍ/ቤት ነው? ዋስትናው ሊፈቀድ ይገባል ወይም አይገባም የሚለውን ውሳኔ መስጠት የሚችለውስ የትኛው ፍ/ቤት ነው? ዋስትናውን በመፍቀድ ወይም በመከልከል የተሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ የሚቀርበውን ይግባኝ የሚመረምረው ፍ/ቤት ስልጣን እና ተግባሩ ምንድነው? የሚሉት ነጥቦች በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለባቸው መሠረታዊ ነጥቦች ነው፡፡

የተያዘው ሰው በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ በማናቸውም ጊዜ መጠየቅ የሚችል መሆኑን፤ የሚቀርበውንም ማመልከቻ ማናቸውም ፍ/ቤት መፍቀድ የሚችል መሆኑን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 64 እና 65 ድንጋጌዎች ያስገነዝቡናል፡፡ የዋስትና መብት በማናቸውም ፍ/ቤት ሊጠየቅ እስከቻለ ድረስ እና ዋስትናን ሊፈቀድ ወይም ሊነፈግ ስለሚችልባቸው ሁኔታዎች አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 እና 67 ላይ የተደነገጉት ድንጋጌዎችም የሕግ ክርክሮች በመሆናቸው ጉዳዩን በቀጥታ በሚያየው ፍ/ቤት የቀረቡ መሆናቸው እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ በይግባኝ ደረጃ ክርክር አልቀረበባቸውም ተብሎ የሚታለፉ ሳይሆኑ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በአግባቡ ተመርምረው ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚገባ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተከሳሾች ላቀረቡት የዋስትና መብት ጥያቄ ዓቃቤሕግ በሰጠው አስተያየት ተጠሪዎች የተከሰሱበት የህግ አንቀጽ እስከ አስራ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እና በተከሳሾች ቀጥታ ድርጊት ባይሆንም የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 መሠረት ሊከለከሉ ይገባል በማለት አስተያየት የሰጠ ሲሆን ፍ/ቤቱ ይህን በበቂ ምክንያት የሚያልፈው ቢሆን ተከሳሾች ቢለቀቁ ቀጠሮ አክብረው ሊቀርቡ የማይችሉ በመሆኑ፤ በማረሚያ ቆይታቸው ተቋሙን ሲረብሹ የነበሩ እና በጊዜ ቀጠሮም ፍ/ቤት ፖሊሶች ላይ ሲዝቱ ስለነበር በዋስትና ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ስለሚችሉ እና ምስክሮች ላይ ተጽእኖ ሊያደርሱ ስለሚችሉ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት በግልጽ ተቃውሞታል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሾች በፈጸሙት የሕገ መንግስታዊ ስልጣን ተግባራዊነት ማሰናከል ወንጀል ምክንያት የተፈጠረው ሁከት እና ብጥብጥ የከፋ ውጤት እንዳያመጣ ሲባል በጸጥታ ሀይሎች በተወሰደው እርምጃ ምክንያት የሁለት ሰዎች ሕይወት ያለፈ በመሆኑ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 መሠረት ሊፈቀድ አይገባም በማለት ውድቅ ያደረገው በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ ዋስትናውን ለማስከልከል የሚያስችሉ በቂ ሁኔታዎች አሉ በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ያቀረባቸውን ምክንያቶች አልመረመረም፡፡ ከሣሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግም የተጠሪዎች የዋስትና መብት በሕግ የተከለከለ ነው በማለት የተወሰነ በመሆኑ እና በውሳኔው ውጤትም ተጠቃሚ በመሆኑ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ አልጠየቀበትም፡፡

ተጠሪዎች የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት በዋስትናው ላይ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡትም የስር ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 መሠረት የዋስትና መብታችንን መከልከሉ አግባብ አይደለም በሚል ሲሆን ዓቃቤ ሕጉ ምላሽ የሰጠውም ይህንኑ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63/1 በተከሳሾች ላይ ተፈጻሚ አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ ሲሆን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መከልከያ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተጠሪዎች የዋስትና መብት ሊነፈግ አይገባም በማለት የተጠሪዎች የዋስትና መብት ሊነፈግ አይገባም በሚል ወስኗል፡፡ የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ መሠረት በማድረግ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ዓቃቤ ሕግ በስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተከሳሾች ቢለቀቁ ቀጠሮ አክብረው ሊቀርቡ የማይችሉ በመሆኑ፤ በማረሚያ ቆይታቸው ተቋሙን ሲረብሹ የነበሩ እና በጊዜ ቀጠሮም ፖሊሶች ላይ ሲዝቱ ስለነበር በዋስትና ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ ስለሚችሉ እና ምስክሮች ላይ ተጽእኖ ሊያደርሱ ስለሚችሉ የተከሳሾች የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ሊከለከል ይገባል በማለት የጠየቀ መሆኑ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ወሳኔ በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ ሳለ ይህንኑ ምክንያት መርምሮ ራሱ ውሳኔ ሊሰጥበት ወይም ጉዳዩን ለስር ከፍተኛው ፍ/ቤት በመመለስ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ምክንያቶቹ ዋስትናን ለማስከልከል የሚያስችሉ በቂ እና አሳማኝ ምክንያቶች መሆናቸውን መርምሮ እና መዝኖ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ሲገባው ዓቃቤ ሕግ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 (ሀ)(ለ)እና(ሐ) መሠረት ለስር ከፍተኛው ፍ/ቤቱ ያቀረባቸው ምክንያቶች ከመነሻውም እንዳልቀረቡ በመቁጠር በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መከልከያ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ የተጠሪዎች የዋስትና መብት ሊነፈግ አይገባም በማለት የተጠሪዎችን የዋስትና መብት በመንፈግ የሰጠው ውሳኔ ዋስትናን አስመልክቶ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና ፍ/ቤቶች ክርክርን በመምራት ረገድ ሊከተሉት የሚገባውን የክርክር አመራር ስርዓት ያላገናዘበ በመሆኑ አብላጫው ድምጽ በዚህ ረገድ የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል በደረሰበት መደምደሚያ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

ቤ/ፍ የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ.163947

ሐምሌ 15 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች:- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ጌታቸው ዋለልኝ

2. አቶ ብሩክ አስፋው ወሰን

3. አቶ ፍስሐ ጸጋዬ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መስከረም 22 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 209610 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ብይን በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 156419 ሐምሌ 12 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ በሙስና ወንጀል ተከሶ የነበረን ሰው ምስክር ስለማድረግ በሚመለከት የቀረበ የማስረጃን ተቀባይነት (Admissibility) ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪዎች ላይ በስር ፍ/ቤት አቅርቦባቸው የነበሩት ክሶች ሶስት ሲሆኑ ይዘታቸውም፡- 1ኛ ክስ፡- ተጠሪዎች የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32/2 ድንጋጌን በመተላለፍ 1ኛ ተጠሪ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ሠራተኛነቱን በመጠቀም ለሀገራዊ ስራ ነው በሚል ሙሉጌታ ተመስገን እና ኑርሁሴን ጠይብ የተባሉ ሰዎችን በመመልመል በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አማካኝነት ሀሰተኛ የሆኑ የኢምባሲ

መታወቂያዎች እና ሌሎች ሰነዶችን በማዘጋጀት የማይገባ ብልጽግና ለማግኘት ከባድ የአታላይነት ወንጀል ፈጽመዋል፡፡ በ2ኛ ክስ የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23/2/ ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለጸው ሁኔታ ሀሰተኛ ሰነድ እንዲዘጋጅ ካደረጉ በኋላ በሀሰተኛ ስም ከየመን እና ከአንጎላ ኤምባሲ ዕቃዎች ፍተሻ ሳይከናወንባቸው እና ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር እንዲገቡ እና ለነጋዴ እንዲከፋፈሉ በማድረግ በወንጀል ድርጊት እና በተገኘው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ያልተገባ የገንዘብ ጥቅም በማግኘት በግብረአበርነት በፈጸሙት ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ 3ኛ ክስ 1ኛ ተጠሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 166/1 ድንጋጌን በመተላለፍ በጉምሩክ ወንጀል የተጠረጠረን ዕቃ በማጓጓዝ ላይ የነበረን ተሸከርካሪ ፍተሻ እንዳይደረግበት እና እንዲያመልጥ በማድረግ ሀሰተኛ መረጃ ለጉምሩክ ኢንተልጀንስ ሠራተኞች በመስጠት የጉምሩክ ቁጥጥርን የማሰናከል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ክሱ ለተጠሪዎች ተነቦላቸው ተጠሪዎች መቃወሚያ በማቅረባቸው ዐቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥበት በማድረግ ብይን ለመስጠት በተያዘው ቀነ-ቀጠሮ ዓቃቤ ሕግ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው አቤቱታ 1ኛ እና 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን ተከሳሽ አድርጎ ለማቅረብ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ ደግሞ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 122/1 መሠረት በማንሳት ምስክር ለማድረግ እንዲፈቀድለት ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው አቤቱታ ላይ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ካደረገ በኋላ ዓቃቤ ሕግ በክሱ ማስረጃ ዝርዝር በተ.ቁ 1 እና 2 ላይ የተመለከቱትን ምስክሮች በተከሳሽነት አካቶ ለማቅረብ ያቀረበው ጥያቄ ተገቢ በመሆኑ በዚህ ረገድ ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ተፈቅዶለታል፤ ሆኖም 2ኛ ተጠሪን ከተከሳሽነት ሰርዞ ምስክር አድርጎ ለማቅረብ የጠየቀውን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 እና የአዋጅ ቁጥር 882/2007 እና 434/97 አንቀጽ 43 ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለው መሠረት ግብረአበርን ከክሱ ነጻ በማድረግ በምስክርነት አካቶ የመቅረብ መብት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ጉዳዩ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈጸመው ድርጊት እና ስለተባባሪዎቹ ሚና ግለሰብ ጠቃሚ ማስረጃ ከሰጠ ሲሆን ከዚህ ድንጋጌ ግለሰብ የሚጠቀመው ለክርክሩ አመራር ጠቃሚ ማስረጃ ከሰጠ እና የምርመራውን መንገድ መምራቱ ከተረጋገጠ ሲሆን በዚህ ደረጃ የሚሰጠው መረጃም ምስክሩ በገለልተኝነት ፍትሕን የመረዳቱን ሚና እንዲጫወት የሚረዳው ሲሆን ግለሰቡ በተከሳሽነት ከተካተተ በኋላ ያውም ክሱ ተሰምቶ አጠቃላይ የክርክሩን ሂደት በተረዳ እና ተከሳሽ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመታሰሩ ምክንያት የሚያገኘውን መረጃ እና የቀሪ ተከሳሾችን የክርክር አመራር ከተረዳ በኋላ ወደ ምስክርነት እንዲቀየር መፍቀዱ የክርክሩን ሚዛናው አሰራር የሚጎዳ የተከሳሾችን የመከላከል ሕገ መንግስታዊ መብት የሚሸረሽር በመሆኑ የዓቃቤ ሕግ ጥያቄ በቀጥታ የሙስና አዋጁን ልዩ የስነ-ስርዓት የማስረጃ ሕጉን መሠረት ያላደረገ ቢሆንም ጥያቄው ሊመዘን የሚገባው ችሎቱ በዋነኝነት ከሚመራበት ለጉዳዩ የበለጠ አግባብነት ካለው ከአዋጅ

ቁጥር 882/2007 አንጻር ሊሆን ስለሚገባ ዓቃቤ ሕግ 2ኛ ተጠሪን ምስክር አድርጎ ለማቅረብ ያቀረበው ጥያቄ አግባብነት የለውም በማለት በአብላጫ ድምጽ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ግብረአበር ከክስ ነጻ ተደርጎ ማስረጃ የሚሆነው ጉዳዩ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት ጠቃሚ ማስረጃ ከሰጠ ስለመሆኑ በሕጉ ከማረጋገጣችንም በላይ ሕጉም ይህን ያደረገው በዓላማ በመሆኑ እና አሁን ክስ ይነሳለት የተባለው ግለሰብ ግን ከግብረአበሮቹ ጋር አብሮ በፍ/ቤት ክስ ቀርቦበት የግብረአበሮቹን የክርክር አመራር ከተረዳ በኋላ ስለሆነ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ብይን ሊነቀፍ አይገባም በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 እና አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 43 ... ጉዳዩ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት ... የሚለው መስፈርት የተቀመጠው በምርመራ ወቅት በወንጀል ተሳታፊ የሆኑ ሰዎችን ማስረጃ የሆኑ ሰነዶችን በማምጣት ሆነ ምስክር በመሆን ምርመራውን እንዲያግዙ እና ለፍትሕ ተባባሪ እንዲሆኑ በማድረግ በምርመራው የተጠናከረ ማስረጃ ለማግኘት ሲባል የተቀመጠ ማበረታቻ ነው፤ በሌላ አገላለጽ አንድ ጠቋሚ ወይም በወንጀሉ ውስጥ ተሳትፎ የነበረው ሰው ወደ ምስክር ሊዞር ይገባል የሚል ጥያቄ ቢያቀርብ ጥያቄው ተቀባይነት የሚያገኝበት መስፈርት ብቻ እንጂ ዓቃቤ ሕግ አንድ ጊዜ ክሱን ፍ/ቤት ካቀረበ በኋላ ክሱን በመሰረዝ ወደ ምስክር ማዞር አይችልም የሚል ክልከላ ያስቀመጠ ድንጋጌ አይደለም፤ ዓቃቤ ሕግ በራሱ ውሳኔ በየትኛውም ደረጃ ላይ የሚገኝን ጉዳይ አስመልክቶ ተከሳሽን ከክስ ነጻ በማውጣት ወደ ምስክር ለማዞር ይህ መስፈርት በየትኛውም ሕግ በአስገዳጅነት አልተቀመጠም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ.መ.ቁ 57988 ክስ የቀረበ ቢሆንም ዓቃቤ ሕግ ተከሳሽ የነበረን ሰው ወደ ምስክርነት ማዞር እንደሚችል በመግለጽ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ ዓቃቤ ሕግ 2ኛ ተጠሪን ከተከሳሽነት አውጥቶ ወደ ምስክር ያዞረበት አግባብ ግለሰቡ ተከሶ ፍ/ቤት ከቀረበ እና በኋላም በመታሰሩ ምክንያት ያገኘውን ዕውቀት ለማስመስከር እና የተከሳሾችን የመከላከል መብት በመሸርሸር የክርክሩን ሚዛናዊ አሰራር ለመጉዳት ሳይሆን ግለሰቡ ቀድሞውንም በወንጀሉ አብሮ የተሳተፈ እና ይህንኑም ክስ ከመመስረቱ በፊት ተጠርጣሪ በሆነበት ጊዜ በምርመራ ክፍል ስለተፈጸመው የወንጀል ድርጊት እና ስለተባባሪዎቹ ሚና የራሱንም ተሳትፎ በመጨመር የሰጠውን የተከሳሽነት ቃል በሙሉ ቃል በቃል የምስክርነት ቃሉንም ሲሰጥ ከመድገም ውጪ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመታሰሩ ምክንያት የቀየረው ወይም የጨመረው ቃል በሌለበት የወንጀሉ ዋና ፈጻሚ በሆኑ ሰዎች ላይ ውሳኔ ለማሰጠት እና ይህንንም በሌላ መንገድ በተሰበሰቡት ማስረጃዎች ብቻ ለማሳካት በቂ ባለመሆኑ ምክንያት ነው፤ ዓቃቤሕግ የ2ኛ ተጠሪ ክስ እንዲነሳ የጠየቀው በተናጠል ሳይሆን ምስክር መሆኑን እንደ ቅድመ-ሁኔታ በማስቀመጥ የነበረ ሲሆን 2ኛ ተጠሪን ወደ ምስክር ለማዞር ክስ መነሳቱ አስፈላጊ በመሆኑ ወደ ምስክር መዞሩን ፍ/ቤቱ ከፈቀደ ክስ እንዲነሳለት በሚል እሳቤ እንጂ ተከሳሹ

ወንጀል አልፈጸመም በሚል እሳቤ ክሱ እንዲነሳለት ብቻ ተፈልጎ አይደለም፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች እነኚህን ሁኔታዎች ሳያገናዝቡ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤት የሰው ማስረጃ ከመስማቱ በፊት በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 122/1 መሠረት በቀን 04/07/2010 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ መሠረት በ2ኛ ተከሳሽ ላይ ያቀረብነው ክስ እንዲነሳ እና በቀሪ ተጠርጣሪዎች ላይ ማስረጃ ለማድረግ የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካችን ጥያቄ ውድቅ የማድረጉን አግባብነት በሰ/መ/ቁ 57988 ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ስላልቀረበ መልስ በጽሑፍ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የሰጡት መልስ ይዘት በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ተከሳሹ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር ክስ ቀርቦበት አብሮ ታስሮ ወደ ምስክርነት ሊቀየር የሚችልበት የሕግ መሠረት የለም፤ 2ኛ ተጠሪ አብሮን ክስ ቀርቦበት የነበረ እና ስለተከሰሰንበት ወንጀል አብሮን ተከሳሽ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ከእኛ የሰማውን መረጃ ወደ ምስክርነት ቀይሮ እኛን በሚጎዳ መልኩ እንዲመሰክር መፍቀድ በራሳችን ጉዳይ እኛን የሚጎዳ የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ የማስገደድ ያህል ነው፤ አመልካች የጠቀሰው የሰበር መዝገብም ለጉዳዩ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም፤ አመልካች 2ኛ ተጠሪን በምስክርነት ማቅረብ የፈለገበት ምክንያት በአቤቱታው ላይ እንደገለጸው ሳይሆን ሆን ብሎ ከተጠሪዎች ጋር እንዲታሰር በማድረግ ተከሳሾች ነን በሚል ግለሰቡ ነገ በምስክርነት ይቀርብብናል የሚል ጥርጣሬ በሌለበት ከእኛ ያገኘውን መረጃ እና እውቀት ተጠቅሞ እኛን ለመጉዳት ታስቦ የተደረገ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች 2ኛ ተጠሪ በምስክርነት ሊቀርብ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፤ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባል ተብሎ ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በስር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ በነበረው 2ኛ ተጠሪ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ በማንሳት /በማቋረጥ/ ፤ ሌሎችን በተከሳሽነት በማካተት እና በሌሎች ምክንያት ጭምር ክሱን በማሻሻል 2ኛ ተጠሪን ምስክር አድርጎ ለማቅረብ ያቀረበውን አቤቱታ ፍርድ ቤቱ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ መነሳት ተቀብሎ 2ኛ ተጠሪ ከሌሎች አመልካቾች ጋር ተከሶ የነበረ በመሆኑ ምስክር ሆኖ ሊቀርብ አይችልም በማለት መወሰኑን እና ይኸው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መጽናቱን የሚመለከት በመሆኑ በወንጀል ክስ ክርክር ምክንያት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ተቀባይነት የሌለው ምስክር

(Inadmissible evidence) ነው የሚለውን ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል።

የአገራችን የፍትሕ ስርዓት በአንድ መጽሐፍ ስር የተጠቃለለ ዝርዝር የማስረጃ ሕግ የሌለው ቢሆንም በተለያየ ሁኔታ የማስረጃን ተቀባይነት፣ የማስረጃን አግባብነት፤ አመራመርና ምዘና መርሆችን የሚደነግጉ የማስረጃ ሕግ ድንጋጌዎች በሕገ መንግስቱና በሌሎች የይዘትና የስነ-ስርዓት ሕግ ውስጥ በተበታተነ ሁኔታ ተደንግገው ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ እና የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ተጠቃሽ ነው።

በመሰረታዊነት የአንድን ጉዳይ ዓይነት መሠረት በማድረግ የክርክሩን ጭብጥ ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ የማስረጃ ዓይነት (Admissibility) በልዩ ሁኔታ በህግ እስካልተወሰነ ድረስ በተከራካሪ ወገኖች ክሱን ወይም ክርክሩን ያስረዱልኛል ወይም ይከላከሉልኛል የሚሏቸዉን ማንኛዉንም ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ፣ በዚህ መልኩ በተከራካሪ ወገኖች የሚቀርብ ማስረጃ ደግሞ የተያዘዉን የክስ (ክርክር) ጭብጥ ለማስረዳት አግባብነት ያለው መሆኑ (Relevancy) እስከተረጋገጠ ድረስ የክርክሩን ጭብጥ ለማስረዳት ብቃት አለዉ ተብሎ እንደሚገመት፣ ጉዳዩን የያዘዉ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኝ ያቀረቧቸዉን ማስረጃዎች ለእያንዳንዱ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ በመስጠት ማስረጃዎችን ከነሙሉ ይዘታቸዉ መመዘን እንደሚገባዉ የማስረጃ አቀባበል እና ምዘና መርህ ያስገነዝባል። ስለሆነም አንድ ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ለፍርድ ሥራ በግብዓትነት መቅረብ የሌለበት ነው ወይም ማስረጃው ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ቢያያዝ እንኳን ዳኞች የማስረጃውን ይዘት፣ ተዓማኒነትና ክብደት ለመወሰንና በፍርድ ሥራ በግብዓትነት መጠቀም የሌለባቸው መሆኑን የሚገልጽ፤ማስረጃው በማስረጃነት ቀርቦ ከመመርመርና ከመመዘን የሚከለክለው ግልጽ ከልካይ የሆነ የሕግ ድንጋጌ ሊኖር ይገባል።

ወደያዝነው ጉዳይም በዋነኛነት በወንጀል ክስ ጉዳይ ምክንያት በምስክርነት የሚጠሩ ሰዎች መመስከር የሚጠበቅባቸው ውሳኔ ስለሚሰጥበት ፍሬ ነገር ተገቢ የሆኑትን በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ስለሚያውቃቸው ፍሬ ነገሮች (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.137(1)) በመሆኑ በወንጀል ጉዳይ የቀረበን አንድ ማስረጃን ውድቅ ሊደረግ የሚችለው በማስረጃነት እንዳይቀርብ ሕግ የከለከለው (Inadmissible) ሲሆን እና በፍርድ ቤት ተመዝኖ ተቀባይነት ሲያጣ ነው። ከዚህ ውጪ የወንጀልም ሆነ የሥነሥርዓት ሕጉ የወንጀል ክስን ለማስረዳት ወይም ለመከላከል መቅረብ የሚገባቸውን የማስረጃ ዓይነቶች ለይተው አልደነገጉም። ከዚህ አንጻር አመልካች ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር በ2ኛ ተጠሪ ላይ አቅርቦት የነበረውን ክስ ማንሳቱን ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ አመልካች አሻሽሎ በሚያቀርበው በዚሁ ክስ 2ኛ ተጠሪን ምስክር አድርጎ ለማቅረብ ያቀረበውን አቤቱታ ግን ያልተቀበለው ስለመሆኑ የሰጠው ምክንያት ደግሞ አመልካች ግብረአበርን ከክስ ነጻ በማውጣት በምስክርነት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ነው እንጂ ክስ ቀርቦ ከተሰማና ከሌሎች ተከሳሾች አጠቃላይ የክርክሩን

አካሄድ ከተረዳ በኋላ ሊቀርብ የሚገባ አይደለም፤ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 ፤ አዋጅ ቁጥር 882/2007 ና 434/97 አንቀጽ 43 ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ ነው የሚል ነው፡፡ ይህም የሚመለክተው 2ኛ ተጠሪ ምስክር ሆኖ እንዳይቀርብ የህግ ክልከላ አለ ወይም በህጉ ምስክር አድርጎ ለማቅረብ አልተመለከተም በማለት ውድቅ ማድረጉን የሚያመለክት ነው፡፡

የሙስና ወንጀሎችን የሚደነግገው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 ሆነ የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 41 የሚደነግጉት ከወንጀሉ ልዩ ባህሪ አንጻር በምርመራ ወቅት ፤ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ባሉት ጊዜያት፤ በወንጀል ድርጊቱ ተካፋይ የሆነ ሰው በአዋጁ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ሊቀርብበት ከነበረበት ክስ ነጻ ስለሚወጣበት ሁኔታ ነው፡፡ ስለሆነም ስለወንጀሉ በሰጠው ጠቃሚ መረጃ መሰረት ምርመራውን በማገዙ ምክንያት ፍርድ ቤት ክሱ ከመቅረቡ በፊት የሚያገኘው ነው፡፡ በፍርድ ቤት ምስክር አድርጎ የማቅረብ ጉዳይ አመልካች ምርመራው ተጠናቅቋል ብሎ ሲያምን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 108-122 እንደተመለከተው የክስ ማመልከቻውን አዘጋጅቶ ሲያቀርብ የሚገልጸው ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታም ለስር ፍርድ ቤት የቀረበው በዚሁ የክርክር ደረጃ ላይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ከክስ በፊት ያለውን የሙስና ወንጀሎችን የሚደነግገው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 8 እና የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 41 መሰረት በማድረግ የደረሱበት ድምዳሜ ህጉን ያላገናዘበ ከመሆኑም ባሻገር ድንጋጌዎቹ በዋናነት ግብረአበርን ከክስ ነጻ ማድረግን እንጂ በፍርድ ቤት የሚቀርብ ክስ ላይ ምስክር ማድረግን የሚመለከቱ አይደሉም፡፡ በሰ/መ/ቁ 57988 የተሰጠው ፍርድም የሚስገነዝበው ተካሰሽ የነበረን ሰው ዐቃቤ ሕግ ክሱን በማንሳት ምስክር አድርጎ ማቅረቡንና ይህም የሚጥሰው ህግ አለመኖሩን በመግለጽ ክርክሩን አይቶ ማስረጃውን በመመዘን መወሰኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ አንድ ድርጊት ከመፈፀሙ በፊት፣ ሲፈፀም ወይም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ ዐቃቤ ህግ ስላቀረበው ክስ ማስረጃ ይሆነኛል በማለት በሕጉ አግባብ ያቀረበውን ማስረጃ በማስረጃነት ሊቀርብ የማይችልና ተቀባይነት የሌለው (Inadmissible evidence) ነው የሚል ግልፅ ክልከላ የሚያደርግ የሕግ ድንጋጌ ከሌለ ማስረጃው ቀርቦ፣ በሕጉ አግባብ ተመዝኖ፣ የማስረጃው ትክክለኛነትና ህጋዊነት ተጣርቶ የሚወሰን እንጂ የማስረጃው አስረጂነት ዋጋ ሳይታይና ሳይመዘን በደፈናው ማስረጃው ከተከሳሾች ጋር አብሮ ተከሳሽ የነበረ ነው፤ የተከሳሾችን የመከላከል መብት ይጎዳል በሚል ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ውድቅ ማድረጉ የማስረጃ ተቀባይነት፤አግባብነትና ምዘና መርህን፤ የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትን ያልተከተለ በመሆኑን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 209610 መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠውን ብይን በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 156419 ሐምሌ 12 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች 2ኛ ተጠሪን ምሰክር አድርጎ ለማቅረብ ያቀረበው አቤቱታ በልዩ ሁኔታ በህግ ያልተከለከለ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው (Admissible) ማስረጃ ነው፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 209610 የጀመረውን ክርክር ቀጥሎ ማስረጃዎቹን ሰምቶ ለእያንዳንዱ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ በመስጠት ማስረጃዎችን በመመዘን ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት በማለት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁጥር 182050

ታሕሳስ 24 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ህግ

ተጠሪ፡- ብርጋዴር ጀነራል ሐድጉ ገ/ጊዮርጊስ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የዋስትና ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ 180500 ላይ ሐምሌ 30/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠባቸው ሁለቱም ድንጋጌዎች የዋስትና መብት የማያስከለክሉ በመሆኑ በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ሲል የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪን ጨምሮ በአራት ግለሰቦች ላይ አዋጅ ቁጥር 881/2007 በመጥቀስ ባቀረበው የሙስና ወንጀል ክስ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን ከሰማ በኋላ ሰኔ 07 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን ተጠሪን በተመለከተ ክስ የቀረበበትን የአዋጁን አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/2/ ድንጋጌን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113/2/ መሠረት ወደ አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ በመቀየር እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ብይን ተከትሎ ተጠሪ ባቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ በሁለት ክሶች እንዲከላከሉ የተባለ መሆኑን እና የሁለቱ ክሶች ቅጣት ሲደመር ከ10 ዓመት በላይ መሆኑን በመግለፅ የዋስትና ጥያቄውን በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4 መሠረት ውድቅ አድርጓል፡፡

ተጠሪ የዋስትና ጥያቄውን በሚመለከት በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ብይን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ከዋስትና አንፃር የተሰጠውን ብይን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለክላል የሚለው የሕግ አገላለጽ በግልጽ እንደሚያሳየው ከአራት ዓመት በላይ የሚለው አገላለጽ መነሻ ቅጣቱ አራት ዓመት እና በላይ የሆነ ድንጋጌን የሚመለከት እንደሆነ የሚያሻማ አይደለም፤ ተደራራቢ ወንጀሎች እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጊዜ ዋስትና ሊያስከለክል እንደሚገባ የድንጋጌው ሀሳብ ቢሆን ኖሮ ከአራት ዓመት በላይ የሚለው አገላለጽ ባላስፈለገ ነበር፤ ይህ ከሆነ ደግሞ የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ከአራት ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ተደራራቢ ወንጀልን የሚመለከት እንጂ ተጠሪ እንዲከላከል ብይን የተሰጠበት አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ መነሻ ቅጣቱ አንድ ዓመት ቀላል እሥራት ወይም አንድ ዓመት ጽኑ እሥራት የሚለውን የሚጨምር ነው በሚል የሚተረጎም አይደለም፤ በይግባኝ ባይ ላይ የተለየ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 አኳያ የዋስትና መብቱን የሚያስከለክል ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ ተደራራቢ ወንጀሎች ተደምረው ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ነው በማለት የዋስትና መብት መከልከሉ የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 2 ንኡስ ቁጥር 3/1 ድንጋጌን የሚቃረን ነው በማለት ተጠሪ ለብር 100,000 የሚበቃ ዋስ ሲያቀርቡ ከእስር እንዲፈቱ ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4/1 / በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለው / የድንጋጌው ይዘት ሊተረጎም የሚገባው ከ4 ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል የቅጣት ጣሪያው ከ4 ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ሲሆን እንደሆነ እና መደመር ያለባቸው ተደራራቢ ወንጀሎች የቅጣት ጣሪያቸውን እና የወንጀሎችን ክብደት መሠረት በማድረግ እንደሚደመሩ ሕጉ ሲረቀቅ መነሻ ከተደረጉት ምክንያቶች እና ከወንጀሎቹ ክብደት አኳያ መረዳት እየተቻለ ይግባኝ ሰሚ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 4 ዓመት የተባለውን እንደመነሻ ቅጣት ወስዶ ተጠሪን በዋስትና መልቀቁ ከህጉ መንፈስ ውጭ ከመሆኑም በላይ የአዋጁን ተፈፃሚነት ከጥያቄ የሚያስገባ ነው፤ በዚህ አዋጅ እና በሌሎችም የሙስና ወንጀሎች ድንጋጌዎች መነሻቸው አራት ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የሙስና ወንጀሎች የሉም፤ በሙስና ወንጀል የዋስትና ክርክር ጊዜ ክስ የቀረበበት ድንጋጌ ጣሪያ ቅጣት ሊታይ እንደሚገባ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ 63344 ላይ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ 4 ዓመት የተባለው የቅጣቱ ጣሪያ በሚለው ሊወሰድ ሲገባው በሕጉ ባልተደነገገበት ሁኔታ 4 ዓመትን እንደመነሻ ቅጣት መወሰዱ አግባብ አይደለም፤ ከዋስትና አሰጣጥ አንፃር የቀረበው የክስ ብዛት ከግንዛቤ ሊገባ እንደሚገባ ይኸው ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ 59302 ላይ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ እና ተጠሪ እንዲከላከሉ

ብይን የተሰጠው እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ሊያስቀጡ በሚችሉ ሁለት ወንጀሎች በመሆኑ ተደራራቢ ክሱ ከሚያስከትለው ቅጣት አንፃር የዋስትና ጥያቄው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ መሠረት ሊታይ ሲገባው መታለፉ አግባብ ስላልሆነ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ ተጠሪ በማረሚያ ቤት ሆነው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቹ የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ የአሁን ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9/1/ ስር በሁለት ወንጀሎች እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቶ እያለ የስር ፍርድ ቤት በዋስትና እንዲለቀቁ የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9/1፤ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 2 እና በሰ.መ.ቁ 63344 እና 124750 ላይ ከተሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በተጠቀሰው ድንጋጌ ውስጥ 4 ዓመት የተባለው መነሻ ቅጣት ለመሆኑ ህጉ በግልፅ ያስቀመጠ በመሆኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፤ ዋስትና ሊከለከል የሚችለው ከ4 ዓመት በላይ በሆነ ተደራራቢ ወንጀል ለመሆኑ ሕጉ በግልጽ አስቀምጧል፤ አራት ዓመት እንደቅጣት ጣሪያ ሊወሰድ አይገባም፤ አመልካች ተከላከል የተባልኩበት የሕግ አንቀጽ የቅጣት መነሻ የአንድ ዓመት ቀላል እስራት ነው፤ አመልካች የጠቀሳቸው የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌላቸው ሲሆን በ2007 ዓ.ም በወጣ አዋጅ ላይም ተፈጻሚ አይሆኑም፤ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አተረጓጎም አዋጅ ቁጥር 881/2007 አፈፃፀምን የሚከለክል አይደለም፤ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 እና በተሻሻለው አዋጅ መካከል ልዩነት ካለ አዲሱ ሕግ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል፤ በሰበር ችሎት ማስቀረቢያ ነጥብ ላይ የተጠቀሱት የሰበር ውሳኔዎች አሁን ከቀረበው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ትርጉም ሳይሆን መነሻ እና መድረሻ ቅጣቱ በግልፅ ተለይቶ ባልተጠቀሰ ድንጋጌ ከመሆኑም በላይ በተሻሻለ ሕግ ላይ የተሰጡ በመሆናቸው አሁን ለቀረበው ጉዳይ ተፈፃሚነት የላቸውም፤ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ ድንጋጌ መሠረት የቀረበው ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ በመሆኑም የቀረበው ቅሬታ ውድቅ ተደርጎ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 15/2011 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ ክስ በቀረበበት አዋጅም ሆነ በወንጀል ህጉ መነሻ ቅጣቱ 4 ዓመት የሆነ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ ሕግ አውጪው የማይፈፀም ሕግን ያወጣል ብሎ መውሰድ የሕጉን መንፈስ እና ዓላማ የተከተለ አይደለም፤ ክስ የቀረበበት አዋጅ የሰበር ችሎቱ በሰ.መ.ቁ 63344 ላይ የሰጠውን ትርጉም የሚያጠናክር በመሆኑ ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት የለውም ሊባል አይገባም፤ ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠባቸው ሁለቱም አንቀፆች የቅጣት ጣሪያ ሰበር ችሎቱ በተጠቀሰው መዝገብ ላይ የሰጠው ትርጉም ለአዋጅ ቁጥር 881/2007 ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል፤

የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ/ ድንጋጌን አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ትርጉም በመሆኑ እና የሰበር ክርክር የሕግ አተረጓጎምን የሚመለከት በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሊመለከተው ሲገባው ያለፈውን ጉዳይ ማቅረቡ ተገቢ ነው በማለት የሰበር አቤቱታው በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/1/ ድንጋጌ በሁለት ክሶች እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠ እና የሁለቱም ክሶች ቅጣት ሲደመር ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4 መሠረት የዋስትና ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ያደረገው መሆኑን፤ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ከአራት ዓመት በላይ የሚለው አገላለጽ ከአራት ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ተደራራቢ ወንጀልን የሚመለከት እንጂ ተጠሪ እንዲከላከል ብይን የተሰጠበትን አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ መነሻ ቅጣቱ አንድ ዓመት ቀላል እሥራት ወይም አንድ ዓመት ጽኑ እሥራት የሚለውን የሚጨምር ነው በሚል የሚተረጎም አይደለም በማለት የተጠሪን የዋስ መብት የጠበቀ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልገው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ፡-

1. በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትናን ይከለክላል በማለት የተቀመጠው ሀሳብ መነሻ ቅጣትን የሚመለከት ነው? አይደለም?
2. ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን የተሰጠበት የሕግ አንቀጽ አማራጭ ቅጣትን ባስቀመጠ ጊዜ የዋስትናን መብት ጥያቄን ለመወሰን ሲባል ተፈጻሚ የሚሆነው የትኛው የቅጣት አማራጭ ነው?
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 አኳያ የዋስትና መብቱን የሚያስከለክል መከራከሪያ ባልቀረበበት ሁኔታ የተጠሪ የዋስትና መብት ሊከለከል አይገባም ማለቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡

በመሆኑም ከላይ ለተያዙት መሠረታዊ የክርክሩ ጭብጦች ምላሽ መስጠት ያስችለን ዘንድ የሙስና ወንጀሎችን አስመልክቶ በሐገራችን የወጡትን ሕጎች እና በየጊዜው የወጡትን የማሻሻያ አዋጆች ሕግ አውጪው ሊያሳካው ከፈለገው ግብ እና ከዋስትና መብት መሠረታዊ መርሆዎች እና ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሠረቱ የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/93 እንደተሻሻለ / አዋጅ ቁጥር 239/93 አንቀጽ 51/2 / በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የዋስትና መብት አይኖረውም በማለት ግልጽ ክልከላ ያደረገ አዋጅ የነበረ ሲሆን ሕግ አውጪው አስቀድሞ ባወጣው

የሙስና ወንጀሎች ሕግ ዋስትናን በግልጽ ክልከላ / ገደብ / ያደረገ መሆኑን፤ በሂደት በወጣው የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1/ በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የተከሰሰበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መልቀቅ አይቻልም በማለት የሙስናን ወንጀል ቅጣት መጠንን መሠረት በማድረግ ዋስትናን ለመፍቀድ ወይም ለመንፈግ እንደመስፈርት በማስቀመጥ በዋስ የመለቀቅ መብት በመርህ ደረጃ ሕገ-መንግስታዊ መብት መሆኑን ያመላከተ ነው፡፡

በቀጣይነት የወጣው የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ይህንኑ ሕገመንግስታዊ መብት የበለጠ በማስፋት በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ለፍ/ቤት ማመልከት እንደሚችል ሆኖም የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በቀደሙት አዋጆች እንደተመለከተው በዋስትና መለቀቅ የማይችል መሆኑን፤ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ግን ዋስትና የሚከለክሉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በሙስና ወንጀል የተያዘን ሰው የዋስትና መብትን አስመልክቶ በተለያየ ጊዜ የወጡት ሕጎች ከላይ በዝርዝር የተገለጹት ሲሆኑ እነዚህ ሕጎች ሊያሳኩት የፈለጉት መሠረታዊ ዓላማ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ ዋስትናን አስመልክቶ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በመሠረቱ የተያዙ ሰዎች በሕገ-መንግስቱ ጥበቃ ከተደረጉላቸው መብቶች አንዱ የዋስትና መብት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 19/6 የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመፈታት መብት ያላቸው መሆኑን በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን ይህ በሕገ መንግሥቱ የተከበረው መሠረታዊ መብት ሊነፈግ፣ ሊገደብ ወይም በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ የሚደረገውም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ዝርዝር ሕጎች መሠረት በልዩ ሁኔታ ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዘመናዊው የሕግ አስተሳሰብም በዋስ ለመለቀቅ ከሚያበቁ ምክንያቶች መካከል ጎልቶ የሚታየው ማንኛውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሳይሰጥበት ሊቀጣ አይገባውም የሚለው ነው፡፡ በሕገ-መንግስቱ ልዩ ጥበቃ የተሰጠው ይህ መብት መሠረታዊ ዓላማውም ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኝነቱ ሳይረጋገጥበት በእስር እንዳይቆይ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የዋስትና መብት መርሁ መፍቀድ ሲሆን ልዩ ሁኔታው ደግሞ መከልከል ነው፡፡

ይህን መሠረታዊ መብት አስመልክቶ የመወሰን ስልጣን እና ኃላፊነት የተሰጣቸው ፍ/ቤቶችም በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥሮ ክስ የቀረበበት ሰው የሚያቀርበውን የዋስትና መብት ጥያቄ እና ከሣሽ የሆነው ዓቃቤሕግም በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን አስተያየት በሕገመንግስቱ ዋስትናን አስመልክቶ ከደነገገው መሠረታዊ ዓላማ እና በሌሎች ልዩ ሕጎች ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በጥንቃቄ

መርምረው ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ይህንኑ ተግባራዊ ሲያደርጉም በመርህ ደረጃ የዋስትናን መብት መፍቀድ ያለባቸው ሲሆን በሕጉ ተለይተው በተቀመጡ ምክንያቶች ግን የዋስትናን መብት በልዩ ሁኔታ ሊነፍጉ ይችላሉ። እነዚህም ምክንያቶች መርማሪው ፖሊስ ምርመራውን ገና ያላጠናቀቀ ሲሆን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 59፤ ተከሳሽ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስትና ለመለቀቅ የሚከለክል ሲሆን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 የሕግ ክልከላን መሠረት በማድረግ እና በሌሎች ልዩ ሕጎች፤ ወይም ተከሳሹ ፈጽሞታል የተባለው ወንጀል በዋስ መለቀቅን የማይከለክል ቢሆንም ተጠርጣሪው ቢለቀቅ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 የተገለፁትን ተግባራት ይፈጽማል ተብሎ ሲታመን ነው። የዋስትና መብትን አስመልክቶ በሕገመንግስቱ እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ የተቀመጡት መሠረታዊ መርሆዎች በዝርዝር የተገለጹት ሲሆኑ በሙስና ወንጀል የተጠረጠረን ወይም የተከሰሰን ሰው አስመልክቶ በየጊዜው ተሻሽለው የወጡት ሕጎች ከዋስትና መብት መሠረታዊ መርሆዎች ጋር ተገናዝበው ሲታዩ ሊያሳኩ የፈለጉት መሠረታዊ ዓላማ ምንድነው የሚለውን ቀጥለን እንመልከት።

የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/93 እንደተሻሻለ / አዋጅ ቁጥር 239/93 አንቀጽ 51/2 / በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የዋስትና መብት አይኖረውም በማለት ግልጽ ክልከላ አድርጎ የነበረ አዋጅ ቢሆንም የዋስትና መብት በሕገመንግስቱ እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለምዓቀፍ ስምምነቶች ጥበቃ የተደረገለት መሠረታዊ መብት መሆኑ ታምኖበት በሂደት በወጣው የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1 በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የተከሰሰበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ እንደማይችል በመግለጽ በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በተከሰሰበት ሕግ ላይ ያለውን የቅጣት መጠን መሠረት በማድረግ የዋስትና መብትን በከፊል የፈቀደ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል። የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1 ድንጋጌ ከፍተኛ ቅጣት ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስ ከመልቀቅ ይልቅ በእስር ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ማድረግ፤ በሌላ በኩል ከ10 ዓመት በታች ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በእስር ከማቆየት ይልቅ በዋስ ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ማድረግ የዋስትና መብት ሕገመንግስታዊ ሽፋን የተሰጠው መሠረታዊ መብት መሆኑ ታምኖበት ሕግ አውጪው የዋስትና መብትን አስመልክቶ አስቀድሞ በነበረው አዋጅ ላይ አስቀምጦት የነበረውን ፍጹም ክልከላ በተወሰነ ደረጃ በመተው የዋስትና መብትን በተወሰኑ የሙስና ወንጀሎች ላይ የፈቀደ መሆኑን አመላካች ነው።
በተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው በዋስ እንዲለቀቅ ለፍ/ቤት ማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም። ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል በማለት

ይደነግጋል፡፡ በድንጋጌው የመጀመሪያ ሐሳብ ላይ የተቀመጠው እና የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም የሚለው ሐሳብ በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4/1 የተከሰሰበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም በማለት ከተገለጸው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 የመጀመሪያ ሀሳብ የተለየ ነገር የለውም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ላይ የተቀመጠው ሁለተኛው ሀሳብ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የክርክሩ ጭብጥ በመሆኑ በድንጋጌው ላይ የተቀመጠው ሁለተኛ ሀሳብ መሠረታዊ ዓላማ ከድንጋጌው ይዘት፤ አግባብነት ካላቸው የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች እና ከመደበኛው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ሲሆን ይህ ደግሞ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣ ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ የቀላል እሥራት እና የጽኑ እሥራት ቅጣት መጠን በሚገባ ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106/1 ቀላል እስራት ከ10 ቀን እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጣ መሆኑን፤ የዚሁ ሕግ አንቀጽ 108/1 ድንጋጌ ደግሞ ጽኑ እሥራት ከአንድ ዓመት እስከ 25 ዓመት የሚደርስ እና በሕጉ ተገልጾ የተደነገገ ሲሆንም በዕድሜ ልክ የሚያስቀጣ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ የመጀመሪያ ሀሳብ ላይ የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና መለቀቅ አይችልም በማለት የተገለጸ በመሆኑ ይህ ሀሳብ የሚመለከተው በጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን ነው፡፡ በዚሁ ድንጋጌ ላይ የተቀመጠው ሁለተኛ ሀሳብ የድንጋጌው የመጀመሪያ ሀሳብ በአራት ነጥብ ከተቋጨ በኋላ ይህንኑ ሀሳብ ተከትሎ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል በማለት የተገለጸ በመሆኑ እና በልዩ ሁኔታ ከወንጀሉ ክባድነት የተነሳ በሕጉ ልዩ ክፍል ተደንግጎ ሲገኝ ወይም በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ ወይም ወንጀለኛው በተደጋጋሚ ሲቀጣ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ እንደሚችል እንደተጠበቀ ሆኖ ቀላል እሥራት የሚያስቀጣው ከ10 ቀን እስከ ሶስት ዓመት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ሁለተኛ ሀሳብ ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በማለት የተገለጸው ሀሳብ ከአራት ዓመት በላይ በጽኑ እሥራት ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎችን የሚመለከት እንጂ የቅጣት መነሻቸው አራት ዓመት የሆነ በጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን የሚመለከት እንዳልሆነ ከድንጋጌው አቀራረጽ እና ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ከአራት ዓመት በላይ የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ በሚል የተገለጸው ሁለተኛ ሀሳብ መነሻ ቅጣትን የሚመለከት አይደለም ካልን

በቀላል እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች የፈለገውን ያህል ተደራርበው ቢገኙ ሌላ ሕጋዊ ምክንያት እስካልቀረበ ጊዜ ድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች ናቸው በሚል ምክንያት የተከሰሰውን የዋስትና መብት መከልከል የማይቻል መሆኑ፤ ሆኖም ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እና እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ግን የተከሰሰውን ሰው የዋስትና መብት የሚከለክል መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከላይ የተመለከተውን የሕጉን ትንታኔ መነሻ በማድረግ በሙስና ወንጀል ሕግ አዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ወንጀሎች መኖር አለመኖራቸውን በተመለከተ አዋጁን እንደተመለከትነው በአዋጁ አንቀጽ 13/4/ለ የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት እና በመቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት፤ በአዋጁ አንቀጽ 13/7 የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ከሶስት ዓመት እስከ 7 ዓመት እና ከብር 10,000 እስከ 50,000 መቀጮ፤ በአዋጁ አንቀጽ 17/2 የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ7 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከ 20,000 በማይበልጥ መቀጮ፤ በአዋጁ አንቀጽ 16/1 ላይ የተመለከተው ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ከአንድ ዓመት እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡ ከእነኚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ድንጋጌዎቹን በመተላለፍ የተከሰሰ ሰው ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል አመላካች ድንጋጌዎች መሆናቸውን ነው፡፡

ይህንኑ መሠረት በማድረግ በእጃችን ያለውን ጉዳይ እንደመረመርነው አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው ክርክር መነሻቸው አራት ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የሙስና ወንጀሎች የሉም በማለት የሚከራከር ቢሆንም ከላይ በዝርዝር በተገለጹት ድንጋጌዎች የተከሰሰ ሰው ከአራት አመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል አመላካች ድንጋጌዎች በመሆናቸው እና በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ሁለተኛ ሀሳብ ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በማለት የተገለጸው ሀሳብ ከአራት ዓመት በላይ በጽኑ እሥራት ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎችን የሚመለከት እንጂ መነሻ ቅጣትን የሚመለከት ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው መከራከሪያም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በድንጋጌው ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በሚል የተገለጸው የሕጉ አገላለጽ መነሻ ቅጣቱ አራት ዓመት እና በላይ የሆነን ድንጋጌን የሚመለከት ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረበው ክርክር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 63344 በሙስና ወንጀል የዋስትና ክርክር ጊዜ ክስ የቀረበበት ድንጋጌ ጣሪያ ቅጣት ሊታይ እንደሚገባ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑ 4 ዓመት የተባለው የቅጣቱ ጣሪያ ሊወሰድ

ይገባል በማለት የሚከራከር ከመሆኑ አኳያ ተጠቃሹ የሰበር ሰሚ ችሎት ወሳኔ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 63344 ሐምሌ 28 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ዋስትናን በሚመለከት የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 676/1 በመተላለፍ ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በማለት የተከሰሰን ሰው በሚመለከት የተሰጠ ውሳኔ ሲሆን ድንጋጌው የሚመለከተው ተፈጸመ የተባለውን የወንጀል ድርጊት እና ቅጣቱን የሚመለከት እንጂ አማራጭ ቅጣት አልተቀመጠበትም፤ በድንጋጌው ጥፋተኛ የተባለም ሰው ከአምስት ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ የሚያሰቀጣ መሆኑን ይገልጻል፤ ይህንኑ ድንጋጌ እና የአዋጅ 434/97 አንቀጽ 4 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ በመዝገቡ የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ዝቅተኛ የቅጣት መነሻ መውሰድ የአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 ድንጋጌን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ተፈጻሚ የማያደርግ እና ሕግ አውጭው የፀረሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግን በማውጣት ለማሳካት የሚፈልገውን ግብ የማያሳካ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ አስገዳጅ ትርጉም አንድ ቅጣት ብቻ ተለይቶ የተቀመጠበትን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 676/1 በሚመለከት የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንጂ ተከሳሹ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ አማራጭ ቅጣትን ያስቀመጠ በሆነ ጊዜ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል ፍ/ቤቱ የትኛውን የቅጣት አማራጭ መውሰድ እንዳለበት በመግለጽ የሰጠው የሕግ ትርጉም የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት አለው በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በሰ.መ.ቁ 124750 የተሰጠው ውሳኔም አስቀድሞ በሰ.መ.ቁ 63344 የተሰጠውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ፤ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 58 አዋጁ በስራ ላይ ከመፈጸሙ በፊት የተፈጸሙ ወንጀሎች በነባሩ የስነምግባር እና የጸረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ የሚል በመሆኑ እና አመልካች ፈጸሙት የተባለው የሙስና ወንጀል አዋጅ ቁጥር 882/2007 ከወጣ በኋላ በመሆኑ ተጠቃሾች የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው አይደሉም፡፡

ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠበት የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/1/ እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እስራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ10 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል በሚል አማራጭ ቅጣትን ያስቀመጠ በመሆኑ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰመ.ቁ 63344 ም ሆነ በሰ.መ.ቁ 124750 በሰጠው ውሳኔ ተከሳሽ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ አማራጭ ቅጣትን ባስቀመጠ ጊዜ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል ሊያዝ የሚገባው ቅጣት የትኛው እንደሆነ ገዢ ትርጉም ያልሰጠበት በመሆኑ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል ሊወሰድ የሚገባው የቅጣት አማራጭ የትኛው ነው የሚለው በጥንቃቄ ሊታይ ይገባዋል፡፡

ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ሲሆን ይህ ደግሞ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት እና ከሶስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣ ነው፡፡ ከላይ በዝርዝር ካስቀመጥናቸው የሕጉ ትንታኔዎች አኳያ ፍ/ቤቱ ቀላል የእስራት ቅጣት አማራጩን የሚወስድ ከሆነ የተጠሪ የዋስትና መብት የሚፈቀድ ሲሆን ፍ/ቤቱ የጽኑ እሥራት አማራጭን የሚወስድ ከሆነ ደግሞ የተጠሪ የዋስትና መብት የሚከለከል ይሆናል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ለዋስትና ጉዳይ ሲባል በድንጋጌው ከተቀመጡት ሁለት የቅጣት አማራጮች ውስጥ የትኛውን አማራጭ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ተከሳሹ ፈጽሞታል ከተባለው ድርጊት፤ ከሙስና ወንጀል አዋጆች ልዩ ባሕርይ እና ከዋስትና መብት መሠረታዊ ዓላማ ጋር በማገናዘብ መለየት ይኖርበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የሥር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አስቀድሞ ክስ የቀረበባቸውን የአዋጁን አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/2/ ድንጋጌን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113 በመለወጥ በአንቀፅ 9/1/ሀ/ለ እንዲከላከሉ ብይን ሲሰጥ እንደምክንያት ያስቀመጠው በተጠሪ አድራጎት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን ተጠሪ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ የተቀመጠ አይደለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ፈጽመውታል በተባለው የወንጀል ድርጊት ምክንያት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን በዓቃቤሕግ ክስ ላይ የተገለጸው አይደለም የሚባል ከሆነ ተጠሪ ይከላከሉ ከተባለበት የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ላይ ከተቀመጡት የቀላል እሥራት እና የጽኑ እሥራት የቅጣት አማራጮች ውስጥ የዋስትና መብት ሕገመንግስታዊ ሽፋን የተሰጠው መሠረታዊ መብት ከመሆኑ አኳያ ለዋስትናው ጉዳይ ሲባል የቀላል እሥራት አማራጭን መውሰድ ተመራጭ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ይከላከሉ ከተባለበት የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 9/1/ሀ/ለ ላይ ከተቀመጡት የቀላል እሥራት እና የጽኑ እሥራት የቅጣት አማራጮች ውስጥ ለዋስትናው ጉዳይ ሲባል የቀላል እሥራት አማራጭ የተወሰደ በመሆኑ እና በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 በቀላል እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች የፈለገውን ያህል ተደራርበው ቢገኙ ዋስትናን ለማስከልከል የሚያስችል ሌላ ሕጋዊ ምክንያት እስካልቀረበ ጊዜ ድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች ናቸው በሚል ምክንያት የተከሰሰውን ሰው የዋስትና መብት መከልከል አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው ክርክር ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ሊያስቀጡ በሚችሉ ሁለት ወንጀሎች በመሆኑ ተደራራቢ ክሱ ከሚያስከትለው ቅጣት አንፃር የዋስትና ጥያቄው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67/ሀ መሠረት ሊታይ ሲገባው መታለፉ አግባብ አይደለም በማለት የሚከራከር ከመሆኑ አኳያ የስር ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የዋስትና መብቱን የሚያስከለክል መከራከሪያ ባልቀረበበት ሁኔታ የተጠሪን የዋስትና መብት መከልከል አግባብ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ መሆን አለመሆኑን ቀጥለን እንመልከት፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የተከሰሱበትን የሕግ አንቀጽ በብይን ሲቀይር ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት የዋስትና መብት

እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ በዋስትና ጥያቄው ላይ በሰጠው አስተያየት ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን የተሰጠው በሁለት ክሶች በመሆኑ እና የዋስትና መብት ቢጠበቅላቸው ቅጣቱን በመሸሽ የዋስትና ግዴታቸውን አክብረው ስለማይቀርቡ የዋስትና ጥያቄው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት የተቃወመ ስለመሆኑ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ብይን በግልጽ የሚያሳይ በመሆኑ አመልካች የተጠሪ የዋስትና መብት በሕግ ባይከለከልም ዋስትናን ሊያስከለክሉ በሚችሉ ሁኔታዎች ሊነፈግ ይገባል በማለት የተከራከረ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 4 መሠረት በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 በተገለጸው አግባብ የተጠሪን የዋስትና መብት ለማስከልከል የሚያስችሉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን መመርመር አላስፈለገውም ነበር፡፡ ተጠሪ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት የዋስትና መብታቸውን በመከልከል በሰጠው ብይን ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበው በተደረገው የቃል ክርክር አመልካች ባቀረበው ክርክር ተጠሪ ጥፋተኛ ሆነው ቢገኙ ሊወሰድ የሚችለው ቅጣት ከባድ ሊሆን እንደሚችል ግምት ከተወሰደ የክሶችን ብዛት እና ከባድነት መነሻ በማድረግ የዋስትና መብት ሊከለከሉ ይገባል በማለት የተከራከረ ስለመሆኑ የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት መዝገብ አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ዋስትናን ለማስከልከል የሚያስችል መከራከሪያ አልቀረበም ማለቱ አመልካች በስር ከፍተኛው ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ዋስትናን በሚመለከት ያቀረበውን ክርክር ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የተጠሪ የዋስትና መብት ሊከለከል ይገባል የሚል ክርክር ያቀረበ በመሆኑ የተጠሪ የዋስትና መብት በሁኔታ ሊከለከል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 67 ድንጋጌ ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት የተመለከቱትን ግዴታዎች የማይፈጽም የማይመስል እንደሆነ የዋስትና ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ፍ/ቤቱ ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ በግልጽ አላመላከተም፡፡ በመሆኑም አንድ ተከሣሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን የሚፈጽም እንደማይመስል ግምት የሚወሰደው በቂ እና ሕጋዊ ሊባል በሚችል ምክንያት ሊሆን ይገባል፡፡ እነዚህም ምክንያቶች ከተለያዩ ከባቢያዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባሕርይ አንፃር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበው የሚችለው ነጥብ ነው ተብሎ የሚታሰብ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አስቀድሞ ክስ የቀረበባቸውን የአዋጁን አንቀፅ 9/1/ሀ/ለ/2/ ድንጋጌን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 113 በመለወጥ በአንቀፅ 9/1/ሀ/ለ በሁለት ክሶች እንዲከላከሉ ብይን ሲሰጥ እንደምክንያት ያስቀመጠው በተጠሪ አድራጎት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን ተጠሪ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ የተቀመጠ አይደለም በሚል ነው፡፡ በተጠሪ የወንጀል ድርጊት ምክንያት ደረሰ የተባለው የጉዳት መጠን በዓቃቤሕግ ክስ ላይ የተገለጸው አይደለም የሚባል ከሆነ ተጠሪ በዋስትና

ቢለቀቁ ዋስትናውን አክብረው ሊቀርቡ አይችሉም የሚል ግምት የሚያሲዝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የዋስትና መብታቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ሊከለከል አይገባም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍ/ቤት የተጠሪን የዋስትና መብት በመፍቀድ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት በውጤት ደረጃ ተቀብለነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 180500 ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት በውጤት ደረጃ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ከተሰየምን ዳኞች ውስጥ ሶስት ዳኞች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተጠሪ የዋስትና መብት በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 መሠረት ሊከለከል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረስን በመሆኑ፤ ከችሎቱ ዳኞች ውስጥ አራት ዳኞች አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት የተጠሪ የዋስትና መብት በሁኔታ ሊከለከል ይገባል በማለት መከራከሪያ ያቀረበ ቢሆንም የተጠሪ የዋስትና መብት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 67 መሠረት ሊከለከል አይገባም ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረስን በመሆኑ ተጠሪ በሌላ ወንጀል የሚፈለጉ ካልሆነ በቀር በዋስ ሆነው ጉዳያቸውን ሊከታተሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 180500 ሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ተጠሪ እንዲያስይዙ ካዘዘው የዋስትና መጠን በተጨማሪ ተጠሪ ከሐገር እንዳይወጡ ታግዷል፡፡ ይጻፍ፤ ትዕዛዙ ለሚመለከታቸው አካላት ይድረሳቸው፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

<u>የሀሳብ ልዩነት</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 3 ሥር የተሰየምኩት የችሎቱ ዳኛ ከሌሎቹ የችሎቱ ዳኞች በሃሣብ የሚለየኝ በፍሬ ጉዳዩ በአመልካች ተከላከል የተባሉበት የህግ ድንጋጌዎች ዋስትና መብትን የሚያስነፍግ አይደለም በሚል በአብላጫው ድምጽ የተሰጠውን የውሣኔ ክፍል የምደግፍ በመሆኑ በዚህ ላይ ልዩነት የለኝም፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት በእርግጥ በሕግ ጉዳይ ዋስትና የሚያስነፍግ አይደለም በማለት ውሣኔ መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕግ ዋስትና በሚያስፈቅድ ጉዳይ ዋስትና መፍቀድ የሚችል ቢሆንም

ዋስትና ሊፈቀድ አይገባም በማለት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 ተጠቅሶ ክርክር ካለ ይህንንም መመልከት ይጠበቅበታል፡፡

ነገር ግን የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 67 በሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተነስቶ የነበረ እና ፍ/ቤቱ በዚህ ላይ ግራ ቀኙን ሳያከራክር እና ዓቃቤ ሕግ አለኝ የሚለውን የሕግ ግምት የሚያስጥሉ ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ፤ተከሣሽም በዐቃቤሕግ የተነሳበትን የሕግ ግምትን እና የቀረበበትን ማስረጃ የሚያስተባብሉ መከላከያ እንዲያቀርብ ሳይደረግ ሕጉ ዋስትና መብትን አያስከለክልም በሚል ዋስትና መፈቀዱ ተገቢ ሆኖ ስላላገኘሁት፤እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር ዋስትና ሊፈቀድ አይገባም ብሎ ሲወስን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 የተነሳውን መከራከሪያ በሥር ፍ/ቤት የተነሳ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት አከራክሮ ውሣኔ ያላሳረፈበት መሆኑን ከጉዳዩ ከተረዳ ወደ ሥር ፍ/ቤት ተመልሶ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ክርክር ተደርጎበት ውሣኔ እንዲሰጥ መመለስ ሲገባው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 መሠረት የቀረበ ጥያቄ የለም በማለት ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት ተገቢ ክርክር ተደርጎበት ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ አንፃር ተጣርቶ ዋስትና የመፍቀድ ወይም የመከልከል ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባው የነበረ ሆኖ ይህ ሳያደረግ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማጽናት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ ሆኖ ስላገኘሁት ከወዲሁ በሥር ፍ/ቤት የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ.67 ላይ የተሰጠ ውሣኔ ሳይኖር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ባለበት ደረጃ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 ድንጋጌን በማንሳት ዋስትና ሊፈቀድ ይገባል በሚል በአብላጫው ድምጽ ሊወሰን አይገባም ነበር በማለት ከባልደረቦቼ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

<u>የልዩነት ሀሳብ</u>

- ስማችን በሁለተኛ እና በአራተኛ መስመር ላይ የተጠቀሰው ዳኞች ከወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 67 አንፃር በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የምንስማማ ሲሆን አብላጫው ድምፅ የአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 3(1) ድንጋጌ አተረጓጎምን አስመልክቶ በጠቀሰው ምክንያት እና በደረሰበት ድምዳሜ ያልተስማማን በመሆኑ የልዩነት ሀሳባችንን በሚከተለው መልኩ አስፍረናል፡፡
- በመሰረቱ በአብላጫ ድምፅም እንደተገለፀው በዋስ የመለቀቅ መብት ህገ መንግስታዊ መርህ ሲሆን በህግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል የሚችል ለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 19(6) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ የዋስትና መብትን

በተመለከተ በህግ በልዩ ሁኔታ ገደብ ከተጣለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4(1) ከአስር ዓመት በላይ ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስትና ሊለቀቅ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡

- ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው የተሻሻለው ልዩ የፀረ ሙስና የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 882/2007 በአንቀፅ 3(1) ስር ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ፅኑ እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች የተከሰሰን ሰው ጉዳይ በተመለከተ ከላይ የሰፈረውን ድንጋጌ ቃል በቃል ከደገመ በኋላ ቀጥሎ ባለው ዓረፍተ ነገር ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን አስመልክቶ አዲስ ሀሳብ አስፍሯል፡፡ ይህም ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እየተደመሩ ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል የሚል ነው፡፡
- ግራ ቀኙን ለዚህ ሰበር ችሎት ክርክር ያበቃውም ይኸው በማሻሻያ አዋጁ ውስጥ የተጨመረው አዲስ ሀሳብ አተረጓጎምን የሚመለከት እንጂ ክስ በቀረበበት ወይም ተከላከል በተባለበት አንቀፅ ስር አማራጭ ቅጣት በተቀመጠ ጊዜ ለዋስትና ሲባል የትኛው ቅጣት መታየት አለበት የሚል ባለመሆኑ ለቀረበው ጉዳይ እንደ ዋና ጭብጥ ተደርጎ በአብላጫው ድምፅ መያዙ አግባብ አይመስለንም፡፡ ያም ሆኖ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ተከሳሹ ለሚያቀርበው የዋስትና ጥያቄ ፍርድ ቤቶች ተከሳሹ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ክስ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊጣልበት የሚችለውን የቅጣት ጣሪያ መነሻ በማድረግ ውሳኔ ሊሰጡ እንደሚገባ ይኸው ችሎት በሰ/መ/ቁ/63344 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ዝቅተኛው ቅጣት የሚያዝበት አግባብ የለም፡፡ በእርግጥ አብላጫው ድምፅ ይህ የሰበር ችሎቱ ትርጉም አሁን ለቀረበው ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም ብሏል፡፡ ሆኖም ትርጉሙ የተሰጠው የሙስና ወንጀልን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ከዋስትና ጋር በተያያዘ መነሻ ሊደረግ የሚገባን ነጥብ ያመለከተ እንጂ የቅጣት ዓይነትን ለይቶ የተሰጠ ባለመሆኑ አሁን ለቀረበው ጉዳት ተፈፃሚነት የለውም ሊባል አይገባም፡፡ እናም እነዚህ ነጥቦች ታሳቢ ተደርገው የቀረበውን ጉዳይ በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡
- በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አተረጓጎም መሰረት በድንጋጌው ውስጥ የተጠቀሰው አራት ዓመት መነሻ ቅጣታቸው አራት ዓመት እና በላይ የሆኑ ወንጀሎችን የሚመለከት ነው የሚል ሲሆን በተጠሪ ጠበቃ በኩል ተመሳሳይ አረዳድ መኖሩን ከቀረበው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከአራት ዓመት በላይ ተብሎ የተጠቀሰው መነሻ ቅጣትን ሳይሆን የእያንዳንዱን ተደራራቢ ወንጀሎችን ጣሪያ ቅጣት የሚመለከት ነው የሚል ነው፡፡

- የድንጋጌውን አተረጓጎም ልዩነት በአግባቡ ለመፍታት ይረዳ ዘንድ ጉዳዩን ከሶስት አበይት ነጥቦች አኳያ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የዋስትና መብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እድገታዊ አመጣጥን የሚመለከት ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት የሙስና ወንጀልን በተመለከተ ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ መጀመሪያ የታወጀው በአዋጅ ቁጥር 236/1993 ነው፡፡ ይህ አዋጅ በታወጀ በ20 ቀኑ በአዋጅ ቁጥር 239/1993 የተሻሻለ ሲሆን ማሻሻያ አዋጁ በአንቀፅ 2 ስር በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የዋስትና መብት የሌለው መሆኑን ደንግጓል፡፡ ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 434/1997 ደግሞ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የዋስትና መብት የከለከለው ከአስር ዓመት በላይ በሆነ እስር ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰን ሰው መሆኑን በአንቀፅ 4 ስር ደንግጓል፡፡ በመጨረሻም ይህንን አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 882/2007 ደግሞ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡ ሆነው ነገር ግን ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሰ ሰው የተደራራቢ ወንጀሎቹ ድምር ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ ዋስትና የሚከለከል መሆኑን ደንግጓል፡፡
- የድንጋጌዎቹ የእድገት አመጣጥ የሚያሳየው መጀመሪያ በሙስና ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው ሙሉ በሙሉ ዋስትና ተከለከለ፤ ቀጥሎ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ እስራት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው ብቻ ተከለከለ፤ በመጨረሻም ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሰ እና የተደራራቢ ወንጀሎቹ ድምር ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ የሆነ ተከሳሽ ብቻ እንዲከለከል መደረጉን ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ የእድገቱ አመጣጥ አንፃር አዋጅ ቁጥር 882/2007 በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 434/1997 ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡን ወንጀሎችን በተመለከተ በተቃራኒ ንባብ እውቅና ተሰጥቶት የነበረውን የዋስትና መብትን በልዩ ሁኔታ የሚገድብ እንጂ አብላጫው ድምፅ በገለፀው አኳኋን የዋስትና መብትን በተሻለ የሚያሰፋ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከልዩ ህጎች የሚጠበቀው ዋስትና መፍቀጃ ምክንያቶችን መዘርዘር ሳይሆን በህገ መንግስቱ የተረጋገጠው መብት ሊገደብ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታን ብቻ ለይቶ ማስቀመጥ ነው፡፡ ከተጠቀሱ አዋጆች የእድገት ሂደትም መገንዘብ የሚቻለው ከጊዜ ወደ ጊዜ ዋስትና የሚያስከለክሉ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ እየተለዩ መምጣቸውን ነው፡፡
- አዋጅ ቁጥር 434/1997 ከአስር ዓመት በላይ በሆነ እስራት ሊያስቀጣ በሚችል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው በዋስትና ሊለቀቅ እንደማይችል ከመደንገጉ ውጭ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ስለ ተከሰሰ ሰው ያለው ነገር የለም፡፡ እናም ከፍርድ በፊት ያለመታሰር መብት ህገ መንግስታዊ መርህ በመሆኑ የድንጋጌውን ተቃራኒ ንባብ በመውሰድ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል የተጠረጠረ

ወይም የተከሰሰ ሰው በመደበኛው የወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት ሊቀርቡ የሚችሉ የዋስትና መቃወሚያዎች እንደተጠበቁ ሆነው ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በዋስትና የመለቀቅ መብት ይኖረዋል ማለት ይቻላል፡፡

- ሆኖም ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጡም ሆነው በርካታ ተደራራቢ ወንጀሎች ሊፈፀሙ የሚችሉበት እድል መኖሩ በመዘንጋቱ በአዋጁ ሽፋን አልተሰጠውም፡፡ እናም ከድንጋጌው ይዘት መረዳት የሚቻለው ከዋስትና አንፃር የአዋጅ ቁጥር 882/2007 ዋነኛ ትኩረት ይህንኑ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን ጉዳይ መልክ ማስያዝ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡
- የድንጋጌዎቹ የእድገት አመጣጥ ይህን የሚመስል ከሆነ ቀጥሎ ሊታይ የሚገባው ሁለተኛው አበይት ነጥብ የድንጋጌው የቃላት አጠቃቀም ዘዬ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የድንጋጌው ዋና ዓላማ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት ሊያስቀጡ በሚችሉ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሱ ሰዎችን የዋስትና ሁኔታ መምራት ነው፡፡ ይህ ከሆነ በድንጋጌው ውስጥ "ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች" የሚለው አገላለፅ ለምን አስፈለገ የሚለው በአግባቡ ሊጤን የሚገባው ነጥብ ይሆናል፡፡ ከድንጋጌው የቃላት አጠቃቀም በጥቅሉ መገንዘብ የሚቻለው የህግ አውጭው ዓላማ ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት በሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች የተከሰሱትን ሁሉንም ተከሳሾች ዋስትና መከልከል አለመሆኑን ነው፡፡ ይልቁንም ዋስትና መከልከል የተፈለገው እያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች በሆነ እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ የተደራራቢ ወንጀሎቹ ድምር ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ወንጀል የተከሰሱትን ሰዎችን ብቻ ነው፡፡
- የድንጋጌው መልዕክት ይህ ከሆነ ከአራት ዓመት በላይ የተባለው የሚያመለክተው የተደራቢ ወንጀሉን መነሻ ቅጣት ነው ወይስ ጣሪያ ቅጣት የሚለው ቀጥሎ የሚታይ ሶስተኛው አበይት ነጥብ ይሆናል፡፡ የዚህን ሀረግ ትክክለኛ ትርጉም ለመረዳት የሙስና ወንጀልን በሚደነግገው መደበኛ የወንጀል ህጉ እና በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ስር ለእያንዳንዱ የሙስና ወንጀል የተቀመጠውን ቅጣት መጠን በጥንቃቄ በመፈተሽ ከላይ ከሰፈረው ድንጋጌ ተግባራዊ አፈፃፀም ጋር አዛምዶ ማየትን ይጠይቃል፡፡
- በዚሁ መሰረት በወንጀል ህጉም ሆነ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ውስጥ መነሻ ቅጣቱ አራት ዓመት እስራት የሆነ የሙስና ወንጀል የለም፡፡ መነሻ ቅጣታቸው ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር አመት በታች የሆኑት ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ አንዱ መነሻው አምስት አመት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ መነሻ ቅጣቱ ሰባት ዓመት የሆነ ነው፡፡ የእነዚህ ሁለቱ ቅጣቶች ጣሪያ ቅጣት እንደ ወንጀሉ ዓይነት የሚለያይ ቢሆንም መዳረሻው ግን ከአስራ አምስት እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት ነው፡፡

- በዚሁ አግባብ በድንጋጌው ውስጥ "ከአራት ዓመት በላይ" የሚለው ሀረግ የሚያሳየው የእያንዳንዱን ተደራራቢ ወንጀል መነሻ ቅጣት ነው የሚባል ከሆነ ጣሪያ ቅጣቱ ቢያንስ አስራ አምስት ዓመት ፅኑ እሰራት ይሆናል፡፡ ጉዳዩ ይህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 4(1) እና ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ/63344 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አኳያ የድንጋጌው ጣሪያ ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ በመሆኑ እና በራሱ ከመነሻው ዋስትናን የሚያስከለክል በመሆኑ ስለ ተደራራቢ ወንጀል ማንሳት አያስፈልግም፡፡ በመሆኑም "ከአራት ዓመት በላይ" የሚለው ሀረግ መነሻ ቅጣትን የሚያሳይ ነው የሚለው አተረጓጎም የድንጋጌውን ተግባራዊ አፈፃፀም ትርጉም የሚያሳጣ በመሆኑ የሚያስኬድ አይደለም፡፡
- በአንፃሩ መነሻ ቅጣታቸው ምንም ይሁን ምን ጣሪያ ቅጣታቸው ግን ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሆኑ በአዋጁ ብቻ ከሃያ አንድ በላይ ድንጋጌዎች እንዲሁም ከአራት ዓመት በታች ጣሪያ ቅጣት ያላቸው ወደ አራት ድንጋጌዎች መኖራቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተለያየ ምክንያት አንድን የህግ ድንጋጌን መተርጎም ቢያስፈልግ ከመተርጎሚያ ስልቶች ውስጥ አንዱ ህጉን ማወጅ ካስፈለገበት መሰረታዊ ዓላማ አንፃር ድንጋጌው ተግባራዊ ሊሆን በሚችልበት አግባብ መተርጎም(Purposive Interpretation) ስለመሆኑ የህግ አተረጓጎም መሰረተ ሀሳብ ያስገነዝባል፡፡
- ከዚህ አኳያ የህግ አውጭው ዓላማ ነው ተብሎ ከላይ የተመለከተው ተግባራዊ ሊሆን እና በአግባቡ ከግብ ሊደርስ የሚችለው በድንጋጌው ውስጥ "ከአራት ዓመት በላይ" ተብሎ የተጠቀሰው ሀረግ የእያንዳንዱን ተደራራቢ ወንጀሎች ጣሪያ ቅጣት የሚመለከት ነው በሚል ሲተረጎም ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡
- የድንጋጌው ትርጉም ይህ ከሆነ የአሁን ተጠሪ እንዲከላከሉ ብይን በተሰጠባቸው እያንዳንዱ ድንጋጌ ስር ያለው ጣሪያ ቅጣት ከአስር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ሲሆን የሁለቱ ተደራራቢ ወንጀል ጠቅላላ ቅጣት ከአስር ዓመት በላይ በመሆኑ በፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 3(1) መሰረት ዋስትና የሚያስከለክል ነው፡፡ እናም የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አረዳድ የህጉን መንፈስ የተከተለ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተከተለው አተረጓጎም ከዚህ አኳያ ሊቃና ይገባ ነበር በማለት ከስራ ባልደረቦቻችን የተለየ አቋም ይዘናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ 179416

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ሀለቃ ንጉሴ አብርሃ

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 07 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቃፍታ ሁመራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 1800/11 በቀን 16/07/2011 ዓ.ም አመልካች በሕግ እንደሚፈለግ አውቆ ሆነ ብሎ ሲደበቅ የነበረ እና ሕግን በተከተለ የመጥሪያ ስነ ስርዓት መጥሪያ የተላከለት መሆኑ ስለተረጋገጠ ጉዳዩ ዳግም እንዲታይለት ያቀረበው አቤቱታ ተገቢ አይደለም ሲል የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 115243 ሚያዝያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠ ውሳኔ ይነሳልኝ በሚል የቀረበን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በቃፍታ ሁመራ ቀበሌ ዓዲሹሁ ነዋሪና ባለትዳር እና ገበሬ መሆናቸውን፤ ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው ወደ ሕግ አካል ቀርበው የማያውቁ መሆኑን፤ የመጥሪያ ትዕዛዝ ሳይሰጣቸው በስርቆት ወንጀል የአራት ዓመት ፍርደኛ ነህ ተብለው በቀን 25/06/2011 ዓ.ም ከመኖሪያ ቤታቸው በፖሊስ የተያዙ መሆኑን በመግለጽ ከሕግ ውጪ በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳያቸው ባሉበት እንዲታይ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 162 መሠረት በሌሉበት መታየት የሚችል መሆኑን፤ በፖሊስ መጥሪያ እንዲቀርቡ ታዞ ሊቀርቡ ያልቻሉ መሆኑን፤ በአድራሻቸው እንደሌሉ የሚገልጽ ማስረጃ አመልካች ከሚገኙበት አድራሻ የቀረበ መሆኑን፤ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸውም ስላልቀረቡ ጉዳያቸው በሌሉበት ታይቶ ውሳኔ ያገኘ መሆኑን በመግለጽ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በተደጋጋሚ እንዲያቀርቡ ታዞ በአድራሻቸው እንደሌሉ ማስረጃ ቀርቧል፤ በመቀጠልም በመቃልህ ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ሊቀርቡ አልቻሉም፤ አመልካች በክሱ ላይ በተገለጸው እና መደባይ ዛና ወረዳ ቀበሌ ዓዲ ጸጉራ ቀጠና ወይና አምባ በሚባለው አድራሻ እንዳሉ እና ለግዜው ተሰውረው እንደነበር የሚገልጽ ማስረጃ ከቀበሌው ጸጥታ አስተዳደር ቀርቧል፤ ይህ ማረጋገጫም አመልካች በሕግ የሚፈለጉ መሆኑን እያወቁ ሆን ብለው ሲደበቁ እንደነበረ የሚያሳይ ነው፤ ዓዲ ጎሹ በሚባል ቦታ ነው የነበርኩት በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ማስረጃ አላቀረቡም፤ ለአመልካች የደረሰው መጥሪያ ሕግን የተከተለ የመጥሪያ ስነ ስርዓት በመሆኑ አቤቱታቸው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ገበሬ ባለትዳር እና የልጆች አባት መሆኔ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፤ አመልካች በወንጀል ጥፋተኛ መባሌን ያወቅኩት በቀን 25/06/2011 ዓ.ም በፖሊስ ከተያዝኩ በኋላ ነው፤ ከዚህ ቀን በፊት ለመርማሪ ፖሊስ የሰጠሁት ቃል የለም ክስ እንደቀረበብኝ አልተነገረኝም፤ በምኖርበት አካባቢም የተለጠፈ መጥሪያ የለም፤ አመልካች በመርማሪ ፖሊስ ፊት ቀርቤ ትክክለኛ ስሜን እና አድራሻዬን ባልሰጠሁበት ሁኔታ እና ትክክለኛ ስሜም አለቃ ንጉሰ አብርሃ ተክለ አብዝኒ ሆኖ ሳለ አቶ ንጉሰ አብርሃ ተክሉ ተብሎ በመቃልህ ጋዜጣ መታወጁ አግባብ አይደለም፤ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ አመልካችን የሚመለከት መሆኑ ሳይረጋገጥ በሌለሁበት የተሰጠው ፍርድ ተነስቶ ጉዳዩ ባለሁበት እንዲታይ ያቀረብኩትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በተጠቀሰው አድራሻ የሚገኝ ስለመሆኑ ፖሊስ ቃል ከሰጠ ያስመዘገበው አድራሻ ስለመኖሩ እንዲሁም በአድራሻው የማይገኝ ከሆነም ማረጋገጫ እንዲቀርብ ሳይደረግ፤ የጋዜጣ ጥሪውም በአመልካች ማመልከቻ በተጠቀሰው አግባብ ስለመደረጉ ሳይረጋገጥ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ መደረጉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 942277 ከሰጠው ውሳኔ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ስነ ስርዓቱ በሚያዘው መሠረት መጥሪያ ለአመልካች እንዲደርሰው ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ለፖሊስ ተልኳል፤ ፖሊስ ለፍ/ቤቱ በሰጠው ምላሽ አመልካች በአድራሻው እንደሌለ እና ሊያቀርቡት እንደማይችሉ በመግለጽ ምላሽ በመስጠቱ በጋዜጣ እንዲጠራ ተደርጓል፤ አመልካች በጋዜጣ ተጠርቶ ስላልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፤ አመልካች በአድራሻው የነበረ መሆኑን በማስረጃ አላረጋገጠም፤ አመልካች በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ የመጥሪያ አሰጣጥ ስርዓትን የተከተለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪ ችሎት ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ ከመሰጠቱ በፊት ከመነሻውም ቢሆን አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ በሌሉበት የሚታይ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ የተከሰሱ ሰዎች በሕግ ከተጠበቁላቸው መብቶች መካከል አንዱ የተከሰሱበት ጉዳይ በፍርድ ቤት ሲታይ በችሎት ተገኝቶ የቀረበባቸውን ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረበባቸው ምስክሮችን የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበዉ እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት ነዉ፡፡ ኢትዮጲያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14 ድንጋጌም የተከሰሱ ሰዎች ፍትህ የማግኘት እና በገለልተኛ ፍ/ቤት የመዳኘት እና በአካል ተገኝቶ የመከራከር መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡

ከላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በልዩ ሁኔታ በግልጽ በሕግ ከተመለከቱትና ከተፈቀዱት በስተቀር በመርህ ደረጃ የወንጀል ክስ የሚታየዉም ሆነ ክርክር ተደርጎ ዉሳኔ የሚሰጠዉ ተከሳሽ በችሎት በተገኘበት ነዉ፡፡ በልዩ ሁኔታ ሕግ ፈቅዶ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት የሚታየዉም ከአሥራ ሁለት ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወይም በመንግስት ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሆነዉ በጽኑ እስራት ወይም ከብር 5,000 በላይ የሚያስቀጡ ከባድ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ወንጀሎችን ብቻ ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 162(2) ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሕጉ እነዚህን ወንጀሎች አስመልክቶ በልዩ ሁኔታ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታዩ የፈቀደበትና አብዛኛዎችን ወንጀሎች ተከሳሽ እስካልተገኘ ድረስ ወይም በአግባቡ መጥሪያ ደርሶት በችሎት ቀርቦ የመከራከር መብቱን እስካልተወ ድረስ ጉዳዩ እንዳይታይ የደነገገበት ዓላማ በአንድ በኩል ተከሳሽ ከባድ ወንጀል ፈጽሞ ከፍትሕ በመሠወሩ የወንጀሉ ተጎጂዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሕጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ከባድ ወንጀሎች ውጪ ባሉት ጉዳዮች የተከሳሽ በችሎት ተገኝቶ የመከራከር መብት ከሚጣስ ይልቅ ተከሳሽ እስኪገኝ ድረስ የፍርድ ሂደቱ እንዳይካሄድ ስለመሆኑ ከላይ በዝርዝር ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ድንጋጌ ከአንድ ዓመት በማያንስ ቀላል እሥራት ወይም ከአሥራ አምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ አማራጭ ቅጣቶችን የያዘ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት ክስ የቀረበበት ተከሳሽ አንድም በቀላል እሥራት አልያም በአማራጭ ከተቀመጠው የጽኑ እሥራት ቅጣት ከ12 ዓመት በታች ወይም ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል እንገነዘባለን፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተከሰሰ ተከሳሽ አስመልክቶ ተመራጭ የሚሆነው የፍርድ ሂደት የወንጀሉ ተጎጂዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ሲባል ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል ከወዲሁ ግምት በመውሰድ ጉዳዩን በሌለበት ማየት ነው? ወይስ የተከሳሽ በችሎት ተገኝቶ የመከራከር መብት ከሚጣስ ይልቅ ተከሳሽ እስኪገኝ ድረስ የፍርድ ሂደቱ እንዳይካሄድ ማድረግ? የሚለው በጥንቃቄ ታይቶ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል፡፡

በአካል ፍ/ቤት ተገኝቶ የመከራከር መብት ለተከሰሱ ሰዎች በሕገመንግስቱ አንቀጽ 20/4 እና ኢትዮጲያ በተቀበለችው ዓለም ዓቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14 ላይ የተጠበቀላቸው መሠረታዊ መብት በመሆኑ፤ አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ከባድ የስርቆት ወንጀል ሕግ አውጪው ሊያሳካው ያሰበው ልዩ ዓላማ ኖሮት ለብቻው የሕግ ማዕቀፍ የወጣለት ሳይሆን በመደበኛው የወንጀል ሕግ የተደነገገ በመሆኑ፤ ይህ ድንጋጌም አማራጭ ቅጣቶችን የየዘ በመሆኑ፤ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አመልካች ጥፋተኛ ቢባሉ በቀላል እሥራት፤ ከ12 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት ወይም ከአሥራ ሁለት ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት ሊቀጡ የሚችሉ በመሆኑ ተመራጭ የሚሆነው የፍርድ ሂደት አመልካች በድንጋጌው የተቀመጠው ከፍተኛ ቅጣት ሊቀጡ ይችላሉ ብሎ ከወዲሁ በማሰብ ጉዳዩን በሌሉበት እንዲታይ ማድረግ ሳይሆን የተከሳሽ በችሎት ተገኝቶ የመከራከር መብት ከሚጣስ ይልቅ ተከሳሽ እስኪገኝ ድረስ የፍርድ ሂደቱ እንዳይካሄድ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ተከሳሹ በሌለበት ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት አመልካች የተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌ በሌሉበት የሚታይ አይደለም በማለት አመልካች እስኪገኙ ድረስ የፍርድ ሒደቱ እንዳይካሄድ ማድረግ ሲገባው አመልካች የተከሰሱበት ድንጋጌ በሌሉበት የሚታይ እንደሆነ ግምት በመውሰድ የሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ እና አመልካች ጉዳያቸው ባሉበት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቃፍታ ሁመራ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 1800/11 አመልካች በሌሉበት ጉዳያቸውን በማየት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም በቀን 16/07/2011 ዓ.ም አመልካች በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳያቸው ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡትን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 115243 ሚያዝያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3/ለ ድንጋጌ ተከሳሽ በሌለበት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ስልጣን ያለው ሌላ ችሎት አመልካች ባሉበት ክርክሩን እንዲያይ እና ዓቃቤሕጉም ክሱን ስልጣን ላለው ፍ/ቤት እንዲያቀርብ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 202 መሠረት ተወስኗል፡፡

ትዕዛዝ

- አመልካች በስር ፍ/ቤት ቀርበው በዋስትና ላይ እስኪከራከሩ ድረስ ለብር 10,000 / አሥር ሺህ/ የሚበቃ ዋስ ሲያቀርቡ ወይም ገንዘቡን በሞዴል 85 ሲያስይዙ ከእስር እንዲለቀቁ በአብላጫ ድምጽ ታዟል፡፡

-የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካች በሌሉበት ታይቶ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካች ባሉበት ጉዳያቸው እንዲታይ የተወሰነ መሆኑን አውቆ በዚህ ችሎት እንዲያስይዙ የተወሰነውን የዋስትና ገንዘብ ማስያዛቸው ሲረጋገጥ በሌላ ጉዳይ የማይፈለጉ መሆኑን አረጋግጦ ከእሥር እንዲለቅ ታዟል፡፡

-መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 171521

ታህሳስ 23 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች ፡- እትመት አሰፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤህግ - አቶ ብርሃኑ ታደለ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ትርሃስ መስፍን ገ/እግዚአብሔር - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻው አመልካች በቁጥር 3-3367/1862/07 በ18/06/2011 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ225717 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ በማጽናት በኮ/መ/ቁ. 218556 ህዳር 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በመጠየቁ ነው፡፡

የነገሩ አመጣጥ የወንጀል ክስን የሚመለከት ነው፡፡የአሁን አመልካች /የሥር ከሳሽ/ በቁጥር 2/515/1868/07 በ23/07/07 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ክስ በ1996 የወጣውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አንቀጽ 385 (1) (ለ) ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ ተከሳለች የሚል ነው፡፡የክሱ ዝርዝር፡- ተከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ ጥቅምን ወይም መሻሻልን ለማግኘት በማሰብ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12/45 ክልል ልዩ ቦታው የኢሚግሬሽን የዜግነት ጉዳይ ዋና መመሪያ ውስጥ በቀን 19/06/07 በግምት ከቀኑ 8.00 ሰዓት ሲሆን ተከሳሽ ዜግነቷ ኤርትራዊ ሆኖ እያለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 12 የነዋሪዎች መታወቂያ በማውጣት ቁጥሩ EP 2378734 የሆነ የኢትዮጵያ ፓስፖርት በማውጣቷ ተከሳሽ የማይመለከታትን ትክክለኛ ሰነድ በመገልገል ወንጀል ተከሳለች የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ቀርባ የእምነት ክህደት ቃል ከሰጠች በኋላ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ.225717 በሆነው በቀን 24/02/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን በቀን

4/11/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቃቤ ህግ ያቀረበው ክስና ክርክር እና የተጠቀሰው ድንጋጌ የማይጣጣም በመሆኑ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ እንደተሰጠ፣ይሁን እንጂ ዐቃቤህግ በቀን 10/02/2009 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ክሱ በአግባቡ የቀረበ፣የተከሳሽ ድርጊትም ሊወድቅበት በሚችል የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሠረት የቀረበበ መሆኑ ክስ የሚሻሻልበት አግባብ የለም ማለቱን ገልጾ ዐቃቤህግ በፍርድ ቤቱ የተሰጠውን ትዕዛዝ ተገቢነት የለውም የሚል ከሆነ በይግባኝ የሚያስተካክል ከመሆን ባለፈ ትዕዛዝ አልፈጽምም መባሉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም።ይህ ችሎትም ቀደም ሲል በዚህ ፍርድ ቤት የተሰጠን የክስ ይሻሻል ትዕዛዝ የማንሳት ሥልጣን የሌለው በመሆኑ እንደትዕዛዙ ዐቃቤህግ ክሱን ባለማሻሻሉ መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል ሲል ደምድሞታል።

በዚህ ብይን የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የሥር ፍርድ ቤት ክስ እንዲሻሻል ያስተላለፈው ትዕዛዝ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ ቁጥር 119 (1) ክስ እንዲለወጥ ወይም እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ፍርድ ቤት ማዘዝ የሚችል መሆኑን ህጉ የሚፈቅድ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ይህን ትዕዛዝ ማዘዙ የሚነቀፍ ስላልሆነ የይግባኝ ቅሬታው መልስ ሰጪን አያሰቀርብም ሲል ወስኗል።

አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በቁጥር 3-3367/1862/07 በቀን 18/06/2011 ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ አቅርቧል።የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ፡- የሥር ፍርድቤቶች ተጠሪዋ የውጭ ዜጋ ወይም ኤርትራዊ ሆና እያለ እና ለኢትዮጵያዊያን ብቻ የሚያገለግል የነዋሪዎች መታወቂያ ተጠቅማ ፓስፖርት አውጥተው ባሉበት ሁኔታ አመልካች ይህን በሚያሳይ እንዲሁም የወንጀል ድንጋጌውን በሚገልጽ መልኩ ተጠሪ ለእርሷ አገልግሎት የማይውል ነው ሊባል አይገባም ወይም የክሱ ፍሬ ነገርና የወንጀል ድንጋጌው አይጣጣምም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 385(1) (ለ) ሲተረጉሙ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈፀማቸውን ስለሚያሳይ እንዲታረምልን የሚል ነው።

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረተው የወንጀል ክስ ላይ የተመለከተው የወንጀል ህግ አንቀጽ እና ዝርዝሩ የማይመጣጠን በመሆኑ አመልካች ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ በሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት አመልካች ለማሻሻል ፈቃደኛ አልሆነም፤ቀደም ሲል ክስ እንዲሻሻል የተሰጠውን ትዕዛዝ ማንሳት አይቻልም በሚል የተዘጋበትን አግባብነት ከመሠረታዊ ክርክር አመራር ሥነ-ሥርዓት እና ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ለሰበር ያስቀርባል ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል።

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላት ቀርባ ሐምሌ 9 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጠችው መልስ የሥር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ስህተት ያለበት ነው ብሎ ያመነ በመሆኑ ክስ እንዲሻሻል በሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ

መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክራለች፡፡አመልካቹም በ24/11/2011 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች ብይንም ሆነ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል? ወይስ አልተፈጸመበትም? የሚል ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡የሥር ፍርድ ቤት የቀረበውን ክስ አመልካች እንዲያሻሽል በ4/11/2008 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱ፣ዐቃቤ ህግም በ10/02/2009 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ክሱ የተከሳሽ /የተጠሪ/ ድርጊት ሊወድቅበት በሚችል የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሠረት የቀረበበ መሆኑ ክስ የሚሻሻልበት አግባብ የለም ሲል መከራከሩ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልዳታ ምድብ ችሎት መዝገብ ለመዝጋት መሰረት ያደረገው ዐቃቤ ህግ ክስ እንዲያሻሽል የተሰጠውን ትዕዛዝ የሚቃወም ከሆነ በይግባኝ ከሚያሳርም ውጪ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ትዕዛዝ ሊያነሳ ስለማይችል መዝገቡ ተዘግቷል የሚል ነው፡፡የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በተመለከተ ለሁለት ከፍሎ ማየት ተገቢ ነው፡፡የመጀመሪያው ፍርድ ቤቱ ክስ እንዲሻሻል የሰጠውን ትዕዛዝ እራሱ ማንሳት ይችላል? ወይስ አይችልም? የሚለው ነው፡፡የወንጀል ክርክር የሚመራበት ሥርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ በዝርዝር ተደንግጎ እንመለከታለን፡፡የወንጀልን ጉዳይ የሚመለከት ችሎትም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ላይ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ተከትሎ የቀረበለትን ጉዳይ ይመለከታል ክርክሩንም ይመራል፣ችሎቱንም ይቆጣጠራል፣ክርክሩ ሲጠናቀቅ ወይም ጉዳዩ ሲበስል ፍርድ ይሰጣል፡፡ክርክሩን ከሚመራባቸው ሥልቶች መካካል አንዱ ጉዳዩን በሚያይበት ጊዜ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነውን ትዕዛዝ መስጠት ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት አመልካች ባቀረበው ክስ ላይ የተገለጸው ፍሬ ነገር ከተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ጋር የማይጣጣም ነው በማለት ክሱ እንዲሻሻል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 119(1) መሠረት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡አመልካች ክስ እንዲያሻሽል ትዕዛዝ ሲሰጥ የቀረበው ክስ የሚሻሻልበት ምክንያት አይኖርም በማለት ክስ ለማሻሻል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ አላነሳም ማለቱ ስህተት አይደለም፡፡በያዝነው ጉዳይ ትዕዛዝ የሰጠው ፍርድ ቤት እራሱ ትዕዛዙን ለማንሳት የማይችልበት አንደኛው ምክንያት ክስ እንዲሻሻል በራሱ በኩል አምኖ ትዕዛዝ የሰጠ በመሆኑ የሰጠውን ትዕዛዝ ማንሳት ተገቢ ሆኖ ስለማይታይ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ትዕዛዝ የሰጠው ፍርድ ቤት እራሱ ተመልሶ ትዕዛዙን የሚያነሳ ከሆነ የክርክር አመራር ሥርዓትን ያልተከተለ ስለሚሆንና ተገልጋዩም በፍርድ ቤቱ ላይ ያለውን አመኔታ የሚቀንስ ወይም የሚሸረሽር በመሆኑ ነው፡፡ሶስተኛው ምክንያት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 184 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ ክስ እንዲሻሻል የሰጠው ትዕዛዝ ይግባኝ ሊባል የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ይግባኝ ሊባል የሚችልበትም ፍርድ ቤቱ የቀረበው ክስ መሻሻል አለበት ብሎ ያመነ በመሆኑ ባዘዘው ትዕዛዝ መሠረት ካልተሻሻለ

በስተቀር ክርክሩን ስለማያካሂድ ነው፡፡ከእነዚህ ምክንያቶች ተነስተን ስናይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አላነሳም ማለቱ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ሁለተኛው መሠረታዊ ነገር ፍርድ ቤቱ የቀረበው ክስ ላይ ያለው ፍሬ ነገር እና የተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ አይጣጣምም በማለት አመልካች ክስ እንዲያሻሽል ትዕዛዝ መስጠቱ በክስ ላይ የተገለጸውን እና የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌንያገናዘበ ነው ወይ? የሚለው ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

በመሠረቱ ፍርድ ቤት ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ የሚሰጠዉ በምን አግባብ ነዉ? ህጋዊ ውጤቱስ ምንድነዉ? የሚለው መታየት ያለበት ነው፡፡የወንጀል ክስ ማመልከቻ አዘጋጃጀት አስመልክቶ ይዘቱና ዓይነቱ በምን አኳኋን እና ዝርዝር ሊኖረዉ እንደሚገባ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ አንቀጽ 111 እና 112 ላይ ተመልክቷል፡፡ከነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ ክሱ በዝርዝር እንዲገለጽ ከሚጠበቅባቸዉ መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ዉስጥ በክሱ የተጠቀሰዉ የወንጀል ህግ ድንጋጌ እና ተከሳሹ የፈጸመው የወንጀል ተግባር የክሱ ፍሬ ነገር ከህጉ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንዳለበት ነዉ፡፡የክሱ አዘገጃጀትና ዝርዝር ይዘት ላይ መገለጽ የሚገባው መሰረታዊ ነገር ባለመገለጹ ተከሳሹን ያሳሳተው እንደሆነ ወይም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የማይቻል ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም ማመልከቻ በቀረቡለት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ፣እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 118 እና 119/1/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ስለሆነም ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ የሚሰጠው በክስ ማመልከቻ ፎርም ወይም በክሱ ማመልከቻ ላይ ስለወንጀሉ አስፈላጊ ዝርዝር ውስጥ ስህተት ሲገኝ ወይም ሳይጠቀስ ሲቀርና ይህም መሰረታዊ ነገር ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡በዚህ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ክስ እንዲሻሻል ትእዛዝ ሰጥቶ ዐቃቤ ህግ የተሻሻለ ክስ አዘጋጅቶ ያላቀረበ እንደሆነ ተከሳሽ ለጊዜዉ እንደሚለቀቅ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 122/3/ ድንጋጌ ይገልጻል፡፡ስለሆነም በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መሰረት ክሱ ተሻሽሎ ያልቀረበ እንደሆነ ውጤቱ መዝገቡን ለጊዜዉ በመዝጋት ተከሳሹን መልቀቅ እንደሆነ ህጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡

የክስ ማመልከቻ እንዲሻሻል የሚደረገው ከላይ በተገለጸው አግባብ በክሱ ዝርዝር ላይ መገለጽ የሚገባው መሰረታዊ ጉዳይ ሳይገለጽ የቀረ እንደሆነ ወይም ደግሞ ያለአግባብ የተገለጸው ነገር ተከሳሹን የሚያሳስት ነው ተብሎ ሲታሰብ ነው፡፡

በእጃችን ያለውን ጉዳይ ስንመለከት የዐቃቤ ህግ ክስ ተከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ ጥቅምን ወይም መሻሻልን ለማግኘት በማሰብ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12/45 ክልል ልዩ ቦታው የኢሚግሬሽን የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ውስጥ በቀን 19/06/07 በግምት ከቀኑ 8.00 ሰዓት ሲሆን ተከሳሽ ዜግነቷ ኤርትራዊ ሆኖ እያለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 12 የነዋሪዎች መታወቂያ በማውጣት ቁጥሩ EP 2378734 የሆነ የኢትዮጵያ ፓስፖርት በማውጣቷ ተከሳሽ የማይመለከታትን

ትክክለኛ ሰነድ በመገልገል ወንጀል ህግ አንቀጽ 385(1) (ለ) ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ ተከሳለች የሚል ነው፡፡በዚህ ክስ ላይ የተገለጹት ፍሬ ነገሮች በወንጀል ህግ አንቀጽ 385(1) (ለ) ሥር ከተቀመጠው ጋር ይጣጣማሉ? ወይስ አይጣጣሙም? የሚለውን መመልከት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡የወንጀል ህግ አንቀጽ 385 (1) (ለ) ወደ ሀሰት የተለወጠውን ወይም መስሎ የተሰራውን ሰነድ ወይም ለእርሱ አገልግሎት ያልታሰበውን ወይም እርሱን የማይመለከተውን ትክክለኛ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል ሲል ይደነግጋል፡፡ቀጥሎ ያለው ፓራግራፍም /አንቀጽ/ ተጨማሪ ዝርዝር ነጥቦችንና ቅጣታቸውን ያስቀምጣል፡፡በያዝነው ጉዳይ የአቃቤ ህግ ክስ ተጠሪ ኤርትራዊ ሆና እያለች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 12 የነዋሪዎች መታወቂያ በማውጣት ቁጥሩ EP 2378734 የሆነ የኢትዮጵያ ፓስፖርት በማውጣት የማይመለከታትን ትክክለኛ ሰነድ በመገልገል ተከሳለች የሚል ነው፡፡ተጠሪ የኢትዮጵያን ፓስፖርት ለማውጣት የተጠቀመችው ከላይ የተጠቀሰው ክፍለ ከተማ የወረዳ 12 ነዋሪ እንደሆነች በማድረግ ያወጣችውን መታወቂያ ደብተር በመጠቀም ነው፡፡ይህ ደግሞ በወንጀል ህግ አንቀጽ 385 (1) (ለ) ሥር ከተቀመጡት ነጥቦች መካከል "እርሱን የማይመለከተውን ትክክለኛ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ" የሚለው ከአቃቤ ክስ ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች /ዐቃቤ ህግ/ ባቀረበው ክስ ላይ የተገለጸው ፍሬ ነገር ከተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ጋር አይጣጣምም ሲል የደረሰው ድምዳሜ የተሳሳተ ነው፡፡ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ሳያርም ማለፉ ሲታይ የሚነቀፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ክስ እንዲሻሻል ሲል የሰጠው ትዕዛዝ በክሱ ላይ የተመለከቱትን ፍሬ ነገሮች እና የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌን በአግባቡ ያላጤነ ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ሳያርም ማለፉ ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም ቀጥሎ ያለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ. 225717 በቀን 24/02/2009 ዓ.ም አመልካች ክስ አላሻሽልም ብሏል በማለት መዝገቡ እንዲዘጋ ሲል የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትይህንኑ በማጽናት በኮ/መ/ቁ. 218556 ህዳር 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 195 (2)(ሀ) መሠረት ተሰርዟል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ክስ እንዲሻሻል ሲል የሰጠው ትዕዛዝ በክሱ ላይ የተመለከቱትን ፍሬ ነገሮች እና የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌን በአግባቡ ያላጤነ ሆኖ በመገኘቱ እና ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ሳያርም ማለፉ ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ክስ እንዲሻሻል በ4/11/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠሁትን ትዕዛዝ በራሴ አላነሳም ሲል የደረሰው ድምዳሜ ተገቢ ነው ብለናል፡፡

4. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ክርክሩን ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በወንጀለኛመ ቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 195 (2) (ሀ) መሰረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/አ

ልዩ ልዩ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 159062

ጥር 30ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ መረሳ ወ/ማርያም ቀረቡ:: ወ/ሮ አብረኽት ገ/ፃድቃን ወኪል ቀረቡ::

ተጠሪ፡- ቂስ ወ/ጊዩርጊስ ኪዳኔ ጠ/መኮንን አምቦ ::

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች የአሁን ተጠሪ ላይ በትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አክሱም ምድብ ችሎት የሽያጭ ውልን መነሻ በማድረግ የቀ ረበው ክስ ወፍጮውን እና መሬቱ ከነግንብ አጥሩ ለተከሣሽ የሸጡ በመሆኑ መሬቱን ተከሣሽ ሊለቅ አይገባም ተብሎ መወሰኑና እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ነው በሚል በሰበር ለማሳረም አቤቱታ በመቅረቡ ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረው ክስ በአጭሩ የሚያሳየው በወረዳ ታች ማይጨው ማይበራዝዬ ቀበሌ ዓዲ ንፋስ ጎጥ ልዩ ቦታ ዓውደ ኩሐ በተባለ የኢንቨስትመንት ቦታ አዋሣኙ በክሱ የተገለፀውን ቦታ የእህል ወፍጮ ከነሙሉ መሳሪያው በብር 20,000.00/ሃያ ሺ / ከሣሾች ለተከሣሽ የሸጡላቸውና ገንዘቡንም መቀበላቸውን ሆኖም ግን የተሸጠውን ወፍጮ ከኢንቨስትመንት ቦታው ላይ ሊያነሱ በተደጋጋሚ ተከሣሽን ቢጠይቋቸው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ቢሰጡም ሊያነሱ ስላልቻሉ አንስተው ቦታውን እንዲለቁልን ይወሰንልን በማለት አመልካቾች ክስ አቅርበዋል፡፡

ተከሣሽ/ተጠሪ / በሰጡት መልስ ወፍጮውን የገዛሁት ከነመሬቱ ነው ለአስተዳደሩም ይህንኑ ገልፀው በቀን 12/1/2007 ዓ.ም. በቁጥር 51/11 በክስ የተገለፀ 40 በ30 ካ/ሜ የመጠቀም መብት የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶኛል፡፡ ስለዚህ ህጋዊ ይዞታዬ ነው፡፡ መሬቱንም በብር 20,000.00 ተብሎ ተገምቶ መቅረቡ መሬቱ በገንዘብ አይገመትም ህጋዊነትም የለውም የሚል መልስ በማቅረብ ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ምስክሮችን በመስማት ጉዳዩን መርምሮ ቤትና ቦታውን ከነወፍጮው የሸጡ መሆኑን ስለተረጋገጠ መሬቱን ተከሣሽ የሚለቁበት ምክንያት የለም በማለት መወሰኑን የውሣኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

አመልካች ይግባኝ ብለው ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ቅሬታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱን ተመልክተናል፡፡

አመልካቾች በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ ግንቦት 27 ቀን 2010 ዓ.ም. የተፃፈ 5 ገጽ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- ክርክር ያስነሳውን ይዞታ ስፋቱ 40በ30 የሆነውን ቦታ በሄክታር 125 ተለክቶ በብር 187.5 ሂሣብ በመክፈል ከ2002 — 2052 ዓ.ም. ድረስ የሚፈለገውን ፎርማሊቲ በማሟላት በቦታው ላይ 4 ክፍል ቤት ያረፈበትን በሊዝ አዋጅ መሠረት በኢንቨስትመንት ተረክበን በቁጥጥር ስር አድርገን እየተጠቀምንበት ነበር፡፡

በይዞታው ላይ ብዙ መዋለ ንዋይ አፍሰን 6 ወፍጮ ተክለን በውክልና ለአሁን ተጠሪ እንዲያስተዳድሩ ጥቅማጥቅም እየሰጡን የሚፈለግ የመንግሥት ክፍያ እየከፈሉ ለ2 ዓመት ቆይተዋል፡፡ ቦታውን እና በላዩ ላይ ያሉ ንብረቶችን ተጠሪ እንድንሸጥላቸው ስለጠየቁን በብር 270,000.00 የሸጥንላቸው መሆኑ በመግለጽ የጣቢያው ጽ/ቤት ለወረዳው ጽ/ቤት ድጋፍ እንዲሰጠን በማለት ጠይቀን የወረዳው አስተዳደር የገጠር የሊዝ መሬት አይሸጥም አይለወጥም በማለት ያገዱት በመሆኑ በላዩ ላይ የሰፈረውን ወፍጮ ድንጋዩና ዕቃዎችን ከነመለዋወጫው በብር 20,000.00/ሃያ ሺ ብር/ ሸጠንላቸው እያለ ከ2 ዓመት በኋላ የወረዳውን አስተዳደር በማሳሳት በሊዝ የተረከብንበትን ቦታ ከግለሰቦች ጋር በመመሳጠር ይህን ቦታ ያለአግባብ ሊቀሙን ችለዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት በሽያጩ ውል ላይ የተመለከተው የወፍጮ ቤትና ዕቃዎች በብር 20,000.00/ሃያ ሺ ብር/ መሸጡን እየተመለከተና በሁለቱ ወገኖች ፊርማ የተፈረመ የሰነድ ማስረጃ አቅርበን እያለ የሰጠው ውሣኔ ስህተት ስለሆነ እንዲሻርልን እና የተፈፀመው የህግ ስህተት እንዲታረምልን የሚል ሰፊ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም በግራ ቀኙ የተደረገው የወፍጮ ሽያጭ ውል የአመልካችን አጠቃላይ ይዞታ ስለማጠቃለል አለማጠቃለሉ ግራ ቀኙ በተገኙበት ለማጣራት በሚል ጭብጥ በመያዙ መዝገቡ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

አቤቱታው ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር ለተጠሪ እንዲደርሳቸውና መልሳቸውን እንዲያቀርቡ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሰኔ 29 ቀን 2010 ዓ.ም. የተፃፈ 5 ገጽ መልስ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለ በመሆኑ ውሣኔው እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበው የጽሁፍ ክርክሩ በዚህ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት እኛም አቤቱታውን መልሱን እና የመልስ መልሱን ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት አቅርበውት የነበረው ክስ ወፍጮ ሽጨለት ወፍጮውን ሊያነሳልኝ አልቻለም በመሆኑም እንዲያነሳልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ወፍጮውን የገዛሁት ከኢንቨስትመንት መሬቱ ጋር በመሆኑ ወፍጮውን ላነሳ አይገባኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክርክር ያስነሳው ወፍጮ ያረፈበት መሬት አመልካች ለወፍጮ ሥራ አገልግሎት በኢንቨስትመንት የመሬት ኪራይ ውል መሆኑም በግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ እያከራከረ ያለው ወፍጮው የተሸጠው መሬቱን ጨምሮ ነው ወይስ ወፍጮው ብቻ ነው የሚለው ሲሆን በግራ ቀኙ መካከል ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም. የተፈረመው የሽያጭ ውል የእህል ወፍጮ ሽያጭ ውል መሆኑን ያሳያል፡፡

ከዚህ የሽያጭ ውል መረዳት የሚቻለው አመልካች 5 ቋት የሚሰራ 1 ቋት የተበላሸ ወፍጮዎችን ለተጠሪ በብር 20,000.00/ሃያ ሺ ብር/ የሸጡ መሆኑን ነው፡፡ አመልካችም በዚህ ውል መሠረት ገንዘቡን መቀበላቸውን ገልፀው ተጠሪ ግን በሽያጭ ውሉ መሠረት ወፍጮውን ከኢንቨስትመንት መሬቱ ላይ አላነሳልኝም የሚል ነው፡፡ ውሉ በግልጽ የወፍጮ ቋት ሽያጭ የተፈፀመ መሆኑን የሚያሳይ ከሆነ ተጠሪ እንደሚሉት ወፍጮው በመሸጡ የኢንቨስትመንት የኪራይ መሬቱን የተጠሪ ሊያደርግ ይችላል አይችልም የሚለውን መመልከት ተገቢ ነው፡፡

በቅድሚያ ለወፍጮ ሥራ መሬት መከራየት በተሻሻለው ትግራይ ክልል የኢንቨስትመንት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 ውስጥ የሚካተት ነው ወይንስ አይደለም የሚለውን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ከላይ በተገለፀው አዋጅ አንቀጽ 2 “ትርጓሜ” በሚለው ስር ንዑስ አንቀጽ 9 “የእርሻ ኢንቨስትመንት” ማለት በአዝርዕት መስኖ፣በእንሰሳት ሃብት ልማት፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ በአግሮ ኢንዱስትሪና በሌሎች ተዛማጅ የልማት ሥራዎች የሚካሄድ ኢንቨስትመንት ነው በማለት የደነገገ በመሆኑ ከአስተዳደሩ ጋር በገጠር ይዞታ መሬት ላይ በውል የተደረገው የወፍጮ ሥራ ኢንቨስትመንት በአዋጁ የሚፈቀድ መሆኑን መረዳት ችለናል፡፡

በመሆኑም አመልካች የክልሉ የኢንቨስትመንት አዋጅ በሚፈቅደው ሥራ ተሰማርተው እንዲሰሩ ክርክር ያስነሳውን መሬት ለ5 ዓመት የተከራዩ በመሆኑ ይህን የተከራዩትን የኢንቨስትመነት መሬት ማስተላለፍ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚለውን በተመለከተ በአዋጅ አንቀጽ 24 ስር በተመለከተው መልኩ የገጠር መሬት የእርሻ ኢንቨስትመንትን መብት ከሚተላለፍበት ስርአት ውጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ ስለመሆኑ በአንቀጽ 22/5 ስር በግልጽ የተመለከተ ከመሆኑም ሌላ በአንቀጽ 26/4 ስር ከሚመለከተው አካል እውቅና ውጭ የተከራየውን መሬት ወደ 3ኛ ወገን አስተላልፎ ሲገኝ የኪራይ

ውሉ የሚያቋርጥ ድርጊት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንረዳው የእርሻ የኢንቨስትመንት መሬትን በሚመለከተው አካል እውቅና በሕግ አግባብ መብት ከሚተላለፍበት ስርአት ውጭ በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

ግራ ቀኙ በክርክራቸው እያነሱ ያሉትም መጀመሪያ ከነመሬቱ ወፍጮውን አመልካች ሊሸጡ ተጠሪ ሊገዙ የተስማሙ ቢሆንም አስተዳደሩ መሬት መሸጥ እንደማይቻል የገለፀላቸው በመሆኑ የወፍጮ ቋት ሽያጭ ውል የፈፀሙ ስለ መሆኑን አንስተዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የምንችለው በኪራይ ለኢንቨስትመንት ሥራ የተገኘ መሬት መሸጥ የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም በግራ ቀኙ መካከል የተፈረመው የወፍጮ ቋት ሽያጭ ሆኖ እያለ በውሉ ያልተመለከተ እና በሕግም የእርሻ የኢንቨስትመንት መሬትን በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ በግልጽ ክልከላ የተደረገበት መሆኑ ተደንግጎ እያለ እንዲሁም በግራ ቀኙ መካከል የተፈረመው የሽያጭ ውል የወፍጮ ቋት የሽያጭ ውል ስምምነት መሆኑን በግልጽ እያመለከተ የኢንቨስትመንት የኪራይ ውል የተደረገበትን መሬት ተጠሪ እንደገዙ በማድረግ የኪራዩን መሬት አይለቅም ተብሎ በስር ፍ/ቤት መወሰኑ እና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መጽናቱ ውሉን እና የክልሉን የመሬት አስተዳደር አጠቃቀም አዋጅን ያላገናዘበ እንዲሁም አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ወደ 3ኛ ወገን የሚተላለፍበትን የህግ አግባብ ያልተከተለ ሆኖ በመገኘቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ ሊሻር ይገባል ብለን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. የትግራይ ክልል የማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አክሱም ምድብ ችሎት በመ/ቁ/ 23586 ጥር 23 ቀን 2010 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 103245 ሚያዝያ 05 ቀን 2010 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም. በተደረገ ውል አመልካች ለተጠሪ የሸጡት የእህል ወፍጮ እንጂ የኢንቨስትመንት መሬቱን አይደለም ብለናል፡፡

3. በመሆኑም ተጠሪ በእህል ወፍጮ ሽያጭ ውሉ መሠረት የገዙትን ወፍጮዎች አመልካች በኪራይ ውል ከያዙት ኢንቨስትመንት መሬት ላይ እንዲያነሱና መሬቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡
4. በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ላወጡት ወጪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

5. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

ውሣኔው ሲፃፍ ቆይቶ ዛሬ የካቲት 13 ቀን 2011 ዓ.ም. ተነቧል፡፡

ሠ/ኃ የማይነበብ የ5 ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ 169729

ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች - ተክሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ፀሐይ መንክር

አመልካች - የገቢዎች ሚኒስቴር

ተጠሪ - አቶ አስራት አሰግድ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔና ብይን የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታ ስላቀረበ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በቃሊቲ ወደብ ተርሚናል የመጋዘን ሰራተኛ ሆኜ ስሰራ በወ/ሮ ኤደን ወንዲፍራው ስም ከዱባይ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በቃሊቲ ጉምሩክ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈፀምባቸው ካስገቧቸው ዕቃዎች ውስጥ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በመያዛቸው ለገቢዎችና ጉሙሩክ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በ30/12/2008 ዓ.ም ጥቆማ ሰጥቼ ብር 382,241.60 የሚያወጡ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ አድርጌያለሁ፤ የተከሳሽ መ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ሽልማት የሚገባኝ መሆኑን ገልጾ ፎርም እንድሞላ የተደረገ ሲሆን በዚሁ አግባብ በ29/03/2009 ዓ.ም ፎርም ሞልቼ የጠቋሚ መለያ ቁጥር AAKc/230/03/09 ተሰጥቶኛል፤ የምስጋና ደብዳቤም አግኝቻለሁ፤ ነገር ግን የጠቋሚውን ፎርም ከሞላሁ በኃላ በመመሪያ ቁጥር 78/2004 መሰረት 40% ወሮታ ክፍያ ብር 152,896.61 ተጠሪ እንዲከፍለኝ በተደጋጋሚ ጠይቄ ሊከፍለኝ ፈቃደኛ ስላልሆነ ይህን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 53 እና 132 መሰረት ራሱ በሚጠብቀው መጋዘን ውስጥ ዕቃ እንዳይወጣ መያዙ የሥራ ግዴታውን ተወጥቷል የሚያስብል እንጂ በመመሪያው መሰረት ወሮታ የሚያስከፍል ጥቆማ ሰጥቷል ስለማይባል ክሱ ውደቅ ይደረግልን፤ የጥቆማ ፎርሙ በ10 ቀን መሞላት ነበረበት ወይም ከአቅም በላይ ያልሞላ መሆኑን ቀርቦ ማስረዳት አለበት፤ የጥቆማ ክፍያ አያሰጥም እንጂ ይሰጣል ቢባል እንኳ የጥቆማ ፎርሙን በ10 ቀን ውስጥ

ስላልሞላ እንዲሁም ከሳሽ ጥቆማ ባያደርግ ኖሮ ኃላፊነት አልተወጣም ተብሎ ተጠያቂ ይሆን ስለነበር ክፍያ ሊጠይቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል።

ክሱ በሚሰማበት ጊዜ አመልካች ባይቀርብም ተጠሪ ቀርበው የአመልካች ሰራተኛና የመጋዘን ኃላፊ አለመሆናቸውን፤ አይደለም የመጋዘን ሰራተኛ የፀጥታ አስከባሪዎችም ወሮታ የሚከፈላቸው መሆኑን፤ እቃው ይለቀቅ ተብሎ የመልቀቂያ ቅጽ (release form) የተሞላለት ስለሆነ ጠቁመው ባያስይዙት ኖሮ ምንም ኃላፊነት እንደማይመጣባቸው፤ ጥቆማ የሰጡት በግንባር ቀርበው በመሆኑ በ10 ቀን ውስጥ ፎርም አልሞላም የሚለው ክርክር እንደማይመለከታቸው፤ ይመለከታቸዋል ቢባል እንኳ ዕቃው የተያዘባት ግለሰብ ጠፍታ እርሷ ባለችበት ዕቃውን ለማስፈተሽ ተብሎ በመጠባበቅ የቆየ በመሆኑ እንደ በቂ ምክንያት ሊወሰድ እንደሚገባ ተከራክረዋል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ለተጠሪ የወሮታ ክፍያ ለመክፈል ይገደዳል? ወይስ አይገደድም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል። በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ ወይም፣ የህግ አስከባሪ አባል ባለመሆናቸው የሥራ ግዴታቸውን ተወጥተዋል ተብሎ የወሮታ ክፍያ አያገኙም የሚባልበት የህግ ምክንያት አልተገኘም፤ አመልካች ጠቅሶ የሚከራከረው የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 56 እና 132 ድንጋጌዎችም ተጠሪ ግዴታቸውን ስለተወጡ ክፍያ አያገኙም የሚያስብሉ አይደሉም፤ በተለይም ተጠሪ ለግለሰቧ ዕቃዎቹ እንዲለቀቁላት የመልቀቂያ ፎርም (release form) ተሰጥቶ እንደነበር ተከራክረው በማስረጃም ያረጋገጡ ሲሆን አመልካች ይህን ክዶ ስላልተከራከረም፤ በዚህ መልኩ እንዲለቀቅ የተፈቀደ ዕቃ ላይ ደግሞ በተጠሪ ላይ ኃላፊነት ያስከትል ነበር ማለት ስለማይቻል አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ በ 10 ቀን ውስጥ የጥቆማ ፎርም አልሞሉም የተባለውን በተመለከተም የቀረቡት ማስረጃዎች ተጠሪ በግንባር ጥቆማ ያቀረቡ መሆኑን የሚያስረዱ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን መመላት ነበረባቸው ቢባል እንኳ ተጠሪ የጠቋሚ ቅፅ እንዲሞሉ መደረጉና ቅጹ በአመልካች ኢንስፔክሽን ኦፊሰር ተረጋግጦ መፈረሙ ስለተረጋገጠ ተጠሪ እንደሚሉት ቅፁን ሳይሞሉ የቆዩት ዕቃዎቹ ሳይፈተሹ በመቆየታቸው በበቂ ምክንያት መሆኑን ያስረዳል ስለሆነም በዚህም ረገድ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም። በአጠቃላይ ዳኝነት የተጠየቀበትን 40% የወሮታ ክፍያ ብር 152,896.65 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል።

ይህን ውሳኔ በመቃወም አመልካች ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታውን ቢያቀርብም ውሳኔውን ሊያስነቅፍ የሚችል ምክንያት አልተገኘም ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙ ተሰርዟል።

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች ጥር 22 ቀን 2011 ዓ.ም ያቀረበው ማመልከቻ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ የወሮታ ክፍያ ተጠቃሚ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ለመወሰን የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትርጉም አግባብነት ለማየት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል። ተጠሪ

በሰጡት መልስ የሥር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀና የጠየቁ ሲሆን አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ከተገቢው የህጉ ድንጋጌ ጋር በማያያዝ በሥር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ የወሮታ ክፍያ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን ይቻል ዘንድ የህገ ወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና ወሮታ ክፍያን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 78/2004 ይዘት መመርመሩ ተገቢ ነው፡፡ በመመሪያው አንቀጽ 2(7) መሰረት "የወሮታ ክፍያ" ማለት ለጠቆሙ ወይም ለያዙ ወይም ለተባበሩና ድጋፍ ለሰጡ ሰዎች የሚሰጥ ክፍያ ሲሆን የባለሥልጣኑን ሰራተኛ እና የህግ አስከባሪ አካል አባልን/ሰራተኛን እንደማይጨምር ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ክፍያው የማይመለከታቸው የባለሥልጣኑን ሰራተኛ እና የህግ አስከባሪ አካል አባልን/ሰራተኛን መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በቃሊቲ ወደብ ተርሚናል የመጋዘን ሰራተኛ መሆናቸውን ገልፀው የኮንትሮባንድ ዕቃዎች መኖራቸውን ተጠራጥረው ለገቢዎችና ጉሙሩክ በማሳወቅ ብር 382,241.60 የሚያወጡ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ስላስያዙ 40% ወሮታ ክፍያ ብር 152,896.61 እንዲከፈላቸው እንዲወሰን የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ራሳቸው በሚጠብቁት መጋዘን የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ተወጥተዋል ከሚባል በቀር በመመሪያው መሰረት ወሮታ የሚያስከፍል ሥራ ሰርተዋል ስለማይባል ክሱ ውደቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የአመልካች ሰራተኛ ወይም፣ የህግ አስከባሪ አባል ባለመሆናቸው የሥራ ግዴታቸውን ተወጥተዋል ተብሎ የወሮታ ክፍያ አያገኙም የሚባልበት ምክንያት አለመኖሩን፤ አመልካች የሚከራከርበት የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 56 እና 132 ድንጋጌዎችም ተጠሪ ግዴታቸውን ስለተወጡ ክፍያ አያገኙም የሚያስብሉ አለመሆናቸውን፤ ዕቃዎቹ እንዲለቀቁም የመልቀቂያ ፎርም (release form) ተሰጥቶ እንደነበር በማረጋገጥ ዳኝነት የተጠየቀበትን 40% የወሮታ ክፍያ አመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይኸው መደምደሚያ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ከፍሲል የተጠቀሰው መደምደሚያ እና ውሳኔ ላይ የደረሱት ፍሬ ነገር ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ በተሰጣቸው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ስር እንደተደነገገው የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን በመጨረሻ በተላለፈው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ ማረም እንጅ ፍሬ ነገርን መመርመር አይደለም፡፡ ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ ስልጣኑ የተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች በህጉ

አግባብ ክርክሩን በመምራትና ማስረጃውን በመመዘን ከፍ ሲል የተመለከተው መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡ የህገ ወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና ወሮታ ክፍያን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 2(7) ለ"የወሮታ ክፍያ" ከሰጠው ትርጉም አንጻርም ተጠሪ ክፍያ ሊጠይቁ አይገባም የሚባል አይደለም፡፡ ስለሆነም በዚህ መልኩ ጉዳዩ ታይቶ አመልካች ለተጠሪው ወሮታ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ነገር ግን የኃላፊነቱን መጠን በተመለከተ ተጠሪ የኮንትሮባንድ ዕቃውን ይዘው ለገቢዎችና ጉምሩክ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሪፖርት ማድረጋቸውን ክርክሩ ስለሚያሳይ የወሮታ አበል ሊከፈላቸው የሚገባው የህገ ወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና ወሮታ ክፍያን ለመወሰን ተሻሽሎ በወጣው መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀፅ 19(ለ) መሰረት 10% ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ውሳኔው ሊቃና የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 6886 ግንቦት 6/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 215263 በ02/05/2011 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ለተያዙት ብር 382,241.60 የሚያወጡ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች የወሮታ ክፍያ በመመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀፅ 19(ለ) መሰረት የዕቃውን ዋጋ 10% ብር 38,224.16 (ሰላሳ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ አራት ብር ከ16/100) ከወጪና ኪሳራ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስነናል፡፡
3. በአጣሪ ችሎቱ ጥር 23/2011 ዓ.ም አፈጻፀም እንዲታገድ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይህ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ይፈፀም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

የልዩነት ሀሳብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር ሶስት እና አምስት ላይ የተጠቀስን ዳኞች በዚህ ጉዳይ የአብላጫዉ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በሚከተለዉ ምክንያት ተለይተን የልዩነት ሀሳብ እናስቀምጣለን፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን ተጠሪ በጉምሩክ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት ለጠቋሚ የሚከፈለዉ የወሮታ ክፍያ እንዲከፈለዉ የጠየቀዉን ዳኝነት የሚመለከት ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በቃሊቲ ወደብ ተርሚናል የመጋዘን ሰራተኛ ሆኜ ስሰራ በወ/ሮ ኤደን ወንዲፍራዉ ስም ከዱባይ ወደ ኢትዮጵያ ገብተዉ በቃሊቲ ጉምሩክ

የጉምሩክ ስነሥርዓት እንዲፈጸምላቸዉ ካስገቧቸዉ ዕቃዎች ዉስጥ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በመያዛቸዉ ለገቢዎችና ጉምሩክ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጥቆማ አቅርቤ አስፈላጊዉን ፎርም የሞላሁኝ ቢሆንም የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 78/2004 መሰረት 40% የወሮታ ክፍያ እንዲከፈለዉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ተጠሪ ራሱ በሚጠብቀዉ መጋዘን ዉስጥ የተጠቀሰዉ ዕቃ እንዳይወጣ ቁጥጥር ሥር እንዲዉል እና እንዲያዝ ማድረጉ የሥራ ግዴታዉን ተወጥቷል የሚያስብል እንጂ በመመሪያዉ መሰረት ለጠቋሚ የሚከፈለዉ ክፍያ የሚገባዉ አይደለም በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጡት ዉሳኔ የአሁን ተጠሪ ያቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄ በመቀበል በመመሪያዉ መሰረት 40% የወሮታ ክፍያ እንዲከፈለዉ ወስኗል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የአብላጫዉ ድምጽ ደግሞ የሥር ዉሳኔ በማሻሻል 10% የወሮታ ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፈለዉ ወስኗል፡፡ በዚህ ምክንያት እኛ ስማችን ከፍ ሲል የተጠቀሰዉ ዳኞች ከአብላጫዉ ድምጽ በመለየት የሚከተለዉን የልዩነት ሀሳብ አስቀምጠናል፡፡

በዚህ መሰረት መታየት ያለበት ጉዳይ ተጠሪ በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በቃሊቲ ወደብ ተርሚናል የመጋዘን ሰራተኛ ሆኖ እያለ ከዚህ መጋዘን ገብቶ ሊወጣ ያለዉን ዕቃዎች ዉስጥ የኮንትሮባንድ ዕቃ መኖሩን ጠቁሞ በማስያዙ ምክንያት በመመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 19 መሰረት ለጠቋሚ የሚከፈለዉ ክፍያ ይገባዋል ወይስ አይገባዉም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 50 ዕቃዎችን ወደ ጉምሩክ ስለማስገባትን አስመልክቶ መደንገጉን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ‹‹የጉምሩክ ወደብ የደረሰ ማናቸዉም ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን መግባት አለበት›› በማለት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደሚደነግገዉ ‹‹ማናቸዉም ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ የገባ ዕቃ ዝርዝር ሁኔታዉ እየተገለጸ በመጋዘኑ መዝገብ ላይ ይመዘገባል›› በማለት ተደንግጓል፡፡ ማናቸዉም ወደ ቦንድድ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ በመጋዘን ዲክለራሲዮን ተመዝግቦ ለባለስልጣኑ መቅረብና መፈቀድ እንዳለበት በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባዉ ዕቃ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 ሥር በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ አስፈላጊዉ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተከናዉኖበት ከማከማቻዉ መዉጣት እንዳለበት ተገልጾዋል፡፡ በዚህ አግባብ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገቡት ዕቃዎች ከመጋዘኑ የሚወጡበት ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 52 መሰረት በጉምሩክ ሕጉ እና በዚህ ድንጋጌ ሥር ለተመለከቱት ዓላማዎች ሲባል ብቻ ተመዝግበዉ ከማከማቻዉ ወይም ከመጋዘኑ መዉጣት እንዳለባቸዉ ተጠቅሷል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ‹‹ዕቃዎቹ የሚፈለግባቸዉ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸዉ ለአገር ዉስጥ ፍጆታ እንዲዉሉ ሲለቀቁ›› መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሰረት ወደ መጋዘን የገቡት ዕቃዎች በዲክላራሲዮኑ፤ በጭነት ማኒፌስት ወይም በትራንዚት ሰነድ ከተገለጸዉ መጠን በላይ በትርፍነት የተገኘ ዕቃ ዲክላራሲዮኑ ለቀረበለበት የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ወዲያዉኑ ሪፖርት መደረግ እንዳለበት እና

በትርፍ ዕቃዉ ላይ ተገቢ ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል መደረግ እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 53 ሥር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ወደ ጉምሩክ መጋዘን በገቡት ዕቃዎች ላይ ደግሞ የጉምሩክ ቁጥጥር መከናወን እንደሚገባ እና አስፈላጊዉ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተፈጽሞበት ከመጋዘኑ ሲለቀቅም መደረግ የሚገባቸዉን ተግባራት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 56 ሥር ተጠቅሷል፡፡ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባዉንና የሚወጣዉን ዕቃ በተመለከተ የጉምሩክ መጋዘን ሰራተኞች ዕቃዎቹን ባለስልጣኑ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት የመመዝገብና በየጊዜ ሪፖርት ማድረግ ከተጣለባቸዉ የሥራ ግዴታዎች መካከል አንዱ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 132 (2) ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በወ/ሮ ኤደን ወንድፍራዉ ስም ከዱባይ አገር ወደ ኢትዮጵያ የገባዉ ዕቃ የአሁን ተጠሪ በሚሰራዉ የጉምሩክ መጋዘን ሲገባ እና ሲወጣ በአዋጁ አንቀጽ 50፣52፣ 53፣ 56 እና 132 (2) ሥር የተመለከተዉን አስፈላጊዉን የጉምሩክ ስነስርዓት እንደአስፈላጊነቱ መፈጸም ይገባዉ ነበር፡፡ በወ/ሮ ኤደን ስም የተመዘገበዉ ዕቃ ወደ መጋዘን ሲገባ በሕጉ በተመለከተዉ አግባብ ያልተመዘገበ እና ከመጋዘኑ ሲወጣም ደግሞ በትርፍነት የተገኙት ዕቃዎች ተገቢዉ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ ሊወጣ እንደነበር መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ማለት የአሁን ተጠሪ የሚሰራበት መጋዘን በሕጉ የተጣለበትን የሥራ ግዴታ ሳይወጣ መቅረቱን የሚያስገነዝብ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ የመጋዘኑ ሰራተኞች በሕግ የተጣለባቸዉን የሥራ ግዴታቸዉን ባለመወጣታቸዉ ተጠያቂነትን ሊያስከትልባቸዉ የሚገባዉ ጉዳይ ነበር፡፡ በዚህ አንጻር ሲታይ የአሁን ተጠሪ የሚሰራበት የጉምሩክ መጋዘን በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ በመቅረቱ ተጠሪ ደግሞ ይህን ሁኔታ በማወቁ ለሚመለከተዉ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመጠቆም ማሳወቁ በመጋዘኑ በራሱ እና በሌሎች የመጋዘኑ ሰራተኞች ላይ የተጣለዉን የሥራ ግዴታን ተወጥቷል የሚያስብል ነዉ፡፡

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሰረት ‹‹በአገሪቱ የጉምሩክ ክልል በየትኛዉም ሥፍራ ሕገወጥ ዕቃ መኖሩን የሚያዉቅ ማንኛዉም ሰዉ ወዲያዉኑ በአቅራቢያዉ ለሚገኝ የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ወይም ሕግ አስከባሪ አካል ማሳወቅ አለበት›› በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ አግባብ ጥቆማ ያደረገ ማንኛዉም ሰዉ ደግሞ በመመሪያ አንቀጽ 16 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የወሮታ ክፍያ እንደሚፈጸምለት ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የአሁን ተጠሪን ጨምሮ ሌሎች የጉምሩክ መጋዘን ሰራተኞች የሚሰሩት ሰራተኞች በሕግ የተጣለባቸዉን የሥራ ግዴታ ባለመወጣታቸዉ በወ/ሮ ኤደን ስም ተመዝግቦ የገባዉ ዕቃ ዉስጥ በትርፍነት የተገኘዉ ተገቢዉን ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ሊወጣ ሲል ተጠሪ ደርሶበት ለሚመለከተዉ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመጠቆም ማሳወቁ ተጠሪ በእሱ እና በሌሎች የመጋዘኑ ሰራተኞች ላይ የተጣለዉን የሥራ ግዴታ ተወጥቷል ከሚባል በስተቀር በመመሪያ ቁጥር 78/2004 መሰረት ሕገወጥ ዕቃ በተመለከተ መረጃ በመስጠት በመጠቆም አስይዟል ተብሎ የወሮታ ክፍያ ይገባዋል የሚያስብል የህግ መሰረት የለም፡፡ በመሆኑም የአሁን ተጠሪ ያቀረበዉ የወሮታ ክፍያ ጥያቄ የህግ ድጋፍ የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ በመመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 19 መሰረት ለተጠሪ የወሮታ ክፍያ ሊከፈለዉ ይገባል በማለት የሰጡት ዉሳኔ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ መሰረት የአዋጁንና የመመሪያዉን ዓላማና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ መሻር ይገባቸዉ ነበር ብለን የአብላጫዉ ድምጽ ከሰጠዉ ዉሳኔ በመለየት የልዩነት ሀሳባችን አስቀምጠናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁ.171530

ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተክሊት ይመስል
ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)
ቀነአ ቂጣታ
ተሾመ ሽፈራው
ፀሐይ መንክር

አመልካች - የኢፌዴሪ ሠራተኞና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር -
ነ/ፈጅ ሸዋቀረው አስፋው - ቀረቡ

ተጠሪ - አቶ ሱልጣን ጃቢር መሀመድ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በሥሜ የተመዘገበ ሱልጣን ጃቢር በውጭ ሀገር ሥራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ በአመልካች ፍቃድ ተሰጥቶኝ በዚሁ መሰረት የንግድ ፈቃድ አውጥቼ እና ለሥራውም ዋስትና የሚሆን በብሎክ አካውንት በባንክ ብር 281,200.00 አስቀምጬ ሥሰራ ቆይቼ መንግስት በ2007 ዓ.ም ሥራው ለጊዜው እንዲቆም መመሪያ ሲያስተላልፍ ሥራው ቆሞ የነበረ ቢሆንም ፈቃዱን ግን እያሳደስኩ ቆይቻለሁ፤ ሥራው በአዲስ መልክ ሲፈቀድ 100,000.00 ዶላር (መቶ ሺህ ዶላር) ያሥያዝኩ ሲሆን አስቀድሞ ያስያዝኩትን ገንዘብ አመልካች እንዲለቅልኝ የጠየቅሁ ቢሆንም ከድርጅቴ ጋር ግንኙነት የሌለው አቶ በድሩ ከማል የተባለ ግለሰብ አቤቱታ ስላቀረበ አንለቅልህም ብሏል፤ ስለሆነም አመልካች የያዘብኝን ብር 281,200.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) እንዲለቅ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት በ 3 ግለሰቦች በተቋቋመ የግል ማህበር በመሆኑ በግላቸው ክሥ ማቅረብ አይችሉም፤ ተጠሪ ቀደም ሲል ሱልጣን ጃቢር በውጭ ሀገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ሥም ዜጎችን ለሥራ ሲልክ የቆየ ሲሆን ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የዚህን ኤጀንሲ ሥም በመለወጥ ተጠሪን ጨምሮ 3 ግለሰቦች ሆነው የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ የተመዘገበ ሱልጣን ጃቢር በውጭ ሀገር ሥራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ኃ/የተ/የግል ማህበር አቋቁመው መተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ፅሁፍ ለአመልካች ያቀረቡ በመሆኑ ይህ ማህበር እያለ ተጠሪ በግላቸው በቀድሞው ኤጀንሲ ስም ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፤ ተጠሪ ለአመልካች

መስሪያ ቤት ገንዘቡ እንዲመለስ ጥያቄ ሲያቀርቡ አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመስጠት እንዲቻል ማብራሪያ እንዲሰጡ የተፈለጉ ቢሆንም ባለመቅረባቸው የሚወሰደው አስተዳደራዊ ውሳኔ ሳይነገራቸው ያቀረቡት ክስ አግባብነት የለውም፤ በአጠቃላይ የዋስትና ገንዘቡን በተመለከተ ህጋዊ ሰውነት ያለው ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሥለሆነ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳበት የዋስትና ገንዘብ በሱልጣን ጃቢር ሥራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሥም ገቢ የተደረገ ነው? ወይስ አይደለም? ሊመለስ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ክፍያውን በግላቸው ገቢ ያደረጉት መሆኑን ስላስረዱ በባንክ ገቢ ያደረጉትን ብር 281.200.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ አንድ ሽህ ሁለት መቶ) አመልካች ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲለቅ (እንዲመልስ) በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ በአመልካች በኩል ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ሰምቶ ውሳኔው ስህተት የለበትም በማለት አፅንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 18/2011 ዓ.ም ያቀረበው ማመልከቻ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ጉዳዩን ከኢትዮጵያ የውጪ ሀገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 እና የውጪ ሀገር ስራ ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ አንጻር ለማጣራት ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪም መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ተጠሪ በ26/07/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ውሳኔው ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቋል፡፡ አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረውም በዚህ ሁኔታ ነው፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔና ተገቢነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የውጪ ሀገር ስራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 923/2008 እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የወጣው የውጪ ሀገር ስራ ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ ፈቃድ ስለመመለስና የዋስትና ገንዘብ ስለመልቀቅ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዘዋል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 60(5) ሥር እንደተደነገገው ኤጀንሲው በማናቸውም ሁኔታ ሥራውን ሲያቆም ሚኒስቴሩ የዋስትናውን ገንዘብ የሚለቀው ከሠራተኛ መብትና ጥቅም ጋር የተያያዘ ጥያቄ ስልጣን በተሰጠው አካል በመታየት ላይ ካልሆነ እና በኤጀንሲው አማካኝነት ለስራ ወደ ውጪ አገር የተላኩ ሠራተኞች በሙሉ የሥራ ውላቸው ከተቋረጠ ከ6 ወር በኃላ ነው፡፡ የመመሪያው አንቀጽ 23 የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅ ጥያቄ ሲቀርብ መሟላት ስለሚኖርባቸው ሁኔታዎች ይዘረዝራል፡፡

ከዚህም ሌላ የአዋጁ አንቀጽ 78 የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን አስቀድሞ ሥራ ላይ በነበረው አዋጅ ቁጥር 632/2001 መሰረት ፈቃድ ተሰጥቷቸው የነበሩ ኤጀንሲዎች ስለሚኖርባቸው ኃላፊነት እና ፈቃዱ ተሰርዞ ቢሆን እንኳ ኤጀንሲው ለሥራ ወደውጪ አገር የላካቸው ሰራተኞች ከሚያነሱት ማናቸውም የመብት ጥያቄ ነጻ እንደማይሆን ተመልክቷል፡፡

ከፍሲል ከተጠቀሱት የህጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የዋስትና ገንዘብ የሚያዘው በዋናነት ለሰራተኛው መብትና ደህንነት ዋስትና ማስከበሪያ እንዲውል ሲሆን ኤጀንሲው በሚኒስቴሩ የተሰጠውን ፈቃድ በመመለስ ለሥራ ወደ ውጪ አገር ለላካቸው ዜጎች መብትና ደህንነት ማስከበሪያ በባንክ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅለት ጥያቄ ሲያቀርብ አሟልቶ ሊያቀርብ የሚገባቸው ሁኔታዎች በህጉ ተለይተው የተደነገጉ መሆናቸውን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳበት የዋስትና ገንዘብ አስቀድሞ በሱልጣን ጃቢር ሥራና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ሥም ገቢ የተደረገ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ጭብጥ በመያዝ የወሰነ ቢሆንም በህጉ ከተቀመጡት ሁኔታዎች አንጻር ተገቢው ጭብጥ ተይዞ በዚሁ አንጻር ክርክርና ማስረጃው ታይቶ በአግባቡ ተገናዝቦ የተሰጠ ውሳኔ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡

ይልቁንም በህጉ አግባብ ዋስትና ያስያዘው ኤጀንሲ ፈቃዱን መመለስ አለመመለሱ፤ አስቀድሞ የተሰጠ ፈቃድ ካልተመለሰ ፈቃድ ሳይመለስ የዋስትና ገንዘበ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆን አለመሆኑ፤ እንዲሁም ኤጀንሲው ለሥራ ወደ ውጪ አገር ለላካቸው ዜጎች መብትና ደህንነት ማስከበሪያ በባንክ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅለት ሊያሟላ የሚገባቸው ሁኔታዎች የተሟሉ መሆን አለመሆኑ ሁሉ ከክርክርና ማስረጃው አንጻር ታይቶና በአግባቡ ተገናዝቦ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባ ነበር፡፡

በአጠቃላይ ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆኑ ፍሬ ነገሮች ከህጉና ከማስረጃው አንፃር በአግባቡ እንዲጣሩ ሳይደረግ ተጠሪ ክፍያውን በግላቸው ገቢ ያደረጉት መሆኑን አስረድተዋል በሚል ምክንያት ብቻ ገቢ ያደረጉትን ብር 281.200.00 (ሁለት መቶ ሰማንያ አንድ ሽህ ሁለት መቶ) አመልካች ሊለቅ ይገባል በማለት በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይህን ሳያርም ማለፉ የሚነቀፍ ነው፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 50815 ሰኔ 29 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 219600 በ04/06/2011 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ዋስትና ያስያዘው ኤጀንሲ ፈቃዱን መመለስ አለመመለሱን፤ አስቀድሞ የተሰጠው ፈቃድ ካልተመለሰ ፈቃድ ሳይመለስ የዋስትና ገንዘበ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆን አለመሆኑ፤ እንዲሁም ኤጀንሲው ለሥራ ወደ ውጪ አገር ለላካቸው ዜጎች መብትና ደህንነት ማስከበሪያ በባንክ ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲለቀቅለት ሊያሟላ የሚገባቸው ሁኔታዎች የተሟሉ መሆን አለመሆኑን ሁሉ በመመርመር ጉዳዩን በአግባቡ አጣርቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጥ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 167560

ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ቢቂላ አያኖ

ተጠሪ፡- አቶ አሊቢ ቂላ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 219841 ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች ታህሳስ 15 ቀን 2011 ዓ.ም የተፃፈ 02 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጀመረ ሲሆን አመልካች ከዚህ በፊት ፍርድ ቤቱ ችሎታ የላቸውም በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት መሆኑ በመግለፅ የተደረገላቸው የህግ ክልከላ እንዲነሳ ወሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው፣ አቤቱታ ለማቅረብ ችሎታ የላቸውም በሚል ምክንያት ተቀባይነት ማጣታቸው መነሻ በማድረግ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረበው አቤቱታ ወላጅ አባቴ አቶ ቢቂላ አያኖ (የአሁኑ አመልካች) በጣም ያረጁ እና ጆሮአቸው የማይሰማ በመሆኑ ነገሮችን ማስተዋልና ማስታወስ ስለማይችሉ የፍርድ ክልከላ ይሰጥልኝ በማለት ባቀረበው አቤቱታ መሰረት ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 2600/07 ታህሳስ 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአሁኑ አመልካች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 351 መሰረት የፍርድ ክልከላ ሰጥቷል፡፡ ይህንን ክልከላ ተከትሎ ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 2600/07 የአመልካች ሞግዚት እንዲሆን ሾሞታል፡፡

አሁን የቀረበው አቤቱታ አመልካች የተደረገባቸው ፍርድ ክልከላ እንዲነሳ ፣ክልከላውን ለሰጠው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43358 አቤቱታ አቅርበው ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች የፍርድ ክልከላ ከተሰጠባቸው በኋላ ክስ ለማቅረብ ችሎታ የላቸውም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33(1) እና ፍ/ብ/ሕ/ቁ 377 መሰረት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል። አመልካች በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም የአመልካች አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዞታል። ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች በቀን 15/04/2011 ዓ/ም የተፃፈ 2 ገፅ አቤቱታ አቅርበዋል ። የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ፡-አመልካች የህግ ክልከላ የተሰጠብኝ መሆኑን መሰረት በማድረግ ክልከላው ይነሳልኝ በማለት ያቀረብኩት አቤቱታ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ክልከላ ይነሳ በማለት አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት በፍ/ሕግ ቁጥር 377 ላይ የተገለፁት ግለሰቦች ናቸው በማለት አቤቱታዬን ወድቅ አድርጎታል። ይሁን እንጂ ክልከላ የተደረገበት ሰው ክልከላው በመቃወም አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል በፍ/ሕግ ቁጥር 355 ላይ ተገልፆ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ግንኙነት በሌለው የህግ ድንጋጌ መሰረት አቤቱታዬን ውድቅ በማድረግ መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊሻር ይገባል የሚል ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸው ተለዋውጠዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ፅሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። ለክርክሩ መነሻ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ አባት የሆኑት የአሁኑ አመልካች በጣም ያረጁ እና ጆሮአቸው የማይሰማ በመሆኑ ነገሮችን ማስተዋልና ማስታወስ ስለማይችሉ የፍርድ ክልከላ ይሰጥልኝ በማለት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 43358 በቀን 28/04/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት በአቶ ቢቂላ አያኖ ንብረት ላይ በፍ/ህግ ቁጥር 351(1) የፍርድ ክልከላ የሰጠ መሆኑ በውሳኔው ላይ አስፍሯል። ከዚህ በኋላ አመልካች የህግ ክልከላ የተሰጠብኝ ያለአግባብ ነው ችሎታ አለኝ በማለት ክልከላው ይነሳልኝ አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ክልከላ ይነሳ በማለት አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 377 ላይ የተገለፁት ግለሰቦች ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል።

በመሰረቱ በህግ ችሎታ ያለው ማንኛውም ሰው ክስ ማቅረብ እንደሚችል በፍ/ሥ/ስ/ሕግ ቁጥር 33(1) ተመልክቷል። የፍ/ህግ ዓንቀፅ 377 ስር እንደተመለከተው አእምሮው ከጎደለው ሰው በቀር ስለክልከላው ፍርድ እንዲሰጥ ለመጠየቅ የሚችሉት ሰዎች በማንኛውም ጊዜ የክልከላው ውሳኔ እንዲቀር ለዳኞች ጥያቄ ለማቅረብ ይችላሉ በማለት ተመልክቷል። ከዚሁ ድንጋጌ በመቀጠል ክልከላ እንዲወሰን

ያደረጉት ምክንያቶች በቀሩ ጊዜና የተከለከለ ሰው ንብረቱን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚችል የሆነ እንደሆነ ዳኞች የክልከላው ውሳኔ ማስቀረት (ማንሳት) እንዳለባቸው በፍ/ህግ ዓንቀፅ 378 ተደንግጓል ።በሌላ በኩል በፍ/ሕግ ቁጥር 355 እንደተመለከተው አእምሮው ጎደሎ ወይም ድውይ የሆነው ሰው እራሱ ፣ከባልና ሚስት ደህኛው ከስጋ ወይም ከጋብቻ ዘመዶች አንዱ ወይም ዓቃቤ ህግ ዳኞች ስለክልከላው በሰጡት ፍርድ ላይ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችሉ ተመልክቷል።

ስለሆነም ከላይ ከተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው በፍርድ ክልከላ የተደረገለት ሰው ንብረቱን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚችል የሆነ እንደሆነ ክልከላው ቀሪ እንዲሆን መጠየቅ እንደሚችል ፍርድ ቤቶችም ይህንን ተከትለው ውሳኔ መስጠት እንዳለባቸው የተደነገገ በመሆኑ አመልካች በተደረገለት ክልከላ ምክንያት ሌላ አዲስ ክስ ማቅረብ የማይችል ቢሆንም የተደረገለት ክልከላ እንዲነሳለት ግን ከላይ በተጠቀሰው ህግ መሰረት የሚፈቀድለት በመሆኑ የተደረገለት ክልከላ እንዲነሳለት ላቀረበው አቤቱታ ፍርድቤቱ አመልካች የክስ አቤቱታ ለማቅረብ ችሎታ የላቸውም በማለት መዝገቡን መዘጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

<u>ውሳኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትበመ/ቁጥር 43358 ሰኔ 06 ቀን 2010 ዓ/ም ተወስኖ ፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 219841 ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽረዋል።
2. በአመልካች ክልከላ እንዲነሳላቸው አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉ በመሆናቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ተመልሶለታል ።ይፃፍ።
3. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

ሳ/ፀ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።